

መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ።

የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ።

(ንምራዊ ፡ አቀጻጽ)

ክለሳ ፡ 10.0 ፥

ሐምሌ ፡ 16 ፡ ቀን ፥ 2010 ፡ ዓ.ም. ።

http://www.gzamargna.net http://www.awdeqelem.net

ብሉይ ፡ ኪ.ዳን ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ (ዘፍ.) ።
ኦሪት ፡ ዘጸአት ፡ (ዘጸ.) ።
ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፡ (ዘሌ.) ።
ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ (ዘኍ.) ።
ኦሪት ፡ ዘዳግም ፡ (ዘዳ.) ።
መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ (ኢያ.) ።
መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፡ (መሳ.) ።
መጽሐፈ ፡ ሩት ፡ (ሩት) ።
መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፡ (ሳሙ.1) ።
መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፡ (ሳሙ.2) ።
መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ (ነገ.1) ።
መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፡ (ነገ.2) ።
መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፡ (መዋ.1) ።
መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፡ (መዋ.2) ።
መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ (ዕዝ.) ።
መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፡ (ነሐ.) ።
መጽሐፈ ፡ አስቴር ፡ (አስ.) ።
መጽሐፈ ፡ አዮብ ፡ (አዮ.) ።
መዝሙረ ፡ ዳዊት ፡ (መዝ.) ።
መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (ምሳ.) ።
(መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ ።)
መጽሐፈ ፡ መክብብ ፡ (መክ.) ።
ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፡ (ማሕ.) ።
ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ (ኢሳ.) ።
ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፡ (ኤር.) ።
ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፡ (ሰቈ.) ።
ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፡ (ሕዝ.) ።
ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፡ (ዳን.) ።
ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፡ (ሆሴ.) ።
ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፡ (ዓሞ.) ።
ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፡ (ሚክ.) ።
ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ፡ (ኢዮኤ.) ።
ትንቢተ ፡ ዐብድዩ ፡ (ዐብ.) ።
ትንቢተ ፡ ዮናስ ፡ (ዮና.) ።
ትንቢተ ፡ ናሖም ፡ (ናሖ.) ።
ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፡ (ዕን.) ።
ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ፡ (ሶፎ.) ።
ትንቢተ ፡ ሐጌ ፡ (ሐጌ) ።
ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፡ (ዘካ.) ።
ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፡ (ሚል.) ።

የቀኖና ፡ መጻሕፍት ፤

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ሱቱኤል ፡ (ሱቱ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ካልዕ ፡ (ዕዝ.2) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ጦቢት ፡ (ጦቢ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ዮዲት ፡ (ዮዲ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ አስቴር ፡ (አስ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ቀዳማዊ ፡ (መቃ.1) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ካልዕ ፡ (መቃ.2) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ሣልስ ፡ (መቃ.3.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ሲራክ ፡ (ሲራ.) ። (ይዘጋጃል)
ጾሎተ ፡ ምናሴ ፡ (ምና.) ። (ይዘጋጃል)
ተረፈ ፡ ኤርምያስ ፡ (ኤር.) ። (ይዘጋጃል)
ሶስና ፡ (ሶስ) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ባሮክ ፡ (ባሮ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ጥበብ ፡ (ጥበ.) ። (ይዘጋጃል)
መዝሙረ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ (ሠለ.) ። (ይዘጋጃል)
ተረፈ ፡ ዳንኤል ፡ (ተረ.ዳን.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ፡ (ኩፋ.) ። (ይዘጋጃል)
መጽሐፈ ፡ ሔኖክ ፡ (ሔኖ.) ። (ይዘጋጃል)

ሐዲስ ፡ ኪ.ዳን ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ (ማቴ.) ።
የማርቆስ ፡ ወንጌል ፡ (ማር.) ።
የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ (ሉቃ.) ።
የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ (ዮሐ.) ።
የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ (ሐዋ.) ።
ወደሮሜ ፡ ሰዎች ፡ (ሮሜ.) ።
ወደቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ 1ኛ ፡ (ቆሮ.1) ።
ወደቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ 2ኛ ፡ (ቆሮ.2) ።
ወደገላትያ ፡ ሰዎች ፡ (ገላ.) ።
ወደኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ (ኤፌ.) ።
ወደፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡ (ፊልጵ.) ።
ወደቆላስይስ ፡ ሰዎች ፡ (ቆላ.) ።
ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ 1ኛ ፡ (ተሰ.1) ።
ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ 2ኛ ፡ (ተሰ.2) ።
ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ 1ኛ ፡ (ጢሞ.1) ።
ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ 2ኛ ፡ (ጢሞ.2) ።
ወደ ፡ ቲቶ ፡ (ቲቶ) ።
ወደ ፡ ፊልሞና ፡ (ፊልሞ.) ።
ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ (ዕብ.) ።
የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ 1ኛ ፡ (ጴጥ.1) ።
የጴጥሮስ ፡ መልእክት ፡ 2ኛ ፡ (ጴጥ.2) ።
የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ 1ኛ ፡ (ዮሐ.1) ።
የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ 2ኛ ፡ (ዮሐ.2) ።
የዮሐንስ ፡ መልእክት ፡ 3ኛ ፡ (ዮሐ.3) ።
የያዕቆብ ፡ መልእክት ፡ (ያዕ.) ።
የይሁዳ ፡ መልእክት ፡ (ይሁ.) ።
የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ (ራእ.) ።

ማሳሰቢያ ።

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፥ አሐዱ ፡ አምላክ ፤ አሜን ።

ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በንምራዊ ፡ አቀጻጽ ፡ ሲሰናዳ ፥ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፦

"መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፤ የብሉይና ፡ የሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ። "

ብላ ፥ ባ 1980 ፡ ዓ.ም. ፡ ያሳተመችውን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ ለቅሞ ፡ መዝግቧል ።

ሥራው ፡ የተዝመረው ፡ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 2001 ፡ ዓ.ም. ፥ ፈጽሞ ፡ ባጋጣሚ ፡ ነው ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ሳነብ ፥ አንዳንድ ፡ በማስታወሻ ፡ በተለይ ፡ የያዝኳቸው ፡ ጥቅሶች ፡ ለጥናት ፡ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፦ በማስሊያ ፡ (በ'ኮምፕዩተር') ፡ ልመዝግባቸው ፡ አልኹና ፥ ጥቂቱን ፡ እንደ ፡ መዘገብኹ ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ አይቼው ፡ የነበረ ፣ በንምራዊ ፡ አቀጻጽ ፡ የተሰናዳ ፡ ያማርኛ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መኖሩ ፡ ትዝ ፡ አለኝና ፥ ወዲያው ፡ ሰነዱን ፡ ከኢንተርኔት ፡ ቀዳኹ ።

ንምራዊ ፡ ሰነዱን ፡ በማግኘቴና ፡ ከትርፍ ፡ ድካም ፡ በመዳኔ ፡ እጅግ ፡ ተደሰትኹ ፤ አዘጋጆቹንም ፡ በልቤ ፡ አመሰገንኹ ። ስለእግዚአብሔር ፡ ፍቅርና ፡ ስለሰው ፡ ፍቅር ፡ ሲሉ ፡ የደከሙበት ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ትጋትንና ፡ ድካምን ፡ የሚጠይቅ ፡ ሥራቸው ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያሉ ፡ በሺ ፡ የሚቈጠሩ ፡ አንባብያንን ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ስላስገኘላቸው ፥ ታላቅ ፡ መንፈሳዊ ፡ ደስታ ፡ እንደሚኾንላቸው ፡ አምናለኹ ። እግዚአብሔር ፡ ዋጋቸውን ፡ ይክፈልልን ።

ሰነዱን ፡ በዝርዝር ፡ ስመለከተው ፥ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባ 1980 ፡ ዓ.ም. ፡ ያሳተመችውን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ የመዘገበ ፡ መኾኑን ፡ አረጋገጥኹና ፥ ደስ ፡ አለኝ ። ነገር ፡ ግን ፥ 'የቀኖና ፡ መጻሕፍት' ፡ የተባሉትን ፡ (ከ'መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ሱቱኤል' ፡ እስከ ፡ 'መጽሐፈ ፡ ሔኖክ') ፡ 18 ፡ መጻሕፍት ፡ እንዳልመዘገበ ፤ የመጻሕፍቱም ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ከታተመው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ መለየቱን ፡ ተገነዘብኹ ። ይዘቱን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ሳስተያየውም ፥ ቃል ፡ በቃል ፥ አንድ ፡ ኾኖ ፡ አገኘኹትና ፥ በዚህ ፡ ተማመንኹ ። የፊደል ፡ አጠነቃቀቁን ፡ ተኰር ፡ ብዬ ፡ ስመለከተው ፥ ከታተመው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምንም ፡ ያኽል ፡ እንደማይለይ ፡ አረጋገጥኹ ። የተለመዱ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶች ፡ ቢኖሩበትም ፥ ሰነዱን ፡ የፈለግኹት ፡ ለግል ፡ ጥናት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይበቃኛል ፡ ብዬ ፡ ተረጋጋኹ ።

ግእዝ-ዐማርኛ ፡ ክለሳ ፡ 2.0 ን ፡ አዘጋጅ ፡ ነበርና ፥ 'መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ለምን ፡ አላክልለትም ፡ አንባብያንስ ፡ ለምን ፡ እንደኔው ፡ አይጠቀሙበትም ፡ ' የሚለው ፡ ሐሳብ ፡ ባእምሮዬ ፡ ድንገት ፡ መጥቶ ፥ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ካወጣኹና ፡ ካወረድኹ ፡ በኋላ ፥ ሐሳቡ ፡ ተገቢ ፡ መስሎ ፡ ታየኝ ። ይህኑ ፡ ለማረጋገጥ ፥ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፥ ኹለት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህናትን ፡ በየግላቸው ፡ አማከርኹ ። ዐላማዬ ፦

- መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ እንዳዲስ ፡ ለመተርጐም ፡ ሳይኾን ፥ ራሷ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሰናዳችልንን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በመላ ፡ ዓለም ፡ ለሚገኙ ፡ ወንድሞቻችንና ፡ እኅቶቻችን ፥ በንምራዊ ፡ አቀጻጽ ፥ በነጻ ፡ ለማዳረስ ፤

- ሲዳረስ ፡ ደግሞ ፥ በመጽሐፍ ፡ ቅዱሱ ፡ የሚታዩት ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችም ፡ ኾኑ ፡ ግድፈቶች ፡ እንዳይዛመቱና ፥ ለሃይማኖታችንም ፡ ኾነ ፡ ለቋንቋችን ፡ ጠንቅ ፡ እንዳይኾኑ ፥ በመዝገበ ፡ ቃላት ፡ አማካይነት ፥ አስቀድሞ ፡ በነቂስ ፡ ዐርሞ ፡ ለማስወገድ ፡

መኾኑን ፡ አስረዳኋቸው ። ኹለቱም ፡ ካህናት ፦ ይሄማ ፡ ኹላችንስ ፡ የምንመኘው ፡ አይደለምን ፡ ቃሉ ፡ እስከተጠበቀ ፡ ድረስ ፥ ፊደሉን ፡ ዐርሞ ፡ ማሰናዳትማ ፡ የሚገባ ፡ ነው ፤ በርታ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያበርታኽ ፡ ብለው ፥ የሥራውን ፡ ዕቅድ ፡ ባረኩልኝ ።

ወዲያው ፡ ሥራውን ፡ ተያያዝኩት ። ሰው ፡ የሚሠራው ፡ ዥሉ ፡ ፍጹም ፡ አይኾንምና ፥ የሰነዱን ፡ ይዘት ፡ በዝርዝር ፡ ሳጠና ፥ ገልባጭ ፡ ያሳሳታቸውን ፡ ጥቂት ፡ ስሕተቶች ፡ አገኘኹ ፤ ለምሳሌ ፥ 'እግዚአብሔር' ፡ የሚለው ፡ ቃል ፦

'እግዚብሔር' ፥ 'እግዚአሔር' ፥ 'እግዚአብሄር' ፥ 'እግዚአብሔ' ፥ 'እግዚአብር' ፥ 'እግዚአብሔር'

ተብሎ ፥ በ 6 ፡ ሌሎች ፡ የተሳሳቱ ፡ አጻጻፎች ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ተጽፏል ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የተለመዱ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶች ፡ አሉበት ። የስሕተቶቹን ፡ ዐይነት ፡ እዚህ ፡ መዘርዘሩ ፡ አንባቢን ፡

ማድከም ፡ ስለሚኾን ፥ ቀሪውን ፡ ዝርዝር ፡ ከነሐተታው ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ በማመዛዘኛ ፡ መልክ ፡ አዘጋጃለኹ ። ስለፊደል ፡ አጠነቃቀቅ ፡ ጉዳይ ፡ መመሪያን ፡ ለሚሹ ፥ ያለቃ ፡ ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድን ፡ 'ዐዲስ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት' ፡ ቢመለከቱ ፡ ሙሉ ፡ ትምህርት ፡ ያገኙበታል ፡ (http://www.gzamargna.net/html/amargnaMezgebeQalat.html) ፤ የዋዜማ ፡ ሠርዐት ንም ፡ መመሪያ ፥ ተቀጥላ ፡ ፩ ፡ ቢመለከቱ ፥ ከርሱም ፡ በቂ ፡ መረጃ ፡ ያገኙበታል ፡ (http://www.gzamargna.net) ።

ለጊዜው ፥ ባንድ ፡ አነስተኛ ፡ ጥቅስ ፡ ላይ ፥ በዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ 1 ፡ ቍ.1-5 ፡ ፡ የሚታዩትን ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶች ፡ እንመልከት ፡—

1 ፤ በመ[ጀ]መሪያ [redacted] እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ። ××

2 ፤ ምድርም ባዶ ነበረች ፥ አንዳችም አልነበረባትም ፤ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በው[ኃ] ላይ ሰ[ፍፎ] ነበር ። ××

3 ፤ እግዚአብሔርም [።] ብርሃን ይ[ሁ]ን [ኣ]ለ ፤ ብርሃንም [ሆ]ነ ። ××××

4 ፤ እግዚአብሔርም ብርሃኑ መልካም እንደ [ሆ]ነ አየ ፤ እግ[ዚ.ብ]ሔርም ብርሃንንና ጨለማን ለየ ። ××

5 ፤ እግዚአብሔርም ብርሃኑን ቀን ብሎ ጠራው ፥ ጨለማውንም ሌሊት አለው ። ማታም [ሆ]ነ [ጥዋ]ትም [ሆ]ነ ፥ አንድ ቀን ። ×××

ሲታረም ፡ ደግሞ ፡—

1 ፤ በመ[ዠ]መሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ። ✓

2 ፤ ምድርም ፡ ባዶ ፡ ነበረች ፥ አንዳችም ፡ አልነበረባትም ፤ ጨለማም ፡ በጥልቁ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በው[ሃ] ፡ ላይ ፡ ሰ[ፎ] ፡ ነበር ። ✓

3 ፤ እግዚአብሔርም ፡— ብርሃን ፡ ይ[ኹ]ን ፡ [ኣ]ለ ፤ ብርሃንም ፡ [ኾ]ነ ። ✓

4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃኑ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ [ኾ]ነ ፡ አየ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃንንና ፡ ጨለማን ፡ ለየ ። ✓

5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃኑን ፡ ቀን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፥ ጨለማውንም ፡ ሌሊት ፡ አለው ። ማታም ፡ [ኾ]ነ ፥ [ጧ]ትም ፡ [ኾ]ነ ፥ አንድ ፡ ቀን ። ✓

ጥቅሱ ፡ ከተጻፈባቸው ፡ 175 ፡ የፊደል ፡ ምልክቶች ፡ ውስጥ ፥ 14 ቱ ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ ግድፈት ፡ ኾነው ፡ ታርመዋል ፤ 8%ው ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ባ 10000 ፡ የሚቈጠሩ ፡ የፊደል ፡ ስሕተቶችና ፡ ግድፈቶች ፡ ታርመዋል ፤ አኹንም ፡ ቢኾን ፡ የታለፉ ፡ አይጠፉምና ፥ አንባብያን ፡ ባገኟቸው ፡ ቍጥር ፡ በማስታወሻ ፡ ይዘው ፡ ቢያስታውቁኝ ፡ እጅግ ፡ አመሰግናለኹ ።

ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ በማናበብ ፡ ብቻ ፡ የሚገኙ ፤ ትርጉም ፡ የሚለውጡ ፡ አደገኛ ፡ ስሕተቶች ፡ አሉ ። ለምሳሌ ፥ መጽሐፉ ፡ 'የ[ማ]ያምን' ፡ ያለውን ፥ ገልባጭ ፡ 'የ[ማ]ያምን' ፡ ብሎት ፡ ይኾናል ። እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ስሕተት ፥ ቃል ፡ በቃል ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ እያናበቡ ፡ ካልኾነ ፥ ፈጽሞ ፡ ማስወገድ ፡ አይቻልም ። ሥራው ፡ ከሚያዝያ ፡ 2001 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ ጥር ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፥ በዘጠኝ ፡ ወር ፥ ያውም ፡ በትርፍ ፡ ጊዜ ፥ የተሠራ ፡ በመኾኑ ፥ በከፊል ፡ እንጂ ፡ በሙሉ ፡ አልተናበበምና ፥ አኹንም ፥ አንባብያንን ፡ ዐደራ ፡ እላለኹ ። ከጥር ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ ወዲህ ፡ እስከ ፡ መጋቢት ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፡ ደግሞ ፡ ተጨመማሪ ፡ ዕርማት ፡ ተካኺዷል ።

ሐዋርያው ፡ ዮሐንስ ፡—

በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ ለሚሰማ ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እመሰክራለኹ ፤ ማንም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢጨምር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ መቅሠፍቶች ፡ ይጨምርበታል ፤ ማንምም ፡ በዚህ ፡ በትንቢት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ቃሎች ፡ አንዳች ፡ ቢያጐድል ፥ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ከሕይወት ፡ ዛፍና ፡ ከቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕድሉን ፡ ያጐድልበታል ።

ያለውን ፡ በመጠበቅ ፥ ከጠቅላላው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በእከይ ፡ የጐደለ ፡ የለም ።

ኾኖም ፤

- እላይ ፡ እንዳመለከትኹት ፥ ዐቅም ፡ በማነሱ ፥ ከ 85 ቱ ፡ መጻሕፍት ፡ 18 ቱ ፡ የቀኖና ፡ መጻሕፍት ፡ በጊዜ ፡ ስላልደረሱልኝ ፥ ሳይታከሉ ፡ ቀርተዋል ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፥ ወደፊት ፡ ይታከላሉ ፤

- የቃላቱ ፡ አጻጻፍ ፡ ፊደልን ፡ እንዲጠነቅቅ ፥ በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ መሠረት ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ታርሟል ፤ የነጠብጣቦች ፡ ዕርማት ፥ ገና ፡ ይቀረዋል ። በተከታዮቹ ፡ ክለሳዎች ፡ ዕርማቱ ፡ ይቀጥላል ።

- የቦታና ፡ የሰው ፡ ስሞች ፥ በግእዙም ፡ ኾነ ፡ ባማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፥ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ካይነተኛው ፡ አጠራራቸው ፡ በፊደል ፣ በድምፅ ፣ በላሕይ ፥ ተራርቀው ፡ ይገኛሉ ። ይህም ፡ የኾነበት ፡ ዋነኛ ፡ ምክንያት ፥ መጻሕፍቱ ፡ በቀጥታ ፡ ከዕብራይስጡ ፡ ከመተርጐም ፡ ይልቅ ፥ በተዘዋዋሪ ፡ ከጽርእ ፡ (ግሪክ) ፡ ስለ ፡ ተተረጐሙ ፡ ይመስላል ። ፊደሉ ፡ ሊስተካከል ፡ የተገባውን ፡ (ማለት ፥ ድምፁን ፡ ሳይለውጡ ፥ ፊደሉን ፡ ብቻ ፡ በመጠንቀቅ) ፡ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ለማስተካከል ፡ ሞክሬያለኹ ፤ አጠራሩ ፡ (ወይም ፡ ድምፁ) ፡ ካይነተኛ ፡ አጠራር ፡ ፈጽሞ ፡ የራቀውን ፡ ደግሞ ፥ በኅዳግ ፡ አመልክቼዋለኹ ፤ ኾኖም ፥ ሥራው ፡ ገና ፡ ውጥን ፡ እንጂ ፥ አልተከናወነም ።

- መጥቀሻ ፡ ቁጥሮችም ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ ገና ፡ አልተናበቡም ፤ ስለዚህ ፥ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ስሕተት ፡ ይገኝባቸዋል ። ይህ ፡ የኾነበት ፡ ምክንያት ፥ የያንዳንዱ ፡ ቁጥር ፡ መነሻና ፡ መድረሻ ፡ በታተመው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በልዩ ፡ ምልክት ፡ ስላልተመለከተ ፥ መለየቱ ፡ አስቸግሮ ፡ ነው ። ኾኖም ፥ ከሌላዎች ፡ ምንጮች ፡ ጋራ ፡ እያገናዘቡ ፡ ማስተካከል ፡ ስለሚቻል ፥ ስሕተቶቹ ፡ ኹሉ ፡ በሚከተሉት ፡ ክለሳዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ይወገዳሉ ።

- የመጻሕፍቱ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ በታተመው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ መሠረት ፡ እንዲኾን ፡ አድርጌዋለኹ ። እንዲሁም ፥ የመዝሙረ ፡ ዳዊትን ፡ የመዝሙር ፡ ቁጥሮች ፡ ተራ ፡ ወደነበረው ፡ መልሼዋለኹ ።

እንደምታዩት ፥ ሥራው ፡ ተገባዷል ፤ አልተፈጸመም ፥ ለመፈጸምም ፡ የተቻለው ፡ ኹሉ ፡ ይደረጋል ። እስከዚያው ፡ ድረስ ፡ አንባብያን ፡ እንዲታገሡልን ፡ እየለመንኹ ፥ ይቅርታቸውን ፡ በትሕትና ፡ እጠይቃለኹ ።

ስሕተቶችንና ፡ ግድፈቶችን ፡ ኹሉ ፡ በፍጥነት ፡ ማስወገድ ፡ ይቻል ፡ ዘንድ ፥ አንባብያን ፡ በየበኩላቸው ፡ የሚያገኟቸውን ፡ ስሕተቶችና ፡ ግድፈቶች ፡ ቢያመለክቱኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ አመሰግናለኹ ። እንዲሁም ፥ ገና ፡ በማስሊያ ፡ ያልተለቀሙትን ፡ መጻሕፍት ፡ ለመልቀም ፡ ፈቃደኞች ፡ የሚኾኑት ፡ ኹሉ ፡ እንዲተባበሩኝ ፡ በትሕትና ፡ እጋብዛለኹ ።

ከመቼውም ፡ የበለጠ ፡ በዘመናችን ፥ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቅጂዎች ፡ በዓለም ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ በንምራዊ ፡ አቀጻጽ ፡ ተሰናድተው ፥ በመርበብት ፡ ("Internet") ፡ አማካይነት ፥ በሰፊው ፡ ይሠራጫሉ ።

በግእዝ–ዐማርኛ ፡ ክለሳ ፡ ፪.፯ ፡ ጥር ፡ 7 ፡ ቀን ፡ 2002 ፡ ዓ.ም. ፡ ለመዝመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የወጣውን ፡ ይኸኛውን ፡ ያማርኛ ፡ ቅጂ ፡ ከሌላዎቹ ፡ ያማርኛ ፡ ቅጂዎች ፡ ለየት ፡ የሚያደርገው ፤

- 1 ኛ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መሠረት ፡ መዘጋጀቱ ፤

- 2 ኛ ፤ ፊደሉና ፡ አጻጻፉ ፡ በግእዝና ፡ ባማርኛ ፡ መዛግብተ ፡ ቃላት ፡ መሠረት ፡ መዘጋጀቱ ፡ ነው ።

ጽሑፉ ፡ የተጻፈው ፡ "A0 Desta Unicode" ፡ በተባለው ፡ የዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ ቅርጸት ፡ ነው ፤ ርሱና ፡ ሌላዎችም ፡ ቅርጸቶች ፡ (A0 Tesfa Unicode ፥ A0 Addis Abeba Unicode) ፡ ከዋዜማ ፡ ሥርዐት ፡ መርበቢያ ፡ ከ http://www.gzamargna.net ፡ በነጻ ፡ ይቀዳሉ ።

በዚህ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱሱ ፡ ክለሳ ፡ 8_20080726 ፥ ከቀደሙት ፡ ክለሳዎች ፡ ያለፉ ፡ ጥቃቅን ፡ ስሕተቶች ፡ ታርመዋል ። በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ዐዲስ ፡ የወጣው ፡ "ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ" ፡ መግበር ፡ ባስጨበጠን ፡ ያማርኛ ፡ ፊደል ፡ መጠንቀቂያ ፡ አማካይነት ፥ ፊደሉ ፡ ዳግመኛ ፡ በዝርዝር ፡ ታርሞበታል ([1]) ።

ሊታረም ፡ የሚገባው ፡ ስሕተት ፥ ዐራሚ ፡ ዐጥቶ ፥ የባሰ ፡ ስሕተትን ፡ እየወለደና ፡ እየተራባ ፡ ሲኼድ ፡ እጅን ፡ አጣምሮ ፡

---

1 ከዚሁ ፡ ጋራ ፥ ይህ ፡ የምታዩት ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዝግጅት ፥ እንዲሁም ፡ የእንግሊዝኛ ፣ የፈረንሳይኛና ፡ የሶማልኛ ፡ ክለሳዎቹ ፡ በ".txt" ፡ አቀጻጽ ፡ ከ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መግበር ፡ ጋራ ፡ ተሰናድተው ፡ ስለተያያዙላችኹ ፥ አንባብያን ፥ እጅግ ፡ በተሻለ ፡ ኹኔታ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በዝርዝር ፡ ለማጥናትና ፡ ለመመርመር ፡ እንደሚያስችላችኹ ፡ አልጠራጠርም ። "ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ ነጻ ፡ መግበር ፡ ነው ፤ ከ awdeqelem.net ፡ እና ፡ ከ gzamargna.net ፡ በነጻ ፡ ይቀዳል ።

መመልከት ፥ ሐዋርያው ፡ ያዕቆብ ፥ በመልእክቱ ፡ (4 ፥ 17) ፥ 'እንግዲህ ፡ በጎ ፡ ለማድረግ ፡ ዐውቆ ፥ ለማይሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ነው' ፡ ብሎ ፡ አስተምሯልና ፥ ይህ ፡ እንዳይኾንብኝ ፥ በማወቅ ፡ የተቻለኝን ፥ እንሆ ፥ አበርክቻለኹ ። ባለማወቅ ፥ በድፍረት ፡ ላሳሳትኹት ፡ ኾሉ ፡ ደግሞ ፡ ባለቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ እንዲለኝ ፡ እለምናለኹ ።

ይህ ፡ ሥራ ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ የኾነች ፡ የቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሊቃውንት ፡ እንጂ ፥ የኔ ፡ ያንድ ፡ ተርታ ፡ አባሏ ፡ ሊኾን ፡ ፈጽሞ ፡ ባልተገባው ፡ ነበር ። አኹንም ፡ ቢኾን ፥ ተስፋዬና ፡ እምነቴ ፥ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በፊደልም ፡ በትርጉምም ፡ አሻሽላ ፡ አሰናድታ ፡ ታድለናለች ፡ የሚል ፡ ነው ።

አነሣሥቶ ፡ ላስገኮመረኝ ፥ አስገኮምሮ ፡ ላስፈጸመኝ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፥ ለዘለዓለሙ ፤ አሜን ❖

ወሌ ፡ ነጋ ።

awdeqelem@yegara.net

ስልክ Tel.: (+44) 20 8251 2492 (ለንደን)

awdeqelem.net
gzamargna.net

ለሥራው ፡ ያገለገሉ ፡ መጻሕፍትና ፡ መሳሊያዎች ፤

የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ *መጽሐፍ ፡ ቅዱስ* ። 1980 ፡ ዓ.ም. ።

ደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ (አለቃ) ፤ *ዐዲስ ፡ ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት* ፤ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ፤ 1285 ፡ ገጽ ። (http://www.gzamargna.net/html/amargnaMezgebeQalat.html)

ኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ ፡ (አለቃ) ፤ *መጽሐፈ ፡ ሰዋስው ፡ ወግስ ፡ ወመዝገበ ፡ ቃላት ፡ ሐዲስ* ፤ አርቲስቲክ ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፤ 909 ፡ ገጽ ። (http://www.gzamargna.net/html/gzMezgebeQalat.html)

Joan Comay, *Who's who in the Old Testament,* J. M. Dent, London, 1993 A.D.

e-Sword version 9.5.1, 2009 A.D. (http://www.e-sword.net)

Concordance Bibliquest version 5.0.2, 2005 A.D. (http://www.bibliquest.org)

ዋዜማ ፡ ሥርዐት • Wazéma System • Wazéma Système ፡ ክለሳ ፡ 3 ፡ (http://www.gzamargna.net/) ።

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ ክለሳ ፡ 1.1 • **AwdeQelem Text Processor** v.1.1 • **AwdeQelem traitement de texte** v.1.1 ፡ (http://www.awdeqelem.net) ።

ማሳጠሪያዎች ፤

- ዐማ. ዐማርኛ
- ዐረ. ዐረብኛ
- ዕብ. ዕብራይስጥ
- ፋር. ፋርስ
- ጽር. ጽርእ ፡ (ግሪክ)
- ሮማ. ሮማይስጥ ፡ (ላቲን)
- ሱር. ሱርስት ፡ (አረማይስጥ)

የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በመዠመሪያ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጠረ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ምድርም ፡ ባዶ ፡ ነበረች ፥ አንዳችም ፡ አልነበረባትም ፤ ጨለማም ፡ በጥልቁ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ሰፈ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ብርሃን ፡ ይኹን ፡ አለ ፤ ብርሃንም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃኑ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃንንና ፡ ጨለማን ፡ ለየ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብርሃኑን ፡ ቀን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፥ ጨለማውንም ፡ ሌሊት ፡ አለው ። ማታም ፡ ኾነ ፥ ጧትም ፡ ኾነ ፥ አንድ ፡ ቀን ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በውሃዎች ፡ መካከል ፡ ጠፈር ፡ ይኹን ፥ በውሃና ፡ በውሃ ፡ መካከልም ፡ ይክፈል ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጠፈርን ፡ አደረገ ፥ ከጠፈር ፡ በታችና ፡ ከጠፈር ፡ በላይ ፡ ያሉትንም ፡ ውሃዎች ፡ ለየ ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጠፈርን ፡ ሰማይ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ማታም ፡ ኾነ ፥ ጧትም ፡ ኾነ ፥ ኹለተኛ ፡ ቀን ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ውሃ ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ይሰብሰብ ፥ የብሱም ፡ ይገለጥ ፡ አለ ፡ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የብሱን ፡ ምድር ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ የውሃ ፡ መከማቻውንም ፡ ባሕር ፡ አለው ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ምድር ፡ ዘርን ፡ የሚሰጥ ፡ ሣርንና ፡ ቡቃያን ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ ዘሩ ፡ ያለበትን ፡ ፍሬን ፡ የሚያፈራ ፡ ዛፍን ፡ ታብቅል ፡ አለ ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ምድርም ፡ ዘርን ፡ የሚሰጥ ፡ ሣርንና ፡ ቡቃያን ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ ዘሩም ፡ ያለበትን ፡ ፍሬን ፡ የሚያፈራ ፡ ዛፍን ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ አበቀለች ። እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ማታም ፡ ኾነ ፡ ጧትም ፡ ኾነ ፥ ሦስተኛ ፡ ቀን ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ ቀንና ፡ ሌሊትን ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፡ ብርሃናት ፡ በሰማይ ፡ ጠፈር ፡ ይኹኑ ፤ ለምልክቶች ፡ ለዘመኖች ፡ ለዕለታት ፡ ለዓመታትም ፡ ይኹኑ ፤

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ በሰማይ ፡ ጠፈር ፡ ብርሃናት ፡ ይኹኑ ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኹለት ፡ ታላላቆች ፡ ብርሃናትን ፡ አደረገ ፤ ትልቁ ፡ ብርሃን ፡ በቀን ፡ እንዲሠለጥን ፥ ትንሹም ፡ ብርሃን ፡ በሌሊት ፡ እንዲሠለጥን ፤ ከዋክብትንም ፡ ደግሞ ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ በሰማይ ፡ ጠፈር ፡ አኖራቸው ፤

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ እንዲሠለጥኑ ፥ ብርሃንንና ፡ ጨለማንም ፡ እንዲለዩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ማታም ፡ ኾነ ፡ ጧትም ፡ ኾነ ፥ አራተኛ ፡ ቀን ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ ውሃ ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ያላቸውን ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ታስገኝ ፥ ወፎችም ፡ ከምድር ፡ በላይ ፡ ከሰማይ ፡ ጠፈር ፡ በታች ፡ ይብረሩ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ታላላቆች ፡ ዐንበሪዎችን ፥ ውሃዩቱ ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ ያስገኘቻቸውንም ፡ ተንቀሳቃሾቹን ፡ ሕያዋን ፡ ፍጥረታት ፡ ኹሉ ፥ እንደ ፡ ወገኑ ፡ የሚበሩትንም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ፈጠረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ባረካቸው ፦ ብዙ ፡ ተባዙም ፡ የባሕርንም ፡ ውሃ ፡ ሙሏት ፤ ወፎችም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይብዙ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ማታም ፡ ኾነ ፡ ጧትም ፡ ኾነ ፥ ዐምስተኛ ፡ ቀን ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ ምድር ፡ ሕያዋን ፡ ፍጥረታትን ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፥ እንስሳትንና ፡ ተንቀሳቃሾችን ፡ የምድር ፡ አራዊትንም ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፥ ታውጣ ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ የምድር ፡ አራዊትን ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ አደረገ ፥ እንስሳውንም ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፥ የመሬት ፡ ተንቀሳቃሾችንም ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ ሰውን ፡ በመልካችን ፡ እንደ ፡ ምሳሌያችን ፡ እንፍጠር ፤ የባሕር ፡ ዓሣዎችንና ፡ የሰማይ ፡ ወፎችን ፥ እንስሳትንና ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱትንም ፡ ኹሉ ፡ ይግዙ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰውን ፡ በመልኩ ፡ ፈጠረ ፤ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ፈጠረው ፤ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠራቸው ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባረካቸው ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ብዙ ፥ ተባዙ ፥ ምድርንም ፡ ሙሏት ፥ ግዟትም ፤ የባሕርን ፡ ዓሣዎችና ፡ የሰማይን ፡ ወፎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱትንም ፡ ኹሉ ፡ ግዟቸው ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ መብል ፡ ይኾናችኹ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዘሩ ፡ በርሱ ፡ ያለውን ፡ ሐመልማል ፡ ኹሉ ፥ የዛፍን ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈራውንና ፡ ዘር ፡ ያለውንም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ሰጠኋችኹ ፤

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ ለምድርም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፥ ለሰማይም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፥ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ላላቸው ፡ ለምድር ፡ ተንቀሳቃሾችም ፡ ኹሉ ፡ የሚበቅለው ፡ ሐመልማል ፡ ኹሉ ፡ መብል ፡ ይኹንላቸው ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበረ ። ማታም ፡ ኾነ ፡ ጧትም ፡ ኾነ ፥ ስድስተኛ ፡ ቀን ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሰራዊታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተፈጸሙ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ፈጸመ ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ዐረፈ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰባተኛውን ፡ ቀን ፡ ባረከው ፡ ቀደሰውም ፤ እግዚአብሔር ፡ ሊያደርገው ፡ ከፈጠረው ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ በርሱ ፡ ዐርፏልና ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባደረገ ፡ ቀን ፡ በተፈጠሩ ፡ ጊዜ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ልደት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የሜዳ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ዅሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ገና ፡ አልነበረም ፤ የሜዳውም ፡ ቡቃያ ፡ ዅሉ ፡ ገና ፡ አልበቀለም ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አላዘነበም ፡ ነበርና ፥ ምድርንም ፡ የሚሠራባት ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጉም ፡ ከምድር ፡ ትወጣ ፡ ነበር ፥ የምድርንም ፡ ፊት ፡ ዅሉ ፡ ታጠጣ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ሰውን ፡ ከምድር ፡ ዐፈር ፡ አበጀው ፤ በአፍንጫውም ፡ የሕይወት ፡ እስትንፋስን ፡ እፍ ፡ አለበት ፤ ሰውም ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ በምሥራቅ ፡ በዔዴን ፡ ገነትን ፡ ተከለ ፥ የፈጠረውንም ፡ ሰው ፡ ከዚያው ፡ አኖረው ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ለማየት ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፥ ለመብላትም ፡ መልካም ፡ የኾነውን ፡ ዛፍ ፡ ዅሉ ፡ ከምድር ፡ አበቀለ ፤ በገነትም ፡ መካከል ፡ የሕይወትን ፡ ዛፍ ፥ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ የሚያስታውቀውንም ፡ ዛፍ ፡ አበቀለ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ወንዝም ፡ ገነትን ፡ ያጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከዔዴን ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፤ ከዚያም ፡ ለአራት ፡ ክፍል ፡ ይከፈል ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ የአንደኛው ፡ ወንዝ ፡ ስም ፡ ፊሶን [2] ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ወርቅ ፡ የሚገኝበትን ፡ የኤውላጥ ፡ ምድርን ፡ ይከባል ፤ የዚያም ፡ ምድር ፡ ወርቅ ፡ ጥሩ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ከዚያም ፡ ሉልና ፡ የከበረ ፡ ድንጋይ ፡ ይገኛል ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ የኹለተኛውም ፡ ወንዝ ፡ ስም ፡ ግዮን [3] ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምድር ፡ ዅሉ ፡ ይከባል ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የሦስተኛውም ፡ ወንዝ ፡ ስም ፡ ጤግሮስ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ በአሶር ፡ ምሥራቅ ፡ የሚኼድ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ አራተኛውም ፡ ወንዝ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ሰውን ፡ ወስዶ ፡ ያበጃትም ፡ ይጠብቃትም ፡ ዘንድ ፡ በዔዴን ፡ ገነት ፡ አኖረው ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ሰውን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ። ከገነት ፡ ዛፍ ፡ ዅሉ ፡ ትበላለኽ ፤

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ ከሚያስታውቀው ፡ ዛፍ ፡ አትብላ ፤ ከርሱ ፡ በበላኽ ፡ ቀን ፡ ሞትን ፡ ትሞታለኽና ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ አለ ፦ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ የሚመቸውን ፡ ረዳት ፡ እንፍጠርለት ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ የምድር ፡ አራዊትንና ፡ የሰማይ ፡ ወፎችን ፡ ዅሉ ፡ ከመሬት ፡

---

2 ፊሶን ፤ ዕብ. ፥ ፊሾን ፡ (ኤፌሶን • ጥቀር ፡ አባይ) ።

3 ግዮን ፤ ዕብ. ፥ ጊሖን ፡ (ነጭ ፡ አባይ) ።

አደረገ ፤ በምን ፡ ስም ፡ እንደሚጠራቸውም ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አዳም ፡ አመጣቸው ፤ አዳምም ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ላለው ፡ ሹሉ ፡ በስሙ ፡ እንደ ፡ ጠራው ፡ ስሙ ፡ ያው ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ አዳምም ፡ ለእንስሳት ፡ ሹሉ ፥ ለሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ሹሉ ፥ ለምድር ፡ አራዊትም ፡ ሹሉ ፡ ስም ፡ አወጣላቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአዳም ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ረዳት ፡ አልተገኘለትም ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ በአዳም ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍን ፡ ጣለበት ፥ አንቀላፋም ፤ ከጐኑም ፡ አንዲት ፡ ዐጥንትን ፡ ወስዶ ፡ ስፍራውን ፡ በሥጋ ፡ ዘጋው ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ከአዳም ፡ የወሰዳትን ፡ ዐጥንት ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ሠራት ፤ ወደ ፡ አዳምም ፡ አመጣት ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ አዳምም ፡ አለ ፦ ይህች ፡ ዐጥንት ፡ ከዐጥንቴ ፡ ናት ፥ ሥጋም ፡ ከሥጋዬ ፡ ናት ፤ ርሷ ፡ ከወንድ ፡ ተገኝታለችና ፡ ሴት ፡ ትባል ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፥ በሚስቱም ፡ ይጣበቃል ፤ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ።

ዘፍ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ አዳምና ፡ ሚስቱ ፣ ኹለቱም ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ነበሩ ፥ አይተፋፈሩም ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እባብም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ከፈጠረው ፡ ከምድር ፡ አውሬ ፡ ሹሉ ፡ ይልቅ ፡ ተንኰለኛ ፡ ነበረ ። ሴቲቱንም ፦ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገነት ፡ ዛፍ ፡ ሹሉ ፡ እንዳትበሉ ፡ አዟልን ፧ አላት ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሴቲቱም ፡ ለእባቡ ፡ አለችው ፦ በገነት ፡ ካለው ፥ ከዛፍ ፡ ፍሬ ፡ እንበላለን ፤

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በገነት ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ ከዛፉ ፡ ፍሬ ፥ እግዚአብሔር ፡ አለ ፦ እንዳትሞቱ ፡ ከርሱ ፡ አትብሉ ፡ አትንኩትም ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እባብም ፡ ለሴቲቱ ፡ አላት ፦ ሞትን ፡ አትሞቱም ፤

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ከርሷ ፡ በበላችኹ ፡ ቀን ፡ ዐይኖቻችኹ ፡ እንዲከፈቱ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ የምታውቁ ፡ እንድትኾኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለሚያውቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ሴቲቱም ፡ ዛፉ ፡ ለመብላት ፡ ያማረ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ለዐይንም ፡ እንደሚያስጐመጃ ፥ ለጥበብም ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየች ፤ ከፍሬውም ፡ ወሰደችና ፡ በላች ፤ ለባሏም ፡ ደግሞ ፡ ሰጠችው ፡ ርሱም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በላ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የኹለቱም ፡ ዐይኖች ፡ ተከፈቱ ፥ እነርሱም ፡ ዕራቍታቸውን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ዐወቁ ፤ የበለስንም ፡ ቅጠሎች ፡ ሰፍተው ፡ ለእነርሱ ፡ ለራሳቸው ፡ ግልድም ፡ አደረጉ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እነርሱም ፡ ቀኑ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የአምላክን ፡ ድምፅ ፡ ከገነት ፡ ውስጥ ፡ ሲመላለስ ፡ ሰሙ ፤ አዳምና ፡ ሚስቱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከአምላክ ፡ ፊት ፡ በገነት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ተሸሸጉ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ አዳምን ፡ ጠርቶ ፦ ወዴት ፡ ነኽ ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ በገነት ፡ ድምፅኽን ፡ ሰማኹ ፤ ዕራቍቴንም ፡ ስለ ፡ ኾንኹ ፡ ፈራኹ ፥ ተሸሸግኹም ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ዕራቍትኽን ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ማን ፡ ነገረኽ ፧ ከርሱ ፡ እንዳትበላ ፡ ካዘዝኹኽ ፡ ዛፍ ፡ በእውኑ ፡ በላኽን ፧

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ አዳምም ፡ አለ ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እንድትኾን ፡ የሰጠኸኝ ፡ ሴት ፡ ርሷ ፡ ከዛፉ ፡ ሰጠችኝና ፡ በላኹ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ሴቲቱን ፦ ይህ ፡ ያደረግሽው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላት ። ሴቲቱም ፡ አለች ፦ እባብ ፡ አሳተኝና ፡ በላኹ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ እባቡን ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ስላደረግኽ ፡ ከእንስሳት ፡ ከምድር ፡ አራዊትም ፡ ኹሉ ፡ ተለይተኽ ፡ አንተ ፡ የተረገምኽ ፡ ትኾናለኽ ፤ በሆድኽም ፡ ትኼዳለኽ ፥ ዐፈርንም ፡ በሕይወትኽ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ትበላለኽ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ በአንተና ፡ በሴቲቱ ፡ መካከል ፥ በዘርኽና ፡ በዘሯም ፡ መካከል ፡ ጠላትነትን ፡ አደርጋለኹ ፤ ርሱ ፡ ራስኽን ፡ ይቀጠቅጣል ፥ አንተም ፡ ሰኰናውን ፡ ትቀጠቅጣለኽ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ለሴቲቱም ፡ አለ ፦ በፀነስሽ ፡ ጊዜ ፡ ጭንቅሽን ፡ እጅግ ፡ አበዛለኹ ፤ በጭንቅ ፡ ትወልጃለሽ ፤ ፈቃድሽም ፡ ወደ ፡ ባልሽ ፡ ይኾናል ፥ ርሱም ፡ ገዢሽ ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ አዳምንም ፡ አለው ፦ የሚስትኽን ፡ ቃል ፡ ሰምተኻልና ፥ ከርሱ ፡ እንዳትበላ ፡ ካዘዝኹኽ ፡ ዛፍም ፡ በልተኻልና ፥ ምድር ፡ ከአንተ ፡ የተነሣ ፡ የተረገመች ፡ ትኹን ፤ በሕይወት ፡ ዘመንኽም ፡ ኹሉ ፡ በድካም ፡ ከርሷ ፡ ትበላለኽ ፤

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ሾኽንና ፡ አሜከላን ፡ ታበቅልብኻለች ፤ የምድርንም ፡ ቡቃያ ፡ ትበላለኽ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ወደወጣኽበት ፡ መሬት ፡ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ በፊትኽ ፡ ወዝ ፡ እንጀራን ፡ ትበላለኽ ፤ ዐፈር ፡ ነኽና ፥ ወደ ፡ ዐፈርም ፡ ትመለሳለኽና ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ አዳምም ፡ ለሚስቱ ፦ ሔዋን ፡ ብሎ ፡ ስም ፡ አወጣ ፥ የሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ እናት ፡ ናትና ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ለአዳምና ፡ ለሚስቱ ፡ የቀሩበትን ፡ ልብስ ፡ አደረገላቸው ፥ አለበሳቸውም ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ አዳም ፡ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ ለማወቅ ፡ ከእኛ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነ ፤ አኹንም ፡ እጁን ፡ እንዳይዘረጋ ፥ ደግሞም ፡ ከሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ወስዶ ፡ እንዳይበላ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ እንዳይኖር ፤

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ከዔዴን ፡ ገነት ፡ አስወጣው ፥ የተገኘባትን ፡ መሬት ፡ ያርስ ፡ ዘንድ ።

ዘፍ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ አዳምንም ፡ አስወጣው ፥ ወደሕይወት ፡ ዛፍ ፡ የሚወስደውንም ፡ መንገድ ፡ ለመጠበቅ ፡ ኪሩቤልንና ፡ የምትገለባበጥ ፡ የነበልባል ፡ ሰይፍን ፡ በዔዴን ፡ ገነት ፡ ምሥራቅ ፡ አስቀመጠ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ አዳምም ፡ ሚስቱን ፡ ሔዋንን ፡ ዐወቀ ፤ ፀነሰችም ፥ ቃየንንም ፡ ወለደች ። ርሷም ፦ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አገኘኹ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ደግሞም ፡ ወንድሙን ፡ አቤልን ([4]) ፡ ወለደች ። አቤልም ፡ በግ ፡ ጠባቂ ፡ ነበረ ፤ ቃየንም ፡

---

4 አቤል ፤ ዕብ. ፥ ሀቤል ።

ምድርን ፡ የሚያርስ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ቃየን ፡ ከምድር ፡ ፍሬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ፤

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ አቤልም ፡ ደግሞ ፡ ከበጎቹ ፡ በኵራትና ፡ ከስቡ ፡ አቀረበ ። እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ አቤልና ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ተመለከተ ፤

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ቃየንና ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ግን ፡ አልተመለከተም ። ቃየንም ፡ እጅግ ፡ ተናደደ ፡ ፊቱም ፡ ጠቈረ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቃየንን ፡ አለው ፦ ለምን ፡ ተናደድኽ ፧ ለምንስ ፡ ፊትኽ ፡ ጠቈረ ፧

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ መልካም ፡ ብታደርግ ፡ ፊትኽ ፡ የሚበራ ፡ አይደለምን ፧ መልካም ፡ ባታደርግ ፡ ግን ፡ ኀጢአት ፡ በደጅ ፡ ታደባለች ፤ ፈቃዷም ፡ ወዳንተ ፡ ነው ፥ አንተ ፡ ግን ፡ በርሷ ፡ ንገሥባት ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ቃየንም ፡ ወንድሙን ፡ አቤልን ፦ ና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ እንኺድ ፡ አለው ። በሜዳም ፡ ሳሉ ፡ ቃየን ፡ በወንድሙ ፡ በአቤል ፡ ላይ ፡ ተነሣበት ፥ ገደለውም ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቃየንን ፡ አለው ፦ ወንድምኽ ፡ አቤል ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ርሱም ፡ አለ ፦ አላውቅም ፤ የወንድሜ ፡ ጠባቂው ፡ እኔ ፡ ነኝን ፧

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ አለውም ፦ ምን ፡ አደረግኽ ፧ የወንድምኽ ፡ የደሙ ፡ ድምፅ ፡ ከምድር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይጮኻል ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ የወንድምኽን ፡ ደም ፡ ከእጅኽ ፡ ለመቀበል ፡ አፏን ፡ በከፈተች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አንተ ፡ የተረገምኽ ፡ ነኽ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ምድርንም ፡ ባረስኽ ፡ ጊዜ ፡ እንግዲህ ፡ ኀይሏን ፡ አትሰጥኽም ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ኰብላይና ፡ ተቅበዝባዥ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ቃየንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፦ ኀጢአቴ ፡ ልሸከማት ፡ የማልችላት ፡ ታላቅ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ከምድር ፡ ፊት ፡ አሳደድኸኝ ፤ ከፊትኽም ፡ እሰወራለኹ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ኰብላይና ፡ ተቅበዝባዥ ፡ እኾናለኹ ፤ የሚያገኘኝም ፡ ኹሉ ፡ ይገድለኛል ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ርሱን ፡ አለው ፦ እንግዲህ ፡ ቃየንን ፡ የገደለ ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይበቀልበታል ። እግዚአብሔርም ፡ ቃየንን ፡ ያገኘው ፡ ኹሉ ፡ እንዳይገድለው ፡ ምልክት ፡ አደረገለት ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ቃየንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ፤ ከዔዴንም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በኖድ ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ቃየንም ፡ ሚስቱን ፡ ዐወቀ ፤ ፀነሰችም ፥ ሔኖክንም ፡ ወለደች ። ከተማም ፡ ሠራ ፥ የከተማዉቱንም ፡ ስም ፡ በልጁ ፡ ስም ፡ ሔኖክ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ሔኖክም ፡ ጋይዳድን ([5]) ፡ ወለደ ፤ ጋይዳድም ፡ ሜኤልን ([6]) ፡ ወለደ ፤ ሜኤልም ፡ ማቱሳኤልን ([7]) ፡ ወለደ ፤ ማቱሳኤልም ፡ ላሜሕን ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ላሜሕም ፡ ለራሱ ፡ ኹለት ፡ ሚስቶችን ፡ አገባ ፤ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ዐዳ ፥ የኹለተኛዪቱ ፡ ስም ፡ ሴላ

---

5 ጋይዳድ ፤ ዕብ. ፥ ዒይራድ ።

6 ሜኤል ፤ ዕብ. ፥ ሜሑያኤል ።

7 ማቱሳኤል ፤ ዕብ. ፥ ሜቱሻኤል ።

([8]) ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ዐዳም ፡ ያባልን ፡ ወለደች ፤ ርሱም ፡ በድንኳን ፡ የሚቀመጡት ፡ የዘላኖች ፡ አባት ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ የወንድሙም ፡ ስም ፡ ዩባል ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ በገናንና ፡ መለከትን ፡ ለሚይዙ ፡ አባት ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ሴላም ፡ ደግሞ ፡ ከናስና ፡ ከብረት ፡ የሚቀጠቀጥ ፡ ዕቃን ፡ የሚሠራውን ፡ ቱባልቃይንን ፡ ወለደች ። የቱባልቃይንም ፡ እኅት ፡ ናዕማ ፡ ነበረች ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ላሜሕም ፡ ለሚስቶቹ ፡ ለዐዳና ፡ ለሴላ ፡ አላቸው ፦ እናንት ፡ የላሜሕ ፡ ሚስቶች ፡ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ ነገሬንም ፡ አድምጡ ፤ እኔ ፡ ጕልማሳውን ፡ ለቀ ፡ ስሌ ፥ ብላቴናውንም ፡ ለመወጋቴ ፡ ገድዬዋለ ኹና ፤

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ቃየንን ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይበቀሉታል ፤ ላሜሕን ፡ ግን ፡ ሰባ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይበቀሉታል ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ አዳም ፡ ደግሞ ፡ ሚስቱን ፡ ዐወቀ ፤ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ። ስሙንም ፦ ቃየን ፡ በገደለው ፡ በአቤል ፡ ፋንታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሌላ ፡ ዘር ፡ ተክቶልኛል ፡ ስትል ፡ ሴት ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ለሴት ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደለት ፤ ስሙንም ፡ ሄኖስ ፡ አለው ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መጠራት ፡ ተገ ፡ መረ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ የአዳም ፡ የትውልዱ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ አዳምን ፡ በፈጠረ ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ አደረገው ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ወንድና ፡ ሴት ፡ አድርጎ ፡ ፈጠራቸው ፥ ባረካቸውም ። ስማቸውንም ፡ በፈጠረበት ፡ ቀን ፡ አዳም ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ አዳምም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ልጅንም ፡ በምሳሌው ፡ እንደ ፡ መልኩ ፡ ወለደ ፤ ስሙንም ፡ ሴት ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ አዳምም ፡ ሴትን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ አዳምም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ሴትም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ሄኖስንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ሴትም ፡ ሄኖስን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ሴትም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ሄኖስም ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ቃይናንንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ሄኖስም ፡ ቃይናንን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ሄኖስም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፡ ሞተም ።

---

8 ሴላ ፤ ዕብ. ፥ ጸ.ሳህ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ቃይናንም ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ መላልኤልንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ቃይናንም ፡ መላልኤልን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ቃይናንም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ መላልኤልም ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ያሬድንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ መላልኤልም ፡ ያሬድን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ መላልኤልም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ያሬድም ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ሔኖክንም ፡ ወለደ ፡

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ያሬድም ፡ ሔኖክን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ያሬድም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ሔኖክም ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ማቱሳላንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ሔኖክም ፡ አካኼዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አደረገ ፤ ማቱሳላንም ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ሔኖክም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ሔኖክም ፡ አካኼዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስላደረገ ፡ አልተገኘም ፤ እግዚአብሔር ፡ ወስዶታልና ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ማቱሳላም ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ላሜሕንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ማቱሳላም ፡ ላሜሕን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ማቱሳላም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ላሜሕም ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ልጅንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ስሙንም ፦ እግዚአብሔር ፡ በረገማት ፡ ምድር ፡ ከተግባራችንና ፡ ከእጅ ፡ ሥራችን ፡ ይህ ፡ ያሳርፈናል ፡ ሲል ፡ ኖኅ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ ላሜሕም ፡ ኖኅን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ የኖረው ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ላሜሕ ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ ኖኅም ፡ የዐምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኖኅም ፡ ሴምን ፡ ካምን ፡ ያፌትንም ፡ ወለደ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መብዛት ፡ በገሥመሩ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተወለዱላቸው ፤

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆችም ፡ የሰውን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ መልካሞች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አዩ ፤ ከመረጧቸውም ፡ ሹሉ ፡ ሚስቶችን ፡ ለራሳቸው ፡ ወሰዱ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፦ መንፈሴ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይኖርም ፥ ርሱ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ፤ ዘመኖቹም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ይኾናሉ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ በእነዚያ ፡ ወራት ፡ ኔፊሊም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነበሩ ፤ ደግሞም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የሰውን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ባገቡ ፡ ጊዜ ፡ ልጆችን ፡ ወለዱላቸው ፤ እነርሱም ፡ በዱሮ ፡ ዘመን ፡ ስማቸው ፡ የታወቀ ፡ ኀያላን ፡ ኾኑ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሰው ፡ ክፋት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በዛ ፥ የልቡ ፡ ዐሳብ ፡ ምኞትም ፡ ሹል ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰውን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በመፍጠሩ ፡ ተጸጸተ ፥ በልቡም ፡ ዐዘነ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፦ የፈጠርኩትን ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አጠፋለኹ ፥ ከሰው ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ እስከ ፡ ተንቀሳቃሽም ፡ እስከሰማይ ፡ ወፍም ፡ ድረስ ፤ ስለ ፡ ፈጠርኋቸው ፡ ተጸጽቻለኹና ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ ኖኅ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ አገኘ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ የኖኅ ፡ ትውልድ ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ኖኅም ፡ በትውልዱ ፡ ጻድቅ ፡ ፍጹምም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኖኅ ፡ አካኼዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ ኖኅም ፡ ሦስት ፡ ልጆችን ፡ ሴምን ፡ ካምን ፡ ያፌትንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ ምድርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተበላሽች ፤ ምድርም ፡ ግፍን ፡ ተሞላች ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድርን ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ ተበላሽች ፤ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ሹሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መንገዱን ፡ አበላሽቶ ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፡ አለው ፦ የሥጋ ፡ ሹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ በፊቴ ፡ ደርሷል ፤ ከነርሱ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ በግፍ ፡ ተሞልታለችና ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ከምድር ፡ ጋራ ፡ አጠፋቸዋለኹ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ ከጎፈር ፡ ዕንጨት ፡ መርከብን ፡ ለአንተ ፡ ሥራ ፤ በመርከቢቱም ፡ ጕርጆችን ፡ አድርግ ፥ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ በቅጥራን ፡ ለቅልቃት ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 15 ፤ ርሷንም ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋታለኽ ፤ የመርከቢቱ ፡ ርዝመት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ወርዷ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፥ ከፍታዋ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 16 ፤ ለመርከቢቱም ፡ መስኮትን ፡ ታደርጋለኽ ፤ ከቁመቷም ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ትተኽ ፡ ጨርሳት ፤ የመርከቢቱንም ፡ በር ፡ በጐኗ ፡ አድርግ ፤ ታችኛውንም ፡ ኹለተኛውንም ፡ ሦስተኛውንም ፡ ደርብ ፡ ታደርግላታለኽ ።

ዘፍ. ፥ 6 ፥ 17 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ከሰማይ ፡ በታች ፡ የሕይወት ፡ ነፍስ ፡ ያለውን ፡ ሥጋ ፡ ሹሉ ፡ ለማጥፋት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የጥፋት ፡ ውሃን ፡ አመጣለኹ ፤ በምድር ፡ ያለው ፡ ሹሉ ፡ ይጠፋል ።

ዘፍ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አቆማለኹ ፤ ወደ ፡ መርከብም ፡ አንተ ፡ ልጆችኽንና ፡ ሚስትኽን ፡ የልጆችኽንም ፡ ሚስቶች ፡ ይዘኽ ፡ ትገባለኽ ።

ዘፍ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በሕይወት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋ ፡ ካለው ፡ ከሕያው ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እያደረግኽ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ታገባለኽ ፤ ተባትና ፡ እንስት ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ከወፍ ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፥ ከእንስሳም ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፥ ከምድር ፡ ተንቀሳቃሽም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ወገኑ ፡ በሕይወት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እየኾኑ ፡ ወዳንተ ፡ ይግቡ ።

ዘፍ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ከሚበላውም ፡ መብል ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ውሰድ ፥ ወዳንተም ፡ ትሰበስባለኽ ፤ ርሱም ፡ ለአንተም ፡ ለእነርሱም ፡ መብል ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ኖኅም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችኽን ፡ ኹሉ ፡ ይዘኽ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ግባ ፤ በዚህ ፡ ትውልድ ፡ በፊቴ ፡ ጻድቅ ፡ ኾነኽ ፡ አይቼኻለኹና ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 2-3 ፤ ከንጹሕ ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ተባትና ፡ እንስት ፥ ንጹሕ ፡ ካልኾነ ፡ እንስሳም ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ተባትና ፡ እንስት ፥ ከሰማይ ፡ ወፍ ፡ ደግሞ ፡ ሰባት ፡ ሰባት ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ እያደረግኽ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለዘር ፡ ይቀር ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ከሰባት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብ ፡ አዘንባለኹና ፤ የፈጠርኹትንም ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አጠፋለኹና ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ኖኅም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ኖኅም ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የስድስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ኖኅም ፡ ስለጥፋት ፡ ውሃ ፡ ልጆቹንና ፡ ሚስቱን ፡ የልጆቹንም ፡ ሚስቶች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ከንጹሕ ፡ እንስሳ ፡ ንጹሕም ፡ ካልኾነው ፡ እንስሳ ፥ ከወፎችና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከሚንቀሳቀሰውም ፡ ኹሉ ፥

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኖኅን ፡ እንዳዘዘው ፥ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ እየኾኑ ፡ ወደ ፡ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ከሰባት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ በኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በስድስተኛው ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ዕለት ፥ በዚያው ፡ ቀን ፡ የታላቁ ፡ ቀላይ ፡ ምንጮች ፡ ኹሉ ፡ ተነደሉ ፥ የሰማይም ፡ መስኮቶች ፡ ተከፈቱ ፤

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ዝናቡም ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በዚያውም ፡ ቀን ፡ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ገባ ፥ የኖኅ ፡ ልጆችም ፡ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌትና ፡ የኖኅ ፡ ሚስት ፡ ሦስቱም ፡ የልጆቹ ፡ ሚስቶች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ገቡ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ እነርሱ ፥ አራዊትም ፡ ኹሉ ፡ በየወገናቸው ፥ እንስሳትም ፡ ኹሉ ፡ በየወገናቸው ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ተንቀሳቃሾችም ፡ ኹሉ ፡ በየወገናቸው ፥ ወፎችም ፡ ኹሉ ፡ በየወገናቸው ፥ የሚበሩ ፡ ወፎችም ፡ ኹሉ ፥

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ሥጋ ፡ ያላቸው ፡ ሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እየኾኑ ፡ ወደ ፡ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ሥጋ ፡ ካለው ፡ ኹሉ ፡ የገቡትም ፡ ተባትና ፡ እንስት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ገቡ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በስተኋላው ፡ ዘጋበት ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ የጥፋትም ፡ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ነበረ ፤ ውሃውም ፡ በዛ ፥ መርከቢቱንም ፡ አነሣ ፥ ከምድርም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ውሃውም ፡ አሸነፈ ፥ በምድር ፡ ላይም ፡ እጅግ ፡ በዛ ፤ መርከቢቱም ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ኼደች ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ውሃውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ በጣም ፡ አሸነፈ ፤ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ ታላላቆች ፡ ተራራዎች ፡ ኹሉ ፡ ተሸፈኑ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ውሃው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ተራራዎችም ፡ ተሸፈኑ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ሥጋ ፡ ያለው ፡ የሚንቀሳቀሰው ፡ ኹሉ ፥ ወፉም ፥ እንስሳውም ፥ አራዊቱም ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚርመሰመሰው ፡ ተንቀሳቃሹም ፡ ኹሉ ፥ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ጠፋ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ በየብስ ፡ የነበረው ፡ በአፍንጫው ፡ የሕይወት ፡ ነፍስ ፡ እስትንፋስ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ሞተ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የነበረውም ፡ ኹሉ ፡ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፥ እስከሚርመሰመሰውም ፡ ኹሉ ፡ ድረስ ፥ እስከሰማይ ፡ ወፍ ፡ ድረስ ፡ ተደመሰሰ ፤ ከምድርም ፡ ተደመሰሱ ። ኖኅም ፡ ዐብረውት ፡ በመርከብ ፡ ከነበሩት ፡ ጋራ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ።

ዘፍ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ውሃውም ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ቀን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አሸነፈ ።

———————ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። ———————

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፥ በመርከብም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበረውን ፡ አራዊቱን ፡ ኹሉ ፥ እንስሳውንም ፡ ኹሉ ፡ ዐሰበ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነፋስን ፡ አሳለፈ ፥ ውሃውም ፡ ጐደለ ፤

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ የቀላዩም ፡ ምንጮች ፡ የሰማይም ፡ መስኮቶች ፡ ተደፈኑ ፥ ዝናብም ፡ ከሰማይ ፡ ተከለከለ ፤

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ውሃውም ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ እያደር ፡ እያደር ፡ ቀለለ ፥ ከመቶ ፡ ዐምሳ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ውሃው ፡ ጐደለ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ መርከቢቱም ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በአራራት ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተቀመጠች ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ውሃውም ፡ እስከ ፡ ዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ ይጐድል ፡ ነበር ፤ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የተራራዎቹ ፡ ራሶች ፡ ተገለጡ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ከአርባ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኖኅ ፡ የሠራውን ፡ የመርከቢቱን ፡ መስኮት ፡ ከፈተ ፥

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ቍራንም ፡ ሰደደው ፤ ርሱም ፡ ወጣ ፤ ውሃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ እስኪደርቅ ፡ ድረስ ፡ ወዲያና ፡

ወዲህ ፡ ይበር ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ርግብንም ፡ ውሃው ፡ ከምድር ፡ ፊት ፡ ቀሎ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንድታይ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሰደዳት ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርግብ ፡ እግሯን ፡ የምታሳርፍበት ፡ ስፍራ ፡ አላገኘችም ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ተመለሰች ፥ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾሉ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፤ እጁን ፡ ዘረጋና ፡ ተቀበላት ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ውስጥ ፡ አገባት ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቈየ ፤ ርግብንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ከመርከብ ፡ ሰደደ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ርግብም ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ፤ በአፏም ፥ እንሆ ፥ የለመለመ ፡ የወይራ ፡ ቅጠል ፡ ይዛ ፡ ነበር ። ኖኅም ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ እንደ ፡ ቀለለ ፡ ዐወቀ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ደግሞ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቈየ ፤ ርግብንም ፡ ሰደዳት ፡ ዳግመኛም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አልተመለሰችም ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ በኖኅ ፡ ዕድሜ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ውሃው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ደረቀ ፤ ኖኅም ፡ የመርከቢቱን ፡ ክዳን ፡ አነሣ ፥ እንሆም ፥ ውሃው ፡ ከምድር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ደረቀ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ምድር ፡ ደረቀች ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኖኅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፦

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ አንተ ፡ ሚስትኽንና ፡ ልጆችኽን ፡ የልጆችኽንም ፡ ሚስቶች ፡ ይዘኽ ፡ ከመርከብ ፡ ውጣ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ያሉትን ፡ አራዊት ፡ ኾሉ ፥ ሥጋ ፡ ያላቸውን ፡ ኾሉ ፥ ወፎችንና ፡ እንስሳዎችን ፡ ኾሉ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱትንም ፡ ኾሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አውጣቸው ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ይርመስመሱ ፥ ይዋለዱ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ይብዙ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ኖኅም ፡ ልጆቹንና ፡ ሚስቱን ፡ የልጆቹንም ፡ ሚስቶች ፡ ይዞ ፡ ወጣ ፤

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ አራዊት ፡ ኾሉ ፥ ተንቀሳቃሾች ፡ ኾሉ ፥ ወፎችም ፡ ኾሉ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚርመሰመሰው ፡ ኾሉ ፡ በየዘመዳቸው ፡ ከመርከብ ፡ ወጡ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ኖኅም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያውን ፡ ሠራ ፥ ከንጹሕም ፡ እንስሳ ፡ ኾሉ ፡ ከንጹሓን ፡ ወፎችም ፡ ኾሉ ፡ ወሰደ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረበ ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልካሙን ፡ መዐዛ ፡ አሸተተ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በልቡ ፡ አለ ፦ ምድርን ፡ ዳግመኛ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ አልረግምም ፥ የሰው ፡ ልብ ፡ ዐሳብ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ዠምሮ ፡ ክፉ ፡ ነውና ፤ ደግሞም ፡ ከዚህ ፡ ቀድሞ ፡ እንዳደረግኹት ፡ ሕያዋንን ፡ ኾሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አልመታም ።

ዘፍ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ በምድር ፡ ዘመን ፡ ኾሉ ፡ መዝራትና ፡ ማጨድ ፥ ብርድና ፡ ሙቀት ፥ በጋና ፡ ክረምት ፥ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አያቋርጡም ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅንና ፡ ልጆቹን ፡ ባረካቸው ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ብዙ ፡ ተባዙ ፥ ምድርንም ፡ ሙሏት ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ አስፈሪነታችኹና ፡ አስደንጋጭነታችኹ ፡ በምድር ፡ አራዊት ፥ በሰማይም ፡ ወፎች ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ በሚንቀሳቀሱትም ፥ በባሕር ፡ ዓሣዎችም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ እነርሱም ፡ በእጃችኹ ፡ ተሰጥተዋል ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ሕይወት ፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ መብል ፡ ይኹናችኹ ፤ ኹሉን ፡ እንደ ፡ ለመለመ ፡ ቡቃያ ፡ ሰጠኋችኹ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነፍሱ ፡ ደሙ ፡ ያለችበትን ፡ ሥጋ ፡ አትብሉ ፤

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ነፍሳችኹ ፡ ያለችበትን ፡ ደማችኹን ፡ በርግጥ ፡ እሻዋለኹ ፤ ከአራዊት ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ እሻዋለኹ ፤ ከሰውም ፡ እጅ ፥ ከሰው ፡ ወንድም ፡ እጅ ፥ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ እሻለኹ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ የሰውን ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ፡ ኹሉ ፡ ደሙ ፡ ይፈሳል ፤ ሰውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ፈጥሮታልና ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ እናንተም ፡ ብዙ ፥ ተባዙ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ተዋለዱ ፥ ርቡባትም ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኖኅና ፡ ለልጆቹ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ከእናንተና ፡ በኋላ ፡ ከሚመጣው ፡ ከዘራችኹ ፡ ጋራ ፡ አቆማለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ላሉትም ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ላላቸው ፡ ኹሉ ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ከመርከብ ፡ ለወጡት ፡ ለወፎች ፥ ለእንስሳትም ፡ ለምድር ፡ አራዊትም ፡ ኹሉ ፥ ለማንኛውም ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ለእናንተ ፡ አቆማለኹ ፤ ሥጋ ፡ ያለውም ፡ ኹሉ ፡ ዳግመኛ ፡ በጥፋት ፡ ውሃ ፡ አይጠፋም ፤ ምድርንም ፡ ለማጥፋት ፡ ዳግመኛ ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ አይኾንም ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፥ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ በሕያው ፡ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፥ ለዘለዓለም ፡ የማደርገው ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ቀስቴን ፡ በደመና ፡ አድርጌያለኹ ፥ የቃል ፡ ኪዳኑም ፡ ምልክት ፡ በእኔና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ደመናን ፡ በጋረድኹ ፡ ጊዜ ፡ ቀስቱቱ ፡ በደመናው ፡ ትታያለች ፤

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፥ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ባለውም ፡ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ዐስባለኹ ፤ ሥጋ ፡ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ የጥፋት ፡ ውሃ ፡ አይኾንም ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ቀስቱቱም ፡ በደመና ፡ ትኾናለች ፤ በእኔና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖር ፡ ሥጋ ፡ ባለው ፡ በሕያው ፡ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማሰብ ፡ አያታለኹ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኖኅን ፦ በእኔና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖር ፡ ሥጋ ፡ ባለው ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ያቆምኹት ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ከመርከብ ፡ የወጡት ፡ የኖኅ ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥ ሴም ፥ ካም ፥ ያፌት ፤ ካምም ፡ የከነዓን ፡ አባት ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ የኖኅ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ተሞላች ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ኖኅም ፡ ገበሬ ፡ መኾን ፡ ዠመረ ፥ ወይንም ፡ ተከለ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ከወይን ፡ ጠጁም ፡ ጠጣና ፡ ሰከረ ፤ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ ዕራቍቱን ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ የከነዓን ፡ አባት ፡ ካምም ፡ የአባቱን ፡ ዕራቍትነት ፡ አየ ፥ ወደ ፡ ውጭም ፡ ወጥቶ ፡ ለኹለቱ ፡ ወንድሞቹ ፡ ነገራቸው ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ሴምና ፡ ያፌትም ፡ ሸማ ፡ ወስደው ፡ በጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፥ የኋሊትም ፡ ኼደው ፡ የአባታቸውን ፡ ዕራቍትነት ፡ አለበሱ ፤ ፊታቸውም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ነበረ ፥ የአባታቸውንም ፡ ዕራቍትነት ፡ አላዩም ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ኖኅም ፡ ከወይን ፡ ጠጁ ፡ ስካር ፡ ነቃ ፥ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ያደረገበትንም ፡ ዐወቀ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ከነዓን ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ለወንድሞቹም ፡ የባሪያዎች ፡ ባሪያ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ የሴም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ፥ ከነዓንም ፡ ለእነርሱ ፡ ባሪያ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያፌትን ፡ ያስፋ ፥ በሴምም ፡ ድንኳን ፡ ይደር ፤ ከነዓንም ፡ ለእነርሱ ፡ ባሪያ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ኖኅም ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

ዘፍ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ኖኅም ፡ የኖረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ሞተም ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ የኖኅ ፡ ልጆች ፡ የሴም ፡ የካም ፡ የያፌት ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከጥፋት ፡ ውሃም ፡ በኋላ ፡ ልጆች ፡ ተወለዱላቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ የያፌት ፡ ልጆች ፡ ጋሜር ፥ ማጎግ ፥ ማዴ ፥ ያዋን ፥ ይልሳ ፥ ቶቤል ፥ ሞሳሕ ፥ ቴራስ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ የጋሜርም ፡ ልጆች ፡ አስከናዝ ፥ ሪፋት ፥ ቴርጋማ [9] ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የያዋንም ፡ ልጆች ፡ ኤሊሳ ፥ ተርሴስ ፥ ኪቲም ፥ ሮድኢ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ከነዚህም ፡ የአሕዛብ ፡ ደሴቶች ፡ ኹሉ ፡ በየምድራቸው ፡ በየቋንቋቸው ፡ በየነገዳቸው ፡ በየሕዝባቸው ፡ ተከፋፈሉ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ የካምም ፡ ልጆች ፡ ኩሽ ፥ ምጽራይም ፥ ፉጥ ፥ ከነዓን ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ የኩሽም ፡ ልጆች ፡ ሳባ ፥ ኤውላጥ ፥ ሰብታ ፥ ራዕማ ፥ ሰበቃታ ፡ ናቸው ። የራዕማ ፡ ልጆችም ፡ ሳባ ፥ ድዳን ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ኩሽም ፡ ናምሩድን ፡ ወለደ ፤ ርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀያል ፡ መኾንን ፡ ገፖመረ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኀያል ፡ አዳኝ ፡ ነበረ ፤ ስለዚህም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኀያል ፡ አዳኝ ፡ እንደ ፡ ናምሩድ ፡ ተባለ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ የግዛቱም ፡ መገፖመሪያ ፡ በሰናዖር [10] ፡ አገር ፡ ባቢሎን ፥ ኦሬክ ፥ አርካድ [11] ፥ ካልኔ ፡ ናቸው ።

---

9 ቴርጋማ ፤ ዕብ. ፥ ቶጋርማህ ።

10 ሰናዖር ፤ ዕብ. ፥ ሽንዐር ።

11 አርካድ ፤ ዕብ. ፥ አካድ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ አሶርም ፡ ከዚያች ፡ አገር ፡ ወጣ ፤ ነነዌን ፡ የረሆቦትን ፡ ከተማ ፡ ካለሕን ፡

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ በነነዌና ፡ በካለሕ ፡ መካከልም ፡ ሬሴንን ፡ ሠራ ፤ ርሷም ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ምጽራይምም ፡ ሉዲምን ፡ ዐናሚምን ፡ ላህቢምን ፡ ነፍታሌምን ፡ ፈትሩሲምን ፡

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ከነርሱ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ የወጡባቸውን ፡ ከስሉሂምን ፡ ቀፍቶሪምንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ ከነዓንም ፡ የበኩር ፡ ልጁን ፡ ሲዶንን ፡ ኬጢያውያንንም ፡

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ኢያቡሳውያንንም (12) ፡ አሞራውያንንም ፡ ጌርጌሳውያንንም ፡

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ዔዊያውያንንም ፡ ዐሩኬዎንንም ፡ ሢኒንም ፡

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ አራዴዎንንም ፡ ሰማሪዎንንም ፡ አማቲንም ፡ ወለደ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከነዓናውያን ፡ ነገድ ፡ ተበተኑ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ የከነዓናውያንም ፡ ወሰን ፡ ከሲዶን (13) ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ጌራራ ፡ በኩል ፡ ሲል ፡ እስከ ፡ ጋዛ (14) ፡ ድረስ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ሰዶምና ፡ ወደ ፡ ገሞራ ፡ ወደ ፡ አዳማና ፡ ወደ ፡ ሰቦይም (15) ፡ በኩልም ፡ ሲል ፡ እስከ ፡ ላሣ (16) ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ የካም ፡ ልጆች ፡ በየነገዳቸውና ፡ በየቋንቋቸው ፡ በየምድራቸውና ፡ በየሕዝባቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ለሴምም ፡ ደግሞ ፡ ልጆች ፡ ተወለዱለት ፤ ርሱም ፡ የያፌት ፡ ታላቅ ፡ ወንድምና ፡ የዔቦር ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አባት ፡ የኾነ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ የሴምም ፡ ልጆች ፡ ዔላም ፡ አሶር (17) ፡ አርፋክስድ (18) ፡ ሉድ ፡ አራም ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ የአራምም ፡ ልጆች ፡ ዑፅ ፡ ኡል ፡ ጌቴር ፡ ሞሶሕ (19) ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ አርፋክስድም ፡ ቃይንምን ፡ ወለደ ፤ ቃይንምም ፡ ሳላን (20) ፡ ሳላም ፡ ዔቦርን ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ለዔቦርም ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ተወለዱለት ፤ የአንደኛው ፡ ስሙ ፡ ፋሌቅ (21) ፡ ነው ፥ ምድር ፡ በዘመኑ ፡ ተከፍላለችና ፤ የወንድሙም ፡ ስም ፡ ዮቅጣን ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ዮቅጣንም ፡ ኤልሞዳድን ፥ ሳሌፍንም ፥ ሐስረሞትንም (22) ፥

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ያራሕንም ፥ ሀዶራምንም ፥ አውዛልንም ፥ ደቅላንም ፥

---

12 ኢያቡሳውያን ፤ ዕብ. ፥ የቡሲይ ፡ (የቡሳውያን) ።
13 ዕብ. ፥ ጺዶን ።
14 ዕብ. ፥ ዐዛ ፡ (ዕዙዝ • ብርቱ ፥ ጠንካራ) ።
15 ዕብ. ፥ ጸቦይም ።
16 ዕብ. ፥ ለሻዕ ።
17 ዕብ. ፥ አሹር ።
18 ዕብ. ፥ አርፓክሻድ ።
19 ዕብ. ፥ ማሽ ።
20 ዕብ. ፡ ሼላኅ ።
21 ዕብ. ፥ ፌሌግ ፡ (ፍሉግ • የተከፈለ ፥ የተፈለፈለ) ።
22 ዕብ. ፥ ሐጽረመውት ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ዖባልንም ፥ አቢማኤልንም ፥ ሳባንም ፥

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ኦፊርንም ፥ ኤውላጥንም ፥ ዩባብንም ፡ ወለደ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ስፍራቸውም ፡ ከማሴ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ስፋር ፡ ሲል ፡ እስከምሥራቅ ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ የሴም ፡ ልጆች ፡ በየነገዳቸውና ፡ በየቋንቋቸው ፥ በየምድራቸውና ፡ በየሕዝባቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ የኖኅ ፡ የልጆቹ ፡ ነገዶች ፡ እንደ ፡ ትውልዳቸው ፡ በየሕዝባቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። አሕዛብም ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከነዚህ ፡ ተከፋፈሉ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ቋንቋና ፡ ባንድ ፡ ንግግር ፡ ነበረች ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ከምሥራቅም ፡ ተነሥተው ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፡ በሰናዖር ፡ ምድር ፡ አንድ ፡ ሜዳ ፡ አገኙ ፤ በዚያም ፡ ተቀመጡ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ኑ ፥ ጡብ ፡ እንሥራ ፥ በእሳትም ፡ እንተኩሰው ፡ ተባባሉ ። ጡቡም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ኾነላቸው ፤ የምድርም ፡ ዝፍት ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ ኾነችላቸው ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፦ ኑ ፡ ለእኛ ፡ ከተማና ፡ ራሱ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የሚደርስ ፡ ግንብ ፡ እንሥራ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ሳንበተንም ፡ ስማችንን ፡ እናስጠራው ፡ አሉ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የአዳም ፡ ልጆች ፡ የሠሩትን ፡ ከተማና ፡ ግንብ ፡ ለማየት ፡ ወረደ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ እነርሱ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፥ ለኹሉም ፡ አንድ ፡ ቋንቋ ፡ አላቸው ፤ ይህንም ፡ ለማድረግ ፡ ገመሩ ፤ አኹንም ፡ ያሰቡትን ፡ ኹሉ ፡ ለመሥራት ፡ አይከለከሉም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ኑ ፥ እንውረድ ፤ አንዱ ፡ የአንዱን ፡ ነገር ፡ እንዳይሰማው ፡ ቋንቋቸውን ፡ በዚያ ፡ እንደባልቀው ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከዚያ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በተናቸው ፤ ከተማዉ ፡ ከተማዉ ፡ መሥራት ፡ ተዉ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ስለዚህም ፡ ስሟ ፡ ባቢሎን ፡ ተባለ ፥ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ የምድርን ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ደባልቋልና ፤ ከዚያም ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እነርሱን ፡ በትኗቸዋል ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ የሴም ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ። ሴም ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ አርፋክስድንም ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በኋላ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ሴምም ፡ አርፋክስድን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ አርፋክስድም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ቃይንምንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ አርፋክስድም ፡ ቃይንምን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ። ቃይንምም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ሳላንም ፡ ወለደ ፤ ቃይንምም ፡ ሳላን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ሰስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ሳላም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ዔቦርንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ሳላም ፡ ዔቦርን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ዔቦርም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ፋሌቅንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ዔቦርም ፡ ፋሌቅን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ፋሌቅም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ራግውንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ራግውንም ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ፋሌቅ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ራግውም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ሴሮሕንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ራግውም ፡ ሴሮሕን ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ሴሮሕም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ናኮርንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ናኮርንም ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ሴሮሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ናኮርም ፡ መቶ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ታራንም ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ታራንም ፡ ከወለደ ፡ በኋላ ፡ ናኮር ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ወለደ ፤ ሞተም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ታራም ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ አብራምንና ([23]) ፡ ናኮርን ፡ ሀራንንም ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ የታራም ፡ ትውልድ ፥ እንሆ ፥ ይህ ፡ ነው ፦ ታራ ፡ አብራምንና ፡ ናኮርን ፡ ሀራንንም ፡ ወለደ ፤ ሀራንም ፡ ሎጥን ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ሀራንም ፡ በተወለደበት ፡ አገር ፡ በከለዳውያን ፡ ኡር ፡ በአባቱ ፡ በታራ ፡ ፊት ፡ ሞተ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ አብራምና ፡ ናኮርም ፡ ሚስቶችን ፡ አገቡ ፤ የአብራም ፡ ሚስት ፡ ስሟ ፡ ሦራ ፡ ነው ፤ የናኮር ፡ ሚስት ፡ የሀራን ፡ ልጅ ፡ ሚልካ ፡ ናት ፤ ሀራንም ፡ የሚልካና ፡ የዮስካ ፡ አባት ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ሦራም ፡ መካን ፡ ነበረች ፤ ልጅ ፡ አልነበራትም ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ታራም ፡ ልጁን ፡ አብራምንና ፡ የልጅ ፡ ልጁን ፡ የሀራንን ፡ ልጅ ፡ ሎጥን ፡ የልጁንም ፡ የአብራምን ፡ ሚስት ፡ ምራቱን ፡ ሦራን ፡ ወሰደ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ከከለዳውያን ፡ ኡር ፡ ወጡ ፤ ወደ ፡ ካራንም ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ ተቀመጡ ።

ዘፍ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ የታራም ፡ ዕድሜ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ፤ ታራም ፡ በካራን ፡ ሞተ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ **እግዚአብሔር**ም ፡ አብራምን ፡ አለው ፦ ከአገርኽ ፡ ከዘመዶችኽም ፡ ከአባትኽም ፡ ቤት ፡

---

23 አብራም ፤ ታላቅ ፡ አባት ።

ተለይተኽ ፡ እኔ ፡ ወደማሳይኽ ፡ ምድር ፡ ውጣ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ታላቅ ፡ ሕዝብም ፡ አደርግኻለኹ ፥ እባርክኻለኹ ፥ ስምኽንም ፡ አከብረዋለኹ ፤ ለበረከትም ፡ ኹን ፤

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ የሚባርኩኽንም ፡ እባርካለኹ ፥ የሚረግሙኽንም ፡ እረግማለኹ ፤ የምድር ፡ ነገዶችም ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ይባረካሉ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ አብራምም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ኼደ ፤ ሎጥም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፤ አብራምም ፡ ከካራን ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የሰባ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ አብራምም ፡ ሚስቱን ፡ ሦራንና ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ሎጥን ፥ ያገኙትን ፡ ከብት ፡ ኹሉና ፡ በካራን ፡ ያገኟቸውን ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ ለመኼድ ፡ ወጣ ፤ ወደከነዓንም ፡ ምድር ፡ ገቡ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ አብራምም ፡ እስከሴኬም ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ሞሬ ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ድረስ ፡ በምድር ፡ ዐለፈ ፤ የከነዓን ፡ ሰዎችም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በምድሩ ፡ ነበሩ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአብራም ፡ ተገለጠለትና ፦ ይህችን ፡ ምድር ፡ ለዘርኽ ፡ እሰጣለኹ ፡ አለው ። ርሱም ፡ ለተገለጠለት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ከዚያም ፡ በቤቴል ፡ ምሥራቅ ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፥ በዚያም ፡ ቤቴልን ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ጋይን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አድርጎ ፡ ድንኳኑን ፡ ተከለ ፤ በዚያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ጠራ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ አብራምም ፡ ከዚያ ፡ ተነሣ ፥ እየተጓዘም ፡ ወደ ፡ አዜብ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ በምድርም ፡ ራብ ፡ ኾነ ፤ አብራምም ፡ በዚያ ፡ በእንግድነት ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ፥ በምድር ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ለመግባት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱን ፡ ሦራን ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ አንቺ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ኾንሽ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ፡

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ያዩሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፦ ሚስቱ ፡ ናት ፡ ይላሉ ፡ እኔንም ፡ ይገድሉኛል ፥ አንቺንም ፡ በሕይወት ፡ ይተዉሻል ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ እንግዲህ ፡ ባንቺ ፡ ምክንያት ፡ መልካም ፡ ይኾንልኝ ፡ ዘንድ ፥ ስለ ፡ አንቺም ፡ ነፍሴ ፡ ትድን ፡ ዘንድ ፦ እኅቴ ፡ ነኝ ፡ በዩ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ አብራምም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ሴቲቱን ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ አዩ ፤

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ የፈርዖንም ፡ አለቃዎች ፡ አይዋት ፥ በፈርዖንም ፡ ፊት ፡ አመሰገኗት ፤ ሴቲቱንም ፡ ወደፈርዖን ፡ ቤት ፡ ወሰዷት ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ለአብራምም ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ መልካም ፡ አደረገለት ፤ ለርሱ ፡ በጎችም ፡ በሬዎችም ፡ አህያዎችም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ ግመሎችም ፡ ነበሩት ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በአብራም ፡ ሚስት ፡ በሦራ ፡ ምክንያት ፡ ፈርዖንንና ፡ የቤቱን ፡ ሰዎች ፡ በታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ መታ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ፈርዖንም ፡ አብራምን ፡ ጠርቶ ፡ አለው ፦ ይህ ፡ ያደረግኽብኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ርሷ ፡ ሚስትኽ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ለምን ፡ አልገለጥኽልኝም ፧

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ለምንስ ፦ እኅቴ ፡ ናት ፡ አልኽ ፧ እኔ ፡ ሚስት ፡ ላደርጋት ፡ ወስጃት ፡ ነበር ። አኹንም ፡ ሚስትኽ ፡ እንሂት ፤ ይዘኻት ፡ ኺድ ።

ዘፍ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ፈርዖንም ፡ ሰዎቹን ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አዘዘ ፥ ርሱንም ፡ ሚስቱንም ፡ ከብቱንም ፡ ኹሉ ፡ ሸኟቸው ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ አብራምም ፡ ከግብጽ ፡ ወጣ ፤ ርሱና ፡ ሚስቱ ፡ ለርሱ ፡ የነበረውም ፡ ኹሉ ፡ ሎጥም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አዜብ ፡ ወጡ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ አብራምም ፡ በከብት ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ እጅግ ፡ በለጠገ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ከአዜብ ፡ ባደረገው ፡ በጉዞውም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ በኩል ፡ ኼደ ፤ ያም ፡ ስፍራ ፡ አስቀድሞ ፡ በቤቴልና ፡ በጋይ ፡ መካከል ፡ ድንኳን ፡ ተክሎበት ፡ የነበረው ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ያም ፡ ስፍራ ፡ አስቀድሞ ፡ መሠዊያ ፡ የሠራበት ፡ ነው ፤ በዚያም ፡ አብራም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠራ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ከአብራም ፡ ጋራ ፡ የኼደው ፡ ሎጥ ፡ ደግሞ ፡ የላምና ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ድንኳንም ፡ ነበረው ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ በአንድነትም ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ምድር ፡ አልበቃቸውም ፡ የነበራቸው ፡ እጅግ ፡ ነበረና ፡ በአንድነት ፡ ሊቀመጡ ፡ አልቻሉም ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ የአብራምንና ፡ የሎጥን ፡ መንጋዎች ፡ በሚጠብቁት ፡ መካከልም ፡ ጠብ ፡ ኾነ ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ከነዓናውያንና ፡ ፈርዛውያን ፡ በዚያች ፡ ምድር ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ አብራምም ፡ ሎጥን ፡ አለው ፦ እኛ ፡ ወንድማማች ፡ ነንና ፡ በእኔና ፡ ባንተ ፡ በእረኞቼና ፡ በእረኞችኽ ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ እንዳይኾን ፡ እለምንኻለኹ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ አይደለችምን ፧ ከእኔ ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፤ አንተ ፡ ግራውን ፡ ብትወስድ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ እኼዳለኹ ፤ አንተም ፡ ቀኙን ፡ ብትወስድ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ እኼዳለኹ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ሎጥም ፡ ዐይኑን ፡ አነሣ ፥ በዮርዳኖስ ([24]) ፡ ዙሪያ ፡ ያለውንም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ውሃ ፡ የሞላበት ፡ መኾኑን ፡ አየ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ ከማጥፋቱ ፡ አስቀድሞ ፡ እስከ ፡ ዞዓር ፡ ድረስ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ አምሳል ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ሎጥም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ መረጠ ፤ ሎጥም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ተጓዘ ፤ አንዱም ፡ ከሌላው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተለያዩ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ አብራም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ፡ ሎጥም ፡ በአገሩ ፡ ሜዳ ፡ ባሉት ፡ ከተማዎች ፡ ተቀመጠ ፥ እስከ ፡ ሰዶምም ፡ ድረስ ፡ ድንኳኑን ፡ አዘዋወረ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ የሰዶም ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ክፉዎችና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ነበሩ ።

ዘፍ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ሎጥ ፡ ከተለየው ፡ በኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብራምን ፡ አለው ፦ ዐይንኽን ፡ አንሣና ፡ አንተ ፡

---

24 ዕብ. ፥ ያርዴን ፡ (ወራዲ • የሚወርድ ፥ ወራጅ) ።

ካለኽበት ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ሰሜንና ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅና ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እይ ፤

ዘፍ. ፥ 13 ፥ 15 ፤ የምታያትን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለአንተና ፡ ለዘርኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ እሰጣለኹና ።

ዘፍ. ፥ 13 ፥ 16 ፤ ዘርኽንም ፡ እንደምድር ፡ አሸዋ ፡ አደርጋለኹ ፤ የምድርን ፡ አሸዋን ፡ ይቈጥር ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ዘርኽ ፡ ደግሞ ፡ ይቈጠራል ።

ዘፍ. ፥ 13 ፥ 17 ፤ ተነሣ ፡ በምድር ፡ በርዝመቷም ፡ በስፋቷም ፡ ኺድ ፡ ርሷን ፡ ለአንተ ፡ እሰጣለኹና ።

ዘፍ. ፥ 13 ፥ 18 ፤ አብራምም ፡ ድንኳኑን ፡ ነቀለ ፥ መጥቶም ፡ በኬብሮን ፡ ባለው ፡ በመምሬ ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ተቀመጠ ፤ በዚያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ በሰናዖር ፡ ንጉሥ ፡ በአምራፌል ፥ በእላሣር ፡ ንጉሥ ፡ በአርዮክ ፥ በዔላም ፡ ንጉሥ ፡ በኮሎዶጎምር ([25]) ፥ በአሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ በቲድዓል ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 2 ፤ ከሰዶም ፡ ንጉሥ ፡ ከባላ ፥ ከገሞራ ፡ ንጉሥ ፡ ከብርሳ ፥ ከአዳማ ([26]) ፡ ንጉሥ ፡ ከሰነአብ ፥ ከሰቦይም ፡ ንጉሥ ፡ ከሰሜበር ፥ ዞዓር ፡ ከተባለች ፡ ከቤላ ፡ ንጉሥም ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ አደረጉ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 3 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በሲዲም ፡ ሸለቆ ፡ ተሰብስበው ፡ ተባበሩ ፤ ይኸውም ፡ የጨው ፡ ባሕር ፡ ነው ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 4 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ለኮሎዶጎምር ፡ ተገዝተው ፡ ነበር ፥ በዐሥራ ፡ ሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ ዐመፁ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 5 ፤ በዐሥራ ፡ አራተኛውም ፡ ዓመት ፡ ኮሎዶጎምርና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ መጡ ፤ ራፋይምን ፡ በአስጣሮት ፡ ቃርናይም ፥ ዙዚምንም ፡ በሃም ፥ ኤሚምንም ፡ በሴዊ ፡ ቂርያታይም ፡ መቱ ፤

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 6 ፤ የሖር ፡ ሰዎችንም ፡ በሴይር ፡ ተራራቸው ፥ በበረሓ ፡ አጠገብ ፡ እስካለች ፡ እስከ ፡ ኤል ፡ ፋራን ፡ ድረስ ፡ መቱ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 7 ፤ ተመልሰውም ፡ ቃዴስ ፡ ወደተባለች ፡ ወደ ፡ ዐይንሚስፓጥ ፡ መጡ ፤ የዐማሌቅን ፡ አገር ፡ ኹሉና ፡ ደግሞ ፡ በሐሴሶን ፡ ታማር ፡ የነበረውን ፡ አሞራውያንን ፡ መቱ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 8 ፤ የሰዶም ፡ ንጉሥና ፡ የገሞራ ፡ ንጉሥ ፥ የአዳማ ፡ ንጉሥና ፡ የሰቦይም ፡ ንጉሥ ፥ ዞዓር ፡ የተባለች ፡ የቤላ ፡ ንጉሥም ፡ ወጡ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በሲዲም ፡ ሸለቆ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ለሰልፍ ፡ ወጡ ፤

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 9 ፤ የዔላምን ፡ ንጉሥ ፡ ኮሎዶጎምርን ፥ የአሕዛብን ፡ ንጉሥ ፡ ቲድዓልን ፥ የሰናዖርን ፡ ንጉሥ ፡ አምራፌልን ፥ የእላሣርን ፡ ንጉሥ ፡ አርዮክን ፡ ለመውጋት ፡ ዐምስቱ ፡ ነገሥታት ፡ በእነዚህ ፡ በአራቱ ፡ ላይ ፡ ወጡ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 10 ፤ በሲዲም ፡ ሸለቆ ፡ ግን ፡ የዝፍት ፡ ጕድጓዶች ፡ ነበሩበት ። የሰዶም ፡ ንጉሥ ፡ የገሞራ ፡ ንጉሥም ፡ ሸሹና ፡ ወደዚያ ፡ ወደቁ ፤ የቀሩትም ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ሸሹ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 11 ፤ የሰዶምንና ፡ የገሞራን ፡ ከብት ፡ ኹሉ ፡ መብላቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ወስደው ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፥ 14 ፥ 12 ፤ በሰዶም ፡ ይኖር ፡ የነበረውን ፡ የአብራምን ፡ የወንድም ፡ ልጅ ፡ ሎጥን ፡ ደግሞ ፡ ከብቱንም ፡ ወስደው ፡ ኼዱ ።

---

25 ዕብ. ፥ ኬዶርላዖመር ።

26 ዕብ. ፥ አዳማ ፡ (በቁሙ ፥ ቀይ ፡ ዐፈር) ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ አንድ ፡ የሸሸ ፡ ሰውም ፡ መጣ ፥ ለዕብራዊው ፡ ለአብራምም ፡ ነገረው ፤ ርሱም ፡ የኤስኮል ፡ ወንድምና ፡ የአውናን (27) ፡ ወንድም ፡ በኾነ ፡ በአሞራዊ ፡ መምሬ ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ እነዚያም ፡ ከአብራም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገብተው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ አብራምም ፡ ወንድሙ ፡ እንደ ፡ ተማረከ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በቤቱ ፡ የተወለዱትን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ብላቴናዎቹን ፡ አሰለፈ ፥ ፍለጋቸውንም ፡ ተከትሎ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ብላቴናዎቹንም ፡ ከፍሎ ፡ በሌሊት ፡ ርሱ ፡ ከባሪያዎቹ ፡ ጋራ ፡ ወረደባቸው ፥ መታቸውም ፤ በደማስቆ ፡ ግራ ፡ እስካለችውም ፡ እስከ ፡ ሖባ ፡ ድረስ ፡ አሳደዳቸው ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ከብቱንም ፡ ኹሉ ፡ አስመለሰ ፥ ደግሞም ፡ ወንድሙን ፡ ሎጥንና ፡ ከብቶቹን ፡ ሴቶችንና ፡ ሕዝቡን ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ኮሎዶጎምርንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ነገሥታት ፡ ወግቶ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላም ፡ የሰዶም ፡ ንጉሥ ፡ የንጉሥ ፡ ሸለቆ ፡ በኾነ ፡ በሴዊ ፡ ሸለቆ ፡ ሊቀበለው ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ የሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅም ፡ እንጀራንና ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ አወጣ ፤ ርሱም ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ባረከውም ፦ አብራም ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ለሚገዛ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ጠላቶችኽን ፡ በእጅኽ ፡ የጣለልኽ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ አለውም ። አብራምም ፡ ከኹሉ ፡ ዓሥራትን ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ የሰዶም ፡ ንጉሥም ፡ አብራምን ፦ ሰዎቹን ፡ ስጠኝ ፥ ከብቱን ፡ ግን ፡ ለአንተ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ አብራምም ፡ የሰዶምን ፡ ንጉሥ ፡ አለው ፦ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ወደሚገዛ ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እጄን ፡ ከፍ ፡ አድርጌያለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 14 ፡ 23-24 ፤ አንተ ፦ አብራምን ፡ ባለጠጋ ፡ አደረግኹት ፡ እንዳትል ፥ ብላቴናዎቹ ፡ ከበሉት ፡ በቀር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ከኼዱትም ፡ ድርሻ ፡ በቀር ፥ ፈትልም ፡ ቢኾን ፡ የጫማ ፡ ማዘቢያም ፡ ቢኾን ፥ ለአንተ ፡ ከኾነው ፡ ኹሉ ፡ እንዳልወስድ ፤ አውናን ፡ ኤስኮልም ፡ መምሬም ፡ እነርሱ ፡ ድርሻቸውን ፡ ይውሰዱ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በራእይ ፡ ወደ ፡ አብራም ፡ መጣ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ አብራም ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ እኔ ፡ ለአንተ ፡ ጋሻኽ ፡ ነኝ ፤ ዋጋኽም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ አብራምም ፦ አቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ምንን ፡ ትሰጠኛለኽ ፧ እኔም ፡ ያለልጅ ፡ እኼዳለኹ ፤ የቤቴም ፡ መጋቢ ፡ የደማስቆ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ኤሊዔዘር ፡ ነው ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ አብራምም ፦ ለእኔ ፡ ዘር ፡ አልሰጠኸኝም ፤ እንሆም ፥ በቤቴ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ይወርሰኛል ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ እንሆም ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣለት ፦ ይህ ፡ አይወርስኽም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከጕልበትኽ ፡ የሚወጣው ፡ ይወርስኻል ።

---

27 ዕብ. ፡ ዐነር ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ሜዳም ፡ አወጣውና ፦ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተመልከት ፥ ከዋክብትንም ፡ ልትቈጥራቸው ፡ ትችል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቀ፡ጠር ፡ አለው ። ዘርኽም ፡ እንደዚሁ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ አብራምም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነ ፥ ጽድቅም ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ይህችን ፡ ምድር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ እንድሰጥኽ ፡ ከከለዳውያን ፡ ኡር ፡ ያወጣኹኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ አቤቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እንድወርሳት ፡ በምን ፡ ዐውቃለኹ ፧ አለ ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ጊደር ፥ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ፍየልም ፥ የሦስት ፡ ዓመት ፡ በግም ፥ ዋኖስም ፥ ርግብም ፡ ያዝልኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ወሰደለት ፥ በየኹለትም ፡ ከፈላቸው ፥ የተከፈሉትንም ፡ በየወገኑ ፡ ትይዩ ፡ አደረጋቸው ፤ ወፎችን ፡ ግን ፡ አልከፈለም ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ አሞራዎችም ፡ በሥጋው ፡ ላይ ፡ ወረዱ ፥ አብራምም ፡ አበረራቸው ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ፀሓይም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ በአብራም ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ መጣበት ፤ እንሆም ፥ ድንጋጤና ፡ ታላቅ ፡ ጨለማ ፡ ወደቀበት ፤

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ አብራምንም ፡ አለው ፦ ዘርኽ ፡ ለርሱ ፡ ባልኾነች ፡ ምድር ፡ ስደተኞች ፡ እንዲኾኑ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቅ ፤ ባሪያዎች ፡ አድርገውም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ያስጨንቋቸዋል ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ደግሞም ፡ በባርነት ፡ በሚገዟቸው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ እፈርዳለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ከብት ፡ ይወጣሉ ።

[ኤሊዔዘር ፡ የተባለውን ፥ የግእዙ ፡ መጽሐፍ ፡ ኢ.ያውብር ፡ ይለዋል ።]

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አባቶችኽ ፡ በሰላም ፡ ትኼዳለኽ ፤ በመልካም ፡ ሽምግልና ፡ ትቀበራለኽ ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ በአራተኛው ፡ ትውልድ ፡ ግን ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ፤ የአሞራውያን ፡ ኀጢአት ፡ ገና ፡ አልተፈጸመምና ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ፀሓይም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ጨለማ ፡ ኾነ ፤ የምድጃ ፡ ጢስና ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ በዚያ ፡ በተከፈለው ፡ መካከል ፡ ዐለፈ ።

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብራም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፦ ከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ወንዝ ፡ እስከኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ ለዘርኽ ፡ ሰጥቻለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ቄናውያንን ፡ ቄኔዛውያንንም ፡

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ቀድሞናውያንንም ፡ ኬጢያውያንንም ፡

ዘፍ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ፈሪዛውያንንም ፡ ራፋይምንም ፡ አሞራውያንንም ፡ ከነዓናውያንንም ፡ ጌርጌሳውያንንም ፡ ኢ.ያቡሳውያንንም ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የአብራም ፡ ሚስት ፡ ሦራ ፡ ግን ፡ ለአብራም ፡ ልጅ ፡ አልወለደችለትም ፡ ነበር ፤ ስሟ ፡ አጋር ፡

የተባለ ፡ ግብጻዊት ፡ ባሪያም ፡ ነበረቻት ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ሦራም ፡ አብራምን ፦ እንሆ ፥ እንዳልወልድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘጋኝ ፤ ምናልባት ፡ ከርሷ ፡ በልጅ ፡ እታነጽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ግባ ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ አብራምም ፡ የሦራን ፡ ቃል ፡ ሰማ ። አብራምም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፥ የአብራም ፡ ሚስት ፡ ሦራ ፡ ግብጻዊት ፡ ባሪያዋን ፡ አጋርን ፡ ወስዳ ፡ ለባሏ ፡ ለአብራም ፡ ሚስት ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፡ ሰጠችው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ አጋር ፡ ገባ ፥ አረገዘችም ፤ እንዳረገዘችም ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ እመቤቷን ፡ በዐይኗ ፡ አቃለለች ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ ሦራም ፡ አብራምን ፦ መገፋቴ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ እኔ ፡ ባሪያዬን ፡ በብብትኽ ፡ ሰጠኹኽ ፤ እንዳረገዘችም ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡ በዐይኗ ፡ አቃለለችኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ ይፍረድ ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ አብራምም ፡ ሦራን ፦ እንሆ ፥ ባሪያሽ ፡ በእጅሽ ፡ ናት ፤ እንደ ፡ ወደድሽ ፡ አድርጊባት ፡ አላት ። ሦራም ፡ ባሠቀየቻት ፡ ጊዜ ፡ አጋር ፡ ከፊቷ ፡ ኰበለለች ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ በውሃ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ በበረሓ ፡ አገኛት ፤ ምንጩም ፡ ወደ ፡ ሱር ፡ በምትወስደው ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ የሦራ ፡ ባሪያ ፡ አጋር ፡ ሆይ ፥ ከወዴት ፡ መጣሽ ፧ ወዴትስ ፡ ትኼጃለሽ ፧ አላት ። ርሷም ፦ እኔ ፡ ከእመቤቴ ፡ ከሦራ ፡ የኰበለልኹ ፡ ነኝ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፦ ወደ ፡ እመቤትሽ ፡ ተመለሺ ፥ ከእጇም ፡ በታች ፡ ኾነሽ ፡ ተገዢ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፦ ዘርሽን ፡ እጅግ ፡ አበዛለኹ ፥ ከብዛቱም ፡ የተነሣ ፡ አይቈጠርም ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ አላት ፦ እንሆ ፥ አንቺ ፡ ፀንሰሻል ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ትወልጃለሽ ፤ ስሙንም ፡ እስማኤል ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪዋለሽ ፥ እግዚአብሔር ፡ መቸገርሽን ፡ ሰምቷልና ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ርሱም ፡ የበዳ ፡ አህያን ፡ የሚመስል ፡ ሰው ፡ ይኾናል ፤ እጁ ፡ በሹሉ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ የሹሉም ፡ እጅ ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ርሱም ፡ በወንድሞቹ ፡ ሹሉ ፡ ፊት ፡ ይኖራል ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ርሷም ፡ ይናገራት ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ኤልሮኢ ፡ ብላ ፡ ጠራች ፤ የሚያየኝን ፡ በእውኑ ፡ እዚህ ፡ ደግሞ ፡ አየኹትን ፧ ብላለችና ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ የዚያ ፡ ጕድጓድ ፡ ስም ፡ ብኤርለሃይሮኢ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፤ ርሱም ፡ በቃዴስና ፡ በባሬድ ፡ መካከል ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ አጋርም ፡ ለአብራም ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ፤ አብራምም ፡ አጋር ፡ የወለደችለትን ፡ የልጁን ፡ ስም ፡ እስማኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ አጋር ፡ እስማኤልን ፡ ለአብራም ፡ በወለደችለት ፡ ጊዜ ፡ አብራም ፡ የሰማንያ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ አብራምም ፡ የዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብራም ፡ ተገለጠለትና ፦ እኔ ፡ ኤልሻዳይ ፡ ነኝ ፤ በፊቴ ፡ ተመላለስ ፥ ፍጹምም ፡ ኹን ፤

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ አደርጋለኹ ፥ እጅግም ፡ አበዛኻለኹ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ አብራምም ፡ በግንባሩ ፡ ወደቀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ እንሆ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ለብዙ ፡ አሕዛብም ፡ አባት ፡ ትኾናለኽ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ከዛሬም ፡ ዠምሮ ፡ እንግዲህ ፡ ስምኽ ፡ አብራም ፡ ተብሎ ፡ አይጠራ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስምኽ ፡ አብርሃም ([28]) ፡ ይኾናል ፤ ለብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አባት ፡ አድርጌኻለኹና ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ እጅግም ፡ አበዛኻለኹ ፥ ሕዝብም ፡ አደርግኻለኹ ፥ ነገሥታትም ፡ ከአንተ ፡ ይወጣሉ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ከዘርኽ ፡ ጋራ ፡ በትውልዳቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ኪዳን ፡ አቆማለኹ ፥ ለአንተና ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ለዘርኽ ፡ አምላክ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ በእንግድነት ፡ የምትኖርባትን ፡ ምድር ፥ የከነዓን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ለዘለዓለም ፡ ግዛት ፡ ይኾንኽ ፡ ዘንድ ፡ ለአንተና ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ለዘርኽ ፡ እሰጣለኹ ፤ አምላክም ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ትጠብቃለኽ ፥ አንተ ፣ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ዘርኽ ፡ በትውልዳቸው ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፥ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ በዘርኽ ፡ መካከል ፡ የምትጠብቁት ፡ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከእናንተ ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ይገረዝ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ የቀኑልፈታችኹንም ፡ ሥጋ ፡ ትገረዛላችኹ ፤ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ላለውም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ የስምንት ፡ ቀን ፡ ልጅ ፡ ይገረዝ ፤ በቤት ፡ የተወለደ ፡ ወይም ፡ ከዘራችኹ ፡ ያይደለ ፡ በብርም ፡ ከእንግዳ ፡ ሰው ፡ የተገዛ ፥ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ በትውልዳችኹ ፡ ይገረዝ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ በቤትኽ ፡ የተወለደ ፡ በብርኽም ፡ የተገዛ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገረዝ ። ቃል ፡ ኪዳኔም ፡ በሥጋችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ የቀኑልፈቱን ፡ ሥጋ ፡ ያልተገረዘ ፡ ቈላፍ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፥ ያች ፡ ነፍስ ፡ ከወገኗ ፡ ተለይታ ፡ ትጥፋ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አፍርሳለችና ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ የሚስትኽን ፡ የሦራን ፡ ስም ፡ ሦራ ፡ ብለኽ ፡ አትጥራ ፥ ስሟ ፡ ሳራ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ እባርካታለኹ ፥ ደግሞም ፡ ከርሷ ፡ ልጅ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ እባርካትማለኹ ፥ የአሕዛብም ፡ እናት ፡ ትኾናለች ፤ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ ከርሷ ፡ ይወጣሉ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ አብርሃምም ፡ በግንባሩ ፡ ወደቀ ፥ ሣቀም ፥ በልቡም ፡ አለ ፦ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ በእውኑ ፡

---

28 ዕብ. ፥ አብራሃም ፡ (ታላቅ ፡ አባት ፥ የብዙኃን ፡ አባት) ።

ልጅ ፡ ይወልዳልን ፧ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ የኾናትም ፡ ሳራ ፡ ትወልዳለችን ፧

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ አብርሃምም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እስማኤል ፡ በፊትኽ ፡ ቢኖር ፡ በወደድኹ ፡ ነበር ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ሚስትኽ ፡ ሳራ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ትወልድልኻለች ፥ ስሙንም ፡ ይሥሐቅ ፡ ብለኽ ፡ ትጠራዋለኽ ፤ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዲኾን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አቆማለኹ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ እስማኤልም ፡ ሰምቼኻለኹ ፤ እንሆ ፥ ባርኬዋለኹ ፥ ፍሬያምም ፡ አደርገዋለኹ ፥ እጅግም ፡ አበዛዋለኹ ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አለቃዎችንም ፡ ይወልዳል ፥ ታላቅ ፡ ሕዝብም ፡ እንዲኾን ፡ አደርገዋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 21 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ግን ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ሳራ ፡ ከምትወልድልኽ ፡ ከይሥሐቅ ፡ ጋራ ፡ አቆማለኹ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 22 ፤ ንግግሩንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአብርሃም ፡ ተለይቶ ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 23 ፤ አብርሃምም ፡ ልጁን ፡ እስማኤልን ፥ በቤቱም ፡ የተወለዱትን ፡ ኹሉ ፥ በብሩም ፡ የገዛቸውን ፡ ኹሉ ፥ ከአብርሃም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ወንዶቹን ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፥ የቍልፈታቸውንም ፡ ሥጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለው ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ገረዘ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ አብርሃምም ፡ የቍልፈቱን ፡ ሥጋ ፡ በተገረዘ ፡ ጊዜ ፡ የዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 25 ፤ ልጁ ፡ እስማኤልም ፡ የቍልፈቱን ፡ ሥጋ ፡ በተገረዘ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 26 ፤ በዚያው ፡ ቀን ፡ አብርሃም ፡ ተገረዘ ፥ ልጁ ፡ እስማኤልም ።

ዘፍ. ፡ 17 ፡ 27 ፤ በቤት ፡ የተወለዱትና ፡ በብር ፡ ከእንግዳዎች ፡ የተገዙት ፡ የቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተገረዙ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመምሬ ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ተገለጠለት ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ዐይኑንም ፡ አነሣና ፥ እንሆ ፥ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ በፊቱ ፡ ቆመው ፡ አየ ፤ ባያቸውም ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ከድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ተነሥቶ ፡ ሮጠ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ ሰገደ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ በፊትኽስ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባሪያኽን ፡ አትለፈኝ ፡ ብዬ ፡ እለምናለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ጥቂት ፡ ውሃ ፡ ይምጣላችኹ ፥ እግራችኹን ፡ ታጠቡ ፥ ከዚችም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ዕረፉ ፤

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ ቀሩሽ ፡ እንጀራም ፡ ላምጣላችኹ ፥ ልባችኹንም ፡ ደግፉ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ትኼዳላችኹ ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ባሪያችኹ ፡ መጥታችኋልና ። እነርሱም ፦ እንዳልኽ ፡ አድርግ ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ድንኳን ፡ ወደ ፡ ሳራ ፡ ዘንድ ፡ ፈጥኖ ፡ ገባና ፦ ሦስት ፡ መስፈሪያ ፡ የተሰለቀ ፡ ዱቄት ፡ ፈጥነሽ ፡ አዘጋጂ ፥ ለውሺውም ፥ ዕንጐቻም ፡ አድርጊ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ላሞቹ ፡ ሮጠ ፥ እጅግ ፡ የሰባም ፡ ታናሽ ፡ ጥጃ ፡ ያዘና ፡ ለብላቴናው ፡ ሰጠው ፥ ያዘጋጅም ፡ ዘንድ ፡ ተቻኰለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ርኀና ፡ ወተትም ፡ ያዘጋጀውንም ፡ ጥጃ ፡ አመጣ ፥ በፊታቸውም ፡ አቀረበው ፤ ርሱም ፡ ከዛፉ ፡ በታች ፡ በፊታቸው ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ እነርሱም ፡ በሉ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፦ ሚስትኽ ፡ ሳራ ፡ ወዴት ፡ ናት ፧ አሉት ። ርሱም ፦ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ናት ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ርሱም ፦ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ በእውነት ፡ እመለሳለኹ ፤ ሚስትኽ ፡ ሳራም ፡ ልጅን ፡ ታገኛለች ፡ አለ ። ሳራም ፡ በድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በስተኋላው ፡ ሳለች ፡ ይህን ፡ ሰማች ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ አብርሃምና ፡ ሳራም ፡ በዕድሜያቸው ፡ ሸምግለው ፡ ፈጽመው ፡ አርጅተው ፡ ነበር ፤ በሴቶች ፡ የሚኾነውም ፡ ልማድ ፡ ከሳራ ፡ ተቋርጦ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ሳራም ፡ በልቧ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ሣቀች ፦ ካረጀኹ ፡ በኋላ ፡ በእውኑ ፡ ፍትወት ፡ ይኾንልኛልን ፧ ጌታዬም ፡ ፈጽሞ ፡ ሸምግሏል ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ ካረጀኹ ፡ በኋላ ፡ በእውኑ ፡ እወልዳለኹን ፧ ስትል ፡ ሳራ ፡ ለምን ፡ ሣቀች ፧

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ በእውኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ አለን ፧ የዛሬ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ እመለሳለኹ ፤ ሳራም ፡ ልጅን ፡ ታገኛለች ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ሳራም ፡ ስለ ፡ ፈራች ፦ አልሣቅኹም ፡ ስትል ፡ ካደች ። ርሱም ፦ አይደለም ፥ ሣቅሽ ፡ እንጂ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ሰዎቹም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ሰዶም ፡ አቀኑ ፤ አብርሃምም ፡ ሊሸኛቸው ፡ ዐብሯቸው ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ከአብርሃም ፡ እሰውራለኹን ፧

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ አብርሃም ፡ በእውነት ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ ይኾናልና ፥ የምድር ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ይባረካሉና ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ጽድቅንና ፡ ፍርድን ፡ በማድረግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ልጆቹንና ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ቤቱን ፡ እንዲያዝ ፡ ዐውቃለኹና ፤ ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአብርሃም ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ የሰዶምና ፡ የገሞራ ፡ ጩኸት ፡ እጅግ ፡ በዝቷልና ፥ ኀጢአታቸውም ፡ እጅግ ፡ ከብዳለችና ፥

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ እንግዲህስ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ መጣች ፡ እንደ ፡ ጩኸቷ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወርጄ ፡ አያለኹ ፤ እንዲሁም ፡ ባይኾን ፡ ዐውቃለኹ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ሰዎቹም ፡ ከዚያ ፡ ፊታቸውን ፡ አቀኑ ፥ ወደ ፡ ሰዶምም ፡ ኼዱ ፤ አብርሃም ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ገና ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ አብርሃምም ፡ ቀረበ ፡ አለም ፦ በእውኑ ፡ ጻድቁን ፡ ከኀጢአተኛ ፡ ጋራ ፡ ታጠፋለኽን ፧

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ዐምሳ ፡ ጻድቃን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢገኙ ፡ በእውኑ ፡ ኹሉን ፡ ታጠፋለኽን ፧ ከተማዪቱንስ ፡ በርሷ ፡ ስለሚገኙ ፡ ዐምሳ ፡ ጻድቃን ፡ አትምርምን ፧

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ይህ ፡ ከአንተ ፡ ይራቅ ፤ ጻድቁን ፡ ከኀጢአተኛ ፡ ጋራ ፡ ትገድል ፡ ዘንድ ፥ ጻድቁም ፡ እንደ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ አድራጎት ፡ ከአንተ ፡ ይራቅ ። የምድር ፡ ኹሉ ፡ ፈራጅ ፡ በቅን ፡ ፍርድ ፡ አይፈርድምን ፧

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በሰዶም ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ዐምሳ ፡ ጻድቃን ፡ ባገኝ ፡ ስፍራውን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እምራለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ አብርሃምም ፡ መለሰ ፥ አለም ፦ እኔ ፡ ዐፈርና ፡ ዐመድ ፡ ስኾን ፡ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፥ እንሆ ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝምርኹ ፤

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ከዐምሳው ፡ ጻድቃን ፡ ዐምስት ፡ ቢጐድሉ ፡ ከተማዪቱን ፡ ኹሉ ፡ በዐምስቱ ፡ ምክንያት ፡ ታጠፋለኽን ፧ ከዚያ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ባገኝ ፡ አላጠፋትም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ደግሞም ፡ ተናገረው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ አርባ ፡ ቢገኙሳ ፧ ርሱም ፦ ለአርባው ፡ ስል ፡ አላደርገውም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ ርሱም ፦ ጌታዬ ፡ አይቈጣ ፡ እኔም ፡ እናገራለኹ ፡ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ ሠላሳ ፡ ቢገኙሳ ፧ አለ ። ርሱም ፡ ከዚያ ፡ ሰላሳ ፡ ባገኝ ፡ አላጠፋም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ ደግሞም ፦ እንሆ ፥ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝምርኹ ፤ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ ኻያ ፡ ቢገኙሳ ፧ አለ ። ርሱም ፦ ከዚያ ፡ ኻያ ፡ ቢገኙ ፡ ስለ ፡ ኻያው ፡ አላደርገውም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ብናገር ፡ ጌታዬ ፡ አይቈጣ ፤ ምናልባት ፡ ከዚያ ፡ ዐሥር ፡ ቢገኙሳ ፧ አለ ። ርሱም ፦ ስለ ፡ ዐሥሩ ፡ አላጠፋትም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 18 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከአብርሃም ፡ ጋራ ፡ ንግግሩን ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኼደ ፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ ኹለቱም ፡ መላእክት ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰዶም ፡ ገቡ ፤ ሎጥም ፡ በሰዶም ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። ሎጥም ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበላቸው ፡ ተነሣ ፤ ፊቱንም ፡ ደፍቶ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሰገደ ፥ አላቸውም ፦

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ጌታዎቼ ፡ ሆይ ፥ ወደባሪያችኹ ፡ ቤት ፡ አቅኑ ፥ ከዚያም ፡ ዕደሩ ፥ እግራችኹንም ፡ ታጠቡ ፤ ነገ ፡ ማልዳችኹም ፡ መንገዳችኹን ፡ ትኼዳላችኹ ። እነርሱም ፦ በአደባባዩ ፡ እናድራለን ፡ እንጂ ፥ አይኾንም ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ እጅግም ፡ ዘበዘባቸው ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ አቀኑ ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ገቡ ፤ ማእድ ፡ አቀረበላቸው ፤ ቂጣንም ፡ ጋገረ ፥ እነርሱም ፡ በሉ ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ገናም ፡ ሳይተኙ ፡ የዚያች ፡ ከተማ ፡ የሰዶም ፡ ሰዎች ፥ ከብላቴናው ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ሽማግሌው ፡ ድረስ ፡ በየስፍራው ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ቤቱን ፡ ከበቡት ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ሎጥንም ፡ ጠርተው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ በዚህ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ የገቡት ፡ ሰዎች ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፧ እናውቃቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ አውጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ሎጥም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ወጣ ፡ መዝጊያውንም ፡ በኋላው ፡ ዘጋው ፤

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድርጉ ፤

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ ወንድን ፡ ያላወቁ ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉኝ ፤ እነርሱን ፡ ላውጣላችኹ ፥ እንደ ፡

ወደዳቸኹም ፡ አድርጓቸው ፤ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ምንም ፡ አታድርጉ ፥ እነርሱ ፡ በጣራዬ ፡ ጥላ ፡ ሥር ፡ ገብተዋልና ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 9 ፤ እነርሱም ፦ ወዲያ ፡ ኺድ ፡ አሉት ። ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በእንግድነት ፡ ለመኖር ፡ መጣ ፥ ፍርዱንም ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ይፈልጋል ፤ አኹን ፡ ባንተ ፡ ከነርሱ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ እናደርግብኻለን ። ሎጥንም ፡ እጅግ ፡ ተጋፉት ፥ የደጁንም ፡ መዝጊያ ፡ ለመስበር ፡ ቀረቡ ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 10 ፤ ኹለቱም ፡ ሰዎች ፡ እጃቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ሎጥን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አገቡት ፡ መዝጊያውንም ፡ ዘጉት ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 11 ፤ በቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ የነበሩትንም ፡ ሰዎች ፡ ከታናሻቸው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቃቸው ፡ ድረስ ፡ አሳወሯቸው ፤ ደጃፉንም ፡ ለማግኘት ፡ ሲፈልጉ ፡ ደከሙ ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 12 ፤ ኹለቱም ፡ ሰዎች ፡ ሎጥን ፡ አሉት ፦ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ አለኽ ፧ ዐማችም ፡ ቢኾን ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ብትኾን ፡ በከተማዩቱ ፡ ያለኽን ፡ ኹሉ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ አስወጣቸው ፤

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 13 ፤ እኛ ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ እናጠፋለንና ፥ ጩኸታቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትልቅ ፡ ኾኗልና ፤ እናጠፋውም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰዶናል ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 14 ፤ ሎጥም ፡ ወጣ ፥ ልጆቹን ፡ ለሚያገቡት ፡ ለአማቾቹም ፡ ነገራቸው ፥ አላቸውም ፦ ተነሡ ፤ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ውጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ያጠፋልና ። ለአማቾቹ ፡ ግን ፡ የሚያፈዝባቸው ፡ መሰላቸው ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 15 ፤ ጎሕም ፡ በቀደደ ፡ ጊዜ ፡ መላእክት ፡ ሎጥን ፦ ተነሣ ፥ ሚስትኽንና ፡ ከዚህ ፡ ያሉትን ፡ ኹለቱን ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽን ፡ ውሰድ ፤ በከተማዩቱ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳትጠፋ ፡ እያሉ ፡ ያስቸኵሉት ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 16 ፤ ርሱም ፡ በዘገየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላዘነለት ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ የርሱን ፡ እጅ ፡ የሚስቱንም ፡ እጅ ፡ የኹለቱን ፡ የሴቶች ፡ ልጆቹንም ፡ እጅ ፡ ይዘው ፡ አወጡትና ፡ በከተማዩቱ ፡ ውጭ ፡ አስቀመጡት ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 17 ፤ ወደ ፡ ሜዳም ፡ ካወጧቸው ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ራስኽን ፡ አድን ፤ ወደ ፡ ኋላኽ ፡ አትይ ፥ በዚህም ፡ ዙሪያ ፡ ኹሉ ፡ አትቁም ፡ እንዳትጠፋም ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ሽሽተኽ ፡ አምልጥ ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 18 ፤ ሎጥም ፡ አላቸው ፦ ጌታዎቼ ፡ ሆይ ፥ እንዲህስ ፡ አይኹን ፤

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 19 ፤ እንሆ ፥ ባሪያኽ ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቷል ፥ ነፍሴን ፡ ለማዳን ፡ ያደረግኽልኝን ፡ ምሕረትኽንም ፡ አብዝተኻል ፤ ክፉ ፡ እንዳያገኘኝና ፡ እንዳልሞት ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ሽሽቼ ፡ አመልጥ ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ፤

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 20 ፤ እንሆ ፥ ይህች ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ሽሽቶ ፡ ለማምለጥ ፡ ቅርብ ፡ ናት ፥ ርሷም ፡ ትንሽ ፡ ናት ፤ ነፍሴን ፡ ለማዳን ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ሽሽቼ ፡ ላምልጥ ፤ ርሷ ፡ ትንሽ ፡ ከተማ ፡ አይደለችምን ፧

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 21 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ የተናገርኻትን ፡ ከተማ ፡ እንዳላጠፋት ፥ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ የለመንኸኝን ፡ ተቀብዬኻለኹ ፤

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 22 ፤ በቶሎ ፡ ወደዚያ ፡ ሽሽተኽ ፡ አምልጥ ፤ ወደዚያ ፡ እስክትደርስ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ አልችልምና ። ስለዚህም ፡ የዚያች ፡ ከተማ ፡ ስም ፡ ዞዓር ፡ ተባለ ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 23 ፤ ሎጥ ፡ ወደ ፡ ዞዓር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ፀሓይ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወጣች ።

ዘፍ. ፥ 19 ፥ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሰዶምና ፡ በገሞራ ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ከሰማይ ፡ እሳትና ፡ ዲን ፡

አዘነበ ፤

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ እነዚያንም ፡ ከተማዎች ፥ በዙሪያቸው ፡ ያለውንም ፡ ኹሉ ፥ በከተማዎቹም ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፥ የምድሩንም ፡ ቡቃያ ፡ ኹሉ ፡ ገለበጠ ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ የሎጥም ፡ ሚስት ፡ ወደ ፡ ኋላዋ ፡ ተመለከተች ፥ የጨው ፡ ሐውልትም ፡ ኾነች ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ አብርሃምም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ወደነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ለመኼድ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፤

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ወደ ፡ ሰዶምና ፡ ወደ ፡ ገሞራ ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ ወዳለውም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ተመለከተ ፤ እንሆም ፡ የአገሪቱ ፡ ጢስ ፡ እንደእቶን ፡ ጢስ ፡ ሲነሣ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እነዚያን ፡ የአገር ፡ ከተማዎች ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፡ አብርሃምን ፡ ዐሰበው ፤ ሎጥ ፡ ተቀምጦበት ፡ የነበረውንም ፡ ከተማ ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ጥፋት ፡ መካከል ፡ ሎጥን ፡ አወጣው ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ሎጥም ፡ ከዞዓር ፡ ወጣ ፤ በዞዓር ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ፈራም ፡ ከኹለቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ጋራ ፡ በተራራ ፡ ተቀመጠ ፤ በዋሻም ፡ ከኹለቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ ታላቂቱም ፡ ታናሺቱን ፡ አለቻት ፦ አባታችን ፡ ሽመገለ ፥ በምድርም ፡ ኹሉ ፡ እንዳለው ፡ ልማድ ፡ ሊገናኘን ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ የለም ፤

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ ነዪ ፡ አባታቻንንም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እናጠጣውና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንተኛ ፥ ከአባታችንም ፡ ዘር ፡ እናስቀር ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ አባታቸውን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አጠጡት ፤ ታላቂቱም ፡ ገባች ፥ ከአባቷም ፡ ጋራ ፡ ተኛች ፤ ርሱም ፡ ስትተኛና ፡ ስትነሣ ፡ አላወቀም ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ በነጋውም ፡ ታላቂቱ ፡ ታናሺቱን ፡ አለቻት ፦ እንሆ ፥ ትናንት ፡ ከአባቴ ፡ ጋራ ፡ ተኛኹ ፤ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ደግሞ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እናጠጣው ፡ አንቺም ፡ ግቢና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተኚ ፥ ከአባታችንም ፡ ዘር ፡ እናስቀር ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 35 ፤ አባታቸውንም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ደግሞ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አጠጡት ፤ ታናሺቱም ፡ ገብታ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተኛች ፤ ርሱም ፡ ስትተኛና ፡ ስትነሣ ፡ አላወቀም ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 36 ፤ የሎጥም ፡ ኹለቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከአባታቸው ፡ ፀነሱ ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 37 ፤ ታላቂቱም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ስሙንም ፡ ሞዐብ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ ርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የሞዐባውያን ፡ አባት ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 19 ፡ 38 ፤ ታናሺቱም ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፡ ስሙንም ፦ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ስትል ፡ ዐሞን ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ ርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የአሞናውያን ፡ አባት ፡ ነው ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ አብርሃምም ፡ ከዚያ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደአዜብ ፡ ምድር ፡ ኼደ ፥ በቃዴስና ፡ በሱር ፡ መካከልም ፡ ተቀመጠ ፤ በጌራራም ፡ በእንግድነት ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ አብርሃምም ፡ ሚስቱን ፡ ሳራን ፦ እኅቴ ፡ ናት ፡ አለ ፤ የጌራራ ፡ ንጉሥ ፡ አቢሜሌክም ([29]) ፡ ላከና ፡ ሳራን ፡ ወሰዳት ።

---

29 ዕብ. ፥ አቢመለክ ፡ (አበ ፡ መለክ ፥ የንጉሥ ፡ አባት) ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሌሊት ፡ በሕልም ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ መጣ ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ አንተ ፡ ስለወሰድኻት ፡ ሴት ፡ ምውት ፡ ነኽ ፤ ርሷ ፡ ባለባል ፡ ናትና ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ አቢሜሌክ ፡ ግን ፡ አልቀረባትም ፡ ነበር ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አቤቱ ፥ ጻድቁን ፡ ሕዝብ ፡ ደግሞ ፡ ታጠፋለኽን ፧

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ እኅቴ ፡ ናት ፡ ያለኝ ፡ ርሱ ፡ አይደለምን ፧ ርሷም ፡ ደግሞ ፡ ራሷ ፦ ወንድሜ ፡ ነው ፡ አለች ፤ በልቤ ፡ ቅንነትና ፡ በእጄ ፡ ንጹሕነት ፡ ይህን ፡ አደረግኹ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሕልም ፡ አለው ፦ ይህን ፡ በልብኽ ፡ ቅንነት ፡ እንዳደረግኽ ፡ እኔ ፡ ዐወቅኹ ፥ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በፊቴ ፡ ኀጢአትን ፡ እንዳትሠራ ፡ ከለከልኹኽ ፤ ስለዚህም ፡ ትነካት ፡ ዘንድ ፡ አልተውኹም ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ የሰውዮውን ፡ ሚስት ፡ መልስ ፤ ነቢይ ፡ ነውና ፥ ስለ ፡ አንተም ፡ ይጸልያል ፥ ትድናለኽም ። ባትመልሳት ፡ ግን ፡ አንተ ፡ እንድትሞት ፥ ለአንተ ፡ የኾነውም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሞት ፡ በርግጥ ፡ ዕወቅ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ አቢሜሌክም ፡ በነገታው ፡ ማለደ ፥ ባሪያዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ፥ ይህንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በጐሯቸው ፡ ተናገረ ፤ ሰዎቹም ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ አቢሜሌክም ፡ አብርሃምን ፡ ጠርቶ ፡ አለው ፦ ይህ ፡ ያደረግኽብን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ምንስ ፡ ክፉ ፡ ሠራኹብኽ ፧ በእኔና ፡ በመንግሥቴ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ ኀጢአት ፡ አውርደኻልና ፤ የማይገባ ፡ ሥራ ፡ በእኔ ፡ ሠራኽብኝ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ አቢሜሌክም ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ማድረግኽ ፡ ምን ፡ አይተኽ ፡ ነው ፧

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ አብርሃምም ፡ አለ ፦ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ በእውነት ፡ እንደሌለ ፥ ለሚስቴም ፡ ሲሉ ፡ እንደሚገድሉኝ ፡ ስላሰብኹ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ ርሷም ፡ ደግሞ ፡ በእውነት ፡ እኅቴ ፡ ናት ፤ የእናቴ ፡ ልጅ ፡ አይደለችም ፡ እንጂ ፡ የአባቴ ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ለኔም ፡ ሚስት ፡ ኾነች ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ባወጣኝ ፡ ጊዜ ፡ አልኋት ፦ በገባንበት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ የምታደርጊው ፡ ወሮታ ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ወንድሜ ፡ ነው ፡ ብለሽ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ተናገሪ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ አቢሜሌክም ፡ በጎችንና ፡ ላሞችን ፣ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችን ፡ አመጣ ፥ ለአብርሃምም ፡ ሰጠው ፥ ሚስቱን ፡ ሳራንም ፡ መለሰለት ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ አቢሜሌክም ፦ እንሆ ፥ ምድሬ ፡ በፊትኽ ፡ ናት ፤ በወደድኸው ፡ ተቀመጥ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ሳራንም ፡ አላት ፦ እንሆ ፥ ለወንድምሽ ፡ ሺሕ ፡ ሚዛን ፡ ብር ፡ ሰጠኹት ፤ ያም ፥ እንሆ ፥ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ባሉት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ የዐይኖች ፡ መሸፈኛ ፡ ይኹንሽ ፤ ጽድቅሽ ፡ ለሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ተገልጧልና ።

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አቢሜሌክን ፡ ሚስቱንም ፡ ባሪያዎቹንም ፡ ፈወሳቸው ፥ እነርሱም ፡ ወለዱ ፤

ዘፍ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአብርሃም ፡ ሚስት ፡ በሳራ ፡ ምክንያት ፡ በአቢሜሌክ ፡ ቤት ፡ ማሕፀኖችን ፡ ኹሉ ፡ በፍጹም ፡ ዘግቶ ፡ ነበርና ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ሳራን ፡ ዐሰበ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረው ፡ ለሳራ ፡ አደረገላት ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ ሳራም ፡ ፀነሰች ፥ እግዚአብሔርም ፡ በተናገረው ፡ ወራት ፡ ለአብርሃም ፡ በእርጅናው ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደችለት ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ አብርሃምም ፡ የተወለደለትን ፡ ሳራ ፡ የወለደችለትን ፡ የልጁን ፡ ስም ፡ ይሥሐቅ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ አብርሃምም ፡ ልጁን ፡ ይሥሐቅን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ በስምንተኛ ፡ ቀን ፡ ገረዘው ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ አብርሃምም ፡ ልጁ ፡ ይሥሐቅ ፡ በተወለደለት ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ ሳራም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሣቅ ፡ አድርጎልኛል ፤ ይህንም ፡ የሚሰማ ፡ ኹሉ ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ ይሥቃል ፡ አለች ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 7 ፤ ደግሞም ፦ ሳራ ፡ ልጆችን ፡ እንድታጠባ ፡ ለአብርሃም ፡ ማን ፡ በነገረው ፧ በእርጅናው ፡ ልጅን ፡ ወልጄለታለኹና ፡ አለች ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 8 ፤ ሕፃኑም ፡ አደገ ፥ ጡትንም ፡ ከመጥባት ፡ ተቋረጠ ፤ አብርሃምም ፡ ይሥሐቅን ፡ ጡት ፡ ባስጣለበት ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ ግብዣን ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 9 ፤ ሳራም ፡ ግብጻዊቱ ፡ አጋር ፡ ለአብርሃም ፡ የወለደችለትን ፡ ልጅ ፡ ሲሥቅ ፡ አየችው ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 10 ፤ አብርሃምንም ፦ ይህችን ፡ ባሪያ ፡ ከነልጇ ፡ አሳድ ፤ የዚች ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ ከልጄ ፡ ከይሥሐቅ ፡ ጋራ ፡ አይወርስምና ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ በአብርሃም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ እጅግ ፡ ችግር ፡ ኾነበት ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ ስለ ፡ ባሪያኽና ፡ ስለ ፡ ብላቴናው ፡ አትዘን ፤ ሳራም ፡ የምትነግርኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ስማ ፤ በይሥሐቅ ፡ ዘር ፡ ይጠራልኻልና ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ የባሪያዪቱን ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ ሕዝብ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ዘርኽ ፡ ነውና ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ አብርሃምም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ እንጀራንም ፡ ወሰደ ፥ የውሃ ፡ አቀኑማዳንም ፡ ለአጋር ፡ በትከሻዋ ፡ አሸከማት ፥ ብላቴናውንም ፡ ሰጥቶ ፡ አስወጣት ፤ ርሷም ፡ ኼደች ፡ በቤርሳቤሕም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተቅበዘበዘች ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ ውሃውም ፡ ከአቀኑማዳው ፡ ዐለቀ ፤ ብላቴናውንም ፡ ካንድ ፡ ቀኑጥቋጦ ፡ በታች ፡ ጣለችው ፤

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 16 ፤ ርሷም ፡ ኼደች ፦ ብላቴናው ፡ ሲሞት ፡ አልየው ፡ ብላ ፡ ቀስት ፡ ተወርውሮ ፡ የሚደርስበትን ፡ ያኽል ፡ ርቃ ፡ በአንጻሩ ፡ ተቀመጠች ። ፊት ፡ ለፊትም ፡ ተቀመጠች ፥ ቃሏንም ፡ አሰምታ ፡ አለቀሰች ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የብላቴናውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ አጋርን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ጠራት ፦ አጋር ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ኾንሽ ፧ እግዚአብሔር ፡ የብላቴናውን ፡ ድምፅ ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ሰምቷልና ፥ አትፍሪ ።

ዘፍ. ፥ 21 ፥ 18 ፤ ተነሺ ፥ ብላቴናውንም ፡ አንሺ ፥ እጅሽንም ፡ በርሱ ፡ አጽኚው ፤ ትልቅ ፡ ሕዝብ ፡ አደርገዋለኹና ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዐይኗን ፡ ከፈተላት ፥ የውሃ ፡ ጕድጓድንም ፡ አየች ፤ ኼዳም ፡ አቀ·ማዳውን ፡ በውሃ ፡ ሞላች ፥ ብላቴናውንም ፡ አጠጣች ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከብላቴናው ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ አደገም ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ ተቀመጠ ፥ ቀስተኛም ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ በፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ተቀመጠ ፤ እናቱም ፡ ከምድረ ፡ ግብጽ ፡ ሚስት ፡ ወሰደችለት ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ አቢሜሌክ ፡ ከሙሽራው ፡ ወዳጅ ፡ ከአኮዘት ([30])ና ፡ ከሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ ከፊኮል ([31]) ፡ ጋራ ፡ አብርሃምን ፡ አለው ፦ በምታደርገው ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ አኹንም ፡ በእኔም ፡ በልጄም ፡ በልጅ ፡ ልጄም ፡ ክፉ ፡ እንዳታደርግብኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማልልኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአንተ ፡ ቸርነትን ፡ እንዳደረግኹ ፡ አንተም ፡ ለእኔ ፡ ለተቀመጥኽባትም ፡ ምድር ፡ ቸርነትን ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ አብርሃምም ፦ እኔ ፡ እምላለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ አቢሜሌክንም ፡ ባሪያዎቹ ፡ በነጠቁት ፡ በውሃ ፡ ጕድጓድ ፡ ምክንያት ፡ አብርሃም ፡ ወቀሰው ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ አቢሜሌክም ፡ አለ ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ ያደረገውን ፡ አላወቅኹም ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ አልነገርኸኝም ፥ እኔም ፡ ከዛሬ ፡ በቀር ፡ አልሰማኹም ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ አብርሃምም ፡ በጎችንና ፡ ላሞችን ፡ አምጥቶ ፡ ለአቢሜሌክ ፡ ሰጠው ፤ ኹለቱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ አብርሃምም ፡ ሰባት ፡ ቄቦች ፡ በጎችን ፡ ለብቻቸው ፡ አቆመ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ አቢሜሌክም ፡ አብርሃምን ፦ ለብቻቸው ፡ ያቆምኻቸው ፡ እነዚህ ፡ ሰባት ፡ ቄቦች ፡ በጎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ይህችን ፡ የውሃ ፡ ጕድጓድ ፡ እንደ ፡ ቈፈርኹ ፡ ምስክር ፡ ይኾንልኝ ፡ ዘንድ ፥ እነዚህን ፡ ሰባት ፡ ቄቦች ፡ በጎች ፡ ከእጄ ፡ ትወስዳለኽ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ቤርሳቤሕ ([32]) ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ ከዚያ ፡ ኹለቱ ፡ ተማምለዋልና ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ በቤርሳቤሕም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ አደረጉ ። አቢሜሌክና ፡ የሙሽራው ፡ ወዳጅ ፡ አኮዘት ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ ፊኮልም ፡ ተነሥተው ፡ ወደፍልስጥኤም ፡ ምድር ፡ ተመለሱ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ አብርሃምም ፡ በቤርሳቤሕ ፡ የተምር ፡ ዛፍን ፡ ተከለ ፤ በዚያም ፡ የዘለዓለሙን ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ጠራ ።

ዘፍ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ አብርሃምም ፡ በፍልስጥኤም ፡ ምድር ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ እንግዳ ፡ ኾኖ ፡ ተቀመጠ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ከነዚህም ፡ ነገሮች ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብርሃምን ፡ ፈተነው ፥ እንዲህም ፡

---

30 ዕብ. ፡ አኑዛት ፡ (አኅዘት • ይዘት)

31 ዕብ. ፡ ፊኮል ፡ (አፈ ፡ ኵሉ ፡ የኾሉ ፡ አፍ) ።

32 ዕብ. ፡ ብኤር ፡ ሻባዕ ፡ (ዐዘቅተ ፡ መሐላ • የማሐላ ፡ ጕድጓድ) ።

አለው ፦ አብርሃም ፡ ሆይ ። አብርሃምም ፦ እንሆ ፥ አለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 2 ፤ የምትወደውን ፡ አንድ ፡ ልጅኽን ፡ ይሥሐቅን ፡ ይዘኽ ፡ ወደሞሪያም ፡ ምድር ፡ ኺድ ፤ እኔም ፡ በምነግርኽ ፡ ባንድ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገኽ ፡ ሠዋው ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 3 ፤ አብርሃምም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ አህያውን ፡ ጫነ ፥ ኹለቱንም ፡ ሎሌዎቹንና ፡ ልጁን ፡ ይስሐቅን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፥ ዕንጨትንም ፡ ለመሥዋዕት ፡ ሠነጠቀ ፤ ተነሥቶም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዳለው ፡ ቦታ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 4 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ አብርሃም ፡ ዐይኑን ፡ አነሣና ፡ ቦታውን ፡ ከሩቅ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 5 ፤ አብርሃምም ፡ ሎሌዎቹን ፡ አላቸው ፦ አህያውን ፡ ይዛችኹ ፡ ከዚህ ፡ ቈዩ ፤ እኔና ፡ ልጄ ፡ ወደዚያ ፡ ኼደን ፡ እንሰግዳለን ፥ ወደ ፡ እናንተም ፡ እንመለሳለን ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 6 ፤ አብርሃምም ፡ የመሥዋዕቱን ፡ ዕንጨት ፡ አንሥቶ ፡ ለልጁ ፡ ለይሥሐቅ ፡ አሸከመው ፤ ርሱም ፡ እሳቱንና ፡ ቢላዋውን ፡ በእጁ ፡ ያዘ ፥ ኹለቱም ፡ ዐብረው ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 7 ፤ ይሥሐቅም ፡ አባቱን ፡ አብርሃምን ፡ ተናገረው ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አለ ። ርሱም ፦ እንሆኝ ፥ ልጄ ፡ አለው ፦ እሳቱና ፡ ዕንጨቱ ፡ ይኸው ፡ አለ ፤ የመሥዋዕቱ ፡ በግ ፡ ግን ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አለ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 8 ፤ አብርሃምም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ የመሥዋዕቱን ፡ በግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘጋጃል ፡ አለው ፤ ኹለቱም ፡ ዐብረው ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ወዳለውም ፡ ቦታ ፡ ደረሱ ፤ አብርሃምም ፡ በዚያ ፡ መሠዊያውን ፡ ሠራ ፥ ዕንጨትንም ፡ ረበረበ ፤ ልጁን ፡ ይሥሐቅንም ፡ አስሮ ፡ በመሠዊያው ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ አጋደመው ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 10 ፤ አብርሃምም ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፥ ልጁንም ፡ ያርድ ፡ ዘንድ ፡ ቢላዋ ፡ አነሣ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 11 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ ከሰማይ ፡ ጠራና ፦ አብርሃም ፡ አብርሃም ፡ አለው ፤

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 12 ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለ ። ርሱም ፦ በብላቴናው ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ አትዘርጋ ፥ አንዳችም ፡ አታድርግበት ፤ አንድ ፡ ልጅኽን ፡ ለእኔ ፡ አልከለከልኽምና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ አኹን ፡ ዐውቄያለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 13 ፤ አብርሃምም ፡ ዐይኑን ፡ አነሣ ፥ በኋላውም ፥ እንሆ ፥ አንድ ፡ በግ ፡ በዱር ፡ ውስጥ ፡ ቀንዶቹ ፡ በዕፀ ፡ ሳቤቅ ፡ ተይዞ ፡ አየ ፤ አብርሃምም ፡ ኼደ ፡ በጉንም ፡ ወሰደው ፥ በልጁም ፡ ፋንታ ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ሠዋው ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 14 ፤ አብርሃምም ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ ያህዌ ፡ ይርኤ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ይታያል ፡ ይባላል ።

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክም ፡ አብርሃምን ፡ ከሰማይ ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ጠራው ፥

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 16 ፤ እንዲህም ፡ አለው ፦ እግዚአብሔር ፦ በራሴ ፡ ማልኹ ፡ ይላል ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ አድርገኻልና ፥ አንድ ፡ ልጅኽንም ፡ አልከለከልኽምና ፡

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 17 ፤ በእውነት ፡ በረከትን ፡ እባርክኻለኹ ፥ ዘርኽንም ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብትና ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ አበዛዋለኹ ፤ ዘርኽም ፡ የጠላቶችን ፡ ደጅ ፡ ይወርሳል ፤

ዘፍ. ፥ 22 ፥ 18 ፤ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉም ፡ በዘርኽ ፡ ይባረካሉ ፥ ቃሌን ፡ ሰምተኻልና ።

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ አብርሃምም ፡ ወደ ፡ ብላቴናዎቹ ፡ ተመለሰ ፥ ተነሥተውም ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ዐብረው ፡ ኼዱ ፤ አብርሃምም ፡ በቤርሳቤሕ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ይህም ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፥ ለአብርሃም ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፦ እንሆ ፥ ሚልካ ፡ ደግሞ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለናኮር ፡ ልጆችን ፡ ወለደች ፤

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ በዙሩ ፡ ዑፅ ፥ ወንድሙ ፡ ቡዝ ፥ የአራም ፡ አባት ፡ ቀሙኤል ፥

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ኮዛት ፥ ሐዞ ፥ ፊልዳሥ ፥ የድላፍ ፥ ባቱኤል ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ ባቱኤልም ፡ ርብቃን ፡ ወለደ ፤ እነዚህን ፡ ስምንቱን ፡ ሚልካ ፡ ለአብርሃም ፡ ወንድም ፡ ለናኮር ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ ሬሕማ ፡ የሚሏት ፡ ቁባቱ ፡ ደግሞ ፡ ጥባኽን ፥ ገአምን ፥ ተሐሽን ፥ ሞክሳን ፡ ወለደች ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። _____

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ የሳራም ፡ ዕድሜ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ በቂርያትአርባቅም ፡ ሞተች ፤ ርሷም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ያለች ፡ ኬብሮን ፡ ናት ፤ አብርሃምም ፡ ለሳራ ፡ ሊያዝንላትና ፡ ሊያለቅስላት ፡ ተነሣ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ አብርሃምም ፡ ከሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ተነሣ ፥

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ ለኬጢ ፡ ልጆችም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፦ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስደተኛና ፡ መጻተኛ ፡ ነኝ ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የመቃብር ፡ ርስት ፡ ስጡኝ ፥ ሬሳዬንም ፡ ከፊቴ ፡ ልቅበር ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ የኬጢ ፡ ልጆችም ፡ ለአብርሃም ፡ መለሱ ፥ አሉትም ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስማን ፤ አንተ ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አለቃ ፡ ነኽ ፤ ከመቃብር ፡ ስፍራችን ፡ በመልካሙ ፡ ቦታ ፡ ሬሳኽን ፡ ቅበር ፤ ሬሳኽን ፡ ትቀብር ፡ ዘንድ ፡ ከእኛ ፡ መቃብሩን ፡ የሚከለክልኽ ፡ የለም ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ አብርሃምም ፡ ተነሣ ፥ ለምድሩ ፡ ሕዝብም ፥ ለኬጢ ፡ ልጆች ፥ ሰገደ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ሬሳዬን ፡ ከፊቴ ፡ እንድቀብር ፡ ከወደዳችኹስ ፡ ስሙኝ ፥ ከሰዓር ፡ ልጅ ፡ ከኤፍሮንም ፡ ለምኑልኝ ፤

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ በርሻው ፡ ዳር ፡ ያለችውን ፡ ድርብ ፡ ክፍል ፡ ያላትን ፡ ዋሻውን ፡ በሙሉ ፡ ዋጋ ፡ በመካከላችኹ ፡ ይስጠኝ ፥ መቃብሩ ፡ የእኔ ፡ ርስት ፡ እንዲኾን ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ኤፍሮንም ፡ በኬጢ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ የኬጢ ፡ ሰው ፡ ኤፍሮንም ፡ የኬጢ ፡ ልጆችና ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ የሚገቡ ፡ ኹሉ ፡ ሲሰሙ ፡ ለአብርሃም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ አይደለም ፥ ጌታዬ ፥ ስማኝ ፤ ዕርሻውን ፡ ሰጥቼኻለኹ ፡ በርሱም ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ ዋሻ ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤ በወገኔ ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤ ሬሳኽን ፡ ቅበር ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ አብርሃምም ፡ በአገሩ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ሰገደ ፤

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ የአገሩ ፡ ሰዎችም ፡ ሲሰሙ ፡ ለኤፍሮን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፦ ነገሬን ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፤ የዕርሻውን ፡ ዋጋ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ አንተም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ውሰድ ፥ ሬሳዬንም ፡ በዚያ ፡ እቀብራለኹ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ ኤፍሮንም ፡ ለአብርሃም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ ስማኝ ፤ የአራት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ዋጋ ፡ ምድር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ሬሳኽንም ፡ ቅበር ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ አብርሃምም ፡ የኤፍሮንን ፡ ነገር ፡ ሰማ ፤ አብርሃምም ፡ በኬጢ ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የነገረውን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ መዝኖ ፡ ለኤፍሮን ፡ ሰጠው ፤ ብሩም ፡ ለመሸጫ ፡ ለመለወጫ ፡ የሚተላለፍ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ በመምሬ ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ባለድርብ ፡ ክፍል ፡ የኾነው ፡ የኤፍሮን ፡ ዕርሻ ፡ ለአብርሃም ፡ ጸና ፤

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ዕርሻው ፡ በርሱም ፡ ያለው ፡ ዋሻው ፥ በዕርሻውም ፡ ውስጥ ፡ በዙሪያውም ፡ ያለው ፡ ዕንጨት ፡ ኹሉ ፡ በኬጢ ፡ ልጆችና ፡ በከተማዩቱ ፡ በር ፡ በሚገቡ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ለአብርሃም ፡ ርስቱ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኬብሮን ፡ በምትባል ፡ በመምሬ ፡ ፊት ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ባለው ፡ ዕርሻ ፡ ባለድርብ ፡ ክፍል ፡ በኾነው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ አብርሃም ፡ ሚስቱን ፡ ሳራን ፡ ቀበረ ።

ዘፍ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ ዕርሻውና ፡ በርሱ ፡ ያለው ፡ ዋሻው ፡ በኬጢ ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ለአብርሃም ፡ የመቃብር ፡ ርስት ፡ ኾኖ ፡ ጸና ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ አብርሃምም ፡ ሽመገለ ፡ በዘመኑም ፡ አረጀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አብርሃምን ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ባረከው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ አብርሃምም ፡ ሎሌውን ፡ የቤቱን ፡ ሽማግሌ ፡ የከብቱን ፡ ኹሉ ፡ አዛዥ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ እጅኽን ፡ ከጭኔ ፡ በታች ፡ አድርግ ፥ እኔም ፡ ዐብሬ ፡ ከምኖራቸው ፡ ከከነዓን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ለልጄ ፡ ሚስት ፡ እንዳትወስድለት ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምልኻለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ አገሬና ፡ ወደ ፡ ተወላጆቼ ፡ ትኼዳለኽ ፥ ለልጄ ፡ ለይሥሐቅም ፡ ሚስትን ፡ ትወስድለታለኽ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ሎሌውም ፦ ሴቲቱ ፡ ምናልባት ፡ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ለመምጣት ፡ እንቢ ፡ ያለች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልጅኽን ፡ ወደወጣኽበት ፡ አገር ፡ ልመልሰውን ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ አብርሃምም ፡ አለው ፦ ልጄን ፡ ወደዚያ ፡ እንዳትመልስ ፡ ተጠንቀቅ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ከተወለድኩባት ፡ ምድርም ፡ ያወጣኝ ፦ ይህችንም ፡ ምድር ፡ እሰጥኻለኹ ፡ ብሎ ፡ የነገረኝና ፡ የማለልኝ ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱ ፡ መልአኩን ፡ በፊትኽ ፡ ይሰዳል ፥ ከዚያም ፡ ለልጄ ፡ ሚስትን ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ ሴቲቱም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለመምጣት ፡ እንቢ ፡ ያለች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከዚህ ፡ ካቀረብኹኽ ፡ መሐላ ፡ ንጹሕ ፡ ነኽ ፤ ልጄን ፡ ግን ፡ ወደዚያ ፡ አትመልሰው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ ሎሌውም ፡ ከጌታው ፡ ከአብርሃም ፡ ጭን ፡ በታች ፡ እጁን ፡ አደረገ ፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ማለለት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ሎሌውም ፡ ከጌታው ፡ ግመሎች ፡ መካከል ፡ ዐሥር ፡ ግመሎችን ፡ ወስዶ ፥ ከጌታውም ፡ ዕቃ ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ መስጴጦምያ ፡ ወደናኮር ፡ ከተማ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ሲመሽም ፡ ሴቶች ፡ ውሃ ፡ ሊቀዱ ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡ ከከተማዩቱ ፡ ውጪ ፡ በውሃው ፡

ጕድጓድ ፡ አጠገብ ፡ ግመሎቹን ፡ አስበረከከ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ የጌታዬ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እለምንኻለኹ ፤ መንገዴን ፡ ዛሬ ፡ በፊቴ ፡ አቅናልኝ ፥ ለጌታዬም ፡ ለአብርሃም ፡ ምሕረትን ፡ አድርግ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ እኔ ፡ ቆሜያለኹ ፥ የዚችም ፡ ከተማ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ውሃውን ፡ ሊቀዱ ፡ ይመጣሉ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ውሃ ፡ እጠጣ ፡ ዘንድ ፡ እንስራሽን ፡ አዘንብዪ ፡ የምላት ፡ ርሷም ፦ አንተ ፡ ጠጣ ፥ ግመሎችኽን ፡ ደግሞ ፡ አጠጣለኹ ፡ የምትለኝ ፡ ቈንጕር ፥ ርሷ ፡ ለባሪያኽ ፡ ለይሥሐቅ ፡ ያዘጋጀኻት ፡ ትኹን ፤ በዚህም ፡ ለጌታዬ ፡ ምሕረትን ፡ እንዳደረግኽ ፡ ዐውቃለኹ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ይህን ፡ መናገሩንም ፡ ሳይፈጽም ፥ እንሆ ፥ ሚልካ ፡ የወለደችው ፡ የባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ርብቃ ፡ እንስራዋን ፡ በጫንቃዋ ፡ ተሸክማ ፡ ወጣች ፤ ሚልካም ፡ የአብርሃም ፡ ወንድም ፡ የናኮር ፡ ሚስት ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ብላቴናዪቱም ፡ መልኳ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፥ ወንድ ፡ የማያውቃት ፡ ድንግልም ፡ ነበረች ፤ ወደ ፡ ምንጭም ፡ ወረደች ፡ እንስራዋንም ፡ ሞላች ፥ ተመልሳም ፡ ወጣች ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ ሎሌውም ፡ ሊገናኛት ፡ ሮጠና ፦ ከእንስራሽ ፡ ጥቂት ፡ ውሃ ፡ ታጠጪኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሻለኹ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ ርሷም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ጠጣ ፡ አለችው ፤ ፈጥናም ፡ እንስራዋን ፡ በእጇ ፡ አውርዳ ፡ አጠጣችው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ርሱንም ፡ ካጠጣች ፡ በኋላ ፦ ለግመሎችኽ ፡ ደግሞ ፡ ዥሉም ፡ እስኪረኩ ፡ ድረስ ፡ ውሃ ፡ እቀዳለኹ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ፈጥናም ፡ ውሃውን ፡ ከእንስራዋ ፡ በማጠጫው ፡ ውስጥ ፡ ገለበጠችው ፥ ደግሞም ፡ ልትቀዳ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ሮጠች ፥ ለግመሎቹም ፡ ዥሉ ፡ ውሃ ፡ ቀዳች ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ ሰውዮውም ፡ ትክ ፡ ብሎ ፡ ይመለከታት ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ መንገዱን ፡ አቅንቶለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ እንዳልኾነ ፡ ለማወቅም ፡ ዝም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ግመሎቹም ፡ ከጠጡ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ሰውዮው ፡ ግማሽ ፡ ሰቅል ፡ የሚመዘን ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፥ ለእጆቿም ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የሚመዘን ፡ ጥንድ ፡ የወርቅ ፡ አንባር ፡ አወጣ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ አላት ፦ አንቺ ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነሽ ፧ እስኪ ፡ ንገሪኝ ፤ በአባትሽ ፡ ቤት ፡ የምናድርበት ፡ ስፍራ ፡ ይገኛልን ፧

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ አለችውም ፦ እኔ ፡ ሚልካ ፡ ለናኮር ፡ የወለደችው ፡ የባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ነኝ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ገለባና ፡ ገፈራ ፡ የሚበቃ ፡ ያኽል ፡ አለ ፥ ለማደሪያም ፡ ደግሞ ፡ ስፍራ ፡ አለን ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ ሰውዮውም ፡ አጐነበሰ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገደ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ቸርነቱንና ፡ እውነቱን ፡ ከጌታዬ ፡ ያላራቀ ፡ የጌታዬ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ እኔ ፡ በመንገድ ፡ ሳለኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደጌታዬ ፡ ወንድሞች ፡ ቤት ፡ መራኝ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 28 ፤ ብላቴናዪቱም ፡ ሮጠች ፥ ለእናቷም ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዥሉ ፡ ተናገረች ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 29 ፤ ለርብቃም ፡ ላባ ፡ የተባለ ፡ ወንድም ፡ ነበራት ፤ ላባም ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ወደውሃው ፡ ምንጭ ፡ ወደ ፡ ሰውዮው ፡ ሮጠ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 30 ፤ ቀለበቱንና ፡ አንባሮቹን ፡ በእኅቱ ፡ እጅ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ የእኅቱን ፡ የርብቃንም ፡ ነገር ። ያ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፡ ያለችውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ ወደዚያ ፡ ሰው ፡ መጣ ፤ እንሆም ፥ በውሃው ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ከግመሎቹ ፡ ዘንድ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 31 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቡሩክ ፥ ግባ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ አንተ ፡ በውጪ ፡ ቆመኻል ፧ እኔም ፡ ቤቱን ፡ ለግመሎችኽም ፡ ስፍራ ፡ አዘጋጅቻለኹ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 32 ፤ ሰውዮውም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ ፥ ግመሎቹንም ፡ አራገፈ ፤ ገለባና ፡ ገፈራም ፡ ለግመሎቹ ፡ አቀረበ ፤ እግሩን ፡ ይታጠብ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ላሉት ፡ ሰዎች ፡ እግር ፡ ውሃ ፡ አቀረበ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 33 ፤ መብልንም ፡ በፊቱ ፡ አቀረበለት ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ነገሬን ፡ እስክናገር ፡ ድረስ ፡ አልበላም ፡ አለ ። ርሱም ፦ ተናገር ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 34 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ እኔ ፡ የአብርሃም ፡ ሎሌ ፡ ነኝ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጌታዬን ፡ እጅግ ፡ ባረከው ፥ አገነነውም ፤ በጎችንና ፡ ላሞችን ፥ ብርንም ፥ ወርቅንም ፥ ወንዶች ፡ ባሪያዎችንና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችን ፥ ግመሎችንም ፡ አህያዎችንም ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 36 ፤ ሳራም ፡ የጌታዬ ፡ ሚስት ፡ በእርጅናው ፡ ለጌታዬ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፤ የነበረውንም ፡ ሹሉ ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 37 ፤ ጌታዬም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አማለኝ ፦ እኔ ፡ ካለኹበት ፡ አገር ፡ ከከነዓናውያን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ለልጄ ፡ ሚስትን ፡ አትውሰድ ፡

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 38 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወዳባቴ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ወገኔም ፡ ኺድ ፥ ለልጄም ፡ ሚስትን ፡ ውሰድለት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 39 ፤ ጌታዬንም ፦ ሴቲቱ ፡ ምናልባት ፡ ባትከተለኝሳ ፧ አልኹት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 40 ፤ ርሱም ፡ አለኝ ፦ አካኼዴን ፡ በፊቱ ፡ ያደረግኹለት ፡ እግዚአብሔር ፡ መልአኩን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይልካል ፥ መንገድኽንም ፡ ያቀናል ። ለልጄም ፡ ከወገኖቼ ፡ ከአባቴም ፡ ቤት ፡ ሚስትን ፡ ትወስዳለኽ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 41 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከመሐላዬ ፡ ንጹሕ ፡ ነኽ ፤ ወደ ፡ ዘመዶቼ ፡ ኼደኽ ፡ እነርሱ ፡ ባይሰጡኽ ፡ ካማልኹኽ ፡ መሐላ ፡ ንጹሕ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 42 ፤ ዛሬም ፡ ወደውሃው ፡ ምንጭ ፡ መጣኹ ፥ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ የጌታዬ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡ የምኼድበትን ፡ መንገዴን ፡ ብታቀናልኝ ፤

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 43 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በውሃው ፡ ምንጭ ፡ ላይ ፡ ቆሜያለኹ ፤ ውሃ ፡ ልትቀዳ ፡ ለምትመጣውም ፡ ቈንጉዖ ። ጥቂት ፡ ውሃ ፡ ከእንስራሽ ፡ አጠጪኝ ፡ ስላት ፥

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 44 ፤ ርሷም ፦ አንተ ፡ ጠጣ ፥ ደግሞም ፡ ለግመሎችኽ ፡ እቀዳለኹ ፡ የምትለኝ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለጌታዬ ፡ ልጅ ፡ ያዘጋጃት ፡ ሴት ፡ ርሷ ፡ ትኹን ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 45 ፤ እኔም ፡ የልቤን ፡ መናገር ፡ ገና ፡ ሳልፈጽም ፥ እንሆ ፥ ርብቃ ፡ እንስራዋን ፡ በትከሻዋ ፡ ተሸክማ ፡ ወጣች ፥ ወደ ፡ ምንጭም ፡ ወርዳ ፡ ውሃ ፡ ቀዳች ፤ እኔም ፦ እስኪ ፡ አጠጪኝ ፡ አልኋት ።

ዘፍ. ፡ 24 ፡ 46 ፤ ፈጥናም ፡ እንስራዋን ፡ ከጫንቃዋ ፡ አወረደችና ፦ አንተ ፡ ጠጣ ፥ ግመሎችኽንም ፡ ደግሞ ፡

አጠጣለኹ ፡ አለች ፤ እኔም ፡ ጠጣኹ ፥ ግመሎቼንም ፡ ደግሞ ፡ አጠጣች ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 47 ፤ እኔም ፦ አንቺ ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነሽ ፧ ብዬ ፡ ጠየቅኋት ። ርሷም ፦ ሚልካ ፡ ለናኮር ፡ የወለደችለት ፡ የባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ አለች ፤ ቀለበትም ፡ አደረግኹላት ፥ ለእጆቿም ፡ አንባሮች ፡ አደረግኹላት ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 48 ፤ በግንባሬም ፡ አጐነበስኹ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገድኹ ፤ የጌታዬን ፡ የወንድሙን ፡ ልጅ ፡ ለልጁ ፡ እወስድ ፡ ዘንድ ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ የመራኝን ፡ የጌታዬን ፡ የአብርሃምን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገንኹ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 49 ፤ አኹንም ፡ ቸርነትና ፡ እውነት ፡ ለጌታዬ ፡ ትሠሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ንገሩኝ ፤ ይህም ፡ ባይኾን ፡ ንገሩኝ ፥ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ እል ፡ ዘንድ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 50 ፤ ላባና ፡ ባቱኤልም ፡ መለሱ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ። ነገሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መጥቷል ፡ ክፉም ፡ በጎም ፡ ልንመልስልኽ ፡ አንችልም ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 51 ፤ ርብቃ ፡ እንኋት ፡ በፊትኽ ፡ ናት ፤ ይዘኻት ፡ ኺድ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ለጌታኽም ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ ትኹን ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 52 ፤ የአብርሃምም ፡ ሎሌ ፡ ነገራቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወድቆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰገደ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 53 ፤ ሎሌውም ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ጌጥ ፡ ልብስም ፡ አወጣ ፥ ለርብቃም ፡ ሰጣት ፤ የከበረ ፡ ስጦታንም ፡ ለወንድሟና ፡ ለእናቷ ፡ አቀረበ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 54 ፤ ርሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ በሉ ፡ ጠጡም ፥ ከዚያም ፡ ዐደሩ ፤ ማልደውም ፡ ተነሡና ፦ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብቱኝ ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 55 ፤ ወንድሟና ፡ እናቷም ፦ ብላቴናዪቱ ፡ አንድ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ እንኳ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ትቀመጥ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ትኼዳለች ፡ አሉ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 56 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ መንገዴን ፡ አቅንቶልኛልና ፥ አታዘግዩኝ ፤ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብቱኝ ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 57 ፤ እነርሱም ፦ ብላቴናዪቱን ፡ እንጥራና ፡ ከአፏ ፡ እንጠይቅ ፡ አሉ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 58 ፤ ርብቃንም ፡ ጠርተው ። ከዚህ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ትኼጃለሽን ፧ አሏት ። ርሷም ፦ እኼዳለኹ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 59 ፤ እኅታቸውንም ፡ ርብቃን ፡ ሞግዚቷንም ፡ የአብርሃምን ፡ ሎሌና ፡ ሰዎቹንም ፡ አሰናበቷቸው ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 60 ፤ ርብቃንም ፡ መረቋትና ፦ አንቺ ፡ እኅታችን ፥ እልፍ ፡ አእላፋት ፡ ኹኚ ፤ ዘርሽም ፡ የጠላቶችን ፡ ደጅ ፡ ይውረስ ፡ አሏት ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 61 ፤ ርብቃም ፡ ተነሣች ፡ ደንገጥሮቿም ፥ በግመሎችም ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ተከተሉት ፤ ሎሌውም ፡ ርብቃን ፡ ተቀብሎ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 62 ፤ ይሥሐቅም ፡ ብኤርለሃይሮኢ ፡ በሚሏት ፡ ምንጭ ፡ መንገድ ፡ መጣ ፤ በአዜብ ፡ ምድር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 63 ፤ ይሥሐቅም ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ እያሰላሰለ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ፤ ዐይኖቹንም ፡

አቀና ፥ እንሆም ፡ ግመሎች ፡ ሲመጡ ፡ አየ ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 64 ፤ ርብቃም ፡ ዐይኖቿን ፡ አቀናች ፥ ይሥሐቅንም ፡ አየች ፥ ከግመልም ፡ ወረደች ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 65 ፤ ሎሌውንም ፦ ሊገናኘን ፡ በሜዳ ፡ የሚመጣ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ማን ፡
ነው ፧ አለችው ። ሎሌውም ፦ ርሱ ፡ ጌታዬ ፡ ነው ፡ አላት ፤ ርሷም ፡ መሸፈኛ ፡ ወስዳ ፡ ተከናነበች ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 66 ፤ ሎሌውም ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለይሥሐቅ ፡ ነገረው ።

ዘፍ. ፥ 24 ፥ 67 ፤ ይሥሐቅም ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ወደሳራ ፡ ድንኳን ፡ አገባት ፥ ርብቃንም ፡ ወሰዳት ፥ ሚስትም ፡
ኾነችው ፥ ወደዳትም ፤ ይሥሐቅም ፡ ከእናቱ ፡ ሞት ፡ ተጽናና ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። _____

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 1 ፤ አብርሃምም ፡ ደግሞ ፡ ስሟ ፡ ኬጡራ ([33]) ፡ የተባለች ፡ ሚስት ፡ አገባ ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 2 ፤ ርሷም ፡ ዘምራንን ፥ ዮቅሳንን ፥ ሜዳንን ፥ ምድያምን ፥ የስቦቅን ፥ ስዌሕን ፡ ወለደችለት ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 3 ፤ ዮቅሳንም ፡ ሳባንና ፡ ድዳንን ፡ ወለደ ። የድዳንም ፡ ልጆች ፡ አሶርያውያን ፡
(አሱራውያን) ፥ ለጡሳውያን ፥ ለኡማውያን ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 4 ፤ የምድያምም ፡ ልጆች ፡ ጌፌር ፥ ዔፌር ፥ ሄኖኅ ፥ አቢዳዕ ([34]) ፥ ኤልዳዓ ([35]) ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡
ኹሉ ፡ የኬጡራ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 5 ፤ አብርሃምም ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ለይሥሐቅ ፡ ሰጠው ፤

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 6 ፤ የአብርሃምም ፡ ለነበሩ ፡ ለቁባቶቹ ፡ ልጆች ፡ አብርሃም ፡ ስጦታን ፡ ሰጣቸው ፤ ርሱም ፡ ገና ፡
በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ከልጁ ፡ ከይሥሐቅ ፡ ለይቶ ፡ ወደፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ አገር ፡ ሰደዳቸው ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 7 ፤ አብርሃምም ፡ የኖረበት ፡ የዕድሜው ፡ ዓመታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡
ዓመት ፡ ኖረ ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 8 ፤ አብርሃምም ፡ ነፍሱን ፡ ሰጠ ፥ በመልካም ፡ ሽምግልናም ፡ ሞተ ፤ ሸመገለም ፥ ብዙ ፡ ዘመንም ፡
ጠገበ ፤ ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ ተከማቸ ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 9 ፤ ልጆቹ ፡ ይሥሐቅና ፡ እስማኤልም ፡ በመምሬ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በኬጢያዊ ፡ በሰዓር ፡ ልጅ ፡
በኤፍሮን ፡ ዕርሻ ፡ ላይ ፡ ባለድርብ ፡ ክፍል ፡ በኾነው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ቀበሩት ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 10 ፤ አብርሃም ፡ ከኬጢ ፡ ልጆች ፡ የገዛው ፡ ዕርሻ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አብርሃምና ፡ ሚስቱ ፡ ሳራ ፡ ከዚያ ፡
ተቀበሩ ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 11 ፤ አብርሃምም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ይሥሐቅን ፡ ባረከው ፤ ይሥሐቅም ፡
ብኤርለሃይሮኢ ፡ ተብሎ ፡ በሚጠራው ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ኖረ ።

ዘፍ. ፥ 25 ፥ 12 ፤ የሳራ ፡ ባሪያ ፡ ግብጻዊቱ ፡ አጋር ፡ ለአብርሃም ፡ የወለደችው ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ የእስማኤል ፡
ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

---

33 ዕብ. ፥ ቁጡራ ፡ (ቅታሬ ፥ መዐዛ) ።

34 የዕውቀት ፡ አባት ።

35 የዕውቀት ፡ አምላክ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ የእስማኤልም ፡ የልጆቹ ፡ ስም ፡ በየስማቸውና ፡ በየትውልዳቸው ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤ የእስማኤል ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ነባዮት ፥ ቄዳር ፥ ነብዳኤል ፥ መብሳም ፥ ማስማዕ ፥

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ ዱማ ፥ ማሣ ፥ ኩዳን ፥ ቴማን ፥ ኢጡር ፥ ናፌስ ፥ ቄድማ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥ ስማቸውም ፡ በየመንደራቸውና ፡ በየሰፈራቸው ፡ ይኸው ፡ ነው ፤ በየወገናቸውም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ እስማኤልም ፡ የኖረበት ፡ የዕድሜው ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነው ፤ ነፍሱን ፡ ሰጠ ፥ ሞተም ፤ ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ ተከማቸ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ መኖሪያቸውም ፡ ከኤውላጥ ፡ አንሥቶ ፡ በግብጽ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እስከምትገኝ ፡ እስከ ፡ ሱር ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ በምትወስደው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ እንዲህም ፡ በወንድሞቹ ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ የአብርሃም ፡ ልጅ ፥ የይሥሐቅ ፡ ትውልድም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አብርሃም ፡ ይሥሐቅን ፡ ወለደ ፤

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ ይሥሐቅም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሲኾነው ፡ ርብቃን ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ በኹለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የሶርያዊው ፡ የባቱኤል ፡ ልጅና ፡ የሶርያዊው ፡ የላባ ፡ እኅት ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ ይሥሐቅም ፡ ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፥ መካን ፡ ነበረችና ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተለመነው ፥ ርብቃም ፡ ሚስቱ ፡ ፀነሰች ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ ልጆችም ፡ በሆዷ ፡ ውስጥ ፡ ይገፋፉ ፡ ነበር ፤ ርሷም ፦ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ ይህ ፡ ለእኔ ፡ ምኔ ፡ ነው ፧ አለች ። ከእግዚአብሔርም ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ኼደች ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አላት ፦ ኹለት ፡ ወገኖች ፡ በማሕፀንሽ ፡ ናቸው ፥ ኹለቱም ፡ ሕዝብ ፡ ከሆድሽ ፡ ይከፈላሉ ፤ ሕዝብም ፡ ከሕዝብ ፡ ይበረታል ፤ ታላቁም ፡ ለታናሹ ፡ ይገዛል ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ ትወልድ ፡ ዘንድ ፡ ዘመኗ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜም ፥ እንሆ ፥ በማሕፀኗ ፡ መንታ ፡ ነበሩ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ በፊትም ፡ የወጣው ፡ ቀይ ፡ ነበረ ፥ ኾለንተናውም ፡ ጠጕር ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፤ ስሙም ፡ ዔሳው ፡ ተባለ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወንድሙ ፡ ወጣ ፥ በእጁም ፡ የዔሳውን ፡ ተረከዝ ፡ ይዞ ፡ ነበር ፤ ስሙም ፡ ያዕቆብ ፡ ተባለ ። ርሷ ፡ ልጆችን ፡ በወለደቻቸው ፡ ጊዜ ፡ ይሥሐቅ ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ ኾኖት ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ ብላቴናዎቹም ፡ አደጉ ፤ ዔሳውም ፡ ዐደን ፡ የሚያውቅ ፡ የበረሓ ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ ጭምት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ በድንኳንም ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ይሥሐቅም ፡ ዔሳውን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፥ ካደነው ፡ ይበላ ፡ ነበርና ፤ ርብቃ ፡ ግን ፡ ያዕቆብን ፡ ትወድ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 29 ፤ ያዕቆብም ፡ ወጥ ፡ ሠራ ፤ ዔሳውም ፡ ደክሞ ፡ ከበረሓ ፡ ገባ ፤

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 30 ፤ ዔሳውም ፡ ያዕቆብን ፦ ከዚህ ፡ ከቀዩ ፡ ወጥ ፡ አብላኝ ፥ እኔ ፡ እጅግ ፡ ደክሜያለኹና ፡ አለው ፤ ስለዚህ ፥ ስሙ ፡ ኤዶም ([36]) ፡ ተባለ ።

---

36 ዕብ. ፥ ኤዶም ፡ (ቀይሕ • ቀይ) ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 31 ፤ ያዕቆብም ፦ በመዠመሪያ ፡ ብኵርናኽን ፡ ሸጥልኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 32 ፤ ዔሳውም ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ልሞት ፡ ነው ፤ ይህች ፡ ብኵርና ፡ ለምኔ ፡ ናት ፧ አለ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 33 ፤ ያዕቆብም ፦ እስኪ ፡ በመዠመሪያ ፡ ማልልኝ ፡ አለው ። ማለለትም ፤ ብኵርናውንም ፡ ለያዕቆብ ፡ ሸጠ ።

ዘፍ. ፡ 25 ፡ 34 ፤ ያዕቆብም ፡ ለዔሳው ፡ እንጀራና ፡ የምስር ፡ ወጥ ፡ ሰጠው ፤ በላ ፥ ጠጣ ፥ ተነሥቶም ፡ ኼደ ፤ እንዲሁም ፡ ዔሳው ፡ ብኵርናውን ፡ አቃለላት ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ በምድርም ፡ ቀድሞ ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ከኾነው ፡ ራብ ፡ በላይ ፡ ራብ ፡ ኾነ ፤ ይሥሐቅም ፡ ወደፍልስጥኤም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ ወደ ፡ ጌራራ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ተገለጠለት ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትውረድ ፥ እኔ ፡ በምልኽ ፡ ምድር ፡ ተቀመጥ ፡ እንጂ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ በዚች ፡ ምድር ፡ ተቀመጥ ፥ ከአንተ ፡ ጋራም ፡ እኾናለኹ ፥ እባርክኻለኹም ፤ እነዚህን ፡ ምድሮች ፡ ኹሉ ፡ ለአንተም ፡ ለዘርኽም ፡ እሰጣለኹና ፥ ለአባትኽ ፡ ለአብርሃም ፡ የማልኹለትንም ፡ መሐላ ፡ አጸናለኹ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ዘርኽንም ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ አበዛለኹ ፥ እነዚህንም ፡ ምድሮች ፡ ኹሉ ፡ ለዘርኽ ፡ እሰጣለኹ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በዘርኽ ፡ ይባረካሉ ፤

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ አብርሃም ፡ ቃሌን ፡ ሰምቷልና ፥ ፍርዴን ፡ ትእዛዜን ፡ ሥርዐቴን ፡ ሕጌንም ፡ ጠብቋልና ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ይሥሐቅም ፡ በጌራራ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ የዚያም ፡ ስፍራ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ጠየቁት ፤ ርሱም ፦ እኅቴ ፡ ናት ፡ አለ ፤ የዚህ ፡ ስፍራ ፡ ሰዎች ፡ ለርብቃ ፡ ሲሉ ፡ እንዳይገድሉኝ ፡ ብሎ ፡ ሚስቴ ፡ ናት ፡ ማለትን ፡ ፈርቷልና ፤ ርሷ ፡ ውብ ፡ ነበረችና ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ንጉሥ ፡ አቢሜሌክ ፡ በመስኮት ፡ ኾኖ ፡ ጐበኘ ፥ ይሥሐቅም ፡ ሚስቱን ፡ ርብቃን ፡ ሲዳራት ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ አቢሜሌክም ፡ ይሥሐቅን ፡ ጠራ ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ ሚስትኽ ፡ ናት ፤ እንዴትስ ፡ ርሷን ፦ እኅቴ ፡ ናት ፡ አልኽ ፧ ይሥሐቅም ፦ በርሷ ፡ ምክንያት ፡ እንዳልሞት ፡ ብዬ ፡ ነው ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ አቢሜሌክም ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ያደረግኽብን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ከሕዝብ ፡ አንዱ ፡ ከሚስትኽ ፡ ጋራ ፡ ሊተኛ ፡ ጥቂት ፡ በቀረው ፡ ነበር ፥ ኀጢአትንም ፡ ልታመጣብን ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ አቢሜሌክም ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፦ ይህን ፡ ሰው ፡ ሚስቱንም ፡ የሚነካ ፡ ሞትን ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ይሥሐቅም ፡ በዚያች ፡ ምድር ፡ ዘርን ፡ ዘራ ፥ በዚያች ፡ ዓመትም ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ አገኘ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባረከው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ባለጠጋ ፡ ሰውም ፡ ኾነ ፥ እጅግ ፡ እስኪበልጥ ፡ ድረስም ፡ እየጨመረ ፡ ይበዛ ፡ ነበር ፤

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ የበግና ፡ የላም ፡ ከብትም ፡ ሎሌዎችም ፡ እጅግ ፡ በዙለት ፤ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ቀኑበት ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ በአባቱ ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ የአባቱ ፡ ሎሌዎች ፡ የማሷቸውን ፡ ጕድጓዶች ፡ ኹሉ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ደፈኗቸው ፡ ዐፈርንም ፡ ሞሉባቸው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ አቢሜሌክም ፡ ይሥሐቅን ፦ ከእኛ ፡ ተለይተኽ ፡ ኺድ ፥ ከእኛ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ በርትተኻልና ፥ አለው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ይሥሐቅም ፡ ከዚያ ፡ ኼደ ፥ በጌራራም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፍሮ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ ይሥሐቅም ፡ በአባቱ ፡ በአብርሃም ፡ ዘመን ፡ ቈፍረዋቸው ፡ የነበሩትን ፡ የውሃ ፡ ጕድጓዶች ፡ ደግሞ ፡ አስቈፈረ ፤ አብርሃም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የፍልስጥኤም ፡ ሰዎች ፡ ደፍነዋቸው ፡ ነበሩና ፤ አባቱም ፡ ይጠራቸው ፡ በነበረው ፡ ስም ፡ ጠራቸው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ የይሥሐቅ ፡ ሎሌዎችም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ቈፈሩ ፥ በዚያም ፡ የሚመነጭ ፡ የውሃ ፡ ጕድጓድ ፡ አገኙ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ የጌራራ ፡ አገር ፡ እረኞች ፡ ከይሥሐቅ ፡ እረኞች ፡ ጋራ ፦ ውሃው ፡ የእኛ ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ተከራከሩ ፤ የዚያችንም ፡ ጕድጓድ ፡ ስም ፡ ኤሴቅ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ፥ ለርሷ ፡ ሲሉ ፡ ተጣልተዋልና ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ሌላ ፡ ጕድጓድም ፡ ማሱ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ ደግሞ ፡ ተጣሉ ፤ ስሟንም ፡ ስጥና ፡ ብሎ ፡ ጠራት ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ ከዚያም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ሌላ ፡ ጕድጓድ ፡ አስቈፈረ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ አልተጣሉም ፤ ስሟንም ፡ ርኆቦት ፡ ብሎ ፡ ጠራት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ አኹን ፡ እግዚአብሔር ፡ አሰፋልን ፥ በምድርም ፡ እንበዛለን ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 23-24 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ወጣ ። በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገለጠለት ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ እኔ ፡ የአባትኽ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፤ አትፍራ ፥ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፤ እባርክኻለኹ ፤ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ አብርሃም ፡ ዘርኽን ፡ አበዛለኹ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ በዚያም ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ጠራ ፥ በዚያም ፡ ድንኳን ፡ ተከለ ፤ የይሥሐቅም ፡ ሎሌዎች ፡ በዚያ ፡ ጕድጓድ ፡ ማሱ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ አቢሜሌክና ፡ የሙሽራው ፡ ወዳጅ ፡ አኮዘት ([37]) ፡ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ፊኮል ፡ ከጌራራ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ ይሥሐቅም ፦ ለምን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣችኹ ፧ እናንተ ፡ ጠልታችኹኛል ፥ ከእናንተም ፡ ለይታችኹ ፡ አሳድዳችኹኛል ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 28-29 ፤ እነርሱም ፡ አሉት ፦ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳለ ፡ በርግጥ ፡ አየን ፤ ስለዚህም ፦ በእኛና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ መሐላ ፡ ይኹን ፤ እኛ ፡ አንተን ፡ እንዳልነካንኽ ፥ በጎነትንም ፡ ብቻ ፡ እንዳሳየንኽ ፥ በደኅናም ፡ እንደ ፡ ሰደድንኽ ፥ አንተም ፡ ክፉ ፡ እንዳትሠራብን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እናድርግ ፡ አልን ፤ አንተ ፡ አኹን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተባረክኽ ፡ ነኽ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ ይሥሐቅም ፡ ማእድ ፡ አቀረበላቸው ፥ በሉም ፡ ጠጡም ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ ማልደውም ፡ ተነሡ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ተማማሉ ፤ ይሥሐቅም ፡ አሰናበታቸው ፥ ከርሱም ፡ ወጥተው ፡ በደኅና ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የይሥሐቅ ፡ ሎሌዎች ፡ መጡ ፥ ስለቈፈሯትም ፡ ጕድጓድ ፦ ውሃ ፡ አገኘን ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

---

37 ዕብ. ፡ አኑዘት ፡ (አኅዘት • ይዘት)

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 33 ፤ ስሟንም ፡ ሳቤሀ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ፤ ስለዚህም ፡ የከተማዉ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 34 ፤ ዔሳውም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሲኾነው ፡ የኬጢያዊ ፡ የብኤሪን ፡ ልጅ ፡ ዮዲትን ፥ የኬጢያዊ ፡ የኤሎንን ፡ ልጅ ፡ ቤሴሞትንም ፡ ሚስቶች ፡ አድርጎ ፡ አገባ ፤

ዘፍ. ፡ 26 ፡ 35 ፤ እነርሱም ፡ የይሥሐቅንና ፡ የርብቃን ፡ ልብ ፡ ያሳዝኑ ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። _____

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ይሥሐቅ ፡ ሽምግሎ ፡ ዐይኖቹ ፡ ከማየት ፡ በፈዘዙ ፡ ጊዜ ፡ ታላቁን ፡ ልጁን ፡ ዔሳውን ፡ ጠርቶ ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፡ አለው ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ አለኹ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ አረጀኹ ፥ የምሞትበትን ፡ ቀን ፡ አላውቅም ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ አኹንም ፡ ማደኛኽን ፡ የፍላጻኽን ፡ አፎትና ፡ ቀስትኽን ፡ ውሰድ ፥ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ውጣ ፥ ዐደንም ፡ ዐድንልኝ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ሳልሞትም ፡ ነፍሴ ፡ እንድትባርክኽ ፡ የጣፈጠ ፡ መብል ፡ እኔ ፡ እንደምወደው ፡ አዘጋጅተኽ ፡ እበላ ፡ ዘንድ ፡ አምጣልኝ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ርብቃም ፡ ይሥሐቅ ፡ ለልጁ ፡ ለዔሳው ፡ ሲነግር ፡ ትሰማ ፡ ነበር ። ዔሳውም ፡ ዐደን ፡ ዐድኖ ፡ ሊያመጣ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ ርብቃም ፡ ልጇን ፡ ያዕቆብን ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፦ እንሆ ፥ አባትኽ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለዔሳው ፦

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ዐደን ፡ ዐድነኽ ፡ አምጣልኝ ፥ ሳልሞትም ፡ በልቼ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንድባርክኽ ፡ የጣፈጠ ፡ መብል ፡ አድርግልኝ ፡ ብሎ ፡ ሲነግረው ፡ ሰማኹ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ አኹንም ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ በማዝኽ ፡ ነገር ፡ ስማኝ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ መንጋ ፡ ኼደኽ ፡ ኹለት ፡ መልካካም ፡ ጠቦቶች ፡ አምጣልኝ ፤ እነርሱንም ፡ ጣፋጭ ፡ መብል ፡ ለአባትኽ ፡ እንደሚወደው ፡ አደርጋለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ለአባትኽም ፥ ሳይሞት ፡ እንዲባርክኽ ፥ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ታገባለታለኽ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ ያዕቆብም ፡ ርብቃን ፡ እናቱን ፡ አላት ፦ እንሆ ፥ ዔሳው ፡ ወንድሜ ፡ ጠጕራም ፡ ሰው ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ለስላሳ ፡ ነኝ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ ምናልባት ፡ አባቴ ፡ ቢዳስሰኝ ፡ በፊቱ ፡ እንደሚዘብት ፡ እኾናለኹ ፤ መርገምንም ፡ በላዬ ፡ አመጣለኹ ፥ በረከትን ፡ አይደለም ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ እናቱም ፡ አለችው ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ መርገምኽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ ቃሌን ፡ ብቻ ፡ ስማኝ ፤ ኺድና ፡ አምጣልኝ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ኼዶም ፡ አመጣ ፥ ለእናቱም ፡ ሰጣት ፤ እናቱም ፡ የጣፈጠውን ፡ መብል ፡ አባቱ ፡ እንደሚወደው ፡ አደረገች ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ ርብቃም ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቤት ፡ የነበረችውን ፡ የታላቁን ፡ ልጇን ፡ የዔሳውን ፡ መልካሙን ፡ ልብስ ፡ አመጣች ፥ ታናሹን ፡ ልጇን ፡ ያዕቆብንም ፡ አለበሰችው ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ የጠቦቶችንም ፡ ለምድ ፡ በእጆቹና ፡ በለስላሳው ፡ ዐንገቱ ፡ ላይ ፡ አደረገች ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ የሠራችውን ፡ ጣፋጭ ፡ መብልና ፡ እንጀራውን ፡ ለልጇ ፡ ለያዕቆብ ፡ በእጁ ፡ ሰጠችው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ አባቱም ፡ ገብቶ ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አለው ፡ ርሱም ፦ እንሆኝ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ አለ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ ያዕቆብም ፡ አባቱን ፡ አለው ፦ የበኵር ፡ ልጅኽ ፡ እኔ ፡ ዔሳው ፡ ነኝ ፤ እንዳዘዝኽኝ ፡ አደረግኹ ፤ ነፍስኽ ፡ ትባርከኝ ፡ ዘንድ ፡ ቀና ፡ በልና ፡ ተቀመጥ ፥ ካደንኹትም ፡ ብላ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ ይሥሐቅም ፡ ልጁን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ ፈጥነኽ ፡ አገኘኸው ፧ አለው ። ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ስላቀረበው ፡ ነው ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ልጄ ፡ ዔሳው ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ወይም ፡ እንዳልኾንኽ ፡ እዳስስኽ ፡ ዘንድ ፡ ቅረበኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይሥሐቅ ፡ ቀረበ ፤ ዳሰሰውም ፥ እንዲህም ፦ ይህ ፡ ድምፅ ፡ የያዕቆብም ፡ ድምፅ ፡ ነው ፥ እጆች ፡ ግን ፡ የዔሳው ፡ እጆች ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ አላወቀውም ፡ ነበር ፤ እጆቹ ፡ እንደ ፡ ወንድሙ ፡ እንደ ፡ ዔሳው ፡ እጆች ፡ ጠጕራም ፡ ነበሩና ፤ ስለዚህም ፡ ባረከው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ አለውም ፦ አንተ ፡ ልጄ ፡ ዔሳው ፡ ነኽን ፧ ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ ከልጄ ፡ ዐደን ፡ እንድበላና ፡ ነፍሴ ፡ እንድትባርክኽ ፡ አቅርብልኝ ፡ አለ ። አቀረበለትም ፥ በላም ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አመጣለት ፥ ርሱም ፡ ጠጣ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ አባቱ ፡ ይሥሐቅም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረብ ፡ ሳመኝም ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ቀረበ ፥ ሳመውም ፤ የልብሱንም ፡ ሽታ ፡ አሸተተ ፥ ባረከውም ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የልጄ ፡ ሽታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ባረከው ፡ ዕርሻ ፡ ሽታ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሰማይ ፡ ጠል ፡ ከምድርም ፡ ስብ ፡ የእኽልንም ፡ የወይንንም ፡ ብዛት ፡ ይስጥኽ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 29 ፤ አሕዛብ ፡ ይገዙልኽ ፡ ሕዝብም ፡ ይስገዱልኽ ፤ ለወንድሞችኽ ፡ ጌታ ፡ ኹን ፥ የእናትኽም ፡ ልጆች ፡ ይስገዱልኽ ፤ የሚረግምኽ ፡ ርሱ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፡ የሚባርክኽም ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 30 ፤ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ባርኮ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፥ ያዕቆብም ፡ ከአባቱ ፡ ከይሥሐቅ ፡ ፊት ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፥ ወዲያው ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ዔሳው ፡ ከአደኑ ፡ መጥቶ ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 31 ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ጣፋጭ ፡ መብል ፡ አዘጋጀ ፥ ለአባቱም ፡ አገባ ፤ አባቱንም ፦ አባቴ ፡ ይነሣ ፥ ነፍስኽም ፡ ትባርከኝ ፡ ዘንድ ፡ ከልጁ ፡ ዐደን ፡ ይብላ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 32 ፤ አባቱ ፡ ይሥሐቅም ፦ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ አለው ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ የበኵር ፡ ልጅኽ ፡ ዔሳው ፡ ነኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 33 ፤ ይሥሐቅም ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ያደነውን ፡ ዐደን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ያመጣ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አንተ ፡ ሳትመጣም ፡ ከቸሉ ፡ በላኹ ፡ ባረክኹትም ፤ ርሱም ፡ የተባረከ ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 34 ፤ ዔሳውም ፡ የአባቱን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ እጅግም ፡ መራራ ፡ ጩኸት ፡ ጮኸ ፥ አባቱንም ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ እኔንም ፡ ደግሞ ፡ ባርከኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 35 ፤ ርሱም ፦ ወንድምኽ ፡ በተንኰል ፡ ገብቶ ፡ በረከትኽን ፡ ወሰደብኽ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 36 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ስሙ ፡ ያዕቆብ ፡ ተባለ ፥ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ አሰናክሎኛልና ፤ ብኵርናዬን ፡ ወሰደ ፥ አኹንም ፥ እንሆ ፥ በረከቴን ፡ ወሰደ ። ደግሞም ፦ ለእኔ ፡ በረከትን ፡ አላስቀረኽልኝምን ፧ አለ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 37 ፤ ይሥሐቅም ፡ መለሰ ፥ ዔሳውንም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ ጌታኽ ፡ አደረግኹት ፥ ወንድሞቹንም ፡ ሹሉ ፡ ለርሱ ፡ ተገዢዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰጠኹት ፥ በእኽልም ፡ በወይንም ፡ አበረታኹት ፤ ለአንተ ፡ ግን ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላድርግ ፧

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 38 ፤ ዔሳውም ፡ አባቱን ፡ አለው ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ በረከትኽ ፡ አንዲት ፡ ብቻ ፡ ናትን ፧ አባቴ ፡ ሆይ ፥ እኔንም ፡ ደግሞ ፡ ባርከኝ ። ዔሳውም ፡ ቃሉን ፡ አንሥቶ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 39 ፤ አባቱ ፡ ይሥሐቅም ፡ መለሰ ፥ አለውም ፦ እንሆ ፥ መኖሪያኽ ፡ ከምድር ፡ ስብ ፡ ከላይ ፡ ከሚገኝ ፡ ከሰማይም ፡ ጠል ፡ ይኾናል ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 40 ፤ በሰይፍኽም ፡ ትኖራለኽ ፥ ለወንድምኽም ፡ ትገዛለኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተቃወምኸው ፡ ጊዜ ፡ ቀንበሩን ፡ ከዐንገትኽ ፡ ትጥላለኽ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 41 ፤ ዔሳውም ፡ አባቱ ፡ ስለ ፡ ባረከው ፡ በያዕቆብ ፡ ቂም ፡ ያዘበት ፤ ዔሳውም ፡ በልቡ ፡ አለ ፦ ለአባቴ ፡ የልቅሶ ፡ ቀን ፡ ቀርቧል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወንድሜን ፡ ያዕቆብን ፡ እገድለዋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 42 ፤ ለርብቃም ፡ ይህ ፡ የታላቁ ፡ ልጇ ፡ የዔሳው ፡ ቃል ፡ ደረሰላት ፤ ታናሹን ፡ ልጇን ፡ ያዕቆብንም ፡ አስጠርታ ፡ አስመጣችው ፥ አለችውም ፦ እንሆ ፥ ወንድምኽ ፡ ዔሳው ፡ ሊገድልኽ ፡ ይፈቅዳል ።

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 43 ፤ አኹንም ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ቃሌን ፡ ስማ ፤ ተነሣና ፡ ወደካራን ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ወንድሜ ፡ ወደ ፡ ላባ ፡ ኺድ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 44 ፤ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥ ፥ የወንድምኽ ፡ ቍጣ ፡ እስኪበርድ ፡ ድረስ ፤

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 45 ፤ የወንድምኽ ፡ ቍጣ ፡ ከአንተ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፥ ያደረግኽበትንም ፡ እስኪረሳው ፡ ድረስ ፤ ከዚያም ፡ ልኬ ፡ አስመጣኻለኹ ፤ ባንድ ፡ ቀን ፡ ኹለታችኹን ፡ ለምን ፡ ዐጣለኹ ፧

ዘፍ. ፡ 27 ፡ 46 ፤ ርብቃም ፡ ይሥሐቅን ፡ አለችው ፦ ከኬጢ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ሕይወቴን ፡ ጠላኹት ፤ ያዕቆብ ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሚስትን ፡ የሚያገባ ፡ ከኾነ ፡ በሕይወት ፡ መኖር ፡ ለምኔ ፡ ነው ፧

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ጠራው ፥ ባረከውም ፥ እንዲህ ፡ ብሎም ፡ አዘዘው ፦ ከከነዓናውያን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሚስትን ፡ አታግባ ፤

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ ተነሣና ፡ ወደእናትኽ ፡ አባት ፡ ወደ ፡ ባቱኤል ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ኺድ ፤ ከዚያም ፡ ከእናትኽ ፡ ወንድም ፡ ከላባ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሚስትን ፡ አግባ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክም ፡ ለብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጉባኤ ፡ እንድትኾን ፡ ይባርክኽ ፥ ያፍራኽ ፥ ያብዛኽ ፤

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ ስደተኛ ፡ ኾነኽ ፡ የተቀመጥኽባትን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለአብርሃም ፡ የሰጣትን ፡ ምድር ፡ ትወርስ ፡ ዘንድ ፡ የአብርሃምን ፡ በረከት ፡ ለአንተ ፡ ይስጥኽ ፥ ለዘርኽም ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ አንተ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ሰደደው ፥ ርሱም ፡ የያዕቆብና ፡ የዔሳው ፡ እናት ፡ የርብቃ ፡ ወንድም ፡ የሚኾን ፡ የሶርያዊ ፡ ባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ላባ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ ዔሳውም ፡ ይሥሐቅ ፡ ያዕቆብን ፡ እንደ ፡ ባረከው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ከዚያም ፡ ሚስትን ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኹለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ሰደደው ፥ በባረከውም ፡ ጊዜ ፦ ከከነዓን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሚስትን ፡ አታግባ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘው ፥

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ ያዕቆብም ፡ የአባቱንና ፡ የእናቱን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ የከነዓናውያንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በአባቱ ፡ በይሥሐቅ ፡ ፊት ፡ የተጠሉ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ዔሳው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ዔሳው ፡ ወደ ፡ እስማኤል ፡ ኼደ ፥ ማዕሌትንም ፡ በፊት ፡ ካሉት ፡ ሚስቶቹ ፡ ጋራ ፡ ሚስት ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ የኾነ ፡ የእስማኤል ፡ ልጅና ፡ የነባዮት ፡ እኅት ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ ያዕቆብም ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ካራን ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ አንድ ፡ ስፍራም ፡ ደረሰ ፥ ፀሓይም ፡ ጠልቃ ፡ ነበርና ፥ ከዚያ ፡ ዐደረ ፤ በዚያም ፡ ስፍራ ፡ ድንጋይ ፡ አነሣ ፥ ከራሱም ፡ በታች ፡ ተንተርሶ ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ተኛ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ሕልምም ፡ ዐለመ ፤ እንሆም ፡ መሰላል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተተክሎ ፥ ራሱም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ደርሶ ፥ እንሆም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ይወጡበት ፡ ይወርዱበት ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ ቆሞበት ፡ ነበር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የአባትኽ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ይህችን ፡ አንተ ፡ የተኛኽባትን ፡ ምድር ፡ ለአንተም ፡ ለዘርኽም ፡ እሰጣለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ ዘርኽም ፡ እንደምድር ፡ አሸዋ ፡ ይኾናል ፤ እስከ ፡ ምዕራብና ፡ እስከ ፡ ምሥራቅ ፡ እስከ ፡ ሰሜንና ፡ እስከ ፡ ደቡብ ፡ ትስፋፋለኽ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ በዘርኽም ፡ ይባረካሉ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ እንሆም ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ በምትኼድባትም ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ እጠብቅኻለኹ ፥ ወደዚችም ፡ ምድር ፡ እመልስኻለኹ ፤ የነገርኹኽን ፡ ኹሉ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ አልተውኽምና ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ያዕቆብም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ተነሥቶ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ አላወቅኹም ፡ ነበር ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ፈራ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ስፍራ ፡ እንዴት ፡ ያስፈራ ፤ ይህ ፡ ስፍራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ ይህም ፡ የሰማይ ፡ ደጅ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ ያዕቆብም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ተንተርሶት ፡ የነበረውንም ፡ ድንጋይ ፡ ወስዶ ፡ ሐውልት ፡ አድርጎ ፡ አቆመው ፥ በላዩም ፡ ዘይትን ፡ አፈሰሰበት ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ ያዕቆብም ፡ ያን ፡ ስፍራ ፡ ቤቴል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ አስቀድሞ ፡ ግን ፡ የዚያች ፡ ከተማ ፡ ስም ፡ ሎዛ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ ያዕቆብም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ስእለት ፡ ተሳለ ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ቢኾን ፥ በምኼድባትም ፡ በዚች ፡ መንገድ ፡ ቢጠብቀኝ ፥ የምበላውንም ፡ እንጀራ ፡ የምለብሰውንም ፡ ልብስ ፡ ቢሰጠኝ ፥

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ ወዳባቴ ፡ ቤትም ፡ በጤና ፡ ብመለስ ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ይኾንልኛል ፤

ዘፍ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ለሐውልት ፡ የተከልኹት ፡ ይህም ፡ ድንጋይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይኾናል ፤ ከሰጠኸኝም ፡ ሹሉ ፡ ለአንተ ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እሰጥኻለኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ። _____

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደምሥራቅ ፡ ሰዎች ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ በሜዳውም ፥ እንሆ ፥ ጕድጓድን ፡ አየ ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ የበጎች ፡ መንጋዎች ፡ በላዩ ፡ ተመስገው ፡ ነበር ፤ ከዚያ ፡ ጕድጓድ ፡ በጎቹን ፡ ያጠጡ ፡ ነበርና ፤ በጕድጓዱም ፡ አፍ ፡ የነበረው ፡ ድንጋይ ፡ ትልቅ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ መንጋዎችም ፡ ሹሉ ፡ ከዚያ ፡ በተከማቹ ፡ ጊዜ ፡ ድንጋዩን ፡ ከጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ ገለል ፡ አድርገው ፡ በጎቹን ፡ ያጠጡ ፡ ነበር ፤ ድንጋዩንም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ መልሰው ፡ በጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይገጥሙት ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ ያዕቆብም ፦ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ እናንት ፡ የወዴት ፡ ናችኹ ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እኛ ፡ የካራን ፡ ነን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ የናኮርን ፡ ልጅ ፡ ላባን ፡ ታውቁታላችኹን ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እናውቀዋለን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ ርሱ ፦ ደኅና ፡ ነውን ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ አዎን ፡ ደኅና ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ ልጁ ፡ ራሔል ፡ ከበጎች ፡ ጋራ ፡ መጣች ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ ርሱም ፦ ቀኑ ፡ ገና ፡ ቀትር ፡ ነው ፥ ከብቶቹ ፡ የሚከማቹበት ፡ ሰዓቱም ፡ ገና ፡ አልደረሰም ፤ አኹንም ፡ በጎቹን ፡ አጠጡና ፡ ኼዳችኹ ፡ አሰማሯቸው ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ እነርሱም ፡ አሉ ፦ መንጋዎች ፡ ሹሉ ፡ እስኪከማቹና ፡ ድንጋዩን ፡ ከጕድጓዱ ፡ አፍ ፡ እስኪገለብጡት ፡ ድረስ ፡ አንችልም ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በጎቹን ፡ እናጠጣለን ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፥ እንሆ ፥ የላባ ፡ ልጅ ፡ ራሔል ፡ ከአባቷ ፡ በጎች ፡ ጋራ ፡ ደረሰች ፤ ርሷ ፡ የአባቷን ፡ በጎች ፡ ትጠብቅ ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ ያዕቆብም ፡ የእናቱን ፡ ወንድም ፡ የላባን ፡ ልጅ ፡ ራሔልንና ፡ የአጎቱን ፡ የላባን ፡ በጎች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ቀረበ ፡ ከጕድጓዱም ፡ አፍ ፡ ድንጋዩን ፡ ገለበጠ ፥ የአጎቱን ፡ የላባን ፡ በጎችንም ፡ አጠጣ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ ያዕቆብም ፡ ራሔልን ፡ ሳማት ፥ ቃሉንም ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ ያዕቆብም ፡ የአባቷ ፡ ዘመድና ፡ የርብቃ ፡ ልጅ ፡ መኾኑን ፡ ለራሔል ፡ አስታወቃት ፤ ርሷም ፡ ሮጣ ፡ ኼዳ ፡ ለአባቷ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ነገረችው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ ላባም ፡ የእኅቱን ፡ ልጅ ፡ የያዕቆብን ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበለው ፡ ሮጠ ፥ ዐቅፎም ፡ ሳመው ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አገባው ። ነገሩንም ፡ ሹሉ ፡ ለላባ ፡ ነገረው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ ላባም ፦ በእውነት ፡ አንተ ፡ ዐጥንቴ ፡ ሥጋዬም ፡ ነኽ ፡ አለው ። አንድ ፡ ወር ፡ የሚያኽልም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ ላባም ፡ ያዕቆብን ፦ ወንድሜ ፡ ስለ ፡ ኾንኽ ፡ በከንቱ ፡ ታገለግለኛለኽን ፧ ምንዳኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ንገረኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ ለላባም ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ የታላቂቱ ፡ ስም ፡ ልያ ፡ የታናሺቱ ፡ ስም ፡ ራሔል ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ ልያም ፡ ዐይነ ፡ ልም ፡ ነበረች ፤ ራሔል ፡ ግን ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረች ፥ ፊቷም ፡ ውብ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ ያዕቆብም ፡ ራሔልን ፡ ወደደ ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ስለ ፡ ታናሺቱ ፡ ልጅኽ ፡ ስለ ፡ ራሔል ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ እገዛልኻለኹ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ላባም ፦ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ከምሰጣት ፡ ይልቅ ፡ ለአንተ ፡ ብሰጣት ፡ ይሻላል ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጥ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ ያዕቆብም ፡ ስለ ፡ ራሔል ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተገዛ ፤ ርሷንም ፡ ይወዳት ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኾነለት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ ያዕቆብም ፡ ላባን ፦ ወደ ፡ ርሷ ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ ሚስቴን ፡ ስጠኝ ፥ ቀኔ ፡ ተፈጽሟልና ፥ አለው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ላባም ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ሰርግም ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ልጁን ፡ ልያን ፡ ወስዶ ፡ ለያዕቆብ ፡ አገባለት ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ ላባም ፡ ለልጁ ፡ ለልያ ፡ ባሪያዩቱን ፡ ዘለፋን ፡ ባሪያ ፡ ትኾናት ፡ ዘንድ ፡ ሰጣት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ልያ ፡ ኾና ፡ ተገኘች ፤ ላባንም ፦ ምነው ፡ እንደዚህ ፡ አደረግኽብኝ ፧ ያገለገልኹኽ ፡ ስለ ፡ ራሔል ፡ አልነበረምን ፧ ለምን ፡ አታለልኸኝ ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 26 ፤ ላባም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በአገራችን ፡ ታላቂቱ ፡ ሳለች ፥ ታናሺቱን ፡ እንሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ወግ ፡ አይደለም ፤

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 27 ፤ ይህችንም ፡ ሳምንት ፡ ፈጽም ፤ ሌላ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ እኔን ፡ ስለምታገለግለኝ ፡ አገልግሎት ፡ ርሷን ፡ ደግሞ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 28 ፤ ያዕቆብም ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፥ ይህችንም ፡ ሳምንት ፡ ፈጸመ ፤ ልጁን ፡ ራሔልንም ፡ ለርሱ ፡ ሚስት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 29 ፤ ላባም ፡ ለልጁ ፡ ለራሔል ፡ ባሪያዩቱን ፡ ባላን ፡ ባሪያ ፡ ትኾናት ፡ ዘንድ ፡ ሰጣት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 30 ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ራሔል ፡ ደግሞ ፡ ገባ ። ራሔልንም ፡ ከልያ ፡ ይልቅ ፡ ወደዳት ፤ ሌላ ፡ ሰባት ፡ ዓመትም ፡ ተገዛለት ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ልያ ፡ የተጠላች ፡ መኾኗን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ማሕፀኗን ፡ ከፈተላት ፤ ራሔል ፡ ግን ፡ መካን ፡ ነበረች ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 32 ፤ ልያም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፥ ስሙንም ፡ ሮቤል ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ እግዚአብሔር ፡ መከራዬን ፡ አይቷልና ፥ እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ባሌ ፡ ይወደኛል ፡ ብላለችና ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 33 ፤ ደግሞም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ተጠላኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡

ሰማ ፡ ይህን ፡ ደገመኝ ፡ አለች ፤ ስሙንም ፡ ስምዖን [38] ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 34 ፤ ደግሞም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፤ አኹንም ፡ ባሌ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይጠጋል ፥ ሦስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችን ፡ ወልጄለታለኹና ፡ አለች ፤ ስለዚህም ፡ ስሙን ፡ ሌዊ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 29 ፡ 35 ፤ ደግሞም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ፡ አለች ፤ ስለዚህም ፡ ስሙን ፡ ይሁዳ [39] ፡ ብላ ፡ ጠራችው ። መውለድንም ፡ አቆመች ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ። _____

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ ራሔልም ፡ ለያዕቆብ ፡ ልጆችን ፡ እንዳልወለደች ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በእኅቷ ፡ ቀናችባት ፤ ያዕቆብንም ፦ ልጅ ፡ ስጠኝ ፤ ይህስ ፡ ካልኾነ ፡ እሞታለኹ ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ ያዕቆብም ፡ ራሔልን ፡ ተቈጥቶ ፦ በእውኑ ፡ እኔ ፡ የሆድን ፡ ፍሬ ፡ በነሣሽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቦታ ፡ ነኝን ፧ አላት ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ ርሷም ፡ ባሪያዬ ፡ ባላ ፥ እንሆ ፥ አለች ፤ ድረስባት ፤ በእኔም ፡ ጭን ፡ ላይ ፡ ትውለድ ፥ የርሷም ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ ይኹኑልኝ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ ባሪያዋን ፡ ባላንም ፡ ሚስት ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡ ሰጠችው ፤ ያዕቆብም ፡ ደረሰባት ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ ባላም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደችለት ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ ራሔልም ፦ እግዚአብሔር ፡ ፈረደልኝ ፥ ቃሌንም ፡ ደግሞ ፡ ሰማ ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ሰጠኝ ፡ አለች ፤ ስለዚህ ፥ ስሙን ፡ ዳን [40] ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ የራሔልም ፡ ባሪያ ፡ ባላ ፡ ደግማ ፡ ፀነሰች ፥ ለያዕቆብም ፡ ኹለተኛ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ ራሔልም ፦ ብርቱ ፡ ትግልን ፡ ከእኅቴ ፡ ጋራ ፡ ታገልኹ ፥ አሸነፍኹም ፡ አለች ፤ ስሙንም ፡ ንፍታሌም ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ ልያም ፡ መውለድን ፡ እንዳቆመች ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ባሪያዋን ፡ ዘለፋን ፡ ወሰደች ፥ ሚስት ፡ ትኾነውም ፡ ዘንድ ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጠችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ የልያ ፡ ባሪያ ፡ ዘለፋም ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ ልያም ፦ ጕድ ፡ አለች ፤ ስሙንም ፡ ጋድ [41] ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ የልያ ፡ ባሪያ ፡ ዘለፋም ፡ ዳግመኛ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ልያም ፦ ደስታ ፡ ኾነልኝ ፤ ሴቶች ፡ ያመሰግኑኛልና ፥ አለች ፤ ስሙንም ፡ አሴር ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ሮቤል ፡ ስንዴ ፡ በሚታጨድበት ፡ ወራት ፡ ወጣ ፥ በዕርሻም ፡ እንኮይ ፡ አገኘ ፥ ለእናቱ ፡ ለልያም ፡ አመጣላት ። ራሔልም ፡ ልያን ፦ የልጅሽን ፡ እንኮይ ፡ ስጪኝ ፡ አለቻት ።

---

38 ዕብ. ፥ ሽምዖን ፡ (ሰምዐኒ • ሰማኝ) ።

39 ዕብ. ፥ ይሁዳህ ፡ (አማኒ • አማኝ) ።

40 ዕብ. ፥ ዳን ፡ (ደየነ • ፈረደ) ።

41 ዕብ. ፥ ጋድ ፡ (ገድ ፥ ጋዳ ፥ በረከት ፥ እጅ ፡ መንሻ) ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ርሷም ፦ ባሌን ፡ መውሰድሽ ፡ በእውኑ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ነውን ፧ አኹን ፡ ደግሞ ፡ የልጄን ፡ እንኮይ ፡ ልትወስጂ ፡ ትፈልጊያለሽን ፧ አለቻት ። ራሔልም ፦ እንኪያስ ፡ ስለልጅሽ ፡ እንኮይ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይተኛ ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ ያዕቆብም ፡ ሲመሽ ፡ ከዱር ፡ ገባ ፥ ልያም ፡ ልትቀበለው ፥ ወጣች ፡ እንዲህም ፡ አለችው ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ትገባለኽ ፤ በልጄ ፡ እንኮይ ፡ በርግጥ ፡ ተከራይቼኻለኹና ። በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ተኛ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የልያን ፡ ጸሎት ፡ ሰማ ፥ ፀነሰችም ፥ ዐምስተኛ ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ ልያም ፦ ባሪያዬን ፡ ለባሌ ፡ ስለ ፡ ሰጠኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዋጋዬን ፡ ሰጠኝ ፡ አለች ፤ ስሙንም ፡ ይሳኮር ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ ልያም ፡ ደግማ ፡ ፀነሰች ፥ ስድስተኛ ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ ልያም ፦ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ ስጦታን ፡ ሰጠኝ ፤ እንግዲህስ ፡ ባሌ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ፥ ስድስት ፡ ልጆችን ፡ ወልጄለታለኹና ፡ አለች ፤ ስሙንም ፡ ዛብሎን ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 21 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሴት ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፥ ስሟንም ፡ ዲና ፡ አለቻት ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ራሔልን ፡ ዐሰበ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ተለመናት ፥ ማሕፀኗንም ፡ ከፈተላት ፤

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 23 ፤ ፀነሰችም ፥ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደችና ፦ እግዚአብሔር ፡ ስድቤን ፡ አስወገደ ፡ አለች ፤

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 24 ፤ ስሙንም ፦ እግዚአብሔር ፡ ኹለተኛ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ይጨምርልኝ ፡ ስትል ፡ ዮሴፍ ([42]) ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 25 ፤ ራሔልም ፡ ዮሴፍን ፡ ከወለደች ፡ በኋላ ፡ ያዕቆብ ፡ ላባን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ስፍራዬ ፡ ወደ ፡ አገሬም ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብተኝ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ ስለ ፡ እነርሱ ፡ የተገዛኹላቸውን ፡ ሚስቶቼንና ፡ ልጆቼን ፡ ስጠኝና ፡ ልኺድ ፤ የተገዛኹልኽን ፡ መገዛት ፡ ታውቃለኽና ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 27 ፤ ላባም ፦ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ የማገኝ ፡ ብኾንስ ፡ ከዚሁ ፡ ተቀመጥ ፤ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ባረከኝ ፡ ተመልክቻለኹና ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 28 ፤ ደመ ፡ ወዝኽን ፡ ንገረኝ ፥ ርሱንም ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 29 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ እንዴት ፡ እንዳገለገልኹኽ ፥ ከብትኽንም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጠበቅኹልኽ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 30 ፤ ከእኔ ፡ መምጣት ፡ በፊት ፡ የነበረኽ ፡ ጥቂት ፡ ነበርና ፥ ዛሬም ፡ እጅግ ፡ በዛ ፤ ወዳንተ ፡ በመምጣቴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ባረከኽ ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ለቤቴ ፡ የምሠራው ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 31 ፤ ርሱም ፦ የምሰጥኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ። ያዕቆብም ፡ አለው ፦ ምንም ፡ አትስጠኝ ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ብታደርግልኝ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በጎችኽን ፡ አበላለኹ ፡ እጠብቃለኹም ።

---

42 ዕብ. ፡ ዮሴፍ ፡ (ይስፋ ፥ ይበርክት ፥ ይብዛ) ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 32 ፤ ዛሬ ፡ በመንጋዎችኽ ፡ በኩል ፡ ዐልፋለኹ ፥ በዚያም ፡ ከበጎችኽ ፡ መካከል ፡ ዝንጉርጉርና ፡ ነቍጣ ፡ ያለበቱን ፡ ጥቍሩንም ፡ በግ ፡ ኹሉ ፥ ከፍየሎቹም ፡ ነቍጣና ፡ ዝንጉርጉር ፡ ያለበቱን ፡ እለያለኹ ፤ እነርሱም ፡ ደመ ፡ ወዜ ፡ ይኾናሉ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 33 ፤ ስለዚህም ፡ በፊትኽ ፡ ያለውን ፡ ደመ ፡ ወዜን ፡ ለመመልከት ፡ በመጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ጻድቅነቴ ፡ ይመሰክርልኛል ፤ ከፍየሎች ፡ ዝንጉርጉርና ፡ ነቍጣ ፡ የሌለበት ፡ ከበግ ፡ ጠቦቶችም ፡ ጥቍር ፡ ያልኾኑ ፡ ኹሉ ፥ ርሱ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ቢገኝ ፡ እንደ ፡ ተሰረቀ ፡ ይቈጠርብኝ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 34 ፤ ላባም ፦ እንሆ ፥ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ይኹን ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 35 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከተባቶቹ ፡ ፍየሎች ፡ ሽመልመሌ ፡ መሳይና ፡ ነቍጣ ፡ ያለባቸውን ፥ ከእንስቶቹም ፡ ፍየሎች ፡ ዝንጉርጉርና ፡ ነቍጣ ፡ ያለባቸውን ፥ ነጭ ፡ ያለበትን ፡ ማንኛውንም ፡ ኹሉ ፥ ከበጎቹም ፡ መካከል ፡ ጥቍሩን ፡ በግ ፡ ኹሉ ፡ ለይቶ ፡ ለልጆቹ ፡ ሰጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 36 ፤ በርሱና ፡ በያዕቆብ ፡ መካከልም ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ አራቃቸው ፤ ያዕቆብም ፡ የቀሩትን ፡ የላባን ፡ በጎች ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 37 ፤ ያዕቆብም ፡ ልብን ፣ ለውዝ ፣ ኤርሞን ፡ ከሚባሉ ፡ ዕንጨቶች ፡ ርጥብ ፡ በትርን ፡ ወስዶ ፥ በበትሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ነጭ ፡ እንዲታይ ፥ ነጭ ፡ ሽመልመሌ ፡ አድርጎ ፡ ላጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 38 ፤ የላጣቸውንም ፡ በትሮች ፡ በጎቹ ፡ ውሃ ፡ ሊጠጡ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በውሃ ፡ ማጠጫው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ በበጎቹ ፡ ፊት ፡ አኖራቸው ፤ በጎቹ ፡ ውሃ ፡ ሊጠጡ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ይጐመዝዙ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 39 ፤ በጎቹም ፡ በትሮቹን ፡ አይተው ፡ ከመጐምዠታቸው ፡ የተነሣ ፡ ፀነሱ ፤ በጎቹም ፡ ሽመልመሌ ፡ መሳይና ፡ ዝንጉርጉር ፡ ነቍጣም ፡ ያለበቱን ፡ ወለዱ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 40 ፤ ያዕቆብም ፡ ጠቦቶቹን ፡ ለየ ፥ ሽመልመሌ ፡ መሳይና ፡ ጥቍር ፡ ያለባቸውን ፡ በጎቹንም ፡ ኹሉ ፡ በላባ ፡ በጎች ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አኖረ ፤ መንጋዎቹንም ፡ ለብቻቸው ፡ አቆማቸው ፥ ወደላባም ፡ በጎች ፡ አልጨመራቸውም ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 41 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የበረቱት ፡ በጎች ፡ በጐመዝዙ ፡ ጊዜ ፥ በጎቹ ፡ በትሮቹን ፡ አይተው ፡ በበትሮቹ ፡ አምሳል ፡ ይፀንሱ ፡ ዘንድ ፡ ያዕቆብ ፡ በትሮቹን ፡ በውሃ ፡ ማጠጫው ፡ ገንዳ ፡ ውስጥ ፡ ከበጎቹ ፡ ፊት ፡ አደረገ ፤

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 42 ፤ በደከሙ ፡ በጎችም ፡ ፊት ፡ በትሩን ፡ አያደርገውም ፡ ነበር ፤ የደከሙትም ፡ ለላባ ፥ የበረቱትም ፡ ለያዕቆብ ፡ ኾኑ ።

ዘፍ. ፡ 30 ፡ 43 ፤ ያ ፡ ሰውም ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ኾነ ፤ ብዙም ፡ ከብት ፡ ሴቶችም ፡ ወንዶችም ፡ ባሪያዎች ፡ ግመሎችም ፡ አህያዎችም ፡ ኾኑለት ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ። _____

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ የላባ ፡ ልጆች ፡ ያሉትን ፡ ነገር ፦ ያዕቆብ ፡ ለአባታችን ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፤ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ ክብር ፡ ከአባታችን ፡ ከብት ፡ አገኘ ፡ ሲሉ ፡ ሰማ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ ያዕቆብም ፡ የላባን ፡ ፊት ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ አልኾነም ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዕቆብን ፦ ወዳባትኽ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ዘመዶችኽም ፡ ተመለስ ፤ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ ያዕቆብም ፡ ልኮ ፡ ራሔልንና ፡ ልያን ፡ ወደበጎቹ ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ጠራቸው ፥

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ እንዲሀም ፡ አላቸው ፦ የአባታችኹ ፡ ፊት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ እንዳልኾነ ፡ አያለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቴ ፡ አምላክ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ባለኝ ፡ ጕልበቴ ፡ ኹሉ ፡ አባታችኹን ፡ እንዳገለገልኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ አባታችኹ ፡ ግን ፡ አታለለኝ ፥ ደመ ፡ ወዜንም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ለወጠ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ያደርግብኝ ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደለትም ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ ደመ ፡ ወዝኽ ፡ ዝንጉርጉሮች ፡ ይኹኑ ፡ ቢለኝ ፡ በጎቹ ፡ ኹሉ ፡ ዝንጉርጉሮችን ፡ ወለዱ ፤ ሽመልመሌ ፡ መሳዮቹ ፡ ደመ ፡ ወዝኽ ፡ ይኹኑ ፡ ቢለኝ ፡ በጎቹ ፡ ኹሉ ፡ ሽመልመሌ ፡ መሳዮችን ፡ ወለዱ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የአባታችኹን ፡ በጎች ፡ ኹሉ ፡ ነሥቶ ፡ ለእኔ ፡ ሰጠኝ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 10 ፤ እንዲሀም ፡ ኾነ ፤ በጎቹ ፡ በጕመገቡ ፡ ጊዜ ፡ ዐይኔን ፡ አንሥቼ ፡ በሕልም ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ በበጎችና ፡ በፍየሎች ፡ ላይ ፡ የሚንጠላጠሉት ፡ የበጎችና ፡ የፍየሎች ፡ አውራዎች ፡ ሽመልመሌ ፡ መሳዮችና ፡ ዝንጉርጉሮች ፡ ነቀጣ ፡ ያለባቸውም ፡ ነበሩ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፦ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፡ አለኝ ፤ እኔም ፦ እንሆኝ ፡ አልኹት ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 12 ፤ እንዲሀም ፡ አለኝ ፦ ዐይንኽን ፡ አቅንተኽ ፡ እይ ፤ በበጎችና ፡ በፍየሎች ፡ ላይ ፡ የሚንጠላጠሉት ፡ ዘፍ. ፡ 31 ፡ የበጎችና ፡ የፍየሎች ፡ አውራዎች ፡ ሽመልመሌ ፡ መሳዮችና ፡ ዝንጉርጉሮች ፡ ነቀጣ ፡ ያለባቸውም ፡ ናቸው ፤ ላባ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ ኹሉ ፡ አይቻለኹና ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ ሐውልት ፡ የቀባኽበት ፡ በዚያም ፡ ለእኔ ፡ ስእለት ፡ የተሳልኽበት ፡ የቤቴል ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ አኹንም ፡ ተነሥተኽ ፡ ከዚህ ፡ አገር ፡ ውጣ ፥ ወደ ፡ ተወለድኽበትም ፡ ምድር ፡ ተመለስ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 14 ፤ ራሔልና ፡ ልያም ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ በአባታችን ፡ ቤት ፡ ለእኛ ፡ ድርሻና ፡ ርስት ፡ በእውኑ ፡ ቀርቶልናልን ፧

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ እኛ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ባዕድ ፡ የተቈጠርን ፡ አይደለንምን ፧ ርሱ ፡ እኛን ፡ ሸጦ ፡ ዋጋችንን ፡ በልቷልና ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ የነሣው ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ሀብት ፡ ለእኛና ፡ ለልጆቻችን ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ ያዕቆብም ፡ ተነሣ ፥ ልጆቹንና ፡ ሚስቶቹንም ፡ በግመሎች ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ ፤

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ መንጋዎቹንም ፡ ኹሉ ፥ የቤቱንም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥ በኹለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡ ያገኛቸውን ፡ ከብቶች ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይሥሐቅ ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 19 ፤ ላባ ፡ ግን ፡ በጎቹን ፡ ለመሸለት ፡ ኼዶ ፡ ነበር ፤ ራሔልም ፡ የአባቷን ፡ ተራፊም ፡ ሰረቀች ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 20 ፤ ያዕቆብም ፡ የሶርያውን ፡ ሰው ፡ ላባን ፡ ከድቶ ፡ ከመበለ ፥ መከመበለሉንም ፥ አልነገረውም ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ ከመበለ ፤ ተነሥቶም ፡ ወንዙን ፡ ተሻገረ ፥ ፊቱንም ፡ ወደገለዓድ ፡ ተራራ ፡ አቀና ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 22 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የያዕቆብ ፡ መከመበለ ፡ ለላባ ፡ ተነገረው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 23 ፤ ከወንድሞቹም ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ የሰባት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ ተከተለው ፥ በገለዓድ ፡ ተራራም ፡

ላይ ፡ ደረሰበት ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወደሶርያው ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ላባ ፡ በሌሊት ፡ ሕልም ፡ መጥቶ ፦ ያዕቆብን ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳትናገረው ፡ ተጠንቀቅ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 25 ፤ ላባም ፡ ደረሰበት ፤ ያዕቆብም ፡ ድንኳኑን ፡ በተራራው ፡ ተክሎ ፡ ነበር ፤ ላባም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ በገለዓድ ፡ ተራራ ፡ ድንኳኑን ፡ ተከለ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 26 ፤ ላባም ፡ ያዕቆብን ፡ አለው ፦ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረግኽ ፧ ከእኔ ፡ ከድተኽ ፡ ከሐበለልኽ ፥ ልጆቼንም ፡ በሰይፍ ፡ እንደተማረኩ ፡ ዐይነት ፡ ነዳኻቸው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 27 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ በስውር ፡ ሸሸኽ ፧ ከእኔም ፡ ከድተኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ከሐበለልኽ ፧ በደስታና ፡ በዘፈን ፡ በከበሮና ፡ በበገና ፡ እንድሰድኽ ፡ ለምን ፡ አልነገርኸኝም ፧

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 28 ፤ ወንዶቹንና ፡ ሴቶቹን ፡ ልጆቼን ፡ እንድስም ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልፈቀድኽልኝም ፧ ይህንም ፡ በስንፍና ፡ አደረግኽ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 29 ፤ ክፉ ፡ አደርግባችኹ ፡ ዘንድ ፥ ኀይል ፡ ነበረኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባታችኹ ፡ አምላክ ፡ ትናንት ፥ ያዕቆብን ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ እንዳትናገረው ፡ ተጠንቀቅ ፡ ብሎ ፡ ነገረኝ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 30 ፤ አኹንም ፡ የአባትኽን ፡ ቤት ፡ ከናፈቅኽ ፡ ኺድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላኮቼን ፡ ለምን ፡ ሰረቅኽ ፧

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 31 ፤ ያዕቆብም ፡ መለሰ ፥ ላባንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ልጆችኽን ፡ ከእኔ ፡ የምትቀማኝ ፡ ስለ ፡ መሰለኝና ፡ ስለ ፡ ፈራኹ ፡ ይህን ፡ አደረግኹ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 32 ፤ አምላኮችኽን ፡ የምታገኝበት ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይሙት ፤ የአንተ ፡ የኾነውም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይገኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በወንድሞቻችን ፡ ፊት ፡ ፈልግ ፥ ለአንተም ፡ ውሰደው ፡ አለ ። ራሔል ፡ እንደ ፡ ሰረቀቻቸው ፡ ያዕቆብ ፡ አያውቅም ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 33 ፤ ላባም ፡ ወደያዕቆብ ፡ ድንኳንና ፡ ወደልያ ፡ ድንኳን ፡ ወደኹለቱም ፡ ባሪያዎች ፡ ድንኳን ፡ ገባ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላገኘም ። ከልያም ፡ ድንኳን ፡ ወጥቶ ፡ ወደራሔል ፡ ድንኳን ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 34 ፤ ራሔልም ፡ ተራፊምን ፡ ወስዳ ፡ ከግመል ፡ ኮርቻ ፡ በታች ፡ ሸሸገች ፥ በላዩም ፡ ተቀመጠችበት ። ላባም ፡ ድንኳኑን ፡ ኹሉ ፡ ፈለገ ፥ አንዳችም ፡ አላገኘም ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 35 ፤ ርሷም ፡ አባቷን ፦ በፊትኽ ፡ ለመቆም ፡ ስላልቻልኹ ፡ አትቈጣብኝ ፤ በሴቶች ፡ የሚደርስ ፡ ግዳጅ ፡ ደርሶብኛልና ፥ አለችው ። ርሱም ፡ ፈለገ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ተራፊምን ፡ አላገኘም ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 36 ፤ ያዕቆብም ፡ ተቈጣ ፥ ላባንም ፡ ወቀሰው ፤ ያዕቆብም ፡ መለሰ ፥ ላባንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ የበደልኹኝ ፡ በደል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ኀጢአቴስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፥ ይህን ፡ ያኽል ፡ ያሳደድኸኝ ፧

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 37 ፤ አኹንም ፡ ዕቃዬን ፡ ኹሉ ፡ በረበርኽ ፤ ከቤትኽስ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ምን ፡ አገኘኽ ፧ እነርሱ ፡ በእኛ ፣ በኹለታችን ፡ መካከል ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ በወንድሞቼና ፡ በወንድሞችኽ ፡ ፊት ፡ አቅርበው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 38 ፤ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነበርኹ ፤ በጎችኽና ፡ ፍየሎችኽ ፡ አልጨነገፉም ፤ የመንጋዎችኽንም ፡ ጠቦቶች ፡ አልበላኹም ፤ አውሬ ፡ የሰበረውን ፡ አላመጣኹልኽም ፡ ነበር ፤

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 39 ፤ እኔ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እከፍልኽ ፡ ነበር ፤ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ የተሰረቀውን ፡ ከእጄ ፡ ትሻው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 40 ፤ የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊት ፡ ቍር ፡ ይበላኝ ፡ ነበር ፥ እንቅልፍም ፡ ከዐይኔ ፡ ጠፋ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 41 ፤ እንዲሁ ፡ ባንተ ፡ ቤት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ነበርኹ ፤ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ስለ ፡ ኹለቱ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽ ፥ ስድስት ፡ ዓመትም ፡ ስለ ፡ በጎችኽ ፡ ተገዛኹልኽ ፤ ደመ ፡ ወዜንም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ለዋወጥኸው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 42 ፤ የአባቴ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፣ የይሥሐቅም ፡ ፍርሀት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ባይኾንስ ፥ ዛሬ ፡ ባዶ ፡ እጄን ፡ በሰደድኸኝ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ መከራዬንና ፡ የእጆቼን ፡ ድካም ፡ አየ ፥ ትናንትም ፡ ገሠጸኽ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 43 ፤ ላባም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለያዕቆብ ፡ መለሰለት ፦ ሴቶቹ ፡ ልጆች ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፥ ሕፃናቱም ፡ ሕፃናቴ ፡ ናቸው ፥ መንጋዎቹም ፡ መንጋዎቼ ፡ ናቸው ፥ የምታየውም ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ ዛሬም ፡ በእነዚህ ፡ በሴቶች ፡ ልጆቼና ፡ በወለዷቸው ፡ ልጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ላደርግ ፡ ይቻላል ፧

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 44 ፤ አኹንም ፡ ና ፥ አንተና ፡ እኔ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንጋባ ፤ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከልም ፡ ምስክር ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 45 ፤ ያዕቆብም ፡ ድንጋይ ፡ ወስዶ ፡ ሐውልት ፡ አቆመ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 46 ፤ ያዕቆብም ፡ ወንድሞቹን ፦ ድንጋይ ፡ ሰብስቡ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ ድንጋይ ፡ ሰብስበው ፡ ከመሩ ፤ በድንጋዩም ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ በሉ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 47 ፤ ላባም ፡ ይጋር ፡ ሠሀዱታ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ፤ ያዕቆብም ፡ ገለዓድ ፡ አላት ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 48 ፤ ላባም ፦ ይህች ፡ ክምር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ዛሬ ፡ ምስክር ፡ ናት ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ ስሟ ፡ ገለዓድ ፡ ተባለ ፤

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 49 ፤ ደግሞም ፡ ምጽጳ ፡ ተባለ ፦ እኛ ፡ በተለያየን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ኾኖ ፡ ይጠብቅ ፡ ብሏልና ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 50 ፤ ልጆቼን ፡ ብትበድላቸው ፡ ወይም ፡ በላያቸው ፡ ሚስቶችን ፡ ብታገባባቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የለም ፤ እግዚአብሔር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 51 ፤ ላባም ፡ ያዕቆብን ፡ አለው ፦ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፥ እንሆ ፥ ይህች ፡ ክምር ፥ እንሆም ፡ ያቆምኋት ፡ ሐውልት ፤

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 52 ፤ እኔ ፡ ወዳንተ ፡ ይህችን ፡ ክምር ፡ እንዳላልፍ ፥ አንተም ፡ ለክፋት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይህችን ፡ ክምርና ፡ ይህችን ፡ ሐውልት ፡ እንዳታልፋት ፥ ይህች ፡ ክምር ፡ ምስክር ፡ ናት ፥ ይህችም ፡ ሐውልት ፡ ምስክር ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 53 ፤ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የናኮርም ፡ አምላክ ፡ የአባታቸውም ፡ አምላክ ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ ይፍረድ ። ያዕቆብም ፡ በአባቱ ፡ በይሥሐቅ ፡ ፍርሀት ፡ ማለ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 54 ፤ ያዕቆብም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ መሥዋዕትን ፡ ሠዋ ፥ ወንድሞቹንም ፡ እንጀራ ፡ እንዲበሉ ፡ ጠራ ፤ እነርሱም ፡ እንጀራን ፡ በሉ ፥ በዚያም ፡ በተራራ ፡ ዐደሩ ።

ዘፍ. ፡ 31 ፡ 55 ፤ ላባም ፡ ማልዶ ፡ ተነሥቶ ፡ ወንዶቹንና ፡ ሴቶቹን ፡ ልጆቹን ፡ ሳመ ፡ ባረካቸውም ፤ ላባም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ኼደ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መላእክትም ፡ ተገናኙት ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ ያዕቆብም ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፦ እነዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰራዊት ፡ ናቸው ፡ አለ ፤ የዚያንም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ መሃናይም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ወንድሙ ፡ ወደ ፡ ዔሳው ፡ ወደሴይር ፡ ምድር ፡ ወደኤዶም ፡ አገር ፡ ከፊቱ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፦ ለጌታዬ ፡ ለዔሳው ፦ ባሪያኽ ፡ ያዕቆብ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ በላባ ፡ ዘንድ ፡ በስደት ፡ ተቀመጥኩ ፤ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ቈየኹ ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ ላሞችንም ፡ አህያዎችንም ፡ በጎችን ፡ ወንዶች ፡ ባሪያዎችንም ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችንም ፡ አገኘኹ ፤ አኹንም ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስን ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ ለጌታዬ ፡ ለማስታወቅ ፡ ላክኹ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ መልእክተኞቹም ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ ወደ ፡ ወንድምኽ ፡ ወደ ፡ ዔሳው ፡ ኼደን ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ሊቀበልኽ ፡ ይመጣል ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ ያዕቆብም ፡ እጅግ ፡ ፈርቶ ፡ ተጨነቀ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ መንጋዎችንም ፡ ላሞችንም ፡ ግመሎችንም ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ከፈላቸው ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ዔሳው ፡ መጥቶ ፡ አንዱን ፡ ወገን ፡ የመታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የቀረው ፡ ወገን ፡ ያመልጣል ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ ያዕቆብም ፡ አለ ፦ የአባቴ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የአባቴም ፡ የይሥሐቅ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ። ወደ ፡ ምድርኽ ፡ ወደተወለድኽበትም ፡ ስፍራ ፡ ተመለስ ፥ በጎነትንም ፡ አደርግልኻለኹ ፡ ያልኸኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ ለባሪያኽ ፡ ከሠራኸው ፡ ከምሕረትኽና ፡ ከእውነትኽም ፡ ዅሉ ፡ ትንሽ ፡ ስንኳ ፡ የማይገባኝ ፡ ነኝ ፤ በትሬን ፡ ብቻ ፡ ይዤ ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግሬ ፡ ነበርና ፥ አኹን ፡ ግን ፡ የኹለት ፡ ክፍል ፡ ሰራዊት ፡ ኾንኹ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ ከወንድሜ ፡ ከዔሳው ፡ እጅ ፡ አድነኝ ፤ መጥቶ ፡ እንዳያጠፋኝ ፥ እናቶችንም ፡ ከልጆች ፡ ጋራ ፡ እንዳያጠፋ ፡ እኔ ፡ እፈራዋለኹና ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ አንተም ፦ በርግጥ ፡ መልካም ፡ አደርግልኻለኹ ፥ ዘርኽንም ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ እንደማይቈጠር ፡ እንደባሕር ፡ አሸዋ ፡ አደርጋለኹ ፡ ብለኽ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ከዚያው ፡ ዐደረ ። ከያዘውም ፡ ዅሉ ፡ ለወንድሙ ፡ ለዔሳው ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ አወጣ ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ ኹለት ፡ መቶ ፡ እንስት ፡ ፍየሎችንና ፡ ኻያ ፡ የፍየል ፡ አውራዎችን ፥ ኹለት ፡ መቶ ፡ እንስት ፡ በጎችንና ፡ ኻያ ፡ የበግ ፡ አውራዎችን ፥

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ ሠላሳ ፡ የሚያጠቡ ፡ ግመሎችን ፡ ከግልገሎቻቸው ፡ ጋራ ፥ አርባ ፡ ላም ፥ ዐሥር ፡ በሬ ፥ ኻያ ፡ እንስት ፡ አህያ ፥ ዐሥርም ፡ የአህያ ፡ ግልገሎችን ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ መንጋዎቹን ፡ በየወገኑ ፡ ከፍሎ ፡ በባሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ አደረጋቸው ፤ ባሪያዎቹንም ፦ በፊቴ ፡ ዕለፉ ፡ መንጋውንና ፡ መንጋውንም ፡ አራርቁት ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ የፊተኛውንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፦ ወንድሜ ፡ ዔሳው ፡ ያገኘኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፦ አንተ ፡ የማን ፡ ነኽ ፧ ወዴትስ ፡ ትኼዳለኽ ፧ በፊትኽ ፡ ያለው ፡ ይህስ ፡ የማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ የጠየቀኽም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፦ ለጌታዬ ፡ ለዔሳው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሰደደው ፡ የባሪያኽ ፡ የያዕቆብ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፥ እንሆ ፥ ከኋላችን ፡ ነው ፡ በለው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ እንዲሁም ፡ ኹለተኛውንና ፡ ሦስተኛውን ፡ ከመንጋዎችም ፡ በኋላ ፡ የሚኼዱትን ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፦ ዔሳውን ፡ ባገኛችኹት ፡ ጊዜ ፡ ይህንኑ ፡ ነገር ፡ ንገሩት ፤

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ እንዲሀም ፡ በሉት ፦ እንሆ ፥ ባሪያኽ ፡ ያዕቆብ ፡ ከኋላችን ፡ ነው ። በፊቴ ፡ በሚኼደው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ እታረቀዋለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ምናልባት ፡ ይራራልኛል ፡ ፊቱንም ፡ አያለኹ ፡ ብሏልና ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 21 ፤ እጅ ፡ መንሻው ፡ ከርሱ ፡ ቀድሞ ፡ ዐለፈ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ በሰፈር ፡ ዐደረ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 22 ፤ በዚያች ፡ ሌሊትም ፡ ተነሣ ፥ ኹለቱን ፡ ሚስቶቹንና ፡ ኹለቱን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ዐሥራ ፡ አንዱንም ፡ ልጆቹን ፡ ወስዶ ፡ የያቦቅን ፡ ወንዝ ፡ ተሻገረ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 23 ፤ ወሰዳቸውም ፡ ወንዙንም ፡ አሻገራቸው ፥ ከብቱንም ፡ ኹሉ ፡ አሻገረ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 24 ፤ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ ለብቻው ፡ ቀረ ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ እስከ ፡ ንጋት ፡ ድረስ ፡ ይታገለው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 25 ፤ እንዳላሸነፈውም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የጭኑን ፡ ሹልዳ ፡ ነካው ፤ ያዕቆብም ፡ የጭኑ ፡ ሹልዳ ፡ ሲታገለው ፡ ደነዘዘ ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 26 ፤ እንዲሀም ፡ አለው ፦ ሊነጋ ፡ አቀላልቷልና ፥ ልቀቀኝ ። ርሱም ፦ ካልባረክኸኝ ፡ አልለቅኽም ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 27 ፤ እንዲሀም ፡ አለው ፦ ስምኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱም ፦ ያዕቆብ ፡ ነኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 28 ፤ አለውም ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስምኽ ፡ እስራኤል ፡ ይባል ፡ እንጂ ፡ ያዕቆብ ፡ አይባል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከሰውም ፡ ጋራ ፡ ታግለኽ ፡ አሸንፈኻልና ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 29 ፤ ያዕቆብም ፦ ስምኽን ፡ ንገረኝ ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ርሱም ፦ ስሜን ፡ ለምን ፡ ትጠይቃለኽ ፧ አለው ። በዚያም ፡ ስፍራ ፡ ባረከው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 30 ፤ ያዕቆብም ፦ እግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አየኹ ፥ ሰውነቴም ፡ ድና ፡ ቀረች ፡ ሲል ፡ የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ጵኒኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 31 ፤ ጵኒኤልንም ፡ ሲያልፍ ፡ ፀሓይ ፡ ወጣችበት ፥ ርሱም ፡ በጭኑ ፡ ምክንያት ፡ ያነክስ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 32 ፡ 32 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የወርችን ፡ ሹልዳ ፡ አይበሉም ፤ የያዕቆብን ፡ ጭን ፡ ይዞ ፡ የወርችን ፡ ሹልዳ ፡ አደንዝዟልና ።

[ቀ.30 ፤ ጵኒኤል ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ የግእዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ራእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይለዋል ።]

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ። _____

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ ዐይኑን ፡ አነሣ ፥ እንሆም ፡ ዔሳውን ፡ ሲመጣ ፡ አየው ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ልጆቹንም ፡ ከፍሎ ፡ ወደ ፡ ልያና ፡ ወደ ፡ ራሔል ፡ ወደ ፡ ኹለቱም ፡ ባሪያዎች ፡ አደረጋቸው ፤

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 2 ፤ ባሪያዎችንና ፡ ልጆቻቸውንም ፡ በፊት ፡ አደረገ ፥ ልያንና ፡ ልጆቿንም ፡ በኋለኛው ፡ ስፍራ ፥ ራሔልንና ፡ ዮሴፍንም ፡ ከኹሉ ፡ በኋላ ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በፊታቸው ፡ ዐለፈ ፤ ወደ ፡ ወንድሙም ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰገደ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ ዔሳውም ፡ ሊገናኘው ፡ ሮጠ ፥ ዐንገቱንም ፡ ዐቅፎ ፡ ሳመው ፤ ተላቀሱም ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ ዐይኑንም ፡ አነሣና ፡ ሴቶችንና ፡ ልጆችን ፡ አየ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ እነዚህ ፡ ምኖችኽ ፡ ናቸው ፧ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ የሰጠኝ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ቀርበው ፡ ሰገዱ ፤

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ ደግሞም ፡ ልያና ፡ ልጆቿ ፡ ቀርበው ፡ ሰገዱ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዮሴፍና ፡ ራሔል ፡ ቀርበው ፡ ሰገዱ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ ያገኘኹት ፡ ይህ ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ምንኽ ፡ ነው ፧ አለ ። ርሱም ፦ በጌታዬ ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ዔሳውም ፦ ለእኔ ፡ ብዙ ፡ አለኝ ፤ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ የአንተ ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ ያዕቆብም ፡ አለ ፦ እንደዚህ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፊትኽ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እጅ ፡ መንሻዬን ፡ ተቀበለኝ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ እንደሚያይ ፡ ፊትኽን ፡ አይቻለኹና ፥ በቸርነትም ፡ ተቀብለኸኛልና ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ ይህችንም ፡ ያመጣኹልኽን ፡ በረከቴን ፡ ተቀበል ፤ እግዚአብሔር ፡ በቸርነት ፡ ሰጥቶኛልና ፥ ለኔም ፡ ብዙ ፡ አለኝና ። እስኪቀበለውም ፡ ድረስ ፡ ዘበዘበው ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 12 ፤ ርሱም ፦ ተነሣና ፡ እንኺድ ፥ እኔም ፡ በፊትኽ ፡ እኼዳለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ልጆቹ ፡ ደካማዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ታውቃለኽ ፤ በጎችና ፡ ላሞችም ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ ያጠባሉ ፤ ሰዎችም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በችኮላ ፡ የነዷቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከብቶቹ ፡ ኹሉ ፡ ይሞታሉ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ ጌታዬ ፡ ከባሪያው ፡ ፊት ፡ ቀድሞ ፡ ይለፍ ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ሴይር ፡ ከጌታዬ ፡ ዘንድ ፡ እስክደርስ ፡ ድረስ ፡ ከፊቴ ፡ ባሉት ፡ በእንስሳቱ ፡ ርምጃና ፡ በሕፃናቱ ፡ ርምጃ ፡ መጠን ፡ በዝግታ ፡ እከተላለኹ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ ዔሳውም ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ከፍዬ ፡ ልተውልኽን ፧ አለ ። ርሱም ፦ ይህ ፡ ለምንድር ፡ ነው ፧ በጌታዬ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስን ፡ ማግኘት ፡ ይበቃኛል ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ ዔሳውም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሴይር ፡ መንገዱን ፡ ተመለሰ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ ያዕቆብ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሱኮት ፡ ኼደ ፤ በዚያም ፡ ለርሱ ፡ ቤትን ፡ ሠራ ፥ ለከብቶችም ፡ ዳሶችን ፡ አደረገ ፤ ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ሱኮት ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ያዕቆብም ፡ ከኹለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ከተማ ፡ በደኅንነት ፡ መጣ ፤ በከተማዪቱም ፡ ፊት ፡ ሰፈረ ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ ድንኳኑን ፡ ተክሎበት ፡ የነበረውንም ፡ የዕርሻውን ፡ ክፍል ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡ ከኤሞር ፡ ልጆች ፡ በመቶ ፡ በጎች ፡ ገዛው ።

ዘፍ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ መሠዊያውን ፡ አቆመ ፥ ያንም ፡ ኤል ፡ ኤሎሄ ፡ እስራኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። _____

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 1 ፤ ለያዕቆብ ፡ የወለደችለት ፡ የልያ ፡ ልጅ ፡ ዲናም ፡ የዚያን ፡ አገር ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ለማየት ፡ ወጣች ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 2 ፤ የአገሩ ፡ አለቃ ፡ የዔዊያዊ ፡ ሰው ፡ የኤሞር ፡ ልጅ ፡ ሴኬም ፡ አያት ፤ ወሰዳትም ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ተኛ ፥ አስነወራትም ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 3 ፤ ልቡናውም ፡ በያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ በዲና ፡ ፍቅር ፡ ተነደፈ ፥ ብላቴናዪቱንም ፡ ወደዳት ፥ ልቧንም ፡ ደስ ፡ በሚያሠኛት ፡ ነገር ፡ ተናገራት ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 4 ፤ ሴኬምም ፡ አባቱን ፡ ኤሞርን ፦ ይህችን ፡ ብላቴና ፡ አጋባኝ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 5 ፤ ያዕቆብም ፡ ልጁን ፡ ዲናን ፡ እንዳስነወራት ፡ ሰማ ፤ ልጆቹም ፡ ከከብቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ነበሩ ፤ ያዕቆብም ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 6 ፤ የሴኬም ፡ አባት ፡ ኤሞርም ፡ ይነግረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 7 ፤ የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፤ የያዕቆብን ፡ ልጅ ፡ በመተኛቱ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ስንፍናን ፡ ስላደረገ ፡ ዐዘኑ ፥ እጅግም ፡ ተቈጡ ፤ እንዲህ ፡ አይደረግምና ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 8 ፤ ኤሞርም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፦ ልጄ ፡ ሴኬም ፡ በልጃችኹ ፡ ፍቅር ፡ ልቡ ፡ ተነድፏልና ፥ ሚስት ፡ እንድትኾነው ፡ እባካችኹ ፡ ርሷን ፡ ስጡት ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 9 ፤ ጋብቻዎችም ፡ ኹኑን ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ ስጡን ፥ እናንተም ፡ የእኛን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ውሰዱ ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 10 ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ተቀመጡ ፥ ምድሪቱም ፡ በፊታችኹ ፡ ናት ፤ ኑሩባት ፥ ነግዱም ፥ ግዟትም ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 11 ፤ ሴኬምም ፡ አባቷንና ፡ ወንድሞቿን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በፊታችኹ ፡ ሞገስን ፡ ባገኝ ፡ የምትሉኝን ፡ እሰጣለኹ ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 12 ፤ ብዙ ፡ ማጫና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ አምጣ ፡ በሉኝ ፥ በነገራችኹኝም ፡ መጠን ፡ እሰጣለኹ ፤ ይህችን ፡ ብላቴና ፡ ግን ፡ አጋቡኝ ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 13 ፤ የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ ለሴኬምና ፡ ለአባቱ ፡ ለኤሞር ፡ በተንኰል ፡ መለሱ ፥ እኅታቸውን ፡ ዲናን ፡ አርክሷታልና ፤

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 14 ፤ እንዲህም ፡ አሏቸው ፦ እኅታችንን ፡ ላልተገረዘ ፡ ሰው ፡ ለመስጠት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለንም ፤ ይህ ፡ ነውር ፡ ይኾንብናልና ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 15 ፤ እንደ ፡ እኛ ፡ ኾናችኹ ፡ ወንዶቻችኹን ፡ ኹሉ ፡ ብትገርዙ ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ ዕሺ ፡ እንላችኋለን ፤

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 16 ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻችንን ፡ እንሰጣችኋለን ፥ የእናንተንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንወስዳለን ፤ አንድ ፡ ሕዝብም ፡ ኾነን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንኖራለን ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 17 ፤ ትገረዙ ፡ ዘንድ ፡ እኛን ፡ ባትሰሙ ፡ ግን ፡ ልጃችንን ፡ ይዘን ፡ እንኼዳለን ።

ዘፍ. ፥ 34 ፥ 18 ፤ ነገራቸውም ፡ በኤሞር ፡ ልጅ ፡ በሴኬምና ፡ በኤሞር ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 19 ፤ ብላቴናውም ፡ ያሉትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አልዘገየም ፥ የያዕቆብን ፡ ልጅ ፡ ወዷልና ፤ ርሱም ፡ በአባቱ ፡ ቤት ፡ ካሉት ፡ ሹሉ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 20 ፤ ኤሞርና ፡ ሴኬም ፡ ልጁም ፡ ወደከተማቸው ፡ አደባባይ ፡ ገቡ ፥ ለከተማቸውም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ነገሩ ፦

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 21 ፤ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የሰላም ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ በምድራችን ፡ ይቀመጡ ፥ ይነግዱባትም ፥ እንሆም ፡ ምድሪቱ ፡ ሰፊ ፡ ናት ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ እንውሰድ ፥ ለእነርሱም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንን ፡ እንስጥ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ ኾነን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ዕሺ ፡ ይሉናል ፤ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተገረዙ ፡ ወንዶቻችንን ፡ ሹሉ ፡ ብንገርዝ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 23 ፤ ከብቶቻቸውም ፡ ያላቸውም ፡ ሹሉ ፡ እንስሳዎቻቸውም ፡ ሹሉ ፡ ለእኛ ፡ አይደሉምን ፧ በዚህ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ዕሺ ፡ ያልናቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጣሉ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 24 ፤ ከከተማዩቱም ፡ አደባባይ ፡ የሚወጡ ፡ ሹሉ ፡ ኤሞርንና ፡ ልጁን ፡ ሴኬምን ፡ ዕሺ ፡ አሉ ፤ ከከተማዩቱ ፡ አደባባይ ፡ የሚወጡት ፡ ወንዶች ፡ ሹሉ ፡ ተገረዙ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 25 ፤ ሦስተኛም ፡ ቀን ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ቈስለው ፡ ሳሉ ፥ የዲና ፡ ወንድሞች ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ስምዖንና ፡ ሌዊ ፡ እየራሳቸው ፡ ሰይፋቸውን ፡ ይዘው ፡ ሳይፈሩ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገቡ ፥ ወንዱንም ፡ ሹሉ ፡ ገደሉ ፤

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 26 ፤ ኤሞርንና ፡ ልጁን ፡ ሴኬምንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉ ፥ እኅታቸውን ፡ ዲናንም ፡ ከሴኬም ፡ ቤት ፡ ይዘው ፡ ወጡ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 27 ፤ የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ እኅታቸውን ፡ ዲናን ፡ ሰለ ፡ አረከሷት ፡ ወደሞቱት ፡ ገብተው ፡ ከተማዩቱን ፡ ዘረፉ ፤

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 28 ፤ በጎቻቸውንም ፡ ላሞቻቸውንም ፡ አህያዎቻቸውንም ፡ በውጭም ፡ በከተማም ፡ ያለውን ፡ ወሰዱ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 29 ፤ ሀብታቸውን ፡ ሹሉ ፡ ሕፃናታቸውንና ፡ ሴቶቻቸውንም ፡ ሹሉ ፡ ማረኩ ፥ በቤት ፡ ያለውንም ፡ ሹሉ ፡ ዘረፉ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 30 ፤ ያዕቆብም ፡ ሌዊንና ፡ ስምዖንን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በዚች ፡ አገር ፡ በሚኖሩ ፡ በከነዓናውያንና ፡ በፌርዛውያን ፡ ሰዎች ፡ የተጠላኹ ፡ ታደርጉኝ ፡ ዘንድ ፡ እኔን ፡ አስጨነቃችኹኝ ፤ እኔ ፡ በቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ነኝ ፤ እነርሱ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይሰበሰቡና ፡ ይመቱኛል ፤ እኔም ፡ ከወገኔ ፡ ጋራ ፡ እጠፋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 34 ፡ 31 ፤ እነርሱም ፦ በጋለሞታ ፡ እንደሚደረግ ፡ በእኅታችን ፡ ያደርግባትን ፧ አሉ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዕቆብን ፡ አለው ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ውጣ ፥ በዚያም ፡ ኑር ፤ ከወንድምኽ ፡ ከዔሳው ፡ ፊት ፡ በሸሸኽ ፡ ጊዜ ፡ ለተገለጠልኽ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ መሠዊያውን ፡ አድርግ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ ያዕቆብም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ላሉት ፡ ሹሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እንግዳዎቹን ፡ አማልክት ፡ ከመካከላችኹ ፡ አስወግዱ ፥ ንጹሓንም ፡ ኹኑ ፥ ልብሳችኹንም ፡ ለውጡ ፤

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ ተነሥተንም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ እንውጣ ፤ በዚያም ፡ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ ለሰማኝ ፥ በኼድኩበትም ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ለነበረው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ አደርጋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ በእጃቸው ፡ ያሉትንም ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ በጐሯቸውም ፡ ያሉትን ፡ ጕትቾች ፡ ለያዕቆብ ፡ ሰጡት ፤ ያዕቆብም ፡ በሴኬም ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ቀበራቸው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ ተነሥተውም ፡ ኼዱ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ፍርሀት ፡ በዙሪያቸው ፡ ባሉት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደቀ ፥ የያዕቆብንም ፡ ልጆች ፡ ለማሳደድ ፡ አልተከተሏቸውም ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ ያዕቆብም ፥ ርሱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራም ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሎዛ ፡ መጡ ፤ ርሷም ፡ ቤቴል ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ መሠዊያውን ፡ ሠራ ፥ የዚያንም ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ኤልቤቴል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ ርሱ ፡ ከወንድሙ ፡ ፊት ፡ በሸሸበት ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ተገልጦለት ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ የርብቃ ፡ ሞግዚት ፡ ዲቦራም ፡ ሞተች ፥ በቤቴልም ፡ ከአድባር ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀበረች ፤ ስሙም ፡ አሎንባኩት ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለያዕቆብ ፡ ከኹለት ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ ከሶርያ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተገለጠለት ፥ ባረከውም ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ስምኽ ፡ ያዕቆብ ፡ ነው ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ስምኽ ፡ ያዕቆብ ፡ ተብሎ ፡ አይጠራ ፥ ስምኽ ፡ እስራኤል ፡ ይባል ፡ እንጂ ፡ አለ ፤ ስሙንም ፡ እስራኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ኹሉን ፡ ቻይ ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ብዛ ፥ ተባዛም ፤ ሕዝብና ፡ የአሕዛብ ፡ ማኅበር ፡ ከአንተ ፡ ይኾናል ፥ ነገሥታትም ፡ ከጕልበትኽ ፡ ይወጣሉ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 12 ፤ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅም ፡ የሰጠኋትን ፡ ምድር ፡ ለአንተ ፡ እሰጣለኹ ፥ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለዘርኽ ፡ ምድሪቱን ፡ እሰጣለኹ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተነጋገረበት ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 14 ፤ ያዕቆብም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በተነጋገረበት ፡ ቦታ ፡ የድንጋይ ፡ ሐውልት ፡ ተከለ ፤ የመጠጥ ፡ መሥዋዕትንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፥ ዘይትንም ፡ አፈሰሰበት ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 15 ፤ ያዕቆብም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የተነጋገረበትን ፡ ያን ፡ ቦታ ፡ ቤቴል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 16 ፤ ከቤቴልም ፡ ተነሡ ፤ ወደ ፡ ኤፍራታም ፡ ሊደርሱ ፡ ጥቂት ፡ ሲቀራቸው ፡ ራሔልን ፡ ምጥ ፡ ያዛት ፥ በምጡም ፡ ተጨነቀች ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 17 ፤ ምጡም ፡ ባስጨነቃት ፡ ጊዜ ፡ አዋላጂቱ ፦ አትፍሪ ፥ ይኸኛው ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ይኾንሻልና ፥ አለቻት ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 18 ፤ ርሷም ፡ ስትሞት ፡ ነፍሷ ፡ በምትወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ስሙን ፡ ቤንኦኒ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ ብንያም ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 19 ፤ ራሔልም ፡ ሞተች ፥ ወደ ፡ ኤፍራታ ፡ በምትወስድም ፡ መንገድ ፡ ተቀበረች ፤ ርሷም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 20 ፤ ያዕቆብም ፡ በመቃብሯ ፡ ላይ ፡ ሐውልት ፡ አቆመ ፤ ርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ የራሔል ፡ የመቃብሯ ፡ ሐውልት ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 21 ፤ እስራኤልም ፡ ከዚያ ፡ ተነሣ ፥ ድንኳኑንም ፡ ከጋዴር ፡ ግንብ ፡ በስተወዲያ ፡ ተከለ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 22 ፤ እስራኤልም ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ሮቤል ፡ ኼደ ፡ የአባቱንም ፡ ቁባት ፡ ባላን ፡ ተገናኛት ፤ እስራኤልም ፡ ሰማ ። የያዕቆብም ፡ ልጆች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ናቸው ፤

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 23 ፤ የልያ ፡ ልጆች ፤ የያዕቆብ ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ሮቤል ፥ ስምዖን ፥ ሌዊ ፥ ይሁዳ ፥ ይሳኮር ፥ ዛብሎን ፤

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 24-25 ፤ የራሔል ፡ ልጆች ፤ ዮሴፍ ፥ ብንያም ፤ የራሔል ፡ ባሪያ ፡ የባላ ፡ ልጆችም ፤ ዳን ፥ ንፍታሌም ፤

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 26 ፤ የልያ ፡ ባሪያ ፡ የዘለፋ ፡ ልጆችም ፤ ጋድ ፥ አሴር ፤ እነዚህ ፡ በኹለቱ ፡ ወንዞች ፡ መካከል ፡ በሶርያ ፡ የተወለዱለት ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 27 ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ ይሥሐቅ ፡ አብርሃምና ፡ ይሥሐቅ ፡ እንግዳዎች ፡ ኾነው ፡ ወደተቀመጡባት ፡ ወደ ፡ መምሬ ፡ ወደ ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ ርሷም ፡ ኬብሮን ፡ ወደምትባለው ፡ መጣ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 28 ፤ የይሥሐቅም ፡ ዕድሜ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 35 ፡ 29 ፤ ይሥሐቅም ፡ ነፍሱን ፡ ሰጠ ፥ ሞተም ፤ ሸምግሎ ፡ ዕድሜንም ፡ ጠግቦ ፡ ወደ ፡ ወገኖቹ ፡ ተከማቸ ፤ ልጆቹም ፡ ዔሳውና ፡ ያዕቆብ ፡ ቀበሩት ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ የዔሳው ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ኤዶም ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ ዔሳው ፡ ከከነዓን ፡ ልጆች ፡ ሚስቶችን ፡ አገባ ፤ የኬጢያዊውን ፡ የዔሎንን ፡ ልጅ ፡ ዓዳን ፥ የዔዊያዊው ፡ የዕብዖን ፡ ልጅ ፡ ዐና ([43]) ፡ የወለዳትን ፡ አህሊባማን ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ የእስማኤልን ፡ ልጅ ፡ የነባዮትን ፡ እኅት ፡ ቤሴሞትን ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 4 ፤ ዓዳ ፡ ለዔሳው ፡ ኤልፋዝን ፡ ወለደች ፤ ቤሴሞትም ፡ ራጉኤልን ፡ ወለደች ፤

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 5 ፤ አህሊባማም ፡ የዑስን ፥ የዕላምን ፥ ቆሬን ፡ ወለደች ፤ በከነዓን ፡ ምድር ፡ የተወለዱለት ፡ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 6 ፤ ዔሳውም ፡ ሚስቶቹን ፡ ወንዶች ፡ ልጆቹንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹን ፡ ቤተ ፡ ሰቡንም ፡ ኹሉ ፡ ከብቱንም ፡ ኹሉ ፡ እንስሳዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ በከነዓንም ፡ አገር ፡ ያገኘውን ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ ከወንድሙ ፡ ከያዕቆብ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 7 ፤ ከብታቸው ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ በአንድነት ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤ በእንግድነት ፡ የተቀመጡባትም ፡ ምድር ፡ ከከብታቸው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ልትበቃቸው ፡ አልቻለችም ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 8 ፤ ዔሳውም ፡ በሴይር ፡ ተራራ ፡ ተቀመጠ ፤ ዔሳውም ፡ ኤዶም ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 9 ፤ በሴይር ፡ ተራራ ፡ የሚኖሩ ፡ የኤዶማውያን ፡ አባት ፡ የዔሳው ፡ ትውልድም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 10 ፤ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የዓዳ ፡ ልጅ ፡ ኤልፋዝ ፤ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የቤሴሞት ፡ ልጅ ፡ ራጉኤል ።

---

43 ዕብ. ፥ ዐናህ ፡ (ሥሁል • መልስ ፣ ምሕረት ፡ ያገኘ) ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 11 ፤ የኤልፋዝም ([44]) ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ፤ ቴማን ([45]) ፡ ኦማር ፡ ስፎ ([46]) ፡ ጎቶም ([47]) ፡ ቄኔዝ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ቲምናዕም ፡ ለዔሳው ፡ ልጅ ፡ ለኤልፋዝ ፡ የጫን ፡ ገረድ ፡ ነበረች ፥ ዐማሌቅንም ፡ ለኤልፋዝ ፡
ወለደችለት ፤ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የዓዳ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 13 ፤ የራጉኤልም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ናሖት ፥ ዛራ ፥ ሳማ ፥ ሚዛህ ፤ እነዚህም ፡ የዔሳው ፡
ሚስት ፡ የቤሴሞት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 14 ፤ የፅብዖን ፡ ልጅ ፡ የዐና ፡ ልጅ ፡ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የአህሊባማ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ፤ ለዔሳውም ፡ የዑስን ፥ የዕላማን ፥ ቆሬን ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 15 ፤ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ለዔሳው ፡ የበኵር ፡ ለኤልፋዝ ፡ ልጆች ፤ ቴማን ፡
አለቃ ፥ ኦማር ፡ አለቃ ፥ ስፎ ፡ አለቃ ፥ ቄኔዝ ፡ አለቃ ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 16 ፤ ቆሬ ፡ አለቃ ፥ ጎቶም ፡ አለቃ ፥ ዐማሌቅ ፡ አለቃ ፤ በኤዶም ፡ ምድር ፡ የኤልፋዝ ፡ አለቃዎች ፡
እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ የዓዳ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 17 ፤ የዔሳው ፡ ልጅ ፡ የራጉኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ናሖት ፡ አለቃ ፥ ዛራ ፡ አለቃ ፥ ሳማ ፡
አለቃ ፥ ሚዛህ ፡ አለቃ ፤ በኤዶም ፡ ምድር ፡ የራጉኤል ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እነዚህም ፡ የዔሳው ፡
ሚስት ፡ የቤሴሞት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 18 ፤ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የአህሊባማ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የዑስ ፡ አለቃ ፥ የዕላማ ፡
አለቃ ፥ ቆሬ ፡ አለቃ ፤ የዔሳው ፡ ሚስት ፡ የዐና ፡ ልጅ ፡ የአህሊባማ ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 19 ፤ የዔሳው ፡ ልጆችና ፡ አለቃዎቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ርሱም ፡ ኤዶም ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 20 ፤ በዚያች ፡ አገር ፡ የተቀመጡ ፡ የሖሪው ፡ የሴይር ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ፤ ሎጣን ፥ ሦባል ፥ ፅብዖን ፥ ዐና ፥ ዲሶን ፥ ኤጽር ፥ ዲሳን ፤

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 21 ፤ እነዚህ ፡ በኤዶም ፡ ምድር ፡ የሖሪው ፡ የሴይር ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 22 ፤ የሎጣን ፡ ልጆችም ፡ ሖሪ ፥ ሄማም ፡ ናቸው ፤ የሎጣንም ፡ እኅት ፡ ቲምናዕ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 23 ፤ የሦባል ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ዓልዋን ፥ ማኔሐት ፥ ዔባል ፥ ስፎ ፥ አውናም ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 24 ፤ የፅብዖን ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ አያ ፥ ዐና ፤ ይህም ፡ ዐና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የአባቱን ፡
የፅብዖንን ፡ አህያዎች ፡ ሲጠብቅ ፡ ፍል ፡ ውሃዎችን ፡ ያገኘ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 25 ፤ የዐና ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 26 ፤ ዲሶን ፥ አህሊባማም ፡ የዐና ፡ ሴት ፡ ልጅ ። የዲሶንም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ፤ ሔምዳን ፥ ኤስባን ፥ ይትራን ፥ ክራን ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 27 ፤ የኤጽር ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ቢልሐን ፥ ዛዕዋን ፥ ዐቃን ።

---

44 ዕብ. ፥ ኤሊፋዝ ፡ (ፋዘ ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ ወርቅ) ።
45 ደቡብ ፡ (ተየማን ፥ ወይም ፡ ምሥራቅ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ኾኖ ፡ ከቀኝ ፡ የኾነ ፡ ደቡብ) ።
46 ዕብ. ፥ ጸፎ ፡ (አሰፍሳፊ ፥ ተመልካች) ።
47 ዕብ. ፥ ጋዕታም ፡ (ጋዕት ፥ ጋት ፥ መለኪያ ፤ ፯ቱ ፡ ጋት ፡ ፤ ክንድ ፡ ይኾናል ፥ ኪ.ወ.ክ. ፡ ገ.328) ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 28 ፤ የዲሳን ፡ ልጆችም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ዑፅ ፡ አራን ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 29 ፤ የሖሪ ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ሎጣን ፡ አለቃ ፥ ሦባል ፡ አለቃ ፥ ፅብዖን ፡ አለቃ ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 30 ፤ ዐና ፡ አለቃ ፥ ዲሶን ፡ አለቃ ፥ ኤጽር ፡ አለቃ ፥ ዲሳን ፡ አለቃ ፤ በሴይር ፡ ምድር ፡ አለቃዎች ፡ የኾኑ ፡ የሖሪ ፡ አለቃዎቹ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 31 ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ከመኖሩ ፡ በፊት ፡ በኤዶም ፡ አገር ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 32 ፤ በኤዶምም ፡ የቢዖር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ ነገሠ ፤ የከተማውም ፡ ስም ፡ ዲንሃባ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 33 ፤ ባላቅም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ የባሶራው ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ኢዮባብ ፡ ነገሠ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 34 ፤ ኢዮባብም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ የቴማኒው ፡ አገር ፡ ሑሳም ፡ ነገሠ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 35 ፤ ሑሳምም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ የምድያምን ፡ ሰዎች ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ የመታ ፡ የባዳድ ፡ ልጅ ፡ ሃዳድ ፡ ነገሠ ፤ የከተማውም ፡ ስም ፡ ዓዊት ፡ ተባለ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 36 ፤ ሃዳድም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ የመሥሬቃው ፡ ሰምላ ፡ ነገሠ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 37 ፤ ሰምላም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ በወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከርሆቦት ([48]) ፡ ሳኦል ([49]) ፡ ነገሠ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 38 ፤ ሳኦልም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ በዓልሐናን ፡ ነገሠ ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 39 ፤ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ በዓልሐናንም ፡ ሞተ ፥ በስፍራውም ፡ ሃዳር ፡ ነገሠ ፤ የከተማውም ፡ ስም ፡ ፋዉ ፡ ነው ፤ ሚስቱም ፡ የሜዛሃብ ፡ ልጅ ፡ መጥሬድ ፡ የወለደቻት ፡ መሄጣብኤል ፡ ትባላለች ።

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 40 ፤ የዔሳውም ፡ የአለቃዎቹ ፡ ስም ፡ በወገናቸው ፡ በስፍራቸው ፡ በስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ቲምናዕ ፡ አለቃ ፥ ዓልዋ ፡ አለቃ ፥ የቴት ፡ አለቃ ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 41 ፤ አህሊባማ ፡ አለቃ ፥ ኤላ ፡ አለቃ ፥ ፊኖን ፡ አለቃ ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 42 ፤ ቄኔዝ ፡ አለቃ ፥ ቴማን ፡ አለቃ ፥ ሚብሳር ፡ አለቃ ፥

ዘፍ. ፡ 36 ፡ 43 ፤ መግዲኤል ፡ አለቃ ፥ ዒራም ፡ አለቃ ፥ እነዚህ ፡ በግዛታቸው ፡ ምድር ፡ በየመኖሪያቸው ፡ የኤዶም ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ። የኤዶማውያን ፡ አባት ፡ ይህ ፡ ዔሳው ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ። _____

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ አባቱ ፡ በስደት ፡ በኖረበት ፡ አገር ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 2 ፤ የያዕቆብም ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ። የዮሴፍ ፡ የዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ በጎችን ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ከአባቱ ፡ ሚስቶች ፡ ከባላና ፡ ከዘለፋ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ ብላቴና ፡ ነበረ ፤ የዮሴፍም ፡ የክፉታቸውን ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ አባታቸው ፡ አመጣ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 3 ፤ እስራኤልም ፡ የዮሴፍን ፡ ከልጆቹ ፡ ሹሉ ፡ ይልቅ ፡ ይወደው ፡ ነበር ፥ ርሱ ፡ በሽምግልናው ፡

---

48 ዕብ. ፥ ርሖቦት ፡ (ርሕበት • ፥ ስፋት) ።

49 ዕብ. ፥ ሻውል ፡ (ስኡል ፥ የተለመነ ፥ የተጠየቀ) ።

የወለደው ፡ ነበርና ፤ በብዙ ፡ ሕብር ፡ ያጌጠችም ፡ ቀሚስ ፡ አደረገለት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 4 ፤ ወንድሞቹም ፡ አባታቸው ፡ ከልጆቹ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ እንዲወደው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጠሉት ፥ በሰላም ፡ ይናገሩትም ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 5 ፤ ዮሴፍም ፡ ሕልምን ፡ ዐለመ ፥ ለወንድሞቹም ፡ ነገራቸው ፤ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በብዙ ፡ ጠሉት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ አላቸው ፦ እኔ ፡ ያለምኹትን ፡ ሕልም ፡ ስሙ ፤

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ እኛ ፡ በዕርሻ ፡ መካከል ፡ ነዶ ፡ ስናስር ፡ ነበርና ፥ እንሆም ፥ የእኔ ፡ ነዶ ፡ ቀጥ ፡ ብላ ፡ ቆመች ፤ የእናንተም ፡ ነዶዎች ፡ በዙሪያ ፡ ከበው ፥ እንሆ ፥ ለእኔ ፡ ነዶ ፡ ሰገዱ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 8 ፤ ወንድሞቹም ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡ ልትነግሥብን ፡ ይኾን ፧ ወይስ ፡ ልትገዛ ፡ ይኾን ፧ አሉት ። እንደ ፡ ገናም ፡ ስለ ፡ ሕልሙና ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ይልቁን ፡ ጠሉት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 9 ፤ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ሕልምን ፡ ዐለመ ፥ ለወንድሞቹም ፡ ነገራቸው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ደግሞ ፡ ሌላ ፡ ሕልምን ፡ ዐለምኹ ፤ እንሆ ፥ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከዋክብትም ፡ ሲሰግዱልኝ ፡ አየኹ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 10 ፤ ለአባቱና ፡ ለወንድሞቹም ፡ ነገራቸው ፤ አባቱም ፡ ገሠጸው ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ ይህ ፡ ያለምኸው ፡ ሕልም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእውኑ ፡ እኔና ፡ እናትኽ ፡ ወንድሞችኽም ፡ መጥተን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንሰግድልኽ ፡ ይኾን ፧

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 11 ፤ ወንድሞቹም ፡ ቀኑበት ፡ አባቱ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ ይጠብቀው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 12 ፤ ወንድሞቹ ፡ በሴኬም ፡ የአባታቸውን ፡ በጎች ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 13 ፤ እስራኤልም ፡ ዮሴፍን ፦ ወንድሞችኽ ፡ በሴኬም ፡ በጎችን ፡ የሚጠብቁ ፡ አይደሉምን ፧ ወደ ፡ እነርሱ ፡ እልክኽ ፡ ዘንድ ፡ ና ፡ አለው ። ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ ኼደኽ ፡ ወንድሞችኽና ፡ በጎቹ ፡ ደኅና ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እይ ፥ ወሬያቸውንም ፡ አምጣልኝ ፡ አለው ። እንዲህም ፡ ከኬብሮን ፡ ቈላ ፡ ሰደደው ፥ ወደ ፡ ሴኬምም ፡ መጣ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 15 ፤ እንሆም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሲቅበዘበዝ ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘው ፤ ሰውዮውም ፦ ምን ፡ ትፈልጋለኽ ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 16 ፤ ርሱም ፡ ወንድሞቼን ፡ እፈልጋለኹ ፤ በጎቹን ፡ የሚጠብቁበት ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እባክኽ ፡ ንገረኝ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 17 ፤ ሰውዮውም ፦ ከዚህ ፡ ተነሥተዋል ፤ ወደ ፡ ዶታይን ፡ እንኺድ ፡ ሲሉም ፡ ሰምቻቸዋለኹ ፡ አለው ። ዮሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፡ ተከታትሎ ፡ ኼደ ፥ በዶታይንም ፡ አገኛቸው ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ በሩቅ ፡ ሳለ ፡ አዩት ፥ ወደ ፡ እነርሱም ፡ ገና ፡ ሳይቀርብ ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተማከሩ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 19 ፤ አንዱም ፡ ለአንዱ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ያ ፡ ባለሕልም ፡ ይኸው ፡ መጣ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 20 ፤ አኹንም ፡ ኑ ፥ እንግደለውና ፡ ባንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንጣለው ። ክፉ ፡ አውሬም ፡ በላው ፡ እንላለን ፤ ከሕልሞቹም ፡ የሚኾነውን ፡ እናያለን ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 21 ፤ ሮቤልም ፡ ይህን ፡ ሰማ ፥ ከእጃቸውም ፡ አዳነው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሕይወቱን ፡ አናጥፋ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 22 ፤ ሮቤል ። ደም ፡ አታፍስሱ ፤ በዚች ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ባለችው ፡ ጕድጓድ ፡ ጣሉት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጃችኹን ፡ አትጣሉበት ፡ አላቸው ። እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ ከእጃቸው ፡ ሊያድነውና ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ሊመልሰው ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዮሴፍም ፡ ወደ ፡ ወንድሞቹ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የለበሳትን ፡ በብዙ ፡ ሕብር ፡ ያጌጠቺቱን ፡ ቀሚሱን ፡ ገፈፉት ፤

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 24 ፤ ወስደውም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ጣሉት ፤ ጕድጓዱም ፡ ውሃ ፡ የሌለበት ፡ ደረቅ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 25 ፤ እንጀራም ፡ ሊበሉ ፡ ተቀመጡ ፤ ዐይናቸውንም ፡ አንሥተው ፡ አዩ ፥ እንሆም ፡ የእስማኤላውያን ፡ ነገዶች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ለመውረድ ፡ ከገለዓድ ፡ መጡ ፤ ግመሎቻቸውም ፡ ሽቱና ፡ በለሳን ፡ ከርቤም ፡ ተጭነው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 26 ፤ ይሁዳም ፡ ወንድሞቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ወንድማችንን ፡ ገድለን ፡ ደሙን ፡ ብንሸሽግ ፡ ጥቅማችን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 27 ፤ ኑ ፥ ለእስማኤላውያን ፡ እንሸጠው ፥ እጃችንን ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አንጣል ፥ ወንድማችን ፡ ሥጋችንም ፡ ነውና ። ወንድሞቹም ፡ የርሱን ፡ ነገር ፡ ሰሙት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 28 ፤ የምድያም ፡ ነጋዴዎችም ፡ ዐለፉ ፤ እነርሱም ፡ ዮሴፍን ፡ አንሥተው ፡ ከጕድጓድ ፡ አወጡት ፤ ለእስማኤላውያንም ፡ ዮሴፍን ፡ በኻያ ፡ ብር ፡ ሸጡት ፤ እነርሱም ፡ ዮሴፍን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወሰዱት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 29 ፤ ሮቤልም ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ተመለሰ ፥ እንሆም ፡ ዮሴፍ ፡ በጕድጓድ ፡ የለም ፤ ልብሱንም ፡ ቀደደ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 30 ፤ ወደ ፡ ወንድሞቹም ፡ ተመልሶ ፦ ብላቴናው ፡ የለም ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ወዴት ፡ እኼዳለኹ ፧ አለ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 31 ፤ የዮሴፍንም ፡ ቀሚስ ፡ ወሰዱ ፥ የፍየል ፡ አውራም ፡ ዐርደው ፡ ቀሚሱን ፡ በደም ፡ ነከሩት ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 32 ፤ ብዙ ፡ ሕብር ፡ ያለበትን ፡ ቀሚሱንም ፡ ላኩ ፥ ወደ ፡ አባታቸውም ፡ አገቡት ፥ እንዲህም ፡ አሉት ፦ ይህን ፡ አገኘን ፤ ይህ ፡ የልጅኽ ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ እንዳልኾነ ፡ እስኪ ፡ እየው ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 33 ፤ ርሱም ፡ ዐውቆ ፦ የልጄ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ፤ ክፉ ፡ አውሬ ፡ በልቶታል ፤ ዮሴፍ ፡ በርግጥ ፡ ተበጣጥቋል ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 34 ፤ ያዕቆብም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ በወገቡም ፡ ማቅ ፡ ታጥቆ ፡ ለልጁ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 35 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቹና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹም ፡ ኹሉ ፡ ሊያጽናኑት ፡ ተነሡ ፤ መጽናናትን ፡ እንቢ ፡ አለ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ወደ ፡ ልጄ ፡ ወደ ፡ ሙታን ፡ ስፍራ ፡ እያዘንኹ ፡ እወርዳለኹ ። አባቱም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 37 ፡ 36 ፤ እነዚያ ፡ የምድያም ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ዮሴፍን ፡ በግብጽ ፡ ለፈርዖን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ለዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ለጲጥፋራ ፡ ሸጡት ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ይሁዳ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ተለይቶ ፡ ወረደ ፥ ስሙን ፡ ዔራስ ፡ ወደሚሉት ፡ ወደ ፡ ዓዶሎማዊውም ፡ ሰው ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 2 ፤ ከዚያም ፡ ይሁዳ ፡ የከነዓናዊውን ፡ የሴዋን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ አየ ፤ ወሰዳትም ፥ ወደ ፡ ርሷም ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 3 ፤ ፀነሰችም ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፤ ስሙንም ፡ ዔር ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 4 ፤ ደግሞም ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ፤ ስሙንም ፡ አውናን ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ደግሞ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፥ ስሙንም ፡ ሴሎም ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ ርሱንም ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ክዚብ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ነበረች ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 6 ፤ ይሁዳም ፡ ለበኵር ፡ ልጁ ፡ ለዔር ፡ ትዕማር ፡ የምትባል ፡ ሚስት ፡ አጋባው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 7 ፤ የይሁዳም ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ዔር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቀሠፈው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 8 ፤ ይሁዳም ፡ አውናን ፦ ወደወንድምኽ ፡ ሚስት ፡ ግባ ፥ አግባትም ፥ ለወንድምኽም ፡ ዘርን ፡ አቁምለት ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 9 ፤ አውናንም ፡ ዘሩ ፡ ለርሱ ፡ እንዳይኾን ፡ ዐወቀ ፤ ወደወንድሙ ፡ ሚስት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ እንዳይሰጥ ፡ ዘሩን ፡ በምድር ፡ ያፈሰው ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 10 ፤ ይህም ፡ ሥራው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ኾነበት ፥ ርሱንም ፡ ደግሞ ፡ ቀሠፈው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 11 ፤ ይሁዳም ፡ ምራቱን ፡ ትዕማርን ፦ ልጄ ፡ ሴሎም ፡ እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ በአባትሽ ፡ ቤት ፡ መበለት ፡ ኾነሽ ፡ ተቀመጪ ፡ አላት ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ እንዳይሞት ፡ ብሏልና ። ትዕማርም ፡ ኼዳ ፡ በአባቷ ፡ ቤት ፡ ተቀመጠች ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 12 ፤ ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ ሚስት ፡ የሴዋ ፡ ልጅ ፡ ሞተች ፤ ይሁዳም ፡ ተጽናና ፥ የበጎቹን ፡ ጠጕር ፡ ወደሚሸልቱት ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ወጣ ፥ ርሱም ፡ ዓዶሎማዊው ፡ ወዳጁም ፡ ዔራስ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 13 ፤ ለትዕማርም ፦ እንሆ ፥ ዐማትሽ ፡ ይሁዳ ፡ የበጎቹን ፡ ጠጕር ፡ ይሸልት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ይወጣል ፡ ብለው ፡ ነገሯት ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 14 ፤ ርሷም ፡ የመበለትነቷን ፡ ልብስ ፡ አወለቀች ፥ መጐናጸፊያዋንም ፡ ወሰደች ፥ ተሸፈነችም ፥ ወደ ፡ ተምናም ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ዳር ፡ በኤናይም ፡ ደጅ ፡ ተቀመጠች ፤ ሴሎም ፡ እንደ ፡ አደገ ፡ ሚስትም ፡ እንዳልኾነችው ፡ አይታለችና ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 15 ፤ ይሁዳም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ጋለሞታን ፡ መሰለችው ፤ ፊቷን ፡ ተሸፍና ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ርሷም ፡ አዘነበለ ፦ እባክሽ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ልግባ ፡ አላት ፤ ርሷ ፡ ምራቱ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ አላወቀም ፡ ነበርና ። ርሷም ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ብትገባ ፡ ምን ፡ ትሰጠኛለኽ ፧ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 17 ፤ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ከመንጋዬ ፡ እሰድልኻለኹ ፡ አላት ። ርሷም ፦ እስክትሰድልኝ ፡ ድረስ ፡ መያዣ ፡ ትሰጠኛለኽን ፧ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ ምን ፡ መያዣ ፡ ልስጥሽ ፧ አላት ። ርሷም ፦ ቀለበትኽን ፥ አንባርኽን ፥ በእጅኽ ፡ ያለውን ፡ በትር ፡ አለች ። ርሱም ፡ ሰጣትና ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ደረሰ ፥ ርሷም ፡ ፀነሰችለት ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 19 ፤ ርሷም ፡ ተነሥታ ፡ ኼደች ፥ መጐናጸፊያዋንም ፡ አውልቃ ፡ የመበለትነቷን ፡ ልብስ ፡ ለበሰች ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 20 ፤ ይሁዳም ፡ መያዣውን ፡ ከሴቲቱ ፡ እጅ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ በወዳጁ ፡ በዓዶሎማዊው ፡ እጅ ፡

የፍየሉን ፡ ጠቦት ፡ ላከላት ፤ ርሷንም ፡ አላገኛትም ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ የአገሩን ፡ ሰዎች ፦ በኤናይም ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጣ ፡ የነበረች ፡ ጋለሞታ ፡ ወዴት ፡ ናት ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፦ በዚህ ፡ ጋለሞታ ፡ አልነበረችም ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ ተመልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አላገኘኋትም ፤ የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፦ ከዚህ ፡ ጋለሞታ ፡ አልነበረችም ፡ አሉኝ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 23 ፤ ይሁዳም ፦ እኛ ፡ መዘበቻ ፡ እንዳንኾን ፡ ትውሰደው ፤ እንሆ ፥ የፍየሉን ፡ ጠቦት ፡ ሰደድኹላት ፥ አንተም ፡ አላገኘኻትም ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከሦስት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ ለይሁዳ ፦ ምራትኽ ፡ ትዕማር ፡ ሴሰነች ፤ ደግሞም ፡ በዝሙት ፥ እንሆ ፥ ፀነሰች ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ይሁዳም ፦ አውጧትና ፡ በእሳት ፡ ትቃጠል ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 25 ፤ ርሷም ፡ ባወጧት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አማቷ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ላከች ፦ ለዚህ ፡ ለባለገንዘብ ፡ ነው ፡ የፀነስኹት ፤ ተመልከት ፤ ይህ ፡ ቀለበት ፥ ይህ ፡ አንባር ፥ ይህ ፡ በትር ፡ የማን ፡ ነው ፧

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 26 ፤ ይሁዳም ፡ ዐወቀ ፦ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ርሷ ፡ እውነተኛ ፡ ኾነች ፤ ልጄን ፡ ሴሎምን ፡ አልሰጠኋትምና ፡ አለ ። ደግሞም ፡ አላወቃትም ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 27 ፤ በመውለጃዋም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ መንታ ፡ ልጆች ፡ በሆዷ ፡ ነበሩ ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 28 ፤ ስትወልድም ፡ አንዱ ፡ እጁን ፡ አወጣ ፤ አዋላጂቱም ፡ ቀይ ፡ ፈትል ፡ ወስዳ ፡ በእጁ ፡ አሰረች ፦ ይህ ፡ መዠመሪያ ፡ ይወጣል ፡ አለች ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 29 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ እጁን ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ወንድሙ ፡ ወጣ ፤ ርሷም ፦ ለምን ፡ ጥሰኽ ፡ ወጣኽ ፧ አለች ፤ ስሙንም ፡ ፋሬስ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘፍ. ፡ 38 ፡ 30 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ቀይ ፡ ፈትል ፡ በእጁ ፡ ያለበት ፡ ወንድሙ ፡ ወጣ ፤ ስሙም ፡ ዛራ ፡ ተባለ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 1 ፤ ዮሴፍ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ፤ የፈርዖን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ የሚኾን ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ ጲጥፋራ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ካወረዱት ፡ ከእስማኤላውያን ፡ እጅ ፡ ገዛው ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ ሥራውም ፡ የተከናወነለት ፡ ሰው ፡ ኾነ ፤ በግብጻዊው ፡ ጌታውም ፡ ቤት ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 3 ፤ ጌታውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳለ ፥ ርሱ ፡ የሚሠራውንም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጁ ፡ እንዲያከናውንለት ፡ አየ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 4 ፤ ዮሴፍም ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ አገኘ ፥ ርሱንም ፡ ያገለግለው ፡ ነበር ፤ በቤቱም ፡ ላይ ፡ ሾመው ፥ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ በእጁ ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 5 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በቤቱ ፡ ባለውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከሾመው ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ የግብጻዊውን ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ዮሴፍ ፡ ባረከው ፤ የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ በውጪም ፡ በግቢም ፡ ባለው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 6 ፤ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ ለዮሴፍ ፡ አስረከበ ፤ ከሚበላውም ፡ እንጀራ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ የሚያውቀው ፡ አልነበረም ። የዮሴፍም ፡ ፊቱ ፡ መልከ ፡ መልካምና ፡ ውብ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 7 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የጌታው ፡ ሚስት ፡ በዮሴፍ ፡ ላይ ፡ ዐይኗን ፡ ጣለች ። ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ተኛ ፡ አለችው ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ እንቢ ፡ አለ ፥ ለጌታውም ፡ ሚስት ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ እንሆ ፥ ጌታዬ ፡ በቤቱ ፡ ያለውን ፡ ምንም ፡ ምን ፡ የሚያውቀው ፡ የለም ፥ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ አስረክቦኛል ፤

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 9 ፤ ለዚህ ፡ ቤት ፡ ከእኔ ፡ የሚበልጥ ፡ ሰው ፡ የለም ፤ ሚስቱ ፡ ስለ ፡ ኾንሽ ፡ ከአንቺም ፡ በቀር ፡ ያልሰጠኝ ፡ ነገር ፡ የለም ፤ እንዴት ፡ ይህን ፡ ትልቅ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደርጋለኹ ፧ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዴት ፡ ኀጢአትን ፡ እሠራለኹ ፧

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 10 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ በየዕለቱ ፡ ለዮሴፍ ፡ ትነግረው ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ይተኛ ፡ ዘንድ ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አልሰማትም ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሥራውን ፡ እንዲሠራ ፤ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፤ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ከቤት ፡ ሰዎች ፡ ማንም ፡ አልነበረም ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 12 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተኛ ፡ ስትል ፡ ልብሱን ፡ ተጠማጥማ ፡ ያዘች ፤ ርሱም ፡ ልብሱን ፡ በእጇ ፡ ትቶላት ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ውጭም ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ልብሱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፥

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 14 ፤ የቤቷን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጠርታ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ነገረቻቸው ። እዩ ፤ ዕብራዊው ፡ ሰው ፡ በእኛ ፡ እንዲሣለቅ ፡ አግብቶብናል ፤ ፤ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሊተኛ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ገባ ፥ እኔም ፡ ድምፄን ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ ጮኽኹ ፤

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 15 ፤ ድምፄንም ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ እንደ ፡ ጮኽኹ ፡ ቢሰማ ፡ ልብሱን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ጥሎ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ውጭም ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 16 ፤ ጌታው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስም ፡ ልብሱን ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ አኖረች ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 17 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ ነገረችው ፦ ያገባኽልን ፡ ዕብራዊው ፡ ባሪያ ፡ ሊሣለቅብኝ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ገባ ፤

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 18 ፤ እኔም ፡ ድምፄን ፡ ከፍ ፡ አድርጌ ፡ ስጮኽ ፡ ልብሱን ፡ በእጄ ፡ ተወና ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሸሸ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 19 ፤ ጌታውም ፦ ባሪያኽ ፡ እንዲህ ፡ አደረገኝ ፡ ብላ ፡ የነገረችውን ፡ የሚስቱን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 20 ፤ የዮሴፍም ፡ ጌታ ፡ ወሰደው ፥ የንጉሡ ፡ እስረኞችም ፡ ወደሚታሰሩበት ፡ ስፍራ ፡ ወደግዞት ፡ ቤት ፡ አገባው ፤ ከዚያም ፡ በግዞት ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ምሕረትንም ፡ አበዛለት ፥ በግዞት ፡ ቤቱም ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 22 ፤ የግዞት ፡ ቤቱም ፡ አለቃ ፡ በግዞት ፡ ያሉትን ፡ እስረኞች ፡ ኹሉ ፡ በዮሴፍ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ በዚያም ፡ የሚደረገው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ የሚያደርገው ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 39 ፡ 23 ፤ የግዞት ፡ ቤቱም ፡ አለቃ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አላሰበም ፥ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረና ፤ የሚያደርገውንም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያቀናለት ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ። _____

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 1 ፤ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላም ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ የጠጅ ፡ አሳላፊና ፡ የእንጀራ ፡ አበዛ ፡ ጌታቸውን ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥን ፡ በደሉ ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 2 ፤ ፈርዖንም ፡ በኹለቱ ፡ ሹማምቱ ፡ በጠጅ ፡ አሳላፊዎቹ ፡ አለቃና ፡ በእንጀራ ፡ ዐበዛዎቹ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ፤

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 3 ፤ ዮሴፍ ፡ ታስሮ ፡ በነበረበትም ፡ በግዞት ፡ ስፍራ ፡ በዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ቤት ፡ አስጠበቃቸው ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 4 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ለዮሴፍ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ ርሱም ፡ ያገለግላቸው ፡ ነበር ፤ በግዞት ፡ ቤትም ፡ ዐያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 5 ፤ በግዞት ፡ ቤት ፡ የነበሩት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊና ፡ እንጀራ ፡ ዐበዛ ፡ ኹለቱም ፡ በአንዲት ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ሕልሙ ፡ ትርጓሜ ፡ እየራሳቸው ፡ ሕልምን ፡ ዐለሙ ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 6 ፤ ዮሴፍም ፡ ማልዶ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ገባ ፥ እንሆም ፡ አዝነው ፡ አያቸው ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 7 ፤ በጌታው ፡ ቤት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በግዞት ፡ የነበሩትንም ፡ የፈርዖንን ፡ ሹማምት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፦ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዐዝናችኋል ፧

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 8 ፤ እነርሱም ፦ ሕልምን ፡ ዐልመን ፡ የሚተረጉምልን ፡ ዐጣን ፡ አሉት ። ዮሴፍም ፡ አላቸው ፦ ሕልምን ፡ የሚተረጉም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠው ፡ አይደለምን ፧ እስቲ ፡ ንገሩኝ ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 9 ፤ የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃም ፡ ለዮሴፍ ፡ ሕልሙን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ፦ በሕልሜ ፡ የወይን ፡ ዛፍ ፡ በፊቴ ፡ ኾና ፡ አየኹ ፥

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 10 ፤ በዛፊቱም ፡ ሦስት ፡ ዐረግ ፡ አለባት ፤ ርሷም ፡ ቅጠልና ፡ አበባ ፡ አወጣች ፥ ዘለላም ፡ አንጠለጠለች ፥ የዘለላዋም ፡ ፍሬ ፡ በሰለ ፤

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 11 ፤ የፈርዖንም ፡ ጽዋ ፡ በእጄ ፡ ነበረ ፤ ፍሬውንም ፡ ወስጄ ፡ በፈርዖን ፡ ጽዋ ፡ ጨመቅኹት ፥ ጽዋውንም ፡ ለፈርዖን ፡ በእጁ ፡ ሰጠኹት ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 12 ፤ ዮሴፍም ፡ አለው ፦ የዚህ ፡ ትርጓሜው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሦስቱ ፡ ዐረግ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 13 ፤ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ፈርዖን ፡ ራስኽን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ ወደቀደመው ፡ ሹመትኽም ፡ ይመልስኻል ፤ ጠጅ ፡ አሳላፊ ፡ በነበርኽበት ፡ ጊዜ ፡ ስታደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሥርዐትም ፡ የፈርዖንን ፡ ጽዋ ፡ በእጁ ፡ ትሰጣለኽ ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎ ፡ ነገር ፡ በተደረገልኽ ፡ ጊዜ ፡ እኔን ፡ ዐስበኝ ፥ ምሕረትንም ፡ አድርግልኝ ፥ የእኔንም ፡ ነገር ፡ ለፈርዖን ፡ ነግረኽ ፡ ከዚህ ፡ ቤት ፡ አውጣኝ ፤

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 15 ፤ እኔን ፡ ከዕብራውያን ፡ አገር ፡ ሰርቀው ፡ አምጥተውኛልና ፤ ከዚህም ፡ ደግሞ ፡ በግዞት ፡ ያኖሩኝ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ አላደረግኹም ።

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 16 ፤ የእንጀራ ፡ ዐበዛዎቹ ፡ አለቃም ፡ ሕልሙን ፡ በመልካም ፡ እንደ ፡ ተረጐመ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ዮሴፍን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ሕልም ፡ አይቼ ፡ ነበር ፥ እንሆም ፡ ሦስት ፡ መሶብ ፡ ነጭ ፡ እንጀራ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤

ዘፍ. ፥ 40 ፥ 17 ፤ በላይኛውም ፡ መሶብ ፡ ፈርዖን ፡ ከሚበላው ፡ ከጋጋሪዎች ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ ነበረበት ፤ ወፎችም ፡

በራሴ ፡ ላይ ፡ ከመሶቡ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 18 ፤ ዮሴፍም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ የዚህ ፡ ትርጓሜው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሦስቱ ፡ መሶብ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 19 ፤ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ፈርዖን ፡ ራስኽን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ በዕንጨትም ፡ ላይ ፡ ይሰቅልኻል ፤ ወፎችም ፡ ሥጋኽን ፡ ይበሉታል ።

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 20 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ፈርዖን ፡ የተወለደበት ፡ ቀን ፡ ነበረ ፥ ለሰራዊቱም ፡ ሹሉ ፡ ግብር ፡ አደረገ ፤ የጠጅ ፡ አሳላፊዎቹን ፡ አለቃና ፡ የእንጀራ ፡ ዐበዛዎቹን ፡ አለቃ ፡ በአሽከሮቹ ፡ መካከል ፡ ከፍ ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 21 ፤ የጠጅ ፡ አሳለፊዎቹንም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ መለሰው ፥ ጽዋውንም ፡ በፈርዖን ፡ እጅ ፡ ሰጠ ፤

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 22 ፤ የእንጀራ ፡ ዐበዛዎቹንም ፡ አለቃ ፡ ሰቀለው ፥ ዮሴፍ ፡ እንደተረጐመላቸው ።

ዘፍ. ፡ 40 ፡ 23 ፤ የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ዮሴፍን ፡ አላሰበውም ፥ ረሳው ፡ እንጂ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ። _____

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 1 ፤ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፥ ፈርዖን ፡ ሕልምን ፡ አየ ፥ እንሆም ፥ በወንዙ ፡ ዳር ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ መልካቸው ፡ ያማረ ፡ ሥጋቸውም ፡ የወፈረ ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ከወንዙ ፡ ወጡ ፥ በውሃውም ፡ ዳር ፡ በመስኩ ፡ ይሰማሩ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ መልካቸው ፡ የከፋ ፡ ሥጋቸውም ፡ የከሳ ፡ ሌላዎች ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ከወንዝ ፡ ወጡ ፥ በእነዚያም ፡ ላሞች ፡ አጠገብ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 4 ፤ መልካቸው ፡ የከፋ ፡ ሥጋቸውም ፡ የከሳ ፡ እነዚያም ፡ ላሞች ፡ መልካቸው ፡ ያማረውን ፡ ሥጋቸው ፡ የወፈረውን ፡ ሰባቱን ፡ ላሞች ፡ ዋጧቸው ። ፈርዖንም ፡ ነቃ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ ተኛ ፡ ኹለተኛም ፡ ሕልምን ፡ አየ ። እንሆም ፥ ባንድ ፡ አገዳ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ ያማሩና ፡ መልካም ፡ የኾኑ ፡ ሰባት ፡ እሸቶች ፡ ወጡ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 6 ፤ እንሆም ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ የሰለቱና ፡ በምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ የተመቱ ፡ ሰባት ፡ እሸቶች ፡ ወጡ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 7 ፤ የሰለቱትም ፡ እሸቶች ፡ ሰባቱን ፡ ያማሩና ፡ የዳበሩ ፡ እሸቶች ፡ ዋጧቸው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 8 ፤ ፈርዖንም ፡ ነቃ ፥ እንሆም ፡ ሕልም ፡ ነበረ ። በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ታወከችበት ፤ ወደ ፡ ሕልም ፡ ተርጓሚዎች ፡ ሹሉ ፡ ወደግብጽ ፡ ጠቢባንም ፡ ሹሉ ፡ ልኮ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠራቸው ፤ ፈርዖንም ፡ ሕልሙን ፡ ነገራቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከነርሱ ፡ ለፈርዖን ፡ የሚተረጉም ፡ አልተገኘም ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 9 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የጠጅ ፡ አሳላፊዎቹ ፡ አለቃ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለፈርዖን ፡ ተናገረ ፦ እኔ ፡ ኀጢአቴን ፡ ዛሬ ፡ ዐስባለኹ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 10 ፤ ፈርዖን ፡ በባሪያዎቹ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ፥ እኔንም ፡ የእንጀራ ፡ ዐበዛዎቹንም ፡ አለቃ ፡ በግዞት ፡ ስፍራ ፡ በዘበኞች ፡ አለቃ ፡ ቤት ፡ አኖረን ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 11 ፤ እኛም ፡ በአንዲት ፡ ሌሊት ፡ ሕልምን ፡ ዐለምን ፥ እኔና ፡ ርሱ ፤ እያንዳንዳችን ፡ እንደ ፡ ሕልማችን ፡ ትርጓሜ ፡ ዐለምን ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ባሪያ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ዕብራዊ ፡ ጕልማሳ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ለርሱም ፡ ነገርነው ፥ ሕልማችንንም ፡ ተረጐመልን ፤ ለያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ሕልሙ ፡ ተረጐመልን ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ እንደ ፡ ተረጐመልን ፡ እንደዚያው ፡ ኾነ ፤ እኔ ፡ ወደ ፡ ሹመቴ ፡ ተመለስኹ ፥ ርሱም ፡ ተሰቀለ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 14 ፤ ፈርዖንም ፡ ልኮ ፡ ዮሴፍን ፡ አስጠራ ፥ ከግዞት ፡ ቤትም ፡ አስቸኰሉት ፤ ርሱም ፡ ተላጨ ፥ ልብሱንም ፡ ለወጠ ፥ ወደ ፡ ፈርዖንም ፡ ገባ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 15 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፡ አለው ፦ ሕልምን ፡ አየኹ ፥ የሚተረጕመውም ፡ አልተገኘም ፤ ሕልምን ፡ እንደ ፡ ሰማኽ ፥ እንደ ፡ ተረጐምኽም ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ሰማኹ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 16 ፤ ዮሴፍም ፡ ለፈርዖን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፦ ይህ ፡ በእኔ ፡ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለፈርዖን ፡ በደኅንነት ፡ ይመልስለታል ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 17 ፤ ፈርዖንም ፡ ለዮሴፍ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ በሕልሜ ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ቆሜ ፡ ነበር ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 18 ፤ እንሆም ፥ ሥጋቸው ፡ የወፈረ ፡ መልካቸውም ፡ ያማረ ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ወጡ ፥ በመስኩም ፡ ይሰማሩ ፡ ነበር ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 19 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ የደከሙ ፡ መልካቸውም ፡ እጅግ ፡ የከፋ ፡ ሥጋቸውም ፡ የከሳ ፡ ሌላዎች ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ወጡ ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ መልከ ፡ ክፉ ፡ ከቶ ፡ አላየኹም ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 20 ፤ የከሱትና ፡ መልከ ፡ ክፉዎቹ ፡ ላሞች ፡ የመገሥመሪያዎቹን ፡ ወፍራሞቹን ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ዋጧቸው ፥

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 21 ፤ በሆዳቸውም ፡ ተዋጡ ፤ በሆዳቸውም ፡ እንደተዋጡ ፡ አልታወቀም ፥ መልካቸውም ፡ በመገሥመሪያ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ የከፋ ፡ ነበረ ። ነቃኹም ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 22 ፤ በሕልሜም ፥ እንሆ ፥ የዳበሩና ፡ መልካም ፡ የኾኑ ፡ ሰባት ፡ እሸቶች ፡ ባንድ ፡ አገዳ ፡ ሲወጡ ፡ አየኹ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 23 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ የደረቁና ፡ የሰለቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ የተመቱ ፡ ሰባት ፡ እሸቶች ፡ ወጡ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 24 ፤ የሰለቱት ፡ እሸቶች ፡ ያማሩትን ፡ ሰባቱን ፡ እሸቶች ፡ ዋጧቸው ። ለሕልም ፡ ተርጓሚዎችም ፡ ሕልሜን ፡ ነገርኹ ፥ የሚተረጕምልኝም ፡ ዐጣኹ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 25 ፤ ዮሴፍም ፡ ፈርዖንን ፡ አለው ፦ የፈርዖን ፡ ሕልሙ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሊያደርገው ፡ ያለውን ፡ ለፈርዖን ፡ ነግሮታል ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 26 ፤ ሰባቱ ፡ መልካካሞች ፡ ላሞች ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ናቸው ፥ ሰባቱም ፡ መልካካሞች ፡ እሸቶች ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ናቸው ፤ ሕልሙ ፡ አንድ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 27 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የወጡት ፡ የከሱትና ፡ መልከ ፡ ክፉዎቹ ፡ ሰባት ፡ ላሞች ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ናቸው ፥ የሰለቱትና ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ የመታቸው ፡ ሰባቱም ፡ እሸቶች ፡ እነርሱ ፡ ራብ ፡ የሚኾንባቸው ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 28 ፤ ለፈርዖን ፡ የነገርኹት ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሊያደርገው ፡ ያለውን ፡ ለፈርዖን ፡

አሳየው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 29 ፤ እንሆ ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ እጅግ ፡ ጥጋብ ፡ የሚኾንባቸው ፡ ሰባት ፡ ዓመታት ፡ ይመጣሉ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 30 ፤ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ራብ ፡ ይመጣል ፥ በግብጽ ፡ አገር ፡ የነበረውም ፡ ጥጋብ ፡ ሹሉ ፡ ይረሳል ፤ ራብም ፡ ምድርን ፡ በጣም ፡ ያጠፋል ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 31 ፤ በኋላ ፡ ከሚኾነው ፡ ከዚያ ፡ ራብ ፡ የተነሣም ፡ በምድር ፡ የኾነው ፡ ጥጋብ ፡ አይታወቅም ፥ እጅግ ፡ ጽኑ ፡ ይኾናልና ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 32 ፤ ሕልሙም ፡ ለፈርዖን ፡ ደጋግሞ ፡ መታየቱ ፡ ነገሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተቈረጠ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ፥ እግዚአብሔርም ፡ ፈጥኖ ፡ ያደርገዋል ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 33 ፤ አኹንም ፡ ፈርዖን ፡ ብልኅና ፡ ዐዋቂ ፡ ሰውን ፡ ይፈልግ ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ላይም ፡ ይሹመው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 34 ፤ ፈርዖን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሹማምትን ፡ ይሹም ፤ በሰባቱም ፡ የጥጋብ ፡ ዓመታት ፡ ከሚገኘው ፡ ፍሬ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ከዐምስት ፡ እጅ ፡ አንደኛውን ፡ ይውሰድ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 35 ፤ የሚመጡትን ፡ የመልካሞቹን ፡ ዓመታት ፡ እኽላቸውን ፡ ያከማቹ ፤ ስንዴውንም ፡ ከፈርዖን ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ያኑሩ ፥ እኽሎችም ፡ በከተማዎች ፡ ይጠበቁ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 36 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ስለሚኾነው ፡ ስለሰባቱ ፡ ዓመታት ፡ ራብ ፡ እኽሉ ፡ ተጠብቆ ፡ ይኑር ፥ ምድሪቱም ፡ በራብ ፡ አትጠፋም ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 37 ፤ ነገሩም ፡ በፈርዖንና ፡ በሎሌዎቹ ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ ኾነ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 38 ፤ ፈርዖንም ፡ ሎሌዎቹን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ያለበትን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ እናገኛለንን ፧

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 39 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፡ አለው ፦ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ብልኅ ፡ ዐዋቂም ፡ ሰው ፡ የለም ፥ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሹሉ ፡ ገልጦልኻልና ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 40 ፤ አንተ ፡ በቤቴ ፡ ላይ ፡ ተሾም ፥ ሕዝቤም ፡ ሹሉ ፡ ለቃልኽ ፡ ይታዘዝ ፤ እኔ ፡ በዙፋኔ ፡ ብቻ ፡ ከአንተ ፡ እበልጣለኹ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 41 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፦ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ሾምኹኽ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 42 ፤ ፈርዖን ፡ ቀለበቱን ፡ ከእጁ ፡ አወለቀ ፡ በዮሴፍ ፡ እጅም ፡ አደረገው ፥ ነጭ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስንም ፡ አለበሰው ፥ በዐንገቱም ፡ የወርቅ ፡ ዝርግፍን ፡ አደረገለት ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 43 ፤ የርሱም ፡ በምትኾን ፡ በኹለተኛዪቱ ፡ ሠረገላ ፡ አስቀመጠው ፥ ዐዋጅ ፡ ነጋሪም ፦ ስገዱ ፡ እያለ ፡ በፊት ፡ በፊቱ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ተሾመ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 44 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፡ አለው ፦ እኔ ፡ ፈርዖን ፡ ነኝ ፤ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ያለአንተ ፡ ማንም ፡ እጁንም ፡ እግሩንም ፡ አያንሣ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 45 ፤ ፈርዖንም ፡ የዮሴፍን ፡ ስም ፡ ጸፍናት ፡ ፐዕናህ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ የሄልዮቱ ፡ ከተማ ፡ ካህን ፡ የጶጥፌራ ፡ ልጅ ፡ የምትኾን ፡ አሥናትን ፡ አጋባው ። ዮሴፍም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 46 ፤ ዮሴፍም ፡ በግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ። ዮሴፍም ፡ ከፈርዖን ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ የግብጽ ፡ ምድርንም ፡ ዞሩ ፡ ዞረ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 47 ፤ በሰባቱም ፡ በጥጋብ ፡ ዓመታት ፡ የምድሪቱ ፡ ፍሬ ፡ ክምር ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 48 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ዞሩ ፡ ያለውን ፡ የሰባቱን ፡ ዓመት ፡ እኽል ፡ ዞሩ ፡ ሰበሰበ ፥ እኽልንም ፡ በከተማዎቹ ፡ አደለበ ፤ በየከተማዉቱ ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የዕርሻውን ፡ እኽል ፡ ዞሩ ፡ በዚያው ፡ ከተተ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 49 ፤ ዮሴፍም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የኾነ ፡ ስንዴን ፡ አከማቸ ፥ መስፈርን ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፤ ሊሰፈር ፡ አልተቻለምና ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 50 ፤ ለዮሴፍም ፡ የሄልዮቱ ፡ ከተማ ፡ ካህን ፡ የጶጥፌራ ፡ ልጅ ፡ አሥናት ፡ የወለደችለት ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ የራብ ፡ ዘመን ፡ ገና ፡ ሳይመጣ ፡ ተወለዱለት ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 51 ፤ ዮሴፍም ፡ የበኩር ፡ ልጁን ፡ ስም ፡ ምናሴ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እግዚአብሔር ፡ መከራዬን ፡ ዞሩ ፡ የአባቴንም ፡ ቤት ፡ አስረሳኝ ፤

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 52 ፤ የኹለተኛውንም ፡ ስም ፡ ኤፍሬም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እግዚአብሔር ፡ በመከራዬ ፡ አገር ፡ አፈራኝ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 53 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የነበረውም ፡ የሰባቱ ፡ ዓመት ፡ ጥጋብ ፡ ዐለፈ ፥

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 54 ፤ ዮሴፍም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የሰባቱ ፡ ዓመት ፡ ራብ ፡ ገመረ ። በያገሩም ፡ ዞሩ ፡ ራብ ፡ ኾነ ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ዞሩ ፡ ግን ፡ እኽል ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 55 ፤ የግብጽ ፡ ምድርም ፡ ዞሩ ፡ ተራበ ፥ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ እኽል ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ጮኸ ፤ ፈርዖንም ፡ የግብጽ ፡ ሰዎችን ፡ ዞሩ ፦ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ ኺዱ ፥ ርሱ ፡ ያላችኹንም ፡ ዞሩ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 56 ፤ በምድርም ፡ ዞሩ ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ኾነ ፤ ዮሴፍም ፡ እኽል ፡ ያለበትን ፡ ጐተራ ፡ ዞሩ ፡ ከፍቶ ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ዞሩ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር ፤ ራብም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 41 ፡ 57 ፤ አገሮችም ፡ ዞሩ ፡ እኽል ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ መጡ ፤ በምድር ፡ ዞሩ ፡ ራብ ፡ እጅግ ፡ ጸንቶ ፡ ነበርና ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ። _____

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ በግብጽ ፡ እኽል ፡ እንዳለ ፡ ሰማ ፥ ያዕቆብም ፡ ልጆቹን ፦ ለምን ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትተያያላችኹ ፧ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ስንዴ ፡ በግብጽ ፡ እንዲገኝ ፡ ሰምቻለኹ ፤ ወደዚያ ፡ ውረዱ ፥ እንድንድንና ፡ እንዳንሞትም ፡ ከዚያ ፡ ሸምቱልን ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 3 ፤ የዮሴፍም ፡ ዐሥሩ ፡ ወንድሞቹ ፡ ስንዴን ፡ ከግብጽ ፡ ይሸምቱ ፡ ዘንድ ፡ ወረዱ ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 4 ፤ የዮሴፍን ፡ ወንድም ፡ ብንያምን ፡ ግን ፡ ያዕቆብ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ አልሰደደውም ፦ ምናልባት ፡ ክፉ ፡ እንዳያገኘው ፡ ብሏልና ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለእኽል ፡ ሸመታ ፡ ከመጡቱ ፡ ጋራ ፡ ገቡ ፤ በከነዓን ፡ አገር ፡ ራብ ፡ ነበረና ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 6 ፤ የዮሴፍም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ገዢ ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ ለምድር ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይሸጥ ፡ ነበር ፤ የየዮሴፍም ፡ ወንድሞች ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባራቸው ፡ ሰገዱለት ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 7 ፤ የዮሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፡ አይቶ ፡ ዐወቃቸው ፤ ተለወጠባቸውም ፥ ክፉ ፡ ቃልንም ፡ ተናገራቸው ፦ እናንተ ፡ ከወዴት ፡ መጣችኹ ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ ከከነዓን ፡ ምድር ፡ እኽል ፡ ልንሸምት ፡ የመጣን ፡ ነን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 8 ፤ የዮሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፡ ዐወቃቸው ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላወቁትም ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 9 ፤ የዮሴፍም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አይቶት ፡ የነበረውን ፡ ሕልም ፡ ዐሰበ ። እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ ሰላዮች ፡ ናችኹ ፤ የምድሩን ፡ ዕራቍትነት ፡ ልታዩ ፡ መጥታችኋል ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 10 ፤ እነርሱም ፡ አሉት ፦ ጌታችን ፡ ሆይ ፡ አይደለም ፤ ባሪያዎችኽ ፡ ስንዴን ፡ ሊገዙ ፡ መጥተዋል ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 11 ፤ እኛ ፡ ኹላችን ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ነን ፤ እኛ ፡ እውነተኞች ፡ ነን ፥ ባሪያዎችኽስ ፡ ሰላዮች ፡ አይደሉም ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 12 ፤ ርሱም ፡ አላቸው ፦ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአገሩን ፡ ዕራቍትነት ፡ ልታዩ ፡ መጥታችኋል ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ አሉ ፦ ባሪያዎችኽ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወንድማማች ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ነን ፤ ታናሹም ፥ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ከአባታችን ፡ ጋራ ፡ ነው ፥ አንዱም ፡ ጠፍቷል ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 14 ፤ የዮሴፍም ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ ሰላዮች ፡ ናችኹ ፡ ብዬ ፡ የተናገርኋችኹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 15 ፤ በዚህ ፡ ትፈተናላችኹ ፤ ታናሽ ፡ ወንድማችኹ ፡ ካልመጣ ፡ በቀር ፡ የፈርዖንን ፡ ሕይወት ፡ ከዚህ ፡ አትወጡም ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 16 ፤ እውነትን ፡ የምትናገሩ ፡ ከኾነ ፡ ነገራችኹ ፡ ይፈተን ፡ ዘንድ ፡ ከእናንተ ፡ አንዱን ፡ ስደዱ ፥ ወንድማችኹንም ፡ ይዞ ፡ ይምጣ ፡ እናንተም ፡ ታሥራችኹ ፡ ተቀመጡ ፤ ይህ ፡ ካልኾነ ፡ የፈርዖንን ፡ ሕይወት ፡ ሰላዮች ፡ ናችኹ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 17 ፤ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ጨመራቸው ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 18 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የዮሴፍ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ አድርጉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እፈራለኹና ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 19 ፤ እናንተ ፡ የታመናችኹ ፡ ከኾናችኹ ፡ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ወንድማችኹ ፡ በግዞታችኹ ፡ ቤት ፡ ይታሰር ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ኺዱ ፥ እኽሉንም ፡ ለቤታችኹ ፡ ራብ ፡ ውሰዱ ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 20 ፤ ታናሹንም ፡ ወንድማችኹን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይዛችኹ ፡ ኑ ፤ ነገራችኹም ፡ የታመነ ፡ ይኾናልና ፥ አትሞቱም ። እንዲህም ፡ አደረጉ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ተባባሉ ፦ በእውነት ፡ ወንድማችንን ፡ በድለናል ፥ እኛን ፡ በማማጠን ፡ ነፍሱ ፡ ስትጨነቅ ፡ አይተን ፡ አልሰማነውምና ፤ ስለዚህ ፥ ይህ ፡ መከራ ፡ መጣብን ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 22 ፤ ሮቤልም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ብላቴናውን ፡ አትበድሉ ፡ ብያችኹ ፡ አልነበረምን ፧ እኔም ፡ አልሰማችኹኝም ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ኦኩን ፡ ደሙ ፡ ይፈላለገናል ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፡ የዮሴፍ ፡ ነገራቸውን ፡ እንደሚሰማባቸው ፡ አላወቁም ፥ በመካከላቸው ፡ አስተርጓሚ ፡ ነበረና ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 24 ፤ ከነርሱም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ፤ ደግሞም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተመልሶ ፡ ተናገራቸው ፥ ስምዖንንም ፡ ከነርሱ ፡ ለይቶ ፡ ወስዶ ፡ በፊታቸው ፡ አሰረው ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 25 ፤ የሴፍም ፡ ዐይበታቸውን ፡ እኽል ፡ ይሞሉት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ የየራሳቸውንም ፡ ብር ፡ በየዐይበታቸው ፡ ይመልሱት ፡ ዘንድ ፡ ደግሞም ፡ የመንገድ ፡ ሥንቅ ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። እንዲሁም ፡ ተደረገላቸው ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 26 ፤ እነርሱም ፡ እኽሉን ፡ በአህያዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፥ ከዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ኼዱ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 27 ፤ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ባደሩበት ፡ ስፍራ ፡ ለአህያው ፡ ገፈራን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ዐይበቱን ፡ ሲፈታ ፡ ብሩን ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ በዐይበቱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ነበረች ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 28 ፤ ለወንድሞቹም ፦ ብሬ ፡ ተመለሰችልኝ ፥ ርሷም ፡ በዐይበቴ ፡ አፍ ፡ እንሂት ፡ አላቸው ። ልባቸውም ፡ ደነገጠ ፥ እየተንቀጠቀጡም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተባባሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ ያደረገብን ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 29 ፤ ወደ ፡ አባታቸውም ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ መጡ ፥ የደረሰባቸውንም ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አወሩ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 30 ፤ የአገሩ ፡ ጌታ ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ንግግር ፡ ተናገረን ፥ የምድሪቱም ፡ ሰላዮች ፡ አስመሰለን ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 31 ፤ እኛም ፡ እንዲህ ፡ አልነው ፦ እውነተኞች ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡ እንጂ ፡ ሰላዮች ፡ አይደለንም ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 32 ፤ እኛ ፡ የአባታችን ፡ ልጆች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወንድማማች ፡ ነን ፤ አንዱ ፡ ጠፍቷል ፥ ታናሹም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ዛሬ ፡ ከአባታችን ፡ ጋራ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 33 ፤ የአገሩም ፡ ጌታ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ አለን ፦ የታመናችኹ ፡ ሰዎች ፡ ከኾናችኹ ፡ በዚህ ፡ ዐውቃለኹ ፤ አንደኛውን ፡ ወንድማችኹን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተዉት ፥ ለቤታችኹም ፡ ራብ ፡ እኽልን ፡ ወስዳችኹ ፡ ኺዱ ፤

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 34 ፤ ታናሹንም ፡ ወንድማችኹን ፡ አምጡልኝ ፥ እውነተኞች ፡ እንጂ ፡ ሰላዮች ፡ አለመኾናችኹንም ፡ በዚህ ፡ ዐውቀዋለኹ ፤ ወንድማችኹንም ፡ እሰጣችኋለኹ ፥ እናንተም ፡ በምድሩ ፡ ትነግዳላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 35 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዐይበታቸውን ፡ በፈቱ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ከነርሱ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ብራቸውን ፡ በየዐይበታቸው ፡ ተቋጥሮ ፡ አገኙት ፤ እነርሱም ፡ አባታቸውም ፡ የብራቸውን ፡ ቍጥራት ፡ አይተው ፡ ፈሩ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 36 ፤ አባታቸው ፡ ያዕቆብም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ልጅ ፡ አልባ ፡ አስቀራችኹኝ ፤ የሴፍ ፡ የለም ፥ ስምዖንም ፡ የለም ፥ ብንያምንም ፡ ትወስዱብኛላችኹ ፤ ይህ ፡ ሹሉ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ደረሰ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 37 ፤ ሮቤልም ፡ አባቱን ፡ አለው ፦ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ ያላመጣኹት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹለቱን ፡ ልጆቼን ፡ ግደል ፤ ርሱን ፡ በእጄ ፡ ስጠኝ ፥ እኔም ፡ ወዳንተ ፡ እመልሰዋለኹ ።

ዘፍ. ፡ 42 ፡ 38 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ልጄ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አይወርድም ፤ ወንድሙ ፡ ሞቶ ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ቀርቷልና ፤ በምትኼዱበት ፡ መንገድ ፡ ምናልባት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ቢያገኘው ፡ ሽምግልናዬን ፡ በሐዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ታወርዱታላችኹ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 1-2 ፤ ራብም ፡ በምድር ፡ ጸና ። ከግብጽም ፡ ያመጡትን ፡ እኽል ፡ በልተው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ አባታቸው ፦ እንደ ፡ ገና ፡ ኺዱ ፤ ጥቂት ፡ እኽል ፡ ሸምቱልን ፡ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 3 ፤ ይሁዳም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ያ ፡ ሰው ፦ ወንድማችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ካልኾነ ፡ ፊቴን ፡ አታዩም ፡ ብሎ ፡ በብርቱ ፡ ቃል ፡ አስጠነቀቀን ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 4 ፤ ወንድማችንን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ብትሰደው ፡ እንወርዳለን ፥ እኽልም ፡ እንሸምትልኻለን ፤

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 5 ፤ ባትሰደው ፡ ግን ፡ አንኼድም ፤ ያ ፡ ሰው ፦ ወንድማችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ካልኾነ ፡ ፊቴን ፡ አታዩም ፡ ብሎናልና ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 6 ፤ እስራኤልም ፡ አላቸው ፦ ለምን ፡ በደላችኹኝ ፧ ለዚያውስ ፦ ሌላ ፡ ወንድም ፡ አለን ፡ ብላችኹ ፡ ለምን ፡ ነገራችኹት ፧

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፡ አሉ ፦ ያ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ እኛና ፡ ስለ ፡ ወገናችን ፡ ፈጽሞ ፡ ጠየቀን ፡ እንዲህም ፡ አለን ፦ አባታችኹ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ነው ፧ ወንድምስ ፡ አላችኹን ፧ እኛም ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ ጥያቄው ፡ መለስንለት ፤ በእውኑ ፦ ወንድማችኹን ፡ አምጡ ፡ እንዲለን ፡ እናውቅ ፡ ነበርን ፧

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 8 ፤ ይሁዳም ፡ አባቱን ፡ እስራኤልን ፡ አለው ፦ እኛና ፡ አንተ ፡ ልጆቻችንም ፡ ደግሞ ፡ እንድንድን ፡ እንዳንሞትም ፡ ብላቴናውን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ስደደው ፥ እኛም ፡ ተነሥተን ፡ እንኼዳለን ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እዋሳለኹ ፥ ከእጄ ፡ ትሻዋለኽ ፤ ወዳንተ ፡ ባላመጣው ፥ በፊትኽም ፡ ባላቆመው ፥ በዘመናት ፡ ኹሉ ፡ አንተን ፡ የበደልኹ ፡ ልኹን ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 10 ፤ ባንዘገይስ ፡ ኖሮ ፡ አኹን ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ በተመለስን ፡ ነበር ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 11 ፤ እስራኤልም ፡ አባታቸው ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ ከኾነስ ፡ ይህን ፡ አድርጉ ፤ ከተመሰገነው ፡ ከምድሩ ፡ ፍሬ ፡ በዐይበታችኹ ፡ ይዛችኹ ፡ ኺዱ ፥ ለዚያም ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፥ ጥቂት ፡ በለሳን ፥ ጥቂት ፡ ማር ፥ ሽቱ ፥ ከርቤ ፥ ተምር ፥ ለውዝ ፡ ውሰዱ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 12 ፤ ብሩን ፡ በዐጠፌታ ፡ አድርጋችኹ ፡ በእጃችኹ ፡ ውሰዱ ፤ በዐይበታችኹ ፡ አፍ ፡ የተመለሰውንም ፡ ብር ፡ መልሳችኹ ፡ ውሰዱ ፤ ምናልባት ፡ በስሕተት ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 13 ፤ ወንድማችኹንም ፡ ውሰዱ ፥ ተነሥታችኹም ፡ ወደዚያ ፡ ሰው ፡ ተመለሱ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 14 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክም ፡ ሌላውን ፡ ወንድማችኹንና ፡ ብንያምን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይሰድ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ምሕረትን ፡ ይስጣችኹ ፤ እኔም ፡ ልጆቼን ፡ እንዳጣኹ ፡ ዐጣኹ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 15 ፤ ሰዎቹም ፡ በእጃቸው ፡ ያችን ፡ እጅ ፡ መንሻና ፡ ዐጠፌታውን ፡ ብር ፡ ብንያምንም ፡ ወሰዱ ፤ ተነሥተውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረዱ ፥ በዮሴፍም ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 16 ፤ ዮሴፍም ፡ ብንያምን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፦ እነዚያን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አስገባቸው ፥ ዕርድም ፡ ዕረድ ፡ አዘጋጅም ፥ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ በእኩለ ፡ ቀን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይበላሉና ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 17 ፤ ያ ፡ ሰውም ፡ ዮሴፍ ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፤ ያ ፡ ሰውም ፡ ሰዎቹን ፡ ወደዮሴፍ ፡ ቤት ፡ አስገባ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ ወደዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ገቡ ፡ ፈሩ ፤ እንዲህም ፡ አሉ ፦ በዐይበታችን ፡ ቀድሞ ፡ ስለተመለሰው ፡ ብር ፡ ሊተነኰልብን ፡ ሊወድቅብንም ፥ እኛንም ፡ በባርነት ፡ ሊገዛ ፡ አህያዎቻችንንም ፡ ሊወስድ ፡ ወደዚህ ፡ አስገባን ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 19 ፤ ወደዮሴፍ ፡ ቤት ፡ አዛዥም ፡ ቀረቡ ፥ በቤቱም ፡ ደጅ ፡ ተናገሩት ፥

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 20 ፤ እንዲህም ፡ አሉት ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ቀድሞ ፡ እኽልን ፡ ልንሸምት ፡ ወርደን ፡ ነበር ፤

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 21 ፤ ወደምናድርበትም ፡ ስፍራ ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ዐይበታችንን ፡ ከፈትን ፥ እንሆም ፥ የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ብር ፡ በየዐይበቱ ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ሚዛኑ ፡ ብራችን ፡ ነበረ ፤ አኹንም ፡ በእጃችን ፡ መለስነው ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 22 ፤ እኽል ፡ እንሸምትበት ፡ ዘንድ ፡ ሌላም ፡ ብር ፡ በእጃችን ፡ አመጣን ፤ ብራችንንም ፡ በዐይበታችን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ጨመረው ፡ አናውቅም ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ አላቸው ፦ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ፥ አትፍሩ ፤ አምላካችኹና ፡ የአባታችኹ ፡ አምላክ ፡ በዐይበታችኹ ፡ የተሰወረ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጣችኹ ፤ ብራችኹስ ፡ ደርሶኛል ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 24 ፤ ስምዖንንም ፡ አወጣላቸው ። ሰውዮውም ፡ እነዚያን ፡ ሰዎች ፡ ወደዮሴፍ ፡ ቤት ፡ አስገባቸው ፤ ውሃ ፡ አመጣላቸው ፥ እግራቸውንም ፡ ታጠቡ ፤ ለአህያዎቻቸው ፡ አበቅ ፡ ሰጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 25 ፤ ዮሴፍም ፡ በእኩለ ፡ ቀን ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ እነርሱ ፡ እጅ ፡ መንሻቸውን ፡ አዘጋጁ ፥ ከዚያ ፡ እንጀራን ፡ እንደሚበሉ ፡ ሰምተዋልና ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 26 ፤ ዮሴፍም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በእጃቸው ፡ ያለውን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አቀረቡለት ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ ወድቀው ፡ ሰገዱለት ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ ደኅንነታቸውን ፡ ጠየቃቸው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የነገራችኹኝ ፡ ሽማግሌ ፡ አባታችኹ ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ ገና ፡ በሕይወት ፡ አለን ፧

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 28 ፤ እነርሱም ፡ አሉት ፦ ባሪያኽ ፡ አባታችን ፡ ደኅና ፡ ነው ፤ ገና ፡ በሕይወት ፡ አለ ። አጐንብሰውም ፡ ሰገዱለት ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 29 ፤ ዐይኑንም ፡ አንሥቶ ፡ የእናቱን ፡ ልጅ ፡ ብንያምን ፡ አየው ፥ ርሱም ፡ አለ ፦ የነገራችኹኝ ፡ ታናሽ ፡ ወንድማችኹ ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ እንዲህም ፡ አለው ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 30 ፤ ዮሴፍም ፡ ቸኰለ ፥ አንገቱ ፡ ወንድሙን ፡ ናፍቆታልና ፤ ሊያለቅስም ፡ ወደደ ፤ ወደ ፡ ዕልፍኙም ፡ ገብቶ ፡ ከዚያ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 31 ፤ ፊቱንም ፡ ታጥቦ ፡ ወጣ ፥ ልቡንም ፡ አስታግሦ ፦ እንጀራ ፡ አቅርቡ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 32 ፤ ለርሱም ፡ ለብቻው ፡ አቀረቡ ፥ ለእነርሱም ፡ ለብቻቸው ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለሚበሉት ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎችም ፡ ለብቻቸው ፤ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ከዕብራውያን ፡ ጋራ ፡ መብላት ፡ አይኾንላቸውምና ፥ ይህ ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ መርከስ ፡ ነውና ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 33 ፤ በፊቱም ፡ በኵሩ ፡ እንደ ፡ ታላቅነቱ ፡ ታናሹም ፡ እንደ ፡ ታናሽነቱ ፡ ተቀመጡ ፤ ሰዎቹም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተደነቁ ።

ዘፍ. ፡ 43 ፡ 34 ፤ በፊቱም ፡ ካለው ፡ መብል ፡ ፈንታቸውን ፡ አቀረበላቸው ፤ የብንያምም ፡ ፈንታ ፡ ከዅሉ ፡ ዐምስት ፡ እጅ ፡ የሚበልጥ ፡ ነበረ ። እነርሱም ፡ ጠጡ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 44 ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 1 ፤ ዮሴፍም ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፦ ዐይበታቸው ፡ የሚያነሣውን ፡ ያኽል ፡ እኽል ፡ ሙላላቸው ፥ የዅሉንም ፡ ብር ፡ በየዐይበታቸው ፡ አፍ ፡ ጨምረው ፤

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 2 ፤ በታናሹም ፡ ዐይበት ፡ አፍ ፡ የብሩን ፡ ጽዋዬንና ፡ የእኽሉን ፡ ዋጋ ፡ ጨምረው ። ርሱም ፡ ዮሴፍ ፡

እንዳለው ፡ አደረገ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 3 ፤ ነግህ ፡ በኾነ ፡ ጊዜም ፡ ሰዎቹ ፡ አህያዎቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ተሰናበቱ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 4 ፤ ከከተማዩቱም ፡ ወጥተው ፡ ገና ፡ ሳይርቁ ፡ ዮሴፍ ፡ ለቤቱ ፡ አዛዥ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ተነሥተኽ ፡ ሰዎቹን ፡ ተከተላቸው ፤ በደረስኽባቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ በመልካሙ ፡ ፋንታ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ክፉን ፡ መለሳችኹ ፧

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 5 ፤ ጌታዬ ፡ የሚጠጣበት ፡ ምስጢርንም ፡ የሚያውቅበት ፡ ጽዋ ፡ አይደለምን ፧ ባደረጋችኹት ፡ ነገር ፡ በደላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ ደረሰባቸው ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ ነገራቸው ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፡ አሉት ፦ ጌታዬ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ለምን ፡ ይናገራል ፧ ባሪያዎችኽ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚያደርጉ ፡ አይደሉም ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ በዐይበታችን ፡ አፍ ፡ ያገኘነውን ፡ ብር ፡ ይዘን ፡ ከከነዓን ፡ አገር ፡ ወዳንተ ፡ ተመልሰናል ፤ ከጌታኽ ፡ ቤት ፡ ወርቅ ፡ ወይስ ፡ ብር ፡ እንዴት ፡ እንሰርቃለን ፧

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 9 ፤ ከባሪያዎችኽ ፡ ጽዋው ፡ የተገኘበት ፡ ርሱ ፡ ይሙት ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ ለጌታችን ፡ ባሪያዎች ፡ እንኹን ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 10 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ አኹንም ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ነገራችኹ ፡ ይኹን ፤ ጽዋው ፡ የተገኘበት ፡ ርሱ ፡ ለእኔ ፡ ባሪያ ፡ ይኹነኝ ፥ እናንተም ፡ ንጹሓን ፡ ትኾናላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 11 ፤ እየራሳቸውም ፡ ፈጥነው ፡ ዐይበታቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አወረዱ ፥ እየራሳቸውም ፡ ዐይበታቸውን ፡ ፈቱ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 12 ፤ ርሱም ፡ ከታላቁ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታናሹ ፡ ድረስ ፡ በረበራቸው ፥ ጽዋውንም ፡ በብንያም ፡ ዐይበት ፡ ውስጥ ፡ አገኘው ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 13 ፤ ልብሳቸውንም ፡ ቀደዱ ፥ ዐይበታቸውንም ፡ በያህዮቻቸው ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ ተመለሱ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 14 ፤ ይሁዳም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ ገባ ፥ ርሱም ፡ ገና ፡ ከዚያው ፡ ነበረ ፤ በፊቱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቁ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 15 ፤ ዮሴፍም ፦ ይህ ፡ ያደረጋችኹት ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ምስጢርን ፡ እንዲያውቅ ፡ አታውቁምን ፧ አላቸው ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 16 ፤ ይሁዳም ፡ አለ ፦ ለጌታዬ ፡ ምን ፡ እንመልሳለን ፧ ምንስ ፡ እንናገራለን ፧ ወይስ ፡ በምን ፡ እንነጻለን ፧ እግዚአብሔር ፡ የባሪያዎችኽን ፡ ኀጢአት ፡ ገለጠ ፤ እንሆ ፥ እኛም ፡ ጽዋው ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተገኘበቱም ፡ ደግሞ ፡ ለጌታዬ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ነን ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ እላቸው ፦ ይህን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ አይኾንልኝም ፤ ጽዋው ፡ የተገኘበቱ ፡ ሰው ፡ ርሱ ፡ ባሪያ ፡ ይኹነኝ ፤ እናንተም ፡ ወደ ፡ አባታችኹ ፡ በደኅና ፡ ውጡ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 18 ፤ ይሁዳም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በጌታዬ ፡ ጐሮ ፡ አንዲት ፡ ቃልን ፡ እንድናገር ፡ እለምናለኹ ፤ እኔንም ፡ ባሪያኽን ፡ አትቈጣኝ ፤ አንተ ፡ እንደ ፡ ፈርዖን ፡ ነኽና ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 19 ፤ ጌታዬ ፡ ባሪያዎቹን ፦ አባት ፡ አላችኹን ፡ ወይስ ፡ ወንድም ፧ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 20 ፤ እኛም ፡ ለጌታዬ ፡ እንዲህ ፡ አልን ፦ ሽማግሌ ፡ አባት ፡ አለን ፥ በሽምግልናው ፡ የወለደውም ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ አለ ፤ ወንድሙም ፡ ሞተ ፥ ከእናቱም ፡ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ፥ አባቱም ፡ ይወደዋል ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 21 ፤ አንተም ፡ ለባሪያዎችኽ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፥ እኔም ፡ አየዋለኹ ፡ አልኽ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 22 ፤ ጌታዬንም ፦ ብላቴናው ፡ አባቱን ፡ መተው ፡ አይኾንለትም ፤ የተወው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አባቱ ፡ ይሞታልና ፥ አልነው ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 23 ፤ ባሪያዎችኽንም ፦ ታናሽ ፡ ወንድማችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ካልመጣ ፡ ዳግመኛ ፡ ፊቴን ፡ አታዩም ፡ አልኽን ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 24 ፤ ወደ ፡ ባሪያኽ ፡ ወደ ፡ አባታችን ፡ በተመለስን ፡ ጊዜም ፡ የጌታዬን ፡ ቃል ፡ ነገርነው ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 25 ፤ አባታችንም ፦ ተመልሳችኹ ፡ ጥቂት ፡ እኽል ፡ ሸምቱልን ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 26 ፤ እኛም ፡ አልነው ፦ እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ አይኾንልንም ፤ ታናሹ ፡ ወንድማችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይወርድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኛም ፡ እንወርዳለን ፤ ታናሹ ፡ ወንድማችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ከሌለ ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ አይቻለንምና ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 27 ፤ ባሪያኽ ፡ አባቴም ፡ እንዲህ ፡ አለን ፦ ሚስቴ ፡ ኹለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችን ፡ እንደ ፡ ወለደችልኝ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ፤

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 28 ፤ አንዱም ፡ ከእኔ ፡ ወጣ ፦ አውሬ ፡ በላው ፡ አላችኹኝ ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ አላየኹትም ፤

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 29 ፤ ይህንም ፡ ከእኔ ፡ ለይታችኹ ፡ ደግሞ ፡ ብትወስዱት ፡ ክፋም ፡ ቢያገኘው ፥ ሽበቴን ፡ በሐዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ታወርዱታላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 30 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ ወደ ፡ ባሪያኽ ፡ ብኼድ ፥ ብላቴናውም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ከሌለ ፥ ነፍሱ ፡ በብላቴናው ፡ ነፍስ ፡ ታስራለችና ፡ ብላቴናው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንደሌለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ይሞታል ፤

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 31 ፤ ባሪያዎችኽም ፡ የባሪያኽን ፡ የአባታችንን ፡ ሽበት ፡ በሐዘን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ያወርዳሉ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 32 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ብላቴናው ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ተውሼያለኹና ፦ ርሱንስ ፡ ወዳንተ ፡ ባላመጣው ፡ በአባቴ ፡ ዘንድ ፡ በዘመናት ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአተኛ ፡ እኾናለኹ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 33 ፤ ስለዚህም ፡ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በጌታዬ ፡ ዘንድ ፡ ባሪያ ፡ ኾኜ ፡ በብላቴናው ፡ ፋንታ ፡ ልቀመጥ ፤ ብላቴናውም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ይውጣ ።

ዘፍ. ፡ 44 ፡ 34 ፤ አለዚያም ፡ ብላቴናው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ከሌለ ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ እንዴት ፡ እወጣለኹ ፧ አባቴን ፡ የሚያገኘውን ፡ መከራ ፡ እንዳላይ ።

ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 1 ፤ ዮሴፍም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቆመው ፡ ባሉት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ሊታገሥ ፡ አልተቻለውም ። ሰዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ ከፊቴ ፡ አስወጡልኝ ፡ ብሎ ፡ ጮኾ ፡ ተናገረ ፤ ዮሴፍ ፡ ለወንድሞቹ ፡ ራሱን ፡ በገለጠ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የቆመ ፡ ማንም ፡ አልነበረም ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 2 ፤ ቃሉንም ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ፤ የግብጽ ፡ ሰዎችም ፡ ሰሙ ፥ በፈርዖን ፡ ቤትም ፡ ተሰማ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 3 ፤ ዮሴፍም ፡ ለወንድሞቹ ፦ እኔ ፡ ዮሴፍ ፡ ነኝ ፤ አባቴ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ በሕይወቱ ፡ ነውን ፧ አለ ። ወንድሞቹም ፡ ይመልሱለት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፥ በፊቱ ፡ ደንግጠው ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 4 ፤ ዮሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረቡ ፡ አለ ። ወደ ፡ ርሱም ፡ ቀረቡ ። እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የሸጣችኹኝ ፡ እኔ ፡ ወንድማችኹ ፡ ዮሴፍ ፡ ነኝ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ ወደዚህ ፡ ስለ ፡ ሸጣችኹኝ ፡ አትዘኑ ፥ አትቈርቈሩም ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕይወትን ፡ ለማዳን ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ ሰዶኛልና ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 6 ፤ ይህ ፡ ኹለቱ ፡ ዓመት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ የኾነበት ፡ ነውና ፤ የማይታረስበትና ፡ የማይታጨድበት ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ገና ፡ ቀረ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ቅሬታን ፡ አስቀርላችኹ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ መድኀኒትም ፡ አድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ ላከኝ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ ወደዚህ ፡ የላካችኹኝ ፡ አይደላችኹም ፥ እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ፡ እንጂ ፤ ለፈርዖንም ፡ እንደ ፡ አባት ፡ አደረገኝ ፥ በቤቱም ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ጌታ ፥ በግብጽ ፡ ምድርም ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አደረገኝ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 9 ፤ አኹንም ፡ ፈጥናችኹ ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ ውጡ ፥ እንዲህም ፡ በሉት ፦ ልጅኽ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚለው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ጌታ ፡ አደረገኝ ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ና ፥ አትዘግይ ፤

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 10 ፤ በጌሤምም ፡ ምድር ፡ ትቀመጣለኽ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ትቀርባለኽ ፥ አንተና ፡ ልጆችኽ ፡ የልጆችኽም ፡ ልጆች ፥ በጎችኽና ፡ ላሞችኽ ፡ ከብትኽም ፡ ሹሉ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ አንተና ፡ የቤትኽ ፡ ሰዎች ፡ የአንተ ፡ የኾነው ፡ ሹሉ ፡ እንዳትቸገሩ ፡ እመግብኻለኹ ፡ የራቡ ፡ ዘመን ፡ ገና ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ቀርቷልና ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 12 ፤ እንሆም ፡ ለእናንተ ፡ የተናገረቻችኹ ፡ የእኔ ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ የእናንተ ፡ ዐይኖች ፡ አይተዋል ፥ የወንድሜ ፡ የብንያምም ፡ ዐይኖች ፡ አይተዋል ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 13 ፤ ለአባቴም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ያለኝን ፡ ክብሬን ፡ ሹሉ ፡ ያያችኹትንም ፡ ሹሉ ፡ ንገሩት ፤ አባቴንም ፡ ወደዚህ ፡ ፈጥናችኹ ፡ አምጡት ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 14 ፤ የወንድሙን ፡ የብንያምንም ፡ ዐንገት ፡ ዐቅፎ ፡ አለቀሰ ፤ ብንያምም ፡ በዐንገቱ ፡ ላይ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 15 ፤ ወንድሞቹን ፡ ሹሉ ፡ ሳማቸው ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ አለቀሰ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወንድሞቹ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተጫወቱ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 16 ፤ በፈርዖንም ፡ ቤት ። የዮሴፍ ፡ ወንድሞች ፡ መጡ ፡ ተብሎ ፡ ወሬ ፡ ተሰማ ፤ በዚያውም ፡ ፈርዖንና ፡ ሎላልቱ ፡ ደስ ፡ ተሠኙበት ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 17 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፡ አለው ፦ ለወንድሞችኽ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ይህን ፡ አድርጉ ፤ ከብቶቻችኹን ፡ ጭናችኹ ፡ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡ ኺዱ ፤

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 18 ፤ አባታችኹንና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻችኹን ፡ ይዛችኹም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፤ እኔም ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ በረከት ፡ ሹሉ ፡ እሰጣችኋለኹ ፥ የምድሪቱንም ፡ ስብ ፡ ትበላላችኹ ።

ዘፍ. ፡ 45 ፡ 19 ፤ አንተም ፡ ወንድሞችኽን ፦ እንዲህ ፡ አድርጉ ፡ በላቸው ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ለሕፃናታችኹ ፡

ለሴቶቻችኹም ፡ ሠረገላዎችን ፡ ውሰዱ ፥ አባታችኹንም ፡ ይዛችኹ ፡ ኑ ፤

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 20 ፤ ለዕቃችኹም ፡ ኹሉ ፡ አታስቡ ፥ የግብጽ ፡ በረከት ፡ ኹሉ ፡ ለእናንተ ፡ ነውና ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 21 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ እንደዚሁ ፡ አደረጉ ፤ ዮሴፍም ፡ በፈርዖን ፡ ትእዛዝ ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ለመንገድ ፡ ሥንቅ ፡ ሰጣቸው ፤

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 22 ፤ ለኹሉም ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ሰጣቸው ፥ ለብንያም ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ብርና ፡ ዐምስት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ሰጠው ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 23 ፤ ለአባቱም ፡ እንደዚሁ ፡ ሰደደ ፥ የግብጽን ፡ በረከት ፡ የተሸከሙ ፡ ዐሥር ፡ አህያዎችን ፥ ደግሞም ፡ በመንገድ ፡ ለአባቱ ፡ ሥንቅ ፡ ስንዴና ፡ እንጀራ ፡ የተሸከሙ ፡ ዐሥር ፡ ሴቶች ፡ አህያዎችን ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 24 ፤ ዮሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፡ አሰናበታቸው ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ በመንገድ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አትጣሉ ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 25 ፤ እነርሱም ፡ ኼዱ ፥ ከግብጽ ፡ አገርም ፡ ወጡ ፥ ወደከነዓንም ፡ ምድር ፡ ከአባታቸው ፡ ከያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ ደረሱ ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 26 ፤ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፦ ዮሴፍ ፡ ገና ፡ በሕይወቱ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ገዢ ፡ ኾኗል ። ያዕቆብም ፡ ልቡ ፡ ደነገጠ ፥ አላመናቸውም ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 27 ፤ እነርሱም ፡ ዮሴፍ ፡ የነገራቸውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ነገሩት ፤ ርሱን ፡ ያነሡት ፡ ዘንድ ፡ ዮሴፍ ፡ የሰደዳቸውን ፡ ሠረገላዎች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የአባታቸው ፡ የያዕቆብ ፡ የነፍሱ ፡ ሕይወት ፡ ታደሰች ።

ዘፍ. ፥ 45 ፥ 28 ፤ እስራኤልም ፦ ልጄ ፡ ዮሴፍ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ከኾነ ፡ ይበቃኛል ፤ ሳልሞት ፡ እንዳየው ፡ እኼዳለኹ ፡ አለ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ። _____

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 1 ፤ እስራኤልም ፡ ለርሱ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ ተነሣ ፥ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ መጣ ፥ መሥዋዕትንም ፡ ለአባቱ ፡ ለይሥሐቅ ፡ አምላክ ፡ ሠዋ ።

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፦ ያዕቆብ ፥ ያዕቆብ ፥ ብሎ ፡ ለእስራኤል ፡ ተናገረው ። ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 3 ፤ አለውም ፦ የአባቶችኽ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መውረድ ፡ አትፍራ ፥ በዚያ ፡ ትልቅ ፡ ሕዝብ ፡ አደርግኻለኹና ።

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 4 ፤ እኔ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ዐብሬኽ ፡ እወርዳለኹ ፥ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ አወጣኻለኹ ፤ ዮሴፍም ፡ እጁን ፡ በዐይንኽ ፡ ላይ ፡ ያኖራል ።

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 5 ፤ ያዕቆብም ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ተነሣ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያዕቆብን ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ ፈርዖን ፡ በሰደዳቸው ፡ ሠረገላዎች ፡ አባታቸውን ፡ ያዕቆብንና ፡ ሕፃናታቸውን ፡ ሴቶቻቸውንም ፡ ወሰዱ ።

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 6 ፤ እንስሳዎቻቸውንም ፡ በከነዓን ፡ አገርም ፡ ያገኙትን ፡ ከብታቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይዘው ፡ ያዕቆብና ፡ ዘሩ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መጡ ፤

ዘፍ. ፥ 46 ፥ 7 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቹንና ፡ የልጆቹን ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፥ ሴቶች ፡ ልጆቹንና ፡ የወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፥ ዘሩንም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አስገባቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ የገቡት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ያዕቆብና ፡ ልጆቹ ፤ የያዕቆብ ፡ በኵር ፡ ሮቤል ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 9 ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፤ ሄኖኅ ፥ ፈሉስ ፥ አስሮን ፥ ከርሚ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 10 ፤ የስሞዖን ፡ ልጆች ፤ ይሙኤል ፥ ያሚን ፥ ኦሃድ ፥ ያኪን ፥ ጾሐር ፥ የከነዓናዊት ፡ ልጅ ፡ ሳኡል ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 11 ፤ የሌዊም ፡ ልጆች ፤ ጌድሶን ([50]) ፥ ቀአት ([51]) ፥ ሜራሪ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 12 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፤ ዔር ፥ አውናን ፥ ሴሎም ([52]) ፥ ፋሬስ ([53]) ፥ ዛራ ፤ ዔርና ፡ አውናን ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ሞቱ ፤ የፋሬስም ፡ ልጆች ፡ ኤስሮም ([54]) ፥ ሐሙል ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 13 ፤ የይሳኮርም ፡ ልጆች ፤ ቶላ ([55]) ፥ ፉዋ ፥ ዮብ ፥ ሺምሮን ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 14 ፤ የዛብሎንም ፡ ልጆች ፤ ሴሬድ ፥ ኤሎን ፥ ያሕልኤል ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 15 ፤ ልያ ፡ በመስጴጦምያ ፡ በሶርያ ፡ ለያዕቆብ ፡ የወለደቻቸው ፡ ልጆችና ፡ ሴቲቱ ፡ ልጇ ፡ ዲና ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ልጆቿ ፡ ኹሉ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ነፍስ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 16 ፤ የጋድም ፡ ልጆች ፡ ጽፎን ፥ ሐጊ ፥ ሹኒ ፥ ኤስቦን ([56]) ፥ ዔሪ ፥ አሮዲ ፥ አርኤሊ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 17 ፤ የአሴርም ፡ ልጆች ፤ ዩምና ፥ የሱዋ ፥ የሱዊ ፥ በሪዐ ፥ እኅታቸው ፡ ሤራሕ ፤ የበሪዐ ፡ ልጆችም ፤ ሔቤር ፥ መልኪኤል ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 18 ፤ ላባ ፡ ለልጁ ፡ ለልያ ፡ የሰጣት ፡ የዘለፋ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እነዚህን ፡ ዐሥራ ፡ ስድስቱንም ፡ ነፍስ ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደች ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 19 ፤ የያዕቆብ ፡ ሚስት ፡ የራሔል ፡ ልጆች ፡ ዮሴፍና ፡ ብንያም ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 20 ፤ ለዮሴፍም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ፡ ተወለዱለት ፤ የሄልዮቱ ፡ ከተማ ፡ ካህን ፡ የጶጥፌራ ፡ ልጅ ፡ አሥናት ፡ የወለደቻቸው ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 21 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፤ ቤላ ([57]) ፥ ቤኬር ([58]) ፥ አስቤል ፤ የቤላ ፡ ልጆችም ፤ ጌራ ፥ ናዕማን ፥ አኪ ([59]) ፥ ሮስ ([60]) ፥ ማንፌን ፥ ሑፊም ፤ ጌራም ፡ አርድን ፡ ወለደ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 22 ፤ ለያዕቆብ ፡ የተወለዱለት ፡ የራሔልም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ኹሉም ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ነፍስ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 23 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፤ ሑሺም ።

---

50 ዕብ. ፥ ጌርሾን/ጌርሾም
51 ዕብ. ፥ ቀሀት ።
52 ዕብ. ፥ ሼላሕ ።
53 ዕብ. ፥ ፌሬጽ/ፔሬጽ ።
54 ዕብ. ፥ ሔጽሮን ።
55 ዕብ. ፥ ቶላዕ ፡ (ትል) ።
56 ዕብ. ፥ ኤጽቦን ።
57 ዕብ. ፥ ቤላዕ ፥ (በልዐ ፥ በላ) ።
58 ዕብ. ፥ ቤኬር ፡ (በኵር) ።
59 ዕብ. ፥ አኒ ፡ (አኅው ፥ ወንድማዊ) ።
60 ዕብ. ፥ ሮሽ ፡ (ርእስ ፥ ራስ) ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 24 ፤ የንፍታሌምም ፡ ልጆች ፤ ያሕጽኤል ፥ ጉኒ ፥ ዬጽር ፥ ሺሌም ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 25 ፤ ላባ ፡ ለልጁ ፡ ለራሔል ፡ የሰጣት ፡ የባላ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እነዚህንም ፡ ለያዕቆብ ፡ ወለደችለት ፤ ሹሉም ፡ ሰባት ፡ ነፍስ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 26 ፤ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የገቡት ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ከጕልበቱ ፡ የወጡት ፥ ከልጆቹ ፡ ሚስቶች ፡ ሌላ ፥ ሹላቸው ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 27 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የተወለዱለት ፡ የዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ኹለት ፡ ናቸው ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የገቡት ፡ የያዕቆብ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ሰባ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 28 ፤ ይሁዳንም ፡ በጌሤም ፡ እንዲቀበለው ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ ላከ ፤ ወደ ፡ ጌሤም ፡ ምድርም ፡ ደረሱ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 29 ፤ ዮሴፍም ፡ ሠረገላውን ፡ አዘጋጀ ፥ አባቱንም ፡ እስራኤልን ፡ ሊገናኘው ፡ ወደ ፡ ጌሤም ፡ ወጣ ፤ ባየውም ፡ ጊዜ ፡ በዐንገቱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ ዐቅፎትም ፡ ረዥም ፡ ጊዜ ፡ አለቀሰ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 30 ፤ እስራኤልም ፡ ዮሴፍን ፦ አንተ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ሳለኽ ፡ ፊትኽን ፡ አይቻለኹና ፡ አኹን ፡ ልሙት ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 31 ፤ ዮሴፍም ፡ ወንድሞቹንና ፡ የአባቱን ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እኔ ፡ መጥቼ ፡ ለፈርዖን ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ እነግረዋለኹ ። በከነዓን ፡ ምድር ፡ የነበሩት ፡ ወንድሞቼና ፡ የአባቴ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተዋል ፤

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 32 ፤ እነርሱም ፡ በግ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፥ እንስሳ ፡ ያረቡ ፡ ነበርና ፤ በጎቻቸውንና ፡ ላሞቻቸውን ፡ ያላቸውንም ፡ ሹሉ ፡ አመጡ ።

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 33 ፤ ፈርዖንም ፡ ቢጠራችኹ ፦ ተግባራችኹስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ቢላችኹ ፥

ዘፍ. ፡ 46 ፡ 34 ፤ በግ ፡ ጠባቂ ፡ ሹሉ ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፥ በጌሤም ፡ እንድትቀመጡ ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ከብላቴናነታችን ፡ ዠምረን ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፥ እኛም ፡ አባቶቻችንም ፥ እንስሳ ፡ አርቢዎች ፡ ነን ።

[ቊ.28 ፤ ጌሤም ፡ የሚለውን ፡ የግእዝ ፡ መጽሐፍ ፡ ራምሴ ፡ ይለዋል ።]

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ። _____

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 1 ፤ ዮሴፍም ፡ ገባ ፥ ለፈርዖንም ፡ ነገረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፦ አባቴና ፡ ወንድሞቼ ፡ በጎቻቸውም ፡ ላሞቻቸውም ፡ ያላቸውም ፡ ሹሉ ፡ ከከነዓን ፡ ምድር ፡ ወጡ ፤ እነርሱም ፥ እንሆ ፥ በጌሤም ፡ ምድር ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 2 ፤ ከወንድሞቹም ፡ ዐምስት ፡ ሰዎችን ፡ ወስዶ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ አቆማቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 3 ፤ ፈርዖንም ፡ ወንድሞቹን ፦ ሥራችኹ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ። እነርሱም ፡ ፈርዖንን ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፥ እኛም ፡ አባቶቻችንም ፥ በግ ፡ አርቢዎች ፡ ነን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 4 ፤ ፈርዖንንም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ። በምድር ፡ ልንቀመጥ ፡ በእንግድነት ፡ መጣን ፥ የባሪያዎችኽ ፡ በጎች ፡ የሚሰማሩበት ፡ ስፍራ ፡ የለምና ፤ ራብ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ ጸንቷልና ፤ አኹንም ፡ ባሪያዎችኽ ፡ በጌሤም ፡ ምድር ፡ እንድንቀመጥ ፡ እንለምንኻለን ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 5 ፤ ፈርዖንም ፡ ዮሴፍን ፡ ተናገረው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፦ አባትኽና ፡ ወንድሞችኽ ፡ መጥተውልኻል ፤

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 6 ፤ የግብጽ ፡ ምድር ፡ በፊትኽ ፡ ናት ፤ በመልካሙ ፡ ምድር ፡ አባትኽንና ፡ ወንድሞችኽን ፡ አኑራቸው ፤ በጌሤም ፡ ምድር ፡ ይኑሩ ፤ ከነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ታውቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእንስሳዎቼ ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ አድርጋቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 7 ፤ ዮሴፍም ፡ ያዕቆብን ፡ አባቱን ፡ አስገብቶ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ አቆመው ፤ ያዕቆብም ፡ ፈርዖንን ፡ ባረከው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 8 ፤ ፈርዖንም ፡ ያዕቆብን ፦ የዕድሜኽ ፡ ዘመን ፡ ስንት ፡ ዓመት ፡ ነው ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 9 ፤ ያዕቆብም ፡ ለፈርዖን ፡ አለው ፦ የእንግድነቴ ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነው ፤ የሕይወቴ ፡ ዘመኖች ፡ ጥቂትም ፡ ክፉም ፡ ኾኑብኝ ፥ አባቶቼ ፡ በእንግድነት ፡ የተቀመጡበትንም ፡ ዘመን ፡ አያኽሉም ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 10 ፤ ያዕቆብም ፡ ፈርዖንን ፡ ባረከው ፡ ከፈርዖንም ፡ ፊት ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 11 ፤ ዮሴፍም ፡ አባቱንና ፡ ወንድሞቹን ፡ አኖረ ፥ ፈርዖን ፡ እንዳዘዘም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በተሻለችው ፡ በራምሴ ፡ ምድር ፡ ጕልትን ፡ ሰጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 12 ፤ ዮሴፍም ፡ ለአባቱና ፡ ለወንድሞቹ ፡ ለአባቱም ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸው ፡ መጠን ፡ እኽል ፡ ሰጣቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 13 ፤ በምድርም ፡ ኹሉ ፡ እኽል ፡ አልነበረም ፥ ራብ ፡ እጅግ ፡ ጸንቷልና ፤ ከራብም ፡ የተነሣ ፡ የግብጽ ፡ ምድርና ፡ የከነዓን ፡ ምድር ፡ ተጐዳ ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 14 ፤ ዮሴፍም ፡ ከግብጽ ፡ ምድርና ፡ ከከነዓን ፡ ምድር ፡ በእኽል ፡ ሸመት ፡ የተገኘውን ፡ ብሩን ፡ ኹሉ ፡ አከማቸ ፤ ዮሴፍም ፡ ብሩን ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ቤት ፡ አስገባው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 15 ፤ ብሩም ፡ በግብጽ ፡ ምድርና ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ዐለቀ ፤ የግብጽ ፡ ሰዎችም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ መጡ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፦ እንጀራ ፡ ስጠን ፤ ስለ ፡ ምን ፡ በፊትኽ ፡ እንሞታለን ፧ ብሩ ፡ አልቆብናልና ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 16 ፤ ዮሴፍም ፦ ከብቶቻችኹን ፡ አምጡልኝ ፤ ብር ፡ ካለቀባችኹ ፡ በከብቶቻችኹ ፡ ፋንታ ፡ እኽል ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 17 ፤ ከብቶቻቸውንም ፡ ወደ ፡ ዮሴፍ ፡ አመጡ ፥ ዮሴፍም ፡ በፈረሶቻቸው ፣ በበጎቻቸውም ፣ በላሞቻቸውም ፣ በአህያዎቻቸውም ፡ ፋንታ ፡ እኽልን ፡ ሰጣቸው ፤ በዚያች ፡ ዓመትም ፣ ስለ ፡ ከብቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ እኽልን ፡ መገባቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 18 ፤ ዓመቱም ፡ ተፈጸመ ፤ በኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ እኛ ፡ ከጌታችን ፡ አንሰውርም ፤ ብሩ ፡ በፍጹም ፡ ዐለቀ ፥ ከብታችንም ፡ ከጌታችን ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ከሰውነታችንና ፡ ከምድራችን ፡ በቀር ፡ በጌታችን ፡ ፊት ፡ አንዳች ፡ የቀረ ፡ የለም ፤

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 19 ፤ እኛ ፡ በፊትኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንሞታለን ፧ ምድራችንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትጠፋለች ፧ እኛንም ፡ ምድራችንንም ፡ በእኽል ፡ ግዛን ፥ እኛም ፡ ለፈርዖን ፡ ባሪያዎች ፡ እንኹን ፥ ምድራችንም ፡ ለርሱ ፡ ትኹን ፤ እኛ ፡ እንድንድን ፡ እንዳንሞትም ፡ ምድራችንም ፡ እንዳትጠፋ ፡ ዘር ፡ ስጠን ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 20 ፤ ዮሴፍም ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለፈርዖን ፡ ገዛ ፥ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ራብ ፡ ስለ ፡ ጸናባቸው ፡ ርስታቸውን ፡ ሸጠዋልና ፤ ምድሪቱ ፡ ለፈርዖን ፡ ኾነች ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 21 ፤ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ ከግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሌላው ፡ ዳርቻዋ ፡ ድረስ ፡ ባሪያዎች ፡

አደረጋቸው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 22 ፤ የካህናትን ፡ ምድር ፡ ብቻ ፡ አልገዛም ፥ ካህናቱ ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ድርጎ ፡ ያገኙ ፡ ነበርና ፥ ፈርዖንም ፡ የሰጣቸውን ፡ ድርጎ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፡ ምድራቸውን ፡ አልሸጡም ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 23 ፤ የሴፍም ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ እናንተንና ፡ ምድራችኹን ፡ ለፈርዖን ፡ ገዝቻችኋለኹ ፤ ዘር ፡ ውሰዱና ፡ ምድሪቱን ፡ ዝሩ ፤

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 24 ፤ በመከርም ፡ ጊዜ ፡ ፍሬውን ፡ ከዐምስት ፡ እጅ ፡ አንዱን ፡ እጅ ፡ ለፈርዖን ፡ ስጡ ፤ አራቱም ፡ እጅ ፡ ለእናንተ ፡ ለራሳችኹ ፥ ለዕርሻው ፡ ዘርና ፡ ለእናንተ ፡ ምግብ ፥ ለቤተ ፡ ሰዋችኹና ፡ ለሕፃናታችኹም ፡ ሲሳይ ፡ ይኹን ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 25 ፤ እነርሱም ፦ አንተ ፡ አዳንኸን ፤ በጌታችን ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ እናግኝ ፥ ለፈርዖንም ፡ ባሪያዎች ፡ እንኾናለን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 26 ፤ የሴፍም ፥ ለፈርዖን ፡ ካልኾነችው ፡ ከካህናቱ ፡ ምድር ፡ በቀር ፥ ዐምስተኛው ፡ እጅ ፡ ለፈርዖን ፡ እንዲኾን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሕግ ፡ አደረጋት ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 27 ፤ እስራኤልም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በጌሤም ፡ አገር ፡ ተቀመጠ ፤ ገዟትም ፥ ረቡ ፥ እጅግም ፡ በዙ ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 28 ፤ ያዕቆብም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ፤ የያዕቆብም ፡ መላው ፡ የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 29 ፤ የእስራኤልም ፡ የሞቱ ፡ ቀን ፡ ቀረበ ፤ ልጁን ፡ የሴፍንም ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በፊትኽ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እጅኽን ፡ ከጭኔ ፡ በታች ፡ አድርግ ፥ በግብጽ ፡ ምድርም ፡ እንዳትቀብረኝ ፡ ምሕረትንና ፡ እውነትን ፡ አድርግልኝ ፤

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 30 ፤ ከአባቶቼም ፡ ጋራ ፡ በተኛኹ ፡ ጊዜ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አውጥተኽ ፡ ትወስደኛለኽ ፥ በመቃብራቸውም ፡ ትቀብረኛለኽ ። ርሱም ፦ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ አደርጋለኹ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 47 ፡ 31 ፤ ርሱም ፦ ማልልኝ ፡ አለው ። የሴፍም ፡ ማለለት ፤ እስራኤልም ፡ በዐልጋው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ሰገደ ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 48 ። _____

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ እንሆ ፥ አባትኽ ፡ ታሟል ፡ ብለው ፡ ለዮሴፍ ፡ ነገሩት ፤ ርሱም ፡ ኹለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ምናሴንና ፡ ኤፍሬምን ፡ ይዞ ፡ ኼደ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 2 ፤ ለያዕቆብም ፦ እንሆ ፥ ልጅኽ ፡ የሴፍ ፡ መጥቶልኻል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፤ እስራኤልም ፡ ተጠነካከረ ፥ በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 3 ፤ ያዕቆብ ፡ የሴፍን ፡ አለው ፦ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ በሎዛ ፡ ተገለጠልኝ ፥ ባረከኝም ፡

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ እንሆ ፥ ፍሬያማ ፡ አደርግኻለኹ ፥ አበዛኻለኹም ፥ ለብዙም ፡ ሕዝብ ፡ ጉባኤ ፡ አደርግኻለኹ ፤ ይህችንም ፡ ምድር ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ርስት ፡ ለዘርኽ ፡ እሰጣታለኹ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ወዳንተ ፡ ከመምጣቴ ፡ በፊት ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የተወለዱልኽ ፡ ኹለቱ ፡ ልጆችኽ ፡ ለእኔ ፡ ይኹኑ ፤ ኤፍሬምና ፡ ምናሴ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ሮቤልና ፡ እንደ ፡ ስምዖን ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 6 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የምትወልዳቸው ፡ ልጆች ፡ ለአንተ ፡ ይኹኑ ፤ በርስታቸው ፡ በወንድሞቻቸው ፡

ስም ፡ ይጠሩ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 7 ፤ እኔም ፡ ከመስጴጦምያ ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ኤፍራታ ፡ ለመግባት ፡ ጥቂት ፡ ቀርቶኝ ፡ በመንገድ ፡ ሳለኹ ፥ ራሔል ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ሞተችብኝ ፤ በዚያም ፡ በኤፍራታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፥ ርሷም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ናት ፥ ቀበርኋት ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 8 ፤ እስራኤልም ፡ የዮሴፍን ፡ ልጆች ፡ አይቶ ፦ እነዚህ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧ አለው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 9 ፤ ዮሴፍም ፡ ለአባቱ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ የሰጠኝ ፡ ልጆቼ ፡ ናቸው ፡ አለ ። ርሱም ፦ እባርካቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ አቅርብልኝ ፡ አለ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ዐይኖች ፡ ከሽምግልና ፡ የተነሣ ፡ ከብደው ፡ ነበር ፥ ማየትም ፡ አይችልም ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ አቀረባቸው ፥ ሳማቸውም ፥ ዐቀፋቸውም ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 11 ፤ እስራኤልም ፡ ዮሴፍን ፦ ፊትኽን ፡ አያለኹ ፡ ብዬ ፡ አላሰብኹም ፡ ነበር ፤ እንሆም ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርኽን ፡ ደግሞ ፡ አሳየኝ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 12 ፤ ዮሴፍም ፡ ከጕልበቱ ፡ ፈቀቅ ፡ አደረጋቸው ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ በግንባሩ ፡ ሰገደ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 13 ፤ ዮሴፍም ፡ ኹለቱን ፡ ልጆቹን ፡ ወሰደ ፥ ኤፍሬምንም ፡ በቀኙ ፡ በእስራኤል ፡ ግራ ፥ ምናሴንም ፡ በግራው ፡ በእስራኤል ፡ ቀኝ ፡ አደረገው ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ አቀረባቸው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 14 ፤ እስራኤልም ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ በኤፍሬም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አኖረው ፥ ርሱም ፡ ታናሽ ፡ ነበረ ፥ ግራውንም ፡ በምናሴ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አኖረ ፤ እጆቹንም ፡ አስተላለፈ ፥ ምናሴ ፡ በኵር ፡ ነበርና ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 15 ፤ ያዕቆብም ፡ ዮሴፍን ፡ ባረከ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ አባቶቼ ፡ አብርሃምና ፡ ይሥሐቅ ፡ በፊቱ ፡ የኼዱለት ፡ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፥ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እኔን ፡ የመገበኝ ፡ እግዚአብሔር ፥

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 16 ፤ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ዋሉ ፡ ያዳነኝ ፡ መልአክ ፥ ርሱ ፡ እነዚህን ፡ ብላቴናዎች ፡ ይባርክ ፤ ስሜም ፡ የአባቶቼ ፡ የአብርሃምና ፡ የይሥሐቅም ፡ ስም ፡ በእነርሱ ፡ ይጠራ ፤ በምድርም ፡ መካከል ፡ ይብዙ ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 17 ፤ ዮሴፍም ፡ አባቱ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ በኤፍሬም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አሳዘነው ፤ የአባቱንም ፡ እጅ ፡ በምናሴ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭነው ፡ ዘንድ ፡ ከኤፍሬም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አነሣው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 18 ፤ ዮሴፍም ፡ አባቱን ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፥ በኵሩ ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ ቀኝኽን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 19 ፤ አባቱም ፡ እንቢ ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ዐወቅኹ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ዐወቅኹ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ሕዝብ ፡ ይኾናል ፡ ታላቅም ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ታናሽ ፡ ወንድሙ ፡ ከርሱ ፡ ይበልጣል ፥ ዘሩም ፡ የአሕዛብ ፡ ሙላት ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ባረካቸው ፦ በእናንተ ፡ እስራኤል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይባርካል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኤፍሬምና ፡ እንደ ፡ ምናሴ ፡ ያድርግኽ ። ኤፍሬምንም ፡ ከምናሴ ፡ ፊት ፡ አደረገው ።

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 21 ፤ እስራኤልም ፡ ዮሴፍን ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ እሞታለኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፥ ወደ ፡ አባቶቻችኹም ፡ ምድር ፡ ይመልሳችኋል ፤

ዘፍ. ፡ 48 ፡ 22 ፤ እኔም ፡ ከአሞራውያን ፡ በሰይፌና ፡ በቀስቴ ፡ የወሰድኹትን ፡ ለአንተ ፡ ከወንድሞችኽ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ አብልጬ ፡ ሰጠኹኽ ፡ አለው ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 49 ። _____

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 1 ፤ ያዕቆብም ፡ ልጆቹን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሚያገኛችኹን ፡ እንድነግራችኹ ፡ ተሰብሰቡ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 2 ፤ እናንት ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ተሰብሰቡ ፥ ስሙም ፤ አባታችኹ ፡ እስራኤልንም ፡ አድምጡ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 3 ፤ ሮቤል ፥ አንተ ፡ በኵር ፡ ልጄና ፡ ኀይሌ ፥ የጕብዝናዬም ፡ መዠመሪያ ፡ ነኽ ፤ የክብር ፡ አለቃና ፡ የኀይል ፡ አለቃ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 4 ፤ እንደ ፡ ውሃ ፡ የምትዋልል ፡ ነኽ ፤ አለቅነት ፡ ለአንተ ፡ አይኹን ፤ ወዳባትኽ ፡ መኝታ ፡ ወጥተኻልና ፤ አረከስኸውም ፤ ወደ ፡ ዐልጋዬም ፡ ወጣ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 5 ፤ ስምዖንና ፡ ሌዊ ፡ ወንድማማች ፡ ናቸው ፤ ሰይፎቻቸው ፡ የዐመፃ ፡ መሣሪያ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 6 ፤ በምክራቸው ፥ ነፍሴ ፥ አትግባ ፤ ከጉባኤያቸውም ፡ ጋራ ፥ ክብሬ ፥ አትተባበር ፤ በቀኑጣቸው ፡ ሰውን ፡ ገድለዋልና ፥ በገዛ ፡ ፈቃዳቸውም ፡ በሬን ፡ አስነክሰዋልና ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 7 ፤ ቀኑጣቸው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፥ ጽኑ ፡ ነበርና ፤ ኵርፍታቸውም ፥ ብርቱ ፡ ነበርና ፤ በያዕቆብ ፡ እከፋፍላቸዋለኹ ፥ በእስራኤልም ፡ እበታትናቸዋለኹ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 8 ፤ ይሁዳ ፥ ወንድሞችኽ ፡ አንተን ፡ ያመሰግኑኻል ፤ እጅኽ ፡ በጠላቶችኽ ፡ ደንደስ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ የአባትኽ ፡ ልጆች ፡ በፊትኽ ፡ ይሰግዳሉ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 9 ፤ ይሁዳ ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ነው ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ከዐደንኽ ፡ ወጣኽ ። እንደ ፡ አንበሳ ፡ አሸመቀ ፥ እንደ ፡ ሴት ፡ አንበሳም ፡ አደባ ፤ ያስነሣውስ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 10 ፤ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ከይሁዳ ፡ አይጠፋም ፥ የገዥም ፡ ዘንግ ፡ ከእግሮቹ ፡ መካከል ፥ ገዥ ፡ የኾነው ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፤ የአሕዛብ ፡ መታዘዝም ፡ ለርሱ ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 11 ፤ ውርንጫውን ፡ በወይን ፡ ግንድ ፡ ያስራል ፥ የአህያዩቱንም ፡ ግልገል ፡ በወይን ፡ ዐረግ ፤ ልብሱን ፡ በወይን ፡ ያጥባል ፥ መጐናጸፊያውንም ፡ በወይን ፡ ደም ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 12 ፤ ዐይኑም ፡ ከወይን ፡ ይቀላል ፤ ጥርሱም ፡ ከወተት ፡ ነጭ ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 13 ፤ ዛብሎን ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ይቀመጣል ፤ ርሱም ፡ ለመርከቦች ፡ ወደብ ፡ ይኾናል ፤ ዳርቻውም ፡ እስከ ፡ ሲዶና ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 14 ፤ ይሳኮር ፡ ዐጥንተ ፡ ብርቱ ፡ አህያ ፡ ነው ፥ በበጎች ፡ ጕረኖም ፡ መካከል ፡ ያርፋል ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 15 ፤ ዕረፍትም ፡ መልካም ፡ መኾኗን ፡ አየ ፥ ምድሪቱም ፡ የለማች ፡ መኾኗን ፤ ትከሻውን ፡ ለመሸከም ፡ ዝቅ ፡ አደረገ ፥ በሥራም ፡ ገበሬ ፡ ኾነ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 16 ፤ ዳን ፡ በወገኑ ፡ ይፈርዳል ፥ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ እንደ ፡ አንዱ ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 17 ፤ ዳን ፡ በጐዳና ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ይኾናል ፥ በመንገድም ፡ እንደ ፡ ቀንዳም ፡ እባብ ፤ ፈረሱን ፡ ከሰኰናው ፡ ይነክሳል ፥ ፈረሰኛም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይወድቃል ።

ዘፍ. ፥ 49 ፥ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ መድኀኒትኽን ፡ እጠብቃለኹ ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 19 ፤ ጋድን ፡ ዘማቾች ፡ ይዘምቱበታል ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ተከታትሎ ፡ ይዘምትባቸዋል ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 20 ፤ የአሴር ፡ እንጀራው ፡ ወፍራም ፡ ነው ፥ ለነገሥታቱም ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ መብልን ፡ ይሰጣል ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 21 ፤ ንፍታሌም ፡ የተፈታ ፡ ሚዳቋ ፡ ነው ፤ መልካም ፡ ቃልን ፡ ይሰጣል ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 22 ፤ ዮሴፍ ፡ ትንሹ ፡ የፍሬ ፡ ዛፍ ፡ ነው ፥ በምንጭ ፡ አጠገብ ፡ የሚያፈራ ፡ የፍሬ ፡ ዛፍ ፤ ዐረጎቹ ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ ያድጋሉ ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 23 ፤ ቀስተኞች ፡ አስቸገሩት ፥ ነደፉትም ፥ ተቃወሙትም ፤

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቀስቱ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ቀረ ፤ የእጆቹም ፡ ክንድ ፡ በያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ እጅ ፡ በረታ ፥ በዚያው ፡ በጠባቂው ፡ በእስራኤል ፡ ዐምድ ፥

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 25 ፤ በአባትኽ ፡ አምላክ ፡ ርሱም ፡ የሚረዳኽ ፥ ኹሉንም ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ርሱም ፡ የሚባርክኽ ፥ በሰማይ ፡ በረከት ፡ ከላይ ፡ በሚገኝ ፥ በጥልቅም ፡ በረከት ፡ ከታች ፡ በሚሠራጭ ፥ በጡትና ፡ በማሕፀን ፡ በረከት ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 26 ፤ የአባትኽ ፡ በረከቶች ፡ ጽኑዓን ፡ ከኾኑ ፡ ከተራራዎች ፡ በረከቶች ፡ ይልቅ ፡ ጎያላን ፡ ናቸው ፤ ዘላለማውያን ፡ ከኾኑ ፡ ከኰረብታዎችም ፡ በረከቶች ፡ ይልቅ ፡ ጎያላን ፡ ናቸው ፤ እነርሱም ፡ በዮሴፍ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ፥ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ አለቃ ፡ በኾነው ፡ ራስ ፡ ዐናት ፡ ላይ ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 27 ፤ ብንያም ፡ ነጣቂ ፡ ተኵላ ፡ ነው ፤ የበዘበዘውን ፡ በጧት ፡ ይበላል ፥ የማረከውንም ፡ በማታ ፡ ይካፈላል ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 28 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ናቸው ፤ አባታቸው ፡ የነገራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ባረካቸውም ፤ እያንዳንዳቸውን ፡ እንደ ፡ በረከታቸው ፡ ባረካቸው ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 29 ፤ እንዲህ ፡ ብሎም ፡ አዘዛቸው ፦ እኔ ፡ ወደ ፡ ወገኖቼ ፡ እሰበሰባለኹ ፤ በኬጢያዊ ፡ በኤፍሮን ፡ ዕርሻ ፡ ላይ ፡ ባለችው ፡ ዋሻ ፡ ከአባቶቼ ፡ ጋራ ፡ ቅበሩኝ ፤

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 30 ፤ ርሷም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ በመምሬ ፡ ፊት ፡ ያለች ፥ አብርሃም ፡ ለመቃብር ፡ ርስት ፡ ከኬጢያዊ ፡ ከኤፍሮን ፡ ከዕርሻው ፡ ጋራ ፡ የገዛት ፥ ባለድርብ ፡ ክፍል ፡ ዋሻ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 31 ፤ አብርሃምና ፡ ሚስቱ ፡ ሳራ ፡ ከዚያ ፡ ተቀበሩ ፤ ይሥሐቅና ፡ ሚስቱ ፡ ርብቃ ፡ ከዚያ ፡ ተቀበሩ ፤ ከዚያም ፡ እኔ ፡ ልያን ፡ ቀበርኋት ፤

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 32 ፤ ዕርሻውና ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ያለችው ፡ ዋሻ ፡ ከኬጢ ፡ ልጆች ፡ የተገዙ ፡ ናቸው ።

ዘፍ. ፡ 49 ፡ 33 ፤ ያዕቆብም ፡ ትእዛዙን ፡ ለልጆቹ ፡ ተናግሮ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እግሮቹን ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ሰብስቦ ፡ ሞተ ፥ ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ ተከማች ።

_____ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፥ ምዕራፍ ፡ 50 ። _____

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 1 ፤ ዮሴፍም ፡ በአባቱ ፡ ፊት ፡ ወደቀ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ አለቀሰ ፥ ሳመውም ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 2 ፤ ዮሴፍም ፡ ባለመድኀኒቶች ፡ አገልጋዮቹ ፡ አባቱን ፡ በሽቱ ፡ ያሹት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ባለመድኀኒቶችም ፡ እስራኤልን ፡ በሽቱ ፡ አሹት ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 3 ፤ አርባ ፡ ቀንም ፡ ፈጸሙለት ፤ የሽቱ ፡ መደረጊያው ፡ ወራት ፡ እንደዚሁ ፡

ይፈጸማልና ፤ የግብጽም ፡ ሰዎች ፡ ሰባ ፡ ቀን ፡ አለቀሱለት ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 4 ፤ የልቅሶውም ፡ ወራት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ የዮሴፍ ፡ ለፈርዖን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦ እኔ ፡ በፊታችኹ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ለፈርዖን ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 5 ፤ አባቴ ፡ አምሎኛል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ እሞታለኹ ፤ በቈፈርኹት ፡ መቃብር ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ከዚያ ፡ ቅበረኝ ። አኹንም ፡ ወጥቼ ፡ አባቴን ፡ ልቅበርና ፡ ልመለስ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 6 ፤ ፈርዖንም ፦ ውጣ ፥ አባትኽንም ፡ እንዳማለኽ ፡ ቅበረው ፡ አለው ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 7 ፤ የዮሴፍም ፡ አባቱን ፡ ሊቀብር ፡ ወጣ ፤ የፈርዖን ፡ ሎላልትም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጡ ፥ የቤቱ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ የግብጽ ፡ ምድር ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ኹሉ ፤

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 8 ፤ የዮሴፍም ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ኹሉ ፡ ወንድሞቹም ፡ የአባቱም ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ወጡ ፤ ልጆቻቸውንና ፡ በጎቻቸውን ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ብቻ ፡ በጌሤም ፡ ተዉ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 9 ፤ ሠረገላዎችም ፡ ፈረሰኞችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጡ ፥ ሰራዊቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበረ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 10 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወዳለችው ፡ ወደአጣድ ፡ ዐውድማ ፡ መጡ ፥ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ በኾነ ፡ በጽኑ ፡ ልቅሶም ፡ አለቀሱለት ፤ ለአባቱም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ልቅሶ ፡ አደረገለት ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 11 ፤ በዚያች ፡ ምድር ፡ የሚኖሩ ፡ የከነዓን ፡ ሰዎችም ፡ በአጣድ ፡ ዐውድማ ፡ የኾነውን ፡ ልቅሶ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ ለግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ አቤል ፡ ምጽራይም ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፤ ርሱም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ነው ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 12 ፤ ልጆቹም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ እንደዚያው ፡ አደረጉለት ፤

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 13 ፤ ልጆቹም ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ አጓዙት ፥ ባለኹለት ፡ ክፍል ፡ በኾነች ፡ ዋሻም ፡ ቀበሩት ፤ ርሷም ፡ በመምሬ ፡ ፊት ፡ ያለች ፥ አብርሃም ፡ ለመቃብር ፡ ርስት ፡ ከኬጢያዊ ፡ ከኤፍሮን ፡ ከዕርሻው ፡ ጋራ ፡ የገዛት ፡ ዋሻ ፡ ናት ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 14 ፤ የዮሴፍና ፡ ወንድሞቹ ፡ አባቱንም ፡ ሊቀብሩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የወጡት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አባቱን ፡ ከቀበረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተመለሱ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 15 ፤ የዮሴፍም ፡ ወንድሞች ፡ አባታቸው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ ምናልባት ፡ የዮሴፍ ፡ ይጠላን ፡ ይኾናል ፥ ባደረግንበትም ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ ብድራት ፡ ይመልስብን ፡ ይኾናል ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ የዮሴፍም ፡ መልእክት ፡ ላኩ ፡ እንዲህም ፡ አሉት ፦ አባትኽ ፡ ገና ፡ ሳይሞት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዟል ፦

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 17 ፤ የዮሴፍን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ እባክኽ ፡ የወንድሞችኽን ፡ በደል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ በል ፥ እነርሱ ፡ ባንተ ፡ ከፍተው-ብኻልና ፤ አኹንም ፡ እባክኽ ፡ የአባትኽ ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፡ የበደሉኽን ፡ ይቅር ፡ በል ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 18 ፤ የዮሴፍም ፡ ይህን ፡ ሲሉት ፡ አለቀሰ ። ወንድሞቹ ፡ ደግሞ ፡ መጡ ፡ በፊቱም ፡ ሰግደው ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ ለአንተ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ነን ፡ አሉት ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 19 ፤ የዮሴፍም ፡ አላቸው ፦ አትፍሩ ፤ እኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፋንታ ፡ ነኝን ፧

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ዐሰባችኹብኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ እንደኾነው ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲድን ፡ ለማድረግ ፡ ለመልካም ፡ ዐሰበው ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 21 ፤ አኹንም ፡ አትፍሩ ፤ እኔ ፡ እናንተንና ፡ ልጆቻችኹን ፡ እመግባችኋለኹ ። አጽናናቸውም ፡ ደስ ፡ አሠኛቸውም ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 22 ፤ የሴፍም ፡ በግብጽ ፡ ተቀመጠ ፥ ርሱና ፡ የአባቱም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፤ የሴፍም ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 23 ፤ የሴፍም ፡ የኤፍሬምን ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ትውልድ ፡ አየ ፤ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጆችም ፡ በየሴፍ ፡ ጭን ፡ ላይ ፡ ተወለዱ ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 24 ፤ የሴፍም ፡ ወንድሞቹን ፡ አለ ፦ እኔ ፡ እሞታለኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ መጐብኘትን ፡ ይጐበኛችኋል ፥ ከዚችም ፡ ምድር ፡ ያወጣችኋል ፤ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ ወደማለላቸው ፡ ምድር ፡ ያደርሳችኋል ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 25 ፤ የሴፍም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፦ እግዚአብሔር ፡ ሲያስባችኹ ፡ ዐጥንቴን ፡ ከዚህ ፡ አንሥታችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰዱ ፡ ብሎ ፡ አማላቸው ።

ዘፍ. ፡ 50 ፡ 26 ፤ የሴፍም ፡ በመቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ዕድሜው ፡ ሞተ ፤ በሽቱም ፡ አሹት ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት ❖

ኦሪት ፡ ዘጸአት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ የገቡት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ጋራ ፡ ገባ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ሮቤል ፥

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ስምዖን ፥ ሌዊ ፥ ይሁዳ ፥ ይሳኮር ፥ ዛብሎን ፥

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ብንያም ፥ ዳን ፥ ንፍታሌም ፥ ጋድ ፥ አሴር ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከያዕቆብ ፡ ጕልበት ፡ የወጡት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰባ ፡ ነፍሶች ፡ ነበሩ ፤ ዮሴፍም ፡ አስቀድሞ ፡ በግብጽ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ዮሴፍም ፡ ሞተ ፥ ወንድሞቹም ፥ ያም ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አፈሩ ፥ እጅግም ፡ በዙ ፥ ተባዙም ፥ እጅግም ፡ ጸኑ ፤ ምድሪቱም ፡ በእነርሱ ፡ ሞላች ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ በግብጽም ፡ ዮሴፍን ፡ ያላወቀ ፡ ዐዲስ ፡ ንጉሥ ፡ ተነሣ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ርሱም ፡ ሕዝቡን ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሕዝብ ፡ ከእኛ ፡ ይልቅ ፡ በዝተዋል ፡ በርትተውማል ፤

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እንዳይበዙ ፥ ሰልፍም ፡ በተነሣብን ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻችንን ፡ አግዘው ፡ እንዳይወጉን ፡ ከምድሪቱም ፡ እንዳይወጡ ፥ ኑ ፡ እንጠበብባቸው ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በብርቱ ፡ ሥራም ፡ ያስጨንቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ግብር ፡ አስገባሪዎችን ፡ ሾመባቸው ፤ ለፈርዖንም ፡ ፊቶምንና ፡ ራምሴን ፡ ጽኑ ፡ ከተማዎች ፡ አድርገው ፡ ሠሩ ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳስጨነቋቸው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ በዙ ፥ እጅግም ፡ ጸኑ ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ተጸይፈዋቸው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ግብጻውያንም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በመከራ ፡ ገዟቸው ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ በጽኑ ፡ ሥራ ፥ በጭቃ ፥ በጡብም ፡ በዕርሻም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ በመከራም ፡ በሚያሠሯቸው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ ሕይወታቸውን ፡ ያስመርሯቸው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ አንዲቱ ፡ ሲፓራ ([61]) ፡ ኹለተኛዪቱም ፡ ፉሐ ፡ የሚባሉትን ፡ የዕብራውያንን ፡ አዋላጆች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦

ዘጸ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ እናንተ ፡ የዕብራውያንን ፡ ሴቶች ፡ ስታዋልዱ ፥ ለመውለድ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፥ ወንድ ፡ ቢኾን ፡ ግደሉት ፤ ሴት ፡ ብትኾን ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ትኑር ።

---

61 ዕብ. ፥ ጺፓራህ ፡ (የመስቀል ፡ ወፍ) ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ አዋላጆች ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሩ ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አላደረጉም ፥ ወንዶቹን ፡ ሕፃናትንም ፡ አዳኗቸው ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ አዋላጆችን ፡ ጠርቶ ፦ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረጋችኹ ፧ ወንዶቹን ፡ ሕፃናትንስ ፡ ለምን ፡ አዳናችኹ ፧ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ አዋላጆቹም ፡ ፈርዖንን ፦ የዕብራውያን ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ሴቶች ፡ ስላልኾኑ ፤ እነርሱ ፡ ጠንካራዎች ፡ ናቸውና ፥ አዋላጆች ፡ ሳይገቡ ፡ ስለሚወልዱ ፡ ነው ፡ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአዋላጆች ፡ መልካም ፡ አደረገላቸው ፤ ሕዝቡም ፡ በዛ ፥ እጅግም ፡ ጸና ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ አዋላጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ቤቶችን ፡ አደረገላቸው ።

ዘጸ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ፈርዖንም ፦ የሚወለደውን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ፥ ሴትን ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ አድኗት ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ አዘዘ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ከሌዊ ፡ ወገንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኼዶ ፡ የሌዊን ፡ ልጅ ፡ አገባ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሴቲቱም ፡ ፀነሰች ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ፤ መልካምም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሸሸገችው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ደግሞም ፡ ልትሸሽገው ፡ ባልቻለች ፡ ጊዜ ፥ የደንገል ፡ ሣጥን ፡ ለርሱ ፡ ወስዳ ፡ ዝፍትና ፡ ቅጥራን ፡ ለቀለቀችው ፤ ሕፃኑንም ፡ አኖረችበት ፥ በወንዝም ፡ ዳር ፡ ባለ ፡ በቄጠማ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጠችው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እኅቱም ፡ የሚደረግበትን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ በሩቅ ፡ ቆማ ፡ ትጐበኘው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፡ ልትታጠብ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ወረደች ፤ ደንገጥሮቿም ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ ሣጥኑንም ፡ በቄጠማ ፡ ውስጥ ፡ አየች ፥ ደንገጥሯንም ፡ ልካ ፡ አስመጣችው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ በከፈተችውም ፡ ጊዜ ፡ ሕፃኑን ፡ አየች ፥ እንሆም ፡ ሕፃኑ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ፤ ዐዘነችለትም ፦ ይህ ፡ ከዕብራውያን ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ ነው ፡ አለች ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እኅቱም ፡ ለፈርዖን ፡ ልጅ ፦ ሕፃኑን ፡ ታጠባልሽ ፡ ዘንድ ፡ ኼጄ ፡ የምታጠባ ፡ ሴት ፡ ከዕብራውያን ፡ ሴቶች ፡ ልጥራልሽን ፧ አለቻት ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፦ ኺጂ ፡ አለቻት ፤ ብላቴናዪቱም ፡ ኼዳ ፡ የሕፃኑን ፡ እናት ፡ ጠራች ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፦ ይህን ፡ ሕፃን ፡ ወስደሽ ፡ አጥቢልኝ ፥ ዋጋሽንም ፡ እሰጥሻለኹ ፡ አለቻት ። ሴቲቱም ፡ ሕፃኑን ፡ ወስዳ ፡ አጠባችው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ሕፃኑም ፡ አደገ ፥ ወደፈርዖንም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ አመጣችው ፥ ለርሷም ፡ ልጅ ፡ ኾነላት ፦ እኔ ፡ ከውሃ ፡ አውጥቼዋለኹና ፡ ስትልም ፡ ስሙን ፡ ሙሴ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ ጐበዝ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቹ ፡ ወጣ ፥ የሥራቸውንም ፡ መከራ ፡ ተመለከተ ፤ የግብጽም ፡ ሰው ፡ የወንድሞቹን ፡ የዕብራውያንን ፡ ሰው ፡ ሲመታ ፡ አየ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ ተመለከተ ፥ ማንንም ፡ አላየም ፥ ግብጻዊውንም ፡ ገደለ ፥ በአሸዋም ፡ ውስጥ ፡ ሸሸገው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ወጣ ፥ ኹለቱም ፡ የዕብራውያን ፡ ሰዎች ፡ ሲጣሉ ፡ አየ ፤ በዳዩንም ፦ ለምን ፡ ባልንጀራኽን ፡ ትመታዋለኽ ፧ አለው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ያም ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡ አንተን ፡ አለቃ ፡ ወይስ ፡ ዳኛ ፡ ማን ፡ አደረገኽ ፧ ወይስ ፡ ግብጻዊውን ፡ እንደ ፡ ገደልኸው ፡ ልትገድለኝ ፡ ትሻለኽን ፧ አለው ። ሙሴም ፦ በእውነት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ታውቋል ፡ ብሎ ፡ ፈራ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ፈርዖንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴን ፡ ሊገድለው ፡ ፈለገ ። ሙሴ ፡ ግን ፡ ከፈርዖን ፡ ፊት ፡ ኰበለለ ፥ በምድያምም ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ፤ በውሃም ፡ ጕድጓድ ፡ አጠገብ ፡ ዐረፈ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ለምድያምም ፡ ካህን ፡ ሰባት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ እነርሱም ፡ መጥተው ፡ ውሃ ፡ ቀዱ ፥ የአባታቸውንም ፡ በጎች ፡ ሊያጠጡ ፡ የውሃውን ፡ ገንዳ ፡ ሞሉ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እረኞችም ፡ መጥተው ፡ ገፏቸው ፤ ሙሴ ፡ ግን ፡ ተነሥቶ ፡ ረዳቸው ፥ በጎቻቸውንም ፡ አጠጣላቸው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ አባታቸው ፡ ወደ ፡ ራጉኤልም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ዛሬ ፡ ፈጥናችኹ ፡ መጣችኹ ፧ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፦ አንድ ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ ከእረኞች ፡ እጅ ፡ አዳነን ፥ ደግሞም ፡ ቀዳልን ፥ በጎቻችንንም ፡ አጠጣ ፡ አሉ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ልጆቹንም ፦ ርሱ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ለምንስ ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ተዋችኹት ፧ ጥሩት ፡ እንጀራም ፡ ይብላ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ሙሴም ፡ ከዚያ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ሊቀመጥ ፡ ወደደ ፤ ልጁንም ፡ ሲፓራን ፡ ለሙሴ ፡ ሚስት ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፡ ሰጠው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ። በሌላ ፡ ምድር ፡ መጻተኛ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ ስሙን ፡ ጌርሳም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ከዚያም ፡ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሞተ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከባርነት ፡ የተነሣ ፡ አለቀሱ ፥ ጮኹም ፥ ስለ ፡ ባርነታቸውም ፡ ጩኸታቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የለቅሷቸውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከአብርሃምና ፡ ከይሥሐቅ ፡ ከያዕቆብም ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ዐሰበ ።

ዘጸ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አየ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ዐወቀ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ የዮቶርን ፡ የዐማቱን ፡ የምድያምን ፡ ካህን ፡ በጎች ፡ ይጠብቅ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ዳርቻም ፡ በጎቹን ፡ ነዳ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ኰሬብ ፡ መጣ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ በሾኽ ፡ ቍጥቋጦ ፡ መካከል ፡ ታየው ፤ እንሆም ፡ ቍጥቋጦው ፡ በእሳት ፡ ሲነድ ፡ ቍጥቋጦውም ፡ ሳይቃጠል ፡ አየ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፦ ልኺድና ፡ ቍጥቋጦው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልተቃጠለም ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ራእይ ፡ ልይ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ይመለከት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከቀኑጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ርሱን ፡ ጠርቶ ፦ ሙሴ ፥ ሙሴ ፡ ሆይ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለ ። ወደዚህ ፡ አትቅረብ ፤ አንተ ፡ የቆምኽባት ፡ ስፍራ ፡ የተቀደሰች ፡ መሬት ፡ ናትና ፥ ጫማኽን ፡ ከእግርኽ ፡ አውጣ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ደግሞም ፦ እኔ ፡ የአባትኽ ፡ አምላክ ፥ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ አለው ። ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ፈርቷልና ፥ ፊቱን ፡ ሸፈነ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ በግብጽ ፡ ያለውን ፡ የሕዝቤን ፡ መከራ ፡ በእውነት ፡ አየኹ ፥ ከአስገባሪዎቻቸውም ፡ የተነሣ ፡ ጩኸታቸውን ፡ ሰማኹ ፤ ሥቃያቸውንም ፡ ዐውቄያለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፡ አድናቸው ፡ ዘንድ ፥ ከዚያችም ፡ አገር ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈሰው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሰፈዩቱና ፡ ወደ ፡ መልካሚቱ ፡ አገር ፡ ወደከነዓናውያንም ፡ ወደኬጢያውያንም ፡ ወደአሞራውያንም ፡ ወደፌርዛውያንም ፡ ወደዔዊያውያንም ፡ ወደኢያቡሳውያንም ፡ ስፍራ ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ወረድኹ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጩኸት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ወጣ ፤ ግብጻውያንም ፡ የሚያደርጉባቸውን ፡ ግፍ ፡ ደግሞ ፡ አየኹ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ ና ፥ ሕዝቤን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ እልክኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፦ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ የምኼድ ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ የማወጣ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧ አለው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ርሱም ፦ በእውነት ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ላክኹኽ ፡ ምልክትኽ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሕዝቡን ፡ ከግብጽ ፡ ባወጣኽ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትገዛላችኹ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፦ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ላከኝ ፡ ባልኹም ፡ ጊዜ ፦ ስሙስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፥ ምን ፡ እላቸዋለኹ ፧ አለው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ "ያለና ፡ የሚኖር" ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለው ፤ እንዲህ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ። "ያለና ፡ የሚኖር" ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ላከኝ ፡ ትላለኽ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ትላለኽ ፦ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፥ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ላከኝ ፤ ይህ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ ስሜ ፡ ነው ፥ እስከልጅ ፡ ልጅ ፡ ድረስም ፡ መታሰቢያዬ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ኺድ ፡ የእስራኤልንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰብስብ ። እግዚአብሔር ፡ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ የአብርሃም ፡ የይሥሐቅም ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ። መጐብኘትን ፡ ጐበኘኋችኹ ፥ በግብጽም ፡ የሚደረግባችኹን ፡ አየኹ ፤

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ከግብጽም ፡ መከራ ፡ ወደከነዓናውያን ፡ ወደኬጢያውያንም ፡ ወደአሞራውያንም ፡ ወደፌርዛውያንም ፡ ወደዔዊያውያንም ፡ ወደያቡሳውያንም ፡ አገር ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈስ ፡ አገር ፡ አወጣችኋለኹ ፡ አልኹ ፡ ብሎ ፡ ተገለጠልኝ ፡ በላቸው ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ ቃልኽን ፡ ይሰማሉ ፤ አንተና ፡ የእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ትገባላችኹ ። የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገለጠልን ፤ አኹንም ፡ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንሠዋ ፡ ዘንድ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንኺድ ፡ ትሉታላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጽኑ ፡ እጅ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ እንደማይፈቅድላችኹ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ እጄን ፡ እዘረጋለኹ ፥ በማደርግባቸውም ፡ ተኣምራቴ ፡ ኹሉ ፡ ግብጽን ፡ እመታለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ይለቃችኋል ።

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ በግብጻውያንም ፡ ፊት ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሞገስን ፡ እሰጣለኹ ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ በኼዳችኹ ፡ ጊዜ ፡ ባዶ ፡ እጃችኹን ፡ አትኼዱም ፤

ዘጸ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዲቱ ፡ ሴት ፡ ከጎረቤቷ ፣ በቤቷም ፡ ካለችው ፡ ሴት ፡ የብር ፡ ዕቃ ፣ የወርቅ ፡ ዕቃ ፣ ልብስም ፡ ትለምናለች ፤ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ ልጆቻችኹ ፡ ላይ ፡ ታደርጉታላችኹ ፤ ግብጻውያንንም ፡ ትበዘብዛላችኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ መለሰ ፦ እንሆ ፥ አያምኑኝም ፡ ቃሌንም ፡ አይሰሙም ። እግዚአብሔር ፡ ከቶ ፡ አልተገለጠልኽም ፡ ይሉኛል ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይህች ፡ በእጅኽ ፡ ያለችው ፡ ምንድር ፡ ናት ፧ አለው ። ርሱም ፦ በትር ፡ ናት ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ መሬት ፡ ጣላት ፡ አለው ፤ ርሱም ፡ በመሬት ፡ ጣላት ፥ እባብም ፡ ኾነች ፤ ሙሴም ፡ ከርሷ ፡ ሸሸ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 4-5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፥ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተገለጠልኽ ፡ እንዲያምኑ ፡ እጅኽን ፡ ዘርግተኽ ፡ ኾራቷን ፡ ያዝ ፡ አለው ። እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ያዛት ፡ በእጁም ፡ ውስጥ ፡ በትር ፡ ኾነች ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፦ እጅኽን ፡ ወደ ፡ ብብትኽ ፡ አግባ ፡ አለው ። እጁንም ፡ ወደ ፡ ብብቱ ፡ አገባት ፤ ባወጣትም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ እጁ ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ለምጽ ፡ ኾነች ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ርሱም ፦ እጅኽን ፡ ወደ ፡ ብብትኽ ፡ መልስ ፡ አለው ። እጁንም ፡ ወደ ፡ ብብቱ ፡ መለሳት ፥ ከብብቱም ፡ ባወጣት ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ተመልሳ ፡ ገላውን ፡ መሰለች ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፡ አለው ፦ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ባያምኑኽ ፡ የፊተኛዉቱንም ፡ ምልክት ፡ ነገር ፡ ባይሰሙ ፥ የኹለተኛዉቱን ፡ ምልክት ፡ ነገር ፡ ያምናሉ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እነዚህን ፡ ኹለት ፡ ምልክቶች ፡ ባያምኑ ፡ ቃልኽንም ፡ ባይሰሙ ፥ ከወንዙ ፡ ውሃን ፡ ውሰድ ፥ በደረቁም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ አፍስው ፤ ከወንዙም ፡ የወሰድኸው ፡ ውሃ ፡ በደረቁ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ደም ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ አፌ ፡ ኩልታፋ ፡ ምላሴም ፡ ጸያፍ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ ትናንት ፡ ከትናንት ፡ ወዲያ ፡ ባሪያኽንም ፡ ከተናገርኸኝ ፡ ዠምሮ ፡ አፈ ፡ ትብ ፡ ሰው ፡ አይደለኹም ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፦ የሰውን ፡ አፍ ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ዲዳስ ፡ ደንቈሮስ ፡ የሚያይስ ፡

ዕውርስ ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለኹምን ፧

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 12 ፤ እንግዲህ ፡ አኹን ፡ ኺድ ፥ እኔም ፡ ከአፍኽ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ የምትናገረውንም ፡ አስተምርኻለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 13 ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በምትልከው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ትልክ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሌዋዊው ፡ ወንድምኽ ፡ አሮን ፡ አለ ፡ አይደለምን ፧ ርሱ ፡ ደኅና ፡ እንዲናገር ፡ ዐውቃለኹ ፤ እንሆም ፡ ደግሞ ፡ ሊገናኝኽ ፡ ይመጣል ፤ ባየኽም ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 15 ፤ አንተም ፡ ትናገረዋለኽ ፡ ቃሉንም ፡ በአፉ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ እኔ ፡ ከአፍኽና ፡ ከአፉ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ የምታደርጉትንም ፡ አስተምራችኋለኹ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 16 ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ይናገራል ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ርሱ ፡ አፍ ፡ ይኾንልኻል ፡ አንተም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፋንታ ፡ ትኾንለታለኽ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 17 ፤ ይህችንም ፡ ተአምራት ፡ የምታደርግባትን ፡ በትር ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኻት ፡ ኺድ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 18 ፤ ሙሴም ፡ ኼደ ፥ ወደ ፡ ዐማቱ ፡ ወደ ፡ ዮቶር ፡ ተመለሰ ፦ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በሕይወት ፡ እንዳሉ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሼ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቼ ፡ ልኺድ ፡ አለው ። ዮቶርም ፡ ሙሴን ፦ በሰላም ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በምድያም ፦ ነፍስኽን ፡ የሚሿት ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሞተዋልና ፥ ተመልሰኽ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 20 ፤ ሙሴም ፡ ሚስቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ወሰደ ፥ በአህያ ፡ ላይም ፡ አስቀመጣቸው ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ አገር ፡ ተመለሰ ፤ ሙሴም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በትር ፡ ይዞ ፡ ኼደ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ስትመለስ ፡ በእጅኽ ፡ ያደረግኹትን ፡ ተአምራት ፡ ኹሉ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ተመልከት ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ልቡን ፡ አጸናዋለኹ ፥ ሕዝቡንም ፡ አይለቅም ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 22 ፤ ፈርዖንንም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 23 ፤ እስራኤል ፡ የበኵር ፡ ልጄ ፡ ነው ፤ ይገዛልኝ ፡ ዘንድ ፡ ልጄን ፡ ልቀቅ ፡ አልኹኽ ፤ አንተም ፡ ትለቀው ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አልኽ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ የበኵር ፡ ልጅኽን ፡ እገድላለኹ ፡ ትለዋለኽ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 24 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ባደረበት ፡ ስፍራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገናኘው ፥ ሊገድለውም ፡ ፈለገ ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 25 ፤ ሲፓራም ፡ ሚስቱ ፡ ባልጩት ፡ ወሰደች ፥ የልጇንም ፡ ሸለፈት ፡ ገረዘች ፥ ወደ ፡ እግሩም ፡ ጣለችው ፦ አንተ ፡ ለእኔ ፡ የደም ፡ ሙሽራ ፡ ነኽ ፡ አለች ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 26 ፤ ከርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፦ ስለ ፡ ግርዛቱ ፡ አንተ ፡ የደም ፡ ሙሽራ ፡ ነኽ ፡ አለች ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፦ ኼደኽ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሙሴን ፡ ተገናኘው ፡ አለው ፤ ኼዶም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ተገናኘው ፥ ሳመውም ።

ዘጸ. ፥ 4 ፥ 28 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የላከውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ያዘዘውንም ፡ ተአምራት ፡

ኾሉ ፡ ለአሮን ፡ ተናገረው ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ኼዱ ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኾሉ ፡ ሰበሰቡ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ አሮንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ የነገረውን ፡ ቃል ፡ ኾሉ ፡ ተናገረ ፥ ተአምራቱንም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ሕዝቡም ፡ አመኑ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ጐበኘ ፡ ጭንቀታቸውንም ፡ እንዳየ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ አጐነበሱ ፡ ሰገዱም ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ መጥተው ፡ ፈርዖንን ፡ እንዲህ ፡ አሉት ። የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በምድረ ፡ በዳ ፡ በዓል ፡ ያደርግልኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ፈርዖንም ፦ ቃሉን ፡ እሰማ ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልንስ ፡ እለቅ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማን ፡ ነው ፧ እግዚአብሔርን ፡ አላውቅም ፥ እስራኤልንም ፡ ደግሞ ፡ አልለቅም ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፦ የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ ተገናኘን ፤ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ሰይፍ ፡ እንዳይጥልብን ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንድንኼድ ፥ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንድንሠዋ ፡ እንለምንኻለን ፡ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥም ፦ አንተ ፡ ሙሴ ፡ አንተም ፡ አሮን ፥ ሕዝቡን ፡ ለምን ፡ ሥራቸውን ፡ ታስተዋላችኹ ፧ ወደ ፡ ተግባራችኹ ፡ ኺዱ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ፈርዖንም ፦ እንሆ ፥ የምድሩ ፡ ሕዝብ ፡ አኹን ፡ በዝቷል ፥ እናንተም ፡ ሥራቸውን ፡ ታስፈቷቸዋላችኹ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ፈርዖንም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የሕዝቡን ፡ አስገባሪዎች ፡ ሹማምቶቹንም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ ወትሮው ፡ ለጡብ ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ ገለባ ፡ ለሕዝቡ ፡ አትስጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱ ፡ ኼደው ፡ ገለባ ፡ ይሰብስቡ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ቀድሞ ፡ ያደርጉት ፡ የነበረውን ፡ የጡብ ፡ ቍጥር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አድርጉት ፤ ምንም ፡ ከርሱ ፡ አታጕድሉ ፤ ሥራ ፡ ሰልችተዋልና ፥ ስለዚህ ፦ ለአምላካችን ፡ እንድንሠዋ ፡ እንኺድ ፡ እያሉ ፡ ይጮኻሉ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ርሱንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሥራው ፡ ይክበድባቸው ፤ ከንቱ ፡ ቃልም ፡ አያስቡ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ የሕዝቡም ፡ አስገባሪዎች ፡ ሹማምቶቹም ፡ ወጡ ፥ ሕዝቡንም ፦ ፈርዖን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ገለባ ፡ አልሰጣችኹም ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ ኺዱ ፥ ከምታገኙበትም ፡ ስፍራ ፡ ገለባ ፡ ሰብስቡ ፤ ከሥራችኹ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አይጐድልም ፡ አሏቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ ገለባ ፡ እብቅ ፡ ሊሰበስቡ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ኾሉ ፡ ተበተኑ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ አስገባሪዎቹም ፦ ገለባ ፡ ትቀበሉበት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ጊዜ ፡ የቀን ፡ ሥራችኹን ፡ ጨርሱ ፡ እያሉ ፡ አስቸኰሏቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ የፈርዖንም ፡ አስገባሪዎች ፦ ቀድሞ ፡ ታደርጉ ፡ እንደ ፡ ነበራችኹ ፡ ትናንትናና ፡ ዛሬ ፡

የተቈጠረውን ፡ ጡብ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትጨርሱም ፡፡ እያሉ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ አለቃዎቹን ፡ ገረፉ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አለቃዎችም ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ መጡ ፦ ለምን ፡ በባሪያዎችኽ ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋለኽ ፡፡

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ገለባ ፡ አይሰጡንም ፥ የጡቡንም ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራ ፡ ያዘናል ፤ እንሆም ፡ ባሪያዎችኽን ፡ ይገርፉናል ፤ ግድፈቱ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ሰልችታችኋል ፥ ሰልችታችኋል ፤ ስለዚህም ፦ እንኺድ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ እንሠዋ ፡ ትላላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ አኹንም ፡ ኺዱ ፥ ሥሩ ፤ ገለባ ፡ አይሰጣችኹም ፥ የጡቡን ፡ ቍጥር ፡ ግን ፡ ታመጣላችኹ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፦ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከምትሠሩት ፡ ከጡቡ ፡ ቍጥር ፡ ምንም ፡ አታጕድሉ ፡ ባሏቸው ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ እንደ ፡ ከፋባቸው ፡ አዩ ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ከፈርዖንም ፡ ዘንድ ፡ ሲወጡ ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በፊታቸው ፡ ቆመው ፡ ተገናኟቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፦ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ፊት ፡ ሽታችንን ፡ አግምታችኹታልና ፥ ይገድሉንም ፡ ዘንድ ፡ ሰይፍን ፡ በእጃቸው ፡ ሰጥታችኋቸዋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ይመልከታችኹ ፥ ይፍረድባችኹም ፡ አሏቸው ።

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሰና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ አስከፋኽ ፡፡ ስለ ፡ ምንስ ፡ ላክኸኝ ፡፡

ዘጸ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ በስምኽ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ከገባኹ ፡ ወዲህ ፥ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ አስከፍቶታልና ፤ አንተም ፡ ሕዝብኽን ፡ ከቶ ፡ አላዳንኸውም ፡ አለ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ በጸናች ፡ እጅ ፡ ይለቃችኋልና ፥ በጸናችም ፡ እጅ ፡ ከምድሩ ፡ አስወጥቶ ፡ ይሰዳቸዋልና ፥ አኹን ፡ በፈርዖን ፡ የማደርገውን ፡ ታያለኽ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ተናገረው ፡ አለውም ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ለአብርሃምም ፡ ለይሥሐቅም ፡ ለያዕቆብም ፡ ኹሉን ፡ እንደሚችል ፡ አምላክ ፡ ተገለጥኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስሜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልታወቀላቸውም ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ የተሰደዱባትንም ፡ ምድር ፥ የእንግድነታቸውን ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፥ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አቆምኹ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ግብጻውያን ፡ የገዟቸውን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ልቅሶ ፡ ሰማኹ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ዐሰብኹ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ስለዚህም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ ከግብጻውያንም ፡ ባርነት ፡ አወጣችኋለኹ ፥ ከተገዥነታቸውም ፡ አድናችኋለኹ ፤ በተዘረጋ ፡ ክንድ ፡ በታላቅ ፡ ፍርድም ፡ እታደጋችኋለኹ ፥

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ለኔም ፡ ሕዝብ ፡ እንድትኾኑ ፡ እቀበላችኋለኹ ፥ አምላክም ፡ እኾናችኋለኹ ፤ እኔም ፡

ከግብጻውያን ፡ ባርነት ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ እንደኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ እሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ወደማልኹባት ፡ ምድር ፡ አገባችኋለኹ ፤ ርሷንም ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ እሰጣችኋለኹ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ ይህን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገረ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ከሰውነታቸው ፡ መጨነቅ ፡ ከከባዱም ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ ቃሉን ፡ አልሰሙትም ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ግባ ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ከአገሩ ፡ ይለቅ ፡ ዘንድ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ንገር ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ሙሴም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አልሰሙኝም ፤ እንዴትስ ፡ ፈርዖን ፡ ይሰማኛል ∴ ይልቁንም ፡ እኔ ፡ ከንፈረ ፡ ቈላፍ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ተናገራቸው ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ እንዲያወጣቸው ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ የአባታቸውም ፡ ቤት ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የእስራኤል ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፤ ሄኖኅ ፥ ፈሉስ ፥ አስሮን ፥ ከርሚ ፤ እነዚህ ፡ የሮቤል ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ የስምዖንም ፡ ልጆች ፤ ይሙኤል ፥ ያሚን ፥ ኦሃድ ፥ ያኪን ፥ ዾሐር ፥ የከነዓናዊቱም ፡ ልጅ ፡ ሳኡል ፤ እነዚህ ፡ የስምዖን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ እነዚህም ፡ እንደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ ጌድሶን ፥ ቀአት ፥ ሜራሪ ፡ ናቸው ። የሌዊም ፡ የሕይወት ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ የጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ ሎቤኒ ፥ ሰሜኢ ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ የቀአትም ፡ ልጆች ፡ ዕምበረም (62) ፥ ይስዓር (63) ፥ ኬብሮን ፥ ዑዝኤል (64) ፡ ናቸው ፤ የቀአትም ፡ የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ሞሖሊ ፥ ሙሲ ፡ ናቸው ። እነዚህ ፡ እንደ ፡ ትውልዳቸው ፡ የሌዊ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ዕምበረምም ፡ የአጎቱን ፡ ልጅ ፡ ዮካብድን ፡ አገባ ፥ አሮንና ፡ ሙሴንም ፡ ወለደችለት ፤ የዕምበረምም ፡ የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ የይስአር (65) ፡ ልጆች ፡ ቆሬ ፥ ናፌግ ፥ ዝክሪ ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ የዑዝኤል ፡ ልጆች ፡ ሚሳኤል ፥ ኤልዳፋን ፥ ሥትሪ (66) ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ አሮንም ፡ የዐሚናዳብን ፡ የነአሶንን ፡ እኅት ፡ ኤልሳቤጥን ፡ አገባ ፥ ርሷም ፡ ናዳብንና ፡ አብዮድን

---

62 ዕብ. ፡ ዐምራም ።

63 ዕብ. ፡ ይጽሀር ።

64 ዕብ. ፡ ዑዚኤል ፡ (ዐዚዘ ፡ እግዚአብሔር ፥ የእግዚአብሔር ፡ ብርቱ) ።

65 ዕብ. ፡ ይጽሀር ፡ (የተቀባ) ።

66 ዕብ. ፡ ሚትሪ ፡ (ሥቱር • የተሠነተረ) ።

([67]) ፡ አልዓዛርንና ፡ ኢታምርን ([68]) ፡ ወለደችለት ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ አሴር ፡ ሕልቃና ([69]) ፡ አብያሣፍ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ የአሮንም ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ከፉትኤል ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ አገባ ፥ ርኋም ፡ ፊንሐስን ([70]) ፡ ወለደችለት ። እነዚህ ፡ እንደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ የሌዋውያን ፡ አባቶች ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ እነዚህ ፡ አሮንና ፡ ሙሴ ፡ እግዚአብሔር ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አውጡ ፡ ያላቸው ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ እነዚህ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ከፈርዖን ፡ ጋራ ፡ የተነጋገሩ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ናቸው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሙሴን ፡ በተናገረው ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ የምነግርኽን ፡ ኹሉ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ንገር ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ዘጸ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ከንፈረ ፡ ቈላፍ ፡ ነኝ ፤ እንዴትስ ፡ ፈርዖን ፡ ይሰማኛል ፧ አለ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ እይ ፥ እኔ ፡ ለፈርዖን ፡ አምላክ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ ወንድምኽም ፡ አሮን ፡ ነቢይ ፡ ይኾንልኻል ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ያዘዝኹኽን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ትነግረዋለኽ ፤ ወንድምኽም ፡ አሮን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከአገሩ ፡ ይለቅ ፡ ዘንድ ፡ ከፈርዖን ፡ ጋራ ፡ ይናገራል ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ እኔም ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸናለኹ ፥ በግብጽ ፡ ምድርም ፡ ድንቄንና ፡ ተኣምራቴን ፡ አበዛለኹ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ፈርዖንም ፡ አይሰማችኹም ፥ እጄንም ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፥ ሰራዊቴንም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሕዝቤን ፡ በታላቅ ፡ ፍርድ ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አወጣለኹ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ግብጻውያንም ፥ እጄን ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ በዘረጋኹ ፡ ጊዜ ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ከመካከላቸው ፡ ባወጣኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ፈርዖንንም ፡ በተናገሩት ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ የሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ አሮንም ፡ የሰማንያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገራቸው ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ፈርዖን ፦ ተኣምራትን ፡ አሳዩኝ ፡ ሲላችኹ ፥ አሮንን ፦ በትርኽን ፡ ወስደኽ ፡ እባብ ፡

---

67 ዕብ. ፥ አቢይሁ ፡ (አባቱ) ።

68 የተምር ፡ ደሴት ።

69 ዕብ. ፥ እልቀናህ ።

70 ዕብ. ፥ ፊነሐስ ፡ (አፈ ፡ ነሐስ ፥ አፈ ፡ ከይሲ ፥ አፈ ፡ እባብ ፥ አፈ ፡ ነካሽ) ።

እንድትኾን ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ጣላት ፡ በለው ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ገቡ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ አሮንም ፡ በትሩን ፡ በፈርዖንና ፡ በባሮቹ ፡ ፊት ፡ ጣለ ፥ እባብም ፡ ኾነች ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ፈርዖንም ፡ ጠቢባንንና ፡ መተተኞችን ፡ ጠራ ፤ የግብጽም ፡ ጠንቋዮች ፡ በአስማታቸው ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ በትራቸውን ፡ ጣሉ ፥ እባቦችም ፡ ኾኑ ፤ የአሮን ፡ በትር ፡ ግን ፡ በትራቸውን ፡ ዋጠች ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ጸና ፥ አልሰማቸውምም ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ደነደነ ፥ ሕዝቡንም ፡ ለመልቀቅ ፡ እንቢ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ማልደኽ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ኺድ ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ ውሃ ፡ ይወጣል ፥ ትገናኘውም ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ በወንዝ ፡ ዳር ፡ ትቆማለኽ ፤ እባብም ፡ ኾና ፡ የተለወጠችውን ፡ በትር ፡ በእጅኽ ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ እንዲህም ፡ ትለዋለኽ ፦ የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፦ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዲያገለግሉኝ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወዳንተ ፡ ላከኝ ፤ እንሆም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አልሰማኽም ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ በዚህ ፡ ታውቃለኽ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ የወንዙን ፡ ውሃ ፡ በእጄ ፡ ባለችው ፡ በትር ፡ እመታለኹ ፥ ውሃውም ፡ ተለውጦ ፡ ደም ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በወንዙም ፡ ያሉት ፡ ዓሣዎች ፡ ይሞታሉ ፥ ወንዙም ፡ ይገማል ፤ ግብጻውያንም ፡ የወንዙን ፡ ውሃ ፡ ለመጠጣት ፡ ይጠላሉ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ አሮንን ፦ በትርኽን ፡ ውሰድ ፥ ደምም ፡ እንዲኾኑ ፡ በግብጽ ፡ ውሃዎች ፡ በወንዞቻቸውም ፡ በመስኖቻቸውም ፡ በኩሬዎቻቸውም ፡ በውሃ ፡ ማከማቻዎቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፡ በለው ፤ በግብጽም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በዕንጨት ፡ ዕቃና ፡ በድንጋይ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ደም ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ በትሩንም ፡ አነሣ ፥ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹም ፡ ፊት ፡ የወንዙን ፡ ውሃ ፡ መታ ፤ የወንዙም ፡ ውሃ ፡ ኹሉ ፡ ተለውጦ ፡ ደም ፡ ኾነ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በወንዙም ፡ የነበሩ ፡ ዓሣዎች ፡ ሞቱ ፤ ወንዙም ፡ ገማ ፥ ግብጻውያንም ፡ ከወንዙ ፡ ውሃ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፡ ደሙም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ የግብጽም ፡ ጠንቋዮች ፡ በአስማታቸው ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረ ፡ የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ጸና ፥ አልሰማቸውምም ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ፈርዖንም ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፥ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ በልቡ ፡ አላኖረውም ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ግብጻውያንም ፡ ኹሉ ፡ የወንዙን ፡ ውሃ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉምና ፡ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ውሃ ፡ ሊጠጡ ፡ ቈፈሩ ።

ዘጸ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወንዙን ፡ ከመታ ፡ በኋላ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ተናገረው ፦ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ግባ ፡ እንዲህም ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያገለግለኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ለመልቀቅ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ አገርኽን ፡ ሹሉ ፡ በጓጕንቸሮች ፡ እመታለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ወንዙም ፡ ጓጕንቸሮችን ፡ ያፈላል ፥ ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፥ ወደ ፡ መኝታ ፡ ቤትኽ ፥ ወደ ፡ ዐልጋኽም ፥ ወደባሪያዎችኽም ፡ ቤት ፥ በሕዝብኽም ፡ ላይ ፥ ወደ ፡ ምድጆችኽም ፥ ወደ ፡ ቡሓቃዎችኽም ፡ ይገባሉ ፤

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ጓጕንቸሮችም ፡ ባንተ ፡ በሕዝብኽም ፡ በባሪያዎችም ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ አሮንን ፦ በትርኽን ፡ ይዘኽ ፡ በወንዞቹና ፡ በመስኖቹ ፡ በውሃ ፡ ማከማቻዎቹም ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ጓጕንቸሮችን ፡ አውጣ ፡ በለው ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ አሮንም ፡ በግብጽ ፡ ውሃዎች ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ ጓጕንቸሮቹም ፡ ወጡ ፥ የግብጽንም ፡ አገር ፡ ሸፈኑ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ጠንቋዮችም ፡ በአስማታቸው ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ጓጕንቸሮችን ፡ አወጡ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ጠርቶ ፦ ጓጕንቸሮቹን ፡ ከእኔ ፡ ከሕዝቤም ፡ እንዲያርቅ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩልኝ ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ እለቃለኹ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ ፈርዖንን ፦ ጓጕንቸሮቹ ፡ ከአንተ ፡ ከቤቶችኽም ፡ እንዲጠፉ ፥ በወንዙም ፡ ብቻ ፡ እንዲቀሩ ፥ ለአንተ ፡ ለባሪያዎችኽም ፡ ለሕዝብኽም ፡ መቼ ፡ እንድጸልይ ፡ አስታውቀኝ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ነገ ፥ አለ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ሙሴም ፦ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚመስል ፡ እንደሌለ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ጓጕንቸሮቹም ፡ ከአንተ ፡ ከቤቶችኽም ፡ ከባሪያዎችኽም ፡ ከሕዝብኽም ፡ ይኼዳሉ ፤ በወንዙም ፡ ብቻ ፡ ይቀራሉ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ፤ ሙሴም ፡ በፈርዖን ፡ ላይ ፡ ስላመጣቸው ፡ ጓጕንቸሮች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴ ፡ እንዳለ ፡ አደረገ ፤ ጓጕንቸሮቹም ፡ ከቤት ፣ ከወጀድም ፣ ከሜዳም ፡ ሞቱ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ አድርገው ፡ ሰበሰቧቸው ፤ ምድርም ፡ ገማች ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ፈርዖንም ፡ ጸጥታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልቡን ፡ አደነደነ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረ ፡ አልሰማቸውም ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ አሮንን ፦ በትርኽን ፡ ዘርጋ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ቅማል ፡ እንዲኾን ፡ የምድሩን ፡ ትቢያ ፡ ምታ ፡ በለው ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ እንዲሁም ፡ አደረጉ ፤ አሮንም ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፥ በበትሩም ፡ የምድሩን ፡ ትቢያ ፡ መታው ፥ በሰውና ፡ በእንስሳም ፡ ላይ ፡ ቅማል ፡ ኾነ ፤ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ የምድር ፡ ትቢያ ፡ ሹሉ ፡ ቅማል ፡ ኾነ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ጠንቋዮችም ፡ በአስማታቸው ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልቻሉም ፤ ቅማሉም ፡ በሰውና ፡ በእንስሳ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ ጠንቋዮችም ፡ ፈርዖንን ፦ ይህስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ ነው ፡ አሉት ፤ የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ጸና ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አልሰማቸውም ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ማልደኽ ፡ ተነሣ ፥ በፈርዖንም ፡ ፊት ፡ ቁም ፤ እንሆ ፥ ርሱ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ይወርዳል ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲያገለግለኝ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ሕዝቤንም ፡ ባትለቅ ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ በባሪያዎችኽም ፡ በሕዝብኽም ፡ በቤቶችኽም ፡ ላይ ፡ የዝንብ ፡ መንጋዎች ፡ እሰዳለኹ ፤ የግብጻውያን ፡ ቤቶች ፡ የሚኖሩባትም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በዝንብ ፡ መንጋዎች ፡ ይሞላሉ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደኾንኹ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፥ በዚያ ፡ የዝንብ ፡ መንጋ ፡ እንዳይኾን ፡ ሕዝቤ ፡ የሚቀመጥባትን ፡ የጌሤምን ፡ ምድር ፡ እለያለኹ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ በሕዝቤና ፡ በሕዝብኽ ፡ መካከል ፡ እለያለኹ ፤ ይህም ፡ ተኣምራት ፡ ነገ ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ በፈርዖንም ፡ ቤት ፡ በባሪያዎቹም ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ የዝንብ ፡ መንጋ ፡ መጣ ፤ በግብጽም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከዝንቡ ፡ መንጋ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ጠፋች ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ጠርቶ ፦ ኺዱ ፥ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ለአምላካችኹ ፡ ሠዉ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ሙሴም ፦ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላካችን ፡ የግብጻውያንን ፡ ርኵሰት ፡ እንሠዋለንና ፡ እንዲህ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ፤ እንሆ ፥ እኛ ፡ የግብጻውያንን ፡ ርኵሰት ፡ በፊታቸው ፡ ብንሠዋ ፡ አይወግሩንምን ፧

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ እኛስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላካችን ፡ እንሠዋ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚያዘን ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እንኼዳለን ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ፈርዖንም ፦ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላካችኹ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ትሠዉ ፡ ዘንድ ፡ እለቃችኋለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርቃችኹ ፡ አትኺዱ ፥ ጸልዩልኝ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፦ እንሆ ፥ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ እወጣለኹ ፥ የዝንቡም ፡ መንጋዎች ፡ ከፈርዖን ፡ ከባሪያዎቹም ፡ ከሕዝቡም ፡ ነገ ፡ እንዲኼዱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ እንዳይለቅ ፡ ፈርዖን ፡ እንደገና ፡ አያታለን ፥ አለ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየ ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴ ፡ እንዳለ ፡ አደረገ ፤ የዝንቡንም ፡ መንጋዎች ፡ ከፈርዖን ፡ ከባሪያዎቹም ፡ ከሕዝቡም ፡ አስነሣ ፤ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ።

ዘጸ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ፈርዖንም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ልቡን ፡ አደነደነ ፥ ሕዝቡንም ፡ አልለቀቀም ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገብተኽ ፡ ንገረው ። የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ልትለቃቸውም ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ብትይዛቸውም ፥

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ በከብቶችኽ ፥ በፈረሶችም ፡

በአሀያዎችም ፡ በግመሎችም ፡ በበሬዎችም ፡ በበጎችም ፡ ላይ ፡ ትኾናለች ፤ ብርቱ ፡ ቸነፈርም ፡ ይወርዳል ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤልና ፡ በግብጽ ፡ ከብቶች ፡ መካከል ፡ ይለያል ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከብት ፡ አንዳች ፡ አይጠፋም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ነገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፡ ብሎ ፡ ጊዜን ፡ ወሰነ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያን ፡ ነገር ፡ በነጋው ፡ አደረገ ፥ የግብጽም ፡ ከብት ፡ ኹሉ ፡ ሞተ ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከብት ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልሞተም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ፈርዖንም ፡ ላከ ፥ እንሆም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከብት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልሞተም ። የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ደነደነ ፥ ሕዝቡንም ፡ አልለቀቀም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፦ እጃችኹን ፡ ሞልታችኹ ፡ ከምድጃ ፡ ዐመድ ፡ ውሰዱ ፥ ሙሴም ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይበትነው ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ርሱም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ትቢያ ፡ ይኾናል ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በሰውና ፡ በእንስሳ ፡ ላይ ፡ ሻሕኝ ፡ የሚያመጣ ፡ ቍስል ፡ ይኾናል ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ከምድጃውም ፡ ዐመድ ፡ ወስደው ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በተነው ፥ በሰውና ፡ በእንስሳም ፡ ላይ ፡ ሻሕኝ ፡ የሚያወጣ ፡ ቍስል ፡ ኾነ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ጠንቋዮችም ፡ ቍስል ፡ ስለ ፡ ነበረባቸው ፡ በሙሴ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አልቻሉም ፤ ቍስል ፡ በጠንቋዮችና ፡ በግብጻውያን ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነበረና ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸና ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ እንደተናገረው ፡ አልሰማቸውም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ማልደኽ ፡ ተነሣ ፥ በፈርዖንም ፡ ፊት ፡ ቆመኽ ፡ በለው ፦ የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲያገለግሉኝ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ በምድር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ እንደሌለ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ በሰውነትኽ ፡ በባሪያዎችኽም ፡ በሕዝብኽም ፡ ላይ ፡ መቅሠፍቴን ፡ ኹሉ ፡ አኹን ፡ እልካለኹ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ አኹን ፡ እጄን ፡ ዘርግቼ ፡ አንተን ፡ ሕዝብኽንም ፡ በቸነፈር ፡ በመታኹኽ ፡ ነበር ፥ አንተም ፡ ከምድር ፡ በጠፋኽ ፡ ነበር ፤

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኀይሌን ፡ እገልጥብኽ ፡ ዘንድ ፡ ስሜም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ አስነሥቼኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ እንዳትለቃቸው ፡ ገና ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ትታበያለኽን ፧

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፥ ከተመሠረተች ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ በግብጽ ፡ ኾኖ ፡ የማያውቅ ፥ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ በረዶ ፡ አዘንብብኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ በሜዳ ፡ የተገኘ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ያልገባ ፡ ሰውና ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ በረዶ ፡ ወርዶበት ፡ ይሞታልና ፥ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ላክ ፥ ከብቶችኽንም ፡ በሜዳም ፡ ያለኽን ፡ ኹሉ ፡ አስቸኵል ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ከፈርዖንም ፡ ባሪያዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የፈራ ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ከብቶቹን ፡ ወደ ፡

ቤቶቹ ፡ አሸሸ ፤

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ያላሰበ ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ከብቶቹን ፡ በሜዳ ፡ ተወ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በግብጽ ፡ አገር ፡ በሰው ፡ በእንስሳም ፡ በዕርሻም ፡ ቡቃያ ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፥ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ በረዶ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እጅኽን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርጋ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ሙሴም ፡ በትሩን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ነጐድጓድና ፡ በረዶ ፡ ላከ ፥ እሳትም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወረደ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በረዶ ፡ አዘነበ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ በረዶም ፡ ነበረ ፥ በበረዶውም ፡ መካከል ፡ እሳት ፡ ይቃጠል ፡ ነበር ፥ በረዶውም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ሕዝብ ፡ ከኾነ ፡ ዠምሮ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያልኾነ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ በረዶውም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ በሜዳ ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ መታ ፤ በረዶውም ፡ የዕርሻን ፡ ቡቃያ ፡ ሹሉ ፡ መታ ፥ የአገሩንም ፡ ዛፍ ፡ ሹሉ ፡ ሰበረ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተቀምጠው ፡ በነበሩባት ፡ በጌሤም ፡ አገር ፡ ብቻ ፡ በረዶ ፡ አልወረደም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ፈርዖንም ፡ ልኮ ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ጠራ ፦ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በደልኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፥ እኔና ፡ ሕዝቤም ፡ ኀጢአተኞች ፡ ነን ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ የአምላክ ፡ ነጐድጓድ ፣ በረዶውም ፡ በዝቷልና ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩ ፤ እለቃችኹማለኹ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ አትቀመጡም ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፦ ከከተማ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፡ እጄን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እዘረጋለኹ ፤ ምድሪቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነጐድጓዱ ፡ ይቀራል ፥ በረዶውም ፡ ደግሞ ፡ አይወርድም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተና ፡ ባሪያዎችኽ ፡ አምላክን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ገና ፡ እንደማትፈሩ ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ ገብሱ ፡ አሸቶ ፣ ተልባውም ፡ አፍርቶ ፡ ነበርና ፥ ተልባና ፡ ገብሱ ፡ ተመታ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ ስንዴውና ፡ ዐጃው ፡ ግን ፡ ጊዜው ፡ ገና ፡ ነበርና ፥ አልተመታም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ሙሴም ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ከከተማ ፡ ወጣ ፥ እጁንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘረጋ ፤ ነጐድጓዱም ፡ በረዶውም ፡ ተቋረጠ ፥ ዝናቡም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አልፈሰሰም ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ ፈርዖንም ፡ ዝናቡ ፡ በረዶውም ፡ ነጐድጓዱም ፡ እንደ ፡ ተቋረጠ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአትን ፡ ጨመረ ፥ ርሱና ፡ ባሪያዎቹም ፡ ልባቸውን ፡ አደነደኑ ።

ዘጸ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ የፈርዖንም ፡ ልብ ፡ ጸና ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ አፍ ፡ እንደተናገር ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አልለቀቀም ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 1-2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፥ በግብጻውያን ፡ ያደረግኹትን ፡ ነገር ፥ ያደረግኹባቸውንም ፡ ተኣምራቴን ፥ በልጆኽ ፡ በልጅ ፡ ልጆኽም ፡ ዦሮዎች ፡ ትነግር ፡ ዘንድ ፥ ይህችንም ፡ ተኣምራቴን ፡ በመካከላቸው ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፥ የርሱን ፡ የባሪያዎቹንም ፡ ልብ ፡ አደንድኛለኹና ፥ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ግባ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ አሮንም ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ገቡ ፥ አሉትም ፦ የዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በፊቴ ፡ ለመዋረድ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እንቢ ፡ ትላለኽ ፧ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ ልቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ሕዝቤን ፡ ለመልቀቅ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ ነገ ፡ በአገርኽ ፡ አንበጣዎችን ፡ አመጣለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ የምድሩንም ፡ ፊት ፡ ይሸፍኑታልና ፥ ምድሩን ፡ ለማየት ፡ አይቻልም ፤ ከበረዶውም ፡ አምልጦ ፡ የተረፈላችኹን ፡ ትርፍ ፡ ይበሉታል ፥ ያደገላችኹንም ፡ የዕርሻውን ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይበሉታል ፤

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ቤቶችኽም ፡ የባሪያዎችኽም ፡ ኹሉ ፡ ቤቶች ፡ የግብጻውያንም ፡ ኹሉ ፡ ቤቶች ፡ በእነርሱ ፡ ይሞላል ፤ አባቶችኽ ፡ የአባቶችኽም ፡ አባቶች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከተቀመጡበት ፡ ቀን ፡ ገምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ያላዩት ፡ ነው ። ተመልሶም ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ የፈርዖንም ፡ ባሪያዎች ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ዕንቅፋት ፡ ይኾንብናል ፧ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ልቀቅ ፡ ግብጽስ ፡ እንደ ፡ ጠፋች ፡ ገና ፡ አታውቅምን ፧ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ መልሶ ፡ አስመጣቸው ። ኺዱ ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚኼዱት ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፦ እኛ ፡ እንኼዳለን ፥ የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ኾኖልናልና ፥ ታናናሾቻችንና ፡ ሽማግሌዎቻችን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ በጎቻችንና ፡ ከብቶቻችንም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይኼዳሉ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ፈርዖንም ፦ እናንተን ፡ ከልጆቻችኹ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ በፊታችኹ ፡ እንደሚኾን ፡ ተመልከቱ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ አይደለም ፤ እናንተ ፡ ወንዶቹ ፡ ኺዱ ፥ ይህን ፡ ፈልጋችኋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሉ ፡ አላቸው ። ከፈርዖንም ፡ ፊት ፡ አባረሯቸው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በግብጽ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ እንዲወጡ ፥ ከበረዶውም ፡ የተረፈውን ፡ የምድርን ፡ ቡቃያ ፡ ኹሉ ፡ እንዲበሉ ፥ ስለ ፡ አንበጣዎች ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ በትሩን ፡ ዘረጋ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የምሥራቅን ፡ ነፋስ ፡ ያን ፡ ቀን ፡ ኹሉ ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ አመጣ ፤ ማለዳም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የምሥራቁ ፡ ነፋስ ፡ አንበጣዎቹን ፡ አመጣ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ አንበጣዎችም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጡ ፥ በግብጽም ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፤ ይህንም ፡ የሚያኽል ፡ አንበጣ ፡ በፊት ፡ አልነበረም ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ አይኾንም ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ የምድሩንም ፡ ፊት ፡ ፈጽመው ፡ ሸፈኑት ፡ አገሪቱም ፡ ጨለመች ፤ የአገሪቱን ፡ ቡቃያ ፡ ኹሉ ፡ በረዶውም ፡ የተወውን ፡ በዛፉ ፡ የነበረውን ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በሉ ፤ ለምለም ፡ ነገር ፡ ዛፍም ፡ የምድር ፡ ሣርም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ አልቀረም ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በፍጥነት ፡ ጠራ ፦ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናንተንም ፡ በደልኹ ፤

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ኀጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በሉኝ ፥ ይህንም ፡ ሞት ፡ ብቻ ፡ ከእኔ ፡ ያነሣልኝ ፡ ዘንድ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኑ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ሙሴም ፡ ከፈርዖን ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመነ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከምዕራብ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋሱን ፡ አስወገደ ፥ አንበጣዎችንም ፡ ወስዶ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ጣላቸው ፤ አንድ ፡ አንበጣም ፡ በግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ ዅሉ ፡ አልቀረም ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸና ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አልለቀቀም ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ እጅኽን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርጋ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ የሚዳስሰው ፡ ጽኑ ፡ ጨለማ ፡ ይኹን ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ሙሴም ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ ጨለማ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ኾነ ፤

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ማንም ፡ ወንድሙን ፡ አላየም ፥ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ሙሉ ፡ ከስፍራው ፡ ማንም ፡ አልተነሣም ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ ግን ፡ በተቀመጡበት ፡ ስፍራ ፡ ብርሃን ፡ ነበራቸው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴን ፡ ጠርቶ ፦ ኺዱ ፥ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎቻችኹንና ፡ ከብቶቻችኹን ፡ ተዉ ፤ ልጆቻችኹ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኺዱ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ሙሴም ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምንሠዋው ፡ መሥዋዕትንና ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትን ፡ ትሰጠናለኽ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ከነርሱ ፡ እንወስዳለንና ፡ ከብቶቻችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይኼዳሉ ፥ አንድ ፡ ሰኰናም ፡ አይቀርም ፤ አምላካችን ፡ የምናገለግለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከዚያ ፡ እስክንደርስ ፡ አናውቅም ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔር ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸና ፥ ሊለቃቸውም ፡ አልወደደም ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ፈርዖንም ፦ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ኺድ ፤ ፊቴን ፡ ባየኽበት ፡ ቀን ፡ ትሞታለኽና ፡ ፊቴን ፡ እንዳታይ ፡ ተጠንቀቅ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፦ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ ይኹን ፤ ፊትኽን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አላይም ፡ አለ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በፈርዖንና ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ገና ፡ አንዲት ፡ መቅሠፍት ፡ አመጣለኹ ፥ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ይለቃችኋል ፤ ሲለቃችኹም ፡ አባሮ ፡ ይሰዳችኋል ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ወንዱ ፡ ከወዳጁ ፡ ሴቲቱም ፡ ከወዳጇ ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ በሕዝቡ ፡ ጐሮ ፡ ተናገር ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በግብጻውያን ፡ ፊት ፡ ለሕዝቡ ፡ ሞገስን ፡ ሰጠው ። ሙሴም ፡ በፈርዖን ፡ ባሪያዎችና ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእኩል ፡ ሌሊት ፡ እኔ ፡ በግብጽ ፡ መካከል ፡ እወጣለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ በግብጽም ፡ አገር ፡ ያለ ፡ በኵር ፡ ዅሉ ፥ በዙፋኑ ፡ ከሚቀመጠው ፡ ከፈርዖን ፡ በኵር ፡ ዠምሮ ፥ በወፍጮ ፡ እግር ፡ እስካለችው ፡ እስከባሪያዪቱ ፡ በኵር ፡ ድረስ ፥ የከብቱም ፡ በኵር ፡ ዅሉ ፡ ይሞታል ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ በግብጽም ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያልኾነ ፡ ኧላም ፡ ደግሞ ፡ የማይኾን ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በግብጻውያንና ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ እንዲለይ ፡ እንድታውቁ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ውሻ ፡ ምላሱን ፡ አያንቀሳቅስባቸውም ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ እነዚህም ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ኹሉ ፦ አንተ ፡ ውጣ ፡ የሚከተሉኽም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይውጡ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይወርዳሉ ፥ ለኔም ፡ ይሰግዳሉ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እወጣለኹ ። ሙሴም ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ተአምራቴ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ብዙ ፡ እንዲኾን ፡ ፈርዖን ፡ አይሰማችኹም ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ እነዚህን ፡ ተአምራቶች ፡ ኹሉ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸና ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ከአገሩ ፡ አልለቀቀም ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ይህ ፡ ወር ፡ የወሮች ፡ መዠመሪያ ፡ ይኹናችኹ ፤ የዓመቱም ፡ መዠመሪያ ፡ ወር ፡ ይኹናችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ተናገሩ ፥ በሷቸውም ፦ በዚህ ፡ ወር ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለአባቱ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ጠቦት ፥ ላንድ ፡ ቤትም ፡ አንድ ፡ ጠቦት ፡ ይውሰድ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ የቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥርም ፡ ለጠቦቱ ፡ የማይበቃ ፡ ቢኾን ፡ ርሱና ፡ ለቤቱ ፡ የቀረበው ፡ ጎረቤቱ ፡ እንደ ፡ ነፍሶቻቸው ፡ ቍጥር ፡ አንድ ፡ ጠቦት ፡ ይውሰድ ፤ እያንዳንዱም ፡ እንደሚበላው ፡ መጠን ፡ ከጠቦቱ ፡ ይካፈሉ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ የእናንተ ፡ ጠቦት ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ይኹን ፤ ከበጎች ፡ ወይም ፡ ከፍየሎች ፡ ውሰድ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ በዚህም ፡ ወር ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጠብቁት ፤ የእስራኤልም ፡ ማኅበር ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ሲመሽ ፡ ይረዱት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ከደሙም ፡ ወስደው ፡ በሚበሉበት ፡ ቤት ፡ ኹለቱን ፡ መቃንና ፡ ጕበኑን ፡ ይቅቡት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ በእሳት ፡ የተጠበሰውን ፡ ሥጋውንና ፡ ቂጣውን ፡ እንጀራ ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ይብሉ ፤ ከመራራ ፡ ቅጠል ፡ ጋራ ፡ ይበሉታል ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ጥሬውን ፡ በውሃም ፡ የበሰለውን ፡ አትብሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከራሱ ፡ ከጫኑ ፡ ከሆድ ፡ ዕቃው ፡ ጋራ ፡ በእሳት ፡ የተጠበሰውን ፡ ብሉት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ከርሱም ፡ እስከ ፡ ጧት ፡ አንዳች ፡ አታስቀሩ ፤ እስከ ፡ ጧትም ፡ የቀረውን ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ወገባችኹን ፡ ታጥቃችኹ ፥ ጫማችኹን ፡ በእግራችኹ ፥ በትራችኹንም ፡ በእጃችኹ ፡ አድርጋችኹ ፡ እንዲህ ፡ ብሉት ፥ ፈጥናችኹም ፡ ትበሉታላችኹ ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ እኔም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ዐልፋለኹ ፥ በግብጽም ፡ አገር ፡ ከሰው ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ በኵርን ፡ ኹሉ ፡ እገድላለኹ ፤ በግብጽም ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እፈርድባቸዋለኹ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ደሙም ፡ ባላችኹበት ፡ ቤቶች ፡ ምልክት ፡ ይኾንላችኋል ፤ ደሙንም ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡

ዐልፋለኹ ፤ እኔም ፡ የግብጽን ፡ አገር ፡ በመታኹ ፡ ጊዜ ፡ መቅሠፍቱ ፡ ለጥፋት ፡ አይመጣባችኹም ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ይህም ፡ ቀን ፡ መታሰቢያ ፡ ይኹናችኹ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ በዓል ፡ ታደርጉታላችኹ ፤ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ሥርዐት ፡ ኾኖ ፡ ለዘለዓለም ፡ ታደርጉታላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላላችኹ ፤ በመዠመሪያም ፡ ቀን ፡ ርሾውን ፡ ከቤታችኹ ፡ ታወጣላችኹ ፤ ከመዠመሪያውም ፡ ቀን ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ርሾ ፡ ያለበትን ፡ እንጀራ ፡ የሚበላ ፡ ነፍስ ፡ ከእስራኤል ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲሁም ፡ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኾንላችኋል ። ከሚበላው ፡ በቀር ፡ በእነርሱም ፡ ምንም ፡ አትሠሩም ፥ ይህንም ፡ ብቻ ፡ ታደርጉታላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ በዚህም ፡ ቀን ፡ ሰራዊታችኹን ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አውጥቻለኹና ፡ የቂጣውንም ፡ በዓል ፡ ጠብቁት ፤ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ቀን ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ትጠብቃላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ከወሩም ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ በቤታችኹ ፡ ርሾ ፡ አይገኝ ፤ ርሾ ፡ ያለበትንም ፡ እንጀራ ፡ የሚበላ ፡ ነፍስ ፥ ከመጻተኛው ፡ ዠምሮ ፡ እስከአገር ፡ ልጁ ፡ ድረስ ፥ ከእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ርሾ ፡ ያለበትን ፡ ምንም ፡ አትብሉ ፥ በቤቶቻችኹም ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ብሉ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጠርቶ ፡ አላቸው ፦ በየቤታችኹ ፡ ጠቦት ፡ ምረጡ ፥ ወስዳችኹም ፡ ለፋሲካ ፡ ዕረዱት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ከሂሶጵ ፡ ቅጠልም ፡ ጭብጥ ፡ ውሰዱ ፥ በዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ባለውም ፡ ደም ፡ ንከሩት ፥ በዕቃውም ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ደም ፡ ኹለቱን ፡ መቃኖችና ፡ ጕበኑን ፡ ርጨ ፤ ከእናንተም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከቤቱ ፡ ደጅ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ አይውጣ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግብጻውያንን ፡ ይመታ ፡ ዘንድ ፡ ያልፋልና ፤ ደሙንም ፡ በጕበኑና ፡ በኹለቱ ፡ መቃኖች ፡ ላይ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በደጁ ፡ ላይ ፡ ያልፋል ፥ አጥፊውም ፡ ይመታችኹ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤታችኹ ፡ እንዲገባ ፡ አይተውም ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ ለእናንተ ፡ ለልጆቻችኹም ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ አድርጋችኹ ፡ ይህችን ፡ ነገር ፡ ጠብቁ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ወደሚሰጣችኹ ፡ አገር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አምልኮ ፡ ጠብቁት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ልጆቻችኹ ፦ ይህ ፡ አምልኮ ፡ ለእናንተ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ ባሏችኹ ፡ ጊዜ ፥ እናንተ ፦ በግብጽ ፡ አገር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ዐልፎ ፡ ግብጻውያንን ፡ በመታ ፡ ጊዜ ፥ ቤቶቻችንን ፡ ያዳነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የማለፊ ፡ መሥዋዕት ፡ ይህች ፡ ናት ፡ ትሏቸዋላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ ሕዝቡም ፡ ተጐነበሰ ፥ ሰገደም ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኼዱ ፥ እንዲሁም ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ እኩል ፡ ሌሊት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፥ በዙፋን ፡ ከተቀመጠው ፡

ከፈርዖን ፡ በኵር ፡ ዠምሮ ፡ በግዞት ፡ እስካሉት ፡ እስከ ፡ ምርኮኞቹ ፡ በኵር ፡ ድረስ ፥ የግብጻውያንን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የተገኘውን ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፥ የእንስሳውንም ፡ በኵሮች ፡ ኹሉ ፡ መታ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 30 ፤ ፈርዖንም ፡ ባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ግብጻውያንም ፡ ኹሉ ፡ በሌሊት ፡ ተነሡ ፤ የሞተ ፡ የሌለበት ፡ ቤት ፡ አልነበረምና ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ ኾነ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 31 ፤ ፈርዖንም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በሌሊት ፡ ጠርቶ ፦ እናንተ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተነሡ ፥ ከሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ውጡ ፤ ኺዱም ፥ እንዳላችኹም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገልግሉ ፤

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 32 ፤ እንዳላችኹም ፡ መንጋዎቻችኹንና ፡ ከብቶቻችኹን ፡ ውሰዱ ፥ ኺዱም ፥ እኔንም ፡ ደግሞ ፡ ባርኩኝ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 33 ፤ ግብጻውያንም ፡ ፈጥነው ፡ ከምድሩ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ ያስቸኵሏቸው ፡ ነበር ። ኹላችን ፡ እንሞታለን ፡ ብለዋልና ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 34 ፤ ሕዝቡም ፡ ሊጡን ፡ ሳይቦካ ፡ ተሸከሙ ፥ ቡሓቃውንም ፡ በልብሳቸው ፡ ጠቅልለው ፡ በትከሻቸው ፡ ተሸከሙት ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 35 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉ ፥ ከግብጻውያንም ፡ የብርንና ፡ የወርቅን ፡ ዕቃ ፡ ልብስንም ፡ ለመኑ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 36 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሕዝቡ ፡ በግብጻውያን ፡ ፊት ፡ የፈለጉትን ፡ እንዲሰጧቸው ፡ ሞገስን ፡ ሰጠ ። እነርሱም ፡ ግብጻውያንን ፡ በዘበዙ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 37 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከራምሴ ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ሱኮት ፡ ኼዱ ፤ ከሕፃናቱም ፡ ሌላ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ የሚያኽል ፡ እግረኛ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 38 ፤ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ድብልቅ ፡ ሕዝብ ፡ መንጋዎችና ፡ ላሞችም ፡ እጅግ ፡ ብዙም ፡ ከብቶች ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 39 ፤ ከግብጽም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ያወጡትን ፡ ሊጥ ፡ ጋገሩ ፥ አልቦካም ፡ ነበርና ፥ ቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፡ አደረጉት ፤ ግብጻውያን ፡ በመውጣት ፡ ስላስቸኰሏቸው ፡ ይቈዩ ፡ ዘንድ ፡ አልተቻላቸውም ፥ ሥንቅም ፡ አላሰናዱም ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 40 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የተቀመጡት ፡ ዘመን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 41 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 42 ፤ ይህች ፡ ሌሊት ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ስላወጣቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተጠበቀች ፡ ናት ፤ ይህች ፡ ሌሊት ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እስከልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተጠበቀች ፡ ናት ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 43 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ አለ ፦ ይህ ፡ የፋሲካ ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ ከርሱ ፡ እንግዳ ፡ ሰው ፡ አይብላ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 44 ፤ በብር ፡ የተገዛ ፡ ባሪያ ፡ ቢኖር ፡ ከተገረዘ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ይብላ ።

ዘጸ. ፥ 12 ፥ 45 ፤ መጻተኛና ፡ ሞያተኛ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ አይብሉ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 46 ፤ ባንድ ፡ ቤትም ፡ ይበላ ፤ ከሥጋውም ፡ አንዳች ፡ ከቤት ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ አታውጡ ፤ ዐጥንትም ፡ አትስበሩበት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 47 ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ሹሉ ፡ ያድርጉት ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 48 ፤ እንግዳ ፡ ሰውም ፡ በመካከላችኹ ፡ ቢቀመጥ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ፋሲካን ፡ ሊያደርግ ፡ ቢወድ ፥ አስቀድሞ ፡ ወንድ ፡ ሹሉ ፡ ይገረዝ ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ይቅረብ ፡ ያድርግም ፤ እንደአገር ፡ ልጅም ፡ ይኾናል ፤ ያልተገረዘ ፡ ሹሉ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ አይብላ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 49 ፤ ለአገር ፡ ልጅ ፡ በእናንተ ፡ መካከልም ፡ ለሚቀመጡ ፡ እንግዳዎች ፡ አንድ ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 50 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሹሉ ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 12 ፡ 51 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከሰራዊታቸው ፡ ጋራ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ከሰውም ፡ ከእንስሳም ፡ ማሕፀንን ፡ የሚከፈት ፡ በኵር ፡ ሹሉ ፡ ለእኔ ፡ ቀድስልኝ ፤ የእኔ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ ከባርነት ፡ ቤት ፣ ከግብጽ ፡ የወጣችኹበትን ፡ ይህን ፡ ቀን ፡ ዐስቡ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከዚህ ፡ ቦታ ፡ በብርቱ ፡ እጅ ፡ አውጥቷችኋልና ፤ ስለዚህ ፥ የቦካ ፡ እንጀራ ፡ አትብሉ ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ በአቢብ ([71]) ፡ ወር ፡ ወጥታችኋል ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአንተ ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶችኽ ፡ ወደማለላቸው ፥ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈስ ፡ ምድር ፥ ወደከነዓናውያን ፡ ወደኬጢያውያንም ፡ ወደአሞራውያንም ፡ ወደዔዋያውያንም ፡ ወደኢያቡሳውያንም ፡ ምድር ፡ ባገባኽ ፡ ጊዜ ፡ ይህችን ፡ አምልኮ ፡ በዚህ ፡ ወር ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላለኽ ፥ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ሙሉ ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላለኽ ፥ ባንተም ፡ ዘንድ ፡ ርሾ ፡ ያለበት ፡ እንጀራ ፡ አይታይ ፥ በድንበርኽም ፡ ሹሉ ፡ ርሾ ፡ አይታይ ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ ከግብጽ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላደረገልኝ ፡ ነው ፡ ስትል ፡ ለልጅኽ ፡ ትነግረዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ በብርቱ ፡ እጅ ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቶኻልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ በአፍኽ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በእጅኽ ፡ እንደ ፡ ምልክት ፡ በዐይኖችኽም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ መታሰቢያ ፡ ይኹንልኽ ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በዓመት ፡ በዓመት ፡ በወራቱ ፡ ይህችን ፡ ሥርዐት ፡ ጠብቃት ።

ዘጸ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአንተ ፡ ለአባቶችኽም ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ ወደከነዓናውያን ፡ ምድር ፡ ባገባኽ ፡

---

71 አቢብ ፦ ከክረምት ፡ ቀጥሎ ፡ የሚመጣ ፡ የልምላሜ ፣ የጽጌ ፡ ወራት ፥ መፀው ።

ጊዜ ፥ ርሷንም ፡ በሰጠኸ ፡ ጊዜ ፥

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 12 ፤ ማሕፀንን ፡ የሚከፍተውን ፡ ሹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለይ ፤ ከሚኾንልኽ ፡ ከብት ፡ ሹሉ ፡ ተባት ፡ ኾኖ ፡ አስቀድሞ ፡ የተወለደው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 13 ፤ የአህያውን ፡ በኩር ፡ በጠቦት ፡ ትዋጀዋለኽ ፥ ባትዋጀውም ፡ ዐንገቱን ፡ ትሰብረዋለኽ ፤ የሰውንም ፡ በኩር ፡ ሹሉ ፡ ከልጆችኽ ፡ መካከል ፡ ትዋጀዋለኽ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 14 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ በሚመጣው ፡ ጊዜ ፡ ልጅኽ ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ በጠየቀኽ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ትለዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ በብርቱ ፡ እጅ ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣን ፤

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 15 ፤ ፈርዖንም ፡ እንዳይሰደን ፡ ልቡን ፡ ባጸና ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ በኩር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ በኩር ፡ ድረስ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ በኩር ፡ ሹሉ ፡ ገደለ ፤ ስለዚህ ፥ ወንድ ፡ ኾኖ ፡ ማሕፀንን ፡ የከፈተውን ፡ ሹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሠዋለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የልጆቼን ፡ በኩር ፡ ሹሉ ፡ እዋጃለኹ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በብርቱ ፡ እጅ ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቶናልና ፥ በእጅኽ ፡ እንደ ፡ ምልክት ፥ በዐይኖችኽም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ተንጠለጠለ ፡ ነገር ፡ ይኹንልኽ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 17 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ፈርዖን ፡ ሕዝቡን ፡ በለቀቀ ፡ ጊዜ ፥ ምንም ፡ ቅርብ ፡ ቢኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ምድር ፡ መንገድ ፡ አልመራቸውም ፤ እግዚአብሔር ፦ ሕዝቡ ፡ ሰልፉን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይጸጽተው ፡ ወደ ፡ ግብጽም ፡ እንዳይመለስ ፡ ብሏልና ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ በዙሪያ ፡ መንገድ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ባለችው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መራቸው ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ተሰልፈው ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 19 ፤ ዮሴፍም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሳይጐበኛችኹ ፡ አይቀርም ፥ ዐጥንቶቼንም ፡ ከዚህ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ታወጣላችኹ ፡ ብሎ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አምሏቸው ፡ ነበርና ፥ ሙሴ ፡ የርሱን ፡ ዐጥንቶች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 20 ፤ ከሱኮትም ፡ ተጓዙ ፥ በምድረ ፡ በዳውም ፡ ዳር ፡ በኤታም ፡ ሰፈሩ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 21 ፤ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፥ መንገድ ፡ ሊያሳያቸው ፡ ቀን ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፥ ሊያበራላቸውም ፡ ሌሊት ፡ በእሳት ፡ ዐምድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊታቸው ፡ ኼደ ።

ዘጸ. ፥ 13 ፥ 22 ፤ የደመና ፡ ዐምድ ፡ በቀን ፥ የእሳት ፡ ዐምድ ፡ በሌሊት ፡ ከሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ከቶ ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ዘጸ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፥ 14 ፥ 2 ፤ ተመልሰው ፡ በሚግዶልና ፡ በባሕር ፡ መካከል ፥ በበዓልዛፎንም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በፊሀሒሮት ፡ ፊት ፡ እንዲሰፍሩ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገር ፤ ከርሱም ፡ አጠገብ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ትሰፍራላችኹ ።

ዘጸ. ፥ 14 ፥ 3 ፤ ፈርዖንም ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፦ በምድር ፡ ይቅበዘበዛሉ ፥ ምድረ ፡ በዳም ፡ ዘጋቻቸው ፡ ይላል ።

ዘጸ. ፥ 14 ፥ 4 ፤ እኔም ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸናለኹ ፥ ርሱም ፡ ያባርራቸዋል ፤ በፈርዖንና ፡ በሰራዊቱም ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ አገኛለኹ ፤ ግብጻውያንም ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ። እነርሱም ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፥ 14 ፥ 5 ፤ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ ኰበለሉ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሩት ፤ የፈርዖንና ፡ የባሪያዎቹም ፡ ልብ ፡

በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ተለወጠና ፦ እንዳይገዛልን ፡ እስራኤልን ፡ የለቀቅነው ፡ ምን ፡ አድርገናል ፧ አሉ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ሠረገላውንም ፡ አሰናዳ ፥ ሕዝቡንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፤

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ የተመረጡ ፡ ሠረገላዎችንም ፥ የግብጽንም ፡ ፈረሶች ፡ ኹሉ ፥ በያንዳንዱም ፡ ሠረገላ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሦስተኞችን ፡ ወሰደ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የግብጽን ፡ ንጉሥ ፡ የፈርዖንን ፡ ልብ ፡ አጸና ፥ ርሱም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አሳደደ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከፍ ፡ ባለች ፡ እጅ ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ግብጻውያንም ፡ የፈርዖን ፡ ፈረሶች ፡ ሠረገላዎቹም ፡ ፈረሰኞቹም ፡ ሰራዊቱም ፡ ኹሉ ፥ አሳደዷቸው ፤ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ በበዓልዛፎን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በፊሀሒሮት ፡ አጠገብ ፡ ሰፍረው ፡ አገኟቸው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ፈርዖንም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዐይናቸውን ፡ አነሡ ፥ እንሆም ፡ ግብጻውያን ፡ በኋላቸው ፡ ገሥግሠው ፡ ነበር ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጮኹ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ሙሴንም ፦ በግብጽ ፡ መቃብር ፡ ስላልኖረ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ አወጣኸንን ፧ ከግብጽ ፡ ታወጣን ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ያደረግኽብን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ከምንሞት ፡ ብንገዛላቸው ፡ ይሻላልና ። ተወን ፥ ለግብጻውያን ፡ እንገዛ ፡ ብለን ፡ በግብጽ ፡ ሳለን ፡ ያልንኽ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ ለሕዝቡ ፦ አትፍሩ ፥ ዛሬ ፡ የምታይዋቸውን ፡ ግብጻውያንን ፡ ለዘለዓለም ፡ አታይዋቸውምና ፡ ቁሙ ፥ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ የሚያደርጋትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ እዩ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይዋጋል ፥ እናንተም ፡ ዝም ፡ ትላላችኹ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ለምን ፡ ትጮኽብኛለኽ ፧ እንዲጓዙ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገር ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ አንተም ፡ በትርኽን ፡ አንሣ ፥ እጅኽንም ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ፥ ክፈለውም ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ በየብስ ፡ ያልፋሉ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ እንሆም ፡ እኔ ፡ የግብጻውያንን ፡ ልብ ፡ አጸናለኹ ፥ በኋላቸውም ፡ ይገባሉ ፤ በፈርዖንና ፡ በሰራዊቱም ፡ ኹሉ ፡ በሠረገላዎቹም ፡ በፈረሰኞቹም ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ አገኛለኹ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ግብጻውያንም ፡ በፈርዖንና ፡ በሠረገላዎቹ ፡ በፈረሰኞቹም ፡ ላይ ፡ ክብር ፡ ባገኘኹ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ በእስራኤልም ፡ ሰራዊት ፡ ፊት ፡ ይኼድ ፡ የነበረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ በኋላቸው ፡ ኼደ ፤ የደመናውም ፡ ዐምድ ፡ ከፊታቸው ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ በኋላቸው ፡ ቆመ ፥

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ በግብጻውያን ፡ ሰፈርና ፡ በእስራኤል ፡ ሰፈር ፡ መካከልም ፡ ገባ ፤ በዚያም ፡ ደመናና ፡ ጨለማ ፡ ነበረ ፥ በዚህ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ አበራ ፤ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አልተቃረቡም ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ሙሴም ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ጽኑ ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ አምጥቶ ፡ ባሕሩን ፡ አስወገደው ፥ ባሕሩንም ፡ አደረቀው ፥ ውሃውም ፡ ተከፈለ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በባሕሩ ፡ መካከል ፡ በየብስ ፡ ገቡ ፤ ውሃውም ፡ በቀኛቸውና ፡ በግራቸው ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ኾነላቸው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ግብጻውያንም ፥ የፈርዖን ፡ ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎች ፡ ፈረሰኞቹም ፡ ኹሉ ፥ እያሳደዱ ፡ በኋላቸው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ መካከል ፡ ገቡ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ ንጋትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእሳትና ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፡ ኾኖ ፡ የግብጻውያንን ፡ ሰራዊት ፡ ተመለከተ ፥ የግብጻውያንንም ፡ ሰራዊት ፡ አወከ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ የሠረገላዎቹንም ፡ መንኰራኵር ፡ አሰረ ፥ ወደ ፡ ጭንቅም ፡ አገባቸው ፤ ግብጻውያንም ፦ እግዚአብሔር ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ ይዋጋላቸዋልና ፥ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ እንሽሽ ፡ አሉ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ እጅኽን ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ፥ ውሃውም ፡ በግብጻውያን ፡ በሠረገላዎቻቸውም ፡ በፈረሰኞቻቸውም ፡ ላይ ፡ ይመለስ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ሙሴም ፡ እጁን ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ዘረጋ ፥ ባሕሩም ፡ ማለዳ ፡ ወደ ፡ መፍሰሱ ፡ ተመለሰ ፤ ግብጻውያንም ፡ ከርሱ ፡ ሸሹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ግብጻውያንን ፡ በባሕሩ ፡ መካከል ፡ ጣላቸው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ውሃውም ፡ ተመልሶ ፡ በኋላቸው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የገቡትን ፡ ሠረገላዎችን ፡ ፈረሰኞችንም ፡ የፈርዖንንም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ከደነ ፤ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ በየብስ ፡ ኼዱ ፤ ውሃዎችም ፡ በቀኛቸውና ፡ በግራቸው ፡ እንደ ፡ ግድግዳ ፡ ኾኑላቸው ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ እስራኤልን ፡ እንደዚህ ፡ ከግብጻውያን ፡ እጅ ፡ አዳነ ፤ እስራኤልም ፡ የግብጻውያንን ፡ ሬሳ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ አዩ ።

ዘጸ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ እስራኤልም ፡ እግዚአብሔር ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ ያደረጋትን ፡ ታላቂቱን ፡ እጅ ፡ አዩ ፥ ሕዝቡም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈሩ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ በባሪያውም ፡ በሙሴ ፡ አመኑ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ሙሴና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ መዝሙር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘመሩ ፥ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። በክብር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ እዘምራለኹ ፤ ፈረሱንና ፡ ፈረሰኛውን ፡ በባሕር ፡ ጣለ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ጕልበቴ ፡ ዝማሬዬም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥

መድኀኒቴም ፡ ኾነልኝ ፤

ዘጸ. ፡ 15 ፡ ይህ ፡ አምላኬ ፡ ነው ፡ አመሰግነውማለኹ ፥ የአባቴ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ከፍ ፡ ከፍም ፡ አደርገዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ተዋጊ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ የፈርዖንን ፡ ሠረገላዎች ፡ ሰራዊቱንም ፡ በባሕር ፡ ጣላቸው ፤

የተመረጡት ፡ ሦስተኞች ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ሰጠሙ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ቀላያትም ፡ ከደኗቸው ፤

ወደ ፡ ባሕር ፡ ጥልቀት ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ሰጠሙ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ አቤቱ ፥ ቀኝኽ ፡ በኀይል ፡ ከበረ ፤

አቤቱ ፥ ቀኝኽ ፡ ጠላቱን ፡ አደቀቀ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ በክብርኽም ፡ ብዛት ፡ የተነሡብኽን ፡ አጠፋኽ ፤

ቍጣኽን ፡ ሰደድኽ ፥ እንደ ፡ ገለባም ፡ በላቸው ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ በአፍንጫኽ ፡ እስትንፋስ ፡ ውሃዎች ፡ ተከመሩ ፥

ፈሳሾቹም ፡ እንደ ፡ ክምር ፡ ቆሙ ፤

ሞገዱም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ረጋ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ጠላትም ፦ አሳድጄ ፡ እይዛቸዋለኹ ፥

ምርኮም ፡ እካፈላለኹ ፥ ነፍሴም ፡ ትጠግባቸዋለች ፤ ሰይፌንም ፡ እመዛለኹ ፥ እጄም ፡ ታጠፋቸዋለች ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ነፋስኽን ፡ አነፈስኽ ፥ ባሕርም ፡ ከደናቸው ፤

በኀይለኞች ፡ ውሃዎችም ፡ እንደ ፡ ዐረር ፡ ሰጠሙ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ በአማልክት ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

በምስጋና ፡ የተፈራኽ ፥ ድንቅንም ፡ የምታደርግ ፥

በቅድስና ፡ የከበረ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ቀኝኽን ፡ ዘረጋኽ ፥ ምድርም ፡ ዋጠቻቸው ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ በቸርነትኽ ፡ የተቤዣኻቸውን ፡ ሕዝብኽን ፡ መራኽ ፤

በኀይልኽ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ማደሪያኽ ፡ አገባኻቸው ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ አሕዛብ ፡ ሰሙ ፥ ተንቀጠቀጡም ፤

በፍልስጥኤም ፡ የሚኖሩትን ፡ ምጥ ፡ ያዛቸው ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኤዶም ፡ አለቃዎች ፡ ደነገጡ ፤ የሞዐብን ፡ ኀያላን ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ያዛቸው ፤ በከነዓን ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ቀለጡ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ ሕዝብኽ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፥ የተቤዣኸው ፡ ሕዝብ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፥ ፍርሀትና ፡ ድንጋጤ ፡ ወደቀባቸው ፤ በክንድኽ ፡ ብርታት ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ታስገባቸዋለኽ ፥ በርስትኽ ፡ ተራራም ፡ ትተክላቸዋለኽ ፥ አቤቱ ፥ ለማደሪያኽ ፡ ባደረግኸው ፡ ስፍራ ፥ አቤቱ ፥ እጆችኽ ፡ ባዘጋጁት ፡ መቅደስ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ይነግሣል ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ የፈርዖን ፡ ፈረሶች ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ከፈረሰኞቹም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ገቡ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የባሕሩን ፡ ውሃዎች ፡ መለሰባቸው ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ በባሕሩ ፡ መካከል ፡ በየብስ ፡ ኼዱ ።

ዘጸ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ የአሮን ፡ እኅት ፡ ነቢዩቱ ፡ ማርያምም ፡ ከበሮ ፡ በእጇ ፡ ወሰደች ፤ ሴቶችም ፡ ኹሉ ፡ በከበሮና ፡

በዘፈን ፡ በኧላዋ ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 21 ፤ ማርያምም ፡ እየዘመረች ፡ መለሰችላቸው ፦ በክብር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፤ ፈረሱንና ፡ ፈረሰኛውን ፡ በባሕር ፡ ጣለ ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 22 ፤ ሙሴም ፡ እስራኤልን ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ አስጓዘ ፥ ወደሱርም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጡ ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ኼዱ ፥ ውሃም ፡ አላገኙም ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 23 ፤ ወደ ፡ ማራም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የማራ ፡ ውሃ ፡ መራራ ፡ ነበረና ፡ ሊጠጡ ፡ አልቻሉም ፤ ስለዚህ ፥ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ማራ ([72]) ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 24 ፤ ሕዝቡም ፦ ምን ፡ እንጠጣለን ፧ ብለው ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ አንጐራጐሩ ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 25 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዕንጨትን ፡ አሳየው ፥ በውሃውም ፡ ላይ ፡ ጣለው ፥ ውሃውም ፡ ጣፈጠ ። በዚያም ፡ ሥርዐትንና ፡ ፍርድን ፡ አደረገላቸው ፥ በዚያም ፡ ፈተናቸው ፤

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 26 ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጥብቀኽ ፡ ብትሰማ ፥ በፊቱም ፡ የሚበጀውን ፡ ብታደርግ ፥ ትእዛዙንም ፡ ብታደምጥ ፥ ሥርዐቱንም ፡ ኹሉ ፡ ብትጠብቅ ፥ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ ያመጣኹትን ፡ በሽታ ፡ አላደርስብኽም ፤ እኔ ፡ ፈዋሽኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 15 ፥ 27 ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ኤሊም ፡ መጡ ፥ በዚያም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ የውሃ ፡ ምንጮችና ፡ ሰባ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ነበሩባት ፤ በዚያም ፡ በውሃው ፡ አጠገብ ፡ ሰፈሩ ።

——————————ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። ——————————

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 1 ፤ ከኤሊምም ፡ ተጓዙ ፥ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ከወጡ ፡ በኧላ ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በኤሊምና ፡ በሲና ፡ መካከል ፡ ወዳለችው ፡ ወደሲን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ።

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 2 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ አንጐራጐሩ ።

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፦ ይህን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ በራብ ፡ ልትገድሉ ፡ እኛን ፡ ወደዚች ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አውጥታችኧል ፤ በሥጋው ፡ ምንቸት ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጠን ፡ እንጀራ ፡ ስንበላ ፡ ስንጠግብ ፡ ሳለን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ምነው ፡ በሞትን! ፡ አሏቸው ።

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በሕጌ ፡ ይኼዱ ፡ ወይም ፡ አይኼዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኔ ፡ እንድፈትናቸው ፥ እንሆ ፥ ከሰማይ ፡ እንጀራን ፡ አዘንብላችኧለኹ ፤ ሕዝቡም ፡ ወጥተው ፡ ለዕለት ፡ ለዕለት ፡ የሚበቃቸውን ፡ ይልቀሙ ።

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 5 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ያመጡትን ፡ ያዘጋጁ ፥ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ከሚለቅሙት ፡ ይልቅ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኹን ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 6 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ እንዳወጣችኹ ፡ ማታ ፡ ታውቃላችኹ ፥

ዘጸ. ፥ 16 ፥ 7 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ክብር ፡ ጧት ፡ ታያላችኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ያንጐራጐራችኹትን ፡ ሰምቷልና ፥ በእኛም ፡ ላይ ፡ የምታንጐራጉሩ ፥ እኛ ፡ ምንድር ፡ ነን ፧ አሉ ።

---

72 ዕብ. ፥ ማራህ ፡ (መሪር • መራራ) ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያንጐራጐራችኹበትን ፡ ማንጐራጐራችኹን ፡ ሰምቷልና ፥ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋን ፥ ማልዶም ፡ ትጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ እንጀራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰጣችኋል ፤ እኛም ፡ ምንድር ፡ ነን ፧ ማንጐራጐራችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእኛ ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፦ ማንጐራጐራችኹን ፡ ሰምቷልና ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅረቡ ፡ በል ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ አሮን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፊታቸውን ፡ አቀኑ ፤ እንሆም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ በደመናው ፡ ታየ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማንጐራጐር ፡ ሰማኹ ። ወደ ፡ ማታ ፡ ሥጋን ፡ ትበላላችኹ ፥ ማለዳም ፡ እንጀራን ፡ ትጠግባላችኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፡ በላቸው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ድርጭቶች ፡ መጡ ፥ ሰፈሩንም ፡ ከደኑት ፤ ማለዳም ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ጠል ፡ ወድቆ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ የወደቀውም ፡ ጠል ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በመሬት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደቃቅ ፡ ውርጭ ፡ ኾኖ ፡ ቅርፊት ፡ የሚመስል ፡ ደቃቅ ፡ ነገር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ታየ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላወቁምና ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ተባባሉ ። ሙሴም ፦ ትበሉት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጣችኹ ፡ እንጀራ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፦ እያንዳንዱ ፡ የሚበላውን ፡ ያኽል ፡ ይልቀም ፤ በድንኳኑ ፡ ባሉት ፡ ነፍሶች ፡ ቍጥር ፡ ላንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጎሞር ፡ ውሰዱ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ አንዱ ፡ አብዝቶ ፡ አንዱም ፡ አሳንሶ ፡ ለቀመ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ በጎሞርም ፡ በሰፈሩት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ለለቀመ ፡ አልተረፈውም ፡ ጥቂትም ፡ ለለቀመ ፡ አልጐደለበትም ፤ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ የሚበላውን ፡ ያኽል ፡ ለቀመ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ሙሴም ፦ ማንም ፡ ከርሱ ፡ አንዳች ፡ ለነገ ፡ አያስቀር ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሙሴን ፡ አልሰሙትም ፤ አንዳንድ ፡ ሰዎችም ፡ ከርሱ ፡ ለነገ ፡ አስቀሩ ፥ ርሱም ፡ ተላ ፡ ሸተተም ፤ ሙሴም ፡ ተቈጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚበላውን ፡ ያኽል ፡ በጧት ፡ ለቀመ ፤ ፀሓይም ፡ በተኰሰ ፡ ጊዜ ፡ ቀለጠ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርገው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ኹለት ፡ ጎሞር ፡ እንጀራ ፡ ለቀሙ ፤ የማኅበሩም ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ ለሙሴ ፡ ነገሩት ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ነው ። ነገ ፡ ዕረፍት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የተቀደሰ ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ የምትጋግሩትን ፡ ጋግሩ ፥ የምትቀቅሉትንም ፡ ቀቅሉ ፥ የተረፈውን ፡ ኹሉ ፡ ለነገ ፡ እንዲጠበቅ ፡ አኑሩት ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ሙሴም ፡ እንዳዘዘ ፡ ለነገ ፡ አኖሩት ፤ አልሸተተም ፥ ትልም ፡ አልኾነበትም ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ሙሴም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፡ ዛሬ ፡ ነውና ፥ ብሉት ፤ ዛሬ ፡ በሜዳ ፡ አታገኙትም ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ልቀሙት ፤ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ አይገኝም ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ከሕዝቡ ፡ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፡ ሊለቅሙ ፡ ወጡ ፥ ምንም ፡ ምን ፡ አላገኙም ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ትእዛዞቼንና ፡ ሕጎቼን ፡ ለመጠበቅ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እንቢ ፡ ትላላችኹ ፧

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰንበትን ፡ እንደ ፡ ሰጣችኹ ፡ እዩ ፤ ስለዚህ ፥ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ የኹለት ፡ ቀን ፡ እንጀራ ፡ ሰጣችኹ ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በስፍራው ፡ ይቀመጥ ፥ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ማንም ፡ ከስፍራው ፡ አይኺድ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ሕዝቡም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዐረፈ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ የእስራኤልም ፡ ወገን ፡ ስሙን ፡ መና ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፤ ርሱም ፡ እንደ ፡ ድንብላል ፡ ዘር ፡ ነጭ ፡ ነው ፤ ጣዕሙም ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ቂጣ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ ሙሴም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኋችኹ ፡ ጊዜ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያበላኋችኹን ፡ እንጀራ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱ ፡ አንድ ፡ ጎሞር ፡ ሙሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጆቻችኹ ፡ ይጠበቅ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ አንድ ፡ ማድጋ ፡ ወስደኽ ፡ ጎሞር ፡ ሙሉ ፡ መና ፡ አግባበት ፥ ለልጅ ፡ ልጃችኹም ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አኑረው ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 34 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ አሮን ፡ በምስክሩ ፡ ፊት ፡ አኖረው ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 35 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደሚኖሩባት ፡ ምድር ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ መና ፡ በሉ ፤ ወደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡ ድንበር ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ መና ፡ በሉ ።

ዘጸ. ፡ 16 ፡ 36 ፤ ጎሞርም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፡ ከሲን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሊጓዙ ፡ ተነሡ ፥ በራፊዲምም ፡ ሰፈሩ ፤ ሕዝቡም ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ ውሃ ፡ አልነበረም ።

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ሕዝቡም ፡ ሙሴን ፡ ተጣሉት ፦ የምንጠጣውን ፡ ውሃ ፡ ስጠን ፡ አሉት ። ሙሴም ፦ ለምን ፡ ትጣሉኛላችኹ ፧ እግዚአብሔርንስ ፡ ለምን ፡ ትፈታተናላችኹ ፧ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ሕዝቡም ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ውሃ ፡ ተጠሙ ፦ እኛንና ፡ ልጆቻችንን ፡ ከብቶቻችንንም ፡ በጥማት ፡ ልትገድል ፡ ለምን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣኸን ፧ ሲሉ ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ አንጐራጐሩ ።

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፦ ሊወግሩኝ ፡ ቀርበዋልና ፥ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ዕለፍ ፥ ከእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰድ ፤ ወንዙንም ፡ የመታኽባትን ፡ በትር ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኻት ፡ ኺድ ።

ዘጸ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በዚያ ፡ በኮሬብ ፡ በአለት ፡ ላይ ፡ በፊትኽ ፡ እቆማለኹ ፤ አለቱንም ፡

ትመታለኽ ፥ ሕዝቡም ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ውሃ ፡ ይወጣል ፡ አለው ። ሙሴም ፡ በእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 7 ፤ ስለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ክርክር ፦ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፧ ሲሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ተፈታተኑት ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ማሣህ ፥ ደግሞም ፡ መሪባ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 8 ፤ ዐማሌቅም ፡ መጥቶ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ በራፊድም ፡ ተዋጋ ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 9 ፤ ሙሴም ፡ ኢያሱን ([73]) ፦ ጕልማሳዎችን ፡ ምረጥልን ፥ ወጥተኽም ፡ ከዐማሌቅ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ እኔ ፡ ነገ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በትር ፡ በእጄ ፡ ይዤ ፡ በኰረብታው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እቆማለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 10 ፤ ኢያሱም ፡ ሙሴ ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፥ ከዐማሌቅም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ሖርም ፡ ወደኰረብታው ፡ ራስ ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 11 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ እጁን ፡ ባነሣ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ድል ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ እጁንም ፡ ባወረደ ፡ ጊዜ ፡ ዐማሌቅ ፡ ድል ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 12 ፤ የሙሴ ፡ እጆች ፡ ግን ፡ ከብደው ፡ ነበር ፤ ድንጋይም ፡ ወሰዱ ፥ በበታቹም ፡ አኖሩ ፥ ርሱም ፡ ተቀመጠበት ፤ አሮንና ፡ ሖርም ፡ አንዱ ፡ በዚህ ፡ አንዱ ፡ በዚያ ፡ ኾነው ፡ እጆቹን ፡ ይደግፉ ፡ ነበር ፤ ፀሓይም ፡ እስክትገባ ፡ ድረስ ፡ እጆቹ ፡ ጠነከሩ ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 13 ፤ ኢያሱም ፡ ዐማሌቅንና ፡ ሕዝቡን ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ አሸነፈ ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የዐማሌቅን ፡ ዝክር ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ጨርሼ ፡ እደመስሳለኹና ፡ ይህን ፡ ለመታሰቢያ ፡ በመጽሐፍ ፡ ጻፈው ፥ በኢያሱም ፡ ጐሮ ፡ ተናገር ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 15 ፤ ሙሴም ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ ስሙንም ፡ ያህዌህ ፡ ንሲ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤

ዘጸ. ፥ 17 ፥ 16 ፤ ርሱም ፦ እጁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጣነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰልፍ ፡ በዐማሌቅ ፡ ላይ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኹን ፡ አለ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ዘጸ. ፥ 18 ፥ 1 ፤ የምድያምም ፡ ካህን ፡ የሙሴ ፡ ዐማት ፡ ዮቶር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ እንዳወጣ ፡ ሰማ ።

ዘጸ. ፥ 18 ፥ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሙሴ ፡ ዐማት ፡ ዮቶር ፡ መልሷት ፡ የነበረውን ፡ የሙሴን ፡ ሚስት ፡ ሲፓራን ፡ ኹለቱንም ፡ ልጆቿን ፡ ወሰደ ።

ዘጸ. ፥ 18 ፥ 3 ፤ ከነርሱ ፡ የአንደኛው ፡ ስም ፡ ጌርሳም ፡ ነበረ ፤ አባቱ ፦ በሌላ ፡ አገር ፡ ስደተኛ ፡ ነበርኹ ፡ ብሏልና ፤

ዘጸ. ፥ 18 ፥ 4 ፤ የኹለተኛውም ፡ ስም ፡ አልዓዛር ፡ ነበረ ፦ የአባቴ ፡ አምላክ ፡ ረዳኝ ፥ ከፈርዖንም ፡ ሰይፍ ፡ አዳነኝ ፡ ብሏልና ።

ዘጸ. ፥ 18 ፥ 5 ፤ የሙሴ ፡ ዐማት ፡ ዮቶርም ፡ ከልጆቹና ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ አጠገብ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ሰፈረ ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ መጣ ።

---

73 ዕብ. ፥ ይሹዐ ፡ (ያድኅን • ያድናል ፥ ይታደጋል) ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ሙሴንም ፦ እኔ ፡ ዐማትኽ ፡ ዮቶር ፥ ሚስትኽም ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ኹለቱ ፡ ልጆቿ ፡ መጥተንልኻል ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ ዐማቱን ፡ ሊገናኝ ፡ ወጣ ፥ ሰገደም ፥ ሳመውም ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ደኅንነታቸውን ፡ ተጠያየቁ ፥ ወደ ፡ ድንኳኑም ፡ ገቡ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈርዖንና ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፥ በመንገድም ፡ ያገኛቸውን ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዳናቸው ፡ ለዐማቱ ፡ ነገረው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ዮቶርም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ኹሉ ፥ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፡ ስላዳናቸው ፡ ደስ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ዮቶርም ፦ ከግብጻውያንና ፡ ከፈርዖን ፡ እጅ ፡ ያዳናችኹ ፥ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፡ ሕዝቡን ፡ ያዳነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ትዕቢት ፡ ባደረጉባቸው ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአማልክት ፡ ኹሉ ፡ እንዲበልጥ ፡ አኹን ፡ ዐወቅኹ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ የሙሴ ፡ ዐማት ፡ ዮቶርም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትንና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕትን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወሰደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ከሙሴ ፡ ዐማት ፡ ጋራ ፡ እንጀራ ፡ ሊበሉ ፡ አሮን ፡ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በነጋው ፡ ሙሴ ፡ በሕዝቡ ፡ ሊፈርድ ፡ ተቀመጠ ፤ ሕዝቡም ፡ በሙሴ ፡ ፊት ፡ ከጧት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ የሙሴም ፡ ዐማት ፡ በሕዝቡ ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ በሕዝቡ ፡ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ከጧት ፡ ገቦምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በዙሪያኽ ፡ ቆመው ፡ ሳሉ ፡ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቀምጠኻል ፧ አለው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ ዐማቱን ፦ ሕዝቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣሉ ፤

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ነገርም ፡ ቢኖራቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣሉ ፥ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ሰውም ፡ መካከል ፡ እፈርዳለኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥርዐትና ፡ ሕግ ፡ አስታውቃቸዋለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ የሙሴም ፡ ዐማት ፡ አለው ፦ አንተ ፡ የምታደርገው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ይከብድብኻልና ፥ አንተ ፣ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ትደክማላችኹ ፤ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ ልታደርገው ፡ አትችልም ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ እመክርኻለኹና ፡ ቃሌን ፡ ስማ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፤ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹን ፥ ነገራቸውንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አድርስ ፤

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ሥርዐቱንም ፡ ሕጉንም ፡ አስተምራቸው ፥ የሚኼዱበትን ፡ መንገድ ፡ የሚያደርጉትንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አሳያቸው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ አንተም ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ዐዋቂዎችን ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩትን ፥ የታመኑ ፥ የግፍንም ፡ ረብ ፡ የሚጠሉትን ፡ ሰዎች ፡ ምረጥ ፤ ከነርሱም ፡ የሺሕ ፡ አለቃዎችን ፥ የመቶ ፡ አለቃዎችን ፥ የዐምሳ ፡ አለቃዎችን ፥ የዐሥርም ፡ አለቃዎችን ፡ ሹምላቸው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ ፈራጅ ፤ አውራውን ፡ ነገር ፡ ዘቡሉ ፡ ወዳንተ ፡ ያምጡት ፥ ታናሹንም ፡ ነገር ፡ ዘቡሉ ፡ እነርሱ ፡ ይፍረዱ ፤ እነርሱም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ሸክሙን ፡ ይሸከማሉ ፥ ለአንተም ፡ ይቀልልኻል ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ይህንም ፡ ብታደርግ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ ቢያዝዝ ፥ መቆም ፡ ይቻልኻል ፥ ደግሞም ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘቡሉ ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይደርሳል ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ሙሴም ፡ የዐማቱን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፥ ያለውንም ፡ ዘቡሉ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ሙሴም ፡ ከእስራኤል ፡ ዘቡሉ ፡ ዐዋቂዎችን ፡ መረጠ ፥ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ የሺሕ ፡ አለቃዎች ፥ የመቶም ፡ አለቃዎች ፥ የዐምሳም ፡ አለቃዎች ፥ የዐሥርም ፡ አለቃዎች ፡ አድርጎ ፡ ሾማቸው ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ ዘቡሉ ፡ ፈረዱ ፤ የከበደባቸውንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ አመጡ ፥ ታናሹን ፡ ነገር ፡ ዘቡሉ ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ፈረዱ ።

ዘጸ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ሙሴም ፡ ዐማቱን ፡ ሰደደው ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ በሦስተኛውም ፡ ወር ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወደሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ከራፊድም ፡ ተነሥተው ፡ ወደሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ ሰፈሩ ፤ በዚያም ፡ እስራኤል ፡ በተራራው ፡ ፊት ፡ ሰፈረ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በተራራው ፡ ጠርቶ ፡ አለው ፦ ለያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ በል ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ንገር ፦

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ በግብጻውያን ፡ ያደረግኹትን ፥ በንስርም ፡ ክንፍ ፡ እንደተሸከምኋችኹ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ እንዳመጣኋችኹ ፡ አይታችኋል ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ ቃሌን ፡ በእውነት ፡ ብትሰሙ ፡ ኪዳኔንም ፡ ብትጠብቁ ፥ ምድር ፡ ዘቡሉ ፡ የእኔ ፡ ናትና ፥ ከአሕዛብ ፡ ዘቡሉ ፡ የተመረጠ ፡ ርስት ፡ ትኾኑልኛላችኹ ፤

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ እናንተም ፡ የካህናት ፡ መንግሥት ፡ የተቀደሰም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑልኛላችኹ ። ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የምትነግራቸው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ መጣ ፥ የሕዝቡንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጠርቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ዘቡሉ ፡ በፊታቸው ፡ ተናገረ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ሕዝቡ ፡ ዘቡሉ ፡ አንድ ፡ አፍ ፡ ኾነው ፦ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ዘቡሉ ፡ እናደርጋለን ፡ ብለው ፡ መለሱ ፤ ሙሴም ፡ የሕዝቡን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አደረሰ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ስነጋገር ፡ ሕዝቡ ፡ እንዲሰሙ ፥ ደግሞም ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲያምኑብኽ ፥ እንሆ ፥ በከባድ ፡ ደመና ፡ እመጣልኻለኹ ፡ አለው ። ሙሴም ፡ የሕዝቡን ፡ ቃል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነገረ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ኺድ ፥ ዛሬና ፡ ነገም ፡ ቀድሳቸው ፥ ልብሳቸውንም ፡ ይጠቡ ፤

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሲያዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይወርዳልና ፥ ለሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ይዘጋጁ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ወሰንም ፡ ለሕዝቡ ፡ በዙሪያው ፡ አድርግላቸው ፦ ወደ ፡ ተራራው ፡ እንዳትወጡ ፥ ጫፉንም ፡ እንዳትነኩ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ተራራውንም ፡ የነካ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፤

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ የማንም ፡ እጅ ፡ አይንካ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚነካው ፡ ኹሉ ፡ ይወገራል ፥ ወይም ፡ በፍላጻ ፡ ይወጋል ፤ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ አይድንም ፡ በላቸው ። ሳያቋርጥ ፡ የመለከት ፡ ድምፅ ፡ ሲነፋ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ይውጡ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ሙሴም ፡ ከተራራው ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወረደ ፥ ሕዝቡንም ፡ ቀደሰ ፤ ልብሳቸውንም ፡ ዐጠቡ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ሕዝቡንም ፦ ለሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ተዘጋጁ ፥ ወደ ፡ ሴቶቻችኹ ፡ አትቅረቡ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በማለዳ ፡ ጊዜ ፡ ነጐድጓድና ፡ መብረቅ ፡ ከባድም ፡ ደመና ፡ እጅግም ፡ የበረታ ፡ የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ኾነ ፤ በሰፈሩም ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተንቀጠቀጡ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ሙሴም ፡ ሕዝቡን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ለማገናኘት ፡ ከሰፈር ፡ አወጣቸው ፤ ከተራራውም ፡ እግርጌ ፡ ቆሙ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእሳት ፡ ስለ ፡ ወረደበት ፡ የሲና ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ይጤስ ፡ ነበር ፤ ከርሱም ፡ እንደ ፡ እቶን ፡ ጢስ ፡ ያለ ፡ ጢስ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፥ ተራራውም ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ይናወጥ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ የቀንደ ፡ መለከቱም ፡ ድምፅ ፡ እጅግ ፡ በበረታና ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ተናገረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በድምፅ ፡ መለሰለት ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ወረደ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ራስ ፡ ጠራው ፤ ሙሴም ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ውረድ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ለማየት ፡ ዳርቻውን ፡ እንዳያልፉ ፡ ከነርሱም ፡ ብዙ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ለሕዝቡ ፡ አስጠንቅቃቸው ፤

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚቀርቡት ፡ ካህናት ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳያጠፋቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ይቀድሱ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፦ አንተ ፦ በተራራው ፡ ዙሪያ ፡ ወሰን ፡ አድርግ ፡ ቀድሰውም ፡ ብለኽ ፡ አስጠንቅቀኸናልና ፥ ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ኺድ ፥ ውረድ ፤ አንተ ፡ አሮንም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ትወጣላችኹ ፤ ካህናቱና ፡ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳያጠፋቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አይተላለፉ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወረደ ፥ ይህንም ፡ ነገራቸው ።

፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣኹኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ አይኹኑልኽ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፥ በታችም ፡ በምድር ፡ ካለው ፥ ከምድርም ፡ በታች ፡ በውሃ ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ የማናቸውንም ፡ ምሳሌ ፥ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ለአንተ ፡ አታድርግ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ አትስገድላቸው ፥ አታምልካቸውምም ፤ በሚጠሉኝ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛና ፡ እስከ ፡ አራተኛ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ የአባቶችን ፡ ኀጢአት ፡ በልጆች ፡ ላይ ፡ የማመጣ ፤

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ለሚወዱኝ ፥ ትእዛዜንም ፡ ለሚጠብቁ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ምሕረትን ፡ የማደርግ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ የአምላክኽን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ አትጥራ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ በከንቱ ፡ የሚጠራውን ፡ ከበደል ፡ አያነጻውምና ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ትቀድሰው ፡ ዘንድ ፡ ዐስብ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ተግባርኽንም ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ፤

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላክኽ ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ አንተ ፥ ወንድ ፡ ልጅኽም ፥ ሴት ፡ ልጅኽም ፥ ሎሌኽም ፥ ገረድኽም ፥ ከብትኽም ፥ በደጆችኽም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ እንግዳ ፡ በርሱ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፤

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፥ ባሕርንም ፥ ያለባቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ፈጥሮ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዐርፏልና ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ባርኮታል ፡ ቀድሶታልም ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ዕድሜኽ ፡ እንዲረዝም ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ አትግደል ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ አታመንዝር ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ አትስረቅ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ በባልንጀራኽ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ የባልንጀራኽን ፡ ቤት ፡ አትመኝ ፤ የባልንጀራኽን ፡ ሚስት ፡ ሎሌውንም ፡ ገረዱንም ፡ በሬውንም ፡ አህያውንም ፡ ከባልንጀራኽ ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ማናቸውንም ፡ አትመኝ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ነጐድጓዱንና ፡ መብረቁን ፥ የቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ድምፅ ፥ ተራራውንም ፡ ሲጤስ ፡ አዩ ፤ ሕዝቡም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ተርበደበዱ ፥ ርቀውም ፡ ቆሙ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ሙሴንም ፦ አንተ ፡ ተናገረን ፡ እኛም ፡ እንሰማለን ፤ እንዳንሞት ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ አይናገረን ፡ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ሙሴም ፡ ለሕዝቡ ፦ እግዚአብሔር ፡ ሊፈትናችኹ ፥ ኀጢአትንም ፡ እንዳትሠሩ ፡ ርሱን ፡ መፍራት ፡ በልባችኹ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ መጥቷልና ፥ አትፍሩ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ሕዝቡም ፡ ርቀው ፡ ቆሙ ፥ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ጨለማው ፡ ቀረበ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ እኔ ፡ ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ተናገርኋችኹ ፡ እናንተ ፡ አይታችኋል ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ በአጠገቤ ፡ ምንም ፡ አታድርጉ ፤ የብር ፡ አማልክት ፡ የወርቅም ፡ አማልክት ፡ ለእናንተ ፡ አታድርጉ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ የጭቃ ፡ መሠዊያ ፡ ሥራልኝ ፥ የሚቃጠለውንና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕትኽን ፡ በጎችኽንም ፡ በሬዎችኽንም ፡ ሠዋበት ፤ ስሜን ፡ በማሳስብበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ መጥቼ ፡ እባርክኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ የድንጋይም ፡ መሠዊያ ፡ ብታደርግልኝ ፡ ብረት ፡ በነካው ፡ ድንጋይ ፡ አትሥራው ፤ በመሣሪያ ፡ ብትነካው ፡ ታረክሰዋለኽና ።

ዘጸ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋኽ ፡ በርሱ ፡ እንዳይገለጥ ፡ ወደ ፡ መሠዊያዬ ፡ በደረጃ ፡ አትውጣ ።

፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ በፊታቸው ፡ የምታደርገው ፡ ሥርዐት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ዕብራዊ ፡ ባሪያ ፡ የገዛኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያገልግልኽ ፥ በሰባተኛውም ፡ በከንቱ ፡ ሐራነት ፡ ይውጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ብቻውን ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብቻውን ፡ ይውጣ ፤ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሚስቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትውጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ ጌታው ፡ ሚስት ፡ አጋብቶት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወንዶች ፡ ወይም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ብትወልድለት ፥ ሚስቱና ፡ ልጆቿ ፡ ለጌታው ፡ ይኹኑ ፥ ርሱም ፡ ብቻውን ፡ ይውጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ ባሪያውም ፦ ጌታዬን ፡ ሚስቴን ፡ ልጆቼንም ፡ እወዳለኹ ፥ ሐራነት ፡ አልወጣም ፡ ብሎ ፡ ቢናገር ፥ ጌታው ፡ ወደ ፡ ፈራጆች ፡ ይውሰደው ፥

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ደጁም ፡ ወደ ፡ መቃኑ ፡ አቅርቦ ፡ ጉሮሮውን ፡ በወስፌ ፡ ይብሳው ፤ ለዘለዓለምም ፡ ባሪያው ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ሰውም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ለባርነት ፡ ቢሸጥ ፡ ባሪያዎች ፡ እንደሚወጡ ፡ ርሷ ፡ አትውጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ጌታዋን ፡ ደስ ፡ ባታሠኘው ፡ በወጆ ፡ ይስደዳት ፤ ስለ ፡ ናቃት ፡ ለሌላ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ይሸጣት ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ለልጁም ፡ ብድራት ፥ ለሴት ፡ ልጆች ፡ የሚገባውን ፡ ያድርግላት ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ከርሷ ፡ ሌላም ፡ ቢያጋባው ፥ መኖዋን ፡ ልብሷንም ፡ ለምንጣፉም ፡ ተገቢውን ፡ አያጕድልባት ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ይህንም ፡ ሦስት ፡ ነገር ፡ ባያደርግላት ፡ ያለገንዘብ ፡ በከንቱ ፡ ትውጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ሰው ፡ ሰውን ፡ ቢመታ ፡ ቢሞትም ፥ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ባይሸምቅበትም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ድንገት ፡ በእጁ ፡ ቢጥለው ፥ የሚሸሽበት ፡ ስፍራ ፡ እኔ ፡ አደርግልኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ቢደፍር ፥ ባልንጀራውን ፡ በተንኰል ፡ ቢገድለው ፥ እንዲሞት ፡ ከመሠዊያዬ ፡

አውጥተኽ ፡ ውሰደው ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚመታ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ሰውን ፡ ሰርቆ ፡ ቢሸጥ ፥ ወይም ፡ በእጁ ፡ ቢገኝ ፥ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚሰድብ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ኹለት ፡ ሰዎችም ፡ ቢጣሉ ፥ አንዱም ፡ ሌላውን ፡ በድንጋይ ፡ ወይም ፡ በጡጫ ፡ ቢመታ ፥ ያም ፡ ባይሞት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ታሞ ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ቢተኛ ፥

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ ተነሥቶም ፡ በምርኩዝ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ቢወጣ ፥ የመታው ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተግባሩን ፡ ስላስፈታው ፡ ገንዘብ ፡ ይከፍለው ፡ ዘንድ ፥ ያስፈውሰውም ፡ ዘንድ ፡ ግዴታ ፡ አለበት ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ሰውም ፡ ወንድ ፡ ባሪያውን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ በበትር ፡ ቢመታ ፥ ቢሞትበትም ፥ ፈጽሞ ፡ ይቀጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ የተመታው ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ቢቈይ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ፥ አይቀጣ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ቢጣሉ ፥ ያረገዘችንም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ እስክትጨነግፍ ፡ ቢገፏት ፡ ባትጐዳ ፡ ግን ፥ የሴቲቱ ፡ ባል ፡ የጣነበትን ፡ ያኽል ፡ ካሳ ፡ ይስጥ ፤ ፈራጆቹም ፡ እንደ ፡ ፈረዱበት ፡ ይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ጕዳት ፡ ግን ፡ ቢያገኛት ፡ ሕይወት ፡ በሕይወት ፥

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ዐይን ፡ በዐይን ፥ ጥርስ ፡ በጥርስ ፥ እጅ ፡ በእጅ ፥

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ እግር ፡ በእግር ፥ መቃጠል ፡ በመቃጠል ፥ ቀኑስል ፡ በቀኑስል ፥ ግርፋት ፡ በግርፋት ፡ ይከፈል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ሰውም ፡ የባሪያውን ፡ ወይም ፡ የባሪያዪቱን ፡ ዐይን ፡ ቢመታ ፡ ቢያጠፋውም ፥ ስለ ፡ ዐይኑ ፡ ሐራነት ፡ ያውጣው ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ የባሪያውን ፡ ወይም ፡ የባሪያዪቱን ፡ ጥርስ ፡ ቢሰብር ፥ ስለ ፡ ጥርሱ ፡ ሐራነት ፡ ያውጣው ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ በሬም ፡ ወንድን ፡ ወይም ፡ ሴትን ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ ቢወጋ ፥ በሬው ፡ ይወገር ፥ ሥጋውም ፡ አይበላ ፤ የበሬው ፡ ባለቤት ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ በሬው ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ ተዋጊ ፡ ቢኾን ፥ ሰዎችም ፡ ለባለቤቱ ፡ ቢመሰክሩለት ፡ ባይጠብቀውም ፥ ወንድንም ፡ ወይም ፡ ሴትን ፡ ቢገድል ፥ በሬው ፡ ይወገር ፥ ባለቤቱ ፡ ደግሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ከርሱ ፡ ግን ፡ ካሳ ፡ ቢፈልጉ ፥ የሕይወቱን ፡ ወጆ ፡ የጣነበትን ፡ ያኽል ፡ ይስጥ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ደግሞ ፡ ወንድን ፡ ልጅ ፡ ቢወጋ ፥ ሴትንም ፡ ልጅ ፡ ቢወጋ ፥ ይህንኑ ፡ ፍርድ ፡ ያድርጉበት ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ በሬው ፡ ወንድ ፡ ባሪያ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ ቢወጋ ፥ የበሬው ፡ ባለቤት ፡ ሠላሳ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ለጌታቸው ፡ ይስጥ ፥ በሬውም ፡ ይወገር ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ ሰውም ፡ ጕድጓድ ፡ ቢከፍት ፥ ወይም ፡ ጕድጓድ ፡ ቢቈፍር ፡ ባይከድነውም ፥ በሬም ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ ቢወድቅበት ፥

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ የጕድጓዱ ፡ ባለቤት ፡ ዋጋቸውን ፡ ለባለቤታቸው ፡ ይክፈል ፤ የሞተውም ፡ ለርሱ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 35 ፤ የሰው ፡ በሬ ፡ የሌላውን ፡ በሬ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢወጋ ፥ ደኅናውን ፡ በሬ ፡ ይሸጡ ፥ ዋጋውንም ፡ በትክክል ፡ ይካፈሉ ፤ የሞተውንም ፡ ደግሞ ፡ በትክክል ፡ ይካፈሉ ።

ዘጸ. ፡ 21 ፡ 36 ፤ በሬውም ፡ አስቀድሞ ፡ ተዋጊ ፡ መኾኑ ፡ ቢታወቅ ፥ ባለቤቱም ፡ ባይጠብቀው ፥ በሬውን ፡ በበሬው ፡ ፈንታ ፡ ይስጥ ፥ የሞተውም ፡ ለርሱ ፡ ይኹነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ሰው ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ቢሰርቅ ፥ ቢያርደው ፡ ወይም ፡ ቢሸጠው ፥ በበሬው ፡ ፋንታ ፡ ዐምስት ፡ በሬዎች ፥ በበጉም ፡ ፋንታ ፡ አራት ፡ በጎች ፡ ይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ ሌባው ፡ ቤት ፡ ሲምስ ፡ ቢገኝ ፥ ርሱም ፡ እስኪሞት ፡ ቢመታ ፥ በመታው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የደም ፡ ዕዳ ፡ አይኾንበትም ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ ፀሓይ ፡ ግን ፡ ከወጣችበት ፡ የደም ፡ ዕዳ ፡ አለበት ፤ ሌባው ፡ የሰረቀውን ፡ ይመልስ ፤ የሚከፍለውም ፡ ቢያጣ ፡ ስለሰረቀው ፡ ይሸጥ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ የሰረቀው ፡ ደኅና ፡ ኾኖ ፡ በእጁ ፡ ቢገኝ ፥ በሬም ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ቢኾን ፥ የሰረቀውን ፡ ያክል ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ዕርሻ ፡ ወይም ፡ ወደወይን ፡ ስፍራ ፡ ከብቱን ፡ ቢነዳው ፥ የሌላውንም ፡ ዕርሻ ፡ ቢያስበላ ፥ ከተመረጠ ፡ ዕርሻው ፡ ከማለፊያውም ፡ ወይኑ ፡ ይካስ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ እሳት ፡ ቢነሣ ፥ ሾኽንም ፡ ቢይዝ ፥ ክምሩንም ፡ ወይም ፡ ያልታጨደውን ፡ እኽል ፡ ወይም ፡ ዕርሻውን ፡ ቢያቃጥል ፥ እሳቱን ፡ ያነደደው ፡ ይካስ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ሰው ፡ በባልንጀራው ፡ ዘንድ ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንዲጠብቅለት ፡ ዐደራ ፡ ቢያኖር ፡ ከቤቱም ፡ ቢሰረቅ ፥ ሌባው ፡ ቢገኝ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ኹለት ፡ ይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ ሌባውም ፡ ባይገኝ ፡ ባለቤቱ ፡ ወደ ፡ ፈራጆች ፡ ይቅረብ ፥ እጁንም ፡ በባልንጀራው ፡ ከብት ፡ ላይ ፡ እንዳልዘረጋ ፡ ይማል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ ሰዎች ፡ ስለ ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አህያ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ስለጠፋ ፡ ነገር ፡ ቢካሰሱ ፥ አንዱም ፦ ይህ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ቢል ፥ ክርክራቸው ፡ ወደ ፡ ፈራጆች ፡ ይድረስ ፤ ፈራጆቹም ፡ የፈረዱበት ፡ ርሱ ፡ ለባልንጀራው ፡ ባንድ ፡ ኹለት ፡ ይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ሰው ፡ በባልንጀራው ፡ ዘንድ ፡ አህያ ፡ ወይም ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ እንስሳ ፡ እንዲጠብቅለት ፡ ዐደራ ፡ ቢያኖር ፥ ማንም ፡ ሳያይ ፡ ቢሞት ፡ ወይም ፡ ቢጐዳ ፡ ወይም ፡ ቢማረክ ፥

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ በባልንጀራው ፡ ከብት ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ እንዳልዘረጋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ በኹለታቸው ፡ መካከል ፡ ይኹን ፤ የከብቱም ፡ ባለቤት ፡ መሐላውን ፡ ይቀበል ፥ ርሱም ፡ ምንም ፡ አይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ቢሰረቅ ፡ የጠፋውን ፡ ያክል ፡ ለባለቤቱ ፡ ይመልስ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ተቧጭሮም ፡ ቢገኝ ፡ ለምስክር ፡ ያምጣው ፤ በመቧጨሩም ፡ ምክንያት ፡ አይክፈል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ከባልንጀራው ፡ አንዳች ፡ ቢዋስ ፡ ባለቤቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳይኖር ፡ ቢጐዳ ፥ ወይም ፡ ቢሞት ፥ ፈጽሞ ፡ ይክፈለው ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ባለቤቱ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቢኖር ፡ አይክፈል ፤ ቢከራየው ፡ በክራዩ ፡ ይግባ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ ሰው ፡ ያልታጨችውን ፡ ድንግል ፡ ቢያስታት ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፥ ማጫዋን ፡ ሰጥቶ ፡ ሚስት ፡ ያድርጋት ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ አባቷም ፡ ርሷን ፡ እንዳይሰጠው ፡ ፈጽሞ ፡ እንቢ ፡ ቢል ፡ እንደ ፡ ደናግል ፡ ማጫ ፡ ያኽል ፡ ብር ፡ ይክፈላት ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ መተተኛዪቱን ፡ በሕይወት ፡ እንድትኖር ፡ አትፍቀድላት ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ከእንስሳ ፡ ጋራ ፡ የሚረክስ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ለአንዳች ፡ አምላክ ፡ የሚሠዋ ፡ ፈጽሞ ፡ ይጥፋ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ስደተኞች ፡ ነበራችኹና ፡ ስደተኛውን ፡ አትበድለው ፥ ግፍም ፡ አታድርግበት ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ መበለቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጎቹን ፡ አታስጨንቋቸው ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ ብታስጨንቋቸውና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ቢጮኹ ፡ እኔ ፡ ጩኸታቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ እሰማለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ ቍጣዬም ፡ ይጸናባችኋል ፥ በሰይፍም ፡ አስገድላችኋለኹ ፤ ሚስቶቻችኹም ፡ መበለት ፥ ልጆቻችኹም ፡ ድኻ ፡ አደጎች ፡ ይኾናሉ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለወገኔ ፡ ለድኻው ፡ ገንዘብ ፡ ብታበድረው ፥ እንደ ፡ ባለዐራጣ ፡ አትኹን ፥ ዐራጣም ፡ አትጫንበት ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ የባልንጀራኽን ፡ ልብስ ፡ ለመያዣ ፡ ብትወስድ ፡ ፀሓይ ፡ ሳትገባ ፡ መልስለት ፤

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ ሥጋውን ፡ የሚከድንበት ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ነውና ፤ የሚተኛበትም ፡ ሌላ ፡ የለውምና ፤ ወደ ፡ እኔም ፡ ቢጮኽ ፡ መሐሪ ፡ ነኝና ፡ እሰማዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ፈራጆችን ፡ አትስደብ ፥ የሕዝብኽንም ፡ አለቃ ፡ አትርገመው ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ ነዶኽንም ፡ የወይንኽንም ፡ ጭማቂ ፡ ለማቅረብ ፡ አትዘግይ ፤ የልጆችኽንም ፡ በኵር ፡ ትሰጠኛለኽ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ እንዲሁም ፡ በበሬዎችኽና ፡ በበጎችኽ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጥ ፥ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ለእኔ ፡ ትሰጠዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ ቅዱስ ፡ ወገን ፡ ትኾኑልኛላችኹ ፤ ስለዚህ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ አውሬ ፡ የቧጨረውን ፡ ሥጋ ፡ ለውሻ ፡ ጣሉት ፡ እንጂ ፡ አትብሉት ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ አትቀበል ፤ ሐሰተኛ ፡ ምስክርም ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ከኀጢአተኛ ፡ ጋራ ፡ እጅኽን ፡ አታንሣ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ክፉውን ፡ ለማድረግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አትከተል ፤ ፍርድንም ፡ ለማጥመም ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተስማምተኽ ፡ አትመስክር ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ በፍርድ ፡ ነገርም ፡ ለድኻው ፡ አታድላ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ የጠላትኽን ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ አህያውን ፡ ጠፍቶ ፡ ብታገኘው ፡ በፍጹም ፡ መልስለት ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ የሚጠላኽን ፡ ሰው ፡ አህያ ፡ ከሸክሙ ፡ በታች ፡ ወድቆ ፡ ብታየው ፡ አትተወው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንሣው ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በሚሟገትበት ፡ ጊዜ ፡ የድኻኽን ፡ ፍርድ ፡ አታጥምም ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ከሐሰት ፡ ነገር ፡ ራቅ ፤ እኔ ፡ ኀጢአተኛውን ፡ አላጸድቅምና ፡ ንጹሕንና ፡ ጻድቅን ፡ አትግደል ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ማማለጃን ፡ አትቀበል ፤ ማማለጃ ፡ የዐይናማዎችን ፡ ሰዎች ፡ ዐይን ፡ ያሳውራልና ፥ የጻድቃንንም ፡ ቃል ፡ ያጣምማልና ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ በስደተኛው ፡ ግፍ ፡ አታድርጉ ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ስደተኞች ፡ ስለ ፡ ነበራችኹ ፡ የስደተኛ ፡ ነፍስ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዐውቃችኋልና ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ምድርኽን ፡ ዝራ ፥ ፍሬዋንም ፡ አግባ ፤

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ ተዋት ፡ አሳርፋትም ፤ የሕዝብኽም ፡ ድኻዎች ፡ ይበሉታል ፤ ያስቀሩትንም ፡ የሜዳ ፡ እንስሳ ፡ ይብላው ። እንዲሁም ፡ በወይንኽና ፡ በወይራኽ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራኽን ፡ ሥራ ፤ በሬኽና ፡ አህያኽ ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያኽም ፡ ልጅ ፡ ለመጻተኛውም ፡ ዕረፍት ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ዕረፍ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ያልኋችኹንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ፤ የሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ስም ፡ አትጥሩ ፥ ከአፋችኹም ፡ አይሰማ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በዓል ፡ ታደርግልኛለኽ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ ጠብቅ ፤ በአቢብ ፡ ወር ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ወጥታችኋልና ፥ በዚህ ፡ ወር ፡ እንዳዘዝኹኽ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላለኽ ፤ በፊቴም ፡ ባዶ ፡ እጃችኹን ፡ አትታዩ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ በዕርሻም ፡ የምትዘራትን ፡ የፍሬኽን ፡ በኵራት ፡ የመከር ፡ በዓል ፥ ዓመቱም ፡ ሳያልቅ ፡ ፍሬኽን ፡ ከዕርሻ ፡ ባከማቸኽ ፡ ጊዜ ፡ የመክተቻውን ፡ በዓል ፡ ጠብቅ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ በጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታይ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ የመሥዋዕቴን ፡ ደም ፡ ከቦካ ፡ እንጀራ ፡ ጋራ ፡ አትሠዋ ፤ የበዓሌም ፡ ስብ ፡ እስኪነጋ ፡ አይደር ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ የተመረጠውን ፡ የምድርኽን ፡ ፍሬ ፡ በኵራት ፡ ወደአምላክኽ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አምጣ ። ጠቦትን ፡ በእናቱ ፡ ወተት ፡ አትቀቅል ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ በመንገድ ፡ ይጠብቅኽ ፡ ዘንድ ፡ ወዳዘጋጀኹትም ፡ ስፍራ ፡ ያገባኽ ፡ ዘንድ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ መልአኩን ፡ በፊትኽ ፡ እሰዳለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ በፊቱ ፡ ተጠንቀቁ ፥ ቃሉንም ፡ አድምጡ ፤ ስሜም ፡ በርሱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኀጢአት ፡ ብትሠሩ ፡ ይቅር ፡ አይልምና ፡ አታስመርሩት ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ ብትሰማ ፥ ያልኹኽንም ፡ ኹሉ ፡ ብታደርግ ፥ ጠላቶችኽን ፡ እጣላቸዋለኹ ፥ የሚያስጨንቁኽንም ፡ አስጨንቃቸዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ መልአኬ ፡ በፊትኽ ፡ ይኼዳልና ፥ ወደ ፡ አሞራውያንም ፡ ወደ ፡ ኬጢያውያንም ፡ ወደ ፡ ፌርዛውያንም ፡ ወደ ፡ ከነዓናውያንም ፡ ወደ ፡ ዔዊያውያንም ፡ ወደ ፡ ኢያቡሳውያንም ፡ ያገባኻል ፤ እኔም ፡ አጠፋቸዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ ለአማልክታቸው ፡ አትስገድ ፥ አታምልካቸውም ፤ እንደ ፡ ሥራቸውም ፡ አትሥራ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽመኽ ፡ አፍርሳቸው ፥ ሐውልቶቻቸውንም ፡ ሰባብራቸው ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ አምላካችኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታመልኩታላችኹ ፥ ርሱም ፡ እኽልኽንና ፡ ውሃኽን ፡ ይባርካል ፤ በሽታንም ፡ ከመካከልኽ ፡ አርቃለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ በምድርኽም ፡ መካን ፡ ወይም ፡ የምትጨነግፍ ፡ አትኾንም ፤ የዘመንኽን ፡ ቍጥር ፡ እሞላለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ መፈራቴንም ፡ በፊትኽ ፡ እሰዳለኹ ፥ የምትኼድበትንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ አስደነግጣቸዋለኹ ፥ ጠላቶችኽንም ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ዝርርባቸውን ፡ እንዲያዞሩ ፡ አደርጋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 28 ፤ በፊትኽም ፡ ተርብ ፡ እሰዳለኹ ፥ ዔዊያዊውንም ፡ ከነዓናዊውንም ፡ ኬጢያዊውንም ፡ ከፊትኽ ፡ አባርራለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 29 ፤ ምድር ፡ ባድማ ፡ እንዳትኾን ፥ የምድር ፡ አራዊትም ፡ እንዳይበዙብኽ ፥ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ከፊታችኹ ፡ አላባርራቸውም ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስክትበዛ ፡ ምድርንም ፡ እስክትወርስ ፡ ድረስ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ አባርራቸዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ ድንበርኽንም ፡ ከቀይ ፡ ባሕር ፡ እስከፍልስጥኤም ፡ ባሕር ፥ ከምድረ ፡ በዳም ፡ እስከ ፡ ወንዙ ፡ ድረስ ፡ አደርጋለኹ ፤ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ በእጅኽ ፡ እጥላለኹና ፤ ከፊትኽም ፡ ታባርራቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ ከነርሱና ፡ ከአማልክታቸው ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አታድርግ ።

ዘጸ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ አማልክታቸውንም ፡ ብታመልክ ፡ ወጥመድ ፡ ይኾኑብኻልና ፥ እኔን ፡ እንድትበድል ፡ እንዳያደርጉኽ ፡ በአገርኽ ፡ አይቀመጡ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ ሙሴንም ፦ አንተ ፡ አሮንም ፡ ናዳብም ፡ አብዩድም ፡ ከእስራኤልም ፡ ሰባ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውጡ ፥ በሩቁም ፡ ስገዱ ፤

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ ሙሴም ፡ ብቻውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅረብ ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አይቅረቡ ፤ ሕዝቡም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አይውጡ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ መጣ ፡ ለሕዝቡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ሥርዐቱንም ፡ ኹሉ ፡ ነገረ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገራቸውን ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ እናደርጋለን ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃሎች ፡ ጻፈ ፤ ማለዳም ፡ ተነሣ ፥ ከተራራውም ፡ በታች ፡ መሠዊያን ፥ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ሐውልቶች ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሠራ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲያቀርቡ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ በሬዎችን ፡ እንዲሠዉ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ጐበዛዝት ፡ ሰደደ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ የደሙን ፡ እኩሌታ ፡ ወስዶ ፡ በቄሬ ፡ ውስጥ ፡ አደረገው ፤ የደሙንም ፡ እኩሌታ ፡

በመሠዊያው ፡ ረጨው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ የቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ መጽሐፍ ፡ ወስዶ ፡ ለሕዝቡ ፡ አነበበላቸው ፤ እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ እናደርጋለን ፡ እንታዘዛለንም ፡ አሉ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ ወስዶ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ረጨው ፦ በዚህ ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ደም ፥ እንሆ ፥ አለ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ አሮንም ፡ ናዳብም ፡ አብዩድም ፡ ከእስራኤልም ፡ ሰባ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወጡ ፤

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ አዩ ፤ ከእግሩም ፡ በታች ፡ እንደሰማይ ፡ መልክ ፡ የሚያበራ ፡ እንደ ፡ ብሩህ ፡ ሰንፔር ፡ ድንጋይ ፡ የሚመስል ፡ ወለል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ እጁንም ፡ በእስራኤል ፡ ዐዛውንቶች ፡ ላይ ፡ አልዘረጋም ፤ እነርሱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አዩ ፥ በሉም ፡ ጠጡም ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ውጣ ፥ በዚያም ፡ ኹን ፤ እነርሱን ፡ ታስተምር ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ የጻፍኹትን ፡ ሕግና ፡ ትእዛዝ ፡ የድንጋይም ፡ ጽላት ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ ሙሴና ፡ ሎሌው ፡ ኢያሱ ፡ ተነሡ ፤ ሙሴም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ሽማግሌዎችንም ፦ ወደ ፡ እናንተ ፡ እስክንመለስ ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ቈዩን ፤ አሮንና ፡ ሖርም ፥ እንሆ ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ፥ ነገረተኛም ፡ ቢኖር ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ይምጣ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፥ ደመናውም ፡ ተራራውን ፡ ሸፈነው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፥ ደመናውም ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሸፈነው ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ከደመናው ፡ ውስጥ ፡ ሙሴን ፡ ጠራው ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ መታየት ፡ እንደሚያቃጥል ፡ እሳት ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ደመናው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፡ ወደ ፡ ተራራውም ፡ ወጣ ፤ ሙሴም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ አርባ ፡ ሌሊትም ፡ ቈየ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ስጦታ ፡ ያመጡልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገር ፤ በገዛ ፡ እጁ ፡ ሊሰጠኝ ፡ በልቡ ፡ ከሚያምረው ፡ ሰው ፡ ሹሉ ፡ መባ ፡ ተቀበሉ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ የምትቀበሉት ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ወርቅ ፥ ብር ፥ ናስም ፥ ሰማያዊና ፡ ሐምራዊ ፡ ቀይም ፡ ግምጃ ፥ ጥሩ ፡ በፍታም ፥

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ የፍየልም ፡ ጠጕር ፥ ቀይ ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ ቊርበት ፥ የአቀኑስጣ ፡ ቊርበት ፥ የግራርም ፡ ዕንጨት ፥

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ የመብራትም ፡ ዘይት ፥ ለቅብዐት ፡ ዘይትና ፡ ለጣፋጭ ፡ ዕጣን ፡ ቅመም ፥

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ መረግድም ፥ ለኤፉድና ፡ ለደረት ፡ ኪስ ፡ የሚደረግ ፡ ፈርጥ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ በመካከላቸውም ፡ ዐድር ፡ ዘንድ ፡ መቅደስ ፡ ይሥሩልኝ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ እንደማሳይኽ ፡ ኹሉ ፥ እንደ ፡ ማደሪያው ፡ ምሳሌ ፡ እንደ ፡ ዕቃውም ፡ ኹሉ ፡ ምሳሌ ፥ እንዲሁ ፡ ሥሩት ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ከግራር ፡ ዕንጨትም ፡ ታቦትን ፡ ይሥሩ ፤ ርዝመቱ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ቁመቱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ በውስጥና ፡ በውጭም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለብጠው ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ አድርግለት ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ አራት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶችም ፡ አድርግለት ፥ እነርሱንም ፡ በአራቱ ፡ እግሮቹ ፡ ላይ ፡ አኑር ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ቀለበቶች ፥ በሌላው ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ቀለበቶች ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ መሎጊያዎችንም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሥራ ፥ በወርቅም ፡ ለብጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ለታቦቱ ፡ መሸከሚያ ፡ በታቦቱ ፡ ጐን ፡ ባሉት ፡ ቀለበቶች ፡ መሎጊያዎቹን ፡ አግባ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ በታቦቱ ፡ ቀለበቶች ፡ ውስጥ ፡ ይኑሩ ፥ ከቶም ፡ አይውጡ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ እኔ ፡ የምሰጥኽን ፡ ምስክር ፡ ታስቀምጣለኽ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ርዝመቱ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ የኾነ ፡ የስርየት ፡ መክደኛ ፡ ሥራ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ ኹለት ፡ ኪሩቤል ፡ ከተቀጠቀጠ ፡ ወርቅ ፡ ሥራ ፥ በስርየት ፡ መክደኛውም ፡ ላይ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ከስርየት ፡ መክደኛውም ፡ ጋራ ፡ አንዱን ፡ ኪሩብ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ ኹለተኛውንም ፡ ኪሩብ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ አድርገኽ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ትሠራዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ ኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋሉ ፥ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፡ በክንፎቻቸው ፡ ይሸፍናሉ ፥ ፊታቸውም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ይተያያል ፤ የኪሩቤልም ፡ ፊቶቻቸው ፡ ወደ ፡ ስርየት ፡ መክደኛው ፡ ይመለከታሉ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ እኔም ፡ የምሰጥኽን ፡ ምስክር ፡ በታቦቱ ፡ ውስጥ ፡ ታኖረዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ በዚያም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እገናኛለኹ ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ታዝ ፡ ዘንድ ፡ የምሰጥኽን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በኹለት ፡ ኪሩቤል ፡ መካከል ፥ በስርየት ፡ መክደኛውም ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ እነጋገርኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ ርዝመቱም ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ የኾነ ፡ ገበታ ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሥራ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ትለብጠዋለኽ ፤ በዙሪያውም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ አድርግለት ፤

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ በዙሪያውም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ የሚያኽል ፡ ክፈፍ ፡ አድርግለት ፤ የወርቅም ፡ አክሊል ፡ በክፈፉ ፡ ዙሪያ ፡ አድርግለት ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ አራትም ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ አድርግለት ፤ ቀለበቶቹንም ፡ አራቱ ፡ እግሮቹ ፡ ባሉበት ፡ በአራቱ ፡ ማእዘኖች ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ ገበታውንም ፡ ለመሸከም ፡ መሎጊያዎቹ ፡ እንዲሰኩባቸው ፡ ቀለበቶቹ ፡ በክፈፉ ፡ አቅራቢያ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ገበታውን ፡ ይሸከሙባቸው ፡ ዘንድ ፡ መሎጊያዎቹን ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠርተኽ ፡ በወርቅ ፡ ለብጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 29 ፤ ለማፍሰሻም ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ወጭቶቿን ፡ ጭልፋዎቿንም ፡ መቅጃዎቿንም ፡ ጽዋዎቿንም ፡ አድርግ ፤ እነርሱንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አድርጋቸው ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 30 ፤ በገበታም ፡ ላይ ፡ የገጽ ፡ ኅብስት ፡ ዘውል ፡ ጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 31 ፤ መቅረዝንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አድርግ ፤ መቅረዙ ፡ ከእግሩና ፡ ከአገዳው ፡ ጋራ ፡ በተቀጠቀጠ ፡ ሥራ ፡ ይደረግ ፤ ጽዋዎቹም ፡ ጕብጕቦቹም ፡ አበባዎቹም ፡ አንድነት ፡ በርሱ ፡ ይደረጉበት ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 32 ፤ በስተጐኑ ፡ ስድስት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ይውጡለት ፤ ሦስት ፡ የመቅረዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ ሦስትም ፡ የመቅረዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ይውጡ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 33 ፤ በአንደኛውም ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጕብጕብና ፡ አበባ ፡ ሦስትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፥ በኹለተኛውም ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጕብጕብና ፡ አበባ ፡ ሦስትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፤ እንዲሁም ፡ ከመቅረዙ ፡ ለሚወጡ ፡ ለስድስቱ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 34 ፤ በመቅረዙም ፡ ጕብጕቦቹንና ፡ አበባዎቹን ፡ አራትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 35 ፤ ከመቅረዙ ፡ ለሚወጡ ፡ ለስድስቱ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ከኹለት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጕብጕብ ፥ ከኹለትም ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጕብጕብ ፥ ደግሞ ፡ ከኹለት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጕብጕብ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 36 ፤ ጕብጕቦቹና ፡ ቅርንጫፎቹ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይኹኑ ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ከተቀረጸ ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይደረግ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 37 ፤ ሰባቱንም ፡ መብራቶች ፡ ሥራ ፤ በፊቱ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ መብራቶቹን ፡ ያቀጣጥሏቸዋል ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 38 ፤ መኰስተሪያዎቿን ፡ የኵስታሪ ፡ ማድረጊያዎቿንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 39 ፤ መቅረዙም ፡ ዕቃውም ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ መክሊት ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይሠሩ ።

ዘጸ. ፡ 25 ፡ 40 ፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ እንዳሳየኹኽ ፡ ምሳሌ ፡ እንድትሠራ ፡ ተጠንቀቅ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ ደግሞም ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፥ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ የተሠሩ ፡ ዐሥር ፡ መጋረጃዎች ፡ ያሉበትን ፡ ማደሪያ ፡ ሥራ ፤ ብልኅ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ ኪሩቤል ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ የያንዳንዱ ፡ መጋረጃ ፡ ርዝመት ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፤ የመጋረጃዎቹ ፡ ኹሉ ፡ መጠን ፡ ትክክል ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ዐምስቱ ፡ መጋረጃዎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተጋጠሙ ፡ ይኹኑ ፤ ዐምስቱም ፡ መጋረጃዎች ፡ እንዲሁ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተጋጠሙ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ከሚጋጠሙት ፡ መጋረጃዎች ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ የሰማያዊውን ፡ ግምጃ ፡ ቀለበቶች ፡ አድርግ ፤ ደግሞ ፡ ከተጋጠሙት ፡ ከሌላዎች ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ዐምሳ ፡ ቀለበቶችን ፡ ባንድ ፡ መጋረጃ ፡ አድርግ ፥ ዐምሳውንም ፡ ቀለበቶች ፡ በኹለተኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ አድርግ ፤ ቀለበቶቹ ፡ ኹሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይኾናሉ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ዐምሳ ፡ የወርቅ ፡ መያዣዎች ፡ ሥራ ፤ ማደሪያውንም ፡ አንድ ፡ እንዲኾን ፡ መጋረጃዎችን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመያዣዎች ፡ አጋጥማቸው ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ከማደሪያውም ፡ በላይ ፡ ለድንኳን ፡ የሚኾኑ ፡ መጋረጃዎች ፡ ከፍየል ፡ ጠጕር ፡ አድርግ ፤ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ መጋረጃዎች ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ እያንዳንዱም ፡ መጋረጃ ፡ ርዝመቱ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፥ እያንዳንዱም ፡ መጋረጃ ፡ ወርዱ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፤ የዐሥራ ፡ አንዱም ፡ መጋረጃዎች ፡ መጠናቸው ፡ ትክክል ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ዐምስቱ ፡ መጋረጃዎች ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ይጋጠሙ ፥ ስድስቱም ፡ መጋረጃዎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ይጋጠሙ ፤ ስድስተኛውም ፡ መጋረጃ ፡ በድንኳኑ ፡ ፊት ፡ ይደረብ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ከተጋጠሙት ፡ መጋረጃዎች ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ ዐምሳ ፡ ቀለበቶች ፡ አድርግ ፤ ደግሞ ፡ ከተጋጠሙት ፡ ከሌላዎቹ ፡ በአንድኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ ዐምሳ ፡ ቀለበቶች ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ ዐምሳም ፡ የናስ ፡ መያዣዎችን ፡ ሥራ ፥ መያዣዎችንም ፡ ወደ ፡ ቀለበቶች ፡ አግባቸው ፥ ድንኳኑም ፡ አንድ ፡ እንዲኾን ፡ አጋጥመው ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ከድንኳኑ ፡ መጋረጃዎች ፡ የቀረ ፡ ትርፍ ፡ ግማሽ ፡ መጋረጃ ፡ በማደሪያው ፡ ገርርባ ፡ ይንጠልጠል ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ማደሪያውን ፡ እንዲሸፍን ፡ ከርዝመቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ ባንድ ፡ ወገንም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ከድንኳኑ ፡ መጋረጃዎች ፡ የቀረው ፡ ትርፍ ፡ በማደሪያው ፡ ውጭ ፡ በወዲህና ፡ በወዲያ ፡ ይንጠልጠል ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ ለድንኳኑም ፡ መደረቢያ ፡ ከቀይ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ቍርበት ፥ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ መደረቢያ ፡ ከአቍስጣ ፡ ቍርበት ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ለማደሪያውም ፡ የሚቆሙትን ፡ ሳንቃዎች ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ የሳንቃው ፡ ኹሉ ፡ ርዝመቱ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ለያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚያያይዙ ፡ ኹለት ፡ ማጋጠሚያዎች ፡ ይኹኑለት ፤ ለማደሪያው ፡ ሳንቃዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ ለማደሪያውም ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ኻያ ፡ ሳንቃዎችን ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ከኻያውም ፡ ሳንቃዎች ፡ በታች ፡ አርባ ፡ የብር ፡ እግሮችን ፡ አድርግ ፤ ከያንዳንዱ ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ለኹለት ፡ ማጋጠሚያዎች ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ ለማደሪያው ፡ ለኹለተኛው ፡ ወገን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ኻያ ፡ ሳንቃዎች ፥

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ለእነርሱም ፡ አርባ ፡ የብር ፡ እግሮች ፡ ይኹኑ ፤ ከያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ ለማደሪያውም ፡ በምዕራቡ ፡ ወገን ፡ በስተኋላ ፡ ስድስት ፡ ሳንቃዎችን ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 23 ፤ ለማደሪያውም ፡ ለኹለቱ ፡ ማእዘን ፡ በስተኋላ ፡ ኹለት ፡ ሳንቃዎችን ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ ከታችም ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አንደኛው ፡ ቀለበት ፡ ድረስ ፡ አንዱ ፡ ሳንቃ ፡ ድርብ ፡ ይኹን ፤ እንዲሁም ፡ ለኹለቱ ፡ ይኹን ፤ እነርሱም ፡ ለኹለቱ ፡ ማእዘን ፡ ይኾናሉ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ ስምንት ፡ ሳንቃዎችና ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ የብር ፡ እግሮቻቸው ፡ ይኹኑ ፤ ከያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ ይኾናሉ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ ከግራርም ፡ ዕንጨት ፡ በማደሪያው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፥

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ በማደሪያውም ፡ በኹለተኛው ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፥ በማደሪያውም ፡ በስተኋላ ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ መካከለኛውም ፡ መወርወሪያ ፡ በሳንቃዎች ፡ መካከል ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ይለፍ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 29 ፤ ሳንቃዎቹንም ፡ በወርቅ ፡ ለብጣቸው ፤ ቀለበቶቻቸውንም ፡ የመወርወሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲኾኑላቸው ፡ ከወርቅ ፡ ሥራቸው ፤ መወርወሪያዎችንም ፡ በወርቅ ፡ ለብጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ ማደሪያውንም ፡ በተራራ ፡ እንዳሳየኹኽ ፡ ምሳሌ ፡ አቁም ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ መጋረጃውንም ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ አድርግ ፤ ብልኃ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ ኪሩቤል ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ በወርቅ ፡ በተለበጡት ፡ ከግራር ፡ ዕንጨትም ፡ በተሠሩት ፡ በአራቱ ፡ ምሰሶዎች ፡ ላይ ፡ ስቀለው ፤ ኵላቦቻቸውም ፡ ከወርቅ ፥ አራቱም ፡ እግሮቻቸው ፡ ከብር ፡ የተሠሩ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 33 ፤ መጋረጃውንም ፡ ከመያዣዎቹ ፡ በታች ፡ ታንጠለጥለዋለኽ ፥ በመጋረጃውም ፡ ውስጥ ፡ የምስክርን ፡ ታቦት ፡ አግባው ፤ መጋረጃውም ፡ በቅድስቱና ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ መካከል ፡ መለያ ፡ ይኹናችኹ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 34 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ውስጥ ፡ የስርየት ፡ መክደኛውን ፡ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 35 ፤ ገበታውንም ፡ በመጋረጃው ፡ ውጭ ፥ መቅረዙንም ፡ በገበታው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በማደሪያው ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ አድርግ ፤ ገበታውንም ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ አድርገው ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 36 ፤ ለድንኳኑም ፡ ደጃፍ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ መጋረጃ ፡ አድርግለት ።

ዘጸ. ፡ 26 ፡ 37 ፤ ለመጋረጃውም ፡ ዐምስት ፡ ምሰሶዎች ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አድርግ ፥ በወርቅም ፡ ለብጣቸው ፤ ኵላቦቻቸውም ፡ ከወርቅ ፡ የተሠሩ ፡ ይኹኑ ፤ ዐምስትም ፡ እግሮች ፡ አድርግላቸው ።

———————ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። ———————

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ መሠዊያ ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡

አድርግ ፤ አራት ፡ ማእዘንም ፡ ይኹን ፤ ከፍታውም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ በአራቱም ፡ ማእዘን ፡ ቀንዶችን ፡ ታደርጋለኽ ፥ ቀንዶቹም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ የተሠሩ ፡ ይኹኑ ፤ በናስም ፡ ለብጠው ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ ዐመድ ፡ የሚኾንባቸውን ፡ ምንቸቶች ፥ መጫሪያዎቹንም ፥ ድስቶቹንም ፥ ሜንጦዎቹንም ፥ ማንደጃዎቹንም ፡ አድርግ ፤ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ከናስ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ እንደ ፡ መረብ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ የናስ ፡ መከታ ፡ አድርግለት ፤ ለመከታውም ፡ አራት ፡ የናስ ፡ ቀለበት ፡ በአራት ፡ ማእዘኑ ፡ አድርግለት ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ መከታውም ፡ እስከመሠዊያው ፡ እኩሌታ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡ በመሠዊያው ፡ በሚዞረው ፡ በዕርከኑ ፡ ታች ፡ አድርገው ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ ለመሠዊያውም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ መሎጊያዎችን ፡ ሠርተኽ ፡ በናስ ፡ ለብጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ በቀለበቶች ፡ ውስጥ ፡ ይግቡ ፤ መሠዊያውንም ፡ ስትሸከሙ ፡ መሎጊያዎቹ ፡ በኹለቱ ፡ ወገኖች ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ከሳንቃዎች ፡ ሠርተኽ ፡ ባዶ ፡ አድርገው ፤ በተራራው ፡ እንዳሳየኹኽ ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሁ ፡ ያድርጉት ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ የማደሪያውንም ፡ አደባባይ ፡ ሥራ ፤ በደቡብ ፡ ወገን ፡ የጥሩ ፡ በፍታ ፡ መጋረጃዎች ፡ ይኹኑለት ፥ የአንዱም ፡ ወገን ፡ ርዝመት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፤

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ ኻያ ፡ ምሰሶዎችና ፡ ኻያ ፡ እግሮች ፡ ይኹኑለት ፤ የምሰሶዎቹም ፡ ኩላቦችና ፡ ዘንጎች ፡ የብር ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ እንዲሁም ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸው ፡ መጋረጃዎች ፥ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ ኻያ ፡ ምሰሶች ፡ ኻያም ፡ እግሮች ፡ ይኹኑ ፤ ለምሰሶዎችም ፡ የብር ፡ ኩላቦችና ፡ ዘንጎች ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ በምዕራብም ፡ ወገን ፡ ለአደባባዩ ፡ ስፋት ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸው ፡ መጋረጃዎች ፥ ዐሥርም ፡ ምሰሶዎች ፥ ዐሥርም ፡ እግሮች ፡ ይኹኑለት ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ በምሥራቅም ፡ ወገን ፡ የአደባባዩ ፡ ስፋት ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ የመጋረጃዎቹ ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፤ ምሰሶዎቹም ፡ ሦስት ፥ እግሮቹም ፡ ሦስት ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ በሌላውም ፡ ወገን ፡ የመጋረጃዎች ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፤ ምሰሶዎቹም ፡ ሦስት ፥ እግሮቹም ፡ ሦስት ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ ለአደባባዩም ፡ ደጅ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ መጋረጃ ፡ ይኾናል ፤ ምሰሶዎቹም ፡ አራት ፥ እግሮቹም ፡ አራት ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ በአደባባዩም ፡ ዙሪያ ፡ ላሉት ፡ ምሰሶዎች ፡ ኹሉ ፡ የብር ፡ ዘንጎች ፥ የብርም ፡ ኩላቦች ፥ የናስም ፡ እግሮች ፡ ይኹኑላቸው ።

ዘጸ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ የአደባባዩ ፡ ርዝመት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ስፋቱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፥ የመጋረጃውም ፡

ከፍታ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ይኹን ፤ መጋረጃውም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፥ እግሮቹም ፡ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፥ 27 ፥ 19 ፤ ለማገልገል ፡ ዅሉ ፡ የማደሪያው ፡ ዕቃ ፡ ዅሉ ፥ ካስማዎቹም ፡ ዅሉ ፡ የአደባባዩም ፡ ካስማዎች ፡ ዅሉ ፥ የናስ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፥ 27 ፥ 20 ፤ አንተም ፡ መብራቱን ፡ ዅል ፡ ጊዜ ፡ ያበሩት ፡ ዘንድ ፡ ለመብራት ፡ ተወቅጦ ፡ የተጠለለ ፡ ጥሩ ፡ የወይራ ፡ ዘይት ፡ እንዲያመጡልኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ።

ዘጸ. ፥ 27 ፥ 21 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ መጋረጃ ፡ ውጭ ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ከማታ ፡ እስከ ፡ ማለዳ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲበራ ፡ ያሰናዱት ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኹን ።

፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 1 ፤ አንተም ፡ ወንድምኽን ፡ አሮንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ልጆቹን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለይተኽ ፡ ካህናት ፡ ይኾኑልኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተ ፡ አቅርብ ፤ አሮንን ፡ የአሮንንም ፡ ልጆች ፥ ናዳብን ፡ አብዮድንም ፡ አልዓዛርንም ፡ ኢታምርንም ፥ አቅርብ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 2 ፤ የተቀደሰውንም ፡ ልብስ ፡ ለክብርና ፡ ለጌጥ ፡ እንዲኾን ፡ ለወንድምኽ ፡ ለአሮን ፡ ሥራለት ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 3 ፤ አንተም ፡ ካህን ፡ ኾኖ ፡ እንዲያገለግለኝ ፡ አሮን ፡ ቅዱስ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ልብስ ፡ እንዲሠሩለት ፡ የጥበብ ፡ መንፈስ ፡ ለሞላኹባቸው ፡ በልባቸው ፡ ጥበበኞች ፡ ለኾኑት ፡ ዅሉ ፡ ተናገር ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 4 ፤ የሚሠሯቸውም ፡ ልብሶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የደረት ፡ ኪስ ፡ ኤፉድም ፡ ቀሚስም ፡ ዝንጕርጕር ፡ የደረት ፡ ልብስም ፡ መጠምጠሚያም ፡ መታጠቂያም ፤ እነዚህም ፡ ካህናት ፡ ይኾኑልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለአሮን ፡ ለልጆቹም ፡ የተቀደሰ ፡ ልብስ ፡ ያድርጉ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 5 ፤ ወርቅንም ፥ ሰማያዊና ፡ ሐምራዊ ፡ ቀይም ፡ ግምጃ ፥ ጥሩ ፡ በፍታም ፡ ይውሰዱ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 6 ፤ ኤፉዱንም ፡ በብልኀት ፡ የተሠራ ፡ በወርቅና ፡ በሰማያዊ ፡ በሐምራዊም ፡ በቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ ብልኀ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ ያድርጉ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 7 ፤ ኹለቱ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ እንዲኾን ፡ በኹለቱ ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ የሚጋጠም ፡ ጨርቅ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 8 ፤ በላዩም ፡ መታጠቂያ ፡ ኾኖ ፡ በብልኀት ፡ የተጠለፈው ፡ የኤፉድ ፡ ቋድ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይኹን ፤ ከወርቅና ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊ ፡ ከቀይ ፡ ግምጃም ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ የተሠራ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 9 ፤ ኹለትም ፡ የመረግድ ፡ ድንጋይ ፡ ወስደኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ስማቸውን ፡ ቅረጽባቸው ፤

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 10 ፤ እንደ ፡ አወላለዳቸው ፡ ስድስት ፡ ስም ፡ ባንድ ፡ ድንጋይ ፥ የቀረውንም ፡ ስድስቱን ፡ ስም ፡ በሌላው ፡ ቅረጽ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 11 ፤ በቅርጽ ፡ ሠራተኛ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡ ቅርጽ ፡ አድርገኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ በኹለት ፡ ድንጋዮች ፡ ቅረጽ ፡ በወርቅም ፡ ፈርጥ ፡ አድርግ ።

ዘጸ. ፥ 28 ፥ 12 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ የመታሰቢያ ፡ ድንጋዮች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ኹለቱን ፡ ዕንቊዎች ፡ በኤፉዱ ፡ ጫንቃዎች ፡ ላይ ፡ ታደርጋለኽ ፤ አሮንም ፡ በኹለቱ ፡ ጫንቃዎች ፡ ላይ ፡ ለመታሰቢያ ፡ ስማቸውን ፡

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይሸከማል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ 14 ፤ የወርቅም ፡ ፈርጦች ፡ ኹለትም ፡ ድሪዎች ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሥራ ፤ እንደ ፡ ተገመነገመነም ፡ ገመድ ፡ አድርግ ፤ የተገመነገሙትንም ፡ ድሪዎች ፡ በፈርጦቹ ፡ ላይ ፡ አንጠልጥል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ብልኅ ፡ ሠራተኛም ፡ እንደሚሠራ ፡ የፍርዱን ፡ የደረት ፡ ኪስ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ኤፉዱም ፡ አሠራር ፡ ሥራው ፤ ከወርቅና ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ ሥራው ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ርዝመቱ ፡ ስንዝር ፡ ስፋቱም ፡ ስንዝር ፡ ኾኖ ፡ ትክክልና ፡ ድርብ ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ በአራት ፡ ተራ ፡ የኾነ ፡ የዕንቊ ፡ ፈርጥ ፡ አድርግበት ፤ በፊተኛው ፡ ተራ ፡ ሰርድዮን ፥ ቶጳዝዮን ፥ የሚያብረቀርቅ ፡ ዕንቊ ፤

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ በኹለተኛውም ፡ ተራ ፡ በሉር ፥ ሰንፔር ፥ አልማዝ ፤

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ በሦስተኛውም ፡ ተራ ፡ ያክንት ፥ ኬልቄዶን ፥ አሜቴስጢኖስ ፤

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ በአራተኛውም ፡ ተራ ፡ ቢረሌ ፥ መረግድ ፥ ኢያስጲድ ፡ በወርቅ ፡ ፈርጥ ፡ ይደረጋሉ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ የዕንቊዎቹም ፡ ድንጋዮች ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ይኾናሉ ፤ በየስማቸውም ፡ ማተሚያ ፡ እንደሚቀረጽ ፡ ይቀረጹ ፤ ስለ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ነገዶችም ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ለደረቱ ፡ ኪስም ፡ የተገመነገሙትን ፡ ድሪዎች ፡ እንደ ፡ ገመድ ፡ አድርገኽ ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሥራቸው ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ ለደረቱ ፡ ኪስም ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሥራ ፥ ኹለቱንም ፡ ቀለበቶች ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ በኹለቱ ፡ ወገን ፡ አድርጋቸው ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ የተገመነገሙትንም ፡ ኹለቱን ፡ የወርቅ ፡ ድሪዎች ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ ወገኖች ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ ቀለበቶች ፡ ታገባቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ የኹለቱንም ፡ ድሪዎች ፡ ጫፎች ፡ በኹለቱ ፡ ፈርጦች ፡ ውስጥ ፡ አግብተኽ ፡ በኤፉዱ ፡ ጣንቃዎች ፡ ላይ ፡ በፊታቸው ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶችም ፡ ሥራ ፥ እነርሱንም ፡ በኤፉዱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ በኹለቱ ፡ ጫፎች ፡ ላይ ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ ደግሞም ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሥራ ፥ በኤፉዱም ፡ ፊት ፡ ከጣንቃዎች ፡ በታች ፡ በብልኀት ፡ ከተጠለፈ ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፡ በመያዣው ፡ አጠገብ ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ የደረቱም ፡ ኪስ ፡ በብልኀት ፡ ከተጠለፈ ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፡ እንዲኾን ፡ ከኤፉዱም ፡ እንዳይለይ ፥ የደረቱን ፡ ኪስ ፡ ከቀለበቶቹ ፡ ወደኤፉዱ ፡ ቀለበቶች ፡ በሰማያዊ ፡ ፈትል ፡ ያስሩታል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 29 ፤ አሮንም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘለዓለም ፡ መታሰቢያ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ በፍርዱ ፡ በደረት ፡ ኪስ ፡ ውስጥ ፡ በልቡ ፡ ላይ ፡ ይሸከም ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 30 ፤ በፍርዱ ፡ በደረት ፡ ኪስም ፡ ውስጥ ፡ ኡሪምንና ፡ ቱሚምን ፡ ታደርጋለኽ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በአሮን ፡ ልብ ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ፤ አሮንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘውል ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ፍርድ ፡ በልቡ ፡ ላይ ፡ ይሸከማል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 31 ፤ የኤፉዱንም ፡ ቀሚስ ፡ ኹሉ ፡ ሰማያዊ ፡ አድርገው ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 32 ፤ ከላይም ፡ በመካከል ፡ ዐንገትጌ ፡ ይኹንበት ፤ እንዳይቀደድም ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ የተሠራ ፡ ጥልፍ ፡ በዐንገትጌው ፡ ዙሪያ ፡ ይኹንበት ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 33 ፤ በታችኛውም ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ሮማኖች ፡ አድርግ ፤ በዚያም ፡ መካከል ፡ በዙሪያው ፡ የወርቅ ፡ ሻኵራዎች ፡ አድርግ ፤

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 34 ፤ የወርቅ ፡ ሻኵራ ፡ ሮማንም ፥ ሌላም ፡ የወርቅ ፡ ሻኵራ ፡ ሮማንም ፡ በቀሚሱ ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያውን ፡ ይኾናሉ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 35 ፤ በማገልገል ፡ ጊዜም ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ርሱም ፡ እንዳይሞት ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሲገባና ፡ ሲወጣ ፡ ድምፁ ፡ ይሰማል ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 36 ፤ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ቅጠል ፡ የሚመስል ፡ ምልክት ፡ ሥራ ፥ በርሱም ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡ ቅርጽ ፡ አድርገኽ ፦ ቅድስና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚል ፡ ትቀርጽበታለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 37 ፤ በሰማያዊም ፡ ፈትል ፡ በመጠምጠሚያው ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ታንጠለጥለዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 38 ፤ በአሮንም ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ አሮንም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሚያቀርቡትና ፡ በሚቀድሱት ፡ በቅዱስ ፡ ስጦታቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ኀጢአት ፡ ይሸከም ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ እንዲኾንላቸው ፡ ቅጠል ፡ የሚመስለው ፡ ምልክቱ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 39 ፤ ሸሚዙንም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ ዝንጕርጕር ፡ አድርገኽ ፥ መጠምጠሚያውን ፡ ከበፍታ ፡ ትሠራለኽ ፤ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ መታጠቂያም ፡ ትሠራለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 40 ፤ ለአሮንም ፡ ልጆች ፡ የደረት ፡ ልብሶችን ፡ መታጠቂያዎችንም ፡ ቆቦችንም ፡ ለክብርና ፡ ለጌጥ ፡ ታደርግላቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 41 ፤ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ ወንድምኽን ፡ አሮንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ልጆቹን ፡ ታለብሳቸዋለኽ ፤ በክህነት ፡ እንዲያገለግሉኝ ፡ ትቀባቸዋለኽ ፥ ትክናቸዋለኽ ፥ ትቀድሳቸውማለኽ ።

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 42 ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋቸውንም ፡ ይከድኑበት ፡ ዘንድ ፡ የበፍታ ፡ ሱሪ ፡ ታደርግላቸዋለኽ ፤ ከወገባቸውም ፡ እስከ ፡ ጭናቸው ፡ ይደርሳል ፤

ዘጸ. ፡ 28 ፡ 43 ፤ ኀጢአትም ፡ እንዳይኾንባቸው ፡ እንዳይሞቱም ፥ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ሲገቡ ፡ በመቅደሱም ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ሲቀርቡ ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ለርሱ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ።

——————————ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ። ——————————

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ እኔንም ፡ በክህነት ፡ እንዲያገለግሉኝ ፡ ትቀድሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የምታደርግባቸው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ ቂጣ ፡ እንጀራ ፥ በዘይትም ፡ የተለወሰ ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፥ በዘይትም ፡ የተቀባ ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፡ ከመልካም ፡ ስንዴ ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ ባንድ ፡ ሌማትም ፡ ታደርጋቸዋለኽ ፤ ከወይፈኑና ፡ ከኹለቱ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ጋራ ፡ በሌማቱ ፡ ታቀርባቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ አሮንና ፡ ልጆቹንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ታቀርባቸዋለኽ ፥ በውሃም ፡ ታጥባቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ ልብሶችን ፡ ወስደኽ ፡ ለአሮን ፡ የደረት ፡ ልብስና ፡ የኤፉድ ፡ ቀሚስ ፡ ኤፉድም ፡ የደረት ፡ ኪስም ፡ ታለብሰዋለኽ ፥ በብልኀትም ፡ በተጠለፈ ፡ ቋድ ፡ ታስታጥቀዋለኽ ፤

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ መጠምጠሚያውንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ታደርጋለኽ ፥ የተቀደሰውንም ፡ አክሊል ፡ በመጠምጠሚያው ፡ ላይ ፡ ታኖራለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ የቅብዐትንም ፡ ዘይት ፡ ወስደኽ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ታፈሰዋለኽ ፥ ትቀባውማለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ልጆቹንም ፡ ታቀርባቸዋለኽ ፥ የደረት ፡ ልብሶቹንም ፡ ታለብሳቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ አሮንንና ፡ ልጆቹንም ፡ በመታጠቂያ ፡ ታስታጥቃቸዋለኽ ፥ ቆብንም ፡ ታለብሳቸዋለኽ ፤ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐትም ፡ ክህነት ፡ ይኾንላቸዋል ፤ እንዲሁም ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ ትክናቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ ወይፈኑንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በር ፡ ፊት ፡ ታቀርበዋለኽ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ እጆቻቸውን ፡ በወይፈኑ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናሉ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ ወይፈኑንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ታርደዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ ከወይፈኑም ፡ ደም ፡ ወስደኽ ፡ በመሠዊያው ፡ ቀንዶች ፡ ላይ ፡ በጣትኽ ፡ ትረጨዋለኽ ፤ ደሙንም ፡ ዅሉ ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ ታፈሰዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፡ ዅሉ ፡ በጉልበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ በላያቸውም ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ወስደኽ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ታቃጥላለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ የወይፈኑን ፡ ሥጋ ፡ ግን ፥ ቍርበቱንም ፥ ፈርሱንም ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡ ታቃጥለዋለኽ ፤ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ አንደኛውንም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ትወስደዋለኽ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ይጭናሉ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ ታርደዋለኽ ፥ ደሙንም ፡ ወስደኽ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ትረጨዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ በየብልቱ ፡ ትቈርጠዋለኽ ፥ የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹንም ፡ ታጥባለኽ ፥ ከብልቱና ፡ ከራሱም ፡ ጋራ ፡ ታኖረዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ በሞላው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ታቃጥላለኽ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ ነው ። ለእግዚአብሔር ፡ የቀረበ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ኹለተኛውንም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ትወስደዋለኽ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ እጆቻቸውን ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናሉ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ ታርደዋለኽ ፥ ደሙንም ፡ ትወስዳለኽ ፥ የአሮንንም ፡ የቀኝ ፡ ጐሮ ፡ ጫፍ ፥ የልጆቹንም ፡ የቀኝ ፡ ጐሯቸውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጃቸውንና ፡ የቀኝ ፡ እግራቸውን ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ታስነካለኽ ፤ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ትረጨዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ደም ፣ ከቅብዐት ፡ ዘይትም ፡ ወስደኽ ፡ በአሮንና ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ባሉት ፡ በልጆቹና ፡ በልብሶቻቸው ፡ ላይ ፡ ትረጨዋለኽ ፤ ርሱም ፡ ልብሶቹም ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡

ልጆቹ ፡ ልብሶቻቸውም ፡ ይቀደሳሉ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ደግሞም ፡ የሚካኑበት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ነውና ፥ የበጉን ፡ ስብ ፥ ላቱንም ፥ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፥ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ በላያቸውም ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ የቀኙንም ፡ ወርች ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ አንድ ፡ እንጀራ ፥ አንድም ፡ የዘይት ፡ እንጀራ ፥ አንድም ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሌማት ፡ ካለው ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትወስዳለኽ ፤

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ ኹሉንም ፡ በአሮን ፡ እጆችና ፡ በልጆቹ ፡ እጆች ፡ ታኖረዋለኽ ፤ ለሚወዘወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትወዘውዘዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ ከእጃቸውም ፡ ትቀበለዋለኽ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ እንዲኾን ፡ ታቃጥለዋለኽ ፤ ርሱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 26 ፤ ለአሮንም ፡ ክህነት ፡ የታረደውን ፡ በግ ፡ ፍርምባ ፡ ወስደኽ ፡ ለሚወዘወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትወዘውዘዋለኽ ፤ ርሱም ፡ የአንተ ፡ ወግ ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 27 ፤ ከሚካኑበትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ የተወሰደ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ወግ ፡ የሚኾን ፡ ለመሥዋዕት ፡ የተወዘወዘውን ፡ ፍርምባና ፡ የተነሣውን ፡ ወርች ፡ ትቀድሳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 28 ፤ ያውም ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ነውና ፥ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለም ፡ የአሮንና ፡ የልጆቹ ፡ ወግ ፡ ይኹን ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የሚያቀርቡት ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕታቸው ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ይኾናል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 29 ፤ የተቀደሰውም ፡ የአሮን ፡ ልብስ ፡ ይቀቡበትና ፡ ይካኑበት ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ለልጆቹ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 30 ፤ ከልጆቹም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ካህን ፡ የሚኾነው ፡ በመቅደስ ፡ ለማገልገል ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ሲገባ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይልበሰው ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 31 ፤ የሚካንበትንም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ወስደኽ ፡ ሥጋውን ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ትቀቅለዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 32 ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ የአውራውን ፡ በግ ፡ ሥጋ ፡ በሌማትም ፡ ያለውን ፡ እንጀራ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በር ፡ ይበሉታል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 33 ፤ የተካኑና ፡ የተቀደሱ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ማስተስረያ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ይብሉት ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አይብላው ፤ የተቀደሰ ፡ ነውና ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 34 ፤ የተካኑበትም ፡ ሥጋ ፡ ወይም ፡ እንጀራ ፡ ተርፎ ፡ ቢያድር ፥ የቀረውን ፡ በእሳት ፡ ታቃጥለዋለኽ ፤ የተቀደሰ ፡ ነውና ፥ አይበላም ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 35 ፤ እንዳዘዝኹኽም ፡ ኹሉ ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ እንዲህ ፡ አድርግ ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትክናቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 36 ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ስለ ፡ ማስተስረይ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈኑን ፡ ታቀርባለኽ ፤ ማስተስረያም ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ መሠዊያውን ፡ ታነጻዋለኽ ፤ ቅዱስም ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ትቀባዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 37 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለመሠዊያው ፡ ማስተስረያ ፡ ታደርጋለኽ ፥ ትቀድሰውማለኽ ፤ መሠዊያውም ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይኾናል ፤ መሠዊያውንም ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 38 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ የምታቀርበው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በቀን ፡ በቀን ፡ ዘወትር ፡ ኹለት ፡ የዓመት ፡ ጠቦቶች ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 39 ፤ አንዱን ፡ ጠቦት ፡ በማለዳ ፡ ቍርባን ፡ አድርገኽ ፡ ታቀርበዋለኽ ፤ ኹለተኛውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ ቍርባን ፡ አድርገኽ ፡ ታቀርበዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 40 ፤ ከአንዱ ፡ ጠቦትም ፡ ጋራ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ በኾነ ፡ ተወቅጦ ፡ በተጠለለ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ደግሞ ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 41 ፤ ኹለተኛውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ ታቀርበዋለኽ ፥ እንደ ፡ ማለዳውም ፡ የእኽልና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ ታደርግበታለኽ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ እንዲኾን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 42 ፤ ለአንተ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ በምገናኝበት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይህ ፡ ዘወትር ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 43 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ እገናኛለኹ ፤ ድንኳኑም ፡ በክብሬ ፡ ይቀደሳል ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 44 ፤ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፡ መሠዊያውንም ፡ እቀድሳለኹ ፤ በክህነትም ፡ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ እቀድሳለኹ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 45 ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኖራለኹ ፥ አምላክም ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 29 ፡ 46 ፤ በመካከላቸውም ፡ እኖር ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸው ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፤ እኔ ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ። _____

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ የዕጣን ፡ መሠዊያውን ፡ ሥራ ፤ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አድርገው ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ ርዝመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ አራት ፡ ማእዘን ፡ ይኹን ፤ ከፍታውም ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፤ ቀንዶቹም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ የተሠሩ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ ላይኛውንና ፡ የግድግዳውንም ፡ ዙሪያ ፡ ቀንዶቹንም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ትለብጠዋለኽ ፤ በዙሪያውም ፡ የወርቅ ፡ ክፈፍ ፡ ታደርግለታለኽ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ ከክፈፉም ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ አድርግለት ። በዚህና ፡ በዚያ ፡ በኹለቱ ፡ ጐን ፡ ታደርጋቸዋለኽ ፤ ለመሸከምም ፡ የመሎጊያዎች ፡ ስፍራ ፡ ይኹኑ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ መሎጊያዎቹንም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አድርግ ፥ በወርቅም ፡ ለብጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ አጠገብም ፡ ካለው ፡ መጋረጃ ፡ በፊት ፡ ታኖረዋለኽ ፡ ይህንም ፡ አንተን ፡ በምገናኝበት ፡ ከምስክሩ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በስርየት ፡ መክደኛ ፡ ፊት ፡ ታኖረዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ አሮንም ፡ የጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ ዕጣን ፡ ይጠንበት ፤ በማለዳ ፡ በማለዳ ፡ መብራቶቹን ፡ ሲያዘጋጅ ፡ ይጠነው ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ ይህን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘወትር ፡ ዕጣን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አሮን ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ መብራቶቹን ፡ ሲያበራ ፡ ያጥነዋል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ ሌላም ፡ ዕጣን ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ አታቀርብበትም ፤ የመጠጥም ፡ ቍርባን ፡ አታፈስስበትም ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ አሮንም ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀንዶቹ ፡ ላይ ፡ ማስተስረያ ፡ ያደርጋል ፤ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ማስተስረያ ፡ በሚኾን ፡ በኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ማስተስረያ ፡ ያደርግበታል ። ለእግዚአብሔር ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ናት ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ አንተ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡ ተቀብለኽ ፥ በቈጠርኻቸው ፡ ጊዜ ፡ መቅሠፍት ፡ እንዳይኾንባቸው ፥ በቈጠርኻቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ የነፍሱን ፡ ቤዛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይስጥ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ዐልፎ ፡ የሚቈጠር ፡ ኹሉ ፡ ግማሽ ፡ ሰቅል ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ይሰጣል ፤ የሰቅል ፡ ግማሽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያነሣል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ሰቅሉ ፡ ኻያ ፡ ኦቦሊ ፡ ነው ። ዐልፎ ፡ የተቈጠረ ፡ ኹሉ ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታ ፡ ይሰጣል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ለነፍሳችኹ ፡ ማስተስረያ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታ ፡ ስትሰጡ ፡ ባለጠጋው ፡ ከሰቅል ፡ ግማሽ ፡ አይጨምር ፥ ድኻውም ፡ አያጕድል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ የማስተስረያውንም ፡ ገንዘብ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወስደኽ ፡ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ማገልገያ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ለነፍሳችኹ ፡ ቤዛ ፡ እንዲኾን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መታሰቢያ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ የመታጠቢያ ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውን ፡ ከናስ ፡ ሥራ ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳንና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ ርሱን ፡ አድርገኽ ፡ ውሃን ፡ ትጨምርበታለኽ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ እጆቻቸውንና ፡ እግሮቻቸውን ፡ ይታጠቡበታል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የእሳት ፡ መሥዋዕት ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ሊያገለግሉ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፥ እንዳይሞቱ ፡ ይታጠቡበታል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 21 ፤ እንዳይሞቱም ፡ እጆቻቸውንና ፡ እግሮቻቸውን ፡ ይታጠቡ ፤ ይህም ፡ ለርሱ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾንላቸዋል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 23 ፤ አንተም ፡ ክቡሩን ፡ ሽቱ ፡ ውሰድ ፤ የተመረጠ ፡ ከርቤ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፥ ግማሽም ፡ ጣፋጭ ፡ ቀረፋ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፥ የጠጅ ፡ ሣርም ፡ እንዲሁ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፥

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 24 ፤ ብርጉድም ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፥ የወይራ ፡ ዘይትም ፡ አንድ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ትወስዳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 25 ፤ በቀማሚም ፡ ብልኀት ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ቅመም ፥ የተቀደሰ ፡ የቅብዐት ፡ ዘይት ፡ ታደርገዋለኽ ፤ የተቀደሰ ፡ የቅብዐት ፡ ዘይት ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፥ የምስክሩንም ፡ ታቦት ፥

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 27 ፤ ገበታውንም ፡ ዕቃውንም ፡ ዅሉ ፥ መቅረዙንም ፡ ዕቃውንም ፥ የዕጣን ፡ መሠዊያውንም ፥

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 28 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚ�puኑውን ፡ መሠዊያና ፡ ዕቃውንም ፡ ዅሉ ፥ የመታጠቢያውን ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውንም ፡ ትቀባበታለኽ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 29 ፤ ዅሉንም ፡ ትቀድሳቸዋለኽ ፥ ቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ይኾናሉ ፤ የሚነካቸውም ፡ ዅሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 30 ፤ በክህነትም ፡ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ ቅባቸው ፥ ቀድሳቸውም ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 31 ፤ አንተም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገር ፦ ይህ ፡ ለልጅ ፡ ልጆችኹ ፡ የተቀደሰ ፡ የቅብዐት ፡ ዘይት ፡ ይኹንልኝ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 32 ፤ በሰው ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ አይፍሰስ ፤ እንደ ፡ ርሱም ፡ የተሠራ ፡ ሌላ ፡ ቅብዐት ፡ አታድርጉ ፤ ቅዱስ ፡ ነው ፥ ለእናንተም ፡ ቅዱስ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 33 ፤ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለውን ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፥ በሌላም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሚያፈሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 34 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ ውሰድ ፤ የሚንጠባጠብ ፡ ሙጫ ፥ በዛጐል ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ሽቱ ፥ የሚሸትም ፡ ሙጫ ፥ ጥሩም ፡ ዕጣን ፡ ውሰድ ፤ የዅሉም ፡ መጠን ፡ ትክክል ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 35 ፤ በቀማሚ ፡ ብልኀት ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፥ በጨው ፡ የተቀመመ ፡ ንጹሕና ፡ ቅዱስ ፡ ዕጣን ፡ አድርገው ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 36 ፤ ከርሱም ፡ ጥቂት ፡ ትወቅጣለኽ ፥ ታልመውማለኽ ፤ ከዚያም ፡ ወስደኽ ፡ አንተን ፡ በምገናኝበት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በምስክሩ ፡ ፊት ፡ ታኖረዋለኽ ። ርሱም ፡ የቅዱሳን ፡ ቅዱስ ፡ ይኹንላችኹ ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 37 ፤ እንደ ፡ ርሱ ፡ የተሠራ ፡ ዕጣን ፡ ለእናንተ ፡ አታድርጉ ፤ በእናንተ ፡ ዘንድም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኹን ።

ዘጸ. ፡ 30 ፡ 38 ፤ ሊያሸተውም ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ እይ ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የሚኾን ፡ የሆር ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፥ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ባስልኤልን ፡ በስሙ ፡ ጠርቼዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ በሥራ ፡ ዅሉ ፡ ብልኀት ፡ በጥበብም ፡ በማስተዋልም ፡ በዕውቀትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ ሞላኹበት ፤

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ የጥበብን ፡ ሥራ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፥ በወርቅና ፡ በብር ፡ በናስም ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ፥

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ ለፈርጥ ፡ የሚኾነውን ፡ የዕንቊ ፡ ድንጋይ ፡ ይቀርጽ ፡ ዘንድ ፥ ዕንጨቱንም ፡ ይጠርብ ፡ ዘንድ ፥ ሥራውንም ፡ ዅሉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የሚኾን ፡ የአሂሳሚክን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብን ([74]) ፡ ሰጠኹ ፤ ያዘዝኹኽን ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በልባቸው ፡ ጥበበኞች ፡ በኾኑት ፡ ኹሉ ፡ ጥበብን ፡ አኖርኹ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፥ የምስክሩንም ፡ ታቦት ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የስርየት ፡ መክደኛውን ፥ የድንኳኑንም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ ገበታውንም ፡ ዕቃውንም ፥ ከዕቃው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የነጻውን ፡ መቅረዝ ፥ የዕጣን ፡ መሠዊያውን ፥

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውንም ፡ መሠዊያ ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የመታጠቢያውን ፡ ሰንም ፡ መቀመጫውንም ፥ በብልኀት ፡ የተሠራውንም ፡ ልብስ ፥

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 10 ፤ በክህነት ፡ እኔን ፡ የሚያገለግሉበትን ፡ የካህኑን ፡ የአሮንን ፡ ልብሰ ፡ ተክህኖና ፡ የልጆቹን ፡ ልብስ ፥

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 11 ፤ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፥ ለመቅደሱ ፡ የሚኾን ፡ የጣፋጭ ፡ ሽቱውንም ፡ ዕጣን ፡ እንዳዘዝኹኽ ፡ ኹሉ ፡ ያድርጉ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ እኔ ፡ የምቀድሳችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ምልክት ፡ ነውና ፥ ሰንበቶቼን ፡ ፈጽሞ ፡ ጠብቁ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ለእናንተ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ሰንበትን ፡ ጠብቁ ፤ የሚያረክሰውም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፥ ሥራንም ፡ በርሱ ፡ የሠራ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራን ፡ ሥራ ፤ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በሰንበት ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ፡ ሰንበትን ፡ ይጠብቁ ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ፈጠረ ፥ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሥራው ፡ ስላረፈና ፡ ስለ ፡ ተነፈሰ ፥ በእኔና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ የተናገረውን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ የተጻፈባቸውን ፡ ከድንጋይ ፡ የኾኑ ፡ ኹለቱን ፡ የምስክር ፡ ጽላቶች ፡ ሰጠው ።

፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ ሕዝቡም ፡ ሙሴ ፡ ከተራራው ፡ ሳይወርድ ፡ እንደ ፡ ዘገየ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ አሮን ፡ ተሰብስበው ፦ ይህ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፡ ሰው ፡ ሙሴ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አናውቅምና ፡ ተነሥተኽ ፡ በፊታችን ፡ የሚኼዱ ፡ አማልክት ፡ ሥራልን ፡ አሉት ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ አሮንም ፦ በሚስቶቻችኹ ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ጐሮ ፡ ያሉትን ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሰብራችኹ ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በጐሮዎቻቸው ፡ ያሉትን ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሰብረው ፡ ወደ ፡ አሮን ፡

74 ዕብ. ፥ ኤሊያብ ፡ (ያባቱ ፡ አምላክ)

አመጡለት ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ ከእጃቸውም ፡ ተቀብሎ ፡ በመቅረጫ ፡ ቀረጸው ፥ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ጥጃም ፡ አደረገው ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጡኽ ፡ አማልክትኽ ፡ ናቸው ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ አሮንም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ መሠዊያን ፡ በፊቱ ፡ ሠራ ፤ አሮንም ፦ ነገ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ዐወጀ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ በነጋውም ፡ ማልደው ፡ ተነሥተው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ፥ የደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፤ ሕዝቡም ፡ ሊበሉና ፡ ሊጠጡ ፡ ተቀመጡ ፥ ሊዘፍኑም ፡ ተነሡ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኸው ፡ ሕዝብኽ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተዋልና ፥ ኺድ ፥ ውረድ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ ካዘዝኋቸው ፡ መንገድ ፡ ፈጥነው ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ የጥጃ ፡ ምስል ፡ ለራሳቸው ፡ አደረጉ ፥ ሰገዱለትም ፥ ሠዉለትም ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጡኽ ፡ አማልክትኽ ፡ ናቸው ፡ አሉ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ እኔ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ አየኹት ፥ እንሆም ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ ቍጣዬ ፡ እንዲቃጠልባቸው ፡ እንዳጠፋቸውም ፡ ተወኝ ፤ አንተንም ፡ ለታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ አደርግኻለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ ሙሴም ፡ በእግዚአብሔር ፡ በአምላኩ ፡ ፊት ፡ ጸለየ ፥ አለም ፦ አቤቱ ፥ ቍጣኽ ፡ በታላቅ ፡ ኀይልና ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኸው ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቃጠለ ፧

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ ግብጻውያንስ ፦ በተራራ ፡ መካከል ፡ ሊገድላቸው ፥ ከምድርም ፡ ፊት ፡ ሊያጠፋቸው ፡ ለክፋት ፡ አወጣቸው ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይናገራሉ ፧ ከመዓትኽ ፡ ተመለስ ፥ ለሕዝብኽም ፡ በክፋታቸው ፡ ላይ ፡ ራራ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ ዘራኾኹን ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ አበዛለኹ ፥ ይህችንም ፡ የተናገርኋትን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለዘራኾኹ ፡ እሰጣታለኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ይወርሷታል ፡ ብለኽ ፡ በራስኽ ፡ የማልኽላቸውን ፡ ባሪያዎችኽን ፡ አብርሃምንና ፡ ይሥሐቅን ፡ እስራኤልንም ፡ ዐስብ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሊያደርግ ፡ ስላሰበው ፡ ክፋት ፡ ራራ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ ተመለሰ ፥ ኹለቱንም ፡ የምስክር ፡ ጽላቶች ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ከተራራው ፡ ወረደ ፤ ጽላቶቹም ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ ተጽፎባቸው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ ጽላቶቹም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ነበሩ ፤ ጽሕፈቱም ፡ በጽላቶች ፡ ላይ ፡ የተቀረጸባቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽሕፈት ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ ኢያሱም ፡ እልል ፡ ሲሉ ፡ የሕዝቡን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ ሙሴን ፦ የሰልፍ ፡ ድምፅ ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ ይህ ፡ የድል ፡ ነሺዎች ፡ ወይም ፡ የድል ፡ ተነሺዎች ፡ ድምፅ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የዘፈን ፡ ድምፅ ፡ እሰማለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ሲቀርብ ፡ ጥጃውንም ፡ ዘፈኑንም ፡ አየ ፤ የሙሴም ፡ ቍጣ ፡

ተቃጠለ ፥ ጽላቶቹንም ፡ ከእጁ ፡ ጥሎ ፡ ከተራራው ፡ በታች ፡ ሰበራቸው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 20 ፤ የሠሩትንም ፡ ጥጃ ፡ ወስዶ ፡ በእሳት ፡ አቀለጠው ፥ እንደ ፡ ትቢያም ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ፈጨው ፥ በውሃውም ፡ ላይ ፡ በተነው ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አጠጣው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 21 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ታመጣበት ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ምን ፡ አደረገኽ ፧ አለው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 22 ፤ አሮንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ቍጣኽ ፡ አይቃጠል ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ክፋትን ፡ እንዲወድ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 23 ፤ እነርሱም ፦ ይህ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፡ ሰው ፡ ሙሴ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አናውቅምና ፡ በፊታችን ፡ የሚኼዱ ፡ አማልክት ፡ ሥራልን ፡ አሉኝ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 24 ፤ እኔም ፦ ከእናንተ ፡ ወርቅ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ሰብሮ ፡ ያምጣልኝ ፡ አልኋቸው ፤ ሰጡኝም ፤ በእሳትም ፡ ላይ ፡ ጣልኹት ፥ ይህም ፡ ጥጃ ፡ ወጣ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 25 ፤ ሙሴም ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ እንዲነወሩ ፡ አሮን ፡ ስድ ፡ ለቋቸዋልና ፥ ሕዝቡ ፡ ስድ ፡ እንደ ፡ ተለቀቁ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 26 ፤ በሰፈሩ ፡ ደጅ ፡ ቆሞ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይምጣ! ፡ አለ ፤ የሌዊም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 27 ፤ ርሱም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእናንተ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሰይፉን ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ ይታጠቅ ፥ በሰፈሩም ፡ ውስጥ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ከበር ፡ እስከ ፡ በር ፡ ተመላለሱ ፥ የእናንተም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወንድሙን ፡ ወዳጁንም ፡ ጎረቤቱንም ፡ ይግደል ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 28 ፤ የሌዊም ፡ ልጆች ፡ ሙሴ ፡ እንዳለ ፡ አደረጉ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከሕዝቡ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 29 ፤ ሙሴም ፦ ዛሬ ፡ በረከትን ፡ እንዲያወርድላችኹ ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ በልጃችኹና ፡ በወንድማችኹ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ እጃችኹን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ አድርጉ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 30 ፤ በነጋውም ፡ ሙሴ ፡ ለሕዝቡ ፦ እናንተ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታችኋል ፤ አኹንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እወጣለኹ ፤ ምናልባት ፡ ኀጢአታችኹን ፡ አስተሰርይላችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 31 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፦ ወዮ! ፡ እኒህ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተዋል ፥ ለራሳቸውም ፡ የወርቅ ፡ አማልክት ፡ አድርገዋል ፤

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 32 ፤ አኹን ፡ ይህን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ከጻፍኸው ፡ መጽሐፍኽ ፡ እባክኽ ፡ ደምሰኝ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 33 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የበደለኝን ፡ ርሱን ፡ ከመጽሐፌ ፡ እደመስሰዋለኹ ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 34 ፤ አኹንም ፡ ኺድ ፥ ይህንም ፡ ሕዝብ ፡ ወደነገርኹኽ ፡ ምራ ፤ እንሆ ፥ መልአኬ ፡ በፊትኽ ፡ ይኼዳል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምጐበኝበት ፡ ቀን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ አመጣባቸዋለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፥ 32 ፥ 35 ፤ አሮን ፡ የሠራውን ፡ ጥጃ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ቀሠፈ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 1-2-3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ ኺድ ፥ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፦ ለዘርኽ ፡ እሰጣታለኹ ፡ ብዬ ፡ ወደማልኹባት ፡ ምድር ፥ ወተትና ፡ ማርም ፡ ወደምታፈሰው ፡ ምድር ፡ አንተ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣኸው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ከዚህም ፡ ውጣ ። ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ኾንኽ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ እንዳላጠፋኽ ፡ እኔ ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ አልወጣምና ፡ በፊትኽ ፡ መልአክ ፡ እሰዳለኹ ፤ ከነዓናዊውን ፡ አሞራዊውንም ፡ ኬጢያዊውንም ፡ ፌርዛዊውንም ፡ ዔዊያዊውንም ፡ ኢያቡሳዊውንም ፡ አወጣልኻለኹ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ወሬ ፡ ሰምተው ፡ ዐዘኑ ፤ ከነርሱም ፡ ማንም ፡ ጌጡን ፡ አልለበሰም ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፦ እናንተ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ ናችኹ ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ብወጣ ፡ አጠፋችኋለኹ ፤ አኹንም ፡ የማደርግባችኹን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጌጣችኹን ፡ ከእናንተ ፡ አውጡ ፡ በላቸው ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከኰሬብ ፡ ተራራ ፡ ገምረው ፡ ጌጣቸውን ፡ አወጡ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ ድንኳኑን ፡ እየወሰደ ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ይተክለው ፡ ነበር ፤ ከሰፈሩም ፡ ራቅ ፡ ያደርገው ፡ ነበር ፤ የመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። እግዚአብሔርንም ፡ የፈለገ ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ወዳለው ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይወጣ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ይነሡ ፡ ነበር ፥ እያንዳንዱም ፡ በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ይቆም ፡ ነበር ፥ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የደመና ፡ ዐምድ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ፥ በድንኳኑም ፡ ደጃፍ ፡ ይቆም ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ይናገረው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ የደመናው ፡ ዐምድ ፡ በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ሲቆም ፡ ያየው ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ተነሥቶ ፡ እያንዳንዱ ፡ በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ይሰግድ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ እንደሚነጋገር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ። ሙሴም ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ይመለስ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሎሌው ፡ ብላቴና ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ከድንኳኑ ፡ አይለይም ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 12 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እንሆ ፥ አንተ ፦ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ አውጣ ፡ ትለኛለኽ ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ የምትልከውን ፡ አላስታወቅኸኝም ። አንተም ፦ በስምኽ ፡ ዐወቅኹኽ ፥ ደግሞም ፡ በእኔ ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ አገኘኽ ፡ አልኸኝ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ዐውቅኽ ፡ ዘንድ ፡ በፊትኽም ፡ ሞገስን ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ መንገድኽን ፡ እባክኽ ፡ አሳየኝ ፤ ይህም ፡ ሕዝብ ፡ ሕዝብኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመልከት ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኼዳለኹ ፥ አሳርፍኽማለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ካልወጣኽስ ፥ ከዚህ ፡ አታውጣን ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ በምድርም ፡ ፊት ፡ ካለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ እኔና ፡ ሕዝብኽ ፡ የተለየን ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ካልወጣኽ ፥ እኔና ፡ ሕዝብኽ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ ማግኘታችን ፡ በምን ፡ ይታወቃል ፧ አለው ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በፊቴ ፡ ሞገስ ፡ ስላገኘኽ ፡ በስምኽም ፡ ስላወቅኹኽ ፡ ይህን ፡ ያልኸውን ፡ ነገር ፡ አደርጋለኹ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ እባክኽ ፡ ክብርኽን ፡ አሳየኝ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እኔ ፡ መልካምነቴን ፡ ሁሉ ፡ በፊትህ ፡ አሳልፋለኹ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ በፊትህ ፡ ዐውጃለኹ ፤ ይቅርም ፡ የምለውን ፡ ይቅር ፡ እላለኹ ፥ የምምረውንም ፡ እምራለኹ ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ ደግሞም ፦ ሰው ፡ አይቶኝ ፡ አይድንምና ፡ ፊቴን ፡ ማየት ፡ አይቻልህም ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ስፍራ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፥ በአለቱም ፡ ላይ ፡ ትቆማለህ ፤

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ ክብሬም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ በሰንጣቃው ፡ አለት ፡ አኖርኻለኹ ፥ እስካልፍ ፡ ድረስ ፡ እጄን ፡ በላይህ ፡ እጋርዳለኹ ፤

ዘጸ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ እጄንም ፡ ፈቀቅ ፡ አደርጋለኹ ፥ ገርርባዬንም ፡ ታያለህ ፤ ፊቴ ፡ ግን ፡ አይታይም ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። _____

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ እንደ ፡ ፊተኞች ፡ አድርገኽ ፡ ጥረብ ፤ በሰበርኻቸው ፡ በፊተኞቹ ፡ ጽላቶች ፡ የነበሩትን ፡ ቃሎች ፡ እጽፍባቸዋለኹ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 2 ፤ ነገም ፡ የተዘጋጀኽ ፡ ኹን ፥ በማለዳም ፡ ወደሲና ፡ ተራራ ፡ ወጥተኽ ፡ በዚያ ፡ በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በፊቴ ፡ ቁም ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 3 ፤ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይውጣ ፥ በተራራውም ፡ ሁሉ ፡ ማንም ፡ አይታይ ፤ መንጋዎችና ፡ ከብቶችም ፡ በዚያ ፡ ተራራ ፡ ፊት ፡ አይሰማሩ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ እንደ ፡ ፊተኞቹ ፡ አድርጎ ፡ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ጠረበ ፤ በነጋውም ፡ ማልዶ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ወደሲና ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፥ ኹለቱንም ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ፥

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ ወረደ ፥ በዚያም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቆመ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ዐወጀ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፊቱ ፡ ዐልፎ ፦ እግዚአብሔር ፥ እግዚአብሔር ፡ መሓሪ ፥ ሞገስ ፡ ያለው ፥ ታጋሽም ፥ ባለብዙ ፡ ቸርነትና ፡ እውነት ፥

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 7 ፤ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድም ፡ ቸርነትን ፡ የሚጠብቅ ፥ አበሳንና ፡ መተላለፍን ፡ ኀጢአትንም ፡ ይቅር ፡ የሚል ፥ በደለኛውንም ፡ ከቶ ፡ የማያነጻ ፥ የአባቶችንም ፡ ኀጢአት ፡ በልጆች ፡ እስከ ፡ ሦስትና ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድም ፡ በልጅ ፡ ልጆች ፡ የሚያመጣ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ዐወጀ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ተጐነበሰና ፡ ሰገደ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 9 ፤ አቤቱ ፡ በፊትህስ ፡ ሞገስን ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ይህ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ ነውና ፥ ጌታዬ ፡ በመካከላችን ፡ ይኺድ ፤ ጠማማነታችንንና ፡ ኀጢአታችንንም ፡ ይቅር ፡ በለን ፥ ለርስትህም ፡ ተቀበለን ፡ አለ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 10 ፤ ርሱም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርጋለኹ ፤ በምድር ፡ ሁሉ ፥ በአሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ከቶ ፡ ያልተደረገውን ፡ ተኣምራት ፡ በሕዝብህ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ አደርጋለኹ ፤ እኔም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ የምሠራው ፡ ነገር ፡ የሚያስፈራ ፡ ነውና ፥ አንተ ፡ ያለኽበት ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ያያል ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 11 ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ የማዝኽን ፡ ነገር ፡ ጠብቅ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ አሞራዊውን ፡ ከነዓናዊውንም ፡ ኬጢያዊውንም ፡ ፌርዛዊውንም ፡ ዔዊያዊውንም ፡ ኢያቡሳዊውንም ፡ በፊትህ ፡ አወጣለኹ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 12 ፤ በመካከልኽ ፡ ወጥመድ ፡ እንዳይኾኑብኽ ፡ አንተ ፡ በምትኼድባት ፡ ምድር ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳታደርግ ፡ ተጠንቀቅ ፤

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መሠዊያዎቻቸውን ፡ ታፈርሳላችኹ ፥ ሐውልቶቻቸውንም ፡ ትሰብራላችኹ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቻቸውንም ፡ ትቈርጣላችኹ ፤

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 14 ፤ ስሙ ፡ ቀናተኛ ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ ያለው ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ለሌላ ፡ አምላክ ፡ አትስገድ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 15 ፤ በዚያች ፡ ምድር ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳታደርግ ፥ እነርሱ ፡ አምላኮቻቸውን ፡ ተከትለው ፡ ባመነዘሩና ፡ በሠዉላቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዳይጠሩኽ ፥ ከመሥዋዕታቸውም ፡ እንዳትበላ ፥

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 16 ፤ ሴት ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ከወንድ ፡ ልጆችኽ ፡ ጋራ ፡ እንዳታጋባ ፥ ልጆቻቸውም ፡ አምላኮቻቸውን ፡ ተከትለው ፡ ሲያመነዝሩ ፡ ከአምላኮቻቸው ፡ በኋላ ፡ ኼደው ፡ አመንዝረውም ፡ ልጆችኽን ፡ እንዳያስቱ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 17 ፤ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ የአማልክት ፡ ምስሎች ፡ ለአንተ ፡ አታድርግ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 18 ፤ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ ትጠብቀዋለኽ ። በአቢብ ፡ ወር ፡ ከግብጽ ፡ ወጥተኻልና ፥ በታዘዘው ፡ ዘመን ፡ በአቢብ ፡ ወር ፡ እንዳዘዝኹኽ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ብላ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 19 ፤ ማሕፀንንም ፡ የሚከፍት ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ የከብትኽም ፡ ተባት ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፥ በሬም ፡ ቢኾን ፡ በግም ፡ ቢኾን ፥ የእኔ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 20 ፤ የአህያውንም ፡ በኵር ፡ በጠቦት ፡ ትዋጀዋለኽ ፤ ባትዋጀውም ፡ ዐንገቱን ፡ ትሰብረዋለኽ ። የልጆችኽንም ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ ትዋኻለኽ ። በፊቴም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ አይታይ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 21 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ትሠራለኽ ፥ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ታርፋለኽ ፤ በምታርስበትና ፡ በምታጭድበት ፡ ዘመን ፡ ታርፋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 22 ፤ የሰባቱንም ፡ ሰብዔ ፡ በዓል ፡ ታደርጋለኽ ፥ ርሱም ፡ የስንዴ ፡ መከር ፡ በኵራት ፡ ነው ፤ በዓመቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የመክተቻ ፡ በዓል ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 23 ፤ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይታይ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 24 ፤ አሕዛብን ፡ ከፊትኽ ፡ አወጣለኹ ፥ አገርኽንም ፡ አሰፋለኹ ፤ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመታየት ፡ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ስትወጣ ፡ ማንም ፡ ምድርኽን ፡ አይመኝም ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 25 ፤ የመሥዋዕቴን ፡ ደም ፡ ከቦካ ፡ እንጀራ ፡ ጋራ ፡ አትሠዋ ፤ የፋሲካውም ፡ በዓል ፡ መሥዋዕት ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ አይደር ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 26 ፤ የተመረጠውን ፡ የምድርኽን ፡ ፍሬ ፡ በኵራት ፡ ወደአምላክኽ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ታገባለኽ ። ጠቦቱን ፡ በእናቱ ፡ ወተት ፡ አትቀቅልም ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በእነዚህ ፡ ቃሎች ፡ መጠን ፡ ከአንተና ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጌያለኹና ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ጻፍ ፡ አለው ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 28 ፤ በዚያም ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ እንጀራም ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ። በጽላቶቹም ፡ ዐሥሩን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃሎች ፡ ጻፈ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 29 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ ከሲና ፡ ተራራ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ኹለቱ ፡ የምስክር ፡ ጽላቶች ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ነበሩ ፤ ሙሴም ፡ ከተራራው ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተነጋገረ ፡ የፊቱ ፡ ቍርበት ፡ እንዳንጸባረቀ ፡ አላወቀም ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 30 ፤ አሮንና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ሙሴን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ የፊቱ ፡ ቍርበት ፡ አንጸባረቀ ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ይቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ፈሩ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 31 ፤ ሙሴም ፡ ጠራቸው ፤ አሮንም ፡ የማኅበሩን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሱ ፤ ሙሴም ፡ ተናገራቸው ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 32 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ቀረቡ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አዘዛቸው ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 33 ፤ ሙሴም ፡ ለእነርሱ ፡ ተናግሮ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ በፊቱ ፡ መሸፈኛ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 34 ፤ ሙሴም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እስኪ ፡ ወጣ ፡ ድረስ ፡ መሸፈኛውን ፡ ከፊቱ ፡ አነሣ ፤ በወጣም ፡ ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የታዘዘውን ፡ ነገር ፡ ነገረ ።

ዘጸ. ፡ 34 ፡ 35 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ቍርበት ፡ እንዳንጸባረቀ ፡ ያዩ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሊነጋገር ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በፊቱ ፡ መሸፈኛ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ። _____

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ይደረጋል ፥ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ይኾንላችኋል ፤ የሚሠራበትም ፡ ኹሉ ፡ ይገደል ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ በማደሪያዎቻችኹ ፡ ውስጥ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ እሳትን ፡ አታንድዱ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባንን ፡ አቅርቡ ፤ የልብ ፡ ፈቃድ ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍርባን ፡ ያምጣ ፤ ወርቅና ፡ ብርም ፡ ናስም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ ሰማያዊም ፡ ሐምራዊም ፡ ቀይ ፡ ግምጃም ፥ ጥሩ ፡ በፍታም ፥ የፍየል ፡ ጠጕርም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ ቀይም ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ ቍርበት ፥ የአቀኑስጣም ፡ ቍርበት ፥ የግራርም ፡ ዕንጨት ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ ለመብራትም ፡ ዘይት ፥ ለቅብዐት ፡ ዘይትና ፡ ለጣፋጭ ፡ ዕጣን ፡ ቅመም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ መረግድ ፡ ለኤፉዱና ፡ ለደረት ፡ ኪስ ፡ የሚደረግ ፡ ፈርጥ ፡ ያምጣ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ በልባቸው ፡ ጥበበኞች ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ያድርጉ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 11 ፤ ማደሪያውን ፥ ድንኳኑንም ፡ መደረቢያውንም ፥ መያዣዎቹንም ፥ ሳንቃዎቹንም ፥ መወርወሪያዎቹንም ፥ ምሰሶዎቹንም ፥ እግሮቹንም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 12 ፤ ታቦቱን ፡ መሎጊያዎቹንም ፥ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፡ በርሱም ፡ ፊት ፡ የሚሸፍነውን ፡ መጋረጃ ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 13 ፤ ገበታውን ፡ መሎጊያዎቹንም ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 14 ፤ መብራት ፡ የሚያበሩበትን ፡ መቅረዙን ፡ ዕቃውንም ፥ ቀንዲሉንም ፥ የመብራቱንም ፡ ዘይት ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 15 ፤ የዕጣኑን ፡ መሠዊያም ፡ መሎጊያዎቹንም ፥ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፥ ጣፋጩንም ፡ ዕጣን ፥ ለማደሪያውም ፡ ደጃፍ ፡ የሚኾን ፡ የደጃፉን ፡ መጋረጃ ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 16 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ መሠዊያውን ፥ የናሱንም ፡ መከታ ፥ መሎጊያዎቹንም ፥ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፤ የመታጠቢያውን ፡ ሰንም ፡ መቀመጫውንም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 17 ፤ የአደባባዩን ፡ መጋረጃዎች ፡ ምሰሶዎቹንም ፡ እግሮቻቸውንም ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 18 ፤ የማደሪያውን ፡ ካስማዎች ፥ የአደባባዩንም ፡ ካስማዎች ፡ አውታሮቻቸውንም ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 19 ፤ በመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለማገልገል ፡ በብልኀት ፡ የተሠሩትን ፡ ልብሶች ፥ በክህነት ፡ ያገለግሉበት ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሱትን ፡ የካህኑን ፡ የአሮን ፡ ልብሶች ፥ የልጆቹንም ፡ ልብሶች ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 20 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ከሙሴ ፡ ፊት ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 21 ፤ ከነርሱም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ልቡ ፡ እንዳነሣሣው ፡ መንፈሱም ፡ ዕሺ ፡ እንዳሠኘው ፡ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ሥራ ፡ ለማገልገያውም ፡ ኹሉ ፡ ለተቀደሰውም ፡ ልብስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 22 ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ ልባቸው ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ ማርዳዎችን ፥ ሎቲዎችንም ፥ ቀለበቶችንም ፥ ድሪዎችንም ፥ የወርቅ ፡ ጌጦችንም ፡ ኹሉ ፡ አመጡ ፤ ሰዎችም ፡ ኹሉ ፡ የወርቅ ፡ ስጦታ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀረቡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 23 ፤ ሰማያዊም ፡ ሐምራዊም ፡ ቀይ ፡ ግምጃም ፥ ጥሩ ፡ በፍታም ፥ የፍየል ፡ ጠጕርም ፥ ቀይ ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ ቍርበትም ፥ የአቀኑስጣ ፡ ቍርበትም ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 24 ፤ ስእለት ፡ የተሳለ ፡ ኹሉ ፡ የብርንም ፡ የናስንም ፡ ስጦታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ አቀረበ ፤ የግራርም ፡ ዕንጨት ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለማገልገያ ፡ ሥራ ፡ አመጣ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 25 ፤ በልባቸው ፡ ጥበበኞች ፡ የኾኑ ፡ ሴቶችም ፡ በእጃቸው ፡ ፈተሉ ፥ የፈተሉትንም ፡ ሰማያዊውን ፡ ሐምራዊውንም ፡ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፥ ጥሩውንም ፡ በፍታ ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 26 ፤ ልባቸውም ፡ በጥበብ ፡ ያስነሣቸው ፡ ሴቶች ፡ ኹሉ ፡ የፍየልን ፡ ጠጕር ፡ ፈተሉ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 27 ፤ አለቃዎችም ፡ መረግድን ፥ ለኤፉድና ፡ ለደረት ፡ ኪስ ፡ የሚገቡትንም ፡ ፈርጦችን ፥

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 28 ፤ ለመብራትም ፡ ለቅብዐት ፡ ዘይትም ፡ ለጣፋጭ ፡ ዕጣንም ፡ ሽቱንና ፡ ዘይትን ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 29 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ልባቸው ፡ ያስነሣቸው ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ኹሉ ፡ ሙሴ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዘዘው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ በፈቃዳቸው ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አላቸው ፦ እዩ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የኾነውን ፡ የሆር ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፥ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ባስልኤልን ፡ በስሙ ፡ ጠራው ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 31 ፤ በሥራ ፡ ኹሉ ፡ ብልኀት ፡ በጥበብም ፡ በማስተዋልም ፡ በዕውቀትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ ሞላበት ፤

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 32 ፤ የጥበብን ፡ ሥራ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፥ በወርቅና ፡ በብር ፡ በናስም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፥

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 33 ፤ በፈርጥ ፡ የሚኾነውን ፡ የዕንቊ ፡ ድንጋይ ፡ ይቀርጽ ፡ ዘንድ ፥ ዕንጨቱንም ፡ ይጠርብ ፡ ዘንድ ፥ የብልኀት ፡ ሥራውንም ፡ ኹሉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 34 ፤ ርሱና ፡ የዳን ፡ ነገድ ፡ የኾነው ፡ የአሢሳሚክ ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ በልባቸው ፡ አሳደረባቸው ።

ዘጸ. ፡ 35 ፡ 35 ፤ በአንጥረኛ ፥ በብልኀ ፡ ሠራተኛም ፥ በሰማያዊና ፡ በሐምራዊ ፡ በቀይም ፡ ግምጃ ፡ በጥሩ ፡ በፍታም ፡ በሚሠራ ፡ ጠላፊ ፥ በሸማኔም ፡ ሥራ ፡ የሚሠራውን ፥ ማናቸውንም ፡ ሥራና ፡ በብልኀት ፡ የሚሠራውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በእነርሱ ፡ ልብ ፡ ጥበብን ፡ ሞላ ።

——————————ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ። ——————————

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ ለመቅደስም ፡ ማገልገያ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያውቁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበብንና ፡ ማስተዋልን ፡ የሰጣቸው ፡ ባስልኤልና ፡ ኤልያብ ፡ በልባቸው ፡ ጥበበኞችም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ ሙሴም ፡ ባስልኤልንና ፡ ኤልያብን ፥ እግዚአብሔርም ፡ በልቡ ፡ ጥበብን ፡ ያደረገለትን ፡ በልብ ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፥ ሥራውንም ፡ ለመሥራት ፡ ይቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ልቡ ፡ ያስነሣውን ፡ ኹሉ ፡ ጠራቸው ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለመቅደስ ፡ ማገልገያ ፡ ሥራ ፡ ያመጡትን ፡ ስጦታ ፡ ኹሉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ከሙሴ ፡ ተቀበሉ ። እነዚያም ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ስጦታውን ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 4 ፤ የመቅደሱንም ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩ ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሥራ ፡ ትተው ፡ መጡ ፥

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፡ ሙሴን ፦ እግዚአብሔር ፡ ለማገልገያ ፡ ሥራ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ላዘዘው ፡ ከሚበቃ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ የሚበልጥ ፡ ሕዝቡ ፡ አመጡ ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 6-7 ፤ ያመጡትም ፡ ነገር ፡ ሥራን ፡ ኹሉ ፡ ለመፈጸም ፡ በቅዶ ፡ ገና ፡ ይተርፍ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሙሴ ፡ አዘዘና ፦ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ለመቅደስ ፡ ስጦታ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ የሚያመጣ ፡ አይኑር ፡ ብሎ ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ አሳወጀ ። ሕዝቡም ፡ እንዳያመጡ ፡ ተከለከሉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 8 ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ያሉት ፡ ሥራ ፡ ሊሠሩ ፡ የነበሩት ፡ በልባቸው ፡ ጥበበኞች ፡ ኹሉ ፡ ማደሪያውን ፡ ከዐሥር ፡ መጋረጃዎች ፡ ሠሩ ፤ እነርሱንም ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፥ ከሰማያዊም ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ሠሩ ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ብልኀ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ ኪሩቤልን ፡ አደረጉባቸው ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 9 ፤ የያንዳንዱ ፡ መጋረጃ ፡ ርዝመት ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ የመጋረጃዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ልክ ፡ ትክክል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 10 ፤ ዐምስቱንም ፡ መጋረጃዎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አጋጠሙ ፤ ዐምስቱንም ፡ መጋረጃዎች ፡ እንዲሁ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አጋጠሙ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 11 ፤ ከሚጋጠሙትም ፡ መጋረጃዎች ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ የሰማያዊውን ፡ ግምጃ ፡ ቀለበቶች ፡ አደረጉ ፤ ደግሞ ፡ ከተጋጠሙት ፡ ከሌላዎቹ ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ዐምሳ ፡ ቀለበቶችን ፡ ባንድ ፡ መጋረጃ ፡ አደረጉ ፤ ዐምሳውንም ፡ ቀለበቶች ፡ በኹለተኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ አደረጉ ፤ ቀለበቶቹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የሚተያዩ ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 13 ፤ ዐምሳም ፡ የወርቅ ፡ መያዣዎች ፡ ሠሩ ፤ መጋረጃዎችንም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በመያዣዎች ፡ አጋጠሟቸው ፤ አንድ ፡ ማደሪያም ፡ ኾነ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 14 ፤ ከማደሪያውም ፡ በላይ ፡ ለድንኳን ፡ የሚኾኑ ፡ መጋረጃዎችን ፡ ከፍየል ፡ ጠጕር ፡ አደረጉ ፤ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ መጋረጃዎች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 15 ፤ እያንዳንዱም ፡ መጋረጃ ፡ ርዝመቱ ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፥ እያንዳንዱም ፡ መጋረጃ ፡ ወርዱ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ የዐሥራ ፡ አንዱም ፡ መጋረጃዎች ፡ መጠናቸው ፡ ትክክል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 16 ፤ ዐምስቱንም ፡ መጋረጃዎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ አድርገው ፥ ስድስቱንም ፡ መጋረጃዎች ፡ አንድ ፡ አድርገው ፡ አጋጠሟቸው ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 17 ፤ ከተጋጠሙትም ፡ መጋረጃዎች ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ ዐምሳ ፡ ቀለበቶች ፡ አደረጉ ፤ ደግሞ ፡ ከተጋጠሙት ፡ ከሌላዎቹ ፡ በአንደኛው ፡ መጋረጃ ፡ ዘርፍ ፡ ላይ ፡ ዐምሳ ፡ ቀለበቶች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 18 ፤ ድንኳኑም ፡ አንድ ፡ እንዲኾን ፡ ያጋጥሙት ፡ ዘንድ ፡ ዐምሳ ፡ የናስ ፡ መያዣዎችን ፡ ሠሩ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 19 ፤ ለድንኳኑም ፡ መደረቢያ ፡ ከቀይ ፡ ከአውራ ፡ በግ ፡ ቍርበት ፥ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ሌላ ፡ መደረቢያ ፡ ከአቍስጣ ፡ ቍርበት ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 20 ፤ ለማደሪያውም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ የሚቆሙትን ፡ ሳንቃዎች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 21 ፤ የሳንቃው ፡ ዥሉ ፡ ርዝመቱ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 22 ፤ ለያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ የሚያያይዙ ፡ ኹለት ፡ ማጋጠሚያዎች ፡ ነበሩ ፤ ለማደሪያው ፡ ሳንቃዎች ፡ ዥሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 23 ፤ ለማደሪያውም ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ኻያ ፡ ሳንቃዎችን ፡ አደረጉ ፤

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 24 ፤ ከኻያውም ፡ ሳንቃዎች ፡ በታች ፡ አርባ ፡ የብር ፡ እግሮች ፡ አደረጉ ፤ ከያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ለኹለቱ ፡ ማጋጠሚያዎች ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 25 ፤ ለማደሪያው ፡ ለኹለተኛው ፡ ወገን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ኻያ ፡ ሳንቃዎች ፡ አደረጉ ፤

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 26 ፤ ለእነርሱም ፡ አርባ ፡ የብር ፡ እግሮች ፥ ከያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 27 ፤ ለማደሪያውም ፡ በምዕራቡ ፡ ወገን ፥ በስተኋላ ፡ ስድስት ፡ ሳንቃዎች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 28 ፤ ለማደሪያውም ፡ ለኹለቱ ፡ ማእዘን ፡ በስተኋላ ፡ ኹለት ፡ ሳንቃዎች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 29 ፤ ከታችም ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ አንደኛው ፡ ቀለበት ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ሳንቃ ፡ ድርብ ፡ ነበረ ፤ ለኹለቱም ፡ ማእዘን ፡ እንዲሁ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 36 ፡ 30 ፤ ስምንት ፡ ሳንቃዎችና ፡ ዐሥራ ፡ ስድስቱ ፡ የብር ፡ እግሮቻቸው ፥ ከያንዳንዱም ፡ ሳንቃ ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 31 ፲ ከግራርም ፡ ዕንጨት ፡ በማደሪያው ፡ በአንደኛው ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፥

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 32 ፲ በማደሪያውም ፡ በኹለተኛው ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፥ ከማደሪያውም ፡ በስተኋላ ፡ በምዕራቡ ፡ ወገን ፡ ላሉት ፡ ሳንቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መወርወሪያዎች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 33 ፲ መካከለኛውንም ፡ መወርወሪያ ፡ በሳንቃዎቹ ፡ መካከል ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ አሳለፉ ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 34 ፲ ሳንቃዎቹንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጧቸው ፲ ቀለበቶቻቸውንም ፡ የመወርወሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲኾኑላቸው ፡ ከወርቅ ፡ አደረገ ፲ መወርወሪያዎቹንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጧቸው ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 35 ፲ መጋረጃውንም ፡ ከሰማያዊና ፡ ከሐምራዊ ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፥ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ አደረገ ፲ ብልኀ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ ኪሩቤልን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 36 ፲ ከግራርም ፡ ዕንጨት ፡ አራት ፡ ምሰሶዎች ፡ አደረገለት ፥ በወርቅም ፡ ለበጧቸው ፲ ኵላቦቻቸው ፡ የወርቅ ፡ ነበሩ ፲ ለእነርሱም ፡ አራት ፡ የብር ፡ እግሮች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 37 ፲ ለድንኳኑም ፡ ደጃፍ ፡ ከሰማያዊና ፡ ከሐምራዊ ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፥ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ መጋረጃ ፡ አደረገ ፲

ዘጸ. ፥ 36 ፥ 38 ፲ ዐምስቱንም ፡ ምሰሶዎች ፥ ኵላቦቻቸውንም ፡ አደረገ ፲ ጕልላቶቻቸውንና ፡ ዘንጎቻቸውንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጧቸው ፲ ዐምስቱም ፡ እግሮቻቸው ፡ የናስ ፡ ነበሩ ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 1 ፲ ባስልኤልም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ታቦቱን ፡ ሠራ ፲ ርዝመቱም ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ቁመቱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 2 ፲ በውስጥም ፡ በውጭም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ፲ በዙሪያውም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ አደረገለት ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 3 ፲ አራት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶችም ፡ አደረገለት ፲ እነርሱንም ፡ በአራቱ ፡ እግሮቹ ፡ ላይ ፡ አኖረ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ቀለበቶች ፥ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ቀለበቶች ፡ ኾኑ ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 4 ፲ መሎጊያዎቹንም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 5 ፲ ታቦቱንም ፡ ለመሸከም ፡ በታቦቱ ፡ አጠገብ ፡ ባሉት ፡ ቀለበቶች ፡ መሎጊያዎቹን ፡ አገባ ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 6 ፲ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ርዝመቱ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ የኾነ ፡ የስርየት ፡ መክደኛ ፡ ሠራ ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 7 ፲ ኹለት ፡ ኪሩቤልንም ፡ ከተቀጠቀጠ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ፲ በስርየት ፡ መክደኛውም ፡ ላይ ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ አደረጋቸው ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 8 ፲ ከስርየት ፡ መክደኛውም ፡ ጋራ ፡ አንዱን ፡ ኪሩብ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ ኹለተኛውንም ፡ ኪሩብ ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ አድርጎ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሠራቸው ።

ዘጸ. ፥ 37 ፥ 9 ፲ ኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የዘረጉ ፡ ኾኑ ፥ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፡ በክንፎቻቸው ፡ ሸፈኑ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ተያዩ ፲ የኪሩቤልም ፡ ፊቶቻቸው ፡ ወደ ፡ መክደኛው ፡ ተመለከቱ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 10 ፤ ርዝመቱ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ የኾነውን ፡ ገበታ ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 11 ፤ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ፥ በዙሪያውም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ አደረገለት ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 12 ፤ በዙሪያውም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ የሚያኽል ፡ ክፈፍ ፡ አደረገለት ፤ የወርቅም ፡ አክሊል ፡ በክፈፉ ፡ ዙሪያ ፡ አደረገለት ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 13 ፤ አራትም ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ አደረገለት ፤ ቀለበቶቹንም ፡ አራቱ ፡ እግሮቹ ፡ ባሉበት ፡ በአራቱ ፡ ማእዘኖች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 14 ፤ ገበታውንም ፡ ለመሸከም ፡ መሎጊያዎቹ ፡ እንዲሰኩባቸው ፡ ቀለበቶች ፡ በክፈፉ ፡ አቅራቢያ ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 15 ፤ ገበታውንም ፡ ይሸከሙባቸው ፡ ዘንድ ፡ መሎጊያዎቹን ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠርቶ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 16 ፤ ለማፍሰሻም ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በገበታው ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትን ፡ ዕቃዎች ፥ ወጭቶቹንና ፡ ጭልፋዎቹን ፡ ጽዋዎቹንም ፡ መቅጃዎቹንም ፥ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አደረጋቸው ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 17 ፤ መቅረዙንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አደረገ ፤ መቅረዙንም ፡ ከእግሩና ፡ ከአገዳው ፡ ጋራ ፡ በተቀረጸ ፡ ሥራ ፡ አደረገ ፤ ጽዋዎቹን ፥ ጉብጉቦቹን ፥ አበባዎቹን ፡ ከዚያው ፡ በአንድነት ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 18 ፤ በስተጐኑም ፡ ስድስት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ወጡለት ፤ ሦስቱ ፡ የመቅረዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ባንድ ፡ ወገን ፥ ሦስቱም ፡ የመቅረዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ወጡ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 19 ፤ በአንደኛው ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጉብጉቡንና ፡ አበባውን ፡ ሦስትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፥ በኹለተኛውም ፡ ቅርንጫፍ ፡ ጉብጉቡንና ፡ አበባውን ፡ ሦስትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፥ እንዲሁም ፡ ከመቅረዙ ፡ ለወጡ ፡ ለስድስቱ ፡ ቅርንጫፎች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 20 ፤ በመቅረዙም ፡ ጉብጉቦቹንና ፡ አበባዎቹን ፡ አራትም ፡ የለውዝ ፡ አበባ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጽዋዎች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 21 ፤ ከመቅረዙ ፡ ለወጡ ፡ ለስድስት ፡ ቅርንጫፎች ፡ ከኹለት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጉብጉብ ፥ ከኹለትም ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጉብጉብ ፥ ደግሞ ፡ ከኹለት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ አንድ ፡ ጉብጉብ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 22 ፤ ጉብጉቦቹና ፡ ቅርንጫፎቹ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበሩ ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ ከተቀረጸ ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 23 ፤ ሰባቱንም ፡ መብራቶች ፡ መኮስተሪያዎቹንም ፥ የኵስታሪ ፡ ማድረጊያዎቹንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 24 ፤ መቅረዙንም ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ መክሊት ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 25 ፤ የዕጣን ፡ መሠዊያ ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፥ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበረ ፤ ከፍታውም ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ቀንዶቹም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ የተሠሩ ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 26 ፤ ላይኛውንና ፡ የግድግዳውንም ፡ ዙሪያ ፡ ቀንዶቹንም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ፤ በዙሪያውም ፡ የወርቅ ፡ ክፈፍ ፡ አደረገበት ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 27 ፤ ከክፈፉም ፡ በታች ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ አደረገበት ፥ በዚህና ፡ በዚያ ፡ በኹለቱም ፡ ጐን ፡ አደረጋቸው ፤ ለመሸከምም ፡ የመሎጊያዎች ፡ ስፍራ ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 28 ፤ መሎጊያዎቹንም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አደረገ ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 37 ፡ 29 ፤ የተቀደሰውንም ፡ የቅብዓቱን ፡ ዘይት ፥ ጥሩውንም ፡ የጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ ዕጣን ፡ በቀማሚ ፡ ብልኀት ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ አደረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ። _____

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 1 ፤ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾን ፡ መሠዊያን ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ አደረገ ፤ አራት ፡ ማእዘንም ፡ ነበረ ፤ ከፍታው ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 2 ፤ ቀንዶቹንም ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ አደረገበት ፤ ቀንዶቹም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ የተሠሩ ፡ ነበሩ ፤ በናስም ፡ ለበጠው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 3 ፤ የመሠዊያውንም ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፥ ምንቸቶቹንም ፥ መጫሪያዎቹንም ፥ ድስቶቹንም ፥ ሜንጦዎቹንም ፥ ማንደጃዎቹንም ፡ አደረገ ፤ ዕቃውንም ፡ ሹሉ ፡ ከናስ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 4 ፤ እንደ ፡ መረብ ፡ ኾኖም ፡ የተሠራ ፡ የናስ ፡ መከታ ፡ ለመሠዊያ ፡ አደረገ ፤ መከታውም ፡ እስከመሠዊያው ፡ እኩሌታ ፡ ይደርስ ፡ ዘንድ ፡ በመሠዊያው ፡ በሚዞረው ፡ በደረጃው ፡ ታች ፡ አደረገው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 5 ፤ ለናሱም ፡ መከታ ፡ ለአራቱ ፡ ማእዘን ፡ የመሎጊያዎች ፡ ስፍራ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አራት ፡ ቀለበቶች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 6 ፤ መሎጊያዎቹንም ፡ ከግራር ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፥ በናስም ፡ ለበጣቸው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 7 ፤ ይሸከሙትም ፡ ዘንድ ፡ በመሠዊያ ፡ ጐን ፡ ባሉት ፡ ቀለበቶች ፡ ውስጥ ፡ መሎጊያዎቹን ፡ አገባ ፤ ከሳንቃዎቹም ፡ ሠርቶ ፡ ባዶ ፡ አደረገው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 8 ፤ የመታጠቢያውን ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ከሚያገለግሉ ፡ ከሴቶች ፡ መስተዋት ፡ ከናስ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 9 ፤ አደባባዩንም ፡ አደረገ ፤ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ርዝመቱ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፥ የተፈተለ ፡ የጥሩ ፡ በፍታ ፡ መጋረጃዎች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 10 ፤ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ ኻያውን ፡ ምሰሶዎችና ፡ ኻያውን ፡ እግሮች ፡ አደረገ ፤ የምሰሶዎቹንም ፡ ኩላቦችና ፡ ዘንጎች ፡ ከብር ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 11 ፤ በሰሜኑም ፡ ወገን ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸውን ፡ መጋረጃዎች ፥ ከናስም ፡ የተሠራ ፡ ኻያ ፡ ምሰሶዎችንና ፡ ኻያ ፡ እግሮችን ፥ ለምሰሶዎቹም ፡ የብር ፡ ኩላቦችንና ፡ ዘንጎችን ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 12 ፤ በምዕራብም ፡ ወገን ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸውን ፡ መጋረጃዎች ፥ ዐሥሩንም ፡ ምሰሶዎች ፥ ዐሥሩንም ፡ የናስ ፡ እግሮች ፥ ለምሰሶዎቹም ፡ የብር ፡ ኩላቦችንና ፡ ዘንጎችን ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 13 ፤ በምሥራቅም ፡ ወገን ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸውን ፡ መጋረጃዎች ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 14 ፤ ባንድ ፡ ወገንም ፡ የመጋረጃዎቹ ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ምሰሶዎቹም ፡ ሦስት ፥ እግሮቹም ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 15 ፤ እንዲሁም ፡ በኹለተኛው ፡ ወገን ፡ በአደባባዩ ፡ ደጅ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ርዝመት ፡ ያላቸው ፡ መጋረጃዎች ፥ ሦስትም ፡ ምሰሶዎች ፥ ሦስትም ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 16 ፤ በአደባባዩ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ መጋረጃዎች ፡ ሹሉ ፡ ከተፈተለ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ ተሠርተው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 17 ፤ የምሰሶዎቹም ፡ እግሮች ፡ የናስ ፥ የምሰሶዎቹም ፡ ኵላቦችና ፡ ዘንጎች ፡ የብር ፡ ነበሩ ፤ የምሰሶዎችም ፡ ጕልላቶች ፡ በብር ፡ ተለብጠው ፡ ነበር ፤ በአደባባዩ ፡ ላሉ ፡ ምሰሶዎች ፡ ሹሉ ፡ የብር ፡ ዘንጎች ፡ ነበሯቸው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 18 ፤ የአደባባዩም ፡ ደጅ ፡ መጋረጃ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፥ ከጥሩም ፡ በፍታ ፡ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ፤ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ ቁመቱም ፡ እንደአደባባዩ ፡ መጋረጃዎች ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 19 ፤ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ ምሰሶዎቹም ፡ አራት ፥ እግሮቹም ፡ አራት ፡ ነበሩ ፤ ኵላቦቹ ፡ የብር ፡ ነበሩ ፤ ጕልላቶቹና ፡ ዘንጎቹም ፡ በብር ፡ ተለብጠው ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 20 ፤ የማደሪያውም ፡ ካስማዎች ፡ በዙሪያውም ፡ ያለ ፡ የአደባባዩ ፡ ካስማዎች ፡ የናስ ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 21 ፤ በሙሴ ፡ ትእዛዝ ፡ ለሌዋውያን ፡ ማገልገል ፡ ሊኾን ፡ በካህኑ ፡ በአሮን ፡ ልጅ ፡ በኢታማር ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተቈጠረው ፡ የማደሪያው ፥ የምስክሩ ፡ ማደሪያ ፥ ዕቃ ፡ ድምር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 22 ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድም ፡ የኾነ ፡ የሆር ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፥ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ባስልኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ ሹሉ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 23 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የኾነ ፡ የአሂሳሚክ ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የቅርጽ ፡ ሠራተኛና ፡ ብልኅ ፡ ሠራተኛ ፥ በሰማያዊ ፡ በሐምራዊም ፡ በቀይም ፡ ግምጃ ፥ በጥሩም ፡ በፍታ ፡ የሚሠራ ፡ ጠላፊ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 24 ፤ የተሰጠው ፡ ወርቅ ፡ ሹሉ ፥ በመቅደሱ ፡ ሥራ ፡ ሹሉ ፡ የተደረገው ፡ ወርቅ ፥ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ መክሊት ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 25 ፤ በማኅበሩም ፡ ከሚቈጠሩት ፡ የተገኘ ፡ ብር ፥ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፥ መቶ ፡ መክሊትና ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ከሰባ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 26 ፤ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፥ የሰቅል ፡ ግማሽ ፡ ከተቈጠረው ፡ ከያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የተሰጠ ፡ ነው ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሹሉ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 27 ፤ መቶውም ፡ የብር ፡ መክሊት ፡ የመቅደሱንና ፡ የመጋረጃውን ፡ እግሮች ፡ ለመሥራት ፡ ነበረ ፤ ከመቶውም ፡ መክሊት ፡ መቶ ፡ እግሮች ፡ አደረገ ፤ ላንድ ፡ እግርም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 28 ፤ ከሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፡ የምሰሶዎቹን ፡ ኵላቦችና ፡ ዘንጎች ፡ አደረገ ፥ የምሰሶዎቹንም ፡ ጕልላቶች ፡ ለበጠ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 29 ፤ የተሰጠውም ፡ ናስ ፡ ሰባ ፡ መክሊትና ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 38 ፡ 30 ፤ ከርሱም ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ እግሮች ፥ የናሱንም ፡ መሠዊያ ፥ ለርሱም ፡

የኾነውን ፡ የናሱን ፡ መከታ ፥ የመሠዊያውንም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥

ዘጸ. ፥ 38 ፥ 31 ፤ በአደባባዩ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ እግሮች ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ እግሮች ፥ የማደሪያውንም ፡ ካስማዎች ፡ ኹሉ ፡ በአደባባዩ ፡ ዙሪያም ፡ ያሉትን ፡ ካስማዎች ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ። _____

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ በመቅደሱ ፡ ለማገልገል ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይ ፡ ግምጃም ፡ በብልኀት ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፥ ለአሮንም ፡ የተቀደሰውን ፡ ልብስ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ ኤፉዱን ፡ ከወርቅ ፡ ከሰማያዊም ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይ ፡ ግምጃም ፡ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 3 ፤ ወርቁንም ፡ ቀጥቅጠው ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ሥሥ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ ቈረጡ ። ብልኀ ፡ ሠራተኛም ፡ እንደሚሠራ ፡ ሰማያዊ ፡ ሐምራዊም ፡ ቀይም ፡ ግምጃ ፡ የተፈተለም ፡ ጥሩ ፡ በፍታ ፡ ከርሱ ፡ ጠለፉ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 4 ፤ ኹለቱ ፡ ወገን ፡ እንዲጋጠም ፡ በኹለቱ ፡ ጫንቃዎች ፡ ላይ ፡ የሚጋጠም ፡ ልብስ ፡ አደረጉት ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 5 ፤ በላዩም ፡ መታጠቂያ ፡ ኾኖ ፡ በብልኀት ፡ የተጠለፈው ፡ የኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበረ ፤ ከወርቅና ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊ ፡ ከቀይ ፡ ግምጃም ፡ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ በወርቅ ፡ ፈርጥ ፡ የተያዙ ፡ የመረግድ ፡ ድንጋዮች ፡ ሠርተው ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡ ቅርጽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ቀረጹባቸው ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 7 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የመታሰቢያ ፡ ድንጋዮች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በኤፉዱ ፡ ጫንቃዎች ፡ ላይ ፡ አደረጋቸው ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ የደረቱን ፡ ኪስ ፡ ብልኀ ፡ ሠራተኛ ፡ እንደሚሠራ ፡ እንደ ፡ ኤፉዱ ፡ አሠራር ፡ ከወርቅና ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ አደረገው ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 9 ፤ አራት ፡ ማእዘንም ፡ ነበረ ፤ የደረቱን ፡ ኪስም ፡ ድርብ ፡ አደረጉ ፤ ርዝመቱ ፡ ስንዝር ፥ ወርዱም ፡ ስንዝር ፥ ድርብም ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 10 ፤ ዕንቊዎቹንም ፡ በአራት ፡ ተራ ፡ አደረጉበት ፤ በፊተኛውም ፡ ተራ ፡ ሰርድዮን ፥ ቶጳዝዮን ፥ የሚያብረቀርቅ ፡ ዕንቊ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 11 ፤ በኹለተኛውም ፡ ተራ ፡ በሉር ፥ ሰንፔር ፥ አልማዝ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 12 ፤ በሦስተኛውም ፡ ተራ ፡ ያክንት ፥ ኬልቄዶን ፥ አሜቴስጢኖስ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 13 ፤ በአራተኛውም ፡ ተራ ፡ ቢረሌ ፥ መረግድ ፥ ኢያስጲድ ፡ በወርቅ ፡ ፈርጥ ፡ ተደረጉ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 14 ፤ የዕንቊዎችም ፡ ድንጋዮች ፡ እንደ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ ነበሩ ፤ በየስማቸውም ፡ ማተሚያ ፡ እንደሚቀረጽ ፡ ተቀረጹ ፥ ስለ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ነገዶች ፡ ነበሩ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 15 ፤ ለደረቱ ፡ ኪስም ፡ የተጐነጐኑትን ፡ ድሪዎች ፡ እንደ ፡ ገመድ ፡ አድርገው ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠሩ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 16 ፤ ኹለትም ፡ የወርቅ ፡ ፈርጦች ፥ ኹለትም ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሠሩ ፤ ኹለቱንም ፡ ቀለበቶች ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ በኹለቱ ፡ ወገን ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 17 ፤ ኹለቱንም ፡ የተጐነጐኑትን ፡ የወርቅ ፡ ድሪዎች ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ ወገኖች ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ ቀለበቶች ፡ አገቡ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 18 ፤ የኹለቱንም ፡ ድሪዎች ፡ ጫፎች ፡ በኹለቱ ፡ ፈርጦች ፡ ውስጥ ፡ አግብተው ፡ በኤፉዱ ፡ ጣንቃዎች ፡ ላይ ፡ በፊታቸው ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 19 ፤ ኹለቱንም ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሠሩ ፥ እነርሱንም ፡ በኤፉዱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በደረቱ ፡ ኪስ ፡ በኹለት ፡ ጫፎቹ ፡ ላይ ፡ አደረጓቸው ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 20 ፤ ደግሞም ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ቀለበቶች ፡ ሠሩ ፥ በኤፉዱም ፡ ፊት ፥ ከጣንቃዎች ፡ በታች ፥ በብልኀት ፡ ከተጠለፈ ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፥ በመያዣው ፡ አጠገብ ፡ አደረጓቸው ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 21 ፤ የደረቱ ፡ ኪስ ፡ በብልኀት ፡ ከተጠለፈው ፡ ከኤፉዱ ፡ ቋድ ፡ በላይ ፡ እንዲኾን ፥ ከኤፉዱም ፡ እንዳይለይ ፡ የደረቱን ፡ ኪስ ፡ ከቀለበቶቹ ፡ ጋራ ፡ ወደኤፉዱ ፡ ቀለበቶች ፡ በሰማያዊ ፡ ፈትል ፡ አሰሩት ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ የኤፉዱን ፡ ቀሚስ ፡ ሞላውን ፡ በሸማኔ ፡ ሥራ ፡ ሰማያዊ ፡ አደረገው ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 23 ፤ በቀሚሱም ፡ መካከል ፡ ዐንገትጌ ፡ ነበረ ፤ እንዳይቀደድም ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ የተሠራ ፡ ጥልፍ ፡ በዐንገትጌው ፡ ዙሪያ ፡ ነበረ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 24 ፤ በቀሚሱም ፡ ታችኛ ፡ ዘርፍ ፡ ከሰማያዊ ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፥ ከተፈተለ ፡ በፍታም ፡ ሮማኖች ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 25 ፤ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ኻኵራዎችን ፡ ሠሩ ፥ ኻኵራዎቹንም ፡ ከሮማኖች ፡ መካከል ፡ በቀሚሱ ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 26 ፤ በቀሚሱ ፡ ዘርፍ ፡ ዙሪያ ፡ ኻኵራንና ፡ ሮማንን ፥ ኻኵራንና ፡ ሮማንን ፡ ለማገልገል ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ ሥራ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ የደረት ፡ ልብሶችን ፥

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 28 ፤ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ መጠምጠሚያውን ፥ ከጥሩ ፡ በፍታም ፡ መልካሞቹን ፡ ቆቦች ፥ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ የእግር ፡ ሱሪዎችን ፥

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 29 ፤ ከተፈተለም ፡ ከጥሩ ፡ በፍታ ፥ ከሰማያዊም ፡ ከሐምራዊም ፡ ከቀይም ፡ ግምጃ ፡ በጥልፍ ፡ አሠራር ፡ የተሠራ ፡ መታጠቂያውን ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የተቀደሰውን ፡ የአክሊል ፡ ምልክት ፡ ሠሩ ፤ በርሱም ፡ እንደ ፡ ማኅተም ፡ ቅርጽ ፡ አድርገው ። ቅድስና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚል ፡ ጻፉበት ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 31 ፤ በመጠምጠሚያውም ፡ ላይ ፡ ያንጠለጥሉት ፡ ዘንድ ፡ ሰማያዊውን ፡ ፈትል ፡ አሰሩበት ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 32 ፤ እንዲሁም ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የማደሪያው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተጨረሰ ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አደረጉ ፤ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘጸ. ፡ 39 ፡ 33 ፤ ማደሪያውንም ፥ ድንኳኑንም ፥ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡

አመጡ ፤ መያዣዎቹን ፥ ሳንቃዎቹን ፥ መወርወሪያዎቹን ፥ ምሰሶዎቹንም ፥ እግሮቹንም ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 34 ፤ ከቀይ ፡ ከአውራ ፡ በግ ፡ ቀሦርበትም ፡ የተሠራ ፡ መደረቢያ ፥ ከአቀሥጣ ፡ ቀሦርበትም ፡ የተሠራ ፡ መደረቢያ ፥ የሚሸፍነውንም ፡ መጋረጃ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 35 ፤ የምስክሩንም ፡ ታቦት ፥ መሎጊያዎቹንም ፥ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 36 ፤ ገበታውንም ፥ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 37 ፤ ጥሩውንም ፡ መቅረዝ ፥ መብራቶቹንም ፥ በተራ ፡ የሚኾኑትንም ፡ ቀንዲሎች ፥ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የመብራቱንም ፡ ዘይት ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 38 ፤ የወርቁንም ፡ መሠዊያ ፥ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፥ ጣፋጩንም ፡ ዕጣን ፥ የድንኳኑንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 39 ፤ የናሱንም ፡ መሠዊያ ፥ የናሱንም ፡ መከታ ፥ መሎጊያዎቹንም ፥ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የመታጠቢያውን ፡ ሰንም ፡ መቀመጫውንም ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 40 ፤ የአደባባዩንም ፡ መጋረጃዎች ፥ ምሰሶዎቹንም ፥ እግሮቹንም ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፥ አውታሮቹንም ፥ ካስማዎቹንም ፥ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ለማደሪያው ፡ ማገልገያ ፡ የሚኾኑን ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፤

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 41 ፤ በመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለማገልገል ፡ በብልኀት ፡ የተሠሩትን ፡ ልብሶች ፥ በክህነትም ፡ ያገለግሉበት ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሱትን ፡ የካህኑን ፡ የአሮንን ፡ ልብሶች ፥ የልጆቹንም ፡ ልብሶች ፡ አመጡ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 42 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ ሠሩ ።

ዘጸ. ፥ 39 ፥ 43 ፤ ሙሴም ፡ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ አየ ፥ እንሆም ፡ አድርገውት ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አድርገውት ፡ ነበር ፤ ሙሴም ፡ ባረካቸው ።

ኦሪት ፡ ዘጸአት ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 2 ፤ ከመገመሪያው ፡ ወር ፡ በፊተኛው ፡ ቀን ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ማደሪያ ፡ ትተክላለኽ ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 3 ፤ በርሱም ፡ ውስጥ ፡ የምስክሩን ፡ ታቦት ፡ ታኖራለኽ ፥ ታቦቱንም ፡ በመጋረጃ ፡ ትጋርዳለኽ ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 4 ፤ ገበታውንም ፡ አግብተኽ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የሚኖረውን ፡ ዕቃ ፡ ታሰናዳለኽ ፤ መቅረዙንም ፡ አግብተኽ ፡ ቀንዲሎቹን ፡ ትለኵሳለኽ ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 5 ፤ ለዕጣንም ፡ የሚኾነውን ፡ የወርቅ ፡ መሠዊያ ፡ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ታኖራለኽ ፥ በማደሪያውም ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡ መጋረጃውን ፡ ትጋርዳለኽ ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 6 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውንም ፡ መሠዊያ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በማደሪያው ፡ ደጅ ፡ ፊት ፡ ታኖረዋለኽ ።

ዘጸ. ፥ 40 ፥ 7 ፤ የመታጠቢያውን ፡ ሰንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳንና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ አኑረኽ ፡ ውሃ ፡ ትጨምርበታለኽ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 8 ፤ በዙሪያውም ፡ አደባባዩን ፡ ትተክላለኽ ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ ትዘረጋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 9 ፤ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፡ ወስደኽ ፡ ማደሪያውን ፡ በርሱም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ትቀባለኽ ፥ ርሱንም ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ትቀድሳለኽ ፤ ቅዱስም ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 10 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውንም ፡ መሠዊያ ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ትቀባዋለኽ ፥ መሠዊያውንም ፡ ትቀድሳለኽ ፤ መሠዊያውም ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይኾናል ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 11 ፤ የመታጠቢያውን ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውን ፡ ቀብተኽ ፡ ትቀድሳለኽ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 12 ፤ አሮንንና ፡ ልጆቹንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አቅርበኽ ፡ በውሃ ፡ ታጥባቸዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 13 ፤ የተቀደሰውንም ፡ ልብስ ፡ አሮንን ፡ ታለብሰዋለኽ ፤ በክህነትም ፡ ያገለግለኝ ፡ ዘንድ ፡ ቀብተኽ ፡ ትቀድሰዋለኽ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 14 ፤ ልጆቹንም ፡ አቅርበኽ ፡ የደረት ፡ ልብሶችን ፡ ታለብሳቸዋለኽ ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 15 ፤ በክህነትም ፡ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፡ አባታቸውን ፡ እንደ ፡ ቀባኽ ፡ ትቀባቸዋለኽ ፤ መቀባታቸውም ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ክህነት ፡ ይኾንላቸዋል ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 16 ፤ ሙሴም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 17 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በፊተኛው ፡ ወር ፡ በመገሥመሪያው ፡ ቀን ፡ ማደሪያው ፡ ተተከለ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ ማደሪያውን ፡ ተከለ ፥ እግሮቹንም ፡ አኖረ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆመ ፥ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረገባቸው ፥ ምሰሶዎቹንም ፡ አቆመ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 19 ፤ ድንኳኑንም ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ዘረጋ ፥ የድንኳኑን ፡ መደረቢያ ፡ በላዩ ፡ አደረገበት ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ጽላቱን ፡ ወስዶ ፡ በታቦቱ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ፥ መሎጊያዎቹን ፡ በታቦቱ ፡ ዘንድ ፡ አደረገ ፥ የስርየት ፡ መክደኛውንም ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ አኖረው ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 21 ፤ ታቦቱን ፡ ወደ ፡ ማደሪያው ፡ አገባ ፥ የሚሸፍነውንም ፡ መጋረጃ ፡ አድርጎ ፡ የምስክሩን ፡ ታቦት ፡ ሸፈነ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ገበታውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፥ ከመጋረጃው ፡ ውጭ ፥ በማደሪያው ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አኖረው ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 23 ፤ እንጀራውን ፡ በላዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አሰናዳ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ መቅረዙን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፥ በገበታው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፥ በማደሪያው ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ አኖረ ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 25 ፤ ቀንዲሎቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለኮሰ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ የወርቁን ፡ መሠዊያ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በመጋረጃው ፡ ፊት ፡ አኖረ ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 27 ፤ የጣፋጩን ፡ ሽቱ ፡ ዕጣን ፡ ዐጠነበት ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ በማደሪያው ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡ መጋረጃውን ፡ ዘረጋ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 29 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ መሠዊያ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በማደሪያው ፡ ደጅ ፡ ፊት ፡ አኖረ ፥ የሚቃጠለውንና ፡ የእኽልን ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋበት ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ የመታጠቢያውን ፡ ሰን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳንና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ አኖረ ፥ ለመታጠቢያም ፡ ውሃን ፡ ጨመረበት ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 31 ፤ በርሱም ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ልጆቹም ፡ እጆቻቸውንና ፡ እግሮቻቸውን ፡ ታጠቡ ፤

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 32 ፤ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ መሠዊያውም ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ይታጠቡ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 33 ፤ በማደሪያውና ፡ በመሠዊያውም ፡ ዙሪያ ፡ አደባባዩን ፡ ተከለ ፤ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡ ዘረጋ ። እንዲሁም ፡ ሙሴ ፡ ሥራውን ፡ ፈጸመ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 34 ፤ ደመናውም ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ከደነ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ማደሪያውን ፡ ሞላ ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 35 ፤ ደመናውም ፡ በላዩ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ማደሪያውን ፡ ስለ ፡ ሞላ ፥ ሙሴ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 36 ፤ ደመናውም ፡ ከማደሪያው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በመንገዳቸው ፡ ኹሉ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 37 ፤ ደመናው ፡ ባይነሣ ፡ እስከሚነሣበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አይጓዙም ፡ ነበር ።

ዘጸ. ፡ 40 ፡ 38 ፤ በመንገዳቸውም ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ደመና ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ በቀን ፡ ነበረና ፥ እሳትም ፡ በሌሊት ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ነበረና ❖

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ሙሴን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ከእናንተ ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ ሲያቀርብ ፡ መባችኹን ፡ ከእንስሳ ፡ ወገን ፡ ከላሞች ፡ ወይም ፡ ከበጎች ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ መባውም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከላሞች ፡ መንጋ ፡ ቢኾን ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ተባቱን ፡ ያቀርባል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲሰምር ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እጁንም ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤ ያስተሰርይለትም ፡ ዘንድ ፡ የሰመረ ፡ ይኾንለታል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በሬውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ ያቀርባሉ ፤ ደሙንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ይገፈዋል ፥ በየብልቱም ፡ ይቈርጠዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የካህኑም ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ያነዳሉ ፥ በእሳቱም ፡ ላይ ፡ ዕንጨት ፡ ይደረድራሉ ፤

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፥ የተቈረጡትን ፡ ብልቶች ፡ ራሱንም ፡ ስቡንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ይረበርቡታል ፤

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹን ፡ ግን ፡ በውሃ ፡ ያጥባል ፤ ካህኑም ፡ ኹሉን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የእሳት ፡ ቀርባን ፡ አድርጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ቀርባኑም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከበጎች ፡ ወይም ፡ ከፍየሎች ፡ ቢኾን ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ተባቱን ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በመሠዊያውም ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በየብልቱም ፡ ራሱንም ፡ ስቡንም ፡ ይቈርጠዋል ፤ ካህኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ይረበርበዋል ፤

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹን ፡ ግን ፡ በውሃ ፡ ያጥባል ። ካህኑም ፡ ኹሉን ፡ አቅርቦ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የእሳት ፡ ቀርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚቀርበው ፡ ቀርባን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከወፎች ፡ ቢኾን ፥ ቀርባኑን ፡ ከዋኖስ ፡ ወይም ፡ ከርግብ ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ያቀርበዋል ፥ ራሱንም ፡ ይቈለምመዋል ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ። ደሙም ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ይንጠፈጠፋል ፤

ዘሌ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ ከላባዎች ፡ ጋራ ፡ ለይቶ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ በምሥራቅ ፡ ወገን ፡ በዐመዱ ፡ ስፍራ ፡ ይጥለዋል ፤

ዘሌ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ በክንፎቹም ፡ ይቀደዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይከፍለውም ። ካህኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሲያቀርብ ፡ ቍርባኑ ፡ ከመልካም ፡ ዱቄት ፡ ይኹን ፤ ዘይትም ፡ ያፈስበታል ፥ ዕጣንም ፡ ይጨምርበታል ፤

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ወደአሮንም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ ያመጣዋል ፤ ከመልካም ፡ ዱቄቱና ፡ ከዘይቱም ፡ አንድ ፡ ዕፍኝ ፡ ሙሉና ፡ ዕጣኑን ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ ካህኑ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ለመታሰቢያ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ከእኽሉም ፡ ቍርባን ፡ የተረፈው ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚኾን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ በእቶን ፡ የተጋገረውን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ስታቀርብ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የመልካም ፡ ዱቄት ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፡ ወይም ፡ በዘይት ፡ የተቀባ ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ቍርባንኽም ፡ በምጣድ ፡ የተጋገረ ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ቢኾን ፥ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የመልካም ፡ ዱቄት ፡ ቂጣ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ቈርሰኽም ፡ ዘይት ፡ ታፈስበታለኽ ፤ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ቍርባንኽም ፡ በመቀቀያ ፡ የበሰለ ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ቢኾን ፥ ዘይት ፡ የገባበት ፡ ከመልካም ፡ ዱቄት ፡ የተደረገ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ከዚህም ፡ የተደረገውን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታመጣለኽ ፤ ለካህኑም ፡ ይሰጣል ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ካህኑም ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ መታሰቢያውን ፡ አንሥቶ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ከእኽሉም ፡ ቍርባን ፡ የተረፈው ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚኾን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ርሾ ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ ማርም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አታቀርቡምና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምታቀርቡት ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ርሾ ፡ አይኹንበት ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ እነዚህንም ፡ የበኵራት ፡ ቍርባን ፡ አድርጋችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታቀርባላችኹ ፤ እንደ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ግን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አይቃጠሉም ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ የምታቀርበውን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ በጨው ፡ ታጣፍጠዋለኽ ፤ የአምላክኽንም ፡ ቃል ፡

ኪዳን ፡ ጨው ፡ ከእኽል ፡ ቍርባንኽ ፡ አታጕድልም ፤ በቍርባንኽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ጨው ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ከበኵራትም ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብታቀርብ ፡ ስለዚህ ፡ ቍርባን ፡ በእሳት ፡ የተጠበሰና ፡ የተፈተገ ፡ የእኽል ፡ እሸት ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ዘይትም ፡ ታፈስበታለኽ ፥ ዕጣንም ፡ ትጨምርበታለኽ ፤ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ካህኑም ፡ ከተፈተገው ፡ እኽል ፡ ከዘይቱም ፡ ወስዶ ፡ ከዕጣኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ መታሰቢያውን ፡ ያቃጥላል ፤ ይህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ቍርባኑም ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ቢኾን ፥ ከላሞች ፡ መንጋ ፡ ተባት ፡ ወይም ፡ እንስት ፡ ቢያቀርብ ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቅርብ ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ እጁንም ፡ ለቍርባን ፡ በቀረበው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፥ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ከደኅንነቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ አድርጎ ፡ ያቀርባል ፤ የሆድ ፡ ዕቃውን ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጕድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋራ ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ ያቃጥሉታል ፤ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርበው ፡ ቍርባኑ ፡ ከበጎች ፡ ተባት ፡ ወይም ፡ እንስት ፡ ቢኾን ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ለቍርባኑ ፡ ጠቦትን ፡ ቢያቀርብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ፤

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እጁንም ፡ ለቍርባን ፡ በቀረበው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ከደኅንነቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ አድርጎ ፡ ያቀርባል ፤ ስቡን ፥ እስከ ፡ ገርባውም ፡ ድረስ ፡ የተቈረጠ ፡ ላቱን ፡ ኹሉ ፥ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጕድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋራ ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ካህኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእሳት ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተደረገ ፡ የቍርባን ፡ መብል ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ቍርባኑም ፡ ፍየል ፡ ቢኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ፤

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ እጁንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይጭንበታል ፥ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጩታል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ከርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ አድርጎ ፡ ያቀርበዋል ፤ ሆድ ፡ ዕቃውን ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጐድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋራ ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ካህኑም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የተደረገ ፡ መብል ፡ ነው ። ስቡ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ስብና ፡ ደም ፡ እንዳትበሉ ፡ በምትኖሩበት ፡ ኹሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡ ኀጢአት ፡ በሠራ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አትሥሩ ፡ ካላቸው ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ በተላለፍ ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ የተቀባውም ፡ ካህን ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ እንዲቈጠርባቸው ፡ ኀጢአት ፡ በሠራ ፥ ስለሠራው ፡ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ ነውር ፡ የሌለበት ፡ ወይፈን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ወይፈኑንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያመጣዋል ፤ እጁንም ፡ በወይፈኑ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭነዋል ፥ ወይፈኑንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ የተቀባውም ፡ ካህን ፡ ከወይፈኑ ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ያመጣዋል ፤

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ካህኑም ፡ ጣቱን ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነክሮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመቅደሱ ፡ መጋረጃ ፡ ፊት ፡ ደሙን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ካህኑም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ ጣፋጭ ፡ ዕጣን ፡ በሚታጠንበት ፡ መሠዊያ ፡ ቀንዶች ፡ ላይ ፡ ከደሙ ፡ ያደርጋል ፤ የተረፈውንም ፡ የወይፈኑን ፡ ደም ፡ ኹሉ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጅ ፡ ባለው ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ በታች ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ ከሚታረደው ፡ ወይፈን ፡ ስብን ፡ ኹሉ ፡ ይወስዳል ፤ ሆድ ፡ ዕቃውን ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጐድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶች ፡ ጋራ ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ከታረደው ፡ ወይፈን ፡ እንደተወሰደው ፡ ይወስዳል ። ካህኑም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ የወይፈኑን ፡ ቍርበት ፥ ሥጋውንም ፡ ኹሉ ፥ ራሱንም ፥ እግሮቹንም ፥ ሆድ ፡ ዕቃውንም ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ፈርሱንም ፥ ወይፈኑን ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፥ ዐመድ ፡ ወደሚፈስበት ፥ ወደ ፡ ንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ይወስደዋል ፥ በዕንጨትም ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ ያቃጥለዋል ፤ ዐመድ ፡ በሚፈስበት ፡ ስፍራ ፡ ይቃጠላል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በስቱ ፥ ነገሩም ፡ ከጉባኤው ፡ ፊት ፡

ቢሸሸግ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አትሥሩ ፡ ካላቸው ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ ቢተላለፉ ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ እንዲሀም ፡ ቢበድሉ ፥ የሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ሲታወቅ ፡ ጉባኤው ፡ ስለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈንን ፡ ያቀርባሉ ፤ ወደመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ያመጡታል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ የጉባኤውም ፡ ሽማግሌዎች ፡ እጆቻቸውን ፡ በወይፈኑ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይጭናሉ ፤ ወይፈኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታረዳል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ የተቀባውም ፡ ካህን ፡ ከወይፈኑ ፡ ደም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ያመጣል ፤

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ካህኑም ፡ ጣቱን ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነክሮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመጋረጃው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በዕጣን ፡ መሠዊያው ፡ ቀንዶች ፡ ላይ ፡ ከደሙ ፡ ያደርጋል ፤ ደሙንም ፡ ኹሉ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጅ ፡ ባለው ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ በታች ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ስቡንም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ወስዶ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ እንዲሀም ፡ በወይፈኑ ፡ ያደርጋል ፤ ስለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ በታረደው ፡ ወይፈን ፡ እንዳደረገ ፡ እንዲሁ ፡ በዚህ ፡ ያደርጋል ፤ ካህኑም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ያስተሰርያል ፥ እነርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላሉ ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ወይፈኑንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወስደዋል ፥ የፊተኛውንም ፡ ወይፈን ፡ እንዳቃጠለ ፡ ያቃጥለዋል ፤ ይህ ፡ የማኅበሩ ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ አንድ ፡ መኰንንም ፡ ኀጢአትን ፡ ሲሠሩ ፥ ሳያውቅም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ። አትሥራ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲተላለፍ ፥ እንዲሀም ፡ ሲበድል ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ የሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ቢታወቅ ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ተባት ፡ ፍየል ፡ ለቀኑርባኑ ፡ ያቀርበዋል ፤

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ በፍየሉም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ይጭናል ፤ የሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ በሚታረድበት ፡ ስፍራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያርደዋል ፤ ርሱ ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ካህኑም ፡ ከኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በጣቱ ፡ ወስዶ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ቀንዶች ፡ ያደርገዋል ፤ የተረፈውንም ፡ ደም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ በታች ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ስቡንም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ። ካህኑም ፡ ኀጢአቱን ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ ከአገሩ ፡ ሕዝብም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኀጢአትን ፡ ሳያውቅ ፡ ቢሠራ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አትሥራ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ቢተላለፍ ፥ ቢበድልም ፥

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ ለርሱም ፡ የሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ቢታወቀው ፥ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ነውር ፡ የሌለባትን ፡ እንስት ፡ ፍየል ፡ ለቀኑርባኑ ፡ ያመጣል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ እጁንም ፡ በኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤ የሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ በሚታረድበት ፡ ስፍራ ፡ የኀጢአትን ፡ መሥዋዕት ፡ ያርዳል ።

ዘሌ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ካህኑም ፡ ከደሟ ፡ በጣቱ ፡ ወስዶ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ቀንዶች ፡

ላይ ፡ ያደርገዋል ፥ ደሙንም ፡ ዥሉ ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፥ 4 ፥ 31 ፤ ስቡም ፡ ዥሉ ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ላይ ፡ እንደሚወሰድ ፥ ስቢን ፡ ዥሉ ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ ካህኑም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ያስተሰርያል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፥ 4 ፥ 32 ፤ ስለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ ቢያቀርብ ፥ ነውር ፡ የሌለባትን ፡ እንስት ፡ ያመጣል ።

ዘሌ. ፥ 4 ፥ 33 ፤ እጁንም ፡ በኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፥ የሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ በሚታረድበት ፡ ስፍራ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ያርዳታል ።

ዘሌ. ፥ 4 ፥ 34 ፤ ካህኑም ፡ ከኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በጣቱ ፡ ወስዶ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ቀንዶች ፡ ላይ ፡ ያደርገዋል ፥ ደሙንም ፡ ዥሉ ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፥ 4 ፥ 35 ፤ ስቡ ፡ ዥሉ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ከታረደው ፡ ጠቦት ፡ ላይ ፡ እንደሚወሰድ ፡ ስቢን ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡ በተቃጠለው ፡ ቍርባን ፡ ላይ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ። ካህኑም ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

——————————ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። ——————————

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 1 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚያምለውን ፡ ቃል ፡ ቢሰማ ፥ ምስክር ፡ ኾኖም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አይቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባይናገር ፥ ኀጢአት ፡ መሥራቱ ፡ ነውና ፥ በደሉን ፡ ይሸከማል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 2 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳይታወቀው ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ቢነካ ፥ የረከሰም ፡ አውሬ ፡ በድን ፥ ወይም ፡ የረከሰ ፡ ከብት ፡ በድን ፥ ወይም ፡ የረከሰ ፡ የተንቀሳቀሰ ፡ እንስሳ ፡ በድን ፡ ቢኾን ፥ ርሱም ፡ ርኩስ ፡ ቢኾን ፡ ነገሩ ፡ በታወቀው ፡ ጊዜ ፡ በደል ፡ ይኾንበታል ፤

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 3 ፤ ወይም ፡ ርኩስነቱን ፡ ሳያውቅ ፡ ርኩስን ፡ ሰው ፡ ቢነካ ፥ በማናቸውም ፡ ርኵሰት ፡ ቢረክስ ፥ ነገሩ ፡ በታወቀው ፡ ጊዜ ፡ በደል ፡ ይኾንበታል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡ ክፉን ፡ ወይም ፡ መልካምን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሳያስብ ፡ በከንፈሩ ፡ ተናግሮ ፡ ቢምል ፤ ሳያስብ ፡ የማለው ፡ ስለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፤ በታወቀው ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በአንዱ ፡ በደለኛ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ ከነዚህ ፡ ነገሮች ፡ በአንዲቱ ፡ በደለኛ ፡ ሲኾን ፥ የሠራውን ፡ ኀጢአት ፡ ይናዘዛል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ያመጣል ፤ ርሱም ፡ ከመንጋው ፡ የበግ ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ እንስት ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ይኾናል ፤ ካህኑም ፡ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ ያስተሰርይለታል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦትን ፡ ለማምጣት ፡ ገንዘቡ ፡ ያልበቃ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፥ አንዱን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለተኛውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ ወደ ፡ ካህኑም ፡ ያመጣቸዋል ፤ ርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የኾነውን ፡ ያቀርባል ፥ ራሱንም ፡ ከዐንገቱ ፡ ይቈለምመዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይቈርጠውም ።

ዘሌ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ ከኀጢአቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በመሠዊያው ፡ ግድግዳ ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤ የተረፈውም ፡ ደም ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ ይንጠፈጠፋል ፤ ርሱ ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ እንደ ፡ ሥርዐቱም ፡ ኹለተኛውን ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያዘጋጀዋል ። ካህኑም ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ ለማምጣት ፡ ገንዘቡ ፡ ያልበቃ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርበዋል ፤ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነውና ፥ ዘይት ፡ አያፈስበትም ፥ ዕጣንም ፡ አይጨምርበትም ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ካህኑም ፡ ያመጣዋል ፥ ካህኑም ፡ መታሰቢያው ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ዕፍኝ ፡ ሙሉ ፡ ይውሰድ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ በእሳት ፡ በተቃጠለው ፡ ቍርባን ፡ ላይ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ ርሱም ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ካህኑም ፡ ከነዚያ ፡ በአንዳቸው ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ። የተረፈውም ፡ እንደ ፡ እኽል ፡ ቍርባን ፡ ለካህኑ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢበድል ፥ ሳያውቅም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በተቀደሰው ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ኀጢአትን ፡ ቢሠራ ፥ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመንጋ ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያቀርባል ፤ እንደ ፡ ግምጋሜኽ ፡ መጠን ፡ በብር ፡ ሰቅል ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ በተቀደሰ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ዕዳ ፡ ይከፍላል ፥ ዐምስተኛውንም ፡ እጅ ፡ ይጨምርበታል ፥ ለካህኑም ፡ ይሰጠዋል ። ካህኑም ፡ በበደል ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፥ እግዚአብሔርም ፦ አትሥሩ ፡ ካላቸው ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ ቢተላለፍ ፥ ባያውቅም ፥ ያ ፡ ሰው ፡ በደለኛ ፡ ነው ፥ ኀጢአቱንም ፡ ይሸከማል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ከመንጋው ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ፡ ግምጋሜኽ ፡ መጠን ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያመጣዋል ፤ ካህኑም ፡ ሳያውቅ ፡ ስለሳተው ፡ ስሕተት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ርሱም ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ በእውነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በደለኛ ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ኀጢአትን ፡ ቢሠራ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ቢበድል ፥ ያኖረበትን ፡ ዐደራ ፡ ወይም ፡ ብድር ፡ ወስዶ ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢክድ ፥ ወይም ፡ ቢቀማ ፥ ወይም ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ቢያደርግ ፥

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ወይም ፡ የጠፋውን ፡ ነገር ፡ ቢያገኝ ፥ ያንንም ፡ ሸሽጎ ፡ በሐሰት ፡ ቢምል ፥ ሰው ፡ ከሚያደርጋቸው ፡ ከነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ በአንዲቱ ፡ ቢበድል ፥

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ርሱ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርቶ ፡ በደለኛ ፡ ቢኾን ፥ በቅሚያ ፡ የወሰደውን ፡ ወይም ፡ በግፍ ፡ የተቀበለውን ፡ ወይም ፡ የተሰጠውን ፡ ዐደራ ፡ ወይም ፡ ጠፍቶ ፡ ያገኘውን ፥

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ወይም ፡ በሐሰት ፡ የማለበትን ፡ ነገር ፡ ይመልስ ፤ በሙሉ ፡ ይመልስ ፥ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ዐምስተኛውን ፡ ክፍል ፡ ጨምሮ ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያቀርብበት ፡ ቀን ፡ ለባለገንዘቡ ፡ ይስጠው ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ስለበደል ፡ መሥዋዕትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመንጋው ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ እንደ ፡ ግምጋሜኽ ፡ መጠን ፡ ስለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያምጣ ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ስለዚያም ፡ ስላደረገው ፡ በደል ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ ይባላል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ የሚቃጠለው ፡ የመሥዋዕቱ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ እስከጸባ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ፤ እሳቱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ ይነዳል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ካህኑም ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስና ፡ የበፍታ ፡ ሱሪ ፡ በሥጋው ፡ ላይ ፡ ይለብሳል ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ እሳቱ ፡ ከበላው ፡ በኋላ ፡ ዐመዱን ፡ አንሥቶ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ልብሱንም ፡ ያወልቃል ፥ ሌላም ፡ ልብስ ፡ ይለብሳል ፤ ዐመዱንም ፡ ተሸክሞ ፡ ከሰፈሩ ፡ ንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ያወጣዋል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ እሳቱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ዘወትር ፡ ይነዳል ፥ አይጠፋም ፤ ካህኑም ፡ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ዕንጨት ፡ ያቃጥልበታል ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ይረበርባል ፤ በዚያም ፡ የደኅንነትን ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ ያቃጥላል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ዘወትር ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ፤ አይጠፋም ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ የእኽሉም ፡ ቍርባን ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የአሮን ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ያቀርቡታል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ መልካሙን ፡ ዱቄት ፡ ከዘይት ፡ ጋራ ፡ ዕፍኝ ፡ ሙሉ ፥ ደግሞም ፡ በእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዕጣን ፡ ኹሉ ፡ ያነሣል ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ለመታሰቢያ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ከርሱም ፡ የተረፈውን ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ይበሉታል ፤ ቂጣ ፡ ኾኖ ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይበላል ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዙሪያ ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ይበሉታል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ በርሾ ፡ ቦክቶ ፡ አይጋገርም ። ርሱን ፡ ከእሳቱ ፡ ቍርባኔ ፡ ለእነርሱ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንዲኾን ፡ ሰጠኹ ፤ ርሱም ፡ እንደ ፡ ኀጢአትና ፡ እንደ ፡ በደል ፡ መሥዋዕት ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ከቀረበ ፡ ከእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለዘለዓለም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ እንዲኾን ፡ ከአሮን ፡ ልጆች ፡ ወንዶቹ ፡ ኹሉ ፡ ይበሉታል ። የሚነካቸው ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ በተቀቡበት ፡ ቀን ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ መልካሙን ፡ ዱቄት ፡ እኩሌታውን ፡ በጧት ፥ እኩሌታውንም ፡ በማታ ፡ ለዘወትር ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ አድርገው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርቡት ፡ የአሮንና ፡ የልጆቹ ፡ ቍርባን ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ከዘይት ፡ ጋራ ፡ በምጣድ ፡ ላይ ፡ ይደረጋል ፤ ሲለወስ ፡ ታገባዋለኽ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ቈራርሰኽ ፡ ታቀርበዋለኽ ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ከልጆቹም ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ የተቀባው ፡ ካህን ፡ ያቀርበዋል ። ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኾን ፡ ፈጽሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቃጠላል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ካህኑም ፡ የሚያቀርበው ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃጠላል ፤ ከርሱም ፡ አንዳች ፡ አይበላም ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሚታረድበት ፡ ስፍራ ፡ የኀጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታረዳል ፤ ርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ ለኀጢአት ፡ የሚሠዋው ፡ ካህን ፡ ይበላዋል ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዙሪያ ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይበላል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ሥጋውን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ፤ ማናቸው ፡ ልብስ ፡ ደም ፡ ቢረጭበት ፡ የተረጨበትን ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ታጥበዋለኽ ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ የሚቀቀልበትም ፡ ሸክላ ፡ ይሰበራል ፤ በናስም ፡ ዕቃ ፡ ቢቀቀል ፡ ይፈገፈጋል ፥ በውሃም ፡ ይለቀለቃል ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ከካህናት ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ይበላል ፤ ርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ለማስተስረያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ከደሙ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የሚገባው ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፡ አይበላም ፤ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያርዱበት ፡ ስፍራ ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ያርዱታል ፤ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ስቡንም ፡ ኹሉ ፥ ላቱንም ፥ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፡ ያቀርበዋል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፥ በእነርሱም ፡ ላይና ፡ በጐድኑ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፥ በጕበቱም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መረብ ፡ ከኵላሊቶቹ ፡ ጋራ ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ካህኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ እንዲኾን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፤ ርሱ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ከካህናት ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ይበላዋል ፤ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይበሉታል ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲሁ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ ለኹለቱ ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ የሚያስተሰርይ ፡ ካህን ፡ ይወስደዋል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የማናቸውንም ፡ ሰው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ ካህን ፡ ያቀረበው ፡ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ቍርበት ፡ ለዚያው ፡ ካህን ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በእቶን ፡ የተጋገረው ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፥ በመቀቀያም ፡ ወይም ፡ በምጣድ ፡ የበሰለው ፡ ኹሉ ፡ ለሚያቀርበው ፡ ካህን ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ በዘይትም ፡ የተለወሰው ፡ ወይም ፡ የደረቀው ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ፤ ለኹሉም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ሰው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ለምስጋና ፡ ቢያቀርበው ፥ ከምስጋናው ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፥ በዘይትም ፡ የተቀባ ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፥ በዘይትም ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ለምስጋና ፡ የሚኾነውን ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ርሾ ፡ ያለበትን ፡ ኅብስት ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ከቍርባኑም ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ እንዲኾን ፡ ከነርሱ ፡ አንዱን ፡ ያነሣል ። ርሱም ፡ የደኅንነትን ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ለሚረጨው ፡ ካህን ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ለምስጋና ፡ የሚኾነው ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ በሚቀርብበት ፡ ቀን ፡ ይበሉታል ፤ ከርሱ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ምንም ፡ አያድርም ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ የቍርባኑም ፡ መሥዋዕት ፡ የስእለት ፡ ወይም ፡ የፈቃድ ፡ ቢኾን ፥ መሥዋዕቱ ፡ በሚቀርብበት ፡ ቀን ፡ ይብሉት ፤ ከርሱም ፡ የቀረውን ፡ በነጋው ፡ ይብሉት ፤

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ከመሥዋዕቱም ፡ ሥጋ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ የሚቈየው ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ አይሰምርም ፤ ላቀረበው ፡ ሰው ፡ የተጠላ ፡ ይኾንበታል ፡ እንጂ ፡ ቍርባን ፡ ኾኖ ፡ አይቈጠርለትም ፤ ከርሱም ፡ ቢበላ ፡ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ርኩስ ፡ ነገር ፡ የሚነካውን ፡ ሥጋ ፡ አይብሉት ፤ በእሳት ፡ ይቃጠል ። ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ከሥጋው ፡ ይብላ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሰውም ፡ የረከሰ ፡ ቢኾን ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ከኾነው ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ማናቸውንም ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ቢነካ ፥ የሰውን ፡ ወይም ፡ የረከሰን ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ሌላውን ፡ የተጠላ ፡ ርኩስን ፡ ቢነካ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ከኾነው ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሥጋ ፡ ቢበላ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ የበሬ ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ ስብ ፡ ከቶ ፡ አትብሉ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ የሞተውን ፡ ስብ ፥ አውሬ ፡ የሰበረውንም ፡ ስብ ፡ ለሌላ ፡ ተግባር ፡ አድርጉት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አትብሉ ፤

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡ ከሚቀርበው ፡ ከእንስሳ ፡ ስብ ፡ የሚበላ ፡ ኹሉ ፥ ያ ፡ የበላ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋልና ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ በማደሪያዎቻችኹም ፡ ኹሉ ፡ የወፍ ፡ ወይም ፡ የእንስሳ ፡ ደም ፡ ቢኾን ፡ አትብሉ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ደም ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ቸሉ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ ሰው ፡ ቍርባኑን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከደኅንነቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ያመጣል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ የርሱ ፡ እጆች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳቱን ፡ ቍርባን ፡ ያመጣሉ ፤ ፍርምባው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ይወዘውዝ ፡ ዘንድ ፡ ስቡንና ፡ ፍርምባውን ፡ ያመጣል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 31 ፤ ካህኑም ፡ ስቡን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥላል ፤ ፍርምባውም ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 32 ፤ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕታችኹ ፡ ቀኝ ፡ ወርቹን ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ እንዲኾን ፡ ለካህኑ ፡ ትሰጡታላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ ከአሮንም ፡ ልጆች ፡ የደኅንነትን ፡ መሥዋዕት ፡ ደሙንና ፡ ስቡን ፡ ለሚያቀርብ ፡ ለርሱ ፡ ቀኝ ፡ ወርቹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ የሚወዘወዘውን ፡ ፍርምባና ፡ የሚነሣውን ፡ ወርች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕታቸው ፡ ወስጃለኹ ፥ ለካህኑ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹም ፡ ለዘለዓለም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንዲኾን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ሰጥቻቸዋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በክህነት ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ ባቀረባቸው ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከኾነ ፡ ከእሳት ፡ ቍርባን ፡ የአሮንና ፡ የልጆቹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ እንዲኾን ፡ በቀባቸው ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፥ የኀጢአትና ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፥ የቅድስናና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ቍርባናቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ አሮንን ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ልጆቹን ፥ ልብሱንም ፥ የቅብዓቱንም ፡ ዘይት ፥ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕትም ፡ የኾነውን ፡ ወይፈን ፥ ኹለቱንም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ የቂጣውንም ፡ እንጀራ ፡ ሌማት ፡ ውሰድ ፤

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ማኅበሩንም ፡ ቸሉ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ሰብስባቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ማኅበሩ ፡ ቸሉ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ተሰበሰቡ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ሙሴም ፡ ማኅበሩን ፦ እግዚአብሔር ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ አቀረበ ፥ በውሃም ፡ ዐጠባቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ የደረት ፡ ልብስም ፡ አለበሰው ፥ በመታጠቂያም ፡ አስታጠቀው ፥ ቀሚስም ፡ አለበሰው ፥ ኤፉድም ፡ ደረበለት ፥ በብልኀትም ፡ በተጠለፈ ፡ ቋድ ፡ አስታጠቀውና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አሰረው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ የደረት ፡ ኪስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ በደረቱ ፡ ኪስም ፡ ውስጥ ፡ ኡሪምንና ፡ ቱሚምን ፡ አኖረበት ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መጠምጠሚያውን ፡ አደረገ ፤ በመጠምጠሚያውም ፡ ላይ ፡ በፊቱ ፡ በኩል ፡ የተቀደሰውን ፡ አክሊል ፥ ቅጠል ፡ የሚመስለውን ፡ የወርቅ ፡ ምልክት ፥ አደረገ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ሙሴም ፡ የቅብዓቱን ፡ ዘይት ፡ ወሰደ ፥ ማደሪያውንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ቀብቶ ፡ ቀደሳቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ከርሱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ረጨ ፤ ይቀድሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ መሠዊያውንና ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፥ የመታጠቢያውን ፡ ሰንና ፡ መቀመጫውን ፡ ቀባ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ከቅብዓቱም ፡ ዘይት ፡ በአሮን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፥ ይቀድሰውም ፡ ዘንድ ፡ ቀባው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ አቀረበ ፥ ቀሚሶችንም ፡ አለበሳቸው ፥ በመታጠቂያም ፡ አስታጠቃቸው ፥ ቆብም ፡ ደፋባቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ የኀጢአትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፡ አቀረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በኀጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ጫኑ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ዐረደውም ፤ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ ወስዶ ፡ በጣቱ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንዶች ፡ ዙሪያ ፡ ቀባ ፥ መሠዊያውንም ፡ አነጻው ፤ ደሙንም ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ አፈሰሰው ፥ ያስተሰርይለትም ፡ ዘንድ ፡ ቀደሰው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥ የጕበቱንም ፡ መረብ ፥ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ ስባቸውንም ፡ ወሰደ ፤ ሙሴም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ወይፈኑን ፥ ቍርበቱንም ፥ ሥጋውንም ፥ ፈርሱንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትም ፡ የሚኾን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አቀረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ጫኑ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ ዐረደውም ፤ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ረጨው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ በየብልቱ ፡ ቈረጠ ፤ ሙሴም ፡ ጭንቅላቱን ፡ ብልቶቹንም ፡ ስቡንም ፡ አቃጠለ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹንም ፡ በውሃ ፡ ዐጠበ ፤ ሙሴም ፡ አውራውን ፡ በግ ፡ ኹሉ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ፤ ይህ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ነበረ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ለቅድስናም ፡ የሚኾነውን ፡ ኹለተኛውን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አቀረበ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ጫኑ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ዐረደውም ፤ ሙሴን ፡ ከደሙ ፡ ወስዶ ፡ የአሮንን ፡ የቀኝ ፡ ጐሮውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጁንም ፡

አውራ ፡ ጣት ፡ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ አስነካው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ የአሮንንም ፡ ልጆች ፡ አቀረበ ፤ ሙሴም ፡ የቀኝ ፡ ጐሯቸውን ፡ ጫፍ ፥ የቀን ፡ እጃቸውንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፥ የቀኝ ፡ እግራቸውንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ከደሙ ፡ አስነካ ፤ ሙሴም ፡ ደሙን ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ረጨ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ስቡንና ፡ ላቱን ፥ በሆድ ፡ ዕቃውም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስብ ፡ ኹሉ ፥ የጕበቱንም ፡ መረብ ፥ ኹለቱንም ፡ ኵላሊቶች ፡ ስባቸውንም ፥ ቀኝ ፡ ወርቹንም ፡ ወሰደ ፤

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ካለው ፡ ከቂጣው ፡ እንጀራ ፡ ሌማት ፡ አንድ ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፥ አንድም ፡ የዘይት ፡ እንጀራ ፥ አንድም ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፡ ወስዶ ፡ በስቡና ፡ በቀኝ ፡ ወርቹ ፡ ላይ ፡ አኖራቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ኹሉንም ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ እጆች ፡ ላይ ፡ አደረገ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ወዘወዛቸው ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ሙሴም ፡ ከእጃቸው ፡ ተቀብሎ ፡ በመሠዊያው ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ፤ የጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ መቀደሻ ፡ ነበረ ። ርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ነበረ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፡ ፍርምባውን ፡ ወስዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ወዘወዘው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ይህ ፡ ለቅድስና ፡ ከታረደው ፡ አውራ ፡ በግ ፡ የሙሴ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ኾነ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ ከቅብዓቱ ፡ ዘይትና ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ከደሙ ፡ ወስዶ ፡ በአሮንና ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፥ በልጆቹና ፡ በልጆቹ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ረጨው ፤ አሮንንና ፡ ልብሱንም ፥ ልጆቹንም ፡ የልጆቹንም ፡ ልብስ ፡ ቀደሰ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ ሙሴም ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ አላቸው ፦ ሥጋውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ቀቅሉ ፤ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ይበሉታል ፡ ብዬ ፡ እንዳዘዝኹ ፡ በዚያ ፡ ርሱንና ፡ በሌማቱ ፡ ያለውን ፡ የቅድስናውን ፡ እንጀራ ፡ ብሉ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ከሥጋውና ፡ ከእንጀራውም ፡ የተረፈውን ፡ በእሳት ፡ ታቃጥሉታላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይክናችኋልና ፥ የክህነታችኹ ፡ ቀን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከማኅበሩ ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አትውጡ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ለእናንተ ፡ ለማስተስረያ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ አዞኛልና ፥ እንዳትሞቱ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ሌሊቱንና ፡ ቀኑን ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥርዐት ፡ ጠብቁ ።

ዘሌ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ አሮንና ፡ ልጆቹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ የእስራኤልንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጠራ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ አሮንንም ፡ አለው ፦ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ከመንጋው ፡ እንቦሳውን ፥ ስለሚቃጠልም ፡

መሥዋዕት ፡ አውራውን ፡ በግ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ወስደኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቅርባቸው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 3-4 ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፦ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይገለጥላችኋልና ፥ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ ፍየልን ፥ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የኾናቸውን ፡ እንቦሳና ፡ ጠቦትን ፥ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ በሬንና ፡ አውራን ፡ በግ ፥ በዘይትም ፡ የተለወሰ ፡ የእኽልን ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፡ ውሰዱ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ሙሴም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አመጡ ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ቀርበው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፦ ታደርጉት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ይገለጥላችኋል ፡ አለ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ቀርበኽ ፡ የኀጢአትኽን ፡ መሥዋዕትና ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትኽን ፡ ሠዋ ፥ ለራስኽና ፡ ለሕዝቡም ፡ አስተስርይ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘ ፡ የሕዝቡን ፡ ቍርባን ፡ አቅርብ ፡ አስተስርይላቸውም ፡ አለው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ አሮንም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ቀርቦ ፡ ስለራሱ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የኾነውን ፡ እንቦሳ ፡ ዐረደ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አቀረቡለት ፤ ጣቱንም ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነክሮ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንዶች ፡ አስነካ ፥ ደሙንም ፡ ከመሠዊያው ፡ በታች ፡ አፈሰሰው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ከኀጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ስቡንና ፡ ኵላሊቶቹን ፥ የጕበቱንም ፡ መረብ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ሥጋውንና ፡ ቍርበቱንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ዐረደ ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አመጡለት ፥ ርሱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ረጨው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በየብልቱ ፥ ራሱንም ፡ አመጡለት ፤ ርሱም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ የሆድ ፡ ዕቃውንና ፡ እግሮቹንም ፡ ዐጠበ ፤ በመሠዊያውም ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ የሕዝቡንም ፡ ቍርባን ፡ አቀረበ ፤ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የኾነውን ፡ ፍየል ፡ ወስዶ ፡ ዐረደው ፥ ስለ ፡ ኀጢአትም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ሠዋው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፥ እንደ ፡ ሥርዐቱም ፡ አደረገው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ አቀረበ ፥ ከርሱም ፡ ዕፍኝ ፡ ሙሉ ፡ ወስዶ ፡ በጧት ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለው ።

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ የኾነውን ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ በሬውንና ፡ አውራውን ፡ በግ ፡ ዐረደ ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ደሙን ፡ አመጡለት ፥

ዘሌ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ረጨው ፤ የበሬውንና ፡ የአራውንም ፡ በግ ፡

ስብ ፥ ላቱንም ፥ የሆድ ፡ ዕቃውንም ፡ የሚሸፍነውን ፡ ስብ ፥ ኵላሊቶቹንም ፥ የጕበቱንም ፡ መረብ ፡ አመጡለት ።

ዘሌ. ፥ 9 ፥ 20 ፤ ስቡንም ፡ በፍርምባዎቹ ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፥ ስቡንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ፤

ዘሌ. ፥ 9 ፥ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አሮን ፡ ፍርምባዎቹንና ፡ ቀኝ ፡ ወርቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ወዘወዘው ።

ዘሌ. ፥ 9 ፥ 22 ፤ አሮንም ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ዘረጋ ፡ ባረካቸውም ፤ የኀጢአቱን ፡ የሚቃጠለውንም ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ከሠዋ ፡ በኋላ ፡ ወረደ ።

ዘሌ. ፥ 9 ፥ 23 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ገቡ ፤ ወጡም ፥ ሕዝቡንም ፡ ባረኩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ተገለጠ ።

ዘሌ. ፥ 9 ፥ 24 ፤ እሳትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ስቡንም ፡ በላ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አይተው ፡ እልል ፡ አሉ ፥ በግንባራቸውም ፡ ወደቁ ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ በየራሳቸው ፡ ጥናውን ፡ ወስደው ፡ እሳት ፡ አደረጉበት ፥ በላዩም ፡ ዕጣን ፡ አኖሩበት ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ርሱ ፡ ያላዘዛቸውን ፡ ሌላ ፡ እሳት ፡ አቀረቡ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ እሳትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጥቶ ፡ በላቸው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሞቱ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ እግዚአብሔር ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ በሚቀርቡ ፡ እቀድሳለኹ ፥ በሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ እከብራለኹ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለው ፤ አሮንም ፡ ዝም ፡ አለ ፡

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ ሙሴም ፡ የአሮንን ፡ አጎት ፡ የዑዝኤልን ፡ ልጆች ፡ ሚሳኤልንና ፡ ኤልጻፋንን ፡ ጠርቶ ፦ ቅረቡ ፥ ወንድሞቻችኹንም ፡ ከመቅደሱ ፡ ፊት ፡ አንሥታችኹ ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ውሰዷቸው ፡ አላቸው ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ እነርሱም ፡ ቀርበው ፡ አነሧቸው ፥ ሙሴም ፡ እንዳለ ፡ በቀሚሳቸው ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወሰዷቸው ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፥ ልጆቹንም ፡ አልዓዛርንና ፡ ኢታምርን ፦ እንዳትሞቱ ፡ በማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይወርድ ፡ ራሳችኹን ፡ አትንጨ ፥ ልብሳችኹንም ፡ አትቅደዱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስላቃጠለው ፡ ማቃጠል ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ያልቅሱ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ የቅብዐት ፡ ዘይት ፡ በላያችኹ ፡ ነውና ፥ እንዳትሞቱ ፡ ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አትወጡም ፡ አላቸው ። እንደ ፡ ሙሴ ፡ ቃልም ፡ አደረጉ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ እንዳትሞቱ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ስትገቡ ፡ አንተና ፡ ልጆችኽ ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ የሚያሰክርን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አትጠጡ ፤ ይህም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ፤

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ በተቀደሰውና ፡ ባልተቀደሰው ፥ በርኩሱና ፡ በንጹሑም ፡ መካከል ፡ ትለያላችኹ ፤

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ ቃል ፡ የነገራቸውን ፡ ሥርዐት ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ታስተምራላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፥ የተረፉለትንም ፡ ልጆቹን ፡ አልዓዛርንና ፡ ኢታምርን ፡ አላቸው ፦ ቅዱሰ ፡

ቅዱሳን ፡ ነውና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ከኾነው ፡ ከእሳት ፡ ቍርባን ፡ የቀረውን ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ውሰዱ ፥ ቂጣም ፡ አድርጋችኹ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ብሉት ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አዞኛል ፥

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 13 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ከኾነው ፡ ከእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለአንተም ፡ ለልጆችኽም ፡ የተሰጠ ፡ ሥርዐት ፡ ነውና ፥ በቅዱስ ፡ ስፍራ ፡ ትበሉታላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ እነዚህም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕቶች ፡ ለአንተና ፡ ለልጆችኽ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኾኑ ፡ ስለ ፡ ተሰጡ ፥ የሚወዘወዘውን ፡ ፍርምባ ፥ የሚነሣውንም ፡ ወርች ፡ አንተ ፥ ከአንተ ፡ ጋራም ፡ ልጆችኽ ፥ ሴቶች ፡ ልጆችኽም ፡ በንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ትበላላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ የሚነሣውን ፡ ወርች ፡ የሚወዘወዘውንም ፡ ፍርምባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ እንዲወዘውዙ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ከኾነው ፡ ስብ ፡ ጋራ ፡ ያመጣሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተ ፡ ጋራም ፡ ለልጆችኽ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 16 ፤ ሙሴም ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡ እጅግ ፡ ፈለገው ፥ እንሆም ፡ ተቃጥሎ ፡ ነበር ፤ ሙሴም ፡ የቀሩትን ፡ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ አልዐዛርንና ፡ ኢታምርን ፡ ተቈጥቶ ፦

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 17 ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነውና ፥ የሕዝቡንም ፡ ኀጢአት ፡ እንድትሸከሙ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ እንድታስተሰርዩላቸው ፡ ለእናንተ ፡ ሰጥቶታልና ፥ ስለ ፡ ምን ፡ የኀጢአትን ፡ መሥዋዕት ፡ በቅዱሱ ፡ ስፍራ ፡ አልበላችኹም ፧

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 18 ፤ እንሆ ፥ ደሙን ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አላገባችኹትም ፤ እኔ ፡ እንዳዘዝኹ ፡ በቅዱሱ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ትበሉት ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኹ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 19 ፤ አሮንም ፡ ሙሴን ፦ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ የኀጢአታቸውን ፡ መሥዋዕት ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ፤ ይህም ፡ ኾሉ ፡ ደረሰብኝ ፤ ዛሬስ ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ በበላኹ ፡ ኖሮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ ኖሯልን ፧ አለው ።

ዘሌ. ፥ 10 ፥ 20 ፤ ሙሴም ፡ ሰማ ፡ በፊቱም ፡ መልካም ፡ ኾነ ።

———————ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። ———————

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በሏቸው ፦ ከምድር ፡ እንስሳዎች ፡ ኾሉ ፡ የምትበሏቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ የተሠነጠቀ ፡ ሰኰና ፡ ያለውንና ፡ የሚያመሰኳውን ፡ እንስሳ ፡ ኾሉ ፡ ብሉ ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሚያመሰኩት ፥ ሰኰናቸው ፡ ስንጥቅ ፡ ከኾነው ፡ ከነዚህ ፡ አትበሉም ፤ ግመል ፡ ያመሰኳል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሰኰናው ፡ ስላልተሠነጠቀ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ ሽኮኮ ፡ ያመሰኳል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሰኰናው ፡ ስላልተሠነጠቀ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ ጥንቸልም ፡ ያመሰኳል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሰኰናው ፡ ስላልተሠነጠቀ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ ዕሪያም ፡ ሰኰናው ፡ ተሰንጥቋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለማያመሰኳ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ የእነዚህን ፡ ሥጋ ፡ አትበሉም ፥ በድናቸውንም ፡ አትነኩም ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ እነዚህን ፡ ትበላላችኹ ፡ በውሃዎች ፡ በባሕሮችም ፡ በወንዞችም ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ክንፍና ፡ ቅርፊት ፡ ያላቸውን ፡ ትበላላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በውሃዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ከሚንቀሳቀሱ ፥ በውሃዎች ፡ ውስጥ ፡ የሕይወት ፡ ነፍስ ፡ ካላቸው ፡ ኹሉ ፥ በባሕሮችና ፡ በወንዞች ፡ ውስጥ ፡ ክንፍና ፡ ቅርፊት ፡ የሌላቸው ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፉ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፉ ፡ ይኾናሉ ፤ ሥጋቸውንም ፡ አትበሉም ፥ በድናቸውንም ፡ ትጸየፋላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ክንፍና ፡ ቅርፊትም ፡ የሌላቸው ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፉ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ከወፎችም ፡ ወገን ፡ የምትጸየፏቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ አይበሉም ፤ የተጸየፉ ፡ ናቸው ፤

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ንስር ፥ ገዲ ፥ ዓሣ ፡ አውጫ ፥ ጭላት ፥ ጭልፊት ፡ በየወገኑ ፥

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ቀጐራ ፡ ኹሉ ፡ በየወገኑ ፥

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ሰገሦን ፥ ጠላቋ ፥ ዝዩ ፥ በቋል ፡ በየወገኑ ፥

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 17-18 ፤ ጕጕት ፥ ርኩም ፥ ጋጋኖ ፥ የውሃ ፡ ዶሮ ፥

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ይብራ ፥ ጥምብ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ፥ ሽመላ ፥ ሳቢሳ ፡ በየወገኑ ፥ ጃንጁላቴ ፡ ወፍ ፥ የሌሊት ፡ ወፍ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ የሚበርም ፥ በአራት ፡ እግሮችም ፡ የሚኼድ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፈ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሚበሩት ፥ አራትም ፡ እግሮች ፡ ካሏቸው ፥ ከእግሮቻቸውም ፡ በላይ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚዘሉባቸው ፡ ጭኖች ፡ ካሏቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ እነዚህን ፡ ትበላላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ከነርሱም ፡ እነዚህን ፡ ትበላላችኹ ፤ አራቱን ፡ ዐይነት ፡ አንበጣዎች ፡ በየወገናቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚበር ፥ አራትም ፡ እግሮች ፡ ያሉት ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተጸየፈ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ በእነዚህም ፡ ርኩስ ፡ ትኾናላችኹ ፤ የእነርሱንም ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ከነርሱም ፡ በድን ፡ የሚያነሣ ፡ ኹሉ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ሰኮናም ፡ ያለው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሰኮናው ፡ ያልተሠነጠቀ ፥ የማያመሰኳም ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ርሱን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ በአራት ፡ እግሮቹ ፡ ከሚኼድ ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ በመዳፎቹ ፡ ላይ ፡ የሚኼድ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የርሱን ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ በድናቸውንም ፡ የሚያነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ በምድር ፡ ላይም ፡ ከሚንቀሳቀስ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ እነዚህ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ፤ ሙጭልጭላ ፥ ዐይጥ ፥ እንሽላሊት ፡ በየወገኑ ፥

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ኤሊ ፥ ዐዞ ፥ ገበሎ ፥ አርጃኖ ፥ ዕሥሥት ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ከሚንቀሳቀሱት ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ የሚኾኑ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ከነርሱም ፡ የሞተውን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ ከነርሱም ፡ የሞተውን ፡ የሚነካ ፡ በምንም ፡ ላይ ፡ ቢወድቅ ፡ ርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የዕንጨት ፡ ዕቃ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ቀሚበት ፡ ወይም ፡ ከረጢት ፡ ቢኾን ፡ የሚሠራበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ይደረግ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳች ፡ በውስጡ ፡ የወደቀበትን ፡ የሸክላውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ስበሩት ፥ በውስጡም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፥ ውሃም ፡ የሚፈስበት ፡ የሚበላ ፡ መብል ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ በዚህም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ያለው ፡ የሚጠጣ ፡ መጠጥ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ከነዚህም ፡ በድን ፡ የሚወድቅበት ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ እቶን ፡ ወይም ፡ ምድጃ ፡ ቢኾን ፡ ይሰባበራል ፤ ርኩሶች ፡ ናቸው ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩሶች ፡ ይኾናሉ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምንጭ ፥ ጕድጓዱም ፥ የውሃውም ፡ ኩሬ ፡ ንጹሕን ፡ ናቸው ፤ በድናቸውን ፡ ግን ፡ የሚነካ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 37 ፤ ከበድናቸውም ፡ በሚዘራ ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢወድቅ ፡ ርሱ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 38 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዘሩ ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ቢፈስበት ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከበድናቸው ፡ አንዳች ፡ ቢወድቅበት ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 39 ፤ ለመብል ፡ ከሚኾኑላችኹ ፡ እንስሳዎች ፡ የሞተ ፡ ቢኖር ፥ በድኑን ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 40 ፤ ከበድኑም ፡ የሚበላ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ በድኑንም ፡ የሚያነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 41 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ የተጸየፈ ፡ ነው ፥ አትብሉትም ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 42 ፤ በሆዱ ፡ የሚሳብ ፥ በአራትም ፡ እግሮች ፡ የሚሳብ ፥ ብዙ ፡ እግሮችም ፡ ያሉት ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ኹሉ ፡ የተጸየፉ ፡ ናቸውና ፥ አትብሏቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 43 ፤ በሚንቀሳቀሱ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ኹሉ ፡ ሰውነታችኹን ፡ አታስጸይፉ ፤ በእነርሱም ፡ እንዳትረክሱ ፡ ሰውነታችኹን ፡ አታርክሱባቸው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 44 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝና ፤ ሰውነታችኹን ፡ ቀድሱ ፥ ቅዱሳንም ፡ ኹኑ ፥ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ በሚሳብ ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ ሰውነታችኹን ፡ አታርክሱ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 45 ፤ እኔ ፡ አምላካችኹ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ እናንተ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 46 ፤ የእንስሳና ፡ የወፍ ፥ በውሃም ፡ ውስጥ ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ የፍጥረት ፡ ኹሉ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡

የሚንቀሳቀስ ፡ የፍጥረት ፡ ሹሉ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 11 ፡ 47 ፤ በርኩስና ፡ በንጹሕ ፡ መካከል ፥ የሕይወት ፡ ነፍስ ፡ ካላቸውም ፡ በምትበሉትና ፡ በማትበሉት ፡ መካከል ፡ እንድትለዩ ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ሴት ፡ ብታረግዝ ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ብትወልድ ፥ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ የረከሰች ፡ ናት ፤ እንደ ፡ ሕመሟ ፡ መርገም ፡ ወራት ፡ ትረክሳለች ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ልጁ ፡ ከሥጋው ፡ ሸለፈት ፡ ይገረዝ ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ከደሟም ፡ እስክትነጻ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ትቀመጥ ፤ የመንጻቷ ፡ ቀንም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የተቀደሰን ፡ ነገር ፡ አትንካ ፥ ወደ ፡ መቅደስም ፡ አትግባ ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ሴት ፡ ልጅም ፡ ብትወልድ ፡ እንደ ፡ መርገሟ ፡ ወራት ፡ ኹለት ፡ ሳምንት ፡ ያኽል ፡ የረከሰች ፡ ናት ፤ ከደሟም ፡ እስክትነጻ ፡ ድረስ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ትቀመጥ ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የመንጻቷ ፡ ወራትም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ ለወንድ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፡ ልጅ ፥ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ጠቦት ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ የርግብም ፡ ግልገል ፡ ወይም ፡ ዋኖስ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ታምጣለት ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርበዋል ፡ ያስተሰርይላትማል ፤ ከደሟም ፡ ፈሳሽ ፡ ትነጻለች ። ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ለምትወልድ ፡ ሴት ፡ ሕጉ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ጠቦት ፡ ለማምጣት ፡ ገንዘቧ ፡ ያልበቃት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፥ አንዱን ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላውንም ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባለች ፤ ካህኑም ፡ ያስተሰርይላታል ፥ ርሷም ፡ ትነጻለች ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። _____

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በሥጋው ፡ ቍርበት ፡ ላይ ፡ ዕባጭ ፡ ወይም ፡ ብጉር ፡ ወይም ፡ ቋቍቻ ፡ ቢታይ ፥ በሥጋው ፡ ቍርበት ፡ እንደ ፡ ለምጽ ፡ ደዌ ፡ ቢመስል ፥ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ወይም ፡ ከካህናቱ ፡ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ያምጡት ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ካህኑም ፡ በሥጋው ፡ ቍርበት ፡ ያለውን ፡ ደዌ ፡ ያያል ፤ ጠጕሩም ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፡ ደዌውም ፡ ወደሥጋው ፡ ቍርበት ፡ ቢጠልቅ ፥ ርሱ ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ካህኑም ፡ አይቶ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይበለው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ቋቍቻውም ፡ በሥጋው ፡ ቍርበት ፡ ላይ ፡ ቢነጣ ፥ ከቍርበቱም ፡ የጠለቀ ፡ ባይመስል ፥ ጠጕሩም ፡ ባይነጣ ፥ ካህኑ ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ቢኾን ፥ በቍርበቱም ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፥ ካህኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ደግሞ ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ ቢከስም ፥ ደዌውም ፡ በቍርበቱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፥ ካህኑ ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ዕከክ ፡ ነው ፤ ልብሱንም ፡ ዐጥቦ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ መንጻቱ ፡ በካህኑ ፡ ዘንድ ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ ዕከኩ ፡ በቀሩበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ሊታይ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ይቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ካህኑም ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ዕከኩ ፡ በቀሩበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፥ ካህኑ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ለምጽ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ በሰው ፡ ውስጥ ፡ ቢኾን ፡ ርሱን ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያመጡለታል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ካህኑም ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ በቀሩበቱ ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ዕባጭ ፡ ቢኾን ፥ ጠጕሩም ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፥ ሥጋውም ፡ በዕባጩ ፡ ውስጥ ፡ ቢያኘ ፥

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ርሱ ፡ በሥጋው ፡ ቀሩበት ፡ ላይ ፡ አሮጌ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፥ ካህኑም ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፥ አይዘጋበትም ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ለምጹም ፡ በቀሩበቱ ፡ ላይ ፡ ሰፍቶ ፡ ቢወጣ ፥ ለምጹም ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፡ ቀሩበቱን ፡ ኹሉ ፡ ከራሱ ፡ እስከ ፡ እግሮቹ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ከደነው ፡ ለካህኑ ፡ ቢመስለው ፥ ካህኑ ፡ ያያል ፤

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ እንሆም ፥ ለምጹ ፡ ሥጋውን ፡ ኹሉ ፡ ቢከድን ፡ የታመመውን ፡ ሰው ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ሥጋው ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ተለውጦ ፡ ነጭ ፡ ኾኗል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ የሚያገፐው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ሲታይበት ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ የሚያገፐውን ፡ ሥጋ ፡ አይቶ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ የሚያገፐው ፡ ሥጋ ፡ ለምጽ ፡ ነውና ፥ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ የሚያገፐውም ፡ ሥጋ ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ይመጣል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ካህኑም ፡ ያየዋል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ ቢነጣ ፡ ካህኑ ፡ የታመመውን ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ በሥጋውም ፡ ቀሩበት ፡ ላይ ፡ ቀስል ፡ ቢኾንና ፡ ቢሸር ፥

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ በቀስሉም ፡ ስፍራ ፡ ነጭ ፡ ዕባጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቋቀቻ ፡ ቢወጣ ፥ በካህኑ ፡ ዘንድ ፡ ይታያል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ካህኑም ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ወደ ፡ ቀሩበቱ ፡ ውስጥ ፡ ጠልቆ ፡ ቢታይ ፥ ጠጕሩም ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፥ ካህኑ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ከቀስሉ ፡ ውስጥ ፡ ወጥቷል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ካህኑም ፡ ቢያየው ፥ ነጭም ፡ ጠጕር ፡ ባይኖርበት ፥ ወደ ፡ ቀሩበቱም ፡ ውስጥ ፡ ባይጠልቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ቢከስም ፥ ካህኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ በቀሩበቱም ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፥ ካህኑ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ደዌ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ቋቀቻው ፡ ግን ፡ በስፍራው ፡ ቢቆም ፡ ባይሰፋም ፥ የቀስል ፡ ጠባሳ ፡ ነው ፤ ካህኑም ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ በሥጋውም ፡ ቀሩበት ፡ የእሳት ፡ ትኵሳት ፡ ቢኖርበት ፥ በተቃጠለውም ፡ ስፍራ ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቋቀቻ ፡ ቢታይ ፥

ዘሌ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤ እንሆም ፥ በቋቀቻው ፡ ጠጕሩ ፡ ተለውጦ ፡ ቢነጣ ፥ ወደ ፡ ቀሩበቱም ፡

ውስጥ ፡ ቢጠልቅ ፥ ለምጽ ፡ ነው ፤ ከተቃጠለውም ፡ ስፍራ ፡ ወጥቷል ፤ ካህኑም ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 26 ፤ ካህኑም ፡ ቢያየው ፥ በቋቀቻውም ፡ ነጭ ፡ ጠጕር ፡ ባይኖር ፥ ወደ ፡ ቀኑርበቱም ፡ ባይጠልቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ቢከስም ፥ ካህኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 27 ፤ ካህኑም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ያየዋል ፤ በቀኑርበቱም ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፡ ካህኑ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 28 ፤ ቋቀቻውም ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ ቢቆም ፥ በቀኑርበቱም ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ቢከስም ፥ የትኵሳት ፡ ዕባጭ ፡ ነው ፤ የትኵሳትም ፡ ጠባሳ ፡ ነውና ፥ ካህኑ ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 29 ፤ ማናቸውም ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ በራሱ ፡ ወይም ፡ በአገጩ ፡ ደዌ ፡ ቢኖርበት ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 30 ፤ ካህኑ ፡ ደዌውን ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ወደ ፡ ቀኑርበቱ ፡ ቢጠልቅ ፥ በውስጡም ፡ ቀጭን ፡ ብጫ ፡ ጠጕር ፡ ቢኖርበት ፥ ካህኑ ፦ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ቈረቈር ፡ ነው ፤ የራስ ፡ ወይም ፡ የአገጭ ፡ ለምጽ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 31 ፤ ካህኑም ፡ የቈረቈሩን ፡ ደዌ ፡ ቢያይ ፥ ወደ ፡ ቀኑርበቱም ፡ ባይጠልቅ ፥ ጥቀኵርም ፡ ጠጕር ፡ ባይኖርበት ፥ ካህኑ ፡ የቈረቈር ፡ ደዌ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 32 ፤ ካህኑም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ደዌውን ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ቈረቈሩ ፡ ባይሰፋ ፥ በውስጡም ፡ ብጫ ፡ ጠጕር ፡ ባይኖር ፥ የቈረቈሩም ፡ መልክ ፡ ወደ ፡ ቀኑርበቱ ፡ ባይጠልቅ ፥ ይላጫል ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 33 ፤ ቈረቈሩ ፡ ግን ፡ አይላጭም ፤ ካህኑም ፡ ቈረቈር ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 34 ፤ ካህኑም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ቈረቈሩን ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ቈረቈሩ ፡ በቀኑርበቱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፥ መልኩም ፡ ወደ ፡ ቀኑርበቱ ፡ ባይጠልቅ ፥ ካህኑ ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ልብሱን ፡ ዐጥቦ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 35 ፤ ከነጻ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ቈረቈሩ ፡ በቀኑርበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፥ ካህኑ ፡ ያየዋል ፤

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 36 ፤ እንሆም ፥ ቈረቈሩ ፡ በቀኑርበቱ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፡ ካህኑ ፡ ብጫውን ፡ ጠጕር ፡ አይፈልግም ፤ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 37 ፤ ቈረቈሩ ፡ ግን ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ቢኾን ፥ ጥቀኵርም ፡ ጠጕር ፡ በበቅልበት ፥ ቈረቈሩ ፡ ሸሯል ፡ ርሱም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ ካህኑም ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 38 ፤ ማናቸውም ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ በሥጋው ፡ ቀኑርበት ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ቋቀቻ ፡ ቢኖርበት ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 39 ፤ ካህኑ ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ በሥጋቸው ፡ ቀኑርበት ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ቋቀቻ ፡ ፈገግ ፡ ቢል ፡ አጓጐት ፡ ነው ፤ ከቀኑርበቱ ፡ ውስጥ ፡ ወጥቷል ፤ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 40 ፤ የሰውም ፡ ጠጕር ፡ ከራሱ ፡ ቢመለጥ ፡ ርሱ ፡ ቡሓ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 41 ፤ ጠጕሩም ፡ ከግንባሩ ፡ ቢመለጥ ፡ ርሱ ፡ ራሰ ፡ በራ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንጹሕ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 42 ፤ በቡሓነቱ ፡ ወይም ፡ በራሰ ፡ በራነቱ ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ደዌ ፡ ቢኖርበት ፥ ርሱ ፡ ከቡሓነቱ ፡ ወይም ፡ ከራሰ ፡ በራነቱ ፡ የወጣ ፡ ለምጽ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 43 ፤ ካህኑም ፡ ያየዋል ፤ እንሆም ፥ የደዌው ፡ ዕብጠት ፥ በሥጋው ፡ ቀኑርበት ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡ ለምጽ ፡

መስሎ ፥ በቡሓነቱ ፡ ወይም ፡ በራሰ ፡ በራነቱ ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ቀላ ፡ ያለ ፡ ቢኾን ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 44 ፤ ለምጻም ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ርኩስ ፡ ነው ፤ ካህኑ ፦ በርግጥ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ይለዋል ፤ ደዌው ፡ በራሱ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 45 ፤ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ልብሱ ፡ የተቀደደ ፡ ይኹን ፥ ራሱም ፡ የተገለጠ ፡ ይኹን ፥ ከንፈሩንም ፡ ይሸፍን ፤ ርኩስ ፡ ርኩስ ፡ ነኝ ፡ ይበል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 46 ፤ ደዌው ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ ርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ብቻውን ፡ ይቀመጣል ፤ መኖሪያውም ፡ ከሰፈር ፡ በውጭ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 47 ፤ የለምጽም ፡ ደዌ ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፥ ልብሱም ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ወይም ፡ በፍታ ፡ ቢኾን ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 48 ፤ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፥ በፍታ ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ቢኾን ፥ ዐገሣ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣ ፡ የሚደረግ ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 49 ፤ ደዌው ፡ በልብሱ ፡ ወይም ፡ በዐገሣው ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ በሚደረገው ፡ ነገር ፡ አረንጓዴ ፡ ወይም ፡ ቀይ ፡ ቢኾን ፥ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ነው ፤ ለካህኑ ፡ ይታያል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 50 ፤ ካህኑም ፡ ደዌውን ፡ አይቶ ፡ ደዌው ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 51 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ደዌውን ፡ ያያል ፤ ደዌውም ፡ በልብስ ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ በዐገሣው ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ በሚደረግ ፡ ነገር ፡ ቢሰፋ ፥ ደዌው ፡ እየፋገ ፡ የሚኼድ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፤ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 52 ፤ ልብሱን ፡ ያቃጥል ፤ ድሩ ፡ ወይም ፡ ማጉ ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ወይም ፡ በፍታ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ የተደረገ ፡ ቢኾን ፥ ደዌ ፡ ያለበት ፡ ኹሉ ፥ እየፋገ ፡ የሚኼድ ፡ ለምጽ ፡ ነውና ፥ በእሳት ፡ ይቃጠል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 53 ፤ ካህኑ ፡ ቢያይ ፥ እንሆም ፥ ደዌው ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣ ፡ በተደረገ ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፡ ባይሰፋ ፥

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 54 ፤ ካህኑ ፡ ደዌ ፡ ያለበቱ ፡ ነገር ፡ እንዲታጠብ ፡ ይዘዝ ፤ ሌላም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይዘጋበታል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 55 ፤ ደዌውም ፡ ከታጠበ ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ መልኩን ፡ ባይለውጥ ፡ ባይሰፋም ፥ ርኩስ ፡ ነው ፤ በእሳት ፡ አቃጥለው ፤ ምልክቱ ፡ በውስጥ ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ ቢኾን ፡ እየፋገ ፡ የሚኼድ ፡ ደዌ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 56 ፤ ካህኑም ፡ ቢያይ ፥ እንሆም ፥ ደዌው ፡ ከታጠበ ፡ በኋላ ፡ ቢከስም ፥ ከልብሱ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ ወይም ፡ ከድሩ ፡ ወይም ፡ ከማጉ ፡ ይቅደደው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 57 ፤ በልብሱም ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ በተደረገ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ቢታይ ፥ የወጣ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፤ ደዌው ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ አቃጥለው ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 58 ፤ አንተም ፡ ካጠብኸው ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ ከድሩ ፡ ወይም ፡ ከማጉ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣው ፡ ከተደረገው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ደዌው ፡ ቢጠፋ ፥ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይታጠባል ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 13 ፥ 59 ፤ በበግ ፡ ጠጕር ፡ ልብስ ፡ ወይም ፡ በበፍታ ፡ ወይም ፡ በድሩ ፡ ወይም ፡ በማጉ ፡ ወይም ፡ ከዐገሣ ፡ በተደረገ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፥ ንጹሕ ፡ ወይም ፡ ርኩስ ፡ ያሠኝ ፡ ዘንድ ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ በመንጻቱ ፡ ቀን ፡ የለምጻሙ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ይኾናል ፤ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ይወስዱታል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ካህኑም ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣል ፤ ካህኑም ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ የለምጹ ፡ ደዌ ፡ ከለምጻሙ ፡ ላይ ፡ ቢጠፋ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ካህኑ ፡ ስለሚነጻው ፡ ሰው ፡ ኹለት ፡ ንጹሓን ፡ ወፎች ፡ በሕይወታቸው ፥ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፥ ቀይ ፡ ግምጃም ፥ ሂሶጵም ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያዛል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ካህኑም ፡ ከኹለቱ ፡ ወፎች ፡ አንዱን ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ ያርድ ፡ ዘንድ ፡ ይዛል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ዝግባውንም ፡ ዕንጨት ፡ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፡ ሂሶጹንም ፡ ወስዶ ፡ ከሕያው ፡ ወፍ ፡ ጋራ ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ላይ ፡ በታረደው ፡ ወፍ ፡ ደም ፡ ውስጥ ፡ ይነክራቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ከለምጹ ፡ በሚነጻው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጫል ፤ ንጹሕም ፡ ነው ፡ ይለዋል ፥ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ይለቀዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ የነጻውም ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ጠጕሩንም ፡ ሹሉ ፡ ይላጫል ፥ በውሃም ፡ ይታጠባል ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይገባል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከድንኳኑ ፡ በውጭ ፡ ኾኖ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይቀመጣል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ጠጕሩን ፡ ሹሉ ፡ ይላጫል ፤ ራሱንም ፥ ጢሙንም ፥ ቅንድቡንም ፥ የገላውንም ፡ ጠጕር ፡ ሹሉ ፡ ይላጫል ፤ ልብሱንም ፥ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ያጥባል ፤ ንጹሕም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ኹለት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፥ ነውር ፡ የሌለባትንም ፡ አንዲት ፡ የዓመት ፡ እንስት ፡ ጠቦት ፥ ስለእኽልም ፡ ቍርባን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ የኾነ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ አንድ ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ የሚያነጻውም ፡ ካህን ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ የሚነጻውንም ፡ ሰው ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያኖራቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ካህኑም ፡ አንዱን ፡ ጠቦት ፡ ወስዶ ፡ ስለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርበዋል ፥ ያንንም ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፤ ስለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዘውዘዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ የኀጢአትን ፡ መሥዋዕትና ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያርዱበት ፡ በተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ ጠቦቱን ፡ ያርደዋል ፤ የኀጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ለካህኑ ፡ እንደሚኾን ፥ እንዲሁ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ፤ ቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ካህኑም ፡ ከበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጕሮውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፥ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ያስነካዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ ከዘይቱ ፡ ከሎግ ፡ መስፈሪያው ፡ ወስዶ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ካህኑም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ ዘይት ፡ ቀኝ ፡ ጣቱን ፡ ነክሮ ፡ ከዘይቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ይረጫል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ካህኑም ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ከቀረው ፡ ዘይት ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጉሮሮውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፥ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ባረፈበት ፡ ላይ ፡ ያስነካዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ በካህኑም ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ዘይት ፡ በሚነጻው ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያደርግበታል ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለታል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ካህኑም ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፥ ከርኵሰቱም ፡ ለሚነጻው ፡ ሰው ፡ ያስተሰርይለታል ፤ በኋላም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያርዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ካህኑም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቀርባል ፥ ካህኑም ፡ ያስተሰርይለታል ፤ ርሱም ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ድኻም ፡ ቢኾን ፡ ይህንም ፡ ለማምጣት ፡ ገንዘቡ ፡ ባይበቃው ፥ ማስተስረያ ፡ ይኾንለት ፡ ዘንድ ፡ እንዲወዘወዝ ፡ አንድ ፡ ጠቦት ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፥ ከመስፈሪያውም ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ የኾነ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፥ አንድ ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ እንደሚቻለው ፥ አንዱን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ሌላውን ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ መንጻት ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያመጣቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ ካህኑም ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦት ፡ የሎግ ፡ መስፈሪያውንም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዘውዛቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ የበደሉንም ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦት ፡ ያርዳል ፤ ካህኑም ፡ ከበደሉ ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጉሮሮውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፥ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ያስነካዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ ካህኑም ፡ ከዘይቱ ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ያፈሰዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ካህኑም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ዘይት ፡ በቀኝ ፡ ጣቱ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ካህኑም ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ዘይት ፡ የሚነጻውን ፡ ሰው ፡ የቀኝ ፡ ጉሮሮውን ፡ ጫፍ ፥ የቀኝ ፡ እጁንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፥ የቀኝ ፡ እግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ባረፈበት ፡ ላይ ፡ ያስነካዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለት ፡ ዘንድ ፡ በካህኑ ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ዘይት ፡ በሚነጻው ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያደርገዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ እንደሚቻለው ፡ ከዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ከርግብ ፡ ግልገሎች ፡ አንዱን ፡ ያቀርባል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ እንደሚቻለው ፡ አንዱን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ሌላውንም ፡ ከእኽል ፡ ቍርባን ፡ ጋራ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፡ ካህኑም ፡ ለሚነጻው ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለታል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ለመንጻቱ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ ለማያገኝ ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ ላለበት ፡ ሰው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 34 ፤ ወደምሰጣችኹ ፡ ርስት ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔም ፡ የለምጽ ፡ ደዌ ፡ በርስታችኹ ፡ ምድር ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ባደረግኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 35 ፤ ባለቤቱ ፡ መጥቶ ፡ ካህኑን ፦ ደዌ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ይመስለኛል ፡ ብሎ ፡ ይንገረው ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 36 ፤ ካህኑም ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ እንዳይረክስ ፥ ርሱ ፡ ደዌውን ፡ ለማየት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሳይገባ ፥ ቤቱን ፡ ባዶ ፡ እንዲያደርጉት ፡ ያዛል ፤ በኋላም ፡ ካህኑ ፡ ቤቱን ፡ ለማየት ፡ ይገባል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 37 ፤ ደዌውንም ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ በግንቡ ፡ ላይ ፡ በአረንጓዴና ፡ በቀይ ፡ ቢኾርጐረጕር ፥ መልኩም ፡ ወደ ፡ ግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ቢጠልቅ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 38 ፤ ካህኑ ፡ ከቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወደቤቱ ፡ በር ፡ ወጥቶ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቤቱን ፡ ይዘጋዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 39 ፤ ካህኑም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ተመልሶ ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ በቤቱ ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ ቢሰፋ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 40 ፤ ካህኑ ፡ ደዌ ፡ ያለባቸውን ፡ ድንጋዮች ፡ እንዲያወጡ ፥ ከከተማውም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወደረከሰው ፡ ስፍራ ፡ እንዲጥሏቸው ፡ ያዛል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 41 ፤ ቤቱንም ፡ በውስጡ ፡ በዙሪያው ፡ ያስፍቀዋል ፤ የፋቁትንም ፡ የምርጊቱን ፡ ዐፈር ፡ ከከተማው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወደረከሰ ፡ ስፍራ ፡ ያፈሱታል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 42 ፤ በእነዚያም ፡ ድንጋዮች ፡ ስፍራ ፡ ሌላዎች ፡ ድንጋዮች ፡ ያገባሉ ፤ ሌላም ፡ ጭቃ ፡ ወስደው ፡ ቤቱን ፡ ይመርጉታል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 43 ፤ ደዌውም ፡ ዳግም ፡ ቢመለስ ፥ ድንጋዮቹም ፡ ከወጡ ፡ ቤቱም ፡ ከተፋቀና ፡ ከተመረገ ፡ በኋላ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢሰፋ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 44 ፤ ካህኑ ፡ ገብቶ ፡ ያያል ፤ እንሆም ፥ ደዌው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቢሰፋ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ እየፋገ ፡ የሚኼድ ፡ ለምጽ ፡ ነው ፤ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 45 ፤ ቤቱንም ፥ ድንጋዮቹንም ፥ ዕንጨቱንም ፥ የቤቱንም ፡ ምርጊት ፡ ኹሉ ፡ ያፈርሳል ፤ እነርሱንም ፡ ከከተማው ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወደ ፡ ርኩስ ፡ ስፍራ ፡ ያወጣል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 46 ፤ በተዘጋበትም ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ የሚገባ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 47 ፤ በቤቱም ፡ የሚተኛ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፤ በቤቱም ፡ የሚበላ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 48 ፤ ካህኑም ፡ ገብቶ ፡ ቢያይ ፥ እንሆም ፥ ቤቱ ፡ ከተመረገ ፡ በኋላ ፡ ደዌው ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ባይሰፋ ፥ ደዌው ፡ ስለ ፡ ኻረ ፡ ካህኑ ፡ ቤቱን ፦ ንጹሕ ፡ ነው ፡ ይለዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 49 ፤ ቤቱንም ፡ ለማንጻት ፡ ኹለት ፡ ወፎች ፥ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፥ ቀይ ፡ ግምጃም ፥ ሂሶጵም ፡ ይወስዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 50 ፤ አንደኛውንም ፡ ወፍ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ ከምንጭ ፡ ውሃ ፡ በላይ ፡ ያርዳል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 51 ፤ የዝግባውን ፡ ዕንጨት ፥ ሂሶጹንም ፥ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፥ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ወስዶ ፡ በታረደው ፡ ወፍ ፡ ደምና ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ይነክራቸዋል ፥ ቤቱንም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 52 ፤ ቤቱንም ፡ በወፉ ፡ ደም ፡ በምንጩም ፡ ውሃ ፡ በሕያውም ፡ ወፍ ፡ በዝግባውም ፡ ዕንጨት ፡ በሂሶጱም ፡ በቀዩም ፡ ግምጃ ፡ ያነጻዋል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 53 ፤ ሕያውንም ፡ ወፍ ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ይሰደዋል ፤ ለቤቱም ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 54 ፤ ይህም ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ ለኹሉ ፡ ዐይነት ፡ ለምጽ ፡ ደዌ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 55 ፤ ለቈረቈርም ፥ በልብስና ፡ በቤትም ፡ ላለ ፡ ለምጽ ፥

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 56 ፤ ለዕባጭም ፥ ለብጉርም ፥ ለቋቀጮችም ፤

ዘሌ. ፡ 14 ፡ 57 ፤ በሚረክስና ፡ በሚነጻ ፡ ጊዜ ፡ እንዲያስታውቅ ፡ ይህ ፡ የለምጽ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሯቸው ፦ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሥጋው ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ቢወጣ ፥ ስለሚፈሰው ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ስለሚፈሰው ፡ ነገር ፡ ርኩስነቱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ፈሳሹ ፡ ነገር ፡ ከሥጋው ፡ ቢፈስ ፡ ወይም ፡ ከመፍሰሱ ፡ ቢቆም ፥ ርኩስ ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ የሚተኛበት ፡ መኝታ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የሚቀመጥበትም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ መኝታውንም ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በተቀመጠበት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥበት ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበትን ፡ የሰውን ፡ ሥጋ ፡ የሚነካ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በንጹሕ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ቢተፋ ፥ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ የተቀመጠበት ፡ ኮርቻ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ከበታቹም ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ እነዚህንም ፡ ነገሮች ፡ የሚያነሣ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ በውሃ ፡ ሳይታጠብ ፡ የሚነካው ፡ ኹሉ ፡ ልብሱን ፡ ይጠብ ፥ በውሃም ፡ ይታጠብ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ የሚነካውን ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ይስበሩት ፤ የዕንጨቱም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በውሃ ፡ ይታጠብ ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ከፈሳሹ ፡ ነገር ፡ ሲነጻ ፡ ስለ ፡ መንጻቱ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይቈጥራል ፤ ልብሱንም ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በምንጭ ፡ ውሃ ፡ ይታጠባል ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ ይዞ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይመጣል ፥ ለካህኑም ፡ ይሰጣቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ አንደኛውን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ሌላውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ፈሳሹ ፡ ነገር ፡ ያስተሰርይለታል ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ የማንም ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ ከርሱ ፡ ቢወጣ ፥ ገላውን ፡ ኹሉ ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ዘር ፡ የነካው ፡ ልብስ ፡ ኹሉ ፡ ቍርበትም ፡ ኹሉ ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ወንዱ ፡ በሴቲቱ ፡ ቢደርስባት ፡ ኹለቱ ፡ በውሃ ፡ ይታጠባሉ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ሴት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ቢኖርባት ፡ በሥጋዋም ፡ ያለው ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ደም ፡ ቢኾን ፥ በመርገሟ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቀመጣለች ፤ የሚነካትም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ መርገምም ፡ ስትኾን ፡ የምትተኛበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የምትቀመጥበትም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ መኝታዋንም ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ በውሃም ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ የምትቀመጥበትንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ በውሃም ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ በመኝታዋም ፡ ላይ ፡ ወይም ፡ በምትቀመጥበት ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፡ ሲነካው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ማንም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፡ መርገሟም ፡ ቢነካው ፥ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ የሚተኛበትም ፡ መኝታ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ ሴትም ፡ ከመርገም ፡ ቀን ፡ ሌላ ፡ ደሟ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ቢፈስ ፥ ወይም ፡ ደሟ ፡ ከመርገሟ ፡ ወራት ፡ የሚበልጥ ፡ ቢፈስ ፥ በመርገሟ ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዲሁ ፡ በፈሳሿ ፡ ርኩስነት ፡ ወራት ፡ ትኾናለች ፤ ርኩስ ፡ ናት ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ ደሟም ፡ በሚፈስበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ የምትተኛበት ፡ መኝታ ፡ ኹሉ ፡ በመርገሟ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ መኝታ ፡ ያለ ፡ ይኾንባታል ፤ የምትቀመጥበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገሟ ፡ ርኩስነት ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ እነዚህንም ፡ ነገሮች ፡ የሚነካ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ልብሱንም ፡ ያጥባል ፥ በውሃም ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ ከፈሳሿም ፡ ብትነጻ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቈጥራለች ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ንጹሕ ፡ ትኾናለች ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡

ካህኑ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ታመጣቸዋለች ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ካህኑም ፡ አንደኛውን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ሌላውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፤ ካህኑም ፡ ስለፈሳሿ ፡ ርኩስነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይላታል ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ እንዲሁም ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ያለችውን ፡ ማደሪያዬን ፡ ባረከሱ ፡ ጊዜ ፥ በርኩስነታቸው ፡ እንዳይሞቱ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከርኩስነታቸው ፡ ለያቸው ።

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ላለበት ፡ ሰው ፥ ይረክስም ፡ ዘንድ ፡ ዘሩ ፡ ለሚወጣበት ፡ ሰው ፥

ዘሌ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ በመርገሟም ፡ ለታመመች ፥ ፈሳሽም ፡ ነገር ፡ ላለባቸው ፡ ለወንድም ፡ ለሴትም ፥ የረከሰችንም ፡ ሴት ፡ ለሚገናኝ ፡ ሰው ፡ ሕጉ ፡ ይኸው ፡ ነው ።

——————ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። ——————

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የቀረቡና ፡ የሞቱ ፡ ኹለት ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ተናገረው ፤

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ እኔ ፡ በስርየቱ ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ በደመናው ፡ ውስጥ ፡ እታያለኹና ፡ እንዳይሞት ፡ በመጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ በታቦቱ ፡ ላይ ፡ ወዳለው ፡ ወደስርየቱ ፡ መክደኛ ፡ ወደተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ ሹል ፡ ጊዜ ፡ እንዳይገባ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለአሮን ፡ ንገረው ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ እንዲሁ ፡ አሮን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ይዞ ፡ ወደተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይግባ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ የተቀደሰውን ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስ ፡ ይልበስ ፥ የበፍታውም ፡ ሱሪ ፡ በገላው ፡ ላይ ፡ ይኹን ፥ የበፍታውንም ፡ መታጠቂያ ፡ ይታጠቅ ፥ የበፍታውንም ፡ መጠምጠሚያ ፡ ይጠምጥም ፤ እነዚህ ፡ የተቀደሱ ፡ ልብሶች ፡ ናቸው ፤ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ታጥቦ ፡ ይልበሳቸው ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ይውሰድ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ አሮንም ፡ ለርሱ ፡ ያለውን ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈን ፡ ያቀርባል ፥ ለራሱም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ያስተሰርያል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ ኹለቱንም ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ወስዶ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆማቸዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ አሮንም ፡ በኹለቱ ፡ ፍየሎች ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ይጥልባቸዋል ፥ አንዱን ፡ ዕጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሌላውንም ፡ ዕጣ ፡ ለሚለቀቅ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ አሮንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕጣ ፡ የኾነበትን ፡ ፍየል ፡ ያቀርባል ፥ ስለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ ያደርገዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ የመለቀቅም ፡ ዕጣ ፡ የኾነበትን ፡ ፍየል ፡ ያስተሰርይበት ፡ ዘንድ ፥ ለመለቀቅም ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሰደ፡ው ፡ ዘንድ ፡ በሕይወቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆመዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ አሮንም ፡ ስለራሱ ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈኑን ፡ ያቀርባል ፤ ለራሱም ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ያስተሰርያል ፤ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ የርሱን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈኑን ፡ ያርዳል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ካለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ አምጥቶ ፡ ጥናውን ፡ ይሞላል ፥ ከተወቀጠውም ፡ ከጣፋጭ ፡ ዕጣን ፡ እጁን ፡ ሙሉን ፡ ይወስዳል ፤ ወደ ፡ መጋረጃውም ፡ ውስጥ ፡ ያመጣዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ እንዳይሞትም ፡ የጢሱ ፡ ደመና ፡ በምስክሩ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መክደኛ ፡ ይሸፍን ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዕጣኑን ፡ በእሳቱ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ከወይፈኑም ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ በስርየቱ ፡ መክደኛ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በጣቱ ፡ ይረጨዋል ፤ ከደሙም ፡ በመክደኛው ፡ ፊት ፡ በጣቱ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጫል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ስለሕዝቡም ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠዋውን ፡ መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡ ያርዳል ፥ ደሙም ፡ ወደ ፡ መጋረጃው ፡ ውስጥ ፡ ያመጣዋል ፤ በወይፈኑም ፡ ደም ፡ እንዳደረገ ፡ በፍየሉ ፡ ደም ፡ ያደርጋል ፤ በመክደኛውም ፡ ላይና ፡ በመክደኛውም ፡ ፊት ፡ ይረጨዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርኩስነት ፡ ከመተላለፋቸውም ፡ ከኀጢአታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ለመቅደሱ ፡ ያስተሰርይለታል ፤ እንዲሁም ፡ በርኩስነታቸው ፡ መካከል ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ለኖረች ፡ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ያደርጋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ ለማስተስረይ ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ለራሱ ፥ ለቤተ ፡ ሰቡም ፥ ለእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ሹሉ ፡ አስተስርዮ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ማንም ፡ አይኖርም ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ መሠዊያ ፡ ወጥቶ ፡ ያስተሰርይለታል ፤ ከወይፈኑም ፡ ደም ፡ ከፍየሉም ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ቀንዶች ፡ ያስነካል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ከደሙም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በጣቱ ፡ ይረጫል ፥ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ርኩስነት ፡ ያነጻዋል ፥ ይቀድሰውማል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ መቅደሱንም ፥ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፥ መሠዊያውንም ፡ ማስተስረይ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሕያውን ፡ ፍየል ፡ ያቀርባል ፤

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ አሮንም ፡ ኹለቱን ፡ እጆቹን ፡ በሕያው ፡ ፍየል ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፥ በላዩም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በደል ፡ ሹሉ ፡ መተላለፋቸውንም ፡ ሹሉ ፡ ኀጢአታቸውንም ፡ ሹሉ ፡ ይናዝዛል ፤ በፍየሉም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያሸክመዋል ፥ በተዘጋጀው ፡ ሰውም ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሰደዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ፍየሉም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ይሸከማል ፤ ፍየሉንም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ይለቀዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ አሮንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይገባል ፥ ወደ ፡ መቅደሱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የለበሰውን ፡ የበፍታ ፡ ልብስ ፡ ያወልቃል ፥ በዚያም ፡ ይተወዋል ፤

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ በተቀደሰውም ፡ ስፍራ ፡ ገላውን ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ ሌላውንም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ይወጣል ፤ የርሱንም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ የሕዝቡንም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ፥ ለራሱም ፡ ለሕዝቡም ፡ ያስተሰርያል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ የኀጢአቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ለመለቀቅ ፡ የሚኾነውን ፡ ፍየል ፡ የወሰደ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ይገባል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ለማስተስረያም ፡ እንዲኾን ፡ ደማቸው ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ የገባውን ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈንና ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ፍየል ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡

ያወጧቸዋል ፤ ቍርበታቸውንም ፣ ሥጋቸውንም ፣ ፈርሳቸውንም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ያቃጠላቸውም ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይገባል ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ 30 ፤ ይህም ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኹንላችኹ ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ ትነጹ ፡ ዘንድ ፡ ማስተስረያ ፡ ይኾንላችኋልና ፥ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ ራሳችኹን ፡ አስጨንቋት ፥ የአገር ፡ ልጅም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የተቀመጠም ፡ እንግዳ ፡ ሥራን ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ከኀጢአታችኹ ፡ ኹሉ ፡ ትነጻላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ ታላቅ ፡ ሰንበት ፡ ይኾንላችኋል ፥ ራሳችኹንም ፡ ታዋርዳላችኹ ፤ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ የሚቀባውም ፥ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ ካህን ፡ ሊኾን ፡ የሚካነው ፡ ካህን ፡ ያስተስርይ ፥ የተቀደሰውንም ፡ የበፍታ ፡ ልብስ ፡ ይልበስ ፤

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ያስተስርይ ፤ ለመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ለመሠዊያውም ፡ ያስተስርይ ፤ ለካህናቱም ፡ ለጉባኤውም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ያስተስርይ ።

ዘሌ. ፡ 16 ፡ 34 ፤ ይህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዓመት ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ ኹሉ ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኹንላችኹ ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገር ፦ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ይህ ፡ ነው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ፍየል ፡ ቢያርድ ፥ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ወይም ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ ቢያርደው ፥

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ባያመጣው ፥ ደሙ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይቈጠርበታል ፤ ደም ፡ አፍስሷል ፤ ያም ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሜዳ ፡ የሚያርዱትን ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ያመጡታል ፤ ወደ ፡ ካህኑም ፡ አምጥተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዉታል ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ካህኑም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ደሙን ፡ ይረጨዋል ፥ ስቡንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ያቃጥለዋል ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ መሥዋዕታቸውንም ፡ ደግሞ ፡ ተከትለው ፡ ላመነዘሩባቸው ፡ ለሰይጣናት ፡ አይሠዉ ። ይህ ፡ ለእነርሱ ፡ ለልጅ ፡ ልጃቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ለእነርሱም ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ በመካከላቸውም ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግዳዎች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ቢያቀርብ ፥

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ባያመጣው ፥ ያ ፡ ሰው ፡

ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ በመካከላቸው ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግዳዎች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ቢበላ ፥ ደም ፡ በሚበላው ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብድበታለኹ ፥ ያንንም ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ በደሙ ፡ ውስጥ ፡ ነውና ፤ ደሙም ፡ ከሕይወቱ ፡ የተነሣ ፡ ያስተሰርያልና ፥ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ለነፍሳችኹ ፡ ማስተስረያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ለእናንተ ፡ ሰጠኹት ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፦ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ ደምን ፡ አይበላም ፥ በመካከላችኹም ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግዳዎች ፡ ማንም ፡ ደምን ፡ አይበላም ፡ አልኹ ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በመካከላቸውም ፡ ከሚኖሩ ፡ እንግዳዎች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የሚበላ ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ ወፍ ፡ እያደነ ፡ ቢይዝ ፥ ደሙን ፡ ያፈሳል ፥ በዐፈርም ፡ ይከድነዋል ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ የሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ሕይወትና ፡ ደሙ ፡ አንድ ፡ ነውና ፥ ስለዚህ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፦ የሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ሕይወት ፡ ደሙ ፡ ነውና ፥ የሥጋውን ፡ ኹሉ ፡ ደም ፡ አትብሉ ፤ የሚበላውም ፡ ኹሉ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ፡ አልኋቸው ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ የሞተውን ፡ ወይም ፡ አውሬ ፡ የሰበረውን ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፥ የአገር ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ እንግዳ ፡ ቢኾን ፥ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ በውሃም ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ልብሱንና ፡ ገላውን ፡ ባያጥብ ፡ ግን ፡ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

——————————ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። ——————————

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ እንደ ፡ ተቀመጣችኹባት ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ እንደማገባችኹ ፡ እንደ ፡ ከነዓን ፡ ምድር ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ፤ በሥርዐታቸውም ፡ አትኺዱ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ፍርዴን ፡ አድርጉ ፥ በርሷም ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ሥርዐቴን ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ የሚሠራቸው ፡ ሰው ፡ በእነርሱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራልና ፥ ሥርዐቴንና ፡ ፍርዴን ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋውን ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ዘመዱ ፡ ኹሉ ፡ አይቅረብ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ የአባትኽን ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋና ፡ የእናትኽን ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ እናትኽ ፡ ናት ፤ ኀፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ የአባትኽን ፡ ሚስት ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአባትኽን ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ የእኅትኽን ፡ ኀፍረት ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአባትኽ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የእናትኽ ፡ ልጅ ፥ በቤት ፡ ወይም ፡ በውጭ ፡ የተወለደች ፡ ብትኾን ፥ ኀፍረት ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ የወንድ ፡ ልጅኽን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ ወይም ፡ የሴት ፡ ልጅኽን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአንተ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ከአባትኽ ፡ የተወለደችውን ፡ የአባትኽን ፡ ሚስት ፡ ልጅ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ እኅትኽ ፡ ናት ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ የአባትኽን ፡ እኅት ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የአባትኽ ፡ ዘመድ ፡ ናት ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ የእናትኽን ፡ እኅት ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የእናትኽ ፡ ዘመድ ፡ ናት ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ የአባትኽን ፡ ወንድም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፥ ወደ ፡ ሚስቱም ፡ አትቅረብ ፤ የአጎትኽ ፡ ሚስት ፡ ናት ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ የምራትኽን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የልጅኽ ፡ ሚስት ፡ ናት ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ አትግለጥ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ የወንድምኽን ፡ ሚስት ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የወንድምኽ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ የሴትንና ፡ የሴት ፡ ልጇን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ የወንድ ፡ ልጇን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የሴት ፡ ልጇን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ ትግለጥ ፡ ዘንድ ፡ አታግባ ፤ ዘመዶች ፡ ናቸው ፤ ዝሙት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ሚስትኽ ፡ በሕይወት ፡ ሳለች ፡ እኅቷ ፡ ጣውንቷ ፡ እንዳትኾን ፥ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ እኅቷን ፡ አታግባ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ርሷም ፡ በመርገሟ ፡ ርኵሰት ፡ ሳለች ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴት ፡ አትቅረብ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ እንዳትረክስባትም ፡ ከባልንጀራኽ ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ አትተኛ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ከዘርኽም ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ አሳልፈኽ ፡ አትስጥ ፥ የአምላክኽንም ፡ ስም ፡ አታርክስ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ከሴትም ፡ ጋራ ፡ እንደምትተኛ ፡ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ አትተኛ ፤ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ነውና ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ እንዳትረክስባትም ፡ ከእንስሳ ፡ ጋራ ፡ አትተኛ ፤ ሴት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትተኛ ፡ ዘንድ ፡ በእንስሳ ፡ ፊት ፡ አትቁም ፤ የተጠላ ፡ ነገር ፡ ነውና ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ በእነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ከፊታችኹ ፡ የማሳድዳቸው ፡ አሕዛብ ፡ ረክሰዋልና ፥ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ኹሉ ፡ አትርከሱ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ምድሪቱም ፡ ረከሰች ፤ ስለዚህ ፥ ኀጢአቷን ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ፥ ምድሪቱም ፡ የሚኖሩባትን ፡ ሰዎች ፡ ትተፋለች ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ሥርዐቴንና ፡ ፍርዴን ፡ ጠብቁ ፤ እናንተም ፡ የአገሩ ፡ ልጆች ፡ በእናንተም ፡ መካከል ፡ የሚኖሩት ፡ እንግዳዎች ፡ ከዚህ ፡ ርኵሰት ፡ ምንም ፡ አትሥሩ ፤

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ የአገሩ ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ሠርተዋልና ፥ ምድሪቱም ፡ ረክሳለችና ፤

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ባረከሳችኋት ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ተፋች ፡

እናንተን ፡ እንዳትተፋችኹ ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ከዚህ ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ማናቸውን ፡ የሚያደርግ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋልና ።

ዘሌ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ የሠሩትን ፡ ጸያፍ ፡ የኾነውን ፡ ወግ ፡ ኹሉ ፡ እንዳትሠሩ ፥ በርሱም ፡ እንዳትረክሱ ፡ ሥርዐቴን ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ባላቸው ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ እናንተ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ከእናንተ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እናቱንና ፡ አባቱን ፡ ይፍራ ፥ ሰንበታቴንም ፡ ጠብቁ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ጣዖታትም ፡ ዘወር ፡ አትበሉ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡ የአማልክት ፡ ምስሎች ፡ ለእናንተ ፡ አታድርጉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስትሠዉ ፡ ርሱን ፡ ደስ ፡ እንድታሠኙበት ፡ ሠዉት ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ በምትሠዉት ፡ ቀንና ፡ በነጋው ፡ ይበላል ፤ እስከ ፡ ሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቢተርፍ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ቢበላ ፡ ጸያፍ ፡ ነው ፥ ደስም ፡ አያሠኝም ፤

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ የበላውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ነገር ፡ አርክሷልና ፥ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ የምድራችኹንም ፡ መከር ፡ በሰበሰባችኹ ፡ ጊዜ ፡ የዕርሻችኹን ፡ ድንበር ፡ ፈጽማችኹ ፡ አትጨዱ ፥ የመከሩንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትልቀሙ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ የወይንኽንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትቃርም ፥ የወደቀውንም ፡ የወይንኽን ፡ ፍሬ ፡ አትሰብስብ ፤ ለድኻዎችና ፡ ለእንግዳዎች ፡ ተወው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ አትስረቁ ፥ አትካዱም ፥ ከእናንተም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ሐሰት ፡ አትነጋገሩ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ በስሜም ፡ በሐሰት ፡ አትማሉ ፥ የአምላካችኹንም ፡ ስም ፡ አታርክሱ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ በባልንጀራኽ ፡ ግፍ ፡ አታድርግ ፥ አትቀማውም ። የሞያተኛው ፡ ዋጋ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አይደርብኽ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ደንቈሮውን ፡ አትስደብ ፥ በዕውርም ፡ ፊት ፡ ዕንቅፋት ፡ አታድርግ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽን ፡ ፍራ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ በፍርድ ፡ ዐመፃ ፡ አታድርጉ ፤ ለድኻ ፡ አታድላ ፥ ባለጠጋውንም ፡ አታክብር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለባልንጀራኽ ፡ በእውነት ፡ ፍረድ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ በሕዝብኽ ፡ መካከል ፡ በሸንጋይነት ፡ አትዘር ፤ በባልንጀራኽም ፡ ደም ፡ ላይ ፡ አትቁም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ወንድምኽን ፡ በልብኽ ፡ አትጥላው ፤ በባልንጀራኽ ፡ ምክንያት ፡ ኀጢአት ፡ እንዳይኾንብኽ ፡ ገሥጸው ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ አትበቀልም ፥ በሕዝብኽም ፡ ልጆች ፡ ቂም ፡ አትያዝ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ሥርዐቴን ፡ ጠብቁ ። እንስሳኽ ፡ ከሌላ ፡ ዐይነት ፡ ጋራ ፡ አይደባለቅ ፤ በዕርሻኽም ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ዘር ፡ አትዝራ ፤ ከኹለት ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ አትልበስ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሴት ፡ ባሪያ ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፥ ርሷም ፡ ለባል ፡ የተሰጠች ፡ ዋጋዋም ፡ ያልተከፈለ ፡ ሐራነት ፡ ያልወጣች ፡ ብትኾን ፥ ቅጣት ፡ አለባቸው ፤ ሐራነት ፡ አልወጣችምና ፡ አይገደሉም ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ይዞ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ይመጣል ፥ ለበደልም ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያመጣል ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ካህኑም ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በበደል ፡ መሥዋዕት ፡ በግ ፡ ያስተሰርይለታል ፤ የሠራውም ፡ ኀጢአት ፡ ይቀርለታል ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ አገሩም ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥ የሚበላ ፡ የፍሬ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በተከላችኹም ፡ ጊዜ ፥ ፍሬውን ፡ እንዳልተገረዘ ፡ ትቈጥሩታላችኹ ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እንዳልተገረዘ ፡ ይኾንላችኋል ፤ አይበላም ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ የአራተኛውም ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ቅዱስ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ፍሬውም ፡ ይበዛላችኹ ፡ ዘንድ ፡ የዐምስተኛውን ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ብሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ከደሙ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ አትብሉ ፤ አስማትም ፡ አታድርጉ ፥ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ አትኹኑ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ የራስ ፡ ጠጕራችኹንም ፡ ዙሪያውን ፡ አትከርክሙት ፥ ጢማችኹንም ፡ ዙሪያውን ፡ አትቀሥረጡት ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ስለሞተውም ፡ ሥጋችኹን ፡ አትንጨ ፥ ገላችኹንም ፡ አትንቀሱት ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ምድሪቱ ፡ ከግልሙትና ፡ ከርኵሰትም ፡ እንዳትሞላ ፡ ሴት ፡ ልጅኽን ፡ ታመነዝር ፡ ዘንድ ፡ አታርክሳት ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ሰንበታቴን ፡ ጠብቁ ፥ መቅደሴንም ፡ አክብሩ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ ወደመናፍስት ፡ ጠሪዎችና ፡ ወደ ፡ ጠንቋዮች ፡ አትኺዱ ፤ እንዳትረክሱባቸውም ፡ አትፈልጓቸው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ በሽበታሙ ፡ ፊት ፡ ተነሣ ፥ ሽማግሌውንም ፡ አክብር ፥ አምላክኽንም ፡ ፍራ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ በአገራችኹ ፡ ውስጥ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንግዳ ፡ ቢቀመጥ ፡ ግፍ ፡ አታድርጉበት ።

ዘሌ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ እንግዳዎች ፡ ነበራችኹና ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የሚቀመጥ ፡ እንግዳ ፡

እንደአገር ፡ ልጅ ፡ ይኹንላችኹ ፥ ርሱንም ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፥ 19 ፥ 35 ፤ በፍርድ ፥ በመለካትም ፥ በመመዘንም ፥ በመስፈርም ፡ ዐመፃ ፡ አታድርጉ ።

ዘሌ. ፥ 19 ፥ 36 ፤ የእውነትም ፡ ሚዛን ፥ የእውነትም ፡ መመዘኛ ፥ የእውነትም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፥ የእውነትም ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ይኹንላችኹ ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፥ 19 ፥ 37 ፤ ሥርዐቴን ፡ ኹሉ ፡ ፍርዴንም ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ፡ አድርጉም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 2 ፤ ደግሞ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከሚቀመጡ ፡ እንግዳዎች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ዘሩን ፡ ለሞሎክ ፡ ቢሰጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገረው ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 3 ፤ መቅደሴን ፡ ያረክስ ፡ ዘንድ ፥ የተቀደሰውንም ፡ ስሜን ፡ ያጐሰቍል ፡ ዘንድ ፡ ዘሩን ፡ ለሞሎክ ፡ ሰጥቷልና ፥ እኔ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብዳለኹ ፥ ከሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለኹ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 4 ፤ ዘሩንም ፡ ለሞሎክ ፡ ሲሰጥ ፥ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ያን ፡ ቸል ፡ ቢለው ፡ ባይገድሉትም ፥

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 5 ፤ እኔ ፡ በዚያ ፡ ሰውና ፡ በቤተ ፡ ሰቡ ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብዳለኹ ፤ ርሱንም ፥ ከሞሎክም ፡ ጋራ ፡ ያመነዝሩ ፡ ዘንድ ፡ የሚከተሉትን ፡ ኹሉ ፡ ከሕዝባቸው ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋለኹ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 6 ፤ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችንም ፡ በሚከተል ፥ በሥራቸውም ፡ በሚያመነዝር ፥ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አከብዳለኹ ፥ ከሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ አጠፋዋለኹ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 7 ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝና ፡ ሰውነታችኹን ፡ ቀድሱ ፥ ቅዱሳንም ፡ ኹኑ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 8 ፤ ሥርዐቴን ፡ ጠብቁ ፥ አድርጉትም ፤ እኔ ፡ የምቀድሳችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 9 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ ቢሰድብ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፥ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ሰድቧልና ፤ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 10 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ወይም ፡ ከባልንጀራው ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ ቢያመነዝር ፡ አመንዝራውና ፡ አመንዝራዪቱ ፡ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 11 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፡ የአባቱን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገልጧል ፤ ኹለቱ ፡ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፤ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 12 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከምራቱ ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፡ ኹለቱ ፡ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፤ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ አድርገዋል ፤ ደማቸውም ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 13 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ እንደሚተኛ ፡ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፡ ኹለቱ ፡ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ አድርገዋል ፤ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፤ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

ዘሌ. ፥ 20 ፥ 14 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ እናቲቱንና ፡ ልጂቱን ፡ ቢያገባ ፡ ርኵሰት ፡ ነው ፤ በመካከላችኹ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳይኾን ፡ ርሱና ፡ እነርሱ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠሉ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከእንስሳ ፡ ጋራ ፡ ቢገናኝ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ እንስሳዩቱንም ፡ ግደሏት ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ማናቸዪቱም ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ እንስሳ ፡ ብትቀርብ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ብትገናኝ ፥ ሴቲቱንና ፡ እንስሳውን ፡ ግደል ፤ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፤ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የአባቱን ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ የእናቱን ፡ ልጅ ፡ እኅቱን ፡ ቢያገባ ፥ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋንም ፡ ቢያይ ፥ ርሷም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋውን ፡ ብታይ ፥ ይህ ፡ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ በሕዝባቸውም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ይገደሉ ፤ የእኅቱን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገልጧልና ፥ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከባለመርገም ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋንም ፡ ቢገልጥ ፥ ፈሳሿን ፡ ገልጧልና ፥ ርሷም ፡ የደሟን ፡ ፈሳሽ ፡ ገልጣለችና ፡ ኹለቱ ፡ ከሕዝባቸው ፡ መካከል ፡ ተለይተው ፡ ይጥፉ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ የአባትኽን ፡ ወይም ፡ የእናትኽን ፡ እኅት ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ አትግለጥ ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ የዘመድን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገልጧል ፤ ኀጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ሰውም ፡ ከአጎቱ ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፥ የአጎቱን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገልጧል ፤ ኀጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ያለልጅ ፡ ይሞታሉ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ሰውም ፡ የወንድሙን ፡ ሚስት ፡ ቢያገባ ፡ ርኵሰት ፡ ነው ፤ የወንድሙን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገልጧል ፤ ያለልጅ ፡ ይኾናሉ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ እንግዲህ ፡ ትቀመጡባት ፡ ዘንድ ፡ የማገባችኹ ፡ ምድር ፡ እንዳትተፋችኹ ፡ ሥርዐቴን ፡ ኹሉ ፥ ፍርዴንም ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ፥ አድርጉትም ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ከፊታችኹ ፡ በምጥላቸውም ፡ ሕዝብ ፡ ወግ ፡ አትኺዱ ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አድርገዋልና ፥ ተጸየፍኺቸው ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተን ፦ ምድራቸውን ፡ ትወርሳላችኹ ፤ ትወርሷትም ፡ ዘንድ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈሰውን ፡ ምድር ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ አልኋችኹ ። እኔ ፡ ከአሕዛብ ፡ የለየኋችኹ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ እንግዲህ ፡ ንጹሑን ፡ እንስሳ ፡ ከርኩሱ ፥ ንጹሑንም ፡ ወፍ ፡ ከርኩስ ፡ ትለያላችኹ ፤ ርኩሶች ፡ ናቸው ፡ ብዬ ፡ በለየኋቸው ፡ በእንስሳና ፡ በወፍ ፡ በምድርም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ ነፍሳችኹን ፡ አታርክሱ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፥ ለኔም ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከአሕዛብ ፡ ለይቻችኋለኹና ፡ ቅዱሳን ፡ ትኾኑልኛላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ሰው ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ መናፍስትን ፡ ቢጠሩ ፡ ወይም ፡ ጠንቋዮች ፡ ቢኾኑ ፡ ፈጽመው ፡ ይገደሉ ፤ በድንጋይ ፡ ይውገሯቸው ፤ ደማቸው ፡ በላያቸው ፡ ነው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ለካህናቱ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፡ አለው ፦ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ስለሞተው ፥

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ከሚቀርበው ፡ ዘመዱ ፥ ከእናቱ ፥ ወይም ፡ ከአባቱ ፥ ወይም ፡ ከወንድ ፡ ልጁ ፥ ወይም ፡ ከሴት ፡ ልጁ ፥ ወይም ፡ ከወንድሙ ፡ በቀር ፡ አይርከስ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ወይም ፡ የቀረበችው ፡ ያልተጋባች ፡ ድንግል ፡ እኅቱ ፡ በርሷ ፡ ይርከስ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ የሕዝቡ ፡ አለቃ ፡ ራሱን ፡ ያጐሰቀሉል ፡ ዘንድ ፡ አይርከስ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ ራሳቸውን ፡ አይላጩ ፥ ጢማቸውንም ፡ አይላጩ ፥ ሥጋቸውንም ፡ አይንጩ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ለአምላካቸው ፡ ቅዱሳን ፡ ይኹኑ ፥ የአምላካቸውንም ፡ ስም ፡ አያጐስቀሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ የእሳት ፡ ቍርባንና ፡ የአምላካቸውን ፡ እንጀራ ፡ ያቀርባሉና ፡ ቅዱሳን ፡ ይኹኑ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ለአምላኩ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፥ ጋለሞታን ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ የረከሰችውን ፡ አያግባ ፤ ወይም ፡ ከባሏ ፡ የተፈታችውን ፡ አያግባ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ የአምላክኽን ፡ እንጀራ ፡ ያቀርባልና ፥ ስለዚህ ፡ ትቀድሰዋለኽ ፤ እኔም ፡ የምቀድሳችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ ርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ይኹንልኽ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ የካህንም ፡ ልጅ ፡ ራሷን ፡ በግልሙትና ፡ ብታረክስ ፡ አባቷን ፡ ታረክሰዋለች ፤ በእሳት ፡ ትቃጠል ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ የቅባት ፡ ዘይት ፡ የፈሰሰበት ፥ የክህነትም ፡ ልብስ ፡ ይለብስ ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሰ ፡ ከወንድሞቹ ፡ የበለጠው ፡ ካህን ፡ ራሱን ፡ አይግለጥ ፡ ልብሱንም ፡ አይቅደድ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ በድንም ፡ ዥሉ ፡ አይግባ ፥ በአባቱም ፡ ወይም ፡ በእናቱ ፡ አይርከስ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ የአምላኩም ፡ ቅባት ፡ ዘይት ፡ ቅዱስነት ፡ በላዩ ፡ ነውና ፥ ከመቅደስ ፡ አይውጣ ፥ የአምላኩንም ፡ መቅደስ ፡ አያርክስ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ ሚስትን ፡ በድንግልናዋ ፡ ያግባ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ባሏ ፡ የሞተባትን ፥ ወይም ፡ የተፋታችውን ፥ ወይም ፡ ጋለሞታዪቱን ፡ አያግባ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሕዝቡ ፡ ድንግሊቱን ፡ ያግባ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ እኔም ፡ የምቀድሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ዘሩን ፡ አያጐስቀሉል ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ለአሮን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፦ ከዘርኽ ፡ በትውልዳቸው ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ዥሉ ፡ የአምላኩን ፡ እንጀራ ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ አይቅረብ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ዕውር ፥ ወይም ፡ ዐንካሳ ፥ ወይም ፡ አፍንጫ ፡ ደፍጣጣ ፥ ወይም ፤ ትርፍ ፡ አካል ፡ ያለው ፥

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ ወይም ፡ እግረ ፡ ሰባራ ፥ ወይም ፡ እጀ ፡ ሰባራ ፥

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ወይም ፡ ጕባጣ ፥ ወይም ፡ ድንክ ፥ ወይም ፡ ዐይነ ፡ መጭማጫ ፥ ወይም ፡ ዕከካም ፥ ወይም ፡ ቋቍቻም ፥ ወይም ፡ ጃን ፡ ደረባ ፥ ነውረኛ ፡ ዥሉ ፡ አይቅረብ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ከካህኑ ፡ ከአሮን ፡ ዘር ፡ ነውር ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ አይቅረብ ፤ ነውረኛ ፡ ነው ፤ የአምላኩን ፡ እንጀራ ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ አይቅረብ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ የቅዱሱንና ፡ የቅዱስ ፡ ቅዱሳኑን ፡ የአምላኩን ፡ እንጀራ ፡ ይብላ ፤

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነውረኛ ፡ ነውና ፥ መቅደሶቼን ፡ እንዳያረክስ ፡ ወደ ፡ መጋረጃው ፡ አይግባ ፥ ወደ ፡

መሠዊያውም ፡ አይቅረብ ፤ የምቀድሳቸው ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ሙሴም ፡ ይህን ፡ ለአሮን ፥ ለልጆቹም ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሹሉ ፡ ነገረ ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ ከሚቀድሷቸው ፡ ከቅዱሳን ፡ ነገሮች ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲለዩ ፥ የተቀደሰውንም ፡ ስሜን ፡ እንዳያረክሱ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ንገራቸው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከዘራችኹ ፡ በትውልዳችኹ ፡ ርኵሰት ፡ እያለበት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወደሚቀድሱት ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ቢቀርብ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከፊቴ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ከአሮን ፡ ዘር ፡ ለምጽ ፡ ወይም ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ሹሉ ፡ ንጹሕ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ከተቀደሰው ፡ አይብላ ። ከበድንም ፡ የተነሣ ፡ ርኩስ ፡ የኾነውን ፥ ወይም ፡ ዘሩ ፡ ከርሱ ፡ የሚፈስበትን ፡ የሚነካ ፥

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ወይም ፡ የሚያረክሰውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፥ ወይም ፡ በሹሉ ፡ ዐይነት ፡ የረከሰውን ፡ ሰው ፡ የሚነካ ፥

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ እነዚህን ፡ ሹሉ ፡ የሚነካ ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ ገላውን ፡ በውሃ ፡ ካልታጠበ ፡ ከተቀደሰው ፡ አይብላ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ፀሓይም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንጀራው ፡ ነውና ፥ ከተቀደሰው ፡ ይብላ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ በርሱም ፡ እንዳይረክስ ፥ የሞተውን ፡ አውሬም ፡ የሰበረውን ፡ አይብላ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ ቢያረክሷት ፡ እንዳይሞቱ ፡ ስለ ፡ ርሷም ፡ ኀጢአትን ፡ እንዳይሸከሙ ፥ ሕግን ፡ ይጠብቁ ፤ የምቀድሳቸው ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ልዩ ፡ ሰው ፡ ከተቀደሰው ፡ አይብላ ፡ የካህኑም ፡ እንግዳ ፡ ደመ ፡ ወዘኛውም ፡ ከተቀደሰው ፡ አይብላ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ካህኑ ፡ ግን ፡ በገንዘቡ ፡ ባሪያ ፡ ቢገዛ ፡ ርሱ ፡ ይብላው ፤ በቤቱም ፡ የተወለዱት ፡ ከእንጀራው ፡ ይብሉ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ የካህንም ፡ ልጅ ፡ ከልዩ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ብትጋባ ፥ ርሷ ፡ ከተቀደሰው ፡ ቍርባን ፡ አትብላ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ የካህን ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ባሏ ፡ ቢሞት ፥ ወይም ፡ ብትፋታ ፥ ልጅም ፡ ባይኖራት ፥ በብላቴንነቷ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ወዳባቷ ፡ ቤት ፡ ብትመለስ ፥ ከአባቷ ፡ እንጀራ ፡ ትብላ ፤ ልዩ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ አይብላ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡ ከተቀደሰው ፡ ቢበላ ፡ ዐምስተኛ ፡ እጅ ፡ ጨምሮ ፡ የተቀደሰውን ፡ ለካህኑ ፡ ይስጥ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ 16 ፤ የምቀድሳቸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ ከተቀደሰው ፡ በበሉ ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአትንና ፡ በደልን ፡ እንዳይሸከሙ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያቀርቡትን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሰውን ፡ ነገር ፡ አያርክሱ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከእናንተ ፡ መካከል ፡ ከሚቀመጡት ፡ እንግዳዎች ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ስእለቱን ፡ ኹሉ ፥ በፈቃዱም ፡ የሚያቀርበውን ፡ ኹሉ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ቍርባን ፡ ቢያቀርብ ፥

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ይሰምርላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከበሬ ፡ ወይም ፡ ከበግ ፡ ወይም ፡ ከፍየል ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ተባቱን ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አይሰምርላችኹምና ፡ ነውር ፡ ያለበትን ፡ አታቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ስእለቱን ፡ ለመፈጸም ፡ ወይም ፡ በፈቃዱ ፡ ለማቅረብ ፡ የደኅንነትን ፡ መሥዋዕት ፥ ወይም ፡ በሬን ፡ ወይም ፡ በግን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ቢያቀርብ ፥ ይሰምርለት ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ ይኹን ፥ ነውርም ፡ አይኹንበት ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ዕውር ፡ ወይም ፡ ሰባራ ፡ ወይም ፡ ጕንድሽ ፡ ወይም ፡ የሚመግል ፡ ቀኑል ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ ዕከካም ፡ ወይም ፡ ቋቍቻም ፡ ቢኾን ፥ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አታቅርቡ ፤ እነዚህም ፡ ለእሳት ፡ ቍርባን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አታሳርጉ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ በሬው ፡ ወይም ፡ በጉ ፡ የተጨመረበት ፡ ወይም ፡ የጐደለበት ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፥ ለፈቃድ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ ትችላለኽ ፤ ለስእለት ፡ ግን ፡ አይሰምርም ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ የተሰነጋውን ፡ ወይም ፡ የተቀጠቀጠውን ፡ ወይም ፡ የተሰበረውን ፡ ወይም ፡ የተቈረጠውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አታቅርቡ ፤ በምድራችኹም ፡ እነዚህን ፡ አትሠዉ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ ከነዚህም ፡ ከእንግዳ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ለአምላካችኹ ፡ እንጀራ ፡ አታቅርቡ ፤ ርኵሰትም ፡ ነውርም ፡ አለባቸውና ፥ አይሰምሩላችኹም ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ፍየል ፡ ሲወለድ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከእናቱ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጥ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ የሰመረ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ላም ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ብትኾን ፡ ርሷንና ፡ ልጇን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አትረዱ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ የምስጋናንም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስትሠዉ ፡ እንዲሰምርላችኹ ፡ ሠዉለት ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ በዚያው ፡ ቀን ፡ ይበላል ፤ ከርሱ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ምንም ፡ አትተዉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ ትእዛዛቴን ፡ ጠብቁ ፥ አድርጉትም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 32 ፤ የተቀደሰውንም ፡ ስሜን ፡ አታርክሱ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እቀደሳለኹ ፤

ዘሌ. ፡ 22 ፡ 33 ፤ የምቀድሳችኹ ፥ አምላካችኹም ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ብላችኹ ፡ የምታውጇቸው ፡ በዓላቶቼ ፥ የእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፥ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ይሠራል ፤ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኾንበታል ፤ ምንም ፡ ሥራ ፡ አትሠሩም ፤ በምትኖሩበት ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ እነዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፥ በየዘመናቸው ፡ የምታውጇቸው ፥ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ሲመሽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በዚህም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቂጣ ፡ በዓል ፡ ነው ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ብሉ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ አቅርቡ ፤ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ወደምሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥ መከሩንም ፡ ባጨዳችኹ ፡ ጊዜ ፥ የእናንተን ፡ መከር ፡ በኵራት ፡ ነዶ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ አምጡ ፤

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ ነዶውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲሰምርላችኹ ፡ ይወዝውዘው ፤ በማግስቱ ፡ ከሰንበት ፡ በኋላ ፡ ካህኑ ፡ ይወዝውዘው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ነዶውንም ፡ በወዘወዛችኹበት ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ የእኽልም ፡ ቍርባን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ የኾነ ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ለእሳት ፡ ቍርባን ፡ ይኹን ፤ የመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ እንጀራውንም ፥ የተጠበሰውንም ፡ እሸት ፥ ለምለሙንም ፡ እሸት ፡ የአምላካችኹን ፡ ቍርባን ፡ እስከምታቀርቡበት ፡ እስከዚህ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አትብሉ ። ይህ ፡ በምትቀመጡበት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ የወዘወዛችኹትን ፡ ነዶ ፡ ከምታመጡበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከሰንበት ፡ ማግስት ፡ ፍጹም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቍጠሩ ፤

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ እስከ ፡ ሰባተኛ ፡ ሰንበት ፡ ማግስት ፡ ድረስ ፡ ዐምሳ ፡ ቀን ፡ ቍጠሩ ፤ ዐዲሱንም ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ከየማደሪያችኹ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ ከኾነ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሠራ ፡ ኹለት ፡ የመወዝወዝ ፡ እንጀራ ፡ ታመጣላችኹ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ለበኵራት ፡ ቍርባን ፡ እንዲኾን ፡ በርሾ ፡ ይጋገራል ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ከእንጀራውም ፡ ጋራ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ሰባት ፡ ጠቦቶች ፥ አንድ ፡ ወይፈንም ፥ ኹለትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ይኹኑ ፤ ከእኽልም ፡ ቍርባን ፥ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ጋራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ይኹኑ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ አንድም ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ኹለትም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦቶች ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ ካህኑም ፡ ከበኵራቱ ፡ እንጀራ ፡ ከኹለቱም ፡ ጠቦቶች ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ይወዘውዛቸዋል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ፈንታ ፡ ነው ፤ ለካህኑ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ታውጃላችኹ ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አታድርጉበት ፤ በምትቀመጡበት ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ የምድራችኹንም ፡ መከር ፡ በሰበሰባችኹ ፡ ጊዜ ፡ የዕርሻችኹን ፡ ድንበር ፡ ፈጽማችኹ ፡ አትጨዱ ፥ የመከሩንም ፡ ቃርሚያ ፡ አትልቀሙ ፤ ለድኻዎችና ፡ ለእንግዳዎች ፡ ተዉት ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፥ በመለከት ፡ ድምፅ ፡ መታሰቢያ ፥ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አታድርጉበት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የእሳት ፡ ቍርባንን ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ በዚህ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የማስተስረያ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ ሰውነታችኹን ፡ አስጨንቋት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የእሳት ፡ ቍርባንን ፡ አቅርቡ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 28 ፤ በአምላካችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ማስተስረያ ፡ ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ የማስተስረያ ፡ ቀን ፡ ነውና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አትሥሩ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 29 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የማይዋረድ ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ ተለይቶ ፡ ይጥፋ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ የሚሠራውን ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አጠፋዋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አታድርጉበት ፤ በምትቀመጡበት ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ይኹንላችኹ ፥ ሰውነታችኹንም ፡ አዋርዱ ፤ በወሩ ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፥ ከማታ ፡ ዠምራችኹ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፥ ሰንበታችኹን ፡ አድርጉ ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 34 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ በዚህ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የዳስ ፡ በዓል ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 35 ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹን ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አታድርጉበት ።

ዘሌ. ፡ 23 ፡ 36 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእሳት ፡ ቍርባንን ፡ አቅርቡ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡

ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚቃጠለውን ፡ ቍርባን ፡ አቅርቡ ፤ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ ነው ፤ የተግባር ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አታድርጉበት ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 37 ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፥ መሥዋዕቱንም ፥ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፥ በየቀኑ ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቀርቡባቸው ፡ ዘንድ ፡ የተቀደሱ ፡ ጉባኤዎች ፡ እንዲኾኑ ፡ የምታውጇቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 38 ፤ እነዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሰንበታት ፡ ሌላ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ከምትሰጡት ፡ ከስጦታችኹ ፡ ሌላ ፥ ከስእለታችኹም ፡ ኹሉ ፡ ሌላ ፥ በፈቃዳችኹም ፡ ከምታቀርቧቸው ፡ ኹሉ ፡ ሌላ ፡ ናቸው ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 39 ፤ ከሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ የምድሩን ፡ ፍሬ ፡ ካከማቻችኹ ፡ በኋላ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ በዓል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ጠብቁ ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ይኹን ፥ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 40 ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የመልካም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬ ፥ የሰሌን ፡ ቅርንጫፍ ፥ የለመለመውን ፡ ዛፍ ፡ ቅርንጫፍ ፥ የወንዝም ፡ አሓያ ፡ ዛፍ ፡ ውሰዱ ፤ በአምላካችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 41 ፤ ይህንም ፡ በዓል ፡ በየዓመቱ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አድርጉ ፤ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ነው ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ትጠብቁታላችኹ ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 42 ፤ 43 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዳሶች ፡ ውስጥ ፡ ትቀመጣላችኹ ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኋቸው ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በዳስ ፡ ውስጥ ፡ እንዳስቀመጥኋቸው ፡ የልጅ ፡ ልጆቻችኹ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ በእስራኤል ፡ ያሉት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በዳስ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጡ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፥ 23 ፥ 44 ፤ ሙሴም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በዓላት ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገረ ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 2 ፤ መብራቱን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንድታበራበት ፡ ለመብራት ፡ ጥሩ ፡ ተወቅጦ ፡ የተጠለለ ፡ የወይራ ፡ ዘይት ፡ ያመጡልኽ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 3 ፤ በምስክሩ ፡ መጋረጃ ፡ ውጭ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ አሮን ፡ ከማታ ፡ እስከ ፡ ማለዳ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ያሰናዳው ፤ ለዘለዓለም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ሥርዐት ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 4 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጥሩ ፡ መቅረዝ ፡ ላይ ፡ መብራቶቹን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ያሰናዳቸው ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 5 ፤ መልካሙንም ፡ ዱቄት ፡ ወስደኽ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ኅብስት ፡ ጋግር ፤ ባንድ ፡ ኅብስት ፡ ውስጥ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 6 ፤ እነዚህንም ፡ ስድስት ፡ ስድስቱን ፡ በኹለት ፡ ተርታ ፡ አድርገኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በጥሩ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ አኑራቸው ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 7 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ለእሳት ፡ ቍርባን ፡ በእንጀራው ፡ ላይ ፡ ለመታሰቢያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በኹለቱ ፡ ተርታ ፡ ላይ ፡ ጥሩ ፡ ዕጣን ፡ አድርግ ።

ዘሌ. ፥ 24 ፥ 8 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ኹሉ ፡ በተርታ ፡ ያድርገው ፤ በእስራኤል ፡

ልጆች ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ ለአሮንና ፡ ለልጆቹም ፡ ይኹን ፤ በእሳት ፡ ከተደረገው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ በዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ለርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነውና ፥ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይብሉት ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ አባቱ ፡ ግብጻዊ ፡ የነበረ ፡ የእስራኤላዊት ፡ ልጅ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወጣ ፤ የእስራኤላዊቱ ፡ ልጅና ፡ አንድ ፡ እስራኤላዊ ፡ በሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ተጣሉ ፤

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ የእስራኤላዊቱም ፡ ልጅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ሰደበ ፥ አቃለለውም ፤ ወደ ፡ ሙሴም ፡ አመጡት ። እናቱም ፡ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የደብራይ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፥ ስሟም ፡ ሰሎሚት ፡ ነበረ ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ፍርድ ፡ እስኪወጣላቸው ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ አኖሩት ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ተሳዳቢውን ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጣው ፤ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይጫኑበት ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ይውገረው ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ትነግራለኽ ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ አምላኩን ፡ ቢሰድብ ፡ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ የሚሰድብ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ይውገሩት ፤ መጻተኛ ፡ ወይም ፡ የአገር ፡ ልጅ ፡ ቢኾን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በሰደበ ፡ ጊዜ ፡ ይገደል ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ ሰውንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የሚመታ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ እንስሳንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የሚመታ ፡ ሕይወት ፡ በሕይወት ፡ ፋንታ ፡ ካሣውን ፡ ይክፈል ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ሰውም ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢጐዳ ፥ ርሱ ፡ እንዳደረገ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግበት ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ስብራት ፡ በስብራት ፡ ፋንታ ፥ ዐይን ፡ በዐይን ፡ ፋንታ ፥ ጥርስ ፡ በጥርስ ፡ ፋንታ ፥ ሰውን ፡ እንደ ፡ ጐዳ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግበት ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ እንስሳውንም ፡ የሚገድል ፡ ካሳ ፡ ይተካ ፤ ሰውንም ፡ የሚገድል ፡ ይገደል ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝና ፡ ለመጻተኛና ፡ ለአገር ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ሕግ ፡ ይኹንላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገራቸው ፤ ተሳዳቢውንም ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጡት ፥ በድንጋይም ፡ ወገሩት ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ እኔ ፡ ወደምሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፡ ታድርግ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ዕርሻኽን ፡ ዝራ ፥ ስድስት ፡ ዓመትም ፡ ወይንኽን ፡ ቍረጥ ፡ ፍሬዋንም ፡ አግባ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ግን ፡ ለምድሪቱ ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ሰንበት ፥ ትኹን ፤ ዕርሻኽን ፡ አትዝራ ፥ ወይንኽንም ፡ አትቀሥረጥ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ የምድራችኹን ፡ የገቦ ፡ አትጨደው ፥ ያልተቈረጠውንም ፡ የወይንኽን ፡ ፍሬ ፡ አታከማች ፤ ለምድሪቱ ፡ የዕረፍት ፡ ሰንበት ፡ ዓመት ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ የምድርም ፡ ሰንበት ፡ ለአንተ ፥ ለወንድ ፡ ባሪያኽም ፥ ለሴት ፡ ባሪያኽም ፥ ለምንደኛውም ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለሚኖር ፡ ለመጻተኛም ፡ ምግብ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ ለእንስሳዎችኽም ፥ በምድርኽም ፡ ላሉት ፡ አራዊት ፡ ፍሬዋ ፡ ኹሉ ፡ መኖ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ አድርገኽ ፡ የዓመታትን ፡ ሰንበት ፡ ሰባት ፡ ቍጠር ፤ የሰባት ፡ ዓመታትም ፡ ሰንበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ትቈጥራለኽ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ በቀንደ ፡ መለከት ፡ ታውጃለኽ ፤ በማስተስረያ ፡ ቀን ፡ በምድራችኹ ፡ ኹሉ ፡ በቀንደ ፡ መለከት ፡ ታውጃላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ዐምሳኛውንም ፡ ዓመት ፡ ትቀድሳላችኹ ፥ በምድሪቱም ፡ ለሚኖሩባት ፡ ኹሉ ፡ ነጻነትን ፡ ታውጃላችኹ ፤ ርሱ ፡ ለእናንተ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርስቱና ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ ያ ፡ ዐምሳኛው ፡ ዓመት ፡ ለእናንተ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ይኾናል ፤ በርሱም ፡ አትዝሩ ፥ የገቦውንም ፡ አትጨዱ ፥ የወይኑንም ፡ ፍሬ ፡ አታከማቹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ ኢዮቤልዩ ፡ ነውና ፥ የተቀደሰ ፡ ይኹንላችኹ ፤ በሜዳ ፡ ላይ ፡ የበቀለውን ፡ ብሉ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ በዚች ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለሳል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ለባልንጀራኽም ፡ አንዳች ፡ ብትሸጥለት ፥ ወይም ፡ ከባልንጀራኽ ፡ እጅ ፡ ብትገዛ ፥ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ አያታልል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ ከኢዮቤልዩ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ዓመታቱ ፡ ቍጥር ፡ ከባልንጀራኽ ፡ ትገዛለኽ ፤ ርሱም ፡ እንደ ፡ መከሩ ፡ ዓመታት ፡ ቍጥር ፡ ይሸጥልኻል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ እንደ ፡ ዓመታቱ ፡ ብዛት ፡ ዋጋውን ፡ ታበዛለኽ ፥ እንደ ፡ ዓመታቱም ፡ ማነስ ፡ ዋጋውን ፡ ታሳንሳለኽ ፤ እንደ ፡ መከሩ ፡ ቍጥር ፡ ይሸጥልኻል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝና ፡ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ አያታልል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽን ፡ ፍራ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ ሥርዐቴንም ፡ አድርጉ ፥ ፍርዶቼንም ፡ ጠብቁ ፡ አድርጉትም ፤ በምድሪቱም ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ ትኖራላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ትሰጣለች ፥ እስክትጠግቡም ፡ ድረስ ፡ ትበላላችኹ ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ በጸጥታ ፡ ትኖራላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ እናንተም ፦ ካልዘራን ፥ እኽላችንንም ፡ ካላከማቸን ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ምን ፡ እንበላለን ፧ ብትሉ ፥

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ በረከቴን ፡ በላያችኹ ፡ አዛለኹ ፤ ምድሪቱም ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ በስምንተኛውም ፡ ዓመት ፡ ትዘራላችኹ ፥ ከአሮጌውም ፡ እኽል ፡ ትበላላችኹ ፤ ፍሬዋ ፡ እስኪገባ ፥ እስከ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፥ ከአሮጌው ፡ እኽል ፡ ትበላላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ ምድርም ፡ ለእኔ ፡ ናትና ፥ እናንተም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እንግዳዎችና ፡ መጻተኞች ፡ ናችኹና ፥ ምድርን ፡ ለዘለዓለም ፡ አትሸጡ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ በርስታችኹም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ መቤዠትን ፡ ለምድሪቱ ፡ አድርጉ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ ወንድምኽም ፡ ቢደኸይ ፡ ከርስቱም ፡ ቢሸጥ ፥ ለርሱ ፡ የቀረበ ፡ ዘመዱ ፡ መጥቶ ፡ ወንድሙ ፡ የሸጠውን ፡ ይቤዠዋል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ የሚቤዠውም ፡ ሰው ፡ ቢያጣ ፥ ርሱም ፡ እጁ ፡ ቢረጥብ ፥ ለመቤዠትም ፡ የሚበቃ ፡ ቢያገኝ ፥

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ የሸያጩን ፡ ዘመን ፡ ቈጥሮ ፡ የቀረውን ፡ ወደገዛው ፡ ሰው ፡ ይመልስ ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ለራሱም ፡ ዕዳውን ፡ መክፈል ፡ ባይችል ፥ ሸያጩ ፡ በገዛው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ እስከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይቀመጥ ፤ በኢዮቤልዩም ፡ ዓመት ፡ ይውጣ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይመለስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 29 ፤ ሰውም ፡ ቅጥር ፡ ባለበት ፡ ከተማ ፡ መኖሪያ ፡ ቤትን ፡ ቢሸጥ ፥ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ለመቤዠት ፡ ይችላል ፤ ላንድ ፡ ሙሉ ፡ ዓመት ፡ መቤዠት ፡ ይችላል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 30 ፤ አንድ ፡ ዓመትም ፡ እስኪጨረስ ፡ ባይቤዠው ፥ ቅጥር ፡ ባለበት ፡ ከተማ ፡ የሚኾን ፡ ቤት ፡ ለገዛው ፡ ለልጅ ፡ ልጁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናለታል ፤ በኢዮቤልዩም ፡ ከርሱ ፡ አይወጣም ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 31 ፤ ቅጥር ፡ በሌለበት ፡ መንደር ፡ ያሉ ፡ ቤቶች ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ይቈጠራሉ ፤ ይቤዠሉ ፥ በኢዮቤልዩም ፡ ይወጣሉ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 32 ፤ በእነርሱ ፡ ከተማ ፡ ያለ ፡ የሌዋውያን ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ሌዋውያን ፡ ለዘለዓለም ፡ መቤዠት ፡ ይችላሉ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 33 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሌዋውያን ፡ ቢገዛ ፥ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የሌዋውያን ፡ ከተማ ፡ ቤቶች ፡ ርስቶቻቸው ፡ ናቸውና ፥ በርስቱ ፡ ከተማ ፡ ያለ ፡ የተሸጠው ፡ ቤት ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ይመለሳል ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 34 ፤ በከተማቸውም ፡ ዙሪያ ፡ ያለችው ፡ መሰምሪያ ፡ የዘለዓለም ፡ ርስታቸው ፡ ናትና ፥ አትሸጥም ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 35 ፤ ወንድምኽ ፡ ቢደኸይ ፡ እጁም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢደክም ፥ አጽናው ፤ እንደ ፡ እንግዳና ፡ እንደ ፡ መጻተኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 36 ፤ ወንድምኽ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ምንም ፡ ወለድ ፡ ወይም ፡ ትርፍ ፡ አትውሰድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽን ፡ ፍራ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 37 ፤ ብርኽን ፡ በወለድ ፡ አታበድረው ፤ መኖኽንም ፡ በትርፍ ፡ አትስጠው ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 38 ፤ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ እሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፥ አምላክም ፡ እኾናችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 39 ፤ ወንድምኽም ፡ ቢደኸይ ፡ ራሱንም ፡ ለአንተ ፡ ቢሸጥ ፥ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አድርገኽ ፡ አትግዛው ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 40 ፤ እንደ ፡ ምንደኛና ፡ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ እስከኢዮቤልዩም ፡ ዓመት ፡

ያገልግልኽ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 41 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ርሱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ከአንተ ፡ ይውጣ ፥ ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ ወዳባቱም ፡ ርስት ፡ ይመለስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 42 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸው ፡ ባሪያዎቼ ፡ ናቸውና ፥ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ አይሸጡ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 43 ፤ በጽኑ ፡ እጅ ፡ አትግዛው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽን ፡ ፍራ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 44 ፤ ወንድ ፡ ባሪያና ፡ ሴት ፡ ባሪያ ፡ መግዛት ፡ ብትፈልግ ፡ ግን ፡ በዙሪያችኹ ፡ ካሉት ፡ ከነርሱ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባሪያዎችን ፡ ግዙ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 45 ፤ ደግሞም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ከሚቀመጡት ፡ መጻተኞች ፥ በምድራችኹም ፡ ውስጥ ፡ ከወለዷቸው ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ከሚቀመጡት ፡ ከዘራቸው ፡ ውስጥ ፡ ባሪያዎችን ፡ ግዙ ፤ ርስትም ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 46 ፤ ከእናንተም ፡ በኋላ ፡ ልጆቻችኹ ፡ ይወርሷቸው ፡ ዘንድ ፡ ተዉአቸው ፤ ከነርሱም ፡ ባሪያዎችን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትወስዳላችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ አትግዟቸው ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 47 ፤ ባንተም ፡ ዘንድ ፡ የሚኖር ፡ መጻተኛ ፡ ወይም ፡ እንግዳ ፡ ሀብታም ፡ ቢኾን ፥ ወንድምኽም ፡ በርሱ ፡ አጠገብ ፡ ቢደኸይ ፥ ራሱንም ፡ ለመጻተኛው ፡ ወይም ፡ ለእንግዳው ፡ ወይም ፡ ለወገኖቹ ፡ ዘር ፡ ቢሸጥ ፥

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 48 ፤ ከተሸጠ ፡ በኋላ ፡ መቤዠት ፡ ይችላል ፤ ከወንድሞቹ ፡ አንዱ ፡ ይቤዠው ፤

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 49 ፤ ወይም ፡ አጎቱ ፡ ወይም ፡ የአጎቱ ፡ ልጅ ፡ ይቤዠው ፤ ወይም ፡ ከወገኑ ፡ ለርሱ ፡ የቀረበ ፡ ዘመድ ፡ ይቤዠው ፤ ወይም ፡ ርሱ ፡ እጁ ፡ ቢረጥብ ፡ ራሱን ፡ ይቤዠው ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 50 ፤ ከገዛውም ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ከገዛበት ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ይቀኑጠር ፤ የሸያጩም ፡ ብር ፡ እንደ ፡ ዓመታቱ ፡ ቍጥር ፡ ይኹን ፤ እንደ ፡ ምንደኛውም ፡ ዘመን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 51 ፤ ብዙ ፡ ዓመታትም ፡ ቢቀሩ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ቍጥር ፡ ከሸያጩ ፡ ብር ፡ የመቤዠቱን ፡ ዋጋ ፡ ይመልስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 52 ፤ እስከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ ቢቀሩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይቈጥራል ፤ እንደ ፡ ዓመታቱም ፡ መጠን ፡ የመቤዠቱን ፡ ዋጋ ፡ ይመልስ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 53 ፤ በየዓመቱ ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፤ በፊትኽ ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ አይግዛው ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 54 ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ዥሉ ፡ ግን ፡ ባይቤዥ ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ርሱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ይውጣ ።

ዘሌ. ፡ 25 ፡ 55 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ ባሪያዎች ፡ ናቸውና ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸው ፡ ባሪያዎቼ ፡ ናቸው ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝና ፡ ለእናንተ ፡ ጣዖት ፡ አታድርጉ ፥ የተቀረጸም ፡ ምስል ፡ ወይም ፡ ሐውልት ፡ አታቁሙ ፤ ትሰግዱለትም ፡ ዘንድ ፡ በምድራችኹ ፡ ላይ ፡ የተቀረጸ ፡ ድንጋይ ፡ አታኑሩ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ ሰንበታቴን ፡ ጠብቁ ፥ መቅደሴንም ፡ ፍሩ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ በሥርዐቴ ፡ ብትኼዱ ፥ ትእዛዛቴንም ፡ ብትጠብቁ ፡ ብታደርጉትም ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ዝናባችኹን ፡ በወቅቱ ፡ አዘንባለኹ ፥ ምድሪቱም ፡ እኽሏን ፡ ትሰጣለች ፥ የሜዳው ፡ ዛፎችም ፡ ፍሬያቸውን ፡ ይሰጣሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ የእኽሉም ፡ ማበራየት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እስከወይኑ ፡ መቍረጥ ፡ ይደርሳል ፥ የወይኑም ፡ መቍረጥ ፡ እስከእኽሉ ፡ መዝራት ፡ ይደርሳል ፤ እስክትጠግቡም ፡ ድረስ ፡ እንጀራችኹን ፡ ትበላላችኹ ፥ በምድራችኹም ፡ ላይ ፡ በጸጥታ ፡ ትኖራላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ በምድራችኹም ፡ ላይ ፡ ሰላምን ፡ እሰጣለኹ ፥ ማንም ፡ ሳያስፈራችኹ ፡ ትተኛላችኹ ፤ ክፉዎችንም ፡ አራዊት ፡ ከምድራችኹ ፡ አጠፋለኹ ፥ ሰይፍም ፡ በምድራችኹ ፡ ላይ ፡ አያልፍም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ጠላቶቻችኹንም ፡ ታሳድዳላችኹ ፥ በፊታችኹም ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ ከእናንተም ፡ ዐምስቱ ፡ መቶውን ፡ ያሳድዳሉ ፥ መቶውም ፡ ዐሥሩን ፡ ሺሕ ፡ ያሳድዳሉ ፤ ጠላቶቻችኹም ፡ በፊታችኹ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ፊቴም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይኾናል ፥ እንድታፈሩም ፡ አደርጋችኋለኹ ፥ አበዛችኹማለኹ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አጸናለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የተቀመጠውንም ፡ አሮጌውን ፡ እኽል ፡ ትበላላችኹ ፤ ከዐዲሱም ፡ በፊት ፡ አሮጌውን ፡ ታወጣላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ ማደሪያዬንም ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ አደርጋለኹ ፤ ነፍሴም ፡ አትጸየፋችኹም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ በመካከላችኹም ፡ እኼዳለኹ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ፥ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ባሪያዎች ፡ እንዳትኾኗቸው ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፤ የባርነታችኹን ፡ ቀንበር ፡ ሰብሬያለኹ ፤ ቀና ፡ ብላችኹ ፡ እንድትኼዱ ፡ አድርጌያችኋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባትሰሙኝ ፥ እነዚህንም ፡ ትእዛዛት ፡ ሹሉ ፡ ባታደርጉ ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ሥርዐቴንም ፡ ብትንቁ ፥ ትእዛዛቴንም ፡ ሹሉ ፡ እንዳታደርጉ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ እንድታፈርሱ ፡ ነፍሳችኹ ፡ ፍርዴን ፡ ብትጸየፍ ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ እኔም ፡ እንዲህ ፡ አደርግባችኋለኹ ፤ ፍርሀትን ፥ ክሳትንም ፥ ዐይናችኹንም ፡ የሚያፈዝ ፥ ሰውነታችኹንም ፡ የሚያማስን ፡ ትኵሳት ፡ አወርድባችኋለኹ ፤ ዘራችኹንም ፡ በከንቱ ፡ ትዘራላችኹ ፥ ጠላቶቻችኹ ፡ ይበሉታልና ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ፊቴንም ፡ አከብድባችኋለኹ ፥ በጠላቶቻችኹም ፡ ፊት ፡ ትወድቃላችኹ ፤ የሚጠሏችኹም ፡ ይገዟችኋል ፤ ማንም ፡ ሳያሳድዳችኹ ፡ ትሸሻላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትሰሙኝ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችኹ ፡ በቅጣታችኹ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ እጨምራለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ የኀይላችኹንም ፡ ትዕቢት ፡ እሰብራለኹ ፤ ሰማያችኹንም ፡ እንደ ፡ ብረት ፥ ምድራችኹንም ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ አደርጋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ ጕልበታችኹም ፡ በከንቱ ፡ ያልቃል ፤ ምድራችኹም ፡ እኽሏን ፡ አትሰጥም ፥ የምድርም ፡ ዛፎች ፡

ፍሬያቸውን ፡ አይሰጡም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ በእንቢተኝነትም ፡ ብትኼዱብኝ ፡ ባትሰሙኝም ፥ እንደ ፡ ኀጢአታችኹ ፡ መጠን ፡ በመቅሠፍት ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ እጨምራለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ በመካከላችኹም ፡ የምድርን ፡ አራዊት ፡ እሰዳለኹ ፤ ልጆቻችኹንም ፡ ይነጥቃሉ ፥ እንስሳዎቻችኹንም ፡ ያጠፋሉ ፥ እናንተንም ፡ ያሳንሳሉ ፤ መንገዶቻችኹም ፡ በረሓ ፡ ይኾናሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 23 ፤ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትቀጡ ፥ በእንቢተኝነትም ፡ ብትኼዱ ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በእንቢተኝነት ፡ እኼድባችኋለኹ ፤ ስለ ፡ ኀጢአታችኹም ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ እመታችኋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ የቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ በቀል ፡ ይበቀልባችኹ ፡ ዘንድ ፡ ሰይፍ ፡ አመጣባችኋለኹ ፤ ወደ ፡ ከተማችኹም ፡ ትሰበሰባላችኹ ፥ ቸነፈርንም ፡ እሰድባችኋለኹ ፤ በጠላትም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣችኋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ የእኽላችኹንም ፡ ድጋፍ ፡ በሰበርኹ ፡ ጊዜ ፥ ዐሥር ፡ ሴቶች ፡ እንጀራቸውን ፡ ባንድ ፡ ምጣድ ፡ ይጋግራሉ ፥ በሚዛንም ፡ መዝነው ፡ እንጀራችኹን ፡ ይመልሱላችኋል ፤ በበላችኹም ፡ ጊዜ ፡ አትጠግቡም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ እስከዚህም ፡ ድረስ ፡ ባትሰሙኝ ፥ በእንቢተኝነትም ፡ ብትኼዱብኝ ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በቍጣ ፡ እኼድባችኋለኹ ፤ ስለ ፡ ኀጢአታችኹም ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ እቀጣችኋለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 29 ፤ የወንዶች ፡ ልጆቻችኹንም ፡ ሥጋ ፡ ትበላላችኹ ፤ የሴቶች ፡ ልጆቻችኹንም ፡ ሥጋ ፡ ትበላላችኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቻችኹንም ፡ አፈርሳለኹ ፥ የፀሓይ ፡ ምስሎቻችኹንም ፡ አጠፋለኹ ፥ ሬሳችኹንም ፡ በጣዖቶቻችኹ ፡ ሬሳዎች ፡ ላይ ፡ እጥላለኹ ፤ ነፍሴም ፡ ትጸየፋችኋለች ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ ከተማዎቻችኹንም ፡ ባድማ ፡ አደርጋለኹ ፥ መቅደሶቻችኹንም ፡ አፈርሳለኹ ፥ መልካሙንም ፡ መዐዛችኹን ፡ አላሸትም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ ምድሪቱንም ፡ የተፈታች ፡ አደርጋለኹ ፤ የሚቀመጡባት ፡ ጠላቶቻችኹም ፡ በርሷ ፡ የተነሣ ፡ ይደነቃሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 33 ፤ እናንተንም ፡ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበትናችኋለኹ ፥ ሰይፍንም ፡ አስመዝዝባችኋለኹ ፤ ምድራችኹም ፡ የተፈታች ፡ ትኾናለች ፥ ከተማዎቻችኹም ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 34 ፤ በዚያም ፡ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡ ዥሉ ፡ እናንተም ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ምድር ፡ ሳላችኹ ፥ ምድሪቱ ፡ ሰንበት ፡ በማድረጓ ፡ ትደሰታለች ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ ታርፋለች ፥ ሰንበትንም ፡ በማድረጓ ፡ ትደሰታለች ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 35 ፤ እናንተ ፡ ተቀምጣችኹባት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በሰንበቶቻችኹ ፡ አላረፈችም ፡ ነበርና ፥ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡ ዥሉ ፡ ታርፋለች ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 36 ፤ በጠላቶቻቸውም ፡ ምድሮች ፡ ሳሉ ፡ ከእናንተ ፡ ተለይተው ፡ በቀሩት ፡ ላይ ፡ በልባቸው ፡ ድንጋጤን ፡ እሰድባቸዋለኹ ፤ በነፋስም ፡ የምትንቀሳቀስ ፡ የቅጠል ፡ ድምፅ ፡ ታሸብራቸዋለች ፤ ከሰይፍ ፡ እንደሚሸሹ ፡ ይሸሻሉ ፤ ማንም ፡ ሳያሳድዳቸው ፡ ይወድቃሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 37 ፤ ማንም ፡ ሳያሳድዳቸው ፡ ከሰይፍ ፡ እንዲሸሹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይሰነካከላሉ ፤ እናንተም ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አትችሉም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 38 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ታልቃላችኹ ፥ የጠላቶቻችኹም ፡ ምድር ፡ ትውጣችኋለች ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 39 ፤ ከእናንተም ፡ ተለይተው ፡ የቀሩት ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በኀጢአታቸው ፡ ይከሳሉ ፤ በአባቶቻቸውም ፡ ኀጢአት ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይከሳሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 40 ፤ በእኔም ፡ ላይ ፡ በእንቢተኝነት ፡ ስለ ፡ ኼዱብኝ ፡ የበደሉኝን ፡ በደል ፥ ኀጢአታቸውንም ፥ የአባቶቻቸውንም ፡ ኀጢአት ፡ ይናዘዛሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 41 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በእንቢተኝነት ፡ ኼድኩባቸው ፤ ወደጠላቶቻቸውም ፡ ምድር ፡ አገባኋቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያልተገረዘው ፡ ልባቸው ፡ ቢዋረድ ፥ የኀጢአታቸውንም ፡ ቅጣት ፡ ቢቀበሉ ፥

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 42 ፤ እኔ ፡ ለያዕቆብ ፡ የማልኩትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ዐስባለኹ ፤ ደግሞ ፡ ለይሥሐቅና ፡ ለአብርሃም ፡ የማልኩትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ዐስባለኹ ፤ ምድሪቱንም ፡ ዐስባለኹ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 43 ፤ ምድርም ፡ ከነርሱ ፡ መጥፋት ፡ የተነሣ ፡ ባዶ ፡ ትቀራለች ፤ እነርሱም ፡ ሳይኖሩ ፡ በተፈታችበት ፡ ዘመን ፡ ሰንበት ፡ በማድረጓ ፡ ትደሰታለች ፤ ፍርዴንም ፡ ስለ ፡ ናቁ ፥ ነፍሳቸውም ፡ ሥርዐቴን ፡ ስለ ፡ ተጸየፈች ፡ የኀጢአታቸውን ፡ ቅጣት ፡ ይሸከማሉ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 44 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ ነኝና ፥ እነርሱ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ምድር ፡ ሳሉ ፥ እስካጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ያለኝን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እስካፈርስ ፡ ድረስ ፡ አልጥላቸውም ፥ አልጸየፋቸውምም ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 45 ፤ እኔ ፡ አምላካቸው ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብ ፡ እያዩ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋቸውን ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ዐስባለኹ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘሌ. ፡ 26 ፡ 46 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በርሱና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ያደረጋቸው ፡ ሥርዐቶችና ፡ ፍርዶች ፡ ሕግጋትም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

_____ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። _____

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሰውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሊሰጥ ፡ ቢሳል ፡ አንተ ፡ እንደምትገምተው ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ዋጋውን ፡ ይስጥ ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ ለወንድ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ግምቱ ፡ ዐምሳ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ሴትም ፡ ብትኾን ፡ ግምቷ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ከዐምስት ፡ ዓመትም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ግምቱ ፡ ለወንድ ፡ ኻያ ፡ ሰቅል ፥ ለሴትም ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ ካንድ ፡ ወርም ፡ እስከ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ለወንድ ፡ ግምቱ ፡ ዐምስት ፡ የብር ፡ ሰቅል ፥ ለሴትም ፡ ግምቷ ፡ ሦስት ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ከስድሳ ፡ ዓመትም ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ወንድ ፡ ቢኾን ፡ ግምቱ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡

ሰቅል ፥ ለሴትም ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 8 ፤ ለግምቱም ፡ የሚከፍለውን ፡ ቢያጣ ፡ ግን ፡ በካህኑ ፡ ፊት ፡ ይቁም ፥ ካህኑም ፡ የተሳለውን ፡ ሰው ፡ ይገምተው ፤ ካህኑም ፡ የተሳለው ፡ ሰው ፡ እንደሚችል ፡ መጠን ፡ ይገምተው ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 9 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ የሚያቀርበው ፡ እንስሳ ፡ ቢኾን ፥ ሰው ፡ ከነዚህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሰጠው ፡ ኹሉ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 10 ፤ መልካሙን ፡ በክፉ ፥ ክፉውንም ፡ በመልካም ፡ አይለውጥ ፤ እንስሳንም ፡ በእንስሳ ፡ ቢለውጥ ፡ ርሱና ፡ ልዋጩ ፡ የተቀደሱ ፡ ይኾናሉ ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 11 ፤ እንስሳው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ መኾን ፡ የማይገባው ፡ ርኩስ ፡ ቢኾን ፥ እንስሳውን ፡ በካህኑ ፡ ፊት ፡ ያኑረው ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 12 ፤ መልካምም ፡ ቢኾን ፡ ክፉም ፡ ቢኾን ፡ ካህኑ ፡ ይገምተው ፤ ካህኑም ፡ እንደሚገምተው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ይኹን ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 13 ፤ ይቤዣውም ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፡ ከግምቱ ፡ በላይ ፡ ዐምስተኛ ፡ ይጨምር ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 14 ፤ ሰውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ቤቱን ፡ ቢቀድስ ፥ ካህኑ ፡ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይገምተዋል ፤ ካህኑም ፡ እንደሚገምተው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ይቆማል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 15 ፤ የቀደሰውም ፡ ሰው ፡ ቤቱን ፡ ይቤዣው ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፡ ከግምቱ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ ዐምስተኛ ፡ ይጨምር ፤ ቤቱም ፡ ለርሱ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 16 ፤ ሰውም ፡ ከርስቱ ፡ ዕርሻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቢቀድስ ፥ እንደ ፡ መዘራቱ ፡ መጠን ፡ ይገመት ፤ አንድ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ የሚዘራበት ፡ ዕርሻ ፡ ዐምሳ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ይገመታል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 17 ፤ ዕርሻውንም ፡ ከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ቢቀድስ ፥ እንደ ፡ ግምቱ ፡ መጠን ፡ ይቆማል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 18 ፤ ዕርሻውንም ፡ ከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ቢቀድስ ፥ ካህኑ ፡ እስከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ቀሩት ፡ ዓመታት ፡ ገንዘቡን ፡ ይቈጥርለታል ፤ ከግምቱም ፡ ይጐድላል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 19 ፤ ዕርሻውንም ፡ የቀደሰ ፡ ሰው ፡ ይቤዣው ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፥ ከግምቱ ፡ ገንዘብ ፡ በላይ ፡ ዐምስተኛ ፡ ይጨምር ፤ ለርሱም ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 20 ፤ ዕርሻውንም ፡ ባይቤዣው ፥ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ቢሸጥ ፥ እንደገና ፡ ይቤዣው ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 21 ፤ ዕርሻው ፡ ግን ፡ በኢዮቤልዩ ፡ ሲወጣ ፡ እንደ ፡ ዕርም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ዕርሻ ፡ ይኾናል ፤ ርስቱ ፡ ለካህኑ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 22 ፤ ከርስቱ ፡ ዕርሻ ፡ ያልኾነውን ፡ የገዛውን ፡ ዕርሻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቢቀድስ ፥

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 23 ፤ ካህኑ ፡ እስከኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ የግምቱን ፡ ዋጋ ፡ ይቈጥርለታል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ግምቱን ፡ እንደ ፡ ተቀደሰ ፡ ነገር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰጣል ።

ዘሌ. ፥ 27 ፥ 24 ፤ በኢዮቤልዩ ፡ ዓመት ፡ ዕርሻው ፡ የምድሪቱ ፡ ባለርስት ፡ ወደነበረው ፡ ወደሸጠው ፡ ሰው ፡ ይመለሳል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ ግምቱም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ይኾናል ፤ ሰቅሉ ፡ ኻያ ፡ አቦሊ ([75]) ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የሚቀርበውን ፡ የእንስሳ ፡ በኩራት ፡ ማንም ፡ ይቀድሰው ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ፤ በሬ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ የረከሰም ፡ እንስሳ ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ግምቱ ፡ ይቤዣው ፥ በርሱም ፡ የዋጋውን ፡ ዐምስተኛ ፡ ይጨምርበታል ፤ ባይቤዣውም ፡ እንደ ፡ ግምቱ ፡ ይሸጣል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 28 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ የተለየ ፡ ዕርም ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡ ወይም ፡ የርስቱ ፡ ዕርሻ ፡ ቢኾን ፥ አይሸጥም ፥ አይቤዥም ፤ ዕርም ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 29 ፤ ከሰዎችም ፡ ዕርም ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ አይቤዥም ፤ ፈጽሞ ፡ ይገደላል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 30 ፤ የምድርም ፡ ዓሥራት ፥ ወይም ፡ የምድር ፡ ዘር ፡ ወይም ፡ የዛፍ ፡ ፍሬ ፡ ቢኾን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 31 ፤ ሰውም ፡ ዓሥራቱን ፡ ሊቤዥ ፡ ቢወድ ፥ ዐምስተኛ ፡ ይጨምርበታል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 32 ፤ ከበሬም ፡ ኹሉ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፥ ከእረኛውም ፡ በትር ፡ በታች ፡ ከሚያልፍ ፡ በግና ፡ ፍየል ፡ ኹሉ ፡ ከዐሥር ፡ አንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 33 ፤ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ እንዲኾን ፡ አይመርምር ፥ አይለውጥም ፤ ቢለውጠውም ፡ ርሱና ፡ ልዋጩ ፡ የተቀደሱ ፡ ይኾናሉ ፤ አይቤዣውም ።

ዘሌ. ፡ 27 ፡ 34 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ ትእዛዛት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ❖

---

75 ጽር. ፥ አቦሎስ ፡ (የገንዘብ ፡ ስም ፥ የዲድርክም ፡ ኻያኛ ፥ በዕብራይስጥ ፡ ጌራ ፡ ፤ ሰቅል ፡ እንዲኾን ፥ ኻያው ፡ አቦሊ ፡ ፤ ዲድክርም ፡ ነው ፡ (ከ.ወ.ክ. ፥ ገ.197) ። ዕብ. ፥ ጌራህ ፡ (ገርህ ፥ የንግድ ፡ ዕቃ ፥ ሽቀጥ) ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፥ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ድምር ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ በየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ወንዱን ፡ በየራሱ ፥ ውሰዱ ።

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፥ ከእስራኤል ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡትን ፡ ኹሉ ፥ አንተና ፡ አሮን ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ ቍጠሯቸው ።

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከየነገዱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የአባቶቹ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ የሚቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ስሞቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከሮቤል ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ኤሊሱር ፥ ከስምዖን ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለሚኤል ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ከይሁዳ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአሶን ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ከይሳኮር ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ 10 ፤ ከዛብሎን ፡ የኬሎን ([76]) ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ([77]) ፥ ከዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ከኤፍሬም ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳማ ፥ ከምናሴ ፡ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ ገማልኤል ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ከብንያም ፡ የጋዴዮን ፡ ልጅ ፡ አቢዳን ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ከዳን ፡ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ አኪዔዘር ([78]) ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ከአሴር ፡ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግኤል ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ከጋድ ፡ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፥

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ከንፍታሌም ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡ አኪሬ ([79]) ።

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ከማኅበሩ ፡ የተመረጡ ፡ የእስራኤል ፡ አእላፍ ፡ ታላላቆች ፥ የአባቶቻቸው ፡ ነገድ ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ እነዚህን ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ ወሰዷቸው ፤

ዘኍ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ማኅበሩን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰቧቸው ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡

---

76 ዕብ. ፥ ኀይሎን ፡ (ኀያል) ።

77 ዕብ. ፥ ኤሊያብ ፡ (ያባት ፡ አምላክ)

78 ዕብ. ፥ አኒዔዜር ፡ (የርዳታ ፡ ወንድም) ።

79 ዕብ. ፥ አኒራዕ ፡ (የጥፋት ፡ ወንድም) ።

ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ በየራሱ ፡ በየወገኑም ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ በየስማቸው ፡ ቍጥር ፡ ትውልዳቸውን ፡ ተናገሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ቈጠራቸው ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ የእስራኤል ፡ በኵር ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ በየራሳቸው ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ሹሉ ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ የተቈጠሩ ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ በየራሳቸው ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ወንድ ፡ ሹሉ ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ከስምዖን ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ የጋድ ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ከጋድ ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሰባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ የዛብሎን ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ ከዮሴፍ ፡ ልጆች ፥ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 33 ፤ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 34 ፤ የምናሴ ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 35 ፤ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 36 ፤ የብንያም ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ሹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 37 ፤ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 38 ፤ የዳን ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ኹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 39 ፤ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 40 ፤ የአሴር ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ኹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 41 ፤ ከአሴር ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 42 ፤ የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ በየትውልዳቸው ፥ በየወገናቸው ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ እንደየስማቸው ፡ ቍጥር ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ኹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 43 ፤ ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 44 ፤ የተቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ የእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ የቈጠሯቸው ፥ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እያንዳንዱ ፡ የአባቶቹ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 45 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተቈጠሩት ፡ ኹሉ ፥ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡት ፡ ኹሉ ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 46 ፤ የተቈጠሩት ፡ ኹሉ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 47 ፤ ሌዋውያን ፡ ግን ፡ በያባቶቻቸው ፡ ነገድ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አልተቈጠሩም ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 48 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ የሌዊን ፡ ነገድ ፡ አትቍጠረው ፥

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 49 ፤ ቍጥራቸውንም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አታድርግ ፤

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 50 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምስክሩ ፡ ማደሪያና ፡ በዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ለርሱም ፡ በሚኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሌዋውያንን ፡ አቁማቸው ። ማደሪያውንና ፡ ዕቃዎችን ፡ ኹሉ ፡ ይሸከሙ ፥ ያገልግሉትም ፥ በማደሪያውም ፡ ዙሪያ ፡ ይስፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 51 ፤ ማደሪያውም ፡ ሲነሣ ፡ ሌዋውያን ፡ ይንቀሉት ፤ ማደሪያውም ፡ በሰፈረ ፡ ጊዜ ፡ ሌዋውያን ፡ ይትከሉት ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 52 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ በየሰፈሩ ፥ በየዐላማውም ፥ በየጭፍራውም ፡ ይሰፍራሉ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 53 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይወርድ ፡ ሌዋውያን ፡ በምስክሩ ፡ ማደሪያ ፡ ዙሪያ ፡ ይስፈሩ ፤ ሌዋውያንም ፡ የምስክሩን ፡ ማደሪያ ፡ ይጠብቁ ።

ዘኍ. ፡ 1 ፡ 54 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴና ፡ ለአሮን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ በየዐላማው ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ምልክት ፡ ይስፈሩ ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አፋዛኛ ፡ ዙሪያ ፡ ይስፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወደፀሓይ ፡ መውጫ ፡ የሚሰፍሩት ፡ እንደ ፡ ሰራዊቶቻቸው ፡ የይሁዳ ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ ሰዎች ፡ ይኾናሉ ፤ የይሁዳ ፡ ልጆችም ፡ አለቃ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአሶን ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ሰባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የሚሰፍሩ ፡ የይሳኮር ፡ ነገድ ፡ ይኾናሉ ፤ የይሳኮርም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የዛብሎን ፡ ነገድ ፡ ነበረ ፤ የዛብሎንም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ዐምሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ከይሁዳ ፡ ሰፈር ፡ የተቈጠሩ ፡ ኹሉ ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ አስቀድመው ፡ ይጓዛሉ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ የሮቤል ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡ ኤሊሱር ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ አርባ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የሚሰፍሩ ፡ የስምዖን ፡ ነገድ ፡ ናቸው ፤ የስምዖንም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለሚኤል ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ዐምሳ ፡ ዘጠኝ ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የጋድ ፡ ነገድ ፡ ነበረ ፤ የጋድም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ከሮቤል ፡ ሰፈር ፡ የተቈጠሩ ፡ ኹሉ ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ ቀጥለው ፡ ይጓዛሉ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በሰፈሮቹም ፡ መካከል ፡ የሌዋውያን ፡ ሰፈር ፡ ይጓዛል ፤ እንደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በየስፍራው ፡ በየዐላማውም ፡ ይጓዛሉ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ሰራዊቶቻቸው ፡ የኤፍሬም ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ፤ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳማ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የምናሴ ፡ ነገድ ፡ ይኾናል ፤ የምናሴም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ ገማልኤል ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የብንያም ፡ ነገድ ፡ ይኾናል ፤ ይብንያምም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የጋዴዮን ፡ ልጅ ፡ አቢዳን ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ከኤፍሬም ፡ ሰፈር ፡ የተቈጠሩ ፡ ኹሉ ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ መቶ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ ሦስተኛ ፡ ኾነው ፡ ይጓዛሉ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ሰራዊቶቻቸው ፡ የዳን ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ ይኾናል ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ አኪዔዘር ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የሚሰፍሩ ፡ የአሴር ፡ ነገድ ፡ ይኾናሉ ፤ የአሴርም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግኤል ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ ይኾናል ፤ የንፍታሌምም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡ አኪሬ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ ሰራዊቱም ፥ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 31 ፤ ከዳን ፡ ሰፈር ፡ የተቈጠሩ ፡ ኹሉ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ በየዐላማዎቻቸው ፡ በመጨረሻ ፡ ይጓዛሉ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ የተቈጠሩ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከየሰፈሩ ፡ በየሰራዊቶቻቸው ፡ የተቈጠሩ ፡ ኹሉ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 33 ፤ ሌዋውያን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አልተቈጠሩም ።

ዘኍ. ፡ 2 ፡ 34 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ በዐላማዎቻቸው ፡ አጠገብ ፡ ሰፈሩ ፥ እንዲሁም ፡ በየወገኖቻቸው ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ተጓዙ ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሙሴን ፡ በተናገረበት ፡ ቀን ፡ የአሮንና ፡ የሙሴ ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ የአሮን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በኵሩ ፡ ናዳብ ፥ አብዩድ ፥ አልዓዛር ፥ ኢታምር ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ የተቀቡ ፡ ካህናት ፡ በክህነትም ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ የቀደሳቸው ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ልዩ ፡ እሳት ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሞቱ ፤ ልጆችም ፡ አልነበሯቸውም ። አልዓዛርና ፡ ኢታምር ፡ በአባታቸው ፡ በአሮን ፡ ፊት ፡ በክህነት ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ የሌዊን ፡ ነገድ ፡ አቅርበኽ ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ በካህኑ ፡ በአሮን ፡ ፊት ፡ አቁማቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የማደሪያውንም ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፥ ርሱንና ፡ ማኅበሩን ፡ ኹሉ ፡ ለማገልገል ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ይጠብቁ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ የማደሪያውንም ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፥ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ለማገልገል ፡ የሚያስፈልገውንም ፡ ነገር ፡ ይጠብቁ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ሌዋውያንንም ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ትሰጣለኽ ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለርሱ ፡ ፈጽመው ፡ ተሰጡ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ አሮንንና ፡ ልጆቹን ፡ አቁማቸው ፥ ክህነታቸውንም ፡ ይጠብቁ ፤ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ማሕፀን ፡ በሚከፍተው ፡ በበኩሩ ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ ሌዋውያንን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወስጃለኹ ፤

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ በኩር ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ ነውና ፥ ሌዋውያን ፡ ለእኔ ፡ ይኹኑ ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በኩርን ፡ ኹሉ ፡ በመታኹ ፡ ቀን ፥ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በኩርን ፡ ኹሉ ፥ ሰውንና ፡ እንስሳን ፥ ለእኔ ፡ ለይቻለኹ ፤ ለእኔ ፡ ይኹኑ ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ የሌዊን ፡ ልጆች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ በየወገናቸውም ፡ ቍጠር ፤ ወንዱን ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ቍጠራቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ሙሴም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዳዘዘው ፡ ቈጠራቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ በየስማቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ጌድሶን ፥ ቀአት ፥ ሜራሪ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ የጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ ስሞች ፡ በየወገናቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ሎቤኒ ፥ ሰሜኢ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ የቀአትም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ዕምበረም ፥ ይስዓር ፥ ኬብሮን ፥ ዑዝኤል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ የሜራሪም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ሞሖሊ ፥ ሙሲ ። የሌዋውያን ፡ ወገኖች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ለጌድሶን ፡ የሎቤናውያን ፡ ወገን ፡ የሰሜኣውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩት ፤ የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ከነርሱ ፡ የተቈጠሩት ፡ የወንዶች ፡ ኹሉ ፡ ቍጥር ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የተቈጠሩት ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ ከማደሪያው ፡ በኋላ ፡ በምዕራብ ፡ ብኩል ፡ ይሰፍራሉ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ የጌድሶናውያንም ፡ አባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የዳኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ጌድሶናውያንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ የሚጠብቁት ፡
ማደሪያው ፡ ድንኳኑም ፡ መደረቢያውም ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፡

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ በማደሪያውና ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ያለው ፡ የአደባባዩ ፡ መጋረጃዎች ፡ የአደባባዩም ፡ ደጃፍ ፡
መጋረጃ ፡ ለማገልገሉም ፡ ያሉት ፡ ገመዶች ፡ ሹሉ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ከቀአትም ፡ የዕምበረማውያን ፡ ወገን ፡ የይስዓራውያንም ፡ ወገን ፡ የኬብሮናውያንም ፡
ወገን ፡ የዑዝኤላውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፤ የቀአታውያን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ወንዶች ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡
ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ መቅደሱንም ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ በማደሪያው ፡ አጠገብ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ይሰፍራሉ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ የቀአታውያንም ፡ ወገኖች ፡ አባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የዑዝኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፈን ([80]) ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ ታቦቱንም ፡ ገበታውንም ፡ መቅረዙንም ፡ መሠዊያዎቹንም ፡ የሚያገለግሉበትንም ፡ የመቅደሱን ፡
ዕቃ ፡ መጋረጃውንም ፡ ማገልገያውንም ፡ ሹሉ ፡ ይጠብቃሉ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ የሌዋውያንም ፡ አለቃዎች ፡ አለቃ ፡ የካህኑ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ይኾናል ፤ ርሱም ፡
መቅደሱን ፡ በሚጠብቁት ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 33 ፤ ከሜራሪ ፡ የሞሐላውያን ፡ ወገን ፡ የሙሳያውያንም ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፤ የሜራሪ ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡
ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 34 ፤ ከነርሱም ፡ ወንዶች ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡
የተቈጠሩት ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 35 ፤ የሜራሪም ፡ ወገኖች ፡ አባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የአቢካኢል ([81]) ፡ ልጅ ፡ ሱሪኤል ፡
ነበረ ፤ በማደሪያው ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ይሰፍራሉ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 36 ፤ የሜራሪም ፡ ልጆች ፡ የሚጠብቁት ፡ የማደሪያው ፡
ሳንቃዎች ፡ መወርወሪያዎችም ፡ ተራዳዎችም ፡ እግሮቹም ፡ ዕቃውም ፡ ሹሉ ፡

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 37 ፤ ማገልገያውም ፡ ሹሉ ፡ በዙሪያውም ፡ የሚቆሙ ፡ የአደባባይ ፡
ምሰሶዎች ፡ እግሮቹም ፡ ካስማዎቹም ፡ አውታሮቹም ፡ ይኾናሉ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 38 ፤ በማደሪያውም ፡ ፊት ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ በስተፀሓይ ፡
መውጫ ፡ የሚሰፍሩት ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ ልጆቹም ፡ ይኾናሉ ፡ መቅደሱንም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይጠብቃሉ ፤ ልዩም ፡
ሰው ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 39 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሯቸው ፡ ከሌዋውያን ፡ ወንዶች ፡ ሹሉ ፡
ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ ሹሉ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 40 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ወንዱን ፡ በኵር ፡ ሹሉ ፡ ቍጠር ፤ ካንድ ፡
ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ የስማቸውን ፡ ቍጥር ፡ ውሰድ ፤

---

80 ዕብ. ፡ ኤሊጻፋን ፡ (ጸፈነ ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ሰወረ) ።

81 ዕብ. ፡ አቢኀይል ፡ (አበ ፡ ኀይል / አበ ፡ ክሂል • የኀይል ፡ አባት) ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 41 ፤ ሌዋውያንንም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፥ የሌዋውያንንም ፡ እንስሳዎች ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንስሳዎች ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ ለእኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 42 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ ቈጠረ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 43 ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩ ፡ ወንዶች ፡ በኵሮች ፡ ኹሉ ፡ የበስማቸው ፡ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 44 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 45 ፤ ሌዋውያንን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፥ የሌዋውያንንም ፡ እንስሳዎች ፡ በእንስሳዎቻቸው ፡ ፋንታ ፡ ውሰድ ፤ ሌዋውያንም ፡ ለእኔ ፡ ይኹኑ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 46 ፤ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵር ፡ ስለተረፉት ፡ ስለ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ፡ ቤዛ ፥ በየራሱ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፡ ውሰድ ፤

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 47 ፤ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ትወስዳለኽ ፤ ሰቅሉም ፡ ኻያ ፡ አቦሊ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 48 ፤ ስለተረፉትም ፡ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ስጥ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 49 ፤ ሙሴም ፡ በሌዋውያን ፡ ከተቤዠት ፡ በላይ ፡ ከተረፉት ፡ ዘንድ ፡ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ወሰደ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 50 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵሮች ፡ ገንዘቡን ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ወሰደ ።

ዘኍ. ፡ 3 ፡ 51 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፥ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፥ ሙሴ ፡ የመቤዣውን ፡ ገንዘብ ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ሰጠ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በየወገናቸው ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ የቀአትን ፡ ልጆች ፡ ድምር ፡ ውሰድ ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግሎት ፡ የሚገቡበትን ፡ ኹሉ ፡ ትደምራለኽ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ዘንድ ፡ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ከሰፈሩ ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ገብተው ፡ የሚሸፍነውን ፡ መጋረጃ ፡ ያውርዱ ፥ የምስክሩንም ፡ ታቦት ፡ ይጠቅልሉበት ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በላዩም ፡ የአቀኑስጣውን ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ያድርጉበት ፥ ከርሱም ፡ በላይ ፡ ኹለንተናው ፡ ሰማያዊ ፡ የኾነ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፥ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ በገጽ ፡ ኅብስት ፡ ገበታ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ወጭቶቹን ፥ ጭልፋዎቹንም ፥ ጽዋዎቹንም ፥ ለማፍሰስም ፡ መቅጃዎቹን ፡ ያድርጉ ፤ ኹልጊዜም ፡ የሚኖር ፡ እንጀራ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ቀይ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉ ፥ በአቀኑስጣውም ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፥ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ሰማያዊውንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይውሰዱ ፥ የሚያበራውንም ፡ መቅረዝ ፥ ቀንዲሎቹንም ፥ መኰስተሪያዎቹንም ፥ የኵስታሪ ፡ ማድረጊያዎቹንም ፥ ርሱንም ፡ ለማገልገል ፡ የዘይቱን ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ይሸፍኑ ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ርሱንና ፡ ዕቃዎቹን ፡ ኹሉ ፡ በአቀኑስጣ ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ውስጥ ፡ ያድርጉ ፥ በመሸከሚያውም ፡ ላይ ፡ ያድርጉት ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ በወርቁም ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፥ በአቀኑስጣም ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፥ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ በመቅደስም ፡ ውስጥ ፡ የሚያገልግሉበትን ፡ የማገልገያውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ይውሰዱ ፥ በሰማያዊውም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ውስጥ ፡ ያስቀምጡት ፥ በአቀኑስጣም ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይሸፍኑት ፥ በመሸከሚያውም ፡ ላይ ፡ ያድርጉት ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ዐመዱንም ፡ ከመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያስወግዱ ፥ ሐምራዊውንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይዘርጉበት ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ የሚያገለግሉበትን ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉም ፡ ማንደጃዎቹን ፡ ሜንጦዎቹንም ፡ መጫሪያዎቹንም ፡ ድስቶቹንም ፥ የመሠዊያውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ያስቀምጡበት ፤ በርሱም ፡ የአቀኑስጣን ፡ ቀርበት ፡ መሸፈኛ ፡ ይዘርጉ ፥ መሎጊያዎቹንም ፡ ያግቡ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ከሰፈሩም ፡ ሲነሡ ፥ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ መቅደሱንና ፡ የመቅደሱን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ከሸፈኑ ፡ በኋላ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ሊሸከሙት ፡ ይመጣሉ ፤ እንዳይሞቱ ፡ ግን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ አይንኩ ። በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዘንድ ፡ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ የካህኑም ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ በመብራቱ ፡ ዘይት ፡ በጣፋጭም ፡ ዕጣን ፡ ላይ ፥ ኹልጊዜም ፡ በሚቀርበው ፡ በእኽሉ ፡ ቀርባንና ፡ በቅባቱ ፡ ዘይት ፡ ላይ ፡ ይሾም ፤ ማደሪያውን ፡ ኹሉ ፥ በርሱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፥ መቅደሱንና ፡ ዕቃውን ፡ ይጠብቃል ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ የቀአትን ፡ ወገኖች ፡ ነገድ ፡ ከሌዋውያን ፡ መካከል ፡ አታጥፏቸው ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ እንዳይሞቱ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፤ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ይግቡ ፥ ለሰውም ፡ ኹሉ ፡ ሥራውንና ፡ ሸክሙን ፡ ይዘዙ ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳይሞቱ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳቱን ፡ ለድንገት ፡ እንኳ ፡ ለማየት ፡ አይግቡ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ የጌድሶንን ፡ ልጆች ፡ ድምር ፡ ደግሞ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ በየወገኖቻቸውም ፡ ውሰድ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግሎት ፡ የሚገቡትን ፡ ኹሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቍጠራቸው ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ ሥራ ፡ በማገልገልና ፡ በመሸከም ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ የማደሪያውን ፡ መጋረጃዎች ፥ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፥ መደረቢያውን ፥ በላዩም ፡ ያለውን ፡

የአቀ-ስጣውን ፡ ቀ-ርበት ፡ መደረቢያ ፥ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፥

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 26 ፤ በማደሪያውና ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የአደባባዩን ፡ መጋረጃ ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጃፍ ፡ መጋረጃ ፥ አውታሮቻቸውንም ፥ ለማገልገልም ፡ የሚሠሩበትን ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፡ ይሸከሙ ፤ በዚህ ፡ ያገልግሉ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 27 ፤ የጌድሶናውያን ፡ አገልግሎት ፡ ሹሉ ፥ ሸክማቸውም ፡ ሹሉ ፥ ሥራቸውም ፡ ሹሉ ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ ትእዛዝ ፡ ይኹን ፤ የሚደርስባቸውንም ፡ ሸክም ፡ ሹሉ ፡ ትነግሯቸዋላችኹ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 28 ፤ የጌድሶናውያን ፡ ወገኖች ፡ አገልግሎት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከካህኑ ፡ ከአሮን ፡ ልጅ ፡ ከኢታምር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ይኾናሉ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 29 ፤ የሜራሪንም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ቍጠራቸው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 30 ፤ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግሎት ፡ የሚገቡትን ፡ ሹሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ቍጠራቸው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 31 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ አገልግሎታቸው ፡ ሹሉ ፥ የማደሪያው ፡ ሳንቃዎች ፥ መወርወሪያዎቹም ፥ ተራዳዎቹም ፥ እግሮቹም ፥

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 32 ፤ በዙሪያውም ፡ የሚቆሙት ፡ የአደባባዩ ፡ ምሰሶዎች ፥ እግሮቹም ፥ ካስማዎቹም ፥ አውታሮቹም ፥ ዕቃዎቹና ፡ ማገልገያዎቹ ፡ ሸክማቸው ፡ ነው ፤ የሚጠብቁትንም ፡ የሸክማቸውን ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፡ በስማቸው ፡ ቍጠሩ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 33 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ አገልግሎት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ዘንድ ፡ ከካህኑ ፡ ከአሮን ፡ ልጅ ፡ ከኢታምር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ በያገልግሎታቸው ፡ ሹሉ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 34 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ የሕቡም ፡ አለቃዎች ፡ የቀአትን ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ቈጠሯቸው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 35 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አገልግሎት ፡ የገቡትን ፡ ሹሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ቈጠሯቸው ፤

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 36 ፤ በየወገናቸውም ፡ ከነርሱ ፡ የተቈጠሩት ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 37 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገለገሉት ፡ ሹሉ ፥ ከቀአታውያን ፡ ወገኖች ፡ የተቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሯቸው ፥ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 38 ፤ በየወገናቸውም ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ የተቈጠሩት ፡ የጌድሶን ፡ ልጆች ፥

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 39 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአገልግሎት ፡ የገቡት ፥ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 40 ፤ በየወገናቸውም ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ የተቈጠሩት ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 41 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገለገሉት ፡ ሹሉ ፥ ከጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሯቸው ፥ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኁ. ፥ 4 ፥ 42 ፤ በየወገናቸውም ፡ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተቈጠሩት ፥

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 43 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ አገልግሎት ፡ የገቡት ፡ ኹሉ ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገሮምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 44 ፤ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 45 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፥ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የተቈጠሩት ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የቈጠሯቸው ፥ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 46 ፤ በየወገናቸውና ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ከሌዋውያን ፡ የተቈጠሩት ፡ ኹሉ ፥ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የእስራኤልም ፡ አለቃዎች ፡ የቈጠሯቸው ፥

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 47 ፤ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ሥራውን ፡ ለመሥራትና ፡ ዕቃውን ፡ ለመሸከም ፡ የገቡት ፡ ኹሉ ፥ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ገሮምሮ ፡ እስከ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ያሉት ፥

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 48 ፤ ከነርሱ ፡ የተቈጠሩት ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 4 ፡ 49 ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በያገልግሎታቸውና ፡ በየሸክማቸው ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ተቈጠሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ በርሱ ፡ ተቈጠሩ ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለምጻሙን ፡ ኹሉ ፥ ፈሳሽ ፡ ነገርም ፡ ያለበትን ፡ ኹሉ ፥ በሬሳም ፡ የረከሰውን ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ እንዲያወጡ ፡ እዘዛቸው ፤

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ አውጡ ፤ እኔ ፡ በመካከሉ ፡ የማድርበትን ፡ ሰፈራቸውን ፡ እንዳያረክሱ ፡ ከሰፈሩ ፡ አውጧቸው ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፥ ከሰፈሩ ፡ አወጧቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፦ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ የሚሠራውን ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፥ በዚያም ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ቢኾን ፥ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ይናዘዝ ፤

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ የወሰደውንም ፡ በሙሉ ፡ ይመልስ ፡ ዐምስተኛውንም ፡ ይጨምርበት ፥ ለበደለውም ፡ ሰው ፡ ይስጠው ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ ሰውዮው ፡ ዘመድ ፡ ባይኖረው ፥ ስለ ፡ በደል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚመልሰው ፡ ነገር ፡ ለካህኑ ፡ ይኹን ፥ ይህም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ማስተስረያ ፡ ከሚደረግበት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ በላይ ፡ ይጨመር ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለካህኑ ፡ የሚያቀርቡት ፡ የተቀደሰ ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ለርሱ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ የተቀደሰ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ሰውም ፡ ለካህኑ ፡ የሚሰጠው ፡ ኹሉ ፡ ለርሱ ፡ ይኹን ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፦ የማንኛውም ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ከርሱ ፡ ፈቀቅ ፡ ብትል ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ብትበድል ፥

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከሌላም ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ብትተኛ ፥ ከባሏም ፡ ዐይን ፡ ቢሸሸግ ፥ ርሷም ፡ ተሰውራ ፡ ብትረክስ ፥ ምስክርም ፡ ባይኖርባት ፥ በምንዝርም ፡ ባትገኝ ፥

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በባሏም ፡ ላይ ፡ የቅንአት ፡ መንፈስ ፡ ቢመጣበት ፥ ርሷም ፡ ስትረክስ ፡ ስለ ፡ ሚስቱ ፡ ቢቀና ፤ ወይም ፡ ርሷ ፡ ሳትረክስ ፡ የቅንአት ፡ መንፈስ ፡ ቢመጣበት ፥ ስለ ፡ ሚስቱም ፡ ቢቀና ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያምጣት ፥ የኢፍ ፡ መስፈሪያም ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ገብስ ፡ ዱቄት ፡ ቍርባን ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ያምጣ ፤ የቅንአት ፡ ቍርባን ፡ ነውና ፥ ኀጢአትንም ፡ የሚያሳስብ ፡ የመታሰቢያ ፡ ቍርባን ፡ ነውና ፥ ዘይት ፡ አያፍስበት ፥ ዕጣንም ፡ አይጨምርበት ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ካህኑም ፡ ያቀርባታል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ያቆማታል ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ካህኑም ፡ የተቀደሰ ፡ ውሃ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ይወስዳል ፤ ካህኑም ፡ በማደሪያው ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ትቢያ ፡ ወስዶ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆማታል ፥ የሴቲቱንም ፡ ራስ ፡ ይገልጣል ፥ በእጇም ፡ ለመታሰቢያ ፡ የሚኾነውን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፥ ለቅንአት ፡ ቍርባን ፥ ያኖራል ፤ በካህኑም ፡ እጅ ፡ ርግማንን ፡ የሚያመጣው ፡ መራራ ፡ ውሃ ፡ ይኾናል ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ካህኑም ፡ ያምላታል ፥ ሴቲቱንም ፡ እንዲህ ፡ ይላታል ፦ ሌላ ፡ ወንድ ፡ አልተኛሽ ፥ ባልሽንም ፡ አልተውሽ ፥ ራስሽንም ፡ አላረከሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ርግማንን ፡ ከሚያመጣ ፡ ከዚህ ፡ መራራ ፡ ውሃ ፡ ንጹሕ ፡ ኹኚ ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባልሽን ፡ ትተሽ ፡ ረክሰሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከባልሽም ፡ ሌላ ፡ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ ተኝተሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፡ በመርገም ፡ መሐላ ፡ ያምላታል ፥ ካህኑም ፡ ሴቲቱን ፦ እግዚአብሔር ፡ ጭንሽን ፡ እያሰለሰለ ፡ ሆድሽንም ፡ እየነፋ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለመርገምና ፡ ለመሐላ ፡ በሕዝብሽ ፡ መካከል ፡ ያድርግሽ ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ርግማንንም ፡ የሚያመጣ ፡ ይህ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ሆድሽ ፡ ይግባ ፥ ሆድሽንም ፡ ይንፋው ፥ ጭንሽንም ፡ ያበስብሰው ፡ ይላታል ፤ ሴቲቱም ፦ አሜን ፡ አሜን ፡ ትላለች ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ካህኑም ፡ እነዚህን ፡ መርገሞች ፡ በሰሌዳ ፡ ይጽፈዋል ፥ በመራራውም ፡ ውሃ ፡ ይደመስሰዋል ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ርግማን ፡ የሚያመጣውንም ፡ መራራ ፡ ውሃ ፡ ለሴቲቱ ፡ ያጠጣታል ፤ የርግማኑም ፡ ውሃ ፡ በገባባት ፡ ጊዜ ፡ መራራ ፡ ይኾናል ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ካህኑም ፡ የቅንአቱን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ከሴቲቱ ፡ እጅ ፡ ይወስዳል ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዘውዘዋል ፥ ወደ ፡ መሠዊያውም ፡ ያመጣዋል ፤

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ካህኑም ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ አንድ ፡ ዕፍኝ ፡ ሙሉ ፡ ለመታሰቢያው ፡ ወስዶ ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያቃጥለዋል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለሴቲቱ ፡ ውሃውን ፡ ያጠጣታል ።

ዘኁ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ውሃውን ፡ ካጠጣት ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ረክሳና ፡ በባሏ ፡ ላይ ፡ አመንዝራ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ ርግማንን ፡ የሚያመጣው ፡ ውሃ ፡ ገብቶ ፡ መራራ ፡ ይኾንባታል ፥ ሆዷም ፡ ይነፋል ፥ ጭኗም ፡

ይሰለስላል ፤ ሴቲቱም ፡ በሕዝቧ ፡ መካከል ፡ ለመርገም ፡ ትኾናለች ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ያልረከሰች ፡ ያለነውርም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ ንጹሕ ፡ ትኾናለች ፥ ልጆችንም ፡ ታረግዛለች ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ 30 ፤ ሴት ፡ ባሏን ፡ ትታ ፡ በረከሰች ፡ ጊዜ ፥ ወይም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የቅንአት ፡ መንፈስ ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፥ ስለ ፡ ሚስቱም ፡ በቀና ፡ ጊዜ ፥ የቅንአት ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሴቲቱንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቁማት ፥ ካህኑም ፡ እንደዚህ ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ያድርግባት ።

ዘኍ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ሰውየውም ፡ ከኀጢአት ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ፥ ሴቲቱም ፡ ኀጢአቷን ፡ ትሸከማለች ።

——————————ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። ——————————

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፦ ሰው ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ የናዝራዊነት ፡ ስእለት ፡ ቢሳል ፥

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ከወይን ፡ ጠጅና ፡ ከሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያድርግ ፤ ከወይን ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ ነገር ፡ የሚገኘውን ፡ ሐምጣጤ ፡ አይጠጣ ፥ የወይንም ፡ ጭማቂ ፡ አይጠጣ ፤ የወይን ፡ እሸት ፡ ወይም ፡ ዘቢብ ፡ አይብላ ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ባደረገበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ ከወይን ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከውስጡ ፡ ፍሬ ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ገፈፎው ፡ ድረስ ፡ አይብላ ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ራሱን ፡ ለመለየት ፡ ስእለት ፡ ባደረገበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ምላጭ ፡ አይደርስም ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየበት ፡ ወራት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፥ የራሱንም ፡ ጠጉር ፡ ያሳድጋል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ባደረገበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሬሳ ፡ አይቅረብ ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ለአምላኩ ፡ ያደረገው ፡ ስእለት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ አባቱ ፡ ወይም ፡ እናቱ ፡ ወይም ፡ ወንድሙ ፡ ወይም ፡ እኅቱ ፡ ሲሞቱ ፡ ሰውነቱን ፡ አያርክስባቸው ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ባደረገበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ሰውም ፡ በአጠገቡ ፡ ድንገት ፡ ቢሞት ፡ የተለየውንም ፡ ራሱን ፡ ቢያረክስ ፥ ርሱ ፡ በሚነጻበት ፡ ቀን ፡ ራሱን ፡ ይላጭ ፤ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ይላጨው ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ኹለት ፡ ዋኖሶች ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ግልገሎች ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ያምጣ ፤

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ካህኑም ፡ አንዱን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለተኛውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርበዋል ፤ በሬሳም ፡ የተነሣ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቷልና ፥ ያስተሰርይለታል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ራሱን ፡ ይቀድሰዋል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ራሱን ፡ የተለየ ፡ ያደረገበትን ፡ ወራትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቀድሳል ፥ የአንድ ፡ ዓመትም ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ ያምጣ ፤ ናዝራዊነቱ ፡ ግን ፡ ረክሷልና ፥ ያለፈው ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ የመለየቱ ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የናዝራዊው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ይቅረብ ፤

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ቍርባኑንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቅርብ ፤ ነውር ፡ የሌለበት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ ነውርም ፡ የሌለባትን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ እንስት ፡ ጠቦት ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ነውርም ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፥

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ አንድ ፡ ሌማትም ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፥ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመልካም ፡ ዱቄትም ፡ የተሠሩ ፡ ዕንጐቻዎች ፥ በዘይትም ፡ የተቀባ ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፥ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ ያቅርብ ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቀርባቸዋል ፥ የኀጢአቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ያሳርግለታል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ከሌማቱ ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያቀርባል ፤ ካህኑም ፡ ደግሞ ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡን ፡ ቍርባን ፡ ያቀርባል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ናዝራዊውም ፡ የተለየውን ፡ የራሱን ፡ ጠጕር ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አጠገብ ፡ ይላጫል ፥ የመለየቱንም ፡ ራስ ፡ ጠጕር ፡ ወስዶ ፡ ከደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ በታች ፡ ወዳለው ፡ እሳት ፡ ይጥለዋል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ካህኑም ፡ የተቀቀለውን ፡ የአውራውን ፡ በግ ፡ ወርች ፥ ከሌማቱም ፡ አንድ ፡ ቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፡ አንድም ፡ ሥሥ ፡ ቂጣ ፡ ይወስዳል ፥ የተለየውንም ፡ የራስ ፡ ጠጕር ፡ ከተላጨ ፡ በኋላ ፡ በናዝራዊው ፡ እጆች ፡ ላይ ፡ ያኖራቸዋል ፤

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ካህኑም ፡ እነዚህን ፡ ለመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይወዘውዛቸዋል ፤ ይህም ፡ ከሚወዘወዘው ፡ ፍርምባና ፡ ከሚነሣው ፡ ወርች ፡ ጋራ ፡ ለካህኑ ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ናዝራዊው ፡ ወይን ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ስእለቱን ፡ የተሳለው ፡ የናዝራዊ ፥ እጁም ፡ ከሚያገኘው ፡ ሌላ ፡ ስለ ፡ ናዝራዊነቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ የቍርባኑ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ስእለቱን ፡ እንደ ፡ ተሳለ ፡ እንደ ፡ ናዝራዊነቱ ፡ ሕግ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ንገራቸው ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ስትባርኳቸው ፡ እንዲህ ፡ በሏቸው ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ፥ ይጠብቅኽም ፤

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ያብራልኽ ፥ ይራራልኽም ፤

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፊቱን ፡ ወዳንተ ፡ ያንሣ ፥ ሰላምንም ፡ ይስጥኽ ።

ዘኍ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ እንዲሁ ፡ ስሜን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ያደርጋሉ ፤ እኔም ፡ እባርካቸዋለኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ ማደሪያውን ፡ ፈጽሞ ፡ ከተከለ ፡ በኋላ ፥ ርሱንና ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፡ ከቀባና ፡ ከቀደሰ ፡ በኋላ ፥ መሠዊያውንና ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፡ ከቀባና ፡ ከቀደሰ ፡ በኋላ ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ አለቃዎች ፥ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ቍርባናቸውን ፡ አቀረቡ ፤ እነዚህም ፡ ከተቈጠሩት ፡ በላይ ፡ የተሾሙ ፡ የነገዶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ መባቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ፥ የተከደኑ ፡ ስድስት ፡ ሠረገላዎች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ በሬዎች ፤ በየኹለቱም ፡ አለቃዎች ፡ አንድ ፡ ሠረገላ ፡ አቀረቡ ፥ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ አንድ ፡ በሬ ፡

በማደሪያው ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ለመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ማገልገል ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ ተቀብለኽ ፡ ለሌዋውያን ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ አገልግሎታቸው ፡ ስጣቸው ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ ሠረገላዎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ተቀብሎ ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጣቸው ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ለጌድሶን ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ አገልግሎታቸው ፡ ኹለት ፡ ሠረገላዎችንና ፡ አራት ፡ በሬዎችን ፡ ሰጣቸው ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ከካህኑም ፡ ከአሮን ፡ ልጅ ፡ ከኢታምር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ አገልግሎታቸው ፡ አራት ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ስምንት ፡ በሬዎችን ፡ ሰጣቸው ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ለቀአት ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ መቅደሱን ፡ ማገልገል ፡ የእነርሱ ፡ ነውና ፥ በትከሻቸውም ፡ ይሸከሙት ፡ ነበርና ፥ ምንም ፡ አልሰጣቸውም ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ መሠዊያውም ፡ በተቀባ ፡ ቀን ፡ አለቃዎቹ ፡ መሠዊያውን ፡ ለመቀደስ ፡ ቍርባንን ፡ አቀረቡ ፤ አለቃዎችም ፡ መባቸውን ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ አለቃዎቹ ፡ መሠዊያውን ፡ ለመቀደስ ፡ መባቸውን ፡ እያንዳንዱ ፡ በቀን ፡ በቀኑ ፡ ያቅርቡ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ቀን ፡ መባውን ፡ ያቀረበ ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአሶን ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ የነአሶን ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ የይሳኮር ፡ አለቃ ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፡ አቀረበ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ለመባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉትን ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላውን ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ አቀረበ ፤ የሶገር ፡ ልጅ ፡ የናትናኤ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ የይሳኮር ፡ አለቃ ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፡ አቀረበ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ለመባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉትን ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላውን ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ አቀረበ ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ የናትናኤል ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የዛብሎን ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ የኤልያብ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡ ኤሊሱር ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 31 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 32 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡

ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡ የኤሊሱር ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ በዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለሚኤል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 39 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 40 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 41 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ የሰለሚኤል ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 42 ፤ በስድስተኛውም ፡ ቀን ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 43 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 44 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 45 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 46 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 47 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ የኤሊሳፍ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 48 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳማ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 49 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑ ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 50 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 51 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 52 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 53 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ የኤሊሳማ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 54 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ የምናሴ ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ ገማልኤል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 55 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 56 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 57 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 58 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 59 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ የገማልኤል ፡ መባ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 60 ፤ በዘጠነኛውም ፡ ቀን ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የጋዴዮን ፡ ልጅ ፡ አቢዳን ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 61 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 62 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 63 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 64 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 65 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የጋዴዮን ፡ ልጅ ፡ የአቢዳን ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 66 ፤ በዐሥረኛውም ፡ ቀን ፡ የዳን ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ አኪዔዘር ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 67 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 68 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኁ. ፡ 7 ፡ 69 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡

ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 70 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 71 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ የአኪዔዘር ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 72 ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ቀን ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግዔል ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 73 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 74 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 75 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 76 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 77 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ የፋግዔል ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 78 ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡ አኪሬ ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 79 ፤ መባውም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ የተሞሉ ፥ ሚዛኑ ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ወጭት ፥ ሚዛኑም ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የብር ፡ ድስት ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 80 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞላ ፡ ሚዛኑ ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋ ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 81 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 82 ፤ አንድ ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦት ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 83 ፤ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐምስት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ የዔናን ፡ ልጅ ፡ የአኪሬ ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 84 ፤ መሠዊያው ፡ በተቀባ ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ ለመቀደሻው ፡ ያቀረቡት ፡ ቍርባን ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ የብር ፡ ወጭቶች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ የብር ፡ ድስቶች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋዎች ፤

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 85 ፤ እያንዳንዱም ፡ የብር ፡ ወጭት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰቅል ፥ እያንዳንዱም ፡ ድስት ፡ ሰባ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ የዚህም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ብር ፡ በመቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 86 ፤ ዕጣንም ፡ የተሞሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የወርቅ ፡ ጭልፋዎች ፥ እያንዳንዱ ፡ በመቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ዐሥር ፡ ዐሥር ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ የጭልፋዎቹ ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 87 ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ከብት ፡ ኹሉ ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ጋራ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ ጠቦቶች ፡

ነበሩ ፤ የኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 88 ፤ የደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ከብት ፡ ኹሉ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ በሬዎች ፥ ስድሳም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ስድሳም ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፥ ስድሳም ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበሩ ። መሠዊያው ፡ ከተቀባ ፡ በኋላ ፡ ለመቀደሻው ፡ የቀረበ ፡ ቍርባን ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 7 ፡ 89 ፤ ሙሴም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ርሱን ፡ ለመነጋገር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በምስክሩ ፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ከስርየት ፡ መክደኛ ፡ በላይ ፡ ከኪሩቤልም ፡ መካከል ፡ ድምፁ ፡ ሲናገረው ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ይናገረው ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ መብራቶቹን ፡ ስትለኵስ ፡ ሰባቱ ፡ መብራቶች ፡ በመቅረዙ ፡ ፊት ፡ ያበራሉ ፡ ብለኽ ፡ ለአሮን ፡ ንገረው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ አሮንም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ በመቅረዙ ፡ ፊት ፡ መብራቶቹን ፡ ለኰሰ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ መቅረዙም ፡ እንዲህ ፡ ኾኖ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ ከተቀጠቀጠ ፡ ወርቅ ፡ ተሠራ ፤ እስከ ፡ አገዳውና ፡ እስከ ፡ አበባዎቹ ፡ ድረስ ፡ ከተቀጠቀጠ ፡ ሥራ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳሳየው ፡ ምሳሌ ፡ መቅረዙን ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ሌዋውያንን ፡ ወስደኽ ፡ አንጻቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ታነጻቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ታደርግላቸዋለኽ ፤ ኀጢአትን ፡ የሚያነጻውን ፡ ውሃ ፡ ርጫቸው ፥ በገላቸውም ፡ ኹሉ ፡ ምላጭ ፡ ያሳልፉ ፥ ልብሳቸውንም ፡ ይጠቡ ፥ ይታጠቡም ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ወይፈንን ፥ ለእኽሉም ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄትን ፡ ይውሰዱ ፥ ሌላውንም ፡ ወይፈን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ውሰድ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ሌዋውያንንም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ አቅርብ ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ሰብስብ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ሌዋውያንንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቅርባቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ይጫኑባቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ አሮንም ፡ ሌዋውያን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ስጦታ ፡ አድርጎ ፥ ሌዋውያንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቅርብ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ሌዋውያኑም ፡ በወይፈኖቹ ፡ ራሶች ፡ ላይ ፡ እጆቻቸውን ፡ ይጫኑ ፤ ለሌዋውያንም ፡ ስለ ፡ ማስተስረያ ፡ አንዱን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ ኹለተኛውንም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርብ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ሌዋውያንንም ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ ፊት ፡ አቁማቸው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ስጦታ ፡ አድርገኽ ፡ አቅርባቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ እንዲሁ ፡ ሌዋውያንን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለይ ፤ ሌዋውያንም ፡ ለእኔ ፡ ይኹኑ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌዋውያን ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ይገባሉ ፤ ታነጻቸውማለኽ ፥ ስጦታም ፡ አድርገኽ ፡ ታቀርባቸዋለኽ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ እነርሱም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ፈጽሞ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጥተዋልና ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ኹሉ ፥ ማሕፀን ፡ በሚከፍት ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ ለእኔ ፡ ወስጃቸዋለኹ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፡ በገደልኩበት ፡ ቀን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ኹሉ ፥ ሰው ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፥ ለእኔ ፡ ቀድሻቸዋለኹና ፡ የእኔ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በኵራት ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ ሌዋውያንን ፡ ወስጃለኹ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ መቅሠፍት ፡ እንዳያገኛቸው ፥ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያስተሰርዩላቸው ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አገልግሎት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ሌዋውያንን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለአሮንና ፡ ለልጆቹ ፡ ስጦታ ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቻቸዋለኹ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ስለ ፡ ሌዋውያን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አደረጉላቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ሌዋውያንም ፡ ከኀጢአት ፡ ተጣጠቡ ፥ ልብሳቸውንም ፡ ዐጠቡ ፤ አሮንም ፡ ስጦታ ፡ አድርጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረባቸው ፥ አሮንም ፡ ያነጻቸው ፡ ዘንድ ፡ አስተሰረየላቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሌዋውያን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በአሮንና ፡ በልጆቹ ፡ ፊት ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ስለ ፡ ሌዋውያን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉላቸው ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ የሌዋውያን ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ሥራ ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ይገባሉ ።

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ዕድሜያቸውም ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላ ፡ የአገልግሎታቸውን ፡ ሥራ ፡ ይተዋሉ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይሠሩም ፤

ዘኍ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ የተሰጣቸውን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ያገለግላሉ ፤ የድንኳኑን ፡ አገልግሎት ፡ አይሠሩም ። እንዲሁ ፡ ስለ ፡ ሥራቸው ፡ በሌዋውያን ፡ ላይ ፡ ታደርጋለኽ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጊዜው ፡ ፋሲካውን ፡ ያድርጉ ፤

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ በዚህ ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በጊዜው ፡ አድርጉት ፤ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ፍርዱም ፡ ኹሉ ፡ አድርጉት ።

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ ፋሲካን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ተናገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡

ፋሲካን ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አደረጉ ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ በሞተ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ የረከሱ ፡ ሰዎችም ፡ ነበሩ ፥ ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፋሲካን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ቀረቡ ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ እነዚያም ፡ ሰዎች ፦ በሞተ ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ ረክሰናል ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በጊዜው ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳናቀርብ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንከለከላለን ፧ አሉት ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፦ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚያዘውን ፡ እስክሰማ ፡ ድረስ ፡ ቈዩ ፡ አላቸው ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ከእናንተ ፡ ወይም ፡ ከትውልዶቻችኹ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ በሬሳ ፡ ቢረክስ ፥ ወይም ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ ቢኼድ ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካን ፡ ያድርግ ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ያድርጉት ፤ ከቂጣ ፡ እንጀራና ፡ ከመራራ ፡ ቅጠል ፡ ጋራ ፡ ይብሉት ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ከርሱም ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ምንም ፡ አያስቀሩ ፥ ከርሱም ፡ ዐጥንትን ፡ አይስበሩ ፤ እንደ ፡ ፋሲካ ፡ ሥርዐት ፡ ኹሉ ፡ ያድርጉት ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ በመንገድም ፡ ላይ ፡ ያልኾነ ፡ ፋሲካን ፡ ባያደርግ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቍርባን ፡ በጊዜው ፡ አላቀረበምና ፡ ያ ፡ ሰው ፡ ኀጢአቱን ፡ ይሸከማል ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ በመካከላችኹም ፡ መጻተኛ ፡ ቢኖር ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፥ እንደ ፡ ፋሲካ ፡ ሥርዐት ፡ እንደ ፡ ፍርዱም ፡ እንዲሁ ፡ ያድርግ ፤ ለመጻተኛና ፡ ለአገር ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ሥርዐት ፡ ይኹንላችኹ ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ማደሪያውም ፡ በተተከለ ፡ ቀን ፡ ደመናው ፡ የምስክሩን ፡ ድንኳን ፡ ሸፈነው ፤ ከማታም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጧት ፡ ድረስ ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ እንዲሁ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፤ በቀን ፡ ደመና ፡ በሌሊትም ፡ የእሳት ፡ አምሳል ፡ ይሸፍነው ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ደመናውም ፡ ከድንኳኑ ፡ ላይ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ፤ ደመናውም ፡ በቆመበት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይሰፍሩ ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰፍሩ ፡ ነበር ። ደመናው ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ በተቀመጠበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በሰፈራቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ ደመናውም ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፥ አይጓዙምም ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ደመናው ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ይኾን ፡ ነበር ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በሰፈራቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ደመናው ፡ ከማታ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጧት ፡ ድረስ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ በጧትም ፡ ደመናው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፥ ይጓዙ ፡ ነበር ፤ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ ቢኾን ፥ ደመናው ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ ደመናውም ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ቈይቶ ፡ በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ቢቀመጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሰፈራቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፥ አይጓዙምም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይሰፍሩ ፡ ነበር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ይጓዙ ፡ ነበር ፥ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

——————————ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። ——————————

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ ኹለት ፡ የብር ፡ መለከቶች ፡ አጠፍጥፈኽ ፡ ለአንተ ፡ አድርግ ፤ ማኅበሩን ፡ ለመጥራት ፡ ከሰፈራቸውም ፡ ለማስጓዝ ፡ ይኹኑልኽ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ኹለቱም ፡ መለከቶች ፡ በተነፉ ፡ ጊዜ ፡ ማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ይሰብሰቡ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ አንድ ፡ መለከት ፡ ሲነፉ ፡ ታላላቆቹ ፡ የእስራኤል ፡ አእላፍ ፡ አለቃዎች ፡ ወዳንተ ፡ ይሰብሰቡ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ መለከትንም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ስትነፉ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የሰፈሩት ፡ ይጓዙ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ኹለተኛውንም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ስትነፉ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የሰፈሩት ፡ ይጓዙ ፤ ለማስጓዝ ፡ መለከትን ፡ ይነፉሉ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ጉባኤውም ፡ በሚሰበሰብበት ፡ ጊዜ ፡ ንፉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አታድርጉት ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ መለከቶቹን ፡ ይንፉ ፤ እነርሱም ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኹኑ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ በሚገፋችኹም ፡ ጠላት ፡ ላይ ፡ በምድራችኹ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ስትወጡ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ መለከቶቹን ፡ ንፉ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ በአምላካችኹ ፡ ፊት ፡ ትታሰባላችኹ ፥ ከጠላቶቻችኹም ፡ ትድናላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ደግሞ ፡ በደስታችኹ ፡ ቀን ፥ በበዓላታችኹም ፡ ዘመን ፥ በወርም ፡ መባቻ ፥ በሚቃጠል ፡ መሥዋዕታችኹና ፡ በደኅንነት ፡ መሥዋዕታችኹ ፡ ላይ ፡ መለከቶቹን ፡ ንፉ ፤ እነርሱም ፡ በአምላካችኹ ፡ ፊት ፡ ለመታሰቢያ ፡ ይኾኑላችኋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ በኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያኛው ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ደመናው ፡ ከምስክሩ ፡ ማደሪያ ፡ ላይ ፡ ተነሣ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በየጉዟቸው ፡ ተጓዙ ፤ ደመናውም ፡ በፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ቆመ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ በመገሥመሪያም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ ተጓዙ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ በመገሥመሪያም ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ በየሰራዊታቸው ፡ ተጓዘ ፤ በሰራዊቱም ፡ ላይ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፡ ነአሶን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ በይሳኮርም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የሶገር ፡ ልጅ ፡ ናትናኤል ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ በዛብሎንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የኬሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ማደሪያውም ፡ ተነቀለ ፤ ማደሪያውንም ፡ የተሸከሙ ፡ የጌድሶን ፡ ልጆችና ፡ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ተጓዙ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ የሮቤልም ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ በየሰራዊታቸው ፡ ተጓዘ ፤ በሰራዊቱም ፡ ላይ ፡ የሰዲዮር ፡ ልጅ ፡ ኤሊሱር ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ በስምዖንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የሱሪሰዳይ ፡ ልጅ ፡ ሰለሚኤል ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ በጋድም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፍ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ቀአታውያንም ፡ መቅደሱን ፡ ተሸክመው ፡ ተጓዙ ፤ እነዚህም ፡ እስኪመጡ ፡ ድረስ ፡ እነዚያ ፡ ማደሪያውን ፡ ተከሉ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ የኤፍሬምም ፡ ልጆች ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ በየሰራዊታቸው ፡ ተጓዘ ፤ በሰራዊቱም ፡ ላይ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳማ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ በምናሴም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የፍዳሱር ፡ ልጅ ፡ ገማልኤል ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ በብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የጋዴዮን ፡ ልጅ ፡ አቢዳን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ከሰፈሮቹ ፡ ሹሉ ፡ በኋላ ፡ የኾነ ፡ የዳን ፡ ልጆች ፡ ሰፈር ፡ ዐላማ ፡ በየሰራዊታቸው ፡ ተጓዘ ፤ በሰራዊቱም ፡ ላይ ፡ የአሚሳዳይ ፡ ልጅ ፡ አኪዔዘር ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ በአሴርም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የኤክራን ፡ ልጅ ፡ ፋግኤል ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ በንፍታሌምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሰራዊት ፡ ላይ ፡ የዔናን ፡ ልጅ ፡ አኪሬ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጉዞ ፡ በየሰራዊታቸው ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ ተጓዙ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፡ የሚስቱን ፡ አባት ፡ የምድያማዊውን ፡ የራጉኤልን ፡ ልጅ ፡ ኦባብን ፦ እግዚአብሔር ፦ ለእናንተ ፡ እሰጠዋለኹ ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ እንኼዳለን ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ተናግሯልና ፥ አንተ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ና ፥ መልካምን ፡ እናደርግልኻለን ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ርሱም ፦ አልኼድም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ አገሬና ፡ ወደ ፡ ዘመዶቼ ፡ እኼዳለኹ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ ርሱም ፦ እባክኽ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ የምንሰፍርበትን ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽና ፥ እንደ ፡ ዐይኖቻችንም ፡ ትኾንልናለኽና ፡ አትተወን ፤

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ብትኼድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚያደርግልን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ እኛ ፡ ለአንተ ፡ እናደርጋለን ፡ አለ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ተራራ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ ተጓዙ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ የኪዳኑ ፡ ታቦት ፡ የሚያድርበትን ፡ ስፍራ ፡ ይፈልግላቸው ፡ ዘንድ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ቀደማቸው ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ ከሰፈራቸውም ፡ በተጓዙ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ደመና ፡ ቀን ፡ ቀን ፡ በላያቸው ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ ሙሴም ፡ ታቦቱ ፡ በተጓዘ ፡ ጊዜ ፦ አቤቱ ፥ ተነሣ ፥ ጠላቶችኽም ፡ ይበተኑ ፥ የሚጠሉኽም ፡ ከፊትኽ ፡ ይሸሹ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ ባረፈም ፡ ጊዜ ፦ አቤቱ ፥ ወደ ፡ እስራኤል ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፡ ተመለስ ፡ ይል ፡ ነበር ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ ሕዝቡም ፡ ክፉ ፡ ኾነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰምቶ ፡ ተቈጣ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ በመካከላቸው ፡ ነደደች ፥ የሰፈሩንም ፡ ዳር ፡ በላች ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ ጮኹ ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፥ እሳቲቱም ፡ ጠፋች ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ በመካከላቸው ፡ ስለ ፡ ነደደች ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ተቤራ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ በመካከላቸውም ፡ የነበሩ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ጐመጁ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ። የምንበላውን ፡ ሥጋ ፡ ማን ፡ ይሰጠናል ፧

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ በግብጽ ፡ ያለዋጋ ፡ እንበላው ፡ የነበረውን ፡
ዓሣ ፥ ዱባውንም ፥ በጢሑንም ፥ ኵረቱንም ፥ ቀዩንም ፡ ሽንኵርት ፥ ነጩንም ፡ ሽንኵርት ፡ እናስባለን ፤

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ሰውነታችን ፡ ደረቀች ፤ ዐይናችንም ፡ ከዚህ ፡ መና ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አታይም ፡ አሉ ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ መናውም ፡ እንደ ፡ ድንብላል ፡ ዘር ፡ ነበረ ፥ መልኩም ፡ ሙጫ ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ ሕዝቡም ፡ እየዞሩ ፡ ይለቅሙ ፡ ነበር ፥ በወፍጮም ፡ ይፈጩት ፥ ወይም ፡ በሙቀጫ ፡ ይወቅጡት ፥ በምንቸትም ፡ ይቀቅሉት ፡ ነበር ፥ ዕንጐቻም ፡ ያደርጉት ፡ ነበር ፤ ጣዕሙም ፡ በዘይት ፡ እንደ ፡ ተለወሰ ፡ ዕንጐቻ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 9 ፤ ሌሊትም ፡ ጠል ፡ በሰፈሩ ፡ ላይ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ መናው ፡ በላዩ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 10 ፤ ሙሴም ፡ ሕዝቡ ፡ በወገኖቻቸው ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፥ ሲያለቅሱ ፡
ሰማ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ እጅግ ፡ ነደደ ፤ ሙሴም ፡ ተቈጣ ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 11 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፦ ለምን ፡ በባሪያኽ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ አደረግኽ ፧ ለምንስ ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ አላገኘኹም ፧ ለምንስ ፡ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ሸክም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አደረግኽ ፧

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 12 ፤ አንተ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደማልኽላቸው ፡ ምድር ፡ አደርሳቸው ፡ ዘንድ ፦ ሞግዚት ፡
የሚጠባውን ፡ ልጅ ፡ እንድታቀፍ ፡ በብብትኽ ፡ ዕቀፋቸው ፡ የምትለኝ ፥ በእውኑ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡
ፀነስኹትን ፧ ወለድኹትንስ ፧

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 13 ፤ በፊቴ ፡ ያለቅሳሉና ፦ የምንበላውን ፡ ሥጋ ፡ ስጠን ፡ ይላሉና ፥ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡
የምሰጠው ፡ ሥጋ ፡ ከወዴት ፡ እወስዳለኹ ፧

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 14 ፤ እጅግ ፡ ከብዶኛልና ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ሕዝብ ፡ ልሸከም ፡ አልችልም ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 15 ፤ እንዲህስ ፡ ከምታደርግብኝ ፥ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡
የሚኾነውን ፡ መከራ ፡ እንዳላይ ፥ እባክኽ ፥ ፈጽሞ ፡ ግደለኝ ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ከእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፥ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡
ሽማግሌዎችና ፡ አለቃዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ የምታውቃቸውን ፥ ሰባ ፡ ሰዎች ፡ ሰብስብልኝ ፥ ወደመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡
አምጣቸው ፥ በዚያም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አቁማቸው ።

ዘኍ. ፥ 11 ፥ 17 ፤ እኔም ፡ እወርዳለኹ ፥ በዚያም ፡ እነጋገርኻለኹ ፥ ባንተ ፡ ካለውም ፡ መንፈስ ፡ ወስጄ ፡ በእነርሱ ፡

ላይ ፡ አደርገዋለኹ ፤ አንተም ፡ ብቻ ፡ እንዳትሸከም ፡ የሕዝቡን ፡ ሸክም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይሸከማሉ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ሕዝቡንም ፡ በላቸው ፦ የምንበላውን ፡ ሥጋ ፡ ማን ፡ ይሰጠናል ፧ በግብጽ ፡ ደኅና ፡ ነበረልን ፡ እያላችኹ ፡ ያለቀሳችኹት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጮሮ ፡ ደርሷልና ፥ ለነገ ፡ ተቀደሱ ፥ ሥጋንም ፡ ትበላላችኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሥጋን ፡ ይሰጣችኋል ፥ ትበሉማላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ዐምስት ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ኻያ ፡ ቀን ፡ አትበሉም ፤

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመካከላችኹ ፡ ያለውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ንቃችኋልና ፥ በፊቱም ፦ ለምን ፡ ከግብጽ ፡ ወጣን ፧ ብላችኹ ፡ አልቅሳችኋልና ፥ በአፍንጫችኹ ፡ እስኪወጣ ፡ እስኪሰለቻችኹም ፡ ድረስ ፥ ወር ፡ ሙሉ ፡ ትበሉታላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ሙሴም ፦ እኔ ፡ በመካከላቸው ፡ ያለኹ ፡ ሕዝብ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ እግረኛ ፡ ናቸው ፤ አንተም ፦ ወር ፡ ሙሉ ፡ የሚበሉትን ፡ ሥጋ ፡ እኔ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፡ አልኽ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ እነርሱን ፡ የሚያጠግብ ፡ የበሬና ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ይታረድን ፧ ወይስ ፡ የባሕርን ፡ ዓሣ ፡ ኹሉ ፡ ያጠግባቸው ፡ ዘንድ ፡ ይሰበሰብላቸዋልን ፧ አለ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ዐጪር ፡ ኾነ ፧ አኹን ፡ ቃሌ ፡ ይፈጸም ፡ ወይስ ፡ አይፈጸም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንተ ፡ ታያለኽ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ሙሴም ፡ ወጣ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃሎች ፡ ለሕዝቡ ፡ ነገረ ፤ ከሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ሰባውን ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፡ በድንኳኑ ፡ ዙሪያ ፡ አቆማቸው ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደመናው ፡ ወረደ ፥ ተናገረውም ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ መንፈስ ፡ ወስዶ ፡ በሰባው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ መንፈሱም ፡ በላያቸው ፡ ባደረ ፡ ጊዜ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፤ ከዚያ ፡ በኋል ፡ ግን ፡ አልተናገሩም ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ከነርሱም ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ በሰፈር ፡ ቀርተው ፡ ነበር ፥ የአንዱም ፡ ስም ፡ ኤልዳድ ፡ የኹለተኛውም ፡ ሞዳድ ፡ ነበረ ፤ መንፈስም ፡ ወረደባቸው ፤ እነርሱም ፡ ከተጻፉት ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ግን ፡ አልወጡም ፡ ነበር ፤ በሰፈሩም ፡ ውስጥ ፡ ሳሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ አንድ ፡ ጐበዝ ፡ ሰው ፡ እየሮጠ ፡ መጥቶ ፦ ኤልዳድና ፡ ሞዳድ ፡ በሰፈር ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡ ብሎ ፡ ለሙሴ ፡ ነገረው ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ከልጅነቱ ፡ ዠምሮ ፡ የሙሴ ፡ አገልጋይ ፡ የነበረው ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፦ ጌታዬ ፡ ሙሴ ፡ ሆይ ፥ ከልክላቸው ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ነቢያት ፡ ቢኾኑ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ መንፈሱን ፡ ቢያወርድ ፤ አንተ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ትቀናለኽን ፧ አለው ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ ከእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ተመለሰ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ነፋስም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፥ ከባሕርም ፡ ድርጭቶችን ፡ አመጣ ፥ የአንድ ፡ ቀንም ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ በዚህ ፥ የአንድ ፡ ቀንም ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ በዚያ ፡ በሰፈሩ ፡ ላይ ፡ በተናቸው ፤ በዚያም ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ከፍታው ፡ ከምድር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሹሉ ፡ በሌሊትም ፡ ሹሉ ፡ በነጋውም ፡ ሹሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ተነሥተው ፡ ድርጭትን ፡

ሰበሰቡ ፤ ከ፹ሉ ፡ ጥቂት ፡ የሰበሰበ ፡ ዐሥር ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ የሚያኽል ፡ ሰበሰበ ፤ በሰፈሩም ፡ ዙሪያ ፡ ፹ሉ ፡ አሰጡት ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ ሥጋውም ፡ ገና ፡ በጥርሳቸው ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡ ሳያኝኩትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሕዝቡን ፡ በታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ እጅግ ፡ መታ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ የጐመገዩ ፡ ሕዝብ ፡ በዚያ ፡ ተቀብረዋልና ፥ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የምኞት ፡ መቃብር ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ዘኍ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ሕዝቡም ፡ ከምኞት ፡ መቃብር ፡ ወደ ፡ ሐጼሮት ፡ ተጓዙ ፡ በሐጼሮትም ፡ ተቀመጡ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ ኢትዮጵያዊቱን ፡ አግብቷልና ፥ ባገባት ፡ በኢትዮጵያዊቱ ፡ ምክንያት ፡ ማርያምና ፡ አሮን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገሩ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ እነርሱም ፦ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ ብቻ ፡ ተናግሯልን ፧ በእኛስ ፡ ደግሞ ፡ የተናገረ ፡ አይደለምን ፧ አሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰማ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ፹ሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ትሑት ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወዲያው ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ማርያምንም ፦ ሦስታችኹ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፤ ሦስቱም ፡ ወጡ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፡ ወረደ ፥ በድንኳኑም ፡ ደጃፍ ፡ ቆመ ፤ አሮንንና ፡ ማርያምን ፡ ጠራ ፥ ኹለቱም ፡ ወጡ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፤ በመካከላችኹ ፡ ነቢይ ፡ ቢኖር ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በራእይ ፡ እገለጥለታለኹ ፥ ወይም ፡ በሕልም ፡ እናገረዋለኹ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ባሪያዬ ፡ ሙሴ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ርሱ ፡ በቤቴ ፡ ፹ሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ አፍ ፡ ለአፍ ፡ በግልጥ ፡ እናገረዋለኹ ፥ በምሳሌ ፡ አይደለም ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ መልክ ፡ ያያል ፤ በባሪያዬ ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ ትናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልፈራችኹም ፧ አለ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቶባቸው ፡ ኼደ ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ደመናውም ፡ ከድንኳኑ ፡ ተነሣ ፤ እንሆም ፥ ማርያም ፡ ለምጻም ፡ ኾነች ፥ እንደ ፡ ዐመዳይም ፡ ነጭ ፡ ኾነች ፤ አሮንም ፡ ማርያምን ፡ ተመለከተ ፥ እንሆም ፥ ለምጻም ፡ ኾና ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ አሮንም ፡ ሙሴን ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ስንፍና ፡ አድርገናልና ፥ በድለንማልና ፥ እባክኽ ፥ ኀጢአት ፡ አታድርግብን ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ከእናቱ ፡ ሆድ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ግማሽ ፡ ሥጋው ፡ ተበልቶ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ርሷ ፡ አትኹን ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየጮኸ ፦ አቤቱ ፥ እባክኽ ፥ አድናት ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ አባቷ ፡ ምራቁን ፡ በፊቷ ፡ ቢተፋባት ፡ ስንኳ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ታፍር ፡ ዘንድ ፡ ይገባ፡ ነበር ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ተዘግታ ፡ ትቀመጥ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ትመለስ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ማርያምም ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተዘግታ ፡ ተቀመጠች ፤ ማርያምም ፡ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡ ፡ አልተጓዙም ።

ዘኍ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ከሐጼሮት ፡ ተጓዙ ፥ በፋራንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ።

____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። ____

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የምሰጣትን ፡ የከነዓንን ([82]) ፡ ምድር ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ላክ ፤ ከአባቶች ፡ ነገድ ፡ ሹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በመካከላቸው ፡ አለቃ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ትልካላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ከፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ላካቸው ፤ እነርሱም ፡ ሹሉ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ የዘኩር ፡ ልጅ ፡ ሰሙኤል ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ከስምዖን ፡ ነገድ ፡ የሱሬ ፡ ልጅ ፡ ሰፈጥ ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ይግአል ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ አውሴ ([83]) ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ 10 ፤ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የራፉ ፡ ልጅ ፡ ፈልጢ ፤ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ የሰዲ ፡ ልጅ ፡ ጉዲኤል ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ከዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ ርሱም ፡ የምናሴ ፡ ነገድ ፡ የሱሲ ፡ ልጅ ፡ ጋዲ ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ከዳን ፡ ነገድ ፡ የገማሊ ፡ ልጅ ፡ ዓሚኤል ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ከአሴር ፡ ነገድ ፡ የሚካኤል ([84]) ፡ ልጅ ፡ ሰቱር ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ የያቢ ፡ ልጅ ፡ ናቢ ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ ከጋድ ፡ ነገድ ፡ የማኪ ፡ ልጅ ፡ ጉዲኤል ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ምድሪቱን ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ሙሴ ፡ የላካቸው ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። ሙሴም ፡ የነዌን ፡ ልጅ ፡ አውሴን ፡ ኢያሱ ([85]) ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ሙሴም ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ፥ አላቸውም ። ከዚህ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ውጡ ፥ ወደ ፡ ተራራዎችም ፡ ኺዱ ፤

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ምድሪቱንም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ በርሷም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ብርቱዎች ፡ ወይም ፡ ደካማዎች ፥

---

82 ዕብ. ፥ ክናዓል ፡ (ከነዓን ፥ ነጋዴ) ።

83 ዕብ. ፥ ሆሼዐ ።

84 ዕብ. ፥ ሚይካኤል ፡ (ሚ ፡ ከመ ፡ እግዚአብሔር • ማን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር) ።

85 ዕብ. ፥ የሆሹዐ ፡ (እግዚአብሔር ፡ ይታደገው) ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ ጥቂቶች ፡ ወይም ፡ ብዙዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ የሚኖሩባትም ፡ ምድር ፡ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፥ የሚኖሩባቸውም ፡ ከተማዎች ፡ ሰፈሮች ፡ ወይም ፡ ዐምባዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ምድሪቱም ፡ ወፍራም ፡ ወይም ፡ ሥሥ ፡ ዛፍ ፡ ያለባት ፡ ወይም ፡ የሌለባት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እዩ ፤ ከምድሪቱ ፡ ፍሬ ፡ አምጡ ፤ አይዟችኹ ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ወይኑ ፡ አስቀድሞ ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈራበት ፡ ወራት ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ወጡም ፥ ምድሪቱንም ፡ ከጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በሐማት ፡ ዳር ፡ እስካለችው ፡ እስከ ፡ ረአብ ([86]) ፡ ድረስ ፡ ሰለሉ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ወጡ ፥ ወደ ፡ ኬብሮንም ፡ ደረሱ ፤ በዚያም ፡ የዔናቅ ([87]) ፡ ልጆች ፡ አኪመን ([88]) ፥ ሴሲ ፥ ተላሚ ፡ ነበሩ ። ኬብሮንም ፡ በግብጽ ፡ ካለችው ፡ ከጣኔዎስ ፡ በፊት ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተሠርታ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ ኤሽኮልም ፡ ሸለቆ ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ ከወይኑ ፡ አንድ ፡ ዘለላ ፡ የነበረበትን ፡ ዐረግ ፡ ቈረጡ ፥ ኹለቱም ፡ ሰዎች ፡ በመሎጊያ ፡ ተሸከሙት ፤ ደግሞም ፡ ከሮማኑ ፡ ከበለሱም ፡ አመጡ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከዚያ ፡ ስለ ፡ ቈረጡት ፡ ዘለላ ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የኤሽኮል ([89]) ፡ ሸለቆ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ምድሪቱንም ፡ ሰልለው ፡ ከአርባ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተመለሱ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ በፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳና ፡ በቃዴስ ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ወደእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ኼደው ፡ ደረሱ ፤ ወሬውንም ፡ ለእነርሱና ፡ ለማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ነገሯቸው ፥ የምድሪቱንም ፡ ፍሬ ፡ አሳይዋቸው ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፦ ወደላክኸን ፡ ምድር ፡ ደረስን ፥ ርሷም ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ታፈሳለች ፥ ፍሬዋም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ኀያላን ፡ ናቸው ። ከተማዎቻቸውም ፡ የተመሸጉ ፡ እጅግም ፡ የጸኑ ፡ ናቸው ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ የዔናቅን ፡ ልጆች ፡ አየን ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ በደቡብም ፡ ምድር ፡ ዐማሌቅ ፡ ተቀምጧል ፤ በተራራዎቹም ፡ ኬጢያዊና ፡ ኢያቡሳዊ ፡ አሞራዊም ፡ ተቀምጠዋል ፤ ከነዓናዊም ፡ በባሕር ፡ ዳርና ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጧል ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ ካሌብም ፡ ሕዝቡን ፡ በሙሴ ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ አሠኘና ፦ ማሸነፍ ፡ እንችላለንና ፥ እንውጣ ፥ እንውረሰው ፡ አለ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የወጡ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፦ በኀይል ፡ ከእኛ ፡ ይበረታሉና ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ መውጣት ፡ አንችልም ፡ አሉ ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ ስለሰለሏትም ፡ ምድር ፡ ክፉ ፡ ወሬ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እያወሩ ፦ እኛ ፡ ዞረን ፡ የሰለልናት ፡ ምድር ፡ የሚኖሩባትን ፡ ሰዎች ፡ የምትበላ ፡ ምድር ፡ ናት ፤ በርሷም ፡ ዘንድ ፡ ያየናቸው ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ረዣዥም ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ በዚያም ፡ ከኔፊሊም ፡ ወገን ፡ የኾኑትን ፡ ኔፊሊም ፥ የዔናቅን ፡ ልጆች ፥ አየን ፤ እኛም ፡

---

86 ዕብ. ፥ ርሖብ ፡ (ርሕብ • ስፋት) ።

87 ዕብ. ፥ ዐናቅ ፡ (ያነገተ ፥ የታነቀ ፡ በጌጥ ፤ ረዐይታዊ ፡ ኀያል ፡ ሐርበኛ ፥ ከ.ወ.ክ. ፡ ገ.699-700) ።

88 ዕብ. ፥ አኒማን ፡ (መና ፡ እኅው ፥ የወንድም ፡ መና ፥ መኖ ፥ ስጦታ) ።

89 ዕብ. ፥ ኤሽኮል ፡ (አስካል • በቁሙ ፥ ዘለላ) ።

በዐይናችን ፡ ግምት ፡ እንደ ፡ አንበጣዎች ፡ ነበርን ፥ ደግሞም ፡ እኛ ፡ በዐይናቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበርን ፡ አሉ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ድምፃቸውን ፡ አንሥተው ፡ ጮኹ ፤ ሕዝቡም ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ አለቀሱ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 2 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፦ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ሳለን ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡ ኖሮ! ፡ ወይም ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡ ኖሮ! ፡

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሰይፍ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ለምን ፡ ያገባናል ፧ ሴቶቻችንና ፡ ልጆቻችን ፡ ምርኮ ፡ ይኾናሉ ፤ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መመለስ ፡ አይሻለንምን ፧ አሏቸው ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 4 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ኑ ፥ አለቃ ፡ ሾመን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ እንመለስ ፡ ተባባሉ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 5 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጉባኤ ፡ ፊት ፡ በግንባራቸው ፡ ወደቁ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 6 ፤ ምድርን ፡ ከሰለሉት ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱና ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደዱ ፤

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 7 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፦ ዞረን ፡ የሰለልናት ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ናት ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርስ ፡ ከወደደን ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈሰው ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ያገባናል ፡ ርሷንም ፡ ይሰጠናል ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አታምፁ ፤ እንደ ፡ እንጀራ ፡ ይኾኑልናልና ፥ የምድሪቱን ፡ ሰዎች ፡ አትፍሩ ፤ ጥላቸው ፡ ከላያቸው ፡ ተገፈፈ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ አትፍሯቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 10 ፤ ማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ በድንጋይ ፡ ይወግሯቸው ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ። የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ተገለጠ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይንቀኛል ፧ በፊቱስ ፡ ባደረግኹት ፡ ተአምራት ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ አያምንብኝም ፧

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 12 ፤ ከርስታቸው ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ በቸነፈር ፡ እመታቸዋለኹ ፤ አንተም ፡ ከነርሱ ፡ ለሚበዛና ፡ ለሚጠነክር ፡ ሕዝብ ፡ አደርግኻለኹ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 13 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፦ ግብጻውያን ፡ ይሰማሉ ፤ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ከመካከላቸው ፡ በኀይልኽ ፡ አውጥተኽዋልና ፤

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 14 ፤ ለዚችም ፡ ምድር ፡ ሰዎች ፡ ይናገራሉ ። አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ሰምተዋል ፤ አንተም ፥ አቤቱ ፥ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተገልጠኻል ፥ ደመናኽም ፡ በላያቸው ፡ ቆሟል ፥ በቀንም ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፥ በሌሊትም ፡ በእሳት ፡ ዐምድ ፡ በፊታቸው ፡ ትኼዳለኽ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 15 ፤ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብትገድል ፡ ዝናኽን ፡ የሰሙ ፡ አሕዛብ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ወደማለላቸው ፡ ምድር ፡ ያገባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለምና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ገደላቸው ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 17 ፤ 18 ፤ አኹንም ፥ እባክኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ ታጋሽና ፡ ምሕረቱ ፡ የበዛ ፥ አበሳንና ፡

መተላለፍን ፡ ይቅር ፡ የሚል ፥ ኀጢአተኞችንም ፡ ከቶ ፡ የማያነጻ ፥ የአባቶችን ፡ ኀጢአት ፡ እስከ ፡ ሦስትና ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በልጆች ፡ ላይ ፡ የሚያመጣ ፡ ነው ፡ ብለኽ ፡ እንደ ፡ ተናገርኽ ፥ የጌታ ፡ ኀይል ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 19 ፤ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣኽ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይቅር ፡ እንዳልኻቸው ፥ እባክኽ ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽ ፡ ብዛት ፡ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ይቅር ፡ አልኹ ፤

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ይሞላል ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 22 ፤ በግብጽ ፡ ምድርና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያደረግኹትን ፡ ተኣምራቴንና ፡ ክብሬን ፡ ያዩ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተፈታተኑኝ ፥

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 23 ፤ ነገሬንም ፡ ስላልሰሙ ፥ በእውነት ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልኹላቸውን ፡ ምድር ፡ አያዩም ፤ ከነርሱም ፡ የናቀኝ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አያያትም ፤

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 24 ፤ ባሪያዬ ፡ ካሌብ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ መንፈስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ፈጽሞም ፡ ስለ ፡ ተከተለኝ ፥ ርሱ ፡ ወደገባባት ፡ ምድር ፡ አገባዋለኹ ፤ ዘሩም ፡ ይወርሳታል ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 25 ፤ ዐማሌቅና ፡ ከነዓናዊውም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧል ፤ በነጋው ፡ ተመልሳችኹ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኺዱ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 27 ፤ የሚያጉረመርምብኝን ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እታገሠዋለኹ ። በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚያጉረመርሙትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማጉረምረም ፡ ሰማኹ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 28 ፤ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በጕሮዬ ፡ እንደ ፡ ተናገራችኹት ፡ እንዲሁ ፡ በእውነት ፡ አደርግባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 29 ፤ በድኖቻችኹ ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይወድቃሉ ፤ የተቈጠራችኹ ፡ ኹሉ ፥ እንደ ፡ ቍጥራችኹ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፥ እናንተ ፡ ያጉረመረማችኹብኝ ፥

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 30 ፤ ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብና ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ በቀር ፡ በርሷ ፡ አስቀምጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ እጄን ፡ ዘርግቼ ፡ ወደማልኹላችኹ ፡ ምድር ፡ በእውነት ፡ እናንተ ፡ አትገቡም ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 31 ፤ ምርኮኛ ፡ ይኾናሉ ፡ ያላችኋቸውን ፡ ልጆቻችኹን ፡ እነርሱን ፡ አገባቸዋለኹ ፥ እናንተም ፡ የናቃችኋትን ፡ ምድር ፡ ያውቃሉ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 32 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በድኖቻችኹ ፡ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይወድቃሉ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 33 ፤ ልጆቻችኹም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ይቅበዘበዛሉ ፥ በድኖቻችኹም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ግልሙትናችኹን ፡ ይሸከማሉ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 34 ፤ ምድሪቱን ፡ በሰለላችኹባት ፡ ቀን ፡ ቍጥር ፥ አርባ ፡ ቀን ፥ ስለ ፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፥ ኀጢአታችኹን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ትሸከማላችኹ ፥ ቍጣዬንም ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 14 ፥ 35 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፦ በእኔ ፡ ላይ ፡ በተሰበሰበ ፡ በዚህ ፡ ክፉ ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡

አደርጋለኹ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹ ፤ በዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ያልቃሉ ፥ በዚያም ፡ ይሞታሉ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 36 ፤ ምድሪቱንም ፡ ሊሰልሉ ፡ ሙሴ ፡ ልኳቸው ፡ የተመለሱት ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ወሬም ፡ ስለ ፡ ምድሪቱ ፡ እያወሩ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ማኅበሩ ፡ ዅሉ ፡ እንዲያጕረመርሙ ፡ ያደረጉ ፥

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 37 ፤ ክፉ ፡ ወሬ ፡ ያወሩ ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመቅሠፍት ፡ ሞቱ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 38 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምድሪቱን ፡ ሊሰልሉ ፡ ከኼዱ ፡ ሰዎች ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱና ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ በሕይወት ፡ ተቀመጡ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 39 ፤ ሙሴም ፡ ይህን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ ነገረ ፥ ሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ዐዘኑ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 40 ፤ በነጋውም ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥ ወደተራራውም ፡ ራስ ፡ መጥተው ፦ እንሆ ፥ መጣን ፤ እኛ ፡ በድለናልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ እንወጣለን ፡ አሉ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 41 ፤ ሙሴም ፡ አለ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለምን ፡ ትተላለፋላችኹ ፧ አይጠቅማችኹም ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 42 ፤ እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ አይደለምና ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ፊት ፡ እንዳትወድቁ ፡ አትውጡ ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 43 ፤ ዐማሌቃዊና ፡ ከነዓናዊ ፡ በፊታችኹ ፡ ናቸውና ፥ በሰይፍ ፡ ትወድቃላችኹ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ተመልሳችኋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አይኾንም ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 44 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ወደተራራው ፡ ራስ ፡ ሊወጡ ፡ ደፈሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦትና ፡ ሙሴ ፡ ከሰፈሩ ፡ አልተነሡም ።

ዘኍ. ፡ 14 ፡ 45 ፤ በዚያም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፡ ዐማሌቃዊና ፡ ከነዓናዊ ፡ ወረዱ ፥ መትተዋቸውም ፡ እስከ ፡ ሔርማ ፡ ድረስ ፡ አሳደዷቸው ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ወደምሰጣችኹ ፡ ወደ ፡ መኖሪያችኹ ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ስእለታችኹን ፡ ልትፈጽሙ ፥ ወይም ፡ በፈቃዳችኹ ፥ ወይም ፡ በበዓላችኹ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ከበሬ ፡ ወይም ፡ ከበግ ፡ መንጋ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾን ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብታቀርቡ ፥

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 4-5 ፤ ቍርባኑን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርብ ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ከሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ በኾነ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ የኾነ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፥ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ ያዘጋጃል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 6-7 ፤ ለአንዱም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ሚሶ ፡ በኾነ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ ታዘጋጃለኽ ፤ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ሚሶም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ስእለትን ፡ ለመፈጸም ፡

ወይም ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ወይፈንን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብታዘጋጅ ፥

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 9 ፤ ከወይፈኑ ፡ ጋራ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ግማሽ ፡ በኾነ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 10 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ ለተደረገ ፡ ቍርባን ፥ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ግማሽ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 11 ፤ እንዲሁ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ወይፈን ፡ ወይም ፡ ለያንዳንዱ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ወይም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ይደረጋል ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 12 ፤ እንዳዘጋጃችኹት ፡ ቍጥር ፥ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ታደርጋላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 13 ፤ የአገር ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ቍርባን ፡ በእሳት ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 14 ፤ መጻተኛም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ቢቀመጥ ፥ ወይም ፡ በትውልዳችኹ ፡ መካከል ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ቍርባን ፡ በእሳት ፡ ቢያቀርብ ፥ እናንተ ፡ የምታደርጉትን ፡ ርሱ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 15 ፤ ለእናንተ ፡ በጉባኤው ፡ ላላችኹ ፡ በእናንተም ፡ መካከል ፡ ለሚቀመጥ ፡ መጻተኛ ፡ አንድ ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ፥ ለልጅ ፡ ልጃችኹም ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ እንዲሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መጻተኛ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 16 ፤ ለእናንተና ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ለሚቀመጥ ፡ መጻተኛ ፡ አንድ ፡ ሕግና ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 18 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ወደማመጣችኹ ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 19 ፤ እናንተ ፡ የምድሪቱን ፡ እንጀራ ፡ በበላችኹ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ታደርጋላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 20 ፤ መዠመሪያ ፡ ከምታደርጉት ፡ ሊጥ ፡ አንድ ፡ ዕንጐቻ ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ከዐውድማም ፡ እንደምታነሡት ፡ ቍርባን ፡ እንዲሁ ፡ ታነሣላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 21 ፤ መዠመሪያ ፡ ከምታደርጉት ፡ ሊጥ ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ እስከልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትሰጣላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 22 ፤ ብትስቱም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዛቸውን ፡ እነዚህን ፡ ትእዛዛት ፡ ኹሉ ፡ ባታደርጉ ፥

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ ካዘዘበት ፡ ከፊተኛው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ እስከልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ያዘዛችኹን ፡ ኹሉ ፡ ባታደርጉ ፥

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 24 ፤ ማኅበሩ ፡ ሳያውቁ ፡ በስሕተት ፡ ቢደረግ ፥ ማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባንና ፡ ከመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ያቀርባሉ ።

ዘኍ. ፥ 15 ፥ 25 ፤ ካህኑም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ያስተሰርይላቸዋል ፥ ስሕተትም ፡ ነበረና ፡

ይሰረይላቸዋል ፤ ስለ ፡ ስሕተታቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባናቸውን ፡ በእሳት ፡ አቅርበዋል ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የኀጢአታቸውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርበዋል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ በሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ያለዕውቀት ፡ ተደርጓልና ፥ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በመካከላቸውም ፡ ለሚኖሩት ፡ መጻተኞች ፡ ስርየት ፡ ይደረግላቸዋል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ሳያውቅ ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፥ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አንዲት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ እንስት ፡ ፍየል ፡ ያቀርባል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ ኀጢአት ፡ ሠርቶ ፡ ሳያውቅ ፥ ለሳተ ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ካህኑ ፡ ያስተሰርይለታል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይለታል ፥ ይሰረይለትማል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ ትውልዱ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ቢኾን ፥ ወይም ፡ በመካከላቸው ፡ የሚቀመጥ ፡ መጻተኛ ፡ ቢኾን ፥ ሳያውቅ ፡ ኀጢአትን ፡ ለሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ ሕጉ ፡ አንድ ፡ ይኾንለታል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ የአገር ፡ ልጅ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ መጻተኛ ፡ ቢኾን ፥ አንዳች ፡ በትዕቢት ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሰድቧል ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ናቀ ፥ ትእዛዙንም ፡ ስለ ፡ ሰበረ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ ይጥፋ ፤ ኀጢአቱ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ዕንጨት ፡ ሲለቅም ፡ አገኙ ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ ዕንጨትም ፡ ሲለቅም ፡ ያገኙት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ አሮን ፡ ወደ ፡ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ አመጡት ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 34 ፤ ያደርጉበትም ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ አልተገለጠምና ፥ በግዞት ፡ አስቀመጡት ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ሰውየው ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ ማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገሩት ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 36 ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጡት ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 38 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ እነርሱም ፡ ትውልዶቻቸውም ፡ በልብሳቸው ፡ ጫፍ ፡ ዘርፍ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ በዘርፉም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሰማያዊ ፡ ፈትል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እዘዛቸው ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 39 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ታስቡና ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፥ ርሷን ፡ በመከተል ፡ ያመነዘራችኹባትን ፡ የልባችኹንና ፡ የዐይኖቻችኹን ፡ ፈቃድ ፡ እንዳትከተሉ ፥

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 40 ፤ ትእዛዜን ፡ ኹሉ ፡ ታስቡና ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፥ ለአምላካችኹም ፡ ቅዱሳን ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ዘርፉ ፡ በልብሳችኹ ፡ ላይ ፡ እንዲታይ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 15 ፡ 41 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፤ አምላክ ፡ እኾናችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኋችኹ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የሌዊም ፡ ልጅ ፡ የቀአት ፡ ልጅ ፡ የይስዓር ፡ ልጅ ፡ ቆሬ ፡ ከሮቤልም ፡ ልጆች ፡ የኤልያብ ፡ ልጆች ፡ ዳታን ([90])ና ፡ አቤሮን ([91]) ፡ የፋሌትም ፡ ልጅ ፡ ኦን ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ ተነሡ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰዱ ፤ ከጉባኤው ፡ የተመረጡ ፡ ዝናቸውም ፡ የተሰማ ፡ የማኅበሩ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፦ ማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸውና ፥ እግዚአብሔርም ፡ በመካከላቸው ፡ ነውና ፥ እናንተ ፡ እጅግ ፡ አብዝታችኋል ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ትታበያላችኹ ፧ አሉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ሙሴም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በግንባሩ ፡ ወደቀ ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ ለቆሬም ፡ ለወገኑም ፡ ኹሉ ፦ ነገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርሱ ፡ የሚኾነውን ፥ ቅዱስም ፡ የሚኾነውን ፡ ያስታውቃል ፤ የመረጠውንም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያቀርበዋል ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ እንዲሁ ፡ አድርጉ ፤ ቆሬና ፡ ወገንኽ ፡ ኹሉ ፥ ጥናዎቹን ፡ ውሰዱ ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ ነገም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እሳት ፡ አድርጉባቸው ፥ ዕጣንም ፡ ጨምሩባቸው ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚመርጠው ፡ ርሱ ፡ ቅዱስ ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ እጅግ ፡ አብዝታችኋል ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ሙሴም ፡ ቆሬን ፡ አለው ፦ እናንተ ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፥ ስሙ ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ የለያችኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ማደሪያ ፡ አገልግሎት ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፥ እንድታገለግሏቸውም ፡ በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ ትቆሙ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያቀረባችኹ ፡ አይበቃችኹምን ፧

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ አንተን ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ የሌዊን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞችኽን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አቅርቧል ፤ ክህነትንም ፡ ደግሞ ፡ ትፈልጋላችኹን ፧

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ስለዚህም ፡ አንተና ፡ ወገንኽ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ተሰብስባችኋል ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ታጕረመርሙ ፡ ዘንድ ፡ አሮን ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ሙሴም ፡ የኤልያብን ፡ ልጆች ፡ ዳታንና ፡ አቤሮንን ፡ እንዲጠሯቸው ፡ ላከ ፤ እነርሱም ፦ አንመጣም ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ትገድለን ፡ ዘንድ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ከምታፈሰው ፡ ምድር ፡ ያወጣኸን ፡ አይበቃኽምን ፧ ደግመኽ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ራስኽን ፡ አለቃ ፡ ታደርጋለኽን ፧

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ደግሞ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈስ ፡ ምድር ፡ አላገባኸንም ፥ ዕርሻና ፡ ወይንም ፡ አላወረስኸንም ፤ የእነዚህንስ ፡ ሰዎች ፡ ዐይኖቻቸውን ፡ ታወጣለኽን ፧ አንመጣም ፡ አሉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ እግዚአብሔርንም ፦ ወደ ፡ ቍርባናቸው ፡ አትመልከት ፤ እኔ ፡ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ አህያ ፡ ስንኳ ፡ አልወሰድኹም ፥ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልበደልኹም ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ሙሴም ፡ ቆሬን ፦ ነገ ፡ አንተ ፥ ወገንኽም ፡ ኹሉ ፥ አሮንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኹኑ ፤

---

90 ሥርዐት ፡ (ኪ.ወ.ክ ፥ ገ.364)

91 ዕብ. ፥ አቢራም ፡ (አበ ፡ ራማ ፥ የከፍታ ፡ የልዕልና ፡ አባት) ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ዥላችኹም ፡ ጥናዎቻችኹን ፡ ውሰዱ ፥ ዕጣንም ፡ አድርጉባቸው ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ ጥናዎቻችኹን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አምጡ ፥ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ጥናዎች ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ አሮንም ፡ ጥናዎቻችኹን ፡ አምጡ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ እያንዳንዱም ፡ ጥናውን ፡ ወሰደ ፥ እሳትም ፡ አደረገበት ፥ ዕጣንም ፡ ጨመረበት ፥ ከሙሴና ፡ ከአሮንም ፡ ጋራ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ቆመ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ቆሬም ፡ ማኅበሩን ፡ ዥሉ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ሰበሰበ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ለማኅበሩ ፡ ዥሉ ፡ ተገለጠ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ዥሉን ፡ በቅጽበት ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ እነርሱም ፡ በግንባራቸው ፡ ወድቀው ፦ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ የሰው ፡ ዥሉ ፡ ነፍስ ፡ አምላክ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፡ አንተ ፡ በማኅበሩ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ትቈጣለኽን ፧ አሉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ለማኅበሩ ፦ ከቆሬና ፡ ከዳታን ፡ ከአቤሮንም ፡ ማደሪያ ፡ ዙሪያ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ሙሴም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዳታንና ፡ ወደ ፡ አቤሮን ፡ ኼደ ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተከተሉት ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ማኅበሩንም ፦ እባካችኹ ፥ ከነዚህ ፡ ክፉዎች ፡ ድንኳን ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፤ በኀጢአታቸውም ፡ ዥሉ ፡ እንዳትጠፉ ፡ ለእነርሱ ፡ የኾነውን ፡ ዥሉ ፡ አትንኩ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ከቆሬና ፡ ከዳታን ፡ ከአቤሮንም ፡ ማደሪያ ፡ ከዙሪያውም ፡ ዥሉ ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፤ ዳታንና ፡ አቤሮንም ፡ ሴቶቻቸውም ፡ ልጆቻቸውም ፡ ሕፃናታቸውም ፡ ወጥተው ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ደጃፍ ፡ ቆሙ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ሙሴም ፡ አለ ፦ ይህን ፡ ሥራ ፡ ዥሉ ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እንጂ ፡ ከልቤ ፡ እንዳይደለ ፡ በዚህ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሰው ፡ እንደሚሞት ፡ ቢሞቱ ፥ ወይም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዥሉ ፡ ቢቀሠፉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልላከኝም ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ ቢፈጥር ፥ ምድርም ፡ አፏን ፡ ከፍታ ፡ እነርሱን ፡ ለእነርሱም ፡ ያለውን ፡ ዥሉ ፡ ብትውጣቸው ፥ በሕይወታቸውም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ቢወርዱ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ናቁ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ይህን ፡ ቃል ፡ ዥሉ ፡ መናገር ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ከበታቻቸው ፡ ያለው ፡ መሬት ፡ ተሠነጠቀ ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ ምድሪቱም ፡ አፏን ፡ ከፍታ ፡ እነርሱን ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውንም ፥ ለቆሬም ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዥሉ ፥ ዕቃዎቻቸውንም ፡ ዥሉ ፡ ዋጠቻቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ እነርሱም ፡ ለእነርሱም ፡ የነበሩ ፡ ዥሉ ፡ በሕይወታቸው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወረዱ ፤ ምድሪቱም ፡ ተዘጋችባቸው ፥ ከጉባኤውም ፡ መካከል ፡ ጠፉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 34 ፤ በዙሪያቸው ፡ የነበሩ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከጩኸታቸው ፡ የተነሣ ። ምድሪቱ ፡ እንዳትውጠን ፡ ብለው ፡ በረሩ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 35 ፤ እሳትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወጥታ ፡ ያጥኑ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ በላች ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 36 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 37 ፤ ለካህኑ ፡ ለአሮን ፡ ልጅ ፡ ለአልዓዛር ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፦ ተቀድሰዋልና ፥ ጥናዎቹን ፡ ከተቃጠሉት ፡ ዘንድ ፡ ውሰድ ፥ እሳቱንም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣለው ፤

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 38 ፤ በኀጢአታቸው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያጠፉትን ፡ የእነዚያን ፡ ሰዎች ፡ ጥናዎች ፡ ጠፍጥፈኽ ፡ ለመሠዊያ ፡ መለበጫ ፡ አድርጋቸው ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቅርበዋቸዋልና ፥ የተቀደሱ ፡ ናቸው ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ምልክት ፡ ይኾናሉ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 39 ፤ ካህኑም ፡ አልዓዛር ፡ የተቃጠሉት ፡ ሰዎች ፡ ያቀረቧቸውን ፡ የናስ ፡ ጥናዎች ፡ ወስዶ ፡ ጠፍጥፎም ፡ ለመሠዊያው ፡ መለበጫ ፡ አደረጋቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 40 ፤ በቆሬና ፡ በወገኑ ፡ የደረሰው ፡ እንዳይደርስበት ፥ ከአሮን ፡ ልጆች ፡ ያልኾነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዕጣን ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቀርብ ፥ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፥ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መታሰቢያ ፡ አደረጋቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 41 ፤ በነጋውም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፦ እናንተ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕዝብ ፡ ገድላችኋል ፡ ብለው ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 42 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ማኅበሩ ፡ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ ላይ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አዩ ፤ እንሆም ፥ ደመናው ፡ ሸፈነው ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ተገለጠ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 43 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ መጡ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 44 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 45 ፤ ከዚህ ፡ ማኅበር ፡ መካከል ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፥ እኔም ፡ በቅጽበት ፡ አጠፋቸዋለኹ ። በግንባራቸውም ፡ ወደቁ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 46 ፤ ሙሴም ፡ አሮንን ፦ ጥናኽን ፡ ውሰድ ፥ ከመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ አድርግበት ፥ ዕጣንም ፡ ጨምርበት ፥ ወደ ፡ ማኅበሩም ፡ ፈጥነኽ ፡ ውሰደው ፡ አስተስርይላቸውም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቍጣ ፡ ወጥቷልና ፥ መቅሠፍት ፡ ገምሯል ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 47 ፤ አሮንም ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ ጥናውን ፡ ወስዶ ፡ ወደጉባኤው ፡ መካከል ፡ ሮጠ ፤ እንሆም ፥ መቅሠፍቱ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ገምሮ ፡ ነበር ፤ ዕጣንም ፡ ጨመረ ፥ ለሕዝቡም ፡ አስተሰረየላቸው ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 48 ፤ በሙታንና ፡ በሕያዋን ፡ መካከል ፡ ቆመ ፤ መቅሠፍቱም ፡ ተከለከለ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 49 ፤ በቆሬም ፡ ምክንያት ፡ ከሞቱት ፡ ሌላ ፡ በመቅሠፍቱ ፡ የሞቱት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 16 ፡ 50 ፤ አሮንም ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ተመለሰ ፤ መቅሠፍቱም ፡ ተከለከለ ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ፥ ከነርሱም ፡ ከያንዳንዱ ፡ ከየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ በትር ፥ ከአለቃዎቻቸው ፡ ከየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ በትሮች ፥ ውሰድ ፤ የያንዳንዱንም ፡ ስም ፡ በየበትሩ ፡ ላይ ፡ ጻፍ ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ አንድ ፡ በትርም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ይኾናልና ፥ በሌዊ ፡ በትር ፡ ላይ ፡ የአሮንን ፡ ስም ፡ ጻፍ ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ በምገናኝበት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በምስክሩ ፡ ፊት ፡ አኑራቸው ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ የመረጥኹት ፡ ሰው ፡ በትር ፡ ታቈጠቍጣለች ፤ በእናንተም ፡ ላይ ፡ የሚያጉረመርሙብኝኹን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማጉረምረም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጠፋለኹ ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተናገራቸው ፤ አለቃዎቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ በትሮች ፥ እያንዳንዱም ፡ አለቃ ፡ በያባቱ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ በትር ፥ ሰጡት ፤ የአሮንም ፡ በትር ፡ በበትሮቻቸው ፡ መካከል ፡ ነበረች ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ በትሮቹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በነጋው ፡ ሙሴ ፡ ወደምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ እንሆም ፥ ለሌዊ ፡ ቤት ፡ የኾነች ፡ የአሮን ፡ በትር ፡ አቈጠቈጠች ፥ ለመለመችም ፥ አበባም ፡ አወጣች ፥ የበሰለ ፡ ለውዝም ፡ አፈራች ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ በትሮችን ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አወጣቸው ፤ እነርሱም ፡ አዩ ፥ እያንዳንዱም ፡ በትሩን ፡ ወሰደ ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የአሮንን ፡ በትር ፡ ወደምስክሩ ፡ ፊት ፡ መልስ ፤ ማጉረምረማቸው ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዲጠፋ ፡ እነርሱም ፡ እንዳይሞቱ ፡ ለሚያምፁብኝ ፡ ልጆች ፡ ምልክት ፡ ኾና ፡ ትጠበቅ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ሙሴም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፦ እንሆ ፥ እንሞታለን ፥ እንጠፋለን ፥ ኹላችንም ፡ እንጠፋለን ።

ዘኍ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ የሚቀርብ ፡ ኹሉ ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ የሚቀርብ ፥ ይሞታል ፤ በእውኑ ፡ ኹላችን ፡ እንሞታለንን ፧ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ አለው ፦ አንተ ፣ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ልጆችኽና ፡ የአባቶችኽ ፡ ቤት ፡ የመቅደስን ፡ ኀጢአት ፡ ትሸከማላችኹ ፤ አንተም ፣ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ልጆችኽ ፡ የክህነታችኹን ፡ ኀጢአት ፡ ትሸከማላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ደግሞም ፡ የአባትኽን ፡ የሌዊን ፡ ነገድ ፡ ወንድሞችኽን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አቅርብ ፤ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ይኹኑ ፥ ያገልግሉኽም ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ልጆችኽ ፡ በምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ትኾናላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፡ ትእዛዝኽን ፡ የድንኳኑንም ፡ ኹሉ ፡ አገልግሎት ፡ ይጠብቁ ፤ ነገር ፡

ግን ፥ እንዳይሞቱ ፥ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳትሞቱ ፥ እነርሱ ፡ ወደመቅደሱ ፡ ዕቃና ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ አይቅረቡ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ይኹኑ ፥ ለድንኳኑም ፡ አገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ይጠብቁ ፤ ሌላም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይቅረብ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ገና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይኾንባቸው ፡ እናንተ ፡ መቅደሱንና ፡ መሠዊያውን ፡ ጠብቁ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ሌዋውያንን ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወስጃለኹ ፤ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጡ ፡ ለእናንተ ፡ ስጦታ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ አንተም ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ልጆችኽ ፡ ለመሠዊያው ፡ ሥራ ፡ የሚኾነውን ፡ ኹሉ ፥ በመጋረጃውም ፡ ውስጥ ፡ የሚኾነውን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ክህነታችኹን ፡ ጠብቁ ፥ አገልግሉም ፤ ክህነቱን ፡ ለስጦታ ፡ አገልግሎት ፡ ሰጥቻችኋለኹ ፤ ሌላም ፡ ሰው ፡ ቢቀርብ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ ተናገረው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእኔ ፡ የቀደሱትን ፡ የማንሣት ፡ ቍርባኔን ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ሰጥቼካለኹ ፤ ስለ ፡ መቀባትኽ ፡ ለአንተና ፡ ለልጆችኽ ፡ ድርሻ ፡ እንዲኾን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሰጥቼካለኹ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ በእሳት ፡ ከሚቀርበው ፡ ከተቀደሰው ፡ ይህ ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፤ ለእኔ ፡ የሚያመጡት ፡ መባቸው ፡ ኹሉ ፥ የእኽሉ ፡ ቍርባናቸው ፡ ኹሉ ፥ የኀጢአታቸውም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፥ የበደላቸውም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፥ ለአንተ ፡ ለልጆችኽም ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ብላው ፤ ወንዶች ፡ ኹሉ ፡ ይብሉት ፤ የተቀደሰ ፡ ይኾንልኻል ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ይህም ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለስጦታ ፡ ያቀረቡትን ፡ የማንሣትና ፡ የመወዝወዝ ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችኽ ፡ ድርሻ ፡ እንዲኾን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሰጥቼካለኹ ፤ በቤትኽ ፡ ውስጥ ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ይብላው ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ከሚሰጡት ፡ የፍሬ ፡ መዠመሪያ ፡ ከዘይትና ፡ ከወይን ፡ ከእኽልም ፡ የተመረጠውን ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ሰጥቼካለኹ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያመጡት ፡ በምድራቸው ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ የፍሬ ፡ መዠመሪያ ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፤ በቤትኽ ፡ ውስጥ ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ይብላው ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ዕርም ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ከሰው ፡ ወይም ፡ ከእንስሳ ፡ ቢኾን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ማሕፀን ፡ የሚከፍት ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰውን ፡ በኵራት ፡ ፈጽሞ ፡ ትቤዣዋለኽ ፥ ያልነጻውንም ፡ እንስሳ ፡ በኵራት ፡ ትቤዣዋለኽ ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ካንድ ፡ ወር ፡ ዠምሮ ፡ የምትቤዣውን ፡ እንደ ፡ ግምትኽ ፡ ትቤዣዋለኽ ፤ ግምቱም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ሰቅል ፡ ሚዛን ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፡ ይኾናል ፤ ርሱም ፡ ኻያ ፡ አቦሊ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የላም ፡ በኵራት ፡ ወይም ፡ የበግ ፡ በኵራት ፡ ወይም ፡ የፍየል ፡ በኵራት ፡ አትቤዣም ፤ የተቀደሱ ፡ ናቸው ፤ ደማቸውን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ትረጨዋለኽ ፥ ስባቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ለእሳት ፡ ቍርባን ፡ ታቃጥለዋለኽ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ሥጋቸውም ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፤ እንደ ፡ መወዝወዝ ፡ ፍርምባ ፡ እንደ ፡ ቀኙም ፡ ወርች ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አንሥተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀረቡትን ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆችኽ ፡ ድርሻ ፡ እንዲኾን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ለዘርኽ ፡ የጨው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ አለው ፦ በምድራቸው ፡ ርስት ፡ በመካከላቸውም ፡ ድርሻ ፡ አይኾንልኽም ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ድርሻኽና ፡ ርስትኽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ለሌዊም ፡ ልጆች ፥ እንሆ ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ስለሚያገለግሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ዓሥራት ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኀጢአትን ፡ እንዳይሸከሙ ፡ እንዳይሞቱም ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አይቅረቡ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ሌዋውያን ፡ ግን ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ አገልግሎት ፡ ይሥሩ ፥ እነርሱም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አይወርሱም ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርቡትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ዓሥራት ፡ ለሌዋውያን ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቻለኹ ፤ ስለዚህ ፦ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አይወርሱም ፡ አልኋቸው ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ለሌዋውያን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለእናንተ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ የሰጠኋችኹን ፡ ዓሥራት ፡ በተቀበላችኹ ፡ ጊዜ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ የዓሥራት ፡ ዓሥራት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ የማንሣት ፡ ቍርባናችኹም ፡ እንደ ፡ ዐውድማው ፡ እኽልና ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ መጭመቂያው ፡ ፍሬ ፡ ይቈጠርላችኋል ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከምትቀበሉት ፡ ዓሥራት ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባላችኹ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ለካህኑ ፡ ለአሮን ፡ ትሰጣላችኹ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ከምትቀበሉት ፡ ስጦታ ፡ ኹሉ ፥ ከተመረጠው ፡ ከተቀደሰውም ፡ ድርሻ ፡ ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ትላቸዋለኽ ፦ ከርሱ ፡ የተመረጠውን ፡ ባነሣችኹ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዐውድማው ፡ እኽልና ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ መጭመቂያው ፡ ፍሬ ፡ ለሌዋውያን ፡ ይቈጠራል ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ እናንተም ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻችኹም ፥ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ የማገልገላችኹ ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፥ በኹሉ ፡ ስፍራ ፡ ትበሉታላችኹ ።

ዘኁ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ የተመረጠውንም ፡ ከርሱ ፡ ባነሣችኹ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ኀጢአትን ፡ አትሸከሙም ፤ እንዳትሞቱም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የቀደሱትን ፡ አታረክሱም ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። _____

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ የሕጉ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ መልካሚቱን ፥ ነውርም ፡ የሌለባትን ፥ ቀንበርም ፡ ያልተጫነባትን ፡ ቀይ ፡ ጊደር ፡ ያመጡልኽ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ንገራቸው ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 3 ፤ ርሷንም ፡ ለካህኑ ፡ ለአልዓዛር ፡ ትሰጣላችኹ ፥ ርሷንም ፡ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወስዳታል ፥ አንድ ፡ ሰውም ፡ በፊቱ ፡ ያርዳታል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 4 ፤ ካህኑም ፡ አልዓዛር ፡ ከደሟ ፡ በጣቱ ፡ ይወስዳል ፥ ከደሟም ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይረጫል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 5 ፤ ጊደሪቱም ፡ በፊቱ ፡ ትቃጠላለች ፤ ቍርበቷም ፡ ሥጋዋም ፡ ደሟም ፡ ፈርሷም ፡ ይቃጠላል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 6 ፤ ካህኑም ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ሂሶጵም ፡ ቀይ ፡ ግምጃም ፡ ወስዶ ፡ ጊደሪቱ ፡ በምትቃጠልበት ፡ እሳት ፡ መካከል ፡ ይጥለዋል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 7 ፤ ካህኑም ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ይገባል ፤ ካህኑም ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 8 ፤ ያቃጠላትም ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ በውሃ ፡ ያጥባል ፥ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 9 ፤ ንጹሕም ፡ ሰው ፡ የጊደሪቱን ፡ ዐመድ ፡ ያከማቻል ፡ ከሰፈሩም ፡ ውጭ ፡ በንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ ያኖረዋል ፤ ርኵሰትም ፡ ለሚያነጻ ፡ ውሃ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ይጠበቃል ፤ ከኀጢአት ፡ ለማንጻት ፡ የሚኾን ፡ ነው ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 10 ፤ የጊደሪቱንም ፡ ዐመድ ፡ ያከማቸ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፡ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በመካከላቸውም ፡ ለሚኖር ፡ መጻተኛ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 11 ፤ የሞተውን ፡ ሰው ፡ በድን ፡ የሚነካ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 12 ፤ በዚህም ፡ ውሃ ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ኹለመናውን ፡ ያጠራል ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ኹለመናውን ፡ ባያጠራ ፡ ንጹሕ ፡ አይኾንም ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 13 ፤ የሞተውን ፡ ሰው ፡ በድን ፡ የነካ ፡ ኹለመናውን ፡ ባያጠራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማደሪያ ፡ ያረክሳል ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ የሚያነጻ ፡ ውሃ ፡ አልተረጨምና ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ ርኵሰቱ ፡ ገና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 14 ፤ ሰው ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ቢሞት ፡ ሕጉ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ የሚገባ ፡ ኹሉ ፡ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 15 ፤ መክደኛው ፡ ያልታሰረ ፡ የተከፈተ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 16 ፤ በሜዳም ፡ በሰይፍ ፡ የተገደለውን ፡ ወይም ፡ የሞተውን ፡ በድን ፡ ወይም ፡ የሰውን ፡ ዐጥንት ፡ ወይም ፡ መቃብር ፡ የሚነካ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 19 ፥ 17 ፤ ከኀጢአት ፡ ለማንጻት ፡ እንድትኾን ፡ ከተቃጠለችው ፡ ጊደር ፡ ዐመድ ፡ ለርኩሱ ፡ ይወስዱለታል ፥ በዕቃውም ፡ ውስጥ ፡ የምንጭ ፡ ውሃ ፡ ይቀላቀልበታል ።

ዘኍ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ንጹሕም ፡ ሰው ፡ ሂሶጹን ፡ ወስዶ ፡ በውሃው ፡ ውስጥ ፡ ያጠልቀዋል ፤ በድንኳኑም ፡ በዕቃውም ፡ ሹሉ ፡ በዚያም ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ዐጥንቱንም ፡ ወይም ፡ የተገደለውን ፡ ወይም ፡ የሞተውን ፡ ወይም ፡ መቃብሩን ፡ በነካው ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤

ዘኍ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ንጹሑም ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ በርኩሱ ፡ ላይ ፡ ይረጨዋል ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ያጠራዋል ፤ ርሱም ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፡ ገላውንም ፡ በውሃ ፡ ይታጠባል ፡ በማታም ፡ ጊዜ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ሰውም ፡ ርኩስ ፡ ቢኾን ፡ ኹለመናውንም ፡ ባያጠራ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ አርክሷልና ፡ ከጉባኤው ፡ መካከል ፡ ተለይቶ ፡ ይጠፋል ፤ በሚያነጻ ፡ ውሃ ፡ አልተረጨም ፤ ርኩስ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ይህም ፡ የዘለዓለም ፡ ሥርዐት ፡ ይኾንላችኋል ፤ የሚያነጻውን ፡ ውሃ ፡ የሚረጭ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ያጥባል ፤ የሚያነጻውንም ፡ ውሃ ፡ የሚነካ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ርኩሱም ፡ የሚነካው ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ፤ የሚነካውም ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ርኩስ ፡ ይኾናል ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሹሉ ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ወደጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፤ ሕዝቡም ፡ በቃዴስ ፡ ተቀመጡ ፤ ማርያምም ፡ በዚያ ፡ ሞተች ፡ በዚያም ፡ ተቀበረች ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ለማኅበሩም ፡ ውሃ ፡ አልነበረም ፤ በሙሴና ፡ በአሮንም ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ ሕዝቡም ፡ ሙሴን ፡ ተጣሉት ፡ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ፦ ወንድሞቻችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ እኛም ፡ ምነው ፡ በሞትን ፡ ኖሮ! ፡

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ እኛ ፡ ከብቶቻችንም ፡ በዚያ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጉባኤ ፡ ወደዚህ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ለምን ፡ አመጣችኹ ፧

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ወደዚህ ፡ ክፉ ፡ ስፍራ ፡ ታመጡን ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ለምን ፡ አወጣችኹን ፧ ዘርና ፡ በለስ ፡ ወይንም ፡ ሮማንም ፡ የሌለበት ፡ ስፍራ ፡ ነው ፤ የሚጠጣም ፡ ውሃ ፡ የለበትም ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ከጉባኤው ፡ ፊት ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ኼደው ፡ በግንባራቸው ፡ ወደቁ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ተገለጠላቸው ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ በትርኽን ፡ ውሰድ ፤ አንተና ፡ ወንድምኽ ፡ አሮን ፡ ማኅበሩን ፡ ሰብስቡ ፡ ድንጋዩም ፡ ውሃን ፡ እንዲሰጥ ፡ እነርሱ ፡ ሲያዩ ፡ ተናገሩት ፤ ከድንጋዩም ፡ ውሃ ፡ ታወጣላቸዋለኽ ፤ እንዲሁም ፡ ማኅበሩን ፡ ከብቶቻቸውንም ፡ ታጠጣላቸዋለኽ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ እንደ ፡ ታዘዘ ፡ በትሩን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወሰደ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ሙሴና ፡ አሮንም ፡ ጉባኤውን ፡ በድንጋዩ ፡ ፊት ፡ ሰብስበው ፦ እናንተ ፡ ዐመፀኞች ፡ እንግዲህ ፡ ስሙ ፤ በእውኑ ፡ ከዚህ ፡ ድንጋይ ፡ ውሃን ፡ እናወጣላችኋለን ፧ አላቸው ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ሙሴም ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ድንጋዩን ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ በበትሩ ፡ መታው ፤ ብዙም ፡ ውሃ ፡ ወጣ ፡ ማኅበሩም ፡ ከብቶቻቸውም ፡ ጠጡ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፦ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ትቀድሱኝ ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡

አላመናችኹምና ፡ ስለዚህ ፡ ወደሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ ይህን ፡ ጉባኤ ፡ ይዛችኹ ፡ አትገቡም ፡ አላቸው ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ጠብ ፡ ያደረጉበት ፥ ርሱም ፡ ቅዱስ ፡ መኾኑን ፡ የገለጠበት ፡ ይህ ፡ የመሪባ ፡ ውሃ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ሙሴም ፡ ከቃዴስ ፡ ወደኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተኞችን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ላከ ፦ ወንድምኽ ፡ እስራኤል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያገኘንን ፡ መከራ ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፤

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ አባቶቻችን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረዱ ፥ በግብጽም ፡ እጅግ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጥን ፡ ግብጻውያንም ፡ እኛንና ፡ አባቶቻችንን ፡ በደሉ ፤

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጮኽን ፡ ጊዜ ፡ ድምፃችንን ፡ ሰማ ፥ መልአኩንም ፡ ሰዶ ፡ ከግብጽ ፡ አወጣን ፤ እንሆም ፥ በምድርኽ ፡ ዳርቻ ፡ ባለችው ፡ ከተማ ፡ በቃዴስ ፡ ተቀምጠናል ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ እባክኽ ፥ በምድርኽ ፡ ላይ ፡ እንለፍ ፤ ወደ ፡ ዕርሻም ፡ ወደ ፡ ወይንም ፡ አንገባም ፥ ከጕድጓዶችም ፡ ውሃን ፡ አንጠጣም ፤ በንጉሡ ፡ ጐዳና ፡ እንኼዳለን ፥ ዳርቻኽንም ፡ እስክናልፍ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አንልም ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ ኤዶምያስም ፦ በሰይፍ ፡ እንዳልገጥምኽ ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ አታልፍም ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ። በጐዳናው ፡ እንኼዳለን ፥ እኔም ፡ ከብቶቼም ፡ ከውሃኽ ፡ ብንጠጣ ፡ ዋጋውን ፡ እንከፍላለን ፥ ሌላም ፡ ምንም ፡ አናደርግም ፤ ብቻ ፡ በእግራችን ፡ እንለፍ ፡ አሉት ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ አታልፍም ፡ አለ ። ኤዶምያስም ፡ በብዙ ፡ ሕዝብና ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ ሊገጥመው ፡ ወጣ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ኤዶምያስም ፡ እስራኤል ፡ በዳርቻው ፡ እንዳያልፍ ፡ ከለከለ ፤ ስለዚህ ፥ እስራኤል ፡ ከርሱ ፡ ተመለሰ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ከቃዴስም ፡ ተጓዙ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ወደሖር ፡ ተራራ ፡ መጡ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ባለው ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ አሮን ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይከማች ፤ በመሪባ ፡ ውሃ ፡ ዘንድ ፡ በቃሌ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ዐመፃችኹ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደሰጠኋት ፡ ምድር ፡ አይገባም ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ አሮንና ፡ ልጁን ፡ አልዓዛርን ፡ ይዘኽ ፡ ወደሖር ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አምጣቸው ፤

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ከአሮንም ፡ ልብሱን ፡ አውጣ ፥ ልጁንም ፡ አልዓዛርን ፡ አልብሰው ፤ አሮንም ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይከማች ፥ በዚያም ፡ ይሙት ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረገ ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ ወደሖር ፡ ተራራ ፡ ወጡ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ ሙሴም ፡ የአሮንን ፡ ልብስ ፡ አወጣ ፥ ልጁንም ፡ አልዓዛርን ፡ አለበሰው ፤ አሮንም ፡ በዚያ ፡ በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ሞተ ፤ ሙሴና ፡ አልዓዛርም ፡ ከተራራው ፡ ወረዱ ።

ዘኍ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ለአሮን ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ አለቀሱ ።

ኦሪት ፡ ዘኁልቁ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ ከነዓናዊው ፡ የዓራድ ፡ ንጉሥ ፡ በአታሪም ፡ መንገድ ፡ እስራኤል ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ሰማ ፤ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ አደረገ ፡ ከነርሱም ፡ ምርኮ ፡ ማረከ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ እስራኤልም ፡ ለእግዚአብሔር ፦ እነዚህን ፡ አሳልፈኽ ፡ በእጄ ፡ ብትሰጣቸው ፡ ከተማዎቻቸውን ፡ ዕርም ፡ ብዬ ፡ አጠፋለኹ ፡ ብሎ ፡ ስእለት ፡ ተሳለ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፥ ከነዓናውያንንም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ እነርሱንም ፡ ከተማዎቻቸውንም ፡ ዕርም ፡ ብለው ፡ አጠፉ ፤ የዚያንም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ሔርማ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ ከሖርም ፡ ተራራ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ ርቀው ፡ ሊዞሩ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡ ተጓዙ ፤ የሕዝቡም ፡ ሰውነት ፡ ከመንገዱ ፡ የተነሣ ፡ ደከመ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ ሕዝቡም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሙሴ ፡ ላይ ። በምድረ ፡ በዳ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ለምን ፡ አወጣችኹን ፧ እንጀራ ፡ የለም ፥ ውሃ ፡ የለም ፤ ሰውነታችንም ፡ ይህን ፡ ቀላል ፡ እንጀራ ፡ ተጸየፈ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ እባቦችን ፡ ሰደደ ፥ ሕዝቡንም ፡ ነደፉ ፤ ከእስራኤልም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 7 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ሙሴ ፡ መጥተው ፦ በእግዚአብሔርና ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተናገርን ፡ በድለናል ፤ እባቦችን ፡ ከእኛ ፡ ያርቅልን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይልን ፡ አሉት ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 8 ፤ ሙሴም ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ጸለየ ። እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ እባብን ፡ ሠርተኽ ፡ በዐላማ ፡ ላይ ፡ ስቀል ፤ የተነደፈውም ፡ ኹሉ ፡ ሲያያት ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ አለው ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 9 ፤ ሙሴም ፡ የናሱን ፡ እባብ ፡ ሠርቶ ፡ በዐላማ ፡ ላይ ፡ ሰቀለ ፤ እባብም ፡ የነደፈችው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የናሱን ፡ እባብ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዳነ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጓዙ ፥ በኦቦትም ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ ከኦቦትም ፡ ተጕዘው ፡ በሞዐብ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለችው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፥ በፀሓይ ፡ መውጫ ፡ በኩል ፥ በዒዬዓባሪም (92) ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ ከዚያም ፡ ተጕዘው ፡ በዘሬድ ፡ ሸለቆ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ ከዚያም ፡ ተጕዘው ፡ ከአሞራውያን ፡ ዳርቻ ፡ በሚወጣው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ በአሮኖን ፡ ማዶ ፡ ሰፈሩ ፤ አሮኖን ፡ በሞዐብና ፡ በአሞራውያን ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የሞዐብ ፡ ዳርቻ ፡ ነውና ።

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ የጦርነት ፡ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ተባለ ፦

ዋሄብ ፡ በሡፋ (93) ፥

የአርኖንም ፡ ሸለቆዎች ፥

ዘኁ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ ወደዔር ፡ ማደሪያ ፡ የሚወርድ ፡

---

92 ዕብ. ፥ የዕየይ ፡ ሀዐባሪም ፡ (ዕየየ ፡ ዕቡራን • የኺያጆች ፣ የመንገደኞች ፡ መባዘን) ።

93 ዕብ. ፥ ሡፋህ ፡ (ቀይ ፡ ባሕር) ።

በሞዐብም ፡ ዳርቻ ፡ የሚጠጋ ፡

የሸለቆዎች ፡ ፈሳሽ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ብኤር ፡ ተጓዙ ፤ ይኸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፦ ሕዝቡን ፡ ሰብስብ ፡ ውሃንም ፡ እሰጣቸዋለኹ ፡ ብሎ ፡ የተናገረለት ፡ ጕድጓድ ፡ ነው ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ይህን ፡ መዝሙር ፡ ዘመረ ፦

አንተ ፡ ምንጭ ፡ ሆይ ፥ ፍለቅ ፤ እናንተ ፡ ዘምሩለት ፤

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ በበትረ ፡ መንግሥት ፡ በበትራቸውም ፡

የሕዝብ ፡ ዐዛውንቶች ፡ ያጐደጐዱት ፥

አለቃዎችም ፡ የቈፈሩት ፡ ጕድጓድ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ ከምድረ ፡ በዳም ፡ ወደ ፡ መቴና ፡ ተጓዙ ፤ ከመቴናም ፡ ወደ ፡ ነሃሊኤል ፥ ከነሃሊኤልም ፡ ወደ ፡ ባሞት ፥

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ከባሞትም ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ከላይ ፡ ወደሚመለከተው ፡ ወደፈስጋ ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ በሞዐብ ፡ በረሓ ፡ ወዳለው ፡ ሸለቆ ፡ ተጓዙ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ 22 ፤ እስራኤልም ፦ በምድርኽ ፡ ላይ ፡ እንለፍ ፤ ወደዕርሻና ፡ ወደወይን ፡ ቦታ ፡ አንገባም ፤ ከጕድጓድም ፡ ውሃን ፡ አንጠጣም ፤ ከምድርኽ ፡ ዳርቻ ፡ እስክንወጣ ፡ ድረስ ፡ በንጉሥ ፡ ጐዳና ፡ እንኼዳለን ፡ ብለው ፡ ወደአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሴዎን ፡ መልእክተኞችን ፡ ላኩ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ሴዎንም ፡ እስራኤል ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ፤ ሴዎንም ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ እስራኤልንም ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ያህጽም ፡ መጣ ፥ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ እስራኤልም ፡ በሰይፍ ፡ መታው ፥ ምድሩንም ፡ ከአርኖን ፡ ዠምሮ ፡ እስከዐሞን ፡ ልጆች ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ድረስ ፡ ወረሰ ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ የጸና ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ እስራኤልም ፡ እነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፤ እስራኤልም ፡ በአሞራውያን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በሐሴቦንና ፡ በመንደሮቹ ፡ ኹሉ ፡ ተቀመጠ ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ሐሴቦንም ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ ከተማ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የፊተኛውን ፡ የሞዐብን ፡ ንጉሥ ፡ ወግቶ ፡ እስከ ፡ አርኖን ፡ ድረስ ፡ ምድሩን ፡ ኹሉ ፡ ከእጁ ፡ ወስዶ ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ በምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ ተነገረ ፦

ወደ ፡ ሐሴቦን ፡ ኑ ፤

የሴዎን ፡ ከተማ ፡ ይሠራ ፥ ይመሥረት ፤

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ እሳት ፡ ከሐሴቦን ፥ ነበልባልም ፡ ከሴዎን ፡ ከተማ ፡ ወጣ ፤

የሞዐብን ፡ ዔር ፥ የአርኖንን ፡ ተራራ ፡ አለቃዎች ፡ በላ ፤

ዘኁ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ ሞዐብ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኽ! ፡

የከሞስ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ጠፋኽ ፤

ወንዶች ፡ ልጆቹን ፡ ለሸሽት ፥ ሴቶች ፡ ልጆቹንም ፡ ለምርኮ ፥

ለአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዎን ፡ ሰጠ ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 30 ፤ ገተርናቸው ፤ ከሐሴቦን ፡ እስከ ፡ ዴቦን ፡ ድረስ ፡ ጠፉ ፤

ኖፋም ፡ እስኪደርሱ ፡ እስከ ፡ ሜድባ ፡ አፈረስናቸው ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 31 ፤ እስራኤልም ፡ እንደዚህ ፡ በአሞራውያን ፡ ምድር ፡ ተቀመጡ ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 32 ፤ ሙሴም ፡ ሰላዮችን ፡ ወደ ፡ ኢያዜር ፡ ሰደደ ፤ መንደሮቿንም ፡ ወሰዱ ፥ በዚያም ፡ የነበሩትን ፡ አሞራውያን ፡ አባረሩ ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 33 ፤ ተመልሰውም ፡ በበሳን ፡ መንገድ ፡ ወጡ ፤ የባሳንም ፡ ንጉሥ ፡ ዐግ ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በኤድራይ ፡ ይወጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 34 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ ርሱንና ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ምድሪቱንም ፡ አሳልፌ ፡ በእጅኽ ፡ ሰጥቻለኹና ፡ አትፍራው ፤ በሐሴቦንም ፡ በተቀመጠው ፡ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ እንዳደረግኽ ፡ እንዲሁ ፡ ታደርግበታለኽ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፥ 21 ፥ 35 ፤ ርሱንና ፡ ልጆቹን ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ መቱ ፡ ሰውም ፡ አልቀረለትም ፤ ምድሩንም ፡ ወረሱ ።

ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጓዙ ፥ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ባለው ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 2 ፤ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ እስራኤል ፡ በአሞራውያን ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ አየ ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 3 ፤ ብዙም ፡ ነበረና ፡ ሞዐብ ፡ ከሕዝቡ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ሞዐብ ፡ ደነገጠ ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 4 ፤ ሞዐብም ፡ የምድያምን ፡ ሽማግሌዎች ። በሬ ፡ የለመለመውን ፡ ሣር ፡ እንደሚጨርስ ፡ ይህ ፡ ጭፍራ ፡ በዙሪያችን ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይጨርሳል ፡ አላቸው ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 5-6 ፤ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ በፋቱራ ፡ ወደተቀመጠው ፡ ወደቢዖር ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ በለዓም ፦ እንሆ ፥ ከግብጽ ፡ የወጣ ፡ ሕዝብ ፡ አለ ፤ እንሆም ፥ የምድሩን ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ሸፈነ ፥ በአቅራቢያችንም ፡ ተቀምጧል ፤ አኹንም ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ከእኔ ፡ ይበልጣልና ፥ ልወጋቸውና ፡ ከምድሪቱ ፡ ላሳድዳቸው ፡ እችል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እባክኽ ፥ ና ፡ ርገምልኝ ፤ አንተ ፡ የመረቅኸው ፡ ምሩቅ ፡ የረገምኸውም ፡ ርጉም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ብሎ ፡ ይጠሩት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ላከ ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 7 ፤ የሞዐብ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የምድያም ፡ ሽማግሌዎችም ፡ የሟርቱን ፡ ዋጋ ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ኼዱ ፤ ወደ ፡ በለዓምም ፡ መጡ ፥ የባላቅንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

ዘኍ. ፥ 22 ፥ 8 ፤ ርሱም ፦ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በዚህ ፡ ዕደሩ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደሚነግረኝ ፡ እመልስላችኋለኹ ፡ አላቸው ፤ የሞዐብም ፡ አለቃዎች ፡ በበለዓም ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ መጥቶ ፦ እነዚህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧ አለው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ 11 ፤ በለዓምም ፡ እግዚአብሔርን ፦ የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፦ እንሆ ፥ ከግብጽ ፡ የወጣ ፡ ሕዝብ ፡ የምድርን ፡ ፊት ፡ ሸፈነ ፥ አኹንም ፡ ና ፡ ርሱንም ፡ ርገምልኝ ፤ ምናልባት ፡ እወጋው ፡ አሳድደውም ፡ ዘንድ ፡ እችል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ልኳል ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በለዓምን ፦ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አትኺድ ፤ የተባረከ ፡ ነውና ፥ ሕዝቡን ፡ አትረግምም ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ በለዓምም ፡ ሲነጋ ፡ ተነሥቶ ፡ የባላቅን ፡ አለቃዎች ፦ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልፈቀደምና ፡ ወደ ፡ ምድራችኹ ፡ ኺዱ ፡ አላቸው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ የሞዐብ ፡ አለቃዎች ፡ ተነሡ ፥ ወደ ፡ ባላቅም ፡ መጥተው ፦ በለዓም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደም ፡ አሉት ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ባላቅም ፡ ደግሞ ፡ ከፊተኞች ፡ የበዙና ፡ የከበሩ ፡ ሌላዎችን ፡ አለቃዎች ፡ ሰደደ ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ 17 ፤ ወደ ፡ በለዓምም ፡ መጥተው ፦ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ። ክብርኽን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ አደርገዋለኹና ፥ የተናገርኸውንም ፡ ኹሉ ፡ አደርግልኻለኹና ፡ እባክኽ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ አይከልክልኽ ፤ እባክኽ ፥ ና ፥ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ርገምልኝ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ በለዓምም ፡ መልሶ ፡ የባላቅን ፡ ባሪያዎች ። ባላቅ ፡ በቤቱ ፡ የሞላውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ቢሰጠኝ ፥ በትንሹ ፡ ወይም ፡ በትልቁ ፡ ቢኾን ፡ የአምላኬን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ የሚነግረኝን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፥ እባካችኹ ፥ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ዕደሩ ፡ አላቸው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ በሌሊት ፡ መጥቶ ፦ ሰዎቹ ፡ ይጠሩኽ ፡ ዘንድ ፡ መጥተው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ተነሣ ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ኺድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የምነግርኽን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ታደርጋለኽ ፡ አለው ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ በለዓምም ፡ ሲነጋ ፡ ተነሣ ፥ አህያዪቱንም ፡ ጭኖ ፡ ከሞዐብ ፡ አለቃዎች ፡ ጋራ ፡ ኼደ ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ርሱም ፡ ስለ ፡ ኼደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጣ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ሊቋቋመው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ቆመ ። ርሱም ፡ በአህያዪቱ ፡ ላይ ፥ ኹለቱም ፡ ሎሌዎቹ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ አህያዪቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ የተመዘዘም ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ አየች ፤ ከመንገዱም ፡ ፈቀቅ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ዕርሻው ፡ ውስጥ ፡ ገባች ፤ በለዓምም ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ይመልሳት ፡ ዘንድ ፡ አህያዪቱን ፡ መታት ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከወይኑ ፡ ቦታዎች ፡ መካከል ፡ በወዲያና ፡ በወዲህ ፡ ወገን ፡ ግንብ ፡ በነበረበት ፡ በጠባብ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ አህያዪቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ አይታ ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ተጠጋች ፥ የበለዓምንም ፡ እግር ፡ ከቅጥሩ ፡ ጋራ ፡ አጣበቀች ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ መታት ።

ዘኍ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ኼደ ፥ በቀኝና ፡ በግራ ፡ መተላለፊያ ፡ በሌለበት ፡ በጠባብ ፡ ስፍራ ፡ ቆመ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ አህያዩቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ አየች ፥ ከበለዓምም ፡ በታች ፡ ተኛች ፤ በለዓምም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ አህያዩቱንም ፡ በበትሩ ፡ ደበደባት ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የአህያዩቱን ፡ አፍ ፡ ከፈተ ፥ በለዓምንም ፦ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የመታኸኝ ፡ ምን ፡ አድርጌብኽ ፡ ነው ፧ አለችው ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ በለዓምም ፡ አህያዩቱን ፦ ስላላገጥሽብኝ ፡ ነው ፤ በእጄስ ፡ ሰይፍ ፡ ቢኖር ፡ አኹን ፡ በገደልኹሽ ፡ ነበር ፡ አላት ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ አህያዩቱም ፡ በለዓምን ፦ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የምትቀመጥብኝ ፡ አህያኽ ፡ አይደለኹምን ፧ በእውኑ ፡ እንዲህ ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ልማዴ ፡ ነበረን ፧ አለችው ። ርሱም ፦ እንዲህ ፡ አላደረግሽብኝም ፡ አላት ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የበለዓምን ፡ ዐይኖች ፡ ከፈተ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ የተመዘዘም ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ አየ ፤ ሰገደም ፥ በግንባሩም ፡ ወደቀ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 32 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፦ አህያኽን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ መታኽ ፧ እንሆ ፥ መንገድኽ ፡ በፊቴ ፡ ጠማማ ፡ ነውና ፥ እቋቋምኽ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቻለኹ ፤

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 33 ፤ አህያዩቱም ፡ አይታኝ ፡ ከፊቴ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ፈቀቅ ፡ አለች ፤ ከፊቴስ ፡ ፈቀቅ ፡ ባላለች ፡ በእውነት ፡ አኹን ፡ አንተን ፡ በገደልኹኽ ፥ ርሷንም ፡ ባዳንኋት ፡ ነበር ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 34 ፤ በለዓምም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ በድያለኹ ፤ አንተ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ቆምኽብኝ ፡ አላወቅኹም ፤ እንግዲህም ፡ አኹን ፡ አትወድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እመለሳለኹ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 35 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በለዓምን ፦ ከሰዎቹ ፡ ጋራ ፡ ኺድ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የምናገርኽን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ትናገራለኽ ፡ አለው ። በለዓምም ፡ ከባላቅ ፡ አለቃዎች ፡ ጋራ ፡ ኼደ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 36 ፤ ባላቅም ፡ በለዓም ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በአርኖን ፡ ዳር ፡ ዳርቻ ፡ በመጨረሻ ፡ ወዳለችው ፡ ወደሞዐብ ፡ ከተማ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 37 ፤ ባላቅም ፡ በለዓምን ፦ በእውኑ ፡ አንተን ፡ ለመጥራት ፡ አልላክኹብኽምን ፧ ለምንስ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልመጣኽም ፧ በእውኑ ፡ አንተን ፡ ለማክበር ፡ እኔ ፡ አልችልምን ፧ አለው ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 38 ፤ በለዓምም ፡ ባላቅን ፦ እንሆ ፥ ወዳንተ ፡ መጥቻለኹ ፤ በእውኑ ፡ አኹን ፡ አንዳችን ፡ ነገር ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እችላለኹን ፧ እግዚአብሔር ፡ በአፌ ፡ የሚያደርገውን ፡ ቃል ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 39 ፤ በለዓምም ፡ ከባላቅ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፥ ወደ ፡ ቂርያት ፡ ሐጾትም ፡ መጡ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 40 ፤ ባላቅም ፡ በሬዎችንና ፡ በጎችን ፡ ዐርዶ ፡ ወደ ፡ በለዓም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወዳሉት ፡ አለቃዎች ፡ ላከ ።

ዘኁ. ፡ 22 ፡ 41 ፤ በነጋውም ፡ ባላቅ ፡ በለዓምን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ በዓል ፡ ኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ አወጣው ፤ በዚያም ፡ ኾኖ ፡ የሕዝቡን ፡ ዳርቻ ፡ አየ ።

ኦሪት ፡ ዘኁልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ በለዓምም ፡ ባላቅን ፦ ሰባት ፡ መሠዊያ ፡ በዚህ ፡ ሥራልኝ ፥ ሰባትም ፡ ወይፈን ፡ ሰባትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ በዚህ ፡ አዘጋጅልኝ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ባላቅም ፡ በለዓም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አደረገ ፤ ባላቅና ፡ በለዓምም ፡ በየመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳረጉ ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ በለዓምም ፡ ባላቅን ፦ በመሥዋዕትኽ ፡ ዘንድ ፡ ቈይ ፥ እኔም ፡ እኼዳለኹ ፤ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊገናኘኝ ፡ ይመጣል ፤ ርሱም ፡ የሚገልጥልኝን ፡ እነግርኻለኹ ፡ አለው ። ወደ ፡ ጕብታም ፡ ኼደ ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከበለዓም ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ፤ ርሱም ፦ ሰባት ፡ መሠዊያዎች ፡ አዘጋጀኹ ፥ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳረግኹ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቃልን ፡ በበለዓም ፡ አፍ ፡ አድርጎ ፦ ወደ ፡ ባላቅ ፡ ተመለስ ፥ እንዲህም ፡ በል ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ተመለሰ ፥ እንሆም ፥ ርሱና ፡ የሞዐብ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ዘንድ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ገሖመር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ባላቅ ፡ ከአራም ፡ አመጣኝ ፥

የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ከምሥራቅ ፡ ተራራዎች ፤

ና ፥ ያዕቆብን ፡ ርገምልኝ ፤

ና ፥ እስራኤልን ፡ ተጣላልኝ ፡ ብሎ ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያልረገመውን ፡ እንዴት ፡ እረግማለኹ ፧

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ በዐምባዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ አየዋለኹ ፥

በኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ እመለከተዋለኹ ፤

እንሆ ፥ ብቻውን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፥

በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ አይቈጠርም ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ የያዕቆብን ፡ ትቢያ ፡ ማን ፡ ይቈጥራል ፧

የእስራኤልስ ፡ ርቦ ፡ ማን ፡ ይቈጥራል ፧

የጻድቃንን ፡ ሞት ፡ እኔ ፡ ልሙት ፥

ፍጻሜዬም ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ፍጻሜ ፡ ትኹን ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ባላቅም ፡ በለዓምን ፦ ያደረግኽብኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ጠላቶቼን ፡ ትረግምልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠራኹኽ ፤ እንሆም ፥ ፈጽመኽ ፡ ባረክኻቸው ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአፌ ፡ ያደረገውን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አልጠነቀቅምን ፧ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ባላቅም ፦ በዚያ ፡ ኾነኽ ፡ ታያቸው ፡ ዘንድ ፥ እባክኽ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ቦታ ፡ ና ፡ ዳርቻቸውንም ፡ ብቻ ፡ ታያለኽ ፥ ኹሉን ፡ ግን ፡ አታይም ፤ በዚያም ፡ ኾነኽ ፡ እነርሱን ፡ ርገምልኝ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ ወደጾፌምም ፡ ሜዳ ፡ ወደፈስጋ ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወሰደው ፤ ሰባትም ፡ መሠዊያዎች ፡ ሠራ ፥ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ አንድም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳረገ ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ባላቅንም ፦ እኔ ፡ ወደዚያ ፡ ለመገናኘት ፡ ስኼድ ፡ በዚህ ፡ በመሥዋዕትኽ ፡ ዘንድ ፡ ቈይ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በለዓምን ፡ ተገናኘ ፥ ቃልንም ፡ በአፉ ፡ አድርጎ ፦ ወደ ፡ ባላቅ ፡ ተመለስ ፥ እንዲህም ፡ በል ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ መጣ ፥ እንሆም ፥ ርሱ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የሞዐብ ፡ አለቃዎች ፡ በመሥዋዕቱ ፡ ዘንድ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ባላቅም ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ዠመር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ባላቅ ፡ ሆይ ፥ ተነሣ ፥ ስማ ፤

የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አድምጠኝ ፤

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ሐሰትን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አይደለም ፥

ይጸጸትም ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አይደለም ።

ርሱ ፡ ያለውን ፡ አያደርገውምን ፧

የተናገረውንስ ፡ አይፈጽመውምን ፧

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ እንሆ ፥ ለመባረክ ፡ ትእዛዝን ፡ ተቀብያለኹ ፤

ርሱ ፡ ባርኳል ፥ እመልሰውም ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ አልተመለከተም ፥

በእስራኤልም ፡ ጠማምነትን ፡ አላየም ፤

አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ፥

የንጉሥም ፡ እልልታ ፡ በመካከላቸው ፡ አለ ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቷቸዋል ፤

ጉልበቱ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ነው ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ አስማት ፡ የለም ፥

በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ሟርት ፡ የለም ፤

በጊዜው ፡ ስለ ፡ ያዕቆብና ፡ ስለ ፡ እስራኤል ።

እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ አደረገ! ፡ ይባላል ።

ዘኁ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ እንሆ ፥ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ እንስት ፡ አንበሳ ፡ ይቆማል ፥

እንደ ፡ አንበሳም ፡ ይነሣል ፤

ያደነውን ፡ እስኪበላ ፥

የገደለውንም ፡ ደሙን ፡ እስኪጠጣ ፡ አይተኛም ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 25 ፤ ባላቅም ፡ በለዓምን ፦ ከቶ ፡ አትርገማቸው ፥ ከቶም ፡ አትባርካቸው ፡ አለው ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 26 ፤ በለዓምም ፡ መልሶ ፡ ባላቅን ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለኹ ፡ ብዬ ፡ አልተናገርኹኽምን ፧ አለው ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 27 ፤ ባላቅም ፡ በለዓምን ፦ ና ፥ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ እወስድኻለኹ ፤ ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ኾነኽ ፡ እነርሱን ፡ ትረግምልኝ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወዳል ፡ አለው ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 28 ፤ ባላቅም ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ከላይ ፡ ወደሚመለከተው ፡ ወደ ፡ ፈጎር ፡ ላይ ፡ በለዓምን ፡ ወሰደው ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 29 ፤ በለዓምም ፡ ባላቅን ፦ በዚህ ፡ ሰባት ፡ መሠዊያዎች ፡ ሥራልኝ ፥ በዚህም ፡ ሰባት ፡ ወይፈን ፡ ሰባትም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አዘጋጅልኝ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፥ 23 ፥ 30 ፤ ባላቅም ፡ በለዓም ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፥ በየመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አሳረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኁልቁ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 1 ፤ በለዓምም ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ እንዲወድ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ አስቀድሞ ፡ ያደርግ ፡ የነበረውን ፡ አስማት ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ አልኼደም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፊቱን ፡ አቀና ።

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 2 ፤ በለዓምም ፡ ዐይኑን ፡ አንሥቶ ፡ እስራኤል ፡ በየነገዱ ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በላዩ ፡ መጣ ።

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 3 ፤ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ገጦር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

የቢዖር ፡ ልጅ ፡ በለዓም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፥

ዐይኖቹ ፡ የተከፈቱለት ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 4 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ፥

ሹሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክን ፡ ራእይ ፡ የሚያይ ፥

የወደቀው ፥ ዐይኖቹም ፡ የተከፈቱለት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 5 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ ድንኳኖችኽ ፥

እስራኤል ፡ ሆይ ፡ ማደሪያዎችኽ ፡ ምንኛ ፡ ያምራሉ! ፡

ዘኁ. ፥ 24 ፥ 6 ፤ እንደ ፡ ሸለቆዎች ፥

በወንዝ ፡ ዳር ፡ እንዳሉ ፡ አትክልቶች ፥

እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተከለው ፡ ሬት ፡

በውሃም ፡ ዳር ፡ እንዳሉ ፡ ዝግባዎች ፡ ተዘርግተዋል ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ከማድጋዎቹ ፡ ውሃ ፡ ይፈሳል ፥

ዘሩም ፡ በብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ይኾናል ፥

ንጉሡም ፡ ከአጋግ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ መንግሥቱም ፡ ይከበራል ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቶታል ፤

ጕልበቱ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ነው ፤

ጠላቶቹን ፡ አሕዛብን ፡ ይበላል ፥

ዐጥንቶቻቸውንም ፡ ይሰባብራል ፥

በፍላጻዎቹም ፡ ይወጋቸዋል ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ዐርፎ ፡ ተኝቷል ፥

እንደ ፡ እንስቲቱም ፡ አንበሳ ፡ ተጋድሟል ፤

ማን ፡ ያስነሣዋል ፧

የሚመርቅኽ ፡ ኹሉ ፡ የተመረቀ ፡ ይኹን ፥

የሚረግምኽም ፡ ኹሉ ፡ የተረገመ ፡ ይኹን ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ የባላቅም ፡ ቍጣ ፡ በበለዓም ፡ ላይ ፡ ነደደ ፤ እጆቹንም ፡ አጨበጨበ ፤ ባላቅም ፡ በለዓምን ፦ ጠላቶቼን ፡ ትረግም ፡ ዘንድ ፡ ጠራኹኽ ፥ እንሆም ፥ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመኽ ፡ መረቅኻቸው ፤ አኹንም ፡ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ስፍራኽ ፡ ሽሽ ፤

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ እኔ ፡ አከብርኽ ፡ ዘንድ ፡ ወድጄ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ ክብርኽን ፡ ከለከለ ፡ አለው ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ 13 ፤ በለዓምም ፡ ባላቅን ፡ አለው ፦ ባላቅ ፡ በቤቱ ፡ የሞላውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ቢሰጠኝ ፥ መልካሙን ፡ ወይም ፡ ክፉውን ፡ ከልቤ ፡ ለማድረግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እተላለፍ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለላክኻቸው ፡ መልእክተኞች ፡ አልተናገርኋቸውምን ፧

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ወደ ፡ ሕዝቤ ፡ እኼዳለኹ ፤ ና ፥ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ የሚያደርገውን ፡ እነግርኻለኹ ።

ዘኁ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ዝምር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

የቢዖር ፡ ልጅ ፡ በለዓም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፥

ዐይኖቹም ፡ የተከፈቱለት ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ፥

የልዑልንም ፡ ዕውቀት ፡ የሚያውቅ ፥

ኹሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክን ፡ ራእይ ፡ የሚያይ ፥

የወደቀው ፥ ዐይኖቹም ፡ የተከፈቱለት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ አየዋለኹ ፥ አኹን ፡ ግን ፡ አይደለም ፤

እመለከተዋለኹ ፥ በቅርብ ፡ ግን ፡ አይደለም ፤

ከያዕቆብ ፡ ኮከብ ፡ ይወጣል ፥

ከእስራኤል ፡ በትር ፡ ይነሣል ፥

የሞዐብንም ፡ ማእዘኖች ፡ ይመታል ፥

የሠェትንም ፡ ልጆች ፡ ያጠፋል ።

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ ኤዶምያስም ፡ ርስቱ ፡ ይኾናል ፥

ጠላቱ ፡ ሴይር ፡ ደግሞ ፡ ርስቱ ፡ ይኾናል ፤

እስራኤልም ፡ በኀይል ፡ ያደርጋል ።

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ከያዕቆብም ፡ የሚወጣ ፡ ገዢ ፡ ይኾናል ፥

ከከተማውም ፡ የቀሩትን ፡ ያጠፋል ።

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ዐማሌቅንም ፡ አይቶ ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ገሖመር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ዐማሌቅ ፡ የአሕዛብ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤

ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ።

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ ቄናውያንንም ፡ አይቶ ፡ ምሳሌውን ፡ ይምስል ፡ ገሖመር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ማደሪያኽ ፡ የጸና ፡ ነው ፥

ጐጕኽም ፡ በዐምባ ፡ ላይ ፡ ተሠርቷል ፤

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አሶር ፡ እስኪማርክኽ ፡ ድረስ ፡ ቄናዊው ፡ ለጥፋት ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ ምሳሌውንም ፡ ይመስል ፡ ገሖመር ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሲያደርግ ፡

አወይ! ፡ ማን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፧

ዘኍ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ከኪቲም ፡ ዳርቻ ፡ መርከቦች ፡ ይመጣሉ ፥

አሶርንም ፡ ያስጨንቃሉ ፥

ዔቦርንም ፡ ያስጨንቃሉ ፤

ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ።

ዘኍ. ፥ 24 ፥ 25 ፤ በለዓምም ፡ ተነሣ ፥ ተመልሶም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ኼደ ፤ ባላቅም ፡ ደግሞ ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። _____

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 1 ፤ እስራኤልም ፡ በሰጢም ፡ ተቀመጡ ፤ ሕዝቡም ፡ ከሞዐብ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ያመነዝሩ ፡ ዠመር ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 2 ፤ ሕዝቡንም ፡ ወደ ፡ አምላኮቻቸው ፡ መሥዋዕት ፡ ጠሩ ፤ ሕዝቡም ፡ በሉ ፥ ወደ ፡ አምላኮቻቸውም ፡ ሰገዱ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 3 ፤ እስራኤልም ፡ ብዔልፌጎርን ፡ ተከተለ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የእግዚአብሔር ፡ የቍጣው ፡ ጽናት ፡ ከእስራኤል ፡ እንዲመለስ ፡ የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ወስደኽ ፡ በፀሓዩ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስቀላቸው ፡ አለው ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 5 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ዳኞች ፦ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ብዔልፌጎርን ፡ የተከተሉትን ፡ ሰዎቻችኹን ፡ ግደሉ ፡ አላቸው ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 6 ፤ እንሆም ፥ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፡ በሙሴና ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ምድያማዊቱን ፡ አንዲቱን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ወንድሞቹ ፡ አመጣት ፤ እነርሱም ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 7 ፤ የካህኑም ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ከማኅበሩ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ በእጁ ፡ ጦር ፡ አነሣ ፤

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 8 ፤ ያንም ፡ የእስራኤልን ፡ ሰው ፡ ተከትሎ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ገባ ። እስራኤላዊውንም ፡ ሰውና ፡ ሴቲቱን ፡ ኹለቱን ፡ ሆዳቸውን ፡ ወጋቸው ። ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መቅሠፍቱ ፡ ተከለከለ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 9 ፤ በመቅሠፍትም ፡ የሞተው ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 11 ፤ የካህኑ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ በቅንአቴ ፡ በመካከላቸው ፡ ቀንቷልና ፥ ቍጣዬን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መለሰ ፤ እኔም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በቅንአቴ ፡ አላጠፋኹም ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 12 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የሰላሜን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እሰጠዋለኹ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 13 ፤ ለአምላኩም ፡ ቀንቷልና ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አስተስርዮአልና ፥ ለርሱ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ ክህነት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይኾንለታል ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 14 ፤ ከምድያማዊቱም ፡ ጋራ ፡ የተገደለው ፡ የእስራኤላዊው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ዘንበሪ ([94]) ፡ ነበረ ፤ የአባቱ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የስምዖናውያን ፡ የኾነ ፡ የሰሉ ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 25 ፥ 15 ፤ የተገደለችውም ፡ ምድያማዊት ፡ ስሟ ፡ ከስቢ ፡ ነበረ ፤ ርሷም ፡ የሱር ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፤ ርሱም ፡

---

94 ዘምሪ ፡፡

በምድያም ፡ ዘንድ ፡ የአባቱ ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 25 ፡ 17-18 ፤ በፈጎር ፡ በመቅሠፍቱ ፡ ቀን ፡ ስለተገደለችው ፡ ስለምድያም ፡ አለቃ ፡ ልጅ ፥ ስለ ፡ እኅታቸው ፡ ስለ ፡ ከስቢ ፥ በፈጎር ፡ ምክንያት ፡ በሸነገሏችኹ ፡ ሽንገላ ፡ አስጨንቀዋችኋልና ፥ ምድያማውያንን ፡ አስጨንቋቸው ፥ ግደሏቸውም ።

_____አሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ መቅሠፍቱ ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴንና ፡ የካህኑን ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ አልዓዛርን ፦

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፥ በእስራኤል ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጣውን ፡ ኹሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ቍጠሩ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ የወጡትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዳዘዛቸው ፥ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ሕዝቡን ፡ ቍጠሩ ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ የእስራኤል ፡ በኵር ፡ ሮቤል ፤ የሮቤል ፡ ልጆች ፤ ከሄኖኅ ፡ የሄኖኅውያን ፡ ወገን ፥ ከፈሉስ ፡ የፈሉሳውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ከአስሮን ፡ የአስሮናውያን ፡ ወገን ፥ ከከርሚ ፡ የከርማውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ እነዚህ ፡ የሮቤላውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ የፈሉስም ፡ ልጆች ፤ ኤልያብ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ የኤልያብም ፡ ልጆች ፤ ነሙኤል ፥ ዳታን ፥ አቤሮን ፤ እነዚህ ፡ ዳታንና ፡ አቤሮን ፡ ከማኅበሩ ፡ የተመረጡ ፡ ነበሩ ፤ ከቆሬ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ባመፁ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ተጣሉ ፤

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ያም ፡ ወገን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱ ፡ አፏን ፡ ከፍታ ፡ ከቆሬ ፡ ጋራ ፡ ዋጠቻቸው ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ እሳቱቱ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳውን ፡ ሰዎች ፡ አቃጠለቻቸው ፤ እነርሱም ፡ ለምልክት ፡ ኾኑ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ አልሞቱም ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከነሙኤል ፡ የነሙኤላውያን ፡ ወገን ፥ ከያሚን ፡ የያሚናውያን ፡ ወገን ፥ ከያኪን ፡ የያኪናውያን ፡ ወገን ፥ ከዛራ ፡ የዛራውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ከሳኡል ፡ የሳኡላውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ እነዚህ ፡ የስምዖናውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ የጋድ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከጽፎን ፡ የጽፎናውያን ፡ ወገን ፥ ከሐጊ ፡ የሐጋውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ ከሹኒ ፡ የሹናውያን ፡ ወገን ፥ ከኤስናን ፡ የኤስናናውያን ፡ ወገን ፥ ከዔሪ ፡ የዔራውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ከአሮድ ፡ የአሮዳውያን ፡ ወገን ፥ ከአርኤሊ ፡ የአርኤላውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ እነዚህ ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዔርና ፡ አውናን ፤ ዔርና ፡ አውናንም ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ሞቱ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከሴሎም ፡ የሴሎማውያን ፡ ወገን ፥ ከፋሬስ ፡ የፋሬሳውያን ፡ ወገን ፥ ከዛራ ፡ የዛራውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ የፋሬስም ፡ ልጆች ፤ ከኤስሮም ፡ የኤስሮማውያን ፡ ወገን ፥ ከሐሙል ፡ የሐሙላውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ እነዚህ ፡ የይሁዳ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 23 ፤ የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከቶላ ፡ የቶላውያን ፡ ወገን ፥ ከፉዋ ፡ የፉዋውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ ከያሱብ ፡ የያሱባውያን ፡ ወገን ፥ ከሺምሮን ፡ የሺምሮናውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ እነዚህ ፡ የይሳኮር ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድሳ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ የዛብሎን ፡ ወገኖች ፡ በየወገናቸው ፤ ከሴሬድ ፡ የሴሬዳውያን ፡ ወገን ፥ ከኤሎን ፡ የኤሎናውያን ፡ ወገን ፥ ከያሕልኤል ፡ የያሕልኤላውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ እነዚህ ፡ የዛብሎናውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ስድሳ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 29 ፤ የምናሴ ፡ ልጆች ፤ ከማኪር ፡ የማኪራውያን ፡ ወገን ፤ ማኪርም ፡ ገለዓድን ፡ ወለደ ፤ ከገለዓድ ፡ የገልዓዳውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ የገለዓድ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከኢዔዝር ፡ የኢዔዝራውያን ፡ ወገን ፥ ከኬሌግ ፡ የኬሌጋውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ ከአሥሪኤል ፡ የአሥሪኤላውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ ከሴኬም ፡ የሴኬማውያን ፡ ወገን ፥ ከሸሚዳ ፡ የሸሚዳውያን ፡ ወገን ፥ ከኦፌር ፡ የኦፌራውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 33 ፤ የኦፌርም ፡ ልጅ ፡ ሰለጰዓድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፤ የሰለጰዓድም ፡ የሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ስም ፡ ማህለህ ፥ ኑዓ ፥ ዔግላ ፥ ሚልካ ፥ ቲርጻ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 34 ፤ እነዚህ ፡ የምናሴ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 35 ፤ በየወገናቸው ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከሱቱላ ፡ የሱቱላውያን ፡ ወገን ፥ ከቤኬር ፡ የቤኬራውያን ፡ ወገን ፥ ከታሐን ፡ የታሐናውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 36 ፤ እነዚህ ፡ የሱቱላ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤ ከዔዴን ፡ የዔዴናውያን ፡ ወገን ። ከዔዴን ፡ የዔዴናውያና ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 37 ፤ እነዚህ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። በየወገናቸው ፡ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 38 ፤ የብንያም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከቤላ ፡ የቤላውያን ፡ ወገን ፥ ከአስቤል ፡ የአስቤላውያን ፡ ወገን ፥ ከአኪራን ፡ የአኪራናውያን ፡ ወገን ፥ ከሶፋን ፡ የሶፋናውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 39 ፤ ከሑፋም ፡ የሑፋማውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 40 ፤ የቤላም ([95]) ፡ ልጆች ፤ አርድና ፡ ናዕማን ፤ ከአርድ ፡ የአርዳውያን ፡ ወገን ፥ ከናዕማን ፡ የናዕማናውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 41 ፤ በየወገናቸው ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 42 ፤ በየወገናቸው ፡ የዳን ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከሰምዔ ([96]) ፡ የሰምዔያውያን ፡ ወገን ፤ በየወገናቸው ፡ የዳን ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 43 ፤ የሰምዔያውያን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ከነርሱ ፡ እንደ ፡ ተቈጠሩ ፡ ስድሳ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 44 ፤ የአሴር ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከዩምና ፡ የዩምናውያን ፡ ወገን ፥ ከየሱዋ ፡ የየሱዋውያን ፡ ወገን ፥ ከበሪዐ ፡ የበሪዓውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 45 ፤ ከበሪዐ ፡ ልጆች ፤ ከሔቤር ፡ የሔቤራውያን ፡ ወገን ፥ ከመልኪኤል ፡ የመልኪኤላውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 46 ፤ የአሴርም ፡ የሴት ፡ ልጁ ፡ ስም ፡ ሜራሕ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 47 ፤ እነዚህ ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 48 ፤ የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፤ ከያሕጽኤል ፡ የያሕጽኤላውያን ፡ ወገን ፥ ከጉኒ ፡ የጉናውያን ፡ ወገን ፥

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 49 ፤ ከዬጽር ፡ የዬጽራውያን ፡ ወገን ፥ ከሺሌም ፡ የሺሌማውያን ፡ ወገን ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 50 ፤ በየወገናቸው ፡ የንፍታሌም ፡ ወገኖች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ የተቈጠሩት ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 51 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተቈጠሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 52 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 26 ፡ 53 ፤ ለእነዚህ ፡ በየስማቸው ፡ ቍጥር ፡ ምድሪቱ ፡ ርስት ፡ ኾና ፡ ትከፈላለች ።

---

95 ዕብ. ፥ ቤላዕ ።

96 ዕብ. ፥ ሹሐም ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 54 ፤ ለብዙዎቹ ፡ እንደ ፡ ብዛታቸው ፥ ለጥቂቶቹም ፡ እንደ ፡ ጥቂትነታቸው ፡ መጠን ፡ ርስትን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ። ለዥሉ ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ ርስታቸው ፡ ይሰጣቸዋል ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 55 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምድሪቱ ፡ በዕጣ ፡ ትከፈላለች ፤ እንደአባቶቻቸው ፡ ነገድ ፡ ስም ፡ ይወርሳሉ ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 56 ፤ በብዙዎችና ፡ በጥቂቶች ፡ መካከል ፡ ርስታቸው ፡ በዕጣ ፡ ትከፈላለች ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 57 ፤ ከሌዋውያንም ፡ በየወገናቸው ፡ የተቈጠሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከጌድሶን ፡ የጌድሶናውያን ፡ ወገን ፥ ከቀአት ፡ የቀአታውያን ፡ ወገን ፥ ከሜራሪ ፡ የሜራራውያን ፡ ወገን ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 58 ፤ እነዚህ ፡ የሌዊ ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ፤ የሊብናውያን ፡ ወገን ፥ የኬብሮናውያን ፡ ወገን ፥ የሞሖላውያን ፡ ወገን ፥ የሙሳውያን ፡ ወገን ፥ የቆሬያውያን ፡ ወገን ። ቀአትም ፡ ዕምበረምን ፡ ወለደ ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 59 ፤ የዕምበረም ፡ ሚስት ፡ ስም ፡ ዮካብድ ፡ ነበረ ። ርሷ ፡ በግብጽ ፡ ከሌዊ ፡ የተወለደች ፡ የሌዊ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ፤ ለዕምበረምም ፡ አሮንንና ፡ ሙሴን ፡ እኅታቸውንም ፡ ማርያምን ፡ ወለደችለት ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 60 ፤ ለአሮንም ፡ ናዳብ ፥ አብዩድ ፥ አልዓዛር ፥ ኢታምር ፡ ተወለዱለት ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 61 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሌላ ፡ እሳት ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ ሞቱ ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 62 ፤ ካንድ ፡ ወርም ፡ ዝምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉ ፡ ወንዶች ፡ ዥሉ ፡ ከነርሱ ፡ የተቈጠሩ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ። ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አልተሰጣቸውምና ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አልተቈጠሩም ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 63 ፤ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሲቈጥሩ ፥ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፡ የቈጠሯቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 64 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አሮን ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በቈጠሯቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነበሩት ፡ ከነዚያ ፡ መካከል ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

ዘኁ. ፡ 26 ፡ 65 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፦ በእውነት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይሞታሉ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯልና ። ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብ ፡ ከነዌም ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ በቀር ፡ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አልቀረም ።

_____ኦሪት ፡ ዘኁልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። _____

ዘኁ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ከዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ከምናሴ ፡ ወገኖች ፥ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጅ ፡ የኦፌር ፡ ልጅ ፡ የሰለጰዓድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ቀረቡ ፤ የእነዚህም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ማህለህ ፥ ኑዓ ፥ ዔግላ ፥ ሚልካ ፥ ቲርጻ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በሙሴና ፡ በካህኑ ፡ በአልዓዛር ፡ በአለቃዎቹም ፡ በማኅበሩም ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ ቆመው ።

ዘኁ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ አባታችን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞተ ፤ በራሱ ፡ ኀጢአት ፡ ሞተ ፡ እንጂ ፡ ከቆሬ ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ አልነበረም ፤ ወንዶችም ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ።

ዘኁ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ወንድ ፡ ልጅስ ፡ ባይኖረው ፡ የአባታችን ፡ ስም ፡ ከወገኑ ፡ መካከል ፡ ለምን ፡ ይጠፋል ፧ በአባታችን ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡ ስጠን ፡ አሉ ።

ዘኁ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ሙሴም ፡ ነገራቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረበ ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ የሰለጰዓድ ፡ ልጆች ፡ እውነት ፡ ተናግረዋል ፤ በአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ የርስት ፡ ድርሻ ፡ ስጣቸው ፤ የአባታቸውን ፡ ርስት ፡ ለእነርሱ ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጥ ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ሰው ፡ ቢሞት ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ባይኖረው ፥ ርስቱ ፡ ለሴት ፡ ልጁ ፡ ይለፍ ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ሴት ፡ ልጅም ፡ ባትኖረው ፡ ርስቱን ፡ ለወንድሞቹ ፡ ስጡ ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ወንድሞችም ፡ ባይኖሩት ፡ ርስቱን ፡ ለአባቱ ፡ ወንድሞች ፡ ስጡ ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ የአባቱም ፡ ወንድሞች ፡ ባይኖሩት ፡ ከወገኑ ፡ ለቀረበ ፡ ዘመድ ፡ ርስቱን ፡ ስጡ ፡ ርሱም ፡ ይውረሰው ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ ወደዚህ ፡ ወደዓባሪም ፡ ተራራ ፡ ውጣ ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የሰጠኋትን ፡ ምድር ፡ እይ ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ ባየኻትም ፡ ጊዜ ፡ ወንድምኽ ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ተከማቸ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ወገንኽ ፡ ትከማቻለኽ ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በማኅበሩ ፡ ጠብ ፡ በቃሌ ፡ ላይ ፡ ዐምፃችኋልና ፥ በእነርሱም ፡ ፊት ፡ በውሃው ፡ ዘንድ ፡ አልቀደሳችኹኝምና ። ይህም ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በቃዴስ ፡ ያለው ፡ የመሪባ ፡ ውሃ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ እረኛ ፡ እንደሌለው ፡ መንጋ ፡ እንዳይኾን ፥ በፊታቸው ፡ የሚወጣውን ፡ በፊታቸውም ፡ የሚገባውን ፡ የሚያስወጣቸውንም ፡ የሚያስገባቸውንም ፡ ሰው ፡ የሥጋ ፡ ዥሉ ፡ መንፈስ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማኅበሩ ፡ ላይ ፡ ይሹመው ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ መንፈስ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ የነዌን ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ወስደኽ ፡ እጅኽን ፡ በላዩ ፡ ጫንበት ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ በካህኑ ፡ በአልዓዛርና ፡ በማኅበሩ ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ አቁመው ፥ እነርሱም ፡ እያዩ ፡ እዘዘው ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ዥሉ ፡ እንዲታዘዙት ፡ ከክብርኽ ፡ አኑርበት ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ በካህኑም ፡ በአልዓዛር ፡ ፊት ፡ ይቁም ፤ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በኡሪም ፡ ፍርድ ፡ ይጠይቅለት ፤ ርሱ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ዥሉ ፡ በቃሉ ፡ ይውጡ ፥ በቃሉም ፡ ይግቡ ።

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ሙሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ኢያሱንም ፡ ወስዶ ፡ በካህኑ ፡ በአልዓዛርና ፡ በማኅበሩ ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ አቆመው ፤

ዘኍ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ እጁን ፡ በላዩ ፡ ጫነበት ፥ አዘዘውም ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። _____

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ መብሌን ፥ ለእኔ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡

እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ የተደረገውን ፡ ቍርባኔን ፥ መባዬን ፡ በየጊዜው ፡ ታቀርቡልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ በእሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምታቀርቡት ፡ ቍርባን ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ለዘወትር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ኹለት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ አንዱን ፡ ጠቦት ፡ በማለዳ ፥ ሌላውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ አቅርብ ፤

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ ለእኽልም ፡ ቍርባን ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ በኾነ ፡ ተወቅጦ ፡ በተጠለለ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ታቀርባለኽ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ በእሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የቀረበ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ የተሠራ ፡ ለዘወትር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ላንድ ፡ ጠቦት ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ አራተኛው ፡ እጅ ፡ ነው ፤ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ መጠጥ ፡ ታፈሳለኽ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ ሌላውንም ፡ ጠቦት ፡ በማታ ፡ ጊዜ ፡ ታቀርባለኽ ፤ የእኽሉን ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡን ፡ ቍርባን ፡ በማለዳ ፡ እንዳቀረብኽ ፡ በእሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ ታቀርበዋለኽ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ኹለት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥ ለእኽልም ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላ ፥ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፥ በየሰንበቱ ፡ ኹሉ ፡ የምታቀርቡት ፡ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ በወሩም ፡ መባቻ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ኹለት ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ነውርም ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ለያንዳንዱም ፡ ወይፈን ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለአውራው ፡ በግም ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ለያንዳንዱም ፡ ጠቦት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውም ፡ ላንድ ፡ ወይፈን ፡ የኢን ፡ ግማሽ ፥ ለአውራው ፡ በግም ፡ የኢን ፡ ሢሶ ፥ ለአንዱም ፡ ጠቦት ፡ የኢን ፡ አራተኛ ፡ እጅ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይኾናል ፤ ይህ ፡ ለዓመቱ ፡ የወር ፡ መባቻ ፡ ኹሉ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ታቀርባላችኹ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ይቀርባል ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ከዚህም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ይኾናል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኾናል ፤ በርሱም ፡ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ በእሳትም ፡ የተደረገውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፤ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ላንድ ፡ ወይፈን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራውም ፡ በግ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፥

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ ለሰባቱም ፡ ጠቦቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ማስተስረያ ፡ የሚኾንላችኹን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ ማልዶ ፡ ከሚቀርበው ፡ በዘወትር ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ሌላ ፡ እነዚህን ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ የሚደረገውን ፡ የቍርባኑን ፡ መብል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በየዕለቱ ፡ እንዲሁ ፡ ታቀርባላችኹ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ይቀርባል ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ ደግሞ ፡ በበኩራት ፡ ቀን ፡ ከሰባቱ ፡ ሰብዔ ፡ በዓላችኹ ፡ ዐዲሱን ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባቀረባችኹ ፡ ጊዜ ፥ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኾንላችኋል ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ ለእኽል ፡ ቍርባናቸው ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለያንዳንዱ ፡ ወይፈን ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአንዱም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፥

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 29 ፤ ለሰባቱም ፡ ጠቦቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጠቦት ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 30 ፤ ማስተስረያ ፡ የሚኾንላችኹን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 28 ፡ 31 ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ እነርሱንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ነውርም ፡ የሌለባቸው ፡ ይኹኑ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ። _____

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከወሩ ፡ በመዠመሪያ ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትሥሩበት ፤ መለከቶች ፡ የሚነፉበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ ለእኽል ፡ ቍርባናቸው ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለወይፈኑ ፡ ከመስፈሪያው ፡

ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራው ፡ በግ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 4 ፤ ለሰባቱ ፡ ጠቦቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 5 ፤ ማስተስረያም ፡ የሚኾንላችኹን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 6 ፤ በወሩ ፡ መባቻ ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፥ በዘወትርም ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፥ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፥ እንደ ፡ ሕጋቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 7 ፤ ከዚህም ፡ ከሰባተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ ሰውነታችኹን ፡ አስጨንቁት ፤ ከሥራ ፡ ዅሉ ፡ ምንም ፡ አታድርጉ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 8 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ታቀርባላችኹ ፤ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ይኹኑ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 9 ፤ ለእኽል ፡ ቍርባናቸውም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለወይፈኑ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለአውራው ፡ በግ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 10 ፤ ለሰባቱ ፡ ጠቦቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 11 ፤ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ አቅርቡ ። ከሚያስተሰርየው ፡ ከኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፥ በዘወትርም ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፥ ከመጠጥ ፡ ቍርባናቸውም ፡ ሌላ ፡ አቅርቡት ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 12 ፤ ከሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ አትሥሩበት ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ አድርጉ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 13 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ አቅርቡ ፤ ነውር ፡ የሌለባቸውም ፡ ይኹኑ ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 14 ፤ ለእኽል ፡ ቍርባናቸውም ፡ በዘይት ፡ የተለወሰ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፥ ለዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ወይፈኖች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ሦስት ፡ እጅ ፥ ለኹለቱ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ከዐሥር ፡ እጅ ፡ ኹለት ፡ እጅ ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 15 ፤ ለዐሥራ ፡ አራቱ ፡ ጠቦቶች ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከመስፈሪያው ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 16 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ታቀርባላችኹ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 17 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወይፈኖችን ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎችን ፥ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶችን ፥

ዘኁ. ፥ 29 ፥ 18 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየልን ፡ ታቀርባላችኹ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባናቸው ፡ ሌላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐሥር ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸውም ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 26 ፤ በዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ዘጠኝ ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 27 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 28 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 29 ፤ በስድስተኛውም ፡ ቀን ፡ ስምንት ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 30 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 31 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 32 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖች ፥ ኹለት ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 33 ፤ ለወይፈኖቹና ፡ ለአውራ ፡ በጎቹ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባናቸውንና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፥

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 34 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፥ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 35 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ይኹንላችኹ ፤ የተግባርን ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡

አትሥሩበት ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 36 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እንዲኾን ፡ በእሳት ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ አንድ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ ተባት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ታቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 37 ፤ የእኽል ፡ ቍርባናቸውና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸው ፡ ለወይፈኑ ፡ ለአውራውም ፡ በግ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ይኾናሉ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 38 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ታቀርባላችኹ ፤ በዘወትር ፡ ከሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ከእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ከመጠጡም ፡ ቍርባን ፡ ሌላ ፡ የሚቀርቡ ፡ ናቸው ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 39 ፤ እነዚህንም ፥ ከስእለታችኹና ፡ በፈቃዳችኹ ፡ ከምታመጡት ፡ ሌላ ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፥ ለእኽልም ፡ ለመጠጥም ፡ ቍርባን ፥ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕታችኹ ፡ በበዓላችኹ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ።

ዘኍ. ፡ 29 ፡ 40 ፤ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ነገራቸው ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ። _____

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ አለቃዎች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ ሰው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ ቢሳል ፥ ወይም ፡ ራሱ ፡ በመሐላ ፡ ቢያስር ፥ ቃሉን ፡ አይስበር ፤ ከአፉ ፡ እንደ ፡ ወጣው ፡ ኹሉ ፡ ያድርግ ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ ሴትም ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ ብትሳል ፥ ርሷም ፡ በአባቷ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡ በብላቴንነቷ ፡ ጊዜ ፡ ራሷን ፡ በመሐላ ፡ ብታስር ፥

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ አባቷም ፡ ራሷን ፡ ያሰረችበትን ፡ መሐላ ፡ ስእለቷንም ፡ ቢሰማ ፥ አባቷም ፡ ዝም ፡ ቢላት ፥ ስእለቷ ፡ ኹሉ ፡ ይጸናል ፥ ራሷንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡ ኹሉ ፡ ይጸናል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ አባቷ ፡ ግን ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ቢከለክላት ፥ ስእለቷ ፡ ራሷንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላዋ ፡ አይጸኑም ፤ አባቷ ፡ ከልክሏታልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይላታል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ በተሳለችም ፡ ጊዜ ፡ ራሷንም ፡ በመሐላ ፡ ያሰረችበት ፡ ነገር ፡ ከአፏ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ባል ፡ ያገባች ፡ ብትኾን ፥

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ ባሏም ፡ ቢሰማ ፥ በሰማበትም ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ቢላት ፥ ስእለቷ ፡ ይጸናል ፥ ራሷንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡ ይጸናል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ ባሏ ፡ ግን ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ቢከለክላት ፥ በርሷ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ስእለቷን ፡ ራሷንም ፡ በመሐላ ፡ ያሰረችበትን ፡ የአፏን ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይቅር ፡ ይላታል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ ባሏ ፡ የሞተባት ፡ ወይም ፡ የተፋታች ፡ ግን ፡ ስእለቷ ፡ ራሷንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡ ይጸኑባታል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ ሴትም ፡ በባሏ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡ ብትሳል ፥ ወይም ፡ ራሷን ፡ በመሐላ ፡ ብታስር ፥

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ ባሏም ፡ ሰምቶ ፡ ዝም ፡ ቢላት ፡ ባይከለክላትም ፥ ስእለቷ ፡ ኹሉ ፡ ራሷንም ፡ ያሰረችበት ፡ መሐላ ፡

ኹሉ ፡ ይጸናል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ ባሏ ፡ ግን ፡ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ከንቱ ፡ ቢያደርገው ፥ ስለ ፡ ስእለቷ ፡ ወይም ፡ ራሷን ፡ ስላሰረችበት ፡ መሐላ ፡ ከአፏ ፡ የወጣው ፡ ነገር ፡ አይጸናም ፤ ባሏ ፡ ከንቱ ፡ አድርጎታል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይቅር ፡ ይላታል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ስእለቷን ፡ ኹሉ ፡ ነፍሷንም ፡ የሚያዋርደውን ፡ መሐላ ፡ ኹሉ ፡ ባሏ ፡ ያጸናዋል ፥ ባሏም ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ባሏ ፡ ግን ፡ በየዕለቱ ፡ ዝም ፡ ቢላት ፥ ስእለቷን ፡ ኹሉ ፡ በርሷም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ መሐላ ፡ ኹሉ ፡ አጽንቶታል ፤ በሰማበት ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ብሏታልና ፥ አጽንቶታል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ከሰማው ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከንቱ ፡ ቢያደርገው ፡ ኀጢአቷን ፡ ይሸከማል ።

ዘኍ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ ርሷ ፡ በብላቴንነቷ ፡ ጊዜ ፡ በአባቷ ፡ ቤት ፡ ሳለች ፡ በአባትና ፡ በልጂቱ ፡ መካከል ፥ ወይም ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ መካከል ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ ሥርዐት ፡ ይህ ፡ ነው ።

_____አሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ። _____

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በቀል ፡ ምድያማውያንን ፡ ተበቀል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ወገኖችኽ ፡ ትከማቻለኽ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ ሙሴም ፡ ሕዝቡን ፦ ከእናንተ ፡ መካከል ፡ ሰዎች ፡ ለጦርነት ፡ ይሰለፉ ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ምድያምን ፡ ይበቀሉ ፡ ዘንድ ፡ በምድያም ፡ ላይ ፡ ይኼዱ ፤

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ኹሉ ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ስደዱ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ ከእስራኤልም ፡ አእላፋት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፥ ለጦርነት ፡ የተሰለፉ ፡ ሰዎች ፡ ተሰጡ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሰደደ ፤ እነርሱንና ፡ የካህኑን ፡ የአልዓዛርን ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስን ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሰደዳቸው ፤ የመቅደሱንም ፡ ዕቃ ፡ የሚነፋውንም ፡ መለከት ፡ በእጁ ፡ ሰጠው ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ ከምድያም ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፥ ወንዶችንም ፡ ኹሉ ፡ ገደሉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ ከተገደሉትም ፡ ጋራ ፡ የምድያምን ፡ ነገሥታት ፡ ገደሏቸው ፤ ዐምስቱም ፡ የምድያም ፡ ነገሥታት ፡ ዔዊ ፥ ሮቆም ፥ ሱር ፥ ሑር ፥ ሪባ ፡ ነበሩ ፤ የቢያርንም ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡ ደግሞ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የምድያምን ፡ ሴቶችና ፡ ልጆቻቸውን ፡ ማረኩ ፤ እንስሳዎቻቸውንና ፡ መንጋዎቻቸውንም ፡ ዕቃቸውንም ፡ ኹሉ ፡ በዘበዙ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 10 ፤ የተቀመጡባቸውን ፡ ከተማዎቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ ሰፈሮቻቸውንም ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 11 ፤ የሰውንና ፡ የእንስሳን ፡ ምርኮና ፡ ብዝበዛ ፡ ኹሉ ፡ ወሰዱ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 12 ፤ የማረኳቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ምርኮውንና ፡ ብዝበዛውን ፡ ወደ ፡ ሙሴና ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አልዓዛር ፡ ወደእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፥ በዮርዳኖስም ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡

ወዳለው ፡ ሰፈር ፡ አመጡ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ የማኅበሩም ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ሊገናኟቸው ፡ ወጡ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 14 ፤ ሙሴም ፡ ከዘመቻ ፡ በተመለሱት ፡ በጭፍራ ፡ አለቃዎች ፥ በሻለቃዎችና ፡ በመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ አላቸው ፦ በእውኑ ፡ ሴቶችን ፡ ኹሉ ፡ አዳናችኋቸውን ፧

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ በፌጎር ፡ ምክንያት ፡ በበለዓም ፡ ምክር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይበድሉ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾኑ ፤ ስለዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ፡ ኾነ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ከልጆቹ ፡ ወንዱን ፡ ኹሉ ፡ ግደሉ ፥ ወንድንም ፡ በመኝታ ፡ የሚያውቁትን ፡ ሴቶች ፡ ኹሉ ፡ ግደሉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ ወንድን ፡ የማያውቁትን ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ለራሳችኹ ፡ አድኗቸው ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 19 ፤ ከሰፈሩም ፡ ውጭ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ስፈሩ ፤ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ኹሉ ፡ የተገደለውንም ፡ የዳሰሰ ፡ ኹሉ ፥ እናንተ ፡ የማረካችኋቸውም ፡ በሦስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ሰውነታችኹን ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 20 ፤ ልብስንም ፥ ከቀሮበትም ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኹሉ ፥ ከፍየልም ፡ ጠጕር ፡ ከዕንጨትም ፡ የተሠራውን ፡ ኹሉ ፡ ንጹሕ ፡ አድርጉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 21 ፤ ካህኑም ፡ አልዓዛር ፡ ከሰልፍ ፡ የመጡትን ፡ ሰዎች ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ የሕጉ ፡ ሥርዐት ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 22 ፤ ወርቁንና ፡ ብሩን ፥ ናሱንም ፥ ብረቱንም ፥ ቈርቈሮውንም ፥

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 23 ፤ ዐረሩንም ፥ በእሳት ፡ ለማለፍ ፡ የሚችለውን ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ ታሳልፉታላችኹ ፥ ንጹሕም ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በማንጻት ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ ይጠራል ። በእሳትም ፡ ለማለፍ ፡ የማይችለውን ፡ በውሃ ፡ ታሳልፉታላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 24 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ልብሳችኹን ፡ ዕጠቡ ፥ ንጹሕም ፡ ትኾናላችኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ትቀርባላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 26 ፤ አንተና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፡ የማኅበሩም ፡ አባቶች ፡ አለቃዎች ፡ የተማረኩትን ፡ ሰውና ፡ እንስሳ ፡ ቍጠሩ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 27 ፤ ምርኮውንም ፡ በተዋጉትና ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በወጡት ፥ በማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ አስተካክለኽ ፡ ክፈል ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 28 ፤ ከነዚያም ፡ ከተዋጉት ፡ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ከወጡት ፡ ሰልፈኞች ፡ ዘንድ ፥ ከሰዎችም ፡ ከበሬዎችም ፡ ከአህያዎችም ፡ ከመንጋዎችም ፡ ከዐምስት ፡ መቶ ፡ አንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግብር ፡ አውጣ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 29 ፤ ከድርሻቸው ፡ ወስደኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ለካህኑ ፡ ለአልዓዛር ፡ ስጠው ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 30 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ድርሻ ፡ ከሰዎች ፡ ከበሬዎችም ፡ ከአህያዎችም ፡ ከመንጋዎችም ፡

ከከብቶችም ፡ ኹሉ ፡ ከዐምሳ ፡ አንድ ፡ ትወስዳለኽ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ማደሪያ ፡ አገልግሎት ፡ ለሚጠብቁ ፡ ለሌዋውያን ፡ ትሰጣለኽ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 31 ፤ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 32 ፤ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የወጡ ፡ ሰዎችም ፡ ከወሰዱት ፡ ብዝበዛ ፡ ያስቀሩት ፡ ምርኮ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 33 ፤ 34 ፤ ሰባ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎች ፥ ስድሳ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ አህያዎች ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 35 ፤ ወንድ ፡ ከማያውቁ ፡ ሴቶችም ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ነፍስ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 36 ፤ በዘመቻም ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ድርሻ ፡ የኾነ ፡ እኩሌታ ፡ ከበግ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ በጎች ፡ ነበረ ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 37 ፤ ከበጎችም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ግብር ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 38 ፤ በሬዎችም ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ሰባ ፡ ኹለት ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 39 ፤ አህያዎቹም ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ስድሳ ፡ አንድ ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 40 ፤ ሰዎቹም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ግብር ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 41 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ ሙሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ የኾነውን ፡ ግብር ፡ ለካህኑ ፡ ለአልዓዛር ፡ ሰጠው ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 42 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እኩሌታም ፥ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ከወጡት ፡ ወንዶች ፡ ላይ ፡ ሙሴ ፡ የለየው ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 43 ፤ የማኅበሩ ፡ ድርሻ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ በጎች ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 44 ፤ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎች ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 45 ፤ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ አህያዎች ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 46 ፤ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 47 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ድርሻ ፡ ሙሴ ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳ ፡ ከዐምሳ ፡ አንድ ፡ ወሰደ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማደሪያ ፡ አገልግሎት ፡ ለሚጠብቁ ፡ ሌዋውያን ፡ ሰጠ ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 48 ፤ በሰራዊት ፡ አእላፋት ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፡ አለቃዎች ፥ ሻለቃዎችና ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፥ ወደ ፡ ሙሴ ፡ ቀረቡ ፥

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 49 ፤ ሙሴንም ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የወጡትን ፡ ከእጃችን ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ቈጠርን ፥ ከእኛም ፡ አንድ ፡ አልጐደለም ።

ዘኍ. ፥ 31 ፥ 50 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ካገኘው ፡ ከወርቅ ፡ ዕቃ ፥ ከእግር ፡ አልቦም ፥ ከአንባርም ፥ ከቀለበትም ፥ ከጕትቻም ፥ ከድሪውም ፡ ለነፍሳችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያስተሰርይልን ፡

ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ አምጥተናል ፡ አሉት ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 51 ፤ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ ወርቁንና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የተሠራውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ከእጃቸው ፡ ተቀበሉ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 52 ፤ ሻለቃዎችም ፡ የመቶ ፡ አለቃዎችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ያቀረቡት ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 53 ፤ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የወጡ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከምርኳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ወሰዱ ።

ዘኍ. ፡ 31 ፡ 54 ፤ ሙሴና ፡ ካህኑ ፡ አልዓዛርም ፡ ወርቁን ፡ ከሻለቃዎችና ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ወስደው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መታሰቢያ ፡ ወደመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አገቡት ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡ ምዕራፍ ፡ 32 ። _____

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆችም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ እንስሳዎች ፡ ነበሯቸው ፤ እንሆም ፡ የኢያዜር ፡ ምድርና ፡ የገለዓድ ፡ ምድር ፡ ለእንስሳዎች ፡ የተመቸ ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ የጋድና ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ መጥተው ፡ ሙሴንና ፡ ካህኑን ፡ አልዓዛርን ፡ የማኅበሩንም ፡ አለቃዎች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 3-4 ፤ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ፊት ፡ የመታው ፡ ምድር ፡ ዐጣሮት ፡ ዲቦን ፡ ኢያዜር ፡ ነምራ ፡ ሐሴቦን ፡ ኤልያሊ ፡ ሴባማ ፡ ናባው ፡ ባያን ፡ ለእንስሳዎች ፡ የተመቸ ፡ ምድር ፡ ነው ፤ ለእኛም ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ እንስሳዎች ፡ አሉን ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ እኛስ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስን ፡ አግኝተን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህን ፡ ምድር ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ስጠን ፤ ወደዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ አታሻግረን ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ ሙሴም ፡ ለጋድና ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ አላቸው ፦ ወንድሞቻችኹ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ሲኼዱ ፡ እናንተ ፡ በዚህ ፡ ትቀመጣላችኹን ፧

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጣቸው ፡ ምድር ፡ እንዳይሻገሩ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ ለምን ፡ ታደክማላችኹ ፧

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ ምድሪቱን ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በሰደድኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አባቶቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ ወደኤሽኮልም ፡ ሸለቆ ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፡ ምድሪቱንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሰጣቸው ፡ ምድር ፡ እንዳይገቡ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ አደከሙ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ነደደ ፡

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ 12 ፤ ርሱም ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽመው ፡ ከተከተሉ ፡ ከነዚህ ፡ ከቄኔዛዊው ፡ ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብና ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ በቀር ፡ ከግብጽ ፡ የወጡት ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ እኔን ፡ ፈጽመው ፡ አልተከተሉምና ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የማልኹበትን ፡ ምድር ፡ አያዩም ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ጸና ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ያደረገ ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ አቅበዘበዛቸው ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ እንሆም ፥ የእግዚአብሔርን ፡ መዓት ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አብዝታችኹ ፡ ትጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ እናንተ ፡ የኀጢአተኞች ፡ ትውልድ ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ፋንታ ፡ ቆማችኋል ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ ርሱን ፡ ከመከተል ፡ ብትመለሱ ፡ ርሱ ፡ ሕዝቡን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ደግሞ ፡ ይተዋል ፤ ይህንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ታጠፋላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ቀርበው ፡ አሉት ፦ በዚህ ፡ ለእንስሳዎቻችን ፡ በረቶች ፡ ለልጆቻችንም ፡ ከተማዎች ፡ እንሠራለን ፤

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ለጦርነት ፡ ተዘጋጅተን ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ እስክናገባቸው ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንኼዳለን ፤ በዚህም ፡ ምድር ፡ ስላሉ ፡ ሰዎች ፡ ልጆቻችን ፡ በተመሸጉ ፡ ከተማዎች ፡ ይቀመጣሉ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ርስታቸውን ፡ እስኪወርሱ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ቤቶቻችን ፡ አንመለስም ፤

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ ከዮርዳኖስ ፡ ወዲህ ፡ ወደምሥራቅ ፡ ርስታችን ፡ ደርሰናልና ፥ እኛ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደዚያ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ርስት ፡ አንወርስም ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ ሙሴም ፡ አላቸው ፦ ይህንስ ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ፥ ተዘጋጅታችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ብትኼዱ ፥

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ ጠላቶቹን ፡ ከፊቱ ፡ እስኪያሳድድ ፡ ድረስ ፡ ምድሪቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ድል ፡ እስክትኾን ፡ ድረስ ፡ ከእናንተ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ቢሻገር ፥

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 22 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ትመለሳላችኹ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጹሓን ፡ ትኾናላችኹ ፤ ይህች ፡ ምድርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርስት ፡ ትኾንላችኋለች ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 23 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ባታደርጉ ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ትበድላላችኹ ፤ ኀጢአታችኹም ፡ እንዲያገኛችኹ ፡ ዕወቁ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 24 ፤ ለልጆቻችኹ ፡ ከተማዎች ፥ ለበጎቻችኹም ፡ በረቶች ፡ ሥሩ ፤ ከአፋችኹም ፡ የወጣውን ፡ ነገር ፡ አድርጉ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 25 ፤ የጋድና ፡ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ጌታችን ፡ እንዳዘዘ ፡ እናደርጋለን ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 26 ፤ ልጆቻችን ፥ ሚስቶቻችንም ፥ መንጋዎቻችንም ፥ እንስሳዎቻችንም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ በገለዓድ ፡ ከተማዎች ፡ ይኾናሉ ፤

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 27 ፤ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ግን ፡ ኹላችን ፡ ጋሻ ፡ ጦራችንን ፡ ይዘን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጌታችን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ እንኼዳለን ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 28 ፤ ሙሴም ፡ ካህኑን ፡ አልዓዛርን ፡ የነዌንም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አለቃዎች ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አዘዘ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፦ የጋድና ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ ኹላቸው ፡ ጋሻ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ቢሻገሩ ፥ ምድሪቱንም ፡ ድል ፡ ብትነሡ ፥ የገለዓድን ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አድርጋችኹ ፡ ትሰጧቸዋላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 32 ፡ 30 ፤ ጋሻ ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ባይሻገሩ ፡ ግን ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ በእናንተ ፡

መካከል ፡ ርስታቸውን ፡ ይወርሳሉ ፡ አላቸው ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 31 ፤ የጋድና ፡ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ መልሰው ፦ እግዚአብሔር ፡ ለእኛ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ እንዲሁ ፡ እናደርጋለን ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 32 ፤ ጋሻ ፡ ጦራችንን ፡ ይዘን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ እንሻገራለን ፥ ከዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ከወዲሁ ፡ የወረስነው ፡ ርስት ፡ ይኾንልናል ፡ አሉት ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 33 ፤ ሙሴም ፡ ለጋድና ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ ለዮሴፍም ፡ ልጅ ፡ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፥ የአሞራውያንን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎንን ፡ ግዛት ፡ የባሳንንም ፡ ንጉሥ ፡ የዐግን ፡ ግዛት ፥ ምድሪቱንና ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉትን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጣቸው ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 34 ፤ የጋድም ፡ ልጆች ፡ ዲቦንን ፥ ዐጣሮትን ፥ ዐሮዔርን ፥

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 35 ፤ ዓጥሮትሸፋንን ፥ ኢያዜርን ፥ ዮግብሃን ፥

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 36 ፤ ቤትነምራን ፥ ቤትሃራንን ፡ የተመሸጉ ፡ ከተማዎች ፡ አድርገው ፡ ሠሩ ፤ የበጎች ፡ በረቶችንም ፡ ሠሩ ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 37 ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ሐሴቦንን ፥ ኤልያሊን ፥

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 38 ፤ ቂርያታይምን ፥ ስማቸውም ፡ የተለወጠውን ፡ ናባውን ፥ በዓልሜዎንን ፥ ሴባማን ፡ ሠሩ ፤ እነዚህንም ፡ የሠሯቸውን ፡ ከተማዎች ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ጠሯቸው ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 39 ፤ የምናሴም ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ኼዱ ፥ ወሰዷትም ፥ በርሷም ፡ የነበሩትን ፡ አሞራውያንን ፡ አሳደዱ ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 40 ፤ ሙሴም ፡ ለምናሴ ፡ ልጅ ፡ ለማኪር ፡ ገለዓድን ፡ ሰጠ ፤ በርሷም ፡ ተቀመጠ ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 41 ፤ የምናሴም ፡ ልጅ ፡ ኢያዕር ፡ ኼዶ ፡ መንደሮቿን ፡ ወሰደ ፥ የኢያዕርም ፡ መንደሮች ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ዘኁ. ፡ 32 ፡ 42 ፤ ኖባህም ፡ ኼደ ፡ ቄናትንም ፡ መንደሮቿንም ፡ ወሰደ ፥ በስሙም ፡ ኖባህ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ኦሪት ፡ ዘኁልቁ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጉዞ ፡ ከሙሴና ፡ ከአሮን ፡ እጅ ፡ በታች ፡ በጭፍራዎቻቸው ፡ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 2 ፤ ሙሴም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ጕዟቸው ፡ አወጣጣቸውን ፡ ጻፈ ፤ እንደ ፡ አወጣጣቸውም ፡ ጕዟቸው ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 3 ፤ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ ከራምሴ ፡ ተጓዙ ፤ ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግብጻውያን ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ ከፍ ፡ ባለች ፡ እጅ ፡ ወጡ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ግብጻውያን ፡ እግዚአብሔር ፡ የገደላቸውን ፡ በኩሮቻቸውን ፡ ይቀብሩ ፡ ነበር ፤ በአማልክታቸውም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈረደባቸው ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከራምሴ ፡ ተጕዘው ፡ በሱኮት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ ከሱኮትም ፡ ተጕዘው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዳርቻ ፡ ባለች ፡ በኤታም ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ ከኤታምም ፡ ተጕዘው ፡ በበዓልዛፎን ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ነበረች ፡ ወደ ፡ ፊሀሒሮት ፡ ተመለሱ ፤ በሚግዶልም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ ከፊሀሒሮትም ፡ ተጕዘው ፡ በባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ዐለፉ ፤ በኤታምም ፡ በረሓ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ኼደው ፡ በማራ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ከማራም ፡ ተጕዘው ፡ ወደ ፡ ኤሊም ፡ መጡ ፤ በኤሊምም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ የውሃ ፡ ምንጮች ፡ ሰባ ፡ ዘንባባዎችም ፡ ነበሩ ፤ በዚያም ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ ከኤሊምም ፡ ተጕዘው ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ ከቀይ ፡ ባሕርም ፡ ተጕዘው ፡ በሲን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 12 ፤ ከሲን ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ተጕዘው ፡ በራፋቃ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ ከራፋቃም ፡ ተጕዘው ፡ በኤሉስ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ ከኤሉስም ፡ ተጕዘው ፡ በራፊዲም ፡ ሰፈሩ ፤ በዚያም ፡ ሕዝቡ ፡ የሚጠጡት ፡ ውሃ ፡ አልነበረም ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ ከራፊዲምም ፡ ተጕዘው ፡ በሲና ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ ከሲናም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተጕዘው ፡ በምቖት ፡ መቃብር ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ ከምቖት ፡ መቃብርም ፡ ተጕዘው ፡ በሐጼሮት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ከሐጼሮትም ፡ ተጕዘው ፡ በሪትማ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ ከሪትማም ፡ ተጕዘው ፡ በሬሞን ፡ ዘፋሬስ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ ከሬሞን ፡ ዘፋሬስም ፡ ተጕዘው ፡ በልብና ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ ከልብናም ([97]) ፡ ተጕዘው ፡ በሪሳ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ ከሪሳም ፡ ተጕዘው ፡ በቀሄላታ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ ከቀሄላታም ፡ ተጕዘው ፡ በሻፍር ፡ ተራራ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 24 ፤ ከሻፍር ፡ ተራራም ፡ ተጕዘው ፡ በሐራዳ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 25 ፤ ከሐራዳም ፡ ተጕዘው ፡ በመቅሄሎት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 26 ፤ ከመቅሄሎትም ፡ ተጕዘው ፡ በታሐት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 27 ፤ ከታሐትም ፡ ተጕዘው ፡ በታራ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 28 ፤ ከታራም ፡ ተጕዘው ፡ በሚትቃ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኍ. ፡ 33 ፡ 29 ፤ ከሚትቃም ፡ ተጕዘው ፡ በሐሽሞና ፡ ሰፈሩ ።

---

97 ዕብ. ፡ ሊብናህ ፡ (ልብኔ • ነጭ ፡ ዛፍ) ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 30 ፤ ከሐሽሞናም ፡ ተጕዘው ፡ በሞሴሮት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 31 ፤ ከሞሴሮትም ፡ ተጕዘው ፡ በብኔያዕቃን ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 32 ፤ ከብኔያዕቃንም ፡ ተጕዘው ፡ በሖርሃጊድጋድ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 33 ፤ ከሖርሃጊድጋድም ፡ ተጕዘው ፡ በዮጥባታ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 34 ፤ ከዮጥባታም ፡ ተጕዘው ፡ በዔብሮና ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 35 ፤ ከዔብሮናም ፡ ተጕዘው ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 36 ፤ ከዔጽዮንጋብርም ፡ ተጕዘው ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰፈሩ ፤ ይህችም ፡ ቃዴስ ፡ ናት ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 37 ፤ ከቃዴስም ፡ ተጕዘው ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ባለው ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 38 ፤ ካህኑም ፡ አሮን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ወደሖር ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ በዚያም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በአርባኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ሞተ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 39 ፤ አሮንም ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነበር ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 40 ፤ በከነዓን ፡ ምድርም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ ከነዓናዊው ፡ የዓራድ ፡ ንጉሥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ሰማ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 41 ፤ እነርሱም ፡ ከሖር ፡ ተራራ ፡ ተጕዘው ፡ በሴልሞና ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 42 ፤ ከሴልሞናም ፡ ተጕዘው ፡ በፉኖን ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 43 ፤ ከፉኖንም ፡ ተጕዘው ፡ በኦቦት ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 44 ፤ ከኦቦትም ፡ ተጕዘው ፡ በሞዐብ ፡ ዳርቻ ፡ ባለው ፡ በጋይ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 45 ፤ ከጋይም ፡ ተጕዘው ፡ በዲቦንጋድ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 46 ፤ ከዲቦንጋድም ፡ ተጕዘው ፡ በዐልሞንዲብላታይም ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 47 ፤ ከዐልሞንዲብላታይምም ፡ ተጕዘው ፡ በናባው ፡ ፊት ፡ ባሉ ፡ በዓብሪም ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 48 ፤ ከዓብሪምም ፡ ተራራዎች ፡ ተጕዘው ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 49 ፤ በዮርዳኖስም ፡ አጠገብ ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ከቤትየሺሞት ፡ እስከ ፡ አቤልሰጢም ([98]) ፡ ድረስ ፡ ሰፈሩ ።

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 50 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኁ. ፡ 33 ፡ 51 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ ዮርዳኖስን ፡

98 የሸጢን ፡ መስክ ።

በተሻገራችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘኍ. ፥ 33 ፥ 52 ፤ የአገሩን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከፊታችኹ ፡ ታሳድዳላችኹ ፥ የተቀረጹትንም ፡ ድንጋዮቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ ታጠፋላችኹ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ ታጠፋላችኹ ፥ በከሎረብታ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎቻቸውንም ፡ ታፈርሳላችኹ ፤

ዘኍ. ፥ 33 ፥ 53 ፤ ምድሪቱንም ፡ ለእናንተ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቻችኋለኹና ፡ ምድሪቱን ፡ ትወርሷታላችኹ ፡ ትቀመጡባታላችኹም ።

ዘኍ. ፥ 33 ፥ 54 ፤ ምድሪቱንም ፡ በየወገኖቻችኹ ፡ በዕጣ ፡ ትወርሳላችኹ ፤ ለብዙዎች ፡ እንደ ፡ ብዛታቸው ፡ ለጥቂቶቹም ፡ እንደ ፡ ጥቂትነታቸው ፡ መጠን ፡ ርስትን ፡ ትሰጣላችኹ ፤ እያዳንዱ ፡ ኹሉ ፡ ዕጣ ፡ እንደ ፡ ወደቀለት ፡ በዚያ ፡ ርስቱ ፡ ይኾናል ፤ በያባቶቻችኹ ፡ ነገዶች ፡ ትወርሳላችኹ ።

ዘኍ. ፥ 33 ፥ 55 ፤ የአገሩንም ፡ ሰዎች ፡ ከፊታችኹ ፡ ባታሳድዱ ፥ ያስቀራችኋቸው ፡ ለዐይናችኹ ፡ እንደ ፡ ሾኽ ፡ ለጎናችኹም ፡ እንደሚወጋ ፡ ነገር ፡ ይኾኑባችኋል ፥ በምትቀመጡባትም ፡ ምድር ፡ ያስጨንቋችኋል ።

ዘኍ. ፥ 33 ፥ 56 ፤ እኔም ፡ በእነርሱ ፡ ላደርገው ፡ ዘንድ ፡ ያሰብኹትን ፡ በእናንተ ፡ አደርግባችኋለኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። _____

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 1 ፤ **እግዚአብሔር**ም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 2 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፥ ርስት ፡ ትኾናችኹ ፡ ዘንድ ፡ በዕጣ ፡ የምትደርሳችኹ ፡ ምድር ፥ በዳርቻዋ ፡ ያለች ፡ የከነዓን ፡ ምድር ፥

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 3 ፤ ይህች ፡ ናት ፤ የደቡቡ ፡ ወገን ፡ ከጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በኤዶምያስ ፡ በኩል ፡ ይኾናል ፤ የደቡቡም ፡ ዳርቻ ፡ ከጨው ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ይገምራል ፤

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 4 ፤ ዳርቻችኹም ፡ በአቅረቢም ፡ ዐቀበት ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ይዞራል ፡ ወደ ፡ ጺንም ፡ ያልፋል ፤ መውጫውም ፡ በቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ይኾናል ፤ ወደ ፡ ሐጸርአዳር ፡ ይኼዳል ፡ ወደ ፡ ዓጽሞንም ፡ ያልፋል ፤

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 5 ፤ ዳርቻውም ፡ ከዓጽሞን ፡ ወደግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ይዞራል ፥ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፡ በኩል ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 6 ፤ ለምዕራብም ፡ ዳርቻ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይኾናል ፤ ይህ ፡ የምዕራብ ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 7 ፤ የሰሜንም ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይህ ፡ ይኾናል ፤ ከታላቁ ፡ ባሕር ፡ ወደሖር ፡ ተራራ ፡ ምልክት ፡ ታመለክታላችኹ ፤

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 8 ፤ ከሖርም ፡ ተራራ ፡ ወደሐማት ፡ መግቢያ ፡ ምልክት ፡ ታመለክታላችኹ ፡ የዳርቻውም ፡ መውጫ ፡ በጽዳድ ፡ ይኾናል ፤

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 9 ፤ ዳርቻውም ፡ ወደ ፡ ዚፍሮን ፡ ያልፋል ፡ እስከ ፡ ሐጻረ ፡ ዔኖንም ([99]) ፡ ድረስ ፡ ይወጣል ፤ ይህ ፡ የሰሜን ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይኾናል ።

ዘኍ. ፥ 34 ፥ 10 ፤ የምሥራቁንም ፡ ዳርቻችኹን ፡ ከሐጻረ ፡ ዔኖን ፡ ወደ ፡ ሴፋማ ፡ ምልክት ፡ ታመለክታላችኹ ፤

---

99 ዕብ. ፥ ሐጻር ፡ ዔኖን ፡ (የዐይኖች ፡ ቅጥር ፥ የዔኖን ፡ ዐጥር) ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 11 ፤ ዳርቻውም ፡ ከሴፋማ ፡ በዐይን ፡ ምሥራቅ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ ይወርዳል ፤ እስከ ፡ ኪኔሬት ፡ የባሕር ፡ ወሽመጥ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ይደርሳል ፤

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 12 ፤ ዳርቻውም ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ይወርዳል ፥ መውጫውም ፡ በጨው ፡ ባሕር ፡ ይኾናል ። ምድራችኹ ፡ እንደ ፡ ዳርቻዋ ፡ በዙሪያዋ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። እግዚአብሔር ፡ ለዘጠኝ ፡ ነገድ ፡ ተኩል ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ያዘዘ ፡ በዕጣ ፡ የምትወርሷት ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፤

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 14 ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤት ፥ የጋድም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤት ፥ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስታቸውን ፡ ወርሰዋል ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 15 ፤ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ነገድና ፡ የአንዱ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስታቸውን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወረሱ ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 17 ፤ ምድሪቱን ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ የሚከፍሉላችኹ ፡ ሰዎች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ካህኑ ፡ አልዓዛርና ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 18 ፤ ምድሪቱንም ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ ትወስዳላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 19 ፤ የሰዎቹም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 20 ፤ ከስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ሰላሚኤል ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 21 ፤ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የኪስሎን ፡ ልጅ ፡ ኤልዳድ ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 22 ፤ ከዳን ፡ ልጆች ፡ ንገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የዮግሊ ፡ ልጅ ፡ ቡቂ ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 23 ፤ ከዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ከምናሴ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሱፊድ ([100]) ፡ ልጅ ፡ ዐኒኤል ([101]) ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 24 ፤ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሺፍጣን ፡ ልጅ ፡ ቀሙኤል ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 25 ፤ ከዛብሎን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የፈርናክ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፈን ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 26 ፤ ከይሳኮር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሐዛ ፡ ልጅ ፡ ፈልጢኤል ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 27 ፤ ከአሴር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የሴሌሚ ፡ ልጅ ፡ አኒሁድ ፥

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 28 ፤ ከንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ፈዳሄል ።

ዘኍ. ፡ 34 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስታቸውን ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

_____ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ። _____

---

100 ዕብ. ፥ ኤፉድ ፡ (ልብሰ ፡ ተክህኖ) ።

101 ዕብ. ፥ ሐኒኤል ፡ (ሞገሰ ፡ እግዚእ) ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ ሌዋውያን ፡ የሚቀመጡባቸውን ፡ ከተማዎች ፡ ከርስታቸው ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እዘዛቸው ፤ በከተማዎቹም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ መሰምሪያ ፡ ለሌዋውያን ፡ ስጡ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፡ በከተማዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ፤ መሰምሪያቸውም ፡ ለከብቶቻቸው ፡ ለእንስሳዎቻቸውም ፡ ለእነርሱም ፡ ላለው ፡ ኹሉ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ ለሌዋውያንም ፡ የምትሰጡት ፡ የከተማ ፡ መሰምሪያ ፡ በከተማው ፡ ዙሪያ ፡ ከቅጥሩ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ ከከተማው ፡ ውጭ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፥ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፥ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፥ በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ትከነዳላችኹ ፥ ከተማውም ፡ በመካከል ፡ ይኾናል ፤ ይህም ፡ የከተማዎቹ ፡ መሰምሪያ ፡ ይኾንላቸዋል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ ለሌዋውያንም ፡ የምትሰጧቸው ፡ ስድስቱ ፡ የመማፀኛ ፡ ከተማዎች ፡ ናቸው ፤ እነርሱም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ይሸሸባቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትሰጧቸው ፡ ናቸው ፤ ከነዚህም ፡ ሌላ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎች ፡ ትሰጣላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ ለሌዋውያን ፡ የምትሰጧቸው ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ከተማዎች ፡ ይኾናሉ ፤ ከመሰምሪያቸው ፡ ጋራ ፡ ትሰጧቸዋላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ለሌዋውያን ፡ የምትሰጧቸውን ፡ ከተማዎች ፡ እንዲሁ ፡ ስጡ ፤ ከብዙዎቹ ፡ ብዙ ፥ ከጥቂቶቹ ፡ ጥቂት ፡ ትወስዳላችኹ ፤ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ወረሱት ፡ እንደ ፡ ርስታቸው ፡ መጠን ፡ ከከተማዎቻቸው ፡ ለሌዋውያን ፡ ይሰጣሉ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ ወደከነዓን ፡ ምድር ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገራችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 11 ፤ በስሕተት ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ወደዚያ ፡ ይሸሽ ፡ ዘንድ ፡ የመማፀኛ ፡ ከተማዎች ፡ እንዲኾኑላችኹ ፡ ከተማዎችን ፡ ለእናንት ፡ ለዩ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 12 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፡ እንዳይሞት ፥ ከተማዎቹም ፡ ከደም ፡ ተበቃይ ፡ የመማፀኛ ፡ ከተማዎች ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 13 ፤ የምትሰጧቸውም ፡ ስድስቱ ፡ ከተማዎች ፡ የመማፀኛ ፡ ከተማዎች ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 14 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ትሰጣላችኹ ፥ በከነዓንም ፡ ምድር ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ትሰጣላችኹ ፤ የመማፀኛ ፡ ከተማዎች ፡ ይኾናሉ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 15 ፤ በስሕተት ፡ ነፍስ ፡ የገደለ ፡ ይሸሽበት ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ስድስት ፡ ከተማዎች ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በመካከላቸው ፡ ለሚቀመጡ ፡ እንግዳዎችና ፡ መጻተኞች ፡ መማፀኛ ፡ ይኾናሉ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 16 ፤ በብረት ፡ መሣሪያ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢመታው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 17 ፤ ሰውም ፡ በሚሞትበት ፡ በእጁ ፡ ባለው ፡ ድንጋይ ፡ ቢመታው ፡ የተመታውም ፡ ቢሞት ፥ ርሱ ፡

ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 18 ፤ ሰውም ፡ በሚሞትበት ፡ በእጁ ፡ ባለው ፡ በዕንጨት ፡ መሣሪያ ፡ ቢመታው ፡ የተመታውም ፡ ቢሞት ፥ ርሱ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 19 ፤ ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ራሱ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ይግደል ፤ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ይግደለው ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 20 ፤ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በጥላቻ ፡ ቢደፋው ፥ ወይም ፡ ሸምቆ ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢጥልበት ፥

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 21 ፤ ወይም ፡ በጥላቻ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በእጁ ፡ ቢመታው ፥ የመታው ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፤ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፤ ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ይግደለው ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ያለጥላቻ ፡ ድንገት ፡ ቢደፋው ፥ ሳይሸምቅም ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ ቢጥልበት ፥

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 23 ፤ ወይም ፡ ሳያየው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ የሚሞትበትን ፡ ድንጋይ ፡ ቢጥልበት ፥ ጠላቱም ፡ ባይኾን ፥ ክፉም ፡ ያደርግበት ፡ ዘንድ ፡ ባይሻ ፥

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 24 ፤ ማኅበሩ ፡ በመቷውና ፡ በደም ፡ ተበቃዩ ፡ መካከል ፡ ፍርድን ፡ እንደዚሁ ፡ ይፍረድ ፤

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 25 ፤ ማኅበሩም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ከደም ፡ ተበቃዩ ፡ እጅ ፡ ያድነዋል ፥ ማኅበሩም ፡ ወደ ፡ ሸሸበት ፡ ወደ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ ይመልሰዋል ፤ በቅዱስ ፡ ዘይትም ፡ የተቀባው ፡ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ይቀመጣል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 26 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ግን ፡ ከሸሸበት ፡ ከመማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ዳርቻ ፡ ቢወጣ ፥

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 27 ፤ ደም ፡ ተበቃዩም ፡ ከመማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ዳርቻ ፡ ውጭ ፡ ቢያገኘው ፥ ደም ፡ ተበቃዩም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ቢገድለው ፥ የደም ፡ ዕዳ ፡ አይኾንበትም ፤

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 28 ፤ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በመማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ መቀመጥ ፡ ይገባው ፡ ነበርና ። ዋነኛው ፡ ካህን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ወደርስቱ ፡ ምድር ፡ ይመለሳል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 29 ፤ እነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ለልጅ ፡ ልጃችኹ ፡ በማደሪያችኹ ፡ ኹሉ ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 30 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ኹሉ ፡ በምስክሮች ፡ አፍ ፡ ይገደላል ፤ ባንድ ፡ ምስክር ፡ ግን ፡ ማናቸውንም ፡ ሰው ፡ መግደል ፡ አይገባም ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 31 ፤ ሞት ፡ የተፈረደበትን ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩንም ፡ ለማዳን ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ አትቀበሉ ፤ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 32 ፤ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ ሳይሞት ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መማፀኛው ፡ ከተማ ፡ ከሸሸው ፡ የነፍስ ፡ ዋጋ ፡ አትቀበሉ ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 33 ፤ ደም ፡ ምድሪቱን ፡ ያረክሳታልና ፥ የምትኖሩባትን ፡ ምድር ፡ አታርክሷት ፤ በደም ፡ አፍሳሹ ፡ ደም ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ ምድሪቱ ፡ ከፈሰሰባት ፡ ደም ፡ አትነጻም ።

ዘኍ. ፡ 35 ፡ 34 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ዐድራለኹና ፡ የምትኖሩባትን ፡ በመካከሏም ፡ የማድርባትን ፡ ምድር ፡ አታርክሷት ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ ከዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ አለቃዎች ፡ ቀረቡ ፥ በሙሴና ፡ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አባቶች ፡ አለቃዎች ፡ ፊት ፡ ተናገሩ ፤

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ አሉም ፦ ምድሪቱን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ በዕጣ ፡ ከፍለኽ ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ ጌታችንን ፡ አዘዘኽ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የወንድማችንን ፡ የሰለጰዓድን ፡ ርስት ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አንተን ፡ ጌታችንን ፡ አዘዘ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ ከሌላም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ባል ፡ ቢያገቡ ፥ ርስታቸው ፡ ከአባቶቻችን ፡ ርስት ፡ ይነቀላል ፥ እነርሱም ፡ ለሚኾኑበት ፡ ለሌላው ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይጨመራል ፤ እንደዚህም ፡ የርስታችን ፡ ዕጣ ፡ ይጐድላል ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 4 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ርስታቸው ፡ ለሚኾኑበት ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይጨመራል ፤ እንደዚህም ፡ ርስታቸው ፡ ከአባቶቻችን ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይጐድላል ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 5 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በእውነት ፡ ተናገሩ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለሰለጰዓድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የወደዱትን ፡ ያግቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአባታቸው ፡ ነገድ ፡ ብቻ ፡ ያግቡ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 7 ፤ እንደዚህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ከነገድ ፡ ወደ ፡ ነገድ ፡ ምንም ፡ አይተላለፍ ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ ወዳባቶቹ ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይጠጋ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 8 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ የአባቶቹን ፡ ርስት ፡ ይወርስ ፡ ዘንድ ፥ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ሹሉ ፡ ርስት ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሹሉ ፡ ከአባቷ ፡ ነገድ ፡ ባል ፡ ታግባ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 9 ፤ እንደዚህም ፡ ካንድ ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ነገድ ፡ ምንም ፡ ርስት ፡ አይተላለፍ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ይጠጋ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ የሰለጰዓድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አደረጉ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 11 ፤ የሰለጰዓድ ፡ ልጆች ፡ ማህለህ ፥ ቲርጻ ፥ ዔግላ ፥ ሚልካ ፥ ኑዓ ፡ ከአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ተጋቡ ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ከዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ከምናሴ ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ባሎቻቸውን ፡ አገቡ ፥ ርስታቸውም ፡ በአባታቸው ፡ ነገድ ፡ ጸና ።

ዘኍ. ፡ 36 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ያዘዛቸው ፡ ትእዛዝና ፡ ፍርድ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ❖

ኦሪት ፡ ዘዳግም ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፥ በዐረባ [102] ፡ ውስጥ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፥ በፋራን ፡ በጦፌልም ፡ በላባንም ፡ በሐዜሮትም ፡ በዲዛሃብም ፡ መካከል ፡ ሳሉ ፥ ሙሴ ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ የነገራቸው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ በሴይር ፡ ተራራ ፡ መንገድ ፡ ከኮሬብ ፡ እስከ ፡ ቃዴስ ፡ በርኔ ፡ ድረስ ፡ የዐሥራ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 3-4 ፤ በአርባኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፥ ሙሴ ፥ በሐሴቦን ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ የአሞራውያንን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፥ በዐስታሮትና ፡ በኤድራይ ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ የባሳንን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግን ፡ ከመታ ፡ በኋላ ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገራቸው ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ሙሴ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይህችን ፡ ሕግ ፡ ይገልጥ ፡ ዠመር ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኮሬብ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረን ፦ በዚህ ፡ ተራራ ፡ የተቀመጣችኹት ፡ በቃ ፤

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ተመልሳችኹ ፡ ተጓዙ ፤ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደአሞራውያን ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ድንበሮቹም ፡ ኹሉ ፥ በዐረባም ፡ በደጋውም ፡ በቈላውም ፡ በደቡብም ፡ በባሕርም ፡ ዳር ፡ ወዳሉ ፡ ወደከነዓናውያን ፡ ምድር ፥ ወደ ፡ ሊባኖስም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ወንዝም ፡ እስከ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ድረስ ፡ ኺዱ ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እንሆ ፥ ምድሪቱን ፡ በፊታችኹ ፡ አድርጌያለኹ ፤ ግቡ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለእነርሱ ፡ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘራቸው ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ የማለላቸውንም ፡ ምድር ፡ ውረሱ ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኋችኹ ፦ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ልሸከማችኹ ፡ አልችልም ፤

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብዝቷችኋል ፥ እንሆም ፥ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ብዛት ፡ ናችኹ ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፡ ይጨምር ፥ እንደ ፡ ተናገራችኹም ፡ ይባርካችኹ ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ድካማችኹን ፣ ሸክማችኹንም ፣ ክርክራችኹንም ፡ እሸከም ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ እችላለኹ ፧

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ከእናንተ ፡ ከየነገዳችኹ ፡ ጥበበኞች ፡ አስተዋዮችም ፡ ዐዋቂዎችም ፡ የኾኑትን ፡ ሰዎች ፡ ምረጡ ፥ እኔም ፡ በላያችኹ ፡ አለቃዎች ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ዘዳ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እናንተም ፦ እናደርገው ፡ ዘንድ ፡ የተናገርኸው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብላችኹ ፡

---

102 ዕብ. ፥ ዐራባ ፡ (ዐረብ • ምድረ ፡ በዳ ፥ ከዮርዳኖስ ፡ እስከ ፡ ባሕረ ፡ ጼው ፡ ያለ ፡ በረሓ) ።

መለሳችኹልኝ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ጥበበኞችና ፡ ዐዋቂዎች ፡ የኾኑትን ፡ የነገዶቻችኹን ፡ አለቃዎች ፡ መረጥኹ ፥ በእናንተም ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ የሻለቃዎችም ፡ የመቶ ፡ አለቃዎችም ፡ የዐምሳ ፡ አለቃዎችም ፡ የዐሥር ፡ አለቃዎችም ፡ ገዢዎችም ፡ በየነገዶቻቸው ፡ አደረግኋቸው ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፦ የወንድሞቻችኹን ፡ ነገር ፡ ስሙ ፤ በሰውና ፡ በወንድሙ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ባለው ፡ መጻተኛ ፡ መካከል ፡ በጽድቅ ፡ ፍረዱ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ በፍርድም ፡ አድልዎ ፡ አታድርጉ ፤ ታላቁን ፡ እንደምትሰሙ ፥ ታናሹንም ፡ እንዲሁ ፡ ስሙ ፤ ፍርድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነውና ፥ ከሰው ፡ ፊት ፡ አትፍሩ ፤ ከነገርም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቢከብዳችኹ ፡ ርሱን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፥ እኔም ፡ እሰማዋለኹ ፡ ብዬ ፡ ፈራጆቻችኹን ፡ አዘዝኋቸው ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ልታደርጉት ፡ የሚገባችኹን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አዘዝኋችኹ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ከኰሬብም ፡ ተጓዝን ፥ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘን ፡ በታላቁ ፡ እጅግም ፡ በሚያስፈራ ፡ በዚያ ፡ ባያችኹት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኹሉ ፡ በኩል ፡ በተራራማው ፡ በአሞራውያን ፡ መንገድ ፡ ኼድን ፤ ወደ ፡ ቃዴስ ፡ በርኔም ፡ መጣን ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እኔም ፦ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጠን ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደአሞራውያን ፡ አገር ፡ መጣችኹ ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እንሆ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምድሪቱን ፡ በፊትኽ ፡ አድርጓል ፤ የአባቶችኽ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለኽ ፥ ውጣ ፥ ውረሳት ፤ አትፍራ ፥ አትደንግጥም ፡ አልኋችኹ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ እናንተም ፡ ኹላችኹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ቀርባችኹ ፦ ምድሪቱን ፡ እንዲጐበኙልንና ፡ እንወጣበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባንን ፡ የመንገዱንና ፡ የምንገባባቸውን ፡ የእነዚያን ፡ ከተማዎች ፡ ወሬ ፡ ተመልሰው ፡ እንዲነግሩን ፡ በፊታችን ፡ ሰዎች ፡ እንስደድ ፡ አላችኹኝ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ያም ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አሠኘኝ ፤ ከእናንተም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰው ፡ መረጥኹ ፤ ከየነገዱ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ኼዱም ፥ ወደ ፡ ተራራማውም ፡ ወጡ ፥ ወደኤሽኮልም ፡ ሸለቆ ፡ መጥተው ፡ ጐበኟት ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ከምድሪቱም ፡ ፍሬ ፡ በእጃቸው ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ እኛም ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፦ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጠን ፡ ምድር ፡ መልካም ፡ ናት ፡ ብለውም ፡ አወሩልን ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ዐመፃችኹ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ መውጣትን ፡ እንቢ ፡ አላችኹ ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ በድንኳናችኹም ፡ ውስጥ ፡ እንዲሀ ፡ እያላችኹ ፡ አጕረመረማችኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ጠላን ፥ እንዲያጠፋን ፡ በአሞራውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣን ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ ወዴት ፡ እንወጣለን ፧ ሕዝቡ ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ ቁመቱም ፡ ከእኛ ፡ ይረዝማል ፥ ከተማዎቹም ፡ ታላላቆች ፡ የተመሸጉም ፡ እስከ ፡ ሰማይም ፡ የደረሱ ፡ ናቸው ፥ የዔናቅንም ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ አየናቸው ፡ ብለው ፡ ወንድሞቻችን ፡ ልባችንን ፡ አስፈሩት ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ እኔም ፡ አልኋችኹ ፦ አትደንግጡ ፥ ከነርሱም ፡ አትፍሩ ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ በፊታችኹ ፡ የሚኼደው ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፥ እናንተ ፡ ስታዩ ፡ በግብጽና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳደረገላችኹ ፡ ኹሉ ፥ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይዋጋል ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እስክትመጡ ፡ ድረስ ፡ በኼዳችኹበት ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፥ ሰው ፡ ልጁን ፡ እንዲሸከም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተሸከመኽ ፡ አንተ ፡ አይተኻል ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ 33 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለሰፈራችኹ ፡ የሚገባውን ፡ ስፍራ ፡ እንዲፈልግላችኹ ፥ ትኼዱበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባውንም ፡ መንገድ ፡ እንዲያሳያችኹ ፡ ሌሊት ፡ በእሳት ፥ ቀን ፡ በደመና ፡ በፊታችኹ ፡ በመንገድ ፡ ሲኼድ ፡ የነበረውን ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አላመናችኹም ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 34 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የቃላችኹን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ ተቈጣ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 35 ፤ ለአባቶቻችኹ ፡ እሰጣት ፡ ዘንድ ፡ የማልኹላቸውን ፡ መልካሚቱን ፡ ምድር ፡ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ክፉ ፡ ትውልድ ፡ ማንም ፡ አያይም ፥

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 36 ፤ ከዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ከካሌብ ፡ በቀር ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ያያታል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ ተከትሏልና ፥ የረገጣትን ፡ ምድር ፡ ለርሱ ፡ ለልጆቹም ፡ እሰጣለኹ ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ በእኔ ፡ ተቈጣ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ወደዚያ ፡ አትገባም ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 38 ፤ በፊትኽ ፡ የሚቆም ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ርሱ ፡ ወደዚያ ፡ ይገባል ፤ ርሱ ፡ ለእስራኤል ፡ ምድሪቱን ፡ ያወርሳልና ፥ አደፋፍረው ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 39 ፤ ደግሞ ፦ ለምርኮ ፡ ይኾናሉ ፡ ያላችኋቸው ፡ ሕፃናታችኹ ፥ ዛሬም ፡ መልካሙን ፡ ከክፉ ፡ መለየት ፡ የማይችሉ ፡ ልጆቻችኹ ፥ እነርሱ ፡ ወደዚያ ፡ ይገባሉ ፥ ምድሪቱንም ፡ ለእነርሱ ፡ እሰጣለኹ ፥ ይወርሷታልም ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 40 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ተመልሳችኹ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኺዱ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 41 ፤ እናንተም ፦ እግዚአብሔርን ፡ በድለናል ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘን ፡ ኹሉ ፡ እንወጣለን ፥ እንዋጋማለን ፡ ብላችኹ ፡ መለሳችኹልኝ ። ከእናንተም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ ያዘ ፥ ወደ ፡ ተራራማውም ፡ አገር ፡ መውጣትን ፡ አቀለላችኹት ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 42 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እኔ ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ አይደለኹምና ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ፊት ፡ እንዳትወድቁ ፡ አትውጡ ፥ አትዋጉም ፡ በላቸው ፡ አለኝ ። እኔም ፡ ተናገርኋችኹ ፤

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 43 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ዐመፃችኹ ፡ እንጂ ፡ አልሰማችኹም ፤ በትዕቢታችኹም ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ አገር ፡ ወጣችኹ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 44 ፤ በዚያም ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ይኖሩ ፡ የነበር ፡ አሞራውያን ፡ ወጥተው ፡ ተጋጠሟችኹ ፥ ንብ ፡ እንደምታሳድድም ፡ አሳደዷችኹ ፥ እስከ ፡ ሔርማም ፡ ድረስ ፡ በሴይር ፡ መቷችኹ ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 45 ፤ ተመልሳችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አለቀሳችኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ድምፃችኹን ፡ አልሰማም ፥ ወደ ፡ እናንተም ፡ አላዳመጠም ።

ዘዳ. ፡ 1 ፡ 46 ፤ እንደተቀመጣችኹበትም ፡ ዘመን ፡ መጠን ፡ በቃዴስ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጣችኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳለኝ ፡ ተመልሰን ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡

ኼድን ፤ የሴይርንም ፡ ተራራ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ዞርን ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ይህን ፡ ተራራ ፡ መዞር ፡ ይበቃችኋል ፤ ተመልሳችኹ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ኺዱ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ሕዝቡንም ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ በሴይር ፡ ላይ ፡ በተቀመጡት ፡ በወንድሞቻችኹ ፡ በዔሳው ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ ታልፋላችኹ ፥ እነርሱም ፡ ይፈሯችኋል ፤ እንግዲህ ፡ እጅግ ፡ ተጠንቀቁ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የሴይርን ፡ ተራራ ፡ ለዔሳው ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ስለ ፡ ሰጠኹ ፡ እኔ ፡ ከምድራቸው ፡ የጫማ ፡ መርገጫ ፡ ታኽል ፡ እንኳ ፡ አልሰጣችኹምና ፡ አትጣሏቸው ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ከነርሱ ፡ በገንዘብ ፡ ምግብ ፡ ገዝታችኹ ፡ ትበላላችኹ ፤ ውሃም ፡ ደግሞ ፡ በገንዘብ ፡ ገዝታችኹ ፡ ትጠጣላችኹ ። ብ ፡ ገዝታችኹ ፡ ትጠጣላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእጅኽን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ባርኮልኻልና ፤ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መኼድኽን ፡ ዐውቋል ፤ በዚህ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ አንዳችም ፡ አላጣኽም ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በሴይርም ፡ ከተቀመጡት ፡ ከወንድሞቻችን ፡ ከዔሳው ፡ ልጆች ፡ በዐረባ ፡ መንገድ ፡ ከኤላትና ፡ ከዔጽዮንጋብር ፡ ዐለፍን ። ተመልሰንም ፡ በሞዐብ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ ዐለፍን ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለኝ ፦ እኔ ፡ ዔርን ፡ ለሎጥ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ስለ ፡ ሰጠኹ ፡ ከምድሩ ፡ ርስት ፡ አልሰጣችኹምና ፡ ሞዐብን ፡ አትጣላ ፡ በሰልፍም ፡ አትውጋቸው ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ አስቀድሞ ፡ ታላቅና ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ዔናቅም ፡ ልጆች ፡ በቁመት ፡ የረዘሙ ፡ ኤሚማውያን ፡ በዚያ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ዔናቅ ፡ ልጆች ፡ ራፋይም ፡ ይባሉ ፡ ነበር ፤ ሞዐባውያን ፡ ግን ፡ ኤሚም ፡ ይሏቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ሖራውያንም ፡ ደግሞ ፡ አስቀድሞ ፡ በሴይር ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፥ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ አሳደዷቸው ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሰጠው ፡ በርስቱ ፡ ምድር ፡ እስራኤል ፡ እንዳደረገ ፥ ከፊታቸው ፡ አጠፏቸው ፥ በስፍራቸውም ፡ ተቀመጡ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ተነሡ ፡ የዘሬድንም ፡ ፈፋ ፡ ተሻገሩ ፡ አለ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የዘሬድንም ፡ ፈፋ ፡ ተሻገርን ። የዘሬድንም ፡ ፈፋ ፡ እስከተሻገርንበት ፡ ድረስ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማለባቸው ፡ የሰልፈኞች ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ከሰፈሩ ፡ መካከል ፡ እስከጠፉ ፡ ድረስ ፥ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ የተጓዝንበት ፡ ዘመን ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ኾነ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ከሰፈርም ፡ መካከል ፡ ተቈርጠው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በላያቸው ፡ ነበረ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሰልፈኞቹ ፡ ከጠፉ ፡ ከሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፥

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ አንተ ፡ ዛሬ ፡ የሞዐብን ፡ ዳርቻ ፡ ዔርን ፡ ታልፋለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ለሎጥም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ስለ ፡ ሰጠኹ ፡ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አልሰጥኽምና ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ አቅራቢያ ፡ ስትደርስ ፡ አትጣላቸው ፡ አትውጋቸውም ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ያም ፡ ደግሞ ፡ የራፋይም ፡ ምድር ፡ ተብሎ ፡ ተቈጠረ ፤ ራፋይምም ፡ አስቀድሞ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ አሞናውያን ፡ ግን ፡ ዘምዙማውያን ፡ ብለው ፡ ይጠሯቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ታላቅና ፡ ብዙም ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ዔናቅም ፡ ልጆች ፡ ቁመታቸው ፡ የረዘመ ፡ ነበሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከፊታቸው ፡ አጠፋቸው ፤ እነርሱንም ፡ አሳደው ፡ በስፍራቸው ፡ ተቀመጡ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ሖራውያንን ፡ ከፊታቸው ፡ አጥፍቶ ፡ በሴይር ፡ ለተቀመጡት ፡ ለዔሳው ፡ ልጆች ፡ እንዳደረገ ፡ እንዲሁ ፡ ለእነርሱ ፡ አደረገ ፤ እነርሱንም ፡ አሳደው ፡ በስፍራቸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ እስከ ፡ ጋዛም ፡ ድረስ ፡ በመንደሮች ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩትን ፡ ኤዋውያንን ፡ ከከፍቶር ፡ የወጡ ፡ ከፍቶራውያን ፡ አጠፏቸው ፥ በስፍራቸውም ፡ ተቀመጡ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ደግሞም ፡ አለ ፦ ተነሥታችኹ ፡ ኺዱ ፥ የአርኖንንም ፡ ሸለቆ ፡ ተሻገሩ ፤ እንሆ ፥ አሞራዊውን ፡ የሐሴቦንን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፡ ምድሩንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤ ርሷን ፡ በመውረስ ፡ ዝምር ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ማስደንገጥኽንና ፡ ማስፈራትኽን ፡ እሰድ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እዝምራለኹ ፤ ወሬኽን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በፊትኽ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፥ ድንጋጤም ፡ ይይዛቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ከቅዴሞትም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የሰላምን ፡ ቃል ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ ወደሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሴዎን ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላክኹ ። በአገርኽ ፡ ላይ ፡ ልለፍ ፤

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ በአውራ ፡ ጐዳና ፡ እኼዳለኹ ፥ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አልተላለፍም ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ 29 ፤ የምበላውን ፡ ምግብ ፡ በገንዘብ ፡ ሽጥልኝ ፥ የምጠጣውንም ፡ ውሃ ፡ በገንዘብ ፡ ስጠኝ ፤ በሴይር ፡ የተቀመጡ ፡ የዔሳው ፡ ልጆች ፡ በዔርም ፡ የተቀመጡ ፡ ሞዐባውያን ፡ እንዳደረጉልኝ ፥ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጠን ፡ ምድር ፡ ዮርዳኖስን ፡ እስክሻገር ፡ ድረስ ፡ ብቻ ፡ በእግሬ ፡ ልለፍ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ የሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎን ፡ ግን ፡ ያሳልፈን ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደም ፤ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሱን ፡ አደንድኖታልና ፥ ልቡንም ፡ አጽንቶታልና ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሴዎንንና ፡ ምድሩን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ መስጠት ፥ እንሆ ፥ ዝምርኹ ፤ ምድሩን ፡ ትገዛት ፡ ዘንድ ፡ መውረስ ፡ ዝምር ፡ አለኝ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ ሴዎንም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ሊ.ጋጠሙን ፡ ወደ ፡ ያሀጽ ፡ ወጡ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 33 ፤ አምላካችንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠን ፤ ርሱንም ፡ ልጆቹንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ መታን ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 34 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከተማዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ወሰድን ፡ የተቀመጡባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሴቶችንም ፡ ሕፃናትንም ፡ አጠፋን ፤ አንዳችም ፡ አላስቀረንም ፥

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 35 ፤ ከብቶቻቸውንና ፡ ከከተማዎቻቸው ፡ ያገኘነውን ፡ ብዝበዛ ፡ ለራሳችን ፡ ወሰድን ፡ እንጂ ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 36 ፤ በአርኖን ፡ ቈላ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፡ ከሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ ካለችው ፡ ከተማ ፡ ዝምረን ፡ እስከ ፡ ገለዓድ ፡ ድረስ ፡ ማናቸዉቱም ፡ ከተማ ፡ አልጠነከረችብንም ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹሉን ፡

አሳልፎ ፡ ሰጠን ።

ዘዳ. ፡ 2 ፡ 37 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደከለከለን ፡ ኹሉ ፥ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ በያቦቅም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ በተራራማውም ፡ አገር ፡ ወዳሉት ፡ ከተማዎች ፡ አልደረስንም ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ተመልሰን ፡ በባሳን ፡ መንገድ ፡ ወጣን ፥ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በኤድራይ ፡ ሊዋጉን ፡ ወጡ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ርሱንና ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ምድሩንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹና ፡ አትፍራው ፤ በሐሴቦን ፡ ይኖር ፡ በነበረው ፡ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ ላይ ፡ እንዳደረግኽ ፡ በርሱም ፡ ታደርግበታለኽ ፡ አለኝ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ የባሳንን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግን ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠን ፤ እኛም ፡ መታነው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አምልጦ ፡ አልቀረለትም ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከተማዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ወሰድን ፤ አንድም ፡ ያልወሰድነው ፡ የለም ፤ በባሳን ፡ ያለውን ፡ የዐግን ፡ መንግሥት ፥ የአርጎብን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፥ ስድሳ ፡ ከተማዎችን ፡ ወሰድን ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ በቅጥር ፡ ካልተመሸጉት ፡ ከእጅግ ፡ ብዙ ፡ ከተማዎች ፡ ሌላ ፥ እነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ቁመቱ ፡ ረዥም ፡ በኾነ ፡ ቅጥር ፡ በመዝጊያና ፡ በመወርወሪያም ፡ የተመሸጉ ፡ ነበሩ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ በሐሴቦንም ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ እንዳደረግን ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋናቸው ፤ ከተማዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ከሕፃናትም ፡ ጋራ ፡ አጠፋናቸው ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ከብቶቹን ፡ ኹሉ ፡ የከተማዎቹንም ፡ ምርኮ ፡ ለእኛ ፡ በዘበዝን ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ከአርኖን ፡ ሸለቆ ፡ ዠምሮ ፡ እስከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ምድሪቱን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ከነበሩ ፡ ከኹለቱ ፡ ከአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ ወሰድን ፤

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ሲዶናውያን ፡ አርሞንዔምን ፡ ሢርዮን ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል ፥ አሞራውያንም ፡ ሳኔር ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ በሜዳውም ፡ ያሉትን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ ገለዓድንም ፡ ኹሉ ፥ በባሳንም ፡ ያሉትን ፡ የዐግን ፡ መንግሥት ፡ ከተማዎች ፡ እስከ ፡ ሰልካና ፡ እስከ ፡ ኤድራይ ፡ ድረስ ፡ ባሳንን ፡ ኹሉ ፡ ወሰድን ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ከራፋይም ፡ ወገን ፡ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግ ፡ ብቻውን ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ፤ እንሆ ፥ ዐልጋው ፡ የብረት ፡ ዐልጋ ፡ ነበረ ፤ ርሱ ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ በነበረባት ፡ አለ ፤ ርዝመቱ ፡ ዘጠኝ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ በሰው ፡ ክንድ ፡ ልክ ፡ ነበረ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ይህችንም ፡ ምድር ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ወረስን ፤ በአርኖንም ፡ ሸለቆ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፡ ዠምሮ ፡ የገለዓድን ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ እኩሌታ ፡ ከተማዎቹንም ፡ ለሮቤልና ፡ ለጋድ ፡ ነገድ ፡ ሰጠኋቸው ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ከገለዓድም ፡ የቀረውን ፡ የዐግንም ፡ መንግሥት ፡ ባሳንን ፡ ኹሉ ፥ የአርጎብንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ሰጠኹ ፤ ያችም ፡ ባሳን ፡ ኹሉ ፡ የራፋይም ፡ አገር ፡ ተብላ ፡ ተቈጠረች ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ ኢያዕር ፡ እስከ ፡ ጌሹራውያንና ፡ እስከማዕካታውያን ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ የአርጎብን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፤ ይህችንም ፡ የባሳንን ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በስሙ ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡ ብሎ ፡

ጠራ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ለማኪርም ፡ ገልዓድን ፡ ሰጠኹት ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ለሮቤል ፡ ነገድና ፡ ለጋድም ፡ ነገድ ፡ ከገለዓድ ፡ ዠምሮ ፡ እስከአርኖን ፡ ሸለቆ ፡ ድረስ ፡ የሸለቆውን ፡ እኩሌታ ፡ ዳርቻውንም ፥ እስከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ እስከያቦቅ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፥

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ከኪኔሬት ፡ እስከዐረባ ፡ ባሕር ፡ ርሱም ፡ የጨው ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ ዐረባ ፡ ዮርዳኖስንም ፡ ዳሩንም ፡ ሰጠኋቸው ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ አዘዝኋችኹ ። አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቷችኋል ፤ መሣሪያችኹን ፡ ይዛችኹ ፡ እናንተ ፡ ዐርበኞች ፡ ኹሉ ፡ በወንድሞቻችኹ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ትሻገራላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅግ ፡ ከብቶች ፡ እንዳሏችኹ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ሴቶቻችኹና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ከብቶቻችኹም ፡ በሰጠኋችኹ ፡ ከተማዎች ፡ ይቀመጣሉ ፤

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ይኸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡ እንዳሳረፈ ፥ ወንድሞቻችኹን ፡ እስኪያሳርፍ ፡ ድረስ ፡ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ምድር ፡ እስኪወርሱ ፡ ድረስ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ወደሰጠኋችኹ ፡ ርስት ፡ ትመለሳላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱን ፦ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ በኹለቱ ፡ ነገሥት ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ ዐይኖችኽ ፡ አይተዋል ፤ እንዲሁ ፡ በምታልፍባቸው ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደርጋል ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይዋጋልና ፥ አትፍራቸውም ፡ ብዬ ፡ አዘዝኹት ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ለመንኹ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ታላቅነትኽን ፡ የጸናችውንም ፡ እጅኽን ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ ማሳየት ፡ ዠምረኻል ፤ በሰማይና ፡ በምድርም ፡ እንደ ፡ ሥራኽ ፡ እንደ ፡ ኀይልኽም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ እኔ ፡ ልሻገር ፡ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ያለችውን ፡ መልካሚቱን ፡ ምድር ፡ ያንም ፡ መልካሙን ፡ ተራራማውን ፡ አገር ፡ ሊባኖስንም ፡ ልይ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ተቈጣኝ ፡ አልሰማኝምም ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለኝ ፦ ይበቃኻል ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ ደግመኽ ፡ አትናገረኝ ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ አትሻገርምና ፡ ወደፈስጋ ፡ ራስ ፡ ውጣ ፤ ዐይንኽንም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ አንሥተኽ ፡ በዐይንኽ ፡ ተመልከት ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ኢያሱ ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ይሻገራልና ፥ አንተም ፡ የምታያትን ፡ ምድር ፡ ርሱ ፡ ያወርሳቸዋልና ፥ ኢያሱን ፡ እዘዘው ፥ አደፋፍረውም ፥ አጽናውም ።

ዘዳ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ በቤተ ፡ ፌጎርም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጥን ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ አኹንም ፥ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እንድታደርጓቸው ፡ በሕይወትም ፡ እንድትኖሩ ፥ የአባቶቻችኹም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ ገብታችኹ ፡ እንድትወርሱ ፥ የማስተምራችኹን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ስሙ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ያዘዝኋችኹን ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ትጠብቃላችኹ ፡ እንጂ ፡ ባዘዝኋችኹ ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ አትጨምሩም ፥ ከርሱም ፡ አታጐድሉም ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ብዔልፌጎርን ፡ የተከተሉትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመካከላችኹ ፡ እንዳጠፋ ፥ እግዚአብሔር ፡ በብዔልፌጎር ፡ ያደረገውን ፡ ዐይኖቻችኹ ፡ አይተዋል ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተከተላችኹ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ኹላችኹ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ እናንተ ፡ ገብታችኹ ፡ በምትወርሷት ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ እንዲህ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ሥርዐትንና ፡ ፍርድን ፡ አስተማርኋችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ጠብቋት ፡ አድርጓትም ፤ ይህችን ፡ ሥርዐት ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ። በእውነት ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ጠቢብና ፡ አስተዋይ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፡ በሚሉ ፡ በአሕዛብ ፡ ፊት ፡ ጥበባችኹና ፡ ማስተዋላችኹ ፡ ይህ ፡ ነውና ፤

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በምንጠራው ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ እንደሚቀርበን ፥ አምላኩ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የቀረበው ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ ዛሬ ፡ እንደማኖራት ፡ እንደዚች ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ጽድቅ ፡ የኾነች ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ 10 ፤ እግዚአብሔር ፦ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ሰብስብ ፥ በምድርም ፡ በሕይወት ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ እኔን ፡ መፍራት ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፥ ልጆቻቸውንም ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ቃሌን ፡ አሰማቸዋለኹ ፡ ብሎ ፡ በተናገረኝ ፡ ጊዜ ፥ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በኮሬብ ፡ በቆምኽበት ፡ ቀን ፡ ዐይኖችኽ ፡ ያዩትን ፡ ነገር ፡ እንዳትረሳ ፥ በሕይወትኽም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ከልብኽ ፡ እንዳይወድቅ ፡ ተጠንቀቅ ፥ ነፍስኽንም ፡ በትጋት ፡ ጠብቅ ፤ ለልጆችኽም ፡ ለልጅ ፡ ልጆችኽም ፡ አስታውቀው ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እናንተም ፡ ቀርባችኹ ፡ ከተራራው ፡ በታች ፡ ቆማችኹ ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ሰማይም ፡ መካከል ፡ ድረስ ፡ እሳት ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ይነድ ፡ ነበር ፤ ጨለማና ፡ ደመና ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማም ፡ ነበረ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ተናገራችኹ ፤ የቃልን ፡ ድምፅ ፡ ሰማችኹ ፥ መልክ ፡ ግን ፡ አላያችኹም ፤ ድምፅን ፡ ብቻ ፡ ሰማችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ታደርጉትም ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛችኹን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ዐሥሩን ፡ ቃላት ፡ ነገራችኹ ፤ በኹለቱም ፡ በድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ላይ ፡ ጻፋቸው ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ትወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ተሻግራችኹ ፡ በምትገቡባት ፡ ምድር ፡ የምታደርጓትን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ አስተምራችኹ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አዘዘኝ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔር ፡ በኮሬብ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ በተናገራችኹ ፡ ጊዜ ፡ መልክ ፡ ከቶ ፡ አላያችኹምና ፡ እጅግ ፡ ተጠንቀቁ ፤

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ እንዳትረክሱ ፥ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ የማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ምሳሌ ፥ በወንድ ፡ ወይም ፡ በሴት ፡ መልክ ፡ የተሠራውን ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የእንስሳን ፡ ዅሉ ፡ ምሳሌ ፥ በሰማይም ፡ በታች ፡ የሚበሪውን ፡ የወፍን ፡ ዅሉ ፡ ምሳሌ ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚሽከረከረውን ፡ ዅሉ ፡ ምሳሌ ፥ ከምድርም ፡ በታች ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖረውን ፡ የዓሣን ፡ ዅሉ ፡ ምሳሌ ፡ እንዳታደርጉ ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ዐይኖችኽን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሥተኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ዅሉ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ የሰጣቸውን ፡ ፀሐይንና ፡ ጨረቃን ፡ ከዋክብትንና ፡ የሰማይን ፡ ሰራዊት ፡ ዅሉ ፡ ባየኽ ፡ ጊዜ ፥ ሰግደኽላቸው ፡ አምልከኻቸውም ፡ እንዳትስት ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ እናንተን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዅሉ ፡ የርስቱ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑለት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወስዶ ፡ ከብረት ፡ እቶን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ተቈጣኝ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ እንዳልሻገር ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ወደ ፡ መልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እንዳልገባ ፡ ማለ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ እሞታለኹ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ አልሻገርም ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ትሻገራላችኹ ፥ ያችንም ፡ መልካሚቱን ፡ ምድር ፡ ትወርሳላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የተማማለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳትረሱ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ የከለከለውን ፡ በማናቸውም ፡ ቅርጽ ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ እንዳታደርጉ ፡ ተጠንቀቁ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፡ ቀናተኛም ፡ አምላክ ፡ ነውና ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ልጆችን ፡ የልጅ ፡ ልጆችንም ፥ በወለዳችኹ ፡ ጊዜ ፡ በምድሪቱም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በተቀመጣችኹ ፡ ጊዜ ፥ በረከሳችኹም ፡ ጊዜ ፥ በማናቸውም ፡ ቅርጽ ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ባደረጋችኹ ፡ ጊዜ ፥ ታስቈጡትም ፡ ዘንድ ፡ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ በሠራችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ትወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግራችኹ ፡ ከምትገቡባት ፡ ምድር ፡ ፈጥናችኹ ፡ እንድትጠፉ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በእናንተ ፡ አስመሰክራለኹ ፤ ፈጽሞም ፡ ትጠፋላችኹ ፡ እንጂ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ አትቀመጡባትም ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይበትናችኋል ፥ እግዚአብሔር ፡ በውስጣቸው ፡ በሚያኖራችኹ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከልም ፡ ጥቂቶች ፡ ኾናችኹ ፡ ትቀራላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ በዚያም ፡ የማያዩትን ፡ የማይሰሙትንም ፡ የማይበሉትንም ፡ የማያሸቱትንም ፥ በሰው ፡ እጅ ፡ ከዕንጨትና ፡ ከድንጋይ ፡ የተሠሩትን ፡ አማልክት ፡ ታመልካላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትሻላችኹ ፤ በልብኽም ፡ ዅሉ ፡ በነፍስኽም ፡ ዅሉ ፡ የፈለግኸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታገኘዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ይህም ፡ ዅሉ ፡ በደረሰብኽ ፡ ጊዜ ፥ ስትጨነቅ ፥ በዘመኑ ፡ ፍጻሜ ፡ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትመለሳለኽ ፥ ቃሉንም ፡ ትሰማለኽ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐሪ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ አይተውኽም ፥ አያጠፋኽምም ፥ ለአባቶችኽም ፡ የማለላቸውን ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ አይረሳም ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከፈጠረው ፡ ዠምሮ ፥ ከሰማይ ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳርቻዋ ፡

ድረስ ፡ ከቶ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ተሰምቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ የነበረውን ፡ የቀደመውን ፡ ዘመን ፡ ጠይቅ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 33 ፤ አንተ ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ሲናገር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ሰማኽ ፥ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ሰምቶ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራልን ፧

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 34 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ በግብጽ ፡ ለእናንተ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ ኹሉ ፥ በፈተናና ፡ በተአምራት ፥ በድንቅና ፡ በሰልፍ ፥ በጸናች ፡ እጅና ፡ በተዘረጋ ፡ ክንድ ፡ በታላቅም ፡ ማስፈራት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሌላ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ገብቶ ፡ ለርሱ ፡ ሕዝብን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ሞክሮ ፡ ነበርን ፧

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ለአንተ ፡ ተገለጠ ፤ ከርሱም ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 36 ፤ ያስተምርኽ ፡ ዘንድ ፡ ከሰማይ ፡ ድምፁን ፡ አሰማኽ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ታላቁን ፡ እሳት ፡ አሳየኽ ፤ ከእሳትም ፡ ውስጥ ፡ ቃሉን ፡ ሰማኽ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 37 ፤ 38 ፤ አባቶችኽን ፡ ወዷልና ፥ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ዘራቸውን ፡ መረጠ ፥ ዛሬ ፡ እንደ ኾነው ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ የጸኑትን ፡ ታላላቆችን ፡ አሕዛብ ፡ በፊትኽ ፡ እንዲያወጣ ፥ አንተንም ፡ እንዲያገባኽ ፥ ምድራቸውንም ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ እንዲሰጥኽ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ በታላቅ ፡ ኀይሉ ፡ ከግብጽ ፡ አወጣኽ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 39 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሌላም ፡ እንደሌለ ፡ ዛሬ ፡ ዕወቅ ፥ በልብኽም ፡ ያዝ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 40 ፤ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችኽ ፡ መልካም ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ዕድሜኽ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ የማዝኽን ፡ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 41 ፤ 42 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ትናንት ፡ ከትናንት ፡ በስቲያም ፡ ጠላቱ ፡ ያልኾነውን ፡ ባልንጀራውን ፡ ሳያውቅ ፡ የገደለ ፡ ገዳዩ ፡ ይሸሽባቸው ፡ ዘንድ ፥ ከነዚህም ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ሸሽቶ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ለየ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 43 ፤ ከተማዎቹም ፡ ለሮቤል ፡ ነገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በደልዳላ ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ ቦሶር [103] ፥ ለጋድም ፡ ነገድ ፡ በገለዓድ ፡ ያለ ፡ ራሞት ፥ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ በባሳን ፡ ያለ ፡ ጎላን ፡ ነበሩ ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 44 ፤ ሙሴም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ያኖራት ፡ ሕግ ፡ ይህች ፡ ናት ፤

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 45 ፤ 46 ፤ ሙሴና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በመቱት ፥ በሐሴቦን ፡ ተቀምጦ ፡ በነበረው ፡ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ ምድር ፥ በቤተ ፡ ፌጎር ፡ አንጻር ፡ ባለው ፡ ሸለቆ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፥ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተናገረው ፡ ምስክርና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 47 ፤ የርሱንና ፡ የባሳንን ፡ ንጉሥ ፡ የዐግን ፡ ምድር ፥ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ የነበሩትን ፡ የኹለቱን ፡ የአሞራውያንን ፡ ነገሥታት ፡ ምድር ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 48 ፤ በአርኖን ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፡ ዠምሮ ፡ እስከሲዎን ፡ ተራራ ፡ እስከ ፡ አርሞንዔም ፡ ድረስ ፥

ዘዳ. ፡ 4 ፡ 49 ፤ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ዐረባ ፡ ኹሉ ፡ እስከዐረባ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ወሰዱ ።

---

103 ዕብ. ፥ በጸር ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 1 ፤ ሙሴም ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ጠርቶ ፡ አላቸው ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እንድትማሯት ፡ በማድረግም ፡ እንድትጠብቋት ፡ ዛሬ ፡ በጐሯችኹ ፡ የምናገራትን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ስሙ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 2 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኮሬብ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ በሕይወት ፡ ካለነው ፡ ከእኛ ፡ ከኹላችን ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ይህችን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አላደረገም ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ በተራራው ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተናገራችኹ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ እኔ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እነግራችኹ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ቆሜ ፡ ነበር ፤ እናንተ ፡ በእሳቱ ፡ ምክንያት ፡ ፈርታችኋልና ፥ ወደ ፡ ተራራውም ፡ አልወጣችኹምና ። ርሱም ፡ አለ ፦

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣኹኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ አይኹኑልኽ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፥ በታችም ፡ በምድር ፡ ካለው ፥ ከምድርም ፡ በታች ፡ በውሃ ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ የማናቸውንም ፡ ምሳሌ ፡ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ለአንተ ፡ አታድርግ ፤

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ 10 ፤ በሚጠሉኝ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛና ፡ እስከ ፡ አራተኛ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ የአባቶችን ፡ ኀጢአት ፡ በልጆች ፡ ላይ ፡ የማመጣ ፤ ለሚወዱኝ ፡ ትእዛዜንም ፡ ለሚጠብቁ ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ምሕረትን ፡ የማደርግ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፡ አትስገድላቸው ፥ አታምልካቸውም ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ የአምላክኽን ፡ ስም ፡ በከንቱ ፡ አትጥራ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ በከንቱ ፡ የሚጠራውን ፡ ከበደል ፡ አያነጻውምና ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ እንዳዘዘኽ ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ትቀድሰው ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 13 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ ተግባርኽንም ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ፥

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 14 ፤ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ሰንበት ፡ ነው ፤ አንተ ፡ እንደምታርፍ ፡ ሎሌኽና ፡ ገረድኽ ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ፥ አንተ ፡ ወንድ ፡ ልጅኽም ፡ ሴት ፡ ልጅኽም ፡ ሎሌኽም ፡ ገረድኽም ፡ በሬኽም ፡ አህያኽም ፡ ከብትኽም ፡ ኹሉ ፡ በደጆችኽም ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ እንግዳ ፡ በርሱ ፡ ምንም ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 15 ፤ አንተም ፡ በግብጽ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኽ ፡ ዐስብ ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ በጸናች ፡ እጅና ፡ በተዘረጋ ፡ ክንድ ፡ ከዚያ ፡ አወጣኽ ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘኽ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ እንዳዘዘኽ ፡ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ዕድሜኽ ፡ እንዲረዝም ፥ መልካምም ፡ እንዲኾንልኽ ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 17 ፤ አትግደል ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 18 ፤ አታመንዝር ።

ዘዳ. ፥ 5 ፥ 19 ፤ አትስረቅ ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ በባልንጀራኽ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ አትመስክር ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ የባልንጀራኽን ፡ ሚስት ፡ አትመኝ ፤ የባልንጀራኽንም ፡ ቤት ፡ ዕርሻውንም ፡ ሎሌውንም ፡ ገረዱንም ፡ በሬውንም ፡ አህያውንም ፥ ከባልንጀራኽ ፡ ገንዘብ ፡ ኹሉ ፡ ማናቸውንም ፡ አትመኝ ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ በእሳትና ፡ በደመናው ፡ በጨለማውም ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ለጉባኤያችኹ ፡ ኹሉ ፡ ተናገረ ፤ ምንም ፡ ምን ፡ አልጨመረም ። በኹለቱም ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ላይ ፡ ጻፋቸው ፥ ለኔም ፡ ሰጣቸው ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ተራራው ፡ በእሳት ፡ ሲነድ ፡ ከጨለማው ፡ ውስጥ ፡ ድምፁን ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፥ እናንተ ፥ የነገዶቻችኹ ፡ አለቃዎች ፡ ሽማግሌዎቻችኹም ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ቀረባችኹ ፤

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ አላችኹም ፦ እንሆ ፥ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብሩንና ፡ ታላቅነቱን ፡ አሳይቶናል ፥ ከእሳቱም ፡ ውስጥ ፡ ድምፁን ፡ ሰምተናል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፡ ሰውዮውም ፡ በሕይወት ፡ ሲኖር ፡ ዛሬ ፡ አይተናል ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ይህች ፡ ታላቂቱ ፡ እሳት ፡ ታቃጥለናለችና ፡ ለምን ፡ እንሞታለን ፧ እኛ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ ደግሞ ፡ ብንሰማ ፡ እንሞታለን ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ከሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ እኛ ፡ እንደ ፡ ሰማን ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ሲናገር ፡ የሕያው ፡ አምላክን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ በሕይወቱ ፡ የኖረ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ አንተ ፡ ቅረብ ፥ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚለውን ፡ ኹሉ ፡ ስማ ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለአንተ ፡ የሚናገረውን ፡ ኹሉ ፡ ለእኛ ፡ ንገረን ፤ እኛም ፡ ሰምተን ፡ እናደርገዋለን ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ በተናገራችኹኝም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእናንተን ፡ ቃል ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለኝ ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ የተናገሩኽን ፡ ቃል ፡ ድምፅ ፡ ሰምቻለኹ ፤ የተናገሩኽ ፡ ኹሉ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ለእነርሱም ፡ ለዘለዓለምም ፡ ለልጆቻቸው ፡ መልካም ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፥ እንዲፈሩኝ ፡ ኹልጊዜም ፡ ትእዛዜን ፡ ኹሉ ፡ እንዲጠብቁ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልብ ፡ ምነው ፡ በኾነላቸው! ፡

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ ኼደኽ ፦ ወደ ፡ ድንኳናችኹ ፡ ተመለሱ ፡ በላቸው ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ቁም ፥ ርስት ፡ አድርጌ ፡ በምሰጣቸውም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ያደርጓት ፡ ዘንድ ፡ የምታስተምራቸውን ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ፍርዴንም ፡ ኹሉ ፡ እነግርኻለኹ ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ እንዳዘዛችኹ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፤ ከርሱም ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ አትበሉ ።

ዘዳ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ በሕይወት ፡ እንድትኖሩ ፥ መልካምም ፡ እንዲኾንላችኹ ፥ በምትወርሷትም ፡ ምድር ፡ ዕድሜያችኹ ፡ እንዲረዝም ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ባዘዛችኹ ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኺዱ ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 1-2 ፤ አንተ ፡ ልጅኽም ፡ የልጅ ፡ ልጅኽም ፡ በዕድሜያችኹ ፡ ኹሉ ፡ ልትወርሷት ፡ በምትገቡባት ፡ ምድር ፡ ታደርጓት ፡ ዘንድ ፥ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈርተኽ ፡ እኔ ፡ ለአንተ ፡ ያዘዝኹትን ፡ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ኹሉ ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ ዕድሜኽም ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፥ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳስተምራችኹ ፡ ያዘዛት ፡ ትእዛዝና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድም ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እንግዲህ ፥ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ መልካምም ፡ እንዲኾንልኽ ፥ የአባቶችኽም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ በምታፈሰው ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ እንድትበዛ ፥ ታደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ አንተም ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስኽ ፡ በፍጹምም ፡ ኀይልኽ ፡ ውደድ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ አንተን ፡ የማዘውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በልብኽ ፡ ያዝ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ለልጆችኽም ፡ አስተምረው ፥ በቤትኽም ፡ ስትቀመጥ ፥ በመንገድም ፡ ስትኼድ ፥ ስትተኛም ፥ ስትነሣም ፡ ተጫወተው ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ በእጅኽም ፡ ምልክት ፡ አድርገኽ ፡ እሰረው ፤ በዐይኖችኽም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ክታብ ፡ ይኹንልኽ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ በቤትኽም ፡ መቃኖች ፡ በደጃፍኽም ፡ በሮች ፡ ላይ ፡ ጻፈው ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአንተ ፡ ሊሰጣት ፡ ለአባቶችኽ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ማለላቸው ፡ ምድር ፡ ባገባኽ ፡ ጊዜ ፤ ያልሠራኻቸውንም ፡ ታላቅና ፡ መልካም ፡ ከተማዎች ፥

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ያልሞላኻቸውንም ፡ ሀብትን ፡ የሞሉ ፡ ቤቶች ፥ ያልማስኻቸውንም ፡ የተማሱ ፡ ጕድጓዶች ፥ ያልተከልኻቸውንም ፡ ወይንና ፡ ወይራ ፡ በሰጠኽ ፡ ጊዜ ፥ በበላኽና ፡ በጠገብኽም ፡ ጊዜ ፤

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳትረሳ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ ፤ ርሱንም ፡ አምልክ ፤ በስሙም ፡ ማል ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 14-15 ፤ በመካከልኽ ፡ ያለው ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ የአምላክኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ እንዳይነድ ፡ ከምድርም ፡ ፊት ፡ እንዳያጠፋኽ ፥ በዙሪያችኹ ፡ ያሉት ፡ አሕዛብ ፡ የሚያመልኳቸውን ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ በማሣህ ፡ እንደ ፡ ፈተናችኹት ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተኑት ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ለእናንተ ፡ ያዘዘውን ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ምስክሩንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ አጥብቃችኹ ፡ ጠብቁ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 18-19 ፤ መልካምም ፡ ይኾንልኽ ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለአባቶችኽ ፡ ወደማለላቸው ፡ ወደመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ ገብተኽ ፡ ርሷን ፡ ትወርስ ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ጠላቶችኽን ፡ ኹሉ ፡ ከፊትኽ ፡ ያወጣልኽ ፡ ዘንድ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅኑንና ፡ መልካሙን ፡ አድርግ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ በኋለኛው ፡ ዘመንም ፡ ልጅኽ ፦ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዛችኹ ፡ ምስክርና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ በጠየቀኽ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ አንተ ፡ ልጅኽን ፡ በለው ፦ በግብጽ ፡ የፈርዖን ፡ ባሪያዎች ፡ ነበርን ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ ከግብጽ ፡ አወጣን ፤

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከግብጽና ፡ በፈርዖን ፡ በቤቱም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እኛ ፡ እያየን ፡ ታላቅና ፡ ክፉ ፡

ምልክት ፡ ተአምራትም ፡ አደረገ ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ለአባቶቻችን ፡ ወደማለላቸው ፡ ምድር ፡ አግብቶ ፡ ርሷን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ አወጣን ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ እንደ ፡ ዛሬም ፡ በሕይወት ፡ እንዲያኖረን ፥ ዅልጊዜም ፡ መልካም ፡ እንዲኾንልን ፥ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንፈራ ፡ ዘንድ ፥ ይህችንም ፡ ሥርዐት ፡ ዅሉ ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘዘን ።

ዘዳ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ እንዳዘዘን ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እናደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ዅሉ ፡ ብንጠብቅ ፡ ለእኛ ፡ ጽድቅ ፡ ይኾንልናል ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልትወርሳት ፡ ወደምትገባባት ፡ ምድር ፡ ባመጣኽ ፡ ጊዜ ፥ ከፊትኽም ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፥ ከአንተ ፡ የበለጡትን ፡ የበረቱትንም ፡ ሰባቱን ፡ አሕዛብ ፥ ኬጢያዊውን ፡ ጌርጌሳዊውንም ፡ አሞራዊውንም ፡ ከነዓናዊውንም ፡ ፌርዛዊውንም ፡ ዔዊያዊውንም ፡ ኢያቡሳዊውንም ፡ ባወጣ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ በሰጣቸው ፡ በመታኻቸውም ፡ ጊዜ ፥ ፈጽመኽ ፡ አጥፋቸው ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አታድርግ ፥ አትማራቸውም ፤

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ አትጋባ ፤ ሴት ፡ ልጅኽን ፡ ለወንድ ፡ ልጁ ፡ አትስጥ ፥ ሴት ፡ ልጁንም ፡ ለወንድ ፡ ልጅኽ ፡ አትውሰድ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እንዳይከተለኝ ፡ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ እንዲያመልክ ፡ ልጅኽን ፡ ያስታልና ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ይነድ፡ባችኋል ፥ ፈጥኖም ፡ ያጠፋችኋል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዲህ ፡ አድርጉባቸው ፤ መሠዊያቸውን ፡ አፍርሱ ፥ ሐውልቶቻቸውንም ፡ ሰባብሩ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቻቸውንም ፡ ቍረጡ ፥ የተቀረጸውን ፡ ምስላቸውንም ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽና ፤ በምድር ፡ ፊት ፡ ከሚኖሩ ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ለርሱ ፡ ለራሱ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾንለት ፡ ዘንድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጠኽ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የወደዳችኹና ፡ የመረጣችኹ ፡ ከአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ በቍጥር ፡ ስለ ፡ በዛችኹ ፡ አይደለም ፤ እናንተ ፡ ከአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ በቍጥር ፡ ጥቂቶች ፡ ነበራችኹና ፤

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ወደዳችኹ ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ የማለላቸውን ፡ መሐላ ፡ ስለ ፡ ጠበቀ ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ አወጣችኹ ፥ ከባርነትም ፡ ቤት ፡ ከግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ከፈርዖን ፡ እጅ ፡ አዳናችኹ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ አንተም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ለሚወዱትም ፡ ትእዛዙንም ፡ ለሚጠብቁ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑንና ፡ ምሕረቱን ፡ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ የሚጠብቅ ፡ የታመነ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቅ ፤

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ የሚጠሉትን ፡ ለማጥፋት ፡ በፊታቸው ፡ ብድራት ፡ ይመልስባቸዋል ፤ ለሚጠላው ፡ አይዘገይም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በፊቱ ፡ ብድራት ፡ ይመልስበታል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ ታደርጋት ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ለአንተ ፡ የማዛትን ፡ ትእዛዝና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድንም ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ይህችን ፡ ፍርድ ፡ ሰምተኽ ፡ ብትጠብቃት ፡ ብታደርጋትም ፥ አምላክኽ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለአባቶችኽ ፡ የማለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳንና ፡ ምሕረት ፡ ለአንተ ፡ ይጠብቅልኻል ፤

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ይወድ�longኽማል ፥ ይባርክኽማል ፥ ያበዛኽማል ፤ ይሰጥኽም ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶችኽ ፡ በማለላቸው ፡ ምድር ፡ የሆድኽን ፡ ፍሬ ፡ የመሬትኽንም ፡ ፍሬ ፥ እኽልኽን ፡ ወይንኽንም ፡ ዘይትኽንም ፥ የከብትኽንም ፡ ብዛት ፡ የበግኽንም ፡ መንጋ ፡ ይባርክልኻል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ከአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የተባረክኽ ፡ ትኾናለኽ ፤ በሰውኽና ፡ በከብትኽም ፡ ዘንድ ፡ ወንድ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ብትኾን ፡ መካን ፡ አይኾንብኽም ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሕማምን ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ያርቃል ፤ የምታውቀውንም ፡ ክፉውን ፡ የግብጽ ፡ በሽታ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አያደርስብኽም ፥ በጠላቶችኽም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያመጣባቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ የሚጥላቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ታጠፋቸዋለኽ ፤ ዐይንኽም ፡ አታዝንላቸውም ፤ ያም ፡ ወጥመድ ፡ ይኾንብኻልና ፥ አማልክታቸውን ፡ አታምልካቸው ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ በልብኽም ፦ እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ይበዛሉና ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ እችላለኹ ፧ ብትል ፥ አትፍራቸው ፤

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈርዖንና ፡ በግብጽ ፡ ኹሉ ፡ ያደረገውን ፥

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፥ ዐይንኽ ፡ እያየች ፥ ታላቅን ፡ መቅሠፍት ፡ ምልክትንም ፡ ተአምራትንም ፡ የጸናችውን ፡ እጅ ፡ የተዘረጋውንም ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ እንዳወጣኽ ፥ ዐስብ ፤ እንዲሁ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ በምትፈራቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ደግሞም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀሩት ፡ ከፊትኽም ፡ የተሸሸጉት ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ተርብ ፡ ይሰድባቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፥ ታላቅና ፡ የሚያስፈራ ፡ አምላክ ፥ በመካከልኽ ፡ ነውና ፥ ከነርሱ ፡ የተነሣ ፡ አትደንግጥ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂቱ ፡ ከፊትኽ ፡ ያወጣቸዋል ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ እንዳይበዙብኽ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እነርሱን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸዋል ፥ እስኪጠፉም ፡ ድረስ ፡ በታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ያስደነግጣቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ነገሥታታቸውንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸዋል ፥ ስማቸውንም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ታጠፋለኽ ፤ እስክታጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ በፊትኽ ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ የተቀረጸውንም ፡ የአምላኮቻቸውን ፡ ምስል ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለኽ ፤ የተሠራባቸውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አትመኝ ፤ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፥ እንዳትጠመድበት ፡ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አትውሰድ ።

ዘዳ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ እንደ ፡ ርሱም ፡ ርጉም ፡ እንዳትኾን ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ አታግባ ፤ ርጉም ፡ ነውና ፥ ተጸየፈው ፥ ጥላውም ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዘዳ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በሕይወት ፡ እንድትኖሩ ፥ እንድትበዙም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ወደማለላቸው ፡

ምድር ፡ ገብታችኹ ፡ እንድትወርሷት ፥ ዛሬ ፡ ለአንተ ፡ የማዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትንኽ ፡ ዘንድ ፥ በልብኽም ፡ ያለውን ፡ ትእዛዙን ፡ ትጠብቅ ፡ ወይም ፡ አትጠብቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፥ ሊያስጨንቅኽ ፡ በእነዚህ ፡ በአርባ ፡ ዓመታት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የመራኽን ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ዐስብ ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 3 ፤ ሰውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በሚወጣ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖር ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ በሕይወት ፡ እንዳይኖር ፡ ያስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፡ አስጨነቀኽ ፥ አስራበኽም ፥ አንተም ፡ ያላወቅኸውን ፡ አባቶችኽም ፡ ያላወቁትን ፡ መና ፡ አበላኽ ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 4 ፤ በእነዚህ ፡ አርባ ፡ ዓመታት ፡ የለበስኸው ፡ ልብስ ፡ አላረጀም ፥ እግርኽም ፡ አላበጠም ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 5 ፤ ሰውም ፡ ልጁን ፡ እንደሚገሥጽ ፡ እንዲሁም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ እንዲገሥጽ ፡ በልብኽ ፡ አስተውል ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 6 ፤ በመንገዱም ፡ እንድትኼድ ፡ ርሱንም ፡ እንድትፈራ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 7 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ምድር ፥ ከሸለቆና ፡ ከኰረብታ ፡ የሚመነጨ ፡ የውሃ ፡ ጅረቶችና ፡ ፈሳሾች ፡ ምንጮችም ፡ ወዳሉባት ፡ ምድር ፥

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 8 ፤ ስንዴ ፡ ገብስም ፡ ወይንም ፡ በለስም ፡ ሮማንም ፡ ወይራም ፡ ማርም ፡ ወደሞሉባት ፡ ምድር ፥

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ሳይጐድልኽ ፡ እንጀራን ፡ ወደምትበላባት ፡ አንዳችም ፡ ወደማታጣባት ፡ ምድር ፥ ድንጋይዋ ፡ ብረት ፡ ወደ ፡ ኾነ ፥ ከተራራዋም ፡ መዳብ ፡ ወደሚማስባት ፡ ምድር ፡ ያገባኻል ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 10 ፤ ትበላማለኽ ፥ ትጠግብማለኽ ፥ ስለሰጠኽም ፡ ስለመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትባርካለኽ ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 11 ፤ ዛሬ ፡ እኔ ፡ አንተን ፡ የማዘውን ፡ ትእዛዙንና ፡ ፍርዱን ፡ ሥርዐቱንም ፡ ባለመጠበቅ ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳትረሳ ፡ ተጠንቀቅ ፤

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ከበላኽና ፡ ከጠገብኽ ፡ በኋላ ፥ መልካምም ፡ ቤት ፡ ሠርተኽ ፡ ከተቀመጥኽበት ፡ በኋላ ፥

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ የላምና ፡ የበግ ፡ መንጋ ፡ ከበዛልኽ ፡ በኋላ ፥ ብርኽና ፡ ወርቅኽም ፡ ያለኽም ፡ ኹሉ ፡ ከበዛልኽ ፡ በኋላ ፥ ልብኽ ፡ እንዳይጓደድ ፤

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ያወጣኽን ፥

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 15 ፤ እባብና ፡ ጊንጥ ፡ ጥማትም ፡ ባለባት ፥ ውሃም ፡ በሌለባት ፥ በታላቂቱና ፡ በምታስፈራው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የመራኽን ፥ ከጭንጫ ፡ ድንጋይም ፡ ውሃን ፡ ያወጣልኽን ፥

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 16 ፤ በመጨረሻም ፡ ዘመን ፡ መልካም ፡ ያደርግልኽ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈትንኽ ፡ ሊያዋርድኽም ፡ አባቶችኽ ፡ ያላወቁትን ፡ መና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያበላኽን ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳትረሳ ፤

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 17 ፤ በልብኽም ፦ ጕልበቴ ፡ የእጄም ፡ ብርታት ፡ ይህን ፡ ሀብት ፡ አመጣልኝ ፡ እንዳትል ።

ዘዳ. ፥ 8 ፥ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለአባቶችኽ ፡ የማለውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፥ ሀብት ፡ ለማከማቸት ፡ ርሱ ፡ ጕልበት ፡ ሰጥቶኻልና ፥ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዐስብ ።

ዘዳ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ አምላክ፣ንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብትረሳ ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ብትከተል ፡ ብታመልካቸውም ፡ ብትሰግድላቸውም ፥ ፈጽሞ ፡ እንድትጠፉ ፡ እኔ ፡ ዛሬውኑ ፡ እመሰክርባችኋለኹ ።

ዘዳ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስላልሰማችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊታችኹ ፡ እንደሚያጠፋቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ትጠፋላችኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ ከአንተ ፡ የበለጡትንና ፡ የበረቱትን ፡ አሕዛብ ፥ እስከ ፡ ሰማይም ፡ ድረስ ፡ የተመሸጉትን ፡ ታላላቆች ፡ ከተማዎች ፡ ለመውረስ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ትሻገረዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ አንተም ፡ የምታውቃቸው ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፦ በዔናቅ ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ማን ፡ ይችላል ፧ ሲባል ፡ የሰማኸው ፡ ታላቁና ፡ ረዥሙ ፡ ሕዝብ ፡ የዔናቅ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ አምላክ፣ም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደሚበላ ፡ እሳት ፡ ኾኖ ፡ በፊትኽ ፡ እንዲያልፍ ፡ ዛሬ ፡ ዕወቅ ፤ ርሱ ፡ ያጠፋቸዋል ፥ በፊትኽም ፡ ያዋርዳቸዋል ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ነገረኽ ፡ አንተ ፡ ታሳድዳቸዋለኽ ፥ ፈጥነኽም ፡ ታጠፋቸዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ አምላክ፣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊትኽ ፡ ካወጣቸው ፡ በኋላ ፦ ስለ ፡ ጽድቄ ፡ እወርሳት ፡ ዘንድ ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ እግዚአብሔር ፡ አገባኝ ፡ ስትል ፡ በልብኽ ፡ አትናገር ፤ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊትኽ ፡ ያወጣቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ምድራቸውን ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ የምትገባው ፡ ስለ ፡ ጽድቅኽና ፡ ስለ ፡ ልብኽ ፡ ቅንነት ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክ፣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊትኽ ፡ በሚያጠፋቸው ፡ በእነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ ኀጢአት ፡ ምክንያትና ፡ ለአባቶችኽ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ የማለላቸውን ፡ ቃል ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ ነኽና ፥ አምላክ፣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ መልካም ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠኽ ፡ ስለ ፡ ጽድቅኽ ፡ እንዳይደለ ፡ ዕወቅ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ አምላክ፣ን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳስቈጣኸው ፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ከወጣኽበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ እስከመጣችኹ ፡ ድረስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንዳመፃችኹ ፡ ዐስብ ፥ አትርሳ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ በኮሬብ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣችኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሊያጠፋችኹ ፡ ተቈጣባችኹ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ የድንጋዩን ፡ ጽላቶች ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የተማማለባቸውን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጽላቶች ፥ እቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፥ በተራራው ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር ፤ እንጀራ ፡ አልበላኹም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣኹም ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ የተጻፉትን ፡ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ሰጠኝ ፤ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ በነበረበትም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ የነገራችኹ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ተጽፎባቸው ፡ ነበር ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ከአርባ ፡ ቀንና ፡ ከአርባ ፡ ሌሊትም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹለቱን ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፥ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ጽላቶች ፥ ሰጠኝ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ተነሥተኽ ፡ ከዚህ ፡ ፈጥነኽ ፡ ውረድ ፤ ከግብጽ ፡ ያወጣኻቸው ፡ ሕዝብኽ ፡ ረክሰዋል ፤ ፈጥነው ፡ ካዘዝኋቸው ፡ መንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ፥ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስልም ፡ ለራሳቸው ፡ አድርገዋል ፡ አለኝ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይቻለኹ ፤

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፥ ስማቸውንም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ እደመስስ ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ ፤ አንተንም ፡ ከነርሱ ፡ ለሚበረታና ፡ ለሚበዛ ፡ ሕዝብ ፡ አደርግኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ እኔም ፡ ተመልሼ ፡ ከተራራው ፡ ወረድኹ ፥ ተራራውም ፡ በእሳት ፡ ይነድ ፡ ነበር ፤ ኹለቱም ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ጽላቶች ፡ በኹለቱ ፡ እጆቼ ፡ ነበሩ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ተመለከትኹም ፤ እንሆ ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድላችኹ ፡ ነበር ፥ ለእናንተም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ የጥጃ ፡ ምስል ፡ ሠርታችኹ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔር ፡ ካዘዛችኹ ፡ መንገድ ፡ ፈጥናችኹ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላችኹ ፡ ነበር ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ኹለቱንም ፡ ጽላቶች ፡ ያዝኹ ፥ ከኹለቱም ፡ እጆቼ ፡ ጣልኋቸው ፥ እናንተም ፡ ስታዩ ፡ ሰበርኋቸው ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ 19 ፤ ስለሠራችኹት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፥ ርሱንም ፡ ለማስቈጣት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ስላደረጋችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሊያጠፋችኹ ፡ ከተቈጣባችኹ ፡ ከቀሥጣውና ፡ ከመዓቱ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ፈራኹ ፥ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ወደቅኹ ፤ እንጀራ ፡ አልበላኹም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣኹም ። እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሰማኝ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አሮንን ፡ ሊያጠፋው ፡ እጅግ ፡ ተቈጣው ፤ ስለ ፡ አሮንም ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጸለይኹ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ያደረጋችኹትንም ፡ ኀጢአት ፡ ጥጃውን ፡ ወሰድኹ ፥ በእሳትም ፡ አቃጠልኹት ፥ አደቀቅኹትም ፥ እንደ ፡ ትቢያም ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ፈጨኹት ፤ ትቢያውንም ፡ ከተራራ ፡ በሚወርድ ፡ ወንዝ ፡ ጣልኹት ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ በተቤራም ፣ በማሣህም ፣ በምኞት ፡ መቃብርም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣችኹት ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ውጡ ፥ የሰጠኋችኹንም ፡ ምድር ፡ ውረሱ ፡ ብሎ ፡ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በላካችኹ ፡ ጊዜ ፥ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዐመፃችኹ ፥ በርሱም ፡ አላመናችኹም ፥ ድምፁንም ፡ አልሰማችኹም ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ እናንተን ፡ ካወቅኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐመፀኞች ፡ ነበራችኹ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፦ አጠፋችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተናገረ ፡ በወደቅኹበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደቅኹ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ጸለይኹ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ በታላቅነትኽ ፡ የተቤዠኽውን ፥ በጠነከረችውም ፡ እጅ ፡ ከግብጽ ፡ ያወጣኽውን ፡ ሕዝብኽንና ፡ ርስትኽን ፡ አታጥፋ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ባሪያዎችኽን ፡ አብርሃምንና ፡ ይሥሐቅን ፣ ያዕቆብንም ፡ ዐስብ ፤ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ደንዳናነት ፣ ክፋቱንም ፣ ኀጢአቱንም ፡ አትመልከት ፤

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ከርሷ ፡ እኛን ፡ ያወጣኽባት ፡ ምድር ፡ ሰዎች ፦ እግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ወደሰጣቸው ፡ ምድር ፡ ያገባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለምና ፥ ጠልቷቸውማልና ፥ ስለዚህ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሊገድላቸው ፡ አወጣቸው ፡ እንዳይሉ ።

ዘዳ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ እነርሱም ፡ በታላቅ ፡ ኀይልኽ ፡ በተዘረጋውም ፡ ክንድኽ ፡ ያወጣኻቸው ፡ ሕዝብኽና ፡ ርስትኽ ፡

ናቸው ።

_____አሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፦ እንደ ፡ ፊተኞች ፡ ያሉትን ፡ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ጠርበኽ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ውጣ ፥ ለአንተም ፡ የዕንጨት ፡ ታቦት ፡ ሥራ ፤

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ በሰበርኻቸውም ፡ በፊተኞቹ ፡ ጽላቶች ፡ የነበሩትን ፡ ቃሎች ፡ በእነዚህ ፡ ጽላቶች ፡ እጽፋለኹ ፥ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ ታደርጋቸዋለኽ ፡ አለኝ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ከግራርም ፡ ዕንጨት ፡ ታቦትን ፡ ሠራኹ ፥ እንደ ፡ ፊተኞችም ፡ ኹለት ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ ጠረብኹ ፤ ኹለቱንም ፡ ጽላቶች ፡ በእጄ ፡ ይዤ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ወጣኹ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ በነበረበትም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ የተናገራችኹን ፡ ዐሠርቱን ፡ ቃላት ፡ ቀድሞ ፡ ተጽፈው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በጽላቶቹ ፡ ላይ ፡ ጻፈ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እነርሱን ፡ ለእኔ ፡ ሰጠኝ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ ተመልሼም ፡ ከተራራው ፡ ወረድኹ ፥ ጽላቶችንም ፡ በሠራኹት ፡ ታቦት ፡ ውስጥ ፡ አደረግኋቸው ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘኝ ፡ በዚያ ፡ ኖሩ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከብኤሮት ፡ ብኔያዕቃን ፡ ወደ ፡ ሞሴራ ፡ ተጓዙ ፤ በዚያም ፡ አሮን ፡ ሞተ ፡ በዚያም ፡ ተቀበረ ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ አልዓዛር ፡ ካህን ፡ ኾነ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጉድጉዳ ፡ ተጓዙ ፤ ከጉድጉዳም ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሾች ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ዮጥባታ ፡ ተጓዙ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፥ ርሱንም ፡ ለማገልገል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፥ በስሙም ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሌዊን ፡ ነገድ ፡ ለየ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ለሌዊ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ክፍልና ፡ ርስት ፡ የለውም ፤ አምላኽኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፥ እግዚአብሔር ፡ ርስቱ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ሰማኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሊያጠፋኽ ፡ አልወደደም ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ተነሥተኽ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ተጓዝ ፤ ለአባቶቻቸውም ፡ ልሰጣቸው ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ይግቡ ፡ ይውረሷትም ፡ አለኝ ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ 13 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አኹንስ ፡ አምላኽኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትፈራ ፡ ዘንድ ፥ በመንገዱም ፡ ኹሉ ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፥ አምላኽኽንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፥ በፍጹምም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስኽ ፡ ታመልከው ፡ ዘንድ ፥ መልካምም ፡ እንዲኾንልኽ ፡ ዛሬ ፡ ለአንተ ፡ የማዘዝን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝና ፡ ሥርዐት ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አምላኽኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ የሚፈልገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ እንሆ ፥ ሰማይ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያትም ፥ ምድርም ፡ በርሷም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ የአምላኽኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አባቶችኽ ፡ ደስ ፡ ብሎታል ፥ እነርሱንም ፡ ወዷል ፤ ከነርሱም ፡

በኋላ ፡ እናንተን ፡ ዘራቸውን ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ዥሉ ፡ ከአሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ መካከል ፡ መረጠ ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ 17 ፤ እንግዲህ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፣ የጌታዎችም ፡ ጌታ ፥ ታላቅ ፡ አምላክ ፣ ኀያልም ፡ የሚያስፈራም ፥ በፍርድ ፡ የማያደላ ፥ መማለጃም ፡ የማይቀበል ፡ ነውና ፥ እናንተ ፡ የልባችኹን ፡ ሸለፈት ፡ ግረዙ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ አትኹኑ ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ለድኻ ፡ አደጉና ፡ ለመበለቲቱ ፡ ይፈርዳል ፥ መብልና ፡ ልብስም ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ስደተኛውን ፡ ይወዳል ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ስደተኞች ፡ ነበራችኹና ፡ ስለዚህ ፡ ስደተኛውን ፡ ውደዱ ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ ፥ ርሱንም ፡ አምልክ ፤ ከርሱም ፡ ተጣበቅ ፥ በስሙም ፡ ማል ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ያዩትን ፡ እነዚህን ፡ ታላላቆች ፡ የሚያስፈሩትንም ፡ ነገሮች ፡ ያደረገልኽ ፡ ርሱ ፡ ክብርኽ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ አምላክኽ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ አባቶችኽ ፡ ሰባ ፡ ነፍስ ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረዱ ፤ አኹንም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብዛትኽን ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ አደረገ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ውደድ ፥ ሕጉንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ ፍርዱንም ፡ ትእዛዙንም ፡ ዥል ፡ ጊዜ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተግሣጽ ፥ ታላቅነቱንም ፥ የጸናችም ፡ እጁን ፥ የተዘረጋውንም ፡ ክንዱን ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ በግብጽም ፡ መካከል ፡ በንጉሡ ፡ በፈርዖንና ፡ በአገሩ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጋትን ፡ ተአምራቱንና ፡ ሥራውን ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ በተከተሏችኹም ፡ ጊዜ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ውሃ ፡ እንዳሰጠማቸው ፥ እግዚአብሔርም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዳጠፋቸው ፥ በግብጽ ፡ ፍጥራ ፡ በፈረሶቻቸውም ፡ በሠረገላዎቻቸውም ፡ ያደረገውን ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ እስክትመጡ ፡ ድረስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያደረገላችኹን ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ በእስራኤልም ፡ ዥሉ ፡ መካከል ፡ ምድር ፡ አፏን ፡ ከፍታ ፡ እነርሱንና ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ ድንኳኖቻቸውንም ፡ ለእነርሱም ፡ የነበራቸውን ፡ ዥሉ ፡ በዋጠቻቸው ፡ በሮቤል ፡ ልጅ ፡ በኤልያብ ፡ ልጆች ፡ በዳታንና ፡ በአቤሮን ፡ ያደረገውን ፡ ላላወቁትና ፡ ላላዩት ፡ ልጆቻችኹ ፡ አልነግራቸውምና ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ዕወቁ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ያደረጋትን ፡ ታላቂቱን ፡ ሥራ ፡ ዥሉ ፡ ዐይኖቻችኹ ፡ አይተዋል ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 8-9 ፤ እንግዲህ ፡ እንድትጠነክሩ ፥ ትወርሷትም ፡ ዘንድ ፡ ወደምትሻገሩባት ፡ ምድር ፡ እንድትገቡ ፡ እንድትወርሷትም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለእነርሱና ፡ ለዘራቸው ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ በማለላቸው ፡ ወተትና ፡ ማርም ፡ በምታፈሰው ፡ ምድር ፡ ዕድሜያችኹ ፡ እንዲረዝም ፥ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ የማዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ ዥሉ ፡ ጠብቁ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ የምትገባባት ፡ ምድር ፥ በአትክልት ፡ ስፍራ ፡ እንደሚዘሩ ፡ ዘርኽን ፡ እንደዘራኽባት ፥ በእግርኽም ፡ እንዳጠጣኻት ፥ እንደ ፡ ወጣኽባት ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ አይደለችም ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ትወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ተሻግራችኹ ፡ የምትገቡባት ፡ ምድር ፡ ኰረብታና ፡ ሸለቆ ፡ ያለባት ፡ አገር ፡ ናት ፤ በሰማይ ፡ ዝናብ ፡ ውሃ ፡ ትረካለች ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጐበኛት ፡ አገር ፡ ናት ፤ ከዓመቱ ፡ መገመሪያ ፡ እስከዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ የአምላክኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ዅል ፡ ጊዜ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወዱ ፡ ዘንድ ፥ በፍጹምም ፡ ልባችኹ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍሳችኹ ፡ ታመልኩት ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ የማዘውን ፡ ትእዛዜን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ብትሰሙ ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ እኽልኽን ፡ ወይንኽንም ፡ ዘይትኽንም ፡ ትሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ በየጊዜው ፡ የበልጉን ፡ ዝናብና ፡ የክረምቱን ፡ ዝናብ ፡ ለምድራችኹ ፡ አወርዳለኹ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ በሜዳ ፡ ለእንስሳዎችኽ ፡ ሣርን ፡ እሰጣለኹ ፥ ትበላማለኽ ፥ ትጠግብማለኽ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ልባችኹ ፡ እንዳይስት ፥ ፈቀቅ ፡ እንዳትሉ ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ እንዳታመልኩ ፥ እንዳትሰግዱላቸውም ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ እንዳይነድባችኹ ፥ ዝናብም ፡ እንዳይዘንብ ፡ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ እንዳትሰጥ ፡ ሰማይን ፡ እንዳይዘጋባችኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሚሰጣችኹ ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ ፈጥናችኹ ፡ እንዳትጠፉ ፡ ተጠንቀቁ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ በልባችኹና ፡ በነፍሳችኹ ፡ አኑሩ ፤ እነርሱንም ፡ ለምልክት ፡ በእጃችኹ ፡ ላይ ፡ እሰሯቸው ፥ በዐይኖቻችኹም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ክታብ ፡ ይኹኑ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ልጆቻችኹንም ፡ አስተምሯቸው ፥ በቤትኽም ፡ ስትቀመጥ ፥ በመንገድም ፡ ስትኼድ ፥ ስትተኛም ፡ ስትነሣም ፡ አጫውቷቸው ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ 21 ፤ ርሷንም ፡ እንዲሰጣቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ በማለላቸው ፡ ምድር ፥ እንደሰማይ ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፥ ዘመናችኹ ፡ የልጆቻችኹም ፡ ዘመን ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ በቤትኽ ፡ መቃኖችና ፡ በደጃፍኽም ፡ በሮች ፡ ላይ ፡ ጻፈው ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወዱ ፡ ዘንድ ፥ በመንገዱም ፡ ዅሉ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ትጣበቁ ፡ ዘንድ ፥ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ የማዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ ዅሉ ፡ ብትጠብቁ ፡ ብታደርጓትም ፥

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ከፊታችኹ ፡ ያወጣል ፥ ከእናንተም ፡ የሚበልጡትን ፡ የሚበረቱትንም ፡ አሕዛብ ፡ ትወርሳላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ የእግራችኹ ፡ ጫማ ፡ የምትረግጣት ፡ ስፍራ ፡ ዅሉ ፡ ለእናንተ ፡ ትኾናለች ፤ ከምድረ ፡ በዳም ፡ ከሊባኖስም ፡ ከታላቁም ፡ ከኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ዠምሮ ፡ እስከምዕራብ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ በእናንተም ፡ ፊት ፡ ማንም ፡ መቆም ፡ አይችልም ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገራችኹ ፥ ማስፈራታችኹን ፡ ማስደንገጣችኹንም ፡ በምትረግጧት ፡ ምድር ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ያኖራል ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ በፊታችኹ ፡ በረከትንና ፡ መርገምን ፡ አኖራለኹ ፤

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ በረከትም ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ለእናንተ ፡ የማዘውን ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ብትሰሙ ፤

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ መርገምም ፥ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ባትሰሙ ፥ ዛሬም ፡ ካዘዝኋችኹ ፡ መንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብትሉ ፥ ሌላዎችንም ፡ የማታውቋቸውን ፡ አማልክት ፡ ብትከተሉ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ አንተን ፡ ወደምትኼድባት ፡ ምድር ፡ ባገባኽ ፡ ጊዜ ፥ በረከቱን ፡ በገሪዛን ፡ ተራራ ፥ መርገሙንም ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ታኖራለኽ ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ እነርሱም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፥ ከፀሓይ ፡ መግቢያ ፡ ካለችው ፡ መንገድ ፡ በኋላ ፥ በዐረባ ፡ በተቀመጡት ፡ በከነዓናውያን ፡ ምድር ፥ በገልገላ ([104]) ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞሬ ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ አጠገብ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣችኹን ፡ ምድር ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ትሻገራላችኹ ፥ ትወርሷታላችኹም ፥ ትቀመጡባታላችኹም ።

ዘዳ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ በፊታችኹ ፡ የማኖራትን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ኹሉ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ።

____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። ____

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በምትኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመውረስ ፡ በሰጣችኹ ፡ አገር ፥ የምትጠብቋትና ፡ የምታደርጓት ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ እናንተ ፡ የምትወርሷቸው ፡ አሕዛብ ፡ አማልክታቸውን ፡ ያመለኩባቸውን ፡ በረኸቦም ፡ ተራራዎች ፡ በኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ ከለምለምም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ፈጽማችኹ ፡ አጥፏቸው ፤

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ መሠዊያቸውንም ፡ አፍርሱ ፥ ሐውልቶቻቸውንም ፡ ሰባብሩ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቻቸውንም ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉ ፥ የአማልክታቸውንም ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ አንከታክቱ ፤ ከዚያም ፡ ስፍራ ፡ ስማቸውን ፡ አጥፉ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ለአምላካችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አትሥሩ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከነገዶቻችኹ ፡ ኹሉ ፡ ስሙን ፡ በዚያ ፡ ያኖር ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ወደመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ትመጣላችኹ ፥ ማደሪያውንም ፡ ትሻላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ወደዚያም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፥ ሌላ ፡ መሥዋዕታችኹንም ፥ ዐሥራታችኹንም ፥ በእጃችኹም ፡ ያነሣችኹትን ፡ ቍርባን ፥ ስእለታችኹንም ፥ በፈቃዳችኹ ፡ የምታቀርቡትን ፥ የላማችኹንና ፡ የበጋችኹንም ፡ በኵራት ፡ ውሰዱ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ብሉ ፥ እጃችኹንም ፡ በምትዘረጉበት ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባረከኽ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ እናንተና ፡ ቤተ ፡ ሰባችኹ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፥ እኛ ፡ በዚህ ፡ ዛሬ ፡ የምናደርገውን ፡ ኹሉ ፡ አታደርጉም ፤

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጣችኹ ፡ ዕረፍትና ፡ ርስት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አልገባችኹምና ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ዮርዳኖስን ፡ ግን ፡ በተሻገራችኹ ፡ ጊዜ ፥ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚያወርሳችኹ ፡ ምድር ፡ በተቀመጣችኹ ፡ ጊዜ ፥ ያለፍርሀትም ፡ እንድትኖሩ ፡ ከከበቧችኹ ፡ ጠላቶች ፡ ኹሉ ፡ ዕረፍት ፡ በሰጣችኹ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ወደመረጠው ፡ ስፍራ ፥ እኔ ፡ የማዛችኹን ፡ ኹሉ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፥ ሌላ ፡ መሥዋዕታችኹንም ፥ ዐሥራታችኹንም ፥ በእጃችኹ ፡ ያነሣችኹትንም ፡ ቍርባን ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ተስላችኹ ፡ የመረጣችኹትን ፡ ስእለታችኹን ፡ ኹሉ ፡ ውሰዱ ።

---

104 ዕብ. ፥ ጊልጋል ፡ (መንኰራኵራት) ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ እናንተም ፥ ወንዶች ፡ ልጆቻችኹና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፥ ባሪያዎቻችኹም ፥ ገረዶቻችኹም ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ክፍልና ፡ ርስት ፡ ስለሌለው ፡ በደጆቻችኹ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጠው ፡ ሌዋዊም ፡ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትኽን ፡ በሚታይኽ ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ እንዳታቀርብ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ከነገዶችኽ ፡ ከአንዱ ፡ ዘንድ ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትኽን ፡ አቅርብ ፥ በዚያም ፡ የማዝኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፡ በረከት ፥ ሰውነትኽ ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፥ በደጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ዐርደኽ ፡ ብላ ፤ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ንጹሕም ፡ ያልኾነ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሚዳቋና ፡ እንደ ፡ ዋላ ፡ ያለውን ፡ ይብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ደሙን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አፍሰው ፡ እንጂ ፡ አትብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ የእኽልኽን ፡ የወይን ፡ ጠጅኽን ፡ የዘይትኽንም ፡ ዓሥራት ፥ የላምኽንና ፡ የበግኽንም ፡ በኵራት ፥ የተሳልኸውንም ፡ ስእለት ፡ ኹሉ ፥ በፈቃድኽም ፡ ያቀረብኸውን ፥ በእጅኽም ፡ ያነሣኸውን ፡ ቍርባን ፡ በደጆችኽ ፡ ውስጥ ፡ መብላት ፡ አትችልም ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽም ፥ ባሪያዎችኽና ፡ ገረዶችኽም ፥ በአገርኽም ፡ ደጅ ፡ ያለው ፡ ሌዋዊ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ብሉት ፤ እጅኽንም ፡ በምትዘረጋበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ በምድርኽ ፡ ላይ ፡ በምትኖርበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሌዋዊውን ፡ ችል ፡ እንዳትል ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ነገረኽ ፡ አገርኽን ፡ ባሰፋ ፡ ጊዜ ፥ ሰውነትኽም ፡ ሥጋ ፡ መብላት ፡ ስለ ፡ ወደደች ፦ ሥጋ ፡ ልብላ ፡ ስትል ፥ እንደ ፡ ሰውነትኽ ፡ ፈቃድ ፡ ሥጋን ፡ ብላ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ስሙን ፡ ያኖር ፡ ዘንድ ፡ የመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ከአንተ ፡ ሩቅ ፡ ቢኾንም ፥ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠኽ ፡ ከላምና ፡ ከበግ ፡ መንጋኽ ፡ እንዳዘዝኹኽ ፡ ዕረድ ፥ እንደ ፡ ሰውነትኽም ፡ ፈቃድ ፡ ኹሉ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ሚዳቋና ፡ ዋላ ፡ እንደሚበሉ ፡ እንዲሁ ፡ ብላው ፤ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ንጹሕም ፡ ያልኾነ ፡ ይብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ደሙ ፡ ነፍሱ ፡ ነውና ፥ ነፍሱንም ፡ ከሥጋው ፡ ጋራ ፡ መብላት ፡ አይገባኽምና ፡ ደሙን ፡ እንዳትበላ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፍሰው ፡ እንጂ ፡ አትብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ስታደርግ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችኽ ፡ መልካም ፡ እንዲኾንላችኹ ፥ አትብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የተቀደሰውን ፡ ነገርኽን ፡ ስእለትኽንም ፡ ይዘኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ኺድ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕትኽን ፥ ሥጋውንና ፡ ደሙን ፥ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አቅርብ ፤ የመሥዋዕትኽም ፡ ደም ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይፍሰስ ፥ ሥጋውንም ፡ ብላው ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ስታደርግ ፡ ለአንተ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ለልጆችኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ መልካም ፡ ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ የማዝኽን ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ሰምተኽ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትኼድባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ በፊትኽ ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፥ አንተም ፡ በወረስኻቸው ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 30 ፤ በምድራቸውም ፡ በተቀመጥኽ ፡ ጊዜ ፥ ከፊትኽ ፡ ከጠፉ ፡ በኋላ ፡ እነርሱን ፡ ለመከተል ፡ እንዳትጠመድ ፥— እነዚህስ ፡ አሕዛብ ፡ አማልክታቸውን ፡ ያመለኩት ፡ እንዴት ፡ ነው ፧ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ አደርጋለኹ ፡ ብለኽ ፡ ስለ ፡ አማልክታቸው ፡ እንዳትጠይቅ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚጠላውን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ እነርሱ ፡ ለአማልክታቸው ፡ አድርገዋልና ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ደግሞ ፡ ለአማልክታቸው ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሏቸዋልና ፥ አንተ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ አታድርግ ።

ዘዳ. ፡ 12 ፡ 32 ፤ እኔ ፡ የማዝኽን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ፤ ምንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አትጨምር ፥ ከርሱም ፡ ምንም ፡ አታጕድል ።

———————ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። ———————

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ በመካከልኽም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ሕልም ፡ ዐላሚ ፡ ቢነሣ ፥ ምልክትም ፡ ተአምራትም ፡ ቢሰጥኽ ፥

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ እንደ ፡ ነገረኽም ፡ ምልክቱ ፡ ተአምራቱም ፡ ቢፈጸም ፥ ርሱም ፥— ኼደን ፡ የማታውቃቸውን ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ እንከተል ፡ እናምልካቸውም ፡ ቢልኽ ፥

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍጹም ፡ ልባችኹ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍሳችኹ ፡ ትወዱት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊፈትናችኹ ፡ ነውና ፥ የዚያን ፡ ነቢይ ፡ ቃል ፡ ወይም ፡ ያን ፡ ሕልም ፡ ዐላሚ ፡ አትስማ ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተከተሉ ፥ ርሱንም ፡ ፍሩ ፥ ትእዛዙንም ፡ ጠብቁ ፥ ቃሉንም ፡ ስሙ ፥ ርሱንም ፡ አምልኩ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ተጣበቁ ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኼድባት ፡ ዘንድ ፡ ካዘዘኽ ፡ መንገድ ፡ ሊያወጣኽ ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣችኹ ፡ ከባርነትም ፡ ቤት ፡ ካዳናችኹ ፡ ከአምላካችኹ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሊያስታችኹ ፡ ተናግሯልና ፥ ያ ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ያ ፡ ሕልም ፡ ዐላሚ ፡ ይገደል ፤ እንዲሁም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከመካከልኽ ፡ አርቅ ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 6-7 ፤ የእናትኽ ፡ ልጅ ፡ ወንድምኽ ፡ ወይም ፡ ወንድ ፡ ልጅኽ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጅኽ ፡ ወይም ፡ በብብትኽ ፡ ያለች ፡ ሚስትኽ ፡ ወይም ፡ እንደ ፡ ነፍስኽ ፡ ያለ ፡ ወዳጅኽ ፡ በስውር ፥— ና ፥ ኼደን ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ወዳንተ ፡ የቀረቡት ፡ ከአንተም ፡ የራቁት ፡ አንተን ፡ ከዐውኽ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ከሚያመልኳቸው ፡ አማልክት ፥ አንተም ፡ አባቶችኽም ፡ የማታውቋቸውን ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ እናምልክ ፡ ብሎ ፡ ቢያስትኽ ፥ ዕሺ ፡ አትበለው ፥

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ አትስማውም ፤ ዐይንኽም ፡ አይራራለት ፥ አትማረውም ፥ አትሸሽገውም ፤

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽመኽ ፡ ግደለው ፤ ርሱን ፡ ለመግደል ፡ በፊት ፡ የአንተ ፡ እጅ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ በላዩ ፡ ትኹን ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ካወጣኽ ፡ ከአምላክኽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሊያርቅኽ ፡ ወዷልና ፥ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ውገረው ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ይፈራሉ ፥ እንዲህም ፡ ያለ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ አያደርጉም ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ 13 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልትኖርባት ፡ በሚሰጥኽ ፡ በአንዲቱ ፡ ከተማኽ ፦ ክፋተኞች ፡ ሰዎች ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጥተው ፦ ኼደን ፡ የማታውቋቸውን ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ እናምልክ ፡ ብለው ፡ የከተማቸውን ፡ ሰዎች ፡ አሳቱ ፡ ሲሉ ፡ ወሬ ፡ ብትሰማ ፥

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ትፈልጋለኽ ፥ ትመረምራለኽም ፥ ትጠይቃለኽም ፤ እንሆም ፥ እውነት ፡ ቢኾን ፥ ይህም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በመካከልኽ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ርግጥ ፡ ኾኖ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ የዚያችን ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ፈጽሞ ፡ ትመታቸዋለኽ ፤ ከተማዪቱን ፥ በርሷም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፥ እንስሳውንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ታጠፋቸዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ዕቃዋንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አደባባይዋ ፡ ትሰበሰባለኽ ፥ ከተማዪቱንም ፡ ዕቃዋንም ፡ ኹሉ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡ ፈጽመኽ ፡ ታቃጥላለኽ ፤ ለዘለዓለምም ፡ ወና ፡ ትኾናለች ፥ ደግሞም ፡ አትሠራም ።

ዘዳ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ 18 ፤ ዛሬም ፡ እኔ ፡ የማዝኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስትሰማ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡ ቀኑጣ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፥ ለአባቶችኽም ፡ እንደ ፡ ማለላቸው ፡ ይምርኽ ፡ ዘንድ ፥ ይራራልኽም ፡ ዘንድ ፥ ያበዛኽም ፡ ዘንድ ፥ ዕርም ፡ ከኾነው ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡ በእጅኽ ፡ አይንጠልጠልብኽ ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 1-2 ፤ እናንተ ፡ የአምላካችኹ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ናችኹ ፤ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽና ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ለርሱ ፡ ለራሱ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾንለት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ መርጧልና ፥ ስለሞተው ፡ ሰው ፡ አካላችኹን ፡ አትንጩ ፥ በዐይኖቻችኹም ፡ መካከል ፡ ራሳችኹን ፡ አትላጩ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 3-4 ፤ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አትብላ ። የምትብሏቸው ፡ እንስሳዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ በሬ ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ በግ ፥ ፍየል ፥ ዋላ ፥ ሚዳቋ ፥ የበረሓ ፡ ፍየል ፥ አጋዘን ፥ አጫ ፥ በራይሌ ፥ ድኮላ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ከእንስሳዎች ፡ ሰኰናው ፡ የተሠነጠቀውን ፥ ጥፍሩም ፡ ከኹለት ፡ የተከፈለውን ፥ የሚያመሰኳውንም ፡ እንስሳ ፡ ኹሉ ፡ ትበላለኽ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሚያመሰኩ ፡ ወይም ፡ ሰኰናቸው ፡ ከተሠነጠቀ ፡ እነዚህን ፡ አትበሉም ፤ ግመልን ፥ ጥንቸልን ፥ ሽኮኮን ፡ አትበሉም ። ያመሰኳሉና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሰኰናቸው ፡ አልተሠነጠቀምና ፡ እነዚህ ፡ ለእናንተ ፡ ርኩሶች ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ዕሪያም ፥ ሰኰናው ፡ ስለ ፡ ተሠነጠቀ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስላላመሰኳ ፡ ርሱ ፡ ለእናንተ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ሥጋውን ፡ አትብሉ ፥ በድኑንም ፡ አትንኩ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ በውሃዎች ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ የምትብሏቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ክንፍና ፡ ቅርፊት ፡ ያላቸውን ፡ ትበላላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ክንፍና ፡ ቅርፊትም ፡ የሌላቸውን ፡ አትበሉም ፤ ለእናንተ ፡ ርኩስ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ንጹሕ ፡ የኾኑትን ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ብሉ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ሊበሉ ፡ የማይገባቸው ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ንስር ፥ ገዴ ፥ ዓሣ ፡ አውጭ ፥ ጭልፊት ፥ ጭላት ፡ በየወገኑ ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ 15 ፤ ቀራም ፡ ኹሉ ፡ በየወገኑ ፥ ሰገን ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ጠላቋ ፥ ዝዩ ፥ በቋል ፡ በየወገኑ ፥ ጉጉት ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ጋጋኖ ፥ የውሃ ፡ ዶሮ ፥ ይብራ ፥ ጥምብ ፡ አንሣ ፡ አሞራ ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ርኩም ፥ ሽመላ ፥ ሳቢሳ ፡ በየወገኑ ፥ ጃንጁላቴ ፡ ወፍ ፥ የሌሊት ፡ ወፍ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ የሚበርም ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ ለእናንተ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ አይበላም ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ንጹሕ ፡ የኾኑትን ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ብሉ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ አንተ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽና ፥ የበከተውን ፡ ኹሉ ፡ አትብላ ፤ ይበላው ፡ ዘንድ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ለተቀመጠ ፡ መጻተኛ ፡ ትሰጠዋለኽ ፥ ወይም ፡ ለእንግዳ ፡ ትሸጠዋለኽ ። የፍየሉን ፡ ጠቦት ፡ በእናቱ ፡ ወተት ፡ አትቀቅል ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ከዕርሻኽ ፡ በየዓመቱ ፡ ከምታገኘው ፡ ከዘርኽ ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ ታወጣለኽ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ትማር ፡ ዘንድ ፥ ስሙ ፡ እንዲጠራበት ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የእኽልኽን ፡ የወይን ፡ ጠጅኽንም ፡ የዘይትኽንም ፡ ዓሥራት ፡ የላምኽንና ፡ የበግኽንም ፡ በኩራት ፡ ብላ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባረከኽ ፡ ጊዜ ፥ መንገዱ ፡ ሩቅ ፡ ቢኾን ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ ያኖርበት ፡ ዘንድ ፡ የመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ቢርቅብኽ ፥ ይህን ፡ ወደዚያ ፡ ለመሸከም ፡ ባትችል ፥ ትሸጠዋለኽ ፥

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ የዋጋውንም ፡ ገንዘብ ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ትኼዳለኽ ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ በዚያም ፡ በገንዘቡ ፡ ሰውነትኽ ፡ የፈለገውን ፥ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ወይም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ወይም ፡ ብርቱ ፡ መጠጥ ፡ ሰውነትኽም ፡ የሚሻውን ፡ ኹሉ ፡ ትገዛለኽ ፤ በዚያም ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትበላዋለኽ ፥ አንተና ፡ ቤተ ፡ ሰብኽም ፡ ደስ ፡ ይላችኋል ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ድርሻና ፡ ርስት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ስለሌለው ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ሌዋዊ ፡ ችል ፡ አትበል ።

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ በየሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ በዚያ ፡ ዓመት ፡ የፍሬኽን ፡ ዓሥራት ፡ ኹሉ ፡ አምጥተኽ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ታኖረዋለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ሌዋዊውም ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ክፍልና ፡ ርስት ፡ የለውምና ፥ በአገርኽም ፡ ደጅ ፡ ያለ ፡ መጻተኛ ፡ ድኻ ፡ አደግም ፡ መበለትም ፡ መጥተው ፡ ይበላሉ ፡ ይጠግባሉም ፤ ይኸውም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምታደርገው ፡ በእጅኽ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ይባርክኽ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ በየሰባቱ ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ የዕዳ ፡ ምሕረት ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ለምሕረቱም ፡ የሚገባ ፡ ወግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አበዳሪ ፡ ዅሉ ፡ ለባልንጀራው ፡ ያበደረውን ፡ ይተዋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ይቅርታ ፡ ታውጇልና ፥ ያበደረውን ፡ ከባልንጀራው ፡ ወይም ፡ ከወንድሙ ፡ አይሻ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ከእንግዳ ፡ ላይ ፡ ያበደርኸውን ፡ መፈለግ ፡ ትችላለኽ ፤ በወንድምኽ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዅሉ ፡ ግን ፡ እጅኽ ፡ ይተወዋል ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 4-5 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ በሰጠኽ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ ይባርክኻልና ፥ አንተ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ፈጽመኽ ፡ ብትሰማ ፥ ታደርጋትም ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ የማዝኽን ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ዅሉ ፡ ብትጠብቅ ፥ በመካከልኽ ፡ ድኻ ፡ አይኖርም ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፡ ይባርክኻል ፤ ለብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ታበድራለኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አትበደርም ፤ ብዙ ፡ አሕዛብንም ፡ ትገዛለኽ ፥ አንተን ፡ ግን ፡ አይገዙኽም ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠኽ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከወንድሞችኽ ፡ አንዱ ፡ ቢደኸይ ፥ ልብኽን ፡ አታጽና ፥ በድኻው ፡ ወንድምኽ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ አትጨብጥ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅኽን ፡ ለርሱ ፡ ክፈት ፥ የለመነኽንም ፡ አስፈላጊውን ፡ ነገር ፡ አበድረው ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የዕዳ ፡ ምሕረት ፡ ዓመት ፡ ቀርቧል ፡ ብለኽ ፡ ክፉ ፡ ዐሳብ ፡ በልብኽ ፡ እንዳታስብ ፥ ለድኻውም ፡ ወንድምኽ ፡ አንዳች ፡ የማትሰጥ ፡ እንዳትኾን ፥ ዐይንኽም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ እንዳይኾን ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንዳይጮኽ ፥ ኀጢአትም ፡ እንዳይኾንብኽ ፡ ተጠንቀቅ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ እጅኽን ፡ በምትጥልበት ፡ ዅሉ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለዚህ ፡ በሥራኽ ፡ ዅሉ ፡ ይባርክኻልና ፥ ፈጽመኽ ፡ ስጠው ፥ በሰጠኸውም ፡ ጊዜ ፡ በልብኽ ፡ አትጸጸት ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ድኻዎች ፡ ከምድሪቱ ፡ ላይ ፡ አያልቁምና ፡ ስለዚህ ፡ እኔ ፦ በአገርኽ ፡ ውስጥ ፡ ላለው ፡ ድኻ ፡ ለተቸገረውም ፡ ወንድምኽ ፡ እጅኽን ፡ ትከፍታለኽ ፡ ብዬ ፡ አዝኻለኹ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ አንተም ፡ ወንድምኽን ፡ ዕብራዊውን ፡ ወይም ፡ ዕብራዊቱን ፡ ብትገዛ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያገልግሉኽ ፤ በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ሐራነት ፡ አውጣው ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ከአንተም ፡ ዘንድ ፡ ሐራነት ፡ ባወጣኸው ፡ ጊዜ ፡ ባዶውን ፡ አትስደደው ፤

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከመንጋኽ ፥ ከዐውድማኽም ፥ ከወይንኽም ፡ መጥመቂያ ፡ ትለግስለታለኽ ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ባረከኽ ፡ መጠን ፡ ትሰጠዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ አንተም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኽ ፡ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዳነኽ ፡ ዐስብ ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አዝኻለኹ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አንተንና ፡ ቤትኽን ፡ ስለ ፡ ወደደ ፥ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ኾነለት ፦ ልወጣ ፡ አልወድም ፡ ቢል ፥

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ አንተ ፡ ወስፌ ፡ ወስደኽ ፡ በቤትኽ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ጐሮውን ፡ ትበሳዋለኽ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ባሪያ ፡ ይኾንልኻል ። በሴት ፡ ባሪያኽ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ርሱንም ፡ ሐራነት ፡ ባወጣኸው ፡ ጊዜ ፡ የምንደኛነቱን ፡ ሥራ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ አገልግሎኻልና ፥ አይክበድኽ ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በምትሠራው ፡ ዅሉ ፡ ይባርክኻል ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ላምኽና ፡ በግኽ ፡ የወለዱትን ፡ ተባት ፡ የኾነውን ፡ በኩራት ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትቀድሳለኽ ፤ በበሬኽ ፡ በኩራት ፡ አትሥራበት ፥ የበግኽንም ፡ በኩራት ፡ አትሸልት ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ አንተና ፡ ቤተ ፡ ሰብኽ ፡ በየዓመቱ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ብሏቸው ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ነውረኛ ፡ ወይም ፡ ዐንካሳ ፡ ወይም ፡ ዕውር ፡ ቢኾን ፥ ወይም ፡ አንዳች ፡ ክፉ ፡ ነውር ፡ ቢኖረው ፥ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አትሠዋው ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ትበላዋለኽ ፤ ንጹሕ ፡ ሰው ፡ ንጹሕም ፡ ያልኾነ ፡ ሚዳቋና ፡ ዋላ ፡ እንደሚበሉ ፡ ይበሉታል ።

ዘዳ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ደሙን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አፍስሰው ፡ እንጂ ፡ አትብላው ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ በአቢብ ፡ ወር ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሌሊት ፡ ከግብጽ ፡ ስላወጣኽ ፡ የአቢብን ፡ ወር ፡ ጠብቅ ፥ የአምላክኽንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፋሲካ ፡ አድርግበት ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከበግና ፡ ከላም ፡ መንጋ ፡ ፋሲካ ፡ ሠዋ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ የቦካውን ፡ እንጀራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አትብላ ፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ በችኰላ ፡ ስለ ፡ ወጣኽ ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ የወጣኽበትን ፡ ቀን ፡ በዕድሜኽ ፡ ኹሉ ፡ ታስብ ፡ ዘንድ ፡ የመከራን ፡ እንጀራ ፥ ቂጣ ፡ እንጀራ ፥ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ብላ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ በአገርኽ ፡ ኹሉ ፡ ርሾ ፡ አይታይም ፤ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ከሠዋኸው ፡ ሥጋ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ አይደር ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠኽ ፡ ከአገርኽ ፡ ደጆች ፡ በማንኛዉቱም ፡ ፋሲካን ፡ ትሠዋ ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡ በመረጠው ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ከግብጽ ፡ በወጣኽበት ፡ ወራት ፥ ፀሓይ ፡ ሲገባ ፥ ማታ ፡ ፋሲካን ፡ ሠዋ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ታበስለዋለኽ ፥ ትበላውማለኽ ፤ በነጋውም ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ድንኳንኽ ፡ ትኼዳለኽ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ስድስት ፡ ቀን ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ብላ ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ ይኹን ፤ ሥራን ፡ ኹሉ ፡ አታድርግበት ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ሰባት ፡ ሳምንትም ፡ ትቈጥራለኽ ፤ መከሩን ፡ ማጨድ ፡ ከምትዠምርበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ሰባት ፡ ሳምንት ፡ መቀሥጠር ፡ ትዠምራለኽ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በባረከኽ ፡ መጠን ፡ በፈቃድኽ ፡ የምታቀርበውን ፡ አምጥተኽ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሰባቱ ፡ ሱባዔ ፡ በዓል ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ አንተ ፥ ወንድ ፡ ልጅኽና ፡ ሴት ፡ ልጅኽ ፥ ወንድ ፡ ባሪያኽና ፡ ሴት ፡ ባሪያኽ ፥ በአገርኽም ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሌዋዊ ፥ በመካከልኽም ፡ ያሉት ፡ መጻተኛና ፡ ድኻ ፡ አደግ ፡ መበለትም ፡ አምላክኽ ፡

እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡ በሚመርጠው ፡ ስፍራ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ አንተም ፡ በግብጽ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኽ ፡ ዐስብ ፤ ይህንም ፡ ሥርዐት ፡ ጠብቅ ፥ አድርገውም ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ከዐውድማኽና ፡ ከመጥመቂያኽ ፡ ፍሬኽን ፡ በሰበሰብኽ ፡ ጊዜ ፡ የዳስ ፡ በዓል ፡ ሰባትን ፡ ቀን ፡ ትጠብቃለኽ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ አንተም ፥ ወንድ ፡ ልጅኽና ፡ ሴት ፡ ልጅኽ ፥ ወንድ ፡ ባሪያኽና ፡ ሴት ፡ ባሪያኽ ፥ በአገርኽም ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሌዋዊና ፡ መጻተኛ ፥ ድኻ ፡ አደግና ፡ መበለትም ፡ በበዓል ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍሬኽ ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ይባርኽኻልና ፥ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ታደርጋለኽ ፤ አንተም ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይልኻል ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ በዓመት ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፥ በቂጣ ፡ በዓል ፥ በሰባቱ ፡ ሱባዔም ፡ በዓል ፥ በዳስም ፡ በዓል ፡ ወንዶችኽ ፡ ኹሉ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርሱ ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ ይታዩ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ባዶ ፡ እጃቸውን ፡ አይታዩ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፡ መጠን ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ችሎታው ፡ ይስጥ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጥኽ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ኹሉ ፡ በየነገዶችኽ ፡ ፈራጆችንና ፡ አለቃዎችን ፡ ሹም ፤ ለሕዝቡም ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ይፍረዱ ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ፍርድን ፡ አታጣም ፤ ፊት ፡ አይተኽም ፡ አታድላ ፤ ጉቦ ፡ የጥበበኞችን ፡ ዐይን ፡ ያሳውራልና ፥ የጻድቃንንም ፡ ቃል ፡ ያጣምማልና ፥ ጉቦ ፡ አትቀበል ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ በሕይወት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚሰጥኽን ፡ ምድር ፡ ትወርስ ፡ ዘንድ ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ተከተል ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ለአንተ ፡ በምትሠራው ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ከማናቸውም ፡ ዛፍ ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ አድርገኽ ፡ አትትከል ።

ዘዳ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚጠላውን ፡ ሐውልት ፡ ለአንተ ፡ አታቁም ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ በበእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተጠላ ፡ ነውና ፥ ነውር ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያለበትን ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አትሠዋ ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠኽ ፡ ከአገርኽ ፡ ደጆች ፡ በማንኛዱቱም ፡ ውስጥ ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ቢኾን ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ በማፍረስ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፋት ፡ የሠራ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ኼዶም ፡ ሌላዎች ፡ አማልክትን ፡ ያመለከ ፥ እኔ ፡ ላላዘዝኋቸው ፡ ለፀሓይና ፡ ለጨረቃ ፡ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ የሰገደ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ቢያወሩልኽም ፡ ብትሰማም ፥ ያን ፡ ፈጽመኽ ፡ መርምር ፤ እንሆም ፥ እውነት ፡ ቢኾን ፥ በእስራኤልም ፡ መካከል ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ርኵሰት ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ ርግጥ ፡ ኾኖ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የሠሩትን ፡ ያን ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ያችን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ በርኽ ፡ ታመጣቸዋለኽ ፥ እስኪሞቱም ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ትወግራቸዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ በኹለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክሮች ፡ አፍ ፡ ሞት ፡ የሚገሰው ፡ ይገደል ፤ ባንድ ፡ ምስክር ፡ አፍ ፡ አይገደል ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ርሱን ፡ ለመግደል ፡ በመጐመሪያ ፡ የምስክሮች ፡ እጅ ፡ በኋላም ፡ የሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ትኹንበት ፤ እንዲሁም ፡ ክፋቱን ፡ ከመካከልኽ ፡ አስወግድ ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ በደምና ፡ በደም ፥ በፍርድና ፡ በፍርድ ፥ በመቀሥሰልና ፡ በመቀሥል ፡ መካከል ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ሰዎች ፡ ስለሚከራከሩበት ፡ ክርክር ፡ የሚሳንኽ ፡ የፍርድ ፡ ነገር ፡ ቢነሣ ፥ አንተ ፡ ተነሥተኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መረጠው ፡ ስፍራ ፡ ትወጣለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ወደተሾመው ፡ ፈራጅ ፡ መጥተኽ ፡ ትጠይቃለኽ ፤ እነርሱም ፡ የፍርዱን ፡ ነገር ፡ ይነግሩኻል ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ በመረጠው ፡ ስፍራ ፡ የነገሩኽን ፡ የፍርድ ፡ ነገር ፡ ታደርጋለኽ ፤ እንዳስተማሩኽም ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ እንዳስተማሩኽም ፡ ሕግ ፥ እንደ ፡ ነገሩኽም ፡ ፍርድ ፡ አድርግ ፤ ከነገሩኽ ፡ ፍርድ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አትበል ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢኰራ ፥ በዚያም ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ የሚቆመውን ፡ ካህኑን ፡ ወይም ፡ ፈራጁን ፡ ለመስማት ፡ ባይወድ ፥ ያ ፡ ሰው ፡ ይሙት ፥ ከእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ክፋትን ፡ አስወግድ ፤

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ሰምቶ ፡ ይፈራል ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ አይኰራም ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ በገባኽ ፥ በወረስኻትም ፡ ጊዜ ፥ በተቀመጥኽባትም ፡ ጊዜ ፦ በዙሪያዬ ፡ እንዳሉት ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በላዬ ፡ ንጉሥ ፡ አነግሣለኹ ፡ ስትል ፥

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የመረጠውን ፡ በላይኽ ፡ ታነግሣለኽ ፤ ከወንድሞችኽ ፡ መካከል ፡ የኾነውን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ታነግሣለኽ ፤ ወንድምኽ ፡ ያልኾነውን ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ በላይኽ ፡ ንጉሥ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አይገሰኽም ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለርሱ ፡ ፈረሶችን ፡ አያበዛም ፤ እግዚአብሔር ፦ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ደግማችኹ ፡ አትመለሱም ፡ ብሏችኋልና ፥ ፈረሶችን ፡ ለማብዛት ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አይመልስም ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ልቡም ፡ እንዳይስት ፡ ሚስቶችን ፡ ለርሱ ፡ አያበዛም ፤ ወርቅና ፡ ብርም ፡ ለርሱ ፡ እጅግ ፡ አያበዛም ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ በመንግሥቱም ፡ ዙፋን ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ከሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ወስዶ ፡ ይህን ፡ ሕግ ፡ ለራሱ ፡ በመጽሐፍ ፡ ይጻፍ ።

ዘዳ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ 21 ፤ አምላኩን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ይማር ፡ ዘንድ ፥ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ይህችንም ፡ ሥርዐት ፡ ጠብቆ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ ልቡ ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ እንዳይኰራ ፡ ከትእዛዙም ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ እንዳይል ፥ ርሱም ፡ ልጆቹም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ይነግሡ ፡ ዘንድ ፡ መጽሐፉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኑር ፥ ዕድሜውንም ፡ ኹሉ ፡ ያንብበው ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 1 ፤ ለሌዋውያን ፡ ካህናት ፥ ለሌዊም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ድርሻና ፡ ርስት ፡ አይኾንላቸውም ፤ በእሳት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቀርበውን ፡ መሥዋዕቱንና ፡ ርስቱን ፡ ይበላሉ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 2 ፤ በወንድሞቻቸውም ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አይኾንላቸውም ፤ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ፡ ርስታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 3 ፤ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ሕዝብ ፡ የካህናቱ ፡ ወግ ፡ ይህ ፡ ይኾናል ፤ ወርቹንና ፡ ኹለቱን ፡ ጕንጮቹን ፡ ጨጓራውንም ፡ ለካህኑ ፡ ይሰጣሉ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 4 ፤ የእኽልኽን ፡ የወይን ፡ ጠጅኽን ፡ የዘይትኽንም ፡ በኵራት ፥ አስቀድሞም ፡ የተሸለተውን ፡ የበግኽን ፡ ጠጕር ፡ ለርሱ ፡ ትሰጣለኽ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 5 ፤ ርሱ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ተነሥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለዘለዓለም ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከነገዶችኽ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ መረጠው ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 6 ፤ አንድ ፡ ሌዋዊ ፡ ሰው ፡ ከሚቀመጥባቸው ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ካሉት ፡ ከአገር ፡ ደጆች ፡ ከአንዲቱ ፡ ቢወጣ ፥ በፍጹም ፡ ፈቃድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መረጠው ፡ ስፍራ ፡ ቢመጣ ፥

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደሚቆሙት ፡ እንደ ፡ ወንድሞቹ ፡ እንደ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ያገለግላል ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 8 ፤ ከተሸጠው ፡ ከአባቶቹ ፡ ከብት ፡ ዋጋ ፡ ሌላ ፡ እንደ ፡ ባልንጀራዎቹ ፡ ከመብል ፡ ድርሻውን ፡ ይወስዳል ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 9 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ርኵሰት ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አትማር ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 10 ፤ ወንድ ፡ ልጁን ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ በእሳት ፡ የሚያሳልፍ ፥ ሟርተኛም ፥ ሞራ ፡ ገላጭም ፥

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 11 ፤ አስማተኛም ፥ መተተኛም ፥ በድግምት ፡ የሚጠነቀሉልም ፥ መናፍስትንም ፡ የሚጠራ ፥ ጠንቋይም ፥ ሙታን ፡ ሳቢም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አይገኝ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 12 ፤ ይህንም ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተጠላ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ርኵሰት ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊትኽ ፡ ያሳድዳቸዋል ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 13 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ ኹን ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 14 ፤ የምትወርሳቸው ፡ እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ሞራ ፡ ገላጮችንና ፡ ሟርተኞችን ፡ ያዳምጣሉ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እንዲሁ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከልክሎኻል ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 15 ፤ 16 ፤ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በኮሬብ ፡ ስብሰባ ፡ ተደርጎ ፡ በነበረበት ፡ ቀን ፦ እንዳልሞት ፡ የአምላኬን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ ደግሞ ፡ አልስማ ፥ ይህችን ፡ ታላቅ ፡ እሳት ፡ ደግሞ ፡ አልይ ፡ ብለኽ ፡ እንደ ፡ ለመንኸው ፡ ኹሉ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ መካከል ፡ ከወንድሞችኽ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣልኻል ፤ ርሱንም ፡ ታደምጣለኽ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለኝ ፦ የተናገሩት ፡ መልካም ፡ ነው ፤

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 18 ፤ ከወንድሞቻቸው ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ አስነሣላቸዋለኹ ፤ ቃሌንም ፡ በአፉ ፡

አደርጋለኹ ፥ ያዘዝኹትንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ይነግራቸዋል ፤

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 19 ፤ በስሜም ፡ የሚናገረውን ፡ ቃሌን ፡ የማይሰማውን ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ እበቀልለታለኹ ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ያላዘዝኹትን ፡ በስሜ ፡ በድፍረት ፡ የሚናገር ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ አማልክት ፡ ስም ፡ የሚናገር ፡ ነቢይ ፥ ርሱ ፡ ይገደል ።

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 21 ፤ በልብኽም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያልተናገውን ፡ ቃል ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻለናል ፧ ብትል ፥

ዘዳ. ፥ 18 ፥ 22 ፤ ነቢዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ባይኾን ፡ ባይመጣም ፥ ያ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልተናገረው ፡ ነው ፤ ነቢዩ ፡ በድፍረቱ ፡ ተናግሮታል ፡ ርሱን ፡ አትፍራው ።

——————————ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። ——————————

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 1 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምድራቸውን ፡ የሚሰጥኽን ፡ አሕዛብ ፡ ባጠፋ ፡ ጊዜ ፥ በወረስኻትም ፡ ጊዜ ፥ በከተማዎቻቸውና ፡ በቤቶቻቸውም ፡ በተቀመጥኽ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ በሚሰጥኽ ፡ በምድርኽ ፡ መካከል ፡ ሦስት ፡ ከተማዎችን ፡ ለራስኽ ፡ ትለያለኽ ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 3 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ይሸሽባቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ የሚወስደውን ፡ መንገድ ፡ ታዘጋጃለኽ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚያወርስኽን ፡ ምድር ፡ ከሦስት ፡ አድርገኽ ፡ ትከፍላለኽ ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 4 ፤ የነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ወግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አስቀድሞ ፡ ጠላቱ ፡ ሳይኾን ፡ ባልንጀራውን ፡ ሳያስብ ፡ የገደለ ፡ ወደዚያ ፡ ሸሽቶ ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 5-6 ፤ ሰው ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ ዕንጨት ፡ ሊቈርጥ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ቢኼድ ፥ ዛፉንም ፡ ሊቈርጥ ፡ ምሣሩን ፡ ሲያነሣ ፡ ብረቱ ፡ ከእጀታው ፡ ቢወልቅ ፥ ባልንጀራውንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢመታው ፥ ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ በልቡ ፡ ተናዶ ፡ እንዳያሳድደው ፡ መንገዱም ፡ ሩቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ አግኝቶ ፡ እንዳይገድለው ፥ ከነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ሸሽቶ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፤ አስቀድሞ ፡ ጠላቱ ፤ አልነበረምና ፡ ሞት ፡ አይገባውም ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፦ ለአንተ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎችን ፡ ለይ ፡ ብዬ ፡ አዝዤኻለኹ ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 8 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቶችኽ ፡ እንደ ፡ ማለላቸው ፡ ዳርቻኽን ፡ ቢያሰፋ ፥ ይሰጣቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶችኽ ፡ የተናገረውን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ቢሰጥኽ ፥

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 9 ፤ 10 ፤ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፥ ኹልጊዜም ፡ በመንገዱ ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፥ ዛሬ ፡ የማዝኽን ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡

ታደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ብትጠብቅ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ እንዳይፈስ ፡ ደምም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንዳይኾን ፥ በእነዚህ ፡ በሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ሌላዎች ፡ ሦስት ፡ ከተማዎችን ፡ ትጨምራለኽ ።

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 11 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢጠላ ፥ ቢሸምቅበትም ፥ ተነሥቶም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ቢመታው ፥ ከነዚህም ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ቢሸሽ ፥

ዘዳ. ፥ 19 ፥ 12 ፤ የከተማው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ይልካሉ ፥ ከተማጠነበትም ፡ ከተማ ፡ ይነጥቁታል ፥ እንዲሞትም ፡ በደም ፡ ተበቃዩ ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ ዐይንኽ ፡ አትራራለት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መልካም ፡ ይኾንልኽ ፡ ዘንድ ፡ ንጹሑን ፡ ደም ፡ ከእስራኤል ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ በምትወርሳት ፡ ርስትኽ ፡ የቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ የተከሉትን ፡ የባልንጀራኽን ፡ የድንበር ፡ ምልክት ፡ አትንቀል ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ስለ ፡ በደል ፡ ኹሉ ፥ ክፉ ፡ በማድረግም ፡ ስለሠራት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ምስክር ፡ አይቁም ፤ በኹለት ፡ ምስክሮች ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክሮች ፡ አፍ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይጸናል ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ በዐመፃ ፡ ይከሰው ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ቢቆም ፥

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ኹለቱ ፡ ጠበኞች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በካህናቱና ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በሚፈርዱ ፡ ፈራጆች ፡ ፊት ፡ ይቆማሉ ፤

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ፈራጆቹም ፡ አጥብቀው ፡ ይመረምራሉ ፤ ያም ፡ ምስክር ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ኾኖ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ በሐሰት ፡ ተናግሮ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ያሰበውን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ትመልሱበታላችኹ ፤ እንዲሁም ፡ ከአንተ ፡ መካከል ፡ ክፋቱን ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ የቀሩትም ፡ ሰምተው ፡ ይፈራሉ ፥ እንደዚህ ፡ ያለውንም ፡ ክፋት ፡ ከመካከልኽ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ አያደርጉም ።

ዘዳ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ዐይንኽም ፡ አትራራለት ፤ ነፍስ ፡ በነፍስ ፥ ዐይን ፡ በዐይን ፥ ጥርስ ፡ በጥርስ ፥ እጅ ፡ በእጅ ፥ እግር ፡ በእግር ፥ ይመለሳል ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ ጠላቶችኽን ፡ ለመውጋት ፡ በወጣኽ ፡ ጊዜ ፥ ፈረሶችንና ፡ ሠረገላዎችን ፡ ሕዝቡንም ፡ ከአንተ ፡ ይልቅ ፡ በዝተው ፡ ባየኽ ፡ ጊዜ ፥ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ያወጣኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ አትፍራቸው ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ በቀረባችኹ ፡ ጊዜ ፡ ካህኑ ፡ ይቅረብ ፡ ለሕዝቡም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይንገራቸው ፦

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስሙ ፤ ዛሬ ፡ ጠላቶቻችኹን ፡ ለመውጋት ፡ ትቀርባላችኹ ፤ ልባችኹ ፡ አይታወክ ፥ አትፍሩ ፥ አትንቀጥቀጡ ፥ በፊታቸውም ፡ አትደንግጡ ፤

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የሚኼድ ፥ ያድናችኹም ፡ ዘንድ ፡ ጠላቶቻችኹን ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚወጋ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ አለቃዎችም ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይናገሩ ፦ ዐዲስ ፡ ቤት ፡ ሠርቶ ፡ ያላስመረቀ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በሰልፍ ፡ እንዳይሞት ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እንዳያስመርቀው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ይኺድ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ወይንም ፡ ተክሎ ፡ ፍሬውንም ፡ ያልበላ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በሰልፍ ፡ እንዳይሞት ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ ፍሬውን ፡ እንዳይበላ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ይኺድ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ ሚስትም ፡ ዐጭቶ ፡ ያላገባትም ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ በሰልፍ ፡ እንዳይሞት ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እንዳያገባት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ይኺድ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ አለቃዎቹም ፡ ደግሞ ፡ ጨምረው ፦ ማንም ፡ ፈሪና ፡ ድንጉጥ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ርሱ ፡ ፈርቶ ፡ የወንድሞቹን ፡ ልብ ፡ ደግሞ ፡ እንዳያስፈራ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመልሶ ፡ ይኺድ ፡ ብለው ፡ ለሕዝቡ ፡ ይናገሩ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ አለቃዎቹም ፡ ለሕዝቡ ፡ ነግረው ፡ በጨረሱ ፡ ጊዜ ፡ በየጭፍራው ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ የጦር ፡ አለቃዎችን ፡ ይሹሙ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ከተማ ፡ በደረስኽ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድመኽ ፡ በዕርቅ ፡ ቃል ፡ ጥራቸው ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ የዕርቅ ፡ ቃልም ፡ ቢመልሱልኽ ፡ ደጅም ፡ ቢከፍቱልኽ ፥ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይገብሩልኽ ፡ ያገልግሉኽም ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ የዕርቅ ፡ ቃልም ፡ ባይመልሱልኽ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ ቢወዱ ፥ አንተ ፡ ከተማዪቱን ፡ ትከሳለኽ ፡ ታስጨንቃትማለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ በሰጣት ፡ ጊዜ ፥ በርሷ ፡ ያሉትን ፡ ወንዶች ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ትገድላቸዋለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሴቶቹንና ፡ ሕፃናትን ፡ እንስሳዎቹንም ፡ በከተማዪቱም ፡ ያለውን ፡ ምርኮ ፡ ኹሉ ፡ በዝብዘኽ ፡ ለአንተ ፡ ትወስዳለኽ ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጥኽን ፡ የጠላቶችኽን ፡ ምርኮ ፡ ትበላለኽ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ የእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ከተማዎች ፡ ባይደሉት ፡ ከአንተ ፡ እጅግ ፡ በራቁት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ከሚሰጥኽ ፡ ከነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ከተማዎች ፡ ምንም ፡ ነፍስ ፡ አታድንም ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአማልክታቸው ፡ ያደረጉትን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንዳያስተምሯችኹ ፥ በአምላካችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳትሠሩ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘኽ ፡ ኬጢያዊውን ፡ አሞራዊውንም ፡ ከነዓናዊውንም ፡ ፌርዛዊውንም ፡ ዔዊያዊውንም ፡ ኢያቡሳዊውንም ፡ ፈጽመኽ ፡ ታጠፋቸዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ከተማዪቱን ፡ ለመውሰድ ፡ በመውጋት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከበኽ ፡ ባስጨነቅኻት ፡ ጊዜ ፥ ምሣርኽን ፡ አንሥተኽ ፡ ዛፎቿን ፡ አትቀሥጥ ፤ ከነርሱ ፡ ትበላለኽና ፡ አትቀሥጣቸው ፤ ከበኽ ፡ የምታጠፋው ፡ የምድር ፡ ዛፍ ፡ ሰው ፡ መኾኑ ፡ ነውን ፧

ዘዳ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ለመብል ፡ የማይኾኑትን ፡ የምታውቃቸውን ፡ ዛፎች ፡ ታጠፋቸዋለኽ ፥ ትቈርጣቸውማለኽ ፤ እስከታሸንፋትም ፡ ድረስ ፡ በምትዋጋኽ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ምሽግ ፡ ትመሽጋለኽ ።

——————————ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። ——————————

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ የተገደለ ፡ ሰው ፡ በሜዳ ፡ ወድቆ ፡ ቢገኝ ፥

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ገዳዩም ፡ ባይታወቅ ፥ ሽማግሌዎችኽና ፡ ፈራጆችኽ ፡ ወጥተው ፡ በተገደለው ፡ ሰው ፡ ዙሪያ ፡ እስካሉት ፡ ከተማዎች ፡ ድረስ ፡ በስፍር ፡ ይለኩ ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ወደተገደለውም ፡ ሰው ፡ አቅራቢያ ፡ የኾነችው ፡ የከተማዪቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ለሥራ ፡ ያልደረሰችውን ፡ ቀንበርም ፡ ያልተጫነባትን ፡ ጊደር ፡ ይውሰዱ ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ የዘያችም ፡ ከተማ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጊደሪቱን ፡ ይዘው ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ወዳለበት ፡ ወዳልታረሰና ፡ ዘርም ፡ ወዳልተዘራበት ፡ ሸለቆ ፡ ይኼዳሉ ፤ በዘያም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ የጊደሪቱን ፡ ዐንገት ፡ ይሰብራሉ ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ካህናትም ፡ ይቀርባሉ ፤ በፊቱ ፡ እንዲያገለግሉ ፥ በስሙም ፡ እንዲባርኩ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጧቸዋልና ፥ በእነርሱም ፡ ቃል ፡ ክርክር ፡ ሹሉ ፡ ጕዳትም ፡ ሹሉ ፡ ይቈረጣልና ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ወደተገደለው ፡ ሰው ፡ አቅራቢያ ፡ የኾነችው ፡ የከተማዪቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሹሉ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ዐንገቷ ፡ በተሰበረው ፡ ጊደር ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ሲታጠቡ ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ እጃችን ፡ ይህን ፡ ደም ፡ አላፈሰሰችም ፥ ዐይናችንም ፡ አላየችም ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ የተቤዠኸውን ፡ ሕዝብኽን ፡ እስራኤልን ፡ ይቅር ፡ በል ፤ በሕዝብኽም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የንጹሑን ፡ ደም ፡ በደል ፡ አትቍጠር ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ። ስለ ፡ ደሙም ፡ ይሰረይላቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ አንተም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ የቀናውን ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ የንጹሑን ፡ ደም ፡ በደል ፡ ከመካከልኽ ፡ ታርቃለኽ ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ጠላቶችኽን ፡ ልትወጋ ፡ በወጣኽ ፡ ጊዜ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ በሰጣቸው ፡ በማረክኻቸውም ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ በተማረኩት ፡ መካከል ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ብታይ ፥ ብትመኛትም ፡ ሚስትም ፡ ልታደርጋት ፡ ብትወድ ፥ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ታመጣታለኽ ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ርሷም ፡ ራሷን ፡ ትላጫለች ፥ ጥፍሯንም ፡ ትቈረጣለች ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ የተማረከችበትንም ፡ ልብስ ፡ ታወልቃለች ፥ በቤትኽም ፡ ተቀምጣ ፡ ስለ ፡ አባቷና ፡ ስለ ፡ እናቷ ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ሙሉ ፡ ታለቅሳለች ፤ ከዘያም ፡ በኋላ ፡ ትደርስባታለኽ ፥ ባልም ፡ ትኾናታለኽ ፥ ርሷም ፡ ሚስት ፡ ትኾንልኻለች ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ከዘያም ፡ በኋላ ፡ በርሷ ፡ ደስ ፡ ባይልኽ ፡ ሐራነት ፡ አውጥተኽ ፡ ወደወደደችው ፡ ትሰድዳታለኽ ፤ በዋጋ ፡ ግን ፡ አትሸጣትም ፤ ዕፍረት ፡ አድርገኽባታልና ፥ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አትቈጥራትም ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ላንድ ፡ ሰው ፡ አንዲቱ ፡ የተወደደች ፡ አንዲቱም ፡ የተጠላች ፡ ኹለት ፡ ሚስቶች ፡ ቢኖሩት ፥ ለርሱም ፡ የተወደደችው ፡ ደግሞም ፡ የተጠላችው ፡ ልጆችን ፡ ቢወልዱ ፥ በኵሩም ፡ ከተጠላችው ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ ቢኾን ፥

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ለልጆቹ ፡ ከብቱን ፡ በሚያወርስበት ፡ ቀን ፡ ከተጠላችው ፡ ሚስት ፡ በተወለደው ፡ በበኵሩ ፡ ፊት ፡ ከተወደደችው ፡ ሚስት ፡ የተወለደውን ፡ ልጅ ፡ በኵር ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከከብቱ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ለርሱ ፡ በመስጠት ፡ ከተጠላችው ፡ ሚስት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ በኵር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያስታውቅ ። የኀይሉ ፡ መገመሪያ ፡ ነውና ፥ በኵርነቱ ፡ የርሱ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ለአባቱ ፡ ቃልና ፡ ለእናቱ ፡ ቃል ፡ የማይታዘዝ ፡ ቢቀጡትም ፡ የማይሰማቸው ፡ እልከኛና ፡ ዐመፀኛ ፡ ልጅ ፡ ቢኖረው ፥

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ይዘው ፡ ወደከተማው ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደሚኖሩበትም ፡ ስፍራ ፡ በር ፡ ያምጡት ፤

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ የከተማውንም ፡ ሽማግሌዎች ፦ ይህ ፡ ልጃችን ፡ እልከኛና ፡ ዐመፀኛ ፡ ነው ፥ ለቃላችንም ፡

አይታዘዝም ፡ ሥሥታምና ፡ ሰካራም ፡ ነው ፡ ይበሏቸው ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ የከተማውም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገሩት ፤ እንዲህም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከመካከልኽ ፡ ታርቃለኽ ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ይፈራሉ ።

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃውን ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፥ እንዲሞትም ፡ ቢፈረድበት ፥ በዕንጨትም ፡ ላይ ፡ ብትሰቅለው ፥

ዘዳ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ የተሰቀለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተረገመ ፡ ነውና ፥ ሬሳው ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ አይደር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠኽን ፡ ምድር ፡ እንዳታረክስ ፡ በርግጥ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ቅበረው ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ የወንድምኽ ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ በግ ፡ ጠፍቶ ፡ ብታይ ፡ ቸል ፡ አትበል ፤ ወደ ፡ ወንድምኽ ፡ መልሰው ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ ወንድምኽም ፡ በአቅራቢያኽ ፡ ባይኾን ፡ ወይም ፡ ባታውቀው ፡ ይዘኽ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ትገባለኽ ፤ ወንድምኽ ፡ እስኪሻው ፡ ድረስ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ይቀመጣል ፥ ለርሱም ፡ ትመልሰዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በአህያው ፡ ወይም ፡ በልብሱ ፡ ታደርጋለኽ ፤ እንዲህም ፡ በወንድምኽ ፡ በጠፋበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ባገኘኸው ፡ ጊዜ ፡ ታደርጋለኽ ፤ ቸል ፡ ልትለው ፡ አይገባኽም ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ የወንድምኽ ፡ አህያ ፡ ወይም ፡ በሬው ፡ በመንገድ ፡ ወድቆ ፡ ብታይ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኾነኽ ፡ አነሣሣው ፡ እንጂ ፡ ቸል ፡ አትበለው ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ሴት ፡ የወንድ ፡ ልብስ ፡ አትልበስ ፥ ወንድም ፡ የሴት ፡ ልብስ ፡ አይልበስ ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነውና ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ በመንገድ ፡ ስትኼድ ፡ በዛፍ ፡ ወይም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ እናቲቱ ፡ በጫጩቶቿ ፡ ወይም ፡ በዕንቁላሎቿ ፡ ላይ ፡ ተኝታ ፡ ሳለች ፡ የወፍ ፡ ጐጆ ፡ ብታገኝ ፥ እናቲቱን ፡ ከጫጩቷ ፡ ጋራ ፡ አትውሰድ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መልካም ፡ ይኾንልኽ ፡ ዘንድ ፡ ዕድሜኽም ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ እናቲቱን ፡ ስደድ ፥ ጫጩቶችንም ፡ ለአንተ ፡ ውሰድ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ ዐዲስ ፡ ቤት ፡ በሠራኽ ፡ ጊዜ ፡ ማንም ፡ ከርሱ ፡ ወድቆ ፡ ደሙን ፡ በቤትኽ ፡ ላይ ፡ እንዳታመጣ ፡ በጣራው ፡ ዙሪያ ፡ መከታ ፡ አድርግለት ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ የዘራኸው ፡ ዘርና ፡ ከወይኑ ፡ የወጣው ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ እንዳይጠፉብኽ ፡ በወይንኽ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ዘር ፡ አትዝራ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ በበሬና ፡ በአህያ ፡ በአንድነት ፡ አትረስ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ከተልባ ፡ እግርና ፡ ከበግ ፡ ጠጕር ፡ በአንድነት ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ አትልበስ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ በምትለብሰው ፡ በልብስኽ ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ ዘርፍ ፡ አድርግ ።

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ቢያገባ ፥ ከደረሰባትም ፡ በኋላ ፡ ቢጠላት ፥

ዘዳ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ የነውር ፡ ነገር ፡ አውርቶ ፦ እኔ ፡ ይህችን ፡ ሴት ፡ ሚስት ፡ አድርጌ ፡

አገባኋት ፥ በደርስኩባትም ፡ ጊዜ ፡ ድንግልናዋን ፡ አላገኘኩባትም ፡ ብሎ ፡ በክፉ ፡ ስም ፡ ቢያሳጣት ፥

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 15 ፤ የብላቴናዪቱ ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የድንግልናዋን ፡ ምልክት ፡ ወስደው ፡ በበሩ ፡ በአደባባይ ፡ ወደተቀመጡ ፡ ወደከተማ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያምጡት ፤

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 16 ፤ የብላቴናዪቱም ፡ አባት ፡ ሽማግሌዎቹን ፦ እኔ ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ልጄን ፡ ዳርኩለት ፡ ርሱም ፡ ጠላት ፤

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 17 ፤ እንሆም ፦ በልጅኽ ፡ ድንግልና ፡ አላገኘኩባትም ፡ ብሎ ፡ የነውር ፡ ነገር ፡ አወራባት ፤ የልጄም ፡ ምልክት ፡ ይኸው ፡ ይላቸዋል ። በከተማም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ ልብሱን ፡ ይዘረጋሉ ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 18 ፤ የዚያችም ፡ ከተማ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ወስደው ፡ ይግረፉት ፤

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 19 ፤ በእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ስም ፡ አምጥቷልና ፥ መቶ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ያስከፍሉት ፥ ለብላቴናዪቱም ፡ አባት ፡ ይስጡት ፤ ርሷም ፡ ሚስት ፡ ትኹነው ፥ በዕድሜውም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሊፈታት ፡ አይገባውም ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 20 ፤ ነገሩ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ቢኾን ፥ በብላቴናዪቱም ፡ ድንግልናዋ ፡ ባይገኝ ፥

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 21 ፤ ብላቴናዪቱን ፡ ወዳባቷ ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ያውጧት ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ የማይገባውን ፡ ነገር ፡ አድርጋለችና ፥ በአባቷም ፡ ቤት ፡ አመንዝራለችና ፡ የከተማዋ ፡ ሰዎች ፡ እስክትሞት ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገሯት ፤ እንዲሁም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከመካከልኽ ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 22 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ ተኝቶ ፡ ቢገኝ ፥ አመንዝራውና ፡ አመንዝራዪቱ ፡ ኹለታቸው ፡ ይሙቱ ፤ እንዲሁም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከእስራኤል ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 23 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ድንግልና ፡ ያላትን ፡ ልጃገረድ ፡ ቢያጭ ፥ ሌላ ፡ ሰውም ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ አግኝቶ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ቢተኛ ፥

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 24 ፤ ኹለቱን ፡ ወደዚያች ፡ ከተማ ፡ በር ፡ አውጧቸው ፤ ብላቴናዪቱ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሳለች ፡ አልጮኸችምና ፥ ሰውዮውም ፡ የባልንጀራውን ፡ ሚስት ፡ አስነውሯልና ፥ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ውገሯቸው ፤ እንዲሁም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከመካከልኽ ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ የታጨችውን ፡ ልጃገረድ ፡ በሜዳ ፡ ቢያገኛት ፥ በግድ ፡ አሸንፎም ፡ ቢደርስባት ፥ ያ ፡ የደረሰባት ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ይገደል ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 26 ፤ በብላቴናዪቱ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አታድርጉ ፡ በብላቴናዪቱ ፡ ላይ ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ ኀጢአት ፡ የለባትም ፤ ሰው ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ እንደሚገድለው ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ ነውና ፤

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 27 ፤ በሜዳ ፡ ባገኛት ፡ ጊዜ ፡ የታጨችው ፡ ልጃገረድ ፡ ጮኻለችና ፥ የሚታደጋትም ፡ አልነበረምና ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 28 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ድንግልና ፡ ያላትን ፡ ያልታጨች ፡ ልጃገረድ ፡ ቢያገኝ ፥ ወስዶም ፡ ቢደርስባት ፥ ቢያገኙትም ፥

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 29 ፤ ያ ፡ የደረሰባት ፡ ሰው ፡ ዐምሳ ፡ የብር ፡ ሰቅል ፡ ለብላቴናዪቱ ፡ አባት ፡ ይስጥ ፤ አስነውሯታልና ፥ ሚስት ፡ ትኹነው ፤ በዕድሜውም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሊፈታት ፡ አይገባውም ።

ዘዳ. ፥ 22 ፥ 30 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የአባቱን ፡ ሚስት ፡ አይውሰድ ፥ የአባቱንም ፡ ልብስ ፡ ጫፍ ፡ አይግለጥ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ቀ፡ላው ፡ የተቀጠቀጠ ፡ ብልቱም ፡ የተቈረጠ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ አይግባ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ዲቃላ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ አይግባ ፤ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ አይግባ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 3-4 ፤ ከግብጽ ፡ በወጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ እንጀራና ፡ ውሃ ፡ ይዘው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አልተቀበሏችኹምና ፥ በመስጴጦምያ ፡ ካለው ፡ ከፋቱራ ፡ የቢያርን ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡ ዋጋ ፡ ሰጥተው ፡ ይረግምኽ ፡ ዘንድ ፡ አምጥተውብኻልና ፥ አሞናዊና ፡ ሞዐባዊ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ አይግባ ፡ እስከ ፡ ዐሥር ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ለዘለዓለም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ አይግባ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለዓምን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዶኻልና ፥ ርግማኑን ፡ በረከት ፡ አደረገልኽ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በዘመንኽ ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሰላምና ፡ ልማት ፡ ለእነርሱ ፡ አትሻ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ኤዶማዊው ፡ ወንድምኽ ፡ ነውና ፥ አትጸየፈው ፤ ግብጻዊውንም ፡ በአገሩ ፡ ስደተኛ ፡ ነበርኽና ፡ አትጸየፈው ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ከነርሱም ፡ በሦስተኛው ፡ ትውልድ ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ ይግቡ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ ጠላቶችኽን ፡ ልትወጋ ፡ በወጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሰውነትኽን ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ሌሊት ፡ በሚኾነው ፡ ርኵሰት ፡ የረከስ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፥ ከሰፈር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይውጣ ፥ ወደ ፡ ሰፈርም ፡ አይግባ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ በውሃ ፡ ይታጠብ ፤ ፀሓይም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ይመለስ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ሜዳም ፡ ትወጣበት ፡ ዘንድ ፡ ከሰፈር ፡ ውጭ ፡ ቦታ ፡ ይኹንልኽ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ከመሣሪያኽም ፡ ጋራ ፡ መቈፈሪያ ፡ ያዝ ፤ በሜዳም ፡ በተቀመጥኽ ፡ ጊዜ ፡ ትምስበታለኽ ፥ ዞረኽም ፡ ከአንተ ፡ የወጣውን ፡ በዐፈር ፡ ትከድነዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያድንኽ ፡ ጠላቶችኽንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጥ ፡ በሰፈርኽ ፡ መካከል ፡ ይኼዳልና ፥ ስለዚህ ፡ ነውረኛ ፡ ነገር ፡ እንዳያይብኽ ፥ ፊቱንም ፡ ከአንተ ፡ እንዳይመልስ ፡ ሰፈርኽ ፡ የተቀደስ ፡ ይኹን ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ከጌታው ፡ ኰብሶ ፡ ወዳንተ ፡ የመጣውን ፡ ባሪያ ፡ ለጌታው ፡ አሳልፈኽ ፡ አትስጥ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ ከደጆችኽ ፡ በሚመርጣት ፡ በአንዲቱ ፡ በሚወዳት ፡ ስፍራ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በመካከልኽ ፡ ይቀመጥ ፥ አንተም ፡ አታስጨንቀው ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ከእስራኤል ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሴት ፡ ጋለሞታ ፡ አትገኝ ፥ ከእስራኤልም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ወንድ ፡ ጋለሞታ ፡ አይገኝ ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ስለተሳልኸው ፡ ስእለት ፡ ኹሉ ፡ የጋለሞታዪቱን ፡ ዋጋና ፡ የውሻውን ፡ ዋጋ ፡ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አታቅርብ ፤ ኹለቱም ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚያጸይፉ ፡ ናቸውና ።

ዘዳ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ለወንድምኽ ፡ በወለድ ፡ አታበድር ፤ የብር ፡ ወይም ፡ የእኽል ፡ ወይም ፡ የማናቸውንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ወለድ ፡ አትውሰድ ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 20 ፤ ለእንግዳው ፡ በወለድ ፡ አበድረው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልትወርሳት ፡ በምትገባባት ፡ ምድር ፡ በሥራኽ ፡ ኹሉ ፡ ይባርክኽ ፡ ዘንድ ፡ ለወንድምኽ ፡ በወለድ ፡ አታበድር ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 21 ፤ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ በተሳልኽ ፡ ጊዜ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሻዋልና ፥ ኀጢአትም ፡ ይኾንብኻልና ፥ መክፈሉን ፡ አታዘግይ ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 22 ፤ ባትሳል ፡ ግን ፡ ኀጢአት ፡ የለብኽም ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 23 ፤ በአፍኽ ፡ የተናገርኸውን ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃድኽ ፡ ተስለኻልና ፥ ከከንፈርኽ ፡ የወጣውን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 24 ፤ ወደባልንጀራኽ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እስክትጠግብ ፡ ድረስ ፡ ከወይኑ ፡ ብላ ፤ ወደ ፡ ዕቃኽ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አታግባ ።

ዘዳ. ፥ 23 ፥ 25 ፤ ወደባልንጀራኽ ፡ ዕርሻ ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እሸቱን ፡ በእጅኽ ፡ ቀጥፈኽ ፡ ብላ ፤ ወዳልታጨደው ፡ ወደባልንጀራኽ ፡ እኽል ፡ ግን ፡ ማጭድ ፡ አታግባ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 1 ፤ ሰው ፡ ሴትን ፡ ወስዶ ፡ ቢያገባ ፥ የዕፍረት ፡ ነገር ፡ ስላገኘባት ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ ባታገኝ ፥ የፍቺን ፡ ጽሕፈት ፡ ጽፎ ፡ በእጇ ፡ ይስጣት ፥ ከቤቱም ፡ ይስደዳት ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 2 ፤ ከቤቱም ፡ ከወጣች ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ብታገባ ፥

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 3 ፤ ኹለተኛውም ፡ ባል ፡ ቢጠላት ፥ የፍቺንም ፡ ጽሕፈት ፡ ጽፎ ፡ በእጇ ፡ ቢሰጣት ፥ ከቤቱም ፡ ቢሰዳት ፥ ወይም ፡ ሚስት ፡ አድርጎ ፡ ያገባት ፡ ኹለተኛው ፡ ባሏ ፡ ቢሞት ፥

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 4 ፤ የሰደዳት ፡ የቀድሞ ፡ ባሏ ፡ ከረከሰች ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ያገባት ፡ ዘንድ ፡ አይገ፡ባውም ፤ ያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተጠላ ፡ ነው ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠኽን ፡ ምድር ፡ አታርክስ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 5 ፤ ዐዲስ ፡ ሚስትም ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ አይኺድ ፥ ነገርም ፡ አይጫነበት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ዓመት ፡ በቤቱ ፡ በፈቃዱ ፡ ይቀመጥ ፥ የወሰዳትንም ፡ ሚስቱን ፡ ደስ ፡ ያሠኛት ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 6 ፤ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ እንደ ፡ መውሰድ ፡ ነውና ፥ ወፍጮ ፡ ወይም ፡ መጅ ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ማንም ፡ አይውሰድ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 7 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከወንድሞቹ ፡ አንዱን ፡ ሰርቆ ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ሲያደርግበት ፡ ወይም ፡ ሲሸጠው ፡ ቢገኝ ፥ ያ ፡ ሌባ ፡ ይሙት ፤ እንዲሁም ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ከመካከልኽ ፡ ታስወግዳለኽ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 8 ፤ በለምጽ ፡ ደዌ ፡ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ያስተማሩኽን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመኽ ፡ እንድትጠብቅ ፡ እንድታደርግም ፡ ተጠንቀቅ ፤ እኔ ፡ ያዘዝኋቸውን ፡ እንዲሁ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቅ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 9 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ በወጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ በመንገድ ፡ ሳላችኹ ፡ በማርያም ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ዐስብ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 10 ፤ ለባልንጀራኽ ፡ ባበደርኸው ፡ ጊዜ ፡ መያዣውን ፡ ልትወስድ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አትግባ ።

ዘዳ. ፥ 24 ፥ 11 ፤ አንተ ፡ በውጭ ፡ ቁም ፡ ያበደርኸውም ፡ ሰው ፡ መያዣውን ፡ ያውጣልኽ ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ድኻ ፡ ቢኾን ፡ መያዣውን ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አታሳድር ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ ለብሶት ፡ እንዲተኛ ፡ እንዲባርክኽም ፡ ፀሓይ ፡ ሳይገባ ፡ መያዣውን ፡ ፈጽመኽ ፡ መልስለት ፤ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጽድቅ ፡ ይኾንልኻል ፡

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ድኻና ፡ ችግረኛ ፡ የኾነውን ፡ ምንደኛ ፥ ከወንድሞችኽ ፡ ወይም ፡ በምድርኽ ፡ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ከሚቀመጡት ፡ መጻተኞች ፡ ቢኾን ፥ አታስጨንቀው ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ድኻ ፡ ነውና ፥ ነፍሱም ፡ ጠንክራ ፡ ትፈልገዋለችና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይጮኽብኽ ፡ ኀጢአትም ፡ እንዳይኾንብኽ ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ ፀሓይ ፡ ሳይገባ ፡ በቀኑ ፡ ስጠው ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ አባቶች ፡ ስለ ፡ ልጆች ፡ አይገደሉ ፥ ልጆችም ፡ ስለ ፡ አባቶች ፡ አይገደሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በኀጢአቱ ፡ ይገደል ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ የመጻተኛውንና ፡ የድኻ ፡ አደጉን ፡ ፍርድ ፡ አታጣምባቸው ፤ የመበለቲቱን ፡ ልብስ ፡ ለመያዣ ፡ አትውሰድባት ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ አንተም ፡ በግብጽ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኽ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚያ ፡ እንዳዳነኽ ፡ ዐስብ ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አዝገፍኻለኹ ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ የዕርሻኽን ፡ መከር ፡ ባጨድኽ ፡ ጊዜ ፡ ነዶም ፡ ረስተኽ ፡ በዕርሻኽ ፡ ብታስቀር ፥ ትወስደው ፡ ዘንድ ፡ አትመለስ ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጅኽ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንዲባርክኽ ፥ ለመጻተኛና ፡ ለድኻ ፡ አደግ ፡ ለመበለትም ፡ ተወው ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ የወይራኽን ፡ ፍሬ ፡ ባረገፍኽ ፡ ጊዜ ፡ ከቅርንጫፎቹ ፡ ላይ ፡ ማርገፉን ፡ ለማጣራት ፡ አትመለስ ፤ ለመጻተኛና ፡ ለድኻ ፡ አደግ ፡ ለመበለትም ፡ ይኹን ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ የወይንኽን ፡ ፍሬ ፡ በቈረጥኽ ፡ ጊዜ ፡ ቃርሚያውን ፡ አትልቀመው ፤ ለመጻተኛና ፡ ለድኻ ፡ አደግ ፡ ለመበለትም ፡ ይኹን ።

ዘዳ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ አንተም ፡ በግብጽ ፡ አገር ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኽ ፡ ዐስብ ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ አዝገፍኻለኹ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። _____

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ጠብ ፡ ቢኾን ፥ ወደ ፡ ፍርድም ፡ ቢመጡ ፥ ፈራጆችም ፡ ቢፈርዱባቸው ፥ ጻድቁን ፦ ደኅና ፡ ነኽ ፥ የበደለውንም ፦ በደለኛ ፡ ነኽ ፡ ይበሏቸው ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ በደለኛውም ፡ መገረፍ ፡ ቢገባው ፡ እንዲገረፍ ፡ ፈራጁ ፡ በፊቱ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያጋድመው ፤ የግርፋቱም ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ኀጢአቱ ፡ መጠን ፡ ይኹን ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ግርፋቱም ፡ አርባ ፡ ይኹን ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ጨምሮ ፡ ብዙ ፡ ግርፋት ፡ ቢገርፈው ፥ ወንድምኽ ፡ በፊትኽ ፡ ነውረኛ ፡ ይኾናልና ፥ ከዚህ ፡ በላይ ፡ አይጨመርበት ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ እኽል ፡ የሚያበራየውን ፡ በሬ ፡ አፉን ፡ አትሰር ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ ወንድማማቾች ፡ በአንድነት ፡ ቢቀመጡ ፥ አንዱም ፡ ልጅ ፡ ሳይኖረው ፡ ቢሞት ፥ የሞተው ፡ ሰው ፡ ሚስት ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አትኺድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባሏ ፡ ወንድም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገብቶ ፡ ርሷን ፡ ያግባ ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ይኑር ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ የሚቸ ፡ ስም ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ከርሷ ፡ የሚወለደው ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ በሞተው ፡ በወንድሙ ፡ ስም ፡ ይጠራ ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ ያም ፡ ሰው ፡ የወንድሙን ፡ ሚስት ፡ ማግባት ፡ ባይወድ ፥ ዋርሳዩቱ ፡ በበሩ ፡ አደባባይ ፡ ወደሚቀመጡ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኼዳ ። ዋርሳዬ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ለወንድሙ ፡ ስም ፡ ማቆም ፡ እንቢ ፡ አለ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሊኖርም ፡ አልወደደም ፡ ትበላቸው ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ የከተማውም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጠርተው ፡ ይጠይቁት ፤ ርሱም ፡ በዚያ ፡ ቆሞ ፦ አገባት ፡ ዘንድ ፡ አልወድም ፡ ቢል ፥

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ዋርሳዩቱ ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርባ ፦ የወንድሙን ፡ ቤት ፡ በማይሠራ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ይደረግበታል ፡ ስትል ፡ ጫማውን ፡ ከእግሩ ፡ ታውጣ ፥ በፊቱም ፡ እንትፍ ፡ ትበልበት ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ስሙ ፡ የጫማ ፡ ፈቱ ፡ ቤት ፡ ተብሎ ፡ ይጠራ ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ቢጣሉ ፥ የአንደኛውም ፡ ሚስት ፡ ባሏን ፡ ከሚመታው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ታድነው ፡ ዘንድ ፡ ብትቀርብ ፥ እጇንም ፡ ዘርግታ ፡ ብልቱን ፡ ብትይዝ ፥

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ እጇን ፡ ቀሪጥ ፥ ዐይንኽም ፡ አትራራላት ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ በከረጢትኽ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅና ፡ ታናሽ ፡ የኾነ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ሚዛን ፡ አይኑርልኽ ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ በቤትኽ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅና ፡ ታናሽ ፡ የኾነ ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ መስፈሪያ ፡ አይኑርልኽ ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ 16 ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ክፋትንም ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነውና ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ዕድሜኽ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ እውነተኛና ፡ ፍጹም ፡ ሚዛን ፡ ይኹንልኽ ፤ እውነተኛና ፡ ፍጹም ፡ መስፈሪያም ፡ ይኹንልኽ ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ ከግብጽ ፡ በወጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ ዐማሌቅ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ያደረገብኽን ፡ ዐስብ ፤

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ በመንገድ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቃወመኽ ፥ አንተም ፡ ተስኖኽ ፡ ደክመኽም ፡ ሳለኽ ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ደክመው ፡ የነበሩትን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መታ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አልፈራም ።

ዘዳ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ በሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ከሚከቡኽ ፡ ጠላቶችኽ ፡ ኹሉ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሳረፈኽ ፡ ጊዜ ፥ የዐማሌቅን ፡ ዝክረ ፡ ስሙን ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ አጥፋው ፤ ይህን ፡ አትርሳ ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ በገባኽም ፡ ጊዜ ፥ በወረስኻትም ፡ በኖርኽባትም ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ከምትሰበስበው ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በኵራት ፡ ውሰድ ፡ በእንቅብም ፡ አድርገው ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙ ፡ ይጠራበት ፡ ዘንድ ፡ ወደመረጠውም ፡ ስፍራ ፡ ይዘኽ ፡ ኺድ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ወደሚኾነው ፡ ካህን ፡ መጥተኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ወደማለላቸው ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ገባኹ ፡ ዛሬ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አስታውቃለኹ ፡ በለው ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ካህኑም ፡ እንቅቡን ፡ ከእጅኽ ፡ ወስዶ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ያኑረው ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገር ፦ አባቴ ፡ የተቅበዘበዘ ፡ ሶርያዊ ፡ ነበረ ፤ በቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ፡ በዚያም ፡ ተቀመጠ ፤ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ የበረታም ፡ ቍጥሩም ፡ የበዛ ፡ ሕዝብ ፡ ኾነ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ግብጻውያንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረጉብን ፥ አስጨነቁንም ፥ በላያችንም ፡ ጽኑ ፡ ከባድ ፡ ሥራን ፡ ጫኑብን ፤

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ወዳባቶቻችንም ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽን ፤ እግዚአብሔርም ፡ ድምፃችንን ፡ ሰማ ፥ ጭንቀታችንንም ፡ ድካማችንንም ፡ ግፋችንንም ፡ አየ ፤

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጸናች ፡ እጅና ፡ በተዘረጋ ፡ ክንድ ፥ በታላቅም ፡ ድንጋጤ ፥ በተአምራትም ፥ በድንቅም ፡ ከግብጽ ፡ አወጣን ፤

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ አገባን ፥ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈሰውንም ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ ሰጠን ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ አቤቱ ፥ አንተ ፡ የሰጠኸኝን ፡ የምድሪቱን ፡ ፍሬ ፡ በኩራት ፡ አቅርቤያለኹ ። አንተም ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አኑረው ፥ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስገድ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ አንተም ፡ በመካከልኽም ፡ ያለ ፡ ሌዋዊና ፡ መጻተኛ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአንተና ፡ ለቤትኽ ፡ በሰጠው ፡ ቸርነት ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ዓሥራት ፡ በምታወጣበት ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የፍሬኽን ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ አውጥተኽ ፡ በፈጸምኽ ፡ ጊዜ ፥ በአገርኽ ፡ ደጅ ፡ ውስጥ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ይጠግቡም ፡ ዘንድ ፡ ለሌዋዊው ፡ ለመጻተኛውም ፡ ለድኻ ፡ አደጉም ፡ ለመበለቲቱም ፡ ስጣቸው ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ የተቀደሰውን ፡ ነገር ፡ ከቤቴ ፡ ወስጄ ፡ ለሌዋዊው ፡ ለመጻተኛውም ፡ ለድኻ ፡ አደጉም ፡ ለመበለቲቱም ፡ እንዳዘዝኸኝ ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ሰጥቻለኹ ፤ ትእዛዝኽን ፡ ምንም ፡ አላፈረስኹም ፥ አልረሳኹምም ፤

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ በሐዘኔ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ከርሱ ፡ አልበላኹም ፥ ለርኩስነቴም ፡ ከርሱ ፡ አላወጣኹም ፥ ከርሱም ፡ አንዳች ፡ ለሞተ ፡ ሰው ፡ አልሰጠኹም ፤ የአምላኬንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምቻለኹ ፥ ያዘዝኸኝንም ፡ ኹሉ ፡ አድርጌያለኹ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ከቅዱስ ፡ ማደሪያኽ ፡ ከሰማይ ፡ ጐብኝ ፥ ሕዝብኽንም ፡ እስራኤልን ፡ ለአባቶቻችን ፡ እንደ ፡ ማልኽላቸው ፡ የሰጠኸንንም ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈሰውን ፡ አገር ፡ ባርክ ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ አዞኻል ፤ አንተም ፡ በፍጹም ፡ ልብኽና ፡ በፍጹም ፡ ነፍስኽ ፡ ጠብቀው ፥ አድርገውም ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ አንተ ፡ በመንገዱ ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፥ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ፍርዱንም ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ ቃሉንም ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክኽ ፡ መኾኑን ፡ ዛሬ ፡ አስታውቀኻል ።

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፡ ተስፋ ፡ ገንዘቡና ፡ ሕዝቡ ፡ መኾንኽን ፥ ትእዛዙንም ፡ ኹሉ ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥

ዘዳ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ከፈጠራቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በምስጋና ፡ በስም ፡ በክብር ፡ ከፍ ፡ ያደርግኽ ፡ ዘንድ ፥ ርሱም ፡

እንደ ፡ ተናገረ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ አስታውቋል ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ። _____

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 1 ፤ ሙሴና ፡ የእስራኤል ፡ ሽማግሌዎችም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሕዝቡን ፡ አዘዙ ፦ ዛሬ ፡ ያዘዝኺችኹን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 2 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገርኽ ፡ ጊዜ ፡ ታላላቅ ፡ ድንጋዮችን ፡ ለአንተ ፡ አቁም ፥ በኖራም ፡ ምረጋቸው ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 3 ፤ የአባቶችኽ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፥ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈስ ፡ ምድር ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደሚሰጥኽ ፡ ምድር ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡ በተሻገርኽ ፡ ጊዜ ፥ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ጻፍባቸው ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 4 ፤ ዮርዳኖስንም ፡ በተሻገርኽ ፡ ጊዜ ፥ ዛሬ ፡ እንዳዘዝኹኽ ፥ እነዚህን ፡ ድንጋዮች ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ አቁም ፥ በኖራም ፡ ምረጋቸው ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 5 ፤ በዚያም ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሥራ ፤ መሠዊያውም ፡ ብረት ፡ ካልነካው ፡ ድንጋይ ፡ ይኹን ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 6 ፤ ካልተጠረበም ፡ ድንጋይ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ ሥራ ፤ ለአምላክም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትኽን ፡ አቅርብበት ፤

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 7 ፤ የደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋበት ፥ በዚያም ፡ ብላ ፤ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 8 ፤ የዚህንም ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ የተገለጠ ፡ አድርገኽ ፡ በድንጋዮቹ ፡ ላይ ፡ ጻፍ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 9 ፤ ሙሴና ፡ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ። እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ዝም ፡ ብላችኹ ፡ አድምጡ ፤ ዛሬ ፡ የአምላክኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ኾነኻል ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 10 ፤ ለአምላክኽም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ታዘዝ ፥ ዛሬም ፡ የማዝኽን ፡ ትእዛዙንና ፡ ሥርዐቱን ፡ አድርግ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 11 ፤ ሙሴም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ አዘዘ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 12 ፤ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገራችኹ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ይባርኩ ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፥ ስምዖንና ፡ ሌዊ ፡ ይሁዳና ፡ ይሳኮር ፡ ዮሴፍና ፡ ብንያም ፥ በገሪዛን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይቁሙ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 13 ፤ ይረግሙም ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፥ ሮቤልና ፡ ጋድ ፡ አሴርና ፡ ዛብሎን ፡ ዳንና ፡ ንፍታሌም ፥ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይቁሙ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 14 ፤ ሌዋውያንም ፡ ከፍ ፡ ባለች ፡ ድምፅ ፡ ለእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 15 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ የሠራተኛ ፡ እጅ ፡ ሥራን ፡ የተቀረጸ ፡ ወይም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስልን ፡ የሚያደርግ ፥ በስውርም ፡ የሚያቆመው ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ መልሰው ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፥ 27 ፥ 16 ፤ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚያቃልል ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ የባልንጀራውን ፡ የድንበር ፡ ምልክት ፡ የሚገፋ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ ዕውሩን ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ የሚያደርግ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ በመጻተኛ ፡ በድኻ ፡ አደጉም ፡ በመበለቲቱም ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ የሚያጣምም ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ ከአባቱ ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ የሚተኛ ፡ የአባቱን ፡ ልብስ ፡ ገልጧልና ፥ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ከማናቸዉቱም ፡ እንስሳ ፡ ጋራ ፡ የሚተኛ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ከአባቱ ፡ ወይም ፡ ከእናቱ ፡ ልጅ ፡ ከእኅቱ ፡ ጋራ ፡ የሚተኛ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ ከዐማቱ ፡ ጋራ ፡ የሚተኛ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ ባልንጀራውን ፡ በስውር ፡ የሚመታ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ የንጹሑን ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ለመግደል ፡ ጕቦ ፡ የሚቀበል ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ የማያጸና ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አሜን ፡ ይላሉ ።

——————ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። ——————

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ብትሰማ ፥ ዛሬም ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ትእዛዙን ፡ ኹሉ ፡ ብታደርግ ፡ ብትጠብቅም ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርግኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ የአምላክኽንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ብትሰማ ፡ እነዚህ ፡ በረከቶች ፡ ኹሉ ፡ ይመጡልኻል ፤ ያገኙኽማል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ አንተ ፡ በከተማ ፡ ቡሩክ ፡ ትኾናለኽ ፥ በዕርሻም ፡ ቡሩክ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ የሆድኽ ፡ ፍሬ ፥ የምድርኽም ፡ ፍሬ ፥ የከብትኽም ፡ ፍሬ ፥ የላምኽም ፡ ርቢ ፥ የበግኽም ፡ ርቢ ፡ ቡሩክ ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ እንቅብኽና ፡ ቡሓቃኽ ፡ ቡሩክ ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ አንተም ፡ በመግባትኽ ፡ ቡሩክ ፡ ትኾናለኽ ፥ በመውጣትኽም ፡ ቡሩክ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በላይኽ ፡ የሚቆሙትን ፡ ጠላቶችኽን ፡ በፊትኽ ፡ የተመቱ ፡ ያደርጋቸዋል ፤ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ይመጡብኻል ፥ በሰባትም ፡ መንገድ ፡ ከፊትኽ ፡ ይሸሻሉ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ በረከቱ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ በጐተራኽ ፡ በእጅኽም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንዲወርድ ፡ ያዛል ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጥኽም ፡ ምድር ፡ ይባርክኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ብትጠብቅ ፥ በመንገዱም ፡ ብትኼድ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማለልኽ ፡ ለርሱ ፡ የተቀደሰ ፡ ሕዝብ ፡ አድርጎ ፡ ያቆምኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ የምድር ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፡ አይተው ፡ ይፈሩኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ርኲን ፡ ይሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶችኽ ፡ በማለላቸው ፡ በምድርኽ ፡ ላይ ፥ በሆድኽ ፡ ፍሬ ፥ በከብትኽ ፡ ፍሬ ፥ በዕርሻኽም ፡ ፍሬ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጎነቱን ፡ በላይኽ ፡ ያበዛል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለምድርኽ ፡ በወራቱ ፡ ዝናብ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፥ የእጅኽንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ መዝገብ ፡ ሰማዩን ፡ ይከፍትልኻል ፤ ለብዙ ፡ አሕዝብም ፡ ታበድራለኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ከማንም ፡ አትበደርም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ 14 ፤ ዛሬም ፡ ያዘዝኹኽን ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰምተኽ ፡ ብትጠብቃት ፡ ብታደርጋትም ፥ ዛሬም ፡ ካዘዝኹኽ ፡ ከነዚህ ፡ ቃሎች ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ ባትል ፥ ታመልካቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ባትከተል ፥ እግዚአብሔር ፡ ራስ ፡ ያደርግኻል ፡ እንጂ ፡ ኋራት ፡ አያደርግኽም ፤ ኹልጊዜም ፡ በላይ ፡ እንጂ ፡ በታች ፡ አትኾንም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ባትሰማ ፥ ዛሬም ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ኹሉ ፡ ባትጠብቅ ፡ ባታደርግም ፥ እነዚህ ፡ መርገሞች ፡ ኹሉ ፡ ይመጡብኻል ፡ ያገኙኽማል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ በከተማ ፡ ርጉም ፡ ትኾናለኽ ፥ በዕርሻም ፡ ርጉም ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ እንቅብኽና ፡ ቡሓቃኽ ፡ ርጉም ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ የሆድኽ ፡ ፍሬ ፥ የምድርኽም ፡ ፍሬ ፥ የላምኽም ፡ ርቢ ፥ የበግኽም ፡ ርቢ ፡ ርጉም ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ አንተ ፡ በመግባትኽ ፡ ርጉም ፡ ትኾናለኽ ፥ በመውጣትኽም ፡ ርጉም ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ እኔን ፡ ስለ ፡ ተውኸኝ ፥ ስለሥራኽ ፡ ክፋት ፥ እስክትጠፋ ፡ ፈጥነኽም ፡ እስክታልቅ ፡ ድረስ ፡ በምትሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርገምን ፥ ሽሽትን ፥ ተግሣጽን ፡ ይሰድ፡ብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ ከምትገባባት ፡ ምድር ፡ እስኪ፡ያጠፋኽ ፡ ድረስ ፡ ቸነፈርን ፡ ያጣብቅብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ በክሳት ፥ በንዳድም ፥ በጥብሳትም ፥ በትኵሳትም ፥ በድርቅም ፥ በዋግም ፥ በዐረማሞም ፡ ይመታኻል ፤ እስክትጠፋም ፡ ድረስ ፡ ያሳድዱኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ በራስኽም ፡ ላይ ፡ ሰማይ ፡ ናስ ፡ ይኾንብኻል ፥ ከእግርኽም ፡ በታች ፡ ምድሪቱ ፡ ብረት ፡ ትኾንብኻለች ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ የምድርኽን ፡ ዝናብ ፡ ትቢያና ፡ ዐፈር ፡ ያደርጋል ፤ እስክትጠፋ ፡ ድረስ ፡ ከሰማይ ፡ ይወርድብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጠላቶችኽ ፡ ፊት ፡ የተመታኽ ፡ ያደርግኻል ፤ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ትወጣባቸዋለኽ ፥ በሰባት ፡ መንገድ ፡ ከነርሱ ፡ ትሸሻለኽ ፤ ለምድርም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ድንጋጤ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ ሬሳኽ ፡ ለሰማይ ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ለምድርም ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናል ፥ የሚያስፈራቸውም ፡

የለም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፈውስ ፡ በሌለው ፡ በግብጽ ፡ ቀኖል ፡ በዕባጭም ፡ በቋቍቻም ፡ በችፌም ፡ ይመታኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔር ፡ በእብደት ፥ በዕውርነት ፥ በድንጋጤም ፡ ይመታኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 29 ፤ በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ ዕውር ፡ በጨለማ ፡ እንደሚርመሰመስ ፡ ትርመሰመሳለኽ ፥ መንገድኽም ፡ የቀና ፡ አይኾንም ፤ በዘመንኽም ፡ ኹሉ ፡ የተጨነቅኽ ፡ የተዘረፍኽም ፡ ትኾናለኽ ፥ የሚያድንኽም ፡ የለም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 30 ፤ ሚስት ፡ ታጫለኽ ፥ ሌላም ፡ ሰው ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ይተኛል ፤ ቤት ፡ ትሠራለኽ ፥ አትቀመጥበትም ፤ ወይን ፡ ትተክላለኽ ፥ ከርሱም ፡ አትበላም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 31 ፤ በሬኽ ፡ በፊትኽ ፡ ይታረዳል ፥ ከርሱም ፡ አትበላም ፤ አህያኽ ፡ ከእጅኽ ፡ በግድ ፡ ይወሰዳል ፥ ወዳንተም ፡ አይመለስም ፤ በግኽ ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ትሰጣለች ፥ የሚያድንኽም ፡ አታገኝም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 32 ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽ ፡ ለሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ይሰጣሉ ፥ ዐይኖችኽም ፡ ያያሉ ፥ ኹልጊዜም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ሲባክኑ ፡ ያልቃሉ ፤ በእጅኽም ፡ ኀይል ፡ ምንም ፡ አይገኝም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 33 ፤ የምድርኽን ፡ ፍሬ ፡ ድካምኽንም ፡ ኹሉ ፡ የማታውቀው ፡ ሕዝብ ፡ ይበላዋል ፤ አንተም ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ የተጨነቅኽ ፡ የተገፋኽም ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 34 ፤ ዐይኖችኽም ፡ ከሚያዩት ፡ የተነሣ ፡ እብድ ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፈውስ ፡ በሌለው ፡ በክፉ ፡ ቀኖል ፡ ጕልበትኽንና ፡ ጭንኽን ፡ ከእግርኽ ፡ ጫማ ፡ እስከ ፡ ዐናትኽ ፡ ድረስ ፡ ይመታኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 36 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አንተን ፡ ባንተም ፡ ላይ ፡ የምታነግሠውን ፡ ንጉሥ ፡ አንተና ፡ አባቶችኽ ፡ ወዳላወቃቸኧቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይወስድኻል ፤ በዚያም ፡ ሌላዎችን ፡ የዕንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ አማልክት ፡ ታመልካለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሚያገባኽ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኹሉ ፡ ድንጋጤ ፡ ምሳሌም ፡ ተረትም ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 38 ፤ እጅግ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ዕርሻ ፡ ታወጣለኽ ፤ አንበጣም ፡ ይበላዋልና ፥ ጥቂት ፡ ትሰበስባለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 39 ፤ ወይን ፡ ትተክላለኽ ፡ ታበጀውማለኽ ፤ ትልም ፡ ይበላዋልና ፥ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አትሰበስብም ፥ የወይን ፡ ጠጁንም ፡ አትጠጣም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 40 ፤ የወይራ ፡ ዛፍ ፡ በአገርኽ ፡ ኹሉ ፡ ይኾንልኻል ፤ ወይራኽም ፡ ይረግፋልና ፥ ዘይቱን ፡ አትቀባም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 41 ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይወለዱልኻል ፤ በምርኮም ፡ ይኼዳሉና ፡ ለአንተ ፡ አይኾኑልኽም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 42 ፤ ዛፍኽን ፡ ኹሉ ፡ የምድርኽንም ፡ ፍሬ ፡ ኵብኵባ ፡ ይወርሰዋል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 43 ፤ ባንተ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ መጻተኛ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ አንተም ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ ትላለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 44 ፤ ርሱ ፡ ያበድርኻል ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አታበድረውም ፤ ርሱ ፡ ራስ ፡ ይኾናል ፥ አንተም ፡ ኀራት ፡ ትኾናለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 45 ፤ የአምላክኽንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስላልሰማኽ ፥ ያዘዘኽንም ፡ ትእዛዙንና ፡ ሥርዐቱን ፡ ስላልጠበቅኽ ፥ እስክትጠፋ ፡ ድረስ ፡ እነዚህ ፡ መርገሞች ፡ ኹሉ ፡ ይወርዱብኻል ፥ ያሳድዱኽማል ፥ ያገኙኽማል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 46 ፤ ባንተም ፡ በልጅ ፡ ልጅኽም ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ለምልክትና ፡ ለድንቅ ፡ ይኾናሉ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 47 ፤ ኹሉን ፡ አብዝቶ ፡ ስለ ፡ ሰጠኽ ፡ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍሥሓና ፡ በሐሤት ፡ አላመለክኽምና ፡

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 48 ፤ በራብና ፡ በጥማት ፡ በዕራቍትነትም ፡ ኹሉንም ፡ በማጣት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚልክብኽ ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ትገዛለኽ ፤ እስኪያጠፋኽም ፡ ድረስ ፡ በዐንገትኽ ፡ ላይ ፡ የብረት ፡ ቀንበር ፡ ይጭናል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 49 ፤ 50 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቋንቋቸውን ፡ የማታውቀውን ፥ ፊታቸው ፡ የደነደነውን ፥ ሽማግሌውንም ፡ የማያፍሩትን ፥ ሕፃኑንም ፡ የማይምሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ንስር ፡ እንደሚበር ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ያመጣብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 51 ፤ እስክትጠፋ ፡ ድረስ ፡ የከብትኽን ፡ ፍሬ ፡ የምድርኽንም ፡ ፍሬ ፡ ይበላሉ ፤ እስኪያጠፉኽም ፡ ድረስ ፡ እኽልን ፡ የወይንም ፡ ጠጅ ፡ ዘይትንም ፡ የላምኽንና ፡ የበግኽን ፡ ርቢ ፡ አይተዉልኽም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 52 ፤ በአገርኽ ፡ ኹሉ ፡ ያሉ ፥ ትታመንባቸው ፡ የነበሩ ፥ የረዘሙ ፡ የጸኑም ፡ ቅጥሮች ፡ እስኪፈርሱ ፡ ድረስ ፥ በከተማዎችኽ ፡ ደጆች ፡ ኹሉ ፡ ከዕው ፡ ያስጭንቁኻል ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠኽ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በደጆች ፡ ኹሉ ፡ ከዕው ፡ ያስጨንቁኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 53 ፤ ጠላቶችኽም ፡ ከዕው ፡ ባስጨነቁኽና ፡ መከራ ፡ ባሳዩኽ ፡ ጊዜ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጥኽን ፡ የሆድኽን ፡ ፍሬ ፡ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ልጆችኽን ፡ ሥጋ ፡ ትበላለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 54 ፤ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ የተለሳለሰና ፡ በቅምጥልነት ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ በወንድሙ ፥ ዐቅፋውም ፡ በምትተኛ ፡ በሚስቱ ፥ በቀሩትም ፡ ልጆች ፡ ይቀናል ፤

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 55 ፤ በደጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ጠላቶችኽ ፡ ከዕው ፡ ባስጨነቁኽና ፡ መከራ ፡ ባሳዩኽ ፡ ጊዜ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ የቀረው ፡ የለምና ፡ ከሚበላው ፡ ከልጆቹ ፡ ሥጋ ፡ ለአንዱ ፡ አይሰጥም ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 56 ፤ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለችው ፡ የተለሳለሰችና ፡ በቅምጥልነት ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ትኖር ፡ የነበረችው ፥ ከልስላሴና ፡ ከቅምጥልነት ፡ የተነሣ ፡ የእግር ፡ ጫማዋን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያላደረገችው ፡ ሴት ፥ ዐቅፋ ፡ በተኛችው ፡ ባሏ ፥

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 57 ፤ በወንድና ፡ በሴት ፡ ልጇም ፥ በእግሯ ፡ መካከል ፡ በሚወጣው ፡ በእንግዴ ፡ ልጅ ፥ በምትወልዳቸውም ፡ ልጆች ፡ ትቀናለች ፤ በደጆችኽም ፡ ውስጥ ፡ ጠላቶችኽ ፡ ከዕው ፡ ባስጨነቁኽና ፡ መከራ ፡ ባሳዩኽ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ ስላጣች ፡ በስውር ፡ ትበላቸዋለች ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 58 ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ባትጠብቅ ፥ ይህንም ፡ "አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር" ፡ የተባለውን ፡ የተመሰገነውንና ፡ የተፈራውን ፡ ስም ፡ ባትፈራ ፥

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 59 ፤ እግዚአብሔር ፡ መቅሠፍትኽን ፥ የዘርኽንም ፡ መቅሠፍት ፥ ብዙ ፡ ዘመንም ፡ የሚኖረውን ፡ ታላቅ ፡ መቅሠፍት ፥ ብዙ ፡ ዘመን ፡ የሚኖረውንም ፡ ክፉ ፡ ደዌ ፡ ያደርግብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 60 ፤ የፈራኸውንም ፡ የግብጽ ፡ ደዌ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያመጣብኻል ፥ ይጣበቅብኽማል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 61 ፤ ደግሞም ፡ ይህ ፡ ሕግ ፡ ባለበት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ያልተጻፈውን ፡ ደዌ ፡ ኹሉ ፡ መቅሠፍትም ፡ ኹሉ ፡ እስክትጠፋ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያመጣብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 62 ፤ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማችኹምና ፡ ከብዛታችኹ ፡ የተነሣ ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ የነበረው ፡ ቍጥራችኹ ፡ ጥቂት ፡ ኾኖ ፡ ይቀራል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 63 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ያደርግላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ያበዛችኹም ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያጠፋችኹ ፡ ሊያፈርሳችኹም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ትወርሷትም ፡ ዘንድ ፡ ከምትገቡባት ፡ ምድር ፡ ትነቀላላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 64 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳርቻዋ ፡ ድረስ ፡ ወዳሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይበትንኻል ፤ በዚያም ፡ አንተና ፡ አባቶችኽ ፡ ያላወቃችኋቸውን ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፥ ዕንጨትንና ፡ ድንጋይን ፥ ታመልካለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 65 ፤ በእነዚያም ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ዕረፍት ፡ አታገኝም ፥ ለእግርኽም ፡ ጫማ ፡ ማረፊያ ፡ አይኾንም ፤ በዚያም ፡ እግዚአብሔር ፡ ተንቀጥቃጭ ፡ ልብ ፥ ፈዛዛ ፡ ዐይን ፥ ደካማም ፡ ነፍስ ፡ ያመጣብኻል ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 66 ፤ ነፍስኽም ፡ ታመነታለች ፤ ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ ትፈራለኽ ፥ በሕይወትኽም ፡ አትታመንም ፤

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 67 ፤ አንተ ፡ ስለፈራኽበት ፡ ስለልብኽ ፡ ፍርሀት ፥ በዐይንኽም ፡ ስለምታየው ፡ አስተያየት ፥ ማለዳ ፦ መቼ ፡ ይመሻል ፧ ትላለኽ ፤ ማታም ፦ መቼ ፡ ይነጋል ፧ ትላለኽ ።

ዘዳ. ፡ 28 ፡ 68 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ተመልሰኽ ፡ አታያትም ፡ ባልኹኽ ፡ መንገድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመልስኻል ፤ በዚያም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎች ፡ ትኾኗቸው ፡ ዘንድ ፡ ለጠላቶቻችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ ትሸጣላችኹ ፤ የሚገዛችኹም ፡ አይገኝም ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ በኮሬብ ፡ ካደረገው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ሌላ ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘው ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ቃሎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ ሙሴም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ጠርቶ ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ በፊታችኹ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ በምድሩም ፡ ኹሉ ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ ዐይኖቻችኹ ፡ ያይዋቸውን ፡ ታላላቆች ፡ ፈተናዎች ፥ ታላላቆች ፡ ተአምራትና ፡ ድንቆች ፥ አይታችኋል ፤

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አስተዋይ ፡ ልብ ፥ የሚያዩ ፡ ዐይኖች ፥ የሚሰሙም ፡ ጆሮዎች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አልሰጣችኹም ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ አርባ ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መራኋችኹ ፤ ልብሳችኹም ፡ አላረጀባችኹም ፥ ጫማችኹም ፡ በእግራችኹ ፡ ላይ ፡ አላረጀም ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንጀራ ፡ አልበላችኹም ፥ የወይን ፡ ጠጅና ፡ የሚያሰክረውን ፡ መጠጥ ፡ አልጠጣችኹም ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ በመጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ የሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎን ፡ የባሳንም ፡ ንጉሥ ፡ ዐግ ፡ ሊወጉን ፡ ወጡብን ፥ እኛም ፡ መታናቸው ፤

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ምድራቸውንም ፡ ወስደን ፡ ለሮቤልና ፡ ለጋድ ፡ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስት ፡ አድርገን ፡ ሰጠናቸው ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ በምታደርጉት ፡ ሹሉ ፡ ትከናወኑ ፡ ዘንድ ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃሎች ፡ ጠብቁ ፡ አድርጉም ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ 11 ፤ ሹላችኹ ፥ አለቃዎቻችኹም ፡ ነገዶቻችኹም ፡ ሽማግሌዎቻችኹም ፡ ሹማምቶቻችኹም ፥ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ልጆቻችኹም ፡ ሴቶቻችኹም ፡ በሰፈራችኹም ፡ ያለ ፡ ዕንጨትኽን ፡ የሚቈርጥ ፡ ውሃኽንም ፡ የሚቀዳ ፡ መጻተኛ ፥ ዛሬ ፡ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆማችኋል ፤

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ 13 ፤ ይኸውም ፡ ዛሬ ፡ ለርሱ ፡ ሕዝብ ፡ አድርጎ ፡ ያስነሣኽ ፡ ዘንድ ፥ ርሱም ፡ ለአንተ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ለአባቶችኽም ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ እንደ ፡ ማለ ፡ አምላክ ፡ ይኾንልኽ ፡ ዘንድ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ዛሬ ፡ በሚያደርገው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ትገባ ፡ ዘንድና ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሐላ ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ እኔም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኪዳንና ፡ ይህን ፡ መሐላ ፡ የማደርገው ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዛሬ ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ ከሚቆም ፡ ሰው ፡ ጋራ ፥ ዛሬም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ ከሌለ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኛ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተቀመጥን ፡ በመካከላቸውም ፡ ባለፋችኹባቸው ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ እንዳለፍን ፡ ዐውቃችኋልና ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ ርኩስነታቸውንም ፡ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ የነበሩትን ፡ የዕንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ የብርና ፡ የወርቅም ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ አይታችኋልና ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ ኼዶ ፡ የእነዚያን ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ያመልክ ፡ ዘንድ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ ዛሬ ፡ የሚያስት ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ወገን ፡ ወይም ፡ ነገድ ፡ አይኑርባችኹ ፤ ሐሞትና ፡ ሬትም ፡ የሚያበቅል ፡ ሥር ፡ አይኹንባችኹ ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ የዚህንም ፡ ርግማን ፡ ቃሎች ፡ የሰማ ፡ ሰው ፦ ምንም ፡ እንኳ ፡ በልቤ ፡ ደንዳናነት ፡ ብኼድ ፥ ለጥማቴም ፡ ስካር ፡ ብጨምር ፥ ሰላም ፡ ይኾንልኛል ፡ ብሎ ፡ ሰውነቱን ፡ በልቡ ፡ የሚባርክ ፡ ቢኖር ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ቅንአቱም ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይጤሳል ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታ ፡ አያደርግለትም ፤ በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈው ፡ ርግማን ፡ ሹሉ ፡ በላዩ ፡ ይኖራል ፥ እግዚአብሔርም ፡ ስሙን ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ይደመስሰዋል ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚህ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈው ፡ እንደ ፡ ቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ርግማን ፡ ሹሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ሹሉ ፡ ለጥፋት ፡ ይለየዋል ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሚነሣ ፡ ትውልድ ፡ ከእናንተም ፡ በኋላ ፡ የሚኾኑ ፡ ልጆቻችኹ ፡ ከሩቅ ፡ አገርም ፡ የሚመጣ ፡ እንግዳ ፥ የዚህን ፡ አገር ፡ መቅሠፍት ፥ እግዚአብሔርም ፡ በርሷ ፡ ያደረገውን ፡ ሥቃይዋን ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ ምድርም ፡ በሹለንተናዋ ፡ ዲንና ፡ ጨው ፡ መቃጠልም ፡ እንደ ፡ ኾነባት ፥ እንዳትዘራም ፡ እንዳታበቅልም ፥ ማናቸውም ፡ ሣርና ፡ ልምላሜም ፡ እንዳይወጣባት ፥ እግዚአብሔር ፡ በቍጣውና ፡ በመዓቱ ፡ እንደ ፡ ገለባበጣቸው ፡ እንደ ፡ ሰዶምና ፡ ገሞራ ፡ እንደ ፡ አዳማና ፡ እንደ ፡ ሲባዮ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ አሕዛብ ፡ ሹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ አደረገ ፧ ይህስ ፡ የቍጣው ፡ ታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይላሉ ።

ዘዳ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ ሰዎችም ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ፦ የአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡

ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፥

ዘዳ. ፥ 29 ፥ 26 ፤ ኼደውም ፡ የማያውቋቸውንና ፡ ያልታዘዙትን ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ስላመለኩና ፡ ስለ ፡ ሰገዱላቸው ፥

ዘዳ. ፥ 29 ፥ 27 ፤ ስለዚህ ፥ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ መርገም ፡ ኹሉ ፡ ያወርድባት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ነደደ ፤

ዘዳ. ፥ 29 ፥ 28 ፤ ዛሬም ፡ እንዳሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቍጣና ፡ በመቅሠፍት ፡ በታላቅም ፡ መዓት ፡ ከምድራቸው ፡ ነቀላቸው ፥ ወደ ፡ ሌላም ፡ ምድር ፡ ጣላቸው ።

ዘዳ. ፥ 29 ፥ 29 ፤ ምስጢሩ ፡ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የተገለጠው ፡ ግን ፡ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለእኛ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ለልጆቻችን ፡ ነው ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እኔ ፡ በፊትኽ ፡ ያኖርኹት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ በረከቱና ፡ መርገሙ ፥ በወረደብኽ ፡ ጊዜ ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚበትንኽ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ኾነኽ ፡ በልብኽ ፡ ባሰብኸው ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 2 ፤ ወደ ፡ አምላክኽም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሰኽ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ እንደማዝኽ ፡ ኹሉ ፡ አንተና ፡ ልጆችኽ ፡ በፍጹም ፡ ልብና ፡ በፍጹም ፡ ነፍስ ፡ ለቃሉ ፡ በታዘዝኽ ፡ ጊዜ ፥

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 3 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምርኮኽን ፡ ይመልሳል ፡ ይራራልኽማል ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ ከበተነበት ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ መልሶ ፡ ይሰበስብኻል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 4 ፤ ሰዎችኽም ፡ እስከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ፈልሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚያ ፡ ይሰበስብኻል ፥ ከዚያም ፡ ያመጣኻል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 5 ፤ አባቶችኽም ፡ ወደወረሷት ፡ ምድር ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጋባኻል ፥ ትወርሳትማለኽ ፤ መልካምም ፡ ያደርግልኻል ፥ ከአባቶችኽም ፡ ይልቅ ፡ ያበዛኻል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 6 ፤ በሕይወትም ፡ እንድትኖር ፥ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስኽ ፡ እንድትወድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልብኽን ፡ የዘርኽንም ፡ ልብ ፡ ይገርዛል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 7 ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ መርገም ፡ ኹሉ ፡ በጠላቶችኽና ፡ በሚጠሉኽ ፡ በሚያሳድዱኽም ፡ ላይ ፡ ያመጣታል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 8 ፤ አንተም ፡ ተመልሰኽ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ትሰማለኽ ፥ ዛሬም ፡ እኔ ፡ የማዝኽን ፡ ትእዛዙን ፡ ኹሉ ፡ ታደርጋለኽ ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 9 ፤ 10 ፤ የአምላክኽንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ብትሰማ ፥ በዚህም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ትእዛዙንና ፡ ሥርዐቱን ፡ ብትጠብቅ ፥ በፍጹምም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስኽ ፡ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትመለስ ፥ እግዚአብሔር ፡ በአባቶችኽ ፡ ደስ ፡ እንዳለው ፡ በመልካሙ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለዋልና ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጅኽ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በሆድኽም ፡ ፍሬ ፡ በከብትኽም ፡ ፍሬ ፡ በዕርሻኽም ፡ ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ይባርክኻል ።

ዘዳ. ፥ 30 ፥ 11 ፤ እኔ ፡ ዛሬ ፡ የማዝኽ ፡ ይህች ፡ ትእዛዝ ፡ ከባድ ፡ አይደለችም ፥ ከአንተም ፡ የራቀች ፡ አይደለችም ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ ሰምተን ፡ እናደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጥቶ ፡ ርሷን ፡ የሚያመጣልን ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንዳትል ፡ በሰማይ ፡ አይደለችም ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ሰምተን ፡ እናደርጋት ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ባሕሩን ፡ ተሻግሮ ፡ ርሷን ፡ የሚያመጣልን ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንዳትል ፡ ከባሕሩ ፡ ማዶ ፡ አይደለችም ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ቃሉ ፡ በአፍኽና ፡ በልብኽ ፡ ውስጥ ፡ ለአንተ ፡ እጅግ ፡ ቅርብ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ተመልከት ፤ ዛሬ ፡ በፊትኽ ፡ ሕይወትንና ፡ መልካምነትን ፥ ሞትንና ፡ ክፋትን ፡ አኑሬያለኹ ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ በሕይወትም ፡ እንድትኖር ፡ እንድትባዛም ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ልትወርሳት ፡ በምትገባባት ፡ ምድር ፡ እንዲባርክኽ ፥ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፥ በመንገዱም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙንና ፡ ሥርዐቱን ፡ ፍርዱንም ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እኔ ፡ አዝኻለኹ ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ ልብኽ ፡ ግን ፡ ቢስት ፡ አንተም ፡ ባትሰማ ፥ ብትታለልም ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ብትሰግድ ፡ ብታመልካቸውም ፥

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ ፈጽማችኹ ፡ እንድትጠፉ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ እነግራችኋለኹ ፤ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግረኽ ፡ ትወርሳት ፡ ዘንድ ፡ በምትገባባት ፡ ምድር ፡ ዘመናችኹን ፡ አታስረዝሙም ።

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ በፊታችኹ ፡ ሕይወትንና ፡ ሞትን ፡ በረከትንና ፡ መርገምን ፡ እንዳስቀመጥኹ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አስመሰክራለኹ ፤ እንግዲህ ፡ አንተና ፡ ዘርኽ ፡ በሕይወት ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ሕይወትን ፡ ምረጥ ፤

ዘዳ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአባቶችኽ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ እንዲሰጣቸው ፡ በማለላቸው ፡ በምድሪቱ ፡ ትቀመጥ ፡ ዘንድ ፥ ርሱ ፡ ሕይወትኽ ፡ የዘመንኽም ፡ ርዝመት ፡ ነውና ፥ አምላክኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወደው ፡ ትጠባበቀውም ፡ ቃሉንም ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ምረጥ ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ ኼዶ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ነገረ ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ አላቸውም ፦ እኔ ፡ ዛሬ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ኾኖኛል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እወጣና ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ አትሻገርም ፡ ብሎኛል ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ በፊትኽ ፡ ያልፋል ፤ ርሱ ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ ከፊትኽ ፡ ያጠፋቸዋል ፡ ትወርሳቸውማለኽ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢያሱ ፡ በፊትኽ ፡ ይሻገራል ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባጠፋቸው ፡ በአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ በሴዎንና ፡ በዐግ ፡ በምድራቸውም ፡ እንዳደረገ ፡ ያደርግባቸዋል ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፊታችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ይጥላቸዋል ፥ እንዳዘዝኋችኹም ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ታደርጉባቸዋላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ ጽኑ ፥ አይፈሯችኹ ፥ አትፍሩ ፥ ከፊታቸውም ፡ አትደንግጡ ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኼዳል ፤ አይጥልኽም ፥ አይተውኽም ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ ኢያሱን ፡ ጠርቶ ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፦ አንተ ፡ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እንዲሰጥ ፡ ወደማለላቸው ፡ ምድር ፡ ትገባለኽና ፥ ርሷንም ፡ ለእነርሱ ፡ ታወርሳለኽና ፡
ጽና ፥ አይዞኽ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 8 ፤ በፊትኽም ፡ የሚኼድ ፡ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡
ይኾናል ፥ አይጥልኽም ፥ አይተውኽም ፤ አትፍራ ፥ አትደንግጥ ፡ አለው ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 9 ፤ ሙሴም ፡ ይህችን ፡ ሕግ ፡ ጻፈ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ይሸከሙ ፡
ለነበሩት ፡ ለሌዊ ፡ ልጆች ፡ ለካህናቱ ፡ ለእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰጣት ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 10 ፤ ሙሴም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፥ በዕዳ ፡ ምሕረት ፡
ዘመን ፥ በዳስ ፡ በዓል ፥

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 11 ፤ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፡ ርሱ ፡ በመረጠው ፡
ስፍራ ፡ ሲከማች ፥ ይህን ፡ ሕግ ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ በጕሮው ፡ አንሰው ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 12 ፤ ይሰሙና ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፥ አምላካችኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ፥ የዚህንም ፡ ሕግ ፡
ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ጠብቀው ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ሕፃናትንም ፡ በአገራችኹ ፡ ደጅ ፡
ያለውንም ፡ መጻተኛ ፡ ሰብስብ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 13 ፤ የሕግ ፡ ቃላት ፡ የማያውቁ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግራችኹ ፡ ልትወርሷት ፡
በምትኼዱባት ፡ ምድር ፡ በምትኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይስሙ ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ መፍራት ፡ ይማሩ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፦ የምትሞትበት ፡ ቀን ፥ እንሆ ፥ ቀረበ ፤ ኢያሱን ፡ ጠርተኽ ፡ ርሱን ፡
አዘው ፡ ዘንድ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቁም ፡ አለው ። ሙሴና ፡ ኢያሱም ፡ ኼደው ፡
በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ቆሙ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፡ ተገለጠ ፤ የደመናውም ፡ ዐምድ ፡
በድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ ከአባቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ትተኛለኽ ፤ ይህም ፡ ሕዝብ ፡
ይነሣል ፥ ይቀመጥባትም ፡ ዘንድ ፡ በሚኼድባት ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከትሎ ፡
ያመነዝራል ፥ እኔንም ፡ ይተወኛል ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያፈርሳሉ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 17 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ቍጣዬ ፡ ይነድባቸዋል ፥ እተዋቸውማለኹ ፥ ፊቴንም ፡
እሰውርባቸዋለኹ ፥ ለአሕዛብ ፡ መብል ፡ ይኾናሉ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡
የለምና ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አገኘን ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገርና ፡ ጭንቀት ፡ ይደርስባቸዋል ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 18 ፤ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከትለዋልና ፥ ስላደረጉት ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፈጽሜ ፡
ፊቴን ፡ እሰውራለኹ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 19 ፤ አኹንም ፡ ይህችን ፡ መዝሙር ፡ ለእናንተ ፡ ጻፉ ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡
አስተምሯቸው ፤ ይህችም ፡ መዝሙር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ትኾንልኝ ፡ ዘንድ ፡ በአፋቸው ፡ አድርጓት ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 20 ፤ ለአባቶቻቸው ፡ ወደማልኹላቸው ፥ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈሰው ፡ ምድር ፡ ካገባኋቸው ፡
በኋላ ፥ ከበሉም ፡ ከጠገቡም ፡ ከደነደኑም ፡ በኋላ ፥ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከትለው ፡ ያመልካሉ ፥ እኔንም ፡
ይንቃሉ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ያፈርሳሉ ።

ዘዳ. ፥ 31 ፥ 21 ፤ ዛሬ ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ገና ፡ ሳላገባቸው ፡ የሚያስቡትን ፡ ዐሳብ ፡
ዐውቃለኹና ፥ ከልጆቻቸውም ፡ አፍ ፡ አትረሳምና ፡ ብዙ ፡ ክፉ ፡ ነገርና ፡ ጭንቀት ፡ በደረሰባቸው ፡ ጊዜ ፡ ይህች ፡

መዝሙር ፡ ምስክር ፡ ኾና ፡ በፊታቸው ፡ ትመሰክራለች ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 22 ፤ ሙሴም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ይህችን ፡ መዝሙር ፡ ጻፈ ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ አስተማራት ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 23 ፤ የነዌንም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ታገባለኽና ፡ ጽና ፥ አይዞኽ ፤ እኔም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሙሴ ፡ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ በመጽሐፍ ፡ ከጻፈ ፡ ከፈጸመም ፡ በኋላ ፥

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 25 ፤ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ የሚሸከሙትን ፡ ሌዋውያንን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 26 ፤ ይህን ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ውሰዱ ፥ በዚያም ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፡ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ አጠገብ ፡ አኑሩት ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 27 ፤ እኔ ፡ ዐመፃችኹንና ፡ የዐንገታችኹን ፡ ድንዳኔ ፡ ዐውቃለኹና ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ በሕይወት ፡ ሳለኹ ፡ እናንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ዐምፃችኋል ፤ ይልቁንስ ፡ ከሞትኹ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ፧

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 28 ፤ ይህን ፡ ቃል ፡ በጐሯቸው ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፥ ሰማይንና ፡ ምድርንም ፡ አስመሰክርባቸው ፡ ዘንድ ፡ የነገዶቻችኹን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ አለቃዎቻችኹንም ፡ ሰብስቡልኝ ፤

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 29 ፤ ከሞትኹ ፡ በኋላ ፡ ፈጽማችኹ ፡ እንድትረክሱ ፥ ካዘዝኋችኹም ፡ መንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ እንድትሉ ፡ ዐውቃለኹና ። በእጃችኹም ፡ ሥራ ፡ ታስቈጡት ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ስላደረጋችኹ ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያገኛችኋል ።

ዘዳ. ፡ 31 ፡ 30 ፤ ሙሴም ፡ በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ዦሮ ፡ የዚች ፡ መዝሙር ፡ ቃሎች ፡ እስኪፈጸሙ ፡ ድረስ ፡ ተናገረ ።

_____ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ። _____

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፥ እኔም ፡ እናገራለኹ ፤

ምድርም ፡ የአፌን ፡ ቃሎች ፡ ትስማ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ ትምህርቴ ፡ እንደ ፡ ዝናብ ፡ ትፈሳለች ፥

ነገሬ ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ ትንጠባጠባለች ፤

በልምላሜ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጤዛ ፥

በሣርም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ካፊያ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጠራለኹና ፤

ለአምላካችን ፡ ታላቅነትን ፡ ስጡ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ሥራውም ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤

መንገዱም ፡ ኹሉ ፡ የቀና ፡ ነው ፤

የታመነ ፡ አምላክ ፥ ክፋትም ፡ የሌለበት ፥

ርሱ ፡ እውነተኛና ፡ ቅን ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 5 ፤ እነርሱ ፡ ረከሱ ፤ ልጆቹም ፡ አይደሉም ፤

ነውርም ፡ አለባቸው ፤ ጠማማና ፡ ገልበጥባጣ ፡ ትውልድ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 6 ፤ ደንቈሮ ፡ ብልኀተኛም ፡ ያልኾንኽ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥

ለእግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ትመልሳለኽ ፧

የገዛኽ ፡ አባትኽ ፡ አይደለምን ፧

የፈጠረኽና ፡ ያጸናኽ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 7 ፤ የዱሮውን ፡ ዘመን ፡ ዐስብ ፥

የብዙ ፡ ትውልድንም ፡ ዓመታት ፡ አስተውል ፤

አባትኽን ፡ ጠይቅ ፥ ያስታውቅኽማል ፤

ሽማግሌዎችኽን ፡ ጠይቅ ፥ ይነግሩኽማል ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 8 ፤ ልዑል ፡ ለአሕዛብ ፡ ርስታቸውን ፡ ባወረሰ ፡ ጊዜ ፥

የአዳምን ፡ ልጆች ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፥

እንደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡

የአሕዛብን ፡ ድንበር ፡ አቆመ ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ሕዝቡ ፡ ነው ፤

ያዕቆብም ፡ የርስቱ ፡ ገመድ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 10 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ በጥማት ፥

የነፋስ ፡ ጩኸትም ፡ በሞላበት ፡ ውድማ ፡ አገኘው ፤

ከበበው ፡ ተጠነቀቀለትም ፤

እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌን ፡ ጠበቀው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 11 ፤ ንስር ፡ ጫጩቶቹን ፡ እንደሚያወጣ ፥

በእነርሱም ፡ ላይ ፡ እንደሚሰፍ ፥

ክንፎቹን ፡ ዘርግቶ ፡ ወሰዳቸው ፥

በክንፎቹም ፡ ዐዘላቸው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ብቻውን ፡ መራው ፤

ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አልነበረም ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ በምድር ፡ ከፍታ ፡ ላይ ፡ አወጣው ፤

የዕርሻውን ፡ ፍሬ ፡ በላ ፤

ከአለትም ፡ ድንጋይ ፡ በሚገኝ ፡ ማር ፥

ከጭንጫውም ፡ ድንጋይ ፡ በሚገኝ ፡ ዘይት ፡ አጠባው ፤

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ የላሙንም ፡ ቅቤ ፥ የመንጋውም ፡ ወተት ፥

ከጠቦት ፡ ስብ ፡ ጋራ ፥

የባሳንንም ፡ አውራ ፡ በግ ፥ ፍየሉንም ፥

ከስንዴ ፡ እሸት ፡ ጋራ ፡ በላኽ ፤

ከወይኑም ፡ ደም ፡ ያለውን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣኽ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ ይሹሩን ([105]) ፡ ወፈረ ፥ ረገጠ ፤

ወፈረ ፥ ደነደነ ፥ ሰባ ፤

የፈጠረውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተወ ፤

የመድኀኒቱንም ፡ አምላክ ፡ ናቀ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ በሌላዎች ፡ አማልክት ፡ አስቀኑት ፥

በርኵሰታቸውም ፡ አስቈጡት ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ላልኾኑ ፡ አጋንንት ፥

ለማያውቋቸውም ፡ አማልክት ፥

በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ለተነሡ ፡ ለዐዲሶች ፡

አባቶቻቸውም ፡ ላልፈሯቸው ፡ አማልክት ፡ ሠዉ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ የወለደኽን ፡ አምላክ ፡ ተውኽ ፥

ያሳደገኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረሳኽ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ስላስቈጡት ፡

እግዚአብሔር ፡ አይቶ ፡ ጣላቸው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ፊቴን ፡ እሰውርባቸዋለኹ ፤

---

105 [ቊ.15 ፤ በዕብራይስጥ ፡ 'ይሹሩን' ፡ የሚለውን ፡ ግእዙ ፡ 'ያዕቆብ' ፡ ይለዋል ።]

ፍጻሜያቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አያለኹ ፤

ጠማማ ፡ ትውልድ ፥

ያልታመኑም ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 21 ፤ አምላክ ፡ ባልኾነው ፡ አስቀኑኝ ፤

በምናምንቴዎቻቸውም ፡ አስቈጡኝ ፤

እኔም ፡ ሕዝብ ፡ ባልኾነው ፡ አስቀናቸዋለኹ ፤

በማያስተውል ፡ ሕዝብ ፡ አስቈጣቸዋለኹ ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 22 ፤ እሳት ፡ ከቍጣዬ ፡ ትነዳለችና ፥

እስከ ፡ ሲኦል ፡ ድረስ ፡ ታቃጥላለች ፥

ምድርንም ፡ ከፍሬዋ ፡ ጋራ ፡ ትበላለች ፥

የተራራዎችን ፡ መሠረት ፡ ታነዳለች ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 23 ፤ መከራን ፡ እጨምርባቸዋለኹ ፤

በፍላጻዎቼም ፡ እወጋቸዋለኹ ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 24 ፤ በራብ ፡ በንዳድ ፡ ይጠፋሉ ፤

በንዳድና ፡ በመራራ ፡ ጥፋት ፡ ያልቃሉ ፤

የአራዊትን ፡ ጥርስ ፥

የምድርንም ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ እሰድባቸዋለኹ ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 25 ፤ ጕልማሳውን ፡ ከድንግል ፥ ሕፃኑንም ፡ ከሽማግሌ ፡ ጋራ ፥

በሜዳ ፡ ሰይፍ ፥ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ድንጋጤ ፡ ያጠፋቸዋል ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 26 ፤ እበትናቸዋለኹ ፡ አልኹ ፤

ከሰዎችም ፡ መካከል ፡ መታሰቢያቸውን ፡ አጠፋለኹ ።

ዘዳ. ፥ 32 ፥ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጠላቶቻቸው ፡ እንዳይታበዩ ።

እጃችን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ፡ እንጂ ፡

እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አላደረገም ፡

እንዳይሉ ፥

ስለጠላቱ ፡ ቍጣ ፡ ፈራኹ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 28 ፤ ምክር ፡ ያጡ ፡ ሕዝብ ፡ ናቸው ፥

ማስተዋልም ፡ የላቸውም ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 29 ፤ አእምሮ ፡ ቢኖራቸው ፥

ይህን ፡ ያስተውሉ ፡ ነበር ፥

ፍጻሜያቸውንም ፡ ያስቡ ፡ ነበር ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 30 ፤ ርሱ ፡ አምላካቸው ፡ ካልሸጣቸው ፥

እግዚአብሔርም ፡ አሳልፎ ፡ ካልሰጣቸው ፥

አንድ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ሺሕን ፡ ያሳድድ ፡ ነበር ፧

ኹለቱሳ ፡ እንዴት ፡ ዐሥሩን ፡ ሺሕ ፡ ያሸሹ ፡ ነበር ፧

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 31 ፤ አምላካችን ፡ እንደ ፡ አማልክታቸው ፡ አይደለም ፤

ጠላቶቻችንም ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 32 ፤ ወይናቸው ፡ ከሰዶም ፡ ወይን ፥

ከገሞራም ፡ ዕርሻ ፡ ነው ፤

ፍሬያቸው ፡ ሐሞት ፡ ነው ፤

ዘለላውም ፡ መራራ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 33 ፤ የወይን ፡ ጠጃቸው ፡ የእባብ ፡ መርዝ ፥

የእፍኝትም ፡ ሥራይ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 34 ፤ ይህ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተጠብቆ ፡ የለምን ፧

በመዝገቤስ ፡ የታተመ ፡ አይደለምን ፧

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 35 ፤ የጥፋታቸው ፡ ቀን ፡ ቀርቧልና ፥

የሚመጣባቸውም ፡ ነገር ፡ ይፈጥናልና ፥

እግራቸው ፡ ሲሰናከል ፡

በቀልና ፡ ፍርድ ፡ የእኔ ፡ ነው ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 36 ፤ ኀይላቸውም ፡ እንደ ፡ ደከመ ፥

የተዘጋ ፡ የተለቀቀም ፡ እንደሌለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡

እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ይፈርዳል ፥

ስለ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ያዝናል ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 37 ፤ ርሱም ፡ ይላል ፦ አማልክታቸው ፡ የት ፡ ናቸው ፧

ይታመኑባቸው ፡ የነበሩት ፡ አማልክት ፧

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 38 ፤ የመሥዋዕታቸውን ፡ ስብ ፡ የበሉ ፥

የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውንም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የጠጡ ፧

እነርሱ ፡ ይነሡ ፥ ይርዷችኹም ፥

መጠጊያም ፡ ይኹኑላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 39 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፥

ከእኔም ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ እዩ ፤

እኔ ፡ እገድላለኹ ፥ አድንማለኹ ፤

እኔ ፡ እመታለኹ ፥ እፈውስማለኹ ፤

ከእጄም ፡ የሚያድን ፡ የለም ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 40 ፤ እጄን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እዘረጋለኹና ፥

እንዲህም ፡ እላለኹ ፦ ለዘለዓለም ፡ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 41 ፤ የሚንቦገቦግ ፡ ሰይፌን ፡ እስለዋለኹ ፥

እጄም ፡ ፍርድን ፡ ትይዛለች ፥

ጠላቶቼንም ፡ እበቀላለኹ ፥

ለሚጠሉኝም ፡ ፍዳቸውን ፡ እከፍላለኹ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 42 ፤ ከተወጉት ፡ ከተማረኩትም ፡ ደም ፥

ፍላጻዎቼን ፡ በደም ፡ አሰክራለኹ ፤

ከጠላት ፡ አለቃዎችም ፡ ራስ ፡

ሰይፌ ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 43 ፤ የባሪያዎቹን ፡ ደም ፡ ይበቀላልና ፥

ጠላቶቹንም ፡ ይበቀላቸዋልና ፥

ምድሪቱንና ፡ ሕዝቡን ፡ ይክሳልና ፥

እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 44 ፤ ሙሴም ፡ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የዚችን ፡ መዝሙር ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ በሕዝቡ ፡ ገሮ ፡ ተናገሩ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 45 ፤ ሙሴም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ተናግሮ ፡ ፈጸመ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 46 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የዚህን ፡ ሕግ ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁና ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ልጆቻችኹን ፡ እንድታዘቡት ፡ ዛሬ ፡ የምመሰክርላችኹን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በልባችኹ ፡ አኑሩት ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 47 ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ሕይወታችኹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለእናንተ ፡ ከንቱ ፡ አይደለምና ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ትወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግራችኹ ፡ በምትገቡባት ፡ ምድር ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ትቀመጣላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 48 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 49 ፤ ወደዚህ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ በዓባሪም ፡ ተራራ ፡ ውስጥ ፡ ወዳለው ፡ ወደናባው ፡ ተራራ ፡ ውጣ ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ የምሰጣቸውን ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ እይ ፤

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 50 ፤ ወንድምኽም ፡ አሮን ፡ በሖር ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ እንደ ፡ ተከማቸ ፥ በወጣኽበት ፡ ተራራ ፡ ሙት ፥ ወደ ፡ ወገኖችኽም ፡ ተከማች ፤

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 51 ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በቃዴስ ፡ ባለው ፡ በመሪባ ፡ ውሃ ፡ ስለ ፡ በደላችኹኝ ፥ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ስላልቀደሳችኹኝ ፥

ዘዳ. ፡ 32 ፡ 52 ፤ ምድሪቱን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ታያለኽ ፡ እንጂ ፡ ወደዚያች ፡ እኔ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደምሰጣቸው ፡ ምድር ፡ አትገባም ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሙሴ ፡ ሳይሞት ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የባረከባት ፡ በረከት ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦

እግዚአብሔር ፡ ከሲና ፡ መጣ ፥

በሴይርም ፡ ተገለጠ ፤

ከፋራን ፡ ተራራ ፡ አበራላቸው ፥

ከአእላፋትም ፡ ቅዱሳኑ ፡ መጣ ፤

በስተቀኙም ፡ የእሳት ፡ ሕግ ፡ ነበረላቸው ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 3 ፤ ሕዝቡንም ፡ ወደዳቸው ፤

ቅዱሳኑ ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽ ፡ ናቸው ፤

በእግሮችኽም ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጡ ፤

ቃሎችኽን ፡ ይቀበላሉ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ ሙሴ ፡ ለያዕቆብ ፡ ጉባኤ ፡ ርስት ፡ የኾነውን ፡

ሕግ ፡ አዘዘን ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ የሕዝቡ ፡ አለቃዎች ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡

ሹሉ ፡ ጋራ ፡ በተከማቹ ፡ ጊዜ ፥

ንጉሥ ፡ በይሹሩን ፡ ነበረ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ ሮቤል ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ፥ አይሙት ፤

ሰዎቹም ፡ በቍጥር ፡ ብዙ ፡ ይኹኑ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ የይሁዳ ፡ በረከት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦

አቤቱ ፥ የይሁዳን ፡ ድምፅ ፡ ስማ ፥

ወደ ፡ ወገኖቹም ፡ አግባው ፤

እጆቹ ፡ ይጠንክሩለት ፤

በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ረዳት ፡ ትኾነዋለኽ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ ስለ ፡ ሌዊም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፥

ቱሚምኽና ፡ ኡሪምኽ ፡ ለቅዱስኽ ፡ ሰው ፡ ነው ፥

በማሣህ ፡ ለፈተንኸው ፥

በመሪባ ፡ ውሃም ፡ ለተከራከርኸው ፤

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ አባቱና ፡ ስለ ፡ እናቱ ፦ አላየኹም ፡ ላለ ፥

ወንድሞቹንም ፡ ላላስተዋለ ፥

ልጆቹንም ፡ ላላወቀ ፤

ቃልኽን ፡ አደረጉ ፥

ቃል ፡ ኪዳንኽንም ፡ ጠበቁ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ ፍርድኽን ፡ ለያዕቆብ ፥

ሕግኽንም ፡ ለእስራኤል ፡ ያስተምራሉ ፤

በፊትኽ ፡ ዕጣንን ፥

በመሠዊያኽም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዋሉ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ ሀብቱን ፡ ባርክ ፥

የእጁንም ፡ ሥራ ፡ ተቀበል ፤

የሚነሣበትን ፡ ወገብ ፡ ውጋው ፥

የሚጠሉትም ፡ አይነሡ ።

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 12 ፤ ስለ ፡ ብንያምም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

በእግዚአብሔር ፡ የተወደደ ፡ በርሱ ፡

ዘንድ ፡ ተማምኖ ፡ ይኖራል ፤

ቀኑን ፡ ሹሉ ፡ ይጋርደዋል ፥

በትከሻውም ፡ መካከል ፡ ያድራል ።

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 13 ፤ ስለ ፡ ዮሴፍም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

ምድሩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፤

በሰማያት ፡ ገናንነት ፡ በጠል ፥

በታችኛውም ፡ ቀላይ ፥

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 14 ፤ በፀሓዩ ፡ ፍሬያት ፡ ገናንነት ፥

በጨረቃውም ፡ መውጣት ፡ ገናንነት ፡

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 15 ፤ በቀደሙትም ፡ ተራራዎች ፡ ከፍተኛነት ፥

በዘለዓለሙም ፡ ኰረብታዎች ፡ ገናንነት ፥

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 16 ፤ በምድሪቱም ፡ ገናንነትና ፡ ሞላዋ ፥

በቀጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ ከነበረው ፡ በረከት ፡

በዮሴፍ ፡ ራስ ፡ ላይ ፥ ከወንድሞቹም ፡ በተለየው ፡ ራስ ፡ ዐናት ፡ ላይ ፡ ይውረድ ።

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 17 ፤ ለላሞች ፡ በኩር ፡ ግርማ ፡ ይኾናል ፤

ቀንዶቹ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ናቸው ፤

በእነርሱ ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ያሉትን ፡

አሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ ይወጋል ፤

የኤፍሬም ፡ እልፍ ፡ አእላፋት ፥

የምናሴም ፡ አእላፋት ፡ እነርሱ ፡ ናቸው ።

ዘዳ. ፥ 33 ፥ 18 ፤ ስለ ፡ ዛብሎንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ዛብሎን ፡ ሆይ ፥ በመውጣትኽ ፥

ይሳኮር ፡ ሆይ ፥ በድንኳንኽ ፡ ውስጥ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ የተሰወረውን ፡ የአሸዋውን ፡ መዝገብ ፥

የባሕሩንም ፡ ባለጠግነት ፡ ይጠባሉና ፡

አሕዛብን ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ይጠራሉ ፤

በዚያ ፡ የጽድቅ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዋሉ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ ጋድም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

ጋድን ፡ ሰፊ ፡ ያደረገ ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ፤

እንደ ፡ አንበሳዪቱ ፡ ዐርፋል ፤

ክንድንና ፡ ራስን ፡ ይቀጠቅጣል ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ የአለቃ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ቀርቷልና ፥

የመገሥመሪያውን ፡ ክፍል ፡ ለራሱ ፡ መረጠ ፤

ወደሕዝብ ፡ አለቃዎችም ፡ መጣ ፤

የእግዚአብሔርንም ፡ ጽድቅ ፥

ፍርዱንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ አደረገ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ ስለ ፡ ዳንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

ዳን ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ነው ፤

ከባሳን ፡ ዘሎ ፡ ይወጣል ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ ስለ ፡ ንፍታሌምም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

ንፍታሌም ፡ በሞገስ ፡ ጠግቧል ፥

የእግዚአብሔርንም ፡ በረከት ፡ ተሞልቷል ፤

ባሕሩንና ፡ ደቡቡን ፡ ይወርሳል ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 24 ፤ ስለ ፡ አሴርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

አሴር ፡ በልጆች ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፤

በወንድሞቹ ፡ የተወደደ ፡ ይኹን ፤ እግሩንም ፡ በዘይት ፡ ውስጥ ፡ ያጥልቅ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 25 ፤ ጫማኽ ፡ ብረትና ፡ ናስ ፡ ይኾናል ፤

እንደ ፡ ዕድሜኽ ፡ እንዲሁ ፡ ኀይልኽ ፡ ይኾናል ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 26 ፤ ይሹሩን ፡ ሆይ ፥ በሰማያት ፡ ላይ ፡ ለረድኤትኽ ፥

በደመናትም ፡ ላይ ፡ በታላቅነት ፡ እንደሚኼድ ፡

እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለ ፡ ማንም ፡ የለም ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 27 ፤ መኖሪያኽ ፡ የዘለዓለም ፡ አምላክ ፡ ነው ፥

የዘለዓለምም ፡ ክንዶች ፡ ከአንተ ፡ በታች ፡ ናቸው ፤

ጠላትኽን ፡ ከፊትኽ ፡ አውጥቶ ፦

አጥፋው ፡ ይላል ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 28 ፤ እስራኤልም ፡ ተማምኖ ፥

የያዕቆብም ፡ ምንጭ ፡ ብቻውን ፥

እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ባለባት ፡ ምድር ፡ ይኖራል ፤

ሰማያቱም ፡ ጠልን ፡ ያንጠባጥባሉ ።

ዘዳ. ፡ 33 ፡ 29 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ምስጉን ፡ ነኽ ፤

በእግዚአብሔር ፡ የዳነ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ርሱ ፡ የረድኤትኽ ፡ ጋሻ ፥

የከፍተኛነትኽም ፡ ሰይፍ ፡ ነው ።

ጠላቶችኽም ፡ ይገዙልኻል ፤

አንተም ፡ ከፍታቸውን ፡ ትረግጣለኽ ።

ኦሪት ፡ ዘዳግም ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 1 ፤ ሙሴም ፡ ከሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ በኢያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደናባው ፡ ተራራ ፡ ወደፈስጋ ፡ ራስ ፡ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የገለዓድን ፡ ምድር ፥

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 2 ፤ የንፍታሌምንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ የኤፍሬምንና ፡ የምናሴንም ፡ ምድር ፥ እስከምዕራብም ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የይሁዳን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ደቡብንም ፥

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 3 ፤ እስከ ፡ ዞዓር ፡ ድረስ ፡ ያለውንም ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ያሉባትን ፡ ከተማ ፡ የኢያሪኮን ፡ ሸለቆ ፡ ሜዳ ፡ አሳየው ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለዘርኽ ፡ እሰጣታለኹ ፡ ብዬ ፡ ለአብርሃምና ፡ ለይሥሐቅ ፡ ለያዕቆብም ፡ የማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፤ በዐይንኽ ፡ እንድታያት ፡ አደረግኹኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደዚያች ፡ አትሻገርም ፡ አለው ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያም ፡ ሙሴ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በዚያ ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ሞተ ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 6 ፤ በቤተ ፡ ፌጎርም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ተቀበረ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ መቃብሩን ፡ ማንም ፡ አላወቀም ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 7 ፤ ሙሴም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፤ ዐይኑ ፡ አልፈዘዘም ፥ ጕልበቱም ፡ አልደነገዘም ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ለሙሴ ፡ አለቀሱለት ፤ ለሙሴም ፡ ያለቀሱለት ፡ የልቅሶው ፡ ወራት ፡ ተፈጸመ ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ እጆቹን ፡ ስለ ጫነበት ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የጥበብን ፡ መንፈስ ፡ ተሞላ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ታዘዙለት ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረጉ ።

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንዳወቀው ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አልተነሣም ፤

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 11 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በምድሪቱም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ምልክትንና ፡ ድንቅን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ያለ ፥

ዘዳ. ፡ 34 ፡ 12 ፤ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ በጸናች ፡ እጅ ፡ ኹሉና ፡ በታላቅ ፡ ማስደንገጥ ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረገው ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ያለ ፡ አልተነሣም ❖

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኢያ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፥ እግዚአብሔር ፡ የሙሴን ፡ አገልጋይ ፣ የነዌን ፡ ልጅ ፣ ኢያሱን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ኢያ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ባሪያዬ ፡ ሙሴ ፡ ሞቷል ፤ አኹንም ፡ አንተና ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተነሥታችኹ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደምሰጣቸው ፡ ምድር ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስ ፡ ተሻገሩ ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ለሙሴ ፡ እንደ ፡ ነገርኩት ፡ የእግራችኹ ፡ ጫማ ፡ የሚረግጠውን ፡ ቦታ ፡ ኹሉ ፡ ለእናንተ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከምድረ ፡ በዳው ፡ ከዚህም ፡ ከሊባኖስ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ድረስ ፡ የኬጢያውያን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እስከፀሓይ ፡ መግቢያ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ዳርቻችኹ ፡ ይኾናል ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በሕይወትኽ ፡ ዕድሜ ፡ ኹሉ ፡ ማንም ፡ አይቋቋምኽም ፤ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እንዲሁ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፤ አልጥልኽም ፥ አልተውኽም ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ለአባቶቻቸው ፦ እሰጣችኋለኹ ፡ ብዬ ፡ የማልኹላቸውን ፡ ምድር ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ታወርሳለኽና ፡ ጽና ፥ አይዞኽ ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽና ፥ እጅግ ፡ በርታ ፤ ባሪያዬ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘኽን ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ጠብቅ ፥ አድርገውም ፤ በምትኼድበትም ፡ ኹሉ ፡ እንዲከናወንልኽ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አትበል ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የዚህ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከአፍኽ ፡ አይለይ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የተጻፈበትን ፡ ኹሉ ፡ ትጠብቅና ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በቀንም ፡ በሌሊትም ፡ ዐስበው ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መንገድኽ ፡ ይቀናልኻል ፡ ይከናወንልኻልም ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በምትኼድበት ፡ ኹሉ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ ጽና ፥ አይዞኽ ፤ አትፍራ ፥ አትደንግጥ ፡ ብዬ ፡ አላዘዝኹኽምን ፧

ኢያ. ፥ 1 ፥ 10-11 ፤ ኢያሱም ፡ የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፦ በሰፈሩ ፡ መካከል ፡ ዕለፉ ፥ ሕዝቡንም ፦ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ወደሚሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግራችኹ ፡ ልትወርሷት ፡ ትገቡባታላችኹና ፥ ሥንቃችኹን ፡ አዘጋጁ ፡ ብላችኹ ፡ እዘዟቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ኢያሱም ፡ የሮቤልን ፡ ልጆች ፡ የጋድንም ፡ ልጆች ፡ የምናሴንም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦

ኢያ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያዘዛችኹን ፡ ቃል ፡ ዐስቡ ፦ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳርፋችኋል ፥ ይህችንም ፡ ምድር ፡ ይሰጣችኋል ።

ኢያ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ሚስቶቻችኹና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ከብቶቻችኹም ፡ ሙሴ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ ይቀመጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ኹሉ ፥ ተሰልፋችኹ ፡ በወንድሞቻችኹ ፡ ፊት ፡ ተሻገሩ ፥ ርዷቸውም ፥

ኢያ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ እግዚአብሔር ፡ እናንተን ፡ እንዳሳረፋችኹ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ እስኪያሳርፍ ፡ ድረስ ፥ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣቸውን ፡ ምድር ፡ እስኪወርሱ ፡ ድረስ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡

ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በፀሐይ ፡ መውጫ ፡ ወደሰጣችኹ ፡ ወደርስታችኹ ፡ ምድር ፡ ትመለሳላችኹ ፡ ትወርሷትማላችኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ እነርሱም ፡ ለኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። ያዘዝኸንን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እናደርጋለን ፡ ወደምትልከንም ፡ ስፍራ ፡ እንኼዳለን ።

ኢ.ያ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ በኹሉም ፡ ለሙሴ ፡ እንደ ፡ ታዘዝን ፡ እንዲሁ ፡ ለአንተ ፡ ደግሞ ፡ እንታዘዛለን ፤ ብቻ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ኢ.ያ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ በትእዛዝኽ ፡ የሚያምፅ ፡ ኹሉ ፡ የምታዘውንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ የማይሰማ ፥ ርሱ ፡ ይገደል ፤ ብቻ ፡ ጽና ፥ አይዞኽ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፦ ኼዳችኹ ፡ ምድሪቱንና ፡ ኢያሪኮን ፡ እዩ ፡ ብሎ ፡ ከሰጢም ፡ ኹለት ፡ ሰላዮች ፡ በስውር ፡ ላከ ። ኼዱም ፤ ረዓብም ፡ ወደሚሷት ፡ ጋለሞታ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፥ በዚያም ፡ ዐደሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ የኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፦ እንሆ ፥ ሰዎች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አገሩን ፡ ሊሰልሉ ፡ ወደዚህ ፡ በሌሊት ፡ ገቡ ፡ ሲባል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ የኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፦ አገሩን ፡ ኹሉ ፡ ሊሰልሉ ፡ መጥተዋልና ፥ ወደ ፡ አንቺ ፡ የመጡትን ፡ ወደ ፡ ቤትሽም ፡ የገቡትን ፡ ሰዎች ፡ አውጪ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ረዓብ ፡ ላከ ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ሴቲቱም ፡ ኹለቱን ፡ ሰዎች ፡ ወስዳ ፡ ሸሸገቻቸው ፤ ርሷም ፦ አዎን ፥ ሰዎቹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጡ ፥ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ግን ፡ አላወቅኹም ፤

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በሩም ፡ ሲዘጋ ፥ ሲጨልምም ፡ ሰዎቹ ፡ ወጡ ፤ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኼዱ ፡ አላውቅም ፤ ፈጥናችኹ ፡ አሳዷቸው ፥ ታገኟቸውማላችኹ ፡ አለች ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ አውጥታቸው ፡ ነበር ፤ በዚያም ፡ በረበረበችው ፡ በተልባ ፡ እግር ፡ ውስጥ ፡ ሸሸጋቸው ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ሰዎቹም ፡ ወደዮርዳኖስ ፡ መሻገሪያ ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ አሳደዷቸው ፤ አሳዳጆችም ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፥ በሩ ፡ ተቈለፈ ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እነዚህም ፡ ሳይተኙ ፡ ሴቲቱ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ ወጣች ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ሰዎቹንም ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ ምድሪቱን ፡ እንደ ፡ ሰጣችኹ ፥ እናንተንም ፡ መፍራት ፡ በላያችን ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፥ በምድሪቱም ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ከፊታችኹ ፡ እንደ ፡ ቀለጡ ፡ ዐወቅኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ በፊታችኹ ፡ እንዳደረቀ ፥ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በነበሩት ፡ እናንተም ፡ ፈጽማችኹ ፡ ባጠፋችኋቸው ፡ በኹለቱ ፡ በአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፥ በሴዎንና ፡ በዐግ ፡ ያደረጋችኹትን ፡ ሰምተናል ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ሰምተን ፡ ልባችን ፡ ቀለጠ ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ከእናንተ ፡ የተንሣ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ለማንም ፡ ነፍስ ፡ አልቀረለትም ።

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ አኹንም ፥ እባካችኹ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ማሉልኝ ፥ በእውነትም ፡ ምልክት ፡ ስጡኝ ፥ እኔ ፡ ለእናንተ ፡ ቸርነት ፡ እንደ ፡ ሠራኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ለአባቴ ፡ ቤት ፡ ቸርነት ፡ እንድትሠሩ ፥

ኢ.ያ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ አባቴንና ፡ እናቴንም ፡ ወንድሞቼንና ፡ እኅቶቼንም ፡ ያላቸውንም ፡ ኹሉ ፡

እንድታድኑ ፥ ሰውነታችንንም ፡ ከሞት ፡ እንድታድኑ ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 14 ፤ ሰዎቹም ፦ ይህን ፡ ነገራችንን ፡ ባትገልጪ ፡ ነፍሳችን ፡ በነፍሳችኹ ፡ ፋንታ ፡ ለሞት ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድሪቱን ፡ በሰጠን ፡ ጊዜ ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ቸርነትንና ፡ እውነትን ፡ እናደርጋለን ፡ አሏት ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 15 ፤ ቤቷም ፡ በከተማ ፡ ቅጥር ፡ የተጠጋ ፡ ነበረና ፥ ርሷም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበርና ፥ ከመስኮቱ ፡ በገመድ ፡ አወረደቻቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 16 ፤ ርሷም ፦ አሳዳጆቹ ፡ እንዳያገኟችኹ ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ኺዱ ፤ አሳዳጆቹም ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተሰውራችኹ ፡ ተቀመጡ ፤ ኋላም ፡ መንገዳችኹን ፡ ትኼዳላችኹ ፡ አለቻቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 17 ፤ ሰዎቹም ፡ አሏት ፦ እኛ ፡ ከዚህ ፡ ካማልሽን ፡ መሐላ ፡ ንጹሓን ፡ እንኾናለን ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 18 ፤ እንሆ ፥ እኛ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ቀይ ፡ ፈትል ፡ እኛን ፡ ባወረድሽበት ፡ መስኮት ፡ በኩል ፡ እሰሪው ፤ አባትሽንም ፡ እናትሽንም ፡ ወንድሞችሽንም ፡ የአባትሽንም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ሰብስቢ ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 19 ፤ ከቤትሽም ፡ ደጅ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ የሚወጣ ፡ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ እኛም ፡ ንጹሓን ፡ እንኾናለን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ቢነካው ፡ ደሙ ፡ በእኛ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 20 ፤ ይህን ፡ ነገራችንን ፡ ግን ፡ ብትገልጪ ፡ ከዚህ ፡ ካማልሽን ፡ መሐላ ፡ ንጹሓን ፡ እንኾናለን ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 21 ፤ ርሷም ፦ እንደ ፡ ቃላችኹ ፡ ይኹን ፡ አለች ፤ ሰደደቻቸውም ፡ እነርሱም ፡ ኼዱ ፤ ቀዩንም ፡ ፈትል ፡ በመስኮቱ ፡ በኩል ፡ አንጠለጠለችው ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 22 ፤ እነርሱም ፡ ኼደው ፡ ወደ ፡ ተራራው ፡ ደረሱ ፥ አሳዳጆቹም ፡ እስኪመለሱ ፡ ድረስ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ፤ አሳዳጆቹም ፡ በመንገዱ ፡ ኹሉ ፡ ፈልገው ፡ አላገኟቸውም ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 23 ፤ ኹለቱም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ፥ ከተራራውም ፡ ወርደው ፡ ተሻገሩ ፥ ወደነዌም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢ.ያሱ ፡ መጡ ፤ የደረሰባቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አወሩለት ።

ኢ.ያ. ፥ 2 ፥ 24 ፤ ኢ.ያሱንም ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ አገሩን ፡ ኹሉ ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷል ፤ በአገሩም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በፊታችን ፡ ይቀልጣሉ ፡ አሉት ።

መጽሐፈ ፡ ኢ.ያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 1 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ርሱና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከሰጢም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጡ ፤ ሳይሻገሩም ፡ በዚያ ፡ ዐደሩ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 2 ፤ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ አለቃዎች ፡ በሰፈሩ ፡ መካከል ፡ ዐለፉ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 3 ፤ ሕዝቡን ፦ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦትና ፡ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ተሸክመውት ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፥ ከሰፈራችኹ ፡ ተነሥታችኹ ፡ ተከተሉት ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 4 ፤ በእናንተና ፡ በታቦቱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ርቀት ፡ በስፍር ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ያኽል ፡ ይኹን ፤ በዚህ ፡ መንገድ ፡ በፊት ፡ አልኼዳችኹበትምና ፡ የምትኼዱበትን ፡ መንገድ ፡ እንድታውቁ ፡ ወደ ፡ ታቦቱ ፡ አትቅረቡ ፡ ብለው ፡ አዘዙ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 5 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ ነገ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችኹ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡

ያደርጋልና ፥ ተቀደሱ ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 6 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ካህናቱን ፦ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ተሸክማችኹ ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ዕለፉ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፤ የቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ ታቦት ፡ ተሸክመው ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ዐለፉ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢ.ያሱን ፦ ከሙሴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እንዲሁ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ መኾኔን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግኽ ፡ ዘንድ ፡ እዝምራለኹ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 8 ፤ አንተም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የሚሸከሙትን ፡ ካህናት ። በዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ዳር ፡ ስትደርሱ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውስጥ ፡ ቁሙ ፡ ብለኽ ፡ እዘዝ ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 9 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ። ወደዚህ ፡ ቀርባችኹ ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 10 ፤ ኢ.ያሱም ፡ አለ ፦ ሕያው ፡ አምላክ ፡ በመካከላችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ርሱም ፡ ከፊታችኹ ፡ ከነዓናዊውን ፡ ኬጢያዊውንም ፡ ዔዊያዊውንም ፡ ፌርዛዊውንም ፡ ጌርጌሳዊውንም ፡ አሞራዊውንም ፡ ኢ.ያቡሳዊውንም ፡ ፈጽሞ ፡ እንዲያወጣ ፡ በዚህ ፡ ታውቃላችኹ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 11 ፤ እንሆ ፥ የምድር ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በፊታችኹ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ያልፋል ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 12 ፤ አኹንም ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ምረጡ ፤ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ይኹን ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 13 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ የምድርን ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ እግር ፡ ጫማ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ ሲቆም ፥ ከላይ ፡ የሚወርደው ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ይቋረጣል ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ ኾኖ ፡ ይቆማል ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 14 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሕዝቡ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሊሻገሩ ፡ ከየድንኳናቸው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 15 ፤ እንደ ፡ መከር ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እጅግ ፡ ሞልቶ ፡ ነበርና ፥ ታቦት ፡ ተሸካሚዎቹ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ሲደርሱ ፥ ታቦቱንም ፡ የተሸከሙት ፡ የካህናቱ ፡ እግሮች ፡ በውሃው ፡ ዳር ፡ ሲጠልቁ ፥

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 16 ፤ ከላይ ፡ የሚወርደው ፡ ውሃ ፡ ቆመ ፤ በጻርታን ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ አዳም ፡ በምትባል ፡ ከተማ ፡ በሩቅ ፡ ቆሞ ፡ ባንድ ፡ ክምር ፡ ተነሣ ፤ ወደዐረባ ፡ ባሕር ፡ ወደጨው ፡ ባሕር ፡ የሚወርደው ፡ ውሃ ፡ ፈጽሞ ፡ ተቋረጠ ፤ ሕዝቡም ፡ በኢ.ያሪኮ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሻገሩ ።

ኢ.ያ. ፥ 3 ፥ 17 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ በደረቅ ፡ መሬት ፡ ጸንተው ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ፈጽመው ፡ እስኪሻገሩ ፡ ድረስ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ በደረቅ ፡ መሬት ፡ ተሻገሩ ።

መጽሐፈ ፡ ኢ.ያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ኢ.ያ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ፈጽመው ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ኢ.ያሱን ።

ኢ.ያ. ፥ 4 ፥ 2 ፤ ከሕዝቡ ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ምረጥና ።

ኢ.ያ. ፥ 4 ፥ 3 ፤ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ የካህናት ፡ እግር ፡ ከቆመበት ፡ ስፍራ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ድንጋዮች ፡

አንሡ ፤ ተሸክማችኹም ፡ በዚህ ፡ ሌሊት ፡ በምታድሩበት ፡ ስፍራ ፡ አኑሯቸው ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ከየነገዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፥ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያዘጋጃቸውን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ጠራ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ኢ.ያሱም ፡ አላቸው ፦ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ዕለፉ ፤ ከእናንተም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ቍጥር ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ ከዚያ ፡ ይሸከም ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ይህም ፡ በመካከላችኹ ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ፤ ልጆቻችኹም ፡ በሚመጣው ፡ ዘመን ፦ የእነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ሲጠይቋችኹ ፥

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እናንተ ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ስለ ፡ ተቋረጠ ፡ ነው ፤ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገረ ፡ ጊዜ ፡ የዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ተቋረጠ ፥ እነዚህም ፡ ድንጋዮች ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለዘለዓለም ፡ መታሰቢያ ፡ ይኾናሉ ፡ ትሏቸዋላችኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኢ.ያሱ ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢ.ያሱን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ቍጥር ፡ ከዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ድንጋዮች ፡ አንሥተው ፡ ወደሚያድሩበት ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱ ፥ በዚያም ፡ አኖሯቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ኢ.ያሱም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ እግሮች ፡ በቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ሌላዎችን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ድንጋዮች ፡ ተከለ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ አሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ሙሴም ፡ ኢ.ያሱን ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ ኢ.ያሱን ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲነግር ፡ ያዘዘው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ታቦቱን ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ በዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ ቆመው ፡ ነበርና ፤ ሕዝቡም ፡ ፈጥነው ፡ ተሻገሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ በተሻገሩ ፡ ጊዜ ፥ ሕዝቡ ፡ እያዩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦትና ፡ ካህናቱ ፡ ተሻገሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ሙሴም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፥ የጋድም ፡ ልጆች ፥ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ተሰልፈው ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ተሻገሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰዎች ፡ ጋሻና ፡ ጦራቸውን ፡ ይዘው ፡ ለሰልፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ ተሻገሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢ.ያሱን ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፤ ሙሴንም ፡ እንደ ፡ ፈሩ ፡ በዕድሜው ፡ ኹሉ ፡ ፈሩት ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢ.ያሱን ፦ የምስክሩን ፡ ታቦት ፡ የሚሸከሙትን ፡ ካህናት ፡ ከዮርዳኖስ ፡ እንዲወጡ ፡ እዘዝ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ካህናትን ፦ ከዮርዳኖስ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ካህናት ፡ ከዮርዳኖስ ፡ መካከል ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ የካህናቱም ፡ እግር ፡ ጫማ ፡ ደረቅ ፡ መሬት ፡ መርገጥ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ የዮርዳኖስ ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ፥ ቀድሞም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በዳሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኼደ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ሕዝቡም ፡ በመገቡ ፡ ወር ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ወጡ ፥ በኢያሪኮም ፡

ዳርቻ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በገልገላ ፡ ሰፈሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ከዮርዳኖስም ፡ ውስጥ ፡ የወሰዷቸውን ፡ እነዚያን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ድንጋዮች ፡ ኢያሱ ፡ በገልገላ ፡ አቆማቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ልጆቻችኹ ፡ አባቶቻቸውን ፦ እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ ብለው ፡ ሲጠይቁ ፥

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ለልጆቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ታስታውቃላችኹ ። እስራኤል ፡ ይህን ፡ ዮርዳኖስን ፡ በደረቅ ፡ ተሻገረ ፤

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ እስክንሻገር ፡ ድረስ ፡ አምላካችኹ ፡ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ ከፊታችን ፡ እንዳደረቀ ፡ እንዲሁ ፡ እስክትሻገሩ ፡ ድረስ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዮርዳኖስን ፡ ውሃ ፡ ከፊታችኹ ፡ አደረቀ ።

ኢ.ያ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ይኸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ጠንካራ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ እንዲያውቁ ፥ አምላካችኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለዘለዓለሙ ፡ እንድትፈሩ ፡ ነው ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የነበሩት ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፥ በባሕሩም ፡ አጠገብ ፡ የነበሩ ፡ የከነዓናውያን ፡ ነገሥት ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የዮርዳኖስን ፡ ውሃ ፡ እስኪሻገሩት ፡ ድረስ ፡ እንዳደረቀ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ ልባቸው ፡ ቀለጠ ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ነፍስ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አልቀረላቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፦ የባልጩት ፡ መቀሎረጫ ፡ ሠርተኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ግረዛቸው ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ኢያሱም ፡ የባልጩት ፡ መቀሎረጫ ፡ ሠርቶ ፡ የግርዛት ፡ ኮረብታ ፡ በተባለ ፡ ስፍራ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ገረዘ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ኢያሱ ፡ የገረዘበትም ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከግብጽ ፡ የወጡት ፡ ሕዝብ ፡ ወንዶች ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ከግብጽ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞቱ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ የወጡት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተገርዘው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከግብጽ ፡ በወጡበት ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የተወለዱት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ አልተገረዙም ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈሰውን ፡ ምድር ፡ ለእኛ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማለላቸውን ፡ ምድር ፡ እንዳያሳያቸው ፡ የማለላቸው ፥ ከግብጽ ፡ የወጡ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ያልሰሙ ፥ እነዚያ ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ልጆቻቸውን ፡ በእነርሱ ፡ ፋንታ ፡ አስነሣ ፥ እነዚህንም ፡ ኢያሱ ፡ ገረዛቸው ፤ በመንገድ ፡ ሳሉ ፡ ስላልገረዟቸው ፡ ሸለፈታሞች ፡ ነበሩና ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ በተገረዙ ፡ ጊዜ ፡ እስኪድኑ ፡ ድረስ ፡ በሰፈር ፡ ውስጥ ፡ በየስፍራቸው ፡ ተቀመጡ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፦ ዛሬ ፡ የግብጽን ፡ ነውር ፡ ከእናንተ ፡ ላይ ፡ አንከባልያለኹ ፡ አለው ፤ ስለዚህ ፥ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገልገላ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በገልገላ ፡ ሰፈሩ ፤ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ በኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ ፋሲካ ፡ አደረጉ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ከፋሲካውም ፡ በኋላ ፡ በነጋው ፡ የምድሪቱን ፡ ፍሬ ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፡ ቈሎም ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ በሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ በነጋውም ፡ ከምድሪቱ ፡ ፍሬ ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ መና ፡ ቀረ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መና ፡ አልመጣላቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያው ፡ ዓመት ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ ፍሬ ፡ በሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ኢያሱ ፡ በኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ ፡ ዐይኑን ፡ አንሥቶ ፡ ተመለከተ ፥ እንሆም ፥ የተመዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርቦ ፦ ከእኛ ፡ ወገን ፡ ወይስ ፡ ከጠላቶቻችን ፡ ወገን ፡ ነኽን ፧ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ አይደለኹም ፤ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ኾኜ ፡ አኹን ፡ መጥቻለኹ ፡ አለ ። ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰገደና ፦ ጌታዬ ፡ ለባሪያው ፡ የሚነግረው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ኢያሱን ፦ አንተ ፡ የቆምኽበት ፡ ስፍራ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፥ ጫማኽን ፡ ከእግርኽ ፡ አውልቅ ፡ አለው ። ኢያሱም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ኢያሪኮም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የተነሣ ፡ ፈጽማ ፡ ተዘግታ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሷ ፡ የሚገባ ፡ ከርሷም ፡ የሚወጣ ፡ ማንም ፡ አልነበረም ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ አለው ፦ ተመልከት ፥ ኢያሪኮንና ፡ ንጉሧን ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላኗንም ፡ በእጅኽ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ሰልፈኞቻችኹ ፡ ኹሉ ፡ ከተማዪቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይዙሯት ፤ እንዲሁም ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ አድርጉ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ሰባትም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ይሸከሙ ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ከተማዪቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዙሩ ፥ ካህናቱም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይንፉ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ቀንደ ፡ መለከቱም ፡ ባለማቋረጥ ፡ ሲነፋ ፥ የመለከቱንም ፡ ድምፅ ፡ ስትሰሙ ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ይጩኹ ፤ የከተማዪቱም ፡ ቅጥር ፡ ይወድቃል ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ አቅንቶ ፡ ይገባባታል ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ካህናቱን ፡ ጠርቶ ፦ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ተሸከሙ ፥ ሰባትም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ወስደው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይኺዱ ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ሕዝቡንም ፦ ኺዱ ፥ ከተማዪቱንም ፡ ዙሩ ፥ ሰልፈኞችም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይኺዱ ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ኢያሱም ፡ ለሕዝቡ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፥ ሰባቱ ፡ ካህናት ፡ ሰባቱን ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኼዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱንም ፡ ነፉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ይከተላቸው ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ሰልፈኞቹም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ በሚነፉ ፡ በካህናቱ ፡ ፊት ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፥ የቀረውም ፡ ሕዝብ ፡ ከታቦቱ ፡ በኋላ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፥ ካህናቱም ፡ እየኼዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ እኔ ፦ ጨኹ ፡ እስከምልበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ አትጨኹ ፥ ድምፃችኹንም ፡ አታንሡ ፥ ከአፋችኹም ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አይውጣ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ትጮኻላችኹ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እንዲሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዪቱን ፡ አዞረው ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ተመልሰው ፡ ዐደሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ማለዳ ፡ ተነሣ ፡ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ተሸከሙ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ሰባቱም ፡ ካህናት ፡ ሰባት ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፡ ቀንደ ፡ መለከቱንም ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፤ ሰልፈኞቹም ፡ በፊታቸው ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በኋላ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፥ ካህናቱም ፡ እየኼዱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ከተማዪቱን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዞረው ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ተመለሱ ፤ ስድስት ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥ እንደዚህም ፡ ሥርዐት ፡ ከተማዪቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዞሩ ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ከተማዪቱን ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ዞሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ በሰባተኛውም ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ሲነፉ ፡ ኢ.ያሱ ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ ከተማዪቱን ፡ ሰጥቷችኋልና ፥ ጩኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ከተማዪቱም ፡ በርሷም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዕርም ፡ ይኾናሉ ፤ የላክናቸውን ፡ መልክተኞች ፡ ስለሸሸገች ፡ ጋለሞታዪቱ ፡ ረዓብ ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ በቤቷ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ብቻ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ዕርም ፡ ካደረጋችኹት ፡ በኋላ ፡ ዕርም ፡ ከኾነው ፡ ነገር ፡ ራሳችኹን ፡ ጠብቁ ፤ ዕርም ፡ ከኾነው ፡ አንዳች ፡ የወሰዳችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የእስራኤልን ፡ ሰፈር ፡ የተረገመ ፡ ታደርጉታላችኹ ፥ ታስጨንቁትማላችኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ የናስና ፡ የብረትም ፡ ዕቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኹን ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይግባ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ሕዝቡም ፡ ጮኹ ፥ ካህናቱም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ነፉ ፤ ሕዝቡም ፡ የቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ጩኸት ፡ ጮኹ ፥ ቅጥሩም ፡ ወደቀ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ አቅንቶ ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ወጣ ፥ ከተማዪቱንም ፡ ወሰዱ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ በከተማዪቱም ፡ የነበሩትን ፡ ኹሉ ፥ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፥ ሕፃኑንና ፡ ሽማግሌውን ፥ በሬውንም ፡ በጉንም ፡ አህያውንም ፥ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ፈጽመው ፡ አጠፉ ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ኢ.ያሱም ፡ ምድሪቱን ፡ የሰለሉ ፡ ኹለቱን ፡ ሰዎች ፦ ወደጋለሞታዪቱ ፡ ቤት ፡ ግቡ ፥ ከዚያም ፡ ሴቲቱንና ፡ ያላትን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ማላችኹላት ፡ አውጡ ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ሰላዮቹም ፡ ብላቴናዎች ፡ ገብተው ፡ ረዓብን ፥ አባቷንና ፡ እናቷን ፥ ወንድሞቿንም ፥ ያላትንም ፡ ኹሉ ፥ ቤተ ፡ ዘመዶቿንም ፡ ኹሉ ፡ አወጡ ፤ ከእስራኤልም ፡ ሰፈር ፡ በውጭ ፡ አስቀመጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ከተማዪቱንም ፡ በርሷም ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ የናሱንና ፡ የብረቱንም ፡ ዕቃ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አደረጉት ።

ኢ.ያ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ ኢ.ያሪኮን ፡ ሊሰልሉ ፡ ኢ.ያሱ ፡ የሰደዳቸውንም ፡ መልክተኞች ፡ ስለ ፡ ሸሸገች ፡ ጋለሞታዪቱን ፡

ረዓብን ፥ የአባቷንም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፥ ያላትንም ፡ ኹሉ ፡ ኢያሱ ፡ አዳናቸው ፤ ርሷም ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተቀምጣለች ።

ኢያ. ፥ 6 ፥ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፦ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ኢያሪኮን ፡ ለመሥራት ፡ የሚነሣ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ መሠረቷን ፡ ሲገምር ፡ በኵር ፡ ልጁ ፡ ይጥፋ ፥ በሯንም ፡ ሲያቆም ፡ ታናሹ ፡ ልጁ ፡ ይጥፋ ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ኢያ. ፥ 6 ፥ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኢያሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ዝናውም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ዕርም ፡ በኾነው ፡ ነገር ፡ በደሉ ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የኾነ ፡ ዐካን ፥ ርሱም ፡ የከርሚ ([106]) ፡ ልጅ ፥ የዘንበሪ ([107]) ፡ ልጅ ፥ የዛራ ፡ ልጅ ፥ ዕርም ፡ ከኾነው ፡ ነገር ፡ ወሰደ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ነደደ ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 2 ፤ ኢያሱም ፡ ከቤቴል ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በቤትአዌን ፡ አጠገብ ፡ ወዳለችው ፡ ወደጋይ ፡ ሰዎችን ፡ ከኢያሪኮ ፡ ልኮ ፦ ውጡ ፥ ምድሪቱንም ፡ ሰልሉ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፤ ሰዎቹም ፡ ወጡ ፥ ጋይንም ፡ ሰለሉ ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 3 ፤ ወደ ፡ ኢያሱም ፡ ተመልሰው ፦ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ወጥተው ፡ ጋይን ፡ ይምቱ ፡ እንጂ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ አይውጣ ፤ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ወደዚያ ፡ ለመኼድ ፡ አይድከም ፡ አሉት ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 4 ፤ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰዎችም ፡ ወደዚያ ፡ ወጡ ፤ ከጋይም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ሸሹ ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 5 ፤ የጋይም ፡ ሰዎች ፡ ከነርሱ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ያኽል ፡ ሰዎችን ፡ መቱ ፤ ከበሩ ፡ እስከ ፡ ሸባሪም ፡ ድረስ ፡ አባረሯቸው ፡ በቍልቍለቱም ፡ መታቸው ፤ የሕዝቡም ፡ ልብ ፡ ቀለጠ ፥ እንደ ፡ ውሃም ፡ ኾነ ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ ኢያሱም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ ርሱና ፡ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፉ ፤ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነሰነሱ ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ ኢያሱም ፡ አለ ፦ ዋይ! ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ በአሞራውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጠን ፡ ታጠፋንም ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ለምን ፡ አሻገርኸው ፧ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ መቀመጥን ፡ በወደድን ፡ ነበር ፡ እኮ! ፡

ኢያ. ፥ 7 ፥ 8 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስራኤል ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ከሸሹ ፡ ምን ፡ እላለኹ ፧

ኢያ. ፥ 7 ፥ 9 ፤ ከነዓናውያንም ፡ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ይከቡናል ፥ ስማችንንም ፡ ከምድር ፡ ያጠፋሉ ፤ ለታላቁ ፡ ስምኽም ፡ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢያ. ፥ 7 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ አለው ፦ ለምን ፡ በግንባርኽ ፡ ተደፍተኻል ፧ ቁም ፤

ኢያ. ፥ 7 ፥ 11 ፤ እስራኤል ፡ በድሏል ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አፍርሰዋል ፤ ዕርም ፡ የኾነውንም ፡ ነገር ፡ ወሰዱ ፥ ሰረቁም ፥ ዋሹም ፥ በዕቃቸውም ፡ ውስጥ ፡ ሸሸጉት ።

ኢያ. ፥ 7 ፥ 12 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አይችሉም ፤ የተረገሙ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ይሸሻሉ ፤ ዕርም ፡ የኾነውንም ፡ ነገር ፡ ከመካከላችኹ ፡ ካላጠፋችኹ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አልኾንም ።

---

106 ዕብ. ፥ ከርሚ ፡ (የከርም ፥ ከርሜ ፥ አትክልተኛ) ።

107 ዕብ. ፥ ዘብዲ ፡ (ስጦታ) ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ተነሣና ፡ ሕዝቡን ፡ ቀድስ ፥ እንዲሀም ፡ በላቸው ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ዕርም ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ በመካከልኽ ፡ አለ ፤ ዕርምም ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ከመካከላችኹ ፡ እስክታጠፉ ፡ ድረስ ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ አትችሉም ፡ ብሎ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ እስከ ፡ ነገ ፡ ተቀደሱ ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ነገም ፡ በየነገዳችኹ ፡ ትቀርባላችኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚለየው ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቹ ፡ ይቀርባል ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚለየው ፡ ወገን ፡ በየቤተ ፡ ሰቦቹ ፡ ይቀርባል ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚለየው ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በየሰዉ ፡ ይቀርባል ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ዕርም ፡ የኾነውም ፡ ነገር ፡ የተገኘበት ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሷልና ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ በደል ፡ አድርጓልና ፥ ርሱና ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ኢያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ እስራኤልንም ፡ በየነገዶቻቸው ፡ አቀረበ ፤ የይሁዳም ፡ ነገድ ፡ ተለየ ፤

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ የይሁዳንም ፡ ወገን ፡ አቀረበ ፡ የዛራንም ፡ ወገን ፡ ለየ ፤ የዛራንም ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ አቀረበ ፤

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ዘንበሪም ፡ ተለየ ፤ የቤቱንም ፡ ሰዎች ፡ አቀረበ ፤ ከይሁዳም ፡ ነገድ ፡ የኾነ ፡ የከርሚ ፡ ልጅ ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ዐካን ፡ ተለየ ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ኢያሱም ፡ ዐካንን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ስጥ ፥ ለርሱም ፡ ተናዘዝ ፤ ያደረግኸውንም ፡ ንገረኝ ፤ አትሸሽገኝ ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ዐካንም ፡ መልሶ ፡ ኢያሱን ፦ በእውነት ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድያለኹ ፡ እንዲሀና ፡ እንዲሀም ፡ አድርጌያለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በዘረፋ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ያማረ ፡ የሰናዖር ፡ ካባ ፥ ኹለት ፡ መቶም ፡ ሰቅል ፡ ብር ፥ ሚዛኑም ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ የኾነ ፡ ወርቅ ፡ አይቼ ፡ ተመኘኋቸው ፥ ወሰድኋቸውም ፤ እንሆም ፥ በድንኳኔ ፡ ውስጥ ፡ በመሬት ፡ ተሸሽገዋል ፥ ብሩም ፡ ከኹሉ ፡ በታች ፡ ነው ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ኢያሱም ፡ መልክተኞች ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑም ፡ ሮጡ ፤ እንሆም ፥ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሽጎ ፡ ነበር ፥ ብሩም ፡ በበታቹ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ከድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ኢያሱና ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አመጡት ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ አኖሩት ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ኢያሱና ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ የዛራን ፡ ልጅ ፡ ዐካንን ፥ ብሩንም ፥ ካባውንም ፥ ወርቁንም ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹንም ፥ በሬዎቹንም ፥ አህያዎቹንም ፥ በጎቹንም ፥ ድንኳኑንም ፥ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ ወስደው ፡ ወደዐኮር ፡ ሸለቆ ፡ አመጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ኢያሱም ፦ ለምን ፡ አስጨነቅኸን ፧ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ያስጨንቅኻል ፡ አለው ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ፤ በእሳትም ፡ አቃጠሏቸው ፥ በድንጋይም ፡ ወገሯቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ በላዩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ከመሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከቀሥጣው ፡ ትኵሳት ፡ ተመለሰ ። ስለዚህም ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የዐኮር ፡ ሸለቆ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፦ አትፍራ ፥ አትደንግጥ ፤ ሰልፈኞችን ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡

ውሰድ ፥ ተነሥተኽም ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ውጣ ፤ እይ ፥ የጋይን ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቡንም ፡ ከተማውንም ፡ ምድሩንም ፡ በእጅኽ ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ በኢያሪኮና ፡ በንጉሧም ፡ እንዳደረግኽ ፡ እንዲሁ ፡ በጋይና ፡ በንጉሧ ፡ ታደርጋለኽ ፤ ምርኮዋንና ፡ ከብቷን ፡ ግን ፡ ለራሳችኹ ፡ ትዘርፋላችኹ ፤ ከከተማዩቱም ፡ በስተኋላ ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አስቀምጥ ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ኢያሱም ፡ ሰልፈኞቹም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ሊወጡ ፡ ተነሡ ፤ ኢያሱም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ የኾኑትን ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ መረጠ ፡ በሌሊትም ፡ ሰደዳቸው ፥

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፦ እንሆ ፥ ከከተማዩቱ ፡ በስተኋላ ፡ ተደበቁ ፤ ከከተማዩቱ ፡ አትራቁ ፥ ኹላችኹም ፡ ተዘጋጁ ፤

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እኔ ፡ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ እንቀርባለን ፤ እኛንም ፡ ሊገናኙ ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ከፊታቸው ፡ እንሸሻለን ፤

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ አስቀድመን ፡ እንደ ፡ ሸሽን ፡ የምንሸሽ ፡ ይመስላቸዋልና ፥ ከከተማዩቱ ፡ እስክናርቃቸው ፡ ድረስ ፡ ወጥተው ፡ ይከተሉናል ፤ እኛም ፡ ከፊታቸው ፡ እንሸሻለን ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ እናንተም ፡ ከተደበቃችኹበት ፡ ስፍራ ፡ ተነሡ ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሷን ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣልና ፥ ከተማዩቱን ፡ ያዙ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በያዛችኋትም ፡ ጊዜ ፡ ከተማዩቱን ፡ በእሳት ፡ አቃጥሏት ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አድርጉ ፤ እንሆ ፥ አዝዣችኋለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ኢያሱም ፡ ሰደዳቸው ፤ ወደሚደበቁበትም ፡ ስፍራ ፡ ኼዱ ፥ በጋይና ፡ በቤቴል ፡ መካከልም ፡ በጋይ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ተቀመጡ ፤ ኢያሱ ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ዐደረ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ኢያሱም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ሕዝቡንም ፡ አሰለፈ ፤ ርሱም ፡ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከሕዝቡ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ወጡ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ወጥተው ፡ ቀረቡ ፥ ወደከተማዩቱም ፡ ፊት ፡ ደረሱ ፥ በጋይም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ሰፈሩ ፤ በእነርሱና ፡ በጋይም ፡ መካከል ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰዎችንም ፡ ወስዶ ፡ በቤቴልና ፡ በጋይ ፡ መካከል ፡ በከተማዩቱም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ደብቆ ፡ አስቀመጣቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ በከተማዩቱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ የነበሩትን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በከተማዩቱም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የተደበቁትን ፡ ሕዝብ ፡ አኖሩ ፤ ኢያሱም ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ወደሸለቆው ፡ መካከል ፡ ኼደ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ የጋይም ፡ ንጉሥ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የከተማዩቱ ፡ ሰዎች ፡ ቸኩለው ፡ በማለዳ ፡ ተነሡ ፤ ርሱና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ በዐረባ ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ እስራኤልን ፡ በሰልፍ ፡ ለመገናኘት ፡ ወጡ ፤ ከከተማዩቱ ፡ በስተኋላ ፡ ግን ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ እንዳለ ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ኢያሱም ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ድል ፡ የተነሡ ፡ መስለው ፡ ከፊታቸው ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ መንገድ ፡ ሸሹ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ በከተማዩቱም ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሊያሳድዷቸው ፡ ተጠሩ ፤ ኢያሱንም ፡ አሳደዱት ፥ ከከተማዩቱም ፡ እንዲርቁ ፡ አደረጓቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ በጋይና ፡ በቤቴልም ፡ ውስጥ ፡ እስራኤልን ፡ ለማሳደድ ፡ ያልወጣ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ከተማዩቱንም ፡ ከፍተው ፡ ተዉ ፥ እስራኤልንም ፡ አሳደዱት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፦ ጋይን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹና ፡ በእጅኽ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ በላይዋ ፡ ዘርጋ ፡ አለው ፤ ኢያሱም ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ በከተማዩቱ ፡ ላይ ፡ ዘረጋ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ የተደበቁትም ፡ ፈጥነው ፡ ከስፍራቸው ፡ ተነሡ ፥ ኢያሱም ፡ እጁን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፡ ሮጡ ፥ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ ገብተው ፡ ያዟት ፤ ፈጥነውም ፡ ከተማዩቱን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሏት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ የጋይም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ዞረው ፡ የከተማዩቱ ፡ ጢስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ አዩ ፥ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ መሸሽ ፡ አልቻሉም ፤ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ የሸሹ ፡ ሕዝብ ፡ በሚያሳድዷቸው ፡ ላይ ፡ ተመለሱ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ኢያሱም ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ተደብቀው ፡ የነበሩት ፡ ከተማዩቱን ፡ እንደ ፡ ያዙ ፥ የከተማዩቱም ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ የጋይን ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ሌላዎቹም ፡ በላያቸው ፡ ከከተማዩቱ ፡ ወጡ ፤ የጋይም ፡ ሰዎች ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ኾኑ ፥ እስራኤልም ፡ ከበቧቸው ፤ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ሳያመልጥም ፡ ገደሏቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ የጋይንም ፡ ንጉሥ ፡ ሳይሞት ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ አመጡት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ እስራኤልን ፡ ሊያሳድዱ ፡ ኼደው ፡ የነበሩትን ፡ የጋይን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በሜዳና ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ከገደሏቸው ፡ በኋላ ፥ እነርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ እስኪያልቁ ፡ ድረስ ፡ ከወደቁ ፡ በኋላ ፥ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ተመለሱ ፥ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቷት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የወደቁት ፡ ኹሉ ፡ ወንድም ፡ ሴትም ፡ የጋይ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ነፍስ ፡ ነበሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ኢያሱም ፡ በጋይ ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያጠፋ ፡ ድረስ ፡ ጦር ፡ የዘረጋባትን ፡ እጁን ፡ አላጠፈም ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ኢያሱን ፡ እንዳዘዘው ፡ ቃል ፡ የዚያችን ፡ ከተማ ፡ ከብትና ፡ ምርኮ ፡ እስራኤል ፡ ለራሳቸው ፡ ዘረፉ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ኢያሱም ፡ ጋይን ፡ አቃጠላት ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ድብድባና ፡ በረሓ ፡ ለዘለዓለም ፡ አደረጋት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ የጋይንም ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ሰቀለው ፤ ፀሓይም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ አዘዘ ፥ ሬሳውንም ፡ ከዛፍ ፡ አወረዱት ፥ በከተማዩቱም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ጣሉት ፥ በላዩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ከመሩበት ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ እንዳዘዘ ፥ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈው ፥ መሠዊያው ፡ ካልተወቀረና ፡ ብረት ፡ ካልነካው ፡ ድንጋይ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፥ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሲያዩ ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ በድንጋዮቹ ፡ ላይ ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ ጻፈባቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ የእስራኤልንም ፡ ሕዝብ ፡ አስቀድሞ ፡ ይባርኩ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘ ፥ እስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ሽማግሌዎቻቸውም ፥ አለቃዎቻቸውም ፥ ፈራጆቻቸውም ፥ የአገሩ ፡ ልጆችም ፥ መጻተኞችም ፥ እኩሌታዎቹ ፡ በገሪዛን ፡ ተራራ ፡ ፊት ፡ እኩሌታዎቹም ፡ በጌባል ፡ ተራራ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በተሸከሙት ፡ በሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፥ በታቦቱም ፡ ፊት ፡ በወዲህና ፡ በወዲያ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሕጉ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ኹሉ ፥ የሕጉን ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ በረከቱንና ፡ ርግማኑን ፡ አነበበ ።

ኢ.ያ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ኢያሱም ፡ በእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ በሴቶቹም ፡ በሕፃናቱም ፡ በመካከላቸውም ፡ በሚኖሩት ፡ መጻተኞች ፡ ፊት ፡ ኹሉን ፡ አነበበ ፡ እንጂ ፡ ሙሴ ፡ ካዘዘው ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ አላስቀረም ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በተራራማው ፡ በቈላውም ፡ በታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በሊባኖስም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የነበሩ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፥ ኬጢያዊ ፡ አሞራዊም ፡ ከነዓናዊም ፡ ፌርዛዊም ፡ ዔዊያዊም ፡ ኢያቡሳዊም ፥ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ኢያሱንና ፡ እስራኤልን ፡ ሊወጉ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ተሰበሰቡ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ የገባዖን ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ኢያሱ ፡ በኢያሪኮና ፡ በጋይ ፡ ያደረገውን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ተንኰል ፡ አደረጉ ፤ ለራሳቸውም ፡ ሥንቅ ፡ ያዙ ፥ በአህያዎቻቸውም ፡ ላይ ፡ አሮጌ ፡ ዐይበትና ፡ ያረጀና ፡ የተቀደደ ፡ የተጠቀመም ፡ የጠጅ ፡ አቀኑማዳ ፡ ጫኑ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ያረጀ ፡ የተጠቀመም ፡ ጫማ ፡ በእግራቸው ፡ አደረጉ ፡ አሮጌም ፡ ልብስ ፡ ለበሱ ፤ ለሥንቅም ፡ የያዙት ፡ እንጀራ ፡ ኹሉ ፡ የደረቀና ፡ የሻገተ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ኢያሱም ፡ ወደሰፈረበት ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ኼደው ፡ ለርሱና ፡ ለእስራኤል ፡ ሰዎች ፦ ከሩቅ ፡ አገር ፡ መጥተናል ፤ አኹንም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ኪዳን ፡ አድርጉ ፡ አሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ዔዊያውያንን ፦ ምናልባት ፡ በመካከላችን ፡ የምትቀመጡ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዴትስ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እናደርጋለን ፧ አሏቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ኢያሱንም ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ነን ፡ አሉት ። ኢያሱም ፦ እናንተ ፡ እነማን ፡ ናችኹ ፧ ከወዴትስ ፡ መጣችኹ ፧ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ አሉት ። ከአምላክኽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ከራቀ ፡ አገር ፡ ባሪያዎችኽ ፡ መጥተናል ፤ ዝናውንም ፥ በግብጽም ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፥

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶም ፡ በነበሩት ፡ በኹለቱ ፡ በአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ በሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎን ፡ በዐስታሮትም ፡ በነበረው ፡ በባሳን ፡ ንጉሥ ፡ በዐግ ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ ሰምተናል ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ሽማግሌዎቻችንም ፡ በምድራችንም ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፦ ለመንገድ ፡ ሥንቅ ፡ በእጃችኹ ፡ ያዙ ፥ ልትገናኟቸውም ፡ ኺዱ ፦ እኛ ፡ ባሪያዎቻችኹ ፡ ነን ፤ አኹንም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጉ ፡ በሏቸው ፡ አሉን ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ ለመምጣት ፡ በተነሣንበት ፡ ቀን ፡ ይህን ፡ እንጀራ ፡ ትኵሱን ፡ ለሥንቅ ፡ ከቤታችን ፡ ወሰድነው ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ደርቋል ፥ ሻግቷልም ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እነዚህም ፡ የጠጅ ፡ አቀ-ማዳዎች ፡ ዐዲስ ፡ ሳሉ ፡ ሞላንባቸው ፤ እንሆም ፥ ተቀደዋል ፤ መንገዳችንም ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ራቀብን ፡ እነዚህ ፡ ልብሶቻችንና ፡ ጫማዎቻችን ፡ አርጅተዋል ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ሰዎቹም ፡ ከሥንቃቸው ፡ ወሰዱ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አልጠየቁም ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ኢያሱም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ አደረገ ፥ በሕይወት ፡ እንዲተዋቸውም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፤ የማኅበሩም ፡ አለቃዎች ፡ ማሉላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ካደረጉ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ጎረቤቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ በመካከላቸውም ፡ እንደ ፡ ኖሩ ፡ ሰሙ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተጕዘው ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ መጡ ፤ የከተማዎቻቸውም ፡ ስም ፡ ገባዖን ፥ ከፊራ ፥ ብኤሮት ፥ ቂርያትይዓሪም ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ የሕዝቡም ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ማሉላቸው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አልመቷቸውም ። ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ በአለቃዎቹ ፡ ላይ ፡ አጕረመረሙ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ለማኅበሩ ፡ ኹሉ ፦ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለንላቸዋል ፤ ስለዚህም ፡ እንነካቸው ፡ ዘንድ ፡ አይገባንም ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ስለማልንላቸው ፡ መሐላ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይወርድብን ፡ ይህን ፡ እናድርግባቸው ፥ በሕይወትም ፡ እንተዋቸው ፡ አሏቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ አለቃዎቹም ፦ በሕይወት ፡ ይኑሩ ፡ አሏቸው ፤ አለቃዎቹም ፡ እንደ ፡ ተናገሯቸው ፡ ለማኅበሩ ፡ ኹሉ ፡ ዕንጨት ፡ ቈራጮች ፡ ውሃም ፡ ቀጂዎች ፡ ኾኑ ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ ኢያሱም ፡ ጠርቶ ፦ እናንተ ፡ በመካከላችን ፡ ስትኖሩ ፦ ከእናንተ ፡ እጅግ ፡ የራቅን ፡ ነን ፡ ብላችኹ ፡ ለምን ፡ አታለላችኹን ፧

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ አኹንም ፡ የተረገማችኹ ፡ ናችኹ ፤ ለአምላኬም ፡ ቤት ፡ ዕንጨት ፡ ቈራጭ ፡ ውሃም ፡ ቀጂ ፡ የኾነ ፡ ባሪያ ፡ ከእናንተ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጠፋም ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ መልሰውም ፡ ኢያሱን ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ምድሪቱን ፡ ኹሉ ፡ ይሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፥ በርሷም ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ከፊታችኹ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሪያውን ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ በእውነት ፡ ሰምተናል ፥ ስለዚህም ፡ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ነፍሳችን ፡ እጅግ ፡ ፈራን ፥ ይህንም ፡ ነገር ፡ አድርገናል ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ በእጅኽ ፡ ውስጥ ፡ ነን ፤ ለዐይንኽም ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ የመሰለውን ፡ ነገር ፡ አድርግብን ፡ አሉት ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ እንዲሁም ፡ አደረገባቸው ፥ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ፥ አልገደሏቸውምም ።

ኢ.ያ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ ለማኅበሩ ፡ በመረጠውም ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ዕንጨት ፡ ቈራጮች ፡ ውሃም ፡ ቀጂዎች ፡ አደረጋቸው ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ አዶኒጼዴቅ ፡ ኢያሱ ፡ ጋይን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ፈጽሞም ፡ እንዳጠፋት ፥ በኢያሪኮና ፡ በንጉሧም ፡ ያደረገውን ፡ እንዲሁ ፡ በጋይና ፡ በንጉሧ ፡ እንዳደረገ ፥ የገባዖንም ፡ ሰዎች ፡

ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ እንዳደረጉ ፡ በመካከላቸውም ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ ገባዖን ፡ ከመንግሥታት ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ኾነች ፥ ከጋይም ፡ ስለ ፡ በለጠች ፥ ሰዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ኀያላን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፥ እጅግ ፡ ፈራ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ስለዚህም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ አዶኒጼዴቅ ፡ ወደኬብሮን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሖሃም ፥ ወደየርሙት ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ጲርአም ፥ ወደለኪሶ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ያፊዓ ፥ ወደአዶላም ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ዳቤር ፡ ልኮ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ውጡ ፥

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ ከኢያሱና ፡ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ አድርገዋልና ፥ ገባዖንን ፡ ለመምታት ፡ አግዙኝ ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ ዐምስቱም ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፥ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፥ የኬብሮን ፡ ንጉሥ ፥ የየርሙት ፡ ንጉሥ ፥ የለኪሶ ፡ ንጉሥ ፥ የአዶላም ፡ ንጉሥ ፥ ከሰራዊቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተሰብስበው ፡ ወጡ ፥ ከገባዖንም ፡ ጋራ ፡ ሊጋጠሙ ፡ ከበቧት ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ የገባዖንም ፡ ሰዎች ፡ ኢያሱ ፡ ወደሰፈረበት ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ልከው ፦ ባሪያዎችኽን ፡ ለመርዳት ፡ እጅኽን ፡ አትመልስ ፤ በተራራማው ፡ አገር ፡ የሚኖሩ ፡ የአሞራውያን ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበውብናልና ፥ ፈጥነኽ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ውጣ ፡ አድነንም ፡ ርዳንም ፡ አሉት ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላኑም ፡ ኹሉ ፡ ከገልገላ ፡ ወጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፦ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻቸዋለኹና ፡ አትፍራቸው ፤ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የሚቋቋምኽ ፡ የለም ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ ኢያሱም ፡ ከገልገላ ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ገሥግሦ ፡ በድንገት ፡ መጣባቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ አስደነገጣቸው ፤ በገባዖንም ፡ ታላቅ ፡ መምታት ፡ መታቸው ፥ በቤትሖሮንም ፡ ዐቀበት ፡ በመንገድ ፡ አሳደዳቸው ፥ እስከ ፡ ዓዜቃና ፡ እስከ ፡ መቄዳ ፡ ድረስ ፡ መታቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እየሸሹ ፡ በቤትሖሮን ፡ ቍልቍለት ፡ ሲወርዱ ፥ ወደ ፡ ዓዜቃ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ታላላቅ ፡ የበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ አወረደባቸውና ፡ ሞቱ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በሰይፍ ፡ ከገደሏቸው ፡ ይልቅ ፡ በበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ የሞቱት ፡ በለጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አሞራውያንን ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠ ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተናገረ ፤ በእስራኤልም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በገባዖን ፡ ላይ ፡ ፀሓይ ፡ ትቁም ፥ በኤሎንም ፡ ሸለቆ ፡ ጨረቃ ፤

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 13 ፤ ሕዝቡም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ እስኪበቀሉ ፡ ድረስ ፡ ፀሓይ ፡ ቆመ ፥ ጨረቃም ፡ ዘገየ ። ይህስ ፡ በያሻር ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ ፀሓይም ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ ዘገየ ፥ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሙሉ ፡ ያኽል ፡ ለመግባት ፡ አልቸኰለም ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ይዋጋ ፡ ነበርና ፥ እግዚአብሔር ፡ የሰውን ፡ ቃል ፡ የሰማበት ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ቀን ፡ ከዚያም ፡ በፊት ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አልነበረም ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሰፈራቸው ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ተመለሱ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 16 ፤ እነዚህም ፡ ዐምስት ፡ ነገሥታት ፡ ሸሽተው ፡ በመቄዳ ፡ ዋሻ ፡ ተሸሸጉ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ለኢያሱም ፦ ዐምስቱ ፡ ነገሥታት ፡ በመቄዳ ፡ ዋሻ ፡ ተሸሽገው ፡ ተገኙ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ኢያሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወደዋሻው ፡ አፍ ፡ ታላላቅ ፡ ድንጋይ ፡ አንከባሎ፞ችኹ ፥ ይጠብቋቸው ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ በዚያ ፡ አኑሩ ፤

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ አትዘግዩ ፥ ጠላቶቻችኹንም ፡ አባሯቸው ፥ በኋላም ፡ ያሉትን ፡ ግደሉ ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷቸዋልና ፥ ወደ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ እንዳይገቡ ፡ ከልክሏቸው ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ እስኪጠፉም ፡ ድረስ ፡ ኢያሱና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በታላቅ ፡ መምታት ፡ መምታታቸውን ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፥ ከነርሱም ፡ ያመለጡት ፡ ወደተመሸገ ፡ ከተማ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ወደ ፡ መቄዳ ፡ በደኅና ፡ ተመለሱ ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ምላሱን ፡ ማንቀሳቀስ ፡ የደፈረ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ የለም ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ኢያሱም ፦ የዋሻውን ፡ አፍ ፡ ክፈቱ ፥ እነዚያንም ፡ ዐምስት ፡ ነገሥታት ፡ ከዋሻው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አውጧቸው ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ አደረጉ ፤ ዐምስቱንም ፡ ነገሥታት ፥ የኢየሩሳሌምን ፡ ንጉሥ ፡ የኬብሮንንም ፡ ንጉሥ ፡ የየርሙትንም ፡ ንጉሥ ፡ የለኪሶንም ፡ ንጉሥ ፡ የአዶላምንም ፡ ንጉሥ ፥ ከዋሻው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አወጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ እነዚያንም ፡ ነገሥታት ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ ባወጧቸው ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ የእስራኤልን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የኼዱትን ፡ የሰልፈኞች ፡ አለቃዎች ፦ ቅረቡ ፥ በእነዚህም ፡ ነገሥታት ፡ ዐንገት ፡ ላይ ፡ እግራችኹን ፡ አኑሩ ፡ አላቸው ። ቀረቡም ፥ በዐንገታቸውም ፡ ላይ ፡ እግራቸውን ፡ አኖሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ኢያሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ በምትወጓቸው ፡ በጠላቶቻችኹ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋልና ፥ አትፍሩ ፥ አትደንግጡ ፤ ጽኑ ፥ አይዟችኹ ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ መትተው ፡ ገደሏቸው ፥ በዐምስቱም ፡ ዛፎች ፡ ላይ ፡ ሰቀሏቸው ፤ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ በዛፎቹ ፡ ተሰቅለው ፡ ቈዩ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ፀሓይም ፡ ልትገባ ፡ በቀረበች ፡ ጊዜ ፡ ኢያሱ ፡ አዘዘ ፥ ከዛፎችም ፡ አወረዷቸው ፥ ተሸሽገውም ፡ በነበሩበት ፡ ዋሻ ፡ ጣሏቸው ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዋሻው ፡ አፍ ፡ ታላላቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተደርጓል ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ መቄዳን ፡ ያዛት ፥ ርሷንና ፡ ንጉሧንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መታ ፤ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ፥ ከነርሱም ፡ አንዱን ፡ ስንኳ ፡ አላስቀረም ፤ በኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡ እንዳደረገ ፡ በመቄዳ ፡ ንጉሥ ፡ አደረገ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከመቄዳ ፡ ወደ ፡ ልብና ፡ ዐለፉ ፥ ልብናንም ፡ ወጉ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ርሷንና ፡ ንጉሧን ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ ርሷንም ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መታ ፥ በርሷም ፡ አንዱን ፡ ስንኳ ፡ አላስቀረም ፤ በኢያሪኮም ፡ ንጉሥ ፡ እንዳደረገው ፡ በልብና ፡ ንጉሥ ፡ አደረገ ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከልብና ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ዐለፉ ፥ ከበቧትም ፥ ወጓትም ።

ኢ.ያ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኪሶን ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣት ፥ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡

ያዟት ፤ በልብናም ፡ እንዳደረጉት ፡ ኹሉ ፥ ርሷን ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቷቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 33 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የጌዝር ፡ ንጉሥ ፡ ሆራም ፡ ለኪሶን ፡ ለመርዳት ፡ ወጣ ፤ ኢያሱም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ርሱንና ፡ ሕዝቡን ፡ መታ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 34 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከለኪሶ ፡ ወደ ፡ ኦዶላም ፡ ዐለፉ ፥ ከበቧትም ፥ ወጓትም ፤

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 35 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ያዟት ፥ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቷት ፤ በለኪሶም ፡ እንዳደረገው ፡ ኹሉ ፥ በርሷ ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 36 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከኦዶላም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ወጡ ፥ ወጓትም ፥ ያዟትም ፤

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 37 ፤ ርሷንም ፡ ንጉሧንም ፡ ከተማዎቿንም ፡ ኹሉ ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፤ በኦዶላም ፡ እንዳደረገው ፡ ኹሉ ፡ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤ ርሷንም ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 38 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ዳቤር ፡ ተመለሱ ፥ ወጓትም ፥

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 39 ፤ ርሷንም ፡ ንጉሧንም ፡ ከተማዎቿንም ፡ ያዙ ፤ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቷቸው ፥ በእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ አጠፉ ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤ በኬብሮን ፥ ደግሞ ፡ በልብናና ፡ በንጉሧ ፡ እንዳደረገው ፡ እንዲሁ ፡ በዳቤርና ፡ በንጉሧ ፡ አደረገ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 40 ፤ እንዲሁም ፡ ኢያሱ ፡ ምድሪቱን ፡ ኹሉ ፡ ተራራማውን ፡ አገር ፡ ደቡቡንም ፡ ቈላውንም ፡ ቀኑልቀኑለቱንም ፡ ነገሥታታቸውንም ፡ ኹሉ ፡ መታ ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘውም ፡ ነፍስ ፡ ያለበትን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 41 ፤ ኢያሱም ፡ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ እስከ ፡ ጋዛ ፡ ድረስ ፡ የጎሶምንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ገባዖን ፡ ድረስ ፡ መታ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 42 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ስለ ፡ ተዋጋላቸው ፡ ኢያሱ ፡ እነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ምድራቸውንም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ያዘ ።

ኢ.ያ. ፥ 10 ፥ 43 ፤ ኢያሱም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ተመለሱ ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ኢ.ያ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስ ([108]) ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደማዶን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዮባብ ፥ ወደሺምሮንም ፡ ንጉሥ ፥ ወደአዚፍም ፡ ንጉሥ ፥

ኢ.ያ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ በሰሜንም ፡ በተራራማው ፡ አገር ፥ በኪኔሬትም ፡ ደቡብ ፡ በዐረባ ፥ በቈላውም ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ባለ ፡ በዶር ፡ ኮረብታ ፡ ወደ ፡ ነበሩ ፡ ነገሥታት ፥

ኢ.ያ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ በምሥራቅና ፡ በምዕራብም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ከነዓናዊው ፥ ወደ ፡ አሞራዊውም ፥ ወደ ፡ ኬጢያዊውም ፥ ወደ ፡ ፌርዛዊውም ፥ በተራራማውም ፡ አገር ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ኢያቡሳዊው ፥ ከአርሞንዔምም ፡ በታች ፡ በምጽጳ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ዔዊያዊው ፡ ላከ ።

---

108 ዕብ. ፥ ያቢይን ፡ (ይቤይን • ይለይ ፥ ያስተውል ፥ ይፍረድ) ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ እነዚህም ፡ ከሰራዊቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ከእጅግም ፡ ብዙ ፡ ፈረሰኞችና ፡ ሠረገላዎች ፡ ጋራ ፡ ወጡ ፤ በባሕር ፡ ዳርም ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ እነዚህም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እስራኤልን ፡ ለመውጋት ፡ መጥተው ፡ በማሮን ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ሰፈሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አድርጌ ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹና ፡ አትፍራቸው ፤ የፈረሶቻቸውንም ፡ ቋንጣ ፡ ትቈርጣለኽ ፥ ሠረገላዎቻቸውንም ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለኽ ፡ አለው ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ኢያሱም ፡ ከሰልፈኞቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በድንገት ፡ ወደማሮን ፡ ውሃ ፡ መጣባቸው ፥ ወደቀባቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ መቷቸውም ፥ ወደ ፡ ታላቂቱም ፡ ሲዶና ፥ ወደ ፡ ማሴሮንም ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡ ወደምጽጻ ፡ ሸለቆ ፡ አሳደዷቸው ፤ ማንንም ፡ ሳያስቀሩ ፡ መቷቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ኢያሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገባቸው ፤ የፈረሶቻቸውንም ፡ ቋንጣ ፡ ቈረጠ ፥ ሠረገላዎቻቸውንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ ተመልሶ ፡ አሶርን ፡ ያዘ ፥ ንጉሧንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደለ ፤ አሶርም ፡ አስቀድሞ ፡ የእነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ነበረች ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፥ ፈጽመውም ፡ አጠፏቸው ፤ እስትንፋስ ፡ ያለውንም ፡ አላስቀሩም ፤ አሶርንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠላት ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘው ፥ ኢያሱ ፡ የእነዚህን ፡ ነገሥታት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ ነገሥታታቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ያዘ ፥ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መታቸው ፥ ፈጽሞም ፡ አጠፋቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ እስራኤልም ፡ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ አላቃጠሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስራኤል ፡ አሶርን ፡ ብቻ ፡ አቃጠሏት ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የእነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ ምርኮ ፡ ኹሉ ፡ ከብቶቹንም ፡ ለራሳቸው ፡ ዘረፉ ፤ ሰዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቷቸው ፥ እስትንፋስ ፡ ያለውንም ፡ ኹሉ ፡ አላስቀሩም ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባሪያውን ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘው ፡ እንዲሁ ፡ ሙሴ ፡ ኢያሱን ፡ አዞት ፡ ነበር ፥ ኢያሱም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ ካዘዘው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አላስቀረም ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ኢያሱም ፡ ያን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ተራራማውን ፥ ደቡቡንም ፡ ኹሉ ፥ የጎሶምንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ቈላውንም ፥ ዐረባንም ፥ የእስራኤልንም ፡ ተራራማውንና ፡ ቈላውን ፡ ያዘ ፥

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ እስከ ፡ ሴይርም ፡ ከሚያወጣው ፡ ወና ፡ ከኾነው ፡ ተራራ ፡ ገምሮ ፡ ከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ በሊባኖስም ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ በዓልጋድ ፡ ድረስ ፤ ነገሥታታቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ይዞ ፡ መታቸው ፥ ገደላቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ኢያሱም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከነዚህ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ በገባዖን ፡ ከሚኖሩ ፡ ከዔዊያውያን ፡ በቀር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ ያደረገች ፡

አንዲት ፡ ከተማ ፡ አልነበረችም ፤ ኹሉን ፡ በሰልፍ ፡ ያዙ ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፥ ያጠፏቸው ፡ ዘንድ ፡ ሞገስንም ፡ እንዳያገኙ ፡ ፈጽመውም ፡ እንዲያጠፏቸው ፥ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ይጋጠሙ ፡ ዘንድ ፡ ልባቸውን ፡ እንዲያደነድኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኾነ ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኢያሱ ፡ መጣ ፥ ከተራራማውም ፡ አገር ፡ ከኬብሮንም ፡ ከዳቤርም ፡ ከአናብም ፡ ከእስራኤልም ፡ ተራራማ ፡ ኹሉ ፡ ከይሁዳም ፡ ተራራማ ፡ ኹሉ ፡ የዔናቅን ፡ ልጆች ፡ ገደለ ፤ ኢያሱም ፡ ከከተማዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ በጋዛ ፣ በጌትም ፣ በአዛጦንም ፡ ጥቂቶች ፡ ቀሩ ፡ እንጂ ፥ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ ከዔናቅ ፡ ልጆች ፡ ማንም ፡ አልቀረም ።

ኢ.ያ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ኹሉ ፡ ኢያሱ ፡ ምድሪቱን ፡ ኹሉ ፡ ያዘ ፤ ኢያሱም ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ክፍላቸውና ፡ እንደ ፡ ነገዳቸው ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ምድሪቱን ፡ ሰጣቸው ፤ ምድሪቱም ፡ ከሰልፍ ፡ ዐረፈች ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የመቷቸው ፥ ከአርኖንም ፡ ሸለቆ ፡ ዠምሮ ፡ እስከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ ዐረባ ፡ ኹሉ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ያለውን ፡ አገራቸውን ፡ የወረሷቸው ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ በሐሴቦን ፡ የተቀመጠው ፥ በአርኖንም ፡ ሸለቆ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፥ ከሸለቆውም ፡ መካከል ፡ ዠምሮ ፡ የገለዓድን ፡ እኩሌታ ፡ እስከያቦቅ ፡ ወንዝ ፡ እስከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ዐረባ ፡ እስከኪኔሬት ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፥ በቤትየሺሞት ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ እስካለው ፡ እስከአረባ ፡ ባሕር ፡ እስከጨው ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፥ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡ አፋፍ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ምድር ፡ የገዛው ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎን ፤

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ከራፋይምም ፡ ወገን ፡ የቀረ ፥ በዐስታሮትና ፡ በኤድራይ ፡ የተቀመጠው ፥ የአርሞንዔምንም ፡ ተራራ ፥

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ሰልካን ፥ ባሳንንም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ጌሹራውያንና ፡ እስከማዕካታውያን ፡ ዳርቻ ፥ የገለዓድንም ፡ እኩሌታ ፡ እስከሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ እስከሴዎን ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ የገዛው ፡ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግ ።

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መቷቸው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ ለጋድም ፡ ልጆች ፡ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ምድሪቱን ፡ ሰጣቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 7-8 ፤ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በሊባኖስ ፡ ሸለቆ ፡ ካለችው ፡ ከበዓልጋድ ፡ ወደ ፡ ሴይር ፡ እስከሚያወጣው ፡ ወና ፡ እስከኾነው ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ኢያሱ ፡ በየክፍላቸው ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ለእስራኤል ፡ ነገድ ፡ በሰጣት ፡ ምድር ፥ በተራራማው ፡ አገር ፥ በቈላውም ፥ በዐረባም ፥ በቀ·ልቀ·ለቱም ፥ በምድረ ፡ በዳውም ፥ በደቡቡም ፡ ያሉ ፡ ኬጢያውያን ፡ አሞራውያንም ፡ ከነዓናውያንም ፡ ፈ"ርዛውያንም ፡ ዔዋያውያንም ፡ ኢያቡሳውያንም ፡ የኾኑ ፡ ኢያሱና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የመቷቸው ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ የኢያሪኮ ፡ ንጉሥ ፥ በቤቴል ፡ አጠገብ ፡ ያለችው ፡ የጋይ ፡ ንጉሥ ፥

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፥ የኬብሮን ፡ ንጉሥ ፥

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ የየርሙት ፡ ንጉሥ ፥ የለኪሶ ፡ ንጉሥ ፥

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ 13 ፤ የአዶላም ፡ ንጉሥ ፡ የጌዝር ፡ ንጉሥ ፡ የዳቤር ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ የጌድር ፡ ንጉሥ ፡ የሔርማ ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ የዓራድ ፡ ንጉሥ ፡ የልብና ፡ ንጉሥ ፡ የዓዶላም ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ የመቄዳ ፡ ንጉሥ ፡ የቤቴል ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ 18 ፤ የታጹዋ ፡ ንጉሥ ፡ የኦፌር ፡ ንጉሥ ፡ የአፌቅ ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ የለሸሮን ፡ ንጉሥ ፡ የማዶን ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የሺምሮን ፡ ሜሮን ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ የአዚፍ ፡ ንጉሥ ፡ የታዕናክ ፡ ንጉሥ ፡ የመጊዶ ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ የቃዴስ ፡ ንጉሥ ፡ በቀርሜሎስ ፡ የነበረ ፡ የዮቅንዓም ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ በዶር ፡ ኰረብታ ፡ የነበረ ፡ የዶር ፡ ንጉሥ ፡ የገልገላ ፡ አሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡

ኢ.ያ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ የቲርሳ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥታቱ ፡ ኹሉ ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ናቸው ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ኢያሱም ፡ ሸመገለ ፡ በዕድሜም ፡ አረጀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ሸመገልኽ ፡ በዕድሜኽም ፡ አረጀኽ ፤ ያልተወረሰች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ምድር ፡ ገና ፡ ቀርታለች ፤

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ የቀረችውም ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፡ የፍልስጥኤማውያንና ፡ የጌሹራውያን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ በግብጽ ፡ ፊት ፡ ካለው ፡ ከሺሖር ፡ ወንዝ ፡ ገምሮ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ እስካለችው ፡ የከነዓናውያን ፡ ኾና ፡ እስከተቈጠረችው ፡ እስከዐቃሮን ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ የጋዛ ፡ የአዛጦን ፡ የአስቀሎና ፡ የጌት ፡ የዐቃሮን ([109]) ፡ ዐምስቱ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ መኳንንት ፡

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ የኤዋውያን ፡ የከነዓናውያን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለሲዶናውያንም ፡ የምትኾን ፡ መዓራ ፡ እስከአሞራውያን ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ አፌቅ ፡ ድረስ ፡

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ የጌባላውያውንም ፡ ምድር ፡ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ ካለችው ፡ በዓልጋድ ፡ ገምሮ ፡ እስከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ያለችው ፡ ሊባኖስ ፡ ኹሉ ፡

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ በተራራማውም ፡ አገር ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ከሊባኖስ ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ማሴሮን ፡ ድረስ ፡ ሲዶናውያን ፡ ኹሉ ፤ እነዚህን ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ አባርራቸዋለኹ ፤ እንዳዘዝኹኽም ፡ ምድራቸውን ፡ ለእስራኤል ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ አካፍላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ ይህን ፡ ምድር ፡ ለዘጠኙ ፡ ነገድ ፡ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ክፈለው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ከርሱ ፡ ከምናሴ ፡ ጋራ ፡ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሙሴ ፡ የሰጣቸውን ፡ ርስታቸውን ፡ ተቀበሉ ።

---

109 ዕብ. ፡ ዔቅሮኒይ

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ በአርኖን ፡ ሸለቆ ፡ ዳር ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፥ በሸለቆውም ፡ መካከል ፡ ካለችው ፡ ከተማ ፡ ዝምሮ ፡ የሜድባን ፡ ሜዳ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ዲቦን ፡ ድረስ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በሐሴቦንም ፡ የነገሠ ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ እስከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ገለዓድንም ፥ የጌሹራውያንንና ፡ የማዕካታውያንን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፥ የአርሞንዔምንም ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ባሳንንም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ሰልካ ፡ ድረስ ፥ በባሳን ፡ የነበረውን ፡ በዐስታሮትና ፡ በኤድራይ ፡ የነገሠውን ፡ የዐግን ፡ መንግሥት ፡ ኹሉ ፤ ርሱም ፡ ከራፋይም ፡ የቀረ ፡ ነበረ ፤ እነዚህንም ፡ ሙሴ ፡ መታቸው ፡ አወጣቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ጌሹራውያንንና ፡ ማዕካታውያንን ፡ አላወጡም ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ጌሹርና ፡ ማዕካት ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ይኖራሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ለሌዊ ፡ ነገድ ፡ ግን ፡ ርስት ፡ አልሰጠም ፤ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቀረበው ፡ በእሳት ፡ የተደረገ ፡ መሥዋዕት ፡ ርስታቸው ፡ ነው ፥ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ ለሮቤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ ርስትን ፡ ሰጣቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ድንበራቸውም ፡ በአርኖን ፡ ሸለቆ ፡ ዳር ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፡ ዝምሮ ፡ በሸለቆው ፡ መካከል ፡ ያለችው ፡ ከተማ ፥ የሜድባ ፡ ሜዳ ፡ ኹሉ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ሐሴቦንም ፥ በሜዳውም ፡ ያሉት ፡ ከተማዎቿ ፡ ኹሉ ፥ ዲቦን ፥ ባሞትበዓል ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ቤትበዓልምዖን ፥ ያሀጽ ፥ ቅዴሞት ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ ሜፍዓት ፥ ቂርያታይም ፥ ሴባማ ፥ በሸለቆውም ፡ ተራራ ፡ ያለችው ፡ ጼሬትሻሐር ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ቤተ ፡ ፌጎር ፥ ከፈስጋ ፡ ተራራ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ምድር ፥ ቤትየሺሞት ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ የሜዳውም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ በሐሴቦንም ፡ የነገሠው ፡ የአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ መንግሥት ፡ ኹሉ ፡ ነበረ ፤ ሙሴም ፡ ርሱንና ፡ በምድሪቱ ፡ የተቀመጡትን ፡ የሴዎንን ፡ መሳፍንት ፥ የምድያምን ፡ አለቃዎች ፡ ዔዊን ፥ ሮቆምን ፥ ሱርን ፥ ሑርን ፥ ሪባን ፡ መታቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ከገደሏቸውም ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሟርተኛውን ፡ የቢዖርን ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ ድንበር ፡ የዮርዳኖስ ፡ ወንዝና ፡ ዳርቻው ፡ ነበረ ። የሮቤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ከተማዎቻቸውም ፡ መንደሮቻቸውም ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ሙሴም ፡ ለጋድ ፡ ነገድ ፡ ለጋድም ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ድንበራቸውም ፡ ኢያዜርና ፡ የገለዓድ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ እኩሌታ ፡ በረባት ፡ ፊት ፡ እስካለችው ፡ እስከ ፡ ዐሮዔር ፡ ድረስ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ ከሐሴቦን ፡ ዝምሮ ፡ እስከ ፡ ራማት ፡ ምጽጼ ፥ እስከ ፡ ብጦኒም ፡ ድረስ ፥ ከመሃናይም ፡ ዝምሮ ፡ እስከዳቤር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ በሸለቆውም ፡ ቤትሀራም ፡ ቤትኒምራ ፡ ሱኮት ፡ ጻፎን ፡ የሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎን ፡ መንግሥት ፡ ቅሬታ ፡ ነበረ ። ድንበሩም ፡ ዮርዳኖስና ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ የኪኔሬት ፡ ባሕር ፡ ወዲያኛው ፡ ዳርቻ ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ የጋድ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ከተማዎቻቸውም ፡ መንደሮቻቸውም ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፡ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ፤ ለምናሴም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ ድንበራቸውም ፡ ከመሃናይም ፡ ገምሮ ፡ የባሳን ፡ ንጉሥ ፡ የዐግ ፡ መንግሥት ፥ ባሳን ፡ ኹሉ ፥ በባሳንም ፡ ያሉት ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡ ኹሉ ፡ ስድሳው ፡ ከተማዎች ፥ የገለዓድም ፡ እኩሌታ ፥

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ በባሳንም ፡ ያሉት ፡ የዐግ ፡ መንግሥት ፡ ከተማዎች ፥ ዐስታሮትና ፡ ኤድራይ ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡ ለምናሴ ፡ ልጅ ፡ ለማኪር ፡ ልጆች ፡ ኾኑ ፤ ለማኪር ፡ ልጆች ፡ እኩሌታ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ ሙሴ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ሳለ ፡ የከፈለው ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ለሌዊ ፡ ነገድ ፡ ግን ፡ ሙሴ ፡ ርስት ፡ አልሰጠም ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳላቸው ፡ ርስታቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ የወረሱት ፥ ካህኑ ፡ አልዓዛርና ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ የአባቶቻቸው ፡ አለቃዎች ፡ ያካፈሏቸው ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ ለዘጠኙ ፡ ነገድና ፡ ለእኩሌታው ፡ በየርስታቸው ፡ በዕጣ ፡ አካፈሏቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ለኹለቱ ፡ ነገድና ፡ ለእኩሌታው ፡ ነገድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ሙሴ ፡ ርስት ፡ ሰጥቶ ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመካከላቸው ፡ ለሌዋውያን ፡ ርስት ፡ አልሰጣቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ፡ ኹለት ፡ ነገዶች ፡ ነበሩ ፤ ለሌዋውያንም ፡ ከሚቀመጡባቸው ፡ ከተማዎች ፡ ለእንስሳዎቻቸውና ፡ ለከብቶቻቸውም ፡ ከሚኾን ፡ መሰምሪያቸው ፡ በቀር ፡ በምድሩ ፡ ውስጥ ፡ ድርሻ ፡ አልሰጧቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ አደረጉ ፥ ምድሪቱንም ፡ ተካፈሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በገልገላ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ ቀረቡ ፤ ቄኔዛዊውም ፡ የዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ አለው ፦ ለአምላክኽ ፡ ሰው ፡ ለሙሴ ፡ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃዴስ ፡ በርኔ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ ታውቃለኽ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ምድርን ፡ እሰልል ፡ ዘንድ ፡ ከቃዴስ ፡ በርኔ ፡ በላከኝ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ የአርባ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበርኹ ፥ እኔም ፡ በልቤ ፡ የነበረውን ፡ ቃል ፡ መለስኹለት ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የወጡ ፡ ወንድሞቼ ፡ ግን ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ አቀለጡ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ አምላኬን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሜ ፡ ተከተልኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ሙሴም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፦ አምላኬን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽመኽ ፡ ተከትለኻልና ፥ እግርኽ ፡ የረገጠው ፡ ምድር ፡ ለአንተና ፡ ለልጆችኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ በርግጥ ፡ ርስት ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለሙሴ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥ እስራኤል ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሲዞሩ ፥ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ በሕይወት ፡ አኖረኝ ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ለእኔ ፡ ዛሬ ፡ ሰማንያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኾነኝ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ሙሴም ፡ በላከኝ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበርኹ ፥ ዛሬ ፡ ጕልበታም ፡ ነኝ ፤ ጕልበቴም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እንዲሁ ፡ ዛሬ ፡ ለመዋጋት ፡ ለመውጣትም ፡ ለመግባትም ፡ ጕልበቴ ፡ ያው ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ይህን ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ስጠኝ ፤ አንተ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ዔናቃውያን ፡ ታላላቆችና ፡ የተመሸጉ ፡ ከተማዎችም ፡ በዚያ ፡ እንዳሉ ፡ ሰምተኽ ፡ ነበር ፤ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ አሳድዳቸዋለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ኢያሱም ፡ ባረከው ፤ ለዮፎኒም ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ ኬብሮንን ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሰጠው ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈጽሞ ፡ ስለ ፡ ተከተለ ፡ ኬብሮን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ለቄኔዛዊው ፡ ለዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ ርስት ፡ ኾነች ።

ኢ.ያ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ የኬብሮንም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ አርባቅ ([110]) ፡ በዔናቅ ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ከሹሉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበረ ። ምድሪቱም ፡ ከውጊያ ፡ ዐረፈች ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ለይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ እስከጺን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እስከደቡብ ፡ መጨረሻ ፡ እስከኤዶምያስ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ዕጣ ፡ ኾነላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበራቸው ፡ እስከጨው ፡ ባሕር ፡ መጨረሻ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ እስከሚያይ ፡ እስከባሕር ፡ ልሳን ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ከዚያም ፡ በአቅረቢም ፡ ዐቀበት ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ጺንም ፡ ዐለፈ ፥ በቃዴስ ፡ በርኔ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥ በሐጽሮንም ፡ በኩል ፡ ዐለፈ ፥ ወደ ፡ አዳርም ፡ ወጣ ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ቀርቃ ፡ ዞረ ፥ ወደ ፡ ዐፅሞንም ([111]) ፡ ዐለፈ ፥ በግብጽም ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ወጣ ፥ የድንበሩም ፡ መውጫ ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበር ፡ እስከጨው ፡ ባሕር ፡ እስከዮርዳኖስም ፡ መጨረሻ ፡ ነበረ ። በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበር ፡ በዮርዳኖስ ፡ መጨረሻ ፡ እስካለው ፡ እስከባሕሩ ፡ ልሳን ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ከዚያም ፡ ድንበሩ ፡ ወደ ፡ ቤትሖግላ ፡ ወጣ ፥ በቤትዐረባ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ዐለፈ ፥ ወደሮቤልም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቦሀን ፡ ድንጋይ ፡ ወጣ ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ድንበሩም ፡ ከዐኮር ፡ ሸለቆ ፡ ወደ ፡ ዳቤር ፡ ወጣ ፥ በሰሜን ፡ በኩል ፡ በአዱሚም ፡ ዐቀበት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፥ በወንዙ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ተመለከተ ፤ ድንበሩም ፡ ወደቤት ፡ ሳሚስ ([112]) ፡ ውሃ ፡ ዐለፈ ፥ መውጫውም ፡ በዐይንሮጌል ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፤

---

110 ዕብ. ፥ አርባዕ ።

111 ዕብ. ፥ ዐፅሞን ፡ (ከመ ፡ ዐፅም • እንደ ፡ ዐፅም ፥ ዐፅማዊ) ።

112 ዕብ. ፥ ዐይን ፡ ሼሜሽ ፡ (የፀሓይ ፡ ምንጭ) ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ድንበሩም ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ አጠገብ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደምትባለው ፡ ወደ ፡ ኢያቡሳዊው ፡ ወደደቡብ ፡ ወገን ፡ ወጣ ፤ ድንበሩም ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ዳር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በሄኖም ፡ ሸለቆ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ድንበሩም ፡ ከተራራው ፡ ራስ ፡ ወደኔፍቶ ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ ደረሰ ፥ ወደዔፍሮንም ፡ ተራራ ፡ ከተማዎች ፡ ወጣ ፤ ቂርያትይዓሪም ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ በዓላ ([113]) ፡ ደረሰ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ድንበሩም ፡ ከበዓላ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደሴይር ፡ ተራራ ፡ ዞረ ፤ ክሳሎን ፡ ወደምትባል ፡ ወደይዓሪም ፡ ተራራ ፡ ወገን ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ዐለፈ ፤ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ወረደ ፥ በተምና ፡ በኩልም ፡ ዐለፈ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ዐቃሮን ፡ ወደሰሜን ፡ ወገን ፡ ወጣ ፤ ወደ ፡ ሽክሮን ፡ ደረሰ ፤ ወደበዓላ ፡ ተራራ ፡ ዐለፈ ፥ በየብኒኤል ፡ በኩልም ፡ ወጣ ፤ የድንበሩም ፡ መውጫ ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ በምዕራቡም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ድንበር ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕርና ፡ እስከ ፡ ዳርቻው ፡ ድረስ ፡ ነበረ ። ለይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ድንበራቸው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ እንዳዘዘው ፡ ለዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ የምትባለውን ፡ ከተማ ፡ ድርሻ ፡ አድርጎ ፡ ሰጠው ፤ ርሷም ፡ ኬብሮን ፡ ናት ፥ ይህም ፡ አርባቅ ፡ የዔናቅ ፡ አባት ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ካሌብም ፡ ሦስቱን ፡ የዔናቅን ፡ ልጆች ፡ ሴሲንና ፡ አኪመንን ፡ ተላሚንም ፡ ከዚያ ፡ አሳደደ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ከዚያም ፡ በዳቤር ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ የዳቤርም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ቂርያትሴፍር ፡ ትባል ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ካሌብም ፦ ቂርያትሴፍርን ፡ ለሚመታ ፡ ለሚይዛትም ፡ ልጄን ፡ ዓክሳን ፡ አጋባዋለኹ ፡ አለ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ የካሌብ ፡ ወንድም ፡ የቄኔዝ ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ያዛት ፤ ልጁንም ፡ ዓክሳን ፡ አጋባው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ርሷም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ከአባቷ ፡ ዕርሻ ፡ እንዲለምን ፡ መከረችው ፤ ርሷም ፡ ከአህያዋ ፡ ወረደች ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ካሌብም ፦ ምን ፡ ፈለግሽ ፧ አላት ። ርሷም ፦ በረከትን ፡ ስጠኝ ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ምድር ፡ ሰጥተኸኛልና ፥ አኹን ፡ ደግሞ ፡ የውሃውን ፡ ምንጭ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ። ርሱም ፡ የላይኛውንና ፡ የታችኛውን ፡ ምንጭ ፡ ሰጣት ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ በየወገኖቻቸውም ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ በምድራቸው ፡ ዳርቻ ፡ አጠገብ ፡ እስከኤዶምያስ ፡ ድንበር ፡ ያሉት ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከተማዎች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ቀብስኤል ፥ ዔዴር ፥ ያጉር ፥ ቂና ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ዲሞና ፥ ዓድዓዳ ፥ ቃዴስ ፥ ሐጾር ፥ ዩትናን ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ 25 ፤ ዚፍ ፥ ጤሌም ፥ በዓሎት ፥ ሐጾርሐዳታ ፥ ሐጾር ፡ የምትባለውም ፡ ቂርያትሐጾር ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ 27 ፤ አማም ፥ ሽማዕ ፥ ሞላዳ ፥ ሐጾርጋዳ ፥ ሐሽሞን ፥

---

113 ዕብ. ፥ በዓላህ ፡ (ባዕልት • ባለጠጊት) ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ ቤትጻሌጥ ፡ ሐጸርሹዓል ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ቢዝዮትያ ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ 30 ፤ በዓላ ፡ ዒዩም ፡ ዓጼም ፡ ኤልቶላድ ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ ኪሲል ፡ ሔርማ ፡ ጺቅላግ ፡ ማድማና ፡ ሳንሳና ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ልባዎት ፡ ሺልሂም ፡ ዐይን ፡ ሪሞን ፤ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ 34 ፤ በቄላው ፡ ኤሽታኦል ፡ ጾርዓ ፡ አሽና ፡ ዛኖዋ ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 35 ፤ ዐይንገኒም ፡ ታጹዋ ፡ ዐይናም ፡ የርሙት ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 36 ፤ ዓዶላም ፡ ሰኮት ፡ ዓዜቃ ፡ ሸዓራይም ፡ ዓዲታይም ፡ ግዴራ ፡ ግዴሮታይም ፤ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 37 ፤ 38 ፤ ጽናን ፡ ሐዳሻ ፡ ሚግዳልጋድ ፡ ዲልዓን ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 39 ፤ ምጽጻ ፡ ዮቅትኤል ፡ ለኪሶ ፡ ቦጽቃት ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 40 ፤ 41 ፤ ኦዶላም ፣ ከቦን ፣ ለሕማስ ፣ ኪትሊሽ ፣ ግዴሮት ፣ ቤትዳጎን ፣ ናዕማ ፣ መቄዳ ፤ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 42 ፤ 43 ፤ ልብና ፡ ዔቴር ፡ ዐሻን ፡ ይፍታሕ ፡ አሽና ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 44 ፤ ንጺብ ፡ ቅዒላ ፡ አክዚብ ፡ መሪሳ ፤ ዘጠኝ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 45 ፤ ዐቃሮን ፡ ከተመሸጉና ፡ ካልተመሸጉ ፡ መንደሮቿ ፡ ጋራ ፤

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 46 ፤ ከዐቃሮንም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ በአዛጦን ፡ አጠገብ ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ ከመንደሮቻቸው ፡ ጋራ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 47 ፤ አዛጦንና ፡ የተመሸጉና ፡ ያልተመሸጉ ፡ መንደሮቿም ፥ ጋዛና ፡ የተመሸጉ ፡ ያልተመሸጉም ፡ መንደሮቿ ፥ እስከግብጽ ፡ ወንዝና ፡ እስከታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 48 ፤ በተራራማውም ፡ አገር ፡ ሳምር ፥ የቲር ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 49 ፤ ሶኮ ፥ ደና ፥ ዳቤር ፡ የምትባለው ፡ ቂርያትሰና ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 50 ፤ 51 ፤ ዐናብ ፥ ኤሽትሞዐ ፥ ዓኒም ([114]) ፥ ጎሶም ፥ ሖሎን ፥ ጊሎ ፤ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 52 ፤ አራብ ፥ ዱማ ፥ ኤሽዓን ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 53 ፤ ያኒም ፥ ቤትታጹዋ ፥ አፌቃ ፥

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 54 ፤ ሑምጣ ፥ ኬብሮን ([115]) ፡ የምትባል ፡ ቂርያትአርባቅ ([116]) ፥ ጺዖር ፤ ዘጠኝ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

---

114 ዕብ. ፥ ዐኒይም ፡ (አዕይንት • ምንጮች) ።

115 ዕብ. ፥ ሔብሮን ።

116 ዕብ. ፥ ቂርያት ፡ አርባዕ ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 55 ፤ ማዖን ፡ ቀርሜሎስ ፡ ዚፍ ፡ ዩጣ ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 56 ፤ ኢይዝራኤል (117) ፡ ዮቅድዓም ፡ ዛኖዋሕ ፡

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 57 ፤ ቃይን ፡ ጊብዓ ፡ ተምና ፤ ዐሥር ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 58 ፤ 59 ፤ ሐልሑል ፡ ቤትጹር ፡ ጌዶር ፡ ማዕራት ፡ ቤትዓናት ፡ ኤልትቆን ፤ ስድስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 60 ፤ ቂርያትይዓሪም ፡ የምትባለው ፡ ቂርያትበዓል ፡ ረባት ፤ ኹለት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 61 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ቤትዐረባ ፡ ሚዲን ፡ ስካካ ፡

ኒብሻን ፡ የጨው ፡ ከተማ ፡ ዐይንጋዲ ፤ ስድስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 15 ፡ 63 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡትን ፡ ኢያቡሳውያንን ፡ ግን ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ሊያሳድዷቸው ፡ አልተቻላቸውም ፤ ኢያቡሳውያንም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ዕጣ ፡ በኢያሪኮ ፡ አጠገብ ፡ በምሥራቁ ፡ በኩል ፡ ካለው ፡ ከዮርዳኖስ ፡ አንሥቶ ፡ በምድረ ፡ በዳውና ፡ በተራራማው ፡ በኩል ፡ ከኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወጣ ፤

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ከቤቴል ፡ ወደ ፡ ሎዛ ፡ ወጣ ፥ በአርካውያንም ፡ ዳርቻ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ዐጣሮት ፡ ዐለፈ ፥

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ ምዕራብም ፡ እስከየፍሌጣውያን ፡ ዳርቻ ፡ እስከታችኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ጌዝር ፡ ድረስ ፡ ወረደ ፥ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ የዮሴፍም ፡ ልጆች ፡ ምናሴና ፡ ኤፍሬም ፡ ርስታቸውን ፡ ወረሱ ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ የኤፍሬምም ፡ ልጆች ፡ ድንበር ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፤ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የርስታቸው ፡ ድንበር ፡ ዐጣሮትአዳር ፡ እስከ ፡ ላይኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፤

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ሚክምታት ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወጣ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ተአናትሴሎ ፡ ዞረ ፥ ወደ ፡ ኢያኖክ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ዐለፈ ፥

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ ከኢያኖክም ፡ ወደ ፡ ዐጣሮትና ፡ ወደ ፡ ነዓራት ፡ ወረደ ፤ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ ደረሰ ፥ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ድንበሩም ፡ ከታጹዋ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ እስከቃና ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ዐለፈ ፥ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ይኸውም ፡ በምናሴ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡ ለኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ከተለዩ ፡ ከተማዎች ፡ ጋራ ፥ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ከመንደሮቻቸው ፡ ጋራ ፥ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ በጌዝርም ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ አላሳደዷቸውም ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ከነዓናውያን ፡ በኤፍሬም ፡ መካከል ፡ ተቀምጠዋል ፤ የጕልበት ፡ ግብርም ፡ ያስገብሯቸው ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡ ምዕራፍ ፡ 17 ።

117 ዕብ. ፥ ይዝራኤል ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ ለምናሴ ፡ ነገድ ፡ ዕጣ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የዮሴፍ ፡ በኵር ፡ ርሱ ፡ ነውና ። የምናሴም ፡ በኵር ፡ የገለዓድ ፡ አባት ፡ ማኪር ፡ ብርቱ ፡ ሰልፈኛ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ገለዓድንና ፡ ባሳንን ፡ ወረሰ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ዕጣውም ፡ ለቀሩት ፡ ለምናሴ ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፥ ለአቢዔዝር ፡ ልጆች ፥ ለኬሌግ ፡ ልጆች ፥ ለአሥሪኤል ፡ ልጆች ፥ ለሴኬም ፡ ልጆች ፥ ለኦፌር ፡ ልጆች ፥ ለሸሚዳ ፡ ልጆች ፡ ኾነ ፤ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ የምናሴ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ለምናሴ ፡ ልጅ ፥ ለማኪር ፡ ልጅ ፥ ለገለዓድ ፡ ልጅ ፥ ለኦፌር ፡ ልጅ ፥ ለሰለጰዓድ ፡ ግን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፥ የሴቶች ፡ ልጆቹም ፡ ስም ፡ ማህለህ ፥ ኑዓ ፥ ዔግላ ፥ ሚልካ ፥ ቲርጻ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አልዓዛርና ፡ ወደነዌ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ ወደ ፡ አለቃዎችም ፡ ቀርበው ፦ እግዚአብሔር ፡ በወንድሞቻችን ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ እንዲሰጠን ፡ ሙሴን ፡ አዘዘ ፡ አሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘ ፡ በአባታቸው ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ካለው ፡ ከገለዓድና ፡ ከባሳን ፡ አገር ፡ ሌላ ፡ ለምናሴ ፡ ዐሥር ፡ ዕጣ ፡ ኾነ ፤

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ የምናሴ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በወንዶች ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ ተቀብለዋልና ፤ የገለዓድም ፡ ምድር ፡ ለቀሩት ፡ ለምናሴ ፡ ልጆች ፡ ኾኗልና ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ የምናሴም ፡ ድንበር ፡ ከአሴር ፡ ዠምሮ ፡ በሴኬም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ ሚክምታት ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፤ ድንበሩም ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ዐይንታጹዋ ([118]) ፡ ሰዎች ፡ ዐለፈ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ የታጹዋ ፡ ምድር ፡ ለምናሴ ፡ ነበረ ፤ በምናሴ ፡ ዳርቻ ፡ ያለው ፡ ታጹዋ ፡ ግን ፡ ለኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ኾነ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ድንበሩም ፡ ወደቃና ፡ ወንዝ ፡ ከወንዙ ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ ወረደ ፤ በምናሴም ፡ ከተማዎች ፡ መካከል ፡ የነበሩት ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ለኤፍሬም ፡ ኾኑ ፤ የምናሴም ፡ ድንበር ፡ በወንዙ ፡ በኩል ፡ በሰሜን ፡ ወገን ፡ ነበረ ፥ መውጫውም ፡ በባሕሩ ፥ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ለኤፍሬም ፡ ነበረ ፥ በሰሜንም ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ ለምናሴ ፡ ነበረ ፥ ድንበሩም ፡ ባሕሩ ፡ ነበረ ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አሴር ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ይሳኮር ፡ ደረሰ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ በይሳኮርና ፡ በአሴር ፡ መካከል ፡ ቤትሳንና ፡ መንደሮቿ ፥ ይብልዓምና ፡ መንደሮቿ ፥ ዶርና ፡ የመንደሮቿ ፡ ሰዎች ፥ ዐይንዶርና ፡ የመንደሮቿ ፡ ሰዎች ፥ ታዕናክና ፡ የመንደሮቿ ፡ ሰዎች ፥ መጊዶና ፡ የመንደሮቿ ፡ ሰዎች ፥ ሦስቱ ፡ ኰረብታዎች ፡ ለምናሴ ፡ ነበሩ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ የምናሴ ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ የእነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ ሰዎች ፡ ሊያሳድዷቸው ፡ አልቻሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነዓናውያን ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ በመቀመጥ ፡ ጸኑ ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በጸኑ ፡ ጊዜ ፡ ከነዓናውያንን ፡ የጕልበት ፡ ግብር ፡ አስገበሯቸው ፥ ፈጽመውም ፡ አላሳደዷቸውም ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ኢያሱን ፦ እኔ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ኾንኩ ፡ እስከ ፡ አኹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ባረከኝ ፡ ለምን ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ አንድም ፡ ዕጣ ፡ ብቻ ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ሰጠኸኝ ፧ አሉት ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ኢያሱም ፦ ብዙ ፡ ሕዝብስ ፡ ከኾንኽ ፡ ተራራማውም ፡ የኤፍሬም ፡ አገር ፡ ጠቦኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ወጥተኽ ፡ በፈርዛውያንና ፡ በራፋይም ፡ ምድር ፡ ለአንተ ፡ ስፍራ ፡ መንጥር ፡ አላቸው ።

---

118 ዕብ. ፡ ዐይን ፡ ተፋሕ ፡ (የትፋሕ ፣ የኮል ፡ ምንጭ) ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ የዮሴፍም ፡ ልጆች ። ተራራማው ፡ አገር ፡ አይበቃንም ፤ በሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ ለሚኖሩት ፥ በቤትሳንና ፡ በመንደሮቿ ፡ በኢይዝራኤልም ፡ ሸለቆ ፡ ለሚኖሩት ፡ ከነዓናውያን ፡ የብረት ፡ ሠረገላዎች ፡ አላቸው ፡ አሉት ።

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ኢያሱም ፡ የዮሴፍ ፡ ወገን ፡ ለሚኾኑ ፡ ለኤፍሬምና ፡ ለምናሴ ። አንተ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነኽ ፥ ጽኑም ፡ ኀይል ፡ አለኽ ፡ አንድ ፡ ዕጣ ፡ ብቻ ፡ አይኾንልኽም ፤

ኢ.ያ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተራራማው ፡ አገር ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፥ ዱር ፡ እንኳን ፡ ቢኾንም ፡ ትመነጥረዋለኽ ፥ ለአንተም ፡ ይኾናል ፤ ለከነዓናውያንም ፡ የብረት ፡ ሠረገላዎች ፡ ቢኾኑላቸው ፡ የበረቱም ፡ ቢኾኑ ፡ ታሳድዳቸዋለኽ ፡ አላቸው ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ሹሉ ፡ በሴሎ ፡ ተሰበሰቡ ፥ በዚያም ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ተከሉ ፤ ምድሩም ፡ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተገዛላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ያልተካፈሉ ፡ ሰባት ፡ ነገድ ፡ ቀርተው ፡ ነበር ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ ኢያሱም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አላቸው ፦ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጣችኹን ፡ ምድር ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ለመግባት ፡ ቸል ፡ ትላላችኹ ፧

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ከየነገዱ ፡ ሹሉ ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ምረጡ ፥ እኔም ፡ እልካቸዋለኹ ፤ ተነሥተውም ፡ አገሩን ፡ ይዞራሉ ፥ እንደ ፡ ርስታቸውም ፡ መጠን ፡ ይጽፉታል ፤ ወደ ፡ እኔም ፡ ይመለሳሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ በሰባትም ፡ ክፍል ፡ ይከፍሉታል ፤ ይሁዳ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በዳርቻው ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣል ፤ የዮሴፍ ፡ ወገኖች ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ በዳርቻው ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ እናንተም ፡ ምድሩን ፡ በሰባት ፡ ክፍል ፡ ጻፉት ፥ የጻፋችኹትንም ፡ ወዲህ ፡ አምጡልኝ ፤ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ ዕጣ ፡ አጣጥላችኋለኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ ርስታቸው ፡ ነውና ፥ ለሌዋውያን ፡ በመካከላችኹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ የላቸውም ፤ ጋድም ፡ ሮቤልም ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ የሰጣቸውን ፡ ርስታቸውን ፡ ተቀብለዋል ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፡ ኼዱ ፤ ኢያሱም ፡ ምድሩን ፡ ሊጽፉ ፡ የኼዱትን ፦ ኺዱ ፥ ምድሩንም ፡ ዞራችኹ ፡ ጻፉት ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ተመለሱ ፤ በዚህም ፡ በሴሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዕጣ ፡ አጣጥላችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ሰዎቹም ፡ ኼደው ፡ ምድሩን ፡ ዞሩ ፥ እንደ ፡ ከተማዎችም ፡ በሰባት ፡ ክፍል ፡ ከፈሉት ፥ በመጽሐፍም ፡ ጻፉት ፤ ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ሰፈረበት ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ተመለሱ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ኢያሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሴሎ ፡ ዕጣ ፡ አጣጣላቸው ፤ በዚያም ፡ ኢያሱ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ክፍሎቻቸው ፡ ምድሩን ፡ ከፈለ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ዕጣ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ የዕጣቸውም ፡ ዳርቻ ፡ በይሁዳ ፡ ልጆችና ፡ በዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ድንበራቸው ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ዠመረ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወገን ፡ ወጣ ፥ ከዚያም ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወጣ ፥ መውጫውም ፡ በቤትአዌን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡

ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 13 ፤ ድንበሩም ፡ ከዚያ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ቤቴል ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ ሎዛ ፡ ዐለፈ ፤ ድንበሩም ፡ በታችኛው ፡ ቤትሖሮን ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ዐጣሮትአዳር ፡ ወረደ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 14 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ኼደ ፥ በቤትሖሮንም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ካለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ዞረ ፤ መውጫውም ፡ ቂርያትይዓሪም ፡ በምትባል ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ በቂርያትበዓል ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ የምዕራቡ ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 15 ፤ የደቡብም ፡ ዳርቻ ፡ ከቂርያትይዓሪም ፡ መጨረሻ ፡ ነበረ ፤ ድንበሩም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ነፍቶ ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 16 ፤ ድንበሩም ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ መጨረሻ ፡ ወረደ ፥ ርሱም ፡ በራፋይም ፡ ሸሰቆ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ሄኖም ፡ ሸለቆ ፡ ወደ ፡ ኢያቡስ ፡ ዳር ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወረደ ፥ ወደ ፡ ዐይንሮጌልም ፡ ወረደ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 17 ፤ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ዐለፈ ፡ በቤትሳሚስ ፡ ምንጭ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ በአዱሚም ፡ ዐቀበት ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ጌሊሎት ፡ ደረሰ ፤ ወደሮቤልም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቦሀን ፡ ድንጋይ ፡ ወረደ ፤

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 18 ፤ በሰሜንም ፡ ወገን ፡ ወደዐረባ ፡ አጠገብ ፡ ዐለፈ ፥ ወደ ፡ ዐረባም ፡ ወረደ ፤

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 19 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ቤትሖግላ ፡ ወደሰሜን ፡ ወገን ፡ ዐለፈ ፤ መውጫውም ፡ በዮርዳኖስ ፡ መጨረሻ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በጨው ፡ ባሕር ፡ ልሳን ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ የደቡቡ ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 20 ፤ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ድንበሩ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ነበረ ። ይህ ፡ በዙሪያቸው ፡ ዳርቻ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 21 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከተማዎች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ኢያሪኮ ፥ ቤትሖግላ ፥ ዓመቀጺጽ ፥

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 22 ፤ ቤትዐረባ ፥ ዘማራይም ፥ ቤቴል ፥

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 23 ፤ 24 ፤ ዓዊም ፥ ፋራ ፥ ኤፍራታ ፥ ክፊርዓሞናይ ፥ ዖፍኒ ፥ ጋባ ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 25 ፤ ገባዖን ፥ ራማ ፥ ብኤሮት ፥

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 26 ፤ ምጽጻ ፥ ከፊራ ፥ አሞቂ ፥

ኢ.ያ. ፥ 18 ፥ 27 ፤ 28 ፤ ሬቄም ፥ ይርጴኤል ፥ ተርአላ ፥ ጼላ ፥ ኤሌፍ ([119]) ፥ ኢየሩሳሌም ፡ የምትባል ፡ የኢያቡስ ፡ ከተማ ፥ ቂርያትጊብዓት ፤ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ። የብንያም ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ኢ.ያ. ፥ 19 ፥ 1 ፤ ኹለተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ ርስታቸውም ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡ ነበረ ።

---

119 ዕብ. ፥ ኤሌፍ ፡ (እልፍ) ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ እነዚህም ፡ ርስታቸው ፡ ኾኑላቸው ፤ ቤርሳቤሕ ፡ ሼባ ፡ ሞላዳ ፡

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 3-4 ፤ ሐጸርሹዓል ፡ ባላ ፡ ዔጼም ፡ ኤልቶላድ ፡

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ በቱል ፡ ሔርማ ፡ ጺቅላግ ፡ ቤትማርካቦት ፡

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ሐጸርሱሳ ፡ ቤተ ፡ ለባኦት ፡ ሻሩሔን ፤ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ዐይን ፡ ሪሞን ፡ ዔቴር ፡ ዐሻን ፤ አራት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ እስከ ፡ ባዕላትብኤርና ፡ እስከ ፡ ደቡቡ ፡ ራማት ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ዙሪያ ፡ ያሉ ፡ መንደሮች ፡ ኹሉ ፥— የስምዖን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፍል ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ኾነ ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ስለ ፡ በዛባቸው ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ በርስታቸው ፡ መካከል ፡ ወረሱ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ሦስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለዛብሎን ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ፤ የርስታቸውም ፡ ድንበር ፡ ወደ ፡ ሣሪድ ፡ ደረሰ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ድንበራቸውም ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ መርዓላ ፡ ወጣ ፥ እስከ ፡ ደባሼትም ፡ ደረሰ ፤ በዮቅንዓም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ወንዝ ፡ ደረሰ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ከሣሪድም ፡ ወደፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደኪስሎትታቦር ፡ ዳርቻ ፡ ዞረ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ ወደ ፡ ዳብራትም ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ያፊዓም ፡ ደረሰ ፤ ከዚያም ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ጋትሔፍርና ፡ ወደ ፡ ዒታቃጺን ፡ ዐለፈ ፤ ወደ ፡ ሪምንና ፡ ወደ ፡ ኒዓ ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ድንበሩም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ሐናቶን ፡ ዞረ ፥ መውጫውም ፡ በይፍታሕኤል ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ቀጣት ፥ ነኽላል ፥ ሺምሮን ፥ ይዳላ ፥ ቤተ ፡ ልሔም ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ የዛብሎን ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ አራተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለይሳኮር ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ድንበራቸውም ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፥ ወደ ፡ ከስሎት ፥ ወደ ፡ ሱነም ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ሐፍራይም ፥ ወደ ፡ ሺኦን ፥ ወደ ፡ አናሐራት ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ረቢት ፥ ወደ ፡ ቂሶን ፥ ወደ ፡ አቤጽ ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ወደ ፡ ሬሜት ፥ ወደ ፡ ዐይንጋኒም ፥ ወደ ፡ ዐይንሐዳ ፥ ወደ ፡ ቤትጳጼጽ ፡ ደረሰ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ታቦርና ፡ ወደ ፡ ሻሕጹማ ፥ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ደረሰ ፥ የድንበራቸውም ፡ መውጫ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ነበረ ፤ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ዐምስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለአሴር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ድንበራቸውም ፡ ሔልቃት ፥ ሐሊ ፥ ቤጤን ፥ አዚፍ ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ አላሜሌክ ፥ ዓምዓድ ፥ ሚሽአል ፡ ነበረ ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስና ፡ ወደ ፡ ሺሖርሊብናት ፡ ደረሰ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ወደፀሓይም ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ቤትዳጎን ፡ ዞረ ፥ ወደ ፡ ዛብሎንም ፡ ወደይፍታሕኤል ፡ ሸለቆ ፥ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቤትዔሜቅና ፡ ወደ ፡ ንዒኤልም ፡ ደረሰ ፤ በስተግራ ፡ በኩልም ፡ ወደ ፡ ካቡል ፡ ወጣ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ዔብሮን ፥ ወደ ፡ ረአብ ፥ ወደ ፡ ሐሞን ፥ ወደ ፡ ቃና ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ሲዶናም ፡ ደረሰ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ራማ ፥ ወደተመሸገውም ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ዞረ ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ሖሳ ፡ ዞረ ፤ መውጫውም ፡ በአክዚብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ነበረ ፤

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ዑማ ፥ አፌቅ ፥ ረአብ ([120]) ፡ ደግሞ ፡ ነበሩ ፤ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ የአሴር ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ ስድስተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ ድንበራቸውም ፡ ከሔሌፍ ፥ ከጸዕነኒም ፡ ዛፍ ፥ ከአዳሚኔቄብ ፥ ከየብኒኤል ፡ እስከ ፡ ለቁም ፡ ድረስ ፡ ነበረ ፤ መውጫውም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ ድንበሩም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ አዝኖትታቦር ፡ ዞረ ፥ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሑቆቅ ፡ ወጣ ፤ ከዚያም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ዛብሎን ፥ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ አሴር ፥ በዮርዳኖስም ፡ በፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ደረሰ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 35 ፤ የተመሸጉትም ፡ ከተማዎች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ጺዲም ፥ ጼር ፥ ሐማት ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 36 ፤ ረቃት ፥ ኬኔሬት ፥ አዳማ ፥ ራማ ፥ አሶር ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 37-38 ፤ ቃዴስ ፥ ኤድራይ ፥ ዐይንሐጾር ፥ ይርኦን ፥ ሚግዳልኤል ፥ ሖሬም ፥ ቤትዓናት ፥ ቤትሳሚስ ፤ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 39 ፤ የንፍታሌም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 40 ፤ ሰባተኛውም ፡ ዕጣ ፡ ለዳን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ወጣ ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 41 ፤ የርስታቸውም ፡ ዳርቻ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ጾርዓ ፥ ኤሽታኦል ፥ ዒርሼሜሽ ([121]) ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 42 ፤ 43 ፤ ሻዕለቢን ፥ ኤሎን ፥ ይትላ ፥ ኤሎን ፥ ተምና ፥

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 44 ፤ ዐቃሮን ፥ ኢልተቄ ፥ ገባቶን ፥ ባዕላት ፥

---

120 ዕብ. ፥ ርሖብ ፡ (ርሒብ ፥ ስፉሕ • ሰፊ ፥ ወርዳም) ።

121 ዕብ. ፥ ዒይርሼሜሽ ፡ (የፀሓይ ፡ ሰፈር) ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 45 ፤ 46 ፤ ይሁድ ፡ ብኔብረቅ ፡ ጋትሪሞን ፡ ሜያርቆን ፡ በኢዮጴ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ካለው ፡ ዳርቻ ፡ ጋራ ፡ ራቆን ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 47 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ አልበቃቸውም ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ከሌሼም ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ወጡ ፥ ያዟትም ፥ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቷት ፥ ወረሷትም ፥ ተቀመጡባትም ፤ ስሟንም ፡ በአባታቸው ፡ በዳን ፡ ስም ፡ ዳን ፡ ብለው ፡ ጠሯት ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 48 ፤ የዳን ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ርስት ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮቻቸው ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 49 ፤ ምድሩንም ፡ ዠሉ ፡ በየድንበሩ ፡ ርስት ፡ እንዲኾን ፡ ከፍለው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ለነዌ ፡ ልጅ ፡ ለኢያሱ ፡ በመካከላቸው ፡ ርስት ፡ ሰጡት ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 50 ፤ በኤፍሬም ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ተምናሴራ ፡ የምትባለውን ፡ የፈለጋትን ፡ ከተማ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጡት ፤ ከተማም ፡ ሠርቶ ፡ ተቀመጠባት ።

ኢ.ያ. ፡ 19 ፡ 51 ፤ ካህኑ ፡ አልዓዛር ፥ የነዌም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ የአባቶች ፡ አለቃዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሴሎ ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጃፍ ፡ አጠገብ ፡ በዕጣ ፡ የተካፈሉት ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ። ምድሪቱንም ፡ መካፈል ፡ ጨረሱ ።

መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢያሱን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 2-3 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ ሳይወድ ፡ ሳያውቅም ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ገዳይ ፡ እንዲሸሽባቸው ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የነገርኋችኹን ፡ መማፀኛ ፡ ከተማዎችን ፡ ለዩ ፤ ከደም ፡ ተበቃዩ ፡ መማፀኛ ፡ ይኾኑላችኋል ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ከነዚህም ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ይሸሻል ፥ በከተማዪቱም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ቆሞ ፡ በከተማዪቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጆሮ ፡ ነገሩን ፡ ይናገራል ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ይቀበሉታል ፥ የሚቀመጥበትም ፡ ስፍራ ፡ ይሰጡታል ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ደም ፡ ተበቃዩ ፡ ቢያሳድደው ፥ አስቀድሞ ፡ ሳይጠላው ፡ ባልንጀራውን ፡ በስሕተት ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ በእጁ ፡ አሳልፈው ፡ አይስጡት ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ ለፍርድ ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፥ በዚያም ፡ ወራት ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡ ካህን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በዚያች ፡ ከተማ ፡ ይቀመጥ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩ ፡ ይመለሳል ፥ ወደ ፡ ከተማውም ፡ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደወጣባትም ፡ ከተማ ፡ ይገባል ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ በንፍታሌም ፡ ባለው ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ በገሊላ ፡ ቃዴስን ፥ በኤፍሬምም ፡ ባለው ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ሴኬምን ፥ በይሁዳም ፡ ባለው ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ኬብሮን ፡ የምትባለውን ፡ ቂርያትአርባቅን ፡ ለዩ ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ከኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ በደልዳላው ፡ ስፍራ ፡ ቦሶርን ፥ ከጋድም ፡ ነገድ ፡ በገለዓድ ፡ ራሞትን ፥ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ በባሳን ፡ ጎላንን ፡ ለዩ ።

ኢ.ያ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ በማኅበሩ ፡ ፊት ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፡ በደም ፡ ተበቃዩ ፡ እጅ ፡ እንዳይሞት ፡ ሳያውቅ ፡ ሰውን ፡ የገደለ ፡ ወደዚያ ፡ እንዲሸሽ ፥ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዠሉ ፡ በመካከላቸውም ፡ ለሚቀመጥ ፡ መጻተኛ ፡ የተለዩ ፡ ከተማዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

መጽሐፈ ፡ ኢ.ያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ የሌዋውያን ፡ አባቶች ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አልዓዛር ፥ ወደነዌም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢ.ያሱ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ አለቃዎች ፡ ቀረቡ ፤

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በሴሎ ፦ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የምንቀመጥባቸውን ፡ ከተማዎች ፥ ለከብቶቻችንም ፡ መሰምሪያዎች ፡ ትሰጡን ፡ ዘንድ ፡ አዟል ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ከርስታቸው ፡ እነዚህን ፡ ከተማዎችና ፡ መሰምሪያቸውን ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ ለቀአትም ፡ ወገኖች ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ፤ ሌዋውያንም ፡ ለነበሩ ፡ ለካህኑ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፥ ከስምዖንም ፡ ነገድ ፥ ከብንያምም ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ኾኑላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ ለቀሩትም ፡ ለቀአት ፡ ልጆች ፡ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፥ ከዳንም ፡ ነገድ ፥ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ዐሥር ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ኾኑላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ ለጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፥ ከአሴርም ፡ ነገድ ፥ ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ፥ በባሳንም ፡ ካለው ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ኾኑላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 7 ፤ ለሜራሪም ፡ ልጆች ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ከሮቤል ፡ ነገድ ፥ ከጋድም ፡ ነገድ ፥ ከዛብሎንም ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎች ፡ ኾኑላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህን ፡ ከተማዎችና ፡ መሰምሪያቸውን ፡ ለሌዋውያን ፡ በዕጣ ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 9 ፤ ከይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ከስምዖንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩትን ፡ እነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 10 ፤ የፊተኛው ፡ ዕጣ ፡ ለእነርሱ ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ የቀአት ፡ ወገን ፡ ለኾኑ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ኾኑ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ በይሁዳ ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ የምትባለውን ፡ ከተማ ፡ በዙሪያዋም ፡ ያለውን ፡ መሰምሪያ ፡ ሰጧቸው ፤ ርሷም ፡ ኬብሮን ፡ ናት ፥ ይህም ፡ አርባቅ ፡ የዔናቅ ፡ አባት ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ የከተማዪቱን ፡ ዕርሻ ፡ ግን ፡ መንደሮቿንም ፡ ለዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ሰጡት ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ ለካህኑም ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ እነዚህን ፡ ሰጡ ፤ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የኾነችውን ፡ ኬብሮንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ልብናንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ የቲርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ኤሽትሞዐንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ ሖሎንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዳቤርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 16 ፤ ዐይንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዩጣንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ቤትሳሚስንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ ከነዚህ ፡ ከኹለቱ ፡ ነገዶች ፡ ዘጠኝ ፡ ከተማዎችን ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 17 ፤ ከብንያምም ፡ ነገድ ፡ ገባዖንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ናሲብንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ዐናቶትንና ([122]) ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዐልሞንንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራት ፡ ከተማዎችን ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ የአሮን ፡ ልጆች ፡ የካህናት ፡ ከተማዎች ፡ ከመሰምሪያቸው ፡ ጋራ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ለቀሩትም ፡ ለቀአት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ሌዋውያን ፡ የዕጣቸው ፡ ከተማዎች ፡ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡ ደረሷቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ በኤፍሬም ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የኾነችውን ፡ ሴኬምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ጌዝርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ቂብጻይምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ቤትሖሮንንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ከዳንም ፡ ነገድ ፡ ኤልተቄንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ገባቶንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ኤሎንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ጋትሪሞንንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ታዕናክንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ጋትሪሞንንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ ኹለቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ የቀሩት ፡ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ከመሰምሪያቸው ፡ ጋራ ፡ ዐሥር ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ ለሌዋውያንም ፡ ወገኖች ፡ ለጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ በባሳን ፡ ውስጥ ፡ የኾነችውን ፡ ጎላንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ በኤሽትራንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ ኹለቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ ከይሳኮርም ፡ ነገድ ፡ ቂሶንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዳብራትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ የርሙትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዐይንጋኒምንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ከአሴርም ፡ ነገድ ፡ ሚሽአልንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዐብዶንንና ([123]) ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ሔልቃትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ረአብንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የኾነችውን ፡ በገሊላ ፡ ውስጥ ፡ ቃዴስንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ሐሞትዶርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ቀርታንንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ ሦስቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጧቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ የጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ከመሰምሪያቸው ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ ከሌዋውያንም ፡ ለቀሩት ፡ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ ዮቅንዓምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 35 ፤ ቀርታንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዲምናንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ነኽላልንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፡ 21 ፡ 36 ፤ ከሮቤልም ፡ ነገድ ፡ ቦሶርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ያሀጽንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

---

122 መልስ ፡ ወይም ፡ ስጦታ ።

123 ዕብ. ፥ ዐብዶን ፡ (አገልግሎት) ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 37 ፤ ቅዴሞትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ሜፍዓትንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 38 ፤ ከጋድም ፡ ነገድ ፡ ለነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ መማፀኛ ፡ ከተማ ፡ የኾነችውን ፡ በገለዓድ ፡ ውስጥ ፡ ራሞትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ መሃናይምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 39 ፤ ሐሴቦንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ኢ.ያዜርንና ፡ መሰምሪያዋን ፤ አራቱን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጡ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 40 ፤ ከሌዋውያን ፡ ወገኖች ፡ የቀሩት ፡ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በየወገኖቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ዕጣቸውም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከተማ ፡ ነበረ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 41 ፤ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ መካከል ፡ የነበሩት ፡ የሌዋውያን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ አርባ ፡ ስምንት ፡ ከተማዎችና ፡ መሰምሪያቸው ፡ ነበሩ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 42 ፤ እነዚህም ፡ ከተማዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከመሰምሪያቸው ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፤ እነዚህም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነበሩ ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 43 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማለላቸውን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጠ ፤ ወረሷትም ፥ ተቀመጡባትም ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 44 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ማለላቸው ፡ በዙሪያቸው ፡ ካሉት ፡ አሳረፋቸው ፤ ከጠላቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ይቋቋማቸው ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አልቻለም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 21 ፥ 45 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ከተናገረው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ተፈጸመ ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልቀረም ።

መጽሐፈ ፡ ኢ.ያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኢ.ያሱ ፡ የሮቤልን ፡ ልጆችና ፡ የጋድን ፡ ልጆች ፡ የምናሴንም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛችኹን ፡ ኹሉ ፡ ጠብቃችኋል ፥ እኔም ፡ ላዘዝኋችኹ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታዛችኋል ፤

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 3 ፤ ይህንም ፡ ያኽል ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ አልተዋችኹም ፥ የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቃችኋል ።

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 4 ፤ አኹንም ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራቸው ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ አሳርፏቸዋል ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ተመለሱ ፥ ወደ ፡ ቤታችኹና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደሰጣችኹ ፡ ወደርስታችኹ ፡ ምድር ፡ ኺዱ ።

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 5 ፤ ብቻ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛችኹን ፡ ትእዛዙንና ፡ ሕጉን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወዱ ፡ ዘንድ ፥ መንገዱንም ፡ ኹሉ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፥ ትእዛዙንም ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ትጠጉ ፡ ዘንድ ፥ በፍጹምም ፡ ልባችኹ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍሳችኹ ፡ ታመልኩ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ተጠንቀቁ ።

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 6 ፤ ኢ.ያሱም ፡ መረቃቸው ፥ ሰደዳቸውም ፤ ወደ ፡ ቤታቸውም ፡ ኼዱ ።

ኢ.ያ. ፥ 22 ፥ 7 ፤ ለምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ሙሴ ፡ በባሳን ፡ ውስጥ ፡ ርስት ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ፤ ለቀረው ፡

ለእኩሌታው ፡ ግን ፡ ኢያሱ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ ወገን ፡ በወንድሞቻቸው ፡ መካከል ፡ ርስት ፡
ሰጣቸው ። ኢያሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ በሰደዳቸው ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መረቃቸው ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ በብዙ ፡ ብልጥግና ፡ በእጅግም ፡ ብዙ ፡
ከብት ፥ በብርም ፥ በወርቅም ፥ በናስም ፥ በብረትም ፥ በእጅግም ፡ ብዙ ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ቤታችኹ ፡
ተመለሱ ፤ የጠላቶቻችኹንም ፡ ምርኮ ፡ ከወንድሞቻችኹ ፡ ጋራ ፡ ተካፈሉ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ የሮቤልም ፡ ልጆች ፡ የጋድም ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ኼዱ ፤ በሙሴም ፡ እጅ ፡
በተሰጠ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ወደተቀበሏት ፡ ወደ ፡ ርስታቸው ፡ ወደገለዓድ ፡ ምድር ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በከነዓን ፡
ምድር ፡ ካለችው ፡ ከሴሎ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ተመለሱ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ወዳለው ፡ ወደዮርዳኖስ ፡ አቅራቢያም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡
የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ በዚያ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ ታላቅ ፡ መሠዊያ ፡ ሠሩ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፦ እንሆ ፥ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ በዮርዳኖስ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡
ግዛት ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ባሉበት ፡ ወገን ፥ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡
መሠዊያ ፡ ሠርተዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ደረሰላቸው ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ወጥተው ፡
እነርሱን ፡ ሊዋጉ ፡ በሴሎ ፡ ተሰበሰቡ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ወዳሉት ፡ ወደሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ወደጋድ ፡ ልጆች ፡
ወደምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ የካህኑን ፡ የአልዓዛርን ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስን ፡ ላኩ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐሥር ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ፥ ከእስራኤል ፡ ከየነገዱ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡
የአባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃ ፤ እያንዳንዱም ፡ በእስራኤል ፡ አእላፋት ፡ መካከል ፡ የየአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ በገለዓድም ፡ ምድር ፡ ወዳሉት ፡ ወደሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ወደጋድ ፡ ልጆች ፡ ወደምናሴም ፡ ነገድ ፡
እኩሌታ ፡ መጡ ፥ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነው ። ይህ ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡
ያደረጋችኹት ፡ ኀጢአት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ዛሬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ተመልሳችኋል ፤ ዛሬም ፡ መሠዊያ ፡
በመሥራታችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ዐምፃችኋል ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ እኛ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከርሱ ፡ ያልነጻንበት ፡ የፌጎር ፡ ኀጢአት ፡ ጥቂት ፡
ነውን ፧ በእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ላይ ፡ መቅሠፍት ፡ ወረደ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ትመለሳላችኹን ፧ ዛሬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡
ብታምፁ ፡ ነገ ፡ በእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የርስታችኹ ፡ ምድር ፡ የረከሰ ፡ ቢመስላችኹ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡
ወደሚቀመጥበት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ምድር ፡ ዐልፋችኹ ፡ በመካከላችን ፡ ውረሱ ፤ ከአምላካችንም ፡
ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሌላ ፡ ለእናንተ ፡ መሠዊያ ፡ በመሥራታችኹ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አታምፁ ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ዐካን ፡ ዕርም ፡ ነገር ፡ በመውሰድ ፡ ኀጢአትን ፡ ስለ ፡ ሠራ ፡ በእስራኤል ፡ ማኅበር ፡
ኹሉ ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ አልወረደምን ፧ ርሱም ፡ በኀጢአቱ ፡ ብቻውን ፡ አልሞተም ።

ኢያ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ለእስራኤል ፡ አእላፋት ፡
አለቃዎች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ዐውቆታል ፥ እስራኤልም ፡ ያውቀዋል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ዐምፀንና ፡ ተላልፈን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዛሬ ፡ አታድነን ፤

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ እንድንመለስ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ እንድናሳርግበት ፥ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ እንድናቀርብበት ፡ ብለን ፡ መሠዊያ ፡ ሠርተን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ይበቀለን ፤

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ ይልቁንም ፡ ከልባችን ፡ ፍርሀት ፡ የተነሣ ፦ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ልጆቻችኹ ፡ ልጆቻችንን ፦ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አላችኹ ፧

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ እናንተ ፡ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፥ እግዚአብሔር ፡ በእኛና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ዮርዳኖስን ፡ ድንበር ፡ አድርጓልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ የላችኹም ፡ ይሏቸዋል ፡ ብለን ፡ ይህን ፡ አደረግን ። በዚህም ፡ ልጆቻችኹ ፡ ልጆቻችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመፍራት ፡ አስተዋቸዋል ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ ስለዚህም ፦ መሠዊያ ፡ እንሥራ ፡ አልን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ አይደለም ፤

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእኛና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ከእኛም ፡ በኋላ ፡ በትውልዳችንና ፡ በትውልዳችኹ ፡ መካከል ፡ በሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ በቍርባን ፡ በደኅንነትም ፡ መሥዋዕታችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልክ ፡ ዘንድ ፥ በሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ ልጆቻችኹ ፡ ልጆቻችንን ፦ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ የላችኹም ፡ እንዳይሉ ፡ ምስክር ፡ ይኾናል ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ስለዚህም ፡ አልን ፦ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ለእኛ ፡ ወይም ፡ ለትውልዳችን ፡ ይህን ፡ ሲሉ ፥ እኛ ፦ እንሆ ፥ አባቶቻችን ፡ ያደረጉትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ ምሳሌ ፡ እዩ ፤ በእኛና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ አይደለም ፡ እንላለን ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ በማደሪያው ፡ ፊት ፡ ካለው ፡ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሌላ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ ለሌላ ፡ መሥዋዕትም ፡ የሚኾን ፡ መሠዊያን ፡ የሠራነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በማመፅ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ዛሬ ፡ መከተልን ፡ ለመተው ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህ ፡ ከእኛ ፡ ይራቅ ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ ካህኑ ፡ ፊንሐስና ፡ የማኅበሩ ፡ አለቃዎች ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ የእስራኤል ፡ አእላፋት ፡ አለቃዎች ፥ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ልጆች ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሠኛቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ የካህኑም ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ ለሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ለጋድ ፡ ልጆች ፡ ለምናሴም ፡ ልጆች ። ይህን ፡ መተላለፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ አላደረጋችኹምና ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ እንዳለ ፡ ዛሬ ፡ እናውቃለን ፤ አኹን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ አድናችኋል ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 32 ፤ የካህኑም ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስና ፡ አለቃዎቹ ፡ ከሮቤል ፡ ልጆችና ፡ ከጋድ ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ከገለዓድ ፡ አገር ፡ ወደከነዓን ፡ አገር ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፥ ወሬም ፡ አመጡላቸው ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 33 ፤ ነገሩም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ደስ ፡ አሠኘ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የተቀመጡባትን ፡ ምድር ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ወጥተው ፡ እንዲወጓቸው ፡ አልተናገሩም ።

ኢ.ያ. ፡ 22 ፡ 34 ፤ የሮቤል ፡ ልጆችና ፡ የጋድ ፡ ልጆችም ፦ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህ ፡ በመካከላችን ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ መሠዊያውን ፡ ምስክር ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከኾነ ፡ በኋላ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ በዙሪያቸው ፡ ካሉት ፡ ጠላቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ካሳረፈ ፡ በኋላ ፥ ኢያሱም ፡ በሸመገለ ፡ በዕድሜውም ፡ ባረጀ ፡ ጊዜ ፥

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ኢያሱ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ሽማግሌዎቻቸውንም ፡ አለቃዎቻቸውንም ፡ ፈራጆቻቸውንም ፡ ሹማምቶቻቸውንም ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እኔ ፡ ሸምግያለኹ ፥ በዕድሜም ፡ አርጅቻለኹ ፤

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ እናንተም ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ አይታችኋል ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ የተዋጋ ፡ ርሱ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ካጠፋኋቸው ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ዠምሮ ፡ በፀሓይ ፡ መግቢያ ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ለነገዶቻችኹ ፡ ርስት ፡ እንዲኾኑ ፡ የቀሩትን ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ በዕጣ ፡ ከፈልኩላችኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ከፊታችኹ ፡ በብርቱ ፡ ይበትናቸዋል ፥ ከፊታችኹም ፡ ያሳድዳቸዋል ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራችኹም ፡ ምድራቸውን ፡ ትወርሳላችኹ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ ስለዚህም ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ኹሉ ፡ ለመጠበቅና ፡ ለማድረግ ፡ በጣም ፡ በርቱ ፥ ከርሱም ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ አትበሉ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ወደቀሩት ፡ ወደ ፡ እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ አትግቡ ፤ የአማልክታቸውንም ፡ ስም ፡ አትጥሩ ፥ አትማሉባቸውም ፥ አታምልኳቸውም ፥ አትስገዱላቸውም ፤

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዳደረጋችኹት ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠጉ ፡ እንጂ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላላቆችንና ፡ ኀይለኞችን ፡ አሕዛብ ፡ ከፊታችኹ ፡ አስወጥቷል ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ ሊቋቋማችኹ ፡ አልቻለም ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገራችኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚዋጋ ፡ ርሱ ፡ ነውና ፥ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሺሕ ፡ ሰውን ፡ ያሳድዳል ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትወዱት ፡ ዘንድ ፡ ለራሳችኹ ፡ እጅግ ፡ ተጠንቀቁ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ተመልሳችኹ ፡ በመካከላችኹ ፡ ወደቀሩት ፡ ወደ ፡ እነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ብትጠጉ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ብትጋቡ ፥ እናንተም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ብትደራረሱ ፥

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጣችኹ ፡ ከዚች ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እስክትጠፉ ፡ ድረስ ፡ መውደቂያና ፡ ወጥመድ ፥ በጎናችኹም ፡ መግረፊያ ፥ በዐይናችኹም ፡ ሾኽ ፡ ይኾኑባችኋል ፡ እንጂ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ ከፊታችኹ ፡ እንዳያሳድዳቸው ፡ ፈጽማችኹ ፡ ዕወቁ ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ እንሆም ፥ ዛሬ ፡ የምድርን ፡ ኹሉ ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ፤ እናንተም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ከተናገረው ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳልቀረ ፡ በልባችኹ ፡ ኹሉ ፡ በነፍሳችኹም ፡ ኹሉ ፡ ዕወቁ ፤ ኹሉ ፡ ደርሰላችኋል ፤ ከርሱም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አልቀረም ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ደረሰላችኹ ፥ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጣችኹ ፡ ከዚች ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እናንተን ፡ እስኪያጠፋችኹ ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያመጣባችኋል ።

ኢ.ያ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዛችኹን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስታፈርሱ ፥ ኼዳችኹም ፡ ሌላዎችን ፡

አማልክት ፡ ስታመልኩ ፥ ስትሰግዱላቸውም ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ይነድ፡ባችኋል ፥ ከሰጣችኹም ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ ፈጥናችኹ ፡ ትጠፋላችኹ ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 1 ፤ ኢያሱም ፡ የእስራኤልን ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ሰበሰበ ፥ የእስራኤልንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ አለቃዎቻቸውንም ፡ ፈራጆቻቸውንም ፡ ሹማምቶቻቸውንም ፡ ጠራ ። እነርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 2 ፤ ኢያሱም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አባቶቻችኹ ፥ የአብርሃምና ፡ የናኮር ፡ አባት ፡ ታራ ፥ አስቀድመው ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ተቀመጡ ፤ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ አመለኩ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 3 ፤ አባታችኹንም ፡ አብርሃምን ፡ ከወንዝ ፡ ማዶ ፡ ወስጄ ፡ በከነዓን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ መራኹት ፤ ዘሩንም ፡ አበዛኹ ፥ ይሥሐቅንም ፡ ሰጠኹት ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 4 ፤ ለይሥሐቅም ፡ ያዕቆብንና ፡ ዔሳውን ፡ ሰጠኹት ፤ ለዔሳውም ፡ የሴይርን ፡ ተራራ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ሰጠኹት ፤ ያዕቆብም ፡ ልጆቹም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረዱ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 5 ፤ ሙሴንና ፡ አሮንንም ፡ ላክኹ ፥ በመካከላቸውም ፡ እንዳደረግኹ ፡ ግብጽን ፡ ቀሠፍኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አወጣኋቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 6 ፤ አባቶቻችኹንም ፡ ከግብጽ ፡ አወጣኋቸው ፥ ወደ ፡ ባሕሩም ፡ ደረሳችኹ ፤ ግብጻውያንም ፡ አባቶቻችኹን ፡ በሠረገላዎችና ፡ በፈረሰኞች ፡ እስከ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ አባረሯቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 7 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ በእናንተና ፡ በግብጻውያን ፡ መካከል ፡ ጨለማ ፡ አደረገ ፥ ባሕሩንም ፡ መለሰባቸው ፥ አሰጠማቸውም ፤ ዐይኖቻችኹም ፡ በግብጽ ፡ ያደረግኹትን ፡ አዩ ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጣችኹ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 8 ፤ እኔም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደተቀመጡበት ፡ ወደአሞራውያን ፡ ምድር ፡ አመጣኋችኹ ፤ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፥ አሳልፌም ፡ በእጃችኹ ፡ ሰጠኋችኹ ፥ ምድራቸውንም ፡ ወረሳችኹ ፤ ከፊታችኹም ፡ አጠፋኋቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 9 ፤ የሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ የሴፎር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፡ ተነሥቶ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ እንዲረግማችኹም ፡ የቢያርን ፡ ልጅ ፡ በለዓምን ፡ ልኮ ፡ አስጠራው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 10 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በለዓምን ፡ መስማት ፡ አልወደድኩም ፤ ርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ ባረካችኹ ፥ እኔም ፡ ከእጁ ፡ አዳንኋችኹ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 11 ፤ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገራችኹ ፥ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጣችኹ ፤ የኢያሪኮም ፡ ሰዎች ፥ አሞራዊው ፥ ፌርዛዊው ፥ ከነዓናዊው ፥ ኬጢያዊው ፥ ጌርጌሳዊው ፥ ዔዊያዊው ፥ ኢያቡሳዊው ፡ ተዋጓችኹ ፤ አሳልፌም ፡ በእጃችኹ ፡ ሰጠኋቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 12 ፤ በፊታችኹም ፡ ተርብ ፡ ሰደድኩ ፥ በሰይፍኽም ፡ በቀስትኽም ፡ ሳይኾን ፡ ኹለቱን ፡ የአሞራውያንን ፡ ነገሥታት ፡ ከፊታችኹ ፡ አሳደዳቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 13 ፤ ያልደከማችኹበትንም ፡ ምድር ፥ ያልሠራችኋቸውንም ፡ ከተማዎች ፡ ሰጠኋችኹ ፥ ተቀመጣችኹባቸውም ፤ ካልተከላችኋቸውም ፡ ከወይንና ፡ ከወይራ ፡ በላችኹ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 14 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፥ በፍጹምም ፡ በእውነተኛም ፡ ልብ ፡

አምልኩት ፤ አባቶቻችኹም ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ በግብጽም ፡ ውስጥ ፡ ያመለኳቸውን ፡ አማልክት ፡ ከእናንተ ፡
አርቁ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አምልኩ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 15 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ማምለክ ፡ ክፉ ፡ መስሎ ፡ ቢታያችኹ ፥ አባቶቻችኹ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ሳሉ ፡
ያመለኳቸውን ፡ አማልክት ፡ ወይም ፡ በምድራቸው ፡ ያላችኹባቸውን ፡ የአሞራውያንን ፡ አማልክት ፡ ታመልኩ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ የምታመልኩትን ፡ ዛሬ ፡ ምረጡ ። እኔና ፡ ቤቴ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 16 ፤ ሕዝቡም ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እግዚአብሔርን ፡ ትተን ፡ ሌላዎች ፡ አማልክትን ፡
ማምለክ ፡ ከእኛ ፡ ይራቅ ፤

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 17 ፤ እኛንና ፡ አባቶቻችንን ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፥ በዐይናችንም ፡ ፊት ፡
እነዚያን ፡ ታላላቅ ፡ ተአምራት ፡ ያደረገ ፥ በኼድንባትም ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ባለፍንባቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡
የጠበቀን ፥ ርሱ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፥ በምድሪቱም ፡ የተቀመጡትን ፡ አሞራውያን ፡ ከፊታችን ፡
አሳደደ ፤ ስለዚህ ፥ ርሱ ፡ አምላካችን ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 19 ፤ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ ርሱ ፡ ቅዱስ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ርሱም ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡
ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ ማምለክ ፡ አትችሉም ፤ መተላለፋችኹንና ፡ ኀጢአታችኹን ፡ ይቅር ፡ አይልም ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ትታችኹ ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፥ መልካም ፡ ካደረገላችኹ ፡
በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያደርግባችኋል ፥ ያጠፋችኹማል ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 21 ፤ ሕዝቡም ፡ ኢያሱን ፦ እንዲህ ፡ አይኹን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ፡ አሉት ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 22 ፤ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፦ እንድታመልኩት ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ መረጣችኹ ፡
በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ ምስክሮች ፡ ናችኹ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፦ ምስክሮች ፡ ነን ፡ አሉ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 23 ፤ ርሱም ፦ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ በመካከላችኹ ፡ ያሉትን ፡ እንግዳዎች ፡ አማልክት ፡
አርቁ ፥ ልባችኹንም ፡ ወደእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዘንብሉ ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 24 ፤ ሕዝቡም ፡ ኢያሱን ፦ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናመልካለን ፥ ድምፁንም ፡ እንሰማለን ፡
አሉት ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 25 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢያሱ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፥ በሴኬምም ፡ ሥርዐትና ፡
ፍርድ ፡ አደረገላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 26 ፤ ኢያሱም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈ ፤ ታላቁንም ፡ ድንጋይ ፡
ወስዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ አጠገብ ፡ ከነበረችው ፡ ከአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ አቆመው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 27 ፤ ኢያሱም ፡ ለሕዝቡ ፦ እንሆ ፥ የተናገረንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ሰምቷልና ፥ ይህ ፡
ድንጋይ ፡ ይመሰክርብናል ፤ እንግዲህ ፡ አምላካችኹን ፡ እንዳትክዱ ፡ ይህ ፡ ምስክር ፡ ይኾንባችኋል ፡ አላቸው ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 28 ፤ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፡ በያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ሰደደ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 29 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡
ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሲኾነው ፡ ሞተ ።

ኢ.ያ. ፥ 24 ፥ 30 ፤ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ በገዓስ ፡ ተራራ ፡ በሰሜን ፡ ባለችው ፡ በርስቱ ፡ ዳርቻ ፡

በተምናሴራ ፡ ቀበሩት ።

ኢያ. ፥ 24 ፥ 31 ፤ ኢያሱ ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ከኢያሱም ፡ በኋላ ፡ በነበሩት ፡ ለእስራኤልም ፡ ያደረገውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ባወቁት ፡ በሽማግሌዎች ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ እስራኤል ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመለኩ ።

ኢያ. ፥ 24 ፥ 32 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ያወጡትን ፡ የዮሴፍን ፡ ዐጥንት ፡ ያዕቆብ ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡ ከኤሞር ፡ ልጆች ፡ በመቶ ፡ በግ ፡ በገዛው ፡ ዕርሻ ፡ በሴኬም ፡ ቀበሩት ፤ ዕርሻውም ፡ ለዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ርስት ፡ ኾነ ።

□□.□24□33□ [illegible]

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

መሳ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ እንዲሀም ፡ ኾነ ፤ ኢያሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፦ ከነዓናውያንን ፡ ለመውጋት ፡ ማን ፡ በፊት ፡ ይወጣልናል ፧ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቁ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይሁዳ ፡ ይውጣ ፤ እንሆ ፥ ምድሪቱን ፡ በእጁ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ይሁዳም ፡ ወንድሙን ፡ ስምዖንን ፦ ከነዓናውያንን ፡ እንወጋ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዕጣዬ ፡ ውጣ ፥ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዕጣኽ ፡ እኼዳለኹ ፡ አለው ። ስምዖንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ይሁዳም ፡ ወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከነዓናውያንንና ፡ ፌርዛውያንን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ ከነርሱም ፡ በቤዜቅ ፡ ውስጥ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ አዶኒቤዜቅንም ፡ በቤዜቅ ፡ አገኙትና ፡ ተዋጉት ፤ ከነዓናውያንንና ፡ ፌርዛውያንንም ፡ መቷቸው ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ አዶኒቤዜቅም ፡ ሸሸ ፤ አሳደውም ፡ ያዙት ፥ የእጁንና ፡ የእግሩንም ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ ቈረጡ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ አዶኒቤዜቅም ፦ የእጃቸውና ፡ የእግራቸው ፡ አውራ ፡ ጣት ፡ የተቈረጡ ፡ ሰባ ፡ ነገሥታት ፡ ከገበታዬ ፡ በታች ፡ ፍርፋሪ ፡ ይለቅሙ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ እንዳደረግኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ መለሰልኝ ፡ አለ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ አመጡት ፥ በዚያም ፡ ሞተ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ተዋግተው ፡ ያዟት ፥ በሰይፍ ፡ ስለትም ፡ መቷት ፥ ከተማዪቱንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠሏት ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በተራራማው ፡ አገርና ፡ በደቡቡ ፡ በኩል ፡ በቈላውም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ ሊወጉ ፡ ወረዱ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ይሁዳም ፡ በኬብሮን ፡ የሚኖሩትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ ሊወጋ ፡ ኼደ ። የኬብሮንም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ቂርያትአርባቅ ፡ ነበረ ። ሴሲንና ፡ አኪመንን ፡ ተላሚንም ፡ ገደሉ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ከዚያም ፡ የዳቤርን ፡ ሰዎች ፡ ሊወጋ ፡ ኼደ ፤ አስቀድሞም ፡ የዳቤር ፡ ስም ፡ ቅርያትሤፍር ፡ ነበረ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ካሌብም ፦ ቅርያትሤፍርን ፡ ለሚመታና ፡ ለሚይዝ ፡ ልጄን ፡ ዓክሳን ፡ አጋባዋለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ የካሌብም ፡ ትንሽ ፡ ወንድም ፡ የቄኔዝ ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ያዛት ፤ ልጁንም ፡ ዓክሳን ፡ አጋባው ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ርሷም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ከአባቷ ፡ ዕርሻ ፡ እንዲለምን ፡ መከረችው ። ርሷም ፡ ከአህያዋ ፡ ወረደች ፤ ካሌብም ፦ ምን ፡ ፈለግሽ ፧ አላት ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ርሷም ፦ በረከትን ፡ ስጠኝ ፤ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ ምድር ፡ ሰጥተኸኛልና ፥ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ደግሞ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ። ካሌብም ፡ ላይኛውንና ፡ ታችኛውን ፡ ምንጭ ፡ ሰጣት ።

መሳ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ የቄናዊው ፡ የሙሴ ፡ ዐማት ፡ ልጆችም ፡ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ዘንባባ ፡ ካለባት ፡ ከተማ ፡ ተነሥተው ፡ ከዓራድ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡ ወደይሁዳ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጡ ፤ ኼደውም ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ይሁዳም ፡ ከወንድሙ ፡ ከስምዖን ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፥ በጽፋት ፡ የተቀመጡትንም ፡ ከነዓናውያንን ፡ መቱ ፥ ፈጽመውም ፡ አጠፏት ። የከተማዪቱንም ፡ ስም ፡ ሔርማ ፡ ብለው ፡ ጠሯት ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ይሁዳም ፡ ጋዛንና ፡ ዳርቻዋን ፥ አስቀሎናንና ፡ ዳርቻዋን ፥ ዐቃሮንንና ፡ ዳርቻዋን ፡ ያዘ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ይሁዳም ፡ ተራራማውን ፡ አገር ፡ ወረሰ ፤ በሸለቆው ፡ የሚኖሩት ፡ ግን ፡ የብረት ፡ ሠረገላዎች ፡ ነበሯቸውና ፡ ሊያወጣቸው ፡ አልቻለም ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ሙሴም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ለካሌብ ፡ ኬብሮንን ፡ ሰጡት ፤ ከዚያም ፡ ሦስቱን ፡ የዔናቅ ፡ ልጆች ፡ አወጣ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ኢያቡሳውያንን ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ አላወጧቸውም ፤ ኢያቡሳውያንም ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጠዋል ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ የዮሴፍም ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ በቤቴል ፡ ላይ ፡ ወጡ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ የዮሴፍም ፡ ወገን ፡ ቤቴልን ፡ የሚሰልሉ ፡ ላኩ ። አስቀድሞም ፡ የከተማዪቱ ፡ ስም ፡ ሎዛ ፡ ይባል ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ጠባቂዎቹም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ሲወጣ ፡ አይተው ፦ የከተማዪቱን ፡ መግቢያ ፡ አሳየን ፥ እኛም ፡ ቸርነት ፡ እናደርግልኻለን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ የከተማዪቱንም ፡ መግቢያ ፡ አሳያቸው ፥ ከተማዪቱንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፤ ያን ፡ ሰውና ፡ ወገኖቹን ፡ ግን ፡ ለቀቋቸው ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ሰውየውም ፡ ወደኬጢያውያን ፡ ምድር ፡ ኼደ ፥ በዚያም ፡ ከተማን ፡ ሠራ ፥ ስሟንም ፡ ሎዛ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ስሟ ፡ ይህ ፡ ነው ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ምናሴም ፡ የቤትሳንንና ፡ የመንደሮቿን ፥ የታዕናክንና ፡ የመንደሮቿን ፥ የዶርንና ፡ የመንደሮቿን ፥ የይብለዓምንና ፡ የመንደሮቿን ፥ የመጊዶንና ፡ የመንደሮቿን ፡ ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነዓናውያን ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ በመቀመጥ ፡ ጸኑ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ እስራኤልም ፡ በበረቱ ፡ ጊዜ ፡ ከነዓናውያንን ፡ አስገበሯቸው ፥ ፈጽመውም ፡ አላወጧቸውም ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ኤፍሬምም ፡ በጌዝር ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓናውያንን ፡ አላወጣቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነዓናውያን ፡ በመካከላቸው ፡ በጌዝር ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ ዛብሎንም ፡ የቂድሮንንና ፡ የነኽሎልን ፡ ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነዓናውያን ፡ በመካከላቸው ፡ ተቀመጡ ፥ ግብርም ፡ የሚገብሩለት ፡ ኾኑ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ አሴርም ፡ የዓኮንና ፡ የሲዶንን ፡ የአሕላብንም ፡ የአክዚብንም ፡ የሐልባንም ፡ የአፌቅንም ፡ የረአብንም ፡ ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ በዚያችም ፡ ምድር ፡ የተቀመጡትን ፡ ከነዓናውያን ፡ አላወጧቸውምና ፡ በመካከላቸው ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 33 ፤ ንፍታሌምም ፡ የቤትሳሚስንና ፡ የቤትዓናትን ፡ ሰዎች ፡ አላወጣቸውም ፥ በምድሩም ፡ በተቀመጡት ፡ በከነዓናውያን ፡ መካከል ፡ ተቀመጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የቤትሳሚስና ፡ የቤትዓናት ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ የሚገብሩለት ፡ ኾኑ ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 34 ፤ አሞራውያንም ፡ የዳንን ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ አገር ፡ እንዲያፈገፍጉ ፡ አስገደዷቸው ፥ ወደ ፡ ሸለቆውም ፡ እንዳይወርዱ ፡ ከለከሏቸው ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 35 ፤ አሞራውያን ፡ በሔሬስ ፡ ተራራና ፡ በኤሎን ፡ በሸዓልቢምም ፡ በመቀመጥ ፡ ጸኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዮሴፍ ፡ ቤት ፡ እጅ ፡ ከበደች ፥ አስገበረቻቸውም ።

መሳ. ፡ 1 ፡ 36 ፤ የአሞራውያንም ፡ ድንበር ፡ ከአቅረቢም ፡ ዐቀበት ፡ ከጭንጫው ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ ድረስ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከገልገላ ፡ ወደ ፡ ቦኪም ፡ ወጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እኔ ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቻችኋለኹ ፥ ለአባቶቻችኹም ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ አግብቻችኋለኹ ፤ እኔም ፦ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለዘለዓለም ፡ አላፈርስም ፤

መሳ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እናንተም ፡ መሠዊያቸውን ፡ አፍርሱ ፡ እንጂ ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ከሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አታድርጉ ፡ አልኹ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ቃሌን ፡ አልሰማችኹም ፤

መሳ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ይህንስ ፡ ለምን ፡ አደረጋችኹ ∴ ስለዚህም ፦ ከፊታችኹ ፡ አላወጣቸውም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ያስጨንቋችኋል ፥ አማልክታቸውም ፡ ወጥመድ ፡ ይኾኑባችኋል ፡ አልኹ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ድምፃቸውን ፡ አንሥተው ፡ አለቀሱ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የዚያንም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ ቦኪም ፡ ብለው ፡ ጠሩት ፤ በዚያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠዉ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ኢያሱም ፡ ሕዝቡን ፡ ባሰናበተ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ምድሪቱን ፡ ሊወርሱ ፡ ወደ ፡ እየርስታቸው ፡ ኼዱ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ኢያሱም ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ለእስራኤልም ፡ ያደረገውን ፡ ታላቁን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ባዩት ፥ ከኢያሱ ፡ በኋላ ፡ በነበሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ሕዝቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመለኩ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ የነዌ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ሲኾነው ፡ ሞተ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ በገዓስ ፡ ተራራ ፡ በሰሜን ፡ ባለችው ፡ በርስቱ ፡ ዳርቻ ፡ በተምናሔሬስ ፡ ቀበሩት ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አባቶቻቸው ፡ ተከማቹ ፤ ከነዚያም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለእስራኤልም ፡ ያደረገውን ፡ ሥራ ፡ ያላወቀ ፡ ሌላ ፡ ትውልድ ፡ ተነሣ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ፥ በዓሊምንም ፡ አመለኩ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ከግብጽ ፡ ምድርም ፡ ያወጣቸውን ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተዉ ፥ በዙሪያቸውም ፡ ካሉት ፡ ከአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፥ ሰገዱላቸውም ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አስቈጡ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ትተው ፡ በዓልንና ፡ ዐስታሮትን ፡ አመለኩ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ ወደማረኳቸውም ፡ ማራኪዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ በዙሪያቸውም ፡ ባሉት ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ ጠላቶቻቸውንም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ሊቋቋሙ ፡ አልቻሉም ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ማለ ፥ ወደወጡበት ፡ ሹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ትከፋባቸው ፡ ነበር ፤ እጅግም ፡ ተጨነቁ ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መሳፍንትን ፡ አስነሣላቸው ፥ ከሚማርኳቸውም ፡ እጅ ፡ አዳኗቸው ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ሌላዎች ፡ አማልክትን ፡ ተከትለው ፡ አመነዘሩ ፡ ሰገዱላቸውም ፡ እንጂ ፡ መሳፍንቶቻቸውን ፡ አልሰሙም ፤ አባቶቻቸውም ፡ ይኼዱበት ፡ ከነበረ ፡ መንገድ ፡ ፈጥነው ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፤ አባቶቻቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ታዘዙ ፡ እንዲሁ ፡ አላደረጉም ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መሳፍንትን ፡ ባስነሣላቸው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመስፍኑ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስለሚጋፏቸውና ፡ ስለሚያስጨንቋቸው ፡ በጨኸታቸው ፡ ያዝን ፡ ነበርና ፥ በመስፍኑ ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ መስፍኑ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይመለሱ ፡ ነበር ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ በመከተላቸው ፡ እነርሱንም ፡ በማምለካቸውና ፡ ለእነርሱ ፡ በመስገዳቸው ፡ አባቶቻቸው ፡ አድርገውት ፡ ከነበረው ፡ የከፋ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፤ የእልከኝነታቸውን ፡ መንገድና ፡ ሥራቸውን ፡ አልተዉም ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ያዘዝኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስለ ፡ ተላለፉ ፥ ድምፄንም ፡ ስላልሰሙ ፡ አባቶቻቸውም ፡ እንደ ፡ ጠበቁ ፥

መሳ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ 22 ፤ ይኼዱባት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ይጠብቁ ፡ ወይም ፡ አይጠብቁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እስራኤልን ፡ እፈትንባቸው ፡ ዘንድ ፥ ኢያሱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ከተዋቸው ፡ አሕዛብ ፡ አንዱን ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከፊታቸው ፡ አላወጣም ።

መሳ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እነዚህን ፡ አሕዛብ ፡ አስቀረ ፥ ፈጥኖም ፡ አላወጣቸውም ፥ በኢያሱም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጣቸውም ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 1-2 ፤ ከከነዓናውያንም ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ ያላወቁትን ፡ እስራኤልን ፡ በእነርሱ ፡ ይፈትናቸው ፡ ዘንድ ፥ በፊትም ፡ ሰልፍን ፡ ያልለመዱ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ትውልድ ፡ መዋጋትን ፡ ያውቁና ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስቀራቸው ፡ አሕዛብ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤

መሳ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ዐምስቱ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ መኳንንት ፥ ከነዓናውያንም ፡ ሹሉ ፥ ሲዶናውያንም ፥ ከበዓልአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሐማት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ በሊባኖስ ፡ ተራራ ፡ የሚኖሩትም ፡ ዔዊያውያን ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ያዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ መስማታቸው ፡ እንዲታወቅ ፡ እስራኤል ፡ ይፈተኑባቸው ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ቀሩ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በከነዓናውያን ፡ በኬጢያውያንም ፡ በአሞራውያንም ፡ በፌርዛውያንም ፡ በዔዊያውያንም ፡ በኢያቡሳውያንም ፡ መካከል ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ሴት ፡ ልጆቻቸውንም ፡ አገቧቸው ፥ እነርሱም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለወንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡ ሰጡ ፥ አማልክታቸውንም ፡ አመለኩ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡
አደረጉ ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተው ፡ በዓሊምንና ፡ ዐስታሮትን ፡ አመለኩ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ በመስጴጦምያ ፡ ንጉሥ ፡
በኩሰርሰቴም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለኩሰርሰቴም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ተገዙለት ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚያድናቸውን ፡
አዳኝ ፡ የካሌብን ፡ የታናሽ ፡ ወንድሙን ፡ የቄኔዝን ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያልን ፡ አስነሣላቸው ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ መጣ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡
ነበር ፤ ለሰልፍ ፡ ወጣ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የመስጴጦምያን ፡ ንጉሥ ፡ ኩሰርሰቴምን ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ እጁም ፡
በኩሰርሰቴም ፡ ላይ ፡ አሸነፈች ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ምድሪቱም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ዐረፈች ፤ የቄኔዝም ፡ ልጅ ፡ ጎቶንያል ፡ ሞተ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ሠሩ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሞዐብን ፡ ንጉሥ ፡ ዔግሎምን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡
አበረታባቸው ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ የዐሞንን ፡ ልጆችና ፡ ዐማሌቅን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሰበሰበ ፤ ኼዶም ፡ እስራኤልን ፡ መታ ፥ ዘንባባም ፡
ያለባትን ፡ ከተማ ፡ ያዟት ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ለዔግሎም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ተገዙለት ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብንያማዊውን ፡
የጌራን ፡ ልጅ ፡ ናያድን ፡ ግራኙን ፡ ሰው ፡ አዳኝ ፡ አስነሣላቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በርሱ ፡ እጅ ፡ ወደሞዐብ ፡
ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ዔግሎም ፡ ግብር ፡ ላኩ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ናያድም ፡ ኹለት ፡ አፍ ፡ ያለው ፡ ርዝመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ሰይፍ ፡ አበጀ ፥ ከልብሱም ፡
በታች ፡ በቀኝ ፡ ጭኑ ፡ በኩል ፡ አደረገው ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ለሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ለዔግሎም ፡ ግብሩን ፡ አቀረበ ፤ ዔግሎምም ፡ እጅግ ፡ ወፍራም ፡ ሰው ፡
ነበረ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ግብሩንም ፡ ማቅረብ ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፥ ግብር ፡ የተሸከሙትን ፡ ሰዎች ፡ ሰደደ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ናያድ ፡ ግን ፡ በገልገላ ፡ ከነበሩት ፡ ትክል ፡ ድንጋዮች ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፦ ንጉሥ ፡
ሆይ ፥ የምስጢር ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ አለ ፤ ንጉሡም ፦ ዝም ፡ በል ፡ አለ ፤ በዙሪያውም ፡ የቆሙት ፡ ኹሉ ፡ ወጡ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ናያድም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበ ፤ ርሱም ፡ በሰገነት ፡ ቤት ፡ ለብቻው ፡ ተቀምጦ ፡
ነበር ። ናያድም ፦ የእግዚአብሔር ፡ መልእክት ፡ ለአንተ ፡ አለኝ ፡ አለ ። ከዙፋኑም ፡ ተነሣ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ናያድም ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ከቀኝ ፡ ጭኑ ፡ ሰይፉን ፡ ወሰደ ፥ ሆዱንም ፡ ወጋው ፤

መሳ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ የሰይፉም ፡ እጀታው ፡ ደግሞ ፡ ከስለቱ ፡ በኋላ ፡ ገባ ፤ ስቡም ፡ ስለቱን ፡ ከደነው ፥ ሰይፉንም ፡
ከሆዱ ፡ መልሶ ፡ አላወጣውም ፤ በኋላውም ፡ ወጣ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ናያድም ፡ ወደ ፡ ደርቡ ፡ ወጣ ፥ የሰገነቱንም ፡ ደጅ ፡ ዘግቶ ፡ ቈለፈው ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ናያድም ፡ ከኼደ ፡ በኋላ ፡ ባሪያዎቹ ፡ መጡ ፤ የሰገነቱም ፡ ደጅ ፡ ተቈልፎ ፡ ባዩ ፡

ጊዜ ፦ ምናልባት ፡ በሰገነቱ ፡ ውስጥ ፡ ወገቡን ፡ ይሞክር ፡ ይኾናል ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ እስኪያፍሩም ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ዘገዩ ፤ የሰገነቱንም ፡ ደጅ ፡ እንዳልከፈተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መክፈቻውን ፡ ወስደው ፡ ከፈቱ ፥ እንሆም ፥ ጌታቸው ፡ በምድር ፡ ወድቆ ፡ ሞቶም ፡ አገኙት ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ በዘገዩበትም ፡ ጊዜያት ፡ ናዖድ ፡ ሸሸ ፥ ትክል ፡ ድንጋዮቹንም ፡ ዐለፈ ፥ ወደ ፡ ቤይሮታም ፡ አመለጠ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተራራማው ፡ አገር ፡ ወረዱ ፥ ርሱም ፡ በፊታቸው ፡ ኼደ ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቻችኹን ፡ ሞዐባውያንን ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ ተከተሉኝ ፡ አላቸው ። ተከትለውትም ፡ ወረዱ ፥ ወደ ፡ ሞዐብም ፡ የሚያሻግረውን ፡ የዮርዳኖስን ፡ መሻገሪያ ፡ ያዙ ፥ ማንንም ፡ አላሳለፉም ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከሞዐብ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉትን ፥ ጕልማሳዎችና ፡ ጽኑዓን ፡ ኹሉ ፥ መቱ ፤ አንድ ፡ እንኳ ፡ አላመለጠም ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሞዐብ ፡ ከእስራኤል ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ተዋረደ ፤ ምድሪቱም ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ዐረፈች ።

መሳ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የዓናት ፡ ልጅ ፡ ሰሜጋር ፡ ተነሣ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ በበሬ ፡ መውጊያ ፡ ገደለ ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ እስራኤልን ፡ አዳነ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ናዖድም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በአሶር ፡ (ጎጾር) ፡ በነገሠው ፡ በከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ በኢያቢስ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ በአሕዛብ ፡ ዐሪሶት ([124]) ፡ የተቀመጠው ፡ ሢሣራ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፤ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብረት ፡ ሠረገላዎች ፡ ነበሩትና ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እጅግ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ነቢዩቱ ፡ የለፊዶት ፡ ሚስት ፡ ዲቦራ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ትፈርድ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ርሷም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ በራማና ፡ በቤቴል ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ የዲቦራ ፡ ዛፍ ፡ ከሚባለው ፡ ከዘንባባው ፡ በታች ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ለፍርድ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ልካም ፡ ከቃዴስ ፡ ንፍታሌም ፡ የአቢኒኤምን ፡ ልጅ ፡ ባርቅን ([125]) ፡ ጠርታ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፦ ኼደኽ ፡ ወደታቦር ፡ ተራራ ፡ ውጣ ፥ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ከንፍታሌምና ፡ ከዛብሎን ፡ ልጆች ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ውሰድ ፤

መሳ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እኔም ፡ የኢያቢስን ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ሢሣራን ፡ ሠረገላዎቹንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ ወደቂሶን ፡ ወንዝ ፡ እስባለኹ ፥ በእጅኽም ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፡ ብሎ ፡ አላዘዘኽምን ፧ አለችው ።

---

124 ዕብ. ፥ ሐሮሸት ።

125 ዕብ. ፥ ባራቅ ፡ (በረቀ • በቁመ) ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ባርቅም ፦ አንቺ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ብትኼጂ ፡ እኔ ፡ እኼዳለኹ ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ባትኼጂ ፡ እኔ ፡ አልኼድም ፡ አላት ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ርሷም ፦ በእውነት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኼዳለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ሲሣራን ፡ በሴት ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣልና ፥ በዚህ ፡ በምትኼድበት ፡ መንገድ ፡ ለአንተ ፡ ክብር ፡ አይኾንም ፡ አለችው ። ዲቦራም ፡ ተነሥታ ፡ ከባርቅ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቃዴስ ፡ ኼደች ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ባርቅም ፡ ዛብሎንንና ፡ ንፍታሌምን ፡ ወደ ፡ ቃዴስ ፡ ጠራቸው ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ ሰዎች ፡ ተከትለውት ፡ ወጡ ፤ ዲቦራም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጣች ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ቄናዊውም ፡ ሔቤር ፡ ከሙሴ ፡ ዐማት ፡ ከኦባብ ፡ ልጆች ፡ ከቄናውያን ፡ ተለይቶ ፡ ድንኳኑን ፡ በቃዴስ ፡ አጠገብ ፡ በጻዕናይም ፡ እስከነበረው ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ዛፍ ፡ ድረስ ፡ ተከለ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ የአቢኒኤምም ፡ ልጅ ፡ ባርቅ ፡ ወደታቦር ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ለሲሣራ ፡ ነገሩት ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ሲሣራም ፡ ሠረገላዎቹን ፡ ኹሉ ፥ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ የብረት ፡ ሠረገላዎች ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ከዐሪሶት ፡ ወደቂሶን ፡ ወንዝ ፡ ሰበሰባቸው ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ዲቦራም ፡ ባርቅን ፦ እግዚአብሔር ፡ ሲሣራን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥበት ፡ ቀን ፡ ዛሬ ፡ ነውና ፥ ተነሣ ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በፊትኽ ፡ ወጥቷል ፡ አለችው ። ባርቅም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ተከትለውት ፡ ከታቦር ፡ ተራራ ፡ ወረደ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሲሣራን ፡ ሠረገላዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ ሰራዊቱንም ፡ ኹሉ ፡ ከባርቅ ፡ ፊት ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ አስደነገጣቸው ፤ ሲሣራም ፡ ከሠረገላው ፡ ወርዶ ፡ በእግሩ ፡ ሸሸ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ባርቅም ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ሰራዊቱን ፡ እስከ ፡ ዐሪሶት ፡ ድረስ ፡ አባረረ ፤ የሲሣራም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ወደቀ ፤ አንድ ፡ እንኳ ፡ አልቀረም ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በአሶር ፡ ንጉሥም ፡ በኢያቢስና ፡ በቄናዊው ፡ በሔቤር ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ነበረና ፡ ሲሣራ ፡ በእግሩ ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ቄናዊው ፡ ወደሔቤር ፡ ሚስት ፡ ወደኢያዔል ፡ ድንኳን ፡ ደረሰ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ኢያዔልም ፡ ሲሣራን ፡ ለመገናኘት ፡ ወጥታ ፦ ግባ ፥ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ግባ ፤ አትፍራ ፡ አለችው ። ወደ ፡ ርሷም ፡ ወደ ፡ ድንኳኗ ፡ ገባ ፥ በመጐናጸፊያዋም ፡ ሸፈነችው ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ርሱም ፦ ጠምቶኛልና ፥ እባክሽ ፡ የምጠጣው ፡ ጥቂት ፡ ውሃ ፡ ስጪኝ ፡ አላት ፤ ርሷም ፡ የወተቱን ፡ አቍማዳ ፡ ፈቷ ፡ አጠጣችው ፥ ሸፈነችውም ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ ከድንኳኑ ፡ ደጃፍ ፡ ቁሚ ፤ ሰውም ፡ መጥቶ ፦ በዚህ ፡ ሰው ፡ አለን ፧ ብሎ ፡ ቢጠይቅሽ ፡ አንቺ ፦ የለም ፡ ትዪዋለሽ ፡ አላት ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ የሔቤርም ፡ ሚስት ፡ ኢያዔል ፡ የድንኳን ፡ ካስማ ፡ ወሰደች ፥ በእጇም ፡ መዶሻ ፡ ያዘች ፥ ቀስ ፡ ብላም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበች ፤ በጕሮሮ ፡ ግንዱ ፡ ካስማውን ፡ ቸነከረች ፤ ርሱም ፡ ደክሞ ፡ አንቀላፍቶ ፡ ነበርና ፥ ካስማው ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ ጠለቀ ፥ ርሱም ፡ ሞተ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ እንሆም ፥ ባርቅ ፡ ሲሣራን ፡ ሲያባርር ፡ ኢያዔል ፡ ልትገናኘው ፡ ወጥታ ፦ ና ፥ የምትሻውንም ፡ ሰው ፡ አሳይኻለኹ ፡ አለችው ። ወደ ፡ ርሷም ፡ ገባ ፥ እንሆም ፥ ሲሣራን ፡ ወድቆ ፡ ሞቶም ፡ አገኘው ፥ ካስማውም ፡ ከጕሮሮ ፡ ግንዱ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ የከነዓንን ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡

አዋረደ ።

መሳ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ የከነዓንን ፡ ንጉሥ ፡ ኢያቢስንም ፡ እስኪያጠፉ ፡ ድረስ ፡ በከነዓን ፡ ንጉሥ ፡ በኢያቢስ ፡ ላይ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ እየበረታች ፡ ኼደች ።

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

መሳ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዲቦራና ፡ የአቢኒኤም ፡ ልጅ ፡ ባርቅ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተቀኙ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በእስራኤል ፡ ውስጥ ፡ መሪዎች ፡ ስለ ፡ መሩ ፥

ሕዝቡም ፡ ነፍሳቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ስለ ፡ ሰጡ ፥

እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ነገሥታት ፡ ሆይ ፥ ስሙ ፤

መኳንንት ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፤

እኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እቀኛለኹ ፥

ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እዘምራለኹ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ ከሴይር ፡ በወጣኽ ፡ ጊዜ ፥

ከኤዶምያስም ፡ ሜዳ ፡ በተራመድኽ ፡ ጊዜ ፥

ምድሪቱ ፡ ተናወጠች ፥ ሰማያቱም ፡ አንጠበጠቡ ፤

ደመናትም ፡ ደግሞ ፡ ውሃን ፡ አንጠበጠቡ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ተራራዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ቀለጡ ፥

ያም ፡ ሲና ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የተነሣ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ በዓናት ፡ ልጅ ፡ በሰሜጋር ፡ ዘመን ፥

በኢያዔል ፡ ዘመን ፡ መንገዶች ፡ ተቋረጡ ፤

መንገደኞች ፡ በስርጥ ፡ መንገድ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ አንቺ ፥ ዲቦራ ፥ እስክትነሺ ፡ ድረስ ፥

ለእስራኤልም ፡ እናት ፡ ኾነሽ ፡ እስክትነሺ ፡ ድረስ ፥

ጎያላን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አነሱ ፥ አለቁም ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ዐዲሶች ፡ አማልክትን ፡ መረጡ ፤

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሰልፍ ፡ በበሮች ፡ ኾነ ፤

በአርባ ፡ ሺሕ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ጦርና ፡ ጋሻ ፡ አልታየም ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ልቤ ፡ ወደእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ ነው ፥

በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ነፍሳቸውን ፡ በፈቃዳቸው ፡ ወደሰጡት ፤

እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ በነጫጭ ፡ አህያዎች ፡ ላይ ፡ የምትጫኑ ፥

በወላንሳ ፡ ላይ ፡ የምትቀመጡ ፥

በመንገድም ፡ የምትኼዱ ፥ ተናገሩ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ በማጠጫው ፡ መካከል ፡ ካሉት ፡ ከቀስተኞች ፡ ጩኸት ፡ ርቀው ፥

በዚያ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፥

በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የግዛቱን ፡ ጽድቅ ፡ ይጫወታሉ ፤

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ በሮች ፡ ወረዱ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ንቂ ፥ ንቂ ፥ ዲቦራ ፡ ሆይ ፤

ንቂ ፥ ንቂ ፥ ቅኔውን ፡ ተቀኚ ፤

ባርቅ ፡ ሆይ ፥ ተነሣ ፤

የአቢኒኤም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምርኮኽን ፡ ማርክ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ ወደ ፡ ኀያላኑና ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወረዱ ፤

እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ በኀያላን ፡ ላይ ፡ ወረደ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በዐማሌቅ ፡ ዘንድ ፡ ሥር ፡ የነበራቸው ፡ እነርሱ ፡ ከኤፍሬም ፥

ብንያም ፡ ሆይ ፥ በሕዝብኽ ፡ መካከል ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ወረዱ ፤

አለቃዎች ፡ ከማኪር ፥ የንጉሥንም ፡ ዘንግ ፡ የሚይዙ ፡ ከዛብሎን ፡ ወረዱ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የይሳኮርም ፡ አለቃዎች ፡ ከዲቦራ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፤

ይሳኮርም ፡ እንደ ፡ ባርቅ ፡ ነበረ ፤

ከእግሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሸለቆው ፡ ቸኰሉ ፤

በሮቤል ፡ ፈሳሾች ፡ አጠገብ ፡ ብዙ ፡ የልብ ፡ ማመንታት ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ መንጋዎች ፡ ሲያፏጩ ፡ ለመስማት ፡

በበጎች ፡ ጕረኖ ፡ መካከል ፡ ለምን ፡ ተቀመጥኽ ፧

በሮቤል ፡ ፈሳሾች ፡ አጠገብ ፡ ታላቅ ፡ የልብ ፡ ምርምር ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ገለዓድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ተቀመጠ ፤

ዳንም ፡ ለምን ፡ በመርከብ ፡ ውስጥ ፡ ቀረ ፧

አሴርም ፡ በባሕሩ ፡ ዳር ፡ ተቀመጠ ፥

በወንዞቹም ፡ ዳርቻ ፡ ዐረፈ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ዛብሎን ፡ ነፍሱን ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ያሳለፈ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፥

ንፍታሌምም ፡ በአገሩ ፡ ከሠረብታ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ነገሥታት ፡ መጡ ፥ ተዋጉም ፤

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በመጊዶ ፡ ውሃዎች ፡ አጠገብ ፡ በታዕናክ ፡

የከነዓን ፡ ነገሥታት ፡ ተዋጉ ፤

የብር ፡ ዘረፋም ፡ አልወሰዱም ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ከዋክብት ፡ ከሰማይ ፡ ተዋጉ ፤

በአካኼዳቸውም ፡ ከሢሣራ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ከዱሮ ፡ ዝምሮ ፡ የታወቀ ፡ ያ ፡ የቂሶን ፡ ወንዝ ፥

የቂሶን ፡ ወንዝ ፡ ጠርጎ ፡ ወሰዳቸው ።

ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ በኀይል ፡ ርገጪ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ከኀያላን ፡ ግልቢያ ፡ ብርታት ፡ የተነሣ ፡

የፈረሶች ፡ ጥፍሮች ፡ ተቀጠቀጡ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፦ ሜሮዝን ፡ ርገሙ ፤

እግዚአብሔርን ፡ በኀያላን ፡ መካከል ፡ ለመርዳት ፥

እግዚአብሔርን ፡ ለመርዳት ፡ አልመጡምና ፡

የተቀመጡባትን ፡ ሰዎች ፡ ፈጽማችኹ ፡ ርገሙ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ የቄናዊው ፡ የሔቤር ፡ ሚስት ፡ ኢያዔል ፡

ከሴቶች ፡ ይልቅ ፡ የተባረከች ፡ ትኹን ፤

በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ ሴቶች ፡ ይልቅ ፡ የተባረከች ፡ ትኹን ።

መሳ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ውሃ ፡ ለመነ ፥ ወተትም ፡ ሰጠችው ፤

በተከበረ ፡ ዳካ ፡ ርጎ ፡ አቀረበችለት ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 26 ፤ እጇን ፡ ወደ ፡ ካስማ ፥

ቀኝ ፡ እጇንም ፡ ወደሠራተኛ ፡ መዶሻ ፡ አደረገች ፤

በመዶሻውም ፡ ሢሣራን ፡ መታች ፥ ራሱንም ፡ ቸነከረች ፤

ገሮ ፡ ግንዱንም ፡ በሳች ፥ ጐዳችውም ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 27 ፤ በእግሮቿ ፡ አጠገብ ፡ ተደፋ ፥ ወደቀ ፥ ተኛ ፤

በእግሮቿ ፡ አጠገብ ፡ ተደፋ ፥ ወደቀ ፤

በተደፋበት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 28 ፤ ከመስኮት ፡ ኾና ፡ ተመለከተች ፤

የሢሣራ ፡ እናት ፡ በሠቅሠቅ ፡ ዘልቃ ።

ስለ ፡ ምን ፡ ለመምጣት ፡ ሠረገላው ፡ ዘገየ ፧

ስለ ፡ ምንስ ፡ የሠረገላው ፡ መንኰራኵር ፡ ቈየ ፧ ብላ ፡ ጮኸች ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 29 ፤ ብልኀተኞች ፡ ሴቶቿ ፡ መለሱላት ፤

ርሷ ፡ ደግሞ ፡ ለራሷ ፡ እንዲህ ፡ ብላ ፡ መለሰች ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 30 ፤ ምርኮ ፡ አግኝተው ፡ የለምን ፧ ተካፍለውስ ፡ የለምን ፧

ለያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ምርኮ ፡ አንዲት ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ቈነጕሯት ፤

ለሢሣራ ፡ ምርኮ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ያለው ፡ ልብስ ፥

በዐንገትጌ ፡ ላይ ፡ በኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ የተጠለፈ ፡ ዝንጕርጕር ፡ ልብስ ።

መሳ. ፥ 5 ፥ 31 ፤ አቤቱ ፥ ጠላቶችኽ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ይጥፉ ፤

ወዳጆችኽ ፡ ግን ፡ ፀሓይ ፡ በኀይሉ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚኾን ፥ እንዲሁ ፡ ይኹኑ ። ምድሪቱም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ዐረፈች ።

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

መሳ. ፥ 6 ፥ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድያም ፡ እጅ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 2 ፤ የምድያምም ፡ እጅ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ጠነከረች ፤ ከምድያምም ፡ የተነሣ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ጕድጓድና ፡ ዋሻ ፡ ምሽግም ፡ አበጁ ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ እስራኤልም ፡ ዘር ፡ በዘሩ ፡ ጊዜ ፡ ምድያማውያን ፡ ዐማሌቃውያንም ፡ በምሥራቅም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይመጡባቸው ፡ ነበር ፤

መሳ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ይሰፍሩ ፡ ነበር ፥ እስከ ፡ ጋዛም ፡ ድረስ ፡ የምድሩን ፡ ቡቃያ ፡ ያጠፉ ፡

ነበር ፥ ምግብንም ፡ ለእስራኤል ፡ አይተዉም ፡ ነበር ፤ በግ ፡ ወይም ፡ በሬ ፡ ወይም ፡ አህያ ፡ ቢኾን ፡ አይተዉም ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ እንስሳዎቻቸውንና ፡ ድንኳኖቻቸውን ፡ ይዘው ፡ በብዛት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ ኾነው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፤ ለእነርሱና ፡ ለግመሎቻቸውም ፡ ቍጥር ፡ አልነበራቸውም ፤ ምድሪቱንም ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ ከምድያምም ፡ የተነሣ ፡ እስራኤል ፡ እጅግ ፡ ተጠቁ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በምድያም ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፥

መሳ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነቢይ ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣኋችኹ ፥ ከባርነትም ፡ ቤት ፡ አስለቀቅኋችኹ ፤

መሳ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፥ ከሚጋፏችኹም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ አዳንኋችኹ ፥ ከፊታችኹም ፡ አሳደድኋቸው ፥ አገራቸውንም ፡ ሰጠኋችኹ ፤

መሳ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ እናንተንም ፦ እኔ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ በምድራቸው ፡ የተቀመጣችኹባቸውን ፡ የአሞራያውያንን ፡ አማልክት ፡ አትፍሩ ፡ አልኋችኹ ። እናንተ ፡ ግን ፡ ድምፄን ፡ አልሰማችኹም ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ በዖፍራ ፡ ባለችው ፡ ለአቢዔዝራዊው ፡ ለኢዮአስ ፡ በነበረችው ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀመጠ ፤ ልጁም ፡ ጌዴዎን ፡ ከምድያማውያን ፡ ለመሸሸግ ፡ በወይን ፡ መጥመቂያው ፡ ውስጥ ፡ ስንዴ ፡ ይወቃ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ለርሱ ፡ ተገልጦ ፦ አንተ ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ ጌዴዎንም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ከኾነ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለምን ፡ ደረሰብን ፧ አባቶቻችንስ ። እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ አውጥቶናል ፡ ብለው ፡ ይነግሩን ፡ የነበረ ፡ ተኣምራቱ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ወዴት ፡ አለ ፧ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ትቶናል ፥ በምድያማውያንም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶናል ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፦ በዚህ ፡ በጕልበትኽ ፡ ኺድ ፥ እስራኤልንም ፡ ከምድያም ፡ እጅ ፡ አድን ፤ እንሆ ፥ ልኬኻለኹ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 15 ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስራኤልን ፡ በምን ፡ አድናለኹ ፧ ወገኔ ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የተጠቃ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ የኹሉ ፡ ታናሽ ፡ ነኝ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በርግጥ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ ምድያምንም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አድርገኽ ፡ ትመታለኽ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 17 ፤ ርሱም ፦ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ ካገኘኹ ፥ የምትናገረኝም ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ምልክት ፡ አሳየኝ ፤

መሳ. ፥ 6 ፥ 18 ፤ ወዳንተም ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፥ ቍርባኔንም ፡ አምጥቼ ፡ እስካቀርብልኽ ፡ ድረስ ፥ እባክኽ ፥ ከዚህ ፡ አትላወስ ፡ አለው ። ርሱም ፦ እስክትመለስ ፡ ድረስ ፡ እቈያለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፥ 6 ፥ 19 ፤ ጌዴዎን ፡ ገባ ፡ የፍየሉንም ፡ ጠቦት ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያም ፡ ዱቄት ፡ የቂጣ ፡ ዕንጐቻ ፡ አዘጋጀ ፤ ሥጋውን ፡ በሌማት ፡ አኖረ ፥ መረቁንም ፡ በምንቸት ፡ ውስጥ ፡ አደረገ ፥ ኹሉንም ፡ ይዞ ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ አቀረበለት ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፦ ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡ ዕንጐቻ ፡ ወስደኽ ፡ በዚህ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አኑር ፥ መረቁንም ፡ አፍስ ፡ አለው ። እንዲሁም ፡ አደረገ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ የበትሩን ፡ ጫፍ ፡ ዘርግቶ ፡ ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡ ዕንጐቻ ፡ አስነካ ፤ እሳትም ፡ ከድንጋዩ ፡ ውስጥ ፡ ወጥቶ ፡ ሥጋውንና ፡ የቂጣውን ፡ ዕንጐቻ ፡ በላ ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ከዐይኑ ፡ ተሰወረ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ጌዴዎንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ፤ ጌዴዎንም ፦ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኝ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ አይቻለኹና ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፤ አትፍራ ፤ አትሞትም ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ጌዴዎንም ፡ በዚያ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ ስሙንም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለአቢዔዝራውያን ፡ በምትኾነው ፡ በዖፍራ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ። የአባትኽን ፡ በሬ ፥ ሰባት ፡ ዓመት ፡ የኾነውን ፡ ኹለተኛውን ፡ በሬ ፥ ውሰድ ፥ የአባትኽ ፡ የኾነውንም ፡ የበዓል ፡ መሠዊያ ፡ አፍርስ ፥ በርሱም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ቍረጥ ፤

መሳ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ በዚያም ፡ ከመረብታ ፡ ዐናት ፡ ላይ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ አሳምረኽ ፡ ሥራ ፡ ኹለተኛውንም ፡ በሬ ፡ ውሰድ ፥ በዚያም ፡ በቈረጥኸው ፡ በማምለኪያ ፡ ዐጸዱ ፡ ዕንጨት ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርብ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ጌዴዎንም ፡ ከባሪያዎቹ ፡ ዐሥር ፡ ሰዎችን ፡ ወስዶ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለው ፡ አደረገ ፤ የአባቱን ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ የከተማውንም ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ ይህን ፡ በቀን ፡ ለማድረግ ፡ አልቻለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በሌሊት ፡ አደረገው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ የከተማውም ፡ ሰዎች ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥ እንሆም ፥ የበዓል ፡ መሠዊያ ፡ ፈርሶ ፥ በዙሪያው ፡ ያለውም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ተቈርጦ ፥ በተሠራውም ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ኹለተኛው ፡ በሬ ፡ ተሠውቶ ፡ አገኙት ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ተባባሉ ። በጠየቁና ፡ በመረመሩም ፡ ጊዜ ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ ያደረገ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ ጌዴዎን ፡ ነው ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ የከተማውም ፡ ሰዎች ፡ ኢዮአስን ፦ የበዓልን ፡ መሠዊያ ፡ አፍርሷልና ፥ በዙሪያውም ፡ ያለውን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ቈርጧልና ፥ እንዲሞት ፡ ልጅኽን ፡ አውጣ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 31 ፤ ኢዮአስም ፡ ርሱን ፡ የተቃወሙትን ፡ ኾሉ ፦ ለበዓል ፡ ትሟገቱለታላችኹን ፧ ወይስ ፡ ርሱን ፡ ታድናላችኹን ፧ የሚሟገትለት ፡ ኾሉ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ይሙት ፤ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ከኾነ ፡ መሠዊያውን ፡ ካፈረሰው ፡ ጋራ ፡ ለራሱ ፡ ይሟገት ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 32 ፤ ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፦ መሠዊያውን ፡ አፍርሷልና ፥ በዓል ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይሟገት ፡ ብሎ ፡ ጌዴዎንን ፦ ይሩበዓል ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 33 ፤ ምድያማውያንም ፡ ዐማሌቃውያንም ፡ ኾሉ ፡ የምሥራቅም ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ተሰበሰቡ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገሩ ፥ በኢይዝራኤልም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፈሩ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 34 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በጌዴዎን ፡ ገባበት ፥ ርሱም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ነፋ ፤ የአቢዔዝርም ፡ ሰዎች ፡ ተጠርተው ፡ በኋላው ፡ ተከተሉት ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 35 ፤ ወደምናሴም ፡ ነገድ ፡ ኾሉ ፡ መልክተኞችን ፡ ሰደደ ፡ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ተጠርተው ፡ በኋላው ፡ ተከተሉት ፤ መልክተኞችንም ፡ ወደ ፡ አሴርና ፡ ወደ ፡ ዛብሎን ፡ ወደ ፡ ንፍታሌምም ፡ ሰደደ ፥ እነርሱም ፡ ሊገናኟቸው ፡ ወጡ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 36 ፤ ጌዴዎንም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ ታድን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

መሳ. ፡ 6 ፡ 37 ፤ እንሆ ፥ በዐውድማው ፡ ላይ ፡ የተባዘተ ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ አኖራለኹ ፤ በጠጕሩ ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ጠል ፡ ቢኾን ፡ በምድሩም ፡ ኾሉ ፡ ደረቅ ፡ ቢኾን ፥ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ እንድታድናቸው ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 38 ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ፤ በነጋውም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ጠጕሩንም ፡ ጨመቀው ፥ ከጠጕሩም ፡ የተጨመቀው ፡ ጠል ፡ ቈሬ ፡ ሙሉ ፡ ውሃ ፡ ኾነ ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 39 ፤ ጌዴዎንም ፡ እግዚአብሔርን ፦ እኔ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ስናገር ፡ አትቈጣኝ ፤ እኔ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጠጕሩ ፥ እባክኽ ፥ ልፈትን ፤ አኹንም ፡ በጠጕሩ ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ደረቅ ፡ ይኹን ፥ በምድሩም ፡ ኾሉ ፡ ላይ ፡ ጠል ፡ ይኹን ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 6 ፡ 40 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ፤ በጠጕሩ ፡ ብቻ ፡ ላይ ፡ ደረቅ ፡ ነበረ ፥ በምድሩም ፡ ኾሉ ፡ ላይ ፡ ጠል ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ጌዴዎን ፡ የተባለውም ፡ ይሩበዓል ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኾሉ ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፤ በሐሮድ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብም ፡ ሰፈሩ ፤ የምድያምም ፡ ሰፈር ፡ ከነርሱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ በኩል ፥ በሞሬ ፡ ኮረብታ ፡ አጠገብ ፥ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ በዝቷል ፤ ስለዚህ ፥ እስራኤል ፦ እጄ ፡ አዳነኝ ፡ ብሎ ፡ እንዳይታበይብኝ ፡ እኔ ፡ ምድያምን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጣቸውም ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ አኹንም ፡ እንግዲህ ፦ የፈራ ፡ የደነገጠም ፡ ከገለዓድ ፡ ተራራ ፡ ተነሥቶ ፡ ይመለስ ፡ ብለኽ ፡ በሕዝቡ ፡ ጐሮ ፡ ዐውጅ ፡ አለው ። ከሕዝቡም ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ተመለሱ ፥ ዐሥርም ፡ ሺሕ ፡ ቀሩ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ሕዝቡ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ውሃ ፡ አውርዳቸው ፥ በዚያም ፡ እፈትናቸዋለኹ ፤ እኔም ፦ ይህ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኺድ ፡ የምለው ፡ ርሱ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኼዳል ፤ እኔም ፦ ይህ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አይኺድ ፡ የምለው ፡ ርሱ ፡ አይኼድም ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ሕዝቡንም ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ አወረደ ። እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ ውሻ ፡ እንደሚጠጣ ፡ ውሃ ፡ በምላሱ ፡ የሚጠጣውን ፡ ኾሉ ፥ ርሱን ፡ ለብቻው ፡ አድርገው ፤ እንዲሁም ፡ ሊጠጣ ፡ በጕልበቱ ፡ የሚንበረከከውን ፡ ኾሉ ፡ ለብቻው ፡ አድርገው ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ በእጃቸውም ፡ ውሃ ፡ ወደ ፡ አፋቸው ፡ አድርገው ፡ የጠጡት ፡ ቍጥር ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ፤ የቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ውሃ ፡ ሊጠጡ ፡ በጕልበታቸው ፡ ተንበረከኩ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጌዴዎንን ፦ በእጃቸው ፡ ውሃ ፡ በጠጡት ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ አድናችኋለኹ ፥ ምድያማውያንንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ የቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኾሉ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይመለሱ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የሕዝቡንም ፡ ሥንቅና ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ በእጃቸው ፡ ወሰዱ ፤ የቀሩትንም ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ሰደዳቸው ፥ ሦስቱን ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቃቸው ፤ የምድያምም ፡ ሰፈር ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፦ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻቸዋለኹና ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ውረድ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ አንተም ፡ ለመውረድ ፡ ብትፈራ ፡ አንተ ፡ ከሎሌኽ ፡ ከፉራ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ውረድ ፤

መሳ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ የሚናገሩትንም ፡ ትሰማለኽ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ትወርድ ፡ ዘንድ ፡ እጅኽ ፡ ትበረታለች ፡ አለው ። ርሱና ፡ ሎሌው ፡ ፉራ ፡ በሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ ወደነበሩት ፡ ሰልፈኞች ፡ ወረዱ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ብዛታቸውም ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ የኾነ ፡ ምድያማውያንና ፡ ዐማሌቃውያን ፡ የምሥራቅም ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ሰፍረው ፡ ነበር ፤ የግመሎቻቸውም ፡ ብዛት ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ጌዴዎንም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሕልምን ፡ ለባልንጀራው ፡ ሲያጫውት ፦ እንሆ ፥ ሕልም ፡ ዐለምኹ ፤ እንሆም ፥ አንዲት ፡ የገብስ ፡ ዕንጐቻ ፡ ወደምድያም ፡ ሰፈር ፡ ተንከባላ ፡ ወረደች ፥ ወደ ፡ ድንኳኑም ፡ ደርሳ ፡ እስኪወድቅ ፡ ድረስ ፡ መታችው ፥ ገለበጠችውም ፥ ድንኳኑም ፡ ተጋደመ ፡ ይል ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ባልንጀራውም ፡ መልሶ ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእስራኤል ፡ ሰው ፡ ከኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ ከጌዴዎን ፡ ሰይፍ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አይደለም ፤ እግዚአብሔር ፡ ምድያምንና ፡ ሰራዊቱን ፡ ሹሉ ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷል ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ጌዴዎንም ፡ ሕልሙንና ፡ ትርጓሜውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሰገደ ፤ ወደእስራኤልም ፡ ሰፈር ፡ ተመልሶ ፦ እግዚአብሔር ፡ የምድያምን ፡ ሰራዊት ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ ተነሡ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ሦስቱንም ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ከፈላቸው ፥ በሹሉም ፡ እጅ ፡ ቀንደ ፡ መለከትና ፡ ባዶ ፡ ማሰሮ ፥ በማሰሮውም ፡ ውስጥ ፡ ችቦ ፡ ሰጠ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ እኔን ፡ ተመልከቱ ፥ እንዲሁም ፡ አድርጉ ፤ እንሆም ፥ ወደሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ በደረስኹ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እንደማደርግ ፡ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ አድርጉ ፤

መሳ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ሹሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ስንነፋ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ሹሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከታችኹን ፡ ንፉ ። ለእግዚአብሔርና ፡ ለጌዴዎን ፡ በሉ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ጌዴዎንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ በመካከለኛው ፡ ትጋት ፡ ትጋቱም ፡ በተገመረ ፡ ጊዜ ፡ ወደሰፈሩ ፡ ዳርቻ ፡ መጡ ፤ ቀንደ ፡ መለከቶችንም ፡ ነፉ ፥ በእጃቸውም ፡ የነበሩትን ፡ ማሰሮች ፡ ሰባበሩ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሦስቱም ፡ ወገኖች ፡ ቀንደ ፡ መለከቶችን ፡ ነፉ ፥ ማሰሮችንም ፡ ሰበሩ ፥ በግራ ፡ እጃቸውም ፡ ችቦዎችን ፥ በቀኝ ፡ እጃቸውም ፡ ቀንደ ፡ መለከቶችን ፡ ይዘው ፡ እየነፉ ፦ የእግዚአብሔርና ፡ የጌዴዎን ፡ ሰይፍ ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ሹሉም ፡ በየቦታው ፡ በሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ ቆመ ፤ ሰራዊቱም ፡ ሹሉ ፡ ሮጠ ፥ ጮኸ ፥ ሸሸም ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ሦስቱንም ፡ መቶ ፡ ቀንደ ፡ መለከቶች ፡ ነፉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የሰውን ፡ ሹሉ ፡ ሰይፍ ፡ በባልንጀራውና ፡ በሰራዊቱ ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፤ ሰራዊቱም ፡ በጽሬራ ፡ በኩል ፡ እስከ ፡ ቤትሺጣ ፡ ድረስ ፡ በጠባት ፡

አጠገብ ፡ እስካለው ፡ እስከአቤልምሖላ ([126]) ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ሸሸ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከንፍታሌምና ፡ ከአሴር ፡ ከምናሴም ፡ ዥሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ምድያምን ፡ አሳደዱ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ጌዴዎንም ፦ ምድያምን ፡ ለመገናኘት ፡ ውረዱ ፥ እስከ ፡ ቤትባራም ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ውሃ ፥ ዮርዳኖስን ፥ ያዙባቸው ፡ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ በኤፍሬም ፡ ወዳለው ፡ ተራራማ ፡ አገር ፡ ዥሉ ፡ ሰደደ ። የኤፍሬም ፡ ሰዎችም ፡ ዥሉ ፡ ተሰብስበው ፡ እስከ ፡ ቤትባራ ፡ ድረስ ፡ ውሃውን ፥ ዮርዳኖስን ፥ ያዙ ።

መሳ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ የምድያምን ፡ ኹለቱን ፡ መኳንንት ፡ ሔሬብንና ፡ ዜብን ፡ ያዙ ፤ ሔሬብንም ፡ በሔሬብ ፡ አለት ፡ አጠገብ ፡ ገደሉት ፥ ዜብንም ፡ በዜብ ፡ መጥመቂያ ፡ ላይ ፡ ገደሉት ፤ ምድያምንም ፡ አሳደዱ ፥ የሔሬብንና ፡ የዜብንም ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ ወደዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ጌዴዎን ፡ መጡ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ የኤፍሬም ፡ ሰዎች ፦ ይህ ፡ ያደረግኽብን ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ምድያምን ፡ ለመዋጋት ፡ በወጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ አልጠራኸንም ፧ አሉት ። ጽኑ ፡ ጥልም ፡ ተጣሉት ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ካደረግኹት ፡ እናንተ ፡ ያደረጋችኹት ፡ አይበልጥምን ፧ የኤፍሬም ፡ ወይን ፡ ቃርሚያ ፡ ከአቢዔዝር ፡ ወይን ፡ መከር ፡ አይሻልምን ፧

መሳ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ የምድያምን ፡ መኳንንት ፡ ሔሬብንና ፡ ዜብን ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷቸዋል ፤ እናንተ ፡ ያደረጋችኹትን ፡ የሚመስል ፡ እኔ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እችል ፡ ኖሯል ፧ አላቸው ። ይህን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣቸው ፡ በረደ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ጌዴዎንም ፡ ከሦስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ደርሶ ፡ ተሻገረ ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢደክሙ ፡ ያሳድዱ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ የሱኮትንም ፡ ሰዎች ፦ የምድያምን ፡ ነገሥታት ፡ ዛብሄልንና ፡ ስልማናን ፡ ሳሳድድ ፥ ደክመዋልና ፥ እኔን ፡ ለተከተሉ ፡ ሕዝብ ፡ እንጀራ ፥ እባካችኹ ፥ ስጡ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ የሱኮትም ፡ አለቃዎች ፦ እኛ ፡ ለሰራዊትኽ ፡ እንጀራ ፡ እንድንሰጥ ፡ የዛብሄልና ፡ የስልማና ፡ እጅ ፡ አኹን ፡ በእጅኽ ፡ ነውን ፧ አሉ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ጌዴዎንም ፦ እግዚአብሔር ፡ ዛብሄልንና ፡ ስልማናን ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሲሰጠኝ ፡ እኔ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሾኽና ፡ በኵርንችት ፡ ሥጋችኹን ፡ እገርፋለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጵኒኤል ፡ ወጣ ፥ ለጵኒኤልም ፡ ሰዎች ፡ እንዲሁ ፡ አላቸው ፤ የጵንኤልም ፡ ሰዎች ፡ የሱኮት ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ መለሱ ፡ መለሱለት ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ርሱም ፡ የጵኒኤልን ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፦ በደኅና ፡ በተመለስኹ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ግንብ ፡ አፈርሰዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ዛብሄልና ፡ ስልማናም ፡ ከሰራዊቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ በቀርቀር ፡ ነበሩ ፤ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ወድቀው ፡ ነበርና ፥ ከምሥራቅ ፡ ሰዎች ፡ ሰራዊት ፡ ዥሉ ፡ የቀሩ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ጌዴዎንም ፡ የድንኳን ፡ ተቀማጮች ፡ ባሉበት ፡ መንገድ ፡ በኖባህና ፡ በዮግብሃ ፡ በምሥራቅ ፡

126 የማሕሌት ፡ መስክ ።

በኩል ፡ ወጣ ፤ ሰራዊቱም ፡ ተዘልሎ ፡ ነበርና ፥ ሰራዊቱን ፡ መታ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ዛብሄልና ፡ ስልማናም ፡ ሸሹ ፤ ርሱም ፡ አሳደዳቸው ፥ ኹለቱንም ፡ የምድያም ፡ ነገሥታት ፡ ዛብሄልንና ፡ ስልማናን ፡ ያዘ ፥ ሰራዊቱንም ፡ ሹሉ ፡ አስደነገጠ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ የኢዮአስ ፡ ልጅም ፡ ጌዴዎን ፡ ከሔሬስ ፡ ዳገት ፡ ከሰልፍ ፡ ተመለሰ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ ከሱኮትም ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ብላቴና ፡ ይዞ ፡ ጠየቀው ፤ ርሱም ፡ የሱኮትን ፡ አለቃዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰባ ፡ ሳባት ፡ ሰዎች ፡ ጻፈለት ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 15 ፤ ወደሱኮትም ፡ ሰዎች ፡ መጥቶ ፦ ለደከሙት ፡ ሰዎችኽ ፡ እንጀራ ፡ እንሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የዛብሄልና ፡ የስልማና ፡ እጅ ፡ አኹን ፡ በእጅኽ ፡ ነውን ፧ ብላችኹ ፡ የተላገዳችኹብኝ ፥ ዛብሄልና ፡ ስልማና ፥ እንሆ ፥ አለ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 16 ፤ የከተማዉቱንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያዘ ፥ የምድረ ፡ በዳንም ፡ ሾኽና ፡ ኵርንችት ፡ ወስዶ ፡ የሱኮትን ፡ ሰዎች ፡ ገረፋቸው ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 17 ፤ የጵኒኤልንም ፡ ግንብ ፡ አፈረሰ ፥ የከተማዉቱንም ፡ ሰዎች ፡ ገደላቸው ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 18 ፤ ዛብሄልንና ፡ ስልማናን ፦ በታቦር ፡ የገደላችኋቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እንደ ፡ አንተ ፡ ያሉ ፡ ነበሩ ፥ አንተንም ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ፤ መልካቸውም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ልጆች ፡ መልክ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 19 ፤ ርሱም ፦ የእናቴ ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቼ ፡ ነበሩ ፤ አድናችኋቸው ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እኔ ፡ አልገድላችኹም ፡ ነበር ፡ አለ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 20 ፤ በኵሩንም ፡ ዬቴርን ፦ ተነሥተኽ ፡ ግደላቸው ፡ አለው ፤ ብላቴናው ፡ ግን ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ነበረና ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ ሰይፉን ፡ አልመዘዘም ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 21 ፤ ዛብሄልና ፡ ስልማናም ፦ የሰው ፡ ኀይሉ ፡ እንደ ፡ ሰውነቱ ፡ ነውና ፥ አንተ ፡ ተነሥተኽ ፡ ውደቅብን ፡ አሉት ። ጌዴዎንም ፡ ተነሥቶ ፡ ዛብሄልንና ፡ ስልማናን ፡ ገደለ ፥ በግመሎቻቸውም ፡ ዐንገት ፡ የነበሩትን ፡ ሥሉሴዎች ፡ ማረከ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 22 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ጌዴዎንን ፦ ከምድያም ፡ እጅ ፡ አድነኸናልና ፥ አንተ ፡ ልጅኽም ፡ የልጅ ፡ ልጅኽም ፡ ደግሞ ፡ ግዙን ፡ አሉት ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 23 ፤ ጌዴዎንም ፦ እኔ ፡ አልገዛችኹም ፥ ልጄም ፡ አይገዛችኹም ፤ እግዚአብሔር ፡ ይገዛችኋል ፡ አላቸው ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 24 ፤ እስማኤላውያንም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ የወርቅ ፡ ጕትቻ ፡ ነበራቸውና ፡ ጌዴዎን ፦ ሹላችኹ ፡ ከምርኳችኹ ፡ ጕትቻችኹን ፡ እንድትሰጡኝ ፡ እለምናችኋለኹ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 25 ፤ እነርሱም ፦ ፈቅደን ፡ እንሰጥኻለን ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። መጐናጸፊያም ፡ አነጠፉ ፥ ሰውም ፡ ሹሉ ፡ የምርኮውን ፡ ጕትቻ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ጣለ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 26 ፤ የለመነውም ፡ የወርቅ ፡ ጕትቻ ፡ ሚዛኑ ፥ ከአንባሩ ፥ ከድሪውም ፥ የምድያምም ፡ ነገሥታት ፡ ከለበሱት ፡ ከቀዩ ፡ ቀሚስ ፥ በግመሎቻቸውም ፡ ዐንገት ፡ ከነበሩት ፡ ሥሉሴዎች ፡ ሌላ ፥ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰቅለ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፥ 8 ፥ 27 ፤ ጌዴዎንም ፡ ኤፉድ ፡ አድርጎ ፡ አሠራው ፥ በከተማውም ፡ በዖፍራ ፡ አኖረው ፤ እስራኤልም ፡

ኹሉ ፡ ተከትሎት ፡ አመነዘረበት ፤ ለጌዴዎንና ፡ ለቤቱም ፡ ወጥመድ ፡ ኾነ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ምድያምም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተዋረደ ፥ ራሳቸውንም ፡ ዳግመኛ ፡ አላነሡም ፤ በጌዴዎንም ፡ ዕድሜ ፡ ምድሪቱ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ዐረፈች ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ የኢዮአስም ፡ ልጅ ፡ ይሩበዓል ፡ ኼዶ ፡ በቤቱ ፡ ተቀመጠ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ለጌዴዎንም ፡ ብዙ ፡ ሚስቶች ፡ ነበሩትና ፡ ከወገቡ ፡ የወጡ ፡ ሰባ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ በሴኬምም ፡ የነበረችው ፡ ቁባቱ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደችለት ፥ ስሙንም ፡ አቢሜሌክ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ የኢዮአስም ፡ ልጅ ፡ ጌዴዎን ፡ በመልካም ፡ ሽምግልና ፡ ሞተ ፥ በአቢዔዝራውያንም ፡ ከተማ ፡ በዖፍራ ፡ በነበረችው ፡ በአባቱ ፡ በኢዮአስ ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ጌዴዎን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፥ በዓሊምንም ፡ ተከትለው ፡ አመነዘሩ ፤ በዓልብሪትንም ፡ አምላካቸው ፡ አደረጉ ።

መሳ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በዙሪያቸው ፡ ከነበሩት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያዳናቸውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላሰቡትም ፤

መሳ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ርሱም ፡ ለእስራኤል ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረገ ፡ መጠን ፥ እነርሱ ፡ ለጌዴዎን ፡ ለይሩበዓል ፡ ቤት ፡ ወረታ ፡ አላደረጉም ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ የይሩበዓል ፡ ልጅ ፡ አቢሜሌክም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ወደእናቱ ፡ ወንድሞች ፡ ኼደ ፥ ለእነርሱም ፡ ለእናቱ ፡ አባት ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ ኹሉ ፦

መሳ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጐሮ ፦ ሰባ ፡ የኾኑት ፡ የይሩበዓል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ በገዟችኹ ፡ ወይስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በገዛችኹ ፡ ምን ፡ ይሻላችኋል ፧ ብላችኹ ፡ ንገሯቸው ፡ ብዬ ፡ እለምናችኋለኹ ፤ ደግሞ ፡ እኔ ፡ የዐጥንታችኹ ፡ ፍላጭ ፣ የሥጋችኹ ፡ ቍራጭ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ዐስቡ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ የእናቱም ፡ ወንድሞች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጐሮ ፡ ተናገሩ ፤ እነርሱም ፦ ርሱ ፡ ወንድማችን ፡ ነው ፡ ብለው ፡ አቢሜሌክን ፡ ለመከተል ፡ ልባቸውን ፡ አዘነበሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ከበዓልብሪትም ፡ ቤት ፡ ሰባ ፡ ብር ፡ ሰጡት ፤ በዚያም ፡ አቢሜሌክ ፡ ምናምንቴዎችንና ፡ ወሮ ፡ በላዎችን ፡ ቀጠረበት ፥ እነርሱም ፡ ተከተሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ወዳባቱም ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ዖፍራ ፡ ኼደ ፤ ሰባ ፡ የኾኑትን ፡ የይሩበዓልን ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቹን ፡ ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ዐረዳቸው ፤ ትንሹ ፡ የይሩበዓል ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡ ግን ፡ ተሸሽጎ ፡ ነበርና ፥ ተረፈ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ቤትሚሎም ፡ ኹሉ ፡ ተሰበሰቡ ፥ ኼደውም ፡ በሴኬም ፡ በዐምዱ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ አቢሜሌክን ፡ አነገሡ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ለኢዮአታም ፡ በነገሩት ፡ ጊዜ ፥ ኼዶ ፡ በገሪዛን ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆመ ፥ ድምፁንም ፡ አንሥቶ ፡ ጮኸ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ የሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲሰማችኹ ፡ ስሙኝ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዛፎች ፡ በላያቸው ፡ ንጉሥ ፡ ሊያነግሡ ፡ ኼዱ ፤ ወይራውንም ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡

ንገሥ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ወይራው ፡ ግን ፦ እግዚአብሔርና ፡ ሰዎች ፡ በእኔ ፡ የሚከበሩበትን ፡ ቅባቴን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ እንድሰፍ ፡ ልኺድ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ዛፎችም ፡ በለሱን ፦ መጥተኽ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ በለሱ ፡ ግን ፦ ጣፋጭነቴንና ፡ መልካሙን ፡ ፍሬዬን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ እንድሰፍ ፡ ልኺድ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ዛፎችም ፡ ወይኑን ፦ መጥተኽ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ወይኑም ፦ እግዚአብሔርንና ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ የወይን ፡ ጠጄን ፡ ትቼ ፡ በዛፎች ፡ ላይ ፡ እንድሰፍ ፡ ልኺድ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ዛፎችም ፡ ዥሉ ፡ ዾኽን ፦ መጥተኽ ፡ በላያችን ፡ ንገሥ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ዾኹም ፡ ዛፎችን ፦ በእውነት ፡ እኔን ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ታነግሡኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኑ ፡ ከጥላዬ ፡ በታች ፡ ተጠጉ ። እንዲሁም ፡ ባይኾን ፡ እሳት ፡ ከዾኽ ፡ ይውጣ ፥ የሊባኖስንም ፡ ዝግባ ፡ ያቃጥል ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ አቢሜሌክን ፡ በማንገሣችኹ ፡ እውነትንና ፡ ቅንነትን ፡ አድርጋችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ለይሩበዓልም ፡ ለቤቱም ፡ በጎ ፡ አድርጋችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እንዳደረገውም ፡ መጠን ፡ ለርሱ ፡ የተገባውን ፡ አድርጋችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

መሳ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ አባቴ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተጋድሎ ፡ ነበርና ፥ ከምድያምም ፡ እጅ ፡ ሊያድናችኹ ፡ ነፍሱን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበርና ፥

መሳ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ እናንተም ፡ ዛሬ ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ተነሥታችኺልና ፥ ሰባ ፡ የኾኑትን ፡ ልጆቹንም ፡ ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ዐርዳችኺልና ፥ ወንድማችኹም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የባሪያዪቱን ፡ ልጅ ፡ አቢሜሌክን ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አንግሣችኺልና ፥

መሳ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ለይሩበዓልና ፡ ለቤቱ ፡ እውነትንና ፡ ቅንነትን ፡ ዛሬ ፡ አድርጋችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በአቢሜሌክ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡ ይበለው ፤

መሳ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ እንዲህ ፡ ባይኾን ፡ ግን ፡ ከአቢሜሌክ ፡ እሳት ፡ ይውጣ ፥ የሴኬምንም ፡ ሰዎች ፡ ቤትሚሎንም ፡ ይብላ ፤ ከሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ ከቤትሚሎም ፡ እሳት ፡ ይውጣ ፥ አቢሜሌክንም ፡ ይብላ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ኢዮአታምም ፡ ሸሸቶ ፡ አመለጠ ፥ ወንድሙንም ፡ አቢሜሌክን ፡ ፈርቶ ፡ ወደ ፡ ብኤር ፡ ኼደ ፥ በዚያም ፡ ተቀመጠ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ አቢሜሌክም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአቢሜሌክና ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ክፉን ፡ መንፈስ ፡ ሰደደ ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ በአቢሜሌክ ፡ ላይ ፡ ተንኰል ፡ አደረጉ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፥ በሰባ ፡ የይሩበዓል ፡ ልጆቹ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ዐመፅ ፡ እንዲመጣ ፥ ደማቸውም ፡ በገደላቸው ፡ በወንድማቸው ፡ በአቢሜሌክ ፡ ላይ ፥ ወንድሞቹንም ፡ እንዲገድል ፡ እጆቹን ፡ ባጸኗቸው ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እንዲኾን ፡ ነው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ በተራራዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አደረጉ ፥ መንገድ ፡

ተላላፊዎችንም ፡ ኹሉ ፡ ይዘርፉ ፡ ነበር ፤ አቢሜሌክም ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ ሰማ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ የአቤድም ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ገባ ፤ የሴኬምም ፡ ሰዎች ፡ ታመኑበት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ዕርሻውም ፡ ወጡ ፡ ወይናቸውንም ፡ ለቀሙ ፥ ጠመቁትም ፥ የደስታም ፡ በዓል ፡ አደረጉ ፤ ወደአምላካቸውም ፡ ቤት ፡ ገቡ ፥ በሉም ፡ ጠጡም ፥ አቢሜሌክንም ፡ ሰደቡ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ የአቤድም ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፦ የምንገዛለት ፡ አቢሜሌክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ሴኬምስ ፡ ምንድርነው ፧ ርሱ ፡ የይሩብኣል ፡ ልጅ ፡ አይደለምን ፧ ዜቡልም ፡ የርሱ ፡ ሹም ፡ አይደለምን ፧ ለሴኬም ፡ አባት ፡ ለኤሞር ፡ ሰዎች ፡ ተገዙ ፤

መሳ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ለዚህ ፡ እንገዛለን ፧ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ከእጄ ፡ በታች ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ አቢሜሌክን ፡ አሳድደው ፡ ነበር ፡ አለ ። አቢሜሌክንም ፦ ሰራዊትኽን ፡ አብዝተኽ ፡ ና ፥ ውጣ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ የከተማዩቱ ፡ ገዢ ፡ ዜቡልም ፡ የአቤድን ፡ ልጅ ፡ የገዓልን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ በተንኰል ፡ መልክተኞች ፡ ላከ ፦ እንሆ ፥ የአቤድ ፡ ልጅ ፡ ገዓልና ፡ ወንድሞቹ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተዋል ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ከተማዩቱን ፡ አሸፍተዋል ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ አኹንም ፡ አንተና ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ በሌሊት ፡ ተነሡ ፥ በሜዳም ፡ ሽምቁ ፤

መሳ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ነገም ፡ ፀሓይ ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ማልደኽ ፡ ተነሣ ፥ በከተማዩቱም ፡ ላይ ፡ ውደቅባት ፤ እንሆም ፥ ርሱና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ እጅኽ ፡ እንዳገኘች ፡ አድርግበት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ አቢሜሌክና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በሌሊት ፡ ተነሡ ፥ በሴኬምም ፡ አቅራቢያ ፡ በአራት ፡ ወገን ፡ ሸመቁበት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ የአቤድም ፡ ልጅ ፡ ገዓል ፡ ወጥቶ ፡ በከተማዩቱ ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ቆመ ፤ አቢሜሌክና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ ከሸመቁበት ፡ ስፍራ ፡ ተነሡ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 36 ፤ ገዓልም ፡ ሕዝቡን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዜቡልን ፦ እንሆ ፥ ከተራራዎች ፡ ራስ ፡ ሕዝብ ፡ ይወርዳል ፡ አለው ። ዜቡልም ፦ ሰዎች ፡ የሚመስለውን ፡ የተራራዎችን ፡ ጥላ ፡ ታያለኽ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 37 ፤ ገዓልም ፡ ደግሞ ፦ እንሆ ፥ ሕዝብ ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ይወርዳል ፤ አንድም ፡ ወገን ፡ በምያንኒም ፡ በአድባሩ ፡ ዛፍ ፡ መንገድ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 38 ፤ ዜቡልም ፦ እንገዛለት ፡ ዘንድ ፡ አቢሜሌክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ያልኽበት ፡ አፍኽ ፡ አኹን ፡ የት ፡ አለ ፧ ይህ ፡ የናቅኸው ፡ ሕዝብ ፡ አይደለምን ፧ አኹንም ፡ ወጥተኽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 39 ፤ ገዓልም ፡ በሴኬም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ ከአቢሜሌክም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 40 ፤ አቢሜሌክም ፡ አሳደደው ፤ በፊቱም ፡ ሸሸ ፥ እስከ ፡ በሩም ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ ብዙዎች ፡ ተገሮድተው ፡ ወደቁ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 41 ፤ አቢሜሌክም ፡ በአሩማ ፡ ተቀመጠ ፤ ዜቡልም ፡ ገዓልንና ፡ ወንድሞቹን ፡ በሴኬም ፡ እንዳይኖሩ ፡ አሳደዳቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 42 ፤ በነጋውም ፡ ሕዝቡ ፡ ወደ ፡ ዕርሻ ፡ ወጡ ፤ አቢሜሌክም ፡ ሰማ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 43 ፤ ሕዝቡንም ፡ ወስዶ ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ ከፈላቸው ፥ በሜዳም ፡ ሸመቀ ፤ ተመለከተም ፥ እንሆም ፥ ሕዝቡ ፡ ከከተማ ፡ ወጡ ፥ ተነሣባቸውም ፡ መታቸውም ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 44 ፤ አቢሜሌክም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ወገኖች ፡ ተጣደፉ ፡ በከተማዩቱም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ቆሙ ፤ ኹለቱም ፡ ወገኖች ፡ በዕርሻው ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሮጡባቸው ፥ መቷቸውም ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 45 ፤ አቢሜሌክም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ኹሉ ፡ ከከተማዩቱ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ ከተማዩቱንም ፡ ይዞ ፡ በርሷ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ገደለ ፤ ከተማዩቱንም ፡ አፈረሰ ፥ ጨውም ፡ ዘራባት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 46 ፤ በሴኬምም ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደኤልብሪት ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 47 ፤ አቢሜሌክም ፡ በሴኬም ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ሰማ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 48 ፤ አቢሜሌክና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉትም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወደሰልሞን ፡ ተራራ ፡ ወጡ ፤ አቢሜሌክም ፡ በእጁ ፡ መጥረቢያ ፡ ወስዶ ፡ የዛፉን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ቈረጠ ፥ አንሥቶም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አደረገው ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፦ እኔ ፡ ሳደርግ ፡ ያያችኹትን ፥ እናንተም ፡ ፈጥናችኹ ፡ እኔ ፡ እንዳደረግኹ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 49 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የዛፉን ፡ ቅርንጫፎች ፡ ቈረጡ ፥ አቢሜሌክንም ፡ ተከትለው ፡ በምሽጉ ፡ ዙሪያ ፡ አኖሯቸው ፥ ምሽጉንም ፡ በላያቸው ፡ አቃጠሉት ፤ የሴኬምም ፡ ግንብ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሞቱ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 50 ፤ አቢሜሌክም ፡ ወደ ፡ ቴቤስ ፡ መጣ ፥ ቴቤስንም ፡ ከዖ ፡ ያዛት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 51 ፤ በከተማዩቱም ፡ ውስጥ ፡ ብርቱ ፡ ግንብ ፡ ነበረ ፥ የከተማዩቱም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ ወንዱና ፡ ሴቱ ፡ ኹሉ ፥ ወደዚያ ፡ ሸሹ ፤ ደጁንም ፡ በኋላቸው ፡ ዘጉ ፥ ወደግንቡም ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጡ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 52 ፤ አቢሜሌክም ፡ ወደ ፡ ግንቡ ፡ ቀርቦ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፥ በእሳትም ፡ ሊያቃጥለው ፡ ወደግንቡ ፡ ደጅ ፡ ደረሰ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 53 ፤ አንዲትም ፡ ሴት ፡ በአቢሜሌክ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የወፍጮ ፡ መጅ ፡ ጣለችበት ፥ ዐናቱንም ፡ ሰበረችው ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 54 ፤ ርሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬውን ፡ ጠርቶ ፦ እኔን ፦ ሴት ፡ ገደለችው ፡ እንዳይሉ ፡ ሰይፍኽን ፡ መዘኽ ፡ ግደለኝ ፡ አለው ፤ ጉልማሳውም ፡ ወጋው ፥ ሞተም ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 55 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ አቢሜሌክ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 56 ፤ እንዲሁ ፡ ሰባ ፡ ወንድሞቹን ፡ በመግደል ፡ አቢሜሌክ ፡ በአባቱ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ክፋት ፡ እግዚአብሔር ፡ መለሰበት ።

መሳ. ፡ 9 ፡ 57 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሴኬምን ፡ ሰዎች ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ መለሰባቸው ፤ የይሩበዓልም ፡ ልጅ ፡ የኢዮአታም ፡ ርግማን ፡ ደረሰባቸው ።

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

መሳ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ ከአቢሜሌክም ፡ በኋላ ፡ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ የኾነ ፡ የዱዲ ፡ ልጅ ፡ የፎሐ ፡ ልጅ ፡ ቶላ ፡ እስራኤልን ፡ ለማዳን ፡ ተነሣ ፤ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ባለችው ፡ በሳምር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ፤ ሞተም ፥ በሳምርም ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ገለዓዳዊው ፡ ኢያዕር ፡ ተነሣ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ በሠላሳ ፡ የአህያ ፡ ግልገሎች ፡ ይቀመጡ ፡ የነበሩ ፡ ሠላሳ ፡ ልጆችም ፡ ነበሩት ፤ ለእነርሱም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡ የተባሉ ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ያሉ ፡ ሠላሳ ፡ ከተማዎች ፡ ነበሯቸው ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ ኢያዕርም ፡ ሞተ ፥ በቃሞንም ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠሩ ፡ በዓሊምንና ፡ ዐስታሮትን ፡ የሶርያንም ፡ አማልክት ፥ የሲዶናንም ፡ አማልክት ፥ የሞዐብንም ፡ አማልክት ፥ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ አማልክት ፥ የፍልስጥኤማውያንንም ፡ አማልክት ፡ አመለኩ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ተዉ ፥ አላመለኩትምም ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ በፍልስጥኤማውያንና ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ በዚያም ፡ ዓመት ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሥቃይ ፡ አበዙባቸው ፤ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በአሞራውያን ፡ አገር ፡ በገለዓድ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ተጋፏቸው ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ከይሁዳ ፡ ከብንያምና ፡ ከኤፍሬም ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ ሊዋጋ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ፤ እስራኤልም ፡ እጅግ ፡ ተጨነቁ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፦ አምላካችንን ፡ ትተን ፡ በዓሊምን ፡ አምልከናልና ፥ አንተን ፡ በድለናል ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ አላቸው ፦ ግብጻውያን ፥ አሞራውያንም ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፥

መሳ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፥ ሲዶናውያንም ፥ ዐማሌቃውያንም ፥ ማዖናውያንም ፡ አላስጨነቋችኹምን ፧ ወደ ፡ እኔም ፡ ጮኻችኹ ፥ እኔም ፡ ከእጃቸው ፡ አዳንኋችኹ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 13 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ተዋችኹኝ ፡ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ አመለካችኹ ፤ ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ አላድናችኹም ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ ኼዳችኹም ፡ የመረጣችኋቸውን ፡ አማልክት ፡ ጥሩ ፤ እነርሱም ፡ በመከራችኹ ፡ ጊዜ ፡ ያድኗችኹ ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፦ እኛ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተናል ፤ አንተ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ አድርግብን ፡ ዛሬ ፡ ግን ፥ እባክኽ ፥ አድነን ፡ አሉት ።

መሳ. ፥ 10 ፥ 16 ፤ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ከመካከላቸው ፡ አስወገዱ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አመለኩ ፤ ነፍሱም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ጕስቍልና ፡ ዐዘነች ።

መሳ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ተሰብስበው ፡ በገለዓድ ፡ ሰፈሩ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተሰብስበው ፡ በምጽጳ ፡ ሰፈሩ ።

መሳ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ሕዝቡም ፥ የገለዓድ ፡ አለቃዎች ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ መዋጋት ፡ የሚገሥምር ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ በገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾናል ፡ አሉ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ገለዓዳዊውም ፡ ዮፍታሔ ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ የጋለሞታ ፡ ሴትም ፡ ልጅ ፡ ነበረ ። ገለዓድም ፡ ዮፍታሔን ፡ ወለደ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ የገለዓድም ፡ ሚስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችን ፡ ወለደችለት ፤ ልጆቿም ፡ ባደጉ ፡ ጊዜ ፡ ዮፍታሔን ፦ የልዩ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነኽና ፥ በአባታችን ፡ ቤት ፡ አትወርስም ፡ ብለው ፡ አሳደዱት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ዮፍታሔም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ፊት ፡ ሸሸ ፡ በጦብ ፡ ምድር ፡ ተቀመጠ ፤ ምናምንቴዎችም ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፡ ዮፍታሔን ፡ ተከተሉት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ከዚያም ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ይዋጉ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ በተዋጉ ፡ ጊዜ ፡ የገለዓድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፡ ከጦብ ፡ ምድር ፡ ለማምጣት ፡ ኼዱ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ዮፍታሔንም ፦ ና ፥ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እንድንዋጋ ፡ አለቃችን ፡ ኹን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ዮፍታሔም ፡ የገለዓድን ፡ ሽማግሌዎች ፦ የጠላችኹኝ ፡ ከአባቴም ፡ ቤት ፡ ያሳደዳችኹኝ ፡ እናንተ ፡ አይደላችኹምን ፧ አኹን ፡ በተጨነቃችኹ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣችኹ ፧ አላቸው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ የገለዓድም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፦ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንድትወጣ ፥ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እንድትዋጋ ፥ ስለዚህ ፡ አኹን ፡ ወዳንተ ፡ ተመልሰን ፡ መጣን ፤ በገለዓድም ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ አለቃችን ፡ ትኾናለኽ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ዮፍታሔም ፡ የገለዓድን ፡ ሽማግሌዎች ፦ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ አገሬ ፡ ብትመልሱኝ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ቢሰጣቸው ፥ እኔ ፡ አለቃችኹ ፡ እኾናለኹን ፧ አላቸው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ የገለዓድም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዮፍታሔን ፦ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ ምስክር ፡ ይኹን ፤ በርግጥ ፡ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ዮፍታሔም ፡ ከገለዓድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፥ ሕዝቡም ፡ በላያቸው ፡ ራስና ፡ አለቃ ፡ አደረጉት ፤ ዮፍታሔም ፡ ቃሉን ፡ ሹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በምጽጳ ፡ ተናገረ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ዮፍታሔም ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፦ አገሬን ፡ ለመውጋት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የምትመጣ ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ የዮፍታሔን ፡ መልክተኞች ፦ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከአርኖን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ያቦቅና ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ ምድሬን ፡ ስለ ፡ ወሰደ ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ በሰላም ፡ መልሱልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ዮፍታሔም ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ መልክተኞችን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ላከ ፥

መሳ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ እንዲህም ፡ አለው ፦ ዮፍታሔ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤል ፡ የሞዐብን ፡ ምድር ፡ የዐሞንንም ፡

ልጆች ፡ ምድር ፡ አልወሰደም ፤

መሳ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከግብጽ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ እስራኤልም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ቀይ ፡ ባሕር ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ቃዴስም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥

መሳ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ እስራኤል ፡ ወደኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፦ በምድርኽ ፡ እንዳልፍ ፥ እባክኽ ፥ ፍቀድልኝ ፡ ብሎ ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፤ የኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ አልሰማም ። እንዲሁም ፡ ወደሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ አልፈቀደም ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ እስራኤልም ፡ በቃዴስ ፡ ተቀመጠ ። በምድረ ፡ በዳም ፡ በኩል ፡ ኼዱ ፥ የኤዶምያስንና ፡ የሞዐብንም ፡ ምድር ፡ ዞሩ ፤ ከሞዐብ ፡ ምድርም ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ መጡ ፡ በአርኖንም ፡ ማዶ ፡ ሰፈሩ ፤ አርኖንም ፡ የሞዐብ ፡ ድንበር ፡ ነበረና ፡ የሞዐብን ፡ ድንበር ፡ አላለፉም ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ እስራኤልም ፡ ወደ ፡ አሞራዊው ፡ ወደሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሴዎን ፡ መልክተኞችን ፡ ላከ ፤ እስራኤልም ፦ በምድርኽ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ስፍራችን ፥ እባክኽ ፥ አሳልፈን ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ሴዎንም ፡ እስራኤል ፡ በድንበሩ ፡ እንዲያልፍ ፡ አላመነውም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሴዎን ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ በያሀጽም ፡ ሰፈረ ፥ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሴዎንና ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፥ መቷቸውም ፤ እስራኤልም ፡ በዚያ ፡ ምድር ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩትን ፡ የአሞራውያንን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ወረሰ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ከአርኖንም ፡ እስከ ፡ ያቦቅ ፡ ድረስ ፡ ከምድረ ፡ በዳውም ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ የአሞራውያንን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ወረሱ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ አሞራውያንን ፡ አስወገደ ፤ አንተም ፡ ምድሩን ፡ ትወርሳለኽን ፧

መሳ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ አምላክኽ ፡ ካሞሽ ፡ የሚሰጥኽን ፡ አትወርስምን ፧ እኛም ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፊታችን ፡ ያስወጣቸውን ፡ የእነርሱን ፡ ምድር ፡ እንወርሳለን ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ወይስ ፡ ከሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ከሴፎር ፡ ልጅ ፡ ከባላቅ ፡ አንተ ፡ ትሻላለኽን ፧ በእውኑ ፡ ርሱ ፡ እስራኤልን ፡ ከቶ ፡ ተጣላውን ፧ ወይስ ፡ ተዋጋውን ፧

መሳ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ እስራኤልም ፡ በሐሴቦንና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዐሮዔርና ፡ በመንደሮቿ ፥ በአርኖንም ፡ አቅራቢያ ፡ ባሉት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ ተቀምጦ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልወሰዳችኋቸውም ፡ ነበር ፧

መሳ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ እኔ ፡ አልበደልኹኽም ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እየተዋጋኽ ፡ በድለኸኛል ፤ ፈራጁ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ዛሬ ፡ ይፍረድ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዮፍታሔ ፡ የላከበትን ፡ ቃል ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ አልሰማም ፦

መሳ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በዮፍታሔ ፡ ላይ ፡ መጣ ፤ ርሱም ፡ ገለዓድንና ፡ ምናሴን ፡ ዐለፈ ፥ በገለዓድም ፡ ያለውን ፡ ምጽጻን ፡ ዐለፈ ፥ ከምጽጻም ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዐለፈ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ዮፍታሔም ፦ በእውነት ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ በእጄ ፡ አሳልፈኽ ፡ ብትሰጠኝ ፥

መሳ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ በደኅና ፡ በተመለስኹ ፡ ጊዜ ፥ ሊገናኘኝ ፡ ከቤቴ ፡ ደጅ ፡ የሚወጣው ፡ ማንኛውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይኾናል ፤ ለሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርበዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡

ተሳለ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ ዮፍታሔም ፡ ሊዋጋቸው ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዐለፈ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ ከዐሮዔርም ፡ እስከ ፡ ሚኒትና ፡ እስከ ፡ አቤልክራሚም (127) ፡ ድረስ ፡ ኻያ ፡ ከተማዎችን ፡ በታላቅ ፡ አገዳደል ፡ መታቸው ። የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ተዋረዱ ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ ዮፍታሔም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጣ ፥ እንሆም ፡ ልጁ ፡ ከበሮ ፡ ይዛ ፡ እየዘፈነች ፡ ልትገናኘው ፡ ወጣች ፤ ለርሱም ፡ አንዲት ፡ ብቻ ፡ ነበረች ፤ ከርሷም ፡ በቀር ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አልነበረውም ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ርሷንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፦ አወይ ፡ ልጄ ፡ ሆይ! ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አፌን ፡ ከፍቻለኹና ፥ ከዚያውም ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ አልችልምና ፡ በጣም ፡ አዋረድኸኝ ፡ አስጨነቅኸኝም ፡ አላት ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ርሷም ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ አፍኽን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከከፈትኽ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶችኽ ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ተበቅሎልኻልና ፥ በአፍኽ ፡ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ አድርግብኝ ፡ አለችው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 37 ፤ አባቷንም ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ይደረግልኝ ፤ ከዚህ ፡ ኼጄ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እንድወጣና ፡ እንድወርድ ፥ ከባልንጀራዎቼም ፡ ጋራ ፡ ለድንግልናዬ ፡ እንዳለቅስ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ አሰናብተኝ ፡ አለችው ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ ኺጂ ፡ አለ ። ኹለት ፡ ወርም ፡ አሰናበታት ፤ ከባልንጀራዎቿም ፡ ጋራ ፡ ኼደች ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ ለድንግልናዋ ፡ አለቀሰች ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 39 ፤ ኹለትም ፡ ወር ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አባቷ ፡ ተመለሰች ፥ እንደ ፡ ተሳለውም ፡ ስእለት ፡ አደረገባት ፤ ርሷም ፡ ወንድ ፡ አላወቀችም ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 11 ፡ 40 ፤ የእስራኤልም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በዓመት ፡ በዓመቱ ፡ እየኼዱ ፡ የገለዓዳዊውን ፡ የዮፍታሔን ፡ ልጅ ፡ በዓመት ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ሙሾ ፡ እንዲያወጡ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ኾነ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

መሳ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ የኤፍሬም ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ፥ ወደ ፡ ጻፎንም ፡ ተሻግረው ፡ ዮፍታሔን ፦ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ስታልፍ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንድንኼድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠራኸንም ፧ ቤትኽን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ እናቃጥለዋለን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ዮፍታሔም ፦ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለኔና ፡ ለሕዝቤ ፡ ጽኑ ፡ ጠብ ፡ ነበረን ፤ በጠራኋችኹም ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ አላዳናችኹኝም ።

መሳ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ እንዳላዳናችኹኝም ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሴን ፡ በእጄ ፡ አድርጌ ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ዐለፍኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ ለምንስ ፡ ዛሬ ፡ ልትወጉኝ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣችኹ ፧ አላቸው ።

መሳ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ዮፍታሔም ፡ የገለዓድን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ከኤፍሬምም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ ኤፍሬምም ፦ ገለዓዳውያን ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ መካከል ፡ የተቀመጣችኹት ፡ ከኤፍሬም ፡ ሸሽታችኹ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ አሉ ፡ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ኤፍሬምን ፡ መቱ ።

መሳ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ገለዓዳውያንም ፡ ኤፍሬም ፡ የሚያልፍበትን ፡ የዮርዳኖስን ፡ መሻገሪያ ፡ ያዙባቸው ፤ የሸሸም ፡

---

127 ዐጸደ ፡ ወይን ።

የኤፍሬም ፡ ሰው ፦ ልለፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፥ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፦ አንተ ፡ ኤፍሬማዊ ፡
ነኽን ፧ አሉት ፤ ርሱም ፦ አይደለኹም ፡ ቢል ፥

መሳ. ፥ 12 ፥ 6 ፤ እነርሱ ፦ አኹን ፡ ሺቦሌት ፡ በል ፡ አሉት ፤ ርሱም ፡ አጥርቶ ፡ መናገር ፡
አልቻለምና ፦ ሚቦሌት ፡ አለ ፤ ይዘውም ፡ በዮርዳኖስ ፡ መሻገሪያ ፡ ዐረዱት ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ከኤፍሬም ፡ አርባ ፡
ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ወደቁ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 7 ፤ ዮፍታሔም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ። ገለዓዳዊውም ፡ ዮፍታሔ ፡
ሞተ ፥ ከገለዓድም ፡ ከተማዎች ፡ በአንዲቱ ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 8 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቤተ ፡ ልሔሙ ፡ ኢብጻን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ ኾነ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 9 ፤ ሠላሳም ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ ሠላሳ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ሠላሳ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹንም ፡
ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ዳረ ፤ ለወንዶች ፡ ልጆቹም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ አመጣ ። በእስራኤልም ፡ ላይ ፡
ሰባት ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 10 ፤ ኢብጻንም ፡ ሞተ ፥ በቤተ ፡ ልሔምም ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 11 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ዛብሎናዊው ፡ ኤሎም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ ኾነ ፤ ርሱም ፡ በእስራኤል ፡
ላይ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 12 ፤ ዛብሎናዊውም ፡ ኤሎም ፡ ሞተ ፥ በዛብሎንም ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በኤሎም ፡ ተቀበረ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 13 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የጺርዓቶናዊው ፡ የሂሌል ፡ ልጅ ፡ ዐብዶን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ ኾነ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 14 ፤ አርባም ፡ ልጆች ፡ ሠላሳም ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ በሰባም ፡ አህያ ፡ ግልገሎች ፡ ላይ ፡
ይቀመጡ ፡ ነበር ። በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

መሳ. ፥ 12 ፥ 15 ፤ የጺርዓቶናዊውም ፡ የሂሌል ፡ ልጅ ፡ ዐብዶን ፡ ሞተ ፥ በተራራማውም ፡ በዐማሌቃውያን ፡ ምድር ፡
በኤፍሬም ፡ ባለችው ፡ በጺርዓቶን ፡ ተቀበረ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡
ሠሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 2 ፤ ከዳን ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ማኑሄ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ የጾርዓ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ሚስቱም ፡ መካን ፡
ነበረች ፥ ልጅም ፡ አልወለደችም ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ለሴቲቱ ፡ ተገልጦ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ እንሆ ፥ አንቺ ፡ መካን ፡
ነሽ ፥ ልጅም ፡ አልወለድሽም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ትጸንሻለሽ ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልጃለሽ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 4 ፤ አኹንም ፡ ተጠንቀቂ ፤ የወይን ፡ ጠጅን ፡ የሚያሰክርም ፡ ነገር ፡ አትጠጪ ፥ ርኩስም ፡ ነገር ፡
አትብዪ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 5 ፤ እንሆ ፥ ትፀንሻለሽ ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልጃለሽ ፤ ልጁም ፡ ከእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡
ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ ናዝራዊ ፡ ይኾናልና ፥ በራሱ ፡ ላይ ፡ ምላጭ ፡ አይድረስበት ፤ ርሱም ፡ እስራኤልን ፡
ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ ማዳን ፡ ይዠምራል ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 6 ፤ ሴቲቱም ፡ ወደ ፡ ባሏ ፡ መጥታ ፦ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡

መጣ ፥ መልኩም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እጅግ ፡ የሚያስደነግጥ ፡ ነበረ ፤ ከወዴትም ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አልጠየቅኹትም ፥ ርሱም ፡ ስሙን ፡ አልነገረኝም ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 7 ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ ትፀንሻለሽ ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልጃለሽ ፤ ልጁም ፡ ከእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየ ፡ ናዝራዊ ፡ ይኾናልና ፥ አኹን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያሰክርም ፡ ነገር ፡ አትጠጪ ፥ ርኩስም ፡ ነገር ፡ አትብዩ ፡ አለኝ ፡ ብላ ፡ ተናገረች ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 8 ፤ ማኑሄም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የላክኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፥ እባክኽ ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ይምጣ ፤ ለሚወለደውም ፡ ልጅ ፡ ምን ፡ እንድናደርግ ፡ ያስገንዝበን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመነ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የማኑሄን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ለሴቲቱ ፡ በዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጣ ፡ ሳለች ፡ ተገለጠላት ፤ ባሏ ፡ ማኑሄ ፡ ግን ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ አልነበረም ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 10 ፤ ሴቲቱም ፡ ፈጥና ፡ ሮጠች ፡ ለባሏም ፦ እንሆ ፥ በቀደም ፡ ዕለት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የመጣው ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ተገለጠልኝ ፡ ብላ ፡ ነገረችው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 11 ፤ ማኑሄም ፡ ተነሥቶ ፡ ሚስቱን ፡ ተከተለ ፥ ወደ ፡ ሰውዮውም ፡ መጥቶ ፦ ከዚች ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ የተነጋገርኽ ፡ አንተ ፡ ነኽን ∴ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 12 ፤ ማኑሄም ፦ ቃልኽ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የልጁ ፡ ሥርዐት ፡ ምንድር ፡ ነው ∴ የምናደርግለትስ ፡ ምንድር ፡ ነው ∴ አለው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ማኑሄን ፦ ሴቲቱ ፡ ከነገርኋት ፡ ኹሉ ፡ ትጠንቀቅ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 14 ፤ ከወይንም ፡ ከሚወጣው ፡ ኹሉ ፡ አትብላ ፥ የወይን ፡ ጠጅንም ፡ የሚያሰክርንም ፡ ነገር ፡ አትጠጣ ፥ ርኩስም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አትብላ ፤ ያዘዝኋትን ፡ ኹሉ ፡ ትጠብቅ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 15 ፤ ማኑሄም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ እስክናዘጋጅልኽ ፡ ድረስ ፥ እባክኽ ፥ ቈይ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ማኑሄን ፦ አንተ ፡ የግድ ፡ ብትለኝ ፡ መብልኽን ፡ አልበላም ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ማዘጋጀት ፡ ብትወድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርበው ፡ አለው ። ማኑሄም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መኾኑን ፡ አላወቀም ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 17 ፤ ማኑሄም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ ነገርኽ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንድናከብርኽ ፡ ስምኽ ፡ ማን ፡ ነው ∴ አለው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 18 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፦ ስሜ ፡ ድንቅ ፡ ነውና ፥ ለምን ፡ ትጠይቃለኽ ∴ አለው ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 19 ፤ ማኑሄም ፡ የፍየሉን ፡ ጠቦትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ወስዶ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቀረበው ። መልአኩም ፡ ተኣምራት ፡ አደረገ ፥ ማኑሄና ፡ ሚስቱም ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 20 ፤ ነበልባሉም ፡ ከመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በመሠዊያው ፡ ነበልባል ፡ ውስጥ ፡ ዐረገ ፤ ማኑሄና ፡ ሚስቱም ፡ ተመለከቱ ፥ በምድርም ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፉ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 21 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ዳግመኛ ፡ ላማኑሄና ፡ ለሚስቱ ፡ አልተገለጠም ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ማኑሄ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መኾኑን ፡ ዐወቀ ።

መሳ. ፥ 13 ፥ 22 ፤ ማኑሄም ፡ ሚስቱን ፦ እግዚአብሔርን ፡ አይተናልና ፥ ሞት ፡ እንሞታለን ፡ አላት ።

መሳ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ሚስቱም ፦ እግዚአብሔርስ ፡ ሊገድለን ፡ ቢወድ ፡ ኖሮ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ከእጃችን ፡ ባልተቀበለን ፥ ይህንም ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ባላሳየን ፥ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገርም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባላስታወቀን ፡ ነበር ፡ አለችው ።

መሳ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ሴቲቱም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፥ ስሙንም ፡ ሶምሶን ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ ልጁም ፡ አደገ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ባረከው ።

መሳ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በጾርዓና ፡ በኤሽታኦል ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በዳን ፡ ሰፈር ፡ ውስጥ ፡ ሊያነቃቃው ፡ ገመረ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ ሶምሶንም ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ወረደ ፥ በተምናም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ልጆች ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አየ ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ ወጥቶም ፡ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ። በተምና ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ልጆች ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አይቻለኹ ፤ አኹንም ፡ ርሷን ፡ አጋቡኝ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ አባቱና ፡ እናቱም ፦ ካልተገረዙት ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ሚስት ፡ ለማግባት ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ከወንድሞችኽ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ከሕዝቤም ፡ ዅሉ ፡ መካከል ፡ ሴት ፡ የለምን ፧ አሉት ። ሶምሶንም ፡ አባቱን ፦ ለዐይኔ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሠኝታኛለችና ፡ ርሷን ፡ አጋባኝ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ምክንያት ፡ ይፈልግ ፡ ነበርና ፥ ነገሩ ፡ ከርሱ ፡ ኾነ ፤ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ግን ፡ አላወቁም ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ገዢዎች ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ሶምሶንም ፡ አባቱና ፡ እናቱም ፡ ወደ ፡ ተምና ፡ ወረዱ ፥ በተምናም ፡ ወዳለው ፡ ወደወይኑ ፡ ስፍራ ፡ መጡ ፤ እንሆም ፥ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ እያገሣ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ደረሰ ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ ወረደ ፤ ጠቦትን ፡ እንደሚቈራርጥ ፡ በእጁ ፡ ምንም ፡ ሳይኖር ፡ ቈራረጠው ፤ ያደረገውንም ፡ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ፡ አልነገረም ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ወርዶም ፡ ከሴቲቱ ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ ፤ እጅግም ፡ ደስ ፡ አሠኘችው ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ከጥቂትም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሊያገባት ፡ ተመለሰ ፥ የአንበሳውንም ፡ ሬሳ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፤ እንሆም ፥ በአንበሳው ፡ ሬሳ ፡ ውስጥ ፡ ንብ ፡ ሰፍሮበት ፡ ነበር ፥ ማርም ፡ ነበረበት ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ በእጁም ፡ ወስዶ ፡ መንገድ ፡ ለመንገድ ፡ እየበላ ፡ ኼደ ፤ ወደ ፡ አባቱና ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ መጣ ፥ ማሩንም ፡ ሰጣቸው ፥ እነርሱም ፡ በሉ ፤ ማሩንም ፡ ከአንበሳው ፡ ሬሳ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ወሰደ ፡ አልነገራቸውም ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ አባቱም ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ ወረደ ፤ ጕበዞችም ፡ እንዲህ ፡ ያደርጉ ፡ ነበርና ፥ ሶምሶን ፡ በዚያ ፡ በዓል ፡ አደረገ ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎች ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ሰጡት ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ሶምሶንም ፦ እንቆቅልሽ ፡ ልስጣችኹ ፤ በሰባቱም ፡ በበዓሉ ፡ ቀኖች ፡ ውስጥ ፡ ፈታችኹ ፡ ብትነግሩኝ ፥ ሠላሳ ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስና ፡ ሠላሳ ፡ ልውጥ ፡ ልብስ ፡ እሰጣችኋለኹ ፤

መሳ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ መፍታትም ፡ ባትችሉ ፡ ሠላሳ ፡ የበፍታ ፡ ቀሚስና ፡ ሠላሳ ፡ ልውጥ ፡ ልብስ ፡ ትሰጡኛላችኹ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፦ እንድንሰማው ፡ እንቆቅልሽኽን ፡ ንገረን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ ከበላተኛው ፡ ውስጥ ፡ መብል ፡ ወጣ ፥ ከብርቱም ፡ ውስጥ ፡ ጥፍጥ ፡ ወጣ ፡ አላቸው ። ሦስት ፡ ቀንም ፡ እንቆቅልሹን ፡ መተርጐም ፡ አልቻሉም ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ የሶምሶንን ፡ ሚስት ፦ እንቆቅልሹን ፡ እንዲነግረን ፡ ባልሽን ፡ ሸንግዪው ፥ አለዚያም ፡ እንቺንና ፡ የአባትሽን ፡ ቤት ፡ በእሳት ፡ እናቃጥላለን ፤ ወደዚህ ፡ ጠራችኹን ፡ ልትገፉን ፡ ነውን ፧ አሏት ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ የሶምሶንም ፡ ሚስት ፡ በፊቱ ፡ እያለቀሰች ፦ በእውነት ፡ ጠልተኸኛል ፥ ኩቶም ፡ አትወደኝም ፤ ለሕዝቤ ፡ ልጆች ፡ እንቆቅልሽ ፡ ሰጥተኻቸዋልና ፥ ትርጓሜውንም ፡ አልነገርኸኝም ፡ አለችው ። ርሱም ፦ እንሆ ፥ ለአባቴና ፡ ለእናቴ ፡ አልነገርኋቸውም ፥ ለአንቺ ፡ እነግርሻለኹን ፧ አላት ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ሰባቱንም ፡ የበዓል ፡ ቀን ፡ በፊቱ ፡ አለቀሰች ፤ ርሷም ፡ ነዝንዛዋለችና ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ነገራት ። ትርጓሜውንም ፡ ለሕዝቧ ፡ ልጆች ፡ ነገረች ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ፀሓይ ፡ ሳትገባ ፡ የከተማዩቱ ፡ ሰዎች ፦ ከማር ፡ የሚጣፍጥ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ከአንበሳስ ፡ የሚበረታ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሉት ። ርሱም ፦ በጥጃዬ ፡ ባላረሳችኹ ፡ የእንቆቅልሼን ፡ ትርጓሜ ፡ ባላወቃችኹ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በላዩ ፡ በኀይል ፡ ወረደ ፤ ወደ ፡ አስቀሎናም ፡ ወረደ ፥ ከዚያም ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎችን ፡ ገደለ ፥ ልብሳቸውንም ፡ ወስዶ ፡ እንቆቅልሹን ፡ ለፈቱት ፡ ሰዎች ፡ ሰጠ ። ቍጣውም ፡ ነደደ ፥ ወዳባቱም ፡ ቤት ፡ ወጣ ።

መሳ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ የሶምሶን ፡ ሚስት ፡ ግን ፡ ከተባበሩት ፡ ከሚዜዎቹ ፡ ለአንደኛው ፡ ኾነች ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በስንዴ ፡ መከር ፡ ጊዜ ፡ ሶምሶን ፡ የፍየል ፡ ጠቦት ፡ ይዞ ፡ ሚስቱን ፡ ሊጠይቅ ፡ ኼደና ፦ ወደጫጉላ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ሚስቴ ፡ ልግባ ፡ አለ ፤ አባቷ ፡ ግን ፡ እንዳይገባ ፡ ከለከለው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ አባቷም ፦ ፈጽመኽ ፡ የጠላኻት ፡ መስሎኝ ፡ ለሚዜኽ ፡ አጋባኋት ፤ ታናሽ ፡ እኅቷ ፡ ከርሷ ፡ ይልቅ ፡ የተዋበች ፡ አይደለችምን ፧ እባክኽ ፥ በርሷ ፡ ፋንታ ፡ አግባት ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ሶምሶንም ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ባደርግ ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ሶምሶንም ፡ ኼዶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ቀበሮዎች ፡ ያዘ ፤ ችቦም ፡ ወስዶ ፡ ኹለት ፡ ኹለቱንም ፡ ቀበሮዎች ፡ በኻራታቸው ፡ አሰረ ፥ በኹለቱም ፡ ኻራቶች ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ችቦ ፡ አደረገ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ችቦውንም ፡ አንድዶ ፡ በቆመው ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እኽል ፡ መካከል ፡ ሰደዳቸው ፤ ነዶውንም ፡ የቆመውንም ፡ እኽል ፡ ወይኑንም ፡ ወይራውንም ፡ አቃጠለ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፦ ይህን ፡ ያደረገው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሉ ። እነርሱም ፦ ሚስቱን ፡ ወስዶ ፡ ለሚዜው ፡ አጋብቶበታልና ፥ የተምናዊው ፡ ዐማች ፡ ሶምሶን ፡ ነው ፡ አሉ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወጥተው ፡ ሴቲቱንና ፡ አባቷን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ሶምሶንም ፦ እናንተ ፡ እንዲሁ ፡ ብታደርጉ ፡ እኔ ፡ እበቀላችኋለኹ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዐርፋለኹ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ ጭን ፡ ጭናቸውን ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ አገዳደል ፡ መታቸው ፤ ወርዶም ፡ በኤጣም ፡ አለት ፡

ባለው ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወጡ ፥ በይሁዳም ፡ ሰፈሩ ፥ በሌሒ ፡ ላይም ፡ ተበታትነው ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡ የወጣችኹት ፡ ለምንድር ፡
ነው ፧ አሉ ። እነርሱም ፦ ሶምሶንን ፡ ልናስር ፥ እንዳደረገብንም ፡ ልናደርግበት ፡ መጥተናል ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ከይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉ ፡ በኤጣም ፡ አለት ፡ ወዳለው ፡ ዋሻ ፡ ወርደው ፡
ሶምሶንን ፦ ገዢዎቻችን ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አታውቅምን ፧ ያደረግኽብን ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ አሉት ። ርሱም ፦ እንዳደረጉብኝ ፡ እንዲሁ ፡ አደረግኹባቸው ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ አስረን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፈን ፡ ልንሰጥኽ ፡ መጥተናል ፡
አሉት ። ሶምሶንም ፦ እናንተ ፡ እንዳትገድሉኝ ፡ ማሉልኝ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፦ አስረን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፈን ፡ እንሰጥኻለን ፡ እንጂ ፡ አንገድልኽም ፡ ብለው ፡
ተናገሩት ። በኹለትም ፡ ዐዲስ ፡ ገመድ ፡ አስረው ፡ ከአለቱ ፡ ውስጥ ፡ አወጡት ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሌሒ ፡ በመጣ ፡ ጊዜም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ እልል ፡ እያሉ ፡
ተገናኙት ። የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በኀይል ፡ ወረደበት ፤ ክንዱም ፡ የታሰረበት ፡ ገመድ ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተበላ ፡
እንደ ፡ ተልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ ኾነ ፥ ማሰሪያዎቹም ፡ ከእጁ ፡ ወደቁ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ዐዲስም ፡ የአህያ ፡ መንጋጋ ፡ አገኘ ፥ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ወሰደው ፥ በርሱም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡
ሰው ፡ ገደለ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ሶምሶንም ፦ በአህያ ፡ መንጋጋ ፡ ክምር ፡ በክምር ፡ ላይ ፡ አድርጌያቸዋለኹ ፤ በአህያ ፡ መንጋጋ ፡
አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ገድያለኹ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ መናገሩንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ መንጋጋውን ፡ ከእጁ ፡ ጣለ ፤ የዚያንም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡
ራማትሌሒ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ርሱም ፡ እጅግ ፡ ተጠምቶ ፡ ነበርና ፦ አንተ ፡ ይህችን ፡ ታላቅ ፡ ማዳን ፡ በባሪያኽ ፡ እጅ ፡
ሰጥተኻል ፤ አኹንም ፡ በጥም ፡ እሞታለኹ ፥ ባልተገረዙትም ፡ እጅ ፡ እወድቃለኹ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሌሒ ፡ ያለውን ፡ ዐዘቅት ፡ ሠነጠቀ ፥ ከርሱም ፡ ውሃ ፡ ወጣ ፤ ርሱም ፡
ጠጣ ፥ ነፍሱም ፡ ተመለሰች ፥ ተጠናከረም ። ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ቦታ ፡ ስም ፡ ዐይንሀቆሬ ([128]) ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ ይህም ፡
እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በሌሒ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ በፍልስጥኤማውያንም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ ሶምሶንም ፡ ወደ ፡ ጋዛ ፡ ኼደ ፥ በዚያም ፡ ጋለሞታ ፡ ሴት ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገባ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ የጋዛ ፡ ሰዎችም ፡ ሶምሶን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ሰሙ ፥ ከበቡትም ፥ ሌሊቱንም ፡
ኹሉ ፡ በከተማዩቱ ፡ በር ፡ ሸመቁበት ። ማለዳ ፡ እንገድለዋለን ፡ ብለውም ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ በዝምታ ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ሶምሶንም ፡ እስከ ፡ እኩለ ፡ ሌሊት ፡ ተኛ ፤ እኩለ ፡ ሌሊትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ተነሥቶ ፡
የከተማዩቱን ፡ በር ፡ መዝጊያ ፡ ያዘ ፥ ከኹለቱ ፡ መቃኖችና ፡ ከመወርወሪያውም ፡ ጋራ ፡ ነቀለው ፥ በትከሻውም ፡ ላይ ፡

128 ዕብ. ፡ ዐይን ፡ ሀቆሬ ፡ (የጫኺው ፡ ምንጭ) ።

አደረገ ፥ በኬብሮንም ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተሸክሞት ፡ ወጣ ፡ በዚያም ፡ ጣለው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 4 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሶሬቅ ፡ ሸለቆ ፡ የነበረች ፡ ደሊላ (129) ፡ የተባለች ፡ አንዲት ፡ ሴትን ፡ ወደደ ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 5 ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ መኳንንት ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ወጥተው ፦ ርሱን ፡ ሽንግለሽ ፡ በርሱ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ኀይል ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እኛስ ፡ ርሱን ፡ ለማዋረድ ፡ እናስረው ፡ ዘንድ ፡ የምናሸንፈው ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቂ ፤ እኛም ፡ እያንዳንዳችን ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፡ እንሰጥሻለን ፡ አሏት ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 6 ፤ ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፦ ታላቅ ፡ ኀይልኽ ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እንድትዋረድስ ፡ የምትታሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እባክኽ ፥ ንገረኝ ፡ አለችው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 7 ፤ ሶምሶንም ፦ በሰባት ፡ ባልደረቀ ፡ በርጥብ ፡ ጠፍር ፡ ቢያስሩኝ ፥ እደክማለኹ ፡ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እኾናለኹ ፡ አላት ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 8 ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ መኳንንት ፡ ሰባት ፡ ያልደረቀ ፡ ርጥብ ፡ ጠፍር ፡ አመጡላት ፥ በርሱም ፡ አሰረችው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 9 ፤ በጓዳዋም ፡ ውስጥ ፡ ሰዎች ፡ ተደብቀው ፡ ነበር ። ርሷም ፦ ሶምሶን ፡ ሆይ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብኽ ፡ አለችው ። ርሱም ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ፈትል ፡ እሳት ፡ በሸተተው ፡ ጊዜ ፡ እንዲበጠስ ፡ ጠፍሩን ፡ በጣጠሰው ፤ ኀይሉም ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልታወቀም ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 10 ፤ ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፦ እንሆ ፥ አታለልኸኝ ፥ የነገርኸኝም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ የምትታሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እባክኽ ፥ ንገረኝ ፡ አለችው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 11 ፤ ርሱም ፦ ሥራ ፡ ባልተሠራበት ፡ በዐዲስ ፡ ገመድ ፡ ቢያስሩኝ ፥ እደክማለኹ ፥ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እኾናለኹ ፡ አላት ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 12 ፤ ደሊላም ፡ ዐዲስ ፡ ገመድ ፡ ወስዳ ፡ በርሱ ፡ አሰረችው ፤ በጓዳዋም ፡ የተደበቁ ፡ ሰዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ። ርሷም ፦ ሶምሶን ፡ ሆይ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብኽ ፡ አለችው ። ገመዱንም ፡ ከክንዱ ፡ እንደ ፡ ፈትል ፡ በጣጠሰው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 13 ፤ ደሊላም ፡ ሶምሶንን ፦ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ አታለልኸኝ ፥ የነገርኸኝም ፡ ሐሰት ፡ ነው ፤ የምትታሰርበት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ንገረኝ ፡ አለችው ። ርሱም ፦ የራሴን ፡ ጠጕር ፡ ሰባቱን ፡ ጕንጕን ፡ ከድር ፡ ጋራ ፡ ብትጐነጉኚው ፥ በችካልም ፡ ብትቸክዪው ፥ እደክማለኹ ፥ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡ እኾናለኹ ፡ አላት ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 14 ፤ ሶምሶንም ፡ በተኛ ፡ ጊዜ ፥ ደሊላ ፡ የራሱን ፡ ጠጕር ፣ ሰባቱን ፡ ጕንጕን ፣ ከድሩ ፡ ጋራ ፡ ጐነጐነችው ፥ በችካልም ፡ ቸከለችውና ፦ ሶምሶን ፡ ሆይ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብኽ ፡ አለችው ። ከእንቅልፉም ፡ ነቃ ፥ ችካሉንም ፡ ከነቄንዳላው ፡ ድሩንም ፡ ነቀለ ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 15 ፤ ርሷም ፦ አንተ ፦ እወድሻለኹ ፡ እንዴት ፡ ትለኛለኽ ፥ ልብኽ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አይደለም ፧ ስታታልለኝ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜኽ ፡ ነው ፥ ታላቅ ፡ ኀይልኽም ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልነገርኸኝም ፡ አለችው ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 16 ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ በቃሏ ፡ ነዘነዘችው ፡ አስቸገረችውም ፥ ነፍሱም ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ተጨነቀች ።

መሳ. ፥ 16 ፥ 17 ፤ ርሱም ፦ ከእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ገዖሬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተለየኹ ፡ ነኝና ፥ በራሴ ፡ ላይ ፡ ምላጭ ፡ አልደረሰም ፤ የራሴንም ፡ ጠጕር ፡ ብላጭ ፡ ኀይሌ ፡ ከእኔ ፡ ይኼዳል ፥ እደክማለኹም ፥ እንደ ፡ ሌላም ፡ ሰው ፡

---

129 ዕብ. ፥ ድሊላ ፡ (ቀጭን ፡ ክር ፥ ገመድ ፥ ፈትል ፥ ወይም ፡ ሥሥ ፣ ረቂቅ ፡ መንዲል ፥ የጠጕር ፡ ማሰሪያ ፤ ከ..ወ.ክ.350) ።

እኾናለኹ ፡ ብሎ ፡ የልቡን ፡ ዥሉ ፡ ገለጠላት ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ደሊላም ፡ የልቡን ፡ ዥሉ ፡ እንደ ፡ ገለጠላት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፦ የልቡን ፡ ዥሉ ፡ ገልጦልኛልና ፥ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ኑ ፡ ብላ ፡ ላከችና ፥ የፍልስጥኤማውያንን ፡ መኳንንት ፡ ጠራች ። የፍልስጥኤማውያን ፡ መኳንንትም ፡ ብሩን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ መጡ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ርሷም ፡ በጕልበቷ ፡ ላይ ፡ አስተኛችው ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ጠራች ፥ ርሱም ፡ ሰባቱን ፡ የራሱን ፡ ጕንጕን ፡ ላጨው ። ልታዋርደውም ፡ ዠመረች ፥ ኀይሉም ፡ ከርሱ ፡ ኼደ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ርሷም ፦ ሶምሶን ፡ ሆይ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ መጡብኽ ፡ አለችው ። ከእንቅልፉም ፡ ነቅቶ ፦ እወጣለኹ ፡ እንደ ፡ ወትሮውም ፡ ጊዜ ፡ አደርጋለኹ ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ እንደ ፡ ተለየው ፡ አላወቀም ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ይዘው ፡ ዐይኖቹን ፡ አወጡት ፤ ወደ ፡ ጋዛም ፡ አምጥተው ፡ በናስ ፡ ሰንሰለት ፡ አሰሩት ፤ በግዞትም ፡ ኾኖ ፡ እኽል ፡ ይፈጭ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ የራሱም ፡ ጠጕር ፡ ከላጨት ፡ በኋላ ፡ ያድግ ፡ ዠመር ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ የፍልስጥኤምም ፡ መኳንንት ፦ አምላካችን ፡ ጠላታችንን ፡ ሶምሶንን ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠን ፡ እያሉ ፡ ለአምላካቸው ፡ ለዳጎን ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕት ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፥ ደስም ፡ ይላቸው ፡ ዘንድ ፡ ተሰበሰቡ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፦ ምድራችንን ፡ ያጠፋውን ፥ ከእኛም ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ የገደለውን ፡ ጠላታችንን ፡ አምላካችን ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠን ፡ እያሉ ፡ አምላካቸውን ፡ አመሰገኑ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ልባቸውንም ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፦ በፊታችን ፡ እንዲጫወት ፡ ሶምሶንን ፡ ጥሩት ፡ አሉ ። ሶምሶንንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ ጠሩት ፥ በፊታቸውም ፡ ተጫወተ ፤ ተዘባበቱበትም ፥ በምሰሶና ፡ በምሰሶም ፡ መካከል ፡ አቆሙት ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ሶምሶንም ፡ እጁን ፡ የያዘውን ፡ ብላቴና ፦ ቤቱን ፡ የደገፉትን ፡ ምሰሶዎች ፡ እጠጋባቸው ፡ ዘንድ ፥ እባክኽ ፥ አስይዘኝ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ሞልተውበት ፡ ነበር ፥ የፍልስጥኤምም ፡ መኳንንት ፡ ዥሉ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ፤ በቤቱም ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ሶምሶን ፡ ሲጫወት ፡ የሚያዩ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ሶምሶንም ፦ ስለ ፡ ኹለቱ ፡ ዐይኖቼ ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ አኹን ፡ እንድበቀል ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እባክኽ ፥ ዐስበኝ ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፥ እባክኽ ፥ አበርታኝ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ ሶምሶንም ፡ ቤቱ ፡ ተደግፎባቸው ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ መካከለኞች ፡ ምሰሶዎች ፡ ያዘ ፤ አንዱን ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ አንዱንም ፡ በግራ ፡ እጁ ፡ ይዞ ፡ ተጠጋባቸው ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ሶምሶንም ፦ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ልሙት ፡ አለ ፤ ተጐንብሶም ፡ ምሰሶዎቹን ፡ በሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ ገፋ ፥ ቤቱም ፡ በውስጡ ፡ በነበሩት ፡ በመኳንንቱም ፡ በሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ በሞቱም ፡ የገደላቸው ፡ ሙታን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ከገደላቸው ፡ በዙ ።

መሳ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ ወንድሞቹም ፡ የአባቱ ፡ ቤተ ፡ ሰቦችም ፡ ዥሉ ፡ ወረዱ ፥ ይዘውም ፡ አመጡት ፤ በጾርዓና ፡ በኤሽታኦል ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በአባቱ ፡ በማኑሄ ፡ መቃብር ፡ ቀበሩት ። ርሱም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ፈረደ ።

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

መሳ. ፥ 17 ፥ 1 ፤ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሚካ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 2 ፤ እናቱንም ፦ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ የተወሰደው ፥ የረገምሽበትም ፥ በጐሮዬም ፡ የተናገርሽበት ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ብር ፥ እንሆ ፥ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፤ እኔም ፡ ወስጄዋለኹ ፡ አላት ። እናቱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ፡ አለችው ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 3 ፤ አንዱን ፡ ሺሕ ፡ አንዱን ፡ መቶ ፡ ብርም ፡ መለሰላት ፤ እናቱም ፦ ይህን ፡ ብር ፡ የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስል ፡ አድርጌ ፡ ከእጄ ፡ ስለ ፡ ልጄ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እቀድሰዋለኹ ፤ አኹንም ፡ ለአንተ ፡ እመልሰዋለኹ ፡ አለች ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 4 ፤ ለእናቱም ፡ ገንዘቡን ፡ በመለሰላት ፡ ጊዜ ፡ እናቱ ፡ ኹለቱን ፡ መቶ ፡ ብር ፡ ወስዳ ፡ ለአንጥረኛ ፡ ሰጠችው ፥ ርሱም ፡ የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስል ፡ አደረገው ። ያም ፡ በሚካ ፡ ቤት ፡ ነበረ ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 5 ፤ ሰውዮውም ፡ ሚካ ፡ የአምላክ ፡ ቤት ፡ ነበረው ፤ ኤፉድና ፡ ተራፊም ፡ አደረገ ፥ ከልጆቹም ፡ አንዱን ፡ ቀደሰው ፥ ካህንም ፡ ኾነለት ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 6 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፤ ሰውም ፡ ሹሉ ፡ በፊቱ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 7 ፤ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳም ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ ሌዋዊ ፡ ነበረ ፥ በዚያም ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 8 ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ የሚቀመጥበትን ፡ ስፍራ ፡ ለመሻት ፡ ከከተማው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ወጣ ፤ ሲኼድም ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደኤፍሬም ፡ አገር ፡ ወደሚካ ፡ ቤት ፡ መጣ ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 9 ፤ ሚካም ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ርሱም ፦ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ የኾንኹ ፡ ሌዋዊ ፡ ነኝ ፤ የምቀመጥበትንም ፡ ስፍራ ፡ ለመሻት ፡ እኼዳለኹ ፡ አለው ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 10 ፤ ሚካም ፦ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥ ፥ አባትና ፡ ካህንም ፡ ኹነኝ ፤ እኔም ፡ ልብሶችንና ፡ ምግብኽን ፥ በየዓመቱም ፡ ዐሥር ፡ ብር ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ። ሌዋዊውም ፡ ገባ ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 11 ፤ ሌዋዊውም ፡ ከሰውዮው ፡ ጋራ ፡ መቀመጥን ፡ ፈቀደ ፤ ጕልማሳውም ፡ ከልጆቹ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ኾነለት ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 12 ፤ ሚካም ፡ ሌዋዊውን ፡ ቀደሰ ፥ ጕልማሳውም ፡ ካህኑ ፡ ኾነለት ፥ በሚካም ፡ ቤት ፡ ነበረ ።

መሳ. ፥ 17 ፥ 13 ፤ ሚካም ፦ ሌዋዊ ፡ ካህን ፡ ስለ ፡ ኾነልኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ እንዲሠራልኝ ፡ አኹን ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

_____መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

መሳ. ፥ 18 ፥ 1 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ። እስከዚያም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለዳን ፡ ነገድ ፡ በእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ መካከል ፡ ርስት ፡ አልደረሳቸውም ፡ ነበርና ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሚቀመጡባት ፡ ርስት ፡ ይሹ ፡ ነበር ።

መሳ. ፥ 18 ፥ 2 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ከወገናቸው ፡ ዐምስት ፡ ጽኑዓን ፡ ሰዎች ፡ ምድሪቱን ፡ እንዲሰልሉና ፡ እንዲመረምሩ ፦ ኺዱ ፥ ምድሪቱንም ፡ ሰልሉ ፡ ብለው ፡ ከጾርዓና ፡ ከኤሽታኦል ፡ ሰደዱ ። እነዚያም ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡

ወደኤፍሬም ፡ አገር ፡ ወደሚካ ፡ ቤት ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ ዐደሩ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ በሚካ ፡ ቤት ፡ አጠገብም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ የሌዋዊውን ፡ የጕልማሳውን ፡ ድምፅ ፡ ዐወቁ ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ቀርበው ፦ ወደዚህ ፡ ማን ፡ አመጣኽ ∴ በዚህስ ፡ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ∴ በዚህስ ፡ ምን ፡ አለኽ ∴ አሉት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ርሱም ፦ ሚካ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ አደረገልኝ ፥ ቀጠረኝም ፥ እኔም ፡ ካህን ፡ ኾንኹለት ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፦ የምንኼድበት ፡ መንገድ ፡ የቀና ፡ መኾኑን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፥ እባክኽ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቅልን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ የምትኼዱበት ፡ መንገድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ነውና ፥ በደኅና ፡ ኺዱ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ዐምስቱም ፡ ሰዎች ፡ ኼዱ ፡ ወደ ፡ ሌሳም ፡ መጡ ፥ በውስጡም ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ተዘልለው ፡ አይዋቸው ፥ እንደ ፡ ሲዶናውያንም ፡ ልማድ ፡ ጸጥ ፡ ብለው ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ የሚያስቸግራቸውም ፡ የሚገዛቸውም ፡ አልነበረም ፥ ከሲዶናውያንም ፡ ርቀው ፡ ከሰውም ፡ ዥሉ ፡ ተለይተው ፡ ለብቻቸው ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ወንድሞቻቸውም ፡ ወደ ፡ ጾርዓና ፡ ወደ ፡ ኤሽታኦል ፡ ተመለሱ ፤ ወንድሞቻቸውም ፦ ምን ፡ ወሬ ፡ ይዛችኋል ∴ አሏቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ ምድሪቱን ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ አይተናልና ፥ ተነሡ ፥ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንውጣ ፤ እናንተ ፡ ዝም ፡ ትላላችኹን ∴ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ምድሪቱንም ፡ ለመውረስ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡ ቸል ፡ አትበሉ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ በኼዳችኹ ፡ ጊዜ ፡ ተዘልለው ፡ ወደተቀመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ትደርሳላችኹ ፥ ምድሪቱም ፡ ሰፊ ፡ ናት ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ካለው ፡ ነገር ፡ ዥሉ ፡ አንዳች ፡ የማይጐድልበትን ፡ ስፍራ ፡ በእጃችኹ ፡ ሰጥቷል ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ከዳን ፡ ወገንም ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ የታጠቁ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ከዚያ ፡ ከጾርዓና ፡ ከኤሽታኦል ፡ ተነሥተው ፡ ኼዱ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ወጥተውም ፡ በይሁዳ ፡ ባለችው ፡ በቂርያትይዓሪም ፡ ሰፈሩ ፤ ስለዚህም ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የዳን ፡ ሰፈር ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፤ እንሆም ፥ ከቂርያትይዓሪም ፡ በስተኋላ ፡ ነው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደኤፍሬም ፡ አገር ፡ ዐለፉ ፤ ወደሚካም ፡ ቤት ፡ መጡ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ የሌሳን ፡ ምድር ፡ ሊሰልሉ ፡ ኼደው ፡ የነበሩት ፡ ዐምስቱ ፡ ሰዎችም ፡ ወንድሞቻቸውን ፦ በእነዚህ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ኤፉድና ፡ ተራፊም ፥ የተቀረጸ ፡ ምስልና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስልም ፡ እንዳሉ ፡ ታውቃላችኹን ∴ አኹንም ፡ የምታደርጉትን ፡ ምከሩ ፡ ብለው ፡ ተናገሯቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ከመንገዱም ፡ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ጕልማሳው ፡ ሌዋዊ ፡ ወደነበረበት ፡ ወደሚካ ፡ ቤት ፡ መጡ ፥ ደኅንነቱንም ፡ ጠየቁት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ የጦር ፡ ዕቃ ፡ የታጠቁት ፥ ከዳን ፡ ልጆችም ፡ የኾኑት ፡ ስድስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ በደጃፉ ፡ አጠገብ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ ምድሪቱንም ፡ ሊሰልሉ ፡ ኼደው ፡ የነበሩት ፡ ዐምስቱ ፡ ሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ወደዚያ ፡ ገቡ ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ኤፉዱንም ፡ ተራፊሙንም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስልም ፡ ወሰዱ ፤ ካህኑም ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ከታጠቁት ፡ ከስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በደጃፉ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ እነዚህም ፡ ወደሚካ ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ኤፉዱንም ፡ ተራፊሙንም ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስልም ፡ በወሰዱ ፡ ጊዜ ፥ ካህኑ ፦ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧ አላቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፦ ዝም ፡ በል ፥ እጅኽንም ፡ በአፍኽ ፡ ላይ ፡ ጫን ፥ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ መጥተኽ ፡ አባትና ፡ ካህን ፡ ኹንልን ፤ ላንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ካህን ፡ መኾን ፡ ወይስ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ለነገድና ፡ ለወገን ፡ ካህን ፡ መኾን ፡ ማናቸው ፡ ይሻልኻል ፧ አሉት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ካህኑም ፡ በልቡ ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ኤፉዱንም ፡ ተራፊሙንም ፡ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ወሰደ ፥ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ኼደ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ዞረው ፡ ኼዱ ፥ ሕፃናትንና ፡ ከብቶችን ፡ ዕቃዎችንም ፡ በፊታቸው ፡ አደረጉ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ከሚካም ፡ ቤት ፡ በራቁ ፡ ጊዜ ፡ የሚካ ፡ ጎረቤቶች ፡ ተሰበሰቡ ፥ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ተከትለው ፡ ደረሱባቸው ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ወደዳንም ፡ ልጆች ፡ ጮኹ ፥ የዳንም ፡ ልጆች ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ሚካን ፦ የምትጮኸው ፡ ምን ፡ ኾነኽ ፡ ነው ፧ አሉት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ርሱም ፦ የሠራኋቸውን ፡ አማልክቴን ፡ ካህኑንም ፡ ይዛችኹ ፡ ኼዳችኋል ፤ ሌላ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ እናንተስ ። ምን ፡ ኾነኻል ፡ እንዴት ፡ ትሉኛላችኹ ፧ አለ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ። የተቈጡ ፡ ሰዎች ፡ እንዳይወድቁብኽ ፡ ነፍስኽም ፡ የቤተ ፡ ሰቦችኽም ፡ ነፍስ ፡ እንዳይጠፋብኽ ፥ ድምፅኽን ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ አታሰማ ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ መንገዳቸውን ፡ ኼዱ ፤ ሚካም ፡ ከርሱ ፡ እንደ ፡ በረቱ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ እነርሱም ፡ ሚካ ፡ የሠራውን ፡ ጣዖትና ፡ ለርሱ ፡ የነበረውን ፡ ካህን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሌሳ ፥ ጸጥ ፡ ብሎ ፡ ተዘልሎም ፡ ወደተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፥ መጡ ፤ በሰይፍም ፡ ስለት ፡ መቷቸው ፥ ከተማዪቱንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠሏት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ከተማዪቱ ፡ ከሲዶና ፡ ራቅ ፡ ያለች ፡ ነበረችና ፥ እነርሱም ፡ ከሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ተለይተው ፡ ብቻቸውን ፡ ይኖሩ ፡ ነበርና ፥ የሚታደግ ፡ አልነበራቸውም ። ሌሳም ፡ በቤትሮዖብ ፡ አጠገብ ፡ ባለች ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ነበረች ። ከተማዪቱንም ፡ ሠርተው ፡ ተቀመጡባት ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ከተማዪቱንም ፡ ከእስራኤል ፡ በተወለደው ፡ በአባታቸው ፡ በዳን ፡ ስም ፡ ዳን ፡ ብለው ፡ ጠሯት ፤ የከተማዪቱም ፡ ስም ፡ አስቀድሞ ፡ ሌሳ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ የዳንም ፡ ልጆች ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ለራሳቸው ፡ አቆሙ ፤ የሙሴም ፡ ልጅ ፡ የጌርሳም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ([130]) ፥ ርሱና ፡ ልጆቹ ፡ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ እስከሚማረኩበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የዳን ፡ ነገድ ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ ሚካም ፡ ያደረገውን ፡ የተቀረጸ ፡ ምስል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሴሎ ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ አቆሙ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ማዶ ፡ የተቀመጠ ፡ ሌዋዊ ፡ ነበረ ፤ ከቤተ ፡ ልሔምም ፡ ይሁዳ ፡ ቁባት ፡ አገባ ።

---

130 ዕብ. ፥ የሖናታን ፡ (ንቱን ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ ስጦታ) ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ቁባቱም ፡ አመነዘረችበት ፥ ትታውም ፡ ወዳባቷ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ኼደች ፤ በዚያም ፡ አራት ፡ ወር ፡ ተቀመጠች ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ባሏም ፡ ተነሣ ፥ ከርሷም ፡ ዕርቅ ፡ ሽቶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ሊመልሳት ፡ ፍለጋዋን ፡ ተከትሎ ፡ ኼደ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አሽከር ፥ ኹለትም ፡ አህያዎች ፡ ነበሩ ። ርሷም ፡ ወዳባቷ ፡ ቤት ፡ አገባችው ፤ አባቷም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተገናኘው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ የብላቴናዩቱም ፡ አባት ፡ ዐማቱ ፡ የግድ ፡ አለ ፥ በቤቱም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ፤ በሉም ፥ ጠጡም ፥ በዚያም ፡ ዐደሩ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥ ርሱም ፡ ለመኼድ ፡ ተነሣ ፤ የብላቴናዩቱም ፡ አባት ፡ ዐማቹን ፦ ሰውነትኽን ፡ በቀሩራሽ ፡ እንጀራ ፡ አበርታ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ትኼዳለኽ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ተቀመጡም ፡ ባንድ ፡ ላይም ፡ በሉ ፡ ጠጡም ፤ የብላቴናዩቱም ፡ አባት ፡ ሰውዮውን ፦ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ለማደር ፥ እባክኽ ፥ ፍቀድ ፥ ልብኽንም ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ሰውዮውም ፡ ሊኼድ ፡ ተነሣ ፤ ዐማቱ ፡ ግን ፡ የግድ ፡ አለው ፥ ዳግመኛም ፡ በዚያ ፡ ዐደረ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ በዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ለመኼድ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፤ የብላቴናዩቱም ፡ አባት ፦ እባክኽ ፥ ሰውነትኽን ፡ አበርታ ፥ ቀኑም ፡ እስኪዋገድ ፡ ድረስ ፡ ቈይ ፡ አለው ። ኹለቱም ፡ በሉ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ ሰውዮውም ፡ ከቁባቱና ፡ ከአሽከሩ ፡ ጋራ ፡ ለመኼድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ የብላቴናዩቱ ፡ አባት ፡ ዐማቱ ፦ እንሆ ፥ ቀኑ ፡ ተዋግዷል ፤ በዚህ ፡ ዕደሩ ፤ እንሆ ፥ ቀኑ ፡ ለማለፍ ፡ ተዋግዷል ፤ ልባችኹ ፡ ደስ ፡ እንዲለው ፡ በዚህ ፡ ዕደሩ ፤ ነገም ፡ ወደ ፡ ቤታችኹ ፡ እንድትደርሱ ፡ ማልዳችኹ ፡ መንገዳችኹን ፡ ትኼዳላችኹ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ሰውዮው ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ ለማደር ፡ አልፈቀደም ፥ ተነሥቶም ፡ ኼደ ፥ ኢየሩሳሌምም ፡ ወደተባለች ፡ ወደኢያቡስ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ደረሰ ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ የተጫኑ ፡ አህያዎች ፡ ነበሩ ፥ ቁባቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረች ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ኢያቡስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ መሸባቸው ፥ አሽከሩም ፡ ጌታውን ፦ ና ፥ ወደዚህ ፡ ወደኢያቡሳውያን ፡ ከተማ ፥ እባክኽ ፥ እናቅና ፥ በርሷም ፡ እንደር ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ጌታውም ፦ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ወዳልኾነች ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ ከተማ ፡ አንገባም ፤ እኛ ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ እንለፍ ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ አሽከሩንም ፦ ና ፥ ከነዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ እንቅረብ ፤ በጊብዓ ፡ ወይም ፡ በራማ ፡ እንደር ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ መንገዳቸውንም ፡ ይዘው ፡ ኼዱ ፤ የብንያምም ፡ ነገድ ፡ በምትኾነው ፡ በጊብዓ ፡ አጠገብ ፡ ሳሉ ፡ ፀሓይ ፡ ገባችባቸው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ በጊብዓም ፡ ገብተው ፡ ያድሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ አቀኑ ። በገባም ፡ ጊዜ ፡ ሊያሳድራቸው ፡ ማንም ፡ በቤቱ ፡ አልተቀበላቸውምና ፡ በከተማው ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ከዕርሻው ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ መጣ ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ ከተራራማው ፡ ከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ነበረ ፡ በጊብዓም ፡ በእንግድነት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ የዚያ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ብንያማውያን ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ዐይኑንም ፡ አንሥቶ ፡ መንገደኛውን ፡ በከተማው ፡ አደባባይ ፡ አየ ፤ ሽማግሌውም ፦ ወዴት ፡

ትኼዳለኽ ፡፡ ከወዴትስ ፡ መጣኽ ፡፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ እኛ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ ወደኤፍሬም ፡ አገር ፡ ማዶ ፡ እናልፋለን ፤ እኔ ፡ ከዚያ ፡ ነኝ ፥ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ ይሁዳ ፡ ኼጄ ፡ ነበር ፥ አኹንም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እኼዳለኹ ፤ በቤቱም ፡ የሚያሳድረኝ ፡ ዐጣኹ ፤

መሳ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ለአህያዎቻችን ፡ ገለባና ፡ ገፈራ ፡ አለን ፤ ለኔና ፡ ለገረድኽ ፡ ከባሪያዎችኽም ፡ ጋራ ፡ ላለው ፡ አሽከር ፡ እንጀራና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አለን ፤ አንዳችም ፡ አላጣንም ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ሽማግሌውም ፦ ሰላም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ የምትሻውንም ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ በአደባባይ ፡ ግን ፡ አትደር ፡ አለው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አስገባው ፥ ለአህያዎቹም ፡ ገፈራ ፡ ጣለላቸው ፤ እግራቸውንም ፡ ታጠቡ ፥ በሉም ፡ ጠጡም ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ሰውነታቸውንም ፡ ደስ ፡ ባሠኙ ፡ ጊዜ ፥ ወስላታዎች ፡ የኾኑ ፡ የከተማው ፡ ሰዎች ፡ ቤቱን ፡ ከበቡ ፥ በሩንም ፡ ይደበድቡ ፡ ነበር ፤ ባለቤቱንም ፡ ሽማግሌውን ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ የገባውን ፡ ሰው ፡ እንድንደርስበት ፡ አውጣልን ፡ አሉት ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ባለቤቱም ፡ ሽማግሌው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወጥቶ ፦ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፥ እባካችኹ ፥ አታድርጉ ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ገብቷልና ፥ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኀጢአት ፡ አትሥሩ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ድንግል ፡ ልጄና ፡ የርሱም ፡ ቁባት ፥ እንሆ ፥ አሉ ፥ አኹንም ፡ አወጣቸዋለኹ ፤ አዋርዷቸው ፡ እንደ ፡ ወደዳችኹም ፡ አድርጉባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኀጢአት ፡ አታድርጉ ፡ አላቸው ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ሰዎቹ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ አልሰሙም ፤ ሰውዮውም ፡ ቁባቱን ፡ ይዞ ፡ አወጣላቸው ፤ ደረሱባትም ፥ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ አመነዘሩባት ፤ ጎሕ ፡ በቀደደም ፡ ጊዜ ፡ ለቀቋት ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ሴቲቱም ፡ ማለዳ ፡ መጣች ፥ ጌታዋም ፡ ባለበት ፡ በሰውዮው ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ወድቃ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ቀረች ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ጌታዋም ፡ ማለዳ ፡ ተነሣ ፡ የቤቱንም ፡ ደጅ ፡ ከፈተ ፥ መንገዱንም ፡ ለመኼድ ፡ ወጣ ፤ እንሆም ፡ ቁባቲቱ ፡ ሴት ፡ በቤቱ ፡ ደጃፍ ፡ ወድቃ ፥ እጇም ፡ በመድረክ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ርሱም ፦ ተነሺ ፥ እንኺድ ፡ አላት ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ ሞታ ፡ ነበርና ፥ አልመለሰችም ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በአህያው ፡ ላይ ፡ ጫናት ፥ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ኼደ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ካራ ፡ አነሣ ፥ ቁባቱንም ፡ ይዞ ፡ ከዐጥንቶቿ ፡ መለያያ ፡ ላይ ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ቈራርጦ ፡ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ሰደደ ።

መሳ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ያየም ፡ ኹሉ ፦ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አልተደረገም ፥ አልታየምም ፤ ዐስቡት ፥ በዚህም ፡ ተመካከሩ ፥ ተነጋገሩም ፡ ይባባል ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ወጡ ፥ ማኅበሩም ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፥ ከገለዓድም ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኾነው ፡ ተሰበሰቡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ የኾኑ ፡ የሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ አለቃዎች ፡ ሰይፍ ፡ በሚመዙ ፡ በቀጥርም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ እግረኞች ፡ በኾኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ጉባኤ ፡ ቆሙ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ ሰሙ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፦ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደምን ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ንገሩን ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ የተገደለችውም ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ሌዋዊው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፦ እኔና ፡ ቁባቴ ፡ በዚያ ፡ ለማደር ፡ ወደብንያም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ መጣን ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ የጊብዓም ፡ ሰዎች ፡ ተነሡብኝ ፥ ቤቱንም ፡ በሌሊት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ከበቡት ፤ ሊገድሉኝም ፡ ወደዱ ፥ በቁባቴም ፡ አጥብቀው ፡ አመነዘሩባት ፥ ርሷም ፡ ሞተች ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ እኔም ፡ ቁባቴን ፡ ይዤ ፡ ቈራረጥኋት ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ኀጢአትና ፡ ስንፍና ፡ ስለ ፡ ተሠራ ፡ ወደእስራኤል ፡ ርስት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ሰደድኹ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ኹላችኹ ፥ ምክራችኹንና ፡ ዕዝናታችኹን ፡ በዚህ ፡ ስጡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥተው ፡ አሉ ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ አይኼድም ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አይመለስም ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ የምናደርገው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በዕጣ ፡ እንወጣባታለን ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ብንያም ፡ ጊብዓ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ርሷ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንዳደረገችው ፡ እንደ ፡ ስንፍናዋ ፡ እንዲያደርጉ ፥ ለሕዝብ ፡ ሥንቅ ፡ የሚይዙ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ከመቶው ፡ ዐሥር ፡ ሰው ፡ ከሺሕም ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ከዐሥሩም ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ እንወስዳለን ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኾነው ፡ በከተማዪቱ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ 13 ፤ የእስራኤልም ፡ ነገዶች ፦ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የተደረገ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አኹንም ፡ እንድንገድላቸው ፡ ከእስራኤልም ፡ ክፋትን ፡ እንድናርቅ ፡ በጊብዓ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ምናምንቴዎቹን ፡ ሰዎች ፡ አውጥታችኹ ፡ ስጡን ፡ ብለው ፡ ወደብንያም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ሰዎችን ፡ ላኩ ። የብንያም ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ የወንድሞቻቸውን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ቃል ፡ ሊሰሙ ፡ አልወደዱም ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ከየከተማው ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ተሰበሰቡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከየከተማው ፡ የመጡ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ተቈጠሩ ፤ ቀጥራቸውም ፡ ከጊብዓ ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ከጊብዓም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጠሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ከነዚያም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ የተመረጡ ፡ ግራኝ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ድንጋይ ፡ ይወነጭፉ ፡ ነበር ፤ አንዲት ፡ ጠጕርስ ፡ እንኳ ፡ አይስቱም ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ ሌላ ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰዎች ፡ ተቈጠሩ ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ሰልፈኞች ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወጡ ፥ እግዚአብሔርንም ፦ የብንያምን ፡ ልጆች ፡ ለመውጋት ፡ አስቀድሞ ፡ ማን ፡ ይውጣልን ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይሁዳ ፡ ይቅደም ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በማለዳ ፡ ተነሥተው ፡ በጊብዓ ፡ ፊት ፡ ሰፈሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከብንያም ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ወጡ ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በጊብዓ ፡ አጠገብ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈው ፡ ቆሙ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ከጊብዓ ፡ ወጡ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከእስራኤላውያን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ሕዝቡም ፥ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፥ ተበራቱ ፥ በፊተኛውም ፡ ቀን ፡ በተሰለፉበት ፡ ስፍራ ፡ ደግመው ፡ ተሰለፉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወጥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ አለቀሱ ፤ እግዚአብሔርንም ፦ ከወንድሞቻችን ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ዳግመኛ ፡ እንቀርባለን ፧ ብለው ፡ ጠየቁ ። እግዚአብሔርም ፦ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ቀረቡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ብንያም ፡ ከጊብዓ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጡ ፥ አለቀሱም ፥ በዚያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተቀመጡ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ጾሙ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ 28 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ታቦት ፡ በዚያ ፡ ነበረና ፥ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ በፊቱ ፡ ይቆም ፡ ነበርና ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፦ ከወንድሞቻችን ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ዳግመኛ ፡ እንውጣን ፡ ወይስ ፡ እንቅር ፧ ብለው ፡ ጠየቁ ። እግዚአብሔርም ፦ ነገ ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹና ፥ ውጡ ፡ አለ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ እስራኤልም ፡ በጊብዓ ፡ ዙሪያ ፡ የተደበቁ ፡ ሰዎች ፡ አኖሩባት ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 30 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደብንያም ፡ ልጆች ፡ ወጡ ፥ በጊብዓም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ ተሰለፉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 31 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ወጡ ፥ ከከተማዪቱም ፡ ተሳቡ ፤ እንደ ፡ ቀድሞውም ፡ ጊዜ ፥ በአውራዎቹ ፡ መንገዶች ፥ አንደኛው ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ኹለተኛውም ፡ ወደጊብዓ ፡ ሜዳ ፡ በሚወስዱት ፡ መንገዶች ፡ ላይ ፥ ሕዝቡን ፡ ይመቱ ፡ ይገድሉም ፡ ገቦመር ፤ ከእስራኤልም ፡ ሠላሳ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 32 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፦ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ በፊታችን ፡ ተመቱ ፡ አሉ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፦ እንሸሽ ፥ ከከተማም ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ እንሳባቸው ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 33 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከስፍራቸው ፡ ተነሥተው ፡ በበዓልታማር ፡ ተሰለፉ ። ከእስራኤልም ፡ ተደብቀው ፡ የነበሩት ፡ ከስፍራቸው ፡ ከጊብዓ ፡ ሜዳ ፡ ወጡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 34 ፤ ከእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ የተመረጡ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ወደጊብዓ ፡ አንጻር ፡ መጡ ፤ ሰልፍም ፡ በርትቶ ፡ ነበር ፤ መከራም ፡ እንዲያገኛቸው ፡ አላወቁም ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብንያምን ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ መታ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከብንያም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 36 ፤ የብንያም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ተመቱ ፡ አዩ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ ባኖሩት ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ ታምነዋልና ፥ ለብንያም ፡ ስፍራ ፡ ለቀቁላቸው ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 37 ፤ ተደብቀውም ፡ የነበሩት ፡ ፈጥነው ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ሮጡ ፤ ተደብቀውም ፡ የነበሩት ፡ መጥተው ፡ ከተማውን ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 38 ፤ የተደበቁትም ፡ ሰዎች ፡ ከከተማው ፡ ብዙ ፡ ጢስ ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ እንዲያስነሡ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ በተደበቁት ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ ምልክት ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 39 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከሰልፉ ፡ አፈገፈጉ ፤ ብንያማውያንም ፦ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ሰልፍ ፡ በፊታችን ፡ ተመትተዋል ፡ እያሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሠላሳ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ መምታትና ፡ መግደል ፡ ገሮመሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 40 ፤ ምልክቱ ፡ በጢሱ ፡ ዐምድ ፡ ከከተማው ፡ ሊወጣ ፡ በገሮመረ ፡ ጊዜ ፡ ብንያማውያን ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ተመለከቱ ፥ እንሆም ፥ የሞላ ፡ ከተማው ፡ ጥፋት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 41 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ፥ የብንያምም ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰባቸው ፡ አይተዋልና ፥ ደነገጡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 42 ፤ ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ገርርባቸውን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ ሸሹ ፤ ሰልፉም ፡ ተከታትሎ ፡ ደረሰባቸው ፤ ከየከተማውም ፡ የወጡት ፡ በመካከላቸው ፡ ገደሏቸው ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 43 ፤ ብንያማውያንንም ፡ ከበቡ ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ ጊብዓ ፡ አንጻር ፡ ድረስ ፡ አሳደዷቸው ፥ በመኑሔም ፡ አጠፏቸው ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 44 ፤ ከብንያምም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ሞተ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 45 ፤ ከነርሱም ፡ የተረፉት ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደሬሞን ፡ አለት ፡ ሸሹ ፥ ከነርሱም ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ለቀሙ ፤ ወደ ፡ ጊድአምም ፡ አሳደዷቸው ፥ ከነርሱም ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 46 ፤ እንዲሁም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከብንያም ፡ የሞቱት ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 47 ፤ ስድስቱም ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ተመልሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደሬሞን ፡ አለት ፡ ሸሹ ፥ በሬሞን ፡ አለት ፡ አራት ፡ ወር ፡ ተቀመጡ ።

መሳ. ፡ 20 ፡ 48 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በብንያም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ዳግመኛ ፡ ተመለሱ ፤ ሞላውን ፡ ከተማ ፡ ከብቱንም ፡ ያገኙትንም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መቱ ፤ ያገኙትንም ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ።

መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፦ ከእኛ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ ለብንያም ፡ ልጆች ፡ አያጋባ ፡ ብለው ፡ በምጽጳ ፡ ተማምለው ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ ፥ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ጽኑ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሱ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፦ አቤቱ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡ ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ መታጣቱ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ይህ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ኾነ ፧ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ በነጋውም ፡ ሕዝቡ ፡ ማልደው ፡ ተነሡ ፥ በዚያም ፡ መሠዊያ ፡ ሠሩ ፥ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕትንም ፡ አቀረቡ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጻ ፡ ስላልወጣ ፡ ሰው ፦ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደል ፡ ብለው ፡ ታላቅ ፡ መሐላ ፡ ምለው ፡ ነበርና ። ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያልወጣ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ስለ ፡ ብንያም ፡ ልጆች ፡ ተጸጽተው ፦ ዛሬ ፡ ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ጠፍቷል ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ እኛ ፡ ልጆቻችንን ፡ እንዳንድርላቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለናልና ፥ የተረፉት ፡ ሚስቶችን ፡ እንዲያገኙ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ እነርሱም ፦ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጻ ፡ ያልወጣ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሉ ። እንሆም ፥ ከኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ማንም ፡ አልወጣም ፡ ነበር ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ሕዝቡም ፡ በተቈጠሩ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ የሚኖር ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ማኅበሩም ፡ ወደዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ሰደው ፦ ኺዱ ፡ በኢያቢስ ፡ ገለዓድም ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ከሴቶችና ፡ ከሕፃናት ፡ ጋራ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ግደሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ የምታደርጉትም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወንዱን ፡ ኹሉ ፥ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ የተኛችዉቱንም ፡ ሴት ፡ ኹሉ ፡ ፈጽማችኹ ፡ አጥፉ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸው ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ወንድ ፡ ያላወቁ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ቈነጕዥት ፡ ደናግሎች ፡ በኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ በሚኖሩ ፡ መካከል ፡ አገኙ ፤ በከነዓንም ፡ አገር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ አመጧቸው ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ በሬሞን ፡ አለት ፡ ወዳሉት ፡ ወደብንያም ፡ ልጆች ፡ መልክተኞችን ፡ ላኩ ፥ በዕርቅ ፡ ቃልም ፡ ተናገሯቸው ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ተመለሱ ፤ ከኢያቢስ ፡ ገለዓድም ፡ ሴቶች ፡ ያዳኗቸውን ፡ ሴቶች ፡ አገቧቸው ። ነገር ፡ ግን ፥ የሚበቁ ፡ ሴቶች ፡ አላገኙም ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ውስጥ ፡ ስብራት ፡ ስላደረገ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ብንያም ፡ ተጸጸቱ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ የማኅበሩ ፡ ሽማግሌዎች ፦ ከብንያም ፡ ሴቶች ፡ ጠፍተዋልና ፥ የቀሩት ፡ ሰዎች ፡ ሚስት ፡ እንዲያገኙ ፡ ምን ፡ እናደርጋለን ፧ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ደግሞም ፦ ከእስራኤል ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ እንዳይደመሰስ ፡ ከብንያም ፡ ላመለጡት ፡ ርስት ፡ ይኑር ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፦ ልጁን ፡ ለብንያም ፡ የሚድር ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፡ ብለው ፡ ምለዋልና ፥ እኛ ፡ ልጆቻችንን ፡ ለእነርሱ ፡ ማጋባት ፡ አይኾንልንም ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፦ እንሆ ፥ በቤቴል ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፥ ከቤቴልም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፥ በለቦና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባለችው ፡ በሴሎ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ በየዓመቱ ፡ አለ ፡ አሉ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ የብንያምንም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አዘዟቸው ። ኺዱ ፡ በወይኑ ፡ ስፍራ ፡ ተደበቁ ፤

መሳ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ተመልከቱም ፥ እንሆም ፥ የሴሎ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አታሞ ፡ ይዘው ፡ ለዘፈን ፡ ሲወጡ ፡ ከወይኑ ፡ ስፍራ ፡ ውጡ ፥ ከሴሎም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ለየራሳችኹ ፡ ሚስት ፡ ንጠቁ ፥ ወደብንያም ፡ ምድርም ፡ ኺዱ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ አባቶቻቸውና ፡ ወንድሞቻቸውም ፡ ሊጣሏችኹ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፦ ስለ ፡ እኛ ፡ ማሯቸው ፤ እኛ ፡ ሚስት ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ በሰልፍ ፡ አልወሰድንላቸውምና ፥ እናንተም ፡ በደል ፡ ይኾንባችኹ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አላጋባችኋቸውምና ፥ እንላችኋለን ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፥ በቍጥራቸውም ፡ መጠን ፡ ከተነጠቁት ፡ ዘፋኞች ፡ ሚስት ፡ ወሰዱ ፤ ወደ ፡ ርስታቸውም ፡ ተመልሰው ፡ ኼዱ ፥ ከተማዎችንም ፡ ሠርተው ፡ ተቀመጡባቸው ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከዚያ ፡ ተነሡ ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ነገዱና ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ኼደ ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ ተመለሰ ።

መሳ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ የታየውን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ሩት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ሩት ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሩት ፥ 1 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ መሳፍንት ፡ ይፈርዱ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ኾነ ። አንድ ፡ ሰውም ፡ ከሚስቱና ፡ ከኹለቱ ፡ ልጆቹ ፡ ጋራ ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ሊቀመጥ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 2 ፤ የሰውዮውም ፡ ስም ፡ አቢሜሌክ ፥ የሚስቱም ፡ ስም ፡ ኑኃሚን ፥ የኹለቱም ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ መሐሎንና ፡ ኬሌዎን ፡ ነበረ ፤ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳም ፡ የኤፍራታ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ወደሞዐብም ፡ ምድር ፡ መጡ ፡ በዚያም ፡ ተቀመጡ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 3 ፤ የኑኃሚንም ፡ ባል ፡ አቢሜሌክ ፡ ሞተ ፤ ርሷና ፡ ኹለቱ ፡ ልጆቿ ፡ ቀሩ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 4 ፤ እነርሱም ፡ ከሞዐባውያን ፡ ሴቶች ፡ ሚስት ፡ አገቡ ፤ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ዖርፋ ፡ የኹለተኛዪቱም ፡ ስም ፡ ሩት ፡ ነበረ ። በዚያም ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ተቀመጡ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 5 ፤ መሐሎንና ፡ ኬሌዎንም ፡ ኹለቱ ፡ ሞቱ ፤ ሴቲቱም ፡ ከኹለቱ ፡ ልጆቿና ፡ ከባሏ ፡ ተለይታ ፡ ቀረች ።

ሩት ፥ 1 ፥ 6 ፤ ርሷም ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ሳለች ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ እንደ ፡ ጐበኘ ፡ እንጀራም ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ስለ ፡ ሰማች ፥ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ ልትመለስ ፡ ከኹለቱ ፡ ምራቶቿ ፡ ጋራ ፡ ተነሣች ።

ሩት ፥ 1 ፥ 7 ፤ ርሷም ፡ ከኹለቱ ፡ ምራቶቿ ፡ ጋራ ፡ ከተቀመጠችበት ፡ ስፍራ ፡ ወጣች ፤ ወደይሁዳም ፡ ምድር ፡ ሊመለሱ ፡ በመንገድ ፡ ኼዱ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 8 ፤ ኑኃሚንም ፡ ምራቶቿን ፦ ኺዱ ፥ ወደእናቶቻችኹም ፡ ቤት ፡ ተመለሱ ፤ በእኔና ፡ በሞቱት ፡ እንዳደረጋችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ያድርግላችኹ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ በየባላችኹ ፡ ቤት ፡ ዕረፍት ፡ ይስጣችኹ ፡ አለቻቸው ። ሳመቻቸውም ፤ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አለቀሱ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 10 ፤ እነርሱም ፦ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሕዝብሽ ፡ እንመለሳለን ፡ አሏት ።

ሩት ፥ 1 ፥ 11 ፤ ኑኃሚንም ፡ አለች ፦ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፤ ለምን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትኼዳላችኹ ፧ ባሎቻችኹ ፡ የሚኾኑ ፡ ልጆች ፡ በሆዴ ፡ አሉኝን ፧

ሩት ፥ 1 ፥ 12 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፤ ባል ፡ ለማግባት ፡ አርጅቻለኹና ፡ ኺዱ ፤ ተስፋ ፡ አለኝ ፡ ብል ፥ ዛሬ ፡ ሌሊትስ ፡ እንኳ ፡ ባል ፡ ባገባ ፥ ወንዶች ፡ ልጆችም ፡ ብወልድ ፥

ሩት ፥ 1 ፥ 13 ፤ እነርሱ ፡ እስኪያድጉ ፡ ድረስ ፡ ትቈያላችኹን ፧ ስለ ፡ እነርሱስ ፡ ባል ፡ ማግባት ፡ ትተዋላችኹን ፧ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ወጥቷልና ፥ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ተመርሬያለኹ ።

ሩት ፥ 1 ፥ 14 ፤ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አለቀሱ ፤ ዖርፋም ፡ አማቷን ፡ ሳመች ፤ ሩት ፡ ግን ፡ ተጠጋቻት ።

ሩት ፥ 1 ፥ 15 ፤ ኑኃሚንም ፦ እንሆ ፥ ባልንጀራሽ ፡ ወደ ፡ ሕዝቧና ፡ ወደ ፡ አማልክቷ ፡ ተመልሳለች ፤ አንቺም ፡

ደግሞ ፡ ከባልንጀራሽ ፡ ጋራ ፡ ተመለሽ ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 1 ፡ 16 ፤ ሩትም ፦ ወደምትኼጂበት ፡ እኼዳለኹና ፥ በምታድሪበትም ፡ ዐድራለኹና ፡ እንድተውሽ ፡ ከአንቺም ፡ ዘንድ ፡ እንድመለስ ፡ አታስቸግሪኝ ፤ ሕዝብሽ ፡ ሕዝቤ ፥ አምላክሽም ፡ አምላኬ ፡ ይኾናል ፤

ሩት ፡ 1 ፡ 17 ፤ በምትሞችበትም ፡ ስፍራ ፡ እሞታለኹ ፥ በዚያም ፡ እቀበራለኹ ፤ ከሞት ፡ በቀር ፡ አንቺንና ፡ እኔን ፡ አንዳች ፡ ቢለየን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፡ እንዲሁም ፡ ይጨምርብኝ ፡ አለች ።

ሩት ፡ 1 ፡ 18 ፤ ኑኃሚንም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ለመኼድ ፡ እንደ ፡ ቈረጠች ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ርሷን ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ አለች ።

ሩት ፡ 1 ፡ 19 ፤ ኹለቱም ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ድረስ ፡ ኼዱ ። ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ የከተማዪቱ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፦ ይህች ፡ ኑኃሚን ፡ ናትን ፧ እያሉ ፡ ተንጫጩ ።

ሩት ፡ 1 ፡ 20 ፤ ርሷም ፦ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ አስመርሮኛልና ፥ ማራ ([131]) ፡ በሉኝ ፡ እንጂ ፡ ኑኃሚን ፡ አትበሉኝ ።

ሩት ፡ 1 ፡ 21 ፤ በሙላት ፡ ወጣኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ባዶዬን ፡ መለሰኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ አዋርዶኛልና ፥ ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ አስጨንቆኛልና ፥ ኑኃሚን ፡ ለምን ፡ ትሉኛላችኹ ፧ አለቻቸው ።

ሩት ፡ 1 ፡ 22 ፤ ኑኃሚንም ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ የተመለሰችው ፡ ሞዐባዊቱ ፡ ምራቷ ፡ ሩት ፡ ተመለሱ ። የገብስም ፡ መከር ፡ በተገመረ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ መጡ ።

መጽሐፈ ፡ ሩት ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሩት ፡ 2 ፡ 1 ፤ ለኑኃሚንም ፡ ባል ፡ የሚዘመደው ፡ ከአቢሜሌክ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡ ቦዔዝ ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሩት ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሞዐባዊቱም ፡ ሩት ፡ ኑኃሚንን ፦ በፊቱ ፡ ሞገስ ፡ የማገኘውን ፡ ተከትዬ ፡ እኽል ፡ እንድቃርም ፡ ወደ ፡ ዕርሻ ፡ ልኺድ ፡ አለቻት ። ርሷም ፦ ልጄ ፡ ሖይ ፥ ኺጂ ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 3 ፤ ኼደችም ፥ ከዐጫጆችም ፡ በኋላ ፡ በዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ቃረመች ፤ እንዳጋጣሚውም ፡ የአቢሜሌክ ፡ ወገን ፡ ወደነበረው ፡ ወደቦዔዝ ፡ ዕርሻ ፡ ደረሰች ።

ሩት ፡ 2 ፡ 4 ፤ እንሆም ፥ ቦዔዝ ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ መጣ ፥ ዐጫጆችንም ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፡ አላቸው ። እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 5 ፤ ቦዔዝም ፡ በዐጫጆች ፡ ላይ ፡ አዛዥ ፡ የነበረውን ፡ ሎሌውን ፦ ይህች ፡ ቈንጆ ፡ የማን ፡ ናት ፧ አለው ።

ሩት ፡ 2 ፡ 6 ፤ የዐጫጆቹም ፡ አዛዥ ፦ ይህችማ ፡ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ ከኑኃሚን ፡ ጋራ ፡ የመጣች ፡ ሞዐባዊቱ ፡ ቈንጆ ፡ ናት ፤

ሩት ፡ 2 ፡ 7 ፤ ርሷም ፦ ከዐጫጆቹ ፡ በኋላ ፡ በነዶው ፡ መካከል ፡ እንድቃርምና ፡ እንድለቅም ፥ እባክኽ ፥ ፍቀድልኝ ፡ አለች ፤ መጣችም ፥ ከማለዳም ፡ ገምራ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ቈይታለች ፤ በቤትም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ አላረፈችም ፡ አለው ።

ሩት ፡ 2 ፡ 8 ፤ ቦዔዝም ፡ ሩትን ፦ ልጄ ፡ ሖይ ፥ ትሰሚያለሽን ፧ ቃርሚያ ፡ ለመቃረም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዕርሻ ፡

131 ዕብ. ፥ ማራእ ፡ (መራራ) ።

አትኺጂ ፥ ከዚህም ፡ አትላወሺ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ገረዶቼን ፡ ተጠጊ ።

ሩት ፡ 2 ፡ 9 ፤ ወደሚያጭዱበትም ፡ ስፍራ ፡ ተመልከቺ ፥ ተከተያቸውም ፤ እንዳያስቸግሩሽም ፡ ጕበዛዝቱን ፡ አዝዣለኹ ፤ በተጠማሽም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማድጋው ፡ ኼደሽ ፡ ጕበዛዝቱ ፡ ከቀዱት ፡ ውሃ ፡ ጠጪ ፡ አላት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 10 ፤ በግንባሯም ፡ ተደፍታ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰገደችለት ፦ እኔንስ ፡ ለመቀበል ፡ በምን ፡ ነገር ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ አገኘኹ ፧ እኔ ፡ እንግዳ ፡ አይደለኹምን ፧ አለችው ።

ሩት ፡ 2 ፡ 11 ፤ ቦዔዝም ፦ ባልሽ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ አባትሽንና ፡ እናትሽን ፡ የተወለድሽባትንም ፡ ምድር ፡ ትተሽ ፡ ቀድሞ ፡ ወደማታውቂው ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ መጣሽ ፥ ለዐማትሽ ፡ ያደረግሽውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ ሰምቻለኹ ።

ሩት ፡ 2 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሥራሽ ፡ ይስጥሽ ፤ ከክንፉም ፡ በታች ፡ መጠጊያ ፡ እንድታገኚ ፡ በመጣሽበት ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ደመ ፡ ወዝሽ ፡ ፍጹም ፡ ይኹን ፡ አላት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 13 ፤ ርሷም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ከባሪያዎችኽ ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ሳልኾን ፡ አጽናንተኸኛልና ፥ የባሪያኽንም ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ አሠኝተኻልና ፥ በዐይንኽ ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለችው ።

ሩት ፡ 2 ፡ 14 ፤ በምሳም ፡ ጊዜ ፡ ቦዔዝ ፦ ወደዚህ ፡ ቅረቢ ፤ ምሳ ፡ ብዪ ፥ እንጀራሽንም ፡ በሖምጣጤው ፡ አጥቅሺ ፡ አላት ። በዐጫጆቹም ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠች ፡ የተጠበሰም ፡ እሸት ፡ ሰጣት ፥ በልታም ፡ ጠገበች ፥ አተረፈችም ።

ሩት ፡ 2 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፡ ልትቃርም ፡ በተነሣች ፡ ጊዜ ፡ ቦዔዝ ፡ ጕበዛዝቱን ፦ በነዶው ፡ መካከል ፡ ትቃርም ፥ እናንተም ፡ አታሳፍሯት ፤

ሩት ፡ 2 ፡ 16 ፤ ደግሞ ፡ ከነዶው ፡ አስቀርታችኹ ፡ ተዉላት ፤ ርሷም ፡ ትቃርም ፥ አትውቀሷትም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ሩት ፡ 2 ፡ 17 ፤ በዕርሻውም ፡ ውስጥ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ቃረመች ፤ የቃረመችውንም ፡ ወቃችው ፤ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ያኽልም ፡ ገብስ ፡ ኾነ ።

ሩት ፡ 2 ፡ 18 ፤ ተሸክማውም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባች ፥ አማቷም ፡ የቃረመችውን ፡ አየች ፤ ከጠገበችም ፡ በኋላ ፡ የተረፋትን ፡ አውጥታ ፡ ሰጠቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 19 ፤ አማቷም ፦ ዛሬ ፡ ወዴት ፡ ቃረምሽ ፧ ወዴትስ ፡ ሠራሽ ፧ የተቀበለሽ ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ አለቻት ። ርሷም ፦ ዛሬ ፡ የሠራኹበት ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ቦዔዝ ፡ ይባላል ፡ ብላ ፡ በማን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሠራች ፡ ለአማቷ ፡ ነገረቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 20 ፤ ኑኃሚንም ፡ ምራቷን ፦ ቸርነቱን ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡ አልተወምና ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ አለቻት ። ኑኃሚንም ፡ ደግሞ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ የቅርብ ፡ ዘመዳችን ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ሊቤዥን ፡ ከሚችሉት ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 21 ፤ ሞዐባዊቱ ፡ ሩትም ፦ ደግሞ ፦ መከሬን ፡ እስኪጨርሱ ፡ ድረስ ፡ ጕበዛዝቴን ፡ ተጠጊ ፡ አለኝ ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 22 ፤ ኑኃሚንም ፡ ምራቷን ፡ ሩትን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ከገረዶቹ ፡ ጋራ ፡ ብትወጪ ፥ በሌላም ፡ ዕርሻ ፡ ባያገኙሽ ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 2 ፡ 23 ፤ ሩትም ፡ የገብሱና ፡ የስንዴው ፡ መከር ፡ እስኪጨረስ ፡ ድረስ ፡ ልትቃርም ፡ የቦዔዝን ፡ ገረዶች ፡ ተጠጋች ፤ በአማቷም ፡ ዘንድ ፡ ትቀመጥ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ሩት ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሩት ፥ 3 ፥ 1 ፤ አማቷም ፡ ኑኃሚን ፡ አለቻት ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ መልካም ፡ እንዲኾንልሽ ፡ ዕረፍት ፡ አልፈልግልሽምን ፧

ሩት ፥ 3 ፥ 2 ፤ አኹንም ፡ ከገረዶቹ ፡ ጋራ ፡ የነበርሽበት ፡ ቦዔዝ ፡ ዘመዳችን ፡ አይደለምን ፧ እንሆ ፥ ርሱ ፡ በዛሬ ፡ ሌሊት ፡ በዐውድማው ፡ ላይ ፡ ገብሱን ፡ በመንሽ ፡ ይበትናል ።

ሩት ፥ 3 ፥ 3 ፤ እንግዲህ ፡ ታጠቢ ፥ ተቀቢ ፥ ልብስሽን ፡ ተላበሺ ፥ ወደ ፡ ዐውድማውም ፡ ውረጂ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መብሉንና ፡ መጠጡን ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ ለሰውዮው ፡ አትታዩው ።

ሩት ፥ 3 ፥ 4 ፤ በተኛም ፡ ጊዜ ፡ የሚተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ተመልከቺ ፥ ገብተሽም ፡ እግሩን ፡ ግለጪ ፥ ተጋደሚም ፤ የምታደርጊውንም ፡ ርሱ ፡ ይነግርሻል ።

ሩት ፥ 3 ፥ 5 ፤ ሩትም ፦ የተናገርሺኝን ፡ ኹሉ ፡ አደርጋለኹ ፡ አለቻት ።

ሩት ፥ 3 ፥ 6 ፤ ወደ ፡ ዐውድማውም ፡ ወረደች ፥ አማቷም ፡ ያዘዘቻትን ፡ ኹሉ ፡ አደረገች ።

ሩት ፥ 3 ፥ 7 ፤ ቦዔዝም ፡ ከበላና ፡ ከጠጣ ፡ ሰውነቱንም ፡ ደስ ፡ ካሠኘ ፡ በኋላ ፥ በእኽሉ ፡ ክምር ፡ አጠገብ ፡ ሊተኛ ፡ ኼደ ፤ ሩትም ፡ በቀስታ ፡ መጣች ፥ እግሩንም ፡ ገልጣ ፡ ተኛች ።

ሩት ፥ 3 ፥ 8 ፤ መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ደነገጠ ፥ ዘወርም ፡ አለ ፤ እንሆም ፥ አንዲት ፡ ሴት ፡ እግርጌው ፡ ተኝታ ፡ ነበር ።

ሩት ፥ 3 ፥ 9 ፤ ርሱም ፦ ማን ፡ ነሽ ፧ አለ ። ርሷም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ሩት ፡ ነኝ ፤ ዋርሳዬ ፡ ነኽና ፥ ልብስኽን ፡ በባሪያኽ ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ፡ አለችው ።

ሩት ፥ 3 ፥ 10 ፤ ቦዔዝም ፡ አላት ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ የተባረክሽ ፡ ኹኚ ፤ ባለጠጋም ፡ ድኻም ፡ ብለሽ ፡ ጐበዛዝትን ፡ አልተከተልሽምና ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ በመጨረሻው ፡ ጊዜ ፡ ቸርነት ፡ አድርገሻል ።

ሩት ፥ 3 ፥ 11 ፤ አኹንም ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አትፍሪ ፤ በአገሬ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ምግባረ ፡ መልካም ፡ ሴት ፡ እንደ ፡ ኾንሽ ፡ ያውቃሉና ፡ ያልሽውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አደርግልሻለኹ ።

ሩት ፥ 3 ፥ 12 ፤ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ መኾኔ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእኔ ፡ የቀረበ ፡ ዘመድ ፡ አለ ።

ሩት ፥ 3 ፥ 13 ፤ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ ዕደሪ ፤ ነገም ፡ ርሱ ፡ ዋርሳ ፡ መኾን ፡ ቢወድ ፡ መልካም ፡ ነው ፥ ዋርሳ ፡ ይኹን ፤ ዋርሳ ፡ ሊኾን ፡ ባይወድ ፡ ግን ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እኔ ፡ ዋርሳ ፡ እኾንሻለኹ ፤ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ተኚ ።

ሩት ፥ 3 ፥ 14 ፤ እስኪነጋም ፡ በእግርጌው ፡ ተኛች ፤ ቦዔዝም ፦ ሴት ፡ ወደ ፡ ዐውድማው ፡ እንደ ፡ መጣች ፡ ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፥ ገና ፡ ሰውና ፡ ሰው ፡ ሳይተያይ ፡ ተነሣች ።

ሩት ፥ 3 ፥ 15 ፤ ርሱም ፦ የለበስሽውን ፡ ኩታ ፡ አምጥተሽ ፡ ያዢው ፡ አላት ፤ በያዘችም ፡ ጊዜ ፡ ስድስት ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰፈረላት ፡ አሸከማትም ።

ሩት ፥ 3 ፥ 16 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ ኼደ ። ወደ ፡ አማቷም ፡ መጣች ፥ አማቷም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እንዴት ፡ ነሽ ፧ አለቻት ፤ ርሷም ፡ ሰውዮው ፡ ያደረገላትን ፡ ኹሉ ፡ ነገረቻት ።

ሩት ፥ 3 ፥ 17 ፤ ወደ ፡ ዐማትሽ ፡ ባዶ ፡ እጅሽን ፡ አትኺጂ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ስድስት ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰጠኝ ፡ አለቻት ።

ሩት ፡ 3 ፡ 18 ፤ ርሷም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ሰውዮው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዛሬ ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ አያርፍምና ፡ ፍጻሜው ፡ እስኪታወቅ ፡ ድረስ ፡ ዝም ፡ በዪ ፡ አለች ።

_____መጽሐፈ ፡ ሩት ፡ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ሩት ፡ 4 ፡ 1 ፤ ቦዔዝም ፡ ወደከተማዩቱ ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ወጥቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ። እንሆም ፥ ቦዔዝ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይናገር ፡ የነበረው ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፡ ሲያልፍ ፡ ቦዔዝ ፦ አንተ ፡ ቀርበኽ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ። ርሱም ፡ ቀረብ ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ፦ አንተ ፡ ቀርበኽ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ።

ሩት ፡ 4 ፡ 2 ፤ ቦዔዝም ፡ ከከተማዩቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ጠርቶ ፦ በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ።

ሩት ፡ 4 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፡ ተቀመጡ ። ቦዔዝም ፡ የቅርብ ፡ ዘመዱን ፦ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ የተመለሰችው ፡ ኑኃሚን ፡ የወንድማችንን ፡ የአቢሜሌክን ፡ ጢንጦ ፡ ትሸጣለች ።

ሩት ፡ 4 ፡ 4 ፤ እኔም ፡ በዚህ ፡ በተቀመጡት ፡ በሕዝቤ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ እንድትገዛው ፡ አስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰብኹ ። መቤዠት ፡ ብትወድ ፡ ተቤዠው ፤ መቤዠት ፡ ባትወድ ፡ ግን ፡ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ወራሽ ፡ የለምና ፥ እኔም ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ ነኝና ፥ እንዳውቀው ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ርሱም ፦ እቤዠዋለኹ ፡ አለው ።

ሩት ፡ 4 ፡ 5 ፤ ቦዔዝም ፦ ዕርሻውን ፡ ከኑኃሚን ፡ እጅ ፡ በምትገዛበት ፡ ቀን ፥ ለሞተው ፡ በርስቱ ፡ ስሙን ፡ እንድታስነሣለት ፡ ከሟቹ ፡ ሚስት ፡ ከሞዐባዊቱ ፡ ከሩት ፡ ደግሞ ፡ ትገዛለኽ ፡ አለ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 6 ፤ የቅርብ ፡ ዘመዱም ፦ የራሴን ፡ ርስት ፡ እንዳላበላሽ ፡ መቤዠት ፡ አልችልም ፤ እኔ ፡ መቤዠቱን ፡ አልችልምና ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡ መቤዠቱን ፡ ውሰደው ፡ አለ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 7 ፤ በጥንት ፡ ጊዜም ፥ ማንም ፡ ቢሸጥ ፡ ቢለውጥም ፥ ነገሩን ፡ ለማጽናት ፡ ሰው ፡ ጫማውን ፡ እንዲያወልቅ ፡ ለባልንጀራውም ፡ እንዲሰጠው ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በእስራኤል ፡ ምስክር ፡ ነበረ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 8 ፤ የቅርብ ፡ ዘመዱም ፡ ቦዔዝን ፦ አንተ ፡ ግዛው ፡ አለው ፤ ጫማውንም ፡ አወለቀ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 9 ፤ ቦዔዝም ፡ ሽማግሌዎችንና ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፦ ለአቢሜሌክና ፡ ለኬሌዎን ፡ ለመሐሎንም ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ከኑኃሚን ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ገዛኹ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡ ናችኹ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 10 ፤ ደግሞም ፡ የሟቹ ፡ ስም ፡ ከወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ከአገሩም ፡ ደጅ ፡ እንዳይጠፋ ፥ የሟቹን ፡ ስም ፡ በርስቱ ፡ ላይ ፡ እንዳስነሣ ፡ የመሐሎንን ፡ ሚስት ፡ ሞዐባዊቱን ፡ ሩትን ፡ ሚስት ፡ ትኾነኝ ፡ ዘንድ ፡ ወሰድኋት ፤ እናንተም ፡ ዛሬ ፡ ምስክሮች ፡ ናችኹ ፡ አላቸው ።

ሩት ፡ 4 ፡ 11 ፤ በከተማዩቱ ፡ በር ፡ አደባባይም ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ሽማግሌዎቹም ፦ እኛ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ የምትገባውን ፡ ሴት ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ እንደ ፡ ኹለቱ ፡ እንደ ፡ ራሔልና ፡ እንደ ፡ ልያ ፡ ያድርጋት ፤ አንተም ፡ በኤፍራታ ፡ ባለጠጋ ፡ ኹን ፥ ስምኽም ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ይጠራ ።

ሩት ፡ 4 ፡ 12 ፤ ቤትኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚች ፡ ቈንጕ ፡ ከሚሰጥኽ ፡ ዘር ፡ ትዕማር ፡ ለይሁዳ ፡ እንደ ፡ ወለደችው ፡ እንደ ፡ ፋሬስ ፡ ቤት ፡ ይኹን ፡ አሉት ።

ሩት ፡ 4 ፡ 13 ፤ ቦዔዝም ፡ ሩትን ፡ ወሰደ ፥ ሚስትም ፡ ኾነችው ፤ ደረሰባትም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ፅንስ ፡ ሰጣት ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ።

ሩት ፡ 4 ፡ 14 ፤ ሴቶችም ፡ ኑኃሚንን ፦ ዛሬ ፡ ዋርሳ ፡ ያላሳጣሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ፤ ስሙም ፡ በእስራኤል ፡ ይጠራ ።

ሩት ፥ 4 ፥ 15 ፤ ከሰባትም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ለአንቺ ፡ ከምትሻል ፡ ከምትወድሽ ፡ ምራት ፡
ተወልዷልና ፥ ሰውነትሽን ፡ ያሳድሰዋል ፥ በእርጅናሽም ፡ ይመግብሻል ፡ አሏት ።

ሩት ፥ 4 ፥ 16 ፤ ኑኃሚንም ፡ ሕፃኑን ፡ ወሰደች ፥ ዐቀፈችውም ፥ ሞግዚትም ፡ ኾነችው ።

ሩት ፥ 4 ፥ 17 ፤ ሴቶችም ፡ ጎረቤቶቿ ፥ ለኑኃሚን ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወለደላት ፡ እያሉ ፡ ስም ፡
አወጡለት ፤ ስሙንም ፡ ኢዮቤድ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ። ርሱም ፡ የዳዊት ፡ አባት ፡ የእሴይ ፡ አባት ፡ ነው ።

ሩት ፥ 4 ፥ 18 ፤ የፋሬስም ፡ ትውልድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ፋሬስ ፡ ኤስሮምን ፡ ወለደ ፥

ሩት ፥ 4 ፥ 19 ፤ ኤስሮምም ፡ አራምን ፡ ወለደ ፥ አራምም ፡ ዐሚናዳብን ፡ ወለደ ፥

ሩት ፥ 4 ፥ 20 ፤ ዐሚናዳብም ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ፥ ነአሶንም ፡ ሰልሞንን ፡ ወለደ ፥

ሩት ፥ 4 ፥ 21 ፤ ሰልሞንም ፡ ቦዔዝን ፡ ወለደ ፥

□□□4□22□ □□□

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ከአርማቴም ፡ መሴፋ ([132]) ፡ የኾነ ፡ ስሙ ፡ ሕልቃና ፡ የተባለ ፡ ኤፍሬማዊ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የኢያሬምኤል ([133]) ፡ ልጅ ፡ የኢሊዮ ([134]) ፡ ልጅ ፡ የቶሑ ፡ ልጅ ፡ የናሲብ ([135]) ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ኹለትም ፡ ሚስቶች ፡ ነበሩት ፤ የአንዲቱ ፡ ስም ፡ ሐና ፡ የኹለተኛዪቱም ፡ ስም ፡ ፍናና ፡ ነበረ ፤ ለፍናናም ፡ ልጆች ፡ ነበሯት ፥ ለሐና ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ አልነበራትም ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ያም ፡ ሰው ፡ በሴሎ ([136]) ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ከከተማው ፡ በየዓመቱ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። የእግዚአብሔርም ፡ ካህናት ፡ ኹለቱ ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ሕልቃና ፡ የሚሠዋበት ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜም ፡ ለሚስቱ ፡ ለፍናና ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ ዕጥሉ ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ሰጣቸው ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ሐናንም ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፥ ለሐና ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ሰጣት ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ማሕፀኗን ፡ ዘግቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ማሕፀኗን ፡ ዘግቶ ፡ ነበርና ፥ ጣውንቷ ፡ ታስቈጣት ፡ ታበሳጫትም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ በየዓመቱም ፡ እንዲህ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ርሷም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምትወጣበት ፡ ጊዜ ፡ ታበሳጫት ፡ ነበር ፤ ሐናም ፡ ታለቅስ ፡ ነበር ፥ አንዳችም ፡ አትቀምስም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ባሏም ፡ ሕልቃና ፦ ሐና ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ ታለቅሻለሽ ፧ ለምንስ ፡ አትቀምሺም ፧ ለምንስ ፡ ልብሽ ፡ ያዝንብሻል ፧ እኔስ ፡ ከዐሥር ፡ ልጆች ፡ አልሻልልሽምን ፧ አላት ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 9 ፤ በሴሎ ፡ ከበሉና ፡ ከጠጡ ፡ በኋላ ፡ ሐና ፡ ተነሣች ። ካህኑም ፡ ዔሊ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መቃን ፡ አጠገብ ፡ በመንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ርሷም ፡ በልቧ ፡ ትመረር ፡ ነበር ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጸለየች ፥ ጽኑ ፡ ልቅሶም ፡ አለቀሰች ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ርሷም ፦ አቤቱ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የባሪያህን ፡ መዋረድ ፡ ተመልከተኝ ፡ ብታስበኝ ፥ እኔንም ፡ ባትረሳ ፥ ለባሪያህም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ብትሰጥ ፥ ዕድሜውን ፡ ዕጥሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰጠዋለኹ ፥ ምላጭም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አይደርስም ፡ ብላ ፡ ስእለት ፡ ተሳለች ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ጸሎቷንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባበዛች ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ አፏን ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ሐናም ፡ በልቧ ፡ ትናገር ፡ ነበር ፤ ድምፂም ፡ ሳይሰማ ፡ ከንፈሯን ፡ ታንቀሳቅስ ፡ ነበር ፤ ዔሊም ፡ እንደ ፡ ሰከረች ፡ ቈጠራት ።

---

132 ዕብ. ፥ ራማታይም ፡ ጾፊይም ።
133 ዕብ. ፥ የሮኑም ።
134 ዕብ. ፡ ኤሊሁ ።
135 ዕብ. ፡ ጹፍ ።
136 ዕብ. ፥ ሺይሎህ / ሺሎ ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 14 ፤ ዔሊም ፦ ስካርሽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ የወይን ፡ ጠጅሽን ፡ ከአንቺ ፡ አርቂው ፡ አላት ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 15 ፤ ሐናም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አይደለም ፥ እኔስ ፡ ልቧ ፡ ያዘነባት ፡ ሴት ፡ ነኝ ፤ ጠጅና ፡ ሌላ ፡ የሚያሰክር ፡ ነገር ፡ አልጠጣኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ነፍሴን ፡ አፈሰስኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 16 ፤ ሐዘኔና ፡ ጭንቀቴ ፡ ስለ ፡ በዛ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ተናግሬያለኹና ፡ ባሪያኽን ፡ እንደ ፡ ምናምንቴ ፡ ሴት ፡ አትቊጠረኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 17 ፤ ዔሊም ፦ በደኅና ፡ ኺጂ ፥ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የለመንሽውን ፡ ልመና ፡ ይስጥሽ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 18 ፤ ርሷም ፦ ባሪያኽ ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለች ። ሴቲቱም ፡ መንገዷን ፡ ኼደች ፡ በላችም ፥ ፊቷም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ዐዘንተኛ ፡ መስሎ ፡ አልታየም ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 19 ፤ ማልደው ፡ ተነሥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰገዱ ፥ ተመልሰውም ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ መጡ ። ሕልቃናም ፡ ሚስቱን ፡ ሐናን ፡ ዐወቃት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዐሰባት ፤

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 20 ፤ የመፅነኗም ፡ ወራት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ሐና ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፤ ርሷም ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ለምኜዋለኹ ፡ ስትል ፡ ስሙን ፡ ሳሙኤል ([137]) ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 21 ፤ ሰውዮውም ፡ ሕልቃና ፡ ከቤተ ፡ ሰቡ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የዓመቱን ፡ መሥዋዕትና ፡ ስእለቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 22 ፤ ሐና ፡ ግን ፡ አልወጣችም ፥ ባሏንም ፦ ሕፃኑ ፡ ጡት ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ እቀመጣለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፥ በዚያም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አመጣዋለኹ ፡ አለችው ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 23 ፤ ባሏም ፡ ሕልቃና ፦ በዐይንሽ ፡ ደስ ፡ ያሠኘሽን ፡ አድርጊ ፥ ጡትም ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ ተቀመጪ ፤ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ ያጽና ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡ ልጇን ፡ እያጠባች ፡ ጡት ፡ እስኪተው ፡ ድረስ ፡ በቤቷ ፡ ተቀመጠች ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 24 ፤ ጡትም ፡ በተወ ፡ ጊዜ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ርሱንና ፡ አንድ ፡ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፥ አንድ ፡ አቍማዳ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አመጣችው ፤ ሕፃኑም ፡ ገና ፡ ታናሽ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 25 ፤ ወይፈኑንም ፡ ዐረዱ ፥ ሕፃኑንም ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡ አመጡት ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 26 ፤ ርሷም ፡ አለች ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ በሕያው ፡ ነፍስኽ ፡ እምላለኹ! ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመጸለይ ፡ በዚህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ቆማ ፡ የነበረች ፡ ሴት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፡ ሕፃን ፡ ጸለይኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 1 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የለመንኹትን ፡ ልመናዬን ፡ ሰጥቶኛል ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥቼዋለኹ ፤ ዕድሜውን ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ ይኾናል ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 1 ፤ ሐናም ፡ ስትጸልይ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦ ልቤ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸና ፥ ቀንዴ ፡ በእግዚአብሔር ፡

---

137 ዕብ. ፥ ሸሙኤል ፡ (ዐ. ፥ ስሙ ፡ ኤል)

ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ አፌ ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ተከፈተ ፤ በማዳንኽ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 2 ፤ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ የለምና ፥ እንደ ፡ አምላካችንም ፡ ጻድቅ ፡ የለምና ፤ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ቅዱስ ፡ የለም ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 3 ፤ አትታበዩ ፥ በኵራትም ፡ አትናገሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐዋቂ ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሥራውን ፡ የሚመዝን ፡ ነውና ፥ ከአፋችኹ ፡ የኵራት ፡ ነገር ፡ አይውጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 4 ፤ የኀያላንን ፡ ቀስት ፡ ሰብሯል ፥ ደካማዎችንም ፡ በኀይል ፡ ታጥቀዋል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 5 ፤ ጠግበው ፡ የነበሩ ፡ እንጀራ ፡ ዐጡ ፤ ተርበው ፡ የነበሩ ፡ ከራብ ፡ ዐርፈዋል ፤ መካኒቱ ፡ ሰባት ፡ ወልዳለችና ፥ ብዙም ፡ የወለደችው ፡ ደክማለች ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይገድላል ፡ ያድናልም ፤ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ያወርዳል ፥ ያወጣል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ድኻ ፡ ያደርጋል ፥ ባለጠጋም ፡ ያደርጋል ፤ ያዋርዳል ፥ ደግሞም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ ከሕዝቡ ፡ መኳንንት ፡ ጋራ ፡ ያስቀምጣቸው ፡ ዘንድ ፥ የክብርንም ፡ ዙፋን ፡ ያወርሳቸው ፡ ዘንድ ፥ ችግረኛውን ፡ ከመሬት ፡ ያስነሣል ፥ ምስኪኑንም ፡ ከጕድፍ ፡ ያስነሣል ፤ የምድር ፡ መሠረቶች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ናቸውና ፥ በእነርሱ ፡ ላይም ፡ ዓለምን ፡ አደረገ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ርሱ ፡ የቅዱሳኑን ፡ እግር ፡ ይጠብቃል ፡ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በጨለማ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ሰው ፡ በኀይሉ ፡ አይበረታምና ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚጣሉ ፡ ይደቃሉ ፤ በሰማይም ፡ ያንጐደጕድባቸዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይፈርዳል ፤ ለንጉሡም ፡ ኀይል ፡ ይሰጣል ፤ የመሲሑንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሕልቃናም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ኼደ ፤ ብላቴናውም ፡ በካህኑ ፡ በዔሊ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግል ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ የዔሊም ፡ ልጆች ፡ ምናምንቴዎች ፡ ነበሩ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አያውቁም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ የካህናትም ፡ ልማድ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መሥዋዕት ፡ ሲያቀርብ ፡ ሥጋው ፡ በተቀቀለ ፡ ጊዜ ፡ የካህኑ ፡ ሎሌ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ፥ በእጁም ፡ ሦስት ፡ ጣት ፡ ያለው ፡ ሜንጦ ፡ ነበረ ፤

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ድስቱም ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ምንቸቱ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አፍላሉ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ቶፋው ፡ ይሰደው ፡ ነበር ፤ ሜንጦውም ፡ ያወጣውን ፡ ኹሉ ፡ ካህኑ ፡ ለርሱ ፡ ይወስደው ፡ ነበር ። ወደዚያም ፡ በመጡት ፡ በእስራኤላውያን ፡ ላይ ፡ በሴሎ ፡ እንዲህ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፡ ስቡን ፡ ሳያቃጥሉ ፡ የካህኑ ፡ ሎሌ ፡ መጥቶ ፡ የሚሠዋውን ፡ ሰው ፦ ጥሬውን ፡ እንጂ ፡ የተቀቀለውን ፡ ሥጋ ፡ ከአንተ ፡ አይወስድምና ፡ እጠብስለት ፡ ዘንድ ፡ ለካህኑ ፡ ሥጋ ፡ ስጠኝ ፡ ይለው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ሰውየውም ፦ አስቀድሞ ፡ ስቡን ፡ ያቃጥሉት ፡ ኋላም ፡ ሰውነትኽ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኛትን ፡ ትወስዳለኽ ፡ ቢለው ፥ ርሱ ፦ አይኾንም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ ስጠኝ ፤ እንቢም ፡ ብትል ፡ በግድ ፡ እወስደዋለኹ ፡ ይለው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ሰዎቹም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍርባን ፡ ይንቁ ፡ ነበርና ፥ የጕበዛዝቱ ፡ ኀጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ሳሙኤል ፡ ግን ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ ለብሶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያገለግል ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ እናቱም ፡ ታናሽ ፡ መደረቢያ ፡ ሠራችለት ፥ በየዓመቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ለመሠዋት ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡ ስትወጣ ፡ ታመጣለት ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ ዔሊም ፡ ሕልቃናንና ፡ ሚስቱን ፦ ለእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ተሳለችው ፡ ስጦታ ፡ ፋንታ ፡ ከዚች ፡ ሴት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘር ፡ ይስጥህ ፡ ብሎ ፡ ባረካቸው ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሐናን ፡ ዐሰበ ፥ ፀነሰችም ፥ ሦስት ፡ ወንዶችና ፡ ኹለትም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለደች ። ብላቴናውም ፡ ሳሙኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አደገ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ዔሊም ፡ እጅግ ፡ አረጀ ፤ ልጆቹም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ኹሉ ፥ በመገናኛውም ፡ ድንኳን ፡ ደጅ ፡ ከሚያገለግሉት ፡ ሴቶች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተኙ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ አላቸው ፦ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራችኹ ፡ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ሰምቻለኹና ፡ ስለምን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ታደርጋላችኹ ፧

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 24 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ሕዝብ ፡ ኀጢአተኛ ፡ በማድረጋችኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የደረሰኝ ፡ ወሬ ፡ መልካም ፡ አይደለምና ፡ ይህ ፡ አይኾንም ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 25 ፤ ሰውስ ፡ ሰውን ፡ ቢበድል ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድበታል ፤ ሰው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢበድል ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሚለምን ፡ ማን ፡ ነው ፧ እነርሱ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊገድላቸው ፡ ወዷልና ፥ የአባታቸውን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 26 ፤ ብላቴናውም ፡ ሳሙኤል ፡ እያደገ ፡ ኼደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ በሰውም ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ እያገኘ ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 27 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡ መጥቶ ፡ አለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በግብጽ ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ ባሪያ ፡ ሳለ ፡ ለአባትኽ ፡ ቤት ፡ ተገለጥኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 28 ፤ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ካህን ፡ ይኾነኝ ፡ ዘንድ ፥ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፥ ዕጣንንም ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ ኤፉድንም ፡ በፊቴ ፡ ይለብስ ፡ ዘንድ ፡ ለእኔ ፡ መረጥኹት ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ የእሳት ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ምግብ ፡ ለአባትኽ ፡ ቤት ፡ ሰጠኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 29 ፤ በማደሪያዬ ፡ ያቀርቡት ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹትን ፡ መሥዋዕቴንና ፡ ቍርባኔን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ረገጣችኹ ፧ እንድትወፍሩም ፡ የሕዝቤን ፡ የእስራኤልን ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ መገሥመሪያ ፡ በመብላታችኹ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ልጆችኽን ፡ ለምን ፡ አከበርኽ ፧

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 30 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእውነት ፡ ቤትኽ ፡ የአባትኽም ፡ ቤት ፡ ለዘለዓለም ፡ በፊቴ ፡ እንዲኖር ፡ ተናግሬያለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያከበሩኝን ፡ አከብራለኹና ፥ የናቁኝም ፡ ይናቃሉና ፡ ይህ ፡ አይኾንልኝም ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 31 ፤ እንሆ ፥ ለቤትኽ ፡ ሽማግሌ ፡ እንዳይገኝ ፥ ክንድኽን ፡ የአባትኽንም ፡ ቤት ፡ ክንድ ፡ የምሰብርበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 32 ፤ በእስራኤል ፡ በረከት ፡ ኹሉ ፥ በማደሪያዬ ፡ ጠላትኽን ፡ ታያለኽ ፡ በቤትኽም ፡ ለዘለዓለም ፡ ሽማግሌ ፡ አይገኝም ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 33 ፤ ከመሠዊያዬ ፡ ያልተቈረጠ ፡ ልጅኽ ፡ ቢገኝ ፡ ዐይንኽን ፡ ያፈዘዋል ፥ ነፍስኽንም ፡ ያሳዝናል ፡ ከቤትኽም ፡ የሚወለዱ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በጐልማስነት ፡ ይሞታሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 34 ፤ ይህ ፡ በኹለቱ ፡ ልጆችኽ ፡ በአፍኒንና ፡ በፊንሐስ ፡ ላይ ፡ የሚመጣ ፡ ለአንተ ፡ ምልክት ፡ ነው ፤ ኹለቱ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ይሞታሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 35 ፤ የታመነም ፡ ካህን ፡ ለእኔ ፡ አስነሣለኹ ፥ በልቤም ፡ በነፍሴም ፡ እንዳለ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ፤ እኔም ፡ የታመነ ፡ ቤት ፡ እሠራለታለኹ ፥ ዘመኑን ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ በቀባኹት ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ይኼዳል ።

ሳሙ.1 ፡ 2 ፡ 36 ፤ ከቤትኽም ፡ የቀረው ፡ ኹሉ ፡ ይመጣል ፥ በፊቱም ፡ ሰግዶ ፥ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ እበላ ፡ ዘንድ ፡ ከካህናት ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ዕጣ ፥ እባክኽ ፥ ስደደኝ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ አንድ ፡ እንጀራም ፡ ይለምናል ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ብላቴናውም ፡ ሳሙኤል ፡ በዔሊ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግል ፡ ነበር ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ብርቅ ፡ ነበረ ፤ ራእይም ፡ አይገለጥም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የዔሊ ፡ ዐይኖች ፡ ማየት ፡ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ መፍዘዝ ፡ ገምረው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ዔሊም ፡ በስፍራው ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መብራት ፡ ገና ፡ ሳይጠፋ ፥ ሳሙኤልም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ባለበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፥

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሳሙኤልን ፡ ጠራው ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ዔሊም ፡ ሮጦ ፦ እንሆኝ ፡ የጠራኸኝ ፡ አለው ። ርሱም ፦ አልጠራኹኽም ፤ ተመልሰኽ ፡ ተኛ ፡ አለው ። ኼዶም ፡ ተኛ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፦ ሳሙኤል ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። ሳሙኤልም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡ ኼደና ፦ እንሆኝ ፡ የጠራኸኝ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አልጠራኹኽም ፤ ተመልሰኽ ፡ ተኛ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ሳሙኤል ፡ ግን ፡ ገና ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላወቀም ፡ ነበር ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ገና ፡ አልተገለጠለትም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ጠራው ። ርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዔሊ ፡ ኼደና ፦ እንሆኝ ፡ የጠራኸኝ ፡ አለ ። ዔሊም ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላቴናውን ፡ እንደ ፡ ጠራው ፡ አስተዋለ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ዔሊም ፡ ሳሙኤልን ፦ ኼደኽ ፡ ተኛ ፡ ቢጠራኽም ፦ አቤቱ ፥ ባሪያኽ ፡ ይሰማልና ፥ ተናገር ፡ በለው ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ ኼዶ ፡ በስፍራው ፡ ተኛ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መጥቶ ፡ ቆመ ፥ እንደ ፡ ቀድሞውም ፦ ሳሙኤል ፥ ሳሙኤል ፥ ብሎ ፡ ጠራው ። ሳሙኤልም ፦ ባሪያኽ ፡ ይሰማልና ፥ ተናገር ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ የሰማውን ፡ ኹሉ ፡ ኹለቱ ፡ ጉሮዎቹ ፡ ጭው ፡ የሚያደርግ ፡ አንድ ፡ ነገርን ፡ በእስራኤል ፡ አደርጋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ የተናገርኹትን ፡ ኹሉ ፡ በዔሊ ፡ አወርዳለኹ ፤ እኔም ፡ ገምሬ ፡ እፈጽምበታለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ልጆቹ ፡ የርግማን ፡ ነገር ፡ እንዳደረጉ ፡ ዐውቆ ፡ አልከለከላቸውምና ፡ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ በቤት ፡ ለዘለዓለም ፡ እንድፈርድ ፡ አስታውቄዋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ የዔሊ ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ በመሥዋዕትና ፡ በቍርባን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዳይሰረይለት ፡ ለዔሊ ፡ ቤት ፡ ምያለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ሳሙኤልም ፡ እስከ፡ነጋ ፡ ተኛ ፥ ማልዶም ፡ ተነሥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ከፈተ ። ሳሙኤልም ፡ ራእዩን ፡ ለዔሊ ፡ መንገር ፡ ፈራ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ ዔሊም ፡ ሳሙኤልን ፡ ጠርቶ ፦ ልጄ ፡ ሳሙኤል ፡ ሆይ ፥ አለ ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ የነገረኽ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ከእኔ ፡ አትሸሽግ ፤ ከነገረኽ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሸሸግኸኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያድርግብኽ ፥ እንዲህም ፡ ይጨምርብኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ሳሙኤልም ፡ ነገሩን ፡ ኹሉ ፡ ነገረው ፥ አንዳችም ፡ አልሸሸገውም ። ዔሊም ፦ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ደስ ፡ ያሠኘውን ፡ ያድርግ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 19 ፤ ሳሙኤልም ፡ አደገ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ከቃሉም ፡ አንዳች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይወድቅም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 20 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ ሳሙኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የታመነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በሴሎ ፡ ተገለጠ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለሳሙኤል ፡ በሴሎ ፡ ይገለጥ ፡ ነበር ። የሳሙኤልም ፡ ቃል ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ደረሰ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 1 ፤ እስራኤልም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሊዋጋ ፡ ወጡ ፥ በአቤንዔዘር ([138]) ፡ አጠገብ ፡ ሰፈሩ ፤ ፍልስጥኤማውያን ፡ በአፌቅ ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 2 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ፤ ሰልፉም ፡ በተመደበ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ተመቱ ፤ ጦርነት ፡ በተደረገበትም ፡ ስፍራ ፡ ከእስራኤል ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎችን ፡ ገደሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፦ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መታን ፧ በመካከላችን ፡ እንዲኼዱ ፥ ከጠላቶቻችንም ፡ እጅ ፡ እንዲያድነን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ከሴሎ ፡ እናምጣ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ላኩ ፥ በኪሩቤልም ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ አመጡ ፤ ኹለቱም ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ እልልታ ፡ አደረጉ ፥ ምድሪቱም ፡ አስተጋባች ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእልልታውን ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ በዕብራውያን ፡ ሰፈር ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ የእልልታ ፡ ድምፅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉ ። የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡

---

138 ዕብ. ፥ ኤቤንዔዜር ፡ (እብን ፡ ዐዘር • ረዳት ፡ ድንጋይ) ።

አስተዋሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ፈርተው ፦ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ መጥቷል ፡ አሉ ። ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ ወዮልን ፤ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ አልኾነም ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ወዮልን ፤ ከነዚህ ፡ ከኀያላን ፡ አማልክት ፡ እጅ ፡ ማን ፡ ያድነናል ፧ እነዚህ ፡ አማልክት ፡ ግብጻውያንን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በልዩ ፡ በልዩ ፡ መቅሠፍት ፡ የመቱ ፡ ናቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሆይ ፥ አይዟችኹ ፥ ጐብዙ ፤ እናንተ ፡ ባሪያዎች ፡ እንዳደረጋችኋቸው ፡ ዕብራውያን ፡ ባሪያዎች ፡ እንዳያደርጓችኹ ፡ ጐብዙ ፥ ተዋጉ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ተዋጉ ፤ እስራኤልም ፡ ተመቱ ፥ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ ሸሹ ፤ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ግድያ ፡ ኾነ ፥ ከእስራኤልም ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ እግረኞች ፡ ወደቁ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ተማረከች ፥ ኹለቱም ፡ የዔሊ ፡ ልጆች ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ ሞቱ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ የብንያም ፡ ሰው ፡ ከሰልፍ ፡ እየበረረ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ልቡ ፡ ተናውጦ ፡ ነበርና ፥ በመንገድ ፡ ዳር ፡ በወንበሩ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ሰውዮውም ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ገብቶ ፡ ባወራ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዪቱ ፡ ኹሉ ፡ ተጯጯኸች ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ ዔሊም ፡ የጩኸቱን ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ ጫጫታ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ። ሰውዮውም ፡ ፈጥኖ ፡ መጣና ፡ ለዔሊ ፡ ነገረው ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ ዔሊም ፡ የዘጠና ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፡ ነበረ ፤ ዐይኖቹም ፡ ማየት ፡ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ ፈዘው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ሰውዮውም ፡ ዔሊን ፦ ከሰልፍ ፡ የመጣኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ ዛሬም ፡ ከሰልፍ ፡ ኰበለልኹ ፡ አለ ። ርሱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ነገሩሳ ፡ እንዴት ፡ ኾነ ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ወሬኛውም ፡ መልሶ ፦ እስራኤል ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፤ ደግሞ ፡ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ግድያ ፡ ኾኗል ፥ ኹለቱም ፡ ልጆችኽ ፡ አፍኒንና ፡ ፊንሐስ ፡ ሞተዋል ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ተማርካለች ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ሰውዮውም ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ዔሊ ፡ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ካለው ፡ ከወንበሩ ፡ ወደቀ ፤ ርሱ ፡ ሽምግሎ ፡ ደንግዞም ፡ ነበርና ፥ ዐንገቱ ፡ ተሰብሮ ፡ ሞተ ። ርሱም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ፈራጅ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 19 ፤ ምራቱም ፡ የፊንሐስ ፡ ሚስት ፡ አርግዛ ፡ ልትወልድ ፡ ተቃርባ ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ እንደ ፡ ተማረከች ፥ አማቷና ፡ ባሏም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ምጥ ፡ ደርሶባት ፡ ነበርና ፥ ተንበርክካ ፡ ወለደች ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ሞትም ፡ በቀረበች ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉት ፡ ሴቶች ፦ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወልደሻልና ፥ አትፍሪ ፡ አሏት ። ርሷ ፡ ግን ፡ አልመለሰችላቸውም ፥ በልቧም ፡ አላኖረችውም ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 21 ፤ ርሷም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ስለ ፡ ተማረከች ፡ ስለ ፡ አማቷና ፡ ስለ ፡ ባሏም ፦ ክብር ፡ ከእስራኤል ፡ ለቀቀ ፡ ስትል ፡ የሕፃኑን ፡ ስም ፦ ኢካቦድ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

ሳሙ.1 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ርሷም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ተማርካለችና ፡ ክብር ፡ ከእስራኤል ፡ ለቀቀ ፡ አለች ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወሰዱ ፤ ከአቤንዔዘርም ፡ ወደ ፡ አዛጦን ፡ ይዘውት ፡ መጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወስደው ፡ ወደዳጎን ፡ ቤት ፡ አገቡት ፥ በዳጎንም ፡ አጠገብ ፡ አኖሩት ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ በነጋውም ፡ የአዛጦን ፡ ሰዎች ፡ ማለዱ ፥ እንሆም ፥ ዳጎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ፤ ዳጎንንም ፡ አንሥተው ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ መለሱት ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ በነጋውም ፡ ማለዱ ፥ እንሆም ፥ ዳጎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ፤ የዳጎንም ፡ ራስ ፡ እጆቹም ፡ ተቈርጠው ፡ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ ነበር ፤ የዳጎንም ፡ ደረት ፡ ብቻውን ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ስለዚህም ፡ የዳጎን ፡ ካህናት ፡ ወደዳጎንም ፡ ቤት ፡ የሚገቡት ፡ ኹሉ ፡ በአዛጦን ፡ ያለውን ፡ የዳጎንን ፡ መድረክ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አይረግጡም ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በአዛጦን ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ከበደች ፥ አጠፋቸውም ፥ አዛጦንንና ፡ ድንበራቸውንም ፡ በዕባጭ ፡ መታቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ የአዛጦንም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ እጁ ፡ በእኛና ፡ በአምላካችን ፡ በዳጎን ፡ ላይ ፡ ጠንክራለችና ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አይቀመጥ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ልከውም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ሰበሰቡና ፦ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ አሉ ፤ እነርሱም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ይዙር ፡ ብለው ፡ መለሱ ። የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ወደዚያ ፡ ተሸከሙት ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ከተሸከሙትም ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ በከተማዪቱ ፡ ላይ ፡ ኾነች ፤ ከታናሹም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ የከተማዪቱን ፡ ሰዎች ፡ መታ ፥ ዕባጭም ፡ መጣባቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ አስቀሎና ፡ ሰደዱት ። የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ አስቀሎና ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አስቀሎናውያን ፦ እኛንና ፡ ሕዝባችንን ፡ ሊገድሉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ አመጡብን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ በከተማዪቱ ፡ ኹሉ ፡ የሞት ፡ ድንጋጤ ፡ ነበርና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በዚያ ፡ እጅግ ፡ ከብዳ ፡ ነበርና ፥ ልከው ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰብስበው ፦ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ስደዱ ፥ እኛንና ፡ ሕዝባችንን ፡ እንዳይገድል ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይመለስ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ ያልሞቱትም ፡ ሰዎች ፡ በዕባጭ ፡ ተመቱ ፤ የከተማዪቱም ፡ ዋይታ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 2 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ካህናትንና ፡ ሟርተኞችን ፡ ጠርተው ፦ በእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ላይ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ ወደ ፡ ስፍራውስ ፡ በምን ፡ እንስደደው ፧ አስታውቁን ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፦ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ታቦት ፡ ብትሰዱ ፡ የበደል ፡ መሥዋዕት ፡ መልሱለት ፡ እንጂ ፡ ባዶውን ፡ አትስደዱት ፥ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ትፈወሳላችኹ ፤ እጁም ፡ ከእናንተ ፡ አለመራቁ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቃላችኹ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፦ ስለ ፡ በደል ፡ መሥዋዕት ፡ የምንመልስለት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉ ። እነርሱም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እናንተንና ፡ አለቃዎቻችኹን ፡ ያገኘች ፡ መቅሠፍት ፡ አንዲት ፡ ናትና ፥ እንደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፡ ቍጥር ፡ ዐምስት ፡ የወርቅ ፡ ዕባጮች ፡ ዐምስትም ፡ የወርቅ ፡ ዐይጦች ፡ አቅርቡ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 5 ፤ የዕባጫችኹንም ፡ ምሳሌ ፥ ምድራችኹንም ፡ የሚያጠፉትን ፡ የዐይጦችን ፡ ምሳሌ ፡ አድርጋችኹ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ክብርን ፡ ስጡ ፤ እጁን ፡ ከእናንተና ፡ ከአማልክታችኹ ፡ ከምድራችኹም ፡ ምናልባት ፡ ያቀል ፡ ይኾናል ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ግብጻውያንና ፡ ፈርዖንም ፡ ልባቸውን ፡ እንዳጸኑ ፡ ልባችኹን ፡ ለምን ፡ ታጸናላችኹ ፧ እግዚአብሔር ፡ ኀይሉን ፡ ካደረገባቸው ፡ በኋላ ፡ ያወጧቸው ፡ አይደሉምን ፧

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፡ አልኼዱምን ፧ አኹንም ፡ ወስዳችኹ ፡ አንዲት ፡ ሠረገላ ፡ ሥሩ ፤ የሚያጠቡም ፥ ቀንበር ፡ ያልተጫነባቸውን ፡ ኹለት ፡ ላሞች ፡ በሠረገላ ፡ ጥመዷቸው ፥ እንቦሶቻቸውንም ፡ ለይታችኹ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መልሷቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ወስዳችኹ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ አኑሩት ፤ ስለ ፡ በደልም ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀረባችኹትን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ በሣጥን ፡ ውስጥ ፡ አድርጋችኹ ፡ በታቦቱ ፡ አጠገብ ፡ አኑሩት ፤ ይኼድም ፡ ዘንድ ፡ ስደዱት ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ተመልከቱም ፡ በድንበሩም ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ቢወጣ ፡ ይህን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ያደረገብን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ አለዚያም ፡ እንዲያው ፡ መጥቶብናል ፡ እንጂ ፡ የመታን ፡ የርሱ ፡ እጅ ፡ እንዳልኾነ ፡ እናውቃለን ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ሰዎቹም ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ፤ የሚያጠቡትን ፡ ኹለቱን ፡ ላሞች ፡ ወሰዱ ፥ በሠረገላም ፡ ጠመዷቸው ፥ እንቦሶቻቸውንም ፡ በቤት ፡ ዘጉባቸው ፤

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፥ የወርቁ ፡ ዐይጦችና ፡ የዕባጮቻቸው ፡ ምሳሌ ፡ ያሉበትንም ፡ ሣጥን ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 12 ፤ ላሞችም ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ወደሚወስደው ፡ መንገድ ፡ አቅንተው ፡ እምቧ ፡ እያሉ ፡ በጐዳናው ፡ ላይ ፡ ኼዱ ፥ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አላሉም ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቃዎች ፡ እስከ ፡ ቤትሳሚስ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ በኋላ ፡ በኋላቸው ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 13 ፤ የቤትሳሚስ ፡ ሰዎችም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ስንዴ ፡ ያጭዱ ፡ ነበር ፤ ዐይናቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ታቦቱን ፡ አዩ ፥ በማየታቸውም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ሠረገላውም ፡ ወደ ፡ ቤትሳሚሳዊው ፡ ወደኢያሱ ፡ ዕርሻ ፡ መጣ ፥ ታላቅም ፡ ድንጋይ ፡ በነበረበት ፡ በዚያ ፡ ቆመ ፤ የሠረገላውንም ፡ ዕንጨት ፡ ፈልጠው ፡ ላሞቹን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ሌዋውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበረውንም ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ያለበትን ፡ ሣጥን ፡ አወረዱ ፥ በታላቁም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አኖሩት ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የቤትሳሚስ ፡ ሰዎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፥ መሥዋዕትንም ፡ ሠዉ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 16 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዐምስቱ ፡ አለቃዎች ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አስቀሎና ፡

ተመለሱ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 17 ፤ ፍልስጥኤማውያን ፡ ስለ ፡ በደል ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀረቧቸው ፡ የወርቅ ፡ ዕባጮች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ አንዲቱ ፡ ለአዛጦን ፥ አንዲቱም ፡ ለጋዛ ፥ አንዲቱም ፡ ለአስቀሎና ፥ አንዲቱ ፡ ለጌት ፥

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 18 ፤ አንዲቱ ፡ ለዐቃሮን ፡ የወርቁም ፡ ዐይጦች ፡ ቍጥር ፡ ለዐምስቱ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ቍጥር ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድንጋይ ፡ የሚደርሱ ፡ ከተማዎችና ፡ መንደሮች ፡ ናቸው ። በዚህም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ አስቀመጡ ፥ ድንጋዩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በቤትሳሚሳዊው ፡ በኢያሱ ፡ ዕርሻ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 19 ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ውስጥ ፡ ተመልክተዋልና ፥ የቤትሳሚስን ፡ ሰዎች ፡ መታ ፤ በሕዝቡም ፡ ከዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ሰባ ፡ ሰዎችን ፡ መታ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሕዝቡን ፡ በታላቅ ፡ ግዳይ ፡ ስለ ፡ መታ ፡ ሕዝቡ ፡ አለቀሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 20 ፤ የቤትሳሚስም ፡ ሰዎች ፦ በዚህ ፡ በቅዱስ ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መቆም ፡ ማን ፡ ይችላል ፧ ከእኛስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ማን ፡ ይኼዳል ፧ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 6 ፡ 21 ፤ በቂርያትይዓሪምም ፡ ወደተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ መልክተኞች ፡ ልከው ፦ ፍልስጥኤማውያን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ መልሰዋል ፤ ወርዳችኹም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አውጡት ፡ አሉ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 1 ፤ የቂርያትይዓሪም ፡ ሰዎችም ፡ መጥተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ አወጡ ፥ በኮረብታውም ፡ ላይ ፡ ወዳለው ፡ ወደዐሚናዳብ ፡ ቤት ፡ አገቡት ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ እንዲጠብቅ ፡ ልጁን ፡ አልዓዛርን ፡ ቀደሱት ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 2 ፤ ታቦቱም ፡ በቂርያትይዓሪም ፡ ከተቀመጠበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ወራቱ ፡ ረዘመ ፥ ኻያ ፡ ዓመትም ፡ ኾነ ፤ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ዐዝኖ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተከተለ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 3 ፤ ሳሙኤልም ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፦ በሙሉ ፡ ልባችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተመለሳችኹ ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክትና ፡ ዐስታሮትን ፡ ከመካከላችኹ ፡ አርቁ ፥ ልባችኹንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቅኑ ፥ ርሱንም ፡ ብቻ ፡ አምልኩ ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ ያድናችኋል ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በዓሊምንና ፡ ዐስታሮትን ፡ አራቁ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ብቻ ፡ አመለኩ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ሳሙኤልም ፦ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ሰብስቡ ፥ ስለ ፡ እናንተም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ምጽጳም ፡ ተሰበሰቡ ፤ ውሃም ፡ ቀድተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አፈሰሱ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጾሙ ፥ በዚያም ፦ እግዚአብሔርን ፡ በድለናል ፡ አሉ ። ሳሙኤልም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ በምጽጳ ፡ ፈረደ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 7 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ወጡ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሰምተው ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሳሙኤልን ፦ ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትጸልይልን ፡ ዘንድ ፡ አትታክት ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 9 ፤ ሳሙኤልም ፡ አንድ ፡ የሚጠባ ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ ወስዶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ የሚቃጠል ፡

መሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ አቀረበው ፤ ሳሙኤልም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሰማው ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 10 ፤ ሳሙኤልም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ሲያሳርግ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ቀረቡ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነጐድጓድ ፡ አንጐደጐደ ፥ አስደነገጣቸውም ፡ በእስራኤልም ፡ ፊት ፡ ድል ፡ ተመቱ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 11 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከምጽጳ ፡ ወጡ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ አሳደዱ ፤ በቤትካር ፡ ታችም ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ መቷቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 12 ፤ ሳሙኤልም ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ ወስዶ ፡ በምጽጳና ፡ በሼን ፡ መካከል ፡ አኖረው ፤ ስሙንም ፦ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረድቶናል ፡ ሲል ፡ አቤንዔዘር ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 13 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ተዋረዱ ፥ ዳግመኛም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደእስራኤል ፡ ድንበር ፡ አልወጡም ፤ በሳሙኤል ፡ ዕድሜ ፡ ዘመኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ ነበረች ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 14 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከአስቀሎና ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ጌት ፡ ድረስ ፡ ከእስራኤል ፡ የወሰዷቸው ፡ ከተማዎች ፡ ለእስራኤል ፡ ተመለሱ ፤ እስራኤልም ፡ ድንበሩን ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አዳነ ። በእስራኤልና ፡ በአሞራውያንም ፡ መካከል ፡ ዕርቅ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 15 ፤ ሳሙኤልም ፡ በዕድሜው ፡ ዘመኑ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 16 ፤ በየዓመቱም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ወደ ፡ ምጽጳም ፡ ይዞር ፡ ነበር ፤ በእነዚያም ፡ ስፍራዎች ፡ ዘሙኑ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 7 ፡ 17 ፤ ቤቱም ፡ በዚያ ፡ ነበረና ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ይመለስ ፡ ነበር ፤ በዚያም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፥ በዚያም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሳሙኤል ፡ በሸመገለ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጆች ፡ አደረጋቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 2 ፤ የበኩር ፡ ልጁም ፡ ስም ፡ ኢዮኤል ፥ የኹለተኛውም ፡ ስም ፡ አብያ ([139]) ፡ ነበረ ። እነርሱም ፡ በቤርሳቤሕ ፡ ይፈርዱ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 3 ፤ ልጆቹም ፡ በመንገዱ ፡ አልኼዱም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ረብ ፡ ለማግኘት ፡ ፈቀቅ ፡ አሉ ፥ ጉቦም ፡ እየተቀበሉ ፡ ፍርድን ፡ ያጣምሙ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘሙኑ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ መጡና ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ ሽምግለኻል ፥ ልጆችኽም ፡ በመንገድኽ ፡ አይኼዱም ፤ አኹንም ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ዘሙኑ ፡ የሚፈርድልን ፡ ንጉሥ ፡ አድርግልን ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 6 ፤ የሚፈርድልንም ፡ ንጉሥ ፡ ስጠን ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፡ ነገሩ ፡ ሳሙኤልን ፡ አስከፋው ፤ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ።

---

139 ዕብ. ፥ አቢያህ ፡ (አበ ፡ ያህ ፥ አምላክን ፡ የታመነ ፡ አባት) ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፡ አለው ፦ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንዳልነግሥ ፡ እኔን ፡ እንጂ ፡ አንተን ፡ አልናቁምና ፡ በሚሉኽ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሕዝቡን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 8 ፤ ከግብጽ ፡ ካወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እኔን ፡ ትተው ፡ እንግዳዎች ፡ አማልክት ፡ በማምለካቸው ፡ እንደ ፡ ሥሩት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ባንተ ፡ ደግሞ ፡ ያደርጉብኻል ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 9 ፤ አኹንም ፡ ቃላቸውን ፡ ስማ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽኑ ፡ ምስክር ፡ መስክርባቸው ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የሚነግሠውን ፡ የንጉሡን ፡ ወግ ፡ ንገራቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 10 ፤ ሳሙኤልም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ንጉሥን ፡ ለፈለጉ ፡ ሕዝብ ፡ ነገራቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የሚነግሠው ፡ የንጉሡ ፡ ወግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወንዶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ ወስዶ ፡ ሠረገለኞችና ፡ ፈረሰኞች ፡ ያደርጋቸዋል ፥ በሠረገላዎቹም ፡ ፊት ፡ ይሮጣሉ ፤

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 12 ፤ ለራሱም ፡ የሻለቃዎችና ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ያደርጋቸዋል ፤ ዕርሻውንም ፡ የሚያርሱ ፡ እኽሉንም ፡ የሚያጭዱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውንና ፡ የሠረገላዎቹንም ፡ ዕቃ ፡ የሚሠሩ ፡ ይኾናሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 13 ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹንም ፡ ወስዶ ፡ ሽቶ ፡ ቀማሚዎችና ፡ ወጥቤቶች ፡ ዐበዛዎችም ፡ ያደርጋቸዋል ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 14 ፤ ከዕርሻችኹና ፡ ከወይናችኹም ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ ወስዶ ፡ ለሎሌዎቹ ፡ ይሰጣቸዋል ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 15 ፤ ከዘራችኹና ፡ ከወይናችኹም ፡ ዓሥራት ፡ ወስዶ ፡ ለጃን ፡ ደረባዎቹና ፡ ለሎሌዎቹ ፡ ይሰጣቸዋል ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 16 ፤ ሎሌዎቻችኹንና ፡ ገረዶቻችኹን ፥ ከከብቶቻችኹና ፡ ከአህያዎቻችኹም ፡ መልካም ፡ መልካሞቹን ፡ ወስዶ ፡ ያሠራቸዋል ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 17 ፤ ከበጎቻችኹና ፡ ከፍየሎቻችኹ ፡ ዓሥራት ፡ ይወስዳል ፤ እናንተም ፡ ባሪያዎች ፡ ትኾኑታላችኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ለእናንተ ፡ ከመረጣችኹት ፡ ከንጉሣችኹ ፡ የተነሣ ፡ ትጮኻላችኹ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ አልሰማችኹም ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 19 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ የሳሙኤልን ፡ ነገር ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ። እንዲህ ፡ አይኹን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሥ ፡ ይኹንልን ፥

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 20 ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ እንኾናለን ፤ ንጉሣችንም ፡ ይፈርድልናል ፥ በፊታችንም ፡ ወጥቶ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ይዋጋል ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 21 ፤ ሳሙኤልም ፡ የሕዝቡን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ሰማ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ተናገረ ።

ሳሙ.1 ፡ 8 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፦ ቃላቸውን ፡ ስማ ፥ ንጉሥም ፡ አንግሥላቸው ፡ አለው ። ሳሙኤልም ፡ የእስራኤልን ፡ ሰዎች ፦ እያንዳንዳችኹ ፡ ወደ ፡ ከተማችኹ ፡ ኺዱ ፡ አላቸው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 1 ፤ ስሙ ፡ ቂስ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ብንያማዊ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የአቢኤል ፡ ልጅ ፥ የጽሮር ፡ ልጅ ፥ የብኮራት ፡ ልጅ ፥ የብንያማዊው ፡ የአፌቅ [140] ፡ ልጅ ፥ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 2 ፤ ለርሱም ፡ ሳኦል ፡ የሚባል ፡ የተመረጠ ፡ መልካም ፡ ልጅ ፡ ነበረው ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ መልካም ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ከሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ከትከሻውና ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡

140 ዕብ. ፥ አፍያሕ ።

ቁመቱ ፡ ዘለግ ፡ ያለ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 3 ፤ የሳኦልም ፡ አባት ፡ የቂስ ፡ አህያዎች ፡ ጠፍተው ፡ ነበር ፤ ቂስም ፡ ልጁን ፡ ሳኦልን ፦ ከብላቴናዎቹ ፡ አንዱን ፡ ወስደኽ ፡ ተነሣ ፥ አህያዎችንም ፡ ለመሻት ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 4 ፤ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገርና ፡ በሻሊሻ ፡ ዐለፉ ፥ አላገኟቸውምም ፡ በሻዕሊም ፡ ምድርም ፡ ዐለፉ ፥ በዚያም ፡ አልነበሩም ፤ በብንያም ፡ ምድርም ፡ ዐለፉ ፥ አላገኟቸውምም ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 5 ፤ ወደጹፍ ፡ ምድር ፡ በመጡ ፡ ጊዜም ፡ ሳኦል ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበረውን ፡ ብላቴና ፦ አባቴ ፡ ስለ ፡ አህያዎች ፡ ማሰብ ፡ ትቶ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እንዳይጨነቅ ፥ ና ፥ እንመለስ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ አለ ፤ ርሱም ፡ የተከበረ ፡ ሰው ፡ ነው ፥ የሚናገረውም ፡ ሹሉ ፡ በእውነት ፡ ይፈጸማል ፤ አኹን ፡ ወደዚያ ፡ እንኺድ ፤ ምናልባት ፡ የምንኼድበትን ፡ መንገድ ፡ ይነግረናል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 7 ፤ ሳኦልም ፡ ብላቴናውን ፦ እንሆ ፥ እንኼዳለን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ምን ፡ እናመጣለታለን ፧ እንጀራ ፡ ከከረጢታችን ፡ አልቋልና ፥ እጅ ፡ መንሻም ፡ የለንምና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ የምናመጣለት ፡ ምን ፡ አለን ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 8 ፤ ብላቴናው ፡ ደግሞ ፡ ለሳኦል ፡ መልሶ ፦ እንሆ ፥ በእጄ ፡ የሰቅል ፡ ብር ፡ ሩቡ ፡ አለኝ ፤ ርሱንም ፡ መንገዳችንን ፡ እንዲነግረን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እሰጣለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 9 ፤ ዛሬ ፡ ነቢይ ፡ የሚባለው ፡ ቀድሞ ፡ ባለራእይ ፡ ይባል ፡ ነበርና ፥ አስቀድሞ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ሲኼድ ፦ ኑ ፥ ወደ ፡ ባለራእይ ፡ እንኺድ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ሳኦልም ፡ ብላቴናውን ፦ የተናገረኸው ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ና ፥ እንኺድ ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወዳለበት ፡ ከተማ ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 11 ፤ በከተማዩቱም ፡ ዳገት ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ቈነጕሮች ፡ ውሃውን ፡ ሊቀዱ ፡ ሲወጡ ፡ አገኙና ፦ ባለራእይ ፡ በዚህ ፡ አለ ፡ ወይ ፧ አሏቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ አዎን ፤ እንሆ ፥ በፊታችኹ ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ መጥቷልና ፥ ዛሬም ፡ ሕዝቡ ፡ በኰረብታው ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ መስገጃ ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ አለባቸውና ፡ ፈጥናችኹ ፡ ውጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 13 ፤ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ መሥዋዕቱን ፡ ርሱ ፡ የሚባርክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ርሱ ፡ ሳይወጣ ፡ ሕዝቡ ፡ ምንም ፡ አይቀምሱምና ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የተጠሩት ፡ ይበላሉና ፡ ለመብላት ፡ ወደኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ሳይወጣ ፡ ታገኙታላችኹ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ታገኙታላችኹና ፡ አኹን ፡ ውጡ ፡ አሏቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ ወጡ ፤ በከተማዩቱም ፡ ውስጥ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሳሙኤል ፡ ወደኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ለመውጣት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 15 ፤ ገናም ፡ ሳኦል ፡ ሳይመጣ ፡ ካንድ ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳሙኤልን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገልጦለት ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 16 ፤ ነገ ፡ በዚች ፡ ሰዓት ፡ ከብንያም ፡ አገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እሰድልኻለኹ ፤ ልቅሷቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የደረስ ፡ ሕዝቤን ፡ ተመልክቻለኹና ፡ ለሕዝቤ ፡ ለእስራኤል ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ትቀባዋለኽ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ ሕዝቤን ፡ ያድናል ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 17 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፦ ያ ፡ የነገርኹኽ ፡ ሰው ፡ እንሆ ፤ ርሱም ፡

በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥናል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 18 ፤ ሳኦልም ፡ በበሩ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀርቦ ፦ የባለራእዩ ፡ ቤት ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ እባክኽ ፥ ንገረኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 19 ፤ ሳሙኤልም ፡ መልሶ ፡ ሳኦልን ፦ ባለራእዩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ዛሬም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትበላላችኹና ፡
በፊቴ ፡ ወደከሠረብታው ፡ መስገጃ ፡ ውጡ ፤ ነገም ፡ አሰናብትኻለኹ ፥ በልብኽም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ እነግርኻለኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 20 ፤ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በፊት ፡ የጠፉ ፡ አህያዎችኽ ፡ ተገኝተዋልና ፥ ልብኽን ፡
አትጣልባቸው ። የእስራኤል ፡ ምኞት ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ለአንተና ፡ ለአባትኽ ፡ ቤት ፡ አይደለምን ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 21 ፤ ሳኦልም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ከሚያንስ ፡ ወገን ፡ የኾንኹ ፡ ብንያማዊ ፡
አይደለኹምን ፧ ወገኔስ ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ የሚያንስ ፡ አይደለምን ፧ እንዲህስ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡
ለምን ፡ ነገርኸኝ ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 22 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልንና ፡ ብላቴናውን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ አዳራሽ ፡ አገባቸው ፥ በመርፈቂያውም ፡
ራስ ፡ አስቀመጣቸው ፤ የተጠሩትም ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ያኽል ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 23 ፤ ሳሙኤልም ፡ ወጥቤቱን ፦ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አኑረው ፡ ብዬ ፡ የሰጠኹኽን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡
አምጣ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 24 ፤ ወጥቤቱም ፡ ጭኑንና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ አምጥቶ ፡ በሳኦል ፡ ፊት ፡
አኖረው ። ሳሙኤልም ፦ ሕዝቡን ፡ ከጠራኹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ለአንተ ፡
ተጠብቋልና ፥ እንሆ ፥ የተቀመጠልኽን ፡ በፊትኽ ፡ አኑረኽ ፡ ብላው ፡ አለ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኦል ፡ ከሳሙኤል ፡ ጋራ ፡
በላ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 25 ፤ ከከሠረብታውም ፡ መስገጃ ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ ወረዱ ፤ ሳሙኤልም ፡ ለሳኦል ፡ በሰገነቱ ፡ ላይ ፡
መኝታ ፡ አዘጋጀለት ፥ ርሱም ፡ ተኛ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 26 ፤ ማልዶም ፡ ተነሡ ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳኦልን ፡ ከሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ጠርቶ ፦ ተነሣና ፡
ላሰናብትኽ ፡ አለው ። ሳኦልም ፡ ተነሣ ፥ ርሱና ፡ ሳሙኤልም ፡ ኹለቱ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 9 ፡ 27 ፤ እነርሱም ፡ በከተማዩቱ ፡ ዳር ፡ ሲወርዱ ፡ ሳሙኤል ፡ ሳኦልን ፦ ብላቴናውን ፡ ወደ ፡ ፊታችን ፡
እንዲያልፍ ፡ እዘዘው ፤ አንተ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አሰማኽ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቁም ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡
ዐለፈ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 1 ፤ ሳሙኤልም ፡ የዘይቱን ፡ ብርሌ ፡ ወስዶ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰው ፥ ሳመውም ፥ እንዲህም ፡
አለው ፦ በርስቱ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶኻል ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ሕዝብ ፡
ትገዛለኽ ፥ በዙሪያውም ፡ ካሉ ፡ ጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ታድናቸዋለኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 2 ፤ ዛሬ ፡ ከእኔ ፡ በተለየኽ ፡ ጊዜ ፡ በብንያም ፡ ዳርቻ ፡ በጼልጻህ ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በራሔል ፡
መቃብር ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ታገኛለኽ ፤ እነርሱም ፦ ልትሻቸው ፡ ኼደኽ ፡ የነበርኽላቸው ፡ አህያዎች ፡
ተገኝተዋል ፤ እንሆም ፥ አባትኽ ፡ ስለ ፡ አህያዎች ፡ ማሰብ ፡ ትቶ ፦ የልጄን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ አደርጋለኹ ፧ እያለ ፡
ስለ ፡ እናንተ ፡ ይጨነቃል ፡ ይሉኻል ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 3 ፤ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ትኼዳለኽ ፤ ወደ ፡ ታቦር ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ዛፍ ፡
ትደርሳለኽ ፤ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፥ አንዱ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፥ አንዱ ፡ ሦስት ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶች ፥ ኹለተኛው ፡ ሦስት ፡

ዳቦ ፥ ሦስተኛውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አቀ-ማዳ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ሲወጡ ፡ ያገኙኻል ፤

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 4 ፤ ሰላምታም ፡ ይሰጡኻል ፥ ኹለትም ፡ ዳቦ ፡ ይሰጡኻል ፥ ከእጃቸውም ፡ ትቀበላለኽ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 5 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ ወዳለበት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ኰረብታ ፡ ትመጣለኽ ፤ ወደዚያም ፡ ወደ ፡ ከተማዩቱ ፡ በደረስኽ ፡ ጊዜ ፥ በገናና ፡ ከበሮ ፡ እንቢልታና ፡ መሰንቆ ፡ ይዘው ፡ ትንቢት ፡ እየተናገሩ ፡ ከኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ የሚወርዱ ፡ የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ ያገኙኻል ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በኀይል ፡ ይወርድብኻል ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ትንቢት ፡ ትናገራለኽ ፥ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ኾነኽ ፡ ትለወጣለኽ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 7 ፤ እነዚህም ፡ ምልክቶች ፡ በደረሱኽ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ እጅኽ ፡ የምታገኘውን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 8 ፤ በፊቴም ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ትወርዳለኽ ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፥ የደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ እሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተ ፡ እወርዳለኹ ፤ እኔ ፡ ወዳንተ ፡ እስክመጣና ፡ የምታደርገውን ፡ እስክነግርኽ ፡ ድረስ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ትቈያለኽ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 9 ፤ ከሳሙኤልም ፡ ዘንድ ፡ ለመኼድ ፡ ፊቱን ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሌላ ፡ ልብ ፡ ለወጠለት ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ምልክቶች ፡ ኹሉ ፡ ደረሱለት ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 10 ፤ ወደዚያም ፡ ኰረብታ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ አገኙት ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በኀይል ፡ ወረደበት ፥ በመካከላቸውም ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 11 ፤ ቀድሞም ፡ የሚያውቁት ፡ ኹሉ ፡ ከነቢያት ፡ ጋራ ፡ ትንቢት ፡ ሲናገር ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ። የቂስን ፡ ልጅ ፡ ያገኘው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእውኑ ፡ ሳኦል ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ ነውን ፧ ተባባሉ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 12 ፤ ከዚያም ፡ ስፍራ ፡ ያለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፦ አባታቸውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ መለሰ ። ስለዚህም ፦ ሳኦል ፡ ደግሞ ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ ነውን ፧ የሚል ፡ ምሳሌ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 13 ፤ ትንቢት ፡ መናገሩንም ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወደኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 14 ፤ አጎቱም ፡ ሳኦልንና ፡ ብላቴናውን ፥ ወዴት ፡ ኼዳችኹ ፡ ኖሯል ፧ አላቸው ። ርሱም ፦ አህያዎችን ፡ ልንሻ ፡ ኼደን ፡ ነበር ፤ ባጣናቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣን ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 15 ፤ የሳኦልም ፡ አጎት ፦ ሳሙኤል ፡ የነገረኽን ፥ እባክኽ ፥ ንገረኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 16 ፤ ሳኦልም ፡ አጎቱን ፦ አህያዎች ፡ እንደ ፡ ተገኙ ፡ ገለጠልን ፡ አለው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሳሙኤል ፡ የነገረውን ፡ የመንግሥትን ፡ ነገር ፡ አላወራለትም ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 17 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ጠራ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 18 ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣኹ ፥ ከግብጻውያንም ፡ እጅ ፡ ከሚያስጨንቋችኹም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ አዳንኋችኹ ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 19 ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ ከመከራችኹና ፡ ከጭንቃችኹ ፡ ኹሉ ፡ ያዳናችኹን ፡ አምላካችኹን ፡ ንቃችኹ ። እንዲህ ፡ አይኹን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሥ ፡ አታንግሥልን ፡ አላችኹት ። አኹንም ፡ በየነገዳችኹና ፡ በየወገናችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅረቡ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፥ 10 ፥ 20 ፤ ሳሙኤልም ፡ የእስራኤልን ፡ ነገዶች ፡ ኹሉ ፡ አቀረበ ፥ ዕጣውም ፡ በብንያም ፡ ነገድ ፡ ላይ ፡

ወደቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 21 ፤ የብንያምንም ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ አቀረበ ፥ ዕጣውም ፡ በማጥሪ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡
ወደቀ ። የማጥሪንም ፡ ወገን ፡ በየሰዉ ፡ አቀረበ ፥ ዕጣውም ፡ በቂስ ፡ ልጅ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡
ወደቀ ፤ ፈለጉትም ፥ አላገኙትምም ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 22 ፤ ከእግዚአብሔርም ፦ ገና ፡ ወደዚህ ፡ የሚመጣ ፡ ሰው ፡ አለን ፧ ብለው ፡ ደግሞ ፡
ጠየቁት ፤ እግዚአብሔርም ፦ እንሆ ፥ በዕቃ ፡ መካከል ፡ ተሸሽጓል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፡ ሮጠው ፡ ከዚያ ፡ አመጡት ፤ ርሱም ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ቆመ ፥ ከሕዝቡም ፡
ዥሉ ፡ ይልቅ ፡ ከትከሻው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቁመተ ፡ ረዥም ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 24 ፤ ሳሙኤልም ፡ ለሕዝቡ ፡ ዥሉ ፦ ከሕዝቡ ፡ ዥሉ ፡ ርሱን ፡ የሚመስል ፡ እንደሌለ ፡
እግዚአብሔር ፡ የመረጠውን ፡ ታያላችኹን ፧ አላቸው ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፦ ንጉሥ ፡ ሕያው ፡ ይኹን ፡ እያሉ ፡ እልልታ ፡
አደረጉ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 25 ፤ ሳሙኤልም ፡ የመንግሥቱን ፡ ወግ ፡ ነገረ ፥ በመጽሐፍም ፡ ጻፈው ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡
አኖረው ። ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ ዥሉ ፡ ወደ ፡ እየቤታቸው ፡ አሰናበታቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 26 ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ኼደ ፤ እግዚአብሔር ፡ ልባቸውን ፡ የነካ ፡ ኀያላንም ፡
ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 10 ፡ 27 ፤ ምናምንቴዎች ፡ ሰዎች ፡ ግን ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ያድነናል ፧ ብለው ፡ ናቁት ፥ እጅ ፡
መንሻም ፡ አላመጡለትም ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ካንድ ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ አሞናዊው ፡ ናዖስ ፡ ወጣ ፥ በኢያቢስ ፡ ገለዓድም ፡
ሰፈረ ፤ የኢያቢስም ፡ ሰዎች ፡ ዥሉ ፦ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርግልን ፥ እኛም ፡ እንገዛልኻለን ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 2 ፤ አሞናዊውም ፡ ናዖስ ፦ ቀኝ ፡ ዐይናችኹን ፡ ዥሉ ፡ በማውጣት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
አደርግላችኋለኹ ፤ በእስራኤልም ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ስድብ ፡ አደርጋለኹ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 3 ፤ የኢያቢስም ፡ ሽማግሌዎች ፦ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ ዥሉ ፡ መልክተኞችን ፡ እንድንልክ ፡ ሰባት ፡
ቀን ፡ ቈይልን ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሚያድነን ፡ ባይኖር ፡ ወዳንተ ፡ እንመጣለን ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 4 ፤ መልክተኞቹም ፡ ሳኦል ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ መጥተው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሕዝቡ ፡ ጐሮ ፡
ተናገሩ ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አለቀሱ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 5 ፤ እንሆም ፥ ሳኦል ፡ በሬዎቹን ፡ ተከትሎ ፡ ከዕርሻው ፡ መጣ ፤ ሳኦልም ፦ ሕዝቡ ፡ የሚያለቅስ ፡
ምን ፡ ኾኖ ፡ ነው ፧ አለ ። የኢያቢስንም ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ በሰማው ፡ ጊዜ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በኀይል ፡
ወረደ ፥ ቍጣውም ፡ እጅግ ፡ ነደደ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 7 ፤ ጥምዱንም ፡ በሬዎች ፡ ወስዶ ፡ ቈራረጣቸው ፥ ወደእስራኤልም ፡ ዳርቻ ፡ ዥሉ ፡ በመልክተኞቹ ፡
እጅ ፡ ሰደደና ፦ ሳኦልንና ፡ ሳሙኤልን ፡ ተከትሎ ፡ የማይወጣ ፡ ዥሉ ፥ በበሬዎቹ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግ ፡
አለ ። ድንጋጤም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደቀ ፥ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ኾነው ፡ ወጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 8 ፤ በቤዜቅም ፡ ቈጠራቸው ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፥ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 9 ፤ የመጡትንም ፡ መልክተኞች ፦ የኢያቢስ ፡ ገለዓድን ፡ ሰዎች ፦ ነገ ፡ ፀሓይ ፡ በተኰሰ ፡ ጊዜ ፡ ማዳን ፡ ይኾንላችኋል ፡ በሏቸው ፡ አሏቸው ። መልክተኞችም ፡ መጥተው ፡ ለኢያቢስ ፡ ሰዎች ፡ ነገሩ ፤ ደስም ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 10 ፤ የአያቢስም ፡ ሰዎች ፦ ነገ ፡ እንወጣላችኋለን ፥ ደስ ፡ የሚያሠኛችኹንም ፡ አድርጉብን ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 11 ፤ በነጋውም ፡ ሳኦል ፡ ሕዝቡን ፡ በሦስት ፡ ወገን ፡ አደረጋቸው ፤ ወገግም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ወደሰፈሩ ፡ መካከል ፡ ገቡ ፥ ቀትርም ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ አሞናውያንን ፡ መቱ ፤ የቀሩትም ፡ ተበተኑ ፥ ኹለትም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ አልቀሩላቸውም ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 12 ፤ ሕዝቡም ፡ ሳሙኤልን ፦ ሳኦል ፡ አይንገሥብን ፡ ያሉ ፡ እነማናቸው ፧ አውጧቸውና ፡ እንግደላቸው ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 13 ፤ ሳኦልም ፦ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ማዳን ፡ አድርጓልና ፥ ዛሬ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይሞትም ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 14 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፦ ኑ ፥ ወደ ፡ ገልገላ ፡ እንኺድ ፥ በዚያም ፡ መንግሥቱን ፡ እናድስ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 11 ፡ 15 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ኼዱ ፥ በዚያም ፡ ሳኦልን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በገልገላ ፡ አነገሡት ፤ በዚያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፤ በዚያም ፡ ሳኦልና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ አደረጉ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 1 ፤ ሳሙኤልም ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ አለ ፦ የነገራችኹኝን ፡ ኹሉ ፡ ሰምቼ ፡ አንግሼላችኋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 2 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ንጉሡ ፡ በፊታችኹ ፡ ይኼዳል ፤ እኔም ፡ አርጅቻለኹ ፡ ሽምግያለኹም ፤ እንሆም ፥ ልጆቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ፤ እኔም ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ዠምሬ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በፊታችኹ ፡ ኼድኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 3 ፤ እንሆኝ ፤ በእግዚአብሔርና ፡ ርሱ ፡ በቀባው ፡ ፊት ፡ መስክሩብኝ ፤ የማንን ፡ በሬ ፡ ወሰድኹ ፧ የማንንስ ፡ አህያ ፡ ወሰድኹ ፧ ማንንስ ፡ ሸነገልኹ ፧ በማንስ ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ አደረግኹ ፧ ዐይኖቼንስ ፡ ለማሳወር ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ እጅ ፡ ጉቦ ፡ ተቀበልኹ ፧ እኔም ፡ እመልስላችኋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፦ አልሸነገልኸንም ፥ ግፍም ፡ አላደረግኽብንም ፥ ከሰውም ፡ እጅ ፡ ምንም ፡ አልወሰድኽም ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ በእጄ ፡ ምንም ፡ እንዳላገኛችኹ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ርሱ ፡ የቀባው ፡ ዛሬ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምስክሮች ፡ ናቸው ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፦ ምስክር ፡ ነው ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ያላቀ ፥ አባቶቻችኹንም ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ስላደረገው ፡ ጽድቅ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እሟገታችኹ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ቁሙ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ያዕቆብና ፡ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ግብጻውያን ፡ አስጨነቋቸው ፤ አባቶቻችኹም ፡
ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ላከ ፥ አባቶቻችኹንም ፡ ከግብጽ ፡ አውጥተው ፡
በዚህ ፡ ቦታ ፡ አኖሯቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 9 ፤ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረሱ ፥ ለአሶር ፡ ሰራዊትም ፡ አለቃ ፡ ለሢሣራ ፡
እጅ ፥ ለፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፥ ለሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 10 ፤ እነርሱም ፦ እግዚአብሔርን ፡ ትተን ፡ በዓሊምንና ፡ ዐስታሮትን ፡ በማምለካችን ፡
በድለናል ፤ አኹንም ፡ ከጠላቶቻችን ፡ እጅ ፡ አድነን ፥ እናመልክሽማለን ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይሩበአልም ፥ ባርቅንም ፥ ዮፍታሔንም ፥ ሳሙኤልንም ፡ ላከ ፥ በዙሪያችኹም ፡
ካሉት ፡ ከጠላቶቻችኹ ፡ እጅ ፡ አዳናችኹ ፤ ተዘልላችኹም ፡ ተቀመጣችኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 12 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ናያስ ፡ እንደ ፡ መጣባችኹ ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፥ አምላካችኹ ፡
እግዚአብሔር ፡ ንጉሣችኹ ፡ ሳለ ። እንዲህ ፡ አይኹን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሥ ፡ ይንገሥልን ፡ አላችኹኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ የመረጣችኹትንና ፡ የፈለጋችኹትን ፡ ንጉሥ ፡ እዩ ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡
ንጉሥ ፡ አደረገላችኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ብትፈሩ ፡ ብታመልኩትም ፥ ቃሉንም ፡ ብትሰሙ ፥ በእግዚአብሔርም ፡
ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ ባታምፁ ፥ እናንተና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ንጉሥ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡
ብትከተሉ ፥ መልካም ፡ ይኾንላችኋል ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡
ብታምፁ ፥ በእናንተና ፡ በንጉሣችኹ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ትኾናለች ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 16 ፤ አኹንም ፡ ቁሙ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ ወደሚያደርገው ፡ ወደዚህ ፡ ታላቅ ፡
ነገር ፡ ተመልከቱ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 17 ፤ የስንዴ ፡ መከር ፡ ዛሬ ፡ አይደለምን ፧ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጮኻለኹ ፥ ርሱም ፡ ነጐድጓድና ፡
ዝናብ ፡ ይልካል ፤ እናንተም ፡ ንጉሥ ፡ በመለመናችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያደረጋችኹት ፡ ክፋት ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡
ኾነ ፡ ታውቃላችኹ ፡ ታያላችኹም ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 18 ፤ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ነጐድጓድና ፡
ዝናብ ፡ ላከ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሳሙኤልን ፡ እጅግ ፡ ፈሯቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 19 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ሳሙኤልን ፦ ንጉሥ ፡ በመለመናችን ፡ በኀጢአታችን ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡
ክፋት ፡ ጨምረናልና ፥ እንዳንሞት ፡ ስለ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 20 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ አትፍሩ ፤ በእውነት ፡ ይህን ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡
አደረጋችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔርን ፡ በፍጹም ፡ ልባችኹ ፡ አምልኩት ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡
ፈቀቅ ፡ አትበሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ምናምንቴ ፡ ነውና ፥ የማይረባንና ፡ የማያድን ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ለመከተል ፡ ፈቀቅ ፡ አትበሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለርሱ ፡ ሕዝብ ፡ ያደርጋችኹ ፡ ዘንድ ፡ ወዷልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ታላቅ ፡
ስሙ ፡ ሕዝቡን ፡ አይተውም ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 23 ፤ ደግሞ ፡ መልካሙንና ፡ ቅኑን ፡ መንገድ ፡ አስተምራችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ መጸለይን ፡

በመተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እበድል ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 24 ፤ ብቻ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፥ ያደረገላችኹንም ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አይታችኋልና ፥ በፍጹም ፡ ልባችኹ ፡ በእውነት ፡ አምልኩት ።

ሳሙ.1 ፡ 12 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ ብትሠሩ ፡ እናንተም ፡ ንጉሣችኹም ፡ ትጠፋላችኹ ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። _____

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 1 ፤ ሳኦልም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፥

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 2 ፤ ሳኦል ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ከእስራኤል ፡ መረጠ ፤ ኹለቱም ፡ ሺሕ ፡ በማክማስና ፡ በቤቴል ፡ ተራራ ፡ ከሳኦል ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፥ አንዱም ፡ ሺሕ ፡ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ከዮናታን ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፤ የቀረውንም ፡ ሕዝብ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ አሰናበተ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 3 ፤ ዮናታንም ፡ በናሲብ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ መታ ፥ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ያን ፡ ሰሙ ፤ ሳኦልም ፦ ዕብራውያን ፡ ይስሙ ፡ ብሎ ፡ በአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 4 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ሳኦል ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ እንደ ፡ መታ ፥ ደግሞም ፡ እስራኤል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጸየፉ ፡ ሰሙ ፤ ሕዝቡም ፡ ሳኦልን ፡ ለመከተል ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ተሰበሰቡ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 5 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ተሰበሰቡ ፤ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሠረገላዎች ፡ ስድስትም ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኞች ፡ በባሕርም ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ፤ ወጥተውም ፡ ከቤትአዌን ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በማክማስ ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 6 ፤ ሕዝቡም ፡ ተጨንቀው ፡ ነበርና ፥ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ በጭንቀት ፡ እንዳሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በዋሻና ፡ በሾኽ ፡ ቀጥቋጦ ፡ በገደልና ፡ በግንብ ፡ በጉድጓድም ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸጉ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ከዕብራውያንም ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ ጋድና ፡ ወደገለዓድ ፡ ምድር ፡ ኼዱ ፤ ሳኦል ፡ ግን ፡ ገና ፡ በገልገላ ፡ ነበረ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ተንቀጥቅጠው ፡ ተከተሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 8 ፤ ሳኦልም ፡ ሳሙኤል ፡ እንደ ፡ ቀጠረው ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ቈየ ፤ ሳሙኤል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ አልመጣም ፥ ሕዝቡም ፡ ከርሱ ፡ ተለይተው ፡ ተበታተኑ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 9 ፤ ሳኦልም ፦ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ። የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረገ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 10 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ማሳረግ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሳሙኤል ፡ መጣ ፤ ሳኦልም ፡ እንዲመርቀው ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 11 ፤ ሳሙኤልም ፦ ያደረግኸው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ። ሳኦልም ፦ ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ተለይተው ፡ እንደ ፡ ተበታተኑ ፥ አንተም ፡ በቀጠሮው ፡ እንዳልመጣኽ ፥ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወደ ፡ ማክማስ ፡ እንደ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አየኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፦ ፍልስጥኤማውያን ፡ አኹን ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ይወርዱብኛል ፥ እኔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሞገስ ፡ አልለመንኹም ፡ አልኹ ፤ ስለዚህም ፡ ሳልታገሥ ፡ የሚቃጠልን ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረግኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 13 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፦ አላበጀኽም ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘኽን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅኽም ፤ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትኽን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አጽንቶልኽ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 14 ፤ አኹንም ፡ መንግሥትኽ ፡ አይጸናም ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ልቡ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ መርጧል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘኽን ፡ አልጠበቅኽምና ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አዞታል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 15 ፤ ሳሙኤልም ፡ ከገልገላ ፡ ተነሥቶ ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ሳኦልን ፡ ተከተለው ፡ ሰልፈኞቹን ፡ ሊገናኙ ፡ ኼዱ ። ከገልገላም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ጊብዓ ፡ መጡ ፤ ሳኦልም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ቈጠረ ፥ ስድስት ፡ መቶም ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 16 ፤ ሳኦልና ፡ ልጁ ፡ ዮናታንም ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ተቀመጡ ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ በማክማስ ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 17 ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ሰፈር ፡ ማራኪዎች ፡ በሦስት ፡ ክፍል ፡ ኾነው ፡ ወጡ ፤ አንዱም ፡ ክፍል ፡ በያፍራ ፡ መንገድ ፡ ወደሦጋል ፡ ምድር ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 18 ፤ ኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሖሮን ፡ መንገድ ፡ ዞረ ፤ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ በበረሓው ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ወደሰቦይም ፡ ሸለቆ ፡ በሚመለከተው ፡ በዳርቻ ፡ መንገድ ፡ ዞረ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 19 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፦ ዕብራውያን ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ እንዳይሠሩ ፡ ብለው ፡ ነበርና ፥ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ብረተ ፡ ሠሪ ፡ አልተገኘም ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 20 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ የማረሻውን ፡ ጫፍና ፡ ማጭዱን ፡ መጥረቢያውንና ፡ መቈፈሪያውን ፡ ይስል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ይወርድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 21 ፤ ለማረሻው ፡ ጫፍና ፡ ለመቈፈሪያው ፡ ዋጋው ፡ የሰቅል ፡ ከ፤ ፡ እጅ ፡ ፤ቱ ፡ እጅ ፡ ነበረ ። መጥረቢያውንም ፡ ለማሳል ፡ መውጊያውንም ፡ ለማብጀት ፡ ዋጋው ፡ የሰቅል ፡ ከ 3 ፡ እጅ ፡ ፭ዱ ፡ እጅ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 13 ፡ 22 ፤ ስለዚህም ፡ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ ከሳኦልና ፡ ከዮናታን ፡ ጋራ ፡ በነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ አልተገኘም ፤ ብቻ ፡ በሳኦልና ፡ በልጁ ፡ በዮናታን ፡ ዘንድ ፡ ተገኘ ። የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ ወደማክማስ ፡ መተላለፊያ ፡ ወጡ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 1 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬውን ፦ ና ፥ በዚያ ፡ በኩል ፡ ወዳለው ፡ ወደፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ እንለፍ ፡ አለው ፤ ለአባቱም ፡ አልነገረውም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 2 ፤ ሳኦልም ፡ በመጌዶን ፡ ባለው ፡ በሮማኑ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ በጊብዓ ፡ ዳርቻ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበረ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ የሚያኽል ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 3 ፤ የኢካቦድ ፡ ወንድም ፡ የአኪጦብ ([141]) ፡ ልጅ ፡ የፊንሐስ ፡ ልጅ ፡ የዔሊ ፡ ልጅ ፡ በሴሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ የኾነ ፡ ኤፉድም ፡ የለበሰ ፡ አኪያ ፡ ዐብሮ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡ ፡ ዮናታን ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ አላወቁም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 4 ፤ ዮናታንም ፡ ወደፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ ሊሻገርበት ፡ በወደደው ፡ መተላለፊያ ፡ መካከል ፡ በወዲህ ፡ አንድ ፡ ሾጣጣ ፡ በወዲህ ፡ አንድ ፡ ሾጣጣ ፡ ድንጋዮች ፡ ነበሩ ፤ የአንዱም ፡ ስም ፡ ቦጼጽ ፡ የኹለተኛውም ፡ ስም ፡ ሴኔ ፡ ነበረ ።

---

141 ዕብ. ፥ አኒጦብ ፡ (አኅወ ፡ ጦቢያ ፥ የመልካም ፡ የበጎ ፡ ወንድም) ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 5 ፤ አንዱም ፡ ሾጣጣ ፡ በማክማስ ፡ አንጻር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፥ ኹለተኛውም ፡ በጊብዓ ፡ አንጻር ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የቆሙ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 6 ፤ ዮናታንም ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬውን ፦ ና ፥ ወደ ፡ እነዚህ ፡ ቈላፋን ፡ ጭፍራ ፡ እንለፍ ፤ በብዙ ፡ ወይም ፡ በጥቂት ፡ ማዳን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያስቸግረውምና ፡ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሠራልን ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 7 ፤ ጋሻ ፡ ጭግሬውም ፦ ልብኽ ፡ ያሠኘኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ፤ እንሆ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፤ እንደ ፡ አንተ ፡ ልብ ፡ ኹሉ ፡ የእኔም ፡ ልብ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 8 ፤ ዮናታንም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ እናልፋለን ፡ እንገለጥላቸውማለን ፤

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፦ ወደ ፡ እናንተ ፡ እስክንመጣ ፡ ድረስ ፡ ቈዩ ፡ ቢሉን ፡ በስፍራችን ፡ እንቆማለን ፥ ወደ ፡ እነርሱም ፡ አንወጣም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ወደ ፡ እኛ ፡ ውጡ ፡ ቢሉን ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷቸዋልና ፥ እንወጣለን ፤ ምልክታችንም ፡ ይህ ፡ ይኾናል ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 11 ፤ ኹለታቸውም ፡ ለፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ ተገለጡ ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፦ እንሆ ፥ ዕብራውያን ፡ ከተሸሸጉበት ፡ ጕድጓድ ፡ ይወጣሉ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 12 ፤ የጭፍራው ፡ ሰዎችም ፡ ዮናታንንና ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬውን ፦ ወደ ፡ እኛ ፡ ውጡ ፥ አንድ ፡ ነገርም ፡ እናሳያችኋለን ፡ አሉ ። ዮናታንም ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬውን ፦ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷቸዋልና ፥ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 13 ፤ ዮናታንም ፡ በእጁና ፡ በእግሩ ፡ ወጣ ፥ ጋሻ ፡ ጭግሬውም ፡ ተከተለው ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ በዮናታን ፡ እጅ ፡ ወደቁ ፥ ጋሻ ፡ ጭግሬውም ፡ ተከትሎ ፡ ገደላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 14 ፤ የዮናታንና ፡ የጋሻ ፡ ጭግሬውም ፡ የመጀመሪያ ፡ ግዳያቸው ፡ ባንድ ፡ ትልም ፡ ዕርሻ ፡ መካከል ፡ ኻያ ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 15 ፤ በሰፈሩም ፡ በዕርሻውና ፡ በሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ሽብር ፡ ነበረ ፤ በሰፈሩ ፡ የተቀመጡና ፡ ለምርኮ ፡ የወጡት ፡ ተሸበሩ ፤ ምድሪቱም ፡ ተናወጠች ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 16 ፤ በብንያም ፡ ጊብዓ ፡ ያሉ ፡ የሳኦል ፡ ዘበኞችም ፡ ተመለከቱ ፤ እንሆም ፥ ሰራዊቱ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ እየተራወጡ ፡ ተበታተኑ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 17 ፤ ሳኦልም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ። እስኪ ፡ ተቋጠሩ ፥ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ የኼደ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመልከቱ ፡ አላቸው ። በተቋጠሩም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ዮናታንና ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬው ፡ በዚያ ፡ አልነበሩም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አኪያ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ኤፉድ ፡ ለብሶ ፡ ነበርና ፥ ሳኦል ፦ ኤፉድን ፡ አምጣ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 19 ፤ ሳኦል ፡ ከካህኑ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ሰፈር ፡ ግርግርታ ፡ እየበዛና ፡ እየጠነከረ ፡ ኼደ ፤ ሳኦልም ፡ ካህኑን ፦ እጅኽን ፡ መልስ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 20 ፤ ሳኦልና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ውጊያው ፡ መጡ ፤ እንሆም ፥ የያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 21 ፤ ቀድሞ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ከሰፈሩ ፡ ዙሪያ ፡ የወጡት ፡ ዕብራውያን ፡ ደግሞ ፡ ከሳኦልና ፡ ከዮናታን ፡ ጋራ ፡ ወደነበሩት ፡ እስራኤላውያን ፡ ለመኾን ፡ ዞሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 22 ፤ ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ የተሸሸጉት ፡ ኹሉ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ እንደ ፡ ኰበለሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ሊዋጓቸው ፡ ተከትለው ፡ ገሠገሡ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ እስራኤልን ፡ አዳነ ፤ ውጊያውም ፡ በቤትአዌን ፡ በኩል ፡ ዐለፈ ። ከሳኦልም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ውጊያውም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ተበታትኖ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 24 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተጨነቁ ፤ ሳኦል ። ጠላቶቼን ፡ እስክበቀል ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ መብል ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ አምሏቸው ፡ ነበርና ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ መብል ፡ አልቀመሱም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 25 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ ገባ ፤ ማርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 26 ፤ ሕዝቡም ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ የሚፈስ ፡ ማር ፡ ነበረ ፤ ሕዝቡ ፡ መሐላውን ፡ ፈርቶ ፡ ነበርና ፥ ማንም ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አላደረገም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 27 ፤ ዮናታን ፡ ግን ፡ አባቱ ፡ ሕዝቡን ፡ ባማለ ፡ ጊዜ ፡ አልሰማም ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ በእጁ ፡ ያለችውን ፡ በትር ፡ ጫፏን ፡ ወደ ፡ ወለላው ፡ ነከረ ፥ እጁንም ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አደረገ ፤ ዐይኑም ፡ በራ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 28 ፤ ከሕዝቡም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መልሶ ፦ አባትኽ ፦ ዛሬ ፡ መብል ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡን ፡ መሐላ ፡ አምሏቸዋል ፡ አለው ፤ ሕዝቡም ፡ ደከሙ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 29 ፤ ዮናታንም ፦ አባቴ ፡ ምድሪቱን ፡ አስቸገረ ፤ ከዚህ ፡ ማር ፡ ጥቂት ፡ ብቀምስ ፡ ዐይኔ ፡ እንደ ፡ በራ ፡ እዩ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 30 ፤ ይልቅስ ፡ ሕዝቡ ፡ ካገኙት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ምርኮ ፡ በልተው ፡ ቢኾኑ ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ መመታት ፡ ይበልጥ ፡ አልነበረምን ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 31 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ከማክማስ ፡ እስከ ፡ ኤሎን ፡ ድረስ ፡ መቷቸው ፤ ሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ደከሙ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 32 ፤ ሕዝቡም ፡ ለምርኮ ፡ ሣሡ ፤ በጎችን ፡ በሬዎችንም ፡ ጥጃዎችንም ፡ ወስደው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐረዱ ፤ ሕዝቡም ፡ ከደሙ ፡ ጋራ ፡ በሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 33 ፤ ለሳኦልም ፦ እንሆ ፥ ሕዝቡ ፡ ከደሙ ፡ ጋራ ፡ በመብላታቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደሉ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ። ሳኦልም ፦ እጅግ ፡ ተላለፋችኹ ፤ አኹንም ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ አንከባላችኹ ፡ አቅርቡልኝ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 34 ፤ ሳኦልም ፦ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየዞራችኹ ። እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ በሬውንና ፡ በጉን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ያቅርብ ፥ በዚህም ፡ ዕረዱና ፡ ብሉ ፤ ከደሙም ፡ ጋራ ፡ በመብላታችኹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትበድሉ ፡ በሏቸው ፡ አለው ። እያንዳንዱም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በእጁ ፡ ያለውን ፡ በሬውን ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ አቀረበ ፥ በዚያም ፡ ዐረደው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 35 ፤ ሳኦልም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያን ፡ ሠራ ፤ ይኸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ መገ፞መሪያ ፡ መሠዊያ ፡ ነው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 36 ፤ ሳኦልም ፦ ፍልስጥኤማውያንን ፡ በሌሊት ፡ ተከትለን ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ እንበዝብዛቸው ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አናስቀርላቸው ፡ አለ ። እነርሱም ፦ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ፡

አሉት ። ካህኑም ፦ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንቅረብ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 37 ፤ ሳኦልም ፦ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ልከተልን ፡ በእስራኤልስ ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጣቸዋለኽን ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀው ። በዚያ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ አልመለሰለትም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 38 ፤ ሳኦልም ፦ እናንተ ፡ የሕዝቡ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ወደዚህ ፡ ቅረቡ ፤ ዛሬ ፡ ይህ ፡ ኀጢአት ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቁ ፥ ተመልከቱም ፤

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 39 ፤ እስራኤልን ፡ የሚያድን ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ኀጢአቱ ፡ በልጄ ፡ በዮናታን ፡ ቢኾን ፡ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፡ አለ ። ከሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ የመለሰለት ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 40 ፤ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፦ እናንተ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኹኑ ፥ እኔና ፡ ልጄ ፡ ዮናታንም ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ እንኾናለን ፡ አለ ። ሕዝቡም ፡ ሳኦልን ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ አድርግ ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 41 ፤ ሳኦልም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፦ እውነትን ፡ ግለጥ ፡ አለው ። ሳኦልና ፡ ዮናታንም ፡ ተያዙ ፤ ሕዝቡም ፡ ነጻ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 42 ፤ ሳኦልም ፦ በእኔና ፡ በልጄ ፡ በዮናታን ፡ መካከል ፡ ዕጣ ፡ ጣሉ ፡ አለ ። ዮናታንም ፡ ተያዘ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 43 ፤ ሳኦልም ፡ ዮናታንን ፦ ያደረግኸውን ፡ ንገረኝ ፡ አለው ፤ ዮናታንም ፦ በእጄ ፡ ባለው ፡ በበትሬ ፡ ጫፍ ፡ ጥቂት ፡ ማር ፡ በርግጥ ፡ ቀምሻለኹ ፤ እንሆኝ ፥ እሞታለኹ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 44 ፤ ሳኦልም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያድርግብኝ ፡ እንዲህም ፡ ይጨምርብኝ ፤ ዮናታን ፡ ሆይ ፥ ፈጽመኽ ፡ ትሞታለኽ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 45 ፤ ሕዝቡም ፡ ሳኦልን ፦ በእውኑ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ መድኀኒት ፡ ያደረገ ፡ ዮናታን ፡ ይሞታልን ፡ ይህ ፡ አይኹን ፤ ዛሬ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አድርጓልና ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ከራሱ ፡ ጠጕር ፡ አንዲት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ፡ አሉት ። ሕዝቡም ፡ እንዳይሞት ፡ ዮናታንን ፡ አዳነው ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 46 ፤ ሳኦልም ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ከመከተል ፡ ተመለሰ ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 47 ፤ ሳኦልም ፡ መንግሥቱን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አጸና ፤ በዙሪያውም ፡ ካሉት ፡ ከጠላቶቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፥ ከሞዐብም ፥ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፥ ከኤዶምያስም ፥ ከሱባም ፡ ነገሥታት ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፤ በየኼደበትም ፡ ኹሉ ፡ ድል ፡ ይነሣ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 48 ፤ ርሱም ፡ ገሥግና ፡ ነበረ ፥ ዐማሌቃውያንንም ፡ መታ ፥ እስራኤልንም ፡ ከዘራፊዎቹ ፡ እጅ ፡ አዳነ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 49 ፤ የሳኦልም ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ዮናታን ፥ የሱዊ ፥ ሜልኪሳ ፡ ነበሩ ፤ የኹለቱም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ የታላቂቱ ፡ ስም ፡ ሜሮብ ፥ የታናሺቱም ፡ ስም ፡ ሜልኮል ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 50 ፤ የሳኦልም ፡ ሚስት ፡ ስም ፡ የአኪማዐስ ([142]) ፡ ልጅ ፡ አኪናሖም ([143]) ፡ ነበረ ፤ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ስም ፡ የሳኦል ፡ አጎት ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 51 ፤ የሳኦልም ፡ አባት ፡ ቂስ ፡ ነበረ ፤ የአበኔርም ፡ አባት ፡ ኔር ፡ የአቢኤል ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 14 ፡ 52 ፤ በሳኦልም ፡ ዕድሜ ፡ ኹሉ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ጽኑ ፡ ውጊያ ፡ ነበረ ፤ ሳኦልም ፡ ጽኑ ፡

---

142 ዕብ. ፥ አኒይማጽ ፡ (እኅወ ፡ መዓት ፥ የመዓት ፡ የቀኑጣ ፡ ወንድም) ።

143 ዕብ. ፥ አኒኖዐም ፡ (በጎ ፡ ወንድም) ።

ወይም ፡ ጎያል ፡ ሰው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይሰበስብ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 1 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፡ አለው ፦ በሕዝቡ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንድትኾን ፡ እቀባኽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላከኝ ፥ አኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ ስማ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 2 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ዐማሌቅ ፡ በመንገድ ፡ እየተቃወመ ፡ ያደረገበትን ፡ እበቀላለኹ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 3 ፤ አኹንም ፡ ኼደኽ ፡ ዐማሌቅን ፡ ምታ ፥ ያላቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመኽ ፡ አጥፋ ፥ አትማራቸውም ፤ ወንዱንና ፡ ሴቱን ፡ ብላቴናውንና ፡ ሕፃኑን ፡ በሬውንና ፡ በጉን ፡ ግመሉንና ፡ አህያውን ፡ ግደል ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 4 ፤ ሳኦልም ፡ ሕዝቡን ፡ ጠርቶ ፡ በገልገላ ፡ ቈጠራቸው ፤ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ እግረኞች ፥ ከይሁዳም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 5 ፤ ሳኦልም ፡ ወደዐማሌቅ ፡ ከተማ ፡ ወጣ ፥ በሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ ተደበቀ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 6 ፤ ሳኦል ፡ ቄናውያንን ፦ ተነሥታችኹ ፡ ኺዱ ፤ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቸርነት ፡ አድርጋችኋልና ፥ ከዐማሌቅ ፡ ጋራ ፡ እንዳላጠፋችኹ ፡ ከመካከላቸው ፡ ውረዱ ፡ አላቸው ፤ ቄናውያንም ፡ ከዐማሌቃውያን ፡ መካከል ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 7 ፤ ሳኦልም ፡ ዐማሌቃውያንን ፡ ከኤውላጥ ፡ ዠምሮ ፡ በግብጽ ፡ ፊት ፡ እስካለችው ፡ እስከ ፡ ሱር ፡ ድረስ ፡ መታቸው ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 8 ፤ የዐማሌቅንም ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ በሕይወቱ ፡ ማረከው ፥ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሳኦልና ፡ ሕዝቡ ፡ ለአጋግ ፥ ለተመረጡትም ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ ለሰቡትም ፡ ጥጃዎችና ፡ ጠቦቶች ፥ ለመልካሞቹም ፡ ኹሉ ፡ ራሩላቸው ፥ ፈጽሞ ፡ ሊያጠፏቸውም ፡ አልወደዱም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምናምንቴንና ፡ የተናቀውን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ አጠፉት ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 10 ፤ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ። ሳኦል ፡ እኔ ፡ ከመከተል ፡ ተመልሷልና ፥ ትእዛዜንም ፡ አልፈጸመምና ፡ ስላነገሥኹት ፡ ተጸጸትኹ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣ ። ሳሙኤልም ፡ ተቈጣ ፤ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 12 ፤ ሳሙኤልም ፡ በነጋው ፡ ሳኦልን ፡ ለመገናኘት ፡ ማለደ ። ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ መጣ ፤ እንሆም ፥ የመታሰቢያ ፡ ዐምድ ፡ ባቆመ ፡ ጊዜ ፡ ዞሮ ፡ ዐለፈ ፥ ወደ ፡ ገልገላም ፡ ወረደ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ለሳሙኤል ፡ ደረሰለት ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 13 ፤ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጣ ፤ ሳኦልም ፦ አንተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተባረክኽ ፡ ኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽሜያለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 14 ፤ ሳሙኤልም ፦ ይህ ፡ በጕሮሮዬ ፡ የምሰማው ፡ የበጎች ፡ ጩኸትና ፡ የበሬዎች ፡ ግሣት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፥ 15 ፥ 15 ፤ ሳኦልም ፦ ሕዝቡ ፡ ለአምላክኽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዉአቸው ፡ ዘንድ ፡ መልካሞቹን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ አድነዋቸዋልና ፥ ከዐማሌቃውያን ፡ አምጥተዋቸዋል ፤ የቀሩትንም ፡ ፈጽመን ፡ አጠፋን ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 16 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፦ ቄይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ሌሊት ፡ የነገረኝን ፡ ልንገርኽ ፡ አለው ፤ ርሱም ፦ ተናገር ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 17 ፤ ሳሙኤልም ፡ አለ ፦ በዐይንኽ ፡ ምንም ፡ ታናሽ ፡ ብትኾን ፡ ለእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ አለቃ ፡ አልኾንክምን ፧ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀባኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ኼደኽ ፡ ኀጢአተኞቹን ፡ ዐማሌቃውያንን ፡ ፈጽመኽ ፡ አጥፋቸው ፥ እስኪጠፉም ፡ ድረስ ፡ ውጋቸው ፡ ብሎ ፡ በመንገድ ፡ ላከኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 19 ፤ ለምርኮ ፡ ሣሥተኽ ፡ ለምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማኽም ፧ ለምንስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረግኽ ፧

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 20 ፤ ሳኦልም ፡ ሳሙኤልን ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምቻለኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በላከኝ ፡ መንገድ ፡ ኼጃለኹ ፤ የዐማሌቅን ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ አምጥቻለኹ ፥ ዐማሌቃውያንንም ፡ ፈጽሜ ፡ አጥፍቻለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 21 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፥ ለአምላክኽ ፣ ለእግዚአብሔር ፡ በገልገላ ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፥ ከዕርሙ ፡ የተመረጡትን ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ከምርኮው ፡ ወሰዱ ፥ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 22 ፤ ሳሙኤልም ፦ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመስማት ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚቃጠልና ፡ በሚታረድ ፡ መሥዋዕት ፡ ደስ ፡ ይለዋልን ፧ እንሆ ፥ መታዘዝ ፡ ከመሥዋዕት ፥ ማዳመጥም ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ ስብ ፡ ከማቅረብ ፡ ይበልጣል ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 23 ፤ ዐመፀኝነት ፡ እንደ ፡ ሟርተኛ ፡ ኀጢአት ፥ እልከኝነትም ፡ ጣዖትንና ፡ ተራፊምን ፡ እንደ ፡ ማምለክ ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ንቀኻልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ንጉሥ ፡ እንዳትኾን ፡ ናቀኽ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 24 ፤ ሳኦልም ፡ ሳሙኤልን ፦ ሕዝቡን ፡ ስለ ፡ ፈራኹ ፥ ቃላቸውንም ፡ ስለ ፡ ሰማኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝና ፡ የአንተን ፡ ቃል ፡ በመተላለፍ ፡ በድያለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 25 ፤ አኹንም ፥ እባክኽ ፥ ኀጢአቴን ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተመለስ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 26 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ንቀኻልና ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንዳትኾን ፡ ንቆኻልና ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አልመለስም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 27 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሊኼድ ፡ ዘወር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦል ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ያዘ ፥ ተቀደደም ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 28 ፤ ሳሙኤልም ፦ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ዛሬ ፡ ከአንተ ፡ ቀደዳት ፥ ከአንተም ፡ ለሚሻል ፡ ለጎረቤትኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣት ፤

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 29 ፤ የእስራኤል ፡ ኀይል ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ የሚጸጸት ፡ አይደለምና ፡ አይዋሽም ፡ አይጸጸትምም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 30 ፤ ርሱም ፦ በድያለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በሕዝቤ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ፊትና ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፥ እባክኽ ፥ አክብረኝ ፤ ለአምላክኽም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ተመለስ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 31 ፤ ሳሙኤልም ፡ ከሳኦል ፡ በኋላ ፡ ተመለሰ ፤ ሳኦልም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰገደ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 32 ፤ ሳሙኤልም ፦ የዐማሌቅን ፡ ንጉሥ ፡ አጋግን ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ። አጋግም ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ። አጋግም ፦ በእውኑ ፡ ሞት ፡ እንደዚህ ፡ መራራ ፡ ነውን ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 33 ፤ ሳሙኤልም ፦ ሰይፍኽ ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ አልባ ፡ እንዳደረገቻቸው ፡ እንዲሁ ፡ እናትኽ ፡

በሴቶች ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ ትኾናለች ፡ አለ ፤ ሳሙኤልም ፡ አጋግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በገልገላ ፡ ቈራረጠው ።

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 34 ፤ ሳሙኤልም ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ኼደ ፤

ሳሙ.1 ፡ 15 ፡ 35 ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ወጣ ። ሳሙኤልም ፡ እስከ ፡ ሞተበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሳኦልን ፡ ለማየት ፡ ዳግመኛ ፡ አልኼደም ፥ ሳሙኤልም ፡ ለሳኦል ፡ አለቀሰ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ሳኦልን ፡ ስላነገሠ ፡ ተጸጸተ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳሙኤልን ፦ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንዳይነግሥ ፡ ለናቅኹት ፡ ለሳኦል ፡ የምታለቅስለት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ በቀንድኽ ፡ ዘይቱን ፡ ሞልተኽ ፡ ኺድ ፤ በልጆቹ ፡ መካከል ፡ ንጉሥ ፡ አዘጋጅቻለኹና ፡ ወደ ፡ እሴይ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ እልክኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 2 ፤ ሳሙኤልም ፦ እንዴት ፡ እኼዳለኹ ፧ ሳኦል ፡ ቢሰማ ፡ ይገድለኛል ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ አንዲት ፡ ጊደር ፡ ይዘኽ ፡ ኺድና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ እሠዋ ፡ ዘንድ ፡ መጣኹ ፡ በል ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 3 ፤ እሴይንም ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ጥራው ፥ የምታደርገውንም ፡ አስታውቅኻለኹ ፤ የምነግርኽንም ፡ ቅባልኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 4 ፤ ሳሙኤልም ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ አደረገ ፥ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ መጣ ። የአገሩም ፡ ሽማግሌዎች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ሊገናኙት ፡ መጡና ። የመጣኸው ፡ ለደኅንነት ፡ ነውን ፧ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ለደኅንነት ፡ ነው ፤ ለእግዚአብሔር ፡ እሠዋ ፡ ዘንድ ፡ መጣኹ ፤ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ መሥዋዕቱ ፡ ኑ ፡ አለ ። እሴይንና ፡ ልጆቹንም ፡ ቀደሳቸው ፥ ወደ ፡ መሥዋዕቱም ፡ ጠራቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 6 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤልያብ ፡ ተመልክቶ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀባው ፡ በፊቱ ፡ ነው ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሳሙኤልን ፦ ፊቱን ፡ የቁመቱንም ፡ ዘለግታ ፡ አትይ ፤ ሰው ፡ እንዲያይ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያይምና ፡ ናቅኹት ፤ ሰው ፡ ፊትን ፡ ያያል ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልብን ፡ ያያል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 8 ፤ እሴይም ፡ ዐሚናዳብን ፡ ጠርቶ ፡ በሳሙኤል ፡ ፊት ፡ አሳለፈው ፤ ርሱም ፦ ይህን ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልመረጠውም ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 9 ፤ እሴይም ፡ ሳማን ፡ አሳለፈው ፤ ርሱም ፦ ይህን ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልመረጠውም ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 10 ፤ እሴይም ፡ ከልጆቹ ፡ ሰባቱን ፡ በሳሙኤል ፡ ፊት ፡ አሳለፋቸው ። ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፦ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ አልመረጠም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 11 ፤ ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፦ የቀረ ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አለኽን ፧ አለው ። ርሱም ፦ ታናሹ ፡ ገና ፡ ቀርቷል ፤ እንሆም ፥ በጎችን ፡ ይጠብቃል ፡ አለ ። ሳሙኤልም ፡ እሴይን ፦ ርሱ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አንረፍቅምና ፡ ልኽኽ ፡ አስመጣው ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 12 ፤ ልኮም ፡ አስመጣው ፤ ርሱም ፡ ቀይ ፥ ዐይኑም ፡ የተዋበ ፥ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔርም ፦ ይህ ፡ ነውና ፥ ተነሥተኽ ፡ ቅባው ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 13 ፤ ሳሙኤልም ፡ የዘይቱን ፡ ቀንድ ፡ ወስዶ ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ቀባው ። የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ በኀይል ፡ መጣ ። ሳሙኤልም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከሳኦል ፡ ራቀ ፥ ክፉም ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አሠቃየው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 15 ፤ የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፦ እንሆ ፥ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያሠቃይኻል ፤

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 16 ፤ በገና ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ የሚመታ ፡ ሰው ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ጌታችን ፡ በፊቱ ፡ የሚቆሙትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ይዘዝ ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ በኾነብኽ ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ ሲመታ ፡ አንተ ፡ ደኅና ፡ ትኾናለኽ ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 17 ፤ ሳኦልም ፡ ባሪያዎቹን ፦ መልካም ፡ አድርጎ ፡ በገና ፡ መምታት ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ ፈልጋችኹ ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 18 ፤ ከብላቴናዎቹም ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፦ እንሆ ፥ መልካም ፡ አድርጎ ፡ በገና ፡ የሚመታ ፡ የቤተ ፡ ልሔማዊውን ፡ የእሴይን ፡ ልጅ ፡ አይቻለኹ ፤ ርሱም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ነው ፥ በነገርም ፡ ብልኅ ፥ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነው ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 19 ፤ ሳኦልም ፡ ወደእሴይ ፡ መልክተኞች ፡ ልኮ ፦ ከበጎች ፡ ጋራ ፡ ያለውን ፡ ልጅኽን ፡ ዳዊትን ፡ ላክልኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 20 ፤ እሴይም ፡ እንጀራና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አቀ·ማዳ ፡ የተጫነ ፡ አህያ ፡ የፍየልም ፡ ጠቦት ፡ ወስዶ ፡ በልጁ ፡ በዳዋት ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ላከ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 21 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጣ ፥ በፊቱም ፡ ቆመ ፤ እጅግም ፡ ወደደው ፥ ለርሱም ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬው ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 22 ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ እሴይ ፦ በዐይኔ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቷልና ፥ ዳዊት ፡ በፊቴ ፥ እባክኽ ፥ ይቁም ፡ ብሎ ፡ ላከ ።

ሳሙ.1 ፡ 16 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ በገና ፡ ይዞ ፡ በእጁ ፡ ይመታ ፡ ነበር ፤ ሳኦልንም ፡ ደስ ፡ ያሠኘው ፡ ያሳርፈውም ፡ ነበር ፥ ክፉ ፡ መንፈስም ፡ ከርሱ ፡ ይርቅ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 1 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራዎቻቸውን ፡ በይሁዳ ፡ ባለው ፡ በሰኮት ፡ አከማቹ ፤ በሰኮትና ፡ በዓዜቃ ፡ መካከል ፡ በኤፌስደሚም ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 2 ፤ ሳኦልና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ተከማቹ ፥ በዔላ ፡ ሸለቆም ፡ ሰፈሩ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ተሰለፉ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 3 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ እስራኤልም ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመካከላቸውም ፡ ሸለቆ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 4 ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ሰፈር ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ጎልያድ ፥ ቁመቱም ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ከስንዝር ፡ የኾነ ፥ ዋነኛ ፡ ዣግና ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 5 ፤ በራሱም ፡ የናስ ፡ ቀ፡ር ፡ ደፍቶ ፡ ነበር ፥ ጥሩርም ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፤ የጥሩሩም ፡ ሚዛን ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰቅል ፡ ናስ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 6 ፤ በእግሮቹም ፡ ላይ ፡ የናስ ፡ ገንባሌ ፡ ነበረ ፥ የናስም ፡ ጭሬ ፡ በትከሻው ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 7 ፤ የጦሩም ፡ የቦ ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ ነበረ ፤ የጦሩም ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ብረት ፡ ነበረ ፤ ጋሻ ፡ ጭግሬውም ፡ በፊቱ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ ቆሞ ፡ ወደእስራኤል ፡ ጭፍራዎች ፡ ጮኸ ፦ ለሰልፍ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ወጣችኹ ፧ እኔ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፥ እናንተም ፡ የሳኦል ፡ ባሪያዎች ፡ አይደላችኹምን ፧ ለእናንተ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ምረጡ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ይውረድ ፤

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 9 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ሊዋጋ ፡ ቢችል ፡ ቢገድለኝም ፥ ባሪያዎች ፡ እንኾናችኋለን ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ባሸንፈው ፡ ብገድለውም ፥ እናንተ ፡ ባሪያዎች ፡ ትኾኑናላችኹ ፥ ለእኛም ፡ ትገዛላችኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 10 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፦ ዛሬ ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራዎች ፡ ተገዳደርኋቸው ፤ እንዋጋ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስጡኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 11 ፤ ሳኦልና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚላቸውን ፡ የፍልስጥኤማዊውን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፥ ደነገጡም ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ የዚያ ፡ የኤፍራታዊው ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ይሁዳ ፡ ስሙም ፡ እሴይ ፡ ነበረ ፤ ስምንትም ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ በሳኦልም ፡ ዘመን ፡ በዕድሜ ፡ አርጅቶ ፡ ሽምግሎም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 13 ፤ የእሴይም ፡ ሦስቱ ፡ ታላላቆች ፡ ልጆቹ ፡ ሳኦልን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ሰልፉ ፡ ኼደው ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ሰልፉም ፡ የኼዱት ፡ የሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ታላቁ ፡ ኤልያብ ፡ ኹለተኛውም ፡ ዐሚናዳብ ፡ ሦስተኛውም ፡ ሳማ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 14 ፤ ዳዊት ፡ የኹሉ ፡ ታናሽ ፡ ነበረ ፤ ሦስቱም ፡ ታላላቆች ፡ ሳኦልን ፡ ተከትለው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፡ የአባቱን ፡ በጎች ፡ ለመጠበቅ ፡ ከሳኦል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 16 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ ይቀርብ ፥ አርባ ፡ ቀንም ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 17 ፤ እሴይም ፡ ልጁን ፡ ዳዊትን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ከዚህ ፡ ከተጠበሰው ፡ እሸት ፡ አንድ ፡ የኢ.ፍ ፡ መስፈሪያ ፡ እነዚህንም ፡ ዐሥር ፡ እንጀራዎች ፡ ለወንድሞችኽ ፡ ውሰድ ፥ ወደ ፡ ሰፈሩም ፡ ወደ ፡ ወንድሞችኽ ፡ ፈጥነኽ ፡ አድርሳቸው ፤

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 18 ፤ ይህንም ፡ ዐሥሩን ፡ ዐይብ ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ውሰደው ፤ የወንድሞችኽንም ፡ ደኅንነት ፡ ጠይቅ ፥ ወሬያቸውንም ፡ አምጣልኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 19 ፤ ሳኦልና ፡ እነርሱ ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ እየተዋጉ ፡ በዔላ ፡ ሸለቆ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ በጎቹንም ፡ ለጠባቂ ፡ ተወ ፥ እሴይም ፡ ያዘዘውን ፡ ይዞ ፡ ኼደ ፤ ጭፍራውም ፡ ተሰልፎ ፡ ሲወጣ ፡ ለሰልፍም ፡ ሲጮኽ ፡ በሠረገላዎች ፡ ወደተከበበው ፡ ሰፈር ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 21 ፤ እስራኤልና ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰላልፈው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፡ ዕቃውን ፡ በዕቃ ፡ ጠባቂው ፡ እጅ ፡ አኖረው ፥ ወደ ፡ ሰራዊቱም ፡ ሮጠ ፥ የወንድሞቹንም ፡ ደኅንነት ፡ ጠየቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ ሲነጋገራቸው ፥ እንሆ ፥ ጎልያድ ፡ የተባለው ፡ ያ ፡ ዋነኛ ፡ ዝግና ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፥ የተናገረውንም ፡ ቃል ፡ ተናገረ ፤ ዳዊትም ፡ ሰማ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 24 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰውዮውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈርተው ፡ ከርሱ ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 25 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፦ ይህን ፡ የወጣውን ፡ ሰው ፡ አያችኹትን ፧ በእውነት ፡ እስራኤልን ፡ ሊገዳደር ፡ ወጣ ፤ የሚገድለውንም ፡ ሰው ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ያደርገዋል ፥ ልጁንም ፡ ይድርለታል ፤ ያባቱንም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከግብር ፡ ነጻ ፡ ያወጣቸዋል ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 26 ፤ ዳዊትም ፡ በአጠገቡ ፡ ለቆሙት ፡ ሰዎች ፦ ይህን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ለሚገድል ፥ ከእስራኤልም ፡ ተግዳሮትን ፡ ለሚያርቅ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይደረግለታል ፧ የሕያውን ፡ አምላክ ፡ ጭፍራዎች ፡ የሚገዳደር ፡ ይህ ፡ ያልተገረዘ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 27 ፤ ሕዝቡም ፦ ለሚገድለው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግለታል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ መለሱለት ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 28 ፤ ታላቅ ፡ ወንድሙም ፡ ኤልያብ ፡ ከሰዎች ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገር ፡ ሰማ ፤ የኤልያብም ፡ ቍጣ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ ነዶ ፦ ለምን ፡ ወደዚህ ፡ ወረድኽ ፧ እነዚያንስ ፡ ጥቂቶች ፡ በጎች ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ለማን ፡ ተውኻቸው ፧ እኔ ፡ ኵራትኽንና ፡ የልብኽን ፡ ክፋት ፡ ዐውቃለኹና ፡ ሰልፉን ፡ ለማየት ፡ መጥተኻል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 29 ፤ ዳዊትም ፦ እኔ ፡ ምን ፡ አደረግኹ ፧ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አይደለምን ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 30 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ዘወር ፡ አለ ፥ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፤ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ መለሱለት ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 31 ፤ ዳዊትም ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ተሰማ ፥ ለሳኦልም ፡ ነገሩት ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ አስጠራው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 32 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፦ ስለ ፡ ርሱ ፡ የማንም ፡ ልብ ፡ አይውደቅ ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ኼጄ ፡ ያን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ እወጋዋለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 33 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፦ አንተ ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ነኽና ፥ ርሱም ፡ ከብላቴንነቱ ፡ ዝምሮ ፡ ጦረኛ ፡ ነውና ፥ ይህን ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ ለመውጋት ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 34 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፡ አለው ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ የአባቴን ፡ በጎች ፡ ስጠብቅ ፡ አንበሳና ፡ ድብ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ፥ ከመንጋውም ፡ ጠቦት ፡ ይወስድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 35 ፤ በኋላውም ፡ እከተለውና ፡ እመታው ፡ ነበር ፥ ከአፉም ፡ አስጥለው ፡ ነበር ፤ በተነሣብኝም ፡ ጊዜ ፡ ጕረሮውን ፡ ይገፍ ፡ እመታውና ፡ እገድለው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 36 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ አንበሳና ፡ ድብ ፡ መታኹ ፤ ይህም ፡ ያልተገረዘው ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ የሕያውን ፡ አምላክ ፡ ጭፍራዎች ፡ ተገዳድሯልና ፥ ከነርሱ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይኾናል ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 37 ፤ ዳዊትም ፦ ከአንበሳና ፡ ከድብ ፡ እጅ ፡ ያስጣለኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዚህ ፡ ፍልስጥኤማዊ ፡ እጅ ፡ ያስጥለኛል ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፦ ኺድ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 38 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ልብስ ፡ አለበሰው ፥ በራሱም ፡ ላይ ፡ የናስ ፡ ቍር ፡

ደፋለት ፥ ጥሩርም ፡ አለበሰው ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 39 ፤ ዳዊትም ፡ ሰይፉን ፡ በልብሱ ፡ ላይ ፡ ታጠቀ ፥ ገናም ፡ አልፈተነውምና ፡ መኼድ ፡ ሞከረ ። ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፦ አልፈተንኹትምና ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ መኼድ ፡ አልችልም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 40 ፤ ዳዊትም ፡ አወለቀ ። በትሩንም ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ፥ ከወንዝም ፡ ዐምስት ፡ ድብልብል ፡ ድንጋዮችን ፡ መረጠ ፥ በእረኛ ፡ ኰረጆውም ፡ በኪሱ ፡ ከተታቸው ፤ ወንጭፍም ፡ በእጁ ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ቀረበ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 41 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ቀረበ ፤ ጋሻ ፡ ጐግሬውም ፡ በፊቱ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 42 ፤ ጎልያድም ፡ ዳዊትን ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ አየው ፤ ቀይ ፡ ብላቴና ፡ መልኩም ፡ ያማረ ፡ ነበረና ፡ ናቀው ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 43 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ዳዊትን ፦ በትር ፡ ይዘኽ ፡ የምትመጣብኝ ፡ እኔ ፡ ውሻ ፡ ነኝን ፧ አለው ። ፍልስጥኤማዊውም ፡ በአምላኮቹ ፡ ስም ፡ ዳዊትን ፡ ረገመው ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 44 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ዳዊትን ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ና ፥ ሥጋኽንም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ እሰጣለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 45 ፤ ዳዊትም ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ሰይፍና ፡ ጦር ፡ ጭሬም ፡ ይዘኽ ፡ ትመጣብኛለኽ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ በተገዳደርኸው ፡ በእስራኤል ፡ ጭፍራዎች ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እመጣብኻለኹ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 46 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ አንተን ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፤ እመታኽማለኹ ፥ ራስኽንም ፡ ከአንተ ፡ አነሣዋለኹ ፤ የፍልስጥኤማውያንንም ፡ ሰራዊት ፡ ሬሶች ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ ዛሬ ፡ እሰጣለኹ ። ይኸውም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አምላክ ፡ እንዳለ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፤

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 47 ፤ ይህም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰይፍና ፡ በጦር ፡ የሚያድን ፡ እንዳይደል ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሰልፉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነውና ፤ እናንተንም ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 48 ፤ ፍልስጥኤማዊውም ፡ ተነሥቶ ፡ ዳዊትን ፡ ሊገናኘው ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ሊገናኘው ፡ ወደ ፡ ሰልፉ ፡ ሮጠ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 49 ፤ ዳዊትም ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ኰረጆው ፡ አግብቶ ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ ወሰደ ፥ ወነጨፈውም ፥ ፍልስጥኤማዊውንም ፡ ግንባሩን ፡ መታ ፤ ድንጋዩም ፡ በግንባሩ ፡ ተቀረቀረ ፥ ርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 50 ፤ ዳዊትም ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ በወንጭፍና ፡ በድንጋይ ፡ አሸነፈው ፥ ፍልስጥኤማዊውንም ፡ መቶ ፡ ገደለ ፤ በዳዊትም ፡ እጅ ፡ ሰይፍ ፡ አልነበረም ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 51 ፤ ዳዊትም ፡ ሮጦ ፡ በፍልስጥኤማዊው ፡ ላይ ፡ ቆመ ፤ ሰይፉንም ፡ ይዞ ፡ ከሰገባው ፡ መዘዘው ፥ ገደለውም ፥ ራሱንም ፡ ቈረጠው ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዋናቸው ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 52 ፤ የእስራኤልና ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ እልል ፡ አሉ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ እስከ ፡ ጌትና ፡ እስከ ፡ አስቀሎና ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አሳደዷቸው ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከሸዓራይም ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ጌትና ፡ እስከ ፡ ዐቃሮን ፡ ድረስ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ የተመቱት ፡ ወደቁ ።

ሳሙ.1 ፥ 17 ፥ 53 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመልሰው ፡ ሰፈራቸውን ፡ በዘበዙ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 54 ፤ ዳዊትም ፡ የፍልስጥኤማዊውን ፡ ራስ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አመጣው ፤ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ ግን ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 55 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤማዊው ፡ ሲወጣ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ለሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ ለአበኔር ፦ አበኔር ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ብላቴና ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ ነው ፧ አለው ። አበኔርም ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በሕያው ፡ ነፍስኽ ፡ እምላለኹ! ፡ አላውቅም ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 56 ፤ ንጉሡም ፦ ይህ ፡ ብላቴና ፡ የማን ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንተ ፡ ጠይቅ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 57 ፤ ዳዊትም ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ገድሎ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ አበኔር ፡ ወሰደው ፥ ወደሳኦልም ፡ ፊት ፡ አመጣው ፤ የፍልስጥኤማዊውንም ፡ ራስ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 17 ፡ 58 ፤ ሳኦልም ፦ አንተ ፡ ብላቴና ፥ የማን ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፧ አለው ። ዳዊትም ፦ እኔ ፡ የቤተ ፡ ልሔሙ ፡ የባሪያኽ ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ለሳኦል ፡ መናገሩን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የዮናታን ፡ ነፍስ ፡ በዳዊት ፡ ነፍስ ፡ ታሰረች ፥ ዮናታንም ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ወደደው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኦል ፡ ወሰደው ፥ ወዳባቱም ፡ ቤት ፡ ይመልሰው ፡ ዘንድ ፡ አልተወውም ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 3 ፤ ዮናታንም ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ስለ ፡ ወደደው ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 4 ፤ ዮናታንም ፡ የለበሰውን ፡ ካባ ፡ አውልቆ ፡ ርሱንና ፡ ልብሱን ፡ ሰይፉንም ፡ ሸለመው ። ዮናታንም ፡ የለበሰውን ፡ ካባ ፡ አውልቆ ፡ ርሱንና ፡ ልብሱን ፡ ሰይፉንም ፡ ቀስቱንም ፡ መታጠቂያውንም ፡ ለዳዊት ፡ ሸለመው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦል ፡ ወደሰደደው ፡ ኹሉ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፥ አስተውሎም ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ሳኦልም ፡ በጦረኞች ፡ ላይ ፡ ሾመው ፤ ይህም ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ እና ፡ በሳኦል ፡ ባሪያዎች ፡ ዐይን ፡ መልካም ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 6 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዳዊት ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ገድሎ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፥ እየዘመሩና ፡ እየዘፈኑ ፡ እልልም ፡ እያሉ ፡ ከበሮና ፡ አታሞ ፡ ይዘው ፡ ንጉሡን ፡ ሳኦልን ፡ ሊቀበሉ ፡ ሴቶች ፡ ከእስራኤል ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 7 ፤ ሴቶችም ፦ ሳኦል ፡ ሺሕ ፥ ዳዊትም ፡ እልፍ ፡ ገደለ ፡ እያሉ ፡ እየተቀባበሉ ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 8 ፤ ሳኦልም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡ አስከፋው ፤ ርሱም ፦ ለዳዊት ፡ እልፍ ፡ ሰጡት ፥ ለእኔ ፡ ግን ፡ ሺሕ ፡ ብቻ ፡ ሰጡኝ ፤ ከመንግሥት ፡ በቀር ፡ ምን ፡ ቀረበት ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 9 ፤ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡ ተመቅኝቶ ፡ ተመለከተው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 10 ፤ በነጋውም ፡ ሳኦልን ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያዘው ፥ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። ዳዊትም ፡ በየቀኑ ፡ ያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በእጁ ፡ በገና ፡ ይመታ ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡ ጦሩን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 11 ፤ ሳኦልም ፦ ዳዊትን ፡ ከግንቡ ፡ ጋራ ፡ አጣብቄ ፡ እመታዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ። ዳዊትም ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ከፊቱ ፡ ዘወር ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከሳኦልም ፡ ስለ ፡ ተለየ ፡ ሳኦል ፡ ዳዊትን ፡ ፈራው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 13 ፤ ስለዚህም ፡ ሳኦል ፡ ከርሱ ፡ አራቀው ፥ የሺሕ ፡ አለቃም ፡ አደረገው ፤ በሕዝቡም ፡ ፊት ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ በአካኼዱ ፡ ኹሉ ፡ አስተውሎ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 15 ፤ ሳኦልም ፡ እጅግ ፡ ብልኅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይቶ ፡ እጅግ ፡ ፈራው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፊታቸው ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ እስራኤልና ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ዳዊትን ፡ ወደዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 17 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፦ ታላቂቱ ፡ ልጄ ፡ ሜሮብ ፡ እንሂት ፤ ርሷን ፡ እድርልኻለኹ ፤ ብቻ ፡ ቀልጣፋ ፡ ልጅ ፡ ኹንልኝ ፥ ስለእግዚአብሔርም ፡ ጦርነት ፡ ተጋደል ፡ አለው ። ሳኦልም ፦ የፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ትኹን ፡ እንጂ ፡ የእኔ ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አትኹን ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 18 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፦ ለንጉሥ ፡ ዐማች ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧ ሰውነቴስ ፡ ምንድር ፡ ናት ፧ የአባቴስ ፡ ወገን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ሜሮብ ፡ ዳዊትን ፡ የምታገባበት ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ ለመሐላታዊው ፡ ለኤስድሪኤል ፡ ተዳረች ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 20 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ ዳዊትን ፡ ወደደች ፤ ይህም ፡ ወሬ ፡ ለሳኦል ፡ ደረሰለት ፥ ነገሩም ፡ ደስ ፡ አሠኘው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 21 ፤ ሳኦልም ፦ ወጥመድ ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፥ የፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ርሷን ፡ እድርለታለኹ ፡ አለ ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፦ ዛሬ ፡ ኹለተኛ ፡ ዐማች ፡ ትኾነኛለኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 22 ፤ ሳኦልም ፡ ባሪያዎቹን ፦ እንሆ ፥ ንጉሥ ፡ እጅግ ፡ ወዶኻል ፥ ባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ወደውኻል ፥ አኹንም ፡ ለንጉሥ ፡ ዐማች ፡ ኹን ፡ ብላችኹ ፡ በስውር ፡ ለዳዊት ፡ ንገሩት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 23 ፤ የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በዳዊት ፡ ጐሮ ፡ ተናገሩ ፤ ዳዊትም ፦ እኔ ፡ ድኻ ፡ የተጠቃኹም ፡ ሰው ፡ ስኾን ፡ ለንጉሥ ፡ ዐማች ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ይመስላችኋልን ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 24 ፤ የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፦ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 25 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ ይጥለው ፡ ዘንድ ፡ ዐስቦ ። የንጉሥን ፡ ጠላቶች ፡ ይበቀል ፡ ዘንድ ፡ ከመቶ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሸለፈት ፡ በቀር ፡ ንጉሥ ፡ ማጫ ፡ አይሻም ፡ ብላችኹ ፡ ለዳዊት ፡ ንገሩት ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 26 ፤ የሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፥ ለንጉሥም ፡ ዐማች ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 27 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ተነሥተው ፡ ኼዱ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፤ ዳዊትም ፡ ለንጉሥ ፡ ዐማች ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰለባቸውን ፡ አምጥቶ ፡ በቍጥራቸው ፡ ልክ ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጠ ። ሳኦልም ፡ ልጁን ፡ ሜልኮልን ፡ ዳረለት ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 28 ፤ ሳኦልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አየ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ወደዱት ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 29 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ አጥብቆ ፡ ፈራው ፤ ሳኦልም ፡ ዕድሜውን ፡ ኹሉ ፡ ለዳዊት ፡ ጠላት ፡ ኾነ ።

ሳሙ.1 ፡ 18 ፡ 30 ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቃዎች ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፤ በወጡም ፡ ጊዜ ፡ ዅሉ ፡ ከሳኦል ፡ ባሪያዎች ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ዳዊት ፡ አስተውሎ ፡ ያደርግ ፡ ነበርና ፥ ስሙ ፡ እጅግ ፡ ተጠርቶ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 1 ፤ ሳኦልም ፡ ለልጁ ፡ ለዮናታንና ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ዅሉ ፡ ዳዊትን ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ነገራቸው ። የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ግን ፡ ዳዊትን ፡ እጅግ ፡ ይወድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 2 ፤ ዮናታንም ፦ አባቴ ፡ ሳኦል ፡ ሊገድልኽ ፡ ፈልጓል ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ለነገው ፡ ተጠንቅቀኽ ፡ ተሸሸግ ፥ በስውርም ፡ ተቀመጥ ፤

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 3 ፤ እኔም ፡ እወጣለኹ ፡ አንተም ፡ ባለኽበት ፡ ዕርሻ ፡ በአባቴ ፡ አጠገብ ፡ እቆማለኹ ፥ ስለ ፡ አንተም ፡ ከአባቴ ፡ ጋራ ፡ እነጋገራለኹ ፤ የኾነውንም ፡ አይቼ ፡ እነግርኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ዮናታንም ፡ ለአባቱ ፡ ለሳኦል ፦ ርሱ ፡ አልበደለኽምና ፥ ሥራውም ፡ ለአንተ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ኾኗልና ፥ ንጉሡ ፡ ባሪያውን ፡ ዳዊትን ፡ አይበድለው ፤

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 5 ፤ ነፍሱንም ፡ በእጁ ፡ ጥሎ ፡ ፍልስጥኤማዊውን ፡ ገደለ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ታላቅ ፡ መድኀኒት ፡ አደረገ ፤ አንተም ፡ አይተኽ ፡ ደስ ፡ አለኽ ፤ በከንቱ ፡ ዳዊትን ፡ በመግደልኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ላይ ፡ ትበድላለኽ ፧ ብሎ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ መልካም ፡ ተናገረ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 6 ፤ ሳኦልም ፡ የዮናታንን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፤ ሳኦልም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ዳዊት ፡ አይገደልም ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 7 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፡ ጠርቶ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ነገረው ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ አመጣው ፥ እንደ ፡ ቀድሞውም ፡ በፊቱ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፡ ጦርነት ፡ ኾነ ፤ ዳዊትም ፡ ወጥቶ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፥ ታላቅ ፡ ግዳይም ፡ ገደላቸው ፥ ከፊቱም ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 9 ፤ ሳኦልም ፡ ጦሩን ፡ ይዞ ፡ በቤቱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያዘው ። ዳዊትም ፡ በእጁ ፡ በገና ፡ ይመታ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 10 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ ከግንብ ፡ ጋራ ፡ ያጣብቀው ፡ ዘንድ ፡ ጦሩን ፡ ወረወረ ፤ ዳዊትም ፡ ከሳኦል ፡ ፊት ፡ ዘወር ፡ አለ ፥ ጦሩም ፡ በግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ተተከለ ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ዳዊት ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 11 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ ጠብቀው ፡ በነጋው ፡ እንዲገድሉት ፡ መልእክተኞቹን ፡ ወደዳዊት ፡ ቤት ፡ ላከ ፤ ሚስቱም ፡ ሜልኮል ፦ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ነፍስኽን ፡ ካላዳንኽ ፡ ነገ ፡ ትገደላለኽ ፡ ብላ ፡ ነገረችው ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 12 ፤ ሜልኮልም ፡ ዳዊትን ፡ በመስኮት ፡ አወረደችው ፤ ኼደም ፥ ሸሽቶም ፡ አመለጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 13 ፤ ሜልኮልም ፡ ተራፊምን ፡ ወስዳ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ አኖረችው ፥ በራስጌውም ፡ ጕንጕን ፡ የፍየል ፡ ጠጕር ፡ አደረገች ፥ በልብስም ፡ ከደነችው ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 14 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ እንዲያመጡት ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፥ ርሷም ፦ ታሟል ፡ አለቻቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 15 ፤ ሳኦልም ፦ እገድለው ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ ከነ ፡ ዐልጋው ፡ አምጡልኝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ሰደደ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 16 ፤ መልእክተኞቹም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ተራፊሙን ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ አገኙ ፥ በራስጌውም ፡

ጕንጕን ፡ የፍየል ፡ ጠጕር ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 17 ፤ ሳኦልም ፡ ሜልኮልን ፦ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አድርገሽ ፡ አታለልሽኝ ፧ ጠላቴን ፡ አስኰበለልሽው ፡ አላት ። ሜልኮልም ፡ ለሳኦል ፦ ርሱ ፦ አውጥተሽ ፡ ስደዺኝ ፥ አለዚያም ፡ እገድልሻለኹ ፡ አለኝ ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 18 ፤ ዳዊትም ፡ ሸሽቶ ፡ አመለጠ ፥ ወደ ፡ አርማቴምም ፡ ወደ ፡ ሳሙኤል ፡ መጣ ፥ ሳኦልም ፡ ያደረገበትን ፡ ኹሉ ፡ ነገረው ፤ ርሱና ፡ ሳሙኤልም ፡ ኼዱ ፡ በነዋትዘራማም ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 19 ፤ ሳኦልም ፦ ዳዊት ፥ እንሆ ፥ በአርማቴም ፡ አገር ፡ በነዋትዘራማ ፡ ተቀምጧል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 20 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ፤ የነቢያት ፡ ጉባኤ ፡ ትንቢት ፡ ሲናገሩ ፥ ሳሙኤልም ፡ አለቃቸው ፡ ኾኖ ፡ ሲቆም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በሳኦል ፡ መልእክተኞች ፡ ላይ ፡ ወረደ ፥ እነርሱም ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ገቦምር ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 21 ፤ ሳኦልም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሌላዎች ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ፥ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ። ሳኦልም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ፥ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 22 ፤ የሳኦልም ፡ ቍጣ ፡ ነደደ ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አርማቴም ፡ መጣ ፥ በሤኩም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ የውሃ ፡ ጕድጓድ ፡ ደረሰ ። ሳሙኤልና ፡ ዳዊት ፡ የት ፡ ናቸው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀ ፤ አንድ ፡ ሰውም ፦ እንሆ ፥ በአርማቴም ፡ አገር ፡ በነዋትዘራማ ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 23 ፤ ወደአርማቴምም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ነዋትዘራማ ፡ ኼደ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በርሱ ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ፥ ርሱም ፡ ኼደ ፥ ወደአርማቴምም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ነዋትዘራማ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ትንቢት ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 19 ፡ 24 ፤ ልብሱንም ፡ አወለቀ ፥ በሳሙኤልም ፡ ፊት ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፥ ዕራቍቱንም ፡ ወድቆ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ኹሉ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ኹሉ ፡ ተጋደመ ። ስለዚህ ፦ ሳኦል ፡ ደግሞ ፡ ከነቢያት ፡ መካከል ፡ ነውን ፧ ይባባሉ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ከአርማቴም ፡ አገር ፡ ከነዋትዘራማ ፡ ሸሽ ፥ ወደ ፡ ዮናታንም ፡ መጥቶ ፦ ምን ፡ አደረግኹ ፧ እኔንስ ፡ ለመግደል ፡ የሚፈልግ ፡ በአባትኽ ፡ ፊት ፡ ጠማምነቴና ፡ ኀጢአቴ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 2 ፤ ዮናታንም ፦ ይህንስ ፡ ያርቀው ፥ አትሞትም ፤ እንሆ ፥ አባቴ ፡ አስቀድሞ ፡ ለእኔ ፡ ሳይገልጥ ፡ ትልቅም ፡ ትንሽም ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ አያደርግም ፤ አባቴስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ይሰውረኛል ፧ እንዲህ ፡ አይደለም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፦ እኔ ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ እንዳገኘኹ ፡ አባትኽ ፡ በእውነት ፡ ያውቃል ፤ ርሱም ፦ ዮናታን ፡ እንዳይከፋው ፡ አይወቅ ፡ ይላል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ! ፡ በእኔና ፡ በሞት ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ርምጃ ፡ ያኽል ፡ ቀርቷል ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 4 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፦ ነፍስኽ ፡ የወደደችውን ፡ ኹሉ ፡ አደርግልኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ዮናታንን ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ ነገ ፡ መባቻ ፡ ነው ፤ በንጉሥም ፡ አጠገብ ፡ ለምሳ ፡ አልቀመጥም ፤ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በውጭ ፡ በሜዳ ፡ እንድሸሸግ ፡ አሰናብተኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 6 ፤ አባትኽም ፡ ቢፈልገኝ ። ለዘመዶቹ ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ የዓመት ፡ መሥዋዕት ፡ አላቸውና ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ፈጥኖ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አጽንቶ ፡ ለምኖኛል ፡ በለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 7 ፤ ርሱም ፦ መልካም ፡ ነው ፡ ቢል ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ ደኅንነት ፡ ይኾናል ፤ ቢቈጣ ፡ ግን ፡ ክፋት ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተቈረጠች ፡ ዕወቅ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 8 ፤ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከባሪያኽ ፡ ጋራ ፡ አድርገኻልና ፥ ለባሪያኽ ፡ ቸርነት ፡ አድርግ ፤ በደል ፡ ግን ፡ ቢገኝብኝ ፡ አንተ ፡ ግደለኝ ፤ ለምን ፡ ወደ ፡ አባትኽ ፡ ታደርሰኛለኽ ፧

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 9 ፤ ዮናታንም ፦ ይህ ፡ ከአንተ ፡ ይራቅ ፤ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ክፋት ፡ በላይኽ ፡ እንደ ፡ ተቈጠረች ፡ ያወቅኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አልነግርኽምን ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ ዮናታንን ፦ አባትኽ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የነገረኽ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ማን ፡ ይነግረኛል ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 11 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፦ ና ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ እንውጣ ፡ አለው ። ኹለቱም ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 12 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፡ አለው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ይኹን ፤ ነገ ፡ ወይም ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አባቴን ፡ መርምሬ ፥ እንሆ ፥ በዳዊት ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ ቢያስብ ፡ ልኬ ፡ እገልጥልኻለኹ ፤

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 13 ፤ አባቴም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ክፋት ፡ ማድረግ ፡ ቢወድ ፡ እኔም ፡ ባላስታውቅኽ ፡ በደኅና ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ባላሰናብትኽ ፥ እግዚአብሔር ፡ በዮናታን ፡ ይህን ፡ ያድርግ ፡ ይህንም ፡ ይጨምር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከአባቴ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 14 ፤ እኔም ፡ እንዳልሞት ፡ በሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ አድርግልኝ ፤

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ የዳዊትን ፡ ጠላቶች ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከምድር ፡ ባጠፋቸው ፡ ጊዜ ፡ ለዘለዓለም ፡ ቸርነትኽን ፡ ከቤቴ ፡ አታርቀው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 16 ፤ ዮናታንም ፦ እግዚአብሔር ፡ ከዳዊት ፡ ጠላቶች ፡ እጅ ፡ ይፈልገው ፡ ብሎ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 17 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ማለለት ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 18 ፤ ዮናታንም ፡ አለው ፦ ነገ ፡ መባቻ ፡ ነው ፥ መቀመጫኽም ፡ ባዶ ፡ ኾኖ ፡ ይገኛልና ፥ ትታሰባለኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 19 ፤ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ያኽል ፡ ቈይ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፈጥነኽ ፡ ውረድ ፥ ነገሩም ፡ በተደረገበት ፡ ቀን ፡ ወደተሸሸግኽበት ፡ ስፍራ ፡ ኺድ ፥ በኤዜል ፡ ድንጋይም ፡ አጠገብ ፡ ቈይ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ በዐላማ ፡ ላይ ፡ እወረውራለኹ ፡ ብዬ ፡ ሦስት ፡ ፍላጻዎችን ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ እወረውራለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 21 ፤ እንሆም ፦ ኺድ ፡ ፍላጻዎችን ፡ ፈልግ ፡ ብዬ ፡ ብላቴናውን ፡ እልከዋለኹ ፤ ብላቴናውንም ፦ እንሆ ፥ ፍላጻው ፡ ከአንተ ፡ ወደዚህ ፡ ነው ፤ ይዘኸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ና ፡ ያልኹት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ለአንተ ፡ ደኅንነት ፡ ነውና ፥ ምንም ፡ የለብኽም ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 22 ፤ ብላቴናውን ፡ ግን ፦ እንሆ ፥ ፍላጻው ፡ ከአንተ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ያልኹት ፡ እንደ ፡

ኾነ ፥ እግዚአብሔር ፡ አሰናብቶኻልና ፥ መንገድኽን ፡ ኺድ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 23 ፤ አንተና ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ተነጋገርነው ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ በመካከላችን ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 24 ፤ ዳዊትም ፡ በሜዳው ፡ ተሸሸገ ፤ መባቻም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ግብር ፡ ለመብላት ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ በግንቡ ፡ አጠገብ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፤ ዮናታንም ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ አበኔርም ፡ በሳኦል ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ፤ የዳዊትም ፡ ስፍራ ፡ ባዶውን ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 26 ፤ ሳኦልም ፦ አንድ ፡ ነገር ፡ ኾኗል ፥ ንጹሕም ፡ አይደለም ፤ በእውነት ፡ ንጹሕ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ዐስቧልና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ምንም ፡ አልተናገረም ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 27 ፤ ከመባቻም ፡ በኋላ ፡ በማግስቱ ፡ በኹለተኛው ፡ ቀን ፡ የዳዊት ፡ ስፍራ ፡ ባዶውን ፡ ነበረ ፤ ሳኦልም ፡ ልጁን ፡ ዮናታንን ፦ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ትናንትና ፡ ወይም ፡ ዛሬ ፡ ግብር ፡ ሊበላ ፡ ያልመጣ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 28 ፤ ዮናታንም ፡ ለሳኦል ፦ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አጽንቶ ፡ ለመነኝ ፤

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 29 ፤ ርሱም ፦ ዘመዶቼ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መሥዋዕት ፡ አላቸውና ፥ ወንድሜም ፡ ጠርቶኛልና ፥ እባክኽ ፥ አሰናብተኝ ፤ አኹንም ፡ በዐይኖችኽ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልኺድና ፡ ወንድሞቼን ፡ ልይ ፡ አለ ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሰደቃ ፡ አልመጣም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 30 ፤ የሳኦልም ፡ ቍጣ ፡ በዮናታን ፡ ላይ ፡ ነደደና ። አንተ ፡ የጠማማ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፥ የእሴይን ፡ ልጅ ፡ ለአንተ ፡ ማፈሪያ ፡ ለእናትኽም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ማፈሪያ ፡ እንደ ፡ መረጥኽ ፡ እኔ ፡ አላውቅምን ፧

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 31 ፤ የእሴይም ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በሕይወት ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ አንተና ፡ መንግሥትኽ ፡ አትጸኑም ፤ አኹንም ፡ የሞት ፡ ልጅ ፡ ነውና ፥ ልከኽ ፡ አስመጣልኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 32 ፤ ዮናታንም ፡ ለአባቱ ፡ ለሳኦል ። ስለ ፡ ምን ፡ ይሞታል ፧ ያደረገውስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 33 ፤ ሳኦልም ፡ ሊወጋው ፡ ጦሩን ፡ ወረወረበት ፤ ዮናታንም ፡ አባቱ ፡ ዳዊትን ፡ ፈጽሞ ፡ ሊገድለው ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ ዐወቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 34 ፤ አባቱ ፡ ዳዊትን ፡ ስላሳፈረው ፡ ዮናታን ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ዐዝኗልና ፥ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ከሰደቃው ፡ ተነሣ ፥ በመባቻውም ፡ በኹለተኛ ፡ ቀን ፡ ግብር ፡ አልበላም ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 35 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በነጋው ፡ ዮናታን ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ወደተቃጠረበት ፡ ቦታ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 36 ፤ ብላቴናውንም ፦ ሮጠኽ ፡ የምወረውራቸውን ፡ ፍላጻዎች ፡ ፈልግልኝ ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡ በሮጠ ፡ ጊዜ ፡ ፍላጻውን ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ ወረወረው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 37 ፤ ብላቴናውም ፡ ዮናታን ፡ ፍላጻውን ፡ ወደወረወረበት ፡ ስፍራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ዮናታን ፦ ፍላጻው ፡ ከአንተ ፡ ወዲያ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ብላቴናው ፡ ጮኸ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 38 ፤ ዮናታንም ፡ ደግሞ ፦ ቶሎ ፡ ፍጠን ፥ አትቈይ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ብላቴናው ፡ ጮኸ ፤ የዮናታንም ፡

ብላቴና ፡ ፍላጻዎቹን ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 39 ፤ ዮናታንና ፡ ዳዊት ፡ ብቻ ፡ ነገሩን ፡ ያውቁ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ብላቴናው ፡ ምንም ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 40 ፤ ዮናታንም ፡ መሣሪያውን ፡ ለብላቴናው ፡ ሰጥቶ ፦ ወደ ፡ ከተማ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 41 ፤ ብላቴናውም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ከስፍራው ፡ በደቡብ ፡ አጠገብ ፡ ተነሣ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ፥ ሦስት ፡ ጊዜም ፡ ለሰላምታ ፡ ሰገደ ፤ እየተላቀሱም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተሳሳሙ ፥ ይልቁንም ፡ ዳዊት ፡ እጅግ ፡ አለቀሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 20 ፡ 42 ፤ ዮናታንም ፡ ዳዊትን ፦ በደኅና ፡ ኺድ ፤ እንሆ ፥ እኛ ፡ ኹለታችን ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፥ በዘሬና ፡ በዘርኽ ፡ መካከል ፡ ለዘለዓለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይኹን ፡ ብለን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተማምለናል ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ፤ ዮናታንም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ ወደ ፡ ኖብ ፡ መጣ ፤ አቢሜሌክም ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ዳዊትን ፡ ሊገናኘው ፡ መጣና ፦ ስለ ፡ ምን ፡ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ ነኽ ፧ ከአንተስ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ማንም ፡ የለም ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ ካህኑን ፡ አቢሜሌክን ፦ የተላክኽበትን ፡ ነገርና ፡ የሰጠኹኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፡ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አዞኛል ፤ ስለዚህም ፡ ብላቴናዎቹን ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ተውኋቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 3 ፤ አኹንስ ፡ በእጅኽ ፡ ምን ፡ አለ ፧ ዐምስት ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ የተገኘውን ፡ በእጄ ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 4 ፤ ካህኑም ፡ ለዳዊት ፡ መልሶ ፦ ኹሉ ፡ የሚበላው ፡ እንጀራ ፡ የለኝም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የተቀደስ ፡ እንጀራ ፡ አለ ፤ ብላቴናዎቹ ፡ ከሴቶቹ ፡ ንጹሓን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ መብላት ፡ ይቻላል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ለካህኑ ፡ መልሶ ፦ በእውነት ፡ ከወጣን ፡ ዠምረን ፡ እኛ ፡ ሰውነታችንን ፡ ከሴቶች ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ጠብቀናል ፤ የብላቴናዎችም ፡ ዕቃ ፡ የተቀደሰች ፡ ናት ፤ ስለዚህ ፥ ዛሬ ፡ ዕቃቸው ፡ የተቀደሰች ፡ በመኾኗ ፥ እንጀራው ፡ እንደሚበላ ፡ እንጀራ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 6 ፤ ካህኑም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ትኵስ ፡ እንጀራ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከተነሣው ፡ ከገጹ ፡ ኀብስት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንጀራ ፡ አልነበረምና ፡ የተቀደሰውን ፡ እንጀራ ፡ ሰጠው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከሳኦል ፡ ባሪያዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተገኝቶ ፡ ነበር ፤ ስሙም ፡ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ ነበረ ፥ ለሳኦልም ፡ የእረኞቹ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ አቢሜሌክን ፦ የንጉሥ ፡ ጕዳይ ፡ ስላስቸኰለኝ ፡ ሰይፌንና ፡ መሣሪያዬን ፡ አላመጣኹምና ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ጦር ፡ ወይም ፡ ሰይፍ ፡ አለ ፡ ወይ ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 9 ፤ ካህኑም ፦ በኤላ ፡ ሸለቆ ፡ የገደልኸው ፡ የፍልስጥኤማዊው ፡ የጎልያድ ፡ ሰይፍ ፥ እንሆ ፥ በመጐናጸፊያ ፡ ተጠቅሶ ፡ ከዚህ ፡ ከኤፉዱ ፡ በኋላ ፡ አለ ፤ ትወደውም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ውሰደው ፤ ሌላ ፡ ከዚህ ፡ የለም ፡ አለ ። ዳዊትም ፦ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ የለምና ፡ ርሱን ፡ ስጠኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ ተነሣ ፡ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኦልን ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፥ ወደጌትም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አንኩስ

(144) ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 11 ፤ የአንኩስ ፡ ባሪያዎችም ፦ ይህ ፡ ዳዊት ፡ የአገሩ ፡ ንጉሥ ፡ አይደለምን ፧ ሳኦል ፡ ሺሕ ፡ ዳዊትም ፡ እልፍ ፡ ገደለ ፡ ብለው ፡ ሴቶች ፡ በዘፈን ፡ የዘመሩለት ፡ ርሱ ፡ አይደለምን ፧ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በልቡ ፡ አኖረ ፥ የጌትንም ፡ ንጉሥ ፡ አንኩስን ፡ እጅግ ፡ ፈራ ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 13 ፤ በፊታቸውም ፡ አእምሮውን ፡ ለወጠ ፥ በያዙትም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ ኾነ ፥ በበሩም ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ተንፈራፈረ ፥ ልጋጉም ፡ በጢሙ ፡ ላይ ፡ ይወርድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 21 ፡ 14 ፤ አንኩስም ፡ ባሪያዎቹን ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ እብድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታችኋል ፤ ለምን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አመጣችኹት ፧ በፊቴ ፡ ያብድ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ያመጣችኹት ፡ እብድ ፡ ጠፍቶብኝ ፡ ነውን ፧ እንዲህ ፡ ያለውስ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ይገባልን ፧ አላቸው ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ ተነሣ ፡ ወደዓዶላም ፡ ዋሻ ፡ ኰበለለ ፤ ወንድሞቹና ፡ የአባቱም ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወደዚያ ፡ ወረዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 2 ፤ የተጨነቀውም ፡ ኹሉ ፥ ብድርም ፡ ያለበት ፡ ኹሉ ፥ የተከፋም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተከማቸ ፤ ርሱም ፡ በላያቸው ፡ አለቃ ፡ ኾነ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ በሞዐብ ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ምጽጻ ፡ ኼደ ፤ የሞዐብንም ፡ ንጉሥ ፦ እግዚአብሔር ፡ የሚያደርግልኝን ፡ እስካውቅ ፡ ድረስ ፡ አባቴና ፡ እናቴ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 4 ፤ በሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ አመጣቸው ፤ ዳዊትም ፡ በዐምባ ፡ ውስጥ ፡ በነበረበት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 5 ፤ ነቢዩ ፡ ጋድም ፡ ዳዊትን ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደይሁዳ ፡ ምድር ፡ ኺድ ፡ እንጂ ፡ በዐምባው ፡ ውስጥ ፡ አትቀመጥ ፡ አለው ፤ ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደሔሬት ፡ ዱር ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 6 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ እንደ ፡ ተገለጡ ፡ ሰማ ። ሳኦልም ፡ በጊብዓ ፡ በዐጣጥ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፤ በኰረብታው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፥ በእጁም ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ ነበር ፤ ባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 7 ፤ ሳኦልም ፡ በአጠገቡ ፡ የቆሙትን ፡ ባሪያዎቹን ፦ ብንያማውያን ፡ ሆይ ፥ እንግዲህ ፡ ስሙ ፤ በእውኑ ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ዕርሻና ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ለኹላችኹ ፡ ይሰጣችኋልን ፧ ኹላችኹንስ ፡ ሻለቃዎችና ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ያደርጋችኋልን ፧

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 8 ፤ ኹላችኹ ፡ በላዬ ፡ ዶልታችኹ ፡ ተነሣችኹብኝ ፤ ልጄ ፡ ከእሴይ ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ ሲማማል ፡ ምንም ፡ አይገልጥልኝም ፤ ከእናንተም ፡ አንድ ፡ ለእኔ ፡ የሚያዝን ፡ የለም ፥ ዛሬም ፡ እንደኾነው ፡ ኹሉ ፡ ልጄ ፡ ባሪያዬን ፡ እንዲዶልት ፡ ሲያስነሣብኝ ፡ ማንም ፡ አላስታወቀኝም ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 9 ፤ በሳኦልም ፡ ባሪያዎች ፡ አጠገብ ፡ የቆመው ፡ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ መልሶ ፦ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኖብ ፡ ወደአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አቢሜሌክ ፡ ሲመጣ ፡ አይቼዋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ጠየቀለት ፥ ሥንቅንም ፡ ሰጠው ፥ የፍልስጥኤማዊውንም ፡ የጎልያድን ፡

---

144 ዕብ. ፥ አኪ.ሽ ።

ሰይፍ ፡ ሰጠው ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ የአኪጦብን ፡ ልጅ ፡ ካህኑን ፡ አቢሜሌክን ፡ በኖብም ፡ ያሉትን ፡ ካህናት ፡ የአባቱን ፡ ቤት ፡ ሹሉ ፡ ልኮ ፡ አስጠራቸው ፤ ሹላቸውም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 12 ፤ ሳኦልም ፦ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንግዲህ ፡ ስማ ፡ አለ ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፥ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 13 ፤ ሳኦልም ፦ አንተና ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ ለምን ፡ ዶለታችኹብኝ ፧ እንጀራና ፡ ሰይፍ ፡ ሰጠኸው ፥ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ትውልድ ፡ ጠላት ፡ ኾኖ ፡ ይነሣብኝ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ጠየቅኽለት ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 14 ፤ አቢሜሌክም ፡ መልሶ ፡ ንጉሡን ፦ ከባሪያዎችኽ ፡ ሹሉ ፡ የታመነ ፥ ለንጉሥም ፡ ዐማች ፡ የኾነ ፥ በትእዛዝኽ ፡ የሚኼድ ፥ በቤትኽም ፡ የከበረ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 15 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ ዝምርኹን ፧ ይህ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ይህን ፡ ሹሉ ፡ እጅግ ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ቢኾን ፡ አላውቅምና ፡ ንጉሡ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ በእኔ ፡ በባሪያውና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ አያኑር ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 16 ፤ ንጉሡም ፦ አቢሜሌክ ፡ ሆይ ፥ አንተና ፡ የአባትኽ ፡ ቤት ፡ ሹሉ ፡ ፈጽማችኹ ፡ ትሞታላችኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ በዙሪያው ፡ የቆሙትን ፡ እግረኞች ፦ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ እጅ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ ኵብለላውንም ፡ ሲያውቁ ፡ በገሮዴ ፡ አልገለጡምና ፡ ዞራችኹ ፡ ግደሏቸው ፡ አላቸው ። የንጉሡ ፡ ባሪያዎች ፡ ግን ፡ እጃቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ ላይ ፡ ይዘረጉ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ዶይቅን ፦ አንተ ፡ ዞረኽ ፡ በካህናቱ ፡ ላይ ፡ ውደቅባቸው ፡ አለው ። ኤዶማዊውም ፡ ዶይቅ ፡ ዞሮ ፡ በካህናቱ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ የለበሱትን ፡ ሰማንያ ፡ ዐምስት ፡ ሰዎች ፡ ገደለ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 19 ፤ የካህናቱም ፡ ከተማ ፡ ኖብን ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ መታ ፤ ወንዶችንና ፡ ሴቶችንም ፥ ብላቴናዎችንና ፡ ጡት ፡ የሚጠቡትን ፥ በሬዎችንና ፡ አህያዎችንም ፡ በጎችንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደለ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 20 ፤ ከአኪጦብም ፡ ልጅ ፡ ከአቢሜሌክ ፡ ልጆች ፡ ስሙ ፡ አብያታር ([145]) ፡ የሚባል ፡ አንዱ ፡ ልጅ ፡ አምልጦ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ሸሸ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 21 ፤ አብያታርም ፡ ሳኦል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ ፈጀ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 22 ፤ ዳዊት ፡ አብያታርን ፦ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ በዚያ ፡ መኖሩን ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፦ ለሳኦል ፡ በርግጥ ፡ ይነግራል ፡ ብዬ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ዐውቄዋለኹ ፤ ለአባትኽ ፡ ቤት ፡ ነፍስ ፡ ሹሉ ፡ የጥፋታቸው ፡ ምክንያት ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 22 ፡ 23 ፤ ነፍሴን ፡ የሚፈልግ ፡ የአንተን ፡ ነፍስ ፡ ይፈልጋልና ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ተጠብቀኽ ፡ ትኖራለኽና ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥ ፥ አትፍራ ፡ አለው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 1 ፤ ለዳዊትም ፦ እንሆ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ ቅዒላን ፡ ይወጋሉ ፥ ዐውድማውንም ፡ ይዘርፋሉ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ደረሰው ።

---

145 ዕብ. ፥ አቢያታር ፡ (አበ ፡ ተረፍ ፥ የትርፍ ፡ አባት) ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፦ ልኺድን ፧ እነዚህንስ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ልምታን ፧ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዳዊትን ፦ ኺድ ፥ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ምታ ፡ ቅዒላንም ፡ አድን ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 3 ፤ የዳዊትም ፡ ሰዎች ፦ እንሆ ፥ በዚህ ፡ በይሁዳ ፡ መቀመጥ ፡ እንፈራለን ፥ ይልቁንስ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራዎች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ብንኼድ ፡ እንዴት ፡ ነው ፧ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፦ ፍልስጥኤማውያንን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹና ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ውረድ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 5 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ኼዱ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ እንስሳዎቻቸውንም ፡ ማረኩ ፥ በታላቅም ፡ አገዳደል ፡ ገደሏቸው ። ዳዊትም ፡ በቅዒላ ፡ የሚኖሩትን ፡ አዳነ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 6 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የአቢሜሌክ ፡ ልጅ ፡ አብያታር ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ በኰበለለ ፡ ጊዜ ፡ ኤፉዱን ፡ ይዞ ፡ ወርዶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 7 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሰማ ፤ ሳኦልም ፦ መዝጊያና ፡ መወርወሪያ ፡ ወዳለባት ፡ ከተማ ፡ ገብቶ ፡ ተገኝቷልና ፥ እግዚአብሔር ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 8 ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ወርደው ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፥ ዳዊትንና ፡ ሰዎቹንም ፡ ይከቡ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ አዘዘ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦል ፡ ክፉን ፡ እንዳሰበበት ፡ ዐወቀ ፤ ካህኑን ፡ አብያታርንም ፦ ኤፉዱን ፡ ወደዚህ ፡ አምጣ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ ከተማዪቱን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ቅዒላ ፡ ሊመጣ ፡ እንደሚፈልግ ፡ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ፈጽሜ ፡ ሰምቻለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 11 ፤ የቅዒላ ፡ ሰዎች ፡ በእጁ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡኛልን ፧ ባሪያኽስ ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ ሳኦል ፡ በእውኑ ፡ ይወርዳልን ፧ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ እንድትነግረኝ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ ይወርዳል ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፦ የቅዒላ ፡ ሰዎች ፡ እኔንና ፡ ሰዎቼን ፡ በሳኦል ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡናልን ፧ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 13 ፤ ዳዊትና ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ የሚኾኑ ፡ ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፡ ከቅዒላ ፡ ወጡ ፥ መኼድም ፡ ወደሚችሉበት ፡ ኼዱ ። ሳኦልም ፡ ዳዊት ፡ ከቅዒላ ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡ ሰማ ፤ ስለዚህም ፡ ከመውጣት ፡ ቀረ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በዐምባ ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፥ ከዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ባለው ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ተቀመጠ ፤ ሳኦልም ፡ ዘውትር ፡ ጊዜ ፡ ይፈልገው ፡ ነበር ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠውም ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦል ፡ ነፍሱን ፡ ሊፈልግ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ አየ ፤ ዳዊትም ፡ በዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በጥሻው ፡ ውስጥ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 16 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጥሻው ፡ ስጥ ፡ ኼደ ፤ እጁንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጽንቶ ፦

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 17 ፤ የአባቴ ፡ የሳኦል ፡ እጅ ፡ አታገኝኽምና ፡ አትፍራ ፤ አንተም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾናለኽ ፥ እኔም ፡ ከአንተ ፡ በታች ፡ ኹለተኛ ፡ እኾናለኹ ፤ ይህን ፡ ደግሞ ፡ አባቴ ፡ ሳኦል ፡ ያውቃል ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 18 ፤ ኹለቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ፤ ዳዊትም ፡ በጥሻው ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ፥ ዮናታንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 19 ፤ የዚፍ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ መጥተው ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ በየሴሞን ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ በኤኬላ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ በጥሻ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ ዐምባዎች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡ የለምን ፧

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 20 ፤ አኹንም ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ትወርድ ፡ ዘንድ ፡ ነፍስኽ ፡ እንደ ፡ ወደደች ፡ ውረድ ፤ በንጉሡም ፡ እጅ ፡ ርሱን ፡ አሳልፎ ፡ ለመስጠት ፡ እኛ ፡ አለን ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 21 ፤ ሳኦልም ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ዐዝናችኋልና ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተባረካችኹ ፡ ኹኑ ፤

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 22 ፤ አኹንም ፡ ደግሞ ፡ ኺዱ ፤ ርሱም ፡ እጅግ ፡ ተንኰለኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰምቻለኹና ፡ አጥብቃችኹ ፡ ፈልጉት ፥ እግሩም ፡ የሚኼድበትን ፡ ስፍራ ፡ እዩና ፡ ዕወቁ ፥ በዚያ ፡ ያየውንም ፡ ሰው ፡ አግኙ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ የሚደበቅበትንና ፡ የሚሸሸግበትን ፡ ስፍራ ፡ እዩና ፡ ዕወቁ ፥ በርግጥም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፥ እኔም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እኼዳለኹ ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ቢሸሸግ ፡ በይሁዳ ፡ አእላፋት ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ እፈልገዋለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 24 ፤ እነዚያም ፡ ተነሥተው ፡ ከሳኦል ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ዚፍ ፡ ኼዱ ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ ግን ፡ በየሴሞን ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ በዐረባ ፡ በማዖን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 25 ፤ ሳኦልና ፡ ሰዎቹም ፡ ሊፈልጉት ፡ ኼዱ ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አለቱ ፡ ወርዶ ፡ በማዖን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተቀመጠ ፤ ሳኦልም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊትን ፡ በማዖን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አሳደደው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 26 ፤ ሳኦልም ፡ በተራራው ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኼደ ፥ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ በተራራው ፡ በሌላው ፡ ወገን ፡ ኼዱ ። ሳኦልና ፡ ሰዎቹም ፡ ዳዊትንና ፡ ሰዎቹን ፡ ለመያዝ ፡ ከዐዋቸው ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ ከሳኦል ፡ ፊት ፡ ያመልጥ ፡ ዘንድ ፡ ፈጠነ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ሳኦልም ፡ መልእክተኛ ፡ መጥቶ ፦ ፍልስጥኤማውያን ፡ አገሩን ፡ ወረውታልና ፥ ፈጥነኽ ፡ ና ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 28 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊትን ፡ ማሳደድ ፡ ትቶ ፡ ተመለሰ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋራ ፡ ሊዋጋ ፡ ኼደ ። ስለዚህ ፡ የዚህ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የማምለጥ ፡ አለት ፡ ተባለ ።

ሳሙ.1 ፡ 23 ፡ 29 ፤ ዳዊትም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ በዐይንጋዲ ፡ ዐምባዎች ፡ ተቀመጠ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሳኦል ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ከማሳደድ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ በዐይንጋዲ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አለ ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ደረሰለት ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 2 ፤ ሳኦልም ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ የተመረጡትን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ፥ ዳዊትንና ፡ ሰዎቹንም ፡ ለመፈለግ ፡ የበረሓ ፡ ፍየሎች ፡ ወደነበሩባቸው ፡ አለቶች ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 3 ፤ በመንገድም ፡ አጠገብ ፡ ወዳሉት ፡ የበጎች ፡ ማደሪያዎች ፡ መጣ ፥ በዚያም ፡ ዋሻ ፡ ነበረ ፤ ሳኦልም ፡ ወገቡን ፡ ይሞክር ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ገባ ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ከዋሻው ፡ በውስጠኛው ፡ ቦታ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 4 ፤ የዳዊትም ፡ ሰዎች ፦ እንሆ ፥ ጠላትኽን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ በዐይንኽም ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ ታደርግበታለኽ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የነገረኽ ፡ ቀን ፥ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ነው ፡ አሉት ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ የሳኦልን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ዘርፍ ፡ በቀስታ ፡ ቈረጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 5 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የሳኦልን ፡ የልብሱን ፡ ዘርፍ ፡ ስለ ፡ ቈረጠ ፡ የዳዊት ፡ ልብ ፡ በሐዘን ፡ ተመታ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 6 ፤ ሰዎቹንም ፦ እግዚአብሔር ፡ የቀባው ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እጄንም ፡ እጥልበት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ያርቀው ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ሰዎቹን ፡ ከለከላቸው ፥ በሳኦልም ፡ ላይ ፡ ይነሡ ፡ ዘንድ ፡ አልተዋቸውም ፤ ሳኦልም ፡ ከዋሻው ፡ ተነሥቶ ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 8 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ ተነሣ ፥ ከዋሻውም ፡ ወጣ ፥ ከሳኦልም ፡ በኋላ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ብሎ ፡ ጮኸ ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለከተ ፥ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተጐንብሶ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ ሳኦልን ፡ አለው ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይሻብኻል ፡ የሚሉኽን ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ለምን ፡ ትሰማለኽ ፧

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 10 ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ በዋሻው ፡ ውስጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠኽ ፡ ዐይንኽ ፡ አይታለች ፤ አንተንም ፡ እንድገድልኽ ፡ ሰዎች ፡ ተናገሩኝ ፤ እኔ ፡ ግን ፦ በእግዚአብሔር ፡ የተቀባ ፡ ነውና ፥ እጄን ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ አልዘረጋም ፡ ብዬ ፡ ራራኹልኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 11 ፤ ደግሞም ፥ አባቴ ፡ ሆይ ፥ የልብስኽ ፡ ዘርፍ ፡ በእጄ ፡ እንዳለ ፡ ተመልከተኽ ፡ ዕወቅ ፤ የልብስኽንም ፡ ዘርፍ ፡ በቈረጥኹ ፡ ጊዜ ፡ አልገደልኹኽም ፤ ስለዚህም ፡ በእጄ ፡ ክፋትና ፡ በደል ፡ እንደሌለ ፥ አንተም ፡ ነፍሴን ፡ ልትወስድ ፡ ምንም ፡ ብታሳድደኝ ፡ እንዳልበደልኹኽ ፡ ተመልከተኽ ፡ ዕወቅ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ በእኔና ፡ በአንተ ፡ መካከል ፡ ይፍረድ ፥ እግዚአብሔርም ፡ አንተን ፡ ይበቀልልኝ ፤ እጄ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አትኾንም ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 13 ፤ በጥንት ፡ ምሳሌ ፦ ከኀጢአተኞች ፡ ኀጢአት ፡ ይወጣል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፤ እጄ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አትኾንም ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 14 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ማንን ፡ ለማሳደድ ፡ መጥቷል ፧ አንተስ ፡ ማንን ፡ ታሳድዳለኽ ፧ የሞተ ፡ ውሻን ፡ ወይስ ፡ ቍንጫን ፡ ታሳድዳለኽን ፧

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዳኛ ፡ ይኹን ፥ በእኔና ፡ በአንተም ፡ መካከል ፡ ይፍረድ ፥ አይቶም ፡ ይሟገትልኝ ፥ ከእጅኽም ፡ ያድነኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 16 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዳዊት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለሳኦል ፡ መናገር ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ ሳኦል ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ዳዊት ፥ ይህ ፡ ድምፅኽ ፡ ነውን ፧ አለ ፤ ሳኦልም ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 17 ፤ ዳዊትን ፡ አለው ፦ እኔ ፡ ክፉ ፡ በመለስኹልኽ ፡ ፋንታ ፡ በጎ ፡ መልሰኽልኛልና ፥ አንተ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶኝ ፡ ሳለ ፡ አልገደልኸኝምና ፥ ለእኔ ፡ መልካም ፡ እንዳደረግኽልኝ ፡ አንተ ፡ ዛሬ ፡ አሳየኸኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 19 ፤ ጠላቱን ፡ አግኝቶ ፡ በመልካም ፡ መንገድ ፡ ሸኝቶ ፡ የሚሰድ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ስለዚህ ፡ ለእኔ ፡

ስላደረግኸው ፡ ቸርነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመልስልኽ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 20 ፤ አኹንም ፡ እንሆ ፡ አንተ ፡ በርግጥ ፡ ንጉሥ ፡ እንድትኾን ፡ የእስራኤልም ፡ መንግሥት ፡ በእጅኽ ፡ እንድትጸና ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 21 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ዘሬን ፡ እንዳትቈርጥ ፡ ከአባቴም ፡ ቤት ፡ ስሜን ፡ እንዳታጠፋው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማልልኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 24 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፡ ለሳኦል ፡ ማለለት ፤ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፥ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ዐምባው ፡ ወጡ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 1 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሞተ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበው ፡ አለቀሱለት ፥ በአርማቴምም ፡ በቤቱ ፡ ቀበሩት ። ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደፋራን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወረደ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 2 ፤ በማዖንም ፡ የተቀመጠ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ ከብቱም ፡ በቀርሜሎስ ፡ ነበረ ፤ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ ለርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ በጎችና ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ፍየሎች ፡ ነበሩት ፤ በቀርሜሎስም ፡ በጎቹን ፡ ይሸልት ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 3 ፤ የሰውዮውም ፡ ስም ፡ ናባል ፥ የሚስቱም ፡ ስም ፡ አቢግያ ([146]) ፡ ነበረ ፤ የሴቲቱም ፡ አእምሮ ፡ ታላቅ ፥ መልኳም ፡ የተዋበ ፡ ነበረ ፤ ሰውዮው ፡ ግን ፡ ባለጌ ፡ ነበረ ፥ ግብሩም ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፤ ከካሌብም ፡ ወገን ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳለ ፦ ናባል ፡ በጎቹን ፡ ይሸልታል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ዐሥር ፡ ጕልማሳዎች ፡ ላከ ፡ ለጕልማሳዎችም ፡ አለ ፦ ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ወጥታችኹ ፡ ወደ ፡ ናባል ፡ ኺዱ ፥ በስሜም ፡ ስለ ፡ ሰላም ፡ ጠይቁት ፤

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 6 ፤ እንዲህም ፡ በሉት ፦ በደኅንነት ፡ ኑር ፥ ለአንተና ፡ ለቤትኽም ፡ ለአንተም ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ ሰላም ፡ ይኹን ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ በጎችኽን ፡ እንድትሸልት ፡ ሰምቻለኹ ፤ እረኞችኽም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፥ ከቶ ፡ አልበደልናቸውም ፤ በቀርሜሎስም ፡ በተቀመጡበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ከመንጋው ፡ አንዳች ፡ አልጐደለባቸውም ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 8 ፤ ጕልማሳዎችኽን ፡ ጠይቃቸው ፥ እነርሱም ፡ ይነግሩኻል ፤ አኹንም ፡ እንግዲህ ፡ በመልካም ፡ ቀን ፡ መጥተንብኻልና ፥ ጕልማሳዎች ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ ያግኙ ፤ በእጅኽም ፡ ከተገኘው ፡ ለባሪያዎችኽና ፡ ለልጅኽ ፡ ለዳዊት ፥ እባክኽ ፥ ስጥ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 9 ፤ የዳዊትም ፡ ጕልማሳዎች ፡ መጡ ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በዳዊት ፡ ስም ፡ ለናባል ፡ ነግረው ፡ ዝም ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 10 ፤ ናባልም ፡ ለዳዊት ፡ ባሪያዎች ። ዳዊት ፡ ማን ፡ ነው ፧ የእሴይስ ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እያንዳንዳቸው ፡ ከጌታዎቻቸው ፡ የኰበለሉ ፡ ባሪያዎች ፡ ዛሬ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 11 ፤ እንጀራዬንና ፡ የወይን ፡ ጠጄን ፡ ለሸላቾቼም ፡ ያረድኹትን ፡ ሥጋ ፡ ወስጄ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ለማላውቃቸው ፡ ሰዎች ፡ እሰጣለኹን ፧ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 12 ፤ የዳዊትም ፡ ጕልማሳዎች ፡ ዞረው ፡ በመጡበት ፡ መንገድ ፡ ተመለሱ ፥ መጥተውም ፡ ይህን ፡

---

146 ዕብ. ፥ አቢጋይል ።

ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ሰዎቹን ፦ ኹላችኹ ፡ ሰይፋችኹን ፡ ታጠቁ ፡ አላቸው ። ኹሉም ፡ ሰይፋቸውን ፡ ታጠቁ ፥ ዳዊትም ፡ ሰይፉን ፡ ታጠቀ ፤ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎችም ፡ ዳዊትን ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ፥ ኹለት ፡ መቶውም ፡ በዕቃው ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 14 ፤ ከብላቴናዎቹ ፡ አንዱ ፡ ለናባል ፡ ሚስት ፡ ለአቢግያ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራት ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳለ ፡ ጌታችንን ፡ ሊባርኩ ፡ መልእክተኞች ፡ ላከ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሰደባቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 15 ፤ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ ነበሩ ፤ አልበደሉንምም ፥ ከነርሱም ፡ በኼድንበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሳለን ፡ አንዳች ፡ አልጠፋብንም ፤

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 16 ፤ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ኾነን ፡ መንጋውን ፡ በጠበቅንበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ዐጥር ፡ ኾነውን ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 17 ፤ ስለዚህም ፡ በጌታችንና ፡ በቤቱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንዲመጣ ፡ ተቈርጧልና ፥ ርሱ ፡ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ማንም ፡ ሊናገረው ፡ አይችልምና ፡ የምታደርጊውን ፡ ተመልከቺና ፡ ዕወቂ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 18 ፤ አቢግያም ፡ ፈጥና ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ እንጀራ ፥ ኹለት ፡ አቍማዳ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ዐምስትም ፡ የተዘጋጁ ፡ በጎች ፥ ዐምስትም ፡ መስፈሪያ ፡ ጥብስ ፡ እሸት ፥ አንድ ፡ መቶ ፡ ዘለላ ፡ ዘቢብ ፥ ኹለት ፡ መቶም ፡ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ ወሰደች ፥ በአህያዎችም ፡ ላይ ፡ አስጫነች ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 19 ፤ ለብላቴናዎቿም ፦ አስቀድማችኹ ፡ በፊቴ ፡ ኺዱ ፥ እንሆም ፥ እከተላችኋለኹ ፡ አለች ። ይህንም ፡ ለባሏ ፡ ለናባል ፡ አልነገረችውም ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 20 ፤ ርሷም ፡ በአህያው ፡ ላይ ፡ ተቀምጣ ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ በተሰወረ ፡ ስፍራ ፡ በወረደች ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ወረዱ ፤ ርሷም ፡ ተገናኘቻቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 21 ፤ ዳዊትም ፦ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ከኾነው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንዳይጠፋበት ፡ በእውነት ፡ ከብቱን ፡ ኹሉ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በከንቱ ፡ ጠበቅኹ ፥ ርሱም ፡ ስለ ፡ በጎነቴ ፡ ክፋት ፡ መለሰልኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 22 ፤ ለርሱም ፡ ከኾነው ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ስንኳ ፡ ብተው ፥ እግዚአብሔር ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያድርግ ፡ እንዲህም ፡ ይጨምር ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 23 ፤ አቢግያም ፡ ዳዊትን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ከአህያዋ ፡ ላይ ፡ ፈጥና ፡ ወረደች ፥ በዳዊትም ፡ ፊት ፡ በግንባሯ ፡ ወደቀች ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ ነሣች ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 24 ፤ በእግሩም ፡ ላይ ፡ ወደቀች ፥ እንዲህም ፡ አለች ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ኀጢአት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በጐሮኽ ፡ ልናገር ፥ የባሪያኽንም ፡ ቃል ፡ አድምጥ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 25 ፤ በዚህ ፡ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ በናባል ፡ ላይ ፡ ጌታዬ ፡ ልቡን ፡ እንዳይጣል ፡ እለምናለኹ ፤ እንደ ፡ ስሙ ፡ እንዲሁ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ስሙ ፡ ናባል ፡ ነው ፥ ስንፍናም ፡ ዐድሮበታል ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ግን ፡ ከአንተ ፡ የተላኩትን ፡ የጌታዬን ፡ ጕልማሳዎች ፡ አላየኹም ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 26 ፤ አኹንም ፥ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ! ፡ ወደ ፡ ደም ፡ እንዳትገባ ፥ እጅኽም ፡ ራስኽን ፡ እንዳታድን ፡ የከለከለኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ ጠላቶችኽና ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ የሚሹ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ናባል ፡ ይኹኑ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 27 ፤ አኹንም ፡ ባሪያኽ ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ ያመጣችው ፡ ይህ ፡ መተያያ ፡ ጌታዬን ፡ ለሚከተሉ ፡

ጕልማሳዎች ፡ ይሰጥ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 28 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጦርነት ፡ ስለምትዋጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ ለጌታዬ ፡ የታመነ ፡ ቤት ፡ ይሠራልና ፥ የእኔን ፡ የባሪያኽን ፡ ኀጢአት ፥ እባክኽ ፥ ይቅር ፡ በል ፤ በዘመንኽም ፡ ኹሉ ፡ ክፋት ፡ አይገኝብኽም ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 29 ፤ ያሳድድኽ ፡ ዘንድ ፡ ነፍስኽንም ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ቢነሣ ፥ የጌታዬ ፡ ነፍስ ፡ በሕያዋን ፡ ወገን ፡ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታሰረች ፡ ትኾናለች ፤ የጠላቶችኽንም ፡ ነፋስ ፡ ከወንጭፍ ፡ እንደሚጣል ፡ እንዲሁ ፡ ይጥላታል ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለጌታዬ ፡ የተናገረውን ፡ ቸርነት ፡ ኹሉ ፡ ባደረገልኽ ፡ ጊዜ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ባስነሣኽ ፡ ጊዜ ፥

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 31 ፤ አንተ ፡ በከንቱ ፡ ደም ፡ እንዳላፈሰስኽ ፥ በገዛ ፡ እጅኽም ፡ እንዳልተካስኽ ፡ ይህ ፡ ዕንቅፋትና ፡ የኀሊና ፡ ጸጸት ፡ በጌታዬ ፡ አይኾንልኽም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለጌታዬ ፡ በጎ ፡ ባደረገልኽ ፡ ጊዜ ፥ ባሪያኽን ፡ ዐስብ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 32 ፤ ዳዊትም ፡ አቢግያን ፡ አላት ፦ ዛሬ ፡ እኔን ፡ ለመገናኘት ፡ አንቺን ፡ የሰደደ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 33 ፤ ወደ ፡ ደም ፡ እንዳልኼድ ፥ በእጄም ፡ በቀል ፡ እንዳላደርግ ፡ ዛሬ ፡ የከለከለኝ ፡ አእምሮሽ ፡ የተመሰገነ ፡ ይኹን ፥ አንቺም ፡ የተመሰገንሽ ፡ ኹኚ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ እንዳላደርግብሽ ፡ የከለከለኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እኔን ፡ ለመገናኘት ፡ ፈጥነሽ ፡ ባልመጣሽ ፡ ኖሮ ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ለናባል ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ስንኳ ፡ ባልቀረውም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 35 ፤ ዳዊትም ፡ ያመጣችውን ፡ ከእጇ ፡ ተቀብሎ ፦ በደኅና ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ኺጂ ፤ እንሆ ፥ ቃልሽን ፡ ሰማኹ ፥ ፊትሽንም ፡ አከበርኹ ፡ አላት ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 36 ፤ አቢግያም ፡ ወደ ፡ ናባል ፡ መጣች ፤ እንሆም ፥ በቤቱ ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ግብዣ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ናባልም ፡ እጅግ ፡ ሰክሮ ፡ ነበርና ፥ ልቡ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አልነገረችውም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 37 ፤ በነጋውም ፡ የጠጁ ፡ ስካር ፡ ከናባል ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ሚስቱ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ነገረችው ፤ ልቡም ፡ በውስጡ ፡ ሞተ ፥

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 38 ፤ እንደ ፡ ድንጋይም ፡ ኾነ ፤ ከዐሥር ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናባልን ፡ ቀሠፈው ፥ ርሱም ፡ ሞተ ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 39 ፤ ዳዊትም ፡ ናባል ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ከናባል ፡ እጅ ፡ የስድቤን ፡ ፍርድ ፡ የፈረደልኝ ፥ ባሪያውንም ፡ ከክፋት ፡ የጠበቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ እግዚአብሔርም ፡ የናባልን ፡ ክፋት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መለሰ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ ልኮ ፡ ያገባት ፡ ዘንድ ፡ አቢግያን ፡ ተነጋገራት ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 40 ፤ የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ወደ ፡ አቢግያ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፦ ዳዊት ፡ ያገባሽ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ልኮናል ፡ ብለው ፡ ነገሯት ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 41 ፤ ተነሥታም ፡ በግንባሯ ፡ ወድቃ ፡ እጅ ፡ ነሣችና ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ገረድኽ ፡ የጌታዬን ፡ ሎሌዎች ፡ እግር ፡ ዐጥብ ፡ ዘንድ ፡ አገልጋይ ፡ ነኝ ፡ አለች ።

ሳሙ.1 ፡ 25 ፡ 42 ፤ አቢግያም ፡ ፈጥና ፡ ተነሣች ፤ በአህያም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠች ፥ ዐምስቱም ፡ ገረዶቿ ፡

ተከተሏት ፤ የዳዊትንም ፡ መልእክተኞች ፡ ተከትላ ፡ ኼደች ፥ ሚስትም ፡ ኾነችው ።

ሳሙ.1 ፥ 25 ፥ 43 ፤ ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ ኢይዝራኤላዊቱን ፡ አኪናሖምን ፡ ወሰደ ፤ ኹለቱም ፡ ሚስቶች ፡ ኾኑለት ።

ሳሙ.1 ፥ 25 ፥ 44 ፤ ሳኦል ፡ ግን ፡ የዳዊትን ፡ ሚስት ፡ ልጁን ፡ ሜልኮልን ፡ አገሩ ፡ ጋሊም ፡ ለነበረው ፡ ለሌሳ ፡ ልጅ ፡ ለፈልጢ ፡ ሰጥቶ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 1 ፤ የዚፍ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ጊብዓ ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጥተው ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ በየሴሞን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በኤኬላ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ ተሸሽጓል ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 2 ፤ ሳኦልም ፡ ተነሥቶ ፡ ዳዊትን ፡ በዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ የተመረጡ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ ወደዚፍ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወረደ ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 3 ፤ ሳኦልም ፡ በየሴሞን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ በኤኬላ ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ በመንገዱ ፡ አጠገብ ፡ ሰፈረ ። ዳዊትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥ ሳኦልም ፡ በስተኋላው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አየ ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 4 ፤ ዳዊትም ፡ ሰላዮች ፡ ሰደደ ፥ ሳኦልም ፡ ወደዚህ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በርግጥ ፡ ዐወቀ ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ሳኦል ፡ ወደሰፈረበት ፡ ቦታ ፡ መጣ ፤ ሳኦልና ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርም ፡ የተኙበትን ፡ ስፍራ ፡ አየ ፤ ሳኦልም ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በዙሪያው ፡ ሰፍሮ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 6 ፤ ዳዊትም ፡ ኬጢያዊውን ፡ አቢሜሌክንና ([147]) ፡ የጽሩያን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብን ([148]) ፡ ወንድም ፡ አቢሳን ፦ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሚወርድ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፤ አቢሳም ፦ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እወርዳለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 7 ፤ ዳዊትና ፡ አቢሳም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ በሌሊት ፡ መጡ ፤ እንሆም ፥ ሳኦል ፡ ጦሩ ፡ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ በምድር ፡ ተተክሎ ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፤ አበኔርና ፡ ሕዝቡም ፡ በዙሪያው ፡ ተኝተው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 8 ፤ አቢሳም ፡ ዳዊትን ፦ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላትኽን ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ በጦር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከምድር ፡ ጋራ ፡ ላጣብቀው ፥ ኹለተኛም ፡ አያዳግምም ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 9 ፤ ዳዊትም ፡ አቢሳን ፦ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ የሚዘረጋ ፡ ንጹሕ ፡ አይኾንምና ፡ አትግደለው ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 10 ፤ ደግሞም ፡ ዳዊት ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመታዋል ፥ ወይም ፡ ቀኑ ፡ ደርሶ ፡ ይሞታል ፥ ወይም ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ወርዶ ፡ ይገደላል ፤

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 11 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ እዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኔ ፡ ያርቀው ፤ አኹንም ፡ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ጦርና ፡ የውሃውን ፡ መንቀል ፡ ይዘኽ ፡ እንኺድ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፥ 26 ፥ 12 ፤ ዳዊትም ፡ በሳኦል ፡ ራስ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ ጦርና ፡ የውሃውን ፡ መንቀል ፡ ወሰደ ፤ ማንም ፡ ሳያይ ፡ ሳያውቅም ፡ ኼዱ ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ከባድ ፡ እንቅልፍ ፡ ወድቆባቸው ፡ ነበርና ፥ ኹሉ ፡ ተኝተው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ የነቃ ፡ አልነበረም ።

---

147 ዕብ. ፥ አኒመለክ ፡ (የንጉሥ ፡ ወንድም) ።

148 ዕብ. ፥ የውአብ ፡ (አምላክ ፡ አባቱ) ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ወደዚያ ፡ ተሻገረ ፤ በተራራውም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ርቆ ፡ ቆመ ፤ በመካከላቸውም ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ ለሕዝቡና ፡ ለኔር ፡ ልጅ ፡ ለአበኔር ፦ አበኔር ፡ ሆይ ፥ አትመልስምን ፧ ብሎ ፡ ጮኸ ። አበኔርም ፡ መልሶ ፡ ለንጉሡ ፦ የምትጮኸው ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፡ አበኔርን ፦ አንተ ፡ ጕልማሳ ፡ አይደለኽምን ፧ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ ማን ፡ ነው ፧ ጌታኽን ፡ ንጉሡን ፡ ለመግደል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ ነበርና ፥ ጌታኽን ፡ ንጉሡን ፡ የማትጠብቅ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 16 ፤ ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ ጌታችኹን ፡ አልጠበቃችኹምና ፥ ሞት ፡ ይገባችኋል ፤ አኹንም ፡ የንጉሡ ፡ ጦርና ፡ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ የነበረው ፡ የውሃው ፡ መንቀል ፡ የት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመልከት ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 17 ፤ ሳኦልም ፡ የዳዊት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቆ ፦ ልጄ ፡ ዳዊት ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ድምፅኽ ፡ ነውን ፧ አለው ። ዳዊትም ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ድምፄ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 18 ፤ ደግሞ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ባሪያውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያሳድዳል ፧ ምን ፡ አደረግኹ ፧ ምንስ ፡ ክፋት ፡ በእጄ ፡ ላይ ፡ ተገኝብኝ ፧

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ የእኔን ፡ የባሪያኽን ፡ ቃል ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አስነሥቶኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ቍርባንን ፡ ይቀበል ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ ቢኾኑ ፦ ኺድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አምልክ ፡ ብለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ላይ ፡ እንዳልቀመጥ ፡ ዛሬ ፡ ጥለውኛልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርጉማን ፡ ይኹኑ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 20 ፤ አኹንም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ ቆቅን ፡ እንደሚሻ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነፍሴን ፡ ለመሻት ፡ ወጥቷልና ፥ ደሜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርቆ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይፍሰስ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 21 ፤ ሳኦልም ፦ በድያለኹ ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ዳዊት ፥ ተመለስ ፤ ዛሬ ፡ ነፍሴ ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ከብራለችና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ክፉ ፡ አላደርግብኽም ፥ እንሆ ፥ ስንፍና ፡ አድርጌያለኹ ፥ እጅግ ፡ ብዙም ፡ ስቻለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፡ መልሶ ፡ አለ ፦ የንጉሥ ፡ ጦር ፥ እንሆ ፥ ከብላቴናዎችም ፡ አንድ ፡ ይምጣና ፡ ይውሰዳት ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 23 ፤ ዛሬም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶኽ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀባው ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ እዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ አልወደድኹምና ፡ ለኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጽድቁና ፡ እንደ ፡ እምነቱ ፡ ፍዳውን ፡ ይክፈለው ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 24 ፤ ነፍስኽም ፡ ዛሬ ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ከበረች ፡ እንዲሁ ፡ ነፍሴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ፊት ፡ ትክበር ፥ ከመከራም ፡ ኹሉ ፡ ያድነኝ ።

ሳሙ.1 ፡ 26 ፡ 25 ፤ ሳኦል ፡ ዳዊትን ፦ ልጄ ፡ ዳዊት ፡ ሆይ ፥ ቡሩክ ፡ ኹን ፤ ማድረግን ፡ ታደርጋለኽ ፥ መቻልንም ፡ ትችላለኽ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ፥ ሳኦልም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተመለሰ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ በልቡ ፦ አንድ ፡ ቀን ፡ በሳኦል ፡ እጅ ፡ እጠፋለኹ ፤ ወደፍልስጥኤማውያንም ፡ ምድር ፡ ከመሸሽ ፡ በቀር ፡ የሚሻለኝ ፡ የለም ፤ ሳኦልም ፡ በእስራኤል ፡ አውራጃ ፡ ኹሉ ፡ እኔን ፡ መሻት ፡ ይተዋል ፥ እንዲሁም ፡ ከእጁ ፡ እድናለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ስድስቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ወደጌት ፡ ንጉሥ ፡ ወደአሜኽ ፡ (ወደማያክ) ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ ዐለፉ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 3 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከነ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ከአንኩስ ፡ ጋራ ፡ በጌት ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፤ ከዳዊትም ፡ ጋራ ፡ ኢይዝራኤላዊቱ ፡ አኪናሖምና ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡ አቢግያ ፡ ኹለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 4 ፤ ሳኦልም ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ እንደ ፡ ኰበለለ ፡ ሰማ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አልፈለገውም ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ አንኩስን ፦ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ በአንዲቱ ፡ ከተማ ፡ የምቀመጥበት ፡ ስፍራ ፡ ስጠኝ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በንጉሥ ፡ ከተማ ፡ እቀመጣለኹ ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አንኩስ ፡ ጺቅላግን ፡ ሰጠው ፤ ስለዚህም ፡ ጺቅላግ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ለይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ኾነች ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ አገር ፡ የተቀመጠበት ፡ የዘመን ፡ ቍጥር ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከአራት ፡ ወር ፡ ነበረ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 8 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወጥተው ፡ በጌሹራውያንና ፡ በጌርዛውያን ፡ በዐማሌቃውያንም ፡ ላይ ፡ ዘመቱ ፤ እነዚህም ፡ እስከ ፡ ሱር ፡ እስከ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ድሮውኑ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ ምድሪቱን ፡ መታ ፤ ወንድ ፡ ኾነ ፡ ሴትም ፡ ኾነ ፡ ማንንም ፡ በሕይወት ፡ አልተወም ፤ በጎችንና ፡ ላሞችን ፡ አህያዎችንና ፡ ግመሎችን ፡ ልብስንም ፡ ማረከ ፥ ተመልሶም ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ መጣ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 10 ፤ አንኩስም ፦ ዛሬ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ዘመታችኹ ፧ አለ ፤ ዳዊትም ፦ በይሁዳ ፡ ደቡብ ፥ በይረሕምኤላውያንም ፡ ደቡብ ፥ በቄናውያንም ፡ ደቡብ ፡ ላይ ፡ ዘመትን ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 11 ፤ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ በሚቀመጥበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ልማዱ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ እንዳይናገሩብን ፡ ብሎ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ወንድም ፡ ኾነ ፡ ሴትም ፡ ኾነ ፡ ማንንም ፡ በሕይወት ፡ አልተወም ።

ሳሙ.1 ፡ 27 ፡ 12 ፤ አንኩስም ፦ በሕዝቡ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ የተጠላ ፡ ኾኗል ፤ ስለዚህም ፡ ለዘለዓለም ፡ ባሪያ ፡ ይኾነኛል ፡ ብሎ ፡ ዳዊትን ፡ አመነው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ይዋጉ ፡ ዘንድ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ጭፍራዎቻቸውን ፡ ለሰልፍ ፡ ሰበሰቡ ፤ አንኩስም ፡ ዳዊትን ፦ አንተና ፡ ሰዎችኽ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እንድትወጡ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቅ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ አንኩስን ፦ አኹን ፡ ባሪያኽ ፡ የሚያደርገውን ፡ ታያለኽ ፡ አለው ። አንኩስም ፡ ዳዊትን ፦ እንግዲህ ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ራሴን ፡ ጠባቂ ፡ አደርግኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 3 ፤ ሳሙኤል ፡ ግን ፡ ሞቶ ፡ ነበር ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ አልቅሰውለት ፡ ነበር ፥ በከተማውም ፡ በአርማቴም ፡ ቀብረውት ፡ ነበር ። ሳኦልም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችን ፡ ከምድር ፡ አጥፍቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 4 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ተሰብስበው ፡ መጡ ፡ በሱነምም ፡ ሰፈሩ ፤ ሳኦልም ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡

ሰበሰበ ፥ በጊልቦዓም ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 5 ፤ ሳኦልም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ፥ ልቡም ፡ እጅግ ፡ ተንቀጠቀጠ ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 6 ፤ ሳኦልም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሕልም ፡ ወይም ፡ በኡሪም ፡ ወይም ፡ በነቢያት ፡ አልመለሰለትም ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 7 ፤ ሳኦልም ፡ ባሪያዎቹን ፦ ወደ ፡ ርሷ ፡ ኼጄ ፡ እጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ መናፍስትን ፡ የምትጠራ ፡ ሴት ፡ ፈልጉልኝ ፡ አላቸው ፤ ባሪያዎቹም ፦ እንሆ ፥ መናፍስትን ፡ የምትጠራ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በዐይንዶር ፡ አለች ፡ አሉት ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 8 ፤ ሳኦልም ፡ መልኩን ፡ ለውጦ ፡ ሌላ ፡ ልብስም ፡ ለብሶ ፡ ኼደ ፥ ኹለትም ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፥ በሌሊትም ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ መጡ ። ርሱም ፦ እባክሽ ፥ በመናፍስት ፡ አሟርቺልኝ ፥ የምልሽንም ፡ አስነሺልኝ ፡ አላት ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 9 ፤ ሴቲቱም ፦ እንሆ ፥ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችን ፡ ከምድር ፡ እንዳጠፋ ፡ ሳኦል ፡ ያደረገውን ፡ ታውቃለኽ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ እኔን ፡ ለማስገደል ፡ ወጥመድ ፡ ለነፍሴ ፡ ታደርጋለኽ ፧ አለችው ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 10 ፤ ሳኦልም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ቅጣት ፡ አያገኝሽም ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማለላት ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 11 ፤ ሴቲቱም ፦ ማንን ፡ ላስነሣልኽ ፧ አለች ፤ ርሱም ፦ ሳሙኤልን ፡ አስነሺልኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 12 ፤ ሴቲቱም ፡ ሳሙኤልን ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸች ፤ ሴቲቱም ፡ ሳኦልን ፦ አንተ ፡ ሳኦል ፡ ስትኾን ፡ ለምን ፡ አታለልኸኝ ፧ ብላ ፡ ተናገረችው ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 13 ፤ ንጉሡም ፦ አትፍሪ ፤ ያየሽው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላት ። ሴቲቱም ፡ ሳኦልን ፦ አማልክት ፡ ከምድር ፡ ሲወጡ ፡ አየኹ ፡ አለችው ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 14 ፤ ርሱም ፦ መልኩ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ፧ አላት ። ርሷም ፦ ሽማግሌ ፡ ሰው ፡ ወጣ ፤ መጐናጸፊያም ፡ ተጐናጽፏል ፡ አለች ። ሳኦልም ፡ ሳሙኤል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀ ፥ በፊቱም ፡ ተጐነበሰ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 15 ፤ ሳሙኤልም ፡ ሳኦልን ፦ ለምን ፡ አወክኸኝ ፧ ለምንስ ፡ አስነሣኸኝ ፧ አለው ። ሳኦልም ፡ መልሶ ፦ ፍልስጥኤማውያን ፡ ይወጉኛልና ፥ እጅግ ፡ ተጨንቄያለኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከእኔ ፡ ርቋል ፤ በነቢያት ፡ ወይም ፡ በሕልም ፡ አልመለሰልኝም ፤ ስለዚህም ፡ የማደርገውን ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠራኹኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 16 ፤ ሳሙኤልም ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ ከራቀኽ ፡ ጠላትም ፡ ከኾነኽ ፡ ለምን ፡ ትጠይቀኛለኽ ፧

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በቃሌ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አድርጓል ፤ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥትኽን ፡ ከእጅኽ ፡ ነጥቆ ፡ ለጎረቤትኽ ፡ ለዳዊት ፡ ሰጥቶታል ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 18 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማኽምና ፥ በዐማሌቅም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ ቍጣውን ፡ አላደረግኽምና ፡ ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አድርጎብኻል ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እስራኤልን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፤ ነገም ፡ አንተና ፡ ልጆችኽ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትኾናላችኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራ ፡ ደግሞ ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

ሳሙ.1 ፥ 28 ፥ 20 ፤ ሳኦልም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቁመቱ ፡ ሙሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ ከሳሙኤልም ፡ ቃል ፡

የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ፈራ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ዥሉ ፡ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ዥሉ ፡ እንጀራ ፡ አልበላምና ፡ ኀይል ፡ አልቀረለትም ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 21 ፤ ሴቲቱም ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ መጣች ፥ እጅግም ፡ ደንግጦ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አይታ ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ቃልኽን ፡ ሰማኹ ፥ ነፍሴንም ፡ በእጄ ፡ ጣልኹ ፥ የነገርኸኝንም ፡ ቃል ፡ ሰማኹ ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 22 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ የባሪያኽን ፡ ቃል ፡ እንድትሰማ ፡ እለምንኻለኹ ፥ በፊትኽም ፡ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ ላኑርልኽ ፤ በመንገድም ፡ ስትኼድ ፡ ትበረታ ፡ ዘንድ ፡ ብላ ፡ አለችው ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ አልበላም ፡ ብሎ ፡ እንቢ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባሪያዎቹና ፡ ሴቲቱ ፡ አስገደዱት ፥ ቃላቸውንም ፡ ሰማ ፤ ከምድርም ፡ ተነሥቶ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 24 ፤ ለሴቲቱም ፡ ማለፊያ ፡ እንበሳ ፡ ነበራት ፤ ፈጥና ፡ ዐረደችው ፤ ዱቄቱንም ፡ ወስዳ ፡ ለወሰችው ፥ ቂጣም ፡ እንጀራ ፡ አድርጋ ፡ ጋገረችው ።

ሳሙ.1 ፡ 28 ፡ 25 ፤ በሳኦልና ፡ በባሪያዎቹም ፡ ፊት ፡ አቀረበችው ፤ በልተውም ፡ ተነሡ ፥ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ኼዱ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 1 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራዎቻቸውን ፡ ዥሉ ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ሰበሰቡ ፤ እስራኤላውያንም ፡ በኢይዝራኤል ፡ ባለው ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 2 ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቃዎች ፡ በመቶ ፡ በመቶ ፡ በሺሕ ፡ በሺሕ ፡ እየኾኑ ፡ ያልፉ ፡ ነበር ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ከአንኩስ ፡ ጋራ ፡ በኋለኛው ፡ ጭፍራ ፡ በኩል ፡ ያልፉ ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 3 ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቃዎች ፦ እነዚህ ፡ ዕብራውያን ፡ በዚህ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፧ አሉ ፤ አንኩስም ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ አለቃዎች ፦ ይህ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የሳኦል ፡ ባሪያ ፡ ዳዊት ፡ አይደለምን ፧ ርሱም ፡ በእነዚህ ፡ ቀኖች ፡ በእነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ከተጠጋበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ አላገኘኹበትም ፡ አላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 4 ፤ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ ተቈጥተው ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ባስቀመጥኸው ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ይመለስ ፤ በሰልፉ ፡ ውስጥ ፡ ጠላት ፡ እንዳይኾነን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ አይውረድ ፤ ከጌታው ፡ ጋራ ፡ በምን ፡ ይታረቃል ፧ የእነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ራስ ፡ በመቍረጥ ፡ አይደለምን ፧

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 5 ፤ ወይስ ፡ ሴቶች ፦ ሳኦል ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፥ ዳዊት ፡ እልፍ ፡ ገደለ ፡ ብለው ፡ በዘፈን ፡ የዘመሩለት ፡ ይህ ፡ ዳዊት ፡ አይደለምን ፧ አሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 6 ፤ አንኩስም ፡ ዳዊትን ፡ ጠርቶ ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ አንተ ፡ ቅን ፡ ነኽ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ በጭፍራው ፡ በኩል ፡ መውጣትኽና ፡ መግባትኽ ፡ በፊቴ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ወደ ፡ እኔም ፡ ከመጣኽ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አንዳች ፡ ክፋት ፡ አላገኘኹብኽም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በአለቃዎች ፡ ዘንድ ፡ አልተወደድኽም ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ ተመልሰኽ ፡ በደኅና ፡ ኺድ ፥ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አለቃዎች ፡ ዐይን ፡ ክፋት ፡ አታድርግ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ አንኩስን ፦ ምን ፡ አድርጌያለኹ ፧ ኼጄስ ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ጠላቶች ፡ ጋራ ፡ እንዳልዋጋ ፥ በፊትኽ ፡ ከተቀመጥኹ ፡ ዠምሬ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእኔ ፡ በባሪያኽ ፡ ምን ፡ አግኝተኽብኛል ፧ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 9 ፤ አንኩስም ፡ መልሶ ፡ ዳዊትን ፦ እንደ ፡ አምላክ ፡ መልእክተኛ ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ዐውቃለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፦ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ አይወጣም ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ የመጡ ፡ የጌታኽ ፡ ባሪያዎች ፡ ማልዳችኹ ፡ ተነሡ ፤ ሲነጋም ፡ ተነሥታችኹ ፡ ኺዱ ፡ አለው ።

ሳሙ.1 ፡ 29 ፡ 11 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ማልደው ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፥ ወደፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ተነሡ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወጡ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጺቅላግ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፥ ዐማሌቃውያን ፡ በደቡብ ፡ አገርና ፡ በጺቅላግ ፡ ላይ ፡ ዘምተው ፡ ነበር ፥ ጺቅላግንም ፡ መትተው ፡ በእሳት ፡ አቃጥለዋት ፡ ነበር ፤

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 2 ፤ ሴቶቹንና ፡ በውስጧም ፡ የነበሩትን ፡ ኹሉ ፡ ከታናሽ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ድረስ ፡ ማርከው ፡ ነበር ፤ ኹሉንም ፡ ወስደው ፡ መንገዳቸውን ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ አልገደሉም ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 3 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በእሳት ፡ ተቃጥላ ፥ ሚስቶቻቸውም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ ተማርከው ፡ አገኙ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 4 ፤ ዳዊት ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ለማልቀስ ፡ ኀይል ፡ እስኪያጡ ፡ ድረስ ፡ አለቀሱ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 5 ፤ የዳዊትም ፡ ኹለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ኢይዝራኤላዊቱ ፡ አኪናሖምና ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡ የነበረችው ፡ አቢግያ ፡ ተማርከው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 6 ፤ ስለ ፡ ወንዶችና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸው ፡ የሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ ተቈጥቶ ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡ ፡ ሊወግሩት ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ ዳዊት ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ፤ ዳዊት ፡ ግን ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ አበረታ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ የአቢሜሌክን ፡ ልጅ ፡ ካህኑን ፡ አብያታርን ፦ ኤፉዱን ፡ አቅርብልኝ ፡ አለው ፤ አብያታርም ፡ ኤፉዱን ፡ ለዳዊት ፡ አቀረበለት ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፦ የእነዚህን ፡ ሰራዊት ፡ ፍለጋ ፡ ልከተልን ፧ አገኛቸዋለኹን ፧ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ ርሱም ፦ ታገኛቸዋለኽና ፥ ፈጽመኽም ፡ ምርኮውን ፡ ትመልሳለኽና ፡ ፍለጋቸውን ፡ ተከተል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ኼዱ ፥ እስከ ፡ ቦሦር [149] ፡ ወንዝ ፡ ድረስም ፡ መጡ ፤ ከነርሱም ፡ የቀሩት ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ አሳደዱ ፤ ኹለቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ የቦሦር ፡ ወንዝን ፡ መሻገር ፡ ደክመዋልና ፥ እኧላ ፡ ቀሩ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 11 ፤ በበረሓውም ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ግብጻዊ ፡ አግኝተው ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፤ እንጀራም ፡ ሰጡትና ፡ በላ ፥ ውሃም ፡ አጠጡት ፤

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 12 ፤ ከበለሱም ፡ ጥፍጥፍ ፡ ቍራጭና ፡ ኹለት ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ ሰጡት ፤ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፡ ውሃም ፡ አልጠጣም ፡ ነበርና ፥ በበላ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፦ አንተ ፡ የማን ፡ ነኽ ፧ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ የዐማሌቃዊ ፡ ባሪያ ፡ ግብጻዊ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ፤ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በፊት ፡ ታምሜ ፡ ነበርና ፥ ጌታዬ ፡ ጥሎኝ ፡ ኼደ ።

---

149 ዕብ. ፥ ቦሦር ፤ (በሥረ • በሠረ)

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 14 ፤ እኛም ፡ በከሊታውያን ፡ ደቡብ ፥ በይሁዳም ፡ ምድር ፥ በካሌብም ፡ ደቡብ ፡ ላይ ፡ ዘመትን ፤ ጺቅላግንም ፡ በእሳት ፡ አቃጠልናት ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፦ ወደ ፡ እነዚያ ፡ ሰራዊት ፡ ዘንድ ፡ ልትመራኝ ፡ ትወዳለኽን ፧ አለው ፤ ርሱም ፦ እንዳትገድለኝ ፥ ለጌታዬም ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ እንዳትሰጠኝ ፡ በአምላክ ፡ ማልልኝ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እነዚያ ፡ ሰራዊት ፡ እመራኻለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ታችም ፡ እንዲወርድ ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ከፍልስጥኤማውያንና ፡ ከይሁዳ ፡ ምድር ፡ ከወሰዱት ፡ ከብዙ ፡ ምርኮ ፡ ዥሉ ፡ የተነሣ ፡ በልተው ፡ ጠጥተውም ፡ የበዓልም ፡ ቀን ፡ አድርገው ፡ በምድር ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡ ነበር ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ ከማታ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማግስቱ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ መታቸው ፤ ከነርሱም ፡ በግመል ፡ ተቀምጠው ፡ ከሸሹ ፡ ከአራት ፡ መቶ ፡ ጕልማሳዎች ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ያመለጠ ፡ የለም ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 18 ፤ ዳዊትም ፡ ዐማሌቃውያን ፡ የወሰዱትን ፡ ዥሉ ፡ አስጣላቸው ፥ ኹለቱንም ፡ ሚስቶቹን ፡ አዳነ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 19 ፤ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፥ ከወሰዱትም ፡ ምርኮ ፡ ዥሉ ፥ ታላቅም ፡ ኾነ ፡ ታናሽም ፡ ኾነ ፥ ምንም ፡ የጐደለባቸው ፡ የለም ፤ ዳዊትም ፡ ዥሉን ፡ አስጣለ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ የበጉንና ፡ የላሙን ፡ መንጋ ፡ ዥሉ ፡ ወሰደ ፥ ከራሱም ፡ ከብት ፡ ፊት ፡ እየነዳ ፦ ይህ ፡ የዳዊት ፡ ምርኮ ፡ ነው ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 21 ፤ ዳዊትም ፡ ደክመው ፡ ዳዊትን ፡ ይከተሉት ፡ ዘንድ ፡ ወዳልቻሉ ፥ በቦሦር ፡ ወንዝ ፡ ወዳስቀራቸው ፡ ወደ ፡ ኹለቱ ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ መጣ ፤ እነርሱም ፡ ዳዊትን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ሊቀበሉ ፡ ወጡ ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ደኅንነታቸውን ፡ ጠየቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 22 ፤ ከዳዊትም ፡ ጋራ ፡ ከኼዱ ፡ ሰዎች ፡ ክፉዎቹና ፡ ምናምንቴዎቹ ፡ ዥሉ ፦ እነዚህ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አልመጡምና ፡ እየራሳቸው ፡ ሚስቶቻቸውንና ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይዘው ፡ ይኺዱ ፡ እንጂ ፡ ካስጣልነው ፡ ምርኮ ፡ ምንም ፡ አንሰጣቸውም ፡ አሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 23 ፤ ዳዊትም ፦ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ የጠበቀን ፡ በእኛም ፡ ላይ ፡ የመጣውን ፡ ጭፍራ ፡ በእጃችን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ አታድርጉ ፤

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 24 ፤ ይህንስ ፡ ነገ ፡ ማን ፡ ይሰማችኋል ፧ ነገር ፡ ግን ፡ የተዋጉትና ፡ ዕቃውን ፡ የጠበቁት ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እኩል ፡ ይኾናል ፥ አንድነት ፡ ይካፈላሉ ፡ አለ ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 25 ፤ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ለእስራኤል ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ አደረገው ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 26 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ጺቅላግ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ለዘመዶቹ ፡ ለይሁዳ ፡ ሽማግሌዎች ፦ እንሆ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ምርኮ ፡ በረከትን ፡ ተቀበሉ ፡ ብሎ ፡ ከምርኮው ፡ ሰደደላቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 27 ፤ በቤቴል ፡ ለነበሩ ፥ በራሞት ፡ በደቡብ ፡ ለነበሩ ፡

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 28 ፤ በየቲር ፡ ለነበሩ ፥ በዐሮዔር ፡ ለነበሩ ፥ በሚፍሞት ፡ ለነበሩ ፥ በኤሽትሞዐ ፡ ለነበሩ ፥

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 29 ፤ በቀርሜሎስ ፡ ለነበሩ ፥ በይረሕምኤላውያንና ፡ በቄናውያን ፡ ከተማዎችም ፡ ለነበሩ ፥

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 30 ፤ በሔርማ ፡ ለነበሩ ፥ በቦራሣን ፡ ለነበሩ ፥ በዓታክ ፡ ለነበሩ ፥ በኬብሮን ፡ ለነበሩ ፥

ሳሙ.1 ፡ 30 ፡ 31 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ በተመላለሱበት ፡ ስፍራ ፡ ለነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ላከ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 1 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ ተወግተውም ፡ በጊልቦዓ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወደቁ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 2 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሳኦልንና ፡ ልጆቹን ፡ በእግር ፡ በእግራቸው ፡ ተከትለው ፡ አባረሯቸው ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የሳኦልን ፡ ልጆች ፡ ዮናታንንና ፡ ዐሚናዳብን ፡ ሜልኪሳንም ፡ ገደሉ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 3 ፤ ሰልፍም ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ ጠነከረ ፥ ቀስተኞችም ፡ አገኙት ፤ ርሱም ፡ ከቀስተኞቹ ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 4 ፤ ሳኦልም ፡ ጋሻ ፡ ጐግሬውን ፦ እነዚህ ፡ ቈላፋን ፡ መጥተው ፡ እንዳይወጉኝና ፡ እንዳይሣለቁብኝ ፡ ሰይፍኽን ፡ መዘ፡ኽ ፡ ውጋኝ ፡ አለው ። ጋሻ ፡ ጐግሬው ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፈርቶ ፡ ነበርና ፥ እንቢ ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ሰይፉን ፡ ወስዶ ፡ በላዩ ፡ ወደቀ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 5 ፤ ጋሻ ፡ ጐግሬውም ፡ ሳኦል ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በሰይፉ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሞተ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሳኦል ፡ ሦስቱም ፡ ልጆቹ ፡ ጋሻ ፡ ጐግሬውም ፡ ሰዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 7 ፤ በሸለቆውም ፡ ማዶና ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ የነበሩ ፡ እስራኤላውያን ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ሸሹ ፥ ሳኦልና ፡ ልጆቹም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዎቹን ፡ ለቀው ፡ ሸሹ ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ ተቀመጡባቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 8 ፤ በማግስቱም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ የሞቱትን ፡ ለመግፈፍ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦልና ፡ ሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ በጊልቦዓ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ አገኟቸው ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 9 ፤ የሳኦልንም ፡ ራስ ፡ ቈረጠው ፡ የጦር ፡ ዕቃውን ፡ ገፈ፡ው ፡ ለጣዖታቱ ፡ መቅደስ ፡ ለሕዝቡም ፡ የምሥራች ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደፍልስጥኤማውያን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ሰደዱ ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 10 ፤ የጦር ፡ ዕቃውንም ፡ በዐስታሮት ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት ፤ ሬሳውንም ፡ በቤትሳን ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ አንጠለጠሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 11 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ የኢ.ያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 12 ፤ ዝግናዎች ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ተነሥተው ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ፥ የሳኦልንም ፡ ሬሳ ፡ የልጆቹንም ፡ ሬሳ ፡ ከቤትሳን ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ አወረዱ ፤ ወደ ፡ ኢ.ያቢስም ፡ መጡ ፥ በዚያም ፡ አቃጠሉት ።

ሳሙ.1 ፡ 31 ፡ 13 ፤ ዐጥንታቸውንም ፡ ወሰዱ ፡ በኢ.ያቢስም ፡ ባለው ፡ በዐጣጡ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ቀበሩት ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ጾሙ ። ❖

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፥ ሳኦል ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ዐማሌቃውያንን ፡ ከመግደል ፡ ተመልሶ ፡ በጺቅላግ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፥ እንሆ ፥ ከሳኦል ፡ ሰፈር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ መጣ ፤ ወደ ፡ ዳዊትም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ዳዊትም ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ∴ አለው ፡ ርሱም ፦ ከእስራኤል ፡ ሰፈር ፡ ኰብልዬ ፡ መጣኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ዳዊትም ፦ ነገሩ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ኾነ ∴ እስኪ ፡ ንገረኝ ፡ አለው ። ርሱም ፡ መልሶ ፦ ሕዝቡ ፡ ከሰልፉ ፡ ሸሽቷል ፥ ከሕዝቡ ፡ ብዙው ፡ ወደቁ ፡ ሞቱም ፤ ሳኦልና ፡ ልጁም ፡ ዮናታን ፡ ደግሞ ፡ ሞተዋል ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ወሬኛውን ፡ ጕልማሳ ፦ ሳኦልና ፡ ልጁ ፡ ዮናታን ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በምን ፡ ታውቃለኽ ∴ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ወሬኛውም ፡ ጕልማሳ ፡ አለ ፦ በድንገት ፡ ወደጊልቦዓ ፡ ተራራ ፡ መጣኹ ፥ እንሆም ፥ ሳኦል ፡ ጦሩን ፡ ተመርኵዞ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ ሠረገላዎችና ፡ ፈረሰኞችም ፡ ተከትለው ፡ ደረሱበት ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ወደ ፡ ኋላውም ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ እኔን ፡ አይቶ ፡ ጠራኝ ፤ እኔም ፦ እንሆኝ ፡ አልኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ∴ አለኝ ፤ እኔም ፦ ዐማሌቃዊ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ መለስኹለት ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ርሱም ፦ ሰውነቴ ፡ ዝሏልና ፥ ደግሞ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ነፍሴ ፡ ገና ፡ ፈጽማ ፡ ሕያው ፡ ናትና ፥ በላዬ ፡ ቆመኽ ፡ ግደለኝ ፡ አለኝ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 10 ፤ እኔም ፡ ከወደቀ ፡ በኋላ ፡ አለመዳኑን ፡ አይቼ ፡ በላዩ ፡ ቆሜ ፡ ገደልኹት ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ ዘውድ ፡ በክንዱም ፡ የነበረውን ፡ ቢተዋ ፡ ወሰድኹ ፥ ወደዚህም ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ አመጣኹት ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ዳዊትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ልብሳቸውን ፡ ይዘው ፡ ቀደዱ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ በሰይፍም ፡ ወድቀዋልና ፥ ለሳኦልና ፡ ለልጁ ፡ ለዮናታን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ሕዝብ ፡ ለእስራኤልም ፡ ወገን ፡ እንባ ፡ እያፈሰሱ ፡ አለቀሱ ፥ እስከ ፡ ማታም ፡ ድረስ ፡ ጾሙ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ወሬኛውን ፡ ጕልማሳ ። አንተ ፡ ከወዴት ፡ ነኽ ∴ አለው ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ የመጻተኛው ፡ የዐማሌቃዊው ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 14 ፤ ዳዊትም ፦ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ ለመግደል ፡ እጅኽን ፡ ስትዘረጋ ፡ ለምን ፡ አልፈራኽም ∴ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 15 ፤ ዳዊትም ፡ ከጕልማሳዎቹ ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ፦ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቅረብና ፡ ውደቅበት ፡ አለው ። ርሱም ፡ መታው ፥ ሞተም ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 16 ፤ ዳዊትም ፦ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ እኔ ፡ ገድያለኹ ፡ ብሎ ፡ አፍኽ ፡ በላይኽ ፡

መስክሯልና ፥ ደምኽ ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 17 ፤ ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ሳኦልና ፡ ሰለ ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ዮናታን ፡ ይህን ፡ የሐዘን ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘ ፥

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 18 ፤ የይሁዳንም ፡ ልጆች ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። እንሆ ፥ ይህ ፡ በያሻር ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 19 ፤ የእስራኤል ፡ ክብር ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ተወግቶ ፡ ሞተ ፤ ኀያላን ፡ እንዴት ፡ ወደቁ! ፡

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 20 ፤ የፍልስጥኤማውያን ፡ ቈነጕሾች ፡ ደስ ፡ እንዳይላቸው ፥ የቈላፋንም ፡ ቈነጕሾች ፡ እልል ፡ እንዳይሉ ፥ በጌት ፡ ውስጥ ፡ አታውሩ ፤ በአስቀሎናም ፡ አደባባይ ፡ የምሥራች ፡ አትበሉ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 21 ፤ እናንተ ፡ የጊልቦዓ ፡ ተራራዎች ፡ ሆይ ፥ የሳኦል ፡ ጋሻ ፡ በዘይት ፡ እንዳልተቀባ ፥ የኀያላን ፡ ጋሻ ፡ በዚያ ፡ ወድቋልና ፥ ዝናብና ፡ ጠል ፡ አይውረድባችኹ ፥ ቍርባንንም ፡ የሚያበቅል ፡ ዕርሻ ፡ አይኹንባችኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 22 ፤ ከሞቱት ፡ ደምና ፡ ከኀያላን ፡ ስብ ፡ የዮናታን ፡ ቀስት ፡ አልተመለሰችም ፥ የሳኦልም ፡ ሰይፍ ፡ በከንቱ ፡ አልተመለሰም ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 23 ፤ ሳኦልና ፡ ዮናታን ፡ የተዋደዱና ፡ የተስማሙ ፡ ነበሩ ፤ በሕይወታቸውና ፡ በሞታቸው ፡ አልተለያዩም ፤ ከንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ነበሩ ፤ ከአንበሳም ፡ ይልቅ ፡ ብርቱዎች ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 24 ፤ የእስራኤል ፡ ቈነጕሾች ፡ ሆይ ፥ ቀይ ፡ ሐርና ፡ ጥሩ ፡ ግምጃ ፡ ያለብሳችኹ ፡ ለነበረ ፥ በወርቀ ፡ ዘቦም ፡ ላስጌጣችኹ ፡ ለሳኦል ፡ አልቅሱለት ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 25 ፤ ኀያላንም ፡ በሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ወደቁ! ፡ ዮናታንም ፡ በኰረብታዎችኽ ፡ ላይ ፡ ወድቋል ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 26 ፤ ወንድሜ ፡ ዮናታን ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እጨነቃለኹ ፤ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ውድኽ ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡ ነበረ ፤ ከሴት ፡ ፍቅር ፡ ይልቅ ፡ ፍቅርኽ ፡ ለእኔ ፡ ግሩም ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፥ 1 ፥ 27 ፤ ኀያላን ፡ እንዴት ፡ ወደቁ! ፡ የሰልፍም ፡ ዕቃ ፡ እንዴት ፡ ጠፉ! ፡

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 1 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፦ ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ልውጣን ፧ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፦ ውጣ ፡ አለው ። ዳዊትም ፦ ወዴት ፡ ልውጣ ፧ አለ ። ርሱም ፦ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ውጣ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 2 ፤ ዳዊትም ፡ ከኹለቱ ፡ ሚስቶቹ ፡ ከኢይዝራኤላዊቱ ፡ ከአኪናሖምና ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡ ከነበረችው ፡ ከአቢግያ ፡ ጋራ ፡ ወደዚያ ፡ ወጣ ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎችና ፡ ቤተ ፡ ሰባቸውን ፡ ኹሉ ፡ አመጣ ፤ በኬብሮንም ፡ ከተማዎች ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 4 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ በይሁዳ ፡ ቤት ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ በዚያ ፡ ቀቡት ። ሳኦልን ፡ የቀበሩት ፡ የኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ወደኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ መልእክተኞችን ፡ ልኮ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። እናንተ ፡ ለጌታችኹ ፡ ለሳኦል ፡ ይህን ፡ ቸርነት ፡ አድርጋችኋልና ፥ ቀብራችኹትማልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ የተባረካችኹ ፡ ኹኑ ።

ሳሙ.2 ፥ 2 ፥ 6 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸርነትንና ፡ እውነትን ፡ ያድርግላችኹ ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ አድርጋችኋልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ቸርነት ፡ እመልስላችኋለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ ጌታችኹ ፡ ሳኦል ፡ ሞቷልና ፥ እጃችኹ ፡ ትጽና ፥ እናንተም ፡ ጨክኑ ፤ ዳግም ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀብተውኛል ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 8 ፤ የሳኦልም ፡ ጭፍራ ፡ አለቃ ፣ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፥ የሳኦልን ፡ ልጅ ፣ ኢያቡስቴን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ አሻገረው ፤

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 9 ፤ በገለዓድና ፡ በአሹራውያን ፡ በኢይዝራኤልም ፡ በኤፍሬምም ፡ በብንያምም ፡ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አነገሠው ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 10 ፤ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ኢያቡስቴም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንገሥ ፡ በገዮመረ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡ ዓመት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኹለት ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ዳዊትን ፡ ተከተለ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ በይሁዳ ፡ ቤት ፡ ነግሦ ፡ በኬብሮን ፡ የተቀመጠበት ፡ ዘመን ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርና ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ የኢያቡስቴ ፡ ባሪያዎች ፡ ከመሃናይም ፡ ወደ ፡ ገባዖን ፡ ወጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብና ፡ የዳዊት ፡ ባሪያዎች ፡ ወጥተው ፡ በገባዖን ፡ ውሃ ፡ መቆሚያ ፡ አጠገብ ፡ ተገናኟቸው ፤ በውሃውም ፡ መቆሚያ ፡ በአንዱ ፡ ወገን ፡ እነዚህ ፥ በሌላውም ፡ ወገን ፡ እነዚያ ፡ ኾነው ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ አበኔርም ፡ ኢዮአብን ፦ ጕልማሳዎች ፡ ይነሡ ፥ በፊታችንም ፡ ይቈራቈሱ ፡ አለው ፤ ኢዮአብም ፦ ይነሡ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ለብንያም ፡ ወገንና ፡ ለሳኦል ፡ ልጅ ፡ ለኢያቡስቴ ፡ አስራ ፡ ኹለት ፥ ከዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ተቈጥረው ፡ ተነሡ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ የወደረኛውን ፡ ራስ ፡ ያዘ ፥ ሰይፉንም ፡ በወደረኛው ፡ ጐን ፡ ሻጠ ፥ ተያይዘውም ፡ ወደቁ ። የዚያም ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ዕርሻ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፥ ርሱም ፡ በገባዖን ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጽኑ ፡ ሰልፍ ፡ ኾነ ፤ በዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ፊት ፡ አበኔርና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ተሸነፉ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ሦስቱ ፡ የጽሩያ ፡ ልጆች ፡ ኢዮአብና ፡ አቢሳ ፡ ዐሳሄልም ፡ ነበሩ ፤ ዐሳሄልም ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ሚዳቋ ፡ በሩጫ ፡ ፈጣን ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ዐሳሄልም ፡ የአበኔርን ፡ ፍለጋ ፡ ተከታተለ ፥ አበኔርንም ፡ ከማሳደድ ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ አላለም ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 20 ፤ አበኔርም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተና ፦ አንተ ፡ ዐሳሄል ፡ ነኽን ፧ አለ ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 21 ፤ አበኔርም ፦ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ፈቀቅ ፡ በል ፤ አንድ ፡ ጕልማሳ ፡ ያዝ ፥ መሣሪያውንም ፡ ውሰድ ፡ አለው ። ዐሳሄል ፡ ግን ፡ ርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ፈቀቅ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 22 ፤ አበኔርም ፡ ዐሳሄልን ፦ ከምድር ፡ ጋራ ፡ እንዳላጣብቅኽ ፡ እኔን ፡ ከማሳደድ ፡ ፈቀቅ ፡ በል ፤ ወደ ፡ ወንድምኽ ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ፊቴን ፡ አቅኝቼ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከርሱ ፡ ፈቀቅ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ፤ አበኔርም ፡ በጦሩ ፡ ጫፍ ፡ ሆዱን ፡ ወጋው ፥ ጦሩም ፡ በኋላው ፡ ወጣ ፥ በዚያም ፡ ስፍራ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ። ዐሳሄልም ፡ ወድቆ ፡ በሞተበቱ ፡ ስፍራ ፡ የሚያልፍ ፡ ኹሉ ፡ ይቆም ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 24 ፤ ኢዮአብና ፡ አቢሳም ፡ አበኔርን ፡ አሳደዱ ፤ በገባዖንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ በጋይ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እስካለው ፡ እስከ ፡ አማ ፡ ኰረብታ ፡ ድረስ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ፀሓይ ፡ ጠለቀች ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 25 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ አበኔር ፡ ተሰበሰቡ ፥ በአንድነትም ፡ ኾኑ ፥ በኰረብታም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 26 ፤ አበኔርም ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ጮኸ ፦ ሰይፍ ፡ በእውኑ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ያጠፋልን ፧ ፍጻሜውሳ ፡ መራራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቅምን ፧ ሕዝቡ ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ከማሳደድ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ የማትናገር ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 27 ፤ ኢዮአብም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ባትናገር ፡ ኖሮ ፡ ሕዝቡ ፡ በጧት ፡ ወጥተው ፡ በኼዱ ፡ ነበር ፥ ወንድሞቻቸውንም ፡ ማሳደድ ፡ በተዉ ፡ ነበር ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 28 ፤ ኢዮአብም ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ቆመ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እስራኤልን ፡ አላሳደደም ፥ ሰልፍም ፡ አላደረገም ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 29 ፤ አበኔርና ፡ ሰዎቹም ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ዐረባ ፡ እያለፉ ፡ ኼዱ ፤ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገሩ ፥ ቢትሮንንም ፡ ኹሉ ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ መጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 30 ፤ ኢዮአብም ፡ አበኔርን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሰ ፤ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ከዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ከዐሳሄል ፡ ሌላ ፡ ዐሥራ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዎች ፡ ጐደሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 31 ፤ የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ከብንያምና ፡ ከአበኔር ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ያኽል ፡ ገደሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 2 ፡ 32 ፤ ዐሳሄልንም ፡ አንሥተው ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ በአባቱ ፡ መቃብር ፡ ቀበሩት ፤ ኢዮአብና ፡ ሰዎቹም ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ፥ በኬብሮንም ፡ አነጉ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 1 ፤ በሳኦል ፡ ቤትና ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ጦርነት ፡ ኾነ ፤ የዳዊት ፡ ቤት ፡ እየበረታ ፥ የሳኦል ፡ ቤት ፡ ግን ፡ እየደከመ ፡ የሚኼድ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ለዳዊትም ፡ ወንድ ፡ ልጆች ፡ በኬብሮን ፡ ተወለዱለት ፤ በኵሩም ፡ ከኢይዝራኤላዊቱ ፡ ከአኪናሖም ፡ የተወለደው ፡ አምኖን ([150]) ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ኹለተኛውም ፡ የቀርሜሎሳዊው ፡ የናባል ፡ ሚስት ፡ ከነበረች ፡ ከአቢግያ ፡ የተወለደው ፡ ዶሎሕያ ([151]) ፡ ነበረ ። ሦስተኛውም ፡ ከጌሹር ፡ ንጉሥ ፡ ከተልማይ ([152]) ፡ ልጅ ፡ ከመዓካ ፡ የተወለደው ፡ አቤሴሎም ([153]) ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ አራተኛውም ፡ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፥ ዐምስተኛውም ፡ የአቢጣል ፡ ልጅ ፡ ሰፋጥያስ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ስድስተኛውም ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ የዔግላ ፡ ልጅ ፡ ይትረኃም ፡ ነበረ ። እነዚህም ፡ ለዳዊት ፡

---

150 አማኝ ።

151 ዕብ. ፥ ኪልአብ ፡ (ከልአ ፡ አብ • ከላ ፥ ከለከለ ፡ አባት) ።

152 ዕብ. ፥ ታልማይ ፡ (ተላሚ ፥ ዐራሽ) ።

153 ዕብ. ፥ አቢሻሎም ፡ (አበ ፡ ሰላም ፥ የሰላም ፡ አባት) ።

በኬብሮን ፡ ተወለዱለት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 6 ፤ በሳኦል ፡ ቤትና ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ጦርነት ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ አበኔር ፡ በሳኦል ፡ ቤት ፡ ይበረታ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ለሳኦልም ፡ የኢዮሄል ፡ ልጅ ፡ ሪጽፋ ፡ የተባለች ፡ ቁባት ፡ ነበረችው ፤ ኢያቡስቴም ፡ አበኔርን ፦ ወዳባቴ ፡ ቁባት ፡ ለምን ፡ ገባኽ ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ አበኔርም ፡ በኢያቡስቴ ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እኔ ፡ ለአባትኽ ፡ ለሳኦል ፡ ቤት ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዘመዶቹም ፡ ቸርነት ፡ አድርጌያለኹ ፥ አንተንም ፡ ለዳዊት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጠኹም ፤ አንተም ፡ ዛሬ ፡ ከዚች ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ስለሠራኹት ፡ ኀጢአት ፡ ትከሰኛለኽ ፤ በእውኑ ፡ እኔ ፡ የውሻ ፡ ራስ ፡ ነኝን ፧

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ 10 ፤ መንግሥትን ፡ ከሳኦል ፡ ቤት ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ የዳዊትንም ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ከዳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ እንደ ፡ ማለለት ፡ እንዲሁ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ባላደርግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአበኔር ፡ ይህን ፡ ያድርግበት ፡ ይህንም ፡ ይጨምርበት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ኢያቡስቴም ፡ አበኔርን ፡ ይፈራው ፡ ነበርና ፥ አንዳች ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 12 ፤ አበኔርም ፡ ለዳዊት ፦ ምድሪቱ ፡ ለማን ፡ ናት ፧ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርግ ፥ እጄም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ትኾናለች ፥ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ እመልሰዋለኹ ፡ ብለው ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞች ፡ ሰደደለት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፦ ይኹን ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርጋለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ነገር ፡ ከአንተ ፡ እሻለኹ ፤ ፊቴን ፡ ለማየት ፡ በመጣኽ ፡ ጊዜ ፥ የሳኦልን ፡ ልጅ ፡ ሜልኮልን ፡ ካላመጣኽልኝ ፡ ፊቴን ፡ አታይም ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ ወደሳኦል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያቡስቴ ፦ በመቶ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ሸለፈት ፡ ያጨኺትን ፡ ሚስቴን ፡ ሜልኮልን ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ሰደደ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ኢያቡስቴም ፡ ልኮ ፡ ከሌሳ ፡ ልጅ ፡ ከባሏ ፡ ከፈልጢኤል ፡ ወሰዳት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ ባሏም ፡ እያለቀሰ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፥ እስከ ፡ ብራቂም ፡ ድረስ ፡ ተከተላት ። አበኔርም ፦ ኺድ ፥ ተመለስ ፡ አለው ፤ ርሱም ፡ ተመለሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ አበኔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፦ አስቀድሞ ፡ ዳዊት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ፈልጋችኹ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፦ በባሪያዬ ፡ በዳዊት ፡ እጅ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅና ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ አድናለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯልና ፥ እንግዲህ ፡ አኹን ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 19 ፤ አበኔርም ፡ ደግሞ ፡ በብንያም ፡ ወገን ፡ ዠሮ ፡ ተናገረ ፤ አበኔርም ፡ ደግሞ ፡ በእስራኤልና ፡ በብንያም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መልካም ፡ የነበረውን ፡ ለዳዊት ፡ ሊነግረው ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 20 ፤ አበኔርም ፡ ከኻያ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጣ ። ዳዊትም ፡ ለአበኔርና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ግብዣ ፡ አደረገላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 21 ፤ አበኔርም ፡ ዳዊትን ፦ ተነሥቼ ፡ ልኺድ ፥ ከአንተ ፡ ጋራም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡

እንዲያደርጉ ፥ ነፍስኽም ፡ እንደ ፡ ወደደች ፡ ዥሉን ፡ እንድትገዛ ፡ እስራኤልን ፡ ዥሉ ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ ልሰብስብ ፡ አለው ። ዳዊትም ፡ አበኔርን ፡ አሰናበተው ፥ በደኅናም ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 22 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የዳዊት ፡ ባሪያዎችና ፡ ኢዮአብ ፡ ከዘመቻ ፡ ታላቅ ፡ ምርኮ ፡ ይዘው ፡ መጡ ። አበኔር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ አሰናብቶት ፡ በደኅና ፡ ኼዶ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በኬብሮን ፡ አልነበረም ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 23 ፤ ኢዮአብና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ ጭፍራ ፡ ዥሉ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፦ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጣ ፥ አሰናበተውም ፡ በደኅናውም ፡ ኼደ ፡ ብለው ፡ ሰዎች ፡ ለኢዮአብ ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 24 ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ገብቶ ፦ ምን ፡ አደረግኽ ፧ እንሆ ፥ አበኔር ፡ መጥቶልኽ ፡ ነበር ፤ በደኅና ፡ እንዲኼድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሰናበትኸው ፧

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 25 ፤ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፡ ያታልልኽ ፡ ዘንድ ፥ መውጣኽንና ፡ መግቢያኽንም ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፥ የምታደርገውንም ፡ ነገር ፡ ዥሉ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አታውቅምን ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 26 ፤ ኢዮአብም ፡ ከዳዊት ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞችን ፡ ከአበኔር ፡ በኺላ ፡ ላከ ፥ ከሴይርም ፡ ጕድጓድም ፡ መለሱት ። ዳዊት ፡ ግን ፡ ይህን ፡ አላወቀም ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 27 ፤ አበኔርም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮአብ ፡ በበር ፡ ውስጥ ፡ በቄይታ ፡ ይናገረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አጠገቡ ፡ ወሰደው ፤ በዚያም ፡ ለወንድሙ ፡ ለዐሳሄል ፡ ደም ፡ ተበቅሎ ፡ ሆዱን ፡ መታው ፥ ሞተም ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 28 ፤ በኺላም ፡ ዳዊት ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ከኔር ፡ ልጅ ፡ ከአበኔር ፡ ደም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለም ፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፥ መንግሥቴም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 29 ፤ በኢዮአብ ፡ ራስ ፡ ላይና ፡ በአባቱ ፡ ቤት ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ይምጣበት ፤ በኢዮአብም ፡ ቤት ፡ ፈሳሽ ፡ ነገር ፡ ያለበት ፡ ወይም ፡ ለምጻም ፡ ወይም ፡ ዐንካሳ ፡ ወይም ፡ በሰይፍ ፡ የሚወድቅ ፡ ወይም ፡ እንጀራ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ አይታጣ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 30 ፤ ኢዮአብና ፡ ወንድሙ ፡ አቢሳም ፡ በሰልፍ ፡ በገባዖን ፡ ወንድማቸው ፡ ዐሳሄልን ፡ ገድሎ ፡ ነበርና ፥ አበኔርን ፡ ገደሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 31 ፤ ዳዊትም ፡ ኢዮአብንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ዥሉ ፦ ልብሳችኹን ፡ ቅደዱ ፥ ማቅም ፡ ልበሱ ፥ በአበኔርም ፡ ፊት ፡ አልቅሱ ፡ አላቸው ። ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ከቃሬዛው ፡ በኺላ ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 32 ፤ አበኔርንም ፡ በኬብሮን ፡ ቀበሩት ፤ ንጉሡም ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ በአበኔር ፡ መቃብር ፡ አጠገብ ፡ አለቀሰ ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ አለቀሱ ። ንጉሡም ፡ ለአበኔር ፦

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 33 ፤ አበኔር ፡ ሰነፍ ፡ እንደሚሞት ፡ ይምታልን ፧

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 34 ፤ እጅኽ ፡ አልታሰረም ፥ እግርኽም ፡ በሰንሰለት ፡ አልተያዘም ፤ ሰው ፡ በዐመፀኞች ፡ ፊት ፡ እንደሚወድቅ ፡ አንተ ፡ እንዲሁ ፡ ወደቅኽ ፡ ብሎ ፡ የልቅሶ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኘለት ። ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ዋይታ ፡ አብዝተው ፡ አለቀሱ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 35 ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ገና ፡ ሳይመሽ ፡ ዳዊትን ፡ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ሊጋብዙት ፡ መጡ ፤ ዳዊት ፡ ግን ፦ ፀሓይ ፡ ሳትጠልቅ ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ብቀምስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፥ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ፡ ብሎ ፤ ማለ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 36 ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ይህን ፡ ተመለከቱ ፥ ደስ ፡ አሠኛቸውም ፤ በሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ ንጉሥ ፡ ያደረገው ፡ ዥሉ ፡ ደስ ፡ አሠኛቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 37 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ የአበኔር ፡ ሞት ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልኾነ ፡ ዐወቁ ።

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 38 ፤ ንጉሡም ፡ ባሪያዎቹን ፦ ዛሬ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መኰንንና ፡ ታላቅ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ አታውቁምን ፧

ሳሙ.2 ፡ 3 ፡ 39 ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ምንም ፡ ለመንገሥ ፡ የተቀባኹ ፡ ብኾን ፡ ደካማ ፡ ነኝ ፤ እነዚህም ፡ ሰዎች ፡ የጽሩያ ፡ ልጆች ፡ በርትተው ብኖል ፤ እግዚአብሔር ፡ ክፋት ፡ በሠራ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ክፋቱ ፡ ይመልስበት ፡ አላቸው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 1 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ኢያቡስቴ ፡ አበኔር ፡ በኬብሮን ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጁ ፡ ደከመች ፥ እስራኤላውያንም ፡ ኹሉ ፡ ደነገጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 2 ፤ ለሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ለኢያቡስቴ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩት ፤ የአንዱም ፡ ስም ፡ በዓና ፥ የኹለተኛውም ፡ ስም ፡ ሬካብ ፡ ነበረ ፥ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ የብኤሮታዊው ፡ የሬሞን ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፤ ብኤሮትም ፡ ለብንያም ፡ ተቈጥራ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ብኤሮታውያንም ፡ ወደ ፡ ጌቴም ፡ ሸሽተው ፡ ነበር ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተጠግተው ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 4 ፤ ለሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ለዮናታን ፡ አንድ ፡ ሽባ ፡ የኾነ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ። የሳኦልና ፡ የዮናታን ፡ ወሬ ፡ ከኢይዝራኤል ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የዐምስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ ሞግዚቱም ፡ ዐዝላው ፡ ሸሸች ፤ ፈጥናም ፡ ስትሸሽ ፡ ወድቆ ፡ ሽባ ፡ ኾነ ። ስሙም ፡ ሜምፊቦስቴ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 5 ፤ የብኤሮታዊውም ፡ የሬሞን ፡ ልጆች ፡ ሬካብና ፡ በዓና ፡ ቀኑ ፡ ሲሞቅ ፡ ወደኢያቡስቴ ፡ ቤት ፡ መጡ ፤ ርሱም ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ በምንጣፍ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 6 ፤ በረኛዉቱም ፡ ስንዴ ፡ ታበጥር ፡ ነበር ፥ አንቀላፍታም ፡ ተኝታ ፡ ነበር ፤ ሬካብና ፡ ወንድሙ ፡ በዓናም ፡ በቀስታ ፡ ገቡ ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ በዕልፍኙ ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ ሳለ ፡ መቱት ፥ ገደሉትም ፤ ራሱንም ፡ ቈርጠው ፡ ወሰዱት ፥ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 8 ፤ የኢያቡስቴንም ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ፥ ንጉሡንም ፦ ነፍስኽን ፡ ይሻ ፡ የነበረው ፡ የጠላትኽ ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ የኢያቡስቴ ፡ ራስ ፡ እንሆ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዛሬ ፡ ከሳኦልና ፡ ከዘሩ ፡ ለጌታችን ፡ ለንጉሥ ፡ ተበቀለለት ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ ለብኤሮታዊው ፡ ለሬሞት ፡ ልጆች ፡ ለሬካብና ፡ ለወንድሙ ፡ ለበዓና ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። ነፍሴን ፡ ከመከራ ፡ ኹሉ ፡ ያዳነ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 10 ፤ መልካም ፡ ወሬ ፡ የያዘ ፡ መስሎት ፦ እንሆ ፥ ሳኦል ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ የነገረኝን ፡ የምሥራቹ ፡ ዋጋ ፡ እንዲኾን ፡ ይገፍ ፡ በጺቅላግ ፡ ገደልኩት ።

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 11 ፤ ይልቁንስ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ የገደላችኹትን ፡ እናንተን ፡ ኀጢአተኞችንማ ፡ እንዴት ፡ ነዋ ፧ ደሙን ፡ ከእጃችኹ ፡ አልሻውምን ፧ ከምድርም ፡ አላጠፋችኹምን ፧

ሳሙ.2 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ ጕልማሳዎቹን ፡ አዘዘ ፥ ገደሏቸውም ፤ እጃቸውንና ፡ እግራቸውን ፡ ቈርጠው ፡ በኬብሮን ፡ በውሃ ፡ መቆሚያ ፡ አጠገብ ፡ አንጠለጠሏቸው ። የኢያቡስቴንም ፡ ራስ ፡ ወስደው ፡ በአበኔር ፡ መቃብር ፡

በኬብሮን ፡ ቀበሩት ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥተው ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ የዐጥንትኽ ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋኽ ፡ ቍራጭ ፡ ነን ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 2 ፤ አስቀድሞ ፡ ሳኦል ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ እስራኤልን ፡ የምታወጣና ፡ የምታገባ ፡ አንተ ፡ ነበርኽ ፤ እግዚአብሔርም ፦ አንተ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ትጠብቃለኽ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትኾናለኽ ፡ ብሎኽ ፡ ነበር ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ በኬብሮን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አደረገ ፤ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ ቀቡት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ አርባ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 5 ፤ በኬብሮን ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 6 ፤ ንጉሡና ፡ ሰዎቹም ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ ከተቀመጡት ፡ ከኢያቡሳውያን ፡ ጋራ ፡ ለመዋጋት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኼዱ ፤ እነርሱም ፦ ዳዊት ፡ ወደዚህ ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ፡ ብለው ፡ ዐስበው ፡ ነበርና ፥ ዳዊትን ፦ ዕውሮችንና ፡ ዐንካሳዎችን ፡ ካላወጣኽ ፡ በቀር ፡ ወደዚህ ፡ አትገባም ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዳዊት ፡ ዐምባዩቱን ፡ ጽዮንን ፡ ያዘ ፥ ርሷም ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ናት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፦ ኢያቡሳውያንን ፡ የሚመታ ፡ በውሃ ፡ መኼጃው ፡ ይውጣ ፤ የዳዊትም ፡ ነፍስ ፡ የምትጠላቸውን ፡ ዕውሮችንና ፡ ዐንካሳዎችን ፡ ያውጣ ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ በምሳሌ ፦ ዕውርና ፡ ዐንካሳ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አይግቡ ፡ ተባለ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ በዐምባዩቱ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ፥ የዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ብሎ ፡ ጠራት ። ዳዊትም ፡ ዙሪያዋን ፡ ከሚሎ ፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ቀጠራት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ እየበረታ ፡ ኼደ ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 11 ፤ የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መልእክተኞችን ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨትንም ፡ ዐናጢዎችንም ፡ ጠራቢዎችንም ፡ ላከ ፤ ለዳዊትም ፡ ቤት ፡ ሠሩለት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ እንዳጸናው ፥ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ እስራኤልም ፡ መንግሥቱን ፡ ከፍ ፡ እንዳደረገ ፡ ዐወቀ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ከኬብሮን ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ሌላዎቹን ፡ ቁባቶቹንና ፡ ሚስቶቹን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወሰደ ፤ ለዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተወለዱለት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 14 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የተወለዱለት ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሳሙስ ፥

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 15 ፤ ሶባብ ፥ ናታን ፥ ሰሎሞን ([154]) ፥ ኢያቤሐር ፥ ኤሊሱዔ ፥

---

154 ዕብ. ፥ ሸሎሞህ ፡ (ሰላማዊ) ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ናፌቅ ፥ ያፍያ ፥ ኤሊሳማ ፥ ኤሊዳሄ ፥ ኤሊፋላት ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 17 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዳዊት ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ሰሙ ፥ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ኹሉ ፡ ዳዊትን ፡ ሊፈልጉ ፡ ወጡ ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምሽጉ ፡ ወረደ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 18 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ተበትነው ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፦ ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ልውጣን ፧ በእጄስ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጣቸዋለኽን ፧ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፡ ዳዊትን ፦ ፍልስጥኤማውያንን ፡ በርግጥ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹና ፡ ውጣ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ በዓልፐራሲም ፡ መጣ ፥ በዚያም ፡ መታቸውና ፦ ውሃ ፡ እንዲያፈርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቼን ፡ በፊቴ ፡ አፈረሳቸው ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ በዓልፐራሲም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 21 ፤ ጣዖቶቻቸውንም ፡ በዚያ ፡ ተዉ ፥ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ ወሰዷቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 22 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ደግሞ ፡ መጡ ፥ በራፋይምም ፡ ሸለቆ ፡ ተበትነው ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 23 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ ርሱም ፦ በኋላቸው ፡ ዞረኽ ፡ በሾላው ፡ ዛፍ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ግጠማቸው ፡ እንጂ ፡ አትውጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 24 ፤ በሾላውም ፡ ዛፍ ፡ ራስ ፡ ውስጥ ፡ የሽውሽውታ ፡ ድምፅ ፡ ስትሰማ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ ለመምታት ፡ በፊትኽ ፡ ወጥቶ ፡ ይኾናልና ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቸኩል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 5 ፡ 25 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ከገባዖንም ፡ እስከ ፡ ጌዝር ፡ ድረስ ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ መታ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ዳግም ፡ ከእስራኤል ፡ የተመረጡትን ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ሰበሰበ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 2 ፤ ዳዊትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ካለች ፡ ከበዓል ፡ ተነሥተው ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ በተቀመጠ ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተጠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ኼዱ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ በዐዲስ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፥ በኮረብታውም ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ ከዐሚናዳብ ፡ ቤት ፡ አመጡት ፤ የዐሚናዳብ ፡ ልጆችም ፡ ዖዛ ፡ እና ፡ አኒዮ ፡ ዐዲሱን ፡ ሠረገላ ፡ ይነዱ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 4 ፤ በኮረብታውም ፡ ላይ ፡ ከነበረው ፡ ከዐሚናዳብ ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ባመጡ ፡ ጊዜ ፡ አኒዮ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ይኼድ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 5 ፤ ዳዊትና ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ በቅኔና ፡ በበገና ፡ በመሰንቆም ፡ በከበሮም ፡ በነጋሪትና ፡ በጸናጽል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሙሉ ፡ ኀይላቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ወደናኮንም ፡ ዐውድማ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በሬዎቹ ፡ ይፋንኑ ፡ ነበርና ፥ ዖዛ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ያዘ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቀሥጣ ፡ በዖዛ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ድፍረቱ ፡ በዚያው ፡ ቀሠፈው ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ አጠገብ ፡ በዚያው ፡ ሞተ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዖዛን ፡ ስለ ፡ ሰበረው ፡ ዳዊት ፡ ዐዘነ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የዚያ ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የዖዛ ፡ ስብራት ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈራና ፦ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ ይመጣል ∴ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ ያመጣው ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፤ ዳዊትም ፡ በጌት ፡ ሰው ፡ በዐቢዳራ ([155]) ፡ ቤት ፡ አገባው ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ በጌት ፡ ሰው ፡ በዐቢዳራ ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዐቢዳራንና ፡ ቤቱን ፡ ኹሉ ፡ ባረከ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 12 ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ የዐቢዳራን ፡ ቤትና ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ እንደ ፡ ባረከ ፡ ሰማ ። ዳዊትም ፡ ኼዶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከዐቢዳራ ፡ ቤት ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ በደስታ ፡ አመጣው ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙ ፡ ስድስት ፡ ርምጃ ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ በሬና ፡ አንድ ፡ ፍሪዳ ፡ ሠዋ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ በሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይዘፍን ፡ ነበር ፤ ዳዊትም ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ዳዊትና ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ እየነፉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ አመጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ በመስኮት ፡ ኾና ፡ ተመለከተች ፥ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሲዘልና ፡ ሲዘፍን ፡ አየች ፤ በልቧም ፡ ናቀችው ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ አገቡ ፥ ዳዊትም ፡ በተከለለት ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ በስፍራው ፡ አኖሩት ፤ ዳዊትም ፡ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አሳረገ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 18 ፤ ዳዊትም ፡ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ማሳረግ ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መረቀ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 19 ፤ ለሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ወገን ፡ ለወንዱም ፡ ለሴቱም ፡ ለያንዳንዱ ፡ አንዳንድ ፡ እንጀራ ፡ አንዳንድም ፡ የሥጋ ፡ ቍራጭ ፡ አንዳንድም ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አከፋፈለ ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ቤተ ፡ ሰቡን ፡ ሊመርቅ ፡ ተመለሰ ። የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ ዳዊትን ፡ ለመቀበል ፡ ወጣችና ፦ ምናምንቴዎች ፡ ዕርቃናቸውን ፡ እንደሚገልጡ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በባሪያዎቹ ፡ ቈነጕሎች ፡ ፊት ፡ ዕርቃኑን ፡ በመግለጡ ፡ ምንኛ ፡ የተከበረ ፡ ነው! ፡ አለችው ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 21 ፤ ዳዊትም ፡ ሜልኮልን ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘፍኛለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከአባትሽና ፡ ከቤቱ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የመረጠኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ ስለዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጫወታለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 6 ፡ 22 ፤ አኹንም ፡ ከኾንኹት ፡ ይልቅ ፡ የተናቅኹ ፡ እኾናለኹ ፥ በዐይንሽም ፡ እዋረዳለኹ ፤ ነገር ፡

155 ዕብ. ፥ ያበድ ፡ ኤዶም ፡ (የኤዶም ፡ አገልጋይ) ።

ግን ፥ በተናገርሽው ፡ ቈነጣሾት ፡ ዘንድ ፡ እከብራለኹ ፡ አላት ።

ሳሙ.2 ፥ 6 ፥ 23 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ እስከሞተችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልጅ ፡ አልወለደችም ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ንጉሡ ፡ በቤቱ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በዙሪያው ፡ ካሉት ፡ ጠላቶቹ ፡ ሹሉ ፡ ባሳረፈው ፡ ጊዜ ፥

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 2 ፤ ንጉሡ ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፦ እኔ ፡ ከዝግባ ፡ በተሠራ ፡ ቤት ፡ ተቀምጫለኹ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ግን ፡ በመጋረጃዎች ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ እይ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 3 ፤ ናታንም ፡ ንጉሡን ፦ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ ኺድ ፥ በልብኽም ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 4 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ናታን ፡ መጣ ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 5-6 ፤ ኺድ ፥ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ ንገረው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በድንኳንና ፡ በማደሪያ ፡ እኼድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በቤት ፡ አልተቀመጥኹምና ፡ አንተ ፡ የምኖርበትን ፡ ቤት ፡ አትሠራልኝም ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 7 ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሹሉ ፡ ጋራ ፡ ባለፍኹበት ፡ ስፍራ ፡ ሹሉ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ቤትን ፡ ከዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አልሠራችኹልኝም ፧ ብዬ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ላዘዝኹት ፡ ለአንዱ ፡ በእውኑ ፡ ተናግሬያለኹን ፧

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 8 ፤ አኹንም ፡ ዳዊትን ፡ ባሪያዬን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፡ መንጋውን ፡ ስትከተል ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ከበግ ፡ ጥበቃ ፡ ወሰድኹኽ ፤

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 9 ፤ በኼድኽበትም ፡ ሹሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነበርኹ ፥ ጠላቶችኽንም ፡ ሹሉ ፡ ከፊትኽ ፡ አጠፋኹ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ ታላላቆቹ ፡ ስም ፡ ታላቅ ፡ ስም ፡ አደርግልኻለኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 10 ፤ 11 ፤ ለሕዝቤም ፡ ለእስራኤል ፡ ስፍራ ፡ አደርግለታለኹ ፥ እተክለውማለኹ ፤ በስፍራውም ፡ ይቀመጣል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይናወጥ ፤ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ዘመንና ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጆች ፡ እንዳስነሣኹበት ፡ ጊዜ ፡ ግፈኞች ፡ ተመልሰው ፡ አያስጨንቁትም ፤ ከጠላቶችኽም ፡ አሳርፍኻለኹ ። እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፦ ቤት ፡ እሠራልኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ይነግርኻል ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 12 ፤ ዕድሜኽም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶችኽም ፡ ጋራ ፡ ባንቀላፋኽ ፡ ጊዜ ፥ ከወገብኽ ፡ የሚወጣውን ፡ ዘርኽን ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ አስነሣለኹ ፥ መንግሥቱንም ፡ አጸናለኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 13 ፤ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፤ የመንግሥቱንም ፡ ዙፋን ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 14 ፤ እኔም ፡ አባት ፡ እኾነዋለኹ ፥ ርሱም ፡ ልጅ ፡ ይኾነኛል ፤ ክፉ ፡ ነገርም ፡ ቢያደርግ ፥ ሰው ፡ በሚቀጣበት ፡ በትርና ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መቀጫ ፡ እገሥጸዋለኹ ፤

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 15 ፤ ከፊቴም ፡ ከጣልኹት ፡ ከሳኦል ፡ እንዳራቅኹ ፡ ምሕረቴን ፡ ከርሱ ፡ አላርቅም ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 16 ፤ ቤትኽና ፡ መንግሥትኽም ፡ በፊቴ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጠነክራል ፥ ዙፋንኽም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናል ።

ሳሙ.2 ፥ 7 ፥ 17 ፤ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ እንደዚህም ፡ ራእይ ፡ ሹሉ ፡ ናታን ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 18 ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ገባ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እስከዚህ ፡ ያደረስኸኝ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 19 ፤ ቤቴስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ በፊትኽ ፡ ጥቂት ፡ ነበረ ፤ ስለ ፡ ባሪያኽም ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ለሩቅ ፡ ዘመን ፡ ተናገርኽ ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ የሰው ፡ ሕግ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 20 ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ባሪያኽን ፡ ታውቃለኽና ፡ ዳዊትስ ፡ ይናገርኽ ፡ ዘንድ ፡ የሚጨምረው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 21 ፤ ለባሪያኽም ፡ ታስታውቀው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ቃልኽ ፡ ምክንያትና ፡ እንደ ፡ ልብኽ ፡ ዐሳብ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አደረግኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 22 ፤ ስለዚህም ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ የለምና ፥ በጐሯችንም ፡ እንደ ፡ ሰማን ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ነኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 23 ፤ ለርሱ ፡ ለራሱ ፡ እንዲኾን ፡ ሕዝብን ፡ ይቤዥ ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡ ለራሱም ፡ ስም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ በአሕዛብና ፡ በአምላኮቻቸውም ፡ ፊት ፡ ከግብጽ ፡ በተቤዠው ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ተአምራትንና ፡ ድንቅን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኼደለት ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ያለ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ምን ፡ ሕዝብ ፡ አለ ፧

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 24 ፤ ሕዝብኽንም ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕዝብ ፡ አድርገኽ ፡ አጽንተኸዋል ፤ አንተም ፥ አቤቱ ፥ አምላክ ፡ ኾነኻቸዋል ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 25 ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አኹንም ፡ ለባሪያኽና ፡ ለቤቱ ፡ የተናገርኸውን ፡ ለዘለዓለም ፡ አጽናው ፥ እንደ ፡ ተናገርኽም ፡ አድርግ ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 26 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ዘንድ ፡ ስምኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፤ የባሪያኽም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ በፊትኽ ፡ የጸና ፡ ይኹን ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 27 ፤ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፦ እኔ ፡ ቤት ፡ እሠራልኻለኹ ፡ ብለኽ ፡ ለባሪያኽ ፡ ገልጠኻልና ፥ ስለዚህ ፡ ባሪያኽ ፡ ይህችን ፡ ጸሎት ፡ ወዳንተ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ደፈረ ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 28 ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አኹንም ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፥ ቃልኽም ፡ እውነት ፡ ነው ፥ ይህንም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለባሪያኽ ፡ ተናግረኻል ።

ሳሙ.2 ፡ 7 ፡ 29 ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ተናግረኻልና ፥ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ለዘለዓለም ፡ በፊትኽ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የባሪያኽን ፡ ቤት ፥ እባክኽ ፥ ባርክ ፤ በበረከትኽም ፡ የባሪያኽ ፡ ቤት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይባረክ ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ መታ ፥ አዋረዳቸውም ፤ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ ሜቴግ ፡ አማ ፡ የተባለችውን ፡ ከተማ ፡ ወሰደ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 2 ፤ ሞዐብን ፡ መታ ፥ ሞዐባውያንንም ፡ በምድር ፡ ጥሎ ፡ በገመድ ፡ ሰፈራቸው ፤ በኹለትም ፡ ገመድ ፡ ለሞት ፥ በአንድም ፡ ገመድ ፡ ሙሉ ፡ ለሕይወት ፡ ሰፈራቸው ፤ ሞዐባውያንም ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡ ኾኑ ፥ ግብርም ፡ አመጡለት ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ ግዛት ፡ መልሶ ፡ ለመያዝ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ የረአብን ፡ ልጅ ፡ የሱባን ፡ ንጉሥ ፡ አድርዐዛርን ፡ መታ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ፈረሰኞች ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ እግረኞች ፡ ያዘ ፤ ዳዊትም ፡ የሠረገለኛውን ፡ ፈረስ ፡ ዅሉ ፡ ቋንጥ ፡ ቈረጠ ፤ ለመቶ ፡ ሠረገላ ፡ ብቻ ፡ አስቀረ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 5 ፤ ከደማስቆም ፡ ሶርያውያን ፡ የሱባን ፡ ንጉሥ ፡ አድርዐዛርን ፡ ሊረዱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ከሶርያውያን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ገደለ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ በደማስቆ ፡ ሶርያ ፡ ጭፍራዎች ፡ አኖረ ፥ ሶርያውያንም ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡ ኾኑ ፥ ግብርም ፡ አመጡለት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዳዊት ፡ በኼደበት ፡ ዅሉ ፡ ድልን ፡ ሰጠው ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ ለአድርዐዛር ፡ ባሪያዎች ፡ የነበሩትን ፡ የወርቅ ፡ ጋሻዎች ፡ ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ይዟቸው ፡ መጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ከአድርዐዛር ፡ ከተማዎች ፡ ከቤጣሕና ፡ ከቤሮታይ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናስ ፡ ወሰደ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 9 ፤ የሐማትም ፡ ንጉሥ ፡ ቶዑ ፡ ዳዊት ፡ የአድርዐዛርን ፡ ጭፍራ ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ መታ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 10 ፤ ቶዑም ፡ ከአድርዐዛር ፡ ጋራ ፡ ዅልጊዜ ፡ ይዋጋ ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ አድርዐዛርን ፡ ድል ፡ ስለ ፡ መታ ፡ ቶዑ ፡ ልጁን ፡ አዶራምን ፡ ደኅንነቱን ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፥ ይመርቀውም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ላከው ፤ ርሱም ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ የናስም ፡ ዕቃ ፡ ይዞ ፡ መጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 11 ፤ 12 ፤ ንጉሥ ፡ ዳዊትም ፡ ካሸነፋቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ከሶርያ ፡ ከሞዐብም ፡ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ከዐማሌቅም ፡ ከረአብም ፡ ልጅ ፡ ከሱባ ፡ ንጉሥ ፡ ከአድርዐዛር ፡ ምርኮ ፡ ከቀደሰው ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ጋራ ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀደሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ በጨው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ በመምታቱ ፡ ስሙ ፡ ተጠራ ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 14 ፤ በኤዶምያስ ፡ ዅሉ ፡ ጭፍራዎች ፡ አኖረ ፥ ኤዶማውያንም ፡ ዅሉ ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡ ኾኑ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዳዊት ፡ በሚኼድበት ፡ ዅሉ ፡ ድልን ፡ ሰጠው ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ ዳዊትም ፡ ለሕዝቡ ፡ ዅሉ ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ አደረገላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 16 ፤ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብም ፡ የሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ የአኒሉድም ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ([156]) ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ፤

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 17 ፤ የአኪጦብም ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፥ የአቢሜሌክም ፡ ልጅ ፡ አብያታር ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ፤ ሰራያም ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ፤

ሳሙ.2 ፡ 8 ፡ 18 ፤ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ በከሊታውያንና ፡ በፈሊታውያን ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ የዳዊትም ፡ ልጆች ፡ አማካሪዎች ፡ ነበሩ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፦ ስለ ፡ ዮናታን ፡ ቸርነት ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ ከሳኦል ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀርቷልን ፧ አለ ።

---

156 ዕብ. ፥ የሆሻፋጥ ፡ (አምላክ ፡ ፈረደለት) ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 2 ፤ ከሳኦልም ፡ ቤት ፡ ሲባ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ነበረ ፥ ወደ ፡ ዳዊትም ፡ ጠሩት ፤ ንጉሡም ፦ አንተ ፡ ሲባ ፡ ነኽን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ ከሳኦል ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልቀረምን ፧ አለ ። ሲባም ፡ ንጉሡን ፦ እግሩ ፡ ሽባ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ የዮናታን ፡ ልጅ ፡ አለ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፦ ወዴት ፡ ነው ፧ አለው ፤ ሲባም ፡ ንጉሡን ፦ እንሆ ፥ ርሱ ፡ በሎዶባር ፡ በዓሚኤል ፡ ልጅ ፡ በማኪር ፡ ቤት ፡ አለ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ልኮ ፡ ከሎዶባር ፡ ከዓሚኤል ፡ ልጅ ፡ ከማኪር ፡ ቤት ፡ አስመጣው ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 6 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ የዮናታን ፡ ልጅ ፡ ሜምፊቦስቴ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጣ ፥ በግንባሩም ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣ ፤ ዳዊትም ፦ ሜምፊቦስቴ ፡ ሆይ ፥ አለ ፤ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ ባሪያኽ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፦ ስለ ፡ አባትኽ ፡ ስለ ፡ ዮናታን ፡ ቸርነት ፡ ፈጽሜ ፡ አደርግልኻለኹና ፡ አትፍራ ፤ የአባትኽንም ፡ የሳኦልን ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እመልስልኻለኹ ፥ አንተም ፡ ኹልጊዜ ፡ ከገበታዬ ፡ እንጀራ ፡ ትበላለኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ የሞተ ፡ ውሻ ፡ ወደምመስል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የተመለከትኽ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ምንድር ፡ ነኝ ፧ ብሎ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 9 ፤ ንጉሡም ፡ የሳኦልን ፡ ባሪያ ፣ ሲባን ፡ ጠርቶ ፦ ለሳኦልና ፡ ለቤቱ ፡ ኹሉ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ለጌታኽ ፡ ልጅ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 10 ፤ አንተና ፡ ልጆችኽ ፡ ሎሌዎችኽም ፡ ምድሩን ፡ ዕረሱለት ፤ ለጌታኽም ፡ ልጅ ፡ እንጀራ ፡ ይኾነው ፡ ዘንድ ፡ ፍሬውን ፡ አግባ ፤ የጌታኽ ፡ ልጅ ፡ ሜምፊቦስቴ ፡ ግን ፡ ኹልጊዜ ፡ ከገበታዬ ፡ ይበላል ፡ አለው ። ለሲባም ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ልጆችና ፡ ኻያ ፡ ባሪያዎች ፡ ነበሩት ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 11 ፤ ሲባም ፡ ንጉሡን ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ባሪያውን ፡ እንዳዘዘ ፡ እንዲሁ ፡ ባሪያኽ ፡ ያደርጋል ፡ አለው ። ሜምፊቦስቴም ፡ ከንጉሡ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ከዳዊት ፡ ገበታ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 12 ፤ ለሜምፊቦስቴም ፡ ሚካ ፡ የተባለ ፡ ታናሽ ፡ ልጅ ፡ ነበረው ። በሲባም ፡ ቤት ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ለሜምፊቦስቴ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 9 ፡ 13 ፤ ሜምፊቦስቴም ፡ ከንጉሥ ፡ ገበታ ፡ ኹልጊዜ ፡ እየበላ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ኹለት ፡ እግሩም ፡ ሽባ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ሞተ ፥ ልጁም ፡ ሐኖን ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፦ አባቱ ፡ ወረታ ፡ እንዳደረገልኝ ፡ እኔ ፡ ለናዖስ ፡ ልጅ ፡ ለሐኖን ፡ ቸርነት ፡ አደርጋለኹ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ አባቱ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ሊያጽናናው ፡ ባሪያዎቹን ፡ ላከ ፤ የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ መጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 3 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ጌታቸውን ፡ ሐኖንን ፦ ዳዊት ፡ አባትኽን ፡ አክብሮ ፡ ሊያጽናናኽ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወዳንተ ፡ የላከ ፡ ይመስልኻልን ፧ ዳዊትስ ፡ ከተማዪቱን ፡ ለመመርመርና ፡ ለመሰለል ፡ ለማጥፋትም ፡ ባሪያዎቹን ፡ የላከ ፡ አይደለምን ፧ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 4 ፤ ሐኖንም ፡ የዳዊትን ፡ ባሪያዎች ፡ ወስዶ ፡ የጢማቸውን ፡ ገሚስ ፡ ላጨ ፥ ልብሳቸውንም ፡ እስከ ፡ ወገባቸው ፡ ድረስ ፡ ከኹለት ፡ ቀዶ ፡ ሰደዳቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ሰዎቹ ፡ እጅግ ፡ ዐፍረው ፡ ነበርና ፥ ተቀባዮች ፡ ላከ ። ንጉሡም ፦ ጢማችኹ ፡ እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ በኢያሪኮ ፡ ተቀመጡ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 6 ፤ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጠሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ልከው ፡ ከሶርያውያን ፡ ከቤትሮዖብና ፡ ከሱባ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ እግረኞች ፥ ከመዓካ ፡ ንጉሥም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፥ ከጦብም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ቀጠሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮአብንና ፡ የኀያላኑን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ላከ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 8 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ወጥተው ፡ በበሩ ፡ መግቢያ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተሰለፉ ፤ የሱባና ፡ የረአብ ፡ ሶርያውያን ፥ የጦብና ፡ የመዓካም ፡ ሰዎች ፡ ለብቻቸው ፡ በሰፊ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 9 ፤ ኢዮአብም ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ሰልፍ ፡ እንደ ፡ ከበበው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ምርጥ ፡ ምርጦቹን ፡ ኹሉ ፡ መረጠ ፥ በሶርያውያንም ፡ ፊት ፡ ለሰልፍ ፡ አኖራቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 10 ፤ የቀረውንም ፡ ሕዝብ ፡ በወንድሙ ፡ በአቢሳ ፡ እጅ ፡ አድርጎ ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ለሰልፍ ፡ አኖራቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 11 ፤ ሶርያውያን ፡ ቢበረቱብኝ ፡ ትረዳኛለኽ ፤ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ቢበረቱብኽ ፡ እኔ ፡ መጥቼ ፡ እረዳኻለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 12 ፤ አይዞኽ ፤ ስለ ፡ ሕዝባችንና ፡ ስለ ፡ አምላካችንም ፡ ከተማዎች ፡ እንበርታ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደስ ፡ ያሠኘውን ፡ ያድርግ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 13 ፤ ኢዮአብና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ከሶርያውያን ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ቀረቡ ፥ እነርሱም ፡ ከፊቱ ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 14 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ሶርያውያን ፡ እንደ ፡ ሸሹ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከአቢሳ ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ ገቡ ፤ ኢዮአብም ፡ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 15 ፤ ሶርያውያንም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በአንድነት ፡ ተሰበሰቡ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 16 ፤ አድርዐዛርም ፡ ልኮ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ የነበሩትን ፡ ሶርያውያን ፥ አመጣ ፤ ወደ ፡ ዔላምም ፡ መጡ ፥ የአድርዐዛርም ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ሶባክ ፡ በፊታቸው ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻግሮ ፡ ወደዔላም ፡ መጣ ፤ ሶርያውያንም ፡ በዳዊት ፡ ፊት ፡ ተሰልፈው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 18 ፤ ሶርያውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፤ ዳዊትም ፡ ከሶርያውያን ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠረገለኞች ፡ አርባ ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞች ፡ ገደለ ፤ የሰራዊቱንም ፡ አለቃ ፡ ሶባክን ፡ መታ ፥ ርሱም ፡ በዚያ ፡ ሞተ ።

ሳሙ.2 ፡ 10 ፡ 19 ፤ ለአድርዐዛርም ፡ የሚገብሩ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፥ ገበሩላቸውም ፦ ሶርያውያንም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ ፈሩ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዓመቱ ፡ መለወጫ ፡ ነገሥታት ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፥ ዳዊት ፡

ኢዮአብን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ባሪያዎቹን ፡ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፡ ሰደደ ። የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ አጠፉ ፥ ረባትንም ፡
ከበቡ ፤ ዳዊት ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ማታ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ከምንጣፉ ፡ ተነሣ ፥ በንጉሥም ፡ ቤት ፡ በሰገነት ፡
ላይ ፡ ተመላለሰ ፤ በሰገነቱ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ስትታጠብ ፡ አየ ፤ ሴቲቱም ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረች ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ልኮ ፡ ስለ ፡ ሴቲቱ ፡ ጠየቀ ፤ አንድ ፡ ሰውም ፦ ይህች ፡ የኤልያብ ፡ ልጅ ፡
የኬጢያዊው ፡ የኦርዮ (157) ፡ ሚስት ፡ ቤርሳቤሕ ፡ አይደለችምን ፧ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ መልእክተኞች ፡ ልኮ ፡ አስመጣት ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ገባች ፥ ከርኵሰቷም ፡ ነጽታ ፡
ነበርና ፥ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ተኛ ፤ ወደ ፡ ቤቷም ፡ ተመለሰች ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 5 ፤ ሴቲቱም ፡ አረገዘች ፥ ወደ ፡ ዳዊትም ፦ አርግዤያለኹ ፡ ብላ ፡ ላከችበት ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፦ ኬጢያዊውን ፡ ኦርዮን ፡ ስደድልኝ ፡ ብሎ ፡ ላከ ። ኢዮአብም ፡
ኦርዮን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ሰደደው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 7 ፤ ኦርዮም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ የኢዮአብንና ፡ የሕዝቡን ፡ ደኅንነት ፥ ሰልፉም ፡
እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጠየቀው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ ኦርዮን ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፥ እግርኽንም ፡ ታጠብ ፡ አለው ። ኦርዮም ፡ ከንጉሡ ፡
ቤት ፡ ሲወጣ ፡ ማለፊያ ፡ የንጉሥ ፡ መብል ፡ ተከትሎት ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 9 ፤ ኦርዮ ፡ ግን ፡ ከጌታው ፡ ባሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ተኛ ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡
አልወረደም ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 10 ፤ ኦርዮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አልኼደም ፡ ብለው ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፤ ዳዊትም ፡ ኦርዮን ፦ አንተ ፡
ከመንገድ ፡ የመጣኽ ፡ አይደለምን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ አልወረድኽም ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 11 ፤ ኦርዮም ፡ ዳዊትን ፦ ታቦቱና ፡ እስራኤል ፡ ይሁዳም ፡ በጐጎር ፡ ተቀምጠዋል ፤ ጌታዬ ፡ ኢዮአብና ፡
የጌታዬም ፡ ባሪያዎች ፡ በሰፈ ፡ ሜዳ ፡ ሰፍረዋል ፤ እኔ ፡ ልበላና ፡ ልጠጣ ፡ ወይስ ፡ ከሚስቴ ፡ ጋራ ፡ ልተኛ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡
እኼዳለኹን ፧ በሕይወትኽና ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽ ፡ እምላለኹ! ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አላደርገውም ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ ኦርዮን ፦ ዛሬ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጥ ፥ ነገም ፡ አሰናብትኻለኹ ፡
አለው ። ኦርዮም ፡ በዚያ ፡ ቀንና ፡ በነጋው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ጠራው ፥ በፊቱም ፡ በላና ፡ ጠጣ ፥ አሰከረውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡
ከጌታው ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ በምንጣፉ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አልወረደም ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 14 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፥ ዳዊት ፡ ለኢዮአብ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ፥ በኦርዮም ፡ እጅ ፡ ላከው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 15 ፤ በደብዳቤውም ፦ ኦርዮን ፡ ጽኑ ፡ ሰልፍ ፡ ባለበት ፡ በፊተኛው ፡ ስፍራ ፡ አቁሙት ፥ ተመቶም ፡
ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ከኋላው ፡ ሽሹ ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 16 ፤ ኢዮአብም ፡ ከተማዪቱን ፡ በከበበ ፡ ጊዜ ፥ ዝምግናዎች ፡ እንዳሉበት ፡ በሚያውቀው ፡ ስፍራ ፡
ኦርዮን ፡ አቆመው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 17 ፤ የከተማዪቱም ፡ ሰዎች ፡ ወጥተው ፡ ከኢዮአብ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ ከዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ከሕዝቡ ፡

---

157 ዕብ. ፥ ኡሪያህ ፡ (የጌታ ፡ ነበልባል) ።

አንዳንዱ ፡ ወደቁ ፤ ኬጢያዊው ፡ ኦርዮም ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 18 ፤ ኢዮአብም ፡ ልኮ ፡ በሰልፍ ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 19 ፤ ለመልእክተኛውም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ፦ የሰልፉን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ነግረኽ ፡ በፈጸምኽ ፡ ጊዜ ፦

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 20 ፤ ስትዋጉ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ለምን ፡ ቀረባችኹ ፧ ከቅጥሩ ፡ በላይ ፡ ፍላጻ ፡ እንዲወረወር ፡ አታውቁምን ፧

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 21 ፤ የሩቤሼትን ፡ ልጅ ፡ አቢሜሌክን ፡ ማን ፡ ገደለው ፧ ከቅጥር ፡ ላይ ፡ የወፍጮ ፡ መጅ ፡ ጥላ ፡ በቴቤስ ፡ ላይ ፡ የገደለችው ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አይደለችምን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ እንደዚህ ፡ ቀርባችኹ ፧ ብሎ ፡ ንጉሡ ፡ ሲቈጣ ፡ ብታይ ፥ አንተ ፦ ባሪያኽ ፡ ኬጢያዊው ፡ ኦርዮ ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ፡ በለው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 22 ፤ መልእክተኛውም ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ፥ ኢዮአብም ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 23 ፤ መልእክተኛውም ፡ ዳዊትን ፦ ሰዎቹ ፡ በረቱብን ፥ ወደ ፡ ሜዳም ፡ ወጡብን ፤ እኛም ፡ ወደቅንባቸው ፥ እስከከተማዪቱም ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ተከተልናቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 24 ፤ ፍላጻ ፡ የሚወረውሩም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ በባሪያዎችኽ ፡ ላይ ፡ ወረወሩ ፤ ከንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ አንዳንድ ፡ ሞቱ ፥ ባሪያኽም ፡ ኬጢያዊው ፡ ኦርዮ ፡ ደግሞ ፡ ሞተ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 25 ፤ ዳዊትም ፡ መልእክተኛውን ፦ ሰይፍ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ያን ፡ ያጠፋልና ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በዐይንኽ ፡ አይክፋ ፤ ከተማዪቱን ፡ የሚወጉትን ፡ አበርታ ፥ አፍርሳትም ፡ ብለኽ ፡ ለኢዮአብ ፡ ንገረው ፤ አንተም ፡ አጽናው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 26 ፤ የኦርዮም ፡ ሚስት ፡ ባሏ ፡ ኦርዮ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፥ ለባሏ ፡ አለቀሰች ።

ሳሙ.2 ፡ 11 ፡ 27 ፤ የልቅሶዋም ፡ ወራት ፡ ሲፈጸም ፡ ዳዊት ፡ ልኮ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አስመጣት ፥ ሚስትም ፡ ኾነችው ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደችለት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዳዊት ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ኾነ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ናታንን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ላከ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ አለው ፦ ባንድ ፡ ከተማ ፡ አንዱ ፡ ባለጠጋ ፡ አንዱም ፡ ድኻ ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 2 ፤ ባለጠጋውም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ በግና ፡ ላም ፡ ነበረው ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 3 ፤ ለድኻው ፡ ግን ፡ ከገዛት ፡ አንዲት ፡ ታናሽ ፡ በግ ፡ በቀር ፡ አንዳች ፡ አልነበረውም ፤ አሳደጋትም ፥ ከልጆቹም ፡ ጋራ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ አደገች ፤ እንጀራውንም ፡ ትበላ ፥ ከዋንጫውም ፡ ትጠጣ ፥ በብብቱም ፡ ትተኛ ፡ ነበር ፥ እንደ ፡ ልጁም ፡ ነበረች ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ባለጠጋውም ፡ እንግዳ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከበጉና ፡ ከላሙ ፡ ወስዶ ፡ ለዚያ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለመጣው ፡ እንግዳ ፡ ያዘጋጅለት ፡ ዘንድ ፡ ሣሣ ፤ የዚያንም ፡ የድኻውን ፡ ሰው ፡ በግ ፡ ወስዶ ፡ ለዚያ ፡ ለመጣው ፡ ሰው ፡ አዘጋጀ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ናታንን ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ይህን ፡ ያደረገ ፡ ሰው ፡ የሞት ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ይህን ፡ አድርጓልና ፥ አላዘነምና ፡ ስለ ፡ አንዲቱ ፡ በግ ፡ አራት ፡ ይመልስ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 7 ፤ ናታንም ፡ ዳዊትን ፡ አለው ፦ ያ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነኽ ። የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ልትኾን ፡ ቀባኹኽ ፥ ከሳኦልም ፡ እጅ ፡ አዳንኹኽ ፤

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 8 ፤ የጌታኽንም ፡ ቤት ፡ ሰጠኹኽ ፥ የጌታኽንም ፡ ሚስቶች ፡ በብብትኽ ፡ ጣልኹልኽ ፤ የእስራኤልንና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ ሰጠኹኽ ፤ ይህም ፡ አንሶ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ እጨምርልኽ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 9 ፤ አኹንስ ፡ በፊቱ ፡ ክፉ ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ አቃለልኽ ፧ ኬጢያዊውን ፡ ኦርዮን ፡ በሰይፍ ፡ መትተኻል ፥ ሚስቱንም ፡ ለአንተ ፡ ሚስት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ወስደኻል ፤ ርሱንም ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ሰይፍ ፡ ገድለኻል ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ስለዚህም ፡ አቃለኸኛልና ፥ የኬጢያዊውንም ፡ የኦርዮን ፡ ሚስት ፡ ለአንተ ፡ ሚስት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ወስደኻልና ፡ ለዘለዓለም ፡ ከቤትኽ ፡ ሰይፍ ፡ አይርቅም ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከቤትኽ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አስነሣብኻለኹ ፤ ሚስቶችኽንም ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ እወስዳለኹ ፥ ለዘመድኽም ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ በዚችም ፡ ፀሓይ ፡ ዐይን ፡ ፊት ፡ ከሚስቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ይተኛል ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 12 ፤ አንተ ፡ ይህን ፡ በስውር ፡ አድርገኸዋል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊትና ፡ በፀሓይ ፡ ፊት ፡ አደርገዋለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ናታንን ፦ እግዚአብሔርን ፡ በድያለኹ ፡ አለው ። ናታንም ፡ ዳዊትን ፦ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ ኀጢአትኽን ፡ አርቆልኻል ፤ አትሞትም ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ ታላቅ ፡ የስድብ ፡ ምክንያት ፡ አድርገኻልና ፡ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ የተወለደልኽ ፡ ልጅ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 15 ፤ ናታንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ። እግዚአብሔርም ፡ የኦርዮ ፡ ሚስት ፡ ለዳዊት ፡ የወለደችውን ፡ ሕፃን ፡ ቀሠፈ ፥ እጅግም ፡ ታሞ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፤ ዳዊትም ፡ ጾመ ፥ ገብቶም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተኛ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 17 ፤ የቤቱም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተነሥተው ፡ ከምድር ፡ ያነሡት ፡ ዘንድ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሙ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ አለ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 18 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕፃኑ ፡ ሞተ ። የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ። ሕፃኑ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ብንነግረው ፡ አልሰማንም ፤ ይልቁንስ ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ብንነግረው ፡ እንዴት ፡ ይኾን ፧ በነፍሱ ፡ ክፉ ፡ ያደርጋል ፡ ብለው ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ይነግሩት ፡ ዘንድ ፡ ፈሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፡ ባሪያዎቹ ፡ በሹክሹክታ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ሕፃኑ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ዐወቀ ፤ ዳዊትም ፡ ባሪያዎቹን ፦ ሕፃኑ ፡ ሞቷል ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ ሞቷል ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ከምድር ፡ ተነሥቶ ፡ ታጠበ ፥ ተቀባም ፥ ልብሱንም ፡ ለወጠ ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ሰገደ ። ወደ ፡ ቤቱም ፡ መጣ ፦ እንጀራ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፤ በፊቱም ፡ አቀረቡለት ፥ በላም ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ባሪያዎቹም ፦ ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡

ጾምኽና ፡ አለቀስኽ ፤ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተነሥተኽ ፡ እንጀራ ፡ በላኽ ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 22 ፤ ርሱም ፦ ሕፃኑ ፡ ሕያው ፡ ሳለ ። እግዚአብሔር ፡ ይምረኝ ፥ ሕፃኑም ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፧ ብዬ ፡ ጾምኹ ፡ አለቀስኹም ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 23 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ሞቷል ፤ የምጾመው ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእውኑ ፡ እንግዲህ ፡ እመልሰው ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኛልን ፧ እኔ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እኼዳለኹ ፡ እንጂ ፡ ርሱ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አይመለስም ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 24 ፤ ዳዊትም ፡ ሚስቱን ፡ ቤርሳቤሕን ፡ አጽናናት ፥ ወደ ፡ ርሷም ፡ ገባ ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ተኛ ፤ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ፥ ስሙንም ፡ ሰሎሞን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ። እግዚአብሔርም ፡ ወደደው ፤

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 25 ፤ ደግሞም ፡ በነቢዩ ፡ በናታን ፡ እጅ ፡ ልኮ ፡ ስሙን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይዲድያ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 26 ፤ ኢዮአብም ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ ረባትን ፡ ወጋ ፥ የውሃውንም ፡ ከተማ ፡ ያዘ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 27 ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፦ ረባትን ፡ ወግቻለኹ ፥ የውሃውንም ፡ ከተማ ፡ ይጐርሰኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 28 ፤ አኹንም ፡ ከተማዩቱን ፡ እንዳልይዝ ፥ በስሜም ፡ እንዳትጠራ ፥ የቀረውን ፡ ሕዝብ ፡ ሰብስብ ፥ ከተማዩቱንም ፡ ከበኽ ፡ ያዝ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 29 ፤ ዳዊትም ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ረባት ፡ ኼደ ፥ ወግቶም ፡ ያዛት ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 30 ፤ የንጉሣቸውንም ፡ ዘውድ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ወሰደ ። ክብደቱም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ያኽል ፡ ነበር ፥ ክቡር ፡ ዕንቊም ፡ ነበረበት ፤ ዳዊትም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አደረገው ። ከከተማዩቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አወጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 12 ፡ 31 ፤ በውስጧም ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ አውጥቶ ፡ በመጋዝና ፡ በብረት ፡ መቈፈሪያና ፡ በብረት ፡ መጥረቢያ ፡ እንዲሠሩ ፡ አደረጋቸው ፤ የሸክላ ፡ ጡብም ፡ እንዲያቃጥሉ ፡ አደረጋቸው ፤ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ። ዳዊትም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ ለአቤሴሎም ፡ አንዲት ፡ የተዋበች ፡ እኅት ፡ ነበረችው ፥ ስሟም ፡ ትዕማር ፡ ነበረ ፤ የዳዊትም ፡ ልጅ ፡ አምኖን ፡ ወደዳት ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 2 ፤ አምኖንም ፡ ከእኅቱ ፡ ከትዕማር ፡ የተነሣ ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ተከዘ ፡ ታመመ ፤ ድንግልም ፡ ነበረችና ፡ አንዳች ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ ጭንቅ ፡ ኾኖበት ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 3 ፤ ለአምኖንም ፡ የዳዊት ፡ ወንድም ፡ የሳምዓ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ የሚባል ፡ ወዳጅ ፡ ነበረው ፤ ኢዮናዳብም ፡ እጅግ ፡ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 4 ፤ ርሱም ፦ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ቀን ፡ በቀን ፡ እንዲህ ፡ ከሳኽ ፧ አትነግረኝምን ፧ አለው ። አምኖንም ፦ የወንድሜን ፡ የአቤሴሎምን ፡ እኅት ፡ ትዕማርን ፡ እወዳታለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 5 ፤ ኢዮናዳብም ፦ ታምሜያለኹ ፡ ብለኽ ፡ በዐልጋኽ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፤ አባትኽም ፡ ሊያይኽ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፦ እኅቴ ፡ ትዕማር ፡ እንድትመጣና ፡ እኔ ፡ የምበላውን ፡ እንጀራ ፡ እንድትሰጠኝ ፥ መብሉንም ፡ እኔ ፡ እያየኹ ፡ እንድታዘጋጅልኝ ፥ ከእጇም ፡ እንድበላው ፡ እለምንኻለኹ ፡ በል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 6 ፤ እንዲሁም ፡ አምኖን ፦ ታምሜያለኹ ፡ ብሎ ፡ ተኛ ፤ ንጉሡም ፡ ሊያየው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አምኖን ፡ ንጉሡን ፦ እኅቴ ፡ ትዕማር ፡ እንድትመጣና ፡ እኔ ፡ እያየኹ ፡ ኹለት ፡ ዕንጐቻ ፡ እንድታደርግልኝ ፥ ከእጇም ፡

እንድበላ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፦ መብልን ፡ ታዘጋጂለት ፡ ዘንድ ፡ ወደወንድምሽ ፡ ወደአምኖን ፡ ቤት ፡ ኺጂ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ወደትዕማር ፡ ቤት ፡ ላከ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 8 ፤ ትዕማርም ፡ ወደወንድሟ ፡ ወደአምኖን ፡ ቤት ፡ ኼደች ፥ ተኝቶም ፡ ነበር ፤ ዱቄትም ፡ ወስዳ ፡ ለወሰች ፥ እያየም ፡ ዕንጐቻ ፡ አደረገች ፥ ጋገረችም ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 9 ፤ ምጣዱንም ፡ ወስዳ ፡ በፊቱ ፡ ገለበጠች ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ። አምኖንም ፦ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አስወጡ ፡ አለ ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 10 ፤ አምኖንም ፡ ትዕማርን ፦ ከእጅሽ ፡ እበላ ፡ ዘንድ ፡ መብሉን ፡ ወደ ፡ ዕልፍኙ ፡ አግቢው ፡ አላት ፤ ትዕማርም ፡ የሠራችውን ፡ ዕንጐቻ ፡ ወስዳ ፡ ወንድሟ ፡ አምኖን ፡ ወዳለበት ፡ ዕልፍኝ ፡ አገባችው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 11 ፤ መብሉንም ፡ ባቀረበች ፡ ጊዜ ፡ ያዛትና ፦ እኅቴ ፡ ሆይ ፥ ነዪ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ተኚ ፡ አላት ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 12 ፤ ርሷ ፡ መልሳ ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ አይኾንም ፤ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አይገ፡ባምና ፡ አታሳፍረኝ ፤ ይህንም ፡ ነውረኛ ፡ ሥራ ፡ አታድርግ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 13 ፤ እኔም ፡ ነውሬን ፡ ወዴት ፡ ልሸከም ፧ አንተም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከምናምንቴዎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ትኾናለኽ ፤ እንግዲህስ ፡ ለንጉሡ ፡ ንገረው ፥ እኔንም ፡ አይነሣኽም ፡ አለችው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 14 ፤ ቃሷን ፡ ግን ፡ አልሰማም ፤ ከርሷም ፡ ይልቅ ፡ ብርቱ ፡ ነበረና ፡ በግድ ፡ አስነወራት ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ተኛ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 15 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አምኖን ፡ ፈጽሞ ፡ ጠላት ፤ አስቀድሞም ፡ ከወደዳት ፡ ውድ ፡ ይልቅ ፡ በኋላ ፡ የጠላት ፡ ጥል ፡ በለጠ ። አምኖንም ፦ ተነሥተሽ ፡ ኺጂ ፡ አላት ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 16 ፤ ርሷም ፦ አይኾንም ፤ ቀድሞ ፡ ከሠራኸው ፡ ክፋት ፡ ይልቅ ፡ እኔን ፡ በማውጣትኽ ፡ የበለጠ ፡ ክፋት ፡ ትሠራለኽ ፡ አለችው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማትም ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 17 ፤ የሚያገለግለውንም ፡ ብላቴና ፡ ጠርቶ ፦ ይህችን ፡ ሴት ፡ ከፊቴ ፡ አስወጥተኽ ፡ በሩን ፡ ዝጋባት ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 18 ፤ ብዙ ፡ ሕብር ፡ ያለውንም ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ነበር ፥ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ልብስ ፡ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ደናግሉ ፡ ይለብሱ ፡ ነበርና ፤ አገልጋዩም ፡ አስወጥቶ ፡ በሩን ፡ ዘጋባት ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 19 ፤ ትዕማርም ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ ዐመድ ፡ ነስንሳ ፥ ብዙ ፡ ሕብርም ፡ ያለውን ፡ ልብሷን ፡ ተርትራ ፥ እጇንም ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ ጭና ፡ እየጮኸች ፡ ኼደች ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 20 ፤ ወንድሟም ፡ አቤሴሎም ፦ ወንድምሽ ፡ አምኖን ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ነበረን ፧ እኅቴ ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ዝም ፡ በዪ ፤ ወንድምሽ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ በልብሽ ፡ አትያዢው ፡ አላት ። ትዕማርም ፡ በወንድሟ ፡ በአቤሴሎም ፡ ቤት ፡ ብቻዋን ፡ ተቀመጠች ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የበኵር ፡ ልጁ ፡ ነበረና ፡ ስለ ፡ ወደደው ፡ የልጁን ፡ የአምኖን ፡ ነፍስ ፡ አላሳዘነም ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 22 ፤ አቤሴሎምም ፡ እኅቱን ፡ ትዕማርን ፡ ስላሳፈራት ፡ አምኖንን ፡ ጠልቶታልና ፡ አቤሴሎም ፡ አምኖንን ፡ ክፉም ፡ ኾነ ፡ መልካምም ፡ አልተናገረውም ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 23 ፤ ከኹለት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ በኤፍሬም ፡ አቅራቢያ ፡ ባለችው ፡ በቤላሶር ፡ በጎቹን ፡ አሸለተ ፤ አቤሴሎምም ፡ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 24 ፤ አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥቶ ፦ እንሆ ፥ ባሪያኽ ፡ በጎቹን ፡ ያሸልታል ፤ ንጉሡና ፡ ሎሌዎቹ ፡ ከባሪያኽ ፡ ጋራ ፡ ይኺዱ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፡ አቤሴሎምን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እንከብድብኻለንና ፡ ኹላችን ፡ እንመጣ ፡ ዘንድ ፡ አይኾንም ፡ አለው ። የግድም ፡ አለው ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ መረቀው ፡ እንጂ ፡ ለመኼድ ፡ እንቢ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 26 ፤ አቤሴሎምም ፦ አንተ ፡ እንቢ ፡ ካልኽ ፡ ወንድሜ ፡ አምኖን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንዲኼድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ። ንጉሡም ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ ይኼዳል ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 27 ፤ አቤሴሎምም ፡ የግድ ፡ አለው ፥ አምኖንንና ፡ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰደደ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 28 ፤ አቤሴሎምም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ግብዣ ፡ ያለ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፤ አቤሴሎምም ፡ አገልጋዮቹን ፦ አምኖን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጥቶ ፡ ልቡን ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ እዩ ። አምኖንን ፡ ግደሉ ፡ ባልኋችኹም ፡ ጊዜ ፡ ግደሉት ፥ አትፍሩም ፤ ያዘዝኋችኹም ፡ እኔ ፡ ነኝና ፡ በርቱ ፡ ጽኑም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 29 ፤ የአቤሴሎም ፡ አገልጋዮች ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳዘዛቸው ፡ በአምኖን ፡ ላይ ፡ አደረጉበት ። የንጉሡም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ተነሥተው ፡ በየበቅሎዎቻቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 30 ፤ ገናም ፡ በመንገድ ፡ ሲኼዱ ፡ ለዳዊት ፦ አቤሴሎም ፡ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ገድሏል ፥ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ አልቀረም ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ መጣለት ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 31 ፤ ንጉሡም ፡ ተነሥቶ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ በምድር ፡ ላይም ፡ ወደቀ ፤ ባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሙ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 32 ፤ የዳዊትም ፡ ወንድም ፡ የሳምዓ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፦ ጌታዬ ፡ ጕልማሳዎቹ ፡ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አያስብ ፤ እኅቱን ፡ ትዕማርን ፡ በግድ ፡ ካስነወራት ፡ ዠምሮ ፡ በአቤሴሎም ፡ ዘንድ ፡ የተቈረጠ ፡ ነገር ፡ ነበረና ፡ የሞተ ፡ አምኖን ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 33 ፤ አኹንም ፡ የሞተ ፡ አምኖን ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ሞቱ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ አያኑር ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 34 ፤ አቤሴሎምም ፡ ኰበለለ ። ጕበኛውም ፡ ጕልማሳ ፡ ዐይኑን ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፥ እንሆም ፥ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በኋላው ፡ በተራራው ፡ አጠገብ ፡ በመንገድ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 35 ፤ ኢዮናዳብም ፡ ንጉሡን ፦ እንሆ ፥ የንጉሡ ፡ ልጆች ፡ መጥተዋል ፤ ባሪያኽ ፡ እንዳለው ፡ እንዲሁ ፡ ኾኗል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 36 ፤ ተናግሮም ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ወዲያው ፡ የንጉሥ ፡ ልጆች ፡ ገቡ ፥ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ አለቀሱ ፤ ደግሞ ፡ ንጉሡና ፡ ባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሱ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 37 ፤ አቤሴሎም ፡ ግን ፡ ኰብሎ ፡ ወደጌሹር ፡ ንጉሥ ፡ ወደዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ተልማይ ፡ ኼደ ። ዳዊትም ፡ ኹልጊዜ ፡ ለልጁ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 38 ፤ አቤሴሎም ፡ ኰብሎ ፡ ወደ ፡ ጌሹር ፡ ኼደ ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 13 ፡ 39 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ስለ ፡ አምኖን ፡ ሞት ፡ ተጽናንቶ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡

ናፈቀ ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፡ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 1 ፤ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ የንጉሡ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳዘነበለ ፡ ዐወቀ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 2 ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ቴቁሔ ፡ ልኮ ፡ ከዚያ ፡ ብልኀተኛ ፡ ሴት ፡ አስመጣና ፦ አልቅሺ ፥ የሐዘንም ፡ ልብስ ፡ ልበሺ ፥ ዘይትም ፡ አትቀቢ ፥ ስለ ፡ ሞተ ፡ ሰውም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንደምታለቅሺ ፡ ኹኚ ፤

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገብተሽ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ንገሪው ፡ አላት ፤ ኢዮአብም ፡ ቃሉን ፡ በርሷ ፡ አፍ ፡ አደረገ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 4 ፤ እንዲሁም ፥ የቴቁሔዩቱ ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ገብታ ፡ በግንባሯ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቀች ፥ እጅ ፡ ነሥታም ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አድነኝ ፡ አለች ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ኾነሻል ፧ አላት ። ርሷም ፡ መልሳ ፡ አለች ፦ በእውነት ፡ እኔ ፡ ባሌ ፡ የሞተብኝ ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ ነኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 6 ፤ ለኔም ፡ ለባሪያኽ ፡ ኹለት ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩኝ ፥ በሜዳም ፡ ተጣሉ ፤ የሚገላግላቸውም ፡ አልነበረም ፥ አንዱም ፡ ሌላውን ፡ መቶ ፡ ገደለው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 7 ፤ እንሆም ፥ ዘመዶች ፡ ኹሉ ፡ በባሪያኽ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፦ ስለገደለው ፡ ስለወንድሙ ፡ ነፍስ ፡ እንገድለው ፡ ዘንድ ፡ ወንድሙን ፡ የገደለውን ፡ አውጪ ፡ አሉኝ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ወራሹን ፡ የቀረውን ፡ መብራቴን ፡ ያጠፋሉ ፥ የባሌን ፡ ስምና ፡ ዘርም ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አያስቀሩም ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ ሴቲቱን ፦ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ኺጂ ፥ እኔም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ አዛለኹ ፡ አላት ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 9 ፤ የቴቁሔዩቱም ፡ ሴት ፡ ንጉሡን ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ኀጢአቱ ፡ በእኔና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ ንጉሡና ፡ ዙፋኑ ፡ ንጹሕ ፡ ይኹን ፡ አለችው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፦ የሚናገርሽን ፡ አምጪልኝ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ አይነካሽም ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 11 ፤ ርሷም ፦ ደም ፡ ተበቃዮችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳያጠፉ ፡ ልጄንም ፡ እንዳይገድሉ ፥ ንጉሡ ፡ አምላኩን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስብ ፡ አለች ። ርሱም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ከልጅሽ ፡ አንድ ፡ ጠጕር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይወድቅም ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 12 ፤ ሴቲቱም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ልናገር ፡ አለች ፤ ርሱም ፦ ተናገሪ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 13 ፤ ሴቲቱም ፡ አለች ፦ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዐሰብኽ ፧ ንጉሡ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናግሯልና ፡ ያሳደደውን ፡ ስላላስመለሰ ፡ በደለኛ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 14 ፤ ኹላችን ፡ እንሞታለን ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰና ፡ እንደማይመለስ ፡ ውሃ ፡ ነን ፤ እግዚአብሔርም ፡ የነፍስን ፡ ጥፋት ፡ አይወድም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የተጣለ ፡ ሰው ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳይጠፋ ፡ በምክሩ ፡ ያስባል ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ሕዝቡ ፡ ስለሚያስፈራኝ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፡ እነግረው ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለኹ ፤ እኔም ፡ ባሪያኽ ፦ ምናልባት ፡ የእኔን ፡ የባሪያውን ፡ ልመና ፡ ንጉሡ ፡ ያደርግልኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለንጉሡ ፡ ልናገር ፤

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 16 ፤ ርሷንና ፡ ልጇን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ርስት ፡ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከሚሻ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ ባሪያውን ፡ ይሰማል ፡ አልኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 17 ፤ እኔም ፡ ባሪያኽ ፦ መልካሙንና ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡ ንጉሡ ፡ ጌታዬ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ነውና ፥ የጌታዬ ፡ የንጉሡ ፡ ቃል ፡ ያጽናናኛል ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፡ አልኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ለሴቲቱ ፡ መልሶ ፦ የምጠይቅሽን ፡ ነገር ፡ አትሰውሪኝ ፡ አላት ። ሴቲቱም ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ይናገር ፡ አለች ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 19 ፤ ንጉሡም ፦ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ የኢዮአብ ፡ እጅ ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ነውን ፧ አላት ። ሴቲቱም ፡ መልሳ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በሕያው ፡ ነፍስኽ ፡ እምላለኹ! ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ከተናገረው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ሊል ፡ የሚችል ፡ የለም ፤ ባሪያኽ ፡ ኢዮአብ ፡ አዞኛል ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በባሪያኽ ፡ አፍ ፡ አደረገው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 20 ፤ ባሪያኽ ፡ ኢዮአብ ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ መልክ ፡ እንዲለወጥ ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ጠቢብ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አንተም ፡ ጌታዬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጠቢብ ፡ ነኽ ፡ አለች ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአብን ፦ እንሆ ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ አድርጌያለኹ ፤ እንግዲህ ፡ ኺድና ፡ ብላቴናውን ፡ አቤሴሎምን ፡ መልሰው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 22 ፤ ኢዮአብም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ወድቆ ፡ እጅ ፡ ነሣ ፥ ንጉሡንም ፡ ባረከ ፤ ኢዮአብም ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ የባሪያኽን ፡ ነገር ፡ አድርገኻልና ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ እንዳገኘ ፡ ባሪያኽ ፡ ዛሬ ፡ ዐወቀ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 23 ፤ ኢዮአብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጌሹር ፡ ኼደ ፥ አቤሴሎምንም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይዞ ፡ መጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፦ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይኺድ ፡ እንጂ ፡ ፊቴን ፡ እንዳያይ ፡ አለ ፤ አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፥ የንጉሡንም ፡ ፊት ፡ አላየም ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 25 ፤ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አቤሴሎም ፡ በውበቱ ፡ የተመሰገነ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፤ ከእግሩ ፡ እስከ ፡ ራሱ ፡ ድረስ ፡ ነውር ፡ አልነበረበትም ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 26 ፤ ጠጕሩም ፡ ይከብደው ፡ ነበርና ፥ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይቈርጠው ፡ ነበር ፤ ሲቈረጥም ፡ የራሱ ፡ ጠጕር ፡ በንጉሥ ፡ ሚዛን ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ያኽል ፡ ይመዘን ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 27 ፤ ለአቤሴሎምም ፡ ሦስት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተወለዱለት ፤ የሴቲቱም ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ትዕማር ፡ ነበረ ፥ ርሷም ፡ የተዋበች ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 28 ፤ አቤሴሎምም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ የንጉሡን ፡ ፊት ፡ ሳያይ ፡ ተቀመጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 29 ፤ አቤሴሎምም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ይልከው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ላከ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ሊመጣ ፡ አልወደደም ፤ ኹለተኛም ፡ ላከበት ፥ ሊመጣ ፡ ግን ፡ አልወደደም ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 30 ፤ ባሪያዎቹንም ፦ በዕርሻዬ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ የኢዮአብን ፡ ዕርሻ ፡ እዩ ፥ በዚያም ፡ ገብስ ፡ አለው ፤ ኺዳችኹ ፡ በእሳት ፡ አቃጥሉት ፡ አላቸው ። የአቤሴሎምም ፡ ባሪያዎች ፡ ዕርሻውን ፡ አቃጠሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 31 ፤ ኢዮአብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጣና ፦ ባሪያዎችኽ ፡ ዕርሻዬን ፡ ስለ ፡

ምን ፡ አቃጠሉት ፡፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 32 ፤ አቤሴሎምም ፡ ኢዮአብን ፡ መልሶ ፦ ከጌሹር ፡ ለምን ፡ መጣኹ ፡፡ በዚያም ፡ ተቀምጬ ፡ ብኾን ፡ ይሻለኝ ፡ ነበር ፡ ብለኽ ፡ እንድትነግረው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እልክኽ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ጠራኹኽ ፤ አኹንም ፡ የንጉሡን ፡ ፊት ፡ ልይ ፥ ኀጢአት ፡ ቢኾንብኝ ፡ ይግደለኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 14 ፡ 33 ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጥቶ ፡ ነገረው ፤ አቤሴሎምንም ፡ ጠራው ፥ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገብቶ ፡ በንጉሥ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ፤ ንጉሡም ፡ አቤሴሎምን ፡ ሳመው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ሠረገላና ፡ ፈረሶች ፥ በፊቱም ፡ የሚሮጡ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ አዘጋጀ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 2 ፤ አቤሴሎምም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ በበሩ ፡ አደባባይ ፡ ይቆም ፡ ነበር ፤ አቤሴሎምም ፡ ከንጉሥ ፡ ለማስፈረድ ፡ ጕዳይ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እየጠራ ፦ አንተ ፡ ከወዴት ፡ ከተማ ፡ ነኽ ፡፡ ብሎ ፡ ይጠይቅ ፡ ነበር ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ከአንዲቱ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ይመልስ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 3 ፤ አቤሴሎምም ፦ ነገርኽ ፡ እውነትና ፡ ቅን ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከንጉሥ ፡ ታዘ ፡ የሚሰማኽ ፡ የለም ፡ ይለው ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 4 ፤ አቤሴሎምም ፦ ነገርና ፡ ክርክር ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ቅንም ፡ ፍርድ ፡ እፈርድለት ፡ ዘንድ ፡ በአገር ፡ ላይ ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ ፡ ማን ፡ በሾመኝ ፡፡ ይል ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 5 ፤ ሰውም ፡ እጅ ፡ ሊነሣው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ይይዝና ፡ ይስመው ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 6 ፤ እንዲሁም ፡ አቤሴሎም ፡ ከንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ሊሰማ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በሚመጣ ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ አቤሴሎምም ፡ የእስራኤልን ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ሰረቀ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 7 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከአራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ አቤሴሎም ፡ ንጉሡን ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የተሳልኹትን ፡ ስእለት ፡ ለመስጠት ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፥ እባክኽ ፥ ልኺድ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በሶርያ ፡ ጌሹር ፡ ሳለኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቢመልሰኝ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርባለኹ ፡ ብዬ ፡ ስእለት ፡ ተስዬ ፡ ነበር ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 9 ፤ ንጉሡም ፦ በደኅና ፡ ኺድ ፡ አለው ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 10 ፤ አቤሴሎምም ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፦ የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፦ አቤሴሎም ፡ በኬብሮን ፡ ነገሠ ፡ በሉ ፡ የሚሉ ፡ ጉበኞች ፡ ላከ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 11 ፤ የተጠሩትም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋራ ፡ በየዋህነት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ኼዱ ፤ የሚኾነውንም ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ አያውቁም ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 12 ፤ አቤሴሎምም ፡ የዳዊት ፡ መካር ፡ የነበረውን ፡ የጊሎ ፡ ሰው ፡ አኪጦፌልን ፡ ከከተማው ፡ ከጊሎ ፡ መሥዋዕት ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ አስጠራው ። ሤራውም ፡ ጽኑ ፡ ኾነ ፤ ከአቤሴሎምም ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ እየበዛ ፡ ኼደ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 13 ፤ ለዳዊትም ፦ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋራ ፡ ኾኗል ፡ የሚል ፡ ወሬኛ ፡

መጣለት ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያሉትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ኹሉ ፦ ተነሡ ፥ እንሽሽ ፡ ያለዚያ ፡ ከአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ የሚድን ፡ ከእኛ ፡ የለምና ፤ መጥቶም ፡ እንዳይዘን ፥ ክፉም ፡ እንዳያመጣብን ፡ ከተማዪቱንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ እንዳይመታ ፡ ፈጥናችኹ ፡ እንኺድ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 15 ፤ የንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ ንጉሡን ፦ እንሆ ፥ ጌታችን ፡ ንጉሡ ፡ የመረጠውን ፡ ኹሉ ፡ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ዕሺ ፡ ብለን ፡ እናደርጋለን ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 16 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ ሰቡ ፡ ኹሉ ፡ ወጡ ፤ ንጉሡም ፡ ዐሥሩን ፡ ሴቶች ፡ ቁባቶቹን ፡ ቤቱን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ተወ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ወጡ ፥ በቤትሜርሐቅም ፡ ቆሙ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 18 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ዐለፉ ፤ ከሊታውያንና ፡ ፈሊታውያንም ፡ ኹሉ ፥ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ከጌት ፡ የመጡት ፡ ስድስት ፡ መቶው ፡ ጌትያውን ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ዐለፉ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 19 ፤ ንጉሡም ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ኢታይን ፦ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለምን ፡ መጣኽ ፧ አንተ ፡ ከስፍራኽ ፡ የመጣኽ ፡ እንግዳና ፡ ስደተኛ ፡ ነኽና ፥ ተመለስ ፥ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ ተቀመጥ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 20 ፤ የመጣኸው ፡ ትናንት ፡ ነው ፤ ዛሬ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ላዘርኽን ፧ እኔ ፡ ወደምኼድበት ፡ እኼዳለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ተመለስ ፥ ወንድሞችኽንም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰድ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ምሕረቱንና ፡ እውነቱን ፡ ያድርግልኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 21 ፤ ኢታይም ፡ ለንጉሡ ፡ መልሶ ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በጌታዬም ፡ በንጉሡ ፡ ሕይወት ፡ እምላለኹ! ፡ በእውነት ፡ ጌታዬ ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፥ በሞትም ፡ ቢኾን ፡ በሕይወትም ፥ በዚያ ፡ ደግሞ ፡ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ እኾናለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፡ ኢታይን ፦ ኺድ ፡ ተሻገር ፡ አለው ፤ የጌት ፡ ሰው ፡ ኢታይና ፡ ሰዎቹም ፡ ኹሉ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕፃናት ፡ ኹሉ ፡ ተሻገሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 23 ፤ በአገርም ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ አለቀሱ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ተሻገሩ ፥ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ የቄድሮንን ፡ ፈፋ ፡ ተሻገረ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ ተሻገሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 24 ፤ እንሆም ፥ ደግሞ ፡ ሳዶቅ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ተሸክመው ፡ መጡ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ አስቀመጡ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ከከተማዪቱ ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ አብያታር ፡ ወጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፡ ሳዶቅን ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መልስ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፥ መልሶ ፡ ርሱንና ፡ ማደሪያውን ፡ ያሳየኛል ፤

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ አልወድኽም ፡ ቢለኝ ፥ እንሆኝ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ ያድርግብኝ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅን ፦ እንሆ ፥ አንተና ፡ ልጅኽ ፡ አኪማዐስ ፡ የአብያታርም ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ኹለቱ ፡ ልጆቻችኹ ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ተመለሱ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 28 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ እስኪመጣልኝ ፡ ድረስ ፡ በምድረ ፡ በዳው ፡ መሻገሪያ ፡ እቈያለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 29 ፤ ሳዶቅም ፡ አብያታርም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መለሱት ፥ በዚያም ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 30 ፤ ዳዊትም ፡ ተከናንቦ ፡ ያለጫማ ፡ እያለቀሰ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ዐቀበት ፡ ወጣ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተከናንበው ፡ እያለቀሱ ፡ ወጡ ፦

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 31 ፤ አኪጦፌል ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋራ ፡ በሤራ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፤ ዳዊትም ፦ አቤቱ ፥ የአኪጦፌልን ፡ ምክር ፡ ስንፍና ፡ አድርገኽ ፡ እንድትለውጥ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 32 ፤ ዳዊትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወደሰገደበት ፡ ወደተራራው ፡ ራስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ አርካዊው ፡ ኩሲ ([158]) ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሶ ፡ ሊገናኘው ፡ መጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 33 ፤ ዳዊትም ፡ አለው ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ብትመጣ ፡ ትከብደኛለኽ ፤

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 34 ፤ ወደ ፡ ከተማ ፡ ግን ፡ ተመልሰኽ ፡ ለአቤሴሎም ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ባሪያ ፡ እኾንኻለኹ ፤ አስቀድሞ ፡ ለአባትኽ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ነበርኹ ፡ እንዲሁ ፡ አኹን ፡ ለአንተ ፡ ባሪያ ፡ እኾንኻለኹ ፡ ብትለው ፡ የአኪጦፌልን ፡ ምክር ፡ ከንቱ ፡ ታደርግልኛለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 35 ፤ ካህናቱ ፡ ሳዶቅና ፡ አብያታርም ፡ በዚያ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አይደሉምን ፧ ከንጉሡ ፡ ቤትም ፡ የምትሰማውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለካህናቱ ፡ ለሳዶቅና ፡ ለአብያታር ፡ ንገራቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 36 ፤ እንሆ ፥ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማዐስና ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ልጆቻቸው ፡ በዚያ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አሉ ፤ የምትሰሙትን ፡ ኹሉ ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ላኩልኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 15 ፡ 37 ፤ የዳዊትም ፡ ወዳጅ ፡ ኩሲ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መጣ ፤ አቤሴሎምም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ከተራራው ፡ ራስ ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የሜምፊቦስቴ ፡ ባሪያ ፡ ሲባ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ እንጀራ ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ ዘለላ ፡ ዘቢብ ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ በለስ ፥ አንድ ፡ አቍማዳም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የተጫነ ፡ ኹለት ፡ አህያዎች ፡ እየነዳ ፡ ተገናኘው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ሲባን ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ። ሲባም ፦ አህያዎቹ ፡ የንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ይቀመጡባቸው ፡ ዘንድ ፥ እንጀራውና ፡ በለሱ ፡ ብላቴናዎቹ ፡ ይበሉት ፡ ዘንድ ፥ የወይን ፡ ጠጁም ፡ በበረሓ ፡ የሚደክሙት ፡ ይጠጡት ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፦ የጌታኽ ፡ ልጅ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አለ ። ሲባም ፡ ንጉሡን ፦ እንሆ ፦ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዛሬ ፡ የአባቴን ፡ መንግሥት ፡ ይመልስልኛል ፡ ብሎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀምጧል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ሲባን ፦ እንሆ ፥ ለሜምፊቦስቴ ፡ የነበረው ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ አለው ። ሲባም ፦ እጅ ፡ እነሣለኹ ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ ላግኝ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 5 ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ብራቂም ፡ መጣ ፤ እንሆም ፥ ሳሚ ፡ የሚባል ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ከሳኦል ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከዚያ ፡ ወጣ ፥ እየኼደም ፡ ይረግመው ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ዳዊትና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደዳዊት ፡ ባሪያዎችም ፡ ድንጋይ ፡ ይወረውር ፡ ነበር ፤ በንጉሡም ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉና ፡ ኀያላኑ ፡ ኹሉ ፡ ነበሩ ።

---

158 ዕብ. ፥ ሑሲ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 7 ፤ ሳሚም ፡ ሲረግም ፦ ኺድ ፥ አንተ ፡ የደም ፡ ሰው ፥ ምናምንቴ ፥ ኺድ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 8 ፤ በፋንታው ፡ ነግሠኻልና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሳኦልን ፡ ቤት ፡ ደም ፡ ኹሉ ፡ መለሰብኽ ፤ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥትን ፡ ለልጅኽ ፡ ለአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፤ እንሆም ፥ አንተ ፡ የደም ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ በመከራ ፡ ተይዘኻል ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 9 ፤ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ አቢሳ ፡ ንጉሡን ፦ ይህ ፡ የሞተ ፡ ውሻ ፡ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይረግማል ፧ ልኺድና ፡ ራሱን ፡ ልቀሥረጠው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፦ እናንተ ፡ የጽሩም ፡ ልጆች ፥ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ እግዚአብሔር ፦ ዳዊትን ፡ ስደበው ፡ ብሎ ፡ አዞታልና ፥ ይርገመኝ ፤ ለምንስ ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ አቢሳንና ፡ ባሪያዎቹን ፡ ኹሉ ፦ እንሆ ፥ ከወገቤ ፡ የወጣው ፡ ልጄ ፡ ነፍሴን ፡ ይሻል ፤ ይልቁንስ ፡ ይህ ፡ የብንያም ፡ ልጅ ፡ እንዴት ፡ ነዋ ፧ እግዚአብሔር ፡ አዞታልና ፥ ተዉት ፥ ይርገመኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 12 ፤ ምናልባት ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ መከራዬን ፡ አይቶ ፡ ስለ ፡ ርግማኑ ፡ መልካም ፡ ይመልስልኛል ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 13 ፤ ዳዊትና ፡ ሰዎቹም ፡ በመንገድ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ ሳሚም ፡ በተራራው ፡ አጠገብ ፡ በርሱ ፡ ትይዩ ፡ እየኼደ ፡ ይራገም ፤ ድንጋይም ፡ ይወረውር ፥ ትቢያም ፡ ይበትን ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 14 ፤ ንጉሡና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደክመው ፡ ነበር ፥ በዚያም ፡ ዐረፉ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 15 ፤ አቤሴሎምና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ አኪጦፌልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 16 ፤ የዳዊትም ፡ ወዳጅ ፡ አርካዊው ፡ ኩሲ ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ ኩሲ ፦ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ያንግሥኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 17 ፤ አቤሴሎምም ፡ ኩሲን ፦ ስለ ፡ ወዳጅኽ ፡ ያደረግኸው ፡ ቸርነት ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ ከወዳጅኽ ፡ ጋራ ፡ ያልኼድኽ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 18 ፤ ኩሲም ፡ አቤሴሎምን ፦ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ከእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ለተመረጠው ፡ ለርሱ ፡ እኾናለኹ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እቀመጣለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 19 ፤ ዳግምም ፡ የማገለግል ፡ ለማን ፡ ነው ፧ በንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ፊት ፡ አይደለምን ፧ በአባትኽ ፡ ፊት ፡ እንዳገለገልኹ ፡ እንዲሁ ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ እኾናለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 20 ፤ አቤሴሎምም ፡ አኪጦፌልን ፦ ምከሩ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 21 ፤ አኪጦፌልም ፡ አቤሴሎምን ፦ ቤት ፡ ሊጠብቁ ፡ ወደተዋቸው ፡ ወዳባትኽ ፡ ቁባቶች ፡ ግባ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ አባትኽን ፡ እንዳሳፈርኸው ፡ ይሰማሉ ፤ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ እጃቸው ፡ ይበረታል ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 22 ፤ ለአቤሴሎምም ፡ በሰገነት ፡ ላይ ፡ ድንኳን ፡ ተከሉለት ፤ አቤሴሎምም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ወዳባቱ ፡ ቁባቶች ፡ ገባ ።

ሳሙ.2 ፡ 16 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የመከራት ፡ የአኪጦፌል ፡ ምክር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ መጠየቅ ፡ ነበረች ፤ የአኪጦፌልም ፡ ምክር ፡ ኹሉ ፡ ከዳዊትና ፡ ከአቤሴሎም ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡ ነበረች ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 1 ፤ አኪጦፌልም ፡ አቤሴሎምን ፦ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ልምረጥና ፡

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 1 ፤ አኪጦፌልም ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ተነሥቼ ፡ ዳዊትን ፡ ላሳድ ። ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 2 ፤ ደክሞና ፡ እጁ ፡ ዝሎ ፡ ሳለ ፡ እወድቅበታለኹ ፥ አስፈራውማለኹ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይሸሻል ፥ ንጉሡንም ፡ ብቻውን ፡ እመታዋለኹ ፤

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 3 ፤ ሙሽራ ፡ ወደ ፡ ባሏ ፡ እንደምትመለስ ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ እመልሰዋለኹ ፤ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ደኅና ፡ ይኾናል ፤ የምትፈልገው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 4 ፤ ነገሩም ፡ አቤሴሎምንና ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ አሠኘ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 5 ፤ አቤሴሎምም ፦ አርካዊውን ፡ ኩሲን ፡ ጥሩ ፥ ደግሞም ፡ ርሱ ፡ የሚለውን ፡ እንስማ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 6 ፤ ኩሲም ፡ ወደ ፡ አቤሴሎም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አቤሴሎም ፦ አኪጦፌል ፡ ያለው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ነገሩን ፡ እናደርገው ፡ ዘንድ ፡ ይገባልን ፧ ባይኾን ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ንገረን ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 7 ፤ ኩሲም ፡ አቤሴሎምን ፦ አኪጦፌል ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የመከራት ፡ ምክር ፡ መልካም ፡ አይደለችም ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 8 ፤ ኩሲ ፡ ደግሞ ፡ አለ ፦ ግልገሎቿ ፡ በዱር ፡ በተነጠቁ ፡ ጊዜ ፡ ድብ ፡ መራራ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ በልባቸው ፡ መራሮች ፡ እጅግም ፡ ኀያላን ፡ መኾናቸውን ፡ አባትኽንና ፡ ሰዎቹን ፡ ታውቃለኽ ፤ አባትኽ ፡ ዐርበኛ ፡ ነው ፥ ከሕዝብም ፡ ጋራ ፡ አያድርም ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 9 ፤ አኹንም ፡ ምናልባት ፡ ባንድ ፡ ጕድጓድ ፡ ወይም ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ ተሸሽጎ ፡ ይኾናል ፤ በመገሥመሪያም ፡ ከነርሱ ፡ ዐያሌዎች ፡ ቢወድቁ ፥ የሚሰማው ፡ ኹሉ ፦ አቤሴሎምን ፡ የተከተለው ፡ ሕዝብ ፡ ተመታ ፡ ይላል ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 10 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ አባትኽ ፡ ኀያል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ጽኑዓን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ያውቃልና ፥ ጽኑዕ ፡ ልቡም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ልብ ፡ የኾነው ፡ ፈጽሞ ፡ ይቀልጣል ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የምመክርኽ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ያለ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ በብዛቱ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ኾኖ ፡ ወዳንተ ፡ ይሰብሰብ ፥ አንተም ፡ በመካከላቸው ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ውጣ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 12 ፤ ርሱንም ፡ ወደምናገኝበት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ እንደርስበታለን ፥ ጠልም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደሚወድቅ ፡ እንወርድበታለን ፤ ርሱና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አናስቀርም ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 13 ፤ ወደ ፡ ከተማም ፡ ቢገባ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደዚያች ፡ ከተማ ፡ ገመድ ፡ ይወስዳል ፥ እኛም ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ እንኳ ፡ እስከማይገኝባት ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ወንዙ ፡ ውስጥ ፡ እንስባታለን ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 14 ፤ አቤሴሎምና ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፦ የአርካዊው ፡ የኩሲ ፡ ምክር ፡ ከአኪጦፌል ፡ ምክር ፡ ይሻላል ፡ አሉ ። እግዚአብሔርም ፡ በአቤሴሎም ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መልካሚቱን ፡ የአኪጦፌልን ፡ ምክር ፡ እንዲበትን ፡ አዘዘ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 15 ፤ ኩሲም ፡ ለካህናቱ ፡ ለሳዶቅና ፡ ለአብያታር ፦ አኪጦፌል ፡ ለአቤሴሎምና ፡ ለእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ መክሯል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ መክሬያለኹ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 16 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ንጉሡና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡

እንዳይዋጡ ፥ ፈጥናችኹ ። ሳትዘገይ ፡ ተሻገር ፡ እንጂ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መሻገሪያ ፡ አትደር ፡ ብላችኹ ፡ ለዳዊት ፡ ንገሩት ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 17 ፤ ዮናታንና ፡ አኪማዐስ ፡ ተገልጠው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፡ ነበርና ፥ በዐይንሮጌል ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ አንዲትም ፡ ባሪያ ፡ ኼዳ ፡ ትነግራቸው ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ኼደው ፡ ለንጉሡ ፡ ለዳዊት ፡ ይነግሩት ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 18 ፤ አንድ ፡ ብላቴናም ፡ አይቶ ፡ ለአቤሴሎም ፡ ነገረው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ፈጥነው ፡ ኼዱ ፤ ወደ ፡ ብራቂምም ፡ ወዳንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ መጡ ፤ በግቢውም ፡ ውስጥ ፡ ጕድጓድ ፡ ነበረ ፥ ወደዚያም ፡ ውስጥ ፡ ወረዱ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 19 ፤ ሴቲቱም ፡ በጕድጓድ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ዳውጃ ፡ ዘረጋችበት ፥ የተከካ ፡ እኽልም ፡ በላዩ ፡ አሰጣችበት ፤ ነገሩም ፡ እንዲህ ፡ ተሰወረ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 20 ፤ የአቤሴሎም ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ሴቲቱ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መጥተው ፦ አኪማዐስና ፡ ዮናታን ፡ የት ፡ አሉ ፧ አሉ ፤ ሴቲቱም ፦ ፈፋውን ፡ ተሻግረው ፡ ኼዱ ፡ አለቻቸው ። እነርሱም ፡ ፈልገው ፡ ባላገኟቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 21 ፤ ከኼዱም ፡ በኋላ ፡ እነርሱ ፡ ከጕድጓድ ፡ ወጥተው ፡ ኼዱ ፥ ለንጉሡም ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ፥ ዳዊትንም ፦ አኪጦፌል ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ መክሯልና ፥ ተነሡ ፥ ፈጥናችኹም ፡ ውሃውን ፡ ተሻገሩ ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 22 ፤ ዳዊትና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ተነሥተው ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ፤ እስኪነጋም ፡ ድረስ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሳይሻገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አልቀረም ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 23 ፤ አኪጦፌልም ፡ ምክሩን ፡ እንዳልተከተሉ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አህያውን ፡ ጫነ ፥ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ኼደ ፤ ቤቱንም ፡ አደራጅቶ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ታንቆ ፡ ሞተ ፥ በአባቱም ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 24 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ መጣ ፤ አቤሴሎምም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 25 ፤ አቤሴሎምም ፡ በጭፍራው ፡ ላይ ፡ በኢዮአብ ፡ ስፍራ ፡ ዐማሳይን ፡ ሾመ ፤ ዐማሳይም ፡ የይስማኤላዊ ፡ ሰው ፡ የዬቴር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የኢዮአብን ፡ እናት ፡ የጽሩያን ፡ እኅት ፡ የናዖስን ፡ ልጅ ፡ አቢግያን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 26 ፤ እስራኤልና ፡ አቤሴሎምም ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 27 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ በረባት ፡ የነበረ ፡ የናዖስ ፡ ልጅ ፡ ኡኤስቢ ፥ የሎዶባርም ፡ ሰው ፡ የዓሚኤል ፡ ልጅ ፡ ማኪር ፥ የሮግሊምም ፡ ሰው ፡ ገለዓዳዊ ፡ ቤርዜሊ ፥

ሳሙ.2 ፥ 17 ፥ 28 ፤ 29 ፤ ሕዝቡ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ተርቧል ፥ ደክሟል ፥ ተጠምቷል ፡ ብለው ፡ ምንጣፍ ፥ ዳካ ፥ የሸክላም ፡ ዕቃ ፥ ይበሉም ፡ ዘንድ ፡ ስንዴ ፥ ገብስ ፥ ዱቄት ፥ የተጠበሰ ፡ እሸት ፥ ባቄላ ፥ ምስር ፥ የተቈላ ፡ ሽንብራ ፥ ማር ፥ ቅቤ ፥ በጎች ፥ የላምም ፡ ርጎ ፡ ለዳዊትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ አመጡላቸው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ሳሙ.2 ፥ 18 ፥ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ቈጠረ ፥ ሻለቃዎችንና ፡ የመቶ ፡ አለቃዎችንም ፡ ሾመላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ ሕዝቡን ፡ ከኢዮአብ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ሚሶውን ፥ ከኢዮአብም ፡ ወንድም ፡ ከጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ከአቢሳ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ሚሶውን ፥ ከጌት ፡ ሰውም ፡ ከኢታይ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ሚሶውን ፡ ሰደደ ። ንጉሡም ፡ ሕዝቡን ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እወጣለኹ ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 3 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፦ አትወጣም ፤ ብንሸሽ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አያስቡም ፤ ከእኛም ፡ እኩሌታው ፡ ቢሞት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አያስቡም ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ለብቻኽ ፡ ከእኛ ፡ ከዐሥሩ ፡ ሺሕ ፡ ይልቅ ፡ ትበልጣለኽ ፤ አኹንም ፡ በከተማ ፡ ተቀምጠኽ ፡ ብትረዳን ፡ ይሻላል ፡ አሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፦ መልካም ፡ የሚመስላችኹን ፡ አደርጋለኹ ፡ አላቸው ። ንጉሡም ፡ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ መቶ ፡ በመቶ ፡ ሺሕ ፡ በሺሕ ፡ እየኾኑ ፡ ወጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአብንና ፡ አቢሳን ፣ ኢታይንም ፦ ለብላቴናው ፡ ለአቤሴሎም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ራሩለት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ንጉሡም ፥ ስለ ፡ አቤሴሎም ፥ አለቃዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ሲያዝ ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 6 ፤ ሕዝቡም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ፤ ሰልፉም ፡ በኤፍሬም ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ በዳዊት ፡ ባሪያዎች ፡ ፊት ፡ ተመቱ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ውጊያ ፡ በዚያ ፡ ኾነ ፥ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ሰውም ፡ ሞተ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 8 ፤ ከዚያም ፡ ሰልፉ ፡ በአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ተበተነ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰይፍ ፡ ከዋጠው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ዱር ፡ ብዙ ፡ ዋጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 9 ፤ አቤሴሎም ፡ ከዳዊት ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ በድንገት ፡ ተገናኘ ፤ አቤሴሎምም ፡ በበቅሎ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥ በቅሎውም ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ባለው ፡ በታላቅ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ገባ ፥ ራሱም ፡ በዛፉ ፡ ተያዘ ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ተንጠለጠለ ፥ ተቀምጦበትም ፡ የነበረ ፡ በቅሎ ፡ ዐለፈ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 10 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ አይቶ ፦ እንሆ ፥ አቤሴሎም ፡ በትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ አየኹ ፡ ብሎ ፡ ለኢዮአብ ፡ ነገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 11 ፤ ኢዮአብም ፡ ለነገረው ፡ ሰው ፦ እንሆ ፥ ካየኸው ፡ ለምን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አልመታኸውም ፧ ዐሥር ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ ድግ ፡ እሰጥኽ ፡ ነበር ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 12 ፤ ሰውዮውም ፡ ኢዮአብን ፦ እኛ ፡ ስንሰማ ፡ ንጉሡ ፡ አንተንና ፡ አቢሳን ፡ ኢታይንም ፦ ብላቴናውን ፡ አቤሴሎምን ፡ ማንም ፡ እንዳይነካው ፡ ተጠንቀቁ ፡ ብሎ ፡ አዟልና ፥ ሺሕ ፡ ብር ፡ በእጄ ፡ ላይ ፡ ብትመዝን ፡ እጄን ፡ በንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ባልዘረጋኹም ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ ቅሉ ፡ በነፍሱ ፡ ላይ ፡ ብወነጅል ፡ ኖሮ ፥ ይህ ፡ ከንጉሥ ፡ ባልተሰወረም ፥ አንተም ፡ በተነሣኽብኝ ፡ ነበር ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 14 ፤ ኢዮአብም ፦ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡ እዘገይ ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ ሦስት ፡ ጦሮች ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ፥ አቤሴሎምም ፡ ገና ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ሕያው ፡ ሳለ ፡ በልቡ ፡ ላይ ፡ ተከላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 15 ፤ ዐሥሩም ፡ የኢዮአብ ፡ ጋሻ ፡ ጐግሬዎች ፡ ከበቡት ፥ አቤሴሎምንም ፡ መትተው ፡ ገደሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 16 ፤ ኢዮአብም ፡ ሕዝቡን ፡ ከልክሎ ፡ ነበርና ፥ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ፥ ሕዝቡም ፡ እስራኤልን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 17 ፤ አቤሴሎምንም ፡ ወስደው ፡ በዱር ፡ ባለ ፡ በታላቅ ፡ ጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት ፥ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ከመሩበት ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 18 ፤ አቤሴሎምም ፡ ሕያው ፡ ሳለ ፦ ለስሜ ፡ መታሰቢያ ፡ የሚኾን ፡ ልጅ ፡ የለኝም ፡ ብሎ ፥ ሐውልት ፡ ወስዶ ፥ በንጉሥ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ለራሱ ፡ አቁሞ ፡ ነበር ፤ ሐውልቱንም ፡ በስሙ ፡ ጠርቶት ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የአቤሴሎም ፡ መታሰቢያ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 19 ፤ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማዐስ ፡ ግን ፦ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቹን ፡ እንደ ፡ ተበቀለለት ፡ ሮጬ ፡ ለንጉሥ ፡ የምሥራች ፡ ልንገር ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 20 ፤ ኢዮአብም ፦ በሌላ ፡ ቀን ፡ እንጂ ፡ ዛሬ ፡ ወሬ ፡ አትናገርም ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ሞቷልና ፥ ዛሬ ፡ ወሬ ፡ አትናገርም ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 21 ፤ ኢዮአብም ፡ ኩሲን ([159]) ፦ ኺድ ፥ ያየኸውንም ፡ ለንጉሡ ፡ ንገር ፡ አለው ። ኩሲም ፡ ለኢዮአብ ፡ እጅ ፡ ነሥቶ ፡ ሮጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 22 ፤ ዳግመኛም ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ አኪማዐስ ፡ ኢዮአብን ፦ የኾነ ፡ ኾኖ ፡ ኩሲን ፡ ተከትዬ ፥ እባክኽ ፥ ልሩጥ ፡ አለው ። ኢዮአብም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ መልካም ፡ ወሬ ፡ የምትወስድ ፡ አይደለኽምና ፡ ትሮጥ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ ትወዳለኽ ፧ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ብሮጥ ፡ ምን ፡ ይገዳል ፧ አለ ። ርሱም ፦ ሩጥ ፡ አለው ። አኪማዐስም ፡ በሜዳው ፡ መንደር ፡ በኩል ፡ ሮጠ ፥ ኩሲንም ፡ ቀደመው ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 24 ፤ ዳዊትም ፡ በኹለት ፡ በር ፡ መካከል ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ዘበኛውም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ ሰገነት ፡ ወጣ ፥ ዐይኑንም ፡ አቅንቶ ፡ ብቻውን ፡ የሚሮጥ ፡ ሰው ፡ አየ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 25 ፤ ዘበኛውም ፡ ለንጉሡ ፡ ሊነግረው ፡ ጮኸ ። ንጉሡም ፦ ብቻውን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በአፉ ፡ ወሬ ፡ ይኖራል ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ቀረበ ። ዘበኛውም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ሲሮጥ ፡ አየ ፤ ዘበኛውም ፡ ለደጅ ፡ ጠባቂው ፡ ጮኾ ፦ እንሆ ፥ ብቻውን ፡ የሚሮጥ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አየኹ ፡ አለ ። ንጉሡም ፦ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ወሬ ፡ ይዞ ፡ ይኾናል ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 27 ፤ ዘበኛውም ፦ የፊተኛው ፡ ሩጫ ፡ እንደ ፡ ሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ አኪማዐስ ፡ ሩጫ ፡ ይመስላል ፡ አለ ፤ ንጉሡም ፦ ርሱ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነው ፥ መልካምም ፡ ወሬ ፡ ያመጣል ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 28 ፤ አኪማዐስም ፡ ጮኾ ፡ ንጉሡን ፦ ኹሉ ፡ ደኅና ፡ ኾኗል ፡ አለው ። በንጉሡም ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፦ በንጉሡ ፡ በጌታዬ ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ያነሡትን ፡ ሰዎች ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፦ ብላቴናው ፡ አቤሴሎም ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ አለ ። አኪማዐስም ፦ ኢዮአብ ፡ እኔን ፡ ባሪያኽንና ፡ የንጉሡን ፡ ባሪያ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ ሽብር ፡ አይቻለኹ ፥ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ አላወቅኹም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፦ ፈቀቅ ፡ ብለኽ ፡ ቁም ፡ አለ ፤ ርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ቆመ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 31 ፤ እንሆም ፥ ኩሲ ፡ መጣ ፤ ኩሲም ፦ እግዚአብሔር ፡ በላይኽ ፡ የተነሡትን ፡ ኹሉ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ተበቀለልኽ ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሡ ፡ ወሬ ፡ አምጥቻለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 32 ፤ ንጉሡም ፡ ኩሲን ፦ ብላቴናው ፡ አቤሴሎም ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ አለው ። ኩሲም ፦ የጌታዬ ፡ የንጉሡ ፡ ጠላቶች ፥ በክፉም ፡ የተነሡብኽ ፡ ኹሉ ፡ እንደዚያ ፡ ብላቴና ፡ ይኹኑ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

---

159 ዕብ. ፡ ኩሻ ፡ (ኩሳይ • የኩሽ ፡ ሰው ፥ ኢትዮጵያዊ) ።

ሳሙ.2 ፡ 18 ፡ 33 ፤ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ዐዘነ ፥ በበሩም ፡ ላይ ፡ ወዳለችው ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡
አለቀሰ ፤ ሲኼድም ፦ ልጄ ፡ አቤሴሎም ፡ ሆይ ፥ ልጄ ፥ ልጄ ፡ አቤሴሎም ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ ፋንታ ፡ ሞቼ ፡ ኖሮ ፡
ቢኾን ፥ ልጄ ፡ አቤሴሎም ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ይል ፡ ነበር ። ኾ ፡

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 1 ፤ ኢዮአብም ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳለቀሰና ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ እንዳለ ፡ ሰማ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ ዐዘነ ፡ ሲባል ፡ ሕዝቡ ፡ ሰምቷልና ፥ የዚያ ፡ ቀን ፡ ድል ፡
በሕዝቡ ፡ ኾሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሐዘን ፡ ተለወጠ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 3 ፤ ሕዝቡም ፡ ከሰልፍ ፡ የሸሸ ፡ ሕዝብ ፡ ዐፍሮ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ እንዲል ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡
ከተማ ፡ ተሰርቆ ፡ ገባ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ሸፈነ ፥ ንጉሡም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ ልጄ ፡ አቤሴሎም ፡ ሆይ ፥ ልጄ ፡
አቤሴሎም ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 5 ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ዛሬ ፡ ነፍስኽንና ፡ የወንዶችና ፡
የሴቶች ፡ ልጆችኽን ፡ ነፍስ ፡ የሚስቶችኽንና ፡ የቁባቶችኽን ፡ ነፍስ ፡ ያዳኑትን ፡ የባሪያዎችኽን ፡ ኾሉ ፡ ፊት ፡ ዛሬ ፡
አሳፍረኻል ፤

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ የሚጠሉኽን ፡ ትወዳለኽ ፥ የሚወዱኽንም ፡ ትጠላለኽ ። መሳፍንትኽንና ፡ ባሪያዎችኽን ፡
እንዳታስብ ፡ ዛሬ ፡ ገልጠኻል ፤ ዛሬ ፡ ኾላችን ፡ ሞተን ፡ ቢኾን ፡ ኖር ፡ አቤሴሎምም ፡ ድኖ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ ደስ ፡
ያሠኘኽ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዛሬ ፡ አያለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 7 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ተነሥተኽ ፡ ውጣ ፥ ለባሪያዎችኽም ፡ የሚያጽናናቸውን ፡ ነገር ፡
ተናገራቸው ፤ ያልወጣኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ እንዳይቀር ፡
በእግዚአብሔር ፡ እምላለኹ ፤ ይህም ፡ ከብላቴናነትኽ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ካገኘኽ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኾሉ ፡
ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ይኾንብኻል ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ ተነሥቶ ፡ በበሩ ፡ ተቀመጠ ፤ ሕዝቡም ፡ ኾሉ ፡ ንጉሡ ፡ በበሩ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡
ሰማ ፤ ሕዝቡም ፡ ኾሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ መጣ ። እስራኤልም ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሽቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 9 ፤ ሕዝቡም ፡ ኾሉ ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኾሉ ፡ ውስጥ ። ንጉሡ ፡ ከጠላቶቻችን ፡ እጅ ፡
ታድጎናል ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ አድኖናል ፤ አኹንም ፡ ስለ ፡ አቤሴሎም ፡ ከአገር ፡ ሸሽቷል ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 10 ፤ በላያችን ፡ እንዲኾን ፡ የቀባነው ፡ አቤሴሎም ፡ በሰልፍ ፡ ሞቷል ፤ አኹንም ፡ እንግዲህ ፡ ንጉሡን ፡
ለመመለስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ትላላችኹ ፧ እያለ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ይከራከር ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ለካህናቱ ፡ ለሳዶቅና ፡ ለአብያታር ፡ ልኮ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ለይሁዳ ፡
ሽማግሌዎች ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ተናገሯቸው ፦ የእስራኤል ፡ ኾሉ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ደርሷልና ፥ ንጉሡን ፡
ወደ ፡ ቤቱ ፡ ከመመለስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዘገያችኹ ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ ወንድሞቼ ፥ የዐጥንቴ ፡ ፍላጭና ፡ የሥጋዬ ፡ ቍራጭ ፡ ናችኹ ፤ እናንተ ፡ ንጉሡን ፡
ከመመለስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዘገያችኹ ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 13 ፤ ለዐማሳይም ፦ አንተ ፡ የዐጥንቴ ፡ ፍላጭና ፡ የሥጋዬ ፡ ቍራጭ ፡ አይደለኽምን ፧ በዘመንኽም ፡
ኾሉ ፡ በኢዮአብ ፡ ፋንታ ፡ በፊቴ ፡ የሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ሳትኾን ፡ ብትቀር ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፡ ይህንም ፡
ይጨምርብኝ ፡ በሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 14 ፤ የይሁዳንም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ አድርጎ ፡ አዘነበለ ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ልከው ፦ አንተ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተመለስ ፡ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፡ ተመልሶ ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ መጣ ። የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ንጉሡን ፡ ሊቀበሉ ፡ ንጉሡንም ፡ ዮርዳኖስን ፡ ሊያሻግሩ ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ መጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 16 ፤ ከብራቂምም ፡ አገር ፡ የነበረው ፡ ብንያማዊው ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፡ ከይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ዳዊትን ፡ ሊቀበል ፡ ፈጥኖ ፡ ወረደ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 17 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ብንያማውያን ፡ የኾኑ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፥ የሳኦልም ፡ ቤት ፡ ባሪያ ፡ ሲባ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስቱ ፡ ልጆችና ፡ ኻያው ፡ ባሪያዎች ፡ ነበሩ ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ፈጥነው ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 18 ፤ ታንኳውም ፡ የንጉሥን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ያሻግር ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡም ፡ ደስ ፡ ያሠኘውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይሸጋገር ፡ ነበር ። ንጉሡም ፡ ዮርዳኖስን ፡ ከተሻገረ ፡ በኋላ ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 19 ፤ ንጉሡንም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ኀጢአቴን ፡ አትቍጠርብኝ ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ በወጣኽ ፡ ቀን ፡ ባሪያኽ ፡ የበደልኹኽን ፡ አታስብብኝ ፥ ንጉሡም ፡ በልቡ ፡ አያኑረው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 20 ፤ ባሪያኽ ፡ በደለኛ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ዐውቄያለኹና ፥ እንሆ ፥ ከዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ዛሬ ፡ መጣኹ ፥ ጌታዬንም ፡ ንጉሡን ፡ ልቀበል ፡ ወረድኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 21 ፤ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ አቢሳ ፡ ግን ፦ ሳሚ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ ሰድቧልና ፥ ሞት ፡ የተገባው ፡ አይደለምን ፧ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፦ እናንተ ፡ የጽሩያ ፡ ልጆች ፥ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠላቶች ፡ ትኾኑብኛላችኹ ፧ ዛሬስ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ሊሞት ፡ ይገባልን ፧ ዛሬስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ነገሥኹ ፡ አላወቅኹምን ፧ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 23 ፤ ንጉሡም ፡ ሳሚን ፦ አትሞትም ፡ አለው ። ንጉሡም ፡ ማለለት ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 24 ፤ የሳኦልም ፡ ልጅ ፡ ሜምፊቦስቴ ፡ ንጉሡን ፡ ሊቀበል ፡ ወረደ ፤ ንጉሡም ፡ ከኼደ ፡ ዠምሮ ፡ በደኅና ፡ እስከተመለሰበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እግሩን ፡ አልጠገነም ፥ ጢሙንም ፡ አልቈረጠም ፥ ልብሱንም ፡ አላጠበም ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፡ ሊቀበለው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ። ሜምፊቦስቴ ፡ ሆይ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልወጣኽም ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፡ አለ ፦ ጌታዬን ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ባሪያዬ ፡ አታለለኝ ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ዐንካሳ ፡ ነኝና ። ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ የምቀመጥበትን ፡ አህያ ፡ ልጫን ፡ አልኹት ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ ለጌታዬ ፡ ለንጉሡ ፡ አማ ፤ አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ነኽ ፤ ደስም ፡ ያሠኘኽን ፡ አድርግ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 28 ፤ የአባቴ ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ሞት ፡ የሚገባቸው ፡ ነበሩ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ በገበታኽ ፡ በሚበሉ ፡ መካከል ፡ አስቀመጥኸኝ ፤ ለንጉሥ ፡ ደግሞ ፡ ለመናገር ፡ ምን ፡ መብት ፡ አለኝ ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፦ ነገርኽን ፡ ለምን ፡ ታበዛለኽ ፧ አንተና ፡ ሲባ ፡ ዕርሻውን ፡ ትካፈሉ ፡ ዘንድ ፡ ብያለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 30 ፤ ሜምፊቦስቴም ፡ ንጉሡን ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ከተመለሰ ፡ ርሱ ፡ ኹሉን ፡ ይውሰደው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 31 ፤ ገለዓዳዊውም ፡ ቤርዜሊ ፡ ከሮግሊም ፡ ወረደ ፤ ሊሸኘውም ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገረ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 32 ፤ ቤርዜሊም ፡ እጅግ ፡ ያረጀ ፡ የሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፡ ነበረ ፤ እጅግም ፡ ትልቅ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ ንጉሡ ፡ በመሃናይም ፡ ሳለ ፡ ይቀልበው ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 33 ፤ ንጉሡም ፡ ቤርዜሊን ፦ በኢየሩሳሌም ፡ እቀልብኽ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዕለፍ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 34 ፤ ቤርዜሊም ፡ ንጉሡን ፡ አለው ፦ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እወጣ ፡ ዘንድ ፡ ከሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ቀረኝ ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 35 ፤ ዛሬ ፡ የሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ፤ መልካሙንና ፡ ክፉውን ፡ መለየት ፡ እችላለኹን ፧ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ የምበላውንና ፡ የምጠጣውን ፡ ጣዕሙን ፡ መለየት ፡ እችላለኹን ፧ የወንዱንና ፡ የሴቲቱን ፡ ዘፈን ፡ ድምፅ ፡ መስማት ፡ እችላለኹን ፧ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ እከብድብኻለኹ ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 36 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግሬ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ጥቂት ፡ ልኼድ ፡ ነበር ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ወረታ ፡ ለምን ፡ ይመልስልኛል ፧

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 37 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ተመልሼ ፡ በከተማዬ ፡ በአባቴና ፡ በእናቴ ፡ መቃብር ፡ አጠገብ ፥ እባክኽ ፥ ልሙት ። ነገር ፡ ግን ፥ ባሪያኽን ፡ ከመዓምን ፡ እይ ፤ ርሱ ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ይለፍ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኝኽንም ፡ ለርሱ ፡ አድርግ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 38 ፤ ንጉሡም ፦ ከመዓም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይለፍ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኝኽንም ፡ አደርግለታለኹ ፤ አንተም ፡ ከእኔ ፡ የምትሻውን ፡ ኹሉ ፡ አደርግልኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 39 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገረ ፥ ንጉሡም ፡ ተሻገረ ፤ ንጉሡም ፡ ቤርዜሊን ፡ ሳመው ፥ መረቀውም ፤ ወደ ፡ ስፍራውም ፡ ተመለሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 40 ፤ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ተሻገረ ፥ ከመዓምም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፤ የይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞም ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ እኩሌታ ፡ ንጉሡን ፡ አሻገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 41 ፤ እንሆም ፥ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ መጡ ፥ ንጉሡንም ፦ ወንድሞቻችን ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ ሰረቁኽ ፧ ንጉሡንም ፡ ቤተ ፡ ሰቡንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የዳዊትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዮርዳኖስን ፡ አሻገሩ ፧ አሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 42 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ መልሰው ፦ ንጉሡ ፡ ለእኛ ፡ ቅርባችን ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ምን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ትቈጣላችኹ ፧ በእውኑ ፡ ከንጉሡ ፡ አንዳች ፡ በልተናልን ፧ ወይስ ፡ ርሱ ፡ በረከት ፡ ሰጥቶናልን ፧ አሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 19 ፡ 43 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ መልሰው ፦ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ለእኛ ፡ ዐሥር ፡ ክፍል ፡ አለን ፥ በዳዊትም ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ መብት ፡ አለን ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ናቃችኹን ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ ንጉሣችንን ፡ ለመመለስ ፡ ቀድሞ ፡ ምክር ፡ አልጠየቃችኹንም ፧ አሉ ። የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ከእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ቃል ፡ ይልቅ ፡ ጠነከረ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 1 ፤ እንዲሀም ፡ ኾነ ፤ አንድ ፡ ብንያማዊ ፡ የቢክሪ ፡ ልጅ ፡ ስሙ ፡ ሳቤዔ ፡ የሚባል ፡ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፦ ከዳዊት ፡ ዘንድ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ የለንም ፥ ከእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እያንዳንድኽ ፡ ወደ ፡ ድንኳንኽ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ነፋ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 2 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከዳዊት ፡ ተለይተው ፡ የቢክሪን ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔን ፡ ተከተሉ ፤ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ዠምረው ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስኪደርሱ ፡ ንጉሣቸውን ፡ ተከተሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ መጣ ፤ ንጉሡም ፡ ቤቱን ፡ ሊጠብቁ ፡ የተዋቸውን ፡ ዐሥሩን ፡ ቁባቶች ፡ ወስዶ ፡ ለጠባቂ ፡ ሰጣቸው ፥ ቀለብም ፡ ሰጣቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አልገባም ፤ በቤት ፡ ተዘግተው ፡ እስኪሞቱም ፡ ድረስ ፡ ባልቴቶች ፡ ኾነው ፡ ተቀመጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ዐማሳይን ፦ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ጥራልኝ ፥ አንተም ፡ ዐብረኽ ፡ በዚህ ፡ ኹን ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 5 ፤ ዐማሳይም ፡ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይጠራ ፡ ዘንድ ፡ ኼደ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ የተቀጠረውን ፡ ቀን ፡ አሳልፎ ፡ ዘገየ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ አቢሳን ፦ አኹን ፡ ከአቤሴሎም ፡ ይልቅ ፡ የሚጐዳን ፡ የቢክሪ ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ አግኝቶ ፡ ከዐይናችን ፡ እንዳያመልጥ ፥ አንተ ፡ የጌታኽን ፡ ባሪያዎች ፡ ወስደኽ ፡ አሳደው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 7 ፤ አቢሳንም ፡ ተከትለው ፡ የኢዮአብ ፡ ሰዎች ፡ ከሊታውያንም ፡ ፈሊታውያንም ፡ ኀያላንም ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ፤ የቢክሪንም ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔን ፡ ለማሳደድ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 8 ፤ በገባዖንም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ድንጋይ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዐማሳይ ፡ ሊገናኛቸው ፡ መጣ ፤ ኢዮአብም ፡ የሰልፍ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፥ በላዩም ፡ መታጠቂያ ፡ ነበረ ፥ በወገቡም ፡ ላይ ፡ ሰገባ ፡ ያለው ፡ ሰይፍ ፡ ታጥቆ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ሲራመድ ፡ ሰይፉ ፡ ወደቀ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 9 ፤ ኢዮአብም ፡ ዐማሳይን ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ ደኅና ፡ ነኽን ፧ አለው ፡ ኢዮአብም ፡ ዐማሳይን ፡ የሚስም ፡ መስሎ ፡ በቀን ፡ እጁ ፡ ጢሙን ፡ ያዘው ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 10 ፤ ዐማሳይ ፡ ግን ፡ በኢዮአብ ፡ እጅ ፡ ከነበረው ፡ ሰይፍ ፡ አልተጠነቀቀም ፡ ነበር ፤ ኢዮአብም ፡ ሆዱን ፡ ወጋው ፥ አንገቱንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዘረገፈው ፤ ኹለተኛም ፡ አልወጋውም ፥ ሞተም ። ኢዮአብና ፡ ወንድሙ ፡ አቢሳ ፡ የቢክሪን ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔን ፡ አሳደዱ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 11 ፤ ከኢዮአብም ፡ ብላቴናዎች ፡ አንዱ ፡ በዐማሳይ ፡ ሬሳ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፦ ለኢዮአብ ፡ ወዳጅ ፡ የሚኾን ፡ ለዳዊትም ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ኢዮአብን ፡ ይከተል ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 12 ፤ ዐማሳይም ፡ በመንገድ ፡ መካከል ፡ ወድቆ ፡ በደሙ ፡ ላይ ፡ ይንከባለል ፡ ነበር ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚመጣ ፡ ኹሉ ፡ ሲቆም ፡ አይቷልና ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ዐማሳይን ፡ ከመንገድ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ፈቀቅ ፡ አደረገው ፥ በልብስም ፡ ከደነው ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 13 ፤ ከመንገድ ፡ ራቅ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የቢክሪን ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔን ፡ ለማሳደድ ፡ ኢዮአብን ፡ ተከትሎ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 14 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አቤል ፥ ወደ ፡ ቤትመዓካ ፥ ወደ ፡ ቤሪም ፡ ኹሉ ፡ ዐለፈ ፤ ሰዎችም ፡ ደግሞ ፡ ተሰብስበው ፡ ተከተሉት ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 15 ፤ በቤትመዓካ ፡ ባለ ፡ በአቤልም ፡ መጥተው ፡ ከበቡት ፥ በከተማዩ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ቅጥሯ ፡

ድረስ ፡ የዐፈርን ፡ ድልድል ፡ ደለደሉ ፤ ቅጥሩንም ፡ ያፈርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከኢዮአብ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይደባደቡ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 16 ፤ ከከተማዪቱም ፡ አንዲት ፡ ብልኀተኛ ፡ ሴት ፦ ስሙ ፥ ስሙ ፤ ኢዮአብንም ፦ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ ቅረብ ፡ በሉት ፡ ስትል ፡ ጮኸች ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ርሷም ፡ ቀረበ ፤ ሴቲቱም ፦ ኢዮአብ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለች ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላት ። ርሷም ፦ የባሪያኽን ፡ ቃል ፡ ስማ ፡ አለችው ። ርሱም ፦ እሰማለኹ ፡ አላት ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 18 ፤ ርሷም ፦ ቀድሞ ፦ የሚጠይቅ ፡ በአቤል ፡ ዘንድ ፡ ይጠይቅ ፡ ይባል ፡ ነበር ፤ እንዲሁም ፡ ነገሩ ፡ ይፈጸም ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 19 ፤ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ሰላምንና ፡ እውነትን ፡ ከሚወዱ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ አንተ ፡ በእስራኤል ፡ ያለችውን ፡ ከተማና ፡ እናት ፡ ለማፍረስ ፡ ትሻለኽ ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ርስት ፡ ትውጣለኽ ፧ ብላ ፡ ተናገረች ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 20 ፤ ኢዮአብም ፡ መልሶ ፦ ይህ ፡ መዋጥና ፡ ማጥፋት ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ፤

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 21 ፤ ነገሩ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ከተራራማው ፡ ከኤፍሬም ፡ አገር ፡ የሚኾን ፡ የቢክሪ ፡ ልጅ ፡ ሳቤዔ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ አነሣ ፤ ርሱን ፡ ብቻውን ፡ ስጡኝ ፥ እኔም ፡ ከከተማዪቱ ፡ እርቃለኹ ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡ ኢዮአብን ፦ እንሆ ፥ ራሱ ፡ ከቅጥር ፡ ላይ ፡ ይጣልልኻል ፡ አለችው ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 22 ፤ ሴቲቱም ፡ በብልኀቷ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ኼደች ፤ እነርሱም ፡ የቢክሪን ፡ ልጅ ፡ የሳቤዔን ፡ ራስ ፡ ቈርጠው ፡ ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ጣሉት ። ርሱም ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ነፋ ፥ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ከከተማዪቱ ፡ ርቆ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ኼደ ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 23 ፤ ኢዮአብም ፡ በእስራኤል ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ የዩዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ በከሊታውያንና ፡ በፈሊታውያን ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 24 ፤ አዶኒራምም ፡ ግብር ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ፤ የአኒሉድም ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ፤

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 25 ፤ ሱሳም ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ፤ ሳዶቅና ፡ አብያታርም ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ፤

ሳሙ.2 ፡ 20 ፡ 26 ፤ የኢያዕር ፡ ሰውም ፡ ዒራስ ([160]) ፡ ለዳዊት ፡ አማካሪ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 1 ፤ በዳዊትም ፡ ዘመን ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ቀጥሎ ፡ ራብ ፡ ኾነ ፤ ዳዊትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፦ የገባዖንን ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ገደለ ፡ በሳኦልና ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ደም ፡ አለበት ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ የገባዖንን ፡ ሰዎች ፡ ጠራ ፤ የገባዖን ፡ ሰዎችም ፡ ከአሞራውያን ፡ የተረፉ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ አልነበሩም ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ምለውላቸው ፡ ነበር ፤ ሳኦል ፡ ግን ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ ለይሁዳ ፡ ስለ ፡ ቀና ፡ ሊገድላቸው ፡ ወዶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ የገባዖንን ፡ ሰዎች ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ርስት ፡ ትባርኩ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግላችኹ ፧ ማስተስረያውስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 4 ፤ የገባዖን ፡ ሰዎችም ፦ በእኛና ፡ በሳኦል ፡ ወይም ፡ በእኛና ፡ በቤቱ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ የብርና ፡

---

160 ዕብ. ፥ ዒይራ ።

የወርቅ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ከእስራኤልም ፡ ወገን ፡ እኛ ፡ የምንገድለው ፡ የለም ፡ አሉት ። ርሱም ፦ የምትናገሩትን ፡ አደርግላችኋለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 5 ፤ ንጉሡንም ፦ እኛን ፡ ካጠፋ ፥ በእስራኤልም ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ እንዳንቀመጥ ፡ መፍረሳችንን ፡

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 6 ፤ ካሰበው ፡ ሰው ፡ ልጆች ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጠንና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተመረጠው ፡ በሳኦል ፡ አገር ፡ በጊብዓ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንሰቅላቸዋለን ፡ አሉት ። ንጉሡም ፦ እሰጣችኋለኹ ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 7 ፤ ንጉሡም ፡ በሳኦል ፡ ልጅ ፡ በዮናታንና ፡ በዳዊት ፡ መካከል ፡ ስለነበረው ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ የሳኦልን ፡ ልጅ ፡ የዮናታንን ፡ ልጅ ፡ ሜምፊቦስቴን ፡ አዳነ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ ለሳኦል ፡ የወለደቻቸውን ፡ የኢዮሄል ፡ ልጅ ፡ የሪጽፋን ፡ ኹለቱን ፡ ልጆች ፡ ሄርሞንንና ፡ ሜምፊቦስቴን ፡ ለመሐላታዊውም ፡ ለቤርዜሊ ፡ ልጅ ፡ ለኤስድሪኤል ፡ የወለደቻቸውን ፡ የሳኦልን ፡ ልጅ ፡ የሜሮብን ፡ ዐምስቱን ፡ ልጆች ፡ ወሰደ ፥

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 9 ፤ ለገባዖንም ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ ሰቀሏቸው ፥ ሰባቱም ፡ በአንድነት ፡ ወደቁ ፤ እኽል ፡ በሚታጨድበት ፡ ወራት ፡ በገብሱ ፡ መከር ፡ መገመሪያ ፡ ተገደሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 10 ፤ የኢዮሄልም ፡ ልጅ ፡ ሪጽፋ ፡ ማቅ ፡ ወስዳ ፡ ከመከር ፡ ወራት ፡ ዝምሮ ፡ ዝናብ ፡ ከሰማይ ፡ እስኪዘንብ ፡ ድረስ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ዘረጋችው ፤ በቀንም ፡ ወፎች ፡ በሌሊትም ፡ አራዊት ፡ ያርፉባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልተወችም ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 11 ፤ የሳኦልም ፡ ቁባት ፡ የኢዮሄል ፡ ልጅ ፡ ሪጽፋ ፡ ያደረገችውን ፡ ለዳዊት ፡ ነገሩት ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 12 ፤ ዳዊትም ፡ ኼደ ፥ ሳኦልንም ፡ በጊልቦዓ ፡ በገደሉ ፡ ጊዜ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ከሰቀሏቸው ፡ ስፍራ ፡ ከቤትሳን ፡ አደባባይ ፡ ከሰረቁት ፡ ከኢያቢስ ፡ ገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ የሳኦልንና ፡ የልጁን ፡ የዮናታንን ፡ ዐጥንት ፡ ወሰደ ፤

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 13 ፤ ከዚያም ፡ የሳኦልንና ፡ የልጁን ፡ የዮናታንን ፡ ዐጥንት ፡ ይዞ ፡ መጣ ፤ የተሰቀሉትንም ፡ ሰዎች ፡ ዐጥንት ፡ ሰበሰቡ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 14 ፤ የሳኦልንና ፡ የልጁን ፡ የዮናታንን ፡ ዐጥንት ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ በጼላ ፡ በአባቱ ፡ በቂስ ፡ መቃብር ፡ ቀበሩት ፤ ንጉሡም ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አገሩ ፡ የተለመነውን ፡ ሰማ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 15 ፤ በፍልስጥኤማውያንና ፡ በእስራኤልም ፡ መካከል ፡ ደግሞ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ወረዱ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ ዳዊትም ፡ ደከመ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 16 ፤ ከራፋይም ፡ ወገን ፡ የነበረው ፡ ይሽቢብኖብ ፡ ዳዊትን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ፤ የጦሩም ፡ ሚዛን ፡ ክብደት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ናስ ፡ ነበረ ፥ ዐዲስም ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ታጥቆ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 17 ፤ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ አቢሳ ፡ አዳነው ፥ ፍልስጥኤማዊውንም ፡ መቶ ፡ ገደለው ። ያን ፡ ጊዜም ፡ የዳዊት ፡ ሰዎች ፦ አንተ ፡ የእስራኤልን ፡ መብራት ፡ እንዳታጠፋ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለሰልፍ ፡ አትወጣም ፡ ብለው ፡ ማሉለት ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 18 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በጎብ ፡ ላይ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ ኾነ ፥ ኩሳታዊውም ፡ ሴቦካይ ፡ ከራፋይም ፡ ወገን ፡ የነበረውን ፡ ሳፍን ፡ ገደለ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 19 ፤ ደግሞም ፡ በጎብ ፡ ላይ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ፤ የቤተ ፡ ልሔማዊውም ፡ የየዓሬኦርጊም ፡ ልጅ ፡ ኤልያናን ፡ የጦሩ ፡ የቦ ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ የነበረውን ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ ጎልያድን ፡ ገደለ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 20 ፤ ደግሞም ፡ በጌት ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ ኾነ ፤ በዚያም ፡ በእጁና ፡ በእግሩ ፡ ስድስት ፡ ስድስት ፡
ዥላዥሉ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ጣቶች ፡ የነበሩት ፡ አንድ ፡ ረዥም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከራፋይም ፡ የተወለደ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 21 ፤ እስራኤልንም ፡ በተገዳደረ ፡ ጊዜ ፥ የዳዊት ፡ ወንድም ፣ የሳማ ፡ ልጅ ፣ ዮናታን ፡ ገደለው ።

ሳሙ.2 ፡ 21 ፡ 22 ፤ እነዚያም ፡ አራቱ ፡ በጌት ፡ ውስጥ ፡ ከራፋይም ፡ የተወለዱ ፡ ነበሩ ፤ በዳዊትም ፡
እጅ ፣ በባሪያዎቹም ፡ እጅ ፡ ወደቁ ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሳኦል ፡ እጅና ፡ ከጠላቶቹ ፡ እጅ ፡ ዥሉ ፡ ባዳነው ፡ ቀን ፡ የዚህን ፡
ቅኔ ፡ ቃል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተናገረ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ አለቴ ፣ ዐምባዬ ፣ መድኀኒቴ ፡ ነው ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂዬ ፡ ነው ፥ በርሱም ፡ እታመናለኹ ፤ ጋሻዬና ፡ የረድኤቴ ፡
ቀንድ ፥ መጠጊያዬና ፡ መሸሸጊያዬ ፥ መድኀኒቴ ፡ ሆይ ፥ ከግፍ ፡ ሥራ ፡ ታድነኛለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 4 ፤ ምስጋና ፡ የሚገባውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጠራለኹ ፤ ከጠላቶቼም ፡ እድናለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 5 ፤ የሞት ፡ ጣር ፡ ያዘኝ ፤ የዐመፅ ፡ ፈሳሽም ፡ አስፈራኝ ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 6 ፤ የሲኦል ፡ ጣር ፡ ከበበኝ ፤ የሞት ፡ ወጥመድ ፡ ደረሰብኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 7 ፤ በጨነቀኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራኹት ፥ ወደ ፡ አምላኬም ፡ ጮኽኹ ፤ ከመቅደሱም ፡
ቃሌን ፡ ሰማኝ ፥ ጩኸቴም ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ጐሮው ፡ ገባ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 8 ፤ ምድርም ፡ ተንቀጠቀጠች ፥ ተናወጠችም ፥ የሰማዮችም ፡ መሠረቶች ፡
ተነቃነቁ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቷልና ፥ ተንቀጠቀጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 9 ፤ ከቀኑጣው ፡ ጢስ ፡ ወጣ ፥ ከአፉም ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፤ ፍምም ፡ ከርሱ ፡ በራ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 10 ፤ ሰማዮችን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ ፥ ወረደም ፤ ጨለማም ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 11 ፤ በኪሩብም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በረረ ፤ በነፋስም ፡ ክንፍ ፡ ኾኖ ፡ ታየ ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 12 ፤ መሰወሪያውን ፡ ጨለማ ፥ በዙሪያውም ፡ የነበረውን ፡ ድንኳን ፥ በደመና ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡
የጨለማ ፡ ውሃ ፡ አደረገ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 13 ፤ በፊቱም ፡ ካለው ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ፍም ፡ ተቃጠለ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሰማያት ፡ አንጐደጐደ ፥ ልዑልም ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 15 ፤ ፍላጻውን ፡ ላከ ፥ በተናቸውም ፡ መብረቆችን ፡ ላከ ፥ አወካቸውም ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 16 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘለፋ ፥ ከመዓቱም ፡ መንፈስ ፡ እስትንፋስ ፡ የተነሣ ፥ የባሕር ፡ ፈሳሾች ፡
ታዩ ፥ የዓለም ፡ መሠረቶችም ፡ ተገለጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 17 ፤ ከላይ ፡ ሰደደ ፥ ወሰደኝም ፤ ከብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ አወጣኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 18 ፤ ከብርቱዎች ፡ ጠላቶቼ ፥ ከሚጠሉኝም ፡ አዳነኝ ፤ በርትተውብኝ ፡ ነበርና ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 19 ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ደረሱብኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ደገፉዬ ፡ ኾነ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ስፍራም ፡ አወጣኝ ፤ ወዶኛልና ፥ አዳነኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ፡ ይከፍለኛል ፤ እንደ ፡ እጄ ፡ ንጽሕና ፡ ይመልስልኛል ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 22 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ጠብቄያለኹና ፥ በአምላኬም ፡ አላመፅኹምና ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 23 ፤ ፍርዱ ፡ ኹሉ ፡ በፊቴ ፡ ነበረና ፤ ከሥርዐቱም ፡ አልራቅኹምና ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 24 ፤ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቅን ፡ ነበርኹ ፥ ከኀጢአቴም ፡ ተጠበቅኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ፥ እንደ ፡ እጄም ፡ ንጽሕና ፡ በዐይኖቹ ፡ ፊት ፡ መለሰልኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 26 ፤ ከቸር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ቸር ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤ ከቅን ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ቅን ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 27 ፤ ከንጹሕ ፡ ጋራ ፡ ንጹሕ ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤ ከጠማማም ፡ ጋራ ፡ ጠማማ ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 28 ፤ አንተ ፡ የተጠቃውን ፡ ሕዝብ ፡ ታድናለኽና ፤ የትዕቢተኞችን ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ ታዋርዳለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 29 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ መብራቴ ፡ ነኽና ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጨለማዬን ፡ ያበራል ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 30 ፤ ባንተ ፡ ኀይል ፡ በጭፍራ ፡ ላይ ፡ እሮጣለኹና ፤ በአምላኬም ፡ ቅጥሩን ፡ እዘላለኹና ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 31 ፤ የአምላክ ፡ መንገድ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የነጠረ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ ለሚታመኑት ፡ ኹሉ ፡ ጋሻ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 32 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ከአምላካችንስ ፡ በቀር ፡ ዐምባ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 33 ፤ ኀይልን ፡ የሚያስታጥቀኝ ፥ መንገዴንም ፡ የሚያቃና ፥

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 34 ፤ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ብሔር ፡ እግሮች ፡ የሚያበረታ ፥ በኰረብታዎችም ፡ የሚያቆመኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 35 ፤ እጆቼን ፡ ሰልፍ ፡ ያስተምራል ፤ በክንዴም ፡ የናስ ፡ ቀስት ፡ እገትራለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 36 ፤ የማዳንኽንም ፡ ጋሻ ፡ ሰጠኸኝ ፤ ተግሣጽኽም ፡ አሳደገኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 37 ፤ አረማመዴን ፡ በበታቼ ፡ አሰፋኽ ፥ እግሮቼም ፡ አልተንሸራተቱም ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 38 ፤ ጠላቶቼን ፡ አሳድዳቸዋለኹ ፥ አጠፋቸውማለኹ ፤ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ አልመለስም ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 39 ፤ አስጨንቃቸዋለኹ ፡ መቆምም ፡ አይችሉም ፥ ከእግሬም ፡ በታች ፡ ይወድቃሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 40 ፤ ለሰልፍም ፡ ኀይልን ፡ ታስታጥቀኛለኽ ፤ በላዬ ፡ የቆሙትን ፡ በበታቼ ፡ ታስገዛቸዋለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 41 ፤ የጠላቶቼን ፡ ዝርባ ፡ ሰጠኸኝ ፥ የሚጠሉኝንም ፡ አጠፋኻቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 42 ፤ ጮኹ ፥ የሚረዳቸውም ፡ አልነበረም ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ አልሰማቸውምም ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 43 ፤ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ ፈጨኋቸው ፤ እንደአደባባይ ፡ ጭቃም ፡ ረገጥኋቸው ፥ ደቀደቅኋቸውም ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 44 ፤ ከሕዝብ ፡ ክርክር ፡ ታድነኛለኽ ፤ የአሕዛብም ፡ ራስ ፡ አድርገኽ ፡ ትሾመኛለኽ ፤ የማላውቀው ፡ ሕዝብም ፡ ይገዛልኛል ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 45 ፤ የባዕድ ፡ ልጆች ፡ ደለሉኝ ፤ በጕሮሮ ፡ ሰምተው ፡ ተገዙልኝ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 46 ፤ የባዕድ ፡ ልጆች ፡ እየጠፉ ፡ ይኼዳሉ ፤ ከተዘጉ ፡ ስፍሮች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ይወጣሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 47 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፥ ጠባቂዬም ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፤ የመድኀኒቴ ፡ ጠባቂ ፡ አምላኬ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይበል ፤

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 48 ፤ በቀሌን ፡ የሚመልስልኝ ፡ አምላክ ፥ አሕዛብን ፡ በበታቼ ፡ የሚያስገዛ ፥

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 49 ፤ ከጠላቶቼ ፡ የሚያወጣኝ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ በእኔም ፡ ላይ ፡ ከቆሙ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ታደርገኛለኽ ፤ ከግፈኛ ፡ ሰው ፡ ታድነኛለኽ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 50 ፤ አቤቱ ፥ ስለዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ ለስምኽም ፡ እዘምራለኹ ።

ሳሙ.2 ፡ 22 ፡ 51 ፤ የንጉሡን ፡ መድኀኒት ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋል ፤ ቸርነቱንም ፡ ለቀባው ፥ ለዳዊትና ፡ ለዘሩ ፥ ለዘለዓለም ፡ ይሰጣል ።

_____መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። _____

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 1 ፤ የዳዊትም ፡ የመጨረሻ ፡ ቃሉ ፡ ይህ ፡ ነው ። ከፍ ፡ ከፍ ፡ የተደረገው ፥ በያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ የተቀባው ፥ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ባለቅኔ ፡ የኾነ ፥ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ የዳዊት ፡ ንግግር ፤

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ተናገረ ፤ ቃሉም ፡ በአንደበቴ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 3 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ተናገረኝ ፤ የእስራኤል ፡ ጠባቂ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በሰው ፡ ላይ ፡ በጽድቅ ፡ የሚሠለጥን ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፍርሀት ፡ የሚነግሥ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 4 ፤ ርሱ ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ አወጣጥ ፥ በጧትም ፡ ያለ ፡ ደመና ፡ እንደሚደምቅ ፥ ከዝናብ ፡ በኋላ ፡ ከምድር ፡ እንደሚበቅል ፡ ልምላሜ ፡ ይኾናል ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 5 ፤ በእውኑ ፡ ቤቴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ አይደለምን ፧ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ ቅንና ፡ ጽኑ ፡ የኾነውን ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጓል ፤ መድኀኒቴንና ፡ ፈቃዴን ፡ ኹሉ ፡ ያበቅላል ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 6 ፤ ዐመፀኞች ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ በእጁ ፡ እንደማይዘው ፥ እንደተጣለ ፡ ሾኽ ፡ ናቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 7 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ይነካው ፡ ዘንድ ፡ ቢወደድ ፥ በእጁ ፡ ብረትና ፡ የጦሩን ፡ የቦ ፡ ይይዛል ፤ በሥራቸውም ፡ በእሳት ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃጠላሉ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 8 ፤ የዳዊት ፡ ኀያላን ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። የአለቃዎች ፡ አለቃ ፡ የኾነ ፡ ከነዓናዊው ፡ ኢያቡስቴ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ ጦሩን ፡ አንሥቶ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ያኽል ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ገደለ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 9 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የአሖሓዊው ፡ የዱዲ ፡ ልጅ ፡ ኤልያናን ፡ ነበረ ፤ ለሰልፍ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ በተገዳደሩ ፡ ጊዜ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ከሦስቱ ፡ ኀያላን ፡ አንዱ ፡ ርሱ ፡ ነበረ ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ተመለሱ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 10 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ተነሥቶ ፡ እጁ ፡ እስኪደክምና ፡ ከሰይፉ ፡ ጋራ ፡ እስኪጣበቅ ፡ ድረስ ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ መታ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ መድኀኒት ፡ አደረገ ፤ ሕዝቡም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡

ምርኮ ፡ ለመግፈፍ ፡ ብቻ ፡ ተመለሰ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 11 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የአሮዳዊው ፡ የአጌ ፡ ልጅ ፡ ሳማ ፡ ነበረ ። ፍልስጥኤማውያንም ፡ ምስር ፡ በሞላበት ፡ ዕርሻ ፡ በአንድነት ፡ ኾነው ፡ ተከማችተው ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ በዕርሻው ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ጠበቀ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ ገደለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ታላቅ ፡ መድኀኒት ፡ አደረገ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 13 ፤ ከሠላሳውም ፡ አለቃዎች ፡ ሦስቱ ፡ ወርደው ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ወደዓዶላም ፡ ዋሻ ፡ መጡ ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፍሮ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ዳዊት ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ፥ የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፦ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡ ውሃ ፡ ማን ፡ ባጠጣኝ ፧ ብሎ ፡ ተመኘ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 16 ፤ ሦስቱም ፡ ኀያላን ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ሰራዊት ፡ ቀደው ፡ ኼዱ ፥ በበሩም ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡ ውሃ ፡ ቀዱ ፥ ይዘውም ፡ ለዳዊት ፡ አመጡለት ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሊጠጣ ፡ አልወደደም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ አፍሶ ፦

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ ይህን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ፤ በነፍሳቸው ፡ ደፍረው ፡ የኼዱ ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ አይደለምን ፧ ብሎ ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ። ሦስቱ ፡ ኀያላን ፡ ያደረጉት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 18 ፤ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብ ፡ ወንድም ፡ አቢሳ ፡ የሠላሳው ፡ አለቃ ፡ ነበረ ። ርሱም ፡ ጦሩን ፡ በሦስቱ ፡ መቶ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ ገደላቸው ፤ ስሙም ፡ እንደ ፡ ሦስቱ ፡ ተጠርቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 19 ፤ ርሱ ፡ በሠላሳው ፡ መካከል ፡ የከበረ ፡ አልነበረምን ፧ ስለዚህ ፡ አለቃቸው ፡ ኾኖ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 20 ፤ በቀብጽኤል ፡ የነበረው ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ያደረገው ፡ የጽኑዕ ፡ ሰው ፡ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ የሞዐባዊውን ፡ የቀብስኤልን ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ገደለ ፤ በዐመዳዩም ፡ ወራት ፡ ወርዶ ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ አንበሳ ፡ ገደለ ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 21 ፤ ረኧሙንም ፡ ግብጻዊ ፡ ሰው ፡ ገደለ ፤ ግብጻዊው ፡ በእጁ ፡ ጦር ፡ ነበረው ፤ በናያስ ፡ ግን ፡ በትር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወረደ ፥ ከግብጻዊውም ፡ እጅ ፡ ጦሩን ፡ ነቅሎ ፡ በገዛ ፡ ጦሩ ፡ ገደለው ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 22 ፤ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ስሙም ፡ እንደ ፡ ሦስቱ ፡ ኀያላን ፡ ተጠርቶ ፡ ነበር ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 23 ፤ ከሠላሳውም ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ። ዳዊትም ፡ በክብር ፡ ዘበኞቹ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 24 ፤ የኢዮአብም ፡ ወንድም ፡ ዐሳሄል ፡ በሠላሳው ፡ መካከል ፡ ነበረ ፥ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ሰው ፡ የዱዲ ፡

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 25 ፤ ልጅ ፡ ኤልያናን ፥ አሮዳዊው ፡ ሳማ ፥ ሐሮዳዊው ፡ ኤሊቃ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 26 ፤ ፈልጣዊው ፡ ሴሌስ ፥ የቴቁሐዊው ፡ የዒስካ ፡ ልጅ ፡ ዒራስ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 27 ፤ ዓናቶታዊው ፡ አቢዔዜር ፥ ኩሳታዊው ፡ ምቡናይ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 28 ፤ አሖሓዊው ፡ ጸልሞን ፥ ነጦፋዊው ፡ ኖኤሬ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 29 ፤ የነጦፋዊው ፡ የበዓና ፡ ልጅ ፡ ሔሌብ ፥ ከብንያም ፡ ወገን ፡

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 30 ፤ ከጊብዓ ፡ የሪባይ ፡ ልጅ ፡ ኢታይ ፥ ጲርዓቶናዊው ፡ በናያስ ፥ የገዓስ ፡ ወንዝ ፡ ሰው ፡ ሂዳይ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 31 ፤ ዐረባዊው ፡ አቢዓልቦን ፥ በርሑማዊው ፡ ዓዝሞት ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 32 ፤ ሻዓልቦናዊው ፡ ኤሊያሕባ ፥ የአሳን ፡ ልጆች ፥ ዮናታን ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 33 ፤ አሮዳዊው ፡ ሳማ ፡ የአሮዳዊው ፡ የአራር ፡ ልጅ ፡ አምናን ([161]) ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 34 ፤ የማዕካታዊው ፡ ልጅ ፡ የአሐስባይ ፡ ልጅ ፡ ኤሌፋላት ፥ የጊሎናዊው ፡ የአኪጦፌል ፡ ልጅ ፡ ኤልያብ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 35 ፤ ቀርሜሎሳዊው ([162]) ፡ ሐጽሮ ፥ አርባዊው ፡ ፈዓራይ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 36 ፤ የሱባ ፡ ሰው ፡ የናታን ፡ ልጅ ፡ ይግአል ፥ ጋዳዊው ፡

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 37 ፤ ባኒ ፥ የጽሩያ ፡ ልጅ ፣ የኢዮአብ ፡ ጋሻ ፡ ዣግሬዎች ፥ አሞናዊው ፡ ጼሌቅ ፥ ብኤሮታዊው ፡

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 38 ፤ ነሃራይ ፥ ይትራዊው ፡ ዒራስ ፥ ይትራዊው ፡ ጋሬብ ፥

ሳሙ.2 ፡ 23 ፡ 39 ፤ ኬጢያዊው ፡ ኦርዮ ፤ ኹሉ ፡ በኹሉ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ናቸው ።

መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 1 ፤ ደግሞም ፡ የ**እግዚአብሔር** ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ ዳዊትንም ፦ ኺድ ፥ እስራኤልንና ፡ ይሁዳን ፡ ቍጠር ፡ ብሎ ፡ በላያቸው ፡ አስነሣው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአብንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ የሰራዊት ፡ አለቃዎች ። የሕዝቡን ፡ ድምር ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከዳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ ተመላለሱ ፥ ሕዝቡንም ፡ ቍጠሯቸው ፡ አላቸው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 3 ፤ ኢዮአብም ፡ ንጉሡን ፦ የጌታዬ ፡ የንጉሡ ፡ ዐይን ፡ እያየ ፡ አምላክኽ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ዛሬ ፡ ካለው ፡ ሕዝብ ፡ መጠን ፡ በላይ ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ይጨምርበት ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ይወዳል ፧ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የንጉሡ ፡ ቃል ፡ በኢዮአብና ፡ በሰራዊቱ ፡ አለቃዎች ፡ ላይ ፡ አሸነፈ ። ኢዮአብና ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃዎችም ፡ የእስራኤልን ፡ ሕዝብ ፡ ይቈጥሩ ፡ ዘንድ ፡ ከንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 5 ፤ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻገሩ ፤ በጋድ ፡ ሸለቆ ፡ መካከል ፡ ባለችው ፡ በኢያዜር ፡ ከተማ ፡ ቀኝ ፡ በኩል ፡ በዐሮዔር ፡ ላይ ፡ ሰፈሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ገለዓድም ፡ ወደተባሰን ፡ አዳሰይ ፡ አገር ፡ መጡ ፤ ወደ ፡ ዳንየዓንም ፡ ደረሱ ፥ ወደ ፡ ሲዶናም ፡ ዞሩ ፥

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 7 ፤ ወደጢሮስም ፡ ምሽግ ፡ ወደዔዊያውያንና ፡ ወደከነዓናውያንም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፤ በይሁዳም ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ በቤርሳቤሕ ፡ ወጡ ።

---

161 ዕብ. ፥ አሒያም ፡ (የእናት ፡ ወንድም)

162 ዕብ. ፥ ከርመሊይ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 8 ፤ በአገሪቱም ፡ ዙሉ ፡ ላይ ፡ ተመላልሰው ፡ ከዘጠኝ ፡ ወርና ፡ ከኻያ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 9 ፤ ኢዮአብም ፡ የሕዝቡን ፡ ቍጥር ፡ ድምር ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጠ ፤ በእስራኤልም ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 10 ፤ ሕዝቡንም ፡ ከቈጠረ ፡ በኋላ ፡ ዳዊትን ፡ ልቡ ፡ መታው ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፦ ባደረግኹት ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ በድያለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ታላቅ ፡ ስንፍና ፡ አድርጌያለኹና ፡ የባሪያኽን ፡ ኀጢአት ፡ ታርቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ ማልዶ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደዳዊት ፡ ባለራእይ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ጋድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 12 ፤ ኺድ ፡ ለዳዊት ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሦስት ፡ ነገሮች ፡ በፊትኽ ፡ አኖራለኹ ፤ አደርግብኽ ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ አንዱን ፡ ምረጥ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 13 ፤ ጋድም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥቶ ፦ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ራብ ፡ በአገርኽ ፡ ላይ ፡ ይምጣብኽን ∴ ወይስ ፡ ጠላቶችኽ ፡ እያሳደዱኽ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ከነርሱ ፡ ትሸሽን ∴ ወይስ ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ ቸነፈር ፡ በአገርኽ ፡ ላይ ፡ ይኹን ∴ አኹንም ፡ ለላከኝ ፡ ምን ፡ መልስ ፡ እንደምሰጥ ፡ ዐስብና ፡ መርምር ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ ጋድን ፦ እጅግ ፡ ተጨንቄያለኹ ፤ ምሕረቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ እንውደቅ ፤ በሰው ፡ እጅ ፡ ግን ፡ አልውደቅ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 15 ፤ ዳዊትም ፡ ቸነፈሩን ፡ መረጠ ፤ የስንዴም ፡ መከር ፡ ወራት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ቸነፈሩ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ገሥመረ ፤ ከሕዝቡም ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ሞተ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ እጁን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ክፉው ፡ ነገር ፡ ዐዘነ ፥ ሕዝቡንም ፡ የሚያጠፋውን ፡ መልአክ ፦ እንግዲህ ፡ በቃኽ ፤ እጅኽን ፡ መልስ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ ሕዝቡን ፡ የሚመታውን ፡ መልአክ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ በድያለኹ ፡ ጠማማም ፡ ሥራ ፡ እኔ ፡ አድርጌያለኹ ፤ እነዚህ ፡ በጎች ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ምን ፡ አደረጉ ∴ እጅኽ ፡ በእኔና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እንድትኾን ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጋድ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥቶ ፦ ውጣ ፥ በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሥራ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደ ፡ ጋድ ፡ ነገር ፡ ወጣ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 20 ፤ ኦርናም ፡ ሲመለከት ፡ ንጉሡና ፡ ባሪያዎቹ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲመጡ ፡ አየ ፤ ኦርናም ፡ ወጥቶ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 21 ፤ ኦርናም ፦ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ ወደ ፡ ባሪያው ፡ ያመጣው ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ∴ አለ ። ዳዊትም ፦ መቅሠፍቱ ፡ ከሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ይከለከል ፡ ዘንድ ፡ ዐውድማውን ፡ ከአንተ ፡ ገዝቼ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ልሠራ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 22 ፤ ኦርናም ፡ ዳዊትን ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሡ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ወስዶ ፡ ያቅርብ ፤ እንሆ ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በሬዎች ፥ ለሚቃጠልም ፡ ዕንጨት ፡ የዐውድማ ፡ ዕቃና ፡ የበሬ ፡ ቀንበር ፡ አለ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 23 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ኦርና ፡ ለንጉሡ ፡ ይሰጣል ፡ አለው ፤ ኦርናም ፡
ንጉሡን ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀበልኽ ፡ አለው ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፡ ኦርናን ፦ እንዲህ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በዋጋ ፡ ከአንተ ፡
እገዛለኹ ፤ ለአምላኬም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ያለዋጋ ፡ አላቀርብም ፡ አለው ። ዳዊትም ፡
ዐውድማውንና ፡ በሬዎቹን ፡ በዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ ገዛ ።

ሳሙ.2 ፡ 24 ፡ 25 ፤ በዚያም ፡ ዳዊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ የሚቃጠልና ፡ የደኅንነትንም ፡
መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ አገሪቱ ፡ የተለመነውን ፡ ሰማ ፥ መቅሠፍቱም ፡ ከእስራኤል ፡ ተከለከለ ❖

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ ንጉሡ ፡ ዳዊትም ፡ ሸመገለ ፥ ዕድሜውም ፡ በዛ ፤ ልብስም ፡ ደረቡለት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይሞቀውም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ባሪያዎቹም ፦ ለጌታችን ፣ ለንጉሡ ፡ ድንግል ፡ ትፈለጋለች ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆማ ፡ ታገልግለው ፥ በጌታችንም ፡ በንጉሡ ፡ ብብት ፡ ተኝታ ፡ ታሙቀው ፡ አሉት ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 3 ፤ በእስራኤልም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የተዋበች ፡ ቄንጦ ፡ ፈለጉ ፤ ሱነማዊቱን ፡ አቢሳንም ፡ አገኙ ፥ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ይዘዋት ፡ መጡ ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ቄንጦዊቱም ፡ እጅግ ፡ ውብ ፡ ነበረች ፤ ንጉሡንም ፡ ትረዳውና ፡ ታገለግለው ፡ ነበር ፥ ንጉሡ ፡ ግን ፡ አያውቃትም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ የአጊትም ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፦ ንጉሥ ፡ እኾናለኹ ፡ ብሎ ፡ ተነሣ ፤ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፣ በፊቱም ፡ የሚሮጡ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ አዘጋጀ ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 6 ፤ አባቱም ፡ ከቶ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፦ እንዲህ ፡ ለምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ ብሎ ፡ አልተቈጣውም ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ከአቤሴሎምም ፡ በኋላ ፡ ተወልዶ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ሜራውም ፡ ከጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮአብና ፡ ከካህኑ ፡ ከአብያታር ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ እነርሱም ፡ አዶንያስን ፡ ተከትለው ፡ ይረዱት ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፣ ነቢዩም ፡ ናታን ፣ ሳሚም ፣ ሬሲም ፣ የዳዊትም ፡ ኀያላን ፡ ከአዶንያስ ፡ ጋራ ፡ አልነበሩም ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 9 ፤ አዶንያስም ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፣ ፍሪዳዎችንም ፡ በዐይንሮጌል ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በዞሔሌት ፡ ድንጋይ ፡ ዘንድ ፡ ሠዋ ፤ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቹን ፡ ኹሉ ፥ የንጉሡንም ፡ ባሪያዎች ፥ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነቢዩን ፡ ናታንን ፥ በናያስንም ፥ ኀያላኑንም ፥ ወንድሙንም ፡ ሰሎሞንን ፡ አልጠራም ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ናታንም ፡ የሰሎሞንን ፡ እናት ፡ ቤርሳቤሕን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራት ፦ ጌታችን ፡ ዳዊት ፡ ሳያውቅ ፥ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ አልሰማሽምን ፧

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ አኹንም ፡ ነዪ ፥ የልጅሽን ፡ የሰሎሞንን ፡ ነፍስና ፡ የአንቺን ፡ ነፍስ ፡ እንድታድኚ ፡ እመክርሻለኹ ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ኼደሽ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ግቢና ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ይቀመጣል ፡ ብለኽ ፡ አልማልኽልኝምን ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ አዶንያስ ፡ ይነግሣል ፧ በዩው ።

ነገ.1 ፥ 1 ፥ 14 ፤ እንሆ ፥ አንቺ ፡ በዚያ ፡ ለንጉሥ ፡ ስትነግሪ ፥ እኔ ፡ ከአንቺ ፡ በኋላ ፡ እገባለኹ ፥ ቃልሽንም ፡ አጸናለኹ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 15 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝ ፡ ገባች ፤ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ሸምግሎ ፡ ነበር ፥ ሱነማዊቱም ፡ አቢሳ ፡ ታገለግለው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 16 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ አጐንብሳ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣች ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ትፈልጊያለሽ ፧ አለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 17 ፤ ርሷም ፡ አለችው ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ለባሪያኽ ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ይቀመጣል ፡ ብለኽ ፥ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምለኽልኛል ፤

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 18 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ አዶንያስ ፡ መንገሡ ፡ ነው ፤ አንተም ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ አታውቅም ፤

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፣ በጎችንም ፡ ሠውቷል ፥ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፣ ካህኑንም ፡ አብያታርን ፣ የሰራዊቱንም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብን ፡ ጠርቷል ፤ ባሪያኽን ፡ ሰሎሞንን ፡ ግን ፡ አልጠራውም ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 20 ፤ አኹንም ፥ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሥ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ይመለከትኻል ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 21 ፤ ይህ ፡ ባይኾን ፥ ጌታዬ ፡ ከአባቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ባንቀላፋኽ ፡ ጊዜ ፥ እኔና ፡ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፥ እንደ ፡ ኀጢአተኞች ፡ እንቈጠራለን ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 22 ፤ እንሆም ፥ ለንጉሡ ፡ ስትናገር ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ገባ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 23 ፤ ለንጉሡም ፦ እንሆ ፥ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ መጥቷል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በግንባሩ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 24 ፤ ናታንም ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፦ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ አዶንያስ ፡ ይነግሣል ፥ በዙፋኔም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል ፡ ብለኻልን ፧

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 25 ፤ ርሱ ፡ ዛሬ ፡ ወርዶ ፡ ብዙ ፡ በሬዎችንና ፡ ፍሪዳዎችን ፡ በጎችንም ፡ ሠውቷል ፥ የንጉሡንም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፥ የሰራዊትንም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብን ፥ ካህኑንም ፡ አብያታርን ፡ ጠርቷል ፤ እንሆም ፥ በፊቱ ፡ እየበሉና ፡ እየጠጡ ፦ አዶንያስ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ ይላሉ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔን ፡ ባሪያኽን ፥ ካህኑንም ፡ ሳዶቅን ፥ የዮዳሄንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፥ ባሪያኽንም ፡ ሰሎሞንን ፡ አልጠራም ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 27 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ የተደረገ ፡ ነውን ፧ ለባሪያኽም ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ በጌታዬ ፡ በንጉሡ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ አልነገርኽምን ፧

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 28 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፦ ቤርሳቤሕን ፡ ጥሩልኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገባች ፥ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆመች ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፦ ነፍሴን ፡ ከመከራ ፡ ኹሉ ፡ ያዳነኝ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 30 ፤ በእውነት ፦ ልጅሽ ፡ ሰሎሞን ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይነግሣል ፥ በእኔም ፡ ፋንታ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጣል ፡ ብዬ ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማልኹልሽ ፥ እንዲሁ ፡ ዛሬ ፡ በእውነት ፡ አደርጋለኹ ፡ ብሎ ፡ ማለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 31 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ በግንባሯ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፍታ ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሣችና ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ለዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ይኑር ፡ አለች ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 32 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፦ ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፣ የዮዳዔንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ጥሩልኝ ፡ አለ ። ወደንጉሡም ፡ ፊት ፡ ገቡ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 33 ፤ ንጉሡም ፡ አላቸው ፦ የጌታችኹን ፡ ባሪያዎች ፡ ይዛችኹ ፡ ኺዱ ፥ ልጄንም ፡ ሰሎሞንን ፡ በበቅሎዬ ፡ ላይ ፡ አስቀምጡት ፥ ወደ ፡ ግዮንም ፡ አውርዱት ፤

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 34 ፤ በዚያም ፡ ካህኑ ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ይቅቡት ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ ነፍታችኹ ፦ ሰሎሞን ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ በሉ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 35 ፤ በኋላውም ፡ ተከትላችኹ ፡ ውጡ ፤ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፥ በእኔም ፡ ፋንታ ፡ ይንገሥ ፤ በእስራኤልና ፡ በይሁዳም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አዝዣለኹ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 36 ፤ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ መልሶ ፡ ለንጉሡ ፡ አለ ፥ ያበጅ ፡ ያድርግ ፤ የጌታዬም ፡ የንጉሥ ፡ አምላክ ፡ ይህን ፡ ይናገር ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዲሁ ፡ ከሰሎሞን ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፥ ዙፋኑንም ፡ ከጌታዬ ፡ ከንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 38 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፣ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፣ ከሊታውያንና ፡ ፈሊታውያንም ፡ ወረዱ ፥ ሰሎሞንንም ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀምጠው ፡ ወደ ፡ ግዮን ፡ አመጡት ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 39 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅ ፡ ከድንኳኑ ፡ የቅብዓቱን ፡ ቀንድ ፡ ወስዶ ፡ ሰሎሞንን ፡ ቀባ ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ ነፉ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ ሰሎሞን ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ አሉ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 40 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወጡ ፥ ሕዝቡም ፡ ዘፈን ፡ ይዘፍኑ ፡ ነበር ፥ በታላቅም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ ከጩኸታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 41 ፤ አዶንያስና ፡ ርሱም ፡ የጠራቸው ፡ ኹሉ ፡ መብሉና ፡ መጠጡ ፡ ተፈጽሞ ፡ ሳለ ፡ ሰሙ ፤ ኢዮአብም ፡ የቀንደ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ የሽብር ፡ ድምፅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 42 ፤ ርሱም ፡ ይህን ፡ ሲናገር ፡ የካህኑ ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ መጣ ፤ አዶንያስም ፦ አንተ ፡ መልካም ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ መልካም ፡ ታወራልናለኽና ፡ ግባ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 43 ፤ ዮናታንም ፡ ለአዶንያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፦ በእውነት ፡ ጌታችን ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ ሰሎሞንን ፡ አነገሠው ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 44 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅንና ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፡ የዮዳዔንም ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ከሊታውያንንና ፡ ፈሊታውያንንም ፡ ሰደደ ፥ በንጉሡም ፡ በቅሎ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 45 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅና ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ በግዮን ፡ ንጉሥ ፡ አድርገው ፡ ቀቡት ፤ ከዚያም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወጡ ፥ ከተማዩቱም ፡ አስተጋባች ፤ የሰማችኹትም ፡ ድምፅ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 46 ፤ ደግሞም ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጧል ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 47 ፤ የንጉሡም ፡ ባሪያዎች ፡ ገብተው ፦ እግዚአብሔር ፡ የሰሎሞንን ፡ ስም ፡ ከስምኽ ፡ ዙፋኑንም ፡ ከዙፋንኽ ፡ የበለጠ ፡ ያድርግ ፡ ብለው ፡ ጌታችንን ፡ ንጉሡን ፡ ዳዊትን ፡ ባረኩ ፤ ንጉሡም ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ ሰገደ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 48 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፦ ዐይኔ ፡ እያየ ፡ ዛሬ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጠውን ፡ የሰጠኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 49 ፤ አዶንያስም ፡ የጠራቸው ፡ ኹሉ ፡ ፈሩ ፥ ተነሥተውም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየመንገዳቸው ፡ ኼዱ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 50 ፤ አዶንያስም ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈራ ፥ ተነሥቶም ፡ ኼደ ፥ የመሠዊያውንም ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 51 ፤ ለሰሎሞንም ፦ እንሆ ፥ አዶንያስ ፡ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንን ፡ ፈርቶ ፦ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ባሪያውን ፡ በሰይፍ ፡ እንዳይገድለኝ ፡ ዛሬ ፡ ይማልልኝ ፡ ብሎ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ይዟል ፡ አሉት ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 52 ፤ ሰሎሞንም ፦ ርሱ ፡ አካኼዱን ፡ ያሳመረ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከርሱ ፡ አንዲት ፡ ጠጕር ፡ እንኳ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፋት ፡ የተገኘበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይሞታል ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 1 ፡ 53 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ላከ ፥ ከመሠዊያውም ፡ አወረዱት ፤ መጥቶም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅ ፡ ነሣ ፥ ሰሎሞንም ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ የሚሞትበት ፡ ቀን ፡ ቀረበ ፤ ልጁንም ፡ ሰሎሞንን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ የምድሩን ፡ ኹሉ ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ፤

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 3 ፤ በርታ ፡ ሰውም ፡ ኹን ፤ የምታደርገውንና ፡ የምትኼድበትን ፡ ኹሉ ፡ ታከናውን ፡ ዘንድ ፥ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ሥርዐቱንና ፡ ትእዛዛቱን ፡ ፍርዱንና ፡ ምስክሩንም ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ በመንገዱም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፥ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 4 ፤ ይኸውም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኔ ፦ ልጆችኽ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፥ በፊቴም ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ በእውነት ፡ ቢኼዱ ፡ ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ሰው ፡ አይቈረጥብኽም ፡ ብሎ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 5 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፥ ኹለቱን ፡ የእስራኤልን ፡ ጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ የኔር ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፡ የዬቴሩንም ፡ ልጅ ፡ ዐማሳይን ፡ ገድሎ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያደረገውን ፡ ታውቃለኽ ፤ የሰልፉንም ፡ ደም ፡ በሰላም ፡ አፈሰሰ ፥ በወገቡም ፡ ባለው ፡ ድግና ፡ በእግሩ ፡ ባለው ፡ ጫማ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አኖረ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ አንተም ፡ እንደ ፡ ጥበብኽ ፡ አድርግ ፥ ሽበቱንም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አታውርደው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ከወንድምኽ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ፊት ፡ በሸሸኹ ፡ ጊዜ ፡ ቀርበውኛልና ፥ ለገለዓዳዊው ፡ ለቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ መልካም ፡ ቸርነት ፡ አድርግላቸው ፥ በማእዱኽም ፡ ከሚበሉት ፡ መካከል ፡ ይኹኑ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ እነሆ ፡ ወደ ፡ መሃናይም ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፡ ብርቱ ፡ ርግማን ፡ የረገመኝ ፡ የብራቂም ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የብንያማዊው ፡ የጌራ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዮርዳኖስን ፡ በተሻገርኹ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀበለኝ ፡ ወረደ ፥ እኔም ፦ በሰይፍ ፡ አልገድልኽም ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምዬለታለኹ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ ያለቅጣት ፡ አትተወው ፤ የምታደርግበትንም ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፥ ሽበቱንም ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ አውርድ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የነገሠው ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ። በኬብሮን ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ሰሎሞንም ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ፤ መንግሥቱም ፡ እጅግ ፡ ጸና ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ የአጊት ፡ ልጅ ፡ አዶንያስም ፡ ወደሰሎሞን ፡ እናት ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ መጣ ፤ ርሷም ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ መምጣትኽ ፡ በሰላም ፡ ነውን ፧ አለች ፤

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ በሰላም ፡ ነው ፡ አለ ። ደግሞም ፦ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ጕዳይ ፡ አለኝ ፡ አለ ፤ ርሷም ፦ ተናገር ፡ አለች ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ መንግሥቱ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሥ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንቺ ፡ ታውቂያለሽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኾኖለታልና ፥ መንግሥቱ ፡ ከእኔ ፡ ዐልፎ ፡ ለወንድሜ ፡ ኾኗል ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ አኹንም ፡ አንዲት ፡ ልመና ፡ እለምንሻለኹ ፤ አታሳፍሪኝ ፡ አለ ። ርሷም ፦ ተናገር ፡ አለችው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ አያሳፍርሽምና ፡ ሱነማዊቱን ፡ አቢሳን ፡ ይድርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንድትነግሪው ፡ እለምንሻለኹ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ቤርሳቤሕም ፦ መልካም ፡ ነው ፥ ስለ ፡ አንተ ፡ ለንጉሡ ፡ እነግረዋለኹ ፡ አለች ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ቤርሳቤሕም ፡ የአዶንያስን ፡ ነገር ፡ ትነግረው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ገባች ፤ ንጉሡም ፡ ሊቀበላት ፡ ተነሣ ፡ ሳማትም ፥ በዙፋኑም ፡ ተቀመጠ ፤ ለንጉሡም ፡ እናት ፡ ወንበር ፡ አስመጣላት ፥ በቀኙም ፡ ተቀመጠች ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ ርሷም ፦ አንዲት ፡ ታናሽ ፡ ልመና ፡ እለምንኻለኹ ፤ አታሳፍረኝ ፡ አለች ። ንጉሡም ፦ እናቴ ፡ ሆይ ፥ አላሳፍርሽምና ፡ ለምኝ ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 21 ፤ ርሷም ፦ ሱነማዊቱ ፡ አቢሳ ፡ ለወንድምኽ ፡ ለአዶንያስ ፡ ትዳርለት ፡ አለች ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ለእናቱ ፡ መልሶ ፦ ሱነማዊቱን ፡ አቢሳን ፡ ለአዶንያስ ፡ ለምን ፡ ትለምኝለታለሽ ፧ ታላቅ ፡ ወንድሜ ፡ ነውና ፥ መንግሥትን ፡ ደግሞ ፡ ለምኚለት ፤ ካህኑም ፡ አብያታርና ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፦ አዶንያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሕይወቱ ፡ ላይ ፡ አለመናገሩ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ያድርግብኝ ፥ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 24 ፤ አኹንም ፡ ያጸናኝ ፥ በአባቴም ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀመጠኝ ፥ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ ቤትን ፡ የሠራልኝ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ዛሬ ፡ አዶንያስ ፡ ፈጽሞ ፡ ይገደላል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማለ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ ላከ ፤ ርሱም ፡ ወደቀበት ፥ ሞተም ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 26 ፤ ንጉሡም ፡ ካህኑን ፡ አብያታርን ፦ አንተ ፡ ዛሬ ፡ የሞት ፡ ሰው ፡ ነበርኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአምላክን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ተሸከምኽ ፥ አባቴም ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ ተቀበልኽ ፡ አልገድልኽምና ፡ በዐናቶት ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ዕርሻኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 27 ፤ በሴሎም ፡ በዔሊ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሰሎሞን ፡ አብያታርን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ክህነት ፡ አወጣው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 28 ፤ ለኢዮአብም ፡ ወሬ ፡ ደረሰለት ፤ ኢዮአብም ፡ አቤሴሎምን ፡ አልተከተለም ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ አዶንያስን ፡ ተከትሎ ፡ ነበር ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሸ ፡ የመሠዊያውን ፡ ቀንድ ፡ ያዘ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ኢዮአብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ሸሸ ፡ መሠዊያውን ፡ እንደ ፡ ያዘ ፡ ሰማ ፤ ሰሎሞንም ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፥ ኺድ ፡ ውደቅበት ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 30 ፤ በናያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ መጥቶ ፦ ንጉሡ ፦ ውጣ ፡ ይልኻል ፡ አለው ፤ ርሱም ፦ በዚህ ፡ እሞታለኹ ፡ እንጂ ፡ አልወጣም ፡ አለ ። በናያስም ፦ ኢዮአብ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ የመለሰልኝም ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወሬ ፡ አመጣ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 31 ፤ ንጉሡም ፡ አለው ፦ እንደ ፡ ነገረኽ ፡ አድርግ ፤ ኢዮአብም ፡ በከንቱ ፡ ያፈሰሰውን ፡ ደም ፡ ከእኔና ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ታርቅ ፡ ዘንድ ፡ ገድለኽ ፡ ቅበረው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 32 ፤ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ ሳያውቅ ፡ ከርሱ ፡ የሚሻሉትን ፡ ኹለቱን ፡ ጻድቃን ፡ ሰዎች ፥ የእስራኤልን ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ የኔርን ፡ ልጅ ፡ አበኔርን ፥ የይሁዳንም ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ የዬቴርን ፡ ልጅ ፡ ዐማሳይን ፥ በሰይፍ ፡ ገድሏልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ደሙን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሰው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 33 ፤ ደማቸውም ፡ በኢዮአብ ፡ ራስና ፡ በዘሩ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይመለስ ፤ ለዳዊት ፡ ግን ፡ ለዘሩና ፡ ለቤቱ ፡ ለዙፋኑም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኹን ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 34 ፤ የዮዳሄም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ወጥቶ ፡ ወደቀበት ፡ ገደለውም ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ባለው ፡ በቤቱ ፡ ተቀበረ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 35 ፤ ንጉሡም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የዮዳሄን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃ ፡ አደረገ ፤ በአብያታርም ፡ ፋንታ ፡ ካህኑን ፡ ሳዶቅን ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 36 ፤ ንጉሡም ፡ ልኮ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራውና ። በኢየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ ሠርተኽ ፡ ተቀመጥ ፥ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ አትውጣ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 37 ፤ በወጣኽበትም ፡ ቀን ፥ የቄድሮንንም ፡ ፈፋ ፡ በተሻገርኽበት ፡ ቀን ፡ ፈጽመኽ ፡ እንድትሞት ፡ ዕወቅ ፤ ደምኽ ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 38 ፤ ሳሚም ፡ ንጉሡን ፦ ነገሩ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ባሪያኽ ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋል ፡ አለው ፤ ሳሚም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 39 ፤ ከሦስት ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ከሳሚ ፡ ባሪያዎች ፡ ኹለቱ ፡ ወደጌት ፡ ንጉሥ ፡ ወደመዓካ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ ኰበለሉ ፤ ሳሚንም ፦ እንሆ ፥ ባሪያዎችኽ ፡ በጌት ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 40 ፤ ሳሚም ፡ ተነሣ ፥ አህያውንም ፡ ጭኖ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ወደ ፡ አንኩስ ፡ ዘንድ ፡ ኼደ ፤ ሳሚም ፡ ኼዶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ከጌት ፡ አመጣ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 41 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሳሚ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ጌት ፡ ኼዶ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ሰማ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 42 ፤ ንጉሡም ፡ ልኮ ፡ ሳሚን ፡ አስጠራና ። ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ለመኼድ ፡ በወጣኽ ፡ ቀን ፡ ፈጽመኽ ፡ እንድትሞት ፡ ዕወቅ ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አላስማልኹኽምን ፧ ወይስ ፡ አላስመሰከርኹብኽምን ፧ አንተም ፦ ቃሉ ፡ መልካም ፡ ነው ፥ ሰምቻለኹ ፡ አልኽኝ ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 43 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መሐላ ፡ እኔስ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠበቅኽም ፧ አለው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 44 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ሳሚን ፦ አንተ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ፡ የሠራኽውን ፡ ልብኽም ፡ ያሰበውን ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ ታውቃለኽ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ክፋትኽን ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 45 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ግን ፡ የተባረከ ፡ ይኾናል ፥ የዳዊትም ፡ ዙፋን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናል ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 2 ፡ 46 ፤ ንጉሡም ፡ የዮዳዔን ፡ ልጅ ፡ በናያስን ፡ አዘዘው ፥ ወጥቶም ፡ ወደቀበት ፥ ሞተም ። መንግሥትም ፡ በሰሎሞን ፡ እጅ ፡ ጸና ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ለፈርዖን ፡ ዐማች ፡ ኾነ ፤ የፈርዖንን ፡ ልጅ ፡ አገባ ፥ ቤቱንና ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ያለውን ፡ ቅጥር ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ አመጣት ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ እስከዚያም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መቅደስ ፡ አልተሠራም ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡ ፡ በኰረብታ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ሥርዐት ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፤ ብቻ ፡ በኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ገባዖን ፡ ዋና ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ነበረችና ፡ ንጉሡ ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ኼደ ፤ ሰሎሞንም ፡ በዚያ ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ በሌሊት ፡ በሕልም ፡ ተገለጠለት ፤ እግዚአብሔርም ፦ ምን ፡ እንድሰጥኽ ፡ ለምን ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ ሰሎሞንም ፡ አለ ፦ ርሱ ፡ በፊትኽ ፡ በእውነትና ፡ በጽድቅ ፡ በልብም ፡ ቅንነት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥ ከባሪያኽ ፡ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ቸርነት ፡ አድርገኻል ፤ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ ልጅ ፡ ሰጥተኽ ፡ ታላቁን ፡ ቸርነትኽን ፡ አቈይተኽለታል ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ አንግሠኸኛል ፤ እኔም ፡ መውጫንና ፡ መግቢያን ፡ የማላውቅ ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ ነኝ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ባሪያኽም ፡ ያለው ፡ አንተ ፡ በመረጥኸው ፡ ሕዝብኽ ፡ ስለ ፡ ብዛቱም ፡ ይቈጠርና ፡ ይመጠን ፡ ዘንድ ፡ በማይቻል ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ነው ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ስለዚህም ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ መፍረድ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፥ መልካሙንና ፡ ክፉውንም ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያኽ ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ስጠው ፤ አለዚያማ ፡ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ ሰሎሞንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ለመነ ፥ ነገሩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ፍርድን ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡ ለራስኽ ፡ ማስተዋልን ፡ ለመንኽ ፡ እንጂ ፡ ለራስኽ ፡ ብዙ ፡ ዘመናትን ፡ ባለጠግነትንም ፡ የጠላቶችኽንም ፡ ነፍስ ፡ ሳትለምን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለምነኻልና ፥ እንሆ ፥

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ቃል ፡ አድርጌልኻለኹ ፤ እንሆ ፥ ማንም ፡ የሚመስልኽ ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ እንደሌለ ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ እንዳይነሣ ፡ አድርጌ ፡ ጥበበኛና ፡ አስተዋይ ፡ ልቡና ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ ከነገሥታት ፡ የሚመስልኽ ፡ ማንም ፡ እንዳይኖር ፡ ያልለመንኸውን ፡ ባለጠግነትና ፡ ክብር ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ አባትኽም ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ የኼድኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ዕድሜኽን ፡ አረዝመዋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ሰሎሞንም ፡ ነቃ ፥ እንሆም ፥ ሕልም ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ቆመ ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አሳረገ ፥ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፥ ለባሪያዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኹለት ፡ ጋለሞታዎች ፡ ሴቶች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ አንደኛዪቱም ፡ ሴት ፡ አለች ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እኔና ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ እንኖራለን ፤ እኔም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በቤት ፡ ሳለኹ ፡ ወለድኹ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ከወለድኹ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ ደግሞ ፡ ወለደች ፤ እኛ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ ዐብረን ፡ ነበርን ፥ ከኹለታችንም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 19 ፤ ርሷም ፡ በላዩ ፡ ስለ ፡ ተኛችበት ፡ የዚች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በሌሊት ፡ ሞተ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 20 ፤ ርሷም ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ተነሥታ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ተኝቼ ፡ ሳለኹ ፥ ልጄን ፡ ከአጠገቤ ፡ ወሰደች ፥ በብብቷም ፡ አደረገችው ፥ የሞተውንም ፡ ልጇን ፡ በእኔ ፡ ብብት ፡ አደረገች ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ ልጄንም ፡ አጠባ ፡ ዘንድ ፡ በማለዳ ፡ ብነሣ ፥ እንሆ ፥ ሞቶ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብርሃን ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ተመለከትኹት ፥ እንሆም ፥ የወለድኹት ፡ ልጄ ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 22 ፤ ኹለተኛዪቱም ፡ ሴት ፦ ደኅንኛው ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ የሞተውም ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንቺ ፡ እንደምትዪው ፡ አይደለም ፡ አለች ። ይህችም ፦ የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ ደኅንኛውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አለች ፤ እንዲሁም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፦ ይህች ፦ ደኅንኛው ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፥ የሞተውም ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፤ ያችኛዪቱም ፦ አይደለም ፥ የሞተው ፡ የአንቺ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ደኅንኛውም ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ትላለች ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፦ ሰይፍ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፤ ሰይፍም ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ መጡ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 25 ፤ ንጉሡም ፦ ደኅንኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለኹለት ፡ ከፍላችኹ ፡ ለአንዲቱ ፡ አንዱን ፡ ክፍል ፥ ለኹለተኛዪቱም ፡ ኹለተኛውን ፡ ክፍል ፡ ስጡ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 26 ፤ ደኅንኛውም ፡ የነበራት ፡ ሴት ፡ አንገቷ ፡ ስለ ፡ ልጇ ፡ ናፍቋልና ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ደኅንኛውን ፡ ለርሷ ፡ ስጣት ፡ እንጂ ፡ አትግደል ፡ ብላ ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገረች ። ያችኛዪቱ ፡ ግን ፦ ይከፈል ፡ እንጂ ፡ ለኔም ፡ ለአንቺም ፡ አይኹን ፡ አለች ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ይህችኛዪቱ ፡ እናቱ ፡ ናትና ፥ ደኅንኛውን ፡ ሕፃን ፡ ለርሷ ፡ ስጧት ፡ እንጂ ፡ አትግደሉት ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 3 ፡ 28 ፤ ንጉሡም ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ሰሙ ፤ ፍርድን ፡ ለማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡ ነበረበት ፡ አይተዋልና ፥ ንጉሡን ፡ ፈሩ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 2 ፤ የነበሩትም ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ካህኑ ፡ ዐዛርያስ [163] ፥

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ጸሓፊዎቹም ፡ የሴባ ፡ ልጆች ፡ ኤልያፍና ፡ አኪያ ፥ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአኒሉድ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፥

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ የዮዳዔም ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ የሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ ሳዶቅና ፡ አብያታርም ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ የናታንም ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ የሹሞች ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ የናታንም ፡ ልጅ ፡ ዛቡድ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪና ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ አኒሳርም ፡ የቤት ፡ አዛዥ ፥ የዓብዳም ፡ ልጅ ፡ አዶኒራም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ለንጉሡና ፡ ለቤተ ፡ ሰቡም ፡ ቀለብ ፡ የሚሰጡ ፡ በእስራኤል ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሹሞች ፡ ለሰሎሞን ፡ ነበሩት ። ከዓመቱ ፡ ውስጥ ፡ አንዱን ፡ ወር ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ይቀልቡ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ በተራራማው ፡ አገር ፡ በኤፍሬም ፡ የሑር ፡ ልጅ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ በማቃጽና ፡ በሸዓልቢም ፡ በቤትሳሚስና ፡ በኤሎንቤትሐናን ፡ የዴቀር ፡ ልጅ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ በአሩቦት ፡ የሔሴድ ፡ ልጅ ፥ ለርሱም ፡ ሰኮትና ፡ የኦፌር ፡ አገር ፡ ዥሉ ፡ ነበረ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 11 ፤ በዶር ፡ አገር ፡ ዳርቻ ፡ ዥሉ ፡ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፥ ርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡ ጣፈትን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ከቤትሳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አቤልምሖላና ፡ እስከዮቅምዓም ፡ ማዶ ፡ ድረስ ፡ በታዕናክና ፡ በመጊዶ ፡ በጸርታንም ፡ አጠገብ ፡ በኢይዝራኤል ፡ በታች ፡ ባለው ፡ በቤትሳን ፡ ዥሉ ፡ የአኒሉድ ፡ ልጅ ፡ በዓና ፡ ነበረ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የጌበር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ ለርሱም ፡ በገለዓድ ፡ ያሉት ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የኢያዕር ፡ መንደሮች ፡ ነበሩ ፤ ለርሱም ፡ ደግሞ ፡ በባሳን ፡ በአርጎብ ፡ ዳርቻ ፡ ያሉት ፡ ቅጥርና ፡ የናስ ፡ መወርወሪያዎች ፡ የነበረባቸው ፡ ስድሳ ፡ ታላላቅ ፡ ከተማዎች ፡ ነበሩበት ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ በመሃናይም ፡ የዒዶ ፡ ልጅ ፡ አኒናዳብ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ በንፍታሌም ፡ አኪማዐስ ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ የሰሎሞንን ፡ ልጅ ፡ ባስማትን ፡ አግብቶ ፡ ነበር ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ በአሴር [164]ና ፡ በበዓሎት ፡ የኩሲ ፡ ልጅ ፡ በዓና ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ በይሳኮር ፡ የፋሩዋ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ በብንያም ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ሳሚ ፤

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 19 ፤ በአሞራውያን ፡ ንጉሥ ፡ በሴዎንና ፡ በባሳን ፡ ንጉሥ ፡ በዐግ ፡ አገር ፥ በገለዓድ ፡ አገር ፥ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ጌበር ፡ ነበረ ፤ በዚያችም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ ሹም ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 20 ፤ ይሁዳና ፡ እስራኤልም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ብዛት ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፤ በልተውም ፡ ጠጥተውም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 21 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከወንዙ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ፍልስጥኤም ፡ ድረስ ፡

---

163 ዕብ. ፥ ዐዛርያ ።
164 ዕብ. ፥ አሼር ።

በመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ፤ ግብርም ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ፥ በዕድሜውም ፡ ሙሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይገዙ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ለሰሎሞንም ፡ ለቀን ፡ ለቀኑ ፡ ቀለብ ፡ የሚኾን ፡ ሠላሳ ፡ ኰር ፡ መልካም ፡ ዱቄትና ፡ ስድሳ ፡ ኰር ፡ መናኛ ፡ ድቄት ፥

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 23 ፤ ከዋላና ፡ ከሚዳቋ ፡ ከበረሓ ፡ ፍየልና ፡ ከሰቡ ፡ ወፎች ፡ በቀር ፡ ዐሥር ፡ ፍሪዳዎች ፡ ኻያም ፡ የተሰማሩ ፡ በሬዎች ፡ አንድ ፡ መቶም ፡ በጎች ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 24 ፤ ከወንዙ ፡ ወዲህ ፡ ባሉት ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ከወንዙም ፡ ወዲህ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከቲፍሳ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጋዛ ፡ ድረስ ፡ ነግሦ ፡ ነበር ፤ በዙሪያውም ፡ ባለው ፡ በኹሉ ፡ ወገን ፡ ሰላም ፡ ኾኖለት ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 25 ፤ በሰሎሞንም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይሁዳና ፡ እስራኤል ፡ ከዳን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 26 ፤ ለሰሎሞንም ፡ በአርባ ፡ ሺሕ ፡ ጋጥ ፡ የሚገቡ ፡ የሠረገላ ፡ ፈረሶች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 27 ፤ እነዚያም ፡ ሹሞች ፡ እያንዳንዱ ፡ በየወሩ ፡ ንጉሡን ፡ ሰሎሞንንና ፡ ወደንጉሡ ፡ ወደሰሎሞን ፡ ማእድ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ኹሉ ፡ ይቀልቡ ፡ ነበር ፤ ምንም ፡ አያጐድሉም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 28 ፤ እያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ደንቡ ፡ ለፈረሶቹና ፡ ለሰጋር ፡ በቅሎዎች ፡ ገብስና ፡ ጭድ ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ በባሕርም ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ የልብ ፡ ስፋት ፡ ሰጠው ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 30 ፤ የሰሎሞንም ፡ ጥበብ ፡ በምሥራቅ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጥበብና ፡ ከግብጽ ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፡ በለጠ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 31 ፤ ከሰውም ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ከኢይዝራኤላዊው ፡ ከኤታንና ፡ ከማሖል ([165]) ፡ ልጆች ፣ ከሄማንና ([166]) ፡ ከከልቀድ ፣ ከደራልም ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኛ ፡ ነበረ ። በዙሪያውም ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዝናው ፡ ወጣ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 32 ፤ ርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ምሳሌዎች ፡ ተናገረ ፤ መሐልዩም ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 33 ፤ ስለ ፡ ዛፍም ፡ ከሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ዠምሮ ፡ በቅጥር ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ እስከሚበቅለው ፡ እስከ ፡ ሂሶጵ ፡ ድረስ ፡ ይናገር ፡ ነበር ፤ ደግሞም ፡ ስለ ፡ አውሬዎችና ፡ ስለ ፡ ወፎች ፡ ስለ ፡ ተንቀሳቃሾችና ፡ ስለ ፡ ዓሣዎች ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 4 ፡ 34 ፤ ከአሕዛብም ፡ ኹሉ ፥ ጥበቡንም ፡ ሰምተው ፡ ከነበሩ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ሰዎች ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ የጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ለዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ወዳጅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ ሰሎሞን ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ ንጉሥ ፡ ለመኾን ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ሰምቶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ሰደደ ።

---

165 ዕብ. ፡ ማሖል ፡ (ማሕሌት • በቁሙ) ።

166 ዕብ. ፥ ሄይማን ፡ (ሀይማኒ • አማኝ) ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ኪራም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ላከ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እስኪጥልለት ፡ ድረስ ፡ በዙሪያው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሰልፍ ፡ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ እንዳልቻለ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ አኹንም ፡ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዙሪያዬ ፡ ካሉት ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቶኛል ፤ ጠላትም ፡ ክፉም ፡ ነገር ፡ የለብኝም ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፦ ባንተ ፡ ፋንታ ፡ በዙፋንኽ ፡ ላይ ፡ የማስቀምጠው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፥ ለአምላኬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ ዐስባለኹ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ አኹንም ፡ ከወገኔ ፡ እንደ ፡ ሲዶናውያን ፡ ዕንጨት ፡ መቈረጥ ፡ የሚያውቅ ፡ እንደሌለ ፡ ታውቃለኽና ፡ የዝግባ ፡ ዛፍ ፡ ከሊባኖስ ፡ ይቈርጡልኝ ፡ ዘንድ ፡ ባሪያዎችኽን ፡ እዘዝ ፤ ባሪያዎቼም ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ይኹኑ ፤ የባሪያዎችኽንም ፡ ዋጋ ፡ እንደተናገርኸው ፡ ኹሉ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ ኪራምም ፡ የሰሎሞንን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለውና ፦ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ጥበበኛ ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዛሬ ፡ ይመስገን ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ኪራምም ፦ የላክኽብኝን ፡ ኹሉ ፡ ሰማኹ ፤ ስለ ፡ ዝግባውና ፡ ስለ ፡ ጥዱ ፡ ዕንጨት ፡ ፈቃድኽን ፡ ኹሉ ፡ አደርጋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ባሪያዎቼ ፡ ከሊባኖስ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይጐትቱታል ፤ እኔም ፡ በታንኳ ፡ አድርጌ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እያንሳፈፍኹ ፡ አንተ ፡ እስከወሰንኸው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ አደርስልኻለኹ ፥ በዚያም ፡ እፈታዋለኹ ፥ አንተም ፡ ከዚያ ፡ ታስወስደዋለኽ ፤ አንተም ፡ ፈቃዴን ፡ ታደርጋለኽ ፤ ለቤቴም ፡ ቀለብ ፡ የሚኾነውን ፡ ትሰጠኛለኽ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ላከ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ እንዲሁም ፡ ኪራም ፡ የዝግባውንና ፡ የጥዱን ፡ ዕንጨት ፡ እንደሚሻው ፡ ያኽል ፡ ኹሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ ቀለብ ፡ ኻያ ፡ ሺ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፡ ኻያ ፡ ኮሮም ፡ ጥሩ ፡ ዘይት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ፤ ሰሎሞንም ፡ ለኪራም ፡ በየዓመቱ ፡ ይህን ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ለሰሎሞን ፡ ጥበብን ፡ ሰጠው ፤ በኪራምና ፡ በሰሎሞንም ፡ መካከል ፡ ሰላም ፡ ነበረ ፤ ኹለቱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ተጋቡ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ገባሮቹን ፡ መርጦ ፡ አወጣ ፤ የገባሮቹም ፡ ቍጥር ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ በየወሩም ፡ እያከታተለ ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዐሥር ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ይሰድ ፡ ነበር ፤ አንድ ፡ ወርም ፡ በሊባኖስ ፡ ኹለት ፡ ወርም ፡ በቤታቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። አዶኒራምም ፡ አስገባሪ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 15 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፡ ተሸካሚዎች ፥ ሰማንያ ፡ ሺሕም ፡ በተራራው ፡ ላይ ፡ የሚጠርቡ ፡ ጠራቢዎች ፡ ነበሩት ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ይኸውም ፡ በሠራተኛው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ከተሾሙት ፡ ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሌላ ፡ ነው ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ታላላቅ ፡ ምርጥ ፡ ምርጥ ፡ ድንጋዮችን ፡ ይቈፍሩና ፡ ይጠርቡ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱም ፡

መሠረት ፡ ይረበርቡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ነገ.1 ፡ 5 ፡ 18 ፤ የሰሎሞንና ፡ የኪራምም ፡ ዐናጢዎች ፡ ጌባላውያንም ፡ ወቀሯቸው ፥ ቤቱንም ፡ ለመሥራት ፡ ዕንጨቱንና ፡ ድንጋዮቹን ፡ አዘጋጁ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ ሰሎሞን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፥ ዚፍ ፡ በሚባለው ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ዠመረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 2 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሠራው ፡ ቤት ፡ ርዝመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 3 ፤ በመቅደሱም ፡ ፊት ፡ ወለል ፡ ነበረ ፤ ርዝመቱም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ከቤቱ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 4 ፤ ለቤቱም ፡ በዐይነ ፡ ርግብ ፡ የተዘጉ ፡ መስኮቶች ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 5 ፤ በቤቱም ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፥ በመቅደሱና ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፥ ደርብ ፡ ሠራ ፥ በዙሪያውም ፡ ጓዳዎች ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 6 ፤ የታችኛውም ፡ ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የመካከለኛው ፡ ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፥ የሦስተኛውም ፡ ደርብ ፡ ወርዱ ፡ ሰባት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ። ሠረገላዎቹ ፡ በቤቱ ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ እንዳይገቡ ፡ ከቤቱ ፡ ግንብ ፡ ውጭ ፡ አረፍቶች ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 7 ፤ ቤቱም ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመው ፡ በተወቀሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ተሠራ ፤ በተሠራም ፡ ጊዜ ፡ መራጃና ፡ መጥረቢያ ፡ የብረትም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አልተሰማም ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 8 ፤ የታችኛውም ፡ ደርብ ፡ ጓዳዎች ፡ በር ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡ ደርብ ፥ ከመካከለኛውም ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ በመውጫ ፡ ያስወጣ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ቤቱንም ፡ ሠርቶ ፡ ፈጸመው ፤ በዝግባው ፡ ሠረገላዎችና ፡ ሳንቃዎች ፡ ከደነው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 10 ፤ በቤቱም ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያ ፡ ቁመታቸው ፡ ዐምስት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ደርቦች ፡ ሠራ ፤ ከቤቱም ፡ ጋራ ፡ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አጋጠማቸው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጣ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ስለምትሠራው ፡ ቤት ፡ በሥርዐቴ ፡ ብትኼድ ፥ ፍርዴንም ፡ ብታደርግ ፥ ትመላለስበትም ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዜን ፡ ኹሉ ፡ ብትጠብቅ ፥ ለአባትኽ ፡ ለዳዊት ፡ የነገርኹትን ፡ ቃል ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አጸናለኹ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 13 ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኖራለኹ ፥ ሕዝቤንም ፡ እስራኤልን ፡ አልጥልም ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ሰሎሞንም ፡ ቤቱን ፡ ሠራው ፥ ፈጸመውም ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 15 ፤ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ውስጡን ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ለበጠ ፤ ከቤቱም ፡ መሠረት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡ ድረስ ፡ ውስጡን ፡ በዕንጨት ፡ ለበጠው ፤ ደግሞም ፡ የቤቱን ፡ ወለል ፡ በጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ከደነው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 16 ፤ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ኺለኛውን ፡ ኻያውን ፡ ክንድ ፡ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ጋረደው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 17 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ ያለውም ፡ መቅደስ ፡ ርዝመቱ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 18 ፤ የቤቱንም ፡ ውስጥ ፡ በተጐበጐበና ፡ በፈነዳ ፡ አበባ ፡ በተቀረጸ ፡ ዝግባ ፡ ለበጠው ፤ ኹሉም ፡ ዝግባ ፡ ነበረ ፤ ድንጋዩም ፡ አልታየም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 19 ፤ በዘያም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ያኖር ፡ ዘንድ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳኑን ፡ አበጀ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 20 ፤ የቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ርዝመት ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 21 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ ከዝግባ ፡ የተሠራ ፡ መሠዊያ ፡ አደረገ ፤ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 22 ፤ ቤቱንም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሞ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠው ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ፡ ኹሉ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 23 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ውስጥ ፡ ቁመታቸው ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ኹለት ፡ ኪሩቤል ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 24 ፤ የኪሩብም ፡ አንደኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የኪሩብም ፡ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ከአንደኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ጫፍ ፡ ድረስ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 25 ፤ ኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ኹለቱም ፡ ኪሩቤል ፡ አንድ ፡ ልክና ፡ አንድ ፡ መልክ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 26 ፤ የአንዱ ፡ ኪሩብ ፡ ቁመት ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 27 ፤ ኪሩቤልንም ፡ በውስጠኛው ፡ ቤት ፡ አኖራቸው ፤ የኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸው ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ የአንዱም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ አንደኛውን ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፥ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ኹለተኛውን ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፤ የኹለቱም ፡ ክንፎች ፡ በቤቱ ፡ መካከል ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይነካኩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 28 ፤ ኪሩቤልንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 29 ፤ በቤቱም ፡ ግንብ ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያ ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ የኪሩቤልና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 30 ፤ የቤቱንም ፡ ወለል ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 31 ፤ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ መግቢያ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ደጆች ፡ ሠራ ፤ መድረኩንና ፡ መቃኖቹን ፡ ደፉንም ፡ ዐምስት ፡ ማእዘን ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 32 ፤ ኹለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፤ የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸባቸው ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ፤ ኪሩቤልናና ፡ የዘንባባውን ፡ ዛፍ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 33 ፤ እንዲሁም ፡ ለመቅደሱ ፡ መግቢያ ፡ ከወይራ ፡ ዕንጨት ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ መቃን ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 34 ፤ ኹለቱንም ፡ ደጆች ፡ ከጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ሠራ ፤ አንዱ ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከኹለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደረገ ፥ ኹለተኛውም ፡ ደጅ ፡ በማጠፊያ ፡ ከተያያዘ ፡ ከኹለት ፡ ሳንቃ ፡ ተደረገ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 35 ፤ የኪሩቤልንና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የፈነዳም ፡ አበባ ፡ ምስል ፡ ቀረጸባቸው ፤ በተቀረጸውም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ በወርቅ ፡ ለበጣቸው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 36 ፤ የውስጠኛውንም ፡ አደባባይ ፡ ቅጥር ፡ ሦስቱን ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፥ አንዱንም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ሠራው ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 37 ፤ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ዚፍ ፡ በሚባል ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተመሠረተ ።

ነገ.1 ፡ 6 ፡ 38 ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ዓመት ፡ ቡል ፡ በሚባል ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ ቤቱ ፡ እንደ ፡ ክፍሎቹና ፡ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ ኹሉ ፡ ተጨረሰ ። በሰባትም ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ሠራው ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ በዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሠራ ፥ የቤቱንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጨረሰ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 2 ፤ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ ቤት ፡ የሚባል ፡ ቤትን ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱንም ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱንም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱንም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ አደረገ ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ በተሠሩ ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አግዳሚ ፡ ሠረገላዎች ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 3 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ በነበሩ ፡ አግዳሚዎች ፡ ቤቱ ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ፤ አዕማዱም ፡ በአንዱ ፡ ተራ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፥ በአንዱ ፡ ተራ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ እየኾኑ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 4 ፤ መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ነበሩ ፥ መስኮቶቹም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያዩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ደጆቹና ፡ መስኮቶቹም ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበሩ ፤ መስኮቶቹም ፡ በሦስት ፡ ተራ ፡ ኾነው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይተያዩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 6 ፤ አዕማዱም ፡ ያሉበቱን ፡ ቤት ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፥ ስፋቱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ አዕማድና ፡ መድረክ ፡ ያሉበት ፡ ወለል ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 7 ፤ ደግሞም ፡ የሚፈርድበት ፡ ዙፋን ፡ ያለበትን ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ አደረገ ። ከወለሉም ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ጣራው ፡ ድረስ ፡ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ተሸፍኖ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 8 ፤ ከፍርድ ፡ ሰቀላ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፥ በሌላውም ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ መኖሪያ ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡ ሠራ ። እንደዚሁም ፡ ያለ ፡ ቤት ፡ ሰሎሞን ፡ ላገባት ፡ ለፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ቤት ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 9 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ከመሠረቱ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ጕልላቱ ፡ ድረስ ፡ በጥሩ ፡ በተጠረበና ፡ በውስጥና ፡ በውጭ ፡ በልክ ፡ በተከረከመ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርተው ፡ ነበር ፤ በውጭውም ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 10 ፤ መሠረቱም ፡ ዐሥር ፡ ወይም ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ በኾነ ፡ በጥሩና ፡ በታላቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 11 ፤ በላዩም ፡ ልክ ፡ ኾኖ ፡ የተከረከመ ፡ ጥሩ ፡ ድንጋይና ፡ የዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 12 ፤ በታላቁም ፡ አደባባይ ፡ ዙሪያ ፡ የነበረው ፡ ቅጥር ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ቅጥርና ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወለል ፡ ሦስቱ ፡ ተራ ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ አንዱም ፡ ተራ ፡ በዝግባ ፡

ሳንቃ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ልኮ ፡ ኪራምን ፡ ከጢሮስ ፡ አስመጣ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 14 ፤ ርሱም ፡ ከንፍታሌም ፡ ወገን ፡ የነበረች ፡ የባል ፡ አልባ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ አባቱም ፡ የጢሮስ ፡ ሰው ፡ ናስ ፡ ሠራተኛ ፡ ነበረ ፤ የናስንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ በብልኀትም ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ መጥቶ ፡ ሥራውን ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 15 ፤ ኹለቱን ፡ የናስ ፡ አዕማድ ፡ አደረገ ፤ የአንዱም ፡ ዐምድ ፡ ቁመት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የዙሪያውም ፡ መጠን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ የዐምዱም ፡ ውፍረት ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ፥ ውስጠ ፡ ክፍትም ፡ ነበረ ። ኹለተኛውም ፡ ዐምድ ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 16 ፤ በኹለቱም ፡ አዕማድ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ ከፈሰሰ ፡ ናስ ፡ ኹለት ፡ ጕልላት ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ የኹለተኛውም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 17 ፤ በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ኹለት ፡ እንደ ፡ መርበብ ፡ ሥራ ፡ አደረገ ፤ አንዱም ፡ መርበብ ፡ ለአንዱ ፡ ጕልላት ፡ ኹለተኛውም ፡ መርበብ ፡ ለኹለተኛው ፡ ጕልላት ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 18 ፤ ሮማኖችንም ፡ ሠራ ፤ ባንድ ፡ ጕልላት ፡ ዙሪያ ፡ በተራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ፥ በአንድም ፡ መርበብ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ተራ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ ለኹለተኛው ፡ ጕልላት ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 19 ፤ በወለሉም ፡ አዕማድ ፡ በነበሩት ፡ ጕልላቶች ፡ ላይ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ ሥራ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ቀረጸ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 20 ፤ በኹለቱም ፡ አዕማድ ፡ በነበሩት ፡ ጕልላቶች ፡ ላይ ፡ በመርበቡ ፡ ሥራ ፡ አጠገብ ፡ ሮማኖቹን ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 21 ፤ አዕማዱንም ፡ በመቅደሱ ፡ ወለል ፡ አጠገብ ፡ አቆማቸው ፤ የቀኙንም ፡ ዐምድ ፡ አቁሞ ፡ ያቁም ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ የግራውንም ፡ ዐምድ ፡ አቁሞ ፡ በለዝ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 22 ፤ በአዕማዱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፡ የሚመስል ፡ ሥራ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ የአዕማዱ ፡ ሥራ ፡ ተጨረሰ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 23 ፤ ከፈሰሰም ፡ ናስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ በዙሪያውም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ክብ ፡ ኵሬ ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 24 ፤ ከከንፈሩም ፡ በታች ፡ ላንድ ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፡ ላንድ ፡ ክንድም ፡ ዐሥር ፡ ጕብጕቦች ፡ አዞረበት ፤ ርሱም ፡ በቀለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጕብጕቦቹ ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ቀልጠው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 25 ፤ ኵሬውም ፡ በዐሥራ ፡ ኹለት ፡ በሬዎች ፡ ምስል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ሦስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፥ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። ኵሬውም ፡ በላያቸው ፡ ነበረ ፥ የኹሉም ፡ ገርርባቸው ፡ በስተውስጥ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 26 ፤ ውፍረቱም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ነበረ ፤ ከንፈሩም ፡ እንደ ፡ ጽዋ ፡ ከንፈር ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ እንደ ፡ ሱፍ ፡ አበባዎች ፡ ኾኖ ፡ ተከርክሞ ፡ ነበር ። ኹለት ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 27 ፤ ዐሥርም ፡ የናስ ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፤ የአንዱም ፡ መቀመጫ ፡ ርዝመት ፡ አራት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ አራት ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 28 ፤ የመቀመጫውም ፡ ሥራ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፤ በክፈፎችም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ሰንበር ፡ ይመስል ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 29 ፤ በክፈፎቹም ፡ መካከል ፡ በነበሩ ፡ ሰንበሮች ፡ ላይ ፡ አንበሳዎችና ፡ በሬዎች ፡ ኪሩቤልም ፡ ነበሩ ፤ እንዲሁም ፡ በክፈፎቹ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ ከአንበሳዎቹና ፡ ከበሬዎቹ ፡ በታች ፡ ሻኩራ ፡ የሚመስል ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 30 ፤ በየመቀመጫዎቹም ፡ ሹሉ ፡ አራት ፡ የናስ ፡ መንኰራኵሮች ፡ ነበሩባቸው ፤ መንኰራኵሮቹም ፡ የሚዞሩበትን ፡ የናስ ፡ ወስከምት ፡ ሠራ ፤ ከመታጠቢያውም ፡ ሰን ፡ በታች ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ በምስል ፡ የፈሰሱ ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 31 ፤ በክፈፉም ፡ ውስጥ ፡ የነበረ ፡ ዐንገት ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ዐንገቱም ፡ ድቡልቡል ፡ ነበረ ፥ ቁመቱም ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ። በዐንገቱም ፡ ላይ ፡ ቅርጽ ፡ ነበረበት ፤ ክፈፉ ፡ ግን ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ድቡልቡል ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 32 ፤ አራቱም ፡ መንኰራኵሮች ፡ ከሰንበሮቹ ፡ በታች ፡ ነበሩ ፤ የመንኰራኵሮቹም ፡ ወስከምት ፡ በመቀመጫው ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ፤ የመንኰራኵሩም ፡ ቁመት ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 33 ፤ የመንኰራኵሮቹም ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ሠረገላ ፡ መንኰራኵር ፡ ነበረ ፥ ወስከምቶቹና ፡ የመንኰራኵሮቹ ፡ ክፈፍ ፡ ቅትርቶቹም ፡ ወስከምቱም ፡ የሚገባበት ፡ ቧምቧ ፡ ሹሉ ፡ በምስል ፡ የፈሰሰ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 34 ፤ በያንዳንዱም ፡ መቀመጫ ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ደገፋዎች ፡ ነበሩ ፤ ደገፋዎቹም ፡ ከመቀመጫው ፡ ጋራ ፡ ተገጥመው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 35 ፤ በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ ስንዝር ፡ የሚኾን ፡ ድቡልቡል ፡ ነገር ፡ ነበረ ፤ በመቀመጫውም ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ መያዣዎችና ፡ ሰንበሮች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይጋጠሙ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 36 ፤ በመያዣውና ፡ በሰንበሮቹ ፡ ላይ ፡ ኪሩቤልንና ፡ አንበሳዎችን ፡ የዘንባባውንም ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ መጠናቸው ፡ ቀረጸ ፥ በዙሪያውም ፡ ሻኩራ ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 37 ፤ እንዲሁ ፡ ዐሥሩን ፡ መቀመጫዎች ፡ ሠራ ፤ ሹሉም ፡ በምስልና ፡ በመጠን ፡ በንድፍም ፡ ትክክሎች ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 38 ፤ ዐሥሩንም ፡ የናስ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ሠራ ፤ አንዱ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አርባ ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ያነሣ ፡ ነበር ፤ እያንዳንዱም ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በዐሥሩም ፡ መቀመጫዎች ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 39 ፤ ዐምስቱንም ፡ መቀመጫዎች ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በቤቱ ፡ ግራ ፡ አኖራቸው ፤ ኵሬውንም ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 40 ፤ ኪራምም ፡ ምንችቶችንና ፡ መጫሪያዎችን ፡ ድስቶችንም ፡ ሠራ ፤ ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሹሉ ፡ ጨረሰ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 41 ፤ ኹለቱም ፡ አዕማድ ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኩብ ፡ የሚመስሉትን ፡ ጕልላቶች ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ የሚሸፍኑትን ፡ ኹለቱን ፡ መርበቦች ፥

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 42 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ኹለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ለያንዳንዱ ፡ መርበብ ፡ በኹለት ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ አድርጎ ፡ ለኹለቱ ፡ መርበቦች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 43 ፤ ዐሥሩንም ፡ መቀመጫዎች ፥ በመቀመጫዎችም ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ዐሥሩን ፡ መታጠቢያ ፡ ሰን ፥

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 44 ፤ አንዱንም ፡ ኵሬ ፥ ከኵሬውም ፡ በታች ፡ የሚኾኑትን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ በሬዎች ፥

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 45 ፤ ምንቸቶቹንም ፥ መጫሪያዎቹንም ፥ ድስቶቹንም ፡ አደረገ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራው ፡ ይህ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 46 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ሜዳ ፡ በሱኮትና ፡ በጸርታን ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በወፍራሙ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ አስፈሰሰው ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 47 ፤ ሰሎሞንም ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፡ ሳያስመዝን ፡ አኖረ ፤ የናሱም ፡ ሚዛን ፡ ከብዛቱ ፡ የተነሣ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 48 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አሠራ ፤ የወርቁን ፡ መሠዊያ ፥ የገጹም ፡ ኅብስት ፡ የነበረበትን ፡ የወርቅ ፡ ገበታ ፥

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 49 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑ ፡ ፊት ፡ ዐምስቱ ፡ በቀኝ ፡ ዐምስቱም ፡ በግራ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የተሠሩትንም ፡ መቅረዞች ፥ የወርቁንም ፡ አበባዎችና ፡ ቀንዲሎች ፡ መኰስተሪያዎችም ፥

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 50 ፤ ከጥሩ ፡ ወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ ጽዋዎችና ፡ ጕጠቶች ፥ ድስቶቹንና ፡ ጭልፋዎቹንም ፥ ማንደጃዎቹንም ፥ ለውስጠኛውም ፡ ቤት ፡ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደጆች ፡ ለቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ደጆች ፡ የሚኾኑትን ፡ የወርቅ ፡ ማጠፊያዎች ፡ አሠራ ።

ነገ.1 ፡ 7 ፡ 51 ፤ እንዲሁ ፡ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተፈጸመ ። አባቱም ፡ ዳዊት ፡ የቀደሰውን ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ዕቃም ፥ ሰሎሞን ፡ አገባ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በነበሩ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ አኖረው ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከጽዮን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የነገድ ፡ አለቃዎችን ፡ ኹሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ቤቶች ፡ መሳፍንት ፥ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰባቸው ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 2 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ኤታኒም ፡ በሚባል ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ተከማቹ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፤ ካህናቱም ፡ ታቦቱን ፡ አነሡ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፥ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፥ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አመጡ ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ አመጡ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፥ ከብዛታቸው ፡ የተነሣ ፡ የማይቈጠሩትንና ፡ የማይመጠኑትን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በቤቱ ፡ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ ከኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ አመጡት ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ኪ.ሩቤልም ፡ በታቦቱ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ነበር ፤ ኪ.ሩቤልም ፡ ታቦቱንና ፡ መሎጊያዎቹን ፡ በስተላይ ፡ በኩል ፡ ሸፍነው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 8 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ ረዣዥሞች ፡ ነበሩ ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ፊት ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ጫፎቻቸው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፤ በውጭ ፡ ያለ ፡ ግን ፡ አያያቸውም ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ አሉ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 9 ፤ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥ ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ከኹለቱ ፡ የድንጋይ ፡ ጽላቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልነበረበትም ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 10 ፤ ካህናቱም ፡ ከመቅደሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ደመናው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞላው ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶ ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ከደመናው ፡ የተነሣ ፡ ለማገልገል ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 12 ፤ ሰሎሞንም ፦ እግዚአብሔር ፦ በጨለማው ፡ ውስጥ ፡ እኖራለኹ ፡ ብሏል ፤

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 13 ፤ እኔም ፡ ለዘለዓለም ፡ የምትኖርበት ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ በእውነት ፡ ሠራኹልኽ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 14 ፤ ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መረቀ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 15 ፤ 16 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ በርሷም ፡ ቤት ፡ ይሠራልኝ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ከተማ ፡ አልመረጥኹም ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ መርጫለኹ ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ መርጫለኹ ፡ ብሎ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ በአፉ ፡ የተናገረ ፥ በእጁም ፡ የፈጸመ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 17 ፤ አባቴም ፡ ዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አባቴን ፡ ዳዊትን ፦ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልብኽ ፡ ዐስበኻልና ፥ ይህን ፡ በልብኽ ፡ ማሰብኽ ፡ መልካም ፡ አደረግኽ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወገብኽ ፡ የሚወጣው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡ አንተ ፡ አይደለኽም ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አጸና ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ ተነሣኹ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኹ ፥ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ሠራኹ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 21 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ ባወጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላለበት ፡ ታቦት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ አደረግኹለት ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 22 ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እጆቹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ በላይ ፡ በሰማይ ፡ በታችም ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ በፊትኽ ፡ ለሚኼዱ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡

የምትጠብቅ ፥

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 24 ፤ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸውን ፡ ተስፋ ፡ የጠበቅኽ ፤ በአፍኽ ፡ ተናገርኽ ፥ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀንም ፡ በእጅኽ ፡ ፈጸምኸው ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 25 ፤ አኹንም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ። አንተ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ኼድኽ ፡ ልጆችኽ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፥ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ አታጣም ፡ ብለኽ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠኸውን ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ ጠብቅ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 26 ፤ አኹንም ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የተናገርኸው ፡ ቃል ፥ እባክኽ ፥ ይጽና ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 27 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖራልን ፧ እንሆ ፥ ሰማይ ፡ ከሰማያትም ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ሰማይ ፡ ይይዝኽ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ይልቁንስ ፡ እኔ ፡ የሠራኹት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ያንስ! ፡

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ወደባሪያኽ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ተመልከት ፥ ዛሬም ፡ ባሪያኽ ፡ በፊትኽ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎትና ፡ ጥሪውን ፡ ስማ ፤

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 29 ፤ ባሪያኽ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፦ በዚያ ፡ ስሜ ፡ ይኾናል ፡ ወዳልኸው ፡ ስፍራ ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዐይኖችኽ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 30 ፤ ባሪያኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ልመና ፡ ስማ ፤ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ ሰምተኽም ፡ ይቅር ፡ በል ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 31 ፤ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢበድል ፥ በላዩም ፡ መሐላ ፡ ቢጫን ፥ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በመሠዊያኽ ፡ ፊት ፡ ቢምል ፥

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 32 ፤ በሰማይ ፡ ስማ ፡ አድርግም ፤ በባሪያዎችኽም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ኹን ፤ በበደለኛውም ፡ ላይ ፡ ፍረድ ፥ መንገዱንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መልስበት ፤ ንጹሑን ፡ አጽድቀው ፥ እንደ ፡ ጽድቁም ፡ ክፈለው ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 33 ፤ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ድል ፡ በተመቱ ፡ ጊዜ ፥ ወዳንተ ፡ ቢመለሱ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ በዚህም ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩና ፡ ቢለምኑኽ ፥

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 34 ፤ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የሕዝብኽንም ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፥ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡ ምድር ፡ መልሳቸው ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 35 ፤ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰማይ ፡ በተዘጋ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብም ፡ ባልዘነበ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቢጸልዩ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ ባስጨነቅኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ቢመለሱ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 36 ፤ የሚኼዱበትንም ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ በማሳየት ፡ የባሪያዎችኽንና ፡ የሕዝብኽን ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ለሕዝብኽም ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ለሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ዝናብ ፡ ስጥ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 37 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ፥ ወይም ፡ ቸነፈር ፥ ወይም ፡ ዋግ ፥ ወይም ፡ ዐረማሞ ፥ ወይም ፡ አንበጣ ፥ ወይም ፡ ኵብኵባ ፡ ቢኾን ፥ የሕዝብኽም ፡ ጠላት ፡ የአገሩን ፡ ቀበሌዎች ፡ ከቦ ፡ ቢያስጨንቃቸው ፥ መቅሠፍትና ፡ ደዌ ፡ ኹሉ ፡ ቢኾን ፥

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 38 ፤ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ የልቡን ፡ ሕመም ፡ ዐውቆ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ቢጸልይ ፥ እጆቹንም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ቢዘረጋ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 39 ፤ 40 ፤ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ይቅርም ፡ በል ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ ታውቃለኽና ፡ ልቡን ፡ ለምታውቀው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ኹሉ ፡ መጠን ፡ ክፈለውና ፡ ስጠው ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 41 ፤ 42 ፤ ከሕዝብኽም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ያልኾነ ፡ እንግዳ ፡ ታላቁን ፡ ስምኽን ፥ ብርቱዉቱንም ፡ እጅኽን ፥ የተዘረጋውንም ፡ ክንድኽን ፡ ሰምቶ ፡ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ መጥቶም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 43 ፤ አንተ ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ስምኽን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽም ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፥ በዚህም ፡ በሠራኹት ፡ ቤት ፡ ስምኽ ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንግዳው ፡ የሚለምንኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 44 ፤ ሕዝብኽም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመውጋት ፡ አንተ ፡ በምትልካቸው ፡ መንገድ ፡ ቢወጡ ፥ አንተም ፡ ወደመረጥኻት ፡ ከተማ ፡ እኔም ፡ ለስምኽ ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቢጸልዩ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 45 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 46 ፤ የማይበድልም ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንተን ፡ ቢበድሉ ፥ ተቈጥተኽም ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ብትሰጣቸው ፡ ሩቅ ፡ ወይም ፡ ቅርብ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ወደጠላቶች ፡ አገር ፡ ቢማረኩም ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 47 ፤ በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ኾነው ፡ በልባቸው ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፥ በማራኪዎቹም ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ተመልሰው ፦ ኀጢአት ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፉንም ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ ቢለምኑኽ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 48 ፤ በማረኳቸው ፡ በጠላቶቻቸው ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ ወዳንተ ፡ ቢመለሱ ፥ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኻት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ወደመረጥኻትም ፡ ከተማ ፡ ለስምኽም ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 49 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 50 ፤ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ፥ አንተንም ፡ የበደሉኽን ፡ ሕዝብኽን ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ በደላቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ይራሩላቸውም ፡ ዘንድ ፡ በማረኳቸው ፡ ፊት ፡ ምሕረት ፡ ስጣቸው ፤

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 51 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከብረት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ያወጣኻቸው ፡ ሕዝብኽና ፡ ርስትኽ ፡ ናቸውና ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 52 ፤ በጠሩኽ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ትሰማቸው ፡ ዘንድ ፡ ለባሪያኽና ፡ ለሕዝብኽ ፡ ለእስራኤል ፡ ልመና ፡ ዐይኖችኽ ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 53 ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አባቶቻችንን ፡ ከግብጽ ፡ ባወጣኽ ፡ ጊዜ ፡ በባሪያኽ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ ርስት ፡ ይኾኑኽ ፡ ዘንድ ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ለይተኻቸዋልና ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 54 ፤ ሰሎሞንም ፡ ይህችን ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸልዮ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ እጁንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘርግቶ ፡ ነበርና ፥ ከእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ተነሣ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 55 ፤ ቆሞም ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲመርቅ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 56 ፤ እንደተናገረው ፡ ተስፋ ፡ ኹሉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ዕረፍትን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፤ በባሪያው ፡ በሙሴ ፡ ከሰጠው ፡ ከመልካም ፡ ተስፋ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አልወደቀም ።

ነገ.1 ፡ 8 ፡ 57 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡

ይኹን ፤ አይተወን ፥ አይጣለንም ፤

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 58 ፤ በመንገዱም ፡ ኹሉ ፡ እንኴድ ፡ ዘንድ ፥ ለአባቶቻችንም ፡ ያዘዛትን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ትእዛዙንም ፡ እንጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ ልባችንን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያዘነብል ፡ ዘንድ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 59 ፤ ለባሪያውና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ፍርድን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የለመንኋት ፡ ቃል ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀረበች ፡ ትኹን ፤

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 60 ፤ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 61 ፤ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቀን ፡ በሥርዐቱ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፥ ትእዛዙንም ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ልባችኹ ፡ ፍጹም ፡ ይኹን ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 62 ፤ ንጉሡም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 63 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ ለደኅንነት ፡ መሥዋዕት ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎችና ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ አቀረበ ። ንጉሡና ፡ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀደሱ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 64 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያለው ፡ የናሱ ፡ መሠዊያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ በዚያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ አሳርጓልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የአደባባዩ ፡ መካከል ፡ ንጉሡ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ቀደሰ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 65 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፥ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓሉን ፡ አደረጉ ።

ነገ.1 ፥ 8 ፥ 66 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናበተ ፤ እነርሱም ፡ ንጉሡን ፡ መረቁ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለባሪያው ፡ ለዳዊትና ፡ ለሕዝቡ ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ኹሉ ፡ በልባቸው ፡ ተደስተው ፡ ሐሤትም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ኼዱ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፥ የንጉሡን ፡ ቤትና ፡ ሰሎሞን ፡ የወደደውን ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ኹሉ ፡ ሠርቶ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በገባዖን ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ተገለጠለት ፡ ዳግመኛ ፡ ተገለጠለት ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ በፊቴ ፡ የጸለይኸውን ፡ ጸሎትኽንና ፡ ልመናኽን ፡ ሰምቻለኹ ፤ ለዘለዓለምም ፡ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የሠራኸውን ፡ ቤት ፡ ቀድሻለኹ ፤ ዐይኖቼና ፡ ልቤም ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ይኾናሉ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 4 ፤ ዳዊትም ፡ አባትኽ ፡ በየዋህ ፡ ልብና ፡ በቅንነት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ በፊቴ ፡ ብትኼድ ፥ ያዘዝኹኽንም ፡ ኹሉ ፡ ብታደርግ ፥ ሥርዐቴንም ፡ ፍርዴንም ፡ ብትጠብቅ ፥

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 5 ፤ እኔ ፦ ከእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ከዘርኽ ፡ ሰው ፡ አታጣም ፡ ብዬ ፡ ለአባትኽ ፡ ለዳዊት ፡ እንደ ፡

ተናገርኹ ፥ የመንግሥትኽን ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለኹ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 6 ፤ እናንተና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከመከትል ፡ ብትመለሱ ፥ የሰጠኋችኹንም ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ባትጠብቁ ፥ ኼዳችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፥ ብትሰግዱላቸውም ፥

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 7 ፤ እስራኤልን ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ አጠፋቸዋለኹ ፤ ለስሜም ፡ የቀደስኹትን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ከፊቴ ፡ እጥለዋለኹ ፤ እስራኤልም ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ ይኾናሉ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 8 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውም ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ባድማ ፡ ይኾናል ፤ በዚያም ፡ የሚያልፍ ፡ ኹሉ ፡ እያፏጨ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ አገርና ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፧ ብሎ ፡ ይደነቃል ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 9 ፤ መልሰውም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አባቶቻቸውን ፡ ያወጣውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፥ ስለ ፡ ሰገዱላቸውም ፥ ስለ ፡ አመለኳቸውም ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አመጣባቸው ፡ ይላሉ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ኹለቱን ፡ ቤቶች ፡ የሠራበት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 11 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ በገሊላ ፡ ምድር ፡ ያሉትን ፡ ኻያ ፡ ከተማዎች ፡ ለኪራም ፡ ሰጠው ። የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ የሚሻውን ፡ ያኽል ፡ የዝግባና ፡ የጥድ ፡ ዕንጨት ፡ የሚሻውንም ፡ ያኽል ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ ለሰሎሞን ፡ ሰጥቶት ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 12 ፤ ኪራምም ፡ ሰሎሞን ፡ የሰጠውን ፡ ከተማዎች ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ከጢሮስ ፡ ወጣ ፤ ደስም ፡ አላሠኙትም ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 13 ፤ ርሱም ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ የሰጠኸኝ ፡ እነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አለ ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የከቡል ፡ አገር ፡ ተብለው ፡ ተጠሩ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 14 ፤ ኪራምም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ለንጉሡ ፡ ላከ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የራሱን ፡ ቤት ፥ ሚሎንም ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፥ ሐጾርንም ፥ መጊዶንም ፥ ጌዝርንም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ገባሮችን ፡ መልምሎ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 16 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ወጥቶ ፡ ጌዝርን ፡ ይዞ ፡ ነበር ፥ በእሳትም ፡ አቃጥሎ ፡ ነበር ፥ በከተማም ፡ የኖሩትን ፡ ከነዓናውያን ፡ ገድሎ ፡ ነበር ፤ ለልጁም ፡ ለሰሎሞን ፡ ሚስት ፡ ትሎት ፡ አድርጎ ፡ ሰጥቷት ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 17 ፤ ሰሎሞንም ፡ ጌዝርን ፥ የታችኛውንም ፡ ቤት ፡

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 18 ፤ ሖሮን ፥ ባዕላትንም ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ተድሞርን ፥

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 19 ፤ ለሰሎሞንም ፡ የነበሩትን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ የሠረገላውንም ፡ ከተማዎች ፥ የፈረሰኞችንም ፡ ከተማዎች ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሊባኖስም ፡ በመንግሥቱም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ሰሎሞን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የወደደውን ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 20 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ያልነበሩትን ፡ ከአሞራውያንና ፡ ከኬጢያውያን ፥ ከፌርዛውያን ፥ ከዔዊያውያንና ፡ ከኢያቡሳውያን ፡ የቀሩትን ፥

ነገ.1 ፡ 9 ፡ 21 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያጠፏቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልቻሉትን ፥ በኋላቸው ፡ የቀሩትን ፡

ልጆቻቸውን ፥ ሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገባሮች ፡ አድርጎ ፡ መለመላቸው ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 22 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ ባሪያ ፡ አላደረገም ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ሰልፈኞች ፥ ሎሌዎችም ፥ መሳፍንትም ፥ አለቃዎችም ፥ የሠረገላዎችና ፡ የፈረሶች ፡ ባልደራሶች ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 23 ፤ ሰሎሞንም ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሠራተኛውን ፡ ሕዝብ ፡ የሚያዙ ፡ አለቃዎች ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 24 ፤ የፈርዖንም ፡ ልጅ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ሰሎሞን ፡ ወደሠራላት ፡ ወደ ፡ ቤቷ ፡ ወጣች ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሚሎን ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 25 ፤ ሰሎሞንም ፡ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የሚቃጠለውንና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ዕጣን ፡ ያሳርግ ፡ ነበር ፤ ቤቱንም ፡ ጨረሰ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 26 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ በኤሎት ፡ አጠገብ ፡ ባለችው ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ መርከቦችን ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 27 ፤ ኪራምም ፡ በእነዚያ ፡ መርከቦች ፡ ከሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ የባሕሩን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁ ፡ መርከበኞች ፡ ባሪያዎቹን ፡ ሰደደ ።

ነገ.1 ፥ 9 ፥ 28 ፤ ወደ ፡ ኦፊርም ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ይዘው ፡ መጡ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 1 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የወጣለትን ፡ የሰሎሞንን ፡ ዝና ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 2 ፤ በግመሎችም ፡ ላይ ፡ ሽቱና ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቊ ፡ አስጫና ፡ ከታላቅ ፡ ኀዝ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ገባች ፤ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ በልቧ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አጫወተችው ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ የጠየቀችውን ፡ ኹሉ ፡ ፈታላት ፤ ሊፈታላት ፡ ያልቻለውና ፡ ከንጉሡ ፡ የተሰወረ ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 4 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፥ ሠርቶትም ፡ የነበረውን ፡ ቤት ፥

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 5 ፤ የማእዱንም ፡ መብል ፥ የብላቴናዎቹንም ፡ አቀማመጥ ፥ የሎሌዎቹንም ፡ አሠራር ፡ አለባበሳቸውንም ፥ ጠጅ ፡ አሳላፊዎቹንም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚያሳርገውን ፡ መሥዋዕት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ አልቀረላትም ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 6 ፤ ንጉሡንም ፡ አለችው ፦ ስለ ፡ ነገርኽና ፡ ስለ ፡ ጥበብኽ ፡ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የሰማኹት ፡ ዝና ፡ እውነት ፡ ነው ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 7 ፤ እኔም ፡ መጥቼ ፡ በዐይኔ ፡ እስካይ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንኹም ፡ ነበር ፤ እንሆም ፥ እኩሌታውን ፡ አልነገሩኝም ፡ ነበር ፤ ጥበብኽና ፡ ሥራኽ ፡ ከሰማኹት ፡ ዝና ፡ ይበልጣል ።

ነገ.1 ፥ 10 ፥ 8 ፤ በፊትኽ ፡ ዘልጊዜ ፡ የሚቆሙ ፡ ጥበብኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎችኽና ፡ እነዚህ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 9 ፤ አንተን ፡ የወደደ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ያስቀመጠኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፤ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወዶታልና ፥ ስለዚህ ፡ ጽድቅና ፡ ፍርድ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ አስነሣኽ ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 10 ፤ ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፥ የከበረም ፡ ዕንቊ ፡ ሰጠችው ፤ የሳባ ፡ ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠችው ፡ ያለ ፡ የሽቱ ፡ ብዛት ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አልመጣም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 11 ፤ ከኦፊርም ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ የኪራም ፡ መርከቦች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨትና ፡ የከበረ ፡ ዕንቊ ፡ ከኦፊር ፡ አመጡ ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰንደሉ ፡ ዕንጨት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ለንጉሡ ፡ ቤት ፡ መከታ ፥ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡ በገና ፡ አደረገ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨት ፡ ከቶ ፡ አልመጣም ፡ አልታየምም ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፥ በገዛ ፡ እጁ ፡ ከሰጣት ፡ ሌላ ፥ የወደደችውን ፡ ኹሉ ፡ ከርሱም ፡ የለመነችውን ፡ ኹሉ ፡ ለሳባ ፡ ንግሥት ፡ ሰጣት ፤ ርሷም ፡ ተመልሳ ፡ ከባሪያዎቿ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሯ ፡ ኼደች ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 14 ፤ 15 ፤ ግብርም ፡ የሚያስገብሩ ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎችም ፡ የዐረብም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ የምድርም ፡ ሹማምት ፡ ከሚያወጡት ፡ ሌላ ፥ በየዓመቱ ፡ ለሰሎሞን ፡ የሚመጣለት ፡ የወርቅ ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 16 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 17 ፤ ከጥፍጥፍም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ ጋሻ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ምናን ፡ ነበረ ፤ ንጉሡም ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ከዝኖን ፡ ጥርስ ፡ ታላቅ ፡ ዙፋን ፡ አሠራ ፥ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ዙፋንም ፡ የሚያስኼዱ ፡ ስድስት ፡ ዕርከኖች ፡ ነበሩ ፤ በስተኋላውም ፡ ያለው ፡ የዙፋኑ ፡ ራስ ፡ ክብ ፡ ነበረ ፤ በዚህና ፡ በዚያ ፡ በመቀመጫው ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ የክንድ ፡ መደገፊያዎች ፡ ነበሩበት ፥ በመደገፊያዎቹም ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 20 ፤ በስድስቱም ፡ ዕርከኖች ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተሠራም ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የሚጠጣበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፥ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ የተባለውም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ እንጂ ፡ ብር ፡ አልነበረም ። በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብር ፡ ከቶ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 22 ፤ ለንጉሡም ፡ ከኪራም ፡ መርከቦች ፡ ጋራ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ፤ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ዓመትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፥ የዝኖንም ፡ ጥርስ ፥ ዝንጀሮና ፡ ዝንጕርጕር ፡ ወፍ ፡ ይዘው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 23 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በባለጠግነትና ፡ በጥበብ ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በልጦ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 24 ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ያኖረለትን ፡ ጥበቡን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ የሰሎሞንን ፡ ፊት ፡ ይመኝ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 25 ፤ ከነርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ በዓመቱ ፡ በዓመቱ ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፥ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፥ ልብስና ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፥ ሽቱም ፥ ፈረሶችና ፡ በቅሎዎች ፡ እየያዘ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 26 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሰበሰበ ፤ አንድ ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ፥ በሠረገላዎችም ፡ ከተማዎች ፡ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡ በቈላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 28 ፤ ሰሎሞንም ፡ ፈረሶችን ፡ ከግብጽና ፡ ከቀዌ ፡ አገር ፡ አስመጣ ፤ የንጉሡም ፡ ነጋዴዎች ፡ በገንዘብ ፡ እየገዙ ፡ ከቀዌ ፡ ያመጧቸው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 10 ፡ 29 ፤ አንዱም ፡ ሠረገላ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፥ አንዱም ፡ ፈረስ ፡ በመቶ ፡ ዐምሳ ፡ ብር ፡ ከግብጽ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ለኬጢያውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ሹሉ ፡ በእጃቸው ፡ ያወጡላቸው ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከፈርዖን ፡ ልጅ ፡ ሌላ ፥ በሞዐባውያንና ፡ በአሞናውያን ፡ በኤዶማውያን ፡ በሲዶናውያንና ፡ በኬጢያውያን ፡ ሴቶች ፥ በብዙ ፡ እንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ ፍቅር ፡ ተነደፈ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፦ አምላኮቻቸውን ፡ ትከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ልባችኹን ፡ በእውነት ፡ ያዘነብላሉና ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አትግቡ ፥ እነርሱም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይግቡ ፡ ካላቸው ፡ ከአሕዛብ ፥ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ ሰሎሞን ፡ በፍቅር ፡ ተጣበቀ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 3 ፤ ለርሱም ፡ ወይዛዝር ፡ የኾኑ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሚስቶች ፡ ሦስት ፡ መቶም ፡ ቁባቶች ፡ ነበሩት ፤ ሚስቶቹም ፡ ልቡን ፡ አዘነበሉት ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 4 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሲሸመግል ፡ ሚስቶቹ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አዘነበሉት ፤ የአባቱ ፡ የዳዊት ፡ ልብ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሰሎሞን ፡ ልቡ ፡ እንዲሁ ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 5 ፤ ሰሎሞንም ፡ የሲዶናውያንን ፡ አምላክ ፡ ዐስታሮትን ፥ የአሞናውያንንም ፡ ርኵሰት ፡ ሚልኮምን ፥ ተከተለ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረገ ፥ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመከተል ፡ ፍጹም ፡ አልኾነም ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ ለሞዐብ ፡ ርኵሰት ፡ ለካሞሽ ፥ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ርኵሰት ፡ ለሞሎክ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መስገጃ ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 8 ፤ ለአማልክታቸው ፡ ዕጣን ፡ ለሚያጥኑ ፡ መሥዋዕትም ፡ ለሚሠዉ ፡ ለእንግዳዎች ፡ ሚስቶቹ ፡ ሹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 9 ፤ 10 ፤ ኹለት ፡ ጊዜም ፡ ከተገለጠለት ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ እንዳይከተል ፡ ካዘዘው ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ አርቋልና ፥ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ አልጠበቀምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰሎሞንን ፡ ተቈጣ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ሠርተኻልና ፥ ያዘዝኹኽንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንና ፡

ሥርዐቴን ፡ አልጠበቅኽምና ፡ መንግሥትኽን ፡ ከአንተ ፡ ቀዳድጄ ፡ ለባሪያኽ ፡ አሰጠዋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከልጅኽ ፡ እጅ ፡ እቀደዋለኹ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ አባትኽ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህን ፡ በዘመንኽ ፡ አላደርግም ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊትና ፡ ስለመረጥኋት ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለልጅኽ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ እሰጣለኹ ፡ እንጂ ፡ መንግሥቱን ፡ ኹሉ ፡ አልቀድም ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኤዶምያስ ፡ ነገሥታት ፡ ዘር ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰው ፡ ሃዳድን ፡ ጠላት ፡ አድርጎ ፡ በሰሎሞን ፡ ላይ ፡ አስነሣው ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 15 ፤ 16 ፤ ኢዮአብና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ የኤዶምያስን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ እስኪገድሉ ፡ ድረስ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ በኤዶምያስ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ ተወግተው ፡ የሞቱትን ፡ ሊቀብር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ የኤዶምያስንም ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፥

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 17 ፤ ሃዳድ ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ ሃዳድና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ የኾኑ ፡ የአባቱ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኰብልለው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 18 ፤ ከምድያምም ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ፋራን ፡ መጡ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ከፋራን ፡ ሰዎች ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ መጡ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፤ ርሱም ፡ ቤት ፡ ሰጥቶ ፡ ቀለብ ፡ ዳረገው ፥ ምድርም ፡ ሰጠው ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 19 ፤ የሚስቱንም ፡ የእቴጌዩቱን ፡ የቴቄምናስን ፡ እኅት ፡ እስኪያጋባው ፡ ድረስ ፡ ሃዳድ ፡ በፈርዖን ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ባለሟል ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 20 ፤ የቴቄምናስ ፡ እኅት ፡ ጌንባትን ፡ ወለደችለት ፥ ቴቄምናስም ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ አሳደገችው ፤ ጌንባትም ፡ በፈርዖን ፡ ቤት ፡ በፈርዖን ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 21 ፤ ሃዳድም ፡ በግብጽ ፡ ሳለ ፡ ዳዊት ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ እንዳንቀላፋ ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ ኢዮአብ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ሃዳድ ፡ ፈርዖንን ፦ ወደ ፡ አገሬ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ አሰናብተኝ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 22 ፤ ፈርዖንም ፦ እንሆ ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አገርኽ ፡ መኼድ ፡ የፈለግኽ ፡ ምን ፡ ዐጥተኽ ፡ ነው ፧ አለው ። ርሱም ፦ አንዳች ፡ አላጣኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልኺድ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ። ሃዳድም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ፥ ሃዳድም ፡ ያደረገው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እስራኤልን ፡ አስጨነቀ ፥ በኤዶምያስም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከጌታው ፡ ከሱባ ፡ ንጉሥ ፡ ከአድርዐዛር ፡ የኰበለለውን ፡ የኤልያዳን ፡ ልጅ ፡ ሬዞንን ፡ ጠላት ፡ አድርጎ ፡ አስነሣበት ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 24 ፤ ዳዊትም ፡ የሱባን ፡ ሰዎች ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፡ ሬዞን ፡ ሰዎችን ፡ ሰብስቦ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃ ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ደማስቆም ፡ ኼዱ ፥ በዚያም ፡ ተቀመጡ ፤ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ አነገሡት ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 25 ፤ ሃዳድም ፡ ካደረገው ፡ ክፋት ፡ ሌላ ፡ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤል ፡ ጠላት ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 26 ፤ ከሳሪራ ፡ አገር ፡ የኾነ ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያ ፡ የኤፍሬማዊው ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በንጉሡ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፤ እናቱም ፡ ጽሩዓ ፡ የተባለች ፡ ባልቴት ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 27 ፤ በንጉሡም ፡ ያመፀበት ፡ ምክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሰሎሞን ፡ ሚሎን ፡ ሠራ ፥ የአባቱንም ፡ የዳዊትን ፡ ከተማ ፡ ሰባራውን ፡ ጠገነ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 28 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ሰሎሞንም ፡ ጕልማሳው ፡ በሥራ ፡ የተመሰገነ ፡ መኾኑን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 29 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሴሎናዊው ፡ ነቢዩ ፡ አኪያ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተገናኘው ፤ አኪያም ፡ ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ነበር ፥ ኹለቱም ፡ በሜዳው ፡ ለብቻቸው ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 30 ፤ አኪያም ፡ የለበሰውን ፡ ዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ይዞ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ቈራረጠው ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 31 ፤ ኢዮርብዓምንም ፡ አለው ፦ ዐሥር ፡ ቍራጭ ፡ ውሰድ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ከሰሎሞን ፡ እጅ ፡ መንግሥቱን ፡ እቀዳለኹ ፥ ዐሥሩንም ፡ ነገዶች ፡ እሰጥኻለኹ ፤

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 32 ፤ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ስለመረጥኋት ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ይቀርለታል ፤

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 33 ፤ ጥለውኛልና ፥ ለሲዶናውያንም ፡ አምላክ ፡ ለዐስታሮት ፥ ለሞዐብም ፡ አምላክ ፡ ለካሞሽ ፥ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡ አምላክ ፡ ለሚልኮም ፡ ሰግደዋልና ፥ አባቱም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፡ በፊቴ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ፍርዴንም ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዴ ፡ አልኼዱምና ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 34 ፤ መንግሥቱንም ፡ ኹሉ ፡ ከእጁ ፡ አልወስድም ፤ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ስለጠበቀው ፡ ስለመረጥኹት ፡ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ በዕድሜው ፡ ኹሉ ፡ አለቃ ፡ አደርገዋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 35 ፤ መንግሥቱንም ፡ ከልጁ ፡ እጅ ፡ እወስዳለኹ ፥ ለአንተም ፡ ዐሥሩን ፡ ነገድ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 36 ፤ ስሜንም ፡ ባኖርኹባት ፡ በዚያች ፡ በመረጥኋት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ በፊቴ ፡ ዘልጊዜ ፡ መብራት ፡ ይኾንለት ፡ ዘንድ ፡ ለልጁ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ እሰጠዋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 37 ፤ አንተንም ፡ እወስድኻለኹ ፥ ነፍስኽም ፡ በወደደችው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትነግሣለች ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾናለኽ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 38 ፤ ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፥ ያዘዝኹኽን ፡ ኹሉ ፡ ብትሰማ ፥ በመንገዴም ፡ ብትኼድ ፥ በፊቴም ፡ የቀናውን ፡ ብታደርግ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ብትጠብቅ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ ለዳዊትም ፡ እንደ ፡ ሠራኹለት ፡ ጽኑ ፡ ቤት ፡ እሠራልኻለኹ ፥ እስራኤልንም ፡ ለአንተ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 39 ፤ ስለዚህም ፡ የዳዊትን ፡ ዘር ፡ አስጨንቃለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዘመን ፡ ኹሉ ፡ አይደለም ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 40 ፤ ሰሎሞንም ፡ ኢዮርብዓምን ፡ ሊገድለው ፡ ወደደ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኰበለለ ፥ ወደግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሺሻቅ ፡ መጣ ፥ ሰሎሞንም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በግብጽ ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 41 ፤ የቀረውም ፡ የሰሎሞን ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ ጥበቡም ፥ እንሆ ፥ በሰሎሞን ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 42 ፤ ሰሎሞንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 11 ፡ 43 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ሮብዓም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 1 ፤ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፥ ሮብዓም ፡ ወደ ፡

ሴኬም ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ፊት ፡ ከሙብሶ ፡ በግብጽ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበርና ፥ በግብጽም ፡ ሳለ ፡ ልከው ፡ ጠርተውት ፡ ነበርና ፥

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 3 ፤ ኢዮርብዓምና ፡ የእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ ለሮብዓም ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 4 ፤ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ ጽኑውን ፡ የአባትኽን ፡ አገዛዝ ፥ በላያችንም ፡ የጫነውን ፡ የከበደውን ፡ ቀንበር ፡ አቃልልን ፤ እኛም ፡ እንገዛልኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኼዱ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ አባቱ ፡ ሰሎሞን ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አኹን ፡ ባሪያ ፡ ብትኾን ፡ ብትገዛላቸውም ፥ መልሰኽም ፡ በገርነት ፡ ብትናገራቸው ፥ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑልኻል ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካደጉትና ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ብላቴናዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ አባትኽ ፡ የጫኑብንን ፡ ቀንበር ፡ አቃልልን ፡ ለሚሉኝ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያደጉት ፡ ብላቴናዎች ፦ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብናል ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አቃልልን ፡ ለሚሉኽ ፡ ሕዝብ ፦ ታናሺቱ ፡ ጣቴ ፡ ከአባቴ ፡ ወገብ ፡ ትወፍራለች ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ጭኖባችኋል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኋል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፦ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ መጡ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ጽኑ ፡ ምላሽ ፡ መለሰላቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ብላቴናዎችም ፡ ምክር ። አባቴ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ አድርጎ ፡ ለናባጥ ፡ ልጅ ፡ ለኢዮርብዓም ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲያጸና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተመድቦ ፡ ነበርና ፥ ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ አልሰማም ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 16 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳልሰማቸው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ለንጉሡ ። በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡ አለን ፧ በእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ። እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ድንኳኖቻችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ዳዊት ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ ቤትኽን ፡ ተመልከት ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። እስራኤልም ፡ ወደ ፡ ድንኳኖቻቸው ፡ ኼዱ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 17 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በተቀመጡት ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሮብዓም ፡ ነገሠባቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ አስገባሪውን ፡ አዶኒራምን ፡ ሰደደ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በድንጋይ ፡

ደበደቡት ፥ ሞተም ። ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሸሸ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 19 ፤ እስራኤልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ሸፈተ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 20 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ኢዮርብዓም ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልከው ፡ ወደ ፡ ሸንጎቸው ፡ ጠሩት ፥ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አነገሡት ። ከብቻው ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ በቀረ ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ የተከተለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ሮብዓምም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፥ የእስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ወግተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ኹሉና ፡ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ የተመረጡትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰልፈኞች ፡ ሰዎች ፡ ሰበሰበ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 22 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሳማያ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 23 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ለሮብዓምና ፡ ለይሁዳ ፡ ለብንያምም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ለቀረውም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፦

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ አትውጡ ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ አትውጉ ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፡ ሲል ፡ መጣ ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ሰሙ ፥ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ተመልሰው ፡ ኼዱ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 25 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ሴኬምን ፡ ሠርቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ፤ ደግሞም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ጵኒኤልን ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 26 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ በልቡ ፦ አኹን ፡ መንግሥቱ ፡ ወደዳዊት ፡ ቤት ፡ ይመለሳል ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 27 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሥዋዕትን ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቢወጣ ፥ የዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመለሳል ፥ እኔንም ፡ ይገድሉኛል ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 28 ፤ ንጉሡም ፡ ተማከረ ፥ ኹለትም ፡ የወርቅ ፡ ጥጃዎች ፡ አድርጎ ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትወጡ ፡ ዘንድ ፡ ይበዛባችኋል ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጡኽን ፡ አማልክትኽን ፡ እይ ፡ አላቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 29 ፤ አንዱን ፡ በቤቴል ፥ ኹለተኛውንም ፡ በዳን ፡ አኖረ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 30 ፤ ለአንዱ ፡ ጥጃ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ይኼድ ፡ ነበርና ፥ ይህ ፡ ኀጢአት ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 31 ፤ በኰረብታዎቹም ፡ ላይ ፡ መስገጃዎች ፡ ሠራ ፥ ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ ካይደሉ ፡ ከሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 32 ፤ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ እንደሚደረግ ፡ በዓል ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ አደረገ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፤ ለሠራቸውም ፡ ጥጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ በቤቴል ፡ አደረገ ፤ ለኰረብታ ፡ መስገጃዎችም ፡ የመረጣቸውን ፡ ካህናት ፡ በቤቴል ፡ አኖራቸው ።

ነገ.1 ፡ 12 ፡ 33 ፤ በስምንተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በልቡ ፡ ባሰበው ፡ ቀን ፡ በቤቴል ፡ በሠራው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ሠዋ ፤ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በዓል ፡ አደረገላቸው ፤ በመሠዊያውም ፡ ሠዋ ፥ ዕጣንም ፡ ዐጠነ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። _____

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 1 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ መጣ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ዕጣን ፡ እያጠነ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 2 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፦ መሠዊያ ፡ ሆይ ፥ መሠዊያ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ስሙ ፡ ኢዮስያስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ለዳዊት ፡ ቤት ፡ ይወለዳል ፤ ዕጣንም ፡ የሚያጥኑብኽን ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቹን ፡ ካህናት ፡ ይሠዋብኻል ፥ የሰዎቹንም ፡ ዐጥንት ፡ ያቃጥልብኻል ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጮኸ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ እግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንሆ ፥ መሠዊያው ፡ ይሰነጠቃል ፥ በላዩም ፡ ያለው ፡ ዐመድ ፡ ይፈሳል ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጠ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 4 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የጮኸውን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ኢዮርብዓም ፡ እጁን ፡ ከመሠዊያው ፡ አንሥቶ ፦ ያዙት ፡ አለ ። በርሱም ፡ ላይ ፡ የዘረጋት ፡ እጅ ፡ ደረቀች ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ይመልሳት ፡ ዘንድ ፡ አልተቻለውም ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ምልክት ፡ መሠዊያው ፡ ተሠነጠቀ ፥ ዐመዱም ፡ ከመሠዊያው ፡ ፈሰሰ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 6 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ አኹን ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፊት ፡ ለምን ፥ እጄም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ጸልይ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፥ የንጉሡም ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ፥ እንደ ፡ ቀድሞም ፡ ኾነች ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 7 ፤ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ና ፡ እንጀራም ፡ ብላ ፥ በረከትም ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ንጉሡን ፦ የቤትኽን ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ብትሰጠኝ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አልገባም ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ፤

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 9 ፤ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ታዝዤያለኹና ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 10 ፤ በሌላም ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ወደ ፡ ቤቴልም ፡ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ አልተመለሰም ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 11 ፤ በቤቴልም ፡ አንድ ፡ ሽማግሌ ፡ ነቢይ ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ልጆቹም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በቤቴል ፡ ያደረገውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ነገሩት ፡ ደግሞም ፡ ለንጉሡ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ለአባታቸው ፡ ነገሩት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 12 ፤ አባታቸውም ፦ በማናቸው ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፧ አላቸው ። ልጆቹም ፡ ከይሁዳ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ የኼደበትን ፡ መንገድ ፡ አመለከቱት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 13 ፤ ልጆቹንም ፦ አህያውን ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፤ አህያውንም ፡ በጫኑለት ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠበት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 14 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ በኋላ ፡ ኼደ ፤ በአድባርም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀምጦ ፡ አገኘውና ። ከይሁዳ ፡ የመጣኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 15 ፤ ርሱም ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ና ፥ እንጀራም ፡ ብላ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 16 ፤ ርሱም ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እመለስና ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ከአንተ ፡

ጋራ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ፤

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 17 ፤ በዚያ ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ አትመለስ ፡ በሚል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተብሎልኛልና ፥ አለ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 18 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነቢይ ፡ ነኝ ፤ መልአክም ፦ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ውሃም ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ መልሰው ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተናገረኝ ፡ አለው ። ዋሽቶም ፡ ተናገረው ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 19 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ተመለሰ ፥ በቤቱም ፡ እንጀራ ፡ በላ ፥ ውሃም ፡ ጠጣ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 20 ፤ በማእዱም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደመለሰው ፡ ነቢይ ፡ መጣ ፤

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 21 ፤ ከይሁዳም ፡ ወደመጣው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ዐምፀኻልና ፥ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘኽን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅኽምና ፥

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 22 ፤ ተመልሰኽም ፦ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ውሃም ፡ አትጠጣ ፡ ባለኽ ፡ ስፍራ ፡ እንጀራ ፡ በልተኻልና ፥ ውሃም ፡ ጠጥተኻልና ፥ ሬሳኽ ፡ ወዳባቶችኽ ፡ መቃብር ፡ አይደርስም ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 23 ፤ እንጀራም ፡ ከበላ ፥ ውሃም ፡ ከጠጣ ፡ በኋላ ፡ አህያውን ፡ ጫነለት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 24 ፤ ተመልሶም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ፤ ሬሳውም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ነበር ፥ አህያውም ፡ በርሱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ አንበሳውም ፡ ደግሞ ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 25 ፤ እንሆም ፥ መንገድ ፡ ዐላፊ ፡ ሰዎች ፡ ሬሳው ፡ በመንገዱ ፡ ወድቆ ፡ አንበሳውም ፡ በሬሳው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ አዩ ፡ መጥተውም ፡ ሽማግሌው ፡ ነቢይ ፡ ተቀምጦባት ፡ በነበረው ፡ ከተማ ፡ አወሩ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 26 ፤ ያም ፡ ከመንገድ ፡ የመለሰው ፡ ነቢይ ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ በእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ያመፀ ፡ ያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፥ እግዚአብሔር ፡ ለአንበሳ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶታል ፤ ሰብሮም ፡ ገድሎታል ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 27 ፤ ልጆቹንም ፦ አህያ ፡ ጫኑልኝ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ ጫኑለት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 28 ፤ ኼደም ፥ ሬሳውም ፡ በመንገድ ፡ ወድቆ ፥ በሬሳውም ፡ አጠገብ ፡ አህያውና ፡ አንበሳው ፡ ቆመው ፥ አንበሳው ፡ ሬሳውን ፡ ሳይበላው ፥ አህያውንም ፡ ሳይሰብረው ፡ አገኘ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 29 ፤ ነቢዩም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ ሬሳ ፡ አነሣ ፥ በአህያውም ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፡ መለሰው ፤ ያለቅስለትና ፡ ይቀብረው ፡ ዘንድ ፡ ወደገዛ ፡ ከተማው ፡ ይዞት ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 30 ፤ ሬሳውንም ፡ በገዛ ፡ መቃብሩ ፡ አኖረው ፤ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ አለቀሱለት ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 31 ፤ ከቀበረውም ፡ በኋላ ፡ ልጆቹን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ በሞትኹ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በተቀበረበት ፡ መቃብር ፡ ቅበሩኝ ፤ ዐጥንቶቼንም ፡ በዐጥንቶቹ ፡ አጠገብ ፡ አኑሩ ፤

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 32 ፤ በቤቴል ፡ ባለው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፥ በሰማርያም ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ በኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የጮኸው ፡ ነገር ፡ በእውነት ፡ ይደርሳልና ።

ነገ.1 ፥ 13 ፥ 33 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከክፉ ፡ መንገድ ፡ አልተመለሰም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ አብልጦ ፡ ከሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ካህናትን ፡ አደረገ ፤ የሚወደውንም ፡ ኹሉ ፡ ይቀድስ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡

ለኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ ካህን ፡ ይኾን ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 13 ፡ 34 ፤ እስከ.ፈርስም ፡ ከምድርም ፡ እስከ.ጠፋ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ ኾነ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ አብያ ፡ ታመመ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 2 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ሚስቱን ፦ ተነሺ ፥ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ እንደ ፡ ኾንሽ ፡ እንዳትታወቂ ፡ ልብስሽን ፡ ለውጪና ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ኺጂ ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንድነግሥ ፡ የነገረኝ ፡ ነቢዩ ፡ አኪያ ፡ በዚያ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 3 ፤ በእጅሽም ፡ ዐሥር ፡ እንጀራና ፡ ዕንጐቻዎች ፡ አንድም ፡ ምንቸት ፡ ማር ፡ ይዘሽ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ኺጂ ፤ በልጁም ፡ የሚኾነውን ፡ ይነግርሻል ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 4 ፤ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ እንዲሁ ፡ አደረገች ፥ ተነሥታም ፡ ወደ ፡ ሴሎ ፡ ኼደች ፤ ወደአኪያም ፡ ቤት ፡ መጣች ። አኪያም ፡ ስለ ፡ መሸምገሉ ፡ ዐይኖቹ ፡ ፈዘው ፡ ነበርና ፤ ማየት ፡ አልቻለም ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አኪያን ፦ እንሆ ፥ ስለታመመው ፡ ልጇ ፡ ትጠይቅኽ ፡ ዘንድ ፡ የኢዮርብዓም ፡ ሚስት ፡ ትመጣለች ፤ ሌላ ፡ ሴትም ፡ መስላ ፡ ተሰውራለችና ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ በላት ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 6 ፤ ርሷም ፡ በደጅ ፡ ስትገባ ፡ አኪያ ፡ የእግሯን ፡ ኰቴ ፡ ሰማ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የኢዮርብዓም ፡ ሚስት ፡ ሆይ ፥ ግቢ ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ መሰልሽ ፧ እኔም ፡ ብርቱ ፡ ወሬ ፡ ይገፍ ፡ ተልኬልሻለኹ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 7 ፤ ኺጂ ፥ ለኢዮርብዓምም ፡ እንዲህ ፡ በዩው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከሕዝብ ፡ መካከል ፡ ለይቼ ፡ ከፍ ፡ አድርጌኽ ፡ ነበር ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጌኽ ፡ ነበር ፥

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 8 ፤ ከዳዊትም ፡ ቤት ፡ መንግሥቱን ፡ ቀድጄ ፡ ሰጥቼኽ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ እንደ ፡ ተከተለኝ ፥ በፊቴም ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ እንዳደረገ ፥ ትእዛዜንም ፡ እንደ ፡ ጠበቀ ፡ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ አልኾንኽም ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 9 ፤ ከአንተም ፡ አስቀድመው ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ሠራኽ ፤ ታስቈጣኝም ፡ ዘንድ ፡ ኼደኽ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክትና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎች ፡ አደረግኽ ፥ ወደ ፡ ኋላኽም ፡ ጣልኸኝ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ አመጣለኹ ፥ ከኢዮርብአምም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ እቈርጣለኹ ፤ ሰውም ፡ ፋንድያን ፡ እስከ.ጠፋ ፡ ድረስ ፡ እንደሚጠርግ ፡ እኔ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ፈጽሜ ፡ እጠርጋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 11 ፤ ከኢዮርብዓምም ፡ ወገን ፡ በከተማዩቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሞተውን ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ ተነሥተሽ ፡ ወደ ፡ ቤትሽ ፡ ኺጂ ፤ እግርሽም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ይሞታል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 13 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሱለታል ፥ ይቀብሩትማል ፤ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ልጅ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኝቶበታልና ፥ ከኢዮርብዓም ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ ይቀበራል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ያስነሣል ፤ ርሱም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ያጠፋል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 15 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሸምበቆ ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚንቀሳቀስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሁ ፡ እስራኤልን ፡ ይመታል ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ያስቈጡ ፡ ዘንድ ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ተክለዋልና ፥ ለአባቶቻቸው ፡ ከሰጣቸው ፡ ከዚች ፡ ከመልካሚቱ ፡ ምድር ፡ እስራኤልን ፡ ይነቅላል ፥ በወንዙም ፡ ማዶ ፡ ይበትናቸዋል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 16 ፤ ስለበደለውና ፡ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ ስለ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ እስራኤልን ፡ ይጥላል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 17 ፤ የኢዮርብዓምም ፡ ሚስት ፡ ተነሥታ ፡ ኼደች ፥ ወደ ፡ ቴርሳ ፡ መጣች ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ መድረክ ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ሞተ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 18 ፤ በባሪያውም ፡ በነቢዩ ፡ በአኪያ ፡ እንደተነገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ቀበሩት ፡ አለቀሱለትም ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 19 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮርብዓም ፡ ነገር ፥ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፥ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 20 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፤ ከአባቶቹም ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ ልጁም ፡ ናዳብ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 21 ፤ የሰሎሞንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓም ፡ በይሁዳ ፡ ነገሠ ፤ ሮብዓምም ፡ ንጉሥ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስሙን ፡ ያኖርባት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ በመረጣት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ የእናቱም ፡ ስም ፡ ናዕማ ፡ ነበረ ፤ ርኲም ፡ አሞናዊት ፡ ነበረች ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 22 ፤ ይሁዳም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሠራ ፤ አባቶቻቸውም ፡ ከሠሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አብዝተው ፡ በሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ አስቈጡት ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ ኮረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ ቅጠሉ ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ መስገጃዎችንና ፡ ሐውልቶችን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንም ፡ ለራሳቸው ፡ ሠሩ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 24 ፤ በምድርም ፡ ውስጥ ፡ ሰዶማውያን ፡ ነበሩ ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሳደዳቸውን ፡ የአሕዛብን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 25 ፤ ሮብዓምም ፡ በነገሠ ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መዛግብትንና ፡ የንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብትን ፡ ወሰደ ፤ ኹሉንም ፡ ወሰደ ፤ ሰሎሞንም ፡ የሠራውን ፡ የወርቁን ፡ ጋሻ ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በፋንታው ፡ የናስ ፡ ጋሻዎችን ፡ ሠራ ፥ የንጉሥንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ በሚጠብቁ ፡ በዘበኞች ፡ አለቃዎች ፡ እጅ ፡ አኖራቸው ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 28 ፤ ንጉሡም ፡ ዘወትር ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሲገባ ፡ ዘበኞች ፡ ይሸከሟቸው ፡ ነበር ፤ መልሰውም ፡ በዘበኞች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 29 ፤ የቀረውም ፡ የሮብዓም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 30 ፤ በዘመኑም ፡ ዅሉ ፡ በሮብዓምና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 14 ፡ 31 ፤ ሮብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ። ልጁም ፡ አብያም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 1 ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ አብያም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 2 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተባለች ፡ የአቤሴሎም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 3 ፤ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ባደረገው ፡ በአባቱ ፡ ኀጢአት ፡ ዅሉ ፡ ኼደ ፤ ልቡም ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ልብ ፡ ከአምላኩ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልጁን ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መብራት ፡ ሰጠው ፤

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 5 ፤ ዳዊት ፡ በዘመኑ ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ ካዘዘውም ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፡ ነበርና ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 6 ፤ በኢዮርብዓምና ፡ በሮብዓም ፡ ልጅ ፡ በአብያም ፡ መካከል ፡ በዘመኑ ፡ ዅሉ ፡ ጠብ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 7 ፤ የቀረውም ፡ የአብያም ፡ ነገር ፥ ያደርገውም ፡ ዅሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ በአብያምና ፡ በኢዮርብዓምም ፡ መካከል ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 8 ፤ አብያምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ። ልጁም ፡ አሣ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 9 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮርብዓም ፡ በኻያኛውም ፡ ዓመት ፡ አሣ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 10 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ መዓካ ፡ የተባለች ፡ የአቤሴሎም ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 11 ፤ አሣ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 12 ፤ ከአገሩም ፡ ሰዶማውያንን ፡ አስወገደ ፥ አባቶቹም ፡ ያደረጉትን ፡ ጣዖታትን ፡ ዅሉ ፡ አራቀ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 13 ፤ በማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ጣዖት ፡ ስለ ፡ ሠራች ፡ እናቱን ፡ መዓካን ፡ እቴጌ ፡ እንዳትኾን ፡ ሻራት ፤ ጣዖቷንም ፡ ሰበረው ፥ በቄድሮንም ፡ ፈፋ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አላራቀም ፤ የአሣ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ በዘመኑ ፡ ዅሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 15 ፤ አባቱ ፡ የቀደሰውንና ፡ ርሱም ፡ የቀደሰውን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ዕቃውንም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገባው ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 16 ፤ በአሣና ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በባአስ ፡ መካከል ፥ በዘመናቸው ፡ ዅሉ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 17 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባኦስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከአሣ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ እንዳይወጣ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ማንም ፡ እንዳይገባ ፡ አድርጎ ፡ ራማን ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 18 ፤ አሣም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የቀረውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ በባሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ ሰጣቸው ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ በደማስቆ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለዐዚን ፡ ልጅ ፡ ለጠብሪሞን ፡ ልጅ ፡ ለሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ለወልደ ፡ አዴር ፦

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 19 ፤ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ በአባቴና ፡ በአባትኽም ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ጸንቷል ፤ እንሆ ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ሰድጄልኻለኹ ፤ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዲርቅ ፡ ኼደኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባኦስ ፡ ጋራ ፡ ያለኽን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርስ ፡ ብሎ ፡ ሰደደ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 20 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ ለንጉሡ ፡ ለአሣ ፡ ዕሺ ፡ አለው ፤ የሰራዊቱንም ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ሰዶ ፡ ዒዮንንና ፡ ዳንን ፥ አቤልቤት ፡ መዓካንና ፡ ኪኔሬትን ፡ ኹሉ ፡ የንፍታሌምንም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ መታ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 21 ፤ ባኦስም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ራማን ፡ መሥራት ፡ ትቶ ፡ በቴርሳ ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 22 ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ፤ ማንም ፡ ነጻ ፡ አልነበረም ፤ ባኦስም ፡ የሠራበትን ፡ የራማን ፡ ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡ ወሰዱ ፥ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ የብንያምን ፡ ጌባንና ፡ ምጽጳን ፡ ሠራበት ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 23 ፤ የቀረውም ፡ የአሣ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ጭከናውም ፡ ኹሉ ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ የሠራቸውም ፡ ከተማዎች ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ በሸመገለ ፡ ጊዜ ፡ እግሮቹ ፡ ታመሙ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 24 ፤ አሣም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ። ልጁም ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 25 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ናዳብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 26 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በአባቱም ፡ መንገድ ፡ እስራኤልንም ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 27 ፤ ከይሳኮርም ፡ ቤት ፡ የኾነ ፡ የአኪያ ፡ ልጅ ፡ ባኦስ ፡ ተማማለበት ፤ ናዳብና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ገባቶንን ፡ ከበው ፡ ነበርና ፥ ባኦስ ፡ በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በገባቶን ፡ ገደለው ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 28 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ባኦስ ፡ ናዳብን ፡ ገደለው ፥ በፋንታውም ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 29 ፤ 30 ፤ ንጉሥም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መታ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ስለሠራው ፡ ኀጢአት ፥ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስላስቈጣበት ፡ ማስቈጫ ፥ በባሪያው ፡ በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፥ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ አንድ ፡ ትንፋሽ ፡ ያለው ፡ አላስቀረም ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 31 ፤ የቀረውም ፡ የናዳብ ፡ ነገርና ፡ ያደረገው ፡ ኹሉ ፥

(32 ፤) ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 33 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የአኪያ ፡ ልጅ ፡ ባኦስ ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡

ላይ ፡ በቴርሳ ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 15 ፡ 34 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በኢዮርብዓምም ፡ መንገድ ፡ እስራኤልንም ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በባአስ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ወደዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዩ ([167]) ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ከመሬት ፡ አስነሥቼ ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ኼደኻል ፥ በኀጢአታቸውም ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ አስተኻቸዋል ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 3 ፤ ስለዚህም ፥ እንሆ ፥ ባአስንና ፡ ቤቱን ፡ ፈጽሜ ፡ እጠርጋለኹ ፤ ቤትኽንም ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ አደርጋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 4 ፤ ከባአስም ፡ ወገን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሚሞተውን ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 5 ፤ የቀረውም ፡ የባአስ ፡ ነገር ፥ ሥራውና ፡ ጭከናውም ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 6 ፤ ባአስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በቴርሳም ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኤላ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 7 ፤ በእጁም ፡ ሥራ ፡ ያስቈጣው ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስላደረገው ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ ርሱንም ፡ ስለ ፡ ገደለው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በባአስና ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ወደዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 8 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ የባአስ ፡ ልጅ ፡ ኤላ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በቴርሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 9 ፤ የእኩሌታዎቹም ፡ ሠረገላዎች ፡ አለቃ ፡ ዘምሪ ፡ ተማማለበት ፤ ዔላም ፡ በቴርሳ ፡ ነበረ ፥ በቴርሳም ፡ በነበረው ፡ በቤት ፡ አሽከሮች ፡ አለቃ ፡ በአሳ ፡ ቤት ፡ ይሰክር ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 10 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ዘምሪ ፡ ገብቶ ፡ መታው ፡ ገደለውም ፥ በፋንታውም ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 11 ፤ ንጉሥም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ በዙፋኑም ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፥ የባአስን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መታ ፤ ከዘመዶችና ፡ ከወዳጆች ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ እንኳ ፡ አልቀረም ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 12 ፤ 13 ፤ ባአስና ፡ ልጁ ፡ ኤላ ፡ ስለሠሩት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፥ በምናምንቴም ፡ ሥራቸው ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጡት ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ስላሳቱበት ፡ ኀጢአት ፥ በነቢዩ ፡ በኢዩ ፡ እጅ ፡ በባአስ ፡ ላይ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዘምሪ ፡ የባአስን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አጠፋ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 14 ፤ የቀረውም ፡ የኤላ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 15 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ዘምሪ ፡ በቴርሳ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡

---

167 ዕብ. ፥ የሁ ፡ (ያምላክ) ።

ነገሠ ። ሕዝቡም ፡ በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ የነበረው ፡ ገባቶንን ፡ ከዕው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 16 ፤ ከተማዉቱንም ፡ ከዕው ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዘምሪ ፡ እንደ ፡ ዐመፀ ፥ ንጉሡንም ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ሰሙ ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በሰፈሩ ፡ ውስጥ ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ዘንበሪን ፡ አነገሡ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 17 ፤ ዘንበሪም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ከገባቶን ፡ ወጥተው ፡ ቴርሳን ፡ ከበቡ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 18 ፤ ዘምሪም ፡ ከተማዉቱ ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ፤

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 19 ፤ ስላደረገውም ፡ ኀጢአት ፥ እስራኤልንም ፡ ስላሳተበት ፡ ኀጢአት ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አድርጓልና ፥ በኢዮርብዓምም ፡ መንገድ ፡ ኼዷልና ፥ ሞተ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 20 ፤ የቀረውም ፡ የዘምሪ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ዐመፅ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ በኹለት ፡ ተከፈለ ፤ የሕዝቡም ፡ እኩሌታ ፡ የጎናትን ፡ ልጅ ፡ ታምኒን ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ተከተለው ፤ እኩሌታውም ፡ ዘንበሪን ፡ ተከተለ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 22 ፤ ዘንበሪንም ፡ የተከተለ ፡ ሕዝብ ፡ የጎናትን ፡ ልጅ ፡ ታምኒን ፡ በተከተለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ በረታ ፤ ታምኒም ፡ ሞተ ፥ ዘንበሪም ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 23 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሠላሳ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ዘንበሪ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። በቴርሳም ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 24 ፤ ከሳምርም ፡ በኹለት ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ የሰማርያን ፡ ተራራ ፡ ገዛ ፤ በተራራውም ፡ ላይ ፡ ሠራ ፥ የሠራውንም ፡ ከተማ ፡ በተራራው ፡ ባለቤት ፡ በሳምር ፡ ስም ፡ ሰማርያ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 25 ፤ ዘንበሪም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ ከርሱም ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበሩት ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ከፋ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 26 ፤ በናባጥም ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ በምናምንቴም ፡ ነገራቸው ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጡት ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ባሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 27 ፤ የቀረውም ፡ ዘንበሪ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ጭከና ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 28 ፤ ዘንበሪም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አክአብ ([168]) ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 29 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ በሠላሳ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ የዘንበሪም ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 30 ፤ የዘንበሪም ፡ ልጅ ፡ አክአብ ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 31 ፤ በናባጥም ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ መኼድ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ መሰለው ፥ የሲዶናውያንንም ፡ ንጉሥ ፡ የኤትበዓልን ፡ ልጅ ፡ ኤልዛቤልን ፡ አገባ ፥ ኼዶም ፡ በዓልን ፡ አመለከ ፡

168 ዕብ. ፥ አኀአብ ፡ (እኀወ ፡ አብ ፥ ያባት ፡ ወንድም) ።

ሰገደለትም ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 32 ፤ በሰማርያም ፡ በሠራው ፡ በበዓል ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ለበዓል ፡ መሠዊያ ፡ አቆመ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 33 ፤ አክአብም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ተከለ ፤ አክአብም ፡ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስቈጣውን ፡ ነገር ፡ አበዛ ።

ነገ.1 ፡ 16 ፡ 34 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ የቤቴል ፡ ሰው ፡ አኪኤል ([169]) ፡ ኢያሪኮን ፡ ሠራ ፤ በነዌም ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ እጅ ፡ እንደተነገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፥ በበኵር ፡ ልጅ ፡ በአቢሮን ፡ መሠረቷን ፡ አደረገ ፥ በታናሹ ፡ ልጁም ፡ በሰጉብ ፡ በሮቿን ፡ አቆመ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 1 ፤ በገለዓድ ፡ ቴስቢ ፡ የነበረው ፡ ቴስብያዊው ፡ ኤልያስ ፡ አክአብን ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ከአፌ ፡ ቃል ፡ በቀር ፡ በእነዚህ ፡ ዓመታት ፡ ጠልና ፡ ዝናብ ፡ አይኾንም ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለርሱ ፡ መጣለት ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 3 ፤ ከዚህ ፡ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ኺድ ፥ በዮርዳኖስም ፡ ትይዩ ፡ ባለው ፡ በኮራት ፡ ፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸግ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 4 ፤ ከወንዙም ፡ ትጠጣለኽ ፥ ቍራዎችም ፡ በዚያ ፡ ይመግቡኽ ፡ ዘንድ ፡ አዝዣለኹ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 5 ፤ ኼደም ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ አደረገ ። ኼዶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ትይዩ ፡ ባለው ፡ በኮራት ፡ ፈፋ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 6 ፤ ቍራዎቹም ፡ በየጧትና ፡ በየማታው ፡ እንጀራና ፡ ሥጋ ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ፤ ከወንዙም ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 7 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብ ፡ አልነበረምና ፡ ወንዙ ፡ ደረቀ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 8 ፤ ተነሥተኽም ፡ በሲዶና ፡ አጠገብ ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሰራጵታ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ ተቀመጥ ፤

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 9 ፤ እንሆም ፥ ትመግብኽ ፡ ዘንድ ፡ አንዲት ፡ ባልቴት ፡ አዝዣለኹ ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣለት ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 10 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ሰራጵታ ፡ ኼደ ፤ ወደከተማዉቱም ፡ በር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ባልቴት ፡ በዚያ ፡ ዕንጨት ፡ ትለቅም ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ጠርቶ ፦ የምጠጣው ፡ ጥቂት ፡ ውሃ ፡ በጽዋ ፡ ታመጭልኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሻለኹ ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 11 ፤ ውሃም ፡ ልታመጣለት ፡ በኼደች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጠርቶ ፥ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ በእጅሽ ፡ ይዘሽ ፡ ትመጪ ፡ ዘንድ ፡ እለምንሻለኹ ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 12 ፤ ርሷም ፦ አምላክኽ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በማድጋ ፡ ካለው ፡ ከዕፍኝ ፡ ዱቄት ፥ በማሰሮም ፡ ካለው ፡ ከጥቂት ፡ ዘይት ፡ በቀር ፡ እንጀራ ፡ የለኝም ፤ እንሆም ፥ ገብቼ ፡ ለኔና ፡ ለልጄ ፡ እጋግረው ፡ ዘንድ ፡ በልተነውም ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ ዕንጨት ፡ እሰበስባለኹ ፡ አለች ።

---

169 ዕብ. ፥ ሐይኤል ፡ (ሕያው ፡ እግዚአብሔር) ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 13 ፤ ኤልያስም ፡ አላት ፦ አትፍሪ ፤ ይልቅስ ፡ ኼደሽ ፡ እንዳልሺው ፡ አድርጊ ፤ አስቀድመሽ ፡ ግን ፡ ከዱቄቱ ፡ ለእኔ ፡ ታናሽ ፡ ዕንጐቻ ፡ አድርገሽ ፡ አምጪልኝ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለአንቺና ፡ ለልጅሽ ፡ አድርጊ ፤

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 14 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በምድር ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዝናብ ፡ እስከሚሰጥበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ዱቄቱ ፡ ከማድጋ ፡ አይጨረስም ፥ ዘይቱም ፡ ከማሰሮው ፡ አይጐድልም ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 15 ፤ ርሷም ፡ ኼዳ ፡ እንደ ፡ ኤልያሳ ፡ ቃል ፡ አደረገች ፤ ርሷና ፡ ርሱ ፡ ቤቷም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ በሉ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 16 ፤ በኤልያስም ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ዱቄቱ ፡ ከማድጋው ፡ አልተጨረሰም ፥ ዘይቱም ፡ ከማሰሮው ፡ አልጐደለም ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 17 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የባለቤቲቱ ፡ ልጅ ፡ ታመመ ፤ ትንፋሹም ፡ እስኪታጣ ፡ ድረስ ፡ ደዌው ፡ እጅግ ፡ ከባድ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 18 ፤ ርሷም ፡ ኤልያስን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ኀጢአቴንስ ፡ ታሳስብ ፡ ዘንድ ፥ ልጄንስ ፡ ትገድል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተኻልን ፧ አለችው ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 19 ፤ ኤልያስም ፦ ልጅሽን ፡ ስጪኝ ፡ አላት ። ከብብቷም ፡ ወስዶ ፡ ተቀምጦበት ፡ ወደነበረው ፡ ሰገነት ፡ አወጣው ፡ በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ አጋደመው ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፦ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ልጇን ፡ በመግደልኽ ፡ ይህችን ፡ ትቀልበኝ ፡ የነበረቺቱን ፡ ባልቴት ፡ እንዲህ ፡ ደግሞ ፡ አስጨነቅኻትን ፧ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 21 ፤ በብላቴናውም ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተዘረጋበት ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፦ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ የዚህ ፡ ብላቴና ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ትመለስ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኤልያስን ፡ ቃል ፡ ሰማ ፤ የብላቴናው ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሰች ፥ ርሱም ፡ ዳነ ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 23 ፤ ኤልያስም ፡ ብላቴናውን ፡ ይዞ ፡ ከሰገነቱ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አወረደው ፥ ኤልያስም ፦ እንሆ ፥ ልጅሽ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ ብሎ ፡ ለእናቱ ፡ ሰጣት ።

ነገ.1 ፡ 17 ፡ 24 ፤ ሴቲቱም ፡ ኤልያስን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በአፍኽ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አኹን ፡ ዐወቅኹ ፡ አለችው ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 1 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ። ኺድ ፥ ለአክአብ ፡ ተገለጥ ፥ በምድር ፡ ላይም ፡ ዝናብ ፡ እሰጣለኹ ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 2 ፤ ኤልያስም ፡ ለአክአብ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ኼደ ፤ በሰማርያም ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 3 ፤ አክአብም ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡ ዐብድዩን ([170]) ፡ ጠራ ፤ ዐብድዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ይፈራ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 4 ፤ ኤልዛቤልም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢያት ፡ ባስገደለች ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ መቶውን ፡ ነቢያት ፡ ወስዶ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምሳውን ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጎ ፡ እንጀራና ፡ ውሃ ፡ ይመግባቸው ፡ ነበር ።

---

170 ዕብ. ፥ ዖባድያህ ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ ፥ የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 5 ፤ አክአብም ፡ ዐብድዩን ፦ በአገሩ ፡ መካከል ፡ ወደውሃው ፡ ምንጭ ፡ ኹሉና ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ ኹሉ ፡ ኺድ ፤ እንስሳዎችም ፡ ኹሉ ፡ እንዳይጠፉ ፡ ፈረሶችንና ፡ በቅሎዎችን ፡ የምናድንበት ፡ ሣር ፡ ምናልባት ፡ እናገኛለን ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 6 ፤ ኹለቱም ፡ የሚመለሱበትን ፡ አገር ፡ ተካፈሉ ፤ አክአብም ፡ ለብቻው ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ ዐብድዩም ፡ ለብቻው ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 7 ፤ ዐብድዩም ፡ በመንገድ ፡ ሲኼድ ፥ እንሆ ፥ ኤልያስ ፡ ተገናኘው ፤ ዐብድዩም ፡ ዐወቀው ፥ በግንባሩም ፡ ተደፍቶ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ኤልያስ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 8 ፤ ኤልያስም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ኼደኽ ፡ ለጌታኽ ፦ ኤልያስ ፡ ተገኝቷል ፡ በል ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 9 ፤ ዐብድዩም ፡ አለ ፦ እኔን ፡ ባሪያኽን ፡ እንዲገድል ፡ በአክአብ ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ኀጢአት ፡ አድርጌያለኹ ፧

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 10 ፤ አምላክኽ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ጌታዬ ፡ ይፈልግኽ ፡ ዘንድ ፡ ያልላከበት ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ መንግሥት ፡ የለም ፤ ኹሉም ፦ በዚህ ፡ የለም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ አንተን ፡ እንዳላገኙ ፡ መንግሥቱንና ፡ ሕዝቡን ፡ አምሏቸው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 11 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፦ ኺድ ፥ ኤልያስ ፡ ተገኝ ፡ ብለኽ ፡ ለጌታኽ ፡ ንገር ፡ ትለኛለኽ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 12 ፤ እኔም ፡ ከአንተ ፡ ጥቂት ፡ ራቅ ፡ ስል ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አንሥቶ ፡ ወደማላውቀው ፡ ስፍራ ፡ ይወስድኻል ፤ እኔም ፡ ገብቼ ፡ ለአክአብ ፡ ስናገር ፥ ባያገኝኽ ፡ ይገድለኛል ፤ እኔም ፡ ባሪያኽ ፡ ከትንሽነቴ ፡ ዠምሬ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እፈራ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 13 ፤ ኤልዛቤል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢያት ፡ ባስገደለች ፡ ጊዜ ፥ መቶውን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡ ወስጄ ፥ ዐምሳ ፡ ዐምሳውንም ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጌ ፥ እንጀራና ፡ ውሃ ፡ የመገብኋቸው ፥ ይህ ፡ ያደርግኹት ፡ ነገር ፡ በእውኑ ፡ ለጌታዬ ፡ አልታወቀኽምን ፧

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 14 ፤ አኹንም ፥ ኼደኽ ፦ ኤልያስ ፡ ተገኝ ፡ ብለኽ ፡ ለጌታኽ ፡ ንገር ፡ ትላለኽ ፤ ርሱም ፡ ይገድለኛል ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 15 ፤ ኤልያስም ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ለርሱ ፡ እገለጣለኹ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 16 ፤ ዐብድዩም ፡ አክአብን ፡ ሊገናኘው ፡ ኼደ ፥ ነገረውም ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፡ ሊገናኘው ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 17 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፦ እስራኤልን ፡ የምትገለባብጥ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 18 ፤ ኤልያስም ፦ እስራኤልን ፡ የምትገለባብጡ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ትታችኹ ፡ በዓሊምን ፡ የተከተላችኹ ፥ አንተና ፡ የአባትኽ ፡ ቤት ፡ ናችኹ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ ልከኽ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፥ በኤልዛቤልም ፡ ማእድ ፡ የሚበሉትን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ የበዓልን ፡ ነቢያት ፥ አራት ፡ መቶም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድን ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰብስብ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 20 ፤ አክአብም ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ልኮ ፡ ነቢያቱን ፡ ኹሉ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ሰበሰበ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 21 ፤ ኤልያስም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ሾሉ ፡ ቀርቦ ፦ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በኹለት ፡ ዐሳብ ፡ ታነክሳላችኹ ፧ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ርሱን ፡ ተከተሉ ፤ በዓል ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ቢኾን ፡ ርሱን ፡ ተከተሉ ፡ አለ ። ሕዝቡም ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ አልመለሱለትም ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 22 ፤ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡ አለ ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ቀርቻለኹ ፤ የበዓል ፡ ነቢያት ፡ ግን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 23 ፤ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፡ ይሰጡን ፤ እነርሱም ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ይምረጡ ፧ እየብልቱም ፡ ይቀሥረጡት ፧ በዕንጨትም ፡ ላይ ፡ ያኑሩት ፧ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አይጨምሩ ፤ እኔም ፡ ኹለተኛውን ፡ ወይፈን ፡ አዘጋጃለኹ ፧ በዕንጨቱም ፡ ላይ ፡ አኖረዋለኹ ፧ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አልጨምርም ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 24 ፤ እናንተም ፡ የአምላካችኹን ፡ ስም ፡ ጥሩ ፧ እኔም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጠራለኹ ፤ ሰምቶም ፡ በእሳት ፡ የሚመልስ ፡ አምላክ ፧ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ይኹን ። ሕዝቡም ፡ ሾሉ ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 25 ፤ ኤልያስም ፡ የበዓልን ፡ ነቢያት ፦ እናንተ ፡ ብዙዎች ፡ ናችኹና ፧ አስቀድማችኹ ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ምረጡና ፡ አዘጋጁ ፤ የአምላካችኹንም ፡ ስም ፡ ጥሩ ፧ በበታቹም ፡ እሳት ፡ አትጨምሩ ፡ አላቸው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 26 ፤ ወይፈኑንም ፡ ወስደው ፡ አዘጋጁ ፧ ከጧትም ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፦ በዓል ፡ ሆይ ፧ ስማን ፡ እያሉ ፡ የበዓልን ፡ ስም ፡ ጠሩ ። ድምፅም ፡ አልነበረም ፧ የሚመልስም ፡ አልነበረም ፤ በሠሩትም ፡ መሠዊያ ፡ ዙሪያ ፡ እያነከሱ ፡ ያሸበሽቡ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 27 ፤ በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ። አምላክ ፡ ነውና ፧ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጩኹ ፤ ምናልባት ፡ ዐሳብ ፡ ይዞታል ፧ ወይም ፡ ፈቀቅ ፡ ብሏል ፧ ወይም ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ኼዷል ፧ ወይም ፡ ተኝቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መቀስቀስ ፡ ያስፈልገዋል ፡ እያለ ፡ አላገጠባቸው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 28 ፤ በታላቅም ፡ ቃል ፡ ይጮኹ ፧ እንደ ፡ ልማዳቸውም ፡ ደማቸው ፡ እስኪፈስ ፡ ድረስ ፡ ገላቸውን ፡ በካራና ፡ በቀሜኔ ፡ ይቧጭሩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 29 ፤ ቀትርም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ፡ እስኪደርስ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፤ ድምፅም ፡ አልነበረም ፧ የሚመልስና ፡ የሚያደምጥም ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 30 ፤ ኤልያስም ፡ ሕዝቡን ፡ ሾሉ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረቡ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ሾሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ። ፈርሶ ፡ የነበረውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ አበጀ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 31 ፤ ኤልያስም ፦ ስምኽ ፡ እስራኤል ፡ ይኾናል ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ደረሰለት ፡ እንደ ፡ ያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ቍጥር ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ድንጋዮች ፡ ወሰደ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 32 ፤ ከድንጋዮችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፤ በመሠዊያውም ፡ ዙሪያ ፡ ኹለት ፡ መስፈሪያ ፡ እኽል ፡ የሚያዝ ፡ ጉድጓድ ፡ ቈፈረ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 33 ፤ ዕንጨቱንም ፡ በተርታ ፡ አደረገ ፧ ወይፈኑንም ፡ በብልት ፡ በብልቱ ፡ ቈረጠ ፧ በዕንጨቱም ፡ ላይ ፡ አኖረና ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 34 ፤ አራት ፡ ጋን ፡ ውሃ ፡ ሙሉ ፡ በሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ በዕንጨቱ ፡ ላይ ፡ አፍስሱ ፡ አሉ ። ደግሞም ፦ ድገሙ ፡ አለ ፤ እነርሱም ፡ ደገሙ ። ርሱም ፦ ሦስተኛ ፡ አድርጉ ፡ አለ ፤ ሦስተኛም ፡ አደረጉ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 35 ፤ ውሃውም ፡ በመሠዊያው ፡ ዙሪያ ፡ ፈሰሰ ፤ ደግሞም ፡ ጉድጓዱን ፡ በውሃ ፡ ሞላው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 36 ፤ መሥዋዕተ ፡ ሠርክ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ኤልያስ ፡ ቀርቦ ፦ አቤቱ ፥ የአብርሃምና ፡ የይሥሐቅ ፡ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ እኔም ፡ ባሪያኽ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፥ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ በቃልኽ ፡ እንዳደረግኹ ፡ ዛሬ ፡ ይገለጥ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 37 ፤ አንተ ፥ አቤቱ ፥ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ ልባቸውንም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ መለስኽ ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ስማኝ ፥ አቤቱ ፥ ስማኝ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 38 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ ወደቀች ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕቱንም ፡ ዕንጨቱንም ፡ ድንጋዮቹንም ፡ ዐፈሩንም ፡ በላች ፥ በጕድጓዱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ውሃ ፡ ላሰች ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 39 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ያን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ። እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ አሉ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 40 ፤ ኤልያስም ፦ ከበዓል ፡ ነቢያት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዳያመልጥ ፡ ያዙ ፡ አላቸው ። ያዟቸውም ፤ ኤልያስም ፡ ወደቂሶን ፡ ወንዝ ፡ ወስዶ ፡ በዚያ ፡ አሳረዳቸው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 41 ፤ ኤልያስም ፡ አክአብን ፦ የዝናቡ ፡ ውሽንፍር ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ተነሥተኽ ፡ ውጣ ፥ ብላም ፡ ጠጣም ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 42 ፤ አክአብም ፡ ሊበላና ፡ ሊጠጣ ፡ ወጣ ፤ ኤልያስም ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ዐናት ፡ ወጣ ፤ ፊቱንም ፡ በጕልበቱ ፡ መካከል ፡ አድርጎ ፡ በግንባሩ ፡ ተደፋ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 43 ፤ ብላቴናውንም ፦ ወጥተኽ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ተመልከት ፡ አለው ። ወጥቶም ፡ ተመልክቶም ፦ ምንም ፡ የለም ፡ አለ ። ርሱም ፦ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ተመላለስ ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ተመላለሰ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 44 ፤ በሰባተኛውም ፡ ጊዜ ፦ እንሆ ፥ የሰው ፡ እጅ ፡ የምታኽል ፡ ታናሽ ፡ ደመና ፡ ከባሕር ፡ ወጣች ፡ አለ ። ርሱም ፦ ወጥተኽ ፡ አክአብን ፦ ዝናብ ፡ እንዳይከለክልኽ ፡ ሠረገላን ፡ ጭነኽ ፡ ውረድ ፡ በለው ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 45 ፤ ከጥቂትም ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ሰማዩ ፡ ከደመናውና ፡ ከነፋሱ ፡ የተነሣ ፡ ጨለመ ፥ ብዙም ፡ ዝናብ ፡ ኾነ ፤ አክአብም ፡ በሠረገላው ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 18 ፡ 46 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በኤልያስ ፡ ላይ ፡ ነበረች ፤ ወገቡንም ፡ አሸንፍጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ በአክአብ ፡ ፊት ፡ ይሮጥ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 1 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረገ ፥ ነቢያትንም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ ለኤልዛቤል ፡ ነገራት ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 2 ፤ ኤልዛቤልም ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ነፍስኽን ፡ ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ነፍስ ፡ ባላደርጋት ፥ አማልክት ፡ ይህን ፡ ያድርጉብኝ ፡ ይህንም ፡ ይጨምሩብኝ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መልእክተኛ ፡ ላከች ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 3 ፤ ኤልያስም ፡ ፈርቶ ፡ ተነሣ ፥ ነፍሱንም ፡ ሊያድን ፡ ኼደ ፥ በይሁዳም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ መጥቶ ፡ ብላቴናውን ፡ በዚያ ፡ ተወ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ የሚያኽል ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ኼደ ፤ መጥቶም ፡ ከክትክታ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተቀመጠና ፦ ይበቃኛል ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ከአባቶቼ ፡ አልበልጥምና ፡ ነፍሴን ፡ ውሰድ ፡ ብሎ ፡ እንዲሞት ፡ ለመነ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 5 ፤ በክትክታውም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ተጋደመ ፡ እንቅልፍም ፡ አንቀላፋ ፤ እንሆም ፥ መልአክ ፡ ዳሰሰውና ። ተነሥተኽ ፡ ብላ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 6 ፤ ሲመለከትም ፥ እንሆ ፥ በራሱ ፡ አጠገብ ፡ የተጋገረ ፡ ዕንጐቻና ፡ በማሰሮ ፡ ውሃ ፡ አገኘ ። በላም ፡ ጠጣም ፥ ተመልሶም ፡ ተኛ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ደግሞ ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ መጥቶ ፡ ዳሰሰውና ። የምትኼድበት ፡ መንገድ ፡ ሩቅ ፡ ነውና ፥ ተነሥተኽ ፡ ብላ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 8 ፤ ተነሥቶም ፡ በላ ፡ ጠጣም ፤ በዚያም ፡ ምግብ ፡ ኀይል ፡ እስከእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ እስከ ፡ ኮሬብ ፡ ድረስ ፡ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊት ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 9 ፤ እዚያም ፡ ወዳለ ፡ ዋሻ ፡ መጣ ፥ በዚያም ፡ ዐደረ ፤ እንሆም ፦ ኤልያስ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 10 ፤ ርሱም ፦ ለሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ቀንቻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቃል ፡ ኪዳንኽን ፡ ትተዋልና ፥ መሠዊያዎችኽንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ ነቢያትኽንም ፡ በሰይፍ ፡ ገድለዋልና ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቻለኹ ፤ ነፍሴንም ፡ ሊወስዷት ፡ ይሻሉ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 11 ፤ ርሱም ፦ ውጣ ፥ በተራራውም ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቁም ፡ አለ ። እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ ዐለፈ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ትልቅና ፡ ብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ተራራዎቹን ፡ ሠነጠቀ ፡ አለቶቹንም ፡ ሰባበረ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በነፋሱ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ። ከነፋሱም ፡ በኋላ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በምድር ፡ መናወጥ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 12 ፤ ከምድር ፡ መናወጥ ፡ በኋላ ፡ እሳት ፡ ኾነ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ አልነበረም ። ከእሳቱም ፡ በኋላ ፡ ትንሽ ፡ የዝምታ ፡ ድምፅ ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 13 ፤ ኤልያስም ፡ ያን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ በመጐናጸፊያው ፡ ሸፈነ ፥ ወጥቶም ፡ በዋሻው ፡ ደጃፍ ፡ ቆመ ። እንሆ ፦ ኤልያስ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ ለሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ቀንቻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቃል ፡ ኪዳንኽን ፡ ትተዋልና ፥ መሠዊያዎችኽንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ ነቢያትኽንም ፡ በሰይፍ ፡ ገድለዋልና ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቻለኹ ፤ ነፍሴንም ፡ ሊወስዷት ፡ ይሻሉ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፦ ኺድ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ተመለስ ፤ ከዚያም ፡ በደረስኽ ፡ ጊዜ ፡ በሶርያ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አዛሄልን ፡ ቅባው ፤

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 16 ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የናሜሲን ፡ ልጅ ፡ ኢዩን ፡ ቅባው ፤ በፋንታኽም ፡ ነቢይ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የአቤልምሖላን ፡ ሰው ፡ የሣፋጥን ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕን ፡ ቅባው ፥ ከአዛሄልም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጠውን ፡ ኾሉ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 17 ፤ ኢዩ ፡ ይገድለዋል ፤ ከኢዩም ፡ ሰይፍ ፡ ያመለጠውን ፡ ኾሉ ፡ ኤልሳዕ ፡ ይገድለዋል ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 18 ፤ እኔም ፡ ከእስራኤል ፡ ጕልበታቸውን ፡ ለበዓል ፡ ያላንበረከኩትን ፡ ኾሉ ፥ በአፋቸውም ፡ ያልሳሙትን ፡ ኾሉ ፥ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ለእኔ ፡ አስቀራለኹ ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 19 ፤ ከዚያም ፡ ኼደ ፥ የሣፋጥንም ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕን ፡ በዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ጥማድ ፡ በሬዎች ፡ ሲያርስ ፥ ርሱም ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አገኘው ። ኤልያስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ዐልፎ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ ጣለበት ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 20 ፤ በሬዎቹንም ፡ ተወ ፥ ከኤልያስም ፡ በኋላ ፡ ሮጦ ፦ አባቴንና ፡ እናቴን ፡ እስማቸው ፡ ዘንድ ፥ እባክኽ ፥ ተወኝ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እከተልኻለኹ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ኺድና ፡ ተመለስ ፤ ምን ፡ አድርጌልኻለኹ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 19 ፡ 21 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ተመልሶ ፡ ኹለቱን ፡ በሬዎች ፡ ወስዶ ፡ ዐረዳቸው ፥ ሥጋቸውንም ፡ በበሬዎቹ ፡ ዕቃ ፡ ቀቀለው ፥ ለሕዝቡም ፡ ሰጣቸው ፥ በሉም ፤ ርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ኤልያስን ፡ ተከትሎ ፡ ኼደ ፥ ያገለግለውም ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 1 ፤ ለኢይዝራኤላዊውም ፡ ለናቡቴ ፡ በሰማርያ ፡ ንጉሥ ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 2 ፤ አክአብም ፡ ናቡቴን ፦ በቤቴ ፡ አቅራቢያ ፡ ነውና ፥ የአትክልት ፡ ቦታ ፡ ኣደርገው ፡ ዘንድ ፡ የወይን ፡ ቦታኽን ፡ ስጠኝ ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ከርሱ ፡ የተሻለ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፤ ወይም ፡ ብትወድ ፡ ግምቱን ፡ ገንዘብ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 3 ፤ ናቡቴም ፡ አክአብን ፦ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ እሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያርቅልኝ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 4 ፤ ኢይዝራኤላዊውም ፡ ናቡቴ ፦ የአባቶቼን ፡ ርስት ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ ስለተናገረው ፡ አክአብ ፡ ተቈጥቶና ፡ ተናዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ። በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ፊቱን ፡ ተሸፋፈነ ፥ እንጀራም ፡ አልበላም ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 5 ፤ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥታ ፦ ልብኽ ፡ የሚያዝን ፡ እንጀራስ ፡ የማትበላ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ አለችው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ ኢይዝራኤላዊውን ፡ ናቡቴን ፦ የወይንኽን ፡ ቦታ ፡ በገንዘብ ፡ ስጠኝ ፤ ወይም ፡ ብትወድ ፡ በፋንታው ፡ ሌላ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹት ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የወይን ፡ ቦታዬን ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ መለሰልኝ ፡ ነው ፡ አላት ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 7 ፤ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፦ አንተ ፡ አኹን ፡ የእስራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ትገዛለኽን ፡ ተነሣ ፡ እንጀራም ፡ ብላ ፥ ልብኽም ፡ ደስ ፡ ይበላት ፤ የኢይዝራኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለችው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 8 ፤ በአክአብም ፡ ስም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈች ፥ በማኅተሙም ፡ አተመችው ፤ በከተማው ፡ ወደ ፡ ነበሩትና ፡ ከናቡቴም ፡ ጋራ ፡ ወደተቀመጡት ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከበርቴዎች ፡ ደብዳቤውን ፡ ላከች ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 9 ፤ በደብዳቤውም ፦ ስለ ፡ ጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ንገሩ ፥ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አስቀምጡት ፤

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 10 ፤ ኹለትም ፡ ምናምንቴ ፡ ሰዎች ፡ በፊቱ ፡ አስቀምጡና ፦ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድቧል ፡ ብለው ፡ ይመስክሩበት ፤ አውጥታችኹም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ውገሩት ፡ ብላ ፡ ጻፈች ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 11 ፤ በከተማውም ፡ የተቀመጡት ፡ የከተማው ፡ ሰዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከበርቴዎችም ፡ ኤልዛቤል ፡ እንዳዘዘቻቸውና ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ በተላከው ፡ ደብዳቤ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንዲሁ ፡ አደረጉ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 12 ፤ የጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፥ ናቡቴንም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ አስቀመጡት ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 13 ፤ ኹለቱም ፡ ምናምንቴ ፡ ሰዎች ፡ ገብተው ፡ በፊቱ ፡ ተቀመጡ ፤ ምናምንቴዎቹ ፡ ሰዎችም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ። ናቡቴ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሡን ፡ ሰድቧል ፡ ብለው ፡ በናቡቴ ፡ ላይ ፡ መሰከሩ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከከተማ ፡ አውጥተው ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ወገሩት ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ኤልዛቤልም ፦ ናቡቴ ፡ ተወግሮ ፡ ሞተ ፡ ብለው ፡ ላኩ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 15 ፤ ኤልዛቤልም ፡ ናቡቴ ፡ ተወግሮ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ኤልዛቤል ፡ አክአብን ፦ ናቡቴ ፡ ሞቷል ፡ እንጂ ፡ በሕይወት ፡ አይደለምና ፡ በገንዘብ ፡ ይሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ያለውን ፡ የኢይዝራኤላዊውን ፡ የናቡቴን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ተነሥተኽ ፡ ውረስ ፡ አለችው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 16 ፤ አክአብም ፡ ናቡቴ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤላዊው ፡ ወደናቡቴ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ሊወርድ ፡ ተነሣ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 18 ፤ ተነሥተኽ ፡ በሰማርያ ፡ የሚኖረውን ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ አክአብን ፡ ትገናኝ ፡ ዘንድ ፡ ውረድ ፤ እንሆ ፥ ይወርሰው ፡ ዘንድ ፡ በወረደበት ፡ በናቡቴ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 19 ፤ አንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ገድለኽ ፡ ወረስኽውን ፧ ብለኽ ፡ ንገረው ። ደግሞም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ውሻዎች ፡ የናቡቴን ፡ ደም ፡ በላሱበት ፡ ስፍራ ፡ የአንተን ፡ ደም ፡ ደግሞ ፡ ውሻዎች ፡ ይልሱታል ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 20 ፤ አክአብም ፡ ኤልያስን ፦ ጠላቴ ፡ ሆይ ፥ አገኘኽኝን ፧ አለው ። ርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፦ አግኝቼኻለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ ራስኽን ፡ ሸጠኻልና ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 21 ፤ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣብኻለኹ ፥ ፈጽሞም ፡ እጠርግኻለኹ ፥ ከአክአብም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ አጠፋለኹ ፤

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 22 ፤ በሥራኽም ፡ አስቈጥተኽኛልና ፥ እስራኤልንም ፡ አስተኻልና ፥ ቤትኽን ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፥ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፥ እንደአኪያም ፡ ልጅ ፥ እንደ ፡ ባኦስ ፡ ቤት ፡ አደርገዋለኹ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 23 ፤ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤልዛቤል ፦ በኢይዝራኤል ፡ ቅጥር ፡ አጠገብ ፡ ኤልዛቤልን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሏታል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 24 ፤ ከአክአብም ፡ ወገን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የሞተውን ፡ ውሻዎች ፡ ይበሉታል ፤ በሜዳውም ፡ የሞተውን ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይበሉታል ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 25 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፋት ፡ ለመሥራት ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ ሸጠ ፥ ሚስቱም ፡ ኤልዛቤል ፡ እንደ ፡ ነዳችው ፥ እንደ ፡ አክአብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ያጠፋቸው ፡ አሞራውያን ፡ እንደ ፡ ሠሩት ፡ ኹሉ ፥ ጣዖታትን ፡ በመከተል ፡ እጅግ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ሠራ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 27 ፤ አክአብም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፡ ገላውን ፡ ማቅ ፡ አለበሰ ፥ ጾመም ፥ በማቅ ፡ ላይም ፡ ተኛ ፥ ቅስስ ፡ ብሎም ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 20 ፡ 28 ፤ 29 ፤ ደግሞም ፦ አክአብ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ተዋረደ ፡ አየኽን ፧ በፊቴ ፡ የተዋረደ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በልጁ ፡ ዘመን ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣለኹ ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላመጣም ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ቴስብያዊው ፡ ወደ ፡ ኤልያስ ፡ መጣ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 1 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ጭፍራውን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነገሥት ፡ ነበሩ ፥ ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎችም ፡ ነበሩ ፤ ወጥቶም ፡ ሰማርያን ፡ ከበበ ፥ ወጋትም ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 2 ፤ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አክአብ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 3 ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብርኽና ፡ ወርቅኽ ፡ ለእኔ ፡ ነው ፤ ሴቶችኽና ፡ መልካካሞቹም ፡ ልጆችኽ ፡ ለእኔ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ እንዳልኽ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ለኔም ፡ የኾነው ፡ ኹሉ ፡ የአንተ ፡ ነው ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ መልእክተኞች ፡ ተመልሰው ፦ ወልደ ፡ አዴር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቀድሞ ፡ ብርኽንና ፡ ወርቅኽን ፡ ሴቶችኽንና ፡ ልጆችኽንም ፡ ትሰጠኛለኽ ፡ ብዬ ፡ ልኬብኽ ፡ ነበር ፤

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 6 ፤ ነገም ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ባሪያዎቼን ፡ እልክብኻለኹ ፥ ቤትኽንም ፡ የባሪያዎችኽንም ፡ ቤቶች ፡ ይበረብራሉ ፤ ደስ ፡ የሚያሠኛቸውንም ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ አድርገው ፡ ይወስዳሉ ፡ አሉ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የአገሩን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ጠርቶ ፦ ተመልከቱ ፥ ይህም ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ እንዲሻ ፡ እዩ ፤ ስለ ፡ ሴቶቼ ፡ ስለ ፡ ልጆቼ ፡ ስለ ፡ ብሬና ፡ ወርቄም ፡ ላከብኝ ፥ እንቢም ፡ አላልኹም ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 8 ፤ ሽማግሌዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ አትስማው ፥ ዕሺም ፡ አትበለው ፡ አሉት ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 9 ፤ ለወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክተኞች ፦ ለጌታዬ ፡ ለንጉሥ ፦ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ በመዠመሪያ ፡ የላክኽብኝን ፡ ኹሉ ፡ አደርጋለኹ ፤ ይህን ፡ ግን ፡ ኣደርገው ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፡ በሉት ፡ አላቸው ። መልእክተኞችም ፡ ተመልሰው ፡ ይህን ፡ አወሩለት ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 10 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፦ ለሚከተለኝ ፡ ሕዝብ ፡ የሰማርያ ፡ ትቢያ ፡ ጭብጥ ፡ ጭብጥ ፡ ይበቃው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አማልክት ፡ ይህን ፡ ያድርጉብኝ ፡ ይህን ፡ ይጨምሩብኝ ፡ ብሎ ፡ ላከበት ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 11 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መልሶ ፦ በቃ ፤ ለሰልፍ ፡ የሚታጠቅ ፡ ጋሻ ፡ ጦሩን ፡ እንደሚያወልቅ ፡ አይመካ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 12 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ ያን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ጋራ ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ፤ ባሪያዎቹንም ፦ ተሰለፉ ፡ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ በከተማዪቱ ፡ ትይዩ ፡ ተሰለፉ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 13 ፤ እንሆም ፥ ነቢይ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አክአብ ፡ ቀርቦ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህን ፡ ብዙ ፡ ጭፍራ ፡ ኹሉ ፡ ታያለኽን ፧ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃለኽ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 14 ፤ አክአብም ፦ በማን ፧ አለ ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአውራጃዎቹ ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፥ አለ ፤ ርሱም ፦ ሰልፉን ፡ ማን ፡ ይገምራል ፧ አለ ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 15 ፤ የአውራጃዎቹንም ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ ቈጠረ ፥ ኹለት ፡ መቶም ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፥ ቈጠረ ፥ ሰባትም ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 16 ፤ ቀትርም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ወጡ ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ ረዳቶቹም ፡ ሠላሳ ፡ ኹለቱ ፡ ነገሥታት ፡ እየጠጡ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ይሰክሩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 17 ፤ የአውራጃዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ አስቀድመው ፡ ወጡ ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፥ እነርሱም ፦ ሰዎች ፡ ከሰማርያ ፡ ወጥተዋል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ ለዕርቅ ፡ ወይም ፡ ለሰልፍ ፡ መጥተው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሕይወታቸው ፡ ያዟቸው ፥ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 19 ፤ እነዚህም ፡ የአውራጃዎች ፡ አለቃዎች ፡ ጕልማሳዎች ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ፥ ሰራዊትም ፡ ተከተላቸው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 20 ፤ ዥሉም ፡ በያንዳንዱ ፡ በፊቱ ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ገደለ ፥ ሶርያውያንም ፡ ሸሹ ፤ እስራኤልም ፡ አሳደዷቸው ፥ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ በፈረሱ ፡ አመለጠ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 21 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥም ፡ ወጥቶ ፡ ፈረሶቹንና ፡ ሠረገላዎቹን ፡ ያዘ ፥ ሶርያውያንንም ፡ በታላቅ ፡ ውጊት ፡ ገደላቸው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 22 ፤ ነቢዩም ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ቀርቦ ፦ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ይመጣብኻልና ፥ ኺድ ፥ በርታ ፥ የምታደርገውንም ፡ ተመልከትና ፡ ዕወቅ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 23 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ አምላካቸው ፡ የተራራዎች ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ በርትተውብን ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሜዳ ፡ ላይ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ብንዋጋ ፡ በርግጥ ፡ እንበረታባቸዋለን ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 24 ፤ ይህንም ፡ አድርግ ፤ ከጭፍራዎችኽ ፡ ነገሥታቱን ፡ አርቅ ፥ በፋንታቸውም ፡ አለቃዎችን ፡ ሹም ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 25 ፤ አንተም ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ጠፋብኽ ፡ ሰራዊት ፥ ፈረሱን ፡ በፈረስ ፡ ፋንታ ፥ ሠረገላውንም ፡ በሠረገላ ፡ ፋንታ ፥ ሰራዊትን ፡ ቀጠር ፤ በሜዳም ፡ ላይ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዋጋለን ፥ በርግጥም ፡ እንበረታባቸዋለን ። ምክራቸውንም ፡ ሰማ ፥ እንዲሁም ፡ አደረገ ። ፣

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 26 ፤ በሚመጣውም ፡ ዓመት ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሶርያውያንን ፡ አሰለፈ ፥ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ወጣ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 27 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ተሰለፉ ፥ ሊገጥሟቸውም ፡ ወጡ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ኹለት ፡ ትናንሾች ፡ የፍየል ፡ መንጋዎች ፡ ኾነው ፡ በፊታቸው ፡ ሰፈሩ ፤ ሶርያውያን ፡ ግን ፡ ምድሩን ፡ ሞልተው ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 28 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሶርያውያን ፦ እግዚአብሔር ፡ የተራራዎች ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሸለቆ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ ብለዋልና ፥ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ጭፍራ ፡ ዥሉ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 29 ፤ እነዚህም ፡ በእነዚያ ፡ ትይዩ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ሰፈሩ ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ተጋጠሙ ፥ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከሶርያውያን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ እግረኛ ፡ ገደሉ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 30 ፤ የቀሩትም ፡ ወደ ፡ አፌቅ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሸሹ ፤ ቅጥሩም ፡ በቀሩት ፡ በኻያ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ወልደ ፡ አዴርም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኙ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 31 ፤ ባሪያዎቹም ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ነገሥታት ፡ መሓሪዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ሰምተናል ፤ በወገባችን ፡ ማቅ ፡ እንታጠቅ ፥ በራሳችንም ፡ ገመድ ፡ እንጠምጥም ፥ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ እንውጣ ፤ ምናልባት ፡ ነፍስኽን ፡ ይምራታል ፡ አሉት ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 32 ፤ ወገባቸውንም ፡ በማቅ ፡ ታጠቁ ፥ በራሳቸውም ፡ ገመድ ፡ ጠመጠሙ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ መጥተው ፦ ባሪያኽ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፦ ነፍሴን ፡ ትምራት ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሏል ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ገና ፡ በሕይወቱ ፡ አለን ፧ ወንድሜ ፡ ነው ፥ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 33 ፤ ሰዎቹም ፡ የደግ ፡ ምልክት ፡ አደረጉትና ፡ ቃሉን ፡ ከአፉ ፡ ተቀብለው ። ወንድምኽ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ አለ ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ኺዱ ፥ አምጡት ፡ አለ ። ወልደ ፡ አዴርም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወጣ ፥ በሠረገላውም ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 34 ፤ ወልደ ፡ አዴርም ፦ አባቴ ፡ ከአባትኽ ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከተማዎች ፡ እመልስልኻለኹ ፤ አባቴ ፡ በሰማርያ ፡ እንዳደረገ ፡ አንተ ፡ በደማስቆ ፡ ገበያ ፡ ታደርጋለኽ ፡ አለው ። አክአብም ፦ እኔም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እሰድኻለኹ ፡ አለ ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጎ ፡ ሰደደው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 35 ፤ ከነቢያትም ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ባልንጀራውን ፦ ምታኝ ፡ አለው ። ሰውየውም ፡ ይመታው ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 36 ፤ ርሱም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማኽምና ፥ እንሆ ፥ ከእኔ ፡ በራቅኽ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ ይገድልኻል ፡ አለው ። ከርሱም ፡ በራቀ ፡ ጊዜ ፡ አንበሳ ፡ አግኝቶ ፡ ገደለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 37 ፤ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አግኝቶ ፦ ምታኝ ፡ አለው ። ሰውየውም ፡ መታው ፥ በመምታቱም ፡ አቈሰለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 38 ፤ ነቢዩም ፡ ኼዶ ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ ንጉሡን ፡ ቈየው ፤ ዐይኖቹንም ፡ በቀጸላው ፡ ሸፍኖ ፡ ተሸሸገ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 39 ፤ ንጉሡም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጮኸ ፦ ባሪያኽ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አመጣና ፦ ይህን ፡ ሰው ፡ ጠብቅ ፥ ቢኰበልልም ፡ ነፍስኽ ፡ በነፍሱ ፡ ፋንታ ፡ ትኾናለች ፥ ወይም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ትከፍላለኽ ፡ አለኝ ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 40 ፤ ባሪያኽም ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ሲመለከት ፡ ጠፋ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ፍርድኽ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ፤ አንተ ፡ ፈርደኽዋል ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 41 ፤ ፈጥኖም ፡ ቀጸላውን ፡ ከዐይኑ ፡ አነሣ ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 42 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ዕርም ፡ ያልኹትን ፡ ሰው ፡ ከእጅኽ ፡ አውጥተኻልና ፥ ነፍስኽ ፡ በነፍሱ ፡ ፋንታ ፡ ሕዝብኽም ፡ በሕዝቡ ፡ ፋንታ ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 21 ፡ 43 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ እየተቈጣና ፡ እየተናደደ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፥ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጣ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 1 ፤ ሶርያና ፡ እስራኤልም ፡ ሳይዋጉ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጡ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 2 ፤ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወረደ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎቹን ፦ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ የእኛ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ እኛም ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ሳንወስዳት ፡ ዝም ፡ እንዳልን ፡ ታውቃላችኹን ፧ አላቸው ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 4 ፤ ኢዮሳፍጥንም ፦ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ እንዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትመጣለኽን ፧ አለው ። ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፥ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፥ ፈረሶቼም ፡ እንደ ፡ ፈረሶችኽ ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 5 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አስቀድመኽ ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነቢያቱን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ የሚያኽሉትን ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፦ ወደ ፡

ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ ልኬድን ፡፡ ወይስ ፡ ልቅር ፡፡ አላቸው ። እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ውጣ ፡ አሉት ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 7 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፦ እንጠይቀው ፡ ዘንድ ፡ ሌላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ፡፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ የይምላ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ([171]) ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይናገርልኝምና ፡ እጠላዋለኹ ፡ አለው ። ኢዮሳፍጥም ፦ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አይበል ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አንዱን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ጠርቶ ፦ የይምላን ፡ ልጅ ፡ ሚክያስን ፡ ፈጥነኽ ፡ አምጣ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 10 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሰው ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ በአደባባይ ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ነቢያቱም ፡ ኹሉ ፡ በፊታቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 11 ፤ የክንዓና ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስም ፡ የብረት ፡ ቀንዶች ፡ ሠርቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ሶርያውያንን ፡ ትወጋለኽ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 12 ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ኺድና ፡ ተከናወን ፡ እያሉ ፡ እንዲህ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 13 ፤ ሚክያስንም ፡ ሊጠራ ፡ የኼደ ፡ መልእክተኛ ፦ እንሆ ፥ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ ኾነው ፡ ለንጉሡ ፡ መልካምን ፡ ይናገራሉ ፤ ቃልኽም ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ እንዲኾን ፡ መልካም ፡ እንድትናገር ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 14 ፤ ሚክያስም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚነግረኝን ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 15 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፦ ሚክያስ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ እንኺድን ፡፡ ወይስ ፡ እንቅር ፡፡ አለው ፤ ርሱም ፦ ውጣና ፡ ተከናወን ፤ እግዚአብሔርም ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 16 ፤ ንጉሡም ፦ ከእውነት ፡ በቀር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንዳትነግረኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ አምልኻለኹ ፡፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 17 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡ አየኹ ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለእነዚህ ፡ ጌታ ፡ የላቸውም ፡ እያንዳንዱም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 18 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ እንደማይናገርልኝ ፡ አላልኹኽምን ፡፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 19 ፤ ሚክያስም ፡ አለ ፦ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፥ የሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡ ቆመው ፡ አየኹ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ወጥቶ ፡ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይወድቅ ፡ ዘንድ ፡ አክአብን ፡ የሚያሳስት ፡

171 ዕብ. ፥ ሚክያህ ፡ (ማን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡) ።

ማን ፡ ነው ፧ አለ ። አንዱም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፥ ሌላውም ፡ እንዲያ ፡ የለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 21 ፤ መንፈስም ፡ ወጣ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፦ እኔ ፡ አሳስተዋለኹ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በምን ፧ አለው ፤ ርሱም ፦ ወጥቼ ፡ በነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ እኾናለኹ ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ ማሳሳትስ ፡ ታሳስተዋለኽ ፥ ይኾንልኻልም ፤ ውጣ ፥ እንዲሁም ፡ አድርግ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 23 ፤ አኹንም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ በነቢያትኽ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ አድርጓል ፤ እግዚአብሔርም ፡ በላይኽ ፡ ክፉ ፡ ተናግሮብኻል ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 24 ፤ የክንዓናም ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ቀረበ ፥ ሚክያስንም ፡ ጕንጭን ፡ በጥፊ ፡ መታውና ። አንተን ፡ ሊናገር ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ ዐለፈ ፧ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 25 ፤ ሚክያስም ፦ እንሆ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ልትሸሸግ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝኽ ፡ በኼድኽ ፡ ጊዜ ፡ ታያለኽ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 26 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ሚክያስን ፡ ውሰዱ ፥ ወደከተማዩቱም ፡ ሹም ፡ ወደ ፡ ዐሞን ፡ ወደንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአስ ፡ መልሳችኹ ፦ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 27 ፤ በደኅና ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ አኑሩት ፥ የመከራም ፡ እንጀራ ፡ መግቡት ፥ የመከራም ፡ ውሃ ፡ አጠጡት ፡ በሉ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 28 ፤ ሚክያስም ፦ በደኅና ፡ ብትመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ የተናገረ ፡ አይደለም ፡ አለ ። ደግሞም ፦ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፡ አለ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 29 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ወጡ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 30 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ልብሴን ፡ ለውጬ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እገባለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ልብስኽን ፡ ልበስ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ ለውጦ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ገባ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 31 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለቱን ፡ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎች ፦ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በቀር ፥ ታናሽ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፡ ከማናቸውም ፡ ጋራ ፡ አትግጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 32 ፤ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎችም ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ይገጥሙትም ፡ ዘንድ ፡ ከበቡት ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ጮኸ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 33 ፤ የሠረገላዎች ፡ አለቃዎችም ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንዳልኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሱ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 34 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ቀስቱን ፡ ድንገት ፡ ገትሮ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ በጥሩሩ ፡ ልብስ ፡ መጋጠሚያ ፡ በኩል ፡ ወጋው ፤ ሠረገለኛውንም ፦ መልሰኽ ፡ ንዳ ፥ ተወግቻለኹና ፡ ከሰልፍ ፡ ውስጥ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 35 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ በረታ ፤ ንጉሡም ፡ በሶርያውያን ፡ ፊት ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተደግፎ ፡ ነበር ፥ ማታም ፡ ሞተ ፤ የቀኑስሉም ፡ ደም ፡ በሠረገላው ፡ ውስጥ ፡ ፈሰሰ ።

ነገ.1 ፥ 22 ፥ 36 ፤ በሰራዊቱም ፡ መካከል ፡ ፀሓይ ፡ ስትገባ ፦ ንጉሡ ፡ ሞቷልና ፥ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይኺድ ፡ የሚል ፡ ጩኸት ፡ ኾነ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 37 ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መጡ ፥ ንጉሡንም ፡ በሰማርያ ፡ ቀበሩት ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 38 ፤ አመንዝራዎች ፡ በታጠቡባት ፡ በሰማርያ ፡ ኵሬ ፡ ሠረገላውን ፡ ዐጠቡት ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፡ ውሻዎች ፡ ደሙን ፡ ላሱት ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 39 ፤ የቀረውም ፡ የአክአብ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ ከዝኖን ፡ ጥርስም ፡ የሠራው ፡ ቤት ፥ የሠራቸውም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 40 ፤ አክአብም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ አካዝያስ ([172]) ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 41 ፤ አክአብም ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሣ ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 42 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ መንገሥ ፡ በጐመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጐበዝ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዓዙባ ፡ የተባለች ፡ የሺልሒ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 43 ፤ በአባቱም ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አላራቀም ፤ ሕዝቡ ፡ ገና ፡ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 44 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ታረቀ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 45 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ጭከና ፥ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 46 ፤ ከአባቱ ፡ ከአሣ ፡ ዘመን ፡ የተረፉትን ፡ ሰዶማውያን ፡ ከምድር ፡ አጠፋ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 47 ፤ በኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፤ ሹሙም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 48 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ወደ ፡ ኦፌር ፡ ኼደው ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ የተርሴስን ፡ መርከቦች ፡ ሠራ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መርከቦቹ ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ ተሰበሩ ፡ እንጂ ፡ አልኼዱም ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 49 ፤ የአክአብም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ባሪያዎቼ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ በመርከብ ፡ ይኺዱ ፡ አለው ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፡ አልወደደም ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 50 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ ኢዮራም ([173]) ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 51 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የአክአብ ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ጐመረ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 52 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፥ በአባቱና ፡ በእናቱም ፡ መንገድ ፥ እስራኤልንም ፡ ባሳተው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ መንገድ ፡ ኼደ ።

ነገ.1 ፡ 22 ፡ 53 ፤ በዓልንም ፡ አመለከ ፡ ሰገደለትም ፤ አባቱም ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣ ❖

---

172 ዕብ. ፥ አኀዝያህ ።

173 ዕብ. ፥ የውራም ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ አክአብም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሞዐብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ አካዝያስም ፡ በሰማርያ ፡ በሰገነቱ ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ ከዐይነ ፡ ርግቡ ፡ ወድቆ ፡ ታመመ ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፡ ከዚህም ፡ ደዌ ፡ እድን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የዐቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ቴስብያዊውን ፡ ኤልያስን ፦ ተነሣ ፥ የሰማርያን ፡ ንጉሥ ፡ መልእክተኞች ፡ ለመገናኘት ፡ ውጣና ። የዐቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ የምትኼዱት ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አምላክ ፡ ስለሌለ ፡ ነውን ፧

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ ከወጣኽበት ፡ ዐልጋ ፡ አትወርድም ፡ በላቸው ፡ አለው ። ኤልያስም ፡ ኼደ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ መልእክተኞችም ፡ ወደ ፡ አካዝያስ ፡ ተመለሱ ፥ ርሱም ፦ ለምን ፡ ተመለሳችኹ ፧ አላቸው ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ እነርሱም ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊገናኘን ፡ መጣና ፦ ኺዱ ፥ ወደላካችኹም ፡ ንጉሥ ፡ ተመልሳችኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የዐቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ የላከኽ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አምላክ ፡ ስለሌለ ፡ ነውን ፧ ስለዚህ ፡ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ ከወጣኽበት ፡ ዐልጋ ፡ አትወርድም ፡ በሉት ፡ አለን ፡ አሉት ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ርሱም ፦ ሊገናኛችኹ ፡ የወጣው ፥ ይህንስ ፡ ቃል ፡ የነገራችኹ ፡ ሰው ፡ መልኩ ፡ ምን ፡ ይመስላል ፧ አላቸው ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ እነርሱም ፦ ሰውዮው ፡ ጠጕራም ፡ ነው ፥ በወገቡም ፡ ጠፍር ፡ ታጥቆ ፡ ነበር ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ቴስብያዊው ፡ ኤልያስ ፡ ነው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ንጉሡም ፡ የዐምሳ ፡ አለቃውን ፡ ከዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ሰደደ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወጣ ፤ እንሆም ፥ በተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ። ርሱም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ንጉሡ ፦ ውረድ ፡ ይልኻል ፡ አለው ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ኤልያስም ፡ መልሶ ፡ የዐምሳ ፡ አለቃውን ፦ እኔስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድ ፥ አንተንም ፥ ዐምሳውንም ፡ ሰዎችኽን ፡ ትብላ ፡ አለው ። እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ ርሱንና ፡ ዐምሳውን ፡ ሰዎቹን ፡ በላች ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ደግሞም ፡ ሌላ ፡ የዐምሳ ፡ አለቃ ፡ ከዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ላከበት ፤ ርሱም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ንጉሡ ፦ ፈጥነኽ ፡ ውረድ ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ኤልያስም ፦ እኔስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ትውረድ ፥ አንተንም ፡ ዐምሳውንም ፡ ሰዎችኽን ፡ ትብላ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ ርሱንና ፡ ዐምሳውን ፡ ሰዎቹን ፡ በላች ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ደግሞም ፡ ሦስተኛ ፡ የዐምሳ ፡ አለቃ ፡ ከዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ሰደደ ፤ ሦስተኛውም ፡ የዐምሳ ፡

አለቃ ፡ ወጥቶ ፡ በኤልያስ ፡ ፊት ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበረከከና ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ነፍሴና ፡ የእነዚህ ፡ የዐምሳው ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ነፍስ ፡ በፊትኽ ፡ የከበረች ፡ ትኹን ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 14 ፤ እንሆ ፥ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዳ ፡ የፊተኞቹን ፡ ኹለቱን ፡ የዐምሳ ፡ አለቃዎችና ፡ ዐምሳ ፡ ዐምሳውን ፡ ሰዎቻቸውን ፡ በላች ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ነፍሴ ፡ በፊትኽ ፡ የከበረች ፡ ትኹን ፡ ብሎ ፡ ለመነው ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 15 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ኤልያስን ፦ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ውረድ ፥ አትፍራውም ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወረደ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 16 ፤ ኤልያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የዐቃሮንን ፡ አምላክ ፡ ብዔልዜቡልን ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ልከኻልና ፥ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ ከወጣኽበት ፡ ዐልጋ ፡ አትወርድም ፡ አለው ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 17 ፤ ኤልያስም ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሞተ ። ልጅም ፡ አልነበረውምና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወንድሙ ፡ ኢዮራም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፥ 1 ፥ 18 ፤ አካዝያስ ፡ ያደረገው ፡ የቀረው ፡ ነገር ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኤልያስን ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሊያወጣው ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ ከኤልሳዕ ፡ ጋራ ፡ ከገልገላ ፡ ተነሣ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 2 ፤ ኤልያስም ፡ ኤልሳዕን ፦ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ልኮኛልና ፥ በዚህ ፡ ቈይ ፡ አለው ። ኤልሳዕም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ ፥ አልለይኽም ፡ አለ ። ወደ ፡ ቤቴልም ፡ ወረዱ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 3 ፤ በቤቴልም ፡ የነበሩ ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ወጥተው ፦ እግዚአብሔር ፡ ጌታኽን ፡ ከራስኽ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ እንዲወስደው ፡ ዐውቀኻልን ፧ አሉት ። ርሱም ፦ አዎን ፥ ዐውቄያለኹ ፤ ዝም ፡ በሉ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 4 ፤ ኤልያስም ፦ ኤልሳዕ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ልኮኛልና ፥ እባክኽ ፥ በዚህ ፡ ቈይ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ ፥ አልለይኽም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 5 ፤ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጡ ። በኢያሪኮም ፡ የነበሩ ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ቀርበው ፦ እግዚአብሔር ፡ ጌታኽን ፡ ከራስኽ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ እንዲወስደው ፡ ዐውቀኻልን ፧ አሉት ። ርሱም ፦ አዎን ፡ ዐውቄያለኹ ፤ ዝም ፡ በሉ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 6 ፤ ኤልያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ልኮኛልና ፥ እባክኽ ፥ በዚህ ፡ ቈይ ፡ አለው ። ርሱም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ ፥ አልለይኽም ፡ አለ ። ኹለቱም ፡ ኼዱ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 7 ፤ ከነቢያትም ፡ ልጆች ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ ኼዱ ፥ በፊታቸውም ፡ ርቀው ፡ ቆሙ ፤ እነዚህም ፡ ኹለቱ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዳር ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 8 ፤ ኤልያስም ፡ መጐናጸፊያውን ፡ ወስዶ ፡ ጠቀለለው ፥ ውሃውንም ፡ መታ ፥ ወዲህና ፡ ወዲያም ፡ ተከፈለ ፤ ኹለቱም ፡ በደረቅ ፡ ተሻገሩ ።

ነገ.2 ፥ 2 ፥ 9 ፤ ከተሻገሩም ፡ በኋላ ፡ ኤልያስ ፡ ኤልሳዕን ፦ ከአንተ ፡ ሳልወሰድ ፡ አደርግልኽ ፡ ዘንድ ፡ የምትሻውን ፡ ለምን ፡ አለው ፤ ኤልሳዕም ፦ መንፈስኽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 10 ፤ ርሱም ፦ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ ለምነኻል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ በተወሰድኹ ፡ ጊዜ ፡ ብታየኝ ፡ ይኾንልኻል ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ አይኾንልኽም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሲኼዱም ፦ እያዘገሙም ፡ ሲጫወቱ ፥ እንሆ ፥ የእሳት ፡ ሠረገላና ፡ የእሳት ፡ ፈረሶች ፡ በመካከላቸው ፡ ገብተው ፡ ከፈሏቸው ፤ ኤልያስም ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ኤልሳዕም ፡ አይቶ ፦ አባቴ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ሠረገላና ፡ ፈረሰኞች ፥ ብሎ ፡ ጮኸ ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ አላየውም ፤ ልብሱንም ፡ ይዞ ፡ ከኹለት ፡ ተረተረው ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ ከኤልያስም ፡ የወደቀውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ አነሣ ፥ ተመልሶም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዳር ፡ ቆመ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ከኤልያስም ፡ የወደቀውን ፡ መጐናጸፊያ ፡ ወስዶ ፡ ውሃውን ፡ መታና ። የኤልያስ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አለ ፤ ውሃውንም ፡ በመታ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ተከፈለ ፤ ኤልሳዕም ፡ ተሻገረ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ከኢያሪኮም ፡ መጥተው ፡ በአንጻሩ ፡ የነበሩት ፡ የነቢያት ፡ ልጆች ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፦ የኤልያስ ፡ መንፈስ ፡ በኤልሳዕ ፡ ላይ ፡ ዐርፏል ፡ አሉ ። ሊገናኙትም ፡ መጥተው ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተደፉ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ እነርሱም ፦ እንሆ ፥ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ዐምሳ ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ተራራ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ሸለቆ ፡ ጥሎት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ኼደው ፡ ጌታኽን ፡ ይፈልጉት ፡ ዘንድ ፡ እንለምንኻለን ፡ አሉት ። ርሱም ፦ አትስደዱ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ እስኪያፍርም ፡ ድረስ ፡ ግድ ፡ ባሉት ፡ ጊዜ ፦ ስደዱ ፡ አለ ፤ ዐምሳም ፡ ሰዎች ፡ ሰደዱ ፤ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ፈልገው ፡ አላገኙትም ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 18 ፤ በኢያሪኮም ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሱ ፤ ርሱም ፦ አትኺዱ ፡ አላልኋችኹምን ፧ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 19 ፤ የከተማዪቱም ፡ ሰዎች ፡ ኤልሳዕን ፦ እንሆ ፥ ጌታችን ፡ እንደምታይ ፡ የዚች ፡ ከተማ ፡ ኑሮ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ውሃው ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ትጨነግፋለች ፡ አሉት ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ ዐዲስ ፡ ማሰሮ ፡ አምጡልኝ ፥ ጨውም ፡ ጨምሩበት ፡ አለ ፤ ያንም ፡ አመጡለት ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 21 ፤ ውሃው ፡ ወዳለበቱም ፡ ምንጭ ፡ ወጥቶ ፡ ጨው ፡ ጣለበትና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህን ፡ ውሃ ፡ ፈውሼዋለኹ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሞትና ፡ ጭንገፋ ፡ አይኾንበትም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ኤልሳዕም ፡ እንደተናገረው ፡ ነገር ፡ ውሃው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተፈውሷል ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወጣ ፤ በመንገድም ፡ ሲወጣ ፡ ብላቴናዎች ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጥተው ፦ አንተ ፡ መላጣ ፥ ውጣ ፤ አንተ ፡ መላጣ ፥ ውጣ ፡ ብለው ፡ አፌዙበት ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 24 ፤ ዘወርም ፡ ብሎ ፡ አያቸው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ ረገማቸው ፤ ከዱርም ፡ ኹለት ፡ ድቦች ፡ ወጥተው ፡ ከብላቴናዎች ፡ አርባ ፡ ኹለቱን ፡ ሰባበሯቸው ።

ነገ.2 ፡ 2 ፡ 25 ፤ ከዚያም ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ኼደ ፥ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ተመለሰ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 1 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ የአክአብ ፡ ልጅ ፡ ኢዮራም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ገመረ ፥ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አባቱ ፡ ያሠራውን ፡ የበዓልን ፡ ሐውልት ፡ አርቋልና ፥ እንደ ፡ አባቱና ፡ እንደ ፡ እናቱ ፡ አልነበረም ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስራኤልን ፡ ባሳታቸው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ ተያዘ ፤ ከርሱም ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ የሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ሞሳ ፡ ባለበጎች ፡ ነበረ ፤ ለእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የመቶ ፡ ሺሕ ፡ ጠቦትና ፡ የመቶ ፡ ሺሕ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ጠጕር ፡ ይገብርለት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ አክአብም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮራም ፡ ከሰማርያ ፡ ወጥቶ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ አሰለፈ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ወደይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኢዮሳፍጥ ፦ የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ዐምፆብኛልና ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ ለሰልፍ ፡ ትኼዳለኽን ፧ ብሎ ፡ ላከ ። ርሱም ፦ እወጣለኹ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፥ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፥ ፈረሶቼም ፡ እንደ ፡ ፈረሶችኽ ፡ ናቸው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፦ በምን ፡ መንገድ ፡ እንኼዳለን ፧ አለ ፤ ርሱም ፦ በኤዶምያስ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ መንገድ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ ኼዱ ፤ የሰባትም ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ዞሩ ፤ ለሰራዊቱና ፡ ለተከተሏቸውም ፡ እንስሳዎች ፡ ውሃ ፡ አልተገኘም ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ወዮ! ፡ እግዚአብሔር ፡ በሞዐብ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እነዚህን ፡ ሦስቱን ፡ ነገሥታት ፡ ጠርቷልና ፥ ወዮ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ኢዮሳፍጥም ፦ በርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ፧ አለ ። ከእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ አንዱ ፦ በኤልያስ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ያፈስ ፡ የነበረው ፡ የሣፋጥ ፡ ልጅ ፡ ኤልሳዕ ፡ እዚህ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 12 ፤ ኢዮሳፍጥም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ፡ አለ ። የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ የኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወረዱ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ኤልሳዕም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ወዳባትኽና ፡ ወደእናትኽ ፡ ነቢያት ፡ ኺድ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ። አይደለም ፥ በሞዐብ ፡ እጅ ፡ ይጥላቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እነዚህን ፡ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ ጠርቷል ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ኤልሳዕም ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ያላፈርኹ ፡ ብኾን ፡ ኖሮ ፡ አንተን ፡ ባልተመለከትኹና ፡ ባላየኹ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ባለበገና ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ። ባለበገናውም ፡ በደረደረ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መጣችበት ፤

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህ ፡ ሸለቆ ፡ ኹሉ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፈሩ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ነፋስ ፡ አታዩም ፥ ዝናብም ፡ አታዩም ፥ ይህ ፡ ሸለቆ ፡ ግን ፡ ውሃ ፡ ይሞላል ፤ እናንተም ፡ ከብቶቻችኹም ፡ እንስሳዎቻችኹም ፡ ትጠጣላችኹ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ይህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ደግሞም ፡ ሞዐባውያንን ፡ በእጃችኹ ፡

አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 19 ፤ የተመሸጉትንና ፡ ያማሩትን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ትመታላችኹ ፥ የሚያፈሩትንም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ትቈርጣላችኹ ፥ የውሃውንም ፡ ምንጮች ፡ ኹሉ ፡ ትደፍናላችኹ ፥ መልካሞችንም ፡ ዕርሻዎች ፡ ኹሉ ፡ በድንጋይ ፡ ታበላሻላችኹ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 20 ፤ በነጋውም ፡ የቀሦርባን ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፥ እንሆ ፥ ውሃ ፡ በኤዶምያስ ፡ መንገድ ፡ መጣ ፥ ምድሪቱም ፡ ውሃ ፡ ሞላች ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 21 ፤ ሞዐባውያንም ፡ ኹሉ ፡ ነገሥታት ፡ ሊወጓቸው ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በወገባቸው ፡ ሰይፍ ፡ የሚታጠቁ ፡ ኹሉ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ወጥተውም ፡ በአገሩ ፡ ድንበር ፡ ላይ ፡ ቆሙ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 22 ፤ ማልደውም ፡ ተነሡ ፤ ፀሓይም ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ አንጸባረቀ ፥ ሞዐባውያንም ፡ በፊታቸው ፡ ውሃው ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ቀልቶ ፡ አዩና ፦ ይህ ፡ ደም ፡ ነው ፤

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 23 ፤ በርግጥ ፡ ነገሥታት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተዋጉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ተጋደሉ ፤ ሞዐብ ፡ ሆይ ፥ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ምርኮኽ ፡ ኺድ ፡ አሉ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 24 ፤ ወደእስራኤል ፡ ሰፈር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤላውያን ፡ ተነሥተው ፡ ሞዐባውያንን ፡ መቱ ፥ እነርሱም ፡ ከፊታቸው ፡ ሸሹ ፤ ሞዐባውያንንም ፡ እየመቱ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ውስጥ ፡ ገቡ ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 25 ፤ ከተማዎችንም ፡ አፈረሱ ፤ በመልካሞቹም ፡ ዕርሻዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እስኪሞሉ ፡ ድረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ድንጋይ ፡ ይጥል ፡ ነበር ፤ የውሃውንም ፡ ምንጮች ፡ ኹሉ ፡ ደፈኑ ፥ የሚያፈሩትንም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ቈረጡ ፤ የቂርሐራሴትን ፡ ድንጋዮች ፡ ብቻ ፡ አስቀሩ ፤ ባለ ፡ ወንጭፎች ፡ ግን ፡ ከበቡ ፡ መቷት ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 26 ፤ የሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ሰልፍ ፡ እንደ ፡ በረታበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፥ ወደኤዶምያስም ፡ ንጉሥ ፡ ያልፉ ፡ ዘንድ ፡ ሞከሩ ፤ አልቻሉምም ።

ነገ.2 ፡ 3 ፡ 27 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ንጉሥ ፡ የሚኾነውን ፡ የበኩር ፡ ልጁን ፡ ወስዶ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ አቀረበው ። በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ቍጣ ፡ ኾነ ፤ ከዚያም ፡ ርቀው ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ተመለሱ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 1 ፤ ከነቢያትም ፡ ወገን ፡ ሚስቶች ፡ አንዲት ፡ ሴት ። ባሌ ፡ ባሪያኽ ፡ ሞቷል ፤ ባሪያኽም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፤ ባለዕዳ ፡ ልጆቼን ፡ ባሪያዎች ፡ አድርጎ ፡ ሊወስዳቸው ፡ መጥቷል ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ኤልሳዕ ፡ ጮኸች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 2 ፤ ኤልሳዕም ፦ አደርግልሽ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ትሻለሽ ፧ በቤትሽ ፡ ያለውን ፡ ንገሪኝ ፡ አላት ። ርሷም ፦ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ ከዘይት ፡ ማሰሮ ፡ በቀር ፡ በቤቴ ፡ አንዳች ፡ የለኝም ፡ አለች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ርሱም ፦ ኼደሽ ፡ ከጎረቤቶችሽ ፡ ኹሉ ፡ ከሜዳ ፡ ባዶ ፡ ማድጋዎችን ፡ ተዋሺ ፤ አታሳንሻቸውም ፡ አላት ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 4 ፤ ገብተሽም ፡ ከአንቺና ፡ ከልጆችሽ ፡ በኋላ ፡ በሩን ፡ ዝጊ ፥ ወደ ፡ እነዚህም ፡ ማድጋዎች ፡ ኹሉ ፡ ዘይቱን ፡ ገልብጪ ፤ የሞላውንም ፡ ፈቀቅ ፡ አድርጊ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 5 ፤ እንዲሁም ፡ ከርሱ ፡ ኼዳ ፡ በሩን ፡ ከርሷና ፡ ከልጆቿ ፡ በኋላ ፡ ዘጋች ፤ እነርሱም ፡ ማድጋዎቹን ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ያመጡ ፡ ነበር ፥ ርሷም ፡ ትገለብጥ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 6 ፤ ማድጋዎቹም ፡ በሞሉ ፡ ጊዜ ፡ ልጇን ፦ ደግሞም ፡ ማድጋ ፡ አምጣልኝ ፡
አለችው ፤ ርሱም ፦ ሌላ ፡ ማድጋ ፡ የለም ፡ አላት ፤ ዘይቱም ፡ ቆመ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 7 ፤ መጥታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ነገረችው ፤ ርሱም ፦ ኼደሽ ፡ ዘይቱን ፡ ሽጪ ፡
ለባለዕዳውም ፡ ክፈዪ ፤ አንቺና ፡ ልጆችሽም ፡ ከተረፈው ፡ ተመገቡ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 8 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ኤልሳዕ ፡ ወደ ፡ ሱነም ፡ ዐለፈ ፥ በዚያም ፡ ታላቅ ፡ ሴት ፡
ነበረች ፤ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የግድ ፡ አለችው ፤ በዚያም ፡ ባለፈ ፡ ቍጥር ፡ እንጀራ ፡ ሊበላ ፡ ወደዚያ ፡ ይገባ ፡
ነበር ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ለባሏም ፦ ይህ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ዘውትር ፡ የሚያልፈው ፡ ቅዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃለኹ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ትንሽ ፡ ቤት ፡ በሰገነቱ ፡ ላይ ፡ እንሥራ ፤ በዚያም ፡ ዐልጋ ፡ ጠረጴዛ ፡ ወንበርና ፡ መቅረዝ ፡
እናኑርለት ፤ ወደ ፡ እኛም ፡ ሲመጣ ፡ ወደዚያ ፡ ይገባል ፡ አለችው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 11 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ወደዚያ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገብቶ ፡ በዚያ ፡ ዐረፈ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ሎሌውንም ፡ ግያዝን ፦ ይህችን ፡ ሱነማዊት ፡ ጥራ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 13 ፤ በጠራትም ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ቆመች ። ርሱም ፦ እንሆ ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ዐሳብ ፡
ዐሰብሺልኝ ፤ አኹንስ ፡ ምን ፡ ላድርግልሽ ፧ ለንጉሥ ፡ ወይስ ፡ ለሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ልንገርልሽን ፧ በላት ፡
አለው ፤ ርሷም ፦ እኔ ፡ በወገኔ ፡ መካከል ፡ ተቀምጫለኹ ፡ ብላ ፡ መለሰች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እናድርግላት ፧ አለ ። ግያዝም ፦ ልጅ ፡ የላትም ፤ ባሏም ፡
ሽምግሏል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ ጥራት ፡ አለ ። በጠራትም ፡ ጊዜ ፡ በደጃፉ ፡ ቆመች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ርሱም ፦ በሚመጣው ፡ ዓመት ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትታቀፊያለሽ ፡
አለ ፤ ርሷም ፦ አይደለም ፡ ጌታዬ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ባሪያኽን ፡ እንዳትዋሻት ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ሴቲቱም ፡ ፀነሰች ፥ በዚያም ፡ ወራት ፡ በዐዲሱ ፡ ዓመት ፡ ኤልሳዕ ፡ እንዳላት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡
ወለደች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ሕፃኑም ፡ አደገ ፥ አንድ ፡ ቀንም ፡ እኽል ፡ ዐጫጆች ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ወጣ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 19 ፤ አባቱንም ፦ ራሴን ፡ ራሴን ፡ አለው ፤ ርሱም ፡ ሎሌውን ፦ ተሸክመኽ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ውሰደው ፡
አለው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 20 ፤ አንሥቶም ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ወሰደው ፤ በጕልበቷም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፡
ተቀመጠ ፥ ሞተም ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 21 ፤ ወጥታም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ አጋደመችው ፥ በሩንም ፡ ዘግታበት ፡ ወጣች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ባሏንም ፡ ጠርታ ፦ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በፍጥነት ፡ ደርሼ ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡
ሎሌና ፡ አንድ ፡ አህያ ፡ ላክልኝ ፡ አለችው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ መባቻ ፡ ወይም ፡ ሰንበት ፡ ያይደለ ፡ ዛሬ ፡ ለምን ፡
ትኼጂበታለሽ ፧ አለ ። ርሷም ፦ ደኅና ፡ ነው ፡ አለች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 24 ፤ አሀያውንም ፡ አስጭና ፡ ሎሌዋን ፦ ንዳ ፥ ኺድ ፤ እኔ ፡ ሳላዝ፟ኽ ፡ አታዘግየኝ ፡ አለችው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 25 ፤ እንዲሁም ፡ ኼደች ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ መጣች ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ከሩቅ ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ሎሌውን ፡ ግያዝን ፥ እንሂት ፡ ሱነማዊቲቱ ፡ መጣች ፤

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 26 ፤ ትቀበላትም ፡ ዘንድ ፡ ሩጥና ፦ በደኅናሽ ፡ ነውን ፧ ባልሽ ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ ልጅሽስ ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ በላት ፡ አለው ። ርሷም ፦ ደኅና ፡ ነው ፡ አለች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ተራራው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ እግሮቹን ፡ ጨበጠች ፤ ግያዝም ፡ ሊያርቃት ፡ ቀረበ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፦ ነፍሷ ፡ ዐዝናለችና ፡ ተዋት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያን ፡ ከእኔ ፡ ሰውሮታል ፡ አልነገረኝምም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 28 ፤ ርሷም ፦ በእውኑ ፡ ከጌታዬ ፡ ልጅን ፡ ለመንኹን ፧ እኔም ፡ አታታሎኝ ፡ አላልኹኽምን ፧ አለች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 29 ፤ ግያዝንም ፦ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፥ በትሬንም ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኽ ፡ ኺድ ፤ ሰውም ፡ ብታገኝ ፡ ሰላም ፡ አትበል ፥ ርሱም ፡ ሰላም ፡ ቢልኽ ፡ አትመልስለት ፤ በትሬንም ፡ በሕፃኑ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ አኑር ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 30 ፤ የሕፃኑም ፡ እናት ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በሕያው ፡ ነፍስኽም ፡ እምላለኹ! ፡ አልተውኽም ፡ አለች ፤ ተነሥቶም ፡ ተከተላት ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 31 ፤ ግያዝም ፡ ቀደማቸው ፥ በትሩንም ፡ በሕፃኑ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ አኖረው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ድምፅ ፡ ወይም ፡ መስማት ፡ አልነበረም ፤ ርሱንም ፡ ሊገናኘው ፡ ተመልሶ ፦ ሕፃኑ ፡ አልነቃም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 32 ፤ ኤልሳዕም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሕፃኑ ፡ ሞቶ ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ተጋድሞ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 33 ፤ ገብቶም ፡ በሩን ፡ ከኹለቱ ፡ በኋላ ፡ ዘጋ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 34 ፤ መጥቶም ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ተኛ ፤ አፉንም ፡ በአፉ ፥ ዐይኑንም ፡ በዐይኑ ፥ እጁንም ፡ በእጁ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ተጋደመበት ፤ የሕፃኑም ፡ ገላ ፡ ሞቀ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 35 ፤ ተመልሶም ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ተመላለሰ ፤ ደግሞም ፡ ወጥቶ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በሕፃኑ ፡ ላይ ፡ ተጋደመ ፤ ሕፃኑም ፡ ዐይኖቹን ፡ ከፈተ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 36 ፤ ግያዝንም ፡ ጠርቶ ፦ ይህችን ፡ ሱነማዊት ፡ ጥራ ፡ አለው ። ጠራትም ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፦ ልጅሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ውሰጂ ፡ አላት ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 37 ፤ ገብታም ፡ በእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ወደቀች ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ተደፋች ፤ ልጇንም ፡ አንሥታ ፡ ወጣች ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 38 ፤ ኤልሳዕም ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ መጣ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ነበረ ፤ የነቢያትም ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፥ ሎሌውንም ፦ ታላቁን ፡ ምንቸት ፡ ጣድ ፥ ለነቢያት ፡ ልጆችም ፡ ወጥ ፡ ሥራ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 39 ፤ አንዱም ፡ ቅጠላቅጠል ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ፥ የምድረ ፡ በዳውንም ፡ ሐረግ ፡ አገኘ ፡ ከዚያም ፡ የበረሓ ፡ ቅል ፡ ሰበሰበ ፥ ልብሱንም ፡ ሞልቶ ፡ ተመለሰ ፥ መትሮም ፡ በወጡ ፡ ምንቸት ፡ ውስጥ ፡ ጨመረው ፤ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ አላወቁም ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 40 ፤ ሰዎቹም ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ቀዱ ፤ ወጡንም ፡ በቀመሱ ፡ ጊዜ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ በምንቸቱ ፡ ውስጥ ፡ ሞት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ጮኹ ፤ ይበሉም ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 41 ፤ ርሱም ፦ ዱቄት ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፤ በምንቸቱም ፡ ውስጥ ፡ ጥሎ ፦ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ቅዱ ፡ አለ ። በምንቸቱም ፡ ውስጥ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልተገኘም ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 42 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ከበዓልሻሊሻ ፡ የበኩራቱን ፡ እንጀራ ፥ ኻያ ፡ የገብስ ፡ እንጀራ ፥ የእኽልም ፡ እሸት ፡ በአቀ-ማዳ ፡ ይዞ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መጣ ፤ ርሱም ፦ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስጣቸው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 43 ፤ ሎሌውም ፦ ይህን ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ለመቶ ፡ ሰው ፡ እሰጣለኹ ፧ አለ ። ርሱም ፦ ይበላሉ ፡ ያተርፋሉም ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስጣቸው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 4 ፡ 44 ፤ እንዲሁም ፡ በፊታቸው ፡ አኖረው ፥ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በሉ ፥ አተረፉም ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 1 ፤ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ንዕማንም ፡ እግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ እጅ ፡ ለሶርያ ፡ ደኅንነትን ፡ ስለ ፡ ሰጠ ፡ በጌታው ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ክቡር ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ደግሞም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ነበረ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለምጻም ፡ ነበረ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 2 ፤ ከሶርያውያንም ፡ አገር ፡ አደጋ ፡ ጣዮች ፡ ወጥተው ፡ ነበር ፥ ከእስራኤልም ፡ ምድር ፡ ታናሽ ፡ ብላቴና ፡ ሴት ፡ ማርከው ፡ ነበር ፤ የንዕማንንም ፡ ሚስት ፡ ታገለግል ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 3 ፤ እመቤቷንም ፦ ጌታዬ ፡ በሰማርያ ፡ ካለው ፡ ከነቢዩ ፡ ፊት ፡ ቢደርስ ፡ ኖሮ ፡ ከለምጹ ፡ በፈወሰው ፡ ነበር ፡ አለቻት ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 4 ፤ ንዕማንም ፡ ገብቶ ፡ ለጌታው ፦ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ የኾነች ፡ አንዲት ፡ ብላቴና ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ብላለች ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 5 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ንዕማንን ፦ ኺድ ፥ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ እልካለኹ ፡ አለው ። ርሱም ፡ ኼደ ፥ ዐሥርም ፡ መክሊት ፡ ብር ፥ ስድስት ፡ ሺሕም ፡ ወርቅ ፥ ዐሥርም ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ በእጁ ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 6 ፤ ለእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፦ ይህች ፡ ደብዳቤ ፡ ወዳንተ ፡ ስትደርስ ፡ ባሪያዬን ፡ ንዕማንን ፡ ከለምጹ ፡ ትፈውሰው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰደድኹልኽ ፡ ዕወቅ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ደብዳቤውን ፡ ባነበበ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፦ ሰውን ፡ ከለምጹ ፡ እፈውስ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መስደዱ ፡ እኔ ፡ በእውኑ ፡ ለመግደልና ፡ ለማዳን ፡ የምችል ፡ አምላክ ፡ ኾኜ ፡ ነውን ፧ ተመልከቱ ፥ የጠብ ፡ ምክንያትም ፡ እንደሚፈልግብኝ ፡ እዩ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ኤልሳዕ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ እንደ ፡ ቀደደ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ ልብስኽን ፡ ለምን ፡ ቀደድኽ ፧ ወደ ፡ እኔ ፡ ይምጣ ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ነቢይ ፡ እንዳለ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ንዕማንም ፡ በፈረሱና ፡ በሠረገላው ፡ መጣ ፥ በኤልሳዕም ፡ ቤት ፡ ደጃፍ ፡ ውጭ ፡ ቆመ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 10 ፤ ኤልሳዕም ፦ ኺድ ፥ በዮርዳኖስም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ታጠብ ፤ ሥጋኽም ፡ ይፈወሳል ፥ አንተም ፡ ንጹሕ ፡ ትኾናለኽ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መልእክተኛ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 11 ፤ ንዕማን ፡ ግን ፡ ተቈጥቶ ፡ ኼደ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚመጣ ፥ ቆሞም ፡ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፥ የለምጹንም ፡ ስፍራ ፡ በእጁ ፡ ዳሰ ፡ የሚፈውሰኝ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 12 ፤ የደማስቆ ፡ ወንዞች ፡ አባናና ([174]) ፡ ፋርፋ ([175]) ፡ ከእስራኤል ፡ ውሃዎች ፡ ኹሉ ፡
አይሻሉምን ፧ በእነርሱስ ፡ ውስጥ ፡ መታጠብና ፡ መንጻት ፡ አይቻለኝም ፡ ኖሯልን ፧ ዘወርም ፡ ብሎ ፡ ተቈጥቶ ፡ ኼደ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 13 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ቀርበው ። አባት ፡ ሆይ ፥ ነቢዩ ፡ ታላቅ ፡ ነገርስ ፡ እንኳ ፡ ቢነግርኽ ፡ ኖሮ ፡
ባደረግኸው ፡ ነበር ፤ ይልቁንስ ። ታጠብና ፡ ንጹሕ ፡ ኹን ፡ ቢልኽ ፡ እንዴት ፡ ነዋ! ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 14 ፤ ወረደም ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ብቅ ፡ ጥልቅ ፡
አለ ፤ ሥጋውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንደ ፡ ትንሽ ፡ ብላቴና ፡ ሥጋ ፡ ኾኖ ፡ ተመለሰ ፥ ንጹሕም ፡ ኾነ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 15 ፤ ርሱም ፡ ከጭፍራው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ተመለሰ ፥ ወጥቶም ፡ በፊቱ ፡
ቆመና ፦ እንሆ ፥ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ ዐወቅኹ ፤ አኹንም ፡ ከባሪያኽ ፡
በረከት ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ርሱም ፦ በፊቱ ፡ የቆምኹት ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ አልቀበልም ፡ አለ ። ይቀበለውም ፡
ዘንድ ፡ ግድ ፡ አለው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እንቢ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 17 ፤ ንዕማንም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ለሌላዎች ፡
አማልክት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ አላቀርብምና ፡ ኹለት ፡ የበቅሎ ፡ ጭነት ፡ ዐፈር ፡
እንድወስድ ፡ ዕሺ ፡ ትለኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ፤ ጌታዬ ፡ በዚያ ፡
ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ እጄን ፡ ተደግፎ ፡ ወደሬሞን ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፥ እኔም ፡ በሬሞን ፡ ቤት ፡ በሰገድኹ ፡
ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ለባሪያኽ ፡ ይቅር ፡ ይበለኝ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 19 ፤ ርሱም ፦ በደኅና ፡ ኺድ ፡ አለው ። አንድ ፡ አግድመትም ፡ ያኽል ፡ ከርሱ ፡ ራቀ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ሎሌ ፡ ግያዝ ፦ ጌታዬ ፡ ሶርያዊውን ፡ ይህን ፡ ንዕማንን ፡
ማረው ፥ ካመጣለትም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ አልተቀበለም ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ በስተኋላው ፡ እሮጣለኹ ፥ ከርሱም ፡
አንዳች ፡ እወስዳለኹ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 21 ፤ ግያዝም ፡ ንዕማንን ፡ ተከተለው ፤ ንዕማንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲሮጥ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ሊገናኘው ፡
ከሠረገላው ፡ ወርዶ ፦ ኹሉ ፡ ደኅና ፡ ነውን ፧ አለው ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 22 ፤ ርሱም ፦ ደኅና ፡ ነው ። አኹን ፡ ከነቢያት ፡ ወገን ፡ የኾኑት ፡ ኹለት ፡ ጕልማሳዎች ፡
ከተራራማው ፡ ከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተዋል ፤ አንድ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ ኹለት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡
ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ጌታዬ ፡ ላከኝ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 23 ፤ ንዕማንም ፦ ኹለት ፡ መክሊት ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ ይፈቀድልኽ ፡ አለ ፤ ግድ ፡
አለውም ፤ ኹለቱንም ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ በኹለት ፡ ከረጢት ፡ ውስጥ ፡ አሰረና ፡ ከኹለት ፡ መለወጫ ፡ ልብስ ፡ ጋራ ፡
ለኹለት ፡ ሎሌዎቹ ፡ አስያዘ ፤ እነርሱም ፡ ተሸክመው ፡ በፊቱ ፡ ኼዱ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 24 ፤ ወደ ፡ ኰረብታውም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከእጃቸው ፡ ወስዶ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡
አኖራቸው ፤ ሰዎቹንም ፡ አሰናበተ ፥ እነርሱም ፡ ኼዱ ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 25 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ገብቶ ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ ቆመ ፤ ኤልሳዕም ፦ ግያዝ ፡ ሆይ ፥ ከወዴት ፡
መጣኽ ፧ አለው ። ርሱም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ወዴትም ፡ አልኼድኹም ፡ አለ ።

---

174 ዕብ. ፥ አባናህ ።

175 ዕብ. ፥ ፋርፋር ፡ (የተፈረፈረ) ።

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 26 ፤ ርሱም ፦ ያ ፡ ሰው ፡ ከሠረገላው ፡ ወርዶ ፡ ሊቀበልኽ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ልቤ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አልኼደምን ፧ ብሩንና ፡ ልብሱን ፥ የወይራውንና ፡ የወይኑን ፡ ቦታ ፥ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፥ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ባሪያዎች ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ጊዜው ፡ ነውን ፧

ነገ.2 ፡ 5 ፡ 27 ፤ እንግዲህስ ፡ የንዕማን ፡ ለምጽ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፥ ለዘለዓለምም ፡ በዘርኽ ፡ ላይ ፡ ይጣበቃል ፡ አለው ። እንደ ፡ በረዶም ፡ ለምጻም ፡ ኾኖ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 1 ፤ የነቢያትም ፡ ልጆች ፡ ኤልሳዕን ፦ እንሆ ፥ በፊትኽ ፡ የምንቀመጥበት ፡ ስፍራ ፡ ጠቦናል ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ እንኺድ ፥ ከእኛም ፡ እያንዳንዱ ፡ ከዚያ ፡ ምሰሶ ፡ ያምጣ ፥ የምንቀመጥበትንም ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ እንሥራ ፡ አሉት ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ አንዱ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ለመኼድ ፡ ፍቀድ ፡ አለ ። ርሱም ፦ እኼዳለኹ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ኼደ ፤ ወደ ፡ ዮርዳኖስም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ዕንጨት ፡ ቈረጡ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 5 ፤ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ምሰሶውን ፡ ሲቈርጥ ፡ የምሣሩ ፡ ብረት ፡ ወደ ፡ ውሃው ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ፤ ርሱም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ወየው! ፡ ወየው! ፡ የተዋስኹት ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፦ የወደቀው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አለ ፡ ስፍራውንም ፡ አሳየው ፤ ዕንጨትም ፡ ቈርጦ ፡ በዚያ ፡ ጣለው ፥ ብረቱም ፡ ተንሳፈፈ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 7 ፤ ርሱም ፦ ውሰደው ፡ አለ ፤ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ወሰደው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 8 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ፤ ከባሪያዎቹም ፡ ጋራ ፡ ተማክሮ ፦ በዚህ ፡ ተደብቀን ፡ እንሰፍራለን ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፦ ሶርያውያን ፡ በዚያ ፡ ተደብቀዋልና ፥ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ እንዳታልፍ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ብሎ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደነገረው ፡ ስፍራ ፡ ሰደደ ፤ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ሳይኾን ፥ ኹለት ፡ ጊዜም ፡ ሳይኾን ፡ በዚያ ፡ ራሱን ፡ አዳነ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 11 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ልብ ፡ ስለዚህ ፡ እጅግ ፡ ታወከ ፤ ባሪያዎቹንም ፡ ጠርቶ ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ የተወዳጀ ፡ እንዳለ ፡ አትነግሩኝምን ፧ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 12 ፤ ከባሪያዎቹም ፡ አንዱ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እንዲህ ፡ እኮ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዕልፍኝኽ ፡ ውስጥ ፡ ኾነኽ ፡ የምትናገረውን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ኤልሳዕ ፡ ለእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ይነግረዋል ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 13 ፤ ርሱም ፦ ልኬ ፡ አስይዘው ፡ ዘንድ ፡ ኼዳችኹ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እዩ ፡ አለ ። እነርሱም ፦ እንሆ ፥ በዶታይን ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ወደዚያም ፡ ፈረሶችንና ፡ ሠረገላዎችን ፡ እጅግም ፡ ጭፍራ ፡ ሰደደ ፤ በሌሊትም ፡ መጥተው ፡ ከተማዪቱን ፡ ከበቡ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሎሌ ፡ ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በከተማዪቱ ፡ ዙሪያ ፡ ጭፍራና ፡ ፈረሶች ፡ ሠረገላዎችም ፡ ነበሩ ። ሎሌውም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ ምን ፡ እናደርጋለን ፧ አለው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 16 ፤ ርሱም ፦ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ካሉት ፡ ይበልጣሉና ፡ አትፍራ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 17 ፤ ኤልሳዕም ፦ አቤቱ ፥ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ዐይኖቹን ፥ እባክኽ ፥ ግለጥ ፡ ብሎ ፡
ጸለየ ። እግዚአብሔርም ፡ የብላቴናውን ፡ ዐይኖች ፡ ገለጠ ፥ አየም ፤ እንሆም ፥ በኤልሳዕ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉት ፡ የእሳት ፡
ፈረሶችና ፡ ሠረገላዎች ፡ ተራራውን ፡ ሞልተውት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ ኤልሳዕ ፦ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ዕውር ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡
እለምንኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ። ኤልሳዕም ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፡ ዕውር ፡ አደረጋቸው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 19 ፤ ኤልሳዕም ፦ መንገዱ ፡ በዚህ ፡ አይደለም ፥ ከተማዩ ቱም ፡ ይህች ፡ አይደለችም ፤ የምትሹትን ፡
ሰው ፡ አሳያችኹ ፡ ዘንድ ፡ ተከተሉኝ ፡ አላቸው ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ መራቸው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፥ ኤልሳዕ ፦ አቤቱ ፥ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ የእነዚህን ፡ ሰዎች ፡ ዐይኖች ፡
ግለጥ ፡ አለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዐይኖቻቸውን ፡ ገለጠ ፥ እነርሱም ፡ አዩ ። እንሆም ፥ በሰማርያ ፡ መካከል ፡ ነበሩ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 21 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ኤልሳዕን ፦ አባቴ ፡
ሆይ ፥ ልግደላቸውን ? ልግደላቸውን ? አለው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 22 ፤ ርሱም ፦ አትግደላቸው ፤ በሰይፍኽና ፡ በቀስትኽ ፡ የማረክኸውን ፡ ትገድል ፡ ዘንድ ፡
ይገባኻልን ? እንጀራና ፡ ውሃ ፡ በፊታቸው ፡ አኑርላቸው ፥ በልተውና ፡ ጠጥተውም ፡ ወደ ፡ ጌታቸው ፡ ይኺዱ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 23 ፤ ብዙም ፡ መብል ፡ አዘጋጀላቸው ፤ በበሉና ፡ በጠጡ ፡ ጊዜም ፡ አሰናበታቸው ፥ እነርሱም ፡ ወደ ፡
ጌታቸው ፡ ኼዱ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሶርያ ፡ አደጋ ፡ ጣዮች ፡ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ አልመጡም ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 24 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሰራዊቱን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ወጥቶም ፡
ሰማርያን ፡ ከበባት ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 25 ፤ በሰማርያም ፡ ታላቅ ፡ ራብ ፡ ኾኖ ፡ ነበር ፤ እንሆም ፥ የአህያ ፡ ራስ ፡ በዐምሳ ፡ ብር ፥ የርግብም ፡
ኩስ ፡ የጎሞር ፡ ስምንተኛ ፡ የሚኾን ፡ በዐምስት ፡ ብር ፡ እስኪሸጥ ፡ ድረስ ፡ ከበቧት ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 26 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ በተመላለሰ ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡
ሆይ ፥ ርዳኝ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጮኸች ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 27 ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያልረዳሽን ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ እረዳሻለኹ ? ከዐውድማው ፡ ወይስ ፡
ከመጥመቂያው ፡ ነውን ? አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 28 ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ኾነሻል ? አላት ፤ ርሷም ፦ ይህች ፡ ሴት ፦ ዛሬ ፡ እንድንበላው ፡ ልጅሽን ፡
አምጪ ፤ ነገም ፡ ልጄን ፡ እንበላለን ፡ አለችኝ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 29 ፤ ልጄንም ፡ ቀቅለን ፡ በላነው ፤ በማግስቱም ፦ እንድንበላው ፡ ልጅሽን ፡ አምጪ ፡
አልኋት ፤ ልጇንም ፡ ሸሸገችው ፡ ብላ ፡ መለሰችለት ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፡ የሴቲቱን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፤ በቅጥርም ፡ ይመላለስ ፡
ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በስተውስጥ ፡ በሥጋው ፡ ላይ ፡ ለብሶት ፡ የነበረውን ፡ ማቅ ፡ አዩ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 31 ፤ ንጉሡም ፦ የሣፋጥ ፡ ልጅ ፡ የኤልሳዕ ፡ ራስ ፡ ዛሬ ፡ በላዩ ፡ ያደረ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡
ይህን ፡ ያድርግብኝ ፥ ይህንም ፡ ይጨምርብኝ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 32 ፤ ኤልሳዕ ፡ ግን ፡ በቤቱ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥ ሽማግሌዎችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠው ፡

ነበር ፤ ንጉሡ ፡ ሰው ፡ ላካ ፤ መልእክተኛውም ፡ ገና ፡ ሳይደርስ ፡ ለሽማግሌዎች ፦ ይህ ፡ የነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ልጅ ፡ ራሴን ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ላከ ፡ እዩ ፤ መልእክተኛውም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ደጁን ፡ ዘግታችኹ ፡ ከልክሉት ፤ የጌታው ፡ የእግሩ ፡ ኰቴ ፡ በኋላው ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 6 ፡ 33 ፤ ሲናገራቸውም ፡ መልእክተኛው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ደረሰ ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ እግዚአብሔርን ፡ ገና ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ምንድር ፡ ነኝ ፧ አለ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 1 ፤ ኤልሳዕም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ አንድ ፡ መስፈሪያ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፥ ኹለትም ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፡ ይሸመታል ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ በእጁ ፡ ተደግፎ ፡ የነበረ ፡ አለቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መልሶ ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፡ መስኮቶች ፡ ቢያደርግ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ይኾናልን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እንሆ ፥ በዐይኖችኽ ፡ ታየዋለኽ ፥ ከዚያም ፡ አትቀምስም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 3 ፤ በበሩም ፡ መግቢያ ፡ አራት ፡ ለምጻም ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ እስከንሞት ፡ ድረስ ፡ በዚህ ፡ ለምን ፡ እንቀመጣለን ፧

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ከተማ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ብንወድ ፡ ራብ ፡ በከተማ ፡ አለ ፥ በዚያም ፡ እንሞታለን ፤ በዚህም ፡ ብንቀመጥ ፡ እንሞታለን ። እንግዲህ ፡ ኑ ፥ ወደሶርያውያን ፡ ሰፈር ፡ እንሸሽ ፤ በሕይወት ፡ ቢያኖሩን ፡ እንኖራለን ፤ ቢገድሉንም ፡ እንሞታለን ፡ ተባባሉ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ጨለምለም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ወደሶርያውያን ፡ ሰፈር ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ተነሡ ፤ ወደሶርያውያንም ፡ ሰፈር ፡ መዠመሪያ ፡ ዳርቻ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ማንም ፡ አልነበረም ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሶርያውያን ፡ የሠረገላና ፡ የፈረስ ፡ የብዙም ፡ ጭፍራ ፡ ድምፅ ፡ አሰምቶ ፡ ነበር ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የኬጢያውያንና ፡ የግብጻውያንን ፡ ነገሥት ፡ ቀጥሮ ፡ አምጥቶብናል ፡ ይባባሉ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 7 ፤ ስለዚህም ፡ ተነሥተው ፡ በጨለማ ፡ ሸሹ ፤ ድንኳኖቻቸውንና ፡ ፈረሶቻቸውን ፡ አህያዎቻቸውንና ፡ ሰፈሩን ፡ እንዳለ ፡ ትተው ፡ ነፍሳቸውን ፡ ያድኑ ፡ ዘንድ ፡ ሸሹ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 8 ፤ እነዚህም ፡ ለምጻሞች ፡ ወደሰፈሩ ፡ መዠመሪያ ፡ ዳርቻ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ድንኳን ፡ ገብተው ፡ በሉ ፡ ጠጡም ፥ ከዚያም ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ልብስም ፡ ወሰዱ ፥ ኼደውም ፡ ሸሸጉት ፤ ተመልሰውም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ድንኳን ፡ ገቡ ፥ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ ወስደው ፡ ሸሸጉ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 9 ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ። መልካም ፡ አላደረግንም ፤ ዛሬ ፡ የመልካም ፡ ምሥራች ፡ ቀን ፡ ነው ፥ እኛም ፡ ዝም ፡ ብለናል ፤ እስኪነጋም ፡ ድረስ ፡ ብንቈይ ፡ በደለኞች ፡ እንኾናለን ፤ ኑ ፥ እንኺድ ፤ ለንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ እንናገር ፡ ተባባሉ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 10 ፤ መጥተውም ፦ ወደሶርያውያን ፡ ሰፈር ፡ መጣን ፥ እንሆም ፥ ፈረሶችና ፡ አህያዎች ፡ ታስረው ፥ ድንኳኖችም ፡ ተተክለው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አልነበረም ፥ የሰውም ፡ ድምፅ ፡ አልነበረም ፡ ብለው ፡ ወደከተማዩቱ ፡ ደጅ ፡ ጠባቂ ፡ ጮኹ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 11 ፤ የደጁም ፡ ጠባቂዎች ፡ ጠሩ ፥ ለንጉሡም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አወሩ ።

ነገ.2 ፡ 7 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፡ በሌሊት ፡ ተነሥቶ ፡ ባሪያዎቹን ፦ ሶርያውያን ፡ ያደረጉብንን ፡

እነግራችኋለኹ ፤ እንደ ፡ ተራብን ፡ ያውቃሉ ፤ ስለዚህ ፦ ከከተማዩቱ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ በሕይወታቸው ፡
እንይዛቸዋለን ፥ ወደ ፡ ከተማም ፡ እንገባለን ፡ ብለው ፡ በሜዳ ፡ ይሸሸጉ ፡ ዘንድ ፡ ከሰፈሩ ፡ ወጥተዋል ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 13 ፤ ከባሪያዎቹም ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፦ በከተማ ፡ ከቀሩት ፡ ፈረሶች ፡ ዐምስት ፡
ይውሰዱ ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ቀሩት ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ፤ እንሆ ፥ እንዳለቁ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡
ወገን ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ፤ እንስደድም ፥ እንይም ፡ አለ ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 14 ፤ ኹለትም ፡ ሠረገላዎች ፡ ከፈረሶች ፡ ጋራ ፡ ወሰዱ ፤ ንጉሡም ፦ ኼዳችኹ ፡ እዩ ፡ ብሎ ፡
ከሶርያውያን ፡ ሰራዊት ፡ በኋላ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 15 ፤ በኋላቸው ፡ እስከ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ድረስ ፡ ኼዱ ፤ እንሆም ፥ ሶርያውያን ፡ ሲሸሹ ፡ የጣሉት ፡
ልብስና ፡ ዕቃ ፡ መንገዱን ፡ ኹሉ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ። መልእክተኞችም ፡ ተመልሰው ፡ ለንጉሡ ፡ ነገሩት ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 16 ፤ ሕዝቡም ፡ ወጥቶ ፡ የሶርያውያንን ፡ ሰፈር ፡ በዘበዘ ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ አንድ ፡
መስፈሪያ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፥ ኹለትም ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፡ ተሸመተ ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ያን ፡ እጁን ፡ ይደግፈው ፡ የነበረውን ፡ አለቃ ፡ በሩን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡
አቆመው ። ሕዝቡም ፡ በበሩ ፡ ረገጠው ፥ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡
ተናገረው ፡ ሞተ ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 18 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ለንጉሡ ፦ ነገ ፡ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ ኹለት ፡ መስፈሪያ ፡
ገብስ ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፥ አንድም ፡ መስፈሪያ ፡ መልካም ፡ ዱቄት ፡ ባንድ ፡ ሰቅል ፡ ይሸመታል ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረው ፡
ነገር ፡ እንዲሁ ፡ ኾነ ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 19 ፤ ያም ፡ አለቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መልሶ ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፡ መስኮቶች ፡
ቢያደርግ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ይኾናልን ፧ ብሎ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ በዐይኖችኽ ፡ ታየዋለኽ ፥ ከዚያም ፡ አትቀምስም ፡
ብሎት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፥ 7 ፥ 20 ፤ እንዲሁም ፡ ደረሰበት ፤ ሕዝቡም ፡ በበሩ ፡ ረገጠውና ፡ ሞተ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ነገ.2 ፥ 8 ፥ 1 ፤ ኤልሳዕም ፡ ልጇን ፡ ያስነሣላትን ፡ ሴት ፦ አንቺ ፡ ከቤተ ፡ ሰብሽ ፡ ጋራ ፡ ተነሥተሽ ፡
ኺጂ ፥ በምታገኚውም ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጪ ፤ እግዚአብሔር ፡ ራብ ፡ ጠርቷል ፤ ሰባት ፡ ዓመትም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ይመጣል ፡ ብሎ ፡ ተናገራት ።

ነገ.2 ፥ 8 ፥ 2 ፤ ሴቲቱም ፡ ተነሥታ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ አደረገች ፤ ከቤተ ፡ ሰቢም ፡ ጋራ ፡ ኼዳ ፡
በፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠች ።

ነገ.2 ፥ 8 ፥ 3 ፤ ሰባቱም ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሴቲቱ ፡ ከፍልስጥኤም ፡ አገር ፡ ተመለሰች ፤ ስለ ፡ ቤቷና ፡
ስለ ፡ መሬቷ ፡ ልትጮኽ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወጣች ።

ነገ.2 ፥ 8 ፥ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሎሌ ፡ ከግያዝ ፡ ጋራ ። ኤልሳዕ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡
ኹሉ ፡ ንገረኝ ፡ እያለ ፡ ይጫወት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፥ 8 ፥ 5 ፤ ርሱም ፡ የሞተውን ፡ እንደ ፡ አስነሣ ፡ ለንጉሡ ፡ ሲናገር ፥ እንሆ ፥ ልጇን ፡ ያስነሣላት ፡ ሴት ፡
ስለ ፡ ቤቷና ፡ ስለ ፡ መሬቷ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ጮኸች ፤ ግያዝም ፦ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሴቲቱ ፡ ይህች ፡
ናት ፥ ኤልሳዕም ፡ ያስነሣው ፡ ልጇ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ ሴቲቱን ፡ ጠየቀ ፥ ነገረችውም ። ንጉሡም ፦ የነበረላትን ፡ ኹሉ ፥ መሬቷንም ፡ ከተወች ፡ ዠምራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ የዕርሻዋን ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ መልስላት ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ጃን ፡ ደረባውን ፡ አዘዘ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ኤልሳዕም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ መጣ ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ታሞ ፡ ነበር ፤ ወሬኞችም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደዚህ ፡ መጥቷል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ አዛሄልን ፦ ገጸ ፡ በረከት ፡ በእጅኽ ፡ ወስደኽ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ ልትገናኝ ፡ ኺድ ፤ በርሱም ፡ አፍ ። ከዚህ ፡ በሽታ ፡ እድናለኹን ፧ ብለኽ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቅ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 9 ፤ አዛሄልም ፡ ሊገናኘው ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከደማስቆ ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የአርባ ፡ ግመል ፡ ጭነት ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ወሰደ ፤ መጥቶም ፡ በፊቱ ፡ ቆመና ፦ ልጅኽ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ወልደ ፡ አዴር ። ከዚህ ፡ በሽታ ፡ እድናለኹን ፧ ሲል ፡ ወዳንተ ፡ ልኮኛል ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 10 ፤ ኤልሳዕም ፦ ኺድ ፥ መዳንስ ፡ ትድናለኽ ፡ በለው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዲሞት ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳይቶኛል ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 11 ፤ እስኪያፍርም ፡ ድረስ ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ አነባ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 12 ፤ አዛሄልም ፦ ጌታዬ ፡ ለምን ፡ ያነባል ፧ አለ ። ርሱም ፦ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የምታደርገውን ፡ ክፋት ፡ ስለማውቅ ፡ ነው ፤ ምሽጎቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለኽ ፥ ጕልማሳዎቻቸውንም ፡ በሰይፍ ፡ ትገድላለኽ ፥ ሕፃናታቸውንም ፡ ትፈጠፍጣለኽ ፥ እርጉዞቻቸውንም ፡ ትቀዳለኽ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 13 ፤ አዛሄልም ፦ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ላደርግ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ውሻ ፡ ባሪያኽ ፡ ምንድር ፡ ነኝ ፧ አለ ። ኤልሳዕም ፦ አንተ ፡ በሶርያ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ እንድትኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳይቶኛል ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 14 ፤ ከኤልሳዕም ፡ ርቆ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ መጣ ፤ ርሱም ፦ ኤልሳዕ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ አለው ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ እንድትፈወስ ፡ ነገረኝ ፡ አለው ። በነጋውም ፡ ለሐፍ ፡ ወስዶ ፡ በውሃ ፡ ነከረው ፡ በፊቱም ፡ ላይ ፡ ሸፈነው ፥ ሞተም ። አዛሄልም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 16 ፤ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በአክአብ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮራም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 17 ፤ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 18 ፤ የአክአብንም ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ነበርና ፥ የአክአብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለርሱና ፡ ለልጆቹ ፡ ለዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ መብራት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፥ ስለ ፡ ባሪያው ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁዳን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 20 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ ኤዶምያስ ፡ ለይሁዳ ፡ እንዳይገብር ፡ ሸፈተ ፥ በላያቸውም ፡ ንጉሥ ፡ አነገሡ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 21 ፤ ኢዮራምም ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጸዓር ፡ ዐለፈ ፤ በሌሊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ርሱንና ፡ የሠረገላዎቹን ፡ አለቃዎች ፡ ከበው ፡ የነበሩትን ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ መታ ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 22 ፤ ኤዶምያስ ፡ ግን ፡ ለይሁዳ ፡ እንዳይገብር ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሸፈተ ። በዚያም ፡ ዘመን ፡

ደግሞ ፡ ልብና ፡ ሸፈተ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 23 ፤ የተረፈውም ፡ የኢዮራም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ሹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 24 ፤ ኢዮራምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ በፋንታውም ፡ ልጁ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 25 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በአክአብ ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 26 ፤ መንገሥ ፡ በገሥመረ ፡ ጊዜ ፡ አካዝያስ ፡ የኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ጎቶልያ ፡ የተባለች ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 27 ፤ በአክአብም ፡ ቤት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ እንደአክአብም ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ ለአክአብ ፡ ቤት ፡ ዐማች ፡ ነበረና ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 28 ፤ ከአክአብም ፡ ልጅ ፡ ከኢዮራም ፡ ጋራ ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄልን ፡ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ሊ.ጋጠም ፡ ኼደ ፤ ሶርያውንም ፡ ኢዮራምን ፡ አቈሰሉት ።

ነገ.2 ፡ 8 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮራም ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛሄል ፡ ጋራ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ በሬማት ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቍስል ፡ ይታከም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመለሰ ። የአክአብም ፡ ልጅ ፡ ኢዮራም ፡ ታሞ ፡ ነበርና ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ሊያየው ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወረደ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 1 ፤ ነቢዩም ፡ ኤልሳዕ ፡ ከነቢያት ፡ ልጆች ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ወገብኽን ፡ ታጥቀኽ ፡ ይህን ፡ የዘይት ፡ ማሰሮ ፡ በእጅኽ ፡ ያዝ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድም ፡ ኺድ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ በደረስኽ ፡ ጊዜ ፡ የናሜሲን ፡ ልጅ ፡ የኢዮሳፍጥን ፡ ልጅ ፡ ኢዩን ፡ ታገኘዋለኽ ፤ ገብተኽም ፡ ከወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ አስነሣው ፥ ወደ ፡ ጓዳም ፡ አግባው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 3 ፤ የዘይቱንም ፡ ማሰሮ ፡ ይዘኽ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፍሰውና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀባኹኽ ፡ በለው ፤ በሩንም ፡ ከፍተኽ ፡ ሽሽ ፥ አትዘግይም ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 4 ፤ እንዲሁም ፡ ጕልማሳው ፡ ነቢይ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ኼደ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 5 ፤ በገባም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ የሰራዊት ፡ አለቃዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ርሱም ፦ አለቃ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ አለ ። ኢዩም ፦ ከማንኛችን ፡ ጋራ ፡ ነው ፧ አለ ። ርሱም ፦ አለቃ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 6 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፤ ዘይቱንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፍሰ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀባኹኽ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 7 ፤ የባሪያዎቼን ፡ የነቢያትን ፡ ደም ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ባሪያዎች ፡ ሹሉ ፡ ደም ፡ ከኤልዛቤል ፡ እጅ ፡ እበቀል ፡ ዘንድ ፡ የጌታኽን ፡ የአክአብን ፡ ቤት ፡ ትመታለኽ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 8 ፤ የአክአብም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋል ፤ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ የታሰረውንና ፡ የተለቀቀውን ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ከአክአብ ፡ አጠፋለኹ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 9 ፤ የአክአብንም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ናባጥ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ቤት ፥ እንደአኪያም ፡ ልጅ ፡ እንደባአስ ፡ ቤት ፡ አደርገዋለኹ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ኤልዛቤልንም ፡ በኢይዝራኤል ፡ ዕርሻ ፡ ውሻዎች ፡ ይበሏታል ፥ የሚቀብራትም ፡ አታገኝም ። በሩንም ፡ ከፍቶ ፡ ሸሸ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 11 ፤ ኢዩም ፡ ወደጌታው ፡ ባሪያዎች ፡ ወጣ ፤ እነርሱም ፦ ደኅና ፡ ነውን ፧ ይህ ፡ እብድ ፡ ለምን ፡ መጣብኽ ፧ አሉት ። ርሱም ፦ ሰውዮውንና ፡ ነገሩን ፡ ታውቃላችኹ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ ሐሰት ፡ ነው ፤ ንገረን ፡ አሉት ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀባኹኽ ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ነገረኝ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 13 ፤ ኹሉም ፡ ፈጥነው ፡ ልብሳቸውን ፡ ወሰዱ ፥ በሰገነቱ ፡ መሰላል ፡ ዕርከን ፡ ላይ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አነጠፉት ፥ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ እየነፉ ፦ ኢዩ ፡ ነግሧል ፡ አሉ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 14 ፤ እንዲሁም ፡ የናሜሲ ፡ ልጅ ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዩ ፡ በኢዮራም ፡ ላይ ፡ ተማማለ ። ኢዮራምና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛሄል ፡ የተነሣ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 15 ፤ ንጉሡ ፡ ኢዮራም ፡ ግን ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛሄል ፡ ጋራ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቍስል ፡ ይታከም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመልሶ ፡ ነበር ። ኢዩም ፦ ልባችኹስ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ከኾነ ፡ በኢይዝራኤል ፡ እንዳያወራ ፡ ማንም ፡ ከከተማ ፡ ኩብሉ ፡ አይውጣ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 16 ፤ ኢዮራምም ፡ በዚያ ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ነበርና ፥ ኢዩ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ኼደ ። የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ ኢዮራምን ፡ ለማየት ፡ ወርዶ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 17 ፤ በኢይዝራኤልም ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ የቆመው ፡ ሰላይ ፡ የኢዩ ፡ ጭፍራ ፡ ሲመታ ፡ አይቶ ፦ ጭፍራ ፡ አያለኹ ፡ አለ ። ኢዮራምም ፦ የሚገናኘው ፡ ፈረሰኛ ፡ ላክ ፥ ርሱም ፦ ሰላም ፡ ነውን ፧ ይበለው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 18 ፤ ፈረሰኛውም ፡ ሊገናኘው ፡ ኼዶ ፦ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰላም ፡ ነውን ፧ አለ ። ኢዩም ፦ አንተ ፡ ከሰላም ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ዐልፈኽ ፡ ተከተለኝ ፡ አለ ። ሰላዩም ፦ መልእክተኛው ፡ ደረሰባቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልተመለሰም ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 19 ፤ ኹለተኛም ፡ ፈረሰኛ ፡ ሰደደ ፥ ወደ ፡ እነርሱም ፡ ደርሶ ፦ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰላም ፡ ነውን ፧ አለ ። ኢዩም ፦ አንተ ፡ ከሰላም ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ዐልፈኽ ፡ ተከተለኝ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 20 ፤ ሰላዩም ፦ ደረሰባቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልተመለሰም ፤ በችኮላ ፡ ይኼዳልና ፥ አካኼዱ ፡ እንደ ፡ ናሜሲ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኢዩ ፡ አካኼድ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 21 ፤ ኢዮራምም ፦ ሠረገላ ፡ አዘጋጁ ፡ አለ ፤ ሠረገላውንም ፡ አዘጋጁለት ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮራም ፡ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ በሠረገላዎቻቸው ፡ ተቀምጠው ፡ ወጡ ፥ ኢዩንም ፡ ሊገናኙት ፡ ኼዱ ፤ በኢይዝራኤላዊው ፡ በናቡቴ ፡ ዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ አገኙት ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 22 ፤ ኢዮራምም ፡ ኢዩን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፦ ኢዩ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ነውን ፧ አለ ። ርሱም ፦ የእናትኽ ፡ የኤልዛቤል ፡ ግልሙትናዋና ፡ መተቷ ፡ ሲበዛ ፡ ምን ፡ ሰላም ፡ አለ ፧ ብሎ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 23 ፤ ኢዮራምም ፡ መልሶ ፡ ነዳና ፡ ሸሸ ፥ አካዝያስንም ፦ አካዝያስ ፡ ሆይ ፥ ዐመፅ ፡ ነው ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 24 ፤ ኢዩም ፡ በእጁ ፡ ቀስቱን ፡ ለጠጠ ፥ ኢዮራምንም ፡ በጫንቃው ፡ መካከል ፡ ወጋው ፤ ፍላጻውም ፡ በልቡ ፡ ዐለፈ ፥ ወደ ፡ ሠረገላውም ፡ ውስጥ ፡ ወደቀ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 25 ፤ ኢዩም ፡ አለቃውን ፡ ቢድቃርን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አንሥተኽ ፡ በኢይዝራኤላዊው ፡ በናቡቴ ፡ ዕርሻ ፡ ጣለው ፥ አንተና ፡ እኔ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ በፈረስ ፡ ተቀምጠን ፡ አባቱን ፡ አክአብን ፡ በተከተልን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተናገረበት ፡ ዐስብ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 26 ፤ በእውነት ፡ የናቡቴንና ፡ የልጆቹን ፡ ደም ፡ ትናንትና ፡ አይቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚህም ፡ ዕርሻ ፡ እመልስብኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደተናገረው ፡ ቃል ፡ ወስደኽ ፡ በዕርሻው ፡ ውስጥ ፡ ጣለው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 27 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ አካዝያስ ፡ ያን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በአትክልት ፡ ቤት ፡ መንገድ ፡ ሸሸ ። ኢዩም ፦ ይህን ፡ ደግሞ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ውጉት ፡ እያለ ፡ ተከተለው ፤ በይብለዓምም ፡ አቅራቢያ ፡ ባለችው ፡ በጉር ፡ ዐቀበት ፡ ላይ ፡ ወጉት ። ወደ ፡ መጊዶም ፡ ሸሸ ፥ በዚያም ፡ ሞተ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 28 ፤ ባሪያዎቹም ፡ በሠረገላው ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወሰዱት ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ በመቃብሩ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 29 ፤ በአክአብም ፡ ልጅ ፡ በኢዮራም ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ አካዝያስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 30 ፤ ኢዩም ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ መጣ ፤ ኤልዛቤልም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ዐይኗን ፡ ተኳለች ፥ ራሷንም ፡ አስጌጠች ፥ በመስኮትም ፡ ዘልቃ ፡ ትመለከት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 31 ፤ ኢዩም ፡ በበሩ ፡ ሲገባ ፦ ጌታውን ፡ የገደለ ፡ ዘምሪ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ነውን ፧ አለችው ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 32 ፤ ፊቱንም ፡ ወደ ፡ መስኮቱ ፡ አንሥቶ ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ። ኹለት ፡ ሦስትም ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለከቱ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 33 ፤ ርሱም ፦ ወደ ፡ ታች ፡ ወርውሯት ፡ አለ ፤ ወረወሯትም ፥ ደሟም ፡ በግንቡና ፡ በፈረሶቹ ፡ ላይ ፡ ተረጨ ፥ ረገጧትም ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 34 ፤ በገባም ፡ ጊዜ ፡ በላ ፡ ጠጣም ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፦ ይህችን ፡ የተረገመች ፡ እዩ ፤ የንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ናትና ፥ ቅበሯት ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 35 ፤ ሊቀብሯትም ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፥ ከዐናቷና ፡ ከእግሯ ፣ ከመዳፍም ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላገኙም ።

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 36 ፤ ተመልሰውም ፡ ነገሩት ፤ ርሱም ፦ በባሪያው ፡ በቴስብያዊ ፡ ኤልያስ ፦ በኢይዝራኤል ፡ ዕርሻ ፡ የኤልዛቤልን ፡ ሥጋ ፡ ውሻዎች ፡ ይበላሉ ፤

ነገ.2 ፡ 9 ፡ 37 ፤ የኤልዛቤልም ፡ ሬሳ ፡ በኢይዝራኤል ፡ ዕርሻ ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፍግ ፡ ይኾናልና ፥ ማንም ፦ ይህች ፡ ኤልዛቤል ፡ ናት ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 1 ፤ ለአክአብም ፡ በሰማርያ ፡ ሰባ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ኢዩም ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ፤ የአክአብን ፡ ልጆች ፡

ለሚያሳድጉ ፡ ለሰማርያ ፡ ታላላቆችና ፡ ሽማግሌዎች ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 2 ፤ ይህ ፡ ደብዳቤ ፡ አኹን ፡ በደረሳችኹ ፡ ጊዜ ፡ የጌታችኹ ፡ ልጆች ፡ ሠረገላዎችና ፡ ፈረሶችም ፡ የተመሸገችም ፡ ከተማ ፡ መሣሪያዎችም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አሉና ፥

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 3 ፤ ከጌታችኹ ፡ ልጆች ፡ ደስ ፡ የሚያሠኛችኹንና ፡ የሚሻላችኹን ፡ ምረጡ ፥ በአባቱም ፡ ዙፋን ፡ አስቀምጡት ፥ ስለ ፡ ጌታችኹም ፡ ቤት ፡ ተዋጉ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ሰደደ ፤

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 4 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፈርተው ፦ እንሆ ፥ ኹለቱ ፡ ነገሥታት ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤ እኛስ ፡ እንዴት ፡ እንቆማለን ፧ አሉ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 5 ፤ የቤቱ ፡ አለቃ ፥ የከተማዉቱም ፡ አለቃ ፥ ሽማግሌዎችና ፡ ልጆቹን ፡ የሚያሳድጉ ፦ እኛ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ነን ፥ ያዘዝኸንም ፡ ኹሉ ፡ እናደርጋለን ፤ ንጉሥም ፡ በላያችን ፡ አናነግሥም ፤ የምትወደውን ፡ አድርግ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ ላኩ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 6 ፤ ኹለተኛም ፦ ወገኖቼስ ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፥ ነገሬንም ፡ ከሰማችኹ ፥ የጌታችኹን ፡ ልጆች ፡ ራስ ፡ ቍረጡ ፥ ነገም ፡ በዚህ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይዛችኹ ፡ ኑ ፡ ብሎ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈላቸው ። የንጉሡም ፡ ልጆች ፡ ሰባው ፡ ሰዎች ፡ በሚያሳድጓቸው ፡ በከተማዉቱ ፡ ታላላቆች ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 7 ፤ ደብዳቤውም ፡ በደረሳቸው ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ሰባውን ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ገደሏቸው ፤ ራሳቸውንም ፡ በቅርጫት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ላኩ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 8 ፤ መልእክተኛም ፡ መጥቶ ፦ የንጉሡን ፡ ልጆች ፡ ራስ ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ርሱም ፦ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ በበሩ ፡ አደባባይ ፡ ኹለት ፡ ክምር ፡ አድርጋችኹ ፡ አኑሯቸው ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 9 ፤ በነጋውም ፡ ወጥቶ ፡ ቆመ ፥ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፦ እናንተ ፡ ንጹሓን ፡ ናችኹ ፤ እንሆ ፥ ጌታዬን ፡ የወነጀልኹ ፡ የገደልኹትም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እነዚህንስ ፡ ኹሉ ፡ የገደለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ከተናገረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ እንዳይወድቅ ፡ አኹን ፡ ዕወቁ ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሪያው ፡ በኤልያስ ፡ የተናገረውን ፡ አድርጓል ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 11 ፤ ኢዩም ፡ ከአክአብ ፡ ቤት ፡ የቀረውን ፡ ኹሉ ፥ ታላላቆቹንም ፡ ኹሉ ፥ ወዳጆቹንና ፡ ካህናቱን ፡ ማንም ፡ ሳይቀር ፡ በኢይዝራኤል ፡ ገደላቸው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ኼደ ፤ በመንገድም ፡ ወዳለው ፡ ወደበግ ፡ ጠባቂዎች ፡ ቤት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 13 ፤ ኢዩ ፡ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከአካዝያስ ፡ ወንድሞች ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፦ እናንተ ፡ እነማን ፡ ናችኹ ፧ አለ ። እነርሱም ፦ እኛ ፡ የአካዝያስ ፡ ወንድሞች ፡ ነን ፤ የንጉሡንና ፡ የእቴጌዉቱን ፡ ልጆች ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠየቅ ፡ እንወርዳለን ፡ አሉት ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ በሕይወታቸው ፡ ያሧቸው ፡ አለ ። ያሧቸውም ፥ በበግ ፡ ጠባቂዎችም ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ ጕድጓድ ፡ አርባ ፡ ኹለቱን ፡ ሰዎች ፡ ገደሏቸው ፤ ማንንም ፡ አላስቀረም ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 15 ፤ ከዚያም ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ የሬካብን ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብን ፡ ተገናኘው ፤ ደኅንነቱንም ፡ ጠይቆ ፦ ልቤ ፡ ከልብኽ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያኽል ፡ ልብኽ ፡ ከልቤ ፡ ጋራ ፡ በቅንነት ፡ ነውን ፧ አለው ፤ ኢዮናዳብም ፦ እንዲሁ ፡ ነው ፡ አለው ። ኢዩም ፦ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ኾነስ ፡ እጅኽን ፡ ስጠኝ ፡ አለ ። እጁንም ፡ ሰጠው ፤ ወደ ፡ ሠረገላውም ፡ አውጥቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስቀመጠውና ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 16 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ና ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ መቅናቴን ፡ እይ ፡ አለው ። በሠረገላውም ፡ አስቀመጠው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ለኤልያስ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እስኪያጠፋው ፡ ድረስ ፡ ከአክአብ ፡ በሰማርያ ፡ የቀረውን ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 18 ፤ ኢዩም ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቦ ፦ አክአብ ፡ በዓልን ፡ በጥቂቱ ፡ አመለከው ፤ ኢዩ ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ ያመልከዋል ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ የበዓልን ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፥ አገልጋዮቹንም ፡ ኹሉ ፥ ካህናቱንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ጥሩ ፤ ማንም ፡ አይቅር ፤ ለበዓል ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀርባለኹ ፥ የቀረውም ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ አይኖርም ፡ አላቸው ። ኢዩም ፡ የበዓልን ፡ አገልጋዮች ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በተንኰል ፡ ይህን ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 20 ፤ ኢዩም ፦ ለበዓል ፡ ዋና ፡ ጉባኤ ፡ ቀድሱ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ዐወጁ ። ኢዩም ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላከ ፥ የበዓልም ፡ አገልጋዮች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፤ ሳይመጣ ፡ የቀረ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልነበረም ። ወደበዓልም ፡ ቤት ፡ ገቡ ፥ የበዓልም ፡ ቤት ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ፤

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 22 ፤ ዕቃ ፡ ቤቱንም ፦ ለበዓል ፡ አገልጋዮች ፡ ኹሉ ፡ ልብስ ፡ አውጣ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 23 ፤ ልብሱንም ፡ አወጣላቸው ፦ ኢዩም ፡ የሬካብም ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ወደበዓል ፡ ቤት ፡ ገቡ ። የበዓልንም ፡ አገልጋዮች ፦ መርምሩ ፥ ከበዓል ፡ አገልጋዮች ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ወገን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ እንዳይኖር ፡ ተመልከቱ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 24 ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕትም ፡ ያቀረቡ ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ፤ ኢዩም ፦ በእጃችኹ ፡ አሳልፌ ፡ ከምሰጣችኹ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያመለጠ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነፍሱ ፡ በዚያ ፡ ነፍስ ፡ ፋንታ ፡ ትኾናለች ፡ ብሎ ፡ በውጪ ፡ ሰማንያ ፡ ሰዎችን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 25 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርበው ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ኢዩ ፡ ዘበኞቹንና ፡ አለቃዎቹን ፦ ግቡና ፡ ግደሏቸው ፤ አንድም ፡ አይውጣ ፡ አላቸው ። በሰይፍም ፡ ስለት ፡ ገደሏቸው ፤ ዘበኞችና ፡ አለቃዎችም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሏቸው ፥ ወደበዓልም ፡ ቤት ፡ ከተማ ፡ ኼዱ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 26 ፤ ከበዓልም ፡ ቤት ፡ ሐውልቶቹን ፡ አወጡ ፡ አቃጠሏቸውም ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 27 ፤ የበዓልን ፡ ሐውልት ፡ ቀጠቀጡ ፥ የበዓልንም ፡ ቤት ፡ አፈረሱ ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የውዳቂ ፡ መጣያ ፡ አደረጉት ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 28 ፤ እንዲሁም ፡ ኢዩ ፡ በዓልን ፡ ከእስራኤል ፡ አጠፋ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 29 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፥ በቤቴልና ፡ በዳን ፡ ከነበሩት ፡ ከወርቁ ፡ እንቦሶች ፥ ኢዩ ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢዩን ፦ በፊቴ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አድርገኻልና ፥ በልቤም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አድርገኻልና ፥ ልጆችኽ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 31 ፤ ኢዩ ፡ ግን ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አልተጠነቀቀም ፤ እስራኤልንም ፡ ካሳተው ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 32 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ እስራኤልን ፡ ይከፋፍላቸው ፡ ዘንድ ፡ ገመረ ፤ አዛሄልም ፡ በእስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ መታቸው ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 33 ፤ በዮርዳኖስ ፡ ምሥራቅ ፡ ያለውን ፡ የገለዓድን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፥ በአርኖን ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከዐሮዔር ፡ ገምሮ ፡ የጋድንና ፡ የሮቤልን ፡ የምናሴንም ፡ አገር ፥ ገለዓድንና ፡ ባሳንን ፡ መታ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 34 ፤ የቀረውም ፡ የኢዩ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ ጭከናውም ፡ ኹሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 35 ፤ ኢዩም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ፡ ቀበሩት ። በፋንታውም ፡ ልጁ ፡ ኢዮአካዝ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 10 ፡ 36 ፤ ኢዩም ፡ በሰማርያ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 1 ፤ የአካዝያስም ፡ እናት ፡ ጎቶልያ ፡ ልጇ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ የመንግሥትን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ አጠፋች ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 2 ፤ የንጉሡ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ የአካዝያስ ፡ እኅት ፡ ዮሳቤት ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአስን ፡ ወስዳ ፡ ከተገደሉት ፡ ከንጉሥ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ሰረቀችው ፤ ርሱንና ፡ ሞግዚቱንም ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝ ፡ ወሰደች ፥ እንዳይገደልም ፡ ከጎቶልያ ፡ ሸሸጉት ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 3 ፤ በርሷም ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ። ጎቶልያም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነገሠች ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 4 ፤ በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ዮዳዔ ፡ ልኮ ፡ በካራውያንና ፡ በዘበኞች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ወሰደ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገባቸው ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አማላቸው ፥ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አሳያቸው ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 5 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። እንዲህ ፡ አድርጉ ፤ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከምትገቡት ፡ ከእናንተ ፡ ከሦስት ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ዘብ ፡ ጠብቁ ፤

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ከእናንተ ፡ ከሦስት ፡ አንዱ ፡ እጅ ፡ በሱር ፡ በር ፡ ኹኑ ፤ አንዱም ፡ እጅ ፡ ከዘበኞች ፡ ቤት ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ በር ፡ ኹኑ ፤ ቤቱንም ፡ ጠብቁ ፥ ከልክሉም ፤

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 7 ፤ ከእናንተም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የምትወጡት ፡ ኹለቱ ፡ እጅ ፡ በንጉሥ ፡ ዙሪያ ፡ ኾናችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ጠብቁ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 8 ፤ ንጉሡንም ፡ በዙሪያው ፡ ክበቡት ፥ የጦር ፡ ዕቃችኹም ፡ በእጃችኹ ፡ ይኹን ፤ በሰልፋችኹ ፡ መካከል ፡ የሚገባ ፡ ይገደል ፤ ንጉሡም ፡ በወጣና ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኹኑ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 9 ፤ መቶ ፡ አለቃዎችም ፡ ካህኑ ፡ ዮዳዔ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ፤ ከነርሱም ፡ እያንዳንዱ ፡ በሰንበት ፡ ይገቡ ፡ የነበሩትን ፥ በሰንበቱም ፡ ይወጡ ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ ዮዳዔ ፡ መጡ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 10 ፤ ካህኑም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡን ፡ የዳዊትን ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ኹሉ ፡ ለመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ሰጣቸው ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 11 ፤ ዘበኞቹም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የጦር ፡ ዕቃቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡

ከቤቱ ፡ ቀኝ ፡ እስከ ፡ ቤቱ ፡ ግራ ፡ ድረስ ፡ በመሠዊያውና ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 12 ፤ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አውጥቶ ፡ ዘውዱን ፡ ጫነበት ፥ ምስክሩንም ፡ ሰጠው ፤ ቀብተውም ፡ ንጉሥ ፡ አደረጉትና ። ንጉሡ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ እያሉ ፡ እጃቸውን ፡ አጨበጨቡ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 13 ፤ ጎቶልያም ፡ የሰራዊቱንና ፡ የሕዝቡን ፡ ድምፅ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መጣች ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 14 ፤ እንሆም ፥ ንጉሡ ፡ እንደተለመደው ፡ በዐምዱ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፥ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ አለቃዎችና ፡ መለከተኞች ፡ ቆመው ፡ አየች ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ቀንደ ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ። ጎቶልያም ፡ ልብሷን ፡ ቀዳ ፦ ዐመፅ ፡ ነው ፥ ዐመፅ ፡ ነው ፡ ብላ ፡ ጮኸች ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 15 ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ በጭፍራው ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፦ ወደሰልፉ ፡ መካከል ፡ አውጧት ፤ የሚከተላትንም ፡ በሰይፍ ፡ ግደሉት ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፤ ካህኑ ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አትገደል ፡ ብሏልና ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 16 ፤ እጃቸውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፥ በፈረሱም ፡ መግቢያ ፡ መንገድ ፡ ወደንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወሰዷት ፥ በዚያም ፡ ገደሏት ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 17 ፤ ዮዳዔም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በንጉሡ ፡ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፤ ደግሞም ፡ በንጉሡና ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 18 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ወደበዓል ፡ ቤት ፡ ኼደው ፡ አፈረሱት ፤ መሠዊያዎቹንና ፡ ምስሎቹን ፡ አደቀቁ ፥ የበዓልንም ፡ ካህን ፡ ማታንን ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ገደሉት ። ካህኑም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አስተዳዳሪዎችን ፡ ሾመ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 19 ፤ መቶ ፡ አለቃዎቹንና ፡ ካራውያንንም ፥ ዘበኞችንና ፡ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ወሰደ ፤ ንጉሡንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አወረዱት ፥ በዘበኞችም ፡ በር ፡ መንገድ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ አመጡት ፤ በነገሥታቱም ፡ ዙፋን ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.2 ፡ 11 ፡ 20 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፥ ከተማዪቱም ፡ ጸጥ ፡ አለች ። ጎቶልያንም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሏት ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 1 ፤ ኢዮአስም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 2 ፤ በኢዩ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ኢዮአስ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ሳብያ ፡ የተባለች ፡ የቤርሳቤሕ ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 3 ፤ ካህኑ ፡ ዮዳዔም ፡ ያስተምረው ፡ በነበረ ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ ኢዮአስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ኢዮአስም ፡ ካህናቱን ፦ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚገባውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ገንዘብ ፡ ሹሉ ፥ ስለነፍሱም ፡ ዋጋ ፡ የሚቀርበውን ፡ ገንዘብ ፥ በልባቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚያመጡትን ፡ ገንዘብ ፡ ሹሉ ፥

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ካህናቱ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ከሚያመጣው ፡ ይውሰዱ ፡ በመቅደስም ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ይጠግኑበት ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ኢዮአስ ፡ እስከ ፡ ኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ካህናቱ ፡ አልጠገኑትም ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ኢዮአስም ፡ ካህኑን ፡ ዮዳሄንና ፡ ካህናቱን ፡ ጠርቶ ፦ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ ስፍራዎች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትጠግኗቸውም ፧ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ገንዘቡ ፡ ለቤቱ ፡ መጠገኛ ፡ ይሰጥ ፡ እንጂ ፡ ከሚያመጡት ፡ ሰዎች ፡ አትቀበሉ ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 9 ፤ ካህናቱም ፦ ከሕዝቡ ፡ ገንዘቡን ፡ አንወስድም ፥ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ የተናዱትን ፡ አንጠግንም ፡ ብለው ፡ ዕሺ ፡ አሉ ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ካህኑ ፡ ዮዳሄ ፡ ግን ፡ ሣጥን ፡ ወስዶ ፡ መክደኛውን ፡ ነደለው ፥ በመሠዊያውም ፡ አጠገብ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሚገቡበት ፡ መግቢያ ፡ በስተቀኝ ፡ አኖረው ፤ ደጁንም ፡ የሚጠብቁ ፡ ካህናት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚመጣውን ፡ ገንዘብ ፡ ሹሉ ፡ ያኖሩበት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 11 ፤ በሣጥንም ፡ ውስጥ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ መኖሩን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ጸሐፊና ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ ቈጥረው ፡ በከረጢት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሩት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 12 ፤ የተመዘነውንም ፡ ገንዘብ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ በተሾሙት ፡ እጅ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 13 ፤ የተናደውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመጠገን ፡ መክፈል ፡ ለሚያሻው ፡ ሹሉ ፡ ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለሚሠሩ ፡ ዐናጢዎችና ፡ ሠራተኞች ፡ ግንበኞችና ፡ ድንጋይ ፡ ወቃሪዎች ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከሚመጣው ፡ ገንዘብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚኾኑ ፡ የብር ፡ ጽዋዎችና ፡ ጕጠቶች ፡ ድስቶችም ፡ መለከቶችም ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃዎችም ፡ አልተሠሩም ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለሚሠሩት ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ጠገኑበት ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ለሠራተኞችም ፡ ይከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ ገንዘቡን ፡ የሚወስዱትን ፡ ሰዎች ፡ አይቈጣጠሯቸውም ፡ ነበር ፤ በታማኝነት ፡ ይሠሩ ፡ ነበርና ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 17 ፤ ስለበደልና ፡ ስለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የቀረበውም ፡ ገንዘብ ፡ ለካህናት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አያገቡትም ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄል ፡ ወጥቶ ፡ ጌትን ፡ ወጋ ፥ ያዘውም ፤ አዛሄልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመውጣት ፡ ፊቱን ፡ አቀና ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 19 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ አባቶቹ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ኢዮሳፍጥና ፡ ኢዮራም ፡ አካዝያስም ፡ የቀደሱትን ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፥ ርሱም ፡ የቀደሰውን ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የተገኘውን ፡ ወርቅ ፡ ሹሉ ፡ ወሰደ ፥ ወደሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አዛሄል ፡ ላከው ። ርሱም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሰ ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 20 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአስ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ሹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ተነሥተው ፡ ዐመፀበት ፥ ወደ ፡ ሲላ ፡ በሚወርደውም ፡ መንገድ ፡ በሚሎ ፡ ቤት ፡

ገደሉት ።

ነገ.2 ፡ 12 ፡ 22 ፤ ባሪያዎቹም ፡ የሰምዓት ፡ ልጅ ፡ የዘካርና ፡ የሾሜር ፡ ልጅ ፡ ዮዛባት ፡ መቱት ፥ ሞተም ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አሜስያስ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአካዝያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአስ ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዩ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአካዝ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ነገሠ ፤ ዐሥራ ፡ ሰባትም ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፥ እስራኤልንም ፡ ያሳተውን ፡ የናባጥን ፡ ልጅ ፡ የኢዮርብዓምን ፡ ኀጢአት ፡ ተከተለ ፤ ከርሷም ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ በዘመኑም ፡ ኹሉ ፡ በሶርያው ፡ ንጉሥ ፡ በአዛሄል ፡ እጅ ፥ በአዛሄልም ፡ ልጅ ፡ በወልደ ፡ አዴር ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 4 ፤ ኢዮአካዝም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤልን ፡ ያስጨነቀበትን ፡ ጭንቀት ፡ አይቷልና ፥ ሰማው ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ታዳጊ ፡ ሰጠ ፥ ከሶርያውያንም ፡ እጅ ፡ ዳኑ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ በድንኳናቸው ፡ ተቀመጡ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በርሷ ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፡ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ አልራቁም ፤ ደግሞም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ በሰማርያ ፡ ቆሞ ፡ ቀረ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ለኢዮአካዝም ፡ ከዐምሳ ፡ ፈረሰኞች ፥ ከዐሥርም ፡ ሠረገላዎች ፥ ከዐሥር ፡ ሺሕም ፡ እግረኞች ፡ በቀር ፡ ሕዝብ ፡ አልቀረለትም ፤ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ አጥፍቷቸዋልና ፥ በዐውድማም ፡ እንዳለ ፡ ዕብቅ ፡ አድቅቋቸዋልና ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 8 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአካዝ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ ጭከናውም ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 9 ፤ ኢዮአካዝም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ዮአስ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 10 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአስ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ነገሠ ፤ ዐሥራ ፡ ስድስትም ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 11 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ በሳተው ፡ በናባጥ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ኼደ ፡ እንጂ ፡ ከርሷ ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 12 ፤ የቀረውም ፡ የዮአስ ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ኹሉ ፥ ከይሁዳም ፡ ከአሜስያስ ፡ ጋራ ፡ የተዋጋበት ፡ ጭከና ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 13 ፤ ዮአስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ ኢዮርብዓምም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፤ ዮአስም ፡ በሰማርያ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 14 ፤ ኤልሳዕም ፡ በሚሞትበት ፡ በሽታ ፡ ታመመ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወርዶ ፡ በፊቱ ፡ አለቀሰና ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ አባቴ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ሠረገላና ፡ ፈረሰኞች ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 15 ፤ ኤልሳዕም ፦ ቀስትና ፡ ፍላጻዎች ፡ ውሰድ ፡ አለው ፤ ቀስቱንና ፡ ፍላጻዎችንም ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 16 ፤ የእስራኤልንም ፡ ንጉሥ ፦ እጅኽን ፡ በቀስቱ ፡ ላይ ፡ ጫን ፡ አለው ። እጁንም ፡ ጫነበት ፤ ኤልሳዕም ፡ እጁን ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ጭኖ ፦

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 17 ፤ የምሥራቁን ፡ መስኮት ፡ ክፈት ፡ አለ ፤ ከፈተውም ። ኤልሳዕም ፦ ወርውር ፡ አለ ፤ ወረወረውም ። ርሱም ፦ የእግዚአብሔር ፡ መድኀኒት ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ በሶርያ ፡ ላይ ፡ የመድኀኒት ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ እስክታጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ሶርያውያንን ፡ በአፌቅ ፡ ትመታለኽ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 18 ፤ ደግሞም ፦ ፍላጻዎቹን ፡ ውሰድ ፡ አለው ፤ ወሰዳቸውም ። የእስራኤልንም ፡ ንጉሥ ፦ ምድሩን ፡ ምታው ፡ አለው ። ሦስት ፡ ጊዜም ፡ መቶ ፡ ቆመ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 19 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ተቈጥቶ ፦ ዐምስት ፡ ወይም ፡ ስድስት ፡ ጊዜ ፡ መትተኸው ፡ ኖሮ ፡ ሶርያን ፡ እስክታጠፋው ፡ ድረስ ፡ በመታኸው ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሶርያን ፡ ትመታለኽ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 20 ፤ ኤልሳዕም ፡ ሞተ ፥ ቀበሩትም ። ከሞዐብም ፡ አደጋ ፡ ጣዮች ፡ በየዓመቱ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይገቡ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 21 ፤ ሰዎችም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲቀብሩ ፡ አደጋ ፡ ጣዮችን ፡ አዩ ፥ ሬሳውንም ፡ በኤልሳዕ ፡ መቃብር ፡ ጣሉት ፤ የኤልሳዕንም ፡ ዐጥንት ፡ በነካ ፡ ጊዜ ፡ ሰውዮው ፡ ድኖ ፡ በእግሩ ፡ ቆመ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 22 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄል ፡ በኢዮአካዝ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ እስራኤልን ፡ አስጨነቀ ፤

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ራራላቸው ፥ ማራቸውም ፥ ከአብርሃምና ፡ ከይሥሐቅ ፡ ከያዕቆብም ፡ ጋራ ፡ ስላደረገውም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እነርሱን ፡ ተመለከተ ፤ ሊያጠፋቸውም ፡ አልወደደም ፥ ፈጽሞም ፡ ከፊቱ ፡ አልጣላቸውም ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 24 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄል ፡ ሞተ ፤ ልጁም ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 13 ፡ 25 ፤ አዛሄልም ፡ ከአባቱ ፡ ከኢዮአካዝ ፡ እጅ ፡ በሰልፍ ፡ የወሰዳቸውን ፡ ከተማዎች ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ከአዛሄል ፡ ልጅ ፡ ከወልደ ፡ አዴር ፡ እጅ ፡ ወሰደ ። ዮአስም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ መታው ፥ የእስራኤልንም ፡ ከተማዎች ፡ መለሰ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 1 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ በዮአስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ አሜስያስ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 2 ፤ መንገሥ ፡ በገፐመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዮዓዳን ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 3 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አባቱ ፡ ኢዮአስ ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ አላደረገም ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 5 ፤ መንግሥቱም ፡ በጸናለት ፡ ጊዜ ፡ አባቱን ፡ የገደሉትን ፡ ባሪያዎች ፡ ገደለ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 6 ፤ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ እግዚአብሔርም ፦ ኹሉ ፡ በኀጢአቱ ፡ ይሙት ፡ እንጂ ፡ አባቶች ፡ በልጆች ፡ አይሙቱ ፥ ልጆችም ፡ በአባቶች ፡ አይሙቱ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮቹን ፡ ልጆች ፡ አልገደለም ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 7 ፤ ርሱም ፡ በጨው ፡ ሸለቆ ፡ ከኤዶምያስ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰው ፡ ገደለ ፤ ሴላን ፡ በሰልፍ ፡ ወስዶ ፡ ስሟን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዮቅትኤል ፡ ብሎ ፡ ጠራት ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አሜስያስ ፦ ና ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንተያይ ፡ ብሎ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደኢዩ ፡ ልጅ ፡ ወደኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮአስ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፦ የሊባኖስ ፡ ኵርንችት ፥ ልጅኽን ፡ ለልጄ ፡ ሚስት ፡ አድርገኽ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ ወደሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ላከ ፤ የሊባኖስም ፡ አውሬ ፡ ዐልፎ ፡ ኵርንችቱን ፡ ረገጠ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 10 ፤ ኤዶምያስን ፡ በእውነት ፡ መታኽ ፥ ልብኽንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግኽ ፤ በዚያ ፡ ተመካ ፥ በቤትኽም ፡ ተቀመጥ ፤ አንተ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡ ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መከራ ፡ ትሻለኽ ፧ ብሎ ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሜስያስ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 11 ፤ አሜስያስ ፡ ግን ፡ አልሰማም ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ ወጣ ፥ ርሱና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስም ፡ በይሁዳ ፡ ባለች ፡ በቤት ፡ ሳሚስ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 12 ፤ ይሁዳም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ተመታ ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 13 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአስ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአስን ፡ ልጅ ፡ አሜስያስን ፡ በቤትሳሚስ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ ከኤፍሬም ፡ በር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አፈረሰ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 14 ፤ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ዅሉ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የነበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ዅሉ ፥ በመያዣም ፡ የተያዙትን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ተመለሰ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 15 ፤ የቀረውም ፡ ያደረገው ፡ የዮአስ ፡ ነገር ፥ ጭከናውም ፥ ከይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ከአሜስያስ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 16 ፤ ዮአስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በሰማርያም ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኢዮርብዓም ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 17 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፣ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፣ አሜስያስ ፥ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፣ ከኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፣ ከዮአስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 18 ፤ የቀረውም ፡ የአሜስያስ ፡ ነገር ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 19 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የዐመፅ ፡ መሐላ ፡ አደረጉበት ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ኰበለለ ፤ በኋላውም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላኩ ፥ በዚያም ፡ ገደሉት ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 20 ፤ በፈረስም ፡ ጭነው ፡ አመጡት ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 21 ፤ የይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ዅሉ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ የነበረውን ፡ ዐዛርያስን ፡ ወስዶ ፡ በአባቱ ፡ በአሜስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠው ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 20 ፤ ንጉሡም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ካንቀላፋ ፡ በኋላ ፥ ኤላትን ፡ ሠርቶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ መለሳት ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 23 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ በአሜስያስ ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዮአስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፤ አርባ ፡ አንድ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 24 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልንም ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡

ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ ዥሉ ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 25 ፤ የጋትሔፌር ፡ በነበረው ፡ በዐማቴ ፡ ልጅ ፡ በባሪያው ፡ በነቢዩ ፡ በዮናስ ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ አምላክ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የእስራኤልን ፡ ድንበር ፡ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዐረባ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ መለሰ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 26 ፤ የታሰረውና ፡ የተለቀቀውም ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፥ እስራኤልንም ፡ የሚረዳ ፡ እንዳልነበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ የመረረውን ፡ የእስራኤልን ፡ ጭንቀት ፡ አየ ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ስም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ይደመስስ ፡ ዘንድ ፡ አልተናገረም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዮአስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ።

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 28 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮርብዓም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ዥሉ ፥ ጭከናውም ፥ እንደ ፡ ተዋጋም ፥ የይሁዳ ፡ የነበረውን ፡ ደማስቆንና ፡ ሐማትን ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ መለሰ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 14 ፡ 29 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፤ ልጁም ፡ ዘካርያ ፡ በፋንታው ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 1 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮርብዓም ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የአሜስያስ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 2 ፤ መንገሥም ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ይኮልያ ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 3 ፤ አባቱ ፡ አሜስያስ ፡ እንዳደረገው ፡ ዥሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ንጉሡን ፡ ቀሠፈው ፥ እስከሚሞትበትም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ለምጻም ፡ ኾነ ፥ በተለየ ፡ ቤትም ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፥ የንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ሠልጥኖ ፡ ለአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 6 ፤ የቀረውም ፡ የዐዛርያስ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ዥሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 7 ፤ ዐዛርያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 8 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዐዛርያስ ፡ በሠላሳ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ የኢዮርብዓም ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ([176]) ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 9 ፤ አባቶቹም ፡ እንዳደረጉት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳታቸው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ አልራቀም ።

---

176 ዕብ. ፥ ዘካርያህ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 10 ፤ የኢ.ያቤስ ([177])ም ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ተማማለበት ፥ በይብልዓም ፡ መቶ ፡ ገደለው ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 11 ፤ የቀረውም ፡ የዘካርያ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 12 ፤ ለኢዩ ፦ ልጆችኽ ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፡ ተብሎ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እንዲሁም ፡ ኾነ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 13 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ የኢ.ያቤስ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ነገሠ ፤ በሰማርያም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 14 ፤ የጋዲም ፡ ልጅ ፡ ምናሔም ፡ ከቴርሳ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ መጣ ፥ በሰማርያም ፡ የኢ.ያቤስን ፡ ልጅ ፡ ሰሎምን ፡ መታ ፥ ገደለውም ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 15 ፤ የቀረውም ፡ የሰሎም ፡ ነገር ፥ የተማማለውም ፡ ዐመፅ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ምናሔም ፡ ከቴርሳ ፡ ወጥቶ ፡ ቲፍሳን ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፡ ዳርቻዋንም ፡ መታ ፤ ይከፍቱለትም ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና ፡ መታት ፤ በርሷም ፡ የነበሩትን ፡ እርጉዞች ፡ ኹሉ ፡ ቀደዳቸው ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 17 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዐዛርያስ ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ የጋዲ ፡ ልጅ ፡ ምናሔም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፤ በሰማርያም ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 18 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 19 ፤ በዘመኑም ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ፎሐ ([178]) ፡ በምድሪቱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ ምናሔምም ፡ መንግሥቱን ፡ በእጁ ፡ ያጸናለት ፡ ዘንድ ፡ የፎሐ ፡ እጅ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዲኾን ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ሰጠው ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 20 ፤ ምናሔምም ፡ ብሩን ፡ ለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ በእስራኤል ፡ ባለጠጋዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በያንዳንዱ ፡ ላይ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ አስገብሮ ፡ አወጣ ። የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ተመለሰ ፥ በአገሪቱም ፡ አልተቀመጠም ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 21 ፤ የቀረውም ፡ የምናሔም ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 22 ፤ ምናሔም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፤ ልጁም ፡ ፋቂስያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 23 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዐዛርያስ ፡ በዐምሳኛው ፡ ዓመት ፡ የምናሔም ፡ ልጅ ፡ ፋቂስያስ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ዠመረ ፤ ኹለት ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 24 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 25 ፤ የሰራዊቱም ፡ አለቃ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ተማማለበት ፥ በሰማርያም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ከአርጎብና ፡ ከአርያ ፡ ጋራ ፡ መታው ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐምሳ ፡ የገለዓድ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ገደለውም ፥ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

---

177 ዕብ. ፥ ያቤሽ ፡ (ይቡስ • የደረቀ) ።

178 ፋል ፥ ወይም ፡ ፕል ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 26 ፤ የቀረውም ፡ የፋቂስያስ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 27 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዐዛርያስ ፡ በዐምሳ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ መንገሥ ፡ ገᎠመረ ፤ ኻያ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 28 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ እስራኤልን ፡ ካሳተው ፡ ከናባጥ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮርብዓም ፡ ኀጢአት ፡ አልራቀም ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 29 ፤ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በፋቁሔ ፡ ዘመን ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ መጥቶ ፡ ዒዮንና ፡ አቤልቤትመዓካን ፥ ያኖዋንም ፥ ቃዴስንና ፡ አሶርንም ፥ ገለዓድንና ፡ ገሊላንም ፥ የንፍታሌምን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፤ ወደ ፡ አሶርም ፡ አፈለሳቸው ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 30 ፤ በዖዝያንም ፡ ልጅ ፡ በኢዮአታም ፡ በኻያኛው ፡ ዓመት ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ሆሴዕ ፡ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ ላይ ፡ ተማማለ ፥ መቶም ፡ ገደለው ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 31 ፤ የቀረውም ፡ የፋቁሔ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 32 ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የዖዝያን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአታም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 33 ፤ መንገሥ ፡ በገᎠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ኢየሩሳ ([179]) ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 34 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ አባቱ ፡ ዖዝያን ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 35 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉት ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ። ርሱም ፡ የላይኛውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ በር ፡ ሠራ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 36 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአታም ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 37 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶንንና ፡ የሮሜልዩን ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔን ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ መስደድ ፡ ገᎠመረ ።

ነገ.2 ፡ 15 ፡ 38 ፤ ኢዮአታም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አካዝ ([180]) ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 1 ፤ በሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ በፋቁሔ ፡ በዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአታም ፡ ልጅ ፡ አካዝ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 2 ፤ አካዝ ፡ መንገሥ ፡ በገᎠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡

179 ዕብ ፡ ፥ የሩሻህ ፡ (ርስት • የተወረሰች) ።
180 ዕብ. ፥ አኃዝ ፡ (አኃዚ ፥ ያኻᎠ ፣ ጠባቂ ፣ መጋቢ) ።

ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አላደረገም ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳሳደዳቸው ፡ እንደአሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ ልጁን ፡ በእሳት ፡ አሳለፈው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 4 ፤ በመስገጃዎችና ፡ በኰረብታዎቹ ፡ ላይ ፡ በለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 5 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶንና ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ሊዋጉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ፤ አካዝንም ፡ ከበቡት ፥ ሊያሸንፉት ፡ ግን ፡ አልቻሉም ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶን ፡ ኤላትን ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ መለሰ ፥ አይሁድንም ፡ ከኤላት ፡ አሳደደ ፤ ኤዶማውያንም ፡ ወደ ፡ ኤላት ፡ መጥተው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በርሷ ፡ ተቀምጠዋል ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 7 ፤ አካዝም ፦ እኔ ፡ ባሪያኽና ፡ ልጅኽ ፡ ነኝ ፤ መጥተኽ ፡ ከተነሡብን ፡ ከሶርያ ፡ ንጉሥና ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነኝ ፡ ብሎ ፡ ወደአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 8 ፤ አካዝም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የተገኘውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ወስዶ ፡ ወደአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ አድርጎ ፡ ሰደደው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 9 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰማው ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ በደማስቆ ፡ ላይ ፡ ወጣባት ፡ ወሰዳትም ፥ ሕዝቧንም ፡ ወደ ፡ ቂር ፡ አፈለሳቸው ፥ ረአሶንንም ፡ ገደለ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፡ የአሶርን ፡ ንጉሠ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶርን ፡ ሊገናኘው ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ኼደ ፤ በደማስቆ ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ፡ አየ ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፡ የመሠዊያውን ፡ ምሳሌና ፡ የአሠራሩን ፡ መልክ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ ኦርያ ፡ ላከው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 11 ፤ ካህኑም ፡ ኦርያ ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፤ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ ከደማስቆ ፡ ልኮ ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ካህኑ ፡ ኦርያ ፡ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ ከደማስቆ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ሠራው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፡ ከደማስቆ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መሠዊያውን ፡ አየ ፤ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ መሠዊያው ፡ ቀርቦ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 13 ፤ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ አሳረገ ፥ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ አፈሰሰ ፥ የደኅንነቱንም ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ረጨ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 14 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የናሱን ፡ መሠዊያ ፡ ከመቅደሱ ፡ ፊት ፡ ከመሠዊያውና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ፈቀቅ ፡ አድርጎ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፦ የሚቃጠለውን ፡ የጧት ፡ መሥዋዕት ፥ የማታውንም ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፥ የንጉሡንም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፥ ለአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ የሚኾን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ በታላቁ ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አቅርብ ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ኹሉ ፡ የሌላ ፡ መሥዋዕቱንም ፡ ደም ፡ ኹሉ ፡ ርጭበት ፤ የናሱ ፡ መሠዊያ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ እጠይቅበት ፡ ዘንድ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ካህኑን ፡ ኦርያን ፡ አዘዘው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 16 ፤ ካህኑ ፡ ኦርያ ፡ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፡ የመቀመጫዎችን ፡ ክፈፍ ፡ ቈረጠ ፥ ከነርሱም ፡ የመታጠቢያውን ፡ ሰኖች ፡ ወሰደ ፤ ኵሬውንም ፡ ከበታቹ ፡ ከነበሩት ፡ ከናሱ ፡ በሬዎች ፡ አወረደው ፥ በጠፍጣፋውም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አኖረው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 18 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የዘፋኑን ፡ መሠረት ፡ ሠራ ፤ ስለአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ በውጭ ፡ ያለውን ፡ የንጉሡን ፡ መንገድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አዞረው ።

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 19 ፤ የቀረውም ፡ አካዝ ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 16 ፡ 20 ፤ አካዝም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ሕዝቅያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በአካዝ ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ የኤላ ፡ ልጅ ፡ ሆሴዕ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በሰማርያ ፡ ንጉሥ ፡ ኾነ ፤ ዘጠኝ ፡ ዓመትም ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ አይደለም ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 3 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ስልምናሶር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፤ ሆሴዕም ፡ ተገዛለት ፥ ግብርም ፡ አመጣለት ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 4 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ በሆሴዕ ፡ ላይ ፡ ዐመፅ ፡ አገኘ ፤ መልእክተኞችን ፡ ወደግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሴጎር ፡ ልኮ ፡ ነበርና ፤ እንደ ፡ ልማዱም ፡ በየዓመቱ ፡ ለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ግብር ፡ አልሰጠምና ፤ ስለዚህ ፥ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ይዞ ፡ በወህኒ ፡ ቤት ፡ አሰረው ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 5 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ ወጥቶ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከበባት ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 6 ፤ በሆሴዕ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰማርያን ፡ ወሰደ ፥ እስራኤልንም ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ አፈለሰ ፥ በአላሔና ፡ በአቦር ፡ በጎዛንም ፡ ወንዝ ፡ በሜዶንም ፡ ከተማዎች ፡ አኖራቸው ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ከፈርዖን ፡ እጅ ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣቸውን ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በድለው ፡ ነበርና ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ አምልከው ፡ ነበርና ፥

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ባሳደዳቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ሥርዐት ፥ የእስራኤልም ፡ ነገሥታት ፡ ባደረጓት ፡ ሥርዐት ፡ ኼደው ፡ ነበርና ፥ እንደዚህ ፡ ኾነ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 9 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በአምላካቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ቅን ፡ ያልኾነን ፡ ንገር ፡ በስውር ፡ አደረጉ ፤ በከተማዎቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ከዘበኞች ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከተመሸገች ፡ ከተማ ፡ ድረስ ፡ በከፍታዎቹ ፡ ላይ ፡ መስገጃዎችን ፡ ሠሩ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 10 ፤ በረዣዥሙ ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ታች ፡ ሐውልቶችንና ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችን ፡ ተከሉ ፤

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከፊታቸው ፡ ያወጣቸው ፡ አሕዛብ ፡ እንዳደረጉት ፥ በኰረብታዎቹ ፡ መስገጃዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያጥኑ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ያስቈጡ ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ፤

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የከለከላቸውን ፡ ጣዖቶች ፡ አመለኩ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ለአባቶቻችኹም ፡

እንዳዘዝኹት ፥ በባሪያዎቼ ፡ በነቢያት ፡ የላክኹላችኹን ፡ ትእዛዜንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ሕጌንም ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ፡ ብሎ ፡
በነቢዩ ፡ ኹሉና ፡ በባለራእዩ ፡ አፍ ፡ ኹሉ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ መሰከረ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳላመኑ ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ ዐንገት ፡
ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙም ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 15 ፤ ሥርዐቱንም ፡ ከአባቶቻቸውም ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፥ ያጸናላቸውንም ፡ ምስክሩን ፡
ናቁ ፤ ከንቱ ፡ ነገርንም ፡ ተከተሉ ፥ ምናምንቴዎችም ፡ ኾኑ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ያዘዛቸውን ፡
በዙሪያቸው ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብን ፡ ተከተሉ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 16 ፤ የአምላካቸውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ተዉ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡
የኹለቱን ፡ እንቦሶች ፡ ምስሎች ፡ አደረጉ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸድንም ፡ ተከሉ ፥ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡
ሰገዱ ፥ በዓልንም ፡ አመለኩ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 17 ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ አሳለፉቸው ፥ ሟርተኞችና ፡ አስማተኞችም ፡
ኾኑ ፥ ያስቈጡትም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ለማድረግ ፡ ራሳቸውን ፡ ሸጡ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 18 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ ከፊቱም ፡
ጣላቸው ፤ ከይሁዳም ፡ ነገድ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አልቀረም ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 19 ፤ ይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ እስራኤል ፡ ባደረጋት ፡ ሥርዐት ፡ ኼደ ፡ እንጂ ፡ የአምላኩን ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቀም ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የእስራኤልን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ ጠላ ፥ አስጨነቃቸውም ፥ ከፊቱም ፡
እስኪጥላቸው ፡ ድረስ ፡ በበዝባዦች ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 21 ፤ እስራኤልንም ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ለየ ፤ የናባጥንም ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓምን ፡
አነገሡ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ እስራኤልን ፡ መለሰ ፥ ታላቅም ፡ ኀጢአት ፡ አሠራቸው ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 22 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኢዮርብዓም ፡ ባደረገው ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ፤

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 23 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በባሪያዎቹ ፡ በነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እስራኤልን ፡ ከፊቱ ፡
እስኪያወጣ ፡ ድረስ ፡ ከርሷ ፡ አልራቁም ። እስራኤልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከምድሩ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ፈለሰ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 24 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ከባቢሎንና ፡ ከኩታ ፡ ከአዋና ፡ ከሐማት ፡ ከሴፈርዋይም ፡ ሰዎችን ፡
አመጣ ፥ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፋንታ ፡ በሰማርያ ፡ ከተማዎች ፡ አኖራቸው ፤ ሰማርያንም ፡ ወረሷት ፤ በከተማዎቿም ፡
ተቀመጡ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 25 ፤ በዚያም ፡ መቀመጥ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አይፈሩትም ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡
አንበሳዎች ፡ ሰደደባቸው ፥ ይገድሏቸውም ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 26 ፤ ስለዚህም ፡ ለአሶር ፡ ንጉሥ ፦ ያፈለስኻቸው ፥ በሰማርያም ፡ ከተማዎች ፡ ያኖርኻቸው ፡ የአገሩን ፡
አምላክ ፡ ወግ ፡ አላወቁም ፤ የአገሩን ፡ አምላክ ፡ ወግ ፡ አላወቁምና ፡ አንበሳዎችን ፡ ሰዶባቸዋል ፥ እንሆም ፥ ገደሏቸው ፡
ብለው ፡ ተናገሩት ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 27 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፦ ከዚያ ፡ ካመጣኻቸው ፡ ካህናት ፡ አንዱን ፡ ውሰዱ ፤ ኼዶም ፡ በዚያ ፡
ይቀመጥ ፥ የአገሩንም ፡ አምላክ ፡ ወግ ፡ ያስተምራቸው ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ነገ.2 ፥ 17 ፥ 28 ፤ ከሰማርያም ፡ ካፈለሷቸው ፡ ካህናት ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፡ በቤቴል ፡ ተቀመጠ ፥ እግዚአብሔርንም ፡

እንዴት ፡ እንዲፈሩት ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 29 ፤ በየሕዝባቸውም ፡ አምላካቸውን ፡ አደረጉ ፥ ሰምራውያንም ፡ በሠሩት ፡ በኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማዎቻቸው ፡ አኖሯቸው ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 30 ፤ የባቢሎንም ፡ ሰዎች ፡ ሱኮትበኖትን ፡ ሠሩ ፤ የኩታም ፡ ሰዎች ፡ ኤርጌልን ([181]) ፡ ሠሩ ፤ የሐማትም ፡ ሰዎች ፡ አሲማትን ([182]) ፡ ሠሩ ፤

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 31 ፤ ዐዋውያንም ፡ ኤልባዝርንና ([183]) ፡ ተርታቅን ፡ ሠሩ ፤ የሴፈርዋይም ፡ ሰዎችም ፡ ለሴፈርዋይም ፡ አማልክት ፡ ለአድራሜሌክና ፡ ለዐነሜሌክ ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ፥ ከመካከላቸውም ፡ ለኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ካህናት ፡ አደረጉ ፥ በኰረብታውም ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ሲፈሩ ፡ ከመካከላቸው ፡ እንደፈለሱት ፡ እንደአሕዛብ ፡ ልማድ ፡ አምላካቸውን ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 34 ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ልማድ ፡ ያደርጋሉ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አይፈሩም ፥ እግዚአብሔርም ፡ እስራኤል ፡ ብሎ ፡ የጠራውን ፡ የያዕቆብን ፡ ልጆች ፡ እንዳዘዛቸው ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ሕግና ፡ ትእዛዝም ፡ አያደርጉም ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 35 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፥ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትፍሩ ፥ አትስገዱላቸው ፥ አታምልኳቸው ፥ አትሠዉላቸው ፤

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 36 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ በተዘረጋችም ፡ ክንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣችኹን ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱን ፡ ፍሩ ፥ ለርሱም ፡ ስገዱ ፥ ለርሱም ፡ ሠዉ ፤

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 37 ፤ የጻፈላችኹንም ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ሕግና ፡ ትእዛዝም ፡ ለዘለዓለም ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ጠብቁ ፤ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ አትፍሩ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 38 ፤ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አትርሱ ፤ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ አትፍሩ ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 39 ፤ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፤ ርሱም ፡ ከጠላቶቻችኹ ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያድናችኋል ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 40 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ልማዳቸው ፡ አደረጉ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙም ።

ነገ.2 ፡ 17 ፡ 41 ፤ እነዚህም ፡ አሕዛብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ፤ ደግሞም ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ያመልኩ ፡ ነበር ፤ ልጆቻቸውም ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸውም ፡ አባቶቻቸው ፡ እንዳደረጉ ፡ እንዲሁ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያደርጋሉ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኤላ ፡ ልጅ ፡ በሆሴዕ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የአካዝ ፡ ልጅ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 2 ፤ መንገሥ ፡ በገፖመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡

181 ዕብ. ፥ ኔርጋል ።
182 ዕብ. ፥ አሺማ ።
183 ዕብ. ፥ ኒብሐዝ ።

ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ አቡ ([184]) ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ አባቱ ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገው ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 4 ፤ በኰረብታም ፡ ያሉትን ፡ መስገጃዎች ፡ አስወገደ ፥ ሐውልቶችንም ፡ ቀለጣጠመ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እስከዚህ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ያጥኑለት ፡ ነበርና ፥ ሙሴ ፡ የሠራውን ፡ የናሱን ፡ እባብ ፡ ሰባበረ ፤ ስሙንም ፡ ነሑሽታን ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 5 ፤ በእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመነ ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ከርሱም ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ ከይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ዅሉ ፡ ርሱን ፡ የሚመስል ፡ አልነበረም ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 6 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ጋራ ፡ ተጣበቀ ፥ ርሱንም ፡ ከመከተል ፡ አልራቀም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ ትእዛዛቱን ፡ ጠበቀ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ የሚኼድበትም ፡ መንገድ ፡ ተከናወነለት ፤ በአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፥ አልገበረለትም ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 8 ፤ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ እስከ ፡ ጋዛና ፡ እስከ ፡ ዳርቻዋ ፡ ድረስ ፥ ከዘበኞች ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከምሽጉ ፡ ከተማ ፡ ድረስ ፡ መታ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 9 ፤ በንጉሡ ፡ በሕዝቅያስ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፥ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኤላ ፡ ልጅ ፡ በሆሴዕ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፥ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ስልምናሶር ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ወጣ ፥ ከበባትም ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 10 ፤ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ ወሰዳት ፤ በሕዝቅያስ ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፥ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በሆሴዕ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፥ ሰማርያ ፡ ተያዘች ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 11 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እስራኤልን ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ አፈለሰ ፥ በአላሔና ፡ በአቦር ፡ በጎዛንም ፡ ወንዝ ፡ በሜዶንም ፡ ከተማዎች ፡ አኖራቸው ፤

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 12 ፤ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙምና ፥ ቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ ዅሉ ፡ አልሰሙምና ፥ አላደረጉምና ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 13 ፤ በንጉሡም ፡ በሕዝቅያስ ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደተመሸጉት ፡ ከተማዎች ፡ ዅሉ ፡ ወጣ ፥ ወሰዳቸውም ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 14 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፦ በድያለኹ ፥ ከእኔ ፡ ተመለስ ፤ የምትጭንብኝን ፡ ዅሉ ፡ እሸከማለኹ ፡ ብሎ ፡ ወደአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላከ ። የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ ሠላሳ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ጫነበት ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 15 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ የተገኘውን ፡ ብር ፡ ዅሉ ፡ ሰጠው ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ደጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ከለበጣቸው ፡ መቃኖች ፡ ወርቁን ፡ ቈረጠ ፥ ለአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰጠው ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 17 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ተርታንንና ፡ ራፌስን ፡ ራፋስቂስንም ፡ ከብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ጋራ ፡ ከለኪሶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላከ ። ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ፤ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ በዐጣቢው ፡ ዕርሻ ፡ መንገድ ፡ ባለችው ፡ በላይኛዪቱ ፡ ኩሬ ፡ መስኖ ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ።

---

184 ዕብ. ፥ አቢይ ፡ (አባዊ • የአባት) ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 18 ፤ ንጉሡንም ፡ ጠሩ ፤ የቤቱም ፡ አዛዥ ፣ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፥ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፣ ታሪክ ፡ ጸሓፊውም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፣ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወጡ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 19 ፤ ራፋስቂስም ፡ አላቸው ፦ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ታላቁ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ የምትታመንበት ፡ መተማመኛ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 20 ፤ የከንፈር ፡ ቃል ፡ ለሰልፍ ፡ ምክርና ፡ ኀይል ፡ እንደሚኾን ፡ ትናገራለኽ ፤ አኹንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያመፅኸው ፡ በማን ፡ ተማምነኽ ፡ ነው ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 21 ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ በተቀጠቀጠ ፡ በሸምበቆ ፡ በትር ፡ በግብጽ ፡ ትታመናለኽ ፤ ሰው ፡ ቢመረኰዘው ፡ ተሰብሮ ፡ በእጁ ፡ ይገባል ፥ ያቈስለውማል ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ለሚታመኑበት ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 22 ፤ እናንተም ፦ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንታመናለን ፡ ብትሉኝ ፥ ሕዝቅያስ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፦ በኢየሩሳሌም ፡ ባለው ፡ በዚህ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ሰገዱ ፡ ብሎ ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቹንና ፡ መሠዊያዎቹን ፡ ያስፈረሰ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 23 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ከጌታዬ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተወራረድ ፥ የሚቀመጡባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ማግኘት ፡ ቢቻልኽ ፡ እኔ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ፈረሶች ፡ እሰጥኻለኹ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 24 ፤ ስለ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ስለ ፡ ፈረሰኞች ፡ በግብጽ ፡ ስትታመን ፥ ከጌታዬ ፡ ባሪያዎች ፡ የሚያንሰውን ፡ የአንዱ ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ትቃወም ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻልኻል ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 25 ፤ አኹን ፡ በእውኑ ፡ ያለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቻለኹን ፧ እግዚአብሔር ፦ ወደዚች ፡ አገር ፡ ወጥተኽ ፡ አጥፋት ፡ አለኝ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 26 ፤ የኬልቅያስም ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ሳምናስም ፡ ዮአስም ፡ ራፋስቂስን ፦ እኛ ፡ እንሰማለንና ፡ እባክኽ ፥ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ ተናገር ፤ በቅጥርም ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ ጮሮ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ አትናገረን ፡ አሉት ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 27 ፤ ራፋስቂስ ፡ ግን ፦ ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተና ፡ ወደ ፡ ጌታኽ ፡ ልኮኛልን ፧ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ዅሳቸውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሽንታቸውንም ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ ወደተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ አይደለምን ፧ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 28 ፤ ራፋስቂስም ፡ ቆሞ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፦ የታላቁን ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 29 ፤ ከእጁ ፡ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ሕዝቅያስ ፡ አያታሏችኹ ፤

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 30 ፤ ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ በርግጥ ፡ ያድነናል ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንድትታመኑ ፡ አያድርጋችኹ ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 31 ፤ ሕዝቅያስንም ፡ አትስሙ ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ውጡ ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ ከወይናችኹና ፡ ከበለሳችኹ ፡ ብሉ ፡ ከጕድጓዳችኹም ፡ ውሃ ፡ ጠጡ ፤

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 32 ፤ ይህም ፡ መጥቼ ፡ ምድራችኹን ፡ ወደምትመስለው ፡ ምድር ፥ እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ እንጀራና ፡ ወይን ፥ ወይራና ፡ ማር ፡ ወዳለባት ፡ ምድር ፡ እስካፈልሳችኹ ፡ ድረስ ፡ በሕይወት ፡ እንድትኖሩ ፡ እንዳትሞቱም ፡ ነው ። ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያድነናል ፡ ብሎ ፡ ቢያታልላችኹ ፡ አትስሙት ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 33 ፤ በእውኑ ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አገሮቻቸውን ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነዋቸዋልን ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 34 ፤ የሐማትና ፡ የአርፋድ ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧ የሴፈርዋይምና ፡ የሄና ፡ የዒዋም ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 35 ፤ ሰማርያን ፡ ከእጄ ፡ አድነዋታልን ፧ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ከአገሮቹ ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ አገሩን ፡ ከእጄ ፡ ያዳነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 36 ፤ ሕዝቡም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ አንዳችም ፡ አልመለሱለትም ፤ ንጉሡ ፡ እንዳይመልሱለት ፡ አዞ ፡ ነበርና ።

ነገ.2 ፡ 18 ፡ 37 ፤ የቤቱ ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጡ ፥ የራፋስቂስንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ ማቅም ፡ ለበሰ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገባ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 2 ፤ የቤቱንም ፡ አዛዥ ፡ ኤልያቄምን ፡ ጸሓፊውንም ፡ ሳምናስን ፡ የካህናቱንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ወደነቢዩ ፡ ወደዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፦ ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ቀን ፡ የመከራና ፡ የተግሣጽ ፡ የዘለፋም ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ልጆች ፡ የሚወለዱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፥ ለመውለድም ፡ ኀይል ፡ የለም ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ምናልባት ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የላከውን ፡ የራፋስቂስን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለሰማው ፡ ቃል ፡ ይገሥጸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ስለዚህ ፡ ለቀረው ፡ ቅሬታ ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 5 ፤ እንዲሁ ፡ የንጉሡ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጡ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 6 ፤ ኢሳይያስም ፦ ለጌታችኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ ስለ ፡ ሰደቡኝ ፥ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፡ አትፍራ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ በላዩ ፡ መንፈስን ፡ እሰዳለኹ ፥ ወሬንም ፡ ይሰማል ፥ ወደ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ፤ በምድሩም ፡ በሰይፍ ፡ እንዲወድቅ ፡ አደርገዋለኹ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 8 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ከለኪሶ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ራፋስቂስ ፡ ተመልሶ ፡ በልብና ፡ ሲዋጋ ፡ አገኘው ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ቴርሐቅ ፡ ሊወጋኽ ፡ መጥቷል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 10 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ኢየሩሳሌም ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ የምትታመንበት ፡ አምላክኽ ፡ አያታልኽ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፥ እንዴትስ ፡ እንዳጠፏቸው ፡ ሰምተኻል ፤ አንተስ ፡ ትድናለኽን ፧

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 12 ፤ አባቶቼ ፡ ያጠፏቸውን ፥ ጎዛንን ፥ ካራንን ፥ ራፌስን ፥ በተላሳር ፡ የነበሩትንም ፡ የዔዴንን ፡ ልጆች ፥ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አዳኗቸውን ፧

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 13 ፤ የሐማት ፡ ንጉሥ ፥ የአርፋድ ፡ ንጉሥ ፥ የሴፈርዋይም ፡ ከተማ ፡ ንጉሥ ፥ የሄናና ፡ የዒዋ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 14 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደብዳቤውን ፡ ከመልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ አነበበው ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘረጋው ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 15 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፦ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጥረኻል ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ ገሮኽን ፡ አዘንብልና ፡ ስማ ፤ አቤቱ ፥ ዐይንኽን ፡ ክፈትና ፡ እይ ፤ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ የላከውን ፡ የሰናክሬምን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ በእውነት ፡ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ አሕዛብንና ፡ ምድራቸውን ፡ አፍርሰዋል ፥

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 18 ፤ አማልክታቸውንም ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጥለዋል ፤ የዕንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ አማልክት ፡ አልነበሩምና ፤ ስለዚህ ፥ አጥፍተዋቸዋል ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 19 ፤ እንግዲህም ፡ አምላካችን ፡ አቤቱ ፥ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁ ፡ እንድታድነን ፡ እለምንኻለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 20 ፤ የዓሞጽም ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላካ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የለመንኸውን ፡ ሰምቻለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ቀላል ፡ አድርጋኻለች ፥ በንቀትም ፡ ሥቃብኻለች ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ በላይኽ ፡ ራሷን ፡ ነቅንቃብኻለች ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 22 ፤ የተገዳደርኸው ፥ የሰደብኸውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ቃልኽንስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኸው ፡ ዐይንኽንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያነሣኸው ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ነው ፧ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 23 ፤ አንተስ ፦ በሠረገላዬ ፡ ብዛት ፡ ወደተራራዎች ፡ ከፍታ ፥ ወደሊባኖስ ፡ ጥግ ፡ ላይ ፡ ወጥቻለኹ ፤ ረዣዥሞቹንም ፡ ዝግባዎች ፡ የተመረጡትንም ፡ ጥዶች ፡ እቈርጣለኹ ፥ ወዳገሩም ፡ ዳርቻና ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ዱር ፡ እገባለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 24 ፤ ቈፈርኹም ፥ እንግዳውንም ፡ ውሃ ፡ ጠጣኹ ፤ የተገደበውንም ፡ ውሃ ፡ ኹሉ ፡ በእግሬ ፡ ጫማ ፡ አደርቃለኹ ፡ ብለኽ ፡ በመልእክተኞችኽ ፡ እጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ተገዳደርኽ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 25 ፤ እኔ ፡ ጥንቱን ፡ እንደ ፡ ሠራኹት ፥ ቀድሞውንም ፡ እንዳደረግኹት ፡ አልሰማኽምን ፧ አኹንም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ እስኪኾኑ ፡ ድረስ ፡ እንድታፈርስ ፡ አደረግኹኽ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 26 ፤ ስለዚህም ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ሰዎች ፡ እጃቸው ፡ ዝሏል ፥ ደንግጠውም ፡ ታውከዋል ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሣር ፥ እንደ ፡ ለምለምም ፡ ቡቃያ ፥ በሰገነትም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሣር ፥ ሳይሸት ፡ ዋግ ፡ እንደ ፡ መታውም ፡ እኽል ፡ ኾነዋል ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 27 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መቀመጫኽንና ፡ መውጫኽንም ፡ መግቢያኽንም ፥ በእኔም ፡ ላይ ፡ የተቈጠኸውን ፡ ቍጣ ፡ ዐውቄያለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 28 ፤ ቍጣኽና ፡ ትዕቢትኽ ፡ ወደ ፡ ገሮዬ ፡ ደርሷልና ፥ ስለዚህ ፡ ስናጋዬን ፡ በአፍንጫኽ ፥ ልጓሜንም ፡ በከንፈርኽ ፡ አደርጋለኹ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ እመልስኻለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 29 ፤ ይህም ፡ ምልክት ፡ ይኾንኻል ፤ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የገቦውን ፡ በኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከገቦው ፡ የበቀለውን ፡ ትበላላችኹ ፤ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ ትዘራላችኹ ፥ ታጭዱማላችኹ ፥ ወይንንም ፡ ትተክላላችኹ ፥ ፍሬውንም ፡ ትበላላችኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 30 ፤ ያመለጠው ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ሥሩን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይሰዳል ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ያፈራል ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 31 ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ ከጽዮንም ፡ ተራራ ፡ ያመለጡት ፡ ይወጣሉና ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ ይህን ፡ ያደርጋል ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 32 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፥ ፍላጻንም ፡ አይወረውርባትም ፥ በጋሻም ፡ አይመጣባትም ፥ የዐፈርንም ፡ ድልድል ፡ አይደለድልባትም ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 33 ፤ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ በዚያው ፡ ይመለሳል ፥ ወደዚችም ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 34 ፤ ስለ ፡ እኔም ፥ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ አድናት ፡ ዘንድ ፡ እጋርዳታለኹ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 35 ፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፥ ከአሶራውያንም ፡ ሰፈር ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፤ ማለዳም ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ኹሉ ፡ በድኖች ፡ ነበሩ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 36 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ፥ ተመልሶም ፡ በነነዌ ፡ ተቀመጠ ።

ነገ.2 ፡ 19 ፡ 37 ፤ በአምላኩም ፡ በናሳራክ ፡ ቤት ፡ ሲሰግድ ፡ ልጆቹ ፡ አደራሜሌክና ፡ ሳራሳር ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ፤ ወደአራራትም ፡ አገር ፡ ኰበለሉ ። ልጁም ፡ አሥራዶን (185) ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ታመመ ። ነቢዩም ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ በሕይወት ፡ አትኖርምና ፡ ቤትኽን ፡ አስተካክል ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 2 ፤ ፊቱንም ፡ ወደ ፡ ግድግዳው ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ በፊትኽ ፡ በእውነትና ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ኼድኩ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኝኽንም ፡ እንዳደረግኩ ፡ ታስብ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ። ሕዝቅያስም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 4 ፤ ኢሳይያስም ፡ ወደመካከለኛው ፡ ከተማ ፡ አደባባይ ፡ ሳይደርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣለት ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 5 ፤ ተመልሰኽ ፡ የሕዝቤን ፡ አለቃ ፡ ሕዝቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የአባትኽ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጸሎትኽን ፡ ሰምቻለኹ ፥ እንባኽንም ፡ አይቻለኹ ፤ እንሆ ፥ እፈውስኻለኹ ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ትወጣለኽ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 6 ፤ በዕድሜኽም ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ እጨምራለኹ ፤ አንተንና ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ እታደጋለኹ ፤ ስለ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ እጋርዳታለኹ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 7 ፤ ኢሳይያስም ፥ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አምጡልኝ ፡ አለ ፤ አምጥተውም ፡ በዕባጩ ፡ ላይ ፡ አደረጉለት ፥ ርሱም ፡ ተፈወሰ ።

---

185 ዕብ. ፥ ኤሣርሐዶን ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 8 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያስን ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲፈውሰኝ ፥ እኔስ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንድወጣ ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 9 ፤ ኢሳይያስም ፥ እግዚአብሔር ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽመው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡ ይህ ፡ ይኸንልኻል ፤ ጥላው ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለኽን ፧ አለ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 10 ፤ ሕዝቅያስም ፥ ጥላው ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ቢጨምር ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ አይኹን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጥላው ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይመለስ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 11 ፤ ነቢዩም ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ፤ ጥላውንም ፡ በአካዝ ፡ የጥላ ፡ ስፍራ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ በወረደበት ፡ መንገድ ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የባልዳን ፡ ልጅ ፡ መሮዳክ ፡ ባልዳን ፡ ሕዝቅያስ ፡ እንደ ፡ ታመመ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ደብዳቤና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላከ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 13 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ግምጃ ፡ ቤቱንም ፡ ኹሉ ፥ ብሩንና ፡ ወርቁንም ፥ ቅመሙንና ፡ የከበረውንም ፡ ዘይት ፥ መሣሪያም ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ በቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ የተገኘውን ፡ ኹሉ ፡ አሳያቸው ፡ በቤቱና ፡ በግዛቱ ፡ ኹሉ ፡ ካለው ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያላሳያቸው ፡ የለም ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 14 ፤ ነቢዩም ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጥቶ ፦ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ አሉ ፧ ከወዴትስ ፡ መጡልኽ ፧ አለው ። ሕዝቅያስም ፦ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ መጡ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ በቤትኽ ፡ ያዩት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ፤ ሕዝቅያስም ፦ በቤቴ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አይተዋል ፤ በቤተ ፡ መዛግብቴ ፡ ካለው ፡ ያላሳየኋቸው ፡ የለም ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 16 ፤ ኢሳይያስም ፡ ሕዝቅያስን ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ በቤትኽ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፥ አባቶችኽም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያከማቹት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚፈልስበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፤ ምንም ፡ አይቀርም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 18 ፤ ከአንተም ፡ ከሚወጡት ፡ ከምትወልዳቸው ፡ ልጆችኽ ፡ ማርከው ፡ ይወስዳሉ ፤ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 19 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያስን ፦ የተናገርኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞም ፦ በዘመኔ ፡ ሰላምና ፡ እውነት ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መልካም ፡ አይደለምን ፧ አለ ።

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 20 ፤ የቀረውም ፡ የሕዝቅያስ ፡ ነገር ፥ ጭከናውም ፡ ኹሉ ፥ ኩሬውንና ፡ መስኖውንም ፡ እንደ ፡ ሠራ ፥ ውሃውንም ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ እንዳመጣ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 20 ፡ 21 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፤ ልጁም ፡ ምናሴ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 1 ፤ ምናሴም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ የእናቱ ፡ ስም ፡ ሐፍሴባ ፡ ነበረ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳወጣቸው ፡ እንደአሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 3 ፤ አባቱም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያፈረሳቸውን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ መልሶ ፡ ሠራ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አክአብ ፡ እንዳደረገው ፡ ለበዓል ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸድንም ፡ ተከለ ፥ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ሰገደ ፡ አመለካቸውም ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ስሜን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራለኹ ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 5 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በኹለቱ ፡ ወለሎች ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 6 ፤ ልጁንም ፡ በእሳት ፡ አሳለፈ ፥ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ ኾነ ፥ አስማትም ፡ አደረገ ፥ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችንም ፡ ሰበሰበ ፤ ያስቈጣውም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፦ በዚህ ፡ ቤት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ በመረጥኋት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስሜን ፡ ለዘለዓለም ፡ አኖራለኹ ፤

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 8 ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ኹሉ ፥ ባሪያዬም ፡ ሙሴ ፡ ያዘዛቸውን ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ቢያደርጉ ፡ ቢጠብቁም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ከሰጠኋት ፡ ምድር ፡ የእስራኤልን ፡ እግር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አላቅበዘብዝም ፡ ባለው ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸድን ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ አቆመ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰሙም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ካጠፋቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ምናሴ ፡ አሳታቸው ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በባሪያዎቹ ፡ በነቢያት ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፦

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 11 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ምናሴ ፡ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ አድርጓልና ፥ ከፊቱም ፡ የነበሩ ፡ አሞራውያን ፡ ከሠሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፥ ይሁዳንም ፡ ደግሞ ፡ በጣዖታቱ ፡ አስቷልና ፥

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የሚሰማውን ፡ ኹሉ ፡ ኹለቱን ፡ ጕሮዎቹን ፡ ጭው ፡ የሚያደርግ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 13 ፤ የሰማርያንም ፡ ገመድ ፡ የአክአብንም ፡ ቤት ፡ ቱንቢ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፡ ሰውም ፡ ወጭቱን ፡ እንዲወለውል ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ወልውዬ ፡ እገለብጣለኹ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 14 ፤ የርስቴንም ፡ ቅሬታ ፡ እጥላለኹ ፥ በጠላቶቻቸውም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ ለጠላቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ምርኮና ፡ ብዝበዛ ፡ ይኾናሉ ፤

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 15 ፤ አባቶቻቸው ፡ ከግብጽ ፡ ከወጡ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ሠርተዋልና ፥ አስቈጥተውኝማልና ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ ምናሴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳን ፡ ካሳተበት ፡ ኀጢአት ፡ ሌላ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እስኪሞላት ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አፈሰሰ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 17 ፤ የምናሴም ፡ የቀረው ፡ ነገርና ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ ያደረገውም ፡ ኀጢአት ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 18 ፤ ምናሴም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በቤቱም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በዖዛ ፡ አትክልት ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ዓሞጽ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 19 ፤ ዓሞጽም ፡ መንገሥ ፡ በገ፞ መረ ፡ ጊዜ ፡ የ፞ኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢ፞የሩሳሌምም ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዮ፞ጥባ ፡ ሰው ፡ የሐሩስ ፡ ልጅ ፡ ሜሶላም ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 20 ፤ አባቱም ፡ ምናሴ ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ሠራ ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 21 ፤ አባቱም ፡ በ፞ኼደበት ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኼደ ፥ አባቱም ፡ ያመለካቸውን ፡ ጣ፞ዖ፞ታት ፡ አመለከ ፡ ሰገደላቸውም ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 22 ፤ የአባቶ፞ቹንም ፡ አ፞ምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተወ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ መንገድ ፡ አልኼደም ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 23 ፤ የዓሞጽም ፡ ባ፞ሪያዎች ፡ አሤሩበት ፥ ንጉሡንም ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ገደሉት ፥

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 24 ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በዓሞጽ ፡ ላይ ፡ ያሴሩበትን ፡ ኹሉ ፡ ገደሉ ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ልጁን ፡ ኢ፞ዮ፞ስያስን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ።

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 25 ፤ የዓሞጽም ፡ የቀረው ፡ ነገርና ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥ፞ታት ፡ ታ፞ሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 21 ፡ 26 ፤ በ፞ዖዛም ፡ አ፞ትክልት ፡ ባለው ፡ በመ፞ቃብሩ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኢ፞ዮ፞ስያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥ፞ት ፡ ካ፞ልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 1 ፤ ኢ፞ዮ፞ስያስም ፡ መንገሥ ፡ በገ፞ መረ ፡ ጊዜ ፥ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ በኢ፞የሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ከባሱሮት ፡ የ፞ኾነ ፡ የአዳያ ፡ ልጅ ፡ ይዲዳ ([186]) ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ አደረገ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኼደ ፥ ቀኝም ፡ ግራም ፡ አላለም ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 3 ፤ በንጉሡም ፡ በኢ፞ዮ፞ስያስ ፡ በፀ፞ሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ ንጉሡ ፡ ጸሓፊውን ፡ የሜሶላምን ፡ ልጅ ፡ የኤ፞ሊ፞ልያስን ፡ ልጅ ፡ ሳፋንን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ላከው ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 4 ፤ የመ፞ቅደሱ ፡ በረኞ፞ች ፡ ከሕዝቡ ፡ የሰበሰ፞ትን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የገባውን ፡ ገንዘብ ፡ ይደምር ፡ ዘንድ ፡ ወደካህናቱ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ኬ፞ልቅ፞ያስ ፡ ኺድ ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 5 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ላሉት ፡ ሠራተኞ፞ች ፡ አለ፞ቃዎች ፡ ይስጡት ፤ እነ፞ርሱም ፡ የተናደውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለ፞ሚጠግኑት ፡ ሠራተኞ፞ች ፥

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 6 ፤ ለፀናጢ.ዎ፞ችና ፡ ለጠራቢ.ዎ፞ች ፥ ለድ.ንጋ.ይም ፡ ወ፞ቃሪዎ፞ች ፥ መ፞ቅደሱንም ፡ ለመጠገን ፡ ዕ.ንጨ፞ትንና ፡ የተወ፞ቀ፞ረውን ፡ ድ.ንጋ.ይ ፡ ለ፞ሚገዙ ፡ ይክ፞ፈ፞ሉት ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነ፞ርሱ ፡ የ፞ታመኑ ፡ ነበሩና ፥ በእ.ጃ፞ቸው ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ አ.ይቈ.ጣጠሯ፞ቸ.ውም ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 8 ፤ ካ.ህ.ኑም ፡ ኬ፞ልቅ.ያስ ፡ ጸ.ሓ.ፊ.ውን ፡ ሳ.ፋ.ንን ፥ የ.ሕ.ጉ.ን ፡ መ.ጽ.ሐ.ፍ ፡ በ.እ.ግ.ዚ.አ.ብ.ሔ.ር ፡ ቤ.ት ፡ አ.ግ.ኝ.ቻ.ለ.ኹ ፡ አ.ለ.ው ፤ ኬ.ል.ቅ.ያ.ስ.ም ፡ መ.ጽ.ሐ.ፉ.ን ፡ ለ.ሳ.ፋ.ን ፡ ሰ.ጠ.ው ፥ ር.ሱ.ም ፡ አ.ነ.በ.በ.ው ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 9 ፤ ጸ.ሓ.ፊ.ው.ም ፡ ሳ.ፋ.ን ፡ ወ.ደ ፡ ን.ጉ.ሡ ፡ መ.ጣ ፥ ለ.ን.ጉ.ሡ.ም ፦ በ.መ.ቅ.ደ.ሱ ፡ የ.ተ.ገ.ኘ.ው.ን ፡ ገ.ን.ዘ.ብ ፡ ባ.ሪ.ያ.ዎ.ች.ኽ ፡ አ.ፈ.ሰ.ሱ.ት ፥ በ.እ.ግ.ዚ.አ.ብ.ሔ.ር.ም ፡ ቤ.ት ፡ ሠ.ራ.ተ.ኞ.ች ፡ ላ.ይ ፡ ለ.ተ.ሾ.ሙ.ት ፡ አ.ለ.ቃ.ዎ.ች ፡ ሰ.ጡ.ት ፡ ብ.ሎ ፡ አ.ወ.ራ.ለ.ት ።

---

186 ዕብ. ፥ የዲ.ይ.ዳ.ህ ፡ (የ.ተ.ወ.ደ.ደ.ች) ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 10 ፤ ጸሓፊውም ፡ ሳፋን ፡ ለንጉሡ ፦ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጥቶኛል ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሳፋንም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አነበበው ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ልብሱን ፡ ቀደደ ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፡ ካህኑን ፡ ኬልቅያስን ፥ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡ አኪ.ቃምን ([187]) ፥ የሚክያስንም ፡ ልጅ ፡ ዓክቦርን ፥ ጸሓፊውንም ፡ ሳፋንን ፥ የንጉሡንም ፡ ብላቴና ፡ ዐሳያን ([188]) ፦

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 13 ፤ አባቶቻችን ፡ በርሷ ፡ የተጻፈውን ፡ ሹሉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ የዚችን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ስላልሰሙ ፡ በላያችን ፡ የነደደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ኼዳችኹ ፡ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ይሁዳም ፡ ሹሉ ፡ የዚችን ፡ የተገኘችውን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 14 ፤ እንዲሁም ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስና ፡ አኪ.ቃም ፡ ዓክቦርም ፡ ሳፋንና ፡ ዐሳያም ፡ ወደ ፡ ልብስ ፡ ጠባቂው ፡ ወደሐስራ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ቲቁዋ ፡ ልጅ ፡ ወደሴሌም ፡ ሚስት ፡ ወደ ፡ ነቢያቱ ፡ ወደ ፡ ሕልዳና ፡ ኼዱ ፤ ርሷም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ፤ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ ተነጋገሩ ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 15 ፤ ርሷም ፡ አለቻቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ለላካችኹ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እንዳነበበው ፡ እንደ ፡ መጽሐፉ ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣለኹ ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 17 ፤ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ሹሉ ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ትተውኛልና ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፥ ቍጣዬ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይነዳ፡ል ፥ አይጠፋምም ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ለላካችኹ ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፥ ልብኽ ፡ ገር ፡ ኾኗልና ፥

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፡ ለድንቅና ፡ ለመርገም ፡ እንዲኾኑ ፡ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ የተናገርኹትን ፡ ሰምተኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተዋርደኻልና ፥ ልብስኽን ፡ ቀዲ፡ኻልና ፥ በፊቴም ፡ አልቅሰኻልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሰምቼኻለኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 20 ፤ ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አባቶችኽ ፡ እሰበስብኻለኹ ፥ በሰላምም ፡ ወደ ፡ መቃብርኽ ፡ ትሰበሰባለኽ ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ የማመጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ዐይኖችኽ ፡ አያዩም ፦ ይህንም ፡ ለንጉሡ ፡ አወሩለት ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ላከ ፤ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሹሉ ፡ ሰበሰባቸው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጣ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ ሹሉ ፥ ካህናቱና ፡ ነቢያቱም ፥ ሕዝቡም ፡ ሹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ወጡ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ በጐሯቸው ፡ አነበበ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፡ በዐምደ ፡ ወርቁ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተከትሎ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፥ ትእዛዙንና ፡ ምስክሩንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሱ ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ በዚሁም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ፤ ሕዝቡም ፡

---

187 ዕብ. ፥ አኒ.ቃም ፡ (እኅውየ ፡ ቆመ ፥ ወንድሜ ፡ ቆመ) ።

188 ዕብ. ፥ ዐሳያህ ፡ (ጌታ ፡ ሠራ) ።

ኹሉ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገቡ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ የካህናቱን ፡ አለቃ ፡ ኬልቅያስን ፡ በኹለተኛውም ፡ መዓርግ ፡ ያሉትን ፡ ካህናትን ፡ በረኞቹንም ፡ ለበዓልና ፡ ለማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ የተሠሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፤ ከኢየሩሳሌምም ፡ ውጭ ፡ በቄድሮን ፡ ሜዳ ፡ አቃጠላቸው ፥ ዐመዱንም ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ወሰደው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 5 ፤ የይሁዳ ፡ ነገሥታትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በነበሩት ፡ በኮረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ መስገጃዎች ፡ ያጥኑ ፡ ዘንድ ፡ ያኖሯቸውን ፡ የጣዖቱን ፡ ካህናት ፥ ለበዓልና ፡ ለፀሓይ ፡ ለጨረቃና ፡ ለከዋክብት ፡ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ያጥኑ ፡ የነበሩትንም ፡ አስወገደ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 6 ፤ የማምለኪያ ፡ ዐጸድንም ፡ ጣዖት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ወደቄድሮን ፡ ፈፋ ፡ አወጣው ፤ በቄድሮንም ፡ ፈፋ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ፥ አድቆም ፡ ትቢያ ፡ አደረገው ፥ ትቢያውንም ፡ በሕዝብ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ጣለው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 7 ፤ ሴቶቹም ፡ ለማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ መጋረጃ ፡ ይፈትሉባቸው ፡ የነበሩትን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የሰዶማውያንን ፡ ቤቶች ፡ አፈረሰ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 8 ፤ ካህናቱንም ፡ ኹሉ ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ አወጣቸው ፤ ከጌባም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ድረስ ፡ ካህናት ፡ ያጥኑበት ፡ የነበረውን ፡ የኮረብታ ፡ መስገጃ ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ አደረገው ። በከተማዩቱም ፡ በር ፡ በግራ ፡ በኩል ፡ በነበረው ፡ በከተማዩቱ ፡ ሹም ፡ በኢያሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ የነበሩትን ፡ የበሮቹን ፡ መስገጃዎች ፡ አፈረሰ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 9 ፤ የኮረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወዳለው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ አይመጡም ፡ ነበር ፤ ብቻ ፡ በወንድሞቻቸው ፡ መካከል ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 10 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ወንድ ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ እንዳያሳልፍ ፡ በሄኖም ፡ ልጆች ፡ ሸለቆ ፡ የነበረውን ፡ ቶፌትን ፡ ርኩስ ፡ አደረገው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 11 ፤ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ በከተማው ፡ አቅራቢያ ፡ በነበረው ፡ በጃን ፡ ደረባው ፡ በናታንሜሌክ ፡ መኖሪያ ፡ አጠገብ ፡ ለፀሓይ ፡ የሰጡትን ፡ ፈረሶች ፡ አስወገደ ፤ የፀሓይንም ፡ ሠረገላዎች ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 12 ፤ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ያሠሩትን ፡ በአካዝ ፡ ቤት ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መሠዊያዎች ፥ ምናሴም ፡ ያሠራውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በኹለቱ ፡ ወለሎች ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መሠዊያዎች ፡ ንጉሡ ፡ አስፈረሳቸው ፥ አደቀቃቸውም ፥ ትቢያቸውንም ፡ በቄድሮን ፡ ፈፋ ፡ ጣለ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 13 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ በርኵሰት ፡ ተራራ ፡ ቀኝ ፡ የነበሩትን ፥ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ ለሲዶናውያን ፡ ርኵሰት ፡ ለዐስታሮት ፡ ለሞዐብም ፡ ርኵሰት ፡ ለካሞሽ ፡ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ርኵሰት ፡ ለሚልኮም ፡ ያሠራቸውን ፡ መስገጃዎች ፡ ንጉሡ ፡ ርኩስ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 14 ፤ ሐውልቶቹንም ፡ ኹሉ ፡ አደቀቀ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፥ በስፍራቸውም ፡ የሙታንን ፡ ዐጥንት ፡ ሞላበት ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፡ በቤቴል ፡ የነበረውን ፡ መሠዊያ ፥ እስራኤልንም ፡ ያሳተ ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ያሠራውን ፡ የኮረብታውን ፡ መስገጃ ፥ ይህን ፡ መሠዊያና ፡ መስገጃ ፡ አፈረሰ ፤ ድንጋዮቹንም ፡ ሰባበረ ፥ አድቆም ፡ ትቢያ ፡ አደረገው ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዱንም ፡ አቃጠለው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 16 ፤ ኢዮስያስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ በተራራው ፡ የነበሩትን ፡ መቃብሮች ፡ አየ ፤ ኢዮርብዓምም ፡

በበዓል ፡ ጊዜ ፡ በመሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ሲቆም ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ የተነባ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፥ ልኮ ፡ ከመቃብሮቹ ፡ ዐጥንቶቹን ፡ አስወጣ ፥ በመሠዊያውም ፡ ላይ ፡ አቃጠላቸው ፥ አረከሰውም ። ዘወርም ፡ ብሎ ፡ ወደተናገረው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መቃብር ፡ ዐይኖቹን ፡ አቅንቶ ፦

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 17 ፤ ያ ፡ የማየው ፡ የመታሰቢያ ፡ ምልክት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ። የዚያችም ፡ ከተማ ፡ ሰዎች ፦ ከይሁዳ ፡ ወጥቶ ፡ በቤቴል ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ያደረግኸውን ፡ ነገር ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ መቃብር ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 18 ፤ ርሱም ፦ ተዉት ፥ ማንም ፡ ዐጥንቱን ፡ አያንቀሳቅሰው ፡ አለ ፤ እነርሱም ፡ ከሰማርያ ፡ ከወጣው ፡ ከነቢዩ ፡ ዐጥንት ፡ ጋራ ፡ ዐጥንቱን ፡ ተዉ ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 19 ፤ በሰማርያም ፡ ከተማዎች ፡ የነበሩትን ፥ እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጡት ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ የሠሩትን ፡ የከሠረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ኢዮስያስ ፡ አስወገዳቸው ፥ በቤቴልም ፡ እንዳደረገው ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገባቸው ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 20 ፤ በዚያም ፡ የነበሩትን ፡ የከሠረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ካህናት ፡ ዅሉ ፡ በመሠዊያዎቹ ፡ ላይ ፡ ገደላቸው ፥ የሰዎቹንም ፡ ዐጥንት ፡ በመሠዊያዎቹ ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ። ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተመለሰ ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቡን ፡ ዅሉ ፦ በዚህ ፡ በቃል ፡ ኪዳን ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈው ፡ ለአምላካችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ አድርጉ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 22 ፤ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ከነበሩ ፡ ከመሳፍንት ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ዅሉ ፡ አልተፈሰከም ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ፋሲካ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተፈሰከ ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 24 ፤ ደግሞም ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ባገኘው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፥ መናፍስት ፡ ጠሪዎቹንና ፡ ጠንቋዮቹን ፡ ተራፊምንና ፡ ጣዖታትንም ፡ በይሁዳ ፡ አገርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተገኘውን ፡ ርኵሰት ፡ ዅሉ ፡ ኢዮስያስ ፡ አስወገደ ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 25 ፤ እንደ ፡ ሙሴም ፡ ሕግ ፡ ዅሉ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍሱ ፡ በፍጹምም ፡ ኀይሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የተመለሰ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ከርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ አልነበረም ፤ እንደ ፡ ርሱም ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ አልተነሣም ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምናሴ ፡ ስላስቈጣው ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ከነደደው ፡ ከታላቁ ፡ ቍጣው ፡ ትኵሳት ፡ አልተመለሰም ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እስራኤልን ፡ እንዳራቅኹት ፡ ይሁዳን ፡ ከፊቴ ፡ አርቀዋለኹ ፤ ይህችንም ፡ የመረጥኋትን ፡ ከተማ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፦ ስሜ ፡ በዚያ ፡ ይኾናል ፡ ያልኹትን ፡ ቤት ፡ እጥላለኹ ፡ አለ ።

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 28 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮስያስ ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፥ 23 ፥ 29 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ኒካዑ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ሊጋጠም ፡ ወደኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ወጣ ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮስያስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሊጋጠም ፡ ወጣ ፤ ፈርዖንም ፡ በተገናኘው ፡ ጊዜ ፡ በመጊዶ ፡ ገደለው ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 30 ፤ ከሞተም ፡ በኋላ ፡ ባሪያዎቹ ፡ በሠረገላው ፡ አድርገው ፡ ከመጊዶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አመጡት ፥ በመቃብሩም ፡ ቀበሩት ። የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክስን ፡ ወሰዱት ፥ ቀብተውም ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 31 ፤ ኢዮአክስም ፡ መንገሥ ፡ በጐመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ። እናቱም ፡ ዐሚጣል ፡ ትባል ፡ ነበር ፥ ርሷም ፡ የልብና ፡ ሰው ፡ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 32 ፤ አባቶቹም ፡ እንዳደረጉ ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 33 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ እንዳይነግሥ ፡ ፈርዖን ፡ ኒካዑ ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በሪብላ ፡ አሰረው ፤ በምድሩም ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ፈሰሴ ፡ ጣለበት ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 34 ፤ ፈርዖን ፡ ኒካዑም ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄምን ፡ በአባቱ ፡ በኢዮስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠ ፥ ስሙንም ፡ ኢዮአቄም ([189]) ፡ ብሎ ፡ ለወጠው ። ኢዮአክስንም ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አፈለሰው ፤ በዚያም ፡ ሞተ ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 35 ፤ ኢዮአቄምም ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ ለፈርዖን ፡ ሰጠው ፤ እንደ ፡ ፈርዖንም ፡ ትእዛዝ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ምድሩን ፡ አስገበረ ፤ ለፈርዖን ፡ ኒካዑም ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ግምጋሜው ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አስከፈለ ።

ነገ.2 ፡ 22 ፡ 36 ፤ ኢዮአቄምም ፡ መንገሥ ፡ በጐመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ዘቢዳ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ ርሷም ፡ የሩማ ፡ ሰው ፡ የፈዳያ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 23 ፡ 37 ፤ አባቶቹም ፡ እንዳደረጉ ፡ ዅሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 1 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወጣ ፥ ኢዮአቄምም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ተገዛለት ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዘወር ፡ አለና ፡ ዐመፀበት ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የከለዳውያንንና ፡ የሶርያውያንን ፡ የሞዐባውያንንም ፡ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ አደጋ ፡ ጣዮች ፡ ሰደደበት ፤ በባሪያዎቹ ፡ በነቢያት ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ሰደዳቸው ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 3 ፤ ምናሴ ፡ ስላደረገው ፡ ኀጢአት ፡ ዅሉ ፡ ስላፈሰሰውም ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ስለ ፡ ሞላ ፡ ከፊቱ ፡ ያስወግዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ኾነ ፤

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይራራ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 5 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአቄም ፡ ነገር ፥ የሠራውም ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፥ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 6 ፤ ኢዮአቄምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፤ ልጁም ፡ ዮአኪን ([190]) ፤ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 7 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ የነበረውን ፡ ዅሉ ፡ ከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ገምሮ ፡

189 ዕብ. ፥ የሆያቂም ፡ (ያቀውም ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ያቆማል) ።
190 ዕብ. ፥ የሆያኪይን ፡ (ይኪውን ፡ በእግዚእ • በጌታ ፡ ይኾናል) ።

እስከኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ወስዶ ፡ ነበርና ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ከአገሩ ፡ አልወጣም ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 8 ፤ የኦኪን ፡ መንገሥ ፡ በገሥመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ኔስታ ፡ ትባል ፡ ነበር ፤ ርሷም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰው ፡ የኤልናታን ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 9 ፤ አባቱም ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 10 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነጾር ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ፥ ከተማዪቱም ፡ ተከበበች ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 11 ፤ ባሪያዎቹም ፡ በከበቧት ፡ ጊዜ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ወጣ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 12 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪንና ፡ እናቱ ፥ ባሪያዎቹም ፥ አለቃዎቹም ፥ ጃን ፡ ደረባዎቹም ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወጡ ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በነገሠ ፡ በስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ያዘው ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መዛግብትን ፡ ኹሉ ፡ የንጉሡም ፡ ቤት ፡ መዛግብትን ፡ ከዚያ ፡ አወጣ ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ የሠራውን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ሰባበረ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 14 ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ ኹሉ ፥ አለቃዎቹንም ፡ ኹሉ ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላኑንም ፡ ኹሉ ፥ ጠራቢዎቹንም ፡ ኹሉ ፥ ብረት ፡ ሠራተኞቹን ፡ ኹሉ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ምርኮኞች ፡ አፈለሰ ፤ ከድኻዎች ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አልቀረም ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 15 ፤ ዮአኪንንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አፈለሰ ፤ የንጉሡንም ፡ እናት ፥ የንጉሡንም ፡ ሚስቶች ፥ ጃን ፡ ደረባዎቹንም ፥ የአገሩንም ፡ ታላላቆች ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረከ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 16 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ብርቱዎቹንና ፡ ሰልፍ ፡ የሚችሉትን ፡ ኹሉ ፥ ኀያላኑን ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፥ ጠራቢዎችና ፡ ብረት ፡ ሠራተኞችም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፥ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረከ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 17 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የዮአኪንን ፡ አጎት ፡ ማታንያን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሠ ፥ ስሙንም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ብሎ ፡ ለወጠው ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 18 ፤ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በገሥመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ዐሚጣል ፡ የተባለች ፡ የልብና ፡ ሰው ፡ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 19 ፤ ኢዮአቄምም ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ነገ.2 ፡ 24 ፡ 20 ፤ ከፊቱ ፡ አውጥቶ ፡ እስኪጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ኾኗልና ፤ ሴዴቅያስም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 1 ፤ ሴዴቅያስም ፡ በነገሠ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥተው ፡ ከበቧት ፤ በዙሪያዋም ፡ ዕርድ ፡ ሠሩባት ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 2 ፤ ከተማዪቱም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡

ተከሳ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 3 ፤ በአራተኛውም ፡ ወር ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ በከተማዪቱ ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበርና ፥ ለአገሩ ፡ ሰዎች ፡ እንጀራ ፡ ታጣ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 4 ፤ ከተማዪቱም ፡ ተሰበረች ፥ ሰልፈኞችም ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በር ፡ ወደንጉሡ ፡ አትክልት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በሌሊት ፡ ሸሹ ፤ ከለዳውያንም ፡ በከተማዪቱ ፡ ዙሪያ ፡ ነበሩ ፤ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 5 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ንጉሡን ፡ ተከታተሉ ፥ በኢያሪኮም ፡ ሜዳ ፡ ያዙት ፤ ሰራዊቱም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ተለይተው ፡ ተበትነው ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 6 ፤ ንጉሡንም ፡ ይዘው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ አመጡት ፤ ፍርድም ፡ ፈረዱበት ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 7 ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ገደሏቸው ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ዐይኖች ፡ አወጡ ፥ በሰንሰለትም ፡ አሰሩት ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ወሰዱት ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 8 ፤ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያ ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ አቃጠለ ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ ታላላቆቹን ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 10 ፤ ከዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ የከለዳውያን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡ ዙሪያዋን ፡ አፈረሱ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 11 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡ ሕዝብ ፥ ሸሽተውም ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የተጠጉትን ፥ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ፡ አፈለሰ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 12 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ከአገሩ ፡ ድኻዎች ፡ ወይን ፡ ተካዮችና ፡ ዐራሾች ፡ እንዲኾኑ ፡ አስቀረ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 13 ፤ ከለዳውያንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የነበሩትን ፡ የናስ ፡ ዐምዶች ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የነበሩትን ፡ መቀመጫዎችና ፡ የናስ ፡ ኩሬ ፡ ሰባበሩ ፥ ናሱንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 14 ፤ ምንቸቶቹንና ፡ መጫሪያዎቹንም ፡ መኰስተሪያዎቹንና ፡ ጭልፋዎቹንም ፡ የሚያገለግሉበትንም ፡ የናስ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ወሰዱ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 15 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ማንደጃዎቹንና ፡ መቀመጫዎቹን ፥ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በወርቅ ፥ የብሩንም ፡ በብር ፡ አድርጎ ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 16 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ዐምዶች ፡ አንዱንም ፡ ኩሬ ፡ መቀመጫዎቹንም ፡ ወሰደ ፤ ለእነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ናስ ፡ ሚዛን ፡ አልነበረውም ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 17 ፤ የአንዱም ፡ ዐምድ ፡ ቁመት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የናስም ፡ ጕልላት ፡ ነበረበት ፤ የጕልላቱም ፡ ርዝመት ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ በጕልላቱም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ የናስ ፡ መርበብና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ በኹለተኛው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ መርበብ ፡ ነበረበት ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 18 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ሰራያን ፡ ኹለተኛውንም ፡ ካህን ፡ ሶፎንያስን ፡ ሦስቱንም ፡

በረኞች ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 19 ፤ ከከተማዉቱም ፡ በሰልፈኞች ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ከነበሩት ፡ አንዱን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፥ በከተማዉቱም ፡ የተገኙትን ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የሚቆሙትን ፡ ዐምስቱን ፡ ሰዎች ፥ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያሰልፍ ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ጸሓፊ ፥ በከተማዉቱም ፡ ከተገኙት ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስድሳ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 20 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወስዶ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ አመጣቸው ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 21 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ መታቸው ፥ በሐማትም ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ። እንዲሁ ፡ ይሁዳ ፡ ከአገሩ ፡ ተማረከ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 22 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ በቀረው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የሳፋንን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ አለቃ ፡ አደረገው ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 23 ፤ የጭፍራዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፥ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፥ የነጦፋዊውም ፡ የተንሑሜት ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፥ የማዕካታዊውም ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፥ ሰዎቻቸውም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ጎዶልያስን ፡ እንደ ፡ ሾመ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 24 ፤ ጎዶልያስም ፦ ከከለዳውያን ፡ ሎሌዎች ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፥ በአገሩ ፡ ተቀመጡ ፥ ለባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ፥ መልካምም ፡ ይኾንላችኋል ፡ ብሎ ፡ ለእነርሱና ፡ ለሰዎቻቸው ፡ ማለላቸው ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 25 ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ግን ፡ የመንግሥት ፡ ዘር ፡ የነበረ ፡ የኤሊሳማ ፡ ልጅ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ጎዶልያስንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በምጽጳ ፡ የነበሩትን ፡ አይሁድንና ፡ ከለዳውያንን ፡ እስኪሞቱ ፡ ድረስ ፡ መቷቸው ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 26 ፤ ከለዳውያንንም ፡ ፈርተው ፡ ነበርና ፥ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የጭፍራዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ መጡ ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 27 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በተማከረ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ዮርማሮዴክ ፡ በነገሠ ፡ በአንደኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪንን ፡ ከወህኒ ፡ አወጣው ፤

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 28 ፤ በፍቅርም ፡ ተናገረው ፥ ዙፋኑንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በባቢሎን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ በላይ ፡ አደረገለት ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 29 ፤ በወህኒም ፡ ውስጥ ፡ ለብሶት ፡ የነበረውን ፡ ልብስ ፡ ለወጠለት ፤ ዮአኪንም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ኹልጊዜ ፡ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ነገ.2 ፡ 25 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ የዘወትር ፡ ቀለብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ❖

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ አዳም ፥ ሴት ፥ ሄኖስ ፥ ቃይናን ፥ መላልኤል ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ያሬድ ፥ ሔኖክ ፥ ማቱሳላ ፥ ላሜሕ ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ኖኅ ፥ ሴም ፥ ካም ፥ ያፌት ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ የያፌት ፡ ልጆች ፤ ጋሜር ፥ ማጎግ ፥ ማዴ ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ያዋን ፥ ቶቤል ፥ ሞሳሕ ፥ ቴራስ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ የጋሜርም ፡ ልጆች ፤ አስከናዝ ፥ ሪፋት ፥ ቴርጋማ ። የያዋንም ፡ ልጆች ፤ ኤሊሳ ፥ ተርሴስ ፥ ኪቲም ፥ ሮድኢ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ የካምም ፡ ልጆች ፤ ኩሽ ፥ ምጽራይም ፥ ፉጥ ፥ ከነዓን ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 9 ፤ የኩሽም ፡ ልጆች ፤ ሳባ ፥ ኤውላጥ ፥ ሰብታ ፥ ራዕማ ፥ ሰብቃታ ። የራዕማም ፡ ልጆች ፤ ሳባ ፥ ድዳን ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ኩሽም ፡ ናምሩድን ፡ ወለደ ፤ ርሱም ፡ በምድር ፡ ኀያል ፡ መኾንን ፡ ገመረ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ምጽራይምም ፡ ሉዲምን ፥ ዐናሚምን ፥ ላህቢምን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ነፍተሂምን ፥ ፈትሩሲምን ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ የወጡበትን ፡ ከስሉሂምን ፥ ከፍቶሪምን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ከነዓንም ፡ የበኩር ፡ ልጁን ፡ ሲዶንን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 14 ፤ ኬጢን ፥ አያቡሳዊውን ፥ አሞራዊውን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 15 ፤ ጌርጌሳዊውን ፥ ዔዊያዊውን ፥ ዐርካዊውን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 16 ፤ ሢኒያዊውን ፥ አራዴዎንን ፥ ሰማሪዎንን ፥ አማቲን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 17 ፤ የሴምም ፡ ልጆች ፤ ዔላም ፥ አሶር ፥ አርፋክስድ ፥ ሉድ ፥ አራም ፥ ዑፅ ፥ ኍል ፥ ጌቴር ፥ ሞሳሕ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 18 ፤ አርፋክስድም ፡ ቃይንምን ፡ ወለደ ፤ ቃይንምም ፡ ሳላን ፡ ወለደ ፤ ሳላም ፡ ዔቦርን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 19 ፤ ለዔቦርም ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ተወለዱለት ፤ በዘመኑ ፡ ምድር ፡ ተከፍላለችና ፡ የአንደኛው ፡ ስም ፡ ፋሌቅ ፡ ተባለ ፤ የወንድሙም ፡ ስም ፡ ዮቅጣን ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 20 ፤ ዮቅጣንም ፡ አልሞዳድን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 21 ፤ ሳሌፍን ፥ ሐስረሞትን ፥ ያራሕን ፥ ሀዶራምን ፥

መዋ.1 ፥ 1 ፥ 22 ፤ አውዛልን ፥ ደቅላን ፥ ዖባልን ፥ አቢማኤልን ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 23 ፤ ሳባን ፥ ኦፊርን ፥ ኤውላጥን ፥ ዮባብን ፡ ወለደ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የዮቅጣን ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 24 ፤ 25 ፤ ሴም ፥ አርፋክስድ ፥ ሳላ ፥ ዔቦር ፥ ፋሌቅ ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 26 ፤ 27 ፤ ራግው ፥ ሴሮሕ ፥ ናኮር ፥ ታራ ፥ አብርሃም ፡ የተባለ ፡ አብራም ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 28 ፤ የአብርሃምም ፡ ልጆች ፤ ይሥሐቅ ፥ እስማኤል ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 29 ፤ ትውልዳቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ። የእስማኤል ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ነባዮት ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቄዳር ፥ ነብዳኤል ፥ መብሳም ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 30 ፤ ማስማዕ ፥ ዱማ ፥ ማሣ ፥ ኩዳን ፥ ቴማን ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 31 ፤ ኢጡር ፥ ናፌስ ፥ ቄድማ ፤ እነዚህ ፡ የእስማኤል ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 32 ፤ የአብርሃምም ፡ ገረድ ፡ የኬጡራ ፡ ልጆች ፤ ዘምራን ፥ ዮቅሳን ፥ ሜዳን ፥ ምድያም ፥ የስቦቅ ፥ ስዌሕ ። የዮቅሳንም ፡ ልጆች ፤ ሳባ ፥ ድዳን ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 33 ፤ የምድያምም ፡ ልጆች ፤ ጌፌር ፥ ዔፌር ፥ ሄኖኅ ፥ አቢዳዕ ፥ ኤልዳዓ ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የኬጡራ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 34 ፤ አብርሃምም ፡ ይሥሐቅን ፡ ወለደ ። የይሥሐቅም ፡ ልጆች ፡ ዔሳውና ፡ እስራኤል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 35 ፤ የዔሳው ፡ ልጆች ፤ ኤልፋዝ ፥ ራጉኤል ፥ የዑስ ፥ የዕላም ፥ ቆሬ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 36 ፤ የኤልፋዝ ፡ ልጆች ፤ ቴማን ፥ አማር ፥ ስፎ ፥ ጎቶም ፥ ቄኔዝ ፥ ቲምናዕ ፥ ዐማሌቅ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 37 ፤ የራጉኤል ፡ ልጆች ፤ ናሖት ፥ ዛራ ፥ ሳማ ፥ ሚዛህ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 38 ፤ የሴይርም ፡ ልጆች ፤ ሎጣን ፥ ሦባል ፥ ጽብዖን ፥ ዐና ፥ ዲሶን ፥ ኤጽር ፥ ዲሳን ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 39 ፤ የሎጣንም ፡ ልጆች ፤ ሖሪ ፥ ሔማም ፤ ቲምናዕ ፡ የሎጣን ፡ እኅት ፡ ነበረች ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 40 ፤ የሦባል ፡ ልጆች ፤ ዓልዋን ፥ ማኔሐት ፥ ዔባል ፥ ስፎ ፥ አውናም ። የጽብዖንም ፡ ልጆች ፤ አያ ፥ ዐና ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 41 ፤ የዐና ፡ ልጅ ፤ ዲሶን ። የዲሶንም ፡ ልጆች ፤ ሔምዳን ፥ ኤስባን ፥ ይትራን ፥ ክራን ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 42 ፤ የኤጽር ፡ ልጆች ፤ ቢልሐን ፥ ዛዕዋን ፥ ዐቃን ። የዲሳን ፡ ልጆች ፤ ዑፅ ፥ አራን ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 43 ፤ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ገና ፡ ንጉሥ ፡ ሳይነግሥ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። የቢያር ፡ ልጅ ፡ ባላቅ ፤ የከተማዉቱም ፡ ስም ፡ ዲንሃባ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 44 ፤ ባላቅም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ የባሶራ ፡ ሰው ፡ የዛራ ፡ ልጅ ፡ ኢዮባብ ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 45 ፤ ኢዮባብም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ የቴማን ፡ አገር ፡ ሰው ፡ ሑሳም ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 46 ፤ ሑሳምም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ምድያምን ፡ የመታው ፡ የባዳድ ፡ ልጅ ፡ ሃዳድ ፡ ነገሠ ፤ የከተማዉቱም ፡ ስም ፡ ዓዊት ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 47 ፤ ሃዳድም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ የመሥሬቃ ፡ ሰው ፡ ሰምላ ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 48 ፤ ሰምላም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ በወንዙ ፡ አጠገብ ፡ ያለችው ፡ የረሆቦት ፡ ሰው ፡ ሳኡል ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 49 ፤ ሳኡልም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ በዓልሐናን ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 50 ፤ በዓልሐናንም ፡ ሞተ ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ሃዳድ ፡ ነገሠ ፤ የከተማዉ ፡ ስም ፡ ፋዉ ፡ ነበረ ፤ ሚስቱም ፡ የሜዛሃብ ፡ ልጅ ፡ የመጥሬድ ፡ ልጅ ፡ መሄጣብኤል ፡ ነበረች ፤ ሃዳድም ፡ ሞተ ።

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 51 ፤ የኤዶምያስም ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ቲምናዕ ፡ አለቃ ፥ ዓልዋ ፡ አለቃ ፥ የቴት ፡ አለቃ ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 52 ፤ አህሊባማ ፡ አለቃ ፥ ኤላ ፡ አለቃ ፥ ፊኖን ፡ አለቃ ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 53 ፤ ቄኔዝ ፡ አለቃ ፥ ቴማን ፡ አለቃ ፥ ሚብሳር ፡ አለቃ ፥

መዋ.1 ፡ 1 ፡ 54 ፤ መግዲኤል ፡ አለቃ ፥ ዒራም ፡ አለቃ ፤ እነዚህ ፡ የኤዶምያስ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ሮቤል ፥ ስምዖን ፥ ሌዊ ፥ ይሁዳ ፥ ይሳኮር ፥ ዛብሎን ፥

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 2 ፤ ዳን ፥ የሴፍ ፥ ብንያም ፥ ንፍታሌም ፥ ጋድ ፥ አሴር ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 3 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፤ ዔር ፥ አውናን ፥ ሴሎም ፤ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ከከነዓናዊቱ ፡ ከሴዋ ፡ ልጅ ፡ ተወለዱለት ። የይሁዳም ፡ የበኩር ፡ ልጅ ፡ ዔር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፤ ገደለውም ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 4 ፤ ምራቱም ፡ ትዕማር ፡ ፋሬስንና ፡ ዛራን ፡ ወለደችለት ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ሹሉ ፡ ዐምስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 5 ፤ የፋሬስ ፡ ልጆች ፤ ኤስሮም ፥ ሐሙል ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ የዛራም ፡ ልጆች ፤ ዘምሪ ፥ ኤታን ፥ ሄማን ፥

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ከልኮል ፥ ዳራ ፤ ሹሉም ፡ ዐምስት ፡ ነበሩ ። የከርሚም ፡ ልጅ ፡ እስራኤልን ፡ ያስጨነቀ ፥ ዕርሙንም ፡ ሰርቆ ፡ የበደለ ፡ ዐካን ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ የኤታንም ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ለኤስሮም ፡ የተወለዱለት ፡ ልጆች ፤ ይረሕምኤል ፣ አራም ፣ ካልብ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ አራምም ፡ ዐሚናዳብን ፡ ወለደ ፤ ዐሚናዳብም ፡ የይሁዳን ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ነአሶንም ፡ ሰልሞንን ፡ ወለደ ፤ ሰልሞንም ፡ ቦዔዝን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ቦዔዝም ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ፤ ኢዮቤድም ፡ እሴይን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ እሴይም ፡ የበኩር ፡ ልጁን ፡ ኤልያብን ፥ ኹለተኛውንም ፡ ዐሚናዳብን ፥ ሦስተኛውንም ፡ ሳማን ፥

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ አራተኛውንም ፡ ናትናኤልን ፥

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ዐምስተኛውንም ፡ ራዳይን ፥ ስድስተኛውንም ፡ አሳምን ፥ ሰባተኛውንም ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ እኅቶቻቸውም ፡ ጽሩያና ፡ አቢግያ ፡ ነበሩ ። የጽሩያም ፡ ልጆች ፡ አቢሳ ፥ ኢዮአብ ፥ ዐሳሄል ፡ ሦስቱ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ አቢግያም ፡ ዐማሳይን ፡ ወለደች ፤ የዐማሳይም ፡ አባት ፡ እስማኤላዊው ፡ ዬቴር ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ የኤስሮምም ፡ ልጅ ፡ ካሌብ ፡ ከሚስቱ ፡ ከዓዙባ ፡ ከይሪያትም ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፤ ልጆቹም ፡ ያሳር ፥ ሶባብ ፥ አርዶን ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ዓዙባም ፡ ሞተች ፥ ካሌብም ፡ ኤፍራታን ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ ሆርን ፡ ወለደችለት ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ ሆርም ፡ ኡሪን ፡ ወለደ ፥ ኡሪም ፡ ባስልኤልን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 21 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ኤስሮም ፡ ስድሳ ፡ ዓመት ፡ በኾነው ፡ ጊዜ ፡ ወዳገባት ፡ ወደገለዓድ ፡ አባት ፡ ወደማኪር ፡ ልጅ ፡ ገባ ፤ ሰጉብንም ፡ ወለደችለት ። ሰጉብም ፡ ኢያዕርን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ለርሱም ፡ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ነበሩት ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ጌሹርና ፡ አራምም ፡ የኢያዕርን ፡ ከተማዎች ፡ ከቄናትና ፡ ከመንደሮቿ ፡ ጋራ ፡ ስድሳውን ፡ ከተማዎች ፡ ወሰዱባቸው ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የገለዓድ ፡ አባት ፡ የማኪር ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 24 ፤ ኤስሮምም ፡ በካሌብ ፡ ኤፍራታ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የኤስሮም ፡ ሚስት ፡ አቢያ ፡ የቴቁሔን ([191]) ፡ አባት ፡ አሽሑርን ፡ ወለደችለት ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 25 ፤ የኤስሮምም ፡ የበኩር ፡ ልጁ ፡ የይረሕምኤል ፡ ልጆች ፡ በኩሩ ፡ ራም ፥ ቡናህ ፥ ኦሬን ፥ ኦጼም ፥ አኪያ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 26 ፤ ለይረሕምኤልም ፡ ዓጣራ ፡ የተባለች ፡ ሌላ ፡ ሚስት ፡ ነበረችው ፤ ርሷም ፡ የኦናም ፡ እናት ፡ ነበረች ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 27 ፤ የይረሕምኤል ፡ የበኩሩ ፡ የራም ፡ ልጆች ፡ መዓስ ፥ ያሚን ፥ ዔቄር ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 28 ፤ የኦናምም ፡ ልጆች ፡ ሸማይና ፡ ያዳ ፡ ነበሩ ። የሸማይ ፡ ልጆች ፡ ናዳብና ፡ አቢሱር ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 29 ፤ የአቢሱርም ፡ ሚስት ፡ አቢካኢል ፡ ነበረች ፤ አኅባንንና ፡ ሞሊድን ፡ ወለደችለት ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 30 ፤ የናዳብም ፡ ልጆች ፡ ሴሊድና ፡ አፋይም ፡ ነበሩ ፤ ሴሌድም ፡ ያለልጆች ፡ ሞተ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 31 ፤ የአፋይምም ፡ ልጅ ፡ ይሽዒ ፥ የይሽዒም ፡ ልጅ ፡ ሶሳን ፥ የሶሳንም ፡ ልጅ ፡ አሕላይ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 32 ፤ የሸማይም ፡ ወንድም ፡ የያዳ ፡ ልጆች ፡ ዬቴርና ፡ ዮናታን ፡ ነበሩ ፤ ዬቴርም ፡ ያለልጆች ፡ ሞተ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 33 ፤ የዮናታንም ፡ ልጆች ፡ ፊሌትና ፡ ዛዛ ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ የይረሕምኤል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 34 ፤ ለሶሳንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፤ ለሶሳንም ፡ ኢዮሄል ፡ የተባለ ፡ ግብጻዊ ፡ አገልጋይ ፡ ነበረው ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 35 ፤ ሶሳንም ፡ ለአገልጋዩ ፡ ለኢዮሄል ፡ ልጁን ፡ አጋባት ፥ ርሷም ፡ ዐታይን ፡ ወለደችለት ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 36 ፤ ዐታይም ፡ ናታንን ፡ ወለደ ፤ ናታንም ፡ ዛባድን ፡ ወለደ ፤

---

191 ዕብ. ፥ ቴቆዐህ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 37 ፤ ዛባድም ፡ ኤፍላልን ፡ ወለደ ፤ ኤፍላልም ፡ ዖቤድን ፡ ወለደ ፤ ዖቤድም ፡ ኢዩን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 38 ፤ ኢዩም ፡ ዐዛርያስን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 39 ፤ ዐዛርያስም ፡ ኬሌስን ፡ ወለደ ፤ ኬሌስም ፡ ኤልዓሣን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 40 ፤ ኤልዓሣም ፡ ሲስማይን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 41 ፤ ሲስማይም ፡ ሰሎምን ፡ ወለደ ፤ ሰሎምም ፡ የቃምያን ፡ ወለደ ፤ የቃምያም ፡ ኤሊሳማን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 42 ፤ የይረሕምኤልም ፡ ወንድም ፡ የካሌብ ፡ ልጆች ፡ በኵሩ ፡ የዚፍ ፡ አባት ፡ ሞሳ ፥ የኬብሮንም ፡ አባት ፡ የመሪሳ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 43 ፤ የኬብሮንም ፡ ልጆች ፡ ቆሬ ፥ ተፉዋ ፥ ሬቄም ፥ ሽማዕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 44 ፤ ሽማዕም ፡ የዮርቅዓምን ፡ አባት ፡ ረሐምን ፡ ወለደ ፤ ሬቄምም ፡ ሽማይን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 45 ፤ የሽማይም ፡ ልጅ ፡ ማዖን ፡ ነበረ ፤ ማዖንም ፡ የቤትጹር ፡ አባት ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 46 ፤ የካሌብም ፡ ቁባት ፡ ዔፋ ፡ ሀራንን ፥ ሞዳን ፥ ጋዜዝን ፡ ወለደች ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 47 ፤ ሀራንም ፡ ጋዜዝን ፡ ወለደ ። የያህዳይም ፡ ልጆች ፡ ሬጌም ፥ ኢዮታም ፥ ጌሻን ፥ ፋሌጥ ፥ ሔፋ ፥ ሸዓፍ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 48 ፤ የካሌብም ፡ ቁባት ፡ ማዕካ ፡ ሸቤርንና ፡ ቲርሐናን ፡ ወለደች ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 49 ፤ ደግሞም ፡ የመድማናን ፡ አባት ፡ ሸዓፍንና ፡ የመክቢናንና ፡ የጊብዓን ፡ አባት ፡ ሱሳን ፡ ወለደች ፤ የካሌብም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዓክሳ ፡ ነበረች ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 50 ፤ የካሌብ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የኤፍራታ ፡ የበኵሩ ፡ የሆር ፡ ልጅ ፡ የቂርያትይዓሪም ፡ አባት ፡ ሦባል ፥

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 51 ፤ የቤተ ፡ ልሔም ፡ አባት ፡ ሰልሞን ፥ የቤት ፡ ጋዴር ፡ አባት ፡ ሐሬፍ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 52 ፤ ለቂርያትይዓሪምም ፡ አባት ፡ ለሦባል ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ሀሮኤ ፡ የመናሕታውያን ፡ እኩሌታ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 53 ፤ የቂርያትይዓሪምም ፡ ወገኖች ፤ ይትራውያን ፥ ፉታውያን ፥ ሹማታውያን ፥ ሚሽራውያን ፤ ከነዚህም ፡ ጾርዓውያንና ፡ ኤሽታአላውያን ፡ ወጡ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 54 ፤ የሰልሞንም ፡ ልጆች ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፥ ነጦፋውያን ፥ ዓጣሮትቤትዮአብ ፥ የመናሕታውያን ፡ እኩሌታ ፥ ጾርዓውያን ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 2 ፡ 55 ፤ በያቤጽም ፡ የተቀመጡ ፡ የጸሓፊዎች ፡ ወገኖች ፤ ቲርዓውያን ፥ ሺምዓታውያን ፥ ሡካታውያን ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ ከሬካብ ፡ ቤት ፡ አባት ፡ ከሐማት ፡ የወጡ ፡ ቄናውያን ፡ ናቸው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ በኬብሮንም ፡ ለዳዊት ፡ የተወለዱለት ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። በኵሩ ፡ አምኖን ፡ ከኢይዝራኤላዊቱ ፡ ከአኪናሖም ፥ ኹለተኛውም ፡ ዳንኤል ([192]) ፡ ከቀርሜሎሳዊቱ ፡ ከአቢግያ ፥

192 ዕብ. ፥ ዳኒኤል ፡ (ደያኔ ፡ እግዚእ • የእግዚአብሔር ፡ ዳኛ) ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሦስተኛው ፡ አቤሴሎም ፡ ከጌሹር ፡ ንጉሥ ፡ ከተልማይ ፡ ልጅ ፡ ከመዓካ ፥ አራተኛው ፡ አዶንያስ ፡ ከአጊት ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ዐምስተኛው ፡ ሰፋጥያስ ፡ ከአቢጣል ፥ ስድስተኛው ፡ ይትረኃም ፡ ከሚስቱ ፡ ከዔግላ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ስድስቱ ፡ በኬብሮን ፡ ተወለዱለት ፤ በዚያም ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተወለዱለት ፤ ከዓሚኤል ፡ ልጅ ፡ ከቤርሳቤሕ ፥ ሳሙስ ፥ ሶባብ ፥ ናታን ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ ሰሎሞን ፥ አራት ፤ ኢያቤሐር ፥ ኤሊሱዔ ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ኤሊፋላት ፥ ኖጋ ፥ ናፌቅ ፥ ያፍያ ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ኤሊሳማ ፥ ኤሊዳሄ ፥ ኤሊፋላት ፥ ዘጠኝ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ከቁባቶች ፡ ልጆች ፡ በቀር ፡ የዳዊት ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፤ ትዕማርም ፡ እኅታቸው ፡ ነበረች ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ የሰሎሞንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓም ፡ ነበረ ፤ ልጁ ፡ አቢያ ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ልጁ ፡ አሣ ፥ ልጁ ፡ ኢዮሳፍጥ ፥ ልጁ ፡ ኢዮራም ፥ ልጁ ፡ አካዝያስ ፥ ልጁ ፡ ኢዮአስ ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ ልጁ ፡ አሜስያስ ፥ ልጁ ፡ ዐዛርያስ ፥ ልጁ ፡ ኢዮአታም ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ልጁ ፡ አካዝ ፥ ልጁ ፡ ሕዝቅያስ ፥ ልጁ ፡ ምናሴ ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ልጁ ፡ ዓሞጽ ፥ ልጁ ፡ ኢዮስያስ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ የኢዮስያስም ፡ ልጆች ፤ በኵሩ ፡ ዮሐናን ፥ ኹለተኛውም ፡ ኢዮአቄም ፥ ሦስተኛውም ፡ ሴዴቅያስ ፥ አራተኛውም ፡ ሰሎም ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ የኢዮአቄምም ፡ ልጆች ፤ ልጁ ፡ ኢኮንያን ፥ ልጁ ፡ ሴዴቅያስ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ የምርኮኛውም ፡ የኢኮንያን ፡ ልጆች ፡ ሰላትያል ፥ መልኪራም ፥

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ፈዳያ ፥ ሼናጻር ፥ ይቃምያ ፥ ሆሻማ ፥ ነዳብያ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 19 ፤ የፈዳያ ፡ ልጆች ፡ ዘሩባቤልና ፡ ሰሜኢ ፡ ነበሩ ፤ የዘሩባቤልም ፡ ልጆች ፤ ሜሱላም ፥ ሐናንያ ፥ እኅታቸውም ፡ ሰሎሚት ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 20 ፤ ሐሹባ ([193]) ፥ ኦሄል ([194]) ፥ በራክያ ([195]) ፥ ሐሳድያ ፥ ዮሻብሐሴድ ፡ ዐምስት ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ የሐናንያም ፡ ልጆች ፡ ፈላጥያና ፡ የሻያ ፡ ነበሩ ። የረፋያ ፡ ልጆች ፥ የአርናን ፡ ልጆች ፥ የዐብድዩ ፡ ልጆች ፥ የሴኬንያ ፡ ልጆች ።

መዋ.1 ፡ 3 ፡ 22 ፤ የሴኬንያም ፡ ልጅ ፡ ሸማያ ፡ ነበረ ። የሸማያም ፡ ልጆች ፡

---

193 ዕብ. ፥ ሐሹባ ፡ (ዕሰባ ፥ ዕስባት) ።

194 ዕብ. ፥ ኦሄል ፡ (ድንኳን) ።

195 ዕብ. ፥ በራክያህ ፡ (ብርክ ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ ጕልበት) ።

ሐጡስ ፥ ይግአል ፥ ባርያሕ ፥ ነዓርያ ፥ ሻፋጥ ፡ ስድስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 3 ፥ 23 ፤ የነዓርያም ፡ ልጆች ፡ ኤልዮዔናይ ፥ ሕዝቅያስ ፥ ዐዝሪቃም ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 3 ፥ 24 ፤ የኤልዮዔናይም ፡ ልጆች ፡ ሆዳይዋ ፥ ኤልያሴብ ፥ ፊልያ ፥ ዐቁብ ([196]) ፥ ዮሐናን ፥ ደላያ ፥ ዓናኒ ፡ ሰባት ፡ ነበሩ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 1 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ፋሬስ ፥ ኤስሮም ፥ ከርሚ ፥ ሆር ፥ ሦባል ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 2 ፤ የሦባልም ፡ ልጅ ፡ ራያ ፡ ኢኤትን ፡ ወለደ ፤ ኢኤትም ፡ አሑማይንና ፡ ላሃድን ፡ ወለደ ። እነዚህ ፡ የጾርዓውያን ፡ ወገኖች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 3 ፤ እነዚህም ፡ የኤጣም ፡ አባት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤ ኢይዝራኤል ፥ ይሽማ ፥ ይድባሽ ፥ እኅታቸውም ፡ ሃጽሌልፎኒ ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 4 ፤ የጌዶርም ፡ አባት ፡ ፋኑኤል ([197]) ፥ የሑሻም ፡ አባት ፡ ኤጽር ፤ እነዚህ ፡ የቤተ ፡ ልሔም ፡ አባት ፡ የኤፍራታ ፡ የበኩሩ ፡ የሆር ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 5 ፤ ለቴቁሔም ፡ አባት ፡ ለአሽሑር ፡ ሔላና ፡ ነዕራ ፡ የተባሉ ፡ ኹለት ፡ ሚስቶች ፡ ነበሩት ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 6 ፤ ነዕራም ፡ አሑዛምን ፥ ኦፌርን ፥ ቴምኒን ፥ አሐሽታሪን ፡ ወለደችለት ። እነዚህ ፡ የነዕራ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 7 ፤ የሔላም ፡ ልጆች ፡ ዴሬት ፥ ይጽሐር ፥ ኤትናን ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 8 ፤ ቆጽ ፡ ዓኑብን ፥ ጾቤባን ፥ የሃሩምንም ፡ ልጅ ፡ የአሐርሔልን ፡ ወገኖች ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 9 ፤ ያቤጽም ፡ ከወንድሞቹ ፡ ይልቅ ፡ የተከበረ ፡ ነበረ ፤ እናቱም ፦ በጣር ፡ ወልጄዋለኹና ፡ ብላ ፡ ስሙን ፦ ያቤጽ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 10 ፤ ያቤጽም ፦ እባክኽ ፥ መባረክን ፡ ባርከኝ ፥ አገሬንም ፡ አስፋው ፤ እጅኽም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትኹን ፤ እንዳያሳዝነኝም ፡ ከክፋት ፡ ጠብቀኝ ፡ ብሎ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ጠራ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የለመነውን ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 11 ፤ የሹሐም ፡ ወንድም ፡ ክሉብ ፡ የኤሽቶንን ፡ አባት ፡ ምሒርን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 12 ፤ ኤሽቶንም ፡ ቤትራ ፡ ፋንና ፡ ፋሴሐን ፡ የዒርናሐሽንም ፡ አባት ፡ ተሒናን ፡ ወለደ ፤ እነዚህ ፡ የሬካ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 13 ፤ የቄኔዝም ፡ ልጆች ፡ ጎቶንያልና ፡ ሰራያ ፡ ነበሩ ። የጎቶንያልም ፡ ልጅ ፡ ሐታት ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 14 ፤ መዖኖታይ ፡ ዖፍራን ፡ ወለደ ። ሰራያም ፡ የጌሃራሽምን ፡ አባት ፡ ኢዮአብን ፡ ወለደ ፤ እነርሱም ፡ ጠራቢዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 4 ፥ 15 ፤ የዮፎኒም ፡ ልጅ ፡ የካሌብ ፡ ልጆች ፡ ዒሩ ፥ ኤላ ፥ ነዓም ፡ ነበሩ ።

---

196 ዕብ. ፥ ዐቁብ ፡ (ዐቃቢ • ከልካይ ፥ ጠባቂ) ።

197 ዕብ. ፥ ፍኑኤል ፡ (ገጸ ፡ አምላክ) ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ የዔላም ፡ ልጅ ፡ ቄኔዝ ፡ ነበረ ። የይሃሌልኤል ፡ ልጆች ፡ ዚፍ ፡ ዚፋ ፡ ቲርያ ፡ አሳርኤል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ የዕዝራም ፡ ልጆች ፡ ዬቴር ፡ ሜሬድ ፡ ዔፌር ፡ ያሎን ፡ ነበሩ ፤ ዬቴርም ፡ ማርያምን ፡ ሸማይን ፡ የኤሽትምዓን ፡ አባት ፡ ይሽባን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ አይሁዳዊቱም ፡ ሚስቱ ፡ የጌዶርን ፡ አባት ፡ ዬሬድን ፡ የሦኮንም ፡ አባት ፡ ሔቤርን ፡ የዛኖዋንም ፡ አባት ፡ ይቁቲኤልን ፡ ወለደች ። እነዚህም ፡ ሜሬድ ፡ ያገባት ፡ የፈርዖን ፡ ልጅ ፡ የቢትያ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 19 ፤ የሆዲያ ([198]) ፡ ሚስት ፡ የነሐም ፡ እኅት ፡ ልጆች ፡ የገርሚው ፡ የቅዒላ ፡ አባትና ፡ ማዕካታዊው ፡ ኤሽትሞዐ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 20 ፤ የሺሞንም ፡ ልጆች ፡ አምኖን ፡ ሪና ፡ ቤንሐናን ፡ ቲሎን ፡ ነበሩ ። የይሺዒም ፡ ልጆች ፡ ዞሔትና ፡ ቢንዞሔት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 21 ፤ የይሁዳም ፡ ልጅ ፡ የሴሎም ፡ ልጆች ፡ የሌካ ፡ አባት ፡ ዔር ፡ የመሪሳ ፡ አባት ፡ ለዓዳ ፡ ከአሽቤዓ ፡ ቤት ፡ የሚኾኑ ፡ ጥሩ ፡ በፍታ ፡ የሚሠሩ ፡ ወገኖች ፡

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ዮቂም ፡ የኮዜባ ፡ ሰዎች ፡ ኢዮአስ ፡ ሞዐብን ፡ የገዛ ፡ ሳራፍ ([199]) ፡ ያሹቢሌሔም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 23 ፤ ይህ ፡ ዝና ፡ ከቀድሞ ፡ ገዦምሮ ፡ ነበረ ። እነዚህ ፡ በነጣዒምና ፡ በጋዴራ ፡ የሚቀመጡ ፡ ሸክላ ፡ ሠራተኞች ፡ ነበሩ ። በዚያ ፡ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 24 ፤ የስምዖንም ፡ ልጆች ፤ ነሙኤል ፡ ያሚን ፡ ያሪን ፡ ዛራ ፡ ሳኡል ፤

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 25 ፤ ልጁ ፡ ሰሎም ፡ ልጁ ፡ መብሳም ፡ ልጁ ፡ ማስማዕ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 26 ፤ የማስማዕም ፡ ልጆች ፤ ልጁ ፡ ሐሙኤል ([200]) ፡ ልጁ ፡ ዘኩር ፡ ልጁ ፡ ሰሜኢ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 27 ፤ ለሰሜኢም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ወንዶችና ፡ ስድስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ለወንድሞቹ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ አልነበሯቸውም ፡ ወገናቸውም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ይሁዳ ፡ ልጆች ፡ አልተባዙም ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 28 ፤ በቤርሳቤሕም ፡ በሞላዳ ፡

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 29 ፤ በሐጸርሹዓል ፡ በቢልሃ ፡ በዔጼም ፡

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 30 ፤ በቶላድ ፡ በቤቱኤል ፡ በሔርማ ፡ በጺቅላግ ፡

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 31 ፤ በቤትማርካቦት ፡ በሐጸርሱሲም ፡ በቤትቢሪ ፡ በሸዓራይም ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ። እስከዳዊትም ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 32 ፤ መንደሮቻቸውም ፡ ኤጣም ፡ ዐይን ፡ ሬሞን ፡ ቶኬን ፡ ዐሻን ፡ ዐምስቱ ፡ ከተማዎች ፤

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 33 ፤ እስከ ፡ በዓልም ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ከተማዎች ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩ ፡ መንደሮቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ነበሩ ። መቀመጫቸውና ፡ የትውልዳቸው ፡ መዝገቦች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 34 ፤ ምሾባብ ፡ የምሌክ ፡ የአሜስያስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮስያ ፡

---

198 ዕብ. ፡ ሆዲያህ ፡ (ይሁዲት) ።

199 ዕብ. ፡ ሳራፍ ፡ (ሰራፊ • ዐጣኝ ፡ አንዳጅ) ።

200 ዕብ. ፡ ሐሙኤል ፡ (ሕማመ ፡ ኤል • የእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፣ ሙቀት) ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 35 ፤ ኢዮኤል ፥ የዮሺብያ ፡ ልጅ ፥ የሰራያ ፡ ልጅ ፡ የዓሚኤል ፡ ልጅ ፡ ኢዩ ፥

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 36 ፤ ኤልዮዔናይ ፥ ያዕቆባ ፥ የሾሐያ ፥ ዐሳያ ፥ ዓዲዔል ፥ ዩሲምኤል ፥ በናያስ ፥

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 37 ፤ የሺፊ ፡ ልጅ ፡ ዚዛ ፥ የአሎን ፡ ልጅ ፡ የይዳያ ፡ ልጅ ፡ የሺምሪ ፡ ልጅ ፡ የሸማያ ፡ ልጅ ፤

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 38 ፤ እነዚህ ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩ ፡ በወገኖቻቸው ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ በዝተው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 39 ፤ ለመንጋዎቻቸው ፡ መሰምሪያ ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ወደጌዶር ፡ መግቢያ ፡ እስከ ፡ ሸለቆው ፡ ምሥራቅ ፡ ድረስ ፡ ኼዱ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 40 ፤ የለመለመችም ፡ እጅግም ፡ ያማረች ፡ መሰምሪያ ፡ አገኙ ፤ ምድሪቱም ፡ ሰፊና ፡ ጸጥተኛ ፡ ሰላም ፡ ያላትም ፡ ነበረች ፤ በቀድሞም ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩ ፡ ከካም ፡ ወገን ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 41 ፤ እነዚህም ፡ በስማቸው ፡ የተጻፉ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ መጥተው ፡ ድንኳኖቻቸውንና ፡ በዚያ ፡ የተገኙትን ፡ ምዑናውያንን ፡ መቱ ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ፈጽመው ፡ አጠፏቸው ፤ በዚያም ፡ ለመንጋዎቻቸው ፡ መሰምሪያ ፡ ነበረና ፡ በስፍራቸው ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 42 ፤ የስምዖንም ፡ ልጆች ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ወደሴይር ፡ ተራራ ፡ ኼዱ ፤ አለቃዎቻቸውም ፡ የይሽዒ ፡ ልጆች ፥ ፈላጥያ ፥ ነዓርያ ፥ ረፋያ ፥ ዑዝኤል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 4 ፡ 43 ፤ ያመለጡትንም ፡ የዐማሌቃውያንን ፡ ቅሬታ ፡ መቱ ፥ በዚያም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ተቀምጠዋል ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ በኵር ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ርሱ ፡ የበኵር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቱን ፡ ምንጣፍ ፡ ስላረከሰ ፡ ብኵርናው ፡ ለእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ለዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ተሰጠ ፤ ትውልዱ ፡ ግን ፡ ከብኵርና ፡ ጋራ ፡ አልተቈጠረም ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ ይሁዳም ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ በረታ ፥ አለቃም ፡ ከርሱ ፡ ኾነ ፤ ብኵርናው ፡ ግን ፡ ለዮሴፍ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ የእስራኤል ፡ በኵር ፡ የሮቤል ፡ ልጆች ፤ ሄኖኅ ፥ ፈሉስ ፥ አስሮን ፥ ከርሚ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ የኢዮኤል ፡ ልጆች ፤ ልጁ ፡ ሸማያ ፥

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ልጁ ፡ ጎግ ፥ ልጁ ፡ ሰሜኢ ፥ ልጁ ፡ ሚካ ፥

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ ልጁ ፡ ራያ ፥ ልጁ ፡ ቢኤል ፥ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ የማረከው ፡ ልጁ ፡ ብኤራ ፤ ርሱ ፡ የሮቤል ፡ ነገድ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ ወንድሞቹ ፡ በየወገናቸው ፡ የትውልዶቻቸው ፡ መዝገብ ፡ በተቈጠረ ፡ ጊዜ ፤ አንደኛው ፡ ኢዮኤል ፥

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ዘካርያስ ፥ እስከ ፡ ናባውና ፡ እስከ ፡ በዓልሜዎን ፡ ድረስ ፡ በዐሮዔር ፡ የተቀመጠው ፡ የኢዮኤል ፡ ልጅ ፡ የሸማዕ ፡ ልጅ ፡ የዾዛዝ ፡ ልጅ ፡ ቤላ ፤

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ በገለዓድ ፡ ምድር ፡ እንስሳዎቻቸው ፡ በዝተው ፡ ነበርና ፥ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ከኤፍራጥስ ፡

ወንዝ ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድረ ፡ በዳው ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጠ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ በሳኦልም ፡ ዘመን ፡ ከአጋራውያን ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፥ እነርሱም ፡ በእጃቸው ፡ ተመትተው ፡ ወደቁ ፤ በገለዓድ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ የጋድም ፡ ልጆች ፡ በባሳን ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ሰልካ ፡ ድረስ ፡ በአፋዛዣቸው ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ አንደኛው ፡ ኢዮኤል ፥ ኹለተኛው ፡ ሳፋም ፥ ያናይ ፥ ሳፋጥ ፡ በበሳን ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ወንድሞች ፡ ሚካኤል ፥ ሜሱላም ፥ ሳባ ፥ ዮራይ ፥ ያካን ፥ ዙኤ ፥ አቤድ ፡ ሰባት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ እነዚህም ፡ የቡዝ ፡ ልጅ ፡ የዬዳይ ፡ ልጅ ፡ የኢዬሳይ ፡ ልጅ ፡ የሚካኤል ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጅ ፡ የኢዳይ ፡ ልጅ ፡ የዑሪ ([201]) ፡ ልጅ ፡ የአቢካኢል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 15 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃ ፡ የጉኒ ፡ ልጅ ፡ የዐብዲኤል ([202]) ፡ ልጅ ፡ ወንድም ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 16 ፤ በገለዓድም ፡ ምድር ፡ በባሳን ፡ በመንደሮቹም ፡ በሳሮንም ፡ መሰምሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ዳርቻቸው ፡ ድረስ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 17 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በትውልዶቻቸው ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮአታም ፡ ዘመንና ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ዘመን ፡ ተቈጠሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 18 ፤ የሮቤልና ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፥ ጽኑዓን ፥ ጋሻና ፡ ሰይፍ ፡ የሚይዙ ፥ ቀስተኞችም ፥ ሰልፍ ፡ የሚያውቁ ፡ ሰልፈኞችም ፥ አርባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 19 ፤ ከአጋራውያንና ፡ ከኢጡር ፡ ከናፌስና ፡ ከናዳብ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 20 ፤ በሚዋጉበትም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸዋልና ፥ በርሱም ፡ ታምነዋልና ፥ ተለመናቸው ፤ በላያቸውም ፡ ረዳት ፡ ኾናቸው ፥ አጋራውያንና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትም ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ ተሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 21 ፤ ከከብቶቻቸውም ፡ ዐምሳ ፡ ሺሕ ፡ ግመሎች ፥ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሺሕም ፡ በጎች ፥ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ አህያዎች ፥ ከሰዎችም ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ማረኩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 22 ፤ ሰልፉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነበረና ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተገድለው ፡ ወደቁ ፤ እስከ ፡ ምርኮም ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በስፍራቸው ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 23 ፤ የምናሴ ፡ የነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ልጆች ፡ በምድሪቱ ፡ ተቀመጡ ። ከባሳንም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ በዓልአርሞንዔምና ፡ እስከ ፡ ሳኔር ፡ እስከአርሞንዔም ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ በዙ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 24 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ዔፌር ፥ ይሽዒ ፥ ኤሊኤል ፥ ዓዝርኤል ፥ ኤርምያ ፥ ሆዳይዋ ፥ ኢየድኤል ፤ እነርሱ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ የታወቁ ፡ ሰዎች ፡ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 25 ፤ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ በደሉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከፊታቸው ፡ ባጠፋቸው ፡ በምድሩ ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አመነዘሩ ።

---

201 ዕብ. ፥ ሑሪይ ።

202 ዕብ. ፥ ዐብዲኤል ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ ፥ የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

መዋ.1 ፡ 5 ፡ 26 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ የፎሐን ፡ መንፈስ ፥ የአሶርንም ፡ ንጉሥ ፡ የቴልጌልቴልፌልሶርን ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ የሮቤልንና ፡ የጋድን ፡ ልጆች ፡ የምናሴንም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ አፈለሰ ፥ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ አላሔና ፡ ወደ ፡ ኦቦር ፥ ወደ ፡ ሃራና ፡ ወደጎዛን ፡ ወንዝ ፡ አመጣቸው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 1 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፤ ጌድሶን ፥ ቀአት ፥ ሜራሪ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 2 ፤ የቀአትም ፡ ልጆች ፤ ዕምበረም ፥ ይስዓር ፥ ኬብሮን ፥ ዑዝኤል ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 3 ፤ የዕምበረምም ፡ ልጆች ፤ አሮን ፥ ሙሴ ፥ ማርያም ። የአሮን ፡ ልጆች ፤ ናዳብ ፥ አብዮድ ፥ አልዓዛር ፥ ኢታምር ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 4 ፤ አልዓዛር ፡ ፊንሐስን ፡ ወለደ ፤ ፊንሐስ ፡ አቢሱን ([203]) ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 5 ፤ አቢሱም ፡ ቡቂን ፡ ወለደ ፤ ቡቂም ፡ ዖዚን ([204]) ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ዖዚም ፡ ዘራእያን ፡ ወለደ ፤ ዘራእያም ፡ መራዮትን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 7 ፤ መራዮት ፡ አማርያን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 8 ፤ አማርያም ፡ አኪጦብን ፡ ወለደ ፤ አኪጦብም ፡ ሳዶቅን ፡ ወለደ ፤ ሳዶቅም ፡ አኪማዐስን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 9 ፤ አኪማዐስም ፡ ዐዛርያስን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ዐዛርያስም ፡ ዮሐናንን ፡ ወለደ ፤ ዮሐናንም ፡ ዐዛርያስን ፡ ወለደ ፤ ርሱም ፡ ሰሎሞን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡ ካህን ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 11 ፤ ዐዛርያስም ፡ አማርያን ፡ ወለደ ፤ አማርያም ፡ አኪጦብን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 12 ፤ አኪጦብም ፡ ሳዶቅን ፡ ወለደ ፤ ሳዶቅም ፡ ሰሎምን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 13 ፤ ሰሎምም ፡ ኬልቅያስን ፡ ወለደ ፤ ኬልቅያስም ፡ ዐዛርያስን ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ዐዛርያስም ፡ ሰራያን ፡ ወለደ ፤ ሰራያም ፡ ኢዮሴዴቅን ([205]) ፡ ወለደ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ ባስማረከ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮሴዴቅ ፡ ተማርኮ ፡ ኼደ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 16 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፤ ጌድሶን ፥ ቀአት ፥ ሜራሪ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 17 ፤ የጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሎቤኒ ፡ ሰሜኢ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 18 ፤ የቀአትም ፡ ልጆች ፤ ዕምበረም ፥ ይስዓር ፥ ኬብሮን ፥ ዑዝኤል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 19 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፤ ሞሖሊም ፥ ሙሲ ። የሌዋውያን ፡ ወገኖች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

---

203 ዕብ. ፥ አቢይሹዐ ።

204 ዕብ. ፥ ዖዚ ፡ (ዕዙዝ • ብርቱ ፥ ጠንካራ) ።

205 ዕብ. ፥ የሆ ፡ ጻዳቅ ፡ (አምላክ ፡ ያጸደቀው) ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 20 ፤ ከጌድሶን ፤ ልጁ ፡ ሎቤኒ ፥ ልጁ ፡ ኢኤት ፥ ልጁ ፡ ዛማት ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 21 ፤ ልጁ ፡ ዮአክ ፥ ልጁ ፡ አዶ ፥ ልጁ ፡ ዛራ ፥ ልጁ ፡ ያትራይ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 22 ፤ የቀአት ፡ ልጆች ፤ ልጁ ፡ ዐሚናዳብ ፥ ልጁ ፡ ቆሬ ፥ ልጁ ፡ አሴር ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 23 ፤ ልጁ ፡ ሕልቃና ፥ ልጁ ፡ አቢሣፍ ([206]) ፥ ልጁ ፡ አሴር ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 24 ፤ ልጁ ፡ ኢኢት ፥ ልጁ ፡ ኡሩኤል ፥ ልጁ ፡ ዖዝያ ፥ ልጁ ፡ ሳውል ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 25 ፤ የሕልቃናም ([207]) ፡ ልጆች ፤ ዐማሲ ፥ አኪሞት ([208]) ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 26 ፤ የሕልቃናም ፡ ልጆች ፤ ልጁ ፡ ሱፊ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 27 ፤ ልጁ ፡ ናሐት ፥ ልጁ ፡ ኤልያብ ፥ ልጁ ፡ ይሮሐም ፥ ልጁ ፡ ሕልቃና ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 28 ፤ የሳሙኤልም ፡ ልጆች ፤ በኩሩ ፡ ኢዮኤል ፥ ኹለተኛውም ፡ አብያ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 29 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፤ ሞሖሊ ፥ ልጁ ፡ ሎቤኒ ፥ ልጁ ፡ ሰሜኢ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 30 ፤ ልጁ ፡ ዖዛ ፥ ልጁ ፡ ሳምዓ ፥ ልጁ ፡ ሐግያ ፥ ልጁ ፡ ዐሳያ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 31 ፤ ዳዊትም ፡ ታቦቱ ፡ ዐርፎ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያቆማቸው ፡ የመዘምራን ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 32 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እስኪሠራ ፡ ድረስ ፡ በመገናኛ ፡ ድንኳን ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ እያዜሙ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ፤ በየተራቸውም ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 33 ፤ አገልጋዮቹና ፡ ልጆቹ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ከቀአት ፡ ልጆች ፡ ዘማሪው ፡ ኤማን ([209]) ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የኢዮኤል ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 34 ፤ የሳሙኤል ፡ ልጅ ፥ የሕልቃና ፡ ልጅ ፥ የይሮሐም ፡ ልጅ ፥ የኤሊኤል ፡ ልጅ ፥ የቶዋ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 35 ፤ የሱፍ ፡ ልጅ ፥ የሕልቃና ፡ ልጅ ፥ የመሐት ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 36 ፤ የዐማሲ ፡ ልጅ ፥ የሕልቃና ፡ ልጅ ፥ የኢዮኤል ፡ ልጅ ፥ የዐዛርያስ ፡ ልጅ ፥ የሶፎንያስ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 37 ፤ የታሐት ፡ ልጅ ፥ የአሴር ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 38 ፤ የአብያሣፍ ፡ ልጅ ፥ የቆሬ ፡ ልጅ ፥ የይስዓር ፡ ልጅ ፥ የቀአት ፡ ልጅ ፥ የሌዊ ፡ ልጅ ፥ የእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 39 ፤ በቀኙም ፡ የቆመ ፡ ወንድሙ ፡ አሣፍ ፡ ነበረ ፤ አሣፍም ፡ የበራክያ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 40 ፤ የሳምዓ ፡ ልጅ ፥ የሚካኤል ፡ ልጅ ፥ የበዓሤያ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 41 ፤ የመልክያ ፡ ልጅ ፥ የኤትኒ ፡ ልጅ ፥ የዛራ ፡ ልጅ ፥

---

206 ዕብ. ፥ ኤቢያሣፍ ።

207 ዕብ. ፥ እልቃናህ ፡ (ቀንአ ፡ እግዚአብሔር ፥ እግዚአብሔር ፡ ቀና) ።

208 ዕብ. ፥ አኒሞት ፡ (እኅወ ፡ ሞት ፥ የሞት ፡ ወንድም) ።

209 ሱር. ፥ ሃይሜን ፡ (ሃይማኒ • አማኝ) ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 42 ፤ የዓዳያ ፡ ልጅ ፥ የኤታን ፡ ልጅ ፥ የዛማት ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 43 ፤ የሰሜኢ ፡ ልጅ ፥ የኢኤት ፡ ልጅ ፥ የጌድሶን ፡ ልጅ ፥ የሌዊ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 44 ፤ በግራቸውም ፡ በኩል ፡ ወንድሞቻቸው ፡ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፤ ኤታን ፡ የቂሳ ፡ ልጅ ፥ የዐብዲ ([210]) ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 45 ፤ የማሎክ ፡ ልጅ ፥ የሐሸብያ ፡ ልጅ ፥ የአሜስያስ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 46 ፤ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፥ የአማሲ ፡ ልጅ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 47 ፤ የባኒ ፡ ልጅ ፥ የሴሜር ፡ ልጅ ፥ የሞሖሊ ፡ ልጅ ፥ የሙሲ ፡ ልጅ ፥ የሜራሪ ፡ ልጅ ፥ የሌዊ ፡ ልጅ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 48 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ሌዋውያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ማደሪያ ፡ አገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ ተሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 49 ፤ አሮንና ፡ ልጆቹ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘው ፡ ኹሉ ፡ ለቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እስራኤልም ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ፥ በዕጣኑም ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ያጥኑ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 50 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ልጁ ፡ አልዓዛር ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 51 ፤ ልጁ ፡ ፊንሐስ ፥ ልጁ ፡ አቢሱ ፥ ልጁ ፡ ቡቂ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 52 ፤ ልጁ ፡ ዖዚ ፥ ልጁ ፡ ዘራእያ ፥ ልጁ ፡ መራዮት ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 53 ፤ ልጁ ፡ አማርያ ፥ ልጁ ፡ አኪጦብ ፥ ልጁ ፡ ሳዶቅ ፥ ልጁ ፡ አኪማዐስ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 54 ፤ ማደሪያዎቻቸውም ፡ በየሰፈራቸው ፡ በየዳርቻቸው ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ለቀአት ፡ ወገኖች ፡ አንደኛው ፡ ዕጣ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 55 ፤ ለእነርሱ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ያለችውን ፡ ኬብሮንን ፥ በርሷም ፡ ዙሪያ ፡ የነበረውን ፡ መሰምሪያ ፡ ሰጡ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 56 ፤ የከተማዪቱን ፡ ዕርሻ ፡ ግን ፡ መንደሮቿንም ፡ ለዮፎኒ ፡ ልጅ ፡ ለካሌብ ፡ ሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 57 ፤ ለአሮንም ፡ ልጆች ፡ የመማፀኛውን ፡ ከተማዎች ፥ ኬብሮንን ፥ ልብናንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ደግሞ ፡ የቲርን ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 58 ፤ ኤሽትሞዐንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ሖሎንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዳቤርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 59 ፤ ዓሳንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ቤትሳሚስንና ፡ መሰምሪያዋን ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 60 ፤ ከብንያምም ፡ ነገድ ፡ ጌባንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ጋሌማትንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዐናቶትንና ፡ መሰምሪያዋን ፡ ሰጡ ። ከተማዎቻቸው ፡ ኹሉ ፡ በየወገናቸው ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 61 ፤ ለቀሩትም ፡ ለቀአት ፡ ልጆች ፡ ከነገዱ ፡ ወገን ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ዐሥር ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ተሰጡ ።

---

210 ዕብ. ፥ ዐብዲይ ፥ (ዐብድ ፥ አገልጋይ) ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 62 ፤ ለጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፥ ከአሴርም ፡ ነገድ ፥ ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ፥ በባሳንም ፡ ካለው ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፥ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ተሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 63 ፤ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡ በየወገናቸው ፡ ከሮቤል ፡ ነገድ ፥ ከጋድም ፡ ነገድ ፥ ከዛብሎንም ፡ ነገድ ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ተሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 64 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ለሌዋውያን ፡ ከተማዎችን ፡ ከመሰምሪያዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 65 ፤ ከይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፥ ከስምዖንም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፥ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፥ እነዚህን ፡ በስማቸው ፡ የተጠሩትን ፡ ከተማዎች ፡ በዕጣ ፡ ሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 66 ፤ ከቀአትም ፡ ልጆች ፡ ወገኖች ፡ ለአንዳንዶቹ ፡ ከኤፍሬም ፡ ነገድ ፡ ከተማዎች ፡ ድርሻ ፡ ነበራቸው ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 67 ፤ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ የመማፀኛውን ፡ ከተማዎች ፡ ሴኬምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ደግሞም ፡ ጌዝርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ዮቅምዓምንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 68 ፤ ቤትሖሮንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 69 ፤ ኤሎንንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ጋትሪሞንንና ፡ መሰምሪያዋን ፡ ሰጧቸው ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 70 ፤ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ዐኔርንና ፡ መሰምሪያዋን ፥ ቢልዓምንና ፡ መሰምሪያዋን ፡ ከቀአት ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ለቀሩት ፡ ሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 71 ፤ ለጌድሶን ፡ ልጆች ፡ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ወገን ፡ በባሳን ፡ ያለችው ፡ ጎላንና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ዐስታሮትና ፡ መሰምሪያዋ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 72 ፤ ከይሳኮርም ፡ ነገድ ፡ ቃዴስና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ዳብራትና ፡ መሰምሪያዋ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 73 ፤ ራሞትና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ዐኔምና ([211]) ፡ መሰምሪያዋ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 74 ፤ ከአሴርም ፡ ነገድ ፡ መዓሳልና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ዐብዶንና ፡ መሰምሪያዋ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 75 ፤ ሑቆቅና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ረአብና ፡ መሰምሪያዋ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 76 ፤ ከንፍታሌምም ፡ ነገድ ፡ በገሊላ ፡ ያለችው ፡ ቃዴስና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ሐሞንና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ቂርያታይምና ፡ መሰምሪያዋ ፡ ተሰጡ ።

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 77 ፤ ከሌዋውያን ፡ ለቀሩት ፡ ለሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ ሬሞንና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ታቦርና ፡ መሰምሪያዋ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 78 ፤ ከሮቤልም ፡ ነገድ ፡ በኢያሪኮ ፡ አንጻር ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያለችው ፡ ቦሶርና ፡ መሰምሪያዋ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 79 ፤ ያሳና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ቅዴሞትና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ሜፍዓትና ፡ መሰምሪያዋ ፤

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 80 ፤ ከጋድም ፡ ነገድ ፡ በገለዓድ ፡ ያለችው ፡ ሬማትና ፡ መሰምሪያዋ ፥ መሃናይምና ፡ መሰምሪያዋ ፥

መዋ.1 ፡ 6 ፡ 81 ፤ ሐሴቦንና ፡ መሰምሪያዋ ፥ ኢያዜርና ፡ መሰምሪያዋ ፡ ተሰጡ ።

---

211 ዕብ. ፥ ዐኔም ፡ (አዕይንት • ምንጮች) ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 1 ፤ የይሳኮርም ፡ ልጆች ፥ ቶላ ፥ ፉዋ ፥ ያሱብ ፡ ሺምሮን ፥ አራት ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 2 ፤ የቶላም ፡ ልጆች ፥ ዖዚ ፥ ራፋያ ፥ ይሪኤል ፥ የሕማይ ፥ ይብሣም ፥ ሽሙኤል ፥ የአባታቸው ፡ የቶላ ፡ ቤት ፡ አለቃዎች ፥ በትውልዳቸው ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ በዳዊት ፡ ዘመን ፡ ቍጥራቸው ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 3 ፤ የዖዚም ፡ ልጆች ፡ ይዝረሕያ ፤ የይዝረሕያም ፡ ልጆች ፡ ሚካኤል ፥ ዐብድዩ ፥ ኢዮኤል ፥ ይሺያ ፡ ዐምስት ፡ ናቸው ፤ ኹሉም ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ በየትውልዳቸው ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ለሰልፍ ፡ የተዘጋጁ ፡ የሰራዊት ፡ ጭፍራዎች ፡ ነበሩ ፤ ብዙም ፡ ሴቶችና ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸውና ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 5 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ በይሳኮር ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ በትውልዳቸው ፡ ኹሉ ፡ የተቈጠሩ ፡ ሰማንያ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 6 ፤ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ቤላ ፥ ቤኬር ፥ ይዲኤል ([212]) ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 7 ፤ የቤላም ፡ ልጆች ፥ ኤሴቦን ፥ ዖዚ ፥ ዑዝኤል ፥ ኢያሪሙት ፥ ዒሪ ፥ ዐምስት ፡ ነበሩ ፤ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ በትውልድ ፡ የተቈጠሩ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሠላሳ ፡ አራት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 8 ፤ የቤኬርም ፡ ልጆች ፤ ዝሚራ ፥ ኢዮአስ ፥ አልዓዛር ፥ ኤልዮዔናይ ፥ ዖምሪ ፥ ኢያሪሙት ፥ አብያ ፥ ዐናቶት ፥ ዓሌሜት ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የቤኬር ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 9 ፤ በየትውልዳቸው ፡ መዝገብ ፡ የተቈጠሩ ፥ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 10 ፤ የይዲኤልም ፡ ልጅ ፡ ቢልሐን ፡ ነበረ ፤ የቢልሐንም ፡ ልጆች ፡ የዑስ ፥ ብንያም ፥ ኤሑድ ([213]) ፥ ክንዓና ([214]) ፥ ዜታን ([215]) ፥ ተርሴስ ([216]) ፥ አኪሳአር ([217]) ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 11 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የይዲኤል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፤ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ ጭፍራ ፡ እየኾኑ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጡ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 12 ፤ ደግሞም ፡ ሳፊን ፥ ሑፊም ፡ የዒር ፡ ልጆች ፥ ሑሺም ፡ የአሔር ፡ ልጆችም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 13 ፤ የንፍታሌም ፡ ልጆች ፥ ያሕጽኤል ፥ ጉኒ ፥ ዬጽር ፥ ሺሌም ፥ የባላ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 14 ፤ የምናሴ ፡ ልጆች ፡ ሶርያዊቱ ፡ ቁባቱ ፡ የወለደችለት ፡ እስርኤልና ፡ የገለዓድ ፡ አባት ፡ ማኪር ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፥ 7 ፥ 15 ፤ ማኪርም ፡ ከሑፊምና ፡ ከሳፊን ፡ ወገን ፡ ሚስት ፡ አገባ ፤ የእኅቷም ፡ ስም ፡ መዓካ ፡

---

212 ዕብ. ፥ ይድያዕኤል ፡ (የድዐ ፡ እግዚአ ፥ ጌታን ፡ ዐወቀ / ደዐተ ፡ እግዚእ ፥ ጌታን ፡ ማወቅ) ።
213 ዕብ. ፥ ኤሑድ ፡ (ዋሕድ • አንድያ) ።
214 ዕብ. ፥ ክንዓና ፡ (የ'ከነዓን' ፡ አንስት ፥ ነጋዴ) ።
215 ዕብ. ፥ ዘይታን ፡ (ወይራ) ።
216 ዕብ. ፥ ተርሺሽ ፡ (ስመ ፡ ዕንቍ) ።
217 ዕብ. ፥ አኒሸሐር ፡ (እኅወ ፡ ጽባሕ ፥ የንጋት ፡ ወንድም) ።

ነበረ ፤ የኹለተኛውም ፡ ስም ፡ ሰለጻአድ ፡ ነበረ ፤ ለሰለጻዓድም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 16 ፤ የማኪርም ፡ ሚስት ፡ መዓካ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፥ ስሙንም ፡ ፋሬስ ፡ ብላ ፡ ጠራችው ፤ የወንድሙም ፡ ስም ፡ ሱሮስ ፡ ነበረ ፤ ልጆቹም ፡ ኡላም ፥ ራቄም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 17 ፤ የኡላምም ፡ ልጅ ፡ ባዳን ፡ ነበረ ፤ እነዚህ ፡ የምናሴ ፡ ልጅ ፡ የማኪር ፡ ልጅ ፡ የገለዓድ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 18 ፤ እኅቱ ፡ መለኬት ፡ ኢሱድን ፥ አቢዔዝርን ፥ መሕላን ፡ ወለደች ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 19 ፤ የሸሚዳም ፡ ልጆች ፡ አኒያን ፥ ሴኬም ፥ ሊቅሒ ፥ አኒዐም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 20 ፤ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፤ ሹቱላ ፥ ልጁ ፡ ባሬድ ፥ ልጁ ፡ ታሐት ፥ ልጁ ፡ ኤልዓዳ ፥ ልጁ ፡ ታሐት ፥ ልጁ ፡ ዛባድ ፥ ልጁ ፡ ሹቱላ ፥

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 21 ፤ የአገሩም ፡ ተወላጆች ፡ የጌት ፡ ሰዎች ፡ ከብቶቻቸውን ፡ ሊወስዱ ፡ ወርደው ፡ ነበርና ፥ የገደሏቸው ፡ ልጆቹ ፡ ኤድርና ፡ ኤልዓድ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 22 ፤ አባታቸውም ፡ ኤፍሬም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ አለቀሰ ፥ ወንድሞቹም ፡ ሊያጽናኑት ፡ መጡ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ ሚስቱም ፡ ገባ ፥ አረገዘችም ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ፤ በቤቱም ፡ መከራ ፡ ኾኗልና ፥ ስሙ ፡ በሪዐ ([218]) ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 24 ፤ ሴት ፡ ልጁም ፡ ታችኛውንና ፡ ላይኛውን ፡ ቤትሖሮንንና ፡ ኡዜንሼራን ፡ የሠራች ፡ ሲአራ ፡ ነበረች ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 25 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቹም ፡ ፋፈ ፥ ሬሴፍ ፥ ልጁ ፡ ቴላ ፥

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 26 ፤ ልጁ ፡ ታሐን ፥ ልጁ ፡ ለአዳን ፥ ልጁ ፡ ዐሚሁድ ፥ ልጁ ፡ ኤሊሳማ ፥

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 27 ፤ ልጁ ፡ ነዌ ፥ ልጁ ፡ ኢያሱ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 28 ፤ ግዛታቸውና ፡ ማደሪያቸው ፡ ቤቴልና ፡ መንደሮቿ ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ነዓራን ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ጌዝርና ፡ መንደሮቿ ፥ ደግሞ ፡ ሴኬምና ፡ መንደሮቿ ፡ እስከ ፡ ጋዛና ፡ እስከ ፡ መንደሮቿ ፡ ድረስ ፥

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 29 ፤ በምናሴም ፡ ልጆች ፡ ዳርቻ ፡ ቤትሳንና ፡ መንደሮቿ ፥ ታዕናክና ፡ መንደሮቿ ፥ መጊዶና ፡ መንደሮቿ ፥ ዶርና ፡ መንደሮቿ ፡ ነበሩ ፤ በእነዚህ ፡ የእስራኤል ፡ ልጅ ፡ የዮሴፍ ፡ ልጆች ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 30 ፤ የአሴር ፡ ልጆች ፡ ዩምና ፥ የሱዋ ፥ የሱዊ ፥ በሪዐ ፥ እኅታቸውም ፡ ሜራሕ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 31 ፤ የበሪዐም ፡ ልጆች ፤ ሔቤር ፥ የቢርዛዊት ፡ አባት ፡ የነበረው ፡ መልኪኤል ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 32 ፤ ሔቤርም ፡ ያፍሌጥን ([219]) ፥ ሳሜርን ፥ ኮታምን ([220]) ፥ እኅታቸውንም ፡ ሶላን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 33 ፤ የያፍሌጥም ፡ ልጆች ፡ ፋሴክ ፥ ቢምኻል ፥ ዐሲት ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ የያፍሌጥ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

---

218 ዕብ. ፥ በርዓያህ ፡ (በርዐ • ራደ) ።

219 ዕብ. ፥ ያፍሌጥ ፡ (ይፈልጥ • ይለያል ፥ ለይቶ ፡ ያድናል) ።

220 ዕብ. ፥ ኖታም ፡ (ማኅተም • በቁሙ ፥ ማተሚያ) ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 34 ፤ የሳሜርም ፡ ልጆች ፡ አኪ ፡ ሮኦጋ ፡ ይሑባ ፡ አራም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 35 ፤ የወንድሙም ፡ የዔላም ፡ ልጆች ፡ ጾፋ ፡ ይምና ፡ ሰሌስ ፡ ዓማል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 36 ፤ የጾፋም ፡ ልጆች ፡ ሱዋ ፡ ሐርኔፍር ፡

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 37 ፤ ሦጋል ፡ ቤሪ ፡ ይምራ ፡ ቤዼር ፡ ሖድ ፡ ሳማ ፡ ሰሊሳ ፡ ይትራን ፡ ብኤራ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 38 ፤ የዬቴር ፡ ልጆች ፡ ዮሮኒ (221) ፡ ፈሥጻ ፡ አራ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 39 ፤ የዑላ ፡ ልጆች ፡ ኤራ ፡ ሐኒኤል ፡ ሪጽያ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 7 ፡ 40 ፤ እነዚህ ፡ ዥሉ ፡ የአሴር ፡ ልጆች ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ የተመረጡ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ የመኳንንቱ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ። በትውልዳቸውም ፡ በሰልፍ ፡ ለመዋጋት ፡ የተቈጠሩ ፡ ኻያ ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 8 ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 1 ፤ ብንያምም ፡ በኵሩን ፡ ቤላን ፡ ኹለተኛውንም ፡ አስቤልን ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 2 ፤ ሦስተኛውንም ፡ አሐራን (222) ፡ አራተኛውንም ፡ ኖሐን ፡ ዐምስተኛውንም ፡ ራፋን (223) ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 3 ፤ ለቤላም ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ አዖር ፡ ጌራ ፡ አቢሁድ ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 4 ፤ አቢሱ ፡ ናዕማን ፡ አኖዋ (224) ፡ ጌራ ፡ ሰፉፋም ፡ ሑራም ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 5-6 ፤ እነዚህም ፡ የኤሑድ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ በጌባ ፡ የሚቀመጡ ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ወደ ፡ መናሐትም ፡ ተማረኩ ፤ ናዕማን ፡ አኪያ ፡ ጌራ ፡ እነርሱም ፡ ተማረኩ ። ዖዛንና ፡ አኒሁድን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 8 ፤ ሻሐራይምም ፡ ሚስቶቹን ፡ ሑሺምንና ፡ በዕራን ፡ ከሰደደ ፡ በኋላ ፡ በሞዐብ ፡ ሜዳ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 9 ፤ ከሚስቱ ፡ ከሖዴሽ ፡ ዮባብን ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 10 ፤ ዲብያን ፡ ማሴን ፡ ማልካምን ፡ ይዑጽን ፡ ሻክያን ፡ ሚርማን ፡ ወለደ ። እነዚህም ፡ ልጆች ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 11 ፤ ከሑሺምም ፡ አቢጡብንና (225) ፡ ኤልፍዓልን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 12 ፤ የኤልፍዓልም ፡ ልጆች ፤ ዔቤር ፡ ሚሻም ፡ ኦኖንና ፡ ሎድን ፡ መንደሮቻቸውንም ፡ የሠራ ፡ ሻሚድ ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 13 ፤ በሪዐ ፡ ሽማዕ ፡ የጌትን ፡ ሰዎች ፡ ያሳደዱ ፡ የኤሎን ፡ ሰዎች ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡

---

221 ዕብ. ፡ የፉኔህ ፡ (ይዘጋጃል) ።

222 ዕብ. ፡ አኅራኅ ፡ (አኃሬ ፡ አኅው • የወንድም ፡ ተከታይ) ።

223 ዕብ. ፡ ራፋ ፡ (ረፋኢ • ፈዋሽ)

224 ዕብ. ፡ አኖአኅ ፡ (ወንድማማች) ።

225 የመልካም ፡ አባት ።

ነበሩ ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 14 ፤ አኒዮ ፡ ሻሻቅ ፡ ይሬምት ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 15 ፤ 16 ፤ ዝባድያ ፡ ዓራድ ፡ ዔድር ፡ ሚካኤል ፡ ይሽጳ ፡ ዮሐ ፡ የበሪዐ ፡ ልጆች ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 17 ፤ ዝባድያ ፡ ሜሱላም ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 18 ፤ ሕዝቂ ፡ ሔቤር ፡ ይሽምራይ ፡ ይዝሊያ ፡ ዮባብ ፡ የኤልፍዓል ፡ ልጆች ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 19 ፤ ያቂም ፡ ዝክሪ ፡ ዘብዲ ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 20 ፤ 21 ፤ ኤሊዔናይ ፡ ጺልታይ ፡ ኤሊኤል ፡ ዓዳያ ፡ ብራያ ፡ ሺምራት ፡ የሰሜኢ ፡ ልጆች ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 22 ፤ ይሽጳን ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 23 ፤ ዔቤር ፡ ኤሊኤል ፡ ዐብዶን ፡ ዝክሪ ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 24 ፤ 25 ፤ ሐናን ፡ ሐናንያ ፡ ዔላም ፡ ዐንቶትያ ([226]) ፡ ይፍዴያ ፡ ፋኑኤል ፡ የሶሴቅ ፡ ልጆች ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 26 ፤ ሸምሸራይ ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 27 ፤ ሸሃሪያ ፡ ጎቶልያ ፡ ያሬሽያ ፡ ኤልያስ ፡ ዝክሪ ፡ የይሮሐም ፡ ልጆች ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 28 ፤ እነዚህ ፡ በትውልዶቻቸው ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ፤ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 29 ፤ የሚስቱ ፡ ስም ፡ መዓካ ፡ የነበረው ፡ የገባዖን ፡ አባት ፡ ይዒኤል ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 30 ፤ የበኩር ፡ ልጁ ፡ ዐብዶን ፡

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 31 ፤ ዱር ፡ ቂስ ፡ በዓል ፡ ናዳብ ፡ ጌዶር ፡ አኒዮ ፡ ዛኩር ፡ በገባዖን ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 32 ፤ ሚቅሎት ፡ ሳምአን ፡ ወለደ ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 33 ፤ ኔር ፡ ቂስን ፡ ወለደ ፤ ቂስም ፡ ሳኦልን ፡ ወለደ ፤ ሳኦልም ፡ ዮናታንን ፡ ሚልኪሳን ፡ ዐሚናዳብን ([227]) ፡ አስበዓልን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 34 ፤ የዮናታንም ፡ ልጅ ፡ መሪበዓል ፡ ነበረ ፤ መሪበዓልም ፡ ሚካን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 35 ፤ የሚካም ፡ ልጆች ፡ ፒቶን ፡ ሜሌክ ፡ ታሬዓ ፡ አካዝ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 36 ፤ አካዝም ፡ ይሆዓዳን ፡ ወለደ ፤ ይሆዓዳም ፡ ዓሌሜትን ፡ ዓዝሞትን ፡ ዘምሪን ፡ ወለደ ፤ ዘምሪም ፡ ሞጻን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 37 ፤ ሞጻም ፡ ቢንዓን ፡ ወለደ ፤ ልጁም ፡ ረፋያ ፡ ነበረ ፡ ልጁ ፡ ኤልዓሣ ፡ ልጁ ፡ ኤሴል ፤

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 38 ፤ ለኤሴልም ፡ ስድስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ስማቸውም ፡ ይህ ፡

---

226 ዕብ. ፡ ዐንቶትያህ ፡ (የጌታ ፡ መልሶች) ።

227 ዕብ. ፡ አቢናዳብ ፤ አለዚያም ፡ ዐሚናዳብ ፡ (ከ.ወ.ክ. ፡ 627) ።

ነበረ ፤ ዐዝሪቃም ፥ ቦክሩ ፥ እስማኤል ፥ ሸዓርያ ፥ ዐብድዩ ፥ ሐናን ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የኤሴል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 39 ፤ የወንድሙም ፡ የአሴል ፡ ልጆች ፤ በኵሩ ፡ ኡላም ፥ ኹለተኛውም ፡ ኢያስ ፥ ሦስተኛውም ፡ ኤሊፋላት ።

መዋ.1 ፡ 8 ፡ 40 ፤ የኡላም ፡ ልጆች ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላንና ፡ ቀስተኞች ፡ ነበሩ ፤ ለእነርሱም ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ የሚያኽሉ ፡ ብዙ ፡ ልጆችና ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ነበሯቸው ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 1 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በየትውልዳቸው ፡ ተቈጠሩ ፤ እንሆም ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፈዋል ። ይሁዳም ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ተማረኩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 2 ፤ በአውራጃዎቻቸውና ፡ በከተማዎቻቸው ፡ መገመሪያ ፡ የተቀመጡ ፡ እስራኤልና ፡ ካህናት ፡ ሌዋውያንም ፡ ናታኒምም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 3 ፤ ከይሁዳ ፡ ልጆችና ፡ ከብንያም ፡ ልጆች ፡ ከኤፍሬምና ፡ ከምናሴ ፡ ልጆች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 4 ፤ ከይሁዳ ፡ ልጅ ፡ ከፋሬስ ፡ ልጆች ፡ የባኒ ፡ ልጅ ፡ የአምሪ ፡ ልጅ ፡ የዖምሪ ፡ ልጅ ፡ የዐሚሁድ ፡ ልጅ ፡ ዑታይ ፡ ደግሞ ፡ ተቀመጠ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 5 ፤ ከሴሎናውያንም ፡ በኵሩ ፡ ዐሣያና ፡ ልጆቹ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 6 ፤ ከዛራም ፡ ልጆች ፡ ይዑኤልና ፡ ወንድሞቻቸው ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 7 ፤ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ የሐስኑአ ፡ ልጅ ፡ የሆዳይዋ ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ ሰሉ ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 8 ፤ የይሮሐም ፡ ልጅ ፡ ብኔያ ፤ የሚክሪ ፡ ልጅ ፡ የዖዚ ፡ ልጅ ፡ ኤላ ፤ የዩብኒያ ፡ ልጅ ፡ የራጉኤል ፡ ልጅ ፡ የሰፋጥያስ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 9 ፤ በየትውልዳቸውም ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ኀምሳ ፡ ስድስት ፡ ነበሩ ፤ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ከካህናቱም ፡ ዮዳዔ ፥ ዮአሪብ ፥ ያኪን ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ የመራዮት ፡ ልጅ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ ልጅ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 12 ፤ የመልኪያ ፡ ልጅ ፡ የጳስኮር ፡ ልጅ ፡ የይሮሐም ፡ ልጅ ፡ ዓዳያ ፤ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ የምሺላሚት ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ የየሕዜራ ፡ ልጅ ፡ የዓዲኤል ፡ ልጅ ፡ መዕሣይ ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 13 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነበሩ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ማገልገል ፡ ሥራ ፡ እጅግ ፡ ብልኀተኞች ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 14 ፤ ከሌዋውያንም ፡ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ የዐሳብያ ([228]) ፡ ልጅ ፡ የዐዝሪቃም ፡ ልጅ ፡ የዐሱብ ([229]) ፡ ልጅ ፡ ሸማያ ፤

---

228 ዕብ. ፥ ሐሻብያህ ፡ (ሐሰቦ ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ዐሰበው) ።

229 ዕብ. ፥ ሐሹብ ፡ (ሐሳቢ • ዐሳቢ) ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 15 ፤ በቅበቃር ፥ ዔሬስ ([230]) ፥ ጋላል ፥ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ የሚካ ፡ ልጅ ፡ መታንያ ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 16 ፤ የኤዶታም ፡ ልጅ ፡ የጋላል ፡ ልጅ ፡ የሰሙስ ፡ ልጅ ፡ ዐብድያ ([231]) ፤ በነጦፋውያንም ፡ መንደሮች ፡ የተቀመጠው ፡ የሕልቃና ፡ ልጅ ፡ የአሣ ፡ ልጅ ፡ በራክያ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 17 ፤ በረኞችም ፡ ሰሎም ፥ ዐቁብ ፥ ጤልሞን ፥ አኒማን ፥ ወንድሞቻቸውም ፡ ነበሩ ፤ ሰሎምም ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 18 ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ በንጉሥ ፡ በር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ነበሩ ፤ ለሌዊ ፡ ልጆች ፡ ሰፈር ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 19 ፤ የቆሬም ፡ ልጅ ፡ የአብያሣፍ ፡ ልጅ ፡ የቆሬ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ከአባቱም ፡ ቤት ፡ የነበሩ ፡ ወንድሞቹ ፡ ቆሬያውያን ፡ በማገልገል ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ነበሩ ፥ የድንኳኑንም ፡ መድረክ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ። አባቶቻቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰፈር ፡ መግቢያ ፡ ጠብቀው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 20 ፤ አስቀድሞም ፡ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፡ ፊንሐስ ፡ አለቃቸው ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 21 ፤ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ፡ የመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ደጅ ፡ በረኛ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 22 ፤ የመድረኩ ፡ በረኞች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ የተመረጡ ፡ እነዚህ ፡ ኾሉ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ። ዳዊትና ፡ ነቢዩ ፡ ሳሙኤል ፡ በሥራቸው ፡ ያቆሟቸው ፡ እነዚህ ፡ በመንደሮቻቸው ፡ በየትውልዳቸው ፡ ተቈጠሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 23 ፤ እነርሱና ፡ ልጆቻቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በድንኳኑ ፡ ደጆች ፡ ላይ ፡ ዘበኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 24 ፤ በአራቱ ፡ ማእዘኖች ፥ በምሥራቅ ፥ በምዕራብ ፥ በሰሜን ፥ በደቡብ ፥ በረኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 25 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ በመንደሮቻቸው ፡ ኾነው ፥ በየሰባትም ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሊኾኑ ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ ይገቡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 26 ፤ ከሌዋውያንም ፡ የነበሩ ፡ አራቱ ፡ የበረኞች ፡ አለቃዎች ፡ ዘወትር ፡ በሥራቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ባሉ ፡ ጓዳዎችና ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 27 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ የሚጠብቁ ፥ ጧት ፡ ጧትም ፡ ደጆቹን ፡ የሚከፍቱ ፡ እነርሱ ፡ ነበሩና ፥ በዚያ ፡ ያድሩ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 28 ፤ ዕቃውም ፡ በቀጥር ፡ ይገባና ፡ ይወጣ ፡ ነበርና ፥ ከነዚህ ፡ አንዳንዱ ፡ በማገልገያው ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ ሹሞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 29 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በመቅደሱ ፡ ዕቃ ፡ ኾሉ ፡ በመልካሙም ፡ ዱቄት ፥ በወይን ፡ ጠጁ ፥ በዘይቱም ፥ በዕጣኑም ፥ በሽቱውም ፡ ላይ ፡ ሹሞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 30 ፤ ከካህናቱም ፡ ልጆች ፡ አንዳንዶቹ ፡ የሽቱውን ፡ ቅባት ፡ ያጣፍጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 31 ፤ የቆሬያዊውም ፡ የሰሎም ፡ በኵር ፡ ሌዋዊው ፡ ማቲትያ ፡ በምጣድ ፡ በሚጋገረው ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሹም ፡ ነበረ ።

---

230 ዕብ. ፥ ሔሬሽ ።

231 ዕብ. ፥ ዖባድያህ ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ ፥ የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 32 ፤ በየሰንበቱም ፡ ያዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ከቀአታውያን ፡ አንዳንዱ ፡ በገጹ ፡ ኅብስት ፡ ላይ ፡ ሹሞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 33 ፤ ከሌዋውያኑም ፡ ወገን ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ የነበሩ ፡ መዘምራን ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ሥራቸውም ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ነበረና ፡ ያለሌላ ፡ ሥራ ፡ በየጓዳቸው ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 34 ፤ እነዚህ ፡ ከሌዋውያን ፡ የአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ በየትውልዳቸው ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 35 ፤ የሚስቱ ፡ ስም ፡ መዓካ ፡ የነበረው ፡ የገባዖን ፡ አባት ፡ ይዒኤል ፥

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 36 ፤ የበኩር ፡ ልጁም ፡ ዐብዶን ፥

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 37 ፤ ጹር ፥ ቂስ ፥ በዓል ፥ ኔር ፥ ናዳብ ፥ ጌዶር ፥ አኒዮ ፥ ዛኩር ፥ ሚቅሎት ፥ በገባአን ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 38 ፤ ሚቅሎትም ፡ ሳምአን ፡ ወለደ ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 39 ፤ ኔርም ፡ ቂስን ፡ ወለደ ፤ ቂስም ፡ ሳኦልን ፡ ወለደ ፤ ሳኦልም ፡ የዮናታንን ፥ ሚልኪሳን ፥ ዐሚናዳብን ፥ አስበዓልን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 40 ፤ የዮናታንም ፡ ልጅ ፡ መሪበዓል ፡ ነበረ ፤ መሪበዓልም ፡ ሚካን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 41 ፤ የሚካም ፡ ልጆች ፡ ፲ቶን ፥ ሜሌክ ፥ ታሬዓ ፥ አካዝ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 42 ፤ አካዝም ፡ የዕራን ፡ ወለደ ፤ የዕራም ፡ ዓሌሜትን ፥ ዓዝሞትን ፥ ዘምሪን ፡ ወለደ ፤ ዘምሪም ፡ ሞጻን ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 43 ፤ ሞጻም ፡ ቢንዓን ፡ ወለደ ፥ ልጁም ፡ ረፋያ ፡ ነበረ ፥ ልጁ ፡ ኤልዓሣ ፥ ልጁ ፡ ኤሴል ፤

መዋ.1 ፡ 9 ፡ 44 ፤ ለኤሴልም ፡ ስድስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ስማቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ዐዝሪቃም ፥ ቦክሩ ፥ እስማኤል ፥ ሸዓሪያ ፥ ዐብድዩ ፥ ሐናን ፤ እነዚህ ፡ የኤሴል ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 1 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ ተወግተውም ፡ በጊልቦአ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወደቁ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 2 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሳኦልንና ፡ ልጆቹን ፡ በእግር ፡ በእግራቸው ፡ ተከትለው ፡ አባረሯቸው ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ የሳኦልን ፡ ልጆች ፡ ዮናታንንና ፡ ዐሚናዳብን ፡ ሜልኪሳንም ፡ ገደሉ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 3 ፤ ሰልፍም ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ ጠነከረ ፥ ቀስተኞችም ፡ አገኙት ፤ ከቀስተኞችም ፡ የተነሣ ፡ ተጨነቀ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 4 ፤ ሳኦልም ፡ ጋሻ ፡ ጭግሬውን ፦ እነዚህ ፡ ቈላፋን ፡ መጥተው ፡ እንዳይዘብቱብኝ ፡ ሰይፍኽን ፡ መዘ፡ኽ ፡ ውጋኝ ፡ አለው ። ጋሻ ፡ ጭግሬው ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ፈርቶ ፡ ነበርና ፥ እንቢ ፡ አለ ። ሳኦልም ፡ ሰይፉን ፡ ወስዶ ፡ በላዩ ፡ ወደቀ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 5 ፤ ጋሻ ፡ ጭግሬውም ፡ ሳኦል ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በሰይፉ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሞተ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 6 ፤ ሳኦልና ፡ ሦስቱ ፡ ልጆቹ ፡ የቤቱም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 7 ፤ በሸለቆውም ፡ የነበሩት ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሸሹ ፥ ሳኦልና ፡ ልጆቹም ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከተማዎቻቸውን ፡ ለቀው ፡ ሸሹ ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ ተቀመጡባቸው ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 8 ፤ በነጋውም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ የሞቱትን ፡ ለመግፈፍ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሳኦልንና ፡ ልጆቹን ፡ በጊልቦአ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ አገኟቸው ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 9 ፤ ገፈፉትም ፥ ራሱንና ፡ መሣሪያውንም ፡ አንሥተው ፡ ለጣዖቶቻቸውና ፡ ለሕዝቡ ፡ የምሥራች ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደፍልስጥኤማውያን ፡ አገር ፡ ዙሪያ ፡ ሰደዱ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 10 ፤ መሣሪያውንም ፡ በአምላኮቻቸው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖሩ ፤ ራሱንም ፡ በዳጎን ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ቸነከሩት ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 11 ፤ የኢያቢስ ፡ ገለዓድም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ በሳኦል ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፡ ኹሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ጽኑአን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ተነሥተው ፡ የሳኦልን ፡ ሬሳ ፡ የልጆቹንም ፡ ሬሳ ፡ ወሰዱ ፥ ወደ ፡ ኢያቢስም ፡ አመጧቸው ፤ በኢያቢስም ፡ ካለው ፡ ከትልቁ ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ ዐጥንቶቻቸውን ፡ ቀበሩ ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ጾሙ ።

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 13 ፤ እንዲሁ ፡ ሳኦል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ስላደረገው ፡ ኀጢአት ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ስላልጠበቀ ፡ ሞተ ። ደግሞም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪ ፡

መዋ.1 ፡ 10 ፡ 14 ፤ ስለ ፡ ጠየቀ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ስላልጠየቀ ፥ ስለዚህ ፡ ገደለው ፥ መንግሥቱንም ፡ ወደእሴይ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ አሳለፈው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 1 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በኬብሮን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ተሰብስበው ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ የዐጥንትኽ ፡ ፍላጭ ፡ የሥጋኽ ፡ ቍራጭ ፡ ነን ፤

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 2 ፤ አስቀድሞ ፡ ሳኦል ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ እስራኤልን ፡ የምታወጣና ፡ የምታገባ ፡ አንተ ፡ ነበርኽ ፤ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔርም ፦ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ አንተ ፡ ትጠብቃለኽ ፤ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትኾናለኽ ፡ ብሎኽ ፡ ነበር ፡ አሉት ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ፤ ዳዊትም ፡ በኬብሮን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አደረገ ፤ በሳሙኤልም ፡ እጅ ፡ እንደተናገረው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ ቀቡት ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ኢያቡስ ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኼዱ ፤ በአገሩም ፡ የተቀመጡ ፡ ኢያቡሳውያን ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 5 ፤ በኢያቡስም ፡ የተቀመጡ ፡ ዳዊትን ፦ ወደዚህ ፡ አትገባም ፡ አሉት ፤ ዳዊት ፡ ግን ፡ ዐምባዩቱን ፡ ጽዮንን ፡ ያዘ ፤ ርሷም ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ናት ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፦ ኢያቡሳውያንን ፡ አስቀድሞ ፡ የሚመታ ፡ ሰው ፡ አለቃና ፡ መኰንን ፡ ይኾናል ፡ አለ ። የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ አስቀድሞ ፡ ወጣ ፥ አለቃም ፡ ኾነ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ በዐምባዩቱ ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጠ ፤ ስለዚህም ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ብለው ፡ ጠሯት ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 8 ፤ ከሚሎም ፡ ዠምሮ ፡ በዙሪያው ፡ ከተማ ፡ ሠራ ፤ ኢዮአብም ፡ የቀረውን ፡ ከተማ ፡ አበጀ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 9 ፤ ዳዊትም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበርና ፥ እየበረታ ፡ ኼደ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 10 ፤ ለዳዊትም ፡ የነበሩት ፡ የኀያላን ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ እንደተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ አጸኑት ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 11 ፤ የዳዊትም ፡ ኀያላን ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ የሠላሳው ፡ አለቃ ፡ የአክሞናዊው ፡ ልጅ ፡ ያሾብአም ፡ ነበረ ፤ ርሱ ፡ ጦሩን ፡ አንሥቶ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 12 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በሦስቱ ፡ ኀያላን ፡ መካከል ፡ የነበረ ፡ የአሆሃዊው ፡ የዱዲ ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ በፈስደሚም ፡ ነበረ ፥ በዚያም ፡ ገብስ ፡ በሞላበት ፡ ዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ለሰልፍ ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ፊት ፡ ሸሹ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 14 ፤ በዕርሻውም ፡ መካከል ፡ ቆመው ፡ ጠበቁት ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ ገደሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ በታላቅ ፡ ማዳን ፡ አዳናቸው ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 15 ፤ ከሠላሳውም ፡ አለቃዎች ፡ ሦስቱ ፡ ወርደው ፡ ዳዊት ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ አለቱ ፡ ወደዓዶላም ፡ ዋሻ ፡ መጡ ፤ የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ሰፍሮ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 16 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ፥ የፍልስጥኤማውያንም ፡ ጭፍራ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፦ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡ ውሃ ፡ ማን ፡ ይሰጠኛል ፧ ብሎ ፡ ተመኘ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 18 ፤ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ሰራዊት ፡ ቀደው ፡ ኼዱ ፥ በበሩም ፡ አጠገብ ፡ ካለችው ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ ምንጭ ፡ ውሃ ፡ ቀዱ ፤ ይዘውም ፡ ለዳዊት ፡ አመጡለት ። ርሱ ፡ ግን ፡ ሊጠጣ ፡ አልወደደም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ አፍሶ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 19 ፤ ይህን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ አምላኬ ፡ ይከልክለኝ ፤ በነፍሳቸው ፡ የደፈሩትም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ደም ፡ እጠጣለኹን ፧ በነፍሳቸው ፡ አምጥተውታል ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ። ሦስቱም ፡ ኀያላን ፡ ያደረጉት ፡ ይህ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 20 ፤ የኢዮአብም ፡ ወንድም ፡ አቢሳ ፡ የሦስቱ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ ጦሩንም ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፡ ገደላቸው ፥ በሦስቱም ፡ መካከል ፡ ስሙ ፡ የተጠራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 21 ፤ በኹለተኛውም ፡ ተራ ፡ በኾኑት ፡ በሦስቱ ፡ መካከል ፡ የከበረ ፡ ነበረ ፥ አለቃቸውም ፡ ኾነ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ፊተኞቹ ፡ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 22 ፤ በቀብስኤልም ፡ የነበረው ፥ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ያደረገው ፡ የጽኑዕ ፡ ሰው ፡ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ የሞዐባዊን ፡ የአሪኤል ፡ ኹለቱን ፡ ልጆች ፡ ገደለ ፤ በዐመዳይም ፡ ወራት ፡ ወርዶ ፡ በጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ አንበሳ ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 23 ፤ ቁመቱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ የነበረውን ፡ ረዥሙን ፡ ግብጻዊውን ፡ ሰው ፡ ገደለ ፤ በግብጻዊውም ፡ እጅ ፡ የሸማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ የመሰለ ፡ ጦር ፡ ነበረ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ በትር ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡

ወረደ ፥ ከግብጻዊውም ፡ እጅ ፡ ጦሩን ፡ ነቅሎ ፡ በገዛ ፡ ጦሩ ፡ ገደለው ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 24 ፤ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ስሙም ፡ በሦስቱ ፡ ኀያላን ፡ መካከል ፡ የተጠራ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 25 ፤ እንሆ ፥ ከሠላሳው ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ነበረ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ፊተኞቹ ፡ ወደ ፡ ሦስቱ ፡ አልደረሰም ። ዳዊትም ፡ በዘበኞቹ ፡ ላይ ፡ ሾመው ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 26 ፤ ደግሞም ፡ በጭፍራዎች ፡ ዘንድ ፡ የነበሩት ፡ ኀያላን ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የኢዮአብ ፡ ወንድም ፡ ዐሳሄል ፥ የቤተ ፡ ልሔሙ ፡ ሰው ፡ የዱዲ ፡ ልጅ ፡ ኤልያናን ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 27 ፤ ሃሮራዊው ፡ ሳሞት ፥ ፈሎናዊው ፡ ሴሌስ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 28 ፤ የቴቁሔ ፡ ሰው ፡ የዒስካ ፡ ልጅ ፡ ዒራስ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 29 ፤ ዓናቶታዊው ፡ አቢዔዜር ፥ ኩሳታዊው ([232]) ፡ ሴቤካይ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 30 ፤ አሖሓዊው ፡ ዔላይ ፥ ነጦፋዊው ፡ ኖኤሬ ፥ የነጦፋዊው ፡ የበዓና ፡ ልጅ ፡ ሔሌድ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 31 ፤ ከብንያም ፡ ወገን ፡ ከግብዓ ፡ የሪባይ ፡ ልጅ ፡ ኤታይ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 32 ፤ ጺርዓቶናዊው ፡ በናያስ ፥ የገዓስ ፡ ወንዝ ፡ ሰው ፡ ኡሪ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 33 ፤ ዐረባዊው ፡ አቢኤል ፥ ባሕሩማዊው ፡ ዓዝሞት ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 34 ፤ ሰዓልቦናዊው ፡ ኤሊያሕባ ፥ የጊዞናዊው ፡ የአሣን ፡ ልጆች ፥ የሃራራዊው ፡ የሻጌ ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 35 ፤ የአሮዳዊው ፡ የአራር ፡ ልጅ ፡ አምናን ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 36 ፤ የኡር ፡ ልጅ ፡ ኤሊፋል ፥ ሚኬራታዊው ፡ ኦፌር ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 37 ፤ ፍሎናዊው ፡ አኪያ ፥ ቀርሜሎሳዊው ፡ ሐጽሮ ፥ የኤዝባይ ፡ ልጅ ፡ ነዕራይ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 38 ፤ የናታንም ፡ ወንድም ፡ ኢዮኤል ፥ የሐግሪ ፡ ልጅ ፡ ሚብሐር ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 39 ፤ አሞናዊው ፡ ጼሌቅ ፥ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ የኢዮአብ ፡ ጋሻ ፡ ጕግሬ ፡ ቤሮታዊው ፡ ነሃራይ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 40 ፤ ይትራዊው ፡ ዒራስ ፥ ይትራዊው ፡ ጋሬብ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 41 ፤ ኬጢያዊው ፡ ኦርዮ ፥ የአሕላይ ፡ ልጅ ፡ ዛባድ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 42 ፤ የሮቤላዊው ፡ የሺዛ ፡ ልጅ ፡ ዓዲና ፥ ርሱ ፡ የሮቤላውያን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 43 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፥ የማዕካ ፡ ልጅ ፡ ሐናን ፥ ሚትናዊው ፡ ኢዮሳፍጥ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 44 ፤ ዐስታሮታዊው ፡ ዖዝያ ፥ የአሮኤራዊው ፡ የኮታም ፡ ልጆች ፡ ሻማና ፡ ይዒኤል ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 45 ፤ የሽምሪ ፡ ልጅ ፡ ይድኤል ፥ ወንድሙም ፡ ይድኤል ፥ ወንድሙም ፡ ቲዳዊው ፡ ዮሐ ፥

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 46 ፤ መሐዋዊው ፡ ኤሊኤል ፥ ይሪባይ ፥ ዮሻዊያ ፥ የኤልናዓም ፡ ልጆች ፥ ሞዐባዊው ፡ ይትማ ፥

---

232 ዕብ. ፥ ሑሻቲ ፡ (ሑሰታዊ • የሑሰት ፣ የፍጥነት ፡ ወገን) ።

መዋ.1 ፡ 11 ፡ 47 ፤ ኤልኤል ፥ ያቤድ ፥ ምጾባዊው ፡ የዕሚኤል ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 1 ፤ በጺቅላግም ፡ ከቂስ ፡ ልጅ ፡ ከሳኦል ፡ በተሸሸገ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ የመጡ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ በሰልፍም ፡ ባገዙት ፡ ኀያላን ፡ መካከል ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 2 ፤ ቀስተኞችም ፡ ነበሩ ፥ በቀኝና ፡ በግራም ፡ እጃቸው ፡ ድንጋይ ፡ ሊወነጭፉ ፡ ፍላጻም ፡ ሊወረውሩ ፡ ይችሉ ፡ ነበር ፤ ከብንያም ፡ ወገን ፡ የሳኦል ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 3 ፤ አለቃቸው ፡ አኒዔዝር ፡ ነበረ ፥ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ኢዮአስ ፥ የጊብዓዊው ፡ የሸማዓ ፡ ልጆች ፤ ይዝኤል ፥ ፋሌጥ ፥ የዓዝሞት ፡ ልጆች ፤ በራኪያ ፥ ዓናቶታዊው ፡ ኢዩ ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 4 ፤ ገባዖናዊው ፡ ሰማያስ ፥ ርሱ ፡ በሠላሳው ፡ መካከልና ፡ በሠላሳው ፡ ላይ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኤርምያስ ፥ የሕዚኤል ፥ ዮሐናን ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ገድሮታዊው ፡ ዮዛባት ፥ ኤሉዛይ ፥ ኢያሪሙት ፥ በዓልያ ፥ ሰማራያ ፥ ሐሩፋዊው ፡ ሰፋጥያስ ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ቆርያውያን ፡ ሕልቃና ፥ ይሺያ ፥ ዐዛርኤል ፥ ዮዛር ፥ ያሾቢአም ፤

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 7 ፤ የጌዶር ፡ ሰው ፡ የይሮሃም ፡ ልጆች ፡ የኤላ ፥ ዝባድያ ፡

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ውስጥ ፡ ባለችው ፡ በዐምባዩቱ ፡ ሳለ ፡ ከጋድ ፡ ወገን ፡ የኾኑ ፡ እነዚህ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የሚይዙ ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፥ ሰልፈኞች ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተጠጉ ፤ ፊታቸውም ፡ እንደአንበሳ ፡ ፊት ፡ ነበረ ፥ በተራራም ፡ ላይ ፡ እንደሚዘል ፡ ሚዳቋ ፡ ፈጣኖች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 9 ፤ አለቃው ፡ ዔዜር ፥ ኹለተኛው ፡ ዐብድዩ ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ሦስተኛው ፡ ኤልያብ ፥ አራተኛው ፡ መስመና ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 11 ፤ ዐምስተኛው ፡ ኤርምያስ ፥ ስድስተኛው ፡ አታይ ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 12 ፤ ሰባተኛው ፡ ኤሊኤል ፥ ስምንተኛው ፡ ዮሐናን ፥

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 13 ፤ ዘጠነኛው ፡ ኤልዛባድ ፥ ዐሥረኛው ፡ ኤርምያስ ፥ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ መክበናይ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 14 ፤ እነዚህ ፡ የጋድ ፡ ልጆች ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ፤ ከነርሱም ፡ ታናሹ ፡ ከመቶ ፥ ታላቁ ፡ ከሺሕ ፡ ይመዛዘኑ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 15 ፤ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ዮርዳኖስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ሞልቶ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የተሻገሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ በሸለቆውም ፡ ውስጥ ፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ የተቀመጡትን ፡ ኹሉ ፡ አባረሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ዳዊትም ፡ ወደነበረባት ፡ ወደ ፡ ዐምባዩቱ ፡ ከብንያምና ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ መጡ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ ሊገናኛቸው ፡ ወጥቶ ፦ ትረዱኝ ፡ ዘንድ ፡ በሠላም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥታችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልቤ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይኾናል ፤ ለጠላቶቼ ፡ አሳልፋችኹ ፡ ልትሰጡኝ ፡ መጥታችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፥ በእጄ ፡ ዐመፅ ፡ የለብኝምና ፡ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ይመልከተው ፥ ይፍረደውም ፡ አላቸው ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 18 ፤ መንፈስም ፡ በሠላሳው ፡ አለቃ ፡ በአማሳይ ፡ ላይ ፡ መጣ ፥ ርሱም ፦ ዳዊት ፡ ሆይ ፥ እኛ ፡ የአንተ ፡ ነን ፤ የእሴል ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እኛ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነን ፤ አምላክኽ ፡ ይረዳኻልና ፥ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ለአንተ ፡

ይኹን ፥ ለሚረዱኽም ፡ ሰላም ፡ ይኹን ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ ተቀበላቸው ፥ የጭፍራም ፡ አለቃዎች ፡ አደረጋቸው ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሳኦልን ፡ ሊወጋ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከምናሴ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከዱ ፤ የፍልስጥኤማውያን ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፦ በራሳችን ፡ ላይ ፡ ጕዳት ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡ ሳኦል ፡ ይመለሳል ፡ ሲሉ ፡ ተማክረው ፡ ሰደውታልና ፥ እነርሱ ፡ አልረዷቸውም ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ጺቅላግም ፡ ሲኼድ ፡ ከምናሴ ፡ ወገን ፡ የምናሴ ፡ ሻለቃዎች ፡ የነበሩ ፡ ዓድና ፥ ዮዛባት ፥ ይዲኤል ፥ ሚካኤል ፥ ዮዛባት ፥ ኤሊሁ ፥ ጺልታይ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ከዱ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ኹሉም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላንና ፡ በሰራዊቱ ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩና ፥ በአደጋ ፡ ጣዮቹ ፡ ላይ ፡ ዳዊትን ፡ አገዙት ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 22 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ሰራዊት ፡ ታላቅ ፡ ሰራዊት ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ዳዊትን ፡ ለመርዳት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 23 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የሳኦልን ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ በኬብሮን ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ የመጡት ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃዎች ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 24 ፤ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ተሸክመው ፡ ለሰልፍ ፡ የተዘጋጁ ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 25 ፤ ለሰልፍ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ የነበሩ ፡ የስምዖን ፡ ልጆች ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 26 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 27 ፤ የአሮንም ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ ዮዳዔ ፡ ነበረ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 28 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ ጕልማሳ ፡ ሳዶቅ ፡ ነበረ ፥ ከአባቱም ፡ ቤት ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 29 ፤ የሳኦልም ፡ ወንድሞች ፡ ከኾኑ ፡ ከብንያም ፡ ወንድሞች ፡ የሚበልጠው ፡ ክፍል ፡ እስከዚያ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሳኦልን ፡ ቤት ፡ ይከተል ፡ ነበርና ፥ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የመጡ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 30 ፤ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ የኾኑ ፡ በአባቶቻቸውም ፡ ቤት ፡ የታወቁ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 31 ፤ በየስማቸውም ፡ የተጻፉ ፡ ዳዊትን ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ የመጡ ፡ የምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 32 ፤ እስራኤልም ፡ የሚገባውን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ዘመኑን ፡ የሚያውቁ ፡ ጥበበኞች ፡ ሰዎች ፡ የይሳኮር ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ይታዘዟቸው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 33 ፤ በጭፍራውም ፡ ውስጥ ፡ የወጡ ፡ ለሰልፍም ፡ የተዘጋጁ ፥ የማያመነቱ ፥ መሣሪያም ፡ ኹሉ ፡ የያዙ ፡ የዛብሎን ፡ ሰዎች ፡ ዐምሳ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 34 ፤ የንፍታሌምም ፡ አለቃዎች ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የሚይዙ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 35 ፤ ለሰልፍም ፡ የተዘጋጁ ፡ የዳን ፡ ሰዎች ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 36 ፤ በጫፍራውም ፡ ውስጥ ፡ የሚወጡ ፥ ለሰልፍም ፡ የተዘጋጁ ፡ የአሴር ፡ ሰዎች ፡ አርባ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 37 ፤ በዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ካሉ ፡ ከሮቤልና ፡ ከጋድ ፡ ሰዎች ፡ ከምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ መሣሪያን ፡ ዅሉ ፡ ይዘው ፡ የመጡ ፡ መቶ ፡ ዻያ ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 38 ፤ እነዚህ ፡ ዅሉ ፡ ዳዊትን ፡ በእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ዐርበኞችና ፡ ሰልፈኞች ፥ እየኾኑ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ ወደ ፡ ኬብሮን ፡ መጡ ፤ ደግሞም ፡ ከእስራኤል ፡ የቀሩት ፡ ዅሉ ፡ ዳዊትን ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 39 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ አዘጋጅተውላቸው ፡ ነበርና ፥ እየበሉና ፡ እየጠጡ ፡ በዚያ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.1 ፡ 12 ፡ 40 ፤ ደግሞም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ደስታ ፡ ኾኗልና ፥ እስከ ፡ ይሳኮርና ፡ እስከ ፡ ዛብሎን ፡ እስከ ፡ ንፍታሌምም ፡ ድረስ ፡ ለርሱ ፡ አቅራቢያ ፡ የነበሩ ፡ በአህያና ፡ በግመል ፡ በበቅሎና ፡ በበሬ ፡ ላይ ፡ እንጀራና ፡ ዱቄት ፡ የበለስ ፡ ጥፍጥፍና ፡ የዘቢብ ፡ ዘለላ ፡ የወይንም ፡ ጠጅ ፡ ዘይትም ፡ በሬዎችንና ፡ በጎችንም ፡ በብዙ ፡ አድርገው ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ ከሻለቃዎችና ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ከአለቃዎቹም ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ዅሉ ፦ መልካም ፡ መስሎ ፡ የታያችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ወጥቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በእስራኤል ፡ አገር ፡ ዅሉ ፡ ለቀሩት ፡ ወንድሞቻችን ፡ በከተማዎቻቸውና ፡ በመሰምሪያዎቻቸውም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ፡ እንላክ ፤

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 3 ፤ በሳኦልም ፡ ዘመን ፡ አልፈለግነውምና ፡ የአምላካችንን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ እንመልስ ፡ አላቸው ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 4 ፤ ነገሩም ፡ በሕዝቡ ፡ ዅሉ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ቅን ፡ ነበረና ፡ ጉባኤው ፡ ዅሉ ፦ እንዲሁ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ከቂርያትይዓሪም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊት ፡ እስራኤልን ፡ ዅሉ ፡ ከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ከሺሖር ፡ ገቦምሮ ፡ እስከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ እስራኤልም ፡ ዅሉ ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የተቀመጠውን ፡ ስሙም ፡ በርሱ ፡ የተጠራውን ፡ የአምላክን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ከዚያ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳ ፡ ወዳለችው ፡ ቂርያትይዓሪም ፡ ወደተባለች ፡ ወደ ፡ በዓላ ፡ ኼዱ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ በዐዲስ ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ ጫኑት ፥ ከዐሚናዳብም ፡ ቤት ፡ አመጡት ፤ ዖዛና ፡ አኒዮም ፡ ሠረገላውን ፡ ይነዱ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 8 ፤ ዳዊትና ፡ እስራኤል ፡ ዅሉ ፡ በቅኔና ፡ በበገና ፡ በመሰንቆና ፡ በከበሮ ፡ በጸናጽልና ፡ በመለከት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሙሉ ፡ ኀይላቸው ፡ ይጫወቱ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 9 ፤ ወደኪዶንም ፡ ዐውድማ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ በሬዎቹ ፡ ይፋንኑ ፡ ነበርና ፥ ታቦቱን ፡ ሊይዝ ፡ ዖዛ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በዖዛ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ እጁንም ፡ ወደ ፡ ታቦቱ ፡ ስለ ፡ ዘረጋ ፡ ቀሠፈው ፤ በዚያም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሞተ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዖዛን ፡ ስለ ፡ ቀሠፈው ፡ ዳዊት ፡ ዐዘነ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ የዖዛ ፡ ስብራት ፡ ብሎ ፡ ጠራው ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዴት ፡ አመጣለኹ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈራ ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ታቦቱን ፡ ወደጌት ፡ ሰው ፡ ወደዐቢዳራ ፡ ቤት ፡ አሳለፈው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ አላመጣውም ።

መዋ.1 ፡ 13 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ በዐቢዳራ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡ ዘንድ ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የዐቢዳራን ፡ ቤትና ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ባረከ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 1 ፤ የጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ኪራም ፡ ቤት ፡ ይሠሩለት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨትንም ፡ ጠራቢዎችንም ፡ ዐናጢዎችንም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ላከ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 2 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ መንግሥቱ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አድርጎ ፡ እንዳጸናው ፡ ዳዊት ፡ ዐወቀ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሚስቶችን ፡ ጨምሮ ፡ ሌላዎችን ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 4 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የወለዳቸው ፡ የልጆቹ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሳሙስ ፥

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 5 ፤ ሶባብ ፥ ናታን ፥ ሰሎሞን ፥ ኢያቤሐር ፥ ኤሊሱዔ ፥

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 6 ፤ ኤሊፋላት ፥ ኖጋ ፥ ናፌቅ ፥ ያፍያ ፥

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 7 ፤ ኤሊሳማ ፥ ኤሊዳሄ ፥ ኤሊፋላት ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 8 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ዳዊት ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ሰሙ ፥ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ኹሉ ፡ ዳዊትን ፡ ሊፈልጉ ፡ ወጡ ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ሊጋጠማቸው ፡ ወጣ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 9 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ መጥተው ፡ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 10 ፤ ዳዊትም ፦ ወደ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ልውጣን ፧ በእጄስ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጣቸዋለኽን ፧ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ። እግዚአብሔርም ፦ በእጅኽ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹና ፡ ውጣ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ በአልፐራሲም ፡ ወጡ ፥ በዚያም ፡ ዳዊት ፡ መታቸው ። ዳዊትም ፦ ውሃ ፡ እንዲያፈርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠላቶቼን ፡ በእጄ ፡ አፈረሳቸው ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ የዚያን ፡ ስፍራ ፡ ስም ፡ በአልፐራሲም ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 12 ፤ አማልክታቸውንም ፡ በዚያ ፡ ተዉ ፤ ዳዊትም ፡ አዘዘ ፥ በእሳትም ፡ አቃጠሏቸው ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 13 ፤ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ደግሞ ፡ በሸለቆው ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠየቀ ፤ እግዚአብሔርም ፦ ከነርሱ ፡ ዞረኽ ፡ በሾላው ፡ ዛፍ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ግጠማቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አትውጣ ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 15 ፤ በሾላውም ፡ ዛፍ ፡ ራስ ፡ ውስጥ ፡ የሽውሽውታ ፡ ድምፅ ፡ ስትሰማ ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ ሊመታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊትኽ ፡ ይወጣልና ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ውጣ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 16 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ከገባዖንም ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ጌዝር ፡ ድረስ ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ጭፍራ ፡ መቱት ።

መዋ.1 ፡ 14 ፡ 17 ፤ የዳዊትም ፡ ዝና ፡ በያገሩ ፡ ኹሉ ፡ ወጣ ፤ መፈራቱንም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ አደረገው ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ ለራሱ ፡ ቤቶችን ፡ ሠራ ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ስፍራ ፡ አዘጋጀ ፥ ድንኳንም ፡ ተከለለት ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ዳዊት ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ይሸከሙ ፡ ዘንድ ፥ ለዘለዓለሙም ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመረጣቸው ፡ ከሌዋውያን ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ወዳዘጋጀለት ፡ ስፍራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ የአሮንን ፡ ልጆችና ፡ ሌዋውያንን ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 5 ፤ ከቀአት ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ኡርኤል ፥ ወንድሞቹም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፤

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 6 ፤ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ዐሳያ ፥ ወንድሞቹም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፤

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 7 ፤ ከጌድሶን ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ኢዮኤል ፥ ወንድሞቹም ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፤

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 8 ፤ ከኤሊጻፋን ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ሸማያ ፥ ወንድሞቹም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፤

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 9 ፤ ከኬብሮን ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ኤሊኤል ፥ ወንድሞቹም ፡ ሰማንያ ፤

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 10 ፤ ከዑዝኤል ፡ ልጆች ፤ አለቃው ፡ ዐሚናዳብ ፥ ወንድሞቹም ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ ካህናቱን ፡ ሳዶቅንና ፡ አቢያታርን ፥ ሌዋውያንንም ፡ ኡርኤልን ፥ ዐሳያን ፥ ኢዮኤልን ፥ ሸማያን ፥ ኤሊኤልን ፥ ዐሚናዳብንም ፡ ጠርቶ ፦

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ የሌዋውያን ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ናችኹ ፤ ወዳዘጋጀኹለት ፡ ስፍራ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ታመጡ ፡ ዘንድ ፡ እናንተና ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ ተቀደሱ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 13 ፤ ቀድሞም ፡ አልተሸከማችኹምና ፥ እንደ ፡ ሥርዐቱም ፡ አልፈለግነውምና ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ ስብራት ፡ አደረገ ፡ አላቸው ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 14 ፤ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ ተቀደሱ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 15 ፤ ሙሴም ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሌዋውያን ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታቦት ፡ በትከሻቸው ፡ ላይ ፡ በመሎጊያዎቹ ፡ ተሸከሙ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 16 ፤ ዳዊትም ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡ በመሰንቆና ፡ በበገና ፡ በጸናጽልም ፡ እንዲያዜሙ ፥ ድምፃቸውንም ፡ በደስታ ፡ ከፍ ፡ እንዲያደርጉ ፡ መዘምራኑን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ፡ ለሌዋውያን ፡ አለቃዎች ፡ ተናገረ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 17 ፤ ሌዋውያኑም ፡ የኢዮኤልን ፡ ልጅ ፡ ኤማንን ፥ ከወንድሞቹም ፡ የበራክያን ፡ ልጅ ፡ አሣፍን ፥ ከወንድሞቻቸውም ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ የቂሳን ፡ ልጅ ፡ ኤታንን ፥

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 18 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ በኹለተኛው ፡ ተራ ፡ የኾኑትን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ዘካርያስን ፥ ቤንን ፥ ያዝኤልን ፥ ሰሚራሞትን ፥ ይሒኤልን ፥ ዑኒን ፥ ኤልያብን ፥ በናያስን ፥ መዕሴያን ፥ መቲትያን ፥ ኤሊፍሌሁን ፥ ሚቅንያን ፥ በረኞችንም ፡ ዖቤድኤዶምንና ፡ ይዒኤልን ፡ አቆሙ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 19 ፤ መዘምራንም ፡ ኤማንና ፡ አሣፍ ፡ ኤታንም ፡ በናስ ፡ ጸናጽል ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ያሰሙ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 20 ፤ ዘካርያስ ፥ ዓዝዔል ፥ ሰሚራሞት ፥ ይሒኤል ፥ ዑኒ ፥ ኤልያብ ፥ መዕሴያ ፥ በናያስ ፡ በመሰንቆ ፡ ምስጢር ፡ ነገር ፡ ያዜሙ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 21 ፤ መቲትያ ፥ ኤልፍሌሁ ፥ ሚቅኒያ ፥ ዖቤድኤዶም ፥ ይዒኤል ፥ ዓዛዝያ ፡ ስምንት ፡ አውታር ፡ ባለው ፡ በገና ፡ ይዘምሩ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 22 ፤ የሌዋውያኑም ፡ አለቃ ፡ ክናንያ ፡ በዜማ ፡ ላይ ፡ ተሹሞ ፡ ነበር ። ብልኀተኛ ፡ ነበረና ፡ ዜማ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 23 ፤ በራክያና ፡ ሕልቃናም ፡ ለታቦቱ ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 24 ፤ ካህናቱም ፡ ሰበንያ ፥ ኢዮሳፍጥ ፥ ናትናኤል ፥ ዐማሳይ ፥ ዘካርያስ ፥ በናያስ ፥ አልዓዛር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታቦይ ፡ ፊት ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ። ዖቤድኤዶምና ፡ ይሒያም ፡ ለታቦቱ ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 25 ፤ ዳዊትም ፥ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፥ የሻለቃዎችም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦት ፡ ከዐቢዳራ ፡ ቤት ፡ በደስታ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ኼዱ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 26 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ የተሸከሙትን ፡ ሌዋውያንን ፡ እግዚአብሔር ፡ በረዳቸው ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ በሬዎችና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ሠዉ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 27 ፤ ዳዊትም ፥ ታቦቱንም ፡ የተሸከሙ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፥ መዘምራኑም ፥ የመዘምራኑም ፡ አለቃ ፡ ክናንያ ፡ የጥሩ ፡ በፍታ ፡ ቀሚስ ፡ ለብሰው ፡ ነበር ፤ ዳዊትም ፡ የበፍታ ፡ ኤፉድ ፡ ነበረው ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 28 ፤ እንዲሁ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ሆ ፡ እያሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከትና ፡ እንቢልታ ፡ እየነፉ ፥ ጸናጽልና ፡ መሰንቆም ፡ በገናም ፡ እየመቱ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ አመጡ ።

መዋ.1 ፡ 15 ፡ 29 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሳኦል ፡ ልጅ ፡ ሜልኮል ፡ በመስኮት ፡ ኾና ፡ ተመለከተች ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ሲዘፍንና ፡ ሲጫወት ፡ አይታ ፡ በልቧ ፡ ናቀችው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ታቦት ፡ ይዘው ፡ ገቡ ፥ ዳዊትም ፡ በተከለለት ፡ ድንኳን ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡

በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ሕዝቡን ፡ ባረከ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 3 ፤ ለእስራኤልም ፡ ለወንዱም ፡ ለሴቱም ፡ ለያንዳንዱ ፡ አንዳንድ ፡ እንጀራ ፤ አንዳንድም ፡ ቍራጭ ፡ ሥጋ ፡ አንዳንድም ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አካፈለ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 4 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይወድሱት ፡ ዘንድ ፥ ያመሰግኑትና ፡ ያከብሩትም ፡ ዘንድ ፡ ከሌዋውያን ፡ ወገን ፡ አቆመ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 5 ፤ አለቃው ፡ አሣፍ ፡ ነበረ ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡
ዘካርያስ ፥ ይዒኤል ፥ ሰሚራሞት ፥ ይሒኤል ፥ መቲትያ ፥ ኤልያብ ፥ በናያስ ፥ ዖቤድኤዶም ፥ ይዒኤል ፡ በመሰንቆና ፡ በበገና ፡ አሣፍም ፡ በጸናጽል ፡ ይዘምሩ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 6 ፤ ካህናቱም ፡ በናያስና ፡ የሕዚኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ዘውትር ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ዳዊት ፡ በአሣፍና ፡ በወንድሞቹ ፡ እጅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያመሰግኑ ፡ ትእዛዝን ፡ ሰጠ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ስሙን ፡ ጥሩ ፤ ለአሕዛብ ፡ ሥራውን ፡ አውሩ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 9 ፤ ተቀኙለት ፥ ዘምሩለት ፤ ተኣምራቱንም ፡ ዘምሩ ፡ ተናገሩ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 10 ፤ በቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ተጓደዱ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈልግ ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፈልጉት ፥ ትጸናላችኹም ፤ ዘውልጊዜ ፡ ፊቱን ፡ ፈልጉ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 12 ፤ 13 ፤ ባሪያዎቹ ፡ የእስራኤል ፡ ዘር ፥ ለርሱም ፡ የተመረጣችኹ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ የሠራትን ፡ ድንቅ ፡ ዐስቡ ፥ ተኣምራቱንም ፡ የአፉንም ፡ ፍርድ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 14 ፤ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ነው ፤ ፍርዱ ፡ በምድር ፡ ዘውትር ፡ ነው ። ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ለዘለዓለም ፥ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ያዘዘውን ፡ ቃሉን ፡ ዐሰበ ፥

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 16 ፤ ለአብርሃም ፡ ያደረገውን ፥ ለይሥሐቅም ፡ የማለውን ፤

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 17 ፤ ለያዕቆብ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኾን ፡ ለእስራኤልም ፡ የዘለዓለም ፡ ኪዳን ፡ እንዲኾን ፡ አጸና ፤

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 18 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ለአንተ ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ የርስታችኹን ፡ ገመድ ፡ እሰጣለኹ ፤

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 19 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ እነርሱ ፡ በቍጥር ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፥ እጅግ ፡ ጥቂቶችና ፡ ስደተኞች ፡ ሲኾኑ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 20 ፤ ከሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፥ ከመንግሥትም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ዐለፉ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 21 ፤ 22 ፤ የቀባኋቸውን ፡ አትዳስሱ ፥ በነቢያቴም ፡ ክፉ ፡ አታድርጉ ፡ ብሎ ፥ ሰው ፡ ግፍ ፡ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደም ፤ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ነገሥታትን ፡ ገሠጸ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 23 ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ማዳኑን ፡ አውሩ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 24 ፤ ክብሩን ፡ ለአሕዛብ ፥ ተኣምራቱንም ፡ ለወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ንገሩ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፥ ምስጋናውም ፡ ብዙ ፡ ነውና ፤ በአማልክትም ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ የተፈራ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 26 ፤ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ዅሉ ፡ ጣዖታት ፡ ናቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰማያትን ፡ ሠራ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 27 ፤ ክብርና ፡ ግርማ ፡ በፊቱ ፥ ኀይልና ፡ ደስታ ፡ በስፍራው ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 28 ፤ የአሕዛብ ፡ ወገኖች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፥ ክብርንና ፡ ኀይልን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 29 ፤ ለስሙ ፡ የሚገባ ፡ ክብርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፤ ቍርባንን ፡ ይዛችኹ ፡ በፊቱ ፡ ግቡ ፤ በቅድስናው ፡ ስፍራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 30 ፤ ምድር ፡ ዅሉ ፡ በፊቱ ፡ ትነዋወጥ ፤ ዓለሙም ፡ እንዳይናወጥ ፡ ጸንቷል ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 31 ፤ ሰማያት ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፥ ምድርም ፡ ሐሴትን ፡ ታድርግ ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ። እግዚአብሔር ፡ ነገሠ ፡ በሉ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 32 ፤ ባሕርና ፡ ሞላዋ ፡ ትናወጥ ፤ በረሓ ፡ በርሷም ፡ ያሉ ፡ ዅሉ ፡ ሐሤትን ፡ ያድርጉ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 33 ፤ በምድር ፡ ሊፈርድ ፡ ይመጣልና ፥ የዱር ፡ ዛፎች ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 34 ፤ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 35 ፤ የመዳናችን ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አድነን ፤ ቅዱስ ፡ ስምኽን ፡ እናመሰግን ፡ ዘንድ ፥ በምስጋናኽም ፡ እንመካ ፡ ዘንድ ፥ ከአሕዛብ ፡ ሰብስበኽ ፡ ታደገን ፡ በሉ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 36 ፤ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ። ሕዝቡም ፡ ዅሉ ፡ አሜን ፡ ይበሉ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ያመስግኑ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 37 ፤ እንዲሁም ፡ በየቀኑ ፡ እንደሚገባቸው ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ዘወትር ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ አሣፍንና ፡ ወንድሞቹን ፥ ዖቤድኤዶምንም ፥ ስድሳ ፡ ስምንቱንም ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ፊት ፡ ተዋቸው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 38 ፤ የኤዶታምም ፡ ልጅ ፡ ዖቤድኤዶምና ፡ ሖሳ ፡ በረኞች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ተዋቸው ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 39 ፤ ካህኑም ፡ ሳዶቅንና ፡ ካህናቱን ፡ ወንድሞቹን ፡ በገባዖን ፡ በኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ አቆማቸው ፥

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 40 ፤ ለእስራኤልም ፡ ባዘዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ዅሉ ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ዅል ፡ ጊዜ ፡ ጧትና ፡ ማታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 41 ፤ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ኤማንንና ፡ ኤዶታምን ፥ በስማቸውም ፡ የተጻፉትን ፡ ተመርጠው ፡ የቀሩትን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አቆመ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 42 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ካህናቱ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ለማሰማት ፡ መለከትና ፡ ጸናጽል ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ መዝሙራት ፡ የዜማ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ነበር ፤ የኤዶታምም ፡ ልጆች ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 16 ፡ 43 ፤ ሕዝቡ ፡ ዅሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፤ ዳዊትም ፡ ቤቱን ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፡ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ዳዊት ፡ በቤቱ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ነቢዩን ፡ ናታንን ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ከዝግባ ፡ በተሠራ ፡ ቤት ፡ ተቀምጫለኹ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ በመጋረጃዎች ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧል ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 2 ፤ ናታንም ፡ ዳዊትን ፦ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ በልብኽ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 3 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ናታን ፡ መጣ ፡ እንዲህም ፡ አለው ፦

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 4-5 ፤ ኺድ ፥ ለባሪያዬ ፡ ለዳዊት ፡ ንገረው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤልን ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከድንኳን ፡ ወደ ፡ ድንኳን ፥ ከማደሪያም ፡ ወደ ፡ ማደሪያ ፡ እኼድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በቤት ፡ ውስጥ ፡ አልኖርኹምና ፡ የምኖርበትን ፡ ቤት ፡ አትሠራልኝም ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 6 ፤ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ባለፍኹበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ቤትን ፡ ከዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ አልሠራችኹልኝም ፧ ብዬ ፡ ሕዝቤን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ፈራጆች ፡ ላዘዝኹት ፡ ለአንዱ ፡ በእውኑ ፡ ተናግሬያለኹን ፧

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ ባሪያዬን ፡ ዳዊትን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፡ መንጋውን ፡ ስትከተል ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ከበግ ፡ ጥበቃ ፡ ወሰድኹኽ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 8 ፤ በኼድኽበትም ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነበርኹ ፥ ጠላቶችኽንም ፡ ኹሉ ፡ ከፊትኽ ፡ አጠፋኹ ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ እንደታላላቆች ፡ ስም ፡ ለአንተ ፡ ስም ፡ አደርጋለኹ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 9 ፤ 10 ፤ ለሕዝቤም ፡ ለእስራኤል ፡ ስፍራ ፡ አደርግለታለኹ ፥ እተክለውማለኹ ፥ በስፍራውም ፡ ይቀመጣል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይናወጥም ፤ እንደቀድሞው ፡ ዘመንና ፡ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ፈራጆች ፡ እንዳስነሣኹበት ፡ ጊዜ ፡ ግፈኞች ፡ ተመልሰው ፡ አያስጨንቁትም ፤ ጠላቶችኽንም ፡ ኹሉ ፡ አዋርዳቸዋለኹ ። እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ ቤት ፡ እንዲሠራልኽ ፡ እነግርኻለኹ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ አባቶችኽም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ዕድሜኽ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ከልጆችኽ ፡ የሚኾነውን ፡ ዘርኽን ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ አስነሣለኹ ፤ መንግሥቱንም ፡ አጸናለኹ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ ቤት ፡ ይሠራልኛል ፤ ዙፋኑንም ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለኹ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 13 ፤ እኔም ፡ አባት ፡ እኾነዋለኹ ፥ ርሱም ፡ ልጅ ፡ ይኾነኛል ፤ ከአንተ ፡ አስቀድሞ ፡ ከነበረው ፡ እንዳራቅኹ ፥ ምሕረቴን ፡ ከርሱ ፡ አላርቅም ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 14 ፤ በቤቴና ፡ በመንግሥቴም ፡ ለዘለዓለም ፡ አቆመዋለኹ ፤ ዙፋኑም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናል ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 15 ፤ እንደዚህ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህም ፡ ራእይ ፡ ኹሉ ፡ ናታን ፡ ለዳዊት ፡ ነገረው ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 16 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ገባ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ተቀምጦ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እስከዚህ ፡ ያደረስኸኝ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧ ቤቴስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 17 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፡ ይህ ፡ በፊትኽ ፡ ጥቂት ፡ ነበረ ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ባሪያኽ ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ለሩቅ ፡ ዘመን ፡ ተናገርኽ ፤ እንደ ፡ አንድ ፡ ባለማዕርግ ፡ ሰው ፡ ተመለከትኸኝ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 18 ፤ አንተ ፡ ባሪያኽን ፡ ታውቀዋለኽና ፡ ለባሪያኽ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ክብር ፡ ዳዊት ፡ ጨምሮ ፡ የሚለው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታስታውቀው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ባሪያኽ ፡ እንደ ፡ ልብኽም ፡ ይህን ፡ ተአምራት ፡ ኹሉ ፡ አድርገኻል ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 20 ፤ አቤቱ ፥ እንዳንተ ፡ ያለ ፡ የለም ፥ በገሮሯችንም ፡ እንደ ፡ ሰማን ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለም ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 21 ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣኸው ፡ ከሕዝብኽ ፡ ፊት ፡ አሕዛብን ፡ በማሳደድ ፡ በታላቅና ፡ በሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ ስም ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፥ ለአንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትቤኻ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ኼድኽለት ፡ እንዳንተ ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ያለ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ አለን ፧

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 22 ፤ ሕዝብኽንም ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕዝብኽ ፡ አደረግኸው ፤ አንተም ፥ አቤቱ ፥ አምላክ ፡ ኾነኸዋል ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 23 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ባሪያኽና ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ የተናገርኸው ፡ ለዘለዓለም ፡ የጸና ፡ ይኹን ፤ እንደ ፡ ተናገርኽም ፡ አድርግ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 24 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ነው ፥ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ይባል ፡ ዘንድ ፡ ስምኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጽኑና ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፤ የባሪያኽም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ በፊትኽ ፡ ጸንቷል ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 25 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ቤት ፡ እንድሠራለት ፡ ለባሪያኽ ፡ ገልጠኻልና ፥ ስለዚህ ፡ ባሪያኽ ፡ ወዳንተ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ደፈረ ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 26 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፥ ይህንም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለባሪያኽ ፡ ተናግረኻል ።

መዋ.1 ፡ 17 ፡ 27 ፤ አኹንም ፡ በፊትኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ የባሪያኽን ፡ ቤት ፡ እንድትባርክ ፡ ፈቅደኻል ፤ አንተም ፥ አቤቱ ፥ ባርከኸዋል ፥ ለዘለዓለምም ፡ ቡሩክ ፡ ይኾናል ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳዊት ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ መታ ፥ አዋረዳቸውም ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ እጅ ፡ ጌትንና ፡ መንደሮቿን ፡ ወሰደ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 2 ፤ ሞዐብን ፡ መታ ፤ ሞዐባውያንም ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡ ኾኑ ፤ ግብርም ፡ አመጡለት ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ የነበረውን ፡ ግዛት ፡ ለመያዝ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ የሱባን ፡ ንጉሥ ፡ አድርዐዛርን ፡ እስከ ፡ ሃማት ፡ ድረስ ፡ መታ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 4 ፤ ዳዊትም ፡ ከርሱ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ሠረገላዎች ፥ ሰባት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞች ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ እግረኞች ፡ ወሰደ ፤ ዳዊት ፡ ለመቶ ፡ ሠረገላዎች ፡ የሚኾኑትን ፡ ብቻ ፡ አስቀርቶ ፡ የሠረገላዎቹን ፡ ፈረሶች ፡ ቋንጣ ፡ ቈረጠ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 5 ፤ ከደማስቆም ፡ ሶርያውያን ፡ የሱባን ፡ ንጉሥ ፡ አድርዐዛርን ፡ ሊረዱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ከሶርያውያን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችን ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ በደማስቆ ፡ ሶርያ ፡ ጭፍራዎች ፡ አኖረ ፤ ሶርያውያንም ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡

ኾኑ ፥ ግብርም ፡ አመጡለት ። እግዚአብሔርም ፡ ዳዊት ፡ በኼደበት ፡ ኹሉ ፡ ድል ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ ለአድርዐዛር ፡ ባሪያዎች ፡ የነበሩትን ፡ የወርቅ ፡ ጋሻዎች ፡ ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ይዟቸው ፡ መጣ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 8 ፤ ከአድርዐዛርም ፡ ከተማዎች ፡ ከጢብሐትና ፡ ከኩን ፡ ዳዊት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናስ ፡ ወሰደ ፤ ከዚህም ፡ ሰሎሞን ፡ የናሱን ፡ ኵሬና ፡ ዐምዶች ፡ የናሱንም ፡ ዕቃ ፡ ሠራ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 9 ፤ የሐማትም ፡ ንጉሥ ፡ ቶዑ ፡ ዳዊት ፡ የሱባን ፡ ንጉሥ ፡ የአድርዐዛርን ፡ ጭፍራ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መታ ፡ ሰማ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 10 ፤ ቶዑም ፡ ከአድርዐዛር ፡ ጋራ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ይዋጋ ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ አድርዐዛርን ፡ ወግቶ ፡ ስለ ፡ መታው ፡ ደኅንነቱን ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ይመርቀውም ፡ ዘንድ ፡ ልጁን ፡ አዶራምን ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ላከው ፤ ርሱም ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ የናስም ፡ ዕቃ ፡ ይዞ ፡ መጣ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ከኤዶምና ፡ ከሞዐብ ፡ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ ከዐማሌቅም ፡ ከማረከው ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ጋራ ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀደሰ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 12 ፤ ደግሞ ፡ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ አቢሳ ፡ ከኤዶማውያን ፡ በጨው ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 13 ፤ በኤዶምያስም ፡ ጭፍራዎች ፡ አኖረ ፥ ኤዶማውያንም ፡ ኹሉ ፡ ለዳዊት ፡ ገባሮች ፡ ኾኑ ። እግዚአብሔርም ፡ ዳዊት ፡ በኼደበት ፡ ኹሉ ፡ ድል ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 14 ፤ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ ለሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅም ፡ አደረገላቸው ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 15 ፤ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብም ፡ የሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ የአኒሉድም ፡ ልጅ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 16 ፤ የአኪጦብም ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፥ የአቢሜሌክም ፡ ልጅ ፡ አብያታር ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ፤ ሱሳ ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 18 ፡ 17 ፤ የዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ በከሊታውያንና ፡ በፈሊታውያን ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ የዳዊትም ፡ ልጆች ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። _____

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ናያስ ፡ ሞተ ፥ ልጁም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፦ አባቱ ፡ ስላደረገልኝ ፡ ወረታ ፡ እኔ ፡ ለናያስ ፡ ልጅ ፡ ለሐኖን ፡ ቸርነት ፡ አደርጋለኹ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ አባቱ ፡ ስለ ፡ ሞተ ፡ ሊያጽናናው ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፤ የዳዊትም ፡ ባሪያዎች ፡ ሊያጽናኑት ፡ ወደ ፡ ሐኖን ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ መጡ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 3 ፤ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ ሐኖንን ፦ ዳዊት ፡ አባትኽን ፡ አክብሮ ፡ የሚያጽናኑኽን ፡ ወዳንተ ፡ የላከ ፡ ይመስልኻልን ፧ ባሪያዎቹስ ፡ አገሪቱን ፡ ለመመርመር ፥ ለማጥፋት ፥ ለመሰለልም ፡ ወዳንተ ፡ የመጡ ፡ አይደሉምን ፧ አሉት ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ሐኖንም ፡ የዳዊትን ፡ ባሪያዎች ፡ ወስዶ ፡ አስላጫቸው ፥ ልብሳቸውንም ፡ እስከ ፡ ወገባቸው ፡

ድረስ ፡ ከኹለት ፡ ቀዶ ፡ ሰደዳቸው ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 5 ፤ ወሬኞችም ፡ ኼደው ፡ በሰዎቹ ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ለዳዊት ፡ አስታወቁት ። ሰዎቹም ፡ በብዙ ፡ ዐፍረዋልና ፥ ተቀባዮች ፡ ላከ ፤ ንጉሡም ፦ ጢማችኹ ፡ እስኪያድግ ፡ ድረስ ፡ በኢያሪኮ ፡ ተቀመጡ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ተመለሱ ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 6 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጠሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሐኖንና ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከመስጴጦምያ ፥ ከአራምመዓካ ፥ ከሱባ ፡ ሠረገላዎችንና ፡ ፈረሰኞችን ፡ ይቀጥሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ላኩ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 7 ፤ ሠላሳ ፡ ኹለትም ፡ ሺሕ ፡ ሠረገላዎች ፡ የመዓካንም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቡንም ፡ ቀጠሩ ፤ መጥተውም ፡ በሜድባ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሰፈሩ ። የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ከየከተማዎቻቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ መጡ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ ይህ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮአብንና ፡ የኀያላኑን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ላከ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 9 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ወጥተው ፡ በከተማዩቱ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ተሰለፉ ፤ የመጡትም ፡ ነገሥታት ፡ ለብቻቸው ፡ በሜዳው ፡ ላይ ፡ በሩ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 10 ፤ ኢዮአብም ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ሰልፍ ፡ እንደ ፡ ከበበው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ምርጥ ፡ ምርጦችን ፡ ኹሉ ፡ ለይቶ ፡ በሶርያውያን ፡ ላይ ፡ አሰለፋቸው ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 11 ፤ የቀረውንም ፡ ሕዝብ ፡ ለወንድሙ ፡ ለአቢሳ ፡ ሰጠው ፥ በዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 12 ፤ ርሱም ፦ ሶርያውያን ፡ ቢበረቱብኝ ፡ ርዳኝ ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ቢበረቱብኽ ፡ እረዳኻለኹ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 13 ፤ አይዞኽ ፥ ስለ ፡ ሕዝባችንና ፡ ስለአምላካችንም ፡ ከተማዎች ፡ እንበርታ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደስ ፡ ያሠኘውን ፡ ያድርግ ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 14 ፤ ኢዮአብና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ሕዝብ ፡ ለሰልፍ ፡ ወደሶርያውያን ፡ ፊት ፡ ቀረቡ ፥ እነርሱም ፡ ከፊቱ ፡ ሸሹ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 15 ፤ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ሶርያውያን ፡ እንደ ፡ ሸሹ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከወንድሙ ፡ ከአቢሳ ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ ገቡ ። ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 16 ፤ ሶርያውያንም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መልእክተኞች ፡ ልከው ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ የነበሩትን ፡ ሶርያውያን ፡ አስመጡ ፤ የአድርዐዛርም ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ሾፋክ ፡ በፊታቸው ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፥ ዮርዳኖስንም ፡ ተሻግሮ ፡ መጣባቸው ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፤ ዳዊትም ፡ በሶርያውያን ፡ ላይ ፡ በተሰለፈ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋጉ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 18 ፤ ሶርያውያንም ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፤ ዳዊትም ፡ ከሶርያውያን ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሠረገለኞች ፥ አርባ ፡ ሺሕም ፡ እግረኞች ፡ ገደለ ፥ የሰራዊቱንም ፡ አለቃ ፡ ሾፋክን ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፡ 19 ፡ 19 ፤ የአድርዐዛርም ፡ ባሪያዎች ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተሸነፉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፥ ገበሩለትም ፤ ሶርያውያንም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

መዋ.1 ፡ 20 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዓመት ፡ መለወጫ ፡ ነገሥታት ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በሚወጡበት ፡ ጊዜ ፡

ኢዮአብ ፡ ሰራዊቱን ፡ አወጣ ፥ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ አጠፋ ፤ መጥቶም ፡ ረባትን ፡ ከበበ ። ዳዊትም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቈይቶ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 2 ፤ ኢዮአብም ፡ ረባትን ፡ መቶ ፡ አፈረሳት ። ዳዊትም ፡ የንጉሣቸውን ፡ ዘውድ ፡ ከራሱ ፡ ላይ ፡ ወሰደ ፥ ክብደቱም ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ያኽል ፡ ነበር ፥ ክቡርም ፡ ዕንቊ ፡ ነበረበት ፥ በዳዊትም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ፤ ከከተማዪቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ አወጣ ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 3 ፤ በውስጧም ፡ የነበረውን ፡ ሕዝብ ፡ አውጥቶ ፡ በመጋዝና ፡ በብረት ፡ መቈፈሪያ ፡ በመጥረቢያም ፡ እንዲሠሩ ፡ አደረጋቸው ። እንዲሁም ፡ ዳዊት ፡ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ። ዳዊትም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 4 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በጌዝር ፡ ላይ ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ ኾነ ፤ ኩሳታዊውም ፡ ሴቦካይ ፡ ከራፋይም ፡ ወገን ፡ የነበረውን ፡ ሲፋይን ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 5 ፤ ደግሞም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ፤ የያዒርም ፡ ልጅ ፡ ኤልያናን ፡ የጦሩ ፡ የቦ ፡ እንደ ፡ ሽማኔ ፡ መጠቅለያ ፡ የነበረውን ፡ የጌት ፡ ሰው ፡ የጎልያድን ፡ ወንድም ፡ ለሕሚን ፡ ገደለ ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 6 ፤ ደግሞ ፡ በጌት ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ፤ ከዚያም ፡ በእጁና ፡ በእግሩ ፡ ስድስት ፡ ስድስት ፡ ኹላኹሉ ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ጣቶች ፡ ያሉት ፡ አንድ ፡ ረዥም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ከራፋይም ፡ የተወለደ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 7 ፤ እስራኤልንም ፡ በተገዳደረ ፡ ጊዜ ፡ የዳዊት ፡ ወንድም ፡ የሳምዓ ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ገደለው ።

መዋ.1 ፥ 20 ፥ 8 ፤ እነዚያም ፡ በጌት ፡ ውስጥ ፡ ከራፋይም ፡ የተወለዱ ፡ ነበሩ ፤ በዳዊትም ፡ እጅ ፡ በባሪያዎቹም ፡ እጅ ፡ ወደቁ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 1 ፤ ሰይጣንም ([233]) ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ተነሣ ፥ እስራኤልንም ፡ ይቈጥር ፡ ዘንድ ፡ ዳዊትን ፡ አንቀሳቀሰው ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 2 ፤ ዳዊትም ፡ ኢዮአብንና ፡ የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፦ ኺዱ ፥ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ እስራኤልን ፡ ቍጠሩ ፥ ድምራቸውንም ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ አስታውቁኝ ፡ አላቸው ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 3 ፤ ኢዮአብም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ በአኹኑ ፡ ላይ ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ይጨምር ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ኹሉ ፡ የጌታዬ ፡ ባሪያዎች ፡ አይደሉምን ፧ ይህን ፡ ነገር ፡ ጌታዬ ፡ ለምን ፡ ይሻል ፧ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያመጣል ፧

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የንጉሡ ፡ ቃል ፡ በኢዮአብ ፡ ላይ ፡ አሸነፈ ፤ ኢዮአብም ፡ ወጥቶ ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተዘዋወረ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጣ ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 5 ፤ ኢዮአብም ፡ የቈጠራቸውን ፡ የሕዝቡን ፡ ድምር ፡ ለዳዊት ፡ ሰጠ ፤ ከእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ሚልዮን ፡ ከመቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰዎችን ፡ አገኘ ፤ ከይሁዳም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፡ ሰይፍ ፡ የሚመዙ ፡ ሰዎችን ፡ አገኘ ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 6 ፤ የንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ በኢዮአብ ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነበርና ፥ ሌዊና ፡ ብንያም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አልተቈጠሩም ።

መዋ.1 ፥ 21 ፥ 7 ፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቈጣ ፥ እስራኤልንም ፡ ቀሠፈ ።

---

233 ዕብ. ፥ ሳጣን ፡ (ሰይጣን • ጠላት ፥ ባላጋራ ፥ ከሳሽ ፥ አሳጭ) ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 8 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፦ ይህን ፡ በማድረግ ፡ እጅግ ፡ በድያለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ታላቅ ፡ ስንፍና ፡ አድርጌያለኹና ፡ የባሪያኽን ፡ ኀጢአት ፡ ታስወግድ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊት ፡ ባለራእይ ፡ ለጋድ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 10 ፤ ኺድ ፥ ለዳዊት ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሦስቱን ፡ ነገሮች ፡ በፊትኽ ፡ አኖራለኹ ፤ አደርግብኽ ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ አንዱን ፡ ምረጥ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 11 ፤ ጋድም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጥቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የምትወደውን ፡ ምረጥ ፤

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 12 ፤ የሦስት ፡ ዓመት ፡ ራብ ፥ ወይም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የጠላቶችኽ ፡ ሰይፍ ፡ እንዲያገኝኽ ፡ ከጠላቶችኽ ፡ መሰደድን ፥ ወይም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ቸነፈርም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መኾንን ፥ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ማጥፋትን ፡ ምረጥ ፤ አኹንም ፡ ለላከኝ ፡ ምን ፡ እንድመልስ ፡ ተመልከት ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 13 ፤ ዳዊትም ፡ ጋድን ፦ እጅግ ፡ ተጨንቄያለኹ ፤ ምሕረቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ልውደቅ ፤ በሰው ፡ እጅ ፡ ግን ፡ አልውደቅ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ቸነፈርን ፡ ሰደደ ፤ ከእስራኤልም ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ወደቁ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መልአክን ፡ ሰደደ ፤ ሊያጠፋትም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይቶ ፡ ስለ ፡ ክፉው ፡ ነገር ፡ ተጸጸተ ፥ የሚያጠፋውንም ፡ መልአክ ፦ በቃኽ ፤ አኹን ፡ እጅኽን ፡ መልስ ፡ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 16 ፤ ዳዊትም ፡ ዐይኖቹን ፡ አነሣ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፥ የተመዘዘም ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ ኾኖ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተዘርግቶ ፡ አየ ። ዳዊትም ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፉ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ እግዚአብሔርን ፦ ሕዝቡ ፡ ይቈጠር ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹ ፡ እኔ ፡ አይደለኹምን ፧ የበደልኹና ፡ ክፉ ፡ የሠራኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ እነዚህ ፡ በጎች ፡ ግን ፡ ምን ፡ አድርገዋል ፧ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እጅኽ ፡ በእኔና ፡ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ትኹን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይቀሠፍ ፡ ዘንድ ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ አትኹን ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ዳዊት ፡ ወጥቶ ፡ በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ለዳዊት ፡ እንዲነግረው ፡ ጋድን ፡ አዘዘው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንደተናገረው ፡ እንደ ፡ ጋድ ፡ ነገር ፡ ወጣ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 20 ፤ ኦርናም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ መልአኩን ፡ አየ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ አራቱ ፡ ልጆቹ ፡ ተሸሸጉ ፤ ኦርናም ፡ ስንዴ ፡ ያበራይ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 21 ፤ ዳዊትም ፡ ወደ ፡ ኦርና ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ኦርና ፡ ተመልክቶ ፡ ዳዊትን ፡ አየ ፤ ከዐውድማውም ፡ ወጥቶ ፡ ዳዊትን ፡ እጅ ፡ ሊነሣ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፋ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 22 ፤ ዳዊትም ፡ ኦርናን ፦ በላዩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ የዐውድማ ፡ ስፍራ ፡ ስጠኝ ፤ በሙሉ ፡ ዋጋ ፡ ስጠኝ ፤ መቅሠፍቱን ፡ ከሕዝቡ ፡ ይከለከላል ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 23 ፤ ኦርናም ፡ ዳዊትን ፦ ለአንተ ፡ ውሰደው ፥ ጌታዬ ፡ ንጉሡም ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡

ያድርግ ፤ እንሆ ፥ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ በሬዎቹን ፥ ለዕንጨትም ፡ የዐውድማውን ፡ ዕቃ ፥ ከእኽልም ፡ ቀ፡ርባን ፡ ስንዴውን ፡ እሰጥኻለኹ ፤ ኹሉን ፡ እሰጣለኹ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ኦ፡ርናን ፦ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለአንተ ፡ ያለውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጥቼ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በከንቱ ፡ አላቀ፡ርብምና ፡ በሙሉ ፡ ዋጋ ፡ እገዛዋለኹ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 25 ፤ ዳዊትም ፡ ስለ ፡ ስፍራው ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ወ፡ርቅ ፡ በሚዛን ፡ ለኦ፡ርና ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 26 ፤ ዳዊትም ፡ በዚያ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ጠራ ፤ ከሰማይም ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ በሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ በእሳት ፡ መለሰለት ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልአኩን ፡ አዘዘው ፥ ሰይፉንም ፡ በአፎቱ ፡ ከተተው ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 28 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢ፡ያቡሳዊው ፡ በኦ፡ርና ፡ ዐውድማ ፡ እንደ ፡ መለሰለት ፡ ዳዊት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሠራት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያና ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በገባዖን ፡ ባለው ፡ በኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 21 ፡ 30 ፤ ዳዊት ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ ሰይፍ ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ወደዚያ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፦ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ነው ፥ ይህም ፡ ለእስራኤል ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነው ፡ መሠዊያ ፡ ነው ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 2 ፤ ዳዊትም ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ የነበሩትን ፡ መጻተኞች ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ የሚወቀሩትን ፡ ድንጋዮች ፡ ይወቅሩ ፡ ዘንድ ፡ ጠራቢዎችን ፡ አኖረ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ለበሮቹ ፡ ሳንቃ ፡ ለሚኾኑ ፡ ለምስማርና ፡ ለመጠረቂያ ፡ ብዙ ፡ ብረት ፥ ከብዛቱም ፡ የተነሣ ፡ የማይመዘን ፡ ናስ ፡ አዘጋጀ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 4 ፤ ሲ፡ዶናውያንና ፡ የጢ፡ሮስ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ያመጡ ፡ ነበ፡ርና ፥ ቀ፡ጥር ፡ የሌላቸውን ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨቶች ፡ አዘጋጀ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 5 ፤ ዳዊትም ፦ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፡ ታናሽና ፡ ለጋ ፡ ብላቴና ፡ ነው ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚሠራው ፡ ቤት ፡ እጅግ ፡ ማለፊያና ፡ በአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ስሙና ፡ ክብሩ ፡ እንዲጠራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይገ፡ባ፡ል ፤ ስለዚህ ፥ አዘጋጅ፡ለታ፡ለኹ ፡ አለ ። ዳዊትም ፡ ሳይሞት ፡ አስቀድሞ ፡ ብዙ ፡ አዘጋጀ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 6 ፤ ልጁንም ፡ ሰሎሞንን ፡ ጠርቶ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 7 ፤ ዳዊትም ፡ ሰሎሞንን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ለአምላኬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ ዐስቤ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፦ እጅግ ፡ ደም ፡ አፍሰ፡ኻል ፥ ታላቅም ፡ ሰልፍ ፡ አድርገ፡ኻል ፤ በፊቴ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ደም ፡ አፍሰ፡ኻልና ፥ ለስሜ ፡ ቤት ፡

አትሠራም ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 9 ፤ እንሆ ፥ የዕረፍት ፡ ሰው ፡ የሚኾን ፡ ልጅ ፡ ይወለድልኻል ፤ በዙሪያው ፡ ካሉ ፡ ከጠላቶቹ ፡ ኹሉ ፡ አሳርፈዋለኹ ፤ ስሙ ፡ ሰሎሞን ፡ ይባላልና ፥ በዘመኑም ፡ ሰላምንና ፡ ጸጥታን ፡ ለእስራኤል ፡ እሰጣለኹ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 10 ፤ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ይሠራል ፥ ልጆም ፡ ይኾነኛል ፥ እኔም ፡ አባት ፡ እኾነዋለኹ ፤ የመንግሥቱንም ፡ ዙፋን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናለኹ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 11 ፤ አኹንም ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ ስለ ፡ አንተም ፡ እንደተናገረው ፡ ያከናውንልኽ ፥ የአምላክኽንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሥራ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 12 ፤ ብቻ ፡ የአምላክኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበብንና ፡ ማስተዋልን ፡ ይስጥኽ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ያሠልጥንኽ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ሙሴን ፡ ያዘዘውን ፡ ሥርዐትና ፡ ፍርድ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ብትጠነቀቅ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይከናወንልኻል ፤ አይዞኽ ፥ በርታ ፤ አትፍራ ፥ አትደንግጥም ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 14 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ በድኽነቴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ወርቅና ፡ አንድ ፡ ሚልዮን ፡ መክሊት ፡ ብር ፥ ሚዛንም ፡ የሌላቸው ፡ ብዙ ፡ ናስና ፡ ብረት ፡ አዘጋጀኹ ፤ ደግሞም ፡ ዕንጨትና ፡ ድንጋዮች ፡ አዘጋጀኹ ፥ አንተም ፡ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ጨምር ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 15 ፤ ባንተም ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሠራተኞች ፥ ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡ ወቃሪዎችና ፡ ጠራቢዎች ፥ ሥራውንም ፡ ኹሉ ፡ ለማድረግ ፡ ጠቢባን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አሉ ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 16 ፤ የሚሠሩበት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ናስና ፡ ብረት ፡ ቍጥር ፡ የለውም ፤ ተነሥተኽ ፡ ሥራ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 17 ፤ ዳዊትም ፡ ደግሞ ፡ ልጁን ፡ ሰሎሞንን ፡ ያግዙ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዛቸው ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 18 ፤ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አይደለምን ፧ በምድርም ፡ የሚቀመጡትን ፡ በእጄ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ ምድርም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ተገዝታለችና ፥ በዙሪያችኹ ፡ ኹሉ ፡ ዕረፍትን ፡ ሰጥቷችኋል ።

መዋ.1 ፡ 22 ፡ 19 ፤ አኹንም ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ ልባችኹንና ፡ ነፍሳችኹን ፡ ስጡ ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ ወደሚሠራው ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ታቦትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ታመጡ ፡ ዘንድ ፡ ተነሥታችኹ ፡ የአምላክን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ሥሩ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። _____

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ በሸመገለ ፡ ጊዜ ፥ ዕድሜንም ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ ልጁን ፡ ሰሎሞንን ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አነገሠው ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 2 ፤ የእስራኤልንም ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ካህናቱንም ፥ ሌዋውያኑንም ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 3 ፤ ሌዋውያንም ፡ ከሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ገምሮ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ተቈጠሩ ፤ ቍጥራቸው ፡ በያንዳንዱ ፡ ነፍስ ፡ ወከፍ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 4 ፤ ከነዚህም ፡ ውስጥ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ የሚያሠሩት ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡

ነበሩ ፤ ስድስቱ ፡ ሺሕም ፡ አለቃዎችና ፡ ፈራጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 5 ፤ አራቱ ፡ ሺሕም ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ፤ አራቱ ፡ ሺሕም ፡ ለምስጋና ፡ በተሠሩት ፡ በዜማ ፡ ዕቃዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 6 ፤ ዳዊትም ፡ እንደ ፡ ሌዊ ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ጌድሶንና ፡ እንደ ፡ ቀአት ፡ እንደ ፡ ሜራሪም ፡ በየሰሞናቸው ፡ ከፈላቸው ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 7 ፤ ከጌድሶናውያን ፡ ለአዳንና ፡ ሰሜኢ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 8 ፤ የለአዳን ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ይሒኤል ፥ ዜቶም ፥ ኢዮኤል ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 9 ፤ የሰሜኢ ፡ ልጆች ፡ ሰሎሚት ፥ ሐዝኤል ፥ ሀራን ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ የለአዳን ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 10 ፤ የሰሜኢ ፡ ልጆች ፡ ኢኢት ፥ ዚዛ ፥ የዑስ ፥ በሪዐ ፡ ነበሩ ። እነዚህ ፡ አራቱ ፡ የሰሜኢ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 11 ፤ አለቃው ፡ ኢኢት ፡ ነበረ ፤ ኹለተኛው ፡ ዚዛ ፡ ነበረ ፤ የዑስና ፡ በሪዐ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ አልነበሯቸውም ፤ ስለዚህ ፥ እንደ ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ቤት ፡ ኾነው ፡ ተቈጠሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 12 ፤ የቀአት ፡ ልጆች ፡ ዕምበረም ፥ ይስዓር ፥ ኬብሮን ፥ ዑዝኤል ፡ አራት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 13 ፤ የዕምበረም ፡ ልጆች ፡ አሮንና ፡ ሙሴ ፡ ነበሩ ፤ አሮንም ፡ ከዥሉ ፡ በላይ ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ተለየ ፥ ርሱና ፡ ልጆቹ ፥ ለዘለዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያጥንና ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፥ በስሙም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይባርክ ፡ ዘንድ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ የሙሴ ፡ ልጆች ፡ በሌዊ ፡ ነገድ ፡ ተቈጠሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 15 ፤ የሙሴ ፡ ልጆች ፡ ጌርሳምና ፡ አልዓዛር ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 16 ፤ የጌርሳም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ ሱባኤል ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 17 ፤ የአልዓዛርም ፡ ልጆች ፡ አለቃ ፡ ረዓብያ ፡ ነበረ ፤ አልዓዛርም ፡ ሌላዎች ፡ ልጆች ፡ አልነበሩትም ፤ የረዓብያ ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 18 ፤ የይስዓር ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ሰሎሚት ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 19 ፤ የኬብሮን ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ይሪያ ፥ ኹለተኛው ፡ አማርያ ፥ ሦስተኛው ፡ የሕዚኤል ፥ አራተኛው ፡ ይቅምዓም ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 20 ፤ የዑዝኤል ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ሚካ ፥ ኹለተኛው ፡ ይሺያ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 21 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ሞሖሊና ፡ ሙሲ ፡ ነበሩ ። የሞሖሊ ፡ ልጆች ፡ አልዓዛርና ፡ ቂስ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 22 ፤ አልዓዛርም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ሳይወልድ ፡ ሞተ ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ የቂስ ፡ ልጆች ፡ አገቧቸው ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 23 ፤ የሙሲ ፡ ልጆች ፡ ሞሖሊ ፥ ዔደር ፥ ኢያሪሙት ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 24 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ በሠሩ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በነበሩ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ በስማቸው ፡ በተቈጠሩት ፡ ላይ ፡ የአባቶች ፡ ቤት ፡ አለቃዎች ፡ የኾኑት ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 25 ፤ ዳዊትም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቷል ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀመጣል ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 26 ፤ ሌዋውያንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ማደሪያውንና ፡ የማገልገያውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አይሸከሙም ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 27 ፤ በመጨረሻውም ፡ በዳዊት ፡ ትእዛዝ ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜ ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉት ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ ተቈጠሩ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 28 ፤ ሥራቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ በያደባባዩና ፡ በየጓዳው ፡ ውስጥ ፡ ለማገልገል ፥ ቅዱሱንም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ለማንጻት ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ለመሥራት ፡ ከአሮን ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 29 ፤ ደግሞም ፡ ገጸ ፡ ኅብስት ፥ ሥሥ ፡ ቂጣም ፡ ቢኾን ፥ በምጣድም ፡ ቢጋገር ፥ ቢለወስም ፥ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ በኾነው ፡ በመልካሙ ፡ ዱቄት ፡ በመስፈሪያና ፡ በልክ ፡ ኹሉ ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 30 ፤ ሥራቸውም ፡ በየጧቱና ፡ በየማታው ፡ ቆመው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማመስገንና ፡ ለማክበር ፥

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 31 ፤ በየሰንበታቱም ፡ በየመባቻዎቹም ፡ በየበዓላቱም ፡ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ ቍጥር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘወትር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፡ ለማቅረብ ፥

መዋ.1 ፡ 23 ፡ 32 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ የመገናኛውን ፡ ድንኳን ፡ ሥርዐት ፡ የመቅደሱንም ፡ ሥርዐት ፡ የወንድሞቻቸውንም ፡ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ ሥርዐት ፡ ለመጠበቅ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 1 ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ሰሞን ፡ ይህ ፡ ነው ። የአሮን ፡ ልጆች ፡ ናዳብ ፥ አብዩድ ፥ አልዓዛር ፥ ኢታምር ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 2 ፤ ናዳብና ፡ አብዩድ ፡ ግን ፡ ልጆች ፡ ሳይወልዱ ፡ ከአባታቸው ፡ በፊት ፡ ሞቱ ፤ አልዓዛርና ፡ ኢታምርም ፡ ካህናት ፡ ኾኑ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 3 ፤ ዳዊትም ፡ ከአልዓዛር ፡ ልጆች ፡ ከሳዶቅ ፡ ጋራ ፥ ከኢታምርም ፡ ልጆች ፡ ከአቢሜሌክ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ አገልግሎታቸው ፡ ሥርዐት ፡ ከፍሎ ፡ መደባቸው ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 4 ፤ የአልዓዛርም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ ከኢታምርም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ በልጠው ፡ ተገኙ ፤ እንዲህም ፡ ተመደቡ ፤ ከአልዓዛር ፡ ልጆች ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፥ ከኢታምርም ፡ ልጆች ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ስምንት ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 5 ፤ ከአልዓዛርና ፡ ከኢታምርም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የመቅደሱና ፡ የእግዚአብሔር ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩና ፥ እነዚህና ፡ እነዚያ ፡ እንዲህ ፡ በዕጣ ፡ ተመደቡ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 6 ፤ ከሌዋውያንም ፡ ወገን ፡ የነበረው ፡ የናትናኤል ፡ ልጅ ፡ ጸሓፊው ፡ ሸማያ ፡ በንጉሡና ፡ በአለቃዎቹ ፡ ፊት ፥ በካህኑ ፡ በሳዶቅና ፡ በአብያታርም ፡ ልጅ ፡ በአቢሜሌክ ፡ ፊት ፥ በካህናቱና ፡ በሌዋውያኑ ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ፊት ፡ ጻፋቸው ፤ አንዱንም ፡ የአባት ፡ ቤት ፡ ለአልዓዛር ፥ አንዱንም ፡ ለኢታምር ፡ ጻፈ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 7 ፤ መዝሙሪያውም ፡ ዕጣ ፡ ለዮአሪብ ፡ ወጣ ፥ ኹለተኛው ፡ ለዮዳዔ ([234]) ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 8 ፤ ሦስተኛው ፡ ለካሪም ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 9 ፤ አራተኛው ፡ ለሥዖሪም ፥ ዐምስተኛው ፡ ለመልክያ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 10 ፤ ስድስተኛው ፡ ለሚያሚን ፥ ሰባተኛው ፡ ለአቆስ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 11 ፤ ስምንተኛው ፡ ለአብያ ፥ ዘጠነኛው ፡ ለኢያሱ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 12 ፤ ዐሥረኛው ፡ ለሴኬንያ ፥ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ለኤልያሴብ ፥ ዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ለያቂም ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 13 ፤ ዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ለኦፓ ፥ ዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ለየሼብአብ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 14 ፤ ዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ለቢልጋ ፥ ዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ለኢሜር ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 15 ፤ ዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ለኤዚር ፥ ዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ለሃፊጼጽ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 16 ፤ ዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ለፈታያ ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 17 ፤ ኻያኛው ፡ ለኤዜቄል ፥ ኻያ ፡ አንደኛው ፡ ለያኪን ፥ ኻያ ፡ ኹለተኛው ፡ ለጋሙል ፥

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 18 ፤ ኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ለድላያ ፥ ኻያ ፡ አራተኛው ፡ ለመዓዝያ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 19 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፥ አባታቸው ፡ አሮን ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ሥርዐት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚገቡበት ፡ የአገልግሎታቸው ፡ ሥርዐት ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 20 ፤ ከቀሩትም ፡ የሌዊ ፡ ልጆች ፤ ከዕምበረም ፡ ልጆች ፡ ሱባኤል ፤ ከሱባኤል ፡ ልጆች ፡ ዬሕድያ ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 21 ፤ 22 ፤ ከረዓብያ ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ይሺያ ፤ ከይስዓራውያን ፡ ሰሎሚት ፤ ከሰሎሚት ፡ ልጆች ፡ ያሐት ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 23 ፤ ከኬብሮንም ፡ ልጆች ፡ አለቃው ፡ ይሪያ ፥ ኹለተኛው ፡ አማርያ ፥ ሦስተኛው ፡ የሕዚኤል ፥ አራተኛው ፡ ይቀምዓም ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 24 ፤ የዑዝኤል ፡ ልጅ ፡ ሚካ ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 25 ፤ የሚካ ፡ ልጅ ፡ ሻሚር ፤ የሚካ ፡ ወንድም ፡ ይሺያ ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 26 ፤ ከይሺያ ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስ ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ሞሖሊ ፥ ሙሲ ፤ ከያዝያ ፡ ልጅ ፡ በኖ ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 27 ፤ የሜራሪ ፡ ልጆች ፤ ከያዝያ ፡ በኖ ፥ ሾሃም ፥ ዘኩር ፥ ዔብሪ ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 28 ፤ ከሞሖሊ ፡ አልዓዛር ፥ ርሱም ፡ ልጆች ፡ አልነበሩት ፤

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 29 ፤ ከቂስ ፤ የቂስ ፡ ልጅ ፡ ይረሕምኤል ፤ የሙሲም ፡ ልጆች ፤ ሞሖሊ ፥ ዔዳር ፥ ኢያሪሙት ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 30 ፤ እነዚህ ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ የሌዋውያን ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 24 ፡ 31 ፤ እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊትና ፡ በሳዶቅ ፡ በአቢሜሌክም ፡ በሌዋውያንና ፡ በካህናት ፡

---

234 ዕብ. ፥ ይዳዕያህ ፡ (ይዳዕ ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ዐወቀ) ።

አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ፊት ፥ ታላቁም ፡ እንደ ፡ ታናሹ ፥ እንደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ እንደአሮን ፡ ልጆች ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 1 ፤ ዳዊትና ፡ የሰራዊቱ ፡ አለቃዎችም ፡ ከአሣፍና ፡ ከኤማን ፡ ከኤዶታም ፡ ልጆች ፡ በመሰንቆና ፡ በበገና ፡ በጸናጽልም ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩትን ፡ ሰዎች ፡ ለማገልገል ፡ ለዩ ፤ በአገልግሎታቸውም ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 2 ፤ ከአሣፍ ፡ ልጆች ፤ ዘኩር ፥ የሴፍ ፥ ነታንያ ፥ አሸርኤላ ፤ እነዚህ ፡ የአሣፍ ፡ ልጆች ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ትንቢት ፡ ከተናገረው ፡ ከአሣፍ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 3 ፤ ከኤዶታም ፡ የኤዶታም ፡ ልጆች ፤ ጎዶልያስ ፥ ጽሪ ፥ የሻያ ፥ ሰሜኢ ፥ ሐሸብያ ፥ መቲትያ ፥ እነዚህ ፡ ስድስቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ በመሰንቆ ፡ ትንቢት ፡ ከተናገረው ፡ ከአባታቸው ፡ ከኤዶታም ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 4 ፤ ከኤማን ፡ የኤማን ፡ ልጆች ፤ ቡቅያ ፥ መታንያ ፥ ዓዛርዔል ፥ ሱባኤል ፥ ኢያሪሙት ፥ ሐናንያ ፥ ሐናኒ ፥ ኤልያታ ፥ ጊዶልቲ ፥ ሮማንቲዔዘር ፥ ዮሽብቃሻ ፥ መሎቲ ፥ ሆቲር ፥ መሐዝዮት ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 5 ፤ እነዚህ ፡ ሹሉ ፡ ቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ከፍ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የንጉሡ ፡ ባለራእይ ፡ የኾነው ፡ የኤማን ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ። እግዚአብሔርም ፡ ለኤማን ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ወንዶች ፡ ልጆችንና ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 6 ፤ እነዚህ ፡ ሹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በጸናጽልና ፡ በበገና ፡ በመሰንቆም ፡ ይዘምሩ ፡ ዘንድ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ ከአባታቸው ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ነበሩ ፤ አሣፍም ፡ ኤዶታምም ፡ ኤማንም ፡ ከንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ በታች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 7 ፤ የብልኀተኞቹም ፡ ቍጥር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማመስገን ፡ ከሚያውቁ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስምንት ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 8 ፤ ሹሉም ፡ ተካክለው ፥ ታናሹ ፡ እንደ ፡ ታላቁ ፥ አስተማሪውም ፡ እንደ ፡ ተማሪው ፥ ለሰሞናቸው ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 9 ፤ የፊተኛው ፡ ዕጣ ፡ ከአሣፍ ፡ ወገን ፡ ለነበረው ፡ ለዮሴፍ ፡ ወጣ ፤ ኹለተኛው ፡ ለጎዶልያስ ፡ ወጣ ፤ ርሱ ፡ ወንድሞቹም ፡ ልጆቹም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 10 ፤ ሦስተኛው ፡ ለዘኩር ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 11 ፤ አራተኛው ፡ ለይጽሪ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 12 ፤ ዐምስተኛው ፡ ለነታንያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 13 ፤ ስድስተኛው ፡ ለቡቅያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 14 ፤ ሰባተኛው ፡ ለይሽርኤል ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 15 ፤ ስምንተኛው ፡ ለየሻያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፥ 25 ፥ 16 ፤ ዘጠነኛው ፡ ለመታንያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 17 ፤ ዐሥረኛው ፡ ለሰሜኢ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 18 ፤ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ለዓዛርኤል ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 19 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ለሐሸብያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 20 ፤ ዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ለሱባኤል ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 21 ፤ ዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ለመቲትያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 22 ፤ ዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ለኢያሪሙት ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 23 ፤ ዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ለሐናንያ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 24 ፤ ዐሥራ ፡ ሰባተኛው ፡ ለዮሽብቃሻ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 25 ፤ ዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ለሐናኒ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 26 ፤ ዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ለመሎቲ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 27 ፤ ኻያኛው ፡ ለኤልያታ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 28 ፤ ኻያ ፡ አንደኛው ፡ ለሆቲር ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 29 ፤ ኻያ ፡ ኹለተኛው ፡ ለጊዶልቲ ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 30 ፤ ኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ለመሐዚዮት ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

መዋ.1 ፡ 25 ፡ 31 ፤ ኻያ ፡ አራተኛው ፡ ለሮማንቲዔዘር ፡ ለልጆቹም ፡ ለወንድሞቹም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ወጣ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 1 ፤ በረኞችም ፡ እንደዚህ ፡ ተመደቡ ፤ ከቆሬያውያን ፡ ከአሣፍ ፡ ልጆች ፡ የቆሬ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 2 ፤ ሜሱላም ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ በኩሩ ፡ ዘካርያስ ፥ ኹለተኛው ፡ ይዲኤል ፥ ሦስተኛው ፡ ዮዛባት ፥

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 3 ፤ አራተኛው ፡ የትኒኤል ፥ ዐምስተኛው ፡ ዔላም ፥ ስድስተኛው ፡ ይሆሐናን ፥ ሰባተኛው ፡ ኤሊሆዔናይ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባርኮታልና ፥ ዖቤድኤዶም ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ በኩሩ ፡ ሸማያ ፥ ኹለተኛው ፡ ዮዛባት ፥ ሦስተኛው ፡ ኢዮአስ ፥ አራተኛው ፡ ሣካር ፥ ዐምስተኛው ፡ ናትናኤል ፥

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 5 ፤ ስድስተኛው ፡ ዓሚኤል ፥ ሰባተኛው ፡ ይሳኮር ፥ ስምንተኛው ፡ ፒላቲ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 6 ፤ ለልጁም ፡ ለሸማያ ፡ ደግሞ ፡ ልጆች ፡ ተወለዱለት ፤ ጽኑዓንም ፡ ኀያላን ፡ ነበሩና ፥ በአባታቸው ፡ ቤት ፡ ሠለጠኑ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 7 ፤ ለሸማያ ፡ ልጆች ፡ ዖትኒ ፥ ራፋኤል ([235]) ፥ ዖቤድ ፥ ወንድሞቹም ፡ ኀያላን ፡ የነበሩ ፡ ኤልዛባድ ፥ ኤልሁ ([236]) ፥ ሰማክያ ።

---

235 ዕብ. ፥ ርፋኤል ፡ (ረፍአ ፡ አምላክ • አምላክ ፡ ፈወሰ ፥ ጠገነ) ።

236 ዕብ. ፥ ኤሊሁ ፡ (አምላኩ) ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 8 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የዖቤድኤዶም ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ ልጆቻቸውም ፡ ወንድሞቻቸውም ፡ ለማገልገል ፡ ኀያላን ፡ የነበሩ ፡ የዖቤድኤዶም ፡ ልጆች ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 9 ፤ ለሜሱላም ፡ ኀያላን ፡ የነበሩ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ልጆችና ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩት ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 10 ፤ ከሜራሪም ፡ ልጆች ፡ ለነበረው ፡ ለሖሳ ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ አለቃውም ፡ ሽምሪ ፡ ነበረ ፤ በኵር ፡ አልነበረም ፥ አባቱ ፡ ግን ፡ አለቃ ፡ አደረገው ፤

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 11 ፤ ኹለተኛውም ፡ ኬልቅያስ ፥ ሦስተኛው ፡ ጥበልያ ፥ አራተኛው ፡ ዘካርያስ ፡ ነበረ ፤ የሖሳ ፡ ልጆችና ፡ ወንድሞች ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 12 ፤ እንደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ኾነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ የበረኞች ፡ የአለቃዎች ፡ ሰሞነኞች ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 13 ፤ በበሩም ፡ ኹሉ ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ታናሹና ፡ ታላቁ ፡ ተካክለው ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 14 ፤ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ዕጣ ፡ ለሰሌምያ ፡ ወደቀ ። ለልጁም ፡ ብልኅ ፡ መካር ፡ ለኾነው ፡ ለዘካርያስ ፡ ዕጣ ፡ ጣሉ ፤ ዕጣውም ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ወጣ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 15 ፤ ለዖቤድኤዶም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፥ ለልጆቹም ፡ ለዕቃ ፡ ቤቱ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 16 ፤ ለሰፊንና ፡ ለሖሳ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፥ በዐቀበቱም ፡ መንገድ ፡ ባለው ፡ በሸሌኬት ፡ በር ፡ በኩል ፡ ጥበቃ ፡ ከጥበቃ ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ወጣ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 17 ፤ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ስድስት ፡ ሌዋውያን ፡ ነበሩ ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ለየዕለቱ ፡ አራት ፥ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ለየዕለቱ ፡ አራት ፥ ለዕቃ ፡ ቤቱም ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 18 ፤ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ በፈርባር ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ አራት ፥ በፈርባርም ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 19 ፤ ከቆሬና ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ የነበሩ ፡ የበረኞች ፡ ሰሞን ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 20 ፤ ከሌዋውያን ፡ አኪያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሚኾኑ ፡ ቤተ ፡ መዛግብትና ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 21 ፤ የለአዳን ፡ ልጆች ፤ ለለአዳን ፡ የኾኑ ፡ የጌድሶናውያን ፡ ልጆች ፥ ለጌድሶናዊ ፡ ለለአዳን ፡ የኾኑ ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ይሒኤሊ ፤

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 22 ፤ የይሒኤሊ ፡ ልጆች ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሚኾኑ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ ዜቶም ፥ ወንድሙም ፡ ኢዮኤል ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 23 ፤ ከዕምበረማውያን ፥ ከይስዓራውያን ፥ ከኬብሮናውያን ፥ ከዑዝኤላውያን ፤

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 24 ፤ የሙሴ ፡ ልጅ ፡ የጌርሳም ፡ ልጅ ፡ ሱባኤል ፡ በቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 25 ፤ ወንድሞቹም ፤ ከአልዓዛር ፡ ልጁ ፡ ረዓብያ ፥ ልጁም ፡ የሻያ ፥ ልጁም ፡ ኢዮራም ፥ ልጁም ፡ ዝክሪ ፥ ልጁም ፡ ሰሎሚት ፡ መጡ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 26 ፤ ይህ ፡ ሰሎሚትና ፡ ወንድሞቹ ፡ ንጉሡ ፡ ዳዊትና ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ ሻለቃዎችና ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፡ የሰራዊቱም ፡ አለቃዎች ፥ በቀደሱት ፡ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡

ነበር ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 27 ፤ በሰልፍም ፡ ከተገኘው ፡ ምርኮ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለማበጀት ፡ ቀደሱ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 28 ፤ ባለራእዩም ፡ ሳሙኤል ፥ የቂስም ፡ ልጅ ፡ ሳኦል ፥ የኔርም ፡ ልጅ ፡ አበኔር ፥ የጽሩያም ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ የቀደሱት ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ኹሉ ፡ ከሰሎሚትና ፡ ከወንድሞቹ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 29 ፤ ከይስዓራውያን ፡ ከናንያና ፡ ልጆቹ ፡ ሹማምትና ፡ ፈራጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በውጭው ፡ ሥራ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 30 ፤ ከኬብሮናውያን ፡ ሐሸብያና ፡ ወንድሞቹ ፥ ጽኑዓን ፡ የነበሩት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ለንጉሡም ፡ አገልግሎት ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 31 ፤ ከኬብሮናውያንም ፡ እንደአባቶች ፡ ቤቶች ፡ ትውልዶች ፡ የኬብሮናውያን ፡ አለቃ ፡ ይርያ ፡ ነበረ ። ዳዊት ፡ በነገሠ ፡ በአርባኛው ፡ ዓመት ፡ ይፈልጓቸው ፡ ነበር ፤ በእነርሱም ፡ መካከል ፡ በገለዓድ ፡ ኢያዜር ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ፤

መዋ.1 ፡ 26 ፡ 32 ፤ ወንድሞቹም ፡ ጽኑዓን ፡ የነበሩት ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ። ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጕዳይ ፡ ኹሉና ፡ ለንጉሡ ፡ ጕዳይ ፡ በሮቤላውያንና ፡ በጋዳውያን ፡ በምናሴም ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ላይ ፡ ሹሞች ፡ አደረጋቸው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችና ፡ የሺሕ ፡ አለቃዎች ፡ የመቶ ፡ አለቃዎችም ፡ በክፍሎች ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡን ፡ ያገለገሉትም ፡ ሹማምት ፡ እንደ ፡ ቍጥራቸው ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ። እነዚህም ፡ ክፍሎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ኾነው ፡ በዓመት ፡ ወራት ፡ ኹሉ ፡ በየወሩ ፡ ይገቡና ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 2 ፤ ለመዠመሪያው ፡ ወር ፡ በአንደኛው ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ የዘብድኤል ፡ ልጅ ፡ ያሾብዓም ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሠፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 3 ፤ ርሱ ፡ ከፋሬስ ፡ ልጆች ፡ ነበረ ፤ ለመዠመሪያው ፡ ወር ፡ በሠፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 4 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ አሖሓዊው ፡ ዱዲ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሠፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 5 ፤ ለሦስተኛው ፡ ወር ፡ ሦስተኛው ፡ የሠፍራ ፡ አለቃ ፡ የካህኑ ፡ የዮዳሄ ፡ ልጅ ፡ በናያስ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሠፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 6 ፤ ይህ ፡ በናያስ ፡ በሠላሳው ፡ መካከል ፡ ኀያል ፡ ኾኖ ፡ በሠላሳው ፡ ላይ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ልጁ ፡ ዓሚዛባድ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 7 ፤ ለአራተኛው ፡ ወር ፡ አራተኛው ፡ አለቃ ፡ የኢዮአብ ፡ ወንድም ፡ ዐሳሄል ፥ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ ዝባድያ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሠፍራ ፡ ነበር ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 8 ፤ ለዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ዐምስተኛው ፡ አለቃ ፡ ይዝራዊው ፡ ሸምሁት ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ሠፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 9 ፤ ለስድስተኛው ፡ ወር ፡ ስድስተኛው ፡ አለቃ ፡ የቴቁሐዊው ፡ የዒስካ ፡ ልጅ ፡ ዒራስ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 10 ፤ ለሰባተኛው ፡ ወር ፡ ሰባተኛው ፡ አለቃ ፡ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ የኾነ ፡ ፍሎናዊው ፡ ሴሌስ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 11 ፤ ለስምንተኛው ፡ ወር ፡ ስምንተኛው ፡ አለቃ ፡ ከዛራውያን ፡ የነበረው ፡ ኩሳታዊው ፡ ሲቦካይ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 12 ፤ ለዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ዘጠነኛው ፡ አለቃ ፡ ከብንያማውያን ፡ የነበረው ፡ ዓናቶታዊው ፡ አቢዔዜር ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 13 ፤ ለዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ዐሥረኛው ፡ አለቃ ፡ ከዛራውያን ፡ የነበረው ፡ ነጦፋዊው ፡ ኖኤሬ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 14 ፤ ለዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ አለቃ ፡ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ የነበረው ፡ ጲርዓቶናዊው ፡ በናያስ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 15 ፤ ለዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ አለቃ ፡ ከጎቶንያል ፡ ወገን ፡ የነበረው ፡ ነጦፋዊው ፡ ሔልዳይ ፡ ነበረ ፤ በርሱም ፡ ክፍል ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጭፍራ ፡ ነበረ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 16 ፤ በእስራኤልም ፡ ነገዶች ፡ ላይ ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፡ በሮቤላውያን ፡ ላይ ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፤ በስምዖናውያን ፡ የመዓካ ፡ ልጅ ፡ ሰፋጥያስ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 17 ፤ በሌዊ ፡ ላይ ፡ የቀሙኤል ፡ ልጅ ፡ ሐሸቢያ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 18 ፤ በአሮን ፡ ላይ ፡ ሳዶቅ ፤ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ከዳዊት ፡ ወንድሞች ፡ ኤሊሁ ፤ በይሳኮር ፡ ላይ ፡ የሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ዖምሪ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 19 ፤ በዛብሎን ፡ ላይ ፡ የዐብድዩ ፡ ልጅ ፡ ይሽማያ ፤ በንፍታሌም ፡ ላይ ፡ የዓዝሪኤል ፡ ልጅ ፡ ኢያሪሙት ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 20 ፤ በኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የዓዛዝያ ፡ ልጅ ፡ ሆሴዕ ፤ በምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ላይ ፡ የፈዳያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮኤል ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 21 ፤ በገለዓድ ፡ ባለው ፡ በምናሴ ፡ ነገድ ፡ እኩሌታ ፡ ላይ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ አዶ ፤ በብንያም ፡ ላይ ፡ የአበኔር ፡ ልጅ ፡ የዕሢኤል ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 22 ፤ በዳን ፡ ላይ ፡ የይሮሐም ፡ ልጅ ፡ ዓዛርኤል ፤ እነዚህ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ያበዛ ፡ ዘንድ ፡ ተናግሮ ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ በታች ፡ የነበሩትን ፡ አልቈጠረም ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 24 ፤ የጽሩያ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአብ ፡ መቍጠር ፡ ገመረ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልፈጸመም ፤ ስለዚህም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ኾነ ፥ ቍጥራቸውም ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ መዝገብ ፡ አልተጻፈም ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 25 ፤ በንጉሡም ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ የዓዲኤል ፡ ልጅ ፡ ዓዝሞት ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤ በሜዳውም ፡ በከተማዎችም ፡ በመንደሮችም ፡ በግንቦችም ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ላይ ፡ የዖዝያ ፡ ልጅ ፡ ዮናታን ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 26 ፤ መሬቱን ፡ የሚያበጃጁትና ፡ ዕርሻውን ፡ በሚያርሱት ፡ ላይ ፡ የክሉብ ፡ ልጅ ፡ ዔዝሪ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 27 ፤ በወይንም ፡ ቦታዎች ፡ ላይ ፡ ራማታዊው ፡ ሰሜኢ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤ ለወይንም ፡ ጠጅ ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ በሚኾነው ፡ በወይኑ ፡ ሰብል ፡ ላይ ፡ ሽፋማዊው ፡ ዘብዲ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 28 ፤ በቈላውም ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ በወይራውና ፡ በሾላው ፡ ዛፎች ፡ ላይ ፡ ጌድራዊው ፡ በአልሐናን ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤ በዘይቱም ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ኢዮአስ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 29 ፤ በሳሮንም ፡ በሚሰማሩ ፡ ከብቶች ፡ ላይ ፡ ሳሮናዊው ፡ ሰጥራይ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤ በሸለቆዎቹም ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ ከብቶች ፡ ላይ ፡ የዓድላይ ፡ ልጅ ፡ ሻፋጥ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 30 ፤ በግመሎችም ፡ ላይ ፡ እስማኤላዊው ፡ ኡቢያስ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤ በአህያዎቹም ፡ ላይ ፡ ሜሮኖታዊው ፡ ይሕድያ ፡ ሹም ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 31 ፤ በመንጋዎቹም ፡ ላይ ፡ አጋራዊው ፡ ያዚዝ ፡ ሹም ፡ ነበረ ። እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ በዳዊት ፡ ሀብት ፡ ላይ ፡ ሹሞች ፡ ነበሩ ።

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 32 ፤ አስተዋይና ፡ ጸሓፊ ፡ የነበረው ፡ የዳዊት ፡ አጎት ፡ ዮናታን ፡ አማካሪ ፡ ነበረ ፤ የሐክሞኒም ፡ ልጅ ፡ ይሒኤል ፡ ከንጉሡ ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 33 ፤ አኪጦፌልም ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪ ፡ ነበረ ፤ አርካዊውም ፡ ኩሲ ፡ የንጉሡ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፤

መዋ.1 ፡ 27 ፡ 34 ፤ ከአኪጦፌልም ፡ ቀጥሎ ፡ የበናያስ ፡ ልጅ ፡ ዮዳዔና ፡ አብያታር ፡ ነበሩ ፤ ኢዮአብም ፡ የንጉሡ ፡ ሰራዊት ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። _____

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 1 ፤ ዳዊትም ፡ የእስራኤልን ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ የነገዶቹንም ፡ አለቃዎች ፥ ንጉሡንም ፡ በክፍል ፡ የሚያገለግሉትን ፡ የጭፍራዎች ፡ አለቃዎች ፥ ሻለቃዎቹንም ፥ የመቶ ፡ አለቃዎችንም ፥ በንጉሥና ፡ በልጆች ፡ ሀብትና ፡ ግዛት ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፥ ጃን ፡ ደረባዎችንም ፥ ጽኑዓን ፡ ኀያላኑንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ በእግሩ ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወንድሞቼና ፡ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ለቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ታቦትና ፡ ለአምላካችን ፡ እግር ፡ ማረፊያ ፡ የዕረፍት ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ እኔ ፡ በልቤ ፡ ዐስቤያለኹ ፤ ለሥራም ፡ የሚያስፈልገውን ፡ አዘጋጅቻለኹ ፤

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፦ የሰልፍ ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ ደምም ፡ አፍሰኻልና ፥ ለስሜ ፡ ቤት ፡ አትሠራም ፡ ብሎኛል ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከአባቴ ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ መርጦኛል ፤ ይሁዳም ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ መርጦታል ፤ ከይሁዳም ፡ ቤት ፡ የአባቴን ፡ ቤት ፡ መርጧል ፤ ከአባቴም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያነግሠኝ ፡ ዘንድ ፡ ሊመርጠኝ ፡ ወደደ ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ ሰጥቶኛልና ፥ ከልጆቼ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ፡ ልጄን ፡ ሰሎሞንን ፡ መርጦታል ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ ልጅ ፡ ይኾነኝ ፡ ዘንድ ፡ መርጨዋለኹና ፥ እኔም ፡ አባት ፡ እኾነዋለኹና ፡ ልጅኽ ፡ ሰሎሞን ፡ ቤቴንና ፡ አደባባዮቼን ፡ ይሠራል ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 7 ፤ ትእዛዜንና ፡ ፍርዴንም ፡ በማድረግ ፡ እንደ ፡ ዛሬው ፡ ቢጸና ፡ መንግሥቱን ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናዋለኹ ፡ አለኝ ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፥ አምላካችንም ፡ እየሰማ ፥ ይህችን ፡ መልካሚቱን ፡ ምድር ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፥ ለልጆቻችኹም ፡ ለዘለዓለም ፡ ታወርሷት ፡ ዘንድ ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ጠብቁ ፥ ፈልጉም ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 9 ፤ አንተም ፥ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ልብን ፡ ኹሉ ፡ ይመረምራልና ፥ የነፍስንም ፡ ዐሳብ ፡ ኹሉ ፡ ያውቃልና ፥ የአባትኽን ፡ አምላክ ፡ ዕወቅ ፤ በፍጹም ፡ ልብና ፡ በነፍስኽ ፡ ፈቃድም ፡ አምልከው ፤ ብትፈልገው ፡ ታገኘዋለኽ ፤ ብትተወው ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጥልኻል ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 10 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለመቅደስ ፡ የሚኾን ፡ ቤትን ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ መርጦኻልና ፥ ጠንክረኽ ፡ ፈጽመው ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 11 ፤ ዳዊትም ፡ ለመቅደሱ ፡ ወለል ፥ ለቤቱም ፥ ለቤተ ፡ መዛግብቱም ፥ ለደርቡና ፡ ለውስጡም ፡ ጓዳዎች ፥ ለስርየቱም ፡ መክደኛ ፡ መቀመጫ ፡ ምሳሌውን ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 12 ፤ ደግሞም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባዮችና ፡ በዙሪያው ፡ ለሚኾኑ ፡ ጓዳዎች ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለሚኾኑ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፥ ለንዋየ ፡ ቅድሳቱም ፡ ለሚኾኑ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ በመንፈሱ ፡ ላሰበው ፡ ኹሉ ፡ ምሳሌን ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 13 ፤ 14 ፤ የካህናቱንና ፡ የሌዋውያኑንም ፡ ክፍላቸውን ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በሚያገለግሉበት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አስታወቀው ። በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለሚያገለግሉበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥ ለአገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ ለሚኾነውም ፡ ለወርቁ ፡ ዕቃ ፡ ወርቁን ፡ በሚዛን ፡ ሰጠው ፤ ለአገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ ለሚኾነውም ፡ ለብር ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ብሩን ፡ በሚዛን ፡ ሰጠው ፤

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 15 ፤ ለወርቁም ፡ መቅረዞችና ፡ ለቀንዲሎችም ፡ ወርቁን ፡ በየመቅረዙና ፡ በየቀንዲሉ ፡ በሚዛን ፡ ሰጠው ፤ ለብሩም ፡ መቅረዞች ፡ እንደ ፡ መቅረዙ ፡ ኹሉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ብሩን ፡ በየመቅረዙና ፡ በየቀንዲሉ ፡ በሚዛን ፡ ሰጠው ፤

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 16 ፤ ለገጹ ፡ ኅብስት ፡ ገበታዎች ፡ ወርቁን ፡ በሚዛን ፡ ለገበታዎቹ ፡ ኹሉ ፥ ብሩንም ፡ ለብሩ ፡ ገበታዎች ፡ ሰጠው ፤

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 17 ፤ ለሜንጦዎቹና ፡ ለድስቶቹ ፡ ለመቅጃዎቹም ፡ ጥሩውን ፡ ወርቅ ፥ ለወርቁም ፡ ጽዋዎች ፡ ወርቁን ፡ በየጽዋው ፡ ኹሉ ፡ በሚዛን ፥ ለብሩም ፡ ጽዋዎች ፡ ብሩን ፡ በየጽዋው ፡ ኹሉ ፡ በሚዛን ፡ ሰጠው ፤

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 18 ፤ ለዕጣኑም ፡ መሠዊያ ፡ ጥሩውን ፡ ወርቅ ፡ በሚዛን ፥ ክንፎቻቸውንም ፡ ዘርግተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ የሸፈኑትን ፡ የኪሩቤልን ፡ የወርቅ ፡ ሠረገላ ፡ ምሳሌ ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 19 ፤ ዳዊትም ፦ የሥራውን ፡ ኹሉ ፡ ምሳሌ ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ተጽፎ ፡ መጣልኝ ፡ አለ ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ልጁን ፡ ሰሎሞንን ፦ ጠንክር ፥ አይዞኽ ፥ አድርገውም ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ አትፍራ ፥ አትደንግጥም ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ የሚኾነው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ርሱ ፡ አይተውኽም ፥ አይጥልኽምም ።

መዋ.1 ፡ 28 ፡ 21 ፤ እንሆም ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ኹሉ ፡ የሚኾኑ ፡ የካህናትና ፡ የሌዋውያን ፡ ክፍሎች ፡ በዚህ ፡ አሉ ፤ ለኹሉም ፡ ዐይነት ፡ አገልግሎትና ፡ ሥር ፡ በብልኀትና ፡ በነፍሱ ፡ ፈቃድ ፡ የሚሠራ ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፤ አለቃዎችና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ ይታዘዙኻል ፡ አለው ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ለጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ ብቻውን ፡ የመረጠው ፡ ልጄ ፡ ሰሎሞን ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ለጋ ፡ ነው ፤ ሕንፃው ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለአምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አይደለምና ፡ ሥራው ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 2 ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ጕልበቴ ፡ ኹሉ ፡ ለአምላኬ ፡ ቤት ፡ ለወርቁ ፡ ዕቃ ፡ ወርቁን ፥ ለብሩም ፡ ዕቃ ፡ ብሩን ፥ ለናሱም ፡ ዕቃ ፡ ናሱን ፥ ለብረቱም ፡ ዕቃ ፡ ብረቱን ፥ ለዕንጨቱም ፡ ዕቃ ፡ ዕንጨቱን ፥ ደግሞም ፡ መረግድንና ፡ በፈርጥ ፡ የሚገባ ፡ ድንጋይን ፥ የሚለጠፍ ፡ ድንጋይን ፥ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልክ ፡ ያለውንም ፡ ድንጋይ ፥ የከበረውንም ፡ ድንጋይ ፡ ከየዐይነቱ ፥ ብዙም ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ አዘጋጅቻለኹ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 3 ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የአምላኬን ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ወደድኹ ፥ ለመቅደሱ ፡ ካዘጋጀኹት ፡ ኹሉ ፡ ሌላ ፡ የግል ፡ ገንዘቤ ፡ የሚኾን ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ አለኝና ፡ ለአምላኬ ፡ ቤት ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 4 ፤ የቤቶቹ ፡ ግንብ ፡ ይለበጡበት ፡ ዘንድ ፡ ከኦፌር ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥ ሰባት ፡ ሺሕም ፡ መክሊት ፡ ጥሩ ፡ ብር ፥

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 5 ፤ በሠራተኞች ፡ እጅ ፡ ለሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ለወርቁ ፡ ዕቃ ፡ ወርቁን ፥ ለብሩም ፡ ዕቃ ፡ ብሩን ፡ ሰጥቻለኹ ። ዛሬ ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቀድስ ፡ ማነው ፧

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 6 ፤ የአባቶችም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፥ የእስራኤልም ፡ ነገዶች ፡ አለቃዎች ፥ ሻለቃዎችም ፥ የመቶ ፡ አለቃዎችም ፥ በንጉሡም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፡ በፈቃዳቸው ፡ አቀረቡ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 7 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ወርቅና ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ዳሪክ ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ መክሊት ፡ ብር ፥ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕም ፡ መክሊት ፡ ናስ ፥ መቶ ፡ ሺሕም ፡ መክሊት ፡ ብረት ፡ ሰጡ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 8 ፤ ዕንቊም ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ለኮነው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ በጌድሶናዊው ፡ በይሒኤል ፡ እጅ ፡ ሰጠ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 9 ፤ ሕዝቡም ፡ ፈቅደው ፡ ሰጥተዋልና ፥ በፍጹም ፡ ልባቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃዳቸው ፡ አቅርበዋልና ፥ ደስ ፡ አላቸው ፤ ንጉሡም ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አለው ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 10 ፤ ዳዊትም ፡ በጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረከ ፤ ዳዊትም ፡ አለ ፦ አቤቱ ፥ የአባታችን ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ተባረክ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 11 ፤ አቤቱ ፥ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፥ ታላቅነትና ፡ ኀይል ፥ ክብርም ፥ ድልና ፡ ግርማ ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ አቤቱ ፥ መንግሥት ፡ የአንተ ፡ ነው ፥ አንተም ፡ በኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያልኽ ፡ ራስ ፡ ነኽ ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 12 ፤ ባለጠግነትና ፡ ክብር ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ አንተም ፡ ኹሉን ፡ ትገዛለኽ ፤ ኀይልና ፡ ብርታት ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፤ ታላቅ ፡ ለማድረግ ፥ ለኹሉም ፡ ኀይልን ፡ ለመስጠት ፡ በእጅኽ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 13 ፤ አኹንም ፡ እንግዲህ ፥ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ እንገዛልኻለን ፥ ለክቡር ፡ ስምኽም ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

መዋ.1 ፥ 29 ፥ 14 ፤ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ ከእጅኽም ፡ የተቀበልነውን ፡ ሰጥተንኻልና ፥ ይህን ፡ ያኽል ፡ ችለን ፡ ልናቀርብልኽ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧ ሕዝቤስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 15 ፤ አባቶቻችንም ፡ ኹሉ ፡ እንደነበሩ ፡ እኛ ፡ በፊትኽ ፡ ስደተኞችና ፡ መጻተኞች ፡ ነን ፤ ዘመናችንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ናት ፥ አትጸናም ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 16 ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ለቅዱስ ፡ ስምኽ ፡ ቤት ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ያዘጋጀነው ፡ ባለጠግነት ፡ ኹሉ ፡ ከእጅኽ ፡ የመጣ ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ የአንተ ፡ ነው ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 17 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ልብን ፡ እንድትመረምር ፥ ቅንነትንም ፡ እንድትወድ ፡ ዐውቃለኹ ፤ እኔም ፡ በልቤ ፡ ቅንነትና ፡ በፈቃዴ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አቅርቤያለኹ ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ያለው ፡ ሕዝብኽ ፡ በፈቃዱ ፡ እንዳቀረበልኽ ፡ በደስታ ፡ አይቻለኹ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 18 ፤ አቤቱ ፥ የአባቶቻችን ፡ የአብርሃምና ፡ የይሥሐቅ ፡ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ዐሳብ ፡ በሕዝብኽ ፡ ልብ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጠብቅ ፥ ልባቸውንም ፡ ወዳንተ ፡ አቅና ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 19 ፤ ትእዛዝኽንም ፡ ምስክርኽንም ፡ ሥርዐትኽንም ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፥ ይህንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ ያዘጋጀኹለትንም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ለልጄ ፡ ለሰሎሞን ፡ ፍጹም ፡ ልብ ፡ ስጠው ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 20 ፤ ዳዊትም ፡ ጉባኤውን ፡ ኹሉ ፦ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ፡ አላቸው ። ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ የአባታቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረኩ ፥ ራሳቸውንም ፡ አዘንብለው ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለንጉሡ ፡ ሰገዱ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 21 ፤ በነጋውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቀረቡ ፤ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ወይፈን ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውንም ፥ ስለ ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 22 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሉ ፡ ጠጡም ። የዳዊትንም ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞንን ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ አነገሡት ፤ ርሱንም ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀቡት ፥ ሳዶቅንም ፡ ካህን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ቀቡት ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 23 ፤ ሰሎሞንም ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፥ ተከናወነለትም ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ታዘዙለት ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 24 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፥ ጎያላኑም ፥ ደግሞም ፡ የንጉሡ ፡ የዳዊት ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እጅ ፡ ሰጡት ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ አገነነው ፤ ከርሱ ፡ በፊትም ፡ ለነበሩት ፡ ለእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ ያልኾነውን ፡ የመንግሥት ፡ ክብር ፡ ሰጠው ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 26 ፤ የእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዳዊት ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 27 ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ የነገሠበት ፡ ዘመን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በኬብሮን ፡ ነገሠ ፥ ሠላሳ ፡ ሦስትም ፡ ዓመት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 28 ፤ ዕድሜም ፥ ባለጠግነትም ፥ ክብርም ፡ ጠግቦ ፡ በመልካም ፡ ሽምግልና ፡ ሞተ ፤ ልጁም ፡ ሰሎሞን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 29 ፤ የንጉሡም ፡ የዳዊት ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በባለራእዩ ፡ በሳሙኤል ፡ ታሪክ ፥ በነቢዩም ፡ በናታን ፡ ታሪክ ፥ በባለራእዩም ፡ በጋድ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.1 ፡ 29 ፡ 30 ፤ እንደዚሁም ፡ የመንግሥቱ ፡ ነገርና ፡ ኀይሉ ፡ ኹሉ ፡ በርሱም ፡ በእስራኤልም ፡ በአገሮችም ፡

መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያለፉት ፡ ዘመናት ፡ ተጽፈዋል ❖

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞን ፡ በመንግሥቱ ፡ በረታ ፤ አምላኩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ እጅግም ፡ አገነነው ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ለሻለቃዎች ፥ ለመቶ ፡ አለቃዎችም ፥ ለፈራጆችም ፥ በእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ለነበሩ ፡ መሳፍንት ፡ ኹሉ ፥ ለአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ተናገረ ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሠራው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መገናኛ ፡ ድንኳን ፡ በዚያ ፡ ነበረና ፡ በገባዖን ፡ ወዳለው ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ኼዱ ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ድንኳን ፡ ተክሎለት ፡ ነበርና ፥ ዳዊት ፡ ከቂርያትይዓሪም ፡ ወዳዘጋጀለት ፡ ስፍራ ፡ አምጥቶት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ የሆርም ፡ ልጅ ፡ የኡሪ ፡ ልጅ ፡ ባስልኤል ፡ የሠራው ፡ የናስ ፡ መሠዊያ ፡ በዚያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ፊት ፡ ነበረ ፤ ሰሎሞንም ፡ ጉባኤውም ፡ ይህን ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደናሱ ፡ መሠዊያ ፡ ወጣ ፥ በዚያም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ እግዚአብሔር ፦ ምን ፡ እንድሰጥኽ ፡ ለምነኝ ፡ ሲል ፡ ለሰሎሞን ፡ ተገለጠ ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አለው ፦ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ ምሕረት ፡ አድርገኻል ፥ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ አንግሠኽኛል ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ቀጥሩ ፡ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ በኾነው ፡ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አንግሠኽኛልና ፥ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸው ፡ ተስፋ ፡ ይጽና ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 10 ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ እወጣና ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ስጠኝ ፤ ይህን ፡ በሚያኽል ፡ በዚህ ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ የለምና ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰሎሞንን ፦ ይህ ፡ በልብኽ ፡ ነበረና ፥ ባለጠግነትንና ፡ ሀብትን ፡ ክብርንና ፡ የጠላቶችኽን ፡ ነፍስ ፡ ረኻርምም ፡ ዕድሜን ፡ አልለመንኽምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ባነገሥኹኽ ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ለመፍረድ ፡ ትችል ፡ ዘንድ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ለራስኽ ፡ ለምነኻልና ፥ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ከአንተ ፡ በፊትም ፡ ከነበሩት ፡ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ከሚነሡት ፡ ነገሥታት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚመስልኽ ፡ እንዳይኖር ፡ ባለጠግነትንና ፡ ሀብትን ፡ ክብርንም ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ሰሎሞንም ፡ በገባዖን ፡ ካለው ፡ ከኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ከመገናኛው ፡ ድንኳን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፤ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፥ 1 ፥ 14 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሠረገላዎቹንና ፡ ፈረሰኞችን ፡ ሰበሰበ ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ፤ በሠረገላዎች ፡ ከተማዎችና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

መዋ.2 ፡ 1 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡ በቈላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 1 ፡ 16 ፤ ሰሎሞንም ፡ ፈረሶችን ፡ ከግብጽና ፡ ከቀዌ ፡ አስመጣ ፤ የንጉሡም ፡ ነጋዴዎች ፡ በገንዘብ ፡ እየገዙ ፡ ከቀዌ ፡ ያመጧቸው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 1 ፡ 17 ፤ አንዱም ፡ ሠረገላ ፡ በስድስት ፡ መቶ ፥ አንዱም ፡ ፈረስ ፡ በመቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ ከግብጽ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፤ እንዲሁም ፡ ለኬጢያውያንና ፡ ለሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በእጃቸው ፡ ያመጡላቸው ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፥ ለመንግሥቱም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሰሎሞንም ፡ የሚሸከሙትን ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፥ ከተራራዎችም ፡ የሚጠርቡትን ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ቈጠረ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኪራም ፡ ላከ ፦ ከአባቴ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ እንዳደረግኽ ፥ የሚቀመጥበትንም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ እንደ ፡ ሰደድኽለት ፥ እንዲሁ ፡ ለእኔ ፡ አድርግ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ ለእስራኤል ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ታዘዘው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የጣፋጭን ፡ ሽቱ ፡ ለማጠን ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ ለማኖር ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በጧትና ፡ በማታ ፡ በሰንበታቱም ፡ በመባቻዎቹም ፡ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፡ ለማቅረብ ፡ ለአምላኬ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ እሠራና ፡ እቀድስ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰብኹ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 5 ፤ አምላካችንም ፡ ከአማልክት ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ የምሠራው ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰማይና ፡ ከሰማያት ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይ ፡ ይይዘው ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ለርሱ ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧ በፊቱ ፡ ዕጣን ፡ ከማጠን ፡ በቀር ፡ ቤት ፡ እሠራለት ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ዳዊት ፡ ካዘጋጃቸው ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ካሉት ፡ ብልኀተኞች ፡ ጋራ ፡ የሚኾን ፥ ወርቁንና ፡ ብሩን ፥ ናሱንና ፡ ብረቱን ፥ ሐምራዊውንና ፡ ቀዩን ፡ ሰማያዊውንም ፡ ግምጃ ፡ የሚሠራ ፥ ቅርጽንም ፡ የሚያውቅ ፡ ብልኀተኛ ፡ ሰው ፡ ላክልኝ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ከሊባኖስ ፡ ዕንጨት ፡ መቍረጥ ፡ እንዲያውቁ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ከሊባኖስ ፡ የዝግባና ፡ የጥድ ፡ የሰንደልም ፡ ዕንጨት ፡ ስደድልኝ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 9 ፤ የምሠራውም ፡ ቤት ፡ እጅግ ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ይኾናልና ፥ ብዙ ፡ ዕንጨት ፡ ያዘጋጁልኝ ፡ ዘንድ ፥ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ ይኾናሉ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 10 ፤ እንሆም ፥ ዕንጨቱን ፡ ለሚቈርጡ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ የተበጠረ ፡ ስንዴ ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ኻያ ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ እሰጣለኹ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ የጢሮስ ፡ ንጉሥም ፡ ኪራም ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ወዷልና ፥ በላያቸው ፡ አነገሠኽ ፡ ብሎ ፡ ለሰሎሞን ፡ መልእክት ፡ ላከ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ኪራምም ፡ ደግሞ ፡ አለ ፦ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለመንግሥቱም ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ጥበበኛና ፡ ብልኀተኛ ፡ አስተዋይም ፡ ልጅ ፡ ለንጉሡ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠ ፡

የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ ከብልኀተኞችኽ ፡ ጋራ ፡ ከጌታዬም ፡ ከአባትኽ ፡ ከዳዊት ፡ ብልኀተኞች ፡ ጋራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ኪራምአቢ ፡ የሚባል ፡ ብልኀተኛና ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ሰድጄልኻለኹ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ እናቱ ፡ ከዳን ፡ ልጆች ፡ ናት ፥ አባቱም ፡ የጢሮስ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ወርቁንና ፡ ብሩንም ፥ ናሱንና ፡ ብረቱን ፥ ድንጋይንና ፡ ዕንጨቱን ፥ ሐምራዊውንና ፡ ሰማያዊውን ፡ ቀዩንም ፡ ግምጃ ፥ ጥሩውንም ፡ በፍታ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፥ ቅርጽም ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ያውቃል ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ጌታዬ ፡ የተናገረውን ፡ ስንዴውንና ፡ ገብሱን ፡ ዘይቱንና ፡ የወይን ፡ ጠጁን ፡ ወደ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ይስደድ ፤

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ እኛም ፡ ከሊባኖስ ፡ የምትሻውን ፡ ያኽል ፡ ዕንጨት ፡ እንቈርጣለን ፥ በታንኳም ፡ አድርገን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ወዳንተ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ እንሰዳለን ፤ አንተም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ታስወስደዋለኽ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ የነበሩትን ፡ መጻተኞች ፡ ኹሉ ፡ አባቱ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ቈጠራቸው ፡ ቈጠረ ፤ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ተገኙ ።

መዋ.2 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ከነርሱም ፡ የሚሸከሙትን ፡ ሰባ ፡ ሺሕ ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ የሚጠርቡትን ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፥ በሕዝቡም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ አደረገ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአባቱ ፡ ለዳዊት ፡ በተገለጠበት ፡ በሞሪያ ፡ ተራራ ፡ ዳዊት ፡ ባዘጋጀው ፡ ስፍራ ፡ በኢያቡሳዊው ፡ በኦርና ፡ ዐውድማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ገመረ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 2 ፤ በነገሠም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ መሥራት ፡ ገመረ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የጣለው ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ርዝመቱም ፡ በዱሮው ፡ ስፍር ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ በቤቱም ፡ ፊት ፡ የነበረው ፡ ወለል ፡ ርዝመቱ ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ውስጡንም ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ታላቁንም ፡ ቤት ፡ በጥድ ፡ ዕንጨት ፡ ከደነው ፥ በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ፤ የዘንባባና ፡ የሰንሰለት ፡ አምሳል ፡ ቀረጸበት ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 6 ፤ ቤቱንም ፡ በዕንቊ ፡ አስጌጠው ፤ ወርቁንም ፡ የፈርዋይም ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ቤቱንም ፡ ሠረገላዎቹንም ፡ መድረኮቹንም ፡ ግንቦቹንም ፡ ደጆቹንም ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ፤ በግንቦቹም ፡ ላይ ፡ ኪሩቤልን ፡ ቀረጸ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ቅድስተ ፡ ቅዱሳኑንም ፡ ሠራ ፤ ርዝመቱም ፡ እንደ ፡ ቤቱ ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ በሚያኽል ፡ በጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ለበጠው ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ የምስማሮቹም ፡ ሚዛን ፡ ዐምሳ ፡ ሰቅል ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ። የደርቡንም ፡ ጓዳዎች ፡ በወርቅ ፡ ለበጠ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 10 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳንም ፡ ውስጥ ፡ ከዕንጨት ፡ ሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ኪሩቤልን ፡ ሠራ ፥ በወርቅም ፡ ለበጣቸው ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 11 ፤ የኪሩቤልም ፡ ክንፎች ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ የአንዱ ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበረ ፤ ኹለተኛው ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የኹለተኛውንም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ይነካ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 12 ፤ የኹለተኛውም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የቤቱንም ፡ ግንብ ፡ ይነካ ፡ ነበር ፤ ኹለተኛውም ፡ ክንፍ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የሌላውንም ፡ ኪሩብ ፡ ክንፍ ፡ ይነካ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ የእነዚህም ፡ ኪሩቤል ፡ ክንፎች ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ሙሉ ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ በእግራቸውም ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ ፊቶቻቸውም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ከሰማያዊውም ፡ ከሐምራዊውም ፡ ከቀዩም ፡ ሐር ፡ ከጥሩም ፡ በፍታ ፡ መጋረጃውን ፡ ሠራ ፥ ኪሩቤልንም ፡ ጠለፈበት ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ በቤቱም ፡ ፊት ፡ ቁመታቸው ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ የነበረውን ፡ ኹለቱን ፡ ዐምዶች ፡ ሠራ ፥ በያንዳንዳቸውም ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ጕልላት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ እንደ ፡ ድሪ ፡ ያሉ ፡ ሰንሰለቶችንም ፡ ሠርቶ ፡ በአዕማዱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አደረጋቸው ፤ መቶም ፡ ሮማኖች ፡ ሠርቶ ፡ በሰንሰለቱ ፡ ላይ ፡ አደረጋቸው ።

መዋ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ አዕማዶቹንም ፡ አንደኛውን ፡ በቀኝ ፥ ኹለተኛውን ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ፊት ፡ አቆማቸው ፤ በቀኝም ፡ የነበረውን ፡ ስም ፡ ያቂም ፡ በግራም ፡ የነበረውን ፡ ስም ፡ በለዝ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 1 ፤ ደግሞም ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ የነበረውን ፡ የናሱን ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 2 ፤ ከፈሰሰም ፡ ናስ ፡ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ በዙሪያውም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ክብ ፡ ኩሬ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 3 ፤ በበታቹም ፡ ላንድ ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፥ ለአንድም ፡ ክንድ ፡ ዐሥር ፥ ጕብጕቦች ፡ አዞረበት ፤ ኩሬውም ፡ በቀለጠ ፡ ጊዜ ፡ ጕብጕቦቹ ፡ በኹለት ፡ ተራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ቀልጠው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 4 ፤ በዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ በሬዎች ፡ ምስል ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ሦስቱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ሦስቱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ ኩሬውም ፡ በላያቸው ፡ ነበር ፥ የኹሉም ፡ ዝርግባቸው ፡ በስተውስጥ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 5 ፤ ውፍረቱም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ፤ ከንፈሩም ፡ እንደ ፡ ጽዋ ፡ ከንፈር ፥ እንደ ፡ ሱፍ ፡ አበባ ፡ ኾኖ ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይይዝ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 6 ፤ ደግሞም ፡ ዐሥር ፡ የመታጠቢያ ፡ ሰኖች ፡ ሠራ ፥ ለሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀርበው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይታጠብባቸው ፡ ዘንድ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ አኖራቸው ፤ ኩሬው ፡ ግን ፡ ካህናት ፡ ይታጠቡበት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ዐሥሩንም ፡ መቅረዞች ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ከወርቅ ፡ ሠርቶ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ዐሥሩንም ፡ ገበታዎች ፡ ሠርቶ ፡ ዐምስቱን ፡ በቀኝ ፥ ዐምስቱንም ፡ በግራ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ። አንድ ፡ መቶም ፡ የወርቅ ፡ ድስቶች ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ደግሞም ፡ የካህናቱን ፡ አደባባይ ፥ ታላቁንም ፡ አደባባይ ፥ የአደባባዩንም ፡ ደጆች ፡ ሠራ ፥ ደጆቻቸውንም ፡ በናስ ፡ ለበጠ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ዠሬውንም ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በአዜብ ፡ በኩል ፡ አኖረው ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 11 ፤ ኪራምም ፡ ምንቸቶቹንና ፡ መጫሪያዎቹን ፡ ድስቶቹንም ፡ ሠራ ። ኪራምም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ዠሉ ፡ ጨረሰ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ዥለቱን ፡ አዕማድ ፥ ጽዋዎቹንም ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ዥለት ፡ ጕልላቶች ፥ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ የጕልላቶች ፡ ዥለቱን ፡ ጽዋዎች ፡ የሚሸፍኑትን ፡ ዥለቱን ፡ መርበቦች ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 13 ፤ በአዕማዱም ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ ዥለቱን ፡ ጕልላቶች ፡ ይሸፍኑ ፡ ዘንድ ፥ ለያንዳንዱ ፡ መርበብ ፡ ዥለት ፡ ዥለት ፡ ተራ ፡ ሮማኖች ፥ ለዥለቱ ፡ መርበቦች ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሮማኖች ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 14 ፤ መቀመጫዎቹንና ፡ በመቀመጫዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ የመታጠቢያ ፡ ሰኖች ፥

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 15 ፤ አንዱንም ፡ ዠሬ ፥ በበታቹም ፡ የሚኾኑትን ፡ ዐሥራ ፡ ዥለት ፡ በሬዎች ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ምንቸቶቹንም ፡ መጫሪያዎቹንም ፡ ሜንጦዎቹንም ፡ ዕቃቸውንም ፡ ዠሉ ፡ ኪራም ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከለስላሳ ፡ ናስ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ በዮርዳኖስ ፡ ሜዳ ፡ በሱኮትና ፡ በጽሬዳ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ በወፍራሙ ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ አስፈሰሰው ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ሰሎሞንም ፡ እነዚህን ፡ ዕቃዎች ፡ ዠሉ ፡ እጅግ ፡ አብዝቶ ፡ ሠራ ፤ የናሱም ፡ ሚዛን ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 19 ፤ ሰሎሞንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ዠሉ ፡ የወርቁንም ፡ መሠዊያ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ የነበረባቸውን ፡ ገበታዎች ፥

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 20 ፤ በቅድስተ ፡ ቅዱሳኑም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ መቅረዞችንና ፡ ቀንዲሎቻቸውን ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 21 ፤ አበባዎቹንና ፡ ቀንዲሎቹን ፡ መኰስተሪያዎቹንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ጕጦቹንም ፡ ድስቶቹንም ፡ ጭልፋዎቹንም ፡ ማንደጃዎቹንም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ሠራ ። የውስጠኛውም ፡ ቤት ፡ የቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ደጆች ፡ የቤተ ፡ መቅደሱም ፡ ደጆች ፡ የወርቅ ፡ ነበሩ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 1 ፤ እንዲሁም ፡ ሰሎሞን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሠራው ፡ ሥራ ፡ ዠሉ ፡ ተጨረሰ ። አባቱም ፡ ዳዊት ፡ የቀደሰውን ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ዠሉ ፡ ሰሎሞን ፡ አምጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በነበረው ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አኖረው ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከጽዮን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የነገድ ፡ አለቃዎች ፡ ዠሉ ፡ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ መሳፍንት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ዠሉ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በበዓሉ ፡ ጊዜ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡

ተከማቹ ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ መጡ ፥ ሌዋውያንም ፡ ታቦቱን ፡ አነሡ ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ታቦቱንም ፡ የመገናኛውንም ፡ ድንኳን ፡ በድንኳኑም ፡ ውስጥ ፡ የነበረውን ፡ የተቀደሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አመጡ ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ አመጡ ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰበሰቡ ፡ የእስራኤል ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ በታቦቱ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ከብዛት ፡ የተነሣ ፡ የማይቈጠሩትንና ፡ የማይመጠኑትን ፡ በጎችና ፡ በሬዎች ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 7 ፤ ካህናቱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ታቦት ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አምጥተው ፡ በቅድስት ፡ ቅዱሳን ፡ ውስጥ ፡ ከኪሩቤል ፡ ክንፍ ፡ በታች ፡ በነበረው ፡ በስፍራው ፡ አኖሩት ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ኪሩቤልም ፡ በታቦቱ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘርግተው ፡ ነበር ፥ ኪሩቤልም ፡ ታቦቱንና ፡ መሎጊያዎቹን ፡ በስተላዩ ፡ በኩል ፡ ይሸፍኑ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 9 ፤ መሎጊያዎቹም ፡ ረዣዥሞች ፡ ነበሩና ፥ በቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ፊት ፡ ከመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ጫፎቻቸው ፡ ይታዩ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከውጪ ፡ አይታዩም ፡ ነበር ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ እዚያ ፡ አሉ ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 10 ፤ በታቦቱም ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ በኮሬብ ፡ ካስቀመጣቸው ፡ ከኹለቱ ፡ ጽላቶች ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልነበረበትም ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ የነበሩት ፡ ካህናት ፡ ኹሉ ፡ ተቀድሰው ፡ ነበር ፥ በሰሞናቸውም ፡ አልተከፈሉም ፡ ነበር ፤

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 12 ፤ መዘምራንም ፡ የነበሩት ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፥ አሣፍና ፡ ኤማን ፡ ኤዶታምም ፡ ልጆቻቸውም ፡ ወንድሞቻቸውም ፥ ጥሩ ፡ በፍታ ፡ ለብሰው ፡ ጸናጽልና ፡ በገና ፡ መሰንቆም ፡ እየመቱ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ካህናት ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ። ካህናቱም ፡ ከመቅደሱ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 13 ፤ መለከቱንም ፡ የሚነፉ ፡ መዘምራኑም ፡ በአንድነት ፡ ኾነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑና ፡ እያከበሩ ፦ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ እያሉ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ድምፃቸውን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በመለከትና ፡ በጸናጽል ፡ በዜማም ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባመሰገኑ ፡ ጊዜ ፥ ደመናው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞላው ።

መዋ.2 ፡ 5 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶት ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ከደመናው ፡ የተነሣ ፡ መቆምና ፡ ማገልገል ፡ አልተቻላቸውም ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፦ እግዚአብሔር ፦ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ እኖራለኹ ፡ ብሏል ፤

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ማደሪያ ፡ ቤትን ፡ ሠራኹልኽ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፡ ፊቱን ፡ ዘወር ፡ አድርጎ ፡ የእስራኤልን ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ መረቀ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ በአፉ ፡ የተናገረ ፡ በእጁም ፡ የፈጸመ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ፤

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ሕዝቤን ፡ ከግብጽ ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ስሜ ፡ የሚጠራበት ፡ ቤት ፡ በዚያ ፡ ይሠራልኝ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ማንኛውንም ፡ ከተማ ፡ አልመረጥኹም ፤ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ማንንም ፡ አልመረጥኹም ፤

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስሜ ፡ በዚያ ፡ እንዲጠራባት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ መርጫለኹ ፥ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ እንዲኾን ፡ ዳዊትን ፡ መርጫለኹ ፡ ብሏልና ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 7 ፤ አባቴም ፡ ዳዊት ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ዐስቦ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አባቴን ፡ ዳዊትን ፦ ለስሜ ፡ ቤት ፡ ትሠራ ፡ ዘንድ ፡ በልብኽ ፡ ዐስበኻልና ፥ ይህን ፡ በልብኽ ፡ መልካም ፡ አደረግኽ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወገብኽ ፡ የሚወጣው ፡ ልጅኽ ፡ ርሱ ፡ ለስሜ ፡ ቤትን ፡ ይሠራል ፡ እንጂ ፡ ቤት ፡ የምትሠራልኝ ፡ አንተ ፡ አይደለኽም ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በአባቴ ፡ በዳዊት ፡ ፋንታ ፡ ተነሣኹ ፥ በእስራኤልም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኹ ፥ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቤት ፡ ሠራኹ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 11 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያለበትን ፡ ታቦት ፡ በዚያው ፡ ውስጥ ፡ አኖርኹ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 12 ፤ 13 ፤ ሰሎሞንም ፡ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፥ ቁመቱም ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ የናስ ፡ መደገፊያ ፡ ሠርቶ ፡ በአደባባዩ ፡ መካከል ፡ ተክሎት ፡ ነበር ፥ በላዩም ፡ ቆመ ፥ በእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዘረጋ ፤ የእስራኤልም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እጆቹንም ፡ ዘርግቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 14 ፤ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማይ ፡ ወይም ፡ በምድር ፡ አንተን ፡ የሚመስል ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡ በፊትኽ ፡ ለሚኼዱ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፥

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ የሰጠኸውን ፡ ተስፋ ፡ የጠበቀኽ ፤ በአፍኽ ፡ ተናገርኽ ፥ ዛሬም ፡ እንደ ኾነው ፡ በእጅኽ ፡ ፈጸምኸው ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 16 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ። አንተ ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ኼድኽ ፡ ልጆችኽ ፡ በሕጌ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ መንገዳቸውን ፡ ቢጠብቁ ፡ በእስራኤል ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ አታጣም ፡ ብለኽ ፡ ተስፋ ፡ የሰጠኸውን ፡ ለባሪያኽ ፡ ለአባቴ ፡ ለዳዊት ፡ ጠብቅ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 17 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ለባሪያኽ ፡ ለዳዊት ፡ የተናገረኸው ፡ ቃል ፡ ይጽና ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 18 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይኖራልን ፧ እንሆ ፥ ሰማይ ፡ ከሰማያትም ፡ በላይ ፡ ያለ ፡ ሰማይ ፡ ይይዝኽ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ይልቁንስ ፡ እኔ ፡ የሠራኹት ፡ ቤት ፡ እንዴት ፡ ያንስ ፡ ይኾን ፧

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ወደባሪያኽ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ተመልከት ፥ ባሪያኽም ፡ በፊትኽ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎትና ፡ ጥሪውን ፡ ስማ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 20 ፤ ባሪያኽ ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ። በዚያ ፡ ስሜ ፡ ይኾናል ፡

ወዳልኸው ፡ ስፍራ ፥ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ዐይኖችኽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ የተገለጡ ፡ ይኹኑ ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 21 ፤ ባሪያኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ የሚጸልዩትን ፡ ልመና ፡ ስማ ፤ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ ሰምተኽም ፡ ይቅር ፡ በል ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 22 ፤ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፡ ቢበድል ፥ በላዩም ፡ መሐላ ፡ ቢጫን ፥ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በመሠዊያኽ ፡ ፊት ፡ ቢምል ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 23 ፤ በሰማይ ፡ ስማ ፥ አድርግም ፥ በባሪያዎችኽም ፡ ላይ ፡ ዳኛ ፡ ኹን ፥ በበደለኛውም ፡ ላይ ፡ ፍረድ ፥ መንገዱንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ መልስበት ፤ ንጹሑንም ፡ አጽድቀው ፥ እንደ ፡ ጽድቁም ፡ ክፈለው ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 24 ፤ ሕዝብኽም ፡ እስራኤል ፡ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ በጠላት ፡ ፊት ፡ ድል ፡ ተመትተው ፡ ወዳንተ ፡ ቢመለሱ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ በዚህም ፡ ቤት ፡ በፊትኽ ፡ ቢጸልዩና ፡ ቢለምኑኽ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 25 ፤ የሕዝብኽንም ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፤ ለእነርሱም ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡ ምድር ፡ መልሳቸው ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 26 ፤ አንተን ፡ ስለ ፡ በደሉ ፡ ሰማያት ፡ በተዘጉ ፡ ጊዜ ፡ ዝናብም ፡ ባልዘነበ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ ቢጸልዩ ፥ ስምኽንም ፡ ቢያከብሩ ፥ ባስጨነቅኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ቢመለሱ ፥ አንተ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 27 ፤ የባሪያዎችኽንና ፡ የሕዝብኽን ፡ የእስራኤልን ፡ ኀጢአት ፡ ይቅር ፡ በል ፥ የሚኼዱበትንም ፡ መልካም ፡ መንገድ ፡ አሳያቸው ፤ ለሕዝብኽም ፡ ርስት ፡ አድርገኽ ፡ ለሰጠኻት ፡ ምድር ፡ ዝናብን ፡ ስጥ ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 28 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብ ፡ ወይም ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ዋግ ፡ ወይም ፡ ዐረማሞ ፡ ወይም ፡ አንበጣ ፡ ወይም ፡ ኵብኵባ ፡ ቢኾን ፥ ጠላቶቻቸውም ፡ የአገሩን ፡ ከተማዎች ፡ ከበው ፡ ቢያስጨንቋቸው ፥ ማናቸውም ፡ መቅሠፍትና ፡ ደዌ ፡ ቢኾን ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 29 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ ሕዝብኽ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ሕመሙንና ፡ ሐዘኑን ፡ ዐውቆ ፡ ጸሎትና ፡ ልመና ፡ ቢያደርግ ፡ እጆቹንም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ ቢዘረጋ ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 30 ፤ 31 ፤ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኸው ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በሚኖሩበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፡ በመንገዶችኽም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፥ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ይቅርም ፡ በል ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ ታውቃለኽና ፡ ልቡን ፡ ለምታውቀው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ኹሉ ፡ መጠን ፡ ክፈለው ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 32 ፤ ከሕዝብኽም ፡ ከእስራኤል ፡ ያልኾነ ፡ እንግዳ ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ ስምኽ ፡ ስለ ፡ ብርቱውም ፡ እጅኽ ፡ ስለተዘረጋውም ፡ ከንድኽ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ መጥቶም ፡ ወደዚህ ፡ ቤት ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 33 ፤ አንተ ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ስምኽን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ሕዝብኽም ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ይፈሩኽ ፡ ዘንድ ፥ በዚህም ፡ በሠራኹት ፡ ቤት ፡ ስምኽ ፡ እንደ ፡ ተጠራ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ እንግዳው ፡ የሚለምንኽን ፡ ኹሉ ፡ አድርግ ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 34 ፤ ሕዝብኽም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ለመውጋት ፡ አንተ ፡ በምትልካቸው ፡ መንገድ ፡ ቢወጡ ፥ አንተም ፡ ወደመረጥኻት ፡ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ እኔም ፡ ለስምኽ ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ለአንተ ፡ ቢጸልዩ ፥

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 35 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ።

መዋ.2 ፥ 6 ፥ 36 ፤ የማይበድል ፡ ሰው ፡ የለምና ፡ አንተን ፡ ቢበድሉ ፥ ተቈጥተኽም ፡ ለጠላት ፡ አሳልፈኽ ፡ ብትሰጣቸው ፥ ሩቅም ፡ ወይም ፡ ቅርብ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ አገር ፡ ቢማርኳቸው ፥

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 37 ፤ በተማረኩበትም ፡ አገር ፡ ኾነው ፡ በልባቸው ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፥ በምርኳቸውም ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ተመልሰው ፦ ኀጢአት ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፉም ፡ አድርገናል ፡ ብለው ፡ ቢለምኑኽ ፥

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 38 ፤ በተማረኩበትም ፡ በምርኳቸው ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ ወዳንተ ፡ ቢመለሱ ፥ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኻት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ ወደመረጥኻትም ፡ ከተማ ፡ ለስምኽም ፡ ወደሠራኹት ፡ ቤት ፡ ቢጸልዩ ፥

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 39 ፤ ጸሎታቸውንና ፡ ልመናቸውን ፡ በማደሪያኽ ፡ በሰማይ ፡ ስማ ፥ ፍርድንም ፡ አድርግላቸው ፤ አንተንም ፡ የበደሉኽን ፡ ሕዝብኽን ፡ ይቅር ፡ በል ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 40 ፤ አኹንም ፥ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደሚኾነው ፡ ጸሎት ፡ ዐይኖችኽ ፡ የተገለጡ ፥ ጐሮዎችኽም ፡ የሚያደምጡ ፡ እንዲኾኑ ፡ እለምንኻለኹ ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 41 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከኀይልኽ ፡ ታቦት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዕረፍትኽ ፡ ተነሣ ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ካህናትኽ ፡ ደኅንነትን ፡ ይልበሱ ፤ ቅዱሳንኽም ፡ በደስታ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

መዋ.2 ፡ 6 ፡ 42 ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የቀባኸውን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ አትመልስ ፡ ለባሪያም ፡ ለዳዊት ፡ ያደረግኽለትን ፡ ምሕረት ፡ ዐስብ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 1 ፤ ሰሎሞንም ፡ ጸሎቱን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕቱን ፡ በላ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ቤቱን ፡ ሞላ ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶት ፡ ነበርና ፥ ካህናቱ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መግባት ፡ አልቻሉም ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እሳቱ ፡ ሲወርድ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ ሲኾን ፡ ያዩ ፡ ነበር ፤ በወለሉም ፡ ላይ ፡ በግንባራቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተደፍተው ፡ ሰገዱ ። ርሱ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ ብለውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በሬዎችና ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ሠዋ ። እንዲሁ ፡ ንጉሡና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀደሱ ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 6 ፤ ካህናቱም ፡ በየሥርዐታቸው ፥ ሌዋውያኑም ፡ ደግሞ ፦ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚለውን ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙር ፡ እየዘመሩ ፥ ንጉሡ ፡ ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማመስገን ፡ የሠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የዜማ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ካህናቱም ፡ በፊታቸው ፡ መለከት ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 7 ፤ ሰሎሞን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የአደባባዩን ፡ ውስጥ ፡ ቀደሰ ፤ ሰሎሞንም ፡ የሠራው ፡ የናስ ፡ መሠዊያ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ስቡንም ፡ መያዝ ፡ አልቻለምና ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፡ በዚያ ፡ አቀረበ ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 8 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የኾኑ ፥ ከሐማት ፡ መግቢያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያሉ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 7 ፡ 9 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ መሠዊያውን ፡ ቀድሰው ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡

ነበርና ፥ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ የተቀደሰውን ፡ ጉባኤ ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 10 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕዝቡን ፡ ወደ ፡ ድንኳናቸው ፡ አሰናበተ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊትና ፡ ለሰሎሞን ፡ ለሕዝቡም ፡ ለእስራኤል ፡ ስላደረገው ፡ ቸርነት ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ሐሴትን ፡ እያደረጉ ፡ ኼዱ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 11 ፤ ሰሎሞንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ ጨረሰ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በራሱ ፡ ቤት ፡ ይሠራው ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ያሰበውን ፡ ኹሉ ፡ አከናወነ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለሰሎሞን ፡ በሌሊት ፡ ተገልጦ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ጸሎትኽን ፡ ሰምቻለኹ ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ ለራሴ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ቤት ፡ መርጫለኹ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 13 ፤ ዝናብ ፡ እንዳይወርድ ፡ ሰማያቱን ፡ ብዘጋ ፥ ወይም ፡ ምድሪቱን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ አንበጣን ፡ ባዘው ፥ ወይም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ቸነፈር ፡ ብሰድ ፥

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 14 ፤ በስሜ ፡ የተጠሩት ፡ ሕዝቤ ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋርደው ፡ ቢጸልዩ ፥ ፊቴንም ፡ ቢፈልጉ ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸውም ፡ ቢመለሱ ፥ በሰማይ ፡ ኾኜ ፡ እሰማለኹ ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ እላለኹ ፥ ምድራቸውንም ፡ እፈውሳለኹ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 15 ፤ አኹንም ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ለሚጸለይ ፡ ጸሎት ፡ ዐይኖቼ ፡ ይገለጣሉ ፥ ጐሮዎቼም ፡ ያደምጣሉ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 16 ፤ አኹንም ፡ ስሜ ፡ ለዘለዓለም ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ መርጫለኹ ፡ ቀድሻለኹም ፤ ዐይኖቼና ፡ ልቤም ፡ ዘወትር ፡ በዚያ ፡ ይኾናሉ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 17 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ አባትኽ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ በፊቴ ፡ ብትኼድ ፥ እንዳዘዝኹኽም ፡ ኹሉ ፡ ብታደርግ ፥ ሥርዐቴንና ፡ ፍርዴንም ፡ ብትጠብቅ ፥

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 18 ፤ ከአባትኽ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ። በእስራኤል ፡ ላይ ፡ አለቃ ፥ የሚኾን ፡ ከዘርኽ ፡ አይታጣም ፡ ብዬ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳደረግኹ ፡ የመንግሥትኽን ፡ ዙፋን ፡ አጸናለኹ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 19 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከመከተል ፡ ብትመለሱ ፥ የሰጠኋችኹንም ፡ ሥርዐቴንና ፡ ትእዛዜን ፡ ብትተዉ ፥ ኼዳችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ብታመልኩ ፡ ብትሰግዱላቸውም ፥

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 20 ፤ ለአባቶቻችኹ ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ እነቅላችኋለኹ ፤ ለስሜም ፡ የቀደስኹትን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ከፊቴ ፡ እጥለዋለኹ ፥ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ምሳሌና ፡ ተረት ፡ አደርገዋለኹ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 21 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የነበረውንም ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ እያዩ ፡ በዚያ ፡ የሚያልፉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ አገርና ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፧ ብለው ፡ ይደነቃሉ ።

መዋ.2 ፥ 7 ፥ 22 ፤ መልሰውም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣቸውን ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፥ ስለ ፡ ሰገዱላቸውም ፥ ስለ ፡ አመለኳቸውም ፥ ስለዚህ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አመጣባቸው ፡ ይላሉ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

መዋ.2 ፥ 8 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ሰሎሞን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ የሠራበት ፡ ኻያ ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

መዋ.2 ፥ 8 ፥ 2 ፤ ኪራም ፡ ለሰሎሞን ፡ የሰጠውን ፡ ከተማዎች ፡ ሰሎሞን ፡ ሠራቸው ፥ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡

አኖረባቸው ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 3 ፤ ሰሎሞንም ፡ ወደ ፡ ሐማትሱባ ፡ ኼደ ፥ አሸነፋትም ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 4 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ያለውን ፡ ተድሞርን ፥ በሐማትም ፡ የሠራቸውን ፡ የዕቃ ፡ ቤቱን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ ቅጥርና ፡ መዝጊያ ፡ መወርወሪያም ፡ የነበራቸውን ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ላይኛውን ፡ ቤትሖሮን ፡ ታችኛውንም ፡ ቤትሖሮን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ባዕላትንም ፥ ለሰሎሞንም ፡ የነበሩትን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ የሠረገላውንም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ የፈረሰኞችንም ፡ ከተማዎች ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሊባኖስም ፡ በመንግሥቱም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ሰሎሞን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የወደደውን ፡ ኹሉ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ከኬጢያውያንም ፡ ከአሞራውያንም ፡ ከፌርዜያውያንም ፡ ከዔዊያውያንም ፡ ከኢያቡሳውያንም ፡ የቀሩትን ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ ያልኾኑትን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ያላጠፏቸውን ፥ በኋላቸው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የቀሩትን ፡ ልጆቻቸውን ፡ ሰሎሞን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ገባሮች ፡ አድርጎ ፡ መለመላቸው ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 9 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለሥራው ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ ባሪያ ፡ አላደረገም ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ሰልፈኞች ፥ የሹማምቶችም ፡ አለቃዎች ፥ የሠረገላዎችና ፡ የፈረሰኞች ፡ ባልደራሶች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 10 ፤ እነዚህም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሠልጥነው ፡ የነበሩ ፡ የንጉሡ ፡ የሰሎሞን ፡ ዐይነተኞች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 11 ፤ ሰሎሞንም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ታቦት ፡ የገባበት ፡ ስፍራ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ሚስቴ ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ አትቀመጥም ፡ ሲል ፡ የፈርዖንን ፡ ልጅ ፡ ከዳዊት ፡ ከተማ ፡ ወደሠራላት ፡ ቤት ፡ አወጣት ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሰሎሞን ፡ በወለሉ ፡ ፊት ፡ በሠራው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 13 ፤ ሙሴም ፡ እንዳዘዘ ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ በየቀኑ ፡ ኹሉ ፥ በየሰንበታቱም ፥ በየመባቻዎቹም ፥ በየተወሰኑትም ፡ በዓላት ፥ በየዓመቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በየቂጣው ፡ በዓልና ፡ በየሰባቱ ፡ ሰብዔ ፡ በዓል ፡ በየዳሱም ፡ በዓል ፡ ቀ፟ርባን ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ ዳዊት ፡ እንዲህ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፥ ካህናቱን ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ሥርዐት ፡ በያገልግሎታቸው ፡ ሰሞን ፡ ከፈላቸው ፤ ሌዋውያንም ፡ እንደ ፡ ሥርዐታቸው ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፥ በካህናቱም ፡ ፊት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ከፈላቸው ፤ በረኞቹንም ፡ ደግሞ ፡ በየበሩ ፡ ኹሉ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ከፈላቸው ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፡ ንጉሡ ፡ ስለ ፡ ነገሩ ፡ ኹሉና ፡ ስለ ፡ መዝገቡ ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አልተላለፉም ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ መሠረት ፡ ከተጣለ ፡ ዠምሮ ፡ እስከተጨረሰ ፡ ድረስ ፡ የሰሎሞን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነበረ ። የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ተፈጸመ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 17 ፤ ሰሎሞንም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ወዳሉ ፡ ወደ ፡ ዔጽዮንጋብርና ፡ ወደ ፡ ኤሎት ፡ ኼደ ።

መዋ.2 ፡ 8 ፡ 18 ፤ ኪራምም ፡ መርከቦችንና ፡ የባሕርን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁትን ፡ መርከበኞች ፡ በባሪያዎቹ ፡ እጅ ፡ ሰደደለት ፤ እነርሱም ፡ ከሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኦፌር ፡ መጡ ፥ ከዚያም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ አመጡ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 1 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ዝና ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ በግመሎች ፡ ላይ ፡ ሽቱና ፡ ብዙ ፡ ወርቅ ፡ የከበረም ፡ ዕንቊ ፡ አስጫና ፡ ከታላቅ ፡ ኃዝ ፡ ጋራ ፡ ሰሎሞንን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእንቆቅልሽ ፡ ትፈትነው ፡ ዘንድ ፡ መጣች ፤ ወደ ፡ ሰሎሞንም ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ በልቧ ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ አጫወተችው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 2 ፤ ሰሎሞንም ፡ የጠየቀችውን ፡ ሹሉ ፡ ፈታላት ፤ ሰሎሞንም ፡ ያልፈታው ፡ ስውር ፡ ነገር ፡ አልነበረም ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 3 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፥ ሠርቶትም ፡ የነበረውን ፡ ቤት ፥ የማእዱንም ፡ መብል ፥

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 4 ፤ የብላቴናዎቹንም ፡ አቀማመጥ ፥ የሎሌዎቹንም ፡ አሠራር ፡ አለባበሳቸውንም ፥ ጠጅ ፡ አሳላፊዎቹንም ፡ አለባበሳቸውንም ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚያሳርገውን ፡ መሥዋዕት ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ አልቀረላትም ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 5 ፤ ንጉሡንም ፡ አለችው ፦ ስለ ፡ ነገርኽና ፡ ስለ ፡ ጥበብኽ ፡ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የሰማኹት ፡ ዝና ፡ እውነት ፡ ነው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መጥቼ ፡ በዐይኔ ፡ እስካየኹ ፡ ድረስ ፡ የነገሩኝን ፡ አላመንኹም ፤ እንሆ ፥ የጥበብኽን ፡ ታላቅነት ፡ እኩሌታ ፡ አልነገሩኝም ፤ ከሰማኹት ፡ ዝና ፡ ትበልጣለኽ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 7 ፤ በፊትኽ ፡ ሹልጊዜ ፡ የሚቆሙ ፡ ጥበብኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎችኽና ፡ እነዚህ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 8 ፤ በአምላክኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ንጉሥ ፡ እንድትኾን ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ያስቀምጥኽ ፡ ዘንድ ፡ የወደደኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ፤ አምላክኽ ፡ እስራኤልን ፡ ለዘለዓለም ፡ ያጸናቸው ፡ ዘንድ ፡ ወዷቸዋልና ፥ ስለዚህ ፡ ፍርድና ፡ ጽድቅ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ በላያቸው ፡ አነገሠኽ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 9 ፤ ለንጉሡም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ሽቱ ፡ የከበረም ፡ ዕንቊ ፡ ሰጠችው ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ሰጠችው ፡ ያለ ፡ ሽቱ ፡ ከቶ ፡ አልነበረም ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ከኦፌርም ፡ ወርቅ ፡ ያመጡ ፡ የኪራም ፡ ባሪያዎችና ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ የሰንደል ፡ ዕንጨትና ፡ የከበረ ፡ ዕንቊ ፡ ደግሞ ፡ አመጡ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰንደሉ ፡ ዕንጨት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ለንጉሡ ፡ ቤት ፡ ደርብ ፥ ለመዘምራኑም ፡ መሰንቆና ፡ በገና ፡ አደረገ ፤ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ከቶ ፡ አልታየም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 12 ፤ የሳባም ፡ ንግሥት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ካመጣችው ፡ የሚበልጥ ፥ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ የወደደችውን ፡ ሹሉ ፡ ከርሱም ፡ የለመነችውን ፡ ሹሉ ፡ ሰጣት ፤ ርሷም ፡ ተመልሳ ፡ ከባሪያዎቿ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሯ ፡ ኼደች ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 13 ፤ ነጋድራሶችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ካመጡለት ፡ ሌላ ፡ በየዓመቱ ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ የሚመጣ ፡ የወርቅ ፡ ሚዛን ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 14 ፤ የዐረብም ፡ ነገሥታት ፡ ሹሉ ፡ የምድሩም ፡ ሹማምት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ወደ ፡ ሰሎሞን ፡ ያመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ በጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻ ፡ ውስጥ ፡ የገባው ፡ ጥፍጥፍ ፡ ወርቅ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 16 ፤ ከጥፍጥም ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ጋሻ ፡ አሠራ ፤ በአንዱም ፡ ጋሻ ፡ የገባው ፡ ወርቅ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰቅል ፡ ነበረ ፤ ንጉሡም ፡ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኖራቸው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ደግሞ ፡ ከዝኖን ፡ ጥርስ ፡ ታላቅ ፡ ዙፋን ፡ አሠራ ፥ በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ለበጠው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 18 ፤ ከዙፋኑም ፡ ጋራ ፡ ተጋጥመው ፡ ወደ ፡ ዙፋኑም ፡ የሚያስኼዱ ፡ ስድስት ፡ ዕርከኖች ፡ ነበሩ ፤ የወርቅ ፡ ብርኵማም ፡ ነበረ ፤ በዚህና ፡ በዚያም ፡ በመቀመጫው ፤ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ የክንድ ፡ መደገፊያዎች ፡ ነበሩበት ፥ በመደገፊያዎችም ፡ አጠገብ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 19 ፤ በስድስቱም ፡ ዕርከኖች ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አንበሳዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ አልተሠራም ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 20 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ የሚጠጣበት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የወርቅ ፡ ነበረ ፥ የሊባኖስ ፡ ዱር ፡ በተባለውም ፡ ቤቱ ፡ የነበረው ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ፤ በሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ብር ፡ ከቶ ፡ አይቈጠርም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 21 ፤ ለንጉሡም ፡ ከኪራም ፡ ባሪያዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ የሚኼዱ ፡ መርከቦች ፡ ነበሩት ፤ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ዓመትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የዝኖንም ፡ ጥርስ ፡ ዝንጀሮና ፡ ዝጉርጉር ፡ ወፍም ፡ ይዘው ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 22 ፤ ንጉሡም ፡ ሰሎሞን ፡ ከምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ በባለጠግነትና ፡ በጥበብ ፡ በለጠ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 23 ፤ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ያኖረውን ፡ ጥበቡን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ የሰሎሞንን ፡ ፊት ፡ ሊያዩ ፡ ይመኙ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 24 ፤ እያንዳንዱም ፡ ገጸ ፡ በረከቱን ፥ የወርቅንና ፡ የብርን ፡ ዕቃ ፥ ልብስንና ፡ የጦር ፡ መሣሪያን ፥ ሽቱውንም ፥ ፈረሶችንና ፡ በቅሎዎችን ፡ እየያዘ ፡ በየዓመቱ ፡ ያመጣ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 25 ፤ ሰሎሞንም ፡ ለፈረሶችና ፡ ለሠረገላዎች ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ጋጥ ፥ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩት ፥ በሠረገላዎችም ፡ ከተማዎች ፥ ከንጉሡም ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አኖራቸው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 26 ፤ ከኤፍራጥስም ፡ ወንዝ ፡ ዠምሮ ፡ እስከፍልስጥኤም ፡ ምድርና ፡ እስከግብጽ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ባሉ ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ብሩን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ እንዲበዛ ፡ አደረገው ፤ የዝግባውንም ፡ ዕንጨት ፡ ብዛት ፡ በቈላ ፡ እንደሚበቅል ፡ ሾላ ፡ አደረገው ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 28 ፤ ለሰሎሞንም ፡ ፈረሶች ፡ ከግብጽና ፡ ከየአገሩ ፡ ኹሉ ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 29 ፤ የቀረውም ፡ ፊተኛውና ፡ ኋለኛው ፡ የሰሎሞን ፡ ነገር ፡ በነቢዩ ፡ በናታን ፡ ታሪክ ፥ በሴሎናዊውም ፡ በአሒያ ፡ ትንቢት ፥ ስለ ፡ ናባጥም ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ባየው ፡ በባለራእዩ ፡ በአዶ ፡ ራእይ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 30 ፤ ሰሎሞንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 9 ፡ 31 ፤ ሰሎሞንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ሮብዓም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 1 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፥ ሮብዓም ፡ ወደ ፡ ሴኬም ፡ ኼደ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 2 ፤ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓምም ፡ ከንጉሡ ፡ ከሰሎሞን ፡ ፊት ፡ ሸሽቶ ፡ በግብጽ ፡ ይኖር ፡ ነበርና ፥ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ከግብጽ ፡ ተመለሰ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 3 ፤ ልከውም ፡ ጠሩት ፤ ኢዮርብዓምና ፡ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ መጥተው ፡ ሮብዓምን ፦

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 4 ፤ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ ጽኑውን ፡ የአባትኽን ፡ አገዛዝ ፥ በላያችንም ፡ የጫነውን ፡ የከበደውን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልን ፥ እኛም ፡ እንገዛልኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ አላቸው ። ሕዝቡም ፡ ኼዱ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ አባቱ ፡ ሰሎሞን ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቸርነት ፡ ብታደርግላቸው ፥ ደስም ፡ ብታሠኛቸው ፥ በገርነትም ፡ ብትናገራቸው ፥ ለዘለዓለም ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑልኻል ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ የመከሩትን ፡ ነገር ፡ ትቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካደጉትና ፡ በፊቱ ፡ ይቆሙ ፡ ከነበሩት ፡ ብላቴናዎች ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ አባትኽ ፡ የጫነብንን ፡ ቀንበር ፡ አቅልልን ፡ ለሚሉኝ ፡ ሕዝብ ፡ እመልስላቸው ፡ ዘንድ ፡ የምትመክሩኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 10 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያደጉት ፡ ብላቴናዎች ፦ አባትኽ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶብን ፡ ነበር ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አቅልልን ፡ ለሚሉኽ ፡ ሕዝብ ፦ ታናሺቱ ፡ ጣቴ ፡ ከአባቴ ፡ ወገብ ፡ ትወፍራለች ፤

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ አባቴ ፡ ከባድ ፡ ቀንበር ፡ ጭኖባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በቀንበራችኹ ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ በላቸው ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፦ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ጽኑ ፡ ምላሽ ፡ መለሰላቸው ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ የሽማግሌዎቹን ፡ ምክር ፡ ትቶ ፦

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 14 ፤ አባቴ ፡ ቀንበር ፡ አክብዶባችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ እጨምርበታለኹ ፤ አባቴ ፡ በዐለንጋ ፡ ገርፏችኹ ፡ ነበር ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በጊንጥ ፡ እገርፋችኋለኹ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ብላቴናዎቹ ፡ ምክር ፡ ተናገራቸው ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሴሎናዊው ፡ በአኪያ ፡ አድርጎ ፡ ለናባጥ ፡ ልጅ ፡ ለኢዮርብዓም ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ እንዲያጸና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተወስኖ ፡ ነበርና ፥ ንጉሡ ፡ ሕዝቡን ፡ አልሰማም ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 16 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ እንዳልሰማቸው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፦ በዳዊት ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡ አለን ፧ በእሴይም ፡ ልጅ ፡ ዘንድ ፡ ርስት ፡ የለንም ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እየድንኳኖቻችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ዳዊት ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ ቤትኽን ፡ ተመልከት ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ መለሱለት ። እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እየድንኳኖቻቸው ፡ ኼዱ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 17 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በተቀመጡት ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ሮብዓም ፡ ነገሠባቸው ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ አስገባሪውን ፡ አዶራምን ፡ ሰደደ ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ፥ ሞተም ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ሠረገላው ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሸሸ ።

መዋ.2 ፡ 10 ፡ 19 ፤ እስራኤልም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ሸፈተ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 1 ፤ ሮብዓምም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እስራኤልን ፡ ወግተው ፡ መንግሥቱን ፡ ወደ ፡ ሮብዓም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ ከይሁዳና ፡ ከብንያም ፡ ቤት ፡ የተመረጡትን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰልፈኞች ፡ ሰዎች ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደሸማያ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 3 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ ለሮብዓም ፥ በይሁዳና ፡ በብንያምም ፡ ላሉት ፡ ለእስራኤል ፡ ሹሉ ፦

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ አትውጡ ፥ ወንድሞቻችኹንም ፡ አትውጉ ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ። የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ሰሙ ፥ በኢዮርብዓምም ፡ ላይ ፡ ከመኼድ ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 5 ፤ ሮብዓምም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ፥ በይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 6 ፤ በይሁዳና ፡ በብንያም ፡ ያሉትንም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፥ ቤተ ፡ ልሔም ፥ ኤጣምን ፥ ቴቁሔን ፥

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 7-8 ፤ ቤትጹርን ፥ ሦኮን ፥ ዓዶላምን ፥ ጌትን ፥ መሪሳን ፥

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 9 ፤ ዚፍን ፥ አዶራይምን ፥ ለኪሶን ፥ ዓዜቃን ፥

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 10 ፤ ጾርዓን ፥ ኤሎንን ፥ ኬብሮንን ፥ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 11 ፤ ምሽጎቹንም ፡ አጠነከረ ፥ አለቃዎችንም ፡ አኖረባቸው ፥ ምግቡንም ፡ ዘይቱንም ፡ የወይን ፡ ጠጁንም ፡ አከማቸባቸው ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 12 ፤ በከተማዎቹ ፡ ሹሉ ፡ ጋሻና ፡ ጦርን ፡ አኖረ ። ከተማዎቹንም ፡ እጅግ ፡ አጠነከራቸው ፤ ይሁዳና ፡ ብንያምም ፡ የርሱ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 13 ፤ በእስራኤልም ፡ ሹሉ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ ከየአገራቸው ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ካህናት ፡ እንዳይኾኑ ፡ ኢዮርብዓምና ፡ ልጆቹ ፡ አስለቅቀዋቸው ፡ ነበርና ፥ ሌዋውያን ፡ መሰመሪያቸውንና ፡ ቦታቸውን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ይሁዳና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 15 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ለኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ለአጋንንቱም ፡ ለሠራቸውም ፡ እንቦሶች ፡ ካህናትን ፡ አቆመ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሠዉ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሹሉ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፈለግ ፡ ልባቸውን ፡ የሰጡ ፡ ሹሉ ፡ እነርሱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 17 ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በዳዊትና ፡ በሰሎሞን ፡ መንገድ ፡ ይኼዱ ፡ ነበርና ፥ ሦስት ፡ ዓመት ፡ የይሁዳን ፡ መንግሥት ፡ አበረቱ ፥ የሰሎሞንንም ፡ ልጅ ፡ ሮብዓምን ፡ አጸኑ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 18 ፤ ሮብዓምም ፡ መሐላትን ፡ አገባ ፤ አባቷ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢያሪሙት ፡ ነበረ ፤ እናቷም ፡ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ የኤልያብ ፡ ልጅ ፡ አቢካኢል ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 19 ፤ ርሷም ፡ የዑስን ፥ ሰማራያን ፥ ዘሃምን ፡ ወንዶች ፡ ልጆች ፡ ወለደችለት ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 20 ፤ ከርሷም ፡ በኋላ ፡ የአቤሴሎምን ፡ ልጅ ፡ መዓካን ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ አብያን ፥ ዐታይን ፥ ዚዛን ፥ ሰሎሚትን ፡ ወለደችለት ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 21 ፤ ሮብዓምም ፡ ከሚስቶቹና ፡ ከቁባቶቹ ፡ ሹሉ ፡ ይልቅ ፡ የአቤሴሎምን ፡ ልጅ ፡ መዓካን ፡ ወደደ ፤ ዐሥራ ፡ ስምንትም ፡ ሚስቶችና ፡ ስድሳ ፡ ቁባቶች ፡ ነበሩት ፥ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ወንዶችና ፡ ስድሳ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 22 ፤ ሮብዓምም ፡ ንጉሥ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ዐስቧልና ፥ የመዓካን ፡ ልጅ ፡ አብያን ፡ በወንድሞቹ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ።

መዋ.2 ፡ 11 ፡ 23 ፤ ተጠበበም ፥ ልጆቹንም ፡ ሹሉ ፡ በይሁዳና ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ በምሽጉ ፡ ከተማዎች ፡ ሹሉ ፡ ከፋፈላቸው ፤ ብዙም ፡ ምግብ ፡ ሰጣቸው ፤ ብዙም ፡ ሚስቶች ፡ ፈለገላቸው ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የሮብዓም ፡ መንግሥት ፡ በጸናች ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፥ ርሱና ፡ እስራኤል ፡ ሹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ተዉ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በድለዋልና ፥ ሮብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ስድሳ ፡ ሺሕ ፡ ፈረሰኞች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 3 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከግብጽ ፡ ለመጣው ፡ ሕዝብ ፡ ቍጥር ፡ አልነበረውም ፤ እነርሱም ፡ የልብያ ፡ ሰዎች ፥ ሱካውያን ፥ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 4 ፤ ለይሁዳም ፡ የነበሩትን ፡ ምሽጎች ፡ ከተማዎች ፡ ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጣ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 5 ፤ ነቢዩም ፡ ሸማያ ፡ ወደ ፡ ሮብዓምና ፡ ከሺሻቅ ፡ ሸሽተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወደተሰበሰቡባት ፡ ወደይሁዳ ፡ መሳፍንት ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ ተዋችኹኝ ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሺሻቅ ፡ እጅ ፡ ተውኋችኹ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ መሳፍንትና ፡ ንጉሡ ። እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋረዱ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰውነታቸውን ፡ እንዳዋረዱ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ። ሰውነታቸውን ፡ አዋርደዋል ፤ አላጠፋቸውም ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ አድናቸዋለኹ ፥ ቍጣዬም ፡ በሺሻቅ ፡ እጅ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አይፈስም ፤

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእኔ ፡ መገዛትንና ፡ ለምድር ፡ ነገሥታት ፡ መገዛትን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገዙለታል ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ሸማያ ፡ መጣ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 9 ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ሺሻቅም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡

መዛግብትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፡ ወሰደ ፤ ኹሉንም ፡ ወሰደ ፤ ደግሞም ፡ ሰሎሞን ፡ የሠራቸውን ፡ የወርቁን ፡ ጋሻዎች ፡ ወሰደ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በእነርሱ ፡ ፋንታ ፡ የናስ ፡ ጋሻዎችን ፡ ሠራ ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ በሚጠብቁ ፡ በዘበኞች ፡ አለቃ ፡ እጅ ፡ አኖራቸው ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ቍጥር ፡ ዘበኞች ፡ መጥተው ፡ ይሸከሟቸው ፡ ነበር ፥ መልሰውም ፡ በዘበኞች ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 12 ፤ ሰውነቱንም ፡ ባዋረደ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ፈጽሞ ፡ እንዳያጠፋው ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ፤ በይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኘ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ሮብዓም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በረታ ፡ ንጉሥም ፡ ኾነ ፤ ሮብዓምም ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ የአርባ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስሙን ፡ ያኖርባት ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በመረጣት ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዐሞን ፡ ሴት ፡ ናዕማ ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ይሻ ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አላዘጋጀም ፡ ነበርና ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 15 ፤ የሮብዓምም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ነገር ፡ በነቢዩ ፡ ሸማያና ፡ በባለራእዩ ፡ በአዶ ፡ የትውልድ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ በሮብዓምና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከልም ፡ በዘመናቸው ፡ ኹሉ ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ሮብዓምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ አብያ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮርብዓም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ አብያ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 2 ፤ ሦስት ፡ ዓመት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነገሠ ፤ የእናቱም ፡ ስም ፡ ሚካያ ፡ ነበረ ፥ የገብዓ ፡ ሰው ፡ የኡርኤል ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 3 ፤ በአብያና ፡ በኢዮርብዓም ፡ መካከልም ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ። አብያም ፡ የተመረጡትን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ኀያላን ፡ ሰልፈኞች ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ ወጣ ፤ ኢዮርብዓምም ፡ የተመረጡትን ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ይዞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተሰለፈ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 4 ፤ አብያም ፡ በተራራማው ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ባለው ፡ በጽማራይም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ኢዮርብዓምና ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 5 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መንግሥትን ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጆቹ ፡ በጨው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በእውኑ ፡ አታውቁምን ፧

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 6 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያ ፡ የናባጥ ፡ ልጅ ፡ ኢዮርብዓም ፡ ግን ፡ ተነሥቶ ፡ በጌታው ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ክፉዎች ፡ ሰዎችና ፡ ምናምንቴዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ሮብዓም ፡ ሕፃንና ፡ ለጋ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፥ ሊቋቋማቸውም ፡ ባልቻለበት ፡ ጊዜ ፥ በሰሎሞን ፡ ልጅ ፡ በሮብዓም ፡ ላይ ፡ በረቱበት ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ በዳዊት ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ የሚኾነውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ልትቋቋሙ ፡ ታስባላችኹ ። እናንተም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ናችኹ ፥ ኢዮርብዓምም ፡ አማልክት ፡ አድርጎ ፡ የሠራላችኹ ፡ የወርቅ ፡ እንቦሶች ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 9 ፤ የአሮንን ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ አላሳደዳችኹምን ፧ እንደ ፡ ሌላዎችም ፡ አሕዛብ ፡ ልማድ ፡ ካህናትን ፡ አላደረጋችኹምን ፧ አንድ ፡ ወይፈንና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ይዞ ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡ የሚመጣ ፡ ኹሉ ፡ አማልክት ፡ ላልኾኑት ፡ ለእነዚያ ፡ ካህን ፡ ይኾናል ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 10 ፤ ለእኛ ፡ ግን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ አልተውነውም ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አገልጋዮች ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ ሌዋውያኑም ፡ በሥራቸው ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 11 ፤ በየጧቱና ፡ በየማታውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ጣፋጩን ፡ ዕጣን ፡ ያሳርጋሉ ፤ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ በንጹሕ ፡ ገበታ ፡ ላይ ፥ የወርቁን ፡ መቅረዝና ፡ ቀንዲሎቹንም ፡ ማታ ፡ ማታ ፡ እንዲያበሩ ፡ ያዘጋጃሉ ፤ እኛም ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እንጠብቃለን ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ትታችኹታል ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 12 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ ነው ፥ መለከቱንም ፡ የሚነፉ ፡ ካህናቱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ፥ በእናንተም ፡ ላይ ፡ ይጮኻሉ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አይበጃችኹምና ፡ ከአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አትዋጉ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 13 ፤ ኢዮርብዓም ፡ ግን ፡ ድብቅ ፡ ጦር ፡ በስተኋላቸው ፡ አዞረ ፤ እነርሱ ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ድብቅ ፡ ጦሩ ፡ በስተኋላቸው ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 14 ፤ ይሁዳም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ በተመለከተ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሰልፉ ፡ በፊቱና ፡ በኋላው ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጮኹ ፥ ካህናቱም ፡ መለከቱን ፡ ነፉ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 15 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ጮኹ ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢዮርብዓምንና ፡ እስራኤልን ፡ ኹሉ ፡ በአብያና ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ መታቸው ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 16 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከይሁዳ ፡ ፊት ፡ ሸሹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 17 ፤ አብያና ፡ ሕዝቡ ፡ ታላቅ ፡ አመታት ፡ መቷቸው ፤ ከእስራኤልም ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ ተገድለው ፡ ወደቁ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተዋረዱ ፥ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ በአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታምነው ፡ ነበርና ፥ አሸነፉ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 19 ፤ አብያም ፡ ኢዮርብዓምን ፡ አሳደደው ፥ ከርሱም ፡ ከተማዎቹን ፥ ቤቴልንና ፡ መንደሮቿን ፥ ይሻናንና ፡ መንደሮቿን ፥ ዔፍሮንንና ፡ መንደሮቿን ፡ ወሰደ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 20 ፤ ኢዮርብዓምም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በአብያ ፡ ዘመን ፡ አልበረታም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቀሠፈው ፥ ሞተም ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 21 ፤ አብያም ፡ ጸና ፥ ዐሥራ ፡ አራትም ፡ ሚስቶች ፡ አገባ ፥ ኻያ ፡ ኹለትም ፡ ወንዶች ፡ ልጆችንና ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ ወለደ ።

መዋ.2 ፡ 13 ፡ 22 ፤ የአብያም ፡ የቀረው ፡ ነገርና ፡ አካኼዱ ፡ የተናገራቸውም ፡ ቃሎች ፡ በነቢዩ ፡ በአዶ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፈዋል ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 1 ፤ አብያም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አሣ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ። በርሱም ፡ ዘመን ፡ ምድሪቱ ፡ ዐሥር ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ዐረፈች ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 2 ፤ አሣም ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 3 ፤ የእንግዳዎቹንም ፡ አማልክት ፡ መሠዊያ ፡ የኰረብታውንም ፡ መስገጃዎች ፡ አፈረሰ ፥ ሐውልቶቹንም ፡ ሰበረ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፤

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 4 ፤ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፥ ሕጉንና ፡ ትእዛዙንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳን ፡ አዘዘ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 5 ፤ ከይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችና ፡ የፀሓይ ፡ ምስሎችን ፡ አስወገደ ፤ መንግሥቱም ፡ በርሱ ፡ ሥር ፡ በሰላም ፡ ተቀመጠች ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 6 ፤ በይሁዳም ፡ ምሽጎች ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዕረፍት ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ምድሪቱ ፡ ጸጥ ፡ ብላ ፡ ነበር ፥ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ሰልፍ ፡ አልነበረም ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 7 ፤ ይሁዳንም ፦ እነዚህን ፡ ከተማዎች ፡ እንሥራ ፥ ቅጥርም ፡ ግንብም ፡ መዝጊያም ፡ መወርወሪያም ፡ እናድርግባቸው ፤ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ፈለግነው ፡ ምድሪቱ ፡ ገና ፡ በፊታችን ፡ ናት ፤ እኛ ፡ ፈልገነዋል ፥ ርሱም ፡ በዙሪያችን ፡ ዕረፍት ፡ ሰጥቶናል ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ሠሩ ፡ አከናወኑም ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 8 ፤ ለአሣም ፡ አላባሽ ፡ አግሬ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ የሚሸከሙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የይሁዳ ፡ ሰራዊት ፥ ጋሻም ፡ የሚሸከሙ ፡ ቀስትም ፡ የሚገትሩ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ የብንያም ፡ ሰዎች ፡ ነበሩት ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 9 ፤ ኢትዮጵያዊውም ፡ ዝሪ ፡ አንድ ፡ ሚልዮን ፡ ሰዎችና ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠረገላዎች ፡ ይዞ ፡ ወጣባቸው ፤ ወደ ፡ መሪሳም ፡ መጣ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 10 ፤ አሣም ፡ ሊጋጠመው ፡ ወጣ ፥ በመሪሳም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በጽፋታ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ተሰለፉ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 11 ፤ አሣም ፦ አቤቱ ፥ በብዙም ፡ ኾነ ፡ በጥቂቱ ፡ ማዳን ፡ አይሳንኽም ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ ታምነናልና ፥ በስምኽም ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ መጥተናልና ፥ ርዳን ፤ አቤቱ ፥ አምላካችን ፡ አንተ ፡ ነኽ ፤ ሰውም ፡ አያሸንፍኽ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኸ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በአሣና ፡ በይሁዳ ፡ ፊት ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ መታ ፤ ኢትዮጵያውያንም ፡ ሸሹ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 13 ፤ አሣም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ሕዝብ ፡ እስከ ፡ ጌራራ ፡ ድረስ ፡ አሳደዷቸው ፤ ኢትዮጵያውያንም ፡ ፈጽመው ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ ወደቁ ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በሰራዊቱ ፡ ፊት ፡ ተሰባብረዋልና ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ ወሰዱ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 14 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ስለ ፡ ወደቀባቸው ፡ በጌራራ ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩትን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ መቱ ፤ በከተማዎቹም ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ብዝበዛ ፡ ነበረና ፡ ከተማዎቹን ፡ ኹሉ ፡ በዘበዙ ።

መዋ.2 ፥ 14 ፥ 15 ፤ የከብቶቹንም ፡ በረት ፡ አፈረሱ ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ በጎችንና ፡ ግመሎችንም ፡ ማረኩ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተመለሱ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በዖዴድ ፡ ልጅ ፡ በዐዛርያስ ፡ ላይ ፡ ኾነ ፤

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 2 ፤ አሣንም ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ አሣ ፡ ይሁዳና ፡ ብንያም ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ እናንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስትኾኑ ፡ ርሱ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ብትፈልጉትም ፡ ይገኝላችኋል ፤ ብትተዉት ፡ ግን ፡ ይተዋችኋል ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 3 ፤ እስራኤልም ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ያለእውነተኛ ፡ አምላክ ፥ ያለአስተማሪም ፡ ካህን ፥ ያለሕግም ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 4 ፤ በመከራቸውም ፡ ወደእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሰው ፡ በፈለጉት ፡ ጊዜ ፡ አገኙት ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 5 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ለሚወጣውና ፡ ለሚገባው ፡ ሰላም ፡ አልነበረም ፥ በምድርም ፡ በሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋጤ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ በመከራው ፡ ኹሉ ፡ ያስጨንቃቸው ፡ ነበርና ፥ ወገን ፡ ከወገን ፡ ጋራ ፥ ከተማም ፡ ከከተማ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 7 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ለሥራችኹ ፡ ብድራት ፡ ይኾንላችኋልና ፥ በርቱ ፥ እጃችኹም ፡ አይላላ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 8 ፤ አሣም ፡ ይህን ፡ ቃልና ፡ የነቢዩን ፡ የዖዴድን ፡ ትንቢት ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ጸና ፥ ከይሁዳና ፡ ከቢንያምም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በተራራማውም ፡ በኤፍሬም ፡ አገር ፡ ከያዛቸው ፡ ከተማዎች ፡ ጸያፉን ፡ ነገር ፡ አስወገደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ ዐደሰ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 9 ፤ አምላኩም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተጠግተው ፡ ነበርና ፥ ርሱ ፡ ይሁዳንና ፡ ብንያምን ፡ ኹሉ ፥ ከኤፍሬምና ፡ ከምናሴም ፡ ከስምዖንም ፡ መጥተው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የተቀመጡትን ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 10 ፤ አሣም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ካመጡት ፡ ምርኮ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ በሬዎችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሠዉ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 12 ፤ በፍጹም ፡ ልባቸውና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሳቸው ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ፤

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 13 ፤ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማይፈልግ ፥ ታናሽ ፡ ወይም ፡ ታላቅ ፥ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ቢኾን ፥ ይገደል ፡ ዘንድ ፡ ማሉ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 14 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅና ፡ በእልልታ ፥ በእንቢልታና ፡ በቀንደ ፡ መለከት ፡ ማሉ ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 15 ፤ በፍጹምም ፡ ልባቸው ፡ ምለዋልና ፥ በፍጹምም ፡ ኀሊናቸው ፡ ፈልገውታልና ፥ ርሱም ፡ ተገኝቶላቸዋልና ፥ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ በመሐላው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዙሪያቸው ፡ ዕረፍት ፡ ሰጣቸው ።

መዋ.2 ፥ 15 ፥ 16 ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ እናቱን ፡ መዓካን ፡ በማምለኪያ ፡ ዐጸድ ፡ ጣዖት ፡ ስላደረገች ፡ ከእቴጌነቷ ፡ አዋረዳት ፤ አሣም ፡ ምስሏን ፡ ቈርጦ ፡ ቀጠቀጠው ፥ በቄድሮንም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ አቃጠለው ።

መዋ.2 ፡ 15 ፡ 17 ፤ በኰረብታ ፡ ላይ ፡ የነበሩትን ፡ መስገጃዎች ፡ ግን ፡ ከእስራኤል ፡ አላራቀም ፤ ይኹን ፡ እንጂ ፡ የአሣ ፡ ልብ ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹም ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 15 ፡ 18 ፤ አባቱም ፡ የቀደሰውን ፥ ርሱም ፡ የቀደሰውን ፡ ወርቁንና ፡ ብሩን ፥ ልዩ ፡ ልዩውንም ፡ ዕቃ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገባ ።

መዋ.2 ፡ 15 ፡ 19 ፤ አሣም ፡ እስከነገሠበት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ሰልፍ ፡ አልነበረም ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 1 ፤ አሣ ፡ በነገሠ ፡ በሠላሳ ፡ ስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ባአስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ወደይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሣ ፡ ማንም ፡ መውጣትና ፡ መግባት ፡ እንዳይችል ፡ ራማን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 2 ፤ አሣም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ መዝገብ ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ወስዶ ፦

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 3 ፤ በአባቴና ፡ በአባትኽ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በእኔና ፡ ባንተ ፡ መካከል ፡ ይኾናል ፤ እንሆ ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ሰድጄልኻለኹ ፤ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንዲርቅ ፡ ኼደኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከባአስ ፡ ጋራ ፡ ያለኽን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርስ ፡ ብሎ ፡ በደማስቆ ፡ ወደተቀመጠው ፡ ወደሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ወልደ ፡ አዴር ፡ ሰደደ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 4 ፤ ወልደ ፡ አዴር ፡ ንጉሡን ፡ አሣን ፡ ዕሺ ፡ አለው ፥ የሰራዊቱም ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤል ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ሰደደ ፤ እነርሱም ፡ ዒዮንንና ፡ ዳንን ፡ አቤልማይምንና ፡ የንፍታሌምን ፡ የዕቃ ፡ ቤት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ መቱ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 5 ፤ ባአስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ራማን ፡ መሥራት ፡ ተወ ፥ ሥራውንም ፡ አቋረጠ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ አሣ ፡ የይሁዳን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ፤ ባአስ ፡ ይሠራበት ፡ የነበረውን ፡ የራማን ፡ ድንጋይና ፡ ዕንጨት ፡ አስወገዱ ፥ ርሱም ፡ ጌባንና ፡ ምጽጳን ፡ ሠራበት ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ባለራእዩ ፡ ዐናኒ ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሣ ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ታምነኻልና ፥ በአምላክኽም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አልታመንኽምና ፡ ስለዚህ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ጭፍራ ፡ ከእጅኽ ፡ አምልጧል ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 8 ፤ ኢትዮጵያውያንና ፡ የልብያ ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ፈረሰኞች ፡ የነበሯቸው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጭፍራ ፡ አልነበሩምን ፧ በእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ታመንኽ ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፥ ልቡ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፥ ዐይኖቹ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ይመለከታሉና ፦ አኹንም ፡ ስንፍና ፡ አድርገኻል ። ስለዚህም ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ሰልፍ ፡ ይኾንብኻል ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 10 ፤ አሣም ፡ በባለራእዩ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ተቈጥቷልና ፥ በግዞት ፡ አኖረው ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አሣ ፡ ከሕዝቡ ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎችን ፡ አስጨነቀ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 11 ፤ የአሣም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 12 ፤ በነገሠም ፡ በሠላሳ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ አሣ ፡ እግሩን ፡ ታመመ ፤ ደዌውም ፡ ጸናበት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ባለመድኀኒቶችን ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልፈለገም ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 13 ፤ አሣም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በነገሠም ፡ በአርባ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ሞተ ።

መዋ.2 ፡ 16 ፡ 14 ፤ ለርሱም ፡ ለራሱ ፡ በሠራው ፡ መቃብር ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ በቀማሚ ፡ ብልኀት ፡ የተሰናዳ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መልካም ፡ ሽቱ ፡ በተሞላ ፡ ዐልጋ ፡ ላይም ፡ አኖሩት ፤ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ የመቃብር ፡ ወግ ፡ አደረጉለት ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፡ ምዕራፍ ፡ 17 ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 1 ፤ በርሱም ፡ ፋንታ ፡ ልጁ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ነገሠ ፡ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ጠነከረ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 2 ፤ በተመሸጉትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወታደሮችን ፡ አኖረ ፥ በይሁዳም ፡ አገር ፡ አባቱም ፡ አሣ ፡ በወሰዳቸው ፡ በኤፍሬም ፡ ከተማዎች ፡ ዘበኞችን ፡ አስቀመጠ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኢዮሳፍጥ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ በፊተኛዉቱ ፡ በአባቱ ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ኼዷልና ፥ በዓሊምንም ፡ አልፈለገምና ፤

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቱን ፡ አምላክ ፡ ፈለገ ፥ በትእዛዙም ፡ ኼደ ፥ የእስራኤልንም ፡ ሥራ ፡ አልሠራም ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መንግሥቱን ፡ በእጁ ፡ አጸና ፤ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ አመጣ ፤ እጅግም ፡ ብዙ ፡ ብልጥግናና ፡ ክብር ፡ ኾነለት ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 6 ፤ ልቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችና ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዱንም ፡ ከይሁዳ ፡ አስወገደ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 7 ፤ በነገሠም ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ መሳፍንቱን ፥ ቤንሃይልን ፥ ዐብድያስን ፥ ዘካርያስን ፥ ናትናኤልን ፥ ሚክያስን ፥ ሰደደ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 8 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌዋውያንን ፡ ሸማያን ፥ ነታንያን ፥ ዝባድያን ፥ ዐሳሄልን ፥ ሰሚራሞትን ፥ ዮናታንን ፥ አዶንያስን ፥ ጦብያን ፥ ጦባዶንያን ፡ ሰደደ ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ካህናቱን ፡ ኤሊሳማንና ፡ ኢዮራምን ፡ ሰደደ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ ይዘው ፡ በይሁዳ ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ፤ ወደይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ኼደው ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 10 ፤ በይሁዳም ፡ ዙሪያ ፡ በነበሩ ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ድንጋጤ ፡ ኾነ ፥ ከኢዮሳፍጥም ፡ ጋራ ፡ አልተዋጉም ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 11 ፤ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ እጅ ፡ መንሻና ፡ የብር ፡ ግብር ፡ ያመጡ ፡ ነበር ፤ ዐረባውያንም ፡ ደግሞ ፡ ከመንጋዎቻቸው ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አውራ ፡ በጎችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ያመጡለት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 12 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ እየበረታና ፡ እጅግም ፡ እየከበረ ፡ ኼደ ፤ በይሁዳም ፡ ግንቦችንና ፡ የጐተራ ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 13 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ብዙ ፡ ሥራ ፡ ሠራ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰልፈኞች ፡ ነበሩት ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 14 ፤ ቍጥራቸውም ፡ እንደአባቶቻቸው ፡ ቤት ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ከይሁዳ ፡ ሻለቃዎች ፡ አለቃው ፡ ዓድና ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 15 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ አለቃው ፡ ይሆሐናን ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 16 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በፈቃዱ ፡ ራሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የቀደሰ ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ ዓማስያ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 17 ፤ ከብንያምም ፡ ጽኑዕ ፡ ኀያል ፡ የነበረው ፡ ኤሊዳሄ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ቀስትና ፡ ጋሻ ፡ የሚይዙ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 18 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የዛባት ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ለሰልፍ ፡ የተዘጋጁ ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 17 ፡ 19 ፤ ንጉሡ ፡ በተመሸጉ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ካኖራቸውም ፡ ሌላ ፡ እነዚህ ፡ ንጉሡን ፡ ያገለግሉ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 1 ፤ ለኢዮሳፍጥም ፡ ብዙ ፡ ብልጥግናና ፡ ክብር ፡ ነበረው ፤ ለአክአብም ፡ ጋብቻ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 2 ፤ ከጥቂት ፡ ዓመት ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ አክአብ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ወረደ ። አክአብም ፡ ለርሱና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ብዙ ፡ በጎችንና ፡ በሬዎችን ፡ ዐረደ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አባበለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አክአብ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ትኼዳለኽን ፧ አለው ። ርሱም ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነኝ ፥ ሕዝቤም ፡ እንደ ፡ ሕዝብኽ ፡ ናቸው ፤ በሰልፍም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንኾናለን ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 4 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አስቀድመኽ ፡ ትጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ነቢያቱን ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሰዎች ፡ ሰብስቦ ፦ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ ልኼድን ፧ ወይስ ፡ ልቅር ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ውጣ ፡ አሉት ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 6 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፦ እንጠይቀው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነቢይ ፡ የኾነ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አይገኝምን ፧ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 7 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ እግዚአብሔርን ፡ የምንጠይቅበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዅል ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ እንጂ ፡ ከቶ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይነግርልኝምና ፡ እጠላዋለኹ ፤ ርሱም ፡ የይምላ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ፡ ነው ፡ አለው ። ኢዮሳፍጥም ፦ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ አይበል ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ አንድ ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ጠርቶ ፦ የይምላን ፡ ልጅ ፡ ሚክያስን ፡ ፈጥነኽ ፡ አምጣው ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 9 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሰው ፡ በሰማርያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ በአደባባይ ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፡ በፊታቸው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 10 ፤ የክንዓና ፡ ልጅ ፡ ሰዴቅያስም ፡ የብረት ፡ ቀንዶች ፡ ሠርቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡

ይላል ፦ ሶርያውያንን ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በእነዚህ ፡ ትወጋለኽ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 11 ፤ ነቢያትም ፡ ኹሉ ፦ እግዚአብሔር ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣታልና ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ኺድና ፡ ተከናወን ፡ እያሉ ፡ እንዲሁ ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 12 ፤ ሚክያስንም ፡ ሊጠራ ፡ የኼደ ፡ መልእክተኛ ፦ እንሆ ፥ ነቢያት ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ ኾነው ፡ ለንጉሡ ፡ መልካም ፡ ይናገራሉ ፤ ቃልኽም ፡ እንደ ፡ ቃላቸው ፡ እንዲኾን ፡ መልካም ፡ እንድትናገር ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 13 ፤ ሚክያስም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ አምላኬ ፡ የሚለውን ፡ ርሱን ፡ እናገራለኹ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፦ ሚክያስ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ለሰልፍ ፡ እንኺድን ፧ ወይስ ፡ እንቅር ፧ አለው ። ርሱም ፦ ውጣ ፥ ተከናወን ፤ በእጅኽም ፡ ዐልፈው ፡ ይሰጣሉ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 15 ፤ ንጉሡም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከእውነት ፡ በቀር ፡ እንዳትነግረኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ አምልኻለኹ ፧ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 16 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ጠባቂ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተበትነው ፡ አየኹ ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለእነዚህ ፡ ጌታ ፡ የላቸውም ፥ እያንዳንዱም ፡ በሰላም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለስ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 17 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ክፉ ፡ እንጂ ፡ መልካም ፡ ትንቢት ፡ አይናገርልኝም ፡ አላልኹኽምን ፧ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 18 ፤ ሚክያስም ፡ አለ ፦ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፥ የሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ በቀኙና ፡ በግራው ፡ ቆመው ፡ አየኹ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ወጥቶ ፡ በሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ይወድቅ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ አክአብን ፡ የሚያታልል ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ። አንዱም ፡ እንደዚህ ፥ ሌላውም ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 20 ፤ መንፈስም ፡ መጣ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፦ እኔ ፡ አታልለዋለኹ ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ በምን ፧ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ ወጥቼ ፡ በነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስ ፡ እኾናለኹ ፡ አለ ። እግዚአብሔርም ፦ ታታልለዋለኽ ፤ ይቀናኻል ፤ ውጣ ፥ እንዲህም ፡ አድርግ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 22 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነዚህ ፡ በነቢያትኽ ፡ አፍ ፡ ሐሰተኛ ፡ መንፈስን ፡ አድርጓል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ተናግሮብኻል ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 23 ፤ የክንዓናም ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ቀረበ ፥ ሚክያስንም ፡ በጥፊ ፡ መታውና ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ ዐለፈ ፧ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 24 ፤ ሚክያስም ፦ እንሆ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ልትሸሸግ ፡ ወደ ፡ ዕልፍኝኽ ፡ ስትኼድ ፡ ታያለኽ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 25 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ። ሚክያስን ፡ ውሰዱ ፥ ወደከተማዩቱም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ዐሞን ፥ ወደንጉሡም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአስ ፡ መልሳቸኹ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 26 ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በደኅና ፡ እስክመለስ ፡ ድረስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ በግዞት ፡ አኑሩት ፥ የመከራም ፡ እንጀራ ፡ መግቡት ፥ የመከራም ፡ ውሃ ፡ አጠጡት ፡ በሉ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 27 ፤ ሚክያስም ፦ በደኅና ፡ ብትመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኔ ፡ የተናገረ ፡ አይደለም ፡ አለ ። ደግሞም ፦ እናንተ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ስሙኝ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 28 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ሬማት ፡ ዘገለዓድ ፡ ወጡ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 29 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥም ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ልብሴን ፡ ለውጬ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እገባለኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ልብስኽን ፡ ልበስ ፡ አለው ። የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ልብሱን ፡ ለወጠ ፥ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ገቡ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 30 ፤ የሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ የሠረገላዎቹን ፡ አለቃዎች ፦ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ በቀር ፡ ትንሽ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ትልቅ ፡ ከማናቸውም ፡ ጋራ ፡ አትጋጠሙ ፡ ብሎ ፡ አዞ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 31 ፤ የሠረገላዎችም ፡ አለቃዎች ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ አሉ ፥ ሊጋጠሙትም ፡ ከበቡት ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ ግን ፡ ጮኸ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ረዳው ፥ አምላኩም ፡ ከርሱ ፡ መለሳቸው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 32 ፤ የሠረገላዎቹም ፡ አለቃዎች ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንዳልኾነ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ርሱን ፡ ከማሳደድ ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 33 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ቀስቱን ፡ በድንገት ፡ ገትሮ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ በጥሩሩ ፡ መጋጠሚያ ፡ በኩል ፡ ሳምባውን ፡ ወጋው ። ሠረገላኛውንም ፦ ተወግቻለኹና ፡ እጅኽን ፡ ግታ ፥ ከሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ አውጣኝ ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 18 ፡ 34 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፍ ፡ በረታ ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በሶርያውያን ፡ ፊት ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ በሠረገላው ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡ ይደግፍ ፡ ነበር ፤ ፀሐይም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 1 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደኅና ፡ ተመለሰ ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 2 ፤ ባለራእዩ ፡ የዐናኒ ፡ ልጅ ፡ ኢዩ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥ ንጉሡንም ፡ ኢዮሳፍጥን ፦ ከሓዲውን ፡ ታግዛለኽን ፧ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚጠሉትን ፡ ትወዳለኽን ፧ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ቍጣ ፡ ኾኖብኻል ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹን ፡ ከምድር ፡ አስወግደኻልና ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ትፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ልብኽን ፡ አዘጋጅተኻልና ፥ መልካም ፡ ነገር ፡ ተገኝቶብኻል ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 4 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጠ ፤ ደግሞም ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ተራራማው ፡ እስከኤፍሬም ፡ አገር ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወጥቶ ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መለሳቸው ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 5 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በተመሸጉት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ፈራጆች ፡ አኖረ ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 6 ፤ ፈራጆቹንም ፦ ለእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አትፈርዱምና ፥ ርሱም ፡ በፍርድ ፡ ነገር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ የምታደርጉትን ፡ ተመልከቱ ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በደልና ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ ማድላት ፡ መማለጃም ፡ መውሰድ ፡ የለምና ፡ ኹሉን ፡ ተጠንቅቃችኹ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 19 ፡ 8 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከሌዋውያንና ፡ ከካህናት ፡ ከእስራኤልም ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡

አለቃዎች ፥ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ፍርድን ፡ እንዲፈርዱ ፡ ክርክርንም ፡ እንዲቈርጡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሾመ ። እነርሱም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ።

መዋ.2 ፥ 19 ፥ 9 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፦ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ በቅንነትም ፡ በፍጹምም ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

መዋ.2 ፥ 19 ፥ 10 ፤ በከተማዎቻቸውም ፡ ከተቀመጡት ፡ ከወንድሞቻችኹ ፡ በደምና ፡ በደም ፡ መካከል ፡ በሕግና ፡ በትእዛዝ ፡ በሥርዐትና ፡ በፍርድም ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ማናቸውም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቢመጣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳይበድሉ ፥ ቍጣም ፡ በእናንተና ፡ በወንድሞቻችኹ ፡ ላይ ፡ እንዳይመጣ ፡ አስጠንቅቋቸው ፤ እንዲህም ፡ ብታደርጉ ፡ በደለኞች ፡ አትኾኑም ።

መዋ.2 ፥ 19 ፥ 11 ፤ እንሆም ፥ ለእግዚአብሔር ፡ በሚኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የካህናቱ ፡ አለቃ ፡ አማርያ ፥ በንጉሡም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የይስማኤል ፡ ልጅ ፡ ዝባድያ ፡ በላያችኹ ፡ ተሾመዋል ፤ ሌዋውያኑም ፡ ደግሞ ፡ በፊታችኹ ፡ አለቃዎች ፡ ይኾናሉ ፤ በርትታችኹም ፡ አድርጉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ መልካም ፡ ከሚያደርግ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሞዐብና ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ምዑናውያን ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ሊወጉ ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 2 ፤ ወሬኞችም ፡ መጥተው ፦ ከባሕሩ ፡ ማዶ ፡ ከሶርያ ፡ ታላቅ ፡ ሰራዊት ፡ መጥቶብኻል ፤ እንሆም ፥ ዐይንጋዲ ፡ በተባለች ፡ በሐሴሶን ፡ ታማር ፡ ናቸው ፡ ብለው ፡ ለኢዮሳፍጥ ፡ ነገሩት ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 3 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ፈራ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ሊፈልግ ፡ ፊቱን ፡ አቀና ፤ በይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ ጾም ፡ ዐወጀ ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 4 ፤ ይሁዳም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ተከማቸ ፤ ከይሁዳ ፡ ከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 5 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ጉባኤ ፡ መካከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በዐዲሱ ፡ አደባባይ ፡ ፊት ፡ ቆመ ፤

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 6 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አቤቱ ፡ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማይ ፡ ያለኽ ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ የአሕዛብንስ ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ የምትገዛ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ ኀይልና ፡ ችሎታ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፥ ሊቋቋምኽም ፡ የሚችል ፡ የለም ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 7 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ምድር ፡ የነበሩትን ፡ አሕዛብ ፡ ከሕዝብኽ ፡ ከእስራኤል ፡ ፊት ፡ ያሳደድኽ ፥ ለወዳጅኽም ፡ ለአብርሃም ፡ ዘር ፡ ለዘለዓለም ፡ የሰጠኻት ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 8 ፤ እነርሱም ፡ የተቀመጡባት ፥ ለስምኽም ፡ መቅደስን ፡ ሠርተውባት ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 9 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፥ የፍርድ ፡ ሰይፍ ፡ ወይም ፡ ቸነፈር ፡ ወይም ፡ ራብ ፥ ቢመጣብን ፡ ስምኽ ፡ ባለበት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ ፊትና ፡ በፊትኽ ፡ ቆመን ፡ በመከራችን ፡ ወዳንተ ፡ እንጮኻለን ፥ አንተም ፡ ሰምተኽ ፡ ታድነናለኽ ፡ አሉ ።

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 10 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ያልፉባቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልፈቀድኽላቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈቀቅ ፡ ብለው ፡ ያላጠፏቸው ፥ የዐሞንና ፡ የሞዐብ ፡ ልጆች ፡ የሴይርም ፡ ተራራ ፡ ሰዎች ፥

መዋ.2 ፥ 20 ፥ 11 ፤ እንሆ ፥ ለወሮታችን ፡ ክፉት ፡ ይመልሱልናል ፤ ከሰጠኸንም ፡ ርስት ፡ ያወጡን ፡ ዘንድ ፡

መጥተዋል ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 12 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ አትፈርድባቸውምን ፧ ይህን ፡ የመጣብንን ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ እንቃወም ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፤ የምናደርገውንም ፡ አናውቅም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐይኖቻችን ፡ ወዳንተ ፡ ናቸው ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 13 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃናታቸውና ፡ ከሚስቶቻቸው ፡ ከልጆቻቸውም ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ከአሣፍ ፡ ወገን ፡ በነበረው ፡ በሌዋዊው ፡ በማታንያ ፡ ልጅ ፡ በይዒኤል ፡ ልጅ ፡ በበናያስ ፡ ልጅ ፡ በዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ በየሕዚኤል ፡ ላይ ፡ በጉባኤው ፡ መካከል ፡ መጣ ፤

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 15 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፥ አንተም ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮሳፍጥ ፥ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላችኋል ። ሰልፉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእናንተ ፡ አይደለምና ፡ ከዚህ ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 16 ፤ ነገ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ውረዱ ፤ እንሆ ፥ በጺጽ ፡ ዐቀበት ፡ ይወጣሉ ፤ በሸለቆውም ፡ መጨረሻ ፡ በይሩኤል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ታገኟቸዋላችኹ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 17 ፤ እናንተ ፡ በዚህ ፡ ሰልፍ ፡ የምትዋጉ ፡ አይደላችኹም ፤ ይሁዳና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ተሰለፉ ፥ ዝም ፡ ብላችኹ ፡ ቁሙ ፥ የሚኾነውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መድኀኒት ፡ እዩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ፥ ነገም ፡ ውጡባቸው ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 18 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተደፋ ፡ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደቁ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገዱ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 19 ፤ ሌዋውያንም ፥ የቀአት ፡ ልጆችና ፡ የቆሬ ፡ ልጆች ፥ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በእጅግ ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ያመሰገኑት ፡ ዘንድ ፡ ቆሙ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 20 ፤ ማልደውም ፡ ተነሡ ፥ ወደቴቁሔም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጡ ፤ ሲወጡም ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ቆመና ፦ ይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ በአምላካችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ፥ ትጸኑማላችኹ ፤ በነቢያቱም ፡ እመኑ ፥ ነገሩም ፡ ይሰላላችኋል ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 21 ፤ ከሕዝቡም ፡ ጋራ ፡ ተማክሮ ፡ በሰራዊቱ ፡ ፊት ፡ የሚኼዱትን ፦ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚሉትንም ፥ ጌጠኛ ፡ ልብስም ፡ ለብሰው ፡ የሚያመሰግኑትን ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ የሚዘምሩትን ፡ መዘምራን ፡ አቆመ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 22 ፤ ዝማሬውንና ፡ ምስጋናውንም ፡ በዝምሩ ፡ ጊዜ ፡ ይሁዳን ፡ ሊወጉ ፡ በመጡት ፡ በዐሞንና ፡ በሞዐብ ፡ ልጆች ፡ በሴይርም ፡ ተራራ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድብቅ ፡ ጦርን ፡ አመጣባቸው ፤ እነርሱም ፡ ተመቱ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 23 ፤ የዐሞንና ፡ የሞዐብ ፡ ልጆችም ፡ በሴይር ፡ ተራራ ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ፈጽመው ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ያጠፏቸውም ፡ ዘንድ ፡ ተነሥተውባቸው ፡ ነበር ፤ በሴይርም ፡ የሚኖሩትን ፡ ካጠፉ ፡ በኋላ ፡ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ለማጥፋት ፡ ተረዳዳ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 24 ፤ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ወደምድረ ፡ በዳ ፡ ግንብ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ አዩ ፤ እንሆም ፥ በምድሩ ፡ ኹሉ ፡ ሬሳ ፡ ሞልቶ ፡ ነበር ፥ ያመለጠም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 25 ፤ ኢዮሳፍጥና ፡ ሕዝቡም ፡ ምርኮ ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ መጡ ፡ ብዙ ፡ ከብትና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕቃም ፥ ልብስም ፥ እጅግም ፡ ያማረ ፡ ዕቃ ፡ አገኙ ፥ በዘበዙትም ፥ ኹሉንም ፡ ይሸከሙ ፡ ዘንድ ፡

አልቻሉም ፤ ከምርኮውም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ይበዘብዙ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 26 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ በበረከት ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ተሰበሰቡ ፥ በዚያም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረኩ ፤ ስለዚህም ፡ ያ ፡ ስፍራ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የበረከት ፡ ሸለቆ ፡ ተባለ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 27 ፤ የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፥ በፊታቸውም ፡ ኢዮሳፍጥ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አሠኝቷቸዋልና ፥ በደስታ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 28 ፤ በበገናም ፡ በመሰንቆም ፡ በመለከትም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገቡ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእስራኤልን ፡ ጠላቶች ፡ እንደ ፡ ወጋ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 30 ፤ የኢዮሳፍጥም ፡ መንግሥት ፡ ጸጥ ፡ አለች ፥ አምላኩም ፡ በዙሪያው ፡ ካሉ ፡ አሳረፈው ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 31 ፤ ኢዮሳፍጥ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜም ፡ የሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የሺልሒ ፡ ልጅ ፡ ዓዙባ ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 32 ፤ በአባቱም ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 33 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ አልተወገዱም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ ልባቸውን ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ አላዘጋጁም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 34 ፤ የቀረውም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኘው ፡ በዐናኒ ፡ ልጅ ፡ በኢዩ ፡ ታሪክ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 35 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮሳፍጥ ፡ ሥራው ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ከኾነ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከአካዝያስ ፡ ጋራ ፡ ተባበረ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 36 ፤ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ የሚኼዱትን ፡ መርከቦች ፡ ያሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ኾኑ ፤ መርከቦቹንም ፡ በዔጽዮንጋብር ፡ አሠሩ ።

መዋ.2 ፡ 20 ፡ 37 ፤ የመሪሳም ፡ ሰው ፡ የዶዳያ ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፦ ከአካዝያስ ፡ ጋራ ፡ ተባብረኻልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ሥራኽን ፡ አፍርሶታል ፡ ብሎ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ። መርከቦቹም ፡ ተሰበሩ ፥ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 1 ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀበረ ፤ ልጁም ፡ ኢዮራም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 2 ፤ ለርሱም ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጆች ፡ ዐዛርያስ ፥ ይሒኤል ፥ ዘካርያስ ፥ ዔዛርያስ ፥ ሚካኤል ፥ ሰፋጥያስ ፡ የሚባሉ ፡ ወንድሞች ፡ ነበሩት ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጆች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 3 ፤ አባታቸውም ፡ ብዙ ፡ ስጦታ ፥ ብርና ፡ ወርቅ ፥ የከበረም ፡ ዕቃ ፥ በይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ ሰጣቸው ፤ መንግሥቱን ፡ ግን ፡ በኵር ፡ ልጁ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለኢዮራም ፡ ሰጠ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 4 ፤ ኢዮራምም ፡ በአባቱ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ተነሥቶ ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞቹን ፡ ኹሉ ፡

ሌላዎችንም ፡ የእስራኤልን ፡ መሳፍንት ፡ በሰይፍ ፡ ገደለ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 5 ፤ ኢዮራምም ፡ መንገሥ ፡ በገ፞ መረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 6 ፤ የአክአብንም ፡ ልጅ ፡ አግብቶ ፡ ነበርና ፥ የአክአብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዳዊት ፡ ጋራ ፡ ስላደረገው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፥ ለርሱና ፡ ለልጆቹም ፡ በዘመናት ፡ ኹሉ ፡ መብራት ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ስለሰጠው ፡ ተስፋ ፥ እግዚአብሔር ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 8 ፤ በርሱም ፡ ዘመን ፡ ኤዶምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፥ ለራሱም ፡ ንጉሥ ፡ አነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 9 ፤ ኢዮራምም ፡ ከአለቃዎቹና ፡ ከሠረገላዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተሻገረ ፤ በሌሊትም ፡ ተነሥቶ ፡ ርሱንና ፡ የሠረገላዎቹን ፡ አለቃዎች ፡ ከ፡ዉ ፡ የነበሩትን ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ መታ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 10 ፤ ኤዶምያስ ፡ ግን ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዐመፀ ፥ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ልብና ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ፥ የአባቶቹን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትቶ ፡ ነበርና ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 11 ፤ ዳግምም ፡ በይሁዳ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ መስገጃዎችን ፡ ሠራ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡትን ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ አደረጋቸው ፥ ይሁዳንም ፡ አ፡ሳተው ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 12 ፤ ከነቢዩም ፡ ከኤልያስ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ መጣባት ፦ የአባትኽ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአባትኽ ፡ በኢዮሳፍጥ ፡ መንገድ ፡ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሣ ፡ መንገድ ፡ አልኼድኽምና ፥

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 13 ፤ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ኼደኻልና ፥ የአክአብም ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ ይሁዳንና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ እንዲያመነዝሩ ፡ አድርገኻልና ፥ ከአንተም ፡ የሚሻሉትን ፡ የአባትኽን ፡ ቤት ፡ ወንድሞችኽን ፡ ገድለኻልና ፥

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝብኽንና ፡ ልጆችኽን ፡ ሚስቶችኽንም ፡ ያለኽንም ፡ ኹሉ ፡ በታላቅ ፡ መቅሠፍት ፡ ይቀሥፋል ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 15 ፤ አንተም ፡ ከደዌው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ አንገትኽ ፡ በየዕለቱ ፡ እስኪ፡ወጣ ፡ ድረስ ፡ በክፉ ፡ የአንገት ፡ ደዌ ፡ ትታመማለኽ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የፍልስጥኤማውያንና ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ አጠገብ ፡ የሚኖሩትን ፡ የዐረባውያንን ፡ መንፈስ ፡ በኢዮራም ፡ ላይ ፡ አስነሣ ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ ወጡ ፥ አፈረሷትም ፥ የንጉሡንም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፥ ወንዶች ፡ ልጆቹንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቹንም ፡ ማረኩ ፤ ከታናሹም ፡ ልጅ ፡ ከአካዝያስ ፡ በቀር ፡ ልጅ ፡ አልቀረለትም ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 18 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ በማይፈወስ ፡ ደዌ ፡ አንገቱን ፡ ቀሠፈው ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 19 ፤ ከቀንም ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከደዌው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ አንገቱ ፡ ወጣ ፥ በክፉም ፡ ደዌ ፡ ሞተ ። ሕዝቡም ፡ ለአባቶቹ ፡ ያደርገው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ለርሱ ፡ የመቃብር ፡ ወግ ፡ አላደረገም ።

መዋ.2 ፡ 21 ፡ 20 ፤ መንገሥ ፡ በገ፞ መረ ፡ ጊዜ ፡ የሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡

ስምንት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ ማንም ፡ ሳያዝንለት ፡ ኼደ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ እንጂ ፡ በነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አልቀበሩትም ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 1 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩትም ፡ ታናሹን ፡ ልጁን ፡ አካዝያስን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ። የመጣባቸው ፡ የዐረብና ፡ የአሊማዘን ፡ የሽፍቶች ፡ ጭፍራ ፡ የርሱን ፡ ታላቆች ፡ ገድለዋቸው ፡ ነበርና ። የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 2 ፤ አካዝያስም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ጎቶሊያ ፡ የተባለች ፡ የዘንበሪ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 3 ፤ እናቱም ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ ትመክረው ፡ ነበርና ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 4 ፤ አባቱም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የአክአብ ፡ ቤት ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ መካሪዎች ፡ ነበሩትና ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 5 ፤ በምክራቸውም ፡ ኼደ ፥ ከእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ከአክአብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮራም ፡ ጋራ ፡ የሶርያን ፡ ንጉሥ ፡ አዛሄልን ፡ በሬማት ፡ ዘገለአድ ፡ ሊዋጋ ፡ ኼደ ፤ ሶርያውያንም ፡ ኢዮራምን ፡ አቈሰሉት ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 6 ፤ ከሶርያም ፡ ንጉሥ ፡ ከአዛሄል ፡ ጋራ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ሶርያውያን ፡ በሬማት ፡ ያቈሰሉትን ፡ ቍስል ፡ ይታከም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ተመለሰ ፤ ታሞም ፡ ነበርና ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ አካዝያስ ፡ የአክአብን ፡ ልጅ ፡ ኢዮራምን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢይዝራኤል ፡ ወረደ ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 7 ፤ አካዝያስም ፡ ወደ ፡ ኢዮራም ፡ በመምጣቱ ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነበረ ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ከኢዮራም ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአክአብን ፡ ቤት ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወደቀባው ፡ ወደናሜሲ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዩ ፡ ወጣ ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 8 ፤ ኢዩም ፡ በአክአብ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ሲፈጽም ፡ የይሁዳን ፡ መሳፍንትና ፡ አካዝያስን ፡ ያገለግሉ ፡ የነበሩትን ፡ የአካዝያስን ፡ ወንድሞች ፡ ልጆች ፡ አግኝቶ ፡ ገደላቸው ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 9 ፤ አካዝያስንም ፡ ፈለገው ፥ በሰማርያ ፡ ተሸሽጎ ፡ ሳለ ፡ አገኙት ፤ ወደ ፡ ኢዩም ፡ አምጥተው ፡ ገደሉትና ፦ በፍጹም ፡ ልብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈለገው ፡ የኢዮሳፍጥ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ቀበሩት ። ከአካዝያስም ፡ ቤት ፡ ማንም ፡ መንግሥትን ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 10 ፤ የአካዝያስም ፡ እናት ፡ ጎቶሊያ ፡ ልጇ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተነሥታ ፡ የይሁዳን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ አጠፋች ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 11 ፤ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ዮሳቤት ፡ ግን ፡ ከተገደሉት ፡ ከንጉሡ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአስን ፡ ሰርቃ ፡ ወሰደች ፤ ርሱንና ፡ ሞግዚቱን ፡ በዕልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ አኖረቻቸው ፤ ጎቶሊያ ፡ እንዳታስገድለው ፡ የንጉሡ ፡ የኢዮራም ፡ ልጅ ፡ የአካዛያስ ፡ እኅት ፡ የካህኑ ፡ የዮዳዔ ፡ ሚስት ፡ ዮሳቤት ፡ እንዲሁ ፡ ሸሸገችው ።

መዋ.2 ፥ 22 ፥ 12 ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ተቀመጠ ፤ ጎቶልያም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነገሠች ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 1 ፤ በሰባተኛውም ፡ ዓመት ፡ ዮዳዔ ፡ በረታ ፥ የመቶ ፡ አለቃዎቹንም ፥ የይሮሐምን ፡ ልጅ ፡

ዐዛርያስን ፥ የይሖሐናንንም ፡ ልጅ ፡ ይስማኤልን ፥ የዖቤድንም ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስን ፥ የዓዳያንም ፡ ልጅ ፡
መዕሴያን ፥ የዝክሪንም ፡ ልጅ ፡ ኤሊሳፋጥን ፡ ወስዶ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 2 ፤ ይሁዳንም ፡ ዞሩ ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ሌዋውያንንና ፡ የእስራኤልን ፡ አባቶች ፡
ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ሰብስበው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 3 ፤ ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡
አደረገ ። ዮዳዔም ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለዳዊት ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ የንጉሡ ፡ ልጅ ፡
ይነግሣል ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 4 ፤ የምታደርጉት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከምትገቡት ፡ ከእናንተ ፡ ከካህናትና ፡ ከሌዋዊውያን ፡
ከሦስት ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ በመግቢያ ፡ በሮች ፡ በረኞች ፡ ኹኑ ፤

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 5 ፤ ከሦስት ፡ አንድ ፡ እጅም ፡ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ኹኑ ፤ አንድ ፡ እጅም ፡ በመካከለኛው ፡ በር ፡
ኹኑ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ይኹኑ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 6 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ከካህናትና ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ሌዋውያን ፡ በቀር ፡ ማንም ፡
አይግባ ፤ እነርሱ ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸውና ፥ ይግቡ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይጠብቅ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 7 ፤ ሌዋውያንም ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ንጉሡን ፡ በዙሪያው ፡
ይክበቡት ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ የሚገባ ፡ ይገደል ፡ ንጉሡም ፡ ሲገባና ፡ ሲወጣ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኹኑ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 8 ፤ ሌዋውያንና ፡ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ ካህኑ ፡ ዮዳዔ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉ ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡
ሰሞነኞቹን ፡ አላሰናበተም ፡ ነበርና ፥ እያንዳንዱ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ይገቡ ፡ የነበሩትን ፡ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ይወጡ ፡
የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 9 ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የንጉሡን ፡ የዳዊትን ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡
አላባሽ ፡ አግሬውንም ፡ ጋሻ ፡ ለመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ሰጣቸው ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 10 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ የጦር ፡ መሣሪያውን ፡ በእጁ ፡ እየያዘ ፡ በንጉሡ ፡ ዙሪያ ፡ ከቤቱ ፡
ቀኝ ፡ እስከቤቱ ፡ ግራ ፡ ድረስ ፡ በመሠዊያውና ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ እንዲቆም ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 11 ፤ የንጉሡንም ፡ ልጅ ፡ አውጥተው ፡ ዘውዱን ፡ ጫነበት ፥ ምስክሩንም ፡
ሰጡት ፥ አነገሡትም ፤ ዮዳዔና ፡ ልጆቹም ፦ ንጉሡ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፡ እያሉ ፡ ቀቡት ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 12 ፤ ጎቶሊያም ፡ የሚሮጡትንና ፡ ንጉሡን ፡ የሚያመሰግኑትን ፡ የሕዝቡን ፡ ድምፅ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡
ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መጣች ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 13 ፤ እንሆም ፥ ንጉሡ ፡ በመግቢያው ፡ በዐምዱ ፡ አጠገብ ፡ ኾኖ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ አለቃዎችና ፡
መለከተኞች ፡ ቆመው ፡ አየች ። የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ መለከቱን ፡ ይነፉ ፡ ነበር ፤ መዘምራንም ፡
በዜማ ፡ ዕቃ ፡ እያዜሙ ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ፡ ይዘምሩ ፡ ነበር ። ጎቶሊያም ፡ ልብሷን ፡ ቀዳ ፦ ዐመፅ ፡ ነው ፥ ዐመፅ ፡
ነው ፡ ብላ ፡ ጮኸች ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 14 ፤ ካህኑም ፡ ዮዳዔ ፡ በጭፍራው ፡ ላይ ፡ የተሾሙትን ፡ የመቶ ፡ አለቃዎች ፦ ወደ ፡ ሰልፉ ፡
መካከል ፡ አውጧት ፤ የሚከተላትም ፡ በሰይፍ ፡ ይገደል ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ። ካህኑም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡
አትግደሏት ፡ አለ ።

መዋ.2 ፥ 23 ፥ 15 ፤ ገለልም ፡ ብለው ፡ አሳለፏት ፤ ርሷም ፡ ወደፈረሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡
ኼደች ፥ በዚያም ፡ ገደሏት ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 16 ፤ ዮዳዔም ፡ በርሱና ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡም ፡ መካከል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 17 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደበዓል ፡ ቤት ፡ ኼደው ፡ አፈረሱት ፥ መሠዊያዎቹንና ፡ ምስሎቹንም ፡ አደቀቁ ፥ የበዓልንም ፡ ካህን ፡ ማታንን ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ ገደሉት ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 18 ፤ ዮዳዔም ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደተጻፈው ፥ እንደ ፡ ዳዊትም ፡ ትእዛዝ ፥ በደስታና ፡ በመዝሙር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የከፈላቸውን ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ሾመ ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 19 ፤ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርኩስ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ እንዳይገባ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ በረኞችን ፡ አኖረ ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 20 ፤ የመቶ ፡ አለቃዎችንም ፥ ከበርቴዎቹንም ፥ የሕዝቡንም ፡ አለቃዎች ፥ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወሰደ ፥ ንጉሡንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አወረደ ፤ በላይኛውም ፡ በር ፡ በኩል ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ መጡ ፥ ንጉሡንም ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ አኖሩት ።

መዋ.2 ፡ 23 ፡ 21 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፥ ከተማዪቱም ፡ ጸጥ ፡ አለች ፤ ጎቶሊያንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደሏት ። ኾ ፡

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 1 ፤ አዮአስም ፡ መንገሥ ፡ በገፖመረ ፡ ጊዜ ፡ የሰባት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ሳብያ ፡ የተባለች ፡ የቤርሳቤሕ ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 2 ፤ በካህኑም ፡ በዮዳዔ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ አዮአስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 3 ፤ ዮዳዔም ፡ ኹለት ፡ ሚስቶች ፡ አጋባው ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ወለደ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 4 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አዮአስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይጠግን ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 5 ፤ ካህናትንና ፡ ሌዋውያንንም ፡ ሰብስቦ ፦ ወደይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ውጡ ፥ የአምላካችኹንም ፡ ቤት ፡ በየዓመቱ ፡ ለማደስ ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ገንዘብን ፡ ሰብስቡ ፤ ነገሩንም ፡ ፈጥናችኹ ፡ አድርጉ ፡ አላቸው ። ሌዋውያን ፡ ግን ፡ ቸል ፡ አሉ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ አለቃውን ፡ ዮዳዔን ፡ ጠርቶ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ ስለምስክሩ ፡ ድንኳን ፡ የእስራኤል ፡ ጉባኤ ፡ እንዲያዋጣ ፡ ያዘዘውን ፡ ግብር ፡ ከይሁዳና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሌዋውያንን ፡ አላተጋኻቸውም ፧ አለው ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 7 ፤ ጎቶሊያ ፡ ከሓዲት ፡ ነበረችና ፡ ልጆቿም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አፍርሰዋልና ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ተቀድሶ ፡ የነበረውን ፡ ኹሉ ፡ ለበዓሊም ፡ ሰጥተዋልና ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ አዘዘ ፥ ሣጥንም ፡ ሠርተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ በስተውጭ ፡ አኖሩት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ ሙሴ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ያዘዘውን ፡ ግብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 10 ፤ አለቃዎቹና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ አቀረቡት ፥ እስኪሞላም ፡ ድረስ ፡ በሣጥኑ ፡

ውስጥ ፡ ጣሉት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 11 ፤ ሣጥኑም ፡ በሌዋውያን ፡ እጅ ፡ ወደንጉሡ ፡ ሹማምት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ ብዙ ፡ ገንዘብም ፡ እንዳለበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ የንጉሡ ፡ ጸሓፊና ፡ የዋነኛው ፡ ካህን ፡ ሹም ፡ እየመጡ ፡ ብሩን ፡ ከሣጥን ፡ ያወጡ ፡ ነበር ፥ ሣጥኑንም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ይመልሱት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ በየቀኑ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፥ ብዙም ፡ ገንዘብ ፡ አከማቹ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 12 ፤ ንጉሡና ፡ ዮዳዔም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለተሾሙት ፡ ሰጧቸው ፤ እነርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የሚጠግኑትን ፡ ጠራቢዎችንና ፡ ዐናጢዎችን ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ የሚያድሱትን ፡ የብረትና ፡ የናስ ፡ ሠራተኞችን ፡ ይገዙበት ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 13 ፤ ሠራተኞችም ፡ ሠሩ ፥ የፈረሰውም ፡ በእጃቸው ፡ ተጠገነ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ እንደቀድሞው ፡ ሥራ ፡ መለሱ ፥ አጽንተውም ፡ አቆሙት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 14 ፤ በጨረሱም ፡ ጊዜ ፡ የተረፈውን ፡ ገንዘብ ፡ በንጉሡና ፡ በዮዳዔ ፡ ፊት ፡ አመጡ ፤ እነርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፥ ለአገልግሎትና ፡ ለቀኑርባን ፡ ዕቃ ፥ ለጭልፋዎችም ፥ ለወርቅና ፡ ለብርም ፡ ዕቃ ፡ አደረጉት ። በዮዳዔም ፡ ዘመን ፡ ዥሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ዥልጊዜ ፡ ያቀርቡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 15 ፤ ዮዳዔም ፡ ሸመገለ ፥ ዕድሜም ፡ ጠግቦ ፡ ሞተ ፤ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዕድሜው ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 16 ፤ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፥ ከእግዚአብሔርና ፡ ከቤቱም ፡ ጋራ ፡ ቸርነትን ፡ ሠርቷልና ፥ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ ከነገሥታቱ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 17 ፤ ዮዳዔም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ገብተው ፡ ለንጉሡ ፡ እጅ ፡ ነሡ ፤ ንጉሡም ፡ ዕሺ ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 18 ፤ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንና ፡ ጣዖታትን ፡ አመለኩ ፤ በዚህ ፡ በደላቸውም ፡ ምክንያት ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ወረደ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመልሷቸው ፡ ዘንድ ፡ ነቢያትን ፡ ይሰድ፡ላቸው ፡ ነበር ፤ መሰከሩባቸውም ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላደመጡም ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በካህኑ ፡ በዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ በዘካርያስ ፡ ላይ ፡ መጣ ፤ ርሱም ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ ቆመና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለምን ፡ ትተላለፋላችኹ ፧ መልካምም ፡ አይኾንላችኹም ፤ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ተዋችኹ ፡ ርሱ ፡ ትቷችኋል ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 21 ፤ ተማማሉበትም ፡ በንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ በድንጋይ ፡ ወገሩት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 22 ፤ እንዲሁም ፡ ንጉሡ ፡ ኢዮአስ ፡ ዮዳዔ ፡ ያደረገለትን ፡ ቸርነት ፡ አላሰበም ፥ ልጁንም ፡ ዘካርያስን ፡ አስገደለው ፤ ርሱም ፡ ሲሞት ። እግዚአብሔር ፡ ይየው ፥ ይፈልገውም ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 23 ፤ ዓመቱም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ የሶርያውያን ፡ ሰራዊት ፡ መጡበት ፤ ወደ ፡ ይሁዳና ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጥተው ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፡ ዥሉ ፡ አጠፉ ፥ ምርኳቸውንም ፡ ዥሉ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ላኩ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 24 ፤ የሶርያውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅን ፡ ሰራዊት ፡ አሳልፎ ፡ በእጃቸው ፡ ሰጣቸው ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡

ነው ። እነርሱም ፡ በኢዮአስ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ ፈረዱበት ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 25 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ዐልፈው ፡ ከኼዱ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ ታሞ ፡ ነበር ፤ የገዛ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ስለ ፡ ካህኑ ፡ ስለዮዳዔ ፡ ልጅ ፡ ተበቅለው ፡ ተማማሉበት ፥ በዐልጋውም ፡ ላይ ፡ ገደሉት ፥ ሞተም ፤ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ እንጂ ፡ በነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አልቀበሩትም ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 26 ፤ የተማማሉበትም ፡ የአሞናዊቱ ፡ የሰምዓት ፡ ልጅ ፡ ዛባድ ፥ የሞዐባዊቱም ፡ የሰማሪት ፡ ልጅ ፡ ዮዛባት ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 24 ፡ 27 ፤ የልጆቹና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ነገር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ማደሱ ፥ እንሆ ፥ በነገሥታቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ። ልጁም ፡ አሜስያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 1 ፤ አሜስያስም ፡ መንገሥ ፡ በጐመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱ ፡ ዮዓዳን ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በፍጹም ፡ ልብ ፡ አይደለም ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 3 ፤ መንግሥትም ፡ በጸናለት ፡ ጊዜ ፡ አባቱን ፡ የገደሉትን ፡ ባሪያዎች ፡ ገደለ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 4 ፤ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ እግዚአብሔርም ፦ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በገዛ ፡ ኀጢአቱ ፡ ይሙት ፡ እንጂ ፡ አባቶች ፡ በልጆች ፡ ፋንታ ፡ አይሙቱ ፥ ልጆችም ፡ በአባቶች ፡ ፋንታ ፡ አይሙቱ ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዘ ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮችን ፡ ልጆች ፡ አልገደለም ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 5 ፤ አሜስያስም ፡ ይሁዳን ፡ ሰበሰበ ፥ በያባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ ከሺሕ ፡ አለቃዎችና ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ እጅ ፡ በታች ፡ አቆማቸው ፤ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ጠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ያሉትን ፡ ይሁዳንና ፡ ብንያምን ፡ ኹሉ ፡ ቈጠረ ፥ ለሰልፍም ፡ የሚወጡ ፥ ጋሻና ፡ ጦርም ፡ የሚይዙ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ የተመረጡ ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 6 ፤ ደግሞም ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፡ በመቶ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ ቀጠረ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 7 ፤ አንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤልና ፡ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አይደለምና ፡ የእስራኤል ፡ ጭፍራ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አይውጣ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 8 ፤ ብትኼድ ፡ ግን ፥ በእነርሱም ፡ ማሸነፍን ፡ ብታስብ ፥ የመርዳትና ፡ የመጣል ፡ ኀይል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔር ፡ በጠላቶችኽ ፡ ፊት ፡ ይጥልኻል ፡ አለው ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 9 ፤ አሜስያስም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፦ ለእስራኤል ፡ ጭፍራ ፡ የሰጠኹት ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ምን ፡ ይኹን ፧ አለው ። የእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፦ ከዚህ ፡ አብልጦ ፡ ይሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይችላል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 10 ፤ አሜስያስም ፡ ከኤፍሬም ፡ የመጡት ፡ ጭፍራዎች ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለይቶ ፡ አሰናበታቸው ፤ ስለዚህም ፡ ቍጣቸው ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ጸና ፥ ወደ ፡ አገራቸውም ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 11 ፤ አሜስያስም ፡ በረታ ፥ ሕዝቡንም ፡ አውጥቶ ፡ ወደጨው ፡ ሸለቆ ፡ ኼደ ፥ ከሴይርም ፡ ልጆች ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 12 ፤ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ሰዎችን ፡ በሕይወታቸው ፡ ማረኩ ፥ ወደአለቱም ፡

ራስ ፡ ላይ ፡ አመጧቸው ፤ ከአለቱም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጣሏቸው ፥ ሹሉም ፡ ተፈጠፈጡ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 13 ፤ አሜስያስ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ እንዳይኼዱ ፡ ያሰናበታቸው ፡ ጭፍራዎች ፡ ከሰማርያ ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ቤትሖሮን ፡ ድረስ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ከነርሱም ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ገደሉ ፥ ብዙ ፡ ምርኮም ፡ ማረኩ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 14 ፤ አሜስያስም ፡ የኤዶምያስን ፡ ሰዎች ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ የሴይርን ፡ ልጆች ፡ አማልክት ፡ አመጣ ፥ የርሱም ፡ አማልክት ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አቆማቸው ፥ ይሰግድላቸውም ፡ ያጥንላቸውም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 15 ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በአሜስያስ ፡ ላይ ፡ ነደደና ፦ ሕዝባቸውን ፡ ከአንተ ፡ እጅ ፡ ያላዳኑትን ፡ የአሕዛብን ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ፈለግኻቸው ፧ የሚል ፡ ነቢይ ፡ ሰደደበት ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 16 ፤ ርሱም ፡ ሲናገር ፡ ንጉሡ ፦ በእውኑ ፡ አንተ ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪ ፡ ልትኾን ፡ ሾመንኻልን ፧ ተው ፤ ቅጣትን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትሻለኽ ፧ አለው ። ነቢዩም ፦ ይህን ፡ አድርገኻልና ፥ ምክሬንም ፡ አልሰማኽምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያጠፋኽ ፡ እንዳሰበ ፡ ዐወቅኹ ፡ ብሎ ፡ ተወ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 17 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስ ፡ ምክር ፡ አደረገና ፦ ና ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እንተያይ ፡ ብሎ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደኢዩ ፡ ልጅ ፡ ወደኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮአስ ፡ ላከ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 18 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮስያስ ፦ የሊባኖስ ፡ ኵርንችት ፦ ልጅኽን ፡ ለልጄ ፡ ሚስት ፡ አድርገኽ ፡ ስጠው ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ላከ ፤ የሊባኖስም ፡ አውሬ ፡ ዐልፎ ፡ ኵርንችቱን ፡ ረገጠ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 19 ፤ አንተም ፦ እንሆ ፥ ኤዶምያስን ፡ መትቻለኹ ፡ ብለኽ ፡ ኰርተኻል ፤ በቤትኽ ፡ ተቀመጥ ፤ አንተ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡ ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መከራን ፡ ትሻለኽ ፧ ብሎ ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ አሜስያስ ፡ ላከ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 20 ፤ የኤዶምያስንም ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ፈለጉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነበረና ፡ አሜስያስ ፡ አልሰማም ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 21 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ ወጣ ፤ ርሱና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ አሜስያስም ፡ በይሁዳ ፡ ባለች ፡ በቤትሳሚስ ፡ ላይ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 22 ፤ ይሁዳም ፡ በእስራኤል ፡ ፊት ፡ ተመታ ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ድንኳኑ ፡ ሸሸ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 23 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአስ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የአካዝያስን ፡ ልጅ ፡ የኢዮአስን ፡ ልጅ ፡ አሜስያስን ፡ በቤትሳሚስ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አመጣው ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ ከኤፍሬም ፡ በር ፡ ዠምሮ ፡ እስከማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አፈረሰ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 24 ፤ ወርቁንና ፡ ብሩን ፡ ሹሉ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ከያቤድኤዶም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ሹሉ ፥ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ መዛግብት ፥ በመያዣ ፡ የተያዙትንም ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ተመለሰ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 25 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአስ ፡ ልጅ ፡ አሜስያስ ፡ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮአስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ኖረ ።

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 26 ፤ የቀረውም ፡ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፡ የአሜስያስ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

መዋ.2 ፥ 25 ፥ 27 ፤ አሜስያስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ ከራቀ ፡ በኋላ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የዐመፅ ፡ መሐላ ፡ አደረጉበት ፥ ወደ ፡ ለኪሶም ፡ ኰበለለ ፤ በስተኋላውም ፡ ወደ ፡ ለኪሶ ፡ ላኩ ፥ በዚያም ፡ ገደሉት ።

መዋ.2 ፡ 25 ፡ 28 ፤ በፈረስም ፡ ጭነው ፡ አመጡት ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ቀበሩት ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 1 ፤ የይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ የነበረውን ፡ ያዝያንን ፡ ወስደው ፡ በአባቱ ፡ በአሜስያስ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡት ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ ካንቀላፋ ፡ በኋላ ፡ ያዝያን ፡ ኤላትን ፡ ሠራ ፥ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ መለሳት ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 3 ፤ ያዝያንም ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ይኮልያ ፡ የተባለች ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 4 ፤ አባቱም ፡ አሜስያስ ፡ እንዳደረገው ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ መፍራት ፡ ባስተማረ ፡ በዘካርያስ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ልብ ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔርንም ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገሩን ፡ አከናወነለት ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 6 ፤ ወጥቶም ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፥ የጌትንና ፡ የየብናን ፡ የአዞጦንንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሰ ፤ በአዛጦንና ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፍልስጥኤማውያንና ፡ በጉርበዓል ፡ በሚኖሩ ፡ ዐረባውያን ፡ በምዑናውያንም ፡ ላይ ፡ ረዳው ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 8 ፤ አሞናውያንም ፡ ለያዝያን ፡ ገበሩ ፤ እጅግም ፡ በርትቶ ፡ ነበርና ፥ ዝናው ፡ እስከግብጽ ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 9 ፤ ያዝያንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በማእዘኑ ፡ በርና ፡ በሸለቆው ፡ በር ፡ ቅጥሩም ፡ በዞረበት ፡ ማእዘን ፡ አጠገብ ፡ ግንቦችን ፡ ሠርቶ ፡ መሸጋቸው ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 10 ፤ ብዙም ፡ እንስሳዎች ፡ ነበሩበትና ፡ በምድረ ፡ በዳና ፡ በቈላው ፡ በደጋውም ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፥ ብዙ ፡ ጕድጓድም ፡ ማሰ ፤ ደግሞም ፡ ዕርሻ ፡ ይወድ ፡ ነበርና ፥ በተራራማውና ፡ በፍሬያማው ፡ ስፍራ ፡ ዐራሾችና ፡ አትክልተኞች ፡ ነበሩት ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 11 ፤ ደግሞም ፡ ለያዝያን ፡ በሰራዊት ፡ ውስጥ ፡ ሰልፈኞች ፡ ነበሩት ፤ በንጉሡ ፡ አለቃ ፡ በሐናንያ ፡ ትእዛዝ ፡ በአለቃው ፡ በመዕሴያና ፡ በጸሓፊው ፡ በይዒኤል ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተቈጠሩ ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ በየቍጥራቸው ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 12 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ የጽኑዓን ፡ ኀያላኑ ፡ ቍጥር ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 13 ፤ ንጉሡንም ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡ ያግዝ ፡ ዘንድ ፥ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚወጣ ፥ ከእጃቸው ፡ በታች ፡ የነበረ ፡ ሰራዊት ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 14 ፤ ያዝያንም ፡ ለጭፍራው ፡ ኹሉ ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፥ ራስ ፡ ቍርና ፡ ጥሩር ፥ ቀስትና ፡ የሚወነጭፉትን ፡ ድንጋይ ፡ አዘጋጀላቸው ።

መዋ.2 ፡ 26 ፡ 15 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ በብልኀተኞች ፡ እጅ ፡ የተሠሩትን ፥ በግንብና ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ የሚኖሩትን ፥ ፍላጻና ፡ መርግ ፡ የሚወረወርባቸውን ፡ መሣሪያዎች ፡ አደረገ ፤ እስኪበረታም ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡

በድንቅ ፡ ረድቶታልና ፥ ዝናው ፡ እስከ ፡ ሩቅ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ ለጥፋት ፡ ልቡ ፡ ታበየ ፥ አምላኩንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በደለ ፤ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ በዕጣን ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ዐጠነ ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 17 ፤ ካህኑም ፡ ዐዛርያስ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ጽኑዓን ፡ የነበሩ ፡ ሰማንያ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ ተከትለው ፡ ገቡ ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 18 ፤ ንጉሡንም ፡ ዖዝያንን ፡ እየተቃወሙ ፦ ዖዝያን ፡ ሆይ ፥ ዕጣን ፡ ማጠን ፡ የተቀደሱት ፡ የአሮን ፡ ልጆች ፡ የካህናቱ ፡ ሹመት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታጥን ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ አይገባኽም ፤ በድለኻልና ፥ ከመቅደሱ ፡ ውጣ ፤ ከአምላክኽም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ አይኾንልኽም ፡ አሉት ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 19 ፤ ዖዝያንም ፡ ተቈጣ ፤ የሚያጥንበትም ፡ ጥና ፡ በእጁ ፡ ነበረ ፤ ካህናቱንም ፡ በተቈጣ ፡ ጊዜ ፡ በካህናቱ ፡ ፊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በዕጣኑ ፡ መሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ሳለ ፡ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ለምጽ ፡ ታየ ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 20 ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ዐዛርያስ ፡ ካህናቱም ፡ ኹሉ ፡ ተመለከቱት ፥ እንሆም ፥ በግንባሩ ፡ ላይ ፡ ለምጽ ፡ ነበረ ፤ ፈጥነውም ፡ አባረሩት ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀሥፎት ፡ ነበርና ፥ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ቸኰለ ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ዖዝያን ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ለምጻም ፡ ነበረ ፤ ለምጻምም ፡ ኾኖ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተቈርጧልና ፥ በተለየ ፡ ቤት ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ኾኖ ፡ በምድሩ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 22 ፤ የቀረውንም ፡ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ የዖዝያንን ፡ ነገር ፡ ነቢዩ ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ጽፎታል ።

መዋ.2 ፥ 26 ፥ 23 ፤ ዖዝያንም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ ለምጻም ፡ ነው ፡ ብለውም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ በነገሥታቱ ፡ መቃብር ፡ ዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ኢዮአታም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 1 ፤ ኢዮአታምም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ ኢየሩሳ ፡ ትባል ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 2 ፤ አባቱም ፡ ዖዝያን ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ አልገባም ፤ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ ይበድል ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 3 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የላይኛውን ፡ በር ፡ ሠራ ፥ በዖፌልም ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 4 ፤ በተራራማውም ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፥ በዱር ፡ ስፍራዎችም ፡ ዐምባዎችንና ፡ ግንቦችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 5 ፤ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፡ አሸነፋቸውም ። በዚያም ፡ ዓመት ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብር ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ የቈሬስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፥ ዐሥር ፡ ሺሕም ፡ የቈሬስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ ሰጡት ። እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ በኹለተኛውና ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ሰጡት ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 6 ፤ ኢዮአታምም ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መንገዱን ፡ አቅንቷልና ፥ በረታ ።

መዋ.2 ፥ 27 ፥ 7 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአታም ፡ ነገር ፥ ሰልፉም ፡ ኹሉ ፥ ሥራውም ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 27 ፡ 8 ፤ መንገሥ ፡ በዝ፮መረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 27 ፡ 9 ፤ ኢዮአታምም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ አካዝ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። _____

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 1 ፤ አካዝ ፡ መንገሥ ፡ በዝ፮መረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እንደ ፡ አባቱም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አላደረገም ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፥ ደግሞም ፡ ለበዓሊም ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 3 ፤ ደግሞም ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ዐጠነ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳሳደዳቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብም ፡ ክፉ ፡ ልማድ ፡ ልጆቹን ፡ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 4 ፤ በኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ በለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ሥሉ ፡ በታች ፡ ይሠዋና ፡ ያጥን ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ ሶርያውያንም ፡ መቱት ፥ ከርሱም ፡ ብዙ ፡ ምርኮኞች ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አመጡ ። ደግሞም ፡ በእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ ርሱም ፡ በታላቅ ፡ አመታት ፡ መታው ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 6 ፤ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተው ፡ ነበርና ፥ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከይሁዳ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፤ ኹሉም ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 7 ፤ ከኤፍሬምም ፡ ወገን ፡ የነበረው ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ዝክሪ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ መዕሴያንና ፡ የቤቱን ፡ አዛዥ ፡ ዐዝሪቃምን ፥ ለንጉሡም ፡ በማዕርግ ፡ ኹለተኛ ፡ የኾነውን ፡ ሕልቃናን ፡ ገደለ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 8 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሺሕ ፡ ሴቶችን ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ማረኩ ፥ እጅግም ፡ ምርኮ ፡ ከነርሱ ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ አገቡ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ዖዴድ ፡ የተባለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ የሚመጣውን ፡ ጭፍራ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ የአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሁዳን ፡ ስለ ፡ ተቈጣ ፡ በእጃችኹ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ እናንተም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በሚደርስ ፡ ቍጣ ፡ ገደላችኋቸው ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጆች ፡ ባሪያዎች ፡ ኾነው ፡ ይገዙላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የበደላችኹት ፡ በደል ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የለምን ፧

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ ስሙኝ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በላያችኹ ፡ ነዷልና ፥ ከወንድሞቻችኹ ፡ የወሰዳችኋቸውን ፡ ምርኮኞች ፡ መልሱ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 12 ፤ ደግሞም ፡ ከኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ አለቃዎች ፡ የዮሐናን ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፥ የምሺሌሞትም ፡ ልጅ ፡ በራክያ ፥ የሰሎምም ፡ ልጅ ፡ ይሒዝቅያ ፥ የሐድላይም ፡ ልጅ ፡ ዓሜሳይ ፡ ከሰልፍ ፡ በተመለሱት ፡ ላይ ፡ ተቃወሟቸው ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በደል ፡ ታመጡብናላችኹና ፥ ኀጢአታችንንና ፡ በደላችንን ፡ ታበዙብናላችኹና ፡ የተማረኩትን ፡ ወደዚህ ፡ አታግቡ ፤ በደላችን ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ የመቅሠፍቱም ፡ ቍጣ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ አሏቸው ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 14 ፤ ሰልፈኞቹም ፡ ምርኮኞቹንና ፡ ምርኮውን ፡ በአለቃዎችና ፡ በጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ተዉ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 15 ፤ በስማቸውም ፡ የተጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ምርኮኞቹን ፡ ወሰዱ ፥ በመካከላቸውም ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ለነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ከምርኮው ፡ አለበሷቸው ፥ አጐናጸፏቸውም ፥ ጫማም ፡ በእግራቸው ፡ አደረጉላቸው ፥ መገቧቸውም ፥ አጠጧቸውም ፥ ቀቧቸውም ፤ ደካማዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ በአህያዎች ፡ ላይ ፡ አስቀመጧቸው ፥ ዘንባባም ፡ ወዳለበት ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ አመጧቸው ፤ ወደ ፡ ሰማርያም ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ ርዳታ ፡ ፈልጎ ፡ ወደአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ላከ ፤

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 17 ፤ የኤዶምያስ ፡ ሰዎች ፡ ዳግመኛ ፡ መጥተው ፥ ይሁዳንም ፡ መትተው ፡ ብዙ ፡ ምርኮኛ ፡ ወስደው ፡ ነበርና ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 18 ፤ ደግሞም ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ በቈላውና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ አደጋ ፡ ጥለው ፡ ነበር ፤ ቤትሳሚስንና ፡ ኤሎንን ፥ ግዴሮትንም ፥ ሦኮንና ፡ መንደሮቿን ፥ ተምናንና ፡ መንደሮቿን ፥ ጊምዞንና ፡ መንደሮቿን ፡ ወስደው ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 19 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክዷልና ፥ ከርሱም ፡ እጅግ ፡ ርቋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይሁዳን ፡ አዋረደው ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 20 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ቴልጌልቴልፌልሶር ፡ መጥቶ ፡ አስጨነቀው ፡ እንጂ ፡ አልረዳውም ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 21 ፤ አካዝም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከንጉሡና ፡ ከአለቃዎቹም ፡ ቤት ፡ እኩሌታውን ፡ ገፈፈ ፥ ለአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰጠ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንዳች ፡ አልተጠቀመበትም ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 22 ፤ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ አካዝ ፡ በተጨነቀ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መበደል ፡ አበዛ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 23 ፤ ለመቱትም ፡ ለደማስቆ ፡ አማልክት ፦ የሶርያን ፡ ነገሥታት ፡ አማልክት ፡ ረድተዋቸዋልና ፥ እኔን ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ እሠዋላቸዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ሠዋላቸው ። ነገር ፡ ግን ፥ ለርሱና ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እንቅፋት ፡ ኾኑ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 24 ፤ አካዝም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ ሰባበራቸው ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ ቈለፈ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ማእዘን ፡ ኹሉ ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 25 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ያጥን ፡ ዘንድ ፡ የከሠረብታ ፡ መስገጃዎች ፡ አሠራ ፤ የአባቶቹንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣ ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 26 ፤ የቀረውም ፡ ነገርና ፡ ሥራው ፡ ኹሉ ፥ የፊተኛውና ፡ የኋለኛው ፥ እንሆ ፥ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 28 ፡ 27 ፤ አካዝም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በከተማዉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቀበሩት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መቃብር ፡ አላገቡትም ፤ ልጁም ፡ ሕዝቅያስ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

መዋ.2 ፡ 29 ፡ 1 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ መንገሥ ፡ ገመረ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ኻያ ፡ ዘጠኝ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ አቡ ፡ ትባል ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 29 ፡ 2 ፤ አባቱም ፡ ዳዊት ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 29 ፡ 3 ፤ በነገሠም ፡ በመገመሪያው ፡ ዓመት ፡ በመገመሪያው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ደጆች ፡

ከፈተ ፥ ዐደሳቸውም ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 4 ፤ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑንም ፡ አስመጣ ፥ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ አደባባይም ፡ ሰበሰባቸው ፥

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 5 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ሌዋውያን ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ ተቀደሱ ፥ የአባቶቻችኹንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቀድሱ ፤ ርኩሰን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከመቅደሱ ፡ አስወግዱ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 6 ፤ አባቶቻችን ፡ ተላልፈዋል ፥ በአምላካችንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አድርገዋል ፤ ርሱንም ፡ ትተዋል ፥ ፊታቸውንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መኖሪያ ፡ መልሰዋል ፥

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 7 ፤ ወደ ፡ ርሷም ፡ ዝርግባቸውን ፡ አዙረዋል ፤ ደግሞም ፡ የወለሉን ፡ ደጆች ፡ ቈልፈዋል ፥ መብራቶቹንም ፡ አጥፍተዋል ፥ በመቅደሱም ፡ ውስጥ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ አላጠኑም ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አላቀረቡም ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 8 ፤ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ኾነ ፥ በዐይናችኹም ፡ እንደምታዩ ፡ ለድንጋጤና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመዘበቻም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 9 ፤ እንሆም ፥ ስለዚህ ፡ አባቶቻችን ፡ በሰይፍ ፡ ወደቁ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ ሚስቶቻችንም ፡ ተማረኩ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 10 ፤ አኹንም ፡ የቍጣው ፡ ጽናት ፡ ከእኛ ፡ እንዲመለስ ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ ዐስቤያለኹ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 11 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ በፊቱ ፡ ትቆሙና ፡ ታገለግሉት ፡ ዘንድ ፥ አገልጋዮቹም ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፥ ታጥኑለትም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጧችኋልና ፥ ቸል ፡ አትበሉ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 12 ፤ ሌዋውያኑም ፥ ከቀአት ፡ ልጆች ፡ የዐማሲ ፡ ልጅ ፡ መሐትና ፡ የዐዛርያስ ፡ ልጅ ፡ ኢዮኤል ፥ ከሜራሪም ፡ ልጆች ፡ የዐብዲ ፡ ልጅ ፡ ቂስና ፡ የይሃሌልኤል ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፥ ከጌድሶንም ፡ ልጆች ፡ የዛማት ፡ ልጅ ፡ ዩአክና ፡ የዩአክ ፡ ልጅ ፡ ዔዴን ፥

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 13 ፤ 14 ፤ ከኤሊጸፋንም ፡ ልጆች ፡ ሺምሪና ፡ ይዒኤል ፥ ከአሣፍም ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስና ፡ መታንያ ፥ ከኤማንም ፡ ልጆች ፡ ይሒኤልና ፡ ሰሜኢ ፥ ከኤዶታምም ፡ ልጆች ፡ ሸማያና ፡ ዑዝኤል ፡ ተነሡ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 15 ፤ ወንድሞቻቸውንም ፡ ሰብስበው ፡ ተቀደሱ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደመጣው ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ያነጹ ፡ ዘንድ ፡ ገቡ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 16 ፤ ካህናቱም ፡ ያነጹት ፡ ዘንድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ውስጡ ፡ ገቡ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ መቅደስ ፡ ያገኙትን ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አወጡት ። ሌዋውያንም ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወደ ፡ ቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 17 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ይቀደሱ ፡ ዠመር ፥ በዚያውም ፡ ወር ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወለል ፡ ደረሱ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ቀደሱ ፥ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ፈጸሙ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 18 ፤ ወደ ፡ ውስጡም ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ገብተው ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፥ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ መሠዊያና ፡ ዕቃውንም ፡ ኹሉ ፥ የገጹንም ፡ ኅብስት ፡ ገበታና ፡ ዕቃውን ፡ ኹሉ ፡ አንጽተናል ፤

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 19 ፤ ንጉሡም ፡ አካዝ ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ፡ በመተላለፍ ፡ ያረከሰውን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ አዘጋጅተናል ፡

ቀድሰናልም ፤ እንሆም ፥ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ኾነዋል ፡ አሉት ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 20 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፡ የከተማዪቱንም ፡ አለቃዎች ፡ ሰበሰበ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ወጣ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 21 ፤ ስለ ፡ መንግሥቱና ፡ ስለ ፡ መቅደሱም ፡ ስለ ፡ ይሁዳም ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖች ፥ ሰባትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ሰባትም ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፥ ሰባትም ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ። የአሮንንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱን ፦ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አሳርጓቸው ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 22 ፤ ወይፈኖቹንም ፡ ዐረዱ ፥ ካህናቱም ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጨት ፤ አውራ ፡ በጎቹንም ፡ ዐረዱ ፥ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጨት ፤ ጠቦቶቹንም ፡ ዐረዱ ፡ ደሙንም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ረጨት ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 23 ፤ የኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾኑትን ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ በንጉሡና ፡ በጉባኤው ፡ ፊት ፡ አቀረቡ ፥ እጃቸውንም ፡ ጫኑባቸው ፥ ካህናቱም ፡ ዐረዷቸው ፤

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 24 ፤ ንጉሡም ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ እንዲደረግ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፥ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ማስተስረያ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ አቀረቡ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 25 ፤ ይሁንም ፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያቱ ፡ እጅ ፡ አዟልና ፥ እንደዳዊትና ፡ እንደንጉሡ ፡ ባለራእይ ፡ እንደጋድ ፥ እንደነቢዩም ፡ እንደናታን ፡ ትእዛዝ ፥ ጸናጽልና ፡ በገና ፡ መሰንቆም ፡ አስይዞ ፡ ሌዋውያንን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አቆመ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 26 ፤ ሌዋውያንም ፡ የዳዊትን ፡ የዜማ ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፥ ካህናቱም ፡ መለከቱን ፡ ይዘው ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 27 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያሳርጉ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ የሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ማረግ ፡ በተዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡ ተዠመረ ፥ መለከቱም ፡ ተነፋ ፥ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የዳዊት ፡ ዜማ ፡ ዕቃ ፡ ተመታ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 28 ፤ ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ ሰገዱ ፥ መዘምራኑም ፡ ዘመሩ ፥ መለከተኞችም ፡ ነፉ ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 29 ፤ ማቅረቡንም ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡ አጐነበሱ ፡ ሰገዱም ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 30 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስና ፡ አለቃዎቹ ፡ ሌዋውያንን ፡ በዳዊትና ፡ በባለራእዩ ፡ በአሣፍ ፡ ቃል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ አዘዙ ። በደስታም ፡ አመሰገኑ ፥ አጐነበሱም ፡ ሰገዱም ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 31 ፤ ሕዝቅያስም ፦ አኹን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀድሳችኋል ፤ ቅረቡ ፥ መሥዋዕቱንና ፡ የምስጋናውን ፡ መሥዋዕት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ። ጉባኤውም ፡ መሥዋዕቱንና ፡ የምስጋናውን ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ፤ ልባቸውም ፡ የፈቀደ ፡ ኹሉ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 32 ፤ ጉባኤውም ፡ ያመጡት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ቍጥር ፡ ሰባ ፡ ወይፈን ፥ መቶም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ኹለት ፡ መቶም ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነበረ ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 33 ፤ የተቀደሱትም ፡ ቍጥር ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ በሬዎች ፡ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ በጎች ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ካህናቱ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለመግፈፍ ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህም ፡

ሌዋውያን ፡ በቅን ፡ ልብ ፡ ከካህናት ፡ ይልቅ ፡ ይቀደሱ ፡ ነበርና ፥ ሥራው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ካህናቱም ፡ እስኪቀደሱ ፡ ድረስ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ሌዋውያን ፡ ያግዟቸው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 35 ፤ የሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ የደኅንነቱም ፡ መሥዋዕት ፡ ስብ ፥ ከሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የሚቀርበው ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፥ ብዙ ፡ ነበረ ። እንዲሁም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ተዘጋጀ ።

መዋ.2 ፥ 29 ፥ 36 ፤ ሕዝቅያስና ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ስላዘጋጀው ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ አላቸው ። ይህም ፡ ነገር ፡ በድንገት ፡ ተደረገ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 1 ፤ ለእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፋሲካ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲመጡ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ እስራኤልና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ላከ ፥ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ኤፍሬምና ፡ ወደ ፡ ምናሴ ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 2-3 ፤ ካህናቱም ፡ በሚበቃ ፡ ቍጥር ፡ ስላልተቀደሱ ፥ ሕዝቡም ፡ ገና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስላልተሰበሰቡ ፡ በጊዜው ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉምና ፡ ንጉሡና ፡ አለቃዎቹ ፡ የኢየሩሳሌምም ፡ ጉባኤ ፡ ኹሉ ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ ፋሲካውን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ተመካከረው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 4 ፤ ነገሩም ፡ ለንጉሡና ፡ ለጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ መልካም ፡ ነበረ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 5 ፤ እንደ ፡ ተጻፈም ፡ በብዙ ፡ ቍጥር ፡ አላደረጉም ፡ ነበርና ፥ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፋሲካ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲመጡ ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዳን ፡ ድረስ ፡ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ ወሰኑ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 6 ፤ እንደ ፡ ንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ መልክተኞቹ ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ የንጉሡንና ፡ የአለቃዎቹን ፡ ደብዳቤ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ እስራኤልና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ኼዱ ። የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአሶር ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ ወዳመለጠ ፡ ቅሬታችኹ ፡ እንዲመለስ ፡ ወደአብርሃምና ፡ ወደይሥሐቅ ፡ ወደእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 7 ፤ እናንተም ፡ እንደምታዩ ፡ የተፈቱ ፡ እስኪያደርጋቸው ፡ ድረስ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ እንደ ፡ አባቶቻችኹና ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ አትኹኑ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 8 ፤ አባቶቻችኹም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳና ፡ አትኹኑ ፤ እጃችኹንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስጡ ፥ ለዘለዓለም ፡ ወደተቀደሰው ፡ ወደ ፡ መቅደሱም ፡ ግቡ ፥ ጽኑ ፡ ቍጣውም ፡ ከእናንተ ፡ እንዲመለስ ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምልኩ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 9 ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸርና ፡ መሓሪ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ብትመለሱ ፡ ፊቱን ፡ ከእናንተ ፡ አያዞርምና ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትመለሱ ፡ ወንድሞቻችኹና ፡ ልጆቻችኹ ፡ በማረኳቸው ፡ ፊት ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛሉ ፥ ደግሞም ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 10 ፤ መልእክተኞቹም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ አገር ፡ እስከ ፡ ዛብሎን ፡ ኼዱ ፤ እነዚያ ፡ ግን ፡ በንቀት ፡ ሣቁባቸው ፥ አፌዙባቸውም ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአሴርና ፡ ከምናሴ ፡ ከዛብሎንም ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውን ፡ አዋረዱ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጡ ።

መዋ.2 ፥ 30 ፥ 12 ፤ ደግሞም ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የኾነውን ፡ የንጉሡንና ፡

የአለቃዎቹን ፡ ትእዛዝ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የኾነ ፡ ሕዝብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተከማቸ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 14 ፤ ተነሥተውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩትን ፡ መሠዊያዎችና ፡ ለጣዖታት ፡ የሚያጥኑበትን ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፡ አስወገዱ ፥ በቄድሮንም ፡ ወንዝ ፡ ጣሉት ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 15 ፤ በኹለተኛውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፡ ዐረዱ ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ዐፈሩ ፥ ተቀደሱም ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አመጡ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 16 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሕግ ፡ በሥርዐታቸው ፡ ቆሙ ፤ ካህናቱም ፡ ከሌዋውያን ፡ እጅ ፡ የተቀበሉትን ፡ ደም ፡ ይረጩ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 17 ፤ በጉባኤውም ፡ ያልተቀደሱ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ስለዚህም ፡ ሌዋውያን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቀድሷቸው ፡ ዘንድ ፡ ንጹሓን ፡ ላልኾኑት ፡ ሹሉ ፡ ፋሲካውን ፡ ያርዱላቸው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 18 ፤ እንደ ፡ ትእዛዙም ፡ ሳይኾን ፡ ከኤፍሬምና ፡ ከምናሴ ፡ ከይሳኮርና ፡ ከዛብሎንም ፡ ወገን ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ሳይነጹ ፡ ፋሲካውን ፡ በሉ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 19 ፤ ሕዝቅያስም ፦ ምንም ፡ እንደ ፡ መቅደሱ ፡ ማንጻት ፡ ባይነጻ ፡ የአባቶቹን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመፈለግ ፡ ልቡን ፡ የሚያቀናውን ፡ ሹሉ ፡ ቸሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ይበለው ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ጸለየ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሕዝቅያስን ፡ ሰማው ፥ ሕዝቡንም ፡ ፈወሰ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 21 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ተገኝተው ፡ የነበሩ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ አደረጉ ፤ ሌዋውያኑና ፡ ካህናቱም ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እየዘመሩ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 22 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ አስተዋዮች ፡ የነበሩትን ፡ ሌዋውያንን ፡ ሹሉ ፡ ያጽናና ፡ ነበር ። የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕት ፡ እያቀረቡ ፥ የአባቶቻቸውንም ፡ አምላክ ፡ እያመሰገኑ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 23 ፤ 24 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ሺሕ ፡ ወይፈኖችና ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለጉባኤው ፡ ሰጥቶ ፡ ነበርና ፥ አለቃዎቹም ፡ ሺሕ ፡ ወይፈኖችና ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፡ ለጉባኤው ፡ ሰጥተው ፡ ነበርና ፥ ከካህናቱም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ተቀድሰው ፡ ነበርና ፥ ጉባኤው ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ፤ በደስታም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 25 ፤ የይሁዳም ፡ ጉባኤ ፡ ሹሉ ፥ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፥ ከእስራኤልም ፡ የመጡ ፡ ጉባኤ ፡ ሹሉ ፥ ከእስራኤልም ፡ አገር ፡ የመጡትና ፡ በይሁዳ ፡ የኖሩት ፡ እንግዳዎች ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 26 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ኾነ ፤ ከእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከዳዊት ፡ ልጅ ፡ ከሰሎሞን ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ በዓል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አልተደረገም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 30 ፡ 27 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ተነሥተው ፡ ሕዝቡን ፡ ባረኩ ፤ ድምፃቸውም ፡ ተሰማ ፥ ጸሎታቸውም ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መኖሪያው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 1 ፤ ይህም ፡ ኹሉ ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የተገኙ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ወደይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ወጥተው ፡ ኹሉን ፡ ፈጽመው ፡ እስካጠፏቸው ፡ ድረስ ፡ ሐውልቶቹን ፡ ሰባበሩ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጡ ፥ በይሁዳና ፡ በብንያምም ፡ ኹሉ ፡ ደግሞም ፡ በኤፍሬምና ፡ በምናሴ ፡ የነበሩትን ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ መሠዊያዎች ፡ አፈረሱ ። የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርስታቸውና ፡ ወደ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ ተመለሱ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ የካህናትንና ፡ የሌዋውያንን ፡ ሰሞን ፡ በየክፍላቸውና ፡ በያገልግሎታቸው ፡ አቆመ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ በሮች ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፥ ያገለግሉም ፡ ዘንድ ፥ ያመሰግኑም ፡ ያከብሩም ፡ ዘንድ ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ አቆመ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 3 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በጧትና ፡ በማታ ፥ በሰንበታቱም ፥ በመባቻዎቹም ፥ በበዓላትም ፡ ለሚቀርበው ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ንጉሡ ፡ ከገንዘቡ ፡ የሚከፍለውን ፡ ወሰነ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 4 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለአገልግሎት ፡ እንዲጸኑ ፡ ለካህናቱና ፡ ለሌዋውያን ፡ ክፍላቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ሕዝብ ፡ አዘዘ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 5 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ እንዳዘዘ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ የዘይቱንና ፡ የማሩንም ፥ የዕርሻውንም ፡ ፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በኩራት ፡ ሰጡ ፤ የኹሉንም ፡ ዓሥራት ፡ አብዝተው ፡ አቀረቡ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 6 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ የሚኖሩ ፡ የእስራኤልና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ የበሬውንና ፡ የበጉን ፡ ዓሥራት ፥ ለአምላካቸውም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ዓሥራት ፡ አመጡ ፥ ከምረውም ፡ አኖሩት ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 7 ፤ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ መከመር ፡ ዠመሩ ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ጨረሱ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 8 ፤ ሕዝቅያስና ፡ አለቃዎቹም ፡ መጥተው ፡ ክምሩን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ሕዝቡን ፡ እስራኤልን ፡ ባረኩ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 9 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ካህናቱንና ፡ ሌዋውያኑን ፡ ስለ ፡ ክምሩ ፡ ጠየቀ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 10 ፤ ከሳዶቅም ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ ዋነኛው ፡ ካህን ፡ ዓዛሪያስ ፦ ሕዝቡ ፡ ቍርባኑን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ማቅረብ ፡ ከዠመረ ፡ ወዲህ ፡ በልተናል ፥ ጠግበናልም ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ባርኳልና ፥ ብዙ ፡ ተርፏል ፤ የተረፈውም ፡ ይህ ፡ ክምር ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 11 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ጕተራ ፡ ያዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ እነርሱም ፡ አዘጋጁ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 12 ፤ ቍርባኑና ፡ ዓሥራቱን ፡ የተቀደሱትንም ፡ በእምነት ፡ ወደዚያ ፡ አገቡት ። ሌዋዊውም ፡ ኮናንያ ፡ ተሾመባቸው ፥ ወንድሙም ፡ ሰሜኢ ፡ በማዕርግ ፡ ኹለተኛ ፡ ነበረ ፤

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 13 ፤ በንጉሡም ፡ በሕዝቅያስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ በዐዛርያስ ፡ ትእዛዝ ፡ ይሒዒል ፥ ዓዛዝያ ፥ ናሖት ፥ ዐሳሄል ፥ ይሬሞት ፥ ዮዛባት ፥ ኤሊኤል ፥ ሰማክያ ፥ መሐት ፥ በናያስ ፥ ከኮናንያና ፡ ከወንድሙ ፡ ከሰሜኢ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ተቈጣጣሪዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 14 ፤ የሌዋዊውም ፡ የይምና ፡ ልጅ ፡ የምሥራቁ ፡ ደጅ ፡ በረኛ ፡ ቆሬ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መባና ፡ የተቀደሱትን ፡ ነገሮች ፡ እንዲያካፍል ፡ ሕዝቡ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃድ ፡ ባቀረቡት ፡ ላይ ፡ ተሾመ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 15 ፤ በካህናቱም ፡ ከተማዎች ፡ ለታላላቆችና ፡ ለታናናሾች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ በየሰሞናቸው ፡ ክፍላቸውን ፡ በእምነት ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ዔዴን ፥ ሚንያሚን ፥ ኢያሱ ፥ ሸማያ ፥ አማርያ ፥ ሴኬንያ ፡ ከእጁ ፡ በታች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 16 ፤ ከሦስትም ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ በየሰሞናቸው ፡ ለሥራቸውና ፡ ለአገልግሎታቸው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ለሚገቡ ፡ ወንዶች ፡ ኹሉ ፤

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 17 ፤ በያባቶቻቸውም ፡ ቤት ፡ ለተቈጠሩ ፡ ካህናት ፥ ከኻያ ፡ ዓመትም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ በየሥርዐታቸውና ፡ በየሰሞናቸው ፡ ለተቈጠሩ ፡ ሌዋውያን ፥

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 18 ፤ በማኅበሩም ፡ ኹሉ ፡ በየትውልዳቸው ፡ ለተቈጠሩ ፡ ለሕፃናታቸውና ፡ ለሚስቶቻቸው ፡ ለወንዶችና ፡ ለሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፤ በእምነት ፡ ተቀድሰዋልና ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 19 ፤ በየከተማዉቱም ፡ ኹሉ ፡ በከተማቸው ፡ መሰምሪያዎቹ ፡ ላሉ ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ለካህናቱ ፥ ከካህናቱም ፡ ወገን ፡ ላሉ ፡ ወንዶች ፡ ኹሉ ፥ በትውልዳቸውም ፡ ለተቈጠሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ኹሉ ፡ ክፍላቸውን ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ በስማቸው ፡ የተጻፉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 20 ፤ ሕዝቅያስም ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምንና ፡ ቅንን ፡ ነገር ፡ እውነትንም ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 31 ፡ 21 ፤ ስለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ በገዖመረው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ በሕጉና ፡ በትእዛዙም ፥ አምላኩን ፡ ለመፈለግ ፡ በፍጹም ፡ ልቡ ፡ አደረገው ፥ ተከናወነለትም ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ ነገርና ፡ ከዚህ ፡ እምነት ፡ በኋላ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ገባ ፥ በተመሸጉትም ፡ ከተማዎች ፡ ፊት ፡ ሰፈረ ፥ ሊወስዳቸውም ፡ ዐሰበ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ሰናክሬም ፡ እንደ ፡ መጣ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ሊወጋ ፡ ፊቱን ፡ እንዳቀና ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 3 ፤ ከከተማዉቱ ፡ በስተውጭ ፡ ያለውን ፡ የውሃውን ፡ ምንጭ ፡ ይደፍኑ ፡ ዘንድ ፡ ከአለቃዎቹና ፡ ከጎያላኑ ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ፤ እነርሱም ፡ ረዱት ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 4 ፤ እጅግም ፡ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ። የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ መጥተው ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያገኛሉ ፧ ብለው ፡ ምንጩን ፡ ኹሉ ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ ይንዶለዶል ፡ የነበረውን ፡ ወንዝ ፡ ደፈኑ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 5 ፤ ሰውነቱንም ፡ አጸናና ፥ የፈረሰውንም ፡ ቅጥር ፡ ኹሉ ፡ ጠገነ ፥ በላዩም ፡ ግንብ ፡ ሠራበት ፥ ከርሱም ፡ በስተውጭ ፡ ሌላ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ያለችውን ፡ ሚሎን ፡ አጠነከረ ፤ ብዙም ፡ መሣሪያና ፡ ጋሻ ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 6 ፤ የጦር ፡ አለቃዎቹንም ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ሾመ ፥ ኹሉንም ፡ በከተማዉቱ ፡ በር ፡ ወዳለው ፡ አደባባይ ፡ ሰብስቦ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 7 ፤ ጽኑ ፥ አይዟችኹ ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካለው ፡ ይበልጣልና ፥ ከአሶር ፡ ንጉሥና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካለው ፡ ሞፍራ ፡ ኹሉ ፡ አትፍሩ ፥ አትደንግጡም ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 8 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሥጋ ፡ ክንድ ፡ ነው ፤ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ግን ፡ የሚረዳንና ፡ የሚዋጋልን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አጸናናቸው ። ሕዝቡም ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ቃል ፡ ተጽናና ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 9 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ከሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በለኪሶ ፡ ፊት ፡ ሳለ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ወደነበሩ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ላከ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 10 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ በማን ፡ ተማምናችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ምሽግ ፡ ትቀመጣላችኹ ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 11 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ያድነናል ፡ እያለ ፡ በራብና ፡ በጥም ፡ እንድትሞቱ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ የሚያባብላችኹ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አይደለምን ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 12 ፤ ባንድ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ስገዱ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ዕጠኑ ፡ እያለ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አዞ ፥ የኰረብታው ፡ መስገጃዎቹና ፡ መሠዊያዎቹን ፡ ያፈረሰ ፡ ይህ ፡ ሕዝቅያስ ፡ አይደለምን ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 13 ፤ እኔና ፡ አባቶቼ ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ያደረግነውን ፡ አላወቃችኹምን ፧ የምድርስ ፡ ኹሉ ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አገራቸውን ፡ ከእጄ ፡ ያድኑ ፡ ዘንድ ፡ በእውኑ ፡ ተቻላቸውን ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 14 ፤ አምላካችኹስ ፡ ከእጄ ፡ እናንተን ፡ ለማዳን ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ አባቶቼ ፡ ካጠፏቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ የቻለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ሕዝቅያስ ፡ አያስታችኹ ፥ እንዲህም ፡ አያባብላችኹ ፥ አትመኑትም ፤ ከአሕዛብና ፡ ከመንግሥታት ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡን ፡ ከእጄና ፡ ከአባቶቼ ፡ እጅ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ አልቻለም ፤ ይልቁንስ ፡ አምላካችኹ ፡ ከእጄ ፡ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 16 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ደግሞ ፡ በአምላክ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በባሪያው ፡ በሕዝቅያስ ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ተናገሩ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 17 ፤ ደግሞም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመስደብ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ለመናገር ። የምድር ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ሕዝባቸውን ፡ ከእጄ ፡ ያድኑ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልቻሉ ፥ እንዲሁ ፡ የሕዝቅያስ ፡ አምላክ ፡ ሕዝቡን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፈ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 18 ፤ ከተማዪቱንም ፡ እንዲወስዱ ፥ በቅጥር ፡ ላይ ፡ የተቀመጡትን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሕዝብ ፡ ያስፈሩና ፡ ያስደነግጡ ፡ ዘንድ ፥ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ይጮኹባቸው ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 19 ፤ በሰውም ፡ እጅ ፡ በተሠሩ ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ላይ ፡ እንደሚናገሩ ፡ መጠን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ተናገሩ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 20 ፤ ንጉሡም ፡ ሕዝቅያስና ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለዚህ ፡ ጸለዩ ፥ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ጮኹ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላኑንና ፡ መሳፍንቱን ፡ አለቃዎቹንም ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰፈር ፡ እንዲያጠፋ ፡ መልአኩን ፡ ሰደደ ። የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ዐፍሮ ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ተመለሰ ። ወደአምላኩም ፡ ቤት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ከወገቡ ፡ የወጡት ፡ ልጆቹ ፡ በዚያ ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 22 ፤ እንዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቅያስንና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ከሰናክሬም ፡ እጅ ፡ ከኹሉም ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ፤ በዙሪያቸውም ፡ ካለው ፡ ኹሉ ፡ አሳረፋቸው ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 23 ፤ ብዙዎቹም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መባ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመጡ ፡ ነበር ፥ ለይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 24 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ታመመ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየ ፤ ርሱም ፡ ተናገረው ፥ ምልክትም ፡ ሰጠው ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 25 ፤ ሕዝቅያስ ፡ ግን ፡ እንደተቀበለው ፡ ቸርነት ፡ መጠን ፡ አላደረገም ፥ ልቡም ፡ ኰራ ፤ ስለዚህም ፡ በርሱና ፡ በይሁዳ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ኾነ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 26 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ስለልቡ ፡ ኵራት ፡ ሰውነቱን ፡ አዋረደ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ አልመጣባቸውም ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 27 ፤ ለሕዝቅያስም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሀብትና ፡ ክብር ፡ ነበረው ፤ ለብርና ፡ ለወርቅም ፥ ለከበረው ፡ ዕንቍና ፡ ለሽቱው ፥ ለጋሻውና ፡ ለከበረው ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ግምጃ ፡ ቤቶች ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 28 ፤ ለእኽልና ፡ ለወይን ፡ ጠጅም ፡ ለዘይትም ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፥ ለልዩ ፡ ልዩም ፡ እንስሳ ፡ ጋጥ ፥ ለመንጋዎችም ፡ በረት ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ጥሪት ፡ ሰጥቶት ፡ ነበርና ፥ ከተማዎችን ፡ ሠራ ፥ ብዙም ፡ የበግና ፡ የላም ፡ መንጋ ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 30 ፤ ይህም ፡ ሕዝቅያስ ፡ የላይኛውን ፡ የግዮንን ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ ደፈነ ፥ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ አቅንቶ ፡ አወረደው ። የሕዝቅያስም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ተከናወነ ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባቢሎን ፡ መሳፍንት ፡ መልእክተኞች ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ ስለተደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ይጠይቁት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በተላኩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትነውና ፡ በልቡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ተወው ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 32 ፤ የሕዝቅያስም ፡ የቀረው ፡ ነገር ፥ ቸርነቱም ፥ እንሆ ፥ በዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ ራእይ ፡ በይሁዳና ፡ በእስራኤልም ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 32 ፡ 33 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በዳዊትም ፡ ልጆች ፡ መቃብር ፡ በላይኛው ፡ ክፍል ፡ ቀበሩት ፤ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ በሞቱ ፡ አከበሩት ። ልጁም ፡ ምናሴ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ። _____

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 1 ፤ ምናሴም ፡ መንገሥ ፡ በገፖመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ እንዳወጣቸው ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ፡ ርኵሰት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 3 ፤ አባቱም ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያፈረሳቸውን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ መልሶ ፡ ሠራ ፤ ለበዓሊምም ፡ መሠዊያ ፡ ሠራ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችንም ፡ ተከለ ፥ ለሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ሰገደ ፥ አመለካቸውም ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ስሜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 5 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በኹለቱ ፡ አደባባዮች ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ መሠዊያዎችን ፡ ሠራ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 6 ፤ በሄኖምም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ልጆቹን ፡ በእሳት ፡ አሳለፈ ፤ ሞራ ፡ ገላጭም ፡ ኾነ ፥ አስማትም ፡ አደረገ ፥ መተተኛም ፡ ነበረ ፥ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችንም ፡ ሰበሰበ ፤ ያስቈጣውም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 7-8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለዳዊትና ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፦ በዚህ ፡ ቤት ፡ ከእስራኤልም ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ በመረጥኋት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስሜን ፡ ለዘለዓለም ፡ አኖራለኹ ፤ ያዘዝኋቸውንም ፡ ኹሉ ፥ በሙሴ ፡ የተሰጠውን ፡ ሕግና ፡ ሥርዐት ፡ ፍርድንም ፡ ኹሉ ፡ ቢያደርጉ ፡ ቢጠብቁም ፥ ለአባቶቻችኹ ፡ ከሰጠኋት ፡ ምድር ፡ የእስራኤልን ፡ እግር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አላርቅም ፡ ባለበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሠራውን ፡ የጣዖት ፡ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ አቆመ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 9 ፤ ምናሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ካጠፋቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ አሳተ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምናሴንና ፡ ሕዝቡን ፡ ተናገራቸው ፤ ግን ፡ አልሰሙትም ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 11 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ አለቃዎች ፡ አመጣባቸው ፤ ምናሴንም ፡ በዛንጅር ፡ ያዙት ፥ በሰንሰለትም ፡ አስረው ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱት ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 12 ፤ በተጨነቀም ፡ ጊዜ ፡ አምላኩን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈለገ ፥ በአባቶቹም ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ ሰውነቱን ፡ እጅግ ፡ አዋረደ ፥

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 13 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ጸለየ ፤ ርሱም ፡ ተለመነው ፥ ጸሎቱንም ፡ ሰማው ፥ ወደ ፡ መንግሥቱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መለሰው ፤ ምናሴም ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 14 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ በስተውጭው ፡ ከግዮን ፡ ምዕራብ ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ እስከዓሳ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ። በዖፌልም ፡ አዞረበት ፥ እጅግም ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፤ በተመሸጉትም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችን ፡ አኖረ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 15 ፤ እንግዳዎችንም ፡ አማልክትና ፡ ጣዖቱንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አራቀ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ባለበት ፡ ተራራ ፡ ላይና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሠራቸውን ፡ መሠዊያዎች ፡ ኹሉ ፡ ወስዶ ፡ ከከተማዪቱ ፡ በስተውጭ ፡ ጣላቸው ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ መሠዊያ ፡ ደግሞ ፡ ዐደሰ ፥ የደኅንነትና ፡ የምስጋናም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋበት ፤ ይሁዳም ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያመልኩ ፡ አዘዘ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 17 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ገና ፡ በኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይሠዋ ፡ ነበር ፤ ቢኾንም ፡ ለአምላኩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 18 ፤ የምናሴም ፡ የቀረው ፡ ነገር ፥ ወደ ፡ አምላኩም ፡ የጸለየው ፡ ጸሎት ፥ በእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የነገሩት ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፥ እንሆ ፥ በእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 19 ፤ ደግሞም ፡ ጸሎቱ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደተለመነው ፥ ኀጢአቱና ፡ መተላለፉ ፡ ኹሉ ፥ ራሱንም ፡ ሳያዋርድ ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎችን ፡ የሠራበት ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዱንና ፡ የተቀረጹትንም ፡ ምስሎች ፡ የተከለበት ፡ ስፍራ ፥ እንሆ ፥ በባለራእዩ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 20 ፤ ምናሴም ፡ ከአባቶቹ ፡ ጋራ ፡ አንቀላፋ ፥ በቤቱም ፡ ቀበሩት ፤ ልጁም ፡ ዓሞጽ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 21 ፤ ዓሞጽ ፡ መንገሥ ፡ በገፍመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 22 ፤ አባቱም ፡ ምናሴ ፡ እንዳደረገ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ ዓሞጽም ፡ አባቱ ፡ ምናሴ ፡ ለሠራቸው ፡ ለተቀረጹት ፡ ምስሎች ፡ ኹሉ ፡ ሠዋ ፥ አመለካቸውም ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 23 ፤ አባቱም ፡ ምናሴ ፡ ሰውነቱን ፡ እንዳዋረደ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አንዳላዋረደ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ሰውነቱን ፡ አላዋረደም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዓሞጽ ፡ መተላለፉን ፡ እጅግ ፡ አበዛ ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 24 ፤ ባሪያዎቹም ፡ ተማምለው ፡ በቤቱ ፡ ገደሉት ።

መዋ.2 ፡ 33 ፡ 25 ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በዓሞጽ ፡ ላይ ፡ የተማማሉትን ፡ ኹሉ ፡ ገደሉ ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ልጁን ፡ ኢዮስያስን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አነገሡ ።

መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 1 ፤ ኢዮስያስም ፡ መንገሥ ፡ በገሥመረ ፡ ጊዜ ፡ የስምንት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሠላሳ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ አደረገ ፥ በአባቱም ፡ በዳዊት ፡ መንገድ ፡ ኼደ ፤ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አላለም ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 3 ፤ በነገሠም ፡ በስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ገና ፡ ብላቴና ፡ ሳለ ፡ የአባቱን ፡ የዳዊትን ፡ አምላክ ፡ ይፈልግ ፡ ዠመር ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከኰረብታው ፡ መስገጃዎችና ፡ ከማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹ ፥ ከተቀረጹትና ፡ ቀልጠው ፡ ከተሠሩት ፡ ምስሎች ፡ ያነጻ ፡ ዠመር ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 4 ፤ የበዓሊምንም ፡ መሠዊያዎች ፡ በፊቱ ፡ አፈረሱ ፤ በላዩም ፡ የነበሩትን ፡ የፀሓዩን ፡ ምስሎች ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንም ፡ ቈረጠ ፤ የተቀረጹትንና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎች ፡ ሰባበረ ፥ አደቀቃቸውም ፥ ይሠዉላቸው ፡ በነበሩት ፡ ሰዎች ፡ መቃብርም ፡ ላይ ፡ በተናቸው ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 5 ፤ የካህናታቸውንም ፡ ዐጥንት ፡ በመሠዊያቸው ፡ ላይ ፡ አቃጠለ ፤ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ አንጻ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 6 ፤ የምናሴንና ፡ የኤፍሬምንም ፡ የስምዖንና ፡ የንፍታሌምንም ፡ ከተማዎች ፥ በዙሪያቸውም ፡ ያለውን ፡ ቦታ ፡ እንዲሁ ፡ አነጻ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 7 ፤ መሠዊያዎቹንም ፡ አፈረሰ ፥ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶቹንና ፡ የተቀረጹትን ፡ ምስሎች ፡ አደቀቀ ፥ በእስራኤልም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የፀሓይን ፡ ምስሎች ፡ ኹሉ ፡ ቈራረጠ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተመለሰ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 8 ፤ በነገሠም ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ምድሪቱንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ካነጻ ፡ በኋላ ፥ የኤዜልያስ ፡ ልጅ ፡ ሳፋን ፥ የከተማዩ ፡ አለቃ ፡ መዕሴያ ፥ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የኢዮአካዝ ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የአምላኩን ፡ ቤት ፡ ይጠግኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰደዳቸው ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ወደ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጡ ፤ ሌዋውያኑም ፡ በረኞች ፡ ከምናሴና ፡ ከኤፍሬም ፡ ከቀረውም ፡ ከእስራኤል ፡ ኹሉ ፥ ከይሁዳና ፡ ከብንያም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ከሚኖሩት ፡ የሰበሰቡትን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡት ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ በሚሠሩት ፡ ላይ ፡ ለተሾሙት ፡ ሰጡ ፤ እነርሱም ፡ ይጠግኑና ፡ ያድሱ ፡ ዘንድ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለሚሠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ ሰጡ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 11 ፤ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ላፈረሱት ፡ ቤት ፡ ሠረገላዎች ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ ለማጋጠሚያም ፡ ዕንጨት ፡ የተጠረበውንም ፡ ድንጋይ ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ለዐናጢዎችና ፡ ለጠራቢዎች ፡ ሰጡ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 12 ፤ ሰዎቹም ፡ ሥራውን ፡ በመታመን ፡ አደረጉ ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የተሾሙት ፥ ሥራውንም ፡ የሚያሠሩት ፡ ሌዋውያን ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ኢኤትና ፡ ዐብድዩ ፥ ከቀአትም ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስና ፡ ሜሱላም ፡ ነበሩ ። ከሌዋውያንም ፡ ወገን ፡ በዜማ ፡ ዕቃ ፡ ዐዋቂዎች ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 13 ፤ በተሸካሚዎችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩ ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ነበር ፤ ጸሓፊዎቹና ፡ አለቃዎቹም ፡ በረኞቹም ፡ ከሌዋውያን ፡ ወገን ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 14 ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ገንዘብ ፡ ባመጡ ፡ ጊዜ ፡ ካህኑ ፡ ኬልቅያስም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የተሰጠውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ አገኘ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 15 ፤ ኬልቅያስም ፡ ጸሓፊውን ፡ ሳፋንን ፦ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አግኝቻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። ኬልቅያስም ፡ መጽሐፉን ፡ ለሳፋን ፡ ሰጠው ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 16 ፤ ሳፋንም ፡ መጽሐፉን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አመጣ ፤ ለንጉሡም ። ባሪያዎችኽ ፡ የተሰጣቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሹሉ ፡ ያደርጋሉ ፤

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 17 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ ገንዘብ ፡ አፈሰሱ ፥ በሥራውም ፡ ላይ ፡ ለተሾሙትና ፡ ለሠራተኞቹ ፡ ሰጡ ፡ ብሎ ፡ አወራለት ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 18 ፤ ጸሓፊውም ፡ ሳፋን ፡ ለንጉሡ ፦ ካህኑ ፡ ኬልቅያስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጠኝ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ። ሳፋንም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ አነበበው ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 19 ፤ ንጉሡም ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 20 ፤ ንጉሡም ፡ ኬልቅያስን ፥ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡ አኪቃምን ፥ የሚክያስንም ፡ ልጅ ፡ ዐብዶንን ፥ ጸሓፊውንም ፡ ሳፋንን ፥ የንጉሡንም ፡ ብላቴና ፡ ዐሳያን ፦

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 21 ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ሹሉ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አባቶቻችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስላልጠበቁ ፥ በላያችን ፡ የነደደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ኼዳችኹ ፡ ስለተገኘው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ለእኔ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳም ፡ ለቀሩት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 22 ፤ ኬልቅያስና ፡ እነዚያ ፡ ንጉሥ ፡ ያዘዛቸው ፡ ወደልብስ ፡ ጠባቂው ፡ ወደሐስራ ፡ ልጅ ፡ ወደቲቁዋ ፡ ልጅ ፡ ወደሴሌም ፡ ሚስት ፡ ወደ ፡ ነቢዩቱ ፡ ወደ ፡ ሕልዳና ፡ ኼዱ ፤ ርሷም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በከተማዩቱ ፡ በኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ነገሯት ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 23 ፤ ርሷም ፡ አለቻቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ለላካችኹ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ በተነበበው ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ ቃላት ፡ ሹሉ ፥ ማለት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፥ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 25 ፤ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ሹሉ ፡ ሊያስቈጡኝ ፡ ትተውኛልና ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፥ ቍጣዬ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ይነዳል ፥ አይጠፋምም ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለመጠየቅ ፡ ለላካችኹ ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፡ ልብኽ ፡ ገር ፡ ኾኗልና ፥

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 27 ፤ በፊቴም ፡ ራስኽን ፡ አዋርደኻልና ፥ በዚህም ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ ቃሌን ፡ በሰማኽ ፡ ጊዜ ፡ ራስኽን ፡ አዋርደኻልና ፥ ልብስኽንም ፡ ቀደኽ ፡ በፊቴ ፡ አልቅሰኻልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 28 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ አባቶችኽ ፡ እሰበስብኻለኹ ፥ በሰላምም ፡ ወደ ፡ መቃብርኽ ፡ ትሰበሰባለኽ ፤ በዚህም ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ የማመጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ ዐይኖችኽ ፡ አያዩም ። ይህንም ፡

ለንጉሥ ፡ አወሩለት ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 29 ፤ ንጉሡም ፡ ላከ ፥ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰበሰበ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩና ፡ ካህናቱ ፥ ሌዋውያኑም ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጡ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተገኘውን ፡ የቃል ፡ ኪዳኑን ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በጐሯቸው ፡ አነበበ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 31 ፤ ንጉሡም ፡ በስፍራው ፡ ቆሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተከትሎ ፡ እንዲኼድ ፥ ትእዛዙንና ፡ ምስክሩን ፡ ሥርዐቱንም ፡ በፍጹም ፡ ልቡና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሱ ፡ እንዲጠብቅ ፥ በዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ እንዲያደርግ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 32 ፤ በኢየሩሳሌምና ፡ በብንያምም ፡ የተገኙትን ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አማለ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩት ፡ የአባቶቻቸው ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንዳዘዘ ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 34 ፡ 33 ፤ ኢዮስያስም ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ርኩሱን ፡ ኹሉ ፡ አስወገደ ፥ በእስራኤልም ፡ የተገኙትን ፡ ኹሉ ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያመልኩ ፡ አደረገ ። በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከመከተል ፡ አልራቁም ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ። _____

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 1 ፤ ኢዮስያስም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ፋሲካ ፡ አደረገ ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፡ ዐረዱ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 2 ፤ ካህናቱንም ፡ በየሥርዐታቸውም ፡ አቆመ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡ አጸናቸው ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 3 ፤ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፡ ያስተምሩ ፡ ለነበሩት ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ለተቀደሱት ፡ ሌዋውያን ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ቅዱሱን ፡ ታቦት ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሰሎሞን ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አኑሩት ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በትከሻችኹ ፡ ላይ ፡ ሸክም ፡ አይኾንባችኹም ፤ አኹንም ፡ አምላካችኹን ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ሕዝቡን ፡ እስራኤልን ፡ አገልግሉ ፤

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 4 ፤ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ልጁም ፡ ሰሎሞን ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ በየሰሞናችኹና ፡ በያባቶቻችኹ ፡ ቤቶች ፡ ተዘጋጁ ፤

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ በያባቶች ፡ ቤቶች ፡ ኾናችኹ ፡ በመቅደሱ ፡ ቁሙ ፤ የሌዋውያንም ፡ ነገድ ፡ በየወገናቸው ፡ እንደ ፡ ተከፈሉ ፡ እናንተ ፡ ተከፈሉ ፤ ፋሲካውንም ፡ ዕረዱ ፥

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 6 ፤ እናንተም ፡ ተቀደሱ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለወንድሞቻችኹ ፡ አዘጋጁ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 7 ፤ ኢዮስያስም ፡ ለፋሲካው ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ በዚያ ፡ ለነበሩት ፡ ለሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ ከመንጋው ፡ ሠላሳ ፡ ሺሕ ፡ የበግና ፡ የፍየል ፡ ጠቦቶች ፥ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ ወይፈኖች ፡ ሰጣቸው ፤ እነዚህም ፡ ከንጉሡ ፡ ሀብት ፡ ነበሩ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 8 ፤ መሳፍንቱም ፡ ለሕዝቡና ፡ ለካህናቱ ፡ ለሌዋውያኑም ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሰጡ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አለቃዎች ፥ ኬልቅያስ ፥ ዘካርያስ ፥ ይሒኤል ፥ ለፋሲካው ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ በጎችና ፡ ፍየሎች ፥ ሦስት ፡ መቶም ፡ በሬዎች ፡ ለካህናቱ ፡ ሰጡ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 9 ፤ የሌዋውያኑም ፡ አለቃዎች ፡ ኮናንያ ፥ ወንድሞቹም ፡ ሸማያና ፡ ናትናኤል ፥ ሐሸቢያ ፥ ይዒኤል ፥ የዛባት ፡ ለፋሲካው ፡ መሥዋዕት ፡ እንዲኾን ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ በጎችና ፡ ፍየሎች ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ በሬዎች ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጡ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 10 ፤ አገልግሎቱም ፡ ተዘጋጀ ፥ ካህናቱም ፡ በስፍራቸው ፥ ሌዋውያኑም ፡ በየክፍላቸው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ትእዛዝ ፡ ቆሙ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 11 ፤ ፋሲካውንም ፡ ዐረዱ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ቍርበቱን ፡ ገፈፉ ፥ ካህናቱም ፡ ከእጃቸው ፡ የተቀበሉትን ፡ ደም ፡ ረጨ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 12 ፤ በሙሴም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ለሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ እንዲሰጡ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለዩ ። እንዲሁም ፡ በበሬዎቹ ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 13 ፤ ፋሲካውንም ፡ እንደ ፡ ሥርዐቱ ፡ በእሳት ፡ ጠበሱ ፤ የተቀደሰውንም ፡ ቍርባን ፡ በምንቸትና ፡ በሰታቴ ፡ በድስትም ፡ ቀቀሉ ፥ ለሕዝቡም ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ በፍጥነት ፡ አደረሱ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 14 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለራሳቸውና ፡ ለካህናቱ ፡ አዘጋጁ ፤ የአሮንም ፡ ልጆች ፡ ካህናቱ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ስቡን ፡ ለማቅረብ ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ይሠሩ ፡ ነበርና ፥ ስለዚህ ፡ ሌዋውያን ፡ ለራሳቸውና ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ለካህናቱ ፡ አዘጋጁ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 15 ፤ የአሣፍም ፡ ልጆች ፡ መዘምራን ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፥ እንደ ፡ አሣፍም ፡ እንደ ፡ ኤማንም ፡ የንጉሡም ፡ ባለራእይ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ኤዶታም ፡ ትእዛዝ ፡ በየስፍራቸው ፡ ነበሩ ፤ በረኞቹም ፡ በሮቹን ፡ ዅሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ሌዋውያን ፡ ያዘጋጁላቸው ፡ ነበርና ፥ ከአገልግሎታቸው ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ አያስፈልጋቸውም ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 16 ፤ እንደ ፡ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ኢዮስያስ ፡ ትእዛዝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፥ ፋሲካውንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ ዅሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ተዘጋጀ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 17 ፤ የተገኙትም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፥ ሰባት ፡ ቀንም ፡ የቂጣ ፡ በዓልን ፡ አደረጉ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 18 ፤ ከነቢዩ ፡ ከሳሙኤል ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አልተደረገም ፤ ከእስራኤልም ፡ ነገሥታት ፡ ዅሉ ፡ ኢዮስያስና ፡ ካህናቱ ፥ ሌዋውያኑም ፥ በዚያም ፡ የተገኙ ፡ የይሁዳና ፡ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚኖሩት ፡ እንዳደረጉት ፡ ያለ ፡ ፋሲካ ፡ ያደረገ ፡ የለም ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 19 ፤ ይህም ፡ ፋሲካ ፡ ኢዮስያስ ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ተደረገ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 20 ፤ ከዚህም ፡ ዅሉ ፡ በኋላ ፥ ኢዮስያስም ፡ ቤተ ፡ መቅደሱን ፡ ካሰናዳ ፡ በኋላ ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ኒካዑ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በከርከሚሽ ፡ ላይ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፤ ኢዮስያስም ፡ ሊጋጠመው ፡ ወጣ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ በምዋጋበት ፡ በሌላ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ አልመጣኹም ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንድቸኵል ፡ አዞኛል ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳያጠፋኽ ፡ ይህን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ከማድረግ ፡ ተመለስ ፡ ብሎ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከበት ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 22 ፤ ኢዮስያስ ፡ ግን ፡ ይዋጋው ፡ ዘንድ ፡ ተጸናና ፡ እንጂ ፡ ፊቱን ፡ ከርሱ ፡ አልመለሰም ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ የተነገረውን ፡ የኒካዑን ፡ ቃል ፡ አልሰማም ፥ በመጊዶም ፡ ሸለቆ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 23 ፤ ቀስተኞችም ፡ ንጉሡን ፡ ኢዮስያስን ፡ ወጉት ፤ ንጉሡም ፡ ብላቴናዎቹን ፦ አጥብቁ ፡ ቈስያለኹና ፡ ከሰልፉ ፡ ውስጥ ፡ አውጡኝ ፡ አላቸው ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 24 ፤ ብላቴናዎቹም ፡ ከሠረገላው ፡ አውርደው ፡ ለርሱ ፡ በነበረው ፡ በኹለተኛው ፡ ሠረገላ ፡ ውስጥ ፡ አስቀመጡት ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ አመጡት ፤ ርሱም ፡ ሞተ ፥ በአባቶቹም ፡ መቃብር ፡ ተቀበረ ፤ ይሁዳና ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ኹሉ ፡ ለኢዮስያስ ፡ አለቀሱ ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 25 ፤ ኤርምያስም ፡ ለኢዮስያስ ፡ የልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ገጠመለት ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ መዘምራን ፡ ኹሉ ፡ በልቅሶ ፡ ግጥማቸው ፡ ስለ ፡ ኢዮስያስ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፤ ይህም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ወግ ፡ ኾኖ ፡ በልቅሶ ፡ ግጥም ፡ ተጽፏል ።

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 26 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮስያስ ፡ ነገር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ያደረገው ፡ ቸርነት ፥

መዋ.2 ፡ 35 ፡ 27 ፤ የፊተኛውና ፡ የኋለኛውም ፡ ነገሩ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ።

_____መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ። _____

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 1 ፤ የአገሩም ፡ ሰዎች ፡ የኢዮስያስን ፡ ልጅ ፡ ኢዮአክስን ፡ ወስደው ፡ በአባቱ ፡ ፋንታ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አነገሡት ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 2 ፤ ኢዮአክስም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 3 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከመንግሥቱ ፡ አወጣው ፥ መቶም ፡ መክሊት ፡ ብርና ፡ አንድ ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፡ ዕዳ ፡ ጣለበት ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 4 ፤ የግብጽም ፡ ንጉሥ ፡ ወንድሙን ፡ ኤልያቄምን ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አነገሠ ፥ ስሙንም ፡ ኢዮአቄም ፡ ብሎ ፡ ለወጠ ፤ ኔካዑም ፡ ወንድሙን ፡ ኢዮአክስን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወሰደው ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 5 ፤ ኢዮአቄምም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 6 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 7 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ዐያሌውን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አፈለሰ ፥ በባቢሎንም ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 8 ፤ የቀረውም ፡ የኢዮአቄም ፡ ነገር ፥ ያደረገውም ፡ ርኵሰት ፥ በርሱም ፡ የተገኘው ፡ ኹሉ ፥ እንሆ ፥ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፏል ፤ ልጁም ፡ ዮአኪን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 9 ፤ ዮአኪንም ፡ መንገሥ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ሦስት ፡ ወርና ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ነገሠ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 10 ፤ ዓመቱ ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ልኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰደው ፥ የከበረውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስወሰደ ፤ ወንድሙንም ፡ ሴዴቅያስን ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 11 ፤ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በገ፞መረ ፡ ጊዜ ፡ የ፞ኻያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡
ነበረ ፥ በኢ፞የሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 12 ፤ በአምላኩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ በተናገረው ፡
በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ፊት ፡ ራሱን ፡ አላወረደም ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምሎት ፡ በነበረው ፡ በንጉሡ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡
ዐመፀ ፤ ወደእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይመለስ ፡ ዐንገቱን ፡ አደነደነ ፡ ልቡንም ፡ አጠነከረ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 14 ፤ ደግሞም ፡ የካህናቱ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ያለ ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡
መተላለፍን ፡ አበዙ ፤ በኢ፞የሩሳሌምም ፡ የቀደሰውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አረከሱ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 15 ፤ የአባቶቻቸውም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡና ፡ ለማደሪያው ፡ ስላዘነ ፡ ማለዳ ፡ ተነሥቶ ፡
በመልእክተኞቹ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ይልክ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 16 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፥ ፈውስም ፡
እስከማይገኝላቸው ፡ ድረስ ፥ በእግዚአብሔር ፡ መልእክተኞች ፡ ይሣለቁ ፥ ቃሉንም ፡ ያቃልሉ ፥ በነቢያቱም ፡ ላይ ፡
ያፌዙ ፡ ነበር ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 17 ፤ ስለዚህም ፡ የከለዳውያንን ፡ ንጉሥ ፡ አመጣባቸው ፤ ርሱም ፡ ጕልማሳዎቻቸውን ፡ በቤተ ፡
መቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ በሰይፍ ፡ ገደላቸው ፤ ጕልማሳውንና ፡ ቈንጕዩቱን ፡ ሽማግሌውንና ፡ አሮጌውን ፡
አልማረም ፤ ኹሉንም ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ታላቁንና ፡ ታናሹን ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡
መዝገብ ፥ የንጉሡንና ፡ የአለቃዎቹን ፡ መዝገብ ፥ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰደ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 19 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ አቃጠሉ ፥ የኢ፞የሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሱ ፥ አዳራሾቿንም ፡
በእሳት ፡ አቃጠሉ ፥ መልካሙንም ፡ ዕቃዋን ፡ ኹሉ ፡ አጠፉ ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 20 ፤ ከሰይፍም ፡ ያመለጡትን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረካቸው ፤ የፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡
ለንጉሡና ፡ ለልጆቹ ፡ ባሪያዎች ፡ ኾኑ ፤

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 21 ፤ በኤርምያስም ፡ አፍ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸም ፥ ምድሪቱ ፡ ሰንበትን ፡
በማድረጓ ፡ እስክታርፍ ፡ ድረስ ፤ በተፈታችበትም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ሰባ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ሰንበትን ፡
አገኘች ።

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 22 ፤ በኤርምያስም ፡ አፍ ፡ የተነገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡
በቂሮስ ፡ በመገ፞መሪያው ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ የፋርስን ፡ ንጉሥ ፡ የቂሮስን ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ ርሱም ፦ የፋርስ ፡
ንጉሥ ፡ ቂሮስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

መዋ.2 ፡ 36 ፡ 23 ፤ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምድርን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ሰጥቶኛል ፤ በይሁዳም ፡
ባለችው ፡ በኢ፞የሩሳሌም ፡ ቤት ፡ እሠራለት ፡ ዘንድ ፡ አዞኛል ፤ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡
አምላኩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፥ ርሱም ፡ ይውጣ ፡ ብሎ ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ዐዋጅ ፡
አስነገረ ፥ ደግሞም ፡ በጽሕፈት ፡ አደረገው ❖

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በኤርምያስም ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ በመገሥመሪያው ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ የፋርስን ፡ ንጉሥ ፡ የቂሮስን ፡ መንፈስ ፡ አስነሣ ፤ ርሱም ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ፥ ደግሞም ፡ በጽሕፈት ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ቂሮስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምድርን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ሰጥቶኛል ፤ በይሁዳም ፡ ባለችው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ እሠራለት ፡ ዘንድ ፡ አዞኛል ፤

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በእንናተ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡ አምላኩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፥ ርሱም ፡ በይሁዳ ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይውጣ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖረው ፡ አምላክ ፥ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይሥራ ፤

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ በሚኖርበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ለቀረው ፡ ሰው ፡ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ በዕቃም ፡ በእንስሳም ፡ ይርዱት ፤ ይህም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በፈቃዳቸው ፡ ከሚያቀርቡት ፡ ሌላ ፡ ይኹን ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ የይሁዳና ፡ የብንያም ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችም ፥ ካህናቱም ፥ ሌዋውያኑም ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሳቸውን ፡ ያነሣሣው ፡ ኹሉ ፡ ተነሡ ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በዙሪያቸውም ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ካቀረቡት ፡ ኹሉ ፡ ሌላ ፡ በብር ፡ ዕቃና ፡ በወርቅ ፡ በገንዘቦችና ፡ በእንስሳዎች ፡ በሌላም ፡ ስጦታ ፡ አገዟቸው ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ንጉሡ ፡ ቂሮስም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወስዶ ፡ በአማልክቱ ፡ ቤት ፡ ያኖራቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ አወጣ ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ቂሮስም ፡ በመዝገቡ ፡ ላይ ፡ በነበረው ፡ በሚትሪዳጡ ፡ እጅ ፡ አወጣቸው ፥ ለይሁዳም ፡ መስፍን ፡ ለሰሳብሳር ፡ ቈጠራቸው ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ቍጥራቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሠላሳ ፡ የወርቅ ፡ አንድ ፡ ሺሕም ፡ የብር ፡ ሳሕኖች ፥ ኻያ ፡ ዘጠኝም ፡ ቢላዎች ፥

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ሠላሳ ፡ የወርቅ ፡ ደካዎች ፥ አራት ፡ መቶ ፡ ዐሥርም ፡ ሌላ ፡ ዐይነት ፡ የብር ፡ ደካዎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ ሌላ ፡ ዕቃ ፡ ነበረ ።

ዕዝ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የወርቁና ፡ የብሩ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ ሰሳብሳር ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከተመለሱ ፡ ምርኮኞቹ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ከማረካቸው ፡ ምርኮኞች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ እየከተማቸው ፡ የተመለሱት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 2 ፤

ከዘሩባቤል ፥ ከኢያሱ ፥ ከነሐምያ ፥ ከሰራያ ፥ ከረዕላያ ፥ ከመርዶክዮስ ፥ ከበላሳን ፥ ከመሴፋር ፥ ከበጉዋይ ፥ ከሬሁም ፥ ከበዓና ፡ ጋራ ፡ መጡ ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ ሕዝብ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የፋሮስ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ የኤራ ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 6 ፤ ከኢያሱና ፡ ከኢዮአብ ፡ ልጆች ፡ የኾኑ ፡ የፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 7 ፤ የዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 8 ፤ የዛቱዕ ፡ ልጆች ፥ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 9 ፤ የዘካይ ፡ ልጆች ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 10 ፤ የባኒ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 11 ፤ የቤባይ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 12 ፤ የዓዝጋድ ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 13 ፤ የአዶኒቃም ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 14 ፤ የበጉዋይ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ዐምሳ ፡ ስድስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 15 ፤ የዓዲን ፡ ልጆች ፥ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 16 ፤ ከሕዝቅያስ ፡ ወገን ፡ የዐጤር ([237]) ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ስምንት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 17 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 18 ፤ የዮራ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 19 ፤ የሐሱም ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 20 ፤ የጋቤር ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ዐምስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 21 ፤ የቤተ ፡ ልሔም ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 22 ፤ የነጦፋ ፡ ሰዎች ፥ ዐምሳ ፡ ስድስት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 23 ፤ የዐናቶት ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ዕዝ. ፥ 2 ፥ 24 ፤ የዓዝሞት ፡ ልጆች ፥ አርባ ፡ ኹለት ።

---

237 ዕብ. ፥ ዐጤር ፡ (ሕጹር ፥ ቅጡር • የታጠረ) ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ የቂርያትይዓሪምና ፡ የከፊራ ፡ የብኤሮትም ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ የራማና ፡ የጌባ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አንድ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ የማክማስ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ የቤቴልና ፡ የጋይ ፡ ሰዎች ፥ ኹለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ የናባው ፡ ልጆች ፥ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ የመጌብስ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ስድስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 31 ፤ የኹለተኛውም ፡ ዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 33 ፤ የሎድና ፡ የሐዲድ ፡ የኦኖም ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 34 ፤ የኢያሪኮ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 35 ፤ የሴናዓ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 36 ፤ ካህናቱ ፤ ከኢያሱ ፡ ወገን ፡ የዮዳዔ ፡ ልጆች ፥ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 37 ፤ የኢሜር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 38 ፤ የፋስኮር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 39 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 40 ፤ ሌዋውያኑ ፤ ከሆዳይዋ ፡ ወገን ፡ የኢያሱና ፡ የቀድምኤል ፡ ልጆች ፥ ሰባ ፡ አራት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 41 ፤ መዘምራኑ ፤ የአሣፍ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 42 ፤ የበረኞች ፡ ልጆች ፤ የሰሎም ፡ ልጆች ፥ የዐጤር ፡ ልጆች ፥ የጤልሞን ፡ ልጆች ፥ የዐቁብ ፡ ልጆች ፥ የሐጢጣ ፡ ልጆች ፥ የሶባይ ፡ ልጆች ፥ ኹሉ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዘጠኝ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 43 ፤ ናታኒም ፤ የሲሐ ፡ ልጆች ፥ የሐሡፋ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 44 ፤ የጠብዖት ፡ ልጆች ፥ የኬራስ ፡ ልጆች ፥ የሲዓ ([238]) ፡ ልጆች ፤

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 45 ፤ የፋዶን ፡ ልጆች ፥ የልባና ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 46 ፤ የአጋባ ፡ ልጆች ፥ የዐቁብ ፡ ልጆች ፥ የአጋብ ፡ ልጆች ፥ የሰምላይ ፡ ልጆች ፥ የሐናን ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 47 ፤ የጌዴል ፡ ልጆች ፥ የጋሐር ፡ ልጆች ፥ የራያ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 48 ፤ የረአሶን ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 49 ፤ የጋሴም ፡ ልጆች ፥ የዖዛ ፡ ልጆች ፥ የፋሴሐ ፡ ልጆች ፥

---

238 ዕብ. ፥ ጺሓ ፥ (ጽሕው • የጠራ ፥ የበራ ፥ ቀ·ልጭ ፡ ያለ) ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 50 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ የአስና ፡ ልጆች ፥ የምዑናውያን ፡ ልጆች ፥ የንፉሰሲም ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 51 ፤ የበቅቡቅ ፡ ልጆች ፥ የሐቁፋ ፡ ልጆች ፥ የሐርሑር ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 52 ፤ የበስሎት ፡ ልጆች ፥ የምሒዳ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 53 ፤ የሐርሳ ፡ ልጆች ፥ የበርቆስ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 54 ፤ የሢሣራ ፡ ልጆች ፥ የቴማ ፡ ልጆች ፥ የንስያ ፡ ልጆች ፥ የሐጢፋ ፡ ልጆች ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 55 ፤ የሰሎሞንም ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፤ የሶጣይ ፡ ልጆች ፥ የሶፌሬት ፡ ልጆች ፥ የፍሩዳ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 56 ፤ የየዕላ ፡ ልጆች ፥ የደርቆን ፡ ልጆች ፥ የጌዴል ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 57 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፥ የሐጢል ፡ ልጆች ፥ የፈከራት ፡ ልጆች ፥ የሐፂቦይም ፡ ልጆች ፥ የአሚ ፡ ልጆች ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 58 ፤ እነዚህ ፡ ናታኒም ፡ ዅሉና ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 59 ፤ ከቴልሜላ ፥ ከቴላሬሳ ፥ ከክሩብ ፥ ከአዳን ፥ ከኢሜር ፡ የወጡ ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቶቻቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ዘራቸውን ፡ ወይም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ መኾናቸውን ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 60 ፤ የዳላያ ፡ ልጆች ፥ የጦብያ ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 61 ፤ ከካህናቱም ፡ ልጆች ፤ የኤብያ ፡ ልጆች ፥ የአቆስ ፡ ልጆች ፥ ከገለዓዳዊው ፡ ከቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፥ በስሙም ፡ የተጠራ ፡ የቤርዜሊ ፡ ልጆች ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 62 ፤ እነዚህ ፡ በትውልድ ፡ መጽሐፍ ፡ ትውልዳቸውን ፡ ፈለጉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልተገኘም ፥ ከክህነትም ፡ ተከለከሉ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 63 ፤ ሐቴርሰታም ፦ በኡሪምና ፡ በቱሚም ፡ የሚፈርድ ፡ ካህን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ ከቅዱሰ ፡ ቅዱሳን ፡ አትበሉም ፡ አላቸው ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 64 ፤ 65 ፤ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ከነበሩ ፡ ከሎሌዎቻቸውና ፡ ከገረዶቻቸው ፡ ሌላ ፡ ጉባኤው ፡ ዅሉ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነበሩ ። ኹለት ፡ መቶም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ መዘምራን ፡ ነበሯቸው ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 66 ፤ ፈረሶቻቸውም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፡ በቅሎዎቻቸውም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፥

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 67 ፤ ግመሎቻቸውም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፥ አህያዎቻቸውም ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ነበሩ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 68 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ወዳለው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ከአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ዐያሌዎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በስፍራው ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ሰጡ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 69 ፤ ስድሳ ፡ አንድ ፡ ሺሕም ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክ ፥ ዐምስት ፡ ሺሕም ፡ ምናን ፡ ብር ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፡ ወደሥራው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አቀረቡ ።

ዕዝ. ፡ 2 ፡ 70 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፥ ከሕዝቡም ፡ ዐያሌዎች ፥ መዘምራኑና ፡ በረኞቹም ፥ ናታኒምም ፡ በከተማዎቻቸው ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ተቀመጡ ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ሳሉ ፥ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ የኢዮሴዴቅም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ ወንድሞቹም ፡ ካህናቱ ፥ የሰላትያልም ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፡ ወንድሞቹም ፡ ተነሥተው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡበት ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ መሠዊያ ፡ ሠሩ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በአገሩም ፡ ካሉት ፡ አሕዛብ ፡ ፈርተው ፡ ነበርና ፥ መሠዊያውን ፡ በስፍራው ፡ ላይ ፡ አስቀመጡት ፥ በጧትና ፡ በማታም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቀረቡበት ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እንደተጻፈውም ፡ የዳስ ፡ በዓል ፡ አደረጉ ፤ እንደ ፡ ሥርዐቱም ፡ ለየዕለቱ ፡ የተገባውን ፡ የየዕለቱን ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በቍጥር ፡ አቀረቡ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዘወትር ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ የመባቻውንም ፡ መሥዋዕት ፥ የተቀደሱትንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ በዓላት ፡ ኹሉ ፡ መሥዋዕት ፥ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃድ ፡ የሰጠውን ፡ ቍርባን ፡ አቀረቡ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ማቅረብ ፡ ዠመሩ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ገና ፡ አልተመሠረተም ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ለጠራቢዎችና ፡ ለዐናጢዎችም ፡ ገንዘብ ፡ ሰጡ ፤ የፋርስም ፡ ንጉሥ ፡ ቂሮስ ፡ እንደ ፡ ፈቀደላቸው ፡ የዝግባ ፡ ዛፍ ፡ ከሊባኖስ ፡ በባሕር ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ለሲዶናና ፡ ለጢሮስ ፡ ሰዎች ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ዘይትም ፡ ሰጡ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ወዳለው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በመጡ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በኹለተኛው ፡ ወር ፡ የሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፥ የኢዮሴዴቅም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ የቀሩትም ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ የተመለሱት ፡ ምርኮኞች ፡ ኹሉ ፡ ዠመሩ ፤ ሌዋውያንንም ፡ ከኻያ ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ እንዲያሠሩት ፡ ሾሟቸው ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ኢያሱም ፡ ልጆቹም ፡ ወንድሞቹም ፥ የይሁዳም ፡ ልጆች ፡ ቀድምኤልና ፡ ልጆቹ ፥ የኤንሐዳድም ፡ ልጆች ፥ ልጆቻቸውና ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ሌዋውያንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የሚሠሩትን ፡ ያሠሩ ፡ ዘንድ ፡ በአንድነት ፡ ቆሙ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ዐናጢዎቹም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ በመሠረቱ ፡ ጊዜ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሳቸውን ፡ ለብሰው ፡ መለከቱን ፡ ይዘው ፥ የአሣፍም ፡ ልጆች ፡ ሌዋውያን ፡ ጸናጽል ፡ ይዘው ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ሥርዐት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፡ ቆሙ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ደግሞ ፦ ቸር ፡ ነውና ፥ ለእስራኤልም ፡ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እያሉ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገኑና ፡ እያከበሩ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያስተዛዝሉ ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እልል ፡ አሉ ።

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ የፊተኛውን ፡ ቤት ፡ ያዩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ የኾኑ ፡ ብዙ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ የአባቶችም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መቅደስ ፡ በፊታቸው ፡ በተመሠረተ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በደስታ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፤

ዕዝ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ የሚጮኹትን ፡ ድምፅ ፡ ከሕዝቡ ፡ ልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ መለየት ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ፤ ሕዝቡም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ፥ ድምፁም ፡ ከሩቅ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ የይሁዳና ፡ የብንያምም ፡ ጠላቶች ፡ ምርኮኞቹ ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ ሠሩ ፡ ሰሙ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ዘሩባቤልና ፡ ወዳባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ቀርበው ፦ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ አስራዶን ፡ ወደዚህ ፡ ካመጣን ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ለአምላካችኹ ፡ እንሠዋለንና ፥ እንደናንተም ፡ እንፈልገዋለንና ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንሥራ ፡ አሏቸው ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ዘሩባቤልና ፡ ኢያሱም ፡ የቀሩትም ፡ የእስራኤል ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ። የአምላካችንን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ለእኛና ፡ ለእናንተ ፡ አይደለም ፤ እኛ ፡ ለብቻችን ፡ ግን ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ቂሮስ ፡ እንዳዘዘን ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንሠራለን ፡ አሏቸው ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ የምድሩም ፡ ሕዝብ ፡ የይሁዳን ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ያደክሙ ፡ ነበር ፥ እንዳይሠሩም ፡ አስፈራሯቸው ፥

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ምክራቸውንም ፡ ያፈርሱ ፡ ዘንድ ፡ በፋርሱ ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ እስከፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ እስከዳርዮስ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡ መካሪዎችን ፡ ገዙባቸው ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በአርጤክስስም ([239]) ፡ መንግሥት ፥ በመንግሥቱም ፡ በመዠመሪያ ፡ ዘመን ፥ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ የክስ ፡ ነገር ፡ ጻፉ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ በአርጤክስስ ፡ ዘመን ፡ ቢሽላም ፥ ሚትሪዳጡ ፥ ጣብኤል ፡ ተባባሪዎቹም ፡ ለፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ለአርጤክስስ ፡ ጻፉ ፤ ደብዳቤውም ፡ በሶርያ ፡ ፊደልና ፡ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ አዛዡ ፡ ሬሁም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሲምሳይ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ለንጉሡ ፡ ለአርጤክስስ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ጻፉ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ አዛዡ ፡ ሬሁም ፥ ጸሓፊውም ፡ ሲምሳይ ፥ የቀሩትም ፡ ተባባሪዎቻቸው ፥ ዲናውያን ፣ አፈርሣትካውያን ፣ ጠርፈላውያን ፣ አፈርሣውያን ፣ አርካውያን ፣ ባቢሎናውያን ፣ ሱስናካውያን ፣ ዴሐውያን ፣ ኤላማውያን ፥

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ታላቁና ፡ ኀይለኛው ፡ አስናፈር ፡ ያፈለሳቸው ፡ በሰማርያና ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ያኖራቸው ፡ የቀሩትም ፡ አሕዛብ ፡ ደብዳቤውን ፡ ጻፉ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ለንጉሡ ፡ ለአርጤክስስ ፡ የላኩት ፡ የደብዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ ይህ ፡ ነው ፦ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ያሉት ፡ ሰዎች ፡ ባሪያዎችኽ ፤

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ አኹንም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ የወጡ ፡ አይሁድ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ መጡ ፡ ንጉሡ ፡ ይወቅ ፤ ዐመፀኛዪቱንና ፡ እጅግም ፡ የከፋቺቱን ፡ ከተማ ፡ ይሠራሉ ፥ ቅጥሯንም ፡ ያድሳሉ ፥ መሠረቷንም ፡ ጠገኑ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ የተሠራች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ቅጥሯም ፡ የታደሰ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ግብርና ፡ ቀረጥ ፡ መጥንም ፡ እንዳይሰጡ ፥ የንጉሡም ፡ ግቢው ፡ እንዲጐድል ፡ ንጉሡ ፡ ይወቅ ።

---

239 ዕብ. ፥ አሐሸቬሮሽ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ የንጉሡንም ፡ ጨው ፡ እንበላለንና ፥ ንጉሡንም ፡ ሲያቃልሉት ፡ ማየት ፡ አይገባንምና ፡ ስለዚህ ፡ ልከን ፡ ለንጉሡ ፡ አስታውቀናል ፤

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ በአባቶችኽ ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ምርመራ ፡ ይደረግ ፤ በዚያም ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ዐመፀኛ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ ነገሥታትንና ፡ አውራጃዎችንም ፡ እንደ ፡ ጐዳች ፥ ከጥንቱም ፡ ሽፍትነት ፡ በርሷ ፡ እንደ ፡ ተገመረ ፡ ታገኛለኽ ፥ ታውቃለኽም ፤ ስለዚህም ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ፈርሳ ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ የተሠራች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ቅጥሯም ፡ የታደሰ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ክፍል ፡ እንደሌለኽ ፡ ለንጉሡ ፡ እናስታውቃለን ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ለአዛዡ ፡ ለሬሁም ፥ ለጸሓፊውም ፡ ለሲምሳይ ፥ በሰማርያና ፡ በወንዝ ፡ ማዶም ፡ ለተቀመጡ ፡ ለቀሩት ፡ ተባባሪዎቻቸው ፡ እንዲህ ፡ የሚለውን ፡ መልስ ፡ ላከ ፦

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ሰላም ፤ አኹንም ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ የላካችኹት ፡ ደብዳቤ ፡ በፊቴ ፡ ተተርጕሞ ፡ ተነበበ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ እኔም ፡ አዝዣለኹ ፥ ተመረመረም ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ከጥንት ፡ ገዥዎራ ፡ በነገሥታት ፡ ላይ ፡ ዐመፀኛ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፥ በርሷም ፡ ዐመፅና ፡ ሽፍትነት ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ተገኘ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ እጅግ ፡ ኀያላን ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩ ፥ በወንዝም ፡ ማዶ ፡ ያለውን ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ይገዙ ፡ ነበር ፤ ግብርንና ፡ ቀረጥን ፡ መጥንንም ፡ ይቀበሉ ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ አኹንም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ሥራውን ፡ እንዲተዉ ፥ እኔም ፡ እስካዝ ፡ ድረስ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ እንዳትሠራ ፡ ትእዛዝ ፡ ስጡ ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ቸልም ፡ እንዳትሉ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ለነገሥታቱ ፡ ጕዳትና ፡ ጥፋት ፡ እየበዛ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይኼዳል ፧

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ የንጉሡም ፡ የአርጤክስስ ፡ ደብዳቤ ፡ ግልባጭ ፡ በሬሁምና ፡ በጸሓፊው ፡ በሲምሳይ ፡ በተባባሪዎቻቸውም ፡ ፊት ፡ በተነበበ ፡ ጊዜ ፥ ፈጥነው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ኼዱ ፤ በግድና ፡ በኀይልም ፡ አስተዉአቸው ።

ዕዝ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ቀረ ፤ እስከፋርስም ፡ ንጉሥ ፡ እስከዳርዮስ ፡ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ተጓጐለ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ዕዝ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ነቢያቱም ፡ ሐጌና ፡ የአዶ ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለነበሩ ፡ አይሁድ ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩላቸው ።

ዕዝ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፡ የኢዮሴዴቅም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ተነሥተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሥራት ፡ ገመሩ ፤ የሚያግዟቸውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።

ዕዝ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ የነበረው ፡ ገዢ ፡ ተንትናይ ፥ ደግሞ ፡ ሰተርቡዝናይ ፥ ተባባሪዎቻቸውም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጥተው ፦ ይህን ፡ ቤት ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፥ ይህንኑም ፡ ቅጥር ፡ ታድሱ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛችኹ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሏቸው ።

ዕዝ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ደግሞም ፦ ይህንስ ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩት ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ጠየቋቸው ።

ዕዝ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ የአምላካቸው ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ በአይሁድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡

ዳርዮስ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፥ መልሱም ፡ በደብዳቤ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አልከለከሏቸውም ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ በወንዙ ፡ ማዶ ፡ የነበረው ፡ ገዥ ፡ ተንትናይ ፡ ደግሞ ፡ ሰተርቡዝናይ ፡ ተባባሪዎቹም ፡ በወንዙ ፡ ማዶ ፡ የነበሩት ፡ አፈርሥካውያን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ዳርዮስ ፡ የላኩት ፡ የደብዳቤው ፡ ግልባጭ ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ እንዲህም ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ ላኩለት ፦ ለንጉሡ ፡ ለዳርዮስ ፡ ሙሉ ፡ ሰላም ፡ ይኹን ፤

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ ወደይሁዳ ፡ አገር ፡ ወደታላቁም ፡ አምላክ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ኼድን ፡ ንጉሡ ፡ ይወቅ ፤ ርሱም ፡ በትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ተሠራ ፥ በቅጥሩም ፡ ውስጥ ፡ ዕንጨት ፡ ተደረገ ፥ ያም ፡ ሥራ ፡ በትጋት ፡ ይሠራል ፥ በእጃቸውም ፡ ይከናወናል ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ እነዚያንም ፡ ሽማግሌዎች ፦ ይህን ፡ ቤት ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፥ ይህንስ ፡ ቅጥር ፡ ታድሱ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዛችኹ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብለን ፡ ጠየቅናቸው ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 10 ፤ ደግሞም ፡ እናስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፥ በእነርሱም ፡ ያሉትን ፡ ሹሞች ፡ ስም ፡ እንጽፍልኽ ፡ ዘንድ ፡ ስማቸውን ፡ ጠየቅን ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ እንደዚህም ፡ ብለው ፡ መለሱልን ፦ እኛ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፥ ከብዙም ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ተሠርቶ ፡ የነበረውን ፥ ታላቁም ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሠርቶ ፡ የፈጸመውን ፡ ቤት ፡ እንሠራለን ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 12 ፤ አባቶቻችንም ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ ካስቈጡ ፡ በኋላ ፡ በከለዳዊው ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ ርሱም ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ አፈረሰ ፥ ሕዝቡንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አፈለሰ ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ ንጉሡ ፡ ቂሮስ ፡ ይህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 14 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ መቅደስ ፡ የወሰደውን ፥ ወደባቢሎንም ፡ መቅደስ ፡ ያፈለሰውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ የወርቅንና ፡ የብርን ፡ ዕቃ ፡ ንጉሡ ፡ ቂሮስ ፡ ከባቢሎን ፡ መቅደስ ፡ አውጥቶ ፡ ሰሳብሳር ፡ ለተባለው ፡ ለሹሙ ፡ ሰጠውና ፦

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 15 ፤ ይህን ፡ ዕቃ ፡ ይዘኽ ፡ ኺድ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ባለው ፡ መቅደስ ፡ አኑረው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በስፍራው ፡ ይሠራ ፡ አለው ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ይህ ፡ ሰሳብሳር ፡ መጣ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ መሠረተ ፤ ከዚያም ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እየተሠራ ፡ አልተጨረሰም ።

ዕዝ. ፥ 5 ፥ 17 ፤ አኹንም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በንጉሡ ፡ ዐይን ፡ መልካም ፡ ቢኾን ፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ከንጉሡ ፡ ከቂሮስ ፡ ታዞ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በባቢሎን ፡ ባለው ፡ በንጉሡ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ይመርመር ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ንጉሡ ፡ ፈቃዱን ፡ ይላክልን ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዕዝ. ፥ 6 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ዳርዮስ ፡ መዛግብት ፡ ባሉበት ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዲመረመር ፡ አዘዘ ።

ዕዝ. ፥ 6 ፥ 2 ፤ በሜዶን ፡ አውራጃ ፡ ባለው ፡ አሕምታ ፡ በሚባል ፡ ከተማ ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ጥቅል ፡ ተገኘ ፥ በውስጡም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ለመታሰቢያ ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ በንጉሡ ፡ በቂሮስ ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ ንጉሡ ፡ ቂሮስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
አዘዘ ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፥ መሥዋዕት ፡ የሚቀርብበት ፡ ቦታ ፥ ይህ ፡ ቤት ፡
ይሠራ ፥ በጽኑም ፡ ይመሥረት ፤ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ይኹን ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ በሦስት ፡ ተራ ፡ ታላላቅ ፡ ድንጋይ ፥ ባንድ ፡ ተራ ፡ ዕንጨት ፡ ይደረግ ፤ ውጪውም ፡ ከንጉሡ ፡
ቤት ፡ ይሰጥ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ካለው ፡ መቅደስ ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያመጣው ፡
የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃ ፡ ይመለስ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ወዳለው ፡ መቅደስ ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡
ይወሰድ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይኑር ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ያለኸው ፡ የአገሩ ፡ ገዢ ፡ ተንትናይ ፡ ደግሞ ፡ ሰተርቡዝናይ ፡
በወንዝ ፡ ማዶም ፡ ያሉ ፡ ተባባሪዎቻችኹ ፡ አፈርሥካውያን ፥ ከዚያ ፡ ራቁ ፤

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ተዉ ፤ የአይሁድም ፡ አለቃና ፡ የአይሁድም ፡
ሽማግሌዎች ፡ ይህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ በስፍራው ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ተዉአቸው ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ይህን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ለአይሁድ ፡ ሽማግሌዎች ፡
የምታደርጉትን ፥ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ካለው ፡ አገር ፡ ከሚመጣው ፡ ግብር ፡ ከንጉሡ ፡ ገንዘብ ፡ ለእነዚህ ፡ ሰዎች ፡
ወጪውን ፡ በትጋት ፡ እንድትሰጧቸው ፡ ሥራም ፡ እንዳታስፈቷቸው ፡ አዝዣለኹ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ለሰማይ ፡ አምላክ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያስፈልገውን ፥ ወይፈኖችና ፡ አውራ ፡ በጎች ፡
ጠቦቶችም ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ ካህናቱ ፡ ቃል ፡ ስንዴና ፡ ጨው ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ዘይት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
ያለማቋረጥ ፡ ስጧቸው ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ይኸውም ፡ ለሰማይ ፡ አምላክ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽቱ ፡ የኾነውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀረቡ ፡ ዘንድ ፡
ለንጉሡና ፡ ለልጆቹም ፡ ዕድሜ ፡ ይጸልዩ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ይህንም ፡ ትእዛዝ ፡ የሚለውጥ ፡ ዥሉ ፥ ምሰሶው ፡ ከቤቱ ፡ ተነቅሎ ፡ ርሱ ፡ ይሰቀልበት ፤ ቤቱም ፡
የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረግ ፡ ብዬ ፡ አዝዣለኹ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ስሙንም ፡ በዚያ ፡ ያኖረው ፡ አምላክ ፡ ይህን ፡ ይለውጡ ፡ ዘንድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውንም ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ያፈርሱት ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ የሚዘረጉትን ፡ ነገሥታትና ፡ አሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ ያጥፋ ። እኔ ፡
ዳርዮስ ፡ ይህን ፡ አዝዣለኹ ፤ በትጋት ፡ ይፈጸም ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ንጉሡም ፡ ዳርዮስ ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ቃል ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ያለ ፡ ገዢ ፡
ተንትናይ ፡ ደግሞ ፡ ሰተርቡዝናይ ፡ ተባባሪዎቻቸውም ፡ እንዲሁ ፡ ተግተው ፡ አደረጉ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ የአይሁድም ፡ ሽማግሌዎች ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌና ፡ በአዶ ፡ ልጅ ፡ በዘካርያስ ፡ ትንቢት ፡ ሠሩ ፡
ተከናወነላቸውም ። እንደ ፡ እስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ትእዛዝ ፥ እንደ ፡ ፋርስም ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ቂሮስና ፡ እንደ ፡
ዳርዮስ ፡ እንደ ፡ አርጤክስስም ፡ ትእዛዝ ፡ ሠርተው ፡ ፈጸሙ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ይህም ፡ ቤት ፡ በንጉሡ ፡ በዳርዮስ ፡ መንግሥት ፡ በስድስተኛው ፡ ዓመት ፡ አዳር ፡ በሚባል ፡
ወር ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ተፈጸመ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፥ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ የቀሩትም ፡ ምርኮኞች ፥ የዚህን ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ቅዳሴ ፡ በደስታ ፡ አደረጉ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ በዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቅዳሴ ፡ መቶ ፡ ወይፈኖችና ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡

አራት ፡ መቶም ፡ ጠቦቶች ፡ አቀረቡ ፡ ፤ ስለ፡ነጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ቍጥር ፡ ለእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ አቀረቡ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ በሙሴም ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተጻፈው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አገልግሎት ፡ ላይ ፡ ካህናቱን ፡ በየማዕርጋቸው ፡ ሌዋውያኑም ፡ በየክፍላቸው ፡ አቆሙ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ምርኮኞቹም ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ፋሲካውን ፡ አደረጉ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ነጽተው ፡ ነበር ፤ ዅሉም ፡ ንጹሓን ፡ ነበሩ ፤ ለምርኮኞቹም ፡ ዅሉ ፥ ለወንድሞቻቸውም ፡ ለካህናቱ ፥ ለራሳቸውም ፡ ፋሲካውን ፡ ዐረዱ ።

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ከምርኮም ፡ ተመልሰው ፡ የመጡት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ ራሳቸውን ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ ለይተው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ ዅሉ ፡ በሉ ፤

ዕዝ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ አሠኝቷቸዋልና ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ለመሥራት ፡ እጃቸውን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መልሷልና ፥ የቂጣውን ፡ በዓል ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በደስታ ፡ አደረጉ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በአርጤክስስ ፡ መንግሥት ፡ ዕዝራ ፡ የሰራያ ፡ ልጅ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የዐዛርያስ ፡ ልጅ ፥ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፥ የሰሎም ፡ ልጅ ፥ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፥ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ የአማርያ ፡ ልጅ ፥ የዐዛርያስ ፡ ልጅ ፥ የመራዮት ፡ ልጅ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ የዘራእያ ፡ ልጅ ፥ የዖዚ ፡ ልጅ ፥ የቡቂ ፡ ልጅ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ የአቢሱ ፡ ልጅ ፥ የፊንሐስ ፡ ልጅ ፥ የአልዓዛር ፡ ልጅ ፥ የታላቁ ፡ ካህን ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፥ ይህ ፡ ዕዝራ ፡ ከባቢሎን ፡ ወጣ ፤

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ ፈጣን ፡ ጸሓፊ ፡ ነበረ ፤ የአምላኩም ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረችና ፡ ንጉሡ ፡ የሻውን ፡ ዅሉ ፡ ሰጠው ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከካህናቱም ፡ ከሌዋውያኑም ፡ ከመዘምራኑም ፡ ከበረኞቹም ፡ ከናታኒምም ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ዐያሌዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ በንጉሡም ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደረሰ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በአንደኛው ፡ ቀን ፡ ከባቢሎን ፡ ሊወጣ ፡ ዠመረ ፥ መልካሚቱም ፡ የአምላኩ ፡ እጅ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረችና ፡ በዐምስተኛ ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደረሰ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ዕዝራም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይፈልግና ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ ለእስራኤልም ፡ ሥርዐትንና ፡ ፍርድን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ አዘጋጅቶ ፡ ነበር ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ አርጤክስስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ቃልና ፡ ለእስራኤል ፡ የኾነውን ፡ ሥርዐት ፡ ይጽፍ ፡ ለነበረው ፡ ለጸሓፊው ፡ ለካህኑ ፡ ለዕዝራ ፡ የሰጠው ፡ የደብዳቤው ፡ ግልባጭ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ከንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከአርጤክስስ ፡ ለሰማይ ፡ አምላክ ፡ ሕግ ፡ ጸሓፊ ፡ ለካህኑ ፡ ለዕዝራ ፥ ሙሉ ፡

ሰላም ፡ ይኹን ፤

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በመንግሥቴ ፡ ውስጥ ፡ ካሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ከካህናቱና ፡ ከሌዋውያኑም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ የሚወድ ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንዲኼድ ፡ አዝዣለኹ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ በእጅኽ ፡ እንዳለችው ፡ እንደአምላክኽ ፡ ሕግ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ትጐበኝ ፡ ዘንድ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ንጉሡንና ፡ አማካሪዎቹም ፡ መኖሪያው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለኾነው ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በፈቃዳቸው ፡ ያቀረቡትን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፥

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ ኹሉ ፡ የምታገኘውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ኹሉ ፥ ሕዝቡና ፡ ካህናቱም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላለው ፡ ለአምላካቸው ፡ ቤት ፡ በፈቃዳቸው ፡ የሚያቀርቡትን ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ በንጉሡና ፡ በሰባቱ ፡ አማካሪዎች ፡ ተልከኻልና ፤

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ በዚህ ፡ ገንዘብ ፡ ወይፈኖችንና ፡ አውራ ፡ በጎችን ፥ ጠቦቶችንም ፥ የእኽላቸውንና ፡ የመጠጣቸውን ፡ ቍርባን ፡ ተግተኽ ፡ ግዛ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ባለው ፡ በአምላካችኹ ፡ ቤት ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ አቅርባቸው ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ከቀረውም ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ አንተና ፡ ወንድሞችኽ ፡ ለማድረግ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኛችኹን ፡ ነገር ፡ እንደአምላካችኹ ፡ ፈቃድ ፡ አድርጉ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ስለአምላክኽም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ የተሰጠኽን ፡ ዕቃ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጥ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለማውጣት ፡ የሚያስፈልግኽን ፡ ለአምላክኽ ፡ ቤት ፡ የሚያሻውን ፡ ነገር ፡ ከንጉሡ ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አውጣ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ እኔም ፡ ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ላሉት ፡ በጅሮንዶች ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቻለኹ ። የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ሕግ ፡ ጸሓፊ ፡ ካህኑ ፡ ዕዝራ ፡ ከእናንተ ፡ የሚፈልገውን ፡ ኹሉ ፡ አዘጋጁለት ፤

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ እስከ ፡ መቶ ፡ መክሊት ፡ ብርም ፡ ቢኾን ፥ እስከ ፡ መቶ ፡ የቈሬስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፥ እስከ ፡ መቶም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ እስከ ፡ መቶም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ ቢኾን ፥ ጨውም ፡ ያለልክ ፡ ቢኾን ፡ ስጡ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ በንጉሡና ፡ በልጆቹ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ እንዳይኾን ፥ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ያዘዘው ፡ ኹሉ ፡ ለሰማይ ፡ አምላክ ፡ ቤት ፡ በሙሉ ፡ ይደረግ ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ደግሞም ፡ በካህናቱና ፡ በሌዋውያን ፡ በመዘምራኑም ፡ በበረኞቹም ፡ በናታኒምም ፡ በዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሚሠሩ ፡ አገልጋዮች ፡ ላይ ፡ ግብርና ፡ ቀረጥ ፡ መጥንም ፡ እንዳይጣል ፡ ብለን ፡ እናስታውቃችኋለን ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ አንተም ፡ ዕዝራ ፥ በእጅኽ ፡ እንዳለው ፡ እንደአምላክኽ ፡ ጥበብ ፡ መጠን ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ባሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የአምላክኽን ፡ ሕግ ፡ በሚያውቁ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ ዳኞችንና ፡ ፈራጆች ፡ አስነሣ ፤ የማያውቁትንም ፡ አስተምሯቸው ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ የአምላክኽንም ፡ ሕግ ፥ የንጉሡንም ፡ ሕግ ፡ በማያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሞት ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ መወረስ ፡ ወይም ፡ ግዞት ፡ በፍጥነት ፡ ይፈረድበት ።

ዕዝ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ 28 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ያሳምር ፡ ዘንድ ፡ እንደዚህ ፡

ያለውን ፡ ነገር ፡ በንጉሡ ፡ ልብ ፡ ያኖረ ፥ በንጉሡም ፡ በአማካሪዎቹም ፡ በንጉሡም ፡ ኀያላን ፡ አለቃዎች ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ ምሕረቱን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የላከ ፡ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ። እኔም ፡ በላዬ ፡ ባለችው ፡ በአምላኬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በረታኹ ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ እንዲወጡ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አለቃዎችን ፡ ሰበሰብኹ ።

_____መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 1 ፤ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ መንግሥት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ከባቢሎን ፡ የወጡ ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ትውልዳቸውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 2 ፤ ከፊንሐስ ፡ ልጆች ፡ ጌርሶን ፥ ከኢታምር ፡ ልጆች ፡ ዳንኤል ፥ ከዳዊት ፡ ልጆች ፡ ሐጡስ ፥ ከሴኬንያ ፡ ልጆች ፥

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 3 ፤ ከፋሮስ ፡ ልጆች ፡ ዘካርያስ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ወንዶች ፡ በትውልድ ፡ ተቈጠሩ ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 4 ፤ ከፋሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጆች ፡ የዘራእያ ፡ ልጅ ፡ ኤሊሆዔናይ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 5 ፤ ከሴኬንያ ፡ ልጆች ፡ የየሕዚኤል ፡ ልጅ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 6 ፤ ከዓዲን ፡ ልጆች ፡ የዮናታን ፡ ልጅ ፡ ዔቤድ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐምሳ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 7 ፤ ከዔላም ፡ ልጆች ፡ የጎቶልያ ፡ ልጅ ፡ የሻያ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሰባ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 8 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፡ የሚካኤል ፡ ልጅ ፡ ዝባድያ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሰማንያ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ከኢዮአብ ፡ ልጆች ፡ የይሒኤል ፡ ልጅ ፡ ዐብድዩ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 10 ፤ ከሰሎሚት ፡ ልጆች ፡ የዮሲፍያ ፡ ልጅ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 11 ፤ ከቤባይ ፡ ልጆች ፡ የቤባይ ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ከዓዝጋድ ፡ ልጆች ፡ የሃቃጣን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ መቶ ፡ ዐሥር ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ ከኋለኞቹ ፡ ከአዶኒቃም ፡ ልጆች ፡ ስማቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ኤሊፋላት ፥ ይዑኤል ፥ ሸማያ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ስድሳ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ ከበጉዋይ ፡ ልጆች ፡ ዑታይና ፡ ዘቡድ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ሰባ ፡ ወንዶች ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 15 ፤ ወደ ፡ አህዋም ፡ ወደሚፈሰ ፡ ወንዝ ፡ ሰበሰብኋቸው ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሰፈርን ፤ ሕዝቡንና ፡ ካህናቱን ፡ ስቈጥራቸው ፡ በዚያ ፡ ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ ማንንም ፡ አላገኘኹም ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 16 ፤ ወደ ፡ አለቃዎቹም ፡ ወደ ፡ አልዓዛር ፥ ወደ ፡ አርኤል ፥ ወደ ፡ ሸማያ ፥ ወደ ፡ ኤልናታን ፥ ወደ ፡ ያሪብ ፥ ወደ ፡ ኤልናታን ፥ ወደ ፡ ናታን ፥ ወደ ፡ ዘካርያስ ፥ ወደ ፡ ሜሱላም ፥ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ዐዋቂዎቹ ፡ ወደ ፡ ዮያሪብና ፡ ወደ ፡ ኤልናታን ፡ ላክኹ ።

ዕዝ. ፥ 8 ፥ 17 ፤ በካሲፍያ ፡ ስፍራ ፡ ወደነበረው ፡ ወደ ፡ አለቃው ፡ ወደ ፡ አዶ ፡ ላክኋቸው ፤ ለአምላካችን ፡ ቤት ፡ አገልጋዮችን ፡ ያመጡልን ፡ ዘንድ ፡ በካሲፍያ ፡ ስፍራ ፡ ለሚኖሩት ፡ ለአዶና ፡ ለወንድሞቹ ፡ ለናታኒም ፡ የሚነግሯቸውን ፡ በአፋቸው ፡ አደረግኹ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ በላያችንም ፡ መልካም ፡ በኾነው ፡ በአምላካችን ፡ እጅ ፡ ከእስራኤል ፡ ልጅ ፡ ከሌዊ ፡ ልጅ ፡ ከሞሖሊ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የነበረውን ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ሰራብያን ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንቱን ፡ ልጆቹንና ፡ ወንድሞቹን ፡ አመጡልን ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ ደግሞም ፡ ሐሸብያን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከሜራሪ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የነበረውን ፡ የሻያንና ፡ ኻያውን ፡ ወንድሞቹንና ፡ ልጆቻቸውን ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ሌዋውያንንም ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ዳዊትና ፡ አለቃዎቹ ፡ ከሰጧቸው ፡ ናታኒም ፡ ውስጥ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ናታኒም ፡ አመጡ ፤ እነዚህም ፡ ሹሉ ፡ በስም ፡ በስማቸው ፡ ተጠሩ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ በአምላካችን ፡ ፊት ፡ ራሳችንን ፡ እናዋርድ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱም ፡ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ለእኛና ፡ ለልጆቻችን ፡ ለንብረታችንም ፡ ሹሉ ፡ እንለምን ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ በአህዋ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ጾም ፡ ዐወጅኩ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ንጉሡንም ፦ የአምላካችን ፡ እጅ ፡ በሚሹት ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ለመልካም ፡ ነው ፤ ኀይሉና ፡ ቍጣው ፡ ግን ፡ ርሱን ፡ በሚተዉ ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ብለን ፡ ተናግረን ፡ ነበርና ፥ በመንገድ ፡ ካለው ፡ ጠላት ፡ ያድኑን ፡ ዘንድ ፥ ጭፍራና ፡ ፈረሰኞች ፡ ከንጉሡ ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ ዐፍሬ ፡ ነበርና ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ጾምን ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመንን ፤ ርሱም ፡ ተለመነን ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ ከካህናቱም ፡ አለቃዎች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዎችን ፥ ሰራብያንና ፡ ሐሸቢያን ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐሥር ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ለየኹ ፤

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ንጉሡና ፡ አማካሪዎቹ ፡ አለቃዎቹም ፡ በዚያም ፡ የተገኙት ፡ እስራኤል ፡ ሹሉ ፡ ያቀረቡትን ፡ ለአምላካችን ፡ ቤት ፡ የቀረበውን ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ ዕቃውንም ፡ መዝኜ ፡ ሰጠኋቸው ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ መክሊት ፡ ብር ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ መክሊት ፡ የብር ፡ ዕቃዎች ፥ አንድ ፡ መቶም ፡ መክሊት ፡ ወርቅ ፥

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ኻያም ፡ ባለሺሕ ፡ ዳሪክ ፡ የወርቅ ፡ ጽዋዎች ፥ ኹለትም ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ የከበሩ ፡ ከጥሩ ፡ ከሚያንጸባርቅ ፡ ናስ ፡ የተሠሩ ፡ ዕቃዎች ፡ መዝኜ ፡ በእጃቸው ፡ ሰጠኹ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ እኔም ፦ እናንተ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀድሳችኋል ፥ ዕቃዎቹም ፡ ቅዱስ ፡ ናቸው ፤ ብሩና ፡ ወርቁም ፡ ለአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በፈቃድ ፡ የቀረበ ፡ ነው ፤

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ በካህናትና ፡ በሌዋውያን ፡ አለቃዎች ፡ በእስራኤልም ፡ አባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ፊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ጓዳዎች ፡ ውስጥ ፡ እስክትመዝኑ ፡ ድረስ ፡ ተግታችኹ ፡ ጠብቁ ፡ አልኋቸው ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡ ብሩንና ፡ ወርቁን ፡ ዕቃዎቹንም ፡ በሚዛን ፡ ተቀበሉ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ ከአህዋ ፡ ወንዝ ፡ ተነሣን ፡ የአምላካችንም ፡ እጅ ፡ በላያችን ፡ ነበረ ፥ በመንገድም ፡ ከጠላትና ፡ ከሚሸምቅ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ አዳነን ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደረስን ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ በአራተኛውም ፡ ቀን ፡ ብሩና ፡ ወርቁ ፡ ዕቃዎቹም ፡ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ በካህኑ ፡ በኦርዮ ፡ ልጅ ፡ በሜሪሞት ፡ እጅ ፡ ተመዘኑ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የፊንሐስ ፡ ልጅ ፡ አልዓዛር ፡ ነበረ ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌዋውያን ፡ የኢያሱ ፡ ልጅ ፡ የዛባትና ፡ የቢንዊ ፡ ልጅ ፡ ኖዓድያ ፡ ነበሩ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ ኹሉም ፡ በቍጥርና ፡ በሚዛን ፡ ተመዘነ ፤ ሚዛኑም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተጻፈ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ከምርኮም ፡ የወጡት ፡ ምርኮኞች ፡ ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወይፈኖች ፥ ዘጠና ፡ ስድስትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፥ ሰባ ፡ ሰባትም ፡ ጠቦቶች ፥ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ አቀረቡ ። ይህ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነበረ ።

ዕዝ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ የንጉሡንም ፡ ትእዛዝ ፡ በወንዙ ፡ ማዶ ፡ ላሉት ፡ ለንጉሡ ፡ ሹማምቶችና ፡ ገዢዎች ፡ ሰጡ ፤ እነርሱም ፡ ሕዝቡንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ አገዙ ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ይህም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ አለቃዎቹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ቀርበው ፦ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ካህናቱም ፡ ሌዋውያኑም ፡ እንደ ፡ ከነዓናውያን ፡ እንደ ፡ ኬጢያውያን ፡ እንደ ፡ ፈርዛውያን ፡ እንደ ፡ ኢያቡሳውያን ፡ እንደ ፡ አሞናውያን ፡ እንደ ፡ ሞዐባውያን ፡ እንደ ፡ ግብጻውያንና ፡ እንደ ፡ አሞራውያን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጋሉ ፡ እንጂ ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ አልተለዩም ፤

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ለራሳቸውና ፡ ለልጆቻቸውም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ወስደዋል ፥ የተቀደሰውንም ፡ ዘር ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ደባልቀዋል ፤ አስቀድሞም ፡ አለቃዎቹና ፡ ሹማምቶቹ ፡ በዚህ ፡ መተላለፍ ፡ መገመሪያ ፡ ኾነዋል ፡ አሉኝ ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ ልብሴንና ፡ መጐናጸፊያዬን ፡ ቀደድኹ ፥ የራሴንና ፡ የጢሜንም ፡ ጠጕር ፡ ነጨኹ ፥ ደንግጬም ፡ ተቀመጥኹ ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ስለምርኮኞቹም ፡ መተላለፍ ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ የሚፈሩ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተሰበሰቡ ፤ እኔም ፡ እስከሠርክ ፡ መሥዋዕት ፡ ድረስ ፡ ደንግጬ ፡ ተቀመጥኹ ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ በሠርክም ፡ መሥዋዕት ፡ ጊዜ ፡ ልብሴና ፡ መጐናጸፊያዬ ፡ እንደ ፡ ተቀደደ ፡ ኾኖ ፡ ከመዋረዴ ፡ ተነሣኹ ፤ በጕልበቴም ፡ ተንበርክኬ ፡ ወደ ፡ አምላኬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጄን ፡ ዘረጋኹ ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ኀጢአታችን ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ በዝቷልና ፥ በደላችንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ፊቴን ፡ ወዳንተ ፡ አነሣ ፡ ዘንድ ፡ ዐፍራለኹ ፥ እፈራማለኹ ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ከአባቶቻችን ፡ ዘመን ፡ ዠምረን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ በድለናል ፤ ዛሬም ፡ እንደ ኾነው ፡ ስለ ፡ ኀጢአታችን ፡ እኛና ፡ ንጉሦቻችን ፡ ካህናታችንም ፡ ለሰይፍና ፡ ለምርኮ ፡ ለብዝበዛና ፡ ለዕፍረት ፡ በምድር ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ ተጣልን ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ ቅሬታ ፡ ይተውልን ፡ ዘንድ ፥ በተቀደሰውም ፡ ስፍራው ፡ ችንካርን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፥ አምላካችንም ፡ ዐይናችንን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፥ በባርነትም ፡ ሳለን ፡ ጥቂት ፡ የሕይወት ፡ መታደስን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከአምላካችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሞገስ ፡ ተሰጥቶናል ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ባሪያዎች ፡ ነንና ፥ አምላካችን ፡ ግን ፡ በባርነታችን ፡ አልተወንም ፤ የሕይወት ፡ መታደስን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፥ የአምላካችንንም ፡ ቤት ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፥ የተፈታውንም ፡ እንጠግን ፡ ዘንድ ፥ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ቅጥር ፡ ይደረግልን ፡ ዘንድ ፡ በፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ፊት ፡ ምሕረቱን ፡ ሰጠን ።

ዕዝ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ 11 ፤ 12 ፤ አኹንስ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፦ ትወርሷት ፡ ዘንድ ፡ የምትገቡባት ፡ ምድር ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ ርኵሰት ፡ ረክሳለች ፥ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳርም ፡ ድረስ ፡ ከርኵሰታቸው ፡ ከጸያፍ ፡ ሥራቸውም ፡ ተሞልታለች ፤ አኹንም ፡ ትበረቱ ፡ ዘንድ ፥ የምድሩንም ፡ ፍሬ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፥ ለዘለዓለም ፡ ለልጆቻችኹ ፡ ታወርሷት ፡ ዘንድ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ ለልጆቻቸው ፡ አትስጡ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ለልጆቻችኹ ፡

አትውሰዱ ፥ ሰላማቸውንና ፡ ደኅንነታቸውንም ፡ ለዘለዓለም ፡ አትሹ ፡ ብለኽ ፡ በባሪያዎችኽ ፡ በነቢያት ፡ ያዘዝኸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ትተናልና ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧

ዕዝ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሥራችንና ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ በደላችን ፡ ካገኘን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በኋላ ፥ አንተ ፡ አምላካችን ፡ እንደ ፡ ኀጢአታችን ፡ ብዛት ፡ አልቀሠፍኸንም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ቅሬታን ፡ ሰጠኸን ።

ዕዝ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ በእውኑ ፡ ተመልሰን ፡ ትእዛዝኽን ፡ እናፈርስ ፡ ዘንድ ፥ ርኩስ ፡ ሥራን ፡ ከሚሠሩ ፡ ከነዚህም ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ይገባናልን ፧ አንተስ ፡ ቅሬታ ፡ የሌለንና ፡ የማናመልጥ ፡ እስክንኾን ፡ ድረስ ፡ እንድታጠፋን ፡ አትቈጣንም ፧

ዕዝ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ አቤቱ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፤ ዛሬም ፡ እንደ ኾነው ፡ እኛ ፡ አምልጠን ፡ ቀርተናል ፤ እንሆ ፥ በፊትኽ ፡ በበደላችን ፡ አለን ፤ ስለዚህ ፥ በፊትኽ ፡ ሊቆም ፡ የሚችል ፡ የለም ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ ዕዝራም ፡ እያለቀሰና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ እየወደቀ ፡ በጸለየና ፡ በተናዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ የወንድና ፡ የሴት ፡ የሕፃናትም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰበ ፤ ሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ አለቀሱ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ ከዔላም ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የነበረም ፡ የይሒኤል ፡ ልጅ ፡ ሴኬንያ ፡ ዕዝራን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦ አምላካችንን ፡ በድለናል ፤ የምድርን ፡ አሕዛብ ፡ እንግዳዎች ፡ ሴቶችን ፡ አግብተናል ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ገና ፡ ለእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ አለ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ አኹንም ፡ እንደ ፡ ጌታዬና ፡ የአምላካችንን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደሚፈሩት ፡ ምክር ፥ ሴቶችን ፡ ኹሉ ፡ ከነርሱም ፡ የተወለዱትን ፡ እንሰድ ፡ ዘንድ ፡ ከአምላካችን ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እናድርግ ፤ እንደ ፡ ሕጉም ፡ ይደረግ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ ይገባልና ፥ እኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነንና ፡ ተነሣ ፥ አይዞኽ ፥ አድርገው ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ ዕዝራም ፡ ተነሣ ፤ አለቃዎቹንና ፡ ካህናቱን ፡ ሌዋውያኑንም ፡ እስራኤልንም ፡ ኹሉ ፡ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አማለ ፤ እነርሱም ፡ ማሉ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ ዕዝራም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ተነሥቶ ፡ ወደኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ ወደዮሐናን ፡ ጓዳ ፡ ገባ ፤ ስለምርኮኞቹም ፡ ኀጢአት ፡ ያለቅስ ፡ ነበርና ፥ ገብቶ ፡ እንጀራ ፡ አልበላም ፥ ውሃም ፡ አልጠጣም ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 7-8 ፤ ምርኮኞቹም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲሰበሰቡ ፥ እንደ ፡ አለቃዎቹና ፡ እንደ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ምክር ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ያልመጣ ፡ ኹሉ ፡ ንብረቱ ፡ ኹሉ ፡ እንዲወረስ ፥ ርሱም ፡ ከምርኮው ፡ ጉባኤ ፡ እንዲለይ ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ ሦስት ፡ ቀንም ፡ ሳያልፍ ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያኛው ፡ ቀን ፡ የይሁዳና ፡ የብንያም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነገርና ፡ ስለ ፡ ታላቁ ፡ ዝናብ ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጡ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ ካህኑም ፡ ዕዝራ ፡ ተነሥቶ ፦ ተላልፋችኋል ፤ የእስራኤልን ፡ በደል ፡ ታበዙ ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎችን ፡ ሴቶች ፡ አግብታችኋል ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ አኹንም ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ አምላክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተናዘዙ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኘውንም ፡ አድርጉ ፤ ከምድርም ፡ አሕዛብና ፡ ከእንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ ተለዩ ፡ አላቸው ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ መልሰው ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እንደ ፡ ተናገርኸን ፡

እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሕዝቡ ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ጊዜውም ፡ የትልቅ ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፡ በሜዳም ፡ ልንቆም ፡ አንችልም ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ በድለናልና ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ የአንድ ፡ ወይም ፡ የኹለት ፡ ቀን ፡ ሥራ ፡ አይደለም ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ አለቃዎቻችንም ፡ በጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ ፋንታ ፡ ይቁሙ ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ የአምላካችን ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከእኛ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡት ፡ በከተማዎቻችን ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ በተቀጠረው ፡ ጊዜ ፡ ይምጡ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የከተማ ፡ ኹሉ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ፈራጆች ፡ ይምጡ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዐሳሄል ፡ ልጅ ፡ ዮናታንና ፡ የቴቁዋ ፡ ልጅ ፡ የሕዝያ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተቃወሙ ፤ ሜሱላምና ፡ ሌዋዊውም ፡ ሳባታይ ፡ ረዷቸው ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ምርኮኞቹም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፤ ካህኑ ፡ ዕዝራም ፡ የአባቶችም ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ በያባቶቻቸው ፡ ቤቶች ፡ ተለዩ ፥ ኹሉም ፡ በየስማቸው ፡ ተጻፉ ፤ በዐሥረኛውም ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ነገሩን ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጡ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ እስከመዠመሪያው ፡ ወር ፡ እስከመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሠረተው ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ መርምረው ፡ ጨረሱ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ከካህናቱም ፡ ወገን ፡ ልጆች ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሴቶች ፡ ያገቡ ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ፤ ከኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ ልጆችና ፡ ከወንድሞቹ ፥ መዕሴያ ፥ አልዓዛር ፥ ያሪብ ፥ ጎዶልያስ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ሚስቶቻቸውን ፡ ይፈቱ ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ ሰጡ ፤ ስለ ፡ በደላቸውም ፡ ከመንጋው ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ለበደል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ከኢሜር ፡ ልጆችም ፤ ዐናኒና ፡ ዝባድያ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ከካሪም ፡ ልጆችም ፡ መዕሴያ ፥ ኤልያስ ፥ ሽማያ ፥ ይሒኤል ፥ ዖዝያ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ከፋስኩር ፡ ልጆችም ፤ ኤልዮዔናይ ፥ መዕሴያ ፥ ይስማኤል ፥ ናትናኤል ፥ ዮዛባት ፥ ኤልዓሣ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ከሌዋውያንም ፤ ዮዛባት ፥ ሰሜኢ ፥ ቆሊጣስ ፡ የሚባል ፡ ቆልያ ፥ ፈታያ ፥ ይሁዳ ፥ አልዓዛር ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ከመዘምራንም ፤ ኤልያሴብ ፤ ከበረኞችም ፤ ሰሎም ፥ ጤሌም ፥ ኡሪ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ከእስራኤልም ፡ ከፋሮስ ፡ ልጆች ፤ ራምያ ፥ ይዝያ ፥ መልክያ ፥ ሚያሚን ፥ አልዓዛር ፥ መልክያ ፥ በናያስ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ከዔላም ፡ ልጆችም ፤ ሙታንያ ([240]) ፥ ዘካርያስ ፥ ይሒኤል ([241]) ፥ ዐብዲ ፥ ይሬሞት ፥ ኤልያ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ከዛቱዕ ፡ ልጆችም ፤ ዔሊዮዔናይ ፥ ኢልያሴብ ፥ ሙታንያ ፥ ይሬሞት ፥ ዛባድ ፥ ዓዚዛ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ከቤባይ ፡ ልጆችም ፤ ይሆሐናን ፥ ሐናንያ ፥ ዘባይ ፥ ዐጥላይ ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ከባኒ ፡ ልጆችም ፤ ሜሱላም ፥ መሉክ ፥ ዓዳያ ፥ ያሱብ ፥ ሸዓል ፥ ራሞት ።

ዕዝ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ከፈሐት ፡ ሞዐብ ፡

---

240 ዕብ. ፥ መታንያህ ፡ (መባአ ፡ አምላክ ፥ ያምላክ ፡ ስጦታ ፤ መጥን) ።

241 ዕብ. ፥ ይሒኤል ፡ (የሐዩ ፡ እግዚእ ፥ ጌታ ፡ ይኖራል) ።

ልጆችም ፤ ዓድና ፥ ክላል ፥ በናያስ ፥ መዕሴያ ፥ ሙታንያ ፥ ባስልኤል ፥ ቢንዊ ፥ ምናሴ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 31 ፤ ከካሪም ፡ ልጆችም ፤ አልዓዛር ፥ ይሺያ ፥ መልክያ ፥ ሽማያ ፥ ስምዖን ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 32 ፤ ብንያም ፥ መሉክ ፥ ሰማራያ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 33 ፤ ከሐሱም ፡ ልጆችም ፤ መትናይ ፥ መተታ ፥ ዛባድ ፥ ኤሊፋላት ፥ ይሬማይ ፥ ምናሴ ፥ ሰሜኢ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 34 ፤ ከባኒ ፡ ልጆችም ፤ መዕዳይ ([242]) ፥ ዓምራም ([243]) ፥ ኡኤል ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 35 ፤ በናያስ ፥ ቤድያ ፥ ኬልቅያ ፡

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 36 ፤ ወንያ ፥ ሜሪሞት ፥ ኤልያሴብ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 37 ፤ መታንያ ፥ መትናይ ፥ የዕሱ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 38 ፤ ባኒ ፥ ቢንዊ ፥ ሰሜኢ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 39 ፤ ሰሌምያ ፥ ናታን ፥ ዓዳያ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 40 ፤ መክነድባይ ፥ ሴሴይ ፥ ሻራይ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 41 ፤ ዔዝርኤል ፥ ሰሌምያ ፥ ሰማራያ ፥

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 42 ፤ ሰሎም ፥ አማርያ ፥ ዮሴፍ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 43 ፤ ከናባው ፡ ልጆችም ፤ ይዔኤል ፥ መቲትያ ፥ ዛባድ ፥ ዘቢና ፥ ያዳይ ፥ ኢዮኤል ፥ በናያስ ።

ዕዝ. ፥ 10 ፥ 44 ፤ እነዚህ ፡ ሹሉ ፡ እንግዳዎቹን ፡ ሚስቶች ፡ አግብተው ፡ ነበር ፤ ከነዚህም ፡ ሚስቶች ፡ ዐያሌዎቹ ፡ ልጆችን ፡ ወልደው ፡ ነበር ❖

242 ዕብ. ፥ መዐዳይ ፡ (ምዕዳው • መሻገሪያ) ።

243 ዕብ. ፥ ዐምራም ፡ (ዐመ ፡ ራማ • የልዕልና ፣ የከፍታ ፡ ሕዝብ)

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ነሐ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የሐካልያ ፡ ልጅ ፡ የነሐምያ ፡ ቃል ፦ በኻያኛው ፡ ዓመት ፡ በካሴሉ ፡ ወር ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤

ነሐ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እኔ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ሳለኹ ፥ ከወንድሞቼ ፡ አንዱ ፡ ዐናኒ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ከይሁዳ ፡ መጡ ፤ እኔም ፡ የዳኑትን ፡ ከምርኮ ፡ የተረፉትን ፡ የአይሁድን ፡ ነገር ፡ የኢየሩሳሌምንም ፡ ነገር ፡ ጠየቅኋቸው ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ እነርሱም ፦ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ያሉት ፡ ከምርኮ ፡ የተረፉት ፡ ቅሬታዎች ፡ በታላቅ ፡ መከራና ፡ ስድብ ፡ አሉ ፤ የኢየሩሳሌምም ፡ ቅጥር ፡ ፈርሷል ፥ በሮቿም ፡ በእሳት ፡ ተቃጥለዋል ፡ አሉኝ ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ ተቀምጬ ፡ አለቀስኹ ፥ ዐያሌ ፡ ቀንም ፡ አዝን ፡ ነበር ፤ በሰማይም ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ እጾምና ፡ እጸልይ ፡ ነበር ፥

ነሐ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ አቤቱ ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ለሚወዱኽና ፡ ትእዛዝኽን ፡ ለሚያደርጉ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፥ ታላቅና ፡ የተፈራኽ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥

ነሐ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ዛሬ ፡ በፊትኽ ፡ ስለ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ የምጸልየውን ፡ ጸሎት ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ዦሮኽ ፡ ያድምጥ ፥ ዐይኖችኽም ፡ ይከፈቱ ፤ ባንተ ፡ ላይም ፡ ያደረግነውን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ኀጢአት ፡ እናዘዝልኻለኹ ፤ እኔና ፡ የአባቴም ፡ ቤት ፡ በድለናል ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እኛም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ሠርተናል ፤ ለባሪያኽም ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዝኸውን ፡ ትእዛዝና ፡ ሥርዐት ፡ ሕግም ፡ አልጠበቅንም ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 8-9 ፤ አኹንም ፡ ብትተላለፉ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበትናችኋለኹ ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ብትመለሱ ፡ ግን ፡ ትእዛዜንም ፡ ብትጠብቁ ፡ ብታደርጓትም ፥ ከእናንተ ፡ ሰዎች ፡ እስከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ቢበተኑ ፡ ከዚያ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ ስሜም ፡ ይኖርበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መረጥኹት ፡ ስፍራ ፡ አመጣቸዋለኹ ፡ ብለኽ ፡ ለባሪያኽ ፡ ለሙሴ ፡ ያዘዝኸውን ፡ ቃል ፡ እባክኽ ፡ ዐስብ ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እነዚህም ፡ በታላቅ ፡ ኀይልኽና ፡ በብርቱ ፡ እጅኽ ፡ የተቤገሥኻቸው ፡ ባሪያዎችኽና ፡ ሕዝብኽ ፡ ናቸው ።

ነሐ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዦሮኽ ፡ የባሪያኽን ፡ ጸሎት ፥ ስምኽንም ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ የሚወዱትን ፥ የባሪያዎችኽን ፡ ጸሎት ፡ ያድምጥ ፤ ዛሬም ፡ ለባሪያኽ ፡ አከናውንለት ፥ በዚህም ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ምሕረትን ፡ ስጠው ። እኔም ፡ ለንጉሡ ፡ ጠጅ ፡ አሳላፊው ፡ ነበርኹ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ነሐ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ በኻያኛው ፡ ዓመት ፡ በኒሳን ፡ ወር ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በፊቱ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ጠጁን ፡ አንሥቼ ፡ ለንጉሡ ፡ ሰጠኹት ። ቀድሞ ፡ ግን ፡ በፊቱ ፡ ያለሐዘን ፡ እኖር ፡ ነበር ።

ነሐ. ፥ 2 ፥ 2 ፤ ንጉሡም ፦ ሳትታመም ፡ ፊትኽ ፡ ለምን ፡ ዐዘነ ፧ ይህ ፡ የልብ ፡ ሐዘን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፡ አለኝ ። እጅግም ፡ ብዙ ፡ አድርጌ ፡ ፈራኹ ።

ነሐ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይንገሥ ፤ የአባቶቼ ፡ መቃብር ፡ ያለባት ፡ ከተማ ፡ ተፈታለችና ፥ በሮቿም ፡ በእሳት ፡ ተቃጥለዋልና ፥ ፊቴ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይዘን ፧ አልኹት ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፦ ምን ፡ ትለምነኛለኽ ፧ አለኝ ። እኔም ፡ ወደሰማይ ፡ አምላክ ፡ ጸለይኹ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ ቢያሠኝኽ ፥ ባሪያኽም ፡ በፊትኽ ፡ ሞገስ ፡ ቢያገኝ ፥ እሠራው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወዳባቶቼ ፡ መቃብር ፡ ከተማ ፡ ስደደኝ ፡ አልኹት ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ንግሥቲቱም ፡ በአጠገቡ ፡ ተቀምጣ ፡ ሳለች ፡ ንጉሡ ፦ መንገድኽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ፧ መቼስ ፡ ትመለሳለኽ ፧ አለኝ ። ንጉሡም ፡ ይሰደኝ ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ እኔም ፡ ዘመኑን ፡ ቀጠርኹለት ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ንጉሡንም ፦ ንጉሡ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፥ እስከይሁዳ ፡ አገር ፡ እንዲያደርሱኝ ፡ በወንዝ ፡ ማዶ ፡ ላሉት ፡ ገዥዎች ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰጠኝ ፤

ነሐ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በቤቱም ፡ አጠገብ ፡ ላለው ፡ ለግንብ ፡ በሮች ፥ ለከተማውም ፡ ቅጥር ፥ ለምገባበትም ፡ ቤት ፡ ዕንጨት ፡ እንዲሰጠኝ ፡ ለንጉሡ ፡ ዱር ፡ ጠባቂ ፡ ለአሣፍ ፡ ደብዳቤ ፡ ይሰጠኝ ፡ አልኹት ። ንጉሡም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነችው ፡ እንደአምላኬ ፡ እጅ ፡ ሰጠኝ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በወንዙም ፡ ማዶ ፡ ወዳሉት ፡ አለቃዎች ፡ መጥቼ ፡ የንጉሡን ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጠኋቸው ፡ ንጉሡም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃዎችና ፡ ፈረሰኞች ፡ ሰደደ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ሖሮናዊውም ፡ ሰንባላጥና ፡ ባሪያው ፡ አሞናዊ ፡ ጦብያ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ የሚሻ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተበሳጨ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ደረስኹ ፥ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ተቀመጥኹ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በሌሊትም ፡ ተነሣኹ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ አደርገው ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ ያኖረውን ፡ ለማንም ፡ አላስታወቅኹም ፤ ተቀምጬበት ፡ ከነበረው ፡ እንስሳ ፡ በቀር ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ እንስሳ ፡ አልነበረም ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ በሸለቆውም ፡ በር ፡ ወጣኹ ፥ ወደዘንዶውም ፡ ምንጭና ፡ ወደጕድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ኼድኹ ፤ የፈረሰውንም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፥ በእሳትም ፡ የተቃጠሉትን ፡ በሮቿን ፡ ተመለከትኹ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ወደምንጩም ፡ በርና ፡ ወደንጉሡ ፡ መዋኛ ፡ ዐለፍኹ ፤ ተቀምጬበትም ፡ የነበረው ፡ እንስሳ ፡ የሚያልፍበት ፡ ስፍራ ፡ አልነበረም ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ በሌሊትም ፡ በፈፋው ፡ በኩል ፡ ወጥቼ ፡ ቅጥሩን ፡ ተመለከትኹ ፤ ዘወርም ፡ ብዬ ፡ በሸለቆው ፡ በር ፡ ገባኹ ፥ እንዲሁም ፡ ተመለስኹ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ሹማምቱ ፡ ግን ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኼድኹ ፥ ምን ፡ እንዳደረግኹም ፡ አላወቁም ፡ ነበር ፤ ለአይሁድና ፡ ለካህናቱ ፥ ለታላላቆችና ፡ ለሹማምቱም ፥ ሥራም ፡ ይሠሩ ፡ ለነበሩት ፡ ለሌላዎች ፡ ገና ፡ አልተናገርኹም ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እኔም ፦ እኛ ፡ ያለንበትን ፡ ጕስቍልና ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ፈረሰች ፥ በሮቿም ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠሉ ፡ ታያላችኹ ፤ አኹንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ መሳለቂያ ፡ እንዳንኾን ፡ ኑና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡ እንሥራ ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ የአምላኬም ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ ንጉሡም ፡ የነገረኝን ፡ ቃል ፡ ነገርኋቸው ። እነርሱም ፦ እንነሣና ፡ እንሥራ ፡ አሉ ። እጃቸውንም ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ አበረቱ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ሖሮናዊውም ፡ ሰንባላጥ ፥ ባሪያውም ፡ አሞናዊው ፡ ጦብያ ፥ ዐረባዊውም ፡ ጌሳም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ በንቀት ፡ ሣቁብን ፤ ቀላል ፡ አድርገውንም ፦ ይህ ፡ የምታደርጉት ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእውኑ ፡ በንጉሡ ፡

ላይ ፡ ትሸፍቱ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳላችኹን ፧ አሉ ።

ነሐ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ መልሼ ፦ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ያከናውንልናል ፥ እኛም ፡ ባሪያዎቹ ፡ ተነሥተን ፡ እንሠራለን ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዕድል ፡ ፈንታና ፡ መብት ፡ መታሰቢያም ፡ የላችኹም ፡ አልኋቸው ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ኤልያሴብ ፡ ወንድሞቹም ፡ ካህናት ፡ ተነሥተው ፡ የበግ ፡ በር ፡ ሠሩ ፤ ቀደሱትም ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፤ እስከሃሜአ (244) ፡ ግንብና ፡ እስከሐናንኤል ፡ ግንብ ፡ ድረስ ፡ ቀደሱት ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ በአጠገቡ ፡ የኢያሪኮ ፡ ሰዎች ፡ ሠሩ ፤ በአጠገባቸውም ፡ የአምሪ ፡ ልጅ ፡ ዘኩር ፡ ሠራ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ የሃስናአ ፡ ልጆችም ፡ የዓሣ ፡ በር ፡ ሠሩ ፤ ሠረገላዎቹን ፡ አኖሩ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቀ·ልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የአቆስ ፡ ልጅ ፡ የኦርዮ ፡ ልጅ ፡ ሜሪሞት ፡ ዐደሰ ። በአጠገባቸውም ፡ የሜሴዜቤል ፡ ልጅ ፡ የበራክያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ ዐደሰ ። በአጠገባቸውም ፡ የበዓና ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ቴቁሐውያን ፡ ዐደሱ ፤ ታላላቆቻቸው ፡ ግን ፡ ለጌታቸው ፡ ሥራ ፡ ዐንገታቸውን ፡ አላዋረዱም ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ የፋሴሐ ፡ ልጅ ፡ ዮዳዔና ፡ የበሶድያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ አሮጌውን ፡ በር ፡ ዐደሱ ፤ ሠረገላዎቹን ፡ አኖሩ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቀ·ልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ገባዖናዊው ፡ መልጥያና ፡ ሜሮኖታዊው ፡ ያዶን ፥ የወንዙም ፡ ማዶ ፡ አለቃ ፡ ግዛት ፡ የኾኑ ፡ የገባዖንና ፡ የምጽጳ ፡ ሰዎች ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ በአጠገባቸውም ፡ ወርቅ ፡ አንጥረኛው ፡ የሐርሃያ ፡ ልጅ ፡ ዑዝኤል ፡ ዐደሰ ። በአጠገቡም ፡ ከሽቱ ፡ ቀማሚዎች ፡ የነበረ ፡ ሐናንያ ፡ ዐደሰ ፤ እስከ ፡ ሰፊው ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ጠገኑ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የሖር ፡ ልጅ ፡ ረፋያ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኤርማፍ (245) ፡ ልጅ ፡ ይዳያ ፡ በቤቱ ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ። በአጠገቡም ፡ የአሰበንያ (246) ፡ ልጅ ፡ ሐጡስ (247) ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ የካሪም ፡ ልጅ ፡ መልክያ ፥ የፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጅም ፡ ዐሱብ ፡ ሌላውን ፡ ክፍልና ፡ የእቶኑን ፡ ግንብ ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ግዛት ፡ እኩሌታና ፡ የመንደሮቿ ፡ አለቃ ፡ የአሎኤስ (248) ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ሐኖንና ፡ የዛኖዋ ፡ ሰዎችም ፡ የሸለቆውን ፡ በር ፡ ዐደሱ ፤ ሠሩት ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆሙ ፥ ቀ·ልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረጉ ፤ ደግሞም ፡ እስከጕድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ የሚኾን ፡ ቅጥር ፡ ሠሩ ።

---

244 ዕብ. ፥ ሜአሀ ፡ (ምእት • መቶ) ።
245 ዕብ. ፥ ሐሩማፍ ።
246 ዕብ. ፥ ሐሻብንያሕ ።
247 ዕብ. ፥ ሐጡሽ ።
248 ዕብ. ፥ ሀ ፡ ሎ·ኄሽ ፡ (ለኋሲ • በለ·ኆሳስ ፡ የሚናገረው) ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የቤትሐካሪምም ፡ ግዛት ፡ አለቃ ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ መልክያ ፡ የጕድፍ ፡ መጣያውን ፡ በር ፡ ዐደሰ ፤ ሠራው ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆመ ፥ ቀኑልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረገ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ የምጽጳም ፡ ግዛት ፡ አለቃ ፡ የኮልሖዜ ፡ ልጅ ፡ ሰሎም ፡ የምንጩን ፡ በር ፡ ዐደሰ ፤ ሠራው ፥ ከደነውም ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ አቆመ ፥ ቀኑልፎቹንና ፡ መወርወሪያዎቹንም ፡ አደረገ ፤ ከዳዊትም ፡ ከተማ ፡ እስከሚወርደው ፡ ደረጃ ፡ ድረስ ፡ በንጉሡ ፡ አትክልት ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ የሼላን ፡ መዋኛ ፡ ቅጥር ፡ ሠራ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቤትጹር ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የዓዝቡቅ ፡ ልጅ ፡ ነሐምያ ፡ በዳዊት ፡ መቃብር ፡ አንጻር ፡ እስካለው ፡ ስፍራ ፥ እስከተሠራውም ፡ መዋኛ ፥ እስከጎያላኑም ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ሌዋውያንና ፡ የባኒ ፡ ልጅ ፡ ሬሁም ፡ ዐደሱ ። በአጠገባቸውም ፡ የቅዒላ ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ ሐሸብያ ፡ ስለ ፡ ግዛቱ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቅዒላ ፡ ግዛት ፡ እኩሌታ ፡ አለቃ ፡ የኤንሐዳድ ፡ ልጅ ፡ በዋይ ፡ ወንድሞቹም ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ በአጠገቡም ፡ የምጽጳ ፡ አለቃ ፡ የኢያሱ ፡ ልጅ ፡ ኤጽር ፡ በማእዘኑ ፡ አጠገብ ፡ በጦር ፡ መሣሪያ ፡ ቤት ፡ አንጻር ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የዘባይ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ከማእዘኑ ፡ ገዖምሮ ፡ እስከታላቁ ፡ ካህን ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡ መግቢያ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ተግቶ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የአቆስ ፡ ልጅ ፡ የኦርዮ ፡ ልጅ ፡ ሜሪሞት ፡ ከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡ መግቢያ ፡ ገዖምሮ ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ቤት ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የቄላው ፡ ሰዎች ፡ ካህናቱ ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ብንያምና ፡ ዐሱብ ፡ በቤታቸው ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሱ ። ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ የመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ በቤቱ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የኤንሐደድ ([249]) ፡ ልጅ ፡ ቢንዊ ፡ ከዐዛርያስ ፡ ቤት ፡ ገዖምሮ ፡ እስከ ፡ ማእዘኑ ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ የኡዛይ ፡ ልጅ ፡ ፋላል ፡ በማእዘኑ ፡ አንጻር ፡ ያለውንና ፡ በዘበኞች ፡ አደባባይ ፡ አጠገብ ፡ ከላይኛው ፡ የንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ የቆመውን ፡ ግንብ ፡ ሠራ ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የፋሮስ ፡ ልጅ ፡ ፈዳያ ፡ ሠራ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ናታኒምም ፡ በዖፌል ፡ በውሃው ፡ በር ፡ አንጻር ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወጥቶ ፡ በቆመው ፡ ግንብ ፡ አጠገብ ፡ እስካለው ፡ ስፍራ ፡ ድረስ ፡ ተቀመጡ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ቴቁሐውያን ፡ ወጥቶ ፡ በቆመው ፡ በታላቁ ፡ ግንብ ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ እስከዖፌል ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፡ ሌላውን ፡ ክፍል ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ከፈረሱ ፡ በር ፡ በላይ ፡ ካህናቱ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየቤታቸው ፡ አንጻር ፡ ዐደሱ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ ሳዶቅ ፡ በቤቱ ፡ አንጻር ፡ ዐደሰ ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የምሥራቁን ፡ በር ፡ ጠባቂ ፡ የሴኬንያ ፡ ልጅ ፡ ሸማያ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ ሐናንያና ፡ የሴሌፍ ፡ ስድስተኛው ፡ ልጁ ፡ ሐኖን ፡ ሌላውን ፡

---

249 ዕብ. ፥ ሐናዳድ ።

ክፍል ፡ ዐደሱ ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የበራክያ ፡ ልጅ ፡ ሜሱላም ፡ በጓዳው ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ከወርቅ ፡ አንጥረኞቹ ፡ የነበረ ፡ መልክያ ፡ እስከ ፡ ናታኒምና ፡ እስከነጋዴዎቹ ፡ ቤት ፡ ድረስ ፡ በሐሚፍቃድ ፡ በር ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ እስከማእዘኑ ፡ መውጫ ፡ ድረስ ፡ ዐደሰ ።

ነሐ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ ከማእዘኑም ፡ መውጫ ፡ ዠምረው ፡ እስከበጉ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ወርቅ ፡ አንጥረኞችና ፡ ነጋዴዎች ፡ ዐደሱ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፡ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ሰንባላጥም ፡ ቅጥሩን ፡ እንደ ፡ ሠራን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ ተበሳጨም ፥ በአይሁድም ፡ አላገጠ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ በወንድሞቹና ፡ በሰማርያ ፡ ሰራዊትም ፡ ፊት ፦ እነዚህ ፡ ደካማዎች ፡ አይሁድ ፡ የሚሠሩት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይተዉላቸዋልን ፧ ይሠዋሉን ፧ ባንድ ፡ ቀንስ ፡ ይጨርሳሉን ፧ የተቃጠለውንስ ፡ ድንጋይ ፡ ከፍርስራሹ ፡ መልሰው ፡ ያድኑታልን ፧ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ አሞናዊውም ፡ ጦብያ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፦ በድንጋይ ፡ በሚሠሩት ፡ ቅጥራቸው ፡ ላይ ፡ ቀበሮ ፡ ቢመጣበት ፡ ያፈርሰዋል ፡ አለ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ተንቀናልና ፥ ስማ ፤ ስድባቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ መልስባቸው ፤ በምርኮ ፡ አገር ፡ ለብዝበዛ ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጣቸው ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ በደላቸውንም ፡ አትክደን ፥ ኀጢአታቸውም ፡ ከፊትኽ ፡ አይደምሰስ ፤ በሠራተኞች ፡ ፊት ፡ አስቈጥተውኻልና ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ቅጥሩንም ፡ ሠራን ፤ ቅጥሩም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ እኩሌታው ፡ ድረስ ፡ ተጋጠመ ፤ የሕዝቡም ፡ ልብ ፡ ለሥራው ፡ ጨከነ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ሰንባላጥና ፡ ጦብያም ፡ ዐረባውያንም ፡ አሞናውያንም ፡ አሽዶዳውያንም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቅጥር ፡ እየታደሰ ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥ የፈረሰውም ፡ ሊጠገን ፡ እንደ ፡ ተዠመረ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጡ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ መጥተውም ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይወጉና ፡ ያሸብሩ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉም ፡ በአንድነት ፡ ተማማሉ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ አምላካችንም ፡ ጸለይን ፥ ከነርሱም ፡ የተነሣ ፡ በአንጻራቸው ፡ ተጠባባቂዎች ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ አደረግን ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ይሁዳም ፦ የተሸካሚዎች ፡ ኀይል ፡ ደከመ ፥ ፍርስራሹም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ቅጥሩንም ፡ እንሠራ ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፡ አሉ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ጠላቶቻችንም ፦ ወደ ፡ መካከላቸው ፡ እስክንመጣና ፡ እስክንገድላቸው ፡ ድረስ ፡ ሥራቸውንም ፡ እስክናስተጓጉል ፡ ድረስ ፡ አያውቁምና ፡ አያዩም ፡ አሉ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ በአጠገባቸውም ፡ የተቀመጡት ፡ አይሁድ ፡ መጥተው ፦ ከስፍራው ፡ ኹሉ ፡ ይመጡብናል ፡ ብለው ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ነገሩን ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ከቅጥሩም ፡ በስተኋላ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በታችኛው ፡ ስፍራ ፡ ሰይፋቸውን ፡ ጦራቸውንም ፡ ቀስታቸውንም ፡ አስይዤ ፡ ሕዝቡን ፡ በየወገናቸው ፡ አቆምኋቸው ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ አይቼም ፡ ተነሣኹ ፥ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱንም ፡ የቀሩትንም ፡

ሕዝብ ፦ አትፍሯቸው ፤ ታላቁንና ፡ የተፈራውን ፡ ጌታ ፡ ዐስቡ ፥ ስለ ፡ ወንድሞቻችኹም ፡ ስለ ፡ ወንዶችና ፡ ስለ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ስለ ፡ ሚስቶቻችኹም ፡ ስለ ፡ ቤቶቻችኹም ፡ ተዋጉ ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ደረሰልን ፥ እግዚአብሔርም ፡ ምክራቸውን ፡ ከንቱ ፡ እንዳደረገው ፡ ሰሙ ፤ እኛም ፡ ዅላችን ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወደ ፡ ሥራችን ፡ ተመለስን ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እኩሌታዎቹ ፡ ብላቴናዎቼ ፡ ሥራ ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፥ እኩሌታዎቹም ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ቀስትና ፡ ጥሩርም ፡ ይዘው ፡ ነበር ፤ አለቃዎቹም ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ዅሉ ፡ በኋላ ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ቅጥሩንም ፡ የሚሠሩትና ፡ ተሸካሚዎቹ ፡ ባንድ ፡ እጃቸው ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፥ ባንድ ፡ እጃቸውም ፡ የጦር ፡ መሣሪያቸውን ፡ ይይዙ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ዐናጢዎቹም ፡ ዅሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሰይፉን ፡ በወገቡ ፡ ታጥቆ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፤ ቀንደ ፡ መለከትም ፡ የሚነፋ ፡ በአጠገቤ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱን ፡ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ። ሥራው ፡ ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ተበታትነናል ፥ አንዱም ፡ ከኹለተኛው ፡ ርቋል ፤

ነሐ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ የቀንደ ፡ መለከቱን ፡ ድምፅ ፡ ወደምትሰሙበት ፡ ስፍራ ፡ ወደዚያ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ተሰብሰቡ ፤ አምላካችን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ይዋጋል ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ሥራውንም ፡ ሠራን ፡ ከማለዳ ፡ ወገግታም ፡ ዠምሮ ፡ ከዋክብት ፡ እስኪወጡ ፡ ድረስ ፡ እኩሌታዎቹ ፡ ጦር ፡ ይይዙ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፦ ዅላችኹ ፡ ከብላቴናዎቻችኹ ፡ ጋራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ዕደሩ ፤ በሌሊትም ፡ ጠባቂዎች ፡ ኹኑልን ፥ በቀንም ፡ ሥሩ ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ እኔና ፡ ወንድሞቼም ፡ ብላቴናዎቼም ፡ በኋላዬም ፡ የነበሩት ፡ ጠባቂዎች ፡ ልብሳችንን ፡ አናወልቅም ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ነሐ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ በወንድሞቻቸውም ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ ትልቅ ፡ የሕዝቡና ፡ የሚስቶቻቸው ፡ ጩኸት ፡ ኾነ ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ዐያሌዎቹም ፦ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ በልተንም ፡ በሕይወት ፡ እንድንኖር ፡ እኽልን ፡ እንሸምት ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ዐያሌዎቹም ፦ ከራብ ፡ የተነሣ ፡ እኽልን ፡ እንሸምት ፡ ዘንድ ፡ ዕርሻችንና ፡ ወይናችንን ፡ ቤታችንንም ፡ አስይዘናል ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ሌላዎቹም ፦ ለንጉሡ ፡ ግብር ፡ ዕርሻችንንና ፡ ወይናችንን ፡ አስይዘን ፡ ገንዘብ ፡ ተበድረናል ፤

ነሐ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ ሥጋችን ፡ እንደ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሥጋ ፥ ልጆቻችንም ፡ እንደ ፡ ልጆቻቸው ፡ ናቸው ፤ እንሆም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡ ባሪያዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰጥተናል ፥ ከሴቶችም ፡ ልጆቻችን ፡ ባሪያዎች ፡ ኾነው ፡ የሚኖሩ ፡ አሉ ፤ ታላላቆችም ፡ ዕርሻችንና ፡ ወይናችንን ፡ ይዘዋልና ፥ ልናድናቸው ፡ አንችልም ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ እኔም ፡ ጩኸታቸውንና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣኹ ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ በልቤም ፡ ዐሰብኹ ፥ ታላላቆቹንና ፡ ሹማምቱንም ፦ ዅላችኹ ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ ወለድ ፡

ትወስዳላችኹ ፡ ብዬ ፡ ተጣላኧቸው ፤ ትልቅም ፡ ጉባኤ ፡ ሰበሰብኹባቸው ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ እኔም ፦ ለአሕዛብ ፡ የተሸጡትን ፡ ወንድሞቻችንን ፡ አይሁድን ፡ በፈቃዳችን ፡ ተቤዝን ፤ እናንተስ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ ትሸጣላችኹን ፧ እነርሱስ ፡ ለእኛ ፡ የተሸጡ ፡ ይኾናሉን ፧ አልኧቸው ። እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ መልስም ፡ አላገኙም ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ደግሞም ፡ አልኹ ፦ የምታደርጉት ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ ጠላቶቻችን ፡ አሕዛብ ፡ እንዳይሰድቡን ፡ አምላካችንን ፡ በመፍራት ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ አይገባችኹምን ፧

ነሐ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ ወንድሞቼም ፡ ብላቴናዎቼም ፡ ገንዘብና ፡ እኽል ፡ ለእነርሱ ፡ አበድረናል ፤ እባካችኹ ፥ ይህን ፡ ወለድ ፡ እንተውላቸው ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ዕርሻቸውንና ፡ ወይናቸውን ፡ ወይራቸውንና ፡ ቤታቸውንም ፡ ከነርሱም ፡ የወሰዳችኹትን ፡ ገንዘቡንና ፡ እኽሉን ፥ ወይን ፡ ጠጁንና ፡ ዘይቱን ፡ ከመቶ ፡ እጅ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ እባካችኹ ፡ ዛሬ ፡ መልሱላቸው ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ እንመልስላቸዋለን ፥ ከነርሱም ፡ ምንም ፡ አንሻም ፤ እንደ ፡ ተናገርኽ ፡ እንዲሁ ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ። ካህናቱንም ፡ ጠርኼ ፡ እንደዚህ ፡ ነገር ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አማልኧቸው ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ ልብሴን ፡ አራገፍኹና ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ የማያደርገውን ፡ ሰው ፡ ከቤቱና ፡ ከሥራው ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያራግፈው ፤ እንዲሁም ፡ የተራገፈና ፡ ባዶ ፡ ይኹን ፡ አልኹ ። ጉባኤውም ፡ ኹሉ ፦ አሜን ፡ አሉ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑ ፤ ሕዝቡም ፡ እንደዚህ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ንጉሡም ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ካዘዘኝ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ከንጉሡ ፡ ከአርጤክስስ ፡ ከኻያኛው ፡ ዓመት ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እኔና ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአለቃ ፡ የሚገባውን ፡ ሥንቅ ፡ አልበላንም ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ከእኔ ፡ አስቀድመው ፡ የነበሩት ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ አክብደው ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ እንጀራውና ፡ ስለ ፡ ወይኑ ፡ አርባ ፡ ሰቅል ፡ ብር ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ፤ ሎሌዎቻቸውም ፡ ደግሞ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥኑ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ ፈራኹ ፡ እንዲህ ፡ አላደረግኹም ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ አጥብቄ ፡ የቅጥሩን ፡ ሥራ ፡ ሠራኹ ፥ ዕርሻም ፡ አልገዛንም ፤ ብላቴናዎቼም ፡ ኹሉ ፡ ወደዚያው ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ተሰበሰቡ ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ደግሞም ፡ በዙሪያችን ፡ ካሉት ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ከመጡት ፡ ሌላ ፡ ከአይሁድና ፡ ከሹማምቱ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሰዎች ፡ በገበታዬ ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ከወፎችም ፡ በቀር ፡ ላንድ ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ በሬና ፡ ስድስት ፡ የሰቡ ፡ በጎች ፥ በዐሥር ፡ በዐሥር ፡ ቀንም ፡ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይዘጋጅልኝ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አገዛዝ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ከብዶ ፡ ነበርና ፥ ለአለቃ ፡ የሚገባውን ፡ ሥንቅ ፡ አልሻም ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ያደረግኹትን ፡ ኹሉ ፡ ለበጎነት ፡ ዐስብልኝ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ነሐ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ቅጥሩን ፡ እንደ ፡ ሠራኹ ፥ ከፍራሹም ፡ አንዳች ፡ እንዳልቀረበት ፡ ሰንባላጥና ፡ ጦብያ ፡ ዐረባዊውም ፡ ጌሳም ፡ የቀሩትም ፡ ጠላቶቻችን ፡ ሰሙ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስከዚያ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ በበሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ሳንቃዎቹን ፡ አላቆምኹም ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ሰንባላጥና ፡ ጌሳም ፦ መጥተኽ ፡ በኦኖ ፡ ቈላ ፡ ውስጥ ፡ ባሉት ፡ መንደሮች ፡ እንገናኝ ፡ ብለው ፡

ላኩብኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉ ፡ ያደርጉብኝ ፡ ዘንድ ፡ ያስቡ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ እኔም ፦ ትልቅ ፡ ሥራ ፡ እሠራለኹ ፥ እወርድም ፡ ዘንድ ፡ አይቻለኝም ፤ ሥራውን ፡ ትቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ በመውረዴ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሥራው ፡ ይታጐላል ፧ ብዬ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላክኹባቸው ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ እንዲህም ፡ ቃል ፡ አራት ፡ ጊዜ ፡ ላኩብኝ ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ቃል ፡ መለስኩላቸው ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ ሰንባላጥም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ጊዜ ፡ ብላቴናውን ፡ ዐምስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ላከብኝ ፤

ነሐ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ በእጁም ፡ ውስጥ ፦ አንተና ፡ አይሁድ ፡ ዐመፅ ፡ እንድታስቡ ፥ ስለዚህም ፡ ቅጥሩን ፡ እንድትሠራ ፥ ንጉሣቸውም ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እንድትወድ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ተሰምቷል ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ ደግሞም ፦ ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ነቢያትን ፡ አቁመኻል ፤ አኹንም ፡ ለንጉሡ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ያወሩለታል ፤ እንግዲህ ፡ መጥተኽ ፡ በአንድነት ፡ እንማከር ፡ የሚል ፡ ክፍት ፡ ደብዳቤ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ እኔም ፦ አንተ ፡ ከልብኽ ፡ ፈጥረኽዋል ፡ እንጂ ፡ እንደተናገርኸው ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ የለም ፡ ብዬ ፡ ላክኹበት ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ እነርሱም ፡ ኹሉ ፡ ሥራው ፡ እንዳይፈጸም ፦ እጃቸው ፡ ይደክማል ፡ ብለው ፡ ያስፈራሩን ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፤ አኹንም ፥ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እጄን ፡ አበርታ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ እኔም ፡ ወደመሔጣብኤል ፡ ልጅ ፡ ወደድላያ ፡ ልጅ ፡ ወደሸማያ ፡ ቤት ፡ ገባኹ ፤ ርሱም ፡ ተዘግቶ ፡ ነበርና ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ እንገናኝ ፡ የመቅደሱንም ፡ ደጆች ፡ እንዝጋ ፤ እነርሱ ፡ መጥተው ፡ ይገድሉኻልና ፥ በሌሊትም ፡ ይገድሉኽ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣሉና ፡ አለ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ እኔም ፦ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ የሸሸና ፥ ነፍሱንስ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ የገባ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኔስ ፡ አልገባም ፡ አልኹት ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ልኮት ፡ እንዳልነበረ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ትንቢት ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ እንሆ ፥ ዐወቅኹ ፤ ጦብያና ፡ ሰንባላጥም ፡ ገዝተውት ፡ ነበር ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ አደርግና ፡ እበድል ፡ ዘንድ ፥ በእኔም ፡ ላይ ፡ ክፋት ፡ እንዲናገሩና ፡ እንዲያላግጡ ፡ ያስፈራራኝ ፡ ዘንድ ፡ ተገዝቶ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ሥራቸው ፡ ጦብያንና ፡ ሰንባላጥን ፡ ያስፈራሩኝም ፡ ዘንድ ፡ የወደዱትን ፡ ነቢዩቱን ፡ ኖዓድያን ፡ የቀሩትንም ፡ ነቢያት ፡ ዐስብ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 15 ፤ ቅጥሩም ፡ በኤሉል ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በዐምሳ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ተጨረሰ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 16 ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያችን ፡ የነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፈሩ ፥ በራሳቸውም ፡ ዐሳብ ፡ እጅግ ፡ ተዋረዱ ፥ ይህም ፡ ሥራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ዐወቁ ።

ነሐ. ፥ 6 ፥ 17 ፤ 18 ፤ ጦብያም ፡ የኤራ ፡ ልጅ ፡ የሴኬንያ ፡ ዐማች ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ ልጁም ፡ ይሖሐናን ፡ የበራክያን ፡ ልጅ ፡ የሜሱላምን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስላገባ ፥ በይሁዳ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተማምለው ፡ ነበርና ፥ በዚያ ፡ ወራት ፡ ብዙ ፡ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ ጦብያ ፡ ደብዳቤዎች ፡ ይልኩ ፡ ነበር ፥ የጦብያም ፡ ደብዳቤዎች ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ደግሞም ፡ በፊቴ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ መልካም ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ ቃሌንም ፡ ያወሩለት ፡ ነበር ፤ ጦብያም ፡ ሊያስፈራራኝ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ይልክ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ነሐ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ቅጥሩ ፡ ከተሠራ ፡ በኋላ ፥ ሳንቃዎቹንም ፡ ካቆምኹ ፡ በኋላ ፥ በረኞቹና ፡ መዘምራኑ ፡ ሌዋውያኑም ፡ ከተሾሙ ፡ በኋላ ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ወንድሜን ፡ ዐናኒንና ፡ የግንቡን ፡ አለቃ ፡ ሐናንያን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ሾምኋቸው ፤ ርሱም ፡ እውነተኛ ፡ ከሌላዎቹም ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ እኔም ፦ ፀሓይ ፡ እስኪሞቅ ፡ ድረስ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ አይከፈቱ ፤ እነርሱም ፡ ቆመው ፡ ሳሉ ፡ ደጆቹን ፡ ይዝጉ ፥ ይቈልፉም ፤ ከኢየሩሳሌምም ፡ ሰዎች ፡ አንዳንዱን ፡ በየተራው ፡ አንዳንዱንም ፡ በየቤቱ ፡ አንጻር ፡ ጠባቂዎችን ፡ አስቀምጡ ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ከተማዪቱም ፡ ሰፊና ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ፤ በውስጧ ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ነበሩ ፥ ቤቶቹም ፡ አልተሠሩም ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ አምላኬም ፡ ታላቆቹንና ፡ ሹማምቱን ፡ ሕዝቡንም ፡ ሰብስቤ ፡ እቈጥራቸው ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ አደረገ ፤ አስቀድመው ፡ የመጡትን ፡ ሰዎች ፡ የትውልድ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ አገኘኹ ፥ በርሱም ፡ እንደዚህ ፡ ተጽፎ ፡ አገኘኹ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከማረካቸው ፡ ምርኮኞች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ እየከተማቸው ፡ የተመለሱት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 7 ፤

ከዘሩባቤል ፥ ከኢያሱ ፥ ከነሐምያ ፥ ከዐዛርያስ ፥ ከረዓምያ ፥ ከነሐማኒ ፥ ከመርዶክዮስ ፥ ከበላሳን ፥ ከሚስጴሬት ፥ ከበጉዋይ ፥ ከነሑም ፥ ከበዓና ፡ ጋራ ፡ መጡ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ ሕዝብ ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የፋሮስ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ የኤራ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ከኢያሱና ፡ ከኢዮአብ ፡ ልጆች ፡ የኾኑ ፡ የፈሐት ፡ ሞዐብ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ የዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ የዛቱዕ ፡ ልጆች ፥ ስምንት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ የዘካይ ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ የቢንዊ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ የቤባይ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ የዓዝጋድ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ የአዶኒቃም ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ የበጉዋይ ፡ ልጆች ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ስድሳ ፡ ሰባት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ የዓዲን ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ የሕዝቅያስ ፡ ወገን ፡ የዐጤር ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ የሐሱም ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አራት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ የሐሪፍ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ የገባዖን ፡ ልጆች ፥ ዘጠና ፡ ዐምስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ የቤተ ፡ ልሔምና ፡ የነጦፋ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ የዓናቶች ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ የቤትዓዝሞት ፡ ሰዎች ፥ አርባ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ የቂርያትይዓሪምና ፡ የከፊራ ፡ የብኤሮትም ፡ ሰዎች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሦስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ የራማና ፡ የጌባ ፡ ሰዎች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አንድ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 31 ፤ የማክማስ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 32 ፤ የቤቴልና ፡ የጋይ ፡ ሰዎች ፥ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ የኹለተኛው ፡ ናባው ፡ ሰዎች ፥ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ የኹለተኛው ፡ ዔላም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ አራት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ ኻያ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ የኢያሪኮ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡

ነሐ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ የሎድና ፡ የሐዲድ ፡ የኦኖም ፡ ልጆች ፥ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ አንድ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ የሴናዓ ፡ ልጆች ፥ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 39 ፤ ካህናቱ ፤ ከኢያሱ ፡ ወገን ፡ የዮዳዔ ፡ ልጆች ፥ ዘጠኝ ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ሦስት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 40 ፤ የኢሜር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐምሳ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 41 ፤ የፋስኮር ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ሰባት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 42 ፤ የካሪም ፡ ልጆች ፥ ሺሕ ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 43 ፤ ሌዋውያኑ ፤ ከሆዳይዋ ፡ ወገን ፡ የኢያሱና ፡ የቀድምኤል ፡ ልጆች ፥ ሰባ ፡ አራት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 44 ፤ መዘምራኑ ፤ የአሣፍ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ አርባ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 45 ፤ በረኞቹ ፤ የሰሎም ፡ ልጆች ፥ የዐጤር ፡ ልጆች ፥ የጤልሞን ፡ ልጆች ፥ የዐቁብ ፡ ልጆች ፥ የሐጢጣ ፡ ልጆች ፥ የሶባይ ፡ ልጆች ፥ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 46 ፤ ናታኒም ፥ የሲሐ ፡ ልጆች ፥ የሐሡፋ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 47 ፤ የጠብዖት ፡ ልጆች ፥ የኬራስ ፡ ልጆች ፥ የሲዓ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 48 ፤ የፋዶን ፡ ልጆች ፥ የልባና ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 49 ፤ የአጋባ ፡ ልጆች ፥ የሰምላይ ፡ ልጆች ፥ የሐናን ፡ ልጆች ፥ የጌዴል ፡ ልጆች ፥ የጋሐር ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 50 ፤ የራያ ፡ ልጆች ፥ የረአሶን ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 51 ፤ የጋሴም ፡ ልጆች ፥ የዖዛ ፡ ልጆች ፥ የፋሴሐ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 52 ፤ የቤሳይ ፡ ልጆች ፥ የምዑናውያን ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 53 ፤ የንፉሰሲም ፡ ልጆች ፥ የበቅቡቅ ፡ ልጆች ፥ የሐቀፋ ፡ ልጆች ፥ የሐርሑር ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 54 ፤ የበስሎት ፡ ልጆች ፥ የምሒዳ ፡ ልጆች ፥ የሐርሻ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 55 ፤ የበርቆስ ፡ ልጆች ፥ የሢሣራ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 56 ፤ የቴማ ፡ ልጆች ፥ የንስያ ፡ ልጆች ፥ የሐጢፋ ፡ ልጆች ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 57 ፤ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፤ የሶጣይ ፡ ልጆች ፥ የሶፌሬት ፡ ልጆች ፥ የፍሩዳ ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 58 ፤ የየዕላ ፡ ልጆች ፥ የደርቆን ፡ ልጆች ፥ የጌዴል ፡ ልጆች ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 59 ፤ የሰፋጥያስ ፡ ልጆች ፥ የሐጢል ፡ ልጆች ፥ የፈከራት ፡ ልጆች ፥ የሐፂቦይም ፡ ልጆች ፥ የዐሞን ፡ ልጆች ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 60 ፤ ናታኒም ፡ ኹሉና ፡ የሰሎሞን ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 61 ፤ ከቴልሜላ ፥ ከቴላሬሳ ፥ ከክሩብ ፥ ከአዳን ፥ ከኢሜር ፡ የወጡ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የአባቶቻቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ዘራቸውን ፡ ወይም ፡ ከእስራኤል ፡ ወገን ፡ መኾናቸውን ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፤

ነሐ. ፡ 7 ፡ 62 ፤ የዳላያ ፡ ልጆች ፥ የጦብያ ፡ ልጆች ፥ የኔቆዳ ፡ ልጆች ፥ ስድስት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ኹለት ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 63 ፤ ከካህናቱም ፡ የኤብያ ፡ ልጆች ፥ የአቆስ ፡ ልጆች ፥ ከገለዓዳዊው ፡ ከቤርዜሊ ፡ ልጆች ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ በስሙም ፡ የተጠራ ፡ የቤርዜሊ ፡ ልጆች ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 64 ፤ እነዚህ ፡ በትውልድ ፡ መጽሐፍ ፡ ትውልዳቸውን ፡ ፈለጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልተገኘም ፤ ከክህነትም ፡ ተከለከሉ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 65 ፤ ሐቴርሰታም ፦ በኡሪምና ፡ በቱሚም ፡ የሚፈርድ ፡ ካህን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፥ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡

አትበሉም ፡ አላቸው ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 66 ፤ 67 ፤ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ከነበሩ ፡ ከሎሌዎቻቸውና ፡ ከገረዶቻቸው ፡ ሌላ ፡ ጉባኤው ፡ ኹሉ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ነበሩ ፤ ኹለቱ ፡ መቶም ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ መዘምራን ፡ ነበሯቸው ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 68 ፤ ፈረሶቻቸውም ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ስድስት ፥ በቅሎዎቻቸውም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፥

ነሐ. ፡ 7 ፡ 69 ፤ ግመሎቻቸውም ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፥ አህያዎቻቸውም ፡ ስድስት ፡ ሺሕ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 70 ፤ ከአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችም ፡ ዐያሌዎቹ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ስጦታ ፡ ሰጡ ። ሐቴርሰታም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክ ፥ ዐምሳም ፡ ድስቶች ፥ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳም ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ በቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ሰጠ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 71 ፤ ከአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎችም ፡ ዐያሌዎቹ ፡ በሥራው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ውስጥ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክ ፥ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶም ፡ ምናን ፡ ብር ፡ ሰጡ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 72 ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ የሰጡት ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የወርቅ ፡ ዳሪክና ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ምናን ፡ ብር ፥ ስድሳ ፡ ሰባትም ፡ የካህናት ፡ ልብስ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 7 ፡ 73 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፥ በረኞቹና ፡ መዘምራኑም ፡ ከሕዝቡም ፡ ዐያሌዎቹ ፥ ናታኒምም ፥ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ተቀመጡ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ሰባተኛውም ፡ ወር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ነበሩ ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በውሃው ፡ በር ፡ ፊት ፡ ወዳለው ፡ አደባባይ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ኾነው ፡ ተሰበሰቡ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ያዘዘውን ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ጸሓፊውን ፡ ዕዝራን ፡ ተናገሩት ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ካህኑም ፡ ዕዝራ ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ሕጉን ፡ በማኅበሩ ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ አስተውለውም ፡ በሚሰሙት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ አመጣው ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ በውሃውም ፡ በር ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ የሚያስተውሉም ፡ ሲሰሙ ፥ ከማለዳ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ቀትር ፡ ድረስ ፡ አነበበው ፤ የሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ጐሮ ፡ የሕጉን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመስማት ፡ ያደምጥ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ጸሓፊውም ፡ ዕዝራ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በተሠራ ፡ በዕንጨት ፡ መረባርብ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በአጠገቡ ፡ መቲትያ ፥ ሸማዕ ፥ ዐናያ ፥ ኦርዮ ፥ ኬልቅያስ ፥ መዕሴያ ፡ በቀኙ ፡ በኩል ፥ ፈዳያ ፥ ሚሳኤል ፥ መልክያ ፥ ሐሱም ፥ ሐሽበዳና ፥ ዘካርያስ ፥ ሜሱላም ፡ በግራው ፡ በኩል ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ዕዝራም ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ መጽሐፉን ፡ ገለጠ ፤ በገለጠውም ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ቆሙ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ዕዝራም ፡ ታላቁን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባረከ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ እየዘረጉ ፦ አሜን ፥ አሜን ፡ ብለው ፡ መለሱ ። ራሳቸውንም ፡ አዘነበሉ ፥ በግንባራቸውም ፡ ተደፍተው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰገዱ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ደግሞ ፡ ኢያሱና ፡
ባኒ ፡ ሰራብያ ፡ ያሚን ፡ ዐቁብ ፡ ሳባታይ ፡ ሆዲያ ፡ መዕሴያ ፡ ቆሊጣስ ፡ ዐዛርያስ ፡ የዛባት ፡ ሐናን ፡ ፈልያ ፡ ሌዋውያኑ
ም ፡ ሕጉን ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡም ፡ በየስፍራቸው ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ አነበቡ ፤ ዕዝራም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡
ያስተምርና ፡ ያስታውቅ ፡ ነበር ፥ ሕዝቡም ፡ የሚነበበውን ፡ ያስተውሉ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ሐቴርሰታ ፡ ነሐምያም ፡ ጸሓፊውም ፡ ካህኑ ፡ ዕዝራ ፡ ሕዝቡንም ፡ የሚያስተምሩ ፡ ሌዋውያን ፡
ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፦ ዛሬ ፡ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ አታልቅሱ ፡ እንባም ፡ አታፍስሱ ፡
አሏቸው ፤ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ያለቅሱ ፡ ነበርና ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፥ የሰባውንም ፡ ብሉ ፥ ጣፋጩንም ፡ ጠጡ ፥ ለእነዚያም ፡ ላልተዘጋጀላቸው ፡
ዕድል ፡ ፈንታቸውን ፡ ስደዱ ፤ ዛሬ ፡ ለጌታችን ፡ የተቀደሰ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ደስታ ፡ ኀይላችኹ ፡
ነውና ፥ አትዘኑ ፡ አላቸው ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ሌዋውያንም ፦ ቀኑ ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፥ ዝም ፡ በሉ ፥ አትዘኑም ፡ ብለው ፡ ሕዝቡን ፡ ኹሉ ፡
ጸጥ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ የተነገረላቸውን ፡ ቃል ፡ አስተውለዋልና ፥ ሊበሉና ፡ ሊጠጡ ፥ ዕድል ፡
ፈንታም ፡ ሊሰዱ ፡ ደስታም ፡ ሊያደርጉ ፡ ኼዱ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ካህናቱም ፡
ሌዋውያኑም ፡ የሕጉን ፡ ቃል ፡ ይተረጉምላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጸሓፊው ፡ ወደ ፡ ዕዝራ ፡ ተሰበሰቡ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ 15 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ባለው ፡ በዓል ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በዳስ ፡ ይቀመጡ ፡
ዘንድ ፡ በከተማዎቻቸውና ፡ በኢየሩሳሌምም ፦ ወደ ፡ ተራራ ፡ ኺዱ ፤ የዘይትና ፡ የበረሓ ፡ ወይራ ፡ የባርሰነትም ፡
የዘንባባም ፡ የለመለመውን ፡ ዛፍ ፡ ቅርንጫፍ ፡ አምጡ ፥ እንደ ፡ ተጻፈውም ፡ ዳሶችን ፡ ሥሩ ፡ ብለው ፡ ይናገሩ ፡
ያውጁም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ እንዳዘዘ ፡ በሕጉ ፡ ውስጥ ፡ ተጽፎ ፡ አገኙ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ ሕዝቡም ፡ ወጥተው ፡ አመጡ ፤ እያንዳንዱም ፡ በቤቱ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፥ በአደባባዩም ፡
ላይ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አደባባዩ ፡ ላይ ፥ በውሃውም ፡ በር ፡ አደባባይና ፡ በኤፍሬም ፡ በር ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ዳስ ፡
ሠራ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ከምርኮም ፡ የተመለሱት ፡ ማኅበር ፡ ኹሉ ፡ ዳስ ፡ ሠሩ ፥ በዳሱም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ። ከነዌም ፡
ልጅ ፡ ከኢያሱ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ አላደረጉም ፡
ነበር ። እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ኾነ ።

ነሐ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ከመዠመሪያውም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ያነብ ፡ ነበር ። በዓሉን ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ አደረጉ ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡
እንደ ፡ ሕጉ ፡ የተቀደሰ ፡ ጉባኤ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ በዚህም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ጾመው ፥ ማቅም ፡
ለብሰው ፥ በላያቸውም ፡ ትቢያ ፡ ነስንሰው ፡ ተከማቹ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ የእስራኤልም ፡ ዘር ፡ ከእንግዳዎች ፡ ኹሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ለዩ ፥ ቆመውም ፡ ኀጢአታቸውንና ፡
የአባቶቻቸውን ፡ ኀጢአት ፡ ተናዘዙ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ በየስፍራቸውም ፡ ቆመው ፡ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ የቀን ፡ ሩብ ፡ ያኽል ፡ አነበቡ ፤ ሦስት ፡ የቀን ፡ ሩብም ፡ ያኽል ፡ ተናዘዙ ፥ ለአምላካቸው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ሰገዱ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ኢያሱና ፡ ባኒ ፥ ቀድምኤል ፥ ሰበንያ ፥ ቡኒ ፥ ሰራብያ ፥ ባኒ ፥ ክናኒ ፡ በደረጃዎች ፡ ላይ ፡ ቆመው ፡ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኹ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ኢያሱ ፥ ቀድምኤል ፥ ባኒ ፥ አሰበንያ ፥ ሰራብያ ፥ ሆዲያ ፥ ሰበንያ ፥ ፈታያ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ቆማችኹ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ። እንዲህም ፡ በሉ ። በበረከትና ፡ በምስጋና ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለው ፡ ክቡር ፡ ስምኽ ፡ ይባረክ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኽ ፤ ሰማዩንና ፡ የሰማያት ፡ ሰማይን ፡ ሰራዊታቸውንም ፡ ዥሉ ፥ ምድሩንና ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ዥሉ ፥ ባሕሮቹንና ፡ በእነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዥሉ ፥ ፈጥረኻል ፥ ዥሉንም ፡ ሕያው ፡ አድርገኻዋል ፤ የሰማዩም ፡ ሰራዊት ፡ ለአንተ ፡ ይሰግዳሉ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ አብራምን ፡ መረጥኽ ፥ ከኡር ፡ ከላውዴዎንም ፡ አወጣኸው ፥ ስሙንም ፡ አብርሃም ፡ አልኸው ፤

ነሐ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ልቡም ፡ በፊትኽ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ አገኘኸው ፤ የከነዓናዊውንና ፡ የኬጢያዊውን ፡ የአሞራዊውንም ፡ የፌርዛዊውንም ፡ የኢያቡሳዊውንም ፡ የጌርጌሳዊውንም ፡ ምድር ፡ ለርሱና ፡ ለዘሩ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረግኽ ፡ አንተም ፡ ጻድቅ ፡ ነኽና ፥ ቃልኽን ፡ ፈጸምኽ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ በግብጽም ፡ ሳሉ ፡ የአባታችንን ፡ መከራ ፡ አየኽ ፥ በቀይ ፡ ባሕርም ፡ ሳሉ ፡ ጨኸታቸውን ፡ ሰማኽ ፤

ነሐ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ እንደ ፡ ታበዩባቸውም ፡ ዐውቀኽ ፡ ነበርና ፥ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ዥሉ ፡ በምድሩም ፡ ሕዝብ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ምልክትና ፡ ተኣምራት ፡ አሳየኽ ፤ ዛሬም ፡ እንደ ኾነው ፡ ስምኽን ፡ አስጠራኽ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ከፊታቸውም ፡ ባሕሩን ፡ ከፈልኽ ፥ በባሕሩም ፡ መካከል ፡ በደረቅ ፡ አልፉ ፤ ጠላቶቻቸውን ፡ ግን ፡ ድንጋይ ፡ ለጥልቅ ፡ ውሃ ፡ እንዲጣል ፡ በቀላይ ፡ ውስጥ ፡ ጣልኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ የሚኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ታበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ በቀን ፡ በደመና ፡ ዐምድ ፥ በሌሊትም ፡ በእሳት ፡ ዐምድ ፡ መራኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ወደሲናም ፡ ተራራ ፡ ወረድኽ ፥ ከሰማይም ፡ ተናገርኻቸው ፤ ቅኑን ፡ ፍርድና ፡ እውነቱን ፡ ሕግ ፡ መልካሙንም ፡ ሥርዐትና ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠኻቸው ፤

ነሐ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ የተቀደሰውንም ፡ ሰንበትኽን ፡ አስታወቅኻቸው ፥ ትእዛዝንና ፡ ሥርዐትን ፡ ሕግንም ፡ በባሪያኽ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ አዘዝኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ለራባቸውም ፡ ከሰማይ ፡ እንጀራ ፡ ሰጠኻቸው ፥ ለጥማታቸውም ፡ ከአለቱ ፡ ውሃ ፡ አመጣኽላቸው ፤ ወደማልኽላቸውም ፡ ምድር ፡ ገብተው ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱና ፡ አባቶቻችን ፡ ታበዩ ፥ ዐንገታቸውንም ፡ አደነደኑ ፥ ትእዛዝኽንም ፡ አልሰሙም ፥

ነሐ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ለመስማትም ፡ እንቢ ፡ አሉ ፥ ያደረግኽላቸውንም ፡ ተኣምራት ፡ አላሰቡም ፤ ዐንገታቸውንም ፡ አደነደኑ ፥ በዐመፃቸውም ፡ ወደ ፡ ባርነታቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አለቃ ፡ አደረጉ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ባይ ፥ ቸርና ፡ መሓሪ ፡ አምላክ ፥ ለቀሥጣም ፡ የምትዘገይ ፥ ምሕረትንም ፡ የምታበዛ ፡ ነኽ ፥ አልተውኻቸውም ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራውንም ፡ እንቦሳ ፡ አድርገው ፦ ከግብጽ ፡ ያወጣኽ ፡ አምላክኽ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፥ እጅግም ፡ ባስቈጡኽ ፡ ጊዜ ፥

ነሐ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ አንተ ፡ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ አልተውኻቸውም ፤ በመንገድም ፡ ይመራቸው ፡ ዘንድ ፡ የደመና ፡ ዐምድ ፡ በቀን ፥ የሚኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ የእሳት ፡ ዐምድ ፡ በሌሊት ፡ ከነርሱ ፡ አልራቀም ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ያስተምራቸውም ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ መንፈስኽን ፡ ሰጠኻቸው ፥ መናኽንም ፡ ከአፋቸው ፡ አልከለከልኽም ፥ ለጥማታቸውም ፡ ውሃ ፡ ሰጠኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ አርባ ፡ ዓመትም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መገብኻቸው ፥ ምንም ፡ አላጡም ፤ ልብሳቸውም ፡ አላረጅም ፥ እግራቸውም ፡ አላበጠም ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ መንግሥታትንና ፡ አሕዛብን ፡ ከፍለኽ ፡ ሰጠኻቸው ፤ የሐሴቦንን ፡ ንጉሥ ፡ የሴዎንን ፡ ምድር ፥ የባሳንንም ፡ ንጉሥ ፡ የዐግን ፡ ምድር ፡ ወረሱ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ እንደሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ አበዛኽ ፤ ይገቡና ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደተናገርኽላቸውም ፡ ምድር ፡ አገባኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ልጆቹም ፡ ገብተው ፡ ምድሩን ፡ ወረሱ ፥ የምድሩን ፡ ሰዎች ፡ ከነዓናውያንን ፡ በፊታቸው ፡ አዋረድኽ ፤ የሚወዱትንም ፡ ነገር ፡ ያደረጉባቸው ፡ ዘንድ ፡ እነርሱንና ፡ ነገሥታታቸውን ፡ የምድሩንም ፡ አሕዛብ ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ምሽጎቹንም ፡ ከተማዎች ፡ የሰባውንም ፡ ምድር ፡ ወሰዱ ፤ መልካሙን ፡ ነገር ፡ የሞሉትን ፡ ቤቶች ፥ የተማሱትንም ፡ ጕድጓዶች ፥ ወይኖቹንና ፡ ወይራዎቹን ፡ ብዙዎቹንም ፡ የፍሬ ፡ ዛፎች ፡ ወረሱ ፤ በሉም ፥ ጠገቡም ፥ ወፈሩም ፥ በታላቅ ፡ በጎነትኽም ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንቢተኞች ፡ ነበሩ ፥ ዐመፀብኽም ፥ ሕግኽንም ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ጣሉት ፤ ወዳንተም ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ የመሰከሩባቸውን ፡ ነቢያትኽን ፡ ገደሉ ፥ እጅግም ፡ አስቈጡኽ ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ፥ አስጨነቋቸውም ፤ በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ ጮኹ ፥ ከሰማይም ፡ ሰማኻቸው ፤ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳኗቸውን ፡ ታዳጊዎችን ፡ ሰጠኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ባረፉም ፡ ጊዜ ፡ ተመልሰው ፡ በፊትኽ ፡ ክፉ ፡ አደረጉ ፤ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ተውኻቸው ፥ ገዟቸውም ፤ ተመልሰውም ፡ ወዳንተ ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ ከሰማይ ፡ ሰማኻቸው ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ ታደግኻቸው ፤

ነሐ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ወደ ፡ ሕግኽም ፡ ትመልሳቸው ፡ ዘንድ ፡ አስመሰከርኽባቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ታበዩ ፥ ትእዛዝኽንም ፡ አልሰሙም ፥ ሰውም ፡ ባደረገው ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ የሚኖርበትን ፡ ፍርድኽን ፡ ተላለፉ ፤ ትከሻቸውንም ፡ ሰጡ ፥ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ፥ አልሰሙምም ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብዙ ፡ ዓመታት ፡ ታገሥኻቸው ፥ በነቢያትኽም ፡ እጅ ፡ በመንፈስኽ ፡ መሰከርኽባቸው ፤ አላደመጡም ፥ ስለዚህም ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ሰጠኻቸው ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ቸርና ፡ መሓሪ ፡ አምላክ ፡ ነኽና ፥ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፡ ፈጽመኽ ፡ አላጠፋኻቸውም ፥ አልተውኻቸውምም ።

ነሐ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ አኹንም ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፡ ታላቅና ፡ ኀያል ፡

የተፈራኸውም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከአሶር ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእኛና ፡ በነገሥታታችን ፡ በአለቃዎቻችንም ፡ በካህናታችንም ፡ በነቢያታችንም ፡ በአባቶቻችንም ፡ በሕዝብኽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የደረሰው ፡ መከራ ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ጥቂት ፡ መስሎ ፡ አይታይኽ ።

ነሐ. ፥ 9 ፥ 33 ፤ በደረሰብንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፥ አንተ ፡ እውነት ፡ አድርገኻልና ፥ እኛም ፡ ኀጢአት ፡ አድርገናል ።

ነሐ. ፥ 9 ፥ 34 ፤ ነገሥታታችንም ፡ አለቃዎቻችንም ፡ ካህናታችንም ፡ አባቶቻችንም ፡ ሕግኽን ፡ አልጠበቁም ፥ የመሰከርኽባቸውንም ፡ ትእዛዝኽንና ፡ ምስክርኽን ፡ አልሰሙኽም ።

ነሐ. ፥ 9 ፥ 35 ፤ በመንግሥታቸውም ፡ በሰጠኻቸውም ፡ ታላቅ ፡ በጎነትኽ ፥ በፊታቸውም ፡ በሰጠኸው ፡ በሰፊው ፡ ምድር ፡ አላመለኩኽም ፥ ከክፉም ፡ ሥራቸው ፡ አልተመለሱም ።

ነሐ. ፥ 9 ፥ 36 ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፤ ፍሬዋንና ፡ በረከቷን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችን ፡ በሰጠኻት ፡ ምድር ፥ እንሆ ፥ በርሷ ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፥

ነሐ. ፥ 9 ፥ 37 ፤ ስለ ፡ ኀጢአታችንም ፡ ለሾምኽብን ፡ ነገሥታት ፡ በረከቷን ፡ ታበዛለች ፤ ሰውነታችንንም ፡ ይገዛሉ ፥ በእንስሳዎቻችንም ፡ የሚወዱትን ፡ ያደርጋሉ ፥ እኛም ፡ በጽኑ ፡ መከራ ፡ ላይ ፡ ነን ።

ነሐ. ፥ 9 ፥ 38 ፤ ስለዚህም ፡ ኹሉ ፡ የታመነውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገን ፡ እንጽፋለን ፤ አለቃዎቻችንም ፡ ሌዋውያናችንም ፡ ካህናታችንም ፡ ያትሙበታል ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ነሐ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ ያተሙትም ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የሐካልያ ፡ ልጅ ፡ ሐቴርሰታ ፡ ነሐምያ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ ሴዴቅያስ ፥ ሰራያ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ዐዛርያስ ፥ ኤርምያስ ፥ ፋስኮር ፥ አማርያ ፥ መልክያ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 4-5 ፤ ሐጡስ ፥ ሰበንያ ፥ መሉክ ፥ ካሪም ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ ሜሪሞት ፥ ዐብድዩ ፥ ዳንኤል ፥ ጌንቶን ፥ ባሮክ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 7-8 ፤ ሜሱላም ፥ አብያ ፥ ሚያሚን ፥ መዓዝያ ፥ ቤልጋል ፥ ሸማያ ፤ እነዚህ ፡ ካህናት ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ ሌዋውያኑም ፤ የአዛንያ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ ከኤንሐዳድ ፡ ልጆች ፡ ቢንዊ ፥ ቀድምኤል ፤

ነሐ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ ሰባንያ ፥ ሆዲያ ፥ ቆሊጣስ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ ፈልያ ፥ ሐናን ፥ ሚካ ፥ ረአብ ፥ ሐሻብያ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ 13 ፤ ዘኩር ፥ ሰራብያ ፥ ሰበንያ ፥ ሆዲያ ፥ ባኒ ፥ ብኒኑ ።

ነሐ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ የሕዝቡ ፡ አለቃዎች ፤ ፋሮስ ፥ ፈሐት ፡ ሞዐብ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ ዔላም ፥ ዛቱዕ ፥ ባኒ ፥ ቡኒ ፥ ዓዝጋድ ፥ ቤባይ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 16 ፤ 17 ፤ አዶንያስ ፥ በጉዋይ ፥ ዓዲን ፥ ዐጤር ፥ ሕዝቅያስ ፥

ነሐ. ፥ 10 ፥ 18 ፤ ዓዙር ፥ ሆዲያ ፥ ሐሱም ፥ ቤሳይ ፥

ነሐ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ሐሪፍ ፡ ዐናቶት ፡ ኖባይ ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ መግጺዓስ ፡ ሜሱላም ፡ ኤዚር ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ሜሴዜቤል ፡ ሳዶቅ ፡ ያዱአ ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ፈላጥያ ፡ ሐናን ፡ ዐናያ ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ሆሴዕ ፡ ሐናንያ ፡ ዐሱብ ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ 25 ፤ አሎኤስ ፡ ፈልሃ ፡ ሶቤቅ ፡ ሬሁም ፡ ሐሰብና ፡

ነሐ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ 27 ፤ መዕሴያ ፡ አኪያ ፡ ሐናን ፡ ዐናን ፡ መሉክ ፡ ካሪም ፡ በዓና ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ካህናቱም ፡ ሌዋውያኑም ፡ በረኞቹም ፡ መዘምራንም ፡ ናታኒምም ፡ ከምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ራሳቸውን ፡ የለዩ ፡ ኹሉ ፡ ሚስቶቻቸውም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ የሚያውቁትና ፡ የሚያስተውሉትም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ወደ ፡ ታላላቆቻቸው ፡ ተጠጉ ፤

ነሐ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ባሪያ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡ በተሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ የጌታችንንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ፍርዱንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ ይጠብቁና ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ርግማንና ፡ መሐላውን ፡ አደረጉ ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ሴቶች ፡ ልጆቻችንንም ፡ ለምድር ፡ አሕዛብ ፡ አንሰጥም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ለልጆቻችን ፡ አንወስድም ፤

ነሐ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ የምድርን ፡ አሕዛብ ፡ ሸቀጥና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እኽል ፡ ሊገበዩ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ቢያመጡ ፡ በሰንበት ፡ ወይም ፡ በተቀደሰው ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ አንገዛም ፤ የሰባተኛውንም ፡ ዓመት ፡ ፍሬና ፡ ዕዳን ፡ ማስከፈል ፡ እንተዋለን ፡ ብለው ፡ ማሉ ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ 33 ፤ ስለአምላካችንም ፡ ቤት ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ገጽ ፡ ኅብስትም ፡ ዘወትርም ፡ በሰንበትና ፡ በመባቻ ፡ ስለ ፡ ማቅረብ ፡ ስለእኽሉ ፡ ቍርባንና ፡ ስለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ስለ ፡ በዓላትም ፡ ስለ ፡ ተቀደሱትም ፡ ነገሮች ፡ ለእስራኤልም ፡ ስለሚያስተሰርየው ፡ ስለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ስለአምላካችንም ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በየዓመቱ ፡ የሰቅል ፡ ሢሶ ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዝ ፡ በራሳችን ፡ ላይ ፡ አደረግን ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ እኛም ፡ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑ ፡ ሕዝቡም ፡ እንደአባቶቻችን ፡ ቤቶች ፡ በተወሰነ ፡ ጊዜ ፡ በየዓመቱ ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ አምጥተን ፡ በሕጉ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ይቃጠል ፡ ዘንድ ፡ ስለዕንጨት ፡ ቍርባን ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣልን ፤

ነሐ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ በየዓመቱም ፡ የመሬታችንን ፡ በኩራት ፡ የኹሉ ፡ ዐይነት ፡ ዛፍ ፡ የፍሬ ፡ ኹሉ ፡ በኩራት ፡ ኹሉ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥

ነሐ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ በሕጉም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የልጆቻችንና ፡ የእንስሳዎቻችንን ፡ በኩራት ፥ የበሬዎቻችንንና ፡ የበጎቻችንን ፡ በኩራት ፡ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ ወደሚያገለግሉት ፡ ካህናት ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥

ነሐ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ የእኽላችንንም ፡ በኩራት ፥ የእጅ ፡ ማንሣታችንን ፡ ቍርባን ፥ የዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ፍሬ ፥ ወይኑንና ፡ ዘይቱንም ፡ ወደ ፡ ካህናቱ ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ ጓዳዎች ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ከከተማዎቻችን ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ ይቀበላሉና ፡ የመሬታችንን ፡ ዓሥራት ፡ ወደ ፡ ሌዋውያን ፡ እናመጣ ፡ ዘንድ ፡ ማልን ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ ሌዋውያኑም ፡ ዓሥራቱን ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ የአሮን ፡ ልጅ ፡ ካህኑ ፡ ከሌዋውያን ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ ሌዋውያኑም ፡ የዓሥራቱን ፡ ዓሥራት ፡ ወደአምላካችን ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጓዳዎች ፡ ወደዕቃ ፡ ቤት ፡ ያምጡት ።

ነሐ. ፡ 10 ፡ 39 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የሌዊ ፡ ልጆችም ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ የማንሣት ፡ ቍርባንን ፡ የመቅደሱ ፡ ዕቃዎችና ፡ የሚያገለግሉት ፡ ካህናት ፡ በረኞቹና ፡ መዘምራኑ ፡ ወዳሉባቸው ፡ ጓዳዎች ፡ ያግቡት ፤ እንዲሁም ፡ የአምላካችንን ፡ ቤት ፡ ከቶ ፡ አንተውም ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፡ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ የሕዝቡም ፡ አለቃዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ፤ ከቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ከዐሥሩ ፡ ክፍል ፡ አንዱ ፡ በቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ በኢየሩሳሌም ፥ ዘጠኙም ፡ በሌላዎች ፡ ከተማዎች ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ሕዝቡም ፡ በፈቃዳቸው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለመቀመጥ ፡ የወደዱትን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ባረኩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡት ፡ የአገሩ ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ ካህናቱም ፡ ሌዋውያኑም ፡ ናታኒምም ፡ የሰሎሞንም ፡ ባሪያዎች ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየርስታቸውና ፡ በየከተማቸው ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ተቀመጡ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ከይሁዳና ፡ ከብንያምም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ። ከይሁዳ ፡ ልጆች ፤ ከፋሬስ ፡ ልጆች ፡ የመላልኤል ፡ ልጅ ፡ የሰፋጥያስ ፡ ልጅ ፡ የአማርያ ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የዖዝያ ፡ ልጅ ፡ ዐታያ (250) ፤

ነሐ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የሴሎናዊውም ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የዮያሪብ ፡ ልጅ ፡ የዓዳያ ፡ ልጅ ፡ የዖዛያ ፡ ልጅ ፡ የኮልሖዜ ፡ ልጅ ፡ የባሮክ ፡ ልጅ ፡ መዕሴያ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡት ፡ የፋሬስ ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስምንት ፡ ጽኑዓን ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፤ የየሻያ ፡ ልጅ ፡ የኢቲኤል ፡ ልጅ ፡ የመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ የቆላያ ፡ ልጅ ፡ የፈዳያ ፡ ልጅ ፡ የዮእድ ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ ሰሉ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ጌቤና ፡ ሳላይ ፡ ዘጠኝ ፡ መቶም ፡ ኻያ ፡ ስምንት ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ አለቃቸውም ፡ የዝክሪ ፡ ልጅ ፡ ኢዮኤል ፡ ነበረ ፤ የሐስኑአም ፡ ልጅ ፡ ይሁዳ ፡ በከተማው ፡ ላይ ፡ ኹለተኛ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ከካህናቱ ፤ የዮያሪብ ፡ ልጅ ፡ ዮዳዔ ፥ ያኪን ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ የአኪጦብ ፡ ልጅ ፡ የመራዮት ፡ ልጅ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጅ ፡ የሜሱላም ፡ ልጅ ፡ የኪልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ የቤቱንም ፡ ሥራ ፡ የሠሩ ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ኹለት ፤ የመልክያ ፡ ልጅ ፡ የፋስኮር ፡ ልጅ ፡ የዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ የአማሲ ፡ ልጅ ፡ የፈላልያ ፡ ልጅ ፡ የይሮሐም ፡ ልጅ ፡ ዓዳያ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ወንድሞቹም ፡ የአባቶቹ ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ኹለት ፤ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ የምሺሌሞት ፡ ልጅ ፡ የአሕዛይ ፡ ልጅ ፡ የዔዝርኤል ፡ ልጅ ፡ ዐማስያ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ስምንት ፡ ጽኑዓን ፡ ኀያላን ፤ አለቃቸውም ፡ የሐግዶሊም ፡ ልጅ ፡

---

250 ዕብ. ፥ ዐታያህ ።

ዘብድኤል ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ከሌዋውያንም ፤ የቡኒ ፡ ልጅ ፡ የዐሳብያ ፡ ልጅ ፡ የዐዝሪቃም ፡ ልጅ ፡ የዐሱብ ፡ ልጅ ፡ ሻማያ ፤

ነሐ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በሜዳ ፡ በነበረው ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ የሌዋውያን ፡ አለቃዎች ፡ ሳባታይና ፡ የዛባት ፤

ነሐ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ በጸሎትም ፡ ጊዜ ፡ ምስጋናን ፡ የሚቀነቅኑ ፡ አለቃው ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ የዘብዲ ፡ ልጅ ፡ የሚካ ፡ ልጅ ፡ መታንያ ፥ በወንድሞቹም ፡ መካከል ፡ ኹለተኛ ፡ የነበረ ፡ በቅበቃር ፥ የኤዶታምም ፡ ልጅ ፡ የጋላል ፡ ልጅ ፡ የሳሙስ ፡ ልጅ ፡ ዐብድያ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ በቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ የነበሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ሹሉ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ አራት ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ በሮቹንም ፡ የሚጠብቁ ፡ በረኞቹ ፥ ዐቁብና ፡ ጤልሞን ፡ ወንድሞቻቸውም ፥ መቶ ፡ ሰባ ፡ ኹለት ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ከእስራኤልም ፡ የቀሩት ፡ ከካህናትና ፡ ከሌዋውያንም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየርስታቸው ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ሹሉ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ናታኒምም ፡ በዖፌል ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፤ ሲሐና ፡ ጊሽጳ ፡ በናታኒም ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ከነበሩ ፡ መዘምራን ፡ ከአሣፍ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ የሚካ ፡ ልጅ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የሐሸብያ ፡ ልጅ ፡ የባኒ ፡ ልጅ ፡ ዖዚ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሌዋውያን ፡ አለቃ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ስለ ፡ እነርሱም ፡ የንጉሥ ፡ ትእዛዝ ፡ ነበረ ፤ የመዘምራኑም ፡ ሥርዐት ፡ ለየዕለቱ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ከይሁዳም ፡ ልጅ ፡ ከዛራ ፡ ወገን ፡ የሜሴዜቤል ፡ ልጅ ፡ ፈታያ ፥ ስለሕዝቡ ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ስለ ፡ መንደሮቹና ፡ ስለ ፡ ርሾቻቸው ፤ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዐያሌዎች ፡ በቂርያትአርባቅና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዲቦንና ፡ በመንደሮቿም ፥ በይቀብጽኤልና ፡ በመንደሮቿም ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ 27 ፤ በኢያሱ ፥ በሞላዳ ፥ በቤትጳሌጥ ፥ በሐጸርሹዓል ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ በቤርሳቤሕና ፡ በመንደሮቿ ፥ በጺቅላግ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ በምኮናና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዐይንሪሞን ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ በጾርዓ ፥ በየርሙት ፥ በዛኖዋ ፡ በዓዶላም ፡ በመንደሮቻቸውም ፥ በለኪሶና ፡ በዕርሻዎቿ ፥ በዓዜቃና ፡ በመንደሮቿ ፡ ተቀመጡ ። እንዲሁ ፡ ከቤርሳቤሕ ፡ ዠምሮ ፡ እስከሄኖም ፡ ሸለቆ ፡ ድረስ ፡ ሰፈሩ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ የብንያምም ፡ ልጆች ፡ ከጌባ ፡ ዠምሮ ፡ በማክማስ ፥ በጋያ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ በቤቴልና ፡ በመንደሮቿ ፥ በዐናቶት ፥ በኖብ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ 34 ፤ በሐናንያ ፥ በሐጾር ፥ በራማ ፥ በጊቴም ፥ በሐዲድ ፥

ነሐ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ በስቦይም ፥ በንበላት ፥ በሎድ ፥ በኦኖ ፥ በጌሐራሺም ፡ ተቀመጡ ።

ነሐ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ በይሁዳም ፡ ከነበሩ ፡ ሌዋውያን ፡ ዐያሌ ፡ ክፍሎች ፡ ወደ ፡ ብንያም ፡ ኾኑ ።

መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፡ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ከሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ከዘሩባቤልና ፡ ከኢያሱ ፡ ጋራ ፡ የወጡት ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ እነዚህ ፡ ነበሩ ፤

ነሐ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ሰራያ ፡ ኤርምያስ ፡ ዕዝራ ፡ አማርያ ፡

ነሐ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ መሉክ ፡ ሐጡስ ፡ ሴኬንያ ፡ ሬሁም ፡ ሜሪሞት ፡

ነሐ. ፡ 12 ፡ 4-5 ፤ አዶ ፡ ጌንቶን ፡ አብያ ፡ ሚያሚን ፡

ነሐ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ መዓድያ ፡ ቢልጋ ፡ ሽማያ ፡ ዮያሪብ ፡ ዮዳዔ ፡

ነሐ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ሰሉ ([251]) ፡ ዐሞቅ ([252]) ፡ ኬልቅያስ ([253]) ፡ ዮዳዔ ፤ እነዚህ ፡ በኢያሱ ፡ ዘመን ፡ የካህናቱና ፡ የወንድሞቻቸው ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ሌዋውያኑም ፤ ኢያሱ ፡ ቢንዊ ፡ ቀድምኤል ፡ ሰራብያ ፡ ይሁዳ ፡ ከወንድሞቹም ፡ ጋራ ፡ በመዘምራን ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ መታንያ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ወንድሞቻቸውም ፡ በቅቡቅያና ፡ ዑኒ ፡ በየሰሞናቸው ፡ በአንጻራቸው ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ኢያሱም ፡ ዮአቂምን ([254]) ፡ ወለደ ፥ ዮአቂምም ፡ ኤልያሴብን ፡ ወለደ ፥ ኤልያሴብም ፡ ዮአዳን ፡ ወለደ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ዮአዳም ፡ ዮናታንን ፡ ወለደ ፥ ዮናታንም ፡ ያዱአን ፡ ወለደ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በዮአቂምም ፡ ዘመን ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እነዚህ ፡ ካህናቱ ፡ ነበሩ ፤ ከሰራያ ፡ ምራያ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ከኤርምያስ ፡ ሐናንያ ፥ ከዕዝራ ፡ ሜሱላም ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ከአማርያ ፡ ይሆሐናን ፥ ከመሉኪ ፡ ዮናታን ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ከሰበንያ ፡ ዮሴፍ ፥ ከካሪም ፡ ዓድና ፥ ከመራዮት ፡ ሔልቃይ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ከአዶ ፡ ዘካርያስ ፥ ከጌንቶን ፡ ሜሱላም ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ከአብያ ፡ ዚክሪ ፥ ከሚያሚን ([255]) ፡ ሞዐድያ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ፈልጣይ ፥ ከቢልጋ ፡ ሳሙስ ፥ ከሽማያ ፡ ዮናታን ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ከዮያሪብ ፡ መትናይ ፥ ከዮዳዔ ፡ ዖዚ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ከሳላይ ፡ ቃላይ ፥ ከዐሞቅ ፡ ዔቤር ፥

---

251 ዕብ. ፥ ሰሉ ፡ (የተሰላ ፥ የተለካ) ።
252 ዕብ. ፥ ዐሞቅ ፡ (ዕመቅ • ጥልቀት ፣ ጕድጓድ) ።
253 ዕብ. ፥ ኂልቂያህ ፡ (የጌታ ፡ ክፍል) ።
254 ዕብ. ፥ ዮያቂም ፡ (ያቀውም ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ያቆማል) ።
255 ዕብ. ፥ ሚንያሚን ፡ (እምየማን • ከቀኝ) ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ከኬልቅያስ ፡ ሐሸብያ ፡ ከዮዳዔ ፡ ናትናኤል ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ከሌዋውያኑም ፡ በኤልያሴብና ፡ በዮአዳ ፡ በዮሐናንና ፡ በያዱአ ፡ ዘመን ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ ተጻፉ ፤ ካህናቱም ፡ በፋርሳዊው ፡ በዳርዮስ ፡ መንግሥት ፡ ዘመን ፡ ተጻፉ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ የሌዊ ፡ ልጆች ፡ የአባቶች ፡ ቤቶች ፡ አለቃዎች ፡ እስከኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ እስከዮሐናን ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጻፉ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ የሌዋውያኑም ፡ አለቃዎች ፤ ሐሸብያ ፡ ሰራብያ ፡ የቀድምኤልም ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ትእዛዝ ፡ በየሰሞናቸው ፡ በወንድሞቻቸው ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ያከብሩና ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ መታንያ ፡ በቅቡቅያ ፡ ዐብድዩ ([256]) ፡ ሜሱላም ፡ ጤልሞን ፡ ዐቁብ ፡ በበሮች ፡ አጠገብ ፡ የሚገኙትን ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ለመጠበቅ ፡ በረኞች ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ እነዚህ ፡ በኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ ልጅ ፡ በዮአቂም ፡ በአለቃውም ፡ በነሐምያ ፡ በጸሓፊውም ፡ በካህኑ ፡ በዕዝራ ፡ ዘመን ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ በቀደሱ ፡ ጊዜ ፡ ቅዳሴውን ፡ በደስታና ፡ በምስጋና ፡ በመዝሙርም ፡ በጸናጽልም ፡ በበገናም ፡ በመሰንቆም ፡ ለማድረግ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጧቸው ፡ ዘንድ ፡ ሌዋውያኑን ፡ በየስፍራቸው ፡ ሹሉ ፡ ፈለጉ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ 29 ፤ መዘምራኑም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ መንደሮች ፡ ሠርተው ፡ ነበርና ፥ የመዘምራኑ ፡ ልጆች ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያና ፡ ከነጦፋውያን ፡ መንደሮች ፥ ከቤትገልገላም ፥ ከጌባና ፡ ከዓዝሞት ፡ ዕርሻዎች ፡ ተሰበሰቡ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 30 ፤ ካህናቱና ፡ ሌዋውያኑም ፡ ራሳቸውን ፡ አነጹ ፤ ሕዝቡንም ፡ በሮቹንም ፡ ቅጥሩንም ፡ አነጹ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 31 ፤ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ላይ ፡ አወጣኋቸው ፤ አመስጋኞቹንም ፡ በኹለት ፡ ታላላቅ ፡ ተርታ ፡ አቆምኋቸው ፤ አንዱም ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ወደጕድፍ ፡ መጣያው ፡ በር ፡ ኼደ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 32 ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ሆሻያ ፥ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ እኩሌታ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 33 ፤ ዐዛርያስ ፥ ዕዝራ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 34 ፤ ሜሱላም ፥ ይሁዳ ፥ ብንያም ፥ ሸማያ ፥ ኤርምያስ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 35 ፤ መለከትም ፡ ይዘው ፡ ከካህናቱ ፡ ልጆች ፡ ዐያሌዎች ፥ የአሣፍም ፡ ልጅ ፡ የዘኩር ፡ ልጅ ፡ የሚካያ ፡ ልጅ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ የዮናታን ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስ ፥

ነሐ. ፡ 12 ፡ 36 ፤ ወንድሞቹም ፡ ሸማያ ፥ ዔዝርኤል ፥ ሚላላይ ፥ ጊላላይ ፥ መዓይ ፥ ናትናኤል ፥ ይሁዳ ፥ ዐናኒ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሰው ፡ የዳዊትን ፡ የዜማውን ፡ ዕቃ ፡ ይዘው ፡ ኼዱ ፤ ጸሓፊውም ፡ ዕዝራ ፡ በፊታቸው ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 37 ፤ በምንጭም ፡ በር ፡ አቅንተው ፡ ኼዱ ፤ በዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ደረጃ ፥ በቅጥሩም ፡ መውጫ ፥ ከዳዊትም ፡ ቤት ፡ በላይ ፡ እስከውሃው ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ኼዱ ።

ነሐ. ፡ 12 ፡ 38 ፤ ኹለተኛውም ፡ የአመስጋኞቹ ፡ ተርታ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ኼደ ፤ እኔና ፡ የሕዝቡም ፡ እኩሌታ ፡ በስተኋላቸው ፡ ነበርን ፤ በቅጥሩም ፡ ላይ ፥ በእቶኑ ፡ ግንብ ፡ በላይ ፡ እስከ ፡ ሰፊው ፡ ቅጥር ፡ ድረስ ፥ ከኤፍሬምም ፡ በር ፡

256 ዕብ. ፥ ያባድያህ ፡ (ዐብደ ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

በላይ ፥

ነሐ. ፥ 12 ፥ 39 ፤ በአሮጌው ፡ በርና ፡ በዓሣ ፡ በር ፡ በሐናንኤልም ፡ ግንብ ፥ በሃሜአ ፡ ግንብ ፡ እስከበጎች ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ኼዱ ፤ በዘበኞችም ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 40 ፤ እንዲሁ ፡ ኹለቱ ፡ የአመስጋኞች ፡ ተርታዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቆሙ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ እኔና ፡ የአለቃዎች ፡ እኩሌታ ፥

ነሐ. ፥ 12 ፥ 41 ፤ ካህናቱም ፡ ኤልያቄም ፥ መዕሴያ ፥ ሚንያሚን ፥ ሚካያ ፥ ኤልዮዔናይ ፥

ነሐ. ፥ 12 ፥ 42 ፤ ዘካርያስ ፥ ሐናንያ ፡ መለከት ፡
ይዘው ፥ መዕሴያ ፥ ሸማያ ፥ አልዓዛር ፥ ዖዚ ፥ ይሆሐናን ፥ መልክያ ፥ ዔላም ፥ ኤጽር ፡ ቆምን ። መዘምራኑም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ዘመሩ ፥ አለቃቸውም ፡ ይዝረሕያ ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 43 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አሠኝቷቸዋልና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ትልቅ ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፥ ደስም ፡ አላቸው ፤ ሴቶቹና ፡ ልጆቹም ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤ የኢየሩሳሌምም ፡ ደስታ ፡ ከሩቅ ፡ ተሰማ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 44 ፤ ይሁዳም ፡ በአገልጋዮቹ ፡ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ ደስ ፡ ስላላቸው ፥ የካህናቱንና ፡ የሌዋውያኑን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ከከተማዎች ፡ ዕርሻዎች ፡ ያከማቹ ፡ ዘንድ ፡ ለእጅ ፡ ማንሣት ፡ ቀሪባንና ፡ ለበኵራት ፡ ለዓሥራትም ፡ በየዕቃ ፡ ቤቶቹ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰዎች ፡ ተሾሙ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 45 ፤ እነርሱም ፡ መዘምራኑና ፡ በረኞቹም ፡ የአምላካቸውን ፡ ሥርዐት ፡ የመንጻታቸውንም ፡ ሥርዐት ፡ እንደ ፡ ዳዊትና ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ እንደ ፡ ሰሎሞን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠበቁ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 46 ፤ አስቀድሞም ፡ በዳዊትና ፡ በአሣፍ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዜማ ፡ ለማመስገንና ፡ ለማክበር ፡ የመዘምራን ፡ አለቃዎች ፡ ነበሩ ።

ነሐ. ፥ 12 ፥ 47 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በዘሩባቤልና ፡ በነሐምያ ፡ ዘመን ፡ ለመዘምራኑና ፡ ለበረኞቹ ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸውን ፡ በየዕለቱ ፡ ይሰጡ ፡ ነበር ፤ የተቀደሰውንም ፡ ነገር ፡ ለሌዋውያን ፡ ሰጡ ፥ ሌዋውያኑም ፡ ከተቀደሰው ፡ ነገር ፡ ለአሮን ፡ ልጆች ፡ ሰጡ ።

_____መጽሐፈ ፡ ነሐምያ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። _____

ነሐ. ፥ 13 ፥ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሙሴን ፡ መጽሐፍ ፡ በሕዝቡ ፡ ጐሮ ፡ አነበቡ ፤ አሞናውያንና ፡ ሞዐባውያንም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዳይገቡ ፡ የሚል ፡ በዚያ ፡ ተገኘ ።

ነሐ. ፥ 13 ፥ 2 ፤ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በእንጀራና ፡ በውሃ ፡ ስላልተቀበሏቸውና ፡ ይረግማቸው ፡ ዘንድ ፡ በለዓምን ፡ ስለ ፡ ገዙባቸው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካችን ፡ ርግማኑን ፡ ወደ ፡ በረከት ፡ መለሰው ።

ነሐ. ፥ 13 ፥ 3 ፤ ሕጉንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ድብልቁን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከእስራኤል ፡ ለዩ ።

ነሐ. ፥ 13 ፥ 4 ፤ ከዚህም ፡ አስቀድሞ ፡ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ ጓዳዎች ፡ ላይ ፡ ተሾሞ ፡ የነበረው ፡ ካህኑ ፡ ኤልያሴብ ፡ ከጦብያ ፡ ጋራ ፡ ተወዳጅቶ ፥

ነሐ. ፥ 13 ፥ 5 ፤ ለሌዋውያን ፥ ለመዘምራን ፥ ለበረኞቹ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ የተሰጣቸውን ፡ የእኽሉን ፡ ቀሪባንና ፡ ዕጣኑን ፥ ዕቃዎቹንም ፥ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ ዓሥራት ፥ ለካህናቱም ፡ የኾነውን ፡ የማንሣት ፡ ቀሪባን ፡ አስቀድሞ ፡ ያስቀመጡበትን ፡ ታላቁን ፡ ጓዳ ፡ አዘጋጅቶለት ፡ ነበር ።

ነሐ. ፥ 13 ፥ 6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በአርጤክስስ ፡ በሠላሳ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡

ኼጄ ፡ ነበርና ፥ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አልነበርኹም ። ከጥቂት ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ የንጉሡን ፡ ፈቃድ ፡ ለመንኹ ፤

ነሐ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጣኹ ፤ ኤልያሴብም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ለጦብያ ፡ ጓዳውን ፡ በማዘጋጀት ፡ ያደረገውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አስተዋልኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ እጅግም ፡ አስከፋኝ ፤ የጦብያንም ፡ የቤቱን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ከጓዳ ፡ ወደ ፡ ውጪ ፡ ጣልኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ጓዳዎቹንም ፡ እንዲያነጹ ፡ አዘዝኹ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቤት ፡ ዕቃዎች ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ መልሼ ፡ በዚያ ፡ አገባኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ለሌዋውያንም ፡ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ እንዳልተሰጠ ፥ የሚያገለግሉትም ፡ ሌዋውያንና ፡ መዘምራን ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ዕርሻው ፡ እንደ ፡ ኼዱ ፡ ተመለከትኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተተወ ፧ ብዬ ፡ ከአለቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹ ። ሰበሰብኋቸውም ፥ በየስፍራቸውም ፡ አቆምኋቸው ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ይሁዳም ፡ ኹሉ ፡ የእኽሉንና ፡ የወይኑን ፡ የዘይቱንም ፡ ዓሥራት ፡ ወደዕቃ ፡ ቤቶች ፡ አመጡ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ በዕቃ ፡ ቤቶችም ፡ ላይ ፡ ካህኑን ፡ ሰሌምያን ፥ ጸሓፊውንም ፡ ሳዶቅን ፥ ከሌዋውያኑም ፡ ፈዳያን ፡ ሾምኹ ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የመታንያ ፡ ልጅ ፡ የዘኩር ፡ ልጅ ፡ ሐናን ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ የታመኑ ፡ ኾነው ፡ ተገኙ ፥ ሥራቸውም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ማከፋፈል ፡ ነበረ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ዐስበኝ ፤ ለአምላኬም ፡ ቤት ፡ ያደረግኹትን ፡ ወረታዬን ፡ አታጥፋ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በይሁዳ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ የወይን ፡ መጥመቂያን ፡ የሚረግጡትን ፥ ነዶም ፡ የሚከመሩትን ፥ የወይኑን ፡ ጠጅና ፡ የወይኑን ፡ ዘለላ ፡ በለሱንም ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ዐይነት ፡ ሸክም ፡ በአህያዎች ፡ ላይ ፡ የሚጭኑትን ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የሚያስገቡትን ፡ አየኹ ፤ ገበያ ፡ ባደረጉበትም ፡ ቀን ፡ አስመሰከርኹባቸው ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ በርሷ ፡ የተቀመጡ ፡ የጢሮስ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ ዓሣዎችን ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ ዐይነት ፡ ሸቀጥ ፡ አምጥተው ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ይሸጡ ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ከይሁዳም ፡ ታላላቆች ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹና ፦ ይህ ፡ የምታደርጉት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ የሰንበትንስ ፡ ቀን ፡ ታረክሳላችኹን ፧

ነሐ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ አባቶቻችኹ ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ አልነበረምን ፧ አምላካችንስ ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእኛና ፡ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አምጥቶ ፡ አልነበረምን ፧ እናንተም ፡ ሰንበትን ፡ በማርከሳችኹ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መዓትን ፡ ትጨምራላችኹ ፡ አልኋቸው ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከሰንበት ፡ በፊት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ ድንግዝግዝታ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ በሮቻ ፡ እንዲዘጉ ፥ ሰንበትም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ እንዳይከፈቱ ፡ አዘዝኹ ። በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክም ፡ እንዳይገባ ፡ ከብላቴናዎቼ ፡ በዐያሌዎቹ ፡ በሮቻን ፡ አስጠበቅኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ዐድረው ፥ ገበያ ፡ አድርገው ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ እኔም ፡ አስመሰከርኹባቸውና ፦ በቅጥሩ ፡ ውጭ ፡ ለምን ፡ ታድራላችኹ ፧ እንደ ፡ ገና ፡ ብታደርጉት ፡ እጆቼን ፡ አነሣባችኋለኹ ፡ አልኋቸው ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አልመጡም ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ሌዋውያኑንም ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲያነጹ ፥ መጥተውም ፡ በሮቹን ፡ እንዲጠብቁ ፥ የሰንበትንም ፡ ቀን ፡ እንዲቀድሱ ፡ ነገርኋቸው ። አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ዐስበኝ ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ ራራልኝ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ የአዛጦንና ፡ የዐሞንን ፡ የሞዐብንም ፡ ሴቶች ፡ ያገቡትን ፡ አይሁድ ፡ አየኹ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ከልጆቻቸውም ፡ እኩሌታዎቹ ፡ በአዛጦን ፡ ቋንቋ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ በአይሁድም ፡ ቋንቋ ፡ መናገር ፡ አያውቁም ፡ ነበር ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ተከራከርኹ ፥ ረገምኋቸውም ፤ ከነርሱም ፡ ዐያሌዎቹን ፡ መታኹ ፥ ጠጕራቸውንም ፡ ነጨኹ ፥ እንዲህም ፡ ብዬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አማልኋቸው ። ሴቶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ ለወንዶች ፡ ልጆቻቸው ፡ አትስጡ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ለእናንተና ፡ ለልጆቻችኹ ፡ አትውሰዱ ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ኀጢአት ፡ አድርጎ ፡ የለምን ፧ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ንጉሥ ፡ አልነበረም ፥ በአምላኩም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነበረ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አንግሦት ፡ ነበር ፤ ርሱንም ፡ እንኳ ፡ እንግዳዎች ፡ ሴቶች ፡ አሳቱት ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ በእውኑ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ እንሠራ ፥ እንግዳዎችንም ፡ ሴቶች ፡ በማግባት ፡ አምላካችን ፡ እንበድል ፡ ዘንድ ፡ እናንተን ፡ እንስማ ፧

ነሐ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ከዋነኛውም ፡ ካህን ፡ ከኤልያሴብ ፡ ልጅ ፡ ከዮአዳ ፡ ልጆች ፡ አንዱ ፡ ለሖሮናዊው ፡ ለሰንባላጥ ፡ ዐማች ፡ ነበረ ፤ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አባረርኹት ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ክህነትን ፡ የክህነትንና ፡ የሌዋውያንንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ስላፈረሱ ፡ ዐስባቸው ።

ነሐ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ ከእንግዳ ፡ ነገርም ፡ ኹሉ ፡ አነጻኋቸው ፤ ለካህናቱና ፡ ለሌዋውያኑም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየሰሞናቸው ፥

ነሐ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ በየጊዜያቸውም ፡ ለዕንጨት ፡ ቍርባን ፡ ለበኵራቱም ፡ ሥርዐት ፡ አደረግኹ ። አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በመልካም ፡ ዐስበኝ ❖

መጽሐፈ ፡ አስቴር ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

አስ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በአርጤክስስም ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ ይህም ፡ አርጤክስስ ፡ ከህንድ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድረስ ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ሰባት ፡ አገሮች ፡ ላይ ፡ ነገሠ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ በነበረው ፡ በመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥

አስ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ለባለሟሎቹና ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ ኹሉ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፤ የፋርስና ፡ የሜዶን ፡ ታላላቆች ፡ ኹሉ ፥ የየአገሩ ፡ ዐዛውንትና ፡ ሹማምት ፥ በፊቱ ፡ ነበሩ ፤

አስ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ የከበረውንም ፡ የመንግሥቱን ፡ ሀብት ፥ የታላቁንም ፡ የግርማዊነቱን ፡ ክብር ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ አሳያቸው ።

አስ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ይህም ፡ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ለተገኙት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከታላቁ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታናሹ ፡ ድረስ ፡ ንጉሡ ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ አደባባይ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ነጭ ፥ አረንጓዴ ፥ ሰማያዊም ፡ መጋረጃዎች ፡ ከጥሩ ፡ በፍታና ፡ ከሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ በተሠራ ፡ ገመድ ፥ በብር ፡ ቀለበትና ፡ በእብነ ፡ በረድ ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ ተዘርግተው ፡ ነበር ፤ ዐልጋዎቹም ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ተሠርተው ፡ በቀይና ፡ በነጭ ፡ በብጫና ፡ በጥቍር ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ ወለል ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ መጠጡም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ በወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ይታደል ፡ ነበር ፤ የንጉሡም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ንጉሡ ፡ ለጋስነት ፡ መጠን ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበረ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ፈቃድ ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱ ፡ አዛዦች ፡ ኹሉ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፥ መጠጡ ፡ እንደ ፡ ወግ ፡ አልነበረም ።

አስ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ንግሥቲቱም ፡ አስጢን ([257]) ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ለሴቶች ፡ ግብዣ ፡ አደረገች ።

አስ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ 11 ፤ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጥቶ ፡ ደስ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፥ ንግሥቲቱ ፡ አስጢን ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረችና ፡ ውበቷ ፡ ለአሕዛብና ፡ ለአለቃዎች ፡ እንዲታይ ፡ የመንግሥቱን ፡ ዘውድ ፡ ጭነው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ ያመጧት ፡ ዘንድ ፡ በፊቱ ፡ የሚያገለግሉትን ፡ ሰባቱን ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ምሁማንን ፥ ባዛንን ፥ ሐርቦናን ፥ ገበታን ፥ ዘቶልታን ፥ ዜታርን ፥ ከርከስን ፡ አዘዛቸው ።

አስ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንግሥቲቱ ፡ አስጢን ፡ በጃን ፡ ደረባዎቹ ፡ እጅ ፡ በላከው ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለች ፤ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፥ በቀጣውም ፡ ተናደደ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ሕግንና ፡ ፍርድን ፡ በሚያውቁ ፥ ኹሉ ፡ ፊት ፡ የንጉሡ ፡ ወግ ፡ እንዲህ ፡ ነበረና ፡ ንጉሡ ፡ የዘመኑን ፡ ነገር ፡ የሚያውቁትን ፡ ጥበበኞችን ፥

አስ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ በመንግሥቱም ፡ ቀዳሚዎች ፡ ኾነው ፡ የሚቀመጡ ፡ የንጉሡ ፡ ባለሟሎች ፡ ሰባቱ ፡ የፋርስና ፡

---

257 ፋር. ፥ ቫሽቲ ።

የሜዶን ፡ መሳፍንት ፡ አርቄስዮስ ([258]) ፥ ሼታር ፥ አድማታ ፥ ተርሺሽ ፥ ሜሬስ ፥ ማሌሴዓር ([259]) ፥ ምሙካን ፡ በአጠገቡ ፡ ሳሉ ፦—

አስ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ በጃን ፡ ደረባዎች ፡ እጅ ፡ የተላከባትን ፡ የንጉሡን ፡ የአርጤክስስን ፡ ትእዛዝ ፡ ስላላደረገች ፥ በንግሥቲቱ ፡ በአስጢን ፡ ላይ ፥ እንደ ፡ ሕጉ ፥ የምናደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

አስ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ምሙካንም ፡ በንጉሡና ፡ በዐዛውንቱ ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦— ንግሥቲቱ ፡ አስጢን ፡ ዐዛውንቱን ፡ ሹሉና ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ አገር ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ በድላለች ፡ እንጂ ፡ ንጉሡን ፡ ብቻ ፡ የበደለች ፡ አይደለችም ።

አስ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ይህ ፡ የንግሥቲቱ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ሴቶች ፡ ሹሉ ፡ ይደርሳልና ፦— ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ ንግሥቲቱ ፡ አስጢን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፥ ርሷ ፡ ግን ፡ አልገባችም ፡ ተብሎ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ባሎቻቸው ፡ በዐይናቸው ፡ ዘንድ ፡ የተናቁ ፡ ይኾናሉ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ ዛሬም ፡ የንግሥቲቱን ፡ ነገር ፡ የሰሙት ፡ የፋርስና ፡ የሜዶን ፡ ወይዛዝር ፡ እንዲህና ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ ዐዛውንት ፡ ሹሉ ፡ ይናገራሉ ፥ ንቀትና ፡ ቍጣም ፡ ይበዛል ።

አስ. ፥ 1 ፥ 19 ፤ ንጉሡም ፡ ቢፈቅድ ፥ አስጢን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አርጤክስስ ፡ ፊት ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳትገባ ፡ የንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ከርሱ ፡ ይውጣ ፥ እንዳይፈርስም ፡ በፋርስና ፡ በሜዶን ፡ ሕግ ፡ ይጻፍ ፤ ንጉሡም ፡ ንግሥትነቷን ፡ ከርሷ ፡ ለተሻለችው ፡ ለሌላዪቱ ፡ ይስጥ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 20 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ በሰፊው ፡ መንግሥቱ ፡ ሹሉ ፡ በተነገረ ፡ ጊዜ ፡ ሴቶች ፡ ሹሉ ፡ ባሎቻቸውን ፡ ታላቁንም ፡ ታናሹንም ፡ ያከብራሉ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 21 ፤ ይህም ፡ ምክር ፡ ንጉሡንና ፡ ዐዛውንቱን ፡ ደስ ፡ አሠኛቸው ፤ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ምሙካን ፡ ቃል ፡ አደረገ ።

አስ. ፥ 1 ፥ 22 ፤ ሰው ፡ ሹሉ ፡ በቤቱ ፡ አለቃ ፡ ይኹን ፤ በሕዝቡም ፡ ቋንቋ ፡ ይናገር ፡ ብሎ ፡ ለአገሩ ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ለሕዝቡም ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ቋንቋው ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ወደንጉሡ ፡ አገሮች ፡ ሹሉ ፡ ሰደደ ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

አስ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ የንጉሡ ፡ የአርጤክስስ ፡ ቍጣ ፡ በበረደ ፡ ጊዜ ፡ አስጢንና ፡ ያደረገችውን ፡ የፈረደባትንም ፡ ነገር ፡ ዐሰበ ።

አስ. ፥ 2 ፥ 2 ፤ ንጉሡንም ፡ የሚያገለግሉ ፡ ብላቴናዎች ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦— መልከ ፡ መልካም ፡ የኾኑ ፡ ደናግል ፡ ለንጉሡ ፡ ይፈለጉለት ፤

አስ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ ሴቶችን ፡ ከሚጠብቅ ፡ ከንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ከሄጌ ፡ እጅ ፡ በታች ፡ እንዲያደርጓቸው ፥ መልከ ፡ መልካሞቹን ፡ ደናግል ፡ ሹሉ ፡ ወደሱሳ ፡ ግንብ ፡ ወደ ፡ ሴቶች ፡ ቤት ፡ ይሰበስቧቸው ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ በመንግሥቱ ፡ አገሮች ፡ ሹሉ ፡ ሹማምቶችን ፡ ያኑር ፤ ቅባትና ፡ የሚያስፈልጋቸውም ፡ ይሰጣቸው ፤

አስ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ ንጉሡንም ፡ ደስ ፡ የምታሠኝ ፡ ቈንጆ ፡ በአስጢን ፡ ስፍራ ፡ ትንገሥ ። ይህም ፡ ነገር ፡ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ፥ እንዲሁም ፡ አደረገ ።

አስ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ የቂስ ፡ ልጅ ፡ የሰሜኢ ፡ ልጅ ፡ የኢያዕር ፡ ልጅ ፡ መርዶክዮስ ፡ የሚባል ፡ ብንያማዊ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ነበረ ።

---

258 ዕብ. ፥ ካርሼና ።

259 ዕብ. ፥ ማርስና ።

አስ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከማረካቸው ፡ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከኢኮንያን ፡ ጋራ ፡ ከተማረኩት ፡ ምርኮኞች ፡ ጋራ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የተማረከ ፡ ነበረ ።

አስ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ አባትና ፡ እናትም ፡ አልነበራትምና ፥ የአጎቱ ፡ ልጅ ፡ ሀደሳ ፡ የተባለችውን ፡ አስቴርን ፡ አሳድጎ ፡ ነበር ፤ ቈንጕዩቱም ፡ የተዋበችና ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረች ፤ አባቷና ፡ እናቷም ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ መርዶክዮስ ፡ እንደ ፡ ልጁ ፡ አድርጎ ፡ ወስዷት ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝና ፡ ዐዋጅ ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፥ ብዙም ፡ ቈነጕዥት ፡ ወደሱሳ ፡ ግንብ ፡ ወደሄጌ ፡ እጅ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፥ አስቴር ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወደሴቶች ፡ ጠባቂው ፡ ወደ ፡ ሄጌ ፡ ተወሰደች ።

አስ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ቈንጕዩቱም ፡ ደስ ፡ አሠኘችው ፥ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ አገኘች ፤ ቅባቷንም ፡ ድርሻዋንም ፡ ከንጉሡም ፡ ቤት ፡ ልታገኝ ፡ የሚገባትን ፡ ሰባት ፡ ደንገጥሮች ፡ ፈጥኖ ፡ ሰጣት ፤ ርሷንና ፡ ደንገጥሮቿንም ፡ በሴቶች ፡ ቤት ፡ በተመረጠ ፡ ስፍራ ፡ አኖረ ።

አስ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ይህንም ፡ እንዳትናገር ፡ መርዶክዮስ ፡ አዟት ፡ ነበርና ፥ አስቴር ፡ ሕዝቧንና ፡ ወገኗን ፡ አልተናገረችም ።

አስ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ መርዶክዮስም ፡ የአስቴርን ፡ ደኅንነትና ፡ የሚኾንላትን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በሴቶች ፡ ቤት ፡ ወለል ፡ ትይዩ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ የመንጻታቸውም ፡ ወራት ፡ ስድስት ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ በከርቤ ፡ ዘይት ፥ ስድስት ፡ ወርም ፡ በጣፋጭ ፡ ሽቱና ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ በሚያነጻ ፡ ነገር ፡ ይፈጸም ፡ ነበርና ፥ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ወግ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ እንዲሁ ፡ ከተደረገላት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ አርጤክስስ ፡ ለመግባት ፡ የአንዳንዲቱ ፡ ቈንጕ ፡ ተራ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥

አስ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ በዚህ ፡ ወግ ፡ ቈንጕዩቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ትገባ ፡ ነበር ፤ ከሴቶች ፡ ቤት ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ለመውሰድ ፡ የምትሻውን ፡ ኹሉ ፡ ይሰጧት ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ማታም ፡ ትገባ ፡ ነበር ፥ ሲነጋም ፡ ተመልሳ ፡ ወደኹለተኛው ፡ ሴቶች ፡ ቤት ፡ ቁባቶችን ፡ ወደሚጠብቅ ፡ ወደንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ወደ ፡ ጋይ ፡ ትመጣ ፡ ነበር ፤ ንጉሡም ፡ ያልፈለጋት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በስሟም ፡ ያልተጠራች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አትገባም ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፡ የመርዶክዮስ ፡ አጎት ፡ የአቢካኢል ፡ ልጅ ፡ የአስቴር ፡ ተራ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ የሴቶች ፡ ጠባቂው ፡ የንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ሄጌ ፡ ከሚለው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አልፈለገችም ፡ ነበር ፤ አስቴርም ፡ በሚያይዋት ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ሞገስ ፡ አግኝታ ፡ ነበርና ።

አስ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ አርጤክስስም ፡ በነገሠ ፡ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ አዳር ፡ በሚባለው ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ አስቴር ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ተወሰደች ።

አስ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ንጉሡም ፡ ከሴቶች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አስቴርን ፡ ወደደ ፥ በዐይኑም ፡ ከደናግል ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ሞገስንና ፡ መወደድን ፡ አገኘች ፤ የመንግሥቱንም ፡ ዘውድ ፡ በራሷ ፡ ላይ ፡ አደረገ ፥ በአስጢንም ፡ ፋንታ ፡ አነገሣት ።

አስ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ስለ ፡ አስቴር ፡ ለባለሟሎቹና ፡ ለአገልጋዮቹ ፡ ኹሉ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፤ ለአገሮቹም ፡ ኹሉ ፡ ይቅርታ ፡ አደረገ ፥ እንደ ፡ ንጉሡም ፡ ለጋስነት ፡ መጠን ፡ ስጦታ ፡ ሰጠ ።

አስ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ደናግሉም ፡ ዳግመኛ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ መርዶክዮስ ፡ በንጉሡ ፡ በር ፡ ይቀመጥ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ አስቴርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳደገችበት ፡ ጊዜ ፡ የመርዶክዮስን ፡ ትእዛዝ ፡ ታደርግ ፡ ነበርና ፥ መርዶክዮስ ፡ እንዳዘዛት ፡ አስቴር ፡ ወገኗንና ፡ ሕዝቧን ፡ አልተናገረችም ።

አስ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ መርዶክዮስ ፡ በንጉሡ ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ደጁን ፡ ከሚጠብቁት ፡ ከንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ኹለቱ ፡ ገበታና ፡ ታራ ፡ ተቈጡ ፥ እጃቸውንም ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ ላይ ፡ ያነሡ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ።

አስ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ነገሩም ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ተገለጠ ፥ ርሱም ፡ ለንግሥቲቱ ፡ ለአስቴር ፡ ነገራት ፤ አስቴርም ፡ በመርዶክዮስ ፡ ስም ፡ ለንጉሡ ፡ ነገረች ።

አስ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ነገሩም ፡ ተመረመረ ፥ እንዲህም ፡ ኾኖ ፡ ተገኘ ፥ ኹለቱም ፡ በዛፍ ፡ ላይ ፡ ተሰቀሉ ፤ ያም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ በታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጻፈ ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

አስ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ ነገር ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ የአጋጋዊውን ፡ የሐመዳቱን ፡ ልጅ ፡ ሐማን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፥ አከበረውም ፥ ወንበሩንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከነበሩት ፡ ዐዛውንት ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ አደረገለት ።

አስ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እንዲሁ ፡ አዘ ፡ ነበርና ፥ በንጉሡ ፡ በር ፡ ያሉት ፡ የንጉሡ ፡ ባሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ ተደፍተው ፡ ለሐማ ፡ ይሰግዱ ፡ ነበር ። መርዶክዮስ ፡ ግን ፡ አልተደፋም ፥ አልሰገደለትም ።

አስ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በንጉሡም ፡ በር ፡ ያሉት ፡ የንጉሡ ፡ ባሪያዎች ፡ መርዶክዮስን ፦ የንጉሡን ፡ ትእዛዝ ፡ ለምን ፡ ትተላለፋለኽ ፧ አሉት ።

አስ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ይህንም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እየተናገሩ ፡ ርሱ ፡ ባልሰማቸው ፡ ጊዜ ፡ አይሁዳዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነግሯቸው ፡ ነበርና ፥ የመርዶክዮስ ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ለሐማ ፡ ነገሩት ።

አስ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ሐማም ፡ መርዶክዮስ ፡ እንዳልተደፋለት ፡ እንዳልሰገደለትም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ።

አስ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ የመርዶክዮስን ፡ ወገን ፡ ነግረውት ፡ ነበርና ፥ በመርዶክዮስ ፡ ብቻ ፡ እጁን ፡ ይጭን ፡ ዘንድ ፡ በዐይኑ ፡ ተናቀ ፤ ሐማም ፡ በአርጤክስስ ፡ መንግሥት ፡ ኹሉ ፡ የነበሩትን ፡ የመርዶክዮስን ፡ ሕዝብ ፡ አይሁድን ፡ ኹሉ ፡ ሊያጠፋ ፡ ፈለገ ።

አስ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በንጉሡም ፡ በአርጤክስስ ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ከመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከኒሳን ፡ ዠምሮ ፡ በየዕለቱና ፡ በየወሩ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ እስከ ፡ አዳር ፡ ድረስ ፡ በሐማ ፡ ፊት ፡ ፉር ፡ የተባለውን ፡ ዕጣ ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ሐማም ፡ ንጉሡን ፡ አርጤክስስን ፦ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በመንግሥትኽ ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ ተበትነዋል ፤ ሕጋቸውም ፡ ከሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሕግ ፡ የተለየ ፡ ነው ፥ የንጉሡንም ፡ ሕግ ፡ አይጠብቁም ፤ ንጉሡም ፡ ይተዋቸው ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ።

አስ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ንጉሡም ፡ ቢፈቅድ ፡ እንዲጠፉ ፡ ይጻፍ ፤ እኔም ፡ ወደንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ያገቡት ፡ ዘንድ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ መክሊት ፡ ብር ፡ የንጉሡን ፡ ሥራ ፡ በሚሠሩት ፡ እጅ ፡ እመዝናለኹ ፡ አለው ።

አስ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፡ ቀለበቱን ፡ ከእጁ ፡ አወለቀ ፥ ለአይሁድም ፡ ጠላት ፡ ለአጋጋዊው ፡ ለሐመዳቱ ፡ ልጅ ፡ ለሐማ ፡ ሰጠው ።

አስ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ ሐማን ፦ ደስ ፡ የሚያሠኝኽን ፡ ነገር ፡ ታደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ ብሩም ፡ ሕዝቡም ፡ ለአንተ ፡ ተሰጥቶኻል ፡ አለው ።

አስ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ በመዠመሪያውም ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ የንጉሡ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ተጠሩ ፤ ከህንድ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድረስ ፡ ወዳሉ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ ሰባት ፡ አገሮች ፥ በያገሩ ፡ ወዳሉ ፡

ሹማምትና ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ገዢዎች ፡ እንደ ፡ ቋንቋቸው ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ ቃል ፡ ሐማ ፡ እንዳዘዘ ፡ ተጻፈ ፥ በንጉሡም ፡ ቀለበት ፡ ታተመ ።

አስ. ፥ 3 ፥ 13 ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ በአዳር ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አይሁድን ፡ ኹሉ ፥ ልጆችንና ፡ ሽማግሌዎችን ፥ ሕፃናትንና ፡ ሴቶችን ፥ ባንድ ፡ ቀን ፡ ያጠፉና ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፥ ይደመስሱም ፡ ዘንድ ፥ ምርኳቸውንም ፡ ይዘርፉ ፡ ዘንድ ፡ ደብዳቤዎች ፡ በመልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ወደንጉሡ ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ ተላኩ ።

አስ. ፥ 3 ፥ 14 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ይዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ የደብዳቤው ፡ ቅጅ ፡ በያገሩ ፡ ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ታወጀ ።

አስ. ፥ 3 ፥ 15 ፤ መልእክተኞቹም ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ እየቸኰሉ ፡ ኼዱ ፥ ዐዋጁም ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ተነገረ ። ንጉሡና ፡ ሐማ ፡ ሊጠጡ ፡ ተቀመጡ ፤ ከተማዪቱ ፡ ሱሳ ፡ ግን ፡ ተደናገጠች ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

አስ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ መርዶክዮስም ፡ የተደረገውን ፡ ኹሉ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ ማቅም ፡ ለበሰ ፡ ዐመድም ፡ ነሰነሰ ፥ ወደከተማዪቱም ፡ መካከል ፡ ወጣ ፥ ታላቅም ፡ የመረረ ፡ ጩኸት ፡ ጮኸ ።

አስ. ፥ 4 ፥ 2 ፤ ማቅም ፡ ለብሶ ፡ በንጉሥ ፡ በር ፡ መግባት ፡ አይገባም ፡ ነበርና ፥ እስከንጉሡ ፡ በር ፡ አቅራቢያ ፡ መጣ ።

አስ. ፥ 4 ፥ 3 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝና ፡ ዐዋጅ ፡ በደረሰበት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ሐዘንና ፡ ጾም ፡ ልቅሶና ፡ ዋይታም ፡ ኾነ ፡ ብዙዎችም ፡ ማቅና ፡ ዐመድ ፡ አነጠፉ ።

አስ. ፥ 4 ፥ 4 ፤ የአስቴርም ፡ ደንገጥሮቿና ፡ ጃን ፡ ደረባዎቿ ፡ መጥተው ፡ ነገሯት ፥ ንግሥቲቱም ፡ እጅግ ፡ ዐዘነች ፤ ማቁንም ፡ ለውጦ ፡ ልብስ ፡ ይለብስ ፡ ዘንድ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ሰደደችለት ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አልተቀበለም ።

አስ. ፥ 4 ፥ 5 ፤ አስቴርም ፡ ያገለግላት ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ ያቆመውን ፡ አክራትዮስን ([260]) ፡ ጠራች ፥ ርሱም ፡ ከጃን ፡ ደረባዎች ፡ አንዱ ፡ ነበረ ፤ ርሷም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምንና ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያስታውቃት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መርዶክዮስ ፡ እንዲኼድ ፡ አዘዘችው ።

አስ. ፥ 4 ፥ 6 ፤ አክራትዮስም ፡ በንጉሥ ፡ በር ፡ ፊት ፡ ወደነበረችው ፡ ወደከተማዪቱ ፡ አደባባይ ፡ ወደ ፡ መርዶክዮስ ፡ ወጣ ።

አስ. ፥ 4 ፥ 7 ፤ መርዶክዮስም ፡ የተደረገውን ፡ ኹሉ ፥ አይሁድንም ፡ ለማጥፋት ፡ ሐማ ፡ በንጉሡ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ይመዝን ፡ ዘንድ ፡ የተናገረውን ፡ የብሩን ፡ ቍጥር ፡ ነገረው ።

አስ. ፥ 4 ፥ 8 ፤ ለአስቴርም ፡ እንዲያሳያት ፡ ለመጥፋታቸው ፡ በሱሳ ፡ የተነገረውን ፡ የዐዋጁን ፡ ጽሕፈት ፡ ቅጅ ፡ ሰጠው ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ገብታ ፡ ስለ ፡ ሕዝቧ ፡ ትለምነውና ፡ ትማልደው ፡ ዘንድ ፡ እንዲነግራትና ፡ እንዲያዛት ፡ ነገረው ።

አስ. ፥ 4 ፥ 9 ፤ አክራትዮስም ፡ መጥቶ ፡ የመርዶክዮስን ፡ ቃል ፡ ለአስቴር ፡ ነገራት ።

አስ. ፥ 4 ፥ 10 ፤ አስቴርም ፡ አክራትዮስን ፡ ተናገረችው ፥ ለመርዶክዮስም ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ ሰጠችው ፦

አስ. ፥ 4 ፥ 11 ፤ የንጉሡ ፡ ባሪያዎችና ፡ በአገሮችም ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ቢኾን ፡ ሳይጠራ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደውስጠኛው ፡ ወለል ፡ የሚገባ ፡ ኹሉ ፥ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ የወርቁን ፡ ዘንግ ፡ ካልዘረጋለት ፡ በቀር ፥ ርሱ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ሕግ ፡ እንዳለ ፡ ያውቃሉ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ለመግባት ፡

---

260 ፋር. ፡ ሀታክ ።

ይህን ፡ ሠላሳውን ፡ ቀን ፡ አልተጠራኹም ።

አስ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ አክራትዮስም ፡ የአስቴርን ፡ ቃል ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ነገረው ።

አስ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ መርዶክዮስም ፡ አክራትዮስን ፦ ኺድና ፡ ለአስቴር ፡ እንዲህ ፡ በላት ፡
አለው ፦ አንቺ ፦ በንጉሥ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ኾንኹ ፡ ከአይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ እድናለኹ ፡ ብለሽ ፡ በልብሽ ፡ አታስቢ ።

አስ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ቸል ፡ ብትዪ ፡ ዕረፍትና ፡ መዳን ፡ ለአይሁድ ፡ ከሌላ ፡ ስፍራ ፡
ይኾንላቸዋል ፥ አንቺና ፡ የአባትሽ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ትጠፋላችኹ ፤ ደግሞስ ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ የመጣሽው ፡ እንደዚህ ፡
ላለው ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፧

አስ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ አስቴርም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ እንዲመልስ ፡ አዘዘችው ።

አስ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ኼደኽ ፡ በሱሳ ፡ ያሉትን ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ሰብስብ ፥ ለኔም ፡ ጹሙ ፤ ሦስት ፡ ቀን ፡ ሌሊቱንና ፡
ቀኑን ፡ አትብሉም ፥ አትጠጡም ፤ እኔና ፡ ደንገጥሮቼ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ እንጾማለን ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያለሕግ ፡ ቢኾን ፡
ወደ ፡ ንጉሡ ፡ እገባለኹ ፤ ብጠፋም ፡ እጠፋለኹ ።

አስ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ መርዶክዮስም ፡ ኼዶ ፡ አስቴር ፡ እንዳዘዘችው ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።

_____መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

አስ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ አስቴር ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቷን ፡ ለብሳ ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ትይዩ ፡ በንጉሡ ፡
ቤት ፡ በውስጠኛው ፡ ወለል ፡ ቆመች ፤ ንጉሡም ፡ በቤቱ ፡ መግቢያ ፡ ትይዩ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ በንጉሡ ፡
ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ንግሥቲቱ ፡ አስቴር ፡ በወለሉ ፡ ላይ ፡ ቆማ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በዐይኑ ፡ ሞገስ ፡
አገኘች ፤ ንጉሡም ፡ በእጁ ፡ የነበረውን ፡ የወርቁን ፡ ዘንግ ፡ ለአስቴር ፡ ዘረጋላት ፤ አስቴርም ፡ ቀርባ ፡ የዘንጉን ፡ ጫፍ ፡
ነካች ።

አስ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፦ ንግሥት ፡ አስቴር ፡ ሆይ ፥ የምትለምኚኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ የምትሺውስ ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ እስከ ፡ መንግሥቴ ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ ይሰጥሻል ፡ አላት ።

አስ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ አስቴርም ፦ ለንጉሡ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፡ ቢታይ ፡ ንጉሡ ፡ ወዳዘጋጀኹለት ፡ ግብዣ ፡ ከሐማ ፡
ጋራ ፡ ዛሬ ፡ ይምጣ ፡ አለች ።

አስ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፦ አስቴር ፡ እንዳለች ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ሐማን ፡ አስቸኵሉት ፡ አለ ። ንጉሡና ፡ ሐማ ፡
አስቴር ፡ ወዳዘጋጀችው ፡ ግብዣ ፡ መጡ ።

አስ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ንጉሡም ፡ በወይኑ ፡ ጠጅ ፡ ግብዣ ፡ ሳለ ፡ አስቴርን ፦ የምትሺው ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ ይሰጥሻል ፤ ልመናሽስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እስከ ፡ መንግሥቴ ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ ይደረግልሻል ፡ አላት ።

አስ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ አስቴርም ፡ መልሳ ፦ ልመናዬና ፡ የምሻው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤

አስ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ በንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ልመናዬንም ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድና ፡ የምሻውን ፡
ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሡ ፡ ደስ ፡ ቢያሠኘው ፥ ንጉሡና ፡ ሐማ ፡ ወደማዘጋጀላቸው ፡ ግብዣ ፡ ይምጡ ፤ እንደ ፡
ንጉሡም ፡ ነገር ፡ ነገ ፡ አደርጋለኹ ፡ አለች ።

አስ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሐማ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በልቡም ፡ ተደስቶ ፡ ወጣ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መርዶክዮስ ፡
በንጉሡ ፡ በር ፡ ያለመነሣትና ፡ ያለመናወጥ ፡ ተቀምጦ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሐማ ፡ በመርዶክዮስ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ።

አስ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ሐማ ፡ ግን ፡ ታግሦ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፤ ልኮም ፡ ወዳጆቹንና ፡ ሚስቱን ፡ ዞሳራን ፡ አስጠራ ።

አስ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ሐማም ፡ የሀብቱን ፡ ክብርና ፡ የልጆቹን ፡ ብዛት ፥ ንጉሡም ፡ ያከበረበትን ፡ ክብር ፡ ኹሉ ፥ በንጉሡም ፡ ዐዛውንትና ፡ ባሪያዎች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዳደረገው ፡ አጫወታቸው ።

አስ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ሐማም ፦ ንግሥቲቱ ፡ አስቴር ፡ ወዳዘጋጀችው ፡ ግብዣ ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ማንንም ፡ አልጠራችም ፤ ደግሞ ፡ ነገ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ተጠርቻለኹ ።

አስ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አይሁዳዊው ፡ መርዶክዮስ ፡ በንጉሡ ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ካየኹ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አይጠቅምም ፡ አለ ።

አስ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ሚስቱም ፡ ዞሳራና ፡ ወዳጆቹ ፡ ኹሉ ፦ ቁመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ግንድ ፡ ይደረግ ፥ ነገም ፡ መርዶክዮስ ፡ ይሰቀልበት ፡ ዘንድ ፡ ለንጉሡ ፡ ተናገር ፤ ደስም ፡ ብሎኻ ፡ ከንጉሡ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ግብዣው ፡ ግባ ፡ አሉት ። ነገራቸውም ፡ ሐማን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ፥ ግንዱንም ፡ አስደረገ ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

አስ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ እንቅልፍ ፡ ከንጉሡ ፡ ሸሸ ፤ የዘመኑንም ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፥ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ተነበበ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ደጁንም ፡ ከሚጠብቁት ፡ ከንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ኹለቱ ፡ ገበታና ፡ ታራ ፡ እጃቸውን ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ ላይ ፡ ያነሡ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ፈለጉ ፥ መርዶክዮስ ፡ እንደ ፡ ነገረው ፡ ተጽፎ ፡ ተገኘ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፦ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ምን ፡ ክብርና ፡ በጎነት ፡ ተደረገለት ፧ አለ ። ንጉሡንም ፡ የሚያገለግሉ ፡ ብላቴናዎች ። ምንም ፡ አልተደረገለትም ፡ አሉት ።

አስ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፦ በአዳራሹ ፡ ማን ፡ አለ ፧ አለ ። ሐማም ፡ ባዘጋጀው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ መርዶክዮስን ፡ ለማሰቀል ፡ ለንጉሡ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወደውጭው ፡ አዳራሽ ፡ ገብቶ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ የንጉሡም ፡ ብላቴናዎች ፦ እንሆ ፥ ሐማ ፡ በአዳራሹ ፡ ቆሟል ፡ አሉት ። ንጉሡም ፦ ይግባ ፡ አለ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ሐማም ፡ ገባ ፤ ንጉሡም ፦ ንጉሡ ፡ ሊያከብረው ፡ ለሚወደው ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይደረግለታል ፧ አለው ። ሐማም ፡ በልቡ ። ንጉሡ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ማንን ፡ ያከብር ፡ ዘንድ ፡ ይወዳል ፧ አለ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ሐማም ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ንጉሡ ፡ ያከብረው ፡ ዘንድ ፡ ለሚወደው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግ ፤

አስ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ንጉሡ ፡ የለበሰው ፡ የክብር ፡ ልብስ ፥ ንጉሡም ፡ የተቀመጠበት ፡ ፈረስ ፡ ይምጣለት ፥ የንጉሡም ፡ ዘውድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይደረግ ፤

አስ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ልብሱንና ፡ ፈረሱንም ፡ ከንጉሡ ፡ ዐዛውንት ፡ በዋነኛው ፡ እጅ ፡ ያስረክቡት ፤ ንጉሡም ፡ ያከብረው ፡ ዘንድ ፡ የሚወደውን ፡ ሰው ፡ ያልብሱት ፤ በፈረሱም ፡ ላይ ፡ አስቀምጠውት ፡ በከተማዪቱ ፡ አደባባይ ፡ ያሳልፉት ፤ በፊቱም ፦ ንጉሡ ፡ ያከብረው ፡ ዘንድ ፡ ለሚወደው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግለታል ፡ ተብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ይነገር ።

አስ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፡ ሐማን ፦ ፍጠን ፥ እንደ ፡ ተናገርኸውም ፡ ልብሱንና ፡ ፈረሱን ፡ ውሰድ ፤ በንጉሡም ፡ በር ፡ ለሚቀመጠው ፡ አይሁዳዊ ፡ ለመርዶክዮስ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግለት ፤ ከተናገርኸውም ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አይቅር ፡ አለው ።

አስ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ሐማም ፡ ልብሱንና ፡ ፈረሱን ፡ ወሰደ ፥ መርዶክዮስንም ፡ አለበሰው ፥ በፈረሱም ፡ ላይ ፡ አስቀመጠው ፥ በከተማዉ፡ም ፡ አደባባይ ፡ በፊቱ ፡ አሳለፈው ። በፊቱም ፦ ንጉሡ ፡ ያከብረው ፡ ዘንድ ፡ ለሚወደው ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይደረግለታል ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ ነገረ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ መርዶክዮስም ፡ ወደንጉሡ ፡ በር ፡ ተመለሰ ። ሐማ ፡ ግን ፡ ዐዝኖና ፡ ራሱን ፡ ተከናንቦ ፡ ቸኮሎ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

አስ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ሐማም ፡ ለሚስቱ ፡ ለዘሳራና ፡ ለወዳጆቹ ፡ ኹሉ ፡ ያገኘውን ፡ ኹሉ ፡ አጫወታቸው ። ጥበበኞቹና ፡ ሚስቱ ፡ ዘሳራም ፦ በፊቱ ፡ መውደቅ ፡ የዠመርኽለት ፡ መርዶክዮስ ፡ ከአይሁድ ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በፊቱ ፡ ፈጽሞ ፡ ትወድቃለኽ ፡ እንጂ ፡ አታሸንፈውም ፡ አሉት ።

አስ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ እነርሱም ፡ ሲናገሩት ፡ ሳሉ ፥ እንሆ ፥ የንጉሡ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ መጡ ፥ አስቴርም ፡ ወዳዘጋጀችው ፡ ግብዣ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ሐማን ፡ አስቸኰሉት ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

አስ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ንጉሡና ፡ ሐማም ፡ ከንግሥቲቱ ፡ ከአስቴር ፡ ጋራ ፡ ለመጠጣት ፡ መጡ ።

አስ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ በወይኑ ፡ ጠጅ ፡ ግብዣ ፡ ሳለ ፡ አስቴርን ፦ ንግሥት ፡ አስቴር ፡ ሆይ ፥ የምትለምኚኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይሰጥሻል ፤ የምትሺውስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እስከመንግሥቴ ፡ እኩሌታ ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ ይደረግልሻል ፡ አላት ።

አስ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ንግሥቲቱም ፡ አስቴር ፡ መልሳ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ንጉሡንም ፡ ደስ ፡ ቢያሠኘው ፥ ሕይወቴ ፡ በልመናዬ ፡ ሕዝቤም ፡ በመሻቴ ፡ ይሰጠኝ ፤

አስ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እኔና ፡ ሕዝቤ ፡ ለመጥፋትና ፡ ለመገደል ፡ ለመደምሰስም ፡ ተሸጠናልና ፦ ባሪያዎች ፡ ልንኾን ፡ ተሸጠን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዝም ፡ ባልኹ ፡ ነበር ፤ የኾነ ፡ ኾኖ ፡ ጠላቱ ፡ የንጉሡን ፡ ጕዳት ፡ ለማቅናት ፡ ባልቻለም ፡ ነበር ፡ አለች ።

አስ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ አርጤክስስ ፡ ንግሥቲቱን ፡ አስቴርን ፦ ይህን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ የደፈረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናገራት ።

አስ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ አስቴርም ፦ ያ ፡ ጠላትና ፡ ባለጋራ ፡ ሰው ፡ ክፉው ፡ ሐማ ፡ ነው ፡ አለች ። ሐማም ፡ በንጉሡና ፡ በንግሥቲቱ ፡ ፊት ፡ ደነገጠ ።

አስ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ንጉሡም ፡ ተቈጥቶ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ከመጠጣቱ ፡ ተነሣ ፥ ወደንጉሡም ፡ ቤት ፡ አታክልት ፡ ውስጥ ፡ ኼደ ። ሐማም ፡ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ታሰበበት ፡ አይቷልና ፥ ከንግሥቲቱ ፡ ከአስቴር ፡ ሕይወቱን ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፡ ቆመ ።

አስ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ንጉሡም ፡ ከቤቱ ፡ አታክልት ፡ ወደ ፡ ወይን ፡ ጠጁ ፡ ግብዣ ፡ ስፍራ ፡ ተመለሰ ፤ ሐማም ፡ አስቴር ፡ ባለችበት ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ነበር ። ንጉሡም ፦ ደግሞ ፡ በቤቴ ፡ በእኔ ፡ ፊት ፡ ንግሥቲቱን ፡ ይጋፋታልን ፧ አለ ። ይህም ፡ ቃል ፡ ከንጉሡ ፡ አፍ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ የሐማን ፡ ፊት ፡ ሸፈኑት ።

አስ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ካሉት ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ አንዱ ፡ ሐርቦና ፦ እንሆ ፥ ሐማ ፡ ለንጉሡ ፡ በጎ ፡ ለተናገረው ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ያሠራው ፡ ርዝመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነው ፡ ግንድ ፡ በሐማ ፡ ቤት ፡ ተተክሏል ፡ አለ ። ንጉሡም ፦ በርሱ ፡ ላይ ፡ ስቀሉት ፡ አለ ።

አስ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ሐማንም ፡ ለመርዶክዮስ ፡ ባዘጋጀው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የንጉሡ ፡ ቍጣ ፡ በረደ ።

_____መጽሐፈ ፡ አስቴር ፡ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

አስ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ንጉሡ ፡ አርጤክስስ ፡ የአይሁድን ፡ ጠላት ፡ የሐማን ፡ ቤት ፡ ለንግሥቲቱ ፡ ለአስቴር ፡ ሰጠ ። አስቴርም ፡ ለርሷ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ነግራው ፡ ነበርና ፥ መርዶክዮስ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ፊት ፡ ገባ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ከሐማ ፡ ያወለቀውን ፡ ቀለበቱን ፡ አወጣ ፥ ለመርዶክዮስም ፡ ሰጠው ። አስቴርም ፡ በሐማ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ መርዶክዮስን ፡ ሾመች ።

አስ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ አስቴርም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ተናገረች ፤ በእግሩም ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፡ እያለቀሰች ፡ የአጋጋዊውን ፡ የሐማን ፡ ክፋትና ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ የተተነኰለውን ፡ ተንኰል ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ ለመነችው ።

አስ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ንጉሡም ፡ የወርቁን ፡ ዘንግ ፡ ለአስቴር ፡ ዘረጋላት ፤ አስቴርም ፡ ተነሥታ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆመችና ፦

አስ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ ቢያሠኘው ፥ በፊቱም ፡ ሞገስ ፡ አግኝቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡ በፊቱ ፡ ቅን ፡ ቢኾን ፥ እኔም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተወድጄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አጋጋዊው ፡ የሐመዳቱ ፡ ልጅ ፡ ሐማ ፡ በንጉሡ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ያሉትን ፡ አይሁድ ፡ ለማጥፋት ፡ የጻፈው ፡ ተንኰል ፡ ይገለበጥ ፡ ዘንድ ፡ ይጻፍ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ የሚወርደውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ እችላለኹ ፧ ወይስ ፡ የዘመዶቼን ፡ ጥፋት ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ እችላለኹ ፧ አለች ።

አስ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ንጉሡም ፡ አርጤክስስ ፡ ንግሥቲቱን ፡ አስቴርንና ፡ አይሁዳዊውን ፡ መርዶክዮስን ፦ እንሆ ፥ የሐማን ፡ ቤት ፡ ለአስቴር ፡ ሰጥቻለኹ ፥ ርሱም ፡ እጆቹን ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ዘረጋ ፡ በግንድ ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በንጉሡ ፡ ስም ፡ የተጻፈና ፡ በንጉሡ ፡ ቀለበት ፡ የታተመ ፡ አይገለበጥምና ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኛችኹን ፡ በንጉሡ ፡ ስም ፡ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ጻፉ ፥ በንጉሡም ፡ ቀለበት ፡ ዐትሙ ፡ አላቸው ።

አስ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ኒሳን ፡ በተባለው ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ የንጉሡ ፡ ጸሓፊዎች ፡ ተጠሩ ፤ መርዶክዮስም ፡ ስለ ፡ አይሁድ ፡ እንዳዘዘው ፡ ሹሉ ፡ ከህንድ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ድረስ ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ሰባቱ ፡ አገሮች ፡ ላሉ ፡ ሹማምትና ፡ አለቃዎች ፡ ዐዛውንትም ፡ ለያንዳንዱም ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ጽሕፈቱ ፡ ለያንዳንዱም ፡ ሕዝብ ፡ እንደ ፡ ቋንቋው ፡ ለአይሁድም ፡ እንደ ፡ ጽሕፈታቸውና ፡ እንደ ፡ ቋንቋቸው ፡ ተጻፈ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ በንጉሡም ፡ በአርጤክስስ ፡ ስም ፡ አስጻፈው ፥ በንጉሡም ፡ ቀለበት ፡ አሳተመው ፤ ደብዳቤውንም ፡ በንጉሡ ፡ ፈረስ ፡ ቤት ፡ በተወለዱት ፥ ለንጉሡም ፡ አገልግሎት ፡ በተለዩ ፡ በፈጣን ፡ ፈረሶች ፡ በተቀመጡ ፡ መልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ሰደደው ።

አስ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ደብዳቤ ፡ በከተማዎቹ ፡ ሹሉ ፡ የሚኖሩት ፡ አይሁድ ፡ እንዲሰበሰቡ ፥ ለሕይወታቸውም ፡ እንዲቆሙ ፥ በጥል ፡ የሚነሡባቸውን ፡ የሕዝቡንና ፡ የአገሩን ፡ ሰራዊት ፡ ሹሉ ፡ ከሕፃናታቸውና ፡ ከሴቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ እንዲያጠፉና ፡ እንዲገድሉ ፡ እንዲደመስሱም ፥ ምርኳቸውንም ፡ እንዲዘርፉ ፡ ንጉሡ ፡ ፈቀደላቸው ።

አስ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ይህም ፡ አዳር ፡ በሚባለው ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ አገሮች ፡ ሹሉ ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ እንዲኾን ፡ ነው ።

አስ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ አይሁድም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ እንዲበቀሉ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ይዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ የደብዳቤው ፡ ቅጅ ፡ በያገሩ ፡ ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ ታወጀ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ለንጉሡ ፡ አገልግሎት ፡ በተለዩ ፡ በፈጣን ፡ ፈረሶች ፡ የተቀመጡት ፡ መልእክተኞች ፡ በንጉሡ ፡

ትእዛዝ ፡ ተርበትብተውና ፡ ቸኵለው ፡ ወጡ ፤ ዐዋጁም ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ተነገረ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ መርዶክዮስም ፡ በሰማያዊና ፡ በነጭ ፡ ሐር ፡ የተሠራውን ፡ የንጉሡን ፡ የክብር ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ ታላቅም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ ደፍቶ ፡ ከጥሩ ፡ በፍታና ፡ ከሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ የተሠራ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ተጐናጽፎ ፡ ከንጉሡ ፡ ፊት ፡ ወጣ ፤ የሱሳም ፡ ከተማ ፡ ደስ ፡ አላት ፥ እልልም ፡ አለች ።

አስ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ ለአይሁድም ፡ ብርሃንና ፡ ደስታ ፡ ተድላና ፡ ክብርም ፡ ኾነ ።

አስ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝና ፡ ዐዋጅ ፡ በደረሰበት ፡ አገርና ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ለአይሁድ ፡ ደስታና ፡ ተድላ ፥ የግብዣም ፡ ቀን ፡ መልካምም ፡ ቀን ፡ ኾነ ። አይሁድንም ፡ መፍራት ፡ ስለ ፡ ወደቀባቸው ፡ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አይሁድ ፡ ኾኑ ።

_____መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

አስ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ አዳር ፡ በሚባለውም ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፥ የንጉሡ ፡ ትእዛዝና ፡ ዐዋጅ ፡ ሊፈጸምበት ፡ በነበረው ፡ ቀን ፥ የአይሁድ ፡ ጠላቶች ፡ ሊሠለጥኑባቸው ፡ በነበረው ፡ ቀን ፥ አይሁድ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ነገሩ ፡ ተገለበጠ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ አይሁድም ፡ ክፋታቸውን ፡ በሚሹት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ይዘረጉ ፡ ዘንድ ፡ በንጉሡ ፡ በአርጤክስስ ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ በነበሩ ፡ ከተማዎቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተሰበሰቡ ፤ እነርሱንም ፡ መፍራት ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ነበርና ፥ እነርሱን ፡ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ አልነበረም ።

አስ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ መርዶክዮስን ፡ መፍራት ፡ በላያቸው ፡ ስለ ፡ ወደቀ ፡ በያገሩ ፡ የነበሩ ፡ ዐዛውንትና ፡ ሹማምቶች ፡ አለቃዎችም ፥ የንጉሡንም ፡ ሥራ ፡ የሚሠሩቱ ፡ ኹሉ ፡ አይሁድን ፡ አገዙ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ያ ፡ ሰው ፡ መርዶክዮስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያለ ፡ ስለ ፡ ኼደ ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ ታላቅ ፡ ኾኖ ፡ ነበርና ፥ የመርዶክዮስም ፡ ዝና ፡ በያገሩ ፡ ኹሉ ፡ ተሰምቶ ፡ ነበርና ።

አስ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ አይሁድም ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ እየመቱ ፡ ገደሏቸው ፥ አጠፏቸውም ፤ በሚጠሏቸውም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ አደረጉባቸው ።

አስ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ አይሁድም ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ያኽል ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፡ አጠፉም ።

አስ. ፡ 9 ፡ 7-8 ፤ ፈርሰኔስ ፥ ደልፎን ፥ ፋስጋ ፥ ፋረዳታ ፥

አስ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ በርያ ፥ ሰርባካ ፥ መርመሲማ ፥ ሩፋዮስ ፥ አርሳዮስ ፥ ዛቡታዮስ ፡ የሚባሉትን ፥

አስ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ የሐመዳቱን ፡ ልጅ ፡ የአይሁድን ፡ ጠላት ፡ ዐሥሩን ፡ የሐማን ፡ ልጆች ፡ ገደሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ብዝበዛው ፡ እጃቸውን ፡ አልዘረጉም ።

አስ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ የተገደሉት ፡ ሰዎች ፡ ቍጥር ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ መጣ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ንጉሡም ፡ ንግሥቲቱን ፡ አስቴርን ፦ አይሁድ ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ሰዎችንና ፡ ዐሥሩን ፡ የሐማ ፡ ልጆች ፡ ገደሉ ፡ አጠፏቸውም ፤ በቀሩትስ ፡ በንጉሡ ፡ አገሮች ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ይኾን! ፡ አኹንስ ፡ ልመናሽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይሰጥሻል ፤ ሌላስ ፡ የምትሺው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይደረጋል ፡ አላት ።

አስ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ አስቴርም ፦ ንጉሡን ፡ ደስ ፡ ቢያሠኘው ፥ በሱሳ ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድ ፡ ዛሬ ፡ እንደተደረገው ፡ ትእዛዝ ፡ ነገ ፡ ደግሞ ፡ ያድርጉ ፤ ዐሥሩም ፡ የሐማ ፡ ልጆች ፡ በግንድ ፡ ላይ ፡ ይሰቀሉ ፡ አለች ።

አስ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ንጉሡም ፡ ይህ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ዐዋጅም ፡ በሱሳ ፡ ተነገረ ፤ ዐሥሩንም ፡ የሐማን ፡

ልጆች ፡ ሰቀሉ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ በሱሳም ፡ የነበሩ ፡ አይሁድ ፡ አዳር ፡ በሚባለው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ ተሰብስበው ፡ በሱሳ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ያኽል ፡ ሰዎች ፡ ገደሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ብዝበዛው ፡ እጃቸውን ፡ አልዘረጉም ።

አስ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ የቀሩትም ፡ በንጉሡ ፡ አገር ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ ተሰብስበው ፡ ለሕይወታቸው ፡ ቆሙ ፥ ከጠላቶቻቸውም ፡ ዐረፉ ፤ ከሚጠሏቸውም ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ገደሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ብዝበዛው ፡ እጃቸውን ፡ አልዘረጉም ።

አስ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ አዳር ፡ በሚባለው ፡ ወር ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ተደረገ ፤ በዐሥራ ፡ አራተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐረፉ ፥ የግብዣና ፡ የደስታም ፡ ቀን ፡ አደረጉ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ በሱሳ ፡ የነበሩት ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛውና ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ተሰበሰቡ ፤ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐረፉ ፥ የመጠጥና ፡ የደስታም ፡ ቀን ፡ አደረጉት ።

አስ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ ስለዚህም ፡ በመንደሮችና ፡ ባልተመሸጉ ፡ ከተማዎች ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድ ፡ አዳር ፡ በሚባለው ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛውን ፡ ቀን ፡ የደስታና ፡ የመጠጥ ፡ የመልካምም ፡ ቀን ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ስጦታ ፡ የሚሰጣጡበት ፡ ቀን ፡ ያደርጉታል ።

አስ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ መርዶክዮስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ጻፈ ፥ በንጉሡም ፡ በአርጤክስስ ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ በቅርብና ፡ በሩቅ ፡ ወዳሉት ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ ላከ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ በየዓመቱም ፡ አዳር ፡ በሚባለው ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛውና ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፥

አስ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ አይሁድ ፡ ከጠላቶቻቸው ፡ ዕረፍትን ፡ ያገኙበት ፡ ቀን ፥ ወሩም ፡ ከሐዘን ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ ከልቅሶም ፡ ወደ ፡ መልካም ፡ ቀን ፡ የተለወጠበት ፡ ወር ፡ ኾኖ ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፥ የግብዣና ፡ የደስታም ፡ ቀን ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ስጦታ ፡ የሚሰጣጡበትና ፡ ለድኻዎች ፡ ስጦታ ፡ የሚሰጡበት ፡ ቀን ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።

አስ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ አይሁድም ፡ ለመሥራት ፡ የገቡመሩትን ፥ መርዶክዮስም ፡ የጻፈላቸውን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ተቀበሉት ፤

አስ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ አጋጋዊው ፡ የሐመዳቴ ፡ ልጅ ፡ የአይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ጠላት ፡ ሐማ ፡ አይሁድን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ተተንኵሎ ፡ ነበር ፤ ሊደመስሳቸውና ፡ ሊያጠፋቸውም ፡ ፉር ፡ የሚባል ፡ ዕጣ ፡ ጥሎ ፡ ነበር ።

አስ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ አስቴርም ፡ ወደንጉሡ ፡ ፊት ፡ በገባች ፡ ጊዜ ፡ በአይሁድ ፡ ላይ ፡ የተተነኰለው ፡ ክፉ ፡ ተንኰል ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እንዲመለስ ፥ ርሱና ፡ ልጆቹም ፡ በግንድ ፡ ላይ ፡ እንዲሰቀሉ ፡ በደብዳቤው ፡ አዘዘ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ስለዚህም ፡ እነዚህ ፡ ቀኖች ፡ እንደ ፡ ፉር ፡ ስም ፡ ፉሪም ፡ ተባሉ ። በዚህም ፡ ደብዳቤ ፡ ስለተጻፈው ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ስላዩትና ፡ ስላገኟቸውም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥

አስ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ 28 ፤ አይሁድ ፡ እነዚህን ፡ ኹለት ፡ ቀኖች ፡ እንደ ፡ ጽሕፈቱና ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ በየዓመቱ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ እነዚህም ፡ ቀኖች ፡ በየትውልዳቸውና ፡ በየወገናቸው ፡ በያገራቸውም ፡ በየከተማቸውም ፡ የታሰቡና ፡ የተከበሩ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፥ እነዚህም ፡ የፉሪም ፡ ቀኖች ፡ በአይሁድ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይሻሩ ፥ መታሰባቸውም ፡ ከዘራቸው ፡ እንዳይቈረጥ ፥ በራሳቸውና ፡ በዘራቸው ፡ ወደ ፡ እነርሱም ፡ በተጠጉት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እንዳይቀር ፡ ሥርዐት ፡ አድርገው ፡ ተቀበሉ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ የአቢካኢልም ፡ ልጅ ፡ ንግሥቲቱ ፡ አስቴርና ፡ አይሁዳዊው ፡ መርዶክዮስ ፡ ይህችን ፡ ስለ ፡ ፉሪም ፡ የምትናገረውን ፡ ኹለተኛዪቱን ፡ ደብዳቤ ፡ በሥልጣናቸው ፡ ኹሉ ፡ ያጸኗት ፡ ዘንድ ፡ ጻፉ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ደብዳቤዎቹንም ፡ በአርጤክስስ ፡ መንግሥት ፡ በመቶ ፡ ኻያ ፡ ሰባቱ ፡ አገሮች ፡ ወዳሉ ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ በሰላምና ፡ በእውነት ፡ ቃል ፡ ላኩ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ እነዚህንም ፡ የፉሪም ፡ ቀኖች ፥ አይሁዳዊው ፡ መርዶክዮስና ፡ ንግሥቲቱ ፡ አስቴር ፡ እንዳዘዙ ፥ ለራሳቸውና ፡ ለዘራቸውም ፡ የጾማቸውንና ፡ የልቅሷቸውን ፡ ነገር ፡ ለማክበር ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፥ በየጊዜያቸው ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ጸፉ ።

አስ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ የአስቴርም ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡ የፉሪምን ፡ ነገር ፡ አጸና ፤ በመጽሐፍም ፡ ተጻፈ ።

መጽሐፈ ፡ አስቴር ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

አስ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ንጉሡም ፡ አርጤክስስ ፡ በምድርና ፡ በባሕር ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ ግብር ፡ ጣለ ።

አስ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ የኀይሉና ፡ የብርታቱም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡም ፡ እስከ ፡ ምን ፡ ድረስ ፡ እንዳከበረው ፡ የመርዶክዮስ ፡ ክብር ፡ ታላቅነት ፥ በሜዶንና ፡ በፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

አስ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ አይሁዳዊውም ፡ መርዶክዮስ ፡ ለንጉሡ ፡ ለአርጤክስስ ፡ በማዕርግ ፡ ኹለተኛ ፡ ነበረ ፤ በአይሁድም ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፥ በብዙ ፡ ወንድሞችም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፥ ለሕዝቡም ፡ መልካምን ፡ የፈለገ ፥ ለዘሩም ፡ ኹሉ ፡ በደኅና ፡ የተናገረ ፡ ነበረ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ያዕ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ስሙ ፡ ኢዮብ ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ያም ፡ ሰው ፡ ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ነበረ ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ሰባትም ፡ ወንዶች ፡ ሦስትም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ተወልደውለት ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ሀብቱም ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ በጎች ፥ ሦስት ፡ ሺሕም ፡ ግመሎች ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፥ ዐምስት ፡ መቶም ፡ እንስት ፡ አህያዎች ፡ ነበረ ፥ እጅግ ፡ ብዙም ፡ ባሪያዎች ፡ ነበሩት ፤ ያም ፡ ሰው ፡ በምሥራቅ ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነበረ ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቹም ፡ ኼደው ፡ በየተራ ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ቤት ፡ ግብዣ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ፤ ሦስቱ ፡ እኅቶቻቸውም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይበሉና ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ እነርሱ ፡ ልከው ፡ ይጠሯቸው ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ የግብዣውም ፡ ቀኖች ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮብ ፦ ምናልባት ፡ ልጆቼ ፡ በድለው ፥ እግዚአብሔርንም ፡ በልባቸው ፡ ሰድበው ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ይልክና ፡ ይቀድሳቸው ፡ ነበር ፤ ኢዮብም ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ እንደ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ኹሉ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረበ ። እንዲሁ ፡ ኢዮብ ፡ ኹልጊዜ ፥ ያደርግ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የአምላክ ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ መጡ ፥ ሰይጣንም ፡ ደግሞ ፡ በመካከላቸው ፡ መጣ ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ሰይጣንም ፦ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ዞርኺት ፥ በርሷም ፡ ተመላለስኹ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መለሰ ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ በእውኑ ፡ ባሪያዬን ፡ ኢዮብን ፡ ተመለከትኸውን ፧ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ የለም ፡ አለው ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ሰይጣንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፦ በእውኑ ፡ ኢዮብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ በከንቱ ፡ ነውን ፧

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ርሱንና ፡ ቤቱን ፡ በዙሪያውም ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፡ አላጠርኽለትምን ፧ የእጁን ፡ ሥራ ፡ ባርከኽለታል ፥ ከብቱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በዝቷል ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅኽን ፡ ዘርግተኽ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ዳብስ ፤ በእውነት ፡ በፊትኽ ፡ ይሰድብኻል ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ እንሆ ፥ ለርሱ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርሱ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ አትዘርጋ ፡ አለው ። ሰይጣንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የኢዮብ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ቤት ፡ ይበሉና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ መልክተኛም ፡ ወደ ፡ ኢዮብ ፡ መጥቶ ፦ በሬዎች ፡ ዕርሻ ፡ ያርሱ ፥ በአጠገባቸውም ፡ አህያዎች ፡ ይሰማሩ ፡ ነበር ፤

ኢዮ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ የሳባም ፡ ሰዎች ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ወሰዷቸውም ፥ ብላቴናዎቹንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፤ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ የእግዚአብሔር ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀች ፥ በጎቹንም ፡ አቃጠለች ፥ ጠባቂዎችንም ፡ በላች ፤ እኔም ፡ እነግርኻ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ ከለዳውያን ፡ በሦስት ፡ ረድፍ ፡ ተከፍለው ፡ በግመሎች ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጣሉ ፥ ወሰዷቸውም ፥ ብላቴናዎቹንም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ገደሉ ፤ እኔም ፡ እነግርኻ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ሌላ ፡ መጥቶ ፦ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽ ፡ በታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ቤት ፡ ይበሉና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ነበር ፤

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እንሆም ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ መጥቶ ፡ የቤቱን ፡ አራቱን ፡ ማእዘን ፡ መታው ፥ በብላቴናዎቹም ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ ሞቱም ፤ እኔም ፡ እነግርኻ ፡ ዘንድ ፡ ብቻዬን ፡ አመለጥኹ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ኢዮብም ፡ ተነሣ ፡ መጐናጸፊያውንም ፡ ቀደደ ፥ ራሱንም ፡ ተላጨ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ተደፍቶ ፡ ሰገደ ፤

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ዕራቍቴን ፡ ከእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ወጥቻለኹ ፥ ዕራቍቴንም ፡ ወደዚያ ፡ እመለሳለኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰጠ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ነሣ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ።

ኢዮ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ኢዮብ ፡ አልበደለም ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ስንፍናን ፡ አልሰጠም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ፤ የአምላክ ፡ ልጆች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ መጡ ፥ ሰይጣን ፡ ደግሞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ በመካከላቸው ፡ መጣ ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ከወዴት ፡ መጣኽ ፧ አለው ። ሰይጣንም ፦ በምድር ፡ ላይ ፡ ዞርኹ ፥ በርሷም ፡ ተመላለስኹ ፡ ብሎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መለሰ ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ በእውኑ ፡ ባሪያዬን ፡ ኢዮብን ፡ ተመለከትኸውን ፧ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ፍጹምና ፡ ቅን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ የለም ፤ በከንቱም ፡ አጠፋው ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ብታንቀሳቅሰኝ ፥ እስከ ፡ አኹን ፡ ፍጹምነቱን ፡ ይዟል ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ሰይጣንም ፡ መልሶ ፡ እግዚአብሔርን ፦ ቍርበት ፡ ስለ ፡ ቍርበት ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ሕይወቱ ፡ ይሰጣል ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ እጅኽን ፡ ዘርግተኽ ፡ ዐጥንቱንና ፡ ሥጋውን ፡ ዳብስ ፤ በእውነት ፡ በፊትኽ ፡ ይሰድብኻል ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ሕይወቱን ፡ ተወው ፡ እንጂ ፥ እንሆ ፥ ርሱ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ሰይጣንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ ኢዮብንም ፡ ከእግሩ ፡ ጫማ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐናቱ ፡ ድረስ ፡ በክፉ ፡ ቀሰል ፡ መታው ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ሥጋውንም ፡ ይፍቅበት ፡ ዘንድ ፡ ገል ፡ ወሰደ ፥ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

ኢዮ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ሚስቱም ፦ እስከ ፡ አኹን ፡ ፍጹምነትኽን ፡ ይዘኻልን ፧ እግዚአብሔርን ፡ ስደብና ፡ ሙት ፡ አለችው ።

(የሚቀጥለው ፡ ከግሪክ ፡ የተጨመረ ፡ ነው) ፡

ዳግመኛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ደጅ ፡ እጠናዋለኹ ፤ ዳግመኛም ፡ መከራውን ፡ እታገሠዋለኹ ፥ የቀድሞ ፡ ኑሮዬንም ፡ ተስፋ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ትላለኽን ፧ አለችው ። እንደዚህሳ ፡ እንዳትል ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፥ እንሆ ፥ ስም ፡ አጠራርኽ ፡ ጠፋ ፤ ሴቶች ፡ ልጆቼና ፡ ወንዶች ፡ ልጆቼም ፡ ሞቱ ፡ እኔስ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ሳረግዝ ፡ ሳምጥ ፡ ስወልድ ፡ ሳይረቡኝ ፡ ሳይጠቅሙኝ ፡ በከንቱ ፡ ደከምኹ ፡ አለች ። አንተም ፡ በመግል ፡ ተውጠኽ ፡ በትል ፡ ተከበኽ ፡ ትኖራለኽ ፤ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ስትዛብር ፡ ታድራለኽ ። እኔ ፡ ግን ፡ እየዞርኹ ፡ እቀላውጣለኹ ። ከአንዱ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ አገር ፡ ከአንዱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ እኼዳለኹ ፤ ከድካሜ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ካለ ፡ ከችግሬም ፡ ዐርፍ ፡ ዘንድ ፡ ከጧት ፡ ገምሮ ፡ ፀሓይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ እጠብቃለኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማይገሳ ፡ ቃል ፡ ተናግረኸው ፡ ሙት ፡ አለች ።

ኢዮ. ፥ 2 ፥ 10 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አንቺ ፡ ከሰነፎች ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ አንዲቱ ፡ ተናገርሽ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መልካሙን ፡ ተቀበልን ፥ ክፉ ፡ ነገርንስ ፡ አንቀበልምን ፧ አላት ። በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ኢዮብ ፡ በከንፈሩ ፡ አልበደለም ።

ኢዮ. ፥ 2 ፥ 11 ፤ ሦስቱም ፡ የኢዮብ ፡ ወዳጆች ፡ ይህን ፡ የደረሰበትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ከየአገራቸው ፡ መጡ ፤ እነርሱም ፡ ቴማናዊው ፡ ኤልፋዝ ፥ ሹሐዊው ፡ በልዳዶስ ፥ ነዕማታዊው ፡ ሶፋር ፡ ነበሩ ። እነርሱም ፡ ሊያዝኑለትና ፡ ሊያጽናኑት ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለመምጣት ፡ ተስማሙ ።

ኢዮ. ፥ 2 ፥ 12 ፤ ከሩቅም ፡ ኾነው ፡ ዐይናቸውን ፡ ባነሡ ፡ ጊዜ ፡ አላወቁትም ፤ ድምፃቸውንም ፡ አሰምተው ፡ አለቀሱ ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ መጐናጸፊያቸውን ፡ ቀደዱ ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነሰነሱ ።

ኢዮ. ፥ 2 ፥ 13 ፤ ሰባት ፡ ቀንና ፡ ሰባት ፡ ሌሊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀመጡ ፤ ሕመሙም ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ በዛ ፡ አይተዋልና ፥ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ የሚናገረው ፡ አልነበረም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 1 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ኢዮብ ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ የተወለደበትን ፡ ቀን ፡ ረገመ ።

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 2 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 3 ፤ ያ ፡ የተወለድኹበት ፡ ቀን ፡ ይጥፋ ፥

ያም ፦ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተፀነሰ ፡ የተባለበት ፡ ሌሊት ።

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 4 ፤ ያ ፡ ቀን ፡ ጨለማ ፡ ይኹን ፤

እግዚአብሔር ፡ ከላይ ፡ አይመልከተው ፥

ብርሃንም ፡ አይብራበት ።

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 5 ፤ ጨለማና ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የራሳቸው ፡ ገንዘብ ፡ ያድርጉት ፤

ዳመናም ፡ ይረፍበት ፤

የቀን ፡ ጨለማ ፡ ኹሉ ፡ ያስፈራው ።

ኢዮ. ፥ 3 ፥ 6 ፤ ያን ፡ ሌሊት ፡ ጨለማ ፡ ይያዘው ፤

በዓመቱ ፡ ቀኖች ፡ መካከል ፡ ደስ ፡ አይበለው ፤

በወሮች ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ አይቈጠር ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ ያ ፡ ሌሊት ፡ መካን ፡ ይኹን ፤

እልልታ ፡ አይግባበት ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ሌዋታንን ፡ ለማንቀሳቀስ ፡ የተዘጋጁ ፡

ቀኑን ፡ የሚረግሙ ፡ ይርገሙት ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ አጥቢያ ፡ ኮከቦች ፡ ይጨልሙ ፤

ብርሃንን ፡ ቢጠባበቅ ፡ አያግኘው ፥

የንጋትንም ፡ ቅንድብ ፡ አይይ ፤

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ የእናቴን ፡ ማሕፀን ፡ ደጅ ፡ አልዘጋምና ፥

መከራንም ፡ ከዐይኔ ፡ አልሰወረምና ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ በማሕፀን ፡ ሳለኹ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልሞትኹም ፧

ከሆድስ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፡ ፈጥኜ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልጠፋኹም ፧

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ጕልበቶች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቀበሉኝ ፧

ጡትስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠባኹ ፧

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ አኹን ፡ ተኝቼ ፡ ዝም ፡ ባልኹ ፡ ነበር ፤

አንቀላፍቼ ፡ ባረፍኹ ፡ ነበር ፤

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የፈረሰውን ፡ ለራሳቸው ፡ ከሚሠሩት ፡

ከምድር ፡ ነገሥታትና ፡ መካሮች ፡ ጋራ ፥

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ወይም ፡ ቤታቸውን ፡ ብር ፡ ከሞሉ ፡

ወርቅም ፡ ካላቸው ፡ መኳንንት ፡ ጋራ ፥

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ወይም ፡ እንደ ፡ ተቀበረ ፡ ጭንጋፍ ፥

ብርሃንም ፡ እንዳላዩ ፡ ሕፃናት ፡ በኾንኹ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ክፉዎች ፡ በዚያ ፡ መናደዳቸውን ፡ ይተዋሉ ፤

በዚያም ፡ ደካማዎች ፡ ያርፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ግዞተኞች ፡ በአንድነት ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠዋል ፤

የአስጨናቂውን ፡ ድምፅ ፡ አይሰሙም ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ታናሽና ፡ ታላቅ ፡ በዚያ ፡ አሉ ፤

ባሪያም ፡ ከጌታው ፡ ነጻ ፡ ወጥቷል ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ በመከራ ፡ ላሉት ፡ ብርሃን ፥

ነፍሳቸው ፡ መራራ ፡ ለኾነችባቸው ፥

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ የተሰወረ ፡ ሀብትን ፡ ከሚቈፍሩ ፡ ይልቅ ፡

ሞትን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ለማያገኙትም ፥

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ መቃብርን ፡ ባገኙ ፡ ጊዜ ፡

በእልልታ ፡ ደስ ፡ ለሚላቸው ፥ ሐሤትንም ፡ ለሚያደርጉ ፡

ሕይወት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተሰጠ ፧

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ መንገዱ ፡ ለተሰወረበት ፡ ሰው ፥

እግዚአብሔርም ፡ በዐጥር ፡ ላጠረው ፡

ብርሃን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተሰጠ ፧

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ከእንጀራዬ ፡ በፊት ፡ ልቅሶዬ ፡ መጥቷልና ፥

ጩኸቴም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ፈሷል ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ የፈራኹት ፡ ነገር ፡ መጥቶብኛልና ፥

የደነገጥኹበትም ፡ ደርሶብኛል ።

ኢዮ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ተዘልዬ ፡ አልተቀመጥኹም ፥ አልተማመንኹም ፥ አላረፍኹም ፤

ነገር ፡ ግን ፡ መከራ ፡ መጣብኝ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ቢሞክር ፡ ትቀየማለኽን ፧

ቃልንስ ፡ ከመናገር ፡ ሊቀር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ ብዙዎችን ፡ ታስተምር ፡ ነበር ፥

የደከሙትንም ፡ እጆች ፡ ታበረታ ፡ ነበር ፥

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ቃልኽ ፡ የሚሰናከለውን ፡ ያስነሣ ፡ ነበር ፥

አንተም ፡ የሚብረከረከውን ፡ ጕልበት ፡ ታጸና ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ፥ አንተም ፡ ደከምኽ ፤

ደርሶብኻል ፥ አንተም ፡ ተቸገርኽ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ አምላክኽን ፡ መፍራትኽ ፡ መጽናናትኽ ፥

የቅንነትኽም ፡ መንገድ ፡ ተስፋኽ ፡ አይደለምን ፧

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እባክኽ ፡ ዐስብ ፥ ንጹሕ ፡ ኾኖ ፡ የጠፋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ከልበ ፡ ቅንስ ፡ የተደመሰሰ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ እንዳየኹ ፥ ኀጢአትን ፡ የሚያርሱ ፥

መከራንም ፡ የሚዘሩ ፡ ይህንኑ ፡ ያጭዳሉ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ይጠፋሉ ፥

በቀኑጣውም ፡ መንፈስ ፡ ያልቃሉ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ የአንበሳ ፡ ጩኸት ፥ የጫኺ ፡ አንበሳ ፡ ድምፅ ፥

የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ጥርስ ፡ ተሰባበረ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ አሮጌ ፡ አንበሳ ፡ ዐደን ፡ በማጣት ፡ ይሞታል ፥

የአንበሳዉቱም ፡ ግልገሎች ፡ ይበተናሉ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ለኔም ፡ በምስጢር ፡ ቃል ፡ መጣልኝ ፥

ገሮሮዬም ፡ ሹክሹክታውን ፡ ሰማች ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ በሌሊት ፡ ሕልም ፡ ዐሳብ ፡ ሲነሣ ፥

የከበደም ፡ እንቅልፍ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፥

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ዐጥንቴን ፡ ኹሉ ፡ ያናወጡ ፡

ድንጋጤና ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ወደቁብኝ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ መንፈስም ፡ በፊቴ ፡ ዐለፈ ፤

የሥጋዬ ፡ ጠጕር ፡ ቆመ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ርሱም ፡ ቆመ ፥ መልኩን ፡ ግን ፡ ለመለየት ፡ አልቻልኹም ፥

ምሳሌም ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ ነበረ ፤

የዝምታ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ ሊኾን ፥

ወይስ ፡ ሰው ፡ በፈጣሪው ፡ ፊት ፡ ሊነጻ ፡ ይችላልን ፧

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ በባሪያዎቹ ፡ አይታመንም ፤

መላእክቱንም ፡ ስንፍና ፡ ይከሳቸዋል ፤

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ይልቁንስ ፡ በጭቃ ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፥

መሠረታቸው ፡ በትቢያ ፡ ውስጥ ፡ የኾነ ፥

ከብል ፡ በፊት ፡ የሚጨፈለቁ ፡ እንዴት ፡ ይኾኑ ፧

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ በጧትና ፡ በማታ ፡ መካከል ፡ ይሰባበራሉ ፤

ማንም ፡ ሳያስብ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጠፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ገመዳቸው ፡ የተነቀለ ፡ አይደለምን ፧

አለጥበብም ፡ ይሞታሉ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ አኹንም ፡ ጥራ ፤ የሚመልስልኽ ፡ አለን ፧

ከቅዱሳንስ ፡ ወደ ፡ ማናቸው ፡ ትዞራለኽ ፧

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ሰነፉን ፡ ሰው ፡ ቍጣ ፡ ይገድለዋል ፥

ሰነፉንም ፡ ቅንአት ፡ ያጠፋዋል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ሥር ፡ ሰዶ ፡ አየኹት ፥

ድንገትም ፡ መኖሪያውን ፡ ረገምኹ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ልጆቹም ፡ ከደኅንነት ፡ ርቀዋል ፥

በበርም ፡ ውስጥ ፡ ተረግጠዋል ፥

የሚታደጋቸውም ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ የሰበሰበውንም ፡ ራብተኛ ፡ ይበላዋል ፥

ከሾኽም ፡ ውስጥ ፡ እንኳ ፡ ያወጣዋል ፤

የተጠማ ፡ ሀብታቸውን ፡ ዋጠ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ችግር ፡ ከትቢያ ፡ አይመጣም ፥

መከራም ፡ ከመሬት ፡ አይበቅልም ፤

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ የአሞራ ፡ ግልገሎች ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እየበረሩ ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፥

ሰው ፡ እንዲሁ ፡ ለመከራ ፡ ተወልዷል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እለምን ፡ ነበር ፥

ነገሬንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቀርብ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ የማይመረመረውን ፡ ታላቅ ፡ ነገርና ፡

የማይቈጠረውን ፡ ተአምራት ፡ ያደርጋል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ዝናብን ፡ ይሰጣል ፥

በዕርሻም ፡ ላይ ፡ ውሃ ፡ ይልካል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ የተዋረዱትን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያወጣል ፥

ሐዘንተኞችንም ፡ ለደኅንነት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እጃቸውም ፡ ምክራቸውን ፡ እንዳይፈጽም ፡

የተንኰለኞችን ፡ ዐሳብ ፡ ከንቱ ፡ ያደርገዋል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ጠቢባንን ፡ በተንኰላቸው ፡ ይይዛቸዋል ፤

የጠማማዎችንም ፡ ምክር ፡ ይዘረዝራል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በቀን ፡ ጨለማን ፡ ያገኛሉ ፥

በቀትርም ፡ ጊዜ ፡ በሌሊት ፡ እንዳሉ ፡ ይርመሰመሳሉ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ድኻውንም ፡ ከአፋቸው ፡ ሰይፍ ፡

ከኀያሉም ፡ እጅ ፡ ያድነዋል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ለምስኪኑም ፡ ተስፋ ፡ አለው ፤

ክፋት ፡ ግን ፡ አፏን ፡ ትዘጋለች ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ የሚገሥጸው ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤

ስለዚህ ፡ ኹሉን ፡ የሚችለውን ፡ የአምላክን ፡ ተግሣጽ ፡ አትናቅ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ርሱ ፡ ይሰብራል ፥ ይጠግንማል ፤

ያቈስላል ፥ እጆቹም ፡ ይፈውሳሉ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ በስድስት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ውስጥ ፡ ያድንኻል ፥

በሰባትም ፡ ውስጥ ፡ ክፋት ፡ አትነካኽም ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ በራብ ፡ ጊዜ ፡ ከሞት ፥

በሰልፍም ፡ ከሰይፍ ፡ እጅ ፡ ያድንኻል ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ከምላስ ፡ ጅራፍ ፡ ትሰወራለኽ ፤

ጥፋትም ፡ ሲመጣ ፡ አትፈራም ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ በጥፋትና ፡ በራብ ፡ ላይ ፡ ትሥቃለኽ ፤

ከምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊትም ፡ አትፈራም ፤

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ቃል ፡ ኪዳንኽ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ድንጋይ ፡ ጋራ ፡ ይኾናልና ፤

የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይስማማሉና ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ድንኳንኽም ፡ በሰላም ፡ እንዲኾን ፡ ታውቃለኽ ፤

በረትኽን ፡ ትጐበኛለኽ ፡ አንዳችም ፡ አይጐድልብኽም ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ዘርኽም ፡ ታላቅ ፡ እንዲኾን ፥

ትውልድኽም ፡ እንደምድር ፡ ሣር ፡ እንዲኾን ፡ ታውቃለኽ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ በወራቱ ፡ የእኽሉ ፡ ነዶ ፡ ወደ ፡ ዐውድማ ፡ እንዲገባ ፥

በረዥም ፡ ዕድሜ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ትገባለኽ ።

ኢዮ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ ይህችን ፡ መረመርን ፥ የሰማነውም ፡ ይህ ፡ ነው ፤

አንተ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ ሠርተኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለራስኽ ፡ ዕወቀው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ትካዜዬ ፡ ምነው ፡ በተመዘነ ፡ ኖሮ! ፡

መከራዬም ፡ ኹሉ ፡ ምነው ፡ በሚዛን ፡ ላይ ፡ በተደረገ ፡ ኖሮ! ፡

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ ይከብድ ፡ ነበርና ፤

ስለዚህ ፡ ቃሌ ፡ ደፋር ፡ ኾኗል ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ ፍላጻ ፡ በሥጋዬ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፥

መርዙንም ፡ ነፍሴ ፡ ትጠጣለች ፤

የእግዚአብሔር ፡ ድንጋጤ ፡ በላዬ ፡ ተሰልፏል ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ በእውኑ ፡ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ሣር ፡ ሳለው ፡ ይጮኻልን ፧

ወይስ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ሳለው ፡ ይጮኻልን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ የማይጣፍጥስ ፡ ነገር ፡ ያለጨው ፡ ይበላልን ፧

ወይስ ፡ የዕንቁላል ፡ ውሃ ፡ ይጥማልን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ሰውነቴ ፡ ትነካው ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አለችው ፤

እንደሚያስጸይፍ ፡ መብል ፡ ኾነብኝ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ልመናዬ ፡ ምነው ፡ በደረሰልኝ! ፡

እግዚአብሔርም ፡ ምኞቴን ፡ ምነው ፡ በሰጠኝ! ፡

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደቀኝ ፡ ዘንድ ፡

እጁንም ፡ ለቆ ፡ ያጠፋኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ! ፡

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ መጽናናት ፡ በኾነልኝ ፡ ነበር ፤

በማይራራ ፡ ሕመም ፡ ሐሤት ፡ ባደረግኹ ፡ ነበር ፥

የቅዱሱን ፡ ቃል ፡ አልካድኩምና ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ጕልበቴ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

እታገሥም ፡ ዘንድ ፡ ፍጻሜዬ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ጕልበቴ ፡ የድንጋይ ፡ ጕልበት ፡ ነውን ፧

ሥጋዬስ ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ ነውን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ በእውኑ ፡ ረድኤት ፡ በእኔ ፡ እንደሌለ ፡

ጥበብም ፡ ዅሉ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተባረረ ፡ አይደለምን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ዅሉን ፡ የሚችለውን ፡ የአምላክን ፡ መፍራት ፡

ለሚተው ፥ ለመዛል ፡ ለቀረበው ፡ ስንኳ ፡

ወዳጁ ፡ ቸርነትን ፡ ሊያሳይ ፡ ይገባል ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ወንድሞቼ ፡ እንደ ፡ ፈፋ ፥

እንደሚያልፍ ፡ ፈፋ ፡ ሐሰተኞች ፡ ኾኑብኝ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ከበረዶ ፡ የተነሣ ፡ ደፈረሱ ፥

ዐመዳይም ፡ ተሰወረባቸው ፤

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ፀሓይ ፡ በተከሰች ፡ ጊዜ ፡ ይደርቃሉ ፤

በሙቀትም ፡ ጊዜ ፡ ከስፍራቸው ፡ ይጠፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ በየዳርቻቸውም ፡ የሚኼዱ ፡ ነጋዴዎች ፡ ፈቀቅ ፡ ይላሉ ፤

ወደ ፡ በረሓ ፡ ወጥተው ፡ ይጠፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ የቴማን ፡ ነጋዴዎች ፡ ተመለከቱ ፥

የሳባ ፡ መንገደኞችም ፡ ተጠባበቋቸው ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ተስፋ ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበርና ፥ ዐፈሩ ፤

ወደዚያ ፡ ደረሱ ፥ ዕፍረትም ፡ ያዛቸው ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ እንደዚሁ ፡ ኾናችኋል ፤

መከራዬን ፡ አይታችኹ ፡ ፈራችኹ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ በእውኑ ፦ አንዳች ፡ ነገር ፡ አምጡልኝ ፤

ወይስ ፦ ከብልጥግናችኹ ፡ ስጦታ ፡ አቅርቡልኝ ፤

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ወይስ ፦ ከጠላቴ ፡ እጅ ፡ አስጥሉኝ ፤

ወይስ ፦ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡ አድኑኝ ፡ አልኋችኹን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ አስተምሩኝ ፥ እኔም ፡ ዝም ፡ እላለኹ ፤

የተሳሳትኹትንም ፡ ንገሩኝ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ የቅንነት ፡ ቃል ፡ እንዴት ፡ ኀይለኛ ፡ ነው! ፥

የእናንተ ፡ ሙግት ፡ ግን ፡ ምን ፡ ይገሥጻል ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ ተስፋ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ንግግር ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ነውና ፥

ቃሌን ፡ ትገሥጹ ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችኹን ፧

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ በድኻ ፡ አደጉ ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ትጣጣላላችኹ ፤

ለወዳጆቻችኹም ፡ ጕድጓድ ፡ ትቈፍራላችኹ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ አኹንም ፥ እባካችኹ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከቱ ፤

በፊታችኹም ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ እባካችኹ ፥ ተመለሱ ፤ በደል ፡ አይኹን ፤

ጽድቄ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ነውና ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተመለሱ ።

ኢዮ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ በእውኑ ፡ በአንደበቴ ፡ በደል ፡ ይገኛልን ፧

አፌስ ፡ ተንኰልን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምን ፧

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ሕይወት ፡ ብርቱ ፡ ሰልፍ ፡ አይደለምን ፧

ወራቱም ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ወራት ፡ አይደለምን ፧

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ አገልጋይ ፡ ጥላ ፡ እንደሚመኝ ፥

ምንደኛም ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ እንደሚጠብቅ ፥

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ እንዲሁ ፡ ዕጣዬ ፡ የከንቱ ፡ ወራት ፡ ኾነብኝ ፥

የድካምም ፡ ሌሊት ፡ ተወሰነችልኝ ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ በተኛኹ ፡ ጊዜ ፦ መቼ ፡ እነሣለኹ ፧ እላለኹ ።

ሌሊቱ ፡ ግን ፡ ይረዝማል ፥

እስኪነጋ ፡ ድረስም ፡ እገለባበጣለኹ ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ሥጋዬ ፡ ትልና ፡ ጓል ፡ ለብሷል ፤

ቍርበቴ ፡ ያፈከፍካል ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ ይመግላል ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ዘመኔ ፡ ከሸማኔ ፡ መወርወሪያ ፡ ይልቅ ፡ ይቸኵላል ፥

ያለ ፡ ተስፋም ፡ ያልቃል ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ሕይወቴ ፡ እስትንፋስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐስብ ፤

ዐይኔ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያይም ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የሚያየኝ ፡ ሰው ፡ ዐይን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያየኝም ፤

ዐይንኽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ እኔም ፡ አልገኝም ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ደመና ፡ ተበትኖ ፡ እንደሚጠፋ ፥

እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ የሚወርድ ፡ ዳግመኛ ፡ አይወጣም ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ዳግመኛ ፡ አይመለስም ፥

ስፍራውም ፡ ዳግመኛ ፡ አያውቀውም ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ስለዚህም ፡ አፌን ፡ አልከለክልም ፤

በመንፈሴ ፡ ጭንቀትን ፡ እናገራለኹ ፤

በነፍሴ ፡ ምሬት ፡ በሐዘን ፡ አንጐራጕራለኹ ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ጠባቂ ፡ ታስነሣብኝ ፡ ዘንድ ፥

እኔ ፡ ባሕር ፡ ወይስ ፡ ዐንበሪ ፡ ነኝን ፧

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ እኔም ፦ ዐልጋዬ ፡ ያጽናናኛል ፥

መኝታዬም ፡ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ ያቀልልኛል ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ አንተ ፡ በሕልም ፡ ታስፈራራኛለኽ ፥

በራእይም ፡ ታስደነግጠኛለኽ ፤

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ነፍሴም ፡ ከዐጥንቴ ፡ ይልቅ ፡

መታነቅንና ፡ ሞትን ፡ መረጠች ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ሕይወቴን ፡ ናቅኋት ፤ ለዘለዓለም ፡ ልኖር ፡ አልወድም ።

የሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ እስትንፋስ ፡ ነውና ፥ ተወኝ ።

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ታከብረው ፡ ዘንድ ፥

ልብኽንስ ፡ ትጥልበት ፡ ዘንድ ፥

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ማለዳ ፡ ማለዳስ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፥

ኹልጊዜስ ፡ ትፈታተነው ፡ ዘንድ ፧

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ የማትተወኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ምራቄንስ ፡ እስክውጥ ፡ ድረስ ፡ የማትለቀኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሰውን ፡ የምትጠብቅ ፡ ሆይ ፥ በድዬስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምን ፡ ላድርግልኽ ፧

ስለ ፡ ምን ፡ እኔን ፡ ለአንተ ፡ ዐላማ ፡ አደረግኸኝ ፧

ስለ ፡ ምን ፡ እኔ ፡ ሸክም ፡ ኾንኩብኽ ፧

ኢዮ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ መተላለፌን ፡ ይቅር ፡ አትልም ፧

ኀጢአቴንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አታስወግድልኝም ፧

አኹን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ እተኛለኹ ፤

ማለዳ ፡ ትፈልገኛለኽ ፥ አታገኘኝም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ይህን ፡ ትናገራለኽ ፧

የአፍኽስ ፡ ቃል ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኾናል ፧

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ ያጣምማልን ፧

ዃሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ጽድቅን ፡ ያጣምማልን ፧

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ልጆችኽ ፡ በድለውት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ርሱ ፡ በበደላቸው ፡ እጅ ፡ ጥሏቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ብትገሠግሥ ፥

ዃሉንም ፡ የሚችለውን ፡ አምላክ ፡ ብትለምን ፥

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ንጹሕና ፡ ቅን ፡ ብትኾን ፥

በእውነት ፡ አኹን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ይነቃል ፥

የጽድቅኽንም ፡ መኖሪያ ፡ ያከናውንልኻል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ዃሮማሬኽ ፡ ታናሽ ፡ ቢኾንም ፡ እንኳ ፡

ፍጻሜኽ ፡ እጅግ ፡ ይበዛል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 8-9 ፤ ዘመናችን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ነውና ፥

እኛ ፡ የትናንት ፡ ብቻ ፡ ነን ፤ ምንም ፡ አናውቅም ፤

ስለዚህ ፡ የቀደመውን ፡ ትውልድ ፡ ጠይቅ ፥

አባቶቻቸውም ፡ ለመረመሩት ፡ ነገር ፡ ትጋ ፤

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ እነርሱ ፡ የሚያስተምሩኽና ፡ የሚነግሩኽ ፥

ቃልንም ፡ ከልባቸው ፡ የሚያወጡ ፡ አይደሉምን ፧

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ በእውኑ ፡ ደንገል ፡ ረግረግ ፡ በሌለበት ፡ መሬት ፡ ይበቅላልን ፧

ወይስ ፡ ቄጠማ ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ይለመልማልን ፧

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ገና ፡ ሲለመልም ፡ ሳይቈረጥም ፥

ከአትክልት ፡ ዃሉ ፡ በፊት ፡ ይደርቃል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚረሱ ፡ ዃሉ ፡ ፍጻሜያቸው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤

የዝንጉም ፡ ሰው ፡ ተስፋ ፡ ይጠፋል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ተስፋው ፡ ይቈረጣል ፥

እምነቱም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ቤት ፡ ይኾናል ።

ኢዮ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ቤቱን ፡ ይደግፈዋል ፥ አይቆምለትም ፤

ይይዘውማል ፥ አይጸናለትም ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 16 ፤ ፀሓይም ፡ ሳይተኵስ ፡ ይለመልማል ፥

ጫፉም ፡ በአታክልቱ ፡ ቦታ ፡ ይወጣል ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 17 ፤ በድንጋይ ፡ ክምር ፡ ላይ ፡ ሥሩ ፡ ይጠመጠማል ፤

የድንጋዮቹን ፡ ቦታ ፡ ይመለከታል ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 18 ፤ ከቦታው ፡ ቢጠፉ ።

አላየኹኽም ፡ ብሎ ፡ ይክደዋል ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 19 ፤ እንሆ ፥ የመንገዱ ፡ ደስታ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤

ሌላዎችም ፡ ከመሬት ፡ ይበቅላሉ ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 20 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ፍጹሙን ፡ ሰው ፡ አይጥለውም ፥

የኀጢአተኞችንም ፡ እጅ ፡ አያበረታም ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 21 ፤ አፍኽን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሣቅ ፡ ይሞላል ፥

ከንፈሮችኽንም ፡ እልልታ ፡ ይሞላል ።

አ.ዮ. ፥ 8 ፥ 22 ፤ የሚጠሉኽ ፡ ዕፍረት ፡ ይለብሳሉ ፤

የኀጢአተኞችም ፡ ድንኳን ፡ አይገኝም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 2 ፤ በእውነት ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቅኹ ፤

ሰውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ መኾን ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 3 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይከራከር ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፥

ከሺሕ ፡ ነገር ፡ አንዱን ፡ መመለስ ፡ አይችልም ።

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 4 ፤ ልቡ ፡ ጠቢብ ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤

ደፍሮትስ ፡ በደኅና ፡ የኼደ ፡ ማን ፡ ነው ፧

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 5 ፤ ተራራዎችን ፡ ይነቅላል ፤ አያውቁትም ፤

በቀኑጣውም ፡ ይገለብጣቸዋል ።

አ.ዮ. ፥ 9 ፥ 6 ፤ ምድርን ፡ ከስፍራው ፡ ያናውጣታል ፥

ምሰሶዎቿም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ፀሓይን ፡ ያዛታል ፥ አትወጣምም ፤

ከዋክብትንም ፡ ያትማል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ሰማያትን ፡ ብቻውን ፡ ይዘረጋል ፥

በባሕሩም ፡ ማዕበል ፡ ላይ ፡ ይረግጣል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ድብ ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብና ፡ ኦሪዮን[261] ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፥ ሰባቱንም ፡ ከዋክብት ፥

በደቡብም ፡ በኩል ፡ ያሉትን ፡ የከዋክብት ፡ ማደሪያዎች ፡ ሠርቷል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ የማይመረመረውን ፡ ታላላቅ ፡ ነገር ፥

የማይቈጠረውንም ፡ ተኣምራት ፡ ያደርጋል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ ቢመጣብኝ ፡ አላየውም ፤

ቢያልፍብኝም ፡ አላውቀውም ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እንሆ ፥ ፈጥኖ ፡ ቢነጥቅ ፡ የሚከለክለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ርሱንስ ፦ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቍጣውን ፡ አይመልስም ፤

ከርሱ ፡ በታች ፡ ረዓብን ፡ የሚረዱ ፡ ይዋረዳሉ ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ይልቁንስ ፡ እመልስለት ፡ ዘንድ ፥

ቃሌንስ ፡ በፊቱ ፡ እመርጥ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፧

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ጻድቅ ፡ ብኾን ፡ ኖሮ ፡ አልመልስለትም ፡ ነበር ፤

ወደ ፡ ፈራጁም ፡ እለምን ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ብጠራው ፡ ርሱም ፡ ቢመልስልኝ ፡ ኖሮ ፥

ቃሌን ፡ እንደ ፡ ሰማ ፡ አላምንም ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይሰብረኛል ፥

ቍስሌንም ፡ ያለምክንያት ፡ ያበዛል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ እተነፍስ ፡ ዘንድ ፡ አይተወኝም ፥

ነገር ፡ ግን ፡ መራራን ፡ ነገር ፡ አጥግቦኛል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ የኀይል ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፡ ርሱ ፡ ኀያል ፡ ነው ፤

261 ጽር. ፥ ኦሬዎን ፡ (አርዮብ ፥ ጉቡኣን ፡ ከዋክብት • ታላቅ ፡ ኮከብ ፥ ካራቱ ፡ ዐበይት ፡ ከዋክብት ፡ አንዱ ፥ ኪ.ወ.ክ. ፥ ገ.241) ።

የፍርድ ፡ ነገር ፡ ቢኾን ፦ ጊዜን ፡ ወሳኙ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይላል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ጻድቅ ፡ ብኾን ፡ አፌ ፡ ይወቅሰኛል ፤

ፍጹምም ፡ ብኾን ፡ ጠማማ ፡ ያደርገኛል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ፍጹም ፡ ነኝ ፡ ራሴንም ፡ አልመለከትም ፤

ሕይወቴንም ፡ እንቃታለኹ ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፦

ፍጹማንንና ፡ ክፉዎችን ፡ ያጠፋል ፡ እላለኹ ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ መቅሠፍቱ ፡ ፈጥኖ ፡ ቢገድል ፥

በንጹሓን ፡ ፈተና ፡ ይሳለቃል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ምድር ፡ በኃጥኣን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፤

የፈራጆቿን ፡ ፊት ፡ ሸፍኗል ፤

ርሱ ፡ ካልኾነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ዘመኔ ፡ ከሚሮጥ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ይፈጥናል ፤

ይሸሻል ፥ መልካምንም ፡ አያይም ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ የደንገል ፡ ታንኳ ፡ እንደሚፈጥን ፥

ንስርም ፡ ወደ ፡ ንጥቂያው ፡ እንደሚበር ፡ ያልፋል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ እኔ ፦ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ እረሳለኹ ፤

ፊቴን ፡ መልሼ ፡ እጽናናለኹ ፡ ብል ፥

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ንጹሕ ፡ እንደማታደርገኝ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ፡

ከመከራዬ ፡ ኹሉ ፡ እፈራለኹ ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ በደለኛ ፡ እንደሚኾን ፡ ሰው ፡ እኾናለኹ ፤

ስለ ፡ ምንስ ፡ በከንቱ ፡ እደክማለኹ ፧

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ በዐመዳይ ፡ ውስጥ ፡ ብታጠብ ፥

እጆቼንም ፡ እጅግ ፡ ባነጻ ፥

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ በዐዘቅት ፡ ውስጥ ፡ ታሰጥመኛለኽ ፥

ልብሴም ፡ ይጸየፈኛል ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ እንድመልስለት ፡ ዐብረን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፥

ርሱ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ እጁን ፡ በኹለታችን ፡ ላይ ፡ የሚያኖር ፡ ዳኛ ፡

በመካከላችን ፡ ምነው ፡ በተገኘ! ፡

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ በትሩን ፡ ከእኔ ፡ ላይ ፡ ያርቅ ፥

ግርማውም ፡ አያስፈራኝ ፤

ኢዮ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ እናገርም ፡ ነበር ፥ አልፈራውምም ፡ ነበር ፤

በራሴ ፡ እንዲህ ፡ አይደለኹምና ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ነፍሴ ፡ ሕይወቴን ፡ ሰለቸቻት ፤

የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬን ፡ እለቀዋለኹ ፤

በነፍሴም ፡ ምሬት ፡ እናገራለኹ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ እለዋለኹ ።

አትፍረድብኝ ፤ የምትከራከረኝ ፡ ለምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ንገረኝ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ልታስጨንቅና ፡ የእጅኽን ፡ ሥራ ፡ ልትንቅ ፡

የኃጥኣንንስ ፡ ምክር ፡ ልታበራ ፡

ባንተ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ነውን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ በእውኑ ፡ የሥጋ ፡ ዐይን ፡ አለኽን ፧

ወይስ ፡ ሰው ፡ እንደሚያይ ፡ ታያለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 5-6 ፤ ወይስ ፡ ክፉቴን ፡ ትፈላለግ ፡ ዘንድ ፥

ኀጢአቴንም ፡ ትመረምር ፡ ዘንድ ፥

ዘመንኽ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዘመን ፡ ነውን ፧

ወይስ ፡ ዓመታትኽ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዓመታት ፡ ናቸውን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በደለኛ ፡ እንዳልኾንኹ ፥

ከእጅኽም ፡ የሚያድን ፡ እንደሌለ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ እጅኽ ፡ ለወሰችኝ ፥ ሠራችኝም ፤

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ዞረኽ ፡ ታጠፋኝ ፡ ዘንድ ፡ ፈለግኽ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ እንደ ፡ ጭቃ ፡ አድርገኽ ፡ እንደ ፡ ለወስኽኝ ፡ ዐስብ ፤

ወደ ፡ ትቢያም ፡ ትመልሰኛለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ በእውኑ ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ አላፈሰስኽኝምን ፧

እንደ ፡ ርጎስ ፡ አላረጋኽኝምን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ቍርበትና ፡ ሥጋ ፡ አለበስኽኝ ፥

በዐጥንትና ፡ በሸምማትም ፡ አጠነከርኽኝ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ሕይወትና ፡ ቸርነት ፡ አደረግኽልኝ ፤

መንፈስ ፡ መንፈሴን ፡ ጠበቀች ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ እነዚህንም ፡ ነገሮች ፡ በልብኽ ፡ ውስጥ ፡ ሰወርኽ ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ በዐሳብኽ ፡ እንዳለ ፡ ዐውቃለኹ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ኀጢአት ፡ ብሠራ ፡ አንተ ፡ ትመለከተኛለኽ ፤

ከኀጢአቴም ፡ ንጹሕ ፡ አታደርገኝም ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ በደለኛ ፡ ብኾን ፡ ወዮልኝ ፤

ጻድቅም ፡ ብኾን ፡ ራሴን ፡ አላነሣም ፤

ጕስቍልናን ፡ ተሞልቻለኹ ፥

መከራዬንም ፡ ተመልከቻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ራሴም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ቢል ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ታድነኛለኽ ፤

ተመልሰኽም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ታደርግብኛለኽ ፡

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ምስክሮችኽን ፡ ታድስብኛለኽ ፤

ቍጣኽንም ፡ ታበዛብኛለኽ ፤

ጭፍራ ፡ በጭፍራ ፡ ላይ ፡ ትጨምርብኛለኽ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ከማሕፀን ፡ አወጣኸኝ ፧

ዐይን ፡ ሳያየኝ ፡ ምነው ፡ በሞትኹ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እንዳልነበረ ፡ በኾንኹ ፤

ከማሕፀንም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ በወሰዱኝ ።

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ የሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ ጥቂት ፡ አይደለምን ፧

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ወደማልመለስበት ፡ ስፍራ ፥

ወደ ፡ ጨለማና ፡ ወደሞት ፡ ጥላ ፡ ምድር ፥

ኢዮ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ እንደ ፡ ጨለማም ፡ ወደጨለመች ፥

ሥርዐትም ፡ ወደሌለባት ፡ ወደሞት ፡ ጥላ ፥

ብርሃኗም ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ምድር ፡ ሳልኼድ ፥

ጥቂት ፡ እጽናና ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ ፥ ልቀቀኝም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ነዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ በእውኑ ፡ ለቃል ፡ ብዛት ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ አይገባምን ፧

ወይስ ፡ ተናጋሪ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጻድቅ ፡ ይቈጠራልን ፧

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ትምክሕትኽስ ፡ ሰዎችን ፡ ዝም ፡ ያሠኛቸዋልን ፧

ብትሳለቅስ ፡ የሚያሳፍርኽ ፡ የለምን ፧

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ አንተ ፦ ትምህርቴ ፡ የተጣራ ፡ ነው ፥

በዐይንኽም ፡ ፊት ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ትላለኽ ።

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ ምነው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢናገርኽ! ፥

ባንተም ፡ ላይ ፡ ከንፈሩን ፡ ቢከፍት! ፥

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ የጥበቡን ፡ ምስጢር ፡ ቢገልጥልኽ! ፥

ማስተዋሉ ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

እግዚአብሔር ፡ ለበደልኽ ፡ ከሚገባው ፡ አሳንሶ ፡ እንደሚያስከፍልኽ ፡ ዕወቅ ።

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ልትመረምር ፡ ትችላለኽን ፧

ወይስ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ፈጽመኽ ፡ ልትመረምር ፡ ትችላለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ከሰማይ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ ምን ፡ ልታደርግ ፡ ትችላለኽ ፧

ከሲኦልም ፡ ይልቅ ፡ ይጠልቃል ፤ ምን ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለኽ ፧

ኢዮ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ርዝመቱ ፡ ከምድር ፡ ይልቅ ፡ ይረዝማል ፥

ከባሕርም ፡ ይልቅ ፡ ይሰፋል ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ርሱ ፡ ቢያልፍ ፥ ቢዘጋም ፥ ጉባኤንም ፡ ቢሰበስብ ፥

የሚከለክለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

አ.የ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ምናምንቴዎችን ፡ ሰዎች ፡ ያውቃልና ፥

በደልንም ፡ ሲያይ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ አይመለከትም ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ የሜዳ ፡ አህያ ፡ ግልገል ፡ ሰው ፡ ኾኖ ፡ ቢወለድ ፥

ያን ፡ ጊዜ ፡ ከንቱ ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ ያገኛል ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ 14 ፤ በእጅኽ ፡ በደል ፡ ቢኖር ፡ አርቀው ፤

በድንኳንኽም ፡ ኀጢአት ፡ አይኑር ፤

አንተ ፡ ልብኽን ፡ ቅን ፡ ብታደርግ ፥

እጅኽንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ብትዘረጋ ፥

አ.የ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእውነት ፡ ፊትኽን ፡ ያለነውር ፡ ታነሣለኽ ፤

ትበረታለኽ ፥ አትፈራምም ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ መከራኽንም ፡ ትረሳለኽ ፤

እንዳለፈ ፡ ውሃ ፡ ታስበዋለኽ ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ከቅትር ፡ ይልቅ ፡ ሕይወትኽ ፡ ይበራል ፤

ጨለማም ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ ጧት ፡ ይኾናል ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ተስፋም ፡ ስለ ፡ አለኽ ፡ ተዘልለኽ ፡ ትቀመጣለኽ ፤

በዙሪያኽ ፡ ትመለከታለኽ ፥ በደኅንነትም ፡ ታርፋለኽ ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ትተኛለኽ ፥ የሚያስፈራኽም ፡ የለም ፤

ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ልመና ፡ ያቀርቡልኻል ።

አ.የ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ የክፉዎች ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ ትጨልማለች ፤

የሚሸሹበትንም ፡ ያጣሉ ፥

ተስፋቸውም ፡ ነፍሳቸውን ፡ ማውጣት ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ አዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

አ.የ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ አዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

አ.የ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ በርግጥ ፡ እናንተ ፡ ዐይነተኞች ፡ ሰዎች ፡ ናችኹ ፤

ጥበብም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይሞታል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ ማስተዋል ፡ አለኝ ፤

ከእናንተም ፡ የማንስ ፡ አይደለኹም ፤

እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ የማያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የጠራኹ ፡ ርሱም ፡ የመለሰልኝ ፡ እኔ ፡

ለባልንጀራው ፡ መሳለቂያ ፡ እንደሚኾን ፡ ሰው ፡ ኾኛለኹ ፤

ጻድቅና ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ መሳለቂያ ፡ ኾኗል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ተዘልሎ ፡ በሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ ዐሳብ ፡ መከራ ፡ ይናቃል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ እግሩን ፡ ሊያድጠው ፡ ተዘጋጅቷል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የቀማኞች ፡ ድንኳን ፡ በደኅንነት ፡ ይኖራል ፥

እግዚአብሔርንም ፡ የሚያስቈጡ ፡ ተዘልለው ፡ ተቀምጠዋል ፤

እግዚአብሔር ፡ ኹሉን ፡ በእጃቸው ፡ አምጥቶላቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እንስሳዎችን ፡ ጠይቅ ፥ ያስተምሩኽማል ፤

የሰማይንም ፡ ወፎች ፡ ጠይቅ ፥ ይነግሩኽማል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ወይም ፡ ለምድር ፡ ተናገር ፥ ርሷም ፡ ታስተምርኻለች ፤

የባሕርም ፡ ዓሣዎች ፡ ይነግሩኻል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ይህን ፡ እንዳደረገ ፡

ከነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የማያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ የሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ ነፍስ ፡

የሰውም ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡ በእጁ ፡ ናት ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ምላስ ፡ መብልን ፡ እንደሚቀምስ ፥

ገሮ ፡ ቃልን ፡ የሚለይ ፡ አይደለምን ፧

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በሽምግልና ፡ ጊዜ ፡ ጥበብ ፥

በዘመንስ ፡ ርዝመት ፡ ማስተዋል ፡ ይገኛል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥበብና ፡ ኀይል ፡ አለ ፤

ለርሱ ፡ ምክርና ፡ ማስተዋል ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ ይፈርሳል ፥ የፈረሰውም ፡ ተመልሶ ፡ አይሠራም ፤

በሰውም ፡ ቢዘጋበት ፡ የሚከፍትለት ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ ውሃዎቹን ፡ ይከለክላል ፥ እነርሱም ፡ ይደርቃሉ ፤

እንደ ፡ ገና ፡ ይሰዳቸዋል ፥ ምድሪቱንም ፡ ይገለብጣሉ ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ኀይልና ፡ ጥበብ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፤

የሚስተውና ፡ የሚያስተው ፡ ለርሱ ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ መካሮችንም ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ይወስዳቸዋል ፥

ፈራጆችንም ፡ ያሳብዳል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ የነገሥታትንም ፡ እስራት ፡ ይፈታል ፥

ወገባቸውንም ፡ በመታጠቂያ ፡ ያስራቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ካህናትን ፡ እንደ ፡ ዘረፋ ፡ ይወስዳቸዋል ፥

ኀያላንንም ፡ ይገለብጣቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ከታመኑ ፡ ሰዎችም ፡ ቋንቋን ፡ ያርቃል ፥

የሽማግሌዎችንም ፡ ማስተዋል ፡ ይወስድባቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ በአለቃዎች ፡ ላይ ፡ ንቀትን ፡ ያፈሳል ፥

የብርቱዎችንም ፡ መታጠቂያ ፡ ያላላል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ከጨለማ ፡ ይገልጣል ፥

የሞትንም ፡ ጥላ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ አሕዛብን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ እነርሱንም ፡ ያጠፋል ፤

አሕዛብንም ፡ ያሰፋል ፥ እነርሱንም ፡ ያፈልሳቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ ከምድር ፡ አሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ ዘንድ ፡ ማስተዋልን ፡ ይወስዳል ፥

መንገድም ፡ በሌለበት ፡ በረሓ ፡ ያቅበዘብዛቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ብርሃንም ፡ ሳይኖር ፡ በጨለማ ፡ ይርመሰመሳሉ ፤

እንደ ፡ ሰካራም ፡ ይቅበዘበዛሉ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ ይህን ፡ ዅሉ ፡ ዐይኔ ፡ አየች ፤

ገሮሮዬም ፡ ሰምታ ፡ አስተዋለችው ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ እናንተ ፡ የምታውቁትን ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ዐውቃለኹ ፤

ከእናንተ ፡ የማንስ ፡ አይደለኹም ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉን ፡ ለሚችል ፡ አምላክ ፡ መናገር ፡ እፈልጋለኹ ፥

ከእግዚአብሔርም ፡ ጋራ ፡ ለመዋቀሥ ፡ እሻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ በሐሰት ፡ ለባጮች ፡ ናችኹ ፤

ኹላችኹ ፡ የማትጠቅሙ ፡ ባለመድኀኒቶች ፡ ናችኹ ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ምነው ፡ ዝም ፡ ብላችኹ ፡ ብትኖሩ! ፡

ይህ ፡ ጥበብ ፡ በኾነላችኹ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ አኹንም ፡ ክርክሬን ፡ ስሙ ፥

የከንፈሬንም ፡ ሙግት ፡ አድምጡ ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሐሰትን ፡ ትናገራላችኹን ፧

ስለ ፡ ርሱም ፡ ሽንገላን ፡ ታወራላችኹን ፧

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ለፊቱስ ፡ ታደላላችኹን ፧

ስለ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ትከራከራላችኹን ፧

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ቢመረምራችኹስ ፡ መልካም ፡ ይኾንላችኋልን ፧

ወይስ ፡ በሰው ፡ እንደምትሣለቁ ፡ ትሣለቁበታላችኹን ፧

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በስውር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ ብታደሉ ፡

ዘለፋ ፡ ይዘልፋችኋል ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ክብሩስ ፡ አያስፈራችኹምን ፧

ግርማውስ ፡ አይወድቅባችኹምን ፧

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ምስሌዎቻችኹ ፡ የዐመድ ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ፤

ምሽጎቻችኹ ፡ የጭቃ ፡ ምሽጎች ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ዝም ፡ በሉ ፥ እናገርም ፡ ዘንድ ፡ ተዉኝ ፤

የኾነው ፡ ነገር ፡ ይምጣብኝ ።

ኢዮ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ሥጋዬን ፡ በጥርሴ ፡ እይዛለኹ ፥

ሕይወቴንም ፡ በእጄ ፡ አኖራለኹ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 15 ፤ እንሆ ፥ ቢገድለኝ ፡ ስንኳ ፡ ርሱን ፡ በትዕግሥት ፡ እጠባበቃለኹ ፤

ነገር ፡ ግን ፡ መንገዴን ፡ በፊቱ ፡ አጸናለኹ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 16 ፤ ዝንጉ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ አይገባምና ፡

ርሱ ፡ መድኀኒት ፡ ይኾንልኛል ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 17 ፤ ነገሬን ፡ ተግታችኹ ፡ ስሙ ፥

ምስክርነቴንም ፡ በገሮሯችኹ ፡ አድምጡ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 18 ፤ እንሆ ፥ ሙግቴን ፡ አዘጋጅቻለኹ ።

እንደምጸድቅም ፡ ዐውቃለኹ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 19 ፤ ከእኔስ ፡ ጋራ ፡ የሚፋረድ ፡ ማን ፡ ነው ፧

አኹን ፡ እኔ ፡ ዝም ፡ ብል ፡ እሞታለኹ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹለት ፡ ነገር ፡ አታድርግብኝ ፤

የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከፊትኽ ፡ አልሰወርም ፤

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 21 ፤ እጅኽን ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ፤

ግርማኽም ፡ አታስደንግጠኝ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 22 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጥራኝ ፥ እኔም ፡ እመልስልኻለኹ ።

ወይም ፡ እኔ ፡ ልናገር ፥ አንተም ፡ መልስልኝ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 23 ፤ ያለብኝስ ፡ በደልና ፡ ኀጢአት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧

መተላለፌንና ፡ ኀጢአቴን ፡ አስታውቀኝ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 24 ፤ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ የሰወርኽ ፥

እንደ ፡ ጠላትኽም ፡ የቈጠርኸኝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 25 ፤ የረገፈውን ፡ ቅጠል ፡ ታስጨንቃለኽን ፧

ወይስ ፡ የደረቀውን ፡ ዕብቅ ፡ ታሳድዳለኽን ፧

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 26 ፤ የመረረ ፡ ነገር ፡ ጽፈኽብኛልና ፤

የሕፃንነቴንም ፡ ኀጢአት ፡ ታወርሰኛለኽ ።

አ.ዮ. ፥ 13 ፥ 27 ፤ እግሬንም ፡ በእግር ፡ ግንድ ፡ አግብተኻል ፥

መንገዴንም ፡ ዥሉ ፡ መርምረኻል ፤

የእግሬን ፡ ፍለጋ ፡ ወስነኻል ።

ኢዮ. ፥ 13 ፥ 28 ፤ እኔ ፡ እንደሚጠፋ ፡ በስባሳ ፡ ነገር ፥

ብልም ፡ እንደሚበላው ፡ ልብስ ፡ ነኝ ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ ከሴት ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡

የሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ነው ፥ መከራም ፡ ይሞላዋል ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 2 ፤ እንደ ፡ አበባ ፡ ይወጣል ፥ ይረግፋልም ፤

እንደ ፡ ጥላም ፡ ይሸሻል ፥ ርሱም ፡ አይጸናም ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 3 ፤ እንደዚህስ ፡ ባለ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ዐይኖችኽን ፡ ትከፍታለኽን ፧

ከአንተስ ፡ ጋራ ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ታገባለኽን ፧

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 4 ፤ ከርኩስ ፡ ነገር ፡ ንጹሕን ፡ ሊያወጣ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

አንድ ፡ እንኳ ፡ የሚችል ፡ የለም ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 5 ፤ የሰው ፡ ዕድሜ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ፥

የወሩም ፡ ቍጥር ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥

ርሱም ፡ ሊተላለፈው ፡ የማይችለውን ፡ ዳርቻ ፡ አደረግኽለት ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 6 ፤ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዕድሜው ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡

ያርፍ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ጥቂት ፡ ዘወር ፡ በል ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 7 ፤ ዛፍ ፡ ቢቈረጥ ፡ ደግሞ ፡ ያቈጠቍጥ ፡ ዘንድ ፥

ቅርንጫፉም ፡ እንዳያልቅ ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 8 ፤ ሥሩም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ቢያረጅ ፥

ግንዱም ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ቢሞት ፥

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 9 ፤ ከውሃ ፡ ሽታ ፡ የተነሣ ፡ ያቈጠቍጣል ፤

እንደ ፡ አትክልት ፡ ቅርንጫፍ ፡ ያወጣል ።

ኢዮ. ፥ 14 ፥ 10 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ይሞትና ፡ ይጋደማል ፤

ሰውም ፡ ነፍሱን ፡ ይሰጣል ፥ ርሱስ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ውሃ ፡ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ያልቃል ፤

ወንዙም ፡ ያንሳል ፡ ይደርቅማል ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ሰውም ፡ ተኝቶ ፡ አይነሣም ፤

ሰማይ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ አይነቃም ፥

ከእንቅልፉም ፡ አይነሣም ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ በሲኦል ፡ ውስጥ ፡ ምነው ፡ በሰወርኸኝ ፡ ኖሮ! ፡

ቍጣኽ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ በሸሸግኸኝ ፡ ኖሮ! ፡

ቀጠሮም ፡ አድርገኽ ፡ ምነው ፡ ባሰብኸኝ ፡ ኖሮ! ፡

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ ተመልሶ ፡ ሕያው ፡ ይኾናልን ፧

መለወጤ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፥

የሰልፌን ፡ ዘመን ፡ ኾሉ ፡ በትዕግሥት ፡ በተጠባበቅኹ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ በጠራኸኝና ፡ በመለስኩልኽ ፡ ነበር ፤

የእጅኽንም ፡ ሥራ ፡ በተመኘኸው ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ርምጃዬን ፡ ቈጥረኸዋል ፤

ኀጢአቴንም ፡ ትጠባበቃለኽ ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ መተላልፌ ፡ በከረጢት ፡ ውስጥ ፡ ታትሟል ፥

ኀጢአቴንም ፡ ለብጠኽበታል ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ተራራ ፡ ሲወድቅ ፡ ይጠፋል ፥

አለቱም ፡ ከስፍራው ፡ ይፈልሳል ፤

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ውሃዎች ፡ ድንጋዮቹን ፡ ይፍቃሉ ፤

ፈሳሾቹም ፡ የምድሩን ፡ ዐፈር ፡ ይወስዳሉ ፤

እንዲሁ ፡ የሰውን ፡ ተስፋ ፡ ታጠፋዋለኽ ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ለዘለዓለም ፡ ታሸንፈዋለኽ ፥ ርሱም ፡ ያልፋል ፤

ፊቱን ፡ ትለውጣለኽ ፥ ርሱንም ፡ ትሰደዋለኽ ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ልጆቹ ፡ ቢከብሩ ፡ አያውቅም ፤

ቢዋረዱም ፡ አያይም ።

ኢዮ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የገዛ ፡ ሥጋው ፡ ሕመም ፡ ብቻ ፡ ይሰማዋል ፥

ለራሱም ፡ ብቻ ፡ ያለቅሳል ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ በእውኑ ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ በኾነ ፡ ዕውቀት ፡ ይመልሳልን ፧

በሆዱስ ፡ የምሥራቅን ፡ ነፋስ ፡ ይሞላልን ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ከማይረባ ፡ ነገር ፥

ወይስ ፡ ከማይጠቅም ፡ ንግግር ፡ ጋራ ፡ ይዋቀሳልን ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ አንተም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ታፈርሳለኽ ፤

በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አምልኮን ፡ ታስቀራለኽ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ በደልኽ ፡ አፍኽን ፡ ያስተምረዋል ፥

የተንኰለኞችንም ፡ አንደበት ፡ ትመርጣለኽ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ የሚፈርድብኽ ፡ አፍኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

ከንፈሮችኽም ፡ ይመሰክሩብኻል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ በእውኑ ፡ መዠመሪያ ፡ የተወለድኽ ፡ ሰው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧

ወይስ ፡ ከተራራዎች ፡ በፊት ፡ ተፀነስኽን ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርንስ ፡ ምስጢር ፡ ሰምተኻልን ፧

ወይስ ፡ ጥበብን ፡ ለብቻኽ ፡ አድርገኻልን ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ እኛ ፡ የማናውቀውን ፡ አንተ ፡ የምታወቀው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ከእኛ ፡ ዘንድስ ፡ የሌለው ፡ የምታስተውለው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ በዕድሜ ፡ ከአባትኽ ፡ የሚበልጡ ፥

ሽበትም ፡ ያላቸው ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አሉ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማጽናናት ፥

በየውሀትም ፡ የተነገረኽ ፡ ቃል ፡ ጥቂት ፡ ነውን ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ልብኽስ ፡ ለምን ፡ ይወስድኻል ፧

ዐይኖችኽስ ፡ ለምን ፡ ይገለምጣሉ ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ መንፈስኽን ፡ እስከ ፡ ማንሣት ፡ ደርሰኽ ፤

ይህንም ፡ ቃል ፡ ከአፍኽ ፡ እስከ ፡ ማውጣት ፡ ደርሰኽ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ንጹሕ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ጻድቅስ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ከሴት ፡ የተወለደ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ በቅዱሳኑ ፡ ስንኳ ፡ አይታመንም ፤

ሰማያትም ፡ በፊቱ ፡ ንጹሓን ፡ አይደሉም ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ይልቁንስ ፡ አስጸያፊና ፡ የረከሰ ፥

ኀጢአትንም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣ ፡ ሰው ፡ ምንኛ ፡ ያንስ ፧

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ 18 ፤ ምድሪቱ ፡ ለብቻቸው ፡ ተሰጥታ ፡ የነበር ፥

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ በመካከላቸውም ፡ እንግዳ ፡ ያልገባባቸው ፡ ጠቢባን ።

ከአባቶቻቸው ፡ ተቀብለው ፡ የተናገሩትን ፡ ያልሸሸጉትንም ፥

እገልጥልኻለኹ ፥ ስማኝ ፤ ያየኹትንም ፡ እነግርኻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ ዕድሜውን ፡ ሙሉ ፥

ከግፈኛ ፡ በተመደቡለት ፡ በዓመታት ፡ ኹሉ ፡ በሕመም ፡ ይጣጣራል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ የሚያስደነግጥ ፡ ድምፅ ፡ በጉሮሮው ፡ ነው ፤

በደኅንነቱም ፡ ሳለ ፡ ቀማኛ ፡ ይመጣበታል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ከጨለማ ፡ ተመልሶ ፡ እንዲወጣ ፡ አያምንም ፥

ሰይፍም ፡ ይሸምቅበታል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ተቅበዝብዞም ፦ ወዴት ፡ አለ ፧ እያለ ፡ እንጀራ ፡ ይለምናል ፤

የጨለማ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ቀረበበት ፡ ያውቃል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ያስፈራሩታል ፤

ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ንጉሥ ፡ ያሸንፉታል ፤

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ እጁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ዘርግቷልና ፥

ኹሉንም ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ደፍሯልና ፥

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ በደንዳና ፡ ዐንገቱና ፡ በወፍራሙ ፡ በጋሻው ፡

ጕብጕብ ፡ እየሰገገ ፡ ይመጣበታልና ፥

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ በስብም ፡ ፊቱን ፡ ከድኗልና ፥

ስቡንም ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ አድርጓልና ፥

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ በተፈቱም ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥ ፥

ሰውም ፡ በሌለባቸው ፥

ክምር ፡ ለመኾን ፡ በተመደቡ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጧልና ፥

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ ባለጠጋ ፡ አይኾንም ፥ ሀብቱም ፡ አይጸናም ፤

ጥላውንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይጥልም ፤

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ከጨለማ ፡ አይወጣም ፤

ነበልባሉም ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ ያደርቃቸዋል ፥

አበባዎቹም ፡ ይረግፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ ዋጋው ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ይኾናልና ፥

ራሱን ፡ እያሳተ ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ አይታመን ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ቀኑ ፡ ሳይደርስ ፡ ጊዜው ፡ ይፈጸማል ፥

ቅርንጫፉም ፡ አይለመልምም ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ እንደ ፡ ወይን ፡ ያልበሰለውን ፡ ዘለላ ፡ ያረግፋል ፤

እንደ ፡ ወይራ ፡ አበባውን ፡ ይጥላል ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 34 ፤ የዝንጉዎች ፡ ጉባኤ ፡ ኾሉ ፡ ለጥፋት ፡ ይኾናል ፥

የጉቦ ፡ ተቀባዮችንም ፡ ድንኳን ፡ እሳት ፡ ትበላለች ።

ኢዮ. ፡ 15 ፡ 35 ፤ ጕዳትን ፡ ይፀንሳሉ ፥ በደልንም ፡ ይወልዳሉ ፥

ሆዳቸውም ፡ ተንኰልን ፡ ያዘጋጃል ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ዐይነት ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ሰማኹ ፤

እናንተ ፡ ኾላችኹ ፡ የምታደክሙ ፡ አጽናኞች ፡ ናችኹ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ በእውኑ ፡ ከንቱ ፡ ቃል ፡ ይፈጸማልን ፧

ወይስ ፡ ትመልስ ፡ ዘንድ ፡ ያነሣሣኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ይቻለኝ ፡ ነበር ፤

ነፍሳችኹ ፡ በነፍሴ ፡ ፋንታ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፥

እኔ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ማሳካት ፥

ራሴንም ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ መነቅነቅ ፡ በተቻለኝ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ በአፌም ፡ ነገር ፡ ባበረታኋችኹ ፡ ነበር ፤

የከንፈሬን ፡ ማጽናናት ፡ ባልከለከልኹም ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ብናገር ፡ ሕማሜ ፡ አይቀነስም ፤

ዝምም ፡ ብል ፡ ከእኔ ፡ አይወገድም ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ አድክሞኛል ፤

ወገኔንም ፡ ኹሉ ፡ አፍርሰኻል ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ መጨማተሬ ፡ ይመሰክርብኛል ፤

ክሳቴም ፡ ተነሥቶብኛል ፤

በፊቴም ፡ ይመሰክርብኛል ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ በቍጣው ፡ ቀደደኝ ፥ ርሱም ፡ ጠላኝ ፤

ጥርሶቹንም ፡ አፋጨብኝ ፤

ጠላቴ ፡ ዐይኑን ፡ አፈጠጠብኝ ፤

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ እነርሱም ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱብኝ ፤

እያላገጡ ፡ ጕንጨን ፡ ጠፈጠፉኝ ፤

በአንድነትም ፡ ተሰበሰቡብኝ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለጠማማ ፡ ሰው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠኝ ፥

በክፉዎችም ፡ እጅ ፡ ጣለኝ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ተዘልዬ ፡ ተቀምጬ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡ ሰበረኝ ፤

ዐንገቴንም ፡ ይዞ ፡ ቀጠቀጠኝ ፤

እንደ ፡ ዐላማ ፡ አድርጎ ፡ አቆመኝ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ቀስተኞቹ ፡ ከበቡኝ ፤

ኵላሊቴንም ፡ ቈራረጠ ፥ ርሱም ፡ አልራራም ፤

ሐሞቴን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ በቀኑስል ፡ ላይ ፡ ቀኑስል ፡ ጨመረብኝ ፤

እንደ ፡ ኀያል ፡ እየሰገገ ፡ ይሮጥብኛል ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ በቀኑርበቴ ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ ሰፋኹ ፥

ቀንዴንም ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ አኖርኹ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ፊቴ ፡ ከልቅሶ ፡ የተነሣ ፡ ቀላ ፤

የሞት ፡ ጥላ ፡ በዐይኖቼ ፡ ቆብ ፡ ላይ ፡ አለ ፤

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእጄ ፡ ዐመፅ ፡ የለም ፤

ጸሎቴም ፡ ንጹሕ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ደሜን ፡ አትክደኚ ፥

ለጩኸቴም ፡ ማረፊያ ፡ አይኹን ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ ምስክሬ ፡ በሰማይ ፡ አለ ፥

የሚመሰክርልኝም ፡ በአርያም ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ጸሎቴ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይድረስ ፥

ዐይኔም ፡ በፊቱ ፡ እንባ ፡ ታፍስ ።

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ እንደሚሟገት ፥

ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመሟገት ፡ ምነው ፡ በቻለ! ፥

ኢዮ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ጥቂቶች ፡ ዓመታት ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡

እኔ ፡ ወደማልመለስበት ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ።

_____መጽሐፈ ፡ አዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ መንፈሴ ፡ ደከመ ፥ ዘመኔ ፡ ዐለቀ ፥

መቃብርም ፡ ተዘጋጅቶልኛል ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ አላጋጮች ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አሉ ፥

ዐይኔም ፡ በማስቈጣታቸው ፡ ዐደረች ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ አኹንም ፡ አንተ ፡ መያዣ ፡ ኾነኽ ፡ ተዋሰኝ ፤

ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አጋና ፡ የሚመታ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ልባቸውም ፡ እንዳያስተውል ፡ ከልክለኸዋል ፤

ስለዚህ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አታደርጋቸውም ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ለብዝበዛ ፡ ባልንጀራዎቹን ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ ፡ ሰው ፥

የልጆቹ ፡ ዐይን ፡ ይጨልማል ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ለሕዝብም ፡ ምሳሌ ፡ አደረገኝ ፤

በፊቱ ፡ ላይ ፡ ጺቅ ፡ እንደሚሉበት ፡ ሰው ፡ ኾንኹ ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ዐይኔም ፡ ከሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ፈዘዘች ፥

ብልቶቼም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ኾኑ ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ቅኖች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ይደነቃሉ ፥

ንጹሕም ፡ በዝንጉው ፡ ላይ ፡ ይበሳጫል ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ መንገዱን ፡ ያጠነክራል ፥

እጁም ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ኀይልን ፡ እየጨመረ ፡ ይኼዳል ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ተመልሳችኹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፤

በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ብልኀተኛ ፡ አላገኝም ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ዕድሜዬ ፡ ዐለፈች ፤

ዐሳቤና ፡ የልቤ ፡ መሣሪያ ፡ ተቈረጠ ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ ይለውጣሉ ፤

ብርሃኑም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ የቀረበ ፡ ይመስላቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ ተስፋ ፡ ባደርግ ፡ ሲኦል ፡ ቤቴ ፡ ናት ፤

ምንጣፌንም ፡ በጨለማ ፡ ዘርግቻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ መበስበስን ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ነኽ ፤

ትልንም ፦ አንቺ ፡ እናቴ ፣ እኅቴም ፡ ነሽ ፡ ብያለኹ ።

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ተስፋዬ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

ተስፋዬንስ ፡ የሚያይ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ዐብረን ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ስናርፍ ፥

ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይወርዳል ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ቃልን ፡ ታጠምዳለኽ ፧

አስተውል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንናገራለን ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ እንደ ፡ እንስሳዎች ፡ ተቈጠርን ፧

ስለ ፡ ምንስ ፡ በዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ረከስን ፧

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ቍጣ ፡ ወርሶኻል ፤ አንተስ ፡ የሞትኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ምድር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለችን ፧

ወይስ ፡ አለት ፡ ከስፍራው ፡ ይነቀላልን ፧

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ የኀጢአተኛ ፡ መብራት ፡ ይጠፋል ፥

የእሳቱም ፡ ነበልባል ፡ ብልጭ ፡ አይልም ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ብርሃን ፡ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ይጨልማል ፥

መብራቱም ፡ በላዩ ፡ ይጠፋል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ የኀይሉም ፡ ርምጃ ፡ ትጠባለች ፥

ምክሩም ፡ ትጥለዋለች ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ እግሩ ፡ በወጥመድ ፡ ትያዛለች ፥

በመረብም ፡ ላይ ፡ ይኼዳል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ አሽክላ ፡ ሰኰናውን ፡ ይይዛል ፥

ወስፈንጠርም ፡ ይበረታበታል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የሸምቀቆ ፡ ገመድ ፥

በመንገዱም ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፡ ለርሱ ፡ ተሰውራለች ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ድንጋጤ ፡ በዙሪያው ፡ ታስፈራዋለች ፥

በስተኋላውም ፡ ኾና ፡ ታባርራቸዋለች ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ኀይሉ ፡ በራብ ፡ ትደክማለች ፥

መቅሠፍትም ፡ እስኪሰናከል ፡ ተዘጋጅቶለታል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ የሰውነቱ ፡ ብልቶች ፡ ይጠፋሉ ፤

የሞትም ፡ በኵር ፡ ልጅ ፡ ብልቶቹን ፡ ይበላል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ ከሚታመንበት ፡ ድንኳን ፡ ይነቀላል ፤

ወደ ፡ ድንጋጤም ፡ ንጉሥ ፡ ያስቸኩሉታል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ ለርሱ ፡ የማይኾነው ፡ ይኖራል ፤

በመኖሪያውም ፡ ላይ ፡ ዲን ፡ ይበተናል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ሥሩ ፡ ከበታቹ ፡ ይደርቃል ፥

ጫፉም ፡ ከበላይ ፡ ይረግፋል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ መታሰቢያው ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ይጠፋል ፥

በሜዳም ፡ ስም ፡ አይቀርለትም ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ከብርሃን ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያፈልሱታል ፥

ከዓለምም ፡ ያሳድዱታል ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ዘርም ፡ ትውልድም ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ አይኾንለትም ፤

በመኖሪያውም ፡ ውስጥ ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ አይቀርለትም ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ የፊተኞች ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ደነገጡ ፥

እንዲሁ ፡ የኋለኞች ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ዘመኑ ፡ ይደነቃሉ ።

ኢዮ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ በእውነት ፡ የኀጢአተኞች ፡ ቤት ፡ እንዲሁ ፡ ናት ፥

እግዚአብሔርንም ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ስፍራ ፡ ይህ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ነፍሴን ፡ የምትነዘንዙ ፥

በቃልስ ፡ የምታደቋኝ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ይኸው ፡ ስትሰድቡኝ ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤

ስታሻክሩኝም ፡ አላፈራችኹም ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ በእውነትም ፡ የሳትኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ስሕተቴ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትኖራለች ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ በእውነትም ፡ ብትጓደዱብኝ ፥

መዋረዴን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ብትከራከሩ ፥

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 6 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለበጠኝ ፥

በመረቡም ፡ እንደ ፡ ከበበኝ ፡ ዕወቁ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 7 ፤ እንሆ ፥ ስለ ተደረገብኝ ፡ ግፍ ፡ ብጮኽ ፡ ማንም ፡ አይመልስልኝም ፤

አሰምቼም ፡ ብጠራ ፡ ፍርድ ፡ የለኝም ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 8 ፤ እንዳላልፍ ፡ መንገዴን ፡ ዘግቶታል ፥

በጐዳናዬም ፡ ጨለማ ፡ አኑሮበታል ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 9 ፤ ክብሬን ፡ ገፈፈኝ ፥

ዘውዴንም ፡ ከራሴ ፡ ላይ ፡ ወሰደ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 10 ፤ በዚህና ፡ በዚያም ፡ አፈረሰኝ ፥ እኔም ፡ ኼድኹ ፤

ተስፋዬንም ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ነቀለው ፤

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 11 ፤ ቍጣውንም ፡ አነደደብኝ ፥

እንደ ፡ ጠላቱም ፡ ቈጠረኝ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 12 ፤ ሰራዊቱ ፡ ዐብረው ፡ መጡ ፥

መንገዳቸውንም ፡ በላዬ ፡ አዘጋጁ ፥

በድንኳኔም ፡ ዙሪያ ፡ ሰፈሩ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 13 ፤ ወንድሞቼን ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አራቀ ፥

የሚያውቁኝም ፡ አጥብቀው ፡ ተለዩኝ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 14 ፤ ዘመዶቼ ፡ ተቋረጡ ፥

ወዳጆቼም ፡ ረሱኝ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 15 ፤ ቤተ ፡ ሰቦቼና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎቼ ፡ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ ቈጠሩኝ ፤

በዐይናቸውም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ኾንኹ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 16 ፤ ባሪያዬን ፡ ብጠራ ፥ በአፌም ፡ ባቈላምጥ ፡ አይመልስልኝም ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 17 ፤ ሚስቴ ፡ እስትንፋሴን ፡ ጠላች ፥

የእናቴም ፡ ማሕፀን ፡ ልጆች ፡ ልመናዬን ፡ ጠሉ ።

ኢዮ. ፥ 19 ፥ 18 ፤ ሕፃናት ፡ እንኳ ፡ አጠቁኝ ፤

ብነሣም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይናገራሉ ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ አማካሪዎቼ ፡ ኹሉ ፡ ተጸየፉኝ ፤

እኔ ፡ የምወዳቸው ፡ በላዬ ፡ ተገለበጡ ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ዐጥንቴ ፡ ከቍርበቴና ፡ ከሥጋዬ ፡ ጋራ ፡ ተጣበቀ ፤

ድድ ፡ ብቻ ፡ ቀርቶልኝ ፡ አመለጥኹ ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ እናንተ ፡ ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፥ ማሩኝ ፤

የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መትቷኛለችና ፡ ማሩኝ ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታሳድዱኛላችኹ ፧

ከሥጋዬስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትጠግቡም ፧

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ምነው ፡ አኹን ፡ ቃሌ ፡ ቢጻፍ! ፡

ምነው ፡ በመጽሐፍ ፡ ውስጥ ፡ ቢታተም! ፡

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ምነው ፡ በብረት ፡ ብርና ፡ በርሳስ ፡

በአለቱ ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ቢቀረጽ! ፡

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ እኔን ፡ ግን ፡ የሚቤዥኝ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

በመጨረሻም ፡ ዘመን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲቆም ፥

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ይህ ፡ ቍርበቴም ፡ ከጠፋ ፡ በኋላ ፥

በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከሥጋዬ ፡ ተለይቼ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዳይ ፡ ዐውቃለኹ ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ አየዋለኹ ፥

ዐይኖቼም ፡ ይመለከቱታል ፥

ከእኔም ፡ ሌላ ፡ አይደለም ።

ልቤ ፡ በመናፈቅ ፡ ዝሏል ።

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ በእውነት ፦ እንዴት ፡ እናሳድደዋለን ፧

የነገሩ ፡ ሥር ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷል ፡ ብትሉ ፥

ኢዮ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ፍርድ ፡ እንዳለ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡

ቍጣ ፡ የሰይፍን ፡ ቅጣት ፡ ያመጣልና ፥

ከሰይፍ ፡ ፍሩ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ ናዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ስለዚህ ፡ በውስጤ ፡ ስላለው ፡ ችኮላ ፡ ዐሳቤ ፡ ትመልስልኛለች ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ የሚያሳፍረኝንም ፡ ተግሣጽ ፡ ሰምቻለኹ ፥

የማስተዋሌም ፡ መንፈስ ፡ ይመልስልኛል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ሰው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠ ፥ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፥

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ የኀጢአተኛ ፡ ፉከራ ፡ ዐጪር ፡ መኾኑን ፡

የዝንጉዎችም ፡ ደስታ ፡ ቅጽበት ፡ መኾኑን ፡ አታውቁምን ፧

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ከፍታው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ቢወጣ ፥

ራሱም ፡ እስከ ፡ ደመና ፡ ቢደርስ ፥

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ ፋንድያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጠፋል ፤

ያዩትም ፦ ወዴት ፡ ነው ፧ ይላሉ ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ እንደ ፡ ሕልም ፡ ይበራል ፥ ርሱም ፡ አይገኝም ፤

እንደ ፡ ሌሊትም ፡ ራእይ ፡ ይሰደዳል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ያየችውም ፡ ዐይን ፡ ዳግመኛ ፡ አታየውም ፤

ስፍራውም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለከተውም ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ልጆቹ ፡ ድኻዎቹን ፡ ያቈላምጣሉ ፤

እጁ ፡ ሀብቱን ፡ ይመልሳል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ዐጥንቶቹ ፡ ብላቴንነቱን ፡ ሞልተዋል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይተኛል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ ክፋት ፡ በአፉ ፡ ውስጥ ፡ ቢጣፍጥ ፥

ከምላሱም ፡ በታች ፡ ቢሰውረው ፥

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ ቢጠብቀውም ፡ ባይተወውም ፥

በጕረሮውም ፡ ቢይዘው ፥

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ መብሉ ፡ በአንጐቱ ፡ ውስጥ ፡ ይገላበጣል ፤

እንደ ፡ እፍኝትም ፡ ሐሞት ፡ በውስጡ ፡ ይኾናል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ የዋጠውን ፡ ሀብት ፡ ይተፋዋል ፤

እግዚአብሔርም ፡ ከሆዱ ፡ ውስጥ ፡ ያወጣዋል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ የእፍኝትን ፡ መርዝ ፡ ይጠባል ፤

የእባብም ፡ ምላስ ፡ ይገድለዋል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ የማሩንና ፡ የቅቤውን ፡ ፈሳሽ ፡

ወንዞቹንም ፡ አይመለከትም ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ የድካሙን ፡ ፍሬ ፡ ሳይውጠው ፡ ይመልሰዋል ፤

እንደ ፡ ንግዱም ፡ ትርፍ ፡ አይደሰትም ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ድኻውን ፡ አስጨንቋል ፥ ትቶታልም ፤

ያልሠራውንም ፡ ቤት ፡ በዝብዟል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ሆዱ ፡ ዕረፍትን ፡ አላወቀምና ፡

የወደደው ፡ ነገር ፡ አላዳነውም ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ርሱ ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ምንም ፡ አልተረፈም ፤

ስለዚህ ፡ በረከቱ ፡ አይከናወንለትም ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ በጠገበ ፡ ጊዜ ፡ ይጨነቃል ፤

የችግረኞችም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ታገኘዋለች ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ሆዱን ፡ ሳያጠግብ ፡

እግዚአብሔር ፡ የቀሥጣውን ፡ ትኵሳት ፡ ይሰድበታል ፥

ሰበላም ፡ ያዘንብበታል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ ከብረት ፡ መሣሪያም ፡ ይሸሻል ፥

የናስም ፡ ቀስት ፡ ይወጋዋል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ ይመዘዋል ፥ ከሥጋውም ፡ ይወጣል ፤

ከሐሞቱም ፡ ብልጭ ፡ ብሎ ፡ ይሠርጻል ፤

ፍርሀትም ፡ ይወድቅበታል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ጨለማ ፡ ኹሉ ፡ ስለከበረው ፡ ዕቃ ፡ ተዘጋጅቷል ፤

በሰው ፡ አፍ ፡ እፍ ፡ የማትባል ፡ እሳት ፡ ትበላዋለች ፤

በድንኳኑ ፡ ውስጥ ፡ የቀረው ፡ ይጨነቅባታል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ሰማይ ፡ ኀጢአቱን ፡ ይገልጥበታል ፥

ምድርም ፡ ትነሣበታለች ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ የቤቱም ፡ ባለጠግነት ፡ ይኼዳል ፤

በቀኑ ፡ ቍጣ ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ያልፋል ።

ኢዮ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የበደለኛ ፡ ሰው ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥

ከእግዚአብሔርም ፡ የተመደበ ፡ ርስቱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ስሙ ፥ ቃሌን ፡ ስሙ ፤

ይህም ፡ መጽናናታችኹ ፡ ይኹን ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ተዉኝ ፤

ከተናገርኹም ፡ በኋላ ፡ ተሣለቁ ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ በእውኑ ፡ የሐዘን ፡ እንጉርጉሮዬ ፡ ለሰው ፡ እናገራለኹን ፧

አለመታገሥ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይገባኝም ፧

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከቱ ፥ ተደነቁም ፤

እጃችኹንም ፡ በአፋችኹ ፡ ላይ ፡ አኑሩ ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ባሰብኹ ፡ ቀኖጥር ፡ እጨነቃለኹ ፥

ጻዕርም ፡ ሥጋዬን ፡ ይይዛል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ኀጢአተኞች ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፧

ስለ ፡ ምንስ ፡ ያረጃሉ ፧ በባለጠግነትስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይበረታሉ ፧

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ዘራቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፥

ልጆቻቸውም ፡ በዐይናቸው ፡ ፊት ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ቤታቸው ፡ ከፍርሀት ፡ ወጥቶ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥

የእግዚአብሔርም ፡ በትር ፡ የለባቸውም ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ኰርማቸው ፡ ይወልዳል ፥ ዘሩንም ፡ አይጥለውም ፤

ላማቸውም ፡ ትወልዳለች ፥ አትጨነግፍም ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ ሕፃናታቸውን ፡ እንደ ፡ መንጋ ፡ ያወጣሉ ፥

ልጆቻቸውም ፡ ይዘፍናሉ ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ ከበሮና ፡ መሰንቆ ፡ ወስደው ፡ ይዘምራሉ ፥

በእንቢልታ ፡ ድምፅ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ ዕድሜያቸውንም ፡ በተድላ ፡ ይፈጽማሉ ፤

ድንገትም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይወርዳሉ ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርንም ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ራቅ ፤

መንገድኽን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ አንወድም ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ እናመልከውስ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ወይስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ብንጸልይ ፡ ምን ፡ ይጠቅመናል ፧ ይላሉ ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 16 ፤ እንሆ ፥ ሀብታቸው ፡ በእጃቸው ፡ ውስጥ ፡ አይደለምን ፧

የኃጥኣን ፡ ምክር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቀች ፡ ናት ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 17 ፤ የኃጥኣን ፡ መብራት ፡ የጠፋው ፥

መቅሠፍትም ፡ የመጣባቸው ፥

እግዚአብሔርም ፡ በቀኑጣው ፡ መከራ ፡ የከፈላቸው ፥

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 18 ፤ በነፋስ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ገለባ ፥

ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደሚወስደው ፡ ትቢያ ፡ የኾኑ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፧

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 19 ፤ እናንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ በደላቸውን ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይጠብቃል ፡ ብላችኋል ።

እነርሱ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ፍዳን ፡ ለራሳቸው ፡ ይክፈል ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 20 ፤ ዐይኖቻቸው ፡ ጥፋታቸውን ፡ ይዩ ፥

ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ቍጣ ፡ ይጠጡ ።

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 21 ፤ የወራታቸውስ ፡ ቍጥር ፡ ቢቈረጥ ፥

ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ የቤታቸው ፡ ደስታ ፡ ምን ፡ ይኾናቸዋል ፧

አ.ዮ. ፥ 21 ፥ 22 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉትስ ፡ ላይ ፡ ለሚፈርድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡

በእውኑ ፡ ሰው ፡ ዕውቀትን ፡ ያስተምራልን ፧

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ በሰላም ፡ ተዘልሎ ፡ ሲቀመጥ ፡

በሙሉ ፡ ኀይሉ ፡ ሳለ ፡ ይሞታል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ በአንገቡቱ ፡ ውስጥ ፡ ስብ ፡ ሞልቷል ፥

የዐጥንቶቹም ፡ ቅልጥም ፡ ረጥቧል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ ሌላውም ፡ ሰው ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ሳይቀምስ ፡

በተመረረች ፡ ነፍስ ፡ ይሞታል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ፥

ትልም ፡ ይከድናቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ ዐሳባችኹን ፥

የመከራችኹብኝንም ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ ዐውቄዋለኹ ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ እናንተ ፦ የከበርቴው ፡ ቤት ፡ የት ፡ ነው ፧

ኀጢአተኛውም ፡ ያደረበት ፡ ድንኳን ፡ የት ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ መንገድ ፡ ዐላፊዎችን ፡ አልጠየቃችኹምን ፧

ምልክታቸውን ፡ አታውቁምን ፧

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ኀጢአተኛው ፡ በመቅሠፍት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተጠበቀ ፥

በቀጣው ፡ ቀን ፡ እንደሚድን ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ መንገዱን ፡ በፊቱ ፡ የሚናገር ፡ ማን ፡ ነው ፧

የሠራውንስ ፡ የሚመልስበት ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይሸከሙታል ፥

ሰዎቹም ፡ በመቃብሩ ፡ ላይ ፡ ይጠብቃሉ ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ የሸለቆው ፡ ጓል ፡ ይጣፍጥለታል ፤

በኋላውም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ይሳባል ፥

በፊቱም ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ጉባኤ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ የምትመልሱልኝ ፡ ውስልትና ፡ ነውና ፥

በከንቱ ፡ እንዴት ፡ ታጽናኑኛላችኹ ፧

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይጠቅመዋልን ፧

በእውነት ፡ ጥበበኛ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ ይጠቅማል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ ጻድቅ ፡ መኾንኽስ ፡ ኹሉን ፡ የሚችለውን ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋልን ፧

መንገድኽን ፡ ማቅናትኽስ ፡ ይጠቅመዋልን ፧

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ርሱንስ ፡ ስለ ፡ ፈራኽ ፡ ይዘልፍኻልን ፧

ወደ ፡ ፍርድስ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይገባልን ፧

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ክፋትኽስ ፡ የበዛ ፡ አይደለምን ፧

ለኀጢአትኽም ፡ ፍጻሜ ፡ የላትም ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ የወንድሞችኽን ፡ መያዣ ፡ በከንቱ ፡ ወስደኻል ፥

የዕርዝተኞቹንም ፡ ልብስ ፡ ዘርፈኻል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ለደካማ ፡ ውሃ ፡ አላጠጣኽም ፥

ለራበተኛም ፡ እንጀራን ፡ ከልክለኻል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ በክንድ ፡ የበረታ ፡ ምድርን ፡ ገዛ ፤

ከበርቴውም ፡ ሰው ፡ ተቀመጠባት ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ መበለቲቱን ፡ አንዳች ፡ አልባ ፡ ሰደኻታል ፤

የድኻ ፡ አደጎችም ፡ ክንድ ፡ ተሰብሯል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ አሽክላ ፡ ከቦኻል ፥

ድንገተኛ ፡ ፍርሀትም ፡ አናውጦኻል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ እንዳታይ ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ ኾነችብኽ ፥

የውሃዎችም ፡ ብዛት ፡ አሰጠመኽ ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አይልምን ፧

ከዋክብትም ፡ እንዴት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንዳሉ ፡ ተመልከት ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ አንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ ያውቃል ፧

በድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ሊፈርድ ፡ ይችላልን ፧

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ እንዳያይ ፡ የጠቈረ ፡ ደመና ፡ ጋርዶታል ፤

በሰማይ ፡ ክበብ ፡ ላይ ፡ ይራመዳል ፡ ብለኻል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ በእውኑ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ሰዎች ፡ የረገጧትን ፡

የዱሮዉቱን ፡ መንገድ ፡ ትጠብቃለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ ጊዜያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ ተነጠቁ ፤

መሠረታቸውም ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ፈሰሰ ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርንም ፦ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ራቅ ፤

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ምን ፡ ሊያደርግልን ፡ ይችላል ፧ አሉት ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቤታቸውን ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ሞላ ፤

የኃጥኣን ፡ ምክር ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቀች ፡ ናት ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ጻድቃን ፡ ያዩታል ፥ ደስም ፡ ይላቸዋል ፤

ንጹሓንም ፡ በንቀት ፡ ይሥቁባቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ በእውነት ፡ ሀብታቸው ፡ ጠፋ ፥

የቀረውንም ፡ እሳት ፡ በላች ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ አኹንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተስማማ ፥ ሰላምም ፡ ይኑርኽ ፤

በዚያም ፡ በጎነት ፡ ታገኛለኽ ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ከአፉም ፡ ሕጉን ፡ ተቀበል ፥

በልብኽም ፡ ቃሉን ፡ አኑር ፤

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ ኹሉን ፡ ወደሚችል ፡ አምላክ ፡ ብትመለስ ፥ ብትዋረድም ፥

ኀጢአትንም ፡ ከድንኳንኽ ፡ ብታርቅ ፥

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ የወርቅን ፡ ዕቃ ፡ በዐፈር ፡ ውስጥ ፥

የኦፊርንም ፡ ወርቅ ፡ በጅረት ፡ ድንጋይ ፡ መካከል ፡ ብትጥል ፥

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ወርቅና ፡ የሚብለጨለጭ ፡ ብር ፡ ይኾንልኻል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ኹሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ይልኻል ፥

ፊትኽንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታነሣለኽ ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ትጸልያለኽ ፥ ርሱም ፡ ይሰማኻል ፤

ስእለትኽንም ፡ ትሰጣለኽ ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ነገርንም ፡ ትመክራለኽ ፥ ርሱም ፡ ይሳካልኻል ፤

ብርሃንም ፡ በመንገድኽ ፡ ላይ ፡ ይበራል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ ቢያዋርዱኽ ፡ አንተ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትላለኽ ፤

ትሑቱንም ፡ ሰው ፡ ያድነዋል ።

ኢዮ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ ንጹሑን ፡ ሰው ፡ ያድነዋል ፤

በእጅኽም ፡ ንጽሕና ፡ ትድናለኽ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ዛሬም ፡ ደግሞ ፡ የሐዘን ፡ እንጕርጕሮዬ ፡ ገና ፡ መራራ ፡ ነው ፤

እጁ ፡ በልቅሶ ፡ ጨኸቴ ፡ ላይ ፡ ከብዳለች ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ ርሱን ፡ ወዴት ፡ እንዳገኘው ፡ ምነው ፡ ባወቅኹ! ፥

ወደተቀመጠበትስ ፡ ስፍራ ፡ ምነው ፡ በደረስኹ! ፥

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ በፊቱ ፡ ሙግቴን ፡ አዘጋጅ ፡ ነበር ፥

አፌንም ፡ በማስረጃ ፡ እሞላው ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ የሚመልስልኝም ፡ ቃል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቅ ፡ ነበር ፥

የሚለኝንም ፡ አስተውል ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በኀይሉ ፡ ብዛት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይሟገት ፡ ነበርን ፧

እንኳን! ፥ ያደምጠኝ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ቅን ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ይከራከር ፡ ነበር ፤

እኔም ፡ ከፈራጁ ፡ ለዘለዓለም ፡ እድን ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እኼዳለኹ ፥ ርሱም ፡ የለም ፤

ወደ ፡ ኋላም ፡ እኼዳለኹ ፥ እኔም ፡ አላስተውለውም ፤

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ ወደሚሠራበት ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ብኼድ ፡ አልመለከተውም ፤

በቀኜም ፡ ይሰወራል ፥ አላየውምም ፤

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ የምኼድበትን ፡ መንገድ ፡ ያውቃል ፤

ከፈተነኝም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ እወጣለኹ ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ እግሬ ፡ ወደ ፡ ርምጃው ፡ ተጣብቋል ፤

መንገዱንም ፡ ጠብቄያለኹ ፥ ፈቀቅም ፡ አላልኹም ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ከከንፈሩ ፡ ትእዛዝ ፡ አልተመለስኹም ፤

የአፉን ፡ ቃል ፡ በልቤ ፡ ሰውሬያለኹ ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ ነው ፤ ርሱንስ ፡ የሚመስለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ነፍሱም ፡ የወደደችውን ፡ ያደርጋል ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ የተወሰነውን ፡ ይፈጽማል ፤

እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ በፊቱ ፡ ደነገጥኹ ፤

ባሰብኹም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ፈራኹ ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ልቤን ፡ አባብቶታልና ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ አስደንግጦኛል ።

ኢዮ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ከጨለማው ፡ የተነሣ ፥

ድቅድቁም ፡ ጨለማ ፡ ፊቴን ፡ ከመክደኑ ፡ የተነሣ ፡ አልደነገጥኹም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ ዘመናት ፡ አልተሰወረምና ፡

ርሱን ፡ የሚያውቁ ፡ ለምን ፡ ወራቱን ፡ አያዩም ፧

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ የድንበሩን ፡ ምልክት ፡ የሚያፈርሱ ፡ አሉ ፤

መንጋዎቹን ፡ በዝብዘው ፡ ያሰማራሉ ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ የድኻ ፡ አደጎቹን ፡ አህያ ፡ ይነዳሉ ፤

የመበለቲቱን ፡ በሬ ፡ ስለ ፡ መያዣ ፡ ይወስዳሉ ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ድኻዎቹን ፡ ከመንገዱ ፡ ያወጣሉ ፤

የምድርም ፡ ችግረኞች ፡ ኹሉ ፡ ይሸሸጋሉ ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡ አህያዎች ፥

መብልን ፡ ፈልገው ፡ ወደ ፡ ሥራቸው ፡ ይወጣሉ ፤

ምድረ ፡ በዳውም ፡ ለልጆቻቸው ፡ መብልን ፡ ይሰጣቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ እነዚያ ፡ በዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ እኽላቸውን ፡ ያጭዳሉ ፤
የበደለኛውንም ፡ ወይን ፡ ይቃርማሉ ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ዕራቍታቸውን ፡ ያለልብስ ፡ ያድራሉ ፥
በብርድ ፡ ጊዜ ፡ መጐናጸፊያ ፡ የላቸውም ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ ከተራራዎች ፡ በሚወርድ ፡ ዝናብ ፡ ይረጥባሉ ፤
መጠጊያም ፡ ዐጥተው ፡ ቋጥኙን ፡ ያቅፋሉ ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ ድኻ ፡ አደጉን ፡ ልጅ ፡ ከጡቱ ፡ የሚነጥሉ ፡ አሉ ፥
ከችግረኛውም ፡ መያዣ ፡ ይወስዳሉ ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ያለ ፡ ልብስ ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ይኼዳሉ ፤
ተርበውም ፡ ነዶዎችን ፡ ይሸከማሉ ፤
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ዐጥር ፡ ውስጥ ፡ ዘይት ፡ ያደርጋሉ ፤
ወይንም ፡ ይጠምቃሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይጠማሉ ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ከከተማውና ፡ ከገዛ ፡ ቤቶቻቸው ፡ ይባረራሉ ፤
የልጆችም ፡ ነፍስ ፡ ለርዳታ ፡ ትጮኻለች ፤
እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ስንፍናቸውን ፡ አይመለከትም ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ እነዚህ ፡ በብርሃን ፡ ላይ ፡ የሚያምፁ ፡ ናቸው ፤
መንገዱን ፡ አያውቁም ፥ በጐዳናውም ፡ አይጸኑም ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ነፍሰ ፡ ገዳዩም ፡ ሳይነጋ ፡ ማልዶ ፡ ይነሣል ፤
ችግረኞችንና ፡ ድኻዎችን ፡ ይገድላል ፤
በሌሊትም ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ነው ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ የአመንዝራም ፡ ዐይን ፡ ድግዝግዝታን ፡ ይጠብቃል ።
የማንም ፡ ዐይን ፡ አያየኝም ፡ ይላል ፥
ፊቱንም ፡ ይሸፍናል ።
ኢዮ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ቤቶቹን ፡ በጨለማ ፡ ይነድላሉ ፤
በቀን ፡ ይሸሸጋሉ ፤
ብርሃንም ፡ አያውቁም ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ የጧት ፡ ብርሃን ፡ ለእነርሱ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ ጥላ ፡ ነው ፤

የሞትን ፡ ጥላ ፡ ድንጋጤ ፡ ያውቃሉና ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ እነርሱ ፡ በውሃ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ በረ፡ው ፡ ያልፋሉ ፤

ዕድል ፡ ፈንታቸውም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተረገመች ፡ ናት ፤

ወደ ፡ ወይኑ ፡ ቦታ ፡ መንገድ ፡ አይዞሩም ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ድርቅና ፡ ሙቀት ፡ የዐመዳዩን ፡ ውሃ ፡ ያጠፋሉ ፤

እንዲሁ ፡ ሲኦል ፡ በደለኞችን ፡ ታጠፋለች ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ማሕፀን ፡ ትረሳዋለች ፤

ትልም ፡ በደስታ ፡ ይጠባዋል ፤

ዳግመኛም ፡ አይታሰብም ፤

ክፋትም ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ይሰበራል ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ የማትወልደውን ፡ መካኒቱን ፡ ይበድላታል ፤

ለመበለቲቱም ፡ በጎነት ፡ አያደርግም ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኀይሉ ፡ ኀያላንን ፡ ይስባል ፤

ርሱም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ በሕይወቱ ፡ አይታመንም ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደኅና ፡ አኑሯቸዋል ፥

በዚያም ፡ ይታመናሉ ፤

ዐይኖቹ ፡ ግን ፡ በመንገዳቸው ፡ ላይ ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ፤

ይኼዳሉ ፥ ይጠወልጋሉም ፤

እንደ ፡ ሌላዎች ፡ ኹሉ ፡ ይከማቻሉ ፤

እንደ ፡ እሸትም ፡ ራስ ፡ ይቈረጣሉ ።

ኢዮ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ እንዲህስ ፡ ባይኾን ፡ ሐሰተኛ ፡ የሚያደርገኝ ፥

ነገሬንስ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ የሚያደርገው ፡ ማን ፡ ነው ፧

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ገዥነትና ፡ መፈራት ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ፤

በከፍታውም ፡ ሰላም ፡ አድራጊ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ በእውኑ ፡ ለሰራዊቶቹ ፡ ቍጥር ፡ አላቸውን ፧

ብርሃኑስ ፡ የማይወጣው ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ሰውስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቅ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥

ከሴትስ ፡ የተወለደ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ ጨረቃ ፡ እንኳ ፡ ብሩህ ፡ አይደለም ፥

ከዋክብትም ፡ በፊቱ ፡ ንጹሓን ፡ አይደሉም ።

ኢዮ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ ይልቁንስ ፡ ብስብስ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፥

ትልም ፡ የኾነ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንኛ ፡ ያንስ! ፡

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ ኀይል ፡ የሌለውን ፡ ምንኛ ፡ ረዳኸው! ፡

ብርታት ፡ የሌለውን ፡ ክንድ ፡ ምንኛ ፡ አዳንኸው! ፡

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ጥበብስ ፡ የሌለውን ፡ ምንኛ ፡ መከርኸው! ፡

ብዙ ፡ ዕውቀትንስ ፡ ምንኛ ፡ ገለጥኽለት! ፡

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ይህንስ ፡ ቃል ፡ በማን ፡ ርዳታ ፡ ተናገርኽ ፧

የማንስ ፡ መንፈስ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፧

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ሙታን ፡ ሰዎች ፡ ከውሃዎች ፡ በታች ፥

በውሃዎችም ፡ ውስጥ ፡ ከሚኖሩ ፡ በታች ፡ ይንቀጠቀጣሉ ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ሲኦል ፡ በፊቱ ፡ ዕራቍኳን ፡ ናት ፥

ለጥፋትም ፡ መጋረጃ ፡ የለውም ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ሰሜንን ፡ በባዶ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥

ምድሪቱንም ፡ በታኟ ፡ አንዳች ፡ አልባ ፡ ያንጠለጥላል ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ ውሃዎችን ፡ በደመናዎቹ ፡ ውስጥ ፡ ያስራል ፥

ደመናዉቱም ፡ ከታች ፡ አልተቀደደችም ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ የዙፋኑን ፡ ፊት ፡ ይከድናል ፥

ደመናውንም ፡ ይዘረጋበታል ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ብርሃንና ፡ ጨለማ ፡ እስከሚለያዩበት ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፥

በውሃዎች ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ድንበርን ፡ አደረገ ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ የሰማይ ፡ አዕማድ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፥

ከተግሣጹም ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ በኀይሉ ፡ ባሕርን ፡ ጸጥ ፡ ያደርጋል ፥

በማስተዋሉም ፡ ረዓብን ፡ ይመታል ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ በመንፈሱ ፡ ሰማያት ፡ ውበትን ፡ አገኙ ፥

እጁም ፡ በራሪዉቱን ፡ እባብ ፡ ወጋች ።

ኢዮ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ የመንገዱ ፡ ዳርቻ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤

ይህም ፡ የሰማነው ፡ ነገር ፡ ምንኛ ፡ ጥቂት ፡ ነው! ፡

የኀይሉንስ ፡ ነጐድጓድ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ደገመ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ ፍርዴን ፡ ያስወገደ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን!

ነፍሴንም ፡ መራራ ፡ ያደረገ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ ሕያው ፡ አምላክን! ፡

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ እስትንፋሴ ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፥

የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ባፍንጫዬ ፡ ውስጥ ፡ ገና ፡ ሳለ ፥

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ከንፈሬ ፡ ኀጢአትን ፡ አትናገርም ፥

አንደበቴም ፡ ሽንገላን ፡ አያወጣም ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ እናንተን ፡ ማጽደቅ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይራቅ ፤

እስክሞት ፡ ድረስ ፡ ፍጹምነቴን ፡ ከእኔ ፡ አላርቅም ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ ጽድቄን ፡ እይዛለኹ ፡ ርሱንም ፡ አልተውም ፤

ከቀኖቼም ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ አንዱ ፡ ልቤ ፡ አይዘልፈኝም ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ጠላቴ ፡ እንደ ፡ በደለኛ ፥

በእኔ ፡ ላይም ፡ የሚነሣ ፡ እንደ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይኹን ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባጠፋውና ፡ ነፍሱን ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፥

የዝንጉ ፡ ሰው ፡ ተስፋው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 9 ፤ በእውኑ ፡ መከራ ፡ በመጣበት ፡ ጊዜ ፥

እግዚአብሔር ፡ ጩኸቱን ፡ ይሰማልን ፧

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 10 ፤ ኹሉንስ ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ይለዋልን ፧

እግዚአብሔርንስ ፡ ኹልጊዜ ፡ ይጠራልን ፧

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 11 ፤ እኔ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ አስተምራችኋለኹ ፤

ኹሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ አልሸሽግም ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 12 ፤ እንሆ ፥ ኹላችኹ ፡ አይታችኋል ፤

ስለ ፡ ምን ፡ ከንቱ ፡ ኾናችኹ ፧

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 13 ፤ ይህች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የበደለኛ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥

ግፈኛም ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ የሚቀበላት ፡ ርስት ፡ ናት ፤

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 14 ፤ ልጆቹ ፡ ቢበዙ ፡ ለሰይፍ ፡ ይኾናሉ ፤

ዘሩም ፡ እንጀራን ፡ አይጠግብም ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 15 ፤ ለርሱም ፡ የቀሩት ፡ በችነፈር ፡ ይቀበራሉ ፤

መበለቶቻቸውም ፡ አያለቅሱም ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 16 ፤ ርሱ ፡ ብርን ፡ እንደ ፡ ዐፈር ፡ ቢከምር ፥

ልብስንም ፡ እንደ ፡ ጭቃ ፡ ቢያዘጋጅ ፥

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 17 ፤ ርሱ ፡ ያዘጋጀው ፡ ይኾናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ጻድቅ ፡ ይለብሰዋል ፤

ብሩንም ፡ ንጹሓን ፡ ይከፋፈሉታል ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 18 ፤ የሚሠራው ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ይሠራል ፥

ጠባቂም ፡ እንደሚሠራው ፡ ጐጆ ፡ ነው ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 19 ፤ ባለጠጋ ፡ ኾኖ ፡ ይተኛል ፥ ዳግመኛም ፡ አይተኛም ፤

ዐይኑን ፡ ይከፍታል ፥ ርሱም ፡ የለም ።

አ.ዮ. ፥ 27 ፥ 20 ፤ ድንጋጤ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ታገኘዋለች ፤

በሌሊትም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ትነጥቀዋለች ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ያነሣዋል ፥ ርሱም ፡ ይኼዳል ፤

ከቦታውም ፡ ይጠርገዋል ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ርሱ ፡ ይጥልበታል ፥ አይራራለትም ፤

ከእጁ ፡ ፈጥኖ ፡ መሸሽ ፡ ይወዳል ።

ኢዮ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ ሰው ፡ በእጁ ፡ ያጨበጭብበታል ፤

ከስፍራውም ፡ በፉጨት ፡ ያስወጡታል ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ በእውነት ፡ ብር ፡ የሚወጣበት ፥

ወርቅም ፡ የሚነጠርበት ፡ ስፍራ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ ብረት ፡ ከመሬት ፡ ውስጥ ፡ ይወሰዳል ፤

መዳብም ፡ ከድንጋይ ፡ ይቀለጣል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ ሰው ፡ ለጨለማ ፡ ፍጻሜን ፡ ያደርጋል ፤

የጨለማውንና ፡ የሞት ፡ ጥላን ፡ ድንጋይ ፡ እስከ ፡ ወሰኑ ፡ ድረስ ፡ ይፈላልጋል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ ሰው ፡ ከሚኖርበት ፡ ርቀው ፡ መውረጃ ፡ ይቈፍራሉ ፤

ከሰውም ፡ እግር ፡ ተረሱ ፥

ከሰዎችም ፡ ርቀው ፡ እየተንጠለጠሉ ፡ ይወዛወዛሉ ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ እንጀራ ፡ ከምድር ፡ ውስጥ ፡ ይወጣል ፤

በእሳትም ፡ እንደሚኾን ፡ ታችኛው ፡ ይገለበጣል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ ድንጋይዋ ፡ የሰንፔር ፡ ስፍራ ፡ ነው ፥

የወርቅም ፡ ድቃቂ ፡ አለው ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ መንገዷን ፡ ጭልፊት ፡ አያውቀውም ፥

የአሞራም ፡ ዐይን ፡ አላየውም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ የትዕቢት ፡ ልጆች ፡ አልረገጧትም ፥

ደቦል ፡ አንበሳ ፡ አላለፈባትም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ሰው ፡ ወደ ፡ ቡላድ ፡ ድንጋይ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ፥

ተራራውንም ፡ ከመሠረቱ ፡ ይገለብጣል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ ከድንጋይ ፡ ውስጥ ፡ መንዶልዶያ ፡ ይወቅራል ፤

ዐይኑም ፡ ዕንቁን ፡ ኹሉ ፡ ታያለች ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ፈሳሹም ፡ እንዳይንጠባጠብ ፡ ይገድባል ፤

የተሰወረውንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጥበብ ፡ የምትገኘው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

የማስተዋልስ ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ሰው ፡ መንገዷን ፡ አያውቅም ፤

በሕያዋን ፡ ምድር ፡ አትገኝም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ ቀላይ ፦ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ የለችም ፡ ይላል ፤

ባሕርም ፦ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ የለችም ፡ ይላል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ በምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ አትገኝም ፥

ብርም ፡ ስለ ፡ ዋጋዋ ፡ አይመዘንም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ በኦፊር ፡ ወርቅ ፥

በከበረም ፡ መረግድና ፡ በሰንፔር ፡ አትገመትም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ወርቅና ፡ ብርጭቆ ፡ አይወዳደሯትም ፥

በጥሩ ፡ ወርቅም ፡ ዕቃ ፡ አትለወጥም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ዛጐልና ፡ ስለ ፡ አልማዝ ፡ አይነገርም ።

የጥበብ ፡ ዋጋ ፡ ከቀይ ፡ ዕንቁ ፡ ይልቅ ፡ ይበልጣል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ቶጳዝዮን ፡ አይተካከላትም ፥

በጥሩም ፡ ወርቅ ፡ አትገመትም ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ እንግዲያሳ ፡ ጥበብ ፡ ከወዴት ፡ ትመጣለች ፧

የማስተዋልስ ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ ከሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ ዐይን ፡ ተሰውራለች ፥

ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ተሸሽጋለች ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ጥፋትና ፡ ሞት ፦ ወሬዋን ፡ በጕሮዎቻችን ፡ ሰማን ፡ ብለዋል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ መንገዷን ፡ ያስተውላል ፥

ርሱም ፡ ስፍራዋን ፡ ያውቃል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ ርሱም ፡ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ይመለከታል ፥

ከሰማይም ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ያያል ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ ለነፋስ ፡ ሚዛንን ፡ ባደረገለት ፡ ጊዜ ፥

ውሃዎችንም ፡ በስፍር ፡ በሰፈረ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ ለዝናብም ፡ ሥርዐትን ፥

ለነጐድጓድ ፡ መብረቅም ፡ መንገድን ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አያት ፥ ገለጣትም ፤

አዘጋጃትም ፥ ደግሞም ፡ መረመራት ።

ኢዮ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ ሰውንም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ፤

ከኀጢአትም ፡ መራቅ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ፡ አለው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ ምሳሌውን ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡ ደገመ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቀኝ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ጊዜ ፥

እንደ ፡ ፊተኛው ፡ ወራት ፡ ምነው ፡ በኾንኹ! ፡

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ በራሴ ፡ ላይ ፡ መብራቱ ፡ በበራ ፡ ጊዜ ፥

እኔም ፡ ጨለማውን ፡ ዐልፌ ፡ በብርሃኑ ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ በሙሉ ፡ ሰውነቴ ፡ እንደ ፡ ነበርኹ ፡ ጊዜ ፥

እግዚአብሔር ፡ ድንኳኔን ፡ በጋረደ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ ሳለ ፥

ልጆቼም ፡ በዙሪያዬ ፡ ሳሉ ፥

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ መንገዴ ፡ በቅቤ ፡ ይታጠብ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥

ድንጋዩ ፡ የዘይት ፡ ፈሳሽ ፡ ያፈስልኝ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ ወደከተማዩቱ ፡ በር ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፥

በአደባባዩም ፡ ወንበሬን ፡ ባኖርኹ ፡ ጊዜ ፥

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ጐበዛዝት ፡ እኔን ፡ አይተው ፡ ተሸሸጉ ፥

ሽማግሌዎችም ፡ ተነሥተው ፡ ቆሙ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ አለቃዎቹ ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ አሉ ፥

እጃቸውንም ፡ በአፋቸው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ የታላላቆቹም ፡ ድምፅ ፡ አረመመ ፤

ምላሳቸውም ፡ በትናጋቸው ፡ ተጣጋ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ የሰማችኝ ፡ ገሮ ፡ አሞገሰችኝ ፥

ያየችኝም ፡ ዐይን ፡ መሰከረችልኝ ፤

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ የሚጮኸውን ፡ ችግረኛ ፥

ድኻ ፡ አደጉንና ፡ ረጂ ፡ የሌለውን ፡ አድኜ ፡ ነበርና ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ ለጥፋት ፡ የቀረበው ፡ በረከት ፡ በላዬ ፡ መጣ ፤

የባልቴቲቱንም ፡ ልብ ፡ እልል ፡ አሠኘኹ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ ጽድቅን ፡ ለበስኹ ፡ ርሷም ፡ ለበሰችኝ ፤

ፍርዴም ፡ እንደ ፡ መጐናጸፊያና ፡ እንደ ፡ ኵፋር ፡ ነበረ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ ለዕውር ፡ ዐይን ፥

ለዐንካሳ ፡ እግር ፡ ነበርኹ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ ለድኻው ፡ አባት ፡ ነበርኹ ፤

የማላውቀውንም ፡ ሰው ፡ ሙግት ፡ መረመርኹ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ የኀጢአተኛውን ፡ መንጋጋ ፡ ሰበርኹ ፥

የነጠቀውንም ፡ ከጥርሱ ፡ ውስጥ ፡ አስጣልኹ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ እኔም ፡ አልኹ ፦ በልጆቼ ፡ መካከል ፡ እሞታለኹ ፥

ዕድሜዬንም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ አበዛለኹ ፤

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ሥሬ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ተዘርግቷል ፥

ጠልም ፡ በቅርንጫፌ ፡ ላይ ፡ ያድራል ፤

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ ክብሬ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ታድሷል ፥

ቀስቴም ፡ በእጄ ፡ ውስጥ ፡ ለምልሟል ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ ሰዎች ፡ እኔን ፡ ሰምተው ፡ በትዕግሥት ፡ ተጠባበቁ ፥

ምክሬንም ፡ ለማዳመጥ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ከቃሌ ፡ በኋላ ፡ አንዳች ፡ አልመለሱም ፤

ንግግሬም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተንጠባጠበ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ ዝናብን ፡ እንደሚጠብቁ ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቁኝ ፤

የጥቢን ፡ ዝናብ ፡ እንደሚሹ ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ እነርሱ ፡ ባልታመኑ ፡ ጊዜ ፡ ሣቅኹላቸው ፤

የፊቴንም ፡ ብርሃን ፡ አላወረዱም ።

ኢዮ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ መንገዳቸውን ፡ መረጥኹ ፤

እንደ ፡ አለቃ ፡ ኾኜ ፡ ተቀመጥኹ ፤

ንጉሥ ፡ በሰራዊቱ ፡ መካከል ፡ እንደሚኖር ፥

ሐዘነተኞችን ፡ እንደሚያጽናና ፡ ኖርኹ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በዕድሜ ፡ ከእኔ ፡ የሚያንሱ ፥

አባቶቻቸውን ፡ ከመንጋዬ ፡ ውሻዎች ፡ ጋራ ፡ ለማኖር ፡ የናቅኋቸው ፥

በእኔ ፡ ላይ ፡ ተሣለቁብኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ ሙሉ ፡ ሰው ፡ መኾናቸው ፡ ጠፍቶባቸው ፡ ነበርና ፥

የእጃቸው ፡ ብርታት ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፧

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ በራብና ፡ በቀጠና ፡ የመነመኑ ፡ ናቸው ፤

የመፍረስና ፡ የመፈታት ፡ ጨለማ ፡ ወዳለበት ፡

ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይሸሻሉ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ በቀጕጥቋጦ ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡

ጨው ፡ ጨው ፡ የሚለውን ፡ አትክልት ፡ ይለቅማሉ ፤

የክትክታ ፡ ሥር ፡ ደግሞ ፡ መብላቸው ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ ከሰዎች ፡ ተለይተው ፡ ተሰደዱ ፤

በሌባ ፡ ላይ ፡ እንደሚጮኽ ፡ ይጮኹባቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ በሸለቆ ፡ ፈረፈርና ፡ በምድር ፡ ጕድጓድ ፡

በድንጋይም ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ በቀጕጥቋጦ ፡ መካከል ፡ ይጮኻሉ ፤

ከሳማ ፡ በታች ፡ ተሰብስበዋል ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ የሰነፎችና ፡ የነውረኞች ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤

ከምድርም ፡ በግርፋት ፡ የተባረሩ ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ መዝፈኛና ፡ መተረቻ ፡ ኾንኋቸው ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ ተጸየፉኝ ፥ ከእኔም ፡ ራቁ ፤

አክታቸውንም ፡ በፊቴ ፡ መትፋትን ፡ አልተዉም ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ የቀስቴን ፡ አውታር ፡ አላልቶብኛል ፥ አዋርዶኝማል ፤

እነርሱም ፡ በፊቴ ፡ ልጓማቸውን ፡ ፈትተዋል ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ በቀኜ ፡ በኩል ፡ ዱርዬዎች ፡ ተነሥተዋል ፥

እግሬንም ፡ ይገለብጣሉ ፤

የጥፋታቸውን ፡ መንገድ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይጐድባሉ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ጐዳናዬን ፡ ያበላሻሉ ፤

ረዳት ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ መከራዬን ፡ ያበዛሉ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ በሰፊ ፡ ፍራሽ ፡ እንደሚመጡ ፡ ይመጡብኛል ፤

በባድማ ፡ ውስጥ ፡ ይንከባለሉብኛል ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ድንጋጤ ፡ በላዬ ፡ ተመለሰችብኝ ፥

ክብሬንም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ያሳድዷታል ፤

ደኅንነቴም ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ ዐልፋለች ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ አኹንም ፡ ነፍሴ ፡ በውስጤ ፡ ፈሰሰች ፤

የመከራም ፡ ዘመን ፡ ያዘችኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ በሌሊት ፡ ዐጥንቴ ፡ በደዌ ፡ ተነደለች ፥

ኾዮማቶቼም ፡ አያርፉም ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ ከታላቁ ፡ ደዌ ፡ ኀይል ፡ የተነሣ ፡ ልብሴ ፡ ተበላሽች ፤

እንደ ፡ ቀሚስ ፡ ክሳድ ፡ ዐነቀችኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ ርሱ ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ጣለኝ ፥

ዐፈርና ፡ ዐመድም ፡ መሰልኩ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ ወዳንተ ፡ ጮኽኩ ፥ አልመለስኽልኝም ፤

ተነሣኩ ፥ አልተመለከትኸኝም ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 21 ፤ ተመልሰኽ ፡ ጨካኝ ፡ ኾንኽብኝ ፤

በእጅኽም ፡ ብረታት ፡ አስጨነቅኸኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 22 ፤ በነፋስ ፡ አነሣኸኝ ፥ በላዩም ፡ አስቀመጥኸኝ ፤

በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ አቀለጥኸኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 23 ፤ ለሞት ፡ ሕያዋንም ፡ ዥሉ ፡ ለሚሰበሰብበት ፡ ቤት ፡ አሳልፈኽ ፡ እንደምትሰጠኝ ፡ ዐውቄያለኹና ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ አይዘረጋምን ፧

በጥፋቱስ ፡ ጊዜ ፡ አይጮኽምን ፧

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 25 ፤ ጭንቅ ፡ ቀን ፡ ላገኘው ፡ ሰው ፡ አላለቀስኹምን ፧

ለችግረኛስ ፡ ነፍሴ ፡ አላዘነችምን ፧

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎነትን ፡ በተጠባበቅኩ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መጣችብኝ ፤

ብርሃንን ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቅኩ ፥ ጨለማም ፡ መጣ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 27 ፤ አንገቴ ፡ ፈላች ፥ አላረፈችም ፤

የመከራም ፡ ዘመን ፡ መጣችብኝ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 28 ፤ ያለፀሓይ ፡ በትካዜ ፡ ኼድኩ ፤

በጉባኤም ፡ መካከል ፡ ቆሜ ፡ ጮኽኩ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 29 ፤ ለቀበሮ ፡ ወንድም ፥

ለሰጐንም ፡ ባልንጀራ ፡ ኾንኩ ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 30 ፤ ቍርበቴ ፡ ጠቈረ ፥ ከእኔም ፡ ተለይቶ ፡ ርግፍግፍ ፡ አለ ፤

ዐጥንቴም ፡ ከትኵሳት ፡ የተነሣ ፡ ተቃጠለች ።

ኢዮ. ፡ 30 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ መሰንቆዬ ፡ ለሐዘን ፥

እንቢልታዬም ፡ ለሚያለቅሱ ፡ ቃል ፡ ኾነ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 1 ፤ ከዐይኔ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባኹ ፤

እንግዲህስ ፡ ቈንጕዩቱን ፡ እንዴት ፡ እመለከታለኹ ፧

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ከላይ ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ርስት ፡ ከአርያም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 3 ፤ መዓትስ ፡ ለኀጢአተኛ ፥

መለየትስ ፡ ለሚበድሉ ፡ አይደለችምን ፧

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 4 ፤ መንገዴን ፡ አያይምን ፧

ርምጃዬንስ ፡ ኹሉ ፡ አይቈጥርምን ፧

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 5-6 ፤ በእውነተኛ ፡ ሚዛን ፡ ልመዘን ፥

እግዚአብሔርም ፡ ቅንነቴን ፡ ይወቅ ።

በሐሰት ፡ ኼጄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡

እግሬም ፡ ለሸንገላ ፡ ቸኮላ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 7 ፤ ርምጃዬ ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፥

ልቤም ፡ ዐይኔን ፡ ተከትሎ ፥

ነውርም ፡ ከእጄ ፡ ጋራ ፡ ተጣብቆ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 8 ፤ እኔ ፡ ልዝራ ፥ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ይብላው ፤

የሚበቅለውም ፡ ኹሉ ፡ ይነቀል ።

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 9 ፤ ልቤ ፡ ወደ ፡ ሌላዪቱ ፡ ሴት ፡ ጐምዥቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

በባልንጀራዬም ፡ ደጅ ፡ አድብቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 10 ፤ ሚስቴ ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ትፍጭ ፥

ሌላዎችም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ይጐንበሱ ።

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 11 ፤ ይህ ፡ ክፉ ፡ አበሳ ፥

ፈራጆችም ፡ የሚቀጡበት ፡ በደል ፡ ነውና ፤

ኢዮ. ፥ 31 ፥ 12 ፤ ይህ ፡ እስከ ፡ ጥፋት ፡ ድረስ ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፥

ቡቃያዬንም ፡ ኹሉ ፡ የሚነቅል ፡ ነውና ።

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ ወንድ ፡ ባሪያዬ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ባሪያዬ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በተሟገቱ ፡ ጊዜ ፥

ሙግታቸውን ፡ ንቄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ አደርጋለኹ ፧

በጐበኘኝ ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ እመልስለታለኹ ፧

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ እኔን ፡ በማሕፀን ፡ የፈጠረ ፡ ርሱንስ ፡ የፈጠረው ፡ አይደለምን ፧

በማሕፀንስ ፡ ውስጥ ፡ የሠራን ፡ አንድ ፡ አይደለንምን ፧

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ ድኻውን ፡ ከልመናው ፡ ከልክዬ ፥

የመበለቲቱን ፡ ዐይን ፡ አጨልሜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ እንጀራዬን ፡ ለብቻዬ ፡ በልቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ድኻ ፡ አደጉም ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ሳይበላ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሬ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አሳድጌው ፡ ነበር ፥

ርሷንም ፡ ከእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ዠምሬ ፡ መራኺት ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 19 ፤ ዕራቍቱን ፡ የኾነው ፡ ሰው ፡ ሲጠፋ ፥

ወይም ፡ ድኻ ፡ ያለልብስ ፡ ሲኾን ፡ አይቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 20 ፤ ጐንና ፡ ጐኑ ፡ ያልባረከችኝ ፥

በበጎቼም ፡ ጠጕር ፡ ያልሞቀ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 21 ፤ በበሩ ፡ ረዳት ፡ ስላየኹ ፥

በድኻ ፡ አደጉ ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ አንሥቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 22 ፤ ትከሻዬ ፡ ከመሠረቷ ፡ ትውደቅ ፥

ክንዴም ፡ ከመገናኛዋ ፡ ትሰበር ።

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 23 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ አስደንግጦኛልና ፤

በክብሩም ፡ ፊት ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አልቻልኹም ።

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 24 ፤ ወርቅን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፥

ጥሩውንም ፡ ወርቅ ፦ ባንተ ፡ እታመናለኹ ፡ ብዬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 25 ፤ ሀብቴ ፡ ስለ ፡ በዛ ፥

እጄም ፡ ብዙ ፡ ስላገኘች ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 26 ፤ ፀሓይ ፡ ሲበራ ፡

ጨረቃ ፡ በክብር ፡ ስትኼድ ፡ አይቼ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 27 ፤ ልቤ ፡ በስውር ፡ ተታሎ ፥

አፌም ፡ እጄን ፡ ስሞ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 28 ፤ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በካድኹ ፡ ነበርና ፥

ይህ ፡ ደግሞ ፡ ፈራጆች ፡ የሚቀጡበት ፡ በደል ፡ በኾነ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 29 ፤ በሚጠላኝ ፡ መጥፋት ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡

ክፉ ፡ ነገርም ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ሐሤት ፡ አድርጌ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመርገም ፡ ነፍሱን ፡ በመሻት ፡

አንደበቴን ፡ ኀጢአት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ አልሰጠኹም ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 31 ፤ በድንኳኔ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፦

በከብቱ ፡ ሥጋ ፡ ያልጠገበ ፡ ማን ፡ ይገኛል ፧ ብለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 32 ፤ መጻተኛው ፡ ግን ፡ በሜዳ ፡ አያድርም ፡ ነበር ፥

ደጄንም ፡ ለመንገደኛ ፡ እከፍት ፡ ነበር ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 33 ፤ በደሌንም ፡ በብብቴ ፡ በመሸሸግ ፡

ኀጢአቴን ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሰውሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 34 ፤ ከሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ፈርቼ ፥

የዘመዶቼም ፡ ንቀት ፡ አስደንግጦኝ ፥

ዝም ፡ ብዬ ፡ ከደጅ ፡ ያልወጣኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 35 ፤ የሚያዳምጠኝ ፡ ምነው ፡ በኖረልኝ! ፡

እንሆ ፥ የእጄ ፡ ምልክት ፡

ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ይመልስልኝ ፤

ከባላጋራዬ ፡ የተጻፈው ፡ የክስ ፡ ጽሑፍ ፡ ምነው ፡ በተገኘልኝ! ፡

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 36 ፤ በትከሻዬ ፡ ላይ ፡ እሸከመው ፥

አክሊልም ፡ አድርጌ ፡ በራሴ ፡ አስረው ፡ ነበር ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 37 ፤ የርምጃዬን ፡ ቍጥር ፡ አስታውቀው ፥

እንደ ፡ አለቃም ፡ ኾኜ ፡ አቀርብለት ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 38 ፤ ዕርሻዬ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ጮኻ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ትልሞቿም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ አልቅሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 39 ፤ ፍሬዋን ፡ ያለዋጋ ፡ በልቼ ፥

የባለቤቶችንም ፡ ነፍስ ፡ አሳዝኜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኢዮ. ፡ 31 ፡ 40 ፤ በስንዴ ፡ ፋንታ ፡ አሜከላ ፥

በገብስም ፡ ፋንታ ፡ ዅርንችት ፡ ይውጣብኝ ። የኢዮብ ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ። _____

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ ራሱን ፡ ጻድቅ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ እነዚያ ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ መመለስን ፡ ተዉ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ ከራም ፡ ወገን ፡ የኾነ ፡ የቡዛዊው ፡ የባርክኤል ፡ ልጅ ፡ የኤሊሁ ፡ ቍጣ ፡ ነደደ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ይልቅ ፡ ራሱን ፡ ጻድቅ ፡ አድርጎ ፡ ነበርና ፥ ኢዮብን ፡ ተቈጣው ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ ደግሞም ፡ በኢዮብ ፡ ፈረዱበት ፡ እንጂ ፡ የሚገባ ፡ መልስ ፡ ስላላገኙ ፥ በሦስቱ ፡ ባልንጀራዎቹ ፡ ላይ ፡ ተቈጣ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ ኤሊሁ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ነበሩና ፥ ከኢዮብ ፡ ጋራ ፡ መናገርን ፡ ጠብቆ ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ ኤሊሁም ፡ በነዚህ ፡ በሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ መልስ ፡ እንደሌለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣው ፡ ነደደ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ የቡዛዊውም ፡ የባርክኤል ፡ ልጅ ፡ ኤሊሁ ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

እኔ ፡ በዕድሜ ፡ ታናሽ ፡ ነኝ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ናችኹ ፤

ስለዚህም ፡ ሠጋኹ ፤ ዕውቀቴን ፡ እገልጥላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ፈራኹ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ እንደዚህም ፡ አልኹ ፦ ዓመታት ፡ በተናገሩ ፡ ነበር ፥

የዓመታትም ፡ ብዛት ፡ ጥበብን ፡ ባስተማረች ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰው ፡ ውስጥ ፡ መንፈስ ፡ አለ ፥

ዅሉንም ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ እስትንፋስ ፡ ማስተዋልን ፡ ይሰጣል ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ በዕድሜ ፡ ያረጁ ፡ ጠቢባን ፡ አይደሉም ፥

ሽማግሌዎችም ፡ ፍርድን ፡ አያስተውሉም ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ ስለዚህም ፦ ስሙኝ ፤

እኔ ፡ ደግሞ ፡ ዕውቀቴን ፡ እገልጥላችኋለኹ ፡ አልኹ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ ቃላችኹን ፡ በትዕግሥት ፡ ጠበቅኹ ፤

የምትናገሩትን ፡ ነገር ፡ እስክትመረምሩ ፡ ድረስ ፤

ብልኀታችኹን ፡ አዳመጥኹ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ እንዲሁም ፡ ልብ ፡ አደረግኹ ፤

እንሆም ፥ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ኢዮብን ፡ ያስረዳ ፥

ወይም ፡ ለቃሉ ፡ የመለሰ ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ እናንተም ፦ ጥበብን ፡ አግኝተናል ፤

እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አያሸንፈውም ፡ እንዳትሉ ፡ ተጠንቀቁ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አልተናገረም ፤

እኔም ፡ በንግግራችኹ ፡ አልመልስለትም ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ እነርሱ ፡ ደነገጡ ፥ ዳግመኛም ፡ አልመለሱም ፤

የሚናገሩትንም ፡ ዐጡ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ እነርሱ ፡ አልተናገሩምና ፥

ቆመው ፡ ዳግመኛ ፡ አልመለሱምና ፡ እኔ ፡ በትዕግሥት ፡ እጠብቃለኹን ፧

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ፈንታዬን ፡ እመልሳለኹ ፥

ዕውቀቴንም ፡ እገልጣለኹ ፤

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ቃል ፡ ተሞልቻለኹና ፥

በውስጤም ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ አስገድዶኛልና ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ በተሓ ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ተሞላና ፡ ሊቀደድ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ አቀኑማዳ ፥

ሊፈነዳ ፡ እንደማይችል ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡

አቀኑማዳ ፥ እንሆ ፥ አንገቴ ፡ ኾነ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ ጥቂት ፡ እንድተነፍስ ፡ እናገራለኹ ፤

ከንፈሬን ፡ ገልጬ ፡ እመልሳለኹ ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 21 ፤ ለሰው ፡ ፊት ፡ ግን ፡ አላደላም ፤

ሰውንም ፡ አላቈላምጥም ።

ኢዮ. ፡ 32 ፡ 22 ፤ በማቈላመጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አላውቅምና ፤

ያለዚያስ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ፈጥኖ ፡ ከሕይወቴ ፡ ይለየኝ ፡ ነበር ።

_____መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ። _____

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ ንግግሬን ፡ እንድትሰማ ፥

ቃሌንም ፡ ሹሉ ፡ እንድታደምጥ ፡ እለምንኻለኹ ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 2 ፤ እንሆ ፥ አፌን ፡ ከፍቻለኹ ፥

አንደበቴም ፡ በትናጋዬ ፡ ተናግሯል ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 3 ፤ ቃሌ ፡ የልቤን ፡ ቅንነት ፡ ያወጣል ፤

ከንፈሮቼም ፡ የሚያውቁትን ፡ በቅንነት ፡ ይናገራሉ ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ፈጠረኝ ፥

ሹሉንም ፡ የሚችል ፡ የአምላክ ፡ እስትንፋስ ፡ ሕይወት ፡ ሰጠኝ ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 5 ፤ ይቻልኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መልስልኝ ፤

ቃልኽንም ፡ አዘጋጅተኽ ፡ በፊቴ ፡ ቁም ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 6 ፤ እንሆ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ነኝ ፤

እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከጭቃ ፡ የተፈጠርኹ ፡ ነኝ ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 7 ፤ እንሆ ፥ ግርማዬ ፡ አታስፈራኽም ፡

እጄም ፡ አትከብድብኽም ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 8 ፤ በጕሮዬ ፡ ተናግረኻል ፥

የቃልኽንም ፡ ድምፅ ፡ ሰምቻለኹ ፥ እንዲህም ፡ ብለኻል ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 9 ፤ እኔ ፡ ያለመተላለፍ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤

ያለነውር ፡ ነኝ ፥ ኀጢአትም ፡ የለብኝም ፤

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 10 ፤ እንሆ ፥ ምክንያት ፡ አግኝቶብኛል ፥

እንደ ፡ ጠላቱም ፡ ቈጥሮኛል ፤

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 11 ፤ እግሬን ፡ በግንድ ፡ አጣበቀ ፥

መንገዴንም ፡ ሹሉ ፡ ተመለከተ ።

ኢዮ. ፥ 33 ፥ 12 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ አይደለኽም ፤

እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ይበልጣል ፡ ብዬ ፡ እመልስልኻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ አንተ ፦ ለቃሌ ፡ ዥሉ ፡ አይመልስልኝም ፡ ብለኽ ፥

ስለ ፡ ምን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትከራከራለኽ ፡፡

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባንድ ፡ መንገድ ፡ በሌላም ፡ ይናገራል ፤

ሰው ፡ ግን ፡ አያስተውለውም ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ በሕልም ፥ በሌሊት ፡ ራእይ ፥

ዐፍላ ፡ እንቅልፍ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ሲወድቅ ፥

በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝተው ፡ ሳሉ ፥

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሰዎችን ፡ ጐሮ ፡ ይከፍታል ፥

በተግሣጹም ፡ ያስደነግጣቸዋል ፥

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ ሰውን ፡ ከክፉ ፡ ሥራው ፡ ይመልሰው ፡ ዘንድ ፡

ከሰውም ፡ ትዕቢትን ፡ ይሰውር ፡ ዘንድ ፤

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ነፍሱን ፡ ከጕድጓድ ፥

በሰይፍም ፡ እንዳይጠፋ ፡ ሕይወቱን ፡ ይጠብቃል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ ደግሞ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ በደዌ ፡ ይገሥጸዋል ፥

ዐጥንቱንም ፡ ዥሉ ፡ ያደነዝዛል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ ሕይወቱም ፡ እንጀራን ፥

ነፍሱም ፡ ጣፋጭ ፡ መብልን ፡ ትጠላለች ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ ሥጋው ፡ እስከማይታይ ፡ ድረስ ፡ ይሰለስላል ፤

ተሸፍኖ ፡ የነበረውም ፡ ዐጥንት ፡ ይገለጣል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፥

ሕይወቱም ፡ ወደሚገድሏት ፡ ቀርባለች ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ የቀናውን ፡ መንገድ ፡ ለሰው ፡ ያስታውቀው ፡ ዘንድ ፥

ከሺሕ ፡ አንድ ፡ ኾኖ ፡ የሚተረጕም ፡ መልአክ ፡ ቢገኝለት ፥

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 24 ፤ እየራራለት ።

ቤዛ ፡ አግኝቻለኹና ፡

ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዳይወርድ ፡ አድነው ፡ ቢለው ፥

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 25 ፤ ሥጋው ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ ሥጋ ፡ ይለመልማል ፤

ወደጕብዝናውም ፡ ዘመን ፡ ይመለሳል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 26 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸልያል ፥

ርሱም ፡ ሞገስን ፡ ይሰጠዋል ፡

ፊቱንም ፡ በደስታ ፡ ያሳየዋል ፤

ለሰውም ፡ ጽድቁን ፡ ይመልስለታል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እየዘመረ ፦

እኔ ፡ በድያለኹ ፥ ቅኑንም ፡ አጣምሜያለኹ ፤

የሚገባኝንም ፡ ብድራት ፡ አልተቀበልኹም ፤

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 28 ፤ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንዳትወርድ ፡ አድኗታል ፥

ሕይወቴም ፡ ብርሃንን ፡ ታያለች ፡ ይላል ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡

ኹለት ፡ ጊዜና ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ያደርጋል ፤

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 30 ፤ ይህም ፡ ነፍሱን ፡ ከጕድጓድ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፥

በሕያዋንም ፡ ብርሃን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 31 ፤ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ አድምጥ ፥ እኔንም ፡ ስማ ፤

ዝም ፡ በል ፥ እኔም ፡ እናገራለኹ ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 32 ፤ ነገር ፡ ቢኖርኽ ፡ መልስልኝ ፤

ትጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹና ፡ ተናገር ።

ኢዮ. ፡ 33 ፡ 33 ፤ ያለዚያም ፡ እኔን ፡ ስማ ፤

ዝም ፡ በል ፥ እኔም ፡ ጥበብን ፡ አስተምርኻለኹ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 2 ፤ እናንተ ፡ ጥበበኞች ፥ ቃሌን ፡ ስሙ ፤

እናንተም ፡ ዐዋቂዎች ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ አድምጡ ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 3 ፤ ትናጋ ፡ መብልን ፡ እንደሚቀምስ ፥

ገሮ ፡ ቃልን ፡ ትለያለችና ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 4 ፤ ቅን ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ እንምረጥ ፤

መልካሙንም ፡ ነገር ፡ በመካከላችን ፡ እንወቅ ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 5 ፤ ኢዮብ ፦ እኔ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፥

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ፍርዴን ፡ አስወገደ ፤

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 6 ፤ ምንም ፡ እውነተኛ ፡ ብኾን ፡ እንደ ፡ ውሸተኛ ፡ ተቈጠርኹ ፤

ምንም ፡ ባልበድል ፡ ቍስሌ ፡ የማይፈወስ ፡ ነው ፡ ብሏል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 7-9 ፤ ኢዮብም ፦ በእግዚአብሔር ፡ መደሰት ፡

ለሰው ፡ ምንም ፡ አይጠቅምም ፡ ብሏልና ፥

ከበደለኞች ፡ ጋራ ፡ የሚተባበር ፥

ክፉ ፡ ከሚያደርጉስ ፡ ጋራ ፡ የሚኼድ ፥

መሳለቅን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣት ፡

እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ አእምሮ ፡ ያላችኹ ፡ ሰዎች ፥ ስሙኝ ፤

ክፋትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፥

በደልንም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ይራቅ ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 11 ፤ ለሰው ፡ ሥራውን ፡ ይመልስለታል ፥

ሰውም ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ያደርጋል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 12 ፤ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉ ፡ አይሠራም ፥

ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ ፍርድን ፡ ጠማማ ፡ አያደርግም ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 13 ፤ ምድርን ፡ ዐደራ ፡ የሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዓለምንስ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያኖረ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 14 ፤ ርሱ ፡ ልቡን ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ቢመልስ ፥

መንፈሱንና ፡ እስትንፋሱን ፡ ወደ ፡ ራሱ ፡ ቢሰበስብ ፥

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 15 ፤ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋል ፥

ሰውም ፡ ወደ ፡ ዐፈር ፡ ይመለሳል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 16 ፤ አስተዋይ ፡ ብትኾን ፡ ይህን ፡ ስማ ፤

የንግግሬንም ፡ ቃል ፡ አድምጥ ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 17 ፤ በእውኑ ፡ ጽድቅን ፡ የሚጠላ ፡ ይሠለጥናልን ፧

ጻድቅና ፡ ኀያል ፡ የኾነውስ ፡ በደለኛ ፡ ታደርገዋለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 18 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ ንጉሡን ፦ በደለኛ ፡ ነኽ ፥

መኳንንቱንም ፦ ክፉዎች ፡ ናችኹ ፡ ይላልን ፧

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 19 ፤ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ የእጁ ፡ ሥራ ፡ ናቸውና ፥

በአለቃዎች ፡ ፊት ፡ አያደላም ፥

ባለጠጋውንም ፡ ሰው ፡ ከድኻው ፡ ይበልጥ ፡ አይመለከትም ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 20 ፤ እነርሱ ፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ በድንገት ፡ ይሞታሉ ፤

ሕዝቡ ፡ ተንቀጥቅጦ ፡ ያልፋል ፥

ኀያላንም ፡ ያለእጅ ፡ ይነጠቃሉ ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 21 ፤ ዐይኖቹ ፡ በሰው ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ናቸው ፥

ርምጃውንም ፡ ኹሉ ፡ ያያል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 22 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ይሰወሩበት ፡ ዘንድ ፡

ጨለማ ፡ ወይም ፡ የሞት ፡ ጥላ ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 23 ፤ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመፈራረድ ፡ እንዲመጣ ፡

ጊዜ ፡ አይወሰንለትም ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 24 ፤ ታላላቆችን ፡ ያለምርመራ ፡ ይሰባብራል ፥

በእነርሱም ፡ ፋንታ ፡ ሌላዎችን ፡ ያቆማል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 25 ፤ ሥራቸውን ፡ ያውቃል ፤

እንዲደቅም ፡ በሌሊት ፡ ይገለባብጣቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 26 ፤ ሰዎች ፡ እያዩ ፡ እንደ ፡ ክፉዎች ፡ ይመታቸዋል ፤

ኢዮ. ፡ 34 ፡ 27 ፤ 28 ፤ የድኻውን ፡ ልቅሶ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያደርሱ ፡ ዘንድ ፥

ርሱም ፡ የችግረኛውን ፡ ድምፅ ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፥

ርሱን ፡ ከመከተል ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋልና ፥

ከመንገዱም ፡ ኹሉ ፡ አንዱን ፡ አልተመለከቱምና ።

አ.የ. ፡ 34 ፡ 29 ፤ በሕዝብ ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ቢኾን ፥

ርሱ ፡ ቢያሳርፍ ፡ የሚፈርድ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ፊቱንስ ፡ ቢሰውር ፡ የሚያየው ፡ ማን ፡ ነው ፧

አ.የ. ፡ 34 ፡ 30 ፤ ይህም ፡ ዝንጉ ፡ ሰው ፡ እንዳይነግሥ ፥

ሕዝቡም ፡ የሚያጠምድ ፡ እንዳይኖር ፡ ነው ።

አ.የ. ፡ 34 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርን ፦ እኔ ፡ ሳልበድል ፡ ቅጣት ፡ ተቀበልኹ ፤

አ.የ. ፡ 34 ፡ 32 ፤ የማላየውን ፡ ነገር ፡ አንተ ፡ አስተምረኝ ፤

ኀጢአትንም ፡ ሠርቼ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ደግሜ ፡ አልሠራም ፡ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

አ.የ. ፡ 34 ፡ 33 ፤ በእውኑ ፡ አንተ ፡ ጥለኸዋልና ፥

ፍዳው ፡ አንተ ፡ እንደምትወደው ፡ ይኾናልን ፧

አንተ ፡ ትመርጣለኽ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ፤

ስለዚህ ፡ የምታውቀውን ፡ ተናገር ።

አ.የ. ፡ 34 ፡ 34 ፤ የሚሰሙኝ ፡ ጥበበኞች ፡ ኹሉ ፥

አስተዋዮችም ፡ እንዲህ ፡ ይሉኛል ።

አ.የ. ፡ 34 ፡ 35 ፤ አዮብ ፡ ያለዕውቀት ፡ ተናግሯል ፥

ቃሉም ፡ በአእምሮ ፡ አይደለችም ።

አ.የ. ፡ 34 ፡ 36 ፤ አዮብ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ምነው ፡ በተፈተነ ፡ ኖሮ! ፥

ርሱ ፡ እንደ ፡ ክፉዎች ፡ መልሷልና ፤

አ.የ. ፡ 34 ፡ 37 ፤ በኀጢአቱም ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ ጨምሯልና ፥

በእኛም ፡ መካከል ፡ በእጁ ፡ ያጨበጭባልና ፥

ቃልንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ያበዛልና ።

መጽሐፈ ፡ አዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

አ.የ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

አ.የ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ ይህ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታስባለኽን ፧

ወይስ ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እኔ ፡ ጻድቅ ፡ ነኝ ፡ ትላለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ አንተ ፦ ምን ፡ ጥቅም ፡ አለኽ ፧

ኀጢአት ፡ ሠርቼ ፡ ከማገኘው ፡ ይልቅ ፡ ኀጢአት ፡ ባልሠራ ፡ ኖሮ ፡ ምን ፡ እጠቀማለኹ ፧ ብለኽ ፡ ጠይቀኻልና ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ለአንተና ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ ለባልንጀራዎችኽ ፡ እመልሳለኹ ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ ዐይኖችኽን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አቅንተኽ ፡ እይ ፤

ከአንተም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ደመናት ፡ ተመልከት ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ ኀጢአት ፡ ብትሠራ ፡ ምን ፡ ትጐዳዋለኽ ፧

መተላለፍኽስ ፡ ቢበዛ ፡ ምን ፡ ታደርገዋለኽ ፧

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ ጻድቅስ ፡ ብትኾን ፡ ምን ፡ ትሰጠዋለኽ ፧

ወይስ ፡ ከእጅኽ ፡ ምንን ፡ ይቀበላል ፧

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ክፋትኽ ፡ ይጐዳዋል ፤

ለሰውም ፡ ልጅ ፡ ጽድቅኽ ፡ ይጠቅመዋል ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ ከግፍ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሰዎች ፡ ይጮኻሉ ፤

ከኀያላንም ፡ ክንድ ፡ የተነሣ ፡ ለርዳታ ፡ ይጠራሉ ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በሌሊት ፡ መዝሙርን ፡ የሚሰጥ ፥

ከምድርም ፡ እንስሳዎች ፡ ይልቅ ፡ የሚያስተምረን ፡

ከሰማይም ፡ ወፎች ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኞች ፡ የሚያደርገን ፤

ፈጣሪዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ የሚል ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ትዕቢት ፡ ይጮኻሉ ፥

ርሱ ፡ ግን ፡ አይመልስላቸውም ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 13 ፤ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ አይሰማም ፥

ኾሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክም ፡ አይመለከተውም ፤

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 14 ፤ ይልቁንም ፦ አላየውም ፤

ነገሩ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ነው ፥ እኔም ፡ አጠብቀዋለኹ ፡ ስትል ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 15 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በቀጣው ፡ አልጐበኘምና ።

በኀጢአት ፡ እጅግ ፡ አያስብም ፡ ትላለኽ ።

ኢዮ. ፡ 35 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ኢዮብ ፡ አፉን ፡ በከንቱ ፡ ይከፍታል ፥

ያለዕውቀትም ፡ ቃሉን ፡ ያበዛል ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ ኤሊሁም ፡ ደግሞ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ ገና ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚነገር ፡ አለኝና ፡

ጥቂት ፡ ቈየኝ ፥ እኔም ፡ አስታውቅኻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ ዕውቀቴን ፡ ከሩቅ ፡ አመጣለኹ ፥

ፈጣሪዬንም ፦ ጻድቅ ፡ ነው ፡ እላለኹ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 4 ፤ ቃሌ ፡ በእውነት ፡ ያለሐሰት ፡ ነው ፤

በዕውቀትም ፡ ፍጹም ፡ የኾነ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ኀያል ፡ ነው ፥ ማንንም ፡ አይንቅም ፤

ርሱም ፡ በማስተዋል ፡ ብርታት ፡ ኀያል ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ የበደለኞችን ፡ ሕይወት ፡ አያድንም ፤

ለችግረኞች ፡ ግን ፡ ፍርዱን ፡ ይሰጣል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 7 ፤ ዐይኑን ፡ ከጻድቃን ፡ ላይ ፡ አያርቅም ፤

ለዘለዓለምም ፡ ከነገሥታት ፡ ጋራ ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ያስቀምጣቸዋል ፥

እነርሱም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 8 ፤ በሰንሰለት ፡ ቢታሰሩ ፥

ወይም ፡ በችግር ፡ ገመድ ፡ ቢጠመዱ ፥

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 9 ፤ ሥራቸውንና ፡ መተላለፋቸውን ፡

በትዕቢትም ፡ እንዳደረጉ ፡ ይናገራቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 10 ፤ ጐሯቸውን ፡ ለተግሣጽ ፡ ይከፍተዋል ፥

ከኀጢአትም ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ያዛቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 11 ፤ ቢሰሙ ፡ ቢያገለግሉትም ፥

ዕድሜያቸውን ፡ በልማት ፥

ዘመናቸውንም ፡ በተድላ ፡ ይፈጽማሉ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ባይሰሙ ፡ ግን ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፋሉ ፥

ያለዕውቀትም ፡ ይሞታሉ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 13 ፤ ዝንጉዎች ፡ ግን ፡ ቍጣን ፡ ያዘጋጃሉ ፤

ርሱም ፡ ባሰራቸው ፡ ጊዜ ፡ አይጮኹም ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 14 ፤ በሕፃንነታቸው ፡ ሳሉ ፡ ይሞታሉ ፥

ሕይወታቸውም ፡ በሰዶማውያን ፡ መካከል ፡ ይጠፋል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 15 ፤ የተቸገረውን ፡ በችግሩ ፡ ያድነዋል ፤

በመከራም ፡ ጐሯቸውን ፡ ይገልጣል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 16 ፤ እንዲሁም ፡ አንተን ፡ ከመከራ ፡

ችግር ፡ ወደሌለበት ፡ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ስፍራ ፡ በወሰደኽ ፡ ነበር ፥

በማእድኽ ፡ ላይ ፡ የተዘጋጀውም ፡ ስብ ፡ በሞላበት ፡ ነበር ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 17 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በበደለኞች ፡ ፍርድ ፡ የተሞላኽ ፡ ነኽ ፤

ስለዚህ ፡ ፍርድና ፡ ብይን ፡ ይይዝኻል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 18 ፤ ቍጣ ፡ ለስድብ ፡ አያታልኽ ፤

የማማለጃም ፡ ብዛት ፡ ፈቀቅ ፡ አያድርግኽ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 19 ፤ ባለጠግነትኽ ፡ የኀይልኽም ፡ ብርታት ፡ ኹሉ ፡

ያለችግር ፡ እንድትኾን ፡ ሊረዳኽ ፡ ይችላልን ፧

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 20 ፤ ወገኖች ፡ ከስፍራቸው ፡ የሚወጡበትን ፡ ሌሊት ፡ አትመኝ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 21 ፤ ከመከራ ፡ ይልቅ ፡ ይህን ፡ መርጠኻልና ፥

ኀጢአትን ፡ እንዳትመለከት ፡ ተጠንቀቅ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 22 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኀይሉ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ፤

እንደ ፡ ርሱስ ፡ ያለ ፡ አስተማሪ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 23 ፤ መንገዱን ፡ ማን ፡ አዘዘለት ፧

ወይስ ፦ ኀጢአትን ፡ ሠርተኻል ፡ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 24 ፤ ሰዎች ፡ የዘመሩትን ፡ ሥራውን ፡ ታከብር ፡ ዘንድ ፡ ዐስብ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 25 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ተመልክተውታል ፤

ሰውም ፡ ከሩቅ ፡ ያየዋል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 26 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ አናውቀውም ።

የዘመኑም ፡ ቍጥር ፡ አይመረመርም ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 27 ፤ የውሃውን ፡ ነጠብጣብ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይስባል ፥

ዝናብም ፡ ከጉም ፡ ይንጠባጠባል ፤

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 28 ፤ ደመናት ፡ ያዘንባሉ ፥

በሰዎችም ፡ ላይ ፡ በብዙ ፡ ያንጠባጥባሉ ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 29 ፤ የደመናውንም ፡ መዘርጋት ፥

የማደሪያውንም ፡ ነጐድጓድ ፡ የሚያስተውል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 30 ፤ እንሆ ፥ በዙሪያው ፡ ብርሃኑን ፡ ይዘረጋል ፤

የባሕሩንም ፡ ጥልቀት ፡ ይከድናል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 31 ፤ በእነዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ይፈርዳል ፤

ብዙም ፡ ምግብ ፡ ይሰጣል ።

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 32 ፤ እጆቹን ፡ በብርሃን ፡ ይሰውራል ፥

በጠላቱም ፡ ላይ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ያዘዋል ፤

ኢዮ. ፡ 36 ፡ 33 ፤ የነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይናገራል ፤

እንስሳዎችም ፡ ደግሞ ፡ ስለሚመጣው ፡ ውሽንፍር ፡ ይጮኻሉ ።

መጽሐፈ ፡ አዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 1 ፤ ስለዚህም ፡ ልቤ ፡ ተንቀጠቀጠ ፥

ከስፍራውም ፡ ተንቀሳቀሰ ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 2 ፤ የድምፁን ፡ መትመም ፡ ስሙ ፥

ከአፉም ፡ የሚወጣውን ፡ ጕርምርምታ ፡ አድምጡ ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 3 ፤ ርሱን ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ ዙሉ ፡ ታች ፥

ብርሃኑንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይሰዳል ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 4 ፤ በስተኋላው ፡ ድምፅ ፡ ይጮኻል ፤

በግርማውም ፡ ድምፅ ፡ ያንጐደጉዳል ፤

ድምፁም ፡ በተሰማ ፡ ጊዜ ፡

መብረቁን ፡ አይከለክልም ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በድምፁ ፡ ድንቅኛ ፡ ያንጐደጉዳል ፤

እኛም ፡ የማናስተውለውን ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 6 ፤ በረዶውንና ፡ ውሽንፍሩን ፡ ብርቱንም ፡ ዝናብ ፦

በምድር ፡ ላይ ፡ ውደቁ ፡ ይላል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 7 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሥራውን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡

የሰውን ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያትማል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 8 ፤ አውሬዎቹም ፡ ወደ ፡ ጫካው ፡ ይገባሉ ፥

በዋሻቸውም ፡ ይቀመጣሉ ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 9 ፤ ከተሰወረ ፡ ማደሪያውም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥

ከሰሜንም ፡ ብርድ ፡ ይወጣል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 10 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ውርጭ ፡ ተሰጥቷል ፤

የውሃዎችም ፡ ስፋት ፡ ይጠባል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 11 ፤ የውሃውንም ፡ ሙላት ፡ በደመና ፡ ላይ ፡ ይጭናል ፤

የብርሃኑንም ፡ ደመና ፡ ይበታትናል ፤

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 12 ፤ 13 ፤ ለተግሣጽ ፡ ወይም ፡ ለምድሩ ፡ ወይም ፡ ለምሕረት ፡ ቢኾን ፥

ሰው ፡ በሚኖርበት ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡

ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡

ፈቃዱ ፡ ወደ ፡ መራችው ፡ ይዞራል ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 14 ፤ ኢዮብ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስማ ፤

ቁም ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ተኣምራት ፡ ዐስብ ።

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 15 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ እንደሚያዛቸው ፥

የደመናውንም ፡ ብርሃን ፡ እንዴት ፡ እንደሚያበራ ፡ ዐውቀኻልን ፧

ኢዮ. ፥ 37 ፥ 16 ፤ ወይስ ፡ የደመናውን ፡ ሚዛን ፥

ወይስ ፡ በዕውቀት ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ተኣምራት ፡ ዐውቀኻልን ፧

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 17 ፤ በደቡብ ፡ ነፋስ ፡ ምድር ፡ ጸጥ ፡ ባለች ፡ ጊዜ ፥

ልብስኽ ፡ የሞቀች ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 18 ፤ እንደ ፡ ቀለጠ ፡ መስተዋት ፡

ብርቱ ፡ የኾኑትን ፡ ሰማያት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ልትዘረጋ ፡ ትችላለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 19 ፤ እኛ ፡ ከጨለማ ፡ የተነሣ ፡ በሥርዐት ፡ መናገር ፡ አንችልምና ፥

የምንለውን ፡ አስታውቀን ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 20 ፤ ማንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ቢናገር ፡ ፈጽሞ ፡ ይዋጣልና ፥

እኔ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ብወድ ፡ ሰው ፡ ይነግረዋልን ፧

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 21 ፤ አኹንም ፡ ነፋስ ፡ ዐልፎ ፡ ካጠራቸው ፡ በኋላ ፥

ሰው ፡ በሰማያት ፡ የሚበራውን ፡ ብርሃን ፡ ሊመለከት ፡ አይችልም ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 22 ፤ ከሰሜን ፡ ወርቅ ፡ የሚመስል ፡ ጌጠኛ ፡ ብርሃን ፡ ይወጣል ፤

በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈራ ፡ ግርማ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 23 ፤ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ አምላክን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፤

በኀይል ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤

በፍርድና ፡ በጽድቅም ፡ አያስጨንቅም ።

ኢዮ. ፡ 37 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ሰዎች ፡ ይፈሩታል ፤

በልባቸውም ፡ ጠቢባን ፡ የኾኑትን ፡ ኹሉ ፡ አይመለከትም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ለኢዮብ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 2 ፤ ያለዕውቀት ፡ በሚነገር ፡ ቃል ፡

ምክርን ፡ የሚያጨልም ፡ ይህ ፡ ማነው ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 3 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፤

እጠይቅኻለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 4 ፤ ምድርን ፡ በመሠረትኹ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ወዴት ፡ ነበርኽ ፧

ታስተውል ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ተናገር ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 5 ፤ ብታውቅስ ፡ መሠፈሪያዋን ፡ የወሰነ ፥

በላይዋስ ፡ የመለኪያ ፡ ገመድ ፡ የዘረጋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 6-7 ፤ አጥቢያ ፡ ኮከቦች ፡ በአንድነት ፡ ሲዘምሩ ፥

የእግዚአብሔርም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ እልል ፡ ሲሉ ፥

መሠረቶቿ ፡ በምን ፡ ላይ ፡ ተተክለው ፡ ነበር ፧

የማእዘኗንስ ፡ ድንጋይ ፡ ያቆመ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 8 ፤ ከማሕፀን ፡ እንደሚወጣ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡

ባሕርን ፡ በመዝጊያዎች ፡ የዘጋ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 9 ፤ ደመናውን ፡ ለልብሱ ፥

ጨለማንም ፡ ለመጠቅለያው ፡ አደረግኹ ፤

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 10 ፤ ድንበሩን ፡ በዙሪያው ፡ አድርጌ ፥

መወርወሪያዎቹንና ፡ መዝጊያዎቹን ፡ አኑሬ ።

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 11 ፤ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ድረሺ ፥ አትለፊ ፤

በዚህም ፡ ለትዕቢተኛው ፡ ማዕበልሽ ፡ ገደብ ፡ ይኹን ፡ አልኹ ።

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 12 ፤ 13 ፤ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ይይዝ ፡ ዘንድ ፥

ከርሷም ፡ በደለኞች ፡ ይናወጡ ፡ ዘንድ ፥

በእውኑ ፡ ከተወለድኽ ፡ ዅምሮ ፡ ማለዳን ፡ አዘኻልን ፧

ለወገግታም ፡ ስፍራውን ፡ አስታወቀኽዋልን ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 14 ፤ ጭቃ ፡ ከማኅተም ፡ በታች ፡ እንደሚለወጥ ፡ እንዲሁ ፡ ርሷ ፡ ትለወጣለች ፤

ነገርም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ተቀልሟል ።

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 15 ፤ ከበደለኞች ፡ ብርሃናቸው ፡ ተከልክሏል ፥

ከፍ ፡ ያለውም ፡ ክንድ ፡ ተሰብሯል ።

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 16 ፤ ወደባሕር ፡ ምንጭስ ፡ ውስጥ ፡ ገብተኻልን ፧

በቀላዩስ ፡ መሠረት ፡ ውስጥ ፡ ተመላልሰኻልን ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 17 ፤ የሞት ፡ በሮች ፡ ተገልጠውልኻልን ፧

የሞትንስ ፡ ጥላ ፡ ደጆች ፡ አይተኻልን ፧

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 18 ፤ ምድርንስ ፡ በስፋቷ ፡ አስተውለኻታልን ፧

ኾሉን ፡ ዐውቀኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገር ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 19 ፤ 20 ፤ ወደ ፡ ዳርቻው ፡ ትነዳው ፡ ዘንድ ፥

ወደ ፡ ቤቱም ፡ የሚያደርሰውን ፡ ጐዳና ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፥

የብርሃን ፡ መኖሪያ ፡ መንገድ ፡ የት ፡ ነው ፧

የጨለማውስ ፡ ቦታ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተወልደኽ ፡ ነበርና ፥

የዕድሜኽም ፡ ቍጥር ፡ ብዙ ፡ ነውና ፤

በእውነት ፡ አንተ ፡ ሳታውቅ ፡ አትቀርም ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 22 ፤ በእውኑ ፡ ወደበረዶው ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ ገብተኻልን ፧

የበረዶውንስ ፡ ቅንጣት ፡ ቤተ ፡ መዛግብት ፡ አይተኻልን ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 23 ፤ ይኸውም ፡ ለመከራ ፡ ጊዜ ፡ ለሰልፍና ፡ ለጦርነት ፡ ቀን ፡ የጠበቅኹት ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 24 ፤ ብርሃንስ ፡ በምን ፡ መንገድ ፡ ይከፈላል ፧

የምሥራቅስ ፡ ነፋስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ይበተናል ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 25 ፤ 26 ፤ ባድማውንና ፡ ውድማውን ፡ እንዲያጠግብ ፥

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 27 ፤ ሣሩንም ፡ እንዲያበቅል ፥

ማንም ፡ በሌለባት ፡ ምድር ፡ ላይ ፥

ሰውም ፡ በሌለባት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ላይ ፡ ዝናብን ፡ ያዘንብ ፡ ዘንድ ፥

ለፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ መንዶልዶያውን ፥

ወይስ ፡ ለሚያንጐደጉድ ፡ መብረቅ ፡ መንገድን ፡ ያበጀ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 28 ፤ በእውኑ ፡ ለዝናብ ፡ አባት ፡ አለውን ፧

ወይስ ፡ የጠልን ፡ ነጠብጣብ ፡ የወለደ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 29 ፤ በረዶስ ፡ ከማን ፡ ማሕፀን ፡ ወጣ ፧

የሰማዩንስ ፡ ዐመዳይ ፡ ማን ፡ ወለደው ፧

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 30 ፤ ውሃዎች ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ ጠነከሩ ፥

የቀላዩም ፡ ፊት ፡ ረግቷል ።

ኢዮ. ፡ 38 ፡ 31 ፤ በእውኑ ፡ የሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ ዘለላ ፡ ታስር ፡ ዘንድ ፥

ወይስ ፡ ኦሪዮን ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 32 ፤ ወይስ ፡ ማዛሮት ፡ የሚባሉትን ፡ ከዋክብት ፡ በጊዜያቸው ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፥

ወይስ ፡ ድብ ፡ የሚባለውን ፡ ኮከብ ፡ ከልጆቹ ፡ ጋራ ፡ ትመራ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 33 ፤ የሰማይን ፡ ሥርዐት ፡ ታውቃለኽን ፡፡

በምድርስ ፡ ለይ ፡ እንዲሠለጥን ፡ ልታደርግ ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 34 ፤ የውሃዎች ፡ ብዛት ፡ ይሸፍንኽ ፡ ዘንድ ፡

ቃልኽን ፡ ወደ ፡ ደመናት ፡ ታነሣ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 35 ፤ መብረቆች ፡ ኼደው ፦ እንሆ ፥ እዚህ ፡ አለን ፡ ይሉኽ ፡ ዘንድ ፡

ልትልካቸው ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 36 ፤ በውስጡስ ፡ ጥበብን ፡ ያኖረ ፥

ለሰውስ ፡ ልብ ፡ ማስተዋልን ፡ የሰጠ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 37 ፤ 38 ፤ የሰማይን ፡ ደመና ፡ በጥበቡ ፡ ሊቈጥር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

ትቢያ ፡ በተበጠበጠ ፡ ጊዜ ፥

ጓሎቹም ፡ በተጣበቁ ፡ ጊዜ ፥

የሰማይን ፡ ረዋት ፡ ሊያዘነብል ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 39 ፤ 40 ፤ በዋሻቸው ፡ ውስጥ ፡ ተጋድመው ፥

በጫካም ፡ ውስጥ ፡ አድብተው ፡ ሳሉ ፥

ለአንበሳዩቱ ፡ ዐደን ፡ ታድናለኽን ፡፡

የልጆቿንስ ፡ ነፍስ ፡ ታጠግብ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 38 ፥ 41 ፤ ልጆቹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲጮኹ ፥

የሚበሉትም ፡ ዐጥተው ፡ ሲቅበዘበዙ ፥

ለቀኑራ ፡ መብልን ፡ የሚሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ኢዮ. ፥ 39 ፥ 1 ፤ የበረሓ ፡ ፍየል ፡ የምትወልድበትን ፡ ጊዜ ፡ ታውቃለኽን ፡፡

ዋላዩቱስ ፡ የምታምጥበትን ፡ ጊዜ ፡ ትመለከታለኽን ፡፡

ኢዮ. ፥ 39 ፥ 2 ፤ ርሷ ፡ የምትፈጽመውንስ ፡ ወራት ፡ ትቈጥራለኽን ፡፡

የምትወልድበትንስ ፡ ጊዜ ፡ ታውቃለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 3 ፤ ይንበረከካሉ ፥ ልጆቻቸውንም ፡ ይወልዳሉ ፥

ከምጣቸውም ፡ ያርፋሉ ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 4 ፤ ልጆቻቸው ፡ ይጠነክራሉ ፥

በሜዳም ፡ ያድጋሉ ፤

ይወጣሉ ፥ ወደ ፡ እነርሱም ፡ አይመለሱም ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 5 ፤ የሜዳውስ ፡ አህያ ፡ ሐራነት ፡ ማን ፡ አወጣው ፧

የበረሓውንስ ፡ አህያ ፡ ከእስራቱ ፡ ማን ፡ ፈታው ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 6 ፤ በረሓውን ፡ ለርሱ ፡ ቤት ፡ አድርጌ ፡ ሰጠኹት ፤

መኖሪያውም ፡ በጨው ፡ ምድር ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 7 ፤ በከተማ ፡ ውካታ ፡ ይዘብታል ፤

የነጂውን ፡ ጩኸት ፡ አይሰማም ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 8 ፤ ተራራውን ፡ እንደ ፡ መሰምሪያው ፡ ይመለከተዋል ፥

ለምለሙንም ፡ ሹሉ ፡ ይፈልጋል ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 9 ፤ ጐሽ ፡ ያገለግልኽ ፡ ዘንድ ፡ ይታዘዛልን ፧

ወይስ ፡ በግርግምኽ ፡ አጠገብ ፡ ያድራልን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 10 ፤ ጐሽ ፡ ይተልምልኽ ፡ ዘንድ ፡ ትጠምደዋለኽን ፧

ወይስ ፡ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ በዕርሻ ፡ ላይ ፡ ይጐለጉላልን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 11 ፤ ጉልበቱስ ፡ ብርቱ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ትታመነዋለኽን ፧

ተግባርኽንስ ፡ ለርሱ ፡ ትተዋለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 12 ፤ ዘርኽንስ ፡ ይመልስልኽ ፡ ዘንድ ፥

በዐውድማኽስ ፡ ያከማችልኽ ፡ ዘንድ ፡ ትታመነዋለኽን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 13 ፤ የሰጐን ፡ ክንፍ ፡ በደስታ ፡ ይንቀሳቀሳል ፤

ነገር ፡ ግን ፡ ክንፉና ፡ ላባው ፡ ጭምተኛ ፡ ነውን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 14 ፤ ዕንቊላሏን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ትተዋለች ፥

በዐፈርም ፡ ውስጥ ፡ ታሞቀዋለች ፤

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 15 ፤ እግር ፡ ይሰብረው ፡ ዘንድ ፥

የምድረ ፡ በዳም ፡ አውሬ ፡ ይረግጠው ፡ ዘንድ ፡ ትረሳለች ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 16 ፤ የርሷ ፡ እንዳልኾኑ ፡ በልጆቿ ፡ ትጨክናለች ።

በከንቱም ፡ ብትሠራ ፡ አትፈራም ፤

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥበብን ፡ ከርሷ ፡ ከልክሏልና ፥

ማስተዋልንም ፡ አልሰጣትምና ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ስትል ፡

በፈረስና ፡ በፈረሰኛው ፡ ትሳለቃለች ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 19 ፤ ለፈረስ ፡ ጕልበቱን ፡ ሰጥተኸዋልን ፧

ዐንገቱንስ ፡ ጋማ ፡ አልብሰኸዋልን ፧

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 20 ፤ እንደ ፡ አንበጣስ ፡ አፈናጠርኸውን ፧

የማንኰራፋቱ ፡ ክብር ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 21 ፤ በኰቴው ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ይጐደፍራል ፥

በጕልበቱም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤

ሰይፍም ፡ የታጠቁትን ፡ ለመገናኘት ፡ ይወጣል ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 22 ፤ በፍርሀት ፡ ላይ ፡ ይሥቃል ፥

ርሱም ፡ አይደነግጥም ፤

ከሰይፍም ፡ ፊት ፡ አይመለስም ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 23 ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ የፍላጻ ፡ ኰረጆና ፡ ብልጭልጭ ፡ የሚል ፡ ጦር ፡

ሠላጢንም ፡ ያንኳኳሉ ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 24 ፤ በጭካኔና ፡ በቍጣ ፡ መሬትን ፡ ይውጣል ፤

የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ቢሰማ ፡ አይቆምም ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 25 ፤ የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ሲሰማ ፦ ዕሠይ! ፡ ይላል ፤

ከሩቅ ፡ ኾኖ ፡ ሰልፍንና ፡ የአለቃዎቹን ፡ ጩኸት ፥

የሰራዊቱንም ፡ ውካታ ፡ ያሸታል ።

ኢዮ. ፡ 39 ፡ 26 ፤ በእውኑ ፡ ከጥበብኽ ፡ የተነሣ ፡ ጭልፊት ፡ ያንጥበባልን ፧

ወይስ ፡ ክንፎቹን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይዘረጋልን ፧

አ.ዮ. ፡ 39 ፡ 27 ፤ በአፍኽ ፡ ትእዛዝ ፡ ንስር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልን ፧

ቤቱንስ ፡ በአርያም ፡ ላይ ፡ ያደርጋልን ፧

አ.ዮ. ፡ 39 ፡ 28 ፤ በገደል ፡ ላይ ፡ ይኖራል ፤

በገደሉ ፡ ገመገምና ፡ በጥጉ ፡ ያድራል ።

አ.ዮ. ፡ 39 ፡ 29 ፤ በዚያም ፡ ኾኖ ፡ የሚነጥቀውን ፡ ይጐበኛል ፤

ዐይኑም ፡ በሩቅ ፡ ትመለከታለች ።

አ.ዮ. ፡ 39 ፡ 30 ፤ ጫጩቶቹም ፡ ደም ፡ ይጠጣሉ ፤

በድን ፡ ባለባትም ፡ ስፍራ ፡ ርሱ ፡ በዚያ ፡ አለ ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፡ ምዕራፍ ፡ 40 ።

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መለሰ ፡ ኢዮብንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 2 ፤ በእውኑ ፡ የሚከራከር ፡ ሰው ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ጋራ ፡ ይከራከራልን ፧

ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ የሚዋቀሥ ፡ ርሱ ፡ ይመልስለት ።

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 3 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ወራዳ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ የምመልስልኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

እጄን ፡ በአፌ ፡ ላይ ፡ እጭናለኹ ።

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 5 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናገርኹ ፥ አልመልስምም ፤

ኹለተኛ ፡ ጊዜም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አልናገርም ።

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ለኢዮብ ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ወንድ ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፤

እጠይቅኻለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 8 ፤ በእውኑ ፡ ፍርዴን ፡ ታፈርሳለኽን ፧

አንተስ ፡ ጻድቅ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ትፈርዳለኽን ፧

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 9 ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡ ያለ ፡ ክንድ ፡ አለኽን ፧

ወይስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ታንጐደጉዳለኽን ፧

አ.ዮ. ፡ 40 ፡ 10 ፤ በታላቅነትና ፡ በልዕልና ፡ ተላበስ ፤

በክብርና ፡ በግርማም ፡ ተጐናጸፍ ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 11 ፤ የቀሥጣኽን ፡ ፈሳሽ ፡ አፍስ ፤

ትዕቢተኛውንም ፡ ኹሉ ፡ ተመልክተኽ ፡ አዋርደው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 12 ፤ ትዕቢተኛውንም ፡ ኹሉ ፡ ተመልከት ፥ ዝቅ ፡ ዝቅም ፡ አድርገው ፤

በደለኞችንም ፡ ወዲያውኑ ፡ ርገጣቸው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 13 ፤ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ በአንድነት ፡ ሰውራቸው ፤

በተሸሸገም ፡ ስፍራ ፡ ፊታቸውን ፡ ሸፍን ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ቀኝ ፡ እጅኽ ፡ ታድንኽ ፡ ዘንድ ፡ እንድትችል ፡

እኔ ፡ ደግሞ ፡ እመሰክርልኻለኹ ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 15 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የሠራኹትን ፡ ጕማሬ ፥ እስኪ ፥ ተመልከት ፤

እንደ ፡ በሬ ፡ ሣር ፡ ይበላል ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 16 ፤ እንሆ ፥ ብርታቱ ፡ በወገቡ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤

ኀይሉም ፡ በሆዱ ፡ ኻሞማት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 17 ፤ ኻራቱን ፡ እንደ ፡ ጥድ ፡ ዛፍ ፡ ያወዛውዛል ፤

የወርቹ ፡ ኻሞማት ፡ የተጐነጐነ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 18 ፤ ዐጥንቱ ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ አገዳ ፡ ነው ፤

አካላቱ ፡ እንደ ፡ ብረት ፡ ዘንጎች ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 19 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ አውራ ፡ ነው ፤

ሠሪውም ፡ ሰይፉን ፡ ሰጠው ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 20 ፤ የሜዳ ፡ እንስሳዎች ፡ ኹሉ ፡ የሚጫወቱበት ፡ ተራራ ፡

ምግብን ፡ ያበቅልለታል ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 21 ፤ ጥላ ፡ ካለው ፡ ዛፍ ፡ በታች ፥

በደንገልና ፡ በረግረግ ፡ ውስጥ ፡ ይተኛል ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 22 ፤ ጥላ ፡ ያለው ፡ ዛፍ ፡ በጥላው ፡ ይሰውረዋል ፤

የወንዝ ፡ አሓያ ፡ ዛፎች ፡ ይከቡታል ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 23 ፤ እንሆ ፥ ወንዙ ፡ ቢጐርፍ ፡ አይደነግጥም ፤

የ-ርዳኖስም ፡ እስከ ፡ አፉ ፡ ድረስ ፡ ቢፈስ ፡ ርሱ ፡ ይተማመናል ።

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 24 ፤ ዐይኖቹ ፡ እያዩ ፡ ይያዛልን ፥

አፍንጫውስ ፡ በወጥመድ ፡ ይበሳልን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 25 ፤ በእውኑ ፡ አዞውን ፡ በመቃጥን ፡ ታወጣለኽን ፥

ምላሱንስ ፡ በገመድ ፡ ታስረዋለኽን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 26 ፤ ወይስ ፡ ስናጋ ፡ በአፍንጫው ፡ ታደርጋለኽን ፥

ወይስ ፡ በችንካር ፡ ጕንጩን ፡ ትበሳለኽን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 27 ፤ በእውኑ ፡ ወዳንተ ፡ እጅግ ፡ ይለምናልን ፥

በጣፈጠስ ፡ ቃል ፡ ይናገርኻልን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 28 ፤ በእውኑ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይገባልን ፥

ወይስ ፡ ለዘለዓለም ፡ ባሪያ ፡ ታደርገዋለኽን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 29 ፤ ከወፍ ፡ ጋራ ፡ እንደምትጫወት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትጫወታለኽን ፥

ወይስ ፡ ለሴት ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ታስረዋለኽን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 30 ፤ አጥማጆች ፡ በርሱ ፡ ይከራከራሉን ፥

ወይስ ፡ ነጋዴዎች ፡ ያካፍሉታልን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 31 ፤ በእውኑ ፡ ቍርበቱን ፡ በጫሬ ፥

ራሱንስ ፡ በዓሣ ፡ ጦር ፡ ትሞላዋለኽን ፥

ኢዮ. ፡ 40 ፡ 32 ፤ እጅኽን ፡ በላዩ ፡ ጫን ፤

ሰልፉን ፡ ዐስብ ፥ እንግዲህም ፡ አትድገም ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ ተስፋው ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤

ያየው ፡ ኹሉ ፡ ስንኳ ፡ በፊቱ ፡ ይዋረዳል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 2 ፤ ያንቀሳቅሰውም ፡ ዘንድ ፡ የሚደፍር ፡ የለም ፤

እንግዲህ ፡ በፊቴ ፡ መቆም ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፥

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 3 ፤ እመልስለትስ ፡ ዘንድ ፡ መገሥመሪያ ፡ የሰጠኝ ፡ ማን ፡ ነው ፥

ከሰማይ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ያለው ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 4 ፤ ስለ ፡ አካላቱና ፡ ስለ ፡ ብርቱ ፡ ኀይሉ ፥

ስለ ፡ መልካም ፡ ሰውነቱ ፡ ዝም ፡ አልልም ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 5 ፤ የውጪ ፡ ልብሱን ፡ ማን ፡ ይገፈል ፧

በጥንድ ፡ መንጋጋውስ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ ይገባል ፧

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 6 ፤ የፊቱንስ ፡ ደጆች ፡ የሚከፍት ፡ ማን ፡ ነው ፧

በጥርሶቹ ፡ ዙሪያ ፡ ግርማ ፡ አለ ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 7 ፤ ቅርፊቶቹ ፡ ጠንካራ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ርሱ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ነው ፤

በጠባብ ፡ ማተሚያ ፡ እንደ ፡ ታተሙ ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 8 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተቀራረቡ ፡ ናቸውና ፥

ነፋስ ፡ በመካከላቸው ፡ መግባት ፡ አይችልም ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 9 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ የተገጣጠሙ ፡ ናቸው ፤

እስከማይለያዩም ፡ ድረስ ፡ ተያይዘዋል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 10 ፤ እንጥሽታው ፡ ብልጭታ ፡ ያወጣል ፥

ዐይኖቹም ፡ እንደ ፡ ወገግታ ፡ ናቸው ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 11 ፤ ከአፉ ፡ ፋናዎች ፡ ይወጣሉ ፥

የእሳትም ፡ ፍንጣሪ ፡ ይረጫል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 12 ፤ እንደ ፡ ፈላ ፡ ድስትና ፡ እንደሚቃጠል ፡ ሸምበቆ ፡

ከአንፍንጫው ፡ ጢስ ፡ ይወጣል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 13 ፤ እስትንፋሱ ፡ ከሰልን ፡ ታቃጥላለች ፥

ነበልባልም ፡ ከአፉ ፡ ይወጣል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 14 ፤ በዐንገቱ ፡ ኀይል ፡ ታድራለች ፤

ግርማ ፡ በፊቱ ፡ ይዘፍናል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 15 ፤ የሥጋውም ፡ ቅርፊት ፡ የተጣበቀ ፡ ነው ፤

እስከማይንቀሳቀሱም ፡ ድረስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጸንተዋል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 16 ፤ ልቡ ፡ እንደ ፡ ድንጋይ ፡ የደነደነ ፡ ነው ፤

እንደ ፡ ወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ የጸና ፡ ነው ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 17 ፤ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ኀያላን ፡ ይፈራሉ ፤

ከድንጋጤም ፡ የተነሣ ፡ ያብዳሉ ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 18 ፤ ሰይፍና ፡ ጦር ፥ ፍላጻና ፡ መውጊያም ፡ ቢያገኙት ፡ አያሸንፉትም ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 19 ፤ ብረትን ፡ እንደ ፡ ገለባ ፥

ናስንም ፡ እንደ ፡ ነቀዘ ፡ ዕንጨት ፡ ይቈጥራቸዋል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 20 ፤ ፍላጻ ፡ ሊያባርረው ፡ አይችልም ፤

የወንጭፍም ፡ ድንጋዮች ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ይኾኑለታል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 21 ፤ በሎታውን ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ይቈጥረዋል ፤

ሠላጢኑም ፡ ሲሰበቅ ፡ ይሥቃል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 22 ፤ ታቹ ፡ እንደ ፡ ስለታም ፡ ገል ፡ ነው ፤

እንደ ፡ መዳመጫም ፡ በጭቃ ፡ ላይ ፡ ያልፋል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 23 ፤ ቀላዩን ፡ እንደ ፡ ድስት ፡ ያፈላዋል ፤

ባሕሩንም ፡ እንደ ፡ ሽቱ ፡ ምንቸት ፡ ያደርገዋል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 24 ፤ በስተኋላው ፡ ብሩሀ ፡ መንገድን ፡ ያበራል ፤

ቀላዩም ፡ ሽበት ፡ ይመስላል ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 25 ፤ ያለፍርሀት ፡ የተፈጠረ ፥

እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የለም ።

ኢዮ. ፡ 41 ፡ 26 ፤ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይመለከታል ፤

በትዕቢተኞችም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 1 ፤ ኢዮብም ፡ መለሰ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 2 ፤ ኹሉን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ቻይ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥

ዐሳብኽም ፡ ይከለከል ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ እንደማይቻል ፡ ዐወቅኹ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 3 ፤ ያለዕውቀት ፡ ምክርን ፡ የሚሰውር ፡ ማን ፡ ነው ፧

ስለዚህ ፡ እኔ ፡ የማላስተውለውን ፥

የማላውቀውንም ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ተናግሬያለኹ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 4 ፤ እባክኽ ፥ ስማኝ ፡ እኔም ፡ ልናገር ፤

እጠይቅኽማለኹ ፥ አንተም ፡ ተናገረኝ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 5 ፤ መስማትንስ ፡ በጕሮ ፡ በመስማት ፡ ሰምቼ ፡ ነበር ፤

አኹን ፡ ግን ፡ ዐይኔ ፡ አየችኽ ፤

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ራሴን ፡ እንቃለኹ ፤

በዐፈርና ፡ በዐመድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጬ ፡ እጸጸታለኹ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለኢዮብ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቴማናዊውን ፡ ኤልፋዝን ፦ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅንን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ አልተናገራችኹምና ፡ ቍጣዬ ፡ በአንተና ፡ በኹለቱ ፡ ባልንጀራዎችኽ ፡ ላይ ፡ ነዷል ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ሰባት ፡ ወይፈኖችና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ይዛችኹ ፡ ወደ ፡ ባሪያዬ ፡ ወደ ፡ ኢዮብ ፡ ዘንድ ፡ ኺዱ ፥ የሚቃጠልንም ፡ መሥዋዕት ፡ ስለ ፡ ራሳችኹ ፡ አሳርጉ ፤ ባሪያዬም ፡ ኢዮብ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይጸልያል ፥ እኔም ፡ እንደ ፡ ስንፍናችኹ ፡ እንዳላደርግባችኹ ፡ ፊቱን ፡ እቀበላለኹ ፤ እንደ ፡ ባሪያዬ ፡ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ቅን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ አልተናገራችኹምና ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 9 ፤ ቴማናዊውም ፡ ኤልፋዝ ፡ ሹሐዊውም ፡ በልዳዶስ ፡ ናዕማታዊውም ፡ ሶፋር ፡ ኼደው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የኢዮብን ፡ ፊት ፡ ተቀበለ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 10 ፤ ኢዮብም ፡ ስለ ፡ ወዳጆቹ ፡ በጸለየ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ምርኮውን ፡ መለሰለት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቀድሞ ፡ በነበረው ፡ ፋንታ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጎ ፡ ለኢዮብ ፡ ሰጠው ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 11 ፤ ወንድሞቹና ፡ እኅቶቹ ፡ ቀድሞም ፡ ያውቁት ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ፥ በቤቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንጀራ ፡ በሉ ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ዐዘኑለት ፥ እግዚአብሔርም ፡ ካመጣበት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አጽናኑት ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ ብርና ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ሰጡት ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛውን ፡ ለኢዮብ ፡ ባረከ ፤ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ሺሕም ፡ በጎች ፥ ስድስት ፡ ሺሕም ፡ ግመሎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ ጥማድ ፡ በሬዎች ፥ አንድ ፡ ሺሕም ፡ እንስት ፡ አህያዎች ፡ ነበሩት ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ ሰባት ፡ ወንዶችና ፡ ሦስት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ኾኑለት ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 14 ፤ የመዠመሪያዪቱንም ፡ ስም ፡ ይሚማ ፥ የኹለተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ ቃስያ ፥ የሦስተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ አማልቶያስ ፡ ቂራስ ፡ ብሎ ፡ ሰየማቸው ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 15 ፤ እንደ ፡ ኢዮብ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ ያሉ ፡ የተዋቡ ፡ ሴቶች ፡ በአገሩ ፡ ኹሉ ፡ አልተገኙም ፤ አባታቸውም ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡ ርስት ፡ ሰጣቸው ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 16 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢዮብ ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ኖረ ፥ ልጆቹንና ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፡ እስከ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ አየ ።

ኢዮ. ፡ 42 ፡ 17 ፤ ኢዮብም ፡ ሽምግሎ ፥ ዕድሜም ፡ ጠግቦ ፡ ሞተ ❖

መዝሙረ ፡ ዳዊት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መዝሙር ፡ 1 ። _____

መዝ. ፡ 1 ፡ 1 ፤ ምስጉን ፡ ነው ፡ በክፉዎች ፡ ምክር ፡ ያልኼደ ፥ በኀጢአተኞችም ፡ መንገድ ፡ ያልቆመ ፥ በዋዘኞችም ፡ ወንበር ፡ ያልተቀመጠ ።

መዝ. ፡ 1 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ ሕጉንም ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ያስባል ።

መዝ. ፡ 1 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በውሃ ፡ ፈሳሾች ፡ ዳር ፡ እንደ ፡ ተተከለች ፥ ፍሬዋን ፡ በየጊዜዋ ፡ እንደምትሰጥ ፥ ቅጠሏም ፡ እንደማይረግፍ ፡ ዛፍ ፡ ይኾናል ፤ የሚሠራውም ፡ ኹሉ ፡ ይከናወንለታል ።

መዝ. ፡ 1 ፡ 4 ፤ ክፉዎች ፡ እንዲህ ፡ አይደሉም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ነፋስ ፡ ጠርጎ ፡ እንደሚወስደው ፡ ትቢያ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 1 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ክፉዎች ፡ በፍርድ ፥ ኀጢአተኞችም ፡ በጻድቃን ፡ ማኅበር ፡ አይቆሙም ።

መዝ. ፡ 1 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጻድቃንን ፡ መንገድ ፡ ያውቃልና ፥ የክፉዎች ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ትጠፋለች ።

_____መዝሙር ፡ 2 ። _____

መዝ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ አሕዛብ ፡ ለምን ፡ ያጉረመርማሉ ፧ ወገኖችስ ፡ ለምን ፡ ከንቱን ፡ ይናገራሉ ፧

መዝ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ተነሡ ፥ አለቃዎችም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በመሲሑ ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ተማከሩ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ማሰሪያቸውን ፡ እንበጥስ ፥ ገመዳቸውንም ፡ ከእኛ ፡ እንጣል ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ በሰማይ ፡ የሚኖር ፡ ርሱ ፡ ይሥቃል ፥ ጌታም ፡ ይሣለቅባቸዋል ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቍጣው ፡ ይናገራቸዋል ፥ በመዓቱም ፡ ያውካቸዋል ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ንጉሤን ፡ ሾምኹ ፡ በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ በጽዮን ፡ ላይ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ትእዛዙን ፡ እናገራለኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ አለኝ ፦ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነኽ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወለድኩኽ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ለምነኝ ፥ አሕዛብን ፡ ለርስትኽ ፡ የምድርንም ፡ ዳርቻ ፡ ለግዛትኽ ፡ እሰጥኻለኹ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በብረት ፡ በትር ፡ ትጠብቃቸዋለኽ ፥ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ዕቃዎች ፡ ትቀጠቅጣቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ እናንት ፡ ነገሥታት ፥ ልብ ፡ አድርጉ ፤ እናንት ፡ የምድር ፡ ፈራጆችም ፥ ተገሠጹ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ በፍርሀት ፡ ተገዙ ፥ በረዓድም ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

መዝ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ተግሣጹን ፡ ተቀበሉ ፡ ጌታ ፡ እንዳይቈጣ ፡ እናንተም ፡ በመንገድ ፡ እንዳትጠፉ ፥ ቍጣው ፡ ፈጥና ፡ ትነዳለችና ። በርሱ ፡ የታመኑ ፡ ኹሉ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ።

_____መዝሙር ፡ 3 ። _____

ከልጁ ፡ ከአቤሴሎም ፡ ፊት ፡ በሸሸ ፡ ጊዜ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ የሚያስጨንቁኝ ፡ ምንኛ ፡ በዙ! ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚቆሙት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነፍሴን ፦ አምላክሽ ፡ አያድንሽም ፡ አሏት ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፥ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ፥ ክብሬንና ፡ ራሴንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የምታደርገው ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጮኻለኹ ፡ ከተቀደሰ ፡ ተራራውም ፡ ይሰማኛል ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እኔ ፡ ተኛኹ ፡ አንቀላፋኹም ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግፎኛልና ፥ ነቃኹ ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ከሚከቡኝ ፡ ከአእላፍ ፡ ሕዝብ ፡ አልፈራም ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ተነሥ ፥ አቤቱ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አድነኝ ፤ አንተ ፡ የጠላቶቼን ፡ መንጋጋ ፡ መትተኻልና ፥ የክፉዎችንም ፡ ጥርስ ፡ ሰብረኻልና ።

መዝ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ማዳን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፥ በረከትኽም ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 4 ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በበገናዎች ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ የጽድቄ ፡ አምላክ ፡ በጠራኹት ፡ ጊዜ ፡ መለሰልኝ ፥ በጭንቀቴም ፡ አሰፋኽልኝ ፤ ማረኝ ፥ ጸሎቴንም ፡ ስማ ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ እናንት ፡ የሰው ፡ ልጆች ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ልባችኹን ፡ ታከብዳላችኹ ፧ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ለምን ፡ ትወዳላችኹ ፧ ሐሰትንም ፡ ለምን ፡ ትሻላችኹ ፧

መዝ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ በጻድቁ ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ ዕወቁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በተጣራኹ ፡ ጊዜ ፡ ይሰማኛል ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ተቈጡ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኀጢአትን ፡ አታድርጉ ፤ በመኝታችኹ ፡ ሳላችኹ ፡ በልባችኹ ፡ ዐስቡ ፤ ዝም ፡ በሉ ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ የጽድቅን ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ታመኑ ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በጎውን ፡ ማን ፡ ያሳየናል ፧ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። አቤቱ ፥ የፊትኽ ፡ ብርሃን ፡ በላያችን ፡ ታወቀ ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ በልቤ ፡ ደስታን ፡ ጨመርኽ ፤ ከስንዴ ፡ ፍሬና ፡ ከወይን ፡ ከዘይትም ፡ ይልቅ ፡ በዛ ።

መዝ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በሰላም ፡ እተኛለኹ ፡ አንቀላፋለኹም ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ በእምነት ፡ አሳድረኽኛልና ።

መዝሙር ፡ 5 ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በዋሽንት ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ቃሌን ፡ አድምጥ ፥ ጭኸቴንም ፡ አስተውል ፤

መዝ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ አድምጥ ፥ ንጉሤና ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ እጸልያለኹና ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ በማለዳ ፡ ድምፄን ፡ ትሰማለኽ ፥ በማለዳ ፡ በፊትኽ ፡ እቆማለኹ ፥ እጠብቃለኹም ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ አንተ ፡ በደልን ፡ የማትወድ ፡ አምላክ ፡ ነኽና ፤ ክፉ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አያድርም ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ በከንቱ ፡ የሚመኩ ፡ በዐይኖችኽ ፡ ፊት ፡ አይኖሩም ፤ ክፉ ፡ አድራጊዎችን ፡ ኹሉ ፡ ጠላኽ ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ሐሰትን ፡ የሚናገሩትን ፡ ታጠፋቸዋለኽ ፤ ደም ፡ አፍሳሹንና ፡ ሸንጋዩን ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጸየፋል ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ እገባለኹ ፤ አንተን ፡ በመፍራት ፡ ወደ ፡ ቅድስናኽ ፡ መቅደስ ፡ እሰግዳለኹ ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ጠላቶቼ ፡ በጽድቅኽ ፡ ምራኝ ፤ መንገዴን ፡ በፊትኽ ፡ አቅና ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ በአፋቸው ፡ እውነት ፡ የለምና ፥ ልባቸውም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ ጕረሯቸው ፡ የተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፤ በምላሳቸው ፡ ይሸነግላሉ ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ ፍረድባቸው ፥ በምክራቸውም ፡ ይውደቁ ፤ ስለ ፡ ክፋታቸውም ፡ ብዛት ፡ አሳዳቸው ፥ እነርሱ ፡ ዐምፀውብኻልና ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ባንተ ፡ የሚታመኑት ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ለዘለዓለሙ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ እነርሱንም ፡ ትጠብቃለኽ ፤ ስምኽንም ፡ የሚወዱ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ይመካሉ ።

መዝ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ አንተ ፡ ጻድቁን ፡ ትባርከዋለኽና ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ጋሻ ፡ በሞገስ ፡ ከለልኸን ።

መዝሙር ፡ 6 ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በበገናዎች ፡ ስለ ፡ ስምንተኛ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በቍጣኽ ፡ አትቅሠፈኝ ፥ በመዓትኽም ፡ አትገሥጸኝ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ድውይ ፡ ነኝና ፡ አቤቱ ፥ ማረኝ ፤ ዐጥንቶቼ ፡ ታውከዋልና ፥ ፈውሰኝ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ነፍሴም ፡ እጅግ ፡ ታወከች ፤ አንተም ፡ አቤቱ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ ተመለስ ፡ ነፍሴንም ፡ አድናት ፥ ስለ ፡ ቸርነትኽም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ በሞት ፡ የሚያስብኽ ፡ የለምና ፥ በሲኦልም ፡ የሚያመሰግንኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በጭንቀቴ ፡ ደክሜያለኹ ፤ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ ዐልጋዬን ፡ ዐጥባለኹ ፥ በዕንባዬም ፡ መኝታዬን ፡ አርሳለኹ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ዐይኔ ፡ ከቍጡ ፡ ዕንባ ፡ የተነሣ ፡ ታወከች ፤ ከጠላቶቼ ፡ ኹሉ ፡ የተነሣ ፡ አረጀኹ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ዐመፃን ፡ የምታደርጉ ፡ ኹሉ ፥ ከእኔ ፡ ራቁ ፥ እግዚአብሔር ፡ የልቅሶዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቷልና ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ሰማኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ጸሎቴን ፡ ተቀበለ ።

መዝ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ጠላቶቼ ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩ ፡ እጅግም ፡ ይጐስቍሉ ፤ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሱ ፥ በፍጥነትም ፡ ይፈሩ ።

_____መዝሙር ፡ 7 ። _____

ስለ ፡ ብንያማዊ ፡ ሰው ፡ ስለኩዝ ፡ ቃል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የዘመረው ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 1 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ባንተ ፡ ታመንኹ ፤ ከሚያሳድዱኝ ፡ ኹሉ ፡ አድነኝና ፡ አውጣኝ ፥

መዝ. ፥ 7 ፥ 2 ፤ ነፍሴን ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ነጥቀው ፡ እንዳይሰብሯት ፥ የሚያድንና ፡ የሚታደግ ፡ ሳይኖር ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 3 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ እንዲህስ ፡ ካደረግኹ ፥ ዐመፃም ፡ በእጄ ፡ ቢኖር ፥

መዝ. ፥ 7 ፥ 4 ፤ ክፉ ፡ ላደረጉብኝም ፡ ክፉን ፡ መልሼላቸው ፡ ብኾን ፥ ጠላቴንም ፡ በከንቱ ፡ ገፍቼው ፡ ብኾን ፥

መዝ. ፥ 7 ፥ 5 ፤ ጠላት ፡ ነፍሴን ፡ ያሳዳት ፡ ያግኛትም ፥ ሕይወቴንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይርገጣት ፥ ክብሬንም ፡ በትቢያ ፡ ላይ ፡ ያዋርዳት ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ አቤቱ ፥ በመዓትኽ ፡ ተነሥ ፥ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ በቀኑጣ ፡ ተነሣባቸው ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ባዘዝኸው ፡ ትእዛዝ ፡ ንቃ ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ የአሕዛብም ፡ ጉባኤ ፡ ይከብኻል ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ከፍታ ፡ ተመለስ ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ይፈርዳል ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ጽድቄ ፡ ፍረድልኝ ፥ እንደ ፡ የዋህነቴም ፡ ይኹንልኝ ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 9 ፤ የኃጥኣን ፡ ክፋት ፡ ይጥፋ ፥ ጻድቁን ፡ ግን ፡ አቅና ፤ እግዚአብሔር ፡ ልቡናንና ፡ ኵላሊትን ፡ ይመረምራል ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጽድቅ ፡ ጋሻዬ ፡ ነው ፡ ልበ ፡ ቅኖችን ፡ የሚያድናቸው ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእውነት ፡ ዳኛ ፡ ነው ፥ ኀይለኛም ፡ ታጋሽም ፡ ነው ፥ ኹልጊዜም ፡ አይቈጣም ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 12 ፤ ባትመለሱ ፡ ግን ፡ ሰይፉን ፡ ይስላል ፥ ቀስቱን ፡ ገተረ ፡ አዘጋጀም ፤

መዝ. ፥ 7 ፥ 13 ፤ የሞት ፡ መሣሪያንም ፡ አዘጋጀበት ፥ ፍላጻዎቹንም ፡ የሚቃጠሉ ፡ አደረገ ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 14 ፤ እንሆ ፥ በዐመፃ ፡ ተጨነቀ ፡ ጕዳትን ፡ ፀነሰ ፡ ኀጢአትንም ፡ ወለደ ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 15 ፤ ጕድጓድን ፡ ማሰ ፡ ቈፈረም ። ባደረገውም ፡ ጕድጓድ ፡ ይወድቃል ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 16 ፤ ጕዳቱ ፡ በራሱ ፡ ይመለሳል ፥ ዐመፃውም ፡ በዐናቱ ፡ ላይ ፡ ትወርዳለች ።

መዝ. ፥ 7 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ጽድቁ ፡ መጠን ፡ አመሰግናለኹ ፥ ለልዑል ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ እዘምራለኹ ።

_____መዝሙር ፡ 8 ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በዋሽንት ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 8 ፥ 1 ፤ አቤቱ ፡ ጌታችን ፥ ስምኽ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ተመሰገነ ፥ ምስጋናኽ ፡ በሰማዮች ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ።

መዝ. ፥ 8 ፥ 2 ፤ ከሕፃናትና ፡ ከሚጠቡ ፡ ልጆች ፡ አፍ ፡ ምስጋናን ፡ አዘጋጀኽ ፡ ስለ ፡ ጠላትኽ ፥ ጠላትንና ፡

ቂመኛን ፡ ለማጥፋት ።

መዝ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ የጣቶችኽን ፡ ሥራ ፡ ሰማዮችን ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፥ ጨረቃንና ፡ ከዋክብትን ፡ አንተ ፡ የሠራኻቸውን ፥

መዝ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ትጐበኘውም ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ከመላእክት ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ አሳነስኸው ፤ በክብርና ፡ በምስጋና ፡ ዘውድ ፡ ከለልኸው ።

መዝ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ በእጆችኽም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾምኸው ፤ ኹሉን ፡ ከእግሮቹ ፡ በታች ፡ አስገዛኽለት ፥

መዝ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ በጎችንም ፡ ላሞችንም ፡ ኹሉ ፡ ደግሞም ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ እንስሳዎች ፥

መዝ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ የሰማይንም ፡ ወፎች ፡ የባሕርንም ፡ ዓሣዎች ፥ በባሕር ፡ መንገድ ፡ የሚኼደውንም ፡ ኹሉ ፡—

መዝ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ አቤቱ ፡ ጌታችን ፥ ስምኽ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ተመሰገነ ።

መዝሙር ፡ 9 ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በሙትላቤን ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በልቤ ፡ ኹሉ ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ ተኣምራትኽንም ፡ ኹሉ ፡ እነግራለኹ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ሐሤትንም ፡ አደርጋለኹ ፤ ልዑል ፡ ሆይ ፥ ለስምኽ ፡ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ጠላቶቼ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፥ ይሰናከላሉ ፡ ከፊትኽም ፡ ይጠፋሉ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ፍርዴንና ፡ በቀሌን ፡ አድርገኽልኛልና ፤ ጽድቅን ፡ እየፈረድኽ ፡ በዙፋንኽ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥኽ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ አሕዛብን ፡ ገሠጽኽ ፥ ዝንጉዎችንም ፡ አጠፋኽ ፥ ስማቸውንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ደመሰስኽ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ጠላቶች ፡ በጦር ፡ ለዘለዓለም ፡ ጠፉ ፥ ከተማዎቻቸውንም ፡ አፈረስኽ ፥ ዝክራቸውም ፡ በአንድነት ፡ ጠፋ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፥ ዙፋኑንም ፡ ለመፍረድ ፡ አዘጋጀ ፤

መዝ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ ዓለምን ፡ በጽድቅ ፡ ይፈርዳታል ፥ አሕዛብንም ፡ በቅንነት ፡ ይዳኛቸዋል ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለድኻዎች ፡ መጠጊያ ፡ ኾናቸው ፥ ርሱም ፡ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ረዳታቸው ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ስምኽን ፡ የሚያውቁ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ይታመናሉ ፥ አቤቱ ፥ የሚሹኽን ፡ አትተዋቸውምና ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ በጽዮን ፡ ለሚኖር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፥ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ አደራረጉን ፡ ንገሩ ፤

መዝ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ደማቸውን ፡ የሚመራመር ፡ ርሱ ፡ ዐስቧልና ፥ የድኻዎችንም ፡ ጩኸት ፡ አልረሳምና ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ ዕዘንልኝ ፥ ጠላቶቼም ፡ የሚያመጡብኝን ፡ መከራ ፡ እይ ፥ ከሞት ፡ ደጆች ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የምታደርገኝ ፤

መዝ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ምስጋናውን ፡ ኹሉ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፤ በጽዮን ፡ ልጅ ፡ በደጆቿ ፡ በማዳንኽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ አሕዛብ ፡ በሠሩት ፡ ጕድጓድ ፡ ወደቁ ፥ በዚያችም ፡ በሸሸጓት ፡ ወጥመድ ፡ እግራቸው ፡ ተጠመደች ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ በማድረግ ፡ የታወቀ ፡ ነው ፤ ኀጢአተኛው ፡ በእጆቹ ፡ ሥራ ፡ ተጠመደ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ኀጢአተኞች ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይመለሳሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚረሱ ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ድኻ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይረሳምና ፥ የችግረኞችም ፡ ተስፋቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጠፋም ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ ተነሥ ፤ ሰውም ፡ አይበርታ ፥ አሕዛብም ፡ በፊትኽ ፡ ይፈረድባቸው ።

መዝ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ አቤቱ ፥ ፍርሀትን ፡ በላያቸው ፡ ጣንባቸው ፤ አሕዛብ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ይወቁ ።

(መዝሙረ ፡ 10 ፡ በዕብራይስጥ) ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ለምን ፡ ርቀኽ ፡ ቆምኽ ፧ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ትሰወራለኽ ፧

መዝ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በኀጢአተኛ ፡ ትዕቢት ፡ ድኻ ፡ ይናደዳል ፤ ባሰቡት ፡ ተንኰላቸው ፡ ተጠመዱ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ኀጢአተኛ ፡ በነፍሱ ፡ ፈቃድ ፡ ይወደሳልና ፥ ዐመፀኛም ፡ ይባርካል ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ኀጢአተኛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አበሳጨው ፥ እንደ ፡ ቍጣውም ፡ ብዛት ፡ አይመራመረውም ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔር ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ መንገዱ ፡ ኹሉ ፡ የረከሰ ፡ ነው ፥ ፍርድኽም ፡ በፊቱ ፡ የፈረሰ ፡ ነው ፥ ጠላቶችንም ፡ ኹሉ ፡ ይገዛቸዋል ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ በልቡ ፡ ይላል ፦ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ አልታወክም ፡ ክፉም ፡ አያገኘኝም ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ አፉ ፡ መርገምንና ፡ ሽንገላን ፡ ተንኰልን ፡ የተመላ ፡ ነው ፤ ከምላሱ ፡ በታች ፡ ጕዳትና ፡ መከራ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ በመንደሮች ፡ መሸመቂያ ፡ ይቀመጣል ፡ ንጹሓንን ፡ በስውር ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፤ ዐይኖቹም ፡ ወደ ፡ ድኻ ፡ ይመለከታሉ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ በችፍግ ፡ ዱር ፡ በስውር ፡ ይሸምቃል ፤ ድኻውን ፡ ለመንጠቅ ፡ ያደባል ፤ ድኻውን ፡ ይነጥቀዋል ፡ በአሽክላውም ፡ ይስበዋል ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ድኻ ፡ ይዋረዳል ፥ ይጐብጣል ፤ በኀያላኑም ፡ እጅግ ፡ ይወድቃል ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ በልቡም ፡ ይላል ፦ እግዚአብሔር ፡ ረስቶኛል ፤ ፈጽሞም ፡ እንዳያይ ፡ ፊቱን ፡ ሰወረ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ አቤቱ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ተነሥ ፡ እጅኽም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትበል ፤ ድኻዎችን ፡ አትርሳ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቈጣው ፧ በልቡ ፦ አይመራመረኝም ፡ ይላልና ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ አየኸው ፥ አንተ ፡ ክፋትንና ፡ ቍጣን ፡ ትመለከታለኽና ፡ በእጅኽ ፡ ፍዳውን ፡ ለመስጠት ፤ ድኻ ፡ ራሱን ፡ ለአንተ ፡ ይተዋል ፥ ለድኻ ፡ አደግም ፡ ረዳቱ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ የኀጢአተኛንና ፡ የክፉን ፡ ክንድ ፡ ስበር ፥ የኀጢአቱንም ፡ ብድራት ፡ ክፈል ፡ ሌላ ፡ እስከማይገኝ ፡

ድረስ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ይነግሣል ፤ አሕዛብ ፡ ከምድሩ ፡ ይጠፋሉ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ የድኻዎችን ፡ ምኞት ፡ ሰማ ፥ ጕሮውም ፡ የልባቸውን ፡ ዐሳብ ፡ አደመጠች ፥

መዝ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ፍርዱ ፡ ለድኻ ፡ አደግና ፡ ለችግረኛ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፥ ሰዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አፋቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ማድረግ ፡ እንዳይደግሙ ።

_____መዝሙር ፡ 10 ፡ (11) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ታመንኹ ፤ ነፍሴን ፦ እንደ ፡ ወፍ ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ተቅበዝበዚ ፡ እንዴት ፡ ትሏታላችኹ ፧

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 2 ፤ ኀጢአተኞች ፥ እንሆ ፥ ቀስታቸውን ፡ ገትረዋልና ፥ ፍላጻቸውንም ፡ በአውታር ፡ አዘጋጅተዋልና ፥ ልበ ፡ ቅኖችን ፡ በስውር ፡ ይነድፉ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 3 ፤ አንተ ፡ የሠራኸውን ፥ እንሆ ፥ እነርሱ ፡ አፍርሰዋልና ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ምን ፡ አደረገ ፧

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ በተቀደሰው ፡ መቅደሱ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፥ ዙፋኑ ፡ በሰማይ ፡ ነው ፤ ዐይኖቹ ፡ ወደ ፡ ድኻ ፡ ይመለከታሉ ፥ ቅንድቦቹም ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ ይመረምራሉ ።

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅንና ፡ ኀጥእን ፡ ይመረምራል ፤ ዐመፃን ፡ የወደዳት ፡ ግን ፡ ነፍሱን ፡ ጠልቷል ።

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 6 ፤ ወጥመድ ፡ በኃጥኣን ፡ ላይ ፡ ያዘንባል ፤ እሳትና ፡ ዲን ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ የጽዋቸው ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 10 ፡ (11) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ፥ ጽድቅንም ፡ ይወዳል ፤ ቅንነት ፡ ግን ፡ ፊቱን ፡ ታየዋለች ።

_____መዝሙር ፡ 11 ፡ (12) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፥ ስለ ፡ ስምንተኛ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አድነኝ ፤ ደግ ፡ ሰው ፡ አልቋልና ፥ ከሰው ፡ ልጆችም ፡ መተማመን ፡ ጐድሏልና ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 2 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ይናገራሉ ፤ በሽንገላ ፡ ከንፈር ፡ ኹለት ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ ይናገራሉ ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 3 ፤ የሽንገላን ፡ ከንፈሮች ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋቸዋል ፥ ታላቅ ፡ ነገርን ፡ የምትናገረውን ፡ ምላስ ፤

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 4 ፤ ምላሳችንን ፡ እናበረታለን ፤ ከንፈራችን ፡ የእኛ ፡ ነው ፥ ጌታችን ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚሉትን ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 5 ፤ ስለድኻዎች ፡ መከራ ፥ ስለችግረኞች ፡ ጩኸት ፡ እግዚአብሔር ፦ አኹን ፡ እነሣለኹ ፡ ይላል ፤ መድኀኒትን ፡ አደርጋለኹ ፥ በላዩም ፡ እገልጣለኹ ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 6 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተፈተነ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጣራ ፡ ብር ። የእግዚአብሔር ፡ ቃላት ፡ የነጹ ፡ ቃላት ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ጠብቀን ፥ ከዚችም ፡ ትውልድ ፡ ለዘለዓለም ፡ ታደገን ።

መዝ. ፡ 11 ፡ (12) ፡ 8 ፤ በሰው ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ምናምንቴ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ክፉዎች ፡ በዙሪያው ፡ ዞሩ ፡ ይመላለሳሉ ።

መዝሙር ፡ 12 ፡ (13) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ፈጽመኽ ፡ ትረሳኛለኽ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ ትሰውራለኽ ፧

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ በነፍሴ ፡ እመካከራለኹ ፧ ትካዜስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ዅልጊዜ ፡ ይኾናል ፧ እስከ ፡ መቼ ፡ ጠላቴ ፡ በላዬ ፡ ይጓደዳል ፧

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ እየኝ ፡ ስማኝም ፤ ጠላቴ ። አሸነፍኹት ፡ እንዳይል ፥

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 4 ፤ የሚያስጨንቁኝም ፡ እኔ ፡ ብናወጥ ፡ ደስ ፡ እንዳይላቸው ፥ ለሞትም ፡ እንዳልተኛ ፡ ዐይኖቼን ፡ አብራ ።

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 5 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በቸርነትኽ ፡ ታመንኹ ፥ ልቤም ፡ በመድኀኒትኽ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

መዝ. ፡ 12 ፡ (13) ፡ 6 ፤ የረዳኝን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ፥ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ስምም ፡ እዘምራለኹ ።

መዝሙር ፡ 13 ፡ (14) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 1 ፤ ሰነፍ ፡ በልቡ ፦ አምላክ ፡ የለም ፡ ይላል ። በሥራቸው ፡ ረከሱ ፥ ጐሰቈሉ ፤ በጎ ፡ ነገርን ፡ የሚሠራ ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 2 ፤ የሚያስተውል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈልግ ፡ እንዳለ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ ተመለከተ ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 3 ፤ ዞሩ ፡ ዐመፁ ፡ በአንድነትም ፡ ረከሱ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ የሚሠራ ፡ የለም ፤ አንድም ፡ ስንኳ ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 4 ፤ ጕረሯቸው ፡ የተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፥ በምላሳቸው ፡ ሸነገሉ ፤

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 5 ፤ ከከንፈራቸው ፡ በታች ፡ የእባብ ፡ መርዝ ፡ አለ ፤ አፋቸው ፡ መርገምንና ፡ መራራን ፡ ተሞልቷል ፤

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 6 ፤ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ እግራቸው ፡ ፈጣን ፡ ነው ፤ ጥፋትና ፡ ጕስቍልና ፡ በመንገዳቸው ፡ አለ ፥ የሰላምን ፡ መንገድ ፡ አላወቋትምና ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ በዐይናቸው ፡ ፊት ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 7 ፤ ሕዝቤን ፡ እንደ ፡ እንጀራ ፡ የሚበሉ ፡ ኀጢአት ፡ የሚሠሩ ፡ ዞሩ ፡ በእውኑ ፡ አያውቁምን ፧ እግዚአብሔርንም ፡ አይጠሩትም ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 8 ፤ በዚያ ፡ በታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጻድቃን ፡ ትውልድ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 9 ፤ የድኻዎችን ፡ ምክር ፡ አሳፈራችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ተስፋቸው ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 13 ፡ (14) ፡ 10 ፤ ከጽዮን ፡ መድኀኒትን ፡ ለእስራኤል ፡ ማን ፡ ይሰጣል ፧ እግዚአብሔር ፡ የሕዝቡን ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፥ ያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ እስራኤልም ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ።

መዝሙር ፡ 14 ፡ (15) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 14 ፡ (15) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በድንኳንኽ ፡ ውስጥ ፡ ማን ፡ ያድራል ፧ በተቀደሰውም ፡ ተራራኽ ፡ ማን ፡ ይኖራል ፧

መዝ. ፡ 14 ፡ (15) ፡ 2 ፤ በቅንነት ፡ የሚኼድ ፥ ጽድቅንም ፡ የሚያደርግ ፥ በልቡም ፡ እውነትን ፡ የሚናገር ።

መዝ. ፡ 14 ፡ (15) ፡ 3 ፤ በአንደበቱ ፡ የማይሸነግል ፥ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ የማያደርግ ፥ ዘመዶቹንም ፡ የማይሰድብ ።

መዝ. ፡ 14 ፡ (15) ፡ 4 ፤ ኀጢአተኛ ፡ በፊቱ ፡ የተናቀ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈሩትን ፡ የሚያከብር ፥ ለባልንጀራው ፡ የሚምል ፡ የማይከዳም ።

መዝ. ፡ 14 ፡ (15) ፡ 5 ፤ ገንዘቡን ፡ በወራጣ ፡ የማያበድር ፥ በንጹሑ ፡ ላይ ፡ መማለጃን ፡ የማይቀበል ። እንዲህ ፡ የሚያደርግ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይታወክም ።

መዝሙር ፡ 15 ፡ (16) ።

የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ባንተ ፡ ታምኛለኹና ፡ ጠብቀኝ ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፦ አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ነኽ ፡ አልኹ ፤ ከአንተ ፡ በቀር ፡ በጎነት ፡ የለኝም ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 3 ፤ ፈቃድኽ ፡ ኾሉ ፡ በምድር ፡ ባሉት ፡ ቅዱሳንና ፡ ክቡራን ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ ለሚፋጠኑት ፡ መከራቸው ፡ ይበዛል ፤ የቀኑርባናቸውን ፡ ደም ፡ እኔ ፡ አላፈሰውም ፥ ስማቸውንም ፡ በከንፈሬ ፡ አልጠራም ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ የርስቴ ፡ ዕድል ፡ ፈንታና ፡ ጽዋዬ ፡ ነው ፥ ዕጣዬንም ፡ የምታጠና ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 6 ፤ ገመድ ፡ ባማረ ፡ ስፍራ ፡ ወደቀችልኝ ፥ ርስቴም ፡ ተዋበችልኝ ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 7 ፤ የመከረኝን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እባርካለኹ ፤ ደግሞም ፡ በሌሊት ፡ ኵላሊቶቼ ፡ ይገሥጹኛል ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 8 ፤ ኾልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፊቴ ፡ አየዋለኹ ፤ በቀኜ ፡ ነውና ፥ አልታወክም ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ልቤን ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ምላሴም ፡ ሐሴት ፡ አደረገች ፤ ሥጋዬም ፡ ደግሞ ፡

በተስፋ ፡ ታድራለች ፤

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 10 ፤ ነፍሴን ፡ በሲኦል ፡ አትተዋትምና ፥ ቅዱስኽንም ፡ መበስበስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትተወውም ።

መዝ. ፡ 15 ፡ (16) ፡ 11 ፤ የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ አሳየኸኝ ፤ ከፊትኽ ፡ ጋራ ፡ ደስታን ፡ አጠገብኸኝ ፥ በቀኝኽም ፡ የዘለዓለም ፡ ፍሥሓ ፡ አለ ።

መዝሙር ፡ 16 ፡ (17) ።

የዳዊት ፡ ጸሎት ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ጽድቄን ፡ ስማ ፡ ጩኸቴንም ፡ አድምጥ ፤ በተንኰለኛም ፡ ከንፈር ፡ ያልኾነውን ፡ ጸሎቴን ፡ አድምጥ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 2 ፤ ፍርዴ ፡ ከፊትኽ ፡ ይውጣ ፥ ዐይኖችኽም ፡ በቅንነት ፡ ይዩ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 3 ፤ ልቤን ፡ ፈተንኸው ፡ በሌሊትም ፡ ጐበኘኸኝ ፤ ፈተንኸኝ ፥ ምንም ፡ አላገኘኽብኝም ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 4 ፤ የሰውን ፡ ሥራ ፡ አፌ ፡ እንዳይናገር ፡ ፈቃዴ ፡ ነው ፤ ስለከንፈሮችኽ ፡ ቃል ፡ ጭንቅ ፡ የኾኑ ፡ መንገዶችን ፡ ጠበቅኹ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 5 ፤ እግሮች ፡ እንዳይናወጡ ፡ አረማመዴን ፡ በመንገድኽ ፡ አጽና ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 6 ፤ አቤቱ ፥ ሰምተኸኛልና ፥ ወዳንተ ፡ ጠራኹ ፤ ጐሮኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብል ፥ ቃሌንም ፡ ስማ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 7 ፤ የሚያምኑኽን ፡ ከሚቃወሙ ፡ በቀኝኽ ፡ የምታድናቸው ፥ ቸርነትኽን ፡ ድንቅ ፡ አድርገኽ ፡ ግለጠው ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 8 ፤ እንደ ፡ ዐይን ፡ ብሌን ፡ ጠብቀኝ ፥ በክንፎችኽ ፡ ጥላ ፡ ሰውረኝ ፥

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 9 ፤ ከሚያስጨንቁኝ ፡ ከኀጢአተኞች ፥ ነፍሴንም ፡ ከሚከቧት ፡ ከጠላቶቼ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 10 ፤ አንገታቸውን ፡ በስብ ፡ ቋጠሩ ፥ በአፋቸውም ፡ ትንቢትን ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ ርምጃችንን ፡ ከበቡ ፤ ዐይናቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረጉ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ ንጥቂያን ፡ እንደሚናፍቅ ፡ አንበሳ ፡ ተሸጕጦም ፡ እንደሚኖር ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦል ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ ተነሥ ፤ ቀድመኽ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ጣለው ፤ ነፍሴን ፡ ከኀጢአተኛ ፡ በሰይፍኽ ፡ አድናት ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 14 ፤ አቤቱ ፥ ከሰዎች ፥ ዕድል ፡ ፈንታቸው ፡ በሕይወታቸው ፡ ከኾነች ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰዎች ፡ በእጅኽ ፡ አድነኝ ፤ ከሰወርኽው ፡ መዝገብኽ ፡ ሆዳቸውን ፡ አጠገብኽ ፤ ልጆቻቸው ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ የተረፋቸውንም ፡ ለሕፃናታቸው ፡ ያተርፋሉ ።

መዝ. ፡ 16 ፡ (17) ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በጽድቅ ፡ ፊትኽን ፡ አያለኹ ፤ ክብርኽን ፡ ሳይ ፡ እጠግባለኹ ።

መዝሙር ፡ 17 ፡ (18) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ ከሳኦል ፡ እጅና ፡ ከጠላቶቹ ፡ ሹሉ ፡ እጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባዳነው ፡ ቀን ፡ በዚህ ፡ መዝሙር ፡ ቃል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተናገረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ። እንዲህም ፡ አለ ፦

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 1 ፤ አቤቱ ፡ ጕልበቴ ፡ ሆይ ፥ እወድሃለኹ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ አለቴ ፥ ዐምባዬ ፥ መድኀኒቴ ፥ አምላኬ ፥ በርሱም ፡ የምተማመንበት ፡ ረዳቴ ፥ መታመኛዬና ፡ የደኅንነቴ ፡ ቀንድ ፡ መጠጊያዬም ፡ ነው ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 3 ፤ ምስጋና ፡ የሚገባውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጠራለኹ ፥ ከጠላቶቼም ፡ እድናለኹ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 4 ፤ የሞት ፡ ጣር ፡ ያዘኝ ፥ የዐመፅ ፡ ፈሳሽም ፡ አስፈራኝ ፤

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 5 ፤ የሲኦል ፡ ጣር ፡ ከበበኝ ፤ የሞት ፡ ወጥመድም ፡ ደረሰብኝ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 6 ፤ በጨነቀኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራኹት ፥ ወደ ፡ አምላኬም ፡ ጮኽኹ ፤ ከመቅደሱም ፡ ቃሌን ፡ ሰማኝ ፥ ጩኸቴም ፡ በፊቱ ፡ ወደ ፡ ጐሮው ፡ ገባ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 7 ፤ ምድርም ፡ ተንቀጠቀጠች ፡ ተናወጠችም ፥ የተራራዎችም ፡ መሠረቶች ፡ ተነቃነቁ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ተቈጥቷልና ፥ ተንቀጠቀጡ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 8 ፤ ከቀኑጣው ፡ ጢስ ፡ ወጣ ፥ ከፊቱም ፡ የሚበላ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፤ ፍምም ፡ ከርሱ ፡ በራ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 9 ፤ ሰማዮችን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረገ ፡ ወረደም ፥ ጨለማ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ነበረ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 10 ፤ በኪሩቤልም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ በረረ ፥ በነፋስም ፡ ክንፍ ፡ በረረ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 11 ፤ መሰወሪያውን ፡ ጨለማ ፡ አደረገ ፤ በዙሪያውም ፡ ድንኳኑ ፤ በደመናት ፡ ውስጥ ፡ የጨለማ ፡ ውሃ ፡ ነበረ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 12 ፤ በፊቱ ፡ ካለው ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፡ ደመናትና ፡ በረዶ ፡ የእሳት ፡ ፍምም ፡ ዐለፉ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሰማያት ፡ አንጐደጐደ ፥ ልዑልም ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 14 ፤ ፍላጻውን ፡ ላከ ፡ በተናቸውም ፤ መብረቆችን ፡ አበዛ ፡ አወካቸውም ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 15 ፤ አቤቱ ፥ ከዘለፋኽ ፡ ከመዓትኽም ፡ መንፈስ ፡ እስትንፋስ ፡ የተነሣ ፥ የውሃዎች ፡ ምንጮች ፡ ታዩ ፥ የዓለም ፡ መሠረቶችም ፡ ተገለጡ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 16 ፤ ከላይ ፡ ሰደደ ፡ ወሰደኝም ፥ ከብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ አወጣኝ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 17 ፤ ከብርቱዎች ፡ ጠላቶቼ ፡ ከሚጠሉኝም ፡ አዳነኝ ፥ በርትተውብኝ ፡ ነበርና ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 18 ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ደረሱብኝ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ደገፋዬ ፡ ኾነ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 19 ፤ ወደ ፡ ሰፊ ፡ ስፍራም ፡ አወጣኝ ፤ ወዶኛልና ፥ አዳነኝ ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ፡ ይከፍለኛል ፤ እንደ ፡ እጄ ፡ ንጽሕና ፡ ይመልስልኛል ።

መዝ. ፥ 17 ፡ (18) ፥ 21 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ጠብቄያለኹና ፥ በአምላኬም ፡ አላመፅኹም ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 22 ፤ ፍርዱ ፡ ኹሉ ፡ በፊቴ ፡ ነበረና ፥ ሥርዐቱንም ፡ ከፊቴ ፡ አላራቅኹም ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 23 ፤ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቅን ፡ ነበርኹ ፥ ከኀጢአቴም ፡ ተጠበቅኹ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 24 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ጽድቄ ፡ እንደ ፡ እጄም ፡ ንጽሕና ፡ በዐይኖቹ ፡ ፊት ፡ መለሰልኝ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 25 ፤ ከቸር ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ቸር ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤ ከቅን ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ቅን ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 26 ፤ ከንጹሕ ፡ ጋራ ፡ ንጹሕ ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ፤ ከጠማማም ፡ ጋራ ፡ ጠማማ ፡ ኾነኽ ፡ ትገኛለኽ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 27 ፤ አንተ ፡ የተጠቃውን ፡ ሕዝብ ፡ ታድናለኽና ፥ የትዕቢተኞችን ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ ታዋርዳለኽ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 28 ፤ አንተ ፡ መብራቴን ፡ ታበራለኽና ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ጨለማዬን ፡ ያበራል ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 29 ፤ ባንተ ፡ ከጥፋት ፡ እድናለኹና ፡ በአምላኬም ፡ ቅጥሩን ፡ እዘላለኹ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 30 ፤ የአምላኬ ፡ መንገድ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የነጠረ ፡ ነው ፥ በርሱ ፡ ለሚታመኑት ፡ ኹሉ ፡ ጋሻ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 31 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ከአምላካችን ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 32 ፤ ኀይልን ፡ የሚያስታጥቀኝ ፡ መንገዴንም ፡ የሚያቃና ፥

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 33 ፤ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ብሔር ፡ እግሮች ፡ የሚያረታ ፡ በኰረብታዎችም ፡ የሚያቆመኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 34 ፤ እጆቼን ፡ ሰልፍ ፡ ያስተምራል ፥ በክንዴም ፡ የናስ ፡ ቀስት ፡ እገትራለኹ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 35 ፤ ለደኅንነቴም ፡ መታመኛን ፡ ሰጠኸኝ ፥ ቀኝኽም ፡ ትረዳኛለች ፥ ትምህርትኽም ፡ ለዘለዓለም ፡ ታጠናኛለች ፥ ተግሣጽኽም ፡ ታስተምረኛለች ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 36 ፤ አረማመዴን ፡ በበታቼ ፡ አሰፋኽ ፥ እግሮቼም ፡ አልተንሸራተቱም ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 37 ፤ ጠላቶቼን ፡ አሳድዳቸዋለኹ ፡ እይዛቸዋለኹም ፥ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ አልመለስም ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 38 ፤ አስጨንቃቸዋለኹ ፡ መቆምም ፡ አይችሉም ፥ ከእግሬም ፡ በታች ፡ ይወድቃሉ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 39 ፤ ለሰልፍም ፡ ኀይልን ፡ ታስታጥቀኛለኽ ፤ በበላዬ ፡ የቆሙትን ፡ ኹሉ ፡ በበታቼ ፡ ታስገዛቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 40 ፤ የጠላቶቼን ፡ ዠርባ ፡ ሰጠኸኝ ፥ የሚጠሉኝንም ፡ አጠፋኻቸው ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 41 ፤ ጮኹ ፡ የሚረዳቸውም ፡ አልነበረም ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጮኹ ፡ አልሰማቸውም ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 42 ፤ እንደ ፡ ትቢያ ፡ በነፋስ ፡ ፊት ፡ እፈጫቸዋለኹ ፥ እንደ ፡ አደባባይም ፡ ጭቃ ፡ እረግጣቸዋለኹ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 43 ፤ ከሕዝብ ፡ ክርክር ፡ ታድነኛለኽ ፥ የአሕዛብም ፡ ራስ ፡ አድርገኽ ፡ ትሾመኛለኽ ፥ የማላውቀው ፡ ሕዝብም ፡ ይገዛልኛል ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 44 ፤ በጕሮ ፡ ሰምተው ፡ ተገዙልኝ ፤ የባዕድ ፡ ልጆች ፡ ደለሉኝ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 45 ፤ የባዕድ ፡ ልጆች ፡ አረጁ ፥ በመንገዳቸውም ፡ ተሰናከሉ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 46 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ነው ፥ አምላኬም ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፥ የመድኀኒቴም ፡ አምላክ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይበል ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 47 ፤ በቀሌን ፡ የሚመልስልኝ ፡ አምላክ ፡ አሕዛብን ፡ በበታቼ ፡ ያስገዛልኛል ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 48 ፤ ከጠላቶቼ ፡ የሚታደገኝ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ በእኔም ፡ ላይ ፡ ከቆሙ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ታደርገኛለኽ ፥ ከግፈኛ ፡ ሰው ፡ ታድነኛለኽ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 49 ፤ አቤቱ ፥ ስለዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ ለስምኽም ፡ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 17 ፡ (18) ፡ 50 ፤ የንጉሡን ፡ መድኀኒት ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋል ፥ ቸርነቱንም ፡ ለቀባው ፡ ለዳዊትና ፡ ለዘሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይሰጣል ።

መዝሙር ፡ 18 ፡ (19) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 1 ፤ ሰማያት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ ይናገራሉ ፥ የሰማይም ፡ ጠፈር ፡ የእጁን ፡ ሥራ ፡ ያወራል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 2 ፤ ቀን ፡ ለቀን ፡ ነገርን ፡ ታወጣለች ፥ ሌሊትም ፡ ለሌሊት ፡ ዕውቀትን ፡ ትናገራለች ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 3 ፤ ነገር ፡ የለም ፡ መናገርም ፡ የለም ፥ ድምፃቸውም ፡ አይሰማም ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 4 ፤ ድምፃቸው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፥ ቃላቸውም ፡ እስከዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ወጣ ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 5 ፤ በእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ የፀሓይን ፡ ድንኳን ፡ አደረገ ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ሙሽራ ፡ ከዕልፍኙ ፡ ይወጣል ፤ እንደ ፡ ዐርበኛ ፡ በመንገዱ ፡ ለመሮጥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 6 ፤ አወጣጡ ፡ ከሰማያት ፡ ዳርቻ ፡ ነው ፥ ዙረቱም ፡ እስከ ፡ ዳርቻቸው ፡ ነው ፤ ከትኵሳቱም ፡ የሚሰወር ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ፍጹም ፡ ነው ፤ ነፍስን ፡ ይመልሳል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ የታመነ ፡ ነው ፤ ሕፃናትን ፡ ጠቢባን ፡ ያደርጋል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሥርዐት ፡ ቅን ፡ ነው ፥ ልብንም ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ብሩህ ፡ ነው ፥ ዐይንንም ፡ ያበራል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍርሀት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እውነትና ፡ ቅንነት ፡ በአንድነት ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 10 ፤ ከወርቅና ፡ ከክቡር ፡ ዕንቊ ፡ ይልቅ ፡ ይወደዳል ፤ ከማርና ፡ ከማር ፡ ወለላም ፡ ይጣፍጣል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 11 ፤ ባሪያኽ ፡ ደግሞ ፡ ይጠብቀዋል ፤ በመጠበቁም ፡ እጅግ ፡ ይጠቀማል ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 12 ፤ ስሕተትን ፡ ማን ፡ ያስተውላታል ፧ ከተሰወረ ፡ ኀጢአት ፡ አንጻኝ ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 13 ፤ የድፍረት ፡ ኀጢአት ፡ እንዳይገዛኝ ፡ ባሪያኽን ፡ ጠብቅ ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፍጹም ፡ እኾናለኹ ፥ ከታላቁም ፡ ኀጢአት ፡ እነጻለኹ ።

መዝ. ፡ 18 ፡ (19) ፡ 14 ፤ አቤቱ ፥ ረድኤቴ ፡ መድኀኒቴም ፥ የአፌ ፡ ቃልና ፡ የልቤ ፡ ዐሳብ ፡ በፊትኽ ፡ ያማረ ፡ ይኹን ።

መዝሙር ፡ 19 ፡ (20) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 1 ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይስማኽ ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ ያቁምኽ ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 2 ፤ ከመቅደሱ ፡ ረድኤትን ፡ ይላክልኽ ፥ ከጽዮንም ፡ ያጥናኽ ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 3 ፤ ቍርባንኽን ፡ ኹሉ ፡ ያስብልኽ ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትኽን ፡ ያለምልምልኽ ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 4 ፤ እንደ ፡ ልብኽ ፡ ይስጥኽ ፡ ፈቃድኽንም ፡ ኹሉ ፡ ይፈጽምልኽ ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 5 ፤ በማዳንኽ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፤ በአምላካችን ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንላለን ፤ ልመናኽን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈጽምልኽ ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ እንዳዳነው ፡ ዛሬ ፡ ዐወቅኹ ፤ ከሰማይ ፡ መቅደሱ ፡ ይመልስለታል ፤ በቀኙ ፡ ብርታት ፡ ማዳን ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 7 ፤ እነዚያ ፡ በሠረገላ ፡ እነዚያም ፡ በፈረስ ፡ ይታመናሉ ፤ እኛ ፡ ግን ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እንላለን ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 8 ፤ እነርሱ ፡ ተሰነካክለው ፡ ወደቁ ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ተነሣን ፥ ጸንተንም ፡ ቆምን ።

መዝ. ፡ 19 ፡ (20) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ ንጉሥን ፡ አድነው ፥ በጠራንኽም ፡ ቀን ፡ ስማን ።

መዝሙር ፡ 20 ፡ (21) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በኀይልኽ ፡ ንጉሥ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ በማዳንኽ ፡ እጅግ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋል ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 2 ፤ የልቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሰጠኸው ፥ የከንፈሩንም ፡ ልመና ፡ አልከለከልኸውም ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 3 ፤ በበጎ ፡ በረከት ፡ ደርሰኽለታልና ፤ ከክቡር ፡ ዕንቊ ፡ የኾነ ፡ ዘውድን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አኖርኽ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 4 ፤ ሕይወትን ፡ ለመነኽ ፡ ሰጠኸውም ፥ ለረኂም ፡ ዘመን ፡ ለዘለዓለሙ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 5 ፤ በማዳንኽ ፡ ክብሩ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ ክብርንና ፡ ምስጋናን ፡ ጨመርኽለት ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 6 ፤ የዘለዓለም ፡ በረከትን ፡ ሰጥተኸዋልና ። በፊትኽም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ታሠኘዋለኽ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 7 ፤ ንጉሥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተማምኗልና ፥ በልዑልም ፡ ምሕረት ፡ አይናወጥም ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 8 ፤ እጅኽ ፡ ጠላቶችኽን ፡ ኹሉ ፡ ታግኛቸው ፥ ቀኝኽም ፡ የሚጠሉኽን ፡ ኹሉ ፡ ታግኛቸው ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 9 ፤ በተቈጣኽም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ አድርጋቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ በቀሣጣው ፡ ያጠፋቸዋል ፥ እሳትም ፡ ትበላቸዋለች ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 10 ፤ ፍሬያቸውን ፡ ከምድር ፡ ዘራቸውንም ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ታጠፋለኽ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 11 ፤ ክፋትን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ዘርግተዋልና ፥ የማይቻላቸውንም ፡ ምክር ፡ ዐሰቡ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ትመልሳቸዋለኽ ፤ ፍላጻን ፡ በፊታቸው ፡ ላይ ፡ ታዘጋጃለኽ ።

መዝ. ፡ 20 ፡ (21) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ በኀይልኽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፤ ጽናትኽንም ፡ እናመሰግናለን ፡ እንዘምርማለን ።

መዝሙር ፡ 21 ፡ (22) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ ስለንጋት ፡ ኀይል ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 1 ፤ አምላኬ ፥ አምላኬ ፥ ለምን ፡ ተውኸኝ ፧ እኔን ፡ ከማዳንና ፡ ከጩኸቴ ፡ ቃል ፡ ሩቅ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 2 ፤ አምላኬ ፥ በቀን ፡ ወዳንተ ፡ እጠራለኹ ፥ አልመለስኽልኝም ፤ በሌሊትም ፡ እንኳ ፡ ዕረፍት ፡ የለኝም ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 3 ፤ በእስራኤል ፡ የተመሰገንኽ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ በቅድስና ፡ ትኖራለኽ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 4 ፤ አባቶቻችን ፡ አንተን ፡ ተማመኑ ፥ ተማመኑ ፡ አንተም ፡ አዳንኻቸው ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 5 ፤ ወዳንተ ፡ ጮኹ ፡ አመለጡም ፥ አንተንም ፡ ተማመኑ ፡ አላፈሩም ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ትል ፡ ነኝ ፡ ሰውም ፡ አይደለኹም ፤ የሰው ፡ ማላገጫ ፡ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ የተናቅኹ ፡ ነኝ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 7 ፤ የሚያዩኝ ፡ ኹሉ ፡ ይላገዱብኛል ፤ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ በከንፈሮቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 8 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ተማመነ ፥ ርሱንም ፡ ያድነው ፤ ቢወደውስ ፡ ያድነው ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ከሆድ ፡ አውጥተኸኛልና ፥ በእናቴ ፡ ጡት ፡ ሳለኹም ፡ ባንተ ፡ ታመንኹ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 10 ፤ ከማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ተጣልኹ ፤ ከእናቴ ፡ ሆድ ፡ ዠምረኽ ፡ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 11 ፤ ጭንቀት ፡ ቀርባለችና ፡ የሚረዳኝም ፡ የለምና ፡ ከእኔ ፡ አትራቅ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 12 ፤ ብዙ ፡ በሬዎች ፡ ከበቡኝ ፥ የሰቡትም ፡ ፍሪዳዎች ፡ ያዙኝ ፤

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 13 ፤ እንደ ፡ ነጣቂና ፡ እንደሚጮኽ ፡ አንበሳ ፡ በላዬ ፡ አፋቸውን ፡ ከፈቱ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ውሃ ፡ ፈሰስኹ ፤ ዐጥንቶቼም ፡ ኹሉ ፡ ተለያዩ ፤ ልቤ ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ኾነ ፥ በአንጎቴም ፡ መካከል ፡ ቀለጠ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 15 ፤ ኀይሌ ፡ እንደ ፡ ገል ፡ ደረቀ ፥ በጕረሮዬም ፡ ምላሴ ፡ ተጣጋ ፥ ወደሞትም ፡ አሸዋ ፡ አወረድኸኝ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 16 ፤ ብዙ ፡ ውሻዎች ፡ ከበውኛልና ፤ የክፋተኞች ፡ ጉባኤም ፡ ያዘኝ ፤ እጆቼንና ፡ እግሮቼን ፡ ቸነከሩኝ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 17 ፤ ዐጥንቶቼ ፡ ኹሉ ፡ ተቈጠሩ ፤ እነርሱም ፡ አዩኝ ፡ ተመለከቱኝም ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 18 ፤ ልብሶቼን ፡ ለራሳቸው ፡ ተከፋፈሉ ፥ በቀሚሴም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 19 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ከእኔ ፡ አትራቅ ፤ አንተ ፡ ጕልበቴ ፥ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ ፍጠን ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 20 ፤ ነፍሴን ፡ ከሰይፍ ፡ አድናት ፥ ብቻነቴንም ፡ ከውሻዎች ፡ እጅ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 21 ፤ ከአንበሳ ፡ አፍ ፡ አድነኝ ፥ ብቻነቴንም ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ ካላቸው ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 22 ፤ ስምኽን ፡ ለወንድሞቼ ፡ እነግራቸዋለኹ ፥ በጉባኤም ፡ መካከል ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩ ፥ አመስግኑት ፤ የያዕቆብ ፡ ዘር ፡ ኹላችኹ ፥ አክብሩት ፥ የእስራኤልም ፡ ዘር ፡ ኹላችኹ ፥ ፍሩት ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 24 ፤ የችግረኛን ፡ ችግር ፡ አልናቀምና ፥ ቸልም ፡ አላለምና ፤ ፊቱንም ፡ ከእኔ ፡ አልሰወረምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ በጮኽኹ ፡ ጊዜ ፡ ሰማኝ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 25 ፤ በታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ምስጋናዬ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ርሱን ፡ በሚፈሩት ፡ ፊት ፡ ስእለቴን ፡ እሰጣለኹ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 26 ፤ ችግረኞች ፡ ይበላሉ ፥ ይጠግቡማል ፤ እግዚአብሔርንም ፡ የሚሹት ፡ ያመሰግኑታል ፤ ልባቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ይኾናል ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 27 ፤ የምድር ፡ ዳርቻዎች ፡ ኹሉ ፡ ያስቡ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለሱ ፤ የአሕዛብ ፡ ነገዶች ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ይሰግዳሉ ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 28 ፤ መንግሥት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነውና ፥ ርሱም ፡ አሕዛብን ፡ ይገዛል ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 29 ፤ የምድር ፡ ደንዳናዎች ፡ ኹሉ ፡ ይበላሉ ፡ ይሰግዳሉም ፤ ወደ ፡ መሬት ፡ የሚወርዱት ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ይንበረከካሉ ፤ ነፍሴም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ።

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 30 ፤ ዘሬ ፡ ይገዛለታል ፤ የምትመጣው ፡ ትውልድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትነግረዋለች ፤

መዝ. ፡ 21 ፡ (22) ፡ 31 ፤ ጽድቁንም ፡ ለሚወለደው ፡ ሕዝብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገውን ፡ ጽድቁን ፡ ይነግራሉ ።

መዝሙር ፡ 22 ፡ (23) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፥ የሚያሳጣኝም ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 2 ፤ በለመለመ ፡ መስክ ፡ ያሳድረኛል ፤ በዕረፍት ፡ ውሃ ፡ ዘንድ ፡ ይመራኛል ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 3 ፤ ነፍሴን ፡ መለሳት ፥ ስለ ፡ ስሙም ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ መራኝ ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 4 ፤ በሞት ፡ ጥላ ፡ መካከል ፡ እንኳ ፡ ብኼድ ፡ አንተ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነኽና ፥ ክፉን ፡ አልፈራም ፤ በትርኽና ፡ ምርኩዝኽ ፡ እነርሱ ፡ ያጽናኑኛል ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 5 ፤ በፊቴ ፡ ገበታን ፡ አዘጋጀኽልኝ ፡ በጠላቶቼ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ራሴን ፡ በዘይት ፡ ቀባኽ ፥ ጽዋዬም ፡ የተረፈ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 22 ፡ (23) ፡ 6 ፤ ቸርነትኽና ፡ ምሕረትኽ ፡ በሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይከተሉኛል ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ለዘለዓለም ፡ እኖራለኹ ።

መዝሙር ፡ 23 ፡ (24) ።

በመዠመሪያ ፡ ሰንበት ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 1 ፤ ምድርና ፡ ሞላዋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ናት ፥ ዓለምም ፡ በርሷም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 2 ፤ ርሱ ፡ በባሕሮች ፡ መሥርቷታልና ፥ በፈሳሾችም ፡ አጽንቷታልና ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 3 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ማን ፡ ይወጣል ፧ በቅድስናውስ ፡ ስፍራ ፡ ማን ፡ ይቆማል ፧

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 4 ፤ እጆቹ ፡ የነጹ ፥ ልቡም ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፥ ነፍሱን ፡ ለከንቱ ፡ ያላነሣ ፥ ለባልንጀራውም ፡ በሽንገላ ፡ ያልማለ ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 5 ፤ ርሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በረከትን ፡ ከመድኀኒቱ ፡ አምላክም ፡ ምሕረትን ፡ ይቀበላል ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 6 ፤ ይህች ፡ ትውልድ ፡ ርሱን ፡ የምትፈልግ ፡ ናት ፥ የያዕቆብን ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ የምትፈልግ ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 7 ፤ እናንት ፡ መኳንንቶች ፥ በሮችን ፡ ክፈቱ ፥ የዘለዓለም ፡ ደጆችም ፡ ይከፈቱ ፥ የክብርም ፡ ንጉሥ ፡ ይግባ ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 8 ፤ ይህ ፡ የክብር ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ ብርቱና ፡ ኀያል ፥ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ በሰልፍ ፡ ኀያል ።

መዝ. ፡ 23 ፡ (24) ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ መኳንንቶች ፥ በሮችን ፡ ክፈቱ ፥ የዘለዓለም ፡ ደጆችም ፡ ይከፈቱ ፥ የክብርም ፡ ንጉሥ ፡ ይግባ ።

መዝ. ፥ 23 ፡ (24) ፥ 10 ፤ ይህ ፡ የክብር ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የጭፍራዎች ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱ ፡ የክብር ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 24 ፡ (25) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 1 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ ነፍሴን ፡ አነሣለኹ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 2 ፤ አምላኬ ፥ አንተን ፡ ታመንኹ ፤ አልፈር ፥ ጠላቶቼ ፡ በእኔ ፡ አይሣቁብኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 3 ፤ አንተን ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉ ፡ አያፍሩም ፤ በከንቱ ፡ የሚገበዙ ፡ ያፍራሉ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 4 ፤ አቤቱ ፥ መንገድኽን ፡ አመልክተኝ ፥ ፍለጋኽንም ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 5 ፤ አንተ ፡ የመድኀኒቴ ፡ አምላክ ፡ ነኽና ፥ በእውነትኽ ፡ ምራኝ ፥ አስተምረኝም ፤ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌያለኹ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 6 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽንና ፡ ቸርነትኽን ፡ ዐስብ ፥ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ናቸውና ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 7 ፤ የልጅነቴን ፡ ኀጢአትና ፡ መተላለፍ ፡ አታስብብኝ ፤ አቤቱ ፥ ስለቸርነትኽ ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ምሕረትኽ ፡ ዐስበኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ቅንም ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ኀጢአተኞችን ፡ በመንገድ ፡ ይመራቸዋል ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 9 ፤ ገሮችን ፡ በፍርድ ፡ ይመራል ፥ ለገሮችም ፡ መንገድን ፡ ያስተምራቸዋል ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ቸርነትና ፡ እውነት ፡ ነው ። ቃል ፡ ኪዳኑንና ፡ ምስክሩን ፡ ለሚጠብቁ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 11 ፤ አቤቱ ፥ ኀጢአቴ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ በሚመርጠው ፡ መንገድ ፡ ያስተምረዋል ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 13 ፤ ነፍሱ ፡ በመልካም ፡ ታድራለች ፥ ዘሩም ፡ ምድርን ፡ ይወርሳል ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ኀይላቸው ፡ ነው ፥ ቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ ያስታውቃቸዋል ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 15 ፤ ርሱ ፡ እግሮቼን ፡ ከወጥመድ ፡ ያወጣቸዋልና ፥ ዐይኖቼ ፡ ዘልጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ናቸው ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 16 ፤ እኔ ፡ ብቻዬንና ፡ ችግረኛ ፡ ነኝና ፡ ፊትኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አድርግ ፡ ማረኝም ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 17 ፤ የልቤ ፡ ችግር ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ከጭንቀቴ ፡ አውጣኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 18 ፤ ድካሜንና ፡ መከራዬን ፡ እይ ፥ ኀጢአቴንም ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

መዝ. ፥ 24 ፡ (25) ፥ 19 ፤ ጠላቶቼ ፡ እንደ ፡ በዙ ፡ እይ ፥ የግፍም ፡ ጥል ፡ ጠልተውኛል ።

መዝ. ፡ 24 ፡ (25) ፡ 20 ፤ ነፍሴን ፡ ጠብቅና ፡ አድነኝ ፤ አንተን ፡ ታምኛለኹና ፡ አልፈር ።

መዝ. ፡ 24 ፡ (25) ፡ 21 ፤ አንተን ፡ ተስፋ ፡ አድርጌያለኹና ፡ የውሀትና ፡ ቅንነት ፡ ይጠብቁኝ ።

መዝ. ፡ 24 ፡ (25) ፡ 22 ፤ አቤቱ ፥ እስራኤልን ፡ ከመከራው ፡ ኹሉ ፡ አድነው ።

_____መዝሙር ፡ 25 ፡ (26) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ በየውሀቴ ፡ ኼጃለኹና ፡ ፍረድልኝ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አምኛለኹና ፡ አልናወጥም ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 2 ፤ አቤቱ ፥ ፍተነኝ ፥ መርምረኝም ፤ ኵላሊቴንና ፡ ልቤን ፡ ፍተን ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 3 ፤ ምሕረትኽ ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ ነውና ፥ በእውነትኽም ፡ ተመላለስኹ ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 4 ፤ በከንቱ ፡ ሸንጎ ፡ አልተቀመጥኹም ፥ ከዐመፀኞችም ፡ ጋራ ፡ አልገባኹም ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 5 ፤ የክፉዎችን ፡ ማኅበር ፡ ጠላኹ ፥ ከዝንጉዎችም ፡ ጋራ ፡ አልቀመጥም ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 6 ፤ እጆቼን ፡ በንጽሕና ፡ ዐጥባለኹ ፤ አቤቱ ፥ መሠዊያኽን ፡ እዞራለኹ ፥

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 7 ፤ የምስጋናን ፡ ድምፅ ፡ እሰማ ፡ ዘንድ ፥ ተኣምራትኽንም ፡ ኹሉ ፡ እነግር ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ የቤትኽን ፡ ስፍራ ፡ የክብርኽንም ፡ ማደሪያ ፡ ቦታ ፡ ወደድኹ ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 9 ፤ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ ነፍሴን ፥ ከደም ፡ ሰዎችም ፡ ጋራ ፡ ሕይወቴን ፡ አታጥፋ ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 10 ፤ በእጃቸው ፡ ተንኰል ፡ አለባቸው ፥ ቀኛቸውም ፡ መማለጃ ፡ ተሞልታለች ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 11 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በየውሀቴ ፡ ኼጃለኹ ፤ አድነኝ ፡ ማረኝም ።

መዝ. ፡ 25 ፡ (26) ፡ 12 ፤ እግሮቼ ፡ በቅንነት ፡ ቆመዋልና ፤ አቤቱ ፥ በማኅበር ፡ አመሰግንኻለኹ ።

_____መዝሙር ፡ 26 ፡ (27) ። _____

ሳይቀባ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ብርሃኔና ፡ መድኀኒቴ ፡ ነው ፤ የሚያስፈራኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እግዚአብሔር ፡ የሕይወቴ ፡ መታመኛዋ ፡ ነው ፤ የሚያስደነግጠኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 2 ፤ ክፉዎች ፥ አስጨናቂዎቼ ፡ ጠላቶቼም ፥ ሥጋዬን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፥ እነርሱ ፡ ተሰናከሉና ፡ ወደቁ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 3 ፤ ሰራዊትም ፡ ቢሰፍርብኝ ፡ ልቤ ፡ አይፈራም ፤ ሰልፍም ፡ ቢነሣብኝ ፡ በዚህ ፡ እተማመናለኹ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ ለመንኹት ፡ ርሷንም ፡ እሻለኹ ፤ በሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እኖር ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውንም ፡ አይ ፡ ዘንድ ፥ መቅደሱንም ፡ እመለከት ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 5 ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ በድንኳኑ ፡ ሰውሮኛልና ፥ በድንኳኑም ፡ መሸሸጊያ ፡ ሸሸጎኛልና ፥ በአለት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጎኛልና ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ አኹን ፡ በዙሪያ ፡ ባሉ ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ራሴን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፤ በድንኳኑም ፡ የእልልታ ፡ መሥዋዕትን ፡ ሠዋኹ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ እቀኛለኹ ፥ እዘምርለትማለኹ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ የጮኽኹትን ፡ ቃሌን ፡ ስማኝ ። ማረኝና ፡ አድምጠኝ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 8 ፤ አንተ ፡ ፊቴን ፡ ሹት ፡ ባልኽ ፡ ጊዜ ፦ አቤቱ ፥ ፊትኽን ፡ እሻለኹ ፡ ልቤ ፡ አንተን ፡ አለ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 9 ፤ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ አትሰውር ፥ ተቈጥተኽ ፡ ከባሪያኽ ፡ ፈቀቅ ፡ አትበል ፤ ረዳት ፡ ኹነኝ ፥ አትጣለኝም ፥ የመድኀኒቴም ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አትተወኝ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 10 ፤ አባቴና ፡ እናቴ ፡ ትተውኛልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ተቀበለኝ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ መንገድኽን ፡ አስተምረኝ ፥ ስለ ፡ ጠላቶቼም ፡ በቀና ፡ መንገድ ፡ ምራኝ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 12 ፤ የሐሰት ፡ ምስክሮችና ፡ ዐመፀኞች ፡ ተነሥተውብኛልና ፥ ለጠላቶቼ ፡ ፈቃድ ፡ አትስጠኝ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነት ፡ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ አምናለኹ ።

መዝ. ፡ 26 ፡ (27) ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ አድርግ ፤ በርታ ፥ ልብኽም ፡ ይጽና ፤ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ አድርግ ።

መዝሙር ፡ 27 ፡ (28) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ እጠራለኹ ፤ ዝም ፡ ብትለኝ ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንደሚወርዱት ፡ እንዳልመስል ፥ አንተ ፡ አምላኬ ፥ ዝም ፡ አትበለኝ ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 2 ፤ ወደ ፡ መቅደስኽ ፡ ማደሪያ ፡ እጄን ፡ ባነሣኹ ፡ ጊዜ ፥ ወዳንተ ፡ የጮኽኹትን ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 3 ፤ ከኃጥኣንና ፡ ከክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ጋራ ፡ ነፍሴን ፡ አትውሰዳት ፤ ክፋትም ፡ በልባቸው ፡ እያለ ፡ ከባልንጀራቸው ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ ከሚናገሩት ፡ ጋራ ፡ አትጣለኝ ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 4 ፤ እንደ ፡ ሥራቸው ፥ እንደአካኼዳቸውም ፡ ክፋት ፡ ስጣቸው ፤ እንደ ፡ እጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ስጣቸው ፤ ፍዳቸውን ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ መልስ ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 5 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ እጆቹም ፡ አደራረግ ፡ አላሰቡምና ፡ ያፈርሳቸዋል ፡ እንጂ ፡ አይሠራቸውም ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 6 ፤ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰምቶኛልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኀይሌና ፡ ጋሻዬ ፡ ነው ፤ ልቤ ፡ በርሱ ፡ ታመነ ፡ እኔም ፡ ተረዳኹ ፤ ሥጋዬም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ ፈቅጄም ፡ አመሰግነዋለኹ ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ኀይላቸው ፡ ነው ፥ ለቀባውም ፡ የመድኀኒቱ ፡ መታመኛ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 27 ፡ (28) ፡ 9 ፤ ሕዝብኽን ፡ አድን ፥ ርስትኽንም ፡ ባርክ ፤ ጠብቃቸው ፥ ለዘለዓለሙም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጋቸው ።

መዝሙር ፡ 28 ፡ (29) ።

ከድንኳን ፡ በመውጣት ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 1 ፤ የአምላክ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ። ክብርንና ፡ ምስጋናን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 2 ፤ የስሙን ፡ ክብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፥ በቅድስናው ፡ ስፍራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ በውሃዎች ፡ ላይ ፥ የክብር ፡ አምላክ ፡ አንጐደጐደ ፥ እግዚአብሔር ፡ በብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ላይ ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ በኀይል ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ በታላቅ ፡ ክብር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ዝግባን ፡ ይሰብራል ፤ እግዚአብሔር ፡ የሊባኖስን ፡ ዝግባ ፡ ይቀጠቅጣል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ጥጃ ፡ ሊባኖስን ፥ አንድ ፡ ቀን ፡ እንዳለው ፡ አውሬ ፡ ልጅ ፡ ስርዮንን ፡ ያዘልላቸዋል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ የእሳቱን ፡ ነበልባል ፡ ይቈርጣል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ያናውጣል ፥ እግዚአብሔር ፡ የቃዴስን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ያናውጣል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ዋላዎችን ፡ ያጠነክራቸዋል ፥ ጫካዎቹንም ፡ ይገልጣል ፤ ኹሉም ፡ በመቅደሱ ፦ ምስጋና ፡ ይላል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጥፋት ፡ ውሃን ፡ ሰብስቧል ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ኾኖ ፡ ይቀመጣል ።

መዝ. ፡ 28 ፡ (29) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ኀይልን ፡ ይሰጣል ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ በሰላም ፡ ይባርካል ።

መዝሙር ፡ 29 ፡ (30) ።

ለቤቱ ፡ መመረቅ ፡ ምስጋና ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ተቀብለኸኛልና ፥ ጠላቶቼንም ፡ ደስ ፡ አላሠኘኽብኝምና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግኻለኹ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 2 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ወዳንተ ፡ ጮኽኩ ፡ ምሕረትም ፡ አደረግኽልኝ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ ከሲኦል ፡ አወጣኻት ፥ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ እንዳልወርድ ፡ አዳንኸኝ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 4 ፤ ቅዱሳን ፡ ሆይ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፥ ለቅድስናውም ፡ መታሰቢያ ፡ አመስግኑ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 5 ፤ ቀሥጣው ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ ሞገሱ ፡ ግን ፡ ለሕይወት ፡ ዘመን ፤ ልቅሶ ፡ ማታ ፡ ይመጣል ፥ ጧት ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ ይኾናል ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 6 ፤ እኔም ፡ በደስታዬ ። ለዘለዓለም ፡ አልታወክም ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ በፈቃድኽ ፡ ለሕይወቴ ፡ ኀይልን ፡ ሰጠኻት ፤ ፊትኽን ፡ መለስኽ ፥ እኔም ፡ ደነገጥኹ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ ጠራኹ ፥ ወደ ፡ አምላኬም ፡ ለመንኹ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ብወርድ ፡ በደሜ ፡ ምን ፡ ጥቅም ፡ አለ ፧ ዐፈር ፡ ያመሰግንኻልን ፧ እውነትኽንም ፡ ይናገራልን ፧

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰማ ፡ ማረኝም ፤ እግዚአብሔር ፡ ረዳቴ ፡ ኾነኝ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 11 ፤ ክብሬ ፡ ትዘምርልኽ ፡ ዘንድ ፡ ዝምም ፡ እንዳትል ፡ ልቅሶዬን ፡ ለደስታ ፡ ለወጥኽልኝ ፥ ማቄን ፡ ቀደኽ ፡ ደስታንም ፡ አስታጠቅኸኝ ።

መዝ. ፡ 29 ፡ (30) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ለዘለዓለም ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝሙር ፡ 30 ፡ (31) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በማድነቅ ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፡ አንተን ፡ ታመንኹ ፤ ለዘለዓለም ፡ አልፈር ፤ በጽድቅኽም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 2 ፤ ጐሮኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብል ፥ ፈጥነኽም ፡ አድነኝ ፤ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ መታመኛ ፡ አምላክና ፡ የመጠጊያ ፡ ቤት ፡ ኹነኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 3 ፤ ዐምባዬና ፡ መጠጊያዬ ፡ አንተ ፡ ነኽና ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ መንገዴን ፡ አቅና ፡ ምራኝም ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 4 ፤ አንተ ፡ መታመኛዬ ፡ ነኽና ፥ ከደበቁብኝ ፡ ወጥመድ ፡ አውጣኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 5 ፤ በእጅኽ ፡ ነፍሴን ፡ እሰጣለኹ ፤ የእውነት ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ ተቤዥተኸኛል ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 6 ፤ ከንቱ ፡ ምናምንቴነትን ፡ የጠበቁትን ፡ ጠላኽ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመንኹ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 7 ፤ መከራዬን ፡ አይተኻልና ፥ ነፍሴንም ፡ ከጭንቀት ፡ አድነኻታልና ፥ በምሕረትኽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ ሐሤትም ፡ አደርጋለኹ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 8 ፤ በጠላቴ ፡ እጅ ፡ አልዘጋኸኝም ፥ በሰፊም ፡ ስፍራ ፡ እግሮቼን ፡ አቆምኽ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 9 ፤ ተቸግሬያለኹና ፡ አቤቱ ፡ ምራኝ ፤ ዐይኔም ፡ ከሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ተፈጀች ፥ ነፍሴም ፡ ሆዴም ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 10 ፤ ሕይወቴ ፡ በሐዘን ፡ አልቃለችና ፥ ዓመታቴም ፡ በልቅሶ ፡ ጨኸት ፤ ኀይሌ ፡ በችግር ፡ ደከመ ፥ ዐጥንቶቼም ፡ ተነዋወጡ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 11 ፤ በጠላቶቼ ፡ ዘንድ ፡ ተነወርኹ ፥ ይልቁንም ፡ በጎረቤቶቼ ፡ ዘንድ ፥ ለሚያውቁኝም ፡ ፍርሀት ፡ ኾንኹ ፤ በሜዳ ፡ ያዩኝም ፡ ከእኔ ፡ ሸሹ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 12 ፤ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰው ፡ ከልብ ፡ ተረሳኹ ፥ እንደ ፡ ተበላሸ ፡ ዕቃም ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 13 ፤ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ስድብ ፡ ሰምቻለኹና ፤ በዙሪያው ፡ ፍርሀት ፡ ነበረ ፤ በላዬ ፡ በአንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሴን ፡ ለመንጠቅ ፡ ተማከሩ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 14 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ባንተ ፡ ታመንኹ ፤ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 15 ፤ ርስቴ ፡ በእጅኽ ፡ ነው ፤ ከጠላቶቼ ፡ እጅና ፡ ከሚያሳድዱኝ ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 16 ፤ ፊትኽን ፡ በባሪያኽ ፡ ላይ ፡ አብራ ፥ ስለ ፡ ምሕረትኽም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ አንተን ፡ ጠርቻለኹና ፡ አልፈር ፤ ክፉዎች ፡ ይፈሩ ፡ በሲኦልም ፡ ዝም ፡ ይበሉ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 18 ፤ በድፍረትና ፡ በትዕቢት ፡ በመናቅም ፡ በጻድቅ ፡ ላይ ፡ የሚናገሩ ፡ የሸንገላ ፡ ከንፈሮች ፡ ድዳ ፡ ይኹኑ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 19 ፤ ባንተ ፡ ለሚያምኑ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ያዘጋጀኻት ፡ ለሚፈሩኽም ፡ የሰወርኻት ፥ ቸርነትኽ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ በዛች! ፡

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 20 ፤ በፊትኽ ፡ መጋረጃ ፡ ከሰው ፡ ክርክር ፡ ትጋርዳቸዋለኽ ፥ በድንኳንኽም ፡ ከአንደበት ፡ ክርክር ፡ ትሸፍናቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 21 ፤ በተከበበ ፡ ከተማ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ምሕረቱን ፡ በእኔ ፡ የገለጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 22 ፤ እኔስ ፡ ከዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ተጣልኹ ፥ በድንጋጤ ፡ አልኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ወዳንተ ፡ በጮኽኹ ፡ ጊዜ ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ ሰማኸኝ ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 23 ፤ ኹላችኹ ፡ ቅዱሳኑ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ውደዱት ፤ እግዚአብሔር ፡ እውነተኞችን ፡ ይፈልጋል ፥ ትዕቢተኞችንም ፡ ፈጽሞ ፡ ይበቀላቸዋል ።

መዝ. ፡ 30 ፡ (31) ፡ 24 ፤ በእግዚአብሔር ፡ የምታምኑ ፡ ኹላችኹ ፥ በርቱ ፡ ልባችኹም ፡ ይጥና ።

መዝሙር ፡ 31 ፡ (32) ።

የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 1 ፤ መተላለፉ ፡ የቀረችለት ፡ ኀጢአቱም ፡ የተከደነችለት ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደልን ፡ የማይቈጥርበት ፡ በመንፈሱም ፡ ሽንገላ ፡ የሌለበት ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 3 ፤ ኹልጊዜ ፡ ከመጮኼ ፡ የተነሣ ፡ ዝም ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፡ ዐጥንቶቼ ፡ ተበላሹ ፤

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 4 ፤ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ እጅኽ ፡ ከብዳብኛለችና ፥ ርጥበቴም ፡ ለበጋ ፡ ትኵሳት ፡ ተለወጠ ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 5 ፤ ኀጢአቴን ፡ ለአንተ ፡ አስታወቅኹ ፥ በደሌንም ፡ አልሸፈንኹም ፤ ለእግዚአብሔር ፡ መተላለፌን ፡ እነግራለኹ ፡ አልኹ ፤ አንተም ፡ የልቤን ፡ ኀጢአት ፡ ተውኽልኝ ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ቅዱስ ፡ ኹሉ ፡ በምቹ ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ ይለምናል ፤ ብዙ ፡ የጥፋት ፡ ውሃም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አይቀርብም ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 7 ፤ አንተ ፡ ለእኔ ፡ መሸሸጊያዬ ፡ ነኽ ፥ ከጣርም ፡ ትጠብቀኛለኽ ፤ ከከበቡኝ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ደስታዬ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 8 ፤ አስተምርኻለኹ ፡ በምትኼድበትም ፡ መንገድ ፡ እመራኻለኹ ፤ ዐይኖቼን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አጠናለኹ ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 9 ፤ ወዳንተ ፡ እንዳይቀርቡ ፡ በልባብና ፡ በልጓም ፡ ጕንጫቸውን ፡ እንደሚለጕሟቸው ፥ ልብ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ ፈረስና ፡ እንደ ፡ በቅሎ ፡ አትኹኑ ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 10 ፤ በኀጢአተኛ ፡ ብዙ ፡ መቅሠፍት ፡ አለበት ፤ በእግዚአብሔር ፡ የሚታመነውን ፡ ግን ፡ ምሕረት ፡ ይከበዋል ።

መዝ. ፡ 31 ፡ (32) ፡ 11 ፤ ጻድቃን ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ሐሤትም ፡ አድርጉ ፤

ልባችኹም ፡ የቀና ፡ ኹላችኹ ፥ እልል ፡ በሉ ።

መዝሙር ፡ 32 ፡ (33) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 1 ፤ ጻድቃን ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ ለቅኖች ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመሰንቆ ፡ አመስግኑት ፥ ዐሥር ፡ አውታርም ፡ ባለው ፡ በበገና ፡ ዘምሩለት ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 3 ፤ ዐዲስ ፡ ቅኔም ፡ ተቀኙለት ፥ በእልልታም ፡ መልካም ፡ ዝማሬ ፡ ዘምሩ ፤

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ቅን ፡ ነውና ፥ ሥራውም ፡ ኹሉ ፡ በእምነት ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 5 ፤ ጽድቅንና ፡ ፍርድን ፡ ይወዳል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ምድርን ፡ ሞላች ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 6 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሰማዮች ፡ ጸኑ ፥ ሰራዊታቸውም ፡ ኹሉ ፡ በአፉ ፡ እስትንፋስ ፤

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 7 ፤ የባሕርን ፡ ውሃ ፡ እንደ ፡ ረዋት ፡ የሚሰበስበው ፥ ቀላዮችንም ፡ በመዝገቦች ፡ የሚያኖራቸው ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 8 ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትፍራው ፥ በዓለም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉም ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ይደንግጡ ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 9 ፤ ርሱ ፡ ተናግሯልና ፥ ኾኑም ፤ ርሱ ፡ አዘዘ ፥ ጸኑም ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የአሕዛብን ፡ ምክር ፡ ያጠፋል ፥ የአሕዛብንም ፡ ዐሳብ ፡ ይመልሳል ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። የልቡም ፡ ዐሳብ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ የሚኾንለት ፡ ሕዝብ ፡ ምስጉን ፡ ነው ፥ ርሱ ፡ ለርስቱ ፡ የመረጠው ፡ ሕዝብ ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ ተመለከተ ፥ የሰውንም ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ አየ ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 14 ፤ ከማደሪያው ፡ ቦታ ፡ ኾኖ ፡ በምድር ፡ ወደሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ተመለከተ ፥

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 15 ፤ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ ልባቸውን ፡ የሠራ ፡ ሥራቸውንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያስተውል ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 16 ፤ ንጉሥ ፡ በሰራዊቱ ፡ ብዛት ፡ አይድንም ፡ ኀያልም ፡ በኀይሉ ፡ ብዛት ፡ አያመልጥም ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 17 ፤ ፈረስም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፥ አያድንም ፤ በኀይሉም ፡ ብዛት ፡ አያመልጥም ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ ወደሚፈሩት ፡ ናቸው ፥ በምሕረቱም ፡ ወደሚታመኑ ፥

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 19 ፤ ነፍሳቸውን ፡ ከሞት ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፥ በራብም ፡ ጊዜ ፡ ይመግባቸው ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 20 ፤ ነፍሳችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ ታደርገዋለች ፥ ረዳታችንና ፡ መጠጊያችን ፡ ርሱ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 21 ፤ ልባችን ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይለዋልና ፥ በቅዱስ ፡ ስሙም ፡ ታምነናልና ።

መዝ. ፡ 32 ፡ (33) ፡ 22 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ በላያችን ፡ ትኹን ፥ ባንተ ፡ እንደ ፡ ታመን ።

መዝሙር ፡ 33 ፡ (34) ።

ባሳደደው ፡ በአቢሜሌክ ፡ ፊት ፡ መልኩን ፡ በለወጠ ፡ ጊዜ ፡ በኼደም ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ዘልጊዜ ፡ እባርከዋለኹ ፥ ምስጋናውንም ፡ ዘወትር ፡ በአፌ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 2 ፤ ነፍሴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትከብራለች ፥ ገሮችም ፡ ሰምተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ታላቅ ፡ አድርጉት ፥ በአንድነትም ፡ ስሙን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እናድርግ ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፈለግኹት ፡ መለሰልኝም ፥ ከመከራዬም ፡ ኹሉ ፡ አዳነኝ ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቅረቡ ፡ ያበራላችኹማል ፥ ፊታችኹም ፡ አያፍርም ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 6 ፤ ይህ ፡ ችግረኛ ፡ ጮኸ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሰማው ፥ ከመከራውም ፡ ኹሉ ፡ አዳነው ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በሚፈሩት ፡ ሰዎች ፡ ዙሪያ ፡ ይሰፍራል ፥ ያድናቸውማል ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቅመሱ ፡ እዩም ፤ በርሱ ፡ የሚታመን ፡ ሰው ፡

ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 9 ፤ የሚፈሩት ፡ አንዳችን ፡ አያጡምና ፡ ቅዱሳኑ ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩት ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 10 ፤ ባለጠጋዎች ፡ ደኸዩ ፥ ተራቡም ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈልጉትን ፡ ግን ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይጐድሉም ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 11 ፤ ልጆቼ ፡ ኑ ፥ ስሙኝ ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ አስተምራችኋለኹ ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 12 ፤ ሕይወትን ፡ የሚፈቅድ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ በጎንም ፡ ዘመን ፡ ለማየት ፡ የሚወድ ፧

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 13 ፤ አንደበትኽን ፡ ከክፉ ፡ ከልክል ፥ ከንፈሮችኽም ፡ ሽንገላን ፡ እንዳይናገሩ ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 14 ፤ ከክፉ ፡ ሽሽ ፡ መልካምንም ፡ አድርግ ፤ ሰላምን ፡ ሻ ፥ ተከተላትም ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ ወደ ፡ ጻድቃን ፥ ጕሮዎቹም ፡ ወደ ፡ ጩኸታቸው ፡ ናቸውና ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 16 ፤ መታሰቢያቸውን ፡ ከምድር ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉን ፡ በሚያደርጉ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 17 ፤ ጻድቃን ፡ ጮኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሰማቸው ፡ ከመከራቸውም ፡ ኹሉ ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ልባቸው ፡ ለተሰበረ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፥ መንፈሳቸው ፡ የተሰበረውንም ፡ ያድናቸዋል ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 19 ፤ የጻድቃን ፡ መከራቸው ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከኹሉ ፡ ያድናቸዋል ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐጥንቶቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቃል ፥ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ አይሰበርም ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 21 ፤ ኀጢአተኞችን ፡ ክፋት ፡ ይገድላቸዋል ፡ ጻድቃንንም ፡ የሚጠሉ ፡ ይጸጸታሉ ።

መዝ. ፡ 33 ፡ (34) ፡ 22 ፤ የባሪያዎቹን ፡ ነፍስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቤዣል ፥ በርሱም ፡ የሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ አይጸጸቱም ።

_____መዝሙር ፡ 34 ፡ (35) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ የሚበድሉኝን ፡ በድላቸው ፥ የሚዋጉኝንም ፡ ተዋጋቸው ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 2 ፤ ጥሩርና ፡ ጋሻ ፡ ያዝ ፥ እኔንም ፡ ለመርዳት ፡ ተነሥ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 3 ፤ ሰይፍኽን ፡ ምዘዝ ፥ የሚያሳድዱኝንም ፡ መንገዳቸውን ፡ ዝጋ ፤ ነፍሴን ፦ መድኀኒትሽ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በላት ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 4 ፤ ነፍሴን ፡ የሚሹ ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩ ፥ ይጐስቈሉም ፤ ክፋትን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚያስቡ ፡ ይፈሩ ፥ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ ይበሉ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 5 ፤ በነፋስ ፡ ፊት ፡ እንዳለ ፡ ትቢያ ፡ ይኹኑ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡

ያስጨንቃቸው ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 6 ፤ መንገዳቸው ፡ ድጥና ፡ ጨለማ ፡ ይኹን ፥ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ያሳዳቸው ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 7 ፤ በከንቱ ፡ ያጠፉኝ ፡ ዘንድ ፡ ወጥመዳቸውን ፡ ሸሽገውብኛልና ፥ ነፍሴን ፡ በከንቱ ፡ አበሳጭተዋልና ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 8 ፤ ያላወቁት ፡ ወጥመድ ፡ ይምጣባቸው ፥ የሸሸጉትም ፡ ወጥመድ ፡ ይያዛቸው ፤ በዚህ ፡ ወጥመድ ፡ ውስጥ ፡ ይውደቁ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 9 ፤ ነፍሴ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይላታል ፥ በማዳኑም ፡ ሐሴት ፡ ታደርጋለች ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 10 ፤ ዐጥንቶቼ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይሉኻል ፦ አቤቱ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ችግረኛን ፡ ከሚቀማው ፡ እጅ ፥ ችግረኛንና ፡ ድኻውንም ፡ ከሚነጥቀው ፡ እጅ ፡ ታድነዋለኽ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 11 ፤ የክፋት ፡ ምስክሮች ፡ ተነሡብኝ ፥ የማላውቀውንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 12 ፤ ስለ ፡ በጎ ፡ ክፋትን ፡ መለሱልኝ ፥ ነፍሴንም ፡ ልጆችን ፡ አሳጧት ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 13 ፤ እኔስ ፡ እነርሱ ፡ በታመሙ ፡ ጊዜ ፡ ማቅ ፡ ለበስኩ ፥ ነፍሴንም ፡ በጾም ፡ አደከምኋት ፤ ጸሎቴም ፡ ወደ ፡ ብብቴ ፡ ተመለሰ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 14 ፤ ለወዳጄና ፡ ለወንድሜ ፡ እንደማደርግ ፡ አደረግኹ ፤ ለእናቱም ፡ እንደሚያለቅስ ፡ ራሴን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አደረግኹ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 15 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ደስም ፡ አላቸው ፤ ግፈኞች ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተሰበሰቡ ፡ እኔም ፡ አላውቅኹም ፤ ቀደዱኝ ፡ አልተዉኝምም ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 16 ፤ ፈተኑኝ ፡ በሣቅም ፡ ዘበቱብኝ ፥ ጥርሳቸውንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አንቀጫቅጨ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ታይልኛለኽ ፧ ነፍሴን ፡ ከክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ብችኑቴንም ፡ ከአንበሳዎች ፡ አድናት ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 18 ፤ አቤቱ ፥ በታላቁ ፡ ጉባኤ ፡ ውስጥ ፡ እገዛልኻለኹ ፥ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ መካከልም ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 19 ፤ በግፍ ፡ የሚጠሉኝ ፡ በላዬ ፡ ደስ ፡ አይበላቸው ፥ በከንቱ ፡ የሚጣሉኝም ፡ በዐይናቸው ፡ አይጣቀሱብኝ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 20 ፤ ለኔስ ፡ ሰላምን ፡ ይናገሩኛልና ፥ በቀኑጣም ፡ ሽንገላን ፡ ይመክራሉ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 21 ፤ አፋቸውንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አላቀቁ ፤ ዕሠይ ፡ ዕሠይ ፥ ዐይናችን ፡ አየው ፡ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 22 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አየኸው ፤ ዝም ፡ አትበል ፤ አቤቱ ፥ ከእኔ ፡ አትራቅ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 23 ፤ አምላኬ ፡ ጌታዬም ፥ ወደ ፡ ፍርዴ ፡ ተነሥ ፥ አቤቱ ፥ ፍርዴን ፡ አድምጥ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 24 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ እንደ ፡ ጽድቅኽ ፡ ፍረድልኝ ፥ በላዬም ፡ ደስ ፡ አይበላቸው ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 25 ፤ በልባቸው ፦ ዕሠይ ፡ ዕሠይ ፥ ነፍሳችንን ፡ ደስ ፡ አላት ፡

አይበሉ ፤ ደግሞም ፦ ዋጥነው ፡ አይበሉ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 26 ፤ በመከራዬ ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ ይፈሩ ፥ በአንድነትም ፡ ይጐስቍሉ ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚታበዩ ፡ ዕፍረትንና ፡ ጕስቍልናን ፡ ይልበሱ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 27 ፤ ጽድቄን ፡ የሚወዷት ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ ሐሴትንም ፡ ያድርጉ ፤ የባሪያውን ፡ ሰላም ፡ የሚወድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፡ ዘወትር ፡ ይበሉ ።

መዝ. ፡ 34 ፡ (35) ፡ 28 ፤ ምላሴ ፡ ጽድቅኽን ፡ ኹልጊዜም ፡ ምስጋናኽን ፡ ይናገራል ።

መዝሙር ፡ 35 ፡ (36) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 1 ፤ ኀጢአተኛ ፡ በራሱ ፡ የሚያስት ፡ ነገርን ፡ ይናገራል ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ፍርሀት ፡ በዐይኖቹ ፡ ፊት ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 2 ፤ በአንደበቱ ፡ ሽንግሏልና ፤ ኀጢአቱ ፡ ባገኘችው ፡ ጊዜ ፡ ይጠላታል ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 3 ፤ የአፉ ፡ ቃል ፡ ግፍና ፡ ሽንገላ ፡ ነው ፤ ማስተዋልን ፡ በጎ ፡ ማድረግንም ፡ ተወ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 4 ፤ በመኝታው ፡ ጠማማነትን ፡ ዐሰበ ፤ መልካም ፡ ባልኾነች ፡ መንገድ ፡ ቆሟል ፤ ክፋትን ፡ አይንቃትም ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ በሰማይ ፡ ነው ፥ እውነትኽም ፡ ወደ ፡ ደመናት ፡ ትደርሳለች ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 6 ፤ ጽድቅኽም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ተራራዎች ፥ ፍርድኽም ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ ናት ፤ አቤቱ ፥ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ ታድናለኽ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽን ፡ እንዴት ፡ አበዛኽ! ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በክንፎችኽ ፡ ጥላ ፡ ይታመናሉ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 8 ፤ ከቤትኽ ፡ ጠል ፡ ይጠጣሉ ፥ ከተድላም ፡ ፈሳሽ ፡ ታጠጣቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 9 ፤ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፤ በብርሃንኽ ፡ ብርሃንን ፡ እናያለን ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 10 ፤ ምሕረትኽን ፡ በሚያውቁኽ ፡ ላይ ፥ ጽድቅኽንም ፡ ልባቸው ፡ በቀና ፡ ላይ ፡ ዘርጋ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 11 ፤ የትዕቢት ፡ እግር ፡ አይምጣብኝ ፥ የኀጢአተኞችም ፡ እጅ ፡ አያውከኝ ።

መዝ. ፡ 35 ፡ (36) ፡ 12 ፤ ዐመፃን ፡ የሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ከዚያ ፡ ወደቁ ፤ ወድቀዋል ፥ መቆምም ፡ አይችሉም ።

መዝሙር ፡ 36 ፡ (37) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 1 ፤ በክፉዎች ፡ ላይ ፡ አትቅና ፥ ዐመፃንም ፡ በሚያደርጉ ፡ ላይ ፡ አትቅና ፤

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 2 ፤ እንደ ፡ ሣር ፡ ፈጥነው ፡ ይደርቃሉና ፥ እንደ ፡ ለመለመ ፡ ቅጠልም ፡ ይረግፋሉና ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 3 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ታመን ፥ መልካምንም ፡ አድርግ ፥ በምድርም ፡

ተቀመጥ ፥ ታምነኽም ፡ ተሰማራ ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 4 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ፥ የልብኽንም ፡ መሻት ፡ ይሰጥኻል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 5 ፤ መንገድኽን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዐደራ ፡ ስጥ ፥ በርሱም ፡ ታመን ፥ ርሱም ፡ ያደርግልኻል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 6 ፤ ጽድቅኽን ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ፍርድኽንም ፡ እንደ ፡ ቀትር ፡ ያመጣል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 7 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዛ ፥ ተስፋም ፡ አድርገው ። መንገድም ፡ በቀናችለትና ፡ ጥመትን ፡ በሚያደርግ ፡ ሰው ፡ አትቅና ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 8 ፤ ከቊጣ ፡ ራቅ ፥ መዓትንም ፡ ተው ፤ እንዳትበድል ፡ አትቅና ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 9 ፤ ክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ይጠፋሉና ፤ እግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርጉ ፡ ግን ፡ እነርሱ ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉ ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 10 ፤ ገና ፡ ጥቂት ፥ ኀጢአተኛም ፡ አይኖርም ፤ ትፈልገዋለኽ ፡ ቦታውንም ፡ አታገኝም ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 11 ፤ ገሮች ፡ ግን ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉ ፥ በብዙም ፡ ሰላም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 12 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ጻድቁን ፡ ይመለካከተዋል ፥ ጥርሱንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያንገጫግጫል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይሥቅበታል ፥ ቀኑ ፡ እንደሚደርስ ፡ አይቷልና ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 14 ፤ ኀጢአተኞች ፡ ሰይፋቸውን ፡ መዘዙ ፥ ቀስታቸውንም ፡ ገተሩ ፡ ድኻውንና ፡ ችግረኛውን ፡ ይጥሉ ፡ ዘንድ ፡ ልበ ፡ ቅኖችንም ፡ ይወጉ ፡ ዘንድ ፤

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 15 ፤ ሰይፋቸው ፡ ወደ ፡ ልባቸው ፡ ይግባ ፥ ቀስታቸውም ፡ ይሰበር ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 16 ፤ ለጻድቅ ፡ ያለው ፡ ጥቂት ፡ ከብዙ ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ሀብት ፡ ይበልጣል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 17 ፤ የኃጥኣን ፡ ክንድ ፡ ትሰበራለችና ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ጻድቃንን ፡ ይደግፋቸዋል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 18 ፤ የንጹሓንን ፡ መንገድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፥ ርስታቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ፤

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 19 ፤ በክፉ ፡ ዘመንም ፡ አያፍሩም ፡ በራብ ፡ ዘመንም ፡ ይጠግባሉ ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 20 ፤ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ ይጠፋሉ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶች ፡ በከበሩና ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ይጠፋሉ ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 21 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ይበደራል ፡ አይከፍልምም ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ይራራል ፡ ይሰጣልም ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 22 ፤ ርሱን ፡ የሚባርኩት ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉና ፤ የሚረግሙት ፡ ግን ፡ ይጠፋሉ ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 23 ፤ የሰው ፡ አካኼድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይጸናል ፥ መንገዱንም ፡ ይወዳል ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 24 ፤ ቢወድቅም ፡ ለድንጋጤ ፡ አይጣልም ፥ እግዚአብሔር ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ይደግፈዋልና ።

መዝ. ፥ 36 ፡ (37) ፥ 25 ፤ ጐለመስኩ ፡ አረጀኩም ፤ ጻድቅ ፡ ሲጣል ፥ ዘሩም ፡ እኽል ፡ ሲለምን ፡ አላየኩም ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 26 ፤ ኹልጊዜ ፡ ይራራል ፡ ያበድርማል ፥ ዘሩም ፡ በበረከት ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 27 ፤ ከክፉ ፡ ሽሽ ፥ መልካምንም ፡ አድርግ ፤ ለዘለዓለምም ፡ ትኖራለኽ ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 28 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍርዱን ፡ ይወዳልና ፥ ቅዱሳኑንም ፡ አይጥላቸውምና ፤ ለዘለዓለምም ፡ ይጠብቃቸዋል ፡ ለንጹሓንም ፡ ይበቀልላቸዋል ፤ የኃጥኣን ፡ ዘር ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 29 ፤ ጻድቃን ፡ ምድርን ፡ ይወርሳሉ ፥ በርሷም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራሉ ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 30 ፤ የጻድቅ ፡ አፍ ፡ ጥበብን ፡ ያስተምራል ፥ አንደበቱም ፡ ፍርድን ፡ ይናገራል ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 31 ፤ የአምላኩ ፡ ሕግ ፡ በልቡ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፥ በርምጃውም ፡ አይሰናከልም ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 32 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ጻድቁን ፡ ይመለከተዋል ፥ ሊገድለውም ፡ ይወዳል ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 33 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በእጁ ፡ አይተወውም ፥ በተፋረደውም ፡ ጊዜ ፡ አያሸንፈውም ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 34 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ደጅ ፡ ጥና ፥ መንገዱንም ፡ ጠብቅ ፥ ምድርንም ፡ ትወርስ ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርግኻል ፤ ኀጢአተኞችም ፡ ሲጠፉ ፡ ታያለኽ ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 35 ፤ ኃጥእን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባም ፡ ለምልሞ ፡ አየኹት ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 36 ፤ ብመለስ ፡ ግን ፡ ዐጣኹት ፤ ፈለግኹት ፡ ቦታውንም ፡ አላገኘኹም ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 37 ፤ ቅንነትን ፡ ጠብቅ ፥ ጽድቅንም ፡ እይ ፤ ለሰላም ፡ ሰው ፡ ቅሬታ ፡ አለውና ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 38 ፤ በደለኞች ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋሉ ። የኀጢአተኞች ፡ ቅሬታ ፡ ይጠፋል ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 39 ፤ የጻድቃን ፡ መድኀኒታቸው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ መጠጊያቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 36 ፡ (37) ፡ 40 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይረዳቸዋል ፥ ያድናቸዋልም ፥ ከኀጢአተኞችም ፡ እጅ ፡ ያወጣቸዋል ፥ ያድናቸዋል ፥ በርሱ ፡ ታምነዋልና ።

መዝሙር ፡ 37 ፡ (38) ።

ለሰንበት ፡ መታሰቢያ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በቀኖጣኽ ፡ አትቅሠፈኝ ፥ በመዓትኽም ፡ አትገሥጸኝ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 2 ፤ ፍላጻዎችኽ ፡ ወግተውኛልና ፥ እጅኽንም ፡ አክብደኽብኛልና ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 3 ፤ ከቀኖጣኽ ፡ የተነሣ ፡ ለሥጋዬ ፡ ጤና ፡ የለውም ፤ ከኀጢአቴም ፡ የተነሣ ፡ ለዐጥንቶቼ ፡ ሰላም ፡ የላቸውም ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 4 ፤ ኀጢአቴ ፡ በራሴ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ እንደ ፡ ከባድ ፡ ሸክምም ፡ በላዬ ፡ ከብዷልና ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 5 ፤ ከስንፍናዬ ፡ የተነሣ ፡ ቀኖሌ ፡ ሸተተ ፡ በሰበሰም ፤

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 6 ፤ እጅግ ፡ ጐሰቈልኹ ፡ ተዋረድኹም ፥ ኹልጊዜም ፡ በትካዜ ፡ እመላለሳለኹ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 7 ፤ ነፍሴ ፡ ስድብን ፡ ተሞልታለችና ፥ ለሥጋዬም ፡ ጤና ፡ የላትምና ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 8 ፤ ታመምኹ ፤ እጅግም ፡ ተቸገርኹ ፥ ከልቤ ፡ ውዝዋዜም ፡ የተነሣ ፡ ጮኽኹ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ ፈቃዴ ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ነው ፥ ጭንቀቴም ፡ ከአንተ ፡ አይሰወርም ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 10 ፤ ልቤ ፡ ደነገጠብኝ ፥ ኀይሌም ፡ ተወችኝ ፥ የዐይኖቼም ፡ ብርሃን ፡ ፈዘዘ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 11 ፤ ወዳጆቼም ፡ ባልንጀራዎቼም ፡ ከቍስሌ ፡ ገለል ፡ ብለው ፡ ቆሙ ፥ ዘመዶቼም ፡ ርቀው ፡ ቆሙ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 12 ፤ ነፍሴንም ፡ የሚሿት ፡ በረቱብኝ ፥ መከራዬንም ፡ የሚፈልጉ ፡ ከንቱን ፡ ተናገሩ ፥ ኹልጊዜም ፡ በሽንገላ ፡ ይመክራሉ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 13 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እንደማይሰማ ፡ ደንቈሮ ፡ አፉንም ፡ እንደማይከፍት ፡ ዲዳ ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 14 ፤ እንደማይሰማ ፡ ሰው ፡ በአፉም ፡ ተግሣጽ ፡ እንደሌለው ፡ ሰው ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 15 ፤ አቤቱ ፥ ባንተ ፡ ታምኛለኹና ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ አንተ ፡ ትሰማኛለኽ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 16 ፤ ጠላቶቼ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ እንዳይላቸው ፡ ብያለኹና ፥ እግሮቼም ፡ ቢሰናከሉ ፡ ራሳቸውን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋሉ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 17 ፤ እኔስ ፡ ወደ ፡ ማንከስ ፡ ቀርቤያለኹና ፥ ቍስሌም ፡ ኹልጊዜም ፡ በፊቴ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 18 ፤ በደሌን ፡ እናገራለኹና ፥ ስለ ፡ ኀጢአቴም ፡ እተክዛለኹ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 19 ፤ ጠላቶቼ ፡ ሕያዋን ፡ ናቸው ፡ ይበረቱብኝማል ፥ በጠማማነትም ፡ የሚጠሉኝ ፡ በዙ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 20 ፤ ጽድቅን ፡ ስለ ፡ ተከተልኹ ፥ በበጎ ፡ ፋንታ ፡ ክፉን ፡ የሚመልሱልኝ ፡ ይጠሉኛል ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 21 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አትጣለኝ ፤ አምላኬ ፥ ከእኔ ፡ አትራቅ ።

መዝ. ፡ 37 ፡ (38) ፡ 22 ፤ አቤቱ ፡ መድኀኒቴ ፥ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ ፍጠን ።

_____መዝሙር ፡ 38 ፡ (39) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፥ ለኤዶታም ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 1 ፤ በአንደበቴ ፡ እንዳልስት ፡ መንገዴን ፡ እጠብቃለኹ ፤ ኀጢአተኛ ፡ በፊቴ ፡ በተቃወመኝ ፡ ጊዜ ፡ በአፌ ፡ ላይ ፡ ጠባቂ ፡ አኖራለኹ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 2 ፤ ከዝምታ ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ዲዳ ፡ ኾንኹ ፥ ለበጎ ፡ እንኳ ፡ ዝም ፡ አልኹ ፥ ቍስሌም ፡ ታደሰብኝ ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 3 ፤ ልቤም ፡ በውስጤ ፡ ሞቀብኝ ፤ ከማሰቤም ፡ የተነሣ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፥ በአንደበቴም ፡ ተናገርኹ ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ ፍጻሜዬን ፡ አስታውቀኝ ፥ የዘመኔ ፡ ቍጥሮች ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ እኔ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንደምቀር ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ ዘመኖቼን ፡ አስረጀኻቸው ፤ አካሌም ፡ በፊትኽ ፡ እንደ ፡ ኢ.ምንት ፡ ነው ። ሕያው ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በእውነት ፡ ከንቱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 6 ፤ በከንቱ ፡ ይታወካል ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጣላ ፡ ይመላለሳል ፤ ያከማቻል ፡ የሚሰበስብለትንም ፡ አያውቅም ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 7 ፤ አኹንስ ፡ ተስፋዬ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እግዚአብሔር ፡ አይደለምን ፧ ትዕግሥቴም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 8 ፤ ከኀጢአቴ ፡ ኹሉ ፡ አድነኝ ፥ ለሰነፎችም ፡ ስድብ ፡ አታድርገኝ ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ሠርተኸኛልና ፥ ዝም ፡ አልኹ ፡ አፌንም ፡ አልከፈትኹም ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 10 ፤ መቅሠፍትኽን ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ፥ ከእጅኽ ፡ ብርታት ፡ የተነሣ ፡ አልቄያለኹና ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 11 ፤ በተግሣጽኽ ፡ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ ሰውን ፡ ዘለፍኸው ፥ ነፍሱም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ታልቃለች ፤ በእውነት ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ ስማ ፥ ጩኸቴንም ፡ አድምጥ ፥ ልቅሶዬንም ፡ ችል ፡ አትበለኝ ፤ እኔ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መጻተኛ ፡ ነኝና ፥ እንደ ፡ አባቶችም ፡ እንግዳ ፡ ነኝና ።

መዝ. ፡ 38 ፡ (39) ፡ 13 ፤ ወደማልመለስበት ፡ ሳልኼድ ፡ ዐርፍ ፡ ዘንድ ፡ ተወኝ ።

መዝሙር ፡ 39 ፡ (40) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 1 ፤ ቈይቼ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደጅ ፡ ጠናኹት ፥ ርሱም ፡ ዘንበል ፡ አለልኝ ፡ ጩኸቴንም ፡ ሰማኝ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 2 ፤ ከጥፋት ፡ ጕድጓድ ፡ ከረግረግም ፡ ጭቃ ፡ አወጣኝ ፥ እግሮቼንም ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ አቆማቸው ፥ አረማመዴንም ፡ አጸና ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 3 ፤ ዐዲስ ፡ ዝማሬን ፡ ለአምላካችን ፡ ምስጋና ፡ በአፌ ፡ ጨመረ ፤ ብዙዎች ፡ ያያሉ ፡ ይፈሩማል ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ይታመናሉ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የታመነ ፡ ወደ ፡ ትዕቢተኛና ፡ ወደ ፡ ሐሰተኛ ፡ ያልተመለከተ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ያደረግኸው ፡ ተኣምራት ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ ዐሳብኽንም ፡ ምንም ፡ የሚመስለው ፡ የለም ፤ ባወራም ፡ ብናገርም ፡ ከቍጥር ፡ ኹሉ ፡ በዛ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 6 ፤ መሥዋዕትንና ፡ ቍርባንን ፡ አልወደድኽም ፤ ሥጋን ፡ አዘጋጀኽልኝ ፤ የሚቃጠለውንና ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ የሚቀርበውን ፡ መሥዋዕት ፡ አልሻኽም ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አልኹ ፦ እንሆ ፥ መጣኹ ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ በመጽሐፍ ፡ ራስ ፡ ተጽፏል ፤

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 8 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ፈቃድኽን ፡ ለማድረግ ፡ ወደድኹ ፥ ሕግኽም ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 9 ፤ በታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ጽድቅን ፡ አወራኹ ፤ እንሆ ፥ ከንፈሮቼን ፡ አልከለክልም ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ጽድቄን ፡ ታውቃለኽ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 10 ፤ እውነትኽንም ፡ በልቤ ፡ ውስጥ ፡ አልሰወርኹም ፥ ማዳንኽንም ፡ ተናገርኹ ፤ ምሕረትኽንና ፡ እውነትኽን ፡ ከታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ አልሰወርኹም ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ምሕረትኽን ፡ ከእኔ ፡ አታርቅ ፤ ቸርነትኽና ፡ እውነትኽ ፡ ዘወትር ፡ ይጠብቁኝ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 12 ፤ ቍጥር ፡ የሌላት ፡ ክፋት ፡ አግኝታኛለችና ፤ ኀጢአቶቼ ፡ ያዙኝ ፥ ማየትም ፡ ተስኖኛል ፡ ከራሴ ፡ ጠጉር ፡ ይልቅ ፡ በዙ ፥ ልቤም ፡ ተወኝ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ ፍቀድ ፤ አቤቱ ፥ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ ፍጠን ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 14 ፤ ነፍሴን ፡ ለማጥፋት ፡ የሚወዱ ፡ ይፈሩ ፥ በአንድነትም ፡ ይጐስቍሉ ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ክፋትን ፡ ሊያደርጉ ፡ የሚወዱ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሱ ፡ ይጐስቍሉም ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 15 ፤ ዕሠይ ፡ ዕሠይ ፡ የሚሉኝ ፡ ዕፍረታቸውን ፡ ወዲያው ፡ ይከፈሉ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ የሚፈልጉኽ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ ሐሤትም ፡ ያድርጉ ፤ ኹልጊዜ ፡ ማዳንኽን ፡ የሚወዱ ፡ ዘወትር ። እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፡ ይበሉ ።

መዝ. ፡ 39 ፡ (40) ፡ 17 ፤ እኔ ፡ ችግረኛና ፡ ምስኪን ፡ ነኝ ፥ ጌታ ፡ ግን ፡ ያስብልኛል ፤ አንተ ፡ ረዳቴና ፡ መድኀኒቴ ፡ ነኽ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አትዘግይ ።

መዝሙር ፡ 40 ፡ (41) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 1 ፤ ለችግረኛና ፡ ለምስኪን ፡ የሚያስብ ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ በክፉ ፡ ቀን ፡ ያድነዋል ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቀዋል ፥ ሕያውም ፡ ያደርገዋል ፥ በምድር ፡ ላይም ፡ ያስመሰግነዋል ፥ በጠላቶቹም ፡ እጅ ፡ አያሳልፈውም ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደዌው ፡ ዐልጋ ፡ ሳለ ፡ ይረዳዋል ፤ መኝታውን ፡ ኹሉ ፡ በበሽታው ፡ ጊዜ ፡ ያነጥፍለታል ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 4 ፤ እኔስ ፦ አቤቱ ፡ ማረኝ ፤ አንተን ፡ በድያለኹና ፡ ነፍሴን ፡ ፈውሳት ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 5 ፤ ጠላቶቼም ፡ በላዬ ፡ ክፋትን ፡ ይናገራሉ ፦ መቼም ፡ ይሞታል ፡ ስሙስ ፡ መቼ ፡ ይሻራል ፧ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 6 ፤ እኔን ፡ ለማየት ፡ ቢገባ ፡ ከንቱን ፡ ይናገራል ፤ ልቡ ፡ ኀጢአትን ፡ ሰበሰበለት ፤ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ይወጣል ፡ ይናገራልም ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 7 ፤ በላዬ ፡ በመተባበር ፡ ጠላቶቼ ፡ ኹሉ ፡ ይሾካሾኩብኛል ፥ በእኔ ፡ ላይም ፡ ክፋትን ፡ ያስባሉ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 8 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ መጣበት ፤ ተኝቷል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይነሣም ፡ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 9 ፤ ደግሞ ፡ የሰላሜ ፡ ሰው ፡ የታመንኩበት ፡ እንጀራዬን ፡ የበላ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተረከዙን ፡ አነሣ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 10 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፥ ማረኝ ፡ እመልስላቸውም ፡ ዘንድ ፡ አስነሣኝ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 11 ፤ ጠላቴ ፡ እልል ፡ አይልብኝምና ፡ ስለዚህ ፡ እንደ ፡ ወደድኸኝ ፡ ዐወቅኹ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 12 ፤ እኔን ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ቅንነቴ ፡ ተቀበልኸኝ ፥ በፊትኽም ፡ ለዘለዓለም ፡ አጸናኸኝ ።

መዝ. ፡ 40 ፡ (41) ፡ 13 ፤ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ። አሜን ፡ አሜን ።

መዝሙር ፡ 41 ፡ (42) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 1 ፤ ዋላ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ እንደሚናፍቅ ፥ አቤቱ ፥ እንዲሁ ፡ ነፍሴ ፡ ወዳንተ ፡ ትናፍቃለች ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 2 ፤ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ተጠማች ፤ መቼ ፡ እደርሳለኹ ፧ የአምላክንስ ፡ ፊት ፡ መቼ ፡ አያለኹ ፧

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 3 ፤ ዘወትር ። አምላክኽ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ሲሉኝ ፡ እንባዬ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ምግብ ፡ ኾነኝ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 4 ፤ ይህን ፡ ሳስብ ፡ ነፍሴ ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ ፈሰሰች ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደምስጋና ፡ መኖሪያ ፡ ስፍራ ፡ እገባለኹና ፤ በዓል ፡ የሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ የደስታና ፡ ምስጋና ፡ ቃል ፡ አሰሙ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 5 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ ታዝኛለሽ ፧ ለምንስ ፡ ታውኪኛለሽ ፧ የፊቴን ፡ መድኀኒት ፡ አምላኬን ፡ አመሰግነው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኚ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 6 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ነፍሴ ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ ታወከች ፤ ስለዚህ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ምድር ፡ በአርሞንኤምም ([262]) ፡ በታናሹ ፡ ተራራ ፡ ዐስብኻለኹ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 7 ፤ በፏፏቴኽ ፡ ድምፅ ፡ ቀላይ ፡ ቀላይን ፡ ትጠራታለች ፤ ማዕበልኽና ፡ ሞገድኽ ፡ ኹሉ ፡ በላዬ ፡ ዐለፈ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቀን ፡ ቸርነቱን ፡ ያዛል ፥ በሌሊትም ፡ ዝማሬው ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይኾናል ፤ የእኔ ፡ ስእለት ፡ ለሕይወቴ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርን ፦ አንተ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ፤ ለምን ፡ ረሳኸኝ ፧ ጠላቶቼ ፡ ሲያስጨንቁኝ ፡ ለምን ፡ ዐዝኜ ፡ እመላለሳለኹ ፧ እለዋለኹ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 10 ፤ ጠላቶቼ ፡ ኹልጊዜ ፦ አምላክኽ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ዐጥንቶቼን ፡ እየቀለጣጠሙ ፡ ሰደቡኝ ።

መዝ. ፡ 41 ፡ (42) ፡ 11 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ ታዝኛለሽ ፧ ለምንስ ፡ ታውኪኛለሽ ፧ የፊቴን ፡ መድኀኒት ፡ አምላኬን ፡ አመሰግነው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኚ ።

---

262 ዕብ. ፥ ሔርሞኒይም ።

_____መዝሙር ፡ 42 ፡ (43) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 42 ፡ (43) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ፍረድልኝ ፥ ከጽድቅ ፡ ከራቁ ፡ ሕዝብም ፡ ክርክሬን ፡ ተከራከር ፤ ከሸንጋይና ፡ ከግፈኛ ፡ ሰው ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 42 ፡ (43) ፡ 2 ፤ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ኀይሌም ፥ ለምን ፡ ትተወኛለኽ ፧ ጠላቶቼ ፡ ሲያስጨንቁኝ ፡ ለምን ፡ ዐዝኜ ፡ እመላለሳለኹ ፧

መዝ. ፡ 42 ፡ (43) ፡ 3 ፤ ብርሃንኽንና ፡ እውነትኽን ፡ ላክ ፤ እነርሱ ፡ ይምሩኝ ፥ ወደቅድስናኽ ፡ ተራራና ፡ ወደ ፡ ማደሪያኽ ፡ ይውሰዱኝ ።

መዝ. ፡ 42 ፡ (43) ፡ 4 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፥ ጕልማሳነቴንም ፡ ደስ ፡ ወዳሠኛት ፡ ወደ ፡ አምላኬ ፡ እገባለኹ ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ በበገና ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 42 ፡ (43) ፡ 5 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ ታዝኛለሽ ፧ ለምንስ ፡ ታውኪኛለሽ ፧ የፊቴን ፡ መድኀኒት ፡ አምላኬን ፡ አመሰግነው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኚ ።

_____መዝሙር ፡ 43 ፡ (44) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በጐሯችን ፡ ሰማን ፥ አባቶቻችንም ፡ በዘመናቸው ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የሠራኸውን ፡ ሥራ ፡ ነገሩን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 2 ፤ እጅኽ ፡ አሕዛብን ፡ አጠፋች ፥ እነርሱንም ፡ ተከልኽ ፤ አሕዛብን ፡ ሣቀይኻቸው ፡ አሳደድኻቸውም ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 3 ፤ በሰይፋቸው ፡ ምድርን ፡ አልወረሱም ፡ ክንዳቸውም ፡ አላዳናቸው ፤ ቀኝኽና ፡ ክንድኽ ፡ የፊትኽም ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወደኻቸዋልና ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 4 ፤ አምላኬና ፡ ንጉሤ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፤ ለያዕቆብ ፡ መድኀኒትን ፡ እዘዝ ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 5 ፤ ባንተ ፡ ጠላቶቻችንን ፡ እንወጋቸዋለን ፥ በስምኽም ፡ በላያችን ፡ የቆሙትን ፡ እናዋርዳቸዋለን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 6 ፤ በቀስቴ ፡ የምታመን ፡ አይደለኹምና ፥ ሰይፌም ፡ አያድነኝምና ፤

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 7 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ከጠላቶቻችን ፡ አዳንኸን ፥ የሚጠሉንንም ፡ አሳፈርኻቸው ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 8 ፤ ዘልጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንከብራለን ፥ ስምኽንም ፡ ለዘለዓለም ፡ እናመሰግናለን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 9 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ጠላኸን ፡ አሳፈርኸንም ፥ ከሰራዊታችንም ፡ ጋራ ፡ አትወጣም ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 10 ፤ ከጠላቶቻችንም ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላችን ፡ መለስኸን ፥ የሚጠሉንም ፡ ተነጣጠቁን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 11 ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ ሊበሉን ፡ ሰጠኸን ፥ ወደ ፡ አሕዛብም ፡ በተንኸን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 12 ፤ ሕዝብኽን ፡ ያለዋጋ ፡ ሰጠኽ ፥ በመለወጣቸውም ፡ ትርፍ ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 13 ፤ ለጎረቤቶቻችን ፡ ስድብ ፥ በዙሪያችንም ፡ ላሉ ፡ መሣቂያና ፡ መዘበቻ ፡ አደረግኸን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 14 ፤ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ምሳሌ ፥ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ የራስ ፡ መንቀሳቀሻ ፡ አደረግኸን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 15 ፤ ጕስቀሉልናዬ ፡ ዘልጊዜም ፡ በፊቴ ፡ ነው ፥ የፊቴም ፡ ዕፍረት ፡ ሸፈነኝ ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 16 ፤ ከሚሳደብና ፡ ከሚላገድ ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፥ ከጠላትና ፡ ከቂመኛ ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 17 ፤ ይህ ፡ ሁሉ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ደረሰ ፥ አልረሳንኽም ፥ ኪዳንኽንም ፡ አልወነጀልንም ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 18 ፤ ልባችን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አልተመለሰም ፥ ፍለጋችንም ፡ ከመንገድኽ ፡ ፈቀቅ ፡ አላለም ፤

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 19 ፤ በክፉ ፡ ስፍራ ፡ አዋርደኸናልና ፥ በሞት ፡ ጥላም ፡ ሰውረኸናልና ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 20 ፤ የአምላካችንን ፡ ስም ፡ ረስተንስ ፡ ቢኾን ፥ እጃችንንም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አንሥተንስ ፡ ቢኾን ፥

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ አይመረምርም ፡ ነበርን ፧ ርሱ ፡ ልብ ፡ የሰወረውን ፡ ያውቃልና ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 22 ፤ ስለ ፡ አንተ ፡ ዘልጊዜም ፡ ተገድለናል ፥ እንደሚታረዱም ፡ በጎች ፡ ኾነናል ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 23 ፤ አቤቱ ፥ ንቃ ፤ ለምንስ ፡ ትተኛለኽ ፧ ተነሥ ፥ ለዘወትርም ፡ አትጣለን ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 24 ፤ ለምንስ ፡ ፊትኽን ፡ ትሰውራለኽ ፧ መከራችንንና ፡ ችግራችንንስ ፡ ለምን ፡ ትረሳለኽ ፧

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 25 ፤ ነፍሳችን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተጐሳቀሉለችና ፥ ሆዳችንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተጣብቃለችና ።

መዝ. ፡ 43 ፡ (44) ፡ 26 ፤ አቤቱ ፥ ተነሥና ፡ ርዳን ፥ ስለ ፡ ስምኽም ፡ ተቤዣን ።

_____መዝሙር ፡ 44 ፡ (45) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በመለኮቶች ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ ትምህርት ፤ የፍቅር ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 1 ፤ ልቤ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ አፈለቀ ፥ እኔ ፡ ሥራዬን ፡ ለንጉሥ ፡ እነግራለኹ ፤ አንደበቴ ፡ እንደ ፡ ፈጣን ፡ ጸሓፊ ፡ ብርዕ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 2 ፤ ውበትኽ ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ያምራል ፤ ሞገስ ፡ በከንፈሮችኽ ፡ ፈሰሰ ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ባረከኽ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 3 ፤ ጎያል ፡ ሆይ ፥ በቀኝኸርናኽና ፡ በውበትኽ ፡ ሰይፍኽን ፡ በወገብኽ ፡ ታጠቅ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 4 ፤ ስለ ፡ ቅንነትና ፡ ስለ ፡ የዋህነት ፡ ስለ ፡ ጽድቅም ፡ አቅና ፡ ተከናወን ፡ ንገሥም ፤ ቀኝኽም ፡ በክብር ፡ ይመራኻል ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 5 ፤ ጎያል ፡ ሆይ ፥ ፍላጻዎችኽ ፡ የተሳሉ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ በንጉሥ ፡ ጠላቶች ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ፥ አሕዛብም ፡ በበታችኽ ፡ ይወድቃሉ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 6 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ዙፋንኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ፤ የመንግሥትኽ ፡ በትር ፡ የቅንነት ፡ በትር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 7 ፤ ጽድቅን ፡ ወደድኽ ፡ ዐመፃንም ፡ ጠላኽ ፤ ስለዚህ ፥ ከባልንጀራዎችኽ ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ የደስታ ፡ ዘይትን ፡ ቀባኽ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 8 ፤ በልብሶችኽ ፡ ኹሉ ፡ ከርቤና ፡ ሽቱ ፡ ዝባድም ፡ አሉ ፤ ከዝኖን ፡ ጥርሶች ፡ አዳራሽ ፡ ደስ ፡ ያሠኙኻል ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 9 ፤ የንጉሦች ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ለክብርኽ ፡ ናቸው ፤ በወርቅ ፡ ልብስ ፡ ተጐናጽፋና ፡ ተሸፋፍና ፡ ንግሥቲቱ ፡ በቀኝኽ ፡ ትቆማለች ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 10 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ስሚ ፡ እዩ ፡ ገሮሽንም ፡ አዘንብዩ ፤ ወገንሽን ፡ ያባትሽንም ፡ ቤት ፡ ርሺ ፤

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 11 ፤ ንጉሥ ፡ ውበትሽን ፡ ወዷልና ፥ ርሱ ፡ ጌታሽ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 12 ፤ የጢሮስ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ይዘው ፡ ይሰግዱለታል ። የምድር ፡ ባለጠጋዎች ፡ አሕዛብ ፡ በፊትኽ ፡ ይማለላሉ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 13 ፤ ለሐሴቦን ፡ ንጉሥ ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ክብሯ ፡ ነው ፤ ልብሷ ፡ የወርቅ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 14 ፤ በኺላዋ ፡ ደናግሉን ፡ ለንጉሥ ፡ ይወስዳሉ ፥ ባልንጀራዎቿንም ፡ ወዳንተ ፡ ያቀርባሉ ፤

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 15 ፤ በደስታና ፡ በሐሴት ፡ ይወስዷቸዋል ፥ ወደንጉሥ ፡ ዕልፍኝም ፡ ያስገቧቸዋል ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 16 ፤ በአባቶችሽ ፡ ፋንታ ፡ ልጆች ፡ ተወለዱልሽ ፥ በምድርም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ገዢዎች ፡ አድርገሽ ፡ ትሾሚያቸዋለሽ ።

መዝ. ፡ 44 ፡ (45) ፡ 17 ፤ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ስምሽን ፡ ያሳስባሉ ፤ ስለዚህ ፥ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለም ፡ አሕዛብ ፡ ይገዙልኻል ።

መዝሙር ፡ 45 ፡ (46) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ስለ ፡ ምስጢር ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 1 ፤ አምላካችን ፡ መጠጊያችንና ፡ ኀይላችን ፥ ባገኘን ፡ በታላቅ ፡ መከራም ፡ ረዳታችን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 2 ፤ ስለዚህ ፥ ምድር ፡ ብትነዋወጥ ፥ ተራራዎችም ፡ ወደባሕር ፡ ልብ ፡ ቢወሰዱ ፥ አንፈራም ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 3 ፤ ውሃዎቻቸው ፡ ጮኹ ፡ ተናወጡም ፥ ተራራዎችም ፡ ከኀይሉ ፡ የተነሣ ፡ ተናወጡ ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 4 ፤ የወንዝ ፡ ፈሳሾች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ከተማ ፡ ደስ ፡ ያሠኛሉ ፤ ልዑል ፡ ማደሪያውን ፡ ቀደሰ ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በመካከሷ ፡ ነው ፡ አትናወጥም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ፈጥኖ ፡ ይረዳታል ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 6 ፤ አሕዛብ ፡ ተናወጡ ፡ መንግሥታትም ፡ ተመለሱ ፤ ርሱ ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፥ ምድርም ፡ ተንቀጠቀጠች ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ መጠጊያችን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፥ በምድር ፡ ያደረገውንም ፡ ተኣምራት ፡ እንድታዩ ፡ ኑ ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 9 ፤ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ጦርነት ፡ ይሽራል ። ቀስትን ፡ ይሰብራል ፥ ጦርንም ፡ ይቈርጣል ፡ በእሳትም ፡ ጋሻን ፡ ያቃጥላል ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 10 ፤ ዕረፉ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾንኩ ፡ ዕወቁ ፤ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እላለኹ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እላለኹ ።

መዝ. ፡ 45 ፡ (46) ፡ 11 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ መጠጊያችን ፡ ነው ።

_____መዝሙር ፡ 46 ፡ (47) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 1 ፤ አሕዛብ ፡ ኹላችኹ ፥ እጆቻችኹን ፡ አጨብጭቡ ፥ በደስታ ፡ ቃልም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እልል ፡ በሉ ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ግሩምም ፡ ነውና ፥ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይም ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 3 ፤ አሕዛብን ፡ ከእኛ ፡ በታች ፥ ወገኖችንም ፡ ከእግራችን ፡ በታች ፡ አስገዛልን ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 4 ፤ ለርስቱ ፡ እኛን ፡ መረጠን ፥ የወደደውን ፡ የያዕቆብን ፡ ውበት ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 5 ፤ አምላክ ፡ በእልልታ ፥ እግዚአብሔር ፡ በመለከት ፡ ድምፅ ፡ ዐረገ ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 6 ፤ ዘምሩ ፥ ለአምላካችን ፡ ዘምሩ ፤ ዘምሩ ፥ ለንጉሣችን ፡ ዘምሩ ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለምድር ፡ ኹሉ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፤ በማስተዋል ፡ ዘምሩ ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅድስናው ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ።

መዝ. ፡ 46 ፡ (47) ፡ 9 ፤ የምድር ፡ ኀይለኞች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ናቸውና ፥ የአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ ወደአብርሃም ፡ አምላክ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ርሱንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉት ።

_____መዝሙር ፡ 47 ፡ (48) ። _____

በኹለተኛ ፡ ሰንበት ፡ የቆሬ ፡ ልጆች ፤ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትልቅ ፡ ነው ፤ በአምላካችን ፡ ከተማ ፡ በተቀደሰ ፡ ተራራ ፡ ምስጋናው ፡ ብዙ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 2 ፤ በሰሜን ፡ ወገን ፡ በመልካም ፡ ስፍራ ፡ የቆመ ፡ የምድር ፡ ኹሉ ፡ ደስታ ፡ የጽዮን ፡ ተራራ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ የትልቁ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአዳራሾቿ ፡ መጠጊያ ፡ ኾኖ ፡ ይታወቃል ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ ነገሥታት ፡ ተከማችተው ፡ በአንድነት ፡ መጥተዋል ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 5 ፤ እነርሱስ ፡ አይተው ፡ ተደነቁ ፥ ደነገጡ ፥ ታወኩ ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 6 ፤ መንቀጥቀጥ ፡ እንደ ፡ ወላድ ፡ ምጥ ፡ በዚያ ፡ ያዛቸው ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 7 ፤ በጎይለኛ ፡ ነፋስ ፡ የተርሴስን ፡ መርከቦች ፡ ትሰብራለኽ ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 8 ፤ እንደ ፡ ሰማን ፡ እንዲሁ ፡ አየን ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከተማ ፥ በአምላካችን ፡ ከተማ ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ያጸናታል ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 9 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሕዝብኽ ፡ መካከል ፡ ምሕረትኽን ፡ ተቀበልን ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 10 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ስምኽ ፡ እንዲሁም ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ምስጋናኽ ፡ ነው ፤ ቀኝኽ ፡ ጽድቅን ፡ የተሞላች ፡ ናት ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ፍርድኽ ፡ የጽዮን ፡ ተራራ ፡ ደስ ፡ ይበለው ፥ የአይሁድም ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ሐሤት ፡ ያድርጉ ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 12 ፤ ጽዮንን ፡ ክበቧት ፥ በዙሪያዋም ፡ ተመላለሱ ፥ ግንቦቿንም ፡ ቍጠሩ ፤

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 13 ፤ በብርታቷ ፡ ልባችኹን ፡ አኑሩ ፤ አዳራሿን ፡ ዐስቡ ፤ ለሚመጣው ፡ ትውልድ ፡ ትነግሩ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 47 ፡ (48) ፡ 14 ፤ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለም ፡ ይህ ፡ አምላካችን ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይመራናል ።

መዝሙር ፡ 48 ፡ (49) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 1 ፤ አሕዛብ ፡ ኹላችኹ ፥ ይህን ፡ ስሙ ፤ በዓለም ፡ የምትኖሩትም ፡ ኹላችኹ ፥ አድምጡ ፤

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 2 ፤ ዝቅተኞችና ፡ ከፍተኞች ፥ ባለጠጋዎችና ፡ ድኻዎች ፡ በአንድነት ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 3 ፤ አፌ ፡ ጥበብን ፡ ይናገራል ፥ የልቤም ፡ ዐሳብ ፡ ማስተዋልን ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 4 ፤ ጐሮዬን ፡ ወደ ፡ ምሳሌ ፡ አዘነብላለኹ ፥ በበገናም ፡ ምስጢሬን ፡ እገልጣለኹ ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 5 ፤ ኀጢአት ፡ ተረከዜን ፡ በከበበኝ ፡ ጊዜ ፡ በክፉ ፡ ቀን ፡ ለምን ፡ እፈራለኹ ፧

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 6 ፤ በጎይላቸው ፡ የሚታመኑ ፥ በባለጠግነታቸውም ፡ ብዛት ፡ የሚመኩ ፤

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 7 ፤ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ አያድንም ፥ ሰውም ፡ አያድንም ፤ ቤዛውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አይሰጥም ፥

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 8-9 ፤ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፥ ጥፋትንም ፡ እንዳያይ ፤ የነፍሳቸው ፡ ለውጥ ፡ ከብሯልና ፥ ለዘለዓለምም ፡ ቀርቷልና ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 10 ፤ ብልኀተኞች ፡ እንዲሞቱ ፥ ሰነፎችና ፡ ደንቈሮዎች ፡ በአንድነት ፡ እንዲጠፉ ፥ ገንዘባቸውንም ፡ ለሌላዎች ፡ እንዲተዉ ፡ አይቷል ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 11 ፤ በልባቸውም ፡ ቤታቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፥ ማደሪያቸውም ፡ ለልጆች ፡ ልጅ ፡ የሚኾን ፡ ይመስላቸዋል ፤ በያገራቸውም ፡ ስማቸው ፡ ይጠራል ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 12 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ክቡር ፡ ኾኖ ፡ ሳለ ፡ አያውቅም ፤ እንደሚጠፉ ፡ እንስሳዎች ፡ መሰለ ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 13 ፤ ይህች ፡ መንገዳቸው ፡ መሰናክላቸው ፡ ናት ፥ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ የሚመጡ ፡ በአፋቸው ፡ ዕሺ ፡ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 14 ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ የሚኼዱ ፡ ናቸው ፥ እረኛቸውም ፡ ሞት ፡ ነው ፤ ቅኖችንም ፡ በማለዳ ፡ ይገዟቸዋል ፥ ውበታቸውም ፡ ከመኖሪያቸው ፡ ተለይታ ፡ በሲኦል ፡ ታረጃለች ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ይቀበለኛልና ፥ ነፍሴን ፡ ከሲኦል ፡ እጅ ፡ ይቤዣታል ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 16 ፤ የሰው ፡ ባለጠግነት ፡ የቤቱም ፡ ክብር ፡ በበዛ ፡ ጊዜ ፡ አትፍራ ፥

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 17 ፤ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ምንም ፡ አይወስድምና ፥ ክብሩም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ አይወርድምና ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 18 ፤ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ነፍሱን ፡ ባርኳልና ፥ ለሰውነቱ ፡ መልካም ፡ ብታደርግለት ፡ ያመሰግንኻል ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 19 ፤ ኾኖም ፡ ወዳባቶቹ ፡ ትውልድ ፡ ይወርዳል ፤ ለዘለዓለም ፡ ብርሃንን ፡ አያይም ።

መዝ. ፡ 48 ፡ (49) ፡ 20 ፤ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ክቡር ፡ ሰው ፡ እንደሚጠፉ ፡ እንስሳዎች ፡ መሰለ ።

_____መዝሙር ፡ 49 ፡ (50) ። _____

የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 1 ፤ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረ ፥ ከፀሓይም ፡ መውጫ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መግቢያዋ ፡ ድረስ ፡ ምድርን ፡ ጠራት ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 2 ፤ ከክብሩ ፡ ውበት ፡ ከጽዮን ፡ እግዚአብሔር ፡ ግልጥ ፡ ኾኖ ፡ ይመጣል ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 3 ፤ አምላካችን ፡ ይመጣል ፡ ዝምም ፡ አይልም ፤ እሳት ፡ በፊት ፡ ይቃጠላል ፥ በዙሪያውም ፡ ብዙ ፡ ዐውሎ ፡ አለ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 4 ፤ በላይ ፡ ያለውን ፡ ሰማይን ፡ ምድርንም ፡ በሕዝቡ ፡ ለመፍረድ ፡ ይጠራል ፤

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 5 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ለመሥዋዕት ፡ ኪዳን ፡ የቆሙትን ፡ ቅዱሳኑን ፡ ሰብስቡለት ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 6 ፤ ሰማያት ፡ ጽድቁን ፡ ይናገራሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ ፈራጅ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 7 ፤ ሕዝቤ ፥ ስማኝ ፥ ልንገርኽ ፤ እስራኤልም ፥ ስማኝ ፥ ልመስክርብኽ ፤ አምላክስ ፡ እኔ ፡ አምላክኽ ፡ ነኝ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 8 ፤ ስለ ፡ ቍርባንኽ ፡ የምዘልፍኽ ፡ አይደለኹም ፤ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትኽ ፡ ዘወትር ፡

በፊቴ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 9 ፤ ከቤትኽ ፡ ፍሪዳን ፡ ከመንጋኽም ፡ አውራ ፡ ፍየልን ፡ አልወስድም ፤

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 10 ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ በሺሕ ፡ ተራራዎች ፡ ያሉ ፡ እንስሳዎችም ፡ የእኔ ፡ ናቸውና ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 11 ፤ የሰማይን ፡ አዕዋፍ ፡ ኹሉ ፡ ዐውቃለኹ ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊትም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 12 ፤ ብራብም ፡ ለአንተ ፡ አልነግርኽም ፥ ዓለምና ፡ ሞላው ፡ የእኔ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 13 ፤ የፍሪዳውን ፡ ሥጋ ፡ እበላለኹን ፧ የፍየሉንስ ፡ ደም ፡ እጠጣለኹን ፧

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 14 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የምስጋናን ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ፥ ለልዑልም ፡ ስእለትኽን ፡ ስጥ ፤

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 15 ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ ጥራኝ ፥ አድንኽማለኹ ፡ አንተም ፡ ታከብረኛለኽ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 16 ፤ ኀጢአተኛውን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ አለው ፦ ለምን ፡ አንተ ፡ ሕጌን ፡ ትናገራለኽ ፧ ኪዳኔንም ፡ በአፍኽ ፡ ለምን ፡ ትወስዳለኽ ፧

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 17 ፤ አንተስ ፡ ተግሣጼን ፡ ጠላኽ ፥ ቃሎቼንም ፡ ወደ ፡ ኋላኽ ፡ ጣልኽ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 18 ፤ ሌባውን ፡ ባየኽ ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ትሮጥ ፡ ነበር ፡ ዕድል ፡ ፈንታኽንም ፡ ከአመንዝራዎች ፡ ጋራ ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 19 ፤ አፍኽ ፡ ክፋትን ፡ አበዛ ፥ አንደበትኽም ፡ ሽንገላን ፡ ተበተበ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 20 ፤ ተቀምጠኽ ፡ ወንድምኽን ፡ ዐማኸው ፥ ለእናትኽም ፡ ልጅ ፡ ዕንቅፋት ፡ አኖርኽ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 21 ፤ ይህን ፡ አድርገኽ ፡ ዝም ፡ አልኹኽ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ጠረጠርኽ ፤ እዘልፍኻለኹ ፡ በፊትኽም ፡ እቆማለኹ ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትረሱ ፡ እናንተ ፥ ይህን ፡ አስተውሉ ፤ አለዚያ ፡ ግን ፡ ይነጥቃል ፡ የሚያድንም ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 49 ፡ (50) ፡ 23 ፤ ምስጋና ፡ የሚሠዋ ፡ ያከብረኛል ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ ለርሱ ፡ የማሳይበት ፡ መንገድ ፡ ከዚያ ፡ አለ ።

_____መዝሙር ፡ 50 ፡ (51) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ወደ ፡ ቤርሳቤሕ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ነቢዩ ፡ ናታን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ መጠን ፡ ማረኝ ፤ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ ብዛት ፡ መተላለፌን ፡ ደምስስ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 2 ፤ ከበደሌ ፡ ፈጽሞ ፡ ዕጠበኝ ፥ ከኀጢአቴም ፡ አንጻኝ ፤

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 3 ፤ እኔ ፡ መተላለፌን ፡ ዐውቃለኹና ፥ ኀጢአቴም ፡ ዘውልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 4 ፤ አንተን ፡ ብቻ ፡ በደልኹ ፥ በፊትኽም ፡ ክፋትን ፡ አደረግኹ ፥ በነገርኽም ፡ ትጸድቅ ፡

ዘንድ ፡ በፍርድኽም ፡ ንጹሕ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 5 ፤ እንሆ ፡ በዐመፃ ፡ ተፀነስኹ ፥ እናቴም ፡ በኀጢአት ፡ ወለደችኝ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 6 ፤ እንሆ ፡ እውነትን ፡ ወደድኽ ፤ የማይታይ ፡ ስውር ፡ ጥበብን ፡ አስታወቅኸኝ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 7 ፤ በሂሶጵ ፡ ርጨኝ ፥ እነጻማለኹ ፤ ዕጠበኝ ፥ ከበረዶም ፡ ይልቅ ፡ ነጭ ፡ እኾናለኹ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 8 ፤ ሐሤትንና ፡ ደስታን ፡ አሰማኝ ፥ የሰበርኻቸውም ፡ ዐጥንቶቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 9 ፤ ከኀጢአቴ ፡ ፊትኽን ፡ መልስ ፥ በደሌንም ፡ ኹሉ ፡ ደምስስልኝ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ ንጹሕ ፡ ልብን ፡ ፍጠርልኝ ፥ የቀናውንም ፡ መንፈስ ፡ በውስጤ ፡ ዐድስ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 11 ፤ ከፊትኽ ፡ አትጣለኝ ፥ ቅዱስ ፡ መንፈስኽንም ፡ ከእኔ ፡ ላይ ፡ አትውሰድብኝ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 12 ፤ የማዳንኽን ፡ ደስታ ፡ ስጠኝ ፥ በእሽታ ፡ መንፈስም ፡ ደግፈኝ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 13 ፤ ለሕግ ፡ ተላላፊዎች ፡ መንገድኽን ፡ አስተምራለኹ ፥ ኀጢአተኞችም ፡ ወዳንተ ፡ ይመለሳሉ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 14 ፤ የመድኀኒቴ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ከደም ፡ አድነኝ ፥ አንደበቴም ፡ ባንተ ፡ ጽድቅ ፡ ትደሰታለች ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 15 ፤ አቤቱ ፥ ከንፈሮቼን ፡ ክፈት ፥ አፌም ፡ ምስጋናኽን ፡ ያወራል ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 16 ፤ መሥዋዕትን ፡ ብትወድስ ፡ በሰጠኹኽ ፡ ነበር ፤ የሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ደስ ፡ አያሠኝኽም ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ የተሰበረ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፥ የተሰበረውንና ፡ የተዋረደውን ፡ ልብ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይንቅም ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 18 ፤ አቤቱ ፥ በውዴታኽ ፡ ጽዮንን ፡ አሰማምራት ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥሮች ፡ ሥራ ።

መዝ. ፡ 50 ፡ (51) ፡ 19 ፤ የጽድቁን ፡ መሥዋዕት ፡ መባውንም ፡ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ በወደድኽ ፡ ጊዜ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ በመሠዊያኽ ፡ ላይ ፡ ፍሪዳዎችን ፡ ይሠዋሉ ።

መዝሙር ፡ 51 ፡ (52) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ኤዶማዊው ፡ ዶይቅ ፡ መጥቶ ፡ ለሳኦል ፦ ዳዊት ፡ ወደአቢሜሌክ ፡ ቤት ፡ መጥቷል ፡ ብሎ ፡ በነገረው ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 51 ፡ (52) ፡ 1 ፤ ኀያል ፡ ሆይ ፥ በክፋት ፡ ለምን ፡ ትጓደዳለኽ ፧ ኹልጊዜስ ፡ በመተላለፍ ፧

መዝ. ፡ 51 ፡ (52) ፡ 2 ፤ አንደበትኽ ፡ ኀጢአትን ፡ ያስባል ፤ እንደ ፡ ተሳለ ፡ ምላጭ ፡ ሽንገላን ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 51 ፡ (52) ፡ 3 ፤ ከመልካም ፡ ይልቅ ፡ ክፋትን ፥ ጽድቅንም ፡ ከመናገር ፡ ይልቅ ፡ ዐመፃን ፡ ወደድኽ ።

መዝ. ፡ 51 ፡ (52) ፡ 4 ፤ የሚያጠፉ ፡ ቃልን ፡ ኹሉ ፥ የሽንገላ ፡ ምላስን ፡ ወደድኽ ።

መዝ. ፡ 51 ፡ (52) ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ያፈርስኻል ፤ ከቤትኽም ፡

ይነቅልኻል ፥ ያፈልስኻልም ፥ ሥርኽንም ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ።

መዝ. ፥ 51 ፡ (52) ፥ 6 ፤ ጻድቃን ፡ አይተው ፡ ይፈራሉ ፤ በርሱም ፡ ይሥቃሉ ፥ እንዲህም ፡ ይላሉ ፦

መዝ. ፥ 51 ፡ (52) ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ረዳቱ ፡ ያላደረገ ፥ በባለጠግነቱም ፡ ብዛት ፡ የታመነ ፥ በከንቱ ፡ ነገርም ፡ የበረታ ፡ ያ ፡ ሰው ፡ እንሆ ።

መዝ. ፥ 51 ፡ (52) ፥ 8 ፤ እኔስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ለመለመ ፥ እንደ ፡ ወይራ ፡ ዛፍ ፡ ነኝ ፤ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ታመንኹ ።

መዝ. ፥ 51 ፡ (52) ፥ 9 ፤ አድርገኽልኛልና ፥ ለዘለዓለም ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ በቅዱሳንኽም ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ስምኽን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

መዝሙር ፡ 52 ፡ (53) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በማኸላት ፤ የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 1 ፤ ሰነፍ ፡ በልቡ ፦ አምላክ ፡ የለም ፡ ይላል ። ረከሱ ፥ በበደላቸውም ፡ ጮሰቈሉ ፤ በጎ ፡ ነገርን ፡ የሚያደርጋት ፡ የለም ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 2 ፤ የሚያስተውል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈልግ ፡ እንዳለ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ የሰው ፡ ልጆችን ፡ ተመለከተ ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 3 ፤ ኹሉ ፡ በደሉ ፥ ዐብረውም ፡ ረከሱ ፤ አንድ ፡ ስንኳ ፡ በጎን ፡ ነገር ፡ የሚያደርጋት ፡ የለም ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 4 ፤ ሕዝቤን ፡ እንጀራ ፡ እንደሚበላ ፡ የሚበሉ ፡ ግፍ ፡ አድራጊዎች ፡ ኹሉ ፡ አያውቁምን ፧ እግዚአብሔርንም ፡ አይጠሩትም ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ የግብዞችን ፡ ዐጥንቶች ፡ በትኗልና ። በዚያ ፡ የሚያስፈራ ፡ ሳይኖር ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ንቋቸዋልና ፥ አሳፈርኻቸው ።

መዝ. ፥ 52 ፡ (53) ፥ 6 ፤ መድኀኒትን ፡ ከጽዮን ፡ ለእስራኤል ፡ ማን ፡ በሰጠ! ፡ እግዚአብሔር ፡ የሕዝቡን ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፥ ያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ እስራኤልም ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ።

መዝሙር ፡ 53 ፡ (54) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በበገናዎች ፤ ዜፋውያን ፡ መጥተው ፡ ለሳኦል ፦ እንሆ ፥ ዳዊት ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ተሸሽጓል ፡ ብለው ፡ በነገሩት ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፥ 53 ፡ (54) ፥ 1 ፤ አቤቱ ፥ በስምኽ ፡ አድነኝ ፥ በኀይልኽም ፡ ፍረድልኝ ።

መዝ. ፥ 53 ፡ (54) ፥ 2 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ ስማኝ ፥ የአፌንም ፡ ቃል ፡ አድምጥ ፤

መዝ. ፥ 53 ፡ (54) ፥ 3 ፤ እንግዳዎች ፡ ቁመውብኛልና ፥ ኀያላንም ፡ ነፍሴን ፡ ሽተዋታልና ። እግዚአብሔርን ፡ በፊታቸው ፡ አላደረጉትም ።

መዝ. ፥ 53 ፡ (54) ፥ 4 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፥ ጌታዬም ፡ ለነፍሴ ፡ ደጋፊዋ ፡ ነው ።

መዝ. ፥ 53 ፡ (54) ፥ 5 ፤ ክፋትን ፡ ወደ ፡ ጠላቶቼ ፡ ይመልሳታል ፤ በእውነትኽም ፡ አጥፋቸው ።

መዝ. ፡ 53 ፡ (54) ፡ 6 ፤ ከፈቃዴ ፡ እሠዋልኻለኹ ፤ አቤቱ ፥ መልካም ፡ ነውና ፥ ስምኽን ፡ አመሰግናለኹ ፤

መዝ. ፡ 53 ፡ (54) ፡ 7 ፤ ከመከራ ፡ ኹሉ ፡ አድኖኛልና ፥ ዐይኔም ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ አይታለችና ።

_____መዝሙር ፡ 54 ፡ (55) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በበገናዎች ፤ የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ አድምጥ ፥ ልመናዬንም ፡ ቸል ፡ አትበል ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 2 ፤ ተመልከተኝ ፡ ስማኝም ። በሐዘኔ ፡ ተቅበዘበዝኹ ፡ ተናወጥኹም ፤

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 3 ፤ ከጠላት ፡ ድምፅ ፡ ከዐመፀኛም ፡ ግፍ ፡ የተነሣ ፤ ዐመፃን ፡ በላዬ ፡ ጥለውብኛልና ፥ በቍጣም ፡ ጠልተውኛልና ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 4 ፤ ልቤ ፡ በላዬ ፡ ተናወጠብኝ ፥ የሞት ፡ ድንጋጤም ፡ ወደቀብኝ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 5 ፤ ፍርሀትና ፡ እንቅጥቅጥ ፡ መጡብኝ ፥ ጨለማም ፡ ሸፈነኝ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 6 ፤ በርሬ ፡ ዐርፍ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ክንፍን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ! ፡

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ ኰብልዬ ፡ በራቅኹ ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ በተቀመጥኹ ፤

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 8 ፤ ከዐውሎና ፡ ከብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ሸሽቼ ፡ በፈጠንኹ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ ግፍንና ፡ ጠብን ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ አይቻለኹና ፥ አስጥማቸው ፥ አንደበታቸውንም ፡ ቀራጥ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 10 ፤ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ በቅጥሯ ፡ ይከቧታል ፤ ዐመፃና ፡ ድካም ፡ ኀጢአትም ፡ በመካከሏ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 11 ፤ ተንኰልና ፡ ሽንገላ ፡ ከአደባባይዋ ፡ አይርቁም ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 12 ፤ ጠላትስ ፡ ቢሰድበኝ ፥ በታገሥኹ ፡ ነበር ፤ የሚጠላኝም ፡ ራሱን ፡ በላዬ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ቢያደርግ ፥ ከርሱ ፡ በተሸሸግኹ ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 13 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ እኩያዬ ፡ ሰው ፥ ባልንጀራዬና ፡ የልቤ ፡ ወዳጅ ፤

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 14 ፤ መብልን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ያጣፈጥኽ ፤ ባንድ ፡ ልብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተራመድን ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 15 ፤ ሞት ፡ ይምጣባቸው ፤ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ይውረዱ ፤ ክፋት ፡ በማደሪያቸውና ፡ በመካከላቸው ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ሰማኝ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 17 ፤ በማታና ፡ በጧት ፡ በቀትርም ፡ እናገራለኹ ፡ እጮኽማለኹ ፥ ቃሌንም ፡ ይሰማኛል ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 18 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ነበሩና ፥ ከሚቃረቡኝ ፡ ነፍሴን ፡ በሰላም ፡ አድናት ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 19 ፤ ቤዛ ፡ የላቸውምና ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አልፈሩትምና ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የነበረ ፡

እግዚአብሔር ፡ ሰምቶ ፡ ያጐሰቀላቸዋል ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 20 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ ኪዳኑንም ፡ አረከሱ ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 21 ፤ አፉ ፡ ከቅቤ ፡ ይልቅ ፡ ለዘበ ፥ በልቡ ፡ ግን ፡ ሰልፍ ፡ ነበረ ፤ ቃሎቹም ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ ለሰለሱ ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተመዘዘ ፡ ሰይፍ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 22 ፤ ትካዜኽን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ጣል ፥ ርሱም ፡ ይደግፍኻል ፤ ለጻድቁም ፡ ለዘለዓለም ፡ ሁከትን ፡ አይሰጠውም ።

መዝ. ፡ 54 ፡ (55) ፡ 23 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ወደሞት ፡ ጕድጓድ ፡ ታወርዳቸዋለኽ ፤ የደም ፡ ሰዎችና ፡ ሸንጋዮች ፡ ዘመናቸው ፡ ግማሽ ፡ አይሞላም ፤ እኔ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ እታመንኻለኹ ።

መዝሙር ፡ 55 ፡ (56) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ከቅዱሳን ፡ ስለራቁ ፡ ሕዝብ ፤ ፍልስጥኤማውያን ፡ በጌት ፡ በያዙት ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ሰው ፡ ረግጦኛልና ፥ ማረኝ ፤ ዅልጊዜም ፡ በሰልፍ ፡ አስጨንቆኛል ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 2 ፤ የሚዋጉኝ ፡ በዝተዋልና ፥ ዅልጊዜ ፡ ቀኑን ፡ ዅሉ ፡ ጠላቶቼ ፡ ረገጡኝ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 3 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ፈራኹ ፡ ባንተም ፡ ታመንኹ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 4 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ አመሰግናለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ታመንኹ ፥ አልፈራም ፤ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፧

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 5 ፤ ዅልጊዜ ፡ ቃሎቼን ፡ ያጸይፉብኛል ፤ በእኔ ፡ ላይም ፡ የሚመክሩት ፡ ዅሉ ፡ ለክፉ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 6 ፤ ይሸምቁብኛል ፡ ይሸሸጉኝማል ፥ እነርሱም ፡ ተረከዜን ፡ ይመለካከታሉ ፥ ዅልጊዜም ፡ ነፍሴን ፡ ይሸምቁባታል ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 7 ፤ በምንም ፡ ምን ፡ አታድናቸውም ፤ አሕዛብን ፡ በቀጣ ፡ ትጥላቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 8 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ሕይወቴን ፡ ነገርኹኽ ፤ እንባዬን ፡ እንደ ፡ ትእዛዝኽ ፡ በፊትኽ ፡ አኖርኽ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 9 ፤ በጠራኹኽ ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቼ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሳሉ ፤ አንተ ፡ አምላኬ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፥ እንሆ ፥ ዐወቅኹ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 10 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ አመሰግናለኹ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ አከብራለኹ ።

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 11 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ታመንኹ ፥ አልፈራም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፧

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ የምስጋና ፡ ስእለት ፡ የምሰጥኽ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 55 ፡ (56) ፡ 13 ፤ ነፍሴን ፡ ከሞት ፥ እግሮቼን ፡ ከመውደቅ ፡ አድነኻልና ፥ በሕያዋን ፡ ብርሃን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አሠኘው ፡ ዘንድ ።

መዝሙር ፡ 56 ፡ (57) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ አታጥፋ ። ከሳአል ፡ ፊት ፡ ሸሽቶ ፡ በዋሻ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 1 ፤ ማረኝ ፥ አቤቱ ፥ ማረኝ ፥ ነፍሴ ፡ አንተን ፡ ታምናለችና ፤ ጕዳት ፡ እስከ ፡ ዕለፍ ፡ ድረስ ፡ በክንፎችኽ ፡ ጥላ ፡ እታመናለኹ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 2 ፤ ወደሚረዳኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ እጮኻለኹ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 3 ፤ ከሰማይ ፡ ልኮ ፡ አዳነኝ ፥ ለረገጡኝም ፡ ውርደትን ፡ ሰጣቸው ፤ እግዚአብሔር ፡ ቸርነቱንና ፡ እውነቱን ፡ ላከ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 4 ፤ ነፍሴን ፡ ከአንበሳዎች ፡ መካከል ፡ አዳናት ። ደንግጬ ፡ ተኛኹ ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ጥርሳቸው ፡ ጦርና ፡ ፍላጻ ፥ አንደበታቸው ፡ የተሳለ ፡ ሾተል ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 5 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማያት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፤ ክብርኽም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትኹን ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 6 ፤ ለእግሮቼ ፡ ወጥመድን ፡ አዘጋጁ ፥ ነፍሴንም ፡ አጐበጧት ፤ ጕድጓድ ፡ በፊቴ ፡ ቈፈሩ ፥ በርሱም ፡ ወደቁ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 7 ፤ ልቤ ፡ ጽኑዓ ፡ ነው ፥ አቤቱ ፥ ልቤ ፡ ጽኑዓ ፡ ነው ፤ እቀኛለኹ ፥ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 8 ፤ ክብሬ ፡ ይነሣ ፥ በገናና ፡ መሰንቆም ፡ ይነሡ ፤ እኔም ፡ ማልጄ ፡ እነሣለኹ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ በወገኖችም ፡ ዘንድ ፡ እዘምርልኻለኹ ፤

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 10 ፤ ምሕረትኽ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ብላለችና ፥ እውነትኽም ፡ እስከ ፡ ደመናት ፡ ድረስ ።

መዝ. ፡ 56 ፡ (57) ፡ 11 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በሰማያት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፤ ክብርኽም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትኹን ።

መዝሙር ፡ 57 ፡ (58) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ አታጥፋ ። የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 1 ፤ በእውነት ፡ ጽድቅን ፡ ብትናገሩስ ፥ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ በቅን ፡ ትፈርዳላችኹ ፤

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 2 ፤ በልባችኹ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ትሠራላችኹና ፥ እጆቻችኹም ፡ ግፍን ፡ ይታታሉና ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 3 ፤ ኃጥኣን ፡ ከማሕፀን ፡ ዠምረው ፡ ተለዩ ፤ ከሆድም ፡ ዠምረው ፡ ሳቱ ፥ ሐሰትንም ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 4 ፤ ቀሣጣቸው ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ መርዝ ፡ ነው ፥ እንደምድር ፡ አውሬም ፡ ጕሮዋ ፡ የተደፈነ ፡ ነው ፥

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 5 ፤ ዐዋቂ ፡ ሲደግምባት ፡ የአስማተኛውን ፡ ቃል ፡ እንደማትሰማ ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥርሳቸውን ፡ በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይሰብራል ፤ እግዚአብሔር ፡

የአንበሳዎቹን ፡ መንጋጋቸውን ፡ ያደቃል ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 7 ፤ እንደሚፈስ ፡ ውሃ ፡ ይቀልጣሉ ፤ እስኪያደክማቸው ፡ ድረስ ፡ ፍላጻዎቹን ፡ ይገትራል ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 8 ፤ እንደሚቀልጥ ፡ ሠም ፡ ያልቃሉ ፤ እሳት ፡ ወደቀች ፥ ፀሓይንም ፡ አላይዋትም ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 9 ፤ እሾኻችኹ ፡ ሳይታወቅ ፡ በትር ፡ ኾነ ፤ ሕያዋን ፡ ሳላችኹ ፡ በመዓቱ ፡ ይነጥቃችኋል ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 10 ፤ ጻድቅ ፡ በቀልን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ በኀጢአተኛው ፡ ደምም ፡ እጁን ፡ ይታጠባል ።

መዝ. ፡ 57 ፡ (58) ፡ 11 ፤ ሰውም ፦ በእውነት ፡ ለጻድቅ ፡ ፍሬ ፡ አለው ፤ በእውነት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚፈርድ ፡ አምላክ ፡ አለ ፡ ይላል ።

_____መዝሙር ፡ 58 ፡ (59) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ አታጥፋ ። ሳኦል ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ ቤቱን ፡ እንዲጠብቁ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 1 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ከጠላቶቼ ፡ አድነኝ ፤ በላዬም ፡ ከቆሙት ፡ አስጥለኝ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 2 ፤ ከግፍ ፡ አድራጊዎች ፡ ታደገኝ ፥ ከደም ፡ ሰዎችም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ ነፍሴን ፡ ሽምቀውባታልና ፥ ብርቱዎችም ፡ በላዬ ፡ ተሰበሰቡ ። አቤቱ ፥ በበደሌም ፡ አይደለም ፥ በኀጢአቴም ፡ አይደለም ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 4 ፤ ያለበደል ፡ ሮጥኹ ፥ ተዘጋጀኹም ፤ ተነሥ ፥ ተቀበለኝ ፥ እይም ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 5 ፤ አንተም ፡ አቤቱ ፥ የኀያላን ፡ አምላክ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፥ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ትጐበኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ተነሥ ፤ ዐመፅ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ኹሉ ፡ አትማራቸው ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 6 ፤ ማታ ፡ ይመለሱ ፡ እንደ ፡ ውሻዎችም ፡ ይራቡ ፥ በከተማም ፡ ይዙሩ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ በአፋቸው ፡ አሰምተው ፡ ይናገራሉ ፤ ሰይፍም ፡ በከንፈሮቻቸው ፡ አለ ፤ ማን ፡ ይሰማል ∴ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 8 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፥ ትሥቅባቸዋለኽ ፥ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ ትንቃቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ መጠጊያዬ ፡ ነውና ፥ ኀይሌን ፡ ወዳንተ ፡ አስጠጋለኹ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 10 ፤ የአምላኬ ፡ ቸርነቱ ፡ ይገናኘኛል ፡ አምላኬ ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ያሳየኛል ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 11 ፤ ሕግኽን ፡ እንዳይረሱ ፡ አትግደላቸው ፤ አቤቱ ፡ ጋሻዬ ፥ በኀይልኽ ፡ በትናቸው ፡ አውርዳቸውም ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 12 ፤ ስለአፋቸው ፡ ኀጢአት ፡ ስለከንፈራቸውም ፡ ቃል ፥ መርገምንና ፡ ሐሰትን ፡ ስለሚናገሩ ፥ በትዕቢታቸው ፡ ይጠመዱ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 13 ፤ በቍጣ ፡ አጥፋቸው ፥ እንዳይኖሩም ፡ አጥፋቸው ፤ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡

እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ እንዲገዛ ፡ ይወቁ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 14 ፤ ማታ ፡ ይመለሱ ፡ እንደ ፡ ውሻዎችም ፡ ይራቡ ፥ በከተማም ፡ ይዙሩ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 15 ፤ እነርሱም ፡ መብል ፡ ለመፈለግ ፡ ይበተኑ ፤ ያልጠገቡ ፡ እንደ ፡ ኾነም ፡ ያንጐረጕራሉ ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለኀይልኽ ፡ እቀኛለኹ ፤ በምሕረትኽም ፡ ማልዶ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ መጠጊያዬና ፡ ዐምባዬ ፡ ኾነኽኛልና ።

መዝ. ፡ 58 ፡ (59) ፡ 17 ፤ ረዳቴ ፡ ሆይ ፥ ለአንተ ፡ ለአምላኬ ፡ እዘምራለኹ ፤ አንተ ፥ አምላኬ ፥ መጠጊያዬ ፡ ምሕረቴም ፡ ነኽና ።

መዝሙር ፡ 59 ፡ (60) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የሶርያን ፡ ኹለቱን ፡ ወንዞችና ፡ የሶርያን ፡ ሶባልን ፡ ባቃጠለ ፡ ጊዜ ፡ ኢዮአብም ፡ ተመልሶ ፡ ከኤዶማውያን ፡ ሰዎች ፡ በጨው ፡ ሸለቆ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ በገደለ ፡ ጊዜ ፡ ለትምህርት ፡ የዳዊት ፡ ቅኔ ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ጣልኸን ፡ አፈረስኸንም ፤ ተቈጣኸን ፡ ይቅርም ፡ አልኸን ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 2 ፤ ምድርን ፡ አናወጥኻት ፡ አወክኻትም ፤ ተናውጣለችና ፡ ቀሥሷን ፡ ፈውስ ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 3 ፤ ለሕዝብኽ ፡ ጭንቅን ፡ አሳየኻቸው ፥ አስደንጋጭንም ፡ ወይን ፡ አጠጣኸን ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 4 ፤ ከቀስት ፡ ፊት ፡ ያመልጡ ፡ ዘንድ ፥ ለሚፈሩኽ ፡ ምልክትን ፡ ሰጠኻቸው ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 5 ፤ ወዳጆችኽ ፡ እንዲድኑ ፡ በቀኝኽ ፡ አድን ፥ አድምጠኝም ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅድስናው ፡ ተናገረ ፤ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ሴኬምንም ፡ እካፈላለኹ ፥ የሱኮትንም ፡ ሸለቆ ፡ እሰፍራለኹ ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 7 ፤ ገለዓድ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ምናሴም ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ ኤፍሬም ፡ የራሴ ፡ መጠጊያ ፡ ነው ። ይሁዳ ፡ ንጉሤ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 8 ፤ ሞዐብ ፡ መታጠቢያዬ ፡ ነው ፥ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ ጫማዬን ፡ እዘረጋለኹ ፤ ፍልስጥኤም ፡ ይገዙልኛል ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ከተማ ፡ ማን ፡ ይወስደኛል ፧ ማንስ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ ይመራኛል ፧

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ የጣልኸን ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከሰራዊታችን ፡ ጋራ ፡ አትወጣም ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 11 ፤ በመከራችን ፡ ረድኤትን ፡ ስጠን ፡ የሰውም ፡ ማዳን ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 59 ፡ (60) ፡ 12 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ኀይልን ፡ እናደርጋለን ፥ ርሱ ፡ የሚያስጨንቁንን ፡ ያዋርዳቸዋልና ።

መዝሙር ፡ 60 ፡ (61) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በበገናዎች ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 1 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ልመናዬን ፡ ስማ ፥ ጸሎቴንም ፡ አድምጥ ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 2 ፤ ልቤ ፡ ተስፋ ፡ በቈረጠ ፡ ጊዜ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ወዳንተ ፡ እጮኻለኹ ፤ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግኸኝ ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 3 ፤ ጽኑ ፡ ግንብ ፡ በጠላት ፡ ፊት ፡ ተስፋዬም ፡ ኾነኸኛልና ፥ መራኸኝ ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 4 ፤ በድንኳንኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ እኖራለኹ ፤ በክንፎችኽም ፡ ጥላ ፡ እጋረዳለኹ ፤

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ስእለቴን ፡ ሰምተኻልና ፤ ስምኽንም ፡ ለሚፈሩ ፡ ርስትኽን ፡ ሰጠኻቸው ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 6 ፤ ለንጉሥ ፡ ከቀን ፡ በላይ ፡ ቀን ፡ ትጨምራለኽ ፥ ዓመታቱም ፡ ከትውልድ ፡ ወደ ፡ ትውልድ ፡ ይኾናሉ ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፤ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ ምሕረትንና ፡ እውነትን ፡ አዘጋጅለት ።

መዝ. ፡ 60 ፡ (61) ፡ 8 ፤ እንዲሁ ፡ ለስምኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ እዘምራለኹ ፡ ስእለቴን ፡ ኹልጊዜ ፡ እፈጽም ፡ ዘንድ ።

_____መዝሙር ፡ 61 ፡ (62) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ስለ ፡ ኤዶታም ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 1 ፤ ነፍሴ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምትገዛ ፡ አይደለችምን ፧ መድኀኒቴ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናትና ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 2 ፤ ርሱ ፡ አምላኬ ፡ መድኀኒቴም ፡ ነውና ፤ ርሱ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነው ፥ እጅግም ፡ አልታወክም ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 3 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ትቆማላችኹ ፧ እናንተ ፡ ኹላችኹ ፡ እንዳዘነበለ ፡ ግድግዳ ፡ እንደ ፡ ፈረሰም ፡ ቅጥር ፡ ትገድላላችኹ ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክብሬን ፡ ይሻሩ ፡ ዘንድ ፡ መከሩ ፥ ሐሰትንም ፡ ይወዳሉ ፤ በአፋቸው ፡ ይባርካሉ ፥ በልባቸውም ፡ ይረግማሉ ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ አንቺ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዢ ፥ ተስፋዬ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ናትና ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ አምላኬ ፡ መድኀኒቴም ፡ ነውና ፤ ርሱ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነው ፤ አልታወክም ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 7 ፤ መድኀኒቴና ፡ ክብሬ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የረድኤቴ ፡ አምላክ ፡ ተስፋዬም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 8 ፤ የሕዝብ ፡ ማኅበር ፡ ኹላችኹ ፥ በርሱ ፡ ታመኑ ፥ ልባችኹንም ፡ በፊቱ ፡ አፍስሱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ረዳታችን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰው ፡ ልጆች ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ፥ የሰው ፡ ልጆችም ፡ ሐሰተኞች ፡ ናቸው ፤ በሚዛንም ፡ ይበድላሉ ፥ እነርሱስ ፡ በፍጹም ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 10 ፤ ዐመፃን ፡ ተስፋ ፡ አታድርጉ ፥ ቅሚያንም ፡ አትተማመኑት ፤ ባለጠግነት ፡ ቢበዛ ፡

ልባችኹ ፡ አይኵራ ።

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተናገረ ፥ እኔም ፡ ይህን ፡ ብቻ ፡ ሰማኹ ፤ ኀይል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፥

መዝ. ፡ 61 ፡ (62) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትም ፡ ያንተ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍዳውን ፡ ትሰጣለኽና ።

መዝሙር ፡ 62 ፡ (63) ።

በኤዶምያስ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 1 ፤ አምላኬ ፥ አምላኬ ፥ ወዳንተ ፡ እገሠግሣለኹ ፤ ነፍሴ ፡ አንተን ፡ ተጠማች ፥ ሥጋዬ ፡ አንተን ፡ እንዴት ፡ ናፈቀች ፡ ዕንጨትና ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ በምድረ ፡ በዳ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 2 ፤ ኀይልኽንና ፡ ክብርኽን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁ ፡ በመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ተመለከትኹኽ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 3 ፤ ምሕረትኽ ፡ ከሕይወት ፡ ይሻላልና ፥ ከንፈሮቼ ፡ ያመሰግኑኻል ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 4 ፤ እንዲህ ፡ በሕይወቴ ፡ ዘመን ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ ባንተም ፡ ስም ፡ እጆቼን ፡ አነሣለኹ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 5 ፤ ነፍሴ ፡ በቅቤና ፡ በስብ ፡ እንደሚጠግቡ ፡ ትጠግባለች ፥ ከንፈሮቼም ፡ ስምኽን ፡ በደስታ ፡ ያመሰግናሉ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 6 ፤ በመኝታዬም ፡ ዐስብኻለኹ ፥ በማለዳም ፡ እናገርልኻለኹ ፤

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 7 ፤ ረዳቴ ፡ ኾነኽኛልና ፥ በክንፎችኽም ፡ ጥላ ፡ ደስ ፡ ይለኛልና ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 8 ፤ ነፍሴ ፡ በኋላኽ ፡ ተከታተለች ፥ እኔንም ፡ ቀኝኽ ፡ ተቀበለችኝ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 9 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ነፍሴን ፡ ለከንቱ ፡ ፈለጓት ፤ ወደ ፡ ምድር ፡ ጥልቅ ፡ ይገባሉ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 10 ፤ ለሰይፍ ፡ እጅ ፡ ዐልፈው ፡ ይሰጣሉ ፥ የቀበሮም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይኾናሉ ።

መዝ. ፡ 62 ፡ (63) ፡ 11 ፤ ንጉሥ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ በርሱ ፡ የሚምል ፡ ኹሉ ፡ ይከብራል ፥ ሐሰትን ፡ የሚናገር ፡ አፍ ፡ ይዘጋልና ።

መዝሙር ፡ 63 ፡ (64) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ በለመንኹ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎቴን ፡ ስማኝ ፥ ከጠላትም ፡ ፍርሀት ፡ ነፍሴን ፡ አድን ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 2 ፤ ከክፉዎች ፡ ሽንጎ ፡ ከዐመፀኞችም ፡ ብዛት ፡ ሰውረኝ ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 3 ፤ እንደ ፡ ሰይፍ ፡ ምላሳቸውን ፡ አሰሉ ፤ መራራ ፡ ነገርን ፡ ለማድረግ ፥

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 4 ፤ ንጹሕንም ፡ በስውር ፡ ለመንደፍ ፡ ቀስትን ፡ ገተሩ ፤ ድንገት ፡ ይነድፉታል ፡

አይፈሩምም ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 5 ፤ ለእነርሱ ፡ ለራሳቸው ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አጸኑ ፤ ወጥመድን ፡ ይሰውሩ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ፤ ማንስ ፡ ያየናል ፧ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 6 ፤ ዐመፃን ፡ ፈለጓት ፥ ሲፈትኑም ፡ ዐለቁ ፤ የሰው ፡ የውስጥ ፡ ዐሳቡና ፡ ልቡ ፡ የጠለቀ ፡ ነው ፥

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ። የድንገትም ፡ ፍላጻ ፡ ያቈስላቸዋል ፤

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 8 ፤ አንደበታቸው ፡ ያሰናክላቸዋል ፥ የሚያይዋቸውም ፡ ኹሉ ፡ ይደነግጣሉ ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 9 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ፈሩ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ ተናገሩ ፥ ሥራውንም ፡ አስተዋሉ ።

መዝ. ፡ 63 ፡ (64) ፡ 10 ፤ ጻድቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ በርሱም ፡ ይታመናል ፤ ልባቸውም ፡ የቀና ፡ ኹሉ ፡ እልል ፡ ይላሉ ።

መዝሙር ፡ 64 ፡ (65) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በጽዮን ፡ ለአንተ ፡ ምስጋና ፡ ይገባል ፥ ለአንተም ፡ ጸሎት ፡ ይቀርባል ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 2 ፤ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ጸሎትን ፡ ወደምትሰማ ፡ ወዳንተ ፡ ይመጣል ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 3 ፤ የዐመፃ ፡ ነገር ፡ በረታብን ፤ ኀጢአታችንንስ ፡ አንተ ፡ ይቅር ፡ ትላለኽ ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 4 ፤ አንተ ፡ የመረጥኸው ፡ በአደባባዮችኽም ፡ ለማደር ፡ የተቀበልኸው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ ከቤትኽ ፡ በረከት ፡ እንጠግባለን ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 5 ፤ ቤተ ፡ መቅደስኽ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ በጽድቅም ፡ ድንቅ ፡ ነው ። በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉና ፡ በሩቅ ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ላሉ ፡ ተስፋቸው ፡ የኾንኽ ፥ አምላካችንና ፡ መድኀኒታችን ፡ ሆይ ፥ ስማን ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 6 ፤ በጕልበትኽ ፡ ተራራዎችን ፡ አጸናኻቸው ፥ በኀይልም ፡ ታጥቀኻል ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 7 ፤ የባሕሩን ፡ ጥልቀት ፡ የሞገድንም ፡ ጩኸት ፡ ታናውጣለኽ ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 8 ፤ ከተአምራትኽ ፡ የተነሣ ፡ አሕዛብ ፡ ይደነግጣሉ ፥ በምድር ፡ ዳርቻም ፡ የሚኖሩ ፡ ይፈራሉ ፤ የጧትንና ፡ የማታን ፡ መውጫ ፡ ደስ ፡ ታሠኛቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 9 ፤ ምድርን ፡ ጐበኘኻት ፡ አጠጣኻትም ፥ ብልጥግናዋንም ፡ እጅግ ፡ አበዛኽ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ወንዝ ፡ ውሃን ፡ የተመላ ፡ ነው ፤ ምግባቸውን ፡ አዘጋጀኽ ፡ እንዲሁ ፡ ታሰናዳለኽና ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 10 ፤ ትልሟን ፡ ታረካለኽ ፥ ቦይዋንም ፡ ታስተካክላለኽ ፤ በነጠብጣብ ፡ ታለሰልሳታለኽ ፥ ቡቃያዋንም ፡ ትባርካለኽ ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 11 ፤ በቸርነትኽ ፡ ዓመትን ፡ ታቀዳጃለኽ ፥ ምድረ ፡ በዳውም ፡ ስብን ፡ ይጠግባል ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 12 ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ ተራራዎች ፡ ይረካሉ ፥ ኰረብታዎችም ፡ በደስታ ፡ ይታጠቃሉ ።

መዝ. ፡ 64 ፡ (65) ፡ 13 ፤ ማሰማሪያዎች ፡ መንጋዎችን ፡ ለበሱ ፥ ሸለቆዎችም ፡ በእኽል ፡ ተሸፈኑ ፤ በደስታ ፡

ይጮኻሉ ፡ ይዘምራሉም ።

_____መዝሙር ፡ 65 ፡ (66) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የመነሣት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 1 ፤ በምድር ፡ ያላችኹ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እልል ፡ በሉ ፥

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 2 ፤ ለስሙም ፡ ዘምሩ ፥ ለምስጋናውም ፡ ክብርን ፡ ስጡ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ ሥራኽ ፡ ግሩም ፡ ነው ፤ ኀይልኽ ፡ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ ጠላቶች ፡ ዋሹብኽ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 4 ፤ በምድር ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ይሰግዳሉ ፥ ለአንተም ፡ ይዘምራሉ ፥ ለስምኽም ፡ ይዘምራሉ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 5 ፤ ኑ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ እዩ ፤ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ በምክር ፡ ግሩም ፡ ነው ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 6 ፤ ባሕርን ፡ የብስ ፡ አደረጋት ፥ ወንዙንም ፡ በእግር ፡ ተሻገሩ ፤ በዚያ ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 7 ፤ በኀይሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይገዛል ፤ ዐይኖቹ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ይመለከታሉ ፤ ዐመፀኞች ፡ ራሳቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አያድርጉ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 8 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ አምላካችንን ፡ ባርኩ ፥ የምስጋናውንም ፡ ድምፅ ፡ አሰሙ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 9 ፤ ነፍሴን ፡ በሕይወት ፡ ያኖራታል ፥ እግሮቼንም ፡ ለመናወጥ ፡ አልሰጠም ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 10 ፤ አቤቱ ፥ ፈትነኸናልና ፥ ብርንም ፡ እንደሚያነጥሩት ፡ አንጥረኸናልና ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 11 ፤ ወደ ፡ ወጥመድ ፡ አገባኸን ፥ በዠርባችንም ፡ መከራን ፡ አኖርኽ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 12 ፤ በራሳችን ፡ ላይ ፡ ሰውን ፡ አስረገጥኸን ፤ በእሳትና ፡ በውሃ ፡ መካከል ፡ ዐለፍን ፥ ወደ ፡ ዕረፍትም ፡ አወጣኸን ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 13-14 ፤ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ እገባለኹ ፤ በመከራዬ ፡ ጊዜ ፡ በአፌ ፡ የተናገርኹትን ፡ ከንፈሮቼም ፡ ያሉትን ፡ ስእለቴን ፡ ለአንተ ፡ እፈጽማለኹ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 15 ፤ ከዕጣንና ፡ ከወጠጤዎች ፡ ጋራ ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ፍሪዳን ፡ አቀርባለኹ ፤ ላሞችንና ፡ ፍየሎችን ፡ እሠዋልኻለኹ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 16 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ኹሉ ፥ ኑ ፥ ስሙኝ ፤ ለነፍሴ ፡ ያደረገላትን ፡ ልንገራችኹ ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 17 ፤ በአፌ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጮኽኹ ፥ በአንደበቴም ፡ አመሰገንኹት ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 18 ፤ በልቤስ ፡ በደልን ፡ አይቼ ፡ ብኾን ፡ ጌታ ፡ አይሰማኝም ፡ ነበር ።

መዝ. ፥ 65 ፡ (66) ፥ 19 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሰማኝ ፤ የልመናዬን ፡ ድምፅ ፡ አደመጠ ።

መዝ. ፡ 65 ፡ (66) ፡ 20 ፤ ጸሎቴን ፡ ያልከለከለኝ ፡ ምሕረቱንም ፡ ከእኔ ፡ ያላራቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

መዝሙር ፡ 66 ፡ (67) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በበገናዎች ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይማረን ፡ ይባርከንም ፥ ፊቱንም ፡ በላያችን ፡ ያብራ ፤

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 2 ፤ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ መካከል ፡ ማዳንህን ፥ መንገድህንም ፡ በምድር ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ አሕዛብ ፡ ያመስግኑህ ፥ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ያመስግኑህ ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 4 ፤ ለአሕዛብ ፡ በቅን ፡ ትፈርድላቸዋለህና ፥ አሕዛብንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ትመራለህና ፡ አሕዛብ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፡ ሐሤትም ፡ ያድርጉ ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አሕዛብ ፡ ያመስግኑህ ፥ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ያመስግኑህ ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 6 ፤ ምድር ፡ ፍሬዋን ፡ ሰጠች ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላካችንም ፡ ይባርከናል ።

መዝ. ፡ 66 ፡ (67) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይባርከናል ፥ የምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩታል ።

መዝሙር ፡ 67 ፡ (68) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይነሣ ፥ ጠላቶቹም ፡ ይበተኑ ፥ የሚጠሉትም ፡ ከፊቱ ፡ ይሸሹ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 2 ፤ ጢስ ፡ እንደሚበን ፡ እንዲሁ ፡ ይብነኑ ፤ ሠም ፡ በእሳት ፡ ፊት ፡ እንደሚቀልጥ ፥ እንዲሁ ፡ ኃጥኣን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይጥፉ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 3 ፤ ጻድቃንም ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ሐሤት ፡ ያድርጉ ፥ በደስታም ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 4 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀኙ ፡ ለስሙም ፡ ዘምሩ ፤ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ለወጣም ፡ መንገድ ፡ አድርጉ ፤ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ በፊቱም ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ በፊቱም ፡ ይደነግጣሉ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅዱስ ፡ ቦታው ፡ ለድኻ ፡ አደጎች ፡ አባት ፥ ለባልቴቶችም ፡ ዳኛ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ብቸኞችን ፡ በቤት ፡ ያሳድራቸዋል ፥ እስረኞችንም ፡ በኀይሉ ፡ ያወጣቸዋል ፤ ዐመፀኞች ፡ ግን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖራሉ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ በሕዝብም ፡ ፊት ፡ በወጣህ ፡ ጊዜ ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ ባለፍህ ፡ ጊዜ ፥ ምድር ፡ ተናወጠች ፥

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 8 ፤ ከሲና ፡ አምላክ ፡ ፊት ፥ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ ሰማያትም ፡ አንጠበጠቡ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ የሞገስን ፡ ዝናብ ፡ ለርስትህ ፡ አዘነብህ ፥ በደከመም ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ አጸናኸው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 10 ፤ እንስሳዎችኽ ፡ በውስጡ ፡ ዐደሩ ፤ አቤቱ ፥ በቸርነትኽ ፡ ለድኻዎች ፡ አዘጋጀኽ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፤ የሚያወሩት ፡ ብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 12 ፤ የሰራዊት ፡ ነገሥታት ፡ ፈጥነው ፡ ይሸሻሉ ፤ በቤትም ፡ የምትኖር ፡ ምርኮን ፡ ተካፈለች ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 13 ፤ በርስቶች ፡ መካከል ፡ ብታድሩ ፥ ከብር ፡ እንደ ፡ ተሠሩ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ክንፎች ፥ በቅጠልያ ፡ ወርቅም ፡ እንደ ፡ ተለበጡ ፡ ላባዎቿ ፡ ትኾናላችኹ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 14 ፤ ሰማያዊ ፡ ንጉሥ ፡ በላይዋ ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፥ በሰልሞን ፡ ላይ ፡ በረዶ ፡ ዘነበ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ የለመለመ ፡ ተራራ ፡ ነው ፤ የጸና ፡ ተራራና ፡ የለመለመ ፡ ተራራ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 16 ፤ የጸኑ ፡ ተራራዎች ፡ ለምን ፡ ይነሣሉ ፧ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ተራራ ፡ ያድርበት ፡ ዘንድ ፡ ወደደው ፤ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ያድርበታል ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሠረገላዎች ፡ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሺሕ ፡ ናቸው ፤ ጌታ ፡ በመቅደሱ ፡ በሲና ፡ በመካከላቸው ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 18 ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ዐረግኽ ፥ ምርኮን ፡ ማረክኽ ፥ ስጦታንም ፡ ለሰዎች ፡ ሰጠኽ ፥ ደግሞም ፡ ለዐመፀኞች ፡ በዚያ ፡ ያድሩ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ በየዕለቱ ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፤ የመድኀኒታችን ፡ አምላክ ፡ ይረዳናል ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 20 ፤ አምላካችንስ ፡ የደኅንነት ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ከሞት ፡ መውጣትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ የጠላቶቹን ፡ ራስ ፥ በኀጢአት ፡ የሚኼድንም ፡ የጠጕሩን ፡ ዐናት ፡ ይቀጠቅጣል ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ከባሳን ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ ከባሕርም ፡ ጥልቅ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 23 ፤ እግሮችኽ ፡ በደም ፡ ይረገጡ ፡ ዘንድ ፥ የውሻዎችኽ ፡ ምላስ ፡ በጠላቶች ፡ ላይ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 24 ፤ የአምላኬ ፡ የንጉሥ ፡ መንገድ ፡ በመቅደሱ ፥ አቤቱ ፥ መንገድኽ ፡ ተገለጠ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 25 ፤ አለቃዎች ፡ ቀደሙ ፥ መዘምራንም ፡ ተከተሉ ፤ ከበሮን ፡ በሚመቱ ፡ በቈነጕሯት ፡ መካከል ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በጉባኤ ፥ ጌታችንንም ፡ በእስራኤል ፡ ምንጭ ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 27 ፤ ወጣቱ ፡ ብንያም ፡ በጕልበቱ ፡ በዚያ ፡ አለ ፥ ገዢዎቻቸው ፡ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ የዛብሎን ፡ አለቃዎችና ፡ የንፍታሌምም ፡ አለቃዎች ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 28 ፤ አቤቱ ፥ ኀይልኽን ፡ እዘዝ ፤ አቤቱ ፥ ይህንም ፡ ለእኛ ፡ የሠራኸውን ፡ አጽናው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 29 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ስላለው ፡ መቅደስኽ ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ለአንተ ፡ ያመጣሉ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 30 ፤ በሸምበቆ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ አራዊት ፥ በአሕዛብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የበሬዎችንና ፡ የወይፈኖችን ፡ ጉባኤ ፡ ገሥጽ ፥ እንደ ፡ ብር ፡ የተፈተኑት ፡ አሕዛብ ፡ እንዳይዘጉ ፤ ሰልፍን ፡ የሚወዱትን ፡ አሕዛብን ፡ በትናቸው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 31 ፤ መኳንንት ፡ ከግብጽ ፡ ይመጣሉ ፤ ኢትዮጵያ ፡ እጆቿን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትዘረጋለች ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 32 ፤ የምድር ፡ ነገሥታት ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀኙ ፥ ለጌታም ፡ ዘምሩ ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 33 ፤ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ሰማየ ፡ ሰማያት ፡ ለወጣ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፤ የኀይል ፡ ቃል ፡ የኾነ ፡ ቃሉን ፥ እንሆ ፥ ይሰጣል ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 34 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ክብርን ፡ ስጡ ፤ ግርማው ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፥ ኀይሉም ፡ በደመናት ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 67 ፡ (68) ፡ 35 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅዱሳኑ ፡ ላይ ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ርሱ ፡ ኀይልን ፡ ብርታትንም ፡ ለሕዝቡ ፡ ይሰጣል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይመስገን ።

መዝሙር ፡ 68 ፡ (69) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በመለከቶች ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ውሃ ፡ እስከ ፡ ነፍሴ ፡ ደርሶብኛልና ፥ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 2 ፤ በጥልቅ ፡ ረግረግ ፡ ጠለቅኹ ፡ መቋሚያም ፡ የለኝም ። ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ገባኹ ፡ ማዕበልም ፡ አሰጠመኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 3 ፤ በጨኸት ፡ ደከምኹ ፡ ጕረሮዬም ፡ ሰለለ ፤ አምላኬን ፡ ስጠብቅ ፡ ዐይኖቼ ፡ ፈዘዙ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 4 ፤ በከንቱ ፡ የሚጠሉኝ ፡ ከራሴ ፡ ጠጕር ፡ በዙ ፤ በዐመፅ ፡ ያሚያሳድዱኝ ፡ ጠላቶቼ ፡ በረቱ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ያልቀማኹትን ፡ መለስኹ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ስንፍናዬን ፡ ታውቃለኽ ፥ ኀጢአቴም ፡ ከአንተ ፡ አልተሰወረም ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 6 ፤ አቤቱ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፥ ተስፋ ፡ የሚያደርጉኽ ፡ በእኔ ፡ አይፈሩ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የሚሹኽ ፡ በእኔ ፡ አይነወሩ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 7 ፤ ስለ ፡ አንተ ፡ ስድብን ፡ ታግሻለኹና ፥ ዕፍረትም ፡ ፊቴን ፡ ሸፍናለችና ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 8 ፤ ለወንድሞቼ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፥ ለእናቴ ፡ ልጆችም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ኾንኹባቸው ፥

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 9 ፤ የቤትኽ ፡ ቅንአት ፡ በልታኛለችና ፥ የሚሰድቡኽም ፡ ስድብ ፡ በላዬ ፡ ወድቋልና ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 10 ፤ ነፍሴን ፡ በጾም ፡ አስመረርኋት ፥ ለስድብም ፡ ኾነብኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 11 ፤ ማቅ ፡ ለበስኹ ፡ ምሳሌም ፡ ኾንኹላቸው ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 12 ፤ በደጅ ፡ የሚቀመጡ ፡ በእኔ ፡ ይጫወታሉ ፤ ወይን ፡ የሚጠጡ ፡ እኔን ፡ ይዘፍናሉ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ በመልካሙ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎቴ ፡ ወዳንተ ፡ ነው ፤ አቤቱ ፥ በምሕረትኽ ፡ ብዛት ፡ በማዳንኽም ፡ እውነት ፡ አድምጠኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 14 ፤ እንዳይውጠኝ ፡ ከረግረግ ፡ አውጣኝ ፤ ከሚጠሉኝና ፡ ከጥልቅ ፡ ውሃ ፡ አስጥለኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 15 ፤ የውሃው ፡ ማዕበል ፡ አያስጥመኝ ፥ ጥልቁም ፡ አይዋጠኝ ፥ ጕድጓድም ፡ አፉን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አይዝጋ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ መልካም ፡ ናትና ፥ ስማኝ ። እንደ ፡ ርኅራኄኽም ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከት ፤

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 17 ፤ ከባሪያኽም ፡ ፊትኽን ፡ አትሰውር ፤ ተጨንቄያለኹና ፡ ፈጥነኽ ፡ አድምጠኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 18 ፤ ነፍሴን ፡ ተመልክተኽ ፡ ተቤዣት ፤ ስለ ፡ ጠላቶቼም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 19 ፤ አንተ ፡ ስድቤን ፡ ዕፍረቴንም ፡ ነውሬንም ፡ ታውቃለኽ ፤ የሚያስጨንቁኝ ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 20 ፤ ነፍሴ ፡ ስድብንና ፡ ኃሣርን ፡ ታገሠች ፤ አስተዛዛኝም ፡ ተመኘኹ ፡ አላገኘኹም ። የሚያጽናናኝም ፡ ዐጣኹ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 21 ፤ ለመብሌ ፡ ሐሞት ፡ ሰጡኝ ፥ ለጥማቴም ፡ ሖምጣጤ ፡ አጠጡኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 22 ፤ ማእዳቸው ፡ በፊታቸው ፡ ለወጥመድ ፡ ለፍዳ ፡ ለዕንቅፋት ፡ ትኹንባቸው ፤

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 23 ፤ ዐይኖቻቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ይጨልሙ ፥ ገርርባቸውም ፡ ዘወትር ፡ ይጕበጥ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 24 ፤ መዓትኽን ፡ በላያቸው ፡ አፍስ ፥ የቀኑጣኽ ፡ መቅሠፍትም ፡ ያግኛቸው ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 25 ፤ ማደሪያቸው ፡ በረሓ ፡ ትኹን ፥ በድንኳኖቻቸውም ፡ የሚቀመጥ ፡ አይገኝ ፤

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 26 ፤ አንተ ፡ የቀሠፍኸውን ፡ እነርሱ ፡ አሳድደዋልና ፥ በቀኑስሌም ፡ ላይ ፡ ጥዝጣዜ ፡ ጨመሩብኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 27 ፤ በኀጢአታቸው ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ጨምርባቸው ፥ በጽድቅኽም ፡ አይግቡ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 28 ፤ ከሕያዋን ፡ መጽሐፍ ፡ ይደምሰሱ ፥ ከጻድቃንም ፡ ጋራ ፡ አይጻፉ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 29 ፤ እኔ ፡ ችግረኛና ፡ ቀኑስለኛ ፡ ነኝ ፤ አቤቱ ፥ የፊትኽ ፡ መድኀኒት ፡ ይቀበለኝ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 30 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በዝማሬ ፡ አመሰግናለኹ ፥ በምስጋናም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገዋለኹ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 31 ፤ ቀንድና ፡ ጥፍር ፡ ካበቀለ ፡ ከእንቦሳ ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋል ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 32 ፤ ችግረኞች ፡ ያያሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፈልጉ ፡ ሕያዋንም ፡ ኹኑ ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 33 ፤ እግዚአብሔር ፡ ችግረኞችን ፡ ሰምቷልና ፥ እስረኞቹንም ፡ አልናቀምና ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 34 ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ባሕርም ፡ በርሷም ፡ የሚንቀሳቀስ ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑታል ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 35 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ ያድናታልና ፥ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፡ ይሠራልና ፤ በዚያም ፡ ይቀመጣሉ ፥ ይወርሷትማል ።

መዝ. ፡ 68 ፡ (69) ፡ 36 ፤ የባሪያዎቹ ፡ ዘር ፡ ይኖሩባታል ። ስሙንም ፡ የሚወዱ ፡ በዚያ ፡ ይቀመጣሉ ።

መዝሙር ፡ 69 ፡ (70) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ለመታሰቢያ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 69 ፡ (70) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እኔን ፡ ለማዳን ፡ ተመልከት ፤ አቤቱ ፥ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ ፍጠን ።

መዝ. ፡ 69 ፡ (70) ፡ 2 ፤ ነፍሴን ፡ የሚሿት ፡ ይፈሩ ፡ ይጐስቍሉም ፥ ክፉንም ፡ የሚመክሩብኝ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሱ ፡ ይፈሩም ።

መዝ. ፡ 69 ፡ (70) ፡ 3 ፤ እንኳ! ፡ እንኳ! ፡ የሚሉኝ ፡ ዐፍረው ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሱ ።

መዝ. ፡ 69 ፡ (70) ፡ 4 ፤ የሚሹኽ ፡ ኹሉ ፡ ባንተ ፡ ሐሤት ፡ ያድርጉ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፤ ማዳንኽን ፡ የሚወዱ ፡ ኹልጊዜ ፦ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

መዝ. ፡ 69 ፡ (70) ፡ 5 ፤ እኔ ፡ ችግረኛና ፡ ምስኪን ፡ ነኝ ፤ አቤቱ ፥ ርዳኝ ፤ ረዳቴ ፡ ታዳጊዬም ፡ አንተ ፡ ነኽ ፤ አቤቱ ፥ አትዘግይ ።

መዝሙር ፡ 70 ፡ (71) ።

አስቀድመው ፡ ስለ ፡ ማረኩ ፡ ስለዐሚናዳብ ፡ ልጆች ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አንተን ፡ ታመንኹ ፤ ለዘለዓለም ፡ አልፈር ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 2 ፤ በጽድቅኽ ፡ አስጥለኝ ፡ ታደገኝም ፤ ጐሮኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብል ፡ አድነኝም ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 3 ፤ በጠንካራ ፡ ቦታ ፡ ታድነኝ ፡ ዘንድ ፡ አምላክና ፡ መሸሸጊያ ፡ ኹነኝ ፤ ኀይሌ ፡ መጠጊያዬ ፡ አንተ ፡ ነኽና ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 4 ፤ አምላኬ ፥ ከኀጢአተኛ ፡ እጅ ፥ ከዐመፀኛና ፡ ከግፈኛም ፡ እጅ ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ተስፋዬ ፡ ነኽና ፥ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ከታናሽነቴ ፡ ዠምረኽ ፡ መታመኛዬ ፡ ነኽና ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 6 ፤ ከማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ ባንተ ፡ ተደገፍኹ ፥ ከእናቴም ፡ ሆድ ፡ ዠምሮ ፡ አንተ ፡ መሸሸጊያዬ ፡ ነኽ ፤ ኹልጊዜም ፡ ዝማሬዬ ፡ ለአንተ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 7 ፤ ለብዙዎች ፡ መደነቂያ ፡ ኾንኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ብርቱ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 8 ፤ አፌን ፡ ምስጋና ፡ ምላ ፡ ኹልጊዜ ፡ ክብርኽንና ፡ ግርማኽን ፡ እዘምር ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 9 ፤ በእርጅናዬ ፡ ዘመን ፡ አትጣለኝ ፥ ጕልበቴም ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ አትተወኝ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 10 ፤ ጠላቶቹ ፡ በላዬ ፡ ተናግረዋልና ፤ ነፍሴንም ፡ የሚሿት ፡ በአንድነት ፡ ተማክረዋልና ፥ እንዲህም ፡ አሉ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትቶታል ፤ የሚያድነው ፡ የለምና ፡ ተከትላችኹ ፡ ያዙት ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 12 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከእኔ ፡ አትራቅ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ ለመርዳት ፡ ፍጠን ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 13 ፤ ነፍሴን ፡ የሚቃወሟት ፡ ይፈሩ ፡ ይጥፉም ፥ ጕዳቴንም ፡ የሚፈልጉ ፡ ዕፍረትንና ፡ ኃሣርን ፡ ይልበሱ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 14 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ፥ በምስጋናኽም ፡ ዘውትር ፡ ላይ ፡ እጨምራለኹ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 15 ፤ ሥራን ፡ አላውቅምና ፡ አፌ ፡ ጽድቅኽን ፡ ዘወትር ፡ ማዳንኽን ፡ ይናገራል ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 16 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ እገባለኹ ፤ አቤቱ ፥ ጽድቅኽን ፡ ብቻ ፡ ዐስባለኹ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 17 ፤ አምላኬ ፥ ከታናሽነቴ ፡ ዠምረኽ ፡ አስተማርኸኝ ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ተኣምራትኽን ፡ እነግራለኹ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 18 ፤ እስካረጅም ፡ እስክሸመግልም ፡ ድረስ ፥ ለሚመጣ ፡ ትውልድም ፡ ዘሩ ፡ ክንድኽን ፡ ኀይልኽንም ፡ ጽድቅኽንም ፡ እስክነግር ፡ ድረስ ፥ አቤቱ ፥ አትተወኝ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ አርያም ፡ ታላላቅ ፡ ነገሮችን ፡ አደረግኽ ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 20 ፤ ብዙ ፡ ጭንቀትንና ፡ መከራን ፡ አሳይተኸኛልና ፥ ተመለስኽ ፡ ሕያውም ፡ አደረግኸኝ ፤ ከምድር ፡ ጥልቅም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አወጣኸኝ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 21 ፤ ጽድቅኽንም ፡ አብዛው ፥ ተመልሰኽም ፡ ደስ ፡ አሠኘኝ ፥ ከጥልቅም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አወጣኸኝ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 22 ፤ እኔም ፡ በበገና ፡ ስለ ፡ እውነትኽ ፡ አመሰግንኻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በመሰንቆ ፡ እዘምርልኻለኹ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 23 ፤ ዝማሬን ፡ ባቀርብኹልኽ ፡ ጊዜ ፡ ከንፈሮቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ አንተ ፡ ያዳንኻትም ፡ ነፍሴ ።

መዝ. ፡ 70 ፡ (71) ፡ 24 ፤ ጕዳቴን ፡ የሚሹ ፡ ባፈሩና ፡ በተነወሩ ፡ ጊዜ ፡ አንደበቴ ፡ ደግሞ ፡ ዘውትር ፡ ጽድቅኽን ፡ ይናገራል ።

መዝሙር ፡ 71 ፡ (72) ።

ስለ ፡ ሰሎሞን ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ፍርድኽን ፡ ለንጉሥ ፡ ስጥ ፥ ጽድቅኽንም ፡ ለንጉሥ ፡ ልጅ ፥

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 2 ፤ ሕዝብኽን ፡ በጽድቅ ፥ ችግረኞችኽንም ፡ በፍርድ ፡ ይዳኝ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 3 ፤ ተራራዎችና ፡ ኰረብታዎች ፡ ለሕዝብኽ ፡ ሰላምን ፡ ይቀበሉ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 4 ፤ ለችግረኞች ፡ ሕዝብ ፡ በጽድቅ ፡ ትፈርዳለኽ ፡ የድኻዎችንም ፡ ልጆች ፡ ታድናለኽ ፤ ክፉውንም ፡ ታዋርደዋለኽ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 5 ፤ ፀሓይ ፡ በሚኖርበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ በጨረቃም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ዝናብ ፡ በታጨደ ፡ መስክ ፡ ላይ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ እንደሚንጠባጠብ ፡ ጠብታ ፡ ይወርዳል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 7 ፤ በዘመኑም ፡ ጽድቅ ፡ ያብባል ፥ ጨረቃም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ሰላም ፡ ብዙ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 8 ፤ ከባሕር ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፥ ከወንዝም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይገዛል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 9 ፤ በፊቱም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ይሰግዳሉ ፥ ጠላቶቹም ፡ ዐፈር ፡ ይልሳሉ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 10 ፤ የተርሴስና ፡ የደሴቶች ፡ ነገሥታት ፡ ስጦታን ፡ ያመጣሉ ፤ የዐረብና ፡ የሳባ ፡ ነገሥታት ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ያቀርባሉ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 11 ፤ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ይሰግዱለታል ። አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ይገዙለታል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 12 ፤ ችግረኛውን ፡ ከቀማኛው ፡ እጅ ፥ ረዳት ፡ የሌለውንም ፡ ምስኪን ፡ ያድነዋልና ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 13 ፤ ለችግረኛና ፡ ለምስኪን ፡ ይራራል ፥ የችግረኞችንም ፡ ነፍስ ፡ ያድናል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 14 ፤ ከግፍና ፡ ከጭንቀት ፡ ነፍሳቸውን ፡ ያድናል ፤ ስማቸው ፡ በፊቱ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 15 ፤ ርሱ ፡ ይኖራል ፡ ከዐረብም ፡ ወርቅ ፡ ይሰጡታል ፤ ኹልጊዜም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይጸልያሉ ፥ ዘወትርም ፡ ይባርኩታል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 16 ፤ በምድር ፡ ውስጥ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ መጠጊያ ፡ ይኾናል ፤ ፍሬውም ፡ ከሊባኖስ ፡ ይልቅ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ እንደምድር ፡ ሣር ፡ በከተማ ፡ ይበቅላል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 17 ፤ ስሙ ፡ ለዘለዓለም ፡ ቡሩክ ፡ ይኾናል ፥ ከፀሓይም ፡ አስቀድሞ ፡ ስሙ ፡ ይኖራል ፤ የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ይባረካሉም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑታል ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 18 ፤ ብቻውን ፡ ተኣምራትን ፡ የሚያደርግ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 19 ፤ የምስጋናው ፡ ስም ፡ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለም ፡ ይባረክ ፤ ምስጋናውም ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ይምላ ። ይኹን ፤ ይኹን ።

መዝ. ፡ 71 ፡ (72) ፡ 20 ፤ የእሴይ ፡ ልጅ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ተፈጸመ ።

_____መዝሙር ፡ 72 ፡ (73) ። _____

የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 1 ፤ ልባቸው ፡ ለቀና ፡ ለእስራኤል ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ቸር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እግሮቼ ፡ ሊሰናከሉ ፥ አረማመዴም ፡ ሊወድቅ ፡ ትንሽ ፡ ቀረ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 3 ፤ የኀጢአተኞችን ፡ ሰላም ፡ አይቼ ፡ በዐመፀኞች ፡ ቀንቼ ፡ ነበርና ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 4 ፤ ለሞታቸው ፡ መጣጣር ፡ የለውምና ፤ ኀይላቸውም ፡ ጠንካራ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ በድካም ፡ አልኾኑም ፥ ከሰው ፡ ጋራም ፡ አልተገረፉም ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ትዕቢት ፡ ያዛቸው ፤ ኀጢአትንና ፡ በደልን ፡ ተጐናጸፏት ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 7 ፤ ዐይናቸው ፡ ስብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ወጣ ፤ ልባቸውም ፡ ከምኞታቸው ፡ ይልቅ ፡ አገኘ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 8 ፤ ዐስበው ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ተናገሩ ። ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብለውም ፡ በዐመፃ ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 9 ፤ አፋቸውን ፡ በሰማይ ፡ አኖሩ ፥ አንደበታቸውም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ተመላለሰ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ሕዝቤ ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ፤ ፍጹም ፡ ጊዜም ፡ በላያቸው ፡ ይገኛል ፤

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ያውቃል ፧ በልዑልስ ፡ ዘንድ ፡ በእውኑ ፡ ዕውቀት ፡ አለ ፧ ይላሉ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 12 ፤ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ይደሰታሉ ፥ ዘልጊዜም ፡ ባለጠግነታቸውን ፡ ያበዛሉ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ በእውኑ ፡ ልቤን ፡ በከንቱ ፡ አጸደቅኹ ፥ እጆቼንም ፡ በንጽሕና ፡ በከንቱ ፡ አጠብኹ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 14 ፤ ዘልጊዜም ፡ የተገረፍኹ ፡ ኾንኹ ፥ መሰደቤም ፡ በማለዳ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 15 ፤ እንደዚህ ፡ ብዬ ፡ ብናገር ፡ ኖሮ ፥ እንሆ ፥ የልጆችኽን ፡ ትውልድ ፡ በበደልኹ ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 16 ፤ ዐውቅም ፡ ዘንድ ፡ ዐሰብኹ ፥ ይህ ፡ ግን ፡ በፊቴ ፡ ችግር ፡ ነበረ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 17 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ እስክገባ ፡ ድረስ ፥ ፍጻሜያቸውንም ፡ እስካስተውል ፡ ድረስ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 18 ፤ በድጥ ፡ ስፍራ ፡ አስቀመጥኻቸው ፥ ወደ ፡ ጥፋትም ፡ ጣልኻቸው ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 19 ፤ እንዴት ፡ ለጥፋት ፡ ኾኑ! ፡ በድንገት ፡ ዐለቁ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸውም ፡ ጠፉ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 20 ፤ ከሕልም ፡ እንደሚነቃ ፥ አቤቱ ፥ ስትነቃ ፡ ምልክታቸውን ፡ ታስነውራለኽ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 21 ፤ ልቤ ፡ ነዷልና ፥ ኵላሊቴም ፡ ቀልጧልና ፤

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 22 ፤ እኔ ፡ የተናቅኹ ፡ ነኝ ፡ አላውቅኹምም ፥ ባንተ ፡ ዘንድም ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 23 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ ቀኝ ፡ እጄንም ፡ ያዝኸኝ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 24 ፤ ባንተ ፡ ምክር ፡ መራኸኝ ፤ ከክብር ፡ ጋራ ፡ ተቀበልኸኝ ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 25 ፤ በሰማይ ፡ ያለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በምድርስ ፡ ውስጥ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ እሻለኹ ፧

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 26 ፤ የልቤ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ልቤና ፡ ሥጋዬ ፡ ዐለቀ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ ከአንተ ፡ የሚርቁ ፡ ይጠፋሉና ፡ ከአንተ ፡ ርቀው ፡ የሚያመነዝሩትንም ፡ ኹሉ ፡ አጠፋኻቸው ።

መዝ. ፡ 72 ፡ (73) ፡ 28 ፤ ለእኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መቅረብ ፡ ይሻለኛል ፤ መታመኛዬም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ በጽዮን ፡ ልጅ ፡ በሮች ፡ ምስጋናኽን ፡ ኹሉ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ።

_____መዝሙር ፡ 73 ፡ (74) ። _____

የአሣፍ ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ለዘወትር ፡ ጣልኸኝ ፧ በማሰማሪያኽ ፡ በጎች ፡ ላይስ ፡ ቍጣኽን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቈጣኽ ፧

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 2 ፤ አስቀድመኽ ፡ የፈጠርኻትን ፡ ማኅበርኽን ፥ የተቤዠኻትንም ፡ የርስትኽን ፡ በትር ፥ በርሷ ፡ ያደርኽባትን ፡ የጽዮንን ፡ ተራራ ፡ ዐስብ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 3 ፤ ጠላት ፡ በቅዱሳንኽ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ከፋ ፡ መጠን ፥ ኹልጊዜም ፡ በትዕቢታቸው ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ አንሣ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 4 ፤ ጠላቶችኽ ፡ በበዓል ፡ መካከል ፡ ተመኩ ፤ የማያውቁትንም ፡ ምልክት ፡ ምልክታቸው ፡ አደረጉ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ላይኛው ፡ መግቢያ ፡ ውስጥ ፡ በዱር ፡ እንዳሉም ፡ ዕንጨቶች ፥ በመጥረቢያ ፡ በሮቿን ፡ ሰበሩ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 6 ፤ እንዲሁ ፡ በመጥረቢያና ፡ በመዶሻ ፡ ሰበሯት ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 7 ፤ መቅደስኽን ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፤ የስምኽንም ፡ ማደሪያ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ አረከሱ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 8 ፤ አንድ ፡ ኾነው ፡ በልባቸው ፡ በየሕዝባቸው ። ኑ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ በዓሎች ፡ ከምድር ፡ እንሻር ፡ አሉ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 9 ፤ ምልክታችንን ፡ አናይም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ነቢይ ፡ የለም ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ እንዲኖር ፡ የሚያውቅ ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ ጠላት ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይሳደባል ፧ ስምኽን ፡ ጠላት ፡ ኹልጊዜ ፡ ያቃልላልን ፧

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 11 ፤ ቀኝኽንም ፡ በብብትኽ ፡ መካከል ፥ እጅኽንም ፡ ፈጽመኽ ፡ ለምን ፡ ትመልሳለኽ ፧

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከዓለም ፡ አስቀድሞ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ መድኀኒትን ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 13 ፤ አንተ ፡ ባሕርን ፡ በኀይልኽ ፡ አጸናኻት ፤ አንተ ፡ የእባቦችን ፡ ራስ ፡ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ሰበርኽ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 14 ፤ አንተም ፡ የዘንዶውን ፡ ራሶች ፡ ቀጠቀጥኽ ፤ ለኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ምግባቸውን ፡ ሰጠኻቸው ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 15 ፤ አንተ ፡ ምንጮቹንና ፡ ፈሳሾቹን ፡ ሰነጠቅኽ ፤ አንተ ፡ ዘልጊዜ ፡ የሚፈሱትን ፡ ወንዞች ፡ አደረቅኽ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 16 ፤ ቀኑ ፡ የአንተ ፡ ነው ፡ ሌሊቱም ፡ የአንተ ፡ ነው ፤ አንተ ፡ ፀሓዩንና ፡ ጨረቃውን ፡ አዘጋጀኽ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 17 ፤ አንተ ፡ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ሠራኽ ፤ በጋንም ፡ ክረምትንም ፡ አንተ ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 18 ፤ ይህን ፡ ፍጥረትኽን ፡ ዐስብ ። ጠላት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተላገደ ፥ ሰነፍ ፡ ሕዝብም ፡ ስሙን ፡ አስቈጣ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 19 ፤ የምትገዛልኽን ፡ ነፍስ ፡ ለአራዊት ፡ አትስጣት ፤ የችግረኞችኽን ፡ ነፍስ ፡ ለዘወትር ፡ አትርሳ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ኪዳንኽ ፡ ተመልከት ፥ የምድር ፡ የጨለማ ፡ ስፍራዎች ፡ በኃጥኣን ፡ ቤቶች ፡ ተሞልተዋልና ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 21 ፤ ችግረኛ ፡ ዐፍሮ ፡ አይመለስ ፤ ችግረኛና ፡ ምስኪን ፡ ስምኽን ፡ ያመሰግናሉ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 22 ፤ አቤቱ ፥ ተነሥ ፡ በቀልኽንም ፡ ተበቀል ፤ ሰነፎች ፡ ዘልጊዜም ፡ የተላገዱኽን ፡ ዐስብ ።

መዝ. ፡ 73 ፡ (74) ፡ 23 ፤ የባሪያዎችኽን ፡ ቃል ፡ አትርሳ ፤ የጠላቶችኽ ፡ ኵራት ፡ ዘልጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ ይወጣል ።

_____መዝሙር ፡ 74 ፡ (75) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ አታጥፋ ። የአሣፍ ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እናመሰግንኻለን ፡ እናመሰግንኻለን ፡ ስምኽንም ፡ እንጠራለን ፤ ተኣምራትኽን ፡ ኹሉ ፡ እናገራለኹ ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 2 ፤ ጊዜውን ፡ ስቀበል ፡ እኔ ፡ በቅን ፡ እፈርዳለኹ ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 3 ፤ ምድርና ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ቀለጡ ፥ እኔም ፡ ምሰሶዋቿን ፡ አጠናኹ ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 4 ፤ ዐመፀኞችን ፦ አትበድሉ ፡ አልኋቸው ፥ ኀጢአተኞችንም ፦ ቀንዳችኹን ፡ አታንሡ ፤

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 5 ፤ ቀንዳችኹን ፡ እስከ ፡ ላይ ፡ አታንሡ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ አትናገሩ ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 6 ፤ ክብር ፡ ከምሥራቅ ፡ ወይም ፡ ከምዕራብ ፡ ወይም ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ የለምና ፤

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፈራጅ ፡ ነውና ፥ ይህን ፡ ያዋርዳል ፡ ይህንም ፡ ያከብራል ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 8 ፤ ጽዋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነውና ፤ ያልተቀላቀለ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ሞላበት ፤ ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ አገላበጠው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አተላው ፡ አልፈሰሰም ፤ የምድር ፡ ኀጢአተኞች ፡ ኹሉ ፡ ይጠጡታል ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ለያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ዝማሬን ፡ አቀርባለኹ ።

መዝ. ፡ 74 ፡ (75) ፡ 10 ፤ የኃጥኣንን ፡ ቀንዶች ፡ ኹሉ ፡ እሰብራለኹ ፤ የጻድቃን ፡ ቀንዶች ፡ ግን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ።

መዝሙር ፡ 75 ፡ (76) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በበገናዎች ፤ ስለ ፡ አሶራውያን ፤ የአሣፍ ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ በይሁዳ ፡ ታወቀ ፥ ስሙም ፡ በእስራኤል ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 2 ፤ ስፍራው ፡ በሳሌም ፥ ማደሪያውም ፡ በጽዮን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 3 ፤ በዚያም ፡ የቀስትን ፡ ኀይል ፥ ጋሻን ፡ ሰይፍን ፡ ሰልፍንም ፡ ሰበረ ፤ በዚያም ፡ ቀንዶችን ፡ ሰበረ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 4 ፤ አንተ ፡ በዘለዓለም ፡ ተራራዎች ፡ ኾነኽ ፡ በድንቅ ፡ ታበራለኽ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 5 ፤ ልበ ፡ ሰነፎች ፡ ኹሉ ፡ ደነገጡ ፥ እንቅልፋቸውንም ፡ አንቀላፉ ፤ ባለጠጋዎች ፡ ኹሉ ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ምንም ፡ አላገኙም ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 6 ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከተግሣጽኽ ፡ የተነሣ ፡ ፈረሰኞች ፡ ኹሉ ፡ አንቀላፉ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 7 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ግሩም ፡ ነኽ ፤ ቍጣኽን ፡ ማን ፡ ይቃወማል ፧

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 8 ፤ ፍርድን ፡ ከሰማይ ፡ አሰማኽ ፤ ምድር ፡ ፈራች ፡ ዝምም ፡ አለች ፥

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 9 ፤ ልበ ፡ የዋሃንን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለፍርድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 10 ፤ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ ያመሰግንኻልና ፥ ከኀሊናቸው ፡ ትርፍም ፡ በዓልኽን ፡ ያደርጋሉ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 11 ፤ ለአምላካችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለትን ፡ ክፈሉ ፤ በዙሪያው ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ መንሻን ፡ ለሚያስፈራው ፡ ያገባሉ ።

መዝ. ፡ 75 ፡ (76) ፡ 12 ፤ የመኳንንትን ፡ ነፍስ ፡ ያወጣል ፤ በምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ዘንድ ፡ ያስፈራል ።

መዝሙር ፡ 76 ፡ (77) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ ስለ ፡ ኤዶታም ፤ የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 1 ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኩ ፥ ቃሌም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ አደመጠኝ ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 2 ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈለግኩት ፤ እጆቼ ፡ በሌሊት ፡ በፊቱ ፡ ናቸው ፥ አላረፍኩምም ፥ ነፍሴም ፡ መጽናናትን ፡ አልቻለችም ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ዐሰብኹት ፡ ደስ ፡ አለኝም ፤ ተናገርኹ ፥ ነፍሴም ፡ ፈዘዘች ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 4 ፤ ዐይኖቼ ፡ እንዲተጉ ፡ ያዝኻቸው ፤ ደነገጥኹ ፡ አልተናገርኹም ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 5 ፤ የዱሮውን ፡ ዘመን ፡ ዐሰብኹ ፤ የዘለዓለሙን ፡ ዓመታት ፡ ዐሰብኹ ፤ አጠናጠንኹም ፡

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 6 ፤ በሌሊት ፡ ከልቤ ፡ ጋራ ፡ ተጣወትኹ ፥ ነፍሴንም ፡ አነቃቃኺት ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጥላልን ፧ እንግዲህስ ፡ ቸርነቱን ፡ አይጨምርምን ፧

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 8 ፤ ለዘለዓለምስ ፡ ምሕረቱ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ተቈረጠችን ፧ የተናገረውስ ፡ ቃል ፡ አልቋልን ፧

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርስ ፡ ሞገሱን ፡ ረሳን ፧ በቀኑጣውስ ፡ ምሕረቱን ፡ ዘጋውን ፧

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 10 ፤ ይህ ፡ ድካሜ ፡ ነው ፡ አልኹ ፥ የልዑል ፡ ቀኝ ፡ እንደ ፡ ተለወጠ ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ አስታወስኹ ፤ የቀደመውን ፡ ተኣምራትኽን ፡ አስታውሳለኹና ፤

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 12 ፤ በምግባርኽም ፡ ኹሉ ፡ እናገራለኹ ፥ በሥራኽም ፡ እጣወታለኹ ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ መንገድኽ ፡ በመቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ አምላካችን ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 14 ፤ ተኣምራትን ፡ የምታደርግ ፡ አምላክ ፡ አንተ ፡ ነኽ ። ለሕዝብኽ ፡ ኀይልን ፡ አስታወቅኻቸው ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 15 ፤ የያዕቆብንና ፡ የዮሴፍን ፡ ልጆች ፥ ሕዝብኽን ፡ በክንድኽ ፡ አዳንኻቸው ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ ውሃዎች ፡ አዩኽ ፥ ውሃዎችም ፡ አይተውኽ ፡ ፈሩ ፤ ጥልቆች ፡ ተነዋወጡ ፥ ውሃዎችም ፡ ጮኹ ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 17 ፤ ደመኖች ፡ ድምፅን ፡ ሰጡ ፥ ፍላጻዎችኽም ፡ ወጡ ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 18 ፤ የነጐድጓድኽ ፡ ድምፅ ፡ በዐውሎ ፡ ነበረ ፤ መብረቆች ፡ ለዓለም ፡ አበሩ ፤ ምድር ፡ ተናወጠች ፡ ተንቀጠቀጠችም ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 19 ፤ መንገድኽ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፥ ፍለጋኽም ፡ በብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ነው ፥ አረማመድኽም ፡ አልታወቀም ።

መዝ. ፡ 76 ፡ (77) ፡ 20 ፤ በሙሴና ፡ በአሮን ፡ እጅ ፡ ሕዝብኽን ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ መራኻቸው ።

_____መዝሙር ፡ 77 ፡ (78) ። _____

የአሣፍ ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 1 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ሕጌን ፡ አድምጡ ፤ ጐሯችኹንም ፡ ወደአፌ ፡ ቃል ፡ አዘንብሉ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 2 ፤ አፌን ፡ በምሳሌ ፡ እከፍታለኹ ፤ ከቀድሞ ፡ ገሮም ፥ ያለውንም ፡ ተምሳሊት ፡

እናገራለኹ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 3 ፤ የሰማነውንና ፡ ያወቅነውን ፥ አባቶቻችንም ፡ የነገሩንን ፥ ለሚመጣ ፡ ትውልድ ፡ ከልጆቻቸው ፡ አልሰወሩም ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋናና ፡ ኀይሉን ፡ ያደረገውንም ፡ ተኣምራት ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 5 ፤ ለልጆቻቸው ፡ ያስታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ያዘዘውን ፡ ምስክር ፡ በያዕቆብ ፡ አቆመ ፥ በእስራኤልም ፡ ሕግን ፡ ሠራ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 6 ፤ የሚመጣ ፥ ትውልድ ፡ የሚወለዱም ፡ ልጆች ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ ተነሥተው ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይነግራሉ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 7 ፤ ተስፋቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንዲያደርጉ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ እንዳይረሱ ፥ ትእዛዙንም ፡ እንዲጠብቁ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 8 ፤ እንደ ፡ አባቶቻቸው ፡ እንዳይኾኑ ፡ ጠማማና ፡ የምታስመርር ፡ ትውልድ ፥ ልቧን ፡ ያላቀናች ፡ ትውልድ ፥ ነፍሷ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያልታመነች ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 9 ፤ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ለሰልፍ ፡ ታጥቀው ፡ ቀስትንም ፡ ገትረው ፡ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ኪዳን ፡ አልጠበቁም ፥ በሕጉም ፡ ለመመላለስ ፡ እንቢ ፡ አሉ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 11 ፤ መልካም ፡ ሥራውንና ፡ ያሳያቸውን ፡ ተኣምራቱን ፡ ረሱ ፥

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 12 ፤ በግብጽ ፡ አገርና ፡ በጣኔዎስ ፡ በረሓ ፡ በአባቶቻቸው ፡ ፊት ፡ የሠራውን ፡ ተኣምራት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 13 ፤ ባሕርን ፡ ከፍሎ ፡ አሳለፋቸው ፤ ውሃዎችን ፡ እንደ ፡ ክምር ፡ አቆመ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 14 ፤ ቀን ፡ በደመና ፡ መራቸው ፥ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ ብርሃን ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 15 ፤ አለቱን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሠነጠቀ ፤ ከጥልቅ ፡ እንደሚገኝ ፡ ያኽል ፡ በብዙ ፡ አጠጣቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 16 ፤ ውሃን ፡ ከጭንጫ ፡ አወጣ ፥ ውሃንም ፡ እንደ ፡ ወንዞች ፡ አፈሰሰ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይበድሉት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ደገሙ ፥ ልዑልንም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አስቈጡት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 18 ፤ ለነፍሳቸው ፡ መብልን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔርን ፡ በልባቸው ፡ ፈተኑት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ዐሙት ፦ እግዚአብሔር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ማእዱን ፡ ያሰናዳ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልን ፧

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 20 ፤ አለቱን ፡ መታ ፤ ውሃዎችም ፡ ወጡ ፥ ወንዞችም ፡ ጐረፉ ፤ እንጀራን ፡ መስጠትስ ፡ ይችላልን ፧ ለሕዝቡስ ፡ ማእዱን ፡ ያዘጋጃልን ፧

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ተቈጣ ፤ በያዕቆብም ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ነደደ ፥ መዓትም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መጣ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 22 ፤ በእግዚአብሔር ፡ አላመኑምና ፥ በመድኀኒቱም ፡ አልተማመኑምና ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 23 ፤ ደመናውንም ፡ ከላይ ፡ አዘዘ ፥ የሰማይንም ፡ ደጆች ፡ ከፈተ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 24 ፤ ይበሉም ፡ ዘንድ ፡ መናን ፡ አዘነበላቸው ፥ የሰማይንም ፡ እንጀራ ፡ ሰጣቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 25 ፤ የመላክትንም ፡ እንጀራ ፡ ሰው ፡ በላ ፡ ሥንቅንም ፡ እስከ ተርፋቸው ፡ ላከላቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 26 ፤ ከሰማይ ፡ የምሥራቅን ፡ ነፋስ ፡ አስነሣ ፥ በኀይሉም ፡ የደቡብን ፡ ነፋስ ፡ አመጣ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 27 ፤ ሥጋን ፡ እንደ ፡ ዐፈር ፥ የሚበሩትንም ፡ ወፎች ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ አዘነበላቸው ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 28 ፤ በሰፈራቸው ፡ መካከል ፥ በድንኳናቸውም ፡ ዙሪያ ፡ ወደቀ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 29 ፤ በሉ ፡ እጅግም ፡ ጠገቡ ፤ ምኞታቸውንም ፡ ሰጣቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 30 ፤ ከወደዱትም ፡ አላሳጣቸውም ፤ መብላቸውም ፡ ገና ፡ በአፋቸው ፡ ሳለ ፥

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 31 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በላያቸው ፡ መጣ ፥ ከነርሱም ፡ ከፍ ፡ ያሉትን ፡ ገደለ ፥ የእስራኤልንም ፡ ምርጦች ፡ አሰናከለ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 32 ፤ ከዚህም ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በደሉ ፥ ተኣምራቱንም ፡ አላመኑም ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 33 ፤ ቀኖቻቸውም ፡ በከንቱ ፡ ዐለቁ ፥ ዓመቶቻቸውም ፡ በችኰላ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 34 ፤ በገደላቸውም ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ፈለጉት ፤ ተመለሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ገሠገሡ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 35 ፤ ረዳታቸውም ፡ እግዚአብሔር ፥ መድኀኒታቸውም ፡ ልዑል ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐሰቡ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 36 ፤ በአፋቸው ፡ ብቻ ፡ ወደዱት ፤ በአንደበታቸውም ፡ ዋሹበት ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 37 ፤ ልባቸውም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አልቀናም ፥ በቃል ፡ ኪዳኑም ፡ አልተማመኑትም ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 38 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መሓሪ ፡ ነው ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ አላቸው ፥ አላጠፋቸውምም ፤ ቍጣውንም ፡ መመለስ ፡ አበዛ ፥ መዓቱንም ፡ ዅሉ ፡ አላቃጠለም ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 39 ፤ ወጥቶ ፡ የማይመለስ ፡ መንፈስ ፥ ሥጋም ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ዐሰበ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 40 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ አስቈጡት ፥ በበረሓም ፡ አሳዘኑት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 41 ፤ ተመለሱ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ፈተኑት ፥ የእስራኤልንም ፡ ቅዱስ ፡ አሳዘኑት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 42 ፤ እነርሱም ፡ እጁን ፡ አላሰቡም ፥ ከጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ያዳነበትን ፡ ቀን ፥

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 43 ፤ በግብጽ ፡ ያደረገውን ፡ ተኣምራቱን ፥ በጣኔዎስም ፡ በረሓ ፡ ያደረገውን ፡ ድንቁን ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 44 ፤ ወንዞቻቸውንም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ለወጠ ፥ ምንጮቻቸውን ፡ ደግሞ ፡ እንዳይጠጡ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 45 ፤ ዝንቦችንም ፡ በላያቸው ፡ ሰደደባቸው ፥ በሏቸውም ፤ በጓጉንቸርም ፡ አጠፋቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 46 ፤ ፍሬያቸውን ፡ ለኵብኵባ ፥ ሥራቸውንም ፡ ለአንበጣ ፡ ሰጠ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 47 ፤ ወይናቸውን ፡ በበረዶ ፥ በለሳቸውንም ፡ በዐመዳይ ፡ አጠፋ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 48 ፤ እንስሳዎቻቸውን ፡ ለበረዶ ፥ ሀብታቸውንም ፡ ለእሳት ፡ ሰጠ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 49 ፤ የመዓቱን ፡ መቅሠፍት ፡ በላያቸው ፡ ሰደደ ፤ መቅሠፍትን ፡ መዓትንም ፡ መከራንም ፡ በክፉዎች ፡ መላእክት ፡ ሰደደ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 50 ፤ ለቀጣው ፡ መንገድን ፡ ጠረገ ፤ ነፍሳቸውንም ፡ ከሞት ፡ አላዳናትም ፥ እንስሳዎቻቸውንም ፡ በሞት ፡ ውስጥ ፡ ዘጋ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 51 ፤ በኵሮቻቸውን ፡ ኹሉ ፡ በግብጽ ፥ የድካማቸውንም ፡ መጠመሪያ ፡ በካም ፡ ድንኳኖች ፡ ገደለ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 52 ፤ ሕዝቡን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ አሰማራቸው ፥ እንደ ፡ መንጋም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መራቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 53 ፤ በተስፋም ፡ መራቸው ፡ አልፈሩምም ፥ ጠላቶቻቸውንም ፡ ባሕር ፡ ደፈናቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 54 ፤ ወደመቅደሱም ፡ ተራራ ፡ አገባቸው ፥ ቀኙ ፡ ወደ ፡ ፈጠረችው ፡ ወደዚች ፡ ተራራ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 55 ፤ ከፊታቸውም ፡ አሕዛብን ፡ አባረረ ፥ ርስቱንም ፡ በገመድ ፡ አካፈላቸው ፥ የእስራኤልንም ፡ ወገኖች ፡ በቤታቸው ፡ አኖረ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 56 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈተኑት ፡ አስቈጡትም ፥ ምስክሩንም ፡ አልጠበቁም ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 57 ፤ ተመለሱም ፡ እንደ ፡ አባቶቻቸውም ፡ ከዱ ፤ እንደ ፡ ጠማማ ፡ ቀስትም ፡ ተገለበጡ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 58 ፤ በኰረብታ ፡ መስገጃዎቻቸውም ፡ አስቈጡት ፥ በተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸውም ፡ አስቀኑት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 59 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ተቈጣ ፥ እስራኤልንም ፡ እጅግ ፡ ናቀ ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 60 ፤ የሴሎምን ፡ ማደሪያ ፡ ተዋት ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያደረገባትን ፡ ድንኳኑን ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 61 ፤ ኀይላቸውን ፡ ለምርኮ ፥ ሽልማቱንም ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ሰጠ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 62 ፤ ሕዝቡንም ፡ በጦር ፡ ውስጥ ፡ ዘጋቸው ፥ ርስቱንም ፡ ቸል ፡ አላቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 63 ፤ ጕልማሳዎቻቸውን ፡ እሳት ፡ በላቸው ፥ ቈነጕሾቻቸውም ፡ አላዘኑም ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 64 ፤ ካህናታቸውም ፡ በሰይፍ ፡ ወደቁ ፥ ባልቴቶቻቸውም ፡ አላለቀሱላቸውም ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 65 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእንቅልፍ ፡ እንደሚነቃ ፡ ተነሣ ፥ የወይን ፡ ስካር ፡ እንደ ፡ ተወው ፡ እንደ ፡ ኀያልም ፡ ሰው ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 66 ፤ ጠላቶቹንም ፡ በኋላቸው ፡ መታ ፤ የዘለዓለምን ፡ ኀሣር ፡ ሰጣቸው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 67 ፤ የዮሴፍንም ፡ ድንኳን ፡ ተዋት ፥ የኤፍሬምንም ፡ ወገን ፡ አልመረጠውም ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 68 ፤ የይሁዳን ፡ ወገን ፡ ግን ፡ መረጠ ፥ የወደደውን ፡ የጽዮንን ፡ ተራራ ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 69 ፤ መቅደሱን ፡ እንደ ፡ አርያም ፡ ሠራ ፥ ለዘለዓለምም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ መሠረታት ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 70 ፤ ዳዊትንም ፡ ባሪያውን ፡ መረጠው ፥ ከበጎቹም ፡ መንጋ ፡ ውስጥ ፡ ወሰደው ፤

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 71 ፤ ከሚያጠቡ ፡ በጎችም ፡ በኋላ ፥ ባሪያውን ፡ ያዕቆብን ፡ ርስቱንም ፡ እስራኤልን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ወሰደው ።

መዝ. ፡ 77 ፡ (78) ፡ 72 ፤ በልቡ ፡ ቅንነት ፡ ጠበቃቸው ፥ በእጁም ፡ ብልኀት ፡ መራቸው ።

መዝሙር ፡ 78 ፡ (79) ።

የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ርስትኽ ፡ ገቡ ፤ የቅድስናኽንም ፡ መቅደስ ፡ አረከሱ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ እንደ ፡ መደብ ፡ አደረጓት ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 2 ፤ የባሪያዎችኽንም ፡ በድኖች ፡ ለሰማይ ፡ ወፎች ፡ መብል ፡ አደረጉ ፥ የጻድቃንኽንም ፡ ሥራ ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፤

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 3 ፤ ደማቸውንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፈሰሱ ፥ የሚቀብራቸውም ፡ ዐጡ ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 4 ፤ ለጎረቤቶቻችንም ፡ ስድብ ፡ ኾን ፥ በዙሪያችንም ፡ ላሉ ፡ ሣቅና ፡ ዘበት ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትቈጣለኽ ፧ ቅንአትኽም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ፧

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 6 ፤ ስምኽን ፡ በማይጠሩ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ በማያውቁኽም ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ መዓትኽን ፡ አፍስ ፤

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 7 ፤ ያዕቆብን ፡ በልተውታልና ፥ ስፍራውንም ፡ ባድማ ፡ አድርገዋልና ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 8 ፤ የቀደመውን ፡ በደላችንን ፡ አታስብብን ፥ ምሕረትኽ ፡ በቶሎ ፡ ታግኘን ፥ እጅግ ፡ ተቸግረናልና ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 9 ፤ አምላካችንና ፡ መድኀኒታችን ፡ ሆይ ፥ ርዳን ፤ ስለስምኽ ፡ ክብር ፥ አቤቱ ፥ ታደገን ፥ ስለ ፡ ስምኽም ፡ ኀጢአታችንን ፡ አስተሰርይልን ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 10 ፤ አሕዛብ ፥ አምላካቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ እንዳይሉ ፥ የፈሰሰውን ፡ የባሪያዎችኽን ፡ ደም ፡ በቀል ፡ በዐይኖቻችን ፡ ፊት ፡ አሕዛብ ፡ ያወቁ ፤

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 11 ፤ የእስረኞች ፡ ጩኸት ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ይግባ ፤ እንደ ፡ ክንድኽም ፡ ታላቅነት ፡ ሊገደሉ ፡ የተፈረደባቸውን ፡ አድን ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ የተዘባበቱብኽን ፡ መዘባበታቸውን ፡ ለጎረቤቶቻችን ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ በብብታቸው ፡ ክፈላቸው ።

መዝ. ፡ 78 ፡ (79) ፡ 13 ፤ እኛ ፡ ሕዝብኽ ፡ ግን ፡ የማሰማሪያኽም ፡ በጎች ፡ ለዘለዓለም ፡ እናመሰግንኻለን ፤ ለልጅ ፡ ልጅም ፡ ምስጋናኽን ፡ እንናገራለን ።

መዝሙር ፡ 79 ፡ (80) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በመለከቶች ፤ ስለ ፡ አሶራውያን ፤ የአሣፍ ፡ የምስክር ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 1 ፤ የዮሴፍን ፡ እንደ ፡ መንጋ ፡ የምትመራ ፡ የእስራኤል ፡ ጠባቂ ፡ ሆይ ፡ አድምጥ ፤ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ ተገለጥ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 2 ፤ በኤፍሬምና ፡ በብንያም ፡ በምናሴም ፤ ኀይልኽን ፡ አንሣ ፡ እኛንም ፡ ለማዳን ፡ ና ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፡ መልሰን ፡ ፊትኽንም ፡ አብራ ፡ እኛም ፡ እንድናለን ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 4 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡ በባሪያኽ ፡ ጸሎት ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትቈጣለኽ ፧

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 5 ፤ የእንባ ፡ እንጀራን ፡ ትመግበናለኽ ፡ እንባም ፡ በስፍር ፡ ታጠጣናለኽ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 6 ፤ ለጎረቤቶቻችን ፡ ክርክር ፡ አደረግኸን ፡ ጠላቶቻችንም ፡ በላያችን ፡ ተሣለቁብን ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 7 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡ መልሰን ፡ ፊትኽንም ፡ አብራ ፡ እኛም ፡ እንድናለን ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 8 ፤ ከግብጽ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ አመጣኽ ፤ አሕዛብን ፡ አባረርኽ ፡ ርሷንም ፡ ተከልኽ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 9 ፤ በፊቷም ፡ ስፍራን ፡ አዘጋጀኽ ፡ ሥሮቿንም ፡ ተከልኽ ፡ ምድርንም ፡ ሞላኽ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 10 ፤ ጥላዋ ፡ ተራራዎችን ፡ ከደነ ፡ ጫፎቿም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ዝግባ ፡ ኾኑ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 11 ፤ ቅርንጫፎቿንም ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ቡቃያዋንም ፡ እስከ ፡ ወንዙ ፡ ዘረጋኽ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 12 ፤ ዐጥሯን ፡ ለምን ፡ አፈረስኽ ፧ መንገድ ፡ ዐላፊም ፡ ኹሉ ፡ ይቀጥፋታል ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 13 ፤ የዱር ፡ ዕሪያ ፡ አረከሳት ፡ የአገር ፡ አውሬም ፡ ተሰማራባት ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 14 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ እንግዲህ ፡ ተመለስ ፤ ከሰማይ ፡ ተመልከት ፡ እይም ፡ ይህችንም ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ ጐብኝ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 15 ፤ በሰው ፡ ልጅ ፡ ለአንተ ፡ ያጸናኸውን ፡ ቀኝኽ ፡ የተከላትን ፡ አንሣ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 16 ፤ በእሳት ፡ ተቃጥላለች ፡ ተነቅላማለች ፤ ከፊትኽ ፡ ተግሣጽም ፡ የተነሣ ፡ ይጠፋሉ ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 17 ፤ ለአንተ ፡ ባጸናኸው ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ በቀኝኽ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እጅኽ ፡ ትኹን ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 18 ፤ ከአንተም ፡ አንራቅ ፤ አድነን ፡ ስምኽንም ፡ እንጠራለን ።

መዝ. ፡ 79 ፡ (80) ፡ 19 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፡ መልሰን ፡ ፊትኽንም ፡ አብራ ፡ እኛም ፡ እንድናለን ።

መዝሙር ፡ 80 ፡ (81) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በዋሽንት ፤ የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 1 ፤ በረድኤታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ለያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ እልል ፡ በሉ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 2 ፤ ዝማሬውን ፡ አንሡ ፡ ከበሮንም ፡ ስጡ ፥ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ በገና ፡ ከመሰንቆ ፡ ጋራ ፤

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 3 ፤ በመባቻ ፡ ቀን ፡ በከፍተኛው ፡ በዓላችን ፡ ቀን ፡ መለከትን ፡ ንፉ ፤

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 4 ፤ ለእስራኤል ፡ ሥርዐቱ ፡ ነውና ፥ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ፍርድ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 5 ፤ ከግብጽ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ለዮሴፍ ፡ ምስክር ፡ አቆመው ። ያላወቅኹትን ፡ ቋንቋ ፡ ሰማኹ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 6 ፤ ጫንቃውን ፡ ከሸክም ፥ እጆቹንም ፡ በቅርጫት ፡ ከመገዛት ፡ አራቅኹ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 7 ፤ በመከራኽ ፡ ጊዜ ፡ ጠራኸኝ ፡ አዳንኹኽም ፥ በተሰወረ ፡ ዐውሎም ፡ መለስኹልኽ ፥ በክርክር ፡ ውሃ ፡ ዘንድም ፡ ፈተንኹኽ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 8 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ስማኝ ፡ እነግርኻለኹም ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እመሰክርልኻለኹ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 9 ፤ አንተስ ፡ ብትሰማኝ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አይኾንልኽም ፥ ለሌላ ፡ አምላክም ፡ አትሰግድም ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 10 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣኹኽ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ነኝና ፤ አፍኽን ፡ አስፋ ፡ እሞላዋለኹም ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 11 ፤ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ ቃሌን ፡ አልሰሙኝም ፥ እስራኤልም ፡ አላዳመጠኝም ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 12 ፤ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ሥራ ፡ ተውኋቸው ፥ በልባቸውም ፡ ዐሳብ ፡ ኼዱ ።

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 13 ፤ ሕዝቤስ ፡ ሰምቶኝ ፡ ቢኾን ፥ እስራኤልም ፡ በመንገዴ ፡ ኼደው ፡ ቢኾን ፤

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 14 ፤ ጠላቶቻቸውን ፡ ፈጥኜ ፡ ባዋረድኋቸው ፡ ነበር ፥ በሚያስጨንቋቸውም ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ በጣልኹ ፡ ነበር ፤

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጠላቶችም ፡ በተገዙለት ፡ ነበር ፥ ዘመናቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ በኾነ ፡ ነበር ፤

መዝ. ፡ 80 ፡ (81) ፡ 16 ፤ ከስንዴም ፡ ስብ ፡ ባበላቸው ፡ ነበር ፥ ከአለቱም ፡ ማር ፡ ባጠገባቸው ፡ ነበር ።

_____መዝሙር ፡ 81 ፡ (82) ። _____

የአሣፍ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአማልክት ፡ ማኅበር ፡ ቆመ ፥ በአማልክትም ፡ መካከል ፡ ይፈርዳል ።

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 2 ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ሐሰትን ፡ ትፈርዳላችኹ ፧ እስከ ፡ መቼ ፡ ለኀጢአተኞች ፡ ፊት ፡ ታደላላችኹ ፧

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 3 ፤ ለድኻዎችና ፡ ለድኻ ፡ አደጎች ፡ ፍረዱ ፤ ለችግረኛውና ፡ ለምስኪኑ ፡ ጽድቅ ፡ አድርጉ ፤

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 4 ፤ ብቸኛውንና ፡ ችግረኛውን ፡ አድኑ ፤ ከኀጢአተኞችም ፡ እጅ ፡ አስጥሏቸው ።

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 5 ፤ አያውቁም ፥ አያስተውሉም ፤ በጨለማ ፡ ውስጥ ፡ ይመላለሳሉ ፤ የምድር ፡ መሠረቶች ፡ ሹሉ ፡ ተናወጡ ።

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ግን ፦ አማልክት ፡ ናችኹ ፥ ሹላችኹም ፡ የልዑል ፡ ልጆች ፡ ናችኹ ፤

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ሰው ፡ ትሞታላችኹ ፥ ከአለቃዎችም ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ትወድቃላችኹ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 81 ፡ (82) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ተነሥ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፥ አንተ ፡ አሕዛብን ፡ ሹሉ ፡ ትወርሳለኽና ።

መዝሙር ፡ 82 ፡ (83) ።

የአሣፍ ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አቤቱ ፥ ዝም ፡ አትበል ፥ ቸልም ፡ አትበል ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 2 ፤ እንሆ ፥ ጠላቶችኽ ፡ ጮኽዋልና ፥ የሚጠሉኽም ፡ ራሳቸውን ፡ አንሥተዋልና ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 3 ፤ ሕዝብኽን ፡ በምክር ፡ ሸነገሏቸው ፥ በቅዱሳንኽም ፡ ላይ ፡ ተማከሩ ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 4 ፤ ኑ ፡ ከሕዝብ ፡ እናጥፋቸው ፥ ደግሞም ፡ የእስራኤል ፡ ስም ፡ አይታሰብ ፡ አሉ ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 5 ፤ አንድ ፡ ኾነው ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ተማከሩ ፤ ባንተ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረጉ ፤

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 6 ፤ የኤዶማውያን ፡ ድንኳኖች ፡ እስማኤላውያንም ፥ ሞዐብም ፡ አጋራውያንም ፥

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 7 ፤ ጌባል ፡ ዐሞንም ፡ ዐማሌቅም ፥ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ከጢሮስ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፤

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 8 ፤ አሶርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተባበረ ፥ ለሎጥ ፡ ልጆችም ፡ ረዳት ፡ ኾኑቸው ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 9 ፤ እንደ ፡ ምድያምና ፡ እንደ ፡ ሢሣራ ፥ በቂሶንም ፡ ወንዝ ፡ እንደ ፡ ኢያቢስ ፡ አድርግባቸው ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 10 ፤ በዐይንዶር ፡ ጠፉ ፥ እንደምድርም ፡ ጕድፍ ፡ ኾኑ ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 11 ፤ አለቃዎቻቸውን ፡ እንደ ፡ ሔሬብና ፡ እንደ ፡ ዜብ ፥ ታላላቆቻቸውንም ፡ እንደ ፡ ዛብሄልና ፡ እንደ ፡ ስልማና ፡ አድርጋቸው ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መሠዊያ ፡ እንወርሳለን ፡ የሚሉትን ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 13 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ትቢያ ፡ በነፋስ ፡ ፊትም ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ አድርጋቸው ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 14 ፤ እሳት ፡ ዱርን ፡ እንደሚያቃጥል ፥ ነበልባልም ፡ ተራራዎች ፡ እንደሚያነድ ፥

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 15 ፤ እንዲሁ ፡ በቍጣኽ ፡ አሳዳቸው ፥ በመቅሠፍትኽም ፡ አስደንግጣቸው ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 16 ፤ ፊታቸውን ፡ ዕፍረት ፡ ሙላው ፥ አቤቱ ፥ ስምኽንም ፡ ይፈልጋሉ ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 17 ፤ ይፈሩ ፡ ለዘለዓለሙም ፡ ይታወኩ ፤ ይጐስቀሉ ፡ ይጥፉም ።

መዝ. ፡ 82 ፡ (83) ፡ 18 ፤ ስምኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይም ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ ልዑል ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ይወቁ ።

መዝሙር ፡ 83 ፡ (84) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ በዋሽንት ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 1 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ማደሪያዎችኽ ፡ እንደምን ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው! ፡

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 2 ፤ ነፍሴ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አደባባዮች ፡ ትወዳለች ፡ ትናፍቅማለች ፤ ልቤም ፡ ሥጋዬም ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ደስ ፡ ተሠኘ ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 3 ፤ ወፍ ፡ ለርሷ ፡ ቤትን ፡ አገኘች ፥ ዋኖስም ፡ ጫጨቶቿን ፡ የምታኖርበት ፡ ቤት ፡ አገኘች ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ንጉሤም ፡ አምላኬም ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ መሠዊያኽ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 4 ፤ በቤትኽ ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው ፤ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለምም ፡ ያመሰግኑኻል ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ርዳታው ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ የኾነለት ፥ በልቡም ፡ የላይኛውን ፡ መንገድ ፡ የሚያስብ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 6 ፤ በልቅሶ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ በወሰነው ፡ ስፍራ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ በረከትን ፡ ይሰጣልና ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 7 ፤ ከኀይል ፡ ወደ ፡ ኀይል ፡ ይኼዳሉ ፤ የአማልክት ፡ አምላክ ፡ በጽዮን ፡ ይታያል ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 8 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ ስማ ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ አድምጥ ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ መታመናችንን ፡ እይልን ፥ ወደ ፡ ቀባኸውም ፡ ፊት ፡ ተመልከት ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 10 ፤ ከአእላፍ ፡ ይልቅ ፡ በአደባባዮችኽ ፡ አንዲት ፡ ቀን ፡ ትሻላለች ፤ በኃጥኣን ፡ ድንኳኖች ፡ ከመቀመጥ ፡ ይልቅ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እጣል ፡ ዘንድ ፡ መረጥኹ ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ምሕረትንና ፡ እውነትን ፡ ስለ ፡ ወደደ ፥ ሞገስንና ፡ ክብርን ፡ ይሰጣል ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅንነት ፡ የሚኼዱትን ፡ ከመልካም ፡ ነገር ፡ አያሳጣቸውም ።

መዝ. ፡ 83 ፡ (84) ፡ 12 ፤ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ የታመነ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 84 ፡ (85) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የቆሬ ፡ ልጆች ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ለምድርኽ ፡ ሞገስን ፡ አደረግኽ ፥ የያዕቆብንም ፡ ምርኮ ፡ መለስኽ ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 2 ፤ የሕዝብኽን ፡ ኀጢአት ፡ አስቀረኽ ፥ አበሳቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ከደንኽ ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 3 ፤ መዓትኽንም ፡ ኹሉ ፡ አስወገድኽ ፤ ከቀሣጣኽ ፡ ፡ መቅሠፍት ፡ ተመለስኽ ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 4 ፤ የመድኀኒታችን ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ መልሰን ፥ ቊጣኽንም ፡ ከእኛ ፡ መልስ ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 5 ፤ በእውኑ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትቈጣናለኽን ፧ ቊጣኽንስ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ታስረዝማለኽን ፧

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 6 ፤ አቤቱ ፥ ትመለሳለኽ ፡ ታድነንማለኽ ፤ ሕዝቡም ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽን ፡ አሳየን ፥ አቤቱ ፥ መድኀኒትኽንም ፡ ስጠን ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ የሚናገረውን ፡ እሰማለኹ ፤ ሰላምን ፡ ለሕዝቡና ፡ ለቅዱሳኑ ፡ ልባቸውንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለሚመልሱ ፡ ይናገራልና ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክብር ፡ በምድራችን ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡ ማዳኑ ፡ ለሚፈሩት ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 10 ፤ ምሕረትና ፡ እውነት ፡ ተገናኙ ፤ ጽድቅና ፡ ሰላም ፡ ተስማሙ ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 11 ፤ እውነት ፡ ከምድር ፡ በቀለች ፥ ጽድቅም ፡ ከሰማይ ፡ ተመለከተች ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ይሰጣል ፥ ምድራችንም ፡ ፍሬዋን ፡ ትሰጣለች ።

መዝ. ፡ 84 ፡ (85) ፡ 13 ፤ ጽድቅ ፡ በፊቱ ፡ ይኼዳል ፥ ፍለጋውንም ፡ በመንገድ ፡ ውስጥ ፡ ያኖራል ።

_____መዝሙር ፡ 85 ፡ (86) ። _____

የዳዊት ፡ ጸሎት ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ገሮኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብል ፡ አድምጠኝም ፥ ችግረኛና ፡ ምስኪን ፡ ነኝና ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 2 ፤ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ ነፍሴን ፡ ጠብቅ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አንተን ፡ የታመነውን ፡ ባሪያኽን ፡ አድነው ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ወዳንተ ፡ እጮኻለኹና ፡ ማረኝ ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 4 ፤ የባሪያኽን ፡ ነፍስ ፡ ደስ ፡ አሠኛት ፥ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ ወዳንተ ፡ አነሣለኹና ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነኽና ፥ ምሕረትኽም ፡ ለሚጠሩኽ ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 6 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ አድምጥ ፥ የልመናዬንም ፡ ድምፅ ፡ ስማ ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 7 ፤ ትመልስልኛለኽና ፡ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ወዳንተ ፡ እጠራለኹ ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ከአማልክት ፡ የሚመስልኽ ፡ የለም ፥ እንደ ፡ ሥራኽም ፡ ያለ ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 9 ፤ ያደረግኻቸው ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይመጣሉ ፥ አቤቱ ፥ በፊትኽም ፡ ይሰግዳሉ ፥ ስምኽንም ፡ ያከብራሉ ፤

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ ድንቅ ፡ የምታደርግ ፡ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ነኽና ፥ አንተም ፡ ብቻኽን ፡ ታላቅ ፡ አምላክ ፡ ነኽና ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ መንገድኽን ፡ ምራኝ ፥ በእውነትኽም ፡ እኼዳለኹ ፤ ስምኽን ፡ ለመፍራት ፡ ልቤ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በልቤ ፡ ኹሉ ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ስምኽን ፡ አከብራለኹ ፤

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 13 ፤ ምሕረትኽ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ናትና ፥ ነፍሴንም ፡ ከታችኛዪቱ ፡ ሲኦል ፡ አድነኻታልና ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 14 ፤ አቤቱ ፥ ዐመፀኞች ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተነሥተዋል ፥ የክፉዎችንም ፡ ማኅበር ፡ ነፍሴን ፡ ፈለጓት ፤ በፊታቸውም ፡ አላደረጉኽም ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 15 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ መሐሪና ፡ ርኅሩኅ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ መዓትኽ ፡ የራቀ ፡ ምሕረትኽም ፡ እውነትኽም ፡ የበዛ ፤

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 16 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከት ፡ ማረኝም ፤ ለባሪያኽ ፡ ኀይልኽን ፡ ስጥ ፥ የሴት ፡ ባሪያኽንም ፡ ልጅ ፡ አድን ።

መዝ. ፡ 85 ፡ (86) ፡ 17 ፤ ምልክትንም ፡ ለመልካም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አድርግ ፤ የሚጠሉኝ ፡ ይዩ ፡ ይፈሩም ፥ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ረድተኸኛልና ፥ አጽንተኸኛልምና ።

መዝሙር ፡ 86 ፡ (87) ።

የቆሬ ፡ ልጆች ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 1 ፤ መሠረቶቹ ፡ በተቀደሱ ፡ ተራራዎች ፡ ናቸው ፤

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 2 ፤ ከያዕቆብ ፡ ድንኳኖች ፡ ይልቅ ፥ እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ደጆች ፡ ይወዳቸዋል ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፥ ባንቺ ፡ የተከበረ ፡ ነገር ፡ ይባላል ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 4 ፤ የሚያውቁኝን ፡ ረዓብንና ፡ ባቢሎንን ፡ ዐስባቸዋለኹ ፤ እንሆ ፥ ፍልስጥኤማውያን ፡ ጢሮስም ፡ የኢትዮጵያም ፡ ሕዝብ ፥ እነዚህ ፡ በዚያ ፡ ተወለዱ ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 5 ፤ ሰው ፡ እናታችን ፡ ጽዮን ፡ ይላል ፥ በውስጧም ፡ ሰው ፡ ተወለደ ፤ ርሱ ፡ ራሱም ፡ ልዑል ፡ መሠረታት ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፥ በውስጧም ፡ ለተወለዱት ፡ አለቃዎቿ ፡ በመጽሐፍ ፡ ይነግራቸዋል ።

መዝ. ፡ 86 ፡ (87) ፡ 7 ፤ ባንቺ ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፡ ይነግራቸዋል ።

መዝሙር ፡ 87 ፡ (88) ።

የቆሬ ፡ ልጆች ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ። ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ በማኸላት ፡ ለመዘመር ፤ የይዝራኤላዊው ፡ የኤማን ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ የመድኀኒቴ ፡ አምላክ ፥ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ በፊትኽ ፡ ጮኽኹ ፤

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 2 ፤ ጸሎቴ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ትግባ ፥ ጕሮሮኽንም ፡ ወደ ፡ ጩኸቴ ፡ አዘንብል ፤

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 3 ፤ ነፍሴ ፡ መከራን ፡ ጠግባለችና ፥ ሕይወቴም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ቀርባለችና ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ተቈጠርኹ ፥ ረዳትም ፡ እንደሌለው ፡ ሰው ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 5 ፤ ለዘለዓለም ፡ እንደማታስባቸው ፥ እንደ ፡ ተገደሉና ፡ በመቃብር ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተጣሉ ፥ በሙታን ፡ ውስጥ ፡ እንዳሉ ፡ የተጣልኹ ፡ ኾንኹ ፤ እነርሱም ፡ ከእጅኽ ፡ ተለዩ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 6 ፤ በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፥ በታችኛው ፡ ጕድጓድ ፡ አስቀመጥኸኝ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 7 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ቀጣኽ ፡ ጸና ፥ መቅሠፍትኽን ፡ ኹሉ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አመጣኽ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 8 ፤ የሚያውቁኝን ፡ ከእኔ ፡ አራቅኽ ፤ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ አደረግኸኝ ፤ ያዙኝ ፥ መውጫም ፡ የለኝም ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 9 ፤ ዐይኖቼም ፡ በመከራ ፡ ፈዘዙ ፤ አቤቱ ፥ ኹልጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፥ እጆቼንም ፡ ወዳንተ ፡ ዘረጋኹ ፥

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 10 ፤ በእውኑ ፡ ለሙታን ፡ ተአምራት ፡ ታደርጋለኽን ፧ የሞቱትስ ፡ ተነሥተው ፡ ያመሰግኑኻልን ፧

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 11 ፤ በመቃብርስ ፡ ውስጥ ፡ ቸርነትኽን ፥ እውነትኽንስ ፡ በጥፋት ፡ ስፍራ ፡ ይናገራሉን ፧

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 12 ፤ ተአምራትኽ ፡ በጨለማ ፥ ጽድቅኽንም ፡ በመርሳት ፡ ምድር ፡ ትታወቃለችን ፧

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፤ በጧት ፡ ጸሎቴ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ትደርሳለች ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 14 ፤ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ ለምን ፡ ትጥላለኽ ፧ ፊትኽንስ ፡ ከእኔ ፡ ለምን ፡ ትሰውራለኽ ፧

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ከታናሽነቴ ፡ ችግረኛ ፡ ለሞትም ፡ የቀረብኹ ፡ ነኝ ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ካልኹ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተዋረድኹ ፡ ተናቅኹም ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 16 ፤ መቅሠፍትኽ ፡ በላዬ ፡ ዐለፈ ፥ ግርማኽም ፡ አስደነገጠኝ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 17 ፤ ኹልጊዜ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ከበቡኝ ፥ በአንድነትም ፡ ያዙኝ ።

መዝ. ፡ 87 ፡ (88) ፡ 18 ፤ ወዳጄንና ፡ ባልንጀራዬን ፡ ዘመዶቼንም ፡ ከመከራ ፡ የተነሣ ፡ ከእኔ ፡ አራቅኽ ።

_____መዝሙር ፡ 88 ፡ (89) ። _____

የይዝራኤላዊው ፡ የኤታን ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽን ፡ ለዘለዓለም ፡ እዘምራለኹ ፥ እውነትኽንም ፡ በአፌ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እናገራለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 2 ፤ እንዲህ ፡ ብለኻልና ። ምሕረት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይመሠረታል ፥ እውነትኽም ፡ በሰማይ ፡ ይጸናል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 3 ፤ ከመረጥኹት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አደረግኹ ፥ ለባሪያዬም ፡ ለዳዊት ፡ ማልኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 4 ፤ ዘርኽን ፡ ለዘለዓለም ፡ አዘጋጃለኹ ፥ ዙፋንኽንም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ እመሠርታለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ሰማያት ፡ ተኣምራትኽን ፡ እውነትኽንም ፡ ደግሞ ፡ በቅዱሳን ፡ ማኅበር ፡ ያመሰግናሉ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በሰማይ ፡ የሚተካከለው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ከአማልክትስ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማን ፡ ይመስለዋል ፧

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 7 ፤ በቅዱሳን ፡ ምክር ፡ እግዚአብሔር ፡ ክቡር ፡ ነው ፤ በዙሪያው ፡ ባሉት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅና ፡ ግሩም ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ብርቱ ፡ ነኽ ፥ እውነትኽም ፡ ይከብ፡ኻል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 9 ፤ የባሕርን ፡ ኀይል ፡ አንተ ፡ ትገዛለኽ ፥ የሞገዱንም ፡ መናወጥ ፡ አንተ ፡ ዝም ፡ ታሠኘዋለኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 10 ፤ አንተ ፡ ረዓብን ፡ እንደ ፡ ተገደለ ፡ አዋረድኸው ፥ በኀይልኽም ፡ ክንድ ፡ ጠላቶችኽን ፡ በተንኻቸው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 11 ፤ ሰማያት ፡ የአንተ ፡ ናቸው ፥ ምድርም ፡ የአንተ ፡ ናት ፤ ዓለምንና ፡ ሞላውም ፡ አንተ ፡ መሠረትኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 12 ፤ ሰሜንና ፡ ደቡብን ፡ አንተ ፡ ፈጠርኽ ፤ ታቦርና ፡ አርሞንዔም ፡ በስምኽ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 13 ፤ ክንድኽ ፡ ከኀይልኽ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ እጅኽ ፡ በረታች ፡ ቀኝኽም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 14 ፤ የዙፋንኽ ፡ መሠረት ፡ ጽድቅና ፡ ፍርድ ፡ ነው ፤ ምሕረትና ፡ እውነት ፡ በፊትኽ ፡ ይኼዳሉ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 15 ፤ እልልታ ፡ የሚያውቅ ፡ ሕዝብ ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ አቤቱ ፥ በፊትኽ ፡ ብርሃን ፡ ይኼዳሉ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 16 ፤ በስምኽ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ በጽድቅኽም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ፤

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 17 ፤ የኀይላቸው ፡ ትምክሕት ፡ አንተ ፡ ነኽና ፥ በሞገስኽም ፡ ቀንዳችን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 18 ፤ ረድኤታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከንጉሣችንም ፡ ከእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 19 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለልጆችኽ ፡ በራእይ ፡ ተናገርኽ ፡ እንዲህም ፡ አልኽ ፦ ረድኤቴን ፡ በኀይል ፡ ላይ ፡ አኖርኹ ፤ ከሕዝቤ ፡ የተመረጠውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 20 ፤ ባሪያዬን ፡ ዳዊትን ፡ አገኘኹት ፥ ቅዱስ ፡ ዘይትም ፡ ቀባኹት ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 21 ፤ እጄም ፡ ትረዳዋለች ፥ ክንዴም ፡ ታጸናዋለች ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 22 ፤ ጠላት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አይጠቀምም ፥ የዐመፃ ፡ ልጅም ፡ መከራ ፡ አይጨምርበትም ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 23 ፤ ጠላቶቹን ፡ ከፊቱ ፡ አጠፋለኹ ፥ የሚጠሉትንም ፡ አዋርዳቸዋለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 24 ፤ እውነቴና ፡ ምሕረቴም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ፥ በስሜም ፡ ቀንዱ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 25 ፤ እጁን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ቀኙንም ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 26 ፤ ርሱ ፦ አባቴ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፥ አምላኬ ፡ የመድኀኒቴም ፡ መጠጊያ ፡ ይላል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 27 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በኵሬ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ከምድር ፡ ነገሥታትም ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 28 ፤ ለዘለዓለምም ፡ ምሕረቴን ፡ ለርሱ ፡ እጠብቃለኹ ፥ ኪዳኔም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 29 ፤ ዘሩንም ፡ ለዓለምና ፡ ለዘለዓለም ፥ ዙፋኑንም ፡ እንደሰማይ ፡ ዘመን ፡ አደርጋለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 30 ፤ ልጆቹ ፡ ግን ፡ ሕጌን ፡ ቢተዉ ፥ በፍርዴም ፡ ባይኼዱ ፤

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 31 ፤ ሥርዐቴንም ፡ ቢያረክሱ ፥ ትእዛዜንም ፡ ባይጠብቁ ፤

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 32 ፤ ኀጢአታቸውን ፡ በበትር ፥ በደላቸውንም ፡ በመቅሠፍት ፡ እጐበኛታለኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 33 ፤ ምሕረቴን ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ አላርቅም ፥ በእውነቴም ፡ አልበድልም ፤

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 34 ፤ ኪዳኔንም ፡ አላረክስም ፥ ከከንፈሬም ፡ የወጣውን ፡ አልለውጥም ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 35 ፤ ዳዊትን ፡ እንዳልዋሸው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቅዱስነቴ ፡ ማልኹ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 36 ፤ ዘሩ ፡ ለዘለዓለም ፥ ዙፋኑም ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 37 ፤ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ ይጸናል ፤ ምስክርነቱ ፡ በሰማይ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 38 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ናቅኸው ፡ ጣልኸውም ፥ የቀባኸውንም ፡ ጣልኸው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 39 ፤ የባሪያኽንም ፡ ኪዳን ፡ አፈረስኽ ፥ መቅደሱንም ፡ በምድር ፡ አረከስኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 40 ፤ ቅጥሩን ፡ ኾሉ ፡ ጣልኽ ፥ ዐምባዎቹንም ፡ አጠፋኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 41 ፤ መንገድ ፡ ዐላፊም ፡ ኾሉ ፡ ተናጠቀው ፥ ለጎረቤቶቹም ፡ ስድብ ፡ ኾነ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 42 ፤ የጠላቶቹንም ፡ ቀኝ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረግኽ ፥ ጠላቶቹንም ፡ ኾሉ ፡ ደስ ፡ አሠኘኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 43 ፤ የሰይፉንም ፡ ረድኤት ፡ መለስኽ ፥ በሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ አልደገፍኸውም ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 44 ፤ ከንጽሕናውም ፡ ሻርኸው ፥ ዙፋኑንም ፡ በምድር ፡ ጣልኽ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 45 ፤ የዙፋኑንም ፡ ዘመን ፡ አሳነስኽ ፥ በዕፍረትም ፡ ሸፈንኸው ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 46 ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ለዘለዓለም ፡ ፊትኽን ፡ ትመልሳለኽ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ ቍጣኽ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይነዳል ፧

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 47 ፤ ችሎታዬ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐስብ ፤ በእውኑ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ኾሉ ፡ ለከንቱ ፡

ፈጠርኸውን ፡፡

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 48 ፤ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ የሚኖር ፥ ሞትንስ ፡ የማያይ ፡ ማን ፡ ነው ፡፡ ነፍሱንስ ፡ ከሲኦል ፡ እጅ ፡ የሚያድን ፡ ማን ፡ ነው ፡፡

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 49 ፤ ለዳዊት ፡ በእውነት ፡ የማልኽ ፥ አቤቱ ፥ የቀድሞ ፡ ምሕረትኽ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡፡

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 50 ፤ አቤቱ ፥ የባሪያዎችኽን ፡ ስድብ ፥ በብብቴ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ የተቀበልኹትን ፥

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 51 ፤ አቤቱ ፥ ጠላቶችኽን ፡ የሰደቡትን ፡ የቀባኸውን ፡ ዘመን ፡ የሰደቡትን ፡ ዐስብ ።

መዝ. ፡ 88 ፡ (89) ፡ 52 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ይባረክ ። ይኹን ፤ ይኹን ።

_____መዝሙር ፡ 89 ፡ (90) ። _____

የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ የሙሴ ፡ ጸሎት ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ለትውልድ ፡ ኹሉ ፡ መጠጊያ ፡ ኾንኽልን ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 2 ፤ ተራራዎች ፡ ሳይወለዱ ፥ ምድርም ፡ ዓለምም ፡ ሳይሠሩ ፥ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 3 ፤ ሰውን ፡ ወደ ፡ ኀሳር ፡ አትመልስም ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፡ ትላለኽ ፤

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 4 ፤ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ በፊትኽ ፡ እንዳለፈች ፡ እንደ ፡ ትናንት ፡ ቀን ፥ እንደ ፡ ሌሊትም ፡ ትጋት ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 5 ፤ ዘመኖች ፡ የተናቁ ፡ ይኾናሉ ፥ በማለዳም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ያልፋል ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 6 ፤ ማልዶ ፡ ያብባል ፡ ያልፋልም ፥ በሠርክም ፡ ጠውልጎና ፡ ደርቆ ፡ ይወድቃል ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 7 ፤ እኛ ፡ በቍጣኽ ፡ አልቀናልና ፥ በመዓትኽም ፡ ደንግጠናልና ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 8 ፤ የተሰወረውን ፡ ኀጢአታችንን ፡ በፊትኽ ፡ ብርሃን ፥ በደላችንንም ፡ በፊትኽ ፡ አስቀመጥኽ ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 9 ፤ ዘመናችን ፡ ኹሉ ፡ ዐልፏልና ፥ እኛም ፡ በመዓትኽ ፡ አልቀናልና ፤ ዘመኖቻችንም ፡ እንደ ፡ ሸረሪት ፡ ድር ፡ ይኾናሉ ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 10 ፤ የዘመኖቻችንም ፡ ዕድሜ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፥ ቢበረታም ፡ ሰማንያ ፡ ዓመት ፡ ነው ፤ ቢበዛ ፡ ግን ፡ ድካምና ፡ መከራ ፡ ነው ፤ ከእኛ ፡ ቶሎ ፡ ያልፋልና ፥ እኛም ፡ እንገሠጻለንና ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 11 ፤ የቍጣኽን ፡ ጽናት ፡ ማን ፡ ያውቃል ፡፡ ከቍጣኽ ፡ ግርማ ፡ የተነሣ ፡ ዐለቁ ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 12 ፤ በልብ ፡ ጥበብን ፡ እንድንማር ፥ ቀኝኽን ፡ እንዲህ ፡ አስታውቀን ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ ተመለስ ፥ እስከ ፡ መቼስ ፡ ነው ፡፡ ስለ ፡ ባሪያዎችኽም ፡ ተሣገት ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 14 ፤ በማለዳ ፡ ምሕረትኽን ፡ እንጠግባለን ፤ በዘመናችን ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ሐሤትም ፡ እናደርጋለን ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 15 ፤ መከራ ፡ ባሳየኸን ፡ ዘመን ፡ ፈንታ ፡ ክፉም ፡ ባየንባቸው ፡ ዘመኖች ፡ ፋንታ ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 16 ፤ ባሪያዎችኽንና ፡ ሥራኽን ፡ እይ ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ምራ ።

መዝ. ፡ 89 ፡ (90) ፡ 17 ፤ የአምላካችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ በላያችን ፡ ይኹን ፦ የእጆቻችንንም ፡ ሥራ ፡ በላያችን ፡ አቅና ።

መዝሙር ፡ 90 ፡ (91) ።

የዳዊት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 1 ፤ በልዑል ፡ መጠጊያ ፡ የሚኖር ፡ ኹሉን ፡ በሚችል ፡ አምላክ ፡ ጥላ ፡ ውስጥ ፡ ያድራል ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፦ አንተ ፡ መታመኛዬ ፡ ነኽ ፡ እለዋለኹ ፤ አምላኬና ፡ መሸሸጊያዬ ፡ ነው ፥ በርሱም ፡ እታመናለኹ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 3 ፤ ርሱ ፡ ከአዳኝ ፡ ወጥመድ ፡ ከሚያስደነግጥም ፡ ነገር ፡ ያድንኻልና ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 4 ፤ በላባዎቹ ፡ ይጋርድኻል ፥ በክንፎቹም ፡ በታች ፡ ትተማመናለኽ ፤ እውነት ፡ እንደ ፡ ጋሻ ፡ ይከብኻል ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 5 ፤ ከሌሊት ፡ ግርማ ፥ በቀን ፡ ከሚበር ፡ ፍላጻ ፥

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 6 ፤ በጨለማ ፡ ከሚኼድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፥ ከአደጋና ፡ ከቀትር ፡ ጋኔን ፡ አትፈራም ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 7 ፤ በአጠገብኽ ፡ ሺሕ ፡ በቀኝኽም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ይወድቃሉ ፤ ወዳንተ ፡ ግን ፡ አይቀርብም ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 8 ፤ በዐይኖችኽ ፡ ብቻ ፡ ትመለከታለኽ ፥ የኃጥኣንንም ፡ ብድራት ፡ ታያለኽ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ተስፋዬ ፡ ነኽና ፤ ልዑልን ፡ መጠጊያኽ ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 10 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ወዳንተ ፡ አይቀርብም ፥ መቅሠፍትም ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ አይገባም ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 11 ፤ በመንገድኽ ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁኽ ፡ ዘንድ ፡ መላእክቱን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ያዛቸዋልና ፤

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 12 ፤ እግርኽም ፡ በድንጋይ ፡ እንዳትሰናከል ፡ በእጆቻቸው ፡ ያነሡኻል ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 13 ፤ በተኩላና ፡ በእባብ ፡ ላይ ፡ ትጫማለኽ ፤ አንበሳውንና ፡ ዘንዶውን ፡ ትረግጣለኽ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 14 ፤ በእኔ ፡ ተማምኗልና ፥ አስጥለዋለኹ ፤ ስሜንም ፡ ዐውቋልና ፥ እጋርደዋለኹ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 15 ፤ ይጠራኛል ፥ እመልስለትማለኹ ፤ በመከራውም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፤ አድነዋለኹ ፥ አከብረውማለኹ ።

መዝ. ፡ 90 ፡ (91) ፡ 16 ፤ ረዥምን ፡ ዕድሜ ፡ አጠግበዋለኹ ፥ ማዳኔንም ፡ አሳየዋለኹ ።

መዝሙር ፡ 91 ፡ (92) ።

በሰንበት ፡ ቀን ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ማመስገን ፡ መልካም ፡ ነው ፥ ልዑል ፡ ሆይ ፥ ለስምኽም ፡ ዝማሬ ፡ ማቅረብ ፤

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 2 ፤ በማለዳ ፡ ምሕረትን ፥ በሌሊትም ፡ እውነትኽን ፡ ማውራት ፡

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 3 ፤ ዐሥር ፡ አውታር ፡ ባለው ፡ በበገና ፥ ከምስጋና ፡ ጋራም ፡ በመሰንቆ ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ በሥራኽ ፡ ደስ ፡ አሠኝተኸኛልና ፤ በእጅኽም ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይለኛልና ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ሥራኽ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ነው ፥ ዐሳብኽም ፡ እጅግ ፡ ጥልቅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 6 ፤ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ አያውቅም ። ልብ ፡ የሌለውም ፡ ይህን ፡ አያስተውለውም ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 7 ፤ ኀጢአተኞች ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ሲበቅሉ ፡ ዐመፃ ፡ የሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ሲለመልሙ ፥ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ እንዲጠፉ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ልዑል ፡ ነኽ ፤

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ እንሆ ፥ ጠላቶችኽ ፡ ይጠፋሉና ፥ ዐመፃንም ፡ የሚሠሩ ፡ ኹሉ ፡ ይበተናሉና ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 10 ፤ ቀንዴ ፡ አንድ ፡ ቀንድ ፡ እንዳለው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ ሽምግልናዬም ፡ በዘይት ፡ ይለመልማል ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 11 ፤ ዐይኔም ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ አየች ፥ ጐሮዬም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ በቆሙ ፡ በክፉዎች ፡ ላይ ፡ ሰማች ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 12 ፤ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ዘንባባ ፡ ያፈራል ፥ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባም ፡ ያድጋል ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ተተክለዋል ፥ በአምላካችንም ፡ አደባባይ ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላሉ ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 14 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በለመለመ ፡ ሽምግልና ፡ ያፈራሉ ፡ ደስተኞችም ፡ ኾነው ፡ ይኖራሉ ።

መዝ. ፡ 91 ፡ (92) ፡ 15 ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይነግራሉ ፥ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ዐመፃ ፡ የለም ።

_____መዝሙር ፡ 92 ፡ (93) ። _____

በሰንበት ፡ ቀን ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 92 ፡ (93) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ነገሠ ፥ ክብርንም ፡ ለበሰ ፤ እግዚአብሔር ፡ ኀይልን ፡ ለበሰ ፥ ታጠቀም ፤ ዓለምን ፡ እንዳትናወጥ ፡ አጸናት ።

መዝ. ፡ 92 ፡ (93) ፡ 2 ፤ ዙፋንኽ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የተዘጋጀ ፡ ነው ፥ አንተም ፡ ከዘለዓለም ፡ ነኽ ።

መዝ. ፡ 92 ፡ (93) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ወንዞች ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፥ ወንዞች ፡ ቃሎቻቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ።

መዝ. ፡ 92 ፡ (93) ፡ 4 ፤ ከብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ድምፅ ፡ ከባሕርም ፡ ታላቅ ፡ ሞገድ ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከፍታው ፡ ድንቅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 92 ፡ (93) ፡ 5 ፤ ምስክርኽ ፡ እጅግ ፡ የታመነ ፡ ነው ፤ አቤቱ ፥ እስከ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ለቤትኽ ፡ ቅድስና ፡ ይገባል ።

መዝሙር ፡ 93 ፡ (94) ።

በአራተኛ ፡ ሰንበት ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ የበቀል ፡ አምላክ ፡ ነው ። የበቀል ፡ አምላክ ፡ ተገለጠ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 2 ፤ የምድር ፡ ፈራጅ ፡ ሆይ ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፤ ለትዕቢተኞች ፡ ፍዳቸውን ፡ ክፈላቸው ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ኀጢአተኞች ፡ እስከ ፡ መቼ ፧ ኀጢአተኞች ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይጓደዳሉ ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 4 ፤ ይከራከራሉ ፥ ዐመፃንም ፡ ይናገራሉ ፤ ዐመፃንም ፡ የሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ይናገራሉ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ሕዝብን ፡ አዋረዱ ፥ ርስትኽንም ፡ አስቸገሩ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 6 ፤ ባልቴቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ ገደሉ ፥ ስደተኛውንም ፡ ገደሉ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ አያይም ፥ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ አያስተውልም ፡ አሉ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 8 ፤ የሕዝብ ፡ ደንቈሮዎች ፡ ሆይ ፥ አስተውሉ ፤ ሰነፎችማ ፡ መቼ ፡ ይጠበባሉ ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 9 ፤ ጐሮን ፡ የተከለው ፡ አይሰማምን ፧ ዐይንን ፡ የሠራው ፡ አያይምን ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 10 ፤ አሕዛብንስ ፡ የሚገሥጸው ፥ ለሰውም ፡ ዕውቀት ፡ የሚያስተምረው ፡ ርሱ ፡ አይዘልፍምን ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 11 ፤ የሰዎች ፡ ዐሳብ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 12-13 ፤ ለኀጢአተኛ ፡ ጕድጓድ ፡ እስኪቈፈር ፡ ድረስ ፡ ከክፉዎች ፡ ዘመናት ፡ ይወገድ ፡ ዘንድ ፥ አቤቱ ፥ አንተ ፡ የገሠጽኸው ፡ ሕግኽንም ፡ ያስተማርኸው ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አይጥልምና ፥ ርስቱንም ፡ አይተውምና ፡

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 15 ፤ ፍርድ ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ እስኪመልስ ፡ ድረስ ፡ ልበ ፡ ቅኖችም ፡ ኹሉ ፡ ይከተሏታል ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 16 ፤ በክፉዎች ፡ ላይ ፡ ለእኔ ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፧ ዐመፃንስ ፡ በሚያደርጉ ፡ ላይ ፡ ለእኔ ፡ የሚከራከር ፡ ማን ፡ ነው ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ የረዳኝ ፡ ባይኾን ፡ ነፍሴ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በሰአል ፡ ባደረች ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 18 ፤ እግሮቼ ፡ ተሰናከሉ ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ ረዳኝ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ ለልቤ ፡ እንደ ፡ መከራዋ ፡ ብዛት ፡ ማጽናናትኽ ፡ ነፍሴን ፡ ደስ ፡ አሠኛት ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 20 ፤ በሕግ ፡ ላይ ፡ ዐመፅን ፡ የሚሠራ ፡ የዐመፅ ፡ ዙፋን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይኾናልን ፧

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 21 ፤ የጻድቅን ፡ ነፍስ ፡ ያደቡባታል ፥ በንጹሕ ፡ ደምም ፡ ይፈርዳሉ ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ መጠጊያ ፡ ኾነኝ ፥ አምላኬ ፡ የተስፋዬም ፡ ረዳት ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 93 ፡ (94) ፡ 23 ፤ እንደ ፡ በደላቸውም ፡ እንደ ፡ ክፋታቸውም ፡ ፍዳቸውን ፡ ይከፍላቸዋል ፥ አምላካችን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያጠፋቸዋል ።

መዝሙር ፡ 94 ፡ (95) ።

የዳዊት ፡ ምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 1 ፤ ኑ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበለን ፤ ለአምላክ ፡ ለመድኀኒታችን ፡ እልል ፡ እንበል ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 2 ፤ በምስጋና ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ እንድረስ ፥ በዝማሬም ፡ ለርሱ ፡ እልል ፡ እንበል ፤

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ በአማልክትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አይጥላቸውም ፤ የምድር ፡ ዳርቻዎችም ፡ በእጁ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ፥ የተራራዎች ፡ ከፍታዎች ፡ የርሱ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 5 ፤ ባሕር ፡ የርሱ ፡ ናት ፥ ርሱም ፡ አደረጋት ፤ የብስንም ፡ እጆቹ ፡ ሠሯት ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 6 ፤ ኑ ፥ እንስገድ ፥ ለርሱም ፡ እንገዛ ፤ በርሱ ፡ ባደረገን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንንበርከክ ፤

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 7 ፤ ርሱ ፡ አምላካችን ፡ ነውና ፥ እኛ ፡ የማሰማሪያው ፡ ሕዝብ ፡ የእጁም ፡ በጎች ፡ ነንና ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 8 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ ተፈታተኑት ፡ እንዳስቈጡት ፡ ጊዜ ፥ ዛሬ ፡ ድምፁን ፡ ብትሰሙ ፡ ልባችኹን ፡ አታጽኑ ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 9 ፤ የተፈታተኑኝ ፡ አባቶቻችኹ ፡ ፈተኑኝ ፡ ሥራዬንም ፡ አዩ ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 10 ፤ ያችን ፡ ትውልድ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ተቈጥቻት ፡ ነበር ። ኹልጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ይስታል ፥ እነርሱም ፡ መንገዴን ፡ አላወቁም ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 94 ፡ (95) ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ዕረፍቴም ፡ እንዳይገቡ ፡ በቀጣዬ ፡ ማልኹ ።

መዝሙር ፡ 95 ፡ (96) ።

ከምርኮ ፡ በኋላ ፡ ቤት ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 1 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ዐዲስ ፡ ምስጋናን ፡ አመስግኑ ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ ስሙንም ፡ ባርኩ ፥ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ማዳኑን ፡ አውሩ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 3 ፤ ክብሩን ፡ ለአሕዛብ ፡ ተኣምራቱንም ፡ ለወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ንገሩ ፤

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ምስጋናውም ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ በአማልክትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተፈራ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 5 ፤ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ አጋንንት ፡ ናቸውና ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰማያትን ፡ ሠራ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 6 ፤ ምስጋናና ፡ ውበት ፡ በፊቱ ፥ ቅዱስነትና ፡ ግርማ ፡ በመቅደሱ ፡ ውስጥ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 7 ፤ የአሕዛብ ፡ ወገኖች ፥ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፥ ክብርና ፡ ምስጋናን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፤

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 8 ፤ ለስሙ ፡ የሚገባ ፡ ክብርን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አምጡ ፤ ቍርባን ፡ ያዙ ፡ ወደ ፡ አደባባዮችም ፡ ግቡ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 9 ፤ በቅድስናው ፡ ስፍራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስገዱ ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ትነዋወጥ ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 10 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ። እግዚአብሔር ፡ ነገሠ ፡ በሉ ። እንዳይናወጥም ፡ ዓለሙን ፡ ርሱ ፡ አጸናው ፥ አሕዛብንም ፡ በቅንነት ፡ ይፈርዳል ።

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 11 ፤ ሰማያት ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፥ ምድርም ፡ ሐሤትን ፡ ታድርግ ፤ ባሕርና ፡ ሞላዋ ፡ ይናወጡ ፤

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 12 ፤ በረሓ ፡ በርሷም ፡ ያሉ ፡ ኹሉ ፡ ሐሤትን ፡ ያድርጉ ፤ የዱር ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤

መዝ. ፡ 95 ፡ (96) ፡ 13 ፤ ይመጣልና ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ ይመጣልና ፤ ርሱም ፡ ዓለምን ፡ በጽድቅ ፡ አሕዛብንም ፡ በቅንነት ፡ ይፈርዳል ።

መዝሙር ፡ 96 ፡ (97) ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ነገሠ ፤ ምድር ፡ ሐሤትን ፡ ታድርግ ፥ ብዙ ፡ ደሴቶችም ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 2 ፤ ደመና ፡ ጭጋግም ፡ በዙሪያው ፡ ናቸው ፤ ጽድቅና ፡ ፍርድ ፡ የዙፋኑ ፡ መሠረት ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 3 ፤ እሳት ፡ በፊቱ ፡ ይኼዳል ፥ ጠላቶቹንም ፡ በዙሪያው ፡ ያቃጥላል ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 4 ፤ መብረቆቹ ፡ ለዓለም ፡ አበሩ ፤ ምድር ፡ አየችና ፡ ተናወጠች ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 5 ፤ ተራራዎችም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፥ ከምድር ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሠም ፡ ቀለጡ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 6 ፤ ሰማያት ፡ የርሱን ፡ ጽድቅ ፡ አወሩ ፥ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ክብሩን ፡ አዩ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 7 ፤ ለተቀረጸ ፡ ምስል ፡ የሚሰግዱ ፡ ኹሉ ፥ በጣዖቶቻቸውም ፡ የሚመኩ ፡ ይፈሩ ፤ መላእክቱ ፡ ኹሉ ፥ ስገዱለት ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ፍርድኽ ፡ ጽዮን ፡ ሰምታ ፡ ደስ ፡ አላት ፥ የይሁዳም ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ደስ ፡ አላቸው ፤

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 9 ፤ አንተ ፥ እግዚአብሔር ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ኹሉ ፡ ልዑል ፡ ነኽና ፥ በአማልክትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብለኻልና ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትወዱ ፥ ክፋትን ፡ ጥሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ የቅዱሳኑን ፡ ነፍሶች ፡ ይጠብቃል ፥ ከኃጥኣንም ፡ እጅ ፡ ያድናቸዋል ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 11 ፤ ብርሃን ፡ ለጻድቃን ፥ ደስታም ፡ ለልበ ፡ ቅኖች ፡ ወጣ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 12 ፤ ጻድቃን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ለቅድስናውም ፡ መታሰቢያ ፡ አመስግኑ ።

_____መዝሙር ፡ 97 ፡ (98) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 1 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ዐዲስ ፡ ምስጋናን ፡ አመስግኑ ፥ እግዚአብሔር ፡ ተኣምራትን ፡ አድርጓልና ፤ ቀኙ ፡ የተቀደሰም ፡ ክንዱ ፡ ለርሱ ፡ ማዳን ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ማዳኑን ፡ አስታወቀ ፥ በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ ጽድቁን ፡ ገለጠ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 3 ፤ ለያዕቆብ ፡ ምሕረቱን ፡ ለእስራኤልም ፡ ቤት ፡ እውነቱን ፡ ዐሰበ ፤ የምድር ፡ ዳርቻዎች ፡ ኹሉ ፡ የአምላካችንን ፡ ማዳን ፡ አዩ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 4 ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ እልል ፡ በሉ ፤ አመስግኑ ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ዘምሩም ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 5 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ በመሰንቆ ፥ በመሰንቆና ፡ በዝማሬ ፡ ድምፅ ፡ ዘምሩ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 6 ፤ በዋሽንትና ፡ በመለከት ፡ ድምፅ ፡ በንጉሥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እልል ፡ በሉ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 7 ፤ ባሕርና ፡ ሞላዋ ፥ ዓለምም ፡ በርሷም ፡ የሚኖሩ ፡ ይናወጡ ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 8 ፤ ወንዞችም ፡ በአንድነት ፡ በእጅ ፡ ያጨብጭቡ ፤ ተራራዎች ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፥ በምድር ፡ ሊፈርድ ፡ ይመጣልና ።

መዝ. ፡ 97 ፡ (98) ፡ 9 ፤ ለዓለምም ፡ በጽድቅ ፡ ለአሕዛብም ፡ በቅንነት ፡ ይፈርዳል ።

_____መዝሙር ፡ 98 ፡ (99) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 98 ፡ (99) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ነገሠ ፥ አሕዛብ ፡ ይደንግጡ ፤ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፥ ምድር ፡ ትናወጥ ።

መዝ. ፡ 98 ፡ (99) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

መዝ. ፡ 98 ፡ (99) ፡ 3 ፤ ግሩምና ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ስምኽን ፡ ያመስግኑ ።

መዝ. ፡ 98 ፡ (99) ፡ 4 ፤ የንጉሥ ፡ ክብር ፡ ፍርድን ፡ ይወዳል ፤ አንተ ፡ ቅንነትን ፡ አጸናኽ ፥ ለያዕቆብ ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ አንተ ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 98 ፡ (99) ፡ 5 ፤ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጉት ፥ ቅዱስ ፡

ነውና ፥ ወደእግሩ ፡ መረገጫ ፡ ስገዱ ።

መዝ. ፥ 98 ፡ (99) ፥ 6 ፤ ሙሴና ፡ አሮን ፡ በካህናቱ ፡ ዘንድ ፥ ሳሙኤልም ፡ ስሙን ፡ በሚጠሩት ፡ ዘንድ ፡ ናቸው ። እግዚአብሔርን ፡ ጠሩት ፥ ርሱም ፡ መለሰላቸው ።

መዝ. ፥ 98 ፡ (99) ፥ 7 ፤ በደመና ፡ ዐምድም ፡ ተናገራቸው ፤ ምስክሩንና ፡ የሰጣቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠበቁ ።

መዝ. ፥ 98 ፡ (99) ፥ 8 ፤ አቤቱ ፡ አምላክችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ሰማኻቸው ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ማርኻቸው ፥ ሥራቸውን ፡ ዅሉ ፡ ግን ፡ ተበቀልኻቸው ።

መዝ. ፥ 98 ፡ (99) ፥ 9 ፤ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጉት ፥ በቅዱስ ፡ ተራራውም ፡ ስገዱ ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ።

መዝሙር ፡ 99 ፡ (100) ።

የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 99 ፡ (100) ፥ 1 ፤ ምድር ፡ ዅሉ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ እልል ፡ በሉ ፥

መዝ. ፥ 99 ፡ (100) ፥ 2 ፤ በደስታም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፥ በሐሤትም ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ግቡ ።

መዝ. ፥ 99 ፡ (100) ፥ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቁ ፤ ርሱ ፡ ሠራን ፡ እኛም ፡ አይደለንም ፤ እኛስ ፡ ሕዝቡ ፡ የማሰማሪያውም ፡ በጎች ፡ ነን ።

መዝ. ፥ 99 ፡ (100) ፥ 4 ፤ ወደ ፡ ደጆቹ ፡ በመገዛት ፥ ወደ ፡ አደባባዮቹም ፡ በምስጋና ፡ ግቡ ፤ አመስግኑት ፥ ስሙንም ፡ ባርኩ ፤

መዝ. ፥ 99 ፡ (100) ፥ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፥ እውነቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ።

መዝሙር ፡ 100 ፡ (101) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 1 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ እቀኝልኻለኹ ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 2 ፤ እዘምራለኹ ፥ ንጹሕ ፡ መንገዱንም ፡ አስተውላለኹ ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ መቼ ፡ ትመጣለኽ ∴ በቤቴ ፡ መካከል ፡ በልቤ ፡ ቅንነት ፡ እኼዳለኹ ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 3 ፤ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አላኖርኹም ፤ ሕግ ፡ ተላላፊዎችን ፡ ጠላኹ ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 4 ፤ ጠማማ ፡ ልብም ፡ አልተጠጋኝም ፤ ክፉ ፡ ከእኔ ፡ በራቀ ፡ ጊዜ ፡ አላወቅኹም ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 5 ፤ ባልንጀራውን ፡ በቀስታ ፡ የሚያማን ፡ ርሱን ፡ አሳደድኹ ፤ በዐይኑ ፡ ትዕቢተኛ ፡ የኾነውና ፡ ልቡ ፡ የሚሣሣው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አይተባበርም ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 6 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፤ ዐይኖቼ ፡ በምድር ፡ ምእመናን ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ በቀና ፡ መንገድ ፡ የሚኼድ ፡ ርሱ ፡ ያገለግለኛል ።

መዝ. ፥ 100 ፡ (101) ፥ 7 ፤ ትዕቢትን ፡ የሚያደርግ ፡ በቤቴ ፡ መካከል ፡ አይኖርም ፤ ዐመፅን ፡ የሚናገር ፡ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ አይቀናም ።

መዝ. ፡ 100 ፡ (101) ፡ 8 ፤ ዐመፃ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከተማ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፥ የምድርን ፡ ኀጢአተኞች ፡ ኹሉ ፡ በማለዳ ፡ እገድላቸዋለኹ ።

_____መዝሙር ፡ 101 ፡ (102) ። _____

ባዘነና ፡ ልመናውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ባፈሰሰ ፡ ጊዜ ፡ የችግረኛ ፡ ጸሎት ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ ስማኝ ፥ ጩኸቴም ፡ ወዳንተ ፡ ይድረስ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 2 ፤ በመከራዬ ፡ ቀን ፡ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ አትመልስ ፤ ጐሮኽን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብል ፤ በጠራኹኽ ፡ ቀን ፡ ፈጥነኽ ፡ ስማኝ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 3 ፤ ዘመኔ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ አልቃለችና ፥ ዐጥንቶቼም ፡ እንደ ፡ መቃጠያ ፡ ተቃጥለዋልና ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 4 ፤ እኽል ፡ መብላት ፡ ተረስቶኛልና ፥ ተቀሠፍኹ ፤ ልቤም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደረቀ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 5 ፤ ከጩኸቴ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ዐጥንቶቼ ፡ ከሥጋዬ ፡ ጋራ ፡ ተጣበቁ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ርኩም ፡ መሰልኹ ፤ በፈረሰ ፡ ቤት ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ጕጕት ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 7 ፤ ተጋኹ ፥ በሰገነትም ፡ እንደሚኖር ፡ ብቸኛ ፡ ድንቢጥ ፡ ኾንኹ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 8 ፤ ጠላቶቼ ፡ ኹልጊዜ ፡ ይሰድቡኛል ፥ የሚያሳድዱኝም ፡ ተማማሉብኝ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 9 ፤ ዐመድን ፡ እንደ ፡ እኽል ፡ ቅሜያለኹና ፥ መጠጤንም ፡ ከእንባዬ ፡ ጋራ ፡ ቀላቅያለኹና ፥

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 10 ፤ ከቀኑጣኽና ፡ ከመዓትኽም ፡ የተነሣ ፤ አንሥተኽኛልና ፥ ጥለኽኝማልና ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 11 ፤ ዘመኖቼ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ አዘንብለዋል ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ደርቄያለኹ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 12 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ለዘለዓለም ፡ ትኖራለኽ ፥ መታሰቢያኽም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 13 ፤ አንተ ፡ ተነሥ ፡ ጽዮንንም ፡ ይቅር ፡ በላት ፥ የምሕረቷ ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፥ ዘመኗም ፡ ደርሷልና ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 14 ፤ ባሪያዎችኽም ፡ ድንጋዮቿን ፡ ወደዋልና ፥ ለመሬቷም ፡ አዝነዋልና ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 15 ፤ አቤቱ ፥ አሕዛብ ፡ ስምኽን ፥ ነገሥታትም ፡ ኹሉ ፡ ክብርኽን ፡ ይፈራሉ ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ ይሠራታልና ፥ በክብሩም ፡ ይገለጣልና ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 17 ፤ ወደችግረኞች ፡ ጸሎት ፡ ተመለከተ ፥ ልመናቸውንም ፡ አልናቀም ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 18 ፤ ይህ ፡ ለሚመጣ ፡ ትውልድ ፡ ይጻፍ ፥ የሚፈጠርም ፡ ሕዝብ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እልል ፡ ይላል ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከመቅደሱ ፡ ከፍታ ፡ ኾኖ ፡ ተመልክቷልና ፥ ከሰማይ ፡ ኾኖ ፡

ምድርን ፡ አይቷልና ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 20 ፤ የእስረኞችን ፡ ጩኸት ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፥ ሊገድሉ ፡ የተፈረደባቸውን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 21 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በጽዮን ፡ ምስጋናውንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 22 ፤ አሕዛብ ፡ በአንድነት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥታትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 23 ፤ በጎይሉ ፡ ጕዳና ፡ መለሰለት ፦ የዘመኔን ፡ አነስተኛነት ፡ ንገረኝ ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 24 ፤ በዘመኔ ፡ እኩሌታ ፡ አትውሰደኝ ፤ ዓመቶችክ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 25 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ከጥንት ፡ ምድርን ፡ መሠረትክ ፥ ሰማያትም ፡ የእጅክ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 26 ፤ እነርሱ ፡ ይጠፋሉ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ትኖራለክ ፤ ኹላቸው ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፥ እንደ ፡ መጐናጸፊያም ፡ ትለውጣቸዋለክ ፥ ይለወጡማል ፤

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 27 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ያው ፡ አንተ ፡ ነክ ፥ ዓመቶችክም ፡ ከቶ ፡ አያልቁም ።

መዝ. ፡ 101 ፡ (102) ፡ 28 ፤ የባሪያዎችክም ፡ ልጆች ፡ ይኖራሉ ፥ ዘራቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ትጸናለች ።

መዝሙር ፡ 102 ፡ (103) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 1 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኪ ፥ ዐጥንቶቼም ፡ ኹሉ ፥ የተቀደሰ ፡ ስሙን ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 2 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኪ ፥ ምስጋናውንም ፡ ኹሉ ፡ አትርሺ ፤

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 3 ፤ ኀጢአትሽን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ የሚል ፥ ደዌሽንም ፡ ኹሉ ፡ የሚፈውስ ፥

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 4 ፤ ሕይወትሽን ፡ ከጥፋት ፡ የሚያድናት ፥ በምሕረቱና ፡ በቸርነቱ ፡ የሚከልልሽ ፥

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 5 ፤ ምኞትሽን ፡ ከበረከቱ ፡ የሚያጠግባት ፥ ጕልማሳነትሽን ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ያድሳል ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይቅርታ ፡ አድራጊ ፡ ነው ፤ ለተበደሉ ፡ ኹሉ ፡ ይፈርዳል ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 7 ፤ ለሙሴ ፡ መንገዱን ፡ አስታወቀ ፥ ለእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ አደራረጉን ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ መሓሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ፥ ከቀሥጣ ፡ የራቀ ፡ ምሕረቱም ፡ የበዛ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 9 ፤ ኹልጊዜም ፡ አይቀሥፍም ፥ ለዘለዓለምም ፡ አይቈጣም ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 10 ፤ እንደ ፡ ኀጢአታችን ፡ አላደረገብንም ፥ እንደ ፡ በደላችንም ፡ አልከፈለንም ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 11 ፤ ሰማይ ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ እንደሚል ፥ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምሕረቱን ፡ በሚፈሩት ፡ ላይ ፡ አጠነከረ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 12 ፤ ምሥራቅ ፡ ከምዕራብ ፡ እንደሚርቅ ፥ እንዲሁ ፡ ኀጢአታችንን ፡ ከእኛ ፡ አራቀ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 13 ፤ አባት ፡ ለልጆቹ ፡ እንደሚራራ ፡ እንዲሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚፈሩት ፡ ይራራል ፤

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 14 ፤ ፍጥረታችንን ፡ ርሱ ፡ ያውቃልና ፤ አቤቱ ፥ እኛ ፡ ዐፈር ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ዐስብ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 15 ፤ ሰውስ ፡ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ዱር ፡ አበባ ፡ እንዲሁ ፡ ያብባል ፤

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 16 ፤ ነፋስ ፡ በነፈሰበት ፡ ጊዜ ፡ ያልፋልና ፥ ስፍራውንም ፡ ደግሞ ፡ አያውቀውምና ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ ግን ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ በሚፈሩት ፡ ላይ ፥ ጽድቁም ፡ በልጅ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 18 ፤ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ በሚጠብቁ ፥ ትእዛዙንም ፡ ያደርጓት ፡ ዘንድ ፡ በሚያስቡ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዙፋኑን ፡ በሰማይ ፡ አዘጋጀ ፥ መንግሥቱም ፡ ኹሉን ፡ ትገዛለች ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 20 ፤ ቃሉን ፡ የምትፈጽሙ ፥ ብርቱዎችና ፡ ኀያላን ፥ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ የምትሰሙ ፡ መላእክቱ ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 21 ፤ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፥ ፈቃዱን ፡ የምታደርጉ ፡ አገልጋዮቹ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ።

መዝ. ፡ 102 ፡ (103) ፡ 22 ፤ ፍጥረቶቹ ፡ ኹሉ ፡ በግዛቱ ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ። ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኪ ።

መዝሙር ፡ 103 ፡ (104) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 1 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኪ ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነኽ ፤ ክብርንና ፡ ግርማን ፡ ለበስኽ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 2 ፤ ብርሃንን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ለበስኽ ፤ ሰማይንም ፡ እንደ ፡ መጋረጃ ፡ ዘረጋኽ ፤

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 3 ፤ ዕልፍኙን ፡ በውሃ ፡ የሚሠራ ፥ ሠረገላውን ፡ ደመና ፡ የሚያደርግ ፥ በነፋስ ፡ ክንፍም ፡ የሚኼድ ፥

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 4 ፤ መላእክቱን ፡ መንፈስ ፡ የሚያደርግ ፥ አገልጋዮቹንም ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 5 ፤ ለዘላለም ፡ እንዳትናወጥ ፡ ምድርን ፡ በመሠረቷ ፡ ላይ ፡ መሠረታት ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 6 ፤ በጥልቅ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ከደንኻት ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ ውሃዎች ፡ ይቆማሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 7 ፤ ከዘለፋኽም ፡ ይሸሻሉ ፥ ከነጐድጓድኽም ፡ ድምፅ ፡ ይደነግጣሉ ፤

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ይወጣሉ ፥ ወደ ፡ ቈላዎች ፡ ወዳዘጋጀኽላቸው ፡ ስፍራ ፡ ይወርዳሉ ፤

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 9 ፤ እንዳያልፉትም ፡ ድንበር ፡ አደረግኽላቸው ፥ ምድርን ፡ ይከድኑ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይመለሱ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 10 ፤ ምንጮችን ፡ ወደ ፡ ቈላዎች ፡ ይልካል ፤ በተራራዎች ፡ መካከል ፡ ውሃዎች ፡ ያልፋሉ ፤

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 11 ፤ የዱር ፡ አራዊትን ፡ ኹሉ ፡ ያጠጣሉ ፥ የበረሓ ፡ አህያዎችም ፡ ጥማታቸውን ፡ ይረካሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 12 ፤ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያድራሉ ፥ በድንጋዩ ፡ ስንጥቅ ፡ መካከልም ፡ ይጮኻሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 13 ፤ ተራራዎችን ፡ ከላይ ፡ የሚያጠጣቸው ፤ ከሥራኽ ፡ ፍሬ ፡ ምድር ፡ ትጠግባለች ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 14 ፤ እንጀራን ፡ ከምድር ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ ለምለሙን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ጥቅም ፥ ሣርንም ፡ ለእንስሳ ፡ ያበቅላል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 15 ፤ ወይን ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ፥ ዘይትም ፡ ፊትን ፡ ያበራል ፥ እኽልም ፡ የሰውን ፡ ጕልበት ፡ ያጠነክራል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዛፎች ፡ ርሱም ፡ የተከላቸው ፡ የሊባኖስ ፡ ዝግባዎች ፡ ይጠግባሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 17 ፤ በዚያም ፡ ወፎች ፡ ይዋለዳሉ ፥ የሽመላ ፡ ቤትም ፡ የእነርሱ ፡ ጎረቤት ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 18 ፤ ረጃኒቮም ፡ ተራራዎች ፡ ለዋላዎች ፥ ድንጋዮችም ፡ ለሽኮኮዎች ፡ መሸሻ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 19 ፤ ጨረቃን ፡ ለጊዜዎች ፡ አደረገ ፤ ፀሓይም ፡ መግቢያውን ፡ ያውቃል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 20 ፤ ጨለማ ፡ ታደርጋለኽ ፥ ሌሊትም ፡ ይሆናል ፤ በርሱም ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ ይወጡበታል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 21 ፤ የአንበሳ ፡ ግልገሎች ፡ ለመንጠቅ ፡ ይጮኻሉ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ ምግባቸውን ፡ ይሻሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 22 ፤ ፀሓይ ፡ ስትወጣ ፡ ይሰበሰባሉ ፥ በየዋሻቸውም ፡ ይተኛሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 23 ፤ ሰው ፡ ወደ ፡ ተግባሩ ፥ እስከ መሸም ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሥራው ፡ ይወጣል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 24 ፤ አቤቱ ፥ ሥራኽ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ ኹሉን ፡ በጥበብ ፡ አደረግኽ ፥ ምድርም ፡ ከፍጥረትኽ ፡ ተሞላች ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 25 ፤ ይህች ፡ ባሕር ፡ ታላቅና ፡ ሰፊ ፡ ናት ፤ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፥ ታላላቆችና ፡ ታናናሾች ፡ እንስሳዎች ፡ አሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ መርከቦች ፡ ይኼዳሉ ፥ በዚያም ፡ ላይ ፡ የፈጠርኸው ፡ ዘንዶ ፡ ይጫወትበታል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 27 ፤ ምግባቸውን ፡ በየጊዜው ፡ ትሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 28 ፤ በሰጠኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ይሰበስባሉ ፤ እጅኽን ፡ ትከፍታለኽ ፥ ከመልካም ፡ ነገርም ፡ ይጠግባሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 29 ፤ ፊትኽን ፡ ስትሰውር ፡ ይደነግጣሉ ፤ ነፍሳቸውን ፡ ታወጣለኽ ፡ ይሞታሉም ፥ ወደ ፡ ዐፈራቸውም ፡ ይመለሳሉ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 30 ፤ መንፈስኽን ፡ ትልካለኽ ፡ ይፈጠራሉም ፥ የምድርንም ፡ ፊት ፡ ታድሳለኽ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 31 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ለዘላለም ፡ ይኹን ፤ እግዚአብሔር ፡ በሥራው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 32 ፤ ምድርን ፡ ያያል ፡ እንድትንቀጠቀጥም ፡ ያደርጋል ፤ ተራራዎችን ፡ ይዳስሳል ፡ ይጤሳሉም ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 33 ፤ በሕይወቴ ፡ ሳለኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እቀኛለኹ ፥ ለአምላኬም ፡ በምኖርበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 34 ፤ ቃሌ ፡ ለርሱ ፡ ይጣፍጠው ፥ እኔም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

መዝ. ፡ 103 ፡ (104) ፡ 35 ፤ ኃጥኣን ፡ ከምድር ፡ ይጥፉ ፤ ዐመፀኞች ፡ እንግዲህ ፡ አይገኙ ። ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኪ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 104 ፡ (105) ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ስሙንም ፡ ጥሩ ፥ ለአሕዛብም ፡ ሥራውን ፡ አውሩ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 2 ፤ ተቀኙለት ፥ ዘምሩለት ፥ ተኣምራቱንም ፡ ኹሉ ፡ ተናገሩ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 3 ፤ በቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ተጓደዱ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈልግ ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፈልጉት ፡ ትጸናላችኹም ፤ ኹልጊዜ ፡ ፊቱን ፡ ፈልጉ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 5-6 ፤ ባሪያዎቹ ፡ የአብርሃም ፡ ዘር ፥ ለርሱም ፡ የተመረጣችኹ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ የሠራትን ፡ ድንቅ ፡ ዐስቡ ፥ ተኣምራቱን ፡ የአፉንም ፡ ፍርድ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 7 ፤ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ነው ፤ ፍርዱ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 8 ፤ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ ለዘለዓለም ፥ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ትውልድ ፡ ያዘዘውን ፡ ቃሉን ፡ ዐሰበ ፥

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 9 ፤ ለአብርሃም ፡ ያደረገውን ፥ ለይሥሐቅም ፡ የማለውን ፤

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 10 ፤ ለያዕቆብ ፡ ሥርዐት ፡ እንዲኾን ፡ ለእስራኤልም ፡ የዘለዓለም ፡ ኪዳን ፡ እንዲኾን ፡ አጸና ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ ለአንተ ፡ የከነዓንን ፡ ምድር ፡ የርስታችኹን ፡ ገመድ ፡ እሰጣለኹ ፤

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 12 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ እነርሱ ፡ በቍጥር ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎች ፥ እጅግ ፡ ጥቂቶችና ፡ ስደተኞች ፡ ሲኾኑ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 13 ፤ ከሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፥ ከመንግሥታትም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ዐለፉ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 14-15 ፤ የቀባኋቸውን ፡ አትዳስሱ ፥ በነቢያቴም ፡ ክፉ ፡ አታድርጉ ፡ ብሎ ፥ ሰው ፡ ግፍ ፡ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደም ፥ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ነገሥታትን ፡ ገሠጸ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 16 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብን ፡ ጠራ ፥ የእኽልን ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ ሰበረ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 17 ፤ በፊታቸው ፡ ሰውን ፡ ላከ ፤ ዮሴፍ ፡ ለባርነት ፡ ተሸጠ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 18 ፤ እግሮቹም ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ደከሙ ፥ ርሱም ፡ በብረት ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 19 ፤ ቃሉ ፡ እስኪመጣለት ፡ ድረስ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፈተነው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 20 ፤ ንጉሥ ፡ ላከ ፡ ፈታውም ፥ የአሕዛብም ፡ አለቃ ፡ አስፈታው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 21 ፤ የቤቱ ፡ ጌታ ፥ የጥሪቱ ፡ ኹሉ ፡ ገዢ ፡ አደረገው ፥

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 22 ፤ አለቃዎቹን ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ይገሥጽ ፡ ዘንድ ፥ ሽማግሌዎቹንም ፡ ጥበበኞች ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 23 ፤ እስራኤልም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ገባ ፥ ያዕቆብም ፡ በካም ፡ አገር ፡ ተቀመጠ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 24 ፤ ሕዝቡንም ፡ እጅግ ፡ አበዛ ፥ ከጠላቶቻቸውም ፡ ይልቅ ፡ አበረታቸው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 25 ፤ ሕዝቡን ፡ ይጠሉ ፡ ዘንድ ፡ በባሪያዎቹም ፡ ላይ ፡ ይተነኰሉ ፡ ዘንድ ፡ ልባቸውን ፡ ለወጠ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 26 ፤ ባሪያውን ፡ ሙሴን ፡ የመረጠውንም ፡ አሮንን ፡ ላከ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 27 ፤ የተአምራቱን ፡ ነገር ፡ በላያቸው ፡ ድንቁንም ፡ በካም ፡ አገር ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 28 ፤ ጨለማን ፡ ላከ ፡ ጨለመባቸውም ፤ በቃሉም ፡ ዐመፁ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 29 ፤ ውሃቸውን ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ለወጠ ፥ ዓሣዎቻቸውንም ፡ ገደለ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 30 ፤ ምድራቸው ፡ የንጉሦቻቸውም ፡ ቤቶች ፡ በጓጉንቸር ፡ ሞሉ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 31 ፤ ተናገረ ፥ የውሻ ፡ ዝንብ ፡ ትንኝም ፡ በዳርቻቸው ፡ መጡ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 32 ፤ ዝናባቸውን ፡ በረዶ ፡ አደረገው ፥ እሳትም ፡ በምድራቸው ፡ ተቃጠለች ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 33 ፤ ወይናቸውንና ፡ በለሳቸውን ፡ መታ ፥ የአገራቸውንም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ሰበረ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 34 ፤ ተናገረ ፥ አንበጣም ፡ ስፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለውም ፡ ኵብኵባ ፡ መጣ ፥

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 35 ፤ የአገራቸውንም ፡ ለምለም ፡ ኹሉ ፡ በላ ፥ የምድራቸውንም ፡ ፍሬ ፡ በላ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 36 ፤ የአገራቸውንም ፡ በኵር ፡ ኹሉ ፥ የጕልበታቸውን ፡ መዠመሪያ ፡ ኹሉ ፡ መታ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 37 ፤ ከወርቅና ፡ ከብርም ፡ ጋራ ፡ አወጣቸው ፥ በወገናቸውም ፡ ውስጥ ፡ ደዌ ፡ አልነበረም ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 38 ፤ ፈርተዋቸው ፡ ነበርና ፥ ግብጽ ፡ በመውጣታቸው ፡ ደስ ፡ አላት ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 39 ፤ ደመናን ፡ ለመሸፈኛ ፡ ዘረጋባቸው ፥ እሳትንም ፡ በሌሊት ፡ ያበራላቸው ፡ ዘንድ ፡ ዘረጋ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 40 ፤ ለመኑ ፥ ድርጭትንም ፡ አመጣላቸው ፥ የሰማይንም ፡ እንጀራ ፡ አጠገባቸው ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 41 ፤ አለቱን ፡ ሠነጠቀ ፥ ውሃውም ፡ ፈሰሰ ፤ ወንዞች ፡ በበረሓ ፡ ኼዱ ፤

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 42 ፤ ለባሪያው ፡ ለአብርሃም ፡ የነገረውን ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉን ፡ ዐስቧልና ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 43 ፤ ሕዝቡንም ፡ በደስታ ፡ የተመረጡትንም ፡ በእልልታ ፡ አወጣ ።

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 44 ፤ የአሕዛብንም ፡ አገሮች ፡ ሰጣቸው ፥ የወገኖችንም ፡ ድካም ፡ ወረሱ ፥

መዝ. ፡ 104 ፡ (105) ፡ 45 ፤ ሕጉን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ሥርዐቱንም ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ። ሃሌ ፡ ሉያ ፡

መዝሙር ፡ 105 ፡ (106) ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ኀይል ፡ ሥራ ፡ ማን ፡ ይናገራል ፧ ምስጋናውንስ ፡ ኹሉ ፡ ማን ፡ ያሰማል ፧

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 3 ፤ ፍርድን ፡ የሚጠብቁ ፥ ጽድቅንም ፡ ኹልጊዜ ፡ የሚያደርጉ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ በሕዝብኽ ፡ ሞገስ ፡ ዐስበን ፥ በመድኀኒትኽም ፡ ጐብኘን ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 5 ፤ የመረጥኻቸውን ፡ በጎነት ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፥ በሕዝብኽም ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ፥ ከርስትኽም ፡ ጋራ ፡ እንጓደድ ፡ ዘንድ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 6 ፤ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠራን ፥ ዐመፅንም ፥ በደልንም ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 7 ፤ አባቶቻችን ፡ በግብጽ ፡ ሳሉ ፡ ተአምራትኽን ፡ አላስተዋሉም ፥ የምሕረትኽንም ፡ ብዛት ፡ አላሰቡም ፤ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ ዐመፁብኽ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 8 ፤ ኀይሉን ፡ ግን ፡ ለማስታወቅ ፥ ስለ ፡ ስሙ ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 9 ፤ ቀይ ፡ ባሕርንም ፡ ገሠጸ ፥ ርሱም ፡ ደረቀ ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በጥልቅ ፡ መራቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 10 ፤ ከሚጠሏቸውም ፡ እጅ ፡ አዳናቸው ፥ ከጠላትም ፡ እጅ ፡ ተቤዣቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 11 ፤ ያሳደዷቸውንም ፡ ውሃ ፡ ደፈናቸው ፥ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ አልቀረም ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በቃሉ ፡ አመኑ ፥ ምስጋናውንም ፡ ዘመሩ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 13 ፤ ፈጥነውም ፡ ሥራውን ፡ ረሱ ፥ በምክሩም ፡ አልታገሡም ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 14 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ምኞትን ፡ ተመኙ ፥ በበረሓም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተፈታተኑት ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 15 ፤ የለመኑትንም ፡ ሰጣቸው ፤ ለነፍሳቸው ፡ ግን ፡ ክሳትን ፡ ላከ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 16 ፤ ሙሴንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀደሰውንም ፡ አሮንን ፡ በሰፈር ፡ ተመቀኛቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 17 ፤ ምድርም ፡ ተከፈተች ፡ ዳታንንም ፡ ዋጠችው ፥ የአቤሮንንም ፡ ወገን ፡ ደፈነች ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 18 ፤ በማኅበራቸውም ፡ እሳት ፡ ነደደች ፥ ነበልባልም ፡ ኃጥኣንን ፡ አቃጠላቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 19 ፤ በኰሬብም ፡ ጥጃን ፡ ሠሩ ፥ ቀልጦ ፡ ለተሠራ ፡ ምስልም ፡ ሰገዱ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 20 ፤ ሣርም ፡ በሚበላ ፡ በበሬ ፡ ምሳሌ ፡ ክብራቸውን ፡ ለወጡ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 21-22 ፤ ታላቅ ፡ ነገርንም ፡ በግብጽ ፥ ድንቅንም ፡ በካራን ፡ ምድር ፥ ግሩም ፡ ነገርንም ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ ያደረገውን ፡ ያዳናቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረሱ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 23 ፤ እንዳያጠፋቸው ፡ ቀጣውን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ የተመረጠው ፡ ሙሴ ፡ በመቅሠፍት ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ባይቆም ፡ ኖሮ ፥ ያጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ተናገረ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 24 ፤ የተወደደችውን ፡ ምድር ፡ ናቁ ፥ በቃሉም ፡ አልታመኑም ፥

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 25 ፤ በድንኳኖቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ አንጐራጐሩ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 26-27 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ይጥላቸው ፡ ዘንድ ፥ ዘራቸውንም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይጥል ፡ ዘንድ ፥ በያገሩም ፡ ይበትናቸው ፡ ዘንድ ፥ እጁን ፡ አነሣባቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 28 ፤ በብዔል ፡ ፌጎርም ፡ ተባበሩበት ፥ የሙታንንም ፡ መሥዋዕት ፡ በሉ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 29 ፤ በሥራቸውም ፡ አስመረሩት ፥ ቸነፈርም ፡ በላያቸው ፡ በዛ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 30 ፤ ፊንሐስም ፡ ተነሥቶ ፡ ፈረደባቸው ፥ ቸነፈሩም ፡ ተወ ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 31 ፤ ያም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 32-33 ፤ በክርክር ፡ ውሃ ፡ ዘንድም ፡ አስቈጡት ፥ መንፈሱን ፡ አስመርረዋታልና ፤ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ሙሴ ፡ ተበሳጨ ፤ በከንፈሮቹም ፡ በስንፍና ፡ ተናገረ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 34 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳላቸው ፡ አሕዛብን ፡ አላጠፉም ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 35 ፤ ከአሕዛብም ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ፥ ሥራቸውንም ፡ ተማሩ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 36 ፤ ለጣዖቶቻቸውም ፡ ተገዙ ፥ ወጥመድም ፡ ኾኑባቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 37 ፤ ወንዶች ፡ ልጆቻቸውንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለአጋንንት ፡ ሠዉ ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 38 ፤ የወንዶች ፡ ልጆቻቸውንና ፡ የሴቶች ፡ ልጆቻችን ፡ ደም ፥ ለከነዓን ፡ ጣዖቶች ፡ የሠዉአቸውን ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አፈሰሱ ፥ ምድርም ፡ በደም ፡ ረከሰች ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 39 ፤ በሥራቸው ፡ ረከሱ ፥ በማድረጋቸውም ፡ አመነዘሩ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 40 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቀጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነደደ ፥ ርስቱንም ፡ ተጸየፈ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 41 ፤ ወደ ፡ አሕዛብም ፡ እጅ ፡ አሳለፋቸው ፥ የሚጠሏቸውም ፡ ገዟቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 42 ፤ ጠላቶቻቸውም ፡ ግፍ ፡ አደረጉባቸው ፥ ከእጃቸውም ፡ በታች ፡ ተዋረዱ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 43 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አዳናቸው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምክራቸው ፡ አስመረሩት ፥ በኀጢአታቸውም ፡ ተዋረዱ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 44 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ጩኸታቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጭንቃቸውን ፡ ተመለከተ ፤

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 45 ፤ ለእነርሱም ፡ ኪዳኑን ፡ ዐሰበ ፥ እንደ ፡ ምሕረቱም ፡ ብዛት ፡ ተጸጸተ ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 46 ፤ በማረኳቸውም ፡ ዅሉ ፡ ፊት ፡ ሞገስን ፡ ሰጣቸው ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 47 ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አድነን ፤ ቅዱስ ፡ ስምኽን ፡ እናመሰግን ፡ ዘንድ ፥ በምስጋናኽም ፡ እንመካ ፡ ዘንድ ፥ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ሰብስበን ።

መዝ. ፡ 105 ፡ (106) ፡ 48 ፤ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ፡ ሕዝብም ፡ ዅሉ ፡ አሜን ፡ ይበል ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

_____መዝሙር ፡ 106 ፡ (107) ። _____

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 1 ፤ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዳናቸው ፥ ከጠላቶች ፡ እጅ ፡ ያዳናቸው ፡ ይናገሩ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 3 ፤ ከምሥራቅና ፡ ከምዕራብ ፥ ከሰሜንና ፡ ከባሕር ፥ ከየአገሩ ፡ ሰበሰባቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 4 ፤ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተቅበዘበዙ ፤ የሚኖሩበትንም ፡ ከተማ ፡ መንገድ ፡ አላገኙም ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 5 ፤ ተራቡ ፡ ተጠሙም ፥ ነፍሳቸውም ፡ በውስጣቸው ፡ ዐለቀች ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 6 ፤ በተጨነቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ ከመከራቸውም ፡ አዳናቸው ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 7 ፤ ወደሚኖሩበት ፡ ከተማ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ የቀና ፡ መንገድን ፡ መራቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 8 ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ስላደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ስለ ፡ ምሕረቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግኑ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 9 ፤ የተራበችን ፡ ነፍስ ፡ አጥግቧልና ፥ የተራቈተችንም ፡ ነፍስ ፡ በበረከት ፡ ሞልቷልና ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 10 ፤ በጨለማ ፡ በሞትም ፡ ጥላ ፡ የተቀመጡ ፥ በችግር ፡ በብረትም ፡ የታሰሩ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ዐመፀ ፥ የልዑልንም ፡ ምክር ፡ ስለ ፡ ናቁ ፥

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 12 ፤ ልባቸው ፡ በድካም ፡ ተዋረደ ፤ ታመሙ ፡ የሚረዳቸውም ፡ ዐጡ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 13 ፤ በተጨነቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ በመከራቸውም ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 14 ፤ ከጨለማና ፡ ከሞት ፡ ጥላ ፡ አወጣቸው ፥ እስራታቸውንም ፡ ሰበረ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 15 ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ስላደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ስለ ፡ ምሕረቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግኑ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 16 ፤ የናሱን ፡ ደጆች ፡ ሰብሯልና ፥ የብረቱንም ፡ መወርወሪያ ፡ ቈርጧልና ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 17 ፤ ስለ ፡ ዐመፃቸው ፡ ሰነፉ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታቸውም ፡ ተቸገሩ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 18 ፤ ሰውነታቸው ፡ መብልን ፡ ሹሉ ፡ ተጸየፈች ፥ ወደሞትም ፡ ደጆች ፡ ቀረቡ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 19 ፤ በተጨነቁ ፡ ጊዜም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ ከመከራቸውም ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 20 ፤ ቃሉን ፡ ላከ ፡ ፈወሳቸውም ፥ ከጥፋታቸውም ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 21 ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ስላደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ስለ ፡ ምሕረቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 22 ፤ የምስጋና ፡ መሥዋዕትንም ፡ ይሠዉለት ፥ በእልልታም ፡ ሥራውን ፡ ይንገሩ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 23 ፤ በመርከቦች ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የሚወርዱ ፥ በታላቅ ፡ ውሃ ፡ ሥራቸውን ፡ የሚሠሩ ፥

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 24 ፤ እነርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፥ በጥልቅም ፡ ያለችውን ፡ ድንቁን ፡ አዩ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 25 ፤ ተናገረ ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ተነሣ ፥ ሞገድም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 26 ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይወጣሉ ፡ ወደ ፡ ጥልቅም ፡ ይወርዳሉ ፤ ነፍሳቸውም ፡ በመከራ ፡ ቀለጠች ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 27 ፤ ደነገጡ ፡ እንደ ፡ ስካርም ፡ ተንገደገዱ ፥ ጥበባቸውም ፡ ሹሉ ፡ ተዋጠች ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 28 ፤ በተጨነቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹ ፥ ከመከራቸውም ፡ አዳናቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 29 ፤ ዐውሎንም ፡ ጸጥ ፡ አደረገ ፥ ሞገዱም ፡ ዝም ፡ አለ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 30 ፤ ዝም ፡ ብሏልና ፥ ደስ ፡ አላቸው ፤ ወደ ፡ ፈለጉትም ፡ ወደብ ፡ መራቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 31 ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ስላደረገው ፡ ተኣምራት ፡ ስለ ፡ ምሕረቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግኑ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 32 ፤ በአሕዛብ ፡ ጉባኤ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያድርጉት ፥ በሽማግሌዎችም ፡ ሸንጎ ፡ ያመስግኑት ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 33 ፤ ወንዞችን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፥ የውሃውንም ፡ ምንጮች ፡ ደረቅ ፡ አደረጋቸው ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 34 ፤ ከተቀመጡባት ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ፍሬያማዋን ፡ ምድር ፡ ጨው ፡ አደረጋት ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 35 ፤ ምድረ ፡ በዳን ፡ ለውሃ ፡ መቆሚያ ፥ ደረቁንም ፡ ምድር ፡ የውሃ ፡ ምንጮች ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 36 ፤ በዚያም ፡ ራብተኞችን ፡ አስቀመጠ ፥ የሚኖርባትንም ፡ ከተማ ፡ ሠሩ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 37 ፤ ዕርሻዎችንም ፡ ዘሩ ፡ ወይኖችንም ፡ ተከሉ ፥ የእኽልንም ፡ ሰብል ፡ አደረጉ ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 38 ፤ ባረካቸውም ፡ እጅግም ፡ በዙ ፤ እንስሳዎቻቸውንም ፡ አላሳነሰባቸውም ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 39 ፤ እነርሱ ፡ በችግር ፡ በክፋት ፡ በጭንቀት ፡ ተዋረዱ ፡ እያነሱም ፡ ኼዱ ፤

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 40 ፤ በአለቆችም ፡ ላይ ፡ ኀሳርን ፡ አፈሰሰ ፥ መንገድም ፡ በሌለበት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አሳታቸው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 41 ፤ ችግረኛንም ፡ ከችግሩ ፡ ረዳው ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ መንጋ ፡ ወገን ፡ አደረገው ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 42 ፤ ቅኖች ፡ ያያሉ ፥ ደስም ፡ ይላቸዋል ፤ ኀጢአትም ፡ ኹሉ ፡ አፏን ፡ ትዘጋለች ።

መዝ. ፡ 106 ፡ (107) ፡ 43 ፤ ጥበበኛ ፡ የኾነና ፡ ይህን ፡ የሚጠብቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምሕረት ፡ ያስተውላል ።

መዝሙር ፡ 107 ፡ (108) ።

የዳዊት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 1 ፤ ልቤ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፥ አቤቱ ፥ ልቤ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፤ እቀኛለኹ ፡ በክብሬም ፡ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 2 ፤ በገና ፡ ሆይ ፥ ተነሥ ፥ መሰንቆም ፤ እኔም ፡ ማልጄ ፡ እነሣለኹ ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አመሰግንኻለኹ ፥ በወገኖችም ፡ መካከል ፡ እዘምርልኻለኹ ፤

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 4 ፤ ምሕረትኽ ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ናትና ፥ እውነትኽም ፡ እስከ ፡ ደመናት ፡ ድረስ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ በሰማያት ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ በል ፥ ክብርኽም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትኹን ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 6 ፤ ወዳጆችኽ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፤ በቀኝኽ ፡ አድን ፡ አድምጠኝም ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቅድስናው ፡ ተናገረ ፦ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ሴኬምንም ፡ እካፈላለኹ ፥ የሱኮትንም ፡ ሸለቆ ፡ እሰፍራለኹ ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 8 ፤ ገለዓድ ፡ የእኔ ፡ ነው ፡ ምናሴም ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ ኤፍሬም ፡ የራሴ ፡ መጠጊያ ፡ ነው ። ይሁዳ ፡ ንጉሤ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 9 ፤ ሞዐብ ፡ መታጠቢያዬ ፡ ነው ፥ በኤዶምያስ ፡ ላይም ፡ ጫማዬን ፡ እዘረጋለኹ ፤ ፍልስጥኤም ፡ ይገዙልኛል ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ከተማ ፡ ማን ፡ ይወስደኛል ፧ ማንስ ፡ እስከ ፡ ኤዶምያስ ፡ ይመራኛል ፧

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ የጣልኸኝ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ከሰራዊታችን ፡ ጋራ ፡ አትወጣም ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 12 ፤ በመከራችን ፡ ረድኤትን ፡ ስጠን ፤ የሰውም ፡ ማዳን ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 107 ፡ (108) ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ኀይልን ፡ እናደርጋለን ፤ ርሱም ፡ የሚያስጨንቁንን ፡ ያዋርዳቸዋል ።

መዝሙር ፡ 108 ፡ (109) ።

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 1 ፤ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ምስጋናዬን ፡ ዝም ፡ አትበል ፥

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 2 ፤ የኀጢአተኛ ፡ አፍና ፡ የተንኰለኛ ፡ አፍ ፡ በላዬ ፡ ተላቀው ብኛልና ፤ በሸንገላ ፡ አንደበትም ፡ በላዬ ፡ ተናገሩ ፤

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 3 ፤ በጥል ፡ ቃል ፡ ከበቡኝ ፥ በከንቱም ፡ ተሰለፉብኝ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 4 ፤ በወደድኋቸው ፡ ፋንታ ፡ አጣሉኝ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ እጸልያለኹ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 5 ፤ በመልካም ፡ ፋንታ ፡ ክፉን ፡ በወደድኋቸውም ፡ ፋንታ ፡ ጠላትነትን ፡ መለሱልኝ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 6 ፤ በላዩ ፡ ኀጢአተኛን ፡ ሹም ፤ ሰይጣንም ፡ በቀኙ ፡ ይቁም ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 7 ፤ በተሟገተም ፡ ጊዜ ፡ ተረቶ ፡ ይውጣ ፤ ጸሎቱም ፡ ኀጢአት ፡ ትኹንበት ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 8 ፤ ዘመኖቹም ፡ ጥቂት ፡ ይኹኑ ፤ ሹመቱንም ፡ ሌላ ፡ ይውሰድ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 9 ፤ ልጆቹም ፡ ድኻ ፡ አደግ ፡ ይኹኑ ፥ ሚስቱም ፡ መበለት ፡ ትኹን ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 10 ፤ ልጆቹም ፡ ተናውጠው ፡ ይቅበዝበዙ ፡ ይለምኑም ፥ ከስፍራቸውም ፡ ይባረሩ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 11 ፤ ባለዕዳም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይበርብረው ፥ እንግዳዎችም ፡ ድካሙን ፡ ኹሉ ፡ ይበዝብዙት ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 12 ፤ የሚያግዘውንም ፡ አያግኝ ። ለድኻ ፡ አደግ ፡ ልጆቹም ፡ የሚራራ ፡ አይኑር ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 13 ፤ ልጆቹ ፡ ይጥፉ ፤ ባንድ ፡ ትውልድ ፡ ስሙ ፡ ይደምሰስ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 14 ፤ የአባቶቹ ፡ ኀጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትታሰብ ፤ የእናቱም ፡ ኀጢአት ፡ አትደምሰስ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 15 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘልጊዜ ፡ ይኑሩ ፤ መታሰቢያቸው ፡ ከምድር ፡ ይጥፋ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 16 ፤ ምሕረትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አላሰበምና ፡ ችግረኛንና ፡ ምስኪንን ፡ ልቡ ፡ የተሰበረውንም ፡ ሰው ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ አሳደደ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 17 ፤ መርገምን ፡ ወደደ ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ መጣች ፤ በረከትንም ፡ አልመረጠም ፡ ከርሱም ፡ ራቀች ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 18 ፤ መርገምን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ለበሳት ፥ እንደ ፡ ውሃም ፡ ወደ ፡ አንጐቱ ፥ እንደ ፡ ቅባትም ፡ ወደ ፡ ዐጥንቱ ፡ ገባች ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 19 ፤ እንደሚለብሰው ፡ ልብስ ። ዘልጊዜም ፡ እንደሚታጠቀው ፡ ትጥቅ ፡ ይኹነው ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 20 ፤ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሚያጣሉኝ ፡ በነፍሴም ፡ ላይ ፡ ክፉን ፡

በሚናገሩ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 21 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ምሕረትኽን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ አድርግ ፤ ምሕረትኽ ፡ መልካም ፡ ናትና ፥ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 22 ፤ እኔ ፡ ችግረኛ ፡ ምስኪንም ፡ ነኝና ፥ ልቤም ፡ በውስጤ ፡ ደነገጠብኝ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 23 ፤ እንዳለፈ ፡ ጥላ ፡ አለቅኹ ፥ እንደ ፡ አንበጣም ፡ ረገፍኹ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 24 ፤ ጕልበቶቼ ፡ በጾም ፡ ደከሙ ፤ ሥጋዬም ፡ ቅቤ ፡ በማጣት ፡ ከሳ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 25 ፤ እኔም ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ለነውር ፡ ኾንኹ ፤ ባዩኝ ፡ ጊዜ ፡ ራሳቸውን ፡ ነቀነቁ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 26 ፤ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ርዳኝ ፥ እንደ ፡ ምሕረትኽም ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 27 ፤ አቤቱ ፥ እጅኽ ፡ ይህች ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ አንተም ፡ ይህችን ፡ እንዳደረግኽ ፡ ይወቁ ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 28 ፤ እነርሱ ፡ ይራገማሉ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ባርክ ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ የሚነሡ ፡ ይፈሩ ፥ ባሪያኽ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 29 ፤ የሚያጣሉኝ ፡ ዕፍረትን ፡ ይልበሱ ፤ ዕፍረታቸውን ፡ እንደ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ይልበሷት ።

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በአፌ ፡ እጅግ ፡ አመሰግነዋለኹ ። በብዙዎችም ፡ መካከል ፡ አከብረዋለኹ ፤

መዝ. ፡ 108 ፡ (109) ፡ 31 ፤ ነፍሱን ፡ ከሚያሳድዷት ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ በድኻ ፡ ቀኝ ፡ ቆሟልና ።

_____መዝሙር ፡ 109 ፡ (110) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጌታዬን ፦ ጠላቶችኽን ፡ ለእግርኽ ፡ መቀመጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ የኀይልን ፡ በትር ፡ ከጽዮን ፡ ይልክልኻል ፤ በጠላቶችኽም ፡ መካከል ፡ ግዛ ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 3 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ቀድሞ ፡ በኀይልኽ ፡ ቀን ፥ በቅዱሳን ፡ ብርሃን ፥ ከአጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ አስቀድሞ ፡ ከሆድ ፡ ወለድኩኽ ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 4 ፤ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሥርዐት ፡ አንተ ፡ ለዘለዓለም ፡ ካህን ፡ ነኽ ፡ ብሎ ፥ እግዚአብሔር ፡ ማለ ፡ አይጸጸትም ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቀኝኽ ፡ ነገሥታትን ፡ በቍጣው ፡ ቀን ፡ ይቀጠቅጣቸዋል ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 6 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይፈርዳል ፥ ሬሳዎችንም ፡ ያበዛል ፤ በሰፊ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ራሶችን ፡ ይቀጠቅጣል ።

መዝ. ፡ 109 ፡ (110) ፡ 7 ፤ በመንገድ ፡ ከፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ይጠጣል ፤ ስለዚህ ፥ ራስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

መዝሙር ፡ 110 ፡ (111) ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። አቤቱ ፥ በቅኖች ፡ ሸንጎ ፡ በጉባኤም ፡ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፥ ደስ ፡ በሚሠኙባት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የተፈለገች ፡ ናት ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 3 ፤ ሥራው ፡ ምስጋናና ፡ ግርማ ፡ ነው ፤ ጽድቁም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 4 ፤ ለተአምራቱ ፡ መታሰቢያን ፡ አደረገ ፤ እግዚአብሔር ፡ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 5 ፤ ለሚፈሩት ፡ ምግብን ፡ ሰጣቸው ፤ ኪዳኑንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ያስባል ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 6 ፤ የአሕዛብን ፡ ርስት ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝቡ ፡ የሥራውን ፡ ብርታት ፡ አሳየ ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 7 ፤ የእጆቹ ፡ ሥራ ፡ እውነትና ፡ ፍርድ ፡ ነው ፤ ትእዛዙም ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 8 ፤ ለዘለዓለምም ፡ የጸና ፡ ነው ፥ በእውነትና ፡ በቅንም ፡ የተሠራ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 9 ፤ መድኀኒትንም ፡ ለሕዝቡ ፡ ሰደደ ፥ ኪዳኑንም ፡ ለዘለዓለም ፡ አዘዘ ፤ ስሙ ፡ የተቀደሰና ፡ የተፈራ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 110 ፡ (111) ፡ 10 ፤ የጥበብ ፡ መገመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ፥ ለሚያደርጓትም ፡ ኹሉ ፡ ደኅና ፡ ማስተዋል ፡ አላቸው ፤ ምስጋናውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

መዝሙር ፡ 111 ፡ (112) ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፥ ትእዛዙንም ፡ እጅግ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 2 ፤ ዘሩ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀያል ፡ ይኾናል ፤ የቅኖች ፡ ትውልድ ፡ ትባረካለች ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 3 ፤ ክብርና ፡ ባለጠግነት ፡ በቤቱ ፡ ነው ፥ ጽድቁም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 4 ፤ ለቅኖች ፡ ብርሃን ፡ በጨለማ ፡ ወጣ ፤ መሐሪና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ጻድቅም ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 5 ፤ ቸር ፡ ሰው ፡ ይራራል ፡ ያበድራልም ፥ በፍርድም ፡ ነገሩን ፡ ይፈጽማል ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 6 ፤ ለዘለዓለም ፡ አይናወጥም ፤ የጻድቅ ፡ መታሰቢያ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 7 ፤ ከክፉ ፡ ነገር ፡ አይፈራም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ለመታመን ፡ ልቡ ፡ የጸና ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 8 ፤ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡ ልቡ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፥ አይፈራም ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 9 ፤ በተነ ፡ ለችግረኞችም ፡ ሰጠ ፤ ጽድቁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ ይኖራል ፤ ቀንዱ ፡ በክብር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

መዝ. ፡ 111 ፡ (112) ፡ 10 ፤ ኀጢአተኛም ፡ አይቶ ፡ ይቈጣል ፥ ጥርሱንም ፡ ያፋጫል ፥ ይቀልጣልም ፤ የኀጢአተኞችም ፡ ምኞት ፡ ትጠፋለች ።

መዝሙር ፡ 112 ፡ (113) ።

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ሆይ ፥ አመስግኑት ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ አመስግኑ ።

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 2 ፤ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 3 ፤ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መግቢያው ፡ ድረስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ይመስገን ።

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍተኛ ፡ ነው ፥ ክብሩም ፡ ከሰማያት ፡ በላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 5 ፤ እንደ ፡ አምላካችን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማን ፡ ነው ፧ በላይ ፡ የሚኖር ፤

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 6 ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ የተዋረዱትን ፡ የሚያይ ፤

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 7-8 ፤ ከአለቃዎች ፡ ጋራ ፡ ከሕዝቡም ፡ አለቃዎች ፡ ጋራ ፡ ያኖረው ፡ ዘንድ ፡ ችግረኛን ፡ ከመሬት ፡ የሚያነሣ ፥ ምስኪኑንም ፡ ከፋንድያ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፤

መዝ. ፡ 112 ፡ (113) ፡ 9 ፤ መካኒቱን ፡ በቤት ፡ የሚያኖራት ፥ ደስ ፡ የተሠኘችም ፡ የልጆች ፡ እናት ፡ የሚያደርጋት ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 113 ፡ (114) ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 1 ፤ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፥ የያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ከእንግዳ ፡ ሕዝብ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 2 ፤ ይሁዳ ፡ መቅደሱ ፥ እስራኤልም ፡ ግዛቱ ፡ ኾነ ።

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 3 ፤ ባሕር ፡ አየች ፡ ሸሸችም ፥ ዮርዳኖስም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ።

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 4 ፤ ተራራዎች ፡ እንደ ፡ ኰርማዎች ፥ ኰረብታዎችም ፡ እንደ ፡ ጠቦቶች ፡ ዘለሉ ።

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 5 ፤ አንቺ ፡ ባሕር ፡ የሸሸሽ ፥ አንቺም ፡ ዮርዳኖስ ፡ ወደ ፡ ኋላሽ ፡ የተመለሽ ፥ ምን ፡ ኾናችኋል ፧

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 6 ፤ እናንተም ፡ ተራራዎች ፥ እንደ ፡ ኰርማዎች ፥ ኰረብታዎችስ ፥ እንደ ፡ ጠቦቶች ፡ ለምን ፡ ዘለላችኹ ፧

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 7 ፤ ከያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ፊት ፥ ከጌታ ፡ ፊት ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፤

መዝ. ፡ 113 ፡ (114) ፡ 8 ፤ ድንጋዩን ፡ ወደውሃ ፡ መቆሚያ ፥ ጭንጫውንም ፡ ወደውሃ ፡ ምንጭ ፡ ከለወጠ ።

መዝሙር ፡ 114 ፡ (115) ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 1 ፤ ለእኛ ፡ አይደለም ፥ አቤቱ ፥ ለእኛ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለስምኽ ፡ ስለ ፡ ምሕረትኽ ፡ ስለ ፡ እውነትኽም ፡ ምስጋናን ፡ ስጥ ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 2 ፤ አሕዛብ ፦ አምላካቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አይበሉ ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 3 ፤ አምላካችንስ ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ነው ፤ በሰማይም ፡ በምድርም ፡ የፈቀደውን ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 4 ፤ የአሕዛብ ፡ ጣዖታቶች ፡ የወርቅና ፡ የብር ፥ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 5 ፤ አፍ ፡ አላቸው ፡ አይናገሩምም ፤ ዐይን ፡ አላቸው ፡ አያዩምም ፤

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 6 ፤ ጐሮ ፡ አላቸው ፡ አይሰሙምም ፤ አፍንጫ ፡ አላቸው ፡ አያሸቱምም ፤

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 7 ፤ እጅ ፡ አላቸው ፡ አይዳሰሱምም ፤ እግር ፡ አላቸው ፡ አይኼዱምም ፤ በጉሮሯቸውም ፡ አይናገሩም ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 8 ፤ የሚሠሯቸውም ፡ የሚያምኑባቸውም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ይኹኑ ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 9 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ፤ ረድኤታቸውና ፡ መታመኛቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 10 ፤ የአሮን ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ፡ ረድኤታቸውና ፡ መታመኛቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩ ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ፤ ረድኤታቸውና ፡ መታመኛቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐሰበን ፡ ይባርከንማል ፤ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ይባረካል ፥ የአሮንንም ፡ ቤት ፡ ይባረካል ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩትን ፥ ትንንሾችንና ፡ ትልልቆችን ፡ ይባርካል ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ በላያችኹ ፥ በላያችኹና ፡ በልጆቻችኹ ፡ ላይ ፡ ይጨምር ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 15 ፤ እናንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ለሠራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተባረካችኹ ፡ ናችኹ ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 16 ፤ የሰማያት ፡ ሰማይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ምድርን ፡ ግን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ሰጣት ።

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ ሙታን ፡ የሚያመሰግኑኽ ፡ አይደሉም ፡ ወደ ፡ ሲኦልም ፡ የሚወርዱ ፡ ኹሉ ፤

መዝ. ፡ 114 ፡ (115) ፡ 18 ፤ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ ግን ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንባርካለን ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 115 ፡ (116) ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ የልመናዬን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቷልና ፥ ወደድኹት ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 2 ፤ ጐሮውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አዘንብሏልና ፥ በዘመኔ ፡ ኹሉ ፡ እጠራዋለኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 3 ፤ የሞት ፡ ጣር ፡ ያዘኝ ፥ የሲኦልም ፡ ሕማም ፡ አገኘኝ ፤ ጭንቀትንና ፡ መከራን ፡

አገኘኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ጠራኹ ፦ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ አድናት ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ መሐሪና ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፥ አምላካችንም ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕፃናትን ፡ ይጠብቃል ፤ ተቸገርኹ ፡ ርሱም ፡ አዳነኝ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 7 ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ዕረፍትሽ ፡ ተመለሺ ፥ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ አድርጎልሻልና ፤

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 8 ፤ ነፍሴን ፡ ከሞት ፥ ዐይኔንም ፡ ከእንባ ፥ እግሬንም ፡ ከመሰናከል ፡ አድኗልና ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 9 ፤ በሕያዋን ፡ አገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እኼዳለኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 10 ፤ አመንኹ ፡ ስለዚህም ፡ ተናገርኹ ፤ እኔም ፡ እጅግ ፡ ተቸገርኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 11 ፤ እኔም ፡ ከድንጋጤዬ ፡ የተነሣ ፦ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 12 ፤ ስላደረገልኝ ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምንን ፡ እመልሳለኹ ፧

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 13 ፤ የመድኀኒትን ፡ ጽዋ ፡ እቀበላለኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ እጠራለኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 14 ፤ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ስእለቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እፈጽማለኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 15 ፤ የቅዱሳኑ ፡ ሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የከበረ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ነኝ ፥ ባሪያኽ ፡ ነኝ ፥ የሴት ፡ ባሪያኽም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤ ሰንሰለቴን ፡ ሰበርኽ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 17 ፤ ለአንተ ፡ የምስጋና ፡ መሥዋዕትን ፡ እሠዋለኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ እጠራለኹ ።

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 18 ፤ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ስእለቴን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እፈጽማለኹ ፥

መዝ. ፡ 115 ፡ (116) ፡ 19 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፥ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ በመካከልሽም ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 116 ፡ (117) ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 116 ፡ (117) ፡ 1 ፤ አሕዛብ ፡ ኹላችኹ ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑት ፥ ወገኖችም ፡ ኹሉ ፡ ያመስግኑት ፤

መዝ. ፡ 116 ፡ (117) ፡ 2 ፤ ምሕረቱ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ጸንታለችና ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እውነት ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኖራለች ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 117 ፡ (118) ።

ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ቸር ፡ ነውና ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ናትና ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 2 ፤ ቸር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ አኹን ፡ ይንገሩ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 3 ፤ ቸር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ የአሮን ፡ ቤት ፡ አኹን ፡ ይንገሩ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 4 ፤ ቸር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ ኹሉ ፡ አኹን ፡ ይንገሩ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 5 ፤ በተጨነቅኹ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጠራኹት ፤ ሰማኝ ፡ አሰፋልኝም ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፥ አልፈራም ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፧

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ረዳቴ ፡ ነው ፥ እኔም ፡ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ አያለኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 8 ፤ በሰው ፡ ከመታመን ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መታመን ፡ ይሻላል ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 9 ፤ በገዥዎች ፡ ተስፋ ፡ ከማድረግ ፡ ይልቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ማድረግ ፡ ይሻላል ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 10 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ከበቡኝ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ አሸነፍኋቸው ፤

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 11 ፤ መክበቡንስ ፡ ከበቡኝ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ አሸነፍኋቸው ፤

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 12 ፤ ንብ ፡ ማርን ፡ እንዲከብ ፡ ከበቡኝ ፥ እሳትም ፡ በሾኽ ፡ ውስጥ ፡ እንዲነድ ፡ ነደዱ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ አሸነፍኋቸው ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 13 ፤ ገፋኸኝ ፥ ለመውደቅም ፡ ተንገዳገድኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አገዘኝ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 14 ፤ ኀይሌም ፡ ዝማሬዬም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ መድኀኒት ፡ ኾነልኝ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 15 ፤ የእልልታና ፡ የመድኀኒት ፡ ድምፅ ፡ በጻድቃን ፡ ድንኳን ፡ ነው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ኀይልን ፡ አደረገች ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገችኝ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ኀይልን ፡ አደረገች ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 17 ፤ አልሞትም ፡ በሕይወት ፡ እኖራለኹ ፡ እንጂ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥራ ፡ እናገራለኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 18 ፤ መገሠጽስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገሠጸኝ ፤ ለሞት ፡ ግን ፡ አልሰጠኝም ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 19 ፤ የጽድቅን ፡ ደጆች ፡ ክፈቱልኝ ፤ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ገብቼ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 20 ፤ ይህች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ደጅ ፡ ናት ፤ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጻድቃን ፡ ይገባሉ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 21 ፤ ሰምተኸኛልና ፥ መድኀኒትም ፡ ኾነኸኛልና ፥ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 22 ፤ ግንበኞች ፡ የናቁት ፡ ድንጋይ ፥ ርሱ ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ ኾነ ፥

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 23 ፤ ይህች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ኾነች ፥ ለዐይናችንም ፡ ድንቅ ፡ ናት ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሠራት ፡ ቀን ፡ ይህች ፡ ናት ፤ ሐሤትን ፡ እናድርግ ፥ በርሷም ፡ ደስ ፡ ይበለን ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 25 ፤ አቤቱ ፥ እባክኽ ፥ አኹን ፡ አድን ፤ አቤቱ ፥ እባክኽ ፥ አኹን ፡ አቅና ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 26 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ ቡሩክ ፡ ነው ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ መረቅናችኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 27 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፥ ለእኛም ፡ በራልን ፤ እስከመሠዊያው ፡ ቀንዶች ፡ ድረስ ፡ የበዓሉን ፡ መሥዋዕት ፡ በገመድ ፡ እሰሩት ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 28 ፤ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፡ አመሰግንኽማለኹ ። አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግኻለኹ ፤ ሰምተኽኛልና ፥ መድኀኒትም ፡ ኾነኽኛልና ፥ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 117 ፡ (118) ፡ 29 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ቸር ፡ ነውና ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ናትና ።

መዝሙር ፡ 118 ፡ (119) ።

አሌፍ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 1 ፤ በመንገዳቸው ፡ ንጹሓን ፡ የኾኑ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ የሚኼዱ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 2 ፤ ምስክሩን ፡ የሚፈልጉ ፥ በፍጹም ፡ ልብ ፡ የሚሹት ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ፤

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 3 ፤ ዐመፅንም ፡ አያደርጉም ፥ በመንገዶቹም ፡ ይኼዳሉ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 4 ፤ ትእዛዛትኽን ፡ እጅግ ፡ እንጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ አዘዝኽ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 5 ፤ ሥርዐትኽን ፡ ለመጠበቅ ፤ መንገዶቼ ፡ ይቀኑ ፡ ዘንድ ፡ እወድ ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 6 ፤ ትእዛዝኽን ፡ ኹሉ ፡ ስመለከት ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አላፍርም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ የጽድቅኽን ፡ ፍርድ ፡ ስማር ፡ በቅን ፡ ልብ ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 8 ፤ ሥርዐትኽን ፡ እጠብቃለኹ ፤ በፍጹም ፡ አትጣለኝ ።

ቤት

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 9 ፤ ጕልማሳ ፡ መንገዱን ፡ በምን ፡ ያነጻል ፧ ቃልኽን ፡ በመጠበቅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 10 ፤ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ ፈለግኹኽ ፥ ከትእዛዝኽ ፡ አታርቀኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 11 ፤ አንተን ፡ እንዳልበድል ፥ ቃልኽን ፡ በልቤ ፡ ሰወርኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ቡሩክ ፡ ነኽ ፤ ሥርዐትኽን ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 13 ፤ የአፍኽን ፡ ፍርድ ፡ ኹሉ ፡ በከንፈሬ ፡ ነገርኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ብልጥግና ፡ ኹሉ ፡ በምስክርኽ ፡ መንገድ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 15 ፤ ትእዛዝኽን ፡ አሰላስላለኹ ፥ መንገድኽንም ፡ እፈልጋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 16 ፤ በትእዛዝኽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ቃልኽንም ፡ አልረሳም ።

ጋሜል

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 17 ፤ ለባሪያኽ ፡ መልካም ፡ አድርግ ፡ ሕያው ፡ እንድኾን ፥ ቃልኽንም ፡ እንድጠብቅ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 18 ፤ ዐይኖቼን ፡ ክፈት ፥ ከሕግኽም ፡ ተኣምራትኽን ፡ አያለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 19 ፤ እኔ ፡ በምድር ፡ እንግዳ ፡ ነኝ ፤ ትእዛዛትኽን ፡ ከእኔ ፡ አትሰውር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 20 ፤ ነፍሴ ፡ ኹልጊዜ ፡ ፍርድኽን ፡ እጅግ ፡ ናፈቀች ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 21 ፤ ከትእዛዛትኽ ፡ የሳቱትን ፡ ትዕቢተኞችንና ፡ ርጉማንን ፡ ዘለፍኽ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 22 ፤ ምስክርኽን ፡ ፈልጌያለኹና ፥ ስድብንና ፡ ነውርን ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 23 ፤ አለቃዎች ፡ ደግሞ ፡ ተቀምጠው ፡ እኔን ፡ ዐሙኝ ፤ ባሪያኽ ፡ ግን ፡ ሕግኽን ፡ ያሰላስል ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 24 ፤ ምስክርኽም ፡ ተድላዬ ፡ ነው ፥ ሥርዐትኽም ፡ መካሪዬ ፡ ነው ።

ዳሌጥ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 25 ፤ ነፍሴ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተጠጋች ፤ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 26 ፤ መንገድኽን ፡ ነገርኹ ፡ ሰማኸኝም ፤ ሥርዐትኽን ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 27 ፤ የሥርዐትኽን ፡ መንገድ ፡ እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፥ ተኣምራትኽንም ፡ አሰላስላለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 28 ፤ ከሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ነፍሴ ፡ አንቀላፋች ፤ በቃልኽ ፡ አጠንክረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 29 ፤ የዐመፅን ፡ መንገድ ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ፥ በሕግኽም ፡ ማረኝ ፤

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 30 ፤ የእውነትኽን ፡ መንገድ ፡ መረጥኹ ፥ ፍርድኽንም ፡ አልረሳኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 31 ፤ አቤቱ ፥ ምስክርኽን ፡ ተጠጋኹ ፤ አታሳፍረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 32 ፤ ልቤን ፡ ባሰፋኸው ፡ ጊዜ ፥ በትእዛዝኽ ፡ መንገድ ፡ ሮጥኹ ።

ሄ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 33 ፤ አቤቱ ፥ የሥርዐትኽን ፡ መንገድ ፡ አስተምረኝ ፥ ኹልጊዜም ፡ እፈልገዋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 34 ፤ እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፥ ሕግኽንም ፡ እፈልጋለኹ ፤ በፍጹም ፡ ልቤም ፡

እጠብቀዋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 35 ፤ ርሷን ፡ ወድጃለኹና ፡ የትእዛዝኽን ፡ መንገድ ፡ ምራኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 36 ፤ ልቤን ፡ ወደ ፡ ምስክርኽ ፡ አዘንብል ፥ ወደ ፡ ሥሥትም ፡ አይኹን ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 37 ፤ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ እንዳያዩ ፡ ዐይኖቼን ፡ መልስ ፤ በመንገድኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 38 ፤ እንዲፈራኽ ፡ ባሪያኽን ፡ በቃልኽ ፡ አጽና ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 39 ፤ ፍርድኽ ፡ መልካም ፡ ናትና ፥ የተጠራጠርኹትን ፡ ስድብ ፡ ከእኔ ፡ አርቅ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 40 ፤ እንሆ ፥ ትእዛዝኽን ፡ ናፈቅኹ ፤ በጽድቅኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ

ዋው

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 41 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ቃልኽ ፥ ምሕረትኽና ፡ መድኀኒትኽ ፡ ይምጡልኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 42 ፤ በቃልኽ ፡ ታምኛለኹና ፡ ለሚሰድቡኝ ፡ በነገር ፡ እመልስላቸዋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 43 ፤ በፍርድኽም ፡ ታምኛለኹና ፡ የእውነትን ፡ ቃል ፡ ከአፌ ፡ ፈጽመኽ ፡ አታርቅ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 44 ፤ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ ዘልጊዜ ፡ ሕግኽን ፡ እጠብቃለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 45 ፤ ትእዛዛትኽንም ፡ ፈልጌያለኹና ፡ አስፍቼ ፡ እኼዳለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 46 ፤ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ምስክርኽን ፡ እናገራለኹ ፥ አላፍርምም ፤

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 47 ፤ እጅግም ፡ በወደድኋቸው ፡ በትእዛዛትኽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 48 ፤ እጆቼንም ፡ ወደ ፡ ወደድኋቸው ፡ ወደ ፡ ትእዛዛትኽ ፡ አነሣለኹ ፤ ሥርዐትኽንም ፡ አሰላስላለኹ ።

ዛይ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 49 ፤ ለባሪያኽ ፡ ተስፋ ፡ ያስደረግኸውን ፡ ቃልኽን ፡ ዐስብ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 50 ፤ ቃልኽ ፡ ሕያው ፡ አድርጎኛልና ፥ ይህች ፡ በመከራዬ ፡ ደስ ፡ አሠኝችኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 51 ፤ ትዕቢተኞች ፡ እጅግ ፡ ዐመፁ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከሕግኽ ፡ አልራቅኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 52 ፤ ከጥንት ፡ የነበረውን ፡ ፍርድኽን ፡ ዐሰብኹ ፥ አቤቱ ፥ ተጽናናኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 53 ፤ ሕግኽን ፡ ከተዉ ፡ ከኀጢአተኞች ፡ የተነሣ ፡ ሐዘን ፡ ያዘኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 54 ፤ በእንግድነቴ ፡ አገር ፡ ሥርዐትኽ ፡ መዝሙር ፡ ኾነችኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 55 ፤ አቤቱ ፥ በሌሊት ፡ ስምኽን ፡ ዐሰብኹ ፥ ሕግኽንም ፡ ጠበቅኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 56 ፤ ትእዛዛትኽንም ፡ ፈልጌያለኹና ፤ ይህች ፡ ኾነችልኝ ።

ሔት

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 57 ፤ እግዚአብሔር ፡ ክፍሌ ፡ ነው ፤ ሕግኽን ፡ እጠብቃለኹ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 58 ፤ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ተማለልኹ ፤ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ማረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 59 ፤ ስለ ፡ መንገዶችኽ ፡ ዐሰብኹ ፥ እግሬንም ፡ ወደ ፡ ምስክሮችኽ ፡ መለስኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 60 ፤ ትእዛዝኽን ፡ ለመጠበቅ ፡ ጨከንኹ ፡ አልዘገየኹምም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 61 ፤ የኃጥኣን ፡ ገመዶች ፡ ተተበተቡብኝ ፤ ሕግኽን ፡ ግን ፡ አልረሳኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 62 ፤ ስለጽድቅኽ ፡ ፍርድ ፥ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ አመሰግንኽ ፡ ዘንድ ፡ እነሣለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 63 ፤ እኔ ፡ ለሚፈሩኽ ፡ ኹሉ ፥ ትእዛዝኽንም ፡ ለሚጠብቁ ፡ ባልንጀራ ፡ ነኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 64 ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ሞላች ፤ ሥርዐትኽን ፡ አስተምረኝ ።

ጤት

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 65 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ለባሪያኽ ፡ መልካም ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 66 ፤ በትእዛዛትኽ ፡ ታምኛለኹና ፡ መልካም ፡ ምክርና ፡ ዕውቀትን ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 67 ፤ እኔ ፡ ሳልጨነቅ ፡ ሳትኹ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ቃልኽን ፡ ጠበቅኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 68 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ቸር ፡ ነኽ ፥ በቸርነትኽም ፡ ሥርዐትኽን ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 69 ፤ የትዕቢተኞች ፡ ዐመፅ ፡ በላዬ ፡ በዛ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ ትእዛዛትኽን ፡ እፈልጋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 70 ፤ ልባቸው ፡ እንደ ፡ ወተት ፡ ረጋ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በሕግኽ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 71 ፤ ሥርዐትኽን ፡ እማር ፡ ዘንድ ፡ ያስጨነቅኸኝ ፡ መልካም ፡ ኾነልኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 72 ፤ ከአእላፋት ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ይልቅ ፡ የአፍኽ ፡ ሕግ ፡ ይሻለኛል ።

ዮድ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 73 ፤ እጆችኽ ፡ ሠሩኝ ፡ አበጃጁኝም ፤ እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፥ ትእዛዛትኽንም ፡ እማራለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 74 ፤ በቃልኽ ፡ ታምኛለኹና ፡ የሚፈሩኽ ፡ እኔን ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 75 ፤ አቤቱ ፥ ፍርድኽ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፥ በእውነትኽም ፡ እንዳስቸገርኸኝ ፡ ዐወቅኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 76 ፤ ምሕረትኽ ፡ ለመጽናናቴ ፡ ትኹነኝ ፥ እንደ ፡ ቃልኽም ፡ ለባሪያኽ ፡ ይኹነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 77 ፤ ሕግኽ ፡ ተድላዬ ፡ ናትና ፥ ቸርነትኽ ፡ ትምጣልኝ ፥ በሕይወትም ፡ ልኑር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 78 ፤ ትዕቢተኞች ፡ በዐመፅ ፡ ጠመውብኛልና ፥ ይፈሩ ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በትእዛዝኽ ፡ እጫወታለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 79 ፤ የሚፈሩኽና ፡ ምስክሮችኽን ፡ የሚያውቁ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሱ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 80 ፤ እንዳላፍር ፡ ልቤ ፡ በሥርዐትኽ ፡ የቀና ፡ ይኹን ።

ካፍ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 81 ፤ ነፍሴ ፡ መድኀኒትኽን ፡ ናፈቀች ፤ በቃልኽም ፡ ታመንኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 82 ፤ መቼ ፡ ታጽናናኛለኽ ፡ እያልኹ ፡ ዐይኖቼ ፡ ስለ ፡ ቃልኽ ፡ ፈዘዙ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 83 ፤ በጢስ ፡ እንዳለ ፡ አቀ፡ማዳ ፡ ኾኛለኹና ፤ ሥርዐትኽን ፡ ግን ፡ አልረሳኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 84 ፤ የባሪያኽ ፡ ዘመኖች ፡ ስንት ፡ ናቸው ፧ በሚያሳድዱኝስ ፡ ላይ ፡ መቼ ፡ ትፈርድልኛለኽ ፧

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 85 ፤ ኀጢአተኞች ፡ ጨዋታን ፡ ነገሩኝ ፥ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ሕግኽ ፡ ግን ፡ አይደለም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 86 ፤ ትእዛዛትኽ ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፡ ናቸው ፤ በዐመፅ ፡ አሳ፡ደውኛል ፤ ርዳኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 87 ፤ ከምድር ፡ ሊያጠፉኝ ፡ ጥቂት ፡ ቀርቷቸው ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ትእዛዛትኽን ፡ አልተውኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 88 ፤ እንደ ፡ ምሕረትኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ፤ የአፍኽንም ፡ ምስክር ፡ እጠብቃለኹ ።

ላሜድ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 89 ፤ አቤቱ ፥ ቃልኽ ፡ በሰማይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 90 ፤ እውነትኽ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ምድርን ፡ መሠረትኻት ፡ ርሷም ፡ ትኖራለች ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 91 ፤ ኹሉም ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ናቸውና ፥ ቀኑ ፡ በትእዛዝኽ ፡ ይኖራል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 92 ፤ ሕግኽ ፡ ተድላዬ ፡ ባይኾን ፥ ቀድሞ ፡ በጕስቍ፡ልናዬ ፡ በጠፋኹ ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 93 ፤ በርሱ ፡ ሕያው ፡ አድርገኸኛልና ፥ ፍርድኽን ፡ ለዘለዓለም ፡ አልረሳም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 94 ፤ እኔ ፡ የአንተ ፡ ነኝ ፤ ፍርድኽን ፡ ፈልጌያልኹና ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 95 ፤ ኀጢአተኞች ፡ ያጠፉኝ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቁኝ ፤ ምስክርኽን ፡ ግን ፡ መረመርኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 96 ፤ የሥራኽን ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ አየኹ ፤ ትእዛዝኽ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ሰፊ ፡ ነው ።

ሜም

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 97 ፤ አቤቱ ፥ ሕግኽን ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እጅግ ፡ ወደድኹ! ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ ትዝታዬ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 98 ፤ ለዘለዓለም ፡ ለእኔ ፡ ነውና ፥ ትእዛዝኽ ፡ ከጠላቶቼ ፡ ይልቅ ፡ አስተዋይ ፡ አደረገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 99 ፤ ምስክርኽ ፡ ትዝታዬ ፡ ነውና ፥ ካስተማሩኝ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አስተዋልኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 100 ፤ ትእዛዝኽን ፡ ፈልጌያለኹና ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ይልቅ ፡ አስተዋልኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 101 ፤ ቃልኽን ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ከክፉ ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ እግሬን ፡ ከለከልኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 102 ፤ አስተምረኽኛልና ፥ ከፍርድኽ ፡ አልራቅኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 103 ፤ ቃልኽ ፡ ለጕረሮዬ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፤ ከማርና ፡ ከወለላ ፡ ይልቅ ፡ ለአፌ ፡ ጣፈጠኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 104 ፤ ከትእዛዝኽ ፡ የተነሣ ፡ አስተዋልኹ ፤ ስለዚህ ፥ የሐሰትን ፡ መንገድ ፡ ጠላኹ ።

ኖን

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 105 ፤ ሕግኽ ፡ ለእግሬ ፡ መብራት ፥ ለመንገዴ ፡ ብርሃን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 106 ፤ የጽድቅኽን ፡ ፍርድ ፡ እጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ማልኹ ፥ አጸናኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 107 ፤ እጅግ ፡ ተቸገርኹ ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 108 ፤ አቤቱ ፥ ከአፌ ፡ የሚወጣውን ፡ ቃል ፡ ውደድ ፥ ፍርድኽንም ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 109 ፤ ነፍሴ ፡ ዘልጊዜ ፡ በእጅኽ ፡ ውስጥ ፡ ናት ፤ ሕግኽን ፡ ግን ፡ አልረሳኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 110 ፤ ኀጢአተኞች ፡ ወጥመድን ፡ ዘረጉብኝ ፤ ከትእዛዝኽ ፡ ግን ፡ አልሳትኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 111 ፤ የልቤ ፡ ደስታ ፡ ነውና ፥ ምስክርኽን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወረስኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 112 ፤ ለዘለዓለም ፡ ለፍጻሜውም ፡ ትእዛዝኽን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ልቤን ፡ አዘነበልኹ ።

ሳምኬት

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 113 ፤ ዐመፀኞችን ፡ ጠላኹ ፥ ሕግኽን ፡ ግን ፡ ወደድኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 114 ፤ አንተ ፡ ረዳቴና ፡ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ፥ በቃልኽም ፡ ተማመንኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 115 ፤ እናንተ ፡ ኀጢአተኞች ፥ ከእኔ ፡ ራቁ ፥ የአምላኬንም ፡ ትእዛዝ ፡ ልፈልግ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 116 ፤ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ደግፈኝ ፥ ሕያውም ፡ እኾናለኹ ። ከተስፋዬም ፡ አልፈር ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 117 ፤ ርዳኝ ፡ እድናለኹም ፥ ዘልጊዜም ፡ ሥርዐትኽን ፡ እመረምራለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 118 ፤ ምኞታቸው ፡ ዐመፃ ፡ ነውና ፥ ከሥርዐትኽ ፡ የሚርቁትን ፡ ኹሉ ፡ አጐሳቈልኻቸው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 119 ፤ የምድርን ፡ ኀጢአተኞች ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ርኵሰት ፡ አጠፋኻቸው ፤ ስለዚህ ፥ ምስክርኽን ፡ ወደድኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 120 ፤ ሥጋዬ ፡ አንተን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ደነገጠ ፤ ከፍርድኽ ፡ የተነሣ ፡ ፈርቻለኹ ።

ዔ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 121 ፤ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ ሠራኹ ፤ ለሚያስጨንቁኝ ፡ አሳልፈኽ ፡ አትስጠኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 122 ፤ ባሪያኽን ፡ በመልካም ፡ ጠብቀው ፤ ትዕቢተኞችም ፡ አይጋፉኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 123 ፤ ዐይኖቼ ፡ ለማዳንኽ ፥ ለጽድቅኽም ፡ ቃል ፡ ፈዘዙ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 124 ፤ ለባሪያኽ ፡ እንደ ፡ ምሕረትኽ ፡ አድርግ ፥ ሥርዐትኽንም ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 125 ፤ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ነኝ ፤ እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፥ ምስክርኽንም ፡ ዐውቃለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 126 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሥራ ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ ሕግኽንም ፡ ሻሩት ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 127 ፤ ስለዚህ ፥ ከወርቅና ፡ ከዕንቊ ፡ ይልቅ ፡ ትእዛዝኽን ፡ ወደድኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 128 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ትእዛዝኽ ፡ ኹሉ ፡ አቀናኹ ፥ የዐመፅንም ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ጠላኹ ።

ፊ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 129 ፤ ምስክሮችኽ ፡ ድንቆች ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፥ ነፍሴ ፡ ፈለገቻቸው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 130 ፤ የቃልኽ ፡ ፍቺ ፡ ያበራል ፥ ሕፃናትንም ፡ አስተዋዮች ፡ ያደርጋል ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 131 ፤ አፌን ፡ ከፈትኹ ፥ አለከለክኹም ፤ ወደ ፡ ትእዛዝኽ ፡ ናፍቄያለኹና ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 132 ፤ ስምኽን ፡ ለሚወዱ ፡ እንደምታደርገው ፡ ፍርድ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመልከት ፥ ማረኝም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 133 ፤ አካኼድን ፡ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ አቅና ፤ ኀጢአትም ፡ ኹሉ ፡ አይግዛኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 134 ፤ ከሰው ፡ ግፍ ፡ አድነኝ ፤ ትእዛዝኽንም ፡ እጠብቃለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 135 ፤ በባሪያኽ ፡ ላይ ፡ ፊትኽን ፡ አብራ ፥ ሥርዐትኽንም ፡ አስተምረኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 136 ፤ ሕግኽን ፡ አልጠበቅኹምና ፡ የውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ ከዐይኖቼ ፡ ፈሰሰ ።

ጻዴ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 137 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፥ ፍርድኽም ፡ ቅን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 138 ፤ ምስክርኽን ፡ በጽድቅ ፡ አዘዝኽ ፥ እጅግም ፡ ቅን ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 139 ፤ ጠላቶቼ ፡ ቃልኽን ፡ ረስተዋልና ፥ የቤትኽ ፡ ቅንአት ፡ አቀለጠኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 140 ፤ ቃልኽ ፡ እጅግ ፡ የነጠረ ፡ ነው ፥ ባሪያኽም ፡ ወደደው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 141 ፤ እኔ ፡ ታናሽና ፡ የተናቅኹ ፡ ነኝ ፤ ትእዛዛትኽን ፡ ግን ፡ አልረሳኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 142 ፤ ጽድቅኽ ፡ የዘለዓለም ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፥ ቃልኽም ፡ እውነት ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 143 ፤ መከራና ፡ ችግር ፡ አገኙኝ ፤ ትእዛዛትኽ ፡ ግን ፡ ተድላዬ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 144 ፤ ምስክርኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፤ እንዳስተውል ፡ አድርገኝ ፥ በሕይወትም ፡ አኑረኝ ።

ቆፍ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 145 ፤ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ ጮኽኹ ፥ አቤቱ ፥ ስማኝ ፤ ሥርዐትኽን ፡ እፈልጋለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 146 ፤ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፤ አድነኝ ፥ ምስክርኽንም ፡ እጠብቃለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 147 ፤ ማለዳ ፡ ጮኽኹ ፤ ቃልኽንም ፡ ተስፋ ፡ አድርጌያለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 148 ፤ ቃልኽን ፡ ዐስብ ፡ ዘንድ ፡ ዐይኖቼ ፡ ለመማለድ ፡ ቀደሙ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 149 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ቸርነትኽ ፡ ድምፄን ፡ ስማ ፤ እንደ ፡ ፍርድኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 150 ፤ በዐመፃ ፡ የሚያሳድዱኝ ፡ ቀረቡ ፥ ከሕግኽም ፡ ራቁ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 151 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ቅርብ ፡ ነኽ ፥ መንገዶችኽም ፡ ኹሉ ፡ ቅኖች ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 152 ፤ ከዘለዓለም ፡ እንደ ፡ መሠረትኽው ፡ ከቀድሞ ፡ ገምሮ ፡ ከምስክርኽ ፡ የተነሣ ፡ ዐወቅኹ ።

ሬስ

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 153 ፤ ሕግኽን ፡ አልረሳኹምና ፡ ችግሬን ፡ ተመልከት ፡ አድነኝም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 154 ፤ ፍርዴን ፡ ፍረድ ፡ አድነኝም ፤ ስለ ፡ ቃልኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 155 ፤ መድኀኒት ፡ ከኃጥኣን ፡ ሩቅ ፡ ነው ፥ ሥርዐትኽን ፡ አልፈለጉምና ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 156 ፤ አቤቱ ፥ ቸርነትኽ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ፍርድኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 157 ፤ ያሳደዱኝና ፡ ያስጨነቁኝ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ ከምስክር ፡ ግን ፡ ፈቀቅ ፡ አላልኹም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 158 ፤ ቃልኽን ፡ አልጠበቁምና ፥ ሰነፎችን ፡ አይቼ ፡ ዐዘንኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 159 ፤ ትእዛዝኽን ፡ እንደ ፡ ወደድኹ ፡ ተመልከት ፤ አቤቱ ፥ በምሕረትኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 160 ፤ የቃልኽ ፡ መገሥመሪያ ፡ እውነት ፡ ነው ፥ የጽድቅኽንም ፡ ፍርድ ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ።

ሳን

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 161 ፤ ገዢዎች ፡ በከንቱ ፡ አሳደዱኝ ፤ ከቃልኽ ፡ የተነሣ ፡ ግን ፡ ልቤ ፡ ደነገጠብኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 162 ፤ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ እንዳገኘ ፡ በቃልኽ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 163 ፤ ዐመፃን ፡ ጠላኹ ፡ ተጸየፍኹም ፤ ሕግን ፡ ግን ፡ ወደድኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 164 ፤ ስለ ፡ ጽድቅኽ ፡ ፍርድ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ በቀን ፡ አመሰግንኻለኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 165 ፤ ሕግኽን ፡ ለሚወዱ ፡ ብዙ ፡ ሰላም ፡ ነው ፥ ዕንቅፋትም ፡ የለባቸውም ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 166 ፤ አቤቱ ፥ ማዳንኽን ፡ ተስፋ ፡ አደርግኹ ፥ ትእዛዛትኽንም ፡ ጠበቅኹ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 167 ፤ ነፍሴ ፡ ምስክርኽን ፡ ጠበቀች ፡ እጅግም ፡ ወደደችው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 168 ፤ መንገዶቼ ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ናቸውና ፥ ትእዛዝኽንና ፡ ምስክርኽን ፡ ጠበቅኹ ።

ታው

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 169 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ትቅረብ ፤ እንደ ፡ ቃልኽም ፡ አስተዋይ ፡ አድርገኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 170 ፤ ልመናዬ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ትድረስ ፤ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 171 ፤ ሥርዐትኽን ፡ አስተምረኽኛልና ፥ ከንፈሮቼ ፡ ምስጋናን ፡ አወጡ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 172 ፤ ትእዛዛትኽ ፡ ኹሉ ፡ ጽድቅ ፡ ናቸውና ፥ አንደበቴ ፡ ቃልኽን ፡ ተናገረ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 173 ፤ ትእዛዛትኽን ፡ መርጫለኹና ፡ እጅኽ ፡ የሚያድነኝ ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 174 ፤ አቤቱ ፥ ማዳንኽን ፡ ናፈቅኹ ፤ ሕግኽም ፡ ተድላዬ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 175 ፤ ነፍሴ ፡ ትኑርልኝ ፡ ታመሰግንኽማለች ፥ ፍርድኽም ፡ ይርዳኝ ።

መዝ. ፡ 118 ፡ (119) ፡ 176 ፤ እንደ ፡ ጠፉ ፡ በግ ፡ ተቅበዘበዝኹ ፤ ትእዛዛትኽን ፡ አልረሳኹምና ፡ ባሪያኽን ፡ ፈልገው ።

መዝሙር ፡ 119 ፡ (120) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 1 ፤ በተጨነቅኹ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኹ ፥ ሰማኝም ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 2 ፤ ከዐመፀኛ ፡ ከንፈር ፡ ከሸንጋይም ፡ አንደበት ፥ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ አድናት ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 3 ፤ ስለሸንገላ ፡ አንደበት ፡ ምንን ፡ ይሰጡኻል ፧ ምንስ ፡ ይጨምሩልኻል ፧

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 4 ፤ እንደ ፡ በረሓ ፡ ዕንጨት ፡ ፍም ፡ የጎያላን ፡ ፍላጻዎች ፡ የተሳሉ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 5 ፤ መኖሪያዬ ፡ የራቀ ፡ እኔ ፡ ወዮልኝ ፤ በቄዳር ፡ ድንኳኖች ፡ ዐደርኹ ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 6 ፤ ሰላምን ፡ ከሚጠሉ ፡ ጋራ ፡ ነፍሴ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኖረች ።

መዝ. ፡ 119 ፡ (120) ፡ 7 ፤ እኔ ፡ ሰላማዊ ፡ ነኝ ፤ በተናገርኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በከንቱ ፡ ተሰለፉብኝ ።

መዝሙር ፡ 120 ፡ (121) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 1 ፤ ዐይኖቼን ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ አነሣኹ ፤ ረዳቴ ፡ ከወዴት ፡ ይምጣ ፧

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 2 ፤ ረዳቴ ፡ ሰማይና ፡ ምድርን ፡ ከሠራ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 3 ፤ እግርኽን ፡ ለመናወጥ ፡ አይሰጠውም ፤ የሚጠብቅኽም ፡ አይተኛም ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ እስራኤልን ፡ የሚጠብቅ ፡ አይተኛም ፡ አያንቀላፋምም ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቅኻል ፥ እግዚአብሔርም ፡ በቀኝ ፡ እጅኽ ፡ በኩል ፡ ይጋርድኻል ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 6 ፤ ፀሓይ ፡ በቀን ፡ አያቃጥልኽም ፡ ጨረቃም ፡ በሌሊት ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከክፉ ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቅኻል ፥ ነፍስኽንም ፡ ይጠብቃታል ።

መዝ. ፡ 120 ፡ (121) ፡ 8 ፤ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ እግዚአብሔር ፡ መውጣትኽና ፡ መግባትኽን ፡ ይጠብቃል ።

_____መዝሙር ፡ 121 ፡ (122) ። _____

የዳዊት ፡ የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 1 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንኺድ ፡ ባሉኝ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለኝ ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 2 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ እግሮቻችን ፡ በአደባባይሽ ፡ ቆሙ ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 3 ፤ ኢየሩሳሌምስ ፡ ርስ ፡ በርሷ ፡ እንደ ፡ ተገጠገጠች ፡ ከተማ ፡ ተሠርታለች ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ያመስግኑ ፡ ዘንድ ፥ ለእስራኤል ፡ ምስክር ፡ ሊኾኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገዶች ፡ ወደዚያ ፡ ይወጣሉ ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 5 ፤ ዙፋኖች ፡ በዚያ ፡ ለፍርድ ፡ ተቀምጠዋልና ፥ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ዙፋኖች ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 6 ፤ ለኢየሩሳሌም ፡ ሰላምን ፡ ለምኑ ፤ አንተንም ፡ ለሚወዱ ፡ ልማት ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 7 ፤ በጎይልኽ ፡ ሰላም ፥ በጌጠኛ ፡ ቤትኽም ፡ ልማት ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 8 ፤ ስለ ፡ ወንድሞቼ ፡ ስለ ፡ ባልንጀራዎቼም ፥ በውስጥሽ ፡ ሰላም ፡ ይኹን ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 121 ፡ (122) ፡ 9 ፤ ስለአምላካችን ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ላንቺ ፡ መልካምነትሽን ፡ ፈለግኹ ።

_____መዝሙር ፡ 122 ፡ (123) ። _____

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 122 ፡ (123) ፡ 1 ፤ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ፥ ዐይኖቼን ፡ ወዳንተ ፡ አነሣኹ ።

መዝ. ፡ 122 ፡ (123) ፡ 2 ፤ እንሆ ፥ የባሪያዎች ፡ ዐይኖች ፡ ወደጌታቸው ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ የባሪያዪቱም ፡ ዐይን ፡ ወደእመቤቷ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እንዲሁ ፡ እስኪ.ምረን ፡ ድረስ ፡ ዐይናችን ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 122 ፡ (123) ፡ 3 ፤ ማረን ፥ አቤቱ ፥ ማረን ፤ ንቀትን ፡ እጅግ ፡ ጠግበናልና ፤

መዝ. ፡ 122 ፡ (123) ፡ 4 ፤ የባለጠጋዎች ፡ ስድብና ፡ የትዕቢተኞችን ፡ ንቀት ፡ ነፍሳችን ፡ እጅግ ፡ ጠገበች ።

_____መዝሙር ፡ 123 ፡ (124) ። _____

የዳዊት ፡ የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ባይኾን ፡ እስራኤል ፡ እንዲህ ፡ ይበል ፦

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ባይኾን ፡ ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፥

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 3 ፤ ቀኣጣቸው ፡ በላያችን ፡ በነደደ ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሕያዋን ፡ ሳለን ፡ በዋጡን ፡ ነበር ፤

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 4 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ውሃ ፡ ባሰጠመን ፡ ነበር ፥ በነፍሳችንም ፡ ላይ ፡ ፈሳሽ ፡ ባለፈ ፡ ነበር ፤

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 5 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የጐርፍ ፡ ውሃ ፡ በነፍሳችን ፡ ላይ ፡ ባለፈ ፡ ነበር ።

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 6 ፤ ለጥርሳቸው ፡ ንክሻ ፡ ያላደረገን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይባረክ ።

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 7 ፤ ነፍሳችን ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ከአዳኞች ፡ ወጥመድ ፡ አመለጠች ፦ ወጥመድ ፡ ተሰበረ ፡ እኛም ፡ አመለጥን ።

መዝ. ፡ 123 ፡ (124) ፡ 8 ፤ ረድኤታችን ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በሠራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 124 ፡ (125) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 124 ፡ (125) ፡ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ የታመኑ ፡ እንደማይታወክ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንደሚኖር ፡ እንደ ፡ ጽዮን ፡ ተራራ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 124 ፡ (125) ፡ 2 ፤ ተራራዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ለዘለዓለም ፤ እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ዙሪያ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 124 ፡ (125) ፡ 3 ፤ ጻድቃን ፡ እጃቸውን ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ እንዳይዘረጉ ፥ የኃጥኣን ፡ በትር ፡ በጻድቃን ፡ ዕጣ ፡ ላይ ፡ አይኖርም ።

መዝ. ፡ 124 ፡ (125) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ ለቸሮች ፡ ልባቸውም ፡ ለቀና ፡ መልካምን ፡ አድርግ ።

መዝ. ፡ 124 ፡ (125) ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ጠማማነት ፡ የሚመለሱትን ፡ ግን ፡ ዐመፃን ፡ ከሚሠሩት ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወስዳቸዋል ። ሰላም ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ይኹን ።

መዝሙር ፡ 125 ፡ (126) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ምርኮ ፡ በመለሰ ፡ ጊዜ ፥ እጅግ ፡ ደስተኞች ፡ ኾን ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አፋችን ፡ ደስታን ፥ አንደበታችንም ፡ ሐሴትን ፡ ሞላ ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ። እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነገርን ፡ አደረገላቸው ፡ ተባለ ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነገርን ፡ አደረገልን ፥ ደስም ፡ አለን ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ በደቡብ ፡ እንዳሉ ፡ ፈሳሾች ፡ ምርኳችንን ፡ መልስ ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 5 ፤ በልቅሶ ፡ የሚዘሩ ፡ በደስታ ፡ ይለቅማሉ ።

መዝ. ፡ 125 ፡ (126) ፡ 6 ፤ በኼዱ ፡ ጊዜ ፥ ዘራቸውን ፡ ተሸክመው ፡ እያለቀሱ ፡ ተሰማሩ ፤ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ነዷቸውን ፡ ተሸክመው ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ይመጣሉ ።

_____መዝሙር ፡ 126 ፡ (127) ። _____

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 126 ፡ (127) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቤትን ፡ ካልሠራ ፥ ሠራተኞች ፡ በከንቱ ፡ ይደክማሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከተማን ፡ ካልጠበቀ ፥ ጠባቂ ፡ በከንቱ ፡ ይተጋል ።

መዝ. ፡ 126 ፡ (127) ፡ 2 ፤ በማለዳ ፡ መገሥገሣችኹም ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ለወዳጆቹ ፡ እንቅልፍን ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፥ እናንተ ፡ የመከራን ፡ እንጀራ ፡ የምትበሉ ፥ ከተቀመጣችኹበት ፡ ተነሡ ።

መዝ. ፡ 126 ፡ (127) ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ ልጆች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ናቸው ፥ የሆድም ፡ ፍሬ ፡ የርሱ ፡ ዋጋ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 126 ፡ (127) ፡ 4 ፤ በጎያል ፡ እጅ ፡ እንዳሉ ፡ ፍላጻዎች ፥ የጐልማስነት ፡ ልጆች ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 126 ፡ (127) ፡ 5 ፤ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ምኞቱን ፡ የሚፈጽም ፡ ብፁዕ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ጠላቶቻቸውን ፡ በአደባባይ ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ አያፍርም ።

_____መዝሙር ፡ 127 ፡ (128) ። _____

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩት ፡ ኹሉ ፥ በመንገዶቹም ፡ የሚኼዱ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 2 ፤ የድካምኽንም ፡ ፍሬ ፡ ትመገባለኽ ፤ ምስጉን ፡ ነኽ ፡ መልካምም ፡ ይኾንልኻል ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 3 ፤ ሚስትኽ ፡ በቤትኽ ፡ ዕልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚያፈራ ፡ ወይን ፡ ናት ፤ ልጆችኽ ፡ በማእዱኽ ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ ወይራ ፡ ቡቃያ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ይባረካል ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጽዮን ፡ ይባርክኽ ፤ በሕይወትኽ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ የኢየሩሳሌምን ፡ መልካምነቷን ፡ ታያለኽ ።

መዝ. ፡ 127 ፡ (128) ፡ 6 ፤ የልጆችኽንም ፡ ልጆች ፡ ታያለኽ ። በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ሰላም ፡ ይኹን ።

_____መዝሙር ፡ 128 ፡ (129) ። _____

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 1 ፤ እስራኤል ። ከትንሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሰለፉብኝ ፡ ይበል ፤

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 2 ፤ ከትንሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሰለፉብኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አላሸነፉኝም ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 3 ፤ ጎጢአተኞች ፡ በዠርባዬ ፡ ላይ ፡ መቱኝ ፥ ጎጢአታቸውንም ፡ አስረዘሟት ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፤ የኀጢአተኞችን ፡ ዐንገታቸውን ፡ ቈረጠ ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 5 ፤ ጽዮንን ፡ የሚጠሉ ፡ ኹሉ ፡ ይፈሩ ፥ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ ይመለሱ ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 6 ፤ በሰገነት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በቀለ ፡ ሣር ፥ ሳይነቀል ፡ እንደሚደርቅ ፥

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 7 ፤ ለሚያጭደው ፡ እጁን ፥ ነዶዎቹን ፡ ለሚሰበስብ ፡ ዕቅፉን ፡ እንደማይሞላ ፡ ይኹኑ ።

መዝ. ፡ 128 ፡ (129) ፡ 8 ፤ በመንገዱም ፡ የሚያልፉ ፦ የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ይኹን ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ እንመርቃችኋለን ፡ አይሉም ።

መዝሙር ፡ 129 ፡ (130) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አንተን ፡ ከጥልቅ ፡ ጠራኹኽ ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 2 ፤ አቤቱ ፥ ድምፄን ፡ ስማ ፤ ገሮኽ ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ የሚያደምጥ ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ኀጢአትንስ ፡ ብትጠባበቅ ፥ አቤቱ ፥ ማን ፡ ይቆማል ፧

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 4 ፤ ይቅርታ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ተስፋ ፡ አደረግኹኽ ፤ ነፍሴ ፡ በሕግኽ ፡ ታገሠች ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 6 ፤ ከማለዳው ፡ ሰዓት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ነፍሴ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመነች ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 7 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምሕረት ፥ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ማዳን ፡ ነውና ፥ እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይታመን ።

መዝ. ፡ 129 ፡ (130) ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ እስራኤልን ፡ ከኀጢአቱ ፡ ኹሉ ፡ ያድነዋል ።

መዝሙር ፡ 130 ፡ (131) ።

የዳዊት ፡ መዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 130 ፡ (131) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ልቤ ፡ አይታበይብኝ ፥ ዐይኖቼም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አይበሉብኝ ፤ ከትልልቆች ፡ ጋራ ፥ ከእኔም ፡ ይበልጥ ፡ ከሚከበሩ ፡ ጋራ ፡ አልኼድኹም ።

መዝ. ፡ 130 ፡ (131) ፡ 2 ፤ ነፍሴን ፡ አሳረፍኋት ፥ የእናቱንም ፡ ጡት ፡ እንዳስተዉት ፡ ዝም ፡ አሠኘኋት ፤ ነፍሴ ፡ የእናቱን ፡ ጡት ፡ እንዳስተዉት ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ ናት ።

መዝ. ፡ 130 ፡ (131) ፡ 3 ፤ ከዛሬ ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ እስራኤል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይታመን ።

መዝሙር ፡ 131 ፡ (132) ።

የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ዳዊትን ፡ ገርነቱንም ፡ ኹሉ ፡ ዐስብ ፤

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 2 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ማለ ፥ ለያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ተሳለ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 3 ፤ በእውነት ፡ ወደቤቴ ፡ ድንኳን ፡ አልገባም ፥ ወደምንጣፌም ፡ ዐልጋ ፡ አልወጣም ፥

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 4 ፤ ለዐይኖቼም ፡ መኝታ ፡ ለሽፋሽፍቶቼም ፡ እንቅልፍ ፥ ለጕንጮቼም ፡ ዕረፍትን ፡ አልሰጥም ፥

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 5 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ስፍራ ፥ ለያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ማደሪያ ፡ እስካገኝ ፡ ድረስ ፡ ብሎ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ በኤፍራታ ፡ ሰማነው ፥ በዱር ፡ ውስጥም ፡ አገኘነው ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 7 ፤ ወደ ፡ ማደሪያዎቹ ፡ እንገባለን ፤ እግሮቹ ፡ በሚቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ እንሰግዳለን ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ወደ ፡ ዕረፍትኽ ፡ ተነሥ ፥ አንተና ፡ የመቅደስኽ ፡ ታቦት ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 9 ፤ ካህናትኽ ፡ ጽድቅን ፡ ይልበሱ ፥ ቅዱሳንኽም ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 10 ፤ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ስለ ፡ ባሪያኽ ፡ የቀባኸውን ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ አትመልስ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዳዊት ፡ በእውነት ፡ ማለ ፥ አይጸጸትምም ፥ እንዲህ ፡ ብሎ ፦ ከሆድኽ ፡ ፍሬ ፡ በዙፋንኽ ፡ ላይ ፡ አስቀምጣለኹ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 12 ፤ ልጆችኽ ፡ ኪዳኔን ፥ ይህንም ፡ የማስተምራቸውን ፡ ምስክሬን ፡ ቢጠብቁ ፥ ልጆቻቸው ፡ ደግሞ ፡ በዙፋንኽ ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀመጣሉ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ መርጧታልና ፥ ማደሪያውም ፡ ትኾነው ፡ ዘንድ ፡ ወዷታልና ፥ እንዲህ ፡ ብሎ ፦

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 14 ፤ ይህች ፡ ለዘለዓለም ፡ ማረፊያዬ ፡ ናት ፤ መርጫታለኹና ፡ በዚች ፡ ዐድራለኹ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 15 ፤ አሮጊቶቿን ፡ እጅግ ፡ እባርካለኹ ፥ ድኻዎቿንም ፡ እንጀራ ፡ አጠግባለኹ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 16 ፤ ካህናቷንም ፡ ደኅንነትን ፡ አለብሳቸዋለኹ ፥ ቅዱሳኗም ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 17 ፤ በዚያ ፡ ለዳዊት ፡ ቀንድን ፡ አበቅላለኹ ፥ ለቀባኹትም ፡ ሰው ፡ መብራትን ፡ አዘጋጃለኹ ።

መዝ. ፡ 131 ፡ (132) ፡ 18 ፤ ጠላቶችንም ፡ ዕፍረትን ፡ አለብሳቸዋለኹ ፤ በርሱ ፡ ግን ፡ ቅድስናዬ ፡ ያብባል ።

መዝሙር ፡ 132 ፡ (133) ።

የዳዊት ፡ የመዓርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 132 ፡ (133) ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ በኅብረት ፡ ቢቀመጡ ፥ እንሆ ፥ መልካም ፡ ነው ፥ እንሆም ፥ ያማረ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 132 ፡ (133) ፡ 2 ፤ ከራስ ፡ እስከ ፡ ጢም ፡ እንደሚፈስ ፥ እስከአሮን ፡ ጢም ፥ በልብሱ ፡ መደረቢያ ፡ እንደሚወርድ ፡ ሽቱ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 132 ፡ (133) ፡ 3 ፤ በጽዮን ፡ ተራራዎች ፡ እንደሚወርድ ፡ እንደ ፡ አርሞንዔም ፡ ጠል ፡ ነው ፤ በዚያ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከቱን ፡ ሕይወትንም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ አዟልና ።

መዝሙር ፡ 133 ፡ (134) ።

የማዕርግ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 133 ፡ (134) ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩ ፥ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ አደባባዮች ፡ የምትቆሙ ፡ እናንተ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ኹላችኹ ።

መዝ. ፡ 133 ፡ (134) ፡ 2 ፤ በሌሊት ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ እጆቻችኹን ፡ አንሡ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ባርኩ ።

መዝ. ፡ 133 ፡ (134) ፡ 3 ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጽዮን ፡ ይባርክኽ ።

_____መዝሙር ፡ 134 ፡ (135) ። _____

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አመስግኑ ፤ እናንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ሆይ ፥ አመስግኑት ፥

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፥ በአምላካችን ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ የምትቆሙ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ለስሙ ፡ ዘምሩ ፥ መልካም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ለራሱ ፥ እስራኤልንም ፡ ለመዝገቡ ፡ መርጦታልና ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ጌታችንም ፡ ከአማልክት ፡ ኹሉ ፡ እንዲበልጥ ፡ ዐውቄያለኹና ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 6 ፤ በሰማይና ፡ በምድር ፡ በባሕርና ፡ በጥልቆች ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 7 ፤ ከምድር ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ያወጣል ፤ በዝናብ ፡ ጊዜ ፡ መብረቅን ፡ አደረገ ፤ ነፋሳትንም ፡ ከመዛግብቱ ፡ ያወጣል ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 8 ፤ የግብጽን ፡ በኵር ፡ ልጆች ፡ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ መታ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 9 ፤ ግብጽ ፡ ሆይ ፥ በመካከልሽ ፡ በፈርዖንና ፡ በባሪያዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተአምራትንና ፡ ድንቅን ፡ ሰደደ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ መታ ፥ ብርቱዎችንም ፡ ነገሥታት ፡ ገደለ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 11 ፤ የአሞራውያንን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፥ የባሳንንም ፡ ንጉሥ ፡ ዐግን ፥ የከነዓንን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 12 ፤ ምድራቸውንም ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ለእስራኤል ፡ ለሕዝቡ ፡ ርስት ፡ ሰጠ ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ ስምኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ፥ ዝክርኽም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቡ ፡ ይፈርዳልና ፥ ባሪያዎቹንም ፡ ይረዳልና ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 15 ፤ የአሕዛብ ፡ ጣዖታት ፡ የብርና ፡ የወርቅ ፥ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 16 ፤ አፍ ፡ አላቸው ፥ አይናገሩምም ፤ ዐይን ፡ አላቸው ፥ አያዩምም ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 17 ፤ ጕሮሮ ፡ አላቸው ፥ አይሰሙምም ፤ እስትንፋስም ፡ በአፋቸው ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 18 ፤ የሚሠሯቸው ፡ ኹሉ ፡ የሚታመኑባቸውም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ይኹን ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 19 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩት ። የአሮን ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩት ፤

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 20 ፤ የሌዊ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩት ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ባርኩት ።

መዝ. ፡ 134 ፡ (135) ፡ 21 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የሚያድር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጽዮን ፡ የተባረከ ፡ ነው ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 135 ፡ (136) ።

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 2 ፤ የአማልክትን ፡ አምላክ ፡ አመስግኑ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 3 ፤ የጌታዎችን ፡ ጌታ ፡ አመስግኑ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 4 ፤ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ ታላቅ ፡ ተኣምራትን ፡ ያደረገ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 5 ፤ ሰማያትን ፡ በብልኀት ፡ የሠራ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 6 ፤ ምድርን ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ያጸና ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 7 ፤ ብቻውን ፡ ታላላቅ ፡ ብርሃናትን ፡ የሠራ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 8 ፤ ለፀሓይ ፡ ቀንን ፡ ያስገዛው ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 9 ፤ ለጨረቃና ፡ ለከዋክብትም ፡ ሌሊትን ፡ ያስገዛቸው ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 10 ፤ ከበኵራቸው ፡ ጋራ ፡ ግብጽን ፡ የመታ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 11 ፤ እስራኤልንም ፡ ከመካከላቸው ፡ ያወጣ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 12 ፤ በጸናች ፡ እጅ ፡ በተዘረጋችም ፡ ክንድ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 13 ፤ ቀይ ፡ ባሕርን ፡ በየክፍሉ ፡ የከፈለ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 14 ፤ እስራኤልን ፡ በመካከሉ ፡ ያሳለፈ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 15 ፤ ፈርዖንንና ፡ ሰራዊቱን ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ የጣለ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 16 ፤ ሕዝቡን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የመራ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 17 ፤ ታላላቅ ፡ ነገሥታትን ፡ የመታ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 18 ፤ ብርቱዎችንም ፡ ነገሥታት ፡ የገደለ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 19 ፤ የአሞራውያንን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዎንን ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 20 ፤ የባሳንን ፡ ንጉሥ ፡ ዐግን ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 21 ፤ ምድራቸውን ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ የሰጠ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 22 ፤ ለባሪያው ፡ ለእስራኤል ፡ ርስት ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 23 ፤ እኛን ፡ በመዋረዳችን ፡ ዐስቦናልና ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 24 ፤ ከጠላቶቻችንም ፡ እጅ ፡ አድኖናልና ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፤

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 25 ፤ ለሥጋ ፡ ኹሉ ፡ ምግብን ፡ የሚሰጥ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 135 ፡ (136) ፡ 26 ፤ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ አመስግኑ ፤ ምሕረቱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ።

መዝሙር ፡ 136 ፡ (137) ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 1 ፤ በባቢሎን ፡ ወንዞች ፡ አጠገብ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጥን ፤ ጽዮንንም ፡ ባሰብናት ፡ ጊዜ ፡ አለቀስን ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 2 ፤ በአሓያ ፡ ዛፎቿ ፡ ላይ ፡ መሰንቆቻችንን ፡ ሰቀልን ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 3 ፤ የማረኩን ፡ በዚያ ፡ የዝማሬን ፡ ቃል ፡ ፈለጉብን ፥ የወሰዱንም ፦ የጽዮንን ፡ ዝማሬ ፡ ዘምሩልን ፡ አሉን ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ዝማሬ ፡ በባዕድ ፡ ምድር ፡ እንዴት ፡ እንዘምራለን ፧

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 5 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ብረሳሽ ፥ ቀኜ ፡ ትርሳኝ ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 6 ፤ ባላስብሽ ፥ ምላሴ ፡ በጉረሮዬ ፡ ይጣበቅ ፤ ከደስታዬ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ባልወድ ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ቀን ፡ የኤዶምን ፡ ልጆች ፡ ዐስብ ። እስከ ፡ መሠረቷ ፡ ድረስ ፡ አፍርሱ ፡ አፍርሱ ፡ ያሏትን ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 8 ፤ አንቺ ፡ ወራዳ ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ተበቀልሽን ፡ የሚበቀልሽ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 136 ፡ (137) ፡ 9 ፤ ሕፃናትሽን ፡ ይዞ ፡ በአለት ፡ ላይ ፡ የሚፈጠፍጣቸው ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 137 ፡ (138) ።

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ በፍጹም ፡ ልቤ ፡ አመሰግንሃለኹ ፥ የአፌን ፡ ነገር ፡ ሰምተኸኛልና ፤ በመላእክት ፡ ፊት ፡ እዘምርልሃለኹ ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስህ ፡ እሰግዳለኹ ፤ ስለ ፡ ምሕረትህና ፡ ስለ ፡ እውነትህ ፡ ስምህንም ፡ አመሰግናለኹ ፥ በኹሉ ፡ ላይ ፡ ቅዱስ ፡ ስምህን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርገሃልና ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 3 ፤ በጠራኹህ ፡ ቀን ፡ በፍጥነት ፡ አድምጠኝ ፤ ነፍሴን ፡ በኀይልህ ፡ በብዙ ፡ አጸናኻት ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 4 ፤ አቤቱ ፥ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑኻል ፤ የአፍኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ሰምተዋልና ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 5 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ መንገድ ፡ ይዘምራሉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ታላቅ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ችግረኞችም ፡ ይመለከታልና ፤ ትዕቢተኞችንም ፡ ከሩቅ ፡ ያውቃል ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 7 ፤ በመከራ ፡ መካከል ፡ እንኳ ፡ ብኼድ ፥ አንተ ፡ ሕያው ፡ ታደርገኛለኽ ፤ በጠላቶቼ ፡ ቍጣ ፡ ላይ ፡ እጆቼን ፡ ትዘረጋለኽ ፥ ቀኝኽም ፡ ታድነኛለች ።

መዝ. ፡ 137 ፡ (138) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ብድራትን ፡ ይመልስልኛል ፤ አቤቱ ፥ ምሕረትኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ፤ አቤቱ ፥ የእጅኽን ፡ ሥራ ፡ ቸል ፡ አትበል ።

_____መዝሙር ፡ 138 ፡ (139) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ መረመርኸኝ ፥ ዐወቅኸኝም ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 2 ፤ አንተ ፡ መቀመጤንና ፡ መነሣቴን ፡ ዐወቅኽ ፤ ዐሳቤን ፡ ኹሉ ፡ ከሩቅ ፡ አስተዋልኽ ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 3 ፤ ፍለጋዬንና ፡ ዕረፍቴን ፡ አንተ ፡ መረመርኽ ፤ መንገዶቼን ፡ ኹሉ ፡ ቀድመኽ ፡ ዐወቅኽ ፥

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 4 ፤ የዐመፃ ፡ ቃል ፡ በአንደበቴ ፡ እንደሌለ ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፥ እንሆ ፥ የቀድሞውንና ፡ የኋላውን ፡ ዐወቅኽ ፤ አንተ ፡ ፈጠርኸኝ ፥ እጅኽንም ፡ በላዬ ፡ አደረግኽ ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 6 ፤ ዕውቀትኽ ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ተደነቀች ፤ በረታች ፥ ወደ ፡ ርሷም ፡ ለመድረስ ፡ አልችልም ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 7 ፤ ከመንፈስኽ ፡ ወዴት ፡ እኼዳለኹ ፧ ከፊትኽስ ፡ ወዴት ፡ እሸሻለኹ ፧

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብወጣ ፥ አንተ ፡ በዚያ ፡ አለኽ ። ወደ ፡ ሲኦልም ፡ ብወርድ ፥ በዚያ ፡ አለኽ ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 9 ፤ እንደ ፡ ንስር ፡ የንጋትን ፡ ክንፍ ፡ ብወስድ ፥ እስከባሕር ፡ መጨረሻም ፡ ብበር ፥

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ እጅኽ ፡ ትመራኛለች ፥ ቀኝኽም ፡ ትይዘኛለች ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 11 ፤ በእውኑ ፡ ጨለማ ፡ ትሸፍነኛለች ፡ ብል ፥ ሌሊት ፡ በዙሪያዬ ፡ ብርሃን ፡ ትኾናለች ፤

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 12 ፤ ጨለማ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አይጨልምምና ፥ ሌሊትም ፡ እንደ ፡ ቀን ፡ ታበራለችና ፤ እንደ ፡ ጨለማዋ ፡ እንዲሁ ፡ ብርሃኗ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 13 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ኵላሊቴን ፡ ፈጥረኻልና ፥ በእናቴም ፡ ሆድ ፡ ሰውረኸኛል ።

መዝ. ፡ 138 ፡ (139) ፡ 14 ፤ ግሩምና ፡ ድንቅ ፡ ኾኜ ፡ ተፈጥሬያለኹና ፡ አመሰግንኻለኹ ፤ ሥራኽ ፡ ድንቅ ፡

ነው ፥ ነፍሴም ፡ እጅግ ፡ ታውቀዋለች ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 15 ፤ እኔ ፡ በስውር ፡ በተሠራኹ ፡ ጊዜ ፥ አካሌም ፡ በምድር ፡ ታች ፡ በተሠራ ፡ ጊዜ ፡ ዐጥንቶቼ ፡ ከአንተ ፡ አልተሰወሩም ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 16 ፤ ያልተሠራ ፡ አካሌን ፡ ዐይኖችኽ ፡ አዩኝ ፤ የተፈጠሩ ፡ ቀኖቼ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ሳይኖር ፡ በመጽሐፍኽ ፡ ተጻፉ ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 17 ፤ አቤቱ ፥ ዐሳቦችኽ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እጅግ ፡ የተከበሩ ፡ ናቸው! ፡ ቍጥራቸውም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ በዛ! ፡

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 18 ፤ ብቈጥራቸው ፡ ከአሸዋ ፡ ይልቅ ፡ ይበዛሉ ፤ ተነሣኹም ፥ እኔም ፡ ገና ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 19 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ኀጢአተኞችን ፡ የምትገድል ፡ ከኾንኽስ ፥ የደም ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ከእኔ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 20 ፤ በክፋት ፡ ይናገሩብኻልና ፤ ጠላቶችኽም ፡ በከንቱ ፡ ያምፁብኻል ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 21 ፤ አቤቱ ፥ የሚጠሉኽን ፡ እኔ ፡ የጠላኹ ፡ አይደለኹምን ፧ ስለ ፡ ጠላቶችኽም ፡ አልተሰቀቅኹምን ፧

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 22 ፤ ፍጹም ፡ ጥል ፡ ጠላኋቸው ፥ ጠላቶችም ፡ ኾኑኝ ።

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 23 ፤ አቤቱ ፥ መርምረኝ ፥ ልቤንም ፡ ዕወቅ ፤ ፍተነኝ ፡ መንገዴንም ፡ ዕወቅ ፤

መዝ. ፥ 138 ፡ (139) ፥ 24 ፤ በደልንም ፡ በእኔ ፡ ውስጥ ፡ ብታገኝ ፡ እይ ፤ የዘለዓለምንም ፡ መንገድ ፡ ምራኝ ።

_____መዝሙር ፡ 139 ፡ (140) ። _____

ለመዘምራን ፡ አለቃ ፡ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 1 ፤ አቤቱ ፥ ከክፉ ፡ ሰው ፡ አድነኝ ፥ በልባቸውም ፡ ክፉ ፡ ካሰቡ ፡ ከዐመፀኞች ፡ ሰዎች ፡ ጠብቀኝ ፤

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 2 ፤ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ለሰልፍ ፡ ይከማቻሉ ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 3 ፤ ምላሳቸውን ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ሳሉ ፤ ከከንፈራቸው ፡ በታች ፡ የእፍኝት ፡ መርዝ ፡ ነው ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 4 ፤ አቤቱ ፥ ከኀጢአተኞች ፡ እጅ ፡ ጠብቀኝ ፥ ርምጃዬንም ፡ ሊያሰናክሉ ፡ ከመከሩ ፡ ከዐመፀኞች ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 5 ፤ ትዕቢተኞች ፡ ወጥመድን ፡ ሰወሩብኝ ፥ ለእግሮቼም ፡ የወጥመድ ፡ ገመድን ፡ ዘረጉ ፤ በመንገድ ፡ ዕንቅፋትን ፡ አኖሩ ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርንም ፦ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፤ የልመናዬን ፡ ቃል ፥ አቤቱ ፥ አድምጥ ፡ አልኹት ።

መዝ. ፥ 139 ፡ (140) ፥ 7 ፤ አቤቱ ፥ ጌታዬ ፥ የመድኀኒቴ ፡ ጕልበት ፥ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ ራሴን ፡ ሸፈንኽ ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ ከምኞቴ ፡ የተነሣ ፡ ለኀጢአተኞች ፡ አትስጠኝ ፤ በላዬ ፡ ተማከሩ ፤ እንዳይጓደዱ ፡ አትተወኝ ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 9 ፤ የሚከቡኝን ፡ ራስ ፡ የከንፈራቸው ፡ ክፋት ፡ ይክደናቸው ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 10 ፤ የእሳት ፡ ፍም ፡ በላያቸው ፡ ይውደቅ ፤ እንዳይነሡም ፡ ወደ ፡ እሳትና ፡ ወደ ፡ ማዕበል ፡ ይጣሉ ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 11 ፤ ተናጋሪ ፡ ሰው ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ አይጸናም ፤ ዐመፀኛን ፡ ሰው ፡ ክፋት ፡ ለጥፋት ፡ ይፈልገዋል ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለድኻ ፡ ዳኝነትን ፡ ለችግረኛም ፡ ፍርድን ፡ እንዲያደርግ ፡ ዐወቅኹ ።

መዝ. ፡ 139 ፡ (140) ፡ 13 ፤ ጻድቃንም ፡ በእውነት ፡ ስምኽን ፡ ያመሰግናሉ ፤ ቀኖችም ፡ በፊትኽ ፡ ይኖራሉ ።

_____መዝሙር ፡ 140 ፡ (141) ። _____

የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፤ ስማኝ ፤ ወዳንተ ፡ ስጮኽም ፡ የልመናዬን ፡ ቃል ፡ አድምጥ ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 2 ፤ ጸሎቴን ፡ በፊትኽ ፡ እንደ ፡ ዕጣን ፡ ተቀበልልኝ ፥ እጅ ፡ መንሣቴም ፡ እንደ ፡ ሠርክ ፡ መሥዋዕት ፡ ትኹን ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ለአፌ ፡ ጠባቂ ፡ አኑር ፥ የከንፈሮቼንም ፡ መዝጊያ ፡ ጠብቅ ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 4 ፤ ልቤን ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አትመልሰው ፥ ዐመፃን ፡ ከሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ለኀጢአት ፡ ምክንያት ፡ እንዳልሰጥ ፤ ከምርጦቻቸውም ፡ ጋራ ፡ አልተባበር ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 5 ፤ ጻድቅ ፡ በምሕረት ፡ ይገሥጸኝ ፥ ይገሥጸኝም ፥ የኀጢአተኛ ፡ ዘይት ፡ ግን ፡ ራሴን ፡ አይቅባ ፤ ጸሎቴ ፡ ገና ፡ በክፋታቸው ፡ ላይ ፡ ነውና ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 6 ፤ ኀያላናቸው ፡ በአለት ፡ አጠገብ ፡ ተጣሉ ፤ ጣፋጭ ፡ ናትና ፥ ቃሌን ፡ ይሰማሉ ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 7 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተሠነጠቀ ፡ እንደ ፡ መሬት ፡ ኃል ፥ እንዲሁ ፡ ዐጥንቶቻችን ፡ በሲኦል ፡ ተበተኑ ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 8 ፤ አቤቱ ፡ ጌታ ፥ ዐይኖቼ ፡ ወዳንተ ፡ ናቸውና ፤ ባንተ ፡ ታመንኹ ፥ ነፍሴን ፡ አታውጣት ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 9 ፤ ከሰወሩብኝ ፡ ወጥመድ ፥ ዐመፅንም ፡ ከሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ ጠብቀኝ ።

መዝ. ፡ 140 ፡ (141) ፡ 10 ፤ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ እስካልፍ ፡ ድረስ ፡ ኀጢአተኞች ፡ በወጥመዳቸው ፡ ይውደቁ ።

_____መዝሙር ፡ 141 ፡ (142) ። _____

ጸሎት ፤ በዋሻ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ ትምህርት ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 1 ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኹ ፤ በቃሌ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመንኹ ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 2 ፤ ልመናዬን ፡ በፊቱ ፡ አፈሳለኹ ፤ መከራዬንም ፡ በፊቴ ፡ እናገራለኹ ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 3 ፤ ነፍሴ ፡ በውስጤ ፡ ባለቀች ፡ ጊዜ ፡ መንገዴን ፡ ዐወቅኹ ፤ በምኼድባት ፡ በዚያች ፡ መንገድ ፡ ወጥመድን ፡ ሰወሩብኝ ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ተመለከትኹ ፡ አየኹም ፥ የሚያውቀኝም ፡ ዐጣኹ ፤ መሸሸጊያም ፡ የለኝም ፥ ስለ ፡ ነፍሴም ፡ የሚመራመር ፡ የለም ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 5 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ ጮኽኹ ፦ አንተ ፡ ተስፋዬ ፡ ነኽ ፥ በሕያዋንም ፡ ምድር ፡ አንተ ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ነኽ ፡ አልኹ ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 6 ፤ እጅግ ፡ ተቸግሬያለኹና ፡ ወደ ፡ ልመናዬ ፡ አድምጥ ፤ በርትተውብኛልና ፥ ከሚያሳድዱኝ ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 141 ፡ (142) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ ስምኽን ፡ አመሰግን ፡ ዘንድ ፤ ነፍሴን ፡ ከወህኒ ፡ አውጣት ፤ ዋጋዬን ፡ እስክትሰጠኝ ፡ ድረስ ፡ ጻድቃን ፡ እኔን ፡ ይጠብቃሉ ።

መዝሙር ፡ 142 ፡ (143) ።

ልጁ ፡ ባሳደደው ፡ ጊዜ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ ጸሎቴን ፡ ስማ ፤ በእውነትኽ ፡ ልመናዬን ፡ አድምጥ ፥ በጽድቅኽም ፡ መልስልኝ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 2 ፤ ሕያው ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ጻድቅ ፡ አይደለምና ፡ ከባሪያኽ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አትግባ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 3 ፤ ጠላትኽ ፡ ነፍሴን ፡ አሳዷታል ፥ ሕይወቴንም ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ አጐስቀሏታል ፤ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰው ፡ በጨለማ ፡ አኑሮኛል ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 4 ፤ ነፍሴ ፡ በውስጤ ፡ ዐለቀችብኝ ፥ ልቤም ፡ በውስጤ ፡ ደነገጠብኝ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 5 ፤ የቀድሞውን ፡ ዘመን ፡ ዐሰብኹ ፥ ሥራኽንም ፡ ኹሉ ፡ አሰላሰልኹ ፤ የእጅኽንም ፡ ሥራ ፡ ተመለከትኹ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 6 ፤ እጆቼን ፡ ወዳንተ ፡ ዘረጋኹ ፤ ነፍሴም ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አንተን ፡ ተጠማች ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 7 ፤ አቤቱ ፥ ፈጥነኽ ፡ ስማኝ ፤ ነፍሴ ፡ አልቃለች ፤ ፊትኽን ፡ ከእኔ ፡ አትመልስ ፥ ወደ ፡ ጉድጓድም ፡ እንደሚወርዱ ፡ አልኹን ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 8 ፤ አንተን ፡ ታምኛለኹና ፡ በማለዳ ፡ ምሕረትኽን ፡ አሰማኝ ፤ አቤቱ ፥ ነፍሴን ፡ ወዳንተ ፡ አንሥቻለኹና ፡ የምኼድበትን ፡ መንገድ ፡ አስታውቀኝ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ ተማፅኛለኹና ፡ ከጠላቶቼ ፡ አድነኝ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 10 ፤ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽና ፥ ፈቃድኽን ፡ ለማድረግ ፡ አስተምረኝ ፤ ቅዱስ ፡ መንፈስኽም ፡ በጽድቅ ፡ ምድር ፡ ይምራኝ ።

መዝ. ፡ 142 ፡ (143) ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ሕያው ፡ አድርገኝ ፤ በጽድቅኽም ፡ ነፍሴን ፡ ከመከራዋ ፡ አውጣት ።

መዝ. ፥ 142 ፡ (143) ፥ 12 ፤ በምሕረትኽ ፡ ጠላቶቼን ፡ ደምስሳቸው ፥ እኔ ፡ ባሪያኽ ፡ ነኝና ፡ ነፍሴን ፡ የሚያስጨንቋትን ፡ ኹሉ ፡ አጥፋቸው ።

መዝሙር ፡ 143 ፡ (144) ።

ስለ ፡ ጎልያድ ፤ የዳዊት ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ይባረክ ፥ ለእጆቼ ፡ ሰልፍን ፥ ለጣቶቼም ፡ ዘመቻን ፡ የሚያስተምር ፤

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 2 ፤ መሐሪዬና ፡ መሸሸጊያዬ ፥ መጠጊያዬና ፡ መድኀኒቴ ፤ ረዳቴና ፡ መታመኛዬም ፤ ሕዝቤንም ፡ ከእኔ ፡ በታች ፡ የሚያስገዛልኝ ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 3 ፤ አቤቱ ፥ ርሱን ፡ ታውቀው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ታስብለት ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 4 ፤ ሰው ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ይመስላል ፤ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ ያልፋል ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 5 ፤ አቤቱ ፥ ሰማዮችኽን ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ አድርጋቸው ፡ ውረድም ፤ ተራራዎችን ፡ ዳስሳቸው ፡ ይጢሱም ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 6 ፤ መብረቆችኽን ፡ ብልጭ ፡ አድርጋቸው ፡ በትናቸውም ፤ ፍላጻዎችኽን ፡ ላካቸው ፥ አስደንግጣቸውም ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 7-8 ፤ እጅኽን ፡ ከአርያም ፡ ላክ ፡ አድነኝም ፡ ከብዙ ፡ ውሃዎች ፥ አፋቸውም ፡ ምናምንን ፡ ከሚናገር ፥ ቀኛቸው ፡ የሐሰት ፡ ቀኝ ፡ ከኾነ ፥ ከባዕድ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አስጥለኝ ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 9 ፤ አቤቱ ፥ ዐዲስ ፡ ቅኔ ፡ እቀኝልኻለኹ ፤ ዐሥር ፡ አውታር ፡ ባለው ፡ በገና ፡ እዘምርልኻለኹ ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 10 ፤ ለነገሥታት ፡ መድኀኒትን ፡ የሚሰጥ ፥ ባሪያውን ፡ ዳዊትን ፡ ከክፉ ፡ ሰይፍ ፡ የሚያድነው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 11 ፤ አድነኝ ፥ አፋቸውም ፡ ምናምንን ፡ ከሚናገር ፥ ቀኛቸውም ፡ የሐሰት ፡ ቀኝ ፡ ከኾነ ፥ ከባዕድ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ አስጥለኝ ።

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 12 ፤ ልጆቻቸው ፡ በጕልማሳነታቸው ፡ እንደ ፡ ዐዲስ ፡ አትክልት ፡ የኾኑ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ እንደ ፡ ዕልፍኝ ፡ ያማሩና ፡ ያጌጡ ፤

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 13 ፤ ዕቃ ፡ ቤቶቻቸውም ፡ የተሞሉ ፡ በየዐይነቱ ፡ ዕቃ ፡ የሚሰጡ ፥ በጎቻቸውም ፡ ብዙ ፡ የሚወልዱ ፥ በማሰማሪያቸውም ፡ የሚበዙ ፥

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 14 ፤ ላሞቻቸውም ፡ የሚሰቡ ፤ ቅጥራቸውም ፡ መፍረሻና ፡ መውጫ ፡ የሌለው ፥ በአደባባዮቻቸውም ፡ ዋይታ ፡ የሌለ ፤

መዝ. ፥ 143 ፡ (144) ፥ 15 ፤ እንደዚህ ፡ የሚኾን ፡ ሕዝብ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላኩ ፡ የኾነ ፡ ሕዝብ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

መዝሙር ፡ 144 ፡ (145) ።

የዳዊት ፡ የምስጋና ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 1 ፤ አምላኬ ፡ ንጉሤ ፡ ሆይ ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግሻለኹ ፥ ስምኽንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ዓለምም ፡ እባርካለኹ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 2 ፤ በየቀኑ ፡ ኹሉ ፡ እባርክሻለኹ ፥ ስምኽንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ዓለምም ፡ አመሰግናለኹ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ እጅግም ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ፤ ለታላቅነቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 4 ፤ ትውልደ ፡ ትውልድ ፡ ሥራኽን ፡ ያመሰግናሉ ፥ ኀይልኽንም ፡ ያወራሉ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 5 ፤ የቅድስናኽን ፡ ግርማ ፡ ክብር ፡ ይናገራሉ ፥ ተኣምራትኽንም ፡ ይነጋገራሉ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 6 ፤ የግርማኽንም ፡ ኀይል ፡ ይናገራሉ ፥ ታላቅነትኽንም ፡ ይነጋገራሉ ፥ ብርታትኽንም ፡ ይነጋገራሉ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 7 ፤ የቸርነትኽን ፡ ብዛት ፡ መታሰብ ፡ ያወጣሉ ፥ በጽድቅኽም ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋሉ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ርኅሩኅና ፡ መሓሪ ፡ ነው ፥ ከቍጣ ፡ የራቀ ፥ ምሕረቱም ፡ ብዙ ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሚታገሡት ፡ ቸር ፡ ነው ። ምሕረቱም ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 10 ፤ አቤቱ ፥ ሥራኽ ፡ ኹሉ ፡ ያመሰግኑኻል ፥ ቅዱሳንኽም ፡ ይባርኩኻል ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 11 ፤ የመንግሥትኽን ፡ ክብር ፡ ይናገራሉ ፥ ኀይልኽንም ፡ ይነጋገራሉ ፥

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 12 ፤ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ኀይልኽን ፡ የመንግሥትኽንም ፡ ግርማ ፡ ክብር ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 13 ፤ መንግሥትኽ ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥት ፡ ናት ፥ ግዛትኽም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ በቃሎቹ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥ በሥራውም ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ የተፍገመገሙትን ፡ ኹሉ ፡ ይደግፋቸዋል ፥ የወደቁትንም ፡ ያነሣቸዋል ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 15 ፤ የኹሉ ፡ ዐይን ፡ አንተን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ፤ አንተም ፡ ምግባቸውን ፡ በየጊዜው ፡ ትሰጣቸዋለኽ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 16 ፤ አንተ ፡ እጅኽን ፡ ትከፍታለኽ ፥ ሕይወት ፡ ላለውም ፡ ኹሉ ፡ መልካምን ፡ ታጠግባለኽ ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ በመንገዱ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፡ በሥራውም ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሚጠሩት ፡ ኹሉ ፥ በእውነት ፡ ለሚጠሩት ፡ ኹሉ ፡ ቅርብ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 19 ፤ ለሚፈሩት ፡ ምኞታቸውን ፡ ያደርጋል ፥ ልመናቸውንም ፡ ይሰማል ፡ ያድናቸዋልም ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚወዱትን ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቃል ፤ ኀጢአተኞችንም ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋል ።

መዝ. ፡ 144 ፡ (145) ፡ 21 ፤ አፌ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ ይናገራል ፤ ሥጋም ፡ ሹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ የተቀደሰውን ፡ ስሙን ፡ ይባርክ ።

መዝሙር ፡ 145 ፡ (146) ።

የሐጌና ፡ የዘካርያስ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኚ ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 2 ፤ በሕይወቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ፤ በምኖርበት ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ ለአምላኬ ፡ እዘምራለኹ ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 3 ፤ ማዳን ፡ በማይችሉ ፡ በሰው ፡ ልጆችና ፡ በአለቃዎች ፡ አትታመኑ ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 4 ፤ ነፍሱ ፡ ትወጣለች ፡ ወደ ፡ መሬቱም ፡ ይመለሳል ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምክሩ ፡ ሹሉ ፡ ይጠፋል ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 5 ፤ የያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ረዳቱ ፡ የኾነ ፡ ተስፋውም ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፥ በእነርሱ ፡ ያለውንም ፡ ሹሉ ፡ የፈጠረ ፤ እውነትን ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚጠብቅ ፤

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 7 ፤ ለተበደሉት ፡ የሚፈርድ ፥ ለተራቡ ፡ ምግብን ፡ የሚሰጥ ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ የታሰሩትን ፡ ይፈታል ፤

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደቁትን ፡ ያነሣል ፤ እግዚአብሔር ፡ ዕውሮችን ፡ ጥበበኞች ፡ ያደርጋቸዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ ጻድቃንን ፡ ይወዳል ፤

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስደተኞችን ፡ ይጠብቃል ፤ ድኻ ፡ አደጎችንና ፡ ባልቴቶችን ፡ ይቀበላል ፤ የኀጢአተኞችንም ፡ መንገድ ፡ ያጠፋል ።

መዝ. ፡ 145 ፡ (146) ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ ይነግሣል ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ አምላክሽ ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 146 ፡ (147) ።

የሐጌና ፡ የዘካርያስ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ መዝሙር ፡ መልካም ፡ ነውና ። ለአምላካችን ፡ ምስጋና ፡ ያማረ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይሠራል ፥ ከእስራኤልም ፡ የተበተኑትን ፡ ይሰበስባል ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 3 ፤ ልባቸውን ፡ የቈሰሉትን ፡ ይፈውሳል ፥ ሕማማቸውንም ፡ ይጠግናል ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 4 ፤ የከዋክብትንም ፡ ብዛት ፡ ይቈጥራል ፥ ሹሉንም ፡ በየስማቸው ፡ ይጠራቸዋል ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 5 ፤ ጌታችን ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ ለጥበቡም ፡ ቍጥር ፡ የለውም ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ የዋሃንን ፡ ያነሣል ፥ ኀጢአተኞችን ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ ያዋርዳል ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 7 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ በምስጋና ፡ ዘምሩ ፥ ለአምላካችንም ፡ በመሰንቆ ፡ ዘምሩ ፤

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 8 ፤ ሰማዩን ፡ በደመናት ፡ ይሸፍናል ፡ ለምድርም ፡ ዝናብን ፡ ያዘጋጃል ፤ ሣርን ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ያበቅላል ፤ ለምለሙንም ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ጥቅም ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 9 ፤ ለሚጠሩት ፡ ለቀሩራዎች ፡ ጫጩቶች ፡ ለእንስሳዎችም ፡ ምግባቸውን ፡ ይሰጣል ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 10 ፤ የፈረስን ፡ ኀይል ፡ አይወድም ፥ በሰውም ፡ ጭን ፡ አይደሰትም ።

መዝ. ፡ 146 ፡ (147) ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሚፈሩት ፥ በምሕረቱም ፡ በሚታመኑት ፡ ይደሰታል ።

መዝሙር ፡ 147 ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 1 ፡ (12) ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኚ ፥

መዝ. ፡ 147 ፥ 2 ፡ (13) ፤ ጽዮንም ፡ ሆይ ፥ ለአምላክሽ ፡ እልል ፡ በዪ ፤ የደጆችሽን ፡ መወርወሪያ ፡ አጽንቷልና ፥ ልጆችንም ፡ በውስጥሽ ፡ ባርኳልና ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 3 ፡ (14) ፤ በወሰንሽም ፡ ሰላምን ፡ አደረገ ፥ የስንዴንም ፡ ስብ ፡ አጠገበሽ ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 4 ፡ (15) ፤ ነገሩን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይሰዳል ፥ ቃሉም ፡ እጅግ ፡ ፈጥኖ ፡ ይሮጣል ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 5 ፡ (16) ፤ ዐመዳዩን ፡ እንደ ፡ ባዘቶ ፡ ይሰጣል ፤ ጉሙን ፡ እንደ ፡ ዐመድ ፡ ይበትነዋል ፤

መዝ. ፡ 147 ፥ 6 ፡ (17) ፤ በረዶውን ፡ እንደ ፡ ፍርፋሪ ፡ ያወርዳል ፤ በበረዶውስ ፡ ፊት ፡ ማን ፡ ይቆማል ፧

መዝ. ፡ 147 ፥ 7 ፡ (18) ፤ ቃሉን ፡ ልኮ ፡ ያቀልጠዋል ፤ ነፋሱን ፡ ያነፍሳል ፥ ውሃዎችንም ፡ ያፈሳል ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 8 ፡ (19) ፤ ቃሉን ፡ ለያዕቆብ ፥ ሥርዐቱንና ፡ ፍርዱን ፡ ለእስራኤል ፡ ይናገራል ።

መዝ. ፡ 147 ፥ 9 ፡ (20) ፤ ለሌላዎች ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አላደረገም ፥ ፍርዱንም ፡ አልገለጠላቸውም ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 148 ።

የሐጌና ፡ የዘካርያስ ፡ መዝሙር ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። እግዚአብሔርን ፡ ከሰማያት ፡ አመስግኑት ፤ በአርያም ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 2 ፤ መላእክቱ ፡ ኹሉ ፥ አመስግኑት ፤ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፥ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 3 ፤ ፀሐይና ፡ ጨረቃ ፥ አመስግኑት ፤ ከዋክብትና ፡ ብርሃን ፡ ኹሉ ፥ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 4 ፤ ሰማየ ፡ ሰማያት ፥ አመስግኑት ፡ የሰማያት ፡ በላይም ፡ ውሃ ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 5 ፤ ርሱ ፡ ብሏልና ፥ ኾኑም ፤ ርሱም ፡ አዟልና ፥ ተፈጠሩም ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ያመስግኑት ።

መዝ. ፡ 148 ፥ 6 ፤ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ አቆማቸው ፤ ትእዛዝን ፡ ሰጠ ፥ አያልፉምም ።

መዝ. ፡ 148 ፡ 7 ፤ እባቦች ፡ ጥልቆችም ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ከምድር ፡ አመስግኑት ፤

መዝ. ፡ 148 ፡ 8 ፤ እሳትና ፡ በረዶ ፡ ዐመዳይና ፡ ውርጭ ፥ ቃሉን ፡ የሚያደርግ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፤

መዝ. ፡ 148 ፡ 9 ፤ ተራራዎች ፡ ኰረብታዎችም ፡ ኹሉ ፥ የሚያፈራም ፡ ዛፍ ፡ ዝግባም ፡ ኹሉ ፤

መዝ. ፡ 148 ፡ 10 ፤ አራዊትም ፡ እንስሳትም ፡ ኹሉ ፥ ተንቀሳቃሾችም ፡ የሚበሩ ፡ ወፎችም ፤

መዝ. ፡ 148 ፡ 11 ፤ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፥ አለቃዎች ፡ የምድርም ፡ ፈራጆች ፡ ኹሉ ፥

መዝ. ፡ 148 ፡ 12 ፤ ጕልማሳዎችና ፡ ቈነጕሯት ፥ ሽማግሌዎችና ፡ ልጆች ፤

መዝ. ፡ 148 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ያመስግኑ ፤ ስሙ ፡ ብቻውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ምስጋናውም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 148 ፡ 14 ፤ የሕዝቡንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፤ የቅዱሳኑንም ፡ ኹሉ ፡ ምስጋና ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለቀረበ ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሕዝብ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 149 ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። ለእግዚአብሔር ፡ ዐዲሱን ፡ ቅኔ ፡ ተቀኙለት ፤ ምስጋናው ፡ በቅዱሳኑ ፡ ጉባኤ ፡ ነው ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 2 ፤ እስራኤል ፡ በፈጣሪው ፡ ደስ ፡ ይበለው ፥ የጽዮንም ፡ ልጆች ፡ በንጉሣቸው ፡ ሐሤትን ፡ ያድርጉ ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 3 ፤ ስሙን ፡ በዘፈን ፡ ያመስግኑ ፥ በከበሮና ፡ በመሰንቆም ፡ ይዘምሩለት ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሕዝቡ ፡ ተደስቷልና ፥ የዋሃንንም ፡ በማዳኑ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋልና ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 5 ፤ ቅዱሳን ፡ በክብር ፡ ይመካሉ ፤ በምንጣፋቸውም ፡ ላይ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋሉ ።

መዝ. ፡ 149 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ በጉረሯቸው ፡ ነው ፤ ኹለት ፡ አፍ ፡ ያለውም ፡ ሰይፍ ፡ በእጃቸው ፡ ነው ፥

መዝ. ፡ 149 ፡ 7 ፤ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ በቀልን ፡ በሰዎችም ፡ መካከል ፡ ቅጣትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፤

መዝ. ፡ 149 ፡ 8 ፤ ንጉሦቻቸውን ፡ በሰንሰለት ፥ አለቃዎቻቸውንም ፡ በእግር ፡ ብረት ፡ ያስሩ ፡ ዘንድ ፤

መዝ. ፡ 149 ፡ 9 ፤ የተጻፈውን ፡ ፍርድ ፡ ያደርጉባቸው ፡ ዘንድ ፦ ለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ይህች ፡ ክብር ፡ ናት ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

መዝሙር ፡ 150 ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 1 ፤ ሃሌ ፡ ሉያ ። እግዚአብሔርን ፡ በመቅደሱ ፡ አመስግኑት ፤ በኀይሉ ፡ ጠፈር ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 2 ፤ በችሎቱ ፡ አመስግኑት ፤ በታላቅነቱ ፡ ብዛት ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 3 ፤ በመለከት ፡ ድምፅ ፡ አመስግኑት ፤ በበገናና ፡ በመሰንቆ ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 4 ፤ በከበሮና ፡ በዘፈን ፡ አመስግኑት ፤ በአውታርና ፡ በእንቢልታ ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 5 ፤ ድምፁ ፡ መልካም ፡ በኾነ ፡ ጸናጽል ፡ አመስግኑት ፤ እልልታ ፡ ባለው ፡ ጸናጽል ፡ አመስግኑት ።

መዝ. ፡ 150 ፡ 6 ፤ እስትንፋስ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን ። ሃሌ ፡ ሉያ ❖

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምሳ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የሰሎሞን ፡ ምሳሌዎች ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ጥበብንና ፡ ተግሣጽን ፡ ለማወቅ ፥ የዕውቀትንም ፡ ቃል ፡ ለማስተዋል ፥

ምሳ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ የጥበብን ፡ ትምህርት ፡ ጽድቅንና ፡ ፍርድን ፡ ቅንነትንም ፡ ለመቀበል ፥

ምሳ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ብልኀትን ፡ ለአላዋቂዎች ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፥ ለጐበዛዝትም ፡ ዕውቀትንና ፡ ጥንቃቄን ፥

ምሳ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ጠቢብ ፡ እነዚህን ፡ ከመስማት ፡ ጥበብን ፡ ይጨምራል ፥ አስተዋይም ፡ መልካም ፡ ምክርን ፡ ገንዘቡ ፡ ያደርጋል ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ምሳሌንና ፡ ትርጓሜን ፥ የጠቢባንን ፡ ቃልና ፡ የተሸሸገውን ፡ ነገር ፡ ለማስተዋል ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የጥበብ ፡ መዠመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ፤ ሰነፎች ፡ ግን ፡ ጥበብንና ፡ ተግሣጽን ፡ ይንቃሉ ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ የአባትኽን ፡ ምክር ፡ ስማ ፥ የእናትኽንም ፡ ሕግ ፡ አትተው ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ለራስኽ ፡ የሞገስ ፡ ዘውድ ፡ ለዐንገትኽም ፡ ድሪ ፡ ይኾንልኻልና ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ኀጢአተኞች ፡ ቢያባብሉኽ ፡ ዕሺ ፡ አትበል ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ና ፡ እናድባ ፥ ለንጹሕም ፡ ያለምክንያት ፡ ወጥመድን ፡ እንሸምቅበት ፡ ቢሉ ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በሕይወታቸው ፡ ሳሉ ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ኾነን ፡ እንዋጣቸው ፥ በሙሉም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ እንደሚወድቁ ፡ ይኹኑ ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ መልካሙን ፡ ሀብት ፡ ኹሉ ፡ እናገኛለን ፥ ከምርኮውም ፡ ቤታችንን ፡ እንሞላለን ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ዕጣኽን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ጣል ፤ ለኹላችንም ፡ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ይኹን ፡ ቢሉ ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በመንገድ ፡ አትኺድ ፥ ከጐዳናቸውም ፡ እግርኽን ፡ ፈቀቅ ፡ አድርግ ፤

ምሳ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ እግሮቻቸው ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ይሮጣሉና ፥ ደም ፡ ለማፍሰስም ፡ ይፈጥናሉና ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ መርበብ ፡ በወፎች ፡ ዐይን ፡ ፊት ፡ በከንቱ ፡ ትተከላለችና ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ እነርሱም ፡ በደማቸው ፡ ላይ ፡ ያደባሉ ፥ በነፍሳቸውም ፡ ላይ ፡ ይሸምቃሉ ።

ምሳ. ፥ 1 ፥ 19 ፤ እንዲሁ ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ ትርፍን ፡ ለማግኘት ፡ የሚሣሣ ፡ ኹሉ ፡ ነው ። የባለቤቱን ፡ ነፍስ ፡ ይነጥቃል ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ጥበብ ፡ በጐዳና ፡ ትጮኻለች ፤ በአደባባይ ፡ ድምፂን ፡ ከፍ ፡ ታደርጋለች ፤

ምሳ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ በአደባባይ ፡ ትጣራለች ፤ በከተማዩቱ ፡ መግቢያ ፡ በር ፡ ቃልን ፡ ትናገራለች ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ እናንተ ፡ አላዋቂዎች ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ አላዋቂነት ፡ ትወዳላችኹ ፧ ፈዘኞችም ፡ ፈዝን ፡ ይፈቅዳሉ ፧ ሰነፎችም ፡ ዕውቀትን ፡ ይጠላሉ ፧

ምሳ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ ዘለፋዬ ፡ ተመለሱ ፤ እንሆ ፥ መንፈሴን ፡ አፈስላችኋለኹ ፤ ቃሌን ፡ አስተምራችኋለኹ ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ እምቢ ፡ ስላላችኹ ፥ እጄን ፡ በዘረጋኹ ፡ ጊዜ ፡ ማንም ፡ ስላላስተዋለ ፥

ምሳ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ምክሬን ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ቸል ፡ ስላላችኹ ፥ ዘለፋዬንም ፡ ስላልፈቀዳችኹ ፤

ምሳ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ እኔም ፡ ስለዚህ ፡ በጥፋታችኹ ፡ እሥቃለኹ ፤ ጥፋታችኹም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አላግጥባችኋለኹ ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ድንጋጤ ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ በደረሰባችኹ ፡ ጊዜ ፥ ጥፋታችኹም ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ ጭንቅና ፡ መከራ ፡ በወረደባችኹ ፡ ጊዜ ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይጠሩኛል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልመልስም ፤ ተግተው ፡ ይሹኛል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አያገኙኝም ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ዕውቀትን ፡ ጠልተዋልና ፥ እግዚአብሔርንም ፡ መፍራት ፡ አልመረጡምና ፤

ምሳ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ ምክሬን ፡ አልፈቀዱምና ፥ ዘለፋዬንም ፡ ኹሉ ፡ ንቀዋልና ፤

ምሳ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ የመንገዳቸውን ፡ ፍሬ ፡ ይበላሉ ፥ ከራሳቸው ፡ ምክር ፡ ይጠግባሉ ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ አላዋቂዎችን ፡ ከጥበብ ፡ መራቅ ፡ ይገድላቸዋልና ፥ ሰነፎችንም ፡ ቸልተኛ ፡ መኾን ፡ ያጠፋቸዋልና ።

ምሳ. ፡ 1 ፡ 33 ፤ የሚሰማኝ ፡ ግን ፡ በርጋታ ፡ ይቀመጣል ፥ ከመከራም ፡ ሥጋት ፡ ያርፋል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ቃሌን ፡ ብትቀበል ፥ ትእዛዜንም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሸሽገኽ ፡ ብትይዛት ፥

ምሳ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ጐሮኽ ፡ ጥበብን ፡ እንዲያደምጥ ፡ ታደርጋለኽ ፥ ልብኽንም ፡ ወደ ፡ ማስተዋል ፡ ታዘነብላለኽ ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ረቂቅ ፡ ዕውቀትን ፡ ብትጠራት ፥ ለማስተዋልም ፡ ድምፅኽን ፡ ብታነሣ ፥

ምሳ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ርሷንም ፡ እንደ ፡ ብር ፡ ብትፈላልጋት ፥ ርሷንም ፡ እንደተቀበረ ፡ ገንዘብ ፡ ብትሻት ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ታውቃለኽ ፥ የአምላክንም ፡ ዕውቀት ፡ ታገኛለኽ ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥበብን ፡ ይሰጣልና ፤ ከአፉም ፡ ዕውቀትና ፡ ማስተዋል ፡ ይወጣሉ ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ርሱ ፡ ለቅኖች ፡ ደኅንነትን ፡ ያከማቻል ፤ ያለነውር ፡ ለሚኼዱትም ፡ ጋሻ ፡ ነው ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ የፍርድን ፡ ጐዳና ፡ ይጠብቃል ፤ የቅዱሳኑንም ፡ መንገድ ፡ ያጸናል ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጽድቅንና ፡ ፍርድን ፡ ቅንነትንና ፡ መልካም ፡ መንገድን ፡ ኹሉ ፡ ታስተውላለኽ ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ጥበብ ፡ ወደ ፡ ልብኽ ፡ ትገባለችና ፥ ዕውቀትም ፡ ነፍስኽን ፡ ደስ ፡ ታሠኛለችና ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ጥንቃቄ ፡ ይጠብቅኻል ፥ ማስተዋልም ፡ ይጋርድኻል ፥

ምሳ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ከክፉ ፡ መንገድ ፡ አንተን ፡ ለማዳን ፥ ጠማማ ፡ ነገርን ፡ ከሚናገሩም ፡ ሰዎች ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ በጨለማ ፡ መንገድ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ የቀናውን ፡ ጐዳና ፡ የሚተዉ ፥

ምሳ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ክፉ ፡ በመሥራት ፡ ደስ ፡ የሚላቸው ፡ በጠማማነትም ፡ ደስታን ፡ የሚያደርጉ ፥

ምሳ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ መንገዳቸውን ፡ የሚጠመዝዙ ፥ አካኼዳቸውንም ፡ የሚያጣምሙ ፡ ናቸው ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ከጋለሞታ ፡ ሴት ፡ አንተን ፡ ለመታደግ ፥ ቃሏን ፡ ከምታለዝብ ፡ ከሌላዪቱም ፡ ሴት ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ የሕፃንነት ፡ ወዳጇን ፡ የምትተው ፡ የአምላኳንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የምትረሳ ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ቤቷ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ያዘነበለ ፡ ነው ፥ አካኼዷም ፡ ወደሙታን ፡ ጥላ ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ርሷ ፡ የሚገቡ ፡ ኹሉ ፡ አይመለሱም ፥ የሕይወትንም ፡ ጐዳና ፡ አያገኙም ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ አንተም ፡ በደጋግ ፡ ሰዎች ፡ መንገድ ፡ እንድትኼድ ፡ የጻድቃንንም ፡ ጐዳና ፡ እንድትጠብቅ ።

ምሳ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ቅኖች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉና ፥ ፍጹማንም ፡ በርሷ ፡ ይኖራሉና ፤

ምሳ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ ከምድር ፡ ይጠፋሉ ፥ ዐመፀኞችም ፡ ከርሷ ፡ ይነጠቃሉ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ሕጌን ፡ አትርሳ ፥ ልብኽም ፡ ትእዛዛቴን ፡ ይጠብቅ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ብዙ ፡ ዘመናትና ፡ ረኀቦም ፡ ዕድሜ ፡ ሰላምም ፡ ይጨምሩልኻልና ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ምሕረትና ፡ እውነት ፡ ከአንተ ፡ አይራቁ ፤ በዐንገትኽ ፡ እሰራቸው ፤ በልብኽ ፡ ጽላት ፡ ጻፋቸው ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ፊትም ፡ ሞገስንና ፡ መልካም ፡ ዝናን ፡ ታገኛለኽ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመን ፥ በራስኽም ፡ ማስተዋል ፡ አትደገፍ ፤

ምሳ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ በመንገድኽ ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ ዕወቅ ፥ ርሱም ፡ ጐዳናኽን ፡ ያቀናልኻል ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በራስኽ ፡ አስተያየት ፡ ጠቢብ ፡ አትኹን ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ ፥ ከክፋትም ፡ ራቅ ፤

ምሳ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ይህም ፡ ለሥጋኽ ፡ ፈውስ ፡ ይኾንልኻል ፥ ለዐጥንትኽም ፡ ጠገን ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከሀብትኽ ፡ አክብር ፥ ከፍሬኽም ፡ ኹሉ ፡ በኩራት ፤

ምሳ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ጐተራኽም ፡ እኽልን ፡ ይሞላል ፥ መጥመቂያኽም ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ሞልታ ፡ ትትረፈረፋለች ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ተግሣጽ ፡ አትናቅ ፥ በገሠጸኽም ፡ ጊዜ ፡ አትመረር ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ ይገሥጻልና ፥ አባት ፡ የሚወደውን ፡ ልጁን ፡ እንደሚገሥጽ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ጥበብን ፡ የሚያገኝ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፥ ማስተዋልንም ፡ ገንዘቡ ፡ የሚያደርግ ፤

ምሳ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ በወርቅና ፡ በብር ፡ ከመነገድ ፡ ይልቅ ፡ በርሷ ፡ መነገድ ፡ ይሻላልና ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ከቀይ ፡ ዕንቊም ፡ ትከብራለች ፥ የተከበረም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይተካከላትም ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ በቀኟ ፡ ረዥም ፡ ዘመን ፡ ነው ፥ በግራዋም ፡ ባለጠግነትና ፡ ክብር ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ መንገዷ ፡ የደስታ ፡ መንገድ ፡ ነው ፥ ጐዳናዋም ፡ ኹሉ ፡ ሰላም ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ርሷ ፡ ለሚይዟት ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ናት ፥ የተመረኰዘባትም ፡ ኹሉ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ በጥበብ ፡ ምድርን ፡ መሠረተ ፥ በማስተዋልም ፡ ሰማያትን ፡ አጸና ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ በዕውቀቱ ፡ ቀላያት ፡ ተቀደዱ ፥ ደመናትም ፡ ጠልን ፡ ያንጠባጥባሉ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ከዐይኖችኽ ፡ አይራቁ ፤ መልካም ፡ ጥበብንና ፡ ጥንቃቄን ፡ ጠብቅ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ለነፍስኽም ፡ ሕይወት ፡ ይኾናሉ ፥ ለዐንገትኽም ፡ ሞገስ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ መንገድኽን ፡ ተማምነኽ ፡ ትኼዳለኽ ፥ እግርኽም ፡ አይሰነካከልም ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ በተኛኽ ፡ ጊዜ ፡ አትፈራም ፤ ትተኛለኽ ፥ እንቅልፍኽም ፡ የጣፈጠ ፡ ይኾንልኻል ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ድንገት ፡ ከሚያስፈራ ፡ ነገር ፥ ከሚመጣውም ፡ ከኃጥኣን ፡ ጥፋት ፡ አትፈራም ፤

ምሳ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔር ፡ መታመኛኽ ፡ ይኾናልና ፥ እግርኽም ፡ እንዳይጠመድ ፡ ይጠብቅኻልና ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ለተቸገረው ፡ ሰው ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ማድረግ ፡ አትከልክል ፥ ልታደርግለት ፡ የሚቻልኽ ፡ ሲኾን ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ወዳጅኽን ፦ ኺድና ፡ ተመለስ ፤ ነገ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አትበለው ፥ በጎ ፡ ነገርን ፡ ማድረግ ፡ ሲቻልኽ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ በወዳጅኽ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ አትሥራ ፥ ርሱ ፡ ተማምኖ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ ከሰው ፡ ጋራ ፡ በከንቱ ፡ አትጣላ ፥ ርሱ ፡ ክፉ ፡ ካልሠራብኽ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ በግፈኛ ፡ ሰው ፡ አትቅና ፥ መንገዱንም ፡ ኹሉ ፡ አትምረጥ ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ ጠማማ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርኩስ ፡ ነውና ፤ ወዳጅነቱ ፡ ግን ፡ ከቅኖች ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 33 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መርገም ፡ በኃጥእ ፡ ቤት ፡ ነው ፥ የጻድቃን ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ይባረካል ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 34 ፤ በፌዘኞች ፡ ርሱ ፡ ያፌዛል ፥ ለትሑታን ፡ ግን ፡ ሞገስን ፡ ይሰጣል ።

ምሳ. ፡ 3 ፡ 35 ፤ ጠቢባን ፡ ክብርን ፡ ይወርሳሉ ፤ የሰነፎች ፡ ከፍታቸው ፡ ግን ፡ መዋረድ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ ልጆች ፥ የአባትን ፡ ተግሣጽ ፡ ስሙ ፥ ማስተዋልንም ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አድምጡ ፤

ምሳ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ መልካም ፡ ትምህርትን ፡ እሰጣችኋለኹና ፤ ሕጌን ፡ አትተዉ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እኔም ፡ አባቴን ፡ የምሰማ ፡ ልጅ ፡ ነበርኹና ፥ በእናቴም ፡ ዘንድ ፡ እወደድ ፡ ነበር ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ያስተምረኝም ፡ ነበር ፡ እንዲህም ፡ ይለኝ ፡ ነበር ፦ ልብኽ ፡ ቃሌን ፡ ይቀበል ፤ ትእዛዜን ፡ ጠብቅ ፡ በሕይወትም ፡ ትኖራለኽ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ጥበብን ፡ አግኝ ፤ ማስተዋልን ፡ አግኝ ፤ አትርሳም ፥ ከአፌም ፡ ቃል ፡ ፈቀቅ ፡ አትበል ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ አትተዋት ፥ ትደግፍኽማለች ፤ ውደዳት ፥ ትጠብቅኽማለች ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ጥበብ ፡ ዐይነተኛ ፡ ነገር ፡ ናትና ፥ ጥበብን ፡ አግኝ ፤ ከሀብትኽም ፡ ኹሉ ፡ ማስተዋልን ፡ አትርፍ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አድርጋት ፥ ርሷም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ታደርግኻለች ፤ ብታቅፋትም ፡ ታከብርኻለች ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ለራስኽ ፡ የሞገስ ፡ አክሊልን ፡ ትሰጥኻለች ፥ የተዋበ ፡ ዘውድንም ፡ ታበረክትኻለች ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፥ ንግግሬንም ፡ ተቀበል ፤ የሕይወትኽም ፡ ዘመን ፡ ትበዛልኻለች ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ የጥበብን ፡ መንገድ ፡ አስተማርኹኽ ፤ በቀናች ፡ ጐዳና ፡ መራኹኽ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ በኼድኽ ፡ ጊዜ ፡ ርምጃኽ ፡ አይጠብብም ፤ በሮጥኽም ፡ ጊዜ ፡ አትሰናከልም ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ተግሣጽን ፡ ያዝ ፥ አትተውም ፤ ጠብቀው ፥ ርሱ ፡ ሕይወትኽ ፡ ነውና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ በኃጥኣን ፡ መንገድ ፡ አትግባ ፥ በክፉ ፡ ሰዎችም ፡ ጐዳና ፡ አትኺድ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ከርሷ ፡ ራቅ ፥ አትኺድባትም ፤ ፈቀቅ ፡ በል ፥ ተዋትም ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ክፉ ፡ ካላደረጉ ፡ አይተኙምና ፥ ካላሰናከሉም ፡ እንቅልፋቸው ፡ ይወገዳልና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ የኀጢአትን ፡ እንጀራ ፡ ይበላሉና ፥ የግፍንም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ የጻድቃን ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ብርሃን ፡ ነው ፥ ሙሉ ፡ ቀን ፡ እስኪኾንም ፡ ድረስ ፡ እየተጨመረ ፡ ይበራል ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ የኃጥኣን ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ጨለማ ፡ ነው ፥ እንዴት ፡ እንደሚሰናከሉም ፡ አያውቁም ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ንግግሬን ፡ አድምጥ ፡ ወደ ፡ ቃሌም ፡ ገሮኽን ፡ አዘንብል ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ከዐይንኽ ፡ አታርቃት ፥ በልብኽም ፡ ውስጥ ፡ ጠብቃት ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ለሚያገኟት ፡ ሕይወት ፥ ለሥጋቸውም ፡ ኹሉ ፡ ፈውስ ፡ ነውና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ አጥብቀኽ ፡ ልብኽን ፡ ጠብቅ ፥ የሕይወት ፡ መውጫ ፡ ከርሱ ፡ ነውና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ የአፍኽን ፡ ጠማማነት ፡ ከአንተ ፡ አውጣ ፥ ሐሰተኞቹን ፡ ከንፈሮችም ፡ ከአንተ ፡ አርቅ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ዐይኖችኽ ፡ አቅንተው ፡ ይዩ ፥ ሽፋሽፍቶችኽም ፡ በቀጥታ ፡ ይመልከቱ ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ የእግርኽን ፡ መንገድ ፡ አቅና ፥ አካኼድኽም ፡ ኹሉ ፡ ይጽና ።

ምሳ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ አትበል ፤ እግርኽንም ፡ ከክፉ ፡ መልስ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ጥበቤ ፡ አድምጥ ፤ ጐሮኽን ፡ ወደ ፡ ትምህርቴ ፡ መልስ ፥

ምሳ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ጥንቃቄን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ከንፈሮችኽም ፡ ዕውቀትን ፡ እንዲጠብቁ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ከጋለሞታ ፡ ሴት ፡ ከንፈር ፡ ማር ፡ ይንጠባጠባልና ፥ አፏም ፡ ከቅቤ ፡ የለሰለሰ ፡ ነውና ፤

ምሳ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ፍጻሜዋ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሬት ፡ የመረረ ፡ ነው ፥ ኹለት ፡ አፍ ፡ እንዳለው ፡ ሰይፍም ፡ የተሳለ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ እግሮቿ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ይወርዳሉ ፥ አረማመዷም ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ነው ፤

ምሳ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ የቀና ፡ የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ አታገኝም ፤ በአካኼዷ ፡ የተቅበዘበዘች ፡ ናት ፥ የሚታወቅም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፥ ከአፌም ፡ ቃል ፡ አትራቁ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ መንገድኽን ፡ ከርሷ ፡ አርቅ ፥ ወደቤቷም ፡ ደጅ ፡ አትቅረብ ፥

ምሳ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ክብርኽ ፡ ለሌላ ፡ እንዳትሰጥ ፥ ዕድሜኽም ፡ ለጨካኝ ፤

ምሳ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ሌላዎች ፡ ከሀብትኽ ፡ እንዳይጠግቡ ፥ ድካምኽም ፡ በባዕድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ እንዳይኾን ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ በመጨረሻም ፡ ሥጋኽና ፡ ሰውነትኽ ፡ በጠፋ ፡ ጊዜ ፡ ታለቅሳለኽ ፥

ምሳ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ትላለኽም ፦ እንዴት ፡ ትምህርትን ፡ ጠላኹ ፥ ልቤም ፡ ዘለፋን ፡ ናቀ! ፥

ምሳ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ የአስተማሪዎቼንም ፡ ቃል ፡ አልሰማኹም ፥ ጐሮዎቼንም ፡ ወደ ፡ አስተማሪዎቼ ፡ አላዘነበልኹም ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በማኅበርና ፡ በጉባኤ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ ኾሉ ፡ ለመድረስ ፡ ጥቂት ፡ ቀረኝ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ከጕድጓድኽ ፡ ውሃ ፥ ከምንጭኽም ፡ የሚፈልቀውን ፡ ውሃ ፡ ጠጣ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ምንጮችኽ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፥ ወንዞችኽ ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፥ ይፈሳሉን ፧

ምሳ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ለአንተ ፡ ብቻ ፡ ይኹኑ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ እንግዳዎችም ፡ አይኹኑ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ምንጭኽ ፡ ቡሩክ ፡ ይኹን ፤ ከጕብዝናኽም ፡ ሚስት ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ እንደ ፡ ተወደደች ፡ ዋላ ፡ እንደ ፡ ተዋበችም ፡ ሚዳቋ ፥ ጡቷ ፡ ኾልጊዜ ፡ ታርካኽ ፥ በፍቅሯም ፡ ኾልጊዜ ፡ ጥገብ ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ጋለሞታ ፡ ሴት ፡ ትወዳለኽ ፧ የሌላዪቱንስ ፡ ብብት ፡ ለምን ፡ ታቅፋለኽ ፧

ምሳ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ የሰው ፡ መንገድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ነውና ፥ አካኼዱንም ፡ ኾሉ ፡ ርሱ ፡ ይመለከታልና ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ኃጥኣንን ፡ ኀጢአቱ ፡ ታጠምደዋለች ፥ በኀጢአቱም ፡ ገመድ ፡ ይታሰራል ።

ምሳ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ አልተቀጣምና ፡ ርሱ ፡ ይሞታል ፤ በስንፍናውም ፡ ብዛት ፡ ይስታል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ለጎረቤትኽ ፡ ዋስ ፡ ብትኾን ፥ ስለ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ እጅኽን ፡ አጋና ፡ ብትመታ ፥

ምሳ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ በአፍኽ ፡ ቃል ፡ ተጠመድኽ ፤ በአፍኽ ፡ ቃል ፡ ተያዝኽ ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አድርግ ፡ ራስኽንም ፡ አድን ፥ በጎረቤትኽ ፡ እጅ ፡ ወድቀኻልና ፤ ፈጥነኽ ፡ ኺድ ፥ ጎረቤትኽንም ፡ ነዝንዘው ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ለዐይንኽ ፡ እንቅልፍን ፡ ለሽፋሽፍቶችኽም ፡ እንጕልቻን ፡ አትስጥ ፥

ምሳ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሚዳቋ ፡ ከአዳኝ ፡ እጅ ፥ እንደ ፡ ወፍም ፡ ከአጥማጅ ፡ እጅ ፡ ትድን ፡ ዘንድ ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ ታካች ፥ ወደ ፡ ገብረ ፡ ጕንዳን ፡ ኺድ ፥ መንገዷንም ፡ ተመልከተኽ ፡ ጠቢብ ፡ ኹን ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ አለቃና ፡ አዛዥ ፡ ገዢም ፡ ሳይኖራት ፡

ምሳ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ መብሏን ፡ በበጋ ፡ ታሰናዳለች ፥ መኖዋንም ፡ በመከር ፡ ትሰበስባለች ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ታካች ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ትተኛለኽ ፧ ከእንቅልፍኽስ ፡ መቼ ፡ ትነሣለኽ ፧

ምሳ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ጥቂት ፡ ትተኛለኽ ፥ ጥቂት ፡ ታንቀላፋለኽ ፥ ትተኛም ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ እጅኽን ፡ ታጥፋለኽ ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ ድኽነትኽ ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፥ ችጋርኽም ፡ ሰይፍ ፡ እንደ ፡ ታጠቀ ፡ ሰው ፡ ይመጣብኻል ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ የበደለኛም ፡ ልጅ ፡ በጠማማ ፡ አፍ ፡ ይኼዳል ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ በዐይኑ ፡ ይጠቅሳል ፥ በእግሩ ፡ ይናገራል ፥ በጣቱ ፡ ያስተምራል ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ጠማማነት ፡ በልቡ ፡ አለ ፥ ዥልጊዜም ፡ ክፋትን ፡ ያስባል ፤ ጠብንም ፡ ይዘራል ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ ጥፋቱ ፡ ድንገት ፡ ይደርስበታል ፤ ድንገት ፡ ይደቃል ፥ ፈውስም ፡ ከቶ ፡ የለውም ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚጠላቸው ፡ ስድስት ፡ ነገሮች ፡ ናቸው ፥ ሰባትንም ፡ ነፍሱ ፡ አጥብቃ ፡ ትጸየፈዋለች ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ትዕቢተኛ ፡ ዐይን ፥ ሐሰተኛ ፡ ምላስ ፥ ንጹሕን ፡ ደም ፡ የምታፈስ ፡ እጅ ፥

ምሳ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ክፉ ፡ ዐሳብን ፡ የሚያበቅል ፡ ልብ ፥ ወደ ፡ ክፉ ፡ የምትሮጥ ፡ እግር ፥

ምሳ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ በሐሰት ፡ የሚናገር ፡ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ በወንድማማች ፡ መካከልም ፡ ጠብን ፡ የሚዘራ ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ የአባትኽን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ፥ የእናትኽንም ፡ ሕግ ፡ አትተው ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ዥልጊዜም ፡ በልብኽ ፡ አኑረው ፥ በዐንገትኽም ፡ አሰረው ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ስትኼድም ፡ ይመራኻል ፤ ስትተኛ ፡ ይጠብቅኻል ፤ ስትነሣ ፡ ያነጋግርኻል ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ትእዛዝ ፡ መብራት ፥ ሕግም ፡ ብርሃን ፡ ነውና ፥ የተግሣጽም ፡ ዘለፋ ፡ የሕይወት ፡ መንገድ ፡ ነውና ፥

ምሳ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ከክፉ ፡ ሴት ፡ ትጠብቅኽ ፡ ዘንድ ፥ ከሌላዪቱም ፡ ሴት ፡ ምላስ ፡ ጥፍጥነት ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ ውበቷን ፡ በልብኽ ፡ አትመኘው ፤ ሽፋሽፍቷም ፡ አያጥምድኽ ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ የጋለሞታ ፡ ዋጋ ፡ እስከ ፡ አንዲት ፡ እንጀራ ፡ ነው ፤ አመንዝራም ፡ ሴት ፡ የሰውን ፡ ሕይወት ፡ ታጠምዳለች ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ በጕያው ፡ እሳትን ፡ የሚታቀፍ ፥ ልብሶቹስ ፡ የማይቃጠሉ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ምሳ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ በፍም ፡ ላይ ፡ የሚኼድ ፡ እግሮቹስ ፡ የማይቃጠሉ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ምሳ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ወደሰው ፡ ሚስት ፡ የሚገባም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ የሚነካትም ፡ ኹሉ ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ ሌባ ፡ በተራበ ፡ ጊዜ ፡ ነፍሱን ፡ ሊያጠግብ ፡ ቢሰርቅ ፡ ሰዎች ፡ አይንቁትም ፤

ምሳ. ፡ 6 ፡ 31 ፤ ቢያገዝም ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይከፍላል ፥ በቤቱም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይሰጣል ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 32 ፤ ከሴት ፡ ጋራ ፡ የሚያመነዝር ፡ ግን ፡ አእምሮው ፡ የጐደለ ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ የሚያደርግ ፡ ነፍሱን ፡ ያጠፋል ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 33 ፤ ቍስልንና ፡ ውርደትን ፡ ያገኛል ፥ ስድቡም ፡ አይደመሰስም ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 34 ፤ ቅንአት ፡ ለሰው ፡ የቀኑጣ ፡ ትኵሳት ፡ ነውና ፥ በበቀል ፡ ቀን ፡ አይራራለትምና ።

ምሳ. ፡ 6 ፡ 35 ፤ ርሱም ፡ ምንም ፡ ካሳ ፡ አይቀበልም ፥ ስጦታም ፡ ብታበዛለት ፡ አይታረቅም ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ቃሌን ፡ ጠብቅ ፡ ትእዛዜንም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ሸሽግ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ትእዛዜን ፡ ጠብቅ ፡ በሕይወትም ፡ ትኖራለኽ ፤ ሕጌንም ፡ እንደ ፡ ዐይንኽ ፡ ብሌን ፡ ጠብቅ ፤

ምሳ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ በጣቶችኽ ፡ እሰራቸው ፤ በልብኽ ፡ ጽላት ፡ ጻፋቸው ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ጥበብን ፦ አንቺ ፡ እኅቴ ፡ ነሽ ፡ በላት ፥ ማስተዋልንም ፦ ወዳጄ ፡ ብለኽ ፡ ጥራት ፥

ምሳ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ከጋለሞታ ፡ ሴት ፡ ትጠብቅኽ ፡ ዘንድ ፡ ቃሏን ፡ ካለዘበች ፡ ከሌላዪቱ ፡ ሴት ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ በቤቴ ፡ መስኮት ፡ ኾኜ ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ተመለከትኹ ፤

ምሳ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ካላዋቂዎች ፡ መካከል ፡ አስተዋልኹ ፤ ከጐበዛዝትም ፡ መካከል ፡ ብላቴናውን ፡ አእምሮ ፡ ጐድሎት ፡ አየኹ ፥

ምሳ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ በአደባባይ ፡ ሲኼድ ፡ በቤቷም ፡ አቅራቢያ ፡ ሲያልፍ ፤ የቤቷን ፡ መንገድ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ አቀና ፥

ምሳ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ማታ ፡ ሲመሽ ፥ ውድቅትም ፡ ሲኾን ፥ በሌሊትም ፡ በጽኑ ፡ ጨለማ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ እንሆ ፥ ሴት ፡ ተገናኘችው ፥ የጋለሞታ ፡ ልብስ ፡ የለበሰች ፥ ነፍሳትን ፡ ለማጥመድ ፡ የተዘጋጀች ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ሁከተኛና ፡ አባያ ፡ ናት ፥ እግሮቿም ፡ በቤቷ ፡ አይቀመጡም ፤

ምሳ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በጐዳና ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በአደባባይ ፥ በማእዘኑም ፡ ኹሉ ፡ ታደባለች ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ያዘችውም ፥ ሳመችውም ፤ ፊቷም ፡ ያለዕፍረት ፡ ኾኖ ፡ እንዲህ ፡ አለችው ፦

ምሳ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ መሥዋዕትንና ፡ የደኅንነት ፡ ቍርባንን ፡ ማቅረብ ፡ ነበረብኝ ፤ ዛሬ ፡ ስእለቴን ፡ ፈጸምኹ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ እንድገናኝኽ ፥ ፊትኽንም ፡ በትጋት ፡ ለመሻት ፡ ወጥቻለኹ ፥ አግኝቼኻለኹም ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ በዐልጋዬ ፡ ላይ ፡ ማለፊያ ፡ ሰርፍ ፡ ዘርግቼበታለኹ ፥ የግብጽንም ፡ ሽመልመሌ ፡ ለሐፍ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ በመኝታዬ ፡ ከርቤንና ፡ ዓልሙን ፣ ቀረፋም ፡ ረጭቼበታለኹ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ና ፥ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ በፍቅር ፡ እንርካ ፥ በተወደደ ፡ መተቃቀፍም ፡ ደስ ፡ ይበለን ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ባለቤቴ ፡ በቤቱ ፡ የለምና ፥ ወደ ፡ ሩቅ ፡ መንገድ ፡ ኼዷልና ፤

ምሳ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ በእጁም ፡ የብር ፡ ከረጢት ፡ ወስዷል ፤ ሙሉ ፡ ጨረቃ ፡ በኾነች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ይመለሳል ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በብዙ ፡ ጨዋታዋ ፡ እንዲስት ፡ ታደርገዋለች ፤ በከንፈሯ ፡ ልዝብነት ፡ ትገፋትዋለች ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ርሱ ፡ እንዲህ ፡ ስቶ ፡ ይከተላታል ፥ በሬ ፡ ለመታረድ ፡ እንዲነዳ ፥ ውሻም ፡ ወደ ፡ እስራት ፡ እንዲኼድ ፥

ምሳ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ወፍ ፡ ወደ ፡ ወጥመድ ፡ እንደሚቸኵል ፥ ለነፍሱ ፡ ጥፋት ፡ እንደሚኾን ፡ ሳያውቅ ፥ ፍላጻ ፡ ጉበቱን ፡ እስኪሰነጥቀው ፡ ድረስ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ስሙኝ ፡ ወደአፌም ፡ ቃል ፡ አድምጡኝ ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ልብኽ ፡ ወደ ፡ መንገዷ ፡ አያዘንብል ፥ በጐዳናዋ ፡ አትሳት ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ወግታ ፡ የጣለቻቸው ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፤ ርሷም ፡ የገደለቻቸው ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ቤቷ ፡ የሲኦል ፡ መንገድ ፡ ነው ፤ ወደሞት ፡ ማጀት ፡ የሚወርድ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በእውኑ ፡ ጥበብ ፡ አትጮኽምን ፧ ማስተዋልስ ፡ ድምፃን ፡ አትሰጥምን ፧

ምሳ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ በኮረብታ ፡ ላይ ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ በጐዳና ፡ መካከል ፡ ትቆማለች ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ በከተማዩቱም ፡ መግቢያ ፥ በደጁ ፡ መግቢያ ፡ ትጮኻለች ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ ሰዎች ፥ እናንተን ፡ እጠራለኹ ፥ ድምፄም ፡ ወደሰዎች ፡ ልጆች ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እናንተ ፡ አላዋቂዎች ፥ ብልኀትን ፡ አስተውሉ ፤ እናንተም ፡ ሰነፎች ፡ ጥበብን ፡ በልባችኹ ፡ ያዙ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ የከበረች ፡ ነገርን ፡ እናገራለኹና ፡ ስሙ ፤ ከንፈሮቼም ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ለመናገር ፡ ይከፈታሉ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ አፌ ፡ እውነትን ፡ ይናገራልና ፥ ከንፈሮቼም ፡ ክፋትን ፡ ይጸየፋሉ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ የአፌ ፡ ቃላት ፡ ኹሉ ፡ ጽድቅ ፡ ናቸው ፤ ጠማማ ፡ ዘወርዋራም ፡ አይደሉም ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ እነርሱ ፡ በሚያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ የቀኑ ፡ ናቸው ፥ ዕውቀትንም ፡ ካገኟት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ የተስማሙ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ተግሣጼን ፡ እንጂ ፡ ብርን ፡ አትቀበሉ ፥ ከምዝምዝ ፡ ወርቅም ፡ ይልቅ ፡ ዕውቀትን ፡ ተቀበሉ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ጥበብ ፡ ከቀይ ፡ ዕንቊ ፡ ትበልጣለችና ፡ የከበረ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይተካከላትም ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ እኔ ፡ ጥበብ ፡ በብልኀት ፡ ተቀምጫለኹ ፥ ዕውቀትንም ፡ ጥንቃቄንም ፡ አግኝቻለኹ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ክፋትን ፡ ይጠላል ፤ ትዕቢትንና ፡ እብሪትን ፡ ክፉንም ፡ መንገድ ፡ ጠማማውንም ፡ አፍ ፡ እጠላለኹ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ምክርና ፡ መልካም ፡ ጥበብ ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ ማስተዋል ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ ብርታትም ፡ አለኝ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ነገሥታት ፡ በእኔ ፡ ይነግሣሉ ፥ ሹማምቶችም ፡ የቀናውን ፡ ነገር ፡ ይደነግጋሉ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ አለቃዎች ፡ በእኔ ፡ ያዛሉ ፥ ክቡራንና ፡ የምድር ፡ ፈራጆችም ፡ ኹሉ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ እኔ ፡ የሚወዱኝን ፡ እወዳለኹ ፥ ተግተው ፡ የሚሹኝም ፡ ያገኙኛል ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ብልጥግናና ፡ ክብር ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ ብዙ ፡ ሀብትና ፡ ጽድቅም ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ ፍሬዬም ፡ ከምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ይሻላል ፥ ቡቃያዬም ፡ ከተመረጠች ፡ ብር ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ እኔ ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ እኼዳለኹ ፥ በፍርድም ፡ ጐዳና ፡ መካከል ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ለሚወዱኝ ፡ ርስት ፡ አወርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ቤተ ፡ መዛግብታቸውንም ፡ እሞላ ፡ ዘንድ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ የመንገዱ ፡ መዠመሪያ ፡ አደረገኝ ፥ በቀድሞ ፡ ሥራው ፡ መዠመሪያ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ከጥንቱ ፡ ከዘለዓለም ፡ ዠምሮ ፡ ተሾምኹ ፤ ምድር ፡ ከመፈጠሯ ፡ አስቀድሞ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ ቀላያት ፡ ገና ፡ ሳይኖሩ ፡ እኔ ፡ ተወለድኹ ፥ የውሃ ፡ ምንጮች ፡ ገና ፡ ሳይፈልቁ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ተራራዎች ፡ ገና ፡ ሳይመሠረቱ ፥ ከኮረብታዎች ፡ በፊት ፡ እኔ ፡ ተወለድኹ ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ምድሪቱንና ፡ ሜዳውን ፡ ገና ፡ ሳይፈጥር ፤ የመዠመሪያውን ፡ የዓለም ፡ ዐፈር ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ሰማዮችን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፡ ዐብሬ ፡ ነበርኹ ፥ በቀላያት ፡ ፊት ፡ ክበብን ፡ በደነገገ ፡ ጊዜ ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ደመናትን ፡ በላይ ፡ ባዘጋጀ ፡ ጊዜ ፥ የቀላይን ፡ ምንጮች ፡ ባጸና ፡ ጊዜ ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ ለባሕርም ፡ ዳርቻን ፡ በወሰነ ፡ ጊዜ ፡ ውሃ ፡ ከትእዛዙ ፡ እንዳያልፍ ፥ የምድርን ፡ መሠረት ፡ በመሠረተ ፡ ጊዜ ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዋና ፡ ሠራተኛ ፡ ነበርኹ ፤ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ደስ ፡ አሠኘው ፡ ነበር ፥ በፊቱም ፡ ዘውልጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለኝ ፡ ነበር ፥

ምሳ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ ደስታዬም ፡ በምድሩ ፡ ተድላዬም ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ነበረ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ አኹንም ፡ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ መንገዴንም ፡ የሚጠብቁ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ ትምህርቴን ፡ ስሙ ፥ ጠቢባንም ፡ ኹኑ ፥ ቸል ፡ አትበሉትም ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ የሚሰማኝ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በቤቴ ፡ መግቢያ ፡ የሚተጋ ፥ የደጄንም ፡ መድረክ ፡ የሚጠብቅ ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ እኔን ፡ ያገኘ ፡ ሕይወትን ፡ ያገኛልና ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ ሞገስን ፡ ያገኛልና ።

ምሳ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ እኔን ፡ ያጣ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ይጐዳል ፤ የሚጠሉኝ ፡ ኹሉ ፡ ሞትን ፡ ይወዳሉ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ጥበብ ፡ ቤቷን ፡ ሠራች ፥ ሰባቱንም ፡ ምሰሶዎቿን ፡ አቆመች ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ፍሪዳዋን ፡ ዐረደች ፥ የወይን ፡ ጠጇን ፡ ደባለቀች ፥ ማእዷን ፡ አዘጋጀች ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ባሪያዎቿን ፡ ልካ ፡ በከተማዩቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ጠራች ፦

ምሳ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ አላዋቂ ፡ የኾነ ፡ ወደዚህ ፡ ፈቀቅ ፡ ይበል ፤ አእምሮ ፡ የጐደላቸውንም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦

ምሳ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ኑ ፥ እንጀራዬን ፡ ብሉ ፥ የደባለቅኹትንም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጡ ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ አላዋቂነትን ፡ ትታችኹ ፡ በሕይወት ፡ ኑሩ ፥ በማስተዋልም ፡ መንገድ ፡ ኺዱ ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ፈዘኛን ፡ የሚገሥጽ ፡ ለራሱ ፡ ስድብን ፡ ይቀበላል ፥ ኃጥእንም ፡ የሚዘልፍ ፡ ነውርን ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ፈዘኛን ፡ አትገሥጽ ፡ እንዳይጠላኽ ፤ ጠቢብን ፡ ገሥጽ ፡ ይወድኽማል ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ለጠቢብ ፡ ሰው ፡ ትምህርትን ፡ ስጠው ፥ ጥበብንም ፡ ያበዛል ፤ ጽድቅንም ፡ አስተምረው ፥ ዕውቀትንም ፡ ያበዛል ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ የጥበብ ፡ መዠመሪያ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ነው ፤ ቅዱሱንም ፡ ማወቅ ፡ ማስተዋል ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ዘመንኽ ፡ በእኔ ፡ ይበዛልና ፥ የሕይወትኽም ፡ ዕድሜ ፡ ይጨመርልኻልና ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ጠቢብ ፡ ብትኾን ፡ ለራስኽ ፡ ጠቢብ ፡ ትኾናለኽ ፥ ፈዘኛም ፡ ብትኾን ፡ ፈዘኛነትኽን ፡ ለብቻኽ ፡ ትሸከማለኽ ።

[የሚቀጥለው ፡ ከግሪክ ፡ የተጨመረ ፡ ነው ።] ፡ ልጄ ፡ ለራስኽ ፡ ዐዋቂ ፡ ብትኾን ፡ ለባልንጀራኽም ፡ ዐዋቂ ፡ ትኾናለኽ ፤ ለራስኽ ፡ ክፉ ፡ ብትኾን ፡ ግን ፡ ክፋትኽን ፡ ትማራለኽ ። ሐሰትን ፡ የሚያዘጋጅ ፡ ሰው ፡ ነፋሳትን ፡ እንደሚያዘጋጅ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ የሚበር ፡ ወፍንም ፡ እንደሚከተል ፡ ይመስላል ። የወይኑ ፡ ቦታ ፡ መንገዱን ፡ ተወ ፤ የሚሠማራባትን ፡ መንገድ ፡ ዘነጋ ፤ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይኼዳል ፡ ለጥም ፡ ወደተሠራች ፡ አገር ፡ ይኼዳል ፤ የማያፈራ ፡ የማይጠቅም ፡ ገንዘብንም ፡ በእጁ ፡ ይሰበስባል ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ሰነፍ ፡ ሴት ፡ ሁከተኛ ፡ ናት ፤ ዐሳብ ፡ የላትም ፥ አንዳችም ፡ አታውቅም ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ በቤቷ ፡ ደጅ ፡ በከተማዩቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ስፍራ ፡ በወንበር ፡ ላይ ፡ ትቀመጣለች ፥

ምሳ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ በመንገድ ፡ የሚያልፉትን ፡ አካኼዳቸውንም ፡ ያቀኑትን ፡ ለመጥራት ፦

ምሳ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ አላዋቂ ፡ የኾነ ፡ ወደዚህ ፡ ፈቀቅ ፡ ይበል ፤ አእምሮ ፡ የጐደለውንም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦

ምሳ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ የስርቆት ፡ ውሃ ፡ ይጣፍጣል ፥ የተሸሸገም ፡ እንጀራ ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ።

ምሳ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ ሙታን ፡ ከዚያ ፡ እንዳሉ ፥ ዕድምተኞቿም ፡ በሲኦል ፡ ጥልቀት ፡ እንዳሉ ፡ አያውቅም ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ የሰሎሞን ፡ ምሳሌዎች ። ጠቢብ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ፤ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ለእናቱ ፡ ሐዘን ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በኀጢአት ፡ የተገኘ ፡ መዝገብ ፡ ጥቅም ፡ የለውም ፤ ጽድቅ ፡ ግን ፡ ከሞት ፡ ያድናል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጻድቁን ፡ ነፍስ ፡ አያስርብም ፤ የኃጥኣንን ፡ ምኞት ፡ ግን ፡ ይገለብጣል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የታካች ፡ እጅ ፡ ችግረኛ ፡ ታደርጋለች ፤ የትጉህ ፡ እጅ ፡ ግን ፡ ባለጠጋ ፡ ታደርጋለች ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ በበጋ ፡ የሚያከማች ፡ ልጅ ፡ አስተዋይ ፡ ነው ፤ በመከር ፡ የሚተኛ ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ራሱን ፡ ያስነውራል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ በረከት ፡ በጻድቅ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ የኃጥኣንን ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ግፍ ፡ ይከድነዋል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ የጻድቅ ፡ መታሰቢያ ፡ ለበረከት ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ ስም ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ በልቡ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ ትእዛዝን ፡ ይቀበላል ፤ በከንፈሩ ፡ የሚሰንፍ ፡ ግን ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ያለነውር ፡ የሚኼድ ፡ ተማምኖ ፡ ይኼዳል ፤ መንገዱን ፡ የሚያጣምም ፡ ግን ፡ ይታወቃል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ በዐይኑ ፡ የሚጠቅስ ፡ መከራን ፡ ያመጣል ፤ ደፍሮ ፡ የሚገሥጽ ፡ ግን ፡ ሰላምን ፡ ያደርጋል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ የጻድቅ ፡ አፍ ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ናት ፤ የኃጥኣንን ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ግፍ ፡ ይከድነዋል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ጥል ፡ ክርክርን ፡ ታስነሣለች ፤ ፍቅር ፡ ግን ፡ ኀጢአትን ፡ ኹሉ ፡ ትከድናለች ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ በብልኀተኛ ፡ ከንፈር ፡ ጥበብ ፡ ትገኛለች ፤ በትር ፡ ግን ፡ አእምሮ ፡ ለጐደለው ፡ ሰው ፡ ገርርባ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ጠቢባን ፡ ዕውቀትን ፡ ይሸሽጋሉ ፤ የሰነፍ ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ለጥፋት ፡ ይቀርባል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ የባለጠጋ ፡ ሀብት ፡ ለርሱ ፡ የጸናች ፡ ከተማ ፡ ናት ፤ የድኻዎች ፡ ጥፋት ፡ ድኽነታቸው ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ የጻድቅ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ለሕይወት ፡ ነው ፤ የኃጥእ ፡ ፍሬ ፡ ግን ፡ ለኀጢአት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ተግሣጽን ፡ የሚጠብቅ ፡ በሕይወት ፡ መንገድ ፡ ይኼዳል ፤ ዘለፋን ፡ የሚተው ፡ ግን ፡ ይስታል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ጥልን ፡ የሚከድን ፡ ሐሰተኛ ፡ ከንፈር ፡ አለው ፤ ሐሜትንም ፡ የሚገልጥ ፡ ሰነፍ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ በቃል ፡ ብዛት ፡ ውስጥ ፡ ኀጢአት ፡ ሳይኖር ፡ አይቀርም ፤ ከንፈሩን ፡ የሚገታ ፡ ግን ፡ አስተዋይ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ የጻድቅ ፡ ምላስ ፡ የተፈተነ ፡ ብር ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ምናምን ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ የጻድቅ ፡ ከንፈሮች ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ይመግባሉ ፤ ሰነፎች ፡ ግን ፡ ከልባቸው ፡ ጕድለት ፡ የተነሣ ፡ ይሞታሉ ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ የእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ባለጠጋ ፡ ታደርጋለች ፥ ሐዘንንም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ አይጨምርም ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ማድረግ ፡ ለሰነፍ ፡ ሰው ፡ ጨዋታ ፡ ነው ፤ እንዲሁም ፡ ጥበብ ፡ ለአስተዋይ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ የኃጥእ ፡ ሰው ፡ ፍርሀት ፡ በላዩ ፡ ይመጣበታል ፥ ለጻድቃንም ፡ ምኞታቸው ፡ ትሰጣቸዋለች ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ሲያልፍ ፡ ኃጥእ ፡ አይገኝም ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ የዘለዓለም ፡ መሠረት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ሐምጣጤ ፡ ጥርስን ፥ ጢስም ፡ ዐይንን ፡ እንደሚጐዳ ፥ እንዲሁም ፡ ታካች ፡ ለላኩት ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ዘመንን ፡ ታረዝማለች ፤ የኃጥኣን ፡ ዕድሜ ፡ ግን ፡ ታጥራለች ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ የጻድቃን ፡ አለኝታ ፡ ደስታ ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ ተስፋ ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ያለነውር ፡ ለሚኼድ ፡ ዐምባ ፡ ነው ፥ ጥፋት ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ ለሚያደርጉ ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ጻድቃን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይናወጡም ፤ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አይቀመጡም ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ የጻድቅ ፡ አፍ ፡ ጥበብን ፡ ይናገራል ፤ ጠማማ ፡ ምላስ ፡ ግን ፡ ትቈረጣለች ።

ምሳ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ የጻድቅ ፡ ከንፈሮች ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ ነገርን ፡ ያውቃሉ ፤ የኃጥኣን ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ጠማማ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ አባይ ፡ ሚዛን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፤ እውነተኛ ፡ ሚዛን ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ትዕቢት ፡ ከመጣች ፡ ውርደት ፡ ትመጣለች ፤ በትሑታን ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ጥበብ ፡ ትገኛለች ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ቅኖች ፡ ቅንነታቸው ፡ ትመራቸዋለች ፤ ወስላታዎችን ፡ ግን ፡ ጠማማነታቸው ፡ ታጠፋቸዋለች ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ በቀኑ ፡ ቀን ፡ ሀብት ፡ አትረባም ፤ ጽድቅ ፡ ግን ፡ ከሞት ፡ ታድናለች ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የፍጹም ፡ ሰው ፡ ጽድቁ ፡ መንገዱን ፡ ያቀናለታል ፤ ኃጥእ ፡ ግን ፡ በኀጢአቱ ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ቅኖችን ፡ ጽድቃቸው ፡ ይታደጋቸዋል ፤ ወስላታዎች ፡ ግን ፡ በምኞታቸው ፡ ይጠመዳሉ ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ኃጥእ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ተስፋው ፡ ይቈረጣል ፥ የኀያል ፡ አለኝታም ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ጻድቅ ፡ ከጭንቀት ፡ ይድናል ፥ ኃጥእም ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ይመጣል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ዝንጉ ፡ ሰው ፡ በአፉ ፡ ባልንጀራውን ፡ ያጠፋል ፤ ጻድቃን ፡ ግን ፡ በዕውቀት ፡ ይድናሉ ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በጻድቃን ፡ ልማት ፡ ከተማ ፡ ደስ ፡ ይላታል ፥ በኃጥኣንም ፡ ጥፋት ፡ እልል ፡ ትላለች ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ በቅኖች ፡ በረከት ፡ ከተማ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትላለች ፤ በኃጥኣን ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ትገለበጣለች ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ወዳጁን ፡ የሚንቅ ፡ ርሱ ፡ አእምሮ ፡ የጐደለው ፡ ነው ፤ አስተዋይ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ለሐሜት ፡ የሚኼድ ፡ ምስጢሩን ፡ ይገልጣል ፤ በመንፈስ ፡ የታመነ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ ይሰውራል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ መልካም ፡ ምክር ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝብ ፡ ይወድቃል ፤ በመካሮች ፡ ብዛት ፡ ግን ፡ ደኅንነት ፡ ይኾናል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ለማያውቅ ፡ የሚዋስ ፡ ክፉ ፡ መከራን ፡ ይቀበላል ፤ ዋስነትን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ ይድናል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ሞገስ ፡ ያላት ፡ ሴት ፡ ክብርን ፡ ታገኛለች ፥ ሀኬተኞችም ፡ ሀብትን ፡ ያገኛሉ ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ቸር ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ መልካም ፡ ያደርጋል ፤ ጨካኝ ፡ ግን ፡ ሥጋውን ፡ ይጐዳል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ የኃጥእ ፡ ሰው ፡ ሞያ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፤ ጽድቅን ፡ የሚዘራ ፡ ግን ፡ የታመነ ፡ ዋጋ ፡ አለው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ በጽድቅ ፡ የሚጸና ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፤ ክፋትን ፡ የሚከተል ፡ ግን ፡ ለሞቱ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ልበ ፡ ጠማማዎች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊዎች ፡ ናቸው ፤ በመንገዳቸው ፡ ፍጹማን ፡ የኾኑ ፡ ግን ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በእጅ ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ፤ የጻድቃን ፡ ዘር ፡ ግን ፡ ይድናል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ በዕሪያ ፡ አፍንጫ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከጥበብ ፡ የተለየች ፡ ቈንጆ ፡ ሴትም ፡ እንዲሁ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ የጻድቃን ፡ ምኞት ፡ በጎ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ ተስፋ ፡ ግን ፡ መቅሠፍት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ያለውን ፡ የሚበትን ፡ ሰው ፡ አለ ፥ ይጨመርለታልም ፤ ያለቅጥ ፡ የሚነፍግ ፡ ሰውም ፡ አለ ፥ ይደኸያልም ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ የምትባረክ ፡ ነፍስ ፡ ትጠግባለች ፥ የረካም ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይረካል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ እኽልን ፡ የሚያስቀር ፡ ሰው ፡ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ይረገማል ፤ በረከት ፡ ግን ፡ በሚሸጠው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ መልካምን ፡ ተግቶ ፡ የሚሻ ፡ ደስታን ፡ ይፈልጋል ፤ ክፉን ፡ በሚፈልግ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ይመጣበታል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ በባለጠግነቱ ፡ የሚተማመን ፡ ሰው ፡ ይወድቃል ፡ ጻድቃን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ይለመልማሉ ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ቤቱን ፡ የሚያውክ ፡ ሰው ፡ ነፋስን ፡ ይወርሳል ፥ ሰነፍም ፡ ለጠቢብ ፡ ተገዢ ፡ ይኾናል ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ የጻድቅ ፡ ፍሬ ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ናት ፥ ነፍሶችንም ፡ የሚሰበስብ ፡ ርሱ ፡ ጠቢብ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ እንሆ ፥ ጻድቅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ፍዳውን ፡ የሚቀበል ፡ ከኾነ ፥ ይልቁንስ ፡ ኃጥእና ፡ ዐመፀኛ ፡ እንዴት ፡ ይኾናሉ! ፡

_____መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ምሳ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ተግሣጽን ፡ የሚወድ ፡ ዕውቀትን ፡ ይወዳል ፤ ዘለፋን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ ደንቈሮ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ደኅና ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ሞገስን ፡ ያገኛል ፤ ተንኰለኛውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይቀሥፈዋል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ሰውን ፡ ዐመፃ ፡ አያጸናውም ፤ የጻድቃን ፡ ሥር ፡ ግን ፡ አይንቀሳቀስም ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ልባም ፡ ሴት ፡ ለባሏ ፡ ዘውድ ፡ ናት ፤ አሳፋሪ ፡ ሴት ፡ ግን ፡ በዐጥንቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ቅንቅን ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ የጻድቃን ፡ ዐሳብ ፡ ቅን ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ ምክር ፡ ግን ፡ ተንኰል ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የኃጥኣን ፡ ቃል ፡ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ ትሸምቃለች ፤ የቅኖች ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ይታደጋቸዋል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ኃጥኣን ፡ ይገለበጣሉ ፥ ደግሞም ፡ አይገኙም ፤ የጻድቃን ፡ ቤት ፡ ግን ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ሰው ፡ በጥበቡ ፡ ይመሰገናል ፤ ልቡ ፡ ጠማማ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይናቃል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ለራሱ ፡ ባሪያ ፡ ኾኖ ፡ የተጠቃ ፡ ሰው ፡ እንጀራ ፡ ጐድሎት ፡ ራሱን ፡ ካከበረው ፡ ሰው ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ለእንስሳው ፡ ነፍስ ፡ ይራራል ፤ የኃጥኣን ፡ ምሕረት ፡ ግን ፡ ጨካኝ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ምድሩን ፡ የሚሠራ ፡ ሰው ፡ እንጀራ ፡ ይጠግባል ፤ ለከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚሮጥ ፡ ግን ፡ አእምሮ ፡ የጐደለው ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ የኃጥኣን ፡ ፈቃድ ፡ የክፉዎች ፡ ወጥመድ ፡ ናት ፤ የጻድቃን ፡ ሥር ፡ ግን ፡ ፍሬን ፡ ያፈራል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ በከንፈሩ ፡ ኀጢአት ፡ ይጠመዳል ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ከመከራ ፡ ያመልጣል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ከአፉ ፡ ፍሬ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ትጠግባለች ፥ ሰውም ፡ እንደ ፡ እጁ ፡ ሥራ ፡ ዋጋውን ፡ ይቀበላል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ የሰነፍ ፡ መንገድ ፡ በዐይኑ ፡ የቀናች ፡ ናት ፤ ጠቢብ ፡ ግን ፡ ምክርን ፡ ይሰማል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ የሰነፍ ፡ ቍጣ ፡ ቶሎ ፡ ይታወቃል ፤ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ነውርን ፡ ይሰውራል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ እውነተኛን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ያወራል ፤ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ግን ፡ ተንኰልን ፡ ያወራል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ እንደሚዋጋ ፡ ሰይፍ ፡ የሚለፈልፍ ፡ ሰው ፡ አለ ፤ የጠቢባን ፡ ምላስ ፡ ግን ፡ ጤና ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ የእውነት ፡ ከንፈር ፡ ለዘለዓለም ፡ ትቆማለች ፤ ውሸተኛ ፡ ምላስ ፡ ግን ፡ ለቅጽበት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ክፉን ፡ በሚያስቡ ፡ ልብ ፡ ውስጥ ፡ ተንኰል ፡ አለ ፤ በሰላም ፡ ለሚመክሩ ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ አላቸው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ጻድቅን ፡ መከራ ፡ አያገኘውም ፤ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ የተሞሉ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ውሸተኛ ፡ ከንፈር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አሰጸያፊ ፡ ነው ፤ እውነትን ፡ የሚያደርጉ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተወደዱ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ዕውቀትን ፡ ይሸሽጋል ፤ የሰነፎች ፡ ልብ ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ያወራል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ የትጉህ ፡ እጅ ፡ ትገዛለች ፤ የታካች ፡ እጅ ፡ ግን ፡ ትገብራለች ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ሰውን ፡ የልቡ ፡ ሐዘን ፡ ያዋርደዋል ፤ መልካም ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋል ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ ጻድቅ ፡ ለባልንጀራው ፡ መንገዱን ፡ ያሳያል ፤ የኃጥኣን ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ታስታቸዋለች ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ ታካች ፡ ሰው ፡ ዐደን ፡ ምንም ፡ አያድንም ፤ ለሰው ፡ የከበረ ፡ ሀብት ፡ ትጋት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፡ በጐዳናዋም ፡ ሞት ፡ የለም ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ባላእምሮ ፡ ልጅ ፡ የአባቱን ፡ ተግሣጽ ፡ ይሰማል ። ፈዘኛ ፡ ግን ፡ ተግሣጽን ፡ አይሰማም ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ሰው ፡ ከአፉ ፡ ፍሬ ፡ መልካምን ፡ ይበላል ፤ የዐመፀኞች ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ ግፍን ፡ ትሻለች ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ አፉን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነፍሱን ፡ ይጠብቃል ፤ ከንፈሩን ፡ የሚያሞጠሙጥ ፡ ግን ፡ ጥፋትን ፡ ያገኘዋል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ የታካች ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ትመኛለች ፤ አንዳችም ፡ አታገኝም ፤ የትጉህ ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ ትጠግባለች ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ጻድቅ ፡ ሐሰትን ፡ ይጠላል ፤ ኃጥእ ፡ ግን ፡ ያሳፍራል ፡ ያስነውራልም ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ በመንገዱ ፡ ያለነውር ፡ የሚኼደውን ፡ ጽድቅ ፡ ይጠብቀዋል ፤ ኀጢአት ፡ ግን ፡ ኀጢአተኛውን ፡ ይጥለዋል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ራሱን ፡ ባለጠጋ ፡ የሚያስመስል ፡ ሰው ፡ አለ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አንዳች ፡ የለውም ፤ ራሱን ፡ ድኻ ፡ የሚያስመስል ፡ አለ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጅግ ፡ ባለጠግነት ፡ አለው ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ለሰው ፡ ነፍስ ፡ ቤዛው ፡ ሀብቱ ፡ ነው ፤ ድኻ ፡ ግን ፡ ተግሣጽን ፡ አይሰማም ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ኹልጊዜ ፡ ለጻድቃን ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ የኃጥኣን ፡ መብራት ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በትዕቢት ፡ ጠብ ፡ ብቻ ፡ ይኾናል ፤ ጥበብ ፡ ግን ፡ ምክርን ፡ በሚቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ በችኰላ ፡ የምትከማች ፡ ሀብት ፡ ትጐድላለች ፤ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ የተከማቸች ፡ ግን ፡ ትበዛለች ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ የምትዘገይ ፡ ተስፋ ፡ ልብን ፡ ታሳዝናለች ፤ የተገኘች ፡ ፈቃድ ፡ ግን ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ትእዛዝን ፡ የሚያቃልል ፡ በትእዛዝ ፡ ተይዞ ፡ ይጠፋል ፤ ትእዛዝን ፡ የሚፈራ ፡ ግን ፡ በደኅንነት ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ሰው ፡ ከሞት ፡ ወጥመድ ፡ ያመልጥ ፡ ዘንድ ፡ የጠቢብ ፡ ሰው ፡ ትምህርት ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ መልካም ፡ ዕውቀት ፡ ሞገስን ፡ ይሰጣል ፤ የወስላታዎች ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ ሻካራ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ብልኅ ፡ ኹሉ ፡ በዕውቀት ፡ ይሠራል ፤ ሰነፍ ፡ ግን ፡ ስንፍናውን ፡ ይገልጣል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ መጥፎ ፡ መልእክተኛ ፡ በክፉ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ፤ የታመነ ፡ መልእክተኛ ፡ ግን ፡ ፈውስ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ድኽነትና ፡ ነውር ፡ ተግሣጽን ፡ ቸል ፡ ለሚሉ ፡ ነው ፤ ዘለፋን ፡ የሚሰማ ፡ ግን ፡ ይከብራል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ የተፈጸመች ፡ ፈቃድ ፡ ሰውነትን ፡ ደስ ፡ ታሠኛለች ፤ ሰነፎች ፡ ግን ፡ ከክፉ ፡ መራቅን ፡ ይጸየፋሉ ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ከጠቢባን ፡ ጋራ ፡ የሚኼድ ፡ ጠቢብ ፡ ይኾናል ፤ የሰነፎች ፡ ባልንጀራ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ መከራን ፡ ይቀበላል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኀጢአተኞችን ፡ ያሳድዳቸዋል ፤ ጻድቃን ፡ ግን ፡ መልካሙን ፡ ዋጋ ፡ ይቀበላሉ ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ለልጅ ፡ ልጆቹ ፡ ያወርሳል ፤ የኀጢአተኛ ፡ ብልጥግና ፡ ግን ፡ ለጻድቅ ፡ ትጠበቃለች ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ በድኻዎች ፡ ዕርሻ ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሲሳይ ፡ አለ ፤ ከፍርድ ፡ መጕደል ፡ የተነሣ ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ በበትር ፡ ከመምታት ፡ የሚራራ ፡ ሰው ፡ ልጁን ፡ ይጠላል ፤ ልጁን ፡ የሚወድ ፡ ግን ፡ ተግቶ ፡ ይገሥጸዋል ።

ምሳ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ጻድቅ ፡ ሰውነቱ ፡ እስክትጠግብ ፡ ድረስ ፡ ይበላል ፤ የኃጥኣን ፡ ሆድ ፡ ግን ፡ ይራባል ።

_____መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ምሳ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ ብልኀተኛ ፡ ሴት ፡ ቤቷን ፡ ትሠራለች ፤ ሰነፍ ፡ ሴት ፡ ግን ፡ በእጇ ፡ ታፈርሰዋለች ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ በቅን ፡ የሚኼድ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈራል ፤ መንገዱን ፡ የሚያጣምም ፡ ግን ፡ ይንቀዋል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ በሰነፍ ፡ አፍ ፡ የትዕቢት ፡ በትር ፡ አለ ፤ የጠቢባን ፡ ከንፈር ፡ ግን ፡ ትጠብቃቸዋለች ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ በሬ ፡ በሌለበት ፡ ስፍራ ፡ እኽል ፡ አይገኝም ፤ ብዙ ፡ ሲሳይ ፡ ግን ፡ በበሬዎች ፡ ኀይል ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ የታመነ ፡ ምስክር ፡ አይዋሽም ፤ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ግን ፡ በሐሰት ፡ ይናገራል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ፈዘኛ ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ ይፈልጋል ፡ አያገኛትም ፤ ለአስተዋይ ፡ ግን ፡ ዕውቀትን ፡ ማግኘት ፡ አያስቸግረውም ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ከሰነፍ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ራቅ ፥ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የዕውቀትን ፡ ከንፈር ፡ አታገኝምና ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ የብልኅ ፡ ሰው ፡ ጥበብ ፡ መንገዱን ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ የሰነፎች ፡ ስንፍና ፡ ግን ፡ ሽንገላ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ሰነፉ ፡ በኀጢአት ፡ ያፌዛል ፤ በቅኖች ፡ መካከል ፡ ግን ፡ ቸርነት ፡ አለች ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ የራሱን ፡ ሐዘን ፡ ልብ ፡ ያውቃል ፤ ከደስታውም ፡ ጋራ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ አይገናኝም ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ የኃጥኣን ፡ ቤት ፡ ይፈርሳል ፤ የቅኖች ፡ ማደሪያ ፡ ግን ፡ ያብባል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ለሰው ፡ ቅን ፡ የምትመስል ፡ መንገድ ፡ አለች ፡ ፍጻሜዋ ፡ ግን ፡ የሞት ፡ መንገድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ በሣቅ ፡ ደግሞ ፡ ልብ ፡ ያዝናል ፥ የደስታም ፡ ፍጻሜ ፡ ልቅሶ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ልቡን ፡ ከጽድቅ ፡ የሚመልስ ፡ ሰው ፡ ከመንገዱ ፡ ፍሬ ፡ ይጠግባል ፥ ጻድቅም ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ በራሱ ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ የዋህ ፡ ቃልን ፡ ኹሉ ፡ ያምናል ፤ ብልኅ ፡ ግን ፡ አካኼዱን ፡ ይመለከታል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ይፈራል ፡ ከክፉም ፡ ይሸሻል ፤ ሰነፍ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ታምኖ ፡ ይኰራል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ቀኑጡ ፡ ሰው ፡ በስንፍና ፡ ይሠራል ፤ አስተዋይ ፡ ግን ፡ ይታገሣል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ አላዋቂዎች ፡ ሰዎች ፡ ስንፍናን ፡ ይወርሳሉ ፤ ብልኖች ፡ ግን ፡ ዕውቀትን ፡ እንደ ፡ ዘውድ ፡ ይጫናሉ ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ኀጢአተኞች ፡ በደጎች ፡ ፊት ፡ ይጐነበሳሉ ፥ ኃጥኣንም ፡ በጻድቃን ፡ በር ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ድኻ ፡ በባልንጀራው ፡ ዘንድ ፡ የተጠላ ፡ ነው ፡ የባለጠጋ ፡ ወዳጆች ፡ ግን ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ባልንጀራውን ፡ የሚንቅ ፡ ይበድላል ፡ ለድኻ ፡ ግን ፡ የሚራራ ፡ ምስጉ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ክፉ ፡ የሚያደርጉ ፡ ይስታሉ ፤ ምሕረትና ፡ እውነት ፡ ግን ፡ መልካምን ፡ ለሚያደርጉ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ በድካም ፡ ኹሉ ፡ ልምላሜ ፡ ይገኛል ፤ ብዙ ፡ ነገር ፡ በሚናገር ፡ ከንፈር ፡ ግን ፡ ድኽነት ፡ ብቻ ፡ አለ ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ የጠቢባን ፡ ዘውድ ፡ ባለጠግነታቸው ፡ ነው ፤ የሰነፎች ፡ ስንፍና ፡ ግን ፡ ስንፍና ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ እውነተኛ ፡ ምስክር ፡ ነፍሶችን ፡ ያድናል ፤ በሐሰት ፡ የሚናገር ፡ ግን ፡ ሸንጋይ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለሚፈራ ፡ ጠንካራ ፡ መታመን ፡ አለው ፥ ለልጆቹም ፡ መጠጊያ ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ሰው ፡ ከሞት ፡ ወጥመድ ፡ ያመልጥ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ የንጉሥ ፡ ክብር ፡ በሕዝብ ፡ ብዛት ፡ ነው ፤ በሰው ፡ ጥቂትነት ፡ ግን ፡ የገዢ ፡ ጥፋት ፡ አለ ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ለትግሥተኛ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ማስተዋል ፡ አለው ፤ ቀኑጡ ፡ ግን ፡ ስንፍናውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ ትሑት ፡ ልብ ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤ ቅንአት ፡ ግን ፡ ዐጥንትን ፡ ያነቅዛል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ ድኻን ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ፈጣሪውን ፡ ይሰድባል ፤ ለድኻ ፡ ምሕረትን ፡ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ ያከብረዋል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ኃጥእ ፡ በክፉቱ ፡ ይደፋል ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ በእውነቱ ፡ ይታመናል ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 33 ፤ በዐዋቂ ፡ ልብ ፡ ጥበብ ፡ ትቀመጣለች ፤ በሰነፎች ፡ ውስጥ ፡ ግን ፡ አትታወቅም ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 34 ፤ ጽድቅ ፡ ሕዝብን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ታደርጋለች ፤ ኀጢአት ፡ ግን ፡ ሕዝብን ፡ ታስነውራለች ።

ምሳ. ፡ 14 ፡ 35 ፤ አስተዋይ ፡ አገልጋይ ፡ በንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ይወደዳል ፤ በሚያሳፍር ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቍጣው ፡ ይኾናል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ የለዘበች ፡ መልስ ፡ ቍጣን ፡ ትመልሳለች ፡ ሻካራ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ቍጣን ፡ ታስነሣለች ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ የጠቢባን ፡ ምላስ ፡ ዕውቀትን ፡ ያሳምራል ፤ የሰነፎች ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ያፈልቃል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ በስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ፤ ክፉዎችንና ፡ ደጎችን ፡ ይመለከታሉ ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ፈዋሽ ፡ ምላስ ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ነው ፤ የጠማማ ፡ ምላስ ፡ ግን ፡ ነፍስን ፡ ይሰብራል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ሰነፍ ፡ የአባቱን ፡ ተግሣጽ ፡ ይንቃል ፤ ዘለፋን ፡ የሚቀበል ፡ ግን ፡ አእምሮው ፡ የበዛ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ በጻድቅ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ ኀይል ፡ አለ ፤ የኃጥእ ፡ ሰው ፡ መዝገብ ፡ ግን ፡ ሁከት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ የጠቢባን ፡ ከንፈር ፡ ዕውቀትን ፡ ትዘራለች ፤ የሰነፎች ፡ ልብ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ የኃጥኣን ፡ መሥዋዕት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፤ የቅኖች ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ የኃጥኣን ፡ መንገድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ጽድቅን ፡ የሚከተል ፡ ይወዳል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ክፉ ፡ መቅሠፍት ፡ መንገድን ፡ በተወ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፥ ዘለፋንም ፡ የሚጠላ ፡ ይሞታል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ሲኦልና ፡ ጥፋት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የታወቁ ፡ ናቸው ፤ ይልቁንም ፡ የሰዎች ፡ ልብ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ፈዘኛ ፡ ሰው ፡ የሚዘልፈውን ፡ አይወድም ፥ ወደ ፡ ጠቢባንም ፡ አይኼድም ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ደስ ፡ ያለው ፡ ልብ ፡ ፊትን ፡ ያበራል ፤ በልብ ፡ ሐዘን ፡ ግን ፡ ነፍስ ፡ ትሰበራለች ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ የዐዋቂ ፡ ልብ ፡ ዕውቀትን ፡ ይፈልጋል ፤ የሰነፎች ፡ አፍ ፡ ግን ፡ በስንፍና ፡ ይሰማራል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ልቡ ፡ የሚያዝን ፡ ሰው ፡ ዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ የከፋች ፡ ናት ፤ የልብ ፡ ደስታ ፡ ግን ፡ ኹልጊዜ ፡ እንደ ፡ ግብዣ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከመፍራት ፡ ጋራ ፡ ያለ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ሁከት ፡ ካለበት ፡ ከብዙ ፡ መዝገብ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ የጐመን ፡ ወጥ ፡ በፍቅር ፡ መብላት ፡ የሰባ ፡ ፍሪዳን ፡ ጥል ፡ ባለበት ፡ ዘንድ ፡ ከመብላት ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ቍጡ ፡ ሰው ፡ ጠብን ፡ ያነሣሣል ፤ ትዕግሥተኛ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ጸጥ ፡ ያሠኘዋል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ የታካች ፡ መንገድ ፡ እንደ ፡ ሾኽ ፡ ዐጥር ፡ ናት ፤ የጻድቃን ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ የተደላደለች ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ጠቢብ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ፤ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እናቱን ፡ ይንቃል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ልብ ፡ ለሌለው ፡ ሰው ፡ ስንፍና ፡ ደስታ ፡ ናት ፤ አስተዋይ ፡ ግን ፡ አካኼዱን ፡ ያቀናል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ምክር ፡ ከሌለች ፡ ዘንድ ፡ የታሰበው ፡ ሳይሳካ ፡ ይቀራል ፤ መካሮች ፡ በበዙበት ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ይጸናል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ሰው ፡ በአፉ ፡ መልስ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ቃልም ፡ በጊዜው ፡ ምንኛ ፡ መልካም ፡ ነው! ፡

ምሳ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ በታች ፡ ካለው ፡ ከሲኦል ፡ ያመልጥ ፡ ዘንድ ፡ የሕይወት ፡ መንገድ ፡ አስተዋዩን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ይወስደዋል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ የትዕቢተኞች ፡ ቤት ፡ ይነቅላል ፤ የባልቴትን ፡ ዳርቻ ፡ ግን ፡ ያጸናል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ የበደለኛ ፡ ዐሳብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ናት ፤ ያማረ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ጥሩ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ የሚሣሣ ፡ ሰው ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ ያውካል ፤ መማለጃን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ የጻድቅ ፡ ልብ ፡ መልሱን ፡ ያስባል ፡ የኃጥኣን ፡ አፍ ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ ያፈልቃል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከኃጥኣን ፡ ይርቃል ፤ የጻድቃንን ፡ ጸሎት ፡ ግን ፡ ይሰማል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ የዐይን ፡ ብርሃን ፡ ልብን ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ፥ መልካም ፡ ወሬም ፡ ዐጥንትን ፡ ያለመልማል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ የሕይወትን ፡ ተግሣጽ ፡ የሚሰማ ፡ ጕሮ ፡ በጠቢባን ፡ መካከል ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ተግሣጽን ፡ ቸል ፡ የሚል ፡ የራሱን ፡ ነፍስ ፡ ይንቃል ፤ ዘለፋን ፡ የሚሰማ ፡ ግን ፡ አእምሮ ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የጥበብ ፡ ትምህርት ፡ ነው ፤ ትሕትናም ፡ ክብረትን ፡ ትቀድማለች ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የልብ ፡ መዘጋጀት ፡ ከሰው ፡ ነው ፤ የምላስ ፡ መልስ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ በዐይኖቹ ፡ ፊት ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ መንፈስን ፡ ይመዝናል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ሥራኽን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዐደራ ፡ ስጥ ፥ ዐሳብኽም ፡ ትጸናለች ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኹሉን ፡ ለርሱ ፡ ለራሱ ፡ ፈጠረ ፥ ኃጥእን ፡ ደግሞ ፡ ለክፉ ፡ ቀን ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ በልቡ ፡ የታበየ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፥ እጅ ፡ በእጅም ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ በምሕረትና ፡ በእውነት ፡ ኀጢአት ፡ ትሰረያለች ፥ እግዚአብሔርንም ፡ በመፍራት ፡ ሰው ፡ ከክፋት ፡ ይመለሳል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ የሰው ፡ አካኼድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሠኘው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ በርሱና ፡ በጠላቶቹ ፡ መካከል ፡ ስንኳ ፡ ሰላምን ፡ ያደርጋል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ በጽድቅ ፡ የሚገኝ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ በዐመፅ ፡ ከሚገኝ ፡ ከብዙ ፡ ትርፍ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ የሰው ፡ ልብ ፡ መንገዱ ፡ ያዘጋጃል ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አካኼዱን ፡ ያቀናለታል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ብይን ፡ በንጉሥ ፡ አፍ ፡ ነው ፥ አፉም ፡ በፍርድ ፡ አይስትም ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ እውነተኛ ፡ ሚዛንና ፡ መመዘኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ናቸው ፤ የከረጢት ፡ መመዘኛች ፡ ኹሉ ፡ የርሱ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ግፍን ፡ መሥራት ፡ በንጉሥ ፡ ዘንድ ፡ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ነው ፥ ዙፋን ፡ በጽድቅ ፡ ይጸናልና ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ የጽድቅ ፡ ከንፈር ፡ የነገሥታት ፡ ደስታ ፡ ናት ፥ በቅን ፡ የሚናገር ፡ ርሱንም ፡ ይወዱታል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ የንጉሥ ፡ ቍጣ ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ መልእክተኛ ፡ ነው ፤ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ያቈላምጠዋል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ በንጉሥ ፡ ፊት ፡ ብርሃን ፡ ዘንድ ፡ ሕይወት ፡ አለ ፥ መልካም ፡ ፈቃዱም ፡ እንደ ፡ በልግ ፡ ዝናብ ፡ ደመና ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ጥበብን ፡ ማግኘት ፡ ምንኛ ፡ ከወርቅ ፡ ይሻላል! ፡ ማስተዋልንም ፡ ማግኘት ፡ ከብር ፡ ይልቅ ፡ የሚመረጥ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ የቅኖች ፡ መንገድ ፡ ከክፋት ፡ መራቅ ፡ ነው ፤ መንገዱን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነፍሱን ፡ ይጠብቃታል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ትዕቢት ፡ ጥፋትን ፥ ኵሩ ፡ መንፈስም ፡ ውድቀትን ፡ ይቀድማል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ከዕቡያን ፡ ጋራ ፡ ምርኮ ፡ ከመካፈል ፥ ከትሑታን ፡ ጋራ ፡ በተዋረደ ፡ መንፈስ ፡ መኾን ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ቃልን ፡ የሚያዳምጥ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ያገኛል ፤ በእግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ልቡ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ አስተዋይ ፡ ይባላል ፥ በከንፈሩም ፡ ጣፋጭ ፡ የኾነ ፡ ትምህርትን ፡ ያበዛል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ገንዘብ ፡ ላደረገው ፡ ሰው ፡ ዕውቀት ፡ የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ነው ፤ ስንፍና ፡ ግን ፡ የሰነፎች ፡ ቅጣት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ የጠቢብ ፡ ልብ ፡ አፉን ፡ ያስተምራል ፥ ለከንፈሩም ፡ ትምህርትን ፡ ይጨምራል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ያማረ ፡ ቃል ፡ የማር ፡ ወለላ ፡ ነው ፤ ለነፍስ ፡ ጣፋጭ ፡ ለዐጥንትም ፡ ጤና ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ለሰው ፡ ቅን ፡ የምትመስል ፡ መንገድ ፡ አለች ፤ ፍጻሜዋ ፡ ግን ፡ የሞት ፡ መንገድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ የሠራተኛ ፡ ራብ ፡ ለርሱ ፡ ይሠራል ፥ አፉ ፡ ይጐተጉተዋልና ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ምናምንቴ ፡ ሰው ፡ ክፋትን ፡ ይምሳል ፥ በከንፈሩም ፡ የሚቃጠል ፡ እሳት ፡ አለ ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ጠማማ ፡ ሰው ፡ ጥልን ፡ ይዘራል ፤ ገሮ ፡ ጠቢ ፡ ሰው ፣ የተማመኑትን ፡ ወዳጆች ፡ ይለያያል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ ግፈኛ ፡ ሰው ፡ ወዳጁን ፡ ያባብላል ፥ መልካምም ፡ ወዳይደለ ፡ መንገድ ፡ ይመራዋል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ዐይኑን ፡ የሚዘጋ ፡ ጠማማ ፡ ዐሳብን ፡ ያስባል ፤ ከንፈሩን ፡ የሚነክስ ፡ ክፋትን ፡ ይፈጽማል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ የሸበተ ፡ ጠጕር ፡ የክብር ፡ ዘውድ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ ይገኛል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ ትዕግሥተኛ ፡ ሰው ፡ ከጎያል ፡ ሰው ፡ ይሻላል ፥ በመንፈሱም ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ ከተማ ፡ ከሚወስዱ ፡ ይበልጣል ።

ምሳ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ ዕጣ ፡ በጕያ ፡ ይጣላል ፤ መደቧ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ ጥል ፡ ባለበት ፡ ዘንድ ፡ ዕርድ ፡ ከሞላበት ፡ ቤት ፡ በጸጥታ ፡ ደረቅ ፡ ቍራሽ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ አስተዋይ ፡ ባሪያ ፡ ነውረኛውን ፡ ልጅ ፡ ይገዛል ፥ በወንድማማች ፡ መካከልም ፡ ርስትን ፡ ይካፈላል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ማቅለጫ ፡ ለብር ፥ ከውር ፡ ለወርቅ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልብን ፡ ይፈትናል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ የበደለኛን ፡ ከንፈር ፡ ይሰማል ፤ ሐሰተኛም ፡ ወደ ፡ ተንኰለኛ ፡ ምላስ ፡ ያደምጣል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ በድኻ ፡ የሚያላግጥ ፡ ፈጣሪውን ፡ ይሰድባል ፤ በጥፋትም ፡ ደስ ፡ የሚለው ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ የሽማግሌዎች ፡ አክሊል ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤ የልጆችም ፡ ክብር ፡ አባቶቻቸው ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ለሰነፍ ፡ የኵራት ፡ አነጋገር ፡ አይገባውም ፤ ይልቁንም ፡ ሐሰተኛ ፡ ከንፈር ፡ ለመኰንን ፡ አይገባውም ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ገንዘብ ፡ ባደረገው ፡ ፊት ፡ መማለጃ ፡ እንደ ፡ ተዋበ ፡ ዕንቊ ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ዞረበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ሥራውን ፡ ያቀናል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚከድን ፡ ሰው ፡ ፍቅርን ፡ ይሻል ፤ ነገርን ፡ የሚደጋግም ፡ ግን ፡ የተማመኑትን ፡ ወዳጆቹን ፡ ይለያያል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ መቶ ፡ ግርፋት ፡ በሰነፍ ፡ ጠልቆ ፡ ከሚገባ ፡ ይልቅ ፡ ተግሣጽ ፡ በአስተዋይ ፡ ሰው ፡ ጠልቆ ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ይገባል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ ዐመፃን ፡ ብቻ ፡ ይሻል ፤ ስለዚህ ፥ ጨካኝ ፡ መልእክ ፡ ይላክበታል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ሰነፍን ፡ በስንፍናው ፡ ከመገናኘት ፡ ልጆቿ ፡ የተነጠቁባትን ፡ ድብ ፡ መገናኘት ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ በመልካም ፡ ፋንታ ፡ ክፉን ፡ የሚመልስ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከቤቱ ፡ አትርቅም ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ የጠብ ፡ መጐመሪያ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፈሳሰስ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ጠብ ፡ ሳይበረታ ፡ አንተ ፡ ክርክርን ፡ ተው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ኃጥኡን ፡ የሚያጸድቅና ፡ በጻድቁ ፡ ላይ ፡ የሚፈርድ ፥ ኹለቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊዎች ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ በሰነፍ ፡ እጅ ፡ የጥበብ ፡ መግዣ ፡ ገንዘብ ፡ መኖሩ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ጥበብን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ አእምሮ ፡ የለውምና ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ወዳጅ ፡ በዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ይወዳል ፤ ወንድምም ፡ ለመከራ ፡ ይወለዳል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ አእምሮ ፡ የጐደለው ፡ ሰው ፡ አጋና ፡ ይመታል ፥ በባልንጀራውም ፡ ፊት ፡ ይዋሳል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ ዐመፃን ፡ የሚወድ ፡ ክርክርን ፡ ይወዳል ፤ ደጁንም ፡ ዘለግ ፡ የሚያደርግ ፡ ውድቀትን ፡ ይሻል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 20 ፤ ጠማማ ፡ ልብ ፡ ያለው ፡ መልካምን ፡ አያገኝም ፥ ምላሱንም ፡ የሚገለብጥ ፡ በክፉ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 21 ፤ ሰነፍን ፡ የሚወልድ ፡ ሐዘን ፡ ይኾንበታል ፥ የደንቈሮ ፡ ልጅም ፡ አባት ፡ ደስ ፡ አይለውም ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 22 ፤ ደስ ፡ ያላት ፡ ልብ ፡ መልካም ፡ መድኀኒት ፡ ናት ፤ ያዘነች ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ ዐጥንትን ፡ ታደርቃለች ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 23 ፤ ኃጥእ ፡ የፍርድን ፡ መንገድ ፡ ለማጥመም ፡ ከብብት ፡ መማለጃን ፡ ይወስዳል ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ በአስተዋይ ፡ ፊት ፡ ጥበብ ፡ ትኖራለች ፤ የሰነፍ ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 25 ፤ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ለአባቱ ፡ ጸጸት ፡ ነው ፥ ለወለደችውም ፡ ምሬት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 26 ፤ ጻድቅን ፡ መቅጣት ፥ ጨዋ ፡ ሰውንም ፡ በጻድቅነቱ ፡ መምታት ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 27 ፤ ጥቂት ፡ ቃልን ፡ የሚናገር ፡ ዐዋቂ ፡ ነው ፥ መንፈሱም ፡ ቀዝቃዛ ፡ የኾነ ፡ አስተዋይ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 17 ፡ 28 ፤ ሰነፍ ፡ ዝም ፡ ቢል ፡ ጠቢብ ፡ ኾኖ ፡ ይቈጠራል ፥ ከንፈሩንም ፡ የሚቈልፍ ፦ ባላእምሮ ፡ ነው ፡ ይባላል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ መለየት ፡ የሚወድ ፡ ምኞቱን ፡ ይከተላል ፥ መልካሙንም ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፡ ይቃወማል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ሰነፍ ፡ የጥበብን ፡ ነገር ፡ አይወድም ፤ በልቡ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ መግለጥ ፡ ብቻ ፡ ይወዳል ፡ እንጂ ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ ኃጥእ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ንቀት ፡ ደግሞ ፡ ይመጣል ፥ ነውርም ፡ ከስድብ ፡ ጋራ ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ የሰው ፡ አፍ ፡ ቃል ፡ የጠለቀ ፡ ውሃ ፡ ነው ፥ የጥበብም ፡ ምንጭ ፡ ፈሳሽ ፡ ወንዝ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ የጻድቅ ፡ ፍርድ ፡ ይጠምም ፡ ዘንድ ፥ ለኃጥእም ፡ ማድላት ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ የሰነፍ ፡ ከንፈር ፡ በጥል ፡ ውስጥ ፡ ትገባለች ፥ አፉም ፡ በትርን ፡ ትጠራለች ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ የሰነፍ ፡ አፍ ፡ ለራሱ ፡ ጥፋት ፡ ነው ፥ ከንፈሩም ፡ ለነፍሱ ፡ ወጥመድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ የገሮ ፡ ጠቢ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ጣፋጭ ፡ መብል ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ እስከሆድ ፡ ጕርጆች ፡ ድረስ ፡ ይወርዳል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ በሥራው ፡ ታካች ፡ የሚኾን ፡ የሀብት ፡ አጥፊ ፡ ወንድም ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የጸና ፡ ግንብ ፡ ነው ፤ ጻድቅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሮጦ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ለባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ሀብቱ ፡ እንደ ፡ ጸናች ፡ ከተማ ፡ ናት ፥ በዐሳቡም ፡ እንደ ፡ ረዥም ፡ ቅጥር ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ሰው ፡ ሳይወድቅ ፡ በፊት ፡ ልቡ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ ትሕትናም ፡ ክብረትን ፡ ትቀድማለች ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ሳይሰማ ፡ ነገርን ፡ በሚመልስ ፡ ስንፍናና ፡ ዕፍረት ፡ ይኾንበታል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ሕመሙን ፡ ይታገሣል ፤ የተቀጠቀጠን ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ማን ፡ ያጠነክረዋል ፧

ምሳ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ የአስተዋይ ፡ ልብ ፡ ዕውቀትን ፡ ያገኛል ፥ የጠቢባንም ፡ ጐሮ ፡ ዕውቀትን ፡ ትፈልጋለች ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ የሰው ፡ ስጦታ ፡ መንገዱን ፡ ታሰፋለታለች ፥ በታላላቆችም ፡ ፊት ፡ ታገባዋለች ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አስቀድሞ ፡ የገባ ፡ ጻድቅ ፡ ይመስላል ፤ ባልንጀራው ፡ ግን ፡ መጥቶ ፡ ይመረምረዋል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ዕጣ ፡ ክርክርን ፡ ትከለክላለች ፥ በኀያላንም ፡ መካከል ፡ ትበይናለች ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ የተበደለ ፡ ወንድም ፡ እንደ ፡ ጸናች ፡ ከተማ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፤ ክርክራቸውም ፡ እንደ ፡ ግንብ ፡ ብረት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ የሰው ፡ ሆድ ፡ ከአፉ ፡ ፍሬ ፡ ይሞላል ፡ ከንፈሩም ፡ ከሚያፈራው ፡ ይጠግባል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ሞትና ፡ ሕይወት ፡ በምላስ ፡ እጅ ፡ ናቸው ፤ የሚወዷትም ፡ ፍሬዋን ፡ ይበላሉ ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ሚስት ፡ ያገኘ ፡ በረከትን ፡ አገኘ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ ሞገስን ፡ ይቀበላል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ድኻ ፡ በትሕትና ፡ እየለመነ ፡ ይናገራል ፤ ባለጠጋ ፡ ግን ፡ በድፍረት ፡ ይመልሳል ።

ምሳ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ ያሉት ፡ ሰው ፡ ይጠፋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወንድም ፡ አብልጦ ፡ የሚጠጋጋ ፡ ወዳጅ ፡ አለ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ በከንፈሩ ፡ ከሚወሳልት ፡ ሰነፍ ፡ ይልቅ ፡ ያለነውር ፡ የሚኼድ ፡ ድኻ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ነፍስ ፡ ዕውቀት ፡ የሌለባት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ እግሩንም ፡ የሚያፈጥን ፡ ከመንገድ ፡ ይስታል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ የሰው ፡ ስንፍና ፡ መንገዱን ፡ ታጣምመበታለች ፤ ልቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ባለጠግነት ፡ ብዙ ፡ ወዳጆች ፡ ይጨምራል ፤ የድኻ ፡ ወዳጅ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ይርቃል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ፥ በሐሰትም ፡ የሚናገር ፡ አያመልጥም ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለጋሱን ፡ ያቈላምጣሉ ፥ ስጦታ ፡ ለሚሰጥም ፡ ኹሉ ፡ ወዳጅ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ድኻን ፡ ሰው ፡ ወንድሞቹ ፡ ኹሉ ፡ ይጠሉታል ፤ ይልቁንም ፡ ወዳጆቹ ፡ ከርሱ ፡ ይርቃሉ ። እነርሱንም ፡ በቃል ፡ ቢከተላቸው ፡ አንዳች ፡ አይረቡትም ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ጥበብን ፡ የሚያገኝ ፡ ነፍሱን ፡ ይወዳል ፥ ማስተዋልንም ፡ የሚጠብቅ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ፤ በሐሰትም ፡ የሚናገር ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ለሰነፍ ፡ ቅምጥልነት ፡ አይገባውም ፥ ይልቁንም ፡ ባሪያ ፡ በአለቃዎች ፡ ላይ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ሰውን ፡ ጠቢብ ፡ አእምሮው ፡ ከቍጣ ፡ ያዘገየዋል ፥ ለበደለኛውም ፡ ይቅር ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ክብር ፡ ይኾንለታል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ግሣት ፡ የንጉሥ ፡ ቍጣ ፡ ነው ፥ ሞገሱም ፡ በመስክ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ጠል ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ ሰነፍ ፡ ልጅ ፡ ለአባቱ ፡ ሐዘን ፡ ነው ፥ ጠበኛም ፡ ሚስት ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ነጠብጣብ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ቤትና ፡ ባለጠግነት ፡ ከአባቶች ፡ ዘንድ ፡ ይወረሳሉ ፤ አስተዋይ ፡ ሚስት ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ተግባር ፡ መፍታት ፡ እንቅልፍን ፡ ታመጣለች ፥ የታካችም ፡ ነፍስ ፡ ትራባለች ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ ትእዛዝን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነፍሱን ፡ ይጠብቃል ፤ መንገዱን ፡ ቸል ፡ የሚል ፡ ግን ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ለድኻ ፡ ቸርነትን ፡ የሚያደርግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያበድራል ፥ በጎነቱንም ፡ መልሶ ፡ ይከፍለዋል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ተስፋ ፡ ገና ፡ ሳለች ፡ ልጅኽን ፡ ገሥጽ ፥ መሞቱንም ፡ አትሻ ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ንዴተኛ ፡ ሰው ፡ መቀጮ ፡ ይከፍላል ፤ ብታድነውም ፡ ደግሞ ፡ ትጨምራለኽ ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ምክርን ፡ ስማ ፥ ተግሣጽንም ፡ ተቀበል ፡ በፍጻሜኽ ፡ ጠቢብ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ በሰው ፡ ልብ ፡ ብዙ ፡ ዐሳብ ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይጸናል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ የሰው ፡ ቸርነት ፡ የርሱ ፡ ፍሬ ፡ ነው ፤ ከሐሰተኛ ፡ ባለጠጋም ፡ እውነተኛ ፡ ድኻ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ይመራል ፤ የሚፈራውም ፡ ጠግቦ ፡ ይኖራል ፥ ክፉ ፡ ነገርም ፡ አያገኘውም ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ታካች ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ በወጭቱ ፡ ያጠልቃታል ፥ ወደ ፡ አፉ ፡ ስንኳ ፡ አይመልሳትም ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ፈዘኛ ፡ ብትገርፈው ፡ አላዋቂ ፡ ብልኀተኛ ፡ ይኾናል ፤ አስተዋይን ፡ ሰው ፡ ብትገሥጸው ፡ ዕውቀትን ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ አባቱን ፡ የሚያስከፋ ፡ እናቱንም ፡ የሚያሳድድ ፡ የሚያሳፍርና ፡ ጐስቋላ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ተግሣጽን ፡ ከሰማኽ ፡ በኋላ ፡ ከዕውቀት ፡ ቃል ፡ መሳሳትን ፡ ተው ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ወስላታ ፡ ምስክር ፡ በፍርድ ፡ ያፌዛል ፥ የኃጥኣንም ፡ አፍ ፡ ክፋትን ፡ ይውጣል ።

ምሳ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ለሚያፌዙ ፡ ሰዎች ፡ ፍርድ ፡ ተዘጋጅታለች ፥ ለሰነፎችም ፡ ገርባ ፡ በትር ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ፈዘኛ ፡ ያደርጋል ፥ ብርቱ ፡ መጠጥም ፡ ጠበኛ ፡ ያደርጋል ፤ በዚህም ፡ የሳተ ፡

ኹሉ ፡ ጠቢብ ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ የንጉሥ ፡ ቍጣ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ግሣት ፡ ነው ፤ የሚያስቈጣውም ፡ ሰው ፡ የራሱን ፡ ነፍስ ፡ ይበድላል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ ከክርክር ፡ ይርቅ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ክብሩ ፡ ነው ፤ ሰነፍ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ እንዲሀ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ ይጣመራል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ታካች ፡ ሰው ፡ በብርድ ፡ ምክንያት ፡ አያርስም ፤ ስለዚህ ፥ በመከር ፡ ይለምናል ፥ ምንም ፡ አያገኝም ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ምክር ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ጠሊቅ ፡ ውሃ ፡ ነው ፤ አእምሮ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይቀዳዋል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ቸርነታቸውን ፡ ያወራሉ ፤ የታመነውን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ማን ፡ ያገኘዋል ፧

ምሳ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ ጻድቅ ፡ ያለነውር ፡ ይኼዳል ፥ ልጆቹም ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ምስጉኖች ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ የተቀመጠ ፡ ንጉሥ ፡ ክፉውን ፡ ኹሉ ፡ በዐይኖቹ ፡ ይበትናል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ልቤን ፡ አነጻኹ ፥ ከኀጢአትም ፡ ጠራኹ ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ምሳ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ሚዛንና ፡ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ መስፈሪያ ፥ ኹለቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርኩሳን ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ሕፃን ፡ ቅንና ፡ ንጹሕ ፡ መኾኑ ፡ በሚያደርገው ፡ ሥራ ፡ ይታወቃል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ የሚሰማ ፡ ጐሮንና ፡ የሚያይ ፡ ዐይንን ፥ ኹለቱን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጠራቸው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ ድኻ ፡ እንዳትኾን ፡ እንቅልፍን ፡ አትውደድ ፤ ዐይንኽን ፡ ክፈት ፥ እንጀራም ፡ ትጠግባለኽ ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ የሚገዛ ፡ ሰው ፦ ክፉ ፡ ነው ፥ ክፉ ፡ ነው ፡ ይላል ፤ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ይመካል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ወርቅና ፡ ብዙ ፡ ቀይ ፡ ዕንቊ ፡ ይገኛል ፤ የዕውቀት ፡ ከንፈር ፡ ግን ፡ የከበረች ፡ ጌጥ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ለማያውቀው ፡ ከተዋሰ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ውሰድ ፥ ለእንግዳ ፡ የተዋሰውንም ፡ ርሱን ፡ ዐግተው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ የሐሰት ፡ እንጀራ ፡ ለሰው ፡ የጣፈጠ ፡ ነው ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አፉ ፡ ጭንጫ ፡ ይሞላል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ ዐሳብ ፡ በምክር ፡ ትጸናለች ፥ በመልካምም ፡ ምክር ፡ ሰልፍ ፡ አድርግ ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ዘዋሪ ፡ ሐሜተኛ ፡ ምስጢርን ፡ ይገልጣል ፤ ከንፈሩን ፡ የሚያሞጠሙጥ ፡ ሰውን ፡ አትገናኘው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚሰድብ ፥ በድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ መብራቱ ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ በመዠመሪያ ፡ ፈጥኖ ፡ የተከማቸ ፡ ርስት ፡ ፍጻሜው ፡ አይባረክም ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ክፉ ፡ እመልሳለኹ ፡ አትበል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ተማመን ፥ ርሱም ፡ ያድንኻል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ኹለት ፡ ዐይነት ፡ ሚዛን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፥ ሐሰተኛ ፡ ሚዛንም ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ የሰው ፡ አካኼዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ እንግዲያስ ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ እንዴት ፡ ያስተውላል ፧

ምሳ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ ሰው ፡ በችኰላ ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ቢሳል ፥ ከተሳለም ፡ በኋላ ፡ ቢጸጸት ፡ ወጥመድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ጠቢብ ፡ ንጉሥ ፡ ኃጥኣንን ፡ በመንሽ ፡ ይበትናቸዋል ፥ መንኰራኵሩንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያንኰራኵርባቸዋል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ የሰው ፡ መንፈስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መብራት ፡ ነው ፥ የሆዱን ፡ ጕርጆች ፡ ኹሉ ፡ የሚመረምር ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ ቸርነትና ፡ እውነት ፡ ንጉሥን ፡ ይጠብቁታል ፤ ዙፋኑም ፡ በቸርነት ፡ ይበረታል ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ የጐበዛዝት ፡ ክብር ፡ ጕልበታቸው ፡ ናት ፥ የሽማግሌዎችም ፡ ጌጥ ፡ ሽበት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 20 ፡ 30 ፤ የሰንበር ፡ ቀሥል ፡ ክፉዎችን ፡ ያነጻል ፤ ግርፋትም ፡ ወደ ፡ ሆድ ፡ ጕርጆች ፡ ይገባል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ የንጉሥ ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሾች ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ነው ፤ ወደወደደውም ፡ ያዘነብለዋል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ የቀናች ፡ ትመስለዋለች ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ልብን ፡ ይመዝናል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከመሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ ጽድቅንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ማድረግ ፡ ይወዳል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ ትዕቢተኛ ፡ ዐይንና ፡ ደፋር ፡ ልብ ፡ የኃጥኣንም ፡ ዕርሻ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ የትጉህ ፡ ዐሳብ ፡ ወደ ፡ ጥጋብ ፡ ያደርሳል ፤ ችኩል ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ለመጕደል ፡ ይቸኵላል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ በሐሰተኛ ፡ ምላስ ፡ መዝገብ ፡ ማከማቸት ፡ የሚበን ፡ ጕም ፡ ነው ፤ ይህን ፡ የሚፈልጉ ፡ ሞትን ፡ ይፈልጋሉ ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ቅን ፡ ነገርን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አይወዱምና ፡ የኃጥኣን ፡ ንጥቂያ ፡ ራሳቸውን ፡ ያጠፋቸዋል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ የበደለኛ ፡ መንገድ ፡ የጠመመች ፡ ናት ፤ የንጹሕ ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ የቀና ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ከጠበኛ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ከመቀመጥ ፡ በውጪ ፡ በቤት ፡ ማእዘን ፡ ላይ ፡ መቀመጥ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ የኃጥእ ፡ ነፍስ ፡ ክፉን ፡ ትመኛለች ፥ በፊቱም ፡ ባልንጀራው ፡ ሞገስን ፡ አያገኝም ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ፈዘኛ ፡ ቅጣትን ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ አላዋቂ ፡ ሰው ፡ ጥበብን ፡ ያገኛል ፤ ጠቢብም ፡ ቢማር ፡ ዕውቀትን ፡ ይቀበላል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ጻድቅ ፡ ስለኃጥእ ፡ ቤት ፡ ያስባል ፥ ኃጥኣንም ፡ ለጥፋት ፡ እንደ ፡ ተገለበጡ ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ የድኻውን ፡ ጩኸት ፡ እንዳይሰማ ፡ ጆሮውን ፡ የሚደፍን ፡ ሰው ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ይጮኻል ፡

አይሰማለትምም ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ስጦታ ፡ በስውር ፡ ቍጣን ፡ ታጠፋለች ፥ የብብትም ፡ ውስጥ ፡ ጕቦ ፡ ጽኑ ፡ ቍጣን ፡ ታበርዳለች ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ፍርድን ፡ ማድረግ ፡ ለጻድቅ ፡ ደስታ ፡ ነው ፤ ኀጢአትን ፡ ለሚያደርጉ ፡ ግን ፡ ጥፋት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ከማስተዋል ፡ መንገድ ፡ የሚሳሳት ፡ ሰው ፡ በሙታን ፡ ጉባኤ ፡ ያርፋል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ተድላን ፡ የሚወድ ፡ ድኻ ፡ ይኾናል ፥ የወይን ፡ ጠጅንና ፡ ዘይትንም ፡ የሚወድ ፡ ባለጠጋ ፡ አይኾንም ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ኃጥእ ፡ የጻድቅ ፡ ቤዛ ፡ ነው ፤ በደለኛም ፡ የቅን ፡ ሰው ፡ ቤዛ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ ከጠበኛና ፡ ከቀጕጡ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ከመቀመጥ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መቀመጥ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ የከበረ ፡ መዝገብና ፡ ዘይት ፡ በጠቢብ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ይኖራል ። አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ይውጠዋል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ጽድቅንና ፡ ምሕረትን ፡ የሚከተል ፡ ሕይወትንና ፡ ጽድቅን ፡ ክብርንም ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ጠቢብ ፡ የኀያላንን ፡ ከተማ ፡ ይገባባታል ፥ የሚታመኑበትንም ፡ ኀይል ፡ ያፈርሳል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ አፉንና ፡ ምላሱን ፡ የሚጠብቅ ፡ ነፍሱን ፡ ከመከራ ፡ ይጠብቃል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ኵሩና ፡ ተጓዳጅ ፡ ሰው ፡ ፈዘኛ ፡ ይባላል ፤ ርሱም ፡ በትዕቢት ፡ ቍጣ ፡ ያደርጋል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ ታካችን ፡ ምኞቱ ፡ ትገድለዋለች ፥ እጆቹ ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አይፈቅዱምና ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ኃጥእ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ምኞትን ፡ ይመኛል ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ይሰጣል ፥ አይሰስትም ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ የኃጥኣን ፡ መሥዋዕት ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፤ ይልቁንም ፡ በክፉ ፡ ዐሳብ ፡ ሲያቀርቡት ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ ሐሰተኛ ፡ ምስክር ፡ ይጠፋል ፤ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ተጠንቅቆ ፡ ይናገራል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ ኃጥእ ፡ ፊቱን ፡ ያጠነክራል ፤ ቅን ፡ ሰው ፡ ግን ፡ መንገዱን ፡ ያጸናል ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ጥበብ ፡ ወይም ፡ ማስተዋል ፡ ወይም ፡ ምክር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የለም ።

ምሳ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ፈረስ ፡ ለጦርነት ፡ ቀን ፡ ይዘጋጃል ፤ ድል ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ መልካም ፡ ስም ፡ ከብዙ ፡ ባለጠግነት ፡ ይሻላል ፥ መልካምም ፡ ሞገስ ፡ ከብርና ፡ ከወርቅ ፡ ይበልጣል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ ባለጠና ፡ ድኻ ፡ ተገናኙ ፤ እግዚአብሔር ፡ የኹላቸው ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ክፉን ፡ አይቶ ፡ ይሸሸጋል ፤ አላዋቂዎች ፡ ግን ፡ ዐልፈው ፡ ይጐዳሉ ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ትሕትናና ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ ባለጠግነት ፡ ክብር ፡ ሕይወትም ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ሾኽና ፡ ወጥመድ ፡ በጠማማ ፡ ሰው ፡ መንገድ ፡ ናቸው ፤ ነፍሱን ፡ ግን ፡ የሚጠብቅ ፡ ከነርሱ ፡ ይርቃል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ ልጅን ፡ በሚኼድበት ፡ መንገድ ፡ ምራው ፥ በሸመገለም ፡ ጊዜ ፡ ከርሱ ፡ ፈቀቅ ፡ አይልም ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ባለጠጋ ፡ ድኻዎችን ፡ ይገዛል ፥ ተበዳሪም ፡ የአበዳሪ ፡ ባሪያ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚዘራ ፡ መከራን ፡ ያጭዳል ፥ የቀሥጣውም ፡ በትር ፡ ይጠፋል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ ርኅሩኅ ፡ የተባረከ ፡ ይኾናል ፥ ከእንጀራው ፡ ለድኻ ፡ ሰጥቷልና ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ፈዘኛን ፡ ብታወጣ ፡ ክርክር ፡ ይወጣል ፥ ጠብና ፡ ስድብም ፡ ያልቃል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ የልብን ፡ ንጽሕና ፡ የሚወድና ፡ ሞገስ ፡ በከንፈሩ ፡ ያለች ፥ ንጉሥ ፡ ወዳጁ ፡ ይኾናል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ ዕውቀትን ፡ ይጠብቃሉ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ የወስላታውን ፡ ቃል ፡ ይገለብጣል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ታካች ፡ ሰው ፦ አንበሳ ፡ በሜዳ ፡ ነው ፤ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ እሞታለኹ ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ የጋለሞታ ፡ ሴት ፡ አፍ ፡ የጠለቀ ፡ ጕድጓድ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ የተቈጣው ፡ በርሷ ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ስንፍና ፡ በሕፃን ፡ ልብ ፡ ታስሯል ፤ የተግሣጽ ፡ በትር ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ያርቃታል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ ለራሱ ፡ ጥቅም ፡ ለመጨመር ፡ ሲል ፡ ድኻን ፡ የሚጐዳ ፥ ለባለጠጋም ፡ የሚሰጥ ፥ ርሱ ፡ ወደ ፡ ድኽነት ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ ጐሮኽን ፡ አዘንብለኽ ፡ የጠቢባንን ፡ ቃላት ፡ ስማ ፥ ልብኽንም ፡ ወደ ፡ ዕውቀቴ ፡ አድርግ ፤

ምሳ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ እነርሱን ፡ በውስጥኽ ፡ ብትጠብቅ ፥ በከንፈሮችኽም ፡ ላይ ፡ የተዘጋጁ ፡ ቢኾኑ ፥ የተወደደ ፡ ነገር ፡ ይኾንልኻልና ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ እምነትኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ ዛሬ ፥ እንሆ ፥ አስታወቅኹኽ ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 20-21 ፤ የእውነትን ፡ ቃል ፡ ርግጥነት ፡ አስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፥ ለሚጠይቅኽም ፡ እውነትን ፡ ቃል ፡ መመለስ ፡ ይቻልኽ ፡ ዘንድ ፥ በምክርና ፡ በዕውቀት ፡ የከበረን ፡ ነገር ፡ አልጻፍኩልኽምን ፧

ምሳ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ድኻን ፡ በግድ ፡ አትበለው ፡ ድኻ ፡ ነውና ፤ ችግረኛውንም ፡ በበር ፡ አትግፋው ፤

ምሳ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእነርሱን ፡ ፍርድ ፡ ይፋረድላቸዋልና ፥ የቀሟቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ሕይወት ፡ ይቀማልና ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ ከቀሥጡ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ባልንጀራ ፡ አትኹን ፥ ከወፈፍተኛም ፡ ጋት ፡ አትኺድ ፥

ምሳ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ መንገዱን ፡ እንዳትማር ፡ ለነፍስኽም ፡ ወጥመድ ፡ እንዳታገኝኽ ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ እጃቸውን ፡ አጋና ፡ እንደሚማቱ ፥ ለባለዕዳዎች ፡ እንደሚዋሱ ፡ አትኹን ፤

ምሳ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ የምትከፍለው ፡ ባይኖርኽ ፥ ምንጣፍኽን ፡ ከበታችኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይወስዳል ፧

ምሳ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ አባቶችኽ ፡ የሠሩትን ፡ የቀድሞውን ፡ የድንበር ፡ ምልክት ፡ አታፍልስ ።

ምሳ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ በሥራው ፡ የቀለጠፈ ([263]) ፡ ሰውን ፡ አይተኻልን ፧ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ይቆማል ፤ በተዋረዱም ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ አይቆምም ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ከመኰንን ፡ ጋራ ፡ ለመብላት ፡ በተቀመጥኽ ፡ ጊዜ ፥ በፊትኽ ፡ ያለውን ፡ በደኅና ፡ አስተውል ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ሰውነትኽም ፡ ቢሣሣ ፥ በጕረሮኽ ፡ ላይ ፡ ካራ ፡ አድርግ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ ጣፋጭ ፡ መብል ፡ አይመርኽ ፡ የሐሰት ፡ እንጀራ ፡ ነውና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ ባለጠጋ ፡ ለመኾን ፡ አትድከም ፤ የገዛ ፡ ራስኽን ፡ ማስተዋል ፡ ተው ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዐይንኽን ፡ ብታዘወትርበት ፡ ይጠፋል ፤ ባለጠግነት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደሚበር ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ለራሱ ፡ ክንፍ ፡ ያበጃልና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ የቀናተኛን ፡ ሰው ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ፥ ጣፋጭ ፡ መብልም ፡ አይመርኽ ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ በልቡ ፡ እንዳሰበ ፡ እንዲሁ ፡ ነውና ፤ ብላ ፡ ጠጣ ፡ ይልኻል ፥ ልቡ ፡ ግን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ የበላኸውን ፡ መብል ፡ ትተፋዋለኽ ፥ ያማረውንም ፡ ቃልኽን ፡ ታጠፋዋለኽ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ በሰነፍ ፡ ጕሮ ፡ አንዳች ፡ አትናገር ፥ የቃልኽን ፡ ጥበብ ፡ ያፌዝብኻልና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ የቀድሞውን ፡ የድንበር ፡ ምልክት ፡ አታፍልስ ፤ ወደ ፡ ድኻ ፡ አደጎች ፡ ዕርሻ ፡ አትግባ ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ታዳጊያቸው ፡ ጽኑ ፡ ነውና ፥ ርሱም ፡ ፍርዳቸውን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳልና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ልብኽን ፡ ለተግሣጽ ፡ ስጥ ፥ ጕሮኽንም ፡ ወደዕውቀት ፡ ቃል ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ሕፃንን ፡ ከመቅጣት ፡ ቸል ፡ አትበል ፥ በበትር ፡ ብትመታው ፡ አይሞትምና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ በበትር ፡ ትመታዋለኽ ፥ ነፍሱንም ፡ ትታደጋለኽ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ልብኽ ፡ ጠቢብ ፡ ቢኾን ፡ ልቤ ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ ከንፈሮችኽም ፡ በቅን ፡ ቢናገሩ ፡ ኵላሊቶቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ልብኽ ፡ በኀጢአተኞች ፡ አይቅና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቀኑን ፡ ሙሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ኑር ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ በእውነት ፡ ፍጻሜ ፡ አለኽና ፥ ተስፋኽም ፡ አይጠፋምና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፡ ጠቢብም ፡ ኹን ፡ ልብኽንም ፡ በቀናው ፡ መንገድ ፡ ምራ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ከሚጠጡ ፡ ጋራ ፡ አትቀመጥ ፡ ለሥጋም ፡ ከሚሣሡ ፡ ጋራ ፤

---

263 የቀለጠፈ ፤ ዕብራይስጡ ፡ 'መሂር' ፡ ይላል ፤ ቀልጣፋ ፡ ማለት ፡ ነው ። ያማርኛው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ (1980 ፡ ዓ.ም.) ፥ 'የቀለጠፈ' ፡ በማለት ፡ ፋንታ ፡ 'የቀጠፈ' ፡ ይላል ፤ የኀትመት ፡ ግድፈት ፡ ነው ። [አዘጋጅ]

ምሳ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ ሰካርና ፡ ሆዳም ፡ ይደኸያሉና ፥ የእንቅልፍም ፡ ብዛት ፡ የተቦጫጨቀ ፡ ጨርቅ ፡ ያስለብሳልና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ የወለደኽን ፡ አባትኽን ፡ ስማ ፥ እናትኽም ፡ ባረጀች ፡ ጊዜ ፡ አትናቃት ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እውነትን ፡ ግዛ ፡ አትሸጣትም ፥ ጥበብን ፡ ተግሣጽን ፡ ማስተዋልንም ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ የጻድቅ ፡ አባት ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ ጠቢብንም ፡ ልጅ ፡ የወለደ ፡ ሐሤትን ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ አባትኽና ፡ እናትኽ ፡ ደስ ፡ ይበላቸው ፥ አንተንም ፡ የወለደች ፡ ደስ ፡ ይበላት ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ልብኽን ፡ ስጠኝ ፥ ዐይኖችኽም ፡ መንገዴን ፡ ይውደዱ ፤

ምሳ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ ጋለሞታ ፡ ሴት ፡ የጠለቀች ፡ ዐዘቅት ፡ ናትና ፥ ሌላዪቱም ፡ ሴት ፡ የጠበበች ፡ ጕድጓድ ፡ ናትና ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 28 ፤ እንደ ፡ ሌባ ፡ ታደባለች ፡ ወስላታዎችንም ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ታበዛለች ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 29 ፤ ዋይታ ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ሐዘን ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ጠብ ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ጭኸት ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ያለምክንያት ፡ መቍሰል ፡ ለማን ፡ ነው ፧ የዐይን ፡ ቅላት ፡ ለማን ፡ ነው ፧

ምሳ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በመጠጣት ፡ ለሚዘገዩ ፡ አይደለምን ፧ የተደባለቀ ፡ የወይንን ፡ ጠጅ ፡ ይፈትኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሚከተሉ ፡ አይደለምን ፧

ምሳ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ ወደወይን ፡ ጠጅ ፡ አትመልከት ፡ በቀላ ፡ ጊዜ ፥ መልኩም ፡ በብርሌ ፡ ባንጸባረቀ ፡ ጊዜ ፥ እየጣፈጠም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ በኋላ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ይነድፋል ፥ እንደ ፡ እፍኝትም ፡ መርዙን ፡ ያፈሳል ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ጋለሞታዎችን ፡ ያያሉ ፥ ልብኽም ፡ ጠማማ ፡ ነገርን ፡ ይናገራል ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 34 ፤ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተኛ ፡ ትኾናለኽ ፥ በደቀልም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተኛ ።

ምሳ. ፡ 23 ፡ 35 ፤ መቱኝ ፥ ያውም ፡ አልተሰማኝም ፤ ጐሰሙኝ ፥ አላወቅኹምም ፥— መቼ ፡ እነሣለኹ ፧ ደግሞ ፡ ጨምሬ ፡ እሻታለኹ ፡ ትላለኽ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ በክፉ ፡ ሰዎች ፡ አትቅና ፥ ከነርሱ ፡ ጋራም ፡ መኾንን ፡ አትውደድ ፤

ምሳ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ ልባቸው ፡ ግፍን ፡ ታስባለችና ፥ ከንፈራቸውም ፡ ሽንገላን ፡ ትናገራለችና ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ቤት ፡ በጥበብ ፡ ይሠራል ፥ በማስተዋልም ፡ ይጸናል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ በዕውቀት ፡ ከከበረውና ፡ ካማረው ፡ ሀብት ፡ ዅሉ ፡ ጓዳዎች ፡ ይሞላሉ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፥ ዐዋቂም ፡ ሰው ፡ ኀይሉን ፡ ያበዛል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ በመልካም ፡ ሥርዐት ፡ ሰልፍ ፡ ታደርጋለኽ ፤ ድልም ፡ ብዙ ፡ ምክር ፡ ባለበት ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ጥበብ ፡ ለሰነፍ ፡ ከፍ ፡ ብላ ፡ የራቀች ፡ ናት ፤ በበርም ፡ አፉን ፡ አይከፍትም ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ የሚያስብ ፡ ተንኰለኛ ፡ ይባላል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ የስንፍና ፡ ሐሳብ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፤ ሰዎች ፡ ፈዘኛውን ፡ ይጸየፉታል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ ብትላላ ፡ ጕልበትኽ ፡ ጥቂት ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ሞት ፡ የሚነዱትን ፡ ታደግ ፤ ሊታረዱ ፡ የተወሰኑትን ፡ አድን ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ እንሆ ፥ ይህን ፡ አላወቀውም ፡ ብትል ፥ ልቦችን ፡ የሚመረምር ፡ ርሱ ፡ አያስተውልምን ፧ ነፍስኽንም ፡ የሚመለከት ፡ ርሱ ፡ አያውቅምን ፧ ለሰውስ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ አይመልስለትምን ፧

ምሳ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ መልካም ፡ ነውና ፥ ማር ፡ ብላ ፤ ወለላም ፡ ለጣምኽ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ጥበብም ፡ ለነፍስኽ ፡ እንዲሁ ፡ እንደሚኾን ፡ ዕወቅ ፤ ብታገኘውም ፡ ፍጻሜኽ ፡ መልካም ፡ ይኾናል ፥ ተስፋኽም ፡ አይጠፋም ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ እንደ ፡ ኃጥእ ፡ በጻድቅ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አትሸምቅ ፤ ማደሪያውንም ፡ አታውክ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ጻድቅ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ ይወድቃልና ፥ ይነሣማል ፤ ኃጥኣን ፡ ግን ፡ በክፉ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ ጠላትኽ ፡ ቢወድቅ ፡ ደስ ፡ አይበልኽ ፥ በመሰናከሉም ፡ ልብኽ ፡ ሐሤት ፡ አያድርግ ፥

ምሳ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያን ፡ አይቶ ፡ በዐይኑ ፡ ክፉ ፡ እንዳይኾን ፥ ቀሣጣውንም ፡ ከርሱ ፡ እንዳይመልስ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ስለ ፡ ኀጢአተኞች ፡ አትቈጣ ፥ በክፉዎችም ፡ አትቅና ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ለኀጢአተኛ ፡ የፍጻሜ ፡ ተስፋ ፡ የለውምና ፥ የኃጥኣንም ፡ መብራት ፡ ይጠፋልና ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሥን ፡ ፍራ ፥ ከዐመፀኞችም ፡ ጋራ ፡ አትደባለቅ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ መከራቸው ፡ ድንገት ፡ ይነሣልና ፤ ከኹለቱ ፡ የሚመጣውን ፡ ጥፋት ፡ ማን ፡ ያውቃል ፧

[የሚቀጥለው ፡ ከግሪክ ፡ የተጨመረ ፡ ነው ።] ፡ የነገሩትን ፡ የሚሰማ ፡ ልጅ ፡ ከጥፋት ፡ የራቀ ፡ ነው ፤ የነገሩትን ፡ የሚቀበልን ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይቀበለዋል ። ከንጉሥ ፡ አንደበት ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ሐሰት ፡ ይነገራል ፡ አይባልም ፤ ከአንደበቱም ፡ የሚወጣ ፡ ሐሰት ፡ የለም ። የንጉሥ ፡ ቃል ፡ ሾተል ፡ ናት ፤ ለጥፋት ፡ የተሰጠችውን ፡ ሰው ፡ ሰውነት ፡ ታጠፋዋለች ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ብቻ ፡ የምታጠፋ ፡ አይደለም ። ሰይፍ ፡ መዓቱ ፡ ብትሳል ፡ ግን ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡ ሰውን ፡ ታጠፋለች ፤ ከአሞሮች ፡ ግልገል ፡ ወገን ፡ የማይበላ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ታቃጥላለች ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ የጠቢባን ፡ ቃሎች ፡ ናቸው ። በፍርድ ፡ ታደላ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ኃጥኡን ፦ ጻድቅ ፡ ነኽ ፡ የሚለውን ፡ ወገኖች ፡ ይረግሙታል ፡ አሕዛብም ፡ ይጠሉታል ፤

ምሳ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ የሚዘልፉት ፡ ግን ፡ ደስታ ፡ ይኾንላቸዋል ፥ በላያቸውም ፡ መልካም ፡ በረከት ፡ ትመጣላቸዋለች ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ በቀና ፡ ነገር ፡ የሚመልስ ፡ ከንፈርን ፡ ይስማል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ በስተሜዳ ፡ ሥራኽን ፡ አሰናዳ ፥ ስለ ፡ አንተ ፡ በዕርሻ ፡ አዘጋጃት ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቤትኽን ፡ ሥራ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 28 ፤ በባልንጀራኽ ፡ ላይ ፡ በከንቱ ፡ ምስክር ፡ አትኹን ፥ በከንፈርኽም ፡ አታባብለው ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 29 ፤ እንዳደረገብኝ ፡ እንዲሁ ፡ አደርግበታለኹ ፥ እንደ ፡ ሥራውም ፡ እመልስበታለኹ ፡ አትበል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 30 ፤ በታካች ፡ ሰው ፡ ዕርሻ ፡ አእምሮ ፡ በጐደለውም ፡ ሰው ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ዐለፍኹ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 31 ፤ እንሆም ፡ ኹሉ ፡ ሾኽ ፡ ሞልቶበታል ፡ ፊቱንም ፡ ሳማ ፡ ሸፍኖታል ፡ የድንጋዩም ፡ ቅጥር ፡ ፈርሷል ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 32 ፤ ተመለከትኹና ፡ ዐሰብኹ ፤ አየኹትና ፡ ተግሣጽን ፡ ተቀበልኹ ።

ምሳ. ፡ 24 ፡ 33 ፤ ጥቂት ፡ ትተኛለኽ ፡ ጥቂትም ፡ ታንቀላፋለኽ ፡ ትተኛም ፡ ዘንድ ፡ ጥቂት ፡ እጅኽን ፡ ታጥፋለኽ ፤

ምሳ. ፡ 24 ፡ 34 ፤ እንግዲህ ፡ ድኽነትኽ ፡ እንደ ፡ ወንበዴ ፡ ችጋርኽም ፡ ሰይፍ ፡ እንደ ፡ ታጠቀ ፡ ሰው ፡ ይመጣብኻል ።

(በግእዝ ፡ መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ ፡ ይባላል ።)

_____መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፡ ምዕራፍ ፡ 25 ። _____

ምሳ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ሰዎች ፡ የቀዷቸው ፡ የሰሎሞን ፡ ምሳሌዎች ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ነገርን ፡ መሰወር ፡ ነው ፤ የነገሥታት ፡ ክብር ፡ ግን ፡ ነገርን ፡ መመርመር ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ እንደሰማይ ፡ ከፍታ ፡ እንደምድርም ፡ ጥልቀት ፡ የነገሥታት ፡ ልብ ፡ አይመረመርም ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ከብር ፡ ዝገትን ፡ አስወግድ ፥ ፈጽሞም ፡ ይጠራል ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ ከንጉሥ ፡ ፊት ፡ ኃጥኣንን ፡ አርቅ ፥ ዙፋኑም ፡ በጽድቅ ፡ ትጸናለች ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ በንጉሥ ፡ ፊት ፡ አትመካ ፥ በታላላቆችም ፡ ስፍራ ፡ አትቁም ፤

ምሳ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ባዩት ፡ በመኰንን ፡ ፊት ፡ ከምትዋረድ ፦ ወደዚህ ፡ ከፍ ፡ በል ፡ ብትባል ፡ ይሻልኻልና ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ባልንጀራኽ ፡ ባሳፈረኽ ፡ ጊዜ ፡ ኋላ ፡ እንዳትጸጸት ፡ ለክርክር ፡ ፈጥነኽ ፡ አትውጣ ፤

ምሳ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ክርክርኽን ፡ ከባልንጀራኽ ፡ ጋራ ፡ ተከራከር ፤ የሌላ ፡ ሰው ፡ ምስጢር ፡ ግን ፡ አትግለጥ ፥

ምሳ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ የሚሰማ ፡ እንዳይነቅፍኽ ፥ አንተንም ፡ ከማነወር ፡ ዝም ፡ እንዳይል ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ የወርቅ ፡ እንኮይ ፡ በብር ፡ ጻሕል ፡ ላይ ፤ የጊዜው ፡ ቃል ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ የምትሰማን ፡ ገሮ ፡ የሚዘልፍ ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ ጕትቻ ፡ እንደሚያንጸባርቅም ፡ ዕንቊ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ በመከር ፡ ወራት ፡ የውርጭ ፡ ጠል ፡ ደስ ፡ እንደሚያሠኝ ፥ እንዲሁ ፡ የታመነ ፡ መልእክተኛ ፡ ለላኩት ፡ ነው ፤ የጌታዎቹን ፡ ነፍስ ፡ ያሳርፋልና ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ስለ ፡ ስጦታው ፡ በሐሰት ፡ የሚመካ ፡ ሰው ፡ ዝናብ ፡ እንደማይከተለው ፡ ደመና ፡ ነፋስም ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ በትዕግሥት ፡ አለቃ ፡ ይለዝባል ፥ የገራም ፡ ምላስ ፡ ዐጥንትን ፡ ይሰብራል ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ አጥብቀኽ ፡ እንዳትጠግብ ፡ እንዳትተፋውም ፡ ማር ፡ ባገኘኽ ፡ ጊዜ ፡ የሚበቃኽን ፡ ብላ ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ እንዳይሰለችኽ ፡ እንዳይጠላኽም ፥ እግርኽን ፡ ወደባልንጀራኽ ፡ ቤት ፡ አታዘውትር ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ በባልንጀራው ፡ በሐሰት ፡ የሚመሰክር ፡ እንደ ፡ መዶሻና ፡ እንደ ፡ ሰይፍ ፡ እንደ ፡ ተሳለም ፡ ፍላጻ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ወስላታውን ፡ ሰው ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ መተማመን ፡ እንደ ፡ ተሰበረ ፡ ጥርስና ፡ እንደ ፡ ሰለለ ፡ እግር ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ ለሚያዝን ፡ ልብ ፡ ዝማሬ ፡ የሚዘምር ፥ ለብርድ ፡ ቀን ፡ መጐናጸፊያውን ፡ እንደሚያስወግድ ፡ በቀ-ስልም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መጻጻ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ ጠላትኽ ፡ ቢራብ ፡ እንጀራ ፡ አብላው ፥ ቢጠማም ፡ ውሃ ፡ አጠጣው ፤

ምሳ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ ፍም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ትሰበስባለኽና ፥ እግዚአብሔርም ፡ ዋጋኽን ፡ ይመልስልኻልና ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ የሰሜን ፡ ነፋስ ፡ ወጀብ ፡ ያመጣል ፤ ሐሜተኛ ፡ ምላስም ፡ የሰውን ፡ ፊት ፡ ያስቈጣል ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ ከጠበኛ ፡ ሴት ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ከመቀመጥ ፡ በሰገነት ፡ ማእዘን ፡ መቀመጥ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ የቀዘቀዘ ፡ ውሃ ፡ ለተጠማች ፡ ነፍስ ፡ ደስ ፡ እንደሚያሠኝ ፥ ከሩቅ ፡ አገር ፡ የመጣ ፡ መልካም ፡ ምሥራች ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ በኃጥእ ፡ ፊት ፡ የሚወድቅ ፡ ጻድቅ ፡ እንደደፈረሰ ፡ ፈሳሽና ፡ እንደ ፡ ረከሰ ፡ ምንጭ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ ብዙ ፡ ማር ፡ መብላት ፡ መልካም ፡ አይደለም ፤ እንዲሁም ፡ የራስን ፡ ክብር ፡ መፈላለግ ፡ አያስከብርም ።

ምሳ. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ቅጥር ፡ እንደሌላት ፡ እንደ ፡ ፈረሰች ፡ ከተማ ፥ መንፈሱን ፡ የማይከለክል ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

_____መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

ምሳ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ በረዶ ፡ በበጋ ፡ ዝናብም ፡ በመከር ፡ እንዳይገባ ፥ እንዲሁ ፡ ለሰነፍ ፡ ክብር ፡ አይገባውም ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ እንደሚተላለፍ ፡ ድንቢጥ ፡ ወዲያና ፡ ወዲህም ፡ እንደሚበር ፡ ጨረባ ፥ እንዲሁ ፡ ከንቱ ፡ ርግማን ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ አይደርስም ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ዐለንጋ ፡ ለፈረስ ፥ ልጓም ፡ ለአህያ ፥ በትርም ፡ ለሰነፍ ፡ ዠርባ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ርሱን ፡ እንዳትመስል ፡ ለሰነፍ ፡ እንደ ፡ ስንፍናው ፡ አትመልስለት ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ለራሱ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ እንዳይመስለው ፡ ለሰነፍ ፡ እንደ ፡ ስንፍናው ፡ መልስለት ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ በሰነፍ ፡ መልእክተኛ ፡ እጅ ፡ ነገርን ፡ የሚልክ ፡ እግሮቹን ፡ ይቈርጣል ፡ ግፍንም ፡ ይጠጣል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ እንደሚንጠለጠሉ ፡ የዐንካሳ ፡ እግሮች ፥ እንዲሁም ፡ ምሳሌ ፡ በሰነፎች ፡ አፍ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ ለሰነፍ ፡ ክብርን ፡ የሚሰጥ ፡ ድንጋይን ፡ በወንጭፍ ፡ እንደሚያስር ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ሾኽ ፡ በስካር ፡ እጅ ፡ እንደሚሰካ ፥ እንዲሁ ፡ ምሳሌ ፡ በሰነፎች ፡ አፍ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ዋና ፡ ሠራተኛ ፡ ኹሉን ፡ ነገር ፡ ይሠራል ፤ ሰነፍን ፡ የሚቀጥር ፡ ግን ፡ መንገድ ፡ ዐላፊውን ፡ እንደሚቀጥር ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ትፋቱ ፡ እንደሚመለስ ፡ ውሻ ፡ ስንፍናውን ፡ የሚደግም ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ለራሱ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ የሚመስለውን ፡ ሰው ፡ አየኸውን ፧ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ለሰነፍ ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ታካች ፡ ሰው ፦ አንበሳ ፡ በመንገድ ፡ አለ ፤ አንበሳ ፡ በጐዳና ፡ አለ ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ ሳንቃ ፡ በማጠፊያው ፡ ላይ ፡ እንደሚዞር ፥ እንዲሁ ፡ ታካች ፡ ሰው ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ይመላለሳል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ታካች ፡ ሰው ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ወጭት ፡ ያጠልቃል ፤ ወደ ፡ አፉም ፡ ይመልሳት ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡ ድካም ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ ታካች ፡ ሰው ፡ በጥበብ ፡ ከሚመልሱ ፡ ከሰባት ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ ለራሱ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ ይመስለዋል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ዐልፎ ፡ በሌላው ፡ ጥል ፡ የሚደባለቅ ፡ ውሻን ፡ በቸቦራቱ ፡ እንደሚይዝ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ ትንታግንና ፡ ፍላጻን ፡ ሞትንም ፡ እንደሚወረውር ፡ እንደ ፡ እብድ ፡ ሰው ፥

ምሳ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ባልንጀራውን ፡ የሚያታልል ፦ በጨዋታ ፡ አደረግኹት ፡ የሚል ፡ ሰውም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ ዕንጨት ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ እሳት ፡ ይጠፋል ፤ ገሮ ፡ ጠቢ ፡ በሌለበትም ፡ ዘንድ ፡ ጠብ ፡ ጸጥ ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ከሰል ፡ ፍምን ፡ ዕንጨትም ፡ እሳትን ፡ እንዲያበዛ ፥ እንዲሁ ፡ ቀኑጡ ፡ ሰው ፡ ጠብን ፡ ያበዛል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ የገሮ ፡ ጠቢ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ጣፋጭ ፡ መብል ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ እስከሆድ ፡ ጕርጆች ፡ ድረስ ፡ ይወርዳል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 23 ፤ ክፋት ፡ በልቡ ፡ ሳለ ፡ ፍቅርን ፡ የሚናገር ፡ ከንፈር ፡ በብር ፡ ዝገት ፡ እንደ ፡ ተለበጠ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ ጠላት ፡ በከንፈሩ ፡ ተስፋ ፡ ይሰጣል ፥ በልቡ ፡ ግን ፡ ተንኰልን ፡ ያኖራል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ በልቡ ፡ ሰባት ፡ ርኵሰት ፡ አለበትና ፡ በቃሉ ፡ አሳምሮ ፡ ቢናገርኽ ፡ አትመነው ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ ጠላትነቱን ፡ በተንኰል ፡ የሚሸሽግ ፥ ክፋቱ ፡ በጉባኤ ፡ መካከል ፡ ይገለጣል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ ጕድጓድን ፡ የሚምስ ፡ ይወድቅበታል ፤ ድንጋይንም ፡ የሚያንከባልል ፡ ይገለበጥበታል ።

ምሳ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ ሐሰተኛ ፡ ምላስ ፡ ያቈሰላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ይጠላል ፤ ልዝብ ፡ አፍም ፡ ጥፋትን ፡ ያመጣል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ቀን ፡ የሚያመጣውን ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቅምና ፡ ነገ ፡ በሚኾነው ፡ አትመካ ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ ሌላ ፡ ያመስግንኽ ፡ እንጂ ፡ አፍኽ ፡ አይደለም ፤ ባዕድ ፡ ሰው ፡ እንጂ ፡ ከንፈርኽ ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ ድንጋይ ፡ ከባድ ፡ ነው ፥ አሸዋም ፡ ሸክሙ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፤ ከኹለቱ ፡ ግን ፡ የሰነፍ ፡ ቍጣ ፡ ይከብዳል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ቍጣ ፡ ምሕረት ፡ የሌለው ፡ ነው ፥ መዓትም ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ነው ፤ በቅንአት ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ማን ፡ ይቆማል ፧

ምሳ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ የተገለጠ ፡ ዘለፋ ፡ ከተሰወረ ፡ ፍቅር ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ የወዳጅ ፡ ማቍሰል ፡ የታመነ ፡ ነው ፤ የጠላት ፡ መሳም ፡ ግን ፡ የበዛ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ የጠገበች ፡ ነፍስ ፡ የማር ፡ ወለላ ፡ ትረግጣለች ፤ ለተራበች ፡ ነፍስ ፡ ግን ፡ የመረረ ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ ይጣፍጣታል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ስፍራውን ፡ የሚተው ፡ ሰው ፥ ቤቱን ፡ ትቶ ፡ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ሽቱና ፡ ዕጣን ፡ ልብን ፡ ደስ ፡ ያሠኛሉ ፤ እንዲሁ ፡ ነፍስ ፡ በወዳጁ ፡ ምክር ፡ ደስ ፡ ይላታል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ወዳጅኽንና ፡ የአባትኽን ፡ ወዳጅ ፡ አትተው ፤ በመከራኽም ፡ ቀን ፡ ወደወንድምኽ ፡ ቤት ፡ አትግባ ፤ የቀረበ ፡ ወዳጅ ፡ ከራቀ ፡ ወንድም ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ጠቢብ ፡ ኹን ፥ ልቤንም ፡ ደስ ፡ አሠኘው ፥ ለሚሰድበኝ ፡ መልስ ፡ መስጠት ፡ ይቻለኝ ፡ ዘንድ ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ ብልኅ ፡ ሰው ፡ ክፉን ፡ አይቶ ፡ ይሸሸጋል ፤ አላዋቂዎች ፡ ግን ፡ ዐልፈው ፡ ይጐዳሉ ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ ለማያውቀው ፡ ከተዋሰ ፡ ሰው ፡ ልብሱን ፡ ውሰድ ፥ ለእንግዳ ፡ የተዋሰውንም ፡ ርሱን ፡ ዐግተው ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ባልንጀራውን ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ማለዳ ፡ የሚባርክ ፡ ሰው ፡ እንደሚራገም ፡ ያኽል ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ በዝናብ ፡ ቀን ፡ የሚያንጠባጥብ ፡ ቤትና ፡ ጠበኛ ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ናቸው ፤

ምሳ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ ርሷንም ፡ መከልከል ፡ ነፍስን ፡ መከልከልና ፡ ዘይትን ፡ በቀኝ ፡ እጅ ፡ መጨበጥ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ ብረት ፡ ብረትን ፡ ይስለዋል ፥ ሰውም ፡ ባልንጀራውን ፡ ይስላል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ በለሱን ፡ የጠበቀ ፡ ፍሬዋን ፡ ይበላል ፥ ጌታውንም ፡ የሚጠብቅ ፡ ይከብራል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ ፊት ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ለፊት ፡ እንደሚታይ ፥ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ ለሰው ፡ ይታያል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ ሲኦልና ፡ ጥፋት ፡ እንዳይጠግቡ ፥ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ዐይን ፡ አይጠግብም ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ብር ፡ በከውር ፡ ወርቅም ፡ በማቅለጫ ፡ ይፈተናል ፤ ሰውም ፡ በሚያመሰገኑት ፡ ሰዎች ፡ አፍ ፡ ይፈተናል ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ሰነፍን ፡ በሙቀጫ ፡ ውስጥ ፡ ከእኽል ፡ ጋራ ፡ በዘነዘና ፡ ብትወቅጠው ፥ ስንፍናው ፡ ከርሱ ፡ አይርቅም ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ የበጎችኽን ፡ መልክ ፡ አስተውለኽ ፡ ዕወቅ ፥ በከብቶችኽም ፡ ላይ ፡ ልብኽን ፡ አኑር ፤

ምሳ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ ባለጠግነት ፡ ለዘለዓለም ፡ አይኖርምና ፥ ዘውድም ፡ ለትውልድ ፡ ሹሉ ፡ አይጸናምና ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ ደረቅ ፡ ሣር ፡ በታጨደ ፡ ጊዜ ፥ ዐዲስ ፡ ለምለም ፡ በታየ ፡ ጊዜ ፥ ከተራራውም ፡ ቡቃያ ፡ በተሰበሰበ ፡ ጊዜ ፥

ምሳ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ በጎች ፡ ለልብስ ፡ ፍየሎችም ፡ የዕርሻ ፡ ዋጋ ፡ ይኾናሉ ።

ምሳ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ ለሲሳይ ፡ ለቤተ ፡ ሰቦችም ፡ ሲሳይ ፡ ለገረዶችም ፡ ምግብ ፡ የፍየል ፡ ወተት ፡ ይበቃል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ ኃጥእ ፡ ማንም ፡ ሳያሳድደው ፡ ይሸሻል ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ያለፍርሀት ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ ስለአገሪቱ ፡ ዐመፀኝነት ፡ አለቃዎቿ ፡ ብዙ ፡ ኾኑ ፤ በአስተዋይና ፡ በዐዋቂ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ዘመኗ ፡ ይረዝማል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ ድኻዎችን ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ምስኪን ፡ ሰው ፡ እኽልን ፡ እንደሚያጠፋ ፡ እንደ ፡ ዶፍ ፡ ዝናብ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ ሕግን ፡ የሚተዉ ፡ ሰዎች ፡ ኃጥኣንን ፡ ያመሰግናሉ ፤ ሕግ ፡ ጠባቂዎች ፡ ግን ፡ ይጠሏቸዋል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ፍርድን ፡ አያስተውሉም ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚሹ ፡ ግን ፡ ሹሉን ፡ ያስተውላሉ ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ በጠማማ ፡ መንገድ ፡ ከሚኼድ ፡ ባለጠጋ ፡ ያለነውር ፡ የሚኼድ ፡ ድኻ ፡ ይሻላል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ ሕግን ፡ የሚጠብቅ ፡ አስተዋይ ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ምናምንቴዎችን ፡ የሚከተል ፡ ግን ፡ አባቱን ፡ ያሳፍራል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ በዐራጣ ፡ ብዛትና ፡ በቅሚያ ፡ ሀብቱን ፡ የሚያበዛ ፡ ለድኻ ፡ ለሚራራ ፡ ያከማችለታል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ሕግን ፡ ከመስማት ፡ ጐሮውን ፡ የሚመልስ ፡ ጸሎቱ ፡ አስጸያፊ ፡ ናት ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ ቅኖችን ፡ በክፉ ፡ መንገድ ፡ የሚያስት ፥ ርሱ ፡ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ ይወድቃል ፤ ፍጹማን ፡ ግን ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ይወርሳሉ ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ለራሱ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ ይመስለዋል ፤ አስተዋይ ፡ ድኻ ፡ ግን ፡ ይመረምረዋል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ጻድቃን ፡ ድል ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ አለ ፤ ኃጥኣን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ይሸሸጋል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ኀጢአቱን ፡ የሚሰውር ፡ አይለማም ፤ የሚናዘዝባትና ፡ የሚተዋት ፡ ግን ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ ሹልጊዜ ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ምስጉን ፡ ነው ፤ ልቡን ፡ የሚያጸና ፡ ግን ፡ በክፉ ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ በድኻ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ ክፉ ፡ መኰንን ፡ እንደሚያገሣ ፡ አንበሳና ፡ እንደ ፡ ተራበ ፡ ድብ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ አእምሮ ፡ የጐደለው ፡ መኰንን ፡ ትልቅ ፡ ግፈኛ ፡ ነው ፤ ግፍን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ የሰው ፡ ደም ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ጕድጓድ ፡ ይሸሻል ፥ ማንም ፡ አያስጠጋውም ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ በቅንነት ፡ የሚኼድ ፡ ይድናል ፤ በጠማምነት ፡ የሚኼድ ፡ ግን ፡ ወዲያው ፡ ይወድቃል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ ምድሩን ፡ የሚያርስ ፡ እንጀራ ፡ ይጠግባል ፤ ምናምንቴዎችን ፡ የሚከተል ፡ ግን ፡ ድኽነት ፡ ይሞላበታል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ የታመነ ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ ይባረካል ፤ ባለጠጋ ፡ ለመኾን ፡ የሚቸኵል ፡ ግን ፡ ሳይቀጣ ፡ አይቀርም ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ ማድላት ፥ በቀራሽ ፡ እንጀራም ፡ መበደል ፡ መልካም ፡ አይደለም ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ምቀኛ ፡ ሰው ፡ ባለጠጋ ፡ ለመኾን ፡ ይቸኵላል ፥ ችጋርም ፡ እንደሚመጣበት ፡ አያውቅም ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ ምላሱን ፡ ከሚያጣፍጥ ፡ ይልቅ ፡ ሰውን ፡ የሚገሥጽ ፡ በኋላ ፡ ሞገስ ፡ ያገኛል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ ከአባቱና ፡ ከእናቱ ፡ የሚሰርቅ ፦ ኀጢአትን ፡ አልሠራኹም ፡ የሚልም ፡ የአጥፊ ፡ ባልንጀራ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ የሚጐመዥር ፡ ሰው ፡ ክርክርን ፡ ያነሣሣል ፤ በእግዚአብሔር ፡ የሚታመን ፡ ግን ፡ ይጠግባል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ በገዛ ፡ ልቡ ፡ የሚታመን ፡ ሰው ፡ ሰነፍ ፡ ነው ፤ በጥበብ ፡ የሚኼድ ፡ ግን ፡ ይድናል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ ለድኻ ፡ የሚሰጥ ፡ አያጣም ፤ ዐይኖቹን ፡ የሚጨፍን ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ይረገማል ።

ምሳ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ ኃጥኣን ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ይሸሸጋሉ ፤ እነርሱ ፡ በጠፉ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ጻድቃን ፡ ይበዛሉ ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተዘልፎ ፡ ዐንገቱን ፡ ያደነደነ ፡ ድንገት ፡ ይሰበራል ፥ ፈውስም ፡ የለውም ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ ጻድቃን ፡ በበዙ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ኃጥኣን ፡ በሠለጠኑ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሕዝብ ፡ ያለቅሳል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ ጥበብን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ አባቱን ፡ ደስ ፡ ያሠኛል ፤ ጋለሞታዎችን ፡ የሚከተል ፡ ግን ፡ ሀብቱን ፡ ያጠፋል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ ንጉሥ ፡ በፍርድ ፡ አገሩን ፡ ያጸናል ፤ መማለጃ ፡ የሚወድ ፡ ግን ፡ ያፈርሰዋል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ ወዳጁን ፡ በለዘበ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ለእግሩ ፡ መርበብን ፡ ይዘረጋል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ በክፉ ፡ ሰው ፡ ዐመፃ ፡ ወጥመድ ፡ ይገኛል ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ እልልም ፡ ይላል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ ጻድቅ ፡ የድኻዎችን ፡ ፍርድ ፡ ይመለከታል ፤ ኃጥእ ፡ ግን ፡ ዕውቀትን ፡ አያስተውልም ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ፈዘኞች ፡ ከተማቸውን ፡ ያቃጥላሉ ፤ ጠቢባን ፡ ግን ፡ ቍጣን ፡ ይመልሳሉ ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ ጠቢብ ፡ ከሰነፍ ፡ ጋራ ፡ ቢጣላ ፥ ሰነፍ ፡ ወይም ፡ ይቈጣል ፡ ወይም ፡ ይሥቃል ፥ ዕረፍትም ፡ የለም ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ የሚሹ ፡ ሰዎች ፡ ፍጹሙን ፡ ሰው ፡ ይጠላሉ ፥ ደግሞም ፡ የቅኑን ፡ ሰው ፡

ነፍስ ፡ ይሻሉ ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ ቍጣውን ፡ ሹሉ ፡ ያወጣል ፤ ጠቢብ ፡ ግን ፡ በውስጡ ፡ ያስቀረዋል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ መኰንን ፡ ሐሰተኛ ፡ ነገርን ፡ ቢያደምጥ ፥ ከርሱ ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ሹሉ ፡ ዐመፅኞች ፡ ይኾናሉ ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ ድኻና ፡ ግፈኛ ፡ ተገናኙ ፤ እግዚአብሔር ፡ የኹለቱንም ፡ ዐይን ፡ ያበራል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ ለድኻ ፡ በእውነት ፡ የሚፈርድ ፡ ንጉሥ ፥ ዙፋኑ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይጸናል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ በትርና ፡ ተግሣጽ ፡ ጥበብን ፡ ይሰጣሉ ፤ ያልተቀጣ ፡ ብላቴና ፡ ግን ፡ እናቱን ፡ ያሳፍራል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ ኃጥኣን ፡ ሲበዙ ፡ ኀጢአት ፡ ትበዛለች ፤ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ውደቀታቸውን ፡ ያያሉ ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ ልጅኽን ፡ ቅጣ ፡ ዕረፍትንም ፡ ይሰጥኻል ፤ ለነፍስኽም ፡ ተድላን ፡ ይሰጣታል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ ራእይ ፡ ባይኖር ፡ ሕዝብ ፡ መረን ፡ ይኾናል ፤ ሕግን ፡ የሚጠብቅ ፡ ግን ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ባሪያ ፡ በቃል ፡ አይገሠጽም ፤ ቢያስተውል ፡ እንኳ ፡ አይመልስምና ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ በቃሉ ፡ የሚቸኵለውን ፡ ሰው ፡ ብታይ ፥ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ለሰነፍ ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ ባሪያውን ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ዠምሮ ፡ በማቀማጠል ፡ የሚያሳድግ ፡ የኋላ ፡ ኋላ ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ያደርገዋል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ቍጡ ፡ ሰው ፡ ክርክርን ፡ ያነሣሣል ። ወፈፍተኛ ፡ ሰውም ፡ ኀጢአትን ፡ ያበዛል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ ሰውን ፡ ትዕቢቱ ፡ ያዋርደዋል ፤ መንፈሱን ፡ የሚያዋርድ ፡ ግን ፡ ክብርን ፡ ይቀበላል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ ከሌባ ፡ ጋራ ፡ የሚካፈል ፡ ነፍሱን ፡ ይጠላል ፤ መርገምን ፡ ይሰማል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ምንም ፡ አይገልጥም ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 25 ፤ ሰውን ፡ መፍራት ፡ ወጥመድ ፡ ያመጣል ፤ በእግዚአብሔር ፡ የሚታመን ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይጠበቃል ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 26 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የሹምን ፡ ፊት ፡ ይሻሉ ፤ የሰው ፡ ፍርድ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ምሳ. ፡ 29 ፡ 27 ፤ ኀጢአተኛ ፡ በጻድቃን ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ፤ በቀና ፡ መንገድ ፡ የሚኼደውም ፡ በኃጥኣን ፡ ዘንድ ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ የማሣ ፡ አገር ፡ ሰው ፡ የያቄ ፡ ልጅ ፡ የአጉር ፡ ቃል ፡ ሰውየው ፡ ለኢቲኤልና ፡ ለኡካል ፡ እንደዚህ ፡ ይናገራል ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ በእውነት ፡ ከሰው ፡ ሹሉ ፡ ይልቅ ፡ ደንቈሮ ፡ ነኝ ፥ የሰውም ፡ ማስተዋል ፡ የለብኝም ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ ጥበብንም ፡ አልተማርኹም ፥ ቅዱሱንም ፡ አላወቅኹትም ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣ ፡ የወረደስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ነፋስንስ ፡ በእጁ ፡ የጨበጠ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ውሃንስ ፡ በልብሱ ፡ የቋጠረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የምድርን ፡ ዳርቻ ፡ ሹሉ ፡ ያጸና ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይህን ፡ ታውቅ ፡ እንደ ፡

ኾንኽ ፥ ስሙ ፡ ማን ፡ የልጁስ ፡ ስም ፡ ማን ፡ ነው ፧

ምሳ. ፥ 30 ፥ 5 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ተፈትናለች ፤ ርሱ ፡ ለሚታመኑት ፡ ጋሻ ፡ ነው ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 6 ፤ እንዳይዘልፍኽ ፥ ሐሰተኛም ፡ እንዳትኾን ፡ በቃሉ ፡ አንዳች ፡ አትጨምር ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 7 ፤ ኹለትን ፡ ነገር ፡ ከአንተ ፡ እሻለኹ ፥ ሳልሞትም ፡ አትከልክለኝ ፤

ምሳ. ፥ 30 ፥ 8 ፤ ከንቱነትንና ፡ ሐሰተኛነትን ፡ ከእኔ ፡ አርቃቸው ፤ ድኽነትንና ፡ ባለጠግነትን ፡ አትስጠኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚያስፈልገኝን ፡ እንጀራ ፡ ስጠኝ ፥

ምሳ. ፥ 30 ፥ 9 ፤ እንዳልጠግብ ፡ እንዳልክድኽም ፦ እግዚአብሔርስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንዳልል ፤ ድኻም ፡ እንዳልኾን ፡ እንዳልሰርቅም ፥ በአምላኬም ፡ ስም ፡ በሐሰት ፡ እንዳልምል ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 10 ፤ እንዳይሰድብኽ ፡ በደለኛም ፡ እንዳትኾን ፡ ባሪያን ፡ በጌታው ፡ ፊት ፡ አትማ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 11 ፤ አባቱን ፡ የሚረግም ፥ እናቱንም ፡ የማይባርክ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 12 ፤ ለራሱ ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ የሚመስለው ፡ ከርኵሰቱ ፡ ያልጠራ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 13 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያሉ ፡ ዐይኖች ፡ ያሉት ፥ ሽፋሽፍቶቹም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚያዩ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 14 ፤ ድኻዎችን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ችግረኞችንም ፡ ከሰው ፡ መካከል ፡ ያጠፋና ፡ ይጨርስ ፡ ዘንድ ፡ ጥርሶቹ ፡ ሰይፍ ፡ መንጋጎቹም ፡ ካራ ፡ የኾኑ ፡ ትውልድ ፡ አለ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 15 ፤ ዐልቅት ፦ ስጠን ፡ ስጠን ፡ የሚሉ ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ አሉት ። ሦስቱ ፡ የማይጠግቡ ፥ አራቱም ፦ በቃን ፡ የማይሉ ፡ ናቸው ፤

ምሳ. ፥ 30 ፥ 16 ፤ እነርሱም ፡ ሲኦልና ፡ የማትወልድ ፡ ማሕፀን ፡ ውሃ ፡ የማትጠግብ ፡ ምድርና ፦ በቃኝ ፡ የማትል ፡ እሳት ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 17 ፤ በአባቷ ፡ የምታላግጥን ፡ የእናቷንም ፡ ትእዛዝ ፡ የምትንቅን ፡ ዐይን ፡ የሸለቆ ፡ ቊራዎች ፡ ይጐጠጉጧታል ፥ አሞራዎችም ፡ ይበሏታል ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 18 ፤ ሦስት ፡ ነገር ፡ ይገርመኛል ፥ አራተኛውንም ፡ ከቶ ፡ አላስተውለውም ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 19 ፤ እነርሱም ፡ የንስር ፡ መንገድ ፡ በሰማይ ፥ የእባብ ፡ መንገድ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፥ የመርከብ ፡ መንገድ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፥ የሰውም ፡ መንገድ ፡ ከቈንጕሮ ፡ ጋራ ፡ ናቸው ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 20 ፤ እንዲሁ ፡ በልታ ፡ አፏን ፡ የምታብስ ፦ አንዳች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላደረግኹም ፡ የምትልም ፡ የአመንዝራ ፡ ሴት ፡ መንገድ ፡ ናት ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 21 ፤ በሦስት ፡ ነገር ፡ ምድር ፡ ትናወጣለች ፥ አራተኛውንም ፡ ትሸከም ፡ ዘንድ ፡ አይቻላትም ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 22 ፤ ባሪያ ፡ በነገሠ ፡ ጊዜ ፡ ሰነፍም ፡ እንጀራ ፡ በጠገበ ፡ ጊዜ ፥

ምሳ. ፥ 30 ፥ 23 ፤ የተጠላች ፡ ሴት ፡ ባል ፡ ባገኘች ፡ ጊዜ ፥ ሴት ፡ ባሪያም ፡ እመቤቷን ፡ በወረሰች ፡ ጊዜ ።

ምሳ. ፥ 30 ፥ 24 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ አራት ፡ ጥቃቅን ፡ ፍጥረቶች ፡ አሉ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ጠቢባን ፡ ናቸው ፤

ምሳ. ፥ 30 ፥ 25 ፤ ገብረ ፡ ጉንዳን ፡ ኀይል ፡ የሌላቸው ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በበጋ ፡ መኗቸውን ፡

ይሰበስባሉ ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ ሽኮኮዎች ፡ ያልበረቱ ፡ ሕዝቦች ፡ ናቸው ፥ ቤታቸውን ፡ ግን ፡ በቋጥኝ ፡ ድንጋይ ፡ ውስጥ ፡ ያደርጋሉ ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 27 ፤ አንበጣዎች ፡ ንጉሥ ፡ የላቸውም ፥ ኹላቸው ፡ ግን ፡ በመልካም ፡ ሥርዐት ፡ ይኼዳሉ ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 28 ፤ እንሽላሊት ፡ በእጅ ፡ ይያዛል ፥ በነገሥታት ፡ ግቢ ፡ ግን ፡ ይኖራል ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 29 ፤ መልካም ፡ አረማመድን ፡ የሚራመዱ ፡ ሦስት ፡ ፍጥረቶች ፡ አሉ ፥ አራተኛውም ፡ መልካም ፡ አካኼድን ፡ ይኼዳል ፤

ምሳ. ፡ 30 ፡ 30 ፤ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ከእንስሳ ፡ ኹሉ ፡ የሚበረታ ፥ የማይመለስ ፥ እንስሳንም ፡ የማይፈራ ፤

ምሳ. ፡ 30 ፡ 31 ፤ በእንስቶች ፡ መካከል ፡ በድፍረት ፡ የሚራመድ ፡ አውራ ፡ ዶሮ ፤ መንጋን ፡ የምመራ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፤ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ በግልጥ ፡ የሚናገር ፡ ንጉሥ ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 32 ፤ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ስትል ፡ ስንፍናን ፡ ያደረግኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ክፉም ፡ ያሰብኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እጅኽን ፡ በአፍኽ ፡ ላይ ፡ ጫን ።

ምሳ. ፡ 30 ፡ 33 ፤ ወተት ፡ መግፋት ፡ ቅቤን ፡ ያወጣል ፥ አፍንጫንም ፡ መጭመቅ ፡ ደምን ፡ ያወጣ ፤ እንዲሁም ፡ ቍጣን ፡ መጐተት ፡ ጠብን ፡ ያወጣል ።

መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ፡ (መጽሐፈ ፡ ተግሣጽ) ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ እናቱ ፡ ርሱን ፡ ያስተማረችበት ፡ የማሣ ፡ ንጉሥ ፡ የልሙኤል ፡ ቃል ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ምንድር ፡ ነው ፧ የሆዴ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምንድር ፡ ነው ፧ የስእለቴ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምንድር ፡ ነው ፧

ምሳ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ ጕልበትኽን ፡ ለሴቶች ፡ አትስጥ ፥ መንገድኽንም ፡ ነገሥታትን ፡ ለሚያጠፉ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ ለነገሥታት ፡ አይገባም ፥ ልሙኤል ፡ ሆይ ፥ ነገሥታት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ። መሳፍንትም ፦ ብርቱ ፡ መጠጥ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ይሉ ፡ ዘንድ ፤

ምሳ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ እንዳይጠጡና ፡ ሕግን ፡ እንዳይረሱ ፥ የድኻ ፡ ልጆችንም ፡ ፍርድ ፡ እንዳያጐድሉ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ ለጥፋት ፡ ለቀረበው ፡ ሰው ፡ ብርቱ ፡ መጠጥ ፡ ስጡት ፥ ነፍሱ ፡ ለመረረውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ስጡት ፤

ምሳ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ ይጠጣ ፡ ድኽነቱንም ፡ ይርሳ ፥ ጕስቍልናውንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያስብ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ አፍኽን ፡ ስለ ፡ ዲዳው ፡ ክፈት ፥ ተስፋ ፡ ስለሌላቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተፋረድ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ አፍኽን ፡ ክፈት ፥ በእውነትም ፡ ፍረድ ፤ ለድኻና ፡ ለምስኪን ፡ ፍረድ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 10 ፤ ልባም ፡ ሴትን ፡ ማን ፡ ሊያገኛት ፡ ይችላል ፧ ዋጋዋ ፡ ከቀይ ፡ ዕንቊ ፡ እጅግ ፡ ይበልጣል ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 11 ፤ የባሏ ፡ ልብ ፡ ይታመንባታል ። ምርኮም ፡ አይጐድልበትም ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 12 ፤ ዕድሜዋን ፡ ሙሉ ፡ መልካም ፡ ታደርግለታለች ፥ ክፉም ፡ አታደርግም ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ የበግ ፡ ጠጕርና ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ትፈልጋለች ፥ በእጆቿም ፡ ደስ ፡ ብሷት ፡ ትሠራለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 14 ፤ ርሷ ፡ እንደ ፡ ነጋዴ ፡ መርከብ ፡ ናት ፤ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ምግቧን ፡ ትሰበስባለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ ገና ፡ ሌሊት ፡ ሳለ ፡ ትነሣለች ፡ ለቤቷም ፡ ሰዎች ፡ ምግባቸውን ፥ ለገረዶቿም ፡ ተግባራቸውን ፡ ትሰጣለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ ዕርሻንም ፡ ተመልክታ ፡ ትገዛለች ፤ ከእጇም ፡ ፍሬ ፡ ወይን ፡ ትተክላለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ ወገቧን ፡ በኀይል ፡ ትታጠቃለች ፥ ክንዷንም ፡ ታበረታለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ ንግዷ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ትመለከታለች ፤ መብራቷ ፡ በሌሊት ፡ አይጠፋም ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 19 ፤ እጇን ፡ ወደ ፡ አመልማሎ ፡ ትዘረጋለች ፥ ጣቶቿም ፡ እንዝርትን ፡ ይይዛሉ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 20 ፤ እጇን ፡ ወደ ፡ ድኻ ፡ ትዘረጋለች ፥ ወደ ፡ ችግረኛም ፡ እጇን ፡ ትሰዳለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 21 ፤ ለቤቷ ፡ ሰዎች ፡ ከበረዶ ፡ ብርድ ፡ የተነሣ ፡ አትፈራም ፥ የቤቷ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ዕጥፍ ፡ ድርብ ፡ የለበሱ ፡ ናቸውና ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 22 ፤ ለራሷም ፡ ግብረ ፡ መርፌ ፡ ስጋጃ ፡ ትሠራለች ፡ ጥሩ ፡ በፍታና ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ትለብሳለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 23 ፤ ባሏ ፡ በአገር ፡ ሽማግሌዎች ፡ መካከል ፡ በሸንጎ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ በበር ፡ የታወቀ ፡ ይኾናል ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 24 ፤ የበፍታ ፡ ቀሚስ ፡ እየሠራች ፡ ትሸጣለች ፥ ለነጋዴም ፡ ድግ ፡ ትሸጣለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 25 ፤ ብርታትና ፡ ከበሬታ ፡ ልብሷ ፡ ነው ፤ በኋላም ፡ ዘመን ፡ ላይ ፡ ትሥቃለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 26 ፤ አፏን ፡ በጥበብ ፡ ትከፍታለች ፤ የርኅራኄም ፡ ሕግ ፡ በምላሷ ፡ አለ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 27 ፤ የቤቷንም ፡ ሰዎች ፡ አካኼድ ፡ በደኅና ፡ ትመለከታለች ፥ የሀኬትንም ፡ እንጀራ ፡ አትበላም ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 28 ፤ ልጆቿ ፡ ይነሣሉ ፥ ምስጋናዋንም ፡ ይናገራሉ ፤ ባሏ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያመሰግናታል ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 29 ፤ መልካም ፡ ያደረጉ ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ አሉ ፥ አንቺ ፡ ግን ፡ ከኹሉ ፡ ትበልጫለሽ ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 30 ፤ ውበት ፡ ሐሰት ፡ ነው ፥ ደም ፡ ግባትም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈራ ፡ ሴት ፡ ግን ፡ ርሷ ፡ ትመሰገናለች ።

ምሳ. ፡ 31 ፡ 31 ፤ ከእጇ ፡ ፍሬ ፡ ስጧት ፥ ሥራዎቿም ፡ በሸንጎ ፡ ያመስግኗት ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

መክ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የነገሠ ፡ የሰባኪው ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ቃል ።

መክ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ሰባኪው ፦ ከንቱ ፥ ከንቱ ፥ የከንቱ ፡ ከንቱ ፥ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ይላል ።

መክ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በሚደክምበት ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፡ የሰው ፡ ትርፉ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ትውልድ ፡ ይኼዳል ፥ ትውልድም ፡ ይመጣል ፤ ምድር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ነው ።

መክ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ፀሓይ ፡ ትወጣለች ፥ ፀሓይም ፡ ትገባለች ፥ ወደምትወጣበትም ፡ ስፍራ ፡ ትቸኵላለች ።

መክ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይኼዳል ፥ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ይዞራል ፤ ዘወትር ፡ በዙረቱ ፡ ይዞራል ፥ ነፋስም ፡ በዙረቱ ፡ ደግሞ ፡ ይመለሳል ።

መክ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ፈሳሾች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይኼዳሉ ፥ ባሕሩ ፡ ግን ፡ አይሞላም ፤ ፈሳሾች ፡ ወደሚኼዱበት ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደዚያ ፡ ይመለሳሉ ።

መክ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያደክማል ፡ ሰው ፡ ይናገረው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ዐይን ፡ ከማየት ፡ አይጠግብም ፥ ጐሮም ፡ ከመስማት ፡ አይሞላም ።

መክ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ የኾነው ፡ ነገር ፡ ርሱ ፡ የሚኾን ፡ ነው ፥ የተደረገውም ፡ ነገር ፡ ርሱ ፡ የሚደረግ ፡ ነው ፤ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ ዐዲስ ፡ ነገር ፡ የለም ።

መክ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ማንም ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ ዐዲስ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ ይችላልን ፧ ርሱ ፡ ከእኛ ፡ በፊት ፡ በነበሩት ፡ ዘመናት ፡ ተደርጓል ።

መክ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ለፊተኞቹ ፡ ነገሮች ፡ መታሰቢያ ፡ የላቸውም ፤ ከኋለኞቹም ፡ ነገሮች ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ በሚነሡት ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ መታሰቢያ ፡ አይገኝላቸውም ።

መክ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እኔ ፡ ሰባኪው ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ ነበርኹ ።

መክ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ከሰማይም ፡ በታች ፡ የተደረገውን ፡ ኹሉ ፡ በጥበብ ፡ እፈልግና ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፡ ልቤን ፡ አተጋኹ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይደክሙባት ፡ ዘንድ ፡ ይህችን ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ የሰጠ ፡ ክፉ ፡ ጥረት ፡ ናት ።

መክ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ የተሠራውን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፥ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

መክ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ጠማማ ፡ ይቀና ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ጐደሎም ፡ ይቈጠር ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

መክ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ እኔ ፡ በልቤ ፦ እንሆ ፥ ከእኔ ፡ አስቀድመው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ከነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ጥበብን ፡ አብዝቼ ፡ ጨመርኹ ፤ ልቤም ፡ ብዙ ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ተመለከተ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹ ።

መክ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ጥበብንና ፡ እብደትን ፡ ሞኝነትንም ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቤን ፡ ሰጠኹ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ነፋስን ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተዋልኹ ።

መክ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ በጥበብ ፡ መብዛት ፡ ትካዜ ፡ ይበዛልና ፤ ዕውቀትንም ፡ የሚጨምር ፡ ሐዘንን ፡ ይጨምራልና ።

_____መጽሐፈ ፡ መክብብ ፡ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

መክ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እኔ ፡ በልቤ ፦ ና ፡ በደስታም ፡ እፈትንሃለኹ ፡ መልካምንም ፡ ቅመስ ፡ አልኹ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ እንሆ ፡ ከንቱ ፡ ነበረ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሣቅን ፦ እብድ ፡ ነኽ ፤ ደስታንም ፦ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ አልኹት ።

መክ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ በሕይወታቸው ፡ ዘመን ፡ ዅሉ ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ ሊሠሩት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እስካይ ፡ ድረስ ፡ ልቤ ፡ በጥበብ ፡ እየመራኝ ፡ ሰውነቴን ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ደስ ፡ ለማሠኘት ፡ ስንፍናንም ፡ ለመያዝ ፡ በልቤ ፡ መረመርኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ትልቅ ፡ ሥራን ፡ ሠራኹ ፡ ቤቶችንም ፡ አደረግኹ ፡ ወይንም ፡ ተከልኹ ፤

መክ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ አትክልትንና ፡ ገነትን ፡ አደረግኹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፍሬ ፡ ያለባቸውንም ፡ ዛፎች ፡ ተከልኹባቸው ፤

መክ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ በዱር ፡ የተተከሉትን ፡ ዛፎች ፡ አጠጣበት ፡ ዘንድ ፡ የውሃ ፡ ማጠራቀሚያ ፡ አደረግኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ባሪያዎች ፡ ገዛኹ ፡ የቤት ፡ ውልድ ፡ ባሪያዎችም ፡ ነበሩኝ ፤ ከእኔ ፡ አስቀድመው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩት ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ከብቶችና ፡ መንጋዎች ፡ ነበሩኝ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ የከበረውንም ፡ የነገሥታትና ፡ የአውራጃዎችን ፡ መዝገብ ፡ ሰበሰብኹ ፤ አዝማሪዎችንና ፡ አረኾዎችን ፡ የሰዎች ፡ ልጆችንም ፡ ተድላ ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ ሴቶችንም ፡ አከማቸኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ታላቅም ፡ ኾንኹ ፡ ከእኔም ፡ አስቀድመው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩት ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ከበርኹ ፤ ደግሞም ፡ ጥበቤ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ጸንታ ፡ ቀረች ።

መክ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ዐይኖቼንም ፡ ከፈለጉት ፡ ዅሉ ፡ አልከለከልኋቸውም ፤ ልቤም ፡ በድካሜ ፡ ዅሉ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ነበርና ፡ ልቤን ፡ ከደስታ ፡ ዅሉ ፡ አላራቅኹትም ፡ ከድካሜም ፡ ዅሉ ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ኾነ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እጄ ፡ የሠራቻትን ፡ ሥራዬን ፡ ዅሉ ፡ የደከምኹበትንም ፡ ድካሜን ፡ ዅሉ ፡ ተመለከትኹ ፤ እንሆ ፡ ዅሉ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነበር ፡ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ ትርፍ ፡ አልነበረም ።

መክ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ እኔም ፡ ጥበብን ፡ እብደትንና ፡ ስንፍናን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ተመለከትኹ ፤ በፊት ፡ ከተደረገው ፡ በቀር ፡ ከንጉሥ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፧

መክ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እኔም ፡ ብርሃን ፡ ከጨለማ ፡ እንደሚበልጥ ፡ እንዲሁ ፡ ጥበብ ፡ ከስንፍና ፡ እንዲበልጥ ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የጠቢብ ፡ ዐይኖች ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ናቸው ፡ ሰነፍ ፡ ግን ፡ በጨለማ ፡ ይኼዳል ፤ ደግሞ ፡ ለኹለቱ ፡ መጨረሻቸው ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተዋልኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እኔም ፡ በልቤ ፦ ለሰነፍ ፡ የሚደርሰው ፡ ለኔም ፡ ይደርሳል ፤ ለምን ፡ እጅግ ፡ ጠቢብ ፡ ኾንኹ ፧ አልኹ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በልቤ ፦ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ የተረሳ ፡ ይኾናልና ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኾን ፡ የጠቢብና ፡ የሰነፍ ፡ መታሰቢያ ፡ አይገኝም ። አዬ ፡ ጕድ! ፡ ጠቢብ ፡ ከሰነፍ ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ ይሞታል! ፡

መክ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ የተሠራው ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ ከብዶብኛልና ፡ ሕይወትን ፡ ጠላኹ ፤ ዅሉም ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

መክ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ለሚመጣው ፡ ሰው ፡ እተወዋለኹና ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ የደከምኹበትን ፡ ኹሉ ፡ ጠላኹት ።

መክ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ጠቢብ ፡ ወይም ፡ ሰነፍ ፡ እንዲኾን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በደከምኹበትና ፡ ጠቢብ ፡ በኾንኹበት ፡ በድካሜ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ጌታ ፡ ይኾንበታል ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ ተመልሼ ፡ ልቤን ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በደከምኹበት ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፡ ተስፋ ፡ አስቈረጥኹት ።

መክ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ሰው ፡ በጥበብና ፡ በዕውቀት ፡ በብልኀትም ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡ ለሌላ ፡ ላልደከመበት ፡ ሰው ፡ ያወርሰዋልና ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ትልቅም ፡ መከራ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በደከመበት ፡ ድካም ፡ ኹሉና ፡ በልቡ ፡ ዐሳብ ፡ የሰው ፡ ጥቅም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ዘመኑ ፡ ኹሉ ፡ ሐዘን ፥ ጥረትም ፡ ትካዜ ፡ ነው ፤ ልቡም ፡ በሌሊት ፡ አይተኛም ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ለሰው ፡ ከሚበላና ፡ ከሚጠጣ ፡ በድካሙም ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ በቀር ፡ የሚሻለው ፡ ነገር ፡ የለም ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ያለርሱ ፡ ፈቃድ ፡ የበላ ፡ ደስ ፡ ብሎትም ፡ ተድላን ፡ የቀመሰ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ ደስ ፡ ለሚያሠኘው ፡ ሰው ፡ ጥበብንና ፡ ዕውቀትን ፡ ደስታንም ፡ ይሰጠዋል ፤ ለኀጢአተኛ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ለሚያሠኘው ፡ ሰው ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሰበስብና ፡ እንዲያከማች ፡ ጥረትን ፡ ይሰጠዋል ። ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

_____መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

መክ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ለኹሉ ፡ ዘመን ፡ አለው ፥ ከሰማይ ፡ በታችም ፡ ለኾነ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ጊዜ ፡ አለው ።

መክ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ለመወለድ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመሞትም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለመትከል ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ የተተከለውንም ፡ ለመንቀል ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ለመግደል ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመፈወስም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለማፍረስ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመሥራትም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ለማልቀስ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመሣቅም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ዋይ ፡ ለማለት ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመዝፈንም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ድንጋይን ፡ ለመጣል ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ድንጋይንም ፡ ለመሰብሰብ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለመተቃቀፍ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ከመተቃቀፍም ፡ ለመራቅ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ለመፈለግ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለማጥፋትም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለመጠበቅ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመጣልም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ለመቅደድ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመስፋትም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ዝም ፡ ለማለት ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመናገርም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤

መክ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ለመውደድ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለመጥላትም ፡ ጊዜ ፡ አለው ፤ ለጦርነት ፡ ጊዜ ፡ አለው ፥ ለሰላምም ፡

ጊዜ ፡ አለው ።

መክ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ለሠራተኛ ፡ የድካሙ ፡ ትርፍ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ይደክሙበት ፡ ዘንድ ፡ የሰጣቸውን ፡ ጥረት ፡ አይቻለኹ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ነገርን ፡ ኹሉ ፡ በጊዜው ፡ ውብ ፡ አድርጎ ፡ ሠራው ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሰው ፡ መርምሮ ፡ እንዳያገኝ ፡ ዘለዓለምነትን ፡ በልቡ ፡ ሰጠው ።

መክ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ሰው ፡ ደስ ፡ ከሚለውና ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከሚያደርግ ፡ በቀር ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እንደሌለ ፡ ዐወቅኹ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ይበላና ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፡ በድካሙም ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያደረገው ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፡ ዐወቅኹ ፤ ሊጨመርበት ፡ ወይም ፡ ከርሱ ፡ ሊጐድል ፡ አይቻልም ፤ እግዚአብሔርም ፡ በፊቱ ፡ ይፈሩ ፡ ዘንድ ፡ አደረገ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ አኹን ፡ ያለው ፡ በፊት ፡ ነበረ ፥ የሚኾነውም ፡ በፊት ፡ ኾኖ ፡ ነበር ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያለፈውን ፡ መልሶ ፡ ይሻዋል ።

መክ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በፍርድ ፡ ስፍራ ፡ ኀጢአት ፥ በጽድቅም ፡ ስፍራ ፡ ኀጢአት ፡ እንዳለ ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ እኔም ፡ በልቤ ፦ በዚያ ፡ ለነገር ፡ ኹሉና ፡ ለሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጊዜ ፡ አለውና ፡ በጻድቅና ፡ በኀጢአተኛ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርዳል ፡ አልኹ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ በልቤ ፡ ስለሰው ፡ ልጆች ፦ እንደ ፡ እንስሳ ፡ መኾናቸውን ፡ እንዲያዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈትናቸዋል ፡ አልኹ ።

መክ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ የሰው ፡ ልጆችና ፡ የእንስሳ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ድርሻቸውም ፡ ትክክል ፡ ነው ፤ አንዱ ፡ እንደሚሞት ፡ ሌላውም ፡ እንዲሁ ፡ ይሞታል ፤ የኹሉም ፡ እስትንፋስ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ኹሉም ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፥ ሰው ፡ ከእንስሳ ፡ ብልጫ ፡ የለውም ።

መክ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ቦታ ፡ ይኼዳል ፤ ኹሉ ፡ ከዐፈር ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ ወደ ፡ ዐፈር ፡ ይመለሳል ።

መክ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ የሰው ፡ ልጆች ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እንደምትወጣ ፥ የእንስሳም ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እንደምትወርድ ፡ የሚያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ያም ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ነውና ፥ ሰው ፡ በሥራው ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እንደሌለው ፡ አየኹ ፤ ከርሱ ፡ በኋላስ ፡ የሚኾነውን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ የሚያመጣው ፡ ማን ፡ ነው ፧

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

መክ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እኔም ፡ ተመለስኹ ፥ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ የሚደረገውን ፡ ግፍ ፡ ኹሉ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ የተገፉት ፡ ሰዎች ፡ እንባ ፡ ነበረ ፤ የሚያጽናናቸውም ፡ አልነበረም ፤ በሚገፏቸውም ፡ እጅ ፡ ኀይል ፡ ነበረ ፥ እነርሱን ፡ ግን ፡ የሚያጽናናቸው ፡ አልነበረም ።

መክ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ እኔም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በሕይወት ፡ ካሉት ፡ ይልቅ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ የሞቱትን ፡ አመሰገንኹ ፤

መክ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ከነዚህም ፡ ከኹለቱ ፡ ይልቅ ፡ ገና ፡ ያልተወለደው ፡ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ የሚደረገውን ፡ ግፍ ፡ ያላየው ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ደግሞም ፡ የሰውን ፡ ድካምና ፡ የብልኀት ፡ ሥራውን ፡ ሹሉ ፡ ተመለከትኹ ፥ በባልንጀራውም ፡ ዘንድ ፡ ቅንአት ፡ እንዲያስነሣ ፡ አየኹ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

መክ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ሰነፍ ፡ እጆቹን ፡ ኰርትሞ ፡ ይቀመጣል ፤ የገዛ ፡ ሥጋውንም ፡ ይበላል ።

መክ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በድካምና ፡ ነፋስን ፡ በመከተል ፡ ከኹለት ፡ እጅ ፡ ሙሉ ፡ ይልቅ ፡ አንድ ፡ እጅ ፡ ሙሉ ፡ በዕረፍት ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እኔም ፡ ተመለስኹ ፥ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ አለ ፥ ኹለተኛም ፡ የለውም ፡ ልጅም ፡ ኾነ ፡ ወንድም ፡ የለውም ፤ ለድካሙ ፡ ግን ፡ መጨረሻ ፡ የለውም ፥ ዐይኖቹም ፡ ከባለጠግነት ፡ አይጠግቡም ፦ ለማን ፡ እደክማለኹ ፥ ሰውነቴንስ ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ እነፍጋታለኹ ፧ ይላል ። ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፣ ክፉም ፡ ጥረት ፡ ነው ።

መክ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ድካማቸው ፡ መልካም ፡ ዋጋ ፡ አለውና ፥ አንድ ፡ ብቻ ፡ ከመኾን ፡ ኹለት ፡ መኾን ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ቢወድቁ ፡ አንዱ ፡ ኹለተኛውን ፡ ያነሣዋልና ፤ አንዱ ፡ ብቻውን ፡ ኾኖ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የሚያነሣው ፡ ኹለተኛ ፡ የለውምና ፡ ወዮለት ።

መክ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ኹለቱም ፡ በአንድነት ፡ ቢተኙ ፥ ይሞቃቸዋል ፤ አንድ ፡ ብቻውን ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ ይሞቀዋል ፧

መክ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ አንዱም ፡ አንዱን ፡ ቢያሸንፍ ፥ ኹለቱ ፡ በፊቱ ፡ ይቆማሉ ፤ በሦስትም ፡ የተገመደ ፡ ገመድ ፡ ፈጥኖ ፡ አይበጠስም ።

መክ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ድኻና ፡ ጠቢብ ፡ ብላቴና ፥ ተግሣጽን ፡ መቀበል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከማያውቅ ፡ ከሰነፍ ፡ ሸማግሌ ፡ ንጉሥ ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ምንም ፡ በመንግሥቱ ፡ አገር ፡ ደግሞ ፡ ችግረኛ ፡ ኾኖ ፡ ቢወለድ ፥ ከግዞቱ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ወጥቷልና ።

መክ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ የሚኼዱትን ፡ ሕያዋን ፡ ሹሉ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ከሚነሣው ፡ ከሌላው ፡ ጐበዝ ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ከርሱ ፡ በፊት ፡ የተገዙለት ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ አይቈጠሩም ፤ በኋላ ፡ የሚመጡት ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ አይላቸውም ። ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

መክ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እግርኽን ፡ ጠብቅ ፤ ለመስማት ፡ መቅረብ ፡ ከሰነፎች ፡ መሥዋዕት ፡ ይበልጣልና ፤ እነርሱም ፡ ክፉ ፡ እንዲያደርጉ ፡ አያውቁምና ።

መክ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሰማይ ፥ አንተም ፡ በምድር ፡ ነኽና ፥ በአፍኽ ፡ አትፍጠን ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ቃልን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ልብኽ ፡ አይቸኵል ፤ ስለዚህም ፡ ቃልኽ ፡ ጥቂት ፡ ትኹን ።

መክ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ሕልም ፡ በሥራ ፡ ብዛት ፡ ይታያል ፤ እንዲሁም ፡ የሰነፍ ፡ ድምፅ ፡ በቃሉ ፡ ብዛት ፡ ይሰማል ።

መክ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ሰነፎች ፡ ደስ ፡ አያሠኙትምና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስእለት ፡ በተሳልኽ ፡ ጊዜ ፡ ትፈጽመው ፡ ዘንድ ፡ አትዘግይ ፤ የተሳልኸውን ፡ ፈጽመው ።

መክ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ተስለኽ ፡ የማትፈጽም ፡ ብትኾን ፡ ባትሳል ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ሥጋኽን ፡ በኀጢአት ፡ እንዳያስተው ፡ ለአፍኽ ፡ ሐራነት ፡ አትስጥ ፥ በመልአክም ፡ ፊት ፦ ስሕተት ፡ ነበረ ፡ አትበል ፤ እግዚአብሔር ፡ በቃልኽ ፡ ይቈጣ ፡ ዘንድ ፡ የእጅኽንም ፡ ሥራ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትሻለኽ ፧

መክ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ብዙ ፡ ሕልም ፡ ባለበት ፡ ዘንድ ፥ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ ባለበት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ ።

መክ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ከፍ ፡ ካለው ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ይመለከታልና ፥ ከነርሱም ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ ሌላዎች ፡ ከፍ ፡ ይላሉና ፡ በአገሩ ፡ ድኻዎች ፡ ሲገፉ ፥ ፍርድና ፡ ጽድቅም ፡ ሲነጠቅ ፡ ባየኽ ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አታድንቅ ።

መክ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ በጠቅላላው ፡ ግን ፡ የአገሩ ፡ ጥቅም ፡ ዕርሻን ፡ የሚወድ ፡ ንጉሥ ፡ ቢኖር ፡ ነው ።

መክ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ብርን ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ብርን ፡ አይጠግብም ፤ ባለጠግነትንም ፡ የሚወድ ፡ ትርፉን ፡ አይጠግብም ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ሀብት ፡ ሲበዛ ፡ የሚበሉት ፡ ይበዛሉ ፤ ሀብቱን ፡ በዐይኑ ፡ ብቻ ፡ ከማየት ፡ በቀር ፡ ለባለቤቱ ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፧

መክ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እጅግ ፡ ወይም ፡ ጥቂት ፡ ቢበላ ፡ የሠራተኛ ፡ እንቅልፍ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፥ የባለጠጋ ፡ ጥጋብ ፡ ግን ፡ እንቅልፍን ፡ ይከለክለዋል ።

መክ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ የሚያሳዝን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አየኹ ፤ ለመከራው ፡ በባለቤቱ ፡ ዘንድ ፡ የተቈጠበች ፡ ባለጠግነት ፡ ናት ።

መክ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ያችም ፡ ባለጠግነት ፡ በክፉ ፡ ነገር ፡ ትጠፋለች ፤ ልጅንም ፡ ቢወልድ ፡ በእጁ ፡ ምንም ፡ የለውም ።

መክ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ከእናቱ ፡ ሆድ ፡ ዕራቍቱን ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ እንዲሁ ፡ እንደመጣው ፡ ይመለሳል ፤ ከጥረቱም ፡ በእጁ ፡ ሊወስድ ፡ የሚችለውን ፡ ምንም ፡ አያገኝም ።

መክ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ የሚያሳዝን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ እንደ ፡ መጣ ፡ እንዲሁ ፡ ይኼዳል ፤ ድካሙም ፡ ለነፋስ ፡ ከኾነ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ዘመኑን ፡ ኹሉ ፡ በጨለማ ፡ በሐዘን ፡ በብስጭት ፡ በደዌና ፡ በቀሣጣ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ያየኹት ፡ መልካምና ፡ የተዋበ ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ይበላና ፡ ይጠጣ ፡ ዘንድ ፥ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ በሚደክምበት ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ነውና ።

መክ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ባለጠግነትንና ፡ ሀብትን ፡ መስጠቱ ፥ ከርሷም ፡ ይበላና ፡ ዕድል ፡ ፈንታውን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ በድካሙም ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ ማሠልጠኑ ፤ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ ደስታን ፡ ስለ ፡ ሰጠው ፡ ርሱ ፡ የሕይወቱን ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ አያስብም ።

መክ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ ያየኹት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አለ ፥ ርሱም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ የከበደ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ሀብትንና ፡ ጥሪትን ፡ ክብርንም ፡ ሰጠው ፥ ከወደደውም ፡ ኹሉ ፡ ለነፍሱ ፡ አልጐደለውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይበላዋል ፡ እንጂ ፡ ከርሱ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላሠለጠነውም ፤ ይህም ፡ ከንቱና ፡ ክፉ ፡ ደዌ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ሰው ፡ መቶ ፡ ልጆች ፡ ቢወልድ ፡ እጅግ ፡ ዘመንም ፡ በሕይወት ፡ ቢኖር ፡ ዕድሜውም ፡ እጅግ ፡ ዓመት ፡ ቢኾን ፥ ነፍሱም ፡ መልካምን ፡ ባትጠግብ ፡ መቃብርንም ፡ ባያገኝ ፥ እኔ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፦ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ጭንጋፍ ፡ ይሻላል ፡ አልኹ ።

መክ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ በከንቱ ፡ መጥቷል ፡ በጨለማ ፡ ይኼዳል ፡ ስሙም ፡ በጨለማ ፡ ይሸፈናል ፤

መክ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ ፀሓይን ፡ አላየውም ፡ አላወቀውምም ፤ ለዚህም ፡ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡ ዕረፍት ፡ አለው ።

መክ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ በሕይወት ፡ ቢኖር ፡ መልካምንም ፡ ባያይ ፥ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ የሚኼድ ፡ አይደለምን ፧

መክ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ የሰው ፡ ድካም ፡ ኹሉ ፡ ለአፉ ፡ ነው ፥ ነፍሱ ፡ ግን ፡ አትጠግብም ።

መክ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ከሰነፍ ፡ ይልቅ ፡ ለጥበበኛ ፡ ጥቅም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በሕያዋን ፡ ፊትስ ፡ መኼድ ፡ ለሚያውቅ ፡ ለድኻ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ በዐይን ፡ ማየት ፡ በነፍስ ፡ ከመቅበዝበዝ ፡ ይሻላል ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነፋስንም ፡ እንደ ፡ መከተል ፡ ነው ።

መክ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ የኾነው ፡ ስሙ ፡ አስቀድሞ ፡ ተጠራ ፥ ሰውም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታወቀ ፤ ከርሱ ፡ ከሚበረታው ፡ ጋራ ፡ ይፋረድ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

መክ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ከንቱን ፡ የሚያበዛ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለና ፡ ለሰው ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ሰው ፡ በከንቱ ፡ ወራቱ ፡ ቍጥርና ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ በሚያሳልፈው ፡ ዘመኑ ፡ በሕይወቱ ፡ ሳለ ፡ ለሰው ፡ የሚሻለውን ፡ የሚያውቅ ፡ ማነው ፧ ወይስ ፡ ለሰው ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ የሚኾነውን ፡ ማን ፡ ይነግረዋል ፧

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

መክ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ከመልካም ፡ ሽቱ ፡ መልካም ፡ ስም ፥ ከመወለድ ፡ ቀንም ፡ የሞት ፡ ቀን ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ወደግብዣ ፡ ቤት ፡ ከመኼድ ፡ ወደልቅሶ ፡ ቤት ፡ መኼድ ፡ ይሻላል ፤ ርሱ ፡ የሰው ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ነውና ፥ ሕያውም ፡ የኾነ ፡ በልቡ ፡ ያኖረዋልና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ከሣቅ ፡ ሐዘን ፡ ይሻላል ፥ ከፊት ፡ ሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ልብ ፡ ደስ ፡ ይሠኛልና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ የጠቢባን ፡ ልብ ፡ በልቅሶ ፡ ቤት ፡ ነው ፤ የሰነፎች ፡ ልብ ፡ ግን ፡ በደስታ ፡ ቤት ፡ ነው ።

መክ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ሰው ፡ የሰነፎችን ፡ ዜማ ፡ ከሚሰማ ፡ ይልቅ ፡ የጠቢባንን ፡ ተግሣጽ ፡ መስማት ፡ ይሻለዋል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ከድስት ፡ በታች ፡ እንደሚቃጠል ፡ ሾኽ ፡ ድምፅ ፡ የሰነፍ ፡ ሣቅ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ግፍ ፡ ጠቢቡን ፡ ያሳብደዋል ፤ ጕቦም ፡ ልቡን ፡ ያጠፋዋል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የነገር ፡ ፍጻሜ ፡ ከመገሥመሪያው ፡ ይሻላል ፤ ታጋሽም ፡ ከትዕቢተኛ ፡ ይሻላል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በነፍስኽ ፡ ለቀኑጣ ፡ ችኩል ፡ አትኹን ፡ ቀኑጣ ፡ በሰነፍ ፡ ብብት ፡ ያርፋልና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ ይልቅ ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ለምን ፡ ተሻለ ፧ ብለኽ ፡ አትናገር ፤ የዚህን ፡ ነገር ፡ በጥበብ ፡ አትጠይቅምና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ጥበብ ፡ ከርስት ፡ ጋራ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ፀሓይንም ፡ ለሚያዩ ፡ ሰዎች ፡ ትርፍን ፡ ይሰጣል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ የጥበብ ፡ ጥላ ፡ እንደ ፡ ገንዘብ ፡ ጥላ ፡ ናትና ፤ የዕውቀትም ፡ ብልጫዋ ፡ ጥበብ ፡ ገንዘብ ፡ ላደረጋት ፡ ሕይወትን ፡ እንድትሰጥ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ተመልከት ፤ ርሱ ፡ ጠማማ ፡ ያደረገውን ፡ ማን ፡ ሊያቀናው ፡ ይችላል ፧

መክ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ በመልካም ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ፤ በክፉም ፡ ቀን ፡ ተመልከት ፤ ሰው ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ መርምሮ ፡ ምንም ፡ እንዳያገኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህንም ፡ ያንም ፡ እንደዚያ ፡ ሠርቷል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ጻድቅ ፡ በጽድቁ ፡ ሲጠፋ ፡ ኃጥእም ፡ በክፋቱ ፡ እጅግ ፡ ዘመን ፡ ሲኖር ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ በኾነ ፡ ዘመኔ ፡ አየኹ ።

መክ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ እጅግ ፡ ጻድቅ ፡ አትኹን ፥ እጅግ ፡ ጠቢብም ፡ አትኹን ፥ እንዳትጠፋ ።

መክ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እጅግ ፡ ክፉ ፡ አትኹን ፥ እልከኛም ፡ አትኹን ፥ ጊዜኽ ፡ ሳይደርስ ፡ እንዳትሞት ።

መክ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ከኹሉ ፡ ይወጣልና ፥ ይህን ፡ ብትይዝ ፡ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ እጅኽን ፡ ባታርቅ ፡ መልካም ፡ ነው ።

መክ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ በከተማ ፡ ከሚኖሩ ፡ ከዐሥር ፡ ገዢዎች ፡ ይልቅ ፡ ጥበብ ፡ ጠቢብን ፡ ታበረታለች ።

መክ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ መልካምን ፡ የሚሠራ ፡ ኀጢአትንም ፡ የማያደርግ ፡ ጻድቅ ፡ አይገኝምና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ባሪያኽ ፡ ሲረግምኽ ፡ እንዳትሰማ ፡ በሚጫወቱበት ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ልብኽን ፡ አትጣል ፤

መክ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ሌላዎችን ፡ እንደ ፡ ረገምኽ ፡ ልብኽ ፡ ያውቃልና ።

መክ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ በጥበብ ፡ ፈተንኹ ፤ ጠቢብ ፡ እኾናለኹ ፡ አልኹ ፥ ርሷ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ራቀች ።

መክ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ የኾነው ፡ ራቀ ፡ እጅግም ፡ ጠለቀ ፤ መርምሮ ፡ የሚያገኘውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

መክ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ዐውቅና ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፥ ጥበብንና ፡ የነገሩን ፡ ኹሉ ፡ መደምደሚያ ፡ እፈልግ ፡ ዘንድ ፥ ኀጢአትም ፡ ስንፍና ፥ ስንፍናም ፡ እብደት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ በልቤ ፡ ዞርኹ ።

መክ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ እኔም ፡ ከሞት ፡ ይልቅ ፡ የመረረ ፡ ነገር ፡ መርምሬ ፡ አገኘኹ ፤ ርሷም ፡ ልቧ ፡ ወጥመድና ፡ መርበብ ፡ የኾነ ፥ እጆቿም ፡ እግር ፡ ብረት ፡ የኾኑ ፡ ሴት ፡ ናት ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ የኾነ ፡ ከርሷ ፡ ያመልጣል ፥ ኀጢአተኛ ፡ ግን ፡ ይጠመድባታል ።

መክ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ አንዱን ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ ጨምሬ ፡ ወደ ፡ ነገሩ ፡ ኹሉ ፡ መደምደሚያ ፡ እደርስ ፡

ዘንድ ፥ እንሆ ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ አገኘኹ ፡ ይላል ፡ ሰባኪው ፤

መክ. ፥ 7 ፥ 28 ፤ ነፍሴ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ትሻታለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላገኘኹም ፤ ከሺሕ ፡ ወንዶች ፡ አንድ ፡ አገኘኹ ፥ ከነዚያ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ግን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አላገኘኹም ።

መክ. ፥ 7 ፥ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰዎችን ፡ ቅኖች ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፥ እንሆ ፥ ይህን ፡ ብቻ ፡ አገኘኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ብልኀትን ፡ ፈለጉ ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

መክ. ፥ 8 ፥ 1 ፤ እንደ ፡ ጠቢብ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ነገርንስ ፡ መተርጐም ፡ የሚያውቅ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሰው ፡ ጥበብ ፡ ፊቱን ፡ ታበራለች ፥ የፊቱንም ፡ ድፍረት ፡ ትለውጣለች ።

መክ. ፥ 8 ፥ 2 ፤ እኔ ፦ በእግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ ምክንያት ፡ የንጉሥን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቅ ፡ እልኻለኹ ።

መክ. ፥ 8 ፥ 3 ፤ የወደደውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርጋልና ፥ ከፊቱ ፡ ትወገድ ፡ ዘንድ ፡ አትቸኩል ፥ ክፉንም ፡ በማድረግ ፡ አትጽና ።

መክ. ፥ 8 ፥ 4 ፤ የንጉሥ ፡ ቃል ፡ ኀይለኛ ፡ ነውና ፤ ይህንስ ፡ ለምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ ማን ፡ ይለዋል ፧

መክ. ፥ 8 ፥ 5 ፤ ትእዛዝን ፡ የሚጠብቅ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አያውቅም ፤ የጠቢብም ፡ ልብ ፡ ጊዜንና ፡ ፍርድን ፡ ያውቃል ።

መክ. ፥ 8 ፥ 6 ፤ የሰው ፡ መከራ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለነገር ፡ ኹሉ ፡ ጊዜና ፡ ፍርድ ፡ አለውና ።

መክ. ፥ 8 ፥ 7 ፤ የሚኾነውንም ፡ አያውቅም ፤ እንዴትስ ፡ እንደሚኾን ፡ የሚነግረው ፡ ማን ፡ ነው ፧

መክ. ፥ 8 ፥ 8 ፤ መንፈስን ፡ ለማስቀረት ፡ በመንፈስ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ የለም ፤ በሞቱም ፡ ቀን ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፤ በሰልፍም ፡ ስንብቻ ፡ የለም ፥ ኀጢአትም ፡ ሠሪውን ፡ አያድነውም ።

መክ. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አየኹ ፥ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ ወደተደረገው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ልቤን ፡ ሰጠኹ ፤ ሰው ፡ ሰውን ፡ ለመጕዳት ፡ ገዢ ፡ የሚኾንበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

መክ. ፥ 8 ፥ 10 ፤ እንዲሁም ፡ ኃጥኣን ፡ ተቀብረው ፡ አየኹ ፥ ወደ ፡ ዕረፍትም ፡ ገቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቅን ፡ አድራጊዎች ፡ ከቅድስት ፡ ስፍራ ፡ ወጡ ፥ በከተማዪቱም ፡ ውስጥ ፡ ተረሱ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፥ 8 ፥ 11 ፤ በክፉ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ፈጥኖ ፡ ፍርድ ፡ አይፈረድምና ፡ ስለዚህ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ ውስጥ ፡ ልባቸው ፡ ክፉን ፡ ለመሥራት ፡ ጠነከረ ።

መክ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ኀጢአተኛ ፡ መቶ ፡ ጊዜ ፡ ክፉን ፡ ቢሠራ ፡ ዘመኑም ፡ ረዥም ፡ ቢኾን ፥ እግዚአብሔርን ፡ ለሚፈሩት ፡ በፊቱም ፡ ለሚፈሩት ፡ ደኅንነት ፡ እንዲኾን ፡ ዐውቃለኹ ፤

መክ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ ለኃጥእ ፡ ግን ፡ ደኅንነት ፡ የለውም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ አይፈራምና ፡ ዘመኑ ፡ እንደ ፡ ጥላ ፡ አትረዝምም ።

መክ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ በምድር ፡ የሚደረግ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ አለ ፤ በኃጥኣን ፡ የሚደረገው ፡ ሥራ ፡ የሚደርስባቸው ፡ ጻድቃን ፡ አሉ ፥ ለጻድቃንም ፡ የሚደረገው ፡ ሥራ ፡ የሚደርስላቸው ፡ ኃጥኣን ፡ አሉ ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

መክ. ፥ 8 ፥ 15 ፤ ከሚበላውና ፡ ከሚጠጣው ፡ ደስም ፡ ከሚለው ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ ሌላ ፡

መልካም ፡ ነገር ፡ የለውምና ፥ እኔ ፡ ደስታን ፡ አመሰገንኹ ፤ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ ከድካሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠው ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ይህ ፡ ደስታው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖራል ።

መክ. ፥ 8 ፥ 16 ፤ ጥበብን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ የሚኾነውንም ፡ ድካም ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ልቤን ፡ ሰጠኹ ፥ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ እንቅልፍን ፡ በዐይኑ ፡ የማያይ ፡ አለና ፤

መክ. ፥ 8 ፥ 17 ፤ ከፀሓይም ፡ በታች ፡ የተደረገውን ፡ ሥራ ፡ መርምሮ ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ እንዳይቻለው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አየኹ ። ሰውም ፡ ሊፈልግ ፡ እጅግ ፡ ቢደክም ፥ መርምሮ ፡ አያገኘውም ፤ ደግሞ ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፦ ይህን ፡ ዐወቅኹ ፡ ቢል ፥ ርሱ ፡ ያገኘው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

መክ. ፥ 9 ፥ 1 ፤ ጻድቃንና ፡ ጠቢባን ፡ ሥራዎቻቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ ይህን ፡ ኹሉ ፡ እመረምር ፡ ዘንድ ፡ በልቤ ፡ አኖርኹ ፤ ፍቅር ፡ ወይም ፡ ጥል ፡ ቢኾን ፡ ሰው ፡ አያውቅም ፤ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ፊታቸው ፡ ነው ።

መክ. ፥ 9 ፥ 2 ፤ የጻድቁና ፡ የበደለኛው ፥ የመልካሙና ፡ የክፉው ፥ የንጹሑና ፡ የርኩሱ ፥ መሥዋዕትን ፡ የሚሠዋውና ፡ የማይሠዋው ፥ የሰው ፡ ኹሉ ፡ ድርሻው ፡ አንድ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ መልካሙ ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ ኀጢአተኛው ፥ እንደ ፡ መሐለኛው ፡ ሰው ፡ እንዲሁ ፡ መሐላን ፡ የሚፈራው ፡ ነው ።

መክ. ፥ 9 ፥ 3 ፤ አንድ ፡ ድርሻ ፡ ኹሉን ፡ እንዲያገኝ ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በተደረገው ፡ ኹሉ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ደግሞም ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ልብ ፡ ክፋትን ፡ ትሞላለች ፥ በሕይወታቸውም ፡ ሳሉ ፡ እብደት ፡ በልባቸው ፡ ነው ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሙታን ፡ ይወርዳሉ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 4 ፤ ያልሞተ ፡ ውሻ ፡ ከሞተ ፡ አንበሳ ፡ ይሻላልና ፥ ሰው ፡ ከሕያዋን ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ቢኖር ፡ ተስፋ ፡ አለው ።

መክ. ፥ 9 ፥ 5 ፤ ሕያዋን ፡ እንዲሞቱ ፡ ያውቃሉና ፤ ሙታን ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ አያውቁም ፤ መታሰቢያቸውም ፡ ተረስቷልና ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ዋጋ ፡ የላቸውም ።

መክ. ፥ 9 ፥ 6 ፤ ፍቅራቸውና ፡ ጥላቸው ፡ ቅንአታቸውም ፡ በአንድነት ፡ ጠፍቷል ፥ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ በሚሠራው ፡ ነገር ፡ ለዘለዓለም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የላቸውም ።

መክ. ፥ 9 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሥራኽን ፡ ተቀብሎታልና ፥ ኺድ ፤ እንጀራኽን ፡ በደስታ ፡ ብላ ፥ የወይን ፡ ጠጅኽንም ፡ በተድላ ፡ ጠጣ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 8 ፤ ኹልጊዜ ፡ ልብስኽ ፡ ነጭ ፡ ይኹን ፤ ቅባትም ፡ ከራስኽ ፡ ላይ ፡ አይታጣ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 9 ፤ በሕይወትኽ ፥ አንተም ፡ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በምትደክምበት ፡ ድካም ፡ ይህ ፡ ዕድል ፡ ፈንታኽ ፡ ነውና ፥ ከንቱ ፡ በኾነ ፡ በሕይወትኽ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ በሰጠኽ ፥ በከንቱ ፡ ዘመንኽ ፡ ኹሉ ፥ ከምትወዳት ፡ ሚስትኽ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 10 ፤ አንተ ፡ በምትኼድበት ፡ በሲኦል ፡ ሥራና ፡ ዐሳብ ፡ ዕውቀትና ፡ ጥበብ ፡ አይገኙምና ፡ እጅኽ ፡ ለማድረግ ፡ የምታገኘውን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ኀይልኽ ፡ አድርግ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 11 ፤ እኔም ፡ ተመለስኹ ፥ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ ሩጫ ፡ ለፈጣኖች ፥ ሰልፍም ፡ ለኀያላን ፥ እንጀራም ፡ ለጠቢባን ፥ ባለጠግነትም ፡ ለአስተዋዮች ፥ ሞገስም ፡ ለዐዋቂዎች ፡ እንዳልኾነ ፡ አየኹ ፤ ጊዜና ፡ ዕድል ፡ ግን ፡ ኹሉን ፡ ይገናኛቸዋል ።

መክ. ፥ 9 ፥ 12 ፤ ሰውም ፡ ጊዜውን ፡ አያውቅም ፤ በክፉ ፡ መረብ ፡ እንደ ፡ ተጠመዱ ፡ ዓሣዎች ፥ በወጥመድም ፡

እንደ ፡ ተያዙ ፡ ወፎች ፥ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ በክፉ ፡ ጊዜ ፡ በድንገት ፡ ሲወድቅባቸው ፡ ይጠመዳሉ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ ከፀሓይ ፡ በታችም ፡ ይህን ፡ ጥበብ ፡ አየኹ ፥ ርሷም ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ መሰለችኝ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ ታናሽ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ፥ ጥቂቶች ፡ ሰዎችም ፡ ነበሩባት ፤ ታላቅ ፡ ንጉሥም ፡ መጣባት ፡ ከበባትም ፥ ታላቅ ፡ ግንብም ፡ ሠራባት ።

መክ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ ጠቢብ ፡ ድኻ ፡ ሰውም ፡ ተገኘባት ፥ ያችንም ፡ ከተማ ፡ በጥበቡ ፡ አዳናት ፤ ያን ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ማንም ፡ አላሰበውም ።

መክ. ፥ 9 ፥ 16 ፤ እኔም ። ከኀይል ፡ ይልቅ ፡ ጥበብ ፡ ትበልጣለች ፤ የድኻው ፡ ጥበብ ፡ ግን ፡ ተናቀች ፡ ቃሉም ፡ አልተሰማችም ፡ አልኹ ።

መክ. ፥ 9 ፥ 17 ፤ በሰነፎች ፡ መካከል ፡ ከሚጮኽ ፡ ከገዢው ፡ ጩኸት ፡ ይልቅ ፡ የጠቢባን ፡ ቃል ፡ በጸጥታ ፡ ትሰማለች ።

መክ. ፥ 9 ፥ 18 ፤ ከጦር ፡ መሣሪያዎች ፡ ይልቅ ፡ ጥበብ ፡ ትሻላለች ፤ አንድ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ መልካምን ፡ ያጠፋል ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

መክ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ የሞቱ ፡ ዝንቦች ፡ የተቀመመውን ፡ የዘይት ፡ ሽቱ ፡ ያገሙታል ፤ እንዲሁም ፡ ትንሽ ፡ ስንፍና ፡ ጥበብንና ፡ ክብርን ፡ ያጠፋል ።

መክ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ የጠቢብ ፡ ልብ ፡ በስተቀኙ ፡ ነው ፥ የሰነፍ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ በስተግራው ፡ ነው ።

መክ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ ደግሞም ፡ ሰነፍ ፡ በመንገድ ፡ ሲመላለስ ፡ ርሱ ፡ ልብ ፡ ይጐድለዋል ፥ የሚያስበውም ፡ ዅሉ ፡ ስንፍና ፡ ነው ።

መክ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ ትዕግሥት ፡ ታላቁን ፡ ኀጢአት ፡ ጸጥ ፡ ያደርጋልና ፥ የገዢ ፡ ቀኑጣ ፡ የተነሣብኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስፍራኽን ፡ አትልቀቅ ።

መክ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ ከፀሓይ ፡ በታች ፡ ያየኹት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አለ ፥ ርሱም ፡ ከገዢ ፡ የሚወጣ ፡ ስሕተት ፡ ነው ፤

መክ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ ሰነፍ ፡ በታላቅ ፡ ማዕርግ ፡ ተሾመ ፥ ባለጠጋዎች ፡ ግን ፡ በተዋረደ ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጡ ።

መክ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ ባሪያዎች ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ሲቀመጡ ፡ መሳፍንትም ፡ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሲኼዱ ፡ አየኹ ።

መክ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ ጕድጓድን ፡ የሚምስ ፡ ይወድቅበታል ፥ ቅጥርንም ፡ የሚያፈርስን ፡ እባብ ፡ ትነድፈዋለች ።

መክ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ ድንጋይን ፡ የሚፈነቅል ፡ ይታመምበታል ፥ ዕንጨትንም ፡ የሚፈልጥ ፡ ይጐዳበታል ።

መክ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ ብረት ፡ ቢደነዝዝ ፡ ሰውም ፡ ባይስለው ፡ ኀይልን ፡ ሊያበዛ ፡ ይገባዋል ፤ ጥበብ ፡ ግን ፡ ሥራውን ፡ ለማከናወን ፡ ትጠቅመዋለች ።

መክ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ ደጋሚ ፡ ሳይደግምባት ፡ እባብ ፡ ብትነድፍ ፡ ለደጋሚው ፡ ትርፍ ፡ የለውም ።

መክ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ የጠቢብ ፡ ሰው ፡ የአፉ ፡ ቃል ፡ ሞገስ ፡ ናት ፤ የሰነፍ ፡ ከንፈሮች ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ይውጡታል ።

መክ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ የአፉ ፡ ቃል ፡ መገ፫መሪያ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፥ የንግግሩ ፡ ፍጻሜም ፡ ክፉ ፡ እብደት ፡ ነው ።

መክ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ሰነፍ ፡ ቃሉን ፡ ያበዛል ፤ ሰው ፡ ግን ፡ የሚኾነውን ፡ አያውቅም ፤ ከርሱስ ፡ በኋላ ፡ የሚኾነውን ፡ ማን ፡ ይነግረዋል ፧

መክ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ የሰነፍ ፡ ሥራ ፡ ያደክመዋል ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መኼድ ፡ አያውቅምና ።

መክ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ንጉሥሽ ፡ ሕፃን ፡ የኾነ ፥ መኳንንቶችሽም ፡ ማልደው ፡ የሚበሉ ፥ አንቺ ፡ አገር ፡ ሆይ ፥ ወዮልሽ! ፡

መክ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ንጉሥሽ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ የኾነ ፥ ለብርታት ፡ እንጂ ፡ ለስካር ፡ ያይደለ ፡ በጊዜ ፡ የሚበሉ ፡ መኳንንት ፡ ያሉሽ ፥ አንቺ ፡ አገር ፡ ሆይ ፥ የተመሰገንሽ ፡ ነሽ ።

መክ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ተግባር ፡ በመፍታት ፡ ጣራው ፡ ይዘብጣል ፥ በእጅም ፡ መታከት ፡ ቤት ፡ ያፈሳል ።

መክ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እንጀራን ፡ ለሣቅ ፡ የወይን ፡ ጠጅንም ፡ ለሕይወት ፡ ደስታ ፡ ያደርጉታል ፥ ዅሉም ፡ ለገንዘብ ፡ ይገዛል ።

መክ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ የሰማይ ፡ ወፍ ፡ ቃሉን ፡ ይወስደዋልና ፥ ባለክንፎችም ፡ ነገሩን ፡ ይናገራሉና ፡ በልብኽ ፡ ዐሳብ ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ ንጉሥን ፡ አትስደብ ፥ በመኝታ ፡ ቤትኽም ፡ ባለጠጋን ፡ አትስደብ ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

መክ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እንጀራኽን ፡ በውሃ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ጣለው ፥ ከብዙ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ታገኘዋለኽና ።

መክ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ለሰባት ፡ ደግሞም ፡ ለስምንት ፡ ዕድል ፡ ፈንታን ፡ ክፈል ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ የሚኾነውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቅምና ።

መክ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ደመናት ፡ ዝናብ ፡ በሞሉ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያፈሱታል ፤ ዛፍም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ቢወድቅ ፥ ዛፉ ፡ በወደቀበት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ ይኖራል ።

መክ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ነፋስን ፡ የሚጠባበቅ ፡ አይዘራም ፥ ደመናንም ፡ የሚመለከት ፡ አያጭድም ።

መክ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የነፋስ ፡ መንገድ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዐጥንትም ፡ በእርጉዝ ፡ ሆድ ፡ እንዴት ፡ እንድትዋደድ ፡ እንደማታውቅ ፥ እንዲሁም ፡ ዅሉን ፡ የሚሠራውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ አታውቅም ።

መክ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ወይም ፡ ይህ ፡ ወይም ፡ ያ ፡ ማናቸው ፡ እንዲበቅል ፡ ወይም ፡ ኹለቱ ፡ መልካም ፡ እንዲኾኑ ፡ አታውቅምና ፡ በማለዳ ፡ ዘርኽን ፡ ዝራ ፥ በማታም ፡ እጅኽን ፡ አትተው ።

መክ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ብርሃን ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፥ ፀሓይንም ፡ ማየት ፡ ለዐይን ፡ መልካም ፡ ነው ።

መክ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ሰው ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ በሕይወት ፡ ቢኖር ፡ በዅሉም ፡ ደስ ፡ ይበለው ፤ ኾኖም ፡ የጨለማውን ፡ ዘመን ፡ ያስብ ፥ ብዙ ፡ ቀን ፡ ይኾናልና ። የሚመጣው ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

መክ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ጐበዝ ፥ በጕብዝናኽ ፡ ደስ ፡ ይበልኽ ፥ በጕብዝናኽም ፡ ወራት ፡ ልብኽን ፡ ደስ ፡ ይበለው ፥ በልብኽም ፡ መንገድ ፡ ዐይኖችኽም ፡ በሚያዩት ፡ ኺድ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ እንዲያመጣኽ ፡ ዕወቅ ።

መክ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ሕፃንነትና ፡ ጕብዝና ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸውና ፥ ከልብኽ ፡ ሐዘንን ፡ አርቅ ፥ ከሰውነትኽም ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አስወግድ ።

መጽሐፈ ፡ መክብብ ፡ ምዕራፍ ፡ 12 ።

መክ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ የጭንቀት ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ በጕብዝናኽ ፡ ወራት ፡ ፈጣሪኽን ፡ ዐስብ ፤ ደስ ፡ አያሠኙም ፡ የምትላቸውም ፡ ዓመታት ፡ ሳይደርሱ ፤

መክ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ፀሓይና ፡ ብርሃን ፡ ጨረቃና ፡ ከዋክብትም ፡ ሳይጨልሙ ፥ ደመናትም ፡ ከዝናብ ፡ በኋላ ፡ ሳይመለሱ ፤

መክ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ቤት ፡ ጠባቂዎች ፡ በሚንቀጠቀጡበት ፥ ኀያላን ፡ ሰዎችም ፡ በሚጐብጡበት ፥ ጥቂቶች ፡ ኾነዋልና ፥ ፈጪታዎች ፡ ሥራ ፡ በሚፈቱበት ፥ በመስኮትም ፡ ኾነው ፡ የሚመለከቱ ፡ በሚጨልሙበት ፥ በአደባባይም ፡ ደጆቹ ፡ በሚዘጉበት ፡ ቀን ፤

መክ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ የወፍጮ ፡ ድምፅ ፡ ሲላሽ ፥ ከወፍ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ ሲነሣ ፥ ዜማም ፡ የሚጮኹ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ኹሉ ፡ ዝግ ፡ ሲሉ ፤

መክ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ደግሞ ፡ ሲፈሩ ፥ ድንጋጤም ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ሲኾን ፤ ለውዝም ፡ ሲያብብ ፥ አንበጣም ፡ እንደ ፡ ሸክም ፡ ሲከብድ ፥ ፈቃድም ፡ ሲጠፋ ፤ ሰው ፡ ወደዘለዓለም ፡ ቤት ፡ ሲኼድ ፥ አልቃሾችም ፡ በአደባባይ ፡ ሲዞሩ ፤

መክ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የብር ፡ ድሪ ፡ ሳይበጠስ ፥ የወርቅም ፡ ኩስኩስት ፡ ሳይሰበር ፥ ማድጋውም ፡ በምንጭ ፡ አጠገብ ፡ ሳይከሰከስ ፥ መንኰራኩሩም ፡ በጕድጓድ ፡ ላይ ፡ ሳይሰበር ፥

መክ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ዐፈርም ፡ ወደነበረበት ፡ ምድር ፡ ሳይመለስ ፥ ነፍስም ፡ ወደሰጠው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይመለስ ፡ ፈጣሪኽን ፡ ዐስብ ።

መክ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ሰባኪው ፦ ከንቱ ፥ ከንቱ ፤ ኹሉ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፡ ይላል ።

መክ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ሰባኪውም ፡ ጠቢብ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለሕዝቡ ፡ ዕውቀትን ፡ አስተማረ ፤ ርሱም ፡ ብዙ ፡ ምሳሌዎችን ፡ መረመረና ፡ ፈላለገ ፡ አስማማም ።

መክ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ሰባኪው ፡ ያማረውን ፡ በቅንም ፡ የተጻፈውን ፡ እውነተኛውን ፡ ቃል ፡ መርምሮ ፡ ለማግኘት ፡ ፈለገ ።

መክ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ የጠቢባን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ መውጊያ ፡ ነው ፥ የተሰበሰቡትም ፡ ካንድ ፡ እረኛ ፡ የተሰጡት ፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ ተቸነከሩ ፡ ችንካሮች ፡ ናቸው ።

መክ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ተግሣጽን ፡ ስማ ፤ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፡ ማድረግ ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፥ እጅግም ፡ ምርምር ፡ ሰውነትን ፡ ያደክማል ።

መክ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ የነገሩን ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ እንስማ ፤ ይህ ፡ የሰው ፡ ኹለንተናው ፡ ነውና ፤ እግዚአብሔርን ፡ ፍራ ፥ ትእዛዙንም ፡ ጠብቅ ።

መክ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሥራን ፡ ኹሉ ፡ የተሰወረውንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ መልካምም ፡ ቢኾን ፡ ክፉም ፡ ቢኾን ፥ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ያመጣዋልና ፞

ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ማሕ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ከመዝሙር ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ የሰሎሞን ፡ መዝሙር ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ በአፉ ፡ መሳም ፡ ይሳመኝ ፥ ፍቅርኽ ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ ይልቅ ፡ መልካም ፡ ነውና ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ዘይትኽ ፡ መልካም ፡ መዐዛ ፡ አለው ፤ ስምኽ ፡ እንደሚፈስ ፡ ዘይት ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ደናግል ፡ ወደዱኽ ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ሳበኝ ፥ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ እንሮጣለን ፤ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ አገባኝ ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፥ ሐሤትም ፡ እናደርጋለን ፤ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ ይልቅ ፡ ፍቅርኽን ፡ እናስባለን ፤ በቅንነት ፡ ይወዱኻል ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕዥት ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ጥቍር ፡ ነኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ውብ ፡ ነኝ ፥ እንደ ፡ ቄዳር ፡ ድንኳኖች ፡ እንደ ፡ ሰሎሞንም ፡ መጋረጃዎች ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ፀሓይ ፡ መልኬን ፡ አክስሎታልና ፤ ጥቍር ፡ ስለ ፡ ኾንኹ ፡ አትዩኝ ፤ የእናቴ ፡ ልጆች ፡ ተጣሉኝ ፥ የወይን ፡ ቦታዎችንም ፡ ጠባቂ ፡ አደረጉኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእኔን ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ አልጠበቅኹም ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ነፍሴ ፡ የወደደችኽ ፡ አንተ ፡ ንገረኝ ፤ ወዴት ፡ ታሰማራለኽ ፧ በቀትርስ ፡ ጊዜ ፡ ወዴት ፡ ትመስጋለኽ ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ ከባልንጀራዎችኽ ፡ መንጋዎች ፡ በኋላ ፡ እቅበዘበዛለኹ ፧

ማሕ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ አንቺ ፡ በሴቶች ፡ ዘንድ ፡ የተዋብሽ ፡ ሆይ ፥ ያላወቅሽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የመንጋዎችን ፡ ፍለጋ ፡ ተከትለሽ ፡ ውጪ ፥ የፍየል ፡ ግልገሎችሽንም ፡ በእረኞች ፡ ድንኳኖች ፡ አጠገብ ፡ አሰማሪ ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ በፈርዖን ፡ ሠረገላዎች ፡ እንዳለ ፡ ፈረስ ፡ መሰልኹሽ ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ የጕንጭሽ ፡ ውበት ፡ በከበረ ፡ ሉል ፥ ዐንገትሽም ፡ በዕንቊ ፡ ድሪ ፡ ያማረ ፡ ነው ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ባለብር ፡ ጕብጕብ ፡ የኾነ ፡ የወርቅ ፡ ጠልሰም ፡ እናደርግልሻለን ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ንጉሡ ፡ በማእዱ ፡ ሳለ ፥ የእኔ ፡ ናርዶስ ፡ መዐዛውን ፡ ሰጠ ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ውዴ ፡ ለእኔ ፡ በጡቶቼ ፡ መካከል ፡ እንደሚያርፍ ፡ እንደ ፡ ተቋጠረ ፡ ከርቤ ፡ ነው ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ውዴ ፡ ለእኔ ፡ በዐይንጋዲ ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ አበባ ፡ ዕቅፍ ፡ ነው ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ውብ ፡ ነሽ ፤ እንሆ ፥ አንቺ ፡ ውብ ፡ ነሽ ፤ ዐይኖችሽም ፡ እንደ ፡ ርግቦች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ውዴ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ አንተ ፡ ውብ ፡ ነኽ ፥ መልከ ፡ መልካምም ፡ ነኽ ፤ ዐልጋችንም ፡ ለምለም ፡ ነው ።

ማሕ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ የቤታችን ፡ ሠረገላ ፡ የዝግባ ፡ ዛፍ ፡ ነው ፥ የጣሪያችንም ፡ ማዋቀሪያ ፡ የጥድ ፡ ዛፍ ፡ ነው ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ማሕ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እኔ ፡ የሳሮን ፡ ጽጌ ፡ ረዳ ፡ የቈላም ፡ አበባ ፡ ነኝ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በሾኽ ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ የሱፍ ፡ አበባ ፥ እንዲሁ ፡ ወዳጄ ፡ በቈነጕሯት ፡ መካከል ፡ ናት ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ በዱር ፡ እንዳለ ፡ እንኮይ ፥ እንዲሁ ፡ ውዴ ፡ በልጆች ፡ መካከል ፡ ነው ። ከጥላው ፡ በታች ፡ እጅግ ፡ ወድጄ ፡ ተቀመጥኹ ፥ ፍሬውም ፡ በጕረሮዬ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ወደወይን ፡ ጠጁም ፡ ቤት ፡ አገባኝ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ዐላማውም ፡ ፍቅር ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በዘቢብም ፡ አጽናኑኝ ፥ በእንኮይ ፡ አበረታቱኝ ፥ በፍቅሩ ፡ ተነድፌ ፡ ታምሜያለኹና ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ግራው ፡ ከራሴ ፡ በታች ፡ ናት ፥ ቀኙም ፡ ታቅፈኛለች ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕሯት ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ እስኪፈልግ ፡ ድረስ ፥ ፍቅርን ፡ እንዳታስነሡትና ፡ እንዳታነሣሡት ፡ በሚዳቋ ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ ዋላ ፡ አምላችኋለኹ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ የውዴ ፡ ቃል! ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ሲዘል ፥ በኮረብታዎችም ፡ ላይ ፡ ሲወረወር ፡ ይመጣል ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ውዴ ፡ ሚዳቋን ፡ ወይም ፡ የዋላን ፡ እንቦሳ ፡ ይመስላል ፤ እንሆ ፥ በመስኮቶች ፡ ሲጐበኝ ፥ በዐይነ ፡ ርግብም ፡ ሲመለከት ፥ ርሱ ፡ ከቅጥራችን ፡ በኋላ ፡ ቆሟል ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ውዴ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ተነሺ ፤ ውበቴ ፡ ሆይ ፥ ነዪ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ ክረምት ፡ ዐለፈ ፥ ዝናቡም ፡ ዐልፎ ፡ ኼደ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ አበባዎች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተገለጡ ፥ የዜማም ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ፥ የቍርዬውም ፡ ቃል ፡ በምድራችን ፡ ተሰማ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ በለሱ ፡ ጐመራ ፥ ወይኖችም ፡ አበቡ ፡ መዐዛቸውንም ፡ ሰጡ ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ተነሺ ፤ ውበቴ ፡ ሆይ ፥ ነዪ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በአለት ፡ ንቃቃትና ፡ በገደል ፡ መሸሸጊያ ፡ ያለሽ ፡ ርግብ ፡ ሆይ ፥ ቃልሽ ፡ መልካም ፡ ፊትሽም ፡ ያማረ ፡ ነውና ፥ መልክሽን ፡ አሳዩኝ ፥ ድምፅሽንም ፡ አሰሚኝ ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ወይናችን ፡ አብቧልና ፥ የወይናችንን ፡ ቦታ ፡ የሚያጠፉትን ፡ ቀበሮዎች ፥ ጥቃቅኑን ፡ ቀበሮዎች ፡ አጥምዳችኹ ፡ ያዙልን ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ውዴ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ እኔም ፡ የርሱ ፡ ነኝ ፤ በሱፍ ፡ አበባዎች ፡ መካከልም ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራል ።

ማሕ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ውዴ ፡ ሆይ ፥ ቀኑ ፡ እስኪነፍስ ፥ ጥላውም ፡ እስኪሸሽ ፡ ድረስ ፡ ተመለስ ፤ በቅመም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሚዳቋውን ፡ ወይም ፡ የዋላውን ፡ እንቦሳ ፡ ምሰል ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ማሕ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ሌሊት ፡ በምንጣፌ ፡ ላይ ፡ ነፍሴ ፡ የወደደችውን ፡ ፈለግኹት ፤ ፈለግኹት ፡ አላገኘኹትም ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ እነሣለኹ ፡ በከተማዪቱም ፡ እዞራለኹ ፥ ነፍሴ ፡ የወደደችውን ፡ በጐዳናና ፡ በአደባባይ ፡ እፈልጋለኹ ፤ ፈለግኹት ፡ አላገኘኹትም ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ከተማዪቱን ፡ የሚዞሩት ፡ ጠባቂዎች ፡ አገኙኝ ፤ ነፍሴ ፡ የወደደችውን ፡ አያችኹትን ፧ አልኋቸውም ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብዬ ፡ ነፍሴ ፡ የወደደችውን ፡ አገኘኹት ፥ ያዝኹትም ፡ ወደእናቴም ፡ ቤት ፡ ወደወላጅ ፡ እናቴም ፡ ዕልፍኝ ፡ እስካገባው ፡ ድረስ ፡ አልተውኹትም ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕዥት ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ እስኪፈልግ ፡ ድረስ ፥ ፍቅርን ፡ እንዳታስነሡትና ፡ እንዳታነሣሡት ፡ በሚዳቋ ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ ዋላ ፡ አምላችኋለኹ ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ መዐዛም ፡ እንደ ፡ ከርቤና ፡ እንደ ፡ ዕጣን ፡ የኾነችው ፥ ከልዩ ፡ ከነጋዴ ፡ ቅመም ፡ ኹሉ ፡ የኾነችው ፥ ይህች ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ ምሰሶ ፡ የወጣችው ፡ ማን ፡ ናት ፧

ማሕ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ የሰሎሞን ፡ ዐልጋ ፡ ናት ፤ ከእስራኤል ፡ ኀያላን ፡ ስድሳ ፡ ኀያላን ፡ በዙሪያው ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ኹሉም ፡ ሰይፍ ፡ የያዙ ፡ ሰልፈኞች ፡ ናቸው ፤ በሌሊት ፡ ከሚወድቀው ፡ ፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሰይፉ ፡ በወገቡ ፡ አለ ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞን ፡ መሸከሚያን ፡ ከሊባኖስ ፡ ዕንጨት ፡ ለራሱ ፡ አሠራ ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ምሰሶዎቹን ፡ የብር ፥ መደገፊያውንም ፡ የወርቅ ፥ መቀመጫውንም ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ አደረገ ፤ ውስጡ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕዥት ፡ ፍቅር ፡ የተሰበጠ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ የጽዮን ፡ ቈነጕዥት ፥ ውጡ ፤ እናቱ ፡ በሰርጉ ፡ ቀንና ፡ በልቡ ፡ ደስታ ፡ ቀን ፡ ያደረገችለትን ፡ አክሊል ፡ ደፍቶ ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ እዩ ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ማሕ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ውብ ፡ ነሽ ፤ እንሆ ፥ አንቺ ፡ ውብ ፡ ነሽ ፤ በዐይነ ፡ ርግብ ፡ መሸፈኛሽ ፡ ውስጥ ፡ ዐይኖችሽ ፡ እንደ ፡ ርግቦች ፡ ናቸው ፤ ጠጕርሽ ፡ በገለዓድ ፡ ተራራ ፡ እንደሚወርድ ፡ እንደ ፡ ፍየል ፡ መንጋ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ጥርሶችሽ ፡ ታጥበው ፡ እንደ ፡ ተሸለቱ ፡ ኹሉም ፡ መንታ ፡ እንደ ፡ ወለዱ ፡ ከነርሱም ፡ መካን ፡ እንደሌለባቸው ፡ መንጋዎች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ከንፈሮችሽ ፡ እንደ ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ ፈትል ፡ ናቸው ፥ አፍሽም ፡ ያማረ ፡ ነው ፤ በዐይነ ፡ ርግብ ፡ መሸፈኛሽ ፡ ውስጥ ፡ ጕንጭና ፡ ጕንጭሽ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ ሮማን ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ዐንገትሽ ፡ ለሰልፍ ፡ ዕቃ ፡ መስቀያ ፡ እንደ ፡ ተሠራው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ግንብ ፡ ነው ፤ ሺሕ ፡ ጋሻ ፡ የኀያላንም ፡ መሣሪያ ፡ ኹሉ ፡ ተንጠልጥሎበታል ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ኹለቱ ፡ ጡቶችሽ ፡ መንታ ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፥ በሱፍ ፡ አበባ ፡ መካከል ፡ እንደሚሰማሩ ፡ እንደ ፡ ሚዳቋ ፡ ግልገሎች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ቀኑ ፡ እስኪነፍስ ፡ ጥላውም ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፥ ወደከርቤው ፡ ተራራ ፡ ወደዕጣኑም ፡ ኰረብታ ፡ እኼዳለኹ ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ኹለንተናሽ ፡ ውብ ፡ ነው ፥ ነውርም ፡ የለብሽም ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ሙሽራዬ ፡ ሆይ ፥ ከሊባኖስ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነዪ ፤ ከሊባኖስ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነዪ ፤ ከአማና ፡ ራስ ፡ ከሳኔርና ፡ ከኤርሞን ፡ ራስ ፥ ከአንበሳዎች ፡ መኖሪያ ፡ ከነብሮችም ፡ ተራራ ፡ ተመልከች ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እኅቴ ፡ ሙሽራ ፡ ሆይ ፥ ልቤን ፡ በደስታ ፡ አሳበድሽው ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በዐይኖችሽ ፥ ከዐንገትሽ ፡ ድሪ ፡ በአንዱ ፡ ልቤን ፡ በደስታ ፡ አሳበድሽው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ እኅቴ ፡ ሙሽራ ፡ ሆይ ፥ ፍቅርሽ ፡ እንዴት ፡ መልካም ፡ ነው! ፡ ፍቅርሽ ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ ይልቅ ፡ እንዴት ፡ ይሻላል! ፡ የዘይትሽም ፡ መዐዛ ፡ ከሽቱ ፡ ሹሉ! ፡

ማሕ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ሙሽራዬ ፡ ሆይ ፥ ከከንፈሮችሽ ፡ ማር ፡ ይንጠበጠባል ፤ ከምላስሽ ፡ በታች ፡ ማርና ፡ ወተት ፡ አለ ፥ የልብስሽም ፡ መዐዛ ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ሽታ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ እኅቴ ፡ ሙሽራ ፡ የተቈለፈ ፡ ገነት ፥ የተዘጋ ፡ ምንጭ ፡ የታተመም ፡ ፈሳሽ ፡ ናት ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ቡቃያሽ ፡ ሮማንና ፡ የተመረጠ ፡ ፍሬ ፥ ቆዕ ፡ ከናርዶስ ፡ ጋራ ፡ ያለበት ፡ ገነት ፡ ነው ፥

ማሕ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ናርዶስ ፡ ከቀጋ ፡ ጋራ ፥ የሽቱ ፡ ሣርና ፡ ቀረፋ ፥ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ዕጣን ፡ ጋራ ፥ ከርቤና ፡ ሬት ፡ ከክቡር ፡ ሽቱ ፡ ሹሉ ፡ ጋራ ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ አንቺ ፡ የገነት ፡ ምንጭ ፥ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ጕድጓድ ፥ ከሊባኖስም ፡ የሚፈሰ ፡ ወንዝ ፡ ነሽ ።

ማሕ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ የሰሜን ፡ ነፋስ ፡ ሆይ ፥ ተነሥ ፥ የደቡብም ፡ ነፋስ ፡ ና ፤ በገነቴ ፡ ላይ ፡ ንፈስ ፥ ሽቱውም ፡ ይፍሰስ ፤ ውዴ ፡ ወደ ፡ ገነቱ ፡ ይግባ ፥ መልካሙንም ፡ ፍሬ ፡ ይብላ ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ማሕ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ እኅቴ ፡ ሙሽራዬ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ገነቴ ፡ ገባኹ ፥ ከርቤዬን ፡ ከሽቱዬ ፡ ጋራ ፡ ለቀምኹ ፥ እንጀራዬን ፡ ከማሬ ፡ ጋራ ፡ በላኹ ፥ የወይን ፡ ጠጄን ፡ ከወተቴ ፡ ጋራ ፡ ጠጣኹ ። ባልንጀራዎቼ ፡ ሆይ ፥ ብሉ ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ጠጪ ፤ እስክትረኪ ፡ ድረስ ፡ ጠጪ ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ተኝቻለኹ ፥ ልቤ ፡ ግን ፡ ነቅቷል ፤ የውዴ ፡ ቃል ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ደጁን ፡ ይመታል ፤ እኅቴ ፥ ወዳጄ ፥ ርግቤ ፥ መደምደሚያዬ ፡ ሆይ ፥ በራሴ ፡ ጠል ፥ በቈንዳላዬም ፡ የሌሊት ፡ ነጠብጣብ ፡ ሞልቶበታልና ፥ ክፈቺልኝ ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ቀሚሴን ፡ አወለቅኹ ፤ እንዴት ፡ እለብሰዋለኹ ፧ እግሬን ፡ ታጠብኹ ፤ እንዴት ፡ አሳድፈዋለኹ ፧

ማሕ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ውዴ ፡ እጁን ፡ በቀዳዳ ፡ ሰደደ ፥ አንገቴም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ታወከ ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ለውዴ ፡ እከፍትለት ፡ ዘንድ ፡ ተነሣኹ ፤ እጆቼ ፡ በደጅ ፡ መወርወሪያ ፡ ላይ ፡ ከርቤን ፡ አፈሰሱ ፥ ጣቶቼ ፡ ፈሳሹን ፡ ከርቤ ፡ አንጠበጠቡ ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ለውዴ ፡ ከፈትኹለት ፥ ውዴ ፡ ግን ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ዐልፎ ፡ ነበር ። ነፍሴ ፡ ከቃሉ ፡ የተነሣ ፡ ደነገጠች ፤ ፈለግኹት ፥ አላገኘኹትም ፤ ጠራኹት ፥ አልመለሰልኝም ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ከተማዩቱን ፡ የሚዞሩት ፡ ጠባቂዎች ፡ አገኙኝ ፤ መቱኝ ፥ አቈሰሉኝም ፤ ቅጥር ፡ ጠባቂዎችም ፡ የዐይነ ፡ ርግብ ፡ መሸፈኛዬን ፡ ወሰዱት ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕዥት ፡ ሆይ ፥ አምላችኋለኹ ፤ ውዴን ፡ ያገኛችኹት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እኔ ፡ ከፍቅር ፡ የተነሣ ፡ መታመሜን ፡ ንገሩት ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ አንቺ ፡ በሴቶች ፡ ዘንድ ፡ የተዋብሽ ፡ ሆይ ፥ ከሌላ ፡ ወዳጅ ፡ ይልቅ ፡ ውድሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይህን ፡ የሚያኽል ፡ አምለሽናልና ፥ ከሌላ ፡ ወዳጅ ፡ ይልቅ ፡ ውድሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ማሕ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ውዴ ፡ ነጭና ፡ ቀይ ፡ ነው ፥ ከእልፍ ፡ የተመረጠ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ራሱ ፡ ምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ ነው ፤ ቈንዳላው ፡ የተዝረፈረፈ ፡ ነው ፥ እንደ ፡ ቀጐራ ፡ ጥቀጐረትም ፡ ጥቀጐር ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ዐይኖቹ ፡ በሙሉ ፡ ፈሳሽ ፡ አጠገብ ፡ እንዳሉ ፡ በወተት ፡ እንደ ፡ ታጠቡ ፡ በፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ተቀመጡ ፡ እንደ ፡ ርግቦች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ጕንጮችና ፡ ጕንጭ ፡ የሽቱ ፡ መደብ ፡ ዕርከን ፡ እንዳለበት ፡ እንደ ፡ ሽቱ ፡ አትክልት ፡ ናቸው ፤ ከንፈሮቹ ፡ እንደ ፡ አበባዎች ፡ ናቸው ፥ የሚፈስ ፡ ከርቤንም ፡ ያንጠበጥባሉ ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ እጆቹ ፡ የቢረሌ ፡ ፈርጥ ፡ እንዳለበት ፡ እንደ ፡ ወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ናቸው ፤ አካሉ ፡ ብልኀተኛ ፡ እንደ ፡ ሠራው ፡ በሰንፔር ፡ እንዳጌጠ ፡ እንደ ፡ ዝኖን ፡ ጥርስ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ እግሮቹ ፡ በምዝምዝ ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ ተመሠረቱ ፡ እንደ ፡ እብነ ፡ በረድ ፡ ምሰሶዎች ፡ ናቸው ፤ መልኩ ፡ እንደ ፡ ሊባኖስና ፡ እንደ ፡ ዝግባ ፡ ዛፍ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ አፉ ፡ እጅግ ፡ ጣፋጭ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ፈጽሞ ፡ ያማረ ፡ ነው ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕዥት ፡ ሆይ ፥ ውዴ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ባልንጀራዬም ፡ ይህ ፡ ነው ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ማሕ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ አንቺ ፡ በሴቶች ፡ ዘንድ ፡ የተዋብሽ ፡ ሆይ ፥ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ እንፈልገው ፡ ዘንድ ፡ ውድሽ ፡ ወዴት ፡ ኼደ ፧ ውድሽስ ፡ ወዴት ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፧

ማሕ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ውዴ ፡ በገነቱ ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራ ፡ ዘንድ ፡ አበባውንም ፡ ይሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ወደሽቱ ፡ መደብ ፡ ወደ ፡ ገነቱ ፡ ወረደ ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እኔ ፡ የውዴ ፡ ነኝ ፡ ውዴም ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ በሱፉ ፡ አበባ ፡ መካከል ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራል ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ቴርሳ ፡ ውብ ፡ ነሽ ፥ እንደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ያማርሽ ፡ ነሽ ፤ ዐላማ ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ተሰለፈ ፡ ሰራዊት ፡ ታስፈሪያለሽ ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ አውከውኛልና ፥ ዐይኖችሽን ፡ ከፊቴ ፡ መልሺ ፤ ጠጕርሽ ፡ ከገለዓድ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ እንደ ፡ ፍየል ፡ መንጋ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ጥርሶችሽ ፡ ታጥበው ፡ እንደወጡ ፡ ኹሉ ፡ መንታ ፡ እንደወለዱ ፡ ከነርሱም ፡ መካን ፡ እንደሌለባቸው ፡ መንጋዎች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ በዐይነ ፡ ርግብ ፡ መሸፈኛሽ ፡ ውስጥ ፡ ጕንጭና ፡ ጕንጭሽ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ ሮማን ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ስድሳ ፡ ንግሥታት ፣ ሰማንያም ፡ ቁባቶች ፣ ቍጥር ፡ የሌላቸውም ፡ ቈነጕዥት ፡ አሉ ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ርግቤ ፡ መደምደሚያዬም ፡ አንዲት ፡ ናት ፤ ለእናቷ ፡ አንዲት ፡ ናት ፥ ለወለደቻትም ፡ የተመረጠች ፡ ናት ። ቈነጕዥትም ፡ አይተው ፡ አሞገሷት ፥ ንግሥታትና ፡ ቁባቶችም ፡ አመሰገኗት ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ይህች ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ብርሃን ፡ የምትጐበኝ ፥ እንደ ፡ ጨረቃ ፡ የተዋበች ፥ እንደ ፡ ፀሓይም ፡ የጠራች ፥ ዐላማ ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ተሰለፈ ፡ ሰራዊት ፡ የምታስፈራ ፡ ማን ፡ ናት ፧

ማሕ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ የወንዙን ፡ ዳር ፡ ልምላሜ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፥ ወይኑ ፡ አብቦ ፣ ሮማኑም ፡ አፍርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡

እመለከት ፡ ዘንድ ፡ ወደገውዝ ፡ ገነት ፡ ወረድኩ ።

ማሕ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ሳላውቅ ፡ ነፍሴ ፡ በከበረው ፡ ሠረገላ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠችኝ ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ማሕ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ አንቺ ፡ ሱላማጢስ ፡ ሆይ ፡ ተመለሽ ፡ ተመለሽ ፤ እናይሽ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሽ ፡ ተመለሽ ። በሱላማጢስ ፡ ምን ፡ ታያላችኹ ፧ ርሷ ፡ እንደ ፡ መሃናይም ፡ ዘፈን ፡ ናት ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ አንቺ ፡ የመኰንን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ እግሮችሽ ፡ በጫማ ፡ ውስጥ ፡ እንዴት ፡ ውቦች ፡ ናቸው! ፡ ዳሌዎችሽስ ፡ በአንጥረኛ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተሠሩ ፡ እንደ ፡ ዕንቁዎች ፡ ይመስላሉ ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ዕንብርትሽ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንደማይጐድልበት ፡ እንደ ፡ ተነጠጠ ፡ ጽዋ ፡ ነው ፤ ሆድሽ ፡ እንደ ፡ ስንዴ ፡ ክምር ፡ በአበባም ፡ እንደ ፡ ታጠረ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ኹለቱ ፡ ጡቶችሽ ፡ እንደ ፡ ኹለቱ ፡ መንታ ፡ እንደ ፡ ሚዳቋ ፡ ግልገሎች ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ዐንገትሽ ፡ እንደ ፡ ዝኖን ፡ ጥርስ ፡ ግንብ ፡ ነው ፤ ዐይኖችሽ ፡ በሐሴቦን ፡ ውስጥ ፡ በባትረቢ ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ኩሬዎች ፡ ናቸው ፤ አፍንጫሽ ፡ ወደደማስቆ ፡ አፋዛኛ ፡ እንደሚመለከት ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ግንብ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ራስሽ ፡ እንደ ፡ ቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ በላይሽ ፡ ነው ፤ የራስሽም ፡ ጠጉር ፡ እንደ ፡ ሐምራዊ ፡ ሐር ፡ ነው ፤ ንጉሡ ፡ በሹርባው ፡ ታስሯል ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ እንዴት ፡ የተዋብሽ ፡ ነሽ! ፡ እንዴትስ ፡ ደስ ፡ ታሠኛለሽ! ፡

ማሕ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ይህ ፡ ቁመትሽ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ይመስላል ፡ ጡቶችሽም ፡ የወይን ፡ ዘለላ ፡ ይመስላሉ ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ወደዘንባባው ፡ ዛፍ ፡ እወጣለኹ ፡ ጫፎቹንም ፡ እይዛለኹ ፡ አልኹ ፤ ጡቶችሽ ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ዘለላ ፡ የአፍንጫሽም ፡ ሽቱ ፡ እንደ ፡ እንኮይ ፡ ናቸው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ጕረሮሽ ፡ ለወዳጄ ፡ እየጣፈጠ ፡ እንደሚገባ ፡ የተኙትን ፡ ከንፈሮች ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚያደርግ ፡ እንደ ፡ ማለፊያ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እኔ ፡ የውዴ ፡ ነኝ ፡ የርሱም ፡ ምኞት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ውዴ ፡ ሆይ ፡ ና ፡ ወደ ፡ መስክ ፡ እንውጣ ፡ በመንደሮችም ፡ እንደር ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ወደወይኑ ፡ ቦታ ፡ ማልደን ፡ እንኺድ ፤ ወይኑ ፡ አብቦ ፡ አበባውም ፡ ፍሬ ፡ አንዠርጎ ፡ ሮማኑም ፡ አፍርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንይ ፤ በዚያ ፡ ውዴን ፡ እሰጥኻለኹ ።

ማሕ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ትርንጎዎች ፡ መዐዛን ፡ ሰጡ ፤ መልካሞች ፡ ፍሬዎች ፡ ኹሉ ፡ አሮጌው ፡ ከዐዲሱ ፡ ጋራ ፡ በደጃችን ፡ አሉ ፤ ውዴ ፡ ሆይ ፡ ኹሉን ፡ ለአንተ ፡ ጠበቅኹልኽ ።

_____ማሕልየ ፡ መሓልይ ፡ ዘሰሎሞን ፡ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ማሕ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ አንተ ፡ የእናቴን ፡ ጡት ፡ እንደ ፡ ጠባ ፡ እንደ ፡ ወንድሜ ፡ ምነው ፡ በኾንኽ! ፡ በሜዳ ፡ ባገኘኹኽ ፡ ጊዜ ፡ በሳምኹኽ ፡ ማንም ፡ ባልናቀኝም ፡ ነበር ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ መርቼ ፡ ወደእናቴ ፡ ቤት ፡ ባገባኹኽ ፡ በዚያም ፡ አንተ ፡ ባስተማርከኝ ፤ እኔም ፡ ከመልካሙ ፡

ወይን ፡ ጠጅ ፡ ከሮማኔም ፡ ውሃ ፡ ባጠጣኹኽ ፡ ነበር ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ግራው ፡ ከራሴ ፡ በታች ፡ በኾነች ፡ ቀኙም ፡ ባቀፈችኝ ፡ ነበር ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቈነጕሮች ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ እስኪፈልግ ፡ ድረስ ፡ ፍቅርን ፡ እንዳታስነሡት ፡ እንዳታነሣሡትም ፡ አምላችኋለኹ ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ በውዷ ፡ ላይ ፡ ተደግፋ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ የምትወጣ ፡ ይህች ፡ ማን ፡ ናት ፧ ከእንኮይ ፡ በታች ፡ አስነሣኹኽ ፤ በዚያ ፡ እናትኽ ፡ ወለደችኽ ፥ በዚያም ፡ ወላጅ ፡ እናትኽ ፡ አማጠችኽ ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ማኅተም ፡ በልብኽ ፥ እንደ ፡ ማኅተም ፡ በክንድኽ ፡ አኑረኝ ፤ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ የበረታች ፡ ናትና ፥ ቅንአትም ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ የጨከነች ፡ ናትና ። ፍንጣሪዋ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ፍንጣሪ ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ነበልባል ፡ ነው ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ፍቅርን ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፥ ፈሳሾችም ፡ አያሰጥሟትም ፤ ሰው ፡ የቤቱን ፡ ሀብት ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ፍቅር ፡ ቢሰጥ ፡ ፈጽሞ ፡ ይንቁታል ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ እኛ ፡ ጡት ፡ የሌላት ፡ ታናሽ ፡ እኅት ፡ አለችን ፤ ስለ ፡ ርሷ ፡ በሚናገሩባት ፡ ቀን ፡ ለእኅታችን ፡ ምን ፡ እናድርግላት ፧

ማሕ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ርሷ ፡ ቅጥር ፡ ብትኾን ፡ የብር ፡ ግንብ ፡ በላይዋ ፡ እንሠራለን ፤ ደጅም ፡ ብትኾን ፡ በዝግባ ፡ ሳንቃ ፡ እንከባ፡ታለን ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ እኔ ፡ ቅጥር ፡ ነኝ ፡ ጡቶቼም ፡ እንደ ፡ ግንብ ፡ ናቸው ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ሰላምን ፡ እንደምታገኝ ፡ ኾንኩ ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ለሰሎሞን ፡ በብኤላሞን ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ፤ የወይኑን ፡ ቦታ ፡ ለጠባቂዎች ፡ አከራየው ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለፍሬው ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ያመጣለት ፡ ነበር ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ለእኔ ፡ ያለኝ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፤ ሰሎሞን ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ለአንተ ፥ ኹለት ፡ መቶውም ፡ ፍሬውን ፡ ለሚጠብቁ ፡ ይኾናል ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ በገነቱ ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ ባልንጀራዎች ፡ የአንቺን ፡ ቃል ፡ ያደምጣሉ ፤ ቃልሽን ፡ አሰሚኝ ።

ማሕ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ውዴ ፡ ሆይ ፥ ፍጠን ፤ በቅመም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሚዳቋን ፡ ወይም ፡ የዋላን ፡ እንቦሳ ፡ ምሰል ❖

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ በዖዝያንና ፡ በኢዮአታም ፡ በአካዝና ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ይሁዳና ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያየው ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ የኢሳይያስ ፡ ራእይ ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ ሰማያት ፡ ስሙ ፥ ምድርም ፡ አድምጪ ፤ ልጆችን ፡ ወለድኩ ፡ አሳደግኩም ፥ እነርሱም ፡ ዐመፁብኝ ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በሬ ፡ የገዢውን ፡ አህያም ፡ የጌታውን ፡ ጋጣ ፡ ዐወቀ ፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ አላወቀም ፥ ሕዝቤም ፡ አላስተዋለም ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ኀጢአተኛ ፡ ወገንና ፡ በደል ፡ የተሞላበት ፡ ሕዝብ ፥ የክፉዎች ፡ ዘር ፥ ርኵሰትን ፡ የምታደርጉ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ወዮላችኹ! ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተዋል ፡ የእስራኤልንም ፡ ቅዱስ ፡ አቃለዋል ፥ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ እየኼዱ ፡ ተለይተዋል ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ደግሞስ ፡ ዐመፃ ፡ እየጨመራችኹ ፡ ለምን ፡ ገና ፡ ትቀሰፋላችኹ ፧ ራስ ፡ ኹሉ ፡ ለሕመም ፥ ልብም ፡ ኹሉ ፡ ለድካም ፡ ኾኗል ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ከእግር ፡ ጫማ ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ራስ ፡ ድረስ ፡ ጤና ፡ የለውም ፤ ቍስልና ፡ ዕበጥ ፡ የሚመግልም ፡ ነው ፤ አልፈረጠም ፥ አልተጠገነም ፥ በዘይትም ፡ አልለዘበም ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ምድራችኹ ፡ ባድማ ፡ ናት ፤ ከተማዎቻችኹ ፡ በእሳት ፡ ተቃጠሉ ፤ ዕርሻችኹንም ፡ በፊታችኹ ፡ ሌላዎች ፡ ይበሉታል ፤ ባዕድ ፡ እንዳፈረሳት ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ ኾነች ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የጽዮንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በወይን ፡ ቦታ ፡ እንዳለ ፡ ዳስ ፥ በዱባ ፡ አትክልትም ፡ እንዳለ ፡ ጐጆ ፥ እንደ ፡ ተከበበችም ፡ ከተማ ፡ ኾና ፡ ቀረች ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘርን ፡ ባያስቀርልን ፡ ኖሮ ፥ እንደ ፡ ሰዶም ፡ በኾንን ፡ እንደ ፡ ገሞራም ፡ በመሰልን ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እናንተ ፡ የሰዶም ፡ አለቃዎች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እናንተ ፡ የገሞራ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ የአምላካችንን ፡ ሕግ ፡ አድምጡ ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የመሥዋዕታችኹ ፡ ብዛት ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡ ይጠቅመኛል ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የሚቃጠለውን ፡ የአውራ ፡ በግ ፡ መሥዋዕትንና ፡ የፍሪዳን ፡ ስብ ፡ ጠግቤያለኹ ፤ የበሬና ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ የአውራ ፡ ፍየልም ፡ ደም ፡ ደስ ፡ አያሠኘኝም ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በእኔ ፡ ፊት ፡ ልትታዩ ፡ ብትመጡ ፡ ይህን ፡ የመቅደሴን ፡ አደባባይ ፡ መርገጣችኹን ፡ ከእጃችኹ ፡ የሚሻ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ምናምንቴውን ፡ ቀርባን ፡ ጨምራችኹ ፡ አታምጡ ፤ ዕጣን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጸያፊ ፡ ነው ፤ መባቻችኹንና ፡ ሰንበታችኹን ፡ በጉባኤ ፡ መሰብሰባችኹን ፡ አልወድም ፤ በደልንም ፡ የተቀደሰውንም ፡ ጉባኤ ፡ አልታገሥም ።

ኢሳ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ መባቻችኹንና ፡ በዓላቶቻችኹን ፡ ነፍሴ ፡ ጠልታለች ፤ ሸክም ፡ ኾነውብኛል ፥ ልታገሣቸውም ፡

ደክሜያለኹ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ እጃችኹንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ብትዘረጉ ፡ ዐይኔን ፡ ከእናንተ ፡ እሰውራለኹ ፥ ልመናንም ፡ ብታበዙ ፡ አልሰማችኹም ፤ እጆቻችኹ ፡ ደም ፡ ተሞልተዋል ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ታጠቡ ፡ ሰውነታችኹንም ፡ አንጹ ፤ የሥራችኹን ፡ ክፋት ፡ ከዐይኔ ፡ ፊት ፡ አስወግዱ ፤ ክፉ ፡ ማድረግን ፡ ተዉ ፥

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ መልካም ፡ መሥራትን ፡ ተማሩ ፥ ፍርድን ፡ ፈልጉ ፥ የተገፋውን ፡ አድኑ ፥ ለድኻ ፡ አደጉ ፡ ፍረዱለት ፡ ስለ ፡ መበለቲቱም ፡ ተሟገቱ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ኑና ፡ እንዋቀሥ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ኀጢአታችኹ ፡ እንደ ፡ ዐለላ ፡ ብትኾን ፡ እንደ ፡ ዐመዳይ ፡ ትነጻለች ፤ እንደ ፡ ደምም ፡ ብትቀላ ፡ እንደ ፡ ባዘቶ ፡ ትጠራለች ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ዕሺ ፡ ብትሉ ፡ ለኔም ፡ ብትታዘዙ ፥ የምድርን ፡ በረከት ፡ ትበላላችኹ ፤

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እምቢ ፡ ብትሉ ፡ ግን ፡ ብታምፁም ፥ ሰይፍ ፡ ይበላችኋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ተናግሯልና ፦

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ፍርድ ፡ ሞልቶባት ፡ የነበረው ፡ የታመነችዪቱ ፡ ከተማ ፡ እንዴት ፡ ጋለሞታ ፡ ኾነች! ፡ ጽድቅ ፡ ዐድሮባት ፡ ነበር ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ገዳዮች ፡ አሉባት ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ብርሽ ፡ ወደ ፡ ዝገት ፡ ተለወጠ ፤ የወይን ፡ ጠጅሽ ፡ ከውሃ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቀ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ አለቃዎችሽ ፡ ዐመፀኞችና ፡ የሌቦች ፡ ባልንጀራዎች ፡ ኾኑ ፤ ኹሉ ፡ ጉቦ ፡ ይወዳሉ ፥ ዋጋም ፡ ለማግኘት ፡ ይሮጣሉ ፤ ለድኻ ፡ አደጉ ፡ አይፈርዱም ፥ የመበለቲቱም ፡ ሙግት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አይደርስም ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ ኀያል ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጠላቶቼ ፡ ላይ ፡ ቍጣዬን ፡ እፈጽማለኹ ፥ የሚቋቋሙኝንም ፡ እበቀላለኹ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ እጄንም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፥ ዝገትሽንም ፡ በጣም ፡ አነጻለኹ ፥ ቈርቈሮሽንም ፡ ኹሉ ፡ አወጣለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ፈራጆችሽንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ አማካሪዎችሽንም ፡ እንደ ፡ መገመሪያው ፡ ጊዜ ፡ መልሼ ፡ አስነሣለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የጽድቅ ፡ ከተማ ፡ የታመነችም ፡ ከተማ ፡ ተብለሽ ፡ ትጠሪያለሽ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ጽዮን ፡ በፍርድ ፡ ከርሷም ፡ የሚመለሱ ፡ በጽድቅ ፡ ይድናሉ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ በደለኞችና ፡ ኀጢአተኞች ፡ ግን ፡ በአንድነት ፡ ይሰበራሉ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ የሚተዉ ፡ ይጠፋሉ ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ በወደዳችኋት ፡ የአድባር ፡ ዛፍ ፡ ታፍራላችኹና ፥ ስለ ፡ መረጣችኋትም ፡ አትክልት ፡ ዕፍረት ፡ ይይዛችኋልና ፤

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ ቅጠሏ ፡ እንደ ፡ ረገፈ ፡ ዛፍ ፥ ውሃም ፡ እንደሌለባት ፡ አትክልት ፡ ትኾናላችኹና ።

ኢሳ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ ኀይለኛውም ፡ እንደ ፡ ተልባ ፡ ጢረት ፥ ሥራውም ፡ እንደ ፡ ጠለሽት ፡ ይኾናል ፤ ዐብረውም ፡ ይቃጠላሉ ፡ እነርሱንም ፡ የሚያጠፋ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ ይሁዳና ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያየው ፡ ቃል ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በዘመኑም ፡ ፍጻሜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተራራ ፡ በተራራዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ይቆማል ፥ ከኰረብታዎችም ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይሰበሰባሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ሕግ ፡ ከጽዮን ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይወጣልና ፥ ብዙዎች ፡ አሕዛብ ፡ ኼደው ፦ ኑ ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፥ ወደያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ቤት ፡ እንውጣ ፤ ርሱም ፡ መንገዱን ፡ ያስተምረናል ፥ በጐዳናውም ፡ እንኼዳለን ፡ ይላሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ይፈርዳል ፥ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ላይ ፡ ይበይናል ፤ ሰይፋቸውንም ፡ ማረሻ ፡ ጦራቸውንም ፡ ማጭድ ፡ ለማድረግ ፡ ይቀጠቅጣሉ ፤ ሕዝብም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሰይፍ ፡ አያነሣም ፥ ሰልፍም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይማሩም ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ኑ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ እንኺድ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ሕዝብኽን ፡ የያዕቆብን ፡ ቤት ፡ ትተኻልና ፤ ይኸውም ፡ የምሥራቅን ፡ ሰዎች ፡ ዐመል ፡ ስለ ፡ ተሞሉ ፥ እንደ ፡ ፍልስጥኤማውያንም ፡ ሟርተኞች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ ከባዕድ ፡ ልጆችም ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተባበሩ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ምድራቸው ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ተሞልታለች ፥ ለመዛግብቶቻቸውም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፤ ምድራቸውም ፡ ደግሞ ፡ በፈረሶች ፡ ተሞልታለች ፥ ለሠረገላዎቻቸውም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ምድራቸው ፡ ደግሞ ፡ በጣዖታት ፡ ተሞልታለች ፤ ጣቶቻቸውም ፡ ላደረጉት ፡ ለእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ይሰግዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ታናሹም ፡ ሰው ፡ ዝቅ ፡ ብሏል ፥ ጨዋውም ፡ ተዋርዷል ፤ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቅር ፡ አትበላቸው ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ማስደንገጥና ፡ ከግርማው ፡ ክብር ፡ የተነሣ ፡ ወደድንጋይ ፡ ዋሻ ፡ ግባ ፥ በመሬትም ፡ ውስጥ ፡ ተሸሸግ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ከፍ ፡ ያለችውም ፡ የሰው ፡ ዐይን ፡ ትዋረዳለች ፥ የሰዎችም ፡ ኵራት ፡ ትወድቃለች ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በትዕቢተኛውና ፡ በኵራተኛው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ ርሱም ፡ ይዋረዳል ፤

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ በረዥሙ ፡ ከፍ ፡ ባለው ፡ በሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በባሳንም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በረዥሙም ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ በረዥሙም ፡ ግንብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በተመሸገውም ፡ ቅጥር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ በተርሴስም ፡ መርከብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ በሚያማምሩ ፡ ጣዖታትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ይዋረዳል ፥ የሰውም ፡ ኵራት ፡ ይወድቃል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ጣዖቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፉሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድርን ፡ ያናውጥ ፡ ዘንድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፥ ሰዎች ፡ ከማስደንገጡና ፡ ከግርማው ፡ ክብሩ ፡ የተነሣ ፥ ወደድንጋይ ፡ ዋሻና ፡ ወደምድር ፡ ንቃቃት ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ይሰግድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ያበጃቸውን ፡ የብሩንና ፡ የወርቁን ፡ ጣዖቶቹን ፡ ለፍልፈልና ፡ ለሌሊት ፡ ወፍ ፡ ይጥላል ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ምድርን ፡ ያናውጥ ፡ ዘንድ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ከማስደንገጡና ፡ ከግርማው ፡ ክብር ፡ የተነሣ ፡ ወደድንጋይ ፡ ዋሻና ፡ ወደተሰነጠቁ ፡ አለቶች ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ።

ኢሳ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እስትንፋሱ ፡ በአፍንጫው ፡ ውስጥ ፡ ያለበትን ፡ ሰው ፡ ተዉት ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይቈጠራል ፧

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከይሁዳ ፡ ድጋፍንና ፡ ብርታትን ፥ የእንጀራን ፡ ድጋፍ ፡ ሹሉ ፡ የውሃውንም ፡ ድጋፍ ፡ ሹሉ ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ጎያሉንም ፥ ተዋጊውንም ፥ ፈራጁንም ፥ ነቢዩንም ፥ ሟርተኛውንም ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ሽማግሌውንም ፥ የዐምሳ ፡ አለቃውንም ፥ ከበርቴውንም ፥ አማካሪውንም ፥ ብልኁንም ፡ ሠራተኛ ፥ አስማት ፡ ዐዋቂውንም ፡ ይነቅላል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ አለቃዎቻቸው ፡ እንዲኾኑ ፡ ብላቴናዎችን ፡ አስነሣባቸዋለኹ ፥ ሕፃናትም ፡ ይገዟቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ሕዝቡም ፥ ሰው ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ሰውም ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፥ ይገፋፋል ፤ ብላቴናውም ፡ በሽማግሌው ፡ ላይ ፡ የተጠቃውም ፡ በከበርቴው ፡ ላይ ፡ ይኰራል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ሰውም ፡ በአባቱ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ ይዞ ፦ አንተ ፡ ልብስ ፡ አለኽ ፡ አለቃም ፡ ኹንልን ፡ ይሀችም ፡ ባድማ ፡ ከእጅኽ ፡ በታች ፡ ትኹን ፡ ሲለው ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፦ እኔ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ የለኝምና ፡ ባለመድኀኒት ፡ አልኾንም ፤ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ አለቃ ፡ አታደርጉኝም ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ የክብሩን ፡ ዐይን ፡ ያስቈጡ ፡ ዘንድ ፡ ምላሳቸውና ፡ ሥራቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ ኢየሩሳሌም ፡ ተፈታች ፥ ይሁዳም ፡ ወደቀ ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ የፊታቸውም ፡ ዕፍረት ፡ ይመሰክርባቸዋል ፤ እንደ ፡ ሰዶምም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ያወራሉ ፥ አይሰውሯትም ። በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ሠርተዋልና ፥ ለነፍሳቸው ፡ ወዮ! ፡

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ የሥራቸውን ፡ ፍሬ ፡ ይበላሉና ፡ ጻድቁን ፦ መልካም ፡ ይኾንልኻል ፡ በሉት ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እንደ ፡ እጁ ፡ ሥራ ፡ ፍዳው ፡ ይደረግበታልና ፥ ለበደለኛ ፡ ወዮ! ፡ ክፉም ፡ ደርሶበታል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ሕዝቤንስ ፡ አስገባሪዎቻቸው ፡ ይገፏቸዋል ፥ አስጨናቂዎችም ፡ ይሠለጥኑባቸዋል ። ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ የመሯችኹ ፡ ያስታችኻል ፡ የምትኼዱበትንም ፡ መንገድ ፡ ያጠፋሉ ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለፍርድ ፡ ተነሥቷል ፡ በሕዝቡም ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ ቆሟል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከአለቃዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳል ፤ የወይኑን ፡ ቦታ ፡ የጨረሳችኹ ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ፤ ከድኻዎች ፡ የበዘበዛችኹት ፡ በቤታችኹ ፡ አለ ፤

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ሕዝቤንም ፡ ለምን ፡ ታደቋቸዋላችኹ ፧ የድኻዎችንስ ፡ ፊት ፡ ለምን ፡ ትፈጫላችኹ ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የጽዮን ፡ ቈነጕዥት ፡ ከሦርተዋልና ፥ ዐንገታቸውንም ፡ እያሰገጉ ፡ በዐይናቸውም ፡ እያጣቀሱ ፥ ፈንጠርም ፡ እያሉ ፥ በእግራቸውም ፡ እያቃጨሉ ፡ ይኼዳሉና ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ የጽዮንን ፡ ቈነጕዥት ፡ ዐናት ፡ በቡሓነት ፡ ይመታል ፥ እግዚአብሔርም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋቸውን ፡ ይገልጣል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጌታ ፡ የእግር ፡ አልቦውን ፡ ክብር ፥ መርበብንም ፥ ጨረቃ ፡ የሚመስለውንም ፡ ጌጥ ፥ የጐሮ ፡ እንጥልጥሉንም ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ አንባሩንም ፥ መሸፈኛውንም ፥ ቀጸላውንም ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ሰንሰለቱንም ፥ መቀነቱንም ፥ የሽቱውንም ፡ ዕቃ ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ዐሸን ፡ ክታቡንም ፥ የእጅና ፡ የአፍንጫ ፡ ቀለበቱንም ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ የዓመት ፡ በዓልንም ፡ ልብስ ፥ መጐናጸፊያውንም ፥ ልግም ፡ በገላውንም ፥ ከረጢቱንም ፥

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ መስተዋቱንም ፥ ከጥሩ ፡ በፍታ ፡ የተሠራውንም ፡ ልብስ ፥ ራስ ፡ ማሰሪያውንም ፥ ዐይነ ፡ ርግቡንም ፡ ያስወግዳል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ በሽቱ ፡ ፋንታ ፡ ግማት ፥ በመታጠቂያውም ፡ ፋንታ ፡ ገመድ ፥ ጠጕርንም ፡ በመንቀስ ፡ ፋንታ ፡ ቡሓነት ፥ በመጐናጸፊያ ፡ ፋንታ ፡ ማቅ ፥ በውበትም ፡ ፋንታ ፡ ጠባሳ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ጕልማሳዎችሽ ፡ በሰይፍ ፥ ኀያላንሽም ፡ በውጊያ ፡ ይወድቃሉ ።

ኢሳ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ በሮቿ ፡ ያዝናሉ ፡ ያለቅሱማል ፤ ርሷም ፡ ብቻዋን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ትቀመጣለች ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ኢሳ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰባት ፡ ሴቶች ፦ የገዛ ፡ እንጀራችንን ፡ እንበላለን ፡ የገዛ ፡ ልብሳችንንም ፡ እንለብሳለን ፤ ስምኽ ፡ ብቻ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ይጠራ ፥ መሰደባችንንም ፡ አርቅ ፡ ብለው ፡ አንዱን ፡ ወንድ ፡ ይይዙታል ።

ኢሳ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጥቋጥ ፡ ለጌጥና ፡ ለክብር ፡ ይኾናል ፥ ከእስራኤልም ፡ ወገን ፡ ላመለጡ ፡ ሰዎች ፡ የምድሪቱን ፡ ፍሬ ፡ ለትምክሕትና ፡ ለውበት ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 4 ፡ 3-4 ፤ ጌታም ፡ የጽዮንን ፡ ቈነጕዥት ፡ እድፍ ፡ ባጠበ ፡ ጊዜ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ደም ፡ በፍርድ ፡ መንፈስና ፡ በሚያቃጥል ፡ መንፈስ ፡ ከመካከሷ ፡ ባነጻ ፡ ጊዜ ፥ በጽዮን ፡ የቀረ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የተረፈ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ለሕይወት ፡ የተጻፈ ፡ ኹሉ ፥ ቅዱስ ፡ ይባላል ።

ኢሳ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ ማደሪያ ፡ ኹሉ ፡ በጉባኤያቸውም ፡ ላይ ፡ በቀን ፡ ዳመናንና ፡ ጢስን ፡ በሌሊትም ፡ የሚቃጠለውን ፡ የእሳት ፡ ብርሃን ፡ ይፈጥራል ፤ በክብርም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መጋረጃ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በቀን ፡ ከሙቀት ፡ ለጥላ ፥ ከዐውሎ ፡ ነፋስና ፡ ከዝናብም ፡ ለመጠጊያና ፡ ለመሸሸጊያ ፡ ጐጆ ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 1 ፤ አኹን ፡ ስለ ፡ ወዳጄና ፡ ስለወይን ፡ ቦታው ፡ ለወዳጄ ፡ ቅኔ ፡ እቀኛለኹ ። ለወዳጄ ፡ በፍሬያማው ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ነበረው ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 2 ፤ በዙሪያው ፡ ቈፈረ ፥ ድንጋዮችንም ፡ ለቅሞ ፡ አወጣ ፥ ምርጥ ፡ የኾነውንም ፡ ዐረግ ፡ ተከለበት ፥ በመካከሉም ፡ ግንብ ፡ ሠራ ፥ ደግሞም ፡ የመጥመቂያ ፡ ጉድጓድ ፡ ማሰበት ፤ ወይንንም ፡ ያፈራ ፡ ዘንድ ፡ ተማመነ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሐምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 3 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ በእኔና ፡ በወይኑ ፡ ቦታዬ ፡ መካከል ፡ እስኪ ፡ ፍረዱ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ ለወይኔ ፡ ያላደረግኹለት ፥ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወይንን ፡ ያፈራል ፡ ብዬ ፡ ስተማመን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሐምጣጣ ፡ ፍሬ ፡ አፈራ ፧

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ አኹንም ፡ በወይኔ ፡ ላይ ፡ የማደርገውን ፡ እነግራችኋለኹ ፤ ዐጥሩን ፡ እነቅላለኹ ፥ ለማሰማሪያም ፡ ይኾናል ፤ ቅጥሩንም ፡ አፈርሳለኹ ፥ ለመራገጫም ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ ባድማ ፡ አደርገዋለኹ ፤ አይቈረጥም ፥ አይኰተኰትም ፤ ኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ ይበቅልበታል ፤ ዝናብንም ፡ እንዳያዘንቡበት ፡ ዳመናዎችን ፡ አዛለኹ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወይን ፡ ቦታ ፡ ርሱ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ነው ፥ የደስታውም ፡ አትክልት ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ ፍርድን ፡ ተስፋ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፥ እንሆም ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ኾነ ፤ ጽድቅንም ፡ ይተማመን ፡ ነበር ፥ እንሆም ፥ ጩኸት ፡ ኾነ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ ስፍራ ፡ እስከማይቀር ፡ ድረስ ፡ እናንተም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ብቻችኹን ፡ እስክትቀመጡ ፡ ድረስ ፥ ቤትን ፡ ከቤት ፡ ጋራ ፡ ለሚያያይዙ ፡ ዕርሻንም ፡ ከዕርሻ ፡ ጋራ ፡ ለሚያቀራርቡ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጐሮዬ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ብዙ ፡ ታላቅና ፡ መልካም ፡ ቤት ፡ ባድማ ፡ ይኾናል ፥ የሚቀመጥበትም ፡ አይገኝም ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 10 ፤ ከወይኑ ፡ ቦታ ፡ ዐሥር ፡ ጥማድ ፡ በሬ ፡ ካረሰው ፡ አንድ ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ይወጣል ፤ አንድ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዘር ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ይሰጣል ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ ስካርን ፡ ለመከተል ፡ በጧት ፡ ለሚማልዱ ፥ የወይን ፡ ጠጅም ፡ እስኪያቃጥላቸው ፡ እስከ ፡ ሌሊት ፡ ድረስ ፡ ለሚዘገዩ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 12 ፤ መሰንቆና ፡ በገና ፡ ከበሮና ፡ እንቢልታም ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ በግብዣቸው ፡ አለ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ግን ፡ አልተመለከቱም ፥ እጁም ፡ ያደረገችውን ፡ አላስተዋሉም ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ሕዝቤ ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ኼዱ ፥ ጌታን ፡ አላወቁትምና ፤ ከበርቴዎቻቸውም ፡ ተራቡ ፥ ሕዝባቸውም ፡ ተጠሙ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 14 ፤ ሲኦልም ፡ ሆዷን ፡ አስፍታለች ፥ አፏንም ፡ ያለልክ ፡ ከፍታለች ፤ ከበርቴዎቻቸውና ፡ ዐዛውንቶቻቸው ፡ ባለጠጋዎቻቸውም ፡ ደስተኞቻቸውም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ይወርዳሉ ።

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 15 ፤ ሰውም ፡ ይጐሰቍላል ፥ ሰውም ፡ ይዋረዳል ፥ የትዕቢተኞችም ፡ ዐይን ፡ ትዋረዳለች ፤

ኢሳ. ፥ 5 ፥ 16 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በፍርድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ፥ ቅዱሱም ፡ አምላክ ፡

በጽድቅ ፡ ተቀድሷል ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ በማሰማሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ ይሰማራሉ ፥ እንግዳዎችም ፡ የሰቡትን ፡ ባድማ ፡ ይበላሉ ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ በደልን ፡ በምናምንቴ ፡ ገመድ ፥ ኀጢአትንም ፡ በሠረገላ ፡ ማሰሪያ ፡ ወደ ፡ ራሳቸው ፡ ለሚስቡ ፡— እናይ ፡ ዘንድ ፡ ይቸኵል ፥

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ሥራውንም ፡ ያፋጥን ፤ እናውቃትም ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ምክር ፡ ትቅረብ ፥ ትምጣ ፡ ለሚሉ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ክፉውን ፡ መልካም ፡ መልካሙን ፡ ክፉ ፡ ለሚሉ ፥ ጨለማውን ፡ ብርሃን ፡ ብርሃኑንም ፡ ጨለማ ፡ ለሚያደርጉ ፥ ጣፋጩን ፡ መራራ ፡ መራራውንም ፡ ጣፋጭ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ በዐይናቸው ፡ ጥበበኞች ፡ በነፍሳቸውም ፡ አስተዋዮች ፡ ለኾኑ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጣት ፡ ኀያላን ፡ የሚያሰክረውንም ፡ ለማደባለቅ ፡ ጨካኞች ፡ ለኾኑ ፤

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ በደለኛውን ፡ ስለ ፡ ጉቦ ፡ ጻድቅ ፡ ለሚያደርጉ ፥ የጻድቁንም ፡ ጽድቅ ፡ ለሚያስወግዱበት ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ቃርሚያን ፡ እንደሚበላ ፥ እብቅም ፡ በነበልባል ፡ ውስጥ ፡ እንደሚጠፋ ፥ እንዲሁ ፡ የእነርሱ ፡ ሥር ፡ የበሰበሰ ፡ ይኾናል ፥ ቡቃያቸውም ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ ይበናል ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ጥለዋልና ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አቃለዋልና ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በሕዝቡ ፡ ላይ ፡ ነዷል ፥ እጁንም ፡ በላያቸው ፡ ዘርግቶ ፡ መትቷቸዋል ፤ ተራራዎችም ፡ ተንቀጠቀጡ ፥ ሬሳቸውም ፡ በአደባባይ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ኾኗል ። በዚህም ፡ ሹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ለአሕዛብም ፡ በሩቅ ፡ ምልክትን ፡ ያቆማል ፥ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ በፉጨት ፡ ይጠራቸዋል ፤ እንሆም ፥ እየተጣደፉ ፡ ፈጥነው ፡ ይመጣሉ ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ደካማና ፡ ስንኩል ፡ የለባቸውም ፥ የሚያንቀላፋና ፡ የሚተኛም ፡ የለም ፤ የወገባቸውም ፡ መቀነት ፡ አይፈታም ፥ የጫማቸውም ፡ ማዘቢያ ፡ አይበጠስም ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ፍላጻዎቻቸው ፡ ተስለዋል ፥ ቀስቶቻቸውም ፡ ሹሉ ፡ ተለጥጠዋል ፤ የፈረሶቻቸውም ፡ ኰቴ ፡ እንደ ፡ ቡላድ ፡ የሠረገላዎቻቸውም ፡ መንኰራኵር ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይቈጠራል ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ጩኸታቸው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ነው ፥ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦሎችም ፡ ያገሣሉ ፤ ንጥቂያንም ፡ ይዘው ፡ ያገሣሉ ፥ ይወስዱትማል ፥ የሚያድንም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ መትመም ፡ ይተምሙባቸዋል ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ ቢመለከቱ ፥ እንሆ ፥ ጨለማና ፡ መከራ ፡ አለ ፤ ብርሃንም ፡ በደመናዎቿ ፡ ውስጥ ፡ ጨልሟል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ኢሳ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ንጉሡ ፡ ዖዝያን ፡ በሞተበት ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔርን ፡ በረዥምና ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ አየኹት ፥ የልብሱም ፡ ዘርፍ ፡ መቅደሱን ፡ ሞልቶት ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ሱራፌልም ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ ለያንዳንዱም ፡ ስድስት ፡ ክንፍ ፡

ነበረው ፤ በኹለት ፡ ክንፍ ፡ ፊቱን ፡ ይሸፍን ፡ ነበር ፥ በኹለቱም ፡ ክንፍ ፡ እግሮቹን ፡ ይሸፍን ፡ ነበር ፥ በኹለቱም ፡ ክንፍ ፡ ይበር ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ አንዱም ፡ ለአንዱ ፦ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ከክብሩ ፡ ተሞልታለች ፡ እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ የመድረኩም ፡ መሠረት ፡ ከጫኺው ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ተናወጠ ፥ ቤቱንም ፡ ጢስ ፡ ሞላበት ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ እኔም ፦ ከንፈሮቼ ፡ የረከሱብኝ ፡ ሰው ፡ በመኾኔ ፥ ከንፈሮቻቸውም ፡ በረከሱባቸው ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ በመቀመጤ ፡ ዐይኖቼ ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ ንጉሡን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ አዩ ፡ ጠፍቻለኹና ፡ ወዮልኝ! ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ ከሱራፌልም ፡ አንዱ ፡ እየበረረ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፥ በእጁም ፡ ከመሠዊያው ፡ በጕጠት ፡ የወሰደው ፡ ፍም ፡ ነበረ ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ አፌንም ፡ ዳሰሰበትና ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ከንፈሮችኽን ፡ ነክቷል ፤ በደልኽም ፡ ከአንተ ፡ ተወገደ ፥ ኀጢአትኽም ፡ ተሰረየልኽ ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ የጌታንም ፡ ድምፅ ፦ ማንን ፡ እልካለኹ ፧ ማንስ ፡ ይኼድልናል ፧ ሲል ፡ ሰማኹ ። እኔም ፦ እንሆኝ ፥ እኔን ፡ ላከኝ ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ ርሱም ፦ ኺድ ፥ ይህን ፡ ሕዝብ ፦ መስማትን ፡ ትሰማላችኹ ፡ አታስተውሉምም ፤ ማየትንም ፡ ታያላችኹ ፡ አትመለከቱምም ፡ በላቸው ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ በዐይናቸው ፡ እንዳያዩ ፥ በጆሯቸውም ፡ እንዳይሰሙ ፥ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፥ ተመልሰውም ፡ እንዳይፈወሱ ፥ የዚህን ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ አደንድን ፥ ጆሯቸውንም ፡ አደንቀር ፥ ዐይናቸውንም ፡ ጨፍን ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፧ አልኹ ። ርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ከተማዎች ፡ የሚኖርባቸውን ፡ ዐጥተው ፡ እስኪፈርሱ ፡ ድረስ ፥ ቤቶችም ፡ ሰው ፡ አልቦ ፡ እስኪኾኑ ፡ ምድርም ፡ ፈጽሞ ፡ ባድማ ፡ ኾና ፡ እስክትቀር ፡ ድረስ ፥

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰዎችን ፡ እስኪያርቅ ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ ውድማው ፡ መሬት ፡ እስኪበዛ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ በርሷም ፡ ዘንድ ፡ ዐሥረኛ ፡ እጅ ፡ ቀርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይቃጠላል ፤ በተቈረጡ ፡ ጊዜ ፡ ጕቶቻቸው ፡ እንደ ፡ ቀሩ ፡ እንደ ፡ ግራርና ፡ እንደ ፡ ኮምበል ፡ ዛፍ ፡ ኾኖ ፥ ጕቶው ፡ የተቀደሰ ፡ ዘር ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ኢሳ. ፥ 7 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ ልጅ ፡ በኢዮአታም ፡ ልጅ ፡ በአካዝ ፡ ዘመን ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ረአሶን ፡ የእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ፋቁሔ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ሊወጉ ፡ ወጡ ፥ ሊያሸንፏትም ፡ አልቻሉም ።

ኢሳ. ፥ 7 ፥ 2 ፤ ለዳዊትም ፡ ቤት ፦ ሶርያ ፡ ከኤፍሬም ፡ ጋራ ፡ ተባብረዋል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ተነገረ ፤ የርሱም ፡ ልብ ፡ የሕዝቡም ፡ ልብ ፡ የዱር ፡ ዛፍ ፡ በነፋስ ፡ እንድትናወጥ ፡ ተናወጠ ።

ኢሳ. ፥ 7 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኢሳይያስን ፡ አለው ፦ አንተና ፡ ልጅኽ ፡ ያሱብ ፡ አካዝን ፡ ትገናኙት ፡ ዘንድ ፡ በልብስ ፡ ዐጣቢው ፡ ዕርሻ ፡ መንገድ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ የኩሬ ፡ መስኖ ፡ ጫፍ ፡ ውጡ ፤

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ ተጠበቅ ፥ ዝምም ፡ በል ፤ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ስለሚጤሱ ፡ ስለ ፡ ኹለት ፡ የዕንጨት ፡ ጠለሸቶች ፥ ስለ ፡ ሶርያና ፡ ስለ ፡ ረአሶን ፡ ስለ ፡ ሮሜልዩም ፡ ልጅ ፡ ቍጣ ፡ አትፍራ ፥ ልብኽም ፡ አይድከም ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 5-6 ፤ ሶርያና ፡ ኤፍሬም ፤ የሮሜልዩም ፡ ልጅ ፦ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ እንውጣ ፡ እናስጨንቀውም ፥ እንስበረውም ፥ የጣብኤልንም ፡ ልጅ ፡ እናንግሥበት ፡ ብለው ፡ ክፋት ፡ ስለ ፡ መከሩብኽ ፤

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ምክር ፡ አይጸናምና ፥ አይኾንም ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የሶርያ ፡ ራስ ፡ ደማስቆ ፡ ነው ፥ የደማስቆም ፡ ራስ ፡ ረአሶን ፡ ነው ፤ በስድሳ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ኤፍሬም ፡ ይሰባበራልና ፥ ሕዝብ ፡ አይኾንም ፤

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ የኤፍሬምም ፡ ራስ ፡ ሰማርያ ፡ ነው ፥ የሰማርያም ፡ ራስ ፡ የሮሜልዩ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ባታምኑ ፡ አትጸኑም ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ አካዝን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ፦

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ከጥልቁ ፡ ወይም ፡ ከከፍታው ፡ ቢኾን ፡ ከአምላክኽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምልክትን ፡ ለምን ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ አካዝም ፦ አልለምንም ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አልፈታተንም ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ስሙ ፤ በእውኑ ፡ ሰውን ፡ ማድከማችኹ ፡ ቀላል ፡ ነውን ፧ አምላኬን ፡ ደግሞ ፡ የምታደክሙ ፤

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ ራሱ ፡ ምልክት ፡ ይሰጣችኋል ፤ እንሆ ፥ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልዳለች ፥ ስሙንም ፡ ዐማኑኤል (264) ፡ ብላ ፡ ትጠራዋለች ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ክፉን ፡ ለመጥላት ፡ መልካሙንም ፡ ለመምረጥ ፡ ሲያውቅ ፡ ቅቤና ፡ ማር ፡ ይበላል ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ሕፃኑ ፡ ክፉን ፡ ለመጥላት ፡ መልካሙን ፡ ለመምረጥ ፡ ሳያውቅ ፡ የፈራኻቸው ፡ የኹለቱ ፡ ነገሥታት ፡ አገር ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ኤፍሬም ፡ ከይሁዳ ፡ ከተለየበት ፡ ቀን ፡ ገምሮ ፡ ያልመጣውን ፡ ዘመን ፡ በአንተና ፡ በሕዝብኽ ፡ በአባትኽም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ ያመጣል ፤ ርሱም ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ መምጣት ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ዳርቻ ፡ ያለውን ፡ ዝምብ ፡ በአሶርም ፡ አገር ፡ ያለውን ፡ ንብ ፡ በፉጨት ፡ ይጠራል ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ይመጡማል ፥ እነርሱም ፡ ኹሉ ፡ በበረሓ ፡ ሸለቆ ፡ በድንጋይም ፡ ዋሻ ፡ ውስጥ ፡ በሾኽ ፡ ቍጥቋጦ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በማሰማሪያውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሰፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከወንዙ ፡ ማዶ ፡ በተከራየው ፡ ምላጭ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የራሱንና ፡ የእግሩን ፡ ጠጉር ፡ ይላጨዋል ፤ ምላጩም ፡ ጢሙን ፡ ደግሞ ፡ ይበላል ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ሰው ፡ አንዲት ፡ ጊደርን ፡ ኹለት ፡ በጎችንም ፡ ያሳድጋል ፤

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ከሚሰጡት ፡ ወተት ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቅቤ ፡ ይበላል ፤ በአገሪቱም ፡ መካከል ፡ የቀረ ፡ ኹሉ ፡ ቅቤና ፡ ማር ፡ ይበላል ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ሺሕ ፡ ብር ፡ የተገመተ ፡ ሺሕ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ በነበረበት ፡

---

264 ዕብ. ፥ ዒማኑኤል ፡ (አምላክ ፡ ምስሌነ • አምላክ ፡ ከኛ ፡ ጋራ) ።

ስፍራ ፡ ዥሉ ፡ ለኵርንችትና ፡ ለሾኽ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ በምድር ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ በፍላጻና ፡ በቀስት ፡ ወደዚያ ፡ ይገባሉ ።

ኢሳ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ በመቈፈሪያም ፡ ወደተቈፈሩ ፡ ኰረብታዎች ፡ ዥሉ ፡ ከኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ ፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ወደዚያ ፡ አትኼድም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የበሬ ፡ ማሰማሪያና ፡ የበግ ፡ መራገጫ ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ታላቅ ፡ ሰሌዳ ፡ ወስደኽ ፦ ምርኮ ፡ ፈጠነ ፥ ብዝበዛ ፡ ቸኰለ ፡ ብለኽ ፡ በሰው ፡ ፊደል ፡ ጻፍበት ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ የታመኑትን ፡ ሰዎች ፡ ካህኑን ፡ ኦርዮንና ፡ የበራክዩን ፡ ልጅ ፡ ዘካርያስን ፡ ምስክሮች ፡ አድርግልኝ ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ ነቢዩቱም ፡ ቀረብኹ ፤ ርሷም ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሕፃኑ ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ መጥራት ፡ ሳያውቅ ፡ የደማስቆን ፡ ሀብትና ፡ የሰማርያን ፡ ምርኮ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ ይወስዳልና ፥ ስሙን ፦ ምርኮ ፡ ፈጠነ ፥ ብዝበዛ ፡ ቸኰለ ፡ ብለኽ ፡ ጥራው ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ተናገረኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በቀስታ ፡ የሚኼደውን ፡ የሰሊሖምን ፡ ውሃ ፡ ጠልቷልና ፥ ረአሶንንና ፡ የሮሜልዩንም ፡ ልጅ ፡ ወዷልና ፥ ስለዚህ ፥

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ብርቱና ፡ ብዙ ፡ የኾነውን ፡ የወንዝ ፡ ውሃ ፥ የአሶርን ፡ ንጉሥና ፡ ክብሩን ፡ ዥሉ ፥ ያመጣባቸዋል ፤ መስኖውንም ፡ ዥሉ ፡ ሞልቶ ፡ ይወጣል ፥ በዳሩም ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ፤

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ እየጐረፈም ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ይገባል ፤ እያጥለቀለቀም ፡ ያልፋል ፥ እስከ ፡ ዐንገትም ፡ ይደርሳል ፤ ዐማኑኤል ፡ ሆይ ፥ የክንፉ ፡ መዘርጋት ፡ የአገርኽን ፡ ስፋት ፡ ትሞላለች ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ዕወቁና ፡ ደንግጡ ፤ እናንተም ፡ ምድራችኹ ፡ የራቀ ፡ ዥሉ ፥ አድምጡ ፤ ታጠቁም ፥ ደንግጡ ፤ ታጠቁ ፤ ደንግጡ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ተመካከሩ ፥ ምክራችኹም ፡ ይፈታል ፤ ቃሉን ፡ ተናገሩ ፥ ቃሉም ፡ አይጸናም ፤ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነውና ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽኑ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ተናገረኝ ፥ በዚህም ፡ ሕዝብ ፡ መንገድ ፡ አንዳልኼድ ፡ አስጠነቀቀኝ ፥ እንዲህም ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ ዱለት ፡ ነው ፡ በሚሉት ፡ ዥሉ ፦ ዱለት ፡ ነው ፡ አትበሉ ፤ መፈራታቸውንም ፡ አትፍሩ ፥ አትደንግጡ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቀድሱት ፤ የሚያስፈራችኹና ፡ የሚያስደነግጣችኹም ፡ ርሱ ፡ ይኹን ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ርሱም ፡ ለመቅደስ ፡ ይኾናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለኹለቱ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤቶች ፡ ለዕንቅፋት ፡ ድንጋይና ፡ ለማሰናከያ ፡ አለት ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለወጥመድና ፡ ለአሽክላ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ብዙዎችም ፡ በርሱ ፡ ይሰናከላሉ ፥ ይወድቁማል ፥ ይሰበሩማል ፥ ይጠመዱማል ፥ ይያዙማል ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ ምስክሩን ፡ እሰር ፤ በደቀ ፡ መዛሙርቴም ፡ መካከል ፡ ሕጉን ፡ ዐትም ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ፊቱን ፡ የመለሰውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጠብቃለኹ ፥ እተማመንበትማለኹ ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ እኔና ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝ ፡ ልጆች ፡ ለእስራኤል ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ከሚኖረው ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክትና ፡ ተአምራት ፡ ነን ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፦ የሚጮኹትንና ፡ ድምፃቸውን ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ የሚናገሩትን ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎችንና ፡ ጠንቋዮችን ፡ ጠይቁ ፡ ባሏችኹ ፡ ጊዜ ፥ ሕዝቡ ፡ ከአምላኩ ፡ መጠየቅ ፡ አይገባውምን ፧ ወይስ ፡ ለሕያዋን ፡ ሲሉ ፡ ሙታንን ፡ ይጠይቃሉን ፧

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ሕግና ፡ ወደ ፡ ምስክር ፡ ኺዱ! ፡ እንዲህም ፡ ያለውን ፡ ቃል ፡ ባይናገሩ ፡ ንጋት ፡ አይበራላቸውም ።

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ተጨንቀውና ፡ ተርበው ፡ ያልፋሉ ፤ በተራቡም ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥተው ፡ ንጉሣቸውንና ፡ አምላካቸውን ፡ ይረግማሉ ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ይመለከታሉ ፤

ኢሳ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ ይመለከታሉ ፥ እንሆም ፥ መከራና ፡ ጨለማ ፡ የሚያስጨንቅም ፡ ጭጋግ ፡ አለ ፤ ወደ ፡ ድቅድቅም ፡ ጨለማ ፡ ይሰደዳሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተጨንቃ ፡ ለነበረች ፡ ጨለማ ፡ አይኾንም ። በመገሥመሪያው ፡ ዘመን ፡ የዛብሎንንና ፡ የንፍታሌምን ፡ ምድር ፡ አቃለለ ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በባሕር ፡ መንገድ ፡ ያለውን ፡ የአሕዛብን ፡ ገሊላ ፡ ያከብራል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ በጨለማ ፡ የኼደ ፡ ሕዝብ ፡ ብርሃን ፡ አየ ፤ በሞት ፡ ጥላ ፡ አገርም ፡ ለኖሩ ፡ ብርሃን ፡ ወጣላቸው ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ሕዝብን ፡ አብዝተኻል ፥ ደስታንም ፡ ጨምረኽላቸዋል ፤ በመከር ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፥ ሰዎችም ፡ ምርኮን ፡ ሲካፈሉ ፡ ደስ ፡ እንደሚላቸው ፡ በፊትኽ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ በምድያም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሸክሙን ፡ ቀንበር ፡ የጫንቃውንም ፡ በትር ፡ የአስጨናቂውንም ፡ ዘንግ ፡ ሰብረኻል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ የሚረግጡ ፡ የሰልፈኞች ፡ ጫማ ፡ ኹሉ ፥ በደምም ፡ የተለወሰ ፡ ልብስ ፡ ለቃጠሎ ፡ ይኾናል ፥ እንደ ፡ እሳት ፡ ማቃጠያም ፡ ኾኖ ፡ ይቃጠላል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ሕፃን ፡ ተወልዶልናልና ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ተሰጥቶናልና ፤ አለቅነትም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ስሙም ፡ ድንቅ ፡ መካር ፥ ኀያል ፡ አምላክ ፥ የዘለዓለም ፡ አባት ፥ የሰላም ፡ አለቃ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ በፍርድና ፡ በጽድቅ ፡ ያጸናውና ፡ ይደግፈው ፡ ዘንድ ፡ በዳዊት ፡ ዙፋንና ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ አለቅነቱ ፡ ይበዛል ፥ ለሰላሙም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ። የእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ ይህን ፡ ያደርጋል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ጌታ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ቃልን ፡ ሰደደ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ 10 ፤ በትዕቢትና ፡ በልብ ፡ ኵራት ፦ ጡቡ ፡ ወድቋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በተወቀረ ፡ ድንጋይ ፡ እንሠራለን ፤ የሾላ ፡ ዛፎች ፡ ተቈርጠዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዝግባን ፡ እንተካባቸዋለን ፡ የሚሉ ፡ በኤፍሬምና ፡ በሰማርያ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ያውቃሉ ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ተቋቋሚ ፡ ያስነሣበታል ፥

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ጠላቶቹን ፡ ሶርያውያንንም ፡ ከምሥራቅ ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ ከምዕራብ ፡ ያንቀሳቅስበታል ፤ እስራኤልንም ፡ በተከፈተ ፡ አፍ ፡ ይበሉታል ። በዚህም ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ወደቀሠፋቸው ፡ አልተመለሱም ፥ የሰራዊትንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልፈለጉም ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ራስና ፡ ኻራትን ፥ የሰሌኑን ፡ ቅርንጫፍና ፡ እንግጫውን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ከእስራኤል ፡ ይቈርጣል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ሽማግሌውና ፡ ከበርቴው ፡ ርሱ ፡ ራስ ፡ ነው ፤ በሐሰትም ፡ የሚያስተምር ፡ ነቢይ ፡ ርሱ ፡ ኻራት ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ የሚመሩ ፡ ያስቷቸዋል ፤ ተመሪዎቹም ፡ ይጠፋሉ ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዝንጉና ፡ ክፉ ፡ ሠሪ ፡ ነውና ፥ አፍም ፡ ኹሉ ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራልና ፥ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ በጕልማሳዎቻቸው ፡ ደስ ፡ አይለውም ፥ ለድኻ ፡ አደጎቻቸውና ፡ ለመበለቶቻቸውም ፡ አይራራም ። በዚህም ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ክፋት ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይቃጠላል ፤ ኵርንችቱንና ፡ ሾኹን ፡ ይበላል ፤ ጭፍቅ ፡ የኾነውንም ፡ ዱር ፡ ያቃጥላል ፥ ጢሱም ፡ ተትጐልጕሎ ፡ እንደ ፡ ዐምድ ፡ ይወጣል ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ምድር ፡ ተቃጥላለች ፤ ሕዝቡም ፡ እሳት ፡ እንደሚበላው ፡ ዕንጨት ፡ ኾኗል ፤ ሰውም ፡ ለወንድሙ ፡ አይራራም ።

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ሰው ፡ በቀኙ ፡ በኩል ፡ ይነቅላል ፡ ይራብማል ፤ በግራም ፡ በኩል ፡ ይበላል ፡ አይጠግብምም ፤ እያንዳንዱም ፡ የክንዱን ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፤

ኢሳ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ምናሴ ፡ ኤፍሬምን ፡ ኤፍሬምም ፡ ምናሴን ፡ ይበላል ፤ እነርሱ ፡ በአንድነት ፡ የይሁዳ ፡ ጠላቶች ፡ ይኾናሉ ። በዚህም ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 1-2 ፤ መበለቶችም ፡ ቅሚያቸው ፡ እንዲኾኑ ፥ ድኻ ፡ አደጎችንም ፡ ብዝበዛቸው ፡ እንዲያደርጉ ፥ የድኻውን ፡ ፍርድ ፡ ያጣምሙ ፡ ዘንድ ፥ የችግረኛውንም ፡ ሕዝቤን ፡ ፍርድ ፡ ያጐድሉ ፡ ዘንድ ፡ የግፍን ፡ ትእዛዛት ፡ ለሚያዙ ፥ ክፉንም ፡ ጽሕፈት ፡ ለሚጽፉ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ በተጐበኛችኹበት ፡ ቀን ፥ መከራም ፡ ከሩቅ ፡ በሚመጣበት ፡ ዘመን ፡ ምን ፡ ታደርጉ ፡ ይኾን ፧ ለረድኤትስ ፡ ወደ ፡ ማን ፡ ትሸሻላችኹ ፧ ክብራችኹንስ ፡ ወዴት ፡ ትተዉታላችኹ ፧

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ከእስረኞች ፡ በታች ፡ ይጐነበሳሉ ፥ ከተገደሉትም ፡ በታች ፡ ይወድቃሉ ። በዚህም ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ቍጣው ፡ አልተመለሰችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁ ፡ ገና ፡ ተዘርግታ ፡ ትኖራለች ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ለቀ-ጣዬ ፡ በትር ፡ ለኾነ ፡ የመዓቴም ፡ ጨንገር ፡ በእጁ ፡ ላለ ፡ ለአሶር ፡ ወዮለት! ፡

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ርሱንም ፡ በዝንጉ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እልካለኹ ፥ ምርኮውንና ፡ ብዝበዛውንም ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አደባባይም ፡ ጭቃ ፡ የተረገጡ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ በምቈጣቸው ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አዘዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ርሱ ፡ እንዲሁ ፡ አያስብም ፥ በልቡም ፡ እንዲህ ፡ አይመስለውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማጥፋት ፥ ጥቂት ፡ ያይደሉትንም ፡ አሕዛብን ፡ መቀ-ረጥ ፡ በልቡ ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መሳፍንቴ ፡ ሹሉ ፡ ነገሥታት ፡ አይደሉምን ፧

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ካልኖ ፡ እንደ ፡ ከርከሚሽ ፡ አይደለችምን ፧ ሐማትስ ፡ እንደ ፡ አርፋድ ፡ አይደለችምን ፧ ሰማርያስ ፡ እንደ ፡ ደማስቆ ፡ አይደለችምን ፧

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ የተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸው ፡ ከኢየሩሳሌምና ፡ ከሰማርያ ፡ ምስሎች ፡ የበለጡትን ፡ የጣዖቶችን ፡ መንግሥታት ፡ እጄ ፡ እንዳገኘች ፥

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ በሰማርያና ፡ በጣዖቶቿም ፡ እንዳደረግኹ ፥ እንዲሁስ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በጣዖቶቿ ፡ አላደርግምን ፧

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ጌታ ፡ ሥራውን ፡ ሹሉ ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ የኵሩ ፡ ልብ ፡ ፍሬን ፡ የዐይኑንም ፡ ከፍታ ፡ ትምክሕት ፡ ይገ-በኛል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፦ አስተዋይ ፡ ነኝና ፡ በእጄ ፡ ኀይልና ፡ በጥበቤ ፡ አደረግኹት ፤ የአሕዛብን ፡ ድንበሮች ፡ አራቅኹ ፥ ሀብታቸውንም ፡ ዘረፍኹ ፥ እንደ ፡ ገ-ግናም ፡ ኾኜ ፡ በምድር ፡ የተቀመጡትን ፡ አዋረድኹ ፤

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ እጄም ፡ የአሕዛብን ፡ ኀይል ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ቤት ፡ አገኘች ፤ የተተወም ፡ ዕንቊላል ፡ እንደሚሰበሰብ ፡ እንዲሁ ፡ እኔ ፡ ምድርን ፡ ሹሉ ፡ ሰበሰብኹ ፤ ክንፉን ፡ የሚያራግብ ፡ አፉንም ፡ የሚከፍት ፡ የሚጮኽም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ በእውኑ ፡ መጥረቢያ ፡ በሚቈርጥበት ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ይመካልን ፧ ወይስ ፡ መጋዝ ፡ በሚስበው ፡ ላይ ፡ ይጓደዳልን ፧ ይህስ ፥ በትር ፡ የሚያነሣውን ፡ እንደ ፡ መነቅነቅ ፡ ዘንግም ፡ ዕንጨት ፡ ያይደለውን ፡ እንደ ፡ ማንሣት ፡ ያኽል ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ስለዚህም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወፍራሞች ፡ ላይ ፡ ክሳትን ፡ ይልካል ፤ ከክብሩም ፡ በታች ፡ ቃጠሎው ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ መቃጠል ፡ ይነዳል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ የእስራኤልም ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ቅዱስም ፡ እንደ ፡ ነበልባል ፡ ይኾናል ፤ ሾኹንና ፡ ዅርንችቱን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ያቃጥላል ፡ ይበላውማል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ከነፍስም ፡ እስከ ፡ ሥጋ ፡ ድረስ ፡ የዱሩንና ፡ የሚያፈራውን ፡ ዕርሻ ፡ ክብር ፡ ይበላል ፤ ይህም ፡ የታመመ ፡ ሰው ፡ እንደሚሰለስል ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ የቀሩትም ፡ የዱር ፡ ዛፎች ፡ በቍጥር ፡ ጥቂት ፡ ይኾናሉ ፥ ታናሽ ፡ ብላቴናም ፡ ይጽፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የእስራኤል ፡ ቅሬታ ፡ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ የዳኑት ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በመቷቸው ፡ ላይ ፡ አይደገፉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በእውነት ፡ ይደገፋሉ ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ የያዕቆብም ፡ ቅሬታ ፡ ወደ ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ ይመለሳሉ ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ የሕዝብኽ ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ቢኾን ፡ ቅሬታው ፡ ይመለሳል ። ጽድቅ ፡ የተትረፈረፈበትም ፡ ጥፋት ፡ ተወስኗል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያለቀ ፡ የተቈረጠ ፡ ነገርን ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ይፈጽማል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጽዮን ፡ የምትኖር ፡ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ አሶር ፡ በበትር ፡ ቢመታኽ ፥ ግብጽም ፡ እንዳደረገ ፡ ዘንጉን ፡ ቢያነሣብኽ ፥ አትፍራው ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ቍጣዬ ፡ እስኪፈጸም ፡ መዓቴም ፡ እስኪያጠፋቸው ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቀርቷልና ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ምድያምን ፡ በሔሬብ ፡ አለት ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ መታው ፡ ጅራፍ ፡ ያነሣበታል ፤ በትሩም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ በግብጽም ፡ እንዳደረገ ፡ ያነሣዋል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሸክሙ ፡ ከጫንቃኽ ፡ ቀንበሩም ፡ ከዐንገትኽ ፡ ላይ ፡ ይወርዳል ፤ ቀንበሩም ፡ ከውፍረት ፡ የተነሣ ፡ ይሰበራል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ወደ ፡ አንጋይ ፡ መጥቷል ፤ በመጌዶን ፡ በኩል ፡ ዐልፏል ፤ በማክማስ ፡ ውስጥ ፡ ዕቃውን ፡ አኑሯል ፤

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ በመተላለፊያ ፡ ዐልፏል ፤ በጌባ ፡ ማደሪያው ፡ ነው ፤ ራማ ፡ ደንግጣለች ፤ የሳኦል ፡ ጊብዓ ፡ ከሠብሳለች ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ አንቺ ፡ የጋሊም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በታላቅ ፡ ድምፅሽ ፡ ጩኺ ፤ ላይሳ ፡ ሆይ ፥ አድምጪ ፤ ዐናቶት ፡ ሆይ ፥ መልሽላት ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ መደቤና ፡ ሸሽታለች ፤ በግቤርም ፡ የሚኖሩ ፡ ቤተ ፡ ሰቦቻቸውን ፡ አሸሽተዋል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ ዛሬ ፡ በኖብ ፡ ይቆማል ፤ በጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተራራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኮረብታ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ያንቀሳቅሳል ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ እንሆ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅርንጫፎቹን ፡ በሚያስፈራ ፡ ኀይል ፡ ይቈርጣል ፤ በቁመት ፡ የረዘሙትም ፡ ይቈረጣሉ ፥ ከፍ ፡ ያሉትም ፡ ይዋረዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ ጫፍቅ ፡ የኾነውንም ፡ ዱር ፡ በብረት ፡ ይቈርጣል ፥ ሊባኖስም ፡ በኀያሉ ፡ እጅ ፡ ይወድቃል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ከእሴይ ፡ ግንድ ፡ በትር ፡ ይወጣል ፥ ከሥሩም ፡ ቍጥቋጥ ፡ ያፈራል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፥ የጥበብና ፡ የማስተዋል ፡ መንፈስ ፥ የምክርና ፡ የኀይል ፡ መንፈስ ፥ የዕውቀትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የመፍራት ፡ መንፈስ ፡ ያርፍበታል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራት ፡ ደስታውን ፡ ያያል ። ዐይኑም ፡ እንደምታይ ፡ አይፈርድም ፥ ጐሮውም ፡ እንደምትሰማ ፡ አይበይንም ፤

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለድኻዎች ፡ በጽድቅ ፡ ይፈርዳል ፥ ለምድርም ፡ የዋሆች ፡ በቅንነት ፡ ይበይናል ፤ በአፉም ፡ በትር ፡ ምድርን ፡ ይመታል ፥ በከንፈሩም ፡ እስትንፋስ ፡ ክፉዎችን ፡ ይገድላል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የወገቡ ፡ መታጠቂያ ፡ ጽድቅ ፥ የጐኑም ፡ መቀነት ፡ ታማኝነት ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ተኵላ ፡ ከበግ ፡ ጠቦት ፡ ጋራ ፡ ይቀመጣል ፥ ነብርም ፡ ከፍየል ፡ ጠቦት ፡ ጋራ ፡ ይተኛል ፤ ጥጃና ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ ፍሪዳም ፡ በአንድነት ፡ ያርፋሉ ፤ ታናሽም ፡ ልጅ ፡ ይመራቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ላምና ፡ ድብ ፡ ዐብረው ፡ ይሰማራሉ ፥ ግልገሎቻቸውም ፡ በአንድነት ፡ ያርፋሉ ፤ አንበሳም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ይበላል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ የሚጠባውም ፡ ሕፃን ፡ በእባብ ፡ ጕድጓድ ፡ ላይ ፡ ይጫወታል ፥ ጡት ፡ የጣለውም ፡ ሕፃን ፡ በእፍኝት ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ይጭናል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አይጐዱም ፡ አያጠፉምም ፤ ውሃ ፡ ባሕርን ፡ እንደሚከድን ፡ ምድር ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማወቅ ፡ ትሞላለችና ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ለአሕዛብ ፡ ምልክት ፡ ሊኾን ፡ የቆመውን ፡ የእሴይን ፡ ሥር ፡ አሕዛብ ፡ ይፈልጉታል ፤ ማረፊያውም ፡ የተከበረ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የቀረውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ከአሶርና ፡ ከግብጽ ፥ ከጳትሮስና ፡ ከኢትዮጵያ ፥ ከዔላምና ፡ ከሰናዖር ፡ ከሐማትም ፥ ከባሕርም ፡ ደሴቶች ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እጁን ፡ ይገልጣል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ለአሕዛብም ፡ ምልክትን ፡ ያቆማል ፥ ከእስራኤልም ፡ የተጣሉትን ፡ ይሰበስባል ፥ ከይሁዳም ፡ የተበተኑትን ፡ ከአራቱ ፡ የምድር ፡ ማእዘኖች ፡ ያከማቻል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ የኤፍሬምም ፡ ምቀኝነት ፡ ይርቃል ፥ ይሁዳንም ፡ የሚያስጨንቁ ፡ ይጠፋሉ ፤ ኤፍሬምም ፡ በይሁዳ ፡ አይቀናም ፥ ይሁዳም ፡ ኤፍሬምን ፡ አያስጨንቅም ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ እየበረሩ ፡ ይወርዳሉ ፥ የምሥራቅንም ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይበዘብዛሉ ፤ በኤዶምያስና ፡ በሞዐብም ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ይዘረጋሉ ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ለእነርሱ ፡ ይታዘዛሉ ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የግብጽን ፡ ባሕር ፡ ያጠፋል ፤ በትኵሱም ፡ ነፋስ ፡ እጁን ፡ በወንዙ ፡ ላይ ፡ ያነሣል ፥ ሰባት ፡ ፈሳሾችንም ፡ አድርጎ ፡ ይመታዋል ፥ ሰዎችም ፡ በጫማቸው ፡ እንዲሻገሩ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ከግብጽም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ለእስራኤል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ ለቀረው ፡ ለሕዝቡ ፡ ቅሬታ ፡ ከአሶር ፡ ጐዳና ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ አቤቱ ፥ ተቈጥተኸኛልና ፥ ቍጣኽንም ፡ ከእኔ ፡ መልሰኻልና ፥ አጽናንተኸኛልምና ፡ አመሰግንኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ እንሆ ፥ አምላክ ፡ መድኀኒቴ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይሌና ፡ ዝማሬዬ ፡ ነውና ፥ መድኀኒቴም ፡ ኾኗልና ፥ በርሱ ፡ ታምኜ ፡ አልፈራም ፡ ትላለኽ ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ውሃውንም ፡ ከመድኀኒት ፡ ምንጮች ፡ በደስታ ፡ ትቀዳላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ትላላችኹ ፦ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፥ ስሙንም ፡ ጥሩ ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ሥራውን ፡ አስታውቁ ፤ ስሙ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተናገሩ ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ ሠርቷልና ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀኙ ፤ ይህንም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አስታውቁ ።

ኢሳ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ አንቺ ፡ በጽዮን ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ በመካከልሽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ እልልም ፡ በዪ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ያየው ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ምድረ ፡ በዳ ፡ በኾነ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ምልክትን ፡ አቁሙ ፥ ድምፅንም ፡ ከፍ ፡ አድርጉባቸው ፤ በአለቃዎችም ፡ ደጆች ፡ እንዲገቡ ፡ በእጅ ፡ ጥቀሱ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ቍጣዬን ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ቅዱሳኔን ፡ አዝዣለኹ ፥ እኔ ፡ ኀያላኔንና ፡ በታላቅነቴ ፡ ደስ ፡ የሚላቸውን ፡ ጠርቻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ የኾነ ፡ የብዙ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ አለ ። የከተማቹት ፡ የአሕዛብ ፡ መንግሥታት ፡ የውካታ ፡ ጫጫታ ፡ አለ ። የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰራዊትን ፡ ለሰልፍ ፡ አሰልፏል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርና ፡ የቍጣው ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ ያጠፏት ፡ ዘንድ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ ይመጣሉ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቧልና ፥ አልቅሱ ፤ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ አምላክ ፡ ዘንድ ፡ እንደሚመጣ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እጅ ፡ ኹሉ ፡ ትዝላለች ፥ የሰውም ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ ይቀልጣል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ይደነግጣሉ ፤ ምጥና ፡ ሕማም ፡ ይይዛቸዋል ፥ እንደምትወልድ ፡ ሴትም ፡ ያምጣሉ ፤ አንዱም ፡ በሌላው ፡ ይደነቃል ፥ ፊታቸውም ፡ የነበልባል ፡ ፊት ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ እንሆ ፥ ምድሪቱን ፡ ባድማ ፡ ሊያደርግ ፥ ኀጢአተኞቿንም ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ ሊያጠፋ ፡ ጨካኝ ፡ ኾኖ ፡ በመዓትና ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ተሞልቶ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ይመጣል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ የሰማይም ፡ ከዋክብትና ፡ ሰራዊቱ ፡ ብርሃናቸውን ፡ አይሰጡም ፥ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ትጨልማለች ፥ ጨረቃም ፡ በብርሃኑ ፡ አያበራም ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ዓለሙን ፡ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ ክፉዎቹንም ፡ ስለ ፡ በደላቸው ፡ እቀጣለኹ ፤ የትዕቢተኞችንም ፡ ኵራት ፡ አዋርዳለኹ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ የቀሩትም ፡ ከጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ የከበሩ ፡ ይኾናሉ ፥ ሰውም ፡ ከኦፊር ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ በጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ቀንም ፡ ሰማያትን ፡ አነቃንቃለኹ ፥ ምድርም ፡ ከስፍራዋ ፡ ትናወጣለች ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ተባረረም ፡ ሚዳቋ ፥ ማንም ፡ እንደማይሰበስበው ፡ እንደ ፡ በግ ፡ መንጋ ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለሳል ፥ ኹሉም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሸሻል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ የተገኘ ፡ ኹሉ ፡ የተወጋ ፡ ይኾናል ፥ የተያዘም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ሕፃናታቸውም ፡ በፊታቸው ፡ ይጨፈጨፋሉ ፥ ቤቶቻቸውም ፡ ይበዘበዛሉ ፥ ሚስቶቻቸውም ፡ ይነወራሉ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ ብር ፡ የማይሹትን ፥ ወርቅም ፡ የማያምራቸውን ፡ ሜዶናውያንን ፡ በላያቸው ፡ አስነሣለኹ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ፍላጻዎቻቸውም ፡ ጐበዞችን ፡ ይጨፈጭፋሉ ፥ የማሕፀንንም ፡ ፍሬ ፡ አይምሩም ፥ ዐይኖቻቸውም ፡ ለሕፃናት ፡ አይራሩም ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ ባፈረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፥ የመንግሥታት ፡ ክብር ፡ የከለዳውያንም ፡ ትዕቢት ፡ ጌጥ ፡ ባቢሎን ፡ እንዲሁ ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚቀመጥባት ፡ አይገኝም ፥ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ አይኖርባትም ፤ ዐረባውያንም ፡ ድንኳንን ፡ በዚያ ፡ አይተክሉም ፥ እረኞችም ፡ መንጋዎቻቸውን ፡ በዚያ ፡ አያሳርፉም ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ያርፋሉ ፥ ጕጕቶችም ፡ በቤቶቻቸው ፡ ይሞላሉ ፤ ሰጐኖችም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፥ በዚያም ፡ አጋንንት ፡ ይዘፍናሉ ።

ኢሳ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ተኵላዎችም ፡ በግንቦቻቸው ፥ ቀበሮዎችም ፡ በሚያማምሩ ፡ አዳራሾቻቸው ፡ ይጮኻሉ ፤ ጊዜዋም ፡ ለመምጣት ፡ ቀርቧል ፥ ቀኗም ፡ አይዘገይም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያዕቆብን ፡ ይምረዋል ፥ እስራኤልንም ፡ ደግሞ ፡ ይመርጠዋል ፥ በአገራቸውም ፡ ያኖራቸዋል ፤ መጻተኛም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፥ ከያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ይጣበቃል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ አሕዛብም ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ያመጧቸዋል ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ሎሌዎችና ፡ እንደ ፡ ገረዶች ፡ አድርገው ፡ ይገዟቸዋል ፤ የማረኳቸውን ፡ ይማርካሉ ፥ አስጨናቂዎችንም ፡ ይገዛሉ ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሐዘንኽና ፡ ከመከራኽ ፡ ከተገዛኽለትም ፡ ከጽኑ ፡ ባርነት ፡ ያሳርፍኻል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ታነሣለኽ ፡ እንዲህም ፡ ትላለኽ ፦ አስጨናቂ ፡ እንዴት ፡ ዐረፈ! ፡ አስገባሪም ፡ እንዴት ፡ ጸጥ ፡ አለ! ፡

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 5-6 ፤ አሕዛብንም ፡ በመዓትና ፡ በማያቋርጥ ፡ መምታት ፡ የመታውን ፥ አሕዛብንም ፡ ባልተከለከለ ፡ መከራ ፡ በቀኑጣው ፡ የገዛውን ፡ የኃጥኣንን ፡ በትር ፡ የአለቃዎችንም ፡ ዘንግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰብሯል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ ዐርፋ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀምጣለች ፡ እልልም ፡ ብላለች ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ጥድና ፡ የሊባኖስ ፡ ዝግባ ፦ አንተ ፡ ከተዋረድኽ ፡ ዠምሮ ፡ ማንም ፡ ይቈርጠን ፡ ዘንድ ፡ አልወጣብንም ፡ ብለው ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ሲኦል ፡ በመምጣትኽ ፡ ልትገናኝኽ ፡ በታች ፡ ታወከች ፤ የሞቱትንም ፥ የምድርን ፡ ታላላቆች ፡ ኹሉ ፥ ለአንተ ፡ አንቀሳቀሰች ፥ የአሕዛብንም ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፡ ከዙፋኖቻቸው ፡ አስነሣች ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ደክመኻልን ፧ እኛንስ ፡ መስለኻልን ፧ ጌጥኽና ፡ የበገናኽ ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወረደ ፤

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ በበታችኽም ፡ ብል ፡ ተነጥፏል ፥ ትልም ፡ መደረቢያኽ ፡ ኾኗል ፡ ብለው ፡ ይመልሱልኻል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ አንተ ፡ የንጋት ፡ ልጅ ፡ አጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ ከሰማይ ፡ ወደቅኽ! ፡ አሕዛብንም ፡ ያዋረድኽ ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ድረስ ፡ ተቈረጥኽ! ፡

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ አንተን ፡ በልብኽ ፦ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐርጋለኹ ፥ ዙፋኔንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከዋክብት ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርጋለኹ ፥ በሰሜንም ፡ ዳርቻ ፡ በመሰብሰቢያ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እቀመጣለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ከዳመናዎች ፡ ከፍታ ፡ በላይ ፡ ዐርጋለኹ ፥ በልዑልም ፡ እመሰላለኹ ፡ አልኽ ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ወደጕድጓዱም ፡ ጥልቅ ፡ ትወርዳለኽ ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ የሚያዩኽ ፡ ይመለከቱኻልና ፦ በእውኑ ፡ ምድርን ፡ ያንቀጠቀጠ ፥ መንግሥታትንም ፡ ያናወጠ ፥

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ዓለሙን ፡ ዥሉ ፡ ባድማ ፡ ያደረገ ፥ ከተማዎችንም ፡ ያፈረሰ ፥ ምርኮኞቹንም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ያልሰደደ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ ብለው ፡ ያስተውሉኻል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ ዥሉ ፡ በየቤታቸው ፡ በክብር ፡ አንቀላፍተዋል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተጠላ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ከመቃብርኽ ፡ ተጥለኻል ፤ በሰይፍም ፡ የተወጉት ፥ ተገድለውም ፡ ወደጕድጓዱ ፡ ድንጋዮች ፡ የወረዱት ፡ ከድነውኻል ፤ እንደ ፡ ተረገጠም ፡ ሬሳ ፡ ኾነኻል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ምድርኽን ፡ አጥፍተኻልና ፥ ሕዝብኽንም ፡ ገድለኻልና ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በመቃብር ፡ በአንድነት ፡ አትኾንም ፤ የክፉዎች ፡ ዘር ፡ ለዘለዓለም ፡ የተጠራ ፡ አይኾንም ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ እንዳይነሡም ፥ ምድርንም ፡ እንዳይወርሱ ፥ የዓለሙንም ፡ ፊት ፡ በከተማዎች ፡ እንዳይሞሉ ፡ ስላባቶቻቸው ፡ በደል ፡ ለልጆቹ ፡ ሞትን ፡ አዘጋጁላቸው ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እነሣለኹ ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ከባቢሎን ፡ ስምንና ፡ ቅሬታን ፥ ዘርንና ፡ ትውልድንም ፡ እቈርጣለኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ የጣርት ፡ መኖሪያ ፡ የውሃም ፡ መቋሚያ ፡ አደርጋታለኹ ፤ በጥፋትም ፡ መጥረጊያ ፡ እጠርጋታለኹ ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ምሏል ። እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ በርግጥ ፡ ይኾናል ፥ እንደ ፡ ዐሰብኹም ፡ እንዲሁ ፡ ይቆማል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ አሶርን ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ እሰብረዋለኹ ፥ በተራራዬም ፡ ላይ ፡ እረግጠዋለኹ ፤ ቀንበሩም ፡ ከነርሱ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ፥ ሸክሙም ፡ ከጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ ይወገዳል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ በምድር ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰበው ፡ ዐሳብ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ በአሕዛብም ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ የተዘረጋች ፡ እጅ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ዐስቧል ፤ የሚያስጥለውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እጁም ፡ ተዘርግታለች ፤ የሚመልሳትስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ንጉሡ ፡ አካዝ ፡ በሞተበት ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ሸክም ፡ ኾነ ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ፍልስጥኤም ፡ ሆይ ፥ ከእባቡ ፡ ሥር ፡ እፍኝት ፡ ይወጣልና ፥ ፍሬውም ፡ የሚበርና ፡ እሳት ፡ የሚመስል ፡ እባብ ፡ ይኾናልና ፥ የመታሽ ፡ በትር ፡ ስለ ፡ ተሰበረ ፡ ዥላችኹም ፡ ደስ ፡ አይበላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ የድኻዎችም ፡ የበኵር ፡ ልጆች ፡ ይሰማራሉ ፥ ችግረኞችም ፡ ተዘልለው ፡ ይተኛሉ ፤ ሥርኽንም ፡ በራብ ፡ እገድላለኹ ፥ ቅሬታኽም ፡ ይገደላል ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ አንተ ፡ በር ፡ ሆይ ፥ ወዮ ፡ በል ፡ አንቺም ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፥ ጩኺ ፤ ፍልስጥኤም ፡ ሆይ ፥ ኹላችኹም ፡ ቀልጣችኺል ፤ ጢስ ፡ ከሰሜን ፡ ይመጣል ፡ ከጭፍራውም ፡ ተለይቶ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ለሕዝቡም ፡ መልእክተኞች ፡ ምን ፡ ብሎ ፡ መመለስ ፡ ይገባል ። እግዚአብሔር ፡ ጽዮንን ፡ እንደ ፡ መሠረተ ፥ የሕዝቡም ፡ ችግረኞች ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚጠጉ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። የሞዐብ ፡ ዔር ፡ በሌሊት ፡ ፈርሶ ፡ ጠፋ ፤ ቂር ፡ የሚባልም ፡ የሞዐብ ፡ ምሽግ ፡ በሌሊት ፡ ፈርሶ ፡ ጠፋ ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ባይት ፡ ወደ ፡ ዲቦንም ፡ ወደከፍ ፡ ብታ ፡ መስገጃዎችም ፡ ለልቅሶ ፡ ወጥተዋል ፤ ሞዐብ ፡ በናባው ፡ በሜድባ ፡ ላይ ፡ ታለቅሳለች ፤ ራሳቸው ፡ ኹሉ ፡ ተነጭቷል ፥ ጢማቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተላጭቷል ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ በየመንገዳቸውም ፡ በማቅ ፡ ታጥቀዋል ፤ በየሰገነቶቻቸውና ፡ በያደባባዮቻቸው ፡ እንባ ፡ እጅግ ፡ እያፈሰሱ ፡ ኹሉም ፡ አልቅሰዋል ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ሐሴቦንና ፡ ኤልያሊ ፡ ጮኹ ፤ ድምፃቸው ፡ እስከ ፡ ያሀጽ ፡ ድረስ ፡ ይሰማል ፤ ስለዚህ ፥ የሞዐብ ፡ ሰልፈኞች ፡ ጮኹ ፤ ነፍሷ ፡ በውስጧ ፡ ተንቀጠቀጠች ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ልቤ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ ጮኸ ፤ ከርሷም ፡ የሚሸሹ ፡ ወደ ፡ ዞዓር ፡ ወደ ፡ ዔግላት [265] ፡ ሺሊሺያ [266] ፡ ኮበለሉ ፤ በሉሒት ፡ ዐቀበት ፡ ላይ ፡ እያለቀሱ ፡ ይወጣሉ ፥ በሖሮናይምም ፡ መንገድ ፡ የዋይታ ፡ ጩኸት ፡ ያነሣሉ ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ የኔምሬም ፡ ውሃዎች ፡ ይደርቃሉ ፤ ሣሩም ፡ ደርቋል ፥ ለጋውም ፡ ጠውልጓል ፥ ልምላሜውም ፡ ኹሉ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ የሰበሰቡትን ፡ ሀብትና ፡ መዝገባቸውን ፡ ወደአሓያ ፡ ዛፍ ፡ ወንዝ ፡ ማዶ ፡ ይወስዱታል ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ጩኸት ፡ የሞዐብን ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ ዞረ ፤ ልቅሶዋም ፡ ወደ ፡ ኤግላይምና ፡ ወደ ፡ ብኤርኢሊም ፡ ደረሰ ።

ኢሳ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ የዲሞንም ፡ ውሃ ፡ ደም ፡ ተሞልታለች ፤ በዲሞንም ፡ ላይ ፡ ሥቃይን ፡ እጨምራለኹ ፥ ከሞዐባውያንም ፡ በሚያመልጡ ፥ ከምድርም ፡ በሚቀሩ ፡ ላይ ፡ አንበሳን ፡ አመጣለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ኢሳ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ለሠለጠነው ፡ አለቃ ፡ የበግ ፡ ጠቦቶችን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ካለችው ፡ ከሴላ ፡ ወደጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ተራራ ፡ ስደዱ ።

ኢሳ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡ እንደ ፡ ተበተኑም ፡ ጫጨቶች ፡ እንዲሁ ፡ የሞዐብ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ በአርኖን ፡ መሻገሪያዎች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ምክርን ፡ ምከሪ ፥ ፍርድን ፡ አድርጊ ፥ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ ጥላሽን ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡

---

265 ዕብ. ፥ ዔግላ ፡ (ዕጉል • ግልገል ፥ እንቦሳ ፥ ጥጃ) ።

266 ዕብ. ፥ ሸሊሺ ፡ (ሣልስት • ሦስተኛት) ።

አድርጊ ፤ የተሰደዱትን ፡ ሸሽጊ ፥ የሸሹትን ፡ አትግለጪ ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 4 ፤ ከሞዐብ ፡ የተሰደዱት ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡ ፤ ከሚያጠፋቸው ፡ ፊት ፡ መጋረጃ ፡ ኹኚላቸው ። የሚያስጨንቁ ፡ አልቀዋል ፥ ጥፋትም ፡ ቀርቷል ፤ ይጨቍኑ ፡ የነበሩ ፡ ከምድር ፡ ጠፍተዋል ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 5 ፤ ዙፋንም ፡ በምሕረት ፡ ይቀናል ፥ በዚያም ፡ ላይ ፡ በዳዊት ፡ ድንኳን ፡ ፍርድን ፡ የሚሻ ፡ ጽድቅንም ፡ የሚያፈጥን ፡ ፈራጅ ፡ በእውነት ፡ ይቀመጣል ፡

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 6 ፤ ስለሞዐብ ፡ ትዕቢት ፡ እጅግ ፡ ስለ ፡ መታበዩ ፥ ስለ ፡ ኵራቱና ፡ ስለ ፡ ትዕቢቱ ፡ ስለ ፡ ቍጣውም ፡ ሰምተናል ፤ ትምክሕቱ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ሞዐብ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፡ ዋይ ፡ ይላል ፤ ኹሉም ፡ ዋይ ፡ ይላል ፤ ስለቂርሐራሴት ፡ መሠራት ፡ በጥልቅ ፡ ሐዘን ፡ ታለቅሳላችኹ ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 8 ፤ የሐሴቦን ፡ ዕርሻዎችና ፡ የሴባማ ፡ ወይን ፡ ግንዶች ፡ አዝነዋል ። የአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ የሰባበሯቸው ፡ ቅርንጫፎች ፡ እስከ ፡ ኢያዜር ፡ ደርሰው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጥተው ፡ ነበር ፤ ቀሥጥቋጦቹም ፡ ተዘርግተው ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረው ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 9 ፤ ስለዚህ ፥ በኢያዜር ፡ ልቅሶ ፡ ስለሴባማ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ሐሴቦንና ፡ ኤልያሊ ፡ ሆይ ፥ በዛፍሽ ፡ ፍሬና ፡ በወይንሽ ፡ መከር ፡ የጦር ፡ ጩኸት ፡ ወድቋልና ፥ በእንባዬ ፡ አረካሻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 10 ፤ ደስታና ፡ ሐሤትም ፡ ከፍሬያማው ፡ ዕርሻ ፡ ተወስዷል ፥ በወይኑም ፡ ቦታዎች ፡ ዝማሬና ፡ እልልታ ፡ የለም ፤ በመጥመቂያም ፡ ወይን ፡ የሚረግጥ ፡ የለም ፤ የረጋጮቹን ፡ እልልታ ፡ አጥፍቻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 11 ፤ ስለዚህ ፥ ልቤ ፡ ስለ ፡ ሞዐብ ፥ አንገቴም ፡ ስለ ፡ ቂርሔሬስ ፡ እንደ ፡ መሰንቆ ፡ ትጮኻለች ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 12 ፤ ሞዐብም ፡ መጥቶ ፡ በኰረብታ ፡ መስገጃ ፡ ላይ ፡ በደከመና ፡ ለጸሎት ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አያሸንፍም ፡

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ በድሮ ፡ ዘመን ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 16 ፥ 14 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፦ በሦስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዓመት ፡ የሞዐብ ፡ ክብርና ፡ የሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ብዛት ፡ ይዋረዳል ፥ ቅሬታውም ፡ እጅግ ፡ ያነሰና ፡ የተጠቃ ፡ ይኾናል ፡ ይላል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ኢሳ. ፥ 17 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ ደማስቆ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፦ እንሆ ፥ ደማስቆ ፡ ከተማ ፡ ከመኾን ፡ ተቋርጣለች ፤ ባድማና ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፥ 17 ፥ 2 ፤ ከተማዎቿ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተፈቱ ፡ ይኾናሉ ፤ ለመንጋ ፡ ማሰማሪያ ፡ ይኾናሉ ፤ መንጋዎች ፡ በዚያ ፡ ያርፋሉ ፡ የሚያስፈራቸውም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፥ 17 ፥ 3 ፤ ምሽግም ፡ ከኤፍሬም ፥ መንግሥትም ፡ ከደማስቆ ፡ ተወገደች ፤ የሶርያም ፡ ቅሬታ ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ክብር ፡ ይኾናል ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፥ 17 ፥ 4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ የያዕቆብ ፡ ክብር ፡ ይደክማል ፡ የሥጋውም ፡ ውፍረት ፡ ይከሳል ።

ኢሳ. ፥ 17 ፥ 5 ፤ ዐጫጅ ፡ የቆመውን ፡ እኽል ፡ በእጁ ፡ ሰብስቦ ፡ ዛላውን ፡ እንደሚያጭድ ፡ ይኾናል ፤ በራፋይም ፡ ሸለቆ ፡ ቃርሚያ ፡ እንደሚለቅም ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ወይራ ፡ በተመታ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ፍሬ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እንደሚቀር ፥ አራት ፡ ወይም ፡ ዐምስት ፡ በዛፊቱ ፡ ጫፍ ፡ እንደሚገኝ ፥ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቃርሚያ ፡ ይቀራል ፡ ይላል ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፈጣሪው ፡ ይመለከታል ፥ ዐይኖቹም ፡ ወደእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ እጁም ፡ የሠራችውን ፡ መሠዊያ ፡ አይመለከትም ፤ ጣቶቹም ፡ ወዳበጀቸው ፥ ወደማምለኪያ ፡ ዐጸዶች ፡ ወይም ፡ ወደፀሓይ ፡ ምስሎች ፥ አያይም ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የአሞራውያንና ፡ የኤውያውያን ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ተፈቱ ፥ እንዲሁ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ይፈታሉ ፥ ባድማም ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ የደኅንነትኽን ፡ አምላክ ፡ ረስተኻል ፥ የረድኤትኽንም ፡ ጌታ ፡ አላሰብኽም ፤ ስለዚህ ፥ ያማረውን ፡ ተክል ፡ ተክለኻል ፥ እንግዳንም ፡ ዘር ፡ ዘርተኻል ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ በተከልኽበት ፡ ቀን ፡ ታበቅለዋለኽ ፥ በነጋውም ፡ ዘርኽን ፡ እንዲያብብ ፡ ታደርገዋለኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሐዘንና ፡ በትካዜ ፡ ቀን ፡ መከሩ ፡ ይሸሻል ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ እንደ ፡ ባሕር ፡ ሞገድ ፡ ድምፅ ፡ ለሚተምሙ ፡ ለወገኖች ፡ ብዛት ፥ እንደ ፡ ኀይለኛም ፡ ውሃ ፡ ጩኸት ፡ ለሚጮኹ ፡ አሕዛብ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ አሕዛብ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ጩኸት ፡ ይጮኻሉ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይገሥጻቸዋል ፥ እነርሱም ፡ እየሸሹ ፡ ይርቃሉ ፥ በተራራም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እብቅ ፡ በነፋስ ፡ ፊት ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚያዞረው ፡ ትቢያ ፡ ይበተናሉ ።

ኢሳ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ በመሸ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ድንጋጤ ፡ አለ ፤ ከማለዳም ፡ በፊት ፡ አይገኙም ። የዘረፉን ፡ ሰዎች ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፥ የበዘበዙን ፡ ዕጣ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ በኢትዮጵያ ፡ ወንዞች ፡ ማዶ ፡ ላለች ፥ ክንፍ ፡ ያላቸው ፡ መርከቦች ፡ ላሉባት ፥

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ መልእክተኞችን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ የደንገል ፡ መርከቦችንም ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ ለምትልክ ፡ ምድር ፡ ወዮላት! ፡ እናንተ ፡ ፈጣኖች ፡ መልእክተኞች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ረኻቦምና ፡ ወደ ፡ ለስላሳ ፡ ሕዝብ ፥ ከመዠመሪያው ፡ አስደንጋጭ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ወገን ፥ ወደሚሰፍርና ፡ ወደሚረግጥ ፥ ወንዞችም ፡ ምድራቸውን ፡ ወደሚከፍሉት ፡ ሕዝብ ፡ ኺዱ ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ በዓለም ፡ የምትኖሩ ፡ ኹሉና ፡ በምድር ፡ የምትቀመጡ ፡ ሆይ ፥ ምልክት ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ እዩ ፤ መለከትም ፡ በተነፋ ፡ ጊዜ ፡ ስሙ ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፦ በፀሓይ ፡ ጮራ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ትኵሳት ፥ በዐጨዳም ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ ደመና ፡ ኾኜ ፡ በማደሪያዬ ፡ በጸጥታ ፡ ተቀምጬ ፡ እመለከታለኹ ፡ ብሎኛልና ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ ርሱ ፡ ከመከር ፡ በፊት ፡ አበባ ፡ በረገፈ ፡ ጊዜ ፡ የወይንም ፡ ፍሬ ፡ ጨርቋ ፡ ሲይዝ ፡ የወይኑን ፡ ዘንግ ፡ በማጭድ ፡ ይቈርጣል ፥ ጫፎቹንም ፡ ይመለምላል ፣ ያስወግድማል ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ ላሉ ፡ ነጣቂዎች ፡ ወፎች ፥ ለምድርም ፡ አውሬዎች ፡ በአንድነት ፡ ይቀራሉ ፤ ነጣቂዎችም ፡ ወፎች ፡ ይባጁባቸዋል ፥ የምድርም ፡ አውሬዎች ፡ ኹሉ ፡ ይከርሙባቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፥ ከረዥምና ፡ ከለስላሳ ፡ ሕዝብ ፥ ከመገመሪያው ፡ አስደንጋጭ ፡ ከኾነ ፡ ወገን ፥ ከሚሰፍርና ፡ ከሚረግጥ ፥ ወንዞችም ፡ ምድራቸውን ፡ ከሚከፍሉት ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ወደሚገኝበት ፡ ስፍራ ፡ ወደጽዮን ፡ ተራራ ፡ ይቀርባል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ ግብጽ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፦ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በፈጣን ፡ ደመና ፡ እይበረረ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመጣል ፤ የግብጽም ፡ ጣዖታት ፡ በፊቱ ፡ ይርዳሉ ፥ የግብጽም ፡ ልብ ፡ በውስጧ ፡ ይቀልጣል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ግብጻውያንን ፡ በግብጻውያን ፡ ላይ ፡ አስነሣለኹ ፤ ወንድምም ፡ ወንድሙን ፥ ሰውም ፡ ባልንጀራውን ፥ ከተማም ፡ ከተማን ፥ መንግሥትም ፡ መንግሥትን ፡ ይወጋል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ የግብጽም ፡ መንፈስ ፡ በውስጧ ፡ ባዶ ፡ ይኾናል ፥ ምክራቸውንም ፡ አጠፋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ በድግምት ፡ የሚጠነቀሉትንም ፡ መናፍስት ፡ ጠሪዎቻቸውንም ፡ ጠንቋዮቻቸውንም ፡ ይጠይቃሉ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ግብጻውያንንም ፡ በጨካኝ ፡ ጌታ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ጨካኝ ፡ ንጉሥም ፡ ይገዛቸዋል ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ውሃዎችም ፡ ከባሕር ፡ ይደርቃሉ ፥ ወንዙም ፡ ያንሳል ፡ ደረቅም ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ወንዞቹም ፡ ይገማሉ ፥ የግብጽም ፡ መስኖች ፡ ያንሳሉ ፡ ይደርቃሉም ፤ ደንገልና ፡ ቄጤማ ፡ ይጠወልጋሉ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ በአባይ ፡ ወንዝ ፡ ዳር ፡ ያለው ፡ መስክ ፡ በአባይም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ የተዘራ ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡ ይደርቃል ፥ ይበተንማል ፥ አይገኝምም ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ዓሣ ፡ አጥማጆቹ ፡ ያዝናሉ ፥ በአባይም ፡ ወንዝ ፡ መቃጥን ፡ የሚጥሉት ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሳሉ ፥ በውሃዎችም ፡ ላይ ፡ መረብ ፡ የሚዘረጉት ፡ ይዝላሉ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ የተበጠረውንም ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ የሚሠሩ ፥ ነጩንም ፡ ልብስ ፡ የሚሠሩ ፡ ሸማኔዎች ፡ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ደገፋዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ይሰባበራሉ ፥ የደመ ፡ ወዘኞችም ፡ ነፍስ ፡ ትተክዛለች ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ የጣኔዎስ ፡ አለቃዎች ፡ ፍጹም ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ፤ ፈርዖንን ፡ የሚመክሩ ፡ ጥበበኞች ፡ ምክራቸው ፡ ድንቁርና ፡ ኾነች ። ፈርዖንን ፦ እኛ ፡ የጥበበኞች ፡ ልጆች ፡ የቀደሙም ፡ ነገሥታት ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ እንዴት ፡ ትሉታላችኹ ፧

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ አኹንስ ፡ ጥበበኞችኽ ፡ የት ፡ አሉ ፧ አኹን ፡ ይንገሩኽ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ያሰበውን ፡ ይወቁ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ የጣኔዎስ ፡ አለቃዎች ፡ ሰነፎች ፡ ኾነዋል ፥ የሜምፎስም ፡ አለቃዎች ፡ ተሸንግለዋል ፤ የነገዶቿ ፡ የማእዘን ፡ ድንጋዮች ፡ የኾኑ ፡ ግብጽን ፡ አሳቱ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ የጠማምነትን ፡ መንፈስ ፡ በውስጧ ፡ ደባልቋል ፤ ሰካር ፡ በትፋቱ ፡ እንዲስት ፡ እንዲሁ ፡ ግብጽን ፡ በሥራዋ ፡ ኹሉ ፡ አሳቱ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ራስ ፡ ወይም ፡ ዥራት ፡ የሰሌን ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወይም ፡ እንግጫ ፡ ቢኾን ፡ ሊሠራ ፡ የሚችል ፡

ሥራ ፡ ለግብጽ ፡ አይኾንላትም ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ግብጻውያን ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ይኾናሉ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ከሚያንቀሳቅሳት ፡ ከእጁ ፡ መንቀሳቀስ ፡ የተነሣ ፡ ይሸበራሉ ፡ ይፈሩማል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ የይሁዳም ፡ ምድር ፡ ግብጽን ፡ የምታስደነግጥ ፡ ትኾናለች ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመከረባት ፡ ምክር ፡ የተነሣ ፡ ወሬዋን ፡ የሚሰማ ፡ ኹሉ ፡ ይፈራል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በከነዓን ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ የሚምሉ ፡ ዐምስት ፡ ከተማዎች ፡ ይኾናሉ ፤ ከነዚህም ፡ አንዲቱ ፡ የጥፋት ፡ ከተማ ፡ ተብላ ፡ ትጠራለች ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሠዊያ ፥ በዳርቻዋም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዐምድ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ይህም ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ምልክትና ፡ ምስክር ፡ ይኾናል ፤ ከሚያስጨንቋቸው ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጮኻሉና ፥ ርሱም ፡ መድኀኒትንና ፡ ኀያልን ፡ ሰዶ ፡ ያድናቸዋልና ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በግብጽ ፡ የታወቀ ፡ ይኾናል ፥ ግብጻውያንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያውቃሉ ፤ በመሥዋዕትና ፡ በቀኑርባን ፡ ያመልካሉ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ ስእለት ፡ ይሳላሉ ፡ ይፈጽሙትማል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ግብጽን ፡ ይመታታል ፤ ይመታታል ፡ ይፈውሳታልም ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለሳሉ ፡ ርሱም ፡ ይለመናቸዋል ፡ ይፈውሳቸውማል ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከግብጽ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ መንገድ ፡ ይኾናል ፥ አሶራዊውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፥ ግብጻዊውም ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ይገባል ፤ ግብጻውያንም ፡ ከአሶራውያን ፡ ጋራ ፡ ይሰግዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ 25 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ሕዝቤ ፡ ግብጽ ፥ የእጄም ፡ ሥራ ፡ አሶር ፥ ርስቴም ፡ እስራኤል ፡ የተባረከ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ይባርካቸዋልና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ እስራኤል ፡ ለግብጽና ፡ ለአሶር ፡ ሦስተኛ ፡ ይኾናል ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡ በረከት ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሳርጎን ፡ ተርታንን ፡ በሰደደ ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ አዛጦን ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ አዛጦንንም ፡ ወግቶ ፡ በያዛት ፡ ጊዜ ፥

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓሞጽን ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስን ፦ ኺድ ፥ ማቅኽን ፡ ከወገብኽ ፡ አውጣ ፥ ጫማኽንም ፡ ከእግርኽ ፡ አውልቅ ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። እንዲህም ፡ አደረገ ፥ ዕራቍቱንም ፡ ባዶ ፡ እግሩንም ፡ ኼደ ።

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አለ ፦ ባሪያዬ ፡ ኢሳይያስ ፡ በግብጽና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ለምልክትና ፡ ለተአምራት ፡ ሊኾን ፡ ዕራቍቱንና ፡ ባዶ ፡ እግሩን ፡ እንደ ፡ ኼደ ፥

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ እንዲሁ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የግብጽንና ፡ የኢትዮጵያን ፡ ምርኮ ፥ ጐበዛዝቱንና ፡ ሽማግሌዎቹን ፥ ዕራቍታቸውንና ፡ ባዶ ፡ እግራቸውን ፡ አድርጎ ፥ ገላቸውንም ፡ ገልጦ ፥ ለግብጽ ፡ ጕስቍልና ፡ ይነዳቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፡ ከተስፋቸው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ከትምክሕታቸውም ፡ ከግብጽ ፡ የተነሣ ፡ ይፈራሉ ፡

ያፍሩማል ፤

ኢሳ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በዚች ፡ ባሕር ፡ ዳርቻ ፡ የሚቀመጡ ፦ እንሆ ፥ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፥ ለርዳታ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ የሸሸንበት ፡ ተስፋችን ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እኛስ ፡ እንዴት ፡ እናመልጣለን ፧ ይላሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ስላለው ፡ ስለ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከደቡብ ፡ እንደሚወጣ ፥ እንዲሁ ፡ ከሚያስፈራ ፡ አገር ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ይወጣል ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ ከባድ ፡ ራእይ ፡ ተነገረኝ ፤ ወንጀለኛው ፡ ይወነጅላል ፥ አጥፊውም ፡ ያጠፋል ። ዔላም ፡ ሆይ ፥ ውጪ ፤ ሜዶን ፡ ሆይ ፥ ክበቢ ፤ ትካዜውን ፡ ሹሉ ፡ አስቀርቻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ወገቤ ፡ ሕመም ፡ ተሞላ ፤ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ ምጥ ፡ ያዘኝ ፤ ከሕመሜ ፡ የተነሣ ፡ አልሰማም ፥ ከድንጋጤም ፡ የተነሣ ፡ አላይም ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ ልቤ ፡ ተንበደበደ ፥ ድንጋጤ ፡ አስፈራኝ ፥ ተስፋ ፡ ያደረግኹትም ፡ ድንግዝግዝታ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ኾነብኝ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ ማዕዱን ፡ ያዘጋጃሉ ፥ ምንጣፉንም ፡ ይዘረጋሉ ፥ ይበሉማል ፥ ይጠጡማል ፤ እናንተ ፡ መሳፍንት ፡ ሆይ ፥ ተነሡ ፥ ጋሻውን ፡ አዘጋጁ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሎኛልና ፦ ኺድ ፥ ጕበኛም ፡ አቁም ፥ የሚያየውንም ፡ ይናገር ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ በከብት ፡ የሚቀመጡትን ፥ ኹለት ፡ ኹለት ፡ እየኾኑ ፡ የሚኼዱት ፡ ፈረሰኞች ፥ በአህያዎች ፡ የሚቀመጡትንና ፡ በግመሎች ፡ የሚቀመጡትን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በጽኑ ፡ ትጋት ፡ አስተውሎ ፡ ተግቶም ፡ ያድምጥ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ያየውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ቀኑን ፡ ሹሉ ፡ ዘወትር ፡ በማማ ፡ ላይ ፡ ቆሜያለኹ ፥ ሌሊቱንም ፡ ሹሉ ፡ በመጠበቂያዬ ፡ ላይ ፡ ተተክያለኹ ፥

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ እንሆም ፥ በፈረሶች ፡ የሚቀመጡ ፥ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ኹነው ፡ የሚኼዱ ፡ ፈረሰኞች ፡ ይመጣሉ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ባቢሎን ፡ ወደቀች ፡ ወደቀች ፥ የተቀረጹም ፡ የአማልክቷ ፡ ምስሎች ፡ ሹሉ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተጥለው ፡ ደቀቁ ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ እናንተ ፡ በዐውድማዬ ፡ ላይ ፡ የተወቃችኹ ፡ የዐውድማዬ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰማኹትን ፡ ነገርኋችኹ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። አንዱ ፡ ከሴይር ። ጕበኛ ፡ ሆይ ፥ ሌሊቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧ ጕበኛ ፡ ሆይ ፥ ሌሊቱ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠራኝ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ጕበኛውም ፦ ይነጋል ፡ ድግሞም ፡ ይመሻል ፤ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ ብትወዱ ፡ ጠይቁ ፤ ተመልሳችኹም ፡ ኑ ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ስለ ፡ ዐረብ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፦ የድዳናውያን ፡ ነጋዴዎች ፡ ሆይ ፥ በዐረብ ፡ ዱር ፡ ውስጥ ፡ ታድራላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ በቴማን ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ወደተጠሙት ፡ ሰዎች ፡ ውሃ ፡ አምጡ ፡ እንጀራ ፡ ይዛችኹ ፡ የሸሹትን ፡ ሰዎች ፡ ተቀበሏቸው ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ከሰይፍ ፥ ከተመዘዘው ፡ ሰይፍ ፥ ከተለጠጠውም ፡ ቀስት ፡ ከጽኑም ፡ ሰልፍ ፡ ሸሽተዋልና ።

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ እንዲህ ፡ ብሎኛልና ፦ እንደ ፡ ምንደኛ ፡ ዓመት ፡ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የቄዳር ፡ ክብር ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋል ፤

ኢሳ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ከቀስተኞች ፡ ቍጥር ፡ የቀሩት ፡ የቄዳር ፡ ልጆች ፡ ኀያላን ፡ ያንሳሉ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ስለራእይ ፡ ሸለቆ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። እናንተ ፡ ኹላችኹ ፡ ወደ ፡ ሰገነት ፡ መውጣታችኹ ፡ ምን ፡ ኾናችኋል ፧

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ ጩኸትና ፡ ፍጅት ፡ የተሞላብሽ ፡ ከተማ ፡ ደስታ ፡ ያለሽ ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ የተገደሉት ፡ በሰይፍ ፡ የተገደሉ ፡ አይደሉም ፡ በሰልፍም ፡ የሞቱ ፡ አይደሉም ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ አለቃዎችሽ ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ሸሹ ፡ ያለቀስትም ፡ ተማረኩ ፤ ከሩቅ ፡ ሸሽተው ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ የተገኙት ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ታሰሩ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ስለዚህ ፦ ፊታችኹን ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አርቁ ፤ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ስለ ፡ ሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጥፋት ፡ ታጽናኑኝ ፡ ዘንድ ፡ አትድከሙ ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የድንጋጤና ፡ የመረገጥ ፡ የድብልቅልቅም ፡ ቀን ፡ የቅጥርም ፡ መፍረስ ፡ ወደ ፡ ተራራም ፡ መጮኽ ፡ በራእይ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ኾኗል ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ ዔላምም ፡ ከሠረገለኞችና ፡ ከፈረሰኞች ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አፎቱን ፡ ተሸከመ ፡ ቂርም ፡ ጋሻውን ፡ ገለጠ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ መልካሞቹንም ፡ ሸለቆዎችሽን ፡ ሠረገላዎች ፡ ሞሉባቸው ፡ ፈረሰኞችም ፡ መቆሚያቸውን ፡ በበር ፡ ላይ ፡ አደረጉ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ የይሁዳንም ፡ መጋረጃ ፡ ገለጠ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በዱር ፡ ቤት ፡ የነበረውን ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ ተመለከትኽ ፡

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ የዳዊትም ፡ ከተማ ፡ ፍራሾች ፡ እንደ ፡ በዙ ፡ አይታችኋል ፡ የታችኛውንም ፡ ኩሬ ፡ ውሃ ፡ አከማችታችኋል ፡

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ የኢየሩሳሌምን ፡ ቤቶች ፡ ቈጠራችኹ ፡ ቅጥሩንም ፡ ለማጥናት ፡ ቤቶችን ፡ አፈረሳችኹ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ በአሮጌው ፡ ኩሬ ፡ ላለው ፡ ውሃ ፡ በኹለቱ ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ መከማቻ ፡ ሠራችኹ ፤ ይህን ፡ ያደረገውን ፡ ግን ፡ አልተመለከታችኹም ፡ ቀድሞ ፡ የሠራውንም ፡ አላያችኹም ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ልቅሶና ፡ ወደ ፡ ዋይታ ፡ ራስን ፡ ወደ ፡ መንጨትና ፡ ማቅንም ፡ ወደ ፡ መልበስ ፡ ጠራ ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ እንሆም ፡ ሐሜትና ፡ ደስታ ፡ በሬውንና ፡ በጉንም ፡ ማረድ ፡ ሥጋንም ፡ መብላት ፡ የወይን ፡ ጠጅንም ፡ መጠጣት ፡ ኾነዋል ፤ እናንተ ፦ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንብላ ፡ እንጠጣ ፡ ብላችኋል ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጐሮ ፡ ተሰማ ፦ እስከትሞቱ ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ በደል ፡ በእውነት ፡ አይሰረይላችኹም ፡ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ተሾመው ፡

ወደዚህ ፡ አዛዥ ፡ ወደ ፡ ሳምናስ ፡ ኺድ ፥ እንዲህም ፡ በለው ፦

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 16 ፤ መቃብር ፡ በዚህ ፡ ያስወቀርኽ ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ ስፍራ ፡ መቃብር ፡ ያሠራኽ ፥ በድንጋይም ፡ ውስጥ ፡ ለራስኽ ፡ መኖሪያ ፡ ያሳነጽኽ ፥ በዚህ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ በዚህስ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ አለ ፧

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 17 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኀይል ፡ ወርውሮ ፡ ይጥልኻል ፥ አጠንክሮም ፡ ይጨብጥኻል ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 18 ፤ ጠቅሎም ፡ ያንከባልልኻል ፥ ወደ ፡ ሰፊዉቱም ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ኳስ ፡ ይጥልኻል ፤ አንተ ፡ የጌታኽ ፡ ቤት ፡ ዕፍረት! ፡ በዚያ ፡ ትሞታለኽ ፥ በዚያም ፡ የክብርኽ ፡ ሠረገላዎች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 19 ፤ ከአዛዥነት ፡ ሥራኽ ፡ አሳድድኻለኹ ፥ ከሹመትኽም ፡ ትሻራለኽ ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ባሪያዬን ፡ የኬልቅያስን ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄምን ፡ እጠራለኹ ፥

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 21 ፤ መጐናጸፊያኽንም ፡ አለብሰዋለኹ ፥ በመታጠቂያኽም ፡ አስታጥቀዋለኹ ፥ ሹመትኽንም ፡ በእጁ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ አባት ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 22 ፤ የዳዊትንም ፡ ቤት ፡ መክፈቻ ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ፤ ርሱም ፡ ይከፍታል ፡ የሚዘጋም ፡ የለም ፡ ርሱም ፡ ይዘጋል ፡ የሚከፍትም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 23 ፤ በታመነም ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ ችንካር ፡ እተክለዋለኹ ፥ ለአባቱም ፡ ቤት ፡ የክብር ፡ ዙፋን ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 24 ፤ የአባቱንም ፡ ቤት ፡ ክብር ፡ ኹሉ ፡ ልጆቹንም ፡ የልጅ ፡ ልጆቹንም ፥ ከጽዋ ፡ ዕቃ ፡ ዠምሮ ፡ እስከማድጋ ፡ ዕቃ ፡ ድረስ ፥ ታናናሹን ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ይሰቅሉበታል ።

ኢሳ. ፥ 22 ፥ 25 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ በታመነው ፡ ስፍራ ፡ የተከለው ፡ ችንካር ፡ ይወልቃል ፡ ተሰብሮም ፡ ይወድቃል ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተሰቀለው ፡ ሸክም ፡ ይጠፋል ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ ጢሮስ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ሆይ ፥ አልቅሱ ፤ ፈርሷልና ፥ ቤት ፡ የለም ፥ መግባትም ፡ የለም ፤ ከኪቲም ፡ አገር ፡ ዠምሮ ፡ ተገልጦላቸዋል ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 2 ፤ እናንተ ፡ በደሴት ፡ የምትኖሩ ፡ በባሕርም ፡ የምትሻገሩ ፡ የሲዶና ፡ ነጋዴዎች ፡ ንግድ ፡ የሞሉባችኹ ፡ ሆይ ፥ ጸጥ ፡ በሉ ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 3 ፤ የሺሖር ፡ ዘርና ፡ የአባይ ፡ ወንዝ ፡ መከር ፡ በብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ላይ ፡ ገቢዋ ፡ ነበረ ፤ ርሷም ፡ የአሕዛብ ፡ መናገጃ ፡ ነበረች ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 4 ፤ ሲዶና ፡ ሆይ ፥ ባሕር ፥ የባሕር ፡ ምሽግ ፦ አላማጥኹም ፥ አልወለድኹም ፤ ጐበዛዝትንም ፡ አላሳደግኹም ፥ ደናግልንም ፡ አላሳደግኹም ፡ ብሎ ፡ ተናግሯልና ፥ ዕፈሪ ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 5 ፤ ወሬዋ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ በጢሮስ ፡ ወሬ ፡ ምጥ ፡ ይይዛቸዋል ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 6 ፤ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ተሻገሩ ፤ እናንተ ፡ በደሴት ፡ የምትኖሩ ፡ አልቅሱ ።

ኢሳ. ፥ 23 ፥ 7 ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ተመሥርታ ፡ የነበረችው ፥ በዚያም ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ኾና ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡ እግሮቿ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ያፈለሷት ፡ የደስታችኹ ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናትን ፧

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ አክሊል ፡ ባስጫነች ፡ ከተማ ፡ በጢሮስ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ የወሰነ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ነጋዴዎቿ ፡ አለቃዎች ፡ ናቸው ፥ በርሷም ፡ የሚሸጡና ፡ የሚለውጡ ፡ የምድር ፡ ክቡራን ፡ ናቸው ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ የክብርን ፡ ዅሉ ፡ ትዕቢት ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ የምድርንም ፡ ክቡራን ፡ ዅሉ ፡ ያስንቅ ፡ ዘንድ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወስኖታል ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ የተርሴስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የሚከለክልሽ ፡ የለምና ፡ እንደ ፡ አባይ ፡ ወንዝ ፡ በአገርሽ ፡ ላይ ፡ ጐርፈሽ ፡ ዕለፊ ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ በባሕር ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፡ መንግሥታትንም ፡ አናወጠ ፤ ምሽጎቿንም ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለከነዓን ፡ አገር ፡ አዘዘ ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ርሱም ፦ አንቺ ፡ የተበደልሽ ፡ የሲዶና ፡ ድንግል ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ደስ ፡ አይበልሽ ፤ ተነሥተሽ ፡ ወደ ፡ ኪቲም ፡ ተሻገሪ ፥ በዚያም ፡ ደግሞ ፡ አታርፊም ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ የከለዳውያን ፡ አገር! ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ኾኖ ፡ አይገኝም ፤ አሶራውያን ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ሰጥተውታል ፤ ግንቦቻቸውን ፡ ሠሩ ፥ አዳራሾቿንም ፡ አፈረሱ ፥ ባድማም ፡ አደረጓት ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ሆይ ፥ ምሽጋችኹ ፡ ፈርሷልና ፥ ዋይ ፡ በሉ ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ጢሮስ ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ንጉሥ ፡ ዘመን ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ያክል ፡ የተረሳች ፡ ትኾናለች ፤ ከሰባ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ለጢሮስ ፡ በጋለሞታ ፡ ዘፈን ፡ እንደሚኾን ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ አንቺ ፡ የተረሳሽ ፡ ጋለሞታ ፡ ሆይ ፥ መሰንቆ ፡ ያዢ ፡ በከተማ ፡ ላይም ፡ ዙሪ ፤ መታሰቢያም ፡ ይኾንልሽ ፡ ዘንድ ፡ ዜማን ፡ አሳምሪ ፡ ዘፈንሽንም ፡ አብዢ ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ከሰባ ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጢሮስን ፡ ይጐበኛታል ፥ ወደ ፡ ዋጋዋም ፡ ትመለሳለች ፥ ደግሞም ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ከኾኑ ፡ ከዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ ትገለሙታለች ።

ኢሳ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ንግዷና ፡ ዋጋዋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፤ ንግዷም ፡ በልተው ፡ ይጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ ማለፊያም ፡ ልብስ ፡ ይለብሱ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለሚኖሩ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ በዕቃ ፡ ቤትና ፡ በግምጃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ አይከተትም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ ባዶ ፡ ያደርጋታል ፥ ባድማም ፡ ያደርጋታል ፥ ይገለብጣትማል ፥ በርሷም ፡ የተቀመጡትን ፡ ይበትናል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ካህኑ ፥ እንደ ፡ ባሪያውም ፡ እንዲሁ ፡ ጌታው ፥ እንደ ፡ ባሪያዪቱም ፡ እንዲሁ ፡ እመቤቷ ፥ እንደሚገዛም ፡ እንዲሁ ፡ የሚሸጠው ፥ እንደ ፡ አበዳሪውም ፡ እንዲሁ ፡ ተበዳሪው ፥ እንደ ፡ ዕዳ ፡ አስከፋዩም ፡ እንዲሁ ፡ ዕዳ ፡ ከፋዩ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ምድር ፡ መፈታትን ፡ ትፈታለች ፥ ፈጽማም ፡ ትበላሻለች ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናግሯልና ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ምድርም ፡ አለቀሰች ፥ ረገፈችም ፤ ዓለም ፡ ደከመች ፥ ረገፈችም ፤ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ ታላላቆች ፡ ደከሙ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ምድርም ፡ ከሚቀመጡባት ፡ በታች ፡ ረክሳለች ፥ ሕጉን ፡ ተላልፈዋልና ፥ ሥርዐቱንም ፡ ለውጠዋልና ፥ የዘለዓለሙንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፍርሰዋልና ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ መርገም ፡ ምድርን ፡ ትበላለች ፥ በርሷም ፡ የተቀመጡ ፡ ይቀጣሉ ፤ ስለዚህ ፥ የምድር ፡ ሰዎች ፡ ይቃጠላሉ ፥ ጥቂት ፡ ሰዎችም ፡ ይቀራሉ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አለቀሰች ፥ የወይን ፡ ንግድ ፡ ደከመች ፥ ልባቸው ፡ ደስ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ተከዙ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ የከበሮው ፡ ሐሤት ፡ ቀርቷል ፥ የደስተኞች ፡ ድምፅ ፡ ዝም ፡ ብሏል ፥ የመሰንቆ ፡ ደስታ ፡ ቀርቷል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ እየዘፈኑም ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ አይጠጡትም ፥ የሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ ለሚጠጡት ፡ መራራ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ባድማ ፡ የኾነችው ፡ ከተማ ፡ ፈረሰች ፤ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ማንም ፡ እንዳይገባበት ፡ ተዘጋ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ስለወይኑም ፡ ጠጅ ፡ በአደባባይ ፡ ጩኸት ፡ ይኾናል ፤ ደስታ ፡ ኹሉ ፡ ጨልሟል ፥ የምድርም ፡ ሐሤት ፡ ፈርሷል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ከተማዪቱም ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፥ በሯም ፡ በጥፋት ፡ ተመትቷል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ የወይራን ፡ ዛፍ ፡ እንደ ፡ መምታት ፥ ከወይንም ፡ መከር ፡ በኋላ ፡ ቃርሚያውን ፡ እንደ ፡ መልቀም ፥ እንዲሁ ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ እነዚህ ፡ ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፥ እልልም ፡ ይላሉ ፥ ስለእግዚአብሔር ፡ ክብርም ፡ ከባሕር ፡ ይጣራሉ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔርን ፡ በምሥራቅ ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ በባሕር ፡ ደሴቶች ፡ አክብሩ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ለጻድቁ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፡ የሚለውን ፡ ዝማሬ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ሰምተናል ። እኔ ፡ ግን ፦ ከሳኹ ፥ ከሳኹ ፥ ወዮልኝ! ፡ ወንጀለኞች ፡ ወንጀለዋል ፤ ወንጀለኞች ፡ እጅግ ፡ ወንጀለዋል ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ፥ ፍርሀትና ፡ ገደል ፡ ወጥመድም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አሉ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ የሰማይ ፡ መስኮቶች ፡ ተከፍተዋልና ፥ የምድርም ፡ መሠረት ፡ ተናውጣለችና ፥ ከፍርሀት ፡ ድምፅ ፡ የሸሸ ፡ በገደል ፡ ይወድቃል ፥ ከገደልም ፡ የወጣ ፡ በወጥመድ ፡ ይያዛል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ምድር ፡ ተሰባበረች ፥ ምድር ፡ ፈጽማ ፡ ደቀቀች ፥ ምድር ፡ ተነዋወጠች ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ምድር ፡ እንደ ፡ ሰካር ፡ ሰው ፡ ትንገዳገዳለች ፥ እንደ ፡ ዳስም ፡ ትወዛወዛለች ፤ መተላለፏ ፡ ይከብድባታል ፥ ትወድቅማለች ፥ ደግማም ፡ አትነሣም ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንደዚህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ በከፍታ ፡ ያለውን ፡ ሰራዊት ፡ በከፍታ ፡ ላይ ፥ በምድርም ፡ ያሉትን ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይቀጣቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ግዞተኞች ፡ በጕድጓድ ፡ እንደሚከማቹ ፡ በአንድነት ፡ ይከማቻሉ ፥ በግዞት ፡ ቤትም ፡ ውስጥ ፡ ተዘግተው ፡ ይኖራሉ ፥ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ይጐበኛሉ ።

ኢሳ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡
ይነግሣልና ፥ በሽማግሌዎቹም ፡ ፊት ፡ ክብር ፡ ይኾናልና ፥ ጨረቃ ፡ ይታወካል ፡ ፀሐይም ፡ ያፍራል ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ። _____

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፤ ድንቅን ፡ ነገር ፡ የዱሮ ፡ ምክርን ፡ በታማኝነትና ፡ በእውነት ፡
አድርገኻልና ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርግኻለኹ ፥ ስምኽንም ፡ አመሰግናለኹ ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ከተማዪቱን ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፥ የተመሸገችውን ፡ ከተማ ፡ ውድማ ፡
እንድትኾን ፥ የኃጥኣንንም ፡ አዳራሽ ፡ ከተማ ፡ እንዳትኾን ፡ አድርገኻል ፤ ከቶ ፡ አትሠራም ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ኀያላኑ ፡ ወገኖች ፡ ያከብሩኻል ፥ የጨካኞች ፡ አሕዛብ ፡ ከተማም ፡ ትፈራኻለች ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ የጨካኞችም ፡ ቍጣ ፡ እስትንፋስ ፡ ቅጥርን ፡ እንደሚመታ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ በኾነ ፡
ጊዜ ፥ ለድኻው ፡ መጠጊያ ፥ ለችግረኛው ፡ በጭንቁ ፡ ጊዜ ፡ መጠጊያ ፥ ከውሽንፍር ፡ መሸሸጊያ ፡ ከሙቀትም ፡ ጥላ ፡
ኾነኻል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሙቀት ፡ በደረቅ ፡ ስፍራ ፡ የኃጥኣንን ፡ ጩኸት ፡ ዝም ፡ ታሠኛለኽ ፤ ሙቀትም ፡
በደመና ፡ ጥላ ፡ እንዲበርድ ፡ እንዲሁ ፡ የጨካኞች ፡ ዝማሬ ፡ ይዋረዳል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ የሰባ ፡
ግብዣ ፥ ያረጀ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ቅልጥም ፡ የሞላባቸው ፡ የሰቡ ፡ ነገሮች ፥ የጥሩና ፡ ያረጀ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ግብዣ ፡
ያደርጋል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ በዚህም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ በወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተጣለውን ፡ መጋረጃ ፥ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡
ላይ ፡ የተዘረጋውን ፡ መሸፈኛ ፡ ያጠፋል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ሞትን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይውጣል ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከፊት ፡ ኹሉ ፡ እንባን ፡
ያብሳል ፥ የሕዝቡን ፡ ስድብ ፡ ከምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያስወግዳል ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፦ እንሆ ፥ አምላካችን ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ተስፋ ፡
አድርገነዋል ፥ ያድነንማል ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ጠብቀነዋል ፤ በማዳኑ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ሐሤትም ፡
እናደርጋለን ፡ ይባላል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ታርፋለች ፥ ሞድም ፡ በሞቃ ፡ ውስጥ ፡
እንደሚረገጥ ፡ እንዲሁ ፡ ሞዐብ ፡ በስፍራው ፡ ይረገጣል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ ዋናተኛም ፡ ሰዋኝ ፡ እጁን ፡ እንደሚዘረጋ ፥ እንዲሁ ፡ በመካከሉ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ፤ ነገር ፡
ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ትዕቢቱን ፡ ከእጁ ፡ ተንከሎ ፡ ጋራ ፡ ያዋርዳል ።

ኢሳ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ የተመሸገውንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለውንም ፡ ቅጥርኽን ፡ ዝቅ ፡
ያደርገዋል ፥ ያዋርደውማል ፥ ወደ ፡ መሬትም ፡ እስከ ፡ ዐፈር ፡ ድረስ ፡ ይጥለዋል ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ። _____

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ቅኔ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይዘመራል ። የጸናች ፡ ከተማ ፡
አለችን ፤ ለቅጥርና ፡ ለምሽግ ፡ መድኀኒትን ፡ ያኖርባታል ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ እውነትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ጻድቅ ፡ ሕዝብ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ በሮችን ፡ ክፈቱ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ባንተ ፡ ታምናለችና ፡ ባንተ ፡ ለምትደገፍ ፡ ነፍስ ፡ ፈጽመኽ ፡ በሰላም ፡ ትጠብቃታለኽ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ዐምባ ፡ ነውና ፥ ለዘለዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ በከፍታ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሰዎች ፡ ዝቅ ፡ ያደርጋል ፤ ከፍ ፡ ያለችውን ፡ ከተማ ፡ ያዋርዳል ፥ እስከ ፡ መሬትም ፡ ድረስ ፡ ያዋርዳታል ፥ እስከ ፡ ዐፈርም ፡ ድረስ ፡ ይጥላታል ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ እግር ፥ የድኻ ፡ እግርም ፡ የችግረኛም ፡ አረጋገጥ ፥ ትረግጣታለች ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ የጻድቃን ፡ መንገድ ፡ ቅን ፡ ናት ፤ አንተ ፡ ቅን ፡ የኾንኽ ፡ የጻድቃንን ፡ መንገድ ፡ ታቃናለኽ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ አቤቱ ፥ በፍርድኽ ፡ መንገድ ፡ ተስፋ ፡ አድርገንኻል ፥ ስምኽም ፡ መታሰቢያኽም ፡ የነፍሳችን ፡ ምኞት ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ፍርድኽን ፡ በምድር ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ በዓለም ፡ የሚኖሩት ፡ ጽድቅን ፡ ይማራሉና ፡ ነፍሴ ፡ በሌሊት ፡ ትናፍቅኻለች ፥ መንፈሴም ፡ በውስጤ ፡ ወዳንተ ፡ ትገሠግሣለች ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ለኀጢአተኛ ፡ ሞገስ ፡ ቢደረግለት ፡ ጽድቅን ፡ አይማርም ፤ በቅኖች ፡ ምድር ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ያደርጋል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ግርማ ፡ አያይም ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ አቤቱ ፥ እጅኽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለች ፡ አላዩምም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ያለኽን ፡ ቅንአት ፡ አይተው ፡ ያፍራሉ ፤ እሳትም ፡ ጠላቶችኽን ፡ ትበላለች ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ ሥራችንን ፡ ኹሉ ፡ ሠርተኽልናልና ፥ ሰላምን ፡ ትሰጠናለኽ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ሌላዎች ፡ ጌታዎች ፡ ገዝተውናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባንተ ፡ ብቻ ፡ ስምኽን ፡ እናስባለን ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ እነርሱ ፡ ሞተዋል ፥ በሕይወት ፡ አይኖሩም ፤ ጠፍተዋል ፥ አይነሡም ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፡ ጐብኝተኻቸዋል ፥ አጥፍተኻቸውማል ፥ መታሰቢያቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ አድርገኻል ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ሕዝብን ፡ አበዛኽ ፥ አቤቱ ፥ ሕዝብን ፡ አበዛኽ ፤ አንተም ፡ ተከበርኽ ፥ የአገሪቱንም ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፡ አሰፋኽ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ፈለጉኽ ፥ በገሰጽኻቸውም ፡ ጊዜ ፡ ልመናቸውን ፡ ወዳንተ ፡ አፈሰሱ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ የፀነሰች ፡ ሴት ፡ ለመውለድ ፡ ስትቀርብ ፡ እንደምትጨነቅና ፡ በምጥ ፡ እንደምትጮኽ ፥ አቤቱ ፥ እንዲሁ ፡ በፊትኽ ፡ ኾነናል ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ እኛ ፡ ፀንሰናል ፡ ምጥም ፡ ይዞናል ፥ ነፋስንም ፡ እንደምንወልድ ፡ ኾነናል ፤ በምድርም ፡ ደኅንነት ፡ አላደረግነም ፤ በዓለምም ፡ የሚኖሩ ፡ ይወድቃሉ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ሙታንኽ ፡ ሕያዋን ፡ ይኾናሉ ፥ ሬሳዎችም ፡ ይነሣሉ ። በምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ጠልኽ ፡ የብርሃን ፡ ጠል ፡ ነውና ፥ ምድርም ፡ ሙታንን ፡ ታወጣለችና ፡ ንቁ ፡ ዘምሩም ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ና ፡ ወደ ፡ ቤትኽም ፡ ግባ ፥ ደጅኽን ፡ በኋላኽ ፡ ዝጋ ፤ ቊጣ ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተሸሸግ ።

ኢሳ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ በምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ በበደላቸው ፡ ምክንያት ፡ ቊጣውን ፡ ያመጣባቸው ፡ ዘንድ ፥ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከስፍራው ፡ ይወጣል ፤ ምድርም ፡ ደሟን ፡ ትገልጣለች ፥ ሙታኗንም ፡ ከእንግዲህ ፡

ወዲህ ፡ አትከድንም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣኑን ፡ እባብ ፡ ሌዋታንን ፡ ጠማማውንም ፡ እባብ ፡ ሌዋታንን ፡ በጠንካራ ፡ በታላቅም ፡ በብርቱም ፡ ሰይፍ ፡ ይቀጣል ፥ በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ዘንዶ ፡ ይገድላል ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ለተወደደው ፡ የወይን ፡ ቦታ ፡ ተቀኙለት ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠባቂው ፡ ነኝ ፤ ዘወትር ፡ አጠጣዋለኹ ፤ ማንም ፡ እንዳይጐዳው ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ እጠብቀዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ አልቈጣም ፤ ሾኽና ፡ ኵርንችት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ምነው ፡ በሰልፍ ፡ በነበሩ! ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ተራምጄ ፡ በአንድነት ፡ ባቃጠልኋቸው ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ወይም ፡ ጕልበቴን ፡ ይያዝ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ ያድርግ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ሰላም ፡ ያድርግ ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ያዕቆብ ፡ ሥር ፡ ይሰዳል ፥ እስራኤልም ፡ ያብባል ፡ ይጨበጭብማል ፤ በፍሬያቸውም ፡ የዓለሙን ፡ ፊት ፡ ይሞላሉ ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ በእውኑ ፡ የመቱትን ፡ እንደ ፡ መታ ፡ እንዲሁ ፡ ርሱን ፡ መታውን ፧ ወይስ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተገደሉበት ፡ መገደል ፡ ርሱ ፡ ተገድሏልን ፧

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ነዳቸው ፡ ሰደዳቸው ፡ ቀሠፋቸው ፤ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ እንደሚነፍስበት ፡ ቀን ፡ በጠንካራ ፡ ዐውሎ ፡ አስወገዳቸው ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ስለዚህም ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችና ፡ የፀሓይ ፡ ምስሎች ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይነሡ ፡ የመሠዊያውን ፡ ድንጋይ ፡ ዘሉ ፡ እንደ ፡ ደቀቀ ፡ እንደ ፡ ኖራ ፡ ድንጋይ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፥ እንዲሁ ፡ የያዕቆብ ፡ በደል ፡ ይሰረያል ፥ ይህም ፡ ኀጢአትን ፡ የማስወገድ ፡ ፍሬ ፡ ዘሉ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ የተመሸገችው ፡ ከተማ ፡ ብቻዋን ፡ ኾነች ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾና ፡ የተፈታችና ፡ የተተወች ፡ መኖሪያ ፡ ናት ፤ በዚያም ፡ ጥጃ ፡ ይሰማራል ፡ በዚያም ፡ ይተኛል ፡ ቅርንጫፉንም ፡ ይበላል ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ ጫፎቿ ፡ በደረቁ ፡ ጊዜ ፡ ይሰበራሉ ፥ ሴቶችም ፡ መጥተው ፡ ያቃጥሏቸዋል ፤ የማያስተውል ፡ ሕዝብ ፡ ነውና ፥ ስለዚህ ፡ ፈጣሪው ፡ አይራራለትም ፡ ሠሪውም ፡ ምሕረት ፡ አያደርግለትም ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔር ፡ ከወንዝ ፡ ፈሳሽ ፡ ዠምሮ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ እኽሉን ፡ ይወቃል ፥ እናንተም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ባንድ ፡ ትሰበሰባላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ታላቅ ፡ መለከት ፡ ይነፋል ፥ በአሶርም ፡ የጠፉ ፥ በግብጽ ፡ ምድርም ፡ የተሰደዱ ፡ ይመጣሉ ፥ በተቀደሰውም ፡ ተራራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዳሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ ለኤፍሬም ፡ ሰካሮች ፡ ትዕቢት ፡ አክሊል ፥ በወይን ፡ ጠጅ ፡ ለተሸነፉ ፡ በወፍራም ፡ ሸለቋቸው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ላለችም ፡ ለረገፈች ፡ ለክብሩ ፡ ጌጥ ፡ አበባ ፡ ወዮ! ፡

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ እንሆ ፥ በጌታ ፡ ዘንድ ፡ ኀያል ፡ ብርቱ ፡ የኾነ ፡ አለ ። እንደ ፡ በረዶ ፡ ወጨፎ ፥ እንደሚያጠፋም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥ እንደሚያጥለቀልቅም ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ በጠነከረ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይጥላል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ የኤፍሬም ፡ ሰካሮች ፡ ትዕቢት ፡ አክሊል ፡ በእግር ፡ ይረገጣል ፤

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ በወፍራሙ ፡ ሸለቆ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ የረገፈች ፡ የክብሩ ፡ ጌጥ ፡ አበባ ፡ ከመከር ፡ በፊት ፡ አስቀድማ ፡ እንደምትበስል ፡ በለስ ፡ ትኾናለች ፤ ሰው ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ በእጁ ፡ እንዳለች ፡ ይበላታል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቀሩት ፡ ሕዝቡ ፡ የክብር ፡ ዘውድና ፡ የጌጥ ፡ አክሊል ፡ ይኾናል ፤

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ላይ ፡ ለሚቀመጥም ፡ የፍርድ ፡ መንፈስ ፥ ሰልፉን ፡ ወደ ፡ በር ፡ ለሚመልሱም ፡ ኀይል ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ የተነሣ ፡ ይስታሉ ፥ ከሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡ ይፋንናሉ ፤ ካህኑና ፡ ነቢዩ ፡ ከሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡ ይስታሉ ፥ በወይን ፡ ጠጅም ፡ ይዋጣሉ ፥ ከሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ የተነሣ ፡ ይፋንናሉ ፤ በራእይ ፡ ይስታሉ ፥ በፍርድም ፡ ይሰናከላሉ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ ማእዱ ፡ ሹሉ ፡ ትፋትንና ፡ ርኵሰትን ፡ ተሞልቷታል ፤ ንጹሕ ፡ ስፍራ ፡ እንኳ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ዕውቀትን ፡ ለማን ፡ ያስተምረዋል ፧ ወይስ ፡ ወሬ ፡ ማስተዋልን ፡ ለማን ፡ ይሰጣል ፧ ወተትን ፡ ለተዉ ፡ ወይስ ፡ ጡትን ፡ ለጣሉ ፡ ነውን ፧

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ጥቂት ፡ በዚህ ፡ ጥቂት ፡ በዚያ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ በባዕድ ፡ አፍ ፡ በልዩም ፡ ልሳን ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ይናገራል ፤ ርሱም ፦ ዕረፍት ፡ ይህች ፡ ናት ፥

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ የደከመውን ፡ አሳርፉ ፤ ይህችም ፡ ማረፊያ ፡ ናት ፡ አላቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ መስማትን ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ኼደው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲወድቁ ፥ እንዲሰበሩም ፥ ተጠምደውም ፡ እንዲያዙ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ትእዛዝ ፡ በትእዛዝ ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ሥርዐት ፡ በሥርዐት ፥ ጥቂት ፡ በዚህ ፡ ጥቂት ፡ በዚያ ፡ ይኾንላቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ያለውን ፡ ሕዝብ ፡ የምትገዙ ፡ ፈዘኞች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ እናንተም ፦ ከሞት ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርገናል ፥ ከሲኦልም ፡ ጋራ ፡ ተማምለናል ፤ ሐሰትን ፡ መሸሸጊያችን ፡ አድርገናልና ፥ በሐሰትም ፡ ተሰውረናልና ፥ የሚትረፈረፍ ፡ መቅሠፍት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ አይደርስብንም ፡ ስላላችኹ ፥

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በጽዮን ፡ ድንጋይን ፡ ለመሠረት ፡ አስቀምጣለኹ ፤ የተፈተነውን ፥ የከበረውን ፥ መሠረቱ ፡ የጸናውን ፡ የማእዘን ፡ ድንጋይ ፤ የሚያምን ፡ አያፍርም ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ለገመድ ፡ ፍርድን ፡ ለቱንቢም ፡ ጽድቅን ፡ አደርጋለኹ ፤ በረዶውም ፡ የሐሰትን ፡ መሸሸጊያ ፡ ይጠርጋል ፥ ውሃዎችም ፡ መሰወሪያውን ፡ ያሰጥማሉ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ ከሞትም ፡ ጋራ ፡ ያደረጋችኹት ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይፈርሳል ፥ ከሲኦልም ፡ ጋራ ፡ የተማማላችኹት ፡ መሐላ ፡ አይጸናም ፤ የሚትረፈረፍ ፡ መቅሠፍት ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ትረገጡበታላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ ባለፈም ፡ ጊዜ ፡ ይወስዳችኋል ፤ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ያልፋል ፤ ወሬውንም ፡

ማስተዋል ፡ ድንጋጤ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ ሰው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ ቢተኛ ፡ ዐልጋው ፡ ዐጪር ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ሰውነቱን ፡ መሸፈን ፡ ቢወድ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ጠባብ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሥራውን ፡ ማለት ፡ እንግዳ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፥ አድራጎቱንም ፡ ማለት ፡ ያልታወቀውን ፡ አድራጎቱን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ በፐራሲም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይነሣል ፥ በገባዖንም ፡ ሸለቆ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ይቈጣል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ አኹንም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚጸናውን ፡ የጥፋት ፡ ትእዛዝ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ሰምቻለኹና ፥ እስራት ፡ እንዳይጸናባችኹ ፡ አታፊዙ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 23 ፤ አድምጡ ፥ ድምፄንም ፡ ስሙ ፤ ልብ ፡ አድርጉ ፥ ንግግሬንም ፡ ስሙ ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 24 ፤ በእውኑ ፡ ገበሬ ፡ ሊዘራ ፡ ኹልጊዜ ፡ ያርሳልን ፧ ወይስ ፡ ኹልጊዜ ፡ ዕርሻውን ፡ ይገለግላልን ፧

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 25 ፤ ጓሉንስ ፡ ይከሰክሳልን ፧ ዕርሻውን ፡ ባስተካከለ ፡ ጊዜ ፡ ጥቁሩን ፡ አዝሙድ ፥ ከሙኑንም ፥ ስንዴውንም ፡ በተርታ ፥ ገብሱንም ፡ በስፍራው ፥ ዐጃንም ፡ በደረጃው ፡ የሚዘራ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 26 ፤ ይህንም ፡ ብልኀት ፡ አምላኩ ፡ ያስታውቀዋል ፡ ያስተምረውማል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 27 ፤ ጥቁሩ ፡ አዝሙድ ፡ በተሳለች ፡ መኼጃ ፡ አያኼድም ፥ የሠረገላም ፡ መንኰራኵር ፡ በከሙን ፡ ላይ ፡ አይዞርም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጥቁሩ ፡ አዝሙድ ፡ በሽመል ፥ ከሙኑም ፡ በበትር ፡ ይወቃል ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 28 ፤ የእንጀራ ፡ እኽል ፡ ይደቃልን ፧ ለዘለዓለም ፡ አያኼደውም ፤ የሠረገላውን ፡ መንኰራኵርና ፡ ፈረሶቹን ፡ ምንም ፡ ቢያስኬድበት ፡ አያደቀውም ።

ኢሳ. ፡ 28 ፡ 29 ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ድንቅ ፡ ምክር ፡ ከሚመክር ፡ በግብሩም ፡ ማለፊያ ፡ ከኾነው ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወጥቷል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 1 ፤ ዳዊት ፡ ለሰፈረባት ፡ ከተማ ፡ ለአርኤል ፡ ወዮላት! ፡ ዓመት ፡ በዓመት ፡ ላይ ፡ ጨምሩ ፥ በዓላትም ፡ ይመለሱ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 2 ፤ አርኤልንም ፡ አስጨንቃለኹ ፥ ልቅሶና ፡ ዋይታም ፡ ይኾንባታል ፤ እንደ ፡ አርኤልም ፡ ትኾንልኛለች ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 3 ፤ በዙሪያሽም ፡ እሰፍራለኹ ፥ በቅጥርም ፡ ከብቤ ፡ አስጨንቅሻለኹ ፥ ዐምባም ፡ በላይሽ ፡ አቆማለኹ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 4 ፤ ትዋረጂማለሽ ፥ በመሬትም ፡ ላይ ፡ ኾነሽ ፡ ትናገሪያለሽ ፥ ቃልሽም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ከዐፈር ፡ ይወጣል ፤ ድምፅሽም ፡ ከመሬት ፡ እንደሚወጣ ፡ እንደ ፡ መናፍስት ፡ ጠሪ ፡ ድምፅ ፡ ይኾናል ፥ ቃልሽም ፡ ከዐፈር ፡ ወጥቶ ፡ ይጮኻል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የጠላቶችሽ ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ደቀቀ ፡ ትቢያ ፥ የጨካኞችም ፡ ብዛት ፡ እንደሚያልፍ ፡ ገለባ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 6 ፤ ድንገትም ፡ ፈጥኖ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነጐድጓድ ፥ በምድርም ፡ መናወጥ ፥ በታላቅም ፡ ድምፅ ፥ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፥ በወጨፎም ፥ በምትበላም ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ይጐበኛታል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 7 ፤ በአርኤልም ፡ ላይ ፡ የሚዋጉ ፥ ርሷንና ፡ ምሽጓንም ፡ የሚወጉ ፡ የሚያስጨንቋትም ፥ የአሕዛብ ፡
ኹሉ ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ሕልምና ፡ እንደ ፡ ሌሊት ፡ ራእይ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ተርቦም ፡ እንደሚያልም ፡ ሰው ፡ ይኾናል ፤ በሕልሙም ፥ እንሆ ፥ ይበላል ፥ ነገር ፡
ግን ፥ ይነቃል ፡ ሰውነቱም ፡ ባዶ ፡ ነው ፤ ተጠምቶም ፡ እንደሚያልም ፡ ሰው ፡
ይኾናል ፤ በሕልሙም ፥ እንሆ ፥ ይጠጣል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይነቃል ፥ እንሆም ፥ ይዝላል ፡ ሰውነቱም ፡ አምሮት ፡
አለው ፤ እንዲሁ ፡ የጽዮንን ፡ ተራራ ፡ የሚወጉ ፡ የአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ብዛት ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ ተደነቁ ፡ ደንግጡም ፤ ተጨፈኑም ፡ ዕውሮችም ፡ ኹኑ ፤ በወይን ፡ ጠጅ ፡ አይኹን ፡ እንጂ ፡
ሰከሩ ፤ በሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ አይኹን ፡ እንጂ ፡ ተንገደገዱ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የእንቅልፍ ፡ መንፈስ ፡ አፍሶባችኋል ፡ ዐይኖቻችኹን ፡ ነቢያትንም ፡
ጨፍኖባችኋል ፡ ራሶቻችኹን ፡ ባለራእዮችን ፡ ሸፍኖባችኋል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ ራእዩም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ታተመ ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ኾኖባችኋል ፤ ማንበብንም ፡
ለሚያውቅ ፦ ይህን ፡ አንብ ፡ ብለው ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፦ ታትሟልና ፥ አልችልም ፡ ይላቸዋል ፤

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ ደግሞም ፡ መጽሐፉን ፡ ማንበብን ፡ ለማያውቅ ፦ ይህን ፡ አንብ ፡ ብለው ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፡
ርሱ ፦ ማንበብ ፡ አላውቅም ፡ ይላቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ ጌታም ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በአፉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይቀርባልና ፥ በከንፈሮቹም ፡ ያከብረኛልና ፥ ልቡ ፡
ግን ፡ ከእኔ ፡ የራቀ ፡ ነውና ፥ በሰዎች ፡ ሥርዐትና ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ ይፈራኛልና ፥

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ድንቅ ፡ ነገርን ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፥ ድንቅ ፡ ነገርን ፡
ተኣምራትንም ፥ እንደ ፡ ገና ፡ አደርጋለኹ ፤ የጥበበኞችም ፡ ጥበብ ፡ ትጠፋለች ፥ የአስተዋዮችም ፡ ማስተዋል ፡
ትሰወራለች ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ ምክራቸውን ፡ ጥልቅ ፡ አድርገው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለሚሰውሩ ፥ ሥራቸውንም ፡ በጨለማ ፡
ውስጥ ፡ አድርገው ። ማን ፡ ያየናል ፧ ወይስ ፡ ማን ፡ ያውቀናል ፧ ለሚሉ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ ይህ ፡ የእናንተ ፡ ጠማምነት ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ጭቃ ፡ የምትቈጠሩ ፡
አይደላችኹምን ፧ በእውኑ ፡ ሥራ ፡ ሠሪውን ፦ አልሠራኸኝም ፡ ይለዋልን ፧ ወይስ ፡ የተደረገው ፡
አድራጊውን ፦ አታስተውልም ፡ ይለዋልን ፧

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ ሊባኖስ ፡ እንደ ፡ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ ሊለወጥ ፡ ፍሬያማውም ፡ ዕርሻ ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ሊቈጠር ፡
ጥቂት ፡ ዘመን ፡ የቀረ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ደንቈሮዎች ፡ የመጽሐፍን ፡ ቃል ፡ ይሰማሉ ፥ የዕውሮችም ፡ ዐይኖች ፡
ከጭጋግና ፡ ከጨለማ ፡ ተለይተው ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ የዋሃን ፡ ደስታቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያበዛሉ ፥ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ችግረኞችም ፡
ሐሤትን ፡ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ያደርጋሉ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ ጨካኙ ፡ ሰው ፡ አልቋልና ፥ ፈዘኛውም ፡ ጠፍቷልና ፥ ለኀጢአትም ፡ የደፈጡ ፡ ኹሉ ፡
ይቈረጣሉና ፤

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ እነዚህም ፡ ሰውን ፡ በነገር ፡ በደለኛ ፡ የሚያደርጉ ፥ በበርም ፡ ለሚገሥጸው ፡ አሽክላ ፡
የሚያኖሩ ፥ ጻድቁንም ፡ በከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያስቱ ፡ ናቸው ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ አብርሃምን ፡ የተቤዠ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስለያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያዕቆብ ፡ አኹን ፡ አያፍርም ፥ ፊቱም ፡ አኹን ፡ አይለወጥም ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእጄን ፡ ሥራ ፡ ልጆቹን ፡ በመካከሉ ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ ስሜን ፡ ይቀድሳሉ ፤ የያዕቆብንም ፡ ቅዱስ ፡ ይቀድሳሉ ፥ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ ይፈራሉ ።

ኢሳ. ፡ 29 ፡ 24 ፤ በመንፈስም ፡ የሳቱ ፡ ማስተዋልን ፡ ያውቃሉ ፥ የሚያጉረመርሙም ፡ ትምህርትን ፡ ይቀበላሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ ለዐመፀኞች ፡ ልጆች ፡ ወዮላቸው! ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነን ፡ ምክር ፡ ይመክራሉ ፥ ኀጢአትንም ፡ በኀጢአት ፡ ላይ ፡ ይጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ ከመንፈሴ ፡ ዘንድ ፡ ያልኾነውን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያደርጋሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ ከአፌም ፡ ነገርን ፡ ሳይጠይቁ ፡ በፈርዖን ፡ ኀይል ፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ በግብጽም ፡ ጥላ ፡ ይታመኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ እንዲወርዱ ፡ ይኼዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ የፈርዖን ፡ ኀይል ፡ ዕፍረት ፥ በግብጽም ፡ ጥላ ፡ መታመን ፡ ስድብ ፡ ይኾንባችኋል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ አለቃዎች ፡ ምንም ፡ በጣኔዎስ ፡ ቢኾኑ ፥ መልክተኞችም ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሐኔስ ፡ ቢደርሱ ፥

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ ዅላቸው ፡ ይጠቅሟቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለማይችሉ ፥ ዕፍረትና ፡ ስድብ ፡ እንጂ ፡ ረድኤትና ፡ ረብ ፡ ስለማይኾኑ ፡ ሕዝብ ፡ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ በደቡብ ፡ ስላሉ ፡ እንስሳዎች ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ። ተባትና ፡ እንስት ፡ አንበሳ ፡ እፍኝትም ፡ ነዘር ፡ እባብም ፡ በሚወጡባት ፡ በመከራና ፡ በጭንቀት ፡ ምድር ፡ በኩል ፡ ብልጥግናቸውን ፡ በአህያዎች ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ መዛግብቶቻቸውንም ፡ በግመሎች ፡ ሻኛ ፡ ላይ ፡ እየጫኑ ፡ ወደማይጠቅሟቸው ፡ ሕዝብ ፡ ይኼዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ የግብጽ ፡ ርዳታ ፡ ከንቱና ፡ ምናምን ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ስሙን ፦ በቤት ፡ የሚቀመጥ ፡ ረዓብ ፡ ብዬ ፡ ጠርቼዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ ኺድ ፥ ለሚመጣውም ፡ ዘመን ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኾን ፡ በሰሌዳ ፡ ላይ ፡ በመጽሐፍም ፡ ውስጥ ፡ ጻፍላቸው ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ ዐመፀኛ ፡ ወገንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ለመስማት ፡ የማይወዱ ፡ የሐሰት ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፤

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ ባለራእዮችን ፦ አትመልከቱ ፡ ይላሉ ፥ ነቢያትንም ፦ ጣፋጭንና ፡ አታላዩን ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ቅኑን ፡ ነገር ፡ አትንገሩን ፡ ከመንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፥

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ ከጐዳናውም ፡ ዘወር ፡ በሉ ፥ የእስራኤልንም ፡ ቅዱስ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አስወግዱ ፡ ይሏቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህችን ፡ ቃል ፡ አቃላችኋልና ፥ በግፍና ፡ በጠማምነት ፡ ታምናችኋልና ፥ በርሱም ፡ ተደግፋችኋልና ፥

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ይህ ፡ በደል ፡ አዘብዝቦ ፡ ለመፍረስ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፥ አፈራረሱም ፡ ፈጥኖ ፡ ድንገት ፡ እንደሚመጣ ፡ እንደ ፡ ረኸም ፡ ቅጥር ፡ ይኾንባችኋል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ የሸክለኛ ፡ ማድጋ ፡ እንደሚሰበር ፡ ይሰብረዋል ፥ ሳይራራም ፡ ያደቀዋል ፤ ከስባሪውም ፡ እሳት ፡ ከማንደጃ ፡ የሚወስዱበት ፡ ወይም ፡ ውሃ ፡ ከጕድጓድ ፡ የሚቀዱበት ፡ ገል ፡ አይገኝም ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በመመለስና ፡ በማረፍ ፡ ትድናላችኹ ፤ በጸጥታና ፡ በመታመን ፡ ኀይል ፡ ይኾንላችኋል ፤ እናንተም ፡ እንቢ ፡ አላችኹ ፥

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠን ፡ እንሸሻለን ፡ እንጂ ፡ እንዲህ ፡ አይኾንም ፡ አላችኹ ፥ ስለዚህም ፡ ትሸሻላችኹ ፤ ደግሞም ፦ በፈጣን ፡ ፈረስ ፡ ላይ ፡ እንቀመጣለን ፡ አላችኹ ፥ ስለዚህም ፡ የሚያሳድዷችኹ ፡ ፈጣኖች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ ካንድ ፡ ሰው ፡ ዛቻ ፡ የተነሣ ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ይሸሻሉ ፤ እናንተም ፡ በተራራ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ምሰሶ ፥ በኮረብታም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ምልክት ፡ ኾናችኹ ፡ እስክትቀሩ ፡ ድረስ ፥ ከዐምስት ፡ ሰዎች ፡ ዛቻ ፡ የተነሣ ፡ ትሸሻላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የፍርድ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይራራላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ይታገሣል ፥ ይምራችኹም ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ ርሱን ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ ኹሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ በጽዮን ፡ የምትኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታለቅስም ፤ በጩኸትም ፡ ድምፅ ፡ ይራራልኻል ፥ በሰማኽም ፡ ጊዜ ፡ ይመልስልኻል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ ጌታም ፡ የጭንቀትን ፡ እንጀራና ፡ የመከራን ፡ ውሃ ፡ ቢሰጥኽም ፡ አስተማሪኽ ፡ እንግዲህ ፡ ከአንተ ፡ አይሰወርም ፤ ዐይኖችኽ ፡ ግን ፡ አስተማሪኽን ፡ ያያሉ ፥

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 21 ፤ ወደ ፡ ቀኝም ፡ ወደ ፡ ግራም ፡ ፈቀቅ ፡ ብትል ፡ ጕሮዎችኽ ፡ በኋላኽ ፦ መንገዱ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ በርሷም ፡ ኺድ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ይሰማሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 22 ፤ በብርም ፡ የተለበጡትን ፡ የተቀረጹትን ፡ ምስሎችኽን ፡ በወርቅም ፡ የተለበጡትን ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎችኽን ፡ ታረክሳለኽ ፤ እንደ ፡ ርኩስም ፡ ነገር ፡ ትጥላቸዋለኽ ፦ ወግዱ ፡ ትላቸውማለኽ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 23 ፤ በምድርም ፡ ለተዘራው ፡ ዘርኽ ፡ ዝናብ ፡ ይሰጣል ፥ ከምድርም ፡ ፍሬ ፡ የሚወጣ ፡ እንጀራ ፡ ወፍራምና ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ከብቶችኽ ፡ በሰፊ ፡ መስክ ፡ ይሰማራሉ ፤

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 24 ፤ መሬትንም ፡ የሚያርሱ ፡ በሬዎችና ፡ አህያዎች ፡ በመንሽና ፡ በወንፊት ፡ የነጻውን ፡ ጨው ፡ ጨው ፡ የሚለውን ፡ ገፈራ ፡ ይበላሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 25 ፤ በታላቅም ፡ እልቂት ፡ ቀን ፡ ግንቦች ፡ በወደቁ ፡ ጊዜ ፡ በረኸሮሙ ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ከፍ ፡ ባለውም ፡ ኮረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወንዞችና ፡ የውሃ ፡ ፈሳሾች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሕዝቡን ፡ ስብራት ፡ በጠገነ ፡ ዕለት ፥ መቅሠፍቱ ፡ የቈሰለውንም ፡ በፈወሰ ፡ ዕለት ፥ የጨረቃ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ብርሃን ፥ የፀሓይም ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከሚነድ ፡ ቍጣ ፡ ከሚትጐለጐልም ፡ ጢስ ፡ ጋራ ፡ ከሩቅ ፡ ይመጣል ፤ ከንፈሮቹም ፡ ቍጣን ፡ የሞሉ ፡ ናቸው ፥ ምላሱም ፡ እንደምትበላ ፡ እሳት ፡ ናት ፤

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 28 ፤ እስትንፋሱም ፡ አሕዛብን ፡ በአጥፊ ፡ ወንፊት ፡ ሊነፋቸው ፡ እንደሚያጥለቀልቅ ፡ እስከ ፡ ዐንገትም ፡ እንደሚደርስ ፡ ወንዝ ፡ ነው ፥ በሕዝብም ፡ መንጋጋ ፡ የሚያስት ፡ ልጓም ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 29 ፤ ዝማሬ ፡ በተቀደሰች ፡ የዐውደ ፡ ዓመት ፡ ሌሊት ፡ እንደሚኾን ፡ ዝማሬ ፡ ይኾንላችኋል ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ተራራ ፡ ወደእስራኤል ፡ ዐምባ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢልታ ፡ ይዞ ፡ እንደሚኼድ ፡ ሰው ፡ የልብ ፡ ደስታ ፡ ይኾንላችኋል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ክቡር ፡ ድምፁን ፡ ያሰማል ፥ የክንዱንም ፡ መውረድ ፡ በሚነድ ፡ ቍጣውና ፡ በምትበላ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ በወጨፎም ፡ በበረዶ ፡ ጠጠርም ፡ ይገልጣል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 31 ፤ አሶርም ፡ በበትር ፡ ከመታው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔር ፡ በላዩ ፡ በሚያወርድበት ፡ የታዘዘበቱ ፡ የበትር ፡ ድብደባ ፡ ዥሉ ፡ በከበሮና ፡ በመሰንቆ ፡ ይኾናል ፤ በጦርነትም ፡ ክንዱን ፡ አንሥቶ ፡ ይዋጋቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 30 ፡ 33 ፤ ከቀድሞም ፡ ዠምሮ ፡ የማቃጠያ ፡ ስፍራ ፡ ተዘጋጅታለች ፥ ለንጉሥም ፡ ተበጅታለች ፤ ጥልቅና ፡ ሰፊም ፡ አድርጓታል ፤ እሳትና ፡ ብዙ ፡ ማገዶ ፡ ተከምሯል ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እስትንፋስ ፡ እንደ ፡ ዲን ፡ ፈሳሽ ፡ ያቃጥለዋል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ ርዳታ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ለሚወርዱ ፡ በፈረሶችም ፡ ለሚደገፉ ፥ ስለ ፡ ብዛታቸውም ፡ በሠረገላዎች ፥ እጅግ ፡ ብርቱዎችም ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በፈረሰኞች ፡ ለሚታመኑ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ለማይመለከቱ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ለማይፈልጉ ፡ ወዮላቸው! ፡

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ጠቢብ ፡ ነው ፥ ክፉንም ፡ ነገር ፡ ያመጣል ፥ ቃሉንም ፡ አይመልስም ፥ በክፉም ፡ አድራጊዎች ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ በደልንም ፡ በሚሠሩ ፡ ረዳት ፡ ላይ ፡ ይነሣል ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ ግብጻውያን ፡ ሰዎች ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደሉም ፥ ፈረሶቻቸውም ፡ ሥጋ ፡ እንጂ ፡ መንፈስ ፡ አይደሉም ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጁን ፡ በዘረጋ ፡ ጊዜ ፥ ረጂው ፡ ይሰናከላል ፡ ተረጂውም ፡ ይወድቃል ፥ ዥሉም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይጠፋሉ ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይለኛልና ፦ አንበሳ ፡ ወይም ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ በንጥቂያው ፡ ላይ ፡ ሲያገሣ ፥ ብዙ ፡ እረኞች ፡ ቢከማቹበት ፡ ከቃላቸው ፡ እንደማይፈራ ፡ ከድምፃቸውም ፡ እንደማይዋረድ ፥ እንዲሁ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኰረብታዋ ፡ ላይ ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ይወርዳል ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ እንደሚበር ፡ ወፍ ፡ እንዲሁ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ይጋርዳታል ፤ ይከልላታል ፥ ይታደጋታል ፥ ዐልፎም ፡ ያድናታል ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አጥብቃችኹ ፡ ወደዐመፃችኹበት ፡ ተመለሱ ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ እጆቻቸው ፡ ለኀጢአት ፡ የሠሩላቸውን ፡ የብሩንና ፡ የወርቁን ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ ይጥላሉ ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ አሶርም ፡ የሰው ፡ ባልኾነ ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃል ፥ የሰውም ፡ ያልኾነ ፡ ሰይፍ ፡ ይበላዋል ፤ ከሰይፍም ፡ ይሸሻሉ ፡ ጐበዛዝቱም ፡ ገባሮች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ ዐምባው ፡ ከፍርሀት ፡ የተነሣ ፡ ያልፋል ፥ መሳፍንቱም ፡ ከዐላማው ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ፥ ይላል ፡ እሳቱ ፡ በጽዮን ፡ እቶኑም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የኾነ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ ንጉሥ ፡ በጽድቅ ፡ ይነግሣል ፥ መሳፍንትም ፡ በፍርድ ፡ ይገዛሉ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ ሰውም ፡ ከነፋስ ፡ እንደ ፡ መሸሸጊያ ፡ ከዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደ ፡ መጠጊያ ፥ በጥም ፡ ቦታም ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ ፈሳሽ ፥ በበረሓም ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ድንጋይ ፡ ጥላ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ የሚያዩትም ፡ ሰዎች ፡ ዐይኖች ፡ አይጨፈኑም ፥ የሚሰሙትም ፡ ጐሮዎች ፡ ያደምጣሉ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ ጥንቃቄ ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ዕውቀትን ፡ ታስተውላለች ፥ የተብታቦችም ፡ ምላስ ፡ ደኅና ፡ አድርጋ ፡ ትናገራለች ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰነፍ ፡ ከበርቴ ፡ ተብሎ ፡ አይጠራም ፥ ንፉግም ፡ ለጋስ ፡ አይባልም ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ ሰነፍ ፡ ግን ፡ ስንፍናን ፡ ይናገራል ፥ ልቡም ፡ ዝንጉነትን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ስሕተትን ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ የተራበችውንም ፡ ሰውነት ፡ ባዶ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከተጠማም ፡ ሰው ፡ መጠጥን ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ በደልን ፡ ይሠራል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ የንፉግም ፡ ዕቃ ፡ ክፉ ፡ ናት ፤ ችግረኛ ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ርሱ ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ ድኻውን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ክፉን ፡ ዐሳብ ፡ ያስባል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ ከበርቴ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ለመከበር ፡ ያስባል ፥ በመከበርም ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ዓለመኞች ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ተነሡ ፡ ድምፄንም ፡ ስሙ ፤ እናንተ ፡ ተማምናችኹ ፡ የምትቀመጡ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ንግግሬን ፡ አድምጡ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ እናንተ ፡ ተማምናችኹ ፡ የምትቀመጡ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ወይንን ፡ መቀሥረጥ ፡ ይጠፋልና ፥ ፍሬም ፡ ማከማቸት ፡ አይመጣምና ፡ ከዓመትና ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ትንቀጠቀጣላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ ዓለመኞች ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ ተጠንቀቁ ፤ ተማምናችኹም ፡ የምትቀመጡ ፡ ሆይ ፥ ተንቀጥቀጡ ፤ ልብሳችኹን ፡ አውልቁ ፥ ዕራቊታችኹን ፡ ኹኑ ፥ ወገባችኹንም ፡ በማቅ ፡ ታጠቁ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ ስለተወደደችውም ፡ ዕርሻ ፡ ስለሚያፈራውም ፡ ወይን ፡ ደረታችኹን ፡ ድቁ ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ በሕዝቤ ፡ ምድር ፡ ላይ ፥ በደስታ ፡ ከተማ ፡ ባሉት ፡ በደስታ ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾኽና ፡ ኵርንችት ፡ ይወጣባቸዋል ፤

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ አዳራሹ ፡ ወና ፡ ትኾናለችና ፥ የብዙ ፡ ሰውም ፡ ከተማ ፡ ትለቀቃለችና ፥ ዐምባውና ፡ ግንቡም ፡ ለዘለዓለም ፡ ዋሻ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አህያ ፡ ደስታ ፥ የመንጋዎችም ፡ ማሰማሪያ ፡ ይኾናልና ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ ይህም ፥ መንፈስ ፡ ከላይ ፡ እስኪፈስልን ፥ ምድረ ፡ በዳውም ፡ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ እስኪኾን ፥ ፍሬያማውም ፡ ዕርሻ ፡ ዱር ፡ ተብሎ ፡ እስኪቈጠር ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ፍርድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖራል ፥ ጽድቅም ፡ በፍሬያማው ፡ ዕርሻ ፡ ያድራል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ የጽድቅም ፡ ሥራ ፡ ሰላም ፥ የጽድቅም ፡ ፍሬ ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸጥታና ፡ መታመን ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ ሕዝቤም ፡ በሰላም ፡ ማደሪያ ፡ በታመነም ፡ ቤት ፡ በጸጥተኛ ፡ ማረፊያ ፡ ይቀመጣል ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ በረዶ ፡ ግን ፡ በዱር ፡ ላይ ፡ ይወርዳል ፥ ከተማም ፡ ፈጽማ ፡ ትዋረዳለች ።

ኢሳ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ የበሬና ፡ የአህያ ፡ እግር ፡ እየነዳችኹ ፡ በውሃ ፡ ኹሉ ፡ አጠገብ ፡ የምትዘሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 1 ፤ አንተ ፡ ሳትጠፋ ፡ የምታጠፋ ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ወንጀል ፡ ሳይደረግ ፡ ወንጀል ፡ የምታደርግ ፡

ወዮልኽ! ፡ ማጥፋትን ፡ በተውኽ ፡ ጊዜ ፡ ትጠፋለኽ ፤ መወንጀልንም ፡ በተውኽ ፡ ጊዜ ፡ ይወነጅሉኻል ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 2 ፤ አቤቱ ፥ ማረን ፤ አንተን ፡ ተማምነናል ፤ ጧት ፡ ጧት ፡ ክንድ ፡ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ ማዳን ፡ ኹነን ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 3 ፤ ከፍጅት ፡ ድምፅ ፡ ወገኖች ፡ ሸሹ ፥ በመነሣትኽም ፡ አሕዛብ ፡ ተበተኑ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ አንበጣ ፡ እንደሚሰበስብ ፡ ምርኳችኹ ፡ ትሰበሰባለች ፥ ኵብኵባም ፡ እንደሚዘል ፡ ሰዎች ፡ ይዘሉበታል ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአርያም ፡ ተቀምጧልና ፥ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ጽዮንን ፡ በፍርድና ፡ በጽድቅ ፡ ሞላት ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ የዘመንኽም ፡ ጸጥታ ፥ የመድኀኒት ፡ ብዛት ፥ ጥበብና ፡ ዕውቀት ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ መዝገቡ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ ኀይለኞቻቸው ፡ በሜዳ ፡ ይጮኻሉ ፤ የሰላም ፡ መልእክተኞች ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ ያለቅሳሉ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ መንገዶች ፡ ባድማ ፡ ኾኑ ፥ ተላላፊም ፡ ቀረ ፤ ርሱም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ አፈረሰ ፡ ከተማዎችንም ፡ ናቀ ፡ ሰውንም ፡ አልተመለከተም ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ምድሪቱ ፡ አለቀሰች ፡ ከሳችም ፤ ሊባኖስ ፡ ዐፈረ ፡ ጠወለገም ፤ ሳሮን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነ ፤ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስ ፡ ቅጠላቸውን ፡ አረገፉ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ አኹን ፡ እነሣለኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አኹን ፡ እከበራለኹ ፤ አኹን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እላለኹ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ ገለባን ፡ ትፀንሳላችኹ ፥ እብቅንም ፡ ትወልዳላችኹ ፤ እስትንፋሳችኹ ፡ የምትበላችኹ ፡ እሳት ፡ ናት ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 12 ፤ አሕዛብም ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡ ኖራ ፥ ተቈርጦም ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፡ ሾኽ ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ በሩቅ ፡ ያላችኹ ፡ የሠራኹትን ፡ ስሙ ፥ እናንተም ፡ በቅርብ ፡ ያላችኹ ፡ ኀይሌን ፡ ዕወቁ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ በጽዮን ፡ ያሉ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ፈሩ ፤ መንቀጥቀጥ ፡ ዝንጉዎቹን ፡ ያዘ ፤ ከምትበላ ፡ እሳት ፡ ጋራ ፡ መኖርን ፡ የሚችል ፡ ከእኛ ፡ ማን ፡ አለ ፧ ለዘለዓለምም ፡ ከምትነድ ፡ እሳት ፡ ጋራ ፡ መኖርን ፡ የሚችል ፡ ከእኛ ፡ ማን ፡ አለ ፧

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ በጽድቅ ፡ የሚኼድ ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ የሚናገር ፥ በሽንገላ ፡ የሚገኝ ፡ ትርፍን ፡ የሚንቅ ፥ መማለጃን ፡ ከመጨበጥ ፡ እጁን ፡ የሚያራግፍ ፥ ደም ፡ ማፍሰስን ፡ ከመስማት ፡ ጐሮዎቹን ፡ የሚያደነቍር ፥ ክፋትንም ፡ ከማየት ፡ ዐይኖቹን ፡ የሚጨፍን ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጣል ፤ ጠንካራ ፡ ዐምባ ፡ መጠጊያው ፡ ይኾናል ፤ እንጀራም ፡ ይሰጠዋል ፥ ውሃውም ፡ የታመነች ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ንጉሥን ፡ በውበቱ ፡ ያዩታል ፤ እነርሱም ፡ በሩቅ ፡ ያለች ፡ ምድርን ፡ ያይዋታል ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ልብኽም ፦ ጸሓፊ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ መዛኝስ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ግንቦቹንስ ፡ የቈጠረ ፡ ወዴት ፡

አለ ፡፡ ብሎ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነገር ፡ ያስባል ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ ጨካኝን ፡ ሕዝብ ፥ ቋንቋው ፡ ለማስተዋል ፡ ጥልቅ ፡ የኾነውንና ፡ አንደበቱ ፡ ለማስተዋል ፡ ጸያፍ ፡ የኾነውን ፡ ሕዝብ ፥ አታይም ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ የበዓላችንን ፡ ከተማ ፡ ጽዮንን ፡ ተመልከት ፤ ዐይኖችኽ ፡ የሰላም ፡ ማደሪያ ፥ ካስማውም ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይነቀል ፡ አውታሩም ፡ ኹሉ ፡ የማይበጠስ ፥ የማይወገድ ፡ ድንኳን ፡ የኾነውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ የሰፉ ፡ ወንዞችና ፡ የመስኖች ፡ ስፍራ ፡ ኾኖ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ በግርማ ፡ ይኾናል ፤ የሚቀዘፉ ፡ መርከቦች ፡ አይገቡባትም ፥ ታላላቆችም ፡ መርከቦች ፡ አያልፉባትም ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፈራጃችን ፡ ነው ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕግን ፡ ሰጪያችን ፡ ነው ፥ እግዚአብሔር ፡ ንጉሣችን ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ያድነናል ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ ገመዶችኽ ፡ ላልተዋል ፥ ደቀላቸውንም ፡ አላጸኑም ፥ ሸራውንም ፡ መዘርጋት ፡ አልቻሉም ። በዚያም ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ምርኮ ፡ ብዝበዛ ፡ ተከፈለ ፤ ዐንካሳዎች ፡ እንኳ ፡ ብዝበዛውን ፡ በዘበዙ ።

ኢሳ. ፡ 33 ፡ 24 ፤ በዚያም ፡ የሚቀመጥ ፦ ታምሜያለኹ ፡ አይልም ፥ በርሷም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ሰዎች ፡ በደላቸው ፡ ይቅር ፡ ይባልላቸዋል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ቅረቡ ፥ ስሙ ፤ እናንተ ፡ ወገኖች ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፤ ምድርና ፡ መላዋ ፥ ዓለምና ፡ ከርሷ ፡ የሚወጣ ፡ ኹሉ ፡ ይስሙ ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መዓቱም ፡ በሰራዊታቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ፈጽሞ ፡ አጠፋቸው ፥ ለመታረድም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ የተገደሉት ፡ ይጣላሉ ፥ የሬሳቸውም ፡ ግማት ፡ ይሸታል ፥ ተራራዎችም ፡ ከደማቸው ፡ የተነሣ ፡ ይርሳሉ ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 4 ፤ የሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ይበሰብሳሉ ፥ ሰማያትም ፡ እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ ይጠቀለላሉ ፥ ከወይንና ፡ ከበለስም ፡ ቅጠል ፡ እንደሚረግፍ ፡ ሰራዊታቸው ፡ ኹሉ ፡ ይረግፋል ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 5 ፤ ሰይፌ ፡ በሰማይ ፡ ኾና ፡ እስክትረካ ፡ ድረስ ፡ ጠጥታለች ፤ እንሆ ፥ በኤዶምያስና ፡ በረገምኹት ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ለፍርድ ፡ ትወርዳለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕት ፡ በባሶራ ፥ ታላቅም ፡ ዕርድ ፡ በኤዶምያስ ፡ ምድር ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ በደም ፡ ተሞልታለች ፥ በስብም ፥ በበግ ፡ ጠቦትና ፡ በፍየል ፡ ደምም ፥ በአውራም ፡ በግ ፡ ኵላሊት ፡ ስብ ፡ ወፍራለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 7 ፤ ጐሽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፥ ወይፈኖችም ፡ ከኰርማዎች ፡ ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ ምድራቸውም ፡ በደም ፡ ትረካለች ፥ ዐፈራቸውም ፡ በስብ ፡ ትወፍራለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ የበቀሉ ፡ ቀን ፥ ስለጽዮንም ፡ ክርክር ፡ የብድራት ፡ ዓመት ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 9 ፤ የኤዶምያስም ፡ ፈሳሾች ፡ ዝፍት ፡ ኾነው ፡ ይለወጣሉ ፥ ዐፈሯም ፡ ዲን ፡ ይኾናል ፥ መሬቷም ፡ የሚቃጠል ፡ ዝፍት ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 10 ፤ በሌሊትና ፡ በቀንም ፡ አትጠፋም ፥ ጢሷም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይወጣል ፤ ከትውልድ ፡ እስከ ፡

ትውልድም ፡ ድረስ ፡ ባድማ ፡ ኾና ፡ ትኖራለች ፤ ለዘለዓለም ፡ ዓለም ፡ ማንም ፡ አያልፍባትም ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 11 ፤ ጴልፊትና ፡ ጉጕት ፡ ግን ፡ ይወርሷታል ፤ ጕጕትና ፡ ቊራም ፡ ይኖሩባታል ፤ በላይዋም ፡ የመፍረስ ፡ ገመድና ፡ የባዶነት ፡ ቱንቢ ፡ ይዘረጋባታል ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 12 ፤ መሳፍንቷን ፡ ወደ ፡ መንግሥት ፡ ይጠራሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ አይገኝባትም ፤ አለቃዎቿም ፡ ሹሉ ፡ ምናምኖች ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 13 ፤ በአዳራሾቿም ፡ ሾኽ ፡ በቅጥሮቿም ፡ ሳማን ፡ አሜከላ ፡ ይበቅሉባታል ፤ የቀበሮም ፡ ማደሪያና ፡ የሰጐን ፡ ስፍራ ፡ ትኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 14 ፤ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ከተኩላዎች ፡ ጋራ ፡ ይገናኛሉ ፥ አጋንንትም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጠራራሉ ፤ ጅንም (267) ፡ በዚያ ፡ ትኖራለች ፥ ለርሷም ፡ ማረፊያ ፡ ታገኛለች ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 15 ፤ በዚያም ፡ ዋሊያ ፡ ቤቷን ፡ ትሠራለች ፡ ዕንቊላልም ፡ ትጥላለች ፡ ትቀፈቅፈውማለች ፡ ልጆቿንም ፡ በጥላዋ ፡ ትሰበስባለች ፤ በዚያም ፡ ደግሞ ፡ አሞራዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ከባልንጀራዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ይሰበሰባሉ ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 16 ፤ በእግዚአብሔር ፡ መጽሐፍ ፡ ፈልጉ ፥ አንዡም ፤ አፌ ፡ አዟልና ፥ መንፈሱም ፡ ሰብስቧቸዋልና ፥ ከነዚህ ፡ አንዲት ፡ አትጠፋም ፥ ባልንጀራውንም ፡ የሚያጣ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 34 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ ዕጣ ፡ ጣለባቸው ፥ እጁም ፡ በገመድ ፡ ከፈለችላቸው ፤ ለዘለዓለም ፡ ይገዟታል ፥ ከትውልድም ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ ይቀመጡባታል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ ምድረ ፡ በዳውና ፡ ደረቁ ፡ ምድር ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ በረሓውም ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ፡ እንደ ፡ ጽጌ ፡ ረዳም ፡ ያብባል ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ እጅግ ፡ ያብባል ፡ በደስታና ፡ በዝማሬ ፡ ሐሤትን ፡ ያደርጋል ፤ የሊባኖስ ፡ ክብር ፥ የቀርሜሎስና ፡ የሳሮን ፡ ግርማ ፡ ይሰጠዋል ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ክብር ፡ የአምላካችንንም ፡ ግርማ ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ የደከሙትን ፡ እጆች ፡ አበርቱ ፥ የላሉትንም ፡ ጕልበቶች ፡ አጽኑ ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ ፈሪ ፡ ልብ ፡ ላላቸው ፦ እንሆ ፥ አምላካችኹ ፡ በበቀል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ብድራት ፡ ይመጣልና ፥ መጥቶም ፡ ያድናችኋልና ፥ በርቱ ፥ አትፍሩ ፡ በሏቸው ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የዕውሮች ፡ ዐይን ፡ ይገለጣል ፤ የደንቈሮዎችም ፡ ጕሮ ፡ ይከፈታል ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ዐንካሳ ፡ እንደ ፡ ሚዳቋ ፡ ይዘላል ፥ የድዳም ፡ ምላስ ፡ ይዘምራል ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውሃ ፥ በበረሓም ፡ ፈሳሽ ፡ ይፈልቃልና ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ ደረቂቁ ፡ ምድር ፡ ኩሬ ፥ የጥማት ፡ መሬት ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ትኾናለች ፤ ቀበሮ ፡ የተኛበት ፡ መኖሪያ ፡ ልምላሜና ፡ ሸምበቆ ፡ ደንገልም ፡ ይኾንበታል ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ጐዳናና ፡ መንገድ ፡ ይኾናል ፡ ርሱም ፡ የተቀደሰ ፡ መንገድ ፡ ይባላል ፤ ንጹሓንም ፡ ያልኾኑ ፡ አያልፉበትም ፥ ለንጹሓን ፡ ግን ፡ ይኾናል ፤ ተላላፊዎችና ፡ ሰነፎች ፡ እንኳ ፡ አይስቱበትም ።

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ አንበሳም ፡ አይኖርበትም ፥ ነጣቂ ፡ አውሬም ፡ አይወጣበትም ፥ ከዚያም ፡ አይገኙም ፤ የዳኑት ፡

---

267 ዕብ. ፥ ልይልይት ፡ (ሊሊት • የሌሊት ፡ ወፍ ፥ አለዚያም ፡ ጕጕት ፤ ግብረ ፡ አጋንንት ፥ ጥንቈላ) ።

ግን ፡ በዚያ ፡ ይኼዳሉ ፤

ኢሳ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተቤዣቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ እየዘመሩም ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ይመጣሉ ፤ የዘለዓለም ፡ ደስታ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ሐሤትንና ፡ ደስታን ፡ ያገኛሉ ፥ ሐዘንና ፡ ትካዜም ፡ ይሸሻሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ። _____

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በንጉሡ ፡ በሕዝቅያስ ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ወደተመሸጉት ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወጥቶ ፡ ወሰዳቸው ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ራፋስቂስን ፡ ከብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ጋራ ፡ ከለኪሶ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ በዐጣቢው ፡ ዕርሻ ፡ መንገድ ፡ ባለችው ፡ በላይኛዪቱ ፡ ኩሬ ፡ መስኖ ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ የቤቱም ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወጡ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 4 ፤ ራፋስቂስም ፡ አላቸው ፦ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ታላቁ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ የምትታመንበት ፡ መተማመኛ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 5 ፤ እኔ ፦ ለሰልፍ ፡ የኾነው ፡ ምክርኽና ፡ ኀያልኽ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ አልኹ ፤ አኹንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያመፅኸው ፡ በማን ፡ ተማምነኽ ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ በዚህ ፡ በተቀጠቀጠ ፡ በሸምበቆ ፡ በትር ፡ በግብጽ ፡ ትታመናለኽ ፤ ሰው ፡ ቢመረኰዘው ፡ ተሰብሮ ፡ በእጁ ፡ ይገባል ፥ ያቈስለውማል ፤ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ለሚታመኑበት ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 7 ፤ አንተም ፦ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንታመናለን ፡ ብትለኝ ፥ ሕዝቅያስ ፡ ይሁዳንና ፡ ኢየሩሳሌምን ፦ በዚህ ፡ መሠዊያ ፡ ፊት ፡ ስገዱ ፡ ብሎ ፡ የኰረብታ ፡ መስገጃዎቹንና ፡ መሠዊያዎቹን ፡ ይስፈረስ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ከጌታዬ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተወራረድ ፥ የሚቀመጡባቸውንም ፡ ሰዎች ፡ ማግኘት ፡ ቢቻልኽ ፡ እኔ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ፈረሶች ፡ እሰጥኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ሠረገላዎችና ፡ ስለ ፡ ፈረሰኞች ፡ በግብጽ ፡ ስትታመን ፥ ከጌታዬ ፡ ባሪያዎች ፡ የሚያንሰውን ፡ የአንዱን ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ትቃወም ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይቻልኻል ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 10 ፤ አኹንም ፡ በእውኑ ፡ ያለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይህን ፡ አገር ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቻለኹን ፧ እግዚአብሔር ፦ ወደዚህ ፡ አገር ፡ ወጥተኽ ፡ አጥፋው ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 11 ፤ ኤልያቄምና ፡ ሳምናስ ፡ ዮአስም ፡ ራፋስቂስን ፦ እኛ ፡ እንሰማለንና ፡ እባክኽ ፥ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፡ ለባሪያዎችኽ ፡ ተናገር ፤ በቅጥርም ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ሕዝብ ፡ ጕሮሮ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ አትናገረን ፡ አሉት ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ራፋስቂስ ፡ ግን ፦ ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ወዳንተና ፡ ወደ ፡ ጌታኽ ፡ ልኮኛልን ፧ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ዅሳቸውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ሽንታቸውንም ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ ወደተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ አይደለምን ፧ አላቸው ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 13 ፤ ራፋስቂስም ፡ ቆሞ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በአይሁድ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ። የታላቁን ፡ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 14 ፤ ንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፡ ሕዝቅያስ ፡ አያታሎ፞ችኹ ፤

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 15 ፤ ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ በርግጥ ፡ ያድነናል ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንድትታመኑ ፡ አያድርጋችኹ ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 16 ፤ ሕዝቅያስንም ፡ አትስሙ ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ውጡ ፤ እያንዳንዳችኹም ፡ ከወይናችኹና ፡ ከበለሳችኹ ፡ ብሉ ፥ ከጕድጓዳችኹም ፡ ውሃ ፡ ጠጡ ፤

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 17 ፤ ይህም ፡ መጥቼ ፡ ምድራችኹን ፡ ወደምትመስለው ፡ ምድር ፥ እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ እንጀራና ፡ ወይን ፡ ወዳለበት ፡ ምድር ፡ እስካፈልሳችኹ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 18 ፤ ሕዝቅያስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያድነናል ፡ ብሎ ፡ እንዳያታልላችኹ ፡ ተጠንቀቁ ። በእውኑ ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አገሮቻቸውን ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አድነዋቸዋልን ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 19 ፤ የሐማትና ፡ የአርፋድ ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧ የሴፈርዋይም ፡ አማልክት ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧ ሰማርያን ፡ ከእጄ ፡ አድነዋታልን ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከእጄ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ከነዚህ ፡ አገሮች ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ አገሩን ፡ ከእጄ ፡ ያዳነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ አንዳችም ፡ አልመለሱለትም ፤ ንጉሡ ፡ እንዳይመልሱለት ፡ አዞ ፡ ነበርና ።

ኢሳ. ፡ 36 ፡ 22 ፤ የቤቱ ፡ አዛዥ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ ኤልያቄም ፡ ጸሓፊውም ፡ ሳምናስ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊም ፡ የአሣፍ ፡ ልጅ ፡ ዮአስ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጡ ፥ የራፋስቂስንም ፡ ቃል ፡ ነገሩት ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ ንጉሡ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፥ ማቅም ፡ ለበሰ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ገባ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 2 ፤ የቤቱንም ፡ አዛዥ ፡ ኤልያቄምን ፡ ጸሓፊውንም ፡ ሳምናስን ፡ የካህናቱንም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ላካቸው ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 3 ፤ እነርሱም ፦ ሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ቀን ፡ የመከራና ፡ የተግሣጽ ፡ የዘለፋም ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ልጆች ፡ የሚወለዱበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ፡ ለመውለድም ፡ ኀይል ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 4 ፤ ምናልባት ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ የላከውን ፡ የራፋስቂስን ፡ ቃል ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለሰማው ፡ ቃል ፡ ይገሥጸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ስለዚህ ፡ ለቀረው ፡ ቅሬታ ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 5 ፤ እንዲሁ ፡ የንጉሡ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ መጡ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 6 ፤ ኢሳይያስም ፦ ለጌታችኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ባሪያዎች ፡ ስለ ፡ ሰደቡኝ ፥ ስለሰማኸው ፡ ቃል ፡ አትፍራ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ በላዩ ፡ መንፈስን ፡ እሰዳለኹ ፥ ወሬንም ፡ ይሰማል ፥ ወደ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ፤ በምድሩም ፡ በሰይፍ ፡ እንዲወድቅ ፡ አደርጋለኹ ፡ በሉት ፡ አላቸው ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 8 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ከለኪሶ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ራፋስቂስ ፡ ተመልሶ ፡ በልብና ፡

ሲዋጋ ፡ አገኘው ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ ቴርሐቅ ፡ ሊዋጋኽ ፡ መጥቷል ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ሰማ ። በሰማም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከ ፥

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 10 ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ለይሁዳ ፡ ንጉሠ ፡ ለሕዝቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሩት ፦ ኢየሩሳሌም ፡ በአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አትሰጥም ፡ ብሎ ፡ የምትታመንበት ፡ አምላክኽ ፡ አያታልኽ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ያደረጉትን ፥ እንዴትስ ፡ እንዳጠፏቸው ፡ ሰምተኻል ፤ አንተስ ፡ ትድናለኽን ፧

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 12 ፤ አባቶቼ ፡ ያጠፏቸውን ፡ ጎዛንን ፥ ካራንን ፥ ራፌስን ፥ በተላሳር ፡ የነበሩትንም ፡ የዔዴንን ፡ ልጆች ፡ የአሕዛብ ፡ አማልክት ፡ አዳኗቸውን ፧

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 13 ፤ የሐማት ፡ ንጉሥ ፥ የአርፋድ ፡ ንጉሥ ፥ የሴፈርዋይም ፡ ከተማ ፡ ንጉሥ ፥ የሄናና ፡ የዒዋ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 14 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደብዳቤውን ፡ ከመልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ተቀብሎ ፡ አነበበው ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዘረጋው ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 15 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 16 ፤ አቤቱ ፥ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ የምትቀመጥ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ብቻኽን ፡ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ፤ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ፈጥረኻል ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ ጐሮኽን ፡ አዘንብልና ፡ ስማ ፤ አቤቱ ፥ ዐይንኽን ፡ ክፈትና ፡ እይ ፤ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ ይገዳደር ፡ ዘንድ ፡ የላከውን ፡ የሰናክሬም ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 18 ፤ አቤቱ ፥ በእውነት ፡ የአሶር ፡ ነገሥታት ፡ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ አገሮቻቸውንም ፡ አፍርሰዋል ፥

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 19 ፤ አማልክታቸውንም ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ጥለዋል ፤ የዕንጨትና ፡ የድንጋይ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ አማልክት ፡ አልነበሩምና ፡ ስለዚህ ፡ አጥፍተዋቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 20 ፤ እንግዲህም ፡ አምላካችን ፡ አቤቱ ፥ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አንተ ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁ ፡ አድነን ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 21 ፤ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ላከ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ሰናክሬም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለምነኻልና ፥

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ቀላል ፡ አድርጋኻለች ፥ በንቀትም ፡ ሥቃብኻለች ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ራሷን ፡ ነቅንቃብኻለች ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 23 ፤ የተገዳደርኸው ፡ የሰደብኸውስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ቃልኽንስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኽበት ፡ ዐይንኽንስ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ያነሣኽበት ፡ ማን ፡ ነው ፧ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 24 ፤ አንተም ፦ በሠረገላዬ ፡ ብዛት ፡ ወደተራራዎች ፡ ከፍታ ፥ ወደሊባኖስ ፡ ጥግ ፡ ላይ ፡ ወጥቻለኹ ፤ ረጃሎሞቹንም ፡ ዝግባዎች ፡ የተመረጡትንም ፡ ጥዶች ፡ እቈርጣለኹ ፥ ወደከፍታውም ፡ ዳርቻ ፡ ወደቀርሜሎስ ፡ ዱር ፡ እገባለኹ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 25 ፤ ቈፈርኹም ፡ ውሃም ፡ ጠጣኹ ፡ የግብጽንም ፡ ወንዞች ፡ ኹሉ ፡ በእግሬ ፡ ጫማ ፡ አደርቃለኹ ፡

ብለኽ ፡ በባሪያዎችኽ ፡ እጅ ፡ በጌታ ፡ ላይ ፡ ተገዳደርኽ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 26 ፤ እኔ ፡ ጥንቱን ፡ እንደ ፡ ሠራኹት ፥ ቀድሞውንም ፡ እንዳደረግኹት ፡ አልሰማኽምን ፧ አኹንም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ እስኪኾኑ ፡ ድረስ ፡ እንድታፈርስ ፡ አደረግኹኽ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ የሚኖሩባቸው ፡ ሰዎች ፡ እጃቸው ፡ ዝሏል ፥ ደንግጠውም ፡ ታውከዋል ፤ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሣር ፥ እንደ ፡ ለመለመም ፡ ቡቃያ ፥ በሰገነትም ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ሣር ፥ ሳይሸት ፡ ዋግ ፡ እንደ ፡ መታው ፡ እኽል ፡ ኾነዋል ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 28 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ መቀመጫኽንና ፡ መውጫኽን ፡ መግቢያኽንም ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ የተቈጣኸውን ፡ ቍጣ ፡ ዐውቄያለኹ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 29 ፤ ቍጣኽና ፡ ትዕቢትኽ ፡ ወደ ፡ ጐሮዬ ፡ ደርሷልና ፥ ስለዚህ ፡ ስናጋዬን ፡ በአፍንጫኽ ፡ ልጓሜንም ፡ በከንፈርኽ ፡ አደርጋለኹ ፥ በመጣኽበትም ፡ መንገድ ፡ እመልስኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 30 ፤ ይህም ፡ ምልክት ፡ ይኾንኻል ፤ በዚህ ፡ ዓመት ፡ የገቦውን ፥ በኹለተኛውም ፡ ዓመት ፡ ከገቦው ፡ የበቀለውን ፡ ትበላላችኹ ፤ በሦስተኛውም ፡ ዓመት ፡ ትዘራላችኹ ፡ ታጭዱማላችኹ ፥ ወይንም ፡ ትተክላላችኹ ፡ ፍሬውንም ፡ ትበላላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 31 ፤ ያመለጠው ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ሥሩን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይሰዳል ፥ ወደ ፡ ላይም ፡ ያፈራል ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 32 ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ ከጽዮንም ፡ ተራራ ፡ ያመለጡት ፡ ይወጣሉና ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ ይህን ፡ ያደርጋል ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 33 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፥ ፍላጻንም ፡ አይወረውርባትም ፥ በጋሻም ፡ አይመጣባትም ፥ የዐፈርንም ፡ ድልድል ፡ አይደለድልባትም ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 34 ፤ በመጣበት ፡ መንገድ ፡ በዚያው ፡ ይመለሳል ፥ ወደዚችም ፡ ከተማ ፡ አይመጣም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 35 ፤ ስለ ፡ እኔም ፡ ስለ ፡ ባሪያዬም ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ አድናት ፡ ዘንድ ፡ እጋርዳታለኹ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 36 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፥ ከአሶራውያንም ፡ ሰፈር ፡ መቶ ፡ ሰማንያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ገደለ ፤ ማለዳም ፡ በተነሡ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ኹሉ ፡ በድኖች ፡ ነበሩ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 37 ፤ የአሶርም ፡ ንጉሥ ፡ ሰናክሬም ፡ ተነሥቶ ፡ ኼደ ፥ ተመልሶም ፡ በነነዌ ፡ ተቀመጠ ።

ኢሳ. ፡ 37 ፡ 38 ፤ በአምላኩም ፡ በናሳራክ ፡ ቤት ፡ ሲሰግድ ፡ ልጆቹ ፡ አድራሜሌክና ፡ ሳራሳር ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉት ፤ ወደአራራትም ፡ አገር ፡ ኰበለሉ ። ልጁም ፡ አስራዶን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሕዝቅያስ ፡ ለሞት ፡ እስኪደርስ ፡ ታመመ ። ነቢዩም ፡ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፡ በሕይወት ፡ አትኖርምና ፡ ቤትኽን ፡ አስተካክል ፡ አለው ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ግድግዳው ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፦

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ በፊትኽ ፡ በእውነትና ፡ በፍጹም ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ኼድኩ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝኽንም ፡ እንዳደረግኩ ፡ ታስብ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ። ሕዝቅያስም ፡ እጅግ ፡ አድርጎ ፡ አለቀሰ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 5 ፤ ኺድ ፥ ሕዝቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የአባትኽ ፡ የዳዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጸሎትኽን ፡ ሰምቻለኹ ፥ እንባኽንም ፡ አይቻለኹ ፤ እንሆ ፥ በዕድሜኽ ፡ ላይ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ዓመት ፡ እጨምራለኹ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 6 ፤ አንተንና ፡ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ከአሶር ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ እታደጋለኹ ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ እጋርዳታለኹ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተገረውን ፡ ነገር ፡ እንዲፈጽመው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡ ይህ ፡ ይኾንልኻል ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ በአካዝ ፡ የጥላ ፡ ስፍረ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ ከፀሓይ ፡ ጋራ ፡ የወረደውን ፡ በደረጃዎች ፡ ያለውን ፡ ጥላ ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እንዲመለስ ፡ አደርጋለኹ ። ፀሓይም ፡ በጥላ ፡ ስፍረ ፡ ሰዓት ፡ ላይ ፡ የወረደበት ፡ ዐሥር ፡ ደረጃ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሰ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 9 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስ ፡ ታሞ ፡ ከደዌው ፡ በተፈወሰ ፡ ጊዜ ፡ የጻፈው ፡ ጽሕፈት ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 10 ፤ እኔ ፦ በሕይወት ፡ ዘመኔ ፡ መካከል ፡ ወደሲኦል ፡ በሮች ፡ እገባለኹ ፤ የቀረው ፡ ዘመኔ ፡ ጐደለብኝ ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 11 ፤ ደግሞም ፦ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላይም ፤ በዓለምም ፡ ከሚኖሩ ፡ ጋራ ፡ ሰውን ፡ እንግዲህ ፡ አልመለከትም ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 12 ፤ ማደሪያዬ ፡ ተነቀለች ፥ እንደ ፡ እረኛ ፡ ድንኳንም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ተወገደች ፤ ሕይወቴንም ፡ እንደ ፡ ሸማኔ ፡ ጠቀለልኹ ፥ ርሱም ፡ ከመጠቅለያው ፡ ይቈርጠኛል ፤ ከማለዳም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ታጠፋኛለኽ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 13 ፤ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ቈይቼ ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ዐጥንቴን ፡ ሹሉ ፡ ሰበረ ፤ ከማለዳ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ታጠፋኛለኽ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ጨረባና ፡ እንደ ፡ ሸመላ ፡ ተንጫጫኹ ፥ እንደ ፡ ርግብም ፡ አጕረመረምኹ ፤ ዐይኖቼ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከማየት ፡ ደከሙ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተጨንቄያለኹና ፡ መከታ ፡ ኹነኝ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 15 ፤ ምን ፡ እላለኹ ∴ ርሱ ፡ ተናግሮኛል ፥ ርሱ ፡ ራሱም ፡ ይህን ፡ አድርጓል ፤ በዘመኔ ፡ ሹሉ ፡ ስለነፍሴ ፡ ምሬት ፡ ቀስ ፡ ብዬ ፡ እኼዳለኹ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ ሰዎች ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፥ በዚህም ፡ ሹሉ ፡ የመንፈሴ ፡ ሕይወት ፡ ነው ፤ አንተም ፡ ፈወስኸኝ ፡ ወደ ፡ ሕይወትም ፡ መለስኸኝ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ ታላቅ ፡ ምሬት ፡ ለደኅንነቴ ፡ ኾነ ፤ አንተም ፡ ነፍሴን ፡ ከጥፋት ፡ ጕድጓድ ፡ አዳንኻት ፥ ኀጢአቴንም ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ ኋላኽ ፡ ጣልኽ ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 18 ፤ ሲኦል ፡ አያመሰግንኽምና ፥ ሞትም ፡ አያከብርኽምና ፤ ወደ ፡ ጕድጓዱ ፡ የሚወርዱ ፡ እውነትኽን ፡ ተስፋ ፡ አያደርጉም ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 19 ፤ እኔ ፡ ዛሬ ፡ እንደማደርግ ፡ ሕያዋን ፡ እነርሱ ፡ ያመሰግኑኻል ፤ አባት ፡ ለልጆች ፡ እውነትኽን ፡ ያስታውቃል ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያድነኛል ፤ ስለዚህ ፡ በዕድሜያችን ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ቅኔዎችን ፡ አውታር ፡ ባለው ፡ ዕቃ ፡ እንዘምራለን ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 21 ፤ ኢሳይያስም ፦ የበለስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ አምጥተው ፡ በዕባጩ ፡ ላይ ፡ ይለብጡት ፥ ርሱም ፡ ይፈወሳል ፡ ብሎ ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 38 ፡ 22 ፤ ሕዝቅያስም ፦ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እወጣ ፡ ዘንድ ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ነበር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የባልዳን ፡ ልጅ ፡ መሮዳክ ፡ ባልዳን ፡ ሕዝቅያስ ፡ ታሞ ፡ እንደ ፡ ተፈወሰ ፡ ሰምቶ ፡ ነበርና ፥ ደብዳቤና ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ላከለት ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 2 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ግምጃ ፡ ቤቱንም ፥ ብሩንና ፡ ወርቁንም ፥ ቅመሙንና ፡ የከበረውንም ፡ ዘይት ፥ መሣሪያም ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፥ በቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ የተገኘውን ፡ ኹሉ ፡ አሳያቸው ፤ በቤቱና ፡ በግዛቱ ፡ ኹሉ ፡ ካለው ፡ ሕዝቅያስ ፡ ያላሳያቸው ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 3 ፤ ነቢዩም ፡ ኢሳይያስ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅያስ ፡ መጥቶ ፦ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ አሉ ፧ ከወዴትስ ፡ መጡልኽ ፧ አለው ። ሕዝቅያስም ፦ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ከባቢሎን ፡ መጡልኝ ፡ አለው ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 4 ፤ ርሱም ፦ በቤትኽ ፡ ያዩት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ፤ ሕዝቅያስም ፦ በቤቴ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ አይተዋል ፤ በቤተ ፡ መዛግብቴ ፡ ካለው ፡ ያላሳየኋቸው ፡ የለም ፡ አለው ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 5 ፤ ኢሳይያስም ፡ ሕዝቅያስን ፦ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ በቤትኽ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፥ አባቶችኽም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያከማቹት ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሚፈልስበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፤ ምንም ፡ አይቀርም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 7 ፤ ከአንተም ፡ ከሚወጡት ፡ ከምትወልዳቸው ፡ ልጆችኽ ፡ ማርከው ፡ ይወስዳሉ ፤ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ይኾናሉ ፡ አለው ።

ኢሳ. ፡ 39 ፡ 8 ፤ ሕዝቅያስም ፡ ኢሳይያስን ፦ የተናገርኸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መልካም ፡ ነው ፡ አለው ። ደግሞም ፦ በዘመኔ ፡ ሰላምና ፡ እውነት ፡ ይኹን ፡ አለ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 1 ፤ አጽናኑ ፥ ሕዝቤን ፡ አጽናኑ ፡ ይላል ፡ አምላካችኹ ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 2 ፤ ለኢየሩሳሌም ፡ ልብ ፡ ተናገሩ ፡ የተቀጠረችበት ፡ ወራት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፥ ኀጢአቷም ፡ እንደ ፡ ተሰረየ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ስለ ፡ ኀጢአቷ ፡ ኹሉ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ እንደ ፡ ተቀበለች ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ጩኹ ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 3 ፤ የዐዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ቃል ። የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ጥረጉ ፥ ለአምላካችንም ፡ ጐዳና ፡ በበረሓ ፡ አስተካክሉ ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 4 ፤ ሸለቆው ፡ ኹሉ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፥ ተራራውና ፡ ኰረብታውም ፡ ኹሉ ፡ ዝቅ ፡ ይላል ፤ ጠማማውም ፡ ይቃናል ፥ ስርጓጉጡም ፡ ሜዳ ፡ ይኾናል ፤

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ይገለጣል ፥ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ያየዋል ፥ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ተናግሯልና ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 6 ፤ ጩኺ ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ቃል ፤ ምን ፡ ብዬ ፡ ልጩኽ ፧ አልኹ ። ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ሣር ፡ ነው ፥ ክብሩም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አበባ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እስትንፋስ ፡ ይነፍስበታልና ፥ ሣሩ ፡ ይደርቃል ፡ አበባውም ፡ ይረግፋል ፤ በእውነት ፡ ሕዝቡ ፡ ሣር ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 8 ፤ ሣሩ ፡ ይደርቃል ፡ አበባውም ፡ ይረግፋል ፥ የአምላካችን ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 9 ፤ የምሥራች ፡ የምትነግሪ ፡ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ከፍ ፡ ወዳለው ፡ ተራራ ፡ ውጪ ፡ የምሥራች ፡ የምትነግሪ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ድምፅሽን ፡ በኀይል ፡ አንሺ ፤ አንሺ ፥ አትፍሪ ፤ ለይሁዳም ፡ ከተማዎች ፦ እንሆ ፥ አምላካችኹ! ፡ ብለሽ ፡ ንገሪ ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 10 ፤ እንሆ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ይመጣል ፡ ክንዱም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ይገዛል ፤ እንሆ ፥ ዋጋው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደመ ፡ ወዙም ፡ በፊቱ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 11 ፤ መንጋውን ፡ እንደ ፡ እረኛ ፡ ያሰማራል ፥ ጠቦቶቹን ፡ በክንዱ ፡ ሰብስቦ ፡ በብብቱ ፡ ይሸከማል ፥ የሚያጠቡትንም ፡ በቀስታ ፡ ይመራል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 12 ፤ ውሃዎችን ፡ በዕፍኙ ፡ የሰፈረ ፥ ሰማይንም ፡ በስንዝር ፡ የለካ ፥ የምድርንም ፡ ዐፈር ፡ በመስፈሪያ ፡ ሰብስቦ ፡ የያዘ ፥ ተራራዎችን ፡ በሚዛን ፡ ኰረብታዎችንም ፡ በሚዛኖች ፡ የመዘነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ ያዘዘ ፥ ወይስ ፡ አማካሪ ፡ ኾኖ ፡ ያስተማረው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 14 ፤ ወይስ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ተመካከረ ፧ ወይስ ፡ ማን ፡ መከረው ፧ የፍርድንም ፡ መንገድ ፡ ማን ፡ አስተማረው ፧ ዕውቀትንስ ፡ ማን ፡ አስተማረው ፧ የማስተዋልንስ ፡ መንገድ ፡ ማን ፡ አሳየው ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ አሕዛብ ፡ በገንቦ ፡ እንዳለች ፡ ጠብታ ፡ ናቸው ፥ በሚዛንም ፡ እንዳለ ፡ ትንሽ ፡ ትቢያ ፡ ተቈጥረዋል ፤ እንሆ ፥ ደሴቶችን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ያነሣል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 16 ፤ ሊባኖስ ፡ ለማንደጃ ፡ እንስሳዎቿም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ አይበቁም ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 17 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ እንዳልነበሩ ፡ ናቸው ፤ ከምናምን ፡ እንደሚያንሱ ፥ እንደ ፡ ከንቱ ፡ ነገርም ፡ ይቈጥራቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማን ፡ ትመስሉታላችኹ ፧ ወይስ ፡ በምን ፡ ምሳሌ ፡ ታስተያዩታላችኹ ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 19 ፤ የተቀረጸውንስ ፡ ምስል ፡ ሠራተኛ ፡ ሠርቶታል ፥ አንጥረኛም ፡ በወርቅ ፡ ለብጦታል ፥ የብሩንም ፡ ሰንሰለት ፡ አፍሶለታል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 20 ፤ ለዚህ ፡ መባዕ ፡ ገንዘቡ ፡ ያልበቃው ፡ ድኻ ፡ የማይነቅዘውን ፡ ዕንጨት ፡ ይመርጣል ፤ ምስሉም ፡ እንዳይናወጥ ፡ ያቆመው ፡ ዘንድ ፡ ብልኅ ፡ ሠራተኛን ፡ ይፈልጋል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 21 ፤ አላወቃችኹምን ፧ ወይስ ፡ አልሰማችኹምን ፧ ከጥንትስ ፡ አልተወራላችኹምን ፧ ወይስ ፡ ምድር ፡ ከተመሠረተች ፡ ዠምሮ ፡ አላስተዋላችኹምን ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 22 ፤ ርሱ ፡ በምድር ፡ ክበብ ፡ ላይ ፡ ይቀምጣል ፥ በርሷም ፡ የሚኖሩት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፡ ናቸው ፤ ሰማያትን ፡ እንደ ፡ መጋረጃ ፡ የሚዘረጋቸው ፡ እንደ ፡ ድንኳንም ፡ ለመኖሪያ ፡ የሚዘረጋቸው ፥

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 23 ፤ አለቃዎችንም ፡ እንዳልነበሩ ፥ የምድርንም ፡ ፈራጆች ፡ እንደ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 24 ፤ ገና ፡ እንደ ፡ ተተከሉና ፡ እንደ ፡ ተዘሩ ፥ በምድርም ፡ ሥር ፡ ገና ፡ እንደ ፡ ሰደዱ ፡ ወዲያውኑ ፡ ነፈሰባቸው ፥ እነርሱም ፡ ደረቁ ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ እንደ ፡ እብቅ ፡ ጠረጋቸው ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 25 ፤ እንግዲህ ፡ እተካከለው ፡ ዘንድ ፡ በማን ፡ መሰላችኹኝ ፧ ይላል ፡ ቅዱሱ ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 26 ፤ ዐይናችኹን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥታችኹ ፡ ተመልከቱ ፤ እነዚህን ፡ የፈጠረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ሰራዊታቸውን ፡ በቀኙጥር ፡ የሚያወጣ ፡ ርሱ ፡ ነው ፥ ኹሉንም ፡ በየስማቸው ፡ ይጠራቸዋል ፤ በኀይሉ ፡ ብዛትና ፡ በችሎቱ ፡ ብርታት ፡ አንድስ ፡ እንኳ ፡ አይታጣውም ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 27 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ እስራኤልም ፡ ሆይ ፦ መንገዴ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተሰውራለች ፡ ፍርዴም ፡ ከአምላኬ ፡ ዐልፋለች ፡ ለምን ፡ ትላለኽ ፧ ለምንስ ፡ እንዲህ ፡ ትናገራለኽ ፧

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 28 ፤ አላወቅኽምን ፧ አልሰማኽምን ፧ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ አምላክ ፥ የምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ፈጣሪ ፡ ነው ፤ አይደክምም ፥ አይታክትም ፥ ማስተዋሉም ፡ አይመረመርም ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 29 ፤ ለደካማ ፡ ኀይልን ፡ ይሰጣል ፥ ጕልበት ፡ ለሌለውም ፡ ብርታትን ፡ ይጨምራል ።

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 30 ፤ ብላቴናዎች ፡ ይደክማሉ ፡ ይታክቱማል ፥ ጐበዛዝቱም ፡ ፈጽሞ ፡ ይወድቃሉ ፤

ኢሳ. ፡ 40 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ ግን ፡ ኀይላቸውን ፡ ያድሳሉ ፤ እንደ ፡ ንስር ፡ በክንፍ ፡ ይወጣሉ ፤ ይሮጣሉ ፥ አይታክቱም ፤ ይኼዳሉ ፥ አይደክሙም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 1 ፤ ደሴቶች ፡ ሆይ ፥ በፊቴ ፡ ዝም ፡ በሉ ፤ አሕዛብም ፡ ኀይላቸውን ፡ ያድሱ ፤ ይቅረቡም ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ይናገሩ ፤ ለፍርድ ፡ ለአንድነት ፡ እንቅረብ ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 2 ፤ ከምሥራቅ ፡ አንዱን ፡ ያስነሣ ፡ በጽድቅም ፡ ወደ ፡ እግሩ ፡ የተጠራው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሕዛብንም ፡ አሳልፎ ፡ በፊቱ ፡ ሰጠው ፥ ነገሥታትንም ፡ አስገዛለት ፤ ለሰይፉ ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፡ ለቀስቱም ፡ እንደ ፡ ተጠረገ ፡ እብቅ ፡ አድርጎ ፡ ሰጣቸው ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 3 ፤ አሳደዳቸው ፥ እግሮቹም ፡ አስቀድመው ፡ ባልኼዱባት ፡ መንገድ ፡ በደኅንነት ፡ ዐለፈ ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 4 ፤ ይህን ፡ የሠራና ፡ ያደረገ ፥ ትውልድንም ፡ ከጥንት ፡ የጠራ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፥ ፊተኛው ፡ በኋለኞችም ፡ ዘንድ ፡ የምኖር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 5 ፤ ደሴቶች ፡ አይተው ፡ ፈሩ ፥ የምድርም ፡ ዳርቻዎች ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ ቀረቡም ፡ ደረሱም ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 6 ፤ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራውን ፡ ይረዳው ፡ ነበር ፥ ወንድሙንም ፦ አይዞኽ ፡ ይለው ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 7 ፤ ዐናጢውም ፡ አንጥረኛውን ፥ በመዶሻም ፡ የሚያሣሣውን ፡ መስፍ ፡ መችውን ፡ አጽናና ፥ ስለማጣበቅ ፡ ሥራውም ፦ መልካም ፡ ነው ፡ አለ ፤ እንዳይንቀሳቀስም ፡ በችንካር ፡ አጋጠመው ።

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 8 ፤ ባሪያዬ ፡ እስራኤል ፥ የመረጥኹኽ ፡ ያዕቆብ ፥ የወዳጄ ፡ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ ሆይ ፥

ኢሳ. ፡ 41 ፡ 9 ፤ አንተ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ የያዝኹኽ ፡ ከማእዘኗም ፡ የጠራኹኽና ፦ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡

ነኝ ፥ መርጨኻለኹ ፡ አልጥልኽም ፡ ያልኹኽ ፡ ሆይ ፥

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 10 ፤ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፤ እኔ ፡ አምላክኽ ፡ ነኝና ፡ አትደንግጥ ፤ አበረታኻለኹ ፥ እረዳኽማለኹ ፥ በጽድቄም ፡ ቀኝ ፡ ደግፌ ፡ እይዝኻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 11 ፤ እንሆ ፥ የሚቈጡኽ ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ፥ ይዋረዱማል ፤ የሚከራከሩኽም ፡ እንዳልነበሩ ፡ ይኾናሉ ፥ ይጠፉማል ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 12 ፤ የሚያጣሉኽንም ፡ ትሻቸዋለኽ ፡ አታገኛቸውምም ፥ የሚዋጉኽም ፡ እንዳልነበሩና ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 13 ፤ እኔ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፦ አትፍራ ፥ እረዳኻለኹ ፡ ብዬ ፡ ቀኝኽን ፡ እይዛለኹና ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 14 ፤ አንተ ፡ ትል ፡ ያዕቆብ ፡ የእስራኤልም ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ አትፍሩ ፤ እረዳኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የሚቤዥኽም ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 15 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ተሳለች ፡ እንደ ፡ ዐዲስ ፡ ባለጥርስ ፡ ማኼጃ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ ተራራዎችንም ፡ ታኼዳለኽ ፡ ታደቃቸውማለኽ ፥ ኰረብታዎችንም ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ታደርጋቸዋለኽ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 16 ፤ ታበጥራቸዋለኽ ፥ ነፋስም ፡ ይጠርጋቸዋል ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ይበትናቸዋል ፤ አንተም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይልኻል ፥ በእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ትመካለኽ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 17 ፤ ድኻዎችና ፡ ምስኪኖችም ፡ ውሃ ፡ ይሻሉ ፡ አያገኙምም ፥ ምላሳቸውም ፡ በጥማት ፡ ደርቋል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እሰማቸዋለኹ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እኔ ፡ አልተዋቸውም ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 18 ፤ በወናዎቹ ፡ ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ወንዞችን ፥ በሸለቆዎችም ፡ መካከል ፡ ምንጮችን ፡ እከፍታለኹ ፤ ምድረ ፡ በዳውን ፡ ለውሃ ፡ መቆሚያ ፥ የጥማትንም ፡ ምድር ፡ ለውሃ ፡ መፍለቂያ ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 19 ፤ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ሠራች ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ፈጠረው ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ያውቁም ፡ ዘንድ ፡ ያስቡም ፡ ዘንድ ፡ በአንድነትም ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዝግባውንና ፡ ግራሩን ፡ ባርሰነቱንና ፡ የዘይቱን ፡ ዛፍ ፡ አበቅላለኹ ፥ በበረሓውም ፡ ጥዱንና ፡ አስታውን ፡ ወይራውንም ፡ በአንድነት ፡ አኖራለኹ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 21 ፤ ክርክራችኹን ፡ አቅርቡ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ማስረጃችኹን ፡ አምጡ ፥ ይላል ፡ የያዕቆብ ፡ ንጉሥ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 22 ፤ ያምጡ ፥ የሚኾነውንም ፡ ይንገሩን ፤ ልብም ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፍጻሜያቸውንም ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፥ የቀደሙት ፡ ነገሮች ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ተናገሩ ፥ የሚመጡትንም ፡ አሳዩን ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 23 ፤ አማልክትም ፡ መኾናችኹን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ በኋላ ፡ የሚመጡትን ፡ ተናገሩ ፤ እንደነግጥም ፡ ዘንድ ፡ በአንድነትም ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ ወይም ፡ ክፉውን ፡ አድርጉ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 24 ፤ እንሆ ፥ እንዳልነበረ ፡ ናችኹ ፥ ሥራችኹም ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ የሚመርጣችኹም ፡ አስጸያፊ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 25 ፤ አንዱን ፡ ከሰሜን ፡ አነሣኹ ፡ መጥቷልም ፤ አንዱም ፡ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ስሜን ፡ የሚጠራ ፡ ይመጣል ፤ በጭቃ ፡ ላይ ፡ እንደሚመጣ ፡ ሰው ፡ ዐፈርም ፡ እንደሚረግጥ ፡ ሸክለኛ ፡ በአለቃዎች ፡ ላይ ፡ ይመጣል ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 26 ፤ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከጥንት ፡ የተናገረው ፦ እውነት ፡ ነው ፡ እንልም ፡ ዘንድ ፡ ቀድሞ ፡

የተናገረው ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚናገር ፡ የለም ፥ የሚገልጥም ፡ የለም ፥ ቃላችኹንም ፡ የሚሰማ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 27 ፤ በመገሥመሪያ ፡ ለጽዮን ፦ እንሂቸው ፡ እላለኹ ፤ ለኢየሩሳሌምም ፡ የምሥራች ፡ ነጋሪን ፡ እሰጣለኹ ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 28 ፤ ብመለከት ፡ ማንም ፡ አልነበረም ፤ ብጠይቃቸውም ፡ የሚመልስልኝ ፡ አማካሪ ፡ በመካከላቸው ፡ የለም ።

ኢሳ. ፥ 41 ፥ 29 ፤ እንሆ ፥ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ፥ ሥራቸውም ፡ ምንም ፡ ምን ፡ ናት ፤ ቀልጠው ፡ የተሠሩት ፡ ምስሎቻቸውም ፡ ነፋስና ፡ ኢምንት ፡ ናቸው ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 1 ፤ እንሆ ፥ ደግፌ ፡ የያዝኹት ፡ ባሪያዬ ፤ ነፍሴ ፡ ደስ ፡ የተሠኘችበት ፡ ምርጤ ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡ አድርጌያለኹ ፥ ርሱም ፡ ለአሕዛብ ፡ ፍርድን ፡ ያወጣል ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 2 ፤ አይጮኽም ፡ ቃሉንም ፡ አያነሣም ፥ ድምፁንም ፡ በሜዳ ፡ አያሰማም ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 3 ፤ የተቀጠቀጠን ፡ ሸምበቆ ፡ አይሰብርም ፥ የሚጤስንም ፡ ክር ፡ አያጠፋም ፤ በእውነት ፡ ፍርድን ፡ ያወጣል ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 4 ፤ በምድርም ፡ ፍርድን ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ይበራል ፡ እንጂ ፡ አይጠፋም ፤ አሕዛብም ፡ በስሙ ፡ ይታመናሉ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 5 ፤ ሰማያትን ፡ የፈጠረ ፡ የዘረጋቸውም ፥ ምድርንና ፡ በውስጧ ፡ ያለውን ፡ ያጸና ፥ በርሷ ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ እስትንፋስን ፥ ለሚኼዱባትም ፡ መንፈስን ፡ የሚሰጥ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 6-7 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ጠርቼኻለኹ ፥ እጅኽንም ፡ እይዛለኹ ፡ እጠብቅኽማለኹ ፥ የዕውሩንም ፡ ዐይን ፡ ትከፍት ፡ ዘንድ ፡ የተጋዘውንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ በጨለማም ፡ የተቀመጡትን ፡ ከወህኒ ፡ ቤት ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝብ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለአሕዛብም ፡ ብርሃን ፡ አድርጌ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 8 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ስሜ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ክብሬን ፡ ለሌላ ፥ ምስጋናዬንም ፡ ለተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ አልሰጥም ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 9 ፤ እንሆ ፥ የቀድሞው ፡ ነገር ፡ ተፈጸመ ፥ ዐዲስ ፡ ነገርንም ፡ እናገራለኹ ፤ አስቀድሞም ፡ ሳይበቅል ፡ ርሱን ፡ አስታውቃችኋለኹ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 10 ፤ ወደ ፡ ባሕር ፡ የምትወርዱ ፡ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ ያላችኹ ፡ ኹሉ ፥ ደሴቶችና ፡ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ዐዲስ ፡ መዝሙር ፥ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ምስጋናውን ፡ ዘምሩ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 11 ፤ ምድረ ፡ በዳውና ፡ ከተማዎቹ ፡ የቄዳርም ፡ ሰዎች ፡ የሚቀመጡባቸው ፡ መንደሮች ፡ ድምፃቸውን ፡ ያንሡ ፤ በሴላ ፡ የሚኖሩ ፡ እልል ፡ ይበሉ ፥ በተራራዎችም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ይጩኹ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 12 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ክብርን ፡ ይስጡ ፥ ምስጋናውንም ፡ በደሴቶች ፡ ይናገሩ ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ይወጣል ፡ እንደ ፡ ሰልፈኛም ፡ ቅንአትን ፡ ያስነሣል ፤ ይጮኻል ፡ ድምፁንም ፡ ያሰማል ፡ በጠላቶቹም ፡ ላይ ፡ ይበረታል ።

ኢሳ. ፥ 42 ፥ 14 ፤ ከድሮ ፡ ዘመን ፡ ዝምን ፡ ብያለኹ ፥ ዝም ፡ ብዬም ፡ ታግሻለኹ ፤ አኹን ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ እጮኻለኹ ፤ አጠፋለኹ ፡ በአንድነትም ፡ እጨርሳለኹ ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 15 ፤ ተራራዎችንና ፡ ኰረብታዎችን ፡ አፈርሳለኹ ፥ ቡቃያዎቻቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አደርቃለኹ ፤ ወንዞችንም ፡ ደሴቶች ፡ አደርጋለኹ ፥ ኩሬዎችንም ፡ አደርቃለኹ ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 16 ፤ ዕውሮችንም ፡ በማያውቋት ፡ መንገድ ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ በማያውቋትም ፡ ጐዳና ፡ እመራቸዋለኹ ፤ በፊታቸውም ፡ ጨለማውን ፡ ብርሃን ፡ አደርጋለኹ ፥ ጠማማውንም ፡ አቀናለኹ ። ይህን ፡ አደርግላቸዋለኹ ፥ አልተዋቸውምም ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 17 ፤ በተቀረጹትም ፡ ምስሎች ፡ የሚታመኑ ፥ ቀልጠው ፡ የተሠሩትንም ፡ ምስሎች ፦ አምላኮቻችን ፡ ናችኹ ፡ የሚሉ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ፈጽመውም ፡ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 18 ፤ እናንተ ፡ ደንቈሮዎች ፥ ስሙ ፤ እናንተም ፡ ዕውሮች ፥ ታዩ ፡ ዘንድ ፡ ተመልከቱ ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 19 ፤ ከባሪያዬ ፡ በቀር ፡ ዕውር ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንደምልከው ፡ መልእክተኛዬስ ፡ በቀር ፡ ደንቈሮ ፡ የኾነ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንደ ፡ ፍጹሙ ፡ ወይስ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ ዕውር ፡ የኾነ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 20 ፤ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ታያላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትጠባበቁትም ፤ ጐሯችኹም ፡ ተከፍተዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትሰሙም ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ጽድቁ ፡ ሕጉን ፡ ታላቅ ፡ ያደርግና ፡ ያከብር ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 22 ፤ ይህ ፡ ግን ፡ የተበዘበዘና ፡ የተዘረፈ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፤ ኹላቸው ፡ በዋሻ ፡ ውስጥ ፡ ተጠምደዋል ፡ በግዞት ፡ ቤትም ፡ ተሸሽገዋል ፤ ብዝበዛ ፡ ኾነዋል ፡ የሚያድንም ፡ የለም ፥ ምርኮም ፡ ኾነዋል ፥ ማንም ፦ መልሱ ፡ አይልም ።

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 23 ፤ ከመካከላችኹ ፡ ይህን ፡ የሚያደምጥ ፥ ለሚመጣውም ፡ ጊዜ ፡ የሚያደምጥና ፡ የሚሰማ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 24 ፤ ያዕቆብን ፡ ለማረኩ ፡ እስራኤልንም ፡ ለበዘበዙ ፡ ሰዎች ፡ የሰጠ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እኛ ፡ የበደልነው ፥ እነርሱም ፡ በመንገዱ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ያልወደዱት ፡ ለሕጉም ፡ ያልታዘዙለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፡ 42 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ የቀሣጣውን ፡ መዓትና ፡ የሰልፉን ፡ ጽናት ፡ አፈሰሰበት ፤ በዙሪያም ፡ አነደደው ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ አላወቀም ፥ አቃጠለውም ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ ልብ ፡ አላደረገም ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ። _____

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 1 ፤ አኹንም ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ የፈጠረኽ ፥ እስራኤልም ፡ ሆይ ፥ የሠራኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ተቤኘቼኻለኹና ፡ አትፍራ ፤ በስምኽም ፡ ጠርቼኻለኹ ፥ አንተ ፡ የእኔ ፡ ነኽ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 2 ፤ በውሃ ፡ ውስጥ ፡ ባለፍኽ ፡ ጊዜ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እኾናለኹ ፥ በወንዞችም ፡ ውስጥ ፡ ባለፍኽ ፡ ጊዜ ፡ አያሰጥሙኽም ፤ በእሳትም ፡ ውስጥ ፡ በኼድኽ ፡ ጊዜ ፡ አትቃጠልም ፥ ነበልባሉም ፡ አይፈጅኽም ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 3 ፤ እኔ ፡ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒትኽ ፡ ነኝ ፤ ግብጽን ፡ ለአንተ ፡ ቤዛ ፡ አድርጌ ፥ ኢትዮጵያንና ፡ ሳባንም ፡ ለአንተ ፡ ፋንታ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 4 ፤ በዐይኔ ፡ ፊት ፡ የከበርኽና ፡ የተመሰገንኽ ፡ ነኽና ፥ እኔም ፡ ወድጄኻለኹና ፡ ስለዚህ ፡ ሰዎችን ፡ ለአንተ ፡ አሕዛብንም ፡ ለነፍስኽ ፡ እሰጣለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 5 ፤ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፤ ዘርኽንም ፡ ከምሥራቅ ፡ አመጣዋለኹ ፥ ከምዕራብም ፡

እሰበስብኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 6-7 ፤ ሰሜንን ፦ መልሰኽ ፡ አምጣ ፥ ደቡብንም ፦ አትከልክል ፤ ወንዶች ፡ ልጆቼን ፡ ከሩቅ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቼንም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፥ በስሜ ፡ የተጠራውን ፡ ለክብሬም ፡ የፈጠርኹትን ፥ የሠራኹትንና ፡ ያደረግኹትን ፡ ኹሉ ፡ አምጣ ፡ እለዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 8 ፤ ዐይኖች ፡ ያሏቸውን ፡ ዕውሮችን ፡ ሕዝብ ፥ ጐሮዎችም ፡ ያሏቸውን ፡ ደንቈሮዎቹን ፡ አውጣ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 9 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ይሰብሰቡ ፡ ወገኖችም ፡ ይከማቹ ፤ ከመካከላቸው ፤ ይህን ፡ የሚናገር ፥ የቀድሞውንስ ፡ ነገር ፡ የሚያሳየን ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይጸድቁ ፡ ዘንድ ፡ ምስክሮቻቸውን ፡ ያምጡ ፥ ሰምተውም ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ይበሉ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 10 ፤ ታውቁና ፡ ታምኑብኝ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ እንደኾንኹ ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፥ እናንተ ፡ የመረጥኹትም ፡ ባሪያዬ ፡ ምስክሮቼ ፡ ናችኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከእኔ ፡ በፊት ፡ አምላክ ፡ አልተሠራም ፡ ከእኔም ፡ በኋላ ፡ አይኾንም ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 11 ፤ እኔ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ ከእኔ ፡ ሌላም ፡ የሚያድን ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 12 ፤ ተናግሬያለኹ ፡ አድኜማለኹ ፡ አሳይቼማለኹ ፥ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ባዕድ ፡ አምላክ ፡ አልነበረም ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ ምስክሮቼ ፡ ናችኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 13 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ከእጄም ፡ የሚያመልጥ ፡ የለም ፤ እሠራለኹ ፥ የሚከለክልስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 14 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፥ የሚቤዣችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ እናንተ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ሰድጃለኹ ፥ ከለዳውያንንም ፡ ኹሉ ፡ ስደተኞች ፡ አድርጌ ፡ በሚመኩባቸው ፡ መርከቦች ፡ አዋርዳቸዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 15 ፤ ቅዱሳችኹ ፥ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፥ ንጉሣችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ መንገድን ፡ በኀይለኛም ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ መተላለፊያን ፡ ያደርጋል ፤

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሠረገላውንና ፡ ፈረሱን ፡ ሰራዊቱንና ፡ ዐርበኛውን ፡ ያወጣል ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ በአንድነት ፡ ተኝተዋል ፥ አይነሡም ፤ ቀርተዋል ፥ እንደ ፡ ጧፍ ፡ ኮስታሪም ፡ ጠፍተዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 18 ፤ የፊተኛውን ፡ ነገር ፡ አታስተውሉ ፥ የጥንቱንም ፡ ነገር ፡ አታስቡ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 19 ፤ እንሆ ፥ ዐዲስ ፡ ነገርን ፡ አደርጋለኹ ፤ ርሱም ፡ አኹን ፡ ይበቅላል ፥ እናንተም ፡ አታውቁትምን ፧ በምድረ ፡ በዳም ፡ መንገድን ፥ በበረሓም ፡ ወንዞችን ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 20 ፤ 21 ፤ ምስጋናዬን ፡ እንዲናገሩ ፡ ለእኔ ፡ የፈጠርኹት ፡ ሕዝብ ፥ የመረጥኹትን ፡ ሕዝቤን ፡ አጠጣ ፡ ዘንድ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ውሃን ፡ በበረሓም ፡ ወንዞችን ፡ ሰጥቻለኹና ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፥ ቀበሮዎችና ፡ ሰጐኖች ፥ ያከብሩኛል ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 22 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አልጠራኸኝም ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ደክመኻል ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 23 ፤ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ በጎችኽን ፡ አላቀረብኽልኝም ፡ በሌላም ፡ መሥዋዕትኽ ፡

አላከበርኸኝም ፤ በእኽልም ፡ ቍርባን ፡ አላስቸገርኩኽም ፡ በዕጣንም ፡ አላደከምኩኽም ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 24 ፤ ዕጣንም ፡ በገንዘብ ፡ አልገዛኽልኝም ፡ በመሥዋዕትኽም ፡ ስብ ፡ አላጠገብኸኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኀጢአትኽ ፡ አስቸገርኸኝ ፥ በበደልኽም ፡ አደከምኸኝ ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 25 ፤ መተላለፍኽን ፦ ስለ ፡ እኔ ፡ ስል ፡ የምደመስስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ኀጢአትኽንም ፡ አላስብም ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 26 ፤ አሳስበኝ ፥ በአንድነትም ፡ ኾነን ፡ እንፋረድ ፤ እንድትጸድቅ ፡ ነገርኽን ፡ ተናገር ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 27 ፤ ፊተኛው ፡ አባትኽ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቷል ፥ መምህሮችኽም ፡ በድለውኛል ።

ኢሳ. ፡ 43 ፡ 28 ፤ ስለዚህ ፥ የመቅደሱን ፡ አለቃዎች ፡ አረከስኩ ፥ ያዕቆብንም ፡ ርግማን ፥ እስራኤልንም ፡ ስድብ ፡ አደረግኩ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 44 ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 1 ፤ አኩንም ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ የመረጥኩኽም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 2 ፤ የፈጠረኽ ፡ ከማሕፀንም ፡ የሠራኽ ፡ የሚረዳኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ የመረጥኩኽም ፡ ይሹሩን ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 3 ፤ በተጠማ ፡ ላይ ፡ ውሃን ፡ በደረቅም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ፈሳሾችን ፡ አፈሳለኹና ፤ መንፈሴን ፡ በዘርኽ ፡ ላይ ፡ በረከቴንም ፡ በልጆችኽ ፡ ላይ ፡ አፈሳለኹ ፥

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 4 ፤ በፈሳሾችም ፡ አጠገብ ፡ እንደሚበቅሉ ፡ እንደ ፡ አሓያ ፡ ዛፎች ፡ በሣር ፡ መካከል ፡ ይበቅላሉ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 5 ፤ ይህ ፦ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ይላል ፥ ያም ፡ በያዕቆብ ፡ ስም ፡ ይጠራል ፤ ይህም ፦ እኔ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በእጁ ፡ ይጽፋል ፥ በእስራኤልም ፡ የቀኑልምጫ ፡ ስም ፡ ይጠራል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 6 ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፥ የሚቤዥም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ፊተኛ ፡ ነኝ ፥ እኔም ፡ ኋለኛ ፡ ነኝ ፤ ከእኔ ፡ ሌላም ፡ አምላክ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይነሣና ፡ ይጥራ ፡ ይናገርም ፤ ከጥንት ፡ የፈጠርኩትን ፡ ሕዝብ ፡ ያዘጋጅልኝ ፥ የሚመጣውም ፡ ነገር ፡ ሳይደርስ ፡ ይንገሩኝ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 8 ፤ አትፍሩ ፡ አትደንግጡም ፤ ከጥንቱ ፡ ገምሬ ፡ አልነገርኋችኹምን ፧ ወይስ ፡ አላሳየኋችኹምን ፧ እናንተ ፡ ምስክሮቼ ፡ ናችኹ ። ከእኔ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አለን ፧ ዐምባ ፡ የለም ፤ ማንንም ፡ አላውቅም ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 9 ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ የሚሠሩ ፡ ሹሉ ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸው ፥ የወደዱትም ፡ ነገር ፡ አይረባቸውም ፤ ምስክሮቻቸውም ፡ አያዩምና ፡ አያውቁም ፤ ስለዚህ ፥ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 10 ፤ አምላክን ፡ የሠራ ፡ ወይስ ፡ ለምንም ፡ የማይረባ ፡ ምስልን ፡ የቀረጸ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ ባልንጀራዎቹ ፡ ሹሉ ፡ ያፍራሉ ፥ ሠራተኞቹም ፡ ከሰዎች ፡ ወገን ፡ ናቸው ፤ ሹላቸው ፡ ተሰብስበው ፡ ይቁሙ ፤ ይፈራሉ ፡ በአንድነትም ፡ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 12 ፤ ብረት ፡ ሠሪ ፡ መጥረቢያውን ፡ ይሠራል ፥ በፍምም ፡ ውስጥ ፡ ያደርገዋል ፥ በመዶሻም ፡ መቶ ፡ ቅርጽ ፡ ይሰጠዋል ፥ በክንዱም ፡ ኀይል ፡ ይሠራዋል ፥ ርሱም ፡ ይራባል ፡ ይደክምማል ፥ ውሃም ፡ አይጠጣም ፡ ይታክትማል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 13 ፤ ጠራቢውም ፡ ገመድ ፡ ይዘረጋል ፡ በበረቅም ፡ ያመለክተዋል ፡ በመቅረጫም ፡ ይቀርጸዋል ፡ በመለኪያም ፡ ይለካዋል ፤ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ በሰው ፡ አምሳልና ፡ በሰው ፡ ውበት ፡ ያስመስለዋል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 14 ፤ የዝግባን ፡ ዛፎች ፡ ይቈርጣል ፤ የዞጲንና ፡ የኮምቦልን ፡ ዛፍ ፡ ይመርጣል ፥ ከዱር ፡ ዛፎችም ፡ መካከል ፡ ይጠነክር ፡ ዘንድ ፡ ይተወዋል ፤ የጥድንም ፡ ዛፍ ፡ ይተክላል ፡ ዝናብም ፡ ያበቅለዋል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 15 ፤ ለሰውም ፡ ማገዶ ፡ ይኾናል ፤ ከርሱም ፡ ወስዶ ፡ ይሞቃል ፥ አንድዶም ፡ እንጀራ ፡ ይጋግርበታል ፤ ከርሱም ፡ አምላክ ፡ አበጅቶ ፡ ይሰግድለታል ፥ የተቀረጸውንም ፡ ምስል ፡ ሠርቶ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ይንበረከካል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 16 ፤ ግማሹን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላል ፥ በዚያ ፡ በግማሹ ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፥ ሥጋም ፡ ይጠብስበትና ፡ ይጠግባል ፤ ይሞቃልና ፦ ዕሠይ ፡ ሞቅኹ ፥ እሳቱን ፡ አይቻለኹ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 17 ፤ የቀረውንም ፡ ዕንጨት ፡ አምላክ ፡ አድርጎ ፡ ምስል ፡ ይቀርጽበታል ፤ በፊቱም ፡ ተጐንብሶ ፡ ይሰግዳል ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ እየጸለየ ፦ አምላኬ ፡ ነኽና ፥ አድነኝ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 18 ፤ አያውቁም ፥ አያስቡም ፤ እንዳያዩ ፡ ዐይኖቻቸውን ፥ እንዳያስተውሉ ፡ ልቦቻቸውን ፡ ጨፍነዋል ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 19 ፤ በልቡም ፡ ማንም ፡ አያስብም ፦ ግማሿን ፡ በእሳት ፡ አቃጥያለኹ ፥ በፍሟም ፡ ላይ ፡ እንጀራን ፡ ጋግሬያለኹ ፥ ሥጋም ፡ ጠብሼ ፡ በልቻለኹ ፤ የቀረውንም ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ አደርጋለኹን ፧ ለዛፍስ ፡ ግንድ ፡ እሰግዳለኹን ፧ እንዲልም ፡ ዕውቀትና ፡ ማስተዋል ፡ የለውም ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 20 ፤ ዐመድ ፡ ይበላል ፥ የተታለለ ፡ ልብ ፡ አስቶታል ፥ ነፍሱን ፡ ለማዳን ፡ አይችልም ፥ ወይም ፦ በቀኝ ፡ እጄ ፡ ሐሰት ፡ አለ ፡ አይልም ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 21 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፥ ባሪያዬ ፡ ነኽና ፥ ይህን ፡ ዐስብ ፤ እኔ ፡ ሠርቼኻለኹ ፡ አንተም ፡ ባሪያዬ ፡ ነኽ ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያልተረሳ ፡ ትኾናለኽ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 22 ፤ መተላለፍኽን ፡ እንደ ፡ ደመና ፥ ኀጢአትኽንም ፡ እንደ ፡ ጭጋግ ፡ ደምስሻለኹ ፤ ተቤዥቼኻለኹና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለስ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 23 ፤ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ አድርጎታልና ፥ ዘምሩ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ተቤዥቷልና ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ይከበራልና ፥ አንተ ፡ የምድር ፡ ጥልቅ ፡ ሆይ ፥ ጩኽ ፤ እናንተም ፡ ተራራዎች ፡ አንተም ፡ ዱር ፡ ባንተም ፡ ያለ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፥ እልል ፡ በሉ ።

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 24 ፤ ከማሕፀን ፡ የሠራኽ ፥ የሚቤዥኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኹሉን ፡ የፈጠርኹ ፥ ሰማያትን ፡ ለብቻዬ ፡ የዘረጋኹ ፡ ምድርንም ፡ ያጸናኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ማን ፡ ነበረ ፧

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 25 ፤ የሐሰተኞችን ፡ ምልክት ፡ ከንቱ ፡ አደርጋለኹ ፥ ሟርተኞችንም ፡ አሳብዳለኹ ፥ ጥበበኞቹንም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ እመልሳለኹ ፡ ዕውቀታቸውንም ፡ ስንፍና ፡ አደርጋለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 26 ፤ የባሪያዬን ፡ ቃል ፡ አጸናለኹ ፥ የመልእክተኞቼንም ፡ ምክር ፡ እፈጽማለኹ ፤ ኢየሩሳሌምን ፦ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትኾኛለሽ ፥ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፦ ትታነጻላችኹ ፡ ፍራሾቻችኹንም ፡ አቆማለኹ ፡ እላለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 27 ፤ ቀላዩንም ፦ ደረቅ ፡ ኹን ፥ ፈሳሾችኽንም ፡ አደርቃለኹ ፡ እላለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 44 ፡ 28 ፤ ቂሮስንም ፦ ርሱ ፡ እረኛዬ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ኢየሩሳሌምን ፦ ትታነጺያለሽ ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡

ይመሠረታል ፡ ብሎ ፡ ፈቃዴን ፡ ሹሉ ፡ ይፈጽማል ፡ እላለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለቀባኹት ፥ አሕዛብንም ፡ በፊቱ ፡ አስገዛ ፡ ዘንድ ፡ የነገሥታትንም ፡ ወገብ ፡ እፈታ ፡ ዘንድ ፥ በሮቹም ፡ እንዳይዘጉ ፡ መዝጊያዎቹን ፡ በፊቱ ፡ እከፍት ፡ ዘንድ ፥ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ለያዝኹት ፡ ለቂሮስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 2 ፤ በፊትኽ ፡ እኼዳለኹ ፡ ተራራዎችንም ፡ ትክክል ፡ አደርጋለኹ ፥ የናሱንም ፡ ደጆች ፡ እሰብራለኹ ፡ የብረቱንም ፡ መወርወሪያዎች ፡ እቈርጣለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 3 ፤ በስምኽም ፡ የምጠራኽ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ በጨለማ ፡ የነበረችውን ፡ መዝገብ ፡ በስውርም ፡ የተደበቀችውን ፡ ሀብት ፡ እሰጥኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 4 ፤ ስለ ፡ ባሪያዬ ፡ ስለ ፡ ያዕቆብ ፥ ስለ ፡ መረጥኹትም ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ብዬ ፡ በስምኽ ፡ ጠርቼኻለኹ ፤ በቀ፡ልምጫ ፡ ስምኽ ፡ ጠራኹኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አላወቅኸኝም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 5-6 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ከእኔም ፡ በቀር ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ በፀሓይ ፡ መውጫና ፡ በምዕራብ ፡ ያሉ ፡ ከእኔ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሌላ ፡ እንደሌለ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አስታጠቅኹኽ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ አላወቅኸኝም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ ሌላ ፡ ማንም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 7 ፤ ብርሃንን ፡ ሠራኹ ፥ ጨለማውንም ፡ ፈጠርኹ ፤ ደኅንነትን ፡ እሠራለኹ ፥ ክፋትንም ፡ እፈጥራለኹ ፤ እነዚህን ፡ ሹሉ ፡ ያደረግኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ሰማያት ፡ ከላይ ፡ አንጠባጥቡ ፥ ደመናትም ፡ ጽድቅን ፡ ያዝንቡ ፤ ምድርም ፡ ትከፈት ፥ መድኀኒትንም ፡ ታብቅል ፥ ጽድቅም ፡ በአንድነት ፡ ይብቀል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጥሬዋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 9 ፤ ከሠሪው ፡ ጋራ ፡ ለሚታገል ፡ ወዮለት! ፡ በምድር ፡ ሸክላዎች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ሸክላ ፡ ነው ። ጭቃ ፡ ሠሪውን ፦ ምን ፡ ትሠራለኽ ፧ ወይስ ፡ ሥራኽ ፦ እጅ ፡ የለውም ፡ ይላልን ፧

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 10 ፤ አባትን ፦ ምን ፡ ወልደኻል ፧ ወይም ፡ ሴትን ፦ ምን ፡ አማጥሽ ፧ ለሚል ፡ ወዮ! ፡

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 11 ፤ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ሠሪውም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሚመጣው ፡ ነገር ፡ ጠይቁኝ ፥ ስለ ፡ ልጆቼና ፡ ስለእጄ ፡ ሥራም ፡ እዘዙኝ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 12 ፤ እኔ ፡ ምድርን ፡ ሠርቻለኹ ፡ ሰውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ እኔ ፡ በእጄ ፡ ሰማያትን ፡ ዘርግቻለኹ ፥ ሰራዊታቸውንም ፡ ሹሉ ፡ አዝዣለኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ በጽድቅ ፡ አስነሥቼዋለኹ ፥ መንገዱንም ፡ ሹሉ ፡ አቀናለኹ ፤ ርሱ ፡ ከተማዬን ፡ ይሠራል ፥ በዋጋም ፡ ወይም ፡ በደመ ፡ ወዝ ፡ ሳይኾን ፡ ምርኮኞቼን ፡ ያወጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የግብጽ ፡ ድካምና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ቁመተ ፡ ረዥሞችም ፡ የሳባ ፡ ሰዎች ፡ ወዳንተ ፡ ያልፋሉ ፤ ለአንተም ፡ ይኾናሉ ፡ እጆቻቸውም ፡ ታስረው ፡ ይከተሉኻል ፤ በፊትኽም ፡ ያልፋሉ ፥ ለአንተም ፡ እየሰገዱ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ አለ ፥ ከርሱም ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፡ ብለው ፡ ይለምኑኻል ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ መድኀኒት ፡ ሆይ ፥ በእውነት ፡ አንተ ፡ ራስኽን ፡ የምትሰውር ፡ አምላክ ፡ ነኽ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 16 ፤ ኹሉም ፡ ያፍራሉ ፡ ይዋረዱማል ፥ ጣዖታትንም ፡ የሚሠሩ ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ውርደት ፡ ይኼዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ በዘላለማዊ ፡ መድኀኒት ፡ ያድነዋል ፥ እናንተም ፡ ለዘለዓለም ፡ አታፍሩምና ፡ አትዋረዱም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 18 ፤ ሰማያትን ፡ የፈጠረ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርሱም ፡ ምድርን ፡ የሠራና ፡ ያደረገ ፡ ያጸናትም ፥ መኖሪያም ፡ ልትኾን ፡ እንጂ ፡ ለከንቱ ፡ እንድትኾን ፡ ያልፈጠራት ፡ አምላክ ፥ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 19 ፤ በስውር ፡ ወይም ፡ በጨለማ ፡ ምድር ፡ ስፍራ ፡ አልተናገርኹም ፤ ለያዕቆብ ፡ ዘር ፦ በከንቱ ፡ ፈልጉኝ ፡ አላልኹም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቅን ፡ እናገራለኹ ፡ ቅንንም ፡ አወራለኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ኾናችኹ ፡ ያመለጣችኹ ፥ ተሰብስባችኹ ፡ ኑ ፡ በአንድነትም ፡ ቅረቡ ፤ የተቀረጸውን ፡ የምስላቸውን ፡ ዕንጨት ፡ የሚሸከሙና ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ወደማይችል ፡ አምላክ ፡ የሚጸልዩ ፡ ዕውቀት ፡ የላቸውም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 21 ፤ ይናገሩ ፡ ይቅረቡም ፡ በአንድነትም ፡ ይማከሩ ፤ ከጥንቱ ፡ ይህን ፡ ያሳየ ፡ ከቀድሞስ ፡ የተናገረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ያሳየኹም ፡ የተናገርኹም ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለኹምን ፧ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለም ፤ እኔ ፡ ጻድቅ ፡ አምላክና ፡ መድኀኒት ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 22 ፤ እናንተ ፡ የምድር ፡ ዳርቻ ፡ ኹሉ ፥ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ዘወር ፡ በሉ ፡ ትድኑማላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 23 ፤ ቃሌ ፡ ከአፌ ፡ በጽድቅ ፡ ወጥታለች ፥ አትመለስም ። ጕልበት ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ ይንበረከካል ፥ ምላስም ፡ ኹሉ ፡ በእኔ ፡ ይምላል ፡ ብዬ ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 24 ፤ ስለ ፡ እኔም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ጽድቅና ፡ ኀይል ፡ አለ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ሰዎች ፡ ይመጣሉ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቈጡ ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፡ 45 ፡ 25 ፤ የእስራኤልም ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይጸድቃሉ ፥ ይመካሉም ፡ ይባላል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 1 ፤ ቤል ፡ ተዋረደ ፥ ናባው ፡ ተሰባበረ ፤ ጣዖቶቻቸው ፡ በእንስሳና ፡ በከብት ፡ ላይ ፡ ተጫነዋል ፤ ሸክሞቻችኹ ፡ ለደካማ ፡ እንስሳ ፡ ከባድ ፡ ጭነት ፡ ኾነዋል ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 2 ፤ ተጐነበሱ ፡ በአንድነትም ፡ ተዋረዱ ፤ ሸክሙን ፡ ለማዳን ፡ አልቻሉም ፥ ራሳቸው ፡ ግን ፡ ተማረኩ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 3 ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ከሆድ ፡ ያነሣኋችኹ ፡ ከማሕፀንም ፡ የተሸከምኋችኹ ፥ ስሙኝ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 4 ፤ እስከ ፡ ሽምግልና ፡ ድረስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ እስከ ፡ ሽበትም ፡ ድረስ ፡ እሸከማችኋለኹ ፤ እኔ ፡ ሠርቻለኹ ፡ እኔም ፡ አነሣለኹ ፤ እኔ ፡ እሸከማለኹ ፡ እኔም ፡ አድናለኹ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 5 ፤ በማን ፡ ትመስሉኛላችኹ ፧ ከማንስ ፡ ጋራ ፡ ታስተካክሉኛላችኹ ፧ እንመሳሰል ፡ ዘንድ ፡ ከማን ፡ ጋራ ፡ ታስተያዩኛላችኹ ፧

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 6 ፤ ወርቁን ፡ ከኰረጆ ፡ የሚያፈሱ ፥ ብሩንም ፡ በሚዛን ፡ የሚመዝኑ ፡ እነርሱ ፡ አንጥረኛውን ፡ ይቀጥራሉ ፥ ርሱም ፡ አምላክ ፡ አድርጎ ፡ ይሠራ ፡ ዋል ፤ ለዚያም ፡ ይጐነበሱለታል ፥ ይሰግዱለትማል ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 7 ፤ በጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ አንሥተው ፡ ይሸከሙታል ፡ በስፍራውም ፡ ያደርጉታል ፥ በዚያም ፡ ይቆማል ፥ ከስፍራውም ፡ ፈቀቅ ፡ አይልም ፤ ሰውም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቢጮኽ ፡ አይሰማውም ፡ ከመከራውም ፡ አያድነውም ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 8 ፤ ይህን ፡ ዐስቡና ፡ አልቅሱ ፤ ተላላፊዎች ፡ ሆይ ፥ ንስሓ ፡ ግቡ ፥ ልባችኹንም ፡ መልሱ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፥ ሌላም ፡ የለምና ፡ የቀድሞውን ፡ የጥንቱን ፡ ነገር ፡ ዐስቡ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ እንደ ፡ እኔም ፡ ያለ ፡ ማንም ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 10 ፤ በመገሥመሪያ ፡ መጨረሻውን ፥ ከጥንትም ፡ ያልተደረገውን ፡ እነግራለኹ ፤ ምክሬ ፡ ትጸናለች ፡ ፈቃዴንም ፡ ኹሉ ፡ እፈጽማለኹ ፡ እላለኹ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 11 ፤ ከምሥራቅ ፡ ነጣቂ ፡ ወፍን ፥ ከሩቅም ፡ አገር ፡ ምክሬን ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰው ፡ እጠራዋለኹ ። ተናግሬያለኹ ፤ እፈጽማለኹ ፤ ዐስቤያለኹ ፡ አደርግማለኹ ።

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ ከጽድቅ ፡ የራቃችኹ ፡ እልከኞች ፥ ስሙኝ ፤

ኢሳ. ፡ 46 ፡ 13 ፤ ጽድቄን ፡ አቀርባለኹ ፥ አይርቅም ፡ መድኀኒቴም ፡ አይዘገይም ፤ ከጽዮን ፡ ለክብር ፡ እንዲኾን ፡ መድኀኒትን ፡ ለእስራኤል ፡ ሰጥቻለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 1 ፤ አንቺ ፡ ድንግል ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ውረጂ ፡ በትቢያም ፡ ላይ ፡ ተቀመጪ ፤ የከለዳውያን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅልጣናምና ፡ ቅምጥል ፡ አትባይምና ፥ ያለዙፋን ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀመጪ ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 2 ፤ ወፍጮ ፡ ወስደሽ ፡ ዱቄትን ፡ ፍጪ ፤ መሸፈኛሽን ፡ አውጪ ፡ ረዥሙንም ፡ ልብስሽን ፡ አውልቀሽ ፡ ጣዩው ፤ ባትሽን ፡ ግለጪ ፥ ወንዙን ፡ ተሻገሪ ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 3 ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽ ፡ ይገለጣል ፡ ዕፍረትሽም ፡ ይታያል ፤ እኔ ፡ እበቀላለኹ ፥ ለማንም ፡ አልራራም ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 4 ፤ ታዳጊያችን ፥ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 5 ፤ የከለዳውያን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፦ የመንግሥታት ፡ እመቤት ፡ አትባይምና ፥ ዝም ፡ ብለሽ ፡ ተቀመጪ ፥ ወደ ፡ ጨለማም ፡ ውስጥ ፡ ግቢ ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 6 ፤ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ተቈጥቼ ፡ ነበር ፡ ርስቴንም ፡ አረከስኹ ፡ በእጅሽም ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋቸው ፤ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ምሕረት ፡ አላደረግሽም ፥ በሽማግሌዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ቀንበርሽን ፡ እጅግ ፡ አክብደሻል ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 7 ፤ አንቺም ፦ እኔ ፡ ለዘለዓለም ፡ እመቤት ፡ እኾናለኹ ፡ ብለሻል ፤ ይህንም ፡ በልብሽ ፡ አላደረግሽም ፡ ፍጻሜውንም ፡ አላሰብሽም ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 8 ፤ አኹንም ፡ አንቺ ፡ ቅምጥል ፡ ተዘልለሽ ፡ የምትቀመጪ ፥ በልብሽም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፤ መበለትም ፡ ኾኜ ፡ አልኖርም ፡ የወላድ ፡ መካንነትንም ፡ አላውቅም ፡ የምትዪ ፡ ይህን ፡ ስሚ ፤

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 9 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፥ የወላድ ፡ መካንነትና ፡ መበለትነት ፥ በድንገት ፡ ይመጡብሻል ፤ ስለ ፡ መተቶችሽ ፡ ብዛትና ፡ ስለ ፡ አስማቶችሽ ፡ ጽናት ፡ ፈጽመው ፡ ይመጡብሻል ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 10 ፤ በክፋትሽ ፡ ታምነሻል ፤ የሚያየኝ ፡ የለም ፡ ብለሻል ፤ ጥበብሽና ፡ ዕውቀትሽ ፡ አታሰውሻል ፡ በልብሽም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ብለሻል ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይመጣብሻል ፡ በሚርትሽም ፡ እንዴት ፡ እንደምታርቂው ፡ አታውቂም ፤ ጕዳት ፡ ይወድቅብሻል ፡ ታስወግጂውም ፡ ዘንድ ፡ አይቻልሽም ፤ የማታውቂያትም ፡ ጕስቍልና ፡ ድንገት ፡ ትመጣብሻለች ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 12 ፤ ምናልባትም ፡ መጠቀም ፡ ትችዪ ፡ ወይም ፡ ታስደነግጪ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከአስማቶችሽና ፡ ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምረሽ ፡ ከደከምሽበት ፡ ከመተቶችሽ ፡ ብዛት ፡ ጋራ ፡ ቁሚ ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 13 ፤ በምክርሽ ፡ ብዛት ፡ ደክመሻል ፤ አኹንም ፡ የሰማይን ፡ ከዋክብት ፡ የሚቈጥሩ ፡ ከዋክብትንም ፡ የሚመለከቱ ፡ በየመባቻውም ፡ የሚመጣውን ፡ ነገር ፡ የሚናገሩ ፡ ተነሥተው ፡ ከሚመጣብሽ ፡ ነገር ፡ ያድኑሽ ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 14 ፤ እንሆ ፡ እንደ ፡ እብቅ ፡ ይኾናሉ ፡ እሳትም ፡ ያቃጥላቸዋል ፡ ሰውነታቸውንም ፡ ከነበልባል ፡ ኀይል ፡ አያድኑም ፤ ርሱም ፡ ሰው ፡ እንደሚሞቀው ፡ ፍም ፡ ወይም ፡ በፊቱ ፡ ሰው ፡ እንደሚቀመጥበት ፡ እሳት ፡ ያለ ፡ አይደለም ።

ኢሳ. ፡ 47 ፡ 15 ፤ የደከምሽባቸው ፡ ነገሮች ፡ እንዲህ ፡ ይኾኑብሻል ፤ ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምረው ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይነግዱ ፡ የነበሩ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ወደ ፡ ስፍራቸው ፡ ይኼዳሉ ፡ የሚያድንሽም ፡ የለም ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 48 ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ በእስራኤል ፡ ስም ፡ የተጠራችኹ ፡ ከይሁዳም ፡ ውሃዎች ፡ የወጣችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የምትምሉ ፡ በእውነት ፡ ሳይኾን ፡ በጽድቅም ፡ ሳይኾን ፡ የእስራኤልን ፡ አምላክ ፡ የምትጠሩ ፡

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 2 ፤ በቅድስት ፡ ከተማ ፡ ስም ፡ የተጠራችኹ ፡ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚባል ፡ በእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የምትደገፉ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ስሙ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 3 ፤ የቀድሞውን ፡ ነገር ፡ ከጥንት ፡ ተናግሬያለኹ ፡ ከአፌም ፡ ወጥቷል ፡ አሳይቼውማለኹ ፤ ድንገት ፡ አድርጌዋለኹ ፡ ተፈጽሞማል ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 4 ፤ አንተ ፡ እልከኛ ፡ ዐንገትኽም ፡ የብረት ፡ ዥማት ፡ ግንባርኽም ፡ ናስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቄያለኹ ፤

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፡ አንተ ፦ ጣዖቴ ፡ ይህን ፡ አድርጓል ፡ የተቀረጸው ፡ ምስሌና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራው ፡ ምስሌ ፡ ይህን ፡ አዘዙኝ ፡ እንዳትል ፡ አስቀድሜ ፡ ነግሬኽ ፡ ነበር ፡ ሳይኾንም ፡ አሳይቼኽ ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 6 ፤ ሰምተኻል ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ተመልከት ፤ እናንተም ፡ የምትናገሩት ፡ አይደላችኹምን ፧ የተሰወሩትን ፡ ያላወቅኻቸውንም ፡ ዐዲሶች ፡ ነገሮችን ፡ ከዚህ ፡ ዠምሬ ፡ አሳይቼኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፡ አኹን ፡ እንጂ ፡ ከጥንት ፡ አልተፈጠሩም ፤ አንተም ፦ እንሆ ፡ ዐውቄያቸዋለኹ ፡ እንዳትል ፡ ከዛሬ ፡ በፊት ፡ አልሰማኻቸውም ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 8 ፤ አልሰማኽም ፡ አላወቅኽም ፡ ዦሮኽ ፡ ከጥንት ፡ አልተከፈተችም ፤ አንተ ፡ ፈጽሞ ፡ ወንጀለኛ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ከማሕፀንም ፡ ዠምረኽ ፡ ተላላፊ ፡ ተብለኽ ፡ እንደ ፡ ተጠራኽ ፡ ዐውቄያለኹና ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ ቍጣዬን ፡ አዘገያለኹ ፡ እንዳላጠፋኽም ፡ ስለ ፡ ምስጋናዬ ፡ እታገሣለኹ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 10 ፤ እንሆ ፡ አንጥሬኻለኹ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ብር ፡ አይደለም ፤ በመከራም ፡ እቶን ፡

ፈትኜ ካለኹ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 11 ፤ ስለ ፡ እኔ ፥ ስለ ፡ ራሴ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ስሜ ፡ ተነቅፏልና ፤ ክብሬንም ፡ ለሌላ ፡ አልሰጥም ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 12 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ የጠራኹኽም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማኝ ፤ እኔ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ ፊተኛው ፡ ነኝ ፡ እኔም ፡ ኋለኛው ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 13 ፤ እጄም ፡ ምድርን ፡ መሥርታለች ፡ ቀኜም ፡ ሰማያትን ፡ ዘርግታለች ፤ በጠራኋቸው ፡ ጊዜ ፡ በአንድነት ፡ ይቆማሉ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ ኹሉ ፥ በአንድነት ፡ ተሰብስባችኹ ፡ ስሙ ፤ ከነርሱ ፡ ይህን ፡ የተናገረ ፡ ማን ፡ ነው ። እግዚአብሔር ፡ የወደደው ፡ ፈቃዱን ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፥ ክንዱም ፡ በከለዳውያን ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ ተናግሬያለኹ ፤ እኔ ፡ ጠርቼዋለኹ ፤ አምጥቼዋለኹ ፥ መንገዱም ፡ ትከናወንለታለች ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ቅረቡ ፡ ይህንም ፡ ስሙ ፤ እኔ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሬ ፡ በስውር ፡ አልተናገርኹም ፤ ከኾነበት ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እኔ ፡ በዚያ ፡ ነበርኹ ፥ አኹንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርና ፡ መንፈሱ ፡ ልከውኛል ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 17 ፤ ታዳጊኽ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ የሚረባኽን ፡ ነገር ፡ የማስተምርኽ ፡ በምትኼድባትም ፡ መንገድ ፡ የምመራኽ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 18 ፤ ትእዛዜን ፡ ብትሰማ ፡ ኖሮ ፥ ሰላምኽ ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ ጽድቅኽም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ሞገድ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፤

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 19 ፤ ዘርኽም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ የሆድኽም ፡ ትውልድ ፡ እንደምድር ፡ ትቢያ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፥ ስሙም ፡ ከፊቴ ፡ ባልጠፋና ፡ ባልፈረሰ ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 20 ፤ ከባቢሎን ፡ ውጡ ፡ ከከለዳውያንም ፡ ኰብልሉ ፤ በእልልታ ፡ ድምፅ ፡ ተናገሩ ፡ ይህንም ፡ ንገሩ ፡ እስከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ አውሩና ፦ እግዚአብሔር ፡ ባሪያውን ፡ ያዕቆብን ፡ ታድጎታል ፡ በሉ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 21 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ በኩል ፡ በመራቸው ፡ ጊዜ ፡ አልተጠሙም ፤ ውሃንም ፡ ከአለቱ ፡ ውስጥ ፡ አፈለቀላቸው ፥ አለቱንም ፡ ሠነጠቀ ፡ ውሃውም ፡ ፈሰሰ ።

ኢሳ. ፡ 48 ፡ 22 ፤ ለክፉዎች ፡ ሰላም ፡ የላቸውም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 49 ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 1 ፤ ደሴቶች ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፥ እናንተም ፡ በሩቅ ፡ ያላችኹ ፡ አሕዛብ ፥ አድምጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ከማሕፀን ፡ ጠርቶኛል ፥ ከእናቴም ፡ ሆድ ፡ ዠምሮ ፡ ስሜን ፡ አንሥቷል ፤

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 2 ፤ አፌንም ፡ እንደ ፡ ተሳለ ፡ ሰይፍ ፡ አድርጓል ፥ በእጁ ፡ ጥላ ፡ ሰውሮኛል ፤ እንደ ፡ ተሳለ ፡ ፍላጻም ፡ አድርጎኛል ፥ በሰገባውም ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጎኛል ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 3 ፤ ርሱም ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ነኽ ፡ ባንተም ፡ እከበራለኹ ፡ አለኝ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ግን ፦ በከንቱ ፡ ደከምኹ ፥ ምንም ፡ ጥቅም ፡ ለሌለውና ፡ ለከንቱ ፡ ጕልበቴን ፡ ፈጀኹ ፤ ፍርዴ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፥ ዋጋዬም ፡ በአምላኬ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ከብሬያለኹና ፥ አምላኬም ፡ ጕልበት ፡ ኾኖኛልና ፥ ያዕቆብን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እንድመልስ ፡ እስራኤልንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እንድሰበስብ ፡ ባሪያ ፡ እኾነው ፡ ዘንድ ፡ ከማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ የሠራኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ የያዕቆብን ፡ ነገዶች ፡ እንድታስነሣ ፡ ከእስራኤልም ፡ የዳኑትን ፡ እንድትመስል ፡ ባሪያዬ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ነውና ፥ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ መድኀኒት ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ አድርጌ ፡ ሰጥቼካለኹ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 7 ፤ የእስራኤል ፡ ታዳጊ ፡ ቅዱሱም ፥ እግዚአብሔር ፥ ሰዎች ፡ ለሚንቁት ፡ ሕዝብም ፡ ለሚጠላው ፡ ለገዢዎች ፡ ባሪያ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ ታማኙ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስለ ፡ መረጠኽም ፡ ስለእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ነገሥታት ፡ አይተው ፡ ይነሣሉ ፥ መሳፍንትም ፡ አይተው ፡ ይሰግዳሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በተወደደ ፡ ጊዜ ፡ ሰምቼካለኹ ፥ በመድኀኒትም ፡ ቀን ፡ ረድቼካለኹ ፤ እጠብቅኽማለኹ ፥ ምድርንም ፡ ታቀና ፡ ዘንድ ፥ ውድማ ፡ የኾኑትንም ፡ ርስቶች ፡ ታወርስ ፡ ዘንድ ፥

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 9 ፤ የተጋዙትንም ፦ ውጡ ፥ በጨለማም ፡ የተቀመጡትን ፦ ተገለጡ ፡ ትል ፡ ዘንድ ፥ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጌ ፡ ለሕዝቡ ፡ ሰጥቼካለኹ ። በመንገድም ፡ ላይ ፡ ይሰማራሉ ፥ ማሰማሪያቸውም ፡ በወና ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 10 ፤ የሚራራላቸውም ፡ ይመራቸዋልና ፥ በውሃም ፡ ምንጮች ፡ በኩል ፡ ይነዳቸዋልና ፥ አይራቡም ፥ አይጠሙም ፥ ትኵሳት ፡ ወይም ፡ ፀሓይ ፡ አይጐዳቸውም ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 11 ፤ ተራራዎቼንም ፡ ኹሉ ፡ መንገድ ፡ አደርጋለኹ ፥ ጐዳኖቼም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 12 ፤ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ ከሩቅ ፥ እንሆም ፥ እነዚህ ፡ ከሰሜንንና ፡ ከምዕራብ ፥ እነዚህም ፡ ከሢኒም ፡ አገር ፡ ይመጣሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አጽናንቷልና ፥ ለችግረኞቹም ፡ ራርቷልና ፥ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ ዘምሩ ፥ ምድር ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ተራራዎችም ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 14 ፤ ጽዮን ፡ ግን ፦ እግዚአብሔር ፡ ትቶኛል ፡ ጌታም ፡ ረስቶኛል ፡ አለች ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 15 ፤ በእውኑ ፡ ሴት ፡ ከማሕፀኗ ፡ ለተወለደው ፡ ልጅ ፡ እስከማትራራ ፡ ድረስ ፡ ሕፃኗን ፡ ትረሳ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለችን ፧ አዎን ፥ ርሷ ፡ ትረሳ ፡ ይኾናል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልረሳሽም ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 16 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በእጄ ፡ መጻፍ ፡ ቀርጬሻለኹ ፥ ቅጥሮችሽም ፡ ዘልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 17 ፤ ልጆችሽ ፡ ይፈጥናሉ ፤ ያፈረሱሽና ፡ ያወደሙሽ ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ይወጣሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 18 ፤ ዐይንሽን ፡ አንሥተሽ ፡ በዙሪያሽ ፡ ተመልከቺ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ። እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ጌጥ ፡ ትለብሻቸዋለሽ ፥ እንደ ፡ ሙሽራም ፡ ትጐናጸፊአቸዋለሽ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 19 ፤ ባድማሽና ፡ ውድማሽ ፡ ወናም ፡ የኾነው ፡ ምድርሽ ፡ ከሚኖሩብሽ ፡ የተነሣ ፡ ዛሬ ፡ ጠባብ ፡ ትኾናለችና ፥ የዋጡሽም ፡ ይርቃሉና ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 20 ፤ የወላድ ፡ መካን ፡ ከኾንሽ ፡ በኋላ ፡ የተወለዱልሽ ፡ ልጆችሽ ፡ በጕሮሽ ፦ ስፍራ ፡ ጠቦኛልና ፥ እቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ቦታ ፡ አስፊልኝ ፡ ይላሉ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 21 ፤ አንቺም ፡ በልብሽ ፥ የወላድ ፡ መካን ፡ ኾኛለኹና ፥ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ተሰድጃለኹና ፡ ተቅበዝብዣለኹምና ፡ እነዚህን ፡ ማን ፡ ወለደልኝ ፧ እነዚህንስ ፡ ማን ፡ አሳደጋቸው ፧ እንሆ ፥ ብቻዬን ፡ ቀርቼ ፡ ነበር ፤ እነዚህስ ፡ ወዴት ፡ ነበሩ ፧ ትያለሽ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 22 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እጄን ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አነሣለኹ ፥ ዐላማዬንም ፡ ወደ ፡ ወገኖች ፡ አቆማለኹ ፤ ወንዶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በብብታቸው ፡ ያመጧቸዋል ፥ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ ይሸከሟቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 23 ፤ ነገሥታትም ፡ አሳዳጊ ፡ አባቶችሽ ፡ ይኾናሉ ፥ እቴጌዎቻቸውም ፡ ሞግዚቶችሽ ፡ ይኾናሉ ፤ ግንባራቸውንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዝቅ ፡ አድርገው ፡ ይሰግዱልሻል ፥ የእግርሽንም ፡ ትቢያ ፡ ይልሳሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ፥ እኔንም ፡ በመተማመን ፡ የሚጠባበቁ ፡ አያፍሩም ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 24 ፤ በእውኑ ፡ ብዝበዛ ፡ ከኀያል ፡ እጅ ፡ ይወሰዳልን ፧ ወይስ ፡ የጨካኙ ፡ ምርኮኞች ፡ ያመልጣሉን ፧

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኀያላን ፡ የተማረኩ ፡ ይወሰዳሉ ፥ የጨካኞችም ፡ ብዝበዛ ፡ ያመልጣል ፤ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ የሚጣሉትን ፡ እጣላቸዋለኹ ፥ ልጆችሽንም ፡ አድናለኹ ።

ኢሳ. ፡ 49 ፡ 26 ፤ አስጨናቂዎችሽንም ፡ ሥጋቸውን ፡ አስበላቸዋለኹ ፥ እንደ ፡ ጣፋጭም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ደማቸውን ፡ ጠጥተው ፡ ይሰክራሉ ፤ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ መድኀኒትሽና ፡ ታዳጊሽ ፥ የያዕቆብ ፡ ኀያል ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 50 ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናታችኹን ፡ የፈታኹበት ፡ የፍቺ ፡ ጽሕፈት ፡ የት ፡ አለ ፧ ወይስ ፡ እናንተን ፡ የሸጥኹ ፡ ከአበዳሪዎች ፡ ለየትኛው ፡ ነው ፧ እንሆ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችኹ ፡ ተሸጣችኋል ፥ ስለ ፡ በደላችኹም ፡ እናታችኹ ፡ ተፈታለች ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 2 ፤ በመጣኹስ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልነበረም ፧ በጠራኹስ ፡ ጊዜ ፡ የሚመልስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልነበረም ፧ መታደግ ፡ እንዳትችል ፡ እጄ ፡ ዐጪር ፡ ኾናለችን ፧ ወይስ ፡ ለማዳን ፡ ኀይል ፡ የለኝምን ፧ እንሆ ፥ በገሠጽኹ ፡ ጊዜ ፡ ባሕርን ፡ አደርቃለኹ ፥ ወንዞችንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ ውሃም ፡ በማጣት ፡ ዓሣዎቻቸው ፡ ይገማሉ ፡ በጥማትም ፡ ይሞታሉ ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 3 ፤ ሰማያትን ፡ ጥቀሩረት ፡ አለብሳቸዋለኹ ፥ መጋረጃቸውንም ፡ ማቅ ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 4 ፤ የደከመውን ፡ በቃል ፡ እንዴት ፡ እንደምደግፍ ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተማሩትን ፡ ምላስ ፡ ሰጥቶኛል ፡ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ያነቃኛል ፥ እንደ ፡ ተማሪዎችም ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ጐሮዬን ፡ ያነቃቃል ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 5 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጐሮዬን ፡ ከፍቷል ፥ እኔም ፡ ዐመፀኛ ፡ አልነበርኹም ፡ ወደ ፡ ኋላዬም ፡ አልተመለስኹም ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 6 ፤ ገርርባዬን ፡ ለገራፊዎች ፡ ጕንጨንም ፡ ለጠጕር ፡ ነጪዎች ፡ ሰጠኹ ፥ ፊቴንም ፡ ከውርደትና ፡ ከትፋት ፡ አልመለስኹም ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 7 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛልና ፥ ስለዚህ ፡ አልታወክኹም ፤ ስለዚህም ፡ ፊቴን ፡ እንደ ፡ ባልጩት ፡ ድንጋይ ፡ አድርጌዋለኹ ፥ እንዳላፍርም ፡ ዐውቃለኹ ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 8 ፤ የሚያጸድቀኝ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፤ ከእኔስ ፡ ጋራ ፡ የሚከራከር ፡ ማን ፡ ነው ፧ በአንድነት ፡ እንቁም ፤ የሚከራከረኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወደ ፡ እኔ ፡ ይቅረብ ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 9 ፤ እንሆ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ፤ ማን ፡ ይፈርድብኛል ፧ እንሆ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፡ ብልም ፡ ይበላቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 10 ፤ ከእናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፥ የባሪያውንም ፡ ቃል ፡ የሚሰማ ፥ በጨለማም ፡ የሚኼድ ፥ ብርሃንም ፡ የሌለው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚታመን ፥ በአምላኩም ፡ የሚደገፍ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፡ 50 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ እሳት ፡ የምታነዱ ፡ የእሳትንም ፡ ወላፈን ፡ የምትታጠቁ ፡ ኹላችኹ ፥ በእሳታችኹ ፡ ነበልባል ፡ ባነደዳችኹትም ፡ ወላፈን ፡ ኺዱ ፤ ይህ ፡ ከእጄ ፡ ይኾንባችኋል ፤ በሐዘን ፡ ትተኛላችኹ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 51 ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ ጽድቅን ፡ የምትከተሉ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የምትሹ ፥ ስሙኝ ፤ ከርሱ ፡ የተቈረጣችኹበትን ፡ ድንጋይ ፡ ከርሱም ፡ የተቈፈራችኹበትን ፡ ጕድጓድ ፡ ተመልከቱ ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ አባታችኹ ፡ ወደ ፡ አብርሃም ፥ ወደ ፡ ወለደቻችኹም ፡ ወደ ፡ ሳራ ፡ ተመልከቱ ፤ አንድ ፡ ብቻውን ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ጠራኹት ፥ ባረክኹትም ፥ አበዛኹትም ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጽዮንን ፡ ያጽናናል ፤ በርሷም ፡ ባድማ ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ያጽናናል ፥ ምድረ ፡ በዳዋንም ፡ እንደ ፡ ዔዴን ፡ በረሓዋንም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ያደርጋል ፤ ደስታና ፡ ተድላ ፡ ምስጋናና ፡ የዝማሬ ፡ ድምፅ ፡ ይገኝበታል ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 4 ፤ ወገኔ ፡ ሆይ ፥ አድምጠኝ ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ስማኝ ፤ ሕግ ፡ ከእኔ ፡ ይወጣልና ፥ ፍርዴም ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ ይኾናልና ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 5 ፤ ጽድቄ ፡ ፈጥኖ ፡ ቀርቧል ፥ ማዳኔም ፡ ወጥቷል ፥ ክንዴም ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ይፈርዳል ፤ ደሴቶች ፡ እኔን ፡ በመተማመን ፡ ይጠባበቃሉ ፥ በክንዴም ፡ ይታመናሉ ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 6 ፤ ዐይናችኹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሡ ፥ ወደ ፡ ታችም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ተመልከቱ ፤ ሰማያት ፡ እንደ ፡ ጢስ ፡ በነው ፡ ይጠፋሉ ፥ ምድርም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ታረጃለች ፥ የሚኖሩባትም ፡ እንዲሁ ፡ ይሞታሉ ፤ ማዳኔ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኾናል ፥ ጽድቄም ፡ አይፈርስም ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 7 ፤ ጽድቅን ፡ የምታውቁ ፡ ሕጌም ፡ በልባችኹ ፡ ያለ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ፤ የሰውን ፡ ተግዳሮት ፡ አትፍሩ ፥ በስድባቸውም ፡ አትደንግጡ ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 8 ፤ እንደ ፡ ልብስም ፡ ብል ፡ ይበላቸዋል ፥ እንደ ፡ በግ ፡ ጠጕርም ፡ ትል ፡ ይበላቸዋል ፤ ጽድቄ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ማዳኔም ፡ ለትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡ ሆይ ፥ ተነሥ ፥ ተነሥ ፥ ኀይልንም ፡ ልበስ ፤ በቀድሞው ፡ ወራትና ፡ በጥንቱ ፡ ዘመን ፡ በነበረው ፡ ትውልድ ፡ እንደኾነው ፡ ተነሥ ። ረዓብን ፡ የቈራረጥኽ ፡ ዘንዶውንም ፡ የወጋኽ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 10 ፤ ባሕሩንና ፡ የታላቁን ፡ ጥልቅ ፡ ውሃ ፡ ያደረቅኸው ፥ የዳኑትም ፡ ይሻገሩ ፡ ዘንድ ፡ ጠሊቁን ፡ ባሕር ፡ መንገድ ፡ ያደረግኽ ፡ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተቤዣቸው ፡ ይመለሳሉ ፡ ወደ ፡ ጽዮንም ፡ ይመጣሉ ፤ የዘለዓለምም ፡ ደስታ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ደስታንና ፡ ተድላን ፡ ያገኛሉ ፥ ሐዘንና ፡ ልቅሶም ፡ ይሸሻል ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 12 ፤ የማጽናናችኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ እኔ ፡ ነኝ ፤ የሚሞተውን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሣርም ፡ የሚጠወልገውን ፡

የሰው ፡ ልጅ ፡ ትፈራ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 13 ፤ ሰማያትንም ፡ የዘረጋው ፡ ምድርንም ፡ የመሠረተውን ፡ ፈጣሪኽን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተኻል ፤ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ባዘጋጀ ፡ ጊዜ ፡ ካስጨናቂው ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ ዅልጊዜ ፡ ቀኑን ፡ ዅሉ ፡ ፈርተኻል ፤ የአስጨናቂው ፡ ቍጣ ፡ የት ፡ አለ ፧

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 14 ፤ ምርኮኛ ፡ ፈጥኖ ፡ ይፈታል ፤ አይሞትም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ አይወርድም ፥ እንጀራም ፡ አይጐድልበትም ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 15 ፤ ሞገዱም ፡ እንዲተምሥ ፡ ባሕርን ፡ የማናውጥ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ ስሜም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 16 ፤ ሰማያትን ፡ እዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ ምድርንም ፡ እመሠርት ፡ ዘንድ ፥ ጽዮንንም ፦ አንቺ ፡ ሕዝቤ ፡ ነሽ ፡ እል ፡ ዘንድ ፡ ቃሌን ፡ በአፍኽ ፡ አድርጌያለኹ ፥ በእጄም ፡ ጥላ ፡ ጋርጄኻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 17 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የቍጣውን ፡ ጽዋ ፡ የጠጣሽ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ንቂ ፥ ንቂ ፥ ቁሚ ፤ የሚያንገደግድን ፡ ዋንጫ ፡ ጠጥተሻል ፡ ጨልጠሽውማል ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 18 ፤ ከወለደቻቸው ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ የሚመራት ፡ የለም ፥ ካሳደገቻቸውም ፡ ልጆች ፡ ዅሉ ፡ እጇን ፡ የሚይዝ ፡ የለም ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 19 ፤ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ ነገሮች ፡ ኾነውብሻል ፥ ማንስ ፡ ያስተዛዝንሻል ፧ መፈታትና ፡ ጥፋት ፡ ራብና ፡ ሰይፍ ፡ ናቸው ፤ እንዴትስ ፡ አድርጌ ፡ አጽናናሻለኹ ፧

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 20 ፤ ልጆችሽ ፡ ዝለዋል ፤ በወጥመድ ፡ እንደተያዘ ፡ ሚዳቋ ፡ በአደባባይ ፡ ዅሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተኝተዋል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣና ፡ በአምላክሽ ፡ ተግሣጽ ፡ ተሞልተዋል ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 21 ፤ ስለዚህም ፡ ያለወይን ፡ ጠጅ ፡ የሰከርሽ ፡ አንቺ ፡ ችግረኛ ፥ ይህን ፡ ስሚ ፤

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 22 ፤ ስለ ፡ ወገኑ ፡ የሚሟገት ፡ አምላክሽ ፡ ጌታሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የሚያንገደግድን ፡ ጽዋ ፡ የቍጣዬንም ፡ ዋንጫ ፡ ከእጅሽ ፡ ወስጃለኹ ፤ ደግመሽም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትጠጪውም ።

ኢሳ. ፡ 51 ፡ 23 ፤ ነፍስሽንም ፦ እንሻገር ፡ ዘንድ ፡ ዝቅ ፡ በዪ ፡ በሚሏት ፡ በአስጨናቂዎችሽ ፡ እጅ ፡ አኖረዋለኹ ፤ ዠርባሽንም ፡ ለሚሻገሩት ፡ እንደ ፡ መሬትና ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ አደረግሽላቸው ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 52 ።

ኢሳ. ፡ 52 ፡ 1 ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ተነሺ ፥ ተነሺ ፥ ኀይልሽን ፡ ልበሺ ፤ ቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ያልተገረዘና ፡ ርኩስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይገባብሽምና ፡ ጌጠኛ ፡ ልብስሽን ፡ ልበሺ ።

ኢሳ. ፡ 52 ፡ 2 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ትቢያን ፡ አራግፊ ፤ ተነሺ ፥ ተቀመጪ ፤ ምርኮኛዪቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የዐንገትሽን ፡ እስራት ፡ ፍቺ ።

ኢሳ. ፡ 52 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በከንቱ ፡ ተሸጣችኹ ፡ ነበር ፥ ያለገንዘብም ፡ ትቤዣላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 52 ፡ 4 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወገኔ ፡ በዚያ ፡ እንግዳ ፡ ኾኖ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ፥ አሶርም ፡ ያለምክንያት ፡ በደለው ።

ኢሳ. ፡ 52 ፡ 5 ፤ ወገኔ ፡ በከንቱ ፡ ተወስዷልና ፥ አኹን ፡ ከዚህ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ይላል ፡

እግዚአብሔር ፤ የሚገዛቸው ፡ ይጮኻሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ስሜም ፡ ዘልጊዜ ፡ ቀኑን ፡ ዘሉ ፡ ይሰደባል ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ወገኔ ፡ ስሜን ፡ ያውቃል ፥ ስለዚህም ፡ የምናገር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኩ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ያውቃሉ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 7 ፤ የምሥራች ፡ የሚናገር ፥ ሰላምንም ፡ የሚያወራ ፥ የመልካምንም ፡ ወሬ ፡ የምሥራች ፡ የሚናገር ፥ መድኀኒትንም ፡ የሚያወራ ፥ ጽዮንንም ፦ አምላክሽ ፡ ነግሧል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ እግሩ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 8 ፤ እንሆ ፥ ጕበኞችሽ ፡ ጮኸዋል ፤ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ዐይን ፡ በዐይን ፡ ይተያያሉና ፡ ድምፃቸውን ፡ ያነሣሉ ፥ በአንድነትም ፡ ይዘምራሉ ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 9 ፤ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ፍርስራሾች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ አጽናንቷልና ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ታድኗልና ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ በአንድነትም ፡ ዘምሩ ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ የተቀደሰውን ፡ ክንዱን ፡ በአሕዛብ ፡ ዘሉ ፡ ፊት ፡ ገልጧል ፥ በምድር ፡ ዳርቻ ፡ የሚኖሩትም ፡ ዘሉ ፡ የአምላካችንን ፡ መድኀኒት ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 11 ፤ እናንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ የምትሸከሙ ፡ ሆይ ፥ እልፍ ፡ በሉ ፥ እልፍ ፡ በሉ ፥ ከዚያ ፡ ውጡ ፥ ርኩስን ፡ ነገር ፡ አትንኩ ፥ ከመካከሏ ፡ ውጡ ፥ ንጹሓን ፡ ኹኑ ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይቀድማችኋልና ፥ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ይከተላችኋልና ፥ በችኮላ ፡ አትወጡም ፡ በመኰብለልም ፡ አትኼዱም ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 13 ፤ እንሆ ፥ ባሪያዬ ፡ በማስተዋል ፡ ያደርጋል ፤ ይከብራል ፡ ከፍ ፡ ከፍም ፡ ይላል ፥ እጅግ ፡ ታላቅም ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 14 ፤ ፊቱ ፡ ከሰዎች ፡ ዘሉ ፡ ይልቅ ፥ መልኩም ፡ ከሰዎች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ተጐሳቀሏልና ፥ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ተደነቁ ፥ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ ያስደንቃል ፤

ኢሳ. ፥ 52 ፥ 15 ፤ ያልተነገረላቸውንም ፡ ያያሉና ፥ ያልሰሙትንም ፡ ያስተውላሉና ፡ ነገሥታት ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አፋቸውን ፡ ይዘጋሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 53 ።

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 1 ፤ የሰማነውን ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አምኗል ፧ የእግዚአብሔርስ ፡ ክንድ ፡ ለማን ፡ ተገልጧል ፧

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 2 ፤ በፊቱ ፡ እንደ ፡ ቡቃያ ፡ ከደረቅም ፡ መሬት ፡ እንደ ፡ ሥር ፡ አድጓል ። መልክና ፡ ውበት ፡ የለውም ፥ ባየነውም ፡ ጊዜ ፡ እንወደው ፡ ዘንድ ፡ ደም ፡ ግባት ፡ የለውም ።

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 3 ፤ የተናቀ ፡ ከሰውም ፡ የተጠላ ፥ የሕማም ፡ ሰው ፡ ደዌንም ፡ የሚያውቅ ፡ ነው ፤ ሰውም ፡ ፊቱን ፡ እንደሚሰውርበት ፡ የተናቀ ፡ ነው ፥ እኛም ፡ አላከበርነውም ።

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 4 ፤ በእውነት ፡ ደዌያችንን ፡ ተቀበለ ፡ ሕመማችንንም ፡ ተሸከሟል ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተቀሠፈ ፡ እንደ ፡ ተቸገረም ፡ ቈጠርነው ።

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 5 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ መተላለፋችን ፡ ቈሰለ ፥ ስለ ፡ በደላችንም ፡ ደቀቀ ፤ የደኅንነታችንም ፡ ተግሣጽ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ በርሱም ፡ ቍስል ፡ እኛ ፡ ተፈወስን ።

ኢሳ. ፥ 53 ፥ 6 ፤ እኛ ፡ ዘሎችን ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዝብዘን ፡ ጠፋን ፤ ከእኛ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ገዛ ፡

መንገዱ ፡ አዘነበለ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኹላችንን ፡ በደል ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አኖረ ።

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 7 ፤ ተጨነቀ ፡ ተሣቀየም ፡ አፉንም ፡ አልከፈተም ፤ ለመታረድ ፡ እንደሚነዳ ፡ ጠቦት ፥ በሸላቾቹም ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ እንደሚል ፡ በግ ፥ እንዲሁ ፡ አፉን ፡ አልከፈተም ።

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 8 ፤ በማስጨነቅና ፡ በፍርድ ፡ ተወሰደ ፤ ስለሕዝቤ ፡ ኀጢአት ፡ ተመቶ ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ከትውልዱ ፡ ማን ፡ አስተዋለ ፧

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 9 ፤ ከክፉዎችም ፡ ጋራ ፡ መቃብሩን ፡ አደረጉ ፥ ከባለጠጋዎችም ፡ ጋራ ፡ በሞቱ ፡ ኾኖም ፡ ግፍን ፡ አላደረገም ፡ ነበር ፥ በአፉም ፡ ተንኰል ፡ አልተገኘበትም ፡ ነበር ።

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በደዌ ፡ ያደቀው ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ፤ ነፍሱን ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ዘሩን ፡ ያያል ፥ ዕድሜውም ፡ ይረዝማል ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ በእጁ ፡ ይከናወናል ።

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 11 ፤ ከነፍሱ ፡ ድካም ፡ ብርሃን ፡ ያያል ፡ ደስም ፡ ይለዋል ፤ ጻድቅ ፡ ባሪያዬም ፡ በዕውቀቱ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያጸድቃል ፥ ኀጢአታቸውን ፡ ይሰከማል ።

ኢሳ. ፡ 53 ፡ 12 ፤ ስለዚህም ፡ ርሱ ፡ ብዙዎችን ፡ ይወርሳል ፥ ከኀያላንም ፡ ጋራ ፡ ምርኮን ፡ ይከፋፈላል ፤ ነፍሱን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ ከዐመፀኞችም ፡ ጋራ ፡ ተቈጥሯልና ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ኀጢአት ፡ ተሸከመ ፥ ስለ ፡ ዐመፀኞችም ፡ ማለደ ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 54 ። _____

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 1 ፤ አንቺ ፡ ያልወለድሽ ፡ መካን ፡ ሆይ ፥ ዘምሪ ፤ አንቺ ፡ ያላማጥሽ ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በዩ ፥ ጩኺም ፤ ባል ፡ ካላት ፡ ይልቅ ፡ ፈት ፡ የኾነቺቱ ፡ ልጆች ፡ በዝተዋልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 2 ፤ የድንኳንሽን ፡ ስፍራ ፡ አስፊ ፥ መጋረጃዎችሽንም ፡ ይዘርጉ ፤ አትቈጥቢ ፤ አውታሮችሽን ፡ አስረዝሚ ፡ ካስማዎችሽንም ፡ አጽኚ ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 3 ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ ትሰፋፊያለሽና ፥ ዘርሽም ፡ አሕዛብን ፡ ይወርሳልና ፥ የፈረሱትንም ፡ ከተማዎች ፡ መኖሪያ ፡ ያደርጋልና ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 4 ፤ አታፍሪምና ፡ አትፍሪ ፤ አትዋረጂምና ፡ አትደንግጪ ፤ የሕፃንነትሽንም ፡ ዕፍረት ፡ ትረሺዋለሽ ፥ የመበለትነትሽንም ፡ ስድብ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታስቢም ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 5 ፤ ፈጣሪሽ ፡ ባልሽ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ ታዳጊሽ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ የምድር ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ ይባላል ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተተወችና ፡ እንደ ፡ ተበሳጨች ፡ በልጅነቷም ፡ እንደ ፡ ተጣለች ፡ ሚስት ፡ ጠርቶሻል ፥ ይላል ፡ አምላክሽ ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 7 ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተውኹሽ ፥ በታላቅም ፡ ምሕረት ፡ እሰበስብሻለኹ ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 8 ፤ በጥቂት ፡ ቍጣ ፡ ለቅጽበት ፡ ዐይን ፡ ፊቴን ፡ ከአንቺ ፡ ሰወርኹ ፥ በዘለዓለምም ፡ ቸርነት ፡ እምርሻለኹ ፥ ይላል ፡ ታዳጊሽ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 9 ፤ ይህ ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ ኖኅ ፡ ውሃ ፡ ነው ፤ የኖኅ ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዳያልፍ ፡ እንደ ፡ ማልኹ ፥ እንዲሁ ፡ አንቺን ፡ እንዳልቈጣ ፡ እንዳልዘልፍሽም ፡ ምያለኹ ።

ኢሳ. ፡ 54 ፡ 10 ፤ ተራራዎች ፡ ይፈልሳሉ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ይወገዳሉ ፤ ቸርነቴ ፡ ግን ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡

አይፈልስም ፡ የሰላሜም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አይወገድም ፥ ይላል ፡ መሐሪሽ ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 11 ፤ አንቺ ፡ የተቸገርሽ ፡ በዐውል ፡ ነፋስም ፡ የተናወጥሽ ፡ ያልተጽናናሽም ፥ እንሆ ፥ ድንጋዮችሽን ፡ ሸላልሜ ፡ እገነባለኹ ፥ በሰንፔርም ፡ እመሠርትሻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 12 ፤ የግንብሽንም ፡ ጕልላት ፡ በቀይ ፡ ዕንቊ ፥ በሮችሽንም ፡ በሚያብረቀርቅ ፡ ዕንቊ ፥ ዳርቻሽንም ፡ ሹሉ ፡ በከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ እሠራለኹ ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 13 ፤ ልጆችሽም ፡ ሹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማሩ ፡ ይኾናሉ ፥ የልጆችሽም ፡ ሰላም ፡ ብዙ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 14 ፤ በጽድቅ ፡ ትታነጻለሽ ፤ ከግፍ ፡ ራቂ ፥ አትፈሪምም ፥ ድንጋጤም ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ አትቀርብም ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 15 ፤ እንሆ ፥ ይሰበሰባሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አይኾንም ፤ ባንቺም ፡ ላይ ፡ የሚሰበሰቡ ፡ ሹሉ ፡ ከአንቺ ፡ የተነሣ ፡ ይወድቃሉ ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 16 ፤ እንሆ ፥ ፍሙን ፡ በወናፍ ፡ የሚያናፋ ፡ ለሥራውም ፡ መሣሪያ ፡ የሚያወጣ ፡ ብረት ፡ ሠሪን ፡ እኔ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ የሚያፈርሰውንም ፡ እንዲያጠፋ ፡ ፈጥሬያለኹ ።

ኢሳ. ፥ 54 ፥ 17 ፤ ባንቺ ፡ ላይ ፡ የተሠራ ፡ መሣሪያ ፡ ሹሉ ፡ አይከናወንም ፤ በፍርድም ፡ በሚነሣብሽ ፡ ምላስ ፡ ሹሉ ፡ ትፈርጂበታለሽ ። የእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ርስት ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ጽድቃቸውም ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 55 ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 1 ፤ እናንተ ፡ የተጠማችኹ ፡ ሹሉ ፥ ወደ ፡ ውሃ ፡ ኑ ፥ ገንዘብም ፡ የሌላችኹ ፡ ኑና ፡ ግዙ ፡ ብሉም ፤ ኑ ፡ ያለገንዘብም ፡ ያለዋጋም ፡ የወይን ፡ ጠጅና ፡ ወተት ፡ ግዙ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 2 ፤ ገንዘብን ፡ እንጀራ ፡ ላይደለ ፥ የድካማችኹንም ፡ ዋጋ ፡ ለማያጠግብ ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትመዝናላችኹ ። አድምጡኝ ፥ በረከትንም ፡ ብሉ ፥ ሰውነታችኹም ፡ በጮማ ፡ ደስ ፡ ይበለው ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 3 ፤ ጐሯችኹን ፡ አዘንብሉ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ቅረቡ ፤ ስሙ ፡ ሰውነታችኹም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ፤ የታመነችዩቱን ፡ የዳዊትን ፡ ምሕረት ፥ የዘለዓለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 4 ፤ እንሆ ፥ ለአሕዛብ ፡ ምስክር ፥ ለወገኖችም ፡ አለቃና ፡ አዛዥ ፡ እንዲኾን ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 5 ፤ እንሆ ፥ የማታውቀውን ፡ ሕዝብ ፡ ትጠራለኽ ፥ የእስራኤልም ፡ ቅዱስ ፡ አክብሮኻልና ፥ ስለ ፡ አምላክኽ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የማያውቁኽ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳንተ ፡ ይሮጣሉ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ በሚገኝበት ፡ ጊዜ ፡ ፈልጉት ፥ ቀርቦም ፡ ሳለ ፡ ጥሩት ፤

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 7 ፤ ክፉ ፡ ሰው ፡ መንገዱን ፡ በደለኛም ፡ ዐሳቡን ፡ ይተው ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይመለስ ፡ ርሱም ፡ ይምረዋል ፥ ይቅርታውም ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ይመለስ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 8 ፤ ዐሳቤ ፡ እንደ ፡ ዐሳባችኹ ፡ መንገዳችኹም ፡ እንደ ፡ መንገዴ ፡ አይደለምና ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 9 ፤ ሰማይ ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ እንደሚል ፥ እንዲሁ ፡ መንገዴ ፡ ከመንገዳችኹ ፡ ዐሳቤም ፡ ከዐሳባችኹ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 10 ፤ ዝናብና ፡ በረዶ ፡ ከሰማይ ፡ እንደሚወርድ ፥ ምድርን ፡ እንደሚያረካት ፥ ታበቅልና ፡ ታፈራም ፡

ዘንድ ፡ እንደሚያደርጋት ፥ ዘርንም ፡ ለሚዘራ ፡ እንጀራንም ፡ ለሚበላ ፡ እንደሚሰጥ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንደማይመለስ ፥

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 11 ፤ ከአፌ ፡ የሚወጣ ፡ ቃሌ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ፤ የምሻውን ፡ ያደርጋል ፡ የላክኹትንም ፡ ይፈጽማል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ በከንቱ ፡ አይመለስም ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 12 ፤ እናንተም ፡ በደስታ ፡ ትወጣላችኹ ፡ በሰላምም ፡ ትሸኛላችኹ ፤ ተራራዎችና ፡ ኰረብታዎች ፡ በፊታችኹ ፡ እልልታ ፡ ያደርጋሉ ፥ የሜዳም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ያጨበጭባሉ ።

ኢሳ. ፥ 55 ፥ 13 ፤ በሾኽም ፡ ፋንታ ፡ ጥድ ፡ በሑርንችትም ፡ ፋንታ ፡ ባርሰነት ፡ ይበቅላል ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ መታሰቢያን ፡ ለዘለዓለምም ፡ የማይጠፋ ፥ ምልክት ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 56 ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ማዳኔ ፡ ሊመጣ ፡ ጽድቄም ፡ ሊገለጥ ፡ ቀርቧልና ፥ ፍርድን ፡ ጠብቁ ፡ ጽድቅንም ፡ አድርጉ ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 2 ፤ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ይህንም ፡ የሚይዝ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፥ እንዳያረክሰው ፡ ሰንበትንም ፡ የሚጠብቅ ፡ እጁንም ፡ ክፋት ፡ ከማድረግ ፡ የሚጠብቅ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 3 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የተጠጋ ፡ መጻተኛ ፦ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ይለየኛል ፡ አይበል ፤ ጃን ፡ ደረባም ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ደረቅ ፡ ዛፍ ፡ ነኝ ፡ አይበል ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሰንበቴን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘኝንም ፡ ነገር ፡ ስለሚመርጡ ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ ስለሚይዙ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 5 ፤ በቤቴና ፡ በቅጥሬ ፡ ውስጥ ፡ ከወንዶችና ፡ ከሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ መታሰቢያና ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ የማይጠፋም ፡ የዘለዓለም ፡ ስም ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 6 ፤ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ስም ፡ ይወዱ ፡ ዘንድ ፡ ባሪያዎቹም ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚጠጉትንም ፡ መጻተኞች ፥ እንዳያረክሱት ፡ ሰንበትን ፡ የሚጠብቁትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ የሚይዙትን ፡ ኹሉ ፥

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 7 ፤ ወደተቀደሰ ፡ ተራራዬ ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ በጸሎቴም ፡ ቤት ፡ ደስ ፡ አሠኛቸዋለኹ ፤ ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የሚኾን ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይባላልና ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታቸውንና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ እቀበላለኹ ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 8 ፤ ከእስራኤል ፡ የተበተኑትን ፡ የሚሰበስብ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ወደተሰበሰቡት ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ እሰበስብለታለኹ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 9 ፤ እናንተ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፥ እናንተም ፡ የዱር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፥ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ቅረቡ ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 10 ፤ ጕበኞቹ ፡ ዕውሮች ፡ ናቸው ፥ ኹሉ ፡ ያለዕውቀት ፡ ናቸው ፤ ኹሉም ፡ ዲዳ ፡ የኾኑ ፡ ውሻዎች ፡ ናቸው ፡ ይጮኹም ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ፤ ሕልምን ፡ ያልማሉ ፤ ይተኛሉ ፤ ማንቀላፋትንም ፡ ይወዳሉ ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 11 ፤ መብል ፡ ወዳጆች ፡ ከቶ ፡ የማይጠግቡ ፡ ውሻዎች ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉ ፡ እረኞች ፡ ናቸው ፤ ኹሉ ፡ ወደ ፡ መንገዳቸው ፥ ከፊተኛው ፡ እስከ ፡ ኋለኛው ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፥ እያንዳንዳቸው ፡ ወደ ፡ ጥቅማቸው ፡ ዘወር ፡ ብለዋል ።

ኢሳ. ፥ 56 ፥ 12 ፤ ኑ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንውሰድ ፥ በሚያሰክርም ፡ መጠጥ ፡ እንርካ ፤ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲሁ ፡ ነገ ፡ ይኾናል ፥ ከዛሬም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ይበልጣል ፡ ይላሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 57 ። _____

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 1 ፤ ጻድቅ ፡ ይሞታል ፥ በልቡም ፡ ነገሩን ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ምሕረተኞችም ፡ ይወገዳሉ ፥ ጽድቅም ፡ ከክፋት ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ተወገደ ፡ ማንም ፡ አያስተውልም ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 2 ፤ ወደ ፡ ሰላም ፡ ይገባል ፤ በቅንነት ፡ የኼደ ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ያርፋል ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 3 ፤ እናንተ ፡ የአስማተኛዪቱ ፡ ልጆች ፥ የአመንዝራውና ፡ የጋለሞታዪቱ ፡ ዘር ፥ ወደዚህ ፡ ቅረቡ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 4 ፤ በማን ፡ ታላግጣላችኹ ፧ በማንስ ፡ ላይ ፡ አፋችኹን ፡ ታላቅቃላችኹ ፧ ምላሳችኹንስ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ ታስረዝማላችኹ ፧

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 5 ፤ እናንተ ፡ በአድባር ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ በለመለመም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ በፍትወት ፡ የምትቃጠሉ ፥ እናንተም ፡ በሸለቆዎች ፡ ውስጥ ፡ በአለትም ፡ ስንጣቂዎች ፡ በታች ፡ ሕፃናትን ፡ የምታርዱ ፥ የዐመፅ ፡ ልጆችና ፡ የሐሰት ፡ ዘር ፡ አይደላችኹምን ፧

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 6 ፤ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የለዘቡ ፡ ድንጋዮች ፡ ዕድል ፡ ፈንታሽ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ ዕጣሽ ፡ ናቸው ፤ ለእነርሱም ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ አፍሰሻል ፥ የእኽልንም ፡ ቍርባን ፡ አቅርበሻል ። እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አልቈጣምን ፧

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 7 ፤ ከፍ ፡ ባለውም ፡ በረዘመውም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ መኝታሽን ፡ አደረግሽ ፥ መሥዋዕትንም ፡ ትሠዊ ፡ ዘንድ ፡ ወደዚያ ፡ ወጣሽ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 8 ፤ ከመዝጊያውና ፡ ከመቃኑ ፡ በኋላ ፡ መታሰቢያሽን ፡ አደረግሽ ፤ እኔን ፡ ትተሽ ፡ ለሌላ ፡ ተገልጠሻል ፥ ወጥተሽ ፡ መኝታሽን ፡ አስፍተሻል ፤ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ ተጋባሻቸው ፥ ባየሽበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ መኝታቸውን ፡ ወደድሽ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 9 ፤ ዘይትም ፡ ይዘሽ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ኼድሽ ፥ ሽቱሽንም ፡ አበዛሽ ፥ መልእክተኞችሽንም ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ላክሽ ፥ እስከ ፡ ሲኦልም ፡ ድረስ ፡ ተዋረድሽ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 10 ፤ በመንገድሽም ፡ ብዛት ፡ ደከምሽ ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ተስፋ ፡ የለም ፡ አላልሽም ፤ የጕልበትን ፡ መታደስ ፡ አገኘሽ ፥ ስለዚህም ፡ አልዛልሽም ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 11 ፤ ሐሰትን ፡ የተናገርሺው ፡ እኔንም ፡ ያላሰብሺው ፡ በልብሽም ፡ ነገሩን ፡ ያላኖርሺው ፡ ማንን ፡ ሠግተሽ ፡ ነው ፧ ማንንስ ፡ ፈርተሽ ፡ ነው ፧ እኔ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዝም ፡ አልኹ ፥ አንቺም ፡ አልፈራሽም ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 12 ፤ እኔ ፡ ጽድቅሽን ፡ እናገራለኹ ፥ ሥራሽም ፡ አይረባሽም ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 13 ፤ ወደ ፡ አንቺ ፡ የሰበሰብሻቸው ፡ በጮኽሽ ፡ ጊዜ ፡ ይታደጉሽ ፤ ነፋስ ፡ ግን ፡ ይወስዳቸዋል ፡ ሽውሽውታም ፡ ኹሉን ፡ ያስወግዳቸዋል ። በእኔ ፡ የታመነ ፡ ግን ፡ ምድሪቱን ፡ ይገዛል ፥ የተቀደሰውንም ፡ ተራራዬን ፡ ይወርሳል ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 14 ፤ ርሱም ፦ ጥረጉ ፥ መንገድን ፡ አዘጋጁ ፥ ከሕዝቤም ፡ መንገድ ፡ ዕንቅፋትን ፡ አውጡ ፡ ይላል ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 15 ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ስሙም ፡ ቅዱስ ፡ የኾነ ፥ ከፍ ፡ ያለው ፡ ልዑል ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የተዋረዱትን ፡ ሰዎች ፡ መንፈስ ፡ ሕያው ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠውንም ፡ ልብ ፡ ሕያው ፡ ኣደርግ ፡

ዘንድ ፥ የተቀጠቀጠና ፡ የተዋረደ ፡ መንፈስ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ በከፍታና ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ እቀመጣለኹ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 16 ፤ መንፈስም ፡ የፈጠርኹትም ፡ ነፍስ ፡ ከፊቴ ፡ እንዳይዝል ፡ ለዘለዓለም ፡ አልጣላም ፥ ዥልጊዜም ፡ አልቈጣም ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 17 ፤ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥቼ ፡ ቀሠፍኹት ፥ ፊቴን ፡ ሰውሬ ፡ ተቈጣኹ ፤ ርሱም ፡ በልቡ ፡ መንገድ ፡ እያፈገፈገ ፡ ኼደ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 18 ፤ መንገዱን ፡ አይቻለኹ ፡ እፈውሰውማለኹ ፥ እመራውማለኹ ፥ ለርሱና ፡ ስለ ፡ ርሱም ፡ ለሚያለቅሱ ፡ መጽናናትን ፡ እመልሳለኹ ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 19 ፤ የከንፈሮችን ፡ ፍሬ ፡ እፈጥራለኹ ፤ በሩቅም ፡ በቅርብም ፡ ላለው ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይኹን ፥ እፈውሰውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 20 ፤ ክፉዎች ፡ ግን ፡ እንደሚንቀሳቀስ ፡ ባሕር ፡ ናቸው ፤ ጸጥ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ አይችልምና ፥ ውሃዎቹም ፡ ጭቃና ፡ ጕድፍ ፡ ያወጣሉና ።

ኢሳ. ፥ 57 ፥ 21 ፤ ለክፉዎች ፡ ሰላም ፡ የላቸውም ፡ ይላል ፡ አምላኬ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 58 ።

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 1 ፤ በኀይልኽ ፡ ጩኽ ፥ አትቈጥብ ፥ ድምፅኽን ፡ እንደ ፡ መለከት ፡ አንሣ ፥ ለሕዝቤ ፡ መተላለፋቸውን ፡ ለያዕቆብ ፡ ቤትም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ንገር ።

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሹኛል ፡ መንገዴንም ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይወዳሉ ፤ ጽድቅን ፡ እንዳደረጉ ፡ የአምላካቸውንም ፡ ፍርድ ፡ እንዳልተዉ ፡ ሕዝብ ፡ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይለምኑኛል ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመቅረብ ፡ ይወዳሉ ።

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 3 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ጾምን ፥ አንተም ፡ አልተመለከትኸንም ፧ ሰውነታችንንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አዋረድን ፥ አንተም ፡ አላወቅኽም ፧ ይላሉ ። እንሆ ፥ በጾማችኹ ፡ ቀን ፡ ፈቃዳችኹን ፡ ታደርጋላችኹ ፥ ሠራተኞቻችኹንም ፡ ዥሉ ፡ ታስጨንቃላችኹ ።

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 4 ፤ እንሆ ፥ ለጥልና ፡ ለክርክር ፡ ትጾማላችኹ ፡ በግፍ ፡ ጡጫም ፡ ትማታላችኹ ፤ ድምፃችኹንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ታሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ዛሬ ፡ እንደምትጾሙት ፡ አትጾሙም ።

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 5 ፤ እኔ ፡ የመረጥኹት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ ሰውስ ፡ ነፍሱን ፡ የሚያዋርደው ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ቀን ፡ ነውን ፧ በእውኑ ፡ ራሱን ፡ እንደ ፡ እንግጫ ፡ ዝቅ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ማቅንና ፡ ዐመድንም ፡ በበታቹ ፡ ያነጥፍ ፡ ዘንድ ፡ ነውን ፧ በእውኑ ፡ ይህን ፡ ጾም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ የተወደደ ፡ ቀን ፡ ትለዋለኽን ፧

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 6 ፤ እኔስ ፡ የመረጥኹት ፡ ጾም ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧ የበደልን ፡ እስራት ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፥ የቀንበርንስ ፡ ጠፍር ፡ ትለቅቁ ፡ ዘንድ ፥ የተገፉትንስ ፡ ሐራነት ፡ ትሰዱ ፡ ዘንድ ፥ ቀንበሩንስ ፡ ዥሉ ፡ ትሰብሩ ፡ ዘንድ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 7 ፤ እንጀራኽንስ ፡ ለተራበ ፡ ትቈርስ ፡ ዘንድ ፥ ስደተኞቹን ፡ ድኻዎች ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ታገባ ፡ ዘንድ ፥ የተራቈተውንስ ፡ ብታይ ፡ ታለብሰው ፡ ዘንድ ፥ ከሥጋ ፡ ዘመድኽ ፡ እንዳትሸሸግ ፡ አይደለምን ፧

ኢሳ. ፥ 58 ፥ 8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብርሃንኽ ፡ እንደ ፡ ንጋት ፡ ይበራል ፥ ፈውስኽም ፡ ፈጥኖ ፡ ይበቅላል ፥ ጽድቅኽም ፡ በፊትኽ ፡ ይኼዳል ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ በኋላኽ ፡ ኾኖ ፡ ይጠብቅኻል ።

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 9 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትጠራለኽ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይሰማኻል ፤ ትጮኻለኽ ፡ ርሱም ፦ እንሆኝ ፡ ይላል ። ከመካከልኽ ፡ ቀንበርን ፡ ብታርቅ ፥ ጣትኽንም ፡ መጥቀስ ፡ ብትተው ፥

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 10 ፤ ባታንጐራጉርም ፥ ነፍስኽንም ፡ ለተራበ ፡ ብታፈስ ፥ የተጨነቀውንም ፡ ነፍስ ፡ ብታጠግብ ፥ ብርሃንኽ ፡ በጨለማ ፡ ይወጣል ፡ ጨለማኽም ፡ እንደ ፡ ቀትር ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዘውትር ፡ ይመራኻል ፤ ነፍስኽንም ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ያጠግባል ፡ ዐጥንትኽንም ፡ ያጠናል ፤ አንተም ፡ እንደሚጠጣ ፡ ገነት ፥ ውሃውም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ምንጭ ፡ ትኾናለኽ ።

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 12 ፤ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ የፈረሱት ፡ ስፍራዎች ፡ ይሠራሉ ፥ የብዙ ፡ ትውልድም ፡ መሠረት ፡ ይታነጻል ፤ አንተም ፦ ሰባራውን ፡ ጠጋኝ ፥ የመኖሪያ ፡ መንገድን ፡ ዐዳሽ ፡ ትባላለኽ ።

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 13 ፤ ፈቃድኽን ፡ በተቀደሰው ፡ ቀኔ ፡ ከማድረግ ፡ እግርኽን ፡ ከሰንበት ፡ ብትመልስ ፥ ሰንበትንም ፡ ደስታ ፥ እግዚአብሔርም ፡ የቀደሰውን ፡ ክቡር ፡ ብትለው ፥ የገዛ ፡ መንገድኽንም ፡ ከማድረግ ፡ ፈቃድኽንም ፡ ከማግኘት ፡ ከንቱ ፡ ነገርንም ፡ ከመናገር ፡ ተከልክለኽ ፡ ብታከብረው ፥

ኢሳ. ፡ 58 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይልኻል ፥ በምድርም ፡ ከፍታዎች ፡ ላይ ፡ አወጣኻለኹ ፥ የአባትኽንም ፡ የያዕቆብን ፡ ርስት ፡ አበላኻለኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ተናግሯልና ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 59 ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ከማዳን ፡ አላጠረችም ፥ ጐሮውም ፡ ከመስማት ፡ አልደነቈረችም ፤

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በደላችኹ ፡ በእናንተና ፡ በአምላካችኹ ፡ መካከል ፡ ለይታለች ፥ እንዳይሰማም ፡ ኀጢአታችኹ ፡ ፊቱን ፡ ከእናንተ ፡ ሰውሮታል ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 3 ፤ እጃችኹ ፡ በደም ፡ ጣታችኹም ፡ በበደል ፡ ረክሳለች ፥ ከንፈራችኹም ፡ ሐሰትን ፡ ተናግሯል ፥ ምላሳችኹም ፡ ኀጢአትን ፡ አሰምቷል ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 4 ፤ በጽድቅ ፡ የሚጠራ ፡ በእውነትም ፡ የሚፈርድ ፡ የለም ፤ በምናምንቴ ፡ ነገር ፡ ታምነዋል ፡ ሐሰትንም ፡ ተናግረዋል ፤ ጕዳትን ፡ ፀንሰዋል ፡ በደልንም ፡ ወልደዋል ፤

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 5 ፤ የእባብን ፡ ዕንቍላል ፡ ቀፈቀፉ ፥ የሸረሪትንም ፡ ድር ፡ አደሩ ፤ ዕንቍላላቸውንም ፡ የሚበላ ፡ ሰው ፡ ይሞታል ፥ ዕንቍላሉም ፡ ሲሰበር ፡ እፍኝት ፡ ይወጣል ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 6 ፤ ድሮቻቸውም ፡ ልብስ ፡ አይኾኑላቸውም ፥ በሥራቸውም ፡ አይሸፈኑም ፤ ሥራቸውም ፡ የበደል ፡ ሥራ ፡ ነው ፥ የግፍም ፡ ሥራ ፡ በእጃቸው ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 7 ፤ እግሮቻቸው ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ይሮጣሉ ፥ ንጹሑን ፡ ደም ፡ ለማፍሰስ ፡ ይፈጥናሉ ፤ ዐሳባቸው ፡ የኀጢአት ፡ ዐሳብ ፡ ነው ፥ ጕስቍልናና ፡ ቅጥቃጤ ፡ በመንገዳቸው ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 8 ፤ የሰላምን ፡ መንገድ ፡ አያውቁም ፥ በአካኼዳቸውም ፡ ፍርድ ፡ የለም ፤ መንገዳቸውን ፡ አጣመዋል ፥ የሚኼድባትም ፡ ሹሉ ፡ ሰላምን ፡ አያውቅም ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ፍርድ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ፥ ጽድቅም ፡ አላገኘንም ፤ ብርሃንን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበር ፥ እንሆም ፥ ጨለማ ፡ ኾነ ፤ ጸዳልን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበር ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በጨለማ ፡ ኼድን ።

ኢሳ. ፡ 59 ፡ 10 ፤ እንደ ፡ ዕውሮች ፡ ወደ ፡ ቅጥሩ ፡ ተርመሰመስን ፥ ዐይን ፡ እንደሌላቸው ፡

ተርመሰመስን ፤ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ በድግዝግዝታ ፡ እንዳለ ፡ ሰው ፡ ተሰናከልን ፥ እንደ ፡ ሙታን ፡ በጨለማ ፡ ስፍራ ፡ ነን ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 11 ፤ ሹላችን ፡ እንደ ፡ ድቦች ፡ እንጮኻለን ፥ እንደ ፡ ርግብ ፡ እንለቃቀሳለን ፤ ፍርድን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቅ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡ የለም ፤ መዳንም ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 12 ፤ ዐመፃችን ፡ ባንተ ፡ ፊት ፡ በዝቷልና ፥ ኀጢአታችን ፡ መስክሮብናልና ፥ ዐመፃችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ በደላችንን ፡ እናውቃለንና ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 13 ፤ ዐምፀናል ፥ ሐሰትን ፡ ተናግረናል ፥ አምላካችንንም ፡ ከመከተል ፡ ተመልሰናል ፤ ግፍንና ፡ ዐመፅንም ፡ ተናግረናል ፥ የኀጢአት ፡ ቃልንም ፡ ፀንሰን ፡ ከልብ ፡ አውጥተናል ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 14 ፤ ፍርድም ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሷል ፥ ጽድቅም ፡ በሩቅ ፡ ቆሟል ፤ እውነትም ፡ በአደባባይ ፡ ላይ ፡ ወድቋልና ፥ ቅንነትም ፡ ሊገባ ፡ አልቻለምና ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 15 ፤ እውነትም ፡ ታጥቷል ፥ ከክፋትም ፡ የራቀ ፡ ሰው ፡ ለብዝበዛ ፡ ኾኗል ።

እግዚአብሔርም ፡ አየ ፥ ፍርድም ፡ ስለሌለ ፡ ተከፋ ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 16 ፤ ሰውም ፡ እንደሌለ ፡ አየ ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚማልድ ፡ እንደሌለ ፡ ተረዳ ፥ ተደነቀም ፤ ስለዚህ ፥ የገዛ ፡ ክንዱ ፡ መድኀኒት ፡ አመጣለት ፥ ጽድቁም ፡ አገዘው ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 17 ፤ ጽድቅንም ፡ እንደ ፡ ጥሩር ፡ ለበሰ ፥ በራሱም ፡ ላይ ፡ የማዳንን ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ አደረገ ፤ የበቀልንም ፡ ልብስ ፡ ለበሰ ፥ በቅንአትም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ተጐናጸፈ ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 18 ፤ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ መጠን ፡ እንዲሁ ፡ ቍጣን ፡ ለባላጋራዎቹ ፥ ፍዳንም ፡ ለጠላቶቹ ፡ ይከፍላል ፤ ለደሴቶችም ፡ ፍዳቸውን ፡ ይከፍላል ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 19 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነፋስ ፡ እንደሚነዳው ፡ እንደ ፡ ጐርፍ ፡ ፈሳሽ ፡ ይመጣልና ፥ በምዕራብ ፡ ያሉት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፥ በፀሓይ ፡ መውጫም ፡ ያሉት ፡ ክብሩን ፡ ይፈራሉ ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 20 ፤ ለጽዮን ፡ ታዳጊ ፡ ይመጣል ፥ በያዕቆብም ፡ ዘንድ ፡ ከኀጢአት ፡ ለሚርቁ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፥ 59 ፥ 21 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ መንፈሴ ፡ በአፍኽም ፡ ውስጥ ፡ ያደረግኹት ፡ ቃሌ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ከአፍኽ ፡ ከዘርኽም ፡ አፍ ፡ ከዘር ፡ ዘርኽም ፡ አፍ ፡ አያልፍም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 60 ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 1 ፤ ብርሃንሽ ፡ መጥቷልና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ወጥቶልሻልና ፥ ተነሺ ፥ አብሪ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 2 ፤ እንሆ ፥ ጨለማ ፡ ምድርን ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማም ፡ አሕዛብን ፡ ይሸፍናል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወጣል ፡ ክብሩም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ይታያል ፤

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 3 ፤ አሕዛብም ፡ ወደ ፡ ብርሃንሽ ፡ ነገሥታትም ፡ ወደ ፡ መውጫሽ ፡ ጸዳል ፡ ይመጣሉ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 4 ፤ ዐይኖችሽን ፡ አንሥተሽ ፡ በዙሪያሽ ፡ ተመልከቺ ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ፤ ወንዶች ፡ ልጆችሽ ፡ ከሩቅ ፡ ይመጣሉ ፥ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ በጫንቃ ፡ ላይ ፡ ይሸከሟቸዋል ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 5 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የባሕሩ ፡ በረከት ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ስለሚመለስ ፥ የአሕዛብም ፡ ብልጥግና ፡ ወደ ፡

አንቺ ፡ ስለሚመጣ ፥ አይተሽ ፡ ደስ ፡ ይልሻል ፥ ልብሽም ፡ ይደነቃል ፡ ይሰፋማል ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 6 ፤ የግመሎች ፡ ብዛት ፥ የምድያምና ፡ የጌፌር ፡ ግመሎች ፥ ይሸፍኑሻል ፤ ሹሉ ፡ ከሳባ ፡ ይመጣሉ ፥ ወርቅንና ፡ ዕጣንን ፡ ያመጣሉ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ምስጋና ፡ ያወራሉ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 7 ፤ የቄዳር ፡ መንጋዎች ፡ ሹሉ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይሰበሰባሉ ፡ የነባዮትም ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ያገለግሉሻል ፤ እኔን ፡ ደስ ፡ ሊያሠኙ ፡ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፥ የክብሬንም ፡ ቤት ፡ አከብራለኹ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 8 ፤ ርግቦች ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ እንደሚበሩ ፥ እነዚህ ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ የሚበሩ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 9 ፤ ርሱ ፡ አክብሮሻልና ፥ ለአምላክሽ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስምና ፡ ለእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ልጆችሽን ፡ ከሩቅ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራም ፡ ብራቸውንና ፡ ወርቃቸውን ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ደሴቶች ፡ የተርሴስ ፡ መርከቦችም ፡ አስቀድመው ፡ ይጠባበቁኛል ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 10 ፤ በቀኑጣዬ ፡ ቀሥፌ ፡ በፍቅሬ ፡ ምሬሻለኹና ፡ መጻተኞች ፡ ቅጥርሽን ፡ ይሠራሉ ፥ ነገሥታታቸውም ፡ ያገለግሉሻል ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 11 ፤ በሮችሽም ፡ ሹልጊዜ ፡ ይከፈታሉ ፤ ሰዎች ፡ የአሕዛብን ፡ ብልጥግና ፡ የተማረኩትንም ፡ ነገሥታታቸውን ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አይዘጉም ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 12 ፤ ለአንቺም ፡ የማይገዛ ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፡ ይጠፋል ፥ እነዚያ ፡ አሕዛብም ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 13 ፤ የመቅደሴንም ፡ ስፍራ ፡ ያስጌጡ ፡ ዘንድ ፡ የሊባኖስ ፡ ክብር ፥ ጥዱና ፡ አስታው ፡ ባርሰነቱም ፥ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ፥ የእግሬንም ፡ ስፍራ ፡ አከብራለኹ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 14 ፤ የአስጨናቂዎችሽም ፡ ልጆች ፡ ዐንገታቸውን ፡ ደፍተው ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ፥ የናቁሽም ፡ ሹሉ ፡ ወደእግርሽ ፡ ጫማ ፡ ይሰግዳሉ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ከተማ ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ የኾንሽ ፡ ጽዮን ፡ ይሉሻል ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 15 ፤ ከሰውም ፡ ማንም ፡ እስከማያልፍብሽ ፡ ድረስ ፡ የተተውሽና ፡ የተጠላሽ ፡ ነበርሽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዘለዓለም ፡ ትምክሕትና ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ደስታ ፡ አደርግሻለኹ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 16 ፤ የአሕዛብንም ፡ ወተት ፡ ትጠጣለሽ ፡ የነገሥታትንም ፡ ጡት ፡ ትጠቢያለሽ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ የያዕቆብ ፡ ኀይል ፥ መድኀኒትሽና ፡ ታዳጊሽ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 17 ፤ በናስ ፡ ፋንታ ፡ ወርቅን ፥ በብረትም ፡ ፋንታ ፡ ብርን ፥ በዕንጨትም ፡ ፋንታ ፡ ናስን ፥ በድንጋይም ፡ ፋንታ ፡ ብረትን ፡ አመጣለኹ ። አለቃዎችሽንም ፡ ሰላም ፥ የበላይ ፡ ገዢዎችሽንም ፡ ጽድቅ ፡ አደርጋለኹ ፤

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 18 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በምድርሽ ፡ ውስጥ ፡ ግፍ ፥ በዳርቻሽም ፡ ውስጥ ፡ ጕስቍልናና ፡ ቅጥቃጤ ፡ አይሰማም ፤ ቅጥርሽን ፡ መዳን ፡ በሮችሽንም ፡ ምስጋና ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪያለሽ ፡

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 19 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ብርሃንሽ ፥ አምላክሽም ፡ ክብርሽ ፡ ይኾናልና ፥ ፀሓይ ፡ በቀን ፡ ብርሃን ፡ አይኾንልሽም ፥ የጨረቃም ፡ ብርሃን ፡ በሌሊት ፡ አይበራልሽም ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ የዘለዓለም ፡ ብርሃንሽ ፡ ይኾናልና ፥ የልቅሶሽም ፡ ወራት ፡ ታልቃለችና ፡ ፀሓይሽ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አትጠልቅም ፡ ጨረቃሽም ፡ አይቋረጥም ።

ኢሳ. ፥ 60 ፥ 21 ፤ ሕዝብሽም ፡ ሹሉ ፡ ጻድቃን ፡ ይኾናሉ ፤ እኔም ፡ እከብር ፡ ዘንድ ፡ የአታክልቴን ፡ ቡቃያ ፥ የእጄ ፡ ሥራ ፡ የምትኾን ፡ ምድሪቱንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይወርሳሉ ።

ኢሳ. ፡ 60 ፡ 22 ፤ ታናሹ ፡ ለሺሕ ፡ የሾሉም ፡ ታናሹ ፡ ለብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ ይኾናል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘመኑ ፡ ይህን ፡ አፋጥነዋለኹ ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 61 ። _____

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 1 ፤ የጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፥ ለድኻዎች ፡ የምሥራችን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶኛልና ፤ ልባቸው ፡ የተሰበረውን ፡ እጠግን ፡ ዘንድ ፥ ለተማረኩትም ፡ ነጻነትን ፡ ለታሰሩትም ፡ መፈታትን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ልኮኛል ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 2 ፤ የተወደደችውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዓመት ፡ አምላካችንም ፡ የሚበቀልበትን ፡ ቀን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፥ የሚያለቅሱትንም ፡ ሾሉ ፡ አጽናና ፡ ዘንድ ፤

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለክብሩ ፡ የተከላቸው ፡ የጽድቅ ፡ ዛፎች ፡ እንዲባሉ ፡ ለጽዮን ፡ አልቃሾች ፡ ኣደርግላቸው ፡ ዘንድ ፥ በዐመድ ፡ ፋንታ ፡ አክሊልን ፥ በልቅሶም ፡ ፋንታ ፡ የደስታን ፡ ዘይት ፥ በሐዘንም ፡ መንፈስ ፡ ፋንታ ፡ የምስጋናን ፡ መጐናጸፊያ ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ልኮኛል ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 4 ፤ ከጥንትም ፡ ዝምሮ ፡ ባድማ ፡ የነበሩትን ፡ ይሠራሉ ፡ ከቀድሞ ፡ የፈረሱትንም ፡ ያቆማሉ ፤ ባድማ ፡ የነበሩትንና ፡ ከብዙ ፡ ትውልድ ፡ በፊት ፡ የፈረሱትን ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይሠራሉ ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 5 ፤ መጻተኞችም ፡ ቆመው ፡ በጎቻችኹን ፡ ያሰማራሉ ፥ ሌላዎች ፡ ወገኖችም ፡ ዐራሾችና ፡ ወይም ፡ ጠባቂዎች ፡ ይኾኑላችኋል ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 6 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ ትባላላችኹ ፥ ሰዎቹም ፡ የአምላካችን ፡ አገልጋዮች ፡ ብለው ፡ ይጠሯችኋል ፤ የአሕዛብን ፡ ሀብት ፡ ትበላላችኹ ፥ በክብራቸውም ፡ ትመካላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 7 ፤ በዕፍረታችኹ ፡ ፋንታ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ይኾንላችኋል ፥ በውርደታችኹም ፡ ፋንታ ፡ ዕድል ፡ ፈንታችኹ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ስለዚህ ፥ በምድራቸው ፡ ሾሉ ፡ ዕጥፍ ፡ ይገዛሉ ፥ የዘለዓለምም ፡ ደስታ ፡ ይኾንላቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ የምወድ ፡ ስርቆትንና ፡ በደልን ፡ የምጠላ ፡ ነኝ ፤ ፍዳቸውንም ፡ በእውነት ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 9 ፤ ዘራቸውም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፥ ልጆቻቸውም ፡ በወገኖች ፡ መካከል ፡ የታወቁ ፡ ይኾናሉ ፤ ያያቸው ፡ ሾሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባረካቸው ፡ ዘር ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ይገነዘባል ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 10 ፤ አክሊልን ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ ሙሽራ ፥ በጌጥ ፡ ሽልማቷም ፡ እንዳጌጠች ፡ ሙሽራ ፥ የማዳንን ፡ ልብስ ፡ አልብሶኛልና ፥ የጽድቅንም ፡ መጐናጸፊያ ፡ ደርቦልኛልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ነፍሴም ፡ በአምላኬ ፡ ሐሤት ፡ ታደርጋለች ።

ኢሳ. ፡ 61 ፡ 11 ፤ ምድርም ፡ ቡቃያዋን ፡ እንደምታወጣ ፥ ገነትም ፡ ዘሩን ፡ እንደሚያበቅል ፥ እንዲሁ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቅንና ፡ ምስጋናን ፡ በአሕዛብ ፡ ሾሉ ፡ ፊት ፡ ያበቅላል ።

_____ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 62 ። _____

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ዝም ፡ አልልም ፥ ስለ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ጸጥ ፡ አልልም ፥ ጽድቋ ፡ እንደ ፡ ጸዳል ፡ መዳኗም ፡ እንደሚበራ ፡ ፋና ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 2 ፤ አሕዛብም ፡ ጽድቅሽን ፡ ነገሥታትም ፡ ሾሉ ፡ ክብርሽን ፡ ያያሉ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አፍ ፡ በሚጠራበት ፡ በዐዲሱ ፡ ስም ፡ ትጠሪያለሽ ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 3 ፤ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ የክብር ፡ አክሊል ፥ በአምላክሽም ፡ እጅ ፡ የመንግሥት ፡ ዘውድ ፡ ትኾኛለሽ ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 4 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። የተተወች ፡ አትባዪም ፤ ምድርሽም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። ውድማ ፡ አትባልም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ብሎታልና ፥ ምድርሽም ፡ ባል ፡ ታገባለችና ፡ አንቺ ። ደስታዬ ፡ የሚኖርባት ፡ ትባያለሽ ፡ ምድርሽም ፦ ባል ፡ ያገባች ፡ ትባላለች ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 5 ፤ ጕልማሳም ፡ ድንግሊቱን ፡ እንደሚያገባ ፥ እንዲሁ ፡ ልጆችሽ ፡ ያገቡሻል ፤ ሙሽራም ፡ በሙሽራዪቱ ፡ ደስ ፡ እንደሚለው ፥ እንዲሁ ፡ አምላክሽ ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 6-7 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ጕበኞችን ፡ በቅጥርሽ ፡ ላይ ፡ አቁሜያለኹ ፤ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ከቶ ፡ ዝም ፡ አይሉም ፤ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምታሳስቡ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ እስኪያጸና ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ምስጋና ፡ እስኪያደርጋት ፡ ድረስ ፡ አትረፉ ፡ ለርሱም ፡ ዕረፍት ፡ አትስጡ ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በርግጥ ፡ ለጠላቶችሽ ፡ መብል ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እኽልሽን ፡ አልሰጥም ፥ መጻተኞችም ፡ የደከምሽበትን ፡ ወይንሽን ፡ አይጠጡም ፤

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰበሰቡት ፡ ይበሉታል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያመሰግናሉ ፥ ያከማቹትም ፡ በመቅደሴ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ይጠጡታል ፡ ብሎ ፡ በቀኙና ፡ በጎይሉ ፡ ክንድ ፡ ምሏል ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 10 ፤ ዕለፉ ፥ በበሮች ፡ በኩል ፡ ዕለፉ ፤ የሕዝቡንም ፡ መንገድ ፡ ጥረጉ ፤ አዘጋጁ ፥ ጐዳናውን ፡ አዘጋጁ ፥ ድንጋዮቹንም ፡ አስወግዱ ፤ ለአሕዛብም ፡ ዐላማ ፡ አንሡ ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለምድር ፡ ዳርቻ ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነግሯል ፦ ለጽዮን ፡ ልጅ ፦ እንሆ ፥ መድኀኒትሽ ፡ ይመጣል ፤ እንሆ ፥ ዋጋው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሥራውም ፡ በፊቱ ፡ አለ ፡ በሏት ።

ኢሳ. ፡ 62 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፦ የተቤዣቸው ፥ የተቀደሰ ፡ ሕዝብ ፡ ብለው ፡ ይጠሯቸዋል ፤ አንቺም ፦ የተፈለገች ፡ ያልተተወችም ፡ ከተማ ፡ ትባያለሽ ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 63 ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 1 ፤ ይህ ፡ ከኤዶምያስ ፥ ልብሱም ፡ የቀላ ፡ ከባሶራ ፡ የሚመጣ ፥ አለባበሱ ፡ ያማረ ፥ በጕልበቱ ፡ ጽናት ፡ የሚራመድ ፡ ማን ፡ ነው ፧ በጽድቅ ፡ የምናገር ፡ ለማዳንም ፡ የምበረታ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 2 ፤ ቀሚስኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቀላ ፧ ልብስኽስ ፡ በወይን ፡ መጥመቂያ ፡ እንደሚረግጥ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ መሰለ ፧

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 3 ፤ መጥመቂያውን ፡ ብቻዬን ፡ ረግጫለኹ ፥ ከአሕዛብም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አልነበረም ፤ በቍጣዬ ፡ ረገጥኋቸው ፡ በመዓቴም ፡ ቀጠቀጥኋቸው ፤ ደማቸውም ፡ በልብሴ ፡ ላይ ፡ ተረጭቷል ፥ ልብሴንም ፡ ኹሉ ፡ አሳድፌያለኹ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 4 ፤ የምበቀልበት ፡ ቀን ፡ በልቤ ፡ ነውና ፥ የምቤዥበትም ፡ ዓመት ፡ ደርሷልና ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 5 ፤ ተመለከትኹ ፥ የሚረዳም ፡ አልተገኘም ፤ የሚያግዝም ፡ አልነበረምና ፡ ተደነቅኹ ፤ ስለዚህ ፥ የገዛ ፡ ክንዴ ፡ መድኀኒት ፡ አመጣልኝ ፥ ቍጣዬም ፡ ርሱ ፡ አገዘኝ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 6 ፤ በቍጣዬም ፡ አሕዛብን ፡ ረገጥኹ ፡ በመዓቴም ፡ ቀጠቀጥኋቸው ፥ ደማቸውንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አፈሰስኹት ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፥ እንደ ፡ ምሕረቱና ፡ እንደ ፡ ቸርነቱም ፡ ብዛት ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሰጠውን ፡ ትልቅ ፡ በጎነት ፡ አሳስባለኹ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ በእውነት ፡ ሕዝቤ ፥ ሐሰትን ፡ የማያደርጉ ፡ ልጆች ፥ ናቸው ፡ አለ ፤ መድኀኒትም ፡ ኾነላቸው ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 9 ፤ በጭንቃቸው ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ ተጨነቀ ፥ የፊቱም ፡ መልአክ ፡ አዳናቸው ፤ በፍቅሩና ፡ በርኅራኄውም ፡ ተቤዣቸው ፥ በቀደመውም ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ አንሥቶ ፡ ተሸከማቸው ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 10 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ዐመፁ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈሱንም ፡ አስመረሩ ፤ ስለዚህ ፥ ተመልሶ ፡ ጠላት ፡ ኾናቸው ፥ ርሱም ፡ ተዋጋቸው ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የቀደመውን ፡ ዘመን ፡ ዐሰበ ። የበጎቹን ፡ እረኛ ፡ ከባሕሩ ፡ ያወጣው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፤ ቅዱስ ፡ መንፈሱንም ፡ በመካከላቸው ፡ ያኖረ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፤

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 12 ፤ የከበረውንም ፡ ክንድ ፡ በሙሴ ፡ ቀኝ ፡ ያስኼደ ፥ ለራሱም ፡ የዘለዓለምን ፡ ስም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ውሃውን ፡ በፊታቸው ፡ የከፈለ ፥

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 13 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ፈረስ ፥ በቀላይ ፡ ውስጥ ፡ ያለዕንቅፋት ፡ ያሳለፋቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ ያለ ፤

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሸለቆ ፡ እንደሚወርዱ ፡ ከብቶች ፥ እንዲሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ዕረፍት ፡ አመጣቸው ፤ እንዲሁም ፡ ለራስኽ ፡ የከበረ ፡ ስም ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝብን ፡ መራኽ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 15 ፤ ከሰማይ ፡ ተመልከት ፥ ከቅዱስነትኽና ፡ ከክብርኽም ፡ ማደሪያ ፡ ጐብኝ ፤ ቅንአትኽና ፡ ኀይልኽስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፤ ለኔም ፡ የኾነው ፡ የልብኽ ፡ ናፍቆትና ፡ ርኅራኄኽ ፡ ተከለከለ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 16 ፤ አብርሃም ፡ ባያውቀን ፡ እስራኤልም ፡ ባይገነዘበን ፡ አንተ ፡ አባታችን ፡ ነኽ ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አባታችን ፡ ነኽ ፥ ስምኽም ፡ ከዘለዓለም ፡ ታዳጊያችን ፡ ነው ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፥ ከመንገድኽ ፡ ለምን ፡ አሳትኸን ፤ እንዳንፈራኽም ፡ ልባችንን ፡ ለምን ፡ አጸናኽብን ፤ ስለ ፡ ባሪያዎችኽ ፡ ስለ ፡ ርስትኽ ፡ ነገዶች ፡ ተመለስ ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 18 ፤ የተቀደሰው ፡ ሕዝብኽ ፡ መቅደስኽን ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ወረሱት ፤ ጠላቶቻችንም ፡ ረግጠውታል ።

ኢሳ. ፡ 63 ፡ 19 ፤ ከዘለዓለም ፡ እንዳልገዛኸን ፡ በስምኽም ፡ እንዳልተጠራን ፡ ኾነናል ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 64 ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 1 ፤ ሰማዮችን ፡ ቀደኽ ፡ ምነው ፡ ብትወርድ! ፡ ተራራዎችም ፡ ምነው ፡ ቢናወጡ! ፡

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 2 ፤ እሳት ፡ ጭራሮውን ፡ እንደሚያቃጥል ፥ እሳትም ፡ ውሃውን ፡ እንደሚያፈላ ፥ ስምኽ ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፥ አሕዛብም ፡ በፊትኽ ፡ ይንቀጠቀጡ ፡ ዘንድ ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 3 ፤ ያልተጠባበቅነውን ፡ የክብርኽን ፡ ሥራ ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፥ ወረድኽ ፡ ተራራዎችም ፡ በፊትኽ ፡ ተንቀጠቀጡ ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 4 ፤ ሰዎች ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ለሚጠብቁኽ ፥ ከምትሠራላቸው ፡ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክን ፡ አልሰሙም ፥ በዣሯቸውም ፡ አልተቀበሉም ፥ ዐይንም ፡ አላየችም ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 5 ፤ ጽድቅን ፡ የሚያደርገውን ፥ በመንገዶችክም ፡ የሚያስቡኽን ፡ ትገናኛቸዋለኽ ። እንሆ ፥ አንተ ፡ ተቈጣኽ ፥ እኛም ፡ ኀጢአት ፡ ሠራን ፤ ስለዚህም ፡ ተሳሳትን ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 6 ፤ ኹላችን ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ሰው ፡ ኾነናል ፥ ጽድቃችንም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ ጨርቅ ፡ ነው ፤ ኹላችንም ፡ እንደ ፡ ቅጠል ፡ ረግፈናል ፥ በደላችንም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ወስዶናል ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 7 ፤ ስምኽንም ፡ የሚጠራ ፥ አንተንም ፡ ሊይዝ ፡ የሚያስብ ፡ የለም ፤ ፊትኽንም ፡ ከእኛ ፡ ሰውረኻል ፥ በኀጢአታችንም ፡ አጥፍተኻናል ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ አንተ ፡ አባታችን ፡ ነኽ ፤ እኛ ፡ ጭቃ ፡ ነን ፡ አንተም ፡ ሠሪያችን ፡ ነኽ ፥ እኛም ፡ ኹላችን ፡ የእጅኽ ፡ ሥራ ፡ ነን ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 9 ፤ አቤቱ ፥ እጅግ ፡ አትቈጣ ፥ ለዘለዓለምም ፡ ኀጢአትን ፡ አታስብ ፤ እንሆ ፥ እባክኽ ፥ ተመልከት ፥ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ሕዝብኽ ፡ ነን ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 10 ፤ የተቀደሱ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነዋል ፤ ጽዮን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ውድማ ፡ ኾናለች ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 11 ፤ አባቶቻችን ፡ አንተን ፡ ያመሰገኑበት ፡ የተቀደሰና ፡ የተዋበ ፡ ቤታችን ፡ በእሳት ፡ ተቃጥሏል ፥ ያማረውም ፡ ስፍራችን ፡ ኹሉ ፡ ፈርሷል ።

ኢሳ. ፡ 64 ፡ 12 ፤ አቤቱ ፥ በእውኑ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ትታገሣለኽን ፧ ዝምስ ፡ ትላለኽን ፧ አጥብቀኽስ ፡ ታስጨንቀናለኽን ፧

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 65 ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 1 ፤ ላልጠየቁኝ ፡ ተገለጥኹ ፥ ላልፈለጉኝም ፡ ተገኘኹ ፤ በስሜም ፡ ያልተጠራውን ፡ ሕዝብ ፦ እንሆኝ ፥ እንሆኝ ፡ አልኹት ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 2 ፤ መልካም ፡ ባልኾነው ፡ መንገድ ፥ ዐሳባቸውን ፡ እየተከተሉ ፥ ወደሚኼዱ ፡ ወደ ፡ ዐመፀኛ ፡ ሕዝብ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ እጆቼን ፡ ዘረጋኹ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 3 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ዘወትር ፡ የሚያስቈጡኝ ፡ ናቸው ፤ እነርሱ ፡ በአትክልት ፡ ውስጥ ፡ የሚሠዉ ፡ በጡብም ፡ ላይ ፡ የሚያጥኑ ፥

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 4 ፤ በመቃብርም ፡ መካከል ፡ የሚቀመጡ ፥ በስውርም ፡ ስፍራ ፡ የሚያድሩ ፥ የዕሪያ ፡ ሥጋም ፡ የሚበሉ ፡ ናቸው ። የረከሰው ፡ መረቅ ፡ በዕቃቸው ፡ ውስጥ ፡ አለ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፦ ለራስኽ ፡ ቁም ፥ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ይልቅ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አትቅረብ ፡ ይላሉ ፤ እነዚህ ፡ በአፍንጫዬ ፡ ዘንድ ፡ ጢስ ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ የምትነድ ፡ እሳት ፡ ናቸው ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ በፊቴ ፡ ተጽፏል ፦ ኀጢአታችኹና ፡ የአባቶቻችኹን ፡ ኀጢአት ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ብብታቸው ፡ ፍዳ ፡ አድርጌ ፡ እመልሳለኹ ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ አልልም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 7 ፤ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ ስላጠኑ ፥ በኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሰደቡኝ ፥ ስለዚህ ፡ አስቀድመው ፡ የሠሩትን ፡ ሥራቸውን ፡ በብብታቸው ፡ እሰፍራለኹ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወይን ፡ በዘለላው ፡ በተገኘች ፡ ጊዜ ፦ በረከት ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ አለና ፡ አታጥፉት ፡ እንደሚባለው ፥ ኹሉን ፡ እንዳላጠፉ ፡ ስለ ፡ ባሪያዎቼ ፡ እንዲሁ ፡ አደርጋለኹ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 9 ፤ ከያዕቆብ ፡ ዘርን ፡ ከይሁዳም ፡ ተራራዎቼን ፡ የሚወርሰውን ፡ አወጣለኹ ፤ እኔም ፡ የመረጥኋቸው ፡ ይወርሷታል ፥ ባሪያዎቼም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 10 ፤ ሳሮንም ፡ የበጎች ፡ ማሰማሪያ ፥ የዐኮርም ፡ ሸለቆ ፡ የላሞች ፡ መመሰጊያ ፡ ለፈለጉኝ ፡ ሕዝቤ ፡ ይኾናል ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 11 ፤ እናንተን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተዋችኹትን ፥ ቅዱሱንም ፡ ተራራዬን ፡ የረሳችኹትን ፥ ጕድ ፡ ለተባለ ፡ ጣዖትም ፡ ማእድ ፡ ያዘጋጃችኹትን ፥ ዕድል ፡ ለተባለ ፡ ጣዖትም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለመጠጥ ፡ ቀኰርባን ፡ የቀዳችኹትን ፥

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 12 ፤ ዕድላችኹን ፡ ለሰይፍ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ኹሉላችኹም ፡ ለመታረድ ፡ ትጐነበሳላችኹ ፤ በፊቴም ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረጋችኹ ፥ ያልወደድኹትንም ፡ መረጣችኹ ፡ እንጂ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ አልመለሳችኹልኝምና ፥ በተናገርኹም ፡ ጊዜ ፡ አልሰማችኹኝምና ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ይበላሉ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ትራባላችኹ ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ይጠጣሉ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ትጠማላችኹ ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ታፍራላችኹ ፤

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ ባሪያዎቼ ፡ ከልባቸው ፡ ደስታ ፡ የተነሣ ፡ ይዘምራሉ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ከልባችኹ ፡ ሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ትጮኻላችኹ ፥ መንፈሳችኹም ፡ ስለ ፡ ተሰበረ ፡ ወዮ ፡ ትላላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 15 ፤ ስማችኹንም ፡ ለተመረጡት ፡ ሕዝቤ ፡ ርግማን ፡ አድርጋችኹ ፡ ትተዋላችኹ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይገድላችኋል ፥ ባሪያዎቹንም ፡ በሌላ ፡ ስም ፡ ይጠራቸዋል ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 16 ፤ እንዲሁም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የተባረከ ፡ በእውነት ፡ አምላክ ፡ ይባረካል ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ የማለ ፡ በእውነት ፡ አምላክ ፡ ይምላል ፤ የቀድሞው ፡ ጭንቀት ፡ ተረስቷልና ፥ ከዐይኔም ፡ ተሰውሯልና ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ ዐዲስ ፡ ሰማይና ፡ ዐዲስ ፡ ምድር ፡ እፈጥራለኹና ፤ የቀደሙትም ፡ አይታሰቡም ፥ ወደ ፡ ልብም ፡ አይገቡም ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፈጠርኹት ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ሐሤት ፡ አድርጉ ፤ እንሆ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ ለሐሤት ፥ ሕዝቧንም ፡ ለደስታ ፡ እፈጥራለኹና ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 19 ፤ እኔም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሐሤት ፡ አደርጋለኹ ፡ በሕዝቤም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ የልቅሶ ፡ ድምፅና ፡ የዋይታ ፡ ድምፅ ፡ አይሰማባትም ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 20 ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ብቻ ፡ የሚኖር ፡ ሕፃን ፥ ወይም ፡ ዕድሜውን ፡ ያልፈጸመ ፡ ሽማግሌ ፡ አይገኝም ፤ ጕልማሳው ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ኾኖት ፡ ይሞታልና ፥ ኀጢአተኛውም ፡ የመቶ ፡ ዓመት ፡ ኾኖት ፡ የተረገመ ፡ ይኾናልና ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 21 ፤ ቤቶችንም ፡ ይሠራሉ ፡ ይቀመጡባቸውማል ፤ ወይኑንም ፡ ይተክላሉ ፡ ፍሬውንም ፡ ይበላሉ ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 22 ፤ ሌላ ፡ እንዲቀመጥበት ፡ አይሠሩም ፥ ሌላም ፡ እንዲበላው ፡ አይተከሉም ፤ የሕዝቤ ፡ ዕድሜ ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ዕድሜ ፡ ይኾናልና ፥ እኔም ፡ የመረጥኋቸው ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ረኻቦም ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 23 ፤ እነርሱ ፡ ከነልጆቻቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቡሩካን ፡ ዘር ፡ ናቸውና ፥ በከንቱ ፡ አይደክሙም ፡ ለጥፋትም ፡ አይወልዱም ።

ኢሳ. ፡ 65 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ ሳይጠሩ ፡ እመልስላቸዋለኹ ፥ ገናም ፡ ሲናገሩ ፡ እሰማለኹ ።

ኢሳ. ፥ 65 ፥ 25 ፤ ተኵላና ፡ ጠቦት ፡ በአንድነት ፡ ይሰማራሉ ፥ አንበሳም ፡ እንደ ፡ በሬ ፡ ገለባ ፡ ይበላል ፥ የእባብም ፡ መብል ፡ ትቢያ ፡ ይኾናል ። በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ኹሉ ፡ አይጐዱም ፥ አያጠፉምም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 66 ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፥ ምድርም ፡ የእግሬ ፡ መረገጫ ፡ ናት ፤ የምትሠሩልኝ ፡ ቤት ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ነው ፧ የማርፍበትስ ፡ ስፍራ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 2 ፤ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ እጄ ፡ ሠርታለችና ፡ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ ትሑት ፥ መንፈሱም ፡ ወደተሰበረ ፥ በቃሌም ፡ ወደሚንቀጠቀጥ ፡ ሰው ፡ እመለከታለኹ ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 3 ፤ በሬን ፡ የሚያርድልኝ ፡ ሰውን ፡ እንደሚገድል ፡ ነው ፤ ጠቦትንም ፡ የሚሠዋ ፡ የውሻውን ፡ ዐንገት ፡ እንደሚሰብር ፡ ነው ፤ የእኽልን ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርብ ፡ የዕሪያን ፡ ደም ፡ እንደሚያቀርብ ፡ ነው ፤ ዕጣንን ፡ የሚያጥን ፡ ጣዖትን ፡ እንደሚባርክ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የገዛ ፡ መንገዳቸውን ፡ መረጡ ፤ ነፍሳቸውም ፡ በርኵሰታቸው ፡ ደስ ፡ ይላታል ፤

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 4 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የተሳለቀባቸውን ፡ እመርጣለኹ ፥ የፈሩትንም ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹ ፤ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አደረጉ ፥ ያልወደድኹትንም ፡ መረጡ ፡ እንጂ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ አልመለሱልኝምና ፥ በተናገርኹም ፡ ጊዜ ፡ አልሰሙኝምና ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 5 ፤ በቃሉ ፡ የምትንቀጠቀጡ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፦ የጠሏችኹ ፡ ስለ ፡ ስሜም ፡ ያባረሯችኹ ፡ ወንድሞቻችኹ ፦ ደስታችኹን ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ብለዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ያፍራሉ ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 6 ፤ የጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ከከተማ ፥ ድምፅም ፡ ከመቅደስ ፥ በጠላቶቹ ፡ ላይ ፡ ፍዳን ፡ የሚያመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 7 ፤ ሳታምጥ ፡ ወለደች ፤ ምጥም ፡ ሳያገኛት ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 8 ፤ ከቶ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቷል ፧ እንዲህስ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ አይቷል ፧ በእውኑ ፡ አገር ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ታምጣለችን ፧ ወይስ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ይወለዳልን ፧ ጽዮን ፡ እንዳማጠች ፡ ወዲያው ፡ ልጆቿን ፡ ወልዳለችና ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 9 ፤ በእውኑ ፡ ወደ ፡ መውለድ ፡ የማደርስ ፡ እኔ ፡ አላስወልድምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የማስወልድስ ፡ ማሕፀንን ፡ እኔ ፡ እዘጋለኹን ፧ ይላል ፡ አምላክሽ ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 10 ፤ እናንተ ፡ የምትወዷት ፡ ኹሉ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋራ ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ እናንተም ፡ የምታለቅሱላት ፡ ኹሉ ፥ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በደስታ ፡ ሐሤትን ፡ አድርጉ ፥

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 11 ፤ ትጠቡ ፡ ዘንድ ፡ ከማጽናናቷም ፡ ጡት ፡ ትጠግቡ ፡ ዘንድ ፤ እጅግ ፡ ጠጥታችኹ ፡ በክብሯ ፡ ሙላት ፡ ደስ ፡ ይላችኹ ፡ ዘንድ ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ሰላምን ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፥ የአሕዛብንም ፡ ክብር ፡ እንደሚጐርፍ ፡ ፈሳሽ ፡ እመልስላታለኹ ፤ ከዚያም ፡ ትጠባላችኹ ፥ በጫንቃ ፡ ላይ ፡ ይሸከሟችኋል ፡ በጕልበትም ፡ ላይ ፡ እያስቀመጡ ፡ ያቀማጥሏችኋል ።

ኢሳ. ፥ 66 ፥ 13 ፤ እናት ፡ ልጇን ፡ እንደምታጽናና ፡ እንዲሁ ፡ አጽናናችኋለኹ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ትጽናናላችኹ ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 14 ፤ ታያላችኹ ፥ ልባችኹም ፡ ሐሤት ፡ ታደርጋለች ፥ ዐጥንታችኹም ፡ እንደ ፡ ለምለም ፡ ሣር ፡ ትበቅላለች ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ለሚፈሩት ፡ ትታወቃለች ፥ በጠላቶቹም ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ መዓቱን ፡ በቍጣ ፥ ዘለፋውንም ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ከእሳት ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፥ ሠረገላዎቹም ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኾናሉ ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በእሳትና ፡ በሰይፉ ፡ ይፈርዳል ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ ይበዛሉ ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 17 ፤ በመካከላቸው ፡ ያለውን ፡ አንዱን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ገነቱ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰውነታቸውን ፡ የሚቀድሱና ፡ የሚያነጹ ፥ የዕሪያንም ፡ ሥጋ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገርንም ፡ ዐይጥንም ፡ የሚበሉ ፡ በአንድነት ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 18 ፤ ሥራቸውንና ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቄያለኹና ፤ አሕዛብንና ፡ ልሳናትን ፡ ኹሉ ፡ የምሰበስብበት ፡ ጊዜ ፡ ይደርሳል ፥ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡ ክብሬንም ፡ ያያሉ ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 19 ፤ በመካከላቸውም ፡ ምልክት ፡ አደርጋለኹ ፥ ከነርሱም ፡ የዳኑትን ፡ ዝናዬን ፡ ወዳልሰሙ ፥ ክብሬንም ፡ ወዳላዩ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ወደ ፡ ፉጥ ፡ ወደ ፡ ሉድ ፡ ወደ ፡ ሞሳሕ ፡ ወደ ፡ ቱቤል ፡ ወደ ፡ ያዋን ፡ በሩቅ ፡ ወዳሉ ፡ ደሴቶች ፡ እልካቸዋለኹ ፥ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ክብሬንም ፡ ይናገራሉ ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 20 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍርባናቸውን ፡ በጥሩ ፡ ዕቃ ፡ አድርገው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደሚያመጡ ፥ እንዲሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ወንድሞቻችኹን ፡ ኹሉ ፥ በፈረሶችና ፡ በሠረገላዎች ፥ በዐልጋዎችና ፡ በበቅሎዎች ፡ በጠያር ፡ ግመሎችም ፡ ላይ ፡ አድርገው ፥ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ወደተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጧቸዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 21 ፤ ካህናትና ፡ ሌዋውያን ፡ እንዲኾኑ ፡ ከነርሱ ፡ እወስዳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 22 ፤ እኔ ፡ የምሠራቸው ፡ ዐዲስ ፡ ሰማይና ፡ ዐዲስ ፡ ምድር ፡ ከፊቴ ፡ ጸንተው ፡ እንደሚኖሩ ፥ እንዲሁ ፡ ዘራችኹና ፡ ስማችኹ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 23 ፤ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ በየመባቻውና ፡ በየሰንበቱ ፡ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ በፊቴ ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ዘወትር ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኢሳ. ፡ 66 ፡ 24 ፤ ወጥተውም ፡ በእኔ ፡ ያመፁብኝን ፡ ሰዎች ፡ ሬሳቸውን ፡ ያያሉ ፤ ትላቸው ፡ አይሞትምና ፥ እሳታቸውም ፡ አይጠፋምና ፤ ለሥጋ ፡ ለባሽም ፡ ኹሉ ፡ አስጸያፊ ፡ ነገር ፡ ይኾናሉ ❖

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኤር. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በብንያም ፡ አገር ፡ በዐናቶት ፡ ከነበሩ ፡ ካህናት ፡ የኾነ ፡ የኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ የኤርምያስ ፡ ቃል ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 2 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ በአሥያስ ፡ ዘመን ፡ በመንግሥቱ ፡ በዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣለት ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በአሥያስ ፡ ልጅ ፡ በአሥአቄም ፡ ዘመን ፥ እስከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ እስከአሥያስ ፡ ልጅ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ፍጻሜ ፥ አሥራሉሌም ፡ እስከተማረኩበት ፡ እስከ ፡ ዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ድረስ ፡ መጣ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በሆድ ፡ ሳልሠራኽ ፡ ዐውቄኻለኹ ፥ ከማሕፀንም ፡ ሳትወጣ ፡ ቀድሼኻለኹ ፥ ለአሕዛብም ፡ ነቢይ ፡ አድርጌኻለኹ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እኔም ፦ ወዮ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እንሆ ፥ ብላቴና ፡ ነኝና ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ አላውቅም ፡ አልኹ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ወደምሰድኽ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ትኼዳለኽና ፥ የማዝኽንም ፡ ኹሉ ፡ ትናገራለኽና ። ብላቴና ፡ ነኝ ፡ አትበል ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እኔ ፡ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ ከፊታቸው ፡ አትፍራ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ አፌን ፡ ዳሰሰ ፥ እግዚአብሔርም ፦ እንሆ ፥ ቃሌን ፡ በአፍኽ ፡ ውስጥ ፡ አኑሬያለኹ ፤

ኤር. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እንሆ ፦ ትነቅልና ፡ ታፈርስ ፡ ዘንድ ፥ ታጠፋና ፡ ትገለብጥ ፡ ዘንድ ፥ ትሠራና ፡ ትተክል ፡ ዘንድ ፡ በአሕዛብና ፡ በመንግሥታት ፡ ላይ ፡ ዛሬ ፡ አድርጌኻለኹ ፡ አለኝ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፦ ኤርምያስ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ታያለኽ ፧ እያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ። እኔም ፦ የለውዝ ፡ በትር ፡ አያለኹ ፡ አልኹ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እፈጽመው ፡ ዘንድ ፡ በቃሌ ፡ እተጋለኹና ፡ መልካም ፡ አይተኻል ፡ አለኝ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፦ ምን ፡ ታያለኽ ፧ እያለ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ። እኔም ፦ የሚፈላ ፡ አፍላል ፡ አያለኹ ፥ ፊቱም ፡ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ነው ፡ አልኹ ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከሰሜን ፡ ወገን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በምድሪቱ ፡ በተቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ።

ኤር. ፥ 1 ፥ 15 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ በሰሜን ፡ ያሉትን ፡ የመንግሥታትን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ እጠራለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እነርሱም ፡ ይመጣሉ ፡ እያንዳንዳቸውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ በዙሪያዋ ፡ በቅጥሯ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዙፋናቸውን ፡ ያስቀምጣሉ ።

ኤር. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ስለ ፡ ክፋታቸውም ፡ ኹሉ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ ስላጠኑ ፥ ለእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፥ ፍርዴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እናገራለኹ ።

ኤር. ፡ 1 ፡ 17 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ወገብኽን ፡ ታጠቅ ፥ ተነሥም ፥ ያዘዝኹኽም ፡ ኹሉ ፡ ንገራቸው ፤ በፊታቸው ፡ እንዳላስፈራኽ ፡ አትፍራቸው ።

ኤር. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ በምድሪቱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በአለቃዎቿና ፡ በካህናቷ ፡ ላይ ፡ በምድሪቱም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተመሸገ ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ብረትም ፡ ዐምድ ፡ እንደ ፡ ናስም ፡ ቅጥር ፡ ዛሬ ፡ አድርጌ ኻለኹ ።

ኤር. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ ድል ፡ አይነሡኽም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ኺድ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ጮሮ ፡ ጨኽ ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የብላቴንነትሽን ፡ ምሕረት ፡ የታጨሽበትንም ፡ ፍቅር ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዘር ፡ ባልተዘራበት ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተከተልሽኝ ፡ ዐስቤያለኹ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እስራኤል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱስ ፡ ነበረ ፥ የቡቃያውም ፡ በኵራት ፡ ነበረ ፤ የበሉት ፡ እንደ ፡ በደለኞች ፡ ይቈጠራሉ ፥ ክፉም ፡ ነገር ፡ ያገኛቸዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 4 ፤ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አባቶቻችኹ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቁ ፥ ከንቱነትንም ፡ የተከተሉ ፥ ከንቱም ፡ የኾኑ ፡ ምን ፡ ክፋት ፡ አግኝተውብኝ ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እነርሱም ፦ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ በባድማ ፡ ጕድጓድም ፡ ባለበት ፡ ምድር ፥ በውሃ ፡ ጥምና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ምድር ፥ ማንም ፡ በማያልፍበትና ፡ ማንም ፡ በማይቀመጥበት ፡ ምድር ፡ የመራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ አላሉም ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ፍሬዋንና ፡ በረከቷንም ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍሬያማ ፡ ምድር ፡ አገባኋችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ ምድሬን ፡ አረከሳችኹ ፥ ርስቴንም ፡ አጐሳቈላችኹ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ካህናቱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ አላሉም ፥ ባለአራቶችም ፡ አላወቁኝም ፤ ገዢዎችም ፡ ዐመፁብኝ ፥ ነቢያትም ፡ በበዓል ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፥ የማይረባንም ፡ ነገር ፡ ተከተሉ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እከራከራለኹ ፥ ከልጆቻችኹም ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እከራከራለኹ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ወደኪቲም ፡ ደሴቶች ፡ ዕለፉና ፡ ተመልከቱ ፥ ወደ ፡ ቄዳርም ፡ ላኩና ፡ እጅግ ፡ መርምሩ ፥ እንደዚህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እዩ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 11 ፤ በእውኑ ፡ አማልክት ፡ ያልኾኑትን ፡ አማልክቱን ፡ የለወጣቸው ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አለን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ ሕዝቤ ፡ ክብሩን ፡ ለማይረባ ፡ ነገር ፡ ለወጠ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ሰማያት ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ተደነቁ ፥ እጅግም ፡ ደንግጡና ፡ ተንቀጥቀጡ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ሕዝቤ ፡ ኹለቱን ፡ ክፉ ፡ ነገሮች ፡ አድርገዋልና ፤ እኔን ፡ የሕያውን ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡

ትተውኛል ፥ የተቀደዱትንም ፡ ጕድጓዶች ፥ ውሃውን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉትን ፡ ጕድጓዶች ፥ ለራሳቸው ፡ ቈፍረዋል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በእውኑ ፡ እስራኤል ፡ ባሪያ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ የቤት ፡ ውላጅ ፡ ነውን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ብዝበዛ ፡ ኾነ ፧

ኤር. ፡ 2 ፡ 15 ፤ የአንበሳ ፡ ደቦሎች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አገሡ ፥ ድምፃቸውንም ፡ ሰጡ ፤ ምድሩንም ፡ ባድማ ፡ አደረጉ ፥ ከተማዎቹም ፡ ተቃጠሉ ፡ የሚቀመጥባቸውም ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 16 ፤ የሜምፎስና ፡ የጣፍናስ ፡ ልጆች ፡ አስነወሩሽ ፡ አላገጡብሽም ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የኾነብሽ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተውሽ ፡ አይደለምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክሽ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 18 ፤ አኹንስ ፡ የሺሖርን ፡ ውሃ ፡ ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በግብጽ ፡ መንገድ ፡ ምን ፡ ጕዳይ ፡ አለሽ ፧ የኤፍራጥስንም ፡ ውሃ ፡ ትጠጪ ፡ ዘንድ ፡ በአሶር ፡ መንገድ ፡ ምን ፡ ጕዳይ ፡ አለሽ ፧

ኤር. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ክፋትሽ ፡ ይገሥጽሻል ፡ ክዳትሽም ፡ ይዘልፍሻል ፤ አምላክሽንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የተውሽ ፡ እኔንም ፡ መፍራት ፡ የሌለብሽ ፡ ክፉና ፡ መራራ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቂ ፥ ተመልከቺ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ቀንበርሽን ፡ ሰብሬያለኹ ፡ እስራትሽንም ፡ ቈርጫለኹ ፤ አንቺም ፦ አላገለግልም ፡ አልሽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ ኮረብታ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከለምለምም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ለማመንዘር ፡ ተጋደምሽ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ የተመረጠች ፡ ወይን ፡ ፍጹምም ፡ እውነተኛ ፡ ዘር ፡ አድርጌ ፡ ተክዬሽ ፡ ነበር ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ የእንግዳ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ ኾነሽ ፡ እንዴት ፡ ተለወጥሽብኝ ፧

ኤር. ፡ 2 ፡ 22 ፤ በእንዶድ ፡ ብትታጠቢም ፥ ለራስሽም ፡ ሳሙና ፡ ብታበዢ ፥ በእኔ ፡ ፊት ፡ በኀጢአትሽ ፡ ረክሰሻል ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 23 ፤ አንቺስ ፦ አልረከስኹም ፥ በዓሊምንም ፡ አልተከተልኹም ፡ እንዴት ፡ ትያለሽ ፧ በቈላ ፡ ያለውን ፡ መንገድሽን ፡ ተመልከቺ ፥ ያደረግሽውንም ፡ ዕወቂ ፤ በመንገድም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተለቀቀች ፡ እንደ ፡ ፈጣን ፡ ግመል ፡ ኾነሻል ፤

ኤር. ፡ 2 ፡ 24 ፤ በምኞቷ ፡ ነፋስን ፡ እንደምታሸት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ እንደ ፡ ሜዳ ፡ አህያ ፡ ነሽ ፤ ከምኞቷ ፡ የሚመልሳት ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚሷት ፡ ኹሉ ፡ አይደክሙም ፥ በወራቷ ፡ ያገኟታል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 25 ፤ እግርሽን ፡ ከሻካራ ፡ መንገድ ፡ ጕረሮሽንም ፡ ከውሃ ፡ ጥም ፡ ከልክዪ ፤ አንቺ ፡ ግን ፦ እጨክናለኹ ፥ እንግዳዎችን ፡ ወድጃለኹና ፥ እከተላቸዋለኹም ፡ አልሽ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ሌባ ፡ በተያዘ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚያፍር ፡ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፥ እነርሱና ፡ ንጉሦቻቸውም ፡ አለቃዎቻቸውም ፡ ካህናታቸውም ፡ ነቢያታቸውም ፡ ያፍራሉ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 27 ፤ ግንዱን ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ነኽ ፤ ድንጋዩንም ፦ አንተ ፡ ወለድኸኝ ፡ ይላሉ ፤ ፊታቸውንም ፡ ሳይኾን ፡ ጠርባቸውን ፡ ሰጡኝ ፥ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ግን ፦ ተነሥተኽ ፡ አድነን ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 28 ፤ ለአንተ ፡ የሠራኻቸው ፡ አማልክትኽ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፧ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አማልክትኽ ፡ እንደ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ቍጥር ፡ እንዲሁ ፡ ናቸውና ፥ ይነሡ ፡ በመከራኽም ፡ ጊዜ ፡ ያድኑኽ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 29 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የምትከራከሩ ፡ ለምንድር ፡ ነው ፧ ዅላችኹ ፡ ዐምፃችኹብኛል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 30 ፤ ልጆቻችኹን ፡ በከንቱ ፡ ቀሥፌአቸዋለኹ ፤ ተግሣጽን ፡ አልተቀበሉም ፤ ሰይፋችኹ ፡ እንደሚሰብር ፡ አንበሳ ፡ ነቢያታችኹን ፡ በልቷል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 31 ፤ ትውልድ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ተመልከቱ ፦ በእውኑ ፡ ለእስራኤል ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወይስ ፡ የጨለመች ፡ ምድር ፡ ኾንኩባትን ፧ ሕዝቤስ ፡ ስለ ፡ ምን ፦ እኛ ፡ ፈርጥጠናል ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወዳንተ ፡ አንመለስም ፡ ይላል ፧

ኤር. ፡ 2 ፡ 32 ፤ በእውኑ ፡ ቈንጕ ፡ ጌጧን ፡ ወይስ ፡ ሙሽራ ፡ ዝርግፍ ፡ ጌጧን ፡ ትረሳለችን ፧ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ የማይቈጠር ፡ ወራት ፡ ረስቶኛል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 33 ፤ ፍቅርን ፡ ለመሻት ፡ መንገድሽን ፡ እንዴት ፡ ታቀኛለሽ! ፡ ስለዚህ ፡ ለክፉዎች ፡ ሴቶች ፡ እንኳ ፡ መንገድሽን ፡ አስተምረሻል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 34 ፤ በእጆችሽም ፡ የንጹሓን ፡ ድኻዎች ፡ ደም ፡ ተገኝቷል ፤ በእነዚህ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ በግልጥ ፡ አገኘኹት ፡ እንጂ ፡ በስውር ፡ ፈልጌ ፡ አላገኘኹትም ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 35 ፤ አንቺ ፡ ግን ፦ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤ በእውነት ፡ ቍጣው ፡ ከእኔ ፡ ተመልሷል ፡ አልሽ ። እንሆ ፦ ኀጢአት ፡ አልሠራኹም ፡ ብለሻልና ፥ በፍርድ ፡ እከስሻለኹ ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 36 ፤ መንገድሽን ፡ ትለውጪ ፡ ዘንድ ፡ ለምን ፡ እጅግ ፡ ትሮጣለሽ ፧ አሶር ፡ እንዳሳፈረሽ ፡ ግብጽ ፡ ያሳፍርሻል ።

ኤር. ፡ 2 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔር ፡ የታመንሽባቸውን ፡ ጥሏልና ፥ በእነርሱም ፡ አይከናወንልሽምና ፡ እጅሽን ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ አድርገሽ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ ትወጣለሽ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 1 ፤ በሰው ፡ ዘንድ ፦ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ቢፈታ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ኼዳ ፡ ሌላ ፡ ወንድ ፡ ብታገባ ፥ በእውኑ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ትመለሳለችን ፧ ያች ፡ ሴት ፡ እጅግ ፡ የረከሰች ፡ አይደለችምን ፧ ይባላል ። አንቺ ፡ ከብዙ ፡ ውሽማዎች ፡ ጋራ ፡ አመንዝረሻል ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ትመለሻለሽን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ዐይንሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ወደ ፡ ወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ተመልከቺ ፤ ያልተጋደምሽበት ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ዐረባዊ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደሚቀመጥ ፡ አንቺ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተቀምጠሽ ፡ ትጠብቂያቸው ፡ ነበር ፤ በግልሙትናሽና ፡ በኀጢአትሽ ፡ ምድሪቱን ፡ አረከሽ ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ካፊያ ፡ ተከለከለ ፥ የኋለኛውም ፡ ዝናብ ፡ ጠፋ ፤ የጋለሞታም ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ነበረብሽ ፥ ታፍሪም ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለሻል ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 4 ፤ አኹንም ፦ አንተ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፥ የብላቴንነቴ ፡ ወዳጅ ፡ ነኽ ፡ ብለሽ ፡ አልጮኽሺልኝምን ፧ ለዘለዓለም ፡ ይቈጣልን ፧

ኤር. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እስከ ፡ ፍጻሜስ ፡ ድረስ ፡ ይጠብቀዋልን ፧ እንሆ ፥ እንዲህ ፡ ብለሽ ፡ ተናገርሽ ፥ እንደ ፡ ተቻለሽም ፡ መጠን ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አደረግሽ ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በንጉሡ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከዳተኛዪቱ ፡ እስራኤል ፡

ያደረገችውን ፡ አየኽን ፧ ወደረዘመው ፡ ተራራ ፡ ኹሉ ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍም ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ኼደች ፡ በዚያም ፡ ጋለሞተች ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ ካደረገች ፡ በኋላ ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመለሳለች ፡ ብዬ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልተመለሰችም ፤ አታላይ ፡ እኅቷም ፡ ይሁዳ ፡ አየች ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ከዳተኛዩቱም ፡ እስራኤል ፡ ስላመነዘረች ፡ ስለዚህ ፡ ፈትቻታለኹ ፡ የፍቺንም ፡ ወረቀት ፡ ሰጥቻታለኹ ፤ አታላይ ፡ እኅቷ ፡ ይሁዳ ፡ ግን ፡ እንዳልፈራች ፡ ርኳም ፡ ደግሞ ፡ ኼዳ ፡ እንደ ፡ ጋለሞተች ፡ አየኹ ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በግልሙትናዋም ፡ በመቅለሏም ፡ ምድሪቱ ፡ ረከሰች ፤ ርኳም ፡ ከድንጋይና ፡ ከግንድ ፡ ጋራ ፡ አመነዘረች ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 10 ፤ በዚህም ፡ ኹሉ ፡ አታላዩቱ ፡ ይሁዳ ፡ በሐሰት ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ ልቧ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሰችም ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ከአታላዩቱ ፡ ከይሁዳ ፡ ይልቅ ፡ ከዳተኛዩቱ ፡ እስራኤል ፡ ጸደቀች ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ኺድና ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ ከዳተኛዩቱ ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ተመለሽ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ መሓሪ ፡ ነኝና ፥ ለዘለዓለምም ፡ አልቈጣምና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ፊቴን ፡ አላደርግም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 13 ፤ በአምላክሽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንዳመፅሽ ፥ መንገድሽንም ፡ ከለመለመ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ለእንግዳዎች ፡ እንደ ፡ ዘረጋሽ ፥ ቃሌንም ፡ እንዳልሰማሽ ፡ ኀጢአትሽን ፡ ብቻ ፡ ዕወቂ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ከዳተኞች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ባላችኹ ፡ ነኝና ፡ ተመለሱ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንዱንም ፡ ከአንዲት ፡ ከተማ ፡ ኹለቱንም ፡ ካንድ ፡ ወገን ፡ እወስዳችኋለኹ ፥ ወደ ፡ ጽዮንም ፡ አመጣችኋለኹ ፤

ኤር. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እንደ ፡ ልቤም ፡ በግ ፡ ጠባቂዎችን ፡ እሰጣችኋለኹ ፥ በዕውቀትና ፡ በማስተዋልም ፡ ይጠብቋችኋል ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 16 ፤ በበዛችኹም ፡ ጊዜ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ በረባችኹ ፡ ጊዜ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፦ የእግዚአብሔር ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ ታቦት ፡ ብለው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይጠሩም ፤ ልብ ፡ አያደርጉትም ፥ አያስቡትምም ፥ አይሹትምም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ አይደረግም ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 17 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ብለው ፡ ይጠሯታል ፥ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ይሰበሰባሉ ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ክፉውን ፡ እልከኛ ፡ ልባቸውን ፡ ተከትለው ፡ አይኼዱም ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ ይኼዳል ፤ በአንድም ፡ ኾነው ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኋት ፡ ምድር ፡ ይመጣሉ ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 19 ፤ እኔ ፡ ግን ፦ ከወንዶች ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ አደርግሻለኹ ፧ ያማረችውንስ ፡ ምድር ፡ የከበረችውን ፡ የአሕዛብን ፡ ሰራዊት ፡ ርስት ፡ እንዴት ፡ እሰጥሻለኹ ፧ ብዬ ፡ ነበር ። ደግሞ ፦ አባቴ ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪኛለሽ ፥ እኔንም ፡ ከመከተል ፡ አትመለሽም ፡ ብዬ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 20 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ሚስት ፡ ባሏን ፡ እንደምታታልል ፡ እንዲሁ ፡ አታለላችኹኝ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 21 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መንገዳቸውን ፡ አጣመዋልና ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተዋልና ፥ በወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ የልመናቸውና ፡ ልቅሷቸው ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ከዳተኞች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፥ ከዳተኛነታችኹንም ፡ እፈውሳለኹ ። እንሆ ፥ አንተ ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኽና ፥ ወዳንተ ፡ እንመጣለን ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 23 ፤ በእውነት ፡ የኰረብታዎችና ፡ የተራራዎች ፡ ፍጅት ፡ ከንቱ ፡ ናት ፤ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ መዳን ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከትንሽነታችን ፡ ዠምሮ ፡ የአባቶቻችን ፡ ድካም ፥ በጎቻቸውንና ፡ ላሞቻቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፥ ዕፍረት ፡ በልቶባቸዋል ።

ኤር. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ከትንሽነታችን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እኛና ፡ አባቶቻችን ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ የአምላካችንንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማንምና ፡ በዕፍረታችን ፡ እንጋደም ፥ ውርደታችንም ፡ ይክደነን ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ብትመለስ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለስ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ርኵሰትኽንም ፡ ከፊቴ ፡ ብታስወግድ ፥ ባትናወጥም ፥

ኤር. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ብለኽም ፡ በእውነትና ፡ በቅንነት ፡ በጽድቅም ፡ ብትምል ፥ አሕዛብ ፡ በርሱ ፡ ይባረካሉ ፡ በርሱም ፡ ይመካሉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለይሁዳና ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ጥጋቱን ፡ ዕርሻ ፡ ዕረሱ ፥ በሾኽም ፡ ላይ ፡ አትዝሩ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 4 ፤ እናንተም ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ስለሥራችኹ ፡ ክፋት ፡ ቍጣዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እንዳይወጣ ፡ የሚያጠፋውም ፡ ሳይኖር ፡ እንዳያቃጥል ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ተገረዙ ፥ የልባችኹንም ፡ ሸለፈት ፡ አስወግዱ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 5 ፤ በይሁዳ ፡ ዘንድ ፡ ተናገሩ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ አውሩና ፦ በአገሪቱ ፡ ላይ ፡ መለከት ፡ ንፉ ፡ በሉ ፤ ጮኻችኹም ፦ ሹላችኹ ፡ ተሰብሰቡ ፡ ወደተመሸጉትም ፡ ከተማዎች ፡ እንግባ ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ከሰሜን ፡ ክፉ ፡ ነገርንና ፡ ጽኑ ፡ ጥፋትን ፡ አመጣለኹና ፡ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ዐላማን ፡ አንሡ ፤ ሽሹ ፥ አትዘግዩ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 7 ፤ አንበሳ ፡ ከጫፍቅ ፡ ዱር ፡ ወጥቷል ፥ አሕዛብንም ፡ የሚዘርፍ ፡ ተነሥቷል ፤ ምድርሽን ፡ ባድማ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከስፍራው ፡ ወጥቷል ፥ ከተማዎችሽም ፡ ሰው ፡ የሌለባቸው ፡ ፍርስራሾች ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ አልተመለሰምና ፡ ማቅ ፡ ልበሱ ፥ አልቅሱም ፡ ዋይም ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የንጉሡና ፡ የመኳንንቱ ፡ ልብ ፡ ይጠፋል ፥ ካህናቱም ፡ ይደነቃሉ ፡ ነቢያቱም ፡ ይደነግጣሉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 10 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ ፥ አንተ ፡ ሰይፍ ፡ እስከ ፡ ነፍስ ፡ ድረስ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፦ ሰላም ፡ ይኾንላችኋል ፡ ብለኽ ፡ ይህን ፡ ሕዝብና ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ እጅግ ፡ አታለልኽ ፡ አልኹ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 11 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብና ፡ ለኢየሩሳሌም ፦ ለማበጠር ፡ ወይም ፡ ለማጥራት ፡ ሳይኾን ፡ የሚያቃጥል ፡ ነፋስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ካሉ ፡ ከወናዎች ፡ ከሠረብታዎች ፡ ወደወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ይመጣል ፤

ኤር. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ ጽኑ ፡ የኾነ ፡ ነፋስ ፡ ከነዚህ ፡ ይመጣል ፡ ይባላል ። አኹንም ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ፍርዴን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እናገራለኹ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ደመና ፡ ይወጣል ፥ ሠረገላዎቹም ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፤ ፈረሶቹም ፡ ከንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ። ጠፍተናልና ፥ ወዮልን ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ትድኚ ፡ ዘንድ ፡ ልብሽን ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ዕጠቢ ። ክፉ ፡ ዐሳብ ፡ የሚኖርብሽ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 4 ፡ 15 ፤ የተናጋሪ ፡ ድምፅ ፡ ከዳን ፡ ዘንድ ፡ ይናገራልና ፥ ከኤፍሬምም ፡ ከሠረብታዎች ፡ መከራን ፡ ያወራልና ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ለአሕዛብ ፡ አሰሙና ፦ እንሆ ፥ ጠባቂዎች ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ይመጣሉ ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ይጮኻሉ ፡ ብላችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አውሩ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በእኔ ፡ ላይ ፡ ዐመፀኛ ፡ ኾናለችና ፡ በዙሪያዋ ፡ ከዐው ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ጠባቂዎች ፡ ኾነውባታል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 18 ፤ መንገድሽና ፡ ሥራሽ ፡ ይህን ፡ አድርጎብሻል ፤ ይህ ፡ ክፋትሽ ፡ መራር ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ልብሽም ፡ ደርሷል ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 19 ፤ አንጐቴ! ፡ አንጐቴ! ፡ ልቤ ፡ በጣም ፡ ታሟል ፥ በውስጤም ፡ ልቤ ፡ ታውኮብኛል ፤ ነፍሴ ፡ ሆይ ፥ የመለከትን ፡ ድምፅና ፡ የሰልፍን ፡ ውካታ ፡ ሰምተሻልና ፥ ዝም ፡ እል ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 20 ፤ መከራ ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ ተጠርቷል ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ ተበዝብዛለችና ፤ በድንገትም ፡ ድንኳኔ ፡ በቅጽበት ፡ ዐይንም ፡ መጋረጃዎቼ ፡ ጠፉ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ዐላማውን ፡ የምመለከት ፥ የመለከቱንስ ፡ ድምፅ ፡ የምሰማ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ሕዝቤ ፡ ሰንፈዋልና ፥ አላወቁኝም ፤ ሰነፎች ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፥ ማስተዋልም ፡ የላቸውም ፤ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ለማድረግ ፡ ብልኀተኞች ፡ ናቸው ፥ በጎ ፡ ነገርን ፡ ማድረግ ፡ ግን ፡ አያውቁም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ምድሪቱን ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ባዶ ፡ ነበረች ፡ አንዳችም ፡ አልነበረባትም ፤ ሰማያትንም ፡ አየኹ ፥ ብርሃንም ፡ አልነበረባቸውም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ተራራዎችን ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ተንቀጠቀጡ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ኹሉ ፡ ተናወጡ ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 25 ፤ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ሰው ፡ አልነበረም ፥ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ሸሽተው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 26 ፤ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነች ፥ ከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ፈርሰው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 27 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽሜ ፡ አላጠፋትም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 28 ፤ ስለዚህ ፥ ምድር ፡ ታለቅሳለች ፥ በላይም ፡ ሰማይ ፡ ይጠቍራል ፤ ተናግሬያለኹና ፥ ዐስቤያለኹም ፤ አልጸጸትም ፡ ከርሱም ፡ አልመለስም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ከፈረሰኞችና ፡ ከቀስተኞች ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ሸሽታለች ፤ ወደችፍግ ፡ ዱርም ፡ ይገባሉ ፡ በቋጥኝ ፡ ላይም ፡ ይወጣሉ ፤ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ተለቃለች ፡ የሚቀመጥባትም ፡ ሰው ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 30 ፤ አንቺም ፡ የተበዘበዝሽ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ታደርጊያለሽ ፧ ቀይ ፡ በለበስሽ ፡ ጊዜ ፥ በወርቅ ፡ አንባርም ፡ ባጌጥሽ ፡ ጊዜ ፥ ዐይንሽንም ፡ በኵል ፡ በተኳልሽ ፡ ጊዜ ፥ በከንቱ ፡ ታጌጣለሽ ፤ ውሽማዎችሽ ፡ አቃለሉሽ ፥ ነፍስሽን ፡ ይሻታል ።

ኤር. ፡ 4 ፡ 31 ፤ እንደምታምጥ ፡ የበኵሯንም ፡ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ ድምፅ ፡ ሰምቻለኹና ፤ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ድምፅ ፡ በድካም ፡ ይሰልላል ፥ እጆቿንም ፡ ትዘረጋለችና ፦ ተገድለው ፡ ከሞቱት ፡ የተነሣ ፡ ነፍሴ ፡ ዝላለችና ፡ ወዮልኝ! ፡ አለች ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 1 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ መንገድ ፡ እየተመላለሳችኹ ፡ ሩጡ ፥ ተመልከቱም ፥ ዕወቁም ፥ በአደባባይዋም ፡ ፈልጉ ፤ ፍርድን ፡ የሚያደርገውን ፡ እውነትንም ፡ የሚሻውን ፡ ሰው ፡ ታገኙ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይቅር ፡ እላታለኹ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 2 ፤ እነርሱም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ቢሉ ፡ የሚምሉት ፡ በሐሰት ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 3 ፤ አቤቱ ፥ ዐይንኽ ፡ እውነትን ፡ የምትመለከት ፡ አይደለችምን ፧ አንተ ፡ ቀሠፈኻቸዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላዘኑም ፥ ቀጥቅጠኻቸውማል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ተግሣጽን ፡ እንቢ ፡ አሉ ፤ ፊታቸውን ፡ ከድንጋይ ፡ ይልቅ ፡ አጠንክረዋል ፤ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 4 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድና ፡ የአምላካቸውን ፡ ሕግ ፡ አላወቁምና ፡ እነዚህ ፡ በእውነት ፡ ድኻዎችና ፡ ሰነፎች ፡ ናቸው ፤

ኤር. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ታላላቆቹ ፡ እኼዳለኹ ፡ እናገራቸውማለኹ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንገንድና ፡ የአምላካቸውን ፡ ሕግ ፡ ያውቃሉና ፡ አልኹ ። እነዚህ ፡ ግን ፡ ቀንበሩን ፡ በአንድነት ፡ ሰብረዋል ፥ እስራቱንም ፡ ቈርጠዋል ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ኀጢአታቸው ፡ በዝቷልና ፥ የክዳታቸውም ፡ ብዛት ፡ ጸንቷልና ፤ ስለዚህ ፥ አንበሳ ፡ ከዱር ፡ ወጥቶ ፡ ይሰብራቸዋል ፥ የበረሓም ፡ ተኵላ ፡ ያጠፋቸዋል ፥ ነብርም ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይተጋል ፥ ከዚያም ፡ የሚወጣ ፡ ኹሉ ፡ ይነጠቃል ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 7 ፤ በእነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ይቅር ፡ የምልሽ ፡ እንዴት ፡ አድርጌ ፡ ነው ፧ ልጆችሽ ፡ ትተውኛል ፡ አማልክትም ፡ ባልኾኑ ፡ ምለዋል ፤ ካጠገብኳቸውም ፡ በኋላ ፡ አመነዘሩ ፡ በጋለሞታዎቹም ፡ ቤት ፡ ተሰበሰቡ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 8 ፤ እንደ ፡ ተቀለቡ ፡ ፈረሶች ፡ ኾኑ ፤ እያንዳንዳቸውም ፡ ከባልንጀራዎቻቸው ፡ ሚስቶች ፡ ኋላ ፡ አሸካኩ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 9 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አልቀሥፍምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አትበቀልምን ፧

ኤር. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ቅጥሯ ፡ ወጥታችኹ ፡ አፍርሱ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽማችኹ ፡ አታጥፉ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ አይደሉምና ፡ ቅርንጫፏን ፡ ውሰዱ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 11 ፤ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ወንጅለዋል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ ርሱ ፡ አይደለም ፥ ክፉ ፡ ነገርም ፡ አይመጣብንም ፡ ሰይፍንና ፡ ራብንም ፡ አናይም ፤ ነቢያትም ፡ ነፋስ ፡ ይኾናሉ ፥

ኤር. ፡ 5 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የለም ፥ እንዲህም ፡ ይደረግባቸዋል ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ክደዋል ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተናግራችኋልና ፥ እንሆ ፥ በአፍኽ ፡ ውስጥ ፡ ቃሌን ፡ እሳት ፡ ይህንም ፡ ሕዝብ ፡ ዕንጨት ፡ አደርጋለኹ ፥ ትበላቸውማለች ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ሕዝብን ፡ ከሩቅ ፡ አመጣባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ኀያል ፡ ጥንታዊ ፡ ሕዝብ ፡ ነው ፥ ቋንቋቸውንም ፡ የማታውቀው ፡ የሚናገሩትንም ፡ የማታስተውለው ፡ ሕዝብ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 16 ፤ የፍላጻቸውም ፡ ሰገባ ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ ኀያላን ፡ ናቸው ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 17 ፤ መከርኽንና ፡ እንጀራኽን ፡ ይበላሉ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽንም ፡ ይበሏቸዋል ፤ በጎችኽንና ፡ ላሞችኽንም ፡ ይበላሉ ፤ ወይንኽንና ፡ በለስኽንም ፡ ይበላሉ ፤ የምትታመናቸውን ፡ የተመሸጉ ፡ ከተማዎችን ፡ በሰይፍ ፡ ይደበድባሉ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ፈጽሜ ፡ አላጠፋችኹም ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 19 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፦ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አደረገብን ፧ ብትሉ ፥ አንተ ፦ እንደ ፡ ተዋችኹኝ ፡ በአገራችኹም ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ እንዳመለካችኹ ፥ እንዲሁ ፡ ለእናንተ ፡ ባልኾነ ፡ አገር ፡ ለሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ትገዛላችኹ ፡ ትላቸዋለኽ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ይህን ፡ በያዕቆብ ፡ ቤት ፡ አውሩ ፥ በይሁዳም ፡ አሰሙ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 21 ፤ እናንተ ፡ ሰነፎች ፡ ልበ ፡ ቢሶች ፥ ዐይን ፡ እያላችኹ ፡ የማታዩ ፥ ጐሮም ፡ እያላችኹ ፡ የማትሰሙ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 22 ፤ በእውኑ ፡ እኔን ፡ አትፈሩምን ፧ ከፊቴስ ፡ አትደነግጡምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንዳያልፍ ፡ አሸዋን ፡ በዘለዓለም ፡ ትእዛዝ ፡ ለባሕር ፡ ዳርቻ ፡ አድርጌያለኹ ፤ ሞገዱም ፡ ቢናወጥ ፡ አያሸንፍም ፥ ቢጮኽም ፡ አያልፍበትም ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ የሸፈተና ፡ ያመፀ ፡ ልብ ፡ አላቸው ፤ ዐምፀዋል ፥ ኼደውማል ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 24 ፤ በልባቸውም ፦ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ዝናብ ፡ በጊዜው ፡ የሚሰጠውን ፥ ለመከርም ፡ የተመደቡትን ፡ ወራት ፡ የሚጠብቅልንን ፡ አምላካችንን ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንፍራ ፡ አላሉም ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 25 ፤ በደላችኹ ፡ እነዚህን ፡ አስቀርታለች ፥ ኀጢአታችኹም ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ከለከለቻችኹ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 26 ፤ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ ተገኝተዋል ፤ እንደ ፡ አጥማጆችም ፡ ያደባሉ ፥ ወጥመድንም ፡ ይዘረጋሉ ፡ ሰዎችንም ፡ ያጠምዳሉ ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ቀፎ ፡ ወፎችን ፡ እንደሚሞላ ፥ እንዲሁ ፡ ቤታቸው ፡ ሽንገላን ፡ ሞልታለች ፤ እንዲሁም ፡ ከብረዋል ፡ ባለጠጋዎችም ፡ ኾነዋል ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ወፍረዋል ፡ ሰብተውማል ፥ ክፋታቸውንም ፡ ያለልክ ፡ አብዝተዋል ፤ የድኻ ፡ አደጎች ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ እንዲኾን ፡ አልተሟገቱላቸውም ፥ የችግረኞችንም ፡ ፍርድ ፡ አልፈረዱላቸውም ።

ኤር. ፡ 5 ፡ 29 ፤ በእውኑ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ አልቀሥፍምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡

ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አትበቀልምን ፡፡

ኤር. ፡ 5 ፡ 30 ፤ የምታስደንቅና ፡ የምታስደነግጥ ፡ ነገር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኾናለች ፤

ኤር. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ነቢያት ፡ በሐሰት ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፥ ካህናትም ፡ በእነዚህ ፡ እጅ ፡ ይገዛሉ ፥ ሕዝቤም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ይወዳሉ ፤ በፍጻሜውስ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፡፡

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ኤር. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ የብንያም ፡ ልጆች ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ ታላቅም ፡ ጥፋት ፡ ከሰሜን ፡ ይጐበኛልና ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ሽሹ ፥ በቴቁሔ ፡ መለከቱን ፡ ንፉ ፥ በቤትሐካሪም ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ አንሡ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 2 ፤ የተዋበችውንና ፡ የተሰባቀለችውን ፡ የጽዮንን ፡ ልጅ ፡ አጐሰቍላለኹ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እረኞችና ፡ መንጋዎቻቸው ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ይመጣሉ ፥ በዙሪያዋም ፡ ድንኳኖቻቸውን ፡ ይተክሉባታል ፥ እያንዳንዱም ፡ በስፍራው ፡ መንጋውን ፡ ያሰማራል ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 4 ፤ በርሷ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አዘጋጁ ፥ ተነሡ ፥ በቀትርም ፡ እንውጣ ። ቀኑ ፡ መሸቷልና ፥ የማታውም ፡ ጥላ ፡ ረዝሟልና ፥ ወየ፡ልን ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ተነሡ ፡ በሌሊትም ፡ እንውጣ ፥ አዳራሾቿንም ፡ እናፍርስ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ዛፎቿን ፡ ቍረጡ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ዐፈርን ፡ ደልድሉ ፤ ይህች ፡ ከተማ ፡ የምትቀሠፍ ፡ ናት ፤ መካከሏ ፡ ሹሉ ፡ ግፍ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 7 ፤ በጕድጓድ ፡ ውሃ ፡ እንደሚፈልቅ ፥ እንዲሁ ፡ ክፋቷ ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ ይፈልቃል ፤ ግፍና ፡ ቅሚያ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ ይሰማል ፥ ደዌና ፡ ቍስልም ፡ ሹልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ነፍሴ ፡ ከአንቺ ፡ እንዳትለይ ፥ አንቺንም ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ እንዳላደርግሽ ፥ ተግሣጽን ፡ ተቀበዪ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰው ፡ ወይኑን ፡ እንደሚቃርም ፥ እንዲሁ ፡ ከእስራኤል ፡ የቀሩትን ፡ ፈጽሞ ፡ ይቃርሚቸዋል ፤ እጅኽንም ፡ እንደ ፡ ለቃሚ ፡ ወደ ፡ እንቅብ ፡ ዘርጋ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ይሰሙኝስ ፡ ዘንድ ፡ ለማን ፡ እናገራለኹ ፡፡ ለማንስ ፡ አስጠነቅቃለኹ ፡፡ እንሆ ፥ ገሮሯቸው ፡ ያልተገረዘች ፡ ናት ፡ ለመስማትም ፡ አይችሉም ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለስድብ ፡ ኾኖባቸዋል ፥ ደስም ፡ አያሠኛቸውም ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ተሞልቻለኹ ፤ ከመታገሥ ፡ ደክሜያለኹ ፤ በሜዳ ፡ በሕፃናት ፡ ላይ ፡ በጉልማሳዎችም ፡ ጉባኤ ፡ ላይ ፡ በአንድነት ፡ አፍሰው ፤ ባል ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ ሽማግሌውም ፡ ከጐበዙ ፡ ጋራ ፡ ይያያዛልና ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 12 ፤ እጄን ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹና ፥ ቤቶቻቸው ፡ ዕርሻዎቻቸውም ፡ ሴቶቻቸውም ፡ በአንድነት ፡ ለሌላዎች ፡ ይኾናሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሹሉ ፡ ሥሥትን ፡ ያስባሉና ፥ ከነቢዩም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ካህኑ ፡ ድረስ ፡ ሹሉ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋሉና ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 14 ፤ የሕዝቤንም ፡ ስብራት ፡ በጥቂቱ ፡ ይፈውሳሉ ፤ ሰላም ፡ ሳይኾን ፦ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ዐፍረዋልን ፧ ምንም ፡ አላፈሩም ፥ ዕፍረትንም ፡ አላወቁም ፤ ስለዚህ ፥ ከሚወድቁ ፡ ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ በጐበኘኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይዋረዳሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ቁሙ ፡ ተመልከቱም ፥ የቀደመችውንም ፡ መንገድ ፡ ጠይቁ ፤ መልካሚቱ ፡ መንገድ ፡ ወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዕወቁ ፥ በርሷም ፡ ላይ ፡ ኺዱ ፥ ለነፍሳችኹም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛላችኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ አንኼድባትም ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 17 ፤ እኔም ፦ የመለከቱን ፡ ድምፅ ፡ አድምጡ ፡ ብዬ ፡ ጠባቂዎችን ፡ ሾምኩባችኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ አናደምጥም ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 18 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ስሙ ፤ ማኅበር ፡ ሆይ ፥ እነዚያ ፡ የሚያገኛቸውን ፡ ዕወቁ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ስሚ ፤ እንሆ ፥ ቃሌን ፡ ስላልሰሙ ፥ ሕጌንም ፡ ስለ ፡ ጣሉ ፥ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የዐሳባቸውን ፡ ፍሬ ፥ ክፉን ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ከሳባ ፡ ዕጣንን ፥ ከሩቅም ፡ አገር ፡ ቀረፋን ፡ ታቀርቡልኛላችኹ ፧ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፡ አልቀበለውም ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕታችኹም ፡ ደስ ፡ አያሠኘኝም ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ፊት ፡ ዕንቅፋቶችን ፡ አደርጋለኹ ፤ አባቶችና ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይሰናከሉባቸዋል ፥ ጎረቤትና ፡ ባልንጀራም ፡ ይጠፋሉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ አገር ፡ ይመጣል ፥ ታላቅ ፡ ሕዝብም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣል ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ቀስትንና ፡ ጦርን ፡ ይይዛሉ ፤ ጨካኞች ፡ ናቸው ፥ ምሕረትንም ፡ አያደርጉም ፤ ድምፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ይተማል ፥ በፈረሶችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ወሬውን ፡ ሰምተናል ፥ እጃችን ፡ ደክማለች ፤ ምጥ ፡ ወላድን ፡ ሴት ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡ ይዞናል ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 25 ፤ የጠላት ፡ ሰይፍና ፡ ድንጋጤ ፡ ከዐዋቾኋልና ፥ ወደ ፡ ሜዳ ፡ አትውጡ ፡ በምንገድም ፡ ላይ ፡ አትኺዱ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 26 ፤ የሕዝቤ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ማቅ ፡ ልበሺ ፡ በዐመድም ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለዪ ፤ አጥፊ ፡ በላያችን ፡ በድንገት ፡ ይመጣብናልና ፥ ለአንድያ ፡ ልጅ ፡ እንደሚደረግ ፡ ልቅሶ ፥ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አልቅሺ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 27 ፤ መንገዳቸውን ፡ እንድታውቅና ፡ እንድትፈትን ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ፈታኝ ፡ አድርጌሻለኹ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 28 ፤ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ዐመፀኞች ፡ ናቸው ፤ በጠማማነት ፡ ይኼዳሉ ፤ ናስና ፡ ብረት ፡ ናቸው ፤ ኹሉ ፡ ርኵሰትን ፡ ያደርጋሉ ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ወናፍ ፡ አናፋ ፡ ርሳሱም ፡ በእሳት ፡ ቀለጠ ፤ አንጥረኛውም ፡ መልሶ ፡ በከንቱ ፡ ያቀልጠዋል ፤ ኀጢአተኞች ፡ አልተወገዱም ።

ኤር. ፡ 6 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጥሏቸዋልና ፥ የተጣለ ፡ ብር ፡ ብለው ፡ ይጠሯቸዋል ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 7 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ ቁም ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገር ፦ እግዚአብሔርን ፡ ልታመልኩ ፡ በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ፡ ከይሁዳ ፡ ያላችኹ ፡ ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 3 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ አሳምሩ ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ አሳድራችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያላችኹ ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ አትታመኑ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 5 ፤ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ብታሳምሩ ፥ በሰውና ፡ በጎረቤቱ ፡ መካከል ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ብትፈርዱ ፥

ኤር. ፡ 7 ፡ 6 ፤ መጻተኛውንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ ባትገፉ ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ ባታፈሱ ፥ ክፉም ፡ ሊኾንባችኹ ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ባትከተሉ ፥

ኤር. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ በሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አሳድራችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ በማትረቡበት ፡ በሐሰት ፡ ቃል ፡ ታምናችኋል ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ትሰርቃላችኹ ፥ ትገድላላችኹ ፥ ታመነዝራላችኹ ፥ በሐሰትም ፡ ትምላላችኹ ፥ ለበዓልም ፡ ታጥናላችኹ ፥ የማታውቋቸውንም ፡ እንግዳዎች ፡ አማልክት ፡ ትከተላላችኹ ፤

ኤር. ፡ 7 ፡ 10 ፤ መጣችኹም ፥ ስሜም ፡ በተጠራበት ፡ በዚህ ፡ ቤት ፡ በፊቴ ፡ ቆማችኹ ፦ ይህን ፡ አስጸያፊ ፡ የኾነ ፡ ነገርን ፡ ኹሉ ፡ አላደረግንም ፡ አላችኹ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ይህስ ፡ ስሜ ፡ የተጠራበት ፡ ቤት ፡ በዐይናችኹ ፡ የሌቦች ፡ ዋሻ ፡ ኾኗልን ፧ እንሆ ፥ እኔ ፡ አይቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ስሜን ፡ ወዳሳደርኹበት ፡ በሴሎ ፡ ወደነበረው ፡ ስፍራዬ ፡ ኺዱ ፥ ከሕዝቤም ፡ ከእስራኤል ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ያደረግኹበትን ፡ እዩ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስላደረጋችኹ ፥ በማለዳም ፡ ተነሥቼ ፡ በተናገርኋችኹ ፡ ጊዜ ፡ ስላልሰማችኹ ፥ በጠራኋችኹም ፡ ጊዜ ፡ ስላልመለሳችኹ ፥

ኤር. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ በሴሎ ፡ እንዳደረግኹ ፡ እንዲሁ ፥ ስሜ ፡ በተጠራበት ፥ በምትታመኑበት ፡ ቤት ፥ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ በሰጠኋችኹ ፡ ስፍራ ፡ አደርጋለኹ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 15 ፤ የኤፍሬምንም ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፥ ወንድሞቻችኹን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ጣልኹ ፥ እንዲሁ ፡ ከፊቴ ፡ እጥላችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 16 ፤ እንግዲህም ፡ አልሰማኽምና ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ልመናና ፡ ጸሎት ፡ አታድርግ ፤ አትማልድላቸው ።

ኤር. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እነርሱስ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ውስጥና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉትን ፡ አታይምን ፧

ኤር. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፥ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ዕንጐቻ ፡ እንዲያደርጉ ፡ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡

የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ እንዲያፈሱ ፡ ልጆች ፡ ዕንጨት ፡ ይሰበስባሉ ፥ አባቶችም ፡ እሳት ፡ ያነዳሉ ፥ ሴቶችም ፡ ዱቄት ፡ ይለውሳሉ ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 19 ፤ እኔን ፡ ያስቈጣሉን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለፊታቸውስ ፡ ዕፍረት ፡ አይደለምን ፧

ኤር. ፥ 7 ፥ 20 ፤ እንግዲህም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ቍጣዬና ፡ መዓቴ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፥ በሰውና ፡ በእንስሳ ፡ ላይ ፥ በዱር ፡ ዛፎችና ፡ በምድር ፡ ፍሬ ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ፤ ይነዳል ፥ አይጠፋምም ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለሌላ ፡ መሥዋዕታችኹ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፡ ጨምሩ ፥ ሥጋውንም ፡ ብሉ ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 22 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኋችኹ ፡ ቀን ፡ ስለሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕት ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ አልተናገርኹምና ፥ አላዘዝኋቸውምም ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ፡ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፤ መልካምም ፡ ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ባዘዝኋችኹ ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ኺዱ ፡ ብዬ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አዘዝኋቸው ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በክፉ ፡ ልባቸው ፡ ዐሳብና ፡ እልከኝነት ፡ ኼዱ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ሳይኾን ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙም ፡ ጐሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 25 ፤ አባቶቻችኹ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ከወጡበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፥ በየዕለቱ ፡ እየማለድኹ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ልኬባችኹ ፡ ነበር ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ፡ እንጂ ፡ አልሰሙኝም ፡ ጐሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ፤ አባቶቻቸውም ፡ ካደረጉት ፡ ይልቅ ፡ የባሰ ፡ አደረጉ ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 27 ፤ በዚህም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይሰሙኽም ፤ ትጠራቸውማለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይመልሱልኽም ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 28 ፤ አንተም ፦ የአምላኩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ያልሰማ ፥ ተግሣጽንም ፡ ያልተቀበለ ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እውነት ፡ ጠፍቷል ፡ ከአፋቸውም ፡ ተቈርጧል ፡ ትላቸዋለኽ ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ የቀኑጣውን ፡ ትውልድ ፡ ጥሏልና ፥ ትቶታልምና ፡ ጠጕርሽን ፡ ቍረጪ ፥ ጣዩውም ፥ በወናዎች ፡ ኰረብታዎችም ፡ ላይ ፡ አሙሺ ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 30 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በፊቴ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ሠርተዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ያረክሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኑረዋል ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 31 ፤ እኔም ፡ ያላዘዝኹትንና ፡ በልቤ ፡ ያላሰብኹትን ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ያለችውን ፡ የቶፌትን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠረተዋል ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 32 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ስፍራ ፡ ከማጣት ፡ የተነሣ ፡ በቶፌት ፡ ይቀበራሉና ፡ የዕርድ ፡ ሸለቆ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ቶፌት ፡ ወይም ፡ የሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 33 ፤ የዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ሬሳ ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናል ፥ የሚያስፈራራቸውም ፡ የለም ።

ኤር. ፥ 7 ፥ 34 ፤ ምድሪቱም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለችና ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡

የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፡ አጠፋለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የይሁዳን ፡ ነገሥታት ፡ ዐጥንትና ፡ የመኳንንቶቹን ፡ ዐጥንት ፥ የካህናቱን ፡ ዐጥንትና ፡ የነቢያቱን ፡ ዐጥንት ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ሰዎች ፡ ዐጥንት ፡ ከመቃብራቸው ፡ ያወጣሉ ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 2 ፤ በወደዷቸውና ፡ ባመለኳቸው ፥ በተከተሏቸውና ፡ በፈለጓቸው ፥ በሰገዱላቸውም ፡ በፀሐይና ፡ በጨረቃ ፡ በሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ሹሉ ፡ ፊት ፡ ይዘረጓቸዋል ፤ አያከማቿቸውም ፡ አይቀብሯቸውምም ፥ በምድርም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 3 ፤ እኔም ፡ ባሳደድኋቸው ፡ ስፍራ ፡ ሹሉ ፡ የቀሩ ፥ ከዚች ፡ ክፉ ፡ ወገን ፡ የተረፉ ፡ ቅሬታዎች ፡ ሹሉ ፥ ከሕይወት ፡ ይልቅ ፡ ሞትን ፡ ይመርጣሉ ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 4 ፤ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የወደቁ ፡ አይነሡምን ፧ የሳተስ ፡ አይመለስምን ፧

ኤር. ፥ 8 ፥ 5 ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሕዝብ ፡ ዘወትር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ይመለሳል ፧ ተንኰልን ፡ ይዟል ፡ ሊመለስም ፡ እንቢ ፡ ብሏል ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 6 ፤ አደመጥኹ ፡ ሰማኹም ፤ ቅንን ፡ ነገር ፡ አልተናገሩም ፤ ማናቸውንም ፦ ምን ፡ አድርጌያለኹ ፧ ብሎ ፡ ከክፋቱ ፡ ንስሓ ፡ የገባ ፡ የለም ፤ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ እንደሚሮጥ ፡ ፈረስ ፡ እያንዳንዱ ፡ በየመንገዱ ፡ ይኼዳል ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 7 ፤ ሽመላ ፡ በሰማይ ፡ ጊዜዋን ፡ ዐውቃለች ፤ ዋኖስና ፡ ጨረባ ፡ ዋልያም ፡ የመምጣታቸውን ፡ ጊዜ ፡ ይጠብቃሉ ፤ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ አላወቁም ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 8 ፤ እናንተስ ፦ ጥበበኞች ፡ ነን ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ ትላላችኹ ፧ እንሆ ፥ የጸሓፊ ፡ ብርዕ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፥ በሐሰትም ፡ አድርጓል ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ጥበበኞች ፡ ዐፍረዋል ፥ ደንግጠውማል ፥ ተማርከውማል ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ጥለዋል ፤ ምን ፡ ዐይነት ፡ ጥበብ ፡ አላቸው ፧

ኤር. ፥ 8 ፥ 10 ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሹሉ ፡ ሥሥትን ፡ ያስባሉና ፥ ከነቢዩም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ካህኑ ፡ ድረስ ፡ ሹሉ ፡ በተንኰል ፡ ያደርጋሉና ፡ ስለዚህ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ለሌላዎች ፥ ዕርሻቸውንም ፡ ለሚወርሱባቸው ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 11 ፤ የሕዝቤንም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስብራት ፡ በጥቂቱ ፡ ይፈውሳሉ ፤ ሰላም ፡ ሳይኾን ፦ ሰለም ፡ ሰላም ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 12 ፤ አስጸያፊ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ ዐፍረዋልን ፧ ምንም ፡ አላፈሩም ፥ ዕፍረትንም ፡ አላወቁም ፤ ስለዚህ ፥ ከሚወድቁ ፡ ጋራ ፡ ይወድቃሉ ፤ በጐበኘኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ይዋረዳሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 13 ፤ ፈጽሜ ፡ አጠፋቸኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በወይን ፡ ላይ ፡ ፍሬ ፥ በበለስ ፡ ዛፍ ፡ ላይ ፡ በለስ ፡ አይኾንም ፥ ቅጠልም ፡ ይረግፋል ፤ የሚያልፉባቸውንም ፡ ሰጠኋቸው ።

ኤር. ፥ 8 ፥ 14 ፤ ዝም ፡ ብለን ፡ ለምን ፡ እንቀመጣለን ፧ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ በደልን ፡ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ አጥፍቶናልና ፥ የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጥቶናልና ፥ ተሰብስባችኹ ፡ ወደተመሸጉ ፡ ከተማዎች ፡ እንግባ ፥ በዚያም ፡ እንጥፋ ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ሰላምን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ መልካምም ፡ አልተገኘም ፤ መጠገንን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ እንሆም ፥ ድንጋጤ ፡ ኾነ ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 16 ፤ የፈረሰኞቹ ፡ ድምፅ ፡ ከዳን ፡ ተሰማ ፤ ከዐርበኞች ፡ ፈረሶች ፡ ማሽካካት ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ተንቀጠቀጠች ፤ መጡም ፡ ምድሪቱንና ፡ በርሷም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፥ ከተማዪቱንና ፡ የተቀመጡባትንም ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 17 ፤ እንሆ ፥ አስማት ፡ የማይከለክላቸውን ፡ እባቦችንና ፡ እፍኝቶችን ፡ እሰድ፡ባ፡ኻለኹ ፤ እነርሱም ፡ ይነድፏ፡ኻል ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ሐዘኔ ፡ የማይጽናና ፡ ነው ፥ ልቤም ፡ በውስጤ ፡ ደክሟል ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እንሆ ፦ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ የለምን ፧ ወይስ ፡ ንጉሧ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ የለምን ፧ የሚል ፡ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ ከሩቅ ፡ አገር ፡ ተሰማ ። በተቀረጹ ፡ ምስሎቻቸውና ፡ በባዕድ ፡ ከንቱነትስ ፡ ያስቈጡኝ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 8 ፡ 20 ፤ መከሩ ፡ ዐልፏል ፥ በጋው ፡ ኼዷል ፥ እኛም ፡ አልዳ፡ንም ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 21 ፤ በሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ስብራት ፡ እኔ ፡ ተሰብሬያለኹ ፡ ጠቍሬማለኹ ፤ አድናቆትም ፡ ይዞኛል ።

ኤር. ፡ 8 ፡ 22 ፤ በገለዓድ ፡ የሚቀባ ፡ መድኀኒት ፡ የለምን ፧ ወይስ ፡ በዚያ ፡ ሐኪም ፡ የለምን ፧ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ፈውስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አልኾነም ፧

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ኤር. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ተወግተው ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ስለሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሰዎች ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ አለቅስ ፡ ዘንድ ፡ ራሴ ፡ ውሃ ፥ ዐይኔም ፡ የእንባ ፡ ምንጭ ፡ በኾነልኝ! ፡

ኤር. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ኹሉም ፡ አመንዝራዎች ፥ የአታላዮች ፡ ጉባኤ ፡ ናቸውና ፥ ሕዝቤን ፡ እተዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱም ፡ እለይ ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የመንገደኞች ፡ ማደሪያን ፡ ማን ፡ በሰጠኝ ፧

ኤር. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ምላሳቸውን ፡ ስለ ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡ ቀስት ፡ ገተሩ ፤ በምድር ፡ በረቱ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለእውነት ፡ አይደለም ፤ ከክፋት ፡ ወደ ፡ ክፋት ፡ ይኼዳሉና ፡ እኔንም ፡ አላወቁምና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ወንድምም ፡ ኹሉ ፡ ያሰናክላልና ፥ ባልንጀራም ፡ ኹሉ ፡ ያማልና ፥ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ከባልንጀራዎቻችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፥ በወንድሞቻችኹም ፡ አትታመኑ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ባልንጀራውን ፡ ያታልላል ፥ በእውነትም ፡ አይናገርም ፤ ሐሰትን ፡ መናገርንም ፡ ምላሳቸው ፡ ተምሯል ፥ ክፉንም ፡ ለማድረግ ፡ ይደክማሉ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ማደሪያኽ ፡ በሽንገላ ፡ መካከል ፡ ነው ፥ ከሽንገላም ፡ የተነሣ ፡ እኔን ፡ ያውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ አቀልጣቸዋለኹ ፡ እፈትናቸውማለኹ ፤ ስለሕዝቤ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ክፋት ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ የማደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ምላሳቸው ፡ የተሳለ ፡ ፍላጻ ፡ ነው ፤ ሽንገላን ፡ ይናገራሉ ፡ ሰው ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ይናገራል ፥ በልቡ ፡ ግን ፡ ያደባበታል ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 9 ፤ በእውኑ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አልቀሥፍምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነፍሴስ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አትበቀልምን ፧

ኤር. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ለተራራዎች ፡ ልቅሶን ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ ማሰማሪያዎችም ፡ ዋይታን ፡ አነሣለኹ ፥ ሰው ፡ እንዳያልፍባቸው ፡ በእሳት ፡ ተቃጥለዋልና ። ሰዎችም ፡ የከብቱን ፡ ድምፅ ፡ አይሰሙም ፤ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ሸሽተው ፡ ኼደዋል ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ የቀበሮም ፡ ማደሪያ ፡ አደርጋታለኹ ፥ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፡ ሰው ፡ የማይቀመጥባት ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ይህን ፡ የሚያስተውል ፡ ጠቢብ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ያወራስ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ለማን ፡ ተናገረ ፧ ሰው ፡ እንዳያልፍባት ፡ ምድርስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ጠፋች ፥ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቃጠለች ፧

ኤር. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የሰጠኋቸውን ፡ ሕጌን ፡ ትተዋልና ፥ ቃሌንም ፡ አልሰሙምና ፥

ኤር. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የልባቸውን ፡ ምኞትና ፡ አባቶቻቸው ፡ ያስተማሯቸውን ፡ በዓሊምን ፡ ተከትለዋልና ፥

ኤር. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህን ፡ ሕዝብ ፡ ሬትን ፡ አበላዋለኹ ፡ የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጣዋለኹ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 16 ፤ እነርሱና ፡ አባቶቻቸውም ፡ ባላወቋቸው ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ እበትናቸዋለኹ ፥ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ በስተኋላቸው ፡ ሰይፍን ፡ እሰድባቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲመጡ ፡ አልቃሾች ፡ ሴቶችን ፡ ጥሩ ፤ እንዲመጡም ፡ ወደ ፡ ብልኀተኞች ፡ ሴቶች ፡ ላኩ ፤

ኤር. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ዐይኖቻችንም ፡ እንባ ፡ እንዲያፈሱ ፡ የዐይናችንም ፡ ሽፋሽፍቶች ፡ ውሃን ፡ እንዲያፈልቁ ፡ ፈጥነው ፡ ለእኛ ፡ ልቅሶውን ፡ ይያዙ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 19 ፤ በጽዮን ፦ እንዴት ፡ ተበዘበዝን! ፡ ምድርንም ፡ ትተናልና ፥ ቤቶቻችንንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ እንዴት ፡ ዐፈርን! ፡ የሚል ፡ የልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ሴቶች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፥ ጐሯችኹም ፡ የአፉን ፡ ቃል ፡ ትቀበል ፥ ለሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ልቅሶውን ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ ለባልንጀራዎቻችኹ ፡ ዋይታውን ፡ አስተምሩ ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ሕፃናቱን ፡ ከመንገድ ፡ ጕልማሳዎቹንም ፡ ከአደባባይ ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ መስኮታችን ፡ ደርሷል ፡ ወደ ፡ አዳራሻችንም ፡ ውስጥ ፡ ገብቷል ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 22 ፤ የሰውም ፡ ሬሳ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ በዕርሻ ፡ ላይ ፥ ማንምም ፡ እንደማይሰበስበው ፡ ከዐጫጆች ፡ በኋላ ፡ እንደሚቀር ፡ ቃርሚያ ፡ ይወድቃል ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 23 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጠቢብ ፡ በጥበቡ ፡ አይመካ ፥ ኀያልም ፡ በኀይሉ ፡ አይመካ ፥ ባለጠጋም ፡ በብልጥግናው ፡ አይመካ ፤

ኤር. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚመካው ፦ ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ ጽድቅንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የማደርግ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ መኾኔን ፡ በማወቁና ፡ በማስተዋሉ ፡ በዚህ ፡ ይመካ ፤ ደስ ፡ የሚያሠኙኝ ፡ እነዚህ ፡ ናቸውና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 9 ፡ 25-26 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ያልተገረዙ ፡ ናቸውና ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ልባቸው ፡ ያልተገረዘ ፡ ነውና ፥ የተገረዙትን ፡ ኹሉ ፥ ግብጽንና ፡ ይሁዳን ፡ ኤዶምያስንም ፡ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ ሞዐብንም ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ የተቀመጡትን ፡ ጠጕራቸውን ፡ በዙሪያ ፡ የተላጨትን ፡ ኹሉ ፥ ባለመገረዛቸው ፡ እነርሱን ፡ የምቀጣበት ፡ ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 1 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሕዛብን ፡ መንገድ ፡ አትማሩ ፡ ከሰማይ ፡ ምልክትም ፡ አትፍሩ ፤ አሕዛብ ፡ ይፈሩታልና ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 3 ፤ የአሕዛብ ፡ ልማድ ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፤ ዛፍ ፡ ከዱር ፡ ይቈረጣል ፥ በሠራተኛም ፡ እንጅ ፡ በመጥረቢያ ፡ ይሠራል ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 4 ፤ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ያስጌጡታል ፥ እንዳይናወጥም ፡ በችንካርና ፡ በመዶሻ ፡ ይቸነክሩታል ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 5 ፤ እንደ ፡ ተቀረጸ ፡ ዐምድ ፡ ናቸው ፥ እነርሱም ፡ አይናገሩም ፤ መራመድም ፡ አይቻላቸውምና ፥ ይሸከሟቸዋል ። ክፉ ፡ መሥራትም ፡ አይቻላቸውምና ፥ ደግሞም ፡ መልካም ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፡ አትፍሯቸው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 6 ፤ አቤቱ ፥ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ የለም ፤ አንተ ፡ ታላቅ ፡ ነኽ ፥ ስምኽም ፡ በኀይል ፡ ታላቅ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 7 ፤ የአሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በአሕዛብ ፡ ጥበበኞች ፡ ዘንድ ፡ መካከል ፡ በመንግሥታቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ ስለሌለ ፥ አንተን ፡ መፍራት ፡ ይገባልና ፥ አንተን ፡ የማይፈራ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፥ 10 ፥ 8 ፤ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰንፈዋል ፥ ደንቍረውማል ፤ ጣዖታት ፡ የሚያስተምሩት ፡ የዕንጨት ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 9 ፤ የሠራተኛና ፡ የአንጥረኛ ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ የኾነ ፡ ከተርሴስ ፡ ጥፍጥፍ ፡ ብር ፡ ከአፌዝም ፡ ወርቅ ፡ ይመጣል ፤ ልብሳቸውም ፡ ሰማያዊና ፡ ቀይ ፡ ግምጃ ፡ ነው ፥ ዘዘኑም ፡ የብልኀተኞች ፡ ሥራ ፡ ናቸው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ሕያው ፡ አምላክና ፡ የዘለዓለም ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ ከቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ትንቀጠቀጣለች ፤ አሕዛብም ፡ መዓቱን ፡ አይችሉም ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 11 ፤ እናንተም ፦ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ያልፈጠሩ ፡ እነዚህ ፡ አማልክት ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ይጠፋሉ ፡ ትሏቸዋላችኹ ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 12 ፤ ምድርን ፡ በኀይሉ ፡ የፈጠረ ፥ ዓለሙን ፡ በጥበቡ ፡ የመሠረተ ፡ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡ የዘረጋ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 13 ፤ ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ ውሃዎች ፡ በሰማይ ፡ ይሰበሰባሉ ፥ ከምድርም ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፤ ለዝናቡም ፡ መብረቅን ፡ ያደርጋል ፥ ነፋስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ ያወጣል ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 14 ፤ ሰው ፡ ዘሉ ፡ ዕውቀት ፡ ዐጥቶ ፡ ሰንፏል ፥ አንጥረኛም ፡ ዘሉ ፡ ከቀረጸው ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡ አፍሯል ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፥ እስትንፋስም ፡ የላቸውምና ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 15 ፤ እነርሱ ፡ ምናምንቴና ፡ የቀልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፤ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋሉ ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 16 ፤ የያዕቆብ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ አይደለም ፤ ርሱ ፡ የዘሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ነውና ፤ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፡ ነገድ ፡ ነውና ፤ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 17 ፤ በምሽግ ፡ ውስጥ ፡ የተቀመጥሽ ፡ ሆይ ፥ ዕቃሽን ፡ ከመሬት ፡ ሰብስቢ ፤

ኤር. ፥ 10 ፥ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ በምድሪቱ ፡ የሚኖሩትን ፡ እስኪሰማቸው ፡ ድረስ ፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እወነጐፋቸዋለኹ ፥ አስጨንቃቸውማለኹ ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 19 ፤ ስለ ፡ ስብራቴ ፡ ወዮልኝ! ፡ ቍስሌም ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፦ በእውነት ፡ የመከራ ፡ ቍስሌ ፡ ነው ፥ ርሱንም ፡ መሸከም ፡ ይገባኛል ፡ አልኹ ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 20 ፤ ድንኳኔ ፡ ተበዘበዘ ፡ አውታሬም ፡ ኹሉ ፡ ተቈረጠ ፤ ልጆቼም ፡ ከእኔ ፡ ወጥተው ፡ አይገኙም ፤ ድንኳኔንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚዘረጋ ፡ መጋረጃዎችንም ፡ የሚያነሣ ፡ የለም ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 21 ፤ እረኞች ፡ ሰንፈዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ አልጠየቁትምና ፡ አልተከናወነላቸውም ፥ መንጋዎቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ተበትነዋል ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 22 ፤ የወሬን ፡ ድምፅ ፡ ስሙ ፤ እንሆም ፥ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ባድማና ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ጽኑ ፡ ሽብር ፡ መጥቷል ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 23 ፤ አቤቱ ፥ የሰው ፡ መንገድ ፡ ከራሱ ፡ እንዳይደለ ፡ ዐውቃለኹ ፥ አካኼዱንም ፡ ለማቅናት ፡ ከሚራመድ ፡ ሰው ፡ አይደለም ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 24 ፤ አቤቱ ፥ ቅጣኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳታዋርደኝ ፡ በመጠን ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ በቀጣ ፡ አይኹን ።

ኤር. ፥ 10 ፥ 25 ፤ ያዕቆብን ፡ በልተውታልና ፥ ውጠውትማልና ፥ አጥፍተውትማልና ፥ ማደሪያውንም ፡ አፍርሰዋልና ፥ በማያውቁኽ ፡ አሕዛብ ፡ ስምኽንም ፡ በማይጠሩ ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ መዓትኽን ፡ አፍስ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 11 ፥ 2 ፤ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስማ ፥ ለይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ተናገር ፥

ኤር. ፥ 11 ፥ 3-4 ፤ እንደዚህም ፡ በላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ከብረት ፡ ምድጃ ፡ ባወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ያዘዝኹትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ የማይሰማ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፤ አልኹም ፦ ቃሌን ፡ ስሙ ፥ ያዘዝኋችኹንም ፡ ኹሉ ፡ አድርጉ ፤ እንዲሁም ፡ እናንተ ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 5 ፤ ይህም ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የምታፈሰውን ፡ ምድር ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ የማልኹትን ፡ መሐላ ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ ነው ። እኔም ፦ አቤቱ ፥ አሜን ፡ ብዬ ፡ መለስኩለት ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ይህችን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ አድርጉትም ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 7 ፤ አባቶቻችኹን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ካወጣኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፥ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ እያስጠነቀቅኹ ። ቃሌን ፡ ስሙ ፡ በማለት ፡ አስጠንቅቄያቸው ፡ ነበር ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 8 ፤ እነርሱ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ በክፉ ፡ ልባቸው ፡ እልከኝነት ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፥ አልሰሙም ፥ ጐሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ፤ ስለዚህ ፥ ያዘዝኋቸውን ፡ እነርሱም ፡ ያላደረጉትን ፡ የዚህን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ አመጣኹባቸው ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ በይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ዐድማ ፡ ተገኝቷል ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 10 ፤ ቃሌንም ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ወዳሉ ፡ ወዳባቶቻቸው ፡ ኀጢአት ፡

ተመለሱ ፥ ያመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎችን ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፤ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አፈረሱ ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሊያመልጡት ፡ የማይችሉትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ይጮኻሉ ፤ እኔም ፡ አልሰማቸውም ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 12 ፤ በይሁዳም ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ኼደው ፡ ወደሚያጥኑላቸው ፡ አማልክት ፡ ይጮኻሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከቶ ፡ አያድኗቸውም ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 13 ፤ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አማልክትኽ ፡ እንደ ፡ ከተማዎችኽ ፡ ቍጥር ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መንገዶች ፡ ቍጥር ፡ ለነውረኛ ፡ ነገር ፡ መሠዊያ ፥ ርሱም ፡ ለበዓል ፡ ታጥኑበት ፡ ዘንድ ፡ መሠዊያ ፥ አድርጋችኋል ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 14 ፤ አንተም ፡ ስለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አትጸልይ ፤ ከመከራቸው ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ በጮኹ ፡ ጊዜ ፡ አልሰማቸውምና ፡ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ጩኸትና ፡ ልመና ፡ አታድርግ ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 15 ፤ ወዳጄ ፡ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ አላት ፧ ስእለት ፡ ወይም ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ ክፋትሽን ፡ ከአንቺ ፡ ያስወግዳልን ፧ ወይስ ፡ በእነዚህ ፡ ታመልጣለሽን ፧

ኤር. ፥ 11 ፥ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስምሽን ፦ በመልካም ፡ ፍሬ ፡ የተዋበች ፡ የለመለመች ፡ የወይራ ፡ ዛፍ ፡ ብሎ ፡ ጠራው ፤ በጽኑ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ጩኸት ፡ እሳትን ፡ አነደደባት ፥ ቅርንጫፎቿም ፡ ተሰብረዋል ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 17 ፤ ለበዓልም ፡ በማጠናቸው ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ለራሳቸው ፡ ስለሠሯት ፡ ስለእስራኤልና ፡ ስለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ክፋት ፡ የተከለሽ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ተናግሮብሻል ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አስታወቀኝ ፡ እኔም ፡ ዐወቅኹ ፤ ሥራቸውንም ፡ ገለጥኽልኝ ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 19 ፤ እኔም ፡ ለመታረድ ፡ እንደሚነዳ ፡ እንደ ፡ የዋህ ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ ኾንኹ ፤ እነርሱም ፦ ዛፉን ፡ ከፍሬው ፡ ጋራ ፡ እንቍረጥ ፥ ስሙም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይታሰብ ፡ ከሕያዋን ፡ ምድር ፡ እናጥፋው ፡ ብለው ፡ ምክርን ፡ እንዳሰቡብኝ ፡ አላወቅኹም ፡ ነበር ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 20 ፤ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትፈትን ፡ በቅንም ፡ የምትፈርድ ፡ አቤቱ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክርክሬን ፡ ገልጬልኻለኹና ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የሚኾን ፡ በቀልኽን ፡ ለይ ።

ኤር. ፥ 11 ፥ 21 ፤ ስለዚህም ፦ በእጃችን ፡ እንዳትሞት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ አትናገር ፡ ብለው ፡ ነፍስኽን ፡ ስለሚሹ ፡ ስለዐናቶት ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እቀጣቸዋለኹ ፤

ኤር. ፥ 11 ፥ 22 ፤ ጐበዛዝታቸው ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታሉ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውም ፡ በራብ ፡ ይሞታሉ ፤ በምጐበኛቸውም ፡ ዓመት ፡ በዐናቶት ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አመጣባቸዋለኹና ፡ ማንም ፡ ከነርሱ ፡ የሚቀር ፡ የለም ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ኤር. ፥ 12 ፥ 1 ፤ አቤቱ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በተሟገትኹ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ፍርድ ፡ ልናገር ። የኀጢአተኞች ፡ መንገድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይቃናል ፧ በደልንስ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ደኅንነት ፡ ይኾናል ፧

ኤር. ፥ 12 ፥ 2 ፤ ተክለኻቸዋል ፤ ሥር ፡ ሰደዋል ፤ አድገዋል ፡ አፍርተውማል ፤ በአፋቸው ፡ አንተ ፡ ቅርብ ፡ ነኽ ፥ ከልባቸው ፡ ግን ፡ ሩቅ ፡ ነኽ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 3 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ዐውቀኸኛል ፤ አይተኸኛል ፥ ልቤንም ፡ በፊትህ ፡ ፈትነኻል ፤ እንደ ፡ በጎች ፡ ለመታረድ ፡ ጐትተኽ ፡ ለያቸው ፥ ለመታረድም ፡ ቀን ፡ አዘጋጃቸው ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ምድሪቱ ፡ የምታለቅሰው ፥ የአገሩ ፡ ሣርስ ፡ ኹሉ ፡ የሚደርቀው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ። የተቀመጡባት ፡ ሰዎች ፦ ፍጻሜያችንን ፡ አያይም ፡ ብለዋልና ፥ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ እንስሳዎችና ፡ ወፎች ፡ ጠፍተዋል ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ከእግረኞች ፡ ጋራ ፡ በሮጥኽ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ቢያደክሙኽ ፥ ከፈረሶች ፡ ጋራ ፡ መታገል ፡ እንዴት ፡ ትችላለኽ ። በሰላምም ፡ ምድር ፡ ታምነኽ ፡ ብትቀመጥ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ እንዴት ፡ ታደርጋለኽ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ወንድሞችኽና ፡ የአባትኽ ፡ ቤት ፡ እነርሱ ፡ ጭምር ፡ አታሉ ውኻልና ፥ በኋላኽም ፡ ጮኸዋልና ፤ በመልካምም ፡ ቢናገሩኽም ፡ አትታመናቸው ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ቤቴን ፡ ትቻለኹ ፡ ርስቴንም ፡ ጥያለኹ ፥ ነፍሴም ፡ የምትወዳትን ፡ በጠላቶቿ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ርስቴ ፡ በዱር ፡ እንዳለ ፡ አንበሳ ፡ ኾናብኛለች ፤ ድምፂን ፡ አንሥታብኛለች ፤ ስለዚህ ፥ ጠልቻታለኹ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ርስቴ ፡ እንደ ፡ ዝንጉርጉር ፡ አሞራ ፡ ኾነችብኝን ። አሞሮችስ ፡ በዙሪያዋና ፡ በላይዋ ፡ ኾነዋልን ። ኺዱ ፥ የምድር ፡ አራዊትን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቡ ፥ ይበሉም ፡ ዘንድ ፡ አምጧቸው ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ እረኞች ፡ የወይኑን ፡ ቦታዬን ፡ አጥፍተዋል ፥ ዕድል ፡ ፈንታዬንም ፡ ረግጠዋል ፤ የአምሮቴን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አድርገውታል ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ባድማ ፡ አድርገውታል ፥ ፈርሶም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ያለቅሳል ፤ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፡ በልቡም ፡ የሚያስባት ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በወናዎች ፡ ኰረብታዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በዝባዥች ፡ መጥተዋል ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ይበላልና ፤ ለሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ሰላም ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ስንዴን ፡ ዘሩ ፡ ሾኽንም ፡ ዐጨዱ ፤ ደከሙ ፥ ምንም ፡ አልረባቸውም ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ከፍሬያችኹ ፡ ታፍራላችኹ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሕዝቤ ፡ ለእስራኤል ፡ ያወረስኹትን ፡ ርስት ፡ ለሚነኩት ፡ ክፉዎች ፡ ጎረቤቶች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ከምድራቸው ፡ እነቅላቸዋለኹ ፥ የይሁዳንም ፡ ቤት ፡ ከመካከላቸው ፡ እነቅለዋለኹ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ከነቀልኋቸውም ፡ በኋላ ፡ መልሼ ፡ እምራቸዋለኹ ፥ እያንዳንዱንም ፡ ወደ ፡ ርስቱ ፡ እያንዳንዱንም ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ እመልሳለኹ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 16 ፤ በበዓል ፡ ይምሉ ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቤን ፡ እንዳስተማሩ ፡ በስሜ ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ብለው ፡ ይምሉ ፡ ዘንድ ፡ የሕዝቤን ፡ መንገድ ፡ በትጋት ፡ ቢማሩ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ ይመሠረታሉ ።

ኤር. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ባይሰሙኝ ፡ ግን ፡ ያን ፡ ሕዝብ ፡ ፈጽሜ ፡ እነቅለዋለኹ ፡ አጠፋውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ኤር. ፡ 13 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ ኺድ ፥ ከተልባ ፡ እግር ፡ የተሠራችን ፡ መታጠቂያ ፡

ለአንተ ፡ ግዛ ፥ ወገብኽንም ፡ ታጠቅባት ፤ በውሃውም ፡ ውስጥ ፡ አትንከራት ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 2 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ መታጠቂያን ፡ ገዛኹ ፡ ወገቤንም ፡ ታጠቅኹባት ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 3-4 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፦ የገዛኻትን ፡ በወገብኽ ፡ ያለችውን ፡ መታጠቂያ ፡ ወስደኽ ፡ ተነሥ ፥ ወደ ፡ ኤፍራጥስም ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ በተሠነጠቀ ፡ አለት ፡ ውስጥ ፡ ሸሽጋት ፡ የሚል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መጣልኝ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ኼድኹ ፡ በኤፍራጥስም ፡ አጠገብ ፡ ሸሸግኋት ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 6 ፤ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔር ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ ትሸሸጋት ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ መታጠቂያ ፡ ከዚያ ፡ ውስጥ ፡ ውሰድ ፡ አለኝ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 7 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ኤፍራጥስ ፡ ኼድኹ ፡ ቈፈርኹም ፥ ከሸሸግኹበትም ፡ ስፍራ ፡ መታጠቂያዉቱን ፡ ወሰድኹ ። እንሆም ፥ መታጠቂያዉቱ ፡ ተበላሽታ ፡ ነበር ፥ ለምንም ፡ አልረባችም ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፤

ኤር. ፥ 13 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲሁ ፡ የይሁዳን ፡ ትዕቢት ፡ ታላቁንም ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ትዕቢት ፡ አበላሻለኹ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 10 ፤ ቃሌን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ የሚሉ ፥ በልባቸውም ፡ እልከኝነት ፡ የሚኼዱ ፥ ያመልኳቸውና ፡ ይሰግዱላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ የሚከተሉ ፡ እነዚህ ፡ ክፉ ፡ ሕዝብ ፡ አንዳች ፡ እንዳማትረባ ፡ እንደዚች ፡ መታጠቂያ ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 11 ፤ መታጠቂያ ፡ በሰው ፡ ወገብ ፡ ላይ ፡ እንደምትጣበቅ ፥ እንዲሁ ፡ ሕዝብና ፡ ስም ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ ይኾኑልኝ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳንም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አጣብቄያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰሙም ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 12 ፤ ስለዚህ ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ማድጋ ፡ ኹሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይሞላል ፡ ብለኽ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፤ እነርሱም ፦ ማድጋ ፡ ኹሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዲሞላ ፡ በእውኑ ፡ እኛ ፡ አናውቅምን ፧ ይሉኻል ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 13 ፤ አንተም ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በዚች ፡ ምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፥ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡትን ፡ ነገሥታት ፡ ካህናቱንም ፡ ነቢያቱንም ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡትን ፡ ኹሉ ፡ በስካር ፡ እሞላቸዋለኹ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 14 ፤ ሰውንም ፡ በሰው ፡ ላይ ፥ አባቶችንና ፡ ልጆችን ፡ ባንድ ፡ ላይ ፥ እቀጠቅጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አጠፋቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልራራም ፥ አላዝንም ፥ አልምርም ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 15 ፤ ስሙ ፥ አድምጡ ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ አትታበዩ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 16 ፤ ሳትጨልም ፡ እግራችኹም ፡ በጨለመችው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሳትሰናከል ፥ በተስፋ ፡ የምትጠባበቁትን ፡ ብርሃን ፡ ለሞት ፡ ጥላና ፡ ለድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ሳይለውጠው ፡ ለአምላካችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብርን ፡ ስጡ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 17 ፤ ይህን ፡ ባትሰሙ ፡ ነፍሴ ፡ ስለ ፡ ትዕቢታችኹ ፡ በስውር ፡ ታለቅሳለች ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንጋ ፡ ተማርኳልና ፥ ዐይኔ ፡ ታነባለች ፥ እንባንም ፡ ታፈሳለች ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 18 ፤ ለንጉሡና ፡ ለንጉሥ ፡ እናት ፡ ለእቴጌዉቱ ፦ የክብራችኹ ፡ አክሊል ፡ ከራሳችኹ ፡

ወርቂልና ፥ ተዋርዳችኹ ፡ ተቀመጡ ፡ በል ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 19 ፤ የደቡብ ፡ ከተማዎች ፡ ተዘግተዋል ፥ የሚከፍታቸውም ፡ የለም ፤ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ተማርኳል ፥ ፈጽሞ ፡ ተማርኳል ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 20 ፤ ዐይናችኹን ፡ አንሥታችኹ ፡ እነዚህን ፡ ከሰሜን ፡ የሚመጡትን ፡ ተመልከቱ ፤ ለአንቺ ፡ የተሰጠ ፡ መንጋ ፥ የተዋበ ፡ መንጋሽ ፥ ወዴት ፡ አለ ፧

ኤር. ፥ 13 ፥ 21 ፤ ወዳጆችሽ ፡ እንዲኾኑ ፡ ያስተማርሻቸውን ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ አለቃዎች ፡ ባደረጋቸው ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ትያለሽ ፧ እንደ ፡ ወላድ ፡ ሴት ፡ ምጥ ፡ አይዝሽምን ፧

ኤር. ፥ 13 ፥ 22 ፤ በልብሽም ፦ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ደረሰብኝ ፧ ብትዪ ፥ ከኀጢአትሽ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የልብስሽ ፡ ዘርፍ ፡ ተገልጧል ፡ ተረከዝሽም ፡ ተገፈ፟ል ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 23 ፤ በእውኑ ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ መልኩን ፡ ወይስ ፡ ነብር ፡ ዝንጕርጕርነትን ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልን ፧ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ክፋትን ፡ የለመዳችኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በጎ ፡ ለማድረግ ፡ ትችላላችኹ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 24 ፤ ስለዚህ ፥ እንደሚያልፍ ፡ እብቅ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ነፋስ ፡ እበትናቸዋለኹ ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 25 ፤ ረስተሽኛልና ፥ በሐሰትም ፡ ታምነሻልና ፥ ዕጣሽ ፡ የለካኹልሽም ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 26 ፤ ስለዚህም ፡ የልብስሽን ፡ ዘርፍ ፡ በፊትሽ ፡ እገልጣለኹ ፡ ዕፍረትሽም ፡ ይታያል ።

ኤር. ፥ 13 ፥ 27 ፤ አስጸያፊ ፡ ሥራሽን ፥ ምንዝርናሽን ፥ ማሽካካትሽን ፥ የግልሙትናሽንም ፡ መዳራት ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ በሜዳም ፡ አይቻለኹ ። ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ወዮልሽ! ፡ ለመንጻት ፡ እንቢ ፡ ብለሻል ፤ ይህስ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 1 ፤ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ ስለ ፡ ድርቅ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 14 ፥ 2 ፤ ይሁዳ ፡ አለቀሰች ፥ ደጆቿም ፡ ባዶ ፡ ኾኑ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ጨለሙ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ጩኸት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏል ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 3 ፤ ታላላቆችም ፡ ብላቴናዎቻቸውን ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ሰደዱ ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ መጡ ፡ ውሃም ፡ አላገኙም ፥ ዕቃቸውንም ፡ ባዶውን ፡ ይዘው ፡ ተመለሱ ፤ ዐፈሩም ፡ ተዋረዱም ፡ ራሳቸውንም ፡ ተከናነቡ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 4 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ አልዘነበምና ፡ መሬቱ ፡ ስንጥቅጥቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ዐራሾች ፡ ዐፈሩ ፥ ራሳቸውንም ፡ ተከናነቡ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 5 ፤ ዋላ ፡ ደግሞ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወለደች ፥ ሣርም ፡ የለምና ፡ ግልገሏን ፡ ተወች ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 6 ፤ የሜዳ ፡ አህያዎችም ፡ በወና ፡ ኰረብታ ፡ ላይ ፡ ቆመዋል ፥ እንደ ፡ ቀበሮም ፡ ወደ ፡ ነፋስ ፡ አለከለኩ ፤ ልምላሜም ፡ የለምና ፡ ዐይኖቻቸው ፡ ጠወለጉ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 7 ፤ አቤቱ ፥ ኀጢአታችን ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ባንተም ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ ኀጢአታችን ፡ ይመሰክርብናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ብለኽ ፡ አድርግ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 8 ፤ አንተ ፡ የእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ሆይ ፡ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ የምታድነው ፥ በምድር ፡ እንደ ፡

እንግዳ ፥ ወደ ፡ ማደሪያ ፡ ዘወር ፡ እንደሚል ፡ መንገደኛ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትኾናለኽ ፧

ኤር. ፥ 14 ፥ 9 ፤ እንዳንቀላፋ ፡ ሰው ፡ ሰው ፥ ያድንም ፡ ዘንድ ፡ እንደማይችል ፡ ኀያል ፡ ስለ ፡ ምን ፡
ትኾናለኽ ፧ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ በመካከላችን ፡ ነኽ ፡ እኛም ፡ በስምኽ ፡ ተጠርተናል ፤ አትተወን ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መቅበዝበዝን ፡ ወደዋል ፥ እግራቸውንም ፡
አልከለከሉም ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእነርሱ ፡ ደስ ፡ አይለውም ፥ በደላቸውንም ፡ አኹን ፡
ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቀጣል ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ አትጸልይላቸው ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 12 ፤ በጾሙ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎታቸውን ፡ አልሰማም ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡
ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ አልቀበላቸውም ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ አጠፋቸዋለኹ ፡ አለኝ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 13 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ እንሆ ፥ ነቢያት ። በእውነት ፡ ሰላምን ፡ በዚህ ፡
ስፍራ ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ ሰይፍን ፡ አታዩም ፥ ራብም ፡ አያገኛችኹም ፡ ይሏቸዋል ፡ አልኹ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ነቢያቱ ፡ ውሸት ፡ በስሜ ፡ ትንቢት ፡
ይናገራሉ ፤ አላክኋቸውም ፥ አላዘዝኋቸውም ፥ አልተናገርኋቸውም ፤ የውሸቱን ፡ ራእይ ፡ ሟርትንም ፡ ከንቱንም ፡ ነገር ፡
የልባቸውንም ፡ ሽንገላ ፡ ይሰብኩላችኋል ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በስሜ ፡ ትንቢት ፡ ስለሚናገሩ ፡ ነቢያት ፦ በዚች ፡ አገር ፡ ሰይፍና ፡
ራብ ፡ አይኾንም ፡ ስለሚሉ ፡ ስላላክኋቸው ፡ ነቢያት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነዚያ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 16 ፤ ትንቢት ፡ የሚናገሩላቸውም ፡ ሰዎች ፡ ከራብና ፡ ከሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡
ይበተናሉ ፤ ክፋታቸውንም ፡ አፈስባቸዋለኹ ፡ እነርሱንና ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡
የሚቀብራቸው ፡ አይገኝም ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 17 ፤ እንደዚህም ፡ ብለኽ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፦ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ድንግሊቱ ፡ በታላቅ ፡ ስብራትና ፡ እጅግ ፡
ክፉ ፡ በኾነ ፡ ቀኑስል ፡ ተሰብራለችና ፡ ዐይኖቼ ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ሳያቋርጡ ፡ እንባ ፡ ያፈሳሉ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 18 ፤ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ብወጣ ፥ እንሆ ፥ በሰይፍ ፡ የሞቱ ፡ አሉ ፤ ወደ ፡ ከተማም ፡ ብገባ ፥ እንሆ ፥ በራብ ፡
የከሱ ፡ አሉ ፤ ነቢዩና ፡ ካህኑም ፡ ወደማያውቋት ፡ አገር ፡ ኼደዋልና ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 19 ፤ በእውኑ ፡ ይሁዳን ፡ ፈጽመኽ ፡ ጥለኽዋልን ፧ ነፍስኽስ ፡ ጽዮንን ፡ ጠልታታለችን ፧ ስለ ፡ ምን ፡
መታኸን ፧ ፈውስስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የለንም ፧ ሰላምን ፡ በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ መልካምም ፡ አልተገኘም ፤ ፈውስን ፡
በተስፋ ፡ ተጠባበቅን ፥ እንሆም ፥ ድንጋጤ ፡ ኾነ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 20 ፤ አቤቱ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተናልና ፥ ክፋታችንንና ፡ የአባቶቻችንን ፡ በደል ፡
እናውቃለን ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 21 ፤ ስለ ፡ ስምኽ ፡ ብለኽ ፡ አትናቀን ፥ የክብርኽንም ፡ ዙፋን ፡ አታስነውር ፤ ከእኛ ፡ ጋራም ፡
ያደረግኸውን ፡ ቃል ፡ ኪዳንኽን ፡ ዐስብ ፡ እንጂ ፡ አታፍርስ ።

ኤር. ፥ 14 ፥ 22 ፤ በእውኑ ፡ በአሕዛብ ፡ ጣዖታት ፡ መካከል ፡ ያዘንብ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ይገኛልን ፧ ወይስ ፡
ሰማይ ፡ ዝናብ ፡ ማፍሰስ ፡ ይችላልን ፧ አቤቱ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ አይደለኽምን ፧ አንተ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡
አድርገኻልና ፥ ስለዚህ ፡ አንተን ፡ በተስፋ ፡ እንጠባበቃለን ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደዚህ ፡ አለኝ ፦ ሙሴና ፡ ሳሙኤል ፡ በፊቴ ፡ ቢቆሙም ፥ ልቤ ፡ ወደዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አይዘነብልም ፤ ከፊቴ ፡ ጣላቸው ፤ ይውጡ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 2 ፤ እነርሱም ፦ ወዴት ፡ እንውጣ ፡ ቢሉኽ ፥ አንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለሞት ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ሞት ፥ ለሰይፍም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ሰይፍ ፥ ለራብም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ራብ ፥ ለምርኮም ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ትላቸዋለኽ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ሰይፍን ፡ ለመግደል ፡ ውሻዎችንም ፡ ለመጐተት ፡ የሰማያትንም ፡ ወፎች ፡ የምድርንም ፡ አራዊት ፡ ለመብላትና ፡ ለማጥፋት ፥ አራቱን ፡ ዐይነት ፡ ጥፋት ፡ አዝዛቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 4 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ የሕዝቅያስ ፡ ልጅ ፡ ምናሴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስላደረገው ፡ ኹሉ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ለመከራ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ የሚራራልሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚያዝንልሽስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ስለ ፡ ደኅንነትሽ ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ የሚል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 15 ፡ 6 ፤ አንቺ ፡ እኔን ፡ ጥለሻል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደ ፡ ኋላሽም ፡ ተመልሰሻል ፤ ስለዚህ ፥ እጄን ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ዘርግቼ ፡ አጥፍቼሻለኹ ፤ ከይቅርታ ፡ ደክሜያለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 7 ፤ በአገርም ፡ ደጆች ፡ ውስጥ ፡ በመንሽ ፡ አበጥሬያቸዋለኹ ፤ የወላድ ፡ መካን ፡ አድርጌያቸዋለኹ ፥ ሕዝቤንም ፡ አጥፍቻለኹ ፤ ከመንገዳቸውም ፡ አልተመለሱም ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 8 ፤ መበለቶቻቸውም ፡ ከባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይልቅ ፡ በዝተውብኛል ፤ በብላቴናዎች ፡ እናት ፡ ላይ ፡ በቀትር ፡ ጊዜ ፡ አጥፊውን ፡ አምጥቻለኹ ፤ ጣርንና ፡ ድንጋጤን ፡ በድንገት ፡ አምጥቼባታለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ሰባት ፡ የወለደች ፡ ደክማለች ፥ ነፍሷንም ፡ አውጥታለች ፤ ቀን ፡ ገና ፡ ሳለ ፡ ፀሓይዋ ፡ ገብታባታለች ፤ ዐፍራለች ፡ ተዋርዳማለች ፤ የተረፉትንም ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ፊት ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 10 ፤ እናቴ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኝ! ፡ ለምድር ፡ ኹሉ ፡ የክርክርና ፡ የጥል ፡ ሰው ፡ የኾንኹትን ፡ ወለድሽኝ ፡ ለማንም ፡ አላበደርኹም ፥ ማንም ፡ ለእኔ ፡ አላበደረም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ ይረግመኛል ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በእውነት ፡ ለደኅንነትኽ ፡ አጸናኻለኹ ፤ በእውነት ፡ በመከራና ፡ በጭንቅ ፡ ጊዜ ፡ ጠላትኽ ፡ እንዲለምንኽ ፡ አደርገዋለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 12 ፤ በእውኑ ፡ ብረትን ፥ የሰሜንን ፡ ብረት ፥ ናስንም ፡ የሚሰብር ፡ አለን ፧

ኤር. ፡ 15 ፡ 13 ፤ በዳርቻኽ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ኀጢአትኽ ፡ ኹሉ ፡ ባለጠግነትኽንና ፡ መዝገብኽን ፡ ለመበዝበዝ ፡ በከንቱ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 14 ፤ የምታቃጥላቸኹ ፡ እሳት ፡ ከቀኑጣዬ ፡ ትነዳለችና ፡ ከጠላቶችኽ ፡ ጋራ ፡ ወደማታውቀው ፡ ምድር ፡ አሳልፍኻለኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 15 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፤ ዐስበኝ ፡ ጐብኝኝም ፡ የሚያሳድዱኝንም ፡ ተበቀላቸው ፡ እንጂ ፡ አትታገሣቸው ፤ ስለ ፡ አንተ ፡ ስድብን ፡ እንደ ፡ ታገሥኹ ፡ ዕወቅ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ቃልኽ ፡ ተገኝቷል ፡ እኔም ፡ በልቼዋለኹ ፤ አቤቱ ፥ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ በስምኽ ፡ ተጠርቻለኹና ፡ ቃልኽ ፡ ሐሤትና ፡ የልብ ፡ ደስታ ፡ ኾነኝ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 17 ፤ በዋዘኞችና ፡ በደስተኞች ፡ ጉባኤ ፡ አልተቀመጥኹም ፤ ቀኑጣን ፡ ሞልተኽብኛልና ፥ በእጅኽ ፡

ፊት ፡ ለብቻዬ ፡ ተቀመጥኹ ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ሕመሜ ፡ አዘወተረኝ ፡ ቍስሌስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የማይፈወስ ፡ ኾነ ፡ ስለ ፡ ምንስ ፦ አልሽርም ፡ አለ ፡ በእውኑ ፡ እንደ ፡ ሐሰተኛ ፡ ምንጭ ፥ እንዳልታመነች ፡ ውሃ ፡ ትኾነኛለኽን ፡

ኤር. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብትመለስ ፡ እመልስኻለኹ ፡ በፊቴም ፡ ትቆማለኽ ፤ የከበረውንም ፡ ከተዋረደው ፡ ብትለይ ፡ እንደ ፡ አፌ ፡ ትኾናለኽ ፤ እነርሱ ፡ ወዳንተ ፡ ይመለሳሉ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አትመለስም ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ የተመሸገ ፡ የናስ ፡ ቅጥር ፡ አደርግኻለኹ ፤ ይዋጉኻል ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ለማዳን ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አያሸንፉኽም ።

ኤር. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ከክፉ ፡ ሰዎችም ፡ እጅ ፡ እታደግኻለኹ ፥ ከጨካኞችም ፡ ጡጫ ፡ እቤዥኻለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 16 ፡ 2 ፤ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ሚስት ፡ አታግባ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችም ፡ አይኹኑልኽ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ስለተወለዱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፥ ስለወለዷቸውም ፡ ስለ ፡ እናቶቻቸው ፥ በዚችም ፡ ምድር ፡ ስለወለዷቸው ፡ ስለ ፡ አባቶቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

ኤር. ፡ 16 ፡ 4 ፤ በክፉ ፡ ሞት ፡ ይሞታሉ ፤ አይለቀስላቸውም ፡ አይቀበሩምም ፥ በመሬትም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይኾናሉ ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ፥ ሬሳቸውም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰላሜን ፥ ቸርነትና ፡ ምሕረትን ፥ ከዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አስወግጃለኹና ፡ ልቅሶ ፡ ወዳለበት ፡ ቤት ፡ አትግባ ፥ ታለቅስም ፥ ታዝንም ፡ ዘንድ ፡ አትኺድ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ታላላቆችና ፡ ታናናሾች ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ይሞታሉ ፤ አይቀበሩም ፥ ሰዎችም ፡ አያለቅሱላቸውም ፥ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ገላን ፡ አይነጨላቸውም ፥ ራስንም ፡ አይላጨላቸውም ፤

ኤር. ፡ 16 ፡ 7 ፤ ሰዎችም ፡ ስለሞቱት ፡ ለማጽናናት ፡ የዕዝን ፡ እንጀራ ፡ አይቈርሱላቸውም ፥ ስለ ፡ አባታቸውና ፡ ስለ ፡ እናታቸውም ፡ የመጽናናት ፡ ጽዋ ፡ አያጠጧቸውም ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ትበላና ፡ ትጠጣ ፡ ዘንድ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደግብዣ ፡ ቤት ፡ አትግባ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 9 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ በዘመናችኹም ፡ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፡ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ አስቀራለኹ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 10 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በተናገርኽ ፡ ጊዜ ፦ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረብን ፡ በደላችንስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ በአምላካችንስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የሠራነው ፡ ኀጢአታችን ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ቢሉኽ ፥

ኤር. ፡ 16 ፡ 11 ፤ አንተ ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለኽ ፦ አባቶቻችኹ ፡ እኔን ፡ ስለ ፡ ተዉ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ሌላዎችንም ፡ አማልክት ፡ ተከተሉ ፡ አመለኳቸውም ፡ ሰገዱላቸውም ፥ እነርሱም ፡ ትተውኛል ፥ ሕጌንም ፡ አልጠበቁም ፤ እናንተም ፡ ከአባቶቻችኹ ፡ ይልቅ ፡ ክፉ ፡ አድርጋችኋል ፤ እንሆም ፥ ኹላችኹ ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ልባችኹ ፡ እልከኝነት ፡ ኼዳችኋል ፡ እኔንም ፡ አልሰማችኹም ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ከዚች ፡ ምድር ፡ እናንተና ፡ አባቶቻችኹ ፡ ወዳላወቃችኋት ፡ ምድር ፡ እጥላችኋለኹ ፤ ምሕረትንም ፡ አላደርግላችኹምና ፥ በዚያ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ታመልካላችኹ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ኤር. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ካሳደዳቸውም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ይባላል ፤ እኔም ፡ ለአባቶቻቸው ፡ ወደሰጠኋት ፡ ወደ ፡ ምድራቸው ፡ እመልሳቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 16 ፤ እንሆ ፥ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ አጥማጆችን ፡ እሰዳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እነርሱም ፡ ያጠምዷቸዋል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ አዳኞችን ፡ እሰዳለኹ ፥ እነርሱም ፡ ከየተራራውና ፡ ከየኰረብታው ፡ ኹሉ ፡ ከየድንጋዩም ፡ ስንጣቂ ፡ ውስጥ ፡ ያድኗቸዋል ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ዐይኔ ፡ በመንገዳቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ከፊቴም ፡ አልተሰወሩም ፥ ኀጢአታቸውም ፡ ከዐይኔ ፡ አልተሸሸገም ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ምድሬንም ፡ በተጠሉ ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ ሬሳዎች ፡ አርክሰዋልና ፥ ርስቴንም ፡ አስጸያፊ ፡ በኾኑ ፡ ነገሮች ፡ ሞልተዋልና ፥ አስቀድሜ ፡ የበደላቸውንና ፡ የኀጢአታቸውን ፡ ዕዳ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ እከፍላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ ኀይሌ ፥ ዐምባዬ ፥ በመከራም ፡ ቀን ፡ መጠጊያዬ ፡ ሆይ ፥ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ አሕዛብ ፡ ወዳንተ ፡ መጥተው ፦ በእውነት ፡ አባቶቻችን ፡ ውሸትንና ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ የማይረባቸውንም ፡ ወርሰዋል ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 16 ፡ 20 ፤ በእውኑ ፡ ሰው ፡ አማልክት ፡ ያልኾኑትን ፡ ለራሱ ፡ አማልክትን ፡ አድርጎ ፡ ይሠራልን ፧

ኤር. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ አስታውቃቸዋለኹ ፥ በዚች ፡ ጊዜ ፡ እጄንና ፡ ኀይሌን ፡ አስታውቃቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ስሜ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 1 ፤ የይሁዳ ፡ ኀጢአት ፡ በብረት ፡ ብርዕና ፡ በተሾለ ፡ እብነ ፡ አልማዝ ፡ ተጽፏል ፤ በልባቸው ፡ ጽላትና ፡ በመሠዊያቸው ፡ ቀንዶች ፡ ተቀርጿል ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ልጆቻቸውም ፡ ከለመለሙ ፡ ዛፎች ፡ በታችና ፡ በረዘሙት ፡ ኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ መሠዊያቸውንና ፡ የማምለኪያ ፡ ዐጸዳቸውን ፡ ያስባሉ ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 3 ፤ በሜዳ ፡ ያለው ፡ ተራራዬ ፡ ሆይ ፥ ባለጠግነትኽንና ፡ መዝገብኽን ፡ ኹሉ ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎችኽም ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ በድንበሮችኽ ፡ ኹሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 4 ፤ አንተም ፡ የሰጠኹኽን ፡ ርስት ፡ ትለቃለኽ ፡ ለዘለዓለምም ፡ በማታውቃትም ፡ ምድር ፡ ለጠላቶቻችኹ ፡ ባሪያ ፡ አደርግኻለኹ ፤ ለዘለዓለም ፡ የሚነደውን ፡ እሳት ፡ በቀኑጣዬ ፡ አንድዳችኋልና ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በሰው ፡ የሚታመን ፡ ሥጋ ፡ ለባሹንም ፡ ክንዱ ፡ የሚያደርግ ፡ ልቡም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚመለስ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 6 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቀጥቋጦ ፡ ይኾናል ፥ መልካምም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አያይም ፤ ሰውም ፡ በሌለበት ፥ ጨው ፡ ባለበት ፡ ምድር ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በደረቅ ፡ ስፍራ ፡ ይቀመጣል ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ እምነቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ቡሩክ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 8 ፤ በውሃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ተተከለ ፥ በወንዝም ፡ ዳር ፡ ሥሩን ፡ እንደሚዘረጋ ፡ ሙቀትም ፡

ሊመጣ ፡ እንደማይፈራ ፡ ቅጠሉም ፡ እንደሚለመልም ፥ በድርቅ ፡ ዓመትም ፡ እንደማይሠጋ ፡ ፍሬውንም ፡ እንደማያቋርጥ ፡ ዛፍ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 9 ፤ የሰው ፡ ልብ ፡ ከሹሉ ፡ ይልቅ ፡ ተንኰለኛ ፡ እጅግም ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ማንስ ፡ ያውቀዋል ፧

ኤር. ፥ 17 ፥ 10 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፥ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ልብን ፡ እመረምራለኹ ፡ ኵላሊትንም ፡ እፈትናለኹ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 11 ፤ ያልወለደችውን ፡ እንደምታቅፍ ፡ ቆቅ ፥ እንዲሁ ፡ በቅን ፡ ሳይኾን ፡ ባለጠግነትን ፡ የሚሰበስብ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ በእኩሌታ ፡ ዘመኑ ፡ ይተወዋል ፥ በፍጻሜውም ፡ ሰነፍ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 12 ፤ የመቅደሳችን ፡ ስፍራ ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የክብር ፡ ዙፋን ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 13 ፤ አቤቱ ፥ የእስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ሆይ ፥ የሚተዉኽ ፡ ሹሉ ፡ ያፍራሉ ፤ ከአንተም ፡ የሚለዩ ፡ የሕይወትን ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትተዋልና ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ይጻፋሉ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 14 ፤ አቤቱ ፥ ፈውሰኝ ፡ እኔም ፡ እፈወሳለኹ ፤ አድነኝ ፡ እኔም ፡ እድናለኹ ፤ አንተ ፡ ምስጋናዬ ፡ ነኽና ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 15 ፤ እንሆ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወዴት ፡ አለች ፧ አኹን ፡ ትምጣ ፡ ይሉኛል ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 16 ፤ እኔም ፡ አንተን ፡ ተከትዬ ፡ እረኛ ፡ ከመኾን ፡ አልቸኰልኹም ፥ የመከራንም ፡ ቀን ፡ አልወደድኹም ፤ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፤ ከከንፈሬ ፡ የወጣው ፡ በፊትኽ ፡ ነበረ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 17 ፤ ለማስፈራራት ፡ አትኹንብኝ ፤ በመከራ ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ መጠጊያዬ ፡ ነኽ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 18 ፤ አሳዳጆቼ ፡ ይፈሩ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልፈር ፤ እነርሱ ፡ ይደንግጡ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አልደንግጥ ፤ ክፉንም ፡ ቀን ፡ አምጣባቸው ፥ በኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ጥፋት ፡ አጥፋቸው ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ ኺድ ፥ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ በሚገቡበትና ፡ በሚወጡበት ፡ በሕዝቡ ፡ ልጆች ፡ በር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ ሹሉ ፡ ቁም ፤

ኤር. ፥ 17 ፥ 20 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ በእነዚህ ፡ በሮች ፡ የምትገቡ ፥ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፥ ይሁዳም ፡ ሹሉ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ሹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክም ፡ አትሸከሙ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሮች ፡ አታግቡ ፥

ኤር. ፥ 17 ፥ 22 ፤ ከቤቶቻችኹም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ሸክምን ፡ አታውጡ ፥ ሥራንም ፡ ሹሉ ፡ አትሥሩበት ፤ አባቶቻችኹንም ፡ እንዳዘዝኹ ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ቀድሱ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 23 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፡ ጐሯቸውን ፡ አላዘነበሉም ፥ እንዳይሰሙና ፡ እንዳይገሠጹም ፡ ዐንገታቸውን ፡ አደነደኑ ።

ኤር. ፥ 17 ፥ 24 ፤ እኔን ፡ ፈጽሞ ፡ ብትሰሙ ፤ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በሮች ፡ ሸክም ፡ ባታገቡ ፥ የሰንበትንም ፡ ቀን ፡ ብትቀድሱ ፡ ሥራንም ፡ ሹሉ ፡ ባትሠሩበት ፥

ኤር. ፥ 17 ፥ 25 ፤ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡ ፡ ነገሥታትና ፡ መሳፍንት ፡ በሠረገላዎችና ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ እየተቀመጡ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በሮች ፡ ይገባሉ ፤ እነርሱና ፡ መሳፍንቶቻቸው ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚቀመጡ ፡ ይገባሉ ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትኾናለች ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 26 ፤ የሚቃጠለው ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕትን ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ የምስጋናውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ይዘው ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ከብንያምም ፡ አገር ፡ ከቈላውም ፡ ከደጋውም ፡ ከደቡብም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይመጣሉ ።

ኤር. ፡ 17 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ እንድትቀድሱ ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ሸክምን ፡ ተሸክማችኹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሮች ፡ እንዳትገቡ ፡ የነገርኋችኹን ፡ ባትሰሙኝ ፥ በበሮቿ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ፥ አትጠፋም ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 1-2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፥ እንዲህም ፡ አለው ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ቤት ፡ ውረድ ፥ በዚያም ፡ ቃሌን ፡ አሰማኻለኹ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 3 ፤ ወደሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ቤትም ፡ ወረድኹ ፥ እንሆም ፥ ሥራውን ፡ በመንኰራኵር ፡ ላይ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ከጭቃም ፡ ይሠራው ፡ የነበረ ፡ ዕቃ ፡ በሸክላ ፡ ሠሪው ፡ እጅ ፡ ተበላሸ ፥ ሸክላ ፡ ሠሪውም ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ መልሶ ፡ ሌላ ፡ ዕቃ ፡ አድርጎ ፡ ሠራው ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 18 ፡ 6 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እንደሚሠራ ፡ በእውኑ ፡ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ መሥራት ፡ አይቻለኝምን ፧ እንሆ ፥ ጭቃው ፡ በሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንዳለ ፥ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ በእኔ ፡ እጅ ፡ አላችኹ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ መንግሥትም ፡ እነቅል ፡ አፈርስም ፡ አጠፋም ፡ ዘንድ ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ይህ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገርኹበት ፡ ሕዝብ ፡ ከክፋቱ ፡ ቢመለስ ፥ እኔ ፡ አደርግበት ፡ ዘንድ ፡ ካሰብኹት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እጸጸታለኹ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ስለ ፡ መንግሥትም ፡ እሠራውና ፡ እተክለው ፡ ዘንድ ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፡ 18 ፡ 10 ፤ በፊቴ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፡ ቃሌንም ፡ ባይሰማ ፥ እኔ ፡ አደርግለት ፡ ዘንድ ፡ ስለተናገርኹት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ እጸጸታለኹ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 11 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ። እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ እፈጥርባችኋለኹ ፥ ዐሳብንም ፡ ዐስብባችኋለኹ ፤ አኹንም ፡ ኹላችኹ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፥ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹንም ፡ አቅኑ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 12 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ እንጨክናለን ፤ ዐሳባችንን ፡ ተከትለን ፡ እንኼዳለን ፡ ኹላችንም ፡ እንደ ፡ ክፉው ፡ ልባችን ፡ እልከኝነት ፡ እናደርጋለን ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በአሕዛብ ፡ መካከል ፦ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ማን ፡ ሰምቷል ፧ ብላችኹ ፡ ጠይቁ ። የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ በጣም ፡ የሚያስደነግጠውን ፡ ነገር ፡ አድርጋለች ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 14 ፤ በእውኑ ፡ የሊባኖስ ፡ በረዶ ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ድንጋይ ፡ ይተዋልን ፧ ወይስ ፡ ከሩቅ ፡ የምትመጣው ፡ ቀዝቃዛዉቱ ፡ ፈሳሽ ፡ ውሃ ፡ ትደርቃለችን ፧

ኤር. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ሕዝቤ ፡ ግን ፡ ረስተውኛል ፡ ለከንቱ ፡ ነገርም ፡ ዐጥነዋል ፤ ከመንገዱም ፡ ተሰናክለዋል ፡ ከቀድሞውም ፡ ጐዳና ፡ ርቀው ፡ ወዳልተሠራው ፡ ወደ ፡ ጠማማው ፡ መንገድ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ምድራቸውን ፡ ለመደነቂያና ፡ ለዘለዓለም ፡ ማፏጫ ፡ አድርገዋል ፤ የሚያልፍባት ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፥ ራሱንም ፡ ያነቃንቃል ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 17 ፤ በጠላት ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ እበትናቸዋለኹ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ ዝርባዬን ፡ እንጂ ፡ ፊቴን ፡ አላሳያቸውም ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፦ ሕግ ፡ ከካህን ፥ ምክርም ፡ ከጠቢብ ፥ ቃልም ፡ ከነቢይ ፡ አይጠፋምና ፡ ኑ ፥ በኤርምያስ ፡ ላይ ፡ ዐሳብን ፡ እናስብ ። ኑ ፥ በምላስ ፡ እንምታው ፥ ቃሉንም ፡ ኹሉ ፡ አናድምጥ ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ አድምጠኝ ፥ የክርክሬንም ፡ ቃል ፡ ስማ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ለነፍሴ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፍረዋልና ፥ በእውኑ ፡ በመልካም ፡ ፋንታ ፡ ክፉ ፡ ይመለሳልን ፧ ስለ ፡ እነርሱ ፡ በመልካም ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ቀጣኸንም ፡ ከነርሱ ፡ እመልስ ፡ ዘንድ ፡ በፊትኽ ፡ እንደ ፡ ቆምኹ ፡ ዐስብ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ ልጆቻቸውን ፡ ለራብ ፡ ስጥ ፥ ለሰይፍም ፡ እጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ስጣቸው ፥ ሚስቶቻቸውም ፡ የወላድ ፡ መካንና ፡ መበለቶች ፡ ይኹኑ ፥ ወንዶቻቸውም ፡ በሞት ፡ ይጥፉ ፥ ጕልማሳዎቻቸውም ፡ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ በሰይፍ ፡ ይመቱ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ሊይዙኝ ፡ ጕድጓድ ፡ ቈፍረዋልና ፥ ለእግሮቼም ፡ ወጥመድ ፡ ሸሽገዋልና ፥ ድንገት ፡ በላያቸው ፡ ጭፍራ ፡ ባመጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ከቤታቸው ፡ ጩኸት ፡ ይሰማ ።

ኤር. ፡ 18 ፡ 23 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፥ ይገድሉኝ ፡ ዘንድ ፡ በላዬ ፡ የመከሩትን ፡ ምክር ፡ ኹሉ ፡ ታውቃለኽ ፤ በደላቸውን ፡ ይቅር ፡ አትበል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ከፊትኽ ፡ አትደምስስ ፤ በፊትኽም ፡ ይውደቁ ፥ በቀጣኽ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ አድርግባቸው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ኺድ ፥ ከሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ገምቦ ፡ ግዛ ፥ ከሕዝቡም ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ከካህናት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰድ ፤

ኤር. ፡ 19 ፡ 2 ፤ በካርሲት ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ኺድ ፥ በዚያም ፡ የምነግርኽን ፡ ቃል ፡ ተናገር ፥

ኤር. ፡ 19 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ የይሁዳ ፡ ነገሥታትና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሰማውን ፡ ሰው ፡ ጆሮ ፡ ጭው ፡ የሚያደርግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ አመጣለኹ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ትተውኛልና ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ እንግዳ ፡ አድርገውታልና ፥ እነርሱና ፡ አባቶቻቸውም ፡ ለማያውቋቸው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ዐጥነዋልና ፥ የይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ በንጹሕ ፡ ደም ፡ ሞልተዋልና ፥

ኤር. ፡ 19 ፡ 5 ፤ እኔም ፡ ያላዘዝኹትን ፡ ያልተናገርኹትንም ፡ ወደ ፡ ልቤም ፡ ያልገባውን ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ለበዓል ፡ ልጆቻቸውን ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሉ ፡ ዘንድ ፡ የበዓልን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠርተዋልና ፥ ስለዚህ ፥

ኤር. ፡ 19 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ ስፍራ ፡ የዕርድ ፡ ሸለቆ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ቶፌት ፡ ወይም ፡ የሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 7 ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ምክር ፡ አፈርሳለኹ ፥ በጠላቶቻቸውም ፡ ፊት ፡

በሰይፍና ፡ ነፍሳቸውን ፡ በሚሹት ፡ እጅ ፡ እጥላቸዋለኹ ፥ ሬሳቸውንም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ አድርጌ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ለመደነቂያና ፡ ለማፏጫ ፡ አደርጋታለኹ ፤ የሚያልፍባትም ፡ ኹሉ ፡ ስለተደረገባት ፡ መቅሠፍት ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፡ ከንፈሩንም ፡ ይመጥጣል ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 9 ፤ የወንዶችና ፡ የሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ሥጋ ፡ አበላቸዋለኹ ፥ ኹሉም ፡ ጠላቶቻቸውንና ፡ ነፍሳቸውን ፡ የሚሹት ፡ በሚያስጨንቋቸው ፡ ጭንቀትና ፡ መከበብ ፡ የባልንጀራዎቻቸውን ፡ ሥጋ ፡ ይበላሉ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ገምቦውንም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በሚኼዱ ፡ ሰዎች ፡ ፊት ፡ ትሰብራለኽ ፥

ኤር. ፡ 19 ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሸክላ ፡ ሠሪው ፡ ዕቃ ፡ እንደሚሰባበር ፡ ደግሞም ፡ ይጠገን ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፥ እንዲሁ ፡ ይህን ፡ ሕዝብና ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ እሰብራለኹ ፤ የሚቀብሩበትም ፡ ስፍራ ፡ ሌላ ፡ የለምና ፡ በቶፌት ፡ ይቀበራሉ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 12 ፤ እንዲሁ ፡ በዚህ ፡ ስፍራና ፡ በሚኖሩበት ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ቶፌት ፡ አደርጋለኹ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 13 ፤ የረከሱትም ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቤቶችና ፡ የይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ ቤቶች ፥ እነዚያ ፡ በሰገነታቸው ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ያጠኑባቸው ፡ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ያፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ እንደ ፡ ቶፌት ፡ ስፍራ ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ኤርምያስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ትንቢት ፡ ሊናገር ፡ ወደዚያ ፡ ልኮት ፡ ከነበረው ፡ ስፍራ ፡ ከቶፌት ፡ መጣ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ቆሞ ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፦

ኤር. ፡ 19 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቃሌን ፡ እንዳይሰሙ ፡ ዐንገታቸውን ፡ አደንድነዋልና ፥ እንሆ ፥ በዚች ፡ ከተማና ፡ በመንደሮቿ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተናገርኹባትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አመጣለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 1 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የተሾመው ፡ አለቃ ፡ የካህኑ ፡ የኢሜር ፡ ልጅ ፡ ጳስኮር ፡ ኤርምያስ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ትንቢት ፡ ሲናገር ፡ ሰማ ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ጳስኮርም ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ መታው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በነበረው ፡ በላይኛው ፡ በብንያም ፡ በር ፡ ባለው ፡ በእግር ፡ ግንድ ፡ ውስጥ ፡ አኖረው ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 3 ፤ በነጋውም ፡ ጳስኮር ፡ ኤርምያስን ፡ ከግንድ ፡ ውስጥ ፡ አወጣው ። ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ እግዚአብሔር ፡ ስምኽን ፦ ማጎርሚሳቢብ ፡ እንጂ ፡ ጳስኮር ፡ ብሎ ፡ አይጠራኽም ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ለራስኽና ፡ ለወዳጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ፍርሀት ፡ አደርግኻለኹ ፤ እነርሱም ፡ በጠላቶቻቸው ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፡ ዐይኖችኽም ፡ ያያሉ ፤ ይሁዳንም ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሳቸዋል ፡ በሰይፍም ፡ ይገድላቸዋል ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 5 ፤ የዚችንም ፡ ከተማ ፡ ባለጠግነት ፡ ኹሉ ፡ ጥሪቷንም ፡ ኹሉ ፡ ክብሯንም ፡ ኹሉ ፡ የይሁዳንም ፡ ነገሥታት ፡ መዝገብ ፡ ኹሉ ፡ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ እነርሱም ፡ ይበዘብዟቸዋል ፡ ይዘውም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሷቸዋል ።

ኤር. ፡ 20 ፡ 6 ፤ አንተም ፥ ጳስኮር ፡ ሆይ ፥ በቤትኽም ፡ የሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ተማርካችኹ ፡

ትኬዳላችኹ ፤ አንተም ፡ በሐሰትም ፡ ትንቢት ፡ የተናገርኽላቸው ፡ ወዳጆችኽ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡
ትገባላችኹ ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ፥ በዚያም ፡ ትቀበራላችኹ ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 7 ፤ አቤቱ ፥ አታለልኸኝ ፡ እኔም ፡ ተታለልኹ ፥ ከእኔም ፡ በረታኽ ፡ አሸነፍኽም ፤ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡
መሳቂያ ፡ ኾኛለኹ ፥ ኹሉም ፡ ያላግጡብኛል ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 8 ፤ በተናገርኹ ፡ ቍጥር ፡ እጮኻለኹ ፤ ግፍና ፡ ጥፋት ፡ ብዬ ፡ እጮኻለኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ ስድብና ፡ ዋዛ ፡ ኾኖብኛልና ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 9 ፤ እኔም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አላነሣም ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ በስሙ ፡ አልናገርም ፡
ብል ፥ በዐጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ እንደሚነድ ፡ እሳት ፡ ያለ ፡ በልቤ ፡ ኾነብኝ ፤ ደከምኹ ፥ መሸከምም ፡
አልቻልኹም ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 10 ፤ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ስድብ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ማስፈራራትም ፡ ከዖኛል ። መውደቄን ፡ የሚጠብቁ ፡
የሰላሜ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፦ ምናልባት ፡ ይታለል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እናሸንፈውም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ርሱንም ፡ እንበቀል ፡ እንደ ፡
ኾነ ፥ ክሰሱት ፡ እኛም ፡ እንከሰዋለን ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኀያልና ፡ እንደ ፡ ጨካኝ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ አሳዳጆቼ ፡
ይሰናከላሉ ፥ አያሸንፉም ፤ አይከናወንላቸውምና ፥ በጽኑ ፡ ዕፍረት ፡ ያፍራሉ ፤ ለዘለዓለምም ፡ በማይረሳ ፡ ጕስቍልና ፡
ይገሰቍላሉ ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 12 ፤ አቤቱ ፥ ጻድቅን ፡ የምትመረምር ፡ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምትመለከት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
ሆይ ፥ ክርክሬን ፡ ገልጬልኻለኹና ፡ በቀልኽን ፡ በላያቸው ፡ ለይ ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 13 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመስግኑ ፤ የችግረኛውን ፡ ነፍስ ፡ ከክፉ ፡
አድራጊዎች ፡ እጅ ፡ አድኗልና ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 14 ፤ የተወለድኹባት ፡ ቀን ፡ የተረገመች ፡ ትኹን ፤ እናቴ ፡ እኔን ፡ የወለደችባት ፡ ቀን ፡ የተባረከች ፡
አትኹን ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 15 ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶልኻል ፡ ብሎ ፡ ለአባቴ ፡ የምሥራች ፡ ነግሮ ፡ ደስ ፡ ያሠኘው ፡ ሰው ፡
የተረገመ ፡ ይኹን ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 16 ፤ ያም ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳይጸጸት ፡ እንደ ፡ ገለበጣቸው ፡ ከተማዎች ፡ ይኹን ፥ በማለዳም ፡
ልቅሶን ፡ በቀትርም ፡ ጩኸትን ፡ ይስማ ፤

ኤር. ፥ 20 ፥ 17 ፤ እናቴ ፡ መቃብር ፡ ትኾነኝ ፡ ዘንድ ፡ ማሕፀኗም ፡ ዘወትር ፡ ይዘኝ ፡ ያቈይ ፡ ዘንድ ፡ በማሕፀን ፡
ውስጥ ፡ አልገደለኝምና ።

ኤር. ፥ 20 ፥ 18 ፤ ድካምንና ፡ ጣርን ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ዘመኔም ፡ በዕፍረት ፡ ታልቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ከማሕፀን ፡
ወጣኹ ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ኤር. ፥ 21 ፥ 1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 21 ፥ 2 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይወጋናልና ፥ ስለ ፡
እኛ ፥ እባክኽ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ጠይቅ ፤ ከእኛም ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡
ተኣምራቱ ፡ ኹሉ ፡ ያደርግ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ የመልክያን ፡ ልጅ ፡ ጻስኮርንና ፡ ካህኑን ፡ የመዕሴያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስ ፡

ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ በላከ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦

ኤር. ፡ 21 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ በቅጥርም ፡ ውጭ ፡ የከበቧችኹን ፡ ከለዳውያንን ፡ የምትወጉበትን ፡ በእጃችኹ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ጦራችኹን ፡ እመልሰዋለኹ ፥ እነዚያንም ፡ ወደዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 5 ፤ እኔም ፡ በተዘረጋች ፡ እጅና ፡ በብርቱ ፡ ክንድ ፥ በቍጣና ፡ በመዓት ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍት ፡ እወጋችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 6 ፤ በዚችም ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ሰዎችንና ፡ እንስሳዎችን ፡ እመታለኹ ፥ በጽኑም ፡ ቸነፈር ፡ ይሞታሉ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ከቸነፈርና ፡ ከሰይፍ ፡ ከራብም ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ የቀሩትንም ፡ ባሪያዎቹንና ፡ ሕዝቡን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ በጠላቶቻቸውና ፡ ነፍሳቸውንም ፡ በሚሹት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ ርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ስለት ፡ ይመታቸዋል ፤ አያዝንላቸውም ፥ አይራራላቸውም ፥ አይምራቸውም ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በፊታችኹ ፡ የሕይወትን ፡ መንገድና ፡ የሞትን ፡ መንገድ ፡ አድርጌያለኹ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 9 ፤ በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ የሚዘገይ ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታል ፤ ወጥቶ ፡ ወደከበቧችኹ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ የሚገባ ፡ ግን ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፥ ነፍሱም ፡ ምርኮ ፡ ትኾንለታለች ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ለመልካም ፡ ሳይኾን ፡ ለክፉ ፡ ፊቴን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አድርጌያለኹና ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ትሰጣለች ፥ ርሱም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላታል ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 11 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 12 ፤ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሥራችኹ ፡ ክፋት ፡ ቍጣዬ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ እንዳይወጣና ፡ ማንም ፡ ሳያጠፋው ፡ እንዳይነድ ፥ በማለዳ ፡ ፍርድን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡ አድኑ ።

ኤር. ፡ 21 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ በሜዳ ፡ ላይም ፡ ባለው ፡ ዐምባ ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤ እናንተም ፦ በእኛ ፡ ላይ ፡ የሚወርድ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ መኖሪያችን ፡ የሚገባ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የምትሉ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤

ኤር. ፡ 21 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ሥራችኹም ፡ ፍሬ ፡ እቀጣችኋለኹ ፤ በዱሯም ፡ ውስጥ ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ በዙሪያዋም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ይበላል ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ ውረድ ፡ በዚያም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ተናገር ፥

ኤር. ፡ 22 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የምትቀመጥ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አንተና ፡ ባሪያዎችኽ ፡ በእነዚህም ፡ በሮች ፡ የሚገባ ፡ ሕዝብኽ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ አድርጉ ፡ የተበዘበዘውንም ፡ ካስጨናቂው ፡ እጅ ፡ አድኑ ፤ መጻተኛውንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ መበለቲቱንም ፡ አትበድሉ ፥ አታምፁባቸውም ፥ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ አታፍስሱ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ፥ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ የሚቀመጡ ፡ ነገሥታት ፥ በሠረገላዎችና ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠው ፥ በዚህ ፡ ቤት ፡ በሮች ፡ ይገባሉ ፤ ርሱም ፡ ባሪያዎቹም ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ይገባሉ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥ ይህ ፡ ቤት ፡ ወና ፡ እንዲኾን ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ አንተ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ገለዓድና ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ራስ ፡ ነኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርግጥ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ማንም ፡ የማይቀመጥባቸውም ፡ ከተማዎች ፡ አደርግኻለኹ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 7 ፤ መሣሪያም ፡ የሚይዙትን ፡ አጥፊዎች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አዘጋጃለኹ ፥ የተመረጡትንም ፡ የዝግባ ፡ ዛፎችኽን ፡ ይቈርጣሉ ፥ በእሳትም ፡ ውስጥ ፡ ይጥሏቸዋል ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 8 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብም ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ ያልፋሉ ፥ ኹሉም ፡ ባልንጀራዎቻቸውን ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚች ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደርገ ፧ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፦ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ትተው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ስለ ፡ ሰገዱ ፡ ስላመለኳቸውም ፡ ነዋ ፡ ብለው ፡ ይመልሳሉ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለስምና ፥ የተወለደባትንም ፡ አገር ፡ አያይምና ፡ ለሚወጣ ፡ እጅግ ፡ አልቅሱ ፡ እንጂ ፡ ለሞተ ፡ አታልቅሱ ፡ አትዘኑለትም ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 11 ፤ በአባቱ ፡ በኢዮስያስ ፡ ፋንታ ፡ ስለነገሠው ፡ ከዚህም ፡ ስፍራ ፡ ስለወጣው ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሰሎም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

ኤር. ፡ 22 ፡ 12 ፤ እንግዲህም ፡ ወደዚህ ፡ አይመለስም ፥ በተማረከባት ፡ አገር ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ፤ ይህችንም ፡ አገር ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያይም ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ቤቱን ፡ በግፍ ፡ ሰገነቱንም ፡ በዐመፅ ፡ ለሚሠራ ፥ ባልንጀራውንም ፡ እንዲያው ፡ በከንቱ ፡ ለሚያሠራ ፥ ዋጋውንም ፡ ለማይሰጠው ፤

ኤር. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ለራሴ ፡ ሰፊ ፡ ቤት ፡ ትልቅም ፡ ሰገነት ፡ እሠራለኹ ፡ ለሚል ፥ መስኮትንም ፡ ለሚያወጣ ፥ በዝግባም ፡ ሥራ ፡ ለሚያሳጌጥ ፥ በቀይ ፡ ቀለምም ፡ ለሚቀባው ፡ ወዮለት! ፡

ኤር. ፡ 22 ፡ 15 ፤ በዝግባ ፡ ዕንጨት ፡ ስለምትወዳደር ፡ በእውኑ ፡ ትነግሣለኽን ፧ በእውኑ ፡ አባትኽ ፡ አይበላምና ፡ አይጠጣም ፡ ነበርን ፧ ፍርድንና ፡ ጽድቅንስ ፡ አያደርግም ፡ ነበርን ፧ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ኾኖለት ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 16 ፤ የድኻውንና ፡ የችግረኛውን ፡ ፍርድ ፡ ይፈርድ ፡ ነበር ፥ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፡ ነበር ። ይህ ፡ እኔን ፡ ማወቅ ፡ አይደለምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 17 ፤ ዐይንኽና ፡ ልብኽ ፡ ግን ፡ ለሥሥት ፡ ንጹሕ ፡ ደምንም ፡ ለማፍሰስ ፡ ዐመፅንና ፡ ግፍንም ፡ ለመሥራት ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ኢዮአቄም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ፥ ወይም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ እያሉ ፡ አያለቅሱለትም ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 19 ፤ አህያም ፡ እንደሚቀበር ፡ ይቀበራል ፥ ከኢየሩሳሌምም ፡ በር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጐትቶ ፡ ይጣላል ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ውሽማዎችሽ ፡ ኹሉ ፡ ጠፍተዋልና ፥ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ ወጥተሽ ፡ ጩኺ ፤ በባሳን ፡ ላይ ፡ ድምፅሽን ፡ አንሺ ፤ በዓባሪምም ፡ ውስጥ ፡ ኾነሽ ፡ ጩኺ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 21 ፤ በደኅንነትሽ ፡ ጊዜ ፡ ተናገርኹሽ ፤ አንቺም ፦ አልሰማም ፡ አልሽ ። ከሕፃንነትሽ ፡ ዠምሮ ፡ ቃሌን ፡ አለመስማትሽ ፡ መንገድሽ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 22 ፤ በግ ፡ ጠባቂዎችሽን ፡ ኹሉ ፡ ነፋስ ፡ ይጠብቃቸዋል ፥ ውሽማዎችሽም ፡ ተማርከው ፡ ይኼዳሉ ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ክፋትሽ ፡ ኹሉ ፡ ታፍሪያለሽ ፡ ትጐሳቈይማለሽ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 23 ፤ አንቺ ፡ በሊባኖስ ፡ የምትቀመጪ ፥ በዝግባ ፡ ዛፍም ፡ ውስጥ ፡ ጐጕሽን ፡ የምትሠሪ ፡ ሆይ ፥ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ሕማም ፡ በያዘሽ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ ታጓሪያለሽ! ፡

ኤር. ፡ 22 ፡ 24 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄም ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያን ፡ የቀኝ ፡ እጄ ፡ ማኅተም ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ እንኳ ፥ ከዚያ ፡ እነቅልኽ ፡ ነበር ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ኤር. ፡ 22 ፡ 25 ፤ ነፍስኽንም ፡ ለሚሹት ፡ ለምትፈራቸውም ፡ እጅ ፥ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 26 ፤ አንተንም ፡ የወለደችኽንም ፡ እናትኽን ፡ ወዳልተወለዳችኹባት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እጥላችኋለኹ ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 27 ፤ ይመለሱባትም ፡ ዘንድ ፡ ነፍሳቸው ፡ ወደምትመኛት ፡ ወደዚያች ፡ ምድር ፡ አይመለሱም ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 28 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ኢኮንያን ፡ የተናቀና ፡ የተሰበረ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ርሱ ፡ ለአንዳች ፡ የማይረባ ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ነውን ፧ ርሱና ፡ ዘሩስ ፡ በማያውቋት ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተጥለው ፡ ወደቁ ፧

ኤር. ፡ 22 ፡ 29 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ ምድር ፡ ሆይ ፥ ምድር ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሚ ።

ኤር. ፡ 22 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ የሚከናወን ፡ በዳዊትም ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ በይሁዳም ፡ የሚነግሥ ፡ እንግዲህ ፡ አይገኝምና ። መካን ፡ በዘመኑም ፡ የማይከናወንለት ፡ ሰው ፡ ብላችኹ ፡ ጻፉ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 1 ፤ የማሰማሪያዬን ፡ በጎች ፡ ለሚያጠፉና ፡ ለሚበትኑ ፡ እረኞች ፡ ወዮላቸው! ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ሕዝቤን ፡ ስለሚጠብቁ ፡ እረኞች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በጎቼን ፡ በትናችኋል ፥ አባራችኋቸውማል ፥ አልጐበኛችኋቸውምም ፤ እንሆ ፥ የሥራችኹን ፡ ክፋት ፡ እጐበኝባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 3 ፤ የመንጋዬም ፡ ቅሬታ ፡ ካባረርኋቸው ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ በረታቸው ፡ ሰብስቤ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያፈራሉ ፥ ይበዙማል ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 4 ፤ የሚጠብቋቸውን ፡ እረኞች ፡ አስነሣላቸዋለኹ ፥ ዳግመኛም ፡ አይፈሩምና ፡ አይደነግጡም ፥ ከነሱም ፡ አንድ ፡ አይጐድልም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ ለዳዊት ፡ ጻድቅ ፡ ቀጥቋጥ ፡ የማስነሣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡

እግዚአብሔር ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ይነግሣል ፥ ይከናወንለታልም ፥ በምድርም ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ ያደርጋል ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በዘመኑም ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፡ እስራኤልም ፡ ተዘልሎ ፡ ይቀመጣል ፥ የሚጠራበትም ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፦ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ዳግመኛ ፡ የማይባልበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ኤር. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ዘር ፡ ከሰሜን ፡ አገርና ፡ ካሰደድኋቸውም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ያወጣና ፡ የመራ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ይባላል ፤ በምድራቸውም ፡ ይቀመጣሉ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ነቢያት ፤ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተሰብሯል ፡ ዐጥንቶቼም ፡ ኹሉ ፡ ታውከዋል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተነሣ ፡ ከቅዱስ ፡ ቃሉም ፡ የተነሣ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳሸነፈው ፡ እንደ ፡ ሰካራም ፡ ሰው ፡ ኾኛለኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ምድር ፡ ከአመንዝራዎች ፡ ተሞልታለችና ፥ ከመርገምም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ አልቅሳለች ፤ የምድረ ፡ በዳ ፡ ማሰማሪያ ፡ ደርቋል ፤ አካኼዳቸው ፡ ክፉ ፡ ነው ፥ ብርታታቸውም ፡ ቅን ፡ አይደለም ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ነቢዩና ፡ ካህኑም ፡ ረክሰዋልና ፥ በቤቴም ፡ ውስጥ ፡ ክፋታቸውን ፡ አግኝቻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ መንገዳቸው ፡ በጨለማ ፡ እንዳለች ፡ እንደ ፡ ድጥ ፡ ስፍራ ፡ ትኾንባቸዋለች ፥ እነርሱም ፡ ፍግምግም ፡ ብለው ፡ ይወድቁባታል ፤ እኔም ፡ በምጐበኛቸው ፡ ዓመት ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አመጣባቸዋለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 13 ፤ በሰማርያ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ስንፍናን ፡ አይቻለኹ ፤ በበዓል ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ፥ ሕዝቤንም ፡ እስራኤል ፡ ያስቱ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 14 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ የሚያስደነግጥን ፡ ነገር ፡ አይቻለኹ ፤ ያመነዝራሉ ፡ በሐሰትም ፡ ይኼዳሉ ፤ ማንም ፡ ከክፋቱ ፡ እንዳይመለስ ፡ የክፉ ፡ አድራጊዎችን ፡ እጅ ፡ ያበረታሉ ፤ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ የሚኖሩባትም ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፡ ኾኑብኝ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ነቢያት ፡ ዘንድ ፡ ርኵሰት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ወጥቷልና ፥ ሬትን ፡ አበላቸዋለኹ ፥ የሐሞትንም ፡ ውሃ ፡ አጠጣቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 16 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ትንቢት ፡ የሚናገሩላችኹን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ አትሰሙ ፤ ከንቱነትን ፡ ያስተምሯችኋል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ ሳይኾን ፡ ከገዛ ፡ ልባቸው ፡ የወጣውን ፡ ራእይ ፡ ይናገራሉ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ለሚንቁኝ ፡ ኹልጊዜ ፦ እግዚአብሔር ፦ ሰላም ፡ ይኾንላችኋል ፡ ብሏል ፡ ይላሉ ፤ በልቡም ፡ እልከኝነት ፡ ለሚኼድ ፡ ኹሉ ፦ ክፉ ፡ ነገር ፡ አያገኛችኹም ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ቃሉን ፡ ያይና ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ የቆመ ፡ ማን ፡ ነውና ፧ ቃሉንስ ፡ ያደመጠ ፡ የሰማስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 23 ፡ 19 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥ ርሱም ፡ ቀጣው ፥ የሚያገለባብጥ ፡ ዐውሎ ፡ ነፍስ ፡ ወጥቷል ፤ የዐመፀኞችን ፡ ራስ ፡ ይገለባብጣል ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀጣ ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመለስም ፤ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ታስተውሉታላችኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ ሳልካቸው ፡ እነዚህ ፡ ነቢያት ፡ ሮጡ ፤ እኔም ፡ ሳልነግራቸው ፡ ትንቢትን ፡ ተናገሩ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 22 ፤ በምክሬ ፡ ግን ፡ ቢቆሙ ፡ ኖሮ ፥ ለሕዝቤ ፡ ቃሌን ፡ ባሰሙ ፡ ነበር ፥ ከክፉም ፡ መንገዳቸው ፡ ከሥራቸውም ፡ ክፋት ፡ በመለሷቸው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እኔ ፡ የቅርብ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የሩቅ ፡ አምላክ ፡ አይደለኹም ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 24 ፤ ሰው ፡ በስውር ፡ ቢሸሸግ ፥ እኔ ፡ አላየውምን ፧ ሰማይንና ፡ ምድርንስ ፡ የሞላኹ ፡ እኔ ፡ አይደለኹምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 25 ፤ ዐለምኹ ፥ ዐለምኹ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገሩትን ፡ የነቢያትን ፡ ነገር ፡ ሰምቻለኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 26 ፤ ትንቢትን ፡ በሐሰት ፡ በሚናገሩ ፥ የልባቸውንም ፡ ሽንገላ ፡ በሚናገሩ ፡ በነቢያት ፡ ልብ ፡ ይህ ፡ የሚኾነው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 23 ፡ 27 ፤ አባቶቻቸው ፡ ስለ ፡ በዓል ፡ ስሜን ፡ እንደ ፡ ረሱ ፥ እያንዳንዱ ፡ ለባልንጀራው ፡ በሚናገራት ፡ ሕልማቸው ፡ ሕዝቤ ፡ ስሜን ፡ ለማስረሳት ፡ ያስባሉ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 28 ፤ የሚያልም ፡ ነቢይ ፡ ሕልምን ፡ ይናገር ፤ ቃሌም ፡ ያለበት ፡ ቃሌን ፡ በእውነት ፡ ይናገር ። ገለባ ፡ ከስንዴ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለው ፧

ኤር. ፡ 23 ፡ 29 ፤ በእውኑ ፡ ቃሌ ፡ እንደ ፡ እሳት ፥ ድንጋዩንም ፡ እንደሚያደቅ ፡ መዶሻ ፡ አይደለችምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እያንዳንዱ ፡ ከባልንጀራው ፡ ዘንድ ፡ ቃሌን ፡ በሚሰርቁ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 31 ፤ እንሆ ፥ ከምላሳቸው ፡ ትንቢትን ፡ አውጥተው ። ርሱ ፡ ይላል ፡ በሚሉ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 32 ፤ እንሆ ፥ ሐሰትን ፡ በሚያልሙ ፡ በሚናገሩም ፡ በሐሰታቸውና ፡ በድፍረታቸውም ፡ ሕዝቤን ፡ በሚያስቱ ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እኔም ፡ አልላክኋቸውም ፡ አላዘዝኋቸውምም ፡ ለእነዚህም ፡ ሕዝብ ፡ በማናቸውም ፡ አይረቧቸውም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 33 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ወይም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ ካህን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ቢጠይቅኽ ፥ አንተ ፦ ሸክሙ ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ፥ እጥላችኹማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ትላቸዋለኽ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 34 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ የሚለውን ፡ ነቢይንና ፡ ካህንን ፡ ሕዝቡንም ፡ ያን ፡ ሰውና ፡ ቤቱን ፡ እቀጣለኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 35 ፤ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለባልንጀራው ፥ አንዱም ፡ አንዱ ፡ ለወንድሙ ፡ እንዲህ ፡ ይበል ፦ እግዚአብሔር ፡ የመለሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እግዚአብሔርስ ፡ ምን ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፧

ኤር. ፡ 23 ፡ 36 ፤ ለሰው ፡ ዅሉ ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይኾንበታልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ይኾንበታልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብላችኹ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትጥሩ ፤ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የሕያውን ፡ አምላክ ፡ ቃል ፡ ለውጣችኋልና ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 37 ፤ ለነቢዩ ፦ እግዚአብሔር ፡ ምን ፡ መለሰልኽ ፧ እግዚአብሔርስ ፡ የተናገረው ፡ ምንድር ፡

ነው ፧ ትላለኽ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 38 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብትሉ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ አትበሉ ፡ ብዬ ፡ ልኬባችኋለኹና ፥ እናንተም ፡ ይህን ፡ ቃል ፦

ኤር. ፡ 23 ፡ 39 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሸክም ፡ ብላችኋልና ፥ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ፈጽሜ ፡ እረሳችኋለኹ ፥ እናንተንም ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ የሰጠኋትን ፡ ከተማ ፡ ከፊቴ ፡ እጥላለኹ ።

ኤር. ፡ 23 ፡ 40 ፤ የዘለዓለምንም ፡ ስድብ ፡ ከቶም ፡ ተረስቶ ፡ የማይጠፋውን ፡ የዘለዓለምን ፡ ዕፍረት ፡ አመጣባችኋለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 1 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንን ፡ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡ ጠራቢዎችንና ፡ ብረት ፡ ሠራተኞችን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኮ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ካፈለሳቸው ፡ በኋላ ፥ እግዚአብሔር ፡ አሳየኝ ፥ እንሆም ፥ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ፊት ፡ ኹለት ፡ ቅርጫት ፡ በለስ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 2 ፤ በአንደኛዉቱ ፡ ቅርጫት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በለስ ፡ የሚመስል ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ በለስ ፡ ነበረባት ፤ በኹለተኛዉቱ ፡ ቅርጫት ፡ ከክፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነበረባት ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ኤርምያስ ፡ ሆይ ፥ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለኝ ። እኔም ፦ በለስን ፡ አያለኹ ፤ እጅግ ፡ መልካም ፡ የኾነ ፡ መልካም ፡ በለስ ፥ ከክፋቱም ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ የኾነ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 24 ፡ 5 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ መልካሙ ፡ በለስ ፥ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡ ስፍራ ፡ ወደከለዳውያን ፡ ምድር ፡ የሰደድኹትን ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ ለበጎነት ፡ እመለከተዋለኹ ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 6 ፤ ዐይኔንም ፡ ለበጎነት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፡ ወደዚችም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ እሠራቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሳቸውም ፤ እተክላቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላቸውም ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 7 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ የሚያውቅ ፡ ልብ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ በፍጹምም ፡ ልባቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሳሉና ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከክፋቱ ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፡ እንደ ፡ ክፉው ፡ በለስ ፥ እንዲሁ ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ አለቃዎቹንም ፡ በዚችም ፡ አገር ፡ የሚቀሩትን ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ቅሬታ ፡ በግብጽም ፡ አገር ፡ የሚቀመጡትን ፡ እጥላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 9 ፤ በማሳድዳቸውም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ለስድብና ፡ ለምሳሌ ፡ ለማላገጫና ፡ ለርግማን ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ለመበተን ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ለእነርሱና ፡ ለአባቶቻቸውም ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በመካከላቸው ፡ ሰይፍንና ፡ ራብን ፡ ቸነፈርንም ፡ እሰዳለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፥ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ በመገዥመሪያው ፡ ዓመት ፥ ስለይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ለይሁዳ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለተቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረው ፦

ኤር. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ከይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ከዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮስያስ ፡ ከዐሥራ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ባሉት ፡ በእነዚህ ፡ በኻያ ፡ ሦስቱ ፡ ዓመታት ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፥ እኔም ፡ ማልጄ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናገርኋችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰማችኹም ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ማልዶ ፡ ተነሥቶ ፡ ባሪያዎቹን ፡ ነቢያትን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ላከ ፤ እናንተም ፡ አላደመጣችኹም ፡ ጐሯችኹንም ፡ አላዘነበላችኹም ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ኧላችኹ ፡ እናንተ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹና ፡ ከሥራችኹ ፡ ክፋት ፡ ተመለሱ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከዘለዓለም ፡ ወደ ፡ ዘለዓለም ፡ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ በሰጣችኹ ፡ ምድር ፡ ተቀመጡ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 6 ፤ ታመልኳቸውም ፡ ትሰግዱላቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ፥ ክፉም ፡ እንዳላደርግባችኹ ፡ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ አታስቈጡኝ ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 7 ፤ ለእናንተ ፡ ጕዳት ፡ እንዲኾን ፡ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ ታስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ አልሰማችኹኝም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቃሌን ፡ አልሰማችኹምና ፥ እንሆ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ልኬ ፡ የሰሜንን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ባሪያዬንም ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርን ፡ እወስዳለኹ ፥ በዚችም ፡ ምድር ፡ በሚቀመጡባትም ፡ ሰዎች ፡ በዙሪያዋም ፡ ባሉ ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ ፈጽሜም ፡ አጠፋቸዋለኹ ፥ ለመደነቂያና ፡ ለማፏጫም ፡ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ከነርሱም ፡ የእልልታን ፡ ድምፅና ፡ የደስታን ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራን ፡ ድምፅ ፥ የወፍጮንም ፡ ድምፅ ፡ የመብራትንም ፡ ብርሃን ፡ አስቀራለኹ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 11 ፤ ይህችም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ባድማና ፡ መደነቂያ ፡ ትኾናለች ፤ እነዚህም ፡ አሕዛብ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ ይገዛሉ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 12 ፤ ሰባው ፡ ዓመትም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ያን ፡ ሕዝብ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታቸው ፡ እቀጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የከለዳውያንንም ፡ ምድር ፡ ለዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 13 ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ የተናገርኹትን ፡ ቃሌን ፡ ኹሉ ፥ ማለት ፡ ኤርምያስ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ የተናገረውን ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ ኹሉ ፥ በዚያች ፡ ምድር ፡ አመጣለኹ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላላቆች ፡ ነገሥታት ፡ እነርሱን ፡ ያስገዟቸዋል ፤ እኔም ፡ እንደ ፡ አደራረጋቸውና ፡ እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ እከፍላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ የዚህን ፡ ቍጣ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጽዋ ፡ ከእጄ ፡ ውሰድ ፡ አንተንም ፡ የምሰድባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ አጠጣቸው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 16 ፤ ከምሰድባቸውም ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ይጠጣሉ ፡ ይወላገዱማል ፡ ያብዳሉም ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 17 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ ጽዋውን ፡ ወሰድኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እኔን ፡ የሰደደባቸውን ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ አጠጣኋቸው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 18 ፤ ዛሬ ፡ እንደ ኾነው ፡ ኹሉ ፡ ባድማና ፡ መደነቂያ ፡ ማፏጫም ፡ ርግማንም ፡ ኣደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ነገሥታቷንም ፡ አለቃዎቿንም ፡ አጠጣኋቸው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 19 ፤ የግብጽንም ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ አለቃዎቹንም ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 20 ፤ የተደባለቀውንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ የዖፅ ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የፍልስጥኤም ፡ ምድር ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፡ አስቀሎናንም ፡ ጋዛንም ፡ ዐቃሮንንም ፡ የአዞጦንንም ፡ ቅሬታ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 21 ፤ ኤዶምያስንም ፥ ሞዐብንም ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 22 ፤ የጤሮስን ፡ ነገሥታትም ፡ ኹሉ ፥ የሲዶናን ፡ ነገሥታት ፡ ኹሉ ፥ በባሕር ፡ ማዶ ፡ ያለች ፡ የደሴት ፡ ነገሥታትንም ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 23 ፤ ድዳንንም ፥ ቴማንንም ፥ ቡዝንም ፥ ጠጕራቸውንም ፡ የሚቈርጡትን ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 24 ፤ የዐረብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚቀመጡ ፡ የድብልቅ ፡ ሕዝብ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 25 ፤ የዘምሪ ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የዔላም ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፡ 25 ፡ 26 ፤ የሜዶን ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ የቀረቡና ፡ የራቁ ፥ አንዱ ፡ ከሌላው ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ የሰሜን ፡ ነገሥታትንም ፡ ኹሉ ፥ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ የዓለም ፡ መንግሥታትንም ፡ ኹሉ ፡ አጠጣኋቸው ፤ የሼሻክም ፡ ንጉሥ ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ይጠጣል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 27 ፤ አንተም ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመካከላችኹ ፡ ከምሰደው ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ ጠጡ ፥ ስከሩም ፥ አስታውኩም ፡ ውደቁም ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አትነሡም ፡ በላቸው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ይጠጡም ፡ ዘንድ ፡ ጽዋውን ፡ ከእጅኽ ፡ ለመቀበል ፡ እንቢ ፡ ቢሉ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፈጽማችኹ ፡ ትጠጣላችኹ ፡ በላቸው ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 29 ፤ እንሆ ፥ ስሜ ፡ የተጠራባትን ፡ ከተማ ፡ አስጨንቃት ፡ ዘንድ ፡ እገሥምራለኹ ፤ በእውኑ ፡ እናንተ ፡ ያልተቀጣችኹ ፡ ትኾናላችኹን ፧ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሰይፍን ፡ እጠራለኹና ፡ ያለቅጣት ፡ አትቀሩም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ትንቢት ፡ ትናገርባቸዋለኽ ፥ እንዲህም ፡ ትላቸዋለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡ ይጮኻል ፥ በቅዱስ ፡ ማደሪያውም ፡ ኾኖ ፡ ድምፁን ፡ ያሰማል ፤ በበረቱ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ይጮኻል ፥ ወይንም ፡ እንደሚጠምቁ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይጮኻል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ ድምፅ ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይደርሳል ፤ ከሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳል ፥ ኀጢአተኞችንም ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 32 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከሕዝብ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጣል ፥ ጽኑም ፡ ዐውሎ ፡ ነፍስ ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 33 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ግዳዩች ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምድር ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ይኾናሉ ፤ አይለቀስላቸውም ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፡ አይከማቹም ፡ አይቀበሩምም ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 34 ፤ ትታረዱና ፡ ትበተኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀናችኹ ፡ ደርሷልና ፥ እንደ ፡ ተወደደም ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ትወድቃላችኹና ፡ እናንተ ፡ እረኞች ፥ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፤ እናንተ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎች ፥ በዐመድ ፡ ውስጥ ፡ ተንከባለሉ ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 35 ፤ ሽሽትም ፡ ከእረኞች ፡ ማምለጥም ፡ ከመንጋ ፡ አውራዎች ፡ ይጠፋል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 36 ፤ እግዚአብሔር ፡ ማሰማሪያቸውን ፡ አጥፍቷልና ፥ የእረኞች ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ የመንጋ ፡ አውራዎችም ፡ ልቅሶ ፡ ኾኗል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 37 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ የሰላም ፡ በረት ፡ ፈርሷል ።

ኤር. ፡ 25 ፡ 38 ፤ እንደ ፡ አንበሳ ፡ መደቡን ፡ ለቋል ፤ ካስጨናቂውም ፡ ሰይፍና ፡ ከጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የተነሣ ፡ ምድራቸው ፡ ባድማ ፡ ኾናለችና ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መጣ ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ቁም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ለሚመጡት ፡ ለይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ ያዘዝኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ተናገራቸው ፤ አንዲትም ፡ ቃል ፡ አታጕድል ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 3 ፤ ምናልባት ፡ ይሰሙ ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸውም ፡ ይመለሱ ፡ ይኾናል ፤ እኔም ፡ ስለሥራቸው ፡ ክፋት ፡ ያሰብኹባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እተዋለኹ ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በፊታችኹ ፡ በሰጠኋት ፡ ሕጌ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ባትሰሙኝ ፥

ኤር. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ያልሰማችኹትን ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የላክኋቸውን ፡ የባሪያዎቼን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥

ኤር. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ይህን ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሴሎ ፡ አደርገዋለኹ ፥ ይህችንም ፡ ከተማ ፡ ለምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ርግማን ፡ አደርጋታለኹ ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ካህናቱም ፡ ነቢያቱም ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ኤርምያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲናገር ፡ ሰሙ ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 8 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ካህናትና ፡ ነቢያት ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፦ ሞትን ፡ ትሞታለኽ ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፦ ይህ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ሴሎ ፡ ይኾናል ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ ትኾናለች ፡ ብለኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትንቢት ፡ ተናገርኽ ፧ ብለው ፡ ያዙት ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በኤርምያስ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 26 ፡ 10 ፤ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡

ወጡ ፥ በዐዲሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ መግቢያ ፡ ተቀመጡ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 11 ፤ ካህናቱና ፡ ነቢያቱም ፡ ለአለቃዎቹና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሹሉ ፦ በገሮሾችኹ ፡ እንደ ፡ ሰማችኹ ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሯልና ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ ሞት ፡ የሚገባው ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 12 ፤ ኤርምያስም ፡ ለአለቃዎችና ፡ ለሕዝቡ ፡ ሹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፦ በሰማችኹት ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ በዚች ፡ ቤትና ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልኮኛል ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 13 ፤ አኹንም ፡ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ አሳምሩ ፥ የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የተናገረባችኹን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ይተዋል ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 14 ፤ እኔ ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ በእጃችኹ ፡ ነኝ ፤ በዐይናችኹ ፡ መልካምና ፡ ቅን ፡ የመሰለውን ፡ አድርጉብኝ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ በገሮሾችኹ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ በእውነት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልኮኛልና ፥ ብትገድሉኝ ፡ ንጹሕ ፡ ደምን ፡ በራሳችኹና ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ በሚኖሩባትም ፡ ላይ ፡ እንድታመጡ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቁ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 16 ፤ አለቃዎቹና ፡ ሕዝቡም ፡ ሹሉ ፡ ለካህናትና ፡ ለነቢያት ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተናግሮናልና ፥ ሞት ፡ አይገባውም ፡ አሉ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 17 ፤ ከአገሩ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ ለሕዝቡ ፡ ጉባኤ ፡ ሹሉ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 18 ፤ ሞሬታዊው ፡ ሚክያስ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሕዝቅያስ ፡ ዘመን ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፤ ለይሁዳም ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጽዮን ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ትታረሳለች ፥ ኢየሩሳሌም ፡ የፍርስራሽ ፡ ክምር ፡ ትኾናለች ፥ የቤቱም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ከፍታ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 19 ፤ በእውኑ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሕዝቅያስና ፡ ሕዝቡ ፡ ሹሉ ፡ ገደሉትን ፧ በእውኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አልፈሩምን ፧ ወደ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ አልተማለሉምን ፧ እግዚአብሔርስ ፡ የተናገረባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አይተውምን ፧ እኛም ፡ በነፍሳችን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ እናደርጋለን ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 20 ፤ ደግሞም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ትንቢት ፡ የተናገረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ የቂርያትይዓሪም ፡ ሰው ፥ የሸማያ ፡ ልጅ ፥ ኦርዮ ፡ ይባል ፡ ነበር ፤ በዚችም ፡ ከተማ ፡ በዚችም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ኤርምያስ ፡ ቃል ፡ ሹሉ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ ኀያላኑም ፡ ሹሉ ፡ አለቃዎቹም ፡ ሹሉ ፡ ቃሉን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ ሊገድለው ፡ ፈለገ ፤ ኦርዮም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ፈርቶ ፡ ሸሸ ፡ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ገባ ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 22 ፤ ንጉሡም ፡ ኢዮአቄም ፡ የዓክቦርን ፡ ልጅ ፡ ኤልናታንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላዎችን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ላካቸው ፤

ኤር. ፥ 26 ፥ 23 ፤ ከግብጽም ፡ ኦርዮን ፡ አውጥተው ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ወደ ፡ ኢዮአቄም ፡ ይዘውት ፡ መጡ ፤ ርሱም ፡ በሰይፍ ፡ ገደለው ፡ ሬሳውንም ፡ ክቡራን ፡ ባልኾኑ ፡ ሰዎች ፡ መቃብር ፡ ጣለው ።

ኤር. ፥ 26 ፥ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝቡ ፡ እጅ ፡ እንዳይሰጥና ፡ እንዳይገድሉት ፡ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ የአኪቃም ፡ እጅ ፡ ከኤርምያስ ፡ ጋራ ፡ ነበረች ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ መንግሥት ፡ መገመሪያ ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፦ እስራትና ፡ ቀንበር ፡ ሥራ ፡ በዐንገትኽም ፡ ላይ ፡ አድርግ ፤

ኤር. ፡ 27 ፡ 3 ፤ ወደይሁዳ ፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በመጡት ፡ መልእክተኞች ፡ እጅ ፡ ወደኤዶምያስ ፡ ንጉሥ ፡ ወደሞዐብም ፡ ንጉሥ ፡ ወደዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ ወደጢሮስም ፡ ንጉሥ ፡ ወደሲዶናም ፡ ንጉሥ ፡ ላካቸው ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ለጌታዎቻቸውም ፡ እንዲነግሩ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ እዘዛቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለጌታዎቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ምድሪቱን ፡ በምድርም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎችንና ፡ እንስሳዎችን ፡ በታላቅ ፡ ኀይሌና ፡ በተዘረጋችው ፡ ክንዴ ፡ ፈጥሬያለኹ ፤ ለዐይኔም ፡ መልካም ፡ ለኾነው ፡ እሰጣታለኹ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 6 ፤ አኹንም ፡ እነዚህን ፡ ምድሮች ፡ ኹሉ ፡ ለባሪያዬ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቻለኹ ፤ ይገዙለትም ፡ ዘንድ ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊትን ፡ ደግሞ ፡ ሰጥቼዋለኹ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 7 ፤ የገዛ ፡ ራሱም ፡ ምድር ፡ ጊዜ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ለርሱና ፡ ለልጅ ፡ ለልጅ ፡ ልጁም ፡ ይገዛሉ ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ አሕዛብና ፡ ታላላቆች ፡ ነገሥታት ፡ ርሱን ፡ ያስገዙታል ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥም ፡ ለናቡከደነጾር ፡ የማይገዛውን ፥ ከባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገቱን ፡ ዝቅ ፡ የማያደርገውን ፡ ሕዝብና ፡ መንግሥት ፥ ያን ፡ ሕዝብ ፡ በእጁ ፡ እስካጠፋው ፡ ድረስ ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እቀጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትገዙም ፡ የሚሏችኹን ፡ ነቢያታችኹንና ፡ ሟርተኞቻችኹን ፥ ሕልም ፡ ዐላሚዎቻችኹንና ፡ ቃላተኞቻችኹን ፡ መተተኞቻችኹንም ፡ አትስሙ ፤

ኤር. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ከምድራችኹ ፡ እንዲያርቋችኹ ፥ እኔም ፡ እንዳሳድዳችኹ ፡ እናንተም ፡ እንድትጠፉ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገሩላችኋልና ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገቱን ፡ ዝቅ ፡ የሚያደርገውንና ፡ የሚገዛለትን ፡ ሕዝብ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ እተወዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያርሷታል ፡ ይቀመጡባትማል ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 12 ፤ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተናገርኹ ፦ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ በታች ፡ ዐንገታችኹን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፥ ለርሱና ፡ ለሕዝቡም ፡ ተገዙላቸው ፥ በሕይወትም ፡ ኑሩ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 13 ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ሕዝብ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ አንተና ፡ ሕዝብኽ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ለምን ፡ ትሞታላችኹ ፧

ኤር. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ሐሰተኛን ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኋልና ። ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትገዙም ፡ የሚሏችኹን ፡ የነቢያትን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ አልላክኋቸውምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ እንዳሳድዳችኹ ፥ እናንተና ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩላችኹ ፡ ነቢያትም ፡ እንድትጠፉ ፡ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገራሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 16 ፤ ለካህናትም ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ተናገርኹ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሐሰተኛውን ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኋልና ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ከባቢሎን ፡ ይመለሳል ፡ የሚሏችኹን ፡ የነቢያታችኹን ፡ ቃል ፡ አትስሙ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 17 ፤ እነርሱም ፡ አትስሙ ፤ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ፡ በሕይወትም ፡ ኑሩ ። ይህችስ ፡ ከተማ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፧

ኤር. ፡ 27 ፡ 18 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ነቢያት ፡ ቢኾኑ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ቢገኝ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የቀረችው ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ እንዳትኼድ ፡ ወደሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይማለሉ ።

ኤር. ፡ 27 ፡ 19-20 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንንና ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ከበርቴዎች ፡ ኹሉ ፡ ማርኮ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ባፈለሳቸው ፡ ጊዜ ፡ ስላልወሰዳቸው ፡ ዐምዶች ፡ ስለ ፡ ኵሬውም ፡ ስለ ፡ መቀመጫዎቹም ፡ በዚችም ፡ ከተማ ፡ ስለቀረች ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፤

ኤር. ፡ 27 ፡ 21 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቤትና ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ስለቀረችው ፡ ዕቃ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ትወሰዳለች ፡ እስከምጐበኛትም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ትኖራለች ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አወጣታለኹ ፡ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳታለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ዓመት ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ መንግሥት ፡ መጀመሪያ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ነቢዩ ፡ የገባዖን ፡ ሰው ፡ የዓዙር ፡ ልጅ ፡ ሐናንያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በካህናትና ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ። የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ ሰብሬያለኹ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 3 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ከዚች ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የወሰዳትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ወደዚች ፡ ስፍራ ፡ እመልሳታለኹ ፤

ኤር. ፡ 28 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ የኼዱትን ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የኢዮአቄምን ፡ ልጅ ፡ ኢኮንያንንና ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ ኹሉ ፡ ወደዚች ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ቀንበር ፡ እሰብራለኹና ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 5 ፤ ነቢዩ ፡ ኤርምያስም ፡ በካህናቱና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በቆሙት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ለነቢዩ ፡ ለሐናንያ ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 6 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አሜን ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያድርግ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ምርኮውንም ፡ ኹሉ ፡ ከባቢሎን ፡ ወደዚህ ፡ ስፍራ ፡ በመመለስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተናገርኸውን ፡ ትንቢት ፡ ይፈጽም ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በገሮሮኽና ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ጐሮ ፡ የምናገረውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤

ኤር. ፡ 28 ፡ 8 ፤ ከጥንት ፡ ከእኔና ፡ ከአንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩ ፡ ነቢያት ፡ በብዙ ፡ አገርና ፡ በታላላቅ ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሰልፍና ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ቸነፈርም ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ሰላም ፡ የተናገረ ፡ ነቢይ ፥ የነቢዩ ፡ ቃል ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ የሰደደው ፡ ነቢይ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይታወቃል ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 10 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ ቀንበሩን ፡ ከነቢዩ ፡ ከኤርምያስ ፡ ዐንገት ፡ ወስዶ ፡ ሰበረው ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ሐናንያም ፡ በሕዝብ ፡ ዅሉ ፡ ፊት ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንዲሁ ፡ በዅለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ የናቡከደነጾርን ፡ ቀንበር ፡ ከአሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ዐንገት ፡ እሰብራለዅ ፡ አለ ። ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ መንገዱን ፡ ኼደ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ ቀንበሩን ፡ ከነቢዩ ፡ ከኤርምያስ ፡ ዐንገት ፡ ከሰበረ ፡ በኋላ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ኺድ ፥ ለሐናንያ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ንገረው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፡ የዕንጨትን ፡ ቀንበር ፡ ሰብረኻል ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ የብረትን ፡ ቀንበር ፡ እሠራለዅ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 14 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ ይገዙለት ፡ ዘንድ ፡ የብረትን ፡ ቀንበር ፡ በእነዚህ ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ዐንገት ፡ ላይ ፡ አድርጌያለዅ ፤ እነርሱም ፡ ይገዙለታል ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ደግሞ ፡ ሰጥቼዋለዅ ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ ነቢዩን ፡ ሐናንያን ፦ ሐናንያ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በሐሰት ፡ እንዲታመን ፡ አድርገኻል ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ አላከኽም ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ከምድር ፡ ላይ ፡ እሰድኻለዅ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በመፅን ፡ ተናግረኻልና ፥ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ትሞታለኽ ፡ አለው ።

ኤር. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ነቢዩም ፡ ሐናንያ ፡ በዚያው ፡ ዓመት ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ሞተ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 1 ፤ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ወደተረፉት ፡ የምርኮ ፡ ሽማግሌዎች ፥ ወደ ፡ ካህናቱም ፥ ወደ ፡ ነቢያቱም ፥ ናቡከደነጾር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማርኮ ፡ ወሰፈለሰውም ፡ ሕዝብ ፡ ዅሉ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የላከው ፡ የደብዳቤው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 2 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ንጉሡ ፡ ኢኮንያን ፣ እናቱም ፡ እቴጌዪቱ ፣ ጃን ፡ ደረባዎቹም ፣ የይሁዳና ፡ የኢየሩሳሌምም ፡ አለቃዎች ፣ ጠራቢዎችና ፡ ብረት ፡ ሠራተኞችም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 3 ፤ ኤርምያስ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በላካቸው ፡ በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በኤልዓሣና ፡ በኬልቅያስ ፡ ልጅ ፡ በገማርያ ፡ እጅ ፡ ደብዳቤውን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ላከው ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ላስማረክኋቸው ፡ ምርኮኞች ፡ ዅሉ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 29 ፡ 5 ፤ ቤት ፡ ሠርታችኹ ፡ ተቀመጡ ፥ አታክልትም ፡ ተክላችኹ ፡ ፍሬዋን ፡ ብሉ ፤

ኤር. ፡ 29 ፡ 6 ፤ ተጋቡ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ውለዱ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹንም ፡ አጋቡ ፥ እነርሱም ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆች ፡ ይውለዱ ፤ ከዚያም ፡ ተባዙ ፡ ጥቂቶችም ፡ አትኹኑ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 7 ፤ በርሷ ፡ ሰላም ፡ ሰላም ፡ ይኾንላችኋልና ፥ ወደ ፡ ርሷ ፡ ላስማርክኋችኹ ፡ ከተማ ፡ ሰላምን ፡ ፈልጉ ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 8 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በመካከላችኹ ፡ ያሉት ፡ ነቢያታችኹና ፡ ሟርተኞቻችኹ ፡ አያታሏችኹ ፥ እናንተም ፡ የምታልሙትን ፡ ሕልም ፡ አትስሙ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 9 ፤ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ይናገሩላችኋልና ፤ እኔም ፡ አላክኋቸውም ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሰባው ፡ ዓመት ፡ በባቢሎን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ እጐበኛችኋለኹ ፥ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳችኹ ፡ ዘንድ ፡ መልካሚቱን ፡ ቃሌን ፡ እፈጽምላችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 11 ፤ ለእናንተ ፡ የማስባትን ፡ ዐሳብ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ፤ ፍጻሜና ፡ ተስፋ ፡ እሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ የሰላም ፡ ዐሳብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የክፉ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 12 ፤ እናንተም ፡ ትጠሩኛላችኹ ፥ ኼዳችኹም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትጸልያላችኹ ፥ እኔም ፡ እሰማችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ ትሹኛላችኹ ፥ በፍጹም ፡ ልባችኹም ፡ ከሻችኹኝ ፡ ታገኙኛላችኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 14 ፤ ከእናንተም ፡ ዘንድ ፡ እገኛለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ምርኳችኹንም ፡ እመልሳለኹ ፥ ከአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እናንተንም ፡ ካሳደድኹበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ እሰበስባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እናንተንም ፡ ለምርኮ ፡ ወዳፈለስኹበት ፡ ስፍራ ፡ እመልሳችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 15 ፤ እናንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ ነቢያትን ፡ አስነሥቶልናል ፡ ብላችኋልና ፤

ኤር. ፡ 29 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዳዊት ፡ ዙፋን ፡ ስለተቀመጠ ፡ ንጉሥ ፡ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ስላልተማረኩት ፡ ወንድሞቻችኹ ፥ በዚች ፡ ከተማ ፡ ስለሚኖሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

ኤር. ፡ 29 ፡ 17 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሰይፍንና ፡ ራብን ፡ ቸነፈርንም ፡ እሰድባቸዋለኹ ፥ ከክፉቱም ፡ የተነሣ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደማይቻል ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ በለስ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 18 ፤ በሰይፍም ፡ በራብም ፡ በቸነፈርም ፡ አሳዳድዳቸዋለኹ ፥ ባሳደድኹባቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ለጥላቻና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለማፏጫም ፡ ለመሰደቢያም ፡ እንዲኾኑ ፡ በምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ለመበተን ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ቃሌን ፡ ስላልሰሙ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ሰድጃለኹና ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ አልሰማችኹም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 20 ፤ ስለዚህ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ የሰደድኋችኹ ፡ ምርኮኞች ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 21 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስሜ ፡ ሐሰተኛ ፡ ትንቢትን ፡ ስለሚናገሩላችኹ ፡ ስለቆላያ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ አክአብና ፡ ስለመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ስለ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ በዐይኖቻችኹም ፡ ፊት ፡ ይገድላቸዋል ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 22 ፤ ከነርሱም ፡ የተነሣ ፡ በባቢሎን ፡ ያሉ ፡ የይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ ኹሉ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ጠበሳቸው ፡ እንደ ፡ ሴዴቅያስና ፡ እንደ ፡ አክአብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያድርግኽ ፡ የምትባል ፡ ርግማንን ፡ ያነሣሉ ፤ እኔም ፡ ዐውቃለኹ ፡ ምስክርም ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 23 ፤ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ አድርገዋልና ፥ ከባልንጀራዎቻቸውም ፡ ሚስቶች ፡ ጋራ ፡ አመንዝረዋልና ፥ ያላዘዝኋቸውንም ፡ ቃል ፡ በስሜ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋልና ።

ኤር. ፡ 29 ፡ 24 ፤ ለኔሔላማዊው ፡ ለሸማያ ፡ እንዲህ ፡ በል ፦

ኤር. ፡ 29 ፡ 25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኢየሩሳሌም ፡

ወዳለው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ ካህኑም ፡ ወደመዕሴያ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሶፎንያስ ፥ ወደ ፡ ካህናቱም ፡ ኹሉ ፡ ደብዳቤዎችን ፡ በስምኽ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ልከኻል ።

ኤር. ፥ 29 ፥ 26 ፤ እያበደ ፡ ትንቢት ፡ የሚናገርን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በእግር ፡ ግንድና ፡ በዛንጅር ፡ ታኖረው ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አለቃ ፡ እንድትኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በካህኑ ፡ በዮዳዔ ፡ ፋንታ ፡ ካህን ፡ አድርጎኻል ።

ኤር. ፥ 29 ፥ 27 ፤ አኹንስ ፡ ትንቢት ፡ ተናጋሪውን ፡ የዓናቶቱን ፡ ሰው ፡ ኤርምያስን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትዘልፈውም ፧

ኤር. ፥ 29 ፥ 28 ፤ ርሱ ፦ ምርኮው ፡ የረዘመው ፡ ነውና ፥ ቤት ፡ ሠርታችኹ ፡ ተቀመጡ ፥ አታክልትንም ፡ ተክላችኹ ፡ ፍሬዋን ፡ ብሉ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ልኳልና ።

ኤር. ፥ 29 ፥ 29 ፤ ካህኑም ፡ ሶፎንያስ ፡ ይህን ፡ ደብዳቤ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ ጕሮ ፡ አነበበው ።

ኤር. ፥ 29 ፥ 30 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፥ 29 ፥ 31 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኔሔላማዊው ፡ ስለ ፡ ሸማያ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ወደ ፡ ምርኮኞች ፡ ኹሉ ፡ ላክ ። እኔ ፡ ሳልከው ፡ ሸማያ ፡ ትንቢት ፡ ተናግሮላችኋልና ፥ በሐሰትም ፡ እንድትታመኑ ፡ አድርጓችኋልና ፤

ኤር. ፥ 29 ፥ 32 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ኔሔላማዊውን ፡ ሸማያንና ፡ ዘሩን ፡ እቀጣለኹ ፤ እኔም ፡ የማደርግላችኹን ፡ መልካሙን ፡ ነገር ፡ የሚያይ ፡ ሰው ፡ በመካከላችኹ ፡ አይኖርላችኹም ፡

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 1 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 30 ፥ 2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የነገርኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ጻፍ ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 3 ፤ እንሆ ፥ የሕዝቤን ፡ የእስራኤልንና ፡ የይሁዳን ፡ ምርኮ ፡ የምመልስባት ፡ ዘመን ፡ ይመጣልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለአባቶቻቸውም ፡ ወደሰጠኋት ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ እነርሱም ፡ ይገዟታል ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እስራኤልና ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 30 ፥ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ የሚያስፈራ ፡ ድምፅ ፡ ሰምተናል ፤ የፍርሀት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሰላም ፡ አይደለም ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 6 ፤ ጠይቁ ፥ ወንድ ፡ ይወልድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመልከቱ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ወላድ ፡ እጁን ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ አድርጎ ፡ ፊቱም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጥቀሩት ፡ ተለውጦ ፡ አየኹ ፧

ኤር. ፥ 30 ፥ 7 ፤ ወዮ! ፡ ያ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ርሱንም ፡ የሚመስል ፡ የለምና ፤ ያ ፡ የያዕቆብ ፡ መከራ ፡ ዘመን ፡ ነው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከርሱ ፡ ይድናል ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ቀንበርን ፡ ከዐንገትኽ ፡ እሰብራለኹ ፥ እስራትኽንም ፡ እበጥሳለኹ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ለሌላ ፡ አትገዛም ፤

ኤር. ፥ 30 ፥ 9 ፤ ለአምላካቸው ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ለማስነሣላቸው ፡ ለንጉሣቸው ፡ ለዳዊትም ፡ ይገዛሉ ፡ እንጂ ፡ ሌላዎች ፡ አሕዛብ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ አይገዟቸውም ።

ኤር. ፥ 30 ፥ 10 ፤ እንሆ ፥ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርኽንም ፡ ከምርኮ ፡ አገር ፡ አድናለኹና ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አትደንግጥ ፤ ያዕቆብም ፡ ይመለሳል ፡ ያርፍማል ፡

ተዘልሎም ፡ ይቀመጣል ፤ ማንም ፡ አያስፈራውም ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 11 ፤ አድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንተንም ፡ የበተንኹባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለኹ ፥ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋኽም ፤ በመጠን ፡ እቀጣኻለኹ ፥ ያለቅጣትም ፡ ከቶ ፡ አልተውኽም ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስብራትኽ ፡ የማይፈወስ ፡ ቍስልኽም ፡ ክፉ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ትጠገን ፡ ዘንድ ፡ ክርክርኽን ፡ የሚፈርድልኽ ፡ የለም ፥ ቍስልኽንም ፡ የሚፈውስ ፡ መድኀኒት ፡ የለኽም ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ውሽማዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ ረስተውኻል ፡ አይፈልጉኽምም ፤ በደልኽ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኀጢአትኽም ፡ ስለ ፡ በዛ ፥ በጠላት ፡ ማቍሰልና ፡ በጨካኝ ፡ ቅጣት ፡ አቍስዬኻለኹና ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 15 ፤ ሕመምኽ ፡ የማይፈወስ ፡ ኾኗልና ፥ ስለ ፡ ስብራትኽ ፡ ለምን ፡ ትጮኻለኽ ፧ በደልኽ ፡ ታላቅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ኀጢአትኽም ፡ ስለ ፡ በዛ ፥ ይህን ፡ አድርጌብኻለኹ ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ የሚውጡኽ ፡ ኹሉ ፡ ይዋጣሉ ፥ ጠላቶችኽም ፡ ኹላቸው ፡ ይማረካሉ ፤ የዘረፉኽም ፡ ይዘረፋሉ ፥ የበዘበዙኽንም ፡ ኹሉ ፡ ለመበዝበዝ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 17 ፤ እኔ ፡ ጤናኽን ፡ እመልስልኻለኹ ፡ ቍስልኽንም ፡ እፈውሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ማንም ፡ የማይሻት ፥ የተጣለች ፡ ጽዮን ፡ ብለው ፡ ጠርተውሻልና ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የያዕቆብን ፡ ድንኳን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ለማደሪያውም ፡ እራራለኹ ፤ ከተማዪቱም ፡ በጕብታዋ ፡ ላይ ፡ ትሠራለች ፥ አዳራሹም ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 19 ፤ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ የምስጋናና ፡ የዘፋኞች ፡ ድምፅ ፡ ይወጣል ፤ እኔም ፡ አበዛቸዋለኹ ፡ አያንሱምም ፥ እኔም ፡ አከብራቸዋለኹ ፡ ታናሽም ፡ አይኾኑም ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 20 ፤ ልጆቻቸውም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ይኾናሉ ፥ ማኅበራቸውም ፡ በፊቴ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፤ የሚያስጨንቋቸውንም ፡ ኹሉ ፡ እቀጣለኹ ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 21 ፤ አለቃቸው ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናል ፥ ገዥቸውም ፡ ከመካከላቸው ፡ ይወጣል ፤ እኔ ፡ አቀርበዋለኹ ፡ ርሱም ፡ ይቀርባል ፤ ይህስ ፡ ባይኾን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ለመቅረብ ፡ የሚደፍር ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 22 ፤ እናንተም ፡ ሕዝብ ፡ ትኾኑኛላችኹ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 23 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፥ ርሱም ፡ ቍጣው ፥ የሚያገለባብጥ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ወጥቷል ፤ የዐመፀኞችንም ፡ ራስ ፡ ይገለባብጣል ።

ኤር. ፡ 30 ፡ 24 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ የልቡን ፡ ዐሳብ ፡ ሠርቶ ፡ እስኪፈጽም ፡ ድረስ ፡ አይመለስም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ታስተውሉታላችኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ለእስራኤል ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤል ፡ ማረፊያ ፡ ሊሻ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ከሰይፍ ፡ የተረፈው ፡ ሕዝብ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሞገስ ፡ አገኘ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከሩቅ ፡ ተገለጠልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ በዘለዓለም ፡ ፍቅር ፡ ወድጄሻለኹ ፤ ስለዚህ ፥ በቸርነት ፡ ሳብኹሽ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ገና ፡ እሠራሻለኹ ፡ አንቺም ፡ ትሠሪያለሽ ፤ እንደ ፡ ገናም ፡ ከበሮሽን ፡ አንሥተሽ ፡ ከዘፋኞች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ዘፈን ፡ ትወጣለሽ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ገናም ፡ በሰማርያ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የወይን ፡ ቦታዎችን ፡ ትተክሊያለሽ ፤ አትክልተኞች ፡ ይተክላሉ ፡ በፍሬውም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 6 ፤ በኤፍሬምም ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ ጠባቂዎች ፦ ተነሡ ፥ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንውጣ ፡ ብለው ፡ የሚጮኹበት ፡ ቀን ፡ ይመጣልና ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ስለ ፡ ያዕቆብ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ስለ ፡ አሕዛብም ፡ አለቃዎች ፡ እልል ፡ በሉ ፤ አውሩ ፥ አመስግኑ ። እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ የእስራኤልን ፡ ቅሬታ ፡ አድኗል ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ ከሰሜን ፡ አገር ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ ከምድርም ፡ ዳርቻ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ በመካከላቸውም ፡ ዕውሩና ፡ ዐንካሳው ፡ ያረገዘችና ፡ የወለደችም ፡ በአንድነት ፤ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ኾነው ፡ ወደዚህ ፡ ይመለሳሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 9 ፤ በልቅሶ ፡ ወጡ ፡ እኔም ፡ በማጽናናት ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ በወንዝ ፡ ዳር ፡ በቅን ፡ መንገድ ፡ አስኬዳቸዋለኹ ፥ በርሱም ፡ አይሰናከሉም ፤ እኔ ፡ ለእስራኤል ፡ አባት ፡ ነኝና ፥ ኤፍሬምም ፡ በኩሬ ፡ ነውና ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 10 ፤ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፥ በሩቅም ፡ ላሉ ፡ ደሴቶች ፡ አውሩና ፦ እስራኤልን ፡ የበተነ ፡ ርሱ ፡ ይሰበስበዋል ፥ እረኛም ፡ መንጋውን ፡ እንደሚጠብቅ ፡ ይጠብቀዋል ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያዕቆብን ፡ ተቤዥቶታል ፥ ከበረቱበትም ፡ እጅ ፡ አድኖታል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 12 ፤ ይመጣሉ ፡ በጽዮንም ፡ ተራራ ፡ እልል ፡ ይላሉ ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ በጎነት ፥ ወደ ፡ እኽልና ፡ ወደ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ወደ ፡ ዘይትም ፥ ወደ ፡ በጎችና ፡ ወደ ፡ ላሞች ፡ ይሰበሰባሉ ፤ ነፍሳቸውም ፡ እንደ ፡ ረካች ፡ ገነት ፡ ትኾናለች ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አያዝኑም ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ድንግሊቱ ፡ በዘፈን ፡ ደስ ፡ ይላታል ፥ ጐበዛዝቱና ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፤ ልቅሷቸውንም ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ እመልሳለኹ ፥ አጽናናቸውማለኹ ፥ ከሐዘናቸውም ፡ ደስ ፡ አሠኛቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 14 ፤ የካህናቱንም ፡ ነፍስ ፡ በብዛት ፡ አረካታለኹ ፡ ሕዝቤም ፡ በጎነቴን ፡ ይጠግባል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የዋይታና ፡ የመራራ ፡ ልቅሶ ፡ ድምፅ ፡ በራማ ፡ ተሰማ ፤ ራሔል ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡ አለቀሰች ፤ የሉምና ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡ መጽናናትን ፡ እንቢ ፡ አለች ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ድምፅሽን ፡ ከልቅሶ ፡ ዐይንሽንም ፡ ከእንባ ፡ ከልክዪ ፤ ለሥራሽ ፡ ዋጋ ፡ ይኾናልና ፥ ከጠላትም ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 17 ፤ ለፍጻሜሽም ፡ ተስፋ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ልጆችሽም ፡ ወደ ፡ ዳርቻቸው ፡ ይመለሳሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 18 ፤ ኤፍሬም ፦ ቀጣኸኝ ፡ እኔም ፡ እንዳልተገራ ፡ ወይፈን ፡ ተቀጣኹ ፤ አንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ነኽና ፥ መልሰኝ ፡ እኔም ፡ እመለሳለኹ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 19 ፤ ከተመለስኹ ፡ በኋላ ፡ ተጸጸትኹ ፥ ከተገሠጽኹም ፡ በኋላ ፡ ጭኔን ፡ ጸፋኹ ፤ የብላቴንነቴንም ፡ ስድብ ፡ ተሸክሜያለኹና ፡ ዐፈርኹ ፥ ተዋረድኹም ፡ ብሎ ፡ ሲያለቅስ ፡ ሰማኹ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 20 ፤ በእውነት ፡ ኤፍሬም ፡ ለእኔ ፡ የከበረ ፡ ልጅ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ የተወደደ ፡ ሕፃን ፡ ነውን ፧ በርሱ ፡ ላይ ፡ በተናገርኹ ፡ ቍጥር ፡ ዐስበዋለኹ ፤ ስለዚህ ፥ አንጐቴ ፡ ታወከችለት ፥ ርኅራኄም ፡ እራራለታለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 21 ፤ ለራስሽ ፡ የመንገድ ፡ ምልክት ፡ አድርጊ ፥ መንገድንም ፡ የሚመሩ ፡ ዐምዶችን ፡ ትከዪ ፥ ልብሽንም ፡ ወደኼድሽበት ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ጥርጊያው ፡ አቅኚ ፤ አንቺ ፡ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ሆይ ፥ ተመለሺ ፥ ወደ ፡ እነዚህም ፡ ወደ ፡ ከተማዎችሽ ፡ ተመለሺ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 22 ፤ አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ትቅበዘበዘሪለሽ ፧ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐዲስ ፡ ነገርን ፡ ፈጥሯልና ፥ ሴት ፡ ወንድን ፡ ትከባለች ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 23 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምርኳቸውን ፡ በመለስኹ ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ በከተማዎቿ ። የጽድቅ ፡ ማደሪያ ፡ ሆይ ፥ የቅድስና ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይባርክኽ ፡ የሚልን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይናገራሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 24 ፤ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በአገሩ ፡ ሹሉ ፡ ከገበሬዎችና ፡ መንጋን ፡ ይዘው ፡ ከሚዞሩ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 25 ፤ የደከመችውን ፡ ነፍስ ፡ አርክቻለኹና ፥ ያዘነችውንም ፡ ነፍስ ፡ ሹሉ ፡ አጥግቤያለኹና ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 26 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ነቃኹ ፡ ተመለከትኹም ፥ እንቅልፌም ፡ ጣፋጭ ፡ ኾነልኝ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 27 ፤ የእስራኤልን ፡ ቤትና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ በሰው ፡ ዘርና ፡ በእንስሳ ፡ ዘር ፡ የምዘራበት ፡ ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 28 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ አፈርሳቸውና ፡ ክፉ ፡ አድርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጋኹባቸው ፥ እንዲሁ ፡ እሠራቸውና ፡ እተክላቸው ፡ ዘንድ ፡ እተጋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 29 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ዳግመኛ ፡ እንዲህ ፡ አይልም ፦ አባቶች ፡ ጨርቋ ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ በሉ ፥ የልጆችም ፡ ጥርሶች ፡ ጠረሱ ፤

ኤር. ፡ 31 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ ሹሉ ፡ በገዛ ፡ በደሉ ፡ ይሞታል ፤ መራራውን ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ የሚበላ ፡ ሹሉ ፡ ጥርሶቹ ፡ ይጠርሳሉ ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 31 ፤ እንሆ ፥ ከእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ዐዲስ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የምገባበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ኤር. ፡ 31 ፡ 32 ፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ በያዝኹበት ፡ ቀን ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ገባኹት ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አይደለም ፤ እነርሱ ፡ በኪዳኔ ፡ አልጸኑምና ፥ እኔም ፡ ቸል ፡ አልኋቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 33 ፤ ከነዚያ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የምገባው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነውና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ አኖራለኹ ፥ በልባቸውም ፡ እጽፈዋለኹ ፤ እኔም ፡ አምላክ ፡

እኾናቸዋለኹ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 34 ፤ እያንዳንዱ ፡ ሰው ፡ ባልንጀራውን ፥ እያንዳንዱም ፡ ወንድሙን ፦ እግዚአብሔርን ፡ ዕወቅ ፡ ብሎ ፡ አያስተምርም ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፡ ያውቁኛልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። በደላቸውን ፡ እምራቸዋለኹና ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስብምና ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 35 ፤ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የሚባል ፥ ፀሓይን ፡ በቀን ፡ የጨረቃንና ፡ የከዋክብትን ፡ ሥርዐት ፡ በሌሊት ፡ ብርሃን ፡ አድርጎ ፡ የሚሰጥ ፥ እንዲተሙም ፡ የባሕርን ፡ ሞገዶች ፡ የሚያናውጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 31 ፡ 36 ፤ ይህ ፡ ሕግ ፡ ከፊቴ ፡ ቢወገድ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ የእስራኤል ፡ ዘር ፡ በፊቴ ፡ ሕዝብ ፡ እንዳይኾን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይቀራል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 37 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰማይ ፡ በላይ ፡ ቢከነዳ ፥ የምድርም ፡ መሠረት ፡ በታች ፡ ቢመረመር ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ስላደረጉት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልን ፡ ዘር ፡ ኹሉ ፡ እጥላለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 38 ፤ ከሐናንኤል ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ከተማ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመን ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 39 ፤ የተለካበትም ፡ ገመድ ፡ ወደጋሬብ ፡ ኰረብታ ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይኼዳል ፥ ወደ ፡ ጎዓም ፡ ይዞራል ።

ኤር. ፡ 31 ፡ 40 ፤ የሬሳም ፡ ሸለቆ ፡ ኹሉ ፡ የዐመድም ፡ ዕርሻ ፡ ኹሉ ፡ እስከቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ እስካለው ፡ እስከፈረስ ፡ በር ፡ ማእዘን ፡ ድረስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይነቀልም ፡ አይፈርስምም ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በዐሥረኛው ፡ ዓመት ፥ በናቡከደነጾር ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 2 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከቦ ፡ ነበር ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ በነበረው ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 3 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አስጠብቆት ፡ ነበርና ፦ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ትንቢት ፡ ትናገራለኽ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፡ ርሱም ፡ ይይዛታል ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 4 ፤ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በእውነት ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ፥ አፍ ፡ ለአፍም ፡ ይናገረዋል ፥ ዐይኑም ፡ ዐይኑን ፡ ያያል ፡ እንጂ ፡ ከከለዳውያን ፡ እጅ ፡ አያመልጥም ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 5 ፤ ርሱም ፡ ሴዴቅያስን ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያፈልሰዋል ፥ እኔም ፡ እስክጐበኘው ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ይኖራል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከከለዳውያን ፡ ጋራ ፡ ብትዋጉ ፡ ምንም ፡ አትረቡም ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 6 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 32 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ የአጎትኽ ፡ የሰሎም ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፡ ወዳንተ ፡ መጥቶ ፦ ትገዛው ፡ ዘንድ ፡ መቤዠቱ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፥ በዐናቶት ፡ ያለውን ፡ ዕርሻዬን ፡ ግዛ ፡ ይልኻል ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 8 ፤ እንደእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የአጎቴ ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፡ እኔ ፡ ወዳለኹበት ፡ ወደግዞቱ ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ መጥቶ ፦ በብንያም ፡ አገር ፡ በዐናቶት ፡ ያለውን ፡ ዕርሻዬን ፥ እባክኽ ፥ ግዛ ፤ ርስቱ ፡ የአንተ ፡ ነውና ፥ መቤገሥቱም ፡ የአንተ ፡ ነውና ፤ ለአንተ ፡ ግዛው ፡ አለኝ ። ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቅኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 9 ፤ በዐናቶትም ፡ ያለውን ፡ ዕርሻ ፡ ከአጎቴ ፡ ልጅ ፡ ከዐናምኤል ፡ ገዛኹ ፥ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ ሰቅል ፡ ብርም ፡ መዘንኹለት ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 10 ፤ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ላይ ፡ ፈረምኹ ፡ ዐተምኹትም ፥ ምስክሮችንም ፡ ጠርቼ ፡ ብሩን ፡ በሚዛን ፡ መዘንኹለት ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 11 ፤ የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወሰድኹ ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 12 ፤ የአጎቴም ፡ ልጅ ፡ ዐናምኤል ፥ የውሉንም ፡ ወረቀት ፡ የፈረሙ ፡ ምስክሮች ፥ በግዞትም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ የተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ እያዩ ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ለመሕሤያ ፡ ልጅ ፡ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠኹት ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 13 ፤ በፊታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ባሮክን ፡ አዘዝኹት ፦

ኤር. ፡ 32 ፡ 14 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ብዙ ፡ ቀን ፡ ይጠበቁ ፡ ዘንድ ፡ የታተመውንና ፡ የተከፈተውን ፡ ይህን ፡ የውል ፡ ወረቀት ፡ ወስደኽ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አኑራቸው ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሰዎች ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ቤትንና ፡ ዕርሻን ፡ የወይን ፡ ቦታንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይገዛሉ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 16 ፤ ለኔርያ ፡ ልጅ ፡ ለባሮክም ፡ የውሉን ፡ ወረቀት ፡ ከሰጠኹት ፡ በኋላ ፥ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለይኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 17 ፤ አቤቱ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ አንተ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ በታላቅ ፡ ኀይልኽና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድኽ ፡ ፈጥረኻል ፥ ከአንተም ፡ የሚያቅት ፡ ነገር ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 18 ፤ ለብዙ ፡ ሺሕ ፡ ምሕረት ፡ ታደርጋለኽ ፥ የአባቶችንም ፡ በደል ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ በልጆቻቸው ፡ ብብት ፡ ትመልሳለኽ ፤ ስምኽ ፡ ታላቅና ፡ ኀያል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 19 ፤ በምክር ፡ ታላቅ ፡ በሥራም ፡ ብርቱ ፡ ነኽ ፤ ለኹሉም ፡ እንደ ፡ መንገዱና ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ፍሬ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ዐይኖችኽ ፡ በአዳም ፡ ልጆች ፡ መንገድ ፡ ኹሉ ፡ ተገልጠዋል ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 20 ፤ እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ምልክትንና ፡ ድንቅን ፡ ነገር ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ደግሞም ፡ በእስራኤልና ፡ በሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ መካከል ፡ አድርገኻል ፥ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ለአንተ ፡ ስም ፡ አድርገኻል ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 21 ፤ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፥ በብርቱ ፡ እጅና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድ ፡ በታላቅም ፡ ግርማ ፡ ሕዝብኽን ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣኽ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 22 ፤ ትሰጣቸውም ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻቸው ፡ የማልኽላቸውን ፡ ምድር ፥ ወተትና ፡ ማርንም ፡ የምታፈሰውን ፡ ምድር ፥ ሰጠኻቸው ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ ወረሷት ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃልኽን ፡ አልሰሙም ፥ በሕግኽም ፡ አልኼዱም ፤ ያደርጉም ፡ ዘንድ ፡ ካዘዝኻቸው ፡ ኹሉ ፡ ምንም ፡ አላደረጉም ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡

አመጣኽባቸው ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 24 ፤ እንሆ ፥ የዐፈር ፡ ድልድል ፥ ሊይዟትም ፡ እስከ ፡ ከተማዪቱ ፡ ድረስ ፡ ቀርበዋል ፤ ከሰይፍና ፡ ከራብ ፡ ከቸነፈርም ፡ የተነሣ ፡ ከተማዪቱ ፡ ለሚዋጓት ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፥ የተናገርኸውም ፡ ኾኗል ፤ እንሆም ፥ አንተ ፡ ታየዋለኽ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 25 ፤ አንተም ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፦ ዕርሻውን ፡ በብር ፡ ግዛ ፡ ምስክሮችንም ፡ ጥራ ፡ አልኸኝ ፤ ከተማዪቱ ፡ ግን ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 32 ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ የሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 28 ፤ በእውኑ ፡ እኔን ፡ የሚያቅተኝ ፡ ነገር ፡ አለን ፧ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ለከለዳውያን ፡ እጅና ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ ርሱም ፡ ይይዛታል ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 29 ፤ ይህችን ፡ ከተማ ፡ የሚወጉ ፡ ከለዳውያን ፡ መጥተው ፡ በእሳት ፡ ያነዷታል ፥ ያስቈጡኝም ፡ ዘንድ ፡ በሰገነታቸው ፡ ላይ ፡ ለበዓል ፡ ካጠኑባቸው ፥ ለሌላዎችም ፡ አማልክት ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ካፈሰሱባቸው ፡ ቤቶች ፡ ጋራ ፡ ያቃጥሏታል ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 30 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ከታናሽነታቸው ፡ ዠምሮ ፡ በፊቴ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ብቻ ፡ አድርገዋልና ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ እኔን ፡ በእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ከማስቈጣት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ አላደረጉምና ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 31 ፤ ከፊቴ ፡ አስወግዳት ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ ከተማ ፡ ከሠሯት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ቍጣዬንና ፡ መዓቴን ፡ ለማነሣሣት ፡ ኾናለችና ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 32 ፤ ይህም ፡ እኔን ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፥ እነርሱና ፡ ነገሥታታቸው ፡ አለቃዎቻቸውም ፡ ካህናታቸውም ፡ ነቢያታቸውም ፡ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የሚንኖሩ ፥ ስላደረጉት ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ ስለይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 33 ፤ ፊታቸውንም ፡ ሳይኾን ፡ ዠርባቸውን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መለሱ ፤ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ሳሰተምራቸው ፡ ተግሣጽን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ አልሰሙም ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 34 ፤ ያረክሱትም ፡ ዘንድ ፡ ስሜ ፡ በተጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ርኵሰታቸውን ፡ አኖሩ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 35 ፤ ይሁዳን ፡ ወደ ፡ ኀጢአት ፡ እንዲያገቡት ፥ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፥ እኔ ፡ ያላዘዝኹትንና ፡ በልቤ ፡ ያላሰብኹትን ፡ ነገር ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ለሞሎክ ፡ በእሳት ፡ ያሳልፉ ፡ ዘንድ ፡ በሄኖም ፡ ልጅ ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ የበዓልን ፡ የኰረብታውን ፡ መስገጃዎች ፡ ሠሩ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 36 ፤ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፦ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ ስለምትላት ፡ ከተማ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 32 ፡ 37 ፤ እንሆ ፥ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በታላቅም ፡ መቅሠፍቴ ፡ እነርሱን ፡ ካሳደድኩባት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ ወደዚህም ፡ ስፍራ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ ተዘልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አደርጋለኹ ፤

ኤር. ፡ 32 ፡ 38 ፤ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 39 ፤ ለእነርሱም ፡ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ለልጆቻቸው ፡ መልካም ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለዘለዓለም ፡

እንዲፈሩኝ ፡ አንድ ፡ ልብና ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 40 ፤ ለእነርሱም ፡ ከማደርገው ፡ በጎነት ፡ አልመለስም ፡ ስል ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የዘለዓለምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እገባለኹ ፤ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳይሉ ፡ መፈራቴን ፡ በልባቸው ፡ ውስጥ ፡ አኖራለኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 41 ፤ ለእነርሱም ፡ መልካምን ፡ በማድረግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ በእውነትም ፡ በፍጹም ፡ ልቤና ፡ በፍጹም ፡ ነፍሴ ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ እተክላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 42 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ይህን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እንዳመጣኹ ፥ እንዲሁ ፡ የተናገርኹላቸውን ፡ በጎነት ፡ ኹሉ ፡ አመጣላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 43 ፤ እናንተም ፦ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ያለች ፡ ባድማ ፡ ናት ፥ ለከለዳውያንም ፡ እጅ ፡ ተሰጥታለች ፡ በምትሏት ፡ ምድር ፡ ዕርሻን ፡ ይገዛሉ ።

ኤር. ፡ 32 ፡ 44 ፤ ምርኮኞቻቸውንም ፡ እመልሳለኹና ፡ በብንያም ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ ስፍራዎች ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ በደጋውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በቈላውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በደቡብም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፥ ሰዎች ፡ ዕርሻውን ፡ በብር ፡ ይገዛሉ ፡ በውሉም ፡ ወረቀት ፡ ፈርመው ፡ ያትማሉ ፡ ምስክሮችንም ፡ ይጠራሉ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 1 ፤ ኤርምያስ ፡ ገና ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣለት ፦

ኤር. ፡ 33 ፡ 2 ፤ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፥ ያደረገው ፡ እግዚአብሔር ፥ ያጸናውም ፡ ዘንድ ፡ የሠራው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 33 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ጩኽ ፥ እኔም ፡ እመልስልኻለኹ ፤ አንተም ፡ የማታውቀውን ፡ ታላቅና ፡ ኀይለኛ ፡ ነገርን ፡ አሳይኻለኹ ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዐፈር ፡ ድልድልና ፡ ለምሽግ ፡ ስለ ፡ ፈረሱ ፡ ስለዚች ፡ ከተማ ፡ ቤቶች ፥ ስለይሁዳም ፡ ነገሥታት ፡ ቤቶች ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦

ኤር. ፡ 33 ፡ 5 ፤ ከለዳውያን ፡ ለመዋጋት ፡ መጥተዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ በገደልኋቸው ፡ ሰዎች ፡ ሬሳዎች ፡ ሊሞሏቸው ፡ ነው ፥ ስለ ፡ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ ፊቴን ፡ ከዚች ፡ ከተማ ፡ ሰውሬያለኹና ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 6 ፤ እንሆ ፥ ፈውስንና ፡ መድኀኒትን ፡ አመጣላታለኹ ፥ እፈውሳቸውማለኹ ፤ የሰላምንና ፡ የእውነትን ፡ ብዛት ፡ እገልጥላቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 7 ፤ የይሁዳን ፡ ምርኮና ፡ የእስራኤልንም ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ቀድሞም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አድርጌ ፡ እሠራቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 8 ፤ እኔንም ፡ ከበደሉበት ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ አነጻቸዋለኹ ፡ እኔንም ፡ የበደሉኝን ፡ ያመፀብኝንም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ እላለኹ ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ እኔ ፡ የምሠራላቸውን ፡ በጎነት ፡ ኹሉ ፡ በሚሰሙ ፡ እኔም ፡ ስላመጣኹላቸው ፡ በጎነትና ፡ ሰላም ፡ ኹሉ ፡ በሚፈሩና ፡ በሚደነግጡ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ለደስታ ፡ ስም ፡ ለምስጋናም ፡ ለክብርም ፡ ትኾናለች ።

ኤር. ፡ 33 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፦ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ያለች ፡ ባድማ ፡ ናት ፡

በምትሷት ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፥ የሚቀመጥባቸው ፡ በሌላ ፥ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ባድማ ፡ በኾኑ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፥

ኤር. ፥ 33 ፥ 11 ፤ የሐሤት ፡ ድምፅና ፡ የደስታ ፡ ድምፅ ፥ የወንድ ፡ ሙሽራ ፡ ድምፅና ፡ የሴት ፡ ሙሽራ ፡ ድምፅ ፦ እግዚአብሔር ፡ ቸር ፡ ነውና ፥ ምሕረቱም ፡ ለዘለዓለም ፡ ነውና ፥ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ የሚሉ ፡ ድምፅ ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የምስጋናን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያመጡት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይሰማል ። የምድርን ፡ ምርኮ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አድርጌ ፡ እመልሳለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 12 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ባድማ ፡ ኾኖ ፥ ያለሰውና ፡ ያለእንስሳ ፡ ባለው ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ በከተማዎችም ፡ ሹሉ ፡ መንጋዎቻቸውን ፡ የሚያሳርፉት ፡ የእረኞች ፡ መኖሪያ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 13 ፤ በደጋው ፡ ላይ ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በቈላውም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፡ በደቡብም ፡ ባሉ ፡ ከተማዎች ፥ በብንያምም ፡ አገር ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ዙሪያ ፡ ባሉ ፡ ስፍራዎች ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ መንጋዎቹ ፡ በተቈጣጣሪው ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያልፋሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 14 ፤ እንሆ ፥ ስለእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ስለይሁዳ ፡ ቤት ፡ የተናገርኹትን ፡ መልካም ፡ ቃል ፡ የምፈጽምበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 15 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ለዳዊት ፡ የጽድቅን ፡ ቀኖጥቋጥ ፡ አበቅልለታለኹ ፤ ርሱም ፡ ፍርድንና ፡ ጽድቅን ፡ በምድር ፡ ያደርጋል ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 16 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ይሁዳ ፡ ይድናል ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ተዘልላ ፡ ትቀመጣለች ፤ የምትጠራበትም ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችን ፡ ተብሎ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ የሚቀመጥ ፡ ሰው ፡ ከዳዊት ፡ ዘንድ ፡ አይታጣም ፤

ኤር. ፥ 33 ፥ 18 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚያቀርብ ፡ የእኽሉንም ፡ ቀኖርባን ፡ የሚያቃጥል ፡ ሹልጊዜም ፡ የሚሠዋ ፡ ሰው ፡ ከሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ዘንድ ፡ በእኔ ፡ ፊት ፡ አይታጣም ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 19 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፥ 33 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ በወራቱ ፡ እንዳይኾን ፡ የቀን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔንና ፡ የሌሊት ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ማፍረስ ፡ ብትችሉ ፥

ኤር. ፥ 33 ፥ 21 ፤ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ የሚነግሥ ፡ ልጅ ፡ እንዳይኾንለት ፡ ከባሪያዬ ፡ ከዳዊት ፡ ጋራ ፥ ከአገልጋዮቼም ፡ ከሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ደግሞ ፡ ይፈርሳል ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 22 ፤ የሰማይን ፡ ሰራዊት ፡ መቀኖጠር ፡ የባሕርንም ፡ አሸዋ ፡ መስፈር ፡ እንደማይቻል ፥ እንዲሁ ፡ የባሪያዬን ፡ የዳዊትን ፡ ዘርና ፡ የሚያገለግሉኝን ፡ ሌዋውያንን ፡ አበዛለኹ ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 23 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፥ 33 ፥ 24 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ እግዚአብሔር ፡ የመረጣቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ወገን ፡ ጥሏቸዋል ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አትመለከትምን ፧ እንዲሁ ፡ በፊታቸው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሕዝብ ፡ እንዳይኾን ፡ ሕዝቤን ፡ አቃለዋል ።

ኤር. ፥ 33 ፥ 25 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የቀንና ፡ የሌሊት ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ የሰማይንና ፡ የምድርንም ፡ ሥርዐት ፡ ያላጸናኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥

ኤር. ፡ 33 ፡ 26 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በአብርሃምና ፡ በይሥሐቅ ፡ በያዕቆብም ፡ ዘር ፡ ላይ ፡ ገዥዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ከዘሩ ፡ እንዳልወስድ ፥ የያዕቆብንና ፡ የባሪያዬን ፡ የዳዊትን ፡ ዘር ፡ እጥላለኹ ፤ ምርኳቸውን ፡ እመልሳለኹና ፥ እምራቸውማለኹና ።

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ። _____

ኤር. ፡ 34 ፡ 1 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ከእጁም ፡ ግዛት ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ የምድር ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ ከተማዎቿን ፡ ኹሉ ፡ ይወጉ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 34 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኺድ ፡ ለይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይህችን ፡ ከተማ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፥ በእሳትም ፡ ያቃጥላታል ፤

ኤር. ፡ 34 ፡ 3 ፤ አንተም ፡ በርግጥ ፡ ትያዛለኽ ፡ በእጅም ፡ አልፈኽ ፡ ትሰጣለኽ ፡ እንጂ ፡ ከእጁ ፡ አታመልጥም ፤ ዐይንኽም ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ዐይን ፡ ታያለች ፥ ርሱም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አፍ ፡ ለአፍ ፡ ይናገራል ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ትገባለኽ ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በሰይፍ ፡ አትሞትም ፥ በሰላም ፡ ትሞታለኽ ፡ እንጂ ፤

ኤር. ፡ 34 ፡ 5 ፤ ከአንተ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ እንደ ፡ ዱሮ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ አባቶችኽ ፡ መቃጠል ፥ እንዲሁ ፡ ያቃጥሉኻልና ፦ ወየው! ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ እያሉ ፡ ያለቅሱልኻል ፤ እኔ ፡ ቃልን ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 6-7 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የቀሩትን ፡ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፥ ከተመሸጉት ፡ ከይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ የተረፉትን ፡ ለኪሶንና ፡ ዓዜቃን ፡ በወጋ ፡ ጊዜ ፥ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ለሴዴቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነገረው ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 8-9 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ዕብራዊ ፡ የኾነውን ፡ ወንድ ፡ ባሪያውንና ፡ ዕብራዊት ፡ የኾነች ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ሐራነት ፡ እንዲያወጣ ፥ አይሁዳዊ ፡ ወንድሙንም ፡ ማንም ፡ እንዳይገዛ ፥ ስለ ፡ ሐራነታቸው ፡ ዐዋጅ ፡ እንዲነገር ፡ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 34 ፡ 10 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ወንድ ፡ ባሪያውንና ፡ ሴት ፡ ባሪያውን ፡ ሐራነት ፡ እንዲያወጣ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ማንም ፡ እንዳይገዛቸው ፡ ወደቃል ፡ ኪዳኑ ፡ የገቡ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉና ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሰሙ ፥ ሐራነትም ፡ አወጧቸው ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ሐራነት ፡ ያወጧቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎቻቸውን ፡ አስመለሱ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ አድርገው ፡ ገዟቸው ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 34 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አባቶቻችኹን ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ባወጣኋቸው ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደረግኹ ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 14 ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የተሸጠላችኹን ፡ ስድስትም ፡ ዓመት ፡ የተገዛላችኹን ፡ ዕብራዊ ፡ ወንድማችኹን ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ ሐራነት ፡ ታወጡታላችኹ ፥ እያንዳንዱም ፡ ያወጣዋል ፤ አባቶቻችኹ ፡ ግን ፡

አልሰሙኝም ፡ ጐሯቸውንም ፡ አላዘነበሉም ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 15 ፤ እናንተም ፡ ዛሬ ፡ ተመልሳችኹ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ባልንጀራውን ፡ ሐራነት ፡ ለማውጣት ፡ ዐዋጅ ፡ በመንገር ፡ ለዐይኔ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝን ፡ ነገር ፡ አድርጋችኹ ፡ ነበር ፥ በስሜም ፡ በሚጠራበት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በፊቴ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አድርጋችኹ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተመልሳችኹ ፡ ስሜን ፡ አስነቀፋችኹ ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ በፈቃዳቸው ፡ እንዲኼዱ ፡ ሐራነት ፡ ያወጣችኻቸውን ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ባሪያዎቻችኹን ፡ አስመለሳችኹ ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ባሪያዎችም ፡ እንዲኾኑላችኹ ፡ ገዛችኻቸው ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለወንድሙና ፡ ለባልንጀራው ፡ የሐራነት ፡ ዐዋጅ ፡ ለመንገር ፡ እኔን ፡ አልሰማችኹም ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ለሰይፍና ፡ ለቸነፈር ፡ ለራብም ፡ የሐራነት ፡ ዐዋጅ ፡ እናገርባችኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በምድርም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ እንድትበተኑ ፡ አደርጋችኻለኹ ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 18 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔንም ፡ የተላለፉትን ፡ ሰዎች ፥ እንቦሳውንም ፡ ቈርጠው ፡ በቀኑራጩ ፡ መካከል ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ በፊቴ ፡ ያደረጉትን ፡ የቃል ፡ ኪዳንን ፡ ቃል ፡ ያልፈጸሙትን ፥

ኤር. ፡ 34 ፡ 19 ፤ የይሁዳን ፡ አለቃዎችና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ አለቃዎች ፡ ጃን ፡ ደረባዎችን ፡ ካህናትንም ፡ በእንቦሳም ፡ ቀኑራጭ ፡ መካከል ፡ ያለፉትን ፡ የአገሩን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፡ 34 ፡ 20 ፤ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለሚሿት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ሬሳቸውም ፡ ለሰማይ ፡ ወፎችና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ መብል ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 21 ፤ የይሁዳንም ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስንና ፡ አለቃዎቹን ፡ ለጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለሚሿት ፡ እጅ ፡ ከእናንተም ፡ ለተመለሱት ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

ኤር. ፡ 34 ፡ 22 ፤ እንሆ ፥ አዛለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደዚችም ፡ ከተማ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ ርሷንም ፡ ይወጋሉ ፡ ይይዟትማል ፡ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ፤ የይሁዳንም ፡ ከተማዎች ፡ ሰው ፡ የሌለበት ፡ ባድማ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ ዘመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 35 ፡ 2 ፤ ወደሬካባውያን ፡ ቤት ፡ ኼደኽ ፡ ተናገራቸው ፥ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ከጓዳዎቹ ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ አግባቸው ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ አጠጣቸው ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 3 ፤ የከባስንን ፡ ልጅ ፡ የኤርምያስን ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያን ፡ ወንድሞቹንም ፡ ልጆቹንም ፡ ኹሉ ፡ የሬካባውያንን ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ ወሰድኻቸው ፤

ኤር. ፡ 35 ፡ 4 ፤ ወደእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በበረኛው ፡ በሰሎም ፡ ልጅ ፡ በመዕሴያ ፡ ጓዳ ፡ በላይ ፡ ባለው ፡ በአለቃዎች ፡ ጓዳ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ወደጌዴልያ ፡ ልጅ ፡ ወደሐናን ፡ ልጆች ፡ ጓዳ ፡ አገባኻቸው ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 5 ፤ በሬካባውያንም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሞላባቸውን ፡ ማድጋዎችንና ፡ ጽዋዎችን ፡ አኑሬ ፦ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ ጠጡ ፡ አልኻቸው ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 6 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ የወይኑን ፡ ጠጅ ፡ አንጠጣም ፥ አባታችን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡

ኢዮናዳብ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አዞናልና ። እናንተና ፡ ልጆቻችኹ ፡ ለዘለዓለም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አትጠጡ ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 7 ፤ በምትኖሩባት ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንድትኖሩ ፥ በዕድሜያችኹ ፡ ሙሉ ፡ በድንኳን ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፡ እንጂ ፡ ቤትን ፡ አትሥሩ ፥ ዘርንም ፡ አትዝሩ ፥ ወይንም ፡ አትትከሉ ፥ አንዳችም ፡ አይኹንላችኹ ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 8 ፤ እኛም ፡ የአባታችንን ፡ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ የኢዮናዳብን ፡ ቃል ፡ ባዘዘን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ታዘናል ፤ እኛም ፡ ሚስቶቻችንም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችንም ፡ ዕድሜያችንን ፡ ሙሉ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አልጠጣንም ፤

ኤር. ፡ 35 ፡ 9 ፤ የምንቀመጥበትንም ፡ ቤት ፡ አልሠራንም ፤ የወይን ፡ ቦታና ፡ ዕርሻ ፡ ዘርም ፡ የለንም ፤

ኤር. ፡ 35 ፡ 10 ፤ በድንኳንም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠናል ፥ ታዘናል ፥ አባታችንም ፡ ኢዮናዳብ ፡ ያዘዘንን ፡ ኹሉ ፡ አድርገናል ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፦ ኑ ፡ ከከለዳውያን ፡ ሰራዊትና ፡ ከሶርያ ፡ ሰራዊት ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንኺድ ፡ አልን ፤ እንዲሁም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተቀመጥን ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 35 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኺድና ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ቃሌን ፡ ትሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ተግሣጽን ፡ አትቀበሉምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 14 ፤ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ ኢዮናዳብ ፡ ልጆቹ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዳይጠጡ ፡ ያዘዛቸው ፡ ቃል ፡ ተፈጸመ ፤ ለአባታቸውም ፡ ትእዛዝ ፡ ታዘዋልና ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አይጠጡም ፤ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ተናግሬያችኋለኹ ፤ ተናገርኹ ፥ ኾኖም ፡ አልሰማችኹኝም ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፦ እያንዳንዳችኹ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፥ ሥራችኹንም ፡ አሳምሩ ፥ ታመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ሌላዎችን ፡ አማልክት ፡ አትከተሉ ፥ ለእናንተና ፡ ለአባቶቻችኹም ፡ በሰጠኹት ፡ ምድር ፡ ትቀመጣላችኹ ፡ እያልኹ ፡ በማለዳ ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ልኬባችኹ ፡ ነበር ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ጐሯችኹን ፡ አላዘነበላችኹም ፡ እኔንም ፡ አልሰማችኹኝም ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 16 ፤ የሬካብ ፡ ልጅ ፡ የኢዮናዳብ ፡ ልጆች ፡ አባታቸው ፡ ያዘዛቸውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጽመዋልና ፥ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ አልሰማኝምና ፤

ኤር. ፡ 35 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በተናገርኋቸው ፡ ጊዜ ፡ አልሰሙምና ፥ በጠራኋቸውም ፡ ጊዜ ፡ አልመለሱልኝምና ፡ የተናገርኹባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አመጣባቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 35 ፡ 18 ፤ ኤርምያስም ፡ ሬካባውያንን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለአባታችኹ ፡ ለኢዮናዳብ ፡ ትእዛዝ ፡ ታዛችኋልና ፥ ትእዛዙንም ፡ ኹሉ ፡ ጠብቃችኋልና ፥ ያዘዛችኹንም ፡ ፈጽማችኋልና ፤

ኤር. ፡ 35 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ በፊቴ ፡ የሚቆም ፡ ሰው ፡ ከሬካብ ፡ ልጅ ፡ ከኢዮናዳብ ፡ ወገን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይታጣም ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 36 ፡ 2 ፤ አንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ ክርታስ ፡ ውሰድ ፥ ለአንተም ፡ ከተናገርኹበት ፡ ቀን ፡ ከኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በእስራኤልና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተናገርኹኽን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ጻፍበት ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 3 ፤ ምናልባት ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፦ እኔ ፡ አደርግባቸዋለኹ ፡ ያልኹትንና ፡ ያሰብኹትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይሰሙ ፡ ይኾናል ፥ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ በደላቸውንና ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ እል ፡ ዘንድ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 4 ፤ ኤርምያስም ፡ የኔርያን ፡ ልጆ ፡ ባሮክን ፡ ጠራ ፥ ባሮክም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለርሱ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመጽሐፉ ፡ ክርታስ ፡ ጻፈ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 5 ፤ ኤርምያስም ፡ ባሮክን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዘዘው ፦ እኔ ፡ ተግዜያለኹ ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እገባ ፡ ዘንድ ፡ አልችልም ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ኺድ ፥ ከአፌም ፡ የጻፍኸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በጾም ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ በክርታሱ ፡ አንብ ፤ ደግሞም ፡ ከከተማዎቻቸው ፡ በሚወጡ ፡ በይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጆሮ ፡ አንበው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ የተናገረው ፡ ቍጣውና ፡ መዓቱ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ምናልባት ፡ ጸሎታቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ትወድቅ ፡ ይኾናል ፥ ኹሉም ፡ ከክፉ ፡ መንገዱ ፡ ይመለስ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 8 ፤ የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘውን ፡ ኹሉ ፡ አደረገ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 9 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የተቀመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ከይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 10 ፤ ባሮክም ፡ የኤርምያስን ፡ ቃል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በላይኛው ፡ አደባባይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በዐዲሱ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ ባለው ፡ በጸሓፊው ፡ በሳፋን ፡ ልጅ ፡ በገማርያ ፡ ጓዳ ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ አነበበ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 11 ፤ የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የገማርያ ፡ ልጅ ፡ ሚክያስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከመጽሐፉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፡ 36 ፡ 12 ፤ ወደንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወደጸሓፊው ፡ ጓዳ ፡ ወረደ ፤ እንሆም ፥ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ጸሓፊው ፡ ኤሊሳማ ፥ የሸማያ ፡ ልጅ ፡ ድላያ ፥ የዓክቦር ፡ ልጅ ፡ ኤልናታን ፥ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ ገማርያ ፥ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 13 ፤ ሚክያስም ፡ ባሮክ ፡ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ በመጽሐፉ ፡ ባነበበ ፡ ጊዜ ፡ የሰማውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ነገራቸው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 14 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፦ በሕዝቡ ፡ ጆሮ ፡ ያነበብኸውን ፡ ክርታስ ፡ በእጅኽ ፡ ይዘኽ ፡ ና ፡ የሚል ፡ መልእክት ፡ በኩሲ ፡ ልጅ ፡ በሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ በናታንያ ፡ ልጅ ፡ በይሁዲ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ባሮክ ፡ ላኩ ። የኔርያም ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ ክርታሱን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፦ እስኪ ፡ ተቀመጥ ፥ በጐሯችንም ፡ አንብ ፡ አሉት ። ባሮክም ፡ በጐሯቸው ፡ አነበበው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 16 ፤ ቃሉንም ፡ ዅሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈርተው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተመካከሩ ፥ ባሮክንም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ዅሉ ፡ በርግጥ ፡ ለንጉሡ ፡ እንናገራለን ፡ አሉት ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 17 ፤ ባሮክንም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ዅሉ ፡ ከአፉ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጻፍኸው ፡ ንገረን ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 18 ፤ ባሮክም ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ከአፉ ፡ ይነግረኝ ፡ ነበር ፥ እኔም ፡ በመጽሐፉ ፡ ላይ ፡ በቀለም ፡ እጽፍ ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 19 ፤ አለቃዎቹም ፡ ባሮክን ፦ አንተና ፡ ኤርምያስ ፡ ኺዱ ፥ ተሸሸጉ ፥ ወዴትም ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፡ አሉት ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ ገቡ ፥ ክርታሱንም ፡ በጸሓፊው ፡ በኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡ አኑረውት ፡ ነበር ፤ ቃሉንም ፡ ዅሉ ፡ በንጉሡ ፡ ጐሮ ፡ ተናገሩ ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ክርታሱን ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዲን ፡ ላከ ፥ ርሱም ፡ ከጸሓፊው ፡ ከኤሊሳማ ፡ ጓዳ ፡ ወሰደው ፤ ይሁዲም ፡ በንጉሡና ፡ በንጉሡ ፡ አጠገብ ፡ በቆሙት ፡ አለቃዎች ፡ ዅሉ ፡ ጐሮ ፡ አነበበው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 22 ፤ ንጉሡም ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በክረምት ፡ ቤት ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፥ በፊቱም ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ ይነድ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 23 ፤ ይሁዲም ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ አራት ፡ ዐምድ ፡ ያኽል ፡ ባነበበ ፡ ቍጥር ፥ ንጉሡ ፡ በካራ ፡ ቀደደው ፤ ክርታሱም ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ባለው ፡ እሳት ፡ ፈጽሞ ፡ እስኪ ቃጠል ፡ ድረስ ፡ በምድጃ ፡ ውስጥ ፡ ወዳለው ፡ እሳት ፡ ጣለው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፡ ይህንም ፡ ቃል ፡ ዅሉ ፡ የሰሙ ፡ ባሪያዎቹ ፡ ዅሉ ፡ አልፈሩም ፡ ልብሳቸውንም ፡ አልቀደዱም ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኤልናታንና ፡ ድላያ ፡ ገማርያም ፡ ክርታሱን ፡ እንዳያቃጥል ፡ ንጉሡን ፡ ለመኑት ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማቸውም ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 26 ፤ ንጉሡም ፡ ጸሓፊውን ፡ ባሮክንና ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፡ የንጉሡን ፡ ልጅ ፡ ይረሕምኤልንና ፡ የዓዝርኤልን ፡ ልጅ ፡ ሰራያን ፡ የዓብድኤልንም ፡ ልጅ ፡ ሰሌምያን ፡ አዘዘ ፥ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ሰወራቸው ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ክርታሱንና ፡ ባሮክ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ የጻፈውን ፡ ቃል ፡ ካቃጠለ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 36 ፡ 28 ፤ ዳግመኛም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡ ውሰድ ፥ የይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ ባቃጠለው ፡ ክርታስ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የቀድሞውን ፡ ቃል ፡ ዅሉ ፡ ጻፍበት ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 29 ፤ የይሁዳንም ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንተ ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በርግጥ ፡ ይመጣል ፡ ይህችንም ፡ አገር ፡ ያፈርሳታል ፡ ከሰውና ፡ ከእንስሳም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋታል ፡ ብለኽ ፡ ለምን ፡ ጻፍኽበት ፧ ብለኽ ፡ ይህን ፡ ክርታስ ፡ አቃጥለኻል ።

ኤር. ፡ 36 ፡ 30 ፤ ስለዚህም ፡ ስለይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኢዮአቄም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዳዊት ፡

ዙፋን ፡ ላይ ፡ ተቀማጭ ፡ አይኖርለትም ፥ ሬሳውም ፡ በቀን ፡ ለትኵሳት ፡ በሌሊትም ፡ ለውርጭ ፡ ይጣላል ።

ኤር. ፥ 36 ፥ 31 ፤ ስለ ፡ ኀጢአታቸውም ፡ ርሱንና ፡ ዘሩን ፡ ባሪያዎቹንም ፡ እቀጣለኹ ፤ እነርሱም ፡ አልሰሙምና ፡ የተናገርኹባቸውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በእነርሱ ፡ ላይና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚቀመጡ ፡ በይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

ኤርምያስም ፡ ሌላ ፡ ክርታስ ፡ ወሰደ ፡ ለኔርያም ፡ ልጅ ፡ ለጸሓፊው ፡ ለባሮክ ፡ ሰጠው ፤ ርሱም ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በእሳት ፡ ያቃጠለውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ ጻፈበት ፥ ደግሞም ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ያለ ፡ ቃል ፡ ብዙ ፡ ቃል ፡ ተጨመረበት ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 1 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በይሁዳ ፡ ያነገሠው ፡ የኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በኢዮአቄም ፡ ልጅ ፡ በኢኮንያን ፡ ፋንታ ፡ ነገሠ ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 2 ፤ ርሱም ፡ ኾነ ፡ ባሪያዎቹ ፡ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 3 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልይ ፡ ብሎ ፡ የሰሌምያን ፡ ልጅ ፡ ዮካልንና ፡ ካህኑን ፡ የመዕሴያን ፡ ልጅ ፡ ሶፎንያስን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ ላከ ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 4 ፤ ርሱንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ገና ፡ አላገቡትም ፡ ነበርና ፥ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ይወጣና ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 5 ፤ የፈርዖንም ፡ ሰራዊት ፡ ከግብጽ ፡ ወጣ ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ ከበዋት ፡ የነበሩ ፡ ከለዳውያን ፡ ይህን ፡ ወሬ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፥ 37 ፥ 7 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእኔ ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ የላካችኹን ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ እንዲህ ፡ በሉት ፦ እንሆ ፥ ሊረዳችኹ ፡ የወጣው ፡ የፈርዖን ፡ ሰራዊት ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳል ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 8 ፤ ከለዳውያንም ፡ ተመልሰው ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ ይዋጓታል ፡ ይይዟትማል ፡ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አይኼዱምና ፦ ከለዳውያን ፡ በርግጥ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ይኼዳሉ ፡ ብላችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ አታታልሉ ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 10 ፤ እናንተም ፡ የሚዋጉትን ፡ የከለዳውያንን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ ብትመቱት ፡ ኖሮ ፥ ከነርሱም ፡ የተወጉት ፡ ብቻ ፡ ቢቀሩ ፡ ኖሮ ፥ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በድንኳኑ ፡ ተነሥቶ ፡ ይህችን ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ ባቃጠሏት ፡ ነበር ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 11 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ከፈርዖን ፡ ሰራዊት ፡ ፊት ፡ የተነሣ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፥ 37 ፥ 12 ፤ ኤርምያስ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ የርስቱን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ከዚያ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደብንያም ፡ አገር ፡ ሊኼድ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

ኤር. ፥ 37 ፥ 13 ፤ በብንያምም ፡ በር ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ የሐናንያ ፡ ልጅ ፡ የሰሌምያ ፡ ልጅ ፡ የሪያ ፡ የተባለ ፡ የዘበኞች ፡ አለቃ ፡ በዚያ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፦ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ መኰብለልኽ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ ያዘው ።

ኤር. ፡ 37 ፡ 14 ፤ ኤርምያስም ፦ ሐሰት ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ መኰብለሌ ፡ አይደለም ፡ አለ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አልሰማውም ፥ የሪያም ፡ ኤርምያስን ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ አለቃዎች ፡ አመጣው ።

ኤር. ፡ 37 ፡ 15 ፤ አለቃዎችም ፡ ተቈጥተው ፡ ኤርምያስን ፡ መቱት ፥ የጸሐፊውንም ፡ የዮናታንን ፡ ቤት ፡ የግዞት ፡ ቤት ፡ አድርገውት ፡ ነበርና ፥ በዚያ ፡ አኖሩት ።

ኤር. ፡ 37 ፡ 16 ፤ ኤርምያስም ፡ ወደጕድጓድ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ጓዳዎቹ ፡ ገባ ፤ ኤርምያስም ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፥

ኤር. ፡ 37 ፡ 17 ፤ ንጉሡ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡ አስመጣው ፥ ንጉሡም ፡ በቤቱ ። በእውኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ ቃል ፡ አለን ፧ ብሎ ፡ በቈይታ ፡ ጠየቀው ። ኤርምያስም ፦ አዎን ፡ አለ ። ደግሞም ፦ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ አልፈኽ ፡ ትሰጣለኽ ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 37 ፡ 18 ፤ ኤርምያስም ፡ ደግሞ ፡ ንጉሡን ፡ ሴዴቅያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በግዞት ፡ ቤት ፡ የጣላችኹኝ ፡ አንተን ፡ ወይስ ፡ ባሪያዎችኽን ፡ ወይስ ፡ ሕዝብኽን ፡ ምን ፡ በድያችኹ ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 37 ፡ 19 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በእናንተና ፡ በዚች ፡ አገር ፡ አይመጣባችኹም ፡ ብለው ፡ ትንቢት ፡ ይናገሩላችኹ ፡ የነበሩ ፡ ነቢያታችኹ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ኤር. ፡ 37 ፡ 20 ፤ ንጉሡ ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እንድትሰማኝ ፡ አኹን ፡ እለምንኻለኹ ፤ እባክኽ ፥ ልመናዬ ፡ ወዳንተ ፡ ይድረስ ፤ በዚያ ፡ እንዳልሞት ፡ ወደጸሐፊው ፡ ወደዮናታን ፡ ቤት ፡ አትመልሰኝ ።

ኤር. ፡ 37 ፡ 21 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ አዘዘ ፥ ኤርምያስንም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አኖሩት ፥ እንጀራም ፡ ኹሉ ፡ ከከተማ ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ከጋጋሪዎች ፡ መንገድ ፡ ይሰጡት ፡ ነበር ። እንዲሁም ፡ ኤርምያስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 1 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ የማታን ፡ ልጅ ፡ ስፋጥያስ ፥ የጳስኮርም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፥ የሰሌምያም ፡ ልጅ ፡ ዮካል ፥ የመልክያም ፡ ልጅ ፡ ጳስኮር ፡ ሰሙ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 2 ፤ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚች ፡ ከተማ ፡ የሚቀመጥ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታል ፤ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ግን ፡ የሚወጣ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፥ ነፍሱም ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ትኾንለታለች ፥ በሕይወትም ፡ ይኖራል ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ይህች ፡ ከተማ ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰራዊት ፡ እጅ ፡ በርግጥ ፡ ትሰጣለች ፥ ርሱም ፡ ይይዛታል ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 4 ፤ አለቃዎቹም ፡ ንጉሡን ፦ ይህን ፡ የመሰለውን ፡ ቃል ፡ ሲነግራቸው ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ የቀሩትን ፡ የሰልፈኞቹን ፡ እጅ ፡ የሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ያደክማልና ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ እንዲገደል ፡ እንለምንኻለን ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ክፋትን ፡ እንጂ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ሰላምን ፡ አይመኝለትምና ፡ አሉት ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ንጉሡ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልምና ፥ እንሆ ፥ በእጃችኹ ፡ ነው ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 6 ፤ ኤርምያስንም ፡ ወሰዱት ፡ በግዞት ፡ ቤቱም ፡ አደባባይ ፡ ወደነበረው ፡ ወደንጉሡ ፡ ልጅ ፡ ወደመልክያ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ጣሉት ፤ ኤርምያስንም ፡ በገመድ ፡ አወረዱት ። በጕድጓድም ፡ ውስጥ ፡ ጭቃ ፡ እንጂ ፡ ውሃ ፡ አልነበረበትም ፤ ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጭቃው ፡ ውስጥ ፡ ገባ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 7 ፤ በንጉሡም ፡ ቤት ፡ የነበረው ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ አቢሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፡ በጕድጓዱ ፡ ውስጥ ፡ እንዳኖሩት ፡ ሰማ ። ንጉሡም ፡ በብንያም ፡ በር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 8 ፤ አቢሜሌክም ፡ ከንጉሡ ፡ ቤት ፡ ወጥቶ ፡ ንጉሡን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦

ኤር. ፡ 38 ፡ 9 ፤ ጌታዬ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ በጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ በመጣላቸው ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በማድረጋቸው ፡ ሹሉ ፡ ክፉ ፡ አድርገዋል ፤ በከተማዪቱም ፡ ውስጥ ፡ እንጀራ ፡ ስለሌለ ፡ በዚያ ፡ በራብ ፡ ይሞታል ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 10 ፤ ንጉሡም ፡ ኢትዮጵያዊውን ፡ አቢሜሌክም ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ሠላሳ ፡ ሰዎች ፡ ከዚህ ፡ ውሰድ ፥ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፡ ሳይሞት ፡ ከጕድጓድ ፡ አውጣው ፡ ብሎ ፡ አዘዘው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 11 ፤ አቢሜሌክም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰዎችን ፡ ይዞ ፡ ኼደ ፥ ከቤተ ፡ መዛግብቱም ፡ በታች ፡ ወደነበረው ፡ ወደንጉሥ ፡ ቤት ፡ ገባ ፥ ከዚያም ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ ዕላቂ ፡ ልብስ ፡ ወሰደ ፥ ወደ ፡ ኤርምያስም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ በገመድ ፡ አወረደው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 12 ፤ ኢትዮጵያዊውም ፡ አቢሜሌክ ፡ ኤርምያስን ፦ ይህን ፡ አሮጌ ፡ ጨርቅና ፡ ዕላቂውን ፡ ልብስ ፡ በብብትኽ ፡ ከገመዱ ፡ በታች ፡ አድርግ ፡ አለው ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 13 ፤ ኤርምያስንም ፡ በገመዱ ፡ ጐተቱት ፡ ከጕድጓድም ፡ አወጡት ፥ ኤርምያስም ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጠ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 14 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ልኮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደነበረው ፡ ወደ ፡ ሦስተኛው ፡ መግቢያ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ነቢዩን ፡ ኤርምያስን ፡ አስመጣው ፤ ንጉሡም ፡ ኤርምያስን ፦ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቅኻለኹ ፤ ምንም ፡ አትሸሽገኝ ፡ አለው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 15 ፤ ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ ብነግርኽ ፡ በእውኑ ፡ አትገድለኝምን ፧ ብመክርኽም ፡ አትሰማኝም ፡ አለው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 16 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፦ ይህችን ፡ ነፍስ ፡ የፈጠረልን ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ አልገድልኽም ፥ ነፍስኽንም ፡ ለሚሹ ፡ ለእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ አልሰጥኽም ፡ ብሎ ፡ በቈይታ ፡ ለኤርምያስ ፡ ማለ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 17 ፤ ኤርምያስም ፡ ሴዴቅያስን ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ብትወጣ ፥ ነፍስኽ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ፡ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ አትቃጠልም ፤ አንተም ፡ ቤትኽም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራላችኹ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 18 ፤ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ባትወጣ ፡ ግን ፥ ይህች ፡ ከተማ ፡ በከለዳውያን ፡ እጅ ፡ ትሰጣለች ፥ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ፡ አንተም ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፡ አለው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 19 ፤ ንጉሡም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኤርምያስን ፦ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ በኰበለሉት ፡ በአይሁድ ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡኛል ፡ እነርሱም ፡ ያፌዙብኛል ፡ ብዬ ፡ እፈራለኹ ፡ አለው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 20 ፤ ኤርምያስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አሳልፈው ፡ አይሰጡኽም ። እኔ ፡ የምነግርኽን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እባክኽ ፥ ስማ ፤ ይቀናኻል ፥ ነፍስኽም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለች ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 21 ፤ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብትል ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ያሳየኝ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 38 ፡ 22 ፤ እንሆ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ቤት ፡ የቀሩትን ፡ ሴቶች ፡ ሹሉ ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡

ያወጣሉ ፤ እነዚያም ፡ ሴቶች ፦ ባለሟሎችኽ ፡ አታለውኻል ፡ አሸንፈውኽማል ፤ እግሮችኽ ፡ ግን ፡ አኹን ፡ በጭቃ ፡ ውስጥ ፡ ከገቡ ፡ እነርሱ ፡ ከአንተ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰዋል ፡ ይላሉ ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 23 ፤ ሚስቶችኽንና ፡ ልጆችኽንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ከለዳውያን ፡ ያወጣሉ ፤ አንተም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ ትያዛለኽ ፡ እንጂ ፡ ከእጃቸው ፡ አታመልጥም ፤ ይህችም ፡ ከተማ ፡ በእሳት ፡ ትቃጠላለች ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 24 ፤ ሴዴቅያስም ፡ ኤርምያስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ይህን ፡ ቃል ፡ ማንም ፡ አይወቅ ፥ አንተም ፡ አትሞትም ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 25 ፤ አለቃዎቹ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተነጋገርኹ ፡ ቢሰሙ ፥ ወዳንተም ፡ መጥተው ፦ ለንጉሡ ፡ ያልኸውን ፡ ንገረን ፡ አትሸሽገንም ፥ እኛም ፡ አንገድልኽም ፤ ደግሞ ፡ ንጉሡ ፡ ያለኽን ፡ ንገረን ፡ ቢሉኽ ፥ አንተ ፦

ኤር. ፡ 38 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ እሞት ፡ ዘንድ ፡ ወደዮናታን ፡ ቤት ፡ አትመልሰኝ ፡ ብዬ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ለመንኹ ፡ በላቸው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 27 ፤ አለቃዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁ ፥ ንጉሡም ፡ እንዳዘዘው ፡ እንደዚህ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ነገራቸው ። ነገሩም ፡ አልተሰማምና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ መነጋገርን ፡ ተው ።

ኤር. ፡ 38 ፡ 28 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ እስከተያዘችበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ተቀመጠ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 1 ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ በተያዘች ፡ ጊዜ ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥተው ፡ ከበቧት ፤

ኤር. ፡ 39 ፡ 2 ፤ በሴዴቅያስም ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ ከተማዪቱ ፡ ተሰበረች ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 3 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፥ ኤርጌል ፡ ሳራስር ፥ ሳምጋርናቦ ፥ ሠርሰኪም ፥ ራፊስ ፥ ኤርጌል ፡ ሳራስር ፥ ራብማግ ፥ ከቀሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ገብተው ፡ በመካከለኛው ፡ በር ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 4 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ ሰልፈኞቹም ፡ ኹሉ ፡ ባይዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ኰበለሉ ፥ በሌሊትም ፡ በንጉሡ ፡ አትክልት ፡ መንገድ ፡ በኹለቱ ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ከነበረው ፡ ደጅ ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ፤ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ወጡ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 5 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ተከታተላቸው ፥ ሴዴቅያስንም ፡ በኢያሪኮ ፡ ሜዳ ፡ አገኙት ፤ ይዘውም ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነጾር ፡ አመጡት ፡ ርሱም ፡ ፍርድን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 6 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በዐይኑ ፡ ፊት ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የይሁዳን ፡ ከበርቴዎች ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 7 ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ዐይን ፡ አወጣ ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 8 ፤ ከለዳውያንም ፡ የንጉሡንና ፡ የሕዝቡን ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ አቃጠሉ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቅጥር ፡ አፈረሱ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 9 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በከተማዪቱ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ የኰበለሉትን ፡ ሰዎች ፡ የቀረውንም ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ማረካቸው ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 10 ፤ አንዳች ፡ ከሌላቸው ፡ ከሕዝቡ ፡ ድኻዎች ፡ ግን ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ተዋቸው ፥ የወይኑን ፡ ቦታና ፡ ዕርሻውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሰጣቸው ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 11-12 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለ ፡ ኤርምያስ ፦ ውሰደውና ፡ በመልካም ፡ ተመልከተው ፥ የሚሻውንም ፡ ነገር ፡ አድርግለት ፡ እንጂ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አታድርግበት ፡ ብሎ ፡ የዘበኞቹን ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳንን ፡ አዘዘ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 13 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ላከ ፥ ናቡሽዝባንም ፡ ራፋስቂስም ፡ ኤርጌል ፡ ሳራስርም ፡ ራብማግም ፡ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ላኩ ፤

ኤር. ፡ 39 ፡ 14 ፤ ኤርምያስንም ፡ ከግዞት ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ አወጡት ፥ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ይወስደው ፡ ዘንድ ፡ ለሳፋን ፡ ልጅ ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ሰጡት ፤ እንዲሀም ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 15 ፤ በግዞትም ፡ ቤት ፡ አደባባይ ፡ ታስሮ ፡ ሳለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 39 ፡ 16 ፤ ኺድ ፡ ለኢትዮጵያዊውም ፡ ለአቢሜሌክ ([268]) ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ለበጎነት ፡ ሳይኾን ፡ ለክፋት ፡ ቃሌን ፡ በዚች ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በፊትኽ ፡ ይፈጸማል ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 17 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ አድንኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በምትፈራቸው ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አልሰጥኽም ።

ኤር. ፡ 39 ፡ 18 ፤ ፈጽሜ ፡ አድንኻለኹ ፡ ነፍስኽም ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ ትኾንልኻለች ፡ እንጂ ፡ በሰይፍ ፡ አትወድቅም ፥ በእኔ ፡ ታምነኻልና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በተማረኩት ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ መካከል ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ በሰንሰለት ፡ አስሮ ፡ በወሰደው ፡ ጊዜ ፡ ከራማ ፡ ከለቀቀው ፡ በኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 2 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ኤርምያስን ፡ ወሰደው ፡ እንዲህም ፡ አለው ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ፤

ኤር. ፡ 40 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አመጣው ፡ እንደ ፡ ተናገረውም ፡ አደረገ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታችኋልና ፥ ቃሉንም ፡ አልሰማችኹምና ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ኾነባችኹ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 4 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ በእጅኽ ፡ ካለችው ፡ ሰንሰለት ፡ ዛሬ ፡ ፈታኹኽ ። ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ቢታይኽ ፥ ና ፥ እኔም ፡ በመልካም ፡ አይኻለኹ ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ መምጣት ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ባይታይኽ ፡ ግን ፥ ተቀመጥ ፤ እንሆ ፥ አገሪቱ ፡ ኹሉ ፡ በፊትኽ ፡ ናት ፤ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ ወደሚታይኽ ፡ ደስ ፡ ወደሚያሠኝኽም ፡ ስፍራ ፡ ኺድ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 5 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሳይመለስ ። የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ወደሾመው ፡ ወደሳፋን ፡ ልጅ ፡ ወደአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ተመለስ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡

268 ዕብ. ፥ ዐበድመለክ ፡ (የንጉሥ ፡ አገልጋይ) ።

ተቀመጥ ፤ ወይም ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ደስ ፡ ወደሚያሠኝኽ ፡ ስፍራ ፡ ኼድ ፡ አለው ። የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ሥንቅና ፡ ስጦታ ፡ ሰጥቶ ፡ አሰናበተው ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 6 ፤ ኤርምያስም ፡ የአኪ.ቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ኼደ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ በቀሩት ፡ ሕዝብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 7 ፤ በየሜዳውም ፡ የነበሩት ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችና ፡ ሰዎቻቸው ፡ ዅሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የአኪ.ቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሾመ ፥ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆችንም ፥ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ያልተማረኩትን ፡ የምድርን ፡ ድኻዎች ፥ እንዳስጠበቀ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፥

ኤር. ፡ 40 ፡ 8 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንና ፡ ዮናታን ፥ የተንሑሜትም ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፥ የነጦፋዊውም ፡ የዮፌ ፡ ልጆች ፡ የማዕካታዊውም ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፡ ከሰዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 9 ፤ የሳፋንም ፡ ልጅ ፡ የአኪ.ቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ለእነርሱና ፡ ለሰዎቻቸው ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ማለ ። ለከለዳውያን ፡ ትገዙ ፡ ዘንድ ፡ አትፍሩ ፤ በምድር ፡ ተቀመጡ ፡ ለባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ ተገዙ ፥ መልካምም ፡ ይኾንላችኋል ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 10 ፤ እኔም ፥ እንሆ ፥ ወደ ፡ እኛ ፡ በሚመጡት ፡ ከለዳውያን ፡ ፊት ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በምጽጳ ፡ እኖራለኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወይንንና ፡ የበጋ ፡ ፍሬ ፡ ዘይትንም ፡ አከማቹ ፥ በየዕቃችኹም ፡ ውስጥ ፡ ክተቱ ፥ በያዛችኋቸውም ፡ ከተማዎቻችኹ ፡ ተቀመጡ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 11 ፤ በሞዐብም ፡ በዐሞንም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ በኤዶምያስም ፡ በምድርም ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ እንዳስቀረ ፥ የሳፋንንም ፡ ልጅ ፡ የአኪ.ቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በላያቸው ፡ እንደ ፡ ሾመው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፡ 40 ፡ 12 ፤ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ ከተሰደዱበት ፡ ስፍራ ፡ ዅሉ ፡ ተመለሱ ፥ ወደይሁዳም ፡ አገር ፡ ጎዶልያስ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጡ ፥ ወይንና ፡ የበጋንም ፡ ፍሬ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ አከማቹ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 13 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ በየሜዳውም ፡ የነበሩ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ መጥተው ፦

ኤር. ፡ 40 ፡ 14 ፤ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ንጉሥ ፡ በዓሊስ ፡ ይገድልኽ ፡ ዘንድ ፡ የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ እንደ ፡ ሰደደ ፡ ታውቃለኽን ፧ አሉት ። የአኪ.ቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ግን ፡ አላመናቸውም ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 15 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፦ እባክኽ ፥ ልኬድ ፤ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ የናታንያን ፡ ልጅ ፡ እስማኤልን ፡ ልግደለው ፤ ወዳንተ ፡ የተሰበሰቡ ፡ አይሁድ ፡ ዅሉ ፡ እንዲበተኑ ፡ የይሁዳም ፡ ቅሬታ ፡ እንዲጠፋ ፡ ነፍስኽን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይገድላል ፧ ብሎ ፡ በምጽጳ ፡ በቈይታ ፡ ለጎዶልያስ ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፡ 40 ፡ 16 ፤ የአኪ.ቃም ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስ ፡ ግን ፡ የቃሬያን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፦ በእስማኤል ፡ ላይ ፡ ሐሰት ፡ ተናግረኻልና ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ አለው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 1 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከመንግሥት ፡ ወገንና ፡ ከንጉሡ ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ አለቃዎች ፡ አንዱ ፡ የኤሊሳማ ፡ ልጅ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምጽጳ ፡ ወደአኪ.ቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ መጣ ፤ በዚያም ፡ በምጽጳ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ እንጀራ ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 2 ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ዐሥሩ ፡ ሰዎች ፡ ተነሥተው ፡ የሳፋንን ፡ ልጅ ፡ የአኪ.ቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በሰይፍ ፡ መቱ ፥ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡

ገደሉ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 3 ፤ እስማኤልም ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ በምጽጳ ፡ የነበሩትን ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፥ በዚያም ፡ የተገኙትን ፡ የከለዳውያንን ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ገደላቸው ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 4 ፤ ጎዶልያስን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሳያውቅ ፡ በኹለተኛው ፡ ቀን ፥

ኤር. ፡ 41 ፡ 5 ፤ ጢማቸውን ፡ ላጭተው ፡ ልብሳቸውንም ፡ ቀደው ፡ ገላቸውንም ፡ ነጭተው ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ የእኽል ፡ ቍርባንና ፡ ዕጣን ፡ በእጃቸው ፡ እየያዙ ፥ ሰማንያ ፡ ሰዎች ፡ ከሴኬምና ፡ ከሴሎ ፡ ከሰማርያም ፡ መጡ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 6 ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከምጽጳ ፡ ወጥቶ ፡ እያለቀሰ ፡ ሊገናኛቸው ፡ ኼደ ፤ በተገናኛቸውም ፡ ጊዜ ፦ ወደአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ጎዶልያስ ፡ ኑ ፡ አላቸው ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 7 ፤ ወደከተማም ፡ መካከል ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ገደሏቸው ፥ በጕድጓድም ፡ መካከል ፡ ጣሏቸው ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 8 ፤ በመካከላቸውም ፡ እስማኤልን ፦ በሜዳ ፡ የተሸሸገ ፡ ስንዴና ፡ ገብስ ፡ ዘይትና ፡ ማርም ፡ አለንና ፡ አትግደለን ፡ የሚሉት ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ። ርሱም ፡ ተዋቸው ፥ ከወንድሞቻቸውም ፡ ጋራ ፡ አልገደላቸውም ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 9 ፤ እስማኤልም ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ የገደላቸውን ፡ የሰዎች ፡ ሬሳ ፡ ኹሉ ፡ የጣለበት ፡ ጕድጓድ ፡ ንጉሡ ፡ አሣ ፡ የእስራኤልን ፡ ንጉሥ ፡ ባኦስን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ የሠራው ፡ ጕድጓድ ፡ ነበረ ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ የገደላቸውን ፡ ሞላበት ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 10 ፤ እስማኤልም ፡ በምጽጳ ፡ የነበረውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ የንጉሡን ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ለአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ለጎዶልያስ ፡ የሰጠውን ፡ በምጽጳ ፡ የቀሩትን ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ማረካቸው ፤ የናታንያም ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ማርኮ ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 11 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ያደረገውን ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፡ 41 ፡ 12 ፤ ሰዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ይዘው ፡ ከናታንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ጋራ ፡ ሊዋጉ ፡ ኼዱ ፥ በገባዖንም ፡ ባለው ፡ በታላቁ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ አገኙት ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 13 ፤ ከእስማኤልም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የቃሬያን ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችን ፡ ኹሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 14 ፤ እስማኤልም ፡ ከምጽጳ ፡ የማረካቸው ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ዘወር ፡ ብለው ፡ ተመለሱ ፥ ወደቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮሐናን ፡ ኼዱ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 15 ፤ የናታንያ ፡ ልጅ ፡ እስማኤል ፡ ግን ፡ ከስምንት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ከዮሐናን ፡ አመለጠ ፡ ወደዐሞንም ፡ ልጆች ፡ ኼደ ።

ኤር. ፡ 41 ፡ 16 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ የአኪቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ በምጽጳ ፡ ከገደለው ፡ በኋላ ፡ ከናታንያ ፡ ልጅ ፡ ከእስማኤል ፡ ያስመለሷቸውን ፡ የሕዝቡን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ከገባዖን ፡ ያስመለሷቸውን ፡ ሰልፈኞች ፥ ሴቶችንም ፥ ልጆችንም ፥ ጃን ፡ ደረባዎችንም ፥ ወሰዱ ፤

ኤር. ፡ 41 ፡ 17 ፤ ተነሥተውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በጌሮት ፡

ከመዓም ፡ ተቀመጡ ፤

ኤር. ፡ 41 ፡ 18 ፤ እስማኤል ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በአገሩ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ የአኪ.ቃምን ፡ ልጅ ፡ ጎዶልያስን ፡ ስለ ፡ ገደለው ፡ ከለዳውያንን ፡ ፈርተዋልና ።

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 42 ። _____

ኤር. ፡ 42 ፡ 1 ፤ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የሆሻያም ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፡ ሕዝብም ፡ ኹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ቀረቡ ፥

ኤር. ፡ 42 ፡ 2-3 ፤ ነቢዩንም ፡ ኤርምያስን ፦ ዐይኖችኽ ፡ እንዳዩን ፡ ከብዙ ፡ ጥቂት ፡ ቀርተናልና ፥ ልመናችን ፥ እባክኽ ፥ በፊትኽ ፡ ትድረስ ፤ አምላክኽም ፡ እግዚአብሔር ፡ የምንኼድበትን ፡ መንገድና ፡ የምናደርገውን ፡ ነገር ፡ ያሳየን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፥ ስለዚህ ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልይ ፡ አሉት ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 4 ፤ ነቢዩም ፡ ኤርምያስ ፦ ሰምቻችኋለኹ ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ቃላችኹ ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጸልያለኹ ፤ እግዚአብሔርም ፡ የሚመልስላችኹን ፡ ኹሉ ፡ እነግራችኋለኹ ፥ ከእናንተም ፡ ምንም ፡ አልሸሸግም ፡ አላቸው ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 5 ፤ ኤርምያስንም ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባንተ ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ የላከውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ባናደርግ ፥ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ እውነተኛና ፡ ታማኝ ፡ ምስክር ፡ ይኹን ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 6 ፤ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በመስማታችን ፡ መልካም ፡ እንዲኾንልን ፥ መልካም ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ቢኾን ፥ አንተን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የምንልክኽ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንሰማለን ፡ አሉት ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 7 ፤ ከዐሥር ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ መጣ ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 8 ፤ የቃሬያንም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናንን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩትን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ሕዝቡንም ፡ ኹሉ ፡ ጠራ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦

ኤር. ፡ 42 ፡ 9 ፤ ጸሎታችኹን ፡ በፊቱ ፡ አቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የላካችኹኝ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ኤር. ፡ 42 ፡ 10 ፤ ስላደረግኹባችኹ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸጽቻለኹና ፡ በዚች ፡ ምድር ፡ ብትቀመጡ ፡ እሠራችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ አላፈርሳችኹም ፥ እተክላችኋለኹ ፡ እንጂ ፡ አልነቅላችኹም ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 11 ፤ ከምትፈሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ አትፍሩ ፤ አድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ ከእጁም ፡ አስጥላችኹ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍሩ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ እንዲምራችኹ ፡ ወደ ፡ አገራችኹም ፡ እንዲመልሳችኹ ፡ እኔ ፡ እምራችኋለኹ ።

ኤር. ፡ 42 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ በዚች ፡ ምድር ፡ አንቀመጥም ፡ ብትሉ ፡ የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ባትሰሙ ፥

ኤር. ፡ 42 ፡ 14 ፤ እናንተም ፦ አይደለም ፤ ሰልፍ ፡ ወደማናይባት ፡ የመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ወደማንሰማባት ፡ ወደማንራብባትም ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ እንኼዳለን ፡ በዚያም ፡ እንቀመጣለን ፡ ብትሉ ፥

ኤር. ፡ 42 ፡ 15 ፤ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡

በዚያም ፡ ትቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታችኹን ፡ ብታቀኑ ፥

ኤር. ፥ 42 ፥ 16 ፤ የምትፈሩት ፡ ሰይፍ ፡ በዚያ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ያገኛችኋል ፥ ስለ ፡ ርሱም ፡ የምትደነግጡበት ፡ ራብ ፡ በዚያ ፡ በግብጽ ፡ ይደርስባችኋል ፥ በዚያም ፡ ትሞታላችኹ ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 17 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ በሚያቀኑ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ይኾንባቸዋል ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይሞታሉ ፤ እኔም ፡ ከማመጣባቸው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ማንም ፡ አይቀርም ፥ ማንም ፡ አያመልጥም ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 18 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ቍጣዬና ፡ መዓቴ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፥ እንዲሁ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ በገባችኹ ፡ ጊዜ ፡ መዓቴ ፡ ይፈስባችኋል ፤ እናንተም ፡ ለጥላቻና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመረገሚያና ፡ ለመሰደቢያ ፡ ትኾናላችኹ ፥ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታዩትም ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 19 ፤ እናንተ ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፦ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትግቡ ፡ ብሎ ፡ ተናግሮባችኋልና ፥ ዛሬ ፡ እንዳስጠነቀቅኋችኹ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቁ ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 20 ፤ እናንተ ፦ ስለ ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸልዩ ፥ አምላካችንም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚናገርኽን ፡ ኹሉ ፡ ንገረን ፡ እኛም ፡ እናደርገዋለን ፡ ብላችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ልካችኹኝ ፡ ነበርና ፥ ራሳችኹን ፡ አታላችኋል ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 21 ፤ እኔም ፡ ዛሬ ፡ ነግሬያችኋለኹ ፥ ወደ ፡ እናንተም ፡ በላከኝ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰማችኹም ።

ኤር. ፥ 42 ፥ 22 ፤ አኹንም ፡ ኼዳችኹ ፡ እንድትቀመጡ ፡ በወደዳችኹበት ፡ ስፍራ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እንድትሞቱ ፡ በርግጥ ፡ ዕወቁ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ።

ኤር. ፥ 43 ፥ 1 ፤ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ለእነርሱ ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ የላከውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ኤርምያስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ መናገርን ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

ኤር. ፥ 43 ፥ 2 ፤ የሆሻያ ፡ ልጅ ፡ ዐዛርያስ ፡ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ ትዕቢተኞችም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ኤርምያስን ፦ ሐሰት ፡ ተናግረኻል ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፦ በዚያ ፡ ትቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ አትግቡ ፡ ብሎ ፡ አላከኽም ፤

ኤር. ፥ 43 ፥ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከለዳውያን ፡ እንዲገድሉን ፡ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ እንዲማርኩን ፡ በእጃቸው ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጠን ፡ ዘንድ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ አነሣሥቶኻል ፡ አሉት ።

ኤር. ፥ 43 ፥ 4 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አልሰሙም ።

ኤር. ፥ 43 ፥ 5 ፤ የቃሬያም ፡ ልጅ ፡ ዮሐናን ፡ የጭፍራ ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ በይሁዳ ፡ ምድር ፡ ለመቀመጥ ፡ ከተሰደዱባቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የተመለሱትን ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፥

ኤር. ፥ 43 ፥ 6 ፤ ወንዶችንና ፡ ሴቶችን ፡ ልጆችንም ፡ የንጉሡንም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፥ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ከሳፋን ፡ ልጅ ፡ ከአኪቃም ፡ ልጅ ፡ ከጎዶልያስ ፡ ጋራ ፡ የተዋቸውን ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ ነቢዩንም ፡ ኤርምያስን ፡ የኔርያንም ፡ ልጅ ፡ ባሮክን ፡ ወሰዱ ፤

ኤር. ፡ 43 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ አልሰሙምና ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ ገቡ ፥ እስከ ፡ ጣፍናስ ፡ ድረስ ፡ መጡ ።

ኤር. ፡ 43 ፡ 8 ፤ በጣፍናስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ኤር. ፡ 43 ፡ 9 ፤ ታላላቆችን ፡ ድንጋዮች ፡ በእጅኽ ፡ ውሰድ ፥ የይሁዳም ፡ ሰዎች ፡ እያዩ ፡ በጣፍናስ ፡ ባለው ፡ በፈርያን ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡ መግቢያ ፡ ሸሽጋቸው ፤

ኤር. ፡ 43 ፡ 10 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ልኬ ፡ ባሪያዬን ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ አመጣለኹ ፥ ዙፋኑንም ፡ እኔ ፡ በሸሸግኋቸው ፡ በእነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ፤ ርሱም ፡ ማለፊያውን ፡ ድንኳኑን ፡ በላያቸው ፡ ይዘረጋል ።

ኤር. ፡ 43 ፡ 11 ፤ መጥቶም ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ይመታል ፥ ለሞትም ፡ የሚኾነውን ፡ ለሞት ፥ ለምርኮም ፡ የሚኾነውን ፡ ለምርኮ ፥ ለሰይፍም ፡ የሚኾነውን ፡ ለሰይፍ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ።

ኤር. ፡ 43 ፡ 12 ፤ በግብጽም ፡ አማልክት ፡ ቤቶች ፡ እሳትን ፡ ያነዳል ፡ ያቃጥላቸውማል ፡ ይማርካቸውማል ፤ እረኛም ፡ ደበሎውን ፡ እንደሚደርብ ፡ እንዲሁ ፡ የግብጽን ፡ አገር ፡ ይደርባል ፤ ከዚያም ፡ በሰላም ፡ ይወጣል ።

ኤር. ፡ 43 ፡ 13 ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ያለውን ፡ የሄልዮቱን ፡ ከተማ ፡ ሐውልቶች ፡ ይሰብራል ፥ የግብጽንም ፡ አማልክት ፡ ቤቶች ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላል ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 44 ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 1 ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በሚግዶልና ፡ በጣፍናስ ፡ በሜምፎስም ፡ በጳትሮስም ፡ አገር ፡ ስለተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 44 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ያመጣኹትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አይታችኋል ፤ እንሆ ፥ ዛሬ ፡ ባድማ ፡ ኾነዋል ፥ የሚቀመጥባቸውም ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 3 ፤ ይህም ፡ የኾነው ፡ ያስቈጡኝ ፡ ዘንድ ፡ ስላደረጉት ፡ ክፋት ፥ ለማያውቋቸውም ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ያጥኑ ፡ ዘንድ ፡ ያመልኳቸውም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ኼዱ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 4 ፤ በማለዳም ፡ ተነሥቼ ፡ ባሪያዎቼን ፡ ነቢያትን ፡ ኹሉ ፡ ሰደድኹባችኹና ፦ እንደዚህ ፡ እንደ ፡ ጠላኹት ፡ ያለ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ አታድርጉ ፡ አልኋችኹ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልሰሙም ፡ ከክፋታቸውም ፡ ተመልሰው ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ እንዳያጥኑ ፡ ዦሯቸውን ፡ አላዘነበሉም ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ መዓቴና ፡ ቍጣዬ ፡ ፈሰሱ ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ነደዱ ፤ ዛሬም ፡ እንደኾነው ፡ ፈረሱ ፡ ባድማም ፡ ኾኑ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 7 ፤ አኹንም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ ቅሬታ ፡ እንዳይቀርላችኹ ፥ ወንድንና ፡ ሴትን ፥ ብላቴናንና ፡ ሕፃንን ፡ ከመካከላችኹ ፡ ታጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ክፋት ፡ በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ ለምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧

ኤር. ፡ 44 ፡ 8 ፤ ሰውነታችኹንም ፡ ታጠፉ ፡ ዘንድ ፡ በምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ መረገሚያና ፡ መሰደቢያ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፥ ለመቀመጥ ፡ በገባችኹባት ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ በማጠናችኹ ፡

በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ ለምን ፡ ታስቈጡኛላችኹ ፡፡

ኤር. ፡ 44 ፡ 9 ፤ በእውኑ ፡ በይሁዳ ፡ ምድርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ያደረጉትን ፡ የአባቶቻችኹን ፡ ክፋት ፥ የይሁዳንም ፡ ነገሥታት ፡ ክፋት ፥ የሚስቶቻቸውንም ፡ ክፋት ፥ የእናንተንም ፡ ክፋት ፥ የሚስቶቻችኹንም ፡ ክፋት ፡ ረስታችኹታልን ፡፡

ኤር. ፡ 44 ፡ 10 ፤ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ አልተዋረዱም ፡ አልፈሩምም ፥ በእናንተና ፡ በአባቶቻችኹም ፡ ፊት ፡ ባኖርኹት ፡ ሕጌና ፡ ሥርዐቴ ፡ አልኼዱም ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 11 ፤ ስለዚህም ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ይሁዳን ፡ ኹሉ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ፊቴን ፡ ለክፋት ፡ በላያችኹ ፡ አደርጋለኹ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያም ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ፊታቸውን ፡ ያቀኑትን ፡ የይሁዳን ፡ ቅሬታ ፡ እወስዳለኹ ፥ ኹሉም ፡ ይጠፋሉ ፥ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ይወድቃሉ ፤ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይጠፋሉ ፤ ከታናሹም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ይሞታሉ ፤ ለጥላቻና ፡ ለመደነቂያ ፡ ለመረገሚያና ፡ ለመሰደቢያ ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 13 ፤ ኢየሩሳሌምንም ፡ እንደ ፡ ቀጣኹ ፥ እንዲሁ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ እቀጣለኹ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ለመቀመጥ ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ ከኼዱ ፥ ወደይሁዳ ፡ አገር ፡ ተመልሰው ፡ በዚያ ፡ ይቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ከሚወዱ ፡ ከይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ወገን ፡ የሚያመልጥና ፡ የሚቀር ፡ ወደዚያም ፡ የሚመለስ ፡ የለም ፤ ከሚያመልጥም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አይመለስም ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 15 ፤ ሚስቶቻቸውም ፡ ለሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ማጠናቸውን ፡ ያወቁ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በዚያም ፡ የቆሙ ፡ ሴቶች ፡ ኹሉ ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ በጳትሮስ ፡ የተቀመጡ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ኾነው ፡ ለኤርምያስ ፡ መለሱለት ፡ እንዲህም ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 16 ፤ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የነገርኸንን ፡ ቃል ፡ አንሰማኽም ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኛና ፡ አባቶቻችን ፡ ነገሥታታችንም ፡ አለቃዎቻችንም ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ እናደርገው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ እናጥን ፡ ዘንድ ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ እናፈስላት ፡ ዘንድ ፡ ከአፋችን ፡ የወጣውን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ በርግጥ ፡ እናደርጋለን ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ እንጀራ ፡ እንጠግብ ፡ ነበር ፥ መልካምም ፡ ይኾንልን ፡ ክፉም ፡ አናይም ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 18 ፤ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ማጠንን ፥ ለርሷም ፡ የመጠጥን ፡ ቍርባን ፡ ማፍሰስን ፡ ከተውን ፡ ወዲህ ፡ ግን ፥ እኛ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ ተቸግረናል ፥ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ አልቀናል ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 19 ፤ እኛስ ፡ ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ ባጠንላት ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ ባፈሰስንላት ፡ ጊዜ ፥ በእውኑ ፡ ያለባሎቻችን ፡ ምስሏን ፡ ለማብጀት ፡ ዕንጐቻ ፡ አድርገንላት ፡ ኖሯልን ፡፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ አፍሰንላት ፡ ኖሯልን ፡፡

ኤር. ፡ 44 ፡ 20 ፤ ኤርምያስም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለመለሱለት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ ለወንዶቹና ፡ ለሴቶቹ ፡ ለሕዝቡም ፡ ኹሉ ፥ መለሰላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 44 ፡ 21 ፤ እናንተና ፡ አባቶቻችኹ ፡ ነገሥታታችኹም ፡ አለቃዎቻችኹም ፡ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ በይሁዳ ፡ ከተማዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ያጠናችኹትን ፡ ዕጣን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያሰበው ፡ በልቡም ፡ ያኖረው ፡ አይደለምን ፡፡

ኤር. ፡ 44 ፡ 22 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሥራችኹን ፡ ክፋትና ፡ ያደረጋችኹትን ፡ ርኵሰት ፡

ይታገሥ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ፤ ስለዚህ ፥ ምድራችኹ ፡ ባድማ ፣ መደነቂያም ፣ መረገሚያም ፡ ኾናለች ፥ ዛሬም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ የሚኖርባት ፡ የለም ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 23 ፤ ስላጠናችኹ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ በደላችኹ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ስላልሰማችኹ ፥ በሕጉና ፡ በሥርዐቱም ፡ በምስክሩም ፡ ስላልኼዳችኹ ፥ ስለዚህ ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አግኝታችኋለች ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 24 ፤ ኤርምያስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ለሴቶቹም ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተና ፡ ሚስቶቻችኹ ፡ በአፋችኹ ። ለሰማይ ፡ ንግሥት ፡ እናጥን ፡ ዘንድ ፡ የመጠጥንም ፡ ቍርባን ፡ እናፈስላት ፡ ዘንድ ፡ የተሳልነውን ፡ ስእለታችንን ፡ በርግጥ ፡ እንፈጽማለን ፡ አላችኹ ፡ በእጃችኹም ፡ አደረጋችኹት ፤ እንግዲህ ፡ ስእለታችኹን ፡ አጽኑ ፡ ስእለታችኹንም ፡ ፈጽሙ ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 26 ፤ እናንተ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የምትኖሩ ፡ ይሁዳ ፡ ኹሉ ፥ ስለዚህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በሚኖር ፡ በይሁዳ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ ስሜ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ። ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ተብሎ ፡ እንዳይጠራ ፥ እንሆ ፥ በታላቅ ፡ ስሜ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 27 ፤ እንሆ ፥ ለመልካም ፡ ሳይኾን ፡ ለክፋት ፡ እተጋባቸዋለኹ ፤ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ያሉት ፡ የይሁዳ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ ያልቃሉ ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 28 ፤ ከሰይፍም ፡ የሚያመልጡ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ኾነው ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ወደይሁዳ ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ፤ ሊቀመጡም ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ የገቡት ፡ የይሁዳ ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ወይም ፡ ከነርሱ ፡ የማናችን ፡ ቃል ፡ እንዲጸና ፡ ያውቃሉ ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 29 ፤ ቃሌም ፡ በላያችኹ ፡ ለክፋት ፡ እንዲጸና ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፡ እንድቀጣችኹ ፡ ምልክታችኹ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 44 ፥ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስን ፡ ጠላቱ ፡ ለኾነው ፡ ነፍሱንም ፡ ለፈለገው ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እንደ ፡ ሰጠኹት ፥ እንዲሁ ፥ እንሆ ፥ የግብጹን ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ሐፍራን ፡ ለጠላቶቹ ፡ ነፍሱንም ፡ ለሚፈልጉ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ኤር. ፥ 45 ፥ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ባሮክ ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ከኤርምያስ ፡ አፍ ፡ በመጽሐፍ ፡ በጻፋቸው ፡ ጊዜ ፥ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 45 ፥ 2 ፤ ባሮክ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይልኻል ።

ኤር. ፥ 45 ፥ 3 ፤ አንተ ፦ እግዚአብሔር ፡ በሕመሜ ፡ ላይ ፡ ሐዘንን ፡ ጨምሮብኛልና ፥ ወዮልኝ! ፡ በልቅሶዬ ፡ ጭኸት ፡ ደክሜያለኹ ፥ ዕረፍትንም ፡ አላገኘኹም ፡ ብለኻል ።

ኤር. ፥ 45 ፥ 4 ፤ እንዲህ ፡ በለው ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የሠራኹትን ፡ አፈርሳለኹ ፥ የተከልኹትንም ፡ እነቅላለኹ ፤ ይኸውም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ነው ።

ኤር. ፥ 45 ፥ 5 ፤ ለራስኽ ፡ ታላቅን ፡ ነገር ፡ ትፈልጋለኽን ፧ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ እንሆ ፥ ክፉ ፡ ነገርን ፡

አመጣለኹና ፡ አትፈልገው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኼድኽበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ነፍስኽን ፡ እንደ ፡ ምርኮ ፡ አድርጌ ፡ እሰጥኻለኹ ።

_____ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ። _____

ኤር. ፥ 46 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 46 ፥ 2 ፤ ስለ ፡ ግብጽ ፤ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ በከርከሚሽ ፡ ስለነበረው ፥ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በኢዮስያስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮአቄም ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለመታው ፡ ስለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ስለፈርዖን ፡ ኒካዑ ፡ ሰራዊት ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 3 ፤ ጋሻ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ፡ ወደ ፡ ሰልፍም ፡ ቅረቡ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 4 ፤ ፈረሰኞች ፡ ሆይ ፥ ፈረሶችን ፡ ለጕሙና ፡ ውጡ ፥ ራስ ፡ ቍርንም ፡ ደፍታችኹ ፡ ቁሙ ፤ ጦርንም ፡ ሰንግሉ ፡ ጥሩርንም ፡ ልበሱ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 5 ፤ ፈርተው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ሲመለሱ ፥ ኀያላናቸውም ፡ ሲደበደቡ ፡ ወደ ፡ ኋላቸውም ፡ ሳይመለከቱ ፡ ፈጥነው ፡ ሲሸሹ ፡ ለምን ፡ አየኹ ፧ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ድንጋጤ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 6 ፤ ፈጣኑ ፡ አያመልጥም ፡ ኀያሉም ፡ አይድንም ፤ በሰሜን ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ በኩል ፡ ተሰናክለው ፡ ወደቁ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 7 ፤ ይህ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ የሚነሣ ፥ ውሃውም ፡ እንደ ፡ ወንዝ ፡ የሚናወጥ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፥ 46 ፥ 8 ፤ ግብጽ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ይነሣል ፡ ውሃውም ፡ እንደ ፡ ወንዙ ፡ ይናወጣል ፤ ርሱም ፦ እነሣለኹ ፡ ምድርንም ፡ ኹሉ ፡ እከድናለኹ ፤ ከተማዎችንና ፡ የሚኖሩባቸውን ፡ አጠፋለኹ ፡ ብሏል ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 9 ፤ ፈረሶች ፡ ሆይ ፥ ውጡ ፤ ሠረገላዎችም ፡ ሆይ ፥ ንጐዱ ፤ ጋሻም ፡ የሚያነግቡ ፡ የኢትዮጵያና ፡ የፋጥ ፡ ኀያላን ፥ ቀስትንም ፡ ይዘው ፡ የሚስቡ ፡ የሉድ ፡ ኀያላን ፡ ይውጡ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 10 ፤ ያ ፡ ቀን ፡ ጠላቶቹን ፡ የሚበቀልበት ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የበቀል ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ሰይፍ ፡ በልቶ ፡ ይጠግባል ፡ በደማቸውም ፡ ይሰክራል ፥ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ በኤፍራጥስ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ መሥዋዕት ፡ አለውና ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 11 ፤ ድንግሊቱ ፡ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ገለዓድ ፡ ውጪ ፥ የሚቀባንም ፡ መድኀኒት ፡ ውሰጂ ፤ መድኀኒትን ፡ ያበዛሽው ፡ በከንቱ ፡ ነው ፤ መዳን ፡ የለሽም ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 12 ፤ ኀያሉ ፡ በኀያሉ ፡ ላይ ፡ ተሰናክሎ ፡ ኹለቱ ፡ በአንድነት ፡ ወድቀዋልና ፥ አሕዛብ ፡ ጕስቍልናሽን ፡ ሰምተዋል ፥ ልቅሶሽም ፡ ምድርን ፡ ሞልቷታል ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 13 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ እንዲመጣና ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ እንዲመታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለነቢዩ ፡ ለኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 46 ፥ 14 ፤ በግብጽ ፡ ተናገሩ ፥ በሚግዶልም ፡ አሰሙ ፥ በሜምፎስና ፡ በጣፍናስ ፡ አሰሙ ፤ ሰይፍ ፡ በዙሪያኽ ፡ ያለውን ፡ በልቷልና ፦ ተነሥ ፡ ተዘጋጅም ፡ በሉ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 15 ፤ ኀይለኞችኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተወገዱ ፧ እግዚአብሔር ፡ ስላደከማቸው ፡ አልቆሙም ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 16 ፤ ብዛታቸውም ፡ ተሰናከለ ፥ ሰውም ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡

ወደቀ ፤ እነርሱም ፦ ተነሡ ፥ ከሚያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ወገናችን ፡ ወደተወለድንባት ፡ ምድር ፡ እንመለስ ፡ አሉ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 17 ፤ በዚያም ፡ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንን ፦ ሰዓቱን ፡ የሚያሳልፍ ፡ ጕረኛ ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 18 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በተራራዎች ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ታቦር ፥ በባሕርም ፡ አጠገብ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ቀርሜሎስ ፥ እንዲሁ ፡ በእውነት ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 19 ፤ አንቺ ፡ በግብጽ ፡ የምትቀመጪ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ሜምፎስ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለችና ፥ ትቃጠልማለችና ፥ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝምና ፡ ለምርኮ ፡ የሚኾን ፡ ዕቃ ፡ አዘጋጂ ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 20 ፤ ግብጽ ፡ የተዋበች ፡ ጊደር ፡ ናት ፤ ጥፋት ፡ ግን ፡ ይመጣል ፥ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ይመጣባታል ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 21 ፤ በርሷም ፡ ያሉ ፡ የተቀጠሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንደ ፡ ሰቡ ፡ ወይፈኖች ፡ ናቸው ፤ የጥፋታቸው ፡ ቀንና ፡ የመጐብኘታቸው ፡ ጊዜ ፡ መጥቶባቸዋልና ፥ ተመለሱ ፥ በአንድነትም ፡ ሸሹ ፥ አልቆሙምም ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 22 ፤ ከሰራዊትም ፡ ጋራ ፡ ይኼዳሉና ፥ ድምፅ ፡ እንደ ፡ እባብ ፡ ይተሣል ፤ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ቈራጮችም ፡ በምሣር ፡ ይመጡባታል ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 23 ፤ ይቈጠሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻሉትን ፡ የዱሯን ፡ ዛፎች ፡ ይቈርጣሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከአንበጣ ፡ ይልቅ ፡ በዝተዋልና ፥ ቍጥርም ፡ የላቸውምና ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 24 ፤ የግብጽ ፡ ልጅ ፡ ታፍራለች ፤ በሰሜን ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ዐልፋ ፡ ትሰጣለች ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 25 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የኖእ ፡ ዐሞንን ፥ ፈርዖንንም ፥ ግብጽንም ፥ አማልክቷንና ፡ ነገሥታቷንም ፥ ፈርዖንና ፡ በርሱም ፡ የሚታመኑትን ፡ እቀጣለኹ ፤

ኤር. ፥ 46 ፥ 26 ፤ ነፍሳቸውንም ፡ በሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፥ በባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፥ በባሪያዎቹም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቀድሞው ፡ ዘመን ፡ የሰው ፡ መኖሪያ ፡ ትኾናለች ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፥ አንተም ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አትደንግጥ ፤ እንሆ ፥ አንተን ፡ ከሩቅ ፡ ዘርኽንም ፡ ከተማረከባት ፡ ምድር ፡ አድናለኹ ፤ ያዕቆብም ፡ ተመልሶ ፡ ያርፋል ፡ ተዘልሎም ፡ ይቀመጣል ፥ ማንም ፡ አያስፈራውምም ።

ኤር. ፥ 46 ፥ 28 ፤ አንተ ፡ ባሪያዬ ፡ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ አትፍራ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ አንተንም ፡ ያሰደድኹባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለኹና ፥ አንተን ፡ ግን ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋኽም ፤ በመጠን ፡ እቀጣኻለኹ ፥ ያለቅጣትም ፡ አልተውኽም ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ።

ኤር. ፥ 47 ፥ 1 ፤ ፈርዖንም ፡ ጋዛን ፡ ሳይመታ ፡ ስለ ፡ ፍልስጥኤማውያን ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፥ 47 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ውሃ ፡ ከሰሜን ፡ ይነሣል ፡ የሚያጥለቀልቅም ፡ ፈሳሽ ፡ ይኾናል ፤ በአገሪቱና ፡ በመላዋ ፡ ኹሉ ፥ በከተማዪቱና ፡ በሚኖሩባት ፡ ላይ ፡ ይጐርፋል ፤ ሰዎቹም ፡ ይጮኻሉ ፥ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሳሉ ።

ኤር. ፡ 47 ፡ 3 ፤ ከጎይለኞች ፡ ፈረሶች ፡ ከኰቴያቸው ፡ መጠብጠብ ፡ ድምፅ ፥ ከሠረገላዎቹም ፡ መሽከርከር ፥ ከመንኰራኵሮቹም ፡ መትመም ፡ የተነሣ ፡ አባቶች ፡ በእጃቸው ፡ ድካም ፡ ምክንያት ፡ ፊታቸውን ፡ መልሰው ፡ ወደ ፡ ልጆቻቸው ፡ አይመለከቱም ።

ኤር. ፡ 47 ፡ 4 ፤ ይህም ፡ የሚኾነው ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ የቀሩትንም ፡ ረዳቶች ፡ ኹሉ ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ይቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚመጣው ፡ ቀን ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍልስጥኤማውያንና ፡ የከፍቶርን ፡ ደሴት ፡ ቅሬታ ፡ ያጠፋልና ።

ኤር. ፡ 47 ፡ 5 ፤ ቡሓነት ፡ በጋዛ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ፤ አስቀሎና ፡ ጠፋች ፤ የዔናቅ ፡ ቅሬታዎች ፡ ሆይ! ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ገላችኹን ፡ ትነጫላችኹ ፧

ኤር. ፡ 47 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰይፍ ፡ ሆይ ፥ ዝም ፡ የማትለው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ ወደ ፡ ሰገባኽ ፡ ግባ ፡ ጸጥ ፡ ብለኽም ፡ ዕረፍ ።

ኤር. ፡ 47 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአስቀሎናና ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጥቷልና ፥ በዚያም ፡ አዘጋጅቶታልና ፥ እንዴት ፡ ዝም ፡ ትላለኽ ፧

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 48 ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ ሞዐብ ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ናባው ፡ ጠፍታለችና ፡ ወዮላት! ፡ ቂርያታይም ፡ ዐፍራለች ፡ ተይዛማለች ፤ ሚሥጋብ ፡ ዐፍራለች ፡ ደንግጣማለች ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 2 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሞዐብ ፡ ትምክሕት ፡ የለም ፤ በሐሴቦን ፡ ላይ ፦ ኑ ፥ ሕዝብ ፡ እንዳትኾን ፡ እናጥፋት ፡ ብለው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ዐስበውባታል ። መድሜን ፡ ሆይ ፥ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትጠፊያለሽ ፡ ሰይፍም ፡ ያሳድድሻል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 3 ፤ መፍረስና ፡ ታላቅ ፡ ጥፋት ፡ የሚል ፡ የጩኸት ፡ ቃል ፡ ከሖሮናይም ፡ ተሰማ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 4 ፤ ሞዐብ ፡ ጠፍታለች ፥ ልጆቿም ፡ ጩኸትን ፡ አሰምተዋል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 5 ፤ በሉሒት ፡ ዐቀበት ፡ ልቅሶ ፡ እያለቀሱ ፡ ይወጣሉና ፥ በሖሮናይምም ፡ ቀ፟ልቀ፟ለት ፡ የጥፋትንና ፡ የመባባትን ፡ ጩኸት ፡ ሰምተዋል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 6 ፤ ሸሽታችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ አድኑ ፤ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ቀ፟ጥቋጦ ፡ ኹኑ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 7 ፤ በሥራሽና ፡ በመዝገብሽ ፡ ታምነሻልና ፥ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ትያዢያለሽ ፤ ካሞሽም ፡ ከካህናቱና ፡ ከአለቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ይማረካል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ አጥፊ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ይመጣል ፡ አንዲትም ፡ ከተማ ፡ አትድንም ፤ ሸለቆውም ፡ ይጠፋል ፡ ሜዳውም ፡ ይበላሻል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 9 ፤ በራ ፡ እንድትወጣ ፡ ለሞዐብ ፡ ክንፍ ፡ ስጧት ፤ ከተማዎቿም ፡ ባድማና ፡ ወና ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ በቸልታ ፡ የሚያደርግ ፡ ርጉም ፡ ይኹን ፥ ሰይፉንም ፡ ከደም ፡ የሚከለክል ፡ ርጉም ፡ ይኹን ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 11 ፤ ሞዐብ ፡ ከታናሽነቱ ፡ ዠምሮ ፡ ቅምጥል ፡ ነበረ ፥ በአምቡላውም ፡ ላይ ፡ ዐርፏል ፥ ከዕቃውም ፡ ወደ ፡ ዕቃ ፡ አልተገላበጠም ፥ ወደ ፡ ምርኮም ፡ አልኼደም ፤ ስለዚህ ፥ ቃናው ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ቀርቷል ፥ መዐዛውም ፡

አልተለወጠም ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የሚያገላብጡትን ፡ የምልክበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እነርሱም ፡ ያገላብጡታል ፤ ጋኖቹንም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋሉ ፥ መስቴዎቹንም ፡ ይሰብራሉ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 13 ፤ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ይታመንባት ፡ ከነበረው ፡ ከቤቴል ፡ እንዳፈረ ፥ እንዲሁ ፡ ሞዐብ ፡ ከካሞሽ ፡ ያፍራል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 14 ፤ እናንተ ፦ እኛ ፡ ኀያላን ፡ በሰልፍም ፡ ጽኑዓን ፡ ነን ፡ እንዴት ፡ ትላላችኹ ፧

ኤር. ፡ 48 ፡ 15 ፤ ሞዐብ ፡ ፈርሷል ፥ ከተማዎቹም ፡ ጠፍተዋል ፥ የተመረጡትም ፡ ጕልማሳዎች ፡ ወደ ፡ መታረድ ፡ ወርደዋል ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ ንጉሥ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 16 ፤ የሞዐብ ፡ ጥፋት ፡ ሊመጣ ፡ ቀርቧል ፡ መከራውም ፡ እጅግ ፡ ይፈጥናል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 17 ፤ በዙሪያው ፡ ያላችኹ ፡ ኹሉ ፡ ስሙንም ፡ የምታውቁ ፡ ኹሉ ፦ ብርቱው ፡ በትር ፥ የከበረው ፡ ሽመል ፥ እንዴት ፡ ተሰበረ! ፡ ብላችኹ ፡ አልቅሱለት ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 18 ፤ በዲቦን ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ ሞዐብን ፡ የሚያጠፋ ፡ ወጥቶብሻልና ፥ ዐምባሽንም ፡ ሰብሯልና ፥ ከክብርሽ ፡ ውረጂ ፥ በጥማትም ፡ ተቀመጪ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 19 ፤ በዐሮዔር ፡ የምትኖሪ ፡ ሆይ ፥ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ ቆመሽ ፡ ተመልከቺ ፤ የሸሸውንና ፡ ያመለጠችውን ፦ ምን ፡ ኾኗል ፧ ብለሽ ፡ ጠይቂ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 20 ፤ ሞዐብም ፡ ፈርሷልና ፥ ዐፈረ ፤ አልቅሱ ፡ ጩኹም ፤ ሞዐብ ፡ እንደ ፡ ተዘረፈ ፡ በአርኖን ፡ አጠገብ ፡ አውሩ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 21 ፤ በሜዳ ፡ ላይ ፥ በሖሎን ፥ በያሳ ፥ በሜፍዓት ፡ ላይ ፥

ኤር. ፡ 48 ፡ 22 ፤ በዲቦን ፥ በናባው ፥ በቤት ፡ ዲብላታይም ፡ ላይ ፥

ኤር. ፡ 48 ፡ 23 ፤ በቂርያታይም ፥ በቤትጋሙል ፥

ኤር. ፡ 48 ፡ 24 ፤ በቤትምዖን ፡ ላይ ፥ በቂርዮት ፥ በባሶራ ፥ በሞዐብም ፡ ምድር ፡ ከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ቅርብና ፡ ሩቅ ፡ በኾኑ ፡ ላይ ፡ ፍርድ ፡ መጥቷል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 25 ፤ የሞዐብ ፡ ቀንድ ፡ ተቈረጠ ፡ ክንዱም ፡ ተሰበረ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 26 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኰርቷልና ፥ አስክሩት ፤ ሞዐብም ፡ በጥፋቱ ፡ ላይ ፡ ይንከባለላል ፥ ደግሞም ፡ መሳቂያ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 27 ፤ እስራኤል ፡ ለአንተ ፡ መሳቂያ ፡ አልኾነምን ፧ ወይስ ፡ በሌባዎች ፡ መካከል ፡ ተገኝቷልን ፧ ስለ ፡ ርሱ ፡ በተናገርኽ ፡ ጊዜ ፡ ራስኽን ፡ ትነቀንቃለኽ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 28 ፤ እናንተ ፡ በሞዐብ ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ ከተማዎችን ፡ ትታችኹ ፡ በአለት ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፥ በገደል ፡ አፋፍም ፡ ቤቷን ፡ እንደምትሠራ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ኹኑ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 29 ፤ እጅግ ፡ እንደ ፡ ታበየ ፡ ስለሞዐብ ፡ ትዕቢት ፡ ስለ ፡ ትምክሕቱም ፡ ስለ ፡ ኵራቱም ፡ ስለ ፡ መጓደዱም ፡ ስለልቡም ፡ ትዕቢት ፡ ሰምተናል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 30 ፤ ቀ፡ጣው ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ፉከራው ፡ ምንም ፡ አልሠራም ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ ለሞዐብ ፡ አለቅሳለኹ ፥ ለሞዐብም ፡ ኹሉ ፡ እጮኻለኹ ፤ ለቂርሔሬስ ፡ ሰዎች ፡ አለቅሳለኹ ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 32 ፤ አንቺ ፡ የሴባማ ፡ ወይን ፡ ሆይ ፥ ከኢ.ያዜር ፡ ልቅሶ ፡ ይልቅ ፡ ለአንቺ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ቅርንጫፎችሽ ፡ ባሕርን ፡ ተሻግረዋል ፥ ወደኢ.ያዜርም ፡ ባሕር ፡ ደርሰዋል ፤ አጥፊው ፡ በሰብልሽና ፡ በወይንሽ ፡ ላይ ፡ መጥቷል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 33 ፤ ሐሤትና ፡ ደስታ ፡ ከፍሬያማው ፡ ዕርሻና ፡ ከሞዐብ ፡ ምድር ፡ ጠፍተዋል ፤ ጠጁን ፡ ከመጥመቂያው ፡ አጥፍቻለኹ ፤ ጠማቂውም ፡ በእልልታ ፡ አይጠምቅም ፥ እልልታቸውም ፡ እልልታ ፡ አይኾንም ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 34 ፤ ከሐሴቦን ፡ ጩኸት ፡ እስከ ፡ ኤልያሊና ፡ እስከ ፡ ያሀጽ ፡ ድረስ ፡ ድምፃቸውን ፡ ሰጥተዋል ፤ ከዞዓር ፡ እስከ ፡ ሖሮናይምና ፡ እስከ ፡ ዔግላት ፡ ሺሊሺያ ፡ ድረስ ፡ ይደርሳል ፤ የኔምሬም ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ ይደርቃል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 35 ፤ በኩሪብታው ፡ መስገጃ ፡ ላይ ፡ የሚሠዋውን ፡ ለአማልክቱም ፡ የሚያጥነውን ፡ ከሞዐብ ፡ አጠፋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 36 ፤ ያተረፈው ፡ ትርፉ ፡ ጠፍቶበታልና ፤ ስለዚህ ፥ ልቤ ፡ ለሞዐብ ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ይጮኻል ፥ ልቤም ፡ ለቂርሔሬስ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ እንቢልታ ፡ ይጮኻል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 37 ፤ ራስ ፡ ኹሉ ፡ መላጣ ፡ ጢምም ፡ ኹሉ ፡ የተላጨ ፡ ነውና ፤ በእጅም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ክትፋት ፡ በወገብም ፡ ላይ ፡ ማቅ ፡ አለና ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 38 ፤ ሞዐብን ፡ እንደማይወደድ ፡ ዕቃ ፡ ሰብሬያለኹና ፡ በሞዐብ ፡ ሰገነት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በአደባባዩም ፡ ላይ ፡ በኹሉም ፡ ቦታ ፡ ልቅሶ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 39 ፤ እንዴት ፡ ተገለበጠ! ፡ በዕፍረትም ፡ የተነሣ ፡ ሞዐብ ፡ ገርርባውን ፡ እንዴት ፡ መለሰ! ፡ ብላችኹ ፡ አልቅሱ ። ሞዐብም ፡ በዙሪያው ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ መሳቂያና ፡ ድንጋጤ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 40 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ እንደ ፡ ንስር ፡ ይበራል ፡ ክንፉንም ፡ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 41 ፤ ከተማዎቹ ፡ ተይዘዋል ፥ ዐምባዎቹም ፡ ተወስደዋል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሞዐብ ፡ ኀያላን ፡ ልብ ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 42 ፤ ሞዐብም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኩርቷልና ፥ ሕዝብ ፡ ከመኾን ፡ ይጠፋል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 43 ፤ በሞዐብ ፡ የምትኖር ፡ ሆይ ፥ ፍርሀትና ፡ ጉድጓድ ፡ ወጥመድም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 44 ፤ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ የመጐብኘትን ፡ ዓመት ፡ አመጣበታለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ በፍርሀት ፡ የሸሸ ፡ በጉድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ፥ ከጉድጓድም ፡ የወጣ ፡ በወጥመድ ፡ ይያዛል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 45 ፤ የሸሹ ፡ ደክመው ፡ ከሐሴቦን ፡ ጥላ ፡ በታች ፡ ቆመዋል ፤ እሳት ፡ ከሐሴቦን ፡ ነበልባልም ፡ ከሴዎን ፡ ወጥቷል ፡ የሞዐብንም ፡ ማእዘን ፡ የሚትንም ፡ ልጆች ፡ ዐናት ፡ በልቷል ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 46 ፤ ሞዐብ ፡ ሆይ ፥ ወዮልኽ! ፡ የካሞሽ ፡ ወገን ፡ ጠፍቷል ፤ ወንዶች ፡ ልጆችኽ ፡ ተማርከዋልና ፥ ሴቶች ፡ ልጆችኽም ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ኼደዋልና ።

ኤር. ፡ 48 ፡ 47 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሞዐብን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። የሞዐብ ፡ ፍርድ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 49 ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 1 ፤ ስለዐሞን ፡ ልጆች ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የሉትምን ፧ ወይስ ፡ ወራሽ ፡ የለውምን ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ሚልኮም ፡ ጋድን ፡ ወረሰ ፧ ሕዝቡስ ፡ በከተማዎቹ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተቀመጠ ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 2 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በዐሞን ፡ ልጆች ፡ ከተማ ፡ በረባት ፡ ላይ ፡ የሰልፍ ፡ ውካታን ፡ የማሰማበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የፍርስራሽ ፡ ክምርም ፡ ትኾናለች ፥ ሴቶች ፡ ልጆቿም ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ፥ እስራኤልም ፡ የወረሱትን ፡ ይወርሳል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 3 ፤ ሐሴቦን ፡ ሆይ ፥ ጋይ ፡ ፈርሳለችና ፡ አልቅሺላት ፡ እናንተም ፡ የረባት ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ሚልኮም ፡ ካህናቱና ፡ አለቃዎቹም ፡ በአንድነት ፡ ይማረካሉና ፡ ጨኺ ፥ ማቅም ፡ ታጠቂ ፥ አልቅሱም ፥ በቅጥሮችም ፡ መካከል ፡ ተሯሯጡ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 4 ፤ ማን ፡ ይመጣብኛል ፡ ብለሽ ፡ በመዝገብሽ ፡ የታመንሽ ፡ አንቺ ፡ ከዳተኛ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በሸለቆዎችሽ ፥ ውሃ ፡ በሚያረካቸው ፡ ሸለቆዎችሽ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ትመኪያለሽ ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ በዙሪያሽ ፡ ካሉት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ፍርሀትን ፡ አመጣብሻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ እያንዳንዳችኹም ፡ በፊታችኹ ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ ትሰደዳላችኹ ፥ የሚሸሹትንም ፡ የሚሰበስብ ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእውኑ ፡ በቴማን ፡ ጥበብ ፡ የለምን ፧ ከብልኀተኞችስ ፡ ምክር ፡ ጠፍቷልን ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 8 ፤ ጥበባቸውስ ፡ አልቋልን ፧ እናንተ ፡ በድዳን ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የዔሳውን ፡ ጥፋት ፥ የምጐበኝበትን ፡ ጊዜ ፥ አመጣበታለኹና ፡ ሽሹ ፥ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ፥ በጥልቅም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 9 ፤ ወይን ፡ ለቃሚዎች ፡ ቢመጡብኽ ፥ ቃርሚያውን ፡ አይተውልኽምን ፧ ሌባዎችስ ፡ በሌሊት ፡ ቢመጡ ፥ የሚያጠፉት ፡ እስኪበቃቸው ፡ ድረስ ፡ አይደለምን ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 10 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ዔሳውን ፡ ዐራቈትኹት ፥ የተሸሸጉትንም ፡ ስፍራዎች ፡ ገለጥኹ ፥ ይሸሸግም ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፤ ዘሩም ፡ ወንድሞቹም ፡ ጎረቤቶቹም ፡ ጠፍተዋል ፡ ርሱም ፡ የለም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 11 ፤ ድኻ ፡ አደጎችኽን ፡ ተው ፥ እኔም ፡ በሕይወት ፡ አኖራቸዋለኹ ፤ መበለቶችኽም ፡ በእኔ ፡ ይታመኑ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ጽዋውን ፡ ያልተገባቸው ፡ ሰዎች ፡ ጠጥተውታል ፤ አንተም ፡ ሳትቀጣ ፡ ትቀራለኽን ፧ በርግጥ ፡ ትጠጣለኽ ፡ እንጂ ፡ ያለቅጣት ፡ አትቀርም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 13 ፤ ባሶራ ፡ መደነቂያና ፡ መሰደቢያ ፡ መረገሚያም ፡ እንድትኾን ፡ በራሴ ፡ ምያለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ከተማዎቿም ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 14 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምቻለኹ ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ። ተሰብሰቡ ፥ በርሷም ፡ ላይ ፡

ኑ ፡ ለሰልፍም ፡ ተነሡ ፡ የሚል ፡ መልእክተኛ ፡ ተልኳል ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ የተጠቃኽ ፥ በሰዎችም ፡ ዘንድ ፡ የተናቅኽ ፡ አድርጌኻለኹ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 16 ፤ በአለት ፡ ንቃቃት ፡ ውስጥ ፡ የምትቀመጥ ፥ የተራራውን ፡ ከፍታ ፡ የምትይዝ ፡
ሆይ ፥ ድፍረትኽና ፡ የልብኽ ፡ ኵራት ፡ አታለውኻል ። ቤትኽን ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ከፍ ፡ ብታደርግ ፥ ከዚያ ፡
አወርድኻለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 17 ፤ ኤዶምያስም ፡ መደነቂያ ፡ ትኾናለች ፥ የሚያልፍባትም ፡ ኹሉ ፡ ይደነቃል ፥ ስለመጣባትም ፡
መቅሠፍት ፡ ኹሉ ፡ ያፏጭባታል ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 18 ፤ ሰዶምና ፡ ገሞራ ፡ በእነርሱም ፡ አጠገብ ፡ የነበሩት ፡ ከተማዎች ፡ እንደ ፡ ተገለበጡ ፥ ይላል ፡
እግዚአብሔር ፥ እንዲሁ ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ አይቀመጥም ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ አይኖርባትም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 19 ፤ እንሆ ፥ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቶሎ ፡ አባርራቸዋለኹና ፡ በጠነከረው ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ከዮርዳኖስ ፡
ትዕቢት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይወጣል ፤ የተመረጠውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ እሾመዋለኹ ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡
ነው ፧ ወይስ ፡ ለእኔ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ፊቴን ፡ የሚቃወም ፡ እረኛ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 20 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ የመከረባትን ፡ ምክር ፥ በቴማንም ፡ በሚኖሩ ፡
ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያሰባትን ፡ ዐሳብ ፡ ስሙ ፤ በእውነት ፡ የመንጋ ፡ ትንንሾች ፡ ይጐተታሉ ፤ በእውነት ፡ ማደሪያቸውን ፡
ባድማ ፡ ያደርግባቸዋል ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 21 ፤ ከመውደቃቸው ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፥ የጩኸታቸውም ፡ ድምፅ ፡ በቀይ ፡
ባሕር ፡ ተሰማ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 22 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ንስር ፡ ወጥቶ ፡ ይበራል ፡ ክንፉንም ፡ በባሶራ ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡
የኤዶምያስ ፡ ኀያላን ፡ ልብ ፡ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ልብ ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 23 ፤ ስለ ፡ ደማስቆ ፤ ክፉ ፡ ወሬ ፡ ሰምተዋልና ፥ ሐማትና ፡ አርፋድ ፡ ዐፈሩ ፥ ቀለጡም ፤ በባሕርም ፡
ላይ ፡ ሐዘን ፡ አለ ፥ ታርፍም ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 24 ፤ ደማስቆ ፡ ደከመች ፡ ትሸሽም ፡ ዘንድ ፡ ዘወር ፡ አለች ፡ እንቅጥቅጥም ፡ ያዛት ፥ እንደ ፡ ወላድም ፡
ሴት ፡ ጣርና ፡ ምጥ ፡ ያዛት ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 25 ፤ የተመሰገነችው ፡ ከተማ ፥ የደስታዬ ፡ ከተማ ፥ ሳትለቀቅ ፡ እንዴት ፡ ቀረች ፧

ኤር. ፡ 49 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ ጕበዛዝቷ ፡ በአደባባይዋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡
ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 27 ፤ በደማስቆም ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ አነዳለኹ ፡ የወልደ ፡ አዴርንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 28 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ስለ ፡ መታ ፡ ስለቄዳርና ፡ ስለአሶር ፡
መንግሥታት ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ተነሡ ፡ ወደ ፡ ቄዳርም ፡ ውጡ ፥ የምሥራቅንም ፡ ልጆች ፡ አጥፉ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 29 ፤ ድንኳናቸውንና ፡ መንጋቸውን ፡ ይወስዳሉ ፤ መጋረጃዎቻቸውንና ፡ ዕቃቸውን ፡ ኹሉ ፡
ግመሎቻቸውንም ፡ ለራሳቸው ፡ ይወስዳሉ ፥ በዙሪያቸውም ፡ ኹሉ ፡ ጥፋትን ፡ ጥሩባቸው ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 30 ፤ እናንተ ፡ በአሶር ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡
ተማክሮባችኋልና ፥ ዐሳብም ፡ ዐስቦባችኋልና ፥ ሽሹ ፥ ወደ ፡ ሩቅም ፡ ኺዱ ፥ በጥልቅም ፡ ውስጥ ፡ ተቀመጡ ፥ ይላል ፡

እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 31 ፤ ተነሡ ፥ ዕርፊት ፡ ወዳለበት ፡ ተዘልሎም ፡ ወደተቀመጠው ፥ ደጅና ፡ መወርወሪያ ፡ ወደሌለው ፡ ብቻውንም ፡ ወደተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ ውጡ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 32 ፤ ግመሎቻቸው ፡ ይበዘበዛሉ ፡ የእንስሳዎቻቸውም ፡ ብዛት ፡ ይማረካል ፤ ጠጕራቸውንም ፡ በዙሪያ ፡ የሚላጨትን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ዥሉ ፡ እበትናቸዋለኹ ፤ ከዳርቻቸውም ፡ ዥሉ ፡ ጥፋት ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 33 ፤ አሶርም ፡ የቀበሮ ፡ መኖሪያና ፡ የዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፤ በዚያም ፡ ሰው ፡ አይኖርም ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡ አይቀመጥባትም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 34 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሴዴቅያስ ፡ መንግሥት ፡ መዠመሪያ ፡ ስለ ፡ ዔላም ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ኤርምያስ ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 49 ፡ 35 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ዋና ፡ የኀይላቸው ፡ መሣሪያ ፡ የኾነውን ፡ የዔላምን ፡ ቀስት ፡ እሰብራለኹ ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 36 ፤ ከአራቱም ፡ ከሰማይ ፡ ማእዘናት ፡ አራቱን ፡ ነፋሳት ፡ በዔላም ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፥ ወደ ፡ እነዚያም ፡ ነፋሳት ፡ ዥሉ ፡ እበትናቸዋለኹ ፤ ከዔላም ፡ የተሰደዱ ፡ ሰዎች ፡ የማይደርሱበት ፡ ሕዝብ ፡ አይገኝም ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 37 ፤ በጠላቶቻቸውና ፡ ነፍሳቸውን ፡ በሚሿት ፡ ፊት ፡ ዔላምን ፡ አስደነግጣለኹ ፤ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ርሱም ፡ ጽኑ ፡ ቍጣዬን ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እስካጠፋቸውም ፡ ድረስ ፡ በኋላቸው ፡ ሰይፍ ፡ እሰድባቸዋለኹ ፤

ኤር. ፡ 49 ፡ 38 ፤ ዙፋኔንም ፡ በዔላም ፡ አኖራለኹ ፥ ከዚያም ፡ ንጉሡንና ፡ አለቃዎቹን ፡ አጠፋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 49 ፡ 39 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የዔላምን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 50 ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለከለዳውያን ፡ ምድር ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኤር. ፡ 50 ፡ 2 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተናገሩ ፡ አውሩም ፥ ዐላማውንም ፡ አንሡ ፤ አውሩ ፥ አትደብቁ ። ባቢሎን ፡ ተወሰደች ፥ ቤል ፡ ዐፈረ ፥ ሜሮዳክ ፡ ደነገጠ ፤ ምስሎቿ ፡ ዐፈሩ ፥ ጣዖታቷ ፡ ደነገጡ ፡ በሉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 3 ፤ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ ወጥቶባታል ፡ ምድሯንም ፡ ባድማ ፡ ያደርጋል ፥ የሚቀመጥባትም ፡ አይገኝም ፤ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ሸሽተው ፡ ኼደዋል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 4 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ኾነው ፡ ይመጣሉ ፥ እያለቀሱም ፡ መንገዳቸውን ፡ ይኼዳሉ ፥ አምላካቸውንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጋሉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 5 ፤ ፊታቸውንም ፡ ወደዚያ ፡ አቅንተው ፦ ኑ ፥ ከቶ ፡ በማይረሳ ፡ በዘለዓለም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተጠጉ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ጽዮን ፡ መንገድ ፡ ይጠይቃሉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 6 ፤ ሕዝቤ ፡ የጠፉ ፡ በጎች ፡ ኾነዋል ፤ እረኞቻቸው ፡ አሳቷቸው ፥ በተራራዎችም ፡ ላይ ፡ የተቅበዘበዙ ፡ አደረጓቸው ፤ ከተራራ ፡ ወደ ፡ ኰረብታ ፡ ዐለፉ ፥ በረታቸውንም ፡ ረሱ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 7 ፤ ያገኟቸው ፡ ዅሉ ፡ በሏቸው ፥ ጠላቶቻቸውም ፦ በጽድቅ ፡ ማደሪያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፥ በአባቶቻቸው ፡ ተስፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠሩ ፡ እኛ ፡ አልበደልንም ፡ አሉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 8 ፤ ከባቢሎን ፡ መካከል ፡ ሽሹ ፥ ከከለዳውያንም ፡ ድር ፡ ውጡ ፥ በመንጋዎችም ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎች ፡ ኹኑ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 9 ፤ እንሆ ፥ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ የታላላቅ ፡ አሕዛብን ፡ ጉባኤ ፡ አስነሣለኹ ፡ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ በርሷም ፡ ላይ ፡ ይሰለፋሉ ፥ ከዚያም ፡ ትወሰዳለች ፤ ፍላጻዎቻቸውም ፡ ባዶውን ፡ እንደማይመለስ ፡ እንደ ፡ ብልኅ ፡ ዝግና ፡ ፍላጻ ፡ ናቸው ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 10 ፤ የከላውዴዎንም ፡ ምድር ፡ ትበዘበዛለች ፥ የሚበዘብዟትም ፡ ዅሉ ፡ ይጠግባሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 11 ፤ ርስቴን ፡ የምትበዘብዙ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ብሏችኋልና ፥ ሐሤትንም ፡ አድርጋችኋልና ፥ በመስክ ፡ ላይም ፡ እንዳለች ፡ ጊደር ፡ ኾናችኹ ፡ ተቀናጥታችኋልና ፥ እንደ ፡ ብርቱዎችም ፡ ፈረሶች ፡ አሸካክታችኋልና ፥

ኤር. ፡ 50 ፡ 12 ፤ እናታችኹ ፡ እጅግ ፡ ታፍራለች ፥ የወለደቻችኹም ፡ ትጐሰቀላለች ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኋለኛዪቱ ፡ ትኾናለች ፤ ምድረ ፡ በዳና ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ በረሓም ፡ ትኾናለች ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 13 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የተነሣ ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አይቀመጥባትም ፤ በባቢሎንም ፡ በኩል ፡ የሚያልፍ ፡ ዅሉ ፡ ይደነቃል ፡ በመጣባትም ፡ መቅሠፍት ፡ ዅሉ ፡ ያፏጫል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ ቀስትን ፡ የምትገትሩ ፡ ሰዎች ፡ ዅሉ ፥ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ በዙሪያዋ ፡ ተሰለፉ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታለችና ፡ ወርውሩባት ፡ ፍላጻዎችንም ፡ አትንፈጉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ነውና ፥ በዙሪያዋ ፡ ጩኹባት ፤ እጇን ፡ ሰጠች ፤ ግንቦቿ ፡ ወደቁ ፡ ቅጥሮቿም ፡ ፈረሱ ፤ ርሷን ፡ ተበቀሉ ፡ እንደ ፡ ሠራችውም ፡ ሥሩባት ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 16 ፤ ዘሪውንና ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፡ ማጭድ ፡ የሚይዘውን ፡ ከባቢሎን ፡ አጥፉ ፤ ከሚያስጨንቅ ፡ ሰይፍ ፡ ፊት ፡ እያንዳንዱ ፡ ወደ ፡ ወገኑ ፡ ይመለሳል ፡ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አገሩ ፡ ይሸሻል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 17 ፤ እስራኤል ፡ የባዘነ ፡ በግ ፡ ነው ፤ አንበሳዎች ፡ አሳደዱት ፤ መዠመሪያ ፡ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ በላው ፥ በመጨረሻም ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ዐጥንቱን ፡ ቈረጠመው ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአሶርን ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ቀጣኹ ፡ እንዲሁ ፥ እንሆ ፥ የባቢሎንን ፡ ንጉሥና ፡ ምድሩን ፡ እቀጣለኹ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 19 ፤ እስራኤልንም ፡ ወደ ፡ ማሰማሪያው ፡ እመልሳለኹ ፥ በቀርሜሎስና ፡ በባሳንም ፡ ላይ ፡ ይሰማራል ፥ ሰውነቱም ፡ በኤፍሬም ፡ ተራራና ፡ በገለዓድ ፡ ላይ ፡ ትጠግባለች ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 20 ፤ እነዚህን ፡ ያስቀረኋቸውን ፡ ይቅር ፡ እላቸዋለኹና ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ በደል ፡ የይሁዳም ፡ ኀጢአት ፡ ይፈለጋል ፡ ምንም ፡ አይገኝም ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 21 ፤ በምራታይም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በፋቁድም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ውጣ ፤ ግደላቸው ፡ ፈጽመኽም ፡ አጥፋቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንዳዘዝኹኽም ፡ ዅሉ ፡ አድርግ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 22 ፤ የሰልፍና ፡ የታላቅ ፡ ጥፋት ፡ ውካታ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አለ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 23 ፤ የምድር ፡ ኹሉ ፡ መዶሻ ፡ እንዴት ፡ ደቀቀ ፥ እንዴትስ ፡ ተሰበረ! ፡ ባቢሎንስ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እንዴት ፡ ባድማ ፡ ኾነች! ፡

ኤር. ፡ 50 ፡ 24 ፤ ባቢሎን ፡ ሆይ ፥ አጥምጄብሻለኹ ፥ አንቺም ፡ ሳታውቂ ፡ ተይዘሻል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተዋጋሽ ፡ ተገኝተሻል ፥ ተይዘሽማል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 25 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሥራ ፡ አለውና ፥ እግዚአብሔር ፡ ዕቃ ፡ ቤቱን ፡ ከፍቶ ፡ የቀሥጣውን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ አውጥቷል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 26 ፤ ከየበኩሉ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ውጡ ፥ ጐተራዎቿንም ፡ ክፈቱ ፤ እንደ ፡ ክምርም ፡ አድርጓት ፥ ፈጽማችኹም ፡ አጥፏት ፥ አንዳችም ፡ አታስቀሩላት ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 27 ፤ ወይፈኖቿን ፡ ኹሉ ፡ ዕረዱ ፥ ወደ ፡ መታረድም ፡ ይውረዱ ፤ ቀናቸው ፣ የመጐብኘታቸው ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፥ ወዮላቸው! ፡

ኤር. ፡ 50 ፡ 28 ፤ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በቀል ፡ የመቅደሱንም ፡ በቀል ፡ በጽዮን ፡ ይነግሩ ፡ ዘንድ ፥ ሸሽተው ፡ ከባቢሎን ፡ አገር ፡ ያመለጡት ፡ ሰዎች ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 29 ፤ ቀስትን ፡ የሚገትሩትን ፡ ቀስተኞችን ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ጥሯቸው ፤ በዙሪያዋ ፡ ስፈሩባት ፡ አንድም ፡ አያምልጥ ፤ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኩርታለችና ፥ እንደ ፡ ሥራዋ ፡ መጠን ፡ መልሱላት ፥ እንዳደረገችም ፡ ኹሉ ፡ አድርጉባት ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ጐበዛዝቷ ፡ በአደባባይዋ ፡ ላይ ፡ ይወድቃሉ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰልፈኞቿ ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 31 ፤ ትዕቢተኛው ፡ ሆይ ፥ የመጐብኘትኽ ፡ ጊዜ ፥ ቀንኽ ፡ ደርሷልና ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 32 ፤ ትዕቢተኛው ፡ ተሰናክሎ ፡ ይወድቃል ፡ የሚያነሣውም ፡ የለም ፤ በከተማዎቹም ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አነዳለኹ ፥ በዙሪያውም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ትበላለች ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 33 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤል ፡ ልጆችና ፡ የይሁዳ ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ተገፍተዋል ፥ የማረኳቸውም ፡ ኹሉ ፡ በጎይል ፡ ይይዟቸዋል ፥ ይለቋቸውም ፡ ዘንድ ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 34 ፤ ተቤዣቸው ፡ ብርቱ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ምድርንም ፡ ያሳርፍ ፡ ዘንድ ፥ በባቢሎንም ፡ የሚኖሩትን ፡ ያውክ ፡ ዘንድ ፥ ሙግታቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ይሟገታል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 35 ፤ ሰይፍ ፡ በከለዳውያንና ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩ ፡ ላይ ፥ በአለቃዎቿና ፡ በጥበበኞቿ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 36 ፤ ሰይፍ ፡ በሚጓደዱት ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ሰነፎችም ፡ ይኾናሉ ፥ ሰይፍም ፡ በጎያላኗ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ እነርሱም ፡ ይደነግጣሉ ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 37 ፤ ሰይፍ ፡ በፈረሶቻቸውና ፡ በሠረገላዎቻቸው ፡ ላይ ፡ በመካከሏም ፡ ባሉት ፡ በልዩ ፡ በልዩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አለ ፥ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ሴቶች ፡ ይኾናሉ ፤ ሰይፍም ፡ በመዝገቧ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ ለብዝበዛም ፡ ይኾናል ።

ኤር. ፡ 50 ፡ 38 ፤ ርሷ ፡ የተቀረጹ ፡ ምስሎች ፡ ምድር ፡ ናት ፥ እነርሱም ፡ በጣዖታት ፡ ይመካሉና ፥ ድርቅ ፡

በውሃዎቿ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ እነርሱም ፡ ይደርቃሉ ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 39 ፤ ስለዚህ ፥ የምድረ ፡ በዳ ፡ አራዊት ፡ ከተኵላዎች ፡ ጋራ ፡ ይቀመጡባታል ፥ ሰጐኖችም ፡ ይቀመጡባታል ፤ ሰውም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይቀመጥባትም ፥ እስከልጅ ፡ ልጅም ፡ ድረስ ፡ የሚኖርባት ፡ የለም ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 40 ፤ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ በአጠገባቸውም ፡ የነበሩትን ፡ ከከተማዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለበጣቸው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንዲሁ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ አይቀመጥም ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ አይኖርባትም ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 41 ፤ እንሆ ፥ ሕዝብ ፡ ከሰሜን ፡ ይመጣል ፤ ታላቅ ፡ ሕዝብና ፡ ብዙ ፡ ነገሥታትም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ይነሣሉ ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 42 ፤ ቀስትንና ፡ ጦርን ፡ ይይዛሉ ፤ ጨካኞች ፡ ናቸው ፥ ምሕረትም ፡ አያደርጉም ፤ ድምፃቸው ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ይተማ፟ል ፥ በፈረሶችም ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ። የባቢሎን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሰልፍ ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ ሰው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰለፉ ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 43 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወሬያቸውን ፡ ሰምቷል ፥ እጁም ፡ ደክማለች ፥ ጭንቀትም ፡ ይዞታል ፥ ምጥ ፡ ወላድ ፡ ሴትን ፡ እንደሚይዛት ፡ ጭንቀት ፡ ይዞታል ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 44 ፤ እንሆ ፥ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ በቶሎ ፡ አባርራቸዋለኹና ፥ በጠነከረው ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ይወጣል ፤ የተመረጠውንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ እሾመዋለኹ ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ለእኔ ፡ ጊዜ ፡ የሚወስን ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ፊቴን ፡ የሚቃወም ፡ እረኛ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ኤር. ፥ 50 ፥ 45 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ የመከረባትን ፡ ምክር ፥ በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ያሰባትን ፡ ዐሳብ ፡ ስሙ ፤ በእውነት ፡ የመንጋ ፡ ትናንሾች ፡ ይጐተታሉ ፤ በእውነት ፡ ማደሪያቸውን ፡ ባድማ ፡ ያደርግባቸዋል ።

ኤር. ፥ 50 ፥ 46 ፤ ከባቢሎን ፡ መያዝ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ተናወጠች ፥ ጩኸትም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ዘንድ ፡ ተሰማ ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 51 ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በባቢሎን ፡ ላይና ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ አጥፊውን ፡ ነፋስ ፡ አስነሣለኹ ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 2 ፤ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚያዘሩትን ፡ ሰዎች ፡ እሰዳ፟ለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያዘሯታል ፥ ምድሯንም ፡ ባዶ ፡ ያደርጋሉ ፤ በመከራም ፡ ቀን ፡ በዙሪያዋ ፡ ይከቧ፟ታል ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 3 ፤ በወርዋሪው ፡ ላይ ፡ በጥሩርም ፡ በሚነሣው ፡ ላይ ፡ ቀስተኛው ፡ ቀስቱን ፡ ይገትር ፤ ለጐበዛዝቷ ፡ አትዘኑ ፡ ሰራዊቷንም ፡ ኹሉ ፡ አጥፉ ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 4 ፤ በከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ተገድለው ፥ በሜዳዋም ፡ ላይ ፡ ተወግተው ፡ ይወድቃሉ ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 5 ፤ ምድራቸው ፡ በእስራኤል ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ በተሠራው ፡ በደል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የተሞላች ፡ ብትኾን ፥ እስራኤልም ፡ ኾነ ፡ ይሁዳ ፡ በአምላኩ ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አልተጣለም ።

ኤር. ፥ 51 ፥ 6 ፤ ከባቢሎን ፡ ውስጥ ፡ ሽሹ ፥ እያንዳንዳችኹም ፡ ነፍሳችኹን ፡ አድኑ ፤ በበደሏ ፡ አትጥፉ ፥ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፥ ርሱም ፡ ብድራቷን ፡ ይከፍላታልና ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 7 ፤ ባቢሎን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ ምድርን ፡ ሹሉ ፡ ያሰከረች ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡
ነበረች ፥ አሕዛብም ፡ ከጠጇ ፡ ጠጥተዋል ፤ ስለዚህ ፥ አሕዛብ ፡ አብደዋል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 8 ፤ ባቢሎን ፡ በድንገት ፡ ወድቃ ፡ ጠፍታለች ፤ አልቅሱላት ፥ ትፈወስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለቍስሏ ፡
መድኀኒት ፡ ውሰዱላት ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 9 ፤ ባቢሎንን ፡ ፈወስናት ፥ ርሷ ፡ ግን ፡ አልተፈወሰችም ፤ ፍርዷ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደርሷልና ፥ እስከ ፡
ደመናም ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ትታችኋት ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ እንኺድ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችንን ፡ አውጥቷል ፤ ኑ ፥ በጽዮን ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ሥራ ፡ እንናገር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 11 ፤ ፍላጻዎችን ፡ ሳሉ ፡ ጋሻዎችንም ፡ አዘጋጁ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋት ፡ ዘንድ ፡ ዐሳቡ ፡ በባቢሎን ፡
ላይ ፡ ነውና ፥ የሜዶንን ፡ ነገሥታት ፡ መንፈስ ፡ አስነሥቷል ፤ የእግዚአብሔር ፡ በቀል ፡ የመቅደሱ ፡ በቀል ፡ ነውና ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 12 ፤ በባቢሎን ፡ ቅጥር ፡ ዐላማውን ፡ አንሡበት ፥ ጥበቃን ፡ አጽኑ ፥ ተመልካቾችን ፡
አቁሙ ፥ ድብቅ ፡ ጦር ፡ አዘጋጁ ። እግዚአብሔር ፡ በባቢሎን ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡
ዐስቧልና ፥ አድርጓልምና ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 13 ፤ አንቺ ፡ በብዙ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ የተቀመጥሽ ፥ በመዝገብም ፡ የበለጠግሽ ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡
ሥሥትሽ ፡ መጠን ፡ ፍጻሜሽ ፡ ደርሷል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 14 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በራሱ ፡ ምሏል ፦ በእውነት ፡ ሰዎችን ፡ እንደ ፡
አንበጣ ፡ እሞላብሻለኹ ፥ እነርሱም ፡ ጩኸት ፡ ያነሡብሻል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 15 ፤ ምድርን ፡ በኀይሉ ፡ የፈጠረ ፥ ዓለሙን ፡ በጥበቡ ፡ የመሠረተ ፥ ሰማያትንም ፡ በማስተዋሉ ፡
የዘረጋ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 16 ፤ ድምፁን ፡ ባሰማ ፡ ጊዜ ፡ ውሃዎች ፡ በሰማይ ፡ ይታወካሉ ፥ ከምድርም ፡ ዳር ፡ ደመናትን ፡ ከፍ ፡
ያደርጋል ፤ ለዝናብም ፡ መብረቅን ፡ ያደርጋል ፥ ነፍስንም ፡ ከቤተ ፡ መዛግብቱ ፡ ያወጣል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 17 ፤ ሰው ፡ ሹሉ ፡ ዕውቀት ፡ ዐጥቶ ፡ ሰንፏል ፥ አንጥረኛም ፡ ሹሉ ፡ ከቀረጸው ፡ ምስል ፡ የተነሣ ፡
አፍሯል ፤ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስሉ ፡ ውሸት ፡ ነውና ፥ እስትንፋስም ፡ የላቸውምና ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ ምናምንቴና ፡ የቀልድ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፤ በተጐበኙ ፡ ጊዜ ፡ ይጠፋሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 19 ፤ የያዕቆብ ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ አይደለም ፥ ርሱ ፡ የኹሉ ፡ ፈጣሪ ፡
ነውና ፤ እስራኤልም ፡ የርስቱ ፡ ነገድ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 20 ፤ አንቺ ፡ መዶሻዬና ፡ የጦር ፡ መሣሪያዬ ፡ ነሽ ፤ ባንቺ ፡ አሕዛብን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡
መንግሥታትን ፡ አጠፋለኹ ፤

ኤር. ፡ 51 ፡ 21 ፤ ባንቺ ፡ ፈረሱንና ፡ ፈረሰኛውን ፡ እሰባብራለኹ ፤

ኤር. ፡ 51 ፡ 22 ፤ ባንቺም ፡ ሠረገላውንና ፡ በላዩ ፡ የሚቀመጠውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡
እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ሽማግሌውንና ፡ ብላቴናውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ ጕልማሳውንና ፡ ቈንጕዮቱን ፡
እሰባብራለኹ ፤

ኤር. ፡ 51 ፡ 23 ፤ ባንቺም ፡ እረኛውንና ፡ መንጋውን ፡ እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ አራሹንና ፡ ጥማጁን ፡

እሰባብራለኹ ፤ ባንቺም ፡ አለቃዎችንና ፡ ሹማምቶችን ፡ እሰባብራለኹ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 24 ፤ በጽዮን ፡ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ ስለሠሩት ፡ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ በባቢሎንና ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ፍዳቸውን ፡ እከፍላለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 25 ፤ አንተ ፡ ምድርን ፡ ኹሉ ፡ የምታጠፋ ፡ አጥፊ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እጄንም ፡ እዘረጋብሻለኹ ፥ ከድንጋዮችም ፡ ላይ ፡ አንከባልልሻለኹ ፥ የተቃጠለም ፡ ተራራ ፡ አደርግሻለኹ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 26 ፤ ከአንተም ፡ ለማእዘንና ፡ ለመሠረት ፡ የሚኾን ፡ ድንጋይ ፡ አይወስዱም ፥ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለኽ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 27 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐላማን ፡ አንሡ ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ መለከት ፡ ንፉ ፥ አሕዛብንም ፡ አዘጋጁባት ፤ የአራራትንና ፡ የሚኒን ፡ የአስከናዝንም ፡ መንግሥታት ፡ ሰብስቡባት ፡ አለቃንም ፡ በላይዋ ፡ አቁሙ ፤ እንደ ፡ ጠጕራም ፡ ኵብኵባ ፡ ፈረሶችን ፡ በላይዋ ፡ አውጡ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 28 ፤ አሕዛብን ፡ የሚዶንንም ፡ ነገሥታት ፡ አለቃዎችንም ፡ ሹማምቶችንም ፡ ኹሉ ፡ የግዛታቸውንም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ አዘጋጁባት ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 29 ፤ ማንም ፡ እንዳይቀመጥባት ፡ የባቢሎንን ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ ያደርጋት ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐሳብ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ጸንቷልና ፥ ምድር ፡ ተናውጣለች ፡ ታመመችም ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 30 ፤ የባቢሎን ፡ ኀያላን ፡ መዋጋትን ፡ ትተዋል ፡ በዐምባዎቻቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ኀይላቸውም ፡ ጠፍቷል ፡ እንደ ፡ ሴቶችም ፡ ኾነዋል ፤ ማደሪያዎቿም ፡ ነደዋል ፡ መወርወሪያዎቿም ፡ ተሰብረዋል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 31-32 ፤ ከዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ድረስ ፡ ከተማው ፡ እንደ ፡ ተያዘች ፡ መልካሞቿም ፡ እንደ ፡ ተያዙ ፥ ቅጥሯም ፡ በእሳት ፡ እንደ ፡ ተቃጠለ ፥ ሰልፈኞችም ፡ እንደ ፡ ደነገጡ ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ይነግር ፡ ዘንድ ፡ ወሬኛው ፡ ወሬኛውን ፡ መልእክተኛውም ፡ መልእክተኛውን ፡ ሊገናኝ ፡ ይሮጣል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 33 ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ዐውድማ ፡ እንደ ፡ ተረገጠ ፡ ጊዜ ፥ እንዲሁ ፡ የባቢሎን ፡ ልጅ ፡ ናት ፤ ጥቂት ፡ ቈይታ ፡ የመከር ፡ ጊዜ ፡ ይደርስባታል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 34 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በላኝ ፥ ከፋፈለኝም ፥ እንደ ፡ ባዶ ፡ ዕቃም ፡ አደረገኝ ፥ እንደ ፡ ዘንዶም ፡ ዋጠኝ ፥ ከሚጣፍጠውም ፡ ምግቤ ፡ ሆዱን ፡ ሞላ ፥ እኔንም ፡ ጣለኝ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 35 ፤ በጽዮን ፡ የምትቀመጥ ፦ በእኔና ፡ በሥጋዬ ፡ የተደረገ ፡ ግፍ ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ ትላለች ፤ ኢየሩሳሌምም ፦ ደሜ ፡ በከለዳውያን ፡ ምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ ትላለች ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 36 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እሟገትልሻለኹ ፡ በቀልሽንም ፡ እበቀልልሻለኹ ፤ ባሕሯንም ፡ ድርቅ ፡ አደርገዋለኹ ፡ ምንጯንም ፡ አደርቀዋለኹ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 37 ፤ ባቢሎንም ፡ የድንጋይ ፡ ቍልልና ፡ የቀበሮ ፡ ማደሪያ ፡ መደነቂያም ፡ ማፏጫም ፡ ትኾናለች ፥ የሚቀመጥባትም ፡ ሰው ፡ አይገኝም ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 38 ፤ በአንድነትም ፡ እንደ ፡ አንበሳዎች ፡ ያገሣሉ ፥ እንደ ፡ አንበሳም ፡ ደቦሎች ፡ ያጉረመርማሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 39 ፤ በሞቃቸው ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ ለዘለዓለምም ፡ አንቀላፍተው ፡ እንዳይነቁ ፡ የመጠጥ ፡ ግብዣ ፡ አደርግላቸዋለኹ ፡ አሰክራቸውማለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 40 ፤ እንደ ፡ ጠቦቶችና ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ እንደ ፡ አውራ ፡ ፍየሎችም ፡ ወደ ፡ መታረድ ፡ አወርዳቸዋለኹ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 41 ፤ ሼሻክ ፡ እንዴት ፡ ተያዘች! ፡ የምድርም ፡ ዥሉ ፡ ምስጋና ፡ እንዴት ፡ ተወሰደች! ፡ ባቢሎንም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ መደነቂያ ፡ እንዴት ፡ ኾነች! ፡

ኤር. ፡ 51 ፡ 42 ፤ ባሕር ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ ወጣ ፡ በሞገዱም ፡ ብዛት ፡ ተከደነች ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 43 ፤ ከተማዎቿ ፡ ባድማና ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ ምድረ ፡ በዳም ፥ ሰውም ፡ የማይቀመጥበት ፡ የሰውም ፡ ልጅ ፡ የማያልፍበት ፡ ምድር ፡ ኾኑ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 44 ፤ በባቢሎንም ፡ ውስጥ ፡ ቤልን ፡ እቀጣለኹ ፡ የዋጠውንም ፡ ከአፉ ፡ አስተፋዋለኹ ፤ አሕዛብም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አይሰበሰቡም ፥ የባቢሎንም ፡ ቅጥር ፡ ይወድቃል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 45 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ከመካከሷ ፡ ውጡ ፡ እያንዳንዳችኹም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጽኑ ፡ ቍጣ ፡ ራሳችኹን ፡ አድኑ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 46 ፤ በምድርም ፡ ከሚሰማ ፡ ወሬ ፡ የተነሣ ፡ አትፍሩ ፡ ልባችኹም ፡ የዛለ ፡ አይኹን ፤ ባንድ ፡ ዓመት ፡ ወሬ ፡ ይመጣል ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሌላው ፡ ዓመት ፡ ወሬ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ይመጣል ፥ አለቃም ፡ በአለቃ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 47 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የተቀረጹትን ፡ የባቢሎን ፡ ምስሎች ፡ የምቀጣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ምድሯም ፡ ዥሉ ፡ ታፍራለች ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱት ፡ ዥሉ ፡ በመካከሷ ፡ ይወድቃሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 48 ፤ አጥፊዎች ፡ ከሰሜን ፡ ይመጡባታልና ፥ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በእነርሱም ፡ ያለው ፡ ዥሉ ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ እልል ፡ ይላሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 49 ፤ ባቢሎንም ፡ ከእስራኤል ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ እንዲወድቁ ፡ እንዳደረገች ፥ እንዲሁ ፡ በባቢሎን ፡ ከምድሩ ፡ ዥሉ ፡ ተወግተው ፡ የሞቱት ፡ ይወድቃሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 50 ፤ ከሰይፍ ፡ ያመለጣችኹ ፡ ሆይ ፥ ኺዱ ፥ አትቁሙ ፤ እግዚአብሔርን ፡ ከሩቅ ፡ ዐስቡ ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ በልባችኹ ፡ ዐስቡ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 51 ፤ ስድብን ፡ ስለ ፡ ሰማን ፡ ዐፍረናል ፤ ባዕዳን ፡ ሰዎችም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብተዋልና ፥ ነውር ፡ ፊታችንን ፡ ከድኖታል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 52 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የተቀረጹትን ፡ ምስሎቿ ፡ የምቀጣበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድሯም ፡ ላይ ፡ ዥሉ ፡ የተወጉት ፡ ያንቋርራሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 53 ፤ ባቢሎን ፡ ምንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ብትወጣ ፥ የኀይሏንም ፡ ከፍታ ፡ ብታጸና ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አጥፊዎች ፡ ይመጡባታል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 54 ፤ ከባቢሎን ፡ ጩኸት ፥ ከከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ የታላቅ ፡ ጥፋት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 55 ፤ እግዚአብሔር ፡ ባቢሎንን ፡ አጥፍቷታልና ፥ ከርሷም ፡ ታላቁን ፡ ድምፅ ፡ ዝም ፡ አሠኝቷልና ፤ ሞገዳቸውም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ይተማል ፥ የድምፃቸውም ፡ ጩኸት ፡ ተሰምቷል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 56 ፤ አጥፊው ፡ በባቢሎን ፡ ላይ ፡ መጥቶባታልና ፥ ኀያላኗ ፡ ተያዙ ፥ ቀስታቸውም ፡ ተሰባበረ ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍዳን ፡ የሚከፍል ፡ አምላክ ፡ ነውና ፥ ፍዳንም ፡ በርግጥ ፡ ይከፍላል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 57 ፤ መሳፍንቷንና ፡ ጥበበኞቿንም ፥ አለቃዎቿንና ፡ ሹማምቷን ፡ ጎያላኗንም ፡ አሰክራለኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ አንቀላፍተው ፡ አይነቁም ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ የተባለው ፡ ንጉሥ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 58 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሰፊው ፡ የባቢሎን ፡ ቅጥር ፡ ፈጽሞ ፡ ይፈርሳል ፡ ረጃዥሞችም ፡ በሮቿ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላሉ ፤ የወገኖችም ፡ ድካም ፡ ከንቱ ፡ ትኾናለች ፥ የአሕዛብም ፡ ሥራ ፡ ለእሳት ፡ ትኾናለች ፤ እነርሱም ፡ ይደክማሉ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 59 ፤ የመሕሜያ ፡ ልጅ ፡ የኔርያ ፡ ልጅ ፡ ሰራያ ፡ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ሴዴቅያስ ፡ በነገሠ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፡ ነቢዩ ፡ ኤርምያስ ፡ ያዘዘው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ። ሰራያም ፡ የቤት ፡ አዛዥ ፡ ነበረ ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 60 ፤ በባቢሎንም ፡ ላይ ፡ የሚመጣውን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ የተጻፈውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፥ ኤርምያስ ፡ በመጽሐፍ ፡ ላይ ፡ ጻፈው ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 61 ፤ ኤርምያስም ፡ ሰራያን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በገባኽ ፡ ጊዜ ፡ እይ ፥ ይህንም ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ አንብና ፦

ኤር. ፡ 51 ፡ 62 ፤ አቤቱ ፥ ከሰው ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ እንዳይቀመጥባት ፥ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ እንድትኾን ፡ ታጠፋት ፡ ዘንድ ፡ በዚች ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ ተናግረኻል ፡ በል ።

ኤር. ፡ 51 ፡ 63 ፤ ይህንም ፡ መጽሐፍ ፡ ማንበብ ፡ ከፈጸምኽ ፡ በኋላ ፥ ድንጋይን ፡ እሰርበት ፡ በኤፍራጥስም ፡ ውስጥ ፡ ጣለው ፤

ኤር. ፡ 51 ፡ 64 ፤ አንተም ፦ እኔ ፡ ከማመጣባት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ እንዲሁ ፡ ባቢሎን ፡ ትሰጥማለች ፡ አትነሣምም ፡ በል ። የኤርምያስ ፡ ቃል ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 52 ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 1 ፤ ሴዴቅያስ ፡ መንገሥ ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፡ የኻያ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ጕልማሳ ፡ ነበረ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ነገሠ ፤ እናቱም ፡ ዐሚጣል ፡ የተባለች ፡ የሊብና ፡ ሰው ፡ የኤርምያስ ፡ ልጅ ፡ ነበረች ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 2 ፤ ኢዮአቄምም ፡ እንዳደረገ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ክፉ ፡ አደረገ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 3 ፤ ከፊቱም ፡ አውጥቶ ፡ እስኪጥላቸው ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ ኾኗልና ፤ ሴዴቅያስም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ዐመፀ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 4 ፤ ሴዴቅያስም ፡ በነገሠ ፡ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርና ፡ ሰራዊቱ ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጥተው ፡ ከበቧት ፡ በዙሪያዋም ፡ ዕርድ ፡ አደረገ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 5 ፤ ከተማዪቱም ፡ እስከ ፡ ንጉሡ ፡ እስከ ፡ ሴዴቅያስ ፡ እስከ ፡ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ተከባ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 6 ፤ በአራተኛውም ፡ ወር ፡ በዘጠነኛው ፡ ቀን ፡ በከተማዪቱ ፡ ራብ ፡ ጸንቶ ፡ ነበር ፥ ለአገሩም ፡ ሰዎች ፡ እንጀራ ፡ ታጣ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 7 ፤ ከተማዪቱም ፡ ተሰበረች ፥ ሰልፈኞችም ፡ ኹሉ ፡ ሸሹ ፥ በኹለቱም ፡ ቅጥር ፡ መካከል ፡ ባለው ፡

በር ፡ ወደንጉሡ ፡ አትክልት ፡ በሚወስደው ፡ መንገድ ፡ በሌሊት ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጡ ። ከለዳውያንም ፡ በከተማዪቱ ፡
ዙሪያ ፡ ነበሩ ፤ በዐረባም ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 8 ፤ የከለዳውያንም ፡ ሰራዊት ፡ ንጉሡን ፡ ተከታተሉት ፥ በኢያሪኮም ፡ ሜዳ ፡ ሴዴቅያስን ፡
ያዙ ፤ ሰራዊቱም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተበትነው ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 9 ፤ ንጉሡንም ፡ ይዘው ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለባት ፡ በሐማት ፡ ምድር ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡
ሪብላ ፡ አመጡት ፤ ርሱም ፡ ፍርድን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ተናገረ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 10 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ የሴዴቅያስን ፡ ልጆች ፡ በፊቱ ፡ ገደላቸው ፥ የይሁዳንም ፡ አለቃዎች ፡
ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 11 ፤ የሴዴቅያስንም ፡ ዐይኖች ፡ አወጣ ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሰንሰለት ፡ አሰረው ፡ ወደ ፡
ባቢሎንም ፡ ወሰደው ፥ እስኪሞትም ፡ ድረስ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ አኖረው ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 12 ፤ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ በዐሥራ ፡ ዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡
ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ፊት ፡ የቆመው ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡
መጣ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 13 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤትና ፡ የንጉሡን ፡ ቤት ፡ አቃጠለ ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቤቶች ፡
ኹሉ ፥ ታላላቆችን ፡ ቤቶች ፡ ኹሉ ፥ በእሳት ፡ አቃጠለ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 14 ፤ ከዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ የከለዳውያን ፡ ሰራዊት ፡ ኹሉ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ቅጥር ፡
ኹሉ ፡ ዙሪያዋን ፡ አፈረሱ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 15 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ የሕዝቡን ፡ ድኻዎች ፥ በከተማም ፡ ውስጥ ፡ የቀረውን ፡
ሕዝብ ፥ ሸሽተውም ፡ ወደባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ የተጠጉትን ፥ የሕዝቡንም ፡ ቅሬታ ፡ አፈለሰ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 16 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፥ ከአገሩ ፡ ድኻዎች ፥ ወይን ፡ ተካዮችና ፡ ዐራሾች ፡
እንዲኾኑ ፥ አስቀረ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 17 ፤ ከለዳውያንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የነበሩትን ፡ የናስ ፡ ዐምዶች ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡
የነበሩትን ፡ መቀመጫዎችና ፡ የናሱን ፡ ኵሬ ፡ ሰባበሩ ፥ ናሱንም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዱ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 18 ፤ ምንቸቶቹንና ፡ መጫሪያዎችንም ፡ መኰስተሪያዎችንና ፡ ድስቶችን ፡ ጭልፋዎችንም ፡
የሚያገለግሉበትንም ፡ የናስ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ወሰዱ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 19 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ጽዋዎቹንና ፡ ማንደጃዎቹን ፡ ድስቶቹንና ፡ ምንቸቶችን ፡ መቅረዞችንና ፡
ጭልፋዎቹን ፡ መንቀሎችንም ፥ የወርቁን ፡ ዕቃ ፡ በወርቅ ፥ የብሩንም ፡ ዕቃ ፡ በብር ፡ አድርጎ ፥ ወሰደ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 20 ፤ ንጉሡ ፡ ሰሎሞንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ያሠራቸውን ፡ ኹለቱን ፡ ዐምዶች ፥ አንዱንም ፡
ኵሬ ፥ ከመቀመጫዎቹም ፡ በታች ፡ የነበሩትን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ የናስ ፡ በሬዎች ፡ ወሰደ ፤ ለእነዚህ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡
ናስ ፡ ሚዛን ፡ አልነበረም ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 21 ፤ ዐምዶቹም ፥ የአንዱ ፡ ዐምድ ፡ ቁመት ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የዙሪያውም ፡ መጠን ፡
ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ ውፍረቱም ፡ አራት ፡ ጣት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ፥ ባዶም ፡ ነበረ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 22 ፤ የናሱም ፡ ጕልላት ፡ በላዩ ፡ ነበረ ፤ የአንዱም ፡ ጕልላት ፡ ቁመት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡
ነበረ ፥ በጕልላቱም ፡ ላይ ፡ በዙሪያው ፡ ኹሉ ፡ ከናስ ፡ የተሠሩ ፡ መረበብና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩበት ፤ በኹለተኛውም ፡

ዐምድ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገርና ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩበት ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 23 ፤ በስተውጭም ፡ ዘጠና ፡ ስድስት ፡ ሮማኖች ፡ ነበሩ ። በመረበቡም ፡ ዙሪያ ፡ የነበሩ ፡ ሮማኖች ፡ ሹሉ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 24 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ሰራያን ፡ ኹለተኛውንም ፡ ካህን ፡ ሶፎንያስን ፡ ሦስቱንም ፡ በረኞች ፡ ወሰደ ፤

ኤር. ፡ 52 ፡ 25 ፤ ከከተማዉቱም ፡ በሰልፈኞች ፡ ላይ ፡ ተሾመው ፡ ከነበሩት ፡ አንዱን ፡ ጃን ፡ ደረባ ፥ በከተማዉቱም ፡ ከሚገኙት ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ከሚቆሙት ፡ ሰባቱን ፡ ሰዎች ፥ የአገሩንም ፡ ሕዝብ ፡ የሚያሰልፈውን ፡ የሰራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ጸሓፊ ፥ በከተማዉቱም ፡ ከተገኙት ፡ ከአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ስድሳ ፡ ሰዎች ፡ ወሰደ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 26 ፤ የዘበኞቹም ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ወስዶ ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወዳለበት ፡ ወደ ፡ ሪብላ ፡ አመጣቸው ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 27 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ መታቸው ፥ በሐማትም ፡ ምድር ፡ ባለችው ፡ በሪብላ ፡ ገደላቸው ። እንዲሁ ፡ ይሁዳ ፡ ከአገሩ ፡ ተማረከ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 28 ፤ ናቡከደነጾር ፡ የማረከው ፡ ሕዝብ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ ኻያ ፡ ሦስት ፡ አይሁድ ፤

ኤር. ፡ 52 ፡ 29 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በዐሥራ ፡ ስምንተኛው ፡ ዓመት ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ኹለት ፡ ነፍስ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ማርኳል ፤

ኤር. ፡ 52 ፡ 30 ፤ በናቡከደነጾር ፡ በኻያ ፡ ሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ ናቡዘረዳን ፡ ከአይሁድ ፡ ሰባት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ ዐምስት ፡ ነፍስ ፡ ማርኳል ፤ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ነበሩ ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 31 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በሠላሳ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ዮርማሮዴክ ፡ በነገሠ ፡ በአንደኛው ፡ ዓመት ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ የዮአኪንን ፡ ራስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ ከወህኒም ፡ አወጣው ፤

ኤር. ፡ 52 ፡ 32 ፤ በመልካምም ፡ ተናገረው ፥ ዙፋኑንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በባቢሎን ፡ ከነበሩት ፡ ነገሥታት ፡ ዙፋን ፡ በላይ ፡ አደረገለት ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 33 ፤ በወህኒም ፡ ውስጥ ፡ ለብሶት ፡ የነበረውን ፡ ልብስ ፡ ለወጠለት ፥ ዮአኪንም ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ በፊቴ ፡ ሹልጊዜ ፡ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ኤር. ፡ 52 ፡ 34 ፤ የባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሹሉ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የዘወትር ፡ ቀለብ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሰጠው ፡ ነበር ❖

ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ አሌፍ ። ሕዝብ ፡ ሞልቶባት ፡ የነበረች ፡ ከተማ ፡ ብቻዋን ፡ እንዴት ፡ ተቀመጠች! ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ የነበረች ፡ እንደ ፡ መበለት ፡ ኾናለች ፤ በአውራጃዎች ፡ መካከል ፡ ልዕልት ፡ የነበረች ፡ ተገዢ ፡ ኾናለች ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ቤት ። በሌሊት ፡ እጅግ ፡ ታላቅሳለች ፥ እንባዋም ፡ በጕንጯ ፡ ላይ ፡ አለ ፤ ከውሽማዎቿ ፡ ዅሉ ፡ የሚያጽናናት ፡ የለም ፤ ወዳጆቿ ፡ ዅሉ ፡ ወነጀሏት ፡ ጠላቶችም ፡ ኾኗት ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ጋሜል ። ይሁዳ ፡ ስለመጨነቅና ፡ ስለባርነት ፡ ብዛት ፡ ተማረከች ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ተቀመጠች ፡ ዕረፍትም ፡ አላገኘችም ፤ የሚያስጨንቋት ፡ ዅሉ ፡ ተጨንቃ ፡ አገኟት ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ዳሌጥ ። ወደ ፡ ዓመት ፡ በዓልም ፡ የሚመጣ ፡ የለምና ፡ የጽዮን ፡ መንገዶች ፡ አለቀሱ ፤ በሮቿ ፡ ዅሉ ፡ ፈርሰዋል ፡ ካህናቷም ፡ እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፤ ደናግሎቿም ፡ ተጨነቁ ፡ ርሷም ፡ በምሬት ፡ አለች ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ሄ ። ስለኀጢአቷ ፡ ብዛት ፡ እግዚአብሔር ፡ አስጨንቋታልና ፥ አስጨናቂዎቿ ፡ ራስ ፡ ኾኑ ፥ ጠላቶቿም ፡ ተከናወነላቸው ፤ ሕፃናቷ ፡ ባስጨናቂዎች ፡ ፊት ፡ ተማርከዋል ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ዋው ። ከጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ውበቷ ፡ ዅሉ ፡ ወጥቷል ፤ አለቃዎቿ ፡ ማሰማሪያ ፡ እንደማያገኙ ፡ ዋላዎች ፡ ኾኑ ፤ ከሚያባርሯቸው ፡ ፊት ፡ ተዳክመው ፡ ኼዱ ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ዛይ ። ኢየሩሳሌም ፡ በጭንቀቷና ፡ በመከራዋ ፡ ወራት ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ የነበረላትን ፡ የከበረን ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ዐሰበች ፤ ሕዝቧ ፡ በአስጨናቂዎች ፡ እጅ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚረዳትም ፡ በሌላት ፡ ጊዜ ፥ አስጨናቂዎች ፡ አይዋት ፡ በመፍረሷም ፡ ሣቁ ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ሔት ። ኢየሩሳሌም ፡ እጅግ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርታለች ፤ ስለዚህ ፥ ረክሳለች ፤ ያከብሯት ፡ የነበሩ ፡ ዅሉ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ አይተዋታልና ፥ አቃለሏት ፤ ርሷም ፡ እየጮኸች ፡ ታለቅሳለች ፥ ወደ ፡ ኋላም ፡ ዘወር ፡ አለች ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ጤት ። አደፏ ፡ በልብሷ ፡ ዘርፍ ፡ ነበረ ፤ ፍጻሜዋን ፡ አላሰበችም ፤ ስለዚህ ፥ በድንቅ ፡ ተዋርዳለች ፥ የሚያጽናናትም ፡ የለም ፤ አቤቱ ፥ ጠላት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ መከራዬን ፡ ተመልከት ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ዮድ ። አስጨናቂው ፡ በከበረ ፡ ነገሯ ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፤ ወደ ፡ ጉባኤኽ ፡ እንዳይገቡ ፡ ያዘዝኻቸው ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ መቅደሷ ፡ ሲገቡ ፡ አይታለችና ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ካፍ ። ሕዝቧ ፡ ዅሉ ፡ እየጮኹ ፡ ያለቅሳሉ ፡ እንጀራም ፡ ይፈልጋሉ ፤ ሰውነታቸውን ፡ ለማበርታት ፡ የከበረ ፡ ሀብታቸውን ፡ ስለ ፡ መብል ፡ ሰጥተዋል ፤ አቤቱ ፥ ተጕሳቍያለኹና ፡ እይ ፥ ተመልከትም ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ላሜድ ። እናንተ ፡ መንገድ ፡ ዐላፊዎች ፡ ዅሉ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለምን ፧ እግዚአብሔር ፡ በጽኑ ፡ ቍጣው ፡ ቀን ፡ እኔን ፡ እንዳስጨነቀበት ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ እንደእኔ ፡ መከራ ፡ የሚመስል ፡ መከራ ፡ እንዳለ ፡ ተመልከቱ ፥ እዩ ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ሜም ። ከላይ ፡ እሳትን ፡ ወደ ፡ ዐጥንቴ ፡ ሰደደ ፡ በረታችበትም ፤ ለእግሬ ፡ ወጥመድ ፡ ዘረጋ ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡ መለሰኝ ፥ አጠፋኝም ፡ ቀኑንም ፡ ዅሉ ፡ አደከመኝ ።

ሰቈ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ኖን ። የኀጢአቶቼ ፡ ቀንበር ፡ በእጁ ፡ ተይዛለች ፤ ታስረው ፡ በዐንገቴ ፡ ላይ ፡

ወጥተዋል ፤ ጕልበቴን ፡ አደከመ ። ጌታ ፡ በፊታቸው ፡ እቆም ፡ ዘንድ ፡ በማልችላቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠኝ ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ሳምኬት ። ጌታ ፡ ኀያላኔን ፡ ኹሉ ፡ ከውስጤ ፡ አስወገዳቸው ፤ ጕልማሳዎቼን ፡ ያደቅ ፡ ዘንድ ፡ ጉባኤን ፡ ጠራብኝ ፤ ጌታ ፡ ድንግሊቱን ፡ የይሁዳን ፡ ልጅ ፡ በመጥመቂያ ፡ እንደሚረገጥ ፡ አድርጎ ፡ ረገጣት ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ዔ ። የሚያጽናናኝ ፡ ነፍሴንም ፡ የሚያበረታት ፡ ከእኔ ፡ ርቋልና ፥ ስለዚህ ፡ አለቅሳለኹ ፤ ዐይኔ ፥ ዐይኔ ፡ ውሃ ፡ ያፈሳል ። ጠላት ፡ በርትቷልና ፥ ልጆቼ ፡ ጠፍተዋል ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ፌ ። ጽዮን ፡ እጇን ፡ ዘረጋች ፤ የሚያጽናናት ፡ የለም ፤ እግዚአብሔር ፡ በያዕቆብ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ እንዲያስጨንቁት ፡ አዘዘ ፤ ኢየሩሳሌም ፡ በመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ኾናለች ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ጻዴ ። በአፉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ዐመፅ ፡ አድርጌያለኹና ፥ እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ነው ። እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፥ እባካችኹ ፡ ስሙ ፥ መከራዬንም ፡ ተመልከቱ ፤ ደናግሎቼና ፡ ጐበዛዝቴ ፡ ተማርከው ፡ ኼዱ ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ቆፍ ። ውሽማዎቼን ፡ ጠራኹ ፥ እነርሱም ፡ አታለሉኝ ፤ ካህናቴና ፡ ሽማግሌዎቼ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያበረቱ ፡ ዘንድ ፡ መብል ፡ ሲፈልጉ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ ሞቱ ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ሬስ ። አቤቱ ፥ ተጨንቄያለኹና ፥ አንጐቴም ፡ ታውኮብኛልና ፥ ተመልከት ፤ ዐመፃን ፡ ፈጽሞ ፡ አድርጌያለኹና ፡ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተገላበጠብኝ ፤ በሜዳ ፡ ሰይፍ ፡ ልጆቼን ፡ አጠፋ ፡ በቤትም ፡ ሞት ፡ አለ ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ሳን ። እኔ ፡ እየጮኽኹ ፡ እንደማለቅስ ፡ ሰምተዋል ፤ የሚያጽናናኝ ፡ የለም ፤ ጠላቶቼ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ መከራዬ ፡ ሰምተዋል ፤ አንተ ፡ አድርገኸዋልና ፥ ደስ ፡ አላቸው ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገርኸውን ፡ ቀን ፡ ታመጣለኽ ፡ እነርሱም ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ይኾናሉ ።

ሰቈ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ታው ። ልቅሶዬ ፡ እጅግ ፡ ነውና ፥ ልቤም ፡ ደክሟልና ፥ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ፊትኽ ፡ ይድረስ ፥ ስለ ፡ ኀጢአቴ ፡ ኹሉ ፡ እንዳደረግኽብኝ ፡ አድርግባቸው ።

ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ አሌፍ ። ጌታ ፡ በቍጣው ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ምን ፡ አደመናት! ፡ የእስራኤልን ፡ ውበት ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለ ፥ በቍጣውም ፡ ቀን ፡ የእግሩን ፡ መረገጫ ፡ አላሰበም ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ቤት ። ጌታ ፡ የያዕቆብን ፡ ማደሪያዎች ፡ ኹሉ ፡ ዋጠ ፥ አልራራምም ፤ በመዓቱ ፡ የይሁዳን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዐምባዎች ፡ አፈረሰ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ አወረዳቸው ፤ መንግሥቱንና ፡ አለቃዎቿን ፡ አረከሰ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ጋሜል ። በጽኑ ፡ ቍጣው ፡ የእስራኤልን ፡ ቀንድ ፡ ኹሉ ፡ ቀጠቀጠ ፤ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ከጠላት ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ መለሰ ፥ በዙሪያውም ፡ እንደሚባላ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ያዕቆብን ፡ አቃጠለ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ዳሌጥ ። ቀስቱን ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ገተረ ፥ እንደ ፡ አስጨናቂ ፡ ቀኝ ፡ እጁን ፡ አጸና ፥ ለዐይንም ፡ የሚያምረውን ፡ ኹሉ ፡ ገደለ ፤ በጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ድንኳን ፡ መዓቱን ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ አፈሰሰ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ሄ ። ጌታ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ኾነ ፥ እስራኤልን ፡ ዋጠ ፤ አዳራሾቿን ፡ ኹሉ ፡ ዋጠ ፥ ዐምባዎቿን ፡ አጠፋ ፤ በይሁዳም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሐዘንና ፡ ልቅሶ ፡ አበዛ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ዋው ። ማደሪያውን ፡ እንደ ፡ አትክልት ፡ ነቀለ ፤ የበዓሉን ፡ ስፍራ ፡ አጠፋ ፤ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ዓመት ፡ በዓሉንና ፡ ሰንበቱን ፡ አስረሳ ፥ በቍጣውም ፡ መዓት ፡ ንጉሡንና ፡ ካህኑን ፡ አቃለለ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ዛይ ። ጌታ ፡ መሠዊያውን ፡ ጣለ ፥ መቅደሱን ፡ ጠላ ፥ የአዳራሾቿንም ፡ ቅጥር ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤ ድምፃቸውን ፡ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ሔት ። እግዚአብሔር ፡ የጽዮንን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥር ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ፤ የመለኪያውን ፡ ገመድ ፡ ዘረጋ ፥ እጁን ፡ ከማጥፋት ፡ አልመለሰም ፤ ምሽጉና ፡ ቅጥሩ ፡ እንዲያለቅሱ ፡ አደረገ ፤ በአንድነት ፡ ደከሙ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ጤት ። በሮቿ ፡ በመሬት ፡ ውስጥ ፡ ሰጠሙ ፥ መወርወሪያዎቿን ፡ አጠፋ ፡ ሰበረም ፤ ንጉሧና ፡ አለቃዎቿ ፡ ሕግ ፡ በሌለባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አሉ ፤ ነቢያቷም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ራእይ ፡ አላገኙም ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ዮድ ። የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ተቀምጠዋል ፤ ትቢያን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነሰነሱ ፥ ማቅም ፡ ታጠቁ ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ደናግል ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አዘነበሉ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ካፍ ። ሕፃኑና ፡ ጡት ፡ የሚጠባው ፡ በከተማዪቱ ፡ ጐዳና ፡ ላይ ፡ ሲዝሉ ፥ ዐይኔ ፡ በእንባ ፡ ደከመች ፥ አንጐቴም ፡ ታወከ ፤ ስለወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ጕበቴ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተዘረገፈ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ላሜድ ። በከተማ ፡ ጐዳና ፡ እንደ ፡ ተወጋ ፡ ሰው ፡ በዛሉ ፡ ጊዜ ፥ ነፍሳቸውም ፡ በእናቶቻቸው ፡ ብብት ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፥ እናቶቻቸውን ፦ እኽልና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ይሏቸዋል ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ሜም ። የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ እመሰክርልሻለኹ ፧ በምንስ ፡ እመስልሻለኹ ፧ ድንግሊቱ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አጽናናሽ ፡ ዘንድ ፡ በምን ፡ አስተካክልሻለኹ ፧ ስብራትሽ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፤ የሚፈውስሽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ኖን ። ነቢያትሽ ፡ ከንቱና ፡ ሐሰተኛ ፡ ራእይ ፡ አይተውልሻል ፤ ምርኮሽንም ፡ ይመልሱ ፡ ዘንድ ፡ በደልሽን ፡ አልገለጡም ፤ ከንቱና ፡ የማይረባ ፡ ነገርንም ፡ አይተውልሻል ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ሳምኬት ። መንገድ ፡ ዐላፊዎች ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ ያጨበጨቡብሻልና ፦ በእውኑ ፡ የውበት ፡ ፍጻሜና ፡ የምድር ፡ ኹሉ ፡ ደስታ ፡ የሚሏት ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናትን ፧ እያሉ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ያፏጫሉ ፥ ራሳቸውንም ፡ ያነቃንቃሉ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ዔ ። ጠላቶችሽ ፡ ኹሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብሽ ፤ እያፏጩና ፡ ጥርሳቸውን ፡ እያፋጩ ፦ ውጠናታል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተስፋ ፡ ያደረግናት ፡ ቀን ፡ ይህች ፡ ናት ፤ አግኝተናታል ፥ አይተናትማል ፡ ይላሉ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ፊ ። እግዚአብሔር ፡ ያሰበውን ፡ አደረገ ፤ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ያዘዘውን ፡ ቃል ፡ ፈጸመ ፤ አፈረሰ ፡ አልራራምም ፤ ጠላትንም ፡ ደስ ፡ አሠኘብሽ ፥ የሚያስጨንቁሽንም ፡ ቀንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ጻዴ ። ልባቸው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ጮኸ ፦ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥር ፡ ሆይ ፥ እንባሽን ፡ እንደ ፡ ፈሳሽ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አፍሺ ፤ ለሰውነትሽ ፡ ዕረፍት ፡ አትስጪ ፤ የዐይንሽ ፡ ብሌን ፡ አታቋርጥ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ቆፍ ። ተነሺ ፥ በሌሊት ፡ በመዝመሪያ ፡ ክፍል ፡ ጩኺ ፥ በጌታም ፡ ፊት ፡ ልብሽን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፍሺ ፤ በጐዳና ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ በራብ ፡ ስለደከሙ ፡ ስለሕፃናትሽ ፡ ነፍስ ፡ እጆችሽን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አንሺ ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ሬስ ። አቤቱ ፥ እይ ፤ በማን ፡ ላይ ፡ እንደዚህ ፡ እንዳደረግኽ ፡ ተመልከት ። በእውኑ ፡ ሴቶች ፡ ፍሬያቸውን ፥ ያቀማጠሏቸውን ፡ ሕፃናት ፥ ይበላሉን ፧ በእውኑ ፡ ካህኑና ፡ ነቢዩ ፡ በጌታ ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ይገደላሉን ፧

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ሳን ። ብላቴናውና ፡ ሽማግሌው ፡ በመንገዶች ፡ ላይ ፡ ተጋደሙ ፤ ደናግሎቼና ፡ ጐበዛዝቴ ፡ በሰይፍ ፡ ወድቀዋል ፤ በቀሣጣኽ ፡ ቀን ፡ ገደልኻቸው ፤ ሳትራራ ፡ ዐረድኻቸው ።

ሰቈ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ታው ። እንደ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ የሚያስፈሩኝን ፡ ከዙሪያዬ ፡ ጠራኽ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቀሣጣ ፡ ቀንም ፡ ያመለጠ ፡ ወይም ፡ የቀረ ፡ አልተገኘም ፤ ያቀማጠልኋቸውንና ፡ ያሳደግኋቸውን ፡ ጠላቴ ፡ በላቸው ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ አሌፍ ። በቀኑጣው ፡ በትር ፡ መከራ ፡ ያየ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ብርሃን ፡ ወደሌለበት ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ መርቶ ፡ ወሰደኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ዘወትር ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ እጁን ፡ በላዬ ፡ መለሰ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ቤት ። ሥጋዬንና ፡ ቍርበቴን ፡ አስረጀ ፥ ዐጥንቴን ፡ ሰበረ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፡ በሐሞትና ፡ በድካምም ፡ ከበበኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ቀድሞ ፡ ሞተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ በጨለማ ፡ አኖረኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ጋሜል ። እንዳልወጣ ፡ በዙሪያዬ ፡ ቅጥር ፡ ሠራብኝ ፤ ሰንሰለቴን ፡ አከበደ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ በጠራኹና ፡ በጮኽኹ ፡ ጊዜ ፡ ጸሎቴን ፡ ከለከለ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ መንገዴን ፡ በተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ ዘጋ ፥ ጐዳናዬንም ፡ አጣመመ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ዳሌጥ ። እንደሚሸምቅ ፡ ድብ ፡ እንደ ፡ ተሸሸገም ፡ አንበሳ ፡ ኾነብኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ መንገዴን ፡ ለወጠ ፥ ገነጣጠለኝም ፤ ባድማ ፡ አደረገኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ቀስቱን ፡ ገተረ ፡ ለፍላጻውም ፡ እንደ ፡ ጊጤ ፡ አደረገኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ሄ ። የሰገባውን ፡ ፍላጻዎች ፡ በኵላሊቴ ፡ ውስጥ ፡ ተከለ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ለወገኔ ፡ ኹሉ ፡ ማላገጫ ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ መሳለቂያ ፡ ኾንኹ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ምሬት ፡ ሞላብኝ ፡ በሬትም ፡ አጠገበኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ዋው ። ጥርሴን ፡ በጭንጫ ፡ ሰበረ ፥ በዐመድም ፡ ከደነኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ነፍሴን ፡ ከሰላም ፡ አራቅኽ ፤ በጎ ፡ ነገርን ፡ ረሳኹ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኔም ፦ ኀይሌ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ተስፋዬ ፡ ጠፋ ፡ አልኹ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ዛይ ። መከራዬንና ፡ ችግሬን ፡ ሬትንና ፡ ሐሞትን ፡ ዐስብ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ነፍሴ ፡ እያሰበችው ፡ በውስጤ ፡ ፈዘዘች ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ይህችን ፡ በልቤ ፡ አኖራለኹ ፥ ስለዚህ ፡ እታገሣለኹ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ሔት ። ያልጠፋነው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ምሕረት ፡ የተነሣ ፡ ነው ፤ ርኅራኄው ፡ አያልቅምና ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ማለዳ ፡ ማለዳ ፡ ዐዲስ ፡ ነው ፤ ታማኝነትኽ ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ነፍሴ ፦ እግዚአብሔር ፡ ዕድል ፡ ፈንታዬ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፥ ተስፋ ፡ አደርገዋለኹ ፡ አለች ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ጤት ። እግዚአብሔር ፡ በተስፋ ፡ ለሚጠብቁት ፡ ለምትሻውም ፡ ነፍስ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ሰው ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ ተስፋ ፡ ቢያደርግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ሰው ፡ በታናሽነቱ ፡ ቀንበር ፡ ቢሸከም ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ የ፡ድ ። ርሱ ፡ አሸክሞታልና ፥ ዝም ፡ ብሎ ፡ ለብቻው ፡ ይቀመጥ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ ተስፋ ፡ የኾነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አፉን ፡ በዐፈር ፡ ውስጥ ፡ ያኑር ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ ጕንጩን ፡ ለሚመታው ፡ ይስጥ ፥ ስድብንም ፡ ይጥገብ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ ካፍ ። ጌታ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጥልምና ፤

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ ቢያሳዝንም ፡ እንደ ፡ ምሕረቱ ፡ ብዛት ፡ ይራራልና ፤

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 33 ፤ የሰውን ፡ ልጆች ፡ ከልቡ ፡ አያስጨንቅም ፥ አያሳዝንምም ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 34 ፤ ላሜድ ። በምድር ፡ የተጋዙትን ፡ ኹሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ይረግጣቸው ፡ ዘንድ ፥

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 35 ፤ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ በልዑል ፡ ፊት ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፥

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 36 ፤ የሰውን ፡ ፍርድ ፡ ያጣምም ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ ዕሺ ፡ አይልም ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 37 ፤ ሜም ። ጌታ ፡ ያላዘዘውን ፡ የሚልና ፡ የሚፈጽም ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 38 ፤ ከልዑል ፡ አፍ ፡ ክፉና ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አይወጣምን ፧

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 39 ፤ ሕያው ፡ ሰው ፡ የሚያጉረመርም ፥ ሰው ፡ ስለ ፡ኀጢአቱ ፡ ቅጣት ፡ የሚያጉረመርም ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 40 ፤ ኖን ። መንገዳችንን ፡ እንመርምርና ፡ እንፈትን ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንመለስ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 41 ፤ ልባችንን ፡ ከእጃችን ፡ ጋራ ፡ በሰማይ ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እናንሣ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 42 ፤ በድለናል ፡ ዐምፀናልም ፥ አንተም ፡ ይቅር ፡ አላልኽም ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 43 ፤ ሳምኬት ። በቀ·ጣ ፡ ከደንኸን ፡ አሳደድኸንም ፤ ገደልኸን ፥ አልራራኽም ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 44 ፤ ጸሎት ፡ እንዳያልፍ ፡ ራስኽን ፡ በደመና ፡ ከደንኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 45 ፤ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ጕድፍና ፡ ውዳቂ ፡ አደረግኸን ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 46 ፤ ዔ ። ጠላቶቻችን ፡ ኹሉ ፡ አፋቸውን ፡ አላቀቁብን ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 47 ፤ ድንጋጤና ፡ ቀ·ጣ ፥ ጥፋትና ፡ ቅጥቃጤ ፡ ኾነብን ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 48 ፤ ስለወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቅጥቃጤ ፡ ዐይኔ ፡ የውሃ ፡ ፈሳሽ ፡ አፈሰሰች ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 49 ፤ 50 ፤ ፊ ። እግዚአብሔር ፡ ከሰማይ ፡ እስኪ·ጐበኝና ፡ እስኪመለከት ፡ ድረስ ፡ ዐይኔ ፡ ሳታቋርጥ ፡ ዝም ፡ ሳትል ፡ እንባ ፡ ታፈሳለች ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 51 ፤ ስለከተማዬ ፡ ቈነጕሯት ፡ ኹሉ ፡ ዐይኔ ፡ ነፍሴን ፡ አሳዘነች ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 52 ፤ ጻዴ ። በከንቱ ፡ ነገር ፡ ጠላቶች ፡ የኾኑኝ ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ማደንን ፡ አደኑኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 53 ፤ ሕይወቴን ፡ በጕድጓድ ፡ አጠፉ ፥ በላዬም ፡ ድንጋይ ፡ ጣሉ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 54 ፤ በራሴ ፡ ላይ ፡ ውሃዎች ፡ ተከነበሉ ፤ እኔም ፦ ጠፋኹ ፡ ብዬ ፡ ነበር ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 55 ፤ ቆፍ ። አቤቱ ፥ በጠለቀ ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ኾኜ ፡ ስምኽን ፡ ጠራኹ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 56 ፤ ድምፄን ፡ ሰማኽ ፤ ገሮኽን ፡ ከልመናዬ ፡ አትመልስ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 57 ፤ በጠራኹኽ ፡ ቀን ፡ ቀርበኽ ፦ አትፍራ ፡ አልኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 58 ፤ ሬስ ። ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ተሟግተኽ ፡ ሕይወቴን ፡ ተቤገሦኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 59 ፤ አቤቱ ፥ ጭንቀቴን ፡ አይተኻል ፥ ፍርዴን ፡ ፍረድልኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 60 ፤ በቀላቸውን ፡ ኹሉና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ኹሉ ፡ አየኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 61 ፤ ሳን ። አቤቱ ፥ ስድባቸውንና ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ኹሉ ፥

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 62 ፤ የተነሡብኝን ፡ ሰዎች ፡ ከንፈሮች ፡ ቀኑንም ፡ ኹሉ ፡ ያሰቡብኝን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ሰማኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 63 ፤ መቀመጣቸውንና ፡ መነሣታቸውን ፡ ተመልከት ፤ እኔ ፡ መሳለቂያቸው ፡ ነኝ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 64 ፤ ታው ። አቤቱ ፥ እንደ ፡ እጃቸው ፡ ሥራ ፡ ፍዳቸውን ፡ ትከፍላቸዋለኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 65 ፤ የልብ ፡ ዕውርነትንና ፡ ርግማንኽን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ።

ሰቈ. ፡ 3 ፡ 66 ፤ አቤቱ ፥ በቍጣ ፡ ታሳድዳቸዋለኽ ፡ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ታጠፋቸዋለኽ ።

ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ አሌፍ ። ወርቁ ፡ እንዴት ፡ ደበሰ! ፡ ጥሩው ፡ ወርቅ ፡ እንዴት ፡ ተለወጠ! ፡ የመቅደሱ ፡ ድንጋዮች ፡ በጐዳና ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ተበተኑ ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ቤት ። ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ የሚመስሉ ፡ የከበሩ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ፥ የሸክላ ፡ ሠሪ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃ ፡ እንዴት ፡ ተቈጠሩ! ፡

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ጋሜል ። ቀበሮዎች ፡ እንኳ ፡ ጡቶታቸውን ፡ ገልጠው ፡ ግልገሎቻቸውን ፡ አጠቡ ፤ የወገኔ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሰጐን ፡ ጨካኝ ፡ ኾነች ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ዳሌጥ ። ጡት ፡ የሚጠባው ፡ የሕፃን ፡ ምላስ ፡ ከጥም ፡ የተነሣ ፡ ወደ ፡ ትናጋው ፡ ተጣበቀ ፤ ሕፃናት ፡ እንጀራ ፡ ለመኑ ፥ የሚቈርስላቸውም ፡ የለም ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ሄ ። የጣፈጠ ፡ ነገር ፡ ይበሉ ፡ የነበሩ ፡ በመንገድ ፡ ጠፉ ፤ በቀይ ፡ ግምጃ ፡ ያድጉ ፡ የነበሩ ፡ የፍግ ፡ ክምር ፡ ዐቀፉ ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ዋው ። የማንም ፡ እጅ ፡ ሳይወድቅባት ፡ ድንገት ፡ ከተገለበጠች ፡ ከሰዶም ፡ ኀጢአት ፡ ይልቅ ፡ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ኀጢአት ፡ በዛች ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ዛይ ። አለቃዎቿ ፡ ከበረዶ ፡ ይልቅ ፡ ጥሩ ፥ ከወተት ፡ ይልቅ ፡ ነጭ ፡ ነበሩ ፤ ገላቸው ፡ ከቀይ ፡ ዕንቊ ፡ ይልቅ ፡ ቀይ ፡ ነበረ ፥ መልካቸውም ፡ እንደ ፡ ሰንፔር ፡ ነበረ ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ሔት ። ፊታቸው ፡ ከጥቀርሻ ፡ ይልቅ ፡ ጠቀሙሯል ፥ በመንገድም ፡ አልታወቁም ፤ ቀሙርበታቸው ፡ ወደ ፡ ዐጥንታቸው ፡ ተጣብቋል ፤ ደርቋል ፤ እንደ ፡ ዕንጨት ፡ ኾኗል ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ጤት ። በሰይፍ ፡ የሞቱ ፡ በራብ ፡ ከሞቱት ፡ ይሻላሉ ፤ እነዚህ ፡ የምድርን ፡ ፍሬ ፡ ዐጥተው ፡ ተወግተውም ፡ ቀጥነዋል ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ዮድ ። የርኅሩኆች ፡ ሴቶች ፡ እጆች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ቀቅለዋል ፤ የወገኔ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ በመቀጥቀጣ ፡ መብል ፡ ኾኗቸው ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ካፍ ። እግዚአብሔር ፡ መዓቱን ፡ ፈጽሟል ፥ ጽኑ ፡ ቀሣጣውን ፡ አፍስሷል ፤ እሳትን ፡ በጽዮን ፡ ውስጥ ፡ አቃጠለ ፥ መሠረቷንም ፡ በላች ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ላሜድ ። የምድር ፡ ነገሥታት ፡ በዓለምም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ አስጨናቂና ፡ ጠላት ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ እንዲገባ ፡ አላመኑም ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ሜም ። የጻድቃንን ፡ ደም ፡ በውስጧ ፡ ስላፈሰሱ ፡ ስለነቢያቷ ፡ ኀጢአትና ፡ ስለካህናት ፡ በደል ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ኖን ። ታውረው ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ተቅበዘበዙ ፤ ልብሳቸው ፡ እንዳይዳሰስ ፡ በደም ፡ ረክሰዋል ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ሳምኬት ። እናንተ ፡ ርኩሳን ፥ ራቁ ፥ ርቃችኹም ፡ ኺዱ ፥ አትንኩ ፡ ብለው ፡ ጮኹባቸው ። በሸሹና ፡ በተቅበዘበዙ ፡ ጊዜ ፥ በአሕዛብ ፡ መካከል ። በዚህ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኖሩም ፡ ተባለ ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ዔ ። የእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በተናቸው ፡ ርሱም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይመለከታቸውም ፤ የካህናቱን ፡ ፊት ፡ አላፈሩም ፥ ሽማግሌዎቹንም ፡ አላከበሩም ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ፌ ። ዐይናችን ፡ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ረዳታችን ፡ ገና ፡ ሲመለከት ፡ ጠፍቷል ፤ በመቈየታችን ፡ ማዳን ፡ የማይቻለውን ፡ ሕዝብ ፡ ጠብቀናል ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ጻዴ ። በአደባባያችን ፡ እንዳንኼድ ፡ ፍለጋችንን ፡ ተከተሉ ፤ ፍጻሜያችን ፡ ቀርቧል ፥ ዕድሜያችን ፡ አልቋል ፥ ፍጻሜያችን ፡ ደርሷል ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ቆፍ ። አሳዳጆቻችን ፡ ከሰማይ ፡ ንስር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ኾኑ ፤ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ አሳደዱን ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሸመቁብን ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ሬስ ። ስለ ፡ ርሱ ፦ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በጥላው ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ፡ ያልነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተቀባ ፥ የሕይወታችን ፡ እስትንፋስ ፥ በጕድጓዳቸው ፡ ተያዘ ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ሳን ። በያዕ ፡ ምድር ፡ የምትኖሪ ፡ የኤዶምያስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ሐሤትም ፡ አድርጊ ፤ ጽዋው ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ያልፋል ፥ አንቺም ፡ ትሰክሪያለሽ ፡ ትራቈቻለሽም ።

ሰቈ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ታው ። የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የበደልሽ ፡ ቅጣት ፡ ተፈጸመ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያስማርክሽም ። የኤዶምያስ ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በደልሽን ፡ ይቀጣል ፤ ኀጢአትሽን ፡ ይገልጣል ።

_____ሰቈቃወ ፡ ኤርምያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ አቤቱ ፥ የኾነብንን ፡ ዐስብ ፤ ተመልከት ፡ ስድባችንንም ፡ እይ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ርስታችን ፡ ለእንግዳዎች ፥ ቤቶቻችን ፡ ለሌላዎች ፡ ኾኑ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ድኻ ፡ አደጎችና ፡ አባት ፡ የሌለን ፡ ኾነናል ፤ እናቶቻችን ፡ እንደ ፡ መበለቶች ፡ ኾነዋል ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ውሃችንን ፡ በብር ፡ ጠጣን ፡ ዕንጨታችንን ፡ በዋጋ ፡ ገዛን ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ አሳዳጆቻችን ፡ በዐንገታችን ፡ ላይ ፡ ናቸው ፤ እኛ ፡ ደክመናል ፡ ዕረፍትም ፡ የለንም ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ለግብጻውያንና ፡ ለአሶራውያን ፡ እንጀራ ፡ እንጠግብ ፡ ዘንድ ፡ እጅ ፡ ሰጠን ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ አባቶቻችን ፡ ኀጢአትን ፡ ሠሩ ፡ ዛሬም ፡ የሉም ፤ እኛም ፡ በደላቸውን ፡ ተሸከምን ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ባሪያዎች ፡ ሠልጥነውብናል ፤ ከእጃቸው ፡ የሚታደገን ፡ የለም ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ሰይፍ ፡ የተነሣ ፡ በሕይወታችን ፡ እንጀራችንን ፡ እናመጣለን ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ከሚያቃጥል ፡ ከራብ ፡ ትኵሳት ፡ የተነሣ ፡ ቀጕርበታችን ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ጠቈረ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ በጽዮን ፡ ሴቶችን ፥ በይሁዳም ፡ ከተማዎች ፡ ደናግልን ፡ አጐሰቈሉ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ አለቃዎች ፡ በእጃቸው ፡ ተሰቀሉ ፤ የሽማግሌዎች ፡ ፊት ፡ አልታፈረም ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ጕልማሳዎች ፡ ወፍጮን ፡ ተሸከሙ ፥ ልጆችም ፡ ከዕንጨት ፡ በታች ፡ ተሰናከሉ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ሽማግሌዎች ፡ ከአደባባይ ፥ ጕልማሳዎች ፡ ከበገናቸው ፡ ተሻሩ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የልባችን ፡ ደስታ ፡ ቀርቷል ፤ ዘፈናችን ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፡ ተለውጧል ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ አክሊል ፡ ከራሳችን ፡ ወድቋል ፤ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ ወዮልን! ፡

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ ልባችን ፡ ታሟል ፤ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ዐይናችን ፡ ፈዟል ፤

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ስለጽዮን ፡ ተራራ ፥ ባድማ ፡ ኾናለችና ፥ ቀበሮዎችም ፡ ተመላልሰውባታልና ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ አንተ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኖራለኽ ፤ ዙፋንኽ ፡ ከትውልድ ፡ እስከ ፡ ትውልድ ፡ ነው ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ለዘለዓለም ፡ ትረሳናለኽ ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ ለረዥም ፡ ዘመን ፡ ትተወናለኽ ፧

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ አቤቱ ፥ ወዳንተ ፡ መልሰን ፡ እኛም ፡ እንመለሳለን ፤ ዘመናችንን ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ዐድስ ።

ሰቈ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፈጽመኽ ፡ ጥለኸናል ፤ እጅግ ፡ ተቈጥተኸናል ❖

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በሠላሳኛው ፡ ዓመት ፡ በአራተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በኮቦር ፡ ወንዝ ፡ በምርኮኞች ፡ መካከል ፡ ሳለኹ ፡ ሰማያት ፡ ተከፈቱ ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ራእይ ፡ አየኹ ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ንጉሡ ፡ ዮአኪን ፡ በተማረከ ፡ በዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከወሩም ፡ በዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በከለዳውያን ፡ አገር ፡ በኮቦር ፡ ወንዝ ፡ ወደቡዝ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ካህኑ ፡ ወደ ፡ ሕዝቅኤል ፡ መጣ ። የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በዚያ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ኾነች ፥

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እኔም ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ከሰሜን ፡ በኩል ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስና ፡ ታላቅ ፡ ደመና ፡ የሚበርቅም ፡ እሳት ፡ መጣ ፥ በዙሪያውም ፡ ጸዳል ፡ ነበረ ፥ በመካከልም ፡ በእሳቱ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚብለጨለጭ ፡ የወርቅ ፡ ምስያ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከመካከልም ፡ የአራት ፡ እንስሳዎች ፡ አምሳያ ፡ ወጣ ። መልካቸውም ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ፥ ሰውም ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ለያዳንዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ፊት ፥ ለያንዳንዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ክንፍ ፡ ነበሩት ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግሮቻቸውም ፡ ቀጥ ፡ ያሉ ፡ እግሮች ፡ ነበሩ ፤ የእግራቸውም ፡ ኰቴ ፡ እንደ ፡ ጥጃ ፡ እግር ፡ ኰቴ ፡ ነበረ ፤ እንደ ፡ ተወለወለ ፡ ናስም ፡ ይብለጨለጭ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ በክንፎቻቸውም ፡ በታች ፡ በያራቱ ፡ ጐድናቸው ፡ እንደሰው ፡ እጅ ፡ ነበረ ፤ ለአራቱም ፡ እንደዚህ ፡ ያሉ ፡ ፊትና ፡ ክንፍ ፡ ነበሯቸው ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ክንፎቻቸው ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተያያዘ ፡ ነበረ ፤ ሲኼዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ፥ እያንዳንዱም ፡ ፊቱን ፡ አቅንቶ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ የፊታቸው ፡ አምሳያ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረ ፥ ለአራቱም ፡ በስተቀኛቸው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ፊት ፥ በስተግራቸውም ፡ እንደ ፡ ላም ፡ ፊት ፡ ነበራቸው ፥ ለአራቱም ፡ ደግሞ ፡ የንስር ፡ ፊት ፡ ነበራቸው ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ክንፋቸውም ፡ በላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ ነበር ፥ የያንዳንዱም ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ክንፋቸው ፡ የተያያዙ ፡ ነበሩ ፥ ኹለት ፡ ኹለቱም ፡ ገላቸውን ፡ ይከድኑ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፤ መንፈስም ፡ ወደሚኼድበት ፡ ዅሉ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፥ ሲኼዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በእንስሳዎቹ ፡ መካከል ፡ እንደሚነድ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ ያለ ፡ ምስያ ፡ ነበረ ፤ በእንስሳዎች ፡ መካከል ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ የሚኼድ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ያለ ፡ ምስያ ፡ ነበረ ፤ ለእሳቱም ፡ ጸዳል ፡ ነበረው ፥ ከእሳቱም ፡ መብረቅ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እንስሳዎቹም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ምስያ ፡ ይሮጡና ፡ ይመለሱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ እንስሳዎችንም ፡ ስመለከት ፥ እንሆ ፥ በአራቱ ፡ እንስሳዎች ፡ አጠገብ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ መንኰራኵር ፡ አየኹ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ የመንኰራኵሩም ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ቢረሌ ፡ ነበረ ፤ አራቱም ፡ አንድ ፡ አምሳያ ፡ ነበሩ ፤ ሥራቸውም ፡ በመንኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ መንኰራኵር ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ በያራቱ ፡ ጐድናቸው ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ ሲኼዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ቁመታቸውም ፡ የረዘመና ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበረ ፤ የአራቱም ፡ ክበብ ፡ ዙሪያው ፡ በዐይን ፡ ተሞልቶ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እንስሳዎቹም ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፡ መንኰራኵሮቹ ፡ በአጠገባቸው ፡ ኼዱ ። እንስሳዎቹም ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ መንኰራኵሮቹ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ መንፈሱ ፡ ወደሚኼድበት ፡ ኹሉ ፡ እነርሱ ፡ ኼዱ ፤ የእንስሳዎች ፡ መንፈስ ፡ በመንኰራኵሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ነበረና ፡ መንኰራኵሮቹ ፡ በእነርሱ ፡ አጠገብ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ የእንስሳዎች ፡ መንፈስ ፡ በመንኰራኵሮቹ ፡ ውስጥ ፡ ነበረና ፡ እነዚያ ፡ ሲኼዱ ፡ እነዚህ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ እነዚያም ፡ ሲቆሙ ፡ እነዚህ ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ፤ እነዚያም ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ሲሉ ፡ መንኰራኵሮቹ ፡ በአጠገባቸው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ከእንስሳዎች ፡ ራስ ፡ በላይ ፡ የሚያስፈራ ፡ በረዶ ፡ የሚመስል ፡ የጠፈር ፡ አምሳያ ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ተዘርግቶ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ከጠፈሩም ፡ በታች ፡ ክንፎቻቸው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተቃንተው ፡ ነበር ፤ ለያንዳንዱም ፡ ገላውን ፡ የሚከድኑ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ክንፎች ፡ ነበሩት ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ሲኼዱም ፡ የክንፎቻቸው ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ድምፅ ፥ እንደ ፡ ኹሉን ፡ የሚችል ፡ የአምላክም ፡ ድምፅ ፥ እንደ ፡ ታላቅም ፡ ሰራዊት ፡ ድምፅ ፡ ኾኖ ፡ ሰማኹ ፤ ሲቆሙም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዝቅ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ ጠፈር ፡ በላይ ፡ ድምፅ ፡ ተሰማ ፤ ሲቆሙም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዝቅ ፡ ያደርጉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ በራሳቸውም ፡ በላይ ፡ ካለው ፡ ጠፈር ፡ በላይ ፡ የሰንፔር ፡ ድንጋይ ፡ የሚመስል ፡ የዙፋን ፡ አምሳያ ፡ ነበረ ፤ በዙፋኑም ፡ አምሳያ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ መልክ ፡ አምሳያ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ከወገቡም ፡ አምሳያ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚብለጨለጭ ፡ የወርቅ ፡ ምስያ ፡ አየኹ ፤ ከወገቡም ፡ አምሳያ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ምስያ ፡ አየኹ ፤ በዙሪያውም ፡ ጸዳል ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ በዝናብ ፡ ቀን ፡ በደመና ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ አምሳያ ፥ እንዲሁ ፡ በዙሪያው ፡ ያለ ፡ ጸዳል ፡ አምሳያ ፡ ነበረ ። የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምሳሌ ፡ መልክ ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ባየኹም ፡ ጊዜ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ፥ የሚናገርንም ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእግርኽ ፡ ቁም ፡ እኔም ፡ እናገርኻለኹ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በተናገረኝም ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ገባብኝ ፡ በእግሬም ፡ አቆመኝ ፥ የሚናገረኝንም ፡ ሰማኹ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ወደዐመፀ ፡ ወደ ፡ ዐመፀኞች ፡ ሰዎች ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እልክኻለኹ ። እነርሱና ፡ አባቶቻቸው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ዐመፁብኝ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እነርሱ ፡ ፊታቸው ፡ የተጨማተረ ፡ ልባቸውም ፡ የደነደነ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ። እኔ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ እልክሻለኹ ፤ አንተም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ፥ ቢሰሙ ፡ ወይም ፡ ባይሰሙ ፡ ነቢይ ፡ በመካከላቸው ፡ እንዳለ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ አንተ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ኵርንችትና ፡ ሾኽ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ቢኖሩም ፥ አንተም ፡ በጊንጦች ፡ መካከል ፡ ብትቀመጥም ፥ አትፍራቸው ፥ ቃላቸውንም ፡ አትፍራ ፤ አንተ ፡ ቃላቸውን ፡ አትፍራ ፥ ከፊታቸውም ፡ የተነሣ ፡ አትደንግጥ ፤ እነርሱ ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እነርሱ ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ፥ ቢሰሙ ፡ ወይም ፡ ባይሰሙ ፡ ቃሌን ፡ ትነግራቸዋለኽ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የምነግርኽን ፡ ስማ ፤ እንደዚያ ፡ እንደ ፡ ዐመፀኛው ፡ ቤት ፡ ዐመፀኛ ፡ አትኹን ፤ አፍኽን ፡ ክፈት ፡ የምሰጥኽንም ፡ ብላ ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ባየኹም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ እጅ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተዘርግታ ፡ ነበር ፤ እንሆም ፥ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ ነበረባት ።

ሕዝ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ በፊቴም ፡ ዘረጋው ፥ በውስጥና ፡ በውጭም ፡ ተጽፎበት ፡ ነበር ፤ ልቅሶና ፡ ሐዘን ፡ ዋይታም ፡ ተጽፎበት ፡ ነበር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ያገኘኸውን ፡ ብላ ፤ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ብላ ፥ ኼደኽም ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ተናገር ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ አፌንም ፡ ከፈትኹ ፡ መጽሐፉንም ፡ አጐረሠኝ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አፍኽ ፡ ይብላ ፥ በምሰጥኽም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ሆድኽን ፡ ሙላ ፡ አለኝ ። እኔም ፡ በላኹት ፥ በአፌም ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ጣፈጠ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ተነሥተኽ ፡ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኺድ ፥ ቃሌንም ፡ ተናገራቸው ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንጂ ፡ ንግግራቸው ፡ ወደጠለቀው ፡ ቋንቋቸውም ፡ ወደማይታወቅ ፡ ሕዝብ ፡ አልተላክኽምና ፤

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ንግግራቸው ፡ ወደጠለቀው ፡ ቋንቋቸውም ፡ ወደማይታወቅ ፡ ቃላቸውንም ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደማይቻልኽ ፡ ሕዝብ ፡ አላኩኽም ። ወደ ፡ እነዚያስ ፡ ልኬኽ ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፡ በሰሙኽ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ የጠነከረ ፡ ግንባርና ፡ የደነደነ ፡ ልብ ፡ አላቸውና ፥ እኔንም ፡ መስማት ፡ እንቢ ፡ ብለዋልና ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ አንተን ፡ አይሰሙም ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ ፊትኽን ፡ በፊታቸው ፡ ግንባርኽንም ፡ በግንባራቸው ፡ አጠንክሬያለኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ከቡላድ ፡ ድንጋይ ፡ ይልቅ ፡ እንዳለ ፡ አልማዝ ፡ ግንባርኽን ፡ አጠንክሬያለኹ ፤ እነርሱ ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ቢኾኑ ፡ አትፍራቸው ፤ ከፊታቸውም ፡ የተነሣ ፡ አትደንግጥ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የነገርኩኽን ፡ ቃሌን ፡ ኹሉ ፡ በልብኽ ፡ ተቀበል ፡ በጐሮኽም ፡ ስማ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ተነሥተኽም ፡ ወደተማረኩ ፡ ወደወገንኽ ፡ ልጆች ፡ ኺድ ፤ እነርሱም ፡ ቢሰሙ ፡ ወይም ፡ ባይሰሙ ፥— ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ መንፈስም ፡ አነሣኝ ፥ በኋላዬም ፥— የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ከቦታው ፡ ይባረክ ፡ የሚል ፡ የጽኑ ፡ ንውጥውጥታ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ የአራቱም ፡ እንስሳ ፡ ክንፎች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲማቱ ፥ በአጠገባቸውም ፡ የመንኰራኵሮችን ፡ ድምፅ ፥ የጽኑውንም ፡ ንውጥውጥታ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ መንፈስ ፡ አንሥቶ ፡ አስወገደኝ ፥ እኔም ፡ በምሬትና ፡ በመንፈሴ ፡ ሙቀት ፡ ኼድኹ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በላዬ ፡ በርትታ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ በቴልአቢብም ፡ ወዳሉ ፡ በኮቦርም ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ወደተቀመጡ ፡ ምርኮኞች ፡ መጣኹ ፥ በተቀመጡበትም ፡ ቦታ ፡ ተቀመጥኹ ፤ በዚያም ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ በድንጋጤ ፡ በመካከላቸው ፡ ተቀመጥኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ከሰባቱም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፥—

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጠባቂ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ ስለዚህ ፥ የአፌን ፡ ቃል ፡ ስማ ፥ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አስጠንቅቃቸው ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ኀጢአተኛውን ፥— በርግጥ ፡ ትሞታለኽ ፡ ባልኹት ፡ ጊዜ ፥ አንተም ፡ ባታስጠነቅቀው ፡ ነፍሱም ፡ እንድትድን ፡ ከክፉ ፡ መንገዱ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ለኀጢአተኛው ፡ አስጠንቅቀኽ ፡ ባትነግረው ፥ ያ ፡ ኀጢአተኛ ፡ በኀጢአት ፡ ይሞታል ፤ ደሙን ፡ ግን ፡ ከእጅኽ ፡ እፈልጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ኀጢአተኛውን ፡ ብታስጠነቅቅ ፡ ርሱም ፡ ከኀጢአቱና ፡ ከክፉ ፡ መንገዱ ፡ ባይመለስ ፥ በኀጢአቱ ፡ ይሞታል ፥ አንተ ፡ ግን ፡ ነፍስኽን ፡ አድነኻል ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ደግሞ ፡ ጻድቁ ፡ ከጽድቁ ፡ ተመልሶ ፡ ኀጢአት ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ በፊቱም ፡ ዕንቅፋትን ፡ ሳደርግ ፥ ርሱ ፡ ይሞታል ፤ አንተም ፡ አላስጠነቀቅኸውምና ፡ በኀጢአቱ ፡ ይሞታል ፥ ያደረጋትም ፡ ጽድቅ ፡ ነገር ፡ አትታሰብለትም ፤ ደሙን ፡ ግን ፡ ከእጅኽ ፡ እፈልጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኀጢአት ፡ እንዳይሠራ ፡ ጻድቁን ፡ ብታስጠነቅቅ ፡ ርሱም ፡ ኀጢአት ፡ ባይሠራ ፥ ተጠንቅቋልና ፥ በርግጥ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፤ አንተም ፡ ነፍስኽን ፡ አድነኻል ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ በዚያም ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነበረች ፥ ርሱም ፥— ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ቈላው ፡ ኺድ ፡ በዚያም ፡ እናገርኻለኹ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ እኔም ፡ ተነሥቼ ፡ ወደ ፡ ቈላው ፡ ኼድኹ ፤ እንሆም ፥ በኮቦር ፡ ወንዝ ፡ እንዳየኹት ፡ ክብር ፡ ያለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ በዚያ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ በግንባሬም ፡ ተደፋኹ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ መንፈስም ፡ ገባብኝ ፡ በእግሬም ፡ አቆመኝ ፥ ተናገረኝም ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፥— ኺድ ፥ ገብተኽ ፡ ቤትኽን ፡ ዝጋ ።

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ገመድ ፡ ያደርጉብኻል ፡ ያስሩኽማል ፥ አንተም ፡ በመካከላቸው ፡ አትወጣም ፤

ሕዝ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ እኔም ፡ ምላስኽን ፡ ከትናጋኽ ፡ ጋራ ፡ አጣብቃታለኹ ፡ አንተም ፡ ዲዳ ፡ ትኾናለኽ ፥ እነርሱም ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ፥ የሚዘልፍ ፡ ሰው ፡ አትኾንባቸውም ።

ሕዝ. ፥ 3 ፥ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተናገርኹኝ ፡ ጊዜ ፡ አፍኝን ፡ እከፍታለኹ ፥ እነርሱም ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ፥ አንተ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሚሰማ ፡ ይስማ ፥ የማይሰማም ፡ አይስማ ፡ ትላቸዋለኽ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጡብን ፡ ወስደኽ ፡ በፊትኽ ፡ አኑራት ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ ከተማ ፡ ሥዕል ፡ ሣልባት ፡ ክበባት ፥

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 2 ፤ ምሽግም ፡ ሥራባት ፥ ዐፈርም ፡ ደልድልባት ፥ ሰፈርም ፡ አቁምባት ፥ በዙሪያዋም ፡ የሚያፈርስ ፡ ግንድ ፡ አድርግባት ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 3 ፤ የብረት ፡ ምጣድም ፡ ወስደኽ ፡ በአንተና ፡ በከተማዪቱ ፡ መካከል ፡ ለብረት ፡ ቅጥር ፡ አድርገው ፥ ፊትኽንም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ አቅና ፥ የተከበበችም ፡ ትኾናለች ፡ አንተም ፡ ትከሳ፡ታለኽ ። ይህም ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 4 ፤ አንተም ፡ በግራ ፡ ጐድንኽ ፡ ተኛ ፡ የእስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ አኑርባት ፤ በምትተኛበትም ፡ ቀን ፡ ቍጥር ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ትሸከማለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 5 ፤ እኔም ፡ የኀጢአታቸውን ፡ ዓመታት ፡ ለአንተ ፡ የቀን ፡ ቍጥር ፡ እንዲኾንልኽ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ቀን ፡ ሰጥቼኻለኹ ፤ የእስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ ትሸከማለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 6 ፤ እነዚህንም ፡ በፈጸምኽ ፡ ጊዜ ፡ በቀኝ ፡ ጐድንኽ ፡ ትተኛለኽ ፥ የይሁዳንም ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ ትሸከማለኽ ፤ አንድን ፡ ዓመት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አድርጌ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 7 ፤ ክንድኽን ፡ ዕራቍቱን ፡ አድርገኽ ፡ ፊትኽን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ክቡ ፡ ታቀናለኽ ፥ ትንቢትም ፡ ትናገርባታለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 8 ፤ እንሆም ፥ ገመድ ፡ አደርግብኻለኹ ፥ የምትከበብበትንም ፡ ወራት ፡ እስክትፈጽም ፡ ድረስ ፡ ከጐድን ፡ ጐድንኽ ፡ አትገላበጥም ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 9 ፤ አንተም ፡ ስንዴንና ፡ ገብስን ፥ ባቄላንና ፡ ምስርን ፥ ጤፍንና ፡ ዐጃን ፡ ወዳንተ ፡ ውሰድ ፥ ባንድ ፡ ዕቃም ፡ ውስጥ ፡ አድርገኽ ፡ እንጀራ ፡ ጋግር ፤ በጐድንኽ ፡ እንደ ፡ ተኛኽበት ፡ ቀን ፡ ቍጥር ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ቀን ፡ ትበላዋለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 10 ፤ የምትበላውም ፡ በሚዛን ፡ በየቀኑ ፡ ኻያ ፡ ኻያ ፡ ሰቅል ፡ ይኹን ፥ በየጊዜው ፡ ትበላዋለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 11 ፤ ውሃውንም ፡ በልክ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ከስድስት ፡ እጅ ፡ አንድን ፡ እጅ ፡ ትጠጣለኽ ፥ በየጊዜው ፡ ትጠጣዋለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 12 ፤ እንደ ፡ ገብስ ፡ ዕንጐቻም ፡ አድርገኽ ፡ ትበላዋለኽ ፥ ከሰውም ፡ በሚወጣ ፡ ፋንድያ ፡ በፊታቸው ፡ ትጋግረዋለኽ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ እንዲሁ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እነርሱን ፡ በምበትንባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ርኩስ ፡ እንጀራቸውን ፡ ይበላሉ ፡ አለ ።

ሕዝ. ፥ 4 ፥ 14 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ እንሆ ፥ ሰውነቴ ፡ አልረከሰችም ፤ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ጥንብና ፡ አውሬ ፡ የሰበረውን ፡ ከቶ ፡ አልበላኹም ፥ ርኩስም ፡ ሥጋ ፡ በአፌ ፡ ውስጥ ፡ አልገባም ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ በሰው ፡ ፋንድያ ፡ ፋንታ ፡ ኮበት ፡ ሰጥቼኻለኹ ፡ በርሱም ፡ እንጀራኽን ፡ ትጋግራለኽ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የኢየሩሳሌምን ፡ እንጀራ ፡ በትር ፡ እሰብራለኹ ፥ እየፈሩም ፡ እንጀራን ፡ በሚዛን ፡ ይበላሉ ፥ እየደነገጡም ፡ ውሃን ፡ በልክ ፡ ይጠጣሉ ፤

ሕዝ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ይህም ፡ እንጀራንና ፡ ውሃን ፡ እንዲያጡ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ እንዲደነቁ ፥ በኀጢአታቸውም ፡ እንዲሰለስሉ ፡ ነው ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የተሳለን ፡ ጐራዴ ፡ ውሰድ ፥ እንደ ፡ ጢም ፡ መላጫ ፡ ወዳንተ ፡ ትወስደዋለኽ ፥ ራስኽንና ፡ ጢምኽንም ፡ ትላጭበታለኽ ፤ ሚዛንንም ፡ ውሰድ ፡ ጠጕሩንም ፡ ትከፋፍላለኽ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ የመከበብም ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በከተማዪቱ ፡ መካከል ፡ ሚሶውን ፡ በእሳት ፡ ታቃጥላለኽ ፤ ሚሶውንም ፡ ወስደኽ ፡ ዙሪያውን ፡ በጐራዴ ፡ ትመታለኽ ፥ ሚሶውንም ፡ ወደ ፡ ነፋስ ፡ ትበትናለኽ ፡ እኔም ፡ በኋላቸው ፡ ጐራዴ ፡ እመዛለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ከዚያም ፡ በጥቂቱ ፡ ውሰድ ፥ በመጐናጸፊያኽም ፡ ጫፍ ፡ ቋጥራቸው ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወስደኽ ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ትጥላለኽ ፡ በእሳትም ፡ ታቃጥላቸዋለኽ ፤ ከዚያም ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ትወጣለች ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህች ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ አድርጌያታለኹ ፥ አገሮችም ፡ በዙሪያዋ ፡ አሉ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ርሷም ፡ ከአሕዛብ ፡ ይልቅ ፡ ፍርዴን ፡ በኀጢአት ፡ ለወጠች ፡ በዙሪያዋም ፡ ካሉ ፡ አገሮች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ትእዛዜን ፡ ተላለፈች ፤ ፍርዴን ፡ ጥለዋልና ፥ በትእዛዜም ፡ አልኼዱምና ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዙሪያችኹ ፡ ላሉት ፡ አሕዛብ ፡ ሰበብ ፡ ኾናችኋልና ፥ በትእዛዜም ፡ አልኼዳችኹምና ፥ ፍርዴንም ፡ አልጠበቃችኹምና ፥ በዙሪያችኹም ፡ እንዳሉ ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ፍርድ ፡ እንኳ ፡ አላደረጋችኹምና ፡

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ራሴ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ አሕዛብም ፡ እያዩ ፥ ፍርድን ፡ በመካከልሽ ፡ አደርጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ ርኵሰትሽም ፡ ኹሉ ፡ ያልሠራኹትን ፥ ርሱንም ፡ የሚመስል ፡ ደግሞ ፡ የማልሠራውን ፥ ነገር ፡ እሠራብሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ በመካከልሽ ፡ አባቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ይበላሉ ፥ ልጆችም ፡ አባቶቻቸውን ፡ ይበላሉ ፤ ፍርድንም ፡ አደርግብሻለኹ ፥ ከአንቺም ፡ የቀረውን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ኹሉ ፡ እበትናለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በእድፍሽና ፡ በርኵሰትሽ ፡ መቅደሴን ፡ ስላረከሽ ፥ ስለዚህ ፡ በእውነት ፡ እኔ ፡ አሳንስሻለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ዐይኔም ፡ አይራራም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ከአንቺም ፡ ሚሶው ፡ በቸነፈር ፡ ይሞታል ፥ በመካከልሽም ፡ በራብ ፡ ያልቃል ፤ ሚሶውም ፡ በዙሪያሽ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ፤ ሚሶውንም ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ኹሉ ፡ እበትናለኹ ፡ በኋላቸውም ፡ ሰይፍ ፡ እመዛለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ቍጣዬም ፡ ይፈጸማል ፡ መዓቴንም ፡ እጨርሳለኹ ፡ እጽናናማለኹ ፥ መዓቴንም ፡

በፈጸምኹባቸው ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅንአቴ ፡ እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በዙሪያሽም ፡ ባሉ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ በሚያልፉም ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ባድማና ፡ መሰደቢያ ፡ አደርግሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ በቀኑጣና ፡ በመዓት ፡ በመዓትም ፡ ዘለፋ ፡ ፍርድን ፡ ባደረግኹብሽ ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያሽ ፡ ላሉ ፡ አሕዛብ ፡ መሰደቢያና ፡ መተረቻ ፡ ተግሣጽና ፡ መደነቂያ ፡ ይኾናል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ተናግሬያለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ለማጥፋትም ፡ የኾነውን ፡ አጠፋችኹም ፡ ዘንድ ፡ የምሰደውን ፡ የራብ ፡ ፍላጻ ፡ በላያችኹ ፡ በሰደድኹ ፡ ጊዜ ፡ ራብን ፡ እጨምርባችኋለኹ ፡ የእንጀራችኹንም ፡ በትር ፡ እሰብራለኹ ።

ሕዝ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ራብንና ፡ ክፉዎችን ፡ አራዊት ፡ እሰድባችኋለኹ ፡ ልጆቻችኹንም ፡ ያጠፋሉ ፤ ቸነፈርና ፡ ደምም ፡ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ያልፋሉ ፤ ሰይፍንም ፡ አመጣብሻለኹ ። እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ተናግሬያለኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡ ፊትኽን ፡ ወደእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ አቅና ፡ ትንቢትም ፡ ተናገርባቸው ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ የእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ሆይ ፡ የጌታን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለተራራዎችና ፡ ለኰረብታዎች ፡ ለምንጮችና ፡ ለሸለቆዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ እንሆ ፡ እኔ ፡ ሰይፍን ፡ አመጣባችኋለኹ ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎቻችኹንም ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ መሠዊያዎቻችኹም ፡ ይፈርሳሉ ፡ የፀሓይም ፡ ምስሎቻችኹ ፡ ይሰበራሉ ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎቻችኹን ፡ በጣዖቶቻችኹ ፡ ፊት ፡ እጥላለኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ የእስራኤልንም ፡ ልጆች ፡ ሬሳዎች ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ ፊት ፡ አኖራለኹ ፡ ዐጥንቶቻችኹንም ፡ በመሠዊያዎቻችኹ ፡ ዙሪያ ፡ እበትናለኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በምትኖሩበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ከተማዎቹ ፡ ይፈርሳሉ ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎችም ፡ ኹሉ ፡ ውድማ ፡ ይኾናሉ ፡ መሠዊያዎቻችኹም ፡ ይፈርሳሉ ፡ ባድማም ፡ ይኾናሉ ፡ ጣዖቶቻችኹም ፡ ይሰበራሉ ፡ ያልቃሉም ፡ የፀሓይም ፡ ምስሎቻችኹ ፡ ይቈረጣሉ ፡ ሥራችኹም ፡ ይሻራል ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱት ፡ በመካከላችኹ ፡ ይወድቃሉ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በአገሮች ፡ በተበተናችኹ ፡ ጊዜ ፡ ከሰይፍ ፡ ያመለጡትን ፡ ቅሬታ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አስቀርላችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ከእናንተም ፡ የዳኑት ፡ ከእኔ ፡ በራቀው ፡ በአመንዝራ ፡ ልባቸውና ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ በተከተሉ ፡ በአመንዝራ ፡ ዐይኖቻቸው ፡ የተሰበርኹትን ፡ እኔን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ በተማረኩት ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኾነው ፡ ያስቡኛል ፤ በርኵሰታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ስላደረጉት ፡ ክፋት ፡ ራሳቸውን ፡ ይጸየፋሉ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፤ ይህን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ መናገሬ ፡ በከንቱ ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእጅኽ ፡ አጨብጭብ ፡ በእግርኽም ፡ አሸብሽብ ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ በሰይፍና ፡ በራብ ፡ በቸነፈርም ፡ ይወድቃሉና ፡ ስለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ አስጸያፊ ፡ ሥራዎቻቸው ፡

ኹሉ ፡ ወዮ! ፡

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ በሩቅ ፡ ያለው ፡ በቸነፈር ፡ ይሞታል ፥ በቅርብም ፡ ያለው ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ፥ የቀረውና ፡ የዳነውም ፡ በራብ ፡ ይሞታል ፤ እንዲሁ ፡ መዓቴን ፡ እፈጽምባቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ተወግተውም ፡ የሞቱ ፡ ሰዎቻቸው ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ መካከልና ፡ በመሠዊያዎቻቸው ፡ ዙሪያ ፥ ለጣዖቶቻቸው ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ ባቀረቡበት ፡ ስፍራ ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ ኮረብታ ፡ ኹሉ ፡ በተራራዎችም ፡ ራስ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፥ ከለመለመውም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ቅጠሉም ፡ ከበዛ ፡ ከአድባር ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ በኾኑ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ እጄንም ፡ እዘረጋባቸዋለኹ ፥ በሚኖሩበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ምድሪቱን ፡ ከዴብላታ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይልቅ ፡ ውድማና ፡ በረሓ ፡ አደርጋታለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእስራኤል ፡ ምድር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፍጻሜ ፥ በምድሪቱ ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ ላይ ፡ ፍጻሜ ፡ ደርሷል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ አኹን ፡ ፍጻሜ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነው ፥ ቍጣዬንም ፡ እሰድ፡ብሻለኹ ፥ እንደ ፡ መንገድሽም ፡ መጠን ፡ እፈርድብሻለኹ ፥ ጕስቍልናሽንም ፡ ኹሉ ፡ አመጣብሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ዐይኔም ፡ አይራራልሽም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ፤ መንገድሽንም ፡ አመጣብሻለኹ ፡ ርኵሰትሽም ፡ በመካከልሽ ፡ ይኾናል ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ክፉ ፡ ነገር ፥ አንድ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ፍጻሜ ፡ መጥቷል ፥ ፍጻሜ ፡ መጥቷል ፥ ነቅቶብሻል ፤ እንሆ ፥ ደርሷል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ በምድር ፡ የምትቀመጥ ፡ ሆይ ፥ ተራኽ ፡ ደርሷል ፥ ጊዜ ፡ መጥቷል ፥ ቀን ፡ ቀርቧል ፤ የሽብር ፡ ቀን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ እልልታ ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ በቅርብ ፡ መዓቴን ፡ አፈስ፡ብሻለኹ ፥ ቍጣዬንም ፡ እፈጽም፡ብሻለኹ ፥ እንደ ፡ መንገድሽም ፡ መጠን ፡ እፈርድብሻለኹ ፥ ጕስቍልናሽንም ፡ ኹሉ ፡ አመጣብሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ዐይኔም ፡ አይራራም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ፤ እንደ ፡ መንገድሽም ፡ መጠን ፡ አመጣብሻለኹ ፥ ርኵሰትሽም ፡ በመካከልሽ ፡ ይኾናል ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ የምቀሥፍ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ እንሆ ፥ ቀኑ ፥ እንሆ ፥ መጥቷል ፤ ተራኽ ፡ ወጥቷል ፤ በትር ፡ አብቧል ፥ ትዕቢትም ፡ አጀፍጅፏል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ግፍ ፡ ወደክፋት ፡ በትር ፡ ተነሥቷል ፤ ከነርሱና ፡ ከብዛታቸው ፡ ከሀብታቸውም ፡ ምንም ፡ አይቀርም ፥ የሚያለቅስላቸውም ፡ የለም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ጊዜው ፡ መጥቷል ፥ ቀኑ ፡ ቀርቧል ፤ መዓት ፡ በብዙዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ የሚገዛ ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ የሚሸጥም ፡ አያልቅስ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ የሚሸጥ ፡ ወደሸጠው ፡ ነገር ፡ አይመለስም ፥ ሰውም ፡ በነፍሱ ፡ ኀጢአት ፡ አይጸናም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ መለከቱን ፡ ነፍተዋል ፡ ኹሉንም ፡ አዘጋጅተዋል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ መዓቴ ፡ በብዙዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ሰልፍ ፡ የሚኼድ ፡ የለም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ሰይፍ ፡ በውጭ ፡ ቸነፈርና ፡ ራብ ፡ በውስጥ ፡ አለ ፤ በሜዳ ፡ ያለው ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታል ፥ በከተማም ፡ ያለውን ፡ ቸነፈርና ፡ ራብ ፡ ይፈጁታል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ከነርሱም ፡ የሚሸሹ ፡ ይድናሉ ፡ በተራራም ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ፤ እኔም ፡ በኀጢአታቸው ፡ ኹሉን ፡ እገድላለኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እጅ ፡ ኹሉ ፡ ትደክማለች ፡ ጕልበትም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ትቀልጣለች ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ማቅም ፡ ይለብሳሉ ፥ ድንጋጤም ፡ ይሸፍናቸዋል ፤ በፊትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዕፍረት ፡ ይኾናል ፥ ራሳቸውንም ፡ ኹሉ ፡ ይነጨሉታል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ብራቸውን ፡ በጐዳናዎቹ ፡ ላይ ፡ ይጥላሉ ፡ ወርቃቸውም ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይኾናል ፤ በእግዚአብሔር ፡ መዓት ፡ ቀን ፡ ብራቸውና ፡ ወርቃቸው ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ። ርሱ ፡ የኀጢአታቸው ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾኗልና ፥ ሰውነታቸውን ፡ አያጠግቡም ፥ ሆዳቸውንም ፡ አይሞሉም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ የክብሩንም ፡ ጌጥ ፡ ወደ ፡ ትዕቢት ፡ ለወጡ ፥ የርኩስነታቸውንም ፡ ምስሎች ፡ አደረጉባት ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ርኩስ ፡ አድርጌያታለኹ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በባዕድም ፡ እጅ ፡ ለንጥቂያ ፥ በምድር ፡ ኀጢአተኞችም ፡ እጅ ፡ ለብዝበዛ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣታለኹ ፤ እነርሱም ፡ ያረክሷታል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ፊቴን ፡ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ እመልሳለኹ ፥ ምስጢሬንም ፡ ያረክሳሉ ፤ ወንበዴዎችም ፡ ይገቡባታል ፡ ያረክሷትማል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ምድር ፡ ደም ፡ ባመጣው ፡ በደል ፥ ከተማም ፡ በግፍ ፡ ተሞልታለችና ፡ ሰንሰለት ፡ ሥራ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ከአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ከኹሉ ፡ የሚከፉትን ፡ አመጣለኹ ፡ ቤቶቻቸውንም ፡ ይወርሳሉ ፤ የኀያላንንም ፡ ትዕቢት ፡ አጠፋለኹ ፥ መቅደሶቻቸውም ፡ ይረክሳሉ ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ጥፋት ፡ መጥቷል ፤ ሰላምም ፡ ይሻሉ ፡ ርሱም ፡ አይገኝም ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ድንጋጤ ፡ በድንጋጤ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፥ ወሬም ፡ ወሬውን ፡ ይከተላል ፥ ከነቢዩም ፡ ዘንድ ፡ ራዕይን ፡ ይሻሉ ፤ ከካህኑም ፡ ዘንድ ፡ ትምህርት ፥ ከሽማግሌዎችም ፡ ዘንድ ፡ ምክር ፡ ይጠፋል ።

ሕዝ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ንጉሡም ፡ ያለቅሳል ፥ አለቃም ፡ ውርደትን ፡ ይለብሳል ፥ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ እጅ ፡ ትንቀጠቀጣለች ፤ እንደ ፡ መንገዳቸውም ፡ መጠን ፡ አደርግባቸዋለኹ ፥ በፍርዳቸውም ፡ መጠን ፡ እፈርድባቸዋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በስድስተኛውም ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በቤቴ ፡ ተቀምጬ ፡ ሳለኹ ፡ የይሁዳም ፡ ሽማግሌዎች ፡ በፊቴ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፥ በዚያ ፡ የጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በላዬ ፡ ወደቀች ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ እኔም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ እንደ ፡ እሳት ፡ የሚመስል ፡ አምሳያ ፡ ነበረ ፤ ከወገቡም ፡ ምሳሌ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ እሳት ፡ ነበረ ፥ ከወገቡም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጸዳል ፡ ምሳሌ ፥ እንደሚብለጨለጭም ፡ የወርቅ ፡ ምሳሌ ፡

ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ እጅ ፡ መሳይንም ፡ ዘረጋ ፡ በራስ ፡ ጠጕሬም ፡ ያዘኝ ፤ መንፈስም ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ አነሣኝ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ራእይ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወደሚመለከተው ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አመጣኝ ፤ በዚያም ፡ ቅንአት ፡ የሚያነሣሣ ፡ የቅንአት ፡ ጣዖት ፡ ተተክሎ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እንሆም ፥ በቈላው ፡ እንዳየኹት ፡ ራእይ ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ በዚያ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ዐይንኽን ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ መንገድ ፡ አንሣ ፡ አለኝ ። ዐይኔንም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ መንገድ ፡ አነሣኹ ፤ እንሆም ፥ በመሠዊያው ፡ በር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ በመግቢያው ፡ ይህ ፡ የቅንአት ፡ ጣዖት ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የሚያደርጉትን ፥ ከመቅደሴ ፡ ያርቁኝ ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ታላቁን ፡ ርኵሰት ፡ ታያለኽን ፧ ደግሞም ፡ ተመልሰኽ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ታላቅ ፡ ርኵሰት ፡ ታያለኽ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ወዳደባባዩም ፡ መግቢያ ፡ አመጣኝ ፤ ባየኹም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በግንቡ ፡ ውስጥ ፡ ፉካ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ግንቡን ፡ ንደለው ፡ አለኝ ፤ ግንቡንም ፡ በነደልኹት ፡ ጊዜ ፡ መዝጊያ ፡ አገኘኹ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ ግባ ፥ በዚህም ፡ የሚያደርጉትን ፡ ክፉውን ፡ ርኵሰት ፡ እይ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ እኔም ፡ ገባኹና ፥ እንሆ ፥ በግንቡ ፡ ዙሪያ ፡ ላይ ፡ የተንቀሳቃሾችና ፡ የርኩሳን ፡ አራዊት ፡ ምሳሌ ፡ የእስራኤልንም ፡ ቤት ፡ ጣዖታት ፡ ኹሉ ፡ ተስለው ፡ አየኹ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ በፊታቸውም ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሰባ ፡ ሰዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ በመካከላቸውም ፡ የሳፋን ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በእጁ ፡ ጥናውን ፡ ይዞ ፡ ነበር ፥ የዕጣኑም ፡ ጢስ ፡ ሽቱ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሽማግሌዎች ፡ በጨለማ ፡ እያንዳንዱ ፡ በሥዕሉ ፡ ቤት ፡ የሚያደርጉትን ፡ አይተኻልን ፧ እነርሱ ፦ እግዚአብሔር ፡ አያየንም ፤ እግዚአብሔር ፡ ምድሪቱን ፡ ትቷታል ፡ ይላሉና ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ርሱም ፦ ደግሞ ፡ ተመልሰኽ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠውን ፡ የሚያደርጉትን ፡ ታላቅ ፡ ርኵሰት ፡ ታያለኽ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ወደሚመለከተው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ አመጣኝ ፤ እንሆም ፥ ሴቶች ፡ ለተሙዝ ፡ እያለቀሱ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አይተኻልን ፧ ደግሞ ፡ ተመልሰኽ ፡ ከዚህ ፡ የበለጠ ፡ ርኵሰት ፡ ታያለኽ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ አመጣኝ ፥ እንሆም ፥ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መግቢያ ፡ ፊት ፡ በወለሉና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ዠርባቸውም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ፊታቸውም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ለፀሓይ ፡ ይሰግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አይተኻልን ፧ በዚህ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ ነውን ፧ ምድሪቱን ፡ በግፍ ፡ ሞልተዋታል ፡ ያስቈጡኝም ፡ ዘንድ ፡ ተመልሰዋል ፤ እንሆም ፥ ቅርንጫፉን ፡ ወደ ፡ አፍንጫው ፡ አቅርበዋል ።

ሕዝ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በመዓት ፡ እሠራለኹ ፤ ዐይኔ ፡ አይራራም ፡ እኔም ፡ አላዝንም ፤ ወደ ፡ ጕሮሮም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ቢጮኹ ፡ አልሰማቸውም ፡ አለኝ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ርሱም ፦ እያንዳንዳቸው ፡ የሚያጠፋ ፡ መሣሪያን ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ከተማዪቱን ፡ የሚቀሥፉ ፡ ይቅረቡ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ በጕሮሮ ፡ ጮኸ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ እያንዳንዳቸው ፡ አጥፊውን ፡ መሣሪያ ፡ በእጃቸው ፡ ይዘው ፡ ስድስት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ከሚመለከተው ፡ ከላይኛው ፡ በር ፡ መንገድ ፡ መጡ ፤ በመካከላቸውም ፡ የበፍታ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ የጸሓፊም ፡ ቀለም ፡ ቀንድ ፡ በወገቡ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እነርሱም ፡ ገብተው ፡ በናሱ ፡ መሠዊያ ፡ አጠገብ ፡ ቆሙ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ በበላዩ ፡ ከነበረበት ፡ ኪሩብ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደቤቱ ፡ መድረክ ፡ ኼዶ ፡ ነበር ፤ በፍታም ፡ የለበሰውን ፡ የጸሓፊውንም ፡ ቀለም ፡ ቀንድ ፡ በወገቡ ፡ የያዘውን ፡ ሰው ፡ ጠራ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በከተማዪቱ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መካከል ፡ ዕለፍ ፥ በመካከሏም ፡ ስለ ፡ ተሠራው ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ በሚያለቅሱና ፡ በሚተክዙ ፡ ሰዎች ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ ምልክት ፡ ጻፍ ፡ አለው ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ እኔም ፡ እየሰማኹ ፡ ለሌላዎቹ ፦ ርሱን ፡ ተከትላችኹ ፡ በከተማዪቱ ፡ መካከል ፡ ዕለፉ ፡ ግደሉም ፤ ዐይናችኹ ፡ አይራራ ፥ አትዘኑም ፤

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ሽማግሌውንና ፡ ጐበዙን ፡ ቈንጕዶቹንም ፡ ሕፃናቶቹንና ፡ ሴቶቹን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ግደሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምልክቱ ፡ ወዳለበት ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ አትቅረቡ ፤ በመቅደሴም ፡ ጕምሩ ፡ አላቸው ። በቤቱም ፡ አንጻር ፡ ባሉ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጕመሩ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ርሱም ፦ ቤቱን ፡ አርክሱ ፥ በተገደሉትም ፡ ሰዎች ፡ አደባባዮችን ፡ ሙሉ ፤ ውጡ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ወጥተው ፡ በከተማዪቱ ፡ ገደሉ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ሲገድሉም ፡ እኔ ፡ ብቻዬን ፡ ቀርቼ ፡ ሳለኹ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፍቼ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ መዓትኽን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ስታፈስ ፡ የእስራኤልን ፡ ቅሬታ ፡ ኹሉ ፡ ታጠፋለኽን ፧ ብዬ ፡ ጮኽኹ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ የእስራኤልና ፡ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ እጅግ ፡ በዝቷል ፡ ምድሪቱም ፡ ደም ፤ ከተማዪቱም ፡ ዐመፅን ፡ ተሞልታለች ፤ እነርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ ምድሪቱን ፡ ትቷታል ፡ እግዚአብሔርም ፡ አያይም ፡ ብለዋል ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በዐይኔ ፡ አልራራም ፡ አላዝንምም ፥ መንገዳቸውንም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ እንሆም ፥ በፍታ ፡ የለበሰው ፡ የቀለም ፡ ቀንድም ፡ በወገቡ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፦ ያዘዝኸኝን ፡ አድርጌያለኹ ፡ ብሎ ፡ በቃሉ ፡ መለሰ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ እኔም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ በኪሩቤል ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ጠፈር ፡ በላያቸው ፡ እንደ ፡ ሰንፔር ፡ ድንጋይ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ዙፋን ፡ የሚመስል ፡ መልክ ፡ ተገለጠ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በፍታም ፡ የለበሰውን ፡ ሰው ፦ በመንኰራኵሮች ፡ መካከል ፡ ከኪሩብ ፡ በታች ፡ ግባ ፥ ከኪሩቤልም ፡ መካከል ፡ ካለው ፡ እሳት ፡ ፍም ፡ እጆችኽን ፡ ሙላ ፦ በከተማዪቱም ፡ ላይ ፡ በትናት ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ። እኔም ፡ እያየኹ ፡ ገባ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ሰውዬውም ፡ ሲገባ ፡ ኪሩቤል ፡ በቤቱ ፡ ቀኝ ፡ በኩል ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ ደመናውም ፡ ውስጠኛውን ፡ አደባባይ ፡ ሞላ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ክብርም ፡ ከኪሩቤል ፡ ወጥቶ ፡ በቤቱ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ቆመ ፤ ቤቱም ፡ በደመናው ፡ ተሞላ ፥ አደባባዩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ጸዳል ፡ ተሞላ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ኹሉንም ፡ የሚችል ፡ አምላክ ፡ እንደሚናገረው ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ እንዲሁ ፡ የኪሩቤል ፡ ክንፎች ፡ ድምፅ ፡ እስከ ፡ ውጭው ፡ አደባባይ ፡ ድረስ ፡ ተሰማ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ በፍታም ፡ የለበሰውን ፡ ሰው ፦ ከመንኰራኵሮች ፡ ከኪሩቤል ፡ መካከል ፡ እሳት ፡ ውሰድ ፡ ብሎ ፡ ባዘዘው ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ገብቶ ፡ ባንድ ፡ መንኰራኵር ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ኪሩብም ፡ ከኪሩቤል ፡ መካከል ፡ እጁን ፡ በኪሩቤል ፡ መካከል ፡ ወዳለው ፡ እሳት ፡ ዘርግቶ ፡ ከዚያ ፡ ወሰደ ፥ በፍታም ፡ በለበሰው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ አኖረው ፤ ርሱም ፡ ይዞ ፡ ወጣ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ በኪሩቤልም ፡ ከክንፎቻቸው ፡ በታች ፡ የሰው ፡ እጅን ፡ መሳይ ፡ ታየ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ እኔም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ በኪሩቤል ፡ አጠገብ ፡ አራት ፡ መንኰራኵሮች ፡ ነበሩ ፤ አንዱ ፡ መንኰራኵር ፡ በአንዱ ፡ ኪሩብ ፥ አንዱ ፡ መንኰራኵር ፡ በአንዱ ፡ ኪሩብ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ። የመንኰራኵሮቹም ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ቢረሌ ፡ ድንጋይ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ የአራቱም ፡ መልክ ፡ አንድ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፥ መልካቸውም ፡ በመንኰራኵር ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ መንኰራኵር ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ሲኼዱም ፡ በአራቱ ፡ ጐድናቸው ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፥ ሲኼዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ፥ ራሱ ፡ ወደምታመለክትበት ፡ ስፍራ ፡ ወደዚያ ፡ ይከተሉ ፡ ነበር ፤ ሲኼዱም ፡ አይገላመጡም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ገላቸውም ፡ ኹሉ ፣ ዠርባቸውም ፣ እጃቸውም ፣ ክንፋቸውም ፣ መንኰራኵሮቹም ፥ ለአራቱ ፡ የነበሩ ፡ መንኰራኵሮች ፥ በዙሪያቸው ፡ ዐይኖች ፡ ተሞልተው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ መንኰራኵሮችም ፡ እኔ ፡ እየሰማኹ ፡ ጌልጌል ፡ ተብለው ፡ ተጠሩ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ለያንዳንዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ፊት ፡ ነበሩት ፤ አንደኛው ፡ ፊት ፡ የኪሩብ ፡ ፊት ፥ ኹለተኛውም ፡ የሰው ፡ ፊት ፥ ሦስተኛው ፡ የአንበሳ ፡ ፊት ፥ አራተኛውም ፡ የንስር ፡ ፊት ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ ኪሩቤልም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ፤ ይህ ፡ በኮቦር ፡ ወንዝ ፡ ያየኹት ፡ እንስሳ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ኪሩቤልም ፡ ሲኼዱ ፡ መንኰራኵሮቹ ፡ በአጠገባቸው ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤ ኪሩቤልም ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ሲዘረጉ ፡ መንኰራኵሮች ፡ ደግሞ ፡ ከአጠገባቸው ፡ ፈቀቅ ፡ አይሉም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ሕይወት ፡ ያላቸው ፡ የእንስሳዎች ፡ መንፈስ ፡ በመንኰራኵሮች ፡ ውስጥ ፡ ነበረና ፡ እነዚህ ፡ ሲቆሙ ፡ እነዚያ ፡ ይቆሙ ፡ ነበር ፥ እነዚህም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ሲሉ ፡ እነዚያ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ከቤቱ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ወጥቶ ፡ በኪሩቤል ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ሕዝ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘረጉ ፡ እኔም ፡ እያየኹ ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አሉ ፤ በወጡም ፡

ጊዜ ፡ መንኰራኵሮች ፡ በአጠገባቸው ፡ ነበሩ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ በምሥራቁ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡
ቆሙ ፥ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 10 ፥ 20 ፤ ይህ ፡ በኮበር ፡ ወንዝ ፡ ከእስራኤል ፡ አምላክ ፡ በታች ፡ ያየኹት ፡ እንስሳ ፡ ነው ፥ ኪሩቤልም ፡
እንደ ፡ ነበሩ ፡ አስተዋልኹ ።

ሕዝ. ፥ 10 ፥ 21 ፤ ለያንዳንዱ ፡ አራት ፡ አራት ፡ ፊት ፥ ለያንዳንዱም ፡ አራት ፡ አራት ፡ ክንፍ ፡ ነበሩት ፥ የሰውም ፡
እጅ ፡ አምሳያ ፡ ከክንፎቻቸው ፡ በታች ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 10 ፥ 22 ፤ ፊቶቻቸውም ፡ በኮቦር ፡ ወንዝ ፡ ያየኋቸውን ፡ ፊቶች ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ፤ እነርሱና ፡
መልካቸውም ፡ እንዲሁ ፡ ነበረ ፤ እያንዳንዱም ፡ አቅንቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይኼድ ፡ ነበር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ መንፈስም ፡ አነሣኝ ፤ ወደፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ወደሚመለከት ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤትም ፡
ወደምሥራቁ ፡ በር ፡ አመጣኝ ። እንሆም ፥ በበሩ ፡ መግቢያ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፥ በመካከላቸውም ፡
የሕዝቡን ፡ አለቃዎች ፡ የዓዙርን ፡ ልጅ ፡ ያእዛንያንና ፡ የበናያስ ፡ ልጅ ፡ ፈላጥያን ፡ አየኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ክፋትን ፡ የሚያስቡ ፡ በዚችም ፡
ከተማ ፡ ክፉን ፡ ምክር ፡ የሚመክሩ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ እነርሱም ፦ በእውኑ ፡ ቤቶችን ፡ የምንሠራበት ፡ ዘመን ፡ የቀረበ ፡ አይደለምን ፧ ይህች ፡ ከተማ ፡
ድስት ፡ እኛም ፡ ሥጋ ፡ ነን ፡ ብለዋል ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ ስለዚህ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ ተናገርባቸው ፤ ትንቢት ፡ ተናገር ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ወደቀብኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡
ብለኽ ፡ ተናገር ። የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናግራችኋል ፥ እኔም ፡ የልባችኹን ፡ ዐሳብ ፡ ዐውቃለኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ በዚች ፡ ከተማ ፡ ውስጥ ፡ ግዳዮቻችኹን ፡ አብዝታችኋል ፥ በጐዳናዎቿም ፡ ግዳዮችን ፡
ሞልታችኋል ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመካከሏ ፡ ያኖራችኋቸው ፡ ግዳዮቻችኹ ፡
እነርሱ ፡ ሥጋው ፡ ናቸው ፥ ይህችም ፡ ከተማ ፡ ድስቱ ፡ ናት ፤ እናንተን ፡ ግን ፡ ከመካከሏ ፡ አወጣችኋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ ሰይፍን ፡ ፈርታችኋል ፡ እኔም ፡ ሰይፍን ፡ አመጣባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 9 ፤ ከመካከሏም ፡ አወጣችኋለኹ ፥ በእንግዳዎችም ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣችኋለኹ ፥ በላያችኹም ፡
ፍርድ ፡ አደርጋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 10 ፤ በሰይፍ ፡ ትወድቃላችኹ ፡ በእስራኤልም ፡ ድንበር ፡ እፈርድባችኋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡
እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 11 ፤ ይህች ፡ ከተማ ፡ ድስት ፡ አትኾንላችኹም ፡ እናንተም ፡ በመካከሏ ፡ ሥጋ ፡ አትኾኑም ፥ እኔም ፡
በእስራኤል ፡ ድንበር ፡ እፈርድባችኋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 12 ፤ በትእዛዜ ፡ አልኼዳችኹምና ፥ ፍርዴንም ፡ አላደረጋችኹምና ፤ በዙሪያችኹም ፡ እንደሚኖሩት ፡
እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ሕግ ፡ አድርጋችኋል ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 13 ፤ ትንቢትም ፡ በተናገርኹ ፡ ጊዜ ፡ የበናያስ ፡ ልጅ ፡ ፈላጥያ ፡ ሞተ ፤ እኔም ፡ በግንባሬ ፡

ተደፍቼ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ በእውኑ ፡ የእስራኤልን ፡ ቅሬታ ፡ ፈጽመኽ ፡ ታጠፋለኽን ፧ ብዬ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኽኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 14 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 15 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ራቁ ፤ ይህች ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ ኾና ፡ ለእኛ ፡ ተሰጥታለች ፡ የሚሏቸው ፡ ወንድሞችኽና ፡ ዘመዶችኽ ፡ የወገኖችኽም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 16 ፤ ስለዚህ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አርቄያቸዋለኹ ፥ ወደ ፡ አገሮችም ፡ በትኛቸዋለኹ ፤ ይኹን ፡ እንጂ ፥ በመጡባቸው ፡ አገሮች ፡ በእነዚያ ፡ ትንሽ ፡ መቅደስ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡ በል ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 17 ፤ ስለዚህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ አከማቻችኋለኹ ፡ ከተበተናችኹባቸውም ፡ አገሮች ፡ እሰበስባችኋለኹ ፥ የእስራኤልንም ፡ ምድር ፡ እሰጣችኋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 18 ፤ ወደዚያም ፡ ይመጣሉ ፥ ጸያፉንና ፡ ርኩሱንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከርሷ ፡ ያወጣሉ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 19 ፤ 20 ፤ በትእዛዜም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ፍርዴንም ፡ ይጠብቁና ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ በውስጣቸውም ፡ ዐዲስ ፡ መንፈስ ፡ እሰጣለኹ ፥ ከሥጋቸውም ፡ ውስጥ ፡ የድንጋዩን ፡ ልብ ፡ አወጣለኹ ፡ የሥጋንም ፡ ልብ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 21 ፤ ልባቸውም ፡ ጸያፍንና ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ በሚከተል ፡ በእነርሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ መንገዳቸውን ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 22 ፤ ኪሩቤልም ፡ ክንፎቻቸውን ፡ ዘረጉ ፥ መንኰራኵሮችም ፡ በአጠገባቸው ፡ ነበሩ ፤ የእስራኤልም ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 23 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ከከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ተነሥቶ ፡ በከተማዪቱ ፡ ምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 24 ፤ መንፈስም ፡ አነሣኝ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ በራእይ ፡ ወደከላውዴዎን ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ምርኮኞቹ ፡ አመጣኝ ። ያየኹትም ፡ ራእይ ፡ ከእኔ ፡ ወጥቶ ፡ ተለየ ።

ሕዝ. ፥ 11 ፥ 25 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያሳየኝን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለምርኮኞች ፡ ተናገርኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ተቀምጠኻል ፤ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ዐይን ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ አያዩም ፥ ይሰሙም ፡ ዘንድ ፡ ጐሮ ፡ አላቸው ፡ እነርሱም ፡ አይሰሙም ፤ እነርሱ ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ናቸውና ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 3 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የስደተኛ ፡ እክት ፡ አዘጋጅ ፡ በፊታቸውም ፡ ቀን ፡ ለቀን ፡ ተማረክ ፥ በፊታቸውም ፡ ከስፍራ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ተማርከኽ ፡ ኺድ ፤ እነርሱም ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ምናልባት ፡ ያስተውሉ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 4 ፤ ቀን ፡ ለቀንም ፡ በፊታቸው ፡ እክትኽን ፡ እንደ ፡ ስደተኛ ፡ እክት ፡ አውጣው ፥ በማታም ፡ ጊዜ ፡ በፊታቸው ፡ ስደተኞች ፡ እንደሚወጡ ፡ እንዲሁ ፡ ውጣ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ በፊታቸውም ፡ ግንቡን ፡ ንደል ፡ በርሱም ፡ አውጣ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ለእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ምልክት ፡ አድርጌ፣ለኹና ፡ በፊታቸው ፡ በጫንቃኽ ፡ ላይ ፡ አንግተው ፥ በጨለማም ፡ ተሸክመኽ ፡ ውጣ ፤ ምድሪቱንም ፡ እንዳታይ ፡ ፊትኽን ፡ ሸፍን ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ እንዳዘዘኝም ፡ አደረግኹ ፤ ቀን ፡ ለቀንም ፡ እክቱን ፡ እንደ ፡ ስደተኛ ፡ እክት ፡ አወጣኹ ፥ በማታም ፡ ጊዜ ፡ ግንቡን ፡ በእጄ ፡ ነደልኹ ፥ በጨለማም ፡ አወጣኹት ፡ በፊታቸውም ፡ በጫንቃዬ ፡ ላይ ፡ አንግቼ ፡ ተሸከምኹት ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ በነጋውም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፦ የምታደርገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላሉኽምን ፧

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ አንተም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህ ፡ ሸክም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በሚኖረው ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ በመካከላቸውም ፡ በሚኖሩት ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነው ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ደግሞም ፦ እኔ ፡ ምልክታችኹ ፡ ነኝ ፤ እኔ ፡ እንዳደረግኹ ፡ እንዲሁ ፡ ይደረግባቸዋል ፥ እነርሱም ፡ በስደት ፡ ወደ ፡ ምርኮ ፡ ይኼዳሉ ፡ በል ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በመካከላቸውም ፡ የሚኖረው ፡ አለቃ ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡ አንግቶ ፡ በጨለማ ፡ ይወጣል ፤ በዚያ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ ግንቡን ፡ ይነድላሉ ፥ በዐይኑም ፡ ምድርን ፡ እንዳያይ ፡ ፊቱን ፡ ይሸፍናል ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ መረቤንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፡ በወጥመዴም ፡ ይያዛል ፥ ወደከለዳውያንም ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ አመጣዋለኹ ፤ ኾኖም ፡ አያያትም ፡ በዚያም ፡ ይሞታል ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ሊረዱትም ፡ በዙሪያው ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፡ ጭፍራዎቹንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ነፋሳት ፡ ኹሉ ፡ እበትናቸዋለኹ ፤ በኋላቸውም ፡ ሰይፍ ፡ እመዛለኹ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ በበተንኋቸው ፡ ጊዜ ፥ በአገሮችም ፡ በዘራኋቸው ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ በሚኼዱባቸውም ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ርኵሰታቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ከሰይፍና ፡ ከራብ ፡ ከቸነፈርም ፡ ጥቂቶች ፡ ሰዎችን ፡ ከነርሱ ፡ አስቀራለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንጀራኽን ፡ በድንጋጤ ፡ ብላ ፡ ውሃኽንም ፡ በመንቀጥቀጥና ፡ በሐዘን ፡ ጠጣ ፤

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ለምድሪቱም ፡ ሕዝብ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ስለሚኖሩ ፡ ስለእስራኤልም ፡ ምድር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለሚኖሩባት ፡ ኹሉ ፡ ግፍ ፡ ምድሪቱ ፡ ከነሞላዋ ፡ ትጠፋ ፡ ዘንድ ፡ እንጀራቸውን ፡ በችግር ፡ ይበላሉ ፡ ውሃቸውንም ፡ በድንጋጤ ፡ ይጠጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ሰዎች ፡ የሚኖሩባቸው ፡ ከተማዎች ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ፡ ምድሪቱም ፡ ውድማ ፡ ትኾናለች ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእስራኤል ፡ ምድር ፦ ዘመኑ ፡ ረዝሟል ፡ ራእዩም ፡ ኹሉ ፡ ጠፍቷል ፡

የምትሉት ፡ ምሳሌ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 23 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ አስቀረዋለኹ ፡ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ምሳሌ ፡ አድርገው ፡ አይናገሩትም ፤ አንተ ፡ ግን ፦ ዘመኑና ፡ የራእዩ ፡ ኹሉ ፡ ነገር ፡ ቀርቧል ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 24 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ከንቱ ፡ ራእይና ፡ ውሸተኛ ፡ ሟርት ፡ አይኾንም ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 25 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ እናገራለኹ ፡ የምናገረውም ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ፥ ደግሞም ፡ አይዘገይም ፤ እናንተ ፡ ዐመፀኛ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በዘመናችኹ ፡ ቃሌን ፡ እናገራለኹ ፡ እፈጽመውማለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 26 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 27 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፦ ይህች ፡ የሚያያት ፡ ራእይ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ናት ፥ ርሱም ፡ ለሩቅ ፡ ወራት ፡ ትንቢት ፡ ይናገራል ፡ ይላሉ ።

ሕዝ. ፥ 12 ፥ 28 ፤ ስለዚህ ፥ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የምናገረው ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ፡ እንጂ ፡ ከቃሌ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ የሚዘገይ ፡ የለም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ በሚናገሩ ፡ በእስራኤል ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ ከገዛ ፡ ልባቸውም ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩትን ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ በላቸው ፤

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 3 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምንም ፡ ምን ፡ ሳያዩ ፡ የገዛ ፡ መንፈሳቸውን ፡ ለሚከተሉ ፡ ለሰነፎች ፡ ነቢያት ፡ ወዮላቸው! ፡

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 4 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ነቢያትኽ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንደሚኖሩ ፡ ቀበሮዎች ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 5 ፤ ወደተሰበረው ፡ ቅጥር ፡ አልወጣችኹም ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ቀን ፡ በሰልፍ ፡ ትቆሙ ፡ ዘንድ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ቅጥር ፡ አልሠራችኹም ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሳይልካቸው ። እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ከንቱ ፡ ነገርንና ፡ ውሸተኛ ፡ ሟርትን ፡ አይተዋል ፤ ቃሉም ፡ ይጠና ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አስደርገዋል ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 7 ፤ እኔም ፡ ሳልናገር ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፡ ስትሉ ፥ ከንቱ ፡ ራእይን ፡ ያያችኹ ፡ ውሸተኛንም ፡ ሟርት ፡ የተናገራችኹ ፡ አይደላችኹምን ፧

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ስለ ፡ ተናገራችኹ ፥ ውሸተኛ ፡ ራእይንም ፡ ስላያችኹ ፥ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 9 ፤ እጄም ፡ ከንቱ ፡ ራእይን ፡ በሚያዩ ፥ በውሸትም ፡ በሚያሟርቱ ፡ ነቢያት ፡ ላይ ፡ ትኾናለች ፤ እነርሱም ፡ በሕዝቤ ፡ ማኅበር ፡ ውስጥ ፡ አይገኙም ፥ በእስራኤልም ፡ ቤት ፡ መጽሐፍ ፡ አይጻፉም ፥ ወደእስራኤልም ፡ ምድር ፡ አይገቡም ፤ እኔም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 10 ፤ ሰላም ፡ ሳይኖር ፦ ሰላም ፡ እያሉ ፡ ሕዝቤን ፡ አታለዋልና ፤ አንዱም ፡ ሰው ፡ ቅጥር ፡

ሲሠራ ፥ እንሆ ፥ ገለባ ፡ በሌለበት ፡ ጭቃ ፡ ይመርጉታልና ፥

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 11 ፤ ገለባ ፡ በሌለበት ፡ ጭቃ ፡ ለሚመርጉት ፡ ሰዎች ፦ ይወድቃል ፡ በላቸው ። የሚያሰጥም ፡ ዝናብ ፡ ይዘንባል ፥ ታላቅም ፡ የበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ ይወድቃል ፥ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ይሰነጣጥቀዋል ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 12 ፤ እንሆ ፥ ግንቡ ፡ በወደቀ ፡ ጊዜ ፦ የመረጋችኹት ፡ ጭቃ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ አይሏችኹምን ፧

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመዓቴ ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ እሰነጣጥቀዋለኹ ፥ ያጠፋውም ፡ ዘንድ ፡ በቀሥጣዬ ፡ የሚያሰጥም ፡ ዝናብ ፥ በመዓቴም ፡ ታላቅ ፡ የበረዶ ፡ ድንጋይ ፡ ይወርዳል ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 14 ፤ ገለባም ፡ በሌለበት ፡ ጭቃ ፡ የመረጋችኹትን ፡ ቅጥር ፡ አፈርሳለኹ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ እጥለዋለኹ ፥ መሠረቱም ፡ ይታያል ። ርሱም ፡ ይናዳል ፥ በመካከሉም ፡ ትጠፋላችኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 15 ፤ መዓቴንም ፡ በግንቡ ፡ ላይ ፡ ገለባም ፡ በሌለበት ፡ ጭቃ ፡ በመረጉት ፡ ላይ ፡ እፈጽማለኹ ፤ እኔም ፦ ግንቡና ፡ መራጊዎቹ ፡ የሉም ፡ እላችኋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 16 ፤ እነርሱም ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩ ፡ የሰላምን ፡ ራእይ ፡ የሚያዩላት ፡ የእስራኤል ፡ ነቢያት ፡ ናቸው ፥ ሰላምም ፡ የለም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 17 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ከገዛ ፡ ልባቸው ፡ ትንቢት ፡ በሚናገሩ ፡ በሕዝብኽ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ፊትኽን ፡ አድርግ ፤ ትንቢትም ፡ ተናገርባቸው ፥

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 18 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ነፍስን ፡ ለማጥመድ ፥ ለእጅ ፡ ድጋፍ ፡ ኹሉ ፡ መከዳ ፡ ለሚሰፉ ፥ ለሰውም ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ እየቁመቱ ፡ ሽፋን ፡ ለሚሠሩ ፡ ሴቶች ፥ ወዮላቸው! ፡ የሕዝቤንም ፡ ነፍስ ፡ ብታጠምዱ ፡ በእውኑ ፡ ነፍሳችኹን ፡ ታድናላችኹን ፧

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 19 ፤ ውሸታችኹን ፡ ለሚሰሙት ፡ ሕዝቤ ፡ እየዋሻችኹ ፡ ሞት ፡ የማይገባቸውን ፡ ነፍሳት ፡ ትገድሉ ፡ ዘንድ ፡ በሕይወትም ፡ መኖር ፡ የማይገባቸውን ፡ ነፍሳት ፡ በሕይወት ፡ ታኖሩ ፡ ዘንድ ፥ ስለ ፡ ጭብጥ ፡ ገብስና ፡ ስለ ፡ ቍራሽ ፡ እንጀራ ፡ በሕዝቤ ፡ ዘንድ ፡ አርክሳችኹኛል ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 20 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ነፍሳትን ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በምታጠምዱባት ፡ በመከዳችኹ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ከክንዳችኹም ፡ ወስጄ ፡ እቀዳታለኹ ፥ እንደ ፡ ወፍም ፡ የምታጠምዷቸውን ፡ ነፍሳት ፡ እለቃለኹ ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 21 ፤ ሽፋኖቻችኹን ፡ ደግሞ ፡ እቀዳለኹ ፡ ሕዝቤንም ፡ ከእጃችኹ ፡ አድናለኹ ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ በእጃችኹ ፡ ለመታደን ፡ አይኾኑም ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 22 ፤ እኔም ፡ ያላሳዘንኹትን ፡ የጻድቁን ፡ ልብ ፡ በውሸት ፡ አሳዝናችኋልና ፥ በሕይወትም ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ከክፉ ፡ መንገድ ፡ እንዳይመለስ ፡ የኀጢአተኛውን ፡ እጅ ፡ አበርትታችኋልና ፥

ሕዝ. ፥ 13 ፥ 23 ፤ ስለዚህ ፥ ከንቱን ፡ ራእይ ፡ እንግዲህ ፡ አታዩም ፡ ሟርትንም ፡ አታሟርቱም ፥ ሕዝቤንም ፡ ከእጃችኹ ፡ አድናለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ሕዝ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ ከእስራኤልም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥተው ፡ በፊቴ ፡ ተቀመጡ ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ በልባቸው ፡ አኑረዋል ፡ የበደላቸውንም ፡ መቅሠፍት ፡ በፊታቸው ፡ አቁመዋል ፤ እኔስ ፡ ከነርሱ ፡ ልጠየቅን ፧

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 4-5 ፤ ስለዚህ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዅሉም ፡ በጣዖቶቻቸው ፡ ከእኔ ፡ ተለይተዋልና ፥ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ በልባቸው ፡ እይዝ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጣዖቶቹን ፡ በልቡ ፡ የሚያኖር ፥ የበደሉንም ፡ መቅሠፍት ፡ በፊቱ ፡ የሚያቆም ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጣዖታቱ ፡ ብዛት ፡ እመልስለታለኹ ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ንስሓ ፡ ግቡ ፥ ከጣዖቶቻችኹም ፡ ተመለሱ ፥ ፊታችኹንም ፡ ከርኵሰታችኹ ፡ ዅሉ ፡ መልሱ ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ከእስራኤልም ፡ ቤት ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ከሚቀመጡ ፡ መጻተኞች ፡ የሚኾን ፥ ከእኔ ፡ ተለይቶ ፡ ጣዖቶቹን ፡ በልቡ ፡ የሚያኖር ፥ የበደሉንም ፡ መቅሠፍት ፡ በፊቱ ፡ የሚያቆም ፡ ሰው ፡ ዅሉ ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ ይጠይቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ በራሴ ፡ እመልስለታለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ፊቴንም ፡ በዚያ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፡ ምልክትና ፡ ምሳሌም ፡ አደርገዋለኹ ፡ ከሕዝቤም ፡ መካከል ፡ አጠፋዋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ነቢዩም ፡ ቢታለል ፡ ቃልንም ፡ ቢናገር ፥ ያን ፡ ነቢይ ፡ ያታለልኹ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፥ እጄንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፡ ከሕዝቤም ፡ ከእስራኤል ፡ መካከል ፡ አጠፋዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ኀጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ፡ እንደሚጠይቀውም ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ እንዲሁ ፡ የነቢዩ ፡ ኀጢአት ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ይኸውም ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ ርቀው ፡ እንዳይስቱ ፡ በኀጢአታቸውም ፡ ዅሉ ፡ እንዳይረክሱ ፡ ነው ። እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ምድር ፡ በማመፅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ስትሠራ ፥ እኔም ፡ እጄን ፡ ስዘረጋባት ፡ የእንጀራዋንም ፡ በትር ፡ ስሰብር ፡ ራብን ፡ ስሰድ፡ባት ፡ ሰውንና ፡ እንስሳውንም ፡ ከርሷ ፡ ሳጠፋ ፥

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፥ ኖኅና ፡ ዳንኤል ፡ ኢዮብም ፥ ቢኖሩባት ፡ በጽድቃቸው ፡ የገዛ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ብቻ ፡ ያድናሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ክፉዎቹን ፡ አራዊት ፡ በምድር ፡ ባሳልፍ ፡ እነርሱም ፡ ልጆቿን ፡ ቢያጠፉ ፡ ስለ ፡ አራዊትም ፡ ማንም ፡ እንዳያልፍባት ፡ ባድማ ፡ ብትኾን ፥

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩባት ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እነርሱ ፡ ብቻቸውን ፡ ይድናሉ ፡ እንጂ ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ አያድኑም ፥ ምድሪቱም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ወይም ፡ በዚያች ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ሰይፍ ፡ አምጥቼ ፦ ሰይፍ ፡ ሆይ ፥ በምድሪቱ ፡ ላይ ፡ ዕለፊ ፡ ብል ፥ ሰውንና ፡ እንስሳውንም ፡ ከርሷ ፡ ባጠፋ ፥

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ እነዚህ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ቢኖሩባት ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እነርሱ ፡ ብቻቸውን ፡ ይድናሉ ፡ እንጂ ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ አያድኑም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ወይም ፡ በዚያች ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ቸነፈር ፡ ብሰድ ፡ ሰውንና ፡ እንስሳውንም ፡ ከርሷ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ መዓቴን ፡ በደም ፡ ባፈስባት ፥

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ኖኅና ፡ ዳንኤል ፡ ኢዮብም ፡ ቢኖሩባት ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በጽድቃቸው ፡ ነፍሳቸውን ፡ ብቻ ፡ ያድናሉ ፡ እንጂ ፡ ወንዶችንና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ አያድኑም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ይልቁንስ ፡ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ ከርሷ ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ አራቱን ፡ ክፉ ፡ ፍርዶቼን ፥ ሰይፍንና ፡ ራብን ፡ ክፉዎችንም ፡ አውሬዎች ፡ ቸነፈርንም ፥ ስሰድባት! ፡

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ የሚያመልጡና ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችን ፡ የሚያመጡ ፡ ይቀሩላታል ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይወጣሉ ፡ እናንተም ፡ መንገዳቸውንና ፡ ሥራቸውን ፡ ታያላችኹ ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ስላመጣኹት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስላመጣኹባትም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ትጽናናላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ መንገዳቸውንና ፡ ሥራቸውን ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፡ ያጽናኗችኋል ፤ ያደረግኹባትንም ፡ ኹሉ ፡ በከንቱ ፡ እንዳላደረግኹባት ፡ ታውቃላችኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የወይን ፡ ግንድ ፥ በዱር ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ የወይን ፡ ዐረግ ፥ ከዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ብልጫው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ በእውኑ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራበትን ፡ ዕንጨት ፡ ከርሱ ፡ ይወስዳሉን ፧ ወይስ ፡ ሰዎች ፡ ዕቃ ፡ የሚንጠለጠልበትን ፡ ኩላብ ፡ ከርሱ ፡ ይወስዳሉን ፧

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ ለመቃጠል ፡ በእሳት ፡ ላይ ፡ ተጥሏል ፥ እሳቱም ፡ ኹለቱን ፡ ጫፎቹን ፡ በልቷል ፥ መካከሉም ፡ ተቃጥሏል ፤ በእውኑ ፡ ለሥራ ፡ ይጠቅማልን ፧

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ ደኅና ፡ ሳለ ፡ ለሥራ ፡ ካልጠቀመ ፥ ይልቁንስ ፡ እሳት ፡ ከበላው ፡ ርሱም ፡ ከተቃጠለ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ሥራ ፡ ይሠራበታል ፧

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዱር ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ እሳት ፡ ይበላው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰጠኹት ፥ እንዲሁ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩትን ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ።

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ፊቴንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፤ ከእሳትም ፡ ይወጣሉ ፥ እሳት ፡ ግን ፡ ይበላቸዋል ፤ ፊቴንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ባደረግኹ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ዐመፅን ፡ አድርገዋልና ፥ ምድሪቱን ፡ ባድማ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለኢየሩሳሌም ፡ ርኵሰቷን ፡ አስታውቃት ፥

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዘርሽና ፡ ትውልድሽ ፡ ከከነዓን ፡ ምድር ፡ ነው ፤ አባትሽ ፡ አሞራዊ ፡ ነበረ ፡ እናትሽም ፡ ኬጢያዊት ፡ ነበረች ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ በተወለድሽ ፡ ጊዜ ፡ በዚያው ፡ ቀን ፡ ዕትብትሽ ፡ አልተቈረጠም ፡ ንጹሕም ፡ ትኾኚ ፡ ዘንድ ፡ በውሃ ፡ አልታጠብሽም ፥ በጨውም ፡ አልተቀባሽም ፡ በጨርቅም ፡ አልተጠቀለልሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ በተወለድሽበት ፡ ቀን ፡ ከሰውነትሽ ፡ ጕስቍልና ፡ የተነሣ ፡ በሜዳ ፡ ላይ ፡ ተጣልሽ ፡ እንጂ ፡ ከዚህ ፡ አንዳች ፡ ይደረግልሽ ፡ ዘንድ ፡ ዐይን ፡ አልራራልሽም ፥ ማንም ፡ አላዘነልሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ባንቺም ፡ ዘንድ ፡ ባለፍኩ ፡ ጊዜ ፡ በደምሽም ፡ ውስጥ ፡ ተለውሰሽ ፡ ባየኩሽ ፡ ጊዜ ፥— በደምሽ ፡ እንዳለሽ ፡ በሕይወት ፡ ኑሪ ፡ አልኩሽ ፤ አዎን ፥— በደምሽ ፡ እንዳለሽ ፡ በሕይወት ፡ ኑሪ ፡ አልኩሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ በዕርሻ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ቡቃያ ፡ አበዛኩሽ ፥ አንቺም ፡ አደግሽ ፡ ታላቅም ፡ ኾንሽ ፥ በእጅጉም ፡ አጌጥሽ ፤ ጡቶችሽም ፡ አጐጠጐጡ ፡ ጠጕርሽም ፡ አደገ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዕርቃንሽን ፡ ኾንሽ ፥ ተራቊተሽም ፡ ነበርሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ባለፍኩና ፡ ባየኩሽ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ጊዜሽ ፡ የፍቅር ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፤ እኔም ፡ መጐናጸፊያዬን ፡ በላይሽ ፡ ዘረጋኩ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽንም ፡ ከደንኩ ፤ ማልኩልሽም ፡ ከአንቺም ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ገባኩ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ አንቺም ፡ ለእኔ ፡ ኾንሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ በውሃም ፡ አጠብኩሽ ፡ ከደምሽም ፡ አጠራኩሽ ፡ በዘይትም ፡ ቀባኩሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ ወርቀ ፡ ዘቦም ፡ አለበስኩሽ ፡ በአቀኑስጣ ፡ ቀርበትም ፡ ጫማ ፡ አደረግኩልሽ ፤ በጥሩ ፡ በፍታ ፡ አስታጠቅኩሽ ፡ በሐርም ፡ ከደንኩሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ በጌጥም ፡ አስጌጥኩሽ ፡ በእጅሽም ፡ ላይ ፡ አንባር ፡ በዐንገትሽም ፡ ላይ ፡ ድሪ ፡ አደረግኩልሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ በአፍንጫሽም ፡ ቀለበት ፡ በጕሮሮሽም ፡ ጕትቻ ፡ በራስሽም ፡ ላይ ፡ የክብር ፡ አክሊል ፡ አደረግኩ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ በወርቅና ፡ በብር ፡ አጌጥሽ ፥ ልብስሽም ፡ ጥሩ ፡ በፍታና ፡ ሐር ፡ ወርቀ ፡ ዘቦም ፡ ነበረ ፤ አንቺም ፡ መልካምን ፡ ዱቄትና ፡ ማርን ፡ ዘይትንም ፡ በላሽ ፤ እጅግ ፡ በጣም ፡ ውብ ፡ ኾንሽ ፡ ለመንግሥትም ፡ ደረስሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ካኖርኋት ፡ ከክብሬ ፡ የተነሣ ፡ ውበትሽ ፡ ፍጹም ፡ ነበረና ፡ ዝናሽ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ወጣ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በውበትሽ ፡ ታምነሻል ፡ ስለ ፡ ዝናሽም ፡ አመንዝረሻል ፡ ምንዝርናሽንም ፡ ከመንገድ ፡ ዐላፊ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ አበዛሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ከልብስሽም ፡ ወስደሽ ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ በዝንጕርጕር ፡ ልብስ ፡ ያስጌጥሻቸውን ፡ መስገጃች ፡ ለራስሽ ፡ ሠራሽ ፡ በዚያም ፡ ገለሞትሽ ፤ እንዲህም ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ካኹን ፡ በፊት ፡ አልነበረም ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ አይኾንም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ከሰጠኹሽም ፡ ከወርቄና ፡ ከብሬ ፡ የተሠራውን ፡ የክብርሽን ፡ ዕቃ ፡ ወስደሽ ፡ የወንድ ፡ ምስሎች ፡ ለራስሽ ፡ አድርገሻል ፥ አመንዝረሽባቸውማል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ወርቀ ፡ ዘቦውን ፡ ልብስሽንም ፡ ወስደሽ ፡ ደረብሽላቸው ፥ ዘይቴንና ፡ ዕጣኔንም ፡ በፊታቸው ፡ አኖርሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ የሰጠኹሽንም ፡ እንጀራዬን ፡ ያበላኹሽንም ፡ መልካሙን ፡ ዱቄትና ፡ ዘይቱን ፡ ማሩንም ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ አድርገሽ ፡ በፊታቸው ፡ አኖርሽ ፥ እንዲሁም ፡ ኾኗል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ለኔም ፡ የወለድሻቸውን ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽን ፡ ወስደሽ ፡ መብል ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሠዋሽላቸው ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ልጆቼን ፡ ዐረድሽ ፤ ለእነርሱም ፡ በእሳት ፡ በኩል ፡ አሳልፈሽ ፡ ሰጠሽ ፤ በእውኑ ፡ ግልሙትናሽ ፡ ጥቂት ፡ ነውን ፧

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ በርኩስነትሽና ፡ በግልሙትናሽ ፡ ዅሉ ፡ ዕርቃንሽን ፡ ኾነሽ ፡ ተራቍተሽም ፡ ሳለሽ ፡ በደምሽም ፡ ተለውሰሽ ፡ ሳለሽ ፡ የሕፃንነትሽን ፡ ወራት ፡ አላሰብሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ ወዮ! ፡ ወዮልሽ! ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ከክፋትሽም ፡ ዅሉ ፡ በኋላ ፡ የምንዝርናን ፡ ስፍራ ፥ በያደባባዩም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታን ፡ ለራስሽ ፡ ሠራሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ በየመንገዱ ፡ ራስ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ቦታሽን ፡ ሠራሽ ፥ ውበትሽንም ፡ አረከሽ ፥ ለመንገድ ፡ ዐላፊም ፡ ዅሉ ፡ እግርሽን ፡ ገለጥሽ ፡ ግልሙትናሽንም ፡ አበዛሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ሥጋቸውም ፡ ከወፈረ ፡ ከጎረቤቶችሽ ፡ ከግብጻውያን ፡ ጋራ ፡ አመነዘርሽ ፥ እኔንም ፡ ታስቈጪ ፡ ዘንድ ፡ ግልሙትናሽን ፡ አበዛሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እጄን ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ዘርግቻለኹ ፡ ድርጎሽንም ፡ አጕድያለኹ ፤ ለሚጠሉሽም ፡ ከክፉ ፡ መንገድሽ ፡ የተነሣ ፡ ለሚያፍሩ ፡ ለፍልስጥኤም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ፈቃድ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጥቼሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ አልጠገብሽምና ፡ ከአሶራውያን ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ ገለሞትሽ ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ አልጠገብሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ እስከነጋዴዎች ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ከላውዴዎን ፡ ድረስ ፡ ግልሙትናሽን ፡ አበዛሽ ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ገና ፡ አልጠገብሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ የማታፍረውን ፡ የጋለሞታን ፡ ሥራ ፡ ዅሉ ፡ ሠርተሻልና ፥ ልብሽ ፡ ምንኛ ፡ ደካማ ፡ ነው ፧ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ በየመንገዱ ፡ ራስ ፡ የምንዝርናሽን ፡ ስፍራ ፡ ሠርተሻል ፡ በያደባባዩም ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ቦታሽን ፡ አድርገሻል ። ዋጋዋን ፡ እንደምትንቅ ፡ እንደ ፡ ጋለሞታ ፡ አልኾንሽም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ በባሏ ፡ ፋንታ ፡ ሌላዎችን ፡ ተቀብላ ፡ የምታመነዝር ፡ ሴትን ፡ ትመስያለሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ ለጋለሞታዎች ፡ ዅሉ ፡ ዋጋ ፡ ይሰጧቸዋል ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ ለውሽማዎችሽ ፡ ዅሉ ፡ ዋጋ ፡ ትሰጣለሽ ፥ ከአንቺም ፡ ጋራ ፡ ለማመንዘር ፡ በዙሪያሽ ፡ ይገቡብሽ ፡ ዘንድ ፡ መማለጃ ፡ ትሰጣቸዋለሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 34 ፤ ግልሙትናሽ ፡ ከሌላዎች ፡ ሴቶች ፡ ግልብጥ ፡ ነው ፤ ማንም ፡ ለግልሙትና ፡ የሚከተልሽ ፡ የለም ፤ ዋጋ ፡ ሳይሰጥሽ ፡ አንቺ ፡ ዋጋ ፡ በመስጠትሽ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ልዩ ፡ ኾነሻል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 35 ፤ ስለዚህ ፥ ጋለሞታ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሚ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 36 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከውሽማዎችሽ ፡ ጋራ ፡ ባደረግሽው ፡ በግልሙትናሽ ፡ ርኵሰትሽ ፡ ስለ ፡ ፈሰሰ ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽም ፡ ስለ ፡ ተገለጠ ፥ ስለ ፡ ርኵሰትሽም ፡ ጣዖታት ፡ ዅሉ ፡ ስለሰጠሻቸውም ፡ ስለልጆች ፡ ደም ፥

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 37 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ያለሽን ፡ የወደድሻቸውንም ፡ ውሽማዎችሽ ፡ ዅሉ ፥ ከጠላሻቸው ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፥ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ባንቺ ፡ ላይ ፡ በዙሪያሽ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽንም ፡ ዅሉ ፡ እንዲያዩ ፡ በፊታቸው ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽን ፡ እገልጣለኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 38 ፤ በአመንዝራዎችና ፡ በደም ፡ አፍሳሾች ፡ ላይ ፡ የሚፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እፈርድብሻለኹ ፥ የመዓትንና ፡ የቅንአትን ፡ ደምም ፡ አመጣብሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 39 ፤ በእጃቸውም ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥሻለኹ ፥ የምንዝርናሽንም ፡ ስፍራ ፡ ያፈርሳሉ ፡ ከፍ ፡ ያለውንም ፡ ቦታሽን ፡ ይገለብጣሉ ፤ ልብስሽንም ፡ ይገፉሻል ፡ የክብርሽንም ፡ ጌጥ ፡ ይወስዳሉ ፥ ዕርቃንሽን ፡ አድርገው ፡ ዕራቍትሽን ፡ ይተዉሻል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 40 ፤ ጉባኤን ፡ ያመጡብሻል ፡ በድንጋይም ፡ ይወግሩሻል ፥ በሰይፋቸውም ፡ ይወጉሻል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 41 ፤ ቤቶችሽንም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ፡ በብዙም ፡ ሴቶች ፡ ፊት ፡ በላይሽ ፡ ፍርድን ፡ ያደርጉብሻል ፤ ግልሙትናሽንም ፡ አስተውሻለኹ ፥ እንግዲህስ ፡ ዋጋ ፡ አትሰጪም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 42 ፤ መዓቴንም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ እጨርሳለኹ ፡ ቅንአቴም ፡ ከአንቺ ፡ ይርቃል ፥ እኔም ፡ ዝም ፡ እላለኹ ፡ ደግሞም ፡ አልቈጣም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 43 ፤ የሕፃንነትሽን ፡ ወራት ፡ አላሰብሽምና ፥ በዚህም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አስቈጥተሽኛልና ፥ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ መንገድሽን ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ሌላንም ፡ ነውር ፡ በርኵሰትሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አትጨምሪም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 44 ፤ እንሆ ፥ በምሳሌ ፡ የሚናገር ፡ ኹሉ ፦ እንደ ፡ እናቲቱ ፡ እንዲሁ ፡ ሴት ፡ ልጂቱ ፡ ናት ፡ እያለ ፡ ምሳሌ ፡ ይመስልብሻል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 45 ፤ አንቺ ፡ ባሏንና ፡ ልጆቿን ፡ የጠላሽ ፡ የእናትሽ ፡ ልጅ ፡ ነሽ ፤ አንቺም ፡ ባሎቻቸውንና ፡ ልጆቻቸውን ፡ የጠሉ ፡ የእኅቶችሽ ፡ እኅት ፡ ነሽ ፤ እናታችኹ ፡ ኬጢያዊት ፡ ነበረች ፡ አባታችኹም ፡ አሞራዊ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 46 ፤ ታላቂቱም ፡ እኅትሽ ፡ ከሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ ጋራ ፡ በስተግራሽ ፡ የምትቀመጥ ፡ ሰማርያ ፡ ናት ፤ ታናሺቱም ፡ እኅትሽ ፡ ከሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ ጋራ ፡ በስተቀኝሽ ፡ የምትቀመጥ ፡ ሰዶም ፡ ናት ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 47 ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ በመንገዳቸው ፡ አልኼድሽም ፡ እንደ ፡ ርኵሰታቸውም ፡ አላደረግሽም ፡ ያው ፡ ለአንቺ ፡ ጥቂት ፡ ነበረና ፡ በመንገድሽ ፡ ኹሉ ፡ ከነርሱ ፡ የሚከፋ ፡ ርኵሰት ፡ አደረግሽ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 48 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ አንቺና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽ ፡ እንዳደረጋችኹት ፡ እንዲሁ ፡ ሰዶምና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ አላደረጉም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 49 ፤ እንሆ ፥ የእኅትሽ ፡ የሰዶም ፡ ኀጢአት ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ ትዕቢት ፡ እንጀራን ፡ መጥገብ ፥ መዝለልና ፡ ሥራ ፡ መፍታት ፡ በርሷና ፡ በሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ ነበረ ፥ የችግረኛውንና ፡ የድኻውንም ፡ እጅ ፡ አላጸናችም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 50 ፤ ኰርተው ፡ ነበር ፥ በፊቴም ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ አደረጉ ፤ ስለዚህ ፥ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ አጠፋኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 51 ፤ ሰማርያም ፡ የኀጢአትሽን ፡ እኩሌታ ፡ አልሠራችም ፤ አንቺ ፡ ግን ፡ ከእኅቶችሽ ፡ ይልቅ ፡ ርኵሰትሽን ፡ አበዛሽ ፥ በሥራሽም ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ አጸደቅሻቸው ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 52 ፤ አኹንም ፡ ለእኅቶችሽ ፡ ስለ ፡ ፈረድሽ ፡ ዕፍረትሽን ፡ ተሸከሚ ፤ ከነርሱ ፡ የባሰ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተሻልና ፥ ከአንቺ ፡ ይልቅ ፡ ጻድቃን ፡ ናቸው ፤ እኅቶችሽንም ፡ ስላጸደቅሻቸው ፡ ዕፈሪ ፥ ዕፍረትሽንም ፡ ተሸከሚ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 53 ፤ ምርኳቸውን ፥ የሰዶምና ፡ የሴቶች ፡ ልጆቿን ፡ ምርኮ ፥ የሰማርያንና ፡ የሴቶች ፡ ልጆቿንም ፡ ምርኮ ፥ በመካከላቸውም ፡ ያሉትን ፡ የምርኮኞችሽን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 54 ፤ ስላጽናናሻቸው ፥ ዕፍረትን ፡ ትሸከሚ ፡ ዘንድ ፡ ስላደረግሽውም ፡ ኹሉ ፡ ታፍሪ ፡ ዘንድ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 55 ፤ እኅቶችሽም ፡ ሰዶምና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ ወደቀድሞ ፡ ኹኔታቸው ፡ ይመለሳሉ ፥ ሰማርያና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿም ፡ ወደቀድሞ ፡ ኹኔታቸው ፡ ይመለሳሉ ፥ አንቺና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽም ፡ ወደቀድሞ ፡ ኹኔታችኹ ፡ ትመለሳላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 56 ፤ ክፋትሽ ፡ ሳይገለጥ ፡ በትዕቢትሽ ፡ ቀን ፡ እኅትሽ ፡ ሰዶም ፡ በአፍሽ ፡ መተረቻ ፡ አልነበረችምን ፧

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 57 ፤ አኹን ፡ ለሶርያ ፡ ሴቶች ፡ ልጆችና ፡ ለጎረቤቶቿ ፡ ኹሉ ፥ በዙሪያሽም ፡ ለሚንቁሽ ፡ ለፍልስጥኤም ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ርኲ ፡ መሰደቢያ ፡ ኾነሻል ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 58 ፤ ምንዝርነትሽንና ፡ ርኩስነትሽን ፡ ተሸክመሻል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 59 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አንቺ ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ በማፍረስ ፡ መሐላን ፡ የናቅሽ ፡ ሆይ ፥ አንቺ ፡ እንዳደረግሽ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አደርግብሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 60 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕፃንነትሽ ፡ ወራት ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ያደረግኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ዐስባለኹ ፡ የዘለዓለምንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አጸናልሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 61 ፤ እኅቶችሽንም ፡ ታላቂቱንና ፡ ታናሺቱን ፡ በተቀበልሽ ፡ ጊዜ ፡ መንገድሽን ፡ ታስቢያለሽ ፡ ታፍሪማለሽ ፤ ለአንቺም ፡ ልጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳንሽ ፡ ግን ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 16 ፡ 62 ፤ 63 ፤ ስላደረግሽውም ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ ባልኹሽ ፡ ጊዜ ፥ ታስቢ ፡ ዘንድ ፡ ታፍሪም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ዕፍረትሽም ፡ ደግሞ ፡ አፍሽን ፡ እንዳትከፍቺ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ አጸናለኹ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእንቆቅልሽ ፡ አጣውት ፥ ለእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ምሳሌ ፡ ንገር ፥ እንዲህም ፡ በል ፦

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ታላቅ ፡ ክንፍ ፡ ረዥምም ፡ ማርገብገቢያ ፡ ያለው ፡ ላባም ፡ የተሞላ ፥ መልከ ፡ ዝንጉርጉር ፡ ታላቅ ፡ ንስር ፡ ወደ ፡ ሊባኖስ ፡ መጣ ፥ የዝግባንም ፡ ጫፍ ፡ ወሰደ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ቀንበጡንም ፡ ቀነጠበ ፡ ወደከነዓንም ፡ ምድር ፡ ወሰደው ፡ በነጋዴዎችም ፡ ከተማ ፡ አኖረው ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ከምድርም ፡ ዘር ፡ ወሰደ ፡ በፍሬያማ ፡ ዕርሻ ፡ ተከለው ፡ በብዙም ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ አሐያ ፡ ዛፍ ፡ አኖረው ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ በበቀለም ፡ ጊዜ ፡ ቁመቱ ፡ ያጠረ ፡ ዐረጉም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የሚመለስ ፡ ሥሩም ፡ በበታቹ ፡ የነበረ ፡ ሰፊ ፡ ወይን ፡ ኾነ ፥ እንዲሁ ፡ ወይን ፡ ኾነ ፡ ዐረግም ፡ ሰደደ ፡ ቀንበጥም ፡ አወጣ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ታላቅ ፡ ክንፍና ፡ ብዙ ፡ ላባም ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ ታላቅ ፡ ንስር ፡ ነበረ ፤ እንሆም ፥ ያጠጣው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ወይን ፡ ሥሩን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አዘነበለ ፡ ዐረጉንም ፡ ከተተከለበት ፡ ከመደቡ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሰደደ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ዐረግም ፡ ያወጣ ፡ ፍሬም ፡ ያፈራ ፡ የከበረም ፡ ወይን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በመልካም ፡ መሬት ፡ ውስጥ ፡ በብዙም ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ ተተክሎ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእውኑ ፡ ይከናወንለት ፡ ይኾንን ፧ ይደርቅስ ፡ ዘንድ ፥ ዐዲስ ፡ የበቀለውስ ፡ ቅጠሉ ፡ ይጠወልግ ፡ ዘንድ ፡ ሥሩን ፡ አይነቅለውምን ፧ ፍሬውንስ ፡ አይለቅመውምን ፧ ሥሩም ፡ የተነቀለው ፡ በብርቱ ፡ ክንድና ፡ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ተተክሎስ ፥ እንሆ ፥ ይከናወንለት ፡ ይኾንን ፧ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ባገኘው ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ አይደርቅምን ፧ በተተከለበት ፡ መደብ ፡ ላይ ፡ ይደርቃል ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ለዐመፀኛ ፡ ቤት ፦ ይህ ፡ ትርጓሜ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቁምን ፧ በላቸው ። እንዲህም ፡ ብለኽ ፡ ንገራቸው ፦ እንሆ ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጣ ፥ ንጉሢንና ፡ መኳንንቷንም ፡ ማረከ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ ወሰዳቸው ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ ከመንግሥትም ፡ ዘር ፡ ወስዶ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አደረገ ፤ አማለውም ፥ የምድሪቱንም ፡ ኀያላን ፡ ወሰደ ፤

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ ይኸውም ፡ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ በመጠበቅ ፡ እንድትጸና ፡ እንጂ ፡ መንግሥቱ ፡ እንድትዋረድና ፡ ከፍ ፡ እንዳትል ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሸፈተ ፡ ፈረሶችንና ፡ ብዙንም ፡ ሕዝብ ፡ ይሰጡት ፡ ዘንድ ፡ መልእክተኞችን ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ላከ ። በእውኑ ፡ ይከናወንለት ፡ ይኾንን ፧ ይህንስ ፡ ያደረገ ፡ ያመልጣልን ፧ ቃል ፡ ኪዳንንስ ፡ አፍርሶ ፡ ያመልጣልን ፧

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ ያነገሠውና ፡ መሐላውን ፡ የናቀበቱ ፥ ቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ ያፈረሰበቱ ፡ ንጉሥ ፡ በሚኖርበት ፡ ስፍራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በባቢሎን ፡ መካከል ፡ በርግጥ ፡ ይሞታል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ብዙዎችን ፡ ነፍሳት ፡ ለማስወገድ ፡ ዐፈርን ፡ በደለደሉ ፡ ምሽግም ፡ በሠሩ ፡ ጊዜ ፥ ፈርዖን ፡ ከብዙ ፡ ሰራዊቱና ፡ ከታላቁ ፡ ጉባኤው ፡ ጋራ ፡ በሰልፍ ፡ አይረዳውም ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ቃል ፡ ኪዳኑንም ፡ በማፍረስ ፡ መሐላውን ፡ ንቋል ፤ እንሆም ፥ እጁን ፡ ሰጠ ፥ ይህንም ፡ ኹሉ ፡ አድርጓል ፤ ስለዚህ ፥ አያመልጥም ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ የናቀውን ፡ መሐላዬን ፡ ያፈረሰውንም ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 20 ፤ መረቤንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፡ በወጥመድም ፡ ይያዛል ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ አመጣዋለኹ ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ ስላደረገው ፡ ዐመፅ ፡ በዚያ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እፋረዳለኹ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 21 ፤ ጭፍራዎቹም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ የቀሩትም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እየነፋሳቱ ፡ ይበተናሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 22 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከረዥሙ ፡ ዝግባ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ ቀንበጥን ፡ ወስጄ ፡ አኖረዋለኹ ፤ ከጫፎቹ ፡ አንዱን ፡ ቀንበጥ ፡ እቀነጥበዋለኹ ፤ በረዥምና ፡ በታላቅ ፡ ተራራም ፡ ላይ ፡ እተክለዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 23 ፤ ከፍ ፡ ባለው ፡ በእስራኤል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ እተክለዋለኹ ፥ ቅርንጫፎችም ፡ ያወጣል ፡ ፍሬም ፡ ያፈራል ፡ የከበረም ፡ ዝግባ ፡ ይኾናል ፤ በበታቹም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ያርፋሉ ፥ በቅርንጫፎቹም ፡ ጥላ ፡ በክንፍ ፡ የሚበር ፡ ኹሉ ፡ ይጠጋል ።

ሕዝ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ የዱር ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ረዥሙን ፡ ዛፍ ፡ ዝቅ ፡ ያደረግኹ ፥ ዐጪሩንም ፡ ዛፍ ፡ ከፍ ፡

ያደረግኹ ፥ የለመለመውንም ፡ ዛፍ ፡ ያደረቅኹ ፥ የደረቀውንም ፡ ዛፍ ፡ ያለመለምኹ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ፡ እኔም ፡ አድርጌያለኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 2 ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ምድር ፦ አባቶች ፡ ጨርቋ ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ በሉ ፥ የልጆችም ፡ ጥርሶች ፡ ጠረሱ ፡ ብላችኹ ፡ የምትመስሉት ፡ ምሳሌ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 3 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ አትመስሉትም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 4 ፤ እንሆ ፥ ነፍሳት ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ናቸው ፤ የአባት ፡ ነፍስ ፡ የእኔ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ደግሞ ፡ የልጅ ፡ ነፍስ ፡ የእኔ ፡ ናት ፤ ኀጢአት ፡ የምትሠራ ፡ ነፍስ ፡ ርሷ ፡ ትሞታለች ።

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 5 ፤ ሰውም ፡ ጻድቅ ፡ ቢኾን ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ቢያደርግ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 6 ፤ በተራራም ፡ ላይ ፡ ባይበላ ፡ ዐይኖቹንም ፡ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጣዖታት ፡ ባያነሣ ፡ የባልንጀራውንም ፡ ሚስት ፡ ባያረክስ ፡ አደፍም ፡ ወዳለባት ፡ ሴት ፡ ባይቀርብ ፤

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 7 ፤ ሰውንም ፡ ባያስጨንቅ ፡ ለባለዕዳም ፡ መያዣውን ፡ ቢመልስ ፡ ፈጽሞም ፡ ባይቀማ ፡ ከእንጀራውም ፡ ለተራበ ፡ ቢሰጥ ፡ የተራቈተውንም ፡ በልብስ ፡ ቢያለብስ ፤

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 8 ፤ በዐራጣ ፡ ባያበድር ፥ ትርፎቻም ፡ ባይወስድ ፥ እጁንም ፡ ከኀጢአት ፡ ቢመልስ ፥ በሰውና ፡ በሰው ፡ መካከልም ፡ የእውነትን ፡ ፍርድ ፡ ቢፈርድ ፤

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 9 ፤ በትእዛዜም ፡ ቢኼድ ፥ እውነትንም ፡ ለማድረግ ፡ ፍርዴን ፡ ቢጠብቅ ፥ ርሱ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፥ ፈጽሞ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 10 ፤ ርሱም ፡ ቀማኛና ፡ ደም ፡ አፍሳሽ ፡ ልጅ ፡ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ አንዳቸውን ፡ የሚያደርገውን ፡ ቢወልድ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 11 ፤ ርሱም ፡ ጻድቅ ፡ አባቱ ፡ የሠራውን ፡ ኹሉ ፡ ባይሠራ ፡ በተራራም ፡ ላይ ፡ ቢበላ ፡ የባልንጀራውንም ፡ ሚስት ፡ ቢያረክስ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 12 ፤ ድኻውንና ፡ ችግረኛውንም ፡ ቢያስጨንቅ ፡ ቢቀማም ፡ መያዣውንም ፡ ባይመልስ ፡ ዐይኖቹንም ፡ ወደ ፡ ጣዖታት ፡ ቢያነሣ ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 13 ፤ በዐራጣ ፡ ቢያበድር ፥ ትርፎቻም ፡ ቢወስድ ፥ በእውኑ ፡ ርሱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራልን ፧ በሕይወት ፡ አይኖርም ፤ ይህን ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ አድርጓልና ፥ ፈጽሞ ፡ ይሞታል ፤ ደሙ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 14 ፤ እንሆም ፥ ልጅ ፡ ቢወልድ ፥ ርሱም ፡ አባቱ ፡ የሠራውን ፡ ኀጢአት ፡ አይቶ ፡ ቢፈራ ፡ እንዲህም ፡ ባይሠራ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 15 ፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ ባይበላ ፡ ዐይኖቹንም ፡ ወደእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጣዖታት ፡ ባያነሣ ፡ የባልንጀራውንም ፡ ሚስት ፡ ባያረክስ ፥

ሕዝ. ፥ 18 ፥ 16 ፤ ሰውንም ፡ ባያስጨንቅ ፡ መያዣውን ፡ ባይወስድ ፡ ባይቀማም ፡ ከእንጀራውም ፡ ለተራበ ፡ ቢሰጥ ፡ ለተራቈተውም ፡ ልብስን ፡ ቢያለብስ ፥

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ እጁንም ፡ ድኻን ፡ ከመበደል ፡ ቢመልስ ፡ ዐራጣን ፡ ትርፎቻንም ፡ ባይወስድ ፡ ፍርዴንም ፡ ቢያደርግ ፡ በትእዛዜም ፡ ቢኼድ ፥ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ በአባቱ ፡ ኀጢአት ፡ አይሞትም ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ ፈጽሞ ፡ በድኅልና ፥ ወንድሙንም ፡ ቀምቷልና ፥ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አድርጓልና ፥ እንሆ ፥ ርሱ ፡ በበደሉ ፡ ይሞታል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ ልጅ ፡ የአባቱን ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይሸከምም ፧ ትላላችኹ ። ልጅ ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ባደረገ ፡ ትእዛዜንም ፡ ኾሉ ፡ በጠበቀና ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ኀጢአትን ፡ የምትሠራ ፡ ነፍስ ፡ ርኳ ፡ ትሞታለች ፤ ልጅ ፡ የአባቱን ፡ ኀጢአት ፡ አይሸከምም ፥ አባትም ፡ የልጁን ፡ ኀጢአት ፡ አይሸከምም ፤ የጻድቁ ፡ ጽድቅ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ የኀጢአተኛውም ፡ ኀጢአት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ኀጢአተኛውም ፡ ካደረጋት ፡ ኀጢአት ፡ ኾሉ ፡ ቢመለስ ፡ ትእዛዜንም ፡ ኾሉ ፡ ቢጠብቅ ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ ቢያደርግ ፡ ፈጽሞ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ የበደለው ፡ በደል ፡ ኾሉ ፡ አይታሰብበትም ፤ በሠራው ፡ ጽድቅ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ በእውኑ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ እፈቅዳለኹን ፧ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ከመንገዱስ ፡ ይመለስና ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አይደለምን ፧

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ጻድቁ ፡ ግን ፡ ከጽድቁ ፡ ቢመለስ ፡ ኀጢአትንም ፡ ቢሠራ ፡ ኀጢአተኛውም ፡ እንደሚያደርገው ፡ ርኵሰት ፡ ኾሉ ፡ ቢያደርግ ፥ በሕይወት ፡ ይኖራልን ፧ የሠራት ፡ ጽድቅ ፡ ኾሉ ፡ አትታሰብለትም ፤ ባደረገው ፡ ዐመፅና ፡ በሠራት ፡ ኀጢአት ፡ በዚያች ፡ ይሞታል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ የጌታ ፡ መንገድ ፡ የቀናች ፡ አይደለችም ፡ ትላላችኹ ። የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እንግዲህ ፡ ስሙ ፤ በእውኑ ፡ መንገዴ ፡ የቀናች ፡ አይደለችምን ፧ ይልቅስ ፡ የእናንተ ፡ መንገድ ፡ ያልቀናች ፡ አይደለችምን ፧

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ጻድቁ ፡ ከጽድቁ ፡ ቢመለስ ፥ ኀጢአትንም ፡ በሠራ ፡ ጊዜ ፥ በዚያም ፡ ቢሞት ፥ ርሱ ፡ ባደረገው ፡ በደል ፡ ይሞታል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ኀጢአተኛውም ፡ ከሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ቢመለስ ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ ቢያደርግ ፡ ነፍሱን ፡ ይጠብቃል ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ዐስቦ ፡ ከሠራው ፡ በደል ፡ ኾሉ ፡ ተመልሷልና ፥ ፈጽሞ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፦ የጌታ ፡ መንገድ ፡ የቀናች ፡ አይደለችም ፡ ይላል ። የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በእውኑ ፡ መንገዴ ፡ የቀናች ፡ አይደለችምን ፧ ይልቅስ ፡ የእናንተ ፡ መንገድ ፡ ያልቀናች ፡ አይደለችምን ፧

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ በየሰዉ ፡ ኾሉ ፡ እፈርድባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ ኀጢአትም ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳይኾንባችኹ ፡ ከኀጢአታችኹ ፡ ኾሉ ፡ ተመለሱ ።

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ የበደላችኹትን ፡ በደል ፡ ኾሉ ፡ ከእናንተ ፡ ጣሉ ፡ ዐዲስ ፡ ልብና ፡ ዐዲስ ፡ መንፈስም ፡ ለእናንተ ፡ አድርጉ ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ትሞታላችኹ ፧

ሕዝ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ የሚቹን ፡ ሞት ፡ አልፈቅድምና ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ስለዚህ ፥ ተመለሱና ፡

በሕይወት ፡ ኑሩ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ አንተም ፡ በእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ ሙሾ ፡ አሙሽ ፥ እንዲህም ፡ በል ፦

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ እናትኽ ፡ ምን ፡ ነበረች ፧ አንበሳ ፡ ነበረች ፤ በአንበሳዎች ፡ መካከል ፡ ተጋደመች ፤ በደቦል ፡ አንበሳዎች ፡ መካከል ፡ ግልገሎቿን ፡ አሳደገች ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ከግልገሎቿም ፡ አንዱን ፡ አወጣች ፥ ርሱም ፡ ደቦል ፡ አንበሳ ፡ ኾነ ፤ ንጥቂያንም ፡ ተማረ ፥ ሰዎችንም ፡ በላ ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ አሕዛብም ፡ ወሬውን ፡ ሰሙ ፥ ርሱም ፡ በጕድጓዳቸው ፡ ተያዘ ፥ በሰንሰለትም ፡ አድርገው ፡ ወደግብጽ ፡ ምድር ፡ ወሰዱት ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ርሷም ፡ እንደ ፡ ደከመችና ፡ ተስፋዋ ፡ እንደ ፡ ጠፋ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፥ ከግልገሎቿ ፡ ሌላን ፡ ወስዳ ፡ ደቦል ፡ አንበሳ ፡ አደረገችው ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ በአንበሳዎች ፡ መካከል ፡ ተመላለሰ ፥ ደቦል ፡ አንበሳም ፡ ኾነ ፤ ንጥቂያም ፡ ተማረ ፥ ሰዎችንም ፡ በላ ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ግንቦቻቸውንም ፡ ዐወቀ ፥ ከተማዎቻቸውንም ፡ አፈረሰ ፤ ከግሣቱም ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ምድሪቱና ፡ ሞላዋ ፡ ጠፋች ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ አሕዛብም ፡ በዙሪያው ፡ ከየአገሩ ፡ ዥሉ ፡ ተሰበሰቡበት ፤ መረባቸውንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዘረጉ ፥ በጕድጓዳቸውም ፡ ተያዘ ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ በሰንሰለትም ፡ አድርገው ፡ በቀፎ ፡ ውስጥ ፡ አኖሩት ፥ ወደባቢሎንም ፡ ንጉሥ ፡ አመጡት ፤ ድምፁም ፡ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ እንዳይሰማ ፡ ወደ ፡ ዐምባ ፡ አገቡት ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ እናትኽ ፡ በመልክኽ ፡ በውሃ ፡ አጠገብ ፡ እንደ ፡ ተተከለች ፡ እንደ ፡ ወይን ፡ ግንድ ፡ ነበረች ፤ ከውሃም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የምታፈራና ፡ የምትሰፋ ፡ ኾነች ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ለርሷም ፡ ብርቱዎች ፡ በትሮች ፡ ነበሯት ፤ እነርሱም ፡ ለነገሥታት ፡ በትሮች ፡ ነበሩ ። ቁመታቸውም ፡ በዛፎች ፡ ቅርንጫፎች ፡ መካከል ፡ ረዘመ ፥ በጫፎቻቸውም ፡ ብዛትና ፡ በርዝመታቸው ፡ ታዩ ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመዓት ፡ ተነቀለች ፥ ወደ ፡ መሬትም ፡ ተጣለች ፥ የምሥራቅም ፡ ነፋስ ፡ ፍሬዋን ፡ አደረቀ ፤ ብርቱዎች ፡ በትሮቿም ፡ ተሰበሩና ፡ ደረቁ ፥ እሳትም ፡ በላቻቸው ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፥ በደረቅና ፡ በተጠማች ፡ መሬት ፡ ተተከለች ።

ሕዝ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ከጫፎቿም ፡ በትሮች ፡ እሳት ፡ ወጣች ፥ ፍሬዋንም ፡ በላች ፤ የነገሥታትም ፡ በትር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ የበረታ ፡ በትር ፡ የለባትም ። ይህ ፡ ሙሾ ፡ ነው ፥ ለልቅሶም ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ ከእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ መጡ ፥ በፊቴም ፡ ተቀመጡ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔን ፡ ትጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ መጥታችኋልን ፧ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አልጠየቅም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ትፈርድባቸዋለኽን ፧ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእውኑ ፡ ትፈርድባቸዋለኽን ፧ የአባቶቻቸውን ፡ ርኵሰት ፡ አስታውቃቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እስራኤልን ፡ በመረጥኹበት ፡ ለያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ዘር ፡ በማልኹበት ፡ ቀን ፡ በግብጽም ፡ ምድር ፡ በተገለጥኹላቸውና ፦ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፡ ብዬ ፡ በማልኹላቸው ፡ ጊዜ ፥

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ወዳዘጋጀኹላቸው ፥ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደምታፈሰው ፥ የምድርም ፡ ዅሉ ፡ ጌጥ ፡ ወደምትኾን ፡ ምድር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ማልኹላቸው ፤

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ እኔም ፦ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ የዐይኑን ፡ ርኵሰት ፡ ይጣል ፥ በግብጽም ፡ ጣዖታት ፡ አትርከሱ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፡ አልኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ዐመፁብኝ ፡ ይሰሙኝም ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱም ፥ ዅሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ የዐይኑን ፡ ርኵሰት ፡ አልጣለም ፡ የግብጽንም ፡ ጣዖታት ፡ አልተወም ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፦ በግብጽ ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ቍጣዬን ፡ እፈጽምባቸው ፡ ዘንድ ፡ መዓቴን ፡ አፈስባቸዋለኹ ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመካከላቸው ፡ ባሉ ፡ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ በፊታቸው ፡ በተገለጥኹላቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ፊት ፡ ስሜ ፡ እንዳይረክስ ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ሠራኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ አወጣኋቸው ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ አመጣኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ሰው ፡ ቢያደርገው ፡ ኖሮ ፡ በሕይወት ፡ የሚኖርበትን ፡ ሥርዐቴንም ፡ ሰጠኋቸው ፥ ፍርዴንም ፡ አስታወቅኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ የምቀድሳቸውም ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ በእኔና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ ምልክት ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሰንበታቴን ፡ ሰጠኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ዐመፁብኝ ፤ ሰው ፡ ቢያደርገው ፡ ኖሮ ፡ በሕይወት ፡ የሚኖርበትንም ፡ ፍርዴን ፡ ጣሱ ፥ በትእዛዜም ፡ አልኼዱም ፥ ሰንበታቴንም ፡ ፈጽመው ፡ አረከሱ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፦ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ቍጣዬን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አፈስባቸዋለኹ ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፊታቸው ፡ ባወጣኋቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ፊት ፡ ስሜ ፡ እንዳይረክስ ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ሠራኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ወተትና ፡ ማርም ፡ ወደምታፈሰው ፡ የምድር ፡ ዅሉ ፡ ጌጥ ፡ ወደምትኾን ፡ ወደሰጠኋቸው ፡ ምድር ፡ አላመጣቸውም ፡ ብዬ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ማልኹባቸው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ልባቸው ፡ ጣዖቶቻቸውን ፡ ተከትሏልና ፤ ፍርዴንም ፡ ጥሰዋልና ፥ በሥርዐቴም ፡ አልኼዱምና ፥ ሰንበታቴንም ፡ አርክሰዋልና ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐይኔ ፡ ራራችላቸው ፡ እኔም ፡ አላጠፋኋቸውም ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ ፈጽሜ ፡ አልፈጀኋቸውም ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ ለልጆቻቸውም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዲህ ፡ አልኋቸው ፦ በአባቶቻችኹ ፡ ሥርዐት ፡

አትኺዱ ፥ ወጋቸውንም ፡ አትጠብቁ ፥ በጣዖቶቻቸውም ፡ አትርከሱ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 19 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፤ በትእዛዜ ፡ ኺዱ ፡ ፍርዴንም ፡ ጠብቁ ፡ አድርጓትም ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 20 ፤ ሰንበታቴንም ፡ ቀድሱ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችኹ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በእኔና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ምልክት ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 21 ፤ ልጆች ፡ ግን ፡ ዐመፁብኝ ፥ ሰው ፡ ቢያደርገው ፡ ኖሮ ፡ በሕይወት ፡ የሚኖርባትን ፡ ፍርዴን ፡ ጠብቀው ፡ አላደረጓትም ፡ በሥርዐቴም ፡ አልኼዱም ፥ ሰንበታቴንም ፡ አረከሱ ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፦ መዓቴን ፡ አፈስባቸዋለኹ ፡ ቍጣዬንም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እፈጽምባቸዋለኹ ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጄን ፡ መለስኹ ፥ በፊታቸውም ፡ ባወጣኋቸው ፡ በአሕዛብ ፡ ፊት ፡ ስሜ ፡ እንዳይረክስ ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ሠራኹ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 23 ፤ ደግሞም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እበትናቸው ፡ ዘንድ ፥ በአገሮችም ፡ እበትናቸው ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ማልኹባቸው ፤ ፍርዴን ፡ አላደረጉምና ፤

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 24 ፤ ሥርዐቴንም ፡ ጥሰዋልና ፤ ሰንበታቴንም ፡ አርክሰዋልና ፤ ዐይናቸውም ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ጣዖታቶች ፡ ተከትለዋልና ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 25 ፤ ደግሞም ፡ መልካም ፡ ያልኾነውን ፡ ሥርዐት ፡ በሕይወት ፡ የማይኖሩበትንም ፡ ፍርድ ፡ ሰጠኋቸው ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 26 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እንዲያውቁ ፡ አጠፋቸው ፡ ዘንድ ፥ ማሕፀን ፡ የሚከፍተውን ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ ባሳለፉ ፡ ጊዜ ፥ በመባቸው ፡ አረከስኋቸው ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 27 ፤ ስለዚህ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህም ፡ ደግሞ ፡ አባቶቻችኹ ፡ ባደረጉት ፡ ዐመፅ ፡ አስቈጡኝ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 28 ፤ እሰጣቸውም ፡ ዘንድ ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ባገባኋቸው ፡ ጊዜ ፥ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ኰረብታ ፡ ኹሉ ፡ ቅጠልማውንም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ አዩ ፥ በዚያም ፡ መሥዋዕታቸውን ፡ ሠዉ ፡ በዚያም ፡ የሚያስቈጣኝን ፡ ቍርባናቸውን ፡ አቀረቡ ፡ በዚያም ፡ ደግሞ ፡ ጣፋጭን ፡ ሽታቸውን ፡ አደረጉ ፡ በዚያም ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባናቸውን ፡ አፈሰሱ ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 29 ፤ እኔም ፦ እናንተ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ የምትኼዱበት ፡ ከፍታ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አልኋቸው ። እስከ ፡ ዛሬም ፡ ድረስ ፡ ስሙ ፡ ባማ ፡ ተብሎ ፡ ተጠርቷል ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንደ ፡ አባቶቻችኹ ፡ ልማድ ፡ ትረክሳላችኹን ፧ ርኵሰታቸውንም ፡ ተከትላችኹ ፡ ታመነዝራላችኹን ፧

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 31 ፤ ቍርባናችኹን ፡ ባቀረባችኹ ፡ ጊዜ ፥ ልጆቻችኹንም ፡ በእሳት ፡ ባሳለፋችኹ ፡ ጊዜ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በጣዖቶቻችኹ ፡ ትረክሳላችኹን ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ከናንተስ ፡ ዘንድ ፡ እጠየቃለኹን ፧ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አልጠየቅም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 32 ፤ ለእናንተም ፦ እንደ ፡ አሕዛብና ፡ እንደምድር ፡ ወገኖች ፡ እንኾናለን ፥ ዕንጨትና ፡ ድንጋይም ፡ እናመልካለን ፡ የሚል ፡ ከልባችኹ ፡ የወጣ ፡ ዐሳብ ፡ አይፈጸምላችኹም ።

ሕዝ. ፥ 20 ፥ 33 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በበረታች ፡ እጅና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድ ፡ በፈሰሰችም ፡ መዓት ፡ እነግሥባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 34 ፤ ከአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ አወጣችኋለኹ ፡ ከተበተናችኹባትም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በበረታች ፡ እጅና ፡ በተዘረጋች ፡ ክንድ ፡ በፈሰሰችም ፡ መዓት ፡ እሰበስባችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 35 ፤ ወደአሕዛብም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አመጣችኋለኹ ፡ በዚያም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እፋረዳለኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 36 ፤ በግብጽ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ከአባቶቻችኹ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተፋረድኹ ፡ እንዲሁ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እፋረዳለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 37 ፤ ከበትርም ፡ በታች ፡ አሳልፋችኋለኹ ፡ ወደቃል ፡ ኪዳንም ፡ እስራት ፡ አገባችኋለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 38 ፤ ከእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ዐመፀኞችንና ፡ የበደሉኝን ፡ እለያለኹ ፤ ከኖሩባትም ፡ ምድር ፡ አወጣቸዋለኹ ፥ ወደእስራኤል ፡ ምድር ፡ ግን ፡ አይገቡም ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 39 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ኺዱ ፥ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ትሰሙኝ ፡ ዘንድ ፡ ባትወዱ ፡ ኹላችኹ ፡ ጣዖቶቻችኹን ፡ አምልኩ ። ነገር ፡ ግን ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በቍርባናችኹና ፡ በጣዖቶቻችኹ ፡ ቅዱሱን ፡ ስሜን ፡ አታረክሱም ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 40 ፤ በቅዱሱ ፡ ተራራዬ ፥ ከፍ ፡ ባለው ፡ በእስራኤል ፡ ተራራ ፡ ላይ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ በዚያ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ኹላቸው ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ያመልኩኛል ፤ በዚያም ፡ እቀበላቸዋለኹ ፥ በዚያም ፡ ቍርባናችኹን ፡ በኩራታችኹንም ፡ የቀደሳችኹትንም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እፈልጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 41 ፤ ከአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ ባወጣኋችኹ ፡ ጊዜ ፡ ከተበተናችኹባትም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ በሰበሰብኋችኹ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ጣፋጭ ፡ ሽታ ፡ እቀበላችኋለኹ ፥ በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ እቀደስባችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 42 ፤ ለአባቶቻችኹም ፡ እሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ወደማልኹላቸው ፡ ምድር ፡ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ ባገባኋችኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 43 ፤ በዚያም ፡ የረከሳችኹባትን ፡ መንገዳችኹንና ፡ ሥራችኹን ፡ ኹሉ ፡ ታስባላችኹ ፤ ስለ ፡ ሠራችኹትም ፡ ክፋታችኹ ፡ ኹሉ ፡ ራሳችኹን ፡ ትጸየፋላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 44 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ክፉ ፡ መንገዳችኹና ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ሥራችኹ ፡ ሳይኾን ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ስል ፡ በሠራኹላችኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 45 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 46 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ አቅና ፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ተናገር ፡ በደቡብም ፡ ባለው ፡ ዱር ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፤

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 47 ፤ ለደቡብም ፡ ዱር ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ እሳት ፡ አነዳለኹ ፤ በውስጥኽም ፡ ያለውን ፡ የለመለመውንና ፡ የደረቀውን ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይበላል ፤ የሚቃጠል ፡ ነበልባል ፡ አይጠፋም ፤ ከደቡብም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሰሜን ፡ ድረስ ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ይቃጠልበታል ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 48 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳነደድኹት ፡ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ያያል ፥ ርሱም ፡ አይጠፋም ፡ በለው ።

ሕዝ. ፡ 20 ፡ 49 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ወዮ! ፡ እነርሱ ፡ ስለ ፡ እኔ ፦ ይህ ፡ ምሳሌን ፡ የሚመስል ፡

አይደለምን ፧ ብለዋል ፡ አልኹ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አቅና ፡ ወደ ፡ መቅደሶችም ፡ ተናገር ፡ በእስራኤልም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ ለእስራኤልም ፡ ምድር ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ሰይፌንም ፡ ከሰገባው ፡ እመዠዋለኹ ፥ ጻድቁንና ፡ ክፉውንም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ እኔም ፡ ጻድቁንና ፡ ክፉውን ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለማጠፋ ፥ ስለዚህ ፡ ሰይፌ ፡ ከደቡብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሰሜን ፡ ድረስ ፡ ባለ ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከሰገባው ፡ ይመዘዛል ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰይፌን ፡ ከሰገባው ፡ እንደ ፡ መዘዝኹ ፡ ያውቃል ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ አይመለስም ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ ስለዚህም ፥ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አልቅስ ፤ ወገብኽን ፡ በማጕበጥ ፡ በፊታቸው ፡ ምርር ፡ ብለኽ ፡ አልቅስ ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 7 ፤ እነርሱም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ታለቅሳለኽ ፧ ቢሉኽ ፥ አንተ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ወሬ ፡ ስለሚመጣ ፡ ነው ፤ ልብም ፡ ኹሉ ፡ ይቀልጣል ፥ እጆችም ፡ ኹሉ ፡ ይዝላሉ ፥ ነፍስም ፡ ኹሉ ፡ ትደክማለች ፥ ጕልበትም ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ ይፈሳል ፤ እንሆ ፥ ይመጣል ፡ ይፈጸምማል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 9 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፦ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፤ ሰይፍ ፡ ሰይፍ ፡ የተሳለ ፡ የተሰነገለም ፡ ነው ፡ በል ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 10 ፤ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ተስሏል ፡ ያብረቀርቅም ፡ ዘንድ ፡ ተሰንግሏል ፤ እኛስ ፡ ደስ ፡ ይለናልን ፧ የልጄን ፡ በትር ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ንቆታል ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ በእጁም ፡ እንዲያዝ ፡ ለመሰንገል ፡ ተሰጠ ፤ ሰይፍ ፡ በገዳይ ፡ እጅ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተሳለና ፡ ተሰነገለ ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በሕዝቤ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ በእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ነውና ፥ ጨኽ ፡ ዋይም ፡ በል ፤ እነርሱ ፡ ከሕዝቤ ፡ ጋራ ፡ ለሰይፍ ፡ ተሰጥተዋል ፤ ስለዚህ ፥ ጭንኽን ፡ ጽፋ ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ ፈተና ፡ ደርሷል ፤ የተናቀ ፡ በትርስ ፡ ደግሞ ፡ ባይኖር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ እጅኽን ፡ አጨብጭብ ፤ የተገደሉ ፡ ሰዎች ፡ ሰይፍ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ይደጋግም ፡ የሚከሳቸው ፡ የተገደለ ፡ የታላቅ ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ ልባቸው ፡ እንዲቀልጥ ፡ መሰናክላቸውም ፡ እንዲበዛ ፡ የሚገድለውን ፡ ሰይፍ ፡ በበሮቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አድርጌያለኹ ፤ ወዮ! ፡ ያብረቀርቅ ፡ ዘንድ ፡ ተሰንግሏል ፡ ይገድልም ፡ ዘንድ ፡ ተስሏል ።

ሕዝ. ፥ 21 ፥ 16 ፤ ተዘጋጅተኽ ፡ ፊትኽ ፡ ወደወደደው ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ኺድ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በእጄ ፡ አጨበጭባለኹ ፡ መዓቴንም ፡ እጨርሳለኹ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰይፍ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ኹለት ፡ መንገዶችን ፡ አድርግ ፤ ኹለቱም ፡ ከአንዲት ፡ ምድር ፡ ይውጡ ፤ ምልክትም ፡ አድርግ ፥ በከተማዪቱ ፡ መንገድ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ አድርገው ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ሰይፍ ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ረባት ፡ ወደ ፡ ይሁዳም ፡ ወደተመሸገች ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ መንገድን ፡ አድርግ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሟርቱን ፡ ያሟርት ፡ ዘንድ ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ በኹለቱ ፡ መንገዶች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ ፍላጻዎችን ፡ ወዘወዘ ፥ ከተራፊምም ፡ ጠየቀ ፥ ጕበትም ፡ ተመለከተ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ የቅጥሩን ፡ ማፍረሻ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ አፍንም ፡ በጨኸት ፡ ይከፍት ፡ ዘንድ ፥ በውካታም ፡ ድምፅን ፡ ከፍ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ የቅጥሩን ፡ ማፍረሻ ፡ በበሮች ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥ ዐፈርን ፡ ይደለድል ፡ ዘንድ ፥ ምሽግም ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ዕጣ ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ መሐላውንም ፡ በማሉ ፡ በዐይናቸው ፡ ዘንድ ፡ የሐሰት ፡ ሟርት ፡ ይመስላል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱ ፡ ይያዙ ፡ ዘንድ ፡ ርሱ ፡ ኀጢአትን ፡ ያሳስባል ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኀጢአታችኹን ፡ ስላሰባችኹ ፥ መተላለፋችኹም ፡ ስለ ፡ ተገለጠ ፥ ኀጢአታችኹም ፡ በሥራችኹ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ታየ ፥ እናንተም ፡ ስለ ፡ ታሰባችኹ ፥ በእጅ ፡ ትያዛላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ አንተም ፡ ቀንኽ ፡ የደረሰብኽ ፥ የኀጢአትኽ ፡ ቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ የደረሰብኽ ፥ ርኩስ ፡ ኀጢአተኛ ፡ የእስራኤል ፡ አለቃ ፡ ሆይ ፥

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መጠምጠሚያውን ፡ አውልቅ ፥ ዘውዱንም ፡ አርቅ ፤ ይህ ፡ እንዲህ ፡ አይኾንም ፤ የተዋረደውን ፡ ከፍ ፡ አድርግ ፥ ከፍ ፡ ያለውንም ፡ አዋርድ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ ባድማ ፥ ባድማ ፥ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ፤ ፍርድ ፡ ያለው ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ይህች ፡ ደግሞ ፡ አትኾንም ፥ ለርሱም ፡ እሰጣታለኹ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ 29 ፤ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለዐሞን ፡ ልጆችና ፡ ስለ ፡ ስድባቸው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፤ ቀናቸው ፡ በደረሰ ፥ የኀጢአታቸው ፡ ቀጠሮ ፡ ጊዜ ፡ በደረሰ ፥ በተገደሉት ፡ ኀጢአተኞች ፡ ዐንገት ፡ ላይ ፡ ያኖሩኽ ፡ ዘንድ ፡ ከንቱን ፡ ራእይ ፡ ነገር ፡ ሲያዩልኽ ፡ በሐሰትም ፡ ሟርት ፡ ሲናገሩልኽ ፦ ሰይፍ ፥ ሰይፍ ፡ ተመዟል ፥ ይገድልም ፡ ዘንድ ፡ ያብረቀርቅም ፡ ዘንድ ፡ ተሰንግሏል ፡ በል ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ወደ ፡ ሰገባውም ፡ መልሰው ፦ በተፈጠርኽበት ፡ ስፍራ ፡ በተወለድኽባትም ፡ ምድር ፡ እፈርድብኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ቍጣዬንም ፡ አፈስብኻለኹ ፥ በመዓቴም ፡ እሳት ፡ አናፋብኻለኹ ፥ ማጥፋትንም ፡ ለሚያውቁ ፡ ለጨካኞች ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ ለእሳት ፡ ማገዶ ፡ ትኾናለኽ ፥ ደምኽም ፡ በምድር ፡ መካከል ፡ ይኾናል ፥ ደግሞም ፡ አትታሰብም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹና ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 2 ፤ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትፈርዳለኽን ፧ ደም ፡ በምታፈሰ ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ትፈርዳለኽን ፧ ርኵሰቷን ፡ ኹሉ ፡ አስታውቃት ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጊዜሽ ፡ እንዲደርስ ፡ በመካከልሽ ፡ ደምን ፡ የምታፈሺ ፡ እንድትረክሺም ፡ በራስሽ ፡ ላይ ፡ ጣዖታትን ፡ የምታደርጊ ፡ ከተማ ፡ ሆይ! ፡

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 4 ፤ ባፈሰስሽው ፡ ደም ፡ በድለሻል ፥ ባደረግሽውም ፡ ጣዖታት ፡ ረክሰሻል ፤ ቀንሽን ፡ አቀረብሽ ፥ ዘመንሽንም ፡ አሳጠርሽ ፤ ስለዚህ ፥ ለአሕዛብ ፡ መሰደቢያ ፥ ለአገሮችም ፡ ኹሉ ፡ መሳለቂያ ፡ አደረግኹሽ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 5 ፤ አንቺ ፡ ስምሽ ፡ የረከሰ ፡ ሽብርም ፡ የሞላብሽ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ አንቺ ፡ የቀረቡና ፡ ከአንቺ ፡ የራቁ ፡ ይሣለቁብሻል ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 6 ፤ እንሆ ፥ የእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ችሎቱ ፡ ደም ፡ ያፈሱ ፡ ዘንድ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 7 ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ አባትንና ፡ እናትን ፡ አቃለሉ ፤ በመካከልሽ ፡ በመጻተኛው ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ አደረጉ ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ድኻ ፡ አደጉንና ፡ መበለቲቱን ፡ አስጨነቁ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 8 ፤ ቅድሳቴንም ፡ ናቅሽ ፡ ሰንበታቴንም ፡ አረከሽ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 9 ፤ ደምን ፡ ያፈሱ ፡ ዘንድ ፥ ቀማኞች ፡ ሰዎች ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ በሉ ፤ በመካከልሽ ፡ ሴሰኝነትን ፡ አደረጉ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 10 ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ የአባቶቻቸውን ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋ ፡ ገለጡ ፤ ባንቺም ፡ ውስጥ ፡ አደፍ ፡ ያለባትን ፡ አዋረዱ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 11 ፤ ሰውም ፡ በባልንጀራው ፡ ሚስት ፡ ርኵሰትን ፡ አደረገ ፥ አባትም ፡ የልጁን ፡ ሚስት ፡ አረከሰ ፥ ባንቺም ፡ ዘንድ ፡ ወንድም ፡ የአባቱን ፡ ልጅ ፡ እኅቱን ፡ አሳፈረ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 12 ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ደምን ፡ ያፈሱ ፡ ዘንድ ፥ ጉቦን ፡ ተቀበሉ ፤ አንቺም ፡ ዐራጣና ፡ ትርፍ ፡ ወስደሻል ፥ ከባልንጀራዎችሽም ፡ በቅሚያ ፡ የሥሥትን ፡ ትርፍ ፡ አገኘሽ ፥ እኔንም ፡ ረሳሽኝ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ አንቺ ፡ ባደረግሽው ፡ ሥሥት ፡ በመካከልሽም ፡ በነበረው ፡ ደም ፡ ላይ ፡ እጄን ፡ አጨበጨብኹ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 14 ፤ በእውኑ ፡ እኔ ፡ በማደርግብሽ ፡ ወራት ፡ ልብሽ ፡ ይታገሣልን ፧ ወይስ ፡ እጅሽ ፡ ትጸናለችን ፧ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ፥ አደርገውማለኹ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 15 ፤ ወደ ፡ አሕዛብም ፡ እበትንሻለኹ ፡ ወደ ፡ አገሮችም ፡ እዘራሻለኹ ፥ ርኵሰትሽንም ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 16 ፤ በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ አንቺ ፡ ትረክሻለሽ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቂያለሽ ።

ሕዝ. ፥ 22 ፥ 17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ለእኔ ፡ እንደ ፡ አተላ ፡ ኾኑብኝ ፤ እነርሱ ፡ ዅሉ ፡ በከውር ፡ ውስጥ ፡ መዳብና ፡ ቈርቈሮ ፡ ብረትና ፡ ርሳስ ፡ ናቸው ፤ የብር ፡ አተላ ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዅላችኹ ፡ አተላ ፡ ኾናችኋልና ፥ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ እሰበስባችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ እንዲያቀልጡት ፡ እሳት ፡ ያናፉበት ፡ ዘንድ ፥ ብርንና ፡ መዳብን ፡ ብረትንና ፡ ርሳስን ፡ ቈርቈሮንም ፡ በከውር ፡ እንደሚሰበስቡ ፥ እንዲሁ ፡ በቍጣዬና ፡ በመዓቴ ፡ እሰበስባችኋለኹ ፥ በዚያም ፡ ውስጥ ፡ እጨምራችኋለኹ ፡ አቀልጣችኹማለኹ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ እሰበስባችኹማለኹ ፡ የመዓቴንም ፡ እሳት ፡ አናፉባችኋለኹ ፡ በውስጡም ፡ ትቀልጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ብርም ፡ በከውር ፡ ውስጥ ፡ እንደሚቀልጥ ፥ እንዲሁ ፡ በውስጣ ፡ ትቀልጣላችኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ መዓቴን ፡ እንዳፈሰስኹባችኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፦ አንቺ ፡ ያልነጻሽ ፡ በቍጣም ፡ ቀን ፡ ያልዘነበብሽ ፡ ምድር ፡ ነሽ ፡ በላት ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ በውስጣ ፡ ያሉ ፡ ነቢያት ፡ እንደሚጮኽና ፡ እንደሚናጠቅ ፡ አንበሳ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ ተማማሉ ፤ ነፍሶችን ፡ በልተዋል ፥ ብልጥግናና ፡ ሀብትን ፡ ወስደዋል ፥ በውስጣም ፡ መበለቶችን ፡ አብዝተዋል ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ ካህናቷም ፡ ሕጌን ፡ በድለዋል ፡ ቅድሳቴንም ፡ አርክሰዋል ፤ ቅዱስ ፡ በኾነና ፡ ቅዱስ ፡ ባልኾነ ፡ መካከልም ፡ አልለዩም ፥ በንጹሕና ፡ በርኩስ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ ልዩነት ፡ አላስታወቁም ፤ ዐይናቸውንም ፡ ከሰንበታቴ ፡ ሰወሩ ፡ እኔም ፡ በመካከላቸው ፡ ረከስኹ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ በውስጣ ፡ ያሉ ፡ አለቃዎቿ ፡ የሥሥትን ፡ ትርፍ ፡ ለማግኘት ፡ ሲሉ ፡ ደምን ፡ ያፈሱ ፡ ዘንድ ፥ ነፍሶችንም ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፥ እንደሚናጠቁ ፡ ተኵላዎች ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሳይናገር ፡ ነቢያቷ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ እያሉ ፡ ከንቱን ፡ ራእይ ፡ በማየት ፡ የሐሰትንም ፡ ሟርት ፡ ለእነርሱ ፡ በማሟረት ፡ ያለገለባ ፡ በጭቃ ፡ ይመርጓቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ የምድርን ፡ ሕዝብ ፡ ግፍ ፡ አደረጉ ፡ ቅሚያም ፡ ሠሩ ፤ ድኻዎችንና ፡ ችግረኞችን ፡ አስጨነቁ ፥ መጻተኛውንም ፡ በደሉ ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ ቅጥርን ፡ የሚጠግንን ፥ ምድሪቱንም ፡ እንዳላጠፋት ፡ በፈረሰበት ፡ በኩል ፡ በፊቴ ፡ የሚቆምላትን ፡ ሰው ፡ በመካከላቸው ፡ ፈለግኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላገኘኹም ።

ሕዝ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ ቍጣዬን ፡ አፈሰስኹባቸው ፥ በመዓቴም ፡ እሳት ፡ አጠፋኋቸው ፤ መንገዳቸውንም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ መለስኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። _____

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የአንዲት ፡ እናት ፡ ልጆች ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ በግብጽም ፡ አመነዘሩ ፥ በኰረዳነታቸው ፡ አመነዘሩ ፤ በዚያ ፡ ጡቶቻቸው ፡ ሟሸሹ ፡ በዚያም ፡ የድንግልናቸውን ፡ ጡቶች ፡ ዳበሱ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ ስማቸውም ፡ የታላቂቱ ፡ ኦሖላ ፡ የእኅቷም ፡ ኦሖሊባ ፡ ነበረ ፥ ለኔም ፡ ኾኑ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችንም ፡ ወለዱ ። ስማቸውም ፡ ኦሖላ ፡ ሰማርያ ፡ ናት ፤ ኦሖሊባ ፡ ደግሞ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ናት ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ ኦሖላም ፡ ገለሞተችብኝ ፥ ውሽማዎቿንም ፡ ጎረቤቶቿን ፡ አሶራውያንን ፡ በፍቅር ፡ ተከተለቻቸው ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ እነርሱም ፡ ሰማያዊ ፡ ሐር ፡ የለበሱ ፡ አለቃዎችና ፡ ሹማምቶች ፥ መልከ ፡ መልካሞች ፡ ጐበዛዝት ፥ በፈረስ ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡ ፡ ፈረሰኞች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ግልሙትናዋንም ፡ ከተመረጡ ፡ ከአሶር ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ አደረገች ፥ በፍቅር ፡ በተከተለቻቸውም ፡ ጣዖቶቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ረከሰች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ በግብጽም ፡ የነበረውን ፡ ግልሙትናዋን ፡ አልተወችም ፤ በዚያ ፡ በከሠረዳነቷ ፡ ጊዜ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ተኝተው ፡ ነበር ፥ የድንግልናዋንም ፡ ጡቶች ፡ ዳብሰው ፡ ነበር ፥ ግልሙትናቸውንም ፡ አፍሰውባት ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ በፍቅር ፡ በተከተለቻቸው ፣ በውሽማዎቿ ፣ በአሶራውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋት ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ እነርሱም ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋን ፡ ገለጡ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿንም ፡ ማርከው ፡ ወሰዱ ፥ ርሷንም ፡ በሰይፍ ፡ ገደሉ ፤ ፍርድንም ፡ ስላደረጉባት ፡ በሴቶች ፡ መካከል ፡ መተረቻ ፡ ኾነች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ እኅቷም ፡ ኦሖሊባ ፡ ይህን ፡ አየች ፤ ኾኖም ፡ ከርሷ ፡ ይልቅ ፡ በፍቅር ፡ በመከተሏ ፡ ረከሰች ፥ ግልሙትናዋም ፡ ከእኅቷ ፡ ግልሙትና ፡ ይልቅ ፡ በዛ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ አለቃዎችንና ፡ ሹማምቶችን ፡ ጎረቤቶቿን ፡ ጌጠኛ ፡ ልብስ ፡ የለበሱትን ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ፈረሰኞች ፥ ኹሉም ፡ መልከ ፡ መልካሞችን ፡ ጐበዛዝት ፡ አሶራውያንን ፡ በፍቅር ፡ ተከተለቻቸው ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ የረከሰችም ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ አየኹ ፥ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ መንገድ ፡ ኼደዋል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ ግልሙትናዋንም ፡ አበዛች ፤ በቀይ ፡ ቀለምም ፡ የተሳለችውን ፡ የከለዳውያንን ፡ ሥዕል ፥ በናስ ፡ ላይ ፡ የተሳሉትን ፡ ሰዎች ፡ አየች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ በወገባቸው ፡ ዝናር ፡ የታጠቁ ፡ ራሳቸውንም ፡ በቀለማዊ ፡ መጠምጠሚያ ፡ የጠመጠሙ ፡ ነበሩ ፤ ኹሉም ፡ ከተወለዱባት ፡ አገር ፡ የኾኑትን ፡ የከለዳውያንን ፡ ልጆች ፡ መስለው ፡ መሳፍንትን ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ ባየቻቸውም ፡ ጊዜ ፡ በፍቅር ፡ ተከተለቻቸው ፥ ወደከላውዴዎን ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መልእክተኞችን ፡ ላከች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ የባቢሎንም ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ፍቅር ፡ ወዳለበት ፡ መኝታ ፡ መጡ ፡ በግልሙትናቸውም ፡ አረከሷት ፤ ርሷም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ረከሰች ፡ ነፍሷም ፡ ከነርሱ ፡ ተለየች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ግልሙትናዋንም ፡ ገለጠች ፡ ኀፍረተ ፡ ሥጋዋንም ፡ አሳየች ፤ ነፍሴም ፡ ከእኅቷ ፡ እንደ ፡ ተለየች ፡ እንዲሁ ፡ ነፍሴ ፡ ከርሷ ፡ ተለየች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በግብጽ ፡ ምድር ፡ የገለሞተችበትን ፡ የከሠረዳነቷን ፡ ዘመን ፡ ዐስባ ፡ ግልሙትናዋን ፡ አበዛች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ ሥጋቸውም ፡ እንደ ፡ አህያዎች ፡ ሥጋ ፡ ዘራቸውም ፡ እንደ ፡ ፈረሶች ፡ ዘር ፡ የኾነውን ፡ እነዚያን ፡ ምልምሎች ፡ በፍቅር ፡ ተከተለቻቸው ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ ስለከሠረዳነትሽ ፡ ምክንያት ፡ ግብጻውያን ፡ ጡቶችሽን ፡ በዳበሱ ፡ ጊዜ ፡ የከሠረዳነትሽን ፡ ሴሰኝነት ፡

ዐሰብሽ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፡ ኦሖሊባ ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ነፍስሽ ፡ ከነርሱ ፡ የተለየች ፡ ውሽማዎችሽን ፡ አስነሣብሻለኹ ፥ በዙሪያሽም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ አመጣቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፡ የባቢሎን ፡ ሰዎች ፡ ከለዳውያንም ፡ ኹሉ ፥ ፋቁድ ፥ ሱሔ ፥ ቆዓ ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ አሶራውያን ፡ ኹሉ ፥ መልከ ፡ መልካሞች ፡ ጐበዛዝት ፥ አለቃዎችና ፡ ሹማምቶች ፡ ኹሉ ፥ መሳፍንቶችና ፡ አማካሪዎች ፡ ኹሉ ፥ በፈረስ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፡ ናቸው ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ በመሣሪያና ፡ በሠረገላ ፡ በመንኰራኵርም ፡ በአሕዛብም ፡ ጉባኤ ፡ ይመጡብሻል ፤ ጋሻና ፡ አላባሽ ፡ ጋሻ ፡ ራስ ፡ ቍርም ፡ ይዘው ፡ በዙሪያሽ ፡ ይዘጋጁብሻል ፤ ፍርድንም ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ እንደ ፡ ፍርዳቸውም ፡ ይፈርዱብሻል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ ቅንአቴንም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፡ በመዓትም ፡ ያደርጉብሻል ፤ አፍንጫሽንና ፡ ጐሮሽንም ፡ ከአንቺ ፡ ይቈርጣሉ ፥ ከአንቺም ፡ የቀረ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃል ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽንም ፡ ማርከው ፡ ይወስዳሉ ፥ ከአንቺም ፡ የቀረውን ፡ እሳት ፡ ትበላቸዋለች ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ ልብስሽንም ፡ ይገፉሻል ፥ የክብርሽንም ፡ ጌጥ ፡ ይወስዳሉ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ ሴሰኝነትሽንም ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣሽውን ፡ ግልሙትናሽንም ፡ ከአንቺ ፡ አስቀራለኹ ፤ ዐይንሽንም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አታነሺም ፡ ግብጽንም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አታስቢም ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 28 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ በጠላሻቸው ፡ እጅ ፥ ነፍስሽ ፡ በተለየቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥሻለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 29 ፤ እነርሱም ፡ በጥል ፡ ያደርጉብሻል ፥ የደከምሽበትንም ፡ ኹሉ ፡ ይወስዳሉ ፥ ዕራቍትሽንና ፡ ዕርቃንሽን ፡ አድርገውም ፡ ይተዉሻል ፤ የግልሙትናሽም ፡ ነውር ፥ ሴሰኝነትሽና ፡ ግልሙትናሽም ፡ ኹሉ ፡ ይገለጣል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ስላመነዘርሽ ፥ በጣዖቶቻቸውም ፡ ስለ ፡ ረከሽ ፥ ይህን ፡ ያደርጉብሻል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ በእኅትሽ ፡ መንገድ ፡ ኼደሻል ፤ ስለዚህ ፥ ጽዋዋን ፡ በእጅሽ ፡ እሰጥሻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የጠለቀውንና ፡ የሰፋውን ፡ ብዙም ፡ የሚይዘውን ፡ የእኅትሽን ፡ ጽዋ ፡ ትጠጪያለሽ ፤ መሳቂያና ፡ መሳለቂያም ፡ ትኾኛለሽ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ በእኅትሽ ፡ በሰማርያ ፡ ጽዋ ፥ በድንጋጤና ፡ በጥፋት ፡ ጽዋ ፥ በስካርና ፡ በውርደት ፡ ትሞልያለሽ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 34 ፤ ትጠጪዋለሽ ፥ ትጨልጪውማለሽ ፤ ገሉንም ፡ ታኝኪዋለሽ ፥ ጡትሽንም ፡ ትሸነትሪዋለሽ ፤ እኔ ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 35 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዘንግተሽኛልና ፥ ወደ ፡ ኋላሽም ፡ ጥለሽኛልና ፥ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ሴሰኝነትሽንና ፡ ግልሙትናሽን ፡ ተሸከሚ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 36 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በኦሖላና ፡ በኦሖሊባ ፡ ትፈርዳለኽን ፧ ኀጢአታቸውንም ፡ ታስታውቃቸዋለኽ ፧

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 37 ፤ አመንዝረዋልና ፥ ደምም ፡ በእጃቸው ፡ አለና ፥ ከጣዖቶቻቸውም ፡ ጋራ ፡ አመንዝረዋልና ፥ ለኔም ፡ የወለዷቸውን ፡ ልጆቻቸውን ፡ መብል ፡ እንዲኾኑላቸው ፡ በእሳት ፡ አሳልፈዋቸዋልና ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 38 ፤ ይህን ፡ ደግሞ ፡ አድርገውብኛል ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ መቅደሴን ፡ አርክሰዋል ፡ ሰንበታቴንም ፡

ሸረዋል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 39 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ ለጣዖቶቻቸው ፡ በሠዉ ፡ ጊዜ ፥ በዚያው ፡ ቀን ፡ ያረክሱት ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ መቅደሴ ፡ ገቡ ፤ እንሆም ፥ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ እንደዚህ ፡ አደረጉ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 40 ፤ ደግሞ ፡ መልእክተኛ ፡ ወደተላከባቸው ፡ ከሩቅም ፡ ወደሚመጡ ፡ ሰዎች ፡ ልካችኋል ፤ እንሆም ፡ መጡ ፥ አንቺም ፡ ታጠብሽላቸው ፡ ዐይኖችሽንም ፡ ተኳልሽ ፡ ጌጥም ፡ አጌጥሽ ፤

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 41 ፤ በክብር ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥሽ ፥ በፊት ፡ ለፊቷም ፡ ማእድ ፡ ተዘጋጅታ ፡ ነበር ፥ ዕጣኔንና ፡ ዘይቴንም ፡ አኖርሽባት ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 42 ፤ የደስተኞችም ፡ ድምፅ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፤ ከብዙም ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ጋራ ፡ ሰካራሞቹ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ መጡ ፤ በእጃቸው ፡ አንባር ፡ በራሳቸውም ፡ የተዋበ ፡ አክሊል ፡ አደረጉ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 43 ፤ እኔም ፡ በምንዝር ፡ ላረጀችው ፦ አኹን ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ያመነዝራሉ ፡ ርሷም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ታመነዝራለች ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 44 ፤ ወደ ፡ ጋለሞታም ፡ እንደሚገቡ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገቡ ፤ እንዲሁ ፡ ይሰስኑ ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ ኦሖላና ፡ ወደ ፡ ኦሖሊባ ፡ ገቡ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 45 ፤ ሴቶቹ ፡ አመንዝራዎች ፡ ናቸውና ፥ በእጃቸውም ፡ ደም ፡ አለና ፡ ጻጽቃን ፡ ሰዎች ፡ በአመንዝሮቹና ፡ በደም ፡ አፍሳሾቹ ፡ ሴቶች ፡ ላይ ፡ በሚፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ይፈርዱባቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 46 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጉባኤን ፡ አመጣባቸዋለኹ ፥ ለመበተንና ፡ ለመበዝበዝም ፡ አሳልፌ ፡ አሰጣቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 47 ፤ ጉባኤውም ፡ በድንጋይ ፡ ይወግሯቸዋል ፡ በሰይፋቸውም ፡ ይቈርጧቸዋል ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውንም ፡ ይገድላሉ ፥ ቤቶቻቸውንም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 48 ፤ ሴቶችም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሴሰኝነታችኹ ፡ እንዳይሠሩ ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፥ ሴሰኝነትን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 23 ፡ 49 ፤ ሴሰኝነታችኹንም ፡ በላያችኹ ፡ ላይ ፡ ይመልሳሉ ፥ እናንተም ፡ የጣዖቶቻችኹን ፡ ኀጢአት ፡ ትሸከማላችኹ ፤ እኔም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ በዘጠነኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የዚህን ፡ ቀን ፥ የዛሬን ፡ ቀን ፡ ስም ፡ ጻፍ ፤ በዚህ ፡ ቀን ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቀረበ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ለዐመፀኛውም ፡ ቤት ፡ ምሳሌን ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጣድ ፥ ምንቸቲቱን ፡ ጣድ ፥ ውሃም ፡ ጨምርባት ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ቍራጫንም ፥ መልካሙን ፡ ቍራጭ ፡ ኹሉ ፥ ጭኑንና ፡ ወርቹን ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ሰብስብ ፥ የተመረጡትንም ፡ ዐጥንቶች ፡ ሙላባት ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ከመንጋው ፡ የተመረጠውን ፡ ውሰድ ፥ ዐጥንቶቹም ፡ እንዲበስሉ ፡ ዕንጨት ፡ በበታቿ ፡

ማግድ ፤ ዐጥንቶቹም ፡ በውስጧ ፡ ይቀቀሉ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዝገቷ ፡ ላለባት ፥ ዝገቷም ፡ ከርሷ ፡ ላልወጣ ፡ ምንቸት ፥ ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! ፡ ቍራጭ ፡ ቍራጩን ፡ አውጣ ፤ ዕጣ ፡ አልወደቀባትም ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ደሟ ፡ በውስጧ ፡ አለ ። በተራቈተ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አደረገችው ፡ እንጂ ፡ በዐፈር ፡ ይከደን ፡ ዘንድ ፥ በመሬት ፡ ላይ ፡ አላፈሰሰችውም ፤

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ መዓቴን ፡ አወጣ ፡ ዘንድ ፥ በቀሌንም ፡ እበቀል ፡ ዘንድ ፥ ደሟ ፡ እንዳይከደን ፡ በተራቈተ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ አደረግኹ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ማገዶዋን ፡ ታላቅ ፡ አደርገዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ዕንጨቱን ፡ አብዛ ፤ እሳቱን ፡ አንድድ ፤ ሥጋውን ፡ ቀቅል ፤ መረቁን ፡ አጣፍጠው ፤ ዐጥንቶቹ ፡ ይቃጠሉ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ትሞቅም ፡ ዘንድ ፥ ናሷም ፡ ትግል ፡ ዘንድ ፥ ርኵሰቷም ፡ በውስጧ ፡ ይቀልጥ ፡ ዘንድ ፥ ዝገቷም ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፥ ባዶዋን ፡ በፍም ፡ ላይ ፡ አድርጋት ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ በከንቱ ፡ ደከመች ፤ ኾኖም ፡ ዝገቷ ፡ በእሳት ፡ ስንኳ ፡ አልለቀቀም ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ በርኵሰትሽ ፡ ሴሰኝነት ፡ አለ ፤ አነጻኹሽ ፥ አልነጻሽምና ፡ መዓቴን ፡ በላይሽ ፡ እስክጨርስ ፡ ድረስ ፡ እንግዲህ ፡ ከርኵሰትሽ ፡ አትነጺም ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ፤ ይመጣል ፥ እኔም ፡ አደርገዋለኹ ፤ አልመለስም ፥ አልራራም ፥ አልጸጸትም ፤ እንደ ፡ መንገድሽና ፡ እንደ ፡ ሥራሽ ፡ ይፈርዱብሻል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ የዐይንኽን ፡ አምሮት ፡ በመቅሠፍት ፡ እወስድብኻለኹ ፤ አንተም ፡ ወይ ፡ አትበል ፡ አታልቅስም ፡ እንባኽንም ፡ አታፍስ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ በቀስታ ፡ ተክዝ ፤ ለሟቾችም ፡ አታልቅስ ፥ መጠምጠሚያኽን ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ አድርግ ፥ ጫማኽንም ፡ በእግርኽ ፡ አጥልቅ ፥ ከንፈሮችኽንም ፡ አትሸፍን ፡ የሰዎችንም ፡ እንጀራ ፡ አትብላ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ እኔም ፡ በማለዳ ፡ ለሕዝቡ ፡ ተናገርኹ ፥ ወደ ፡ ማታም ፡ ሚስቴ ፡ ሞተች ፤ በነጋውም ፡ እንደ ፡ ታዘዝኹ ፡ አደረግኹ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ሕዝቡም ፦ ይህ ፡ የምታደርገው ፡ ነገር ፡ ለእኛ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አትነግረንምን ፧ አሉኝ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ እንዲህ ፡ አልኋቸው ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የኀይላችኹን ፡ ትምክሕት ፥ የዐይናችኹን ፡ አምሮት ፥ የነፍሳችኹን ፡ ምኞት ፡ መቅደሴን ፡ አረክሳለኹ ፤ ያስቀራችኋቸውም ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ እኔም ፡ እንዳደረግኹ ፡ እናንተ ፡ ታደርጋላችኹ ፤ ከንፈራችኹን ፡ አትሸፍኑም ፡ የሰዎችንም ፡ እንጀራ ፡ አትበሉም ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ መጠምጠሚያችኹም ፡ በራሳችኹ ፡ ጫማችኹም ፡ በእግራችኹ ፡ ይኾናል ፤ ዋይ ፡ አትሉም ፡ አታለቅሱምም ፤ በኀጢአታችኹም ፡ ትሰለስላላችኹ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹም ፡ ታንጐራጕራላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ሕዝቅኤልም ፡ ምልክት ፡ ይኾናችኋል ፤ ርሱ ፡ እንዳደረገ ፡ ዅሉ ፡ እናንተ ፡ ታደርጋላችኹ ፤ ይህም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ኀይላቸውን ፥ የተመኩበትንም ፡ ደስታ ፥ የዐይናቸውን ፡ አምሮት ፥ የነፍሳቸውንም ፡ ምኞት ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ በወሰድኹባቸው ፡ ቀን ፥

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ያመለጠው ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በጕሮኽ ፡ ያሰማ ፡ ዘንድ ፥ ወዳንተ ፡ ይመጣል ።

ሕዝ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ አፍኽ ፡ ላመለጠው ፡ ይከፈታል ፥ አንተም ፡ ትናገራለኽ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ዲዳ ፡ አትኾንም ፤ ምልክትም ፡ ትኾናቸዋለኽ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ ወደዐሞን ፡ ልጆች ፡ አቅንተኽ ፡ ትንቢት ፡ ተናገርባቸው ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ለዐሞንም ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ የጌታን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መቅደሴ ፡ በረከሰ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤልም ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ በኾነች ፡ ጊዜ ፡ የይሁዳም ፡ ቤት ፡ በተማረኩ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ዕሠይ ፡ ብለኻልና ፥

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ርስት ፡ አድርጌ ፡ ለምሥራቅ ፡ ልጆች ፡ አሳልፌ ፡ አሰጥኻለኹ ፥ እነርሱም ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ ይሰፍራሉ ፥ ማደሪያዎቻቸውንም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ይሠራሉ ፤ ፍሬኽን ፡ ይበላሉ ፥ ወተትኽንም ፡ ይጠጣሉ ፤

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ የዐሞንን ፡ ከተማ ፡ ለግመሎች ፡ ማሰማሪያ ፥ የዐሞንንም ፡ ልጆች ፡ ለመንጋ ፡ መመሰጊያ ፡ አደርጋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ በእጅኽ ፡ አጨብጭበኻልና ፥ በእግርኽም ፡ አሸብሽበኻልና ፥ በእስራኤልም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በነፍስኽ ፡ ንቀት ፡ ዅሉ ፡ ደስ ፡ ብሎኻልና ፥

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ እጄን ፡ ዘርግቼብኻለኹ ፥ ለአሕዛብም ፡ አስበዘብዝኻለኹ ፥ ከአሕዛብም ፡ ለይቼ ፡ እቈርጥኻለኹ ፥ ከአገሮችም ፡ አጠፋኻለኹ ፡ እፈጅኽማለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃለኽ ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሞዐብና ፡ ሴይር ፦ እንሆ ፥ የይሁዳ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ነው ፡ ብለዋልና ፥

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የሞዐብን ፡ ጫንቃ ፡ ከከተማዎቹ ፥ በዳርቻው ፡ ካሉት ፡ የምድሩ ፡ ትምክሕት ፡ ከኾኑት ፡ ከተማዎቹ ፥ ከቤትየሺሞት ፥ ከበዓልሜዎን ፥

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ከቂርያታይም ፥ ከዐሞን ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ ለምሥራቅ ፡ ልጆች ፡ እከፍታለኹ ። የዐሞን ፡ ልጆች ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይታሰቡ ፡ ርስት ፡ አድርጌ ፡ እሰጣቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ በሞዐብም ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ አደርጋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኤዶምያስ ፡ በይሁዳ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ በቀል ፡

አድርጓልና ፥ ቂም ፡ ይዟልና ፥ ብድራትንም ፡ አስከፍሏልና ፥

ሕዝ. ፥ 25 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እጄን ፡ በኤዶምያስ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፥ ከርሷም ፡ ዘንድ ፡ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ አጠፋለኹ ፥ ከቴማንም ፡ ዠምሮ ፡ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ፥ እስከ ፡ ድዳንም ፡ ድረስ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 25 ፥ 14 ፤ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ እጅ ፡ ኤዶምያስን ፡ እበቀላለኹ ፤ እንደ ፡ ቍጣዬና ፡ እንደ ፡ መዓቴም ፡ መጠን ፡ በኤዶምያስ ፡ ያደርጋሉ ፤ በቀሌንም ፡ ያውቃሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 25 ፥ 15 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ፍልስጥኤማውያን ፡ በቀልን ፡ አድርገዋልና ፥ በዘወትርም ፡ ጠላትነት ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፥ በነፍሳቸው ፡ ንቀት ፡ ተበቅለዋልና ፥

ሕዝ. ፥ 25 ፥ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እጄን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፥ ከሊታውያንንም ፡ እቈርጣለኹ ፥ የባሕሩንም ፡ ዳር ፡ ቅሬታ ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 25 ፥ 17 ፤ በመዓት ፡ መቅሠፍትም ፡ ታላቅ ፡ በቀል ፡ አደርግባቸዋለኹ ፤ በቀሌንም ፡ በላያቸው ፡ ባደረግኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ ከወሩ ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጢሮስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፦ ዕሠይ ፥ የአሕዛብ ፡ በር ፡ የነበረች ፡ ተሰብራለች ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ ተመልሳለች ፤ ርሷ ፡ ፈርሳለችና ፡ እኔ ፡ እሞላለኹ ፡ ብላለችና ፡

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጢሮስ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ባሕርም ፡ ሞገዷን ፡ እንደምታወጣ ፡ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አወጣብሻለኹ ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 4 ፤ የጢሮስንም ፡ ቅጥሮች ፡ ያጠፉ ፡ ግንቦቿንም ፡ ያፈርሳሉ ፤ ትቢያዋንም ፡ ከርሷ ፡ እፍቃለኹ ፥ የተራቈተ ፡ ድንጋይም ፡ አደርጋታለኹ ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 5 ፤ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ የመረብ ፡ ማስጫ ፡ ትኾናለች ፤ እኔ ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለአሕዛብም ፡ ብዝበዛ ፡ ትኾናለች ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 6 ፤ በሜዳ ፡ ያሉትም ፡ ሴቶች ፡ ልጆቿ ፡ በሰይፍ ፡ ይገደላሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 7 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ ከሰሜን ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ የባቢሎንን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾርን ፡ ከፈረሶችና ፡ ከሠረገላዎች ፡ ከፈረሰኞችም ፡ ከጉባኤና ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በጢሮስ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 8 ፤ በሜዳ ፡ ያሉትን ፡ ሴቶች ፡ ልጆችሽን ፡ በሰይፍ ፡ ይገድላቸዋል ፥ ዐምባም ፡ ይሠራብሻል ፡ ዐፈርንም ፡ ይደለድልብሻል ፡ ጋሻም ፡ ያነሣብሻል ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 9 ፤ ማፍረሻውን ፡ በቅጥርሽ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፥ ግንቦችሽንም ፡ በምሣር ፡ ያፈርሳል ።

ሕዝ. ፥ 26 ፥ 10 ፤ ከፈረሶቹም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ትቢያቸው ፡ ይከድንሻል ፤ ሰዎችም ፡ በተናደች ፡ ቅጥር ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ እንደሚገቡ ፡ ርሱ ፡ በበሮችሽ ፡ ሲገባ ፥ ከፈረሰኞችና ፡ ከመንኰራኵሮች ፡ ከሠረገላዎችም ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡

ቅጥርሽ ፡ ትናወጣለች ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ በፈረሶቹ ፡ ኮቴ ፡ ጐዳናዎችሽን ፡ ሹሉ ፡ ይረመርማል ፥ ሕዝብሽንም ፡ በሰይፍ ፡ ይገድላል ፥ የብርታትሽም ፡ ሐውልት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይወድቃል ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ብልጥግናሽንም ፡ ይማርካሉ ፥ ሸቀጥሽንም ፡ ይበዘብዛሉ ፤ ቅጥርሽንም ፡ ያፈርሳሉ ፥ ተድላ ፡ የምታደርጊባቸውን ፡ ቤቶችሽን ፡ ያጠፋሉ ፤ ድንጋይሽንና ፡ ዕንጨትሽን ፡ መሬትሽንም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ይጥላሉ ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ የዘፋኞችሽንም ፡ ብዛት ፡ ዝም ፡ አሠኛለኹ ፤ የመሰንቆሽም ፡ ድምፅ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አይሰማም ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ የተራቈተ ፡ ድንጋይ ፡ አደርግሻለኹ ፡ የመረብም ፡ ማስጫ ፡ ትኾኛለሽ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትሠሪም ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጢሮስን ፡ እንዲህ ፡ ይላታል ፦ የተወጉት ፡ ባንቋረሩ ፡ ጊዜ ፥ በውስጥሽ ፡ እልቂት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ ከውድቀትሽ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ ደሴቶች ፡ ይነዋወጡ ፡ የለምን ፧

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ የባሕርም ፡ አለቃዎች ፡ ሹሉ ፡ ከዙፋኖቻቸው ፡ ይወርዳሉ ፤ መጐናጸፊያቸውን ፡ ያወጣሉ ፡ ወርቀ ፡ ዘቦ ፡ ልብሳቸውንም ፡ ያወልቃሉ ፤ መንቀጥቀጥን ፡ ለብሰው ፡ በመሬት ፡ ላይ ፡ ይቀመጣሉ ፥ ሹልጊዜም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፡ ባንቺም ፡ ይደነቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ ባንቺም ፡ ላይ ፡ ሙሾ ፡ ያሞሻሉ ፥ እንዲህም ፡ ይሉሻል ፦ በባሕር ፡ የተቀመጥሽ ፡ በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ የጸናሽ ፥ ከሚቀመጡብሽም ፡ ጋራ ፡ በዙሪያሽ ፡ የሚኖሩትን ፡ ሹሉ ፡ ያስፈራሽ ፥ የከበርሽ ፡ ከተማ ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ ጠፋሽ! ፡

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ አኹን ፡ በውድቀትሽ ፡ ቀን ፡ ደሴቶች ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፥ በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ ደሴቶች ፡ ከመጥፋትሽ ፡ የተነሣ ፡ ይደነግጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሰው ፡ እንደሌለባቸው ፡ ከተማዎች ፡ ባድማ ፡ ከተማ ፡ ባደረግኹሽ ፡ ጊዜ ፥ ቀላዩንም ፡ ባወጣኹብሽ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ በከደኑሽ ፡ ጊዜ ፥

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ የቀድሞ ፡ ሕዝብ ፡ ወዳሉበት ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱት ፡ ጋራ ፡ አወርድሻለኹ ፤ የሚኖርብሽም ፡ እንዳይገኝ ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ቀድሞ ፡ በፈረሰችው ፡ ስፍራ ፥ በታችኛዩቱ ፡ ምድር ፡ አኖርሻለኹ ፤ ጌጥሽንም ፡ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ አላኖርም ።

ሕዝ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ለድንጋጤ ፡ አደርግሻለኹ ፡ እንግዲህም ፡ አትኖሪም ፤ ትፈለጊያለሽ ፡ ለዘለዓለምም ፡ አትገኚም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ጢሮስ ፡ ሙሾ ፡ አድርግ ፥

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ በባሕር ፡ መግቢያ ፡ የምትኖር ፡ በብዙም ፡ ደሴቶች ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ንግድን ፡ የምታደርግ ፡ ጢሮስንም ፡ እንዲህ ፡ በላት ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጢሮስ ፡ ሆይ ፥ አንቺ ። በውበት ፡ ፍጹም ፡ ነኝ ፡ ብለሻል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ዳርቻሽ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ ሠሪዎችሽ ፡ ውበትሽን ፡ ፈጽመዋል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ሳንቃዎችሽን ፡ ዥሉ ፡ ከሳኔር ፡ ጥድ ፡ ሠርተዋል ፥ ደቀልንም ፡ ይሠሩልሽ ፡ ዘንድ ፥ ከሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ወስደዋል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ ከባሳን ፡ ኮምቦል ፡ መቅዘፊያሽን ፡ ሠርተዋል ፥ በዝኖን ፡ ጥርስ ፡ ከታሻበ ፡ ከኪቲም ፡ ደሴቶች ፡ ዛፍ ፡ መቀመጫዎችሽን ፡ ሠርተዋል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ዐላማ ፡ እንዲኾንልሽ ፡ ሸራሽ ፡ ከግብጽ ፡ በፍታና ፡ ከወርቅ ፡ ዘቦ ፡ ተሠርቷል ፥ መደረቢያሽም ፡ ከኤሊሳ ፡ ደሴቶች ፡ ሰማያዊና ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ ተሠርቷል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ የሲዶናና ፡ የአራድ ፡ ሰዎች ፡ ቀዛፎችሽ ፡ ነበሩ ፤ ጢሮስ ፡ ሆይ ፥ ጥበበኞችሽ ፡ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ፡ የመርከቦችሽም ፡ መሪዎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ የነበሩ ፡ የጌባል ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ጥበበኞቿ ፡ ስብራትሽን ፡ ይጠግኑ ፡ ነበር ፤ ከአንቺም ፡ ጋራ ፡ ይነግዱ ፡ ዘንድ ፥ የባሕር ፡ መርከቦች ፡ ዥሉና ፡ መርከበኞቻቸው ፡ በመካከልሽ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ፋርስና ፡ ሉድ ፡ ፉጥም ፡ በሰራዊትሽ ፡ ሰልፈኞችሽ ፡ ነበሩ ፤ ጋሻና ፡ ራስ ፡ ቀኦርም ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ያንጠለጥሉ ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ውበትሽን ፡ ሰጡ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ የአራድ ፡ ሰዎችና ፡ ሰራዊቶችሽ ፡ በቅጥሮችሽ ፡ ላይ ፡ በዙሪያ ፡ ነበሩ ፥ ገማዳውያንም ፡ በግንቦችሽ ፡ ውስጥ ፡ ነበሩ ፤ ጋሻቸውንም ፡ በዙሪያ ፡ በቅጥርሽ ፡ ላይ ፡ አንጠለጠሉ ፥ ውበትሽንም ፡ ፈጽመዋል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ ከብልጥግናሽ ፡ ዥሉ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ተርሴስ ፡ ነጋዴሽ ፡ ነበረች ፤ በብርና ፡ በብረት ፡ በቈርቈሮና ፡ በርሳስ ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ ያዋንና ፡ ቶቤል ፡ ሞሳሕም ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ፤ የሰዎችን ፡ ነፍሳትና ፡ የናሱን ፡ ዕቃ ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ከቴርጋማ ፡ ቤትም ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ በፈረሶችና ፡ በፈረሰኞች ፡ በበቅሎዎችም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ የድዳን ፡ ሰዎች ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ። ብዙ ፡ ደሴቶች ፡ የእጅሽ ፡ ገበያዎች ፡ ነበሩ ፤ ይለውጡ ፡ ዘንድ ፥ የዝኖን ፡ ጥርስና ፡ ዞጲ ፡ አመጡልሽ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ ከሥራሽ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሶርያ ፡ ነጋዴሽ ፡ ነበረች ፡ በበሉርና ፡ በቀይ ፡ ሐር ፡ በወርቀ ፡ ዘቦም ፡ በጥሩ ፡ በፍታም ፡ በዛጐልም ፡ በቀይ ፡ ዕንቁም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ ይሁዳና ፡ የእስራኤል ፡ ምድር ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ፤ የሚኒትን ፡ ስንዴ ፡ ጣፋጭም ፡ ዕንጐቻ ፥ ማር ፡ ዘይትም ፡ በለሳንም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ ከሥራሽ ፡ ብዛትና ፡ ከብልጥግናሽ ፡ ዥሉ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ደማስቆ ፡ ነጋዴሽ ፡ ነበረች ፤ በኬልቦን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በነጭም ፡ በግ ፡ ጠጉር ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ ዌንዳንና ፡ ያዋን ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ፤ ከኦሴል ፡ የተሠራ ፡ ብረትና ፡ ብርጉድ ፣ ቀረፋም ፡ ሸቀጥሽ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ ድዳን ፡ በከብት ፡ ላይ ፡ ለመቀመጥ ፡ በመረሻት ፡ ነጋዴሽ ፡ ነበረች ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ዐረብና ፡ የቄዳር ፡ አለቃዎች ፡ ዥሉ ፡ የእጅሽ ፡ ነጋዴዎች ፡ ነበሩ ፤ በጠቦቶችና ፡ በአውራ ፡ በጎች ፡ በፍየሎችም ፡ በእነዚህ ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ የሳባና ፡ የራዕማ ፡ ነጋዴዎች ፡ እነዚህ ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ፤ በጥሩ ፡ ሽቶና ፡ በክብር ፡ ድንጋይ ፡ ዥሉ ፡ በወርቅም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ ሸቀጥ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ ካራንና ፡ ካኔ ፡ ዔዴንም ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ፤ አሶርና ፡ ኪልማድ ፡ ነጋዴዎችሽ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ እነዚህ ፡ ባማረ ፡ ልብስ ፡ በሰማያዊ ፡ ካባ ፡ በወርቀ ፡ ዘቦም ፥ በዝግባ ፡ በተሠራች ፡ በገመድም ፡ በታሰረች ፡ በግምጃም ፡ በተሞላች ፡ ሳጥን ፡ በገበያሽ ፡ ይነግዱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ የተርሴስ ፡ መርከቦች ፡ ሸቀጥሽን ፡ የሚሸከሙ ፡ ነበሩ ፤ አንቺም ፡ ተሞልተሽ ፡ ነበር ፡ በባሕርም ፡ ውስጥ ፡ እጅግ ፡ ከበርሽ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ ቀዛፊዎችሽ ፡ ወደ ፡ ትልቁ ፡ ውሃ ፡ አመጡሽ ፤ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ሰበረሽ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ ብልጥግናሽና ፡ ሸቀጥሽ ፡ ንግድሽም ፡ መርከበኞችሽም ፡ መርከብ ፡ መሪዎችሽም ፡ ሰባራሽንም ፡ የሚጠግኑ ፡ ነጋዴዎችሽም ፡ ባንቺም ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ ሰልፈኞችሽ ፡ ዥሉ ፡ በውስጥሽ ፡ ካሉት ፡ ጉባኤ ፡ ዥሉ ፡ ጋራ ፡ በወደቅሽበት ፡ ቀን ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 28 ፤ ከመርከብ ፡ መሪዎች ፡ ጩኸት ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ በዙሪያሽ ፡ ያሉ ፡ ዥሉ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 29 ፤ ቀዛፊዎችም ፡ ዥሉ ፡ መርከበኞችም ፡ መርከብ ፡ መሪዎችም ፡ ዥሉ ፡ ከመርከቦቻቸው ፡ ይወርዳሉ ፡ በመሬትም ፡ ላይ ፡ ይቆማሉ ፤

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 30 ፤ ድምፃቸውንም ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ያሰማሉ ፥ ምርር ፡ ብለውም ፡ ይጮኻሉ ፥ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ይነሰንሳሉ ፥ በዐመድም ፡ ውስጥ ፡ ይንከባለላሉ ፤

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 31 ፤ ስለ ፡ አንቺም ፡ የራሳቸውን ፡ ጠጕር ፡ ይላጫሉ ፡ ማቅም ፡ ያሸርጣሉ ፡ በነፍስ ፡ ምሬትም ፡ ስለ ፡ አንቺ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ ያለቅሳሉ ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 32 ፤ በትካዜያቸውም ፡ ልቅሶ ፡ ያነሡልሻል ፥ ስለ ፡ አንቺም ፡ ሙሾ ፡ ያሞሻሉ ፡ እንዲህም ፡ ይላሉ ፦ በባሕር ፡ መካከል ፡ ጠፍቶ ፡ እንደ ፡ ቀረ ፡ እንደ ፡ ጢሮስ ፡ ያለ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 33 ፤ ሸቀጥሽ ፡ ከባሕር ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አጥግበሻል ፤ በብልጥግናሽና ፡ በንግድሽ ፡ ብዛት ፡ የምድርን ፡ ነገሥታት ፡ ባለጠጋዎች ፡ አድርገሻል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 34 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በጥልቅ ፡ ውሃ ፡ ውስጥ ፡ በባሕር ፡ ተሰብረሻል ፡ ንግድሽና ፡ ጉባኤሽ ፡ ዥሉ ፡ በመካከልሽ ፡ ወድቀዋል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 35 ፤ በደሴቶች ፡ የሚኖሩ ፡ ዥሉ ፡ ተደንቀውብሻል ፥ ነገሥታታቸውም ፡ እጅግ ፡ ፈርተዋል ፡ ፊታቸውም ፡ ተለውጧል ።

ሕዝ. ፡ 27 ፡ 36 ፤ የአሕዛብ ፡ ነጋዴዎች ፡ አፏጨብሽ ፤ አንቺ ፡ ለድንጋጤ ፡ ኾነሻል ፥ እስከ ፡ ዘለዓለምም ፡ አትገኚም ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የጢሮስን ፡ ገዢ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልብኽ ፡ ኰርቷል ፡ አንተም ፦ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ወንበር ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ተቀምጫለኹ ፡ ብለኻል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልብኽን ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ልብ ፡ ብታደርግም ፡ አንተ ፡ ሰው ፡ ነኽ ፡ እንጂ ፡

አምላክ ፡ አይደለኽም ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ ከዳንኤል ፡ ይልቅ ፡ ጥበበኛ ፡ ነኽ ፥ ምስጢርም ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ የተሸሸገ ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ በጥበብኽና ፡ በማስተዋልኽ ፡ ብልጥግናን ፡ ለራስኽ ፡ አግኝተኻል ፡ ወርቅና ፡ ብርም ፡ በግምጃ ፡ ቤትኽ ፡ ውስጥ ፡ ሰብስበኻል ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ በታላቅ ፡ ጥበብኽና ፡ በንግድኽ ፡ ብልጥግናኽን ፡ አብዝተኻል ፡ በብልጥግናኽም ፡ ልብኽ ፡ ኰርቷል ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልብኽን ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ልብ ፡ አድርገኻልና ፥

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ የሌላ ፡ አገር ፡ ሰዎችን ፥ የአሕዛብን ፡ ጨካኞች ፥ አመጣብኻለኹ ፤ ሰይፋቸውንም ፡ በጥበብኽ ፡ ውበት ፡ ላይ ፡ ይመዛሉ ፡ ክብርኽንም ፡ ያረክሳሉ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ያወርዱኻል ፤ ተገድለው ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ትሞታለኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ በእውኑ ፡ በገዳይኽ ፡ ፊት ፦ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ትላለኽን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ በገዳይኽ ፡ እጅ ፡ ሰው ፡ ነኽ ፡ እንጂ ፡ አምላክ ፡ አይደለኽም ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ በእንግዳዎች ፡ እጅ ፡ ያልተገረዙትን ፡ ሰዎች ፡ ሞት ፡ ትሞታለኽ ፤ እኔ ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በጢሮስ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ሙሾ ፡ አሞሽተኽ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጥበብን ፡ የተሞላኽ ፡ ውበትኽም ፡ የተፈጸመ ፡ መደምደሚያ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ በዔዴን ፡ ነበርኽ ፤ የከበረ ፡ ዕንቊስ ፡ ኹሉ ፥ ሰርድዮን ፥ ቶጳዝዮን ፥ አልማዝ ፥ ቢረሌ ፥ መረግድ ፥ ኢያስጲድ ፥ ሰንፔር ፥ በሉር ፥ የሚያብረቀርቅ ፡ ዕንቊ ፥ ወርቅ ፥ ልብስኽ ፡ ነበረ ፤ የከበሮኽና ፡ የእንቢልታኽ ፡ ሥራ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፤ በተፈጠርኽበት ፡ ቀን ፡ ተዘጋጅተው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ አንተ ፡ ልትጋርድ ፡ የተቀባኽ ፡ ኪሩብ ፡ ነበርኽ ፡ በተቀደሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አኖርኹኽ ፤ በእሳት ፡ ድንጋዮች ፡ መካከል ፡ ተመላለስኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ከተፈጠርኽበት ፡ ቀን ፡ ዠምረኽ ፡ በደል ፡ እስኪገኝብኽ ፡ ድረስ ፡ በመንገድኽ ፡ ፍጹም ፡ ነበርኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ በንግድኽ ፡ ብዛት ፡ ግፍ ፡ በውስጥኽ ፡ ተሞላ ፡ ኀጢአትንም ፡ ሠራኽ ፤ ስለዚህ ፥ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ ጣልኹኽ ፤ የምትጋርድ ፡ ኪሩብ ፡ ሆይ ፥ ከእሳት ፡ ድንጋዮች ፡ መካከል ፡ አጠፋኹኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ በውበትኽ ፡ ምክንያት ፡ ልብኽ ፡ ኰርቷል ፤ ከክብርኽ ፡ የተነሣ ፡ ጥበብኽን ፡ አረከስኽ ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ጣልኹኽ ፤ ያዩኽም ፡ ዘንድ ፥ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ሰጠኹኽ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ በበደልኽ ፡ ብዛት ፡ በንግድኽም ፡ ኀጢአት ፡ መቅደስኽን ፡ አረከስኽ ፤ ስለዚህ ፥ እሳትን ፡ ከውስጥኽ ፡ አውጥቻለኹ ፡ ርሷም ፡ በልታኻለች ፥ በሚያዩኽም ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ዐመድ ፡ አድርጌኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ በአሕዛብም ፡ ውስጥ ፡ የሚያውቁኽ ፡ ኹሉ ፡ ይደነቁብኻል ፤ አንተም ፡ ለድንጋጤ ፡

ኾነኻል ፥ እስከ ፡ ዘለዓለምም ፡ አትገኝም ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 21 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ ወደ ፡ ሲዶና ፡ አቅንተኽ ፡ ትንቢት ፡ ተናገርባት ፥ እንዲህም ፡ በል ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 22 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሲዶና ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ በውስጥሽም ፡ እከብራለኹ ፤ ፍርድንም ፡ ባደረግኹባት ፡ ጊዜ ፡ በተቀደስኹባትም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 23 ፤ ቸነፈርንም ፡ በርሷ ፡ ላይ ፥ ደምንም ፡ በጐዳናዋ ፡ እሰዳለኹ ፤ ከዙሪያዋ ፡ በላይዋ ፡ ባለ ፡ ሰይፍ ፡ የተወጉ ፡ በመካከሏ ፡ ይወድቃሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 24 ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሚወጋ ፡ ሾኽ ፥ በዙሪያቸውም ፡ ካሉ ፡ ከናቋቸው ፡ ኹሉ ፡ የሚያቈስል ፡ ኵርንችት ፡ አይኾንም ፤ እኔም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 25 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ከተበተኑባቸው ፡ አሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ በሰበሰብኹ ፡ ጊዜ ፥ በአሕዛብም ፡ ፊት ፡ በተቀደስኹባቸው ፡ ጊዜ ፥ ለባሪያዬ ፡ ለያዕቆብ ፡ በሰጠኋት ፡ ምድራቸው ፡ ይቀመጣሉ ።

ሕዝ. ፥ 28 ፥ 26 ፤ ተዘልለውም ፡ ይቀመጡባታል ፤ ቤቶችንም ፡ ይሠራሉ ፡ ወይኑንም ፡ ይተክላሉ ፡ በዙሪያቸውም ፡ ባሉ ፡ በሚንቋቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ባደረግኹ ፡ ጊዜ ፡ ተዘልለው ፡ ይቀመጣሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 29 ።

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 1 ፤ በዐሥረኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ በግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖን ፡ ላይ ፡ አድርግ ፥ በርሱና ፡ በግብጽ ፡ ኹሉ ፡ ላይም ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፥

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በወንዞች ፡ መካከል ፡ የምትተኛና ፦ ወንዙ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ለራሴም ፡ ሠርቼዋለኹ ፡ የምትል ፡ ታላቅ ፡ ዐዞ ፥ የግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖን ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ።

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 4 ፤ በመንጋጋኽ ፡ መቃጥን ፡ አገባብኻለኹ ፥ የወንዞችኽንም ፡ ዓሣዎች ፡ ወደ ፡ ቅርፊትኽ ፡ አጣብቃለኹ ፤ ከወንዞችኽም ፡ መካከል ፡ አወጣኻለኹ ፥ የወንዞችኽም ፡ ዓሣዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ቅርፊትኽ ፡ ይጣበቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 5 ፤ አንተንና ፡ የወንዞችኽን ፡ ዓሣዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እጥላለኹ ፥ በምድርም ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ትወድቃለኽ ፡ እንጂ ፡ አትከማችም ፡ አትሰበሰብም ፡ መብልም ፡ አድርጌ ፡ ለምድር ፡ አራዊትና ፡ ለሰማይ ፡ ወፎች ፡ ሰጥቼኻለኹ ።

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 6 ፤ በግብጽም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሸንበቆ ፡ በትር ፡ ኾነዋልና ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 29 ፥ 7 ፤ በእጅ ፡ በያዙኽ ፡ ጊዜ ፡ ተሰበርኽ ፡ ጫንቃቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አቈሰልኽ ፤ በተደገፉብኽም ፡ ጊዜ ፡ ተሰበርኽ ፡ ወገባቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አንቀጠቀጥኽ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሰይፍ ፡ አመጣብኻለኹ ፥ ሰውንና ፡ እንስሳንም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 9 ፤ የግብጽም ፡ ምድር ፡ ባድማና ፡ ውድማ ፡ ትኾናለች ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፤ አንተ ፦ ወንዙ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ የሠራኹትም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ብለኻልና ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ በአንተና ፡ በወንዞችኽ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ የግብጽንም ፡ ምድር ፡ ከሚግዶል ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሴዌኔና ፡ እስከኢትዮጵያ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ውድማና ፡ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 11 ፤ የሰው ፡ እግር ፡ አያልፍባትም ፡ የእንስሳም ፡ ኰቴ ፡ አያልፍባትም ፥ እስከ ፡ አርባ ፡ ዓመትም ፡ ድረስ ፡ ማንም ፡ አይኖርባትም ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 12 ፤ ባድማም ፡ በኾኑ ፡ ምድሮች ፡ መካከል ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ አደርጋታለኹ ፥ በፈረሱትም ፡ ከተማዎች ፡ መካከል ፡ ከተማዎቿ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ፈርሰው ፡ ይቀመጣሉ ፤ ግብጻውያንንም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እበትናቸዋለኹ ፡ በአገሮችም ፡ እዘራቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 13 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ግብጻውያንን ፡ ከተበተኑባቸው ፡ አሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ እሰበስባለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 14 ፤ የግብጽንም ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ ወደተወለዱባትም ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ጳትሮስ ፡ እመልሳቸዋለኹ ፤ በዚያም ፡ የተዋረደች ፡ መንግሥት ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 15 ፤ ከሌላዎች ፡ መንግሥታት ፡ ዝቅ ፡ ይልቅ ፡ የተዋረደች ፡ ትኾናለች ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ አትልም ፤ በአሕዛብም ፡ ላይ ፡ እንዳይገዙ ፡ አሳንሳቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 16 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ እነርሱን ፡ በተከተሉ ፡ ጊዜ ፡ ርሷ ፡ በደልን ፡ ታሳስባለች ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ መታመኛ ፡ አትኾንላቸውም ፤ እኔም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 17 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በኻያ ፡ ሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 18 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ሰራዊቱን ፡ በጢሮስ ፡ ላይ ፡ ጽኑ ፡ አገልግሎት ፡ አስገለገለ ፤ ራስ ፡ ኹሉ ፡ የተላጨ ፡ ጫንቃም ፡ ኹሉ ፡ የተላጠ ፡ ኾኗል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በላይዋ ፡ ስላገለገለው ፡ አገልግሎት ፡ ርሱና ፡ ሰራዊቱ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ከጢሮስ ፡ አልተቀበሉም ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ለባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ እሰጠዋለኹ ፥ ብዛቷንም ፡ ይወስዳል ፡ ምርኮዋንም ፡ ይማርካል ፡ ብዝበዛዋንም ፡ ይበዘብዛል ፤ ይህም ፡ ለሰራዊቱ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ ሠርተዋልና ፥ ስላገልግሎቱ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ የግብጽን ፡ ምድር ፡ ሰጥቼዋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 29 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ቀንድን ፡ አበቅላለኹ ፥ በመካከላቸውም ፡ ለአንተ ፡ የተከፈተ ፡ አፍን ፡ እሰጣለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 30 ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዋይ! ፡ በሉ ፥ ለቀኑ ፡ ወዮ! ፡ ቀኑ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፥

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቅርብ ፡ ነው ፥ የደመና ፡ ቀን ፥ የአሕዛብ ፡ ጊዜ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 4 ፤ ሰይፍ ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፥ ሁከትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ይኾናል ፤ የተገደሉትም ፡ በግብጽ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃሉ ፥ ብዛቷንም ፡ ይወስዳሉ ፥ መሠረቷም ፡ ይፈርሳል ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 5 ፤ ኢትዮጵያና ፡ ፉጥ ፡ ሉድም ፡ የተደባለቀም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ኩብም ፡ ቃል ፡ ኪዳንም ፡ የገባችው ፡ ምድር ፡ ልጆች ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ግብጽን ፡ የሚደግፉ ፡ ይወድቃሉ ፥ የኀይሏም ፡ ትዕቢት ፡ ይወርዳል ፤ ከሚግዶል ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሴዌኔ ፡ ድረስ ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 7 ፤ ባድማም ፡ በኾኑ ፡ አገሮች ፡ መካከል ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ፥ ከተማዎቿም ፡ በፈረሱ ፡ ከተማዎች ፡ መካከል ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 8 ፤ እሳትንም ፡ በግብጽ ፡ ባነደድኹ ፡ ጊዜ ፥ ረዳቶቿም ፡ ኹሉ ፡ በተሰበሩ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 9 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ መልእክተኞች ፡ ተዘልለው ፡ የሚኖሩትን ፡ ኢትዮጵያውያንን ፡ ለማስፈራት ፡ ከፊቴ ፡ በመርከብ ፡ ይወጣሉ ፤ እንደ ፡ ግብጽም ፡ ቀን ፡ ሁከት ፡ ይኾንባቸዋል ፤ እንሆ ፥ ይመጣልና ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 10 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የግብጽን ፡ ብዛት ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በናቡከደነጾር ፡ እጅ ፡ እሸራለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 11 ፤ ርሱና ፡ የአሕዛብ ፡ ጨካኞች ፡ ሕዝቡ ፡ ምድሪቱን ፡ ለማጥፋት ፡ ይመጣሉ ፤ ሰይፋቸውንም ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ይመዛሉ ፡ ምድሪቱንም ፡ በተገደሉት ፡ ይሞላሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 12 ፤ ወንዞችንም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አደርጋለኹ ፡ ምድሪቱንም ፡ በክፉ ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ እሸጣለኹ ፥ ምድሪቱንና ፡ መላዋንም ፡ በእንግዳዎች ፡ እጅ ፡ ባድማ ፡ አደርጋለኹ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 13 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጣዖቶቹን ፡ አጠፋለኹ ፡ ምስሎችንም ፡ ከሜምፎስ ፡ እሸራለኹ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ አለቃ ፡ አይኾንም ፥ በግብጽም ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ፍርሀትን ፡ አደርጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 14 ፤ ጳትሮስንም ፡ አፈርሳለኹ ፥ በጣኔዎስም ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ በኖእ ፡ ላይም ፡ ፍርድን ፡ አደርጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 15 ፤ በግብጽም ፡ ምሽግ ፡ በሲን ፡ ላይ ፡ መዓቴን ፡ አፈሳለኹ ፥ የኖእንም ፡ ብዛት ፡ አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 16 ፤ በግብጽም ፡ እሳትን ፡ አነዳለኹ ፥ ሲንም ፡ ትጨነቃለች ፡ ኖእም ፡ ትሰበራለች ፥ በሜምፎስም ፡ በየቀኑ ፡ ጠላቶች ፡ ይኾኑባታል ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 17 ፤ የሄልዮቱ ፡ ከተማና ፡ የቡባስቱም ፡ ጐልማሶች ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፡ ሴቶችም ፡ ይማረካሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 18 ፤ የግብጽን ፡ ቀንበር ፡ በዚያ ፡ በሰበርኹ ፡ ጊዜ ፡ በጣፍናስ ፡ ቀኑ ፡ ይጨልማል ፡ የኀይሏም ፡ ትዕቢት ፡ ይጠፋባታል ፤ ደመናም ፡ ይጋርዳታል ፥ ሴቶች ፡ ልጆቿም ፡ ይማረካሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 19 ፤ እንዲሁ ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ አደርጋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 20 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 21 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የግብጽን ፡ ንጉሥ ፡ የፈርዖንን ፡ ክንድ ፡ ሰብሬያለኹ ፤ እንሆም ፥ በጨርቅ ፡ በመጠቅለል ፡ ይፈወስ ፡ ዘንድ ፥ ሰይፉንም ፡ ለመያዝ ፡ እንዲበረታ ፡ አልታሰረም ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ በግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖን ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ የጸናችውንና ፡ የተሰበረችውንም ፡ ክንዱን ፡ እሰብራለኹ ፥ ሰይፉንም ፡ ከእጁ ፡ አስረግፈዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 23 ፤ ግብጻውያንንም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እበትናለኹ ፡ ወደ ፡ አገሮችም ፡ እዘራቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 24 ፤ የባቢሎንንም ፡ ንጉሥ ፡ ክንድ ፡ አበረታለኹ ፡ ሰይፌንም ፡ በእጁ ፡ እሰጣለኹ ፤ የፈርዖንን ፡ ክንድ ፡ ግን ፡ እሰብራለኹ ፥ ተወግቶም ፡ በሚሞተው ፡ እንጕርጕሮ ፡ በፊቱ ፡ ያንጐራጕራል ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 25 ፤ የባቢሎንንም ፡ ንጉሥ ፡ ክንድ ፡ አጸናለኹ ፡ የፈርዖንም ፡ ክንድ ፡ ይወድቃል ፤ ሰይፌንም ፡ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ እጅ ፡ በሰጠኹ ፡ ጊዜ ፡ ርሱም ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በዘረጋው ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 30 ፡ 26 ፤ ግብጻውያንንም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እበትናለኹ ፡ ወደ ፡ አገሮችም ፡ እዘራቸዋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 31 ። _____

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ዓመት ፡ በሦስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የግብጽን ፡ ንጉሥ ፡ ፈርዖንንና ፡ የሕዝቡን ፡ ብዛት ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ በታላቅነትኽ ፡ ማንን ፡ መስለኻል ፧

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ አሶር ፡ ጫፉ ፡ እንደ ፡ ተዋበ ፥ ችፍግነቱ ፡ ጥላ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፥ ቁመቱም ፡ እንደ ፡ ረዘመ ፥ ራሱም ፡ በደመናዎች ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ዝግባ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 4 ፤ ውሃዎችም ፡ አበቀሉት ፥ ቀላይም ፡ አሳደገው ፥ ወንዞችም ፡ በተተከለበት ፡ ዙሪያ ፡ ይጐርፉ ፡ ነበር ፥ ፈሳሾቹንም ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ሰደደ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ቁመቱ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፥ ቅርንጫፎቹም ፡ በዙ ፥ ጫፎቹንም ፡ ባበቀለ ፡ ጊዜ ፡ ከብዙ ፡ ውሃዎች ፡ የተነሣ ፡ ረዘሙ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 6 ፤ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ጐጕዎቻቸውን ፡ በቅርንጫፎቹ ፡ ላይ ፡ አደረጉ ፥ የምድርም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ ከጫፎቹ ፡ በታች ፡ ተዋለዱ ፥ ከጥላውም ፡ በታች ፡ ታላላቆች ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 7 ፤ ሥሩም ፡ በብዙ ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ ነበረና ፡ በታላቅነቱና ፡ በጫፎቹ ፡ ርዝመት ፡ የተዋበ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 8 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ የነበሩ ፡ ዝግባዎች ፡ አላጨለሙትም ፥ ጥዶችም ፡ ቅርጫፎቹን ፡ አስታ ፡ የሚባለውም ፡ ዛፍ ፡ ጫፎቹን ፡ አይመሳሰሉትም ፡ ነበር ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ገነት ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ በውበቱ ፡ አይመሳሰለውም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 9 ፤ በጫፎቹም ፡ ብዛት ፡ ውብ ፡ አደረግኹት ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ገነት ፡ በዔዴን ፡ የነበሩ ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ቀኑበት ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ቁመትኽ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሏልና ፥ ራሱንም ፡ በደመናዎች ፡ መካከል ፡ አድርጓልና ፥

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 11 ፤ ልቡም ፡ በቁመቱ ፡ ኰርቷልና ፥ ከአሕዛብ ፡ በጨካኙ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጠዋለኹ ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ክፋቱ ፡ መጠን ፡ ያደርግበታል ፡ እኔም ፡ አሳድደዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 12 ፤ የሌላ ፡ አገር ፡ ሰዎች ፥ የአሕዛብ ፡ ጨካኞች ፡ የኾኑ ፥ ቈርጠው ፡ ጣሉት ፤ በተራራዎችና ፡ በሸለቆዎች ፡ ኹሉ ፡ ውስጥ ፡ ጫፎቹ ፡ ወደቁ ፥ ቅርንጫፎቹም ፡ በምድር ፡ ፈሳሾች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተሰባበሩ ፥ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ከጥላው ፡ ተመልሰው ፡ ተዉት ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 13 ፤ 14 ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ በሚወርዱ ፡ በሰው ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ኹላቸው ፡ ለታችኛው ፡ ምድር ፡ ለሞት ፡ ዐልፈው ፡ ተሰጥተዋልና ፥ በውሃ ፡ አጠገብ ፡ ያሉ ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ በቁመታቸው ፡ እንዳይረዝሙ ፥ ራሳቸውንም ፡ በደመናዎች ፡ መካከል ፡ እንዳያደርጉ ፥ ውሃንም ፡ የሚጠጡ ፡ ኀያላናቸው ፡ ኹሉ ፡ በቁመታቸው ፡ እንዳይቆሙ ፥ በወደቀው ፡ ግንድ ፡ ላይ ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ ይቀመጣሉ ፡ የምድርም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ በቅርንጫፎቹ ፡ ላይ ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 15 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በወረደበት ፡ ቀን ፡ ልቅሶ ፡ አስለቀስኹ ፤ ቀላዩንም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ሸፈንኹት ፡ ፈሳሾቹንም ፡ ከለከልኹ ፡ ታላላቆችም ፡ ውሃዎች ፡ ተከለከሉ ፤ ሊባኖስንም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አሳዘንኹት ፥ የዱርም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ዛሉ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ በጣልኹት ፡ ጊዜ ፥ ከመውደቁ ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፥ አሕዛብን ፡ አንቀጠቀጥኹ ፤ ውሃም ፡ የሚጠጡ ፡ ኹሉ ፥ ምርጦችና ፡ መልካካሞች ፡ የሊባኖስ ፡ ዛፎች ፥ የዔዴን ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ በታችኛው ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ ተጽናንተዋል ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 17 ፤ ከንዱም ፡ ወደነበሩት ፡ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ በጥላው ፡ ወደተቀመጡት ፥ በሰይፍ ፡ ወደተገደሉት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወረዱ ።

ሕዝ. ፡ 31 ፡ 18 ፤ በክብርና ፡ በታላቅነት ፡ በዔዴን ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ማንን ፡ መስለኻል ፧ ነገር ፡ ግን ፡ ከዔዴን ፡ ዛፎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ምድር ፡ ያወርዱኻል ፥ በሰይፍም ፡ በተገደሉት ፡ ባልተገረዙት ፡ መካከል ፡ ትተኛለኽ ። ይህም ፡ ፈርዖንና ፡ የሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ ኹሉ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 32 ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ፈርዖን ፡ ሙሾ ፡ አሙሽ ፥ እንዲህም ፡ በለው ፦ የአሕዛብን ፡ አንበሳ ፡ መስለኽ ፡ ነበር ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ባሕር ፡ ዘንዶ ፡ ኾነኻል ፤ በወንዞችኽም ፡ ወጥተኻል ፥ ውሃውንም ፡ በእግርኽ ፡ አደፍርሰኻል ፥ ወንዞችኽንም ፡ አሳድፈኻል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 3 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ጉባኤ ፡ መረቤን ፡ እዘረጋብኻለኹ ፥ እነርሱም ፡ በመረቤ ፡ ያወጡኻል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 4 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ እተውኻለኹ ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ ፊት ፡ እጥልኻለኹ ፥ የሰማይንም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ አሳርፍብኻለኹ ፥ የምድርንም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ አጠግባቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 5 ፤ ሥጋኽን ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ አደርጋለኹ ፡ ሸለቆዎቹንም ፡ በሬሳኽ ፡ ክምር ፡ እሞላለኹ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 6 ፤ የምትዋኝባትንም ፡ ምድር ፡ እስከ ፡ ተራራዎች ፡ ድረስ ፡ በደምኽ ፡ አጠጣለኹ ፥ መስኖችም ፡ ከአንተ ፡ ይሞላሉ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 7 ፤ ባጠፋኹኽም ፡ ጊዜ ፡ ሰማዮችን ፡ እሸፍናለኹ ፥ ከዋክብትንም ፡ አጨልማለኹ ፤ ፀሐዩንም ፡ በደመና ፡ እሸፍናለኹ ፥ ጨረቃም ፡ ብርሃኑን ፡ አይሰጥም ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 8 ፤ የሰማይን ፡ ብርሃኖች ፡ ኹሉ ፡ በላይኽ ፡ አጨልማለኹ ፥ በምድርኽም ፡ ላይ ፡ ጨለማ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 9 ፤ በማታውቃቸውም ፡ አገሮች ፡ ባሉ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ጥፋትኽን ፡ ባመጣኹ ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ ሕዝብን ፡ ልብ ፡ አስጨንቃለኹ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 10 ፤ ብዙም ፡ አሕዛብን ፡ አስደንቅብኻለኹ ፡ ሰይፌንም ፡ በፊታቸው ፡ ባወዛወዝኹ ፡ ጊዜ ፡ ነገሥታታቸው ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ይፈራሉ ፤ በወደቅኽበትም ፡ ቀን ፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ በየጊዜው ፡ ኹሉ ፡ ይንቀጠቀጣል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 11 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ሰይፍ ፡ ይመጣብኻል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 12 ፤ በጎያላን ፡ ሰይፍ ፡ የሕዝብኽን ፡ ብዛት ፡ እጥላለኹ ፤ ኹሉ ፡ የአሕዛብ ፡ ጨካኞች ፡ ናቸው ፤ የግብጽንም ፡ ትዕቢት ፡ ያጠፋሉ ፥ ብዛቷም ፡ ኹሉ ፡ ይጠፋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 13 ፤ በብዙም ፡ ውሃ ፡ አጠገብ ፡ ያሉትን ፡ እንስሳዎች ፡ ኹሉ ፡ አጠፋለኹ ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ የሰው ፡ እግር ፡ አያደፈርሰውም ፡ የእንስሳም ፡ ኰቴ ፡ አይረግጠውም ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ውሃቸውን ፡ አጠራለኹ ፥ ወንዞቻቸውም ፡ እንደ ፡ ዘይት ፡ እንዲፈሱ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 15 ፤ የግብጽንም ፡ ምድር ፡ ባድማና ፡ ውድማ ፡ ባደረግኹ ፡ ጊዜ ፥ ሞላዋንም ፡ ያጣች ፡ ምድር ፡ ባደረግኋት ፡ ጊዜ ፥ የሚኖሩባትንም ፡ ኹሉ ፡ በቀሠፍኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 16 ፤ የሚያለቅሱበት ፡ ልቅሶ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የአሕዛብ ፡ ቈነጕሾች ፡ ያለቅሱበታል ፤ ስለ ፡ ግብጽና ፡ ስለ ፡ ብዛቷ ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሱበታል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 17 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 18 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለግብጽ ፡ ብዛት ፡ ዋይ ፡ በል ፥ ርሷንና ፡ የብርቱዎችን ፡ አሕዛብ ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ምድር ፡ ጣላቸው ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 19 ፤ በውበት ፡ የምትበልጪው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ውረጂ ፡ ካልተገረዙትም ፡ ጋራ ፡ ተኚ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 20 ፤ በሰይፍ ፡ በተገደሉት ፡ መካከል ፡ ይወድቃሉ ፤ ለሰይፍ ፡ ተሰጥታለች ፤ ርሷንና ፡ ብዛቷን ፡ ኹሉ ፡ ጐትቱ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 21 ፤ የጎያላን ፡ አለቃዎች ፡ በሲኦል ፡ ውስጥ ፡ ኾነው ፡ ከረዳቶቹ ፡ ጋራ ፡ ይናገሩታል ፤ በሰይፍም ፡ የተገደሉት ፡ ያልተገረዙ ፡ ወርደው ፡ ተኝተዋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 22 ፤ አሶርና ፡ ጉባኤዋ ፡ ኹሉ ፡ በዚያ ፡ አሉ ፤ መቃብራቸው ፡ በዙሪያቸው ፡ ነው ፤ ኹሉም ፡ በሰይፍ ፡

ወድቀው ፡ ተገደሉ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 23 ፤ መቃብራቸው ፡ በጕድጓዱ ፡ በውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ነው ፥ ጉባኤዋም ፡ በመቃብሯ ፡ ዙሪያ ፡ ነው ፤ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ ያስፈሩ ፡ ዘንdrew ፡ በሰይፍ ፡ ወድቀው ፡ ተገድለዋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 24 ፤ ዔላምም ፡ በዚያ ፡ አለች ፡ ብዛቷም ፡ ዘሉ ፡ በመቃብሯ ፡ ዙሪያ ፡ ነው ፤ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ ያስፈሩ ፡ ዘሉ ፡ በሰይፍ ፡ ወድቀው ፡ ተገድለዋል ፡ ሳይገረዙም ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ምድር ፡ ወርደዋል ፥ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ዕፍረታቸውን ፡ ተሸክመዋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 25 ፤ በተገደሉት ፡ መካከል ፡ ከብዛቷ ፡ ዘሉ ፡ ጋራ ፡ መኝታን ፡ አድርገውላታል ፤ መቃብሯ ፡ በዙሪያዋ ፡ ነው ፥ ዘሉም ፡ ያልተገረዙና ፡ በሰይፍ ፡ የተገደሉ ፡ ናቸው ፤ በሕያዋንም ፡ ምድር ፡ ያስፈሩ ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ዕፍረታቸውን ፡ ተሸክመዋል ፥ በተገደሉትም ፡ መካከል ፡ ተሰጥተዋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 26 ፤ ሞሳሕና ፡ ቶቤል ፡ ብዛታቸውም ፡ ዘሉ ፡ በዚያ ፡ አሉ ፡ መቃብራቸውም ፡ በዙሪያቸው ፡ ነው ፤ ዘሉም ፡ ሳይገረዙ ፡ በሰይፍ ፡ ተገድለዋል ፤ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ ያስፈሩ ፡ ነበርና ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 27 ፤ በሕያዋንም ፡ ምድር ፡ ኀያላኑን ፡ ያስፈሩ ፡ ነበርና ፥ መሣሪያቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ከወረዱ ፥ ሰይፋቸውንም ፡ ከራሳቸው ፡ በታች ፡ ካደረጉ ፥ ኀጢአታቸውም ፡ በዐጥንታቸው ፡ ላይ ፡ ከኾነ ፡ ጋራ ፡ ከወደቁ ፡ ካልተገረዙ ፡ ኀያላን ፡ ጋራ ፡ ይተኛሉ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 28 ፤ አንተም ፡ ባልተገረዙት ፡ መካከል ፡ ትሰበራለኽ ፥ በሰይፍም ፡ ከተገደሉት ፡ ጋራ ፡ ትተኛለኽ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 29 ፤ ኤዶምያስና ፡ ነገሥታቷ ፡ አለቃዎቿም ፡ ዘሉ ፡ በዚያ ፡ አሉ ፤ በሰይፍ ፡ ከተገደሉት ፡ ጋራ ፡ በኀይላቸው ፡ ተኝተዋል ፤ ካልተገረዙትና ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ከሚወርዱ ፡ ጋራ ፡ ይተኛሉ ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 30 ፤ የሰሜን ፡ አለቃዎች ፡ ዘሉ ፡ ሲዶናውያንም ፡ ዘሉ ፡ ከተገደሉት ፡ ጋራ ፡ ወርደው ፡ በዚያ ፡ አሉ ፤ በኀይላቸውም ፡ ያስፈሩ ፡ በነበረው ፡ ፍርሀት ፡ ዐፍረዋል ፥ በሰይፍም ፡ ከተገደሉት ፡ ጋራ ፡ ሳይገረዙ ፡ ተኝተዋል ፥ ወደ ፡ ጕድጓድም ፡ ከሚወርዱት ፡ ጋራ ፡ ዕፍረታቸውን ፡ ተሸክመዋል ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 31 ፤ በሰይፍ ፡ የተገደሉ ፡ ፈርዖንና ፡ ሰራዊቱ ፡ ዘሉ ፡ ያይዋቸዋል ፥ ፈርዖንም ፡ ስለ ፡ ብዛቱ ፡ ዘሉ ፡ ይጽናናል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 32 ፡ 32 ፤ መፈራቱን ፡ በሕያዋን ፡ ምድር ፡ አድርጌያለኹ ፥ ፈርዖንና ፡ ብዛቱም ፡ ዘሉ ፡ በሰይፍ ፡ በተገደሉት ፡ ባልተገረዙት ፡ መካከል ፡ ይተኛሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 33 ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለሕዝብኽ ፡ ልጆች ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ሰይፍን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ባመጣኹ ፡ ጊዜ ፥ የምድር ፡ ሕዝብ ፡ ከመካከላቸው ፡ ሰውን ፡ ወስደው ፡ ለራሳቸው ፡ ጕበኛ ፡ ቢያደርጉ ፥

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የመጣውን ፡ ሰይፍ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ መለከትን ፡ ቢነፋ ፥ ሕዝቡንም ፡ ቢያስጠነቅቅ ፥

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 4 ፤ የመለከቱን ፡ ድምፅ ፡ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ባይጠነቀቅ ፥ ሰይፍ ፡ መጥቶ ፡ ቢወስደው ፥ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 5 ፤ የመለከቱን ፡ ድምፅ ፡ ሰምቶ ፡ ስላልተጠነቀቀ ፡ ደሙ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ቢጠነቀቅስ ፡

ኖሮ ፡ ነፍሱን ፡ ባዳነ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 6 ፤ ጕበኛው ፡ ግን ፡ ሰይፍ ፡ ሲመጣ ፡ ቢያይ ፡ መለከቱንም ፡ ባይነፋ ፡ ሕዝቡንም ፡ ባያስጠነቅቅ ፡ ሰይፍም ፡ መጥቶ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ቢወስድ ፥ ርሱ ፡ በኀጢአቱ ፡ ተወስዷል ፥ ደሙን ፡ ግን ፡ ከጕበኛው ፡ እጅ ፡ እፈልጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 7 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጕበኛ ፡ አድርጌኻለኹ ፤ ከአፌ ፡ ቃሌን ፡ ስማ ፡ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አስጠንቅቃቸው ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 8 ፤ ኀጢአተኛውን ፦ ኀጢአተኛ ፡ ሆይ ፥ በርግጥ ፡ ትሞታለኽ ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥ ኀጢአተኛውን ፡ ከመንገዱ ፡ ታስጠነቅቅ ፡ ዘንድ ፥ ባትናገር ፡ ያ ፡ ኀጢአተኛ ፡ በኀጢአቱ ፡ ይሞታል ፥ ደሙን ፡ ግን ፡ ከእጅኽ ፡ እፈልጋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከመንገዱ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፥ ኀጢአተኛውን ፡ ብታስጠነቅቀው ፡ ርሱም ፡ ከመንገዱ ፡ ባይመለስ ፥ በኀጢአቱ ፡ ይሞታል ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ነፍስኽን ፡ አድነኻል ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 10 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤልን ፡ ቤት ፦ እናንተ ፦ በደላችንና ፡ ኀጢአታችን ፡ በላያችን ፡ አሉ ፥ እኛም ፡ ሰልስለንባቸዋል ፤ እንዴትስ ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ፧ ብላችኹ ፡ ተናግራችኋል ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 11 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ ኀጢአተኛው ፡ ከመንገዱ ፡ ተመልሶ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፥ ኀጢአተኛው ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ አልፈቅድም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ተመለሱ ፥ ከክፉ ፡ መንገዳችኹ ፡ ተመለሱ ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ትሞታላችኹ ፧ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 12 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የሕዝብኽን ፡ ልጆች ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ በበደለበት ፡ ቀን ፡ የጻድቅ ፡ ጽድቁ ፡ አያድነውም ፥ ኀጢአተኛም ፡ ከኀጢአቱ ፡ በተመለሰበት ፡ ቀን ፡ በኀጢአቱ ፡ አይሰናከልም ፤ ጻድቁም ፡ ኀጢአት ፡ በሠራበት ፡ ቀን ፡ በጽድቁ ፡ በሕይወት ፡ አይኖርም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ ጻድቁን ፦ በርግጥ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራለኽ ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ በጽድቁ ፡ ታምኖ ፡ ኀጢአት ፡ ቢሠራ ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ይሞታል ፡ እንጂ ፡ ጽድቁ ፡ አይታሰብለትም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 14 ፤ እኔም ፡ ኀጢአተኛውን ፦ በርግጥ ፡ ትሞታለኽ ፡ ባልኹ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ ከኀጢአቱ ፡ ተመልሶ ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ቢያደርግ ፥

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 15 ፤ ኀጢአተኛውም ፡ መያዣን ፡ ቢመልስ ፡ የነጠቀውንም ፡ ቢመልስ ፡ በሕይወትም ፡ ትእዛዝ ፡ ቢኼድ ፡ ኀጢአትም ፡ ባይሠራ ፥ በሕይወት ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 16 ፤ የሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ አይታሰብበትም ፤ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ አድርጓል ፤ በርግጥ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሕዝብኽ ፡ ልጆች ፦ የጌታ ፡ መንገድ ፡ የቀና ፡ አይደለም ፡ ይላሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእነርሱ ፡ መንገድ ፡ የቀና ፡ አይደለም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 18 ፤ ጻድቅ ፡ ከጽድቁ ፡ ተመልሶ ፡ ኀጢአትን ፡ ቢሠራ ፡ ይሞትባታል ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 19 ፤ ኀጢአተኛውም ፡ ከኀጢአቱ ፡ ተመልሶ ፡ ፍርድንና ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ቢያደርግ ፡ በሕይወት ፡ ይኖርበታል ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ የጌታ ፡ መንገድ ፡ የቀና ፡ አይደለም ፡ ትላላችኹ ። የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በያንዳንዳችኹ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ መንገዳችኹ ፡ እፈርድባችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 21 ፤ እንዲህም ፡ ኾነ ፤ በተማረክን ፡ በዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በዐሥረኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ያመለጠ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥቶ ፦ ከተማዪቱ ፡ ተመታች ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 22 ፤ ያመለጠውም ፡ ሳይመጣ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነበረች ፥ በነጋውም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አፌን ፡ ከፈተ ፤ አፌም ፡ ተከፈተች ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ዲዳ ፡ አልኾንኩም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 23 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 24 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ ባሉ ፡ በባድማ ፡ ስፍራዎች ፡ የተቀመጡ ፦ አብርሃም ፡ ብቻውን ፡ ሳለ ፡ ምድሪቱን ፡ ወረሰ ፤ እኛም ፡ ብዙዎች ፡ ነን ፡ ምድሪቱም ፡ ርስት ፡ ኾና ፡ ለእኛ ፡ ተሰጥታለች ፡ ይላሉ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከደም ፡ ጋራ ፡ ትበላላችኹ ፥ ዐይናችኹንም ፡ ወደ ፡ ጣዖቶቻችኹ ፡ ታነሣላችኹ ፥ ደምንም ፡ ታፈሳላችኹ ፤ በእውኑ ፡ ምድሪቱን ፡ ትወርሳላችኹን ፧

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 26 ፤ ሰይፋችኹን ፡ ይዛችኹ ፡ ቆማችኋል ፥ ርኩስ ፡ ነገርን ፡ ታደርጋላችኹ ፥ የባልንጀራዎቻችኹንም ፡ ሚስቶች ፡ ታስነውራላችኹ ፤ በእውኑ ፡ ምድሪቱን ፡ ትወርሳላችኹን ፧

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 27 ፤ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በባድማ ፡ ስፍራዎች ፡ ያሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ያለውን ፡ ለአራዊት ፡ መብል ፡ አድርጌ ፡ እሰጣለኹ ፥ በዐምባዎችና ፡ በዋሾች ፡ ያሉ ፡ በቸነፈር ፡ ይሞታሉ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 28 ፤ ምድሪቱንም ፡ ባድማና ፡ ውድማ ፡ አደርጋታለኹ ፡ የኀይሏም ፡ ትዕቢት ፡ ይቀራል ፥ የእስራኤልም ፡ ተራራዎች ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ፥ ማንም ፡ አያልፍባቸውም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 29 ፤ ስላደረጉትም ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ምድሪቱን ፡ ባድማና ፡ ውድማ ፡ ባደርግኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 30 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የሕዝብኽ ፡ ልጆች ፡ በቅጥር ፡ አጠገብና ፡ በቤት ፡ ደጆች ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ይናገራሉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፥ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፦ እንኪድና ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንስማ ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 31 ፤ ሕዝብ ፡ እንደሚመጣ ፡ ወዳንተ ፡ ይመጣሉ ፥ እንደ ፡ ሕዝቤም ፡ በፊትኽ ፡ ይቀመጣሉ ፥ ቃልኽንም ፡ ይሰማሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አያደርጉትም ፤ በአፋቸው ፡ ብዙ ፡ ፍቅር ፡ ይገልጣሉ ፥ ልባቸው ፡ ግን ፡ ሥሥታቸውን ፡ ትከተላለች ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 32 ፤ እንሆ ፥ አንተ ፡ መልካም ፡ ድምፅ ፡ እንዳለው ፡ እንደሚወደድ ፡ መዝሙር ፡ ማለፊያም ፡ አድርጎ ፡ በገና ፡ እንደሚጫወት ፡ ሰው ፡ ኾነኽላቸዋል ፤ ቃልኽንም ፡ ይሰማሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አያደርጉትም ።

ሕዝ. ፡ 33 ፡ 33 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ ይመጣል ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ነቢይ ፡ በመካከላቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 34 ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ በእስራኤል ፡ እረኞች ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡

ተናገር ፥ እረኞችንም ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ራሳቸውን ፡ ለሚያሰማሩ ፡ ለእስራኤል ፡ እረኞች ፡ ወዮላቸው! ፡ እረኞች ፡ በጎችን ፡ ያሰማሩ ፡ ዘንድ ፡ አይገባቸውምን ፧

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 3 ፤ ጮማውን ፡ ትበላላችኹ ፡ ጠጕሩንም ፡ ትለብሳላችኹ ፥ የወፈሩትን ፡ ታርዳላችኹ ፤ በጎቹን ፡ ግን ፡ አታሰማሩም ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 4 ፤ የደከመውን ፡ አላጸናችኹትም ፡ የታመመውንም ፡ አላከማችኹትም ፡ የተሰበረውንም ፡ አልጠገናችኹትም ፡ የባዘነውንም ፡ አልመለሳችኹትም ፡ የጠፋውንም ፡ አልፈለጋችኹትም ፡ በኀይልና ፡ በጭቈናም ፡ ገዛችኋቸው ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 5 ፤ እረኛንም ፡ በማጣት ፡ ተበተኑ ፥ ለምድርም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ መብል ፡ ኾኑ ፥ ተበተኑም ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 6 ፤ በጎቼ ፡ በተራራዎች ፡ ኹሉና ፡ በረዘሙ ፡ ኰረብታዎች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተቅበዝብዘዋል ፥ በጎቼም ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ተበትነዋል ፤ የሚሻም ፡ የሚፈልግም ፡ አልነበረም ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 7 ፤ ስለዚህ ፥ እረኞች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 8 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እረኛ ፡ ስለሌለ ፡ እረኞቼም ፡ በጎቼን ፡ ስላልፈለጉ ፡ እረኞችም ፡ ራሳቸውን ፡ እንጂ ፡ በጎቼን ፡ ስላላሰማሩ ፥ በጎቼ ፡ ንጥቂያ ፡ ኾነዋልና ፥ በጎቼም ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ መብል ፡ ኾነዋልና ፥

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 9 ፤ ስለዚህ ፥ እረኞች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 10 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በእረኞች ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ በጎቼንም ፡ ከእጃቸው ፡ እፈልጋለኹ ፥ በጎቼንም ፡ ከማሰማራት ፡ አስተዋቸዋለኹ ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ እረኞች ፡ ራሳቸውን ፡ አያሰማሩም ፤ በጎቼንም ፡ ከአፋቸው ፡ አድናለኹ ፥ መብልም ፡ አይኾኑላቸውም ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 11 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ ራሴ ፡ በጎቼን ፡ እሻለኹ ፡ እፈልግማለኹ ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 12 ፤ እረኛ ፡ በተበተኑት ፡ በጎች ፡ መካከል ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ መንጋውን ፡ እንደሚፈልግ ፥ እንዲሁ ፡ በጎቼን ፡ እፈልጋለኹ ፤ በደመናና ፡ በጨለማ ፡ ቀን ፡ ከተበተኑት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ አድናቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 13 ፤ ከአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ አወጣቸዋለኹ ፡ ከአገሮችም ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፥ ወደ ፡ ገዛ ፡ አገራቸውም ፡ አመጣቸዋለኹ ፤ በእስራኤልም ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ በፈሳሾችም ፡ አጠገብ ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ አሰማራቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 14 ፤ በመልካም ፡ ማሰማሪያ ፡ አሰማራቸዋለኹ ፥ ጕረኗቸውም ፡ በረኻሞቹ ፡ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ በዚያ ፡ በመልካም ፡ ጕረኖ ፡ ውስጥ ፡ ይመሰጋሉ ፥ በእስራኤልም ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ በለመለመ ፡ ማሰማሪያ ፡ ይሰማራሉ ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 15 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ በጎቼን ፡ አሰማራለኹ ፡ አስመስጋቸውማለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 16 ፤ የጠፋውንም ፡ እፈልጋለኹ ፡ የባዘነውንም ፡ እመልሳለኹ ፡ የተሰበረውንም ፡ እጠግናለኹ ፡ የደከመውንም ፡ አጸናለኹ ፤ የወፈረውንና ፡ የበረታውንም ፡ አጠፋለኹ ፤ በፍርድም ፡ እጠብቃቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 34 ፥ 17 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተም ፡ መንጋዬ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ በበግና ፡ በበግ ፡ መካከል ፥ በአውራ ፡ በግና ፡ በአውራ ፡ ፍየልም ፡ መካከል ፥ እፈርዳለኹ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 18 ፤ የቀረውን ፡ ማሰማሪያችኹን ፡ በእግራችኹ ፡ የረገጣችኹት ፥ በመልካሙ ፡ ማሰማሪያ ፡ መሰማራታችኹ ፡ ባይበቃችኹ ፡ ነውን ፧ የቀረውንስ ፡ ውሃ ፡ በእግራችኹ ፡ ያደፈረሳችኹት ፥ ጥሩውን ፡ ውሃ ፡ መጠጣታችኹ ፡ ባይበቃችኹ ፡ ነውን ፧

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 19 ፤ በጎቼም ፡ በእግራችኹ ፡ በረገጣችኹት ፡ ይሰማራሉ ፡ በእግራችኹም ፡ ያደፈረሳችኹትን ፡ ይጠጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 20 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላቸዋል ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ በወፈሩት ፡ በጎችና ፡ በከሱት ፡ በጎች ፡ መካከል ፡ እፈርዳለኹ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 21 ፤ እስክትበትኗቸው ፡ ድረስ ፡ በእንቢያና ፡ በትከሻ ፡ ስለምትገፏቸው ፡ የደከሙትንም ፡ ኹሉ ፡ በቀንዳችኹ ፡ ስለምትወጓቸው ፥

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ መንጋዬን ፡ አድናለኹ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህም ፡ ንጥቂያ ፡ አይኾኑም ፤ በበግና ፡ በበግ ፡ መካከልም ፡ እፈርዳለኹ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 23 ፤ በላያቸውም ፡ አንድ ፡ እረኛ ፡ አቆማለኹ ፡ ርሱም ፡ ያሰማራቸዋል ፥ ርሱም ፡ ባሪያዬ ፡ ዳዊት ፡ ነው ፤ ያሰማራቸዋል ፡ እረኛም ፡ ይኾናቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 24 ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡ ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ በመካከላቸው ፡ አለቃ ፡ ይኾናል ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 25 ፤ የሰላምን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እገባለኹ ፡ ክፉዎችንም ፡ አራዊት ፡ ከምድር ፡ አጠፋለኹ ፤ ተዘልለውም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖራሉ ፡ በዱርም ፡ ውስጥ ፡ ይተኛሉ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 26 ፤ እነርሱንና ፡ በኮረብታዬ ፡ ዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ ስፍራዎች ፡ ለበረከት ፡ አደርጋቸዋለኹ ፥ ዝናቡንም ፡ በጊዜው ፡ አወርዳለኹ ፤ የበረከት ፡ ዝናብ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 27 ፤ የምድረ ፡ በዳም ፡ ዛፍ ፡ ፍሬውን ፡ ይሰጣል ፡ ምድርም ፡ ቡቃያዋን ፡ ትሰጣለች ፥ በምድራቸውም ፡ ተዘልለው ፡ ይኖራሉ ፡ የቀንበራቸውንም ፡ ማነቆ ፡ በሰበርኹ ፡ ጊዜ ፡ ከሚገዟቸውም ፡ እጅ ፡ ባዳንኋቸው ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 28 ፤ እንግዲህም ፡ ለአሕዛብ ፡ ንጥቂያ ፡ አይኾኑም ፡ የምድርም ፡ አራዊት ፡ አይበሏቸውም ፤ ተዘልለውም ፡ ይቀመጣሉ ፡ የሚያስፈራቸውም ፡ የለም ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 29 ፤ የዝናን ፡ ተክል ፡ አቆምላቸዋለኹ ፡ እንግዲህም ፡ ከራብ ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡ አያልቁም ፤ የአሕዛብንም ፡ ስድብ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሸከሙም ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 30 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳለኹ ፥ እነርሱም ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሕዝቤ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ያውቃሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 34 ፡ 31 ፤ እናንተም ፡ በጎቼ ፥ የማሰማሪያዬ ፡ በጎች ፥ ሰዎች ፡ ናችኹ ፡ እኔም ፡ አምላካችኹ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 35 ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ ወደሴይር ፡ ተራራ ፡ አድርግ ፥ ትንቢትም ፡ ተናገርበት ፥

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሴይር ፡ ተራራ ፡
ሆይ ፥ እንሆ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ እጄንም ፡ እዘረጋብኻለኹ ፡ ባድማና ፡ ውድማም ፡ አደርግኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 4 ፤ ከተማዎችኽንም ፡ አፈራርሳቸዋለኹ ፥ አንተም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለኽ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡
እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃለኽ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 5 ፤ የዘለዓለም ፡ ጥል ፡ ስለ ፡ አለኽ ፡ በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ በኋለኛዪቱ ፡ የኀጢአታቸው ፡ ቀጠሮ ፡
ጊዜ ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ በሰይፍ ፡ እጅ ፡ ጥለኻቸዋልና ፥

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ ለደም ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹ ፥ ደምም ፡ ያሳድድኻል ፥ ይላል ፡
ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ደምን ፡ ስላልጠላኽ ፥ ደም ፡ ያሳድድኻል ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 7 ፤ የሴይርንም ፡ ተራራ ፡ ውድማ ፡ አደርገዋለኹ ፥ የሚኼደውንና ፡ የሚመለሰውንም ፡ ከርሱ ፡
አጠፋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 8 ፤ ተራራዎቹንም ፡ በተገደሉት ፡ ሰዎች ፡ እሞላለኹ ፤ በኰረብታዎችኽና ፡ በሸለቆዎችኽ ፡
በፈሳሾችኽም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በሰይፍ ፡ የተገደሉት ፡ ኹሉ ፡ ይወድቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 9 ፤ ለዘለዓለምም ፡ ባድማ ፡ አደርግኻለኹ ፡ ከተማዎችኽም ፡ ሰው ፡ የማይኖርባቸው ፡
ይኾናሉ ፥ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ሳለ ፥ አንተ ፦ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ሕዝቦች ፡ እነዚህም ፡ ኹለቱ ፡
አገሮች ፡ ለእኔ ፡ ይኾናሉ ፡ እኛም ፡ እንወርሳቸዋለን ፡ ብለኻልና ፥

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፥ እንደ ፡ ቊጣኽ ፡ መጠን ፡ እነርሱንም ፡ ጠልተኽ ፡
እንዳደረግኸው ፥ እንደ ፡ ቅንአትኽ ፡ መጠን ፡ እኔ ፡ እሠራለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በፈረድኩብኽም ፡ ጊዜ ፡
በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ የታወቅኹ ፡ እኾናለኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 12 ፤ አንተም ፦ ፈርሰዋል ፡ መብልም ፡ ኾነው ፡ ለእኛ ፡ ተሰጥተዋል ፡ ብለኽ ፡ በእስራኤል ፡
ተራራዎች ፡ ላይ ፡ የተናገርኸውን ፡ ስድብ ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰማኹት ፡ ታውቃለኽ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 13 ፤ በአፋችኹም ፡ ተመካችኹብኝ ፥ ቃላችኹንም ፡ አበዛችኹብኝ ፤ እኔም ፡ ሰምቼዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 14 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ሲላት ፡ አንተን ፡ ባድማ ፡
አደርግኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 35 ፡ 15 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ርስት ፡ ባድማ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ በላዩ ፡ ደስ ፡ እንዳለኽ ፥ እንዲሁ ፡
አደርግብኻለኹ ፤ የሴይር ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ አንተና ፡ ኤዶምያስ ፡ ኹሉ ፡ ኹለንተናውም ፡ ባድማ ፡ ትኾናላችኹ ፤ እኔም ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 36 ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 1 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ለእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ትንቢት ፡ ተናግረኽ ፦ የእስራኤል ፡
ተራራዎች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፡ በል ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 2 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጠላት ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፦ ዕሠይ ፥ የጥንት ፡
ከፍታዎች ፡ ለእኛ ፡ ርስት ፡ ኾነዋል ፡ ብሏልና ፥

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡

ይላል ፦ ለቀሩት ፡ አሕዛብ ፡ ርስት ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፥ በዙሪያችኹ ፡ ያሉ ፡ ባድማ ፡
አድርገዋችኋልና ፥ ውጠዋችኹማልና ፥ እናንተም ፡ የተናጋሪዎች ፡ ከንፈር ፡ መተረቻና ፡ የአሕዛብ ፡ ማላገጫ ፡
ኾናችኋልና ፥

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 4 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ሆይ ፥ የጌታን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡
ስሙ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለተራራዎችና ፡ ለኰረብታዎች ፥ ለፈሳሾችና ፡ ለሸለቆዎች ፡ ለምድረ ፡ በዳዎች ፡ ባዶ ፡
ለኾኑትም ፡ በዙሪያ ፡ ላሉት ፡ ለቀሩት ፡ አሕዛብ ፡ ምርኮና ፡ መሳቂያ ፡ ለኾኑት ፡ ከተማዎች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ያሳድዷትና ፡ ይበዘብዟት ፡
ዘንድ ፥ በልባቸው ፡ ሹሉ ፡ ደስታና ፡ በነፍሳቸው ፡ ንቀት ፡ ምድሬን ፡ ርስት ፡ አድርገው ፡ ለራሳቸው ፡ በሰጡ ፡ በቀሩት ፡
አሕዛብና ፡ በኤዶምያስ ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ በቅንአቴ ፡ እሳት ፡ ተናግሬያለኹ ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ስለእስራኤል ፡ ምድር ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ ለተራራዎችና ፡ ለኰረብታዎችም ፡
ለፈሳሾችና ፡ ለሸለቆዎችም ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የአሕዛብን ፡ ስድብ ፡
ስለ ፡ ተሸከማችኹ ፡ በቅንአቴና ፡ በመዓቴ ፡ ተናግሬያለኹ ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዙሪያችኹ ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ስድባቸውን ፡
በርግጥ ፡ ይሸከማሉ ፡ ብዬ ፡ ምያለኹ ።

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 8 ፤ የእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ቅርንጫፎቻችኹን ፡
ታቈጠቍጣላችኹ ፥ ይመጡም ፡ ዘንድ ፡ ቀርበዋልና ፥ ለሕዝቤ ፡ ለእስራኤል ፡ ፍሬያችኹን ፡ ትሰጣላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 9 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ለእናንተ ፡ ነኝና ፤ ወደ ፡ እናንተም ፡ እመለከታለኹ ፥ እናንተም ፡ ትታረሳላችኹ ፡
ይዘራባችኹማል ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 10 ፤ እኔም ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ሹሉንም ፡ አበዛባችኋለኹ ፥ በከተማዎችም ፡ ሰዎች ፡
ይኖሩባቸዋል ፡ ባድማዎቹም ፡ ስፍራዎች ፡ ይሠራሉ ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 11 ፤ ሰውንና ፡ እንስሳውንም ፡ አበዛባችኋለኹ ፥ እነርሱም ፡ ይበዛሉ ፡ ያፈሩማል ፤ እንደ ፡
ጥንታችኹም ፡ ሰዎችን ፡ አኖርባችኋለኹ ፥ ቀድሞም ፡ ካደረግኹላችኹ ፡ ይልቅ ፡ መልካም ፡ አደርግላችኋለኹ ፤ እኔም ፡
እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 12 ፤ ሰዎችንም ፥ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፥ በእናንተ ፡ ላይ ፡ አስኼዳቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ይወርሱሻል ፡
ርስትም ፡ ትኾኛቸዋለሽ ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ አታደርጊያቸውም ።

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 13 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነርሱ ፦ ሰው ፡ በሊታ ፡ ምድር ፡ ነሽ ፡ ሕዝብሽንም ፡
ልጅ ፡ አልባ ፡ የምታደርጊ ፡ ነሽ ፡ ብለዋችኋልና ፥

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ዳግመኛ ፡ ሰው ፡ በሊታ ፡ አትኾኚም ፥ ዳግመኛም ፡ ሕዝብሽን ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡
አታደርጊም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 15 ፤ ዳግመኛም ፡ የአሕዛብን ፡ ውርደት ፡ አላሰማብሽም ፥ ዳግመኛም ፡ የአሕዛብን ፡ ስድብ ፡
አትሸከሚም ፥ ዳግመኛም ፡ ሕዝብሽን ፡ አታሰናክዪም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 16 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፥ 36 ፥ 17 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ በምድራቸው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ በመንገዳቸውና ፡
በሥራቸው ፡ አረከሷት ፥ መንገዳቸውም ፡ በፊቴ ፡ እንደ ፡ መርገም ፡ አደፍ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 18 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ስላፈሰሱት ፡ ደም ፡ በጣዖቶቻቸውም ፡ ስላረከሷት ፡ መዓቴን ፡ አፈሰስኹባቸው ፤

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ አሕዛብም ፡ በተንኗቸው ፡ ወደ ፡ አገሮችም ፡ ተዘሩ ፤ እንደ ፡ መንገዳቸውና ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ መጠን ፡ ፈረድኹባቸው ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 20 ፤ ወደመጡባቸውም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፥ ሰዎች ፡ እነርሱን ፦ ከምድሩ ፡ የወጡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ ሲሏቸው ፡ ቅዱስ ፡ ስሜን ፡ አረከሱ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ በመጡባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ስላረከሱት ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ስሜ ፡ ስል ፡ ራራኹላቸው ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በመጣችኹባቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ስላረከሳችኹት ፡ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ስሜ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የምሠራ ፡ አይደለኹም ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 23 ፤ በአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ የረከሰውን ፥ በመካከላቸው ፡ ያረከሳችኹትን ፡ ስሜን ፡ እቀድሰዋለኹ ፤ በዐይናቸውም ፡ ዘንድ ፡ በተቀደስኹባችኹ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አሕዛብ ፡ ያውቃሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 24 ፤ ከአሕዛብም ፡ መካከል ፡ አወጣችኋለኹ ፡ ከየአገሩም ፡ ኹሉ ፡ እሰበስባችኋለኹ ፡ ወደገዛ ፡ ምድራችኹም ፡ አመጣችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 25 ፤ ጥሩ ፡ ውሃንም ፡ እረጭባችኋለኹ ፡ እናንተም ፡ ትጠራላችኹ ፥ ከርኵሰታችኹም ፡ ኹሉ ፡ ከጣዖቶቻችኹም ፡ ኹሉ ፡ አጠራችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 26 ፤ ዐዲስም ፡ ልብ ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ ዐዲስም ፡ መንፈስ ፡ በውስጣችኹ ፡ አኖራለኹ ፤ የድንጋዩንም ፡ ልብ ፡ ከሥጋችኹ ፡ አወጣለኹ ፤ የሥጋንም ፡ ልብ ፡ እሰጣችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 27 ፤ መንፈሴንም ፡ በውስጣችኹ ፡ አኖራለኹ ፥ በትእዛዜም ፡ አስኬዳችኋለኹ ፥ ፍርዴንም ፡ ትጠብቃላችኹ ፥ ታደርጉትማላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 28 ፤ ለአባቶቻችኹም ፡ በሰጠኋት ፡ ምድር ፡ ትኖራላችኹ ፤ ሕዝብም ፡ ትኾኑኛላችኹ ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 29 ፤ ከርኵሰታችኹም ፡ ኹሉ ፡ አድናችኋለኹ ፤ እኽልንም ፡ እጠራዋለኹ ፡ አበዛውማለኹ ፡ ራብንም ፡ አላመጣባችኹም ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 30 ፤ ደግሞም ፡ የራብን ፡ ስድብ ፡ ከአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ እንዳትሸከሙ ፡ የዛፍን ፡ ፍሬና ፡ የዕርሻውን ፡ ቡቃያ ፡ አበዛለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 31 ፤ ክፉውን ፡ መንገዳችኹንና ፡ መልካም ፡ ያይደለውን ፡ ሥራችኹንም ፡ ታስባላችኹ ፥ ስለ ፡ በደላችኹና ፡ ስለ ፡ ርኵሰታችኹም ፡ ራሳችኹን ፡ ትጸየፋላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 32 ፤ ይህን ፡ የሠራኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እንዳይደለ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኹን ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ መንገዳችኹ ፡ ዕፈሩና ፡ ተዋረዱ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 33 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከኀጢአታችኹ ፡ ኹሉ ፡ ባነጻኋችኹበት ፡ ቀን ፡ በከተማዎች ፡ ሰዎችን ፡ አኖራለኹ ፥ ባድማዎቹም ፡ ስፍራዎች ፡ ይሠራሉ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 34 ፤ ባድማ ፡ የነበረች ፡ በመንገደኛም ፡ ዥሉ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ባድማ ፡ የነበረች ፡ ምድር ፡ ትታረሳለች ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 35 ፤ ሰዎችም ፦ ባድማ ፡ የነበረች ፡ ይህች ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ዔዴን ፡ ገነት ፡ ኾናለች ፤ የፈረሱት ፣ ባድማ ፡ የኾኑት ፣ የጠፉትም ፡ ከተማዎች ፡ ተመሽገዋል ፥ ሰውም ፡ የሚኖርባቸው ፡ ኾነዋል ፡ ይላሉ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 36 ፤ በዙሪያችኹም ፡ የቀሩት ፡ አሕዛብ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈረሱትን ፡ ስፍራዎች ፡ እንደ ፡ ሠራኹ ፡ ውድማ ፡ የኾነውንም ፡ እንደ ፡ ተከልኹ ፡ ያውቃሉ ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናግሬያለኹ ፥ እኔም ፡ አደርገዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 37 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ላደርግላቸው ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ይሹኛል ፤ ሰውንም ፡ እንደ ፡ መንጋ ፡ አበዛላቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 36 ፡ 38 ፤ እንደ ፡ ተቀደሱ ፡ በጎች ፥ በበዓላቷ ፡ ቀን ፡ እንደሚኾኑ ፡ እንደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በጎች ፥ እንዲሁ ፡ የፈለሱት ፡ ከተማዎች ፡ በሰዎች ፡ መንጋ ፡ ይሞላሉ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 37 ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ እጅ ፡ በላዬ ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በመንፈሱ ፡ አወጣኝ ፡ ዐጥንቶችም ፡ በሞሉባት ፡ ሸለቆ ፡ መካከል ፡ አኖረኝ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 2 ፤ በእነርሱም ፡ አንጻር ፡ በዙሪያቸው ፡ አሳለፈኝ ፤ እንሆም ፥ በሸለቆው ፡ ፊት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፥ እንሆም ፥ እጅግ ፡ ደርቀው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 3 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ዐጥንቶች ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉን ፧ አለኝ ። እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፡ አልኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ በእነዚህ ፡ ዐጥንቶች ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ እናንተ ፡ የደረቃችኹ ፡ ዐጥንቶች ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰሙ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 5 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእነዚህ ፡ ዐጥንቶች ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ትንፋሽን ፡ አገባባችኋለኹ ፡ በሕይወትም ፡ ትኖራላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 6 ፤ ሾሮማትም ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ ሥጋንም ፡ አወጣባችኋለኹ ፡ በእናንተም ፡ ላይ ፡ ቍርበትን ፡ እዘረጋለኹ ፡ ትንፋሽንም ፡ አገባባችኋለኹ ፡ በሕይወትም ፡ ትኖራላችኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 7 ፤ እንዳዘዘኝም ፡ ትንቢት ፡ ተናገርኹ ፤ ስናገርም ፡ ድምፅ ፡ ኾነ ፥ እንሆም ፥ መናወጥ ፡ ኾነ ፥ ዐጥንቶችም ፡ ዐጥንት ፡ ከዐጥንት ፡ ጋራ ፡ ተቀራረቡ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 8 ፤ እኔም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ሾሮማት ፡ ነበረባቸው ፡ ሥጋም ፡ ወጣ ፡ ቍርበትም ፡ በላያቸው ፡ ተዘረጋ ፥ ትንፋሽ ፡ ግን ፡ አልነበረባቸውም ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ ለነፋስ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ ለነፋስም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ነፋስ ፡ ሆይ ፥ ከአራቱ ፡ ነፋሳት ፡ ዘንድ ፡ ና ፥ እነዚህም ፡ የተገደሉት ፡ በሕይወት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እፍ ፡ በልባቸው ፡ በል ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 10 ፤ እንዳዘዘኝም ፡ ትንቢት ፡ ተናገርኹ ፥ ትንፋሽም ፡ ገባባቸው ፡ ሕያዋንም ፡ ኾኑ ፥ እጅግም ፡

ታላቅ ፡ ሰራዊት ፡ ኾነው ፡ በእግራቸው ፡ ቆሙ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ዐጥንቶች ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ናቸው ፤ እንሆ ፦ ዐጥንቶቻችን ፡ ደርቀዋል ፡ ተስፋችንም ፡ ጠፍቷል ፡ ፈጽመንም ፡ ተቈርጠናል ፡ ብለዋል ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ትንቢት ፡ ተናገር ፥ እንዲህም ፡ በላቸው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ መቃብራችኹን ፡ እከፍታለኹ ፡ ከመቃብራችኹም ፡ አወጣችኋለኹ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ምድር ፡ አገባችኋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 13 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ መቃብራችኹን ፡ በከፈትኹ ፡ ጊዜ ፡ ከመቃብራችኹም ፡ ባወጣኋችኹ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 14 ፤ መንፈሴንም ፡ በውስጣችኹ ፡ አሳድራለኹ ፥ እናንተም ፡ በሕይወት ፡ ትኖራላችኹ ፥ በገዛ ፡ ምድራችኹም ፡ አኖራችኋለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ እንዳደረግኹም ፡ ታውቃላችኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 16 ፤ አንተ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ በትር ፡ ውሰድና ፦ ለይሁዳና ፡ ለባልንጀራዎቹ ፣ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ብለኽ ፡ በላዩ ፡ ጻፍ ፤ ሌላም ፡ በትር ፡ ውሰድና ፦ የኤፍሬም ፡ በትር ፡ ለዮሴፍና ፡ ለባልንጀራዎቹ ፣ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ብለኽ ፡ በላዩ ፡ ጻፍ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 17 ፤ አንድ ፡ በትርም ፡ እንዲኾኑ ፡ አንዱን ፡ ከኹለተኛው ፡ ጋራ ፡ ለአንተ ፡ አጋጥም ፥ በእጅኽም ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ይኹኑ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 18 ፤ የሕዝብኽም ፡ ልጆች ፦ ይህ ፡ የምታደርገው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ ማለት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አትነግረንምን ፧ ብለው ፡ በተናገሩኽ ፡ ጊዜ ፥

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 19 ፤ አንተ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በኤፍሬም ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ የዮሴፍን ፡ በትር ፡ ባልንጀራዎቹንም ፡ የእስራኤልን ፡ ነገዶች ፡ እወስዳለኹ ፥ ከርሱም ፡ ከይሁዳ ፡ በትር ፡ ጋራ ፡ አጋጥማቸዋለኹ ፡ አንድ ፡ በትርም ፡ አደርጋቸዋለኹ ፥ በእጄም ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ ይኾናሉ ፡ በላቸው ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 20 ፤ የምትጽፍባቸውም ፡ በትሮች ፡ በዐይናቸው ፡ ፊት ፡ በእጅኽ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 21 ፤ አንተም ፡ እንዲህ ፡ ትላቸዋለኽ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ከኼዱባቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፡ እወስዳለኹ ፡ ከስፍራም ፡ ኹሉ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፡ ወደገዛ ፡ ምድራቸውም ፡ አመጣቸዋለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 22 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ሕዝብ ፡ አደርጋቸዋለኹ ፥ አንድ ፡ ንጉሥም ፡ በኹላቸው ፡ ላይ ፡ ይነግሣል ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ኹለት ፡ ሕዝብ ፡ አይኾኑም ፥ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ኹለት ፡ መንግሥቶች ፡ ኾነው ፡ አይለዩም ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 23 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ በጣዖቶቻቸውና ፡ በርኵሰታቸው ፡ በመተላለፋቸውም ፡ ኹሉ ፡ አይረክሱም ፥ ኀጢአትም ፡ ከሠሩባት ፡ ዐመፅ ፡ ኹሉ ፡ አድናቸዋለኹ ፡ አነጻቸውማለኹ ፤ ሕዝብም ፡ ይኾኑኛል ፡ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 24 ፤ ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ ንጉሥ ፡ ይኾናቸዋል ፤ ለኹሉም ፡ አንድ ፡ እረኛ ፡ ይኾንላቸዋል ፤ በፍርዴም ፡ ይኼዳሉ ፡ ትእዛዜንም ፡ ይጠብቃሉ ፡ ያደርጓትማል ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 25 ፤ አባቶቻችኹም ፡ በኖሩበት ፡ ለባሪያዬ ፡ ለያዕቆብ ፡ በሰጠኋት ፡ ምድር ፡ ይኖራሉ ፤ እነርሱና ፡ ልጆቻቸው ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸውም ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖሩባታል ፤ ባሪያዬም ፡ ዳዊት ፡ ለዘለዓለም ፡ አለቃ ፡ ይኾናቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 26 ፤ የሰላምም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አደርጋለኹ ፥ የዘለዓለምም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይኾንላቸዋል ፤ እኔም ፡ እባርካቸዋለኹ ፡ አበዛቸውማለኹ ፡ መቅደሴንም ፡ ለዘለዓለም ፡ በመካከላቸው ፡ አኖራለኹ ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 27 ፤ ማደሪያዬም ፡ በላያቸው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ።

ሕዝ. ፡ 37 ፡ 28 ፤ መቅደሴም ፡ ለዘለዓለም ፡ በመካከላቸው ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ እኔ ፡ እስራኤልን ፡ የምቀድሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አሕዛብ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 38 ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 2 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ፊትኽን ፡ በጎግ ፡ ላይና ፡ በማጎግ ፡ ምድር ፡ ላይ ፥ በሞሳሕና ፡ በቶቤል ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ አቅናበት ፥ ትንቢትም ፡ ተናገርበት ፥

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሞሳሕና ፡ የቶቤል ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ ጎግ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 4 ፤ እመልስኽማለኹ ፥ በመንጋጋኽም ፡ ልጓም ፡ አገባብኻለኹ ፥ አንተንና ፡ ሰራዊትኽንም ፡ ኹሉ ፥ ፈረሶችንና ፡ ፈረሰኞችን ፥ የጦር ፡ ልብስ ፡ የለበሱትን ፡ ኹሉ ፥ ጋሻና ፡ ራስ ፡ ቀሮን ፡ ሰይፍንም ፡ የያዙትን ፡ ኹሉ ፥ ታላቁን ፡ ወገን ፡ አወጣለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 5 ፤ ፋርስንና ፡ ኢትዮጵያን ፡ ፉጥንም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ጋሻና ፡ የራስ ፡ ቀሮን ፡ የለበሱትን ፡ ኹሉ ፥

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 6 ፤ ጋሜርንና ፡ ጭፍራዎቹን ፡ ኹሉ ፥ በሰሜን ፡ ዳርቻም ፡ ያለውን ፡ የቴርጋማን ፡ ቤትና ፡ ጭፍራዎቹን ፡ ኹሉ ፥ ብዙዎችንም ፡ ሕዝቦች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አወጣለኹ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 7 ፤ አንተና ፡ ወዳንተ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ወገኖችኽ ፡ ኹሉ ፡ ተዘጋጁ ፥ አንተም ፡ ራስኽን ፡ አዘጋጅተኽ ፡ አለቃ ፡ ኹናቸው ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 8 ፤ ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ ትፈለጋለኽ ፤ በኋለኛውም ፡ ዘመን ፥ የዘለዓለም ፡ ባድማ ፡ በነበሩ ፡ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ ወደተሰበሰበች ፥ ከሰይፍ ፡ ወደተመለሰች ፡ ምድር ፡ ትገባለኽ ፤ ርሷም ፡ ከሕዝብ ፡ ውስጥ ፡ ወጥታለች ፡ ኹሉም ፡ ሳይፈሩ ፡ ይቀመጡባታል ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 9 ፤ አንተም ፡ ትወጣለኽ ፥ እንደ ፡ ዐወሎ ፡ ነፋስም ፡ ትመጣለኽ ፤ አንተና ፡ ጭፍራዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ምድርን ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ ትሸፍናላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 10 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚያ ፡ ቀን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ልብኽ ፡ ይገባል ፥

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 11 ፤ ክፉ ፡ ዐሳብንም ፡ ታስባለኽ ፥ እንዲህም ፡ ትላለኽ ፦ ቅጥርን ፡ ወደሌላቸው ፡ መንደሮች ፡ እወጣለኹ ፤ ተዘልለው ፡ ወደሚኖሩ ፥ ኹላቸው ፡ ሳይፈሩ ፡ ያለቅጥርና ፡ ያለመወርወሪያ ፡ ያለመዝጊያም ፡ ወደሚቀመጡ ፡ እገባለኹ ፤

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 12 ፤ ምርኮን ፡ ትማርክ ፡ ዘንድ ፥ ብዝበዛንም ፡ ትበዘብዝ ፡ ዘንድ ፥ ባድማም ፡ በነበሩ ፡ አኹንም ፡ ሰዎች ፡ በሚኖሩባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ ላይ ፥ ከአሕዛብም ፡ በተሰበሰበ ፥ ከብትና ፡ ዕቃንም ፡ ባገኘ ፥ በምድርም ፡ መካከል ፡

በተቀመጠ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ትዘረጋ ፡ ዘንድ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 13 ፤ ሳባና ፡ ድዳን ፡ የተርሴስም ፡ ነጋዴዎች ፡ መንደሮቿም ፡ ኹሉ ፦ ምርኮን ፡ ትማርክ ፡ ዘንድ ፥ መጥተኻልን ፧ ብዝበዛንስ ፡ ትበዘብዝ ፡ ዘንድ ፥ ብርንና ፡ ወርቅንስ ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፥ ከብትንና ፡ ዕቃንስ ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፥ እጅግስ ፡ ብዙ ፡ ምርኮ ፡ ትማርክ ፡ ዘንድ ፥ ወገንኽን ፡ ሰብስበኻልን ፧ ይሉኻል ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 14 ፤ አንተ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ ጎግንም ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚያ ፡ ቀን ፡ ሕዝቤ ፡ እስራኤል ፡ ሳይፈራ ፡ በተቀመጠ ፡ ጊዜ ፡ አንተ ፡ አታውቀውምን ፧

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 15 ፤ አንተም ፥ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ኹላቸው ፡ በፈረሶች ፡ ላይ ፡ የተቀመጡ ፥ ታላቅ ፡ ወገንና ፡ ብርቱ ፡ ሰራዊት ፥ ከሰሜን ፡ ዳርቻ ፡ ከስፍራችኹ ፡ ትመጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 16 ፤ ምድርንም ፡ ትሸፍን ፡ ዘንድ ፥ እንደ ፡ ደመና ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ትወጣለኽ ። በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ይኾናል ፥ ጎግ ፡ ሆይ ፥ በዐይናቸው ፡ ፊት ፡ በተቀደስኩብኽ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ያውቁኝ ፡ ዘንድ ፥ በምድሬ ፡ ላይ ፡ አመጣኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 17 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደማመጣኽ ፡ በዚያች ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ዓመት ፡ ትንቢት ፡ በተናገሩ ፡ በባሪያዎቼ ፡ በእስራኤል ፡ ነቢያት ፡ በቀደመው ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የተናገርኹ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ጎግ ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ መቅሠፍቴ ፡ በመዓቴ ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 19 ፤ በቅንአቴና ፡ በመዓቴ ፡ እሳት ፡ ተናግሬያለኹ ። በርግጥ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡ ምድር ፡ ጽኑ ፡ መናወጥ ፡ ይኾናል ፤

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 20 ፤ ከፊቴም ፡ የተነሣ ፡ የባሕር ፡ ዓሣዎችና ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚንቀሳቀሱ ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ኹሉ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፥ ተራራዎችም ፡ ይገለባበጣሉ ፥ ገደላገደሎችም ፡ ይወድቃሉ ፥ ቅጥርም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይወድቃል ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 21 ፤ በተራራዎቼም ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሰይፍን ፡ እጠራለኹ ፥ የሰውም ፡ ኹሉ ፡ ሰይፍ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 22 ፤ በቸነፈርና ፡ በደም ፡ እፈርድበታለኹ ፤ ዶፍም ፡ የበረዶም ፡ ድንጋይ ፡ እሳትና ፡ ድኝም ፡ በርሱና ፡ በጭፍራዎቹ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ባሉ ፡ በብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አዘንባለኹ ።

ሕዝ. ፡ 38 ፡ 23 ፤ ታላቅ ፡ እኾናለኹ ፡ እቀደስማለኹ ፡ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ዐይን ፡ የታወቅኹ ፡ እኾናለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 39 ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 1 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በጎግ ፡ ላይ ፡ ትንቢትን ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሞሳሕና ፡ የቶቤል ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ ጎግ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፤

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 2 ፤ እመልስኻለኹ ፥ እነዳኽማለኹ ፥ ከሰሜንም ፡ ዳርቻ ፡ እጐትትኻለኹ ፥ ወደእስራኤልም ፡ ተራራዎች ፡ አመጣኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 3 ፤ ከግራ ፡ እጅኽም ፡ ቀስትኽን ፡ አስጥልኻለኹ ፥ ከቀኝ ፡ እጅኽም ፡ ፍላጻዎችኽን ፡ አስረግፍኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 4 ፤ አንተና ፡ ጭፍራዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ ከአንተም ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብ ፡ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ትወድቃላችኹ ፤ ለሚናጠቁ ፡ ወፎች ፡ ኹሉና ፡ ለምድር ፡ አራዊትም ፡ መብል ፡ አድርጌ ፡ እሰጥኻለኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 5 ፤ አንተ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ትወድቃለኽ ፤ እኔ ፡ ተናግሬያለኹና ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 6 ፤ በማጎግም ፡ ላይ ፡ ሳይፈሩም ፡ በደሴቶች ፡ በሚቀመጡ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለኹ ፤ እኔም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 7 ፤ ቅዱሱም ፡ ስሜ ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ አደርጋለኹ ፥ ቅዱሱንም ፡ ስሜን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስረክስም ፤ አሕዛብም ፡ እግዚአብሔር ፥ የእስራኤል ፡ ቅዱስ ፥ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 8 ፤ እንሆ ፥ ይመጣል ፡ ይኾንማል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ያልኹት ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 9 ፤ በእስራኤልም ፡ ከተማዎች ፡ የሚኖሩ ፡ ይወጣሉ ፥ የጦር ፡ መሣሪያዎችንም ፡ በእሳት ፡ ያቃጥላሉ ፤ አላባሽ ፡ ጋሻንና ፡ ጋሻን ፥ ቀስትንና ፡ ፍላጻዎችን ፥ ጐመድንና ፡ ጦርንም ፡ ያቃጥላሉ ፤ ሰባት ፡ ዓመት ፡ በእሳት ፡ ያቃጥሏቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 10 ፤ በጦር ፡ መሣሪያው ፡ እሳትን ፡ ያነዳሉ ፡ እንጂ ፡ ዕንጨትን ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ አይወስዱም ፡ ከዱርም ፡ አይቈርጡም ፤ የገፈፏቸውንም ፡ ይገፈፋሉ ፡ የበዘበዟቸውንም ፡ ይበዘብዛሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ በባሕር ፡ ምሥራቅ ፡ የሚያልፉበትን ፡ ሸለቆ ፡ የመቃብርን ፡ ስፍራ ፡ ለጎግ ፡ እሰጣለኹ ፥ የሚያልፉትንም ፡ ይከለክላል ፤ በዚያም ፡ ጎግንና ፡ ብዛቱን ፡ ኹሉ ፡ ይቀብራሉ ፤ የሸለቆውንም ፡ ስም ፡ ሐሞንጎግ ፡ ብለው ፡ ይጠሩታል ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 12 ፤ ምድሩንም ፡ ያጸዱ ፡ ዘንድ ፥ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ሰባት ፡ ወር ፡ ይቀብሯቸዋል ፥

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 13 ፤ የምድርም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይቀብሯቸዋል ፥ በተመሰገንኹበትም ፡ ቀን ፡ ለክብር ፡ ይኾንላችኋል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 14 ፤ ምድርንም ፡ ለማጽዳት ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ወድቀው ፡ የቀሩትን ፡ የሚቀብሩ ፥ ዘወትር ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ የሚዞሩትን ፡ ሰዎች ፡ ይቀጥራሉ ፤ ከሰባት ፡ ወርም ፡ በኋላ ፡ ይመረምራሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 15 ፤ በምድርም ፡ የሚዞሩት ፡ ያልፋሉ ፤ የሰውንም ፡ ዐጥንት ፡ ቢያዩ ፥ ቀባሪዎች ፡ በሐሞን ፡ ጎግ ፡ ሸለቆ ፡ እስኪቀብሩት ፡ ድረስ ፡ ምልክት ፡ ያኖሩበታል ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ የከተማዪቱ ፡ ስም ፡ ሐሞና ፡ ይባላል ። እንዲሁ ፡ ምድሪቱን ፡ ያጸዳሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 17 ፤ አንተም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለወፎች ፡ ኹሉና ፡ ለምድር ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ ኑ ፥ ተከማቹ ፥ ሥጋንም ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፥ ደምንም ፡ ትጠጡ ፡ ዘንድ ፥ በእስራኤል ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ወደማርድላችኹ ፡ መሥዋዕት ፥ ርሱም ፡ ታላቅ ፡ መሥዋዕት ፥ ከየስፍራው ፡ ኹሉ ፡ ተሰብሰቡ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 18 ፤ የጎያላኑን ፡ ሥጋ ፡ ትበላላችኹ ፡ የምድርንም ፡ አለቃዎች ፥ የአውራ ፡ በጎችንና ፡ የጠቦቶችን ፥ የፍየሎችንና ፡ የወይፈኖችን ፥ የባሳንን ፡ ፍሪዳዎች ፡ ኹሉ ፥ ደም ፡ ትጠጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 19 ፤ እኔም ፡ ከማርድላችኹ ፡ መሥዋዕት ፡ እስክትጠግቡ ፡ ድረስ ፡ ጮማ ፡ ትበላላችኹ ፡ እስክትሰክሩም ፡ ድረስ ፡ ደም ፡ ትጠጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 20 ፤ በሰደቃዬም ፡ ከፈረሶችና ፡ ከፈረሰኞች ፥ ከጎያላንና ፡ ከሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ትጠግባላችኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 21 ፤ ክብሬንም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አኖራለኹ ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ያደርግኹትን ፡ ፍርዴን ፥ በላያቸውም ፡ ያኖርኳትን ፡ እጄን ፡ ያያሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 22 ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 23 ፤ አሕዛብም ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ በጎጢአታቸው ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ተማረኩ ፡ ያውቃሉ ፤ ስለ ፡ በደሉኝ ፡ እኔም ፡ ፊቴን ፡ ከነርሱ ፡ ስለ ፡ ሸሸግኹ ፥ በጠላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኳቸው ፥ እነርሱም ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ወደቁ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 24 ፤ እንደ ፡ ርኵሰታቸውም ፡ እንደ ፡ መተላለፋቸውም ፡ መጠን ፡ አደረግኹባቸው ፡ ፊቴንም ፡ ከነርሱ ፡ ሸሸግኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አኹን ፡ የያዕቆብን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፡ ለእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ እራራለኹ ፥ ስለ ፡ ቅዱስ ፡ ስሜም ፡ እቀናለኹ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 26 ፤ 27 ፤ ማንም ፡ ሳያስፈራቸው ፡ በምድራቸው ፡ ተዘልለው ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ ከአሕዛብም ፡ ዘንድ ፡ በመለስኳቸው ፡ ጊዜ ፡ ከጠላቶቻቸውም ፡ ምድር ፡ በሰበሰብኳቸው ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ፊት ፡ በተቀደስኩባቸው ፡ ጊዜ ፥ ዕፍረታቸውንና ፡ የበደሉኝን ፡ በደላቸውን ፡ ኹሉ ፡ ይሸከማሉ ።

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 28 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አስማርኬያቸዋለኹና ፥ ወደገዛ ፡ ምድራቸውም ፡ ሰብስቤያቸዋለኹና ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፤ በዚያም ፡ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አልተውም ፥

ሕዝ. ፡ 39 ፡ 29 ፤ ፊቴንም ፡ ከነርሱ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አልሸሸግም ፤ መንፈሴን ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አፍስሻለኹና ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 40 ። _____

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 1 ፤ በተማረክን ፡ በኻያ ፡ ዐምስተኛው ፡ ዓመት ፡ በዓመቱ ፡ መዠመሪያ ፡ ከወሩ ፡ በዐሥረኛው ፡ ቀን ፥ ከተማዩቱ ፡ ከተመታች ፡ በኋላ ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ዓመት ፥ በዚያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ ርሱም ፡ ወደዚያ ፡ ወሰደኝ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ራእይ ፡ ወደእስራኤል ፡ ምድር ፡ አመጣኝ ፡ እጅግም ፡ በረዘመ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አኖረኝ ፥ በዚያም ፡ ላይ ፡ በደቡብ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ከተማ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ ነገር ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 3 ፤ ወደዚያም ፡ አመጣኝ ፥ እንሆም ፥ መልኩ ፡ እንደ ፡ ናስ ፡ መልክ ፡ የመሰለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ ነበረ ፥ በእጁም ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ገመድና ፡ የመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 4 ፤ ሰውዬውም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አሳይኽ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ወደዚህ ፡ ተመርተኻልና ፥ በዐይንኽ ፡ እይ ፥ በጐሮኾም ፡ ስማ ፥ በማሳይኽም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ልብኽን ፡ አድርግ ፤ የምታየውንም ፡ ኹሉ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ንገር ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 5 ፤ እንሆም ፥ በቤቱ ፡ ውጭ ፡ በዙሪያው ፡ ቅጥር ፡ ነበረ ፥ በሰውዬውም ፡ እጅ ፡ የክንዱ ፡ ልክ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ከጋት ፡ የኾነ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ያለበት ፡ የመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ነበረ ፤ የቅጥሩንም ፡ ስፋት ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ ቁመቱንም ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደሚመለከተውም ፡ በር ፡ መጣ ፡ በደረጃዎቹም ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ በበሩ ፡ በኩል ፡ ያለውንም ፡ የመድረኩን ፡ ወለል ፡ ወርዱን ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 7 ፤ የዘበኛውም ፡ ጓዳ ፡ ኹሉ ፡ ርዝመቱ ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፥ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ ነበረ ፤ በዘበኛውም ፡ ጓዳዎች ፡ መካከል ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በበሩም ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ በስተውስጥ ፡ በኩል ፡ የሚገኝ ፡ የበሩ ፡ የመድረክ ፡ ወለል ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 8 ፤ በስተውስጥም ፡ ያለውን ፡ የበሩን ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ አንድ ፡ ዘንግ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 9 ፤ የበሩንም ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ ስምንት ፡ ክንድ ፥ የግንቡንም ፡ አዕማድ ፡ ወርድ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ የበሩም ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ በስተውስጥ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 10 ፤ የምሥራቁም ፡ በር ፡ የዘበኛ ፡ ጓዳዎች ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ሦስት ፡ በዚያም ፡ በኩል ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ፥ ለሦስቱም ፡ አንድ ፡ ልክ ፡ ነበረ ፤ የግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ወርድ ፡ በዚህ ፡ በኩልና ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ልክ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 11 ፤ የበሩንም ፡ መግቢያ ፡ ወርድ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ የበሩንም ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 12 ፤ በዘበኛ ፡ ጓዳዎችም ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ በዚያም ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ዳርቻ ፡ ነበረ ፤ የዘበኛ ፡ ጓዳዎቹም ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ በዚያም ፡ በኩል ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 13 ፤ ከአንዱም ፡ የዘበኛ ፡ ጓዳ ፡ ደርብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሌላው ፡ ደርብ ፡ ድረስ ፡ የበሩን ፡ ወርድ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ መዝጊያውና ፡ መዝጊያውም ፡ ትይዩ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 14 ፤ ደጀ ፡ ሰላሙንም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ በበሩም ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ ዙሪያ ፡ አደባባይ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 15 ፤ ከበሩም ፡ መግቢያ ፡ ፊት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ውስጠኛው ፡ የበሩ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 16 ፤ በዘበኛ ፡ ጓዳዎቹም ፡ በበሩ ፡ ውስጥ ፡ በዙሪያው ፡ በነበሩትም ፡ በግንቡ ፡ አዕማድ ፡ የዐይነ ፡ ርግብ ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩባቸው ፤ ደግሞም ፡ በደጀ ፡ ሰላሙ ፡ ውስጥ ፡ በዙሪያው ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩ ፤ በግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ተቀርጾባቸው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 17 ፤ ወደውጭውም ፡ አደባባይ ፡ አመጣኝ ፥ እንሆም ፥ በአደባባዩ ፡ ዙሪያ ፡ የተሠሩ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶችና ፡ ወለል ፡ ነበሩ ፤ በወለሉም ፡ ላይ ፡ ሠላሳ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 18 ፤ ወለሉም ፡ በበሮች ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፡ ይህም ፡ ታችኛው ፡ ወለል ፡ እንደ ፡ በሮቹ ፡ ርዝመት ፡ መጠን ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 19 ፤ ከታችኛውም ፡ በር ፡ ፊት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ፊት ፡ ድረስ ፡ ወርዱን ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ መራኝ ፥ እንሆም ፥ በውጭው ፡ አደባባይ ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ የሚመለከት ፡

በር ፡ ነበረ ፤ ርዝመቱንና ፡ ወርዱንም ፡ ለካ ፥

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 21 ፤ የዘበኛ ፡ ጓዳዎቹም ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ ሦስት ፡ በዚያም ፡ በኩል ፡ ሦስት ፡ ነበሩ ፤ የግንቡ ፡ አዕማድና ፡ መዛነቢያዎቹም ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ በር ፡ ልክ ፡ ነበሩ ፤ ርዝመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 22 ፤ መስኮቶቹም ፡ መዛነቢያዎቹም ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎቹም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ እንደሚመለከተው ፡ በር ፡ ልክ ፡ ነበሩ ። ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ሰባት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩ ፡ መዛነቢያዎቹም ፡ በፊቱ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 23 ፤ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በሰሜኑና ፡ በምሥራቁ ፡ በኩል ፡ በሌላው ፡ በር ፡ አንጻር ፡ በር ፡ ነበረ ፤ ከበርም ፡ ወደ ፡ በር ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 24 ፤ ወደ ፡ ደቡብም ፡ መራኝ ፥ እንሆም ፥ ወደ ፡ ደቡብ ፡ የሚመለከት ፡ በር ፡ ነበረ ፤ የግንቡን ፡ አዕማድና ፡ መዛነቢያዎቹንም ፡ እንደዚያው ፡ መጠን ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 25 ፤ በርሱና ፡ በመዛነቢያዎቹም ፡ ዙሪያ ፡ እንደ ፡ እነዚያ ፡ መስኮቶች ፡ የሚመስሉ ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩ ፤ ርዝመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 26 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ሰባት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩ ፥ መዛነቢያዎቹም ፡ በፊቱ ፡ ነበሩ ፤ በግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ አንዱ ፡ በዚህ ፡ አንዱም ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ ኾኖ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ተቀርጾባቸው ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 27 ፤ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ በር ፡ ነበረ ፤ ከበር ፡ እስከ ፡ በር ፡ ድረስ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 28 ፤ በደቡብም ፡ በር ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ አገባኝ ፤ እንደዚያውም ፡ መጠን ፡ አድርጎ ፡ የደቡብን ፡ በር ፡ ለካ ፤

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 29 ፤ እንደዚያውም ፡ መጠን ፡ አድርጎ ፡ የዘበኛ ፡ ጓዳዎቹንና ፡ የግንቡን ፡ አዕማድ ፡ መዛነቢያዎቹንም ፡ ለካ ፤ በርሱና ፡ በመዛነቢያዎቹም ፡ ዙሪያ ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩ ፤ ርዝመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 30 ፤ በዙሪያውም ፡ ደጀ ፡ ሰላሞች ፡ ነበሩ ፤ ርዝመታቸውም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ወርዳቸውም ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 31 ፤ መዛነቢያዎቹም ፡ ወደ ፡ ውጭው ፡ አደባባይ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ በግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ተቀርጾ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ስምንት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 32 ፤ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ አገባኝ ፥ እንደዚያውም ፡ መጠን ፡ በሩን ፡ ለካ ፤

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 33 ፤ እንደዚያውም ፡ መጠን ፡ የዘበኛ ፡ ጓዳዎቹንና ፡ የግንቡን ፡ አዕማድ ፡ መዛነቢያዎቹንም ፡ ለካ ፤ በርሱና ፡ በመዛነቢያዎቹም ፡ ዙሪያ ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩ ፥ ርዝመቱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 34 ፤ መዛነቢያዎቹም ፡ በስተውጭ ፡ ወዳለው ፡ አደባባይ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ በግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ተቀርጾ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ስምንት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩት ።

ሕዝ. ፥ 40 ፥ 35 ፤ በሰሜንም ፡ ወዳለው ፡ በር ፡ አመጣኝ ፥ እንደዚያውም ፡ መጠን ፡ ለካው ፤

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 36 ፤ የዘበኛ ፡ ጓዳዎቹንና ፡ የግንቡን ፡ አዕማድ ፡ መዛነቢያዎቹንም ፡ ለካ ፤ በዙሪያውም ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩበት ፥ ርዝመቱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 37 ፤ የግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ወደ ፡ ውጭው ፡ አደባባይ ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ በግንቡም ፡ አዕማድ ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ተቀርጾ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ስምንት ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩት ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 38 ፤ በበሮቹም ፡ በግንብ ፡ አዕማድ ፡ አጠገብ ፡ ዕቃ ፡ ቤቱና ፡ መዝጊያው ፡ ነበሩ ፤ በዚያም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያጥቡ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 39 ፤ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ የኀጢአቱንና ፡ የበደሉንም ፡ መሥዋዕት ፡ ያርዱባቸው ፡ ዘንድ ፥ በበሩ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ገበታዎች ፥ በዚያም ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ገበታዎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 40 ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በር ፡ በስተውጭው ፥ በመወጣጫው ፡ ደረጃዎች ፡ አጠገብ ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ ኹለት ፡ ገበታዎች ፡ ነበሩ ፥ በሌላውም ፡ ወገን ፡ በበሩ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ ገበታዎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 41 ፤ በበሩ ፡ አጠገብ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ አራት ፡ ገበታዎች ፡ በዚያም ፡ ወገን ፡ አራት ፡ ገበታዎች ፡ ነበሩ ፤ መሥዋዕት ፡ የሚያርዱባቸው ፡ ገበታዎች ፡ ስምንት ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 42 ፤ ስለሚቃጠለውም ፡ መሥዋዕት ፡ ርዝመታቸው ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ወርዳቸውም ፡ ክንድ ፡ ተኩል ፡ ቁመታቸውም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ የኾኑ ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕቱን ፡ የሚያርዱበትን ፡ ዕቃ ፡ ያኖሩባቸው ፡ ዘንድ ፥ ከተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠሩ ፡ አራት ፡ ገበታዎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 43 ፤ በዙሪያውም ፡ አንድ ፡ ጋት ፡ የኾነ ፡ ክፈፍ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ተቀልብሶ ፡ ነበር ፤ በገበታዎቹም ፡ ላይ ፡ የቀዮርባኑ ፡ ሥጋ ፡ ነበረባቸው ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 44 ፤ ወደ ፡ ውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ አገባኝ ፥ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ፤ አንዱ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ በሚመለከት ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፥ መግቢያውም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ፤ ሌላውም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ በሚመለከተው ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ፥ መግቢያውም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 45 ፤ ሰውዬውም ፦ ይህ ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ የሚመለከት ፡ ቤት ፡ ለማገልገል ፡ ለሚተጉ ፡ ካህናት ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 46 ፤ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ የሚመለከተው ፡ ቤት ፡ መሠዊያውን ፡ ለማገልገል ፡ ለሚተጉ ፡ ካህናት ፡ ነው ፤ እነዚህ ፡ ከሌዊ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀርቡ ፡ የሳዶቅ ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 47 ፤ አደባባዩንም ፡ በአራት ፡ ማእዘኑ ፡ ርዝመቱን ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ወርዱንም ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ መሠዊያውም ፡ በቤቱ ፡ ፊት ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 48 ፤ ወደቤቱም ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ አመጣኝ ፥ የደጀ ፡ ሰላሙንም ፡ የግንብ ፡ አዕማድ ፡ ወርድ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ በዚያም ፡ ወገን ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ የበሩም ፡ ወርድ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ በበሩም ፡ በዚህ ፡ ወገንና ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ የነበሩት ፡ ግንቦች ፡ ሦስት ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 40 ፡ 49 ፤ የደጀ ፡ ሰላሙም ፡ ርዝመት ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚያደርሱ ፡ ዐሥር ፡ ደረጃዎች ፡ ነበሩ ፤ አንድ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ አንድም ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ ኾነው ፡ በመቃኖቹ ፡ አጠገብ ፡ የግንብ ፡ አዕማድ ፡ ነበሩ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 41 ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ መቅደሱም ፡ አገባኝ ፥ የግንቡንም ፡ አዕማድ ፡ ወርድ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡

በዚያም ፡ ወገን ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 2 ፤ የመግቢያውም ፡ ወርድ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የመግቢያውም ፡ መቃኖች ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ በዚያም ፡ ወገን ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበሩ ፤ ርዝመቱንም ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ወርዱንም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 3 ፤ ወደ ፡ ውስጥም ፡ ገባ ፥ የመግቢያውንም ፡ የግንብ ፡ አዕማድ ፡ ወርድ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ፤ የመግቢያውም ፡ ወርድ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፥ የመግቢያውም ፡ ግንብ ፡ ወርድ ፡ በዚህ ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡ ክንድ ፡ በዚያም ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 4 ፤ በመቅደሱም ፡ ፊት ፡ ርዝመቱን ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ወርዱንም ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካና ፦ ይህ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ ነው ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 5 ፤ የመቅደሱንም ፡ ግንብ ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፥ በመቅደሱም ፡ ዙሪያ ፡ ኹሉ ፡ ያሉትን ፡ የጓዳዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ወርድ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 6 ፤ ጓዳዎቹም ፡ አንዱ ፡ ከአንዱ ፡ በላይ ፡ በሦስት ፡ ደርብ ፡ ነበሩ ፥ በያንዳንዱም ፡ ደርብ ፡ ሠላሳ ፡ ጓዳዎች ፡ ነበሩ ። በመቅደሱም ፡ ግንብ ፡ ዙሪያ ፡ ደገፋዎች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፥ አረፍቶች ፡ ነበሩ ፥ በመቅደሱም ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ ደገፋዎች ፡ አልነበሩም ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 7 ፤ በቤቱም ፡ ዙሪያ ፡ ባለ ፡ ግንብ ፡ ውስጥ ፡ በነበሩት ፡ አረፍቶች ፡ ምክንያት ፡ ላይኞቹ ፡ ጓዳዎች ፡ ከታችኞቹ ፡ ጓዳዎች ፡ ይበልጡ ፡ ነበር ፤ ከታችኛውም ፡ ደርብ ፡ ወደ ፡ መካከለኛው ፡ ከመካከለኛውም ፡ ደርብ ፡ ወደ ፡ ላይኛው ፡ የሚወጣበት ፡ ደረጃ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 8 ፤ ለመቅደሱም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ወለል ፡ በዙሪያው ፡ እንዳለው ፡ አየኹ ፤ የጓዳዎቹም ፡ መሠረት ፡ ቁመቱ ፡ ሙሉ ፡ ዘንግ ፡ የሚያኽል ፡ ስድስት ፡ ትልቅ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 9 ፤ የጓዳዎቹም ፡ የውጭው ፡ ግንብ ፡ ውፍረት ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ፤ በመቅደሱም ፡ ጓዳዎች ፡ አጠገብ ፡ የቀረ ፡ አንድ ፡ ባዶ ፡ ስፍራ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 10 ፤ 11 ፤ በዚህም ፡ በባዶው ፡ ስፍራ ፡ አንዱ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አንዱም ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ የጓዳዎች ፡ መግቢያ ፡ ነበረ ፥ የባዶውም ፡ ስፍራ ፡ ወርድ ፡ በዙሪያ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ነበረ ። በመቅደሱም ፡ ዙሪያ ፡ ወርዱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 12 ፤ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ በልዩ ፡ ስፍራ ፡ አንጻር ፡ የነበረ ፡ ግቢ ፡ ስፋቱ ፡ ሰባ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ። በግቢውም ፡ ዙሪያ ፡ የነበረ ፡ ግንብ ፡ ውፍረቱ ፡ ዐምስት ፡ ክንድ ፡ ርዝመቱም ፡ ዘጠና ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 13 ፤ የመቅደሱንም ፡ ርዝመት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ የልዩውን ፡ ስፍራና ፡ ግቢውን ፡ ከግንቡ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 14 ፤ ደግሞም ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ የነበረውን ፡ የመቅደሱንና ፡ የልዩውን ፡ ስፍራ ፡ ወርድ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 15 ፤ ወደ ፡ ኋላውም ፡ ባለው ፡ በልዩ ፡ ስፍራ ፡ አንጻር ፡ የነበረውን ፡ የግቢውን ፡ ርዝመት ፡ በዚህና ፡ በዚያም ፡ ከነበሩት ፡ ከግንቦቹ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 16 ፤ መድረኮቹ ፥ መቅደሱና ፡ በስተውስጥ ፡ ያለው ፡ ክፍል ፡ ደጀ ፡ ሰላሙም ፡ በዕንጨት ፡ ተለብጠው ፡ ነበር ፥ በሦስቱም ፡ ዙሪያ ፡ የዐይነ ፡ ርግብ ፡ መስኮቶች ፡ ነበሩ ። መቅደሱም ፡ በመድረኩ ፡ አንጻር ፡ ከመሬት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መስኮቶቹ ፡ ድረስ ፡ በዕንጨት ፡ ተለብጦ ፡ ነበር ፤ መስኮቶቹም ፡ የዐይነ ፡ ርግብ ፡ ነበሩ ፤

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 17 ፤ በደጁም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ድረስ ፥ በውጭም ፡ ግንቡ ፡ ዙሪሉ ፡ ውስጡም ፡ ውጭውም ፡ ተለብጦ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 18 ፤ ኪሩቤልና ፡ የዘንባባው ፡ ዛፎች ፡ ተቀርጸውበት ፡ ነበር ፤ የዘንባባውም ፡ ዛፍ ፡ ከኪሩብና ፡ ከኪሩብ ፡ መካከል ፡ ነበረ ፤ ለያንዳንዱም ፡ ኪሩብ ፡ ኹለት ፡ ፊት ፡ ነበረው ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 19 ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ወዳለው ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የሰው ፡ ፊት ፡ ይመለከት ፡ ነበር ፥ በሌላውም ፡ ወገን ፡ ወዳለው ፡ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ የአንበሳ ፡ ፊት ፡ ይመለከት ፡ ነበር ፤ በቤቱ ፡ ዙሪያ ፡ እንደዚህ ፡ ተደርጎ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 20 ፤ ከመሬት ፡ አንሥቶ ፡ እስከደጁ ፡ ራስ ፡ ድረስ ፡ ኪሩቤልና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ተቀርጸው ፡ ነበር ። የመቅደሱ ፡ ግንብ ፡ እንደዚህ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 21 ፤ የመቅደሱ ፡ መቃኖችም ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበሩ ፥ የመቅደሱ ፡ ፊትም ፡ መልኩ ፡ እንደ ፡ ሌላው ፡ መልክ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 22 ፤ መሠዊያውም ፡ ቁመቱ ፡ ሦስት ፡ ክንድ ፡ ርዝመቱ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ኾኖ ፡ ከዕንጨት ፡ ተሠርቶ ፡ ነበር ፤ ማእዘኖቹም ፡ እግሩም ፡ አገዳዎቹም ፡ ከዕንጨት ፡ ተሠርተው ፡ ነበር ፤ ርሱም ፦ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያለችው ፡ ገበታ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 23 ፤ ለመቅደሱና ፡ ለተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ ኹለት ፡ መዝጊያዎች ፡ ነበሯቸው ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 24 ፤ ለያንዳንዱ ፡ መዝጊያም ፡ ኹለት ፡ ተዘዋዋሪ ፡ ሳንቃዎች ፡ ነበሩት ፤ ለአንዱ ፡ መዝጊያ ፡ ኹለት ፡ ለሌላውም ፡ መዝጊያ ፡ ኹለት ፡ ሳንቃዎች ፡ ነበሩት ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 25 ፤ በግንቡም ፡ ላይ ፡ በተቀረጹት ፡ ዐይነት ፡ በእነዚህ ፡ በመቅደሱ ፡ መዝጊያዎች ፡ ላይ ፡ ኪሩቤልና ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ተቀርጸው ፡ ነበር ፤ በስተውጭም ፡ ባለው ፡ በደጀ ፡ ሰላሙ ፡ ፊት ፡ የዕንጨት ፡ መድረክ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 41 ፡ 26 ፤ በደጀ ፡ ሰላሙም ፡ በኹለቱ ፡ ወገን ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ የዐይነ ፡ ርግብ ፡ መስኮቶችና ፡ የተቀረጹ ፡ የዘንባባ ፡ ዛፎች ፡ ነበሩበት ፤ የመቅደሱም ፡ ጓዳዎችና ፡ የዕንጨቱ ፡ መድረክ ፡ እንዲሁ ፡ ነበሩ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 42 ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 1 ፤ በውጭም ፡ አደባባይ ፡ በሰሜኑ ፡ መንገድ ፡ አወጣኝ ፥ በልዩውም ፡ ስፍራ ፡ አንጻርና ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ ግቢ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ወዳለው ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ አገባኝ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 2 ፤ መቶ ፡ ክንድ ፡ በኾነው ፡ ርዝመት ፡ ፊት ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ መዝጊያ ፡ ነበረ ፡ ወርዱም ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 3 ፤ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በኻያው ፡ ክንድ ፡ አንጻር ፡ በውጭውም ፡ አደባባይ ፡ በወለሉ ፡ አንጻር ፡ በሦስት ፡ ደርብ ፡ በትይዩ ፡ የተሠራ ፡ መተላለፊያ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 4 ፤ በዕቃ ፡ ቤቶቹም ፡ ፊት ፡ በስተውስጥ ፡ ወርዱ ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ርዝመቱ ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ መንገድ ፡ ነበረ ፤ መዝጊያዎቻቸውም ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 5 ፤ መተላለፊያውም ፡ አሳጥሯቸዋልና ፥ ላይኞቹ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ከመካከለኞቹና ፡ ከታችኞቹ ፡ ይልቅ ፡ ዐጫጊር ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 6 ፤ በሦስትም ፡ ደርብ ፡ ተሠርተው ፡ ነበርና ፥ በአደባባዩም ፡ እንዳሉት ፡ አዕማድ ፥ አዕማድ ፡ አልነበሩላቸውምና ፡ ስለዚህ ፡ ላይኞቹ ፡ ከመካከለኞቹና ፡ ከታችኞቹ ፡ ይልቅ ፡ ጠባብ ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 7 ፤ በውጭ ፡ በዕቃ ፡ ቤቶቹ ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፥ ወደ ፡ ውጭው ፡ አደባባይ ፡ የሚመለከተው ፡ ቅጥር ፥ በዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ትይዩ ፡ የኾነ ፥ ርዝመቱ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 8 ፤ በመቅደሱ ፡ ፊት ፡ የነበሩት ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ርዝመታቸው ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ሲኾን ፡ በውጭው ፡ አደባባይ ፡ በኩል ፡ የነበሩት ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ርዝመታቸው ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ነበረና ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 9 ፤ ከነዚህም ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ በታች ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፥ ሰው ፡ ከውጭው ፡ አደባባይ ፡ የሚገባበት ፡ መግቢያ ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በቅጥሩ ፡ ራስ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 10 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ በልዩው ፡ ስፍራና ፡ በግቢው ፡ አንጻር ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 11 ፤ በስተፊታቸውም ፡ የነበረ ፡ መንገድ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶቹ ፡ መንገድ ፡ ምስያ ፡ ነበረ ። ርዝመታቸውም ፡ ወርዳቸውም ፡ መውጫቸውም ፡ ሥርዐታቸውም ፡ መዝጊያዎቻቸውም ፡ በዚያው ፡ ልክ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 12 ፤ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ካሉት ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፡ በታች ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ በቅጥሩ ፡ ራስ ፡ አጠገብ ፡ መግቢያ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ በልዩ ፡ ስፍራ ፡ አንጻር ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ያሉ ፡ ዕቃ ፡ ቤቶች ፥ እነርሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚቀርቡ ፡ ካህናት ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የተቀደሰውን ፡ ምግብ ፡ የሚበሉባቸው ፡ ቤቶች ፡ ናቸው ። ስፍራው ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ በዚያ ፡ የተቀደሰውን ፡ ነገር ፡ የእኽሉን ፡ ቀርባን ፡ የኀጢአቱንና ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕት ፡ ያኖራሉ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 14 ፤ ካህናቱም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ከመቅደሱ ፡ በውጭው ፡ አደባባይ ፡ አይወጡም ፤ የሚያገለግሉበትን ፡ ልብሳቸውን ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ በዚያ ፡ ያኖሩታል ፥ ሌላም ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 15 ፤ ውስጠኛውንም ፡ ቤት ፡ ለክቶ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በሚመለከት ፡ በር ፡ መንገድ ፡ አወጣኝ ፡ ርሱንም ፡ በዙሪያው ፡ ለካው ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 16 ፤ የምሥራቁን ፡ ወገን ፡ በመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 17 ፤ ዞረም ፥ የሰሜኑንም ፡ ወገን ፡ በመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 18 ፤ ዞረም ፥ የደቡቡንም ፡ ወገን ፡ በመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 19 ፤ ዞረም ፥ የምዕራቡንም ፡ ወገን ፡ በመለኪያ ፡ ዘንግ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አድርጎ ፡ ለካ ።

ሕዝ. ፡ 42 ፡ 20 ፤ በአራቱ ፡ ወገን ፡ ለካው ። የተቀደሰውንና ፡ ያልተቀደሰውን ፡ ይለይ ፡ ዘንድ ፥ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ቅጥር ፡ በዙሪያው ፡ ነበረ ።

_____ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 43 ። _____

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ወደሚመለከተው ፡ በር ፡ አመጣኝ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ ከምሥራቅ ፡ መንገድ ፡ መጣ ፤ ድምፁም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ይተሙ ፡ ነበር ፥ ከክብሩም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ ታበራ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 3 ፤ ያየኹትም ፡ ራእይ ፡ ከተማዪቱን ፡ ለማጥፋት ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፡ እንዳየኹት ፡ ራእይ ፡ ነበረ ፤ ራእዩም ፡ በኮበር ፡ ወንዝ ፡ እንዳየኹት ፡ ራእይ ፡ ነበረ ፤ እኔም ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ በሚመለከት ፡ በር ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ገባ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 5 ፤ መንፈሱም ፡ አነሣኝ ፡ ወደ ፡ ውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ አገባኝ ፤ እንሆም ፥ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ መቅደሱን ፡ ሞልቶት ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 6 ፤ በመቅደሱም ፡ ኾኖ ፡ የሚናገረኝን ፡ ሰማኹ ፥ በአጠገቤም ፡ ሰው ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 7 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ለዘለዓለም ፡ የምቀመጥበት ፡ የዙፋኔ ፡ ስፍራና ፡ የእግሬ ፡ ጫማ ፡ መረገጫ ፡ ይህ ፡ ነው ። ዳግመኛም ፡ የእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ነገሥታታቸው ፡ በግልሙትናቸውና ፡ በከፍታዎቻቸው ፡ ባለው ፡ በነገሥታታቸው ፡ ሬሳ ፡ ቅዱስ ፡ ስሜን ፡ አያረክሱም ፤

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 8 ፤ መድረካቸውን ፡ በመድረኬ ፡ አጠገብ ፥ መቃናቸውንም ፡ በመቃኔ ፡ አጠገብ ፡ አድርገዋልና ። በእኔና ፡ በእነርሱም ፡ መካከል ፡ ግንብ ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፤ በሠሩትም ፡ ርኵሰት ፡ ቅዱስ ፡ ስሜን ፡ አረከሱ ፤ ስለዚህ ፥ በቀኑጣዬ ፡ አጠፋኋቸው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 9 ፤ አኹንም ፡ ግልሙትናቸውንና ፡ የነገሥታታቸውን ፡ ሬሳ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ያርቁ ፥ እኔም ፡ ለዘለዓለም ፡ በመካከላቸው ፡ ዐድራለኹ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 10 ፤ አንተም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፥ ከኀጢአታቸው ፡ የተነሣ ፡ ያፍሩ ፡ ዘንድ ፥ ለእስራኤል ፡ ወገን ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ አሳያቸው ፤ አምሳያውንም ፡ ይለኩ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 11 ፤ ከሠሩትም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተነሣ ፡ ቢያፍሩ ፥ የቤቱን ፡ መልክና ፡ ምሳሌውን ፡ መውጫውንም ፡ መግቢያውንም ፡ ሥርዐቱንም ፡ ሕጉንም ፡ ኹሉ ፡ አስታውቃቸው ፤ ሥርዐቱንና ፡ ሕጉን ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ያደርጉትም ፡ ዘንድ ፥ በፊታቸው ፡ ጻፈው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 12 ፤ የቤቱ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በተራራው ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ዳርቻው ፡ ኹሉ ፡ በዙሪያው ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ። እንሆ ፥ የቤቱ ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 13 ፤ የመሠዊያውም ፡ ልክ ፡ በክንድ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ክንዱም ፡ ክንድ ፡ ተጋት ፡ ነው ። የመሠረቱም ፡ ቁመቱ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነው ፥ አንድ ፡ ስንዝርም ፡ ክፈፍ ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ በዙሪያው ፡ አለ ፤ የመሠዊያው ፡ መሠረት ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 14 ፤ በመሬቱም ፡ ላይ ፡ ካለው ፡ መሠረት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታችኛው ፡ ዕርከን ፡ ድረስ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነው ፤ ከትንሹም ፡ ዕርከን ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ትልቁ ፡ ዕርከን ፡ ድረስ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 15 ፤ ምድጃውም ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነው ፤ በምድጃውም ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ የሚሉ ፡ አራት ፡ ቀንዶች ፡ አሉበት ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 16 ፤ የምድጃውም ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ክንድ ፡ ነው ፥ አራቱም ፡ ማእዘን ፡ ትክክል ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 17 ፤ የዕርከኑም ፡ ርዝመት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ ነው ፥ አራቱም ፡ ማእዘን ፡ ትክክል ፡ ነው ፤ በዙሪያውም ፡ ያለው ፡ ክፈፍ ፡ እኩል ፡ ክንድ ፡ ነው ፥ መሠረቱም ፡ በዙሪያው ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ ነው ፤ ደረጃዎቹም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከታሉ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 18 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርቡበት ፡ ዘንድ ፥ ደሙንም ፡ ይረጩበት ፡ ዘንድ ፥ በሚሠሩበት ፡ ቀን ፡ የመሠዊያው ፡ ሕግ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 19 ፤ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ለሚቀርቡ ፡ ከሳዶቅ ፡ ዘር ፡ ለሚኾኑ ፡ ለሌዋውያኑ ፡ ካህናት ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ወይፈን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 20 ፤ ከደሙም ፡ ትወስዳለኽ ፥ በአራቱ ፡ ቀንዶቹም ፡ በዕርከኑም ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ ላይ ፡ በዙሪያውም ፡ ባለው ፡ ክፈፍ ፡ ላይ ፡ ትረጨዋለኽ ፤ እንዲሁ ፡ ታነጻዋለኽ ፡ ታስተሰርይለትማለኽ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 21 ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ወይፈን ፡ ትወስዳለኽ ፥ በመቅደሱም ፡ ውጭ ፡ በቤቱ ፡ በታዘዘው ፡ ስፍራ ፡ ይቃጠላል ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 22 ፤ በኹለተኛውም ፡ ቀን ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ታቀርባለኽ ፤ በወይፈኑም ፡ እንዳነጹት ፡ እንዲሁ ፡ መሠዊያውን ፡ ያነጹበታል ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 23 ፤ ማንጻቱንም ፡ ከፈጸምኽ ፡ በኋላ ፥ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ወይፈን ፡ ከመንጋውም ፡ የወጣውን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ታቀርባለኽ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 24 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ታቀርባቸዋለኽ ፥ ካህናቱም ፡ ጨው ፡ ይጨምሩባቸዋል ፥ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ አድርገው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀርቧቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 25 ፤ ሰባት ፡ ቀንም ፡ በየዕለቱ ፡ ለኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ አውራ ፡ ፍየልን ፡ ታቀርባለኽ ፥ ነውርም ፡ የሌለባቸውን ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፡ ከመንጋውም ፡ የወጣውን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያቀርባሉ ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 26 ፤ ሰባት ፡ ቀን ፡ ለመሠዊያው ፡ ያስተሰርያሉ ፡ ያነጹትማል ፥ እንዲሁም ፡ ይቀድሱታል ።

ሕዝ. ፡ 43 ፡ 27 ፤ ቀኖቹንም ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ካህናቱ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹን ፡ የደኅንነትንም ፡ መሥዋዕታችኹን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ያደርጋሉ ፤ እኔም ፡ እቀበላችኋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 44 ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ወደሚመለከተው ፡ በስተውጭ ፡ ወዳለው ፡ ወደመቅደሱ ፡ በር ፡ አመጣኝ ፤ ተዘግቶም ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ይህ ፡ በር ፡ ተዘግቶ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይከፈትም ፥ ሰውም ፡ አይገባበትም ፤ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገብቶበታልና ፥ ተዘግቶ ፡ ይኖራል ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 3 ፤ አለቃው ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንጀራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፥ ይቀመጥበታል ፤ በበሩ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ መንገድ ፡ ይገባል ፥ በዚያም ፡ መንገድ ፡ ይወጣል ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 4 ፤ በሰሜኑም ፡ በር ፡ መንገድ ፡ በቤቱ ፡ ፊት ፡ አመጣኝ ፤ እኔም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሞልቶት ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ልብ ፡ አድርግ ፡ ስለእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ሥርዐትና ፡ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ የምናገርኽን ፡ ኹሉ ፡ በዐይንኽ ፡ ተመልከት ፥ በገሮኽም ፡ ስማ ፤ የቤቱንም ፡ መግቢያ ፡ የመቅደሱንም ፡ መውጫ ፡ ኹሉ ፡ ልብ ፡ አድርግ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 6 ፤ ለዐመፀኛው ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ በል ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 7 ፤ እንጀራዬን ፥ ስብንና ፡ ደምን ፥ በምታቀርቡበት ፡ ጊዜ ፡ በመቅደሴ ፡ ውስጥ ፡ ይኾኑ ፡

ዘንድ ፥ ቤቴንም ፡ ያረክሱ ፡ ዘንድ ፥ በልባቸውና ፡ በሥጋቸው ፡ ያልተገረዙትን ፡ እንግዳዎችን ፡ ሰዎች ፡
አግብታችኋልና ፥ እነርሱም ፡ በርኵሰታችኹ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ይጨመሩ ፡ ዘንድ ፥ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡
አፍርሰዋልና ፥ ርኵሰታችኹ ፡ ዥሉ ፡ ይብቃችኹ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 8 ፤ በመቅደሴ ፡ ውስጥ ፡ ለራሳችኹ ፡ ሥርዐቴን ፡ ጠባቂዎች ፡ አደረጋችኹ ፡ እንጂ ፡ የተቀደሰውን ፡
ነገሬን ፡ ሥርዐት ፡ አልጠበቃችኹም ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 9 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ካሉት ፡ ዥሉ ፡
በልቡና ፡ በሥጋው ፡ ያልተገረዘ ፡ እንግዳ ፡ ዥሉ ፡ ወደ ፡ መቅደሴ ፡ አይግባ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 10 ፤ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የራቁ ፥ እስራኤልም ፡ በሳቱ ፡ ጊዜ ፡ ጣዖታቸውን ፡ ተከትለው ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡
የሳቱ ፡ ሌዋውያን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይሸከማሉ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመቅደሴ ፡ ውስጥ ፡ አገልጋዮች ፡ ይኾናሉ ፥ በቤቱም ፡ በሮች ፡ በረኞች ፡ ይኾናሉ ፡
በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ያገለግላሉ ፤ ለሕዝቡም ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ ሌላ ፡ መሥዋዕቱን ፡
ያርዳሉ ፥ ያገለግሏቸውም ፡ ዘንድ ፥ በፊታቸው ፡ ይቆማሉ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 12 ፤ በጣዖቶቻቸውም ፡ ፊት ፡ አገልግለዋቸው ፡ ነበሩና ፥ ለእስራኤልም ፡ ቤት ፡ የኀጢአት ፡ ዕንቅፋት ፡
ኾነዋልና ፥ ስለዚህ ፡ እጄን ፡ በላያቸው ፡ አንሥቻለኹ ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይሸከማሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 13 ፤ ካህናትም ፡ ይኾኑኝ ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ አይቀርቡም ፥ ወደተቀደሰውም ፡ ነገሬና ፡ ወደቅድስተ ፡
ቅዱሳን ፡ ነገር ፡ አይቀርቡም ፤ ዕፍረታቸውንና ፡ የሠሩትንም ፡ ርኵሰታቸውን ፡ ይሸከማሉ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአገልግሎቱ ፡ ዥሉና ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚደረገው ፡ ዥሉ ፡ የቤቱን ፡ ሥርዐት ፡
ጠባቂዎች ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ በሳቱ ፡ ጊዜ ፡ የመቅደሴን ፡ ሥርዐት ፡ የጠበቁ ፡
የሳዶቅ ፡ ልጆች ፡ ሌዋውያን ፡ ካህናት ፡ ያገለግሉኝ ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ይቀርባሉ ፤ ስቡንና ፡ ደሙንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡
ያቀርቡ ፡ ዘንድ ፥ በፊቴ ፡ ይቆማሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 16 ፤ ወደ ፡ መቅደሴም ፡ ይገባሉ ፡ ያገለግሉኝም ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ ገበታዬ ፡ ይቀርባሉ ፡ ሥርዐቴንም ፡
ይጠብቃሉ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 17 ፤ ወደ ፡ ውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በር ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡
ይልበሱ ፤ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በርና ፡ በቤቱ ፡ ውስጥ ፡ ባገለገሉ ፡ ጊዜ ፡ ከበግ ፡ ጠጕር ፡ አንዳች ፡ ነገር ፡
በላያቸው ፡ አይኹን ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 18 ፤ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ መጠምጠሚያ ፡ ይኹን ፥ በወገባቸውም ፡ ላይ ፡ የተልባ ፡
እግር ፡ ሱሪ ፡ ይኹን ፤ የሚያወዛም ፡ ነገር ፡ አይታጠቁ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 19 ፤ ወደ ፡ ውጭውም ፡ አደባባይ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ያገለገሉበትን ፡ ልብሳቸውን ፡
ያውልቁ ፡ በተቀደሰውም ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ያኑሩት ፥ ሕዝቡንም ፡ በልብሳቸው ፡ እንዳይቀድሱ ፡ ሌላውን ፡ ልብስ ፡
ይልበሱ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 20 ፤ ራሳቸውንም ፡ አይላጩ ፡ የራሳቸውንም ፡ ጠጕር ፡ ይከርከሙ ፡ እንጂ ፡ ጠጕራቸውን ፡
አያሳድጉ ።

ሕዝ. ፥ 44 ፥ 21 ፤ ካህናቱም ፡ ዥሉ ፡ በውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ሲገቡ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አይጠጡ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 22 ፤ መበለቲቱንና ፡ የተፈታችዩቱን ፡ አያግቡ ፤ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዘር ፡ ግን ፡ ድንግሊቱን ፡ ወይም ፡ የካህን ፡ ሚስት ፡ የነበረችዩቱን ፡ መበለት ፡ ያግቡ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 23 ፤ በተቀደሰውና ፡ ባልተቀደሰው ፡ መካከል ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፥ ሕዝቤን ፡ ያስተምሩ ፥ ንጹሕና ፡ ንጹሕ ፡ ባልኾነው ፡ መካከል ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ፥ ያሳይዋቸው ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 24 ፤ ክርክርም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ለመፍረድ ፡ ይቁሙ ፤ እንደ ፡ ፍርዴ ፡ ይፍረዱ ፤ በበዓላቴ ፡ ኹሉ ፡ ሕጌንና ፡ ሥርዐቴን ፡ ይጠብቁ ፥ ሰንበታቴንም ፡ ይቀድሱ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 25 ፤ እንዳይረክሱም ፡ ወደሞተ ፡ ሰው ፡ አይግቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአባት ፡ ወይም ፡ ለእናት ፡ ወይም ፡ ለወንድ ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ለሴት ፡ ልጅ ፡ ወይም ፡ ለወንድም ፡ ወይም ፡ ላልተዳረች ፡ እኅት ፡ ይርከሱ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 26 ፤ ከነጻም ፡ በኋላ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ይቈጠርለት ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 27 ፤ በመቅደስም ፡ ውስጥ ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ በሚገባበት ፡ ቀን ፥ የኀጢአትን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቅርብ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 28 ፤ ርስት ፡ ይኾንላቸዋል ፤ እኔ ፡ ርስታቸው ፡ ነኝ ፤ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፥ ግዛት ፡ አትስጧቸው ፤ እኔ ፡ ግዛታቸው ፡ ነኝ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 29 ፤ የእኽሉን ፡ ቍርባንና ፡ የኀጢአትን ፡ መሥዋዕት ፡ የበደልንም ፡ መሥዋዕት ፡ ይበላሉ ፤ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ዕርም ፡ የኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለእነርሱ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 30 ፤ የበኩራቱ ፡ ኹሉ ፡ መዠመሪያ ፡ ከየዐይነቱ ፡ ከቍርባናችኹም ፡ ኹሉ ፡ የማንሣት ፡ ቍርባን ፡ ኹሉ ፡ ለካህናት ፡ ይኾናል ፤ በቤታችኹም ፡ ውስጥ ፡ በረከት ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፥ የዱቄታችኹን ፡ በኩራት ፡ ለካህናቱ ፡ ትሰጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 44 ፡ 31 ፤ የበከተውንና ፡ የተሰበረውን ፥ ወፍ ፡ ወይም ፡ እንስሳ ፡ ቢኾን ፥ ካህናት ፡ አይብሉት ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 45 ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 1 ፤ ርስትም ፡ አድርጋችኹ ፡ ምድርን ፡ በዕጣ ፡ በምታካፍሉበት ፡ ጊዜ ፡ ከምድር ፡ የተቀደሰውን ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ መባ ፡ አድርጋችኹ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታቀርባላችኹ ። ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፤ በዳርቻው ፡ ኹሉ ፡ ዙሪያውን ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 2 ፤ ከርሱም ፡ ርዝመቱ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ወርዱም ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ የኾነ ፡ ቦታ ፡ ለመቅደሱ ፡ ይኾናል ፤ በዙሪያውም ፡ ባዶ ፡ ስፍራ ፡ የሚኾን ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 3 ፤ ከዚያው ፡ ልክ ፡ ደግሞ ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ ስፍራ ፡ ትለካለኽ ፤ በርሱም ፡ ውስጥ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ የኾነ ፡ መቅደስ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 4 ፤ ከምድርም ፡ የተቀደሰ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ፤ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፥ ለሚቀርቡ ፡ ለመቅደሱ ፡ አገልጋዮች ፡ ለካህናቱ ፡ ይኾናል ፥ ለቤቶቻቸውም ፡ የሚኾን ፡ ስፍራ ፡ ለመቅደስም ፡ የሚኾን ፡ የተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 5 ፤ ርዝመቱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ የኾነ ፡ ስፍራ ፡ ለቤቱ ፡ አገልጋዮች ፡ ለሌዋውያን ፡ ይኾናል ፥ ለሚቀመጡባቸውም ፡ ከተማዎች ፡ ለራሳቸውም ፡ የርስት ፡ ይዞታ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 6 ፤ ለከተማዩቱም ፡ ይዞታ ፡ በተቀደሰው ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ መባ ፡ አጠገብ ፡ ወርዱ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡

ርዝመቱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ የኾነውን ፡ ስፍራ ፡ ታደርጋላችኹ ። ርሱም ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 7 ፤ ለአለቃውም ፡ የኾነ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ በተቀደሰው ፡ መባና ፡ በከተማዪቱ ፡ ይዞታ ፡ አጠገብ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ይኾናል ፤ በተቀደሰው ፡ መባና ፡ በከተማዪቱ ፡ ይዞታ ፡ ፊት ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይኾናል ፤ ርዝመቱም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ነገድ ፡ ዕጣ ፡ ክፍል ፡ ኾኖ ፡ ከምድሩ ፡ ከምዕራቡ ፡ ዳርቻ ፡ ዠምሮ ፡ እስከምሥራቁ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 8 ፤ ይህም ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ይዞታ ፡ ይኾንለታል ፥ አለቃዎቼም ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ምድሪቱን ፡ እንደ ፡ ነገዳቸው ፡ መጠን ፡ ይሰጧቸዋል ፡ እንጂ ፡ ሕዝቤን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያስጨንቋቸውም ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 9 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእስራኤል ፡ አለቃዎች ፡ ሆይ ፥ ይብቃችኹ ፤ ግፍንና ፡ ብዝበዛን ፡ አስወግዱ ፥ ፍርድንና ፡ ጽድቅንም ፡ አድርጉ ፤ ቅሚያችኹን ፡ ከሕዝቤ ፡ ላይ ፡ አርቁ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 10 ፤ እውነተኛ ፡ ሚዛን ፡ እውነተኛም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ እውነተኛውም ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይኹንላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 11 ፤ የኢፍና ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ አንድ ፡ ይኹን ፤ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፥ የኢፍ ፡ መስፈሪያውም ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ ይኹን ። መስፈሪያው ፡ እንደ ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ይኹን ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 12 ፤ ሰቅሉም ፡ ኻያ ፡ አቦሊ ፡ ይኹን ፤ ኻያ ፡ ሰቅል ፥ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፥ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ሰቅል ፥ ምናን ፡ ይኹንላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 13 ፤ የምታቀርቡት ፡ መባ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ካንድ ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ስንዴ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፥ ከአንድም ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ገብስ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡ ትሰጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 14 ፤ የዘይቱም ፡ ደንብ ፥ ከያንዳንዱ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ የባዶስን ፡ ዐሥረኛ ፡ ክፍል ፡ ትሰጣላችኹ ፤ ዐሥር ፡ የባዶስ ፡ መስፈሪያ ፡ አንድ ፡ የቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ነውና ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 15 ፤ ውሃም ፡ ካለበት ፡ ከእስራኤል ፡ ማሰማሪያ ፡ ከመንጋው ፡ ከኹለቱ ፡ መቶ ፡ አንዱን ፡ የበግ ፡ ጠቦት ፡ ትሰጣላችኹ ፤ ይህ ፡ ያስተሰርይላችኹ ፡ ዘንድ ፥ ለእኽል ፡ ቍርባንና ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ለደኅንነትም ፡ መሥዋዕት ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 16 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ መባ ፡ ለእስራኤል ፡ አለቃ ፡ ይሰጣሉ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 17 ፤ በየበዓላቱም ፡ በየመባቻውም ፡ በየሰንበታቱም ፡ በእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ኹሉ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የመጠጡንም ፡ ቍርባን ፡ መስጠት ፡ በአለቃው ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ርሱ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፥ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕትና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቀርባል ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 18 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመዠመሪያው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ ወይፈን ፡ ውሰድ ፡ መቅደሱንም ፡ አንጻ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 19 ፤ ካህኑም ፡ ከኀጢአቱ ፡ መሥዋዕት ፡ ደም ፡ ወስዶ ፡ በመቅደሱ ፡ መቃኖችና ፡ በመሠዊያው ፡ ዕርከን ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ በውስጠኛውም ፡ አደባባይ ፡ በበሩ ፡ መቃኖች ፡ ላይ ፡ ይርጨው ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 20 ፤ ከወሩም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ አድርግ ፥ ይኸውም ፡ ስለሳተውና ፡ ስላላወቀው ፡ ኹሉ ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ ስለ ፡ ቤቱ ፡ አስተስርዩ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 21 ፤ በመዠመሪያ ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የፋሲካን ፡ በዓል ፡ ታደርጋላችኹ ። እስከ ፡ ሰባት ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡ ቂጣ ፡ እንጀራ ፡ ትበላላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 22 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አለቃው ፡ ለራሱና ፡ ለአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ወይፈን ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 23 ፤ በበዓሉም ፡ በሰባቱ ፡ ቀኖች ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቅርብ ፤ ሰባቱን ፡ ቀኖች ፡ በየዕለቱ ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰባት ፡ ወይፈንና ፡ ሰባት ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ያቅርብ ፤ ለኀጢአትም ፡ መሥዋዕት ፡ በየዕለቱ ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 24 ፤ ለአንድም ፡ ወይፈን ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ለአንድም ፡ አውራ ፡ በግ ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ለአንድም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ አንድ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ ለእኽል ፡ ቍርባን ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 45 ፡ 25 ፤ በሰባተኛውም ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛው ፡ ቀን ፡ በበዓሉ ፡ ሰባት ፡ ቀኖች ፥ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቃጠለውንም ፡ መሥዋዕት ፡ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ከዘይቱ ፡ ጋራ ፡ እንዲሁ ፡ ያቅርብ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 46 ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 1 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በውስጠኛው ፡ አደባባይ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚመለከተው ፡ በር ፡ ሥራ ፡ በሚሠራበት ፡ በስድስቱ ፡ ቀን ፡ ተዘግቶ ፡ ይቈይ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰንበት ፡ ቀንና ፡ በመባቻ ፡ ቀን ፡ ይከፈት ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 2 ፤ አለቃውም ፡ በስተውጭ ፡ ባለው ፡ በር ፡ በደጀ ፡ ሰላሙ ፡ መንገድ ፡ ገብቶ ፡ በበሩ ፡ መቃን ፡ አጠገብ ፡ ይቁም ፥ ካህናቱም ፡ የርሱን ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቅርቡ ፥ ርሱም ፡ በበሩ ፡ መድረክ ፡ ላይ ፡ ይስገድ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ይውጣ ፥ በሩ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ አይዘጋ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 3 ፤ የአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ በዚያ ፡ በር ፡ መግቢያ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሰንበታትና ፡ በመባቻ ፡ ይስገዱ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 4 ፤ አለቃውም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበው ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌለባቸው ፡ ስድስት ፡ የበግ ፡ ጠቦቶች ፡ ነውርም ፡ የሌለበት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ይኹን ፤

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 5 ፤ የእኽሉም ፡ ቍርባን ፡ ለአውራ ፡ በጉ ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ይኹን ፥ ለጠቦቶቹም ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ እንደሚቻል ፡ ያኽል ፡ ይኹን ፥ ለአንዱም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ አንድ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 6 ፤ በመባቻም ፡ ቀን ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ አንድ ፡ ወይፈን ፥ ነውር ፡ የሌለባቸውንም ፡ ስድስት ፡ ጠቦቶችና ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ ያቅርብ ፤

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 7 ፤ ለወይፈኑም ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ለአውራውም ፡ በግ ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ለጠቦቶቹም ፡ እንደ ፡ ተቻለው ፡ ያኽል ፥ ለአንዱም ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ አንድ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ ለእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 8 ፤ አለቃውም ፡ በሚገባበት ፡ ጊዜ ፡ በበሩ ፡ ደጀ ፡ ሰላም ፡ መንገድ ፡ ይግባ ፡ በዚያውም ፡ ይውጣ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 9 ፤ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ በየክብረ ፡ በዓሉ ፡ ቀን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በሰሜን ፡ በር ፡ በኩል ፡ ሊሰግድ ፡ የሚገባው ፡ በደቡብ ፡ በር ፡ በኩል ፡ ይውጣ ፥ በደቡብም ፡ በር ፡ የሚገባው ፡ በሰሜን ፡ በር ፡ በኩል ፡ ይውጣ ፤ በፊት ፡ ለፊት ፡ ይውጣ ፡ እንጂ ፡ በገባበቱ ፡ በር ፡ አይመለስ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 10 ፤ በሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡ አለቃው ፡ በመካከላቸው ፡ ይግባ ፡ በሚወጡበትም ፡ ጊዜ ፡ ይውጣ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 11 ፤ በበዓላትና ፡ በክብረ ፡ በዓል ፡ ቀኖች ፡ የእኽሉ ፡ ቍርባን ፡ ለወይፈኑ ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፥ ለአውራ ፡ በጉ ፡ አንድ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፥ ለጠቦቶቹም ፡ እንደሚቻለው ፡ ያኽል ፥ ለኢፍ ፡ መስፈሪያም ፡ አንድ ፡ የኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ዘይት ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 12 ፤ አለቃውም ፡ በፈቃዱ ፡ የሚያቀርበውን ፡ መሥዋዕት ፥ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕት ፥ ወይም ፡ በፈቃዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚያቀርበውን ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፥ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ የሚመለከተው ፡ በር ፡ ይከፈትለት ፥ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ እንደሚያደርግ ፡ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የደኅንነቱን ፡ መሥዋዕት ፡ ያቅርብ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ይውጣ ፥ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ በሩ ፡ ይዘጋ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 13 ፤ በየዕለቱም ፡ ለሚቃጠል ፡ መሥዋዕት ፡ ነውር ፡ የሌለበትን ፡ የአንድ ፡ ዓመት ፡ በግ ፡ ጠቦት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቅርብ ፤ በየማለዳው ፡ ያቅርበው ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 14 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የእኽልን ፡ ቍርባን ፥ በኢን ፡ መስፈሪያ ፡ ሚሶ ፡ ዘይት ፡ የተለወሰ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ስድስተኛ ፡ እጅ ፡ መልካም ፡ ዱቄትን ፥ በየማለዳው ፡ ያቅርብ ፤ ይህ ፡ በዘለዓለሙ ፡ ሥርዐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የዘወትር ፡ የእኽል ፡ ቍርባን ፡ ይኹን ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 15 ፤ እንዲሁ ፡ ዘወትር ፡ ለሚቃጠለው ፡ መሥዋዕት ፡ ጠቦቱንና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባን ፡ ዘይቱንም ፡ በየማለዳው ፡ ያቅርብ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ አለቃው ፡ ከልጆቹ ፡ ለአንዱ ፡ ከርስቱ ፡ ስጦታ ፡ ቢሰጥ ፡ ለልጆቹ ፡ ይኹን ፤ የርስት ፡ ይዞታ ፡ ይኾንላቸዋል ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከባሪያዎቹ ፡ ለአንዱ ፡ ከርስቱ ፡ ስጦታ ፡ ቢሰጥ ፥ እስከ ፡ ነጻነት ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ለርሱ ፡ ይኹን ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለአለቃው ፡ ይመለስ ፤ ርስቱ ፡ ግን ፡ ለልጆቹ ፡ ይኹን ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 18 ፤ አለቃውም ፡ ሕዝቡን ፡ ከይዞታቸው ፡ ያወጣቸው ፡ ዘንድ ፥ ከርስታቸው ፡ በግድ ፡ አይውሰድ ፤ ሕዝቤ ፡ ኹሉ ፡ ከይዞታቸው ፡ እንዳይነቀሉ ፡ ከገዛ ፡ ይዞታው ፡ ለልጆች ፡ ርስትን ፡ ይስጥ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 19 ፤ በበሩም ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ መግቢያ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ወደሚመለከተው ፡ ለካህናት ፡ ወደሚኾን ፡ ወደተቀደሰው ፡ ዕቃ ፡ ቤት ፡ አገባኝ ፤ እንሆም ፥ በኋላው ፡ በምዕራብ ፡ በኩል ፡ አንድ ፡ ስፍራ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ ካህናቱ ፡ ሕዝቡን ፡ ለመቀደስ ፡ ወደ ፡ ውጭው ፡ አደባባይ ፡ እንዳያወጡ ፡ የበደሉን ፡ መሥዋዕትና ፡ የኀጢአቱን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀቅሉበት ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ የሚጋግሩበት ፡ ስፍራ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለኝ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 21 ፤ በውጭው ፡ አደባባይ ፡ አወጣኝ ፡ በአደባባይም ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ አራቱ ፡ ማእዘን ፡ አዞረኝ ፤ እንሆም ፥ በአደባባዩ ፡ ማእዘን ፡ ኹሉ ፡ አደባባይ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 22 ፤ በአደባባዩ ፡ በአራቱ ፡ ማእዘን ፡ ርዝመቱ ፡ አርባ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ሠላሳ ፡ ክንድ ፡ የኾነ ፡ የታጠረ ፡ አደባባይ ፡ ነበረ ፤ በማእዘኑ ፡ ላሉ ፡ ለእነዚህ ፡ ለአራቱ ፡ ስፍራዎች ፡ አንድ ፡ ልክ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 23 ፤ በአራቱም ፡ ዙሪያ ፡ ኹሉ ፡ ግንብ ፡ ነበረ ፥ በግንቡም ፡ ሥር ፡ በዙሪያው ፡ የመቀቀያ ፡ ቦታ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፡ 46 ፡ 24 ፤ ርሱም ፦ እነዚህ ፡ የቤቱ ፡ አገልጋዮች ፡ የሕዝቡን ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀቅሉባቸው ፡ ስፍራዎች ፡ ናቸው ፡ አለኝ ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 47 ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 1 ፤ ወደመቅደሱም ፡ መዝጊያ ፡ መለሰኝ ፤ እንሆም ፥ ውሃ ፡ ከቤቱ ፡ መድረክ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፥ የቤቱ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ይመለከት ፡ ነበርና ፤ ውሃውም ፡ ከቤቱ ፡ ከቀኝ ፡ ወገን ፡ በታች ፡ በመሠዊያው ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ይወርድ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 2 ፤ በሰሜኑም ፡ በር ፡ በኩል ፡ አወጣኝ ፤ በስተውጭ ፡ ባለው ፡ መንገድ ፥ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወደሚመለከት ፡ በስተውጭ ፡ ወዳለው ፡ በር ፡ አዞረኝ ፤ እንሆም ፥ ውሃው ፡ በቀኙ ፡ ወገን ፡ ይፈስ ፡ ነበር ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 3 ፤ ሰውዬውም ፡ ገመዱን ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ወጣ ፡ አንድ ፡ ሺሕም ፡ ክንድ ፡ ለካ ፥ በውሃውም ፡ ውስጥ ፡ አሻገረኝ ፥ ውሃም ፡ እስከ ፡ ቀዣርጭምጭሚት ፡ ደረሰ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 4 ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ለካ ፡ በውሃውም ፡ ውስጥ ፡ አሻገረኝ ፥ ውሃውም ፡ እስከ ፡ ጕልበት ፡ ደረሰ ። ደግሞም ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ለካ ፡ በውሃውም ፡ ውስጥ ፡ አሻገረኝ ፥ ውሃውም ፡ እስከ ፡ ወገብ ፡ ደረሰ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 5 ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሺሕ ፡ ለካ ፡ ልሻገረውም ፡ የማልችለው ፡ ወንዝ ፡ ኾነ ፤ ውሃውም ፡ ጥልቅ ፡ ነበረ ፥ የሚዋኝበትም ፡ ውሃ ፡ ነበረ ፤ ሰው ፡ ሊሻገረው ፡ የማይችለው ፡ ወንዝ ፡ ነበረ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 6 ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ አይተኻልን ፧ አለኝ ። አመጣኝም ፥ ወደወንዙም ፡ ዳር ፡ መለሰኝ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 7 ፤ በተመለስኹም ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ በወንዙ ፡ ዳር ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ዛፎች ፡ ነበሩ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 8 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ይህ ፡ ውሃ ፡ ወደምሥራቅ ፡ ምድር ፡ ይወጣል ፡ ወደ ፡ ዐረባም ፡ ይወርዳል ፡ ወደ ፡ ባሕሩም ፡ ይገባል ፤ ወደ ፡ ባሕሩም ፡ ወደረከሰው ፡ ውሃ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ውሃው ፡ ይፈወሳል ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 9 ፤ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ያለው ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ኹሉ ፡ ወንዙ ፡ በመጣበት ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ፤ ይህም ፡ ውሃ ፡ በዚያ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ዓሣዎች ፡ እጅግ ፡ ይበዛሉ ፤ የባሕሩም ፡ ውሃ ፡ ይፈወሳል ፥ ወንዙም ፡ በሚመጣበት ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 10 ፤ አጥማጆችም ፡ በዚያ ፡ ይቆማሉ ፤ ከዐይንጋዲ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዐይንኤግላይም ፡ ድረስ ፡ መረብ ፡ መዘርጊያ ፡ ይኾናል ፤ ዓሣዎችም ፡ እንደ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዓሣዎች ፡ በየወገናቸው ፡ እጅግ ፡ ይበዛሉ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 11 ፤ ረግረጉና ፡ ዕቋሪው ፡ ውሃ ፡ ግን ፡ ጨው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ አይፈወስም ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 12 ፤ በወንዙም ፡ አጠገብ ፡ በዳሩ ፡ ላይ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ፍሬው ፡ የሚበላ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይበቅላል ፥ ቅጠሉም ፡ አይረግፍም ፡ ፍሬውም ፡ አይጐድልም ፤ ውሃውም ፡ ከመቅደስ ፡ ይወጣልና ፥ በየወሩ ፡ ኹሉ ፡ የፍሬ ፡ በኵር ፡ ያገኛል ፤ ፍሬውም ፡ ለመብል ፡ ቅጠሉም ፡ ለመድኀኒት ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 13 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ርስት ፡ አድርጋችኹ ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ምድሪቱን ፡ የምትከፍሉበት ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ። ለዮሴፍ ፡ ኹለት ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 14 ፤ ለአባቶቻችኹ ፡ እሰጣቸው ፡ ዘንድ ፥ ምዬ ፡ ነበርና ፥ እናንተ ፡ እኩል ፡ አድርጋችኹ ፡ ተካፈሉት ፡ ይህችም ፡ ምድር ፡ ርስት ፡ ትኾናችኋለች ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 15 ፤ የምድሪቱም ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ። በሰሜኑ ፡ ወገን ፡ ከታላቁ ፡ ባሕር ፡ ዠምሮ ፡ በሔትሎን ፡ መንገድ ፡ ወደጽዳድ ፡ መግቢያ ፤

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 16 ፤ ሐማት ፥ ቤሮታ ፥ በደማስቆ ፡ ድንበርና ፡ በሐማት ፡ ድንበር ፡ መካከል ፡ ያለው ፡

ሲብራይም ፥ በሐውራን ፡ ድንበር ፡ አጠገብ ፡ ያለው ፡ ሐጸርሃቲኮን ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 17 ፤ ድንበሩ ፡ ከባሕሩ ፡ በደማስቆ ፡ ድንበር ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ ሐጻረ ፡ ዔኖን ፡ ይኾናል ፥ በሰሜንም ፡ በኩል ፡ የሐማት ፡ ድንበር ፡ አለ ። የሰሜኑ ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 18 ፤ የምሥራቁም ፡ ድንበር ፡ በሐውራን ፡ በደማስቆና ፡ በገለዓድ ፡ በእስራኤልም ፡ ምድር ፡ መካከል ፡ ዮርዳኖስ ፡ ይኾናል ። ከሰሜኑ ፡ ድንበር ፡ ዠምሮ ፡ እስከምሥራቁ ፡ ባሕር ፡ እስከ ፡ ታማር ፡ ድረስ ፡ የምሥራቁ ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 19 ፤ የደቡቡም ፡ ድንበር ፡ ከታማር ፡ ዠምሮ ፡ እስከሜርባ ፡ ቃዴስ ፡ ውሃ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ። የደቡቡ ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 20 ፤ የምዕራቡም ፡ ድንበር ፡ ከደቡቡ ፡ ድንበር ፡ ዠምሮ ፡ እስከሐማት ፡ መግቢያ ፡ አንጻር ፡ ድረስ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ይኾናል ። የምዕራቡ ፡ ድንበር ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 21 ፤ እንዲሁ ፡ ይህችን ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነገዶች ፡ መጠን ፡ ለእናንተ ፡ ትካፈላላችኹ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 22 ፤ ለእናንተና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ለሚቀመጡ ፡ በእናንተም ፡ መካከል ፡ ልጆችን ፡ ለሚወልዱ ፡ መጻተኞች ፡ ርስት ፡ አድርጋችኹ ፡ በዕጣ ፡ ትካፈሏታላችኹ ፤ እነርሱም ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እንዳሉ ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ ይኾኑላችኋል ፥ በእስራኤልም ፡ ነገዶች ፡ መካከል ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ርስትን ፡ ይወርሳሉ ።

ሕዝ. ፥ 47 ፥ 23 ፤ መጻተኛውም ፡ በማናቸውም ፡ ነገድ ፡ መካከል ፡ ቢቀመጥ ፡ በዚያ ፡ ርስቱን ፡ ትሰጡታላችኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 48 ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 1 ፤ የነገዶችም ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ። በሔትሎን ፡ መንገድ ፡ አጠገብ ፡ ወደሐማት ፡ መግቢያ ፡ በደማስቆም ፡ ድንበር ፡ ባለው ፡ በሐጻረ ፡ ዔኖን ፥ በሐማትም ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ካለው ፡ ከሰሜን ፡ ድንበር ፡ ይዠምራል ። ወርዳቸውም ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ። ለዳን ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 2 ፤ ከዳንም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለአሴር ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 3 ፤ ከአሴርም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለንፍታሌም ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 4 ፤ ከንፍታሌም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለምናሴ ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 5 ፤ ከምናሴም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለኤፍሬም ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 6 ፤ ከኤፍሬምም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለሮቤል ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፥ 48 ፥ 7 ፤ ከሮቤልም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለይሁዳ ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 8 ፤ ከይሁዳም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለመባ ፡ የኾነ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ፤ ወርዱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፡ ርዝመቱም ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ከዕጣ ፡ ክፍሎች ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ይኾናል ፥ መቅደሱም ፡ በመካከሉ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 9 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የምታቀርቡት ፡ መባ ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 10 ፤ ለእነዚህም ፡ ለካህናቱ ፡ የተቀደሰ ፡ መባ ፡ ይኾናል ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ወርዱ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ወርዱ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፥ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ። የእግዚአብሔርም ፡ መቅደስ ፡ በመካከሉ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 11 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ በሳቱ ፡ ጊዜ ፥ ሌዋውያን ፡ እንደ ፡ ሳቱ ፡ ላልሳቱት ፡ ሥርዐቴን ፡ ለጠበቁት ፡ ከሳዶቅ ፡ ልጆች ፡ ወገን ፡ ለተቀደሱት ፡ ካህናት ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 12 ፤ ከምድርም ፡ መባ ፡ የተለየ ፡ መባ ፡ ይኾንላቸዋል ፥ ከሹሉም ፡ ይልቅ ፡ የተቀደሰ ፡ ይኾናል ፤ በሌዋውያን ፡ ድንበር ፡ አጠገብ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 13 ፤ በካህናቱም ፡ ድንበር ፡ አንጻር ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ የኾነ ፡ ዕጣ ፡ ለሌዋውያን ፡ ይኾናል ፤ ርዝመቱ ፡ ሹሉ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 14 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ፥ ከርሱ ፡ ምንም ፡ አይሸጡም ፡ አይለውጡምም ፥ የምድሩም ፡ በኩራት ፡ አይፋለስም ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 15 ፤ በኻያ ፡ ዐምስቱም ፡ ሺሕ ፡ አንጻር ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርድ ፡ ያለው ፡ የቀረ ፡ ስፍራ ፡ ለከተማዪቱ ፡ ለጋራ ፡ ጕዳይዋ ፥ ለመኖሪያ ፡ ለማስማርያም ፡ ይኾናል ፤ ከተማዪቱም ፡ በመካከሉ ፡ ትኾናለች ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 16 ፤ ልኳም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፥ በደቡብም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 17 ፤ ለከተማዪቱም ፡ ማሰማሪያ ፡ ይኖራታል ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፥ በደቡብም ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፥ በምሥራቅም ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 18 ፤ በተቀደሰው ፡ መባ ፡ አንጻር ፡ የተረፈው ፡ ርዝመቱ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ወደ ፡ ምዕራብም ፡ ዐሥር ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ። በተቀደሰው ፡ መባ ፡ አንጻር ፡ ይኾናል ። ፍሬውም ፡ ከተማዪቱን ፡ ለሚያገለግሉ ፡ ለመብል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 19 ፤ ከእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ሹሉ ፡ ከተማዪቱን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ያርሱታል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 20 ፤ መባው ፡ ሹሉ ፡ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወርዱም ፡ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፤ የተቀደሰውን ፡ መባ ፡ ከከተማዪቱ ፡ ይዞታ ፡ ጋራ ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ አድርጋችኹ ፡ ትሰጣላችኹ ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 21 ፤ በተቀደሰው ፡ መባና ፡ በከተማዪቱ ፡ ይዞታ ፡ በዚህና ፡ በዚያ ፡ ወገን ፡ የቀረው ፡ ለአለቃው ፡ ይኾናል ፤ በመባው ፡ በኻያ ፡ ዐምስቱ ፡ ሺሕ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምሥራቁ ፡ ድንበር ፥ በምዕራብም ፡ በኩል ፡ በኻያ ፡ ዐምስቱ ፡ ሺሕ ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ምዕራቡ ፡ ድንበር ፥ እንደ ፡ ዕጣ ፡ ክፍል ፡ ሹሉ ፡ መጠን ፥ ለአለቃው ፡ ይኾናል ፤ የተቀደሰውም ፡ መባና ፡ ቤተ ፡ መቅደሱ ፡ በመካከሉ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 22 ፤ የሌዋውያንም ፡ ርስት ፡ የከተማዪቱም ፡ ይዞታ ፡ ለአለቃው ፡ በኾነው ፡ መካከል ፡

ይኾናል ፤ በይሁዳ ፡ ድንበርና ፡ በብንያም ፡ ድንበር ፡ መካከል ፡ የአለቃ ፡ ዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 23 ፤ ለቀሩትም ፡ ነገዶች ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለብንያም ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 24 ፤ ከብንያምም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለስምዖን ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 25 ፤ ከስምዖንም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለይሳኮር ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 26 ፤ ከይሳኮርም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለዛብሎን ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 27 ፤ ከዛብሎንም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ ከምሥራቅ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ ድረስ ፡ ለጋድ ፡ አንድ ፡ የዕጣ ፡ ክፍል ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 28 ፤ ከጋድም ፡ ድንበር ፡ ቀጥሎ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ድንበሩ ፡ ከታማር ፡ ዠምሮ ፡ እስከሜሪባ ፡ ቃዴስ ፡ ውሃ ፡ እስከግብጽ ፡ ወንዝ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይኾናል ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 29 ፤ ርስት ፡ አድርጋችኹ ፡ ለእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ በዕጣ ፡ የምታካፍሏት ፡ ምድር ፡ ይህች ፡ ናት ፥ የያንዳንዱም ፡ ዕጣ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 30 ፤ የከተማዪቱም ፡ መውጫዎች ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። በሰሜን ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 31 ፤ የከተማዪቱ ፡ በሮች ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ስም ፡ ይኾናሉ ፤ በሰሜን ፡ በኩል ፡ አንዱ ፡ የሮቤል ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የይሁዳ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የሌዊ ፡ በር ፥ ሦስት ፡ በሮች ፡ ይኾናሉ ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 32 ፤ በምሥራቁም ፡ ወገን ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፤ አንዱ ፡ የዮሴፍ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የብንያም ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የዳን ፡ በር ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 33 ፤ በደቡቡም ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፤ አንዱ ፡ የስምዖን ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የይሳኮር ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የዛብሎን ፡ በር ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 34 ፤ በምዕራቡም ፡ ወገን ፡ ልኩ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፥ ሦስትም ፡ በሮች ፡ አሉ ፤ አንዱ ፡ የጋድ ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የአሴር ፡ በር ፡ አንዱም ፡ የንፍታሌም ፡ በር ፡ ነው ።

ሕዝ. ፡ 48 ፡ 35 ፤ ዙሪያዋም ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሺሕ ፡ ክንድ ፡ ይኾናል ፥ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ የከተማዪቱ ፡ ስም ፦ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ አለ ፡ ተብሎ ፡ ይጠራል ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዳን. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄም ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ የባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ከበባት ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ጌታም ፡ የይሁዳን ፡ ንጉሥ ፡ ኢዮአቄምን ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ዕቃ ፡ ከፍሎ ፡ በእጁ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፤ ርሱም ፡ ወደሰናዖር ፡ ምድር ፡ ወደአምላኩ ፡ ቤት ፡ ወሰደው ፥ ዕቃውንም ፡ ወደአምላኩ ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ አገባው ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 3-4 ፤ ንጉሡም ፡ ነውር ፡ የሌለባቸውንና ፡ መልከ ፡ መልካሞቹን ፥ በጥበብ ፡ ሹሉ ፡ የሚያስተውሉትን ፡ ዕውቀትም ፡ የሞላባቸውን ፡ ብልኀተኞችና ፡ አስተዋዮች ፡ የኾኑትን ፥ በንጉሡም ፡ ቤት ፡ መቆም ፡ የሚችሉትን ፡ ብላቴናዎች ፡ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ከነገሥታቱና ፡ ከመሳፍንቱ ፡ ዘር ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፥ የከለዳውያንንም ፡ ትምህርትና ፡ ቋንቋ ፡ ያስተምሯቸው ፡ ዘንድ ፥ ለጃን ፡ ደረባዎች ፡ አለቃ ፡ ለአስፋኔዝ ፡ ነገረ ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ንጉሡም ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ያሳድጓቸው ፡ ዘንድ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ይቆሙ ፡ ዘንድ ፥ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከሚጠጣውም ፡ ጠጅ ፡ በየዕለቱ ፡ ድርጓቸውን ፡ አዘዘላቸው ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በእነዚህም ፡ መካከል ፡ ከይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ዳንኤልና ፡ ዐናንያ ([269]) ፡ ሚሳኤልና ([270]) ፡ ዐዛርያ ([271]) ፡ ነበሩ ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የጃን ፡ ደረባዎቹም ፡ አለቃ ፡ ስም ፡ አወጣላቸው ፤ ዳንኤልን ፡ ብልጣሶር ([272]) ፥ ዐናንያንም ፡ ሲድራቅ ([273]) ፥ ሚሳኤልንም ፡ ሚሳቅ ፥ ዐዛርያንም ፡ ዐብደናጎ ፡ ብሎ ፡ ጠራቸው ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ መብልና ፡ በሚጠጣው ፡ ጠጅ ፡ እንዳይረክስ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ፤ እንዳይረክስም ፡ የጃን ፡ ደረባዎቹን ፡ አለቃ ፡ ለመነ ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጃን ፡ ደረባዎቹ ፡ አለቃ ፡ ፊት ፡ ለዳንኤል ፡ ሞገስንና ፡ ምሕረትን ፡ ሰጠው ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 10 ፤ የጃን ፡ ደረባዎቹም ፡ አለቃ ፡ ዳንኤልን ፦ መብሉንና ፡ መጠጡን ፡ ያዘዘላችኹን ፡ ጌታዬን ፡ ንጉሡን ፡ እፈራለኹ ፤ በዕድሜ ፡ እንደናንተ ፡ ካሉ ፡ ብላቴናዎች ፡ ይልቅ ፡ ፊታችኹ ፡ ከስቶ ፡ ያየ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ከንጉሡ ፡ ዘንድ ፡ በራሴ ፡ ታስፈርዱብኛላችኹ ፡ አለው ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ዳንኤልም ፡ የጃንደርባዎቹ ፡ አለቃ ፡ በዳንኤልና ፡ በዐናንያ ፡ በሚሳኤልና ፡ በዐዛርያ ፡ ላይ ፡ የሾመውን ፡ ሜልዳርን ።

ዳን. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እኛን ፡ ባሪያዎችኽን ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ትፈትነን ፡ ዘንድ ፥ እለምንኻለኹ ፤ የምንበላውንም ፡ ጥራጥሬ ፡ የምንጠጣውንም ፡ ውሃ ፡ ይስጡን ፤

ዳን. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእኛን ፡ ፊትና ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ የሚበሉትን ፡ የብላቴናዎችን ፡ ፊት ፡ ተመልከት ፤ እንዳየኸውም ፡ ሹሉ ፡ ከባሪያዎችኽ ፡ ጋራ ፡ የወደድኸውን ፡ አድርግ ፡ አለው ።

---

269 ዕብ. ፥ ሐናንያህ ፡ (ምሕረት ፡ እግዚአብሔር) ።
270 ዕብ. ፥ ሚሻኤል ፡ (ማን ፡ እግዚአብሔር) ።
271 ዕብ. ፥ ዐዛርያ ፡ (እግዚአብሔር ፡ የሚረዳው) ።
272 ዕብ. ፥ ብልጥሻጾር ።
273 ዕብ. ፥ ሻድራክ ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 14 ፤ ይህንም ፡ ነገራቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ዐሥር ፡ ቀን ፡ ፈተናቸው ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ከዐሥር ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ከንጉሡ ፡ መብል ፡ ከበሉ ፡ ብላቴናዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ፊታቸው ፡ አምሮ ፡ ሥጋቸውም ፡ ወፍሮ ፡ ታየ ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ሜልዳርም ፡ መብላቸውንና ፡ የሚጠጡትን ፡ ጠጅ ፡ አስቀርቶ ፡ ጥራጥሬውን ፡ ሰጣቸው ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ለእነዚህም ፡ ለአራቱ ፡ ብላቴናዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ኹሉ ፡ ዕውቀትንና ፡ ማስተዋልን ፡ ሰጣቸው ፤ ዳንኤልም ፡ በራእይና ፡ በሕልም ፡ ኹሉ ፡ አስተዋይ ፡ ነበረ ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡ ፡ ያዘዘው ፡ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ የጃን ፡ ደረባዎቹ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ዘንድ ፡ አገባቸው ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ንጉሡም ፡ በተነጋገራቸው ፡ ጊዜ ፡ ከብላቴናዎቹ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ዳንኤልና ፡ እንደ ፡ ዐናንያ ፡ እንደ ፡ ሚሳኤልና ፡ እንደ ፡ ዐዛርያ ፡ ያለ ፡ አልተገኘም ፤ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ንጉሡም ፡ በጠየቃቸው ፡ በጥበብና ፡ በማስተዋል ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በግዛቱ ፡ ኹሉ ፡ ከሚኖሩ ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ አስማተኞች ፡ ኹሉ ፡ እነርሱ ፡ ዐሥር ፡ እጅ ፡ የበለጡ ፡ ኾነው ፡ አገኘባቸው ።

ዳን. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ዳንኤልም ፡ እስከንጉሡ ፡ እስከቂሮስ ፡ መዠመሪያ ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በነገሠ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ናቡከደነጾር ፡ ሕልም ፡ ዐለመ ፤ መንፈሱም ፡ ታወከ ፥ እንቅልፉም ፡ ከርሶ ፡ ራቀ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ለንጉሡም ፡ ሕልሙን ፡ እንዲነግሩት ፡ ንጉሡ ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹንና ፡ አስማተኞቹን ፡ መተተኞቹንና ፡ ከለዳውያኑንም ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፥ አዘዘ ፤ እነርሱም ፡ ገብተው ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ንጉሡም ፦ ሕልም ፡ ዐልሜያለኹ ፥ ሕልሙንም ፡ ለማወቅ ፡ መንፈሴ ፡ ታውኳል ፡ አላቸው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ከለዳውያኑም ፡ ንጉሡን ፡ በሶርያ ፡ ቋንቋ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ ለባሪያዎችኽ ፡ ሕልምኽን ፡ ንገር ፥ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳይኻለን ፡ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ከለዳውያኑንም ፦ ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ፤ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ ባታስታውቁኝ ፥ ትቈረጣላችኹ ፡ ቤቶቻችኹም ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረጋሉ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ ግን ፡ ብታሳዩ ፥ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ ስጦታና ፡ ዋጋ ፡ ብዙ ፡ ክብርም ፡ ትቀበላላችኹ ፤ ስለዚህም ፡ ሕልሙንና ፡ ፍቺውን ፡ አሳዩኝ ፡ አላቸው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ኹለተኛም ፡ ጊዜ ፡ መልሰው ፦ ንጉሡ ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ሕልሙን ፡ ይንገር ፥ እኛም ፡ ፍቺውን ፡ እናሳያለን ፡ አሉት ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ንጉሡ ፡ መልሶ ፦ ነገሩ ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ራቀ ፡ ታውቃላችኹና ፡ ጊዜውን ፡ እንድታስረዝሙ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ሕልሙንም ፡ ባታስታውቁኝ ፡ አንድ ፡ ፍርድ ፡ አለባችኹ ፤ ጊዜውን ፡ ለማሳለፍ ፡ የሐሰትንና ፡ የተንኰልን ፡ ቃል ፡ ልትነግሩኝ ፡ አዘጋጅታችኋል ፤ ስለዚህ ፥ ሕልሙን ፡ ንገሩኝ ፥ ፍቺውንም ፡ ማሳየት ፡ እንድትችሉ ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ከለዳውያኑም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሰው ፦ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የለም ፤ ከነገሥታትም ፡ ታላቅና ፡ ኀይለኛ ፡ የኾነ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚንና ፡ አስማተኛን ፡ ከለዳዊንም ፡ አልጠየቀም ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ የሚጠይቀው ፡ ነገር ፡ የቸገረ ፡ ነው ፤ መኖሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ጋራ ፡ ካልኾነ ፡ ከአማልክት ፡ በቀር ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ የሚያሳየው ፡ ማንም ፡ የለም ፡ አሉ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ስለዚህም ፡ ንጉሡ ፡ ተበሳጨ ፡ እጅግም ፡ ተቈጣ ፥ የባቢሎንንም ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ትእዛዝም ፡ ወጣ ፥ ጠቢባንንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ዠመሩ ፤ ዳንኤልንና ፡ ባልንጀራዎቹንም ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጓቸው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ የወጣውን ፡ የንጉሡን ፡ የዘበኞቹ ፡ አለቃ ፡ አርዮክን ፡ በፈሊጥና ፡ በማስተዋል ፡ ተናገረው ፤

ዳን. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ለንጉሡም ፡ አለቃ ፡ ለአርዮክ ፡ መልሶ ፦ የንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቸኰለ ፧ አለው ። አርዮክም ፡ ነገሩን ፡ ለዳንኤል ፡ አስታወቀው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ዳንኤልም ፡ ገብቶ ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ የሚያስታውቅበት ፡ ጊዜ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡን ፡ ለመነ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 17 ፤ 18 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ። ዳንኤልም ፡ ባልንጀራዎቹም ፡ ከቀሩት ፡ ከባቢሎን ፡ ጠቢባን ፡ ጋራ ፡ እንዳይሞቱ ፡ ስለዚህ ፡ ምስጢር ፡ ምሕረትን ፡ ከሰማይ ፡ አምላክ ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፥ ነገሩን ፡ ለባልንጀራዎቹ ፡ ለዐናንያና ፡ ለሚሳኤል ፡ ለዐዛርያ ፡ አስታወቃቸው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ምስጢሩ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ ለዳንኤል ፡ ተገለጠለት ፤ ዳንኤልም ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ አመሰገነ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ዳንኤልም ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ጥበብና ፡ ኀይል ፡ ለርሱ ፡ ነውና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይባረክ ፤

ዳን. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ጊዜያትንና ፡ ዘመናትን ፡ ይለውጣል ፤ ነገሥታትን ፡ ያፈልሳል ፥ ነገሥታትንም ፡ ያስነሣል ፤ ጥበብን ፡ ለጠቢባን ፡ ዕውቀትንም ፡ ለአስተዋዮች ፡ ይሰጣል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 22 ፤ የጠለቀውንና ፡ የተሰወረውን ፡ ይገልጣል ፤ በጨለማ ፡ ያለውን ፡ ያውቃል ፥ ብርሃንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ጥበብንና ፡ ኀይልን ፡ የሰጠኸኝ ፥ እኛም ፡ የለመንኸን ፡ ነገር ፡ አኹን ፡ ያስታወቅኸኝ ፥ አንተ ፡ የአባቶቼ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ የንጉሡን ፡ ነገር ፡ አስታውቀኸኛልና ፥ እገዛልኻለኹ ፡ አመሰግንኻማለኹ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዳንኤል ፡ ንጉሡ ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ወዳዘዘው ፥ ወደ ፡ አርዮክ ፡ ገባ ፤ በገባም ፡ ጊዜ ፦ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፡ አታጥፋ ፤ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገባኝ ፥ እኔም ፡ ፍቺውን ፡ ለንጉሡ ፡ አሳያለኹ ፡ አለው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 25 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አርዮክ ፡ ዳንኤልን ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ አስገባውና ፦ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ ያለውን ፡ ለንጉሡ ፡ ፍቺውን ፡ የሚያስታውቀውን ፡ ሰው ፡ አግኝቻለኹ ፡ አለው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ንጉሡም ፡ መለሰ ፡ ብልጣሶርም ፡ የሚባለውን ፡ ዳንኤልን ፦ ያየኹትን ፡ ሕልምና ፡ ፍቺውን ፡

ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ትችላለኽን ፧ አለው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 27 ፤ ዳንኤልም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ንጉሡ ፡ የጠየቀውን ፡ ምስጢር ፡ ጠቢባንና ፡ አስማተኞች ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ ቃላተኞች ፡ ለንጉሡ ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ፤

ዳን. ፡ 2 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምስጢር ፡ የሚገልጥ ፡ አምላክ ፡ በሰማይ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፥ ርሱም ፡ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ የሚኾነውን ፡ ለንጉሡ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ አስታውቆታል ። በዐልጋኽ ፡ ላይ ፡ የኾነው ፡ ሕልምና ፡ የራስኽ ፡ ራእይ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 29 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በኋላ ፡ የሚኾነው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በዐልጋኽ ፡ ላይ ፡ ታስብ ፡ ነበር ፤ ምስጢርንም ፡ የሚገልጠው ፡ የሚኾነውን ፡ ነገር ፡ አስታውቆኻል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ምስጢር ፡ ለእኔ ፡ መገለጡ ፡ ፍቼው ፡ ለንጉሡ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፥ አንተም ፡ የልብኽን ፡ ዐሳብ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ካሉ ፡ ሰዎች ፡ ይልቅ ፡ በጥበብ ፡ ስለ ፡ በለጥኹ ፡ አይደለም ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 31 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ታላቅ ፡ ምስል ፡ አየኽ ፤ ይህም ፡ ምስል ፡ ታላቅና ፡ ብልጭልጭታው ፡ የበዛ ፡ ነበረ ፥ በፊትኽም ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ መልኩም ፡ ግሩም ፡ ነበረ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 32 ፤ የዚህም ፡ ምስል ፡ ራስ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፥ ደረቱና ፡ ክንዶቹም ፡ ብር ፥ ሆዱና ፡ ወገቡም ፡ ናስ ፥

ዳን. ፡ 2 ፡ 33 ፤ ጭኖቹም ፡ ብረት ፥ እግሮቹም ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ ነበረ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 34 ፤ እጅም ፡ ሳይነካው ፡ ድንጋይ ፡ ከተራራው ፡ ተፈንቅሎ ፡ ከብረትና ፡ ከሸክላ ፡ የኾነውን ፡ የምስሉን ፡ እግሮች ፡ ሲመታና ፡ ሲፈጭ ፡ አየኽ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 35 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብረቱና ፡ ሸክላው ፥ ናሱና ፡ ብሩ ፡ ወርቁም ፡ በአንድነት ፡ ተፈጨ ፥ በመከርም ፡ ጊዜ ፡ በዐውድማ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ እብቅ ፡ ኾነ ፤ ነፋስም ፡ ወሰደው ፥ ቦታውም ፡ አልታወቀም ፤ ምስሉንም ፡ የመታ ፡ ድንጋይ ፡ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ኾነ ፡ ምድርንም ፡ ፈጽሞ ፡ ሞላ ፡

ዳን. ፡ 2 ፡ 36 ፤ ሕልሙ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አኹንም ፡ ፍቼውን ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ እንናገራለን ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 37 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ መንግሥትንና ፡ ኀይልን ፥ ብርታትንና ፡ ክብርን ፡ የሰጠኽ ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነኽ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 38 ፤ በሚቀመጡበትም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ የሰው ፡ ልጆችንና ፡ የምድር ፡ አራዊትን ፡ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ በእጅኽ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቶኻል ፥ ለኹሉም ፡ ገዢ ፡ አድርጎኻል ፤ አንተ ፡ የወርቁ ፡ ራስ ፡ ነኽ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 39 ፤ ከአንተም ፡ በኋላ ፡ ከአንተ ፡ የሚያንስ ፡ ሌላ ፡ መንግሥት ፡ ይነሣል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ፡ ሌላ ፡ ሦስተኛ ፡ የናስ ፡ መንግሥት ፡ ይነሣል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 40 ፤ አራተኛውም ፡ መንግሥት ፡ ኹሉን ፡ እንደሚቀጠቅጥና ፡ እንደሚያደቅ ፡ ብረት ፡ ይበረታል ፤ እነዚህንም ፡ ኹሉ ፡ እንደሚፈጭ ፡ ብረት ፡ ይቀጠቅጣል ፡ ይፈጭማል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 41 ፤ እግሮቹና ፡ ጣቶቹም ፡ እኩሉ ፡ ሸክላ ፡ እኩሉም ፡ ብረት ፡ ኾኖ ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ የተከፋፈለ ፡ መንግሥት ፡ ይኾናል ፤ ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ እንዳየኹ ፥ የብረት ፡ ብርታት ፡ ለርሱ ፡ ይኾናል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 42 ፤ የእግሮቹም ፡ ጣቶች ፡ እኩሉ ፡ ብረት ፡ እኩሉም ፡ ሸክላ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፥ እንዲሁ ፡ መንግሥቱ ፡

እኩሉ ፡ ብርቱ ፡ እኩሉ ፡ ደካማ ፡ ይኾናል ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 43 ፤ ብረቱም ፡ ከሸክላው ፡ ጋራ ፡ ተደባልቆ ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ ከሰው ፡ ዘር ፡ ጋራ ፡ ይደባለቃሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብረት ፡ ከሸክላ ፡ ጋራ ፡ እንደማይጣበቅ ፥ እንዲሁ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አይጣበቁም ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 44 ፤ በእነዚያም ፡ ነገሥታት ፡ ዘመን ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የማይፈርስ ፡ መንግሥት ፡ ያስነሣል ፤ ለሌላ ፡ ሕዝብም ፡ የማይሰጥ ፡ መንግሥት ፡ ይኾናል ፤ እነዚያንም ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ትፈጫቸዋለች ፡ ታጠፋቸውማለች ፥ ለዘለዓለምም ፡ ትቆማለች ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 45 ፤ ድንጋዩም ፡ እጅ ፡ ሳይነካው ፡ ከተራራ ፡ ተፈንቅሎ ፡ ብረቱንና ፡ ናሱን ፡ ሸክላውንና ፡ ብሩን ፡ ወርቁንም ፡ ሲፈጨው ፡ እንዳየኽ ፥ እንዲሁ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የሚኾነውን ፡ ታላቁ ፡ አምላክ ፡ ለንጉሡ ፡ አስታውቆታል ፤ ሕልሙም ፡ እውነተኛ ፡ ፍቺውም ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 46 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በግንባሩ ፡ ተደፍቶ ፡ ለዳንኤል ፡ ሰገደለት ፥ የእኽሉንም ፡ ቍርባን ፡ ዕጣኑንም ፡ ያቀርቡለት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 47 ፤ ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፦ ይህን ፡ ምስጢር ፡ ትገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ተችሎኻልና ፥ በእውነት ፡ አምላካችኹ ፡ የአማልክት ፡ አምላክ ፥ የነገሥታትም ፡ ጌታ ፥ ምስጢርም ፡ ገላጭ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ተናገረው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 48 ፤ ንጉሡም ፡ ዳንኤልን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደርገው ፥ ብዙም ፡ ታላቅ ፡ ስጦታ ፡ ሰጠው ፥ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሾመው ፥ በባቢሎንም ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ዋነኛ ፡ አለቃ ፡ አደረገው ።

ዳን. ፡ 2 ፡ 49 ፤ ዳንኤልም ፡ ንጉሡን ፡ ለመነ ፥ ርሱም ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሾማቸው ፤ ዳንኤል ፡ ግን ፡ በንጉሡ ፡ በር ፡ ነበረ ።

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዳን. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ቁመቱ ፡ ስድሳ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ስድስት ፡ ክንድ ፡ የኾነውን ፡ የወርቁን ፡ ምስል ፡ አሠራ ፤ በባቢሎንም ፡ አውራጃ ፡ በዱራ ፡ ሜዳ ፡ አቆመው ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ መኳንንትንና ፡ ሹማምቶችን ፥ አዛገሮችንና ፡ ዐዛውንቶችን ፥ በጅሮንዶችንና ፡ አማካሪዎችን ፥ መጋቢዎችንም ፥ አውራጃ ፡ ገዢዎችንም ፡ ኹሉ ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ላከ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ መኳንንቱና ፡ ሹማምቶቹ ፥ አዛገሮቹና ፡ ዐዛውንቶቹ ፥ በጅሮንዶቹና ፡ አማካሪዎቹ ፥ መጋቢዎቹና ፡ አውራጃ ፡ ገዢዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ምስል ፡ ምረቃ ፡ ተሰበሰቡ ፤ ናቡከደነጾርም ፡ ባቆመው ፡ ምስል ፡ ፊት ፡ ቆሙ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ዐዋጅ ፡ ነጋሪውም ፡ እየጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የምትናገሩ ፡ ሆይ ፥

ዳን. ፡ 3 ፡ 5 ፤ የመለከትንና ፡ የእንቢልታን ፥ የመሰንቆንና ፡ የክራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፥ ተደፍታችኹ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንድትሰግዱ ፡ ታዛችኋል ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢልታውን ፥ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፥ የበገናውንና ፡ የዘፈኑንም ፡ ኹሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡

የተናገሩ ፡ ዥሉ ፡ ተደፉ ፥ ንጉሡም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ላቆመው ፡ ለወርቅ ፡ ምስል ፡ ሰገዱ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከለዳውያን ፡ ቀርበው ፡ አይሁድን ፡ ከሰሱ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 9 ፤ ለንጉሡም ፡ ለናቡከደነጾር ፡ ተናገሩ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ። ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 10 ፤ አንተ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፦ የመለከትንና ፡ የእንቢልታን ፥ የመሰንቆንና ፡ የክራርን ፥ የበገናንና ፡ የዋሽንትን ፥ የዘፈንንም ፡ ዥሉ ፡ ድምፅ ፡ የሚሰማ ፡ ሰው ፡ ዥሉ ፡ ተደፍቶ ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ ይስገድ ፤

ዳን. ፥ 3 ፥ 11 ፤ ተደፍቶም ፡ የማይሰግድ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ይጣላል ፡ ብለኽ ፡ አዘዝኽ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 12 ፤ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሾምኻቸው ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ የሚባሉ ፡ አይሁድ ፡ አሉ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝኽን ፡ እንቢ ፡ ብለዋል ፤ አማልክትኽን ፡ አያመልኩም ፥ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አይሰግዱም ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 13 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ በብስጭትና ፡ በቍጣ ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ ያመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ እነዚህንም ፡ ሰዎች ፡ ወደንጉሡ ፡ ፊት ፡ አመጧቸው ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 14 ፤ ናቡከደነጾርም ፦ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ ሆይ ፥ አምላኬን ፡ አለማምለካችኹ ፥ ላቆምኹትም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ አለመስገዳችኹ ፡ እውነት ፡ ነውን ፧

ዳን. ፥ 3 ፥ 15 ፤ አኹንም ፡ የመለከቱንና ፡ የእንቢልታውን ፡ የመሰንቆውንና ፡ የክራሩን ፡ የበገናውንና ፡ የዋሽንቱን ፡ የዘፈኑንም ፡ ዥሉ ፡ ድምፅ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፡ ተደፍታችኹ ፡ ላሠራኹት ፡ ምስል ፡ ብትሰግዱ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ባትሰግዱ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በሚነድ ፡ እሳት ፡ እቶን ፡ ውስጥ ፡ ትጣላላችኹ ፤ ከእጄስ ፡ የሚያድናችኹ ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 16 ፤ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ መለሱ ፡ ንጉሡንም ፦ ናቡከደነጾር ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ነገር ፡ እንመልስልኽ ፡ ዘንድ ፡ አስፈላጊያችን ፡ አይደለም ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 17 ፤ የምናመልከው ፡ አምላካችን ፡ ከሚነደው ፡ ከእሳቱ ፡ እቶን ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ይችላል ፤ ከእጅኽም ፡ ያድነናል ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ! ፡

ዳን. ፥ 3 ፥ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ ባያድነን ፥ አማልክትኽን ፡ እንዳናመልክ ፡ ላቆምኸውም ፡ ለወርቁ ፡ ምስል ፡ እንዳንሰግድለት ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ናቡከደነጾር ፡ በሲድራቅና ፡ በሚሳቅ ፡ በዐብደናጎም ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ሞላበት ፥ የፊቱም ፡ መልክ ፡ ተለወጠባቸው ፤ ርሱም ፡ ተናገረ ፥ የእቶንም ፡ እሳት ፡ ይነድ ፡ ከነበረው ፡ ይልቅ ፡ ሰባት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርገው ፡ እንዲያነዱት ፡ አዘዘ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 20 ፤ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅንም ፡ ዐብደናጎንም ፡ ያስሩ ፡ ዘንድ ፥ ወደሚነድም ፡ ወደእቶን ፡ እሳት ፡ ይጥሏቸው ፡ ዘንድ ፥ በሰራዊቱ ፡ ውስጥ ፡ ከነበሩት ፡ ኀያላን ፡ አዘዘ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 21 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ከሰናፎላቸውና ፡ ከቀሚሳቸው ፡ ከመጐናጸፊያቸውም ፡ ከቀረውም ፡ ልብሳቸው ፡ ጋራ ፡ ታስረው ፡ በሚነድ ፡ በእቶን ፡ እሳት ፡ ውስጥ ፡ ተጣሉ ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 22 ፤ የንጉሡም ፡ ትእዛዝ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የእቶኑም ፡ እሳት ፡ እጅግ ፡ ስለሚነድ ፥ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ የጣሏቸውን ፡ ሰዎች ፡ የእሳቱ ፡ ወላፈን ፡ ገደላቸው ።

ዳን. ፥ 3 ፥ 23 ፤ እነዚህም ፡ ሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፡ ታስረው ፡ በሚነደው ፡ በእቶኑ ፡

እሳት ፡ ውስጥ ፡ ወደቁ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 24 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ተደነቀ ፡ ፈጥኖም ፡ ተነሣ ፤ አማካሪዎቹንም ፦ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ አስረን ፡ በእሳት ፡ ውስጥ ፡ ጥለን ፡ አልነበረምን ፧ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። እነርሱም ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እውነት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ለንጉሡ ፡ መለሱለት ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ እንሆ ፥ እኔ ፡ የተፈቱ ፡ በእሳቱም ፡ መካከል ፡ የሚመላለሱ ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ አያለኹ ፤ ምንም ፡ አላቈሰላቸውም ፤ የአራተኛውም ፡ መልክ ፡ የአማልክትን ፡ ልጅ ፡ ይመስላል ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 26 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ናቡከደነጾር ፡ ወደሚነደው ፡ ወደእሳቱ ፡ እቶን ፡ በር ፡ ቀርቦ ፦ እናንተ ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፥ ሲድራቅና ፡ ሚሳቅ ፡ ዐብደናጎም ፥ ኑ ፡ ውጡ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ። ሲድራቅና ፡ ሚሳቅም ፡ ዐብደናጎም ፡ ከእሳቱ ፡ መካከል ፡ ወጡ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 27 ፤ መሳፍንቱና ፡ ሹማምቶቹም ፡ አዛዦቹና ፡ የንጉሡ ፡ አማካሪዎች ፡ ተሰብስበው ፡ እሳቱ ፡ በእነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አካል ፡ ላይ ፡ ኀይል ፡ እንዳልነበረው ፥ የራሳቸውም ፡ ጠጕር ፡ እንዳልተቃጠለች ፥ ሰናፊላቸውም ፡ እንዳልተለወጠ ፥ የእሳቱም ፡ ሽታ ፡ እንዳልደረሰባቸው ፡ አዩ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ናቡከደነጾርም ፡ መልሶ ፦ መልአኩን ፡ የላከ ፥ ከአምላካቸውም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አምላክ ፡ እንዳያመልኩ ፡ ለርሱም ፡ እንዳይሰግዱ ፡ ሰውነታቸውን ፡ አሳልፈው ፡ የሰጡትን ፡ የንጉሡንም ፡ ቃል ፡ የተላለፉትን ፡ በርሱ ፡ የታመኑትን ፡ ባሪያዎቹን ፡ ያዳነ ፥ የሲድራቅና ፡ የሚሳቅ ፡ የዐብደናጎም ፡ አምላክ ፡ ይባረክ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 29 ፤ እኔም ፡ እንደዚህ ፡ የሚያድን ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለምና ፡ በሲድራቅና ፡ በሚሳቅ ፡ በዐብደናጎም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ የሚናገር ፡ ወገንና ፡ ሕዝብ ፡ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ይቈረጣሉ ፥ ቤቶቻቸውም ፡ የጕድፍ ፡ መጣያ ፡ ይደረጋሉ ፡ ብዬ ፡ አዝዣለኹ ፡ አለ ።

ዳን. ፡ 3 ፡ 30 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ ሲድራቅንና ፡ ሚሳቅን ፡ ዐብደናጎንም ፡ በባቢሎን ፡ አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው ።

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ዳን. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ከንጉሡ ፡ ከናቡከደነጾር ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ወደሚቀመጡ ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ ወደሚናገሩ ፡ ኹሉ ፥ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡ በፊቴ ፡ ያደረገውን ፡ ተኣምራቱንና ፡ ድንቁን ፡ አሳያችኹ ፡ ዘንድ ፡ ወድጃለኹ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ተኣምራቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! ፡ ድንቁም ፡ እንዴት ፡ ጽኑ ፡ ነው! ፡ መንግሥቱም ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፥ ግዛቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በቤቴ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ በአዳራሼም ፡ ተመችቶኝ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ሕልም ፡ ዐለምኹ ፤ ርሷም ፡ አስፈራችኝ ፤ በዐልጋዬም ፡ ላይ ፡ የነበረው ፡ ዐሳቤና ፡ የራሴ ፡ ራእይ ፡ አስጨነቁኝ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ የሕልሙን ፡ ፍቺ ፡ እንዲያስታውቁኝ ፡ የባቢሎን ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኹ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 7 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎቹና ፡ አስማተኞቹ ፡ ከለዳውያኑና ፡ ቃላተኞቹ ፡ ገቡ ፤ ሕልሙንም ፡ በፊታቸው ፡ ተናገርኹ ፥ ፍቺውን ፡ ግን ፡ አላስታወቁኝም ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በመጨረሻም ፡ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ አምላኬ ፡ ስም ፡ ብልጣሶር ፡ የሚባለው ፡ ዳንኤል ፡ በፊቴ ፡ ገባ ፤ እኔም ፡ ሕልሙን ፡ ነገርኹት ፡ እንዲህም ፡ አልኹት ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 9 ፤ የሕልም ፡ ተርጓሚዎች ፡ አለቃ ፡ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፥ ከምስጢርም ፡ ኹሉ ፡ የሚያስቸግርኽ ፡ እንደሌለ ፡ ዐውቄያለኹና ፡ ያለምኹትን ፡ የሕልሜን ፡ ራእይ ፡ ፍቺውንም ፡ ንገረኝ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 10 ፤ የራሴ ፡ ራእይ ፡ በዐልጋዬ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እንሆ ፥ በምድር ፡ መካከል ፡ ዛፍ ፡ አየኹ ፥ ቁመቱም ፡ እጅግ ፡ ረዥም ፡ ነበረ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ዛፉም ፡ ትልቅ ፡ ኾነ ፥ በረታም ፥ ቁመቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ደረሰ ፥ መልኩም ፡ እስከምድር ፡ ኹሉ ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ታየ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ቅጠሉም ፦ የተዋበ ፡ ነበረ ፡ ፍሬውም ፡ ብዙ ፡ ነበረ ፥ ለኹሉም ፡ መብል ፡ ነበረበት ፤ ከጥላውም ፡ በታች ፡ የምድር ፡ አራዊት ፡ ያርፉበት ፡ ነበር ፥ በቅርንጫፎቹም ፡ ውስጥ ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፥ ሥጋ ፡ ለባሹም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 13 ፤ በዐልጋዬም ፡ ላይ ፡ በራሴ ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 14 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየጮኸ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ዛፉን ፡ ቍረጡ ፥ ቅርንጫፎቹንም ፡ ጨፍጭፉ ፥ ቅጠሎቹንም ፡ አራግፉ ፥ ፍሬውንም ፡ በትኑ ፤ አራዊትም ፡ ከበታቹ ፡ ወፎቹም ፡ ከቅርንጫፉ ፡ ይሸሹ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጕቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ተዉት ፥ በመስክም ፡ ውስጥ ፡ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡ ታስሮ ፡ ይቈይ ፤ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ይረስርስ ፡ ዕድል ፡ ፈንታውም ፡ በምድር ፡ ሣር ፡ ውስጥ ፡ ከአራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ልቡም ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ይለወጥ ፥ የአውሬም ፡ ልብ ፡ ይሰጠው ፤ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ይለፉበት ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ልዑሉ ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለወደደውም ፡ እንዲሰጠው ፥ ከሰውም ፡ የተዋረደውን ፡ እንዲሾምበት ፡ ሕያዋን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ የጠባቂዎች ፡ ትእዛዝ ፥ ይህም ፡ ፍርድ ፡ የቅዱሳን ፡ ቃል ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ይህን ፡ ሕልም ፡ ዐልሜያለኹ ፤ አንተም ፥ ብልጣሶር ፥ ፍቺውን ፡ አስታውቀኝ ፥ የመንግሥቴ ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ፍቺውን ፡ ያስታውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ባንተ ፡ ውስጥ ፡ አለና ፡ አንተ ፡ ትችላለኽ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 19 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብልጣሶር ፡ የተባለው ፡ ዳንኤል ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ዐሰበ ፥ ልቡም ፡ ታወከ ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ ሕልሙና ፡ ፍቺው ፡ አያስቸግርኽ ፡ አለው ። ብልጣሶርም ፡ መልሶ ፡ አለ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ሕልሙ ፡ ለሚጠሉኽ ፥ ፍቺውም ፡ ለጠላቶችኽ ፡ ይኹን ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ትልቅ ፡ የነበረው ፡ የበረታውም ፥ ቁመቱም ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ የደረሰው ፥ መልኩም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ድረስ ፡ የታየው ፥

ዳን. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ቅጠሉም ፡ አምሮ ፡ የነበረው ፥ ፍሬውም ፡ የበዛው ፥ ለኹሉም ፡ መብል ፡ የነበረበት ፤ በበታቹም ፡ የምድር ፡ አራዊት ፡ የተቀመጡ ፥ በቅርንጫፎቹም ፡ የሰማይ ፡ ወፎች ፡ ያደሩበት ፡ ያየኸው ፡ ዛፍ ፤

ዳን. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ርሱ ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ የኾንኽ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፤ ታላቅነትኽ ፡ በዝቷል ፥ እስከ ፡ ሰማይም ፡ ደርሷል ፥ ግዛትኽም ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ንጉሡም ፡ ከሰማይ ፡ የወረደውንና ፦ ዛፉን ፡ ቍረጡ ፥ አጥፉትም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጕቶውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ ተዉት ፤ በብረትና ፡ በናስ ፡ ማሰሪያ ፡ ታስሮ ፡ በመስክ ፡ ውስጥ ፡ ይቈይ ፤ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ይረስርስ ፥ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ እስኪያልፉበት ፡ ድረስ ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፡ ያለውን ፡ ቅዱስ ፡ ጠባቂ ፡ ማየቱ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ፍቺው ፡ ይህ ፡ ነው ፤

ዳን. ፡ 4 ፡ 24 ፤ በጌታዬ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ የወረደው ፡ የልዑሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ነው ፤

ዳን. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ልዑሉም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለሚወደውም ፡ እንዲሰጠው ፡ እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይተኽ ፡ ትሰደዳለኽ ፥ መኖሪያኽም ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፥ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ትገደዳለኽ ፥ በሰማይም ፡ ጠል ፡ ትረሰርሳለኽ ፥ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ያልፉብኻል ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 26 ፤ የዛፉንም ፡ ጕቶ ፡ ይተዉት ፡ ዘንድ ፡ ማዘዙ ፥ ሥልጣን ፡ ከሰማያት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ካወቅኽ ፡ በኋላ ፡ መንግሥትኽ ፡ ይቈይልኻል ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 27 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ የደኅንነትኽ ፡ ዘመን ፡ ይረዝም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ምክሬ ፡ ደስ ፡ ያሠኝኽ ፤ ኀጢአትኽንም ፡ በጽድቅ ፥ በደልኽንም ፡ ለድኻዎች ፡ በመመጽወት ፡ አስቀር ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 28 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ በንጉሡ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡ ደረሰ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ በኋላ ፡ በባቢሎን ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፦ ይህች ፡ እኔ ፡ በጕልበቴ ፡ ብርታት ፡ ለግርማዬ ፡ ክብር ፡ የመንግሥት ፡ መኖሪያ ፡ እንድትኾን ፡ ያሠራኋት ፡ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ አይደለችምን ፧ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ቃሉም ፡ ገና ፡ በንጉሡ ፡ አፍ ፡ ሳለ ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀና ፦ ንጉሥ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ሆይ ፦ መንግሥት ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ዐለፈች ፡ ተብሎ ፡ ለአንተ ፡ ተነግሯል ፤

ዳን. ፡ 4 ፡ 32 ፤ ልዑሉም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ ለሚወደውም ፡ እንዲሰጠው ፡ እስክታውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይተኽ ፡ ትሰደዳለኽ ፥ መኖሪያኽም ፡ ከምድር ፡ አራዊት ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ፤ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ትገደዳለኽ ፥ ሰባት ፡ ዘመናትም ፡ ያልፉብኻል ፡ አለው ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 33 ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ነገሩ ፡ በናቡከደነጾር ፡ ላይ ፡ ደረሰ ፤ ጠጕሩም ፡ እንደ ፡ ንስር ፥ ጥፍሩም ፡ እንደ ፡ ወፎች ፡ እስኪረዝም ፡ ድረስ ፡ ከሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ተሰደደ ፥ እንደ ፡ በሬም ፡ ሣር ፡ በላ ፥ አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 34 ፤ ዘመኑም ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ዐይኔን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አነሣኹ ፥ አእምሮዬም ፡ ተመለሰልኝ ፤ ልዑሉንም ፡ ባረክኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ የሚኖረውን ፡ አመሰገንኹ ፡ አከበርኹትም ፤ ግዛቱ ፡ የዘለዓለም ፡ ግዛት ፡ ነውና ፥ መንግሥቱም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነውና ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 35 ፤ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ ይቈጠራሉ ፤ በሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ በሚኖሩ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፤ እጁንም ፡ የሚከለክላት ፡ ወይም ፦ ምን ፡ ታደርጋለኽ ፧ የሚለው ፡ የለም ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 36 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አእምሮዬ ፡ ተመለሰልኝ ፥ ለመንግሥቴም ፡ ክብር ፡ ግርማዬና ፡ ውበቴ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሰ ፤ አማካሪዎቼና ፡ መኳንንቶቼም ፡ ፈለጉኝ ፥ በመንግሥቴም ፡ ውስጥ ፡ ጸናኹ ፥ ብዙም ፡ ክብር ፡ ተጨመረልኝ ።

ዳን. ፡ 4 ፡ 37 ፤ አኹንም ፡ እኔ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የሰማይን ፡ ንጉሥ ፡ አመሰግናለኹ ፥ ታላቅም ፡

አደርገዋለኹ ፥ አከብረውማለኹ ። ሥራው ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፥ መንገዱም ፡ ፍርድ ፡ ነውና ፥ በትዕቢትም ፡ የሚኼዱትን ፡ ያዋርድ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልና ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 1 ፤ ንጉሡ ፡ ብልጣሶር ፡ ለሺሕ ፡ መኳንንቶቹ ፡ ትልቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገ ፥ በሺሑም ፡ ፊት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣ ፡ ነበር ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 2 ፤ ብልጣሶርም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡና ፡ መኳንንቶቹ ፣ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹ ፡ ይጠጡባቸው ፡ ዘንድ ፦ አባቴ ፡ ናቡከደነጾር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ መቅደስ ፡ ያመጣቸውን ፡ የወርቁንና ፡ የብሩን ፡ ዕቃዎች ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 3 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከነበረው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ የመጡትን ፡ የወርቁን ፡ ዕቃዎች ፡ አመጡ ፤ ንጉሡና ፡ መኳንንቶቹም ፡ ሚስቶቹና ፡ ቁባቶቹም ፡ ጠጡባቸው ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 4 ፤ የወይን ፡ ጠጅም ፡ እየጠጡ ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፣ ከናስና ፡ ከብረት ፣ ከዕንጨትና ፡ ከድንጋይ ፡ የተሠሩትን ፡ አማልክት ፡ አመሰገኑ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 5 ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ጣቶች ፡ ወጥተው ፡ በንጉሡ ፡ ቤት ፡ በተለሰነው ፡ ግንብ ፡ ላይ ፡ በመቅረዙ ፡ አንጻር ፡ ጻፉ ፤ ንጉሡም ፡ የሚጽፉትን ፡ ጣቶች ፡ አየ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 6 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሡ ፡ ፊት ፡ ተለወጠበት ፥ ዐሳቡም ፡ አስቸገረው ፥ የወገቡም ፡ ኾሞማቶች ፡ ተፈቱ ፥ ጕልበቶቹም ፡ ተብረከረኩ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 7 ፤ ንጉሡም ፡ አስማተኞቹንና ፡ ከለዳውያኑን ፣ ቃላተኞቹንም ፡ ያገቡ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ፤ ንጉሡም ፡ የባቢሎንን ፡ ጠቢባን ፦ ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ ያነበበ ፥ ፍቺውንም ፡ ያሳየኝ ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ይለብሳል ፥ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በዐንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ ይኾንለታል ፥ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ ይኾናል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሡ ፡ ጠቢባን ፡ ኹሉ ፡ ገቡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽሕፈቱን ፡ ያነቡ ፥ ፍቺውንም ፡ ለንጉሡ ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 9 ፤ ንጉሡም ፡ ብልጣሶር ፡ እጅግ ፡ ደነገጠ ፥ ፊቱም ፡ ተለወጠበት ፥ መኳንንቶቹም ፡ ተደናገጡ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 10 ፤ ንግሥቲቱም ፡ ስለንጉሡና ፡ ስለመኳንንቱ ፡ ቃል ፡ ወደግብዣ ፡ ቤት ፡ ገባች ፤ ንግሥቲቱም ፡ ተናገረች ፥ እንዲህም ፡ አለች ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ፤ ዐሳብኽ ፡ አያስቸግርኽ ፥ ፊትኽም ፡ አይለወጥ ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 11 ፤ የቅዱሳን ፡ አማልክት ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ በመንግሥትኽ ፡ ውስጥ ፡ አለ ፤ በአባትኽም ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ አማልክት ፡ ጥበብ ፡ ያለ ፡ ጥበብና ፡ ማስተዋል ፡ ዕውቀትም ፡ ተገኝበት ፤ አባትኽ ፡ ንጉሡ ፡ ናቡከደነጾር ፡ የሕልም ፡ ተርጓሚዎችና ፡ የአስማተኞች ፣ የከለዳውያንና ፡ የቃላተኞች ፡ አለቃ ፡ አደረገው ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 12 ፤ መልካም ፡ መንፈስ ፣ ዕውቀትም ፣ ማስተዋልም ፣ ሕልምንም ፡ መተርጐም ፥ እንቆቅልሽንም ፡ መግለጥ ፥ የተቋጠረውንም ፡ መፍታት ፡ ንጉሡ ፡ ስሙን ፡ ብልጣሶር ፡ ብሎ ፡ በሰየመው ፡ በዳንኤል ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷልና ። አኹንም ፡ ዳንኤል ፡ ይጠራ ፥ ርሱም ፡ ፍቺውን ፡ ያሳያል ።

ዳን. ፥ 5 ፥ 13 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ ወደንጉሡ ፡ ፊት ፡ ገባ ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረው ፥ ዳንኤልንም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ንጉሡ ፡ አባቴ ፡ ከይሁዳ ፡ ከማረካቸው ፣ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ የኾንኽ ፡ ዳንኤል ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧

ዳን. ፥ 5 ፥ 14 ፤ የአማልክት ፡ መንፈስ ፡ እንዳለብኽ ፥ ዕውቀትና ፡ ማስተዋልም ፣ መልካምም ፡ ጥበብ ፡ እንደ ፡

ተገኘብኽ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ሰምቻለኹ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ ያነቡ ፡ ዘንድ ፥ ፍቺውንም ፡ ያስታውቁኝ ፡ ዘንድ ፥ ጠቢባንና ፡ አስማተኞች ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ገብተው ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የነገሩን ፡ ፍቺ ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 16 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ፍቺን ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፥ የተቋጠረንም ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ እንድትችል ፡ ሰምቻለኹ ፤ አኹንም ፡ ጽሕፈቱን ፡ ታነብ ፡ ዘንድ ፥ ፍቺውንም ፡ ታስታውቀኝ ፡ ዘንድ ፡ ብትችል ፥ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ ትለብሳለኽ ፥ የወርቅም ፡ ማርዳ ፡ በዐንገትኽ ፡ ዙሪያ ፡ ይኾንልኻል ፥ አንተም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ ትኾናለኽ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 17 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ዳንኤል ፡ መለሰ ፥ በንጉሡም ፡ ፊት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ስጦታኽ ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፥ በረከትኽንም ፡ ለሌላ ፡ ስጥ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽሕፈቱን ፡ ለንጉሡ ፡ አነባለኹ ፥ ፍቺውንም ፡ አስታውቃለኹ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ለአባትኽ ፡ ለናቡከደነጾር ፡ መንግሥትንና ፡ ታላቅነትን ፣ ክብርንና ፡ ግርማን ፡ ሰጠው ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ስለሰጠው ፡ ታላቅነት ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፣ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ የሚናገሩ ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ይንቀጠቀጡና ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ፤ የፈቀደውን ፡ ይገድል ፥ የፈቀደውንም ፡ በሕይወት ፡ ያኖር ፡ ነበር ፤ የፈቀደውንም ፡ ያነሣ ፥ የፈቀደውንም ፡ ያዋርድ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ልቡ ፡ ግን ፡ በታበየ ፥ በኵራትም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሱ ፡ በጠነከረ ፡ ጊዜ ፥ ከመንግሥቱ ፡ ዙፋን ፡ ተዋረደ ፥ ክብሩም ፡ ተለየው ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ልዑል ፡ አምላክም ፡ በሰዎች ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ እንዲሠለጥን ፥ የሚወደውንም ፡ እንዲሾምበት ፡ እስኪያውቅ ፡ ድረስ ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ተይለቶ ፡ ተሰደደ ፤ ልቡም ፡ እንደ ፡ አውሬ ፡ ልብ ፡ ኾነ ፥ መኖሪያውም ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ አህያዎች ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ እንደ ፡ በሬ ፡ ሣር ፡ በላ ፥ አካሉም ፡ በሰማይ ፡ ጠል ፡ ረሰረሰ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ብልጣሶር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ልጁ ፡ ስትኾን ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ እያወቅኽ ፡ በሰማይ ፡ ጌታ ፡ ላይ ፡ ኰራኽ ፡ እንጂ ፡ ልብኽን ፡ አላዋረድኽም ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 23 ፤ የመቅደሱንም ፡ ዕቃዎች ፡ በፊትኽ ፡ አመጡ ፥ አንተም ፣ መኳንንትኽም ፣ ሚስቶችኽም ፣ ቁባቶችኽም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣችኹባቸው ፤ ከብርና ፡ ከወርቅም ፣ ከናስና ፡ ከብረትም ፣ ከዕንጨትና ፡ ከድንጋይም ፡ የተሠሩትን ፥ የማያዩትንም ፥ የማይሰሙትንም ፥ የማያውቁትንም ፡ አማልክት ፡ አመሰገንኽ ፤ ትንፋሽኽንና ፡ መንገድኽን ፡ ኹሉ ፡ በእጁ ፡ የያዘውን ፡ አምላክ ፡ አላከበርኽውም ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ስለዚህም ፡ እነዚህ ፡ የእጅ ፡ ጣቶች ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተልከዋል ፤ ይህም ፡ ጽሕፈት ፡ ተጽፏል ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 25 ፤ የተጻፈውም ፡ ጽሕፈት ፦ ማኔ ፡ ቴቄል ፡ ፋሬስ ፡ ይላል ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 26 ፤ የነገሩም ፡ ፍቺ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ማኔ ([274]) ፡ ማለት ፥ እግዚአብሔር ፡ መንግሥትኽን ፡ ቈጠረው ፥ ፈጸመውም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ቴቄል ([275]) ፡ ማለት ፥ በሚዛን ፡ ተመዘንኽ ፥ ቀሎኽም ፡ ተገኘኽ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ፋሬስ ([276]) ፡ ማለት ፥ መንግሥትኽ ፡ ተከፈለ ፥ ለሜዶንና ፡ ለፋርስ ፡ ሰዎችም ፡ ተሰጠ ፡ ማለት ፡

---

274 ሱር. ፥ ምናህ ፡ (ሰፈረ ፥ ቈጠረ ፥ ፈጸመ ፤ ኪ.ወ.ክ.598) ።

275 ሱር. ፥ ትቄል ፡ (ሰቀለ ፥ ደለወ ፥ መዘነ ፤ ኪ.ወ.ክ.902) ።

276 ሱር. ፥ ፋርሲን ፡ (ከፈል • ፍራሽ) ።

ነው ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 29 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብልጣሶር ፡ ለዳንኤል ፡ ሐምራዊ ፡ ግምጃ ፡ እንዲያለብሱት ፥ የወርቅ ፡ ማርዳም ፡ በዐንገቱ ፡ ዙሪያ ፡ እንዲያደርጉለት ፡ አዘዘ ፤ በመንግሥትም ፡ ላይ ፡ ሦስተኛ ፡ ገዢ ፡ እንዲኾን ፡ ዐዋጅ ፡ አስነገረ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 30 ፤ በዚያ ፡ ሌሊት ፡ የከለዳውያን ፡ ንጉሥ ፡ ብልጣሶር ፡ ተገደለ ።

ዳን. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ሜዶናዊውም ፡ ዳርዮስ ፡ መንግሥቱን ፡ ወሰደ ፤ ዕድሜውም ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ነበረ ።

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ዳን. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ዳርዮስም ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲኾኑ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ መሳፍንት ፡ በመንግሥቱ ፡ ላይ ፡ ይሾም ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 2 ፤ መሳፍንቱም ፡ ሒሳቡን ፡ ያመጡላቸው ፡ ዘንድ ፥ ንጉሡም ፡ እንዳይጐዳ ፥ ሦስት ፡ አለቃዎች ፡ በላያቸው ፡ አደረገ ፤ ከነርሱም ፡ አንደኛው ፡ ዳንኤል ፡ ነበረ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ዳንኤልም ፡ መልካም ፡ መንፈስ ፡ ስለ ፡ አለው ፥ ከአለቃዎችና ፡ ከመሳፍንት ፡ በለጠ ፤ ንጉሡም ፡ በመንግሥቱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመው ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 4 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አለቃዎችና ፡ መሳፍንቱ ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሰበብ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የታመነ ፡ ነበረና ፥ ስሕተትና ፡ በደልም ፡ አልተገኘበትምና ፥ በርሱ ፡ ላይ ፡ ሰበብና ፡ በደል ፡ ያገኙበት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 5 ፤ እነዚያም ፡ ሰዎች ፦ ከአምላኩ ፡ ሕግ ፡ በቀር ፥ በዚህ ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ ሌላ ፡ ሰበብ ፡ አናገኝበትም ፡ አሉ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 6 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አለቃዎቹና ፡ መሳፍንቱ ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰብስበው ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 7 ፤ የመንግሥቱ ፡ አለቃዎች ፡ ኹሉ ፤ ሹማምቶችና ፡ መሳፍንት ፤ አማካሪዎችና ፡ አዛዦች ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ልመና ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ ቢለምን ፥ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ ይጣል ፥ የሚል ፡ የንጉሥ ፡ ሕግና ፡ ብርቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 8 ፤ አኹንም ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እንደማይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡ ሕግ ፥ እንዳይለወጥ ፡ ትእዛዙን ፡ አጽና ፥ ጽሕፈቱንም ፡ ጻፍ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ንጉሡም ፡ ዳርዮስ ፡ ጽሕፈቱንና ፡ ትእዛዙን ፡ ጻፈ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ዳንኤልም ፡ ጽሕፈቱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፤ የዕልፍኙም ፡ መስኮቶች ፡ ወደኢየሩሳሌም ፡ አንጻር ፡ ተከፍተው ፡ ነበር ፤ ቀድሞም ፡ ያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ በየዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡ በአምላኩ ፡ ፊት ፡ ጸለየ ፥ አመሰገነም ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እነዚያም ፥ ሰዎች ፡ ተሰብስበው ፥ ዳንኤል ፡ በአምላኩ ፡ ፊት ፡ ሲጸልይና ፡ ሲለምን ፡ አገኙት ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ቀርበው ፥ ስለንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በቀር ፡ እስከ ፡ ሠላሳ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከአምላክ ፡ ወይም ፡ ከሰው ፡ የሚለምን ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ በአንበሳዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ውስጥ ፡ እንዲጣል ፡ ትእዛዝ ፡ አልጻፍኽምን ፧ አሉት ። ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ ነገሩ ፡ እንደማይለወጠው ፡ እንደ ፡ ሜዶንና ፡ እንደ ፡ ፋርስ ፡

ሕግ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 13 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ በንጉሡ ፡ ፊት ፡ መልሰው ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ከይሁዳ ፡ ምርኮኞች ፡ የኾነው ፡ ዳንኤል ፡ በየዕለቱ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ልመናውን ፡ ይለምናል ፡ እንጂ ፥ አንተንና ፡ የጻፍኸውን ፡ ትእዛዝ ፡ አይቀበልም ፡ አሉት ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ንጉሡም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በጣም ፡ ዐዘነ ፥ ያድነውም ፡ ዘንድ ፡ ልቡን ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ አደረገ ፤ ሊያድነውም ፡ ፀሓይ ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ደከመ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 15 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ እነዚያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ተሰብስበው ፡ ንጉሡን ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ንጉሡ ፡ ያጸናው ፡ ትእዛዝ ፡ ወይም ፡ ሥርዐት ፡ ይለወጥ ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባ ፡ የሜዶንና ፡ የፋርስ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቅ ፡ አሉት ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 16 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ አዘዘ ፥ ዳንኤልንም ፡ አምጥተው ፡ በአንበሳዎች ፡ ጉድጓድ ፡ ጣሉት ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረ ፥ ዳንኤልንም ፦ ዘልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክኽ ፡ ርሱ ፡ ያድንኽ ፡ አለው ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ድንጋይም ፡ አምጥተው ፡ በጉድጓዱ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ገጠሙበት ፤ ንጉሡም ፡ በዳንኤል ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ እንዳይለወጥ ፡ በቀለበቱና ፡ በመኳንንቱ ፡ ቀለበት ፡ አተመው ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ፥ ሳይበላም ፡ ዐደረ ፤ መብልም ፡ አላመጡለትም ፥ እንቅልፉም ፡ ከርሱ ፡ ራቀ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 19 ፤ በነጋውም ፡ ንጉሡ ፡ ማልዶ ፡ ተነሣ ፥ ፈጥኖም ፡ ወዳንበሳዎች ፡ ጉድጓድ ፡ ኼደ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ጉድጓዱም ፡ ወደ ፡ ዳንኤል ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፥ በሐዘን ፡ ቃል ፡ ጠራው ፤ ንጉሡም ፡ ተናገረ ፥ ዳንኤልንም ፦ የሕያው ፡ አምላክ ፡ ባሪያ ፡ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ዘልጊዜ ፡ የምታመልከው ፡ አምላክኽ ፡ ከአንበሳዎች ፡ ያድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ችሏልን ፧ አለው ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ዳንኤልም ፡ ንጉሡን ፦ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ንገሥ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 22 ፤ በፊቱ ፡ ቅንነት ፡ ተገኝቶብኛልና ፥ ባንተም ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፥ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ አልበደልኹምና ፥ አምላኬ ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ የአንበሳዎችን ፡ አፍ ፡ ዘጋ ፥ እነርሱም ፡ አልጐዱኝም ፡ አለው ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 23 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሡ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ዳንኤልንም ፡ ከጉድጓዱ ፡ ያወጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ዳንኤልም ፡ ከጉድጓድ ፡ ወጣ ፥ በአምላኩም ፡ ታምኖ ፡ ነበርና ፥ አንዳች ፡ ጉዳት ፡ አልተገኘበትም ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ንጉሡም ፡ አዘዘ ፥ ዳንኤልንም ፡ የከሰሱ ፡ እነዚያን ፡ ሰዎች ፡ አመጧቸው ፥ እነርሱንና ፡ ልጆቻቸውንም ፣ ሚስቶቻቸውንም ፡ በአንበሳዎች ፡ ጉድጓድ ፡ ጣሏቸው ፤ ወደጉድጓዱም ፡ መጨረሻ ፡ ሳይደርሱ ፡ አንበሳዎች ፡ ያዟቸው ፥ ዐጥንታቸውንም ፡ ሹሉ ፡ ሰባበሩ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 25 ፤ የዘያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሥ ፡ ዳርዮስ ፡ በምድር ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ወደሚኖሩ ፡ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፥ በልዩ ፡ ልዩም ፡ ቋንቋ ፡ ወደሚናገሩ ፡ ሹሉ ፡ ጻፈ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 26 ፤ በመንግሥቴ ፡ ግዛት ፡ ሹሉ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ በዳንኤል ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ እንዲፈሩና ፡ እንዲንቀጠቀጡ ፡ አዝዣለኹ ፤ ርሱ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ነውና ፤ መንግሥቱም ፡ የማይጠፋ ፡ ነው ፥ ግዛቱም ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ድረስ ፡ ይኖራል ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ያድናል ፥ ይታደግማል ፤ በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ተአምራትንና ፡ ድንቅን ፡ ይሠራል ፤ ዳንኤልንም ፡ ከአንበሳዎች ፡ አፍ ፡ አድኖታል ።

ዳን. ፡ 6 ፡ 28 ፤ ይህም ፡ ዳንኤል ፡ በዳርዮስ ፡ መንግሥትና ፡ በፋርሳዊው ፡ በቂሮስ ፡ መንግሥት ፡ ኑሮው ፡ ተቃናለት ።

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዳን. ፡ 7 ፡ 1 ፤ በባቢሎን ፡ ንጉሥ ፡ በብልጣሶር ፡ በመገሥመሪያው ፡ ዓመት ፡ ዳንኤል ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ሕልምንና ፡ የራሱን ፡ ራእይ ፡ አየ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሕልሙን ፡ ጻፈ ፥ ዋነኛውንም ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ዳንኤልም ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ በሌሊት ፡ በራእይ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ በታላቁ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ይጋፈጡ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 3 ፤ አራትም ፡ ታላላቅ ፡ አራዊት ፡ ከባሕር ፡ ወጡ ፥ እያንዳንዲቱም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነበረች ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 4 ፤ መገሥመሪያዪቱ ፡ አንበሳ ፡ ትመስል ፡ ነበር ፥ የንስርም ፡ ክንፍ ፡ ነበራት ፤ ክንፎቿም ፡ ከርሷ ፡ እስኪነቀሉ ፡ ድረስ ፡ አይ ፡ ነበር ፥ ከምድርም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ተደረገች ፥ እንደ ፡ ሰውም ፡ በኹለት ፡ እግር ፡ እንድትቆም ፡ ተደረገች ፥ የሰውም ፡ ልብ ፡ ተሰጣት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 5 ፤ እንሆም ፥ ኹለተኛዪቱ ፡ ድብ ፡ የምትመስል ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ ነበረች ፥ ባንድ ፡ ወገንም ፡ ቆመች ፥ ሦስትም ፡ የጐድን ፡ ዐጥንቶች ፡ በአፏ ፡ ውስጥ ፡ በጥርሷ ፡ መካከል ፡ ነበሩ ፤ እንደዚህም ፦ ተነሥተሽ ፡ እጅግ ፡ ሥጋ ፡ ብዪ ፡ ተባለላት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ ነብር ፡ የምትመስል ፡ በገርባዋም ፡ ላይ ፡ አራት ፡ የወፍ ፡ ክንፎች ፡ የነበሯት ፡ ሌላ ፡ አውሬ ፡ አየኹ ፤ ለአውሬዪቱም ፡ አራት ፡ ራሶች ፡ ነበሯት ፥ ግዛትም ፡ ተሰጣት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ የምታስፈራና ፡ የምታስደነግጥ ፡ እጅግም ፡ የበረታች ፥ ታላላቅም ፡ የብረት ፡ ጥርሶች ፡ የነበሯት ፡ አራተኛ ፡ አውሬ ፡ ነበረች ፤ ትበላና ፡ ታደቅ ፡ ነበር ፥ የቀረውንም ፡ በእግሯ ፡ ትረግጥ ፡ ነበር ፤ ከርሷም ፡ በፊት ፡ ከነበሩት ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ የተለየች ፡ ነበረች ፤ ዐሥር ፡ ቀንዶችም ፡ ነበሯት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ቀንዶችንም ፡ ተመለከትኹ ፤ እንሆም ፥ በመካከላቸው ፡ ሌላ ፡ ትንሽ ፡ ቀንድ ፡ ወጣ ፥ በፊቱም ፡ ከቀደሙት ፡ ቀንዶች ፡ ሦስት ፡ ተነቃቀሉ ፤ እንሆም ፥ በዚያ ፡ ቀንድ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዐይኖች ፡ የነበሩ ፡ ዐይኖች ፡ በትዕቢትም ፡ የሚናገር ፡ አፍ ፡ ነበሩበት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ዙፋኖችም ፡ እስኪዘረጉ ፡ ድረስ ፡ አየኹ ፥ በዘመናት ፡ የሸመገለውም ፡ ተቀመጠ ፤ ልብሱም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፥ የራሱም ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ ጥሩ ፡ ጥጥ ፡ ነበረ ፤ ዙፋኑም ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ ነበረ ፥ መንኰራኵሮቹም ፡ የሚነድ ፡ እሳት ፡ ነበሩ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 10 ፤ የእሳትም ፡ ፈሳሽ ፡ ከፊቱ ፡ ይፈልቅና ፡ ይወጣ ፡ ነበር ፤ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ ያገለግሉት ፡ ነበር ፥ እልፍ ፡ አእላፋትም ፡ በፊቱ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ ፍርድም ፡ ኾነ ፥ መጻሕፍትም ፡ ተገለጡ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 11 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቀንዱ ፡ ይናገረው ፡ ከነበረው ፡ ከታላቁ ፡ ቃል ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ አየኹ ፤ አውሬዪቱም ፡ እስክትገደል ፥ አካሏም ፡ እስኪጠፋ ፡ ድረስ ፥ በእሳትም ፡ ለመቃጠል ፡ እስክትሰጥ ፡ ድረስ ፡ አየኹ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ከቀሩትም ፡ አራዊት ፡ ግዛታቸው ፡ ተወሰደ ፤ የሕይወታቸው ፡ ዕድሜ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዘመንና ፡ እስከ ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ረዘመ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ከሰማይ ፡ ደመናት ፡ ጋራ ፡ መጣ ፡ በዘመናት ፡ ወደሸመገለውም ፡ ደረሰ ፤ ወደ ፡ ፊቱም ፡ አቀረቡት ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ወገኖችና ፡ አሕዛብ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋም ፡ የሚናገሩ ፡ ኹሉ ፡ ይገዙለት ፡ ዘንድ ፡ ግዛትና ፡ ክብር ፡ መንግሥትም ፡ ተሰጠው ፤ ግዛቱም ፡ የማያልፍ ፡ የዘለዓለም ፡ ግዛት ፡ ነው ፥ መንግሥቱም ፡ የማይጠፋ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 15 ፤ በእኔም ፡ በዳንኤል ፡ በሥጋዬ ፡ ውስጥ ፡ መንፈሴ ፡ ደነገጠች ፥ የራሴም ፡ ራእይ ፡ አስቸገረኝ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 16 ፤ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቀርቤ ፡ ስለዚህ ፡ ኹሉ ፡ እውነቱን ፡ ጠየቅኹት ፤ ርሱም ፡ ነገረኝ ፥ የነገሩንም ፡ ፍቺ ፡ አስታወቀኝ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እነዚህ ፡ አራቱ ፡ ታላላቅ ፡ አራዊት ፡ ከምድር ፡ የሚነሡ ፡ አራት ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ መንግሥቱን ፡ ይወስዳሉ ፥ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ዓለምም ፡ መንግሥቱን ፡ ይወርሳሉ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከቀሩት ፡ ኹሉ ፡ ተለይታ ፡ እጅግ ፡ ስለምታስፈራው ፥ ጥርሶቿም ፡ የብረት ፡ ጥፍራዎቿም ፡ የናስ ፡ ስለኾኑት ፥ ስለምትበላውና ፡ ስለምታደቅው ፡ የቀረውንም ፡ በእግሯ ፡ ስለምትረግጠው ፡ ስለ ፡ አራተኛዪቱ ፡ አውሬ ፥

ዳን. ፡ 7 ፡ 20 ፤ በራሷም ፡ ላይ ፡ ስለነበሩ ፡ ስለ ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶች ፥ በኋላም ፡ ስለ ፡ ወጣው ፥ በፊቱም ፡ ሦስቱ ፡ ስለ ፡ ወደቁ ፥ ዐይኖችና ፡ ትዕቢት ፡ የተናገረ ፡ አፍ ፡ ስለ ፡ ነበሩት ፥ መልኩም ፡ ከሌላዎች ፡ ስለ ፡ በለጠ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ ቀንድ ፡ እውነቱን ፡ ለማወቅ ፡ ፈቀድኹ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 21 ፤ እንሆም ፥ ያ ፡ ቀንድ ፡ ከቅዱሳን ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ አየኹ ፥

ዳን. ፡ 7 ፡ 22 ፤ በዘመናት ፡ የሸመገለው ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፥ ፍርድም ፡ ለልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፥ ቅዱሳኑም ፡ መንግሥቱን ፡ የሚወስዱበት ፡ ዘመን ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ አሸነፋቸውም ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አራተኛዪቱ ፡ አውሬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አራተኛ ፡ መንግሥት ፡ ትኾናለች ፤ ርሱም ፡ ከመንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ የተለየ ፡ ይኾናል ፥ ምድሪቱንም ፡ ኹሉ ፡ ይበላል ፥ ይረግጣታል ፡ ያደቃትማል ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ዐሥሩም ፡ ቀንዶች ፡ ከዚያ ፡ መንግሥት ፡ የሚነሡ ፡ ዐሥር ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፤ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ይነሣል ፥ ርሱም ፡ ከፊተኞች ፡ የተለየ ፡ ይኾናል ፥ ሦስቱንም ፡ ነገሥታት ፡ ያዋርዳል ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 25 ፤ በልዑሉም ፡ ላይ ፡ ቃልን ፡ ይናገራል ፥ የልዑልንም ፡ ቅዱሳን ፡ ይሰባብራል ፥ ዘመናትንና ፡ ሕግን ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ያስባል ፤ እስከ ፡ ዘመንና ፡ እስከ ፡ ዘመናት ፡ እስከ ፡ እኩሌታ ፡ ዘመንም ፡ በእጁ ፡ ይሰጣሉ ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፍርድ ፡ ይኾናል ፥ እስከ ፡ ፍጻሜም ፡ ድረስ ፡ ያፈርሱትና ፡ ያጠፉት ፡ ዘንድ ፡ ግዛቱን ፡ ያስወግዱታል ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 27 ፤ መንግሥትም ፡ ግዛትም ፡ ከሰማይም ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ ያሉ ፡ የመንግሥታት ፡ ታላቅነት ፡ ለልዑሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ሕዝብ ፡ ይሰጣል ፤ መንግሥቱ ፡ የዘለዓለም ፡ መንግሥት ፡ ነው ፥ ግዛቶችም ፡ ኹሉ ፡ ይገዙለታል ፡ ይታዘዙለትማል ።

ዳን. ፡ 7 ፡ 28 ፤ የነገሩም ፡ ፍጻሜ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ። እኔም ፡ ዳንኤል ፡ በዐሳቤ ፡ እጅግ ፡ ተቸገርኹ ፥ ፊቴም ፡ ተለወጠብኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ነገሩን ፡ በልቤ ፡ ጠብቄያለኹ ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በመገሥመሪያ ፡ ከተገለጠልኝ ፡ ራእይ ፡ በኋላ ፥ ንጉሡ ፡ ብልጣሶር ፡ በነገሠ ፡ በሦስተኛው ፡

ዓመት ፥ ለእኔ ፡ ለዳንኤል ፡ ራእይ ፡ ተገለጠልኝ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 2 ፤ በራእዩም ፡ አየኹ ፤ ባየኹም ፡ ጊዜ ፡ በዔላም ፡ አውራጃ ፡ ባለው ፡ በሱሳ ፡ ግንብ ፡ ነበርኹ ፤ በራእዩም ፡ አየኹ ፡ በኡባል ፡ ወንዝም ፡ አጠገብ ፡ ነበርኹ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 3 ፤ ዐይኔን ፡ አንሥቼ ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ቀንዶች ፡ የነበሩት ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ በግ ፡ በወንዙ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ ኹለቱም ፡ ቀንዶቹ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይሉ ፡ ነበር ፤ አንዱ ፡ ግን ፡ ከኹለተኛው ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ነበረ ፥ ታላቁም ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ወጥቶ ፡ ነበር ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 4 ፤ አውራውም ፡ በግ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ወደ ፡ ሰሜንም ፡ ወደ ፡ ደቡብም ፡ በቀንዱ ፡ ሲገሦሽም ፡ አየኹ ፤ አራዊትም ፡ ኹሉ ፡ ይቋቋሙት ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፥ ከእጁም ፡ የሚያድን ፡ አልነበረም ፤ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ አደረገ ፥ ራሱንም ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 5 ፤ እኔም ፡ ስመለከት ፥ እንሆ ፥ ከምዕራብ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ አውራ ፡ ፍየል ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ ወጣ ፥ ምድርንም ፡ አልነካም ፤ ለፍየሉም ፡ በዐይኖቹ ፡ መካከል ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ቀንድ ፡ ነበረው ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 6 ፤ ኹለትም ፡ ቀንድ ፡ ወዳለው ፡ በወንዝም ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ወዳየኹት ፡ አውራ ፡ በግ ፡ መጣ ፥ በኀይሉም ፡ ቍጣ ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሮጠ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 7 ፤ ወደ ፡ አውራውም ፡ በግ ፡ ሲቀርብ ፡ አየኹት ፤ ርሱም ፡ ተመረረበት ፥ አውራውንም ፡ በግ ፡ መታ ፥ ኹለቱንም ፡ ቀንዶች ፡ ሰበረ ፤ አውራውም ፡ በግ ፡ ሊቋቋመው ፡ ኀይል ፡ አልነበረውም ፥ ርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጥሎ ፡ ረገጠው ፤ አውራውንም ፡ በግ ፡ ከእጁ ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 8 ፤ አውራውም ፡ ፍየል ፡ ራሱን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ፤ በበረታም ፡ ጊዜ ፡ ታላቁ ፡ ቀንዱ ፡ ተሰበረ ፥ ወደ ፡ አራቱም ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ የሚመለከቱ ፡ አራት ፡ ቀንዶች ፡ ከበታቹ ፡ ወጡ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ከነርሱም ፡ ከአንደኛው ፡ አንድ ፡ ታናሽ ፡ ቀንድ ፡ ወጣ ፥ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅም ፡ ወደ ፡ መልካሚቱም ፡ ምድር ፡ እጅግ ፡ ከፍ ፡ አለ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 10 ፤ እስከሰማይም ፡ ሰራዊት ፡ ድረስ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ከሰራዊትና ፡ ከከዋክብትም ፡ ዐያሌዎችን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለ ፥ ረገጣቸውም ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 11 ፤ እስከሰራዊትም ፡ አለቃ ፡ ድረስ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ አደረገ ፤ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ የዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፡ ተሻረ ፥ የመቅደሱም ፡ ስፍራ ፡ ፈረሰ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ሰራዊቱም ፡ ከኀጢአት ፡ የተነሣ ፡ ከዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፡ ጋራ ፡ ተሰጠው ፤ ርሱም ፡ እውነትን ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ጣለ ፥ አደረገም ፡ ተከናወነም ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 13 ፤ ከቅዱሳኑም ፡ አንዱ ፡ ሲናገር ፡ ሰማኹ ፤ ለተናገረው ፡ ለቅዱሱም ፡ ኹለተኛው ፡ ቅዱስ ፦ ስለዘወትሩ ፡ መሥዋዕት ፥ መቅደሱና ፡ ሰራዊቱም ፡ ይረገጡ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚሰጥና ፡ ስለሚያጠፋ ፡ ኀጢአት ፡ የኾነው ፡ ራእይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ይኾናል ፧ አለው ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 14 ፤ ርሱም ፦ እስከ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ማታና ፡ ጧት ፡ ድረስ ፡ ነው ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ መቅደሱ ፡ ይነጻል ፡ አለኝ ።

ዳን. ፥ 8 ፥ 15 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ራእዩን ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ ማስተዋሉን ፡ ፈለግኹ ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ምስያ ፡ በፊቴ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 16 ፤ በኡባልም ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፦ ገብርኤል ([277]) ፡ ሆይ ፥ ራእዩን ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ አስታውቀው ፡ ብሎ ፡ የሚጮኸውን ፡ የሰውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 17 ፤ እኔም ፡ ወደ ፡ ቆምኹበት ፡ ቀረበ ፤ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ ፈርቼ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ፤ ርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ራእዩ ፡ ለፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውል ፡ አለኝ ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ሲናገረኝም ፡ ደንግጬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ፤ ርሱም ፡ ዳሰሰኝ ፡ ቀጥ ፡ አድርጎም ፡ አቆመኝ ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ እንሆ ፥ በመቅሠፍቱ ፡ በመጨረሻ ፡ ዘመን ፡ የሚኾነውን ፡ አስታውቅኻለኹ ፤ ይህ ፡ ለተወሰነው ፡ ለፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ነውና ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ባየኸው ፡ በአውራው ፡ በግ ፡ ላይ ፡ የነበሩ ፡ ኹለቱ ፡ ቀንዶች ፡ እነርሱ ፡ የሜዶንና ፡ የፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 21 ፤ አውራውም ፡ ፍየል ፡ የግሪክ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፤ በዐይኖቹም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ ታላቁ ፡ ቀንድ ፡ መዠመሪያው ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ርሱም ፡ በተሰበረ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ፋንታ ፡ አራቱ ፡ እንደ ፡ ተነሡ ፥ እንዲሁ ፡ ከወገኑ ፡ አራት ፡ መንግሥታት ፡ ይነሣሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በኀይል ፡ አይተካከሉትም ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 23 ፤ በመንግሥታቸውም ፡ መጨረሻ ፥ ኀጢአታቸው ፡ በተሞላች ፡ ጊዜ ፥ እንቆቅልሽን ፡ የሚያስተውል ፡ ፊተ ፡ ጨካኝ ፡ ንጉሥ ፡ ይነሣል ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 24 ፤ ኀይሉም ፡ ይበረታል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በራሱ ፡ ኀይል ፡ አይደለም ፤ በድንቅም ፡ ያጠፋል ፥ ያደርግማል ፥ ይከናወንማል ፤ ኀያላንንና ፡ የቅዱሳንን ፡ ሕዝብ ፡ ያጠፋል ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 25 ፤ በመታለሉ ፡ ተንኰልን ፡ በእጁ ፡ ያከናውናል ፤ በልቡም ፡ ይታበያል ፥ ታምነውም ፡ የሚኖሩትን ፡ ብዙዎችን ፡ ያጠፋል ፤ በአለቃዎቹም ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ይቋቋማል ፤ ያለ ፡ እጅም ፡ ይሰበራል ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 26 ፤ የተነገረውም ፡ የማታውና ፡ የጧቱ ፡ ራእይ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ስለሚኾን ፡ ራእዩን ፡ ዝጋ ።

ዳን. ፡ 8 ፡ 27 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ተኛኹ ፥ ዐያሌም ፡ ቀን ፡ ታመምኹ ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ተነሥቼ ፡ የንጉሡን ፡ ሥራ ፡ እሠራ ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ ራእዩም ፡ አደንቅ ፡ ነበር ፥ የሚያስተውለው ፡ ግን ፡ አልነበረም ።

_____ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዳን. ፡ 9 ፡ 1 ፤ በከለዳውያን ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ በነገሠ ፥ ከሜዶን ፡ ዘር ፡ በነበረ ፡ በአሕሻዊሮስ ፡ ልጅ ፡ በዳርዮስ ፡ በመዠመሪያ ፡ ዓመት ፥

ዳን. ፡ 9 ፡ 2 ፤ በነገሠ ፡ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፡ እኔ ፡ ዳንኤል ፡ የኢየሩሳሌም ፡ መፍረስ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ሰባውን ፡ ዓመት ፥ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡ ለነቢዩ ፡ ለኤርምያስ ፡ የተናገረውን ፡ የዓመቱን ፡ ቍጥር ፡ በመጽሐፍ ፡ አስተዋልኹ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ማቅ ፡ ለብሼ ፡ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ኾኜ ፡ ስጾም ፡ እጸልይና ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ አምላክ ፡ አቀናኹ ።

---

277 ዕብ. ፥ ጋብሪኤል ፡ (ገብረ ፡ እግዚእ • የጌታ ፡ አገልጋይ) ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ አምላኬም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለይኹ ፥ ተናዝገፎም ፡ እንዲህ ፡ አልኹ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ከሚወዱኽና ፡ ትእዛዝኽን ፡ ከሚፈጽሙ ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳንንና ፡ ምሕረትን ፡ የምትጠብቅ ፡ ታላቅና ፡ የምታስፈራ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥

ዳን. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ኀጢአትን ፡ ሠርተናል ፥ በድለንማል ፥ ክፋትንም ፡ አድርገናል ፥ ዐምፀንማል ፥ ከትእዛዝኽና ፡ ከፍርድኽም ፡ ፈቀቅ ፡ ብለናል ፤

ዳን. ፡ 9 ፡ 6 ፤ በስምኽም ፡ ለነገሥታታችንና ፡ ለአለቃዎቻችን ፡ ለአባቶቻችንም ፡ ለአገሩም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የተናገሩትን ፡ ባሪያዎችኽን ፡ ነቢያትን ፡ አልሰማንም ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጽድቅ ፡ ለአንተ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ለእኛ ፡ ለይሁዳ ፡ ሰዎችና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚቀመጡ ፡ ለእስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ በቅርብና ፡ በሩቅም ፡ ላሉት ፡ አንተን ፡ በበደሉበት ፡ በበደላቸው ፡ ምክንያት ፡ በበተንኽበት ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የፊት ፡ ዕፍረት ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ሠራን ፡ ለእኛና ፡ ለነገሥታታችን ፡ ለአለቃዎቻችንና ፡ ለአባቶቻችንም ፡ የፊት ፡ ዕፍረት ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 9 ፤ 10 ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ያመፅን ፡ ብንኾን ፥ በባሪያዎቹም ፡ በነቢያት ፡ እጅ ፡ በፊታችን ፡ ባኖረው ፡ በሕጉ ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ የአምላካችንን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ባንሰማ ፥ ለጌታ ፡ ለአምላካችን ፡ ምሕረትና ፡ ይቅርታ ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 11 ፤ እስራኤልም ፡ ኹሉ ፡ ሕግኽን ፡ ተላልፈዋል ፥ ቃልኽንም ፡ እንዳይሰሙ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ፤ በርሱ ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተናልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ባሪያ ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ የተጻፈው ፡ መሐላና ፡ ርግማን ፡ ፈሰሰብን ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገርንም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በማምጣቱ ፡ በላያችንና ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ በተሾሙት ፡ ፈራጆቻችን ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አጸና ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ እንደተደረገው ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ ከሰማይ ፡ ኹሉ ፡ በታች ፡ አልተደረገም ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 13 ፤ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ መጣብን ፤ ከኀጢአታችንም ፡ እንመለስ ፡ እውነትኽንም ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ወደአምላካችን ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አልለመንንም ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ክፉ ፡ ነገሩን ፡ ጠብቆ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አመጣ ፤ አምላካችን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ጻድቅ ፡ ነውና ፥ እኛም ፡ ቃሉን ፡ አልሰማንምና ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 15 ፤ አኹንም ፡ ሕዝብኽን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ በበረታች ፡ እጅ ፡ ያወጣኽ ፥ እንደ ፡ ዛሬም ፡ ቀን ፡ ዝና ፡ ለአንተ ፡ ያገኘኽ ፡ ጌታ ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ ኀጢአትን ፡ ሠርተናል ፥ ክፋትንም ፡ አድርገናል ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችንና ፡ ስላባቶቻችን ፡ በደል ፡ ኢየሩሳሌምና ፡ ሕዝብኽ ፡ በዙሪያችን ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ መሰደቢያ ፡ ኾነዋልና ፥ እንደ ፡ ጽድቅኽ ፡ ኹሉ ፡ ቍጣኽና ፡ መዓትኽ ፡ ከከተማኽ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ከቅዱስ ፡ ተራራኽ ፡ እንዲመለስ ፡ እለምንኻለኹ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 17 ፤ አኹንም ፥ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ የባሪያኽን ፡ ጸሎትና ፡ ልመናውን ፡ ስማ ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በፈረሰው ፡ በመቅደስኽ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ስትል ፡ ፊትኽን ፡ አብራ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 18 ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ በፊትኽ ፡ የምንለምን ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ምሕረትኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ጽድቃችን ፡ አይደለምና ፡ ጐሮኽን ፡ አዘንብለኽ ፡ ስማ ፤ ዐይንኽን ፡ ገልጠኽ ፡ ጥፋታችንና ፡ ስምኽ ፡ የተጠራባትን ፡ ከተማ ፡ ተመልከት ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ ስማ ፤ አቤቱ ፥ ይቅር ፡ በል ፤ አቤቱ ፥ አድምጥና ፡ አድርግ ፤ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ስምኽ ፡ በከተማኽና ፡ በሕዝብኽ ፡ ላይ ፡ ተጠርቷልና ፥ ስለ ፡ ራስኽ ፡ አትዘግይ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ ገና ፡ ስናገር ፡ ስጸልይ ፥ በኀጢአቴና ፡ በሕዝቤም ፡ በእስራኤል ፡ ኀጢአት ፡ ስናዘዝ ፥ በአምላኬም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስለተቀደሰው ፡ ስለአምላኬ ፡ ተራራ ፡ ስለምን ፥

ዳን. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ገናም ፡ በጸሎት ፡ ስናገር ፡ አስቀድሜ ፡ በራእይ ፡ አይቼው ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ገብርኤል ፥ እንሆ ፥ እየበረረ ፡ መጣ ፤ በማታም ፡ መሥዋዕት ፡ ጊዜ ፡ ዳሰሰኝ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 22 ፤ አስተማረኝም ፥ ተናገረኝም ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ጥበብንና ፡ ማስተዋልን ፡ እሰጥኽ ፡ ዘንድ ፡ አኹን ፡ መጥቻለኹ ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 23 ፤ አንተ ፡ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ነኽና ፥ በልመናኽ ፡ መገሥመሪያ ፡ ላይ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጥቷል ፥ እኔም ፡ እነግርኽ ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለኹ ፤ አኹንም ፡ ነገሩን ፡ መርምር ፥ ራእዩንም ፡ አስተውል ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ዐመፃን ፡ ይጨርስ ፥ ኀጢአትንም ፡ ይፈጽም ፥ በደልንም ፡ ያስተሰርይ ፥ የዘለዓለምን ፡ ጽድቅ ፡ ያገባ ፥ ራእይንና ፡ ትንቢትን ፡ ያትም ፥ ቅዱስ ፡ ቅዱሳኑንም ፡ ይቀባ ፡ ዘንድ ፡ በሕዝብኽና ፡ በቅድስት ፡ ከተማኽ ፡ ላይ ፡ ሰባ ፡ ሱባዔ ፡ ተቀጥሯል ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ ዕወቅ ፡ አስተውልም ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ መጠገንና ፡ መሥራት ፡ ትእዛዙ ፡ ከሚወጣበት ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አለቃው ፡ እስከ ፡ መሲሕ ፡ ድረስ ፡ ሰባት ፡ ሱባዔና ፡ ስድሳ ፡ ኹለት ፡ ሱባዔ ፡ ይኾናል ፤ ርሷም ፡ በጭንቀት ፡ ዘመን ፡ ከጐዳናና ፡ ከቅጥር ፡ ጋራ ፡ ትሠራለች ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ከስድሳ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሰባትም ፡ በኋላ ፡ መሲሕ ፡ ይገደላል ፥ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የለም ፤ የሚመጣውም ፡ አለቃ ፡ ሕዝብ ፡ ከተማዪቱንና ፡ መቅደሱን ፡ ያጠፋሉ ፤ ፍጻሜውም ፡ በጐርፍ ፡ ይኾናል ፥ እስከ ፡ መጨረሻም ፡ ድረስ ፡ ጦርነት ፡ ይኾናል ፤ ጥፋትም ፡ ተቀጥሯል ።

ዳን. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ጽኑ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላንድ ፡ ሱባዔ ፡ ያደርጋል ፤ በሱባዔውም ፡ እኩሌታ ፡ መሥዋዕቱንና ፡ ቍርባኑን ፡ ያስቀራል ፤ በርኵሰትም ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አጥፊው ፡ ይመጣል ፤ እስከተቈረጠውም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ መቅሠፍት ፡ በአጥፊው ፡ ላይ ፡ ይፈሳል ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ዳን. ፡ 10 ፡ 1 ፤ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በቂሮስ ፡ በሦስተኛው ፡ ዓመት ፡ ብልጣሶር ፡ ለተባለው ፡ ለዳንኤል ፡ ነገር ፡ ተገለጠለት ፤ ነገሩም ፡ እውነት ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ ታላቅ ፡ ጦርነት ፡ ነው ፤ ነገሩንም ፡ አስተዋለ ፥ በራእዩም ፡ ውስጥ ፡ ማስተዋል ፡ ተሰጠው ።

ዳን. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ እኔ ፡ ዳንኤል ፡ ሦስት ፡ ሳምንት ፡ ሙሉ ፡ ሳዝን ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ማለፊያ ፡ እንጀራም ፡ አልበላኹም ፥ ሥጋና ፡ ጠጅም ፡ በአፌ ፡ አልገባም ፥ ሦስቱም ፡ ሳምንት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ዘይት ፡ አልተቀባኹም ።

ዳን. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ከመገሥመሪያውም ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ጤግሮስ ፡ በተባለው ፡ በታላቁ ፡ ወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ሳለኹ ፥ ዐይኔን ፡ አነሣኹ ፥

ዳን. ፡ 10 ፡ 5 ፤ እንሆም ፥ በፍታ ፡ የለበሰውን ፡ ጥሩም ፡ የአፌዝን ፡ ወርቅ ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ የታጠቀውን ፡ ሰው ፡ አየኹ ።

ዳን. ፡ 10 ፡ 6 ፤ አካሉም ፡ እንደ ፡ ቢረሌ ፡ ይመስል ፡ ነበር ፥ ፊቱም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ምስያ ፡

ነበረ ፥ ዐይኖቹም ፡ እንደሚንበለበል ፡ ፋና ፥ ክንዶቹና ፡ እግሮቹም ፡ እንደ ፡ ጋለ ፡ ናስ ፥ የቃሉም ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ድምፅ ፡ ነበረ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 7 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ ብቻዬን ፡ ራእዩን ፡ አየኹ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ራእዩን ፡ አላዩም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽኑ ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ወደቀባቸው ፥ ሊሸሸጉም ፡ ሸሹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 8 ፤ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ቀረኹ ፡ ይህንም ፡ ታላቅ ፡ ራእይ ፡ አየኹ ፤ ኀይልም ፡ አልቀረልኝም ፥ ደም ፡ ግባቴም ፡ ወደ ፡ ማሽብሸብ ፡ ተለወጠብኝ ፥ ኀይልም ፡ ዐጣኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 9 ፤ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፤ የቃሉንም ፡ ድምፅ ፡ በሰማኹ ፡ ጊዜ ፡ ደንግጬ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በግንባሬ ፡ ተደፋኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 10 ፤ እንሆም ፥ አንዲት ፡ እጅ ፡ ዳሰሰችኝ ፥ በጕልበቴና ፡ በእጄም ፡ አቆመችኝ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 11 ፤ ርሱም ፦ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ሰው ፡ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወዳንተ ፡ ተልኬያለኹና ፡ የምነግርኽን ፡ ቃል ፡ አስተውል ፥ ቀጥ ፡ ብለኽም ፡ ቁም ፡ አለኝ ። ይህንም ፡ ቃል ፡ ባለኝ ፡ ጊዜ ፡ እየተንቀጠቀጥኹ ፡ ቆምኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 12 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ ልብኽ ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፥ ሰውነትኽም ፡ በአምላክኽ ፡ ፊት ፡ ይዋረድ ፡ ዘንድ ፡ ካደረግኽበት ፡ ከመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ቃልኽ ፡ ተሰምቷል ፤ እኔም ፡ ስለ ፡ ቃልኽ ፡ መጥቻለኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 13 ፤ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ኻያ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተቋቋመኝ ፤ እንሆም ፥ ከዋነኞቹ ፡ አለቃዎች ፡ አንዱ ፡ ሚካኤል ፡ ሊረዳኝ ፡ መጣ ፤ እኔም ፡ ከፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ ጋራ ፡ በዚያ ፡ ተውኹት ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 14 ፤ ራእዩም ፡ ገና ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ነውና ፥ በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ለሕዝብኽ ፡ የሚኾነውን ፡ አስታውቅኽ ፡ ዘንድ ፡ አኹን ፡ መጥቻለኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 15 ፤ ይህንም ፡ ቃል ፡ በተናገረኝ ፡ ጊዜ ፡ ፊቴን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አቀረቀርኹ ፥ ዲዳም ፡ ኾንኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 16 ፤ እንሆም ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ከንፈሬን ፡ ዳሰሰኝ ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አፌን ፡ ከፍቼ ፡ ተናገርኹ ፡ በፊቴም ፡ ቆሞ ፡ የነበረውን ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ ከራእዩ ፡ የተነሣ ፡ ሕመሜ ፡ መጣብኝ ፥ ኀይልም ፡ ዐጣኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 17 ፤ ይህ ፡ የጌታዬ ፡ ባሪያ ፡ ከዚህ ፡ ከጌታዬ ፡ ጋራ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧ አኹንም ፡ ኀይል ፡ ዐጣኹ ፥ እስትንፋስም ፡ አልቀረልኝም ፡ አልኹት ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 18 ፤ ደግሞ ፡ ሰው ፡ የሚመስል ፡ ዳሰሰኝ ፥ አበረታኝም ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 19 ፤ ርሱም ፦ እጅግ ፡ የተወደድኽ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፤ በርታ ፥ ጽና ፡ አለኝ ። በተናገረኝም ፡ ጊዜ ፡ በረታኹና ፦ አበርትተኸኛልና ፥ ጌታዬ ፡ ይናገር ፡ አልኹ ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 20 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ወዳንተ ፡ የመጣኹት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ታውቃለኽን ፧ አኹንም ፡ ከፋርስ ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ እዋጋ ፡ ዘንድ ፡ እመለሳለኹ ፤ እኔም ፡ ስወጣ ፥ እንሆ ፤ የግሪክ ፡ አለቃ ፡ ይመጣል ።

ዳን. ፥ 10 ፥ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእውነት ፡ ጽሑፍ ፡ የተጻፈውን ፡ እነግርኻለኹ ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ከአለቃችኹ ፡ ከሚካኤል ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ የሚያጸናኝ ፡ የለም ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እኔም ፡ በሜዶናዊ ፡ በዳርዮስ ፡ መገ፞መሪያ ፡ ዓመት ፡ አጸናውና ፡ አበረታው ፡ ዘንድ ፡ ቆሜ ፡ ነበር ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 2 ፤ አ፞ኩንም ፡ እውነትን ፡ አሳይ፞ካለ፞ኹ ። እንሆ ፥ ሦስት ፡ ነገሥታት ፡ ደግሞ ፡ በፋርስ ፡ ይነሣሉ ፤ አራተኛውም ፡ ከ፞ሹሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ይ፞ኾናል ፤ በባለጠግነቱም ፡ በበረታ ፡ ጊዜ ፡ በግሪክ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ሹሉን ፡ ያስነሣል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ኀያልም ፡ ንጉሥ ፡ ይነሣል ፥ በትልቅ ፡ አገዛዝም ፡ ይገዛል ፥ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ ያደርጋል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ ይሰበራል ፤ እስከ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ ይከፋፈላል ። ለዘሩ ፡ ግን ፡ አይከፋፈልም ፥ እንደ ፡ ገዛበትም ፡ አገዛዝ ፡ አይ፞ኾንም ፤ መንግሥቱ ፡ ይነቀላልና ፤ ከነዚህም ፡ ለሌላዎች ፡ ይ፞ኾናልና ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 5 ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ከአለቃዎቹም ፡ አንዱ ፡ ይበረታሉ ፤ ርሱም ፡ ይበረታበታል ፡ ይሠለጥንማል ፤ ግዛቱም ፡ ታላቅ ፡ ግዛት ፡ ይ፞ኾናል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ከዘመናትም ፡ በ፟ኋላ ፡ ይጋጠማሉ ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማድረግ ፡ ወደሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ትመጣለች ፤ የክንዷ ፡ ኀይል ፡ ግን ፡ አይጸናም ፥ ርሱና ፡ ክንዱም ፡ አይጸናም ፤ ርሷና ፡ ርሷን ፡ ያመጡ ፡ የወለዳትም ፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ያጸናት ፡ ዐልፈው ፡ ይሰጣሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሥሯ ፡ ቀ፞ጥቋጥ ፡ አንዱ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ወደ ፡ ሰራዊቱም ፡ ይመጣል ፥ ወደሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ዐምባ ፡ ይገባል ፥ በላያቸውም ፡ ያደርጋል ፥ ያሸንፍማል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 8 ፤ አማልክታቸውንና ፡ ቀልጠው ፡ የተሠሩትን ፡ ምስሎቻቸውን ፡ ከብርና ፡ ከወርቅም ፡ የተሠሩትን ፡ የከበሩትን ፡ ዕቃዎች ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይማርካል ፤ እስከ ፡ ጥቂትም ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ሳይዋጋ ፡ ይቀመጣል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ይህም ፡ ወደደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ መንግሥት ፡ ይገባል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደገዛ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ልጆቹም ፡ ይዋጋሉ ፤ ብዙ ፡ ሰራዊትንና ፡ ሕዝብን ፡ ይሰበስባል ፤ ርሱም ፡ ይመጣል ፥ ይጐ፞ርፍማል ፥ ያልፍማል ፤ ተመልሶም ፡ እስከ ፡ ዐምባው ፡ ድረስ ፡ ይዋጋል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 11 ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ ይቈጣል ፡ ወጥቶም ፡ ከሰሜን ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ፤ ብዙ ፡ ሕዝብንም ፡ ለሰልፍ ፡ ያቆማል ፥ ሕዝቡም ፡ ዐልፎ ፡ በእጁ ፡ ይሰጣል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ሕዝቡም ፡ በተወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ልቡ ፡ ይታበያል ፤ አእላፋትንም ፡ ይጥላል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አያሸንፍም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 13 ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመለሳል ፥ ከቀደመውም ፡ የበለጠ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ለሰልፍ ፡ ያቆማል ፤ በዘመናትና ፡ በዓመታትም ፡ ፍጻሜ ፡ ከታላቅ ፡ ሰራዊትና ፡ ከብዙ ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 14 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፤ ከሕዝብ፞ህም ፡ መካከል ፡ የዐመፅ ፡ ልጆች ፡ ራእዩን ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ይነሣሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይወድቃሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 15 ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ይመጣል ፥ ዐፈርንም ፡ ይደለድላል ፥ የተመሸገ፞ችንም ፡ ከተማ ፡ ይወስዳል ፤ የደቡብም ፡ ሰራዊት ፡ የተመረጡትም ፡ ሕዝቡ ፡ አይቆሙም ፤ ለመቋቋምም ፡ ኀይል ፡ የላቸውም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 16 ፤ በርሱም ፡ ላይ ፡ የሚመጣው ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፥ በፊቱም ፡ የሚቆም ፡ የለም ፤ በመልካሚቱም ፡ ምድር ፡ ይቆማል ፥ በእጁም ፡ ውስጥ ፡ ጥፋት ፡ ይ፞ኾናል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ከመንግሥቱም ፡ ኹሉ ፡ ኀይል ፡ ጋራ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ፊቱን ፡ ያቀናል ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድነትን ፡ ያደርጋል ፤ ያረክሳትም ፡ ዘንድ ፡ ሴትን ፡ ልጅ ፡ ይሰጠዋል ፤ ርሷም ፡ አትጸናም ፡ ለርሱም ፡ አትኾንም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ደሴቶች ፡ ይመልሳል ፥ ብዙዎችንም ፡ ይወስዳል ፤ አንድ ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ስድቡን ፡ ይሽራል ፥ ስድቡንም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ፊቱንም ፡ ወደገዛ ፡ ምድሩ ፡ ዐምባዎች ፡ ይመልሳል ፤ ተሰናክሎም ፡ ይወድቃል ፥ አይገኝምም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 20 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በመንግሥቱ ፡ ክብር ፡ መካከል ፡ አስገባሪውን ፡ የሚያሳልፍ ፡ በስፍራው ፡ ይነሣል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቀሣጣው ፡ ሳይኾን ፡ በሰልፍም ፡ ሳይኾን ፡ በጥቂት ፡ ቀን ፡ ይሰበራል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 21 ፤ በርሱም ፡ ስፍራ ፡ የተጠቃ ፡ ሰው ፡ ይነሣል ፡ የመንግሥቱንም ፡ ክብር ፡ አይሰጡትም ፤ በቀስታ ፡ መጥቶ ፡ መንግሥቱን ፡ በማታለል ፡ ይገዛል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 22 ፤ የሚጐርፍም ፡ ሰራዊት ፡ ከፊቱ ፡ ይወሰዳል ፥ ርሱና ፡ የቃል ፡ ኪዳኑ ፡ አለቃ ፡ ይሰበራሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ከተወዳጀ ፡ በኋላ ፥ በተንኰል ፡ ያደርጋል ፤ ከጥቂትም ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ወጥቶ ፡ ይበረታል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 24 ፤ በቀስታ ፡ ከአገር ፡ ኹሉ ፡ ወደለመለመችው ፡ ክፍል ፡ ይገባል ፤ አባቶቹና ፡ የአባቶቹ ፡ አባቶች ፡ ያላደረጉትንም ፡ ያደርጋል ፤ ብዝበዛውንና ፡ ምርኮውንም ፣ ሀብቱንም ፡ በመካከላቸው ፡ ይበትናል ፤ በምሽጎችም ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፡ ዐሳቡን ፡ ይፈጥራል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 25 ፤ በታላቅም ፡ ሰራዊት ፡ ኾኖ ፡ ኀይሉንና ፡ ልቡን ፡ በደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ላይ ፡ ያስነሣል ፤ የደቡብም ፡ ንጉሥ ፡ በታላቅና ፡ በብዙ ፡ ሰራዊት ፡ ኾኖ ፡ በሰልፍ ፡ ይዋጋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐሳብ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይፈጥራሉና ፥ አይጸናም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 26 ፤ መብሉንም ፡ የሚበሉ ፡ ሰዎች ፡ ይሰብሩታል ፤ ሰራዊቱም ፡ ይጐርፋል ፤ ብዙዎችም ፡ ተገድለው ፡ ይወድቃሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 27 ፤ እነዚህም ፡ ኹለት ፡ ነገሥታት ፡ ክፋትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በልባቸው ፡ ያስባሉ ፥ ባንድ ፡ ገበታም ፡ ተቀምጠው ፡ ሐሰት ፡ ይናገራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፍጻሜው ፡ እስከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነውና ፥ አይከናወንላቸውም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ከብዙም ፡ ሀብት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ይመለሳል ፥ ልቡም ፡ በተቀደሰ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ፥ ወደገዛ ፡ ምድሩም ፡ ይመለሳል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 29 ፤ በተወሰነውም ፡ ጊዜ ፡ ይመለሳል ፥ ወደ ፡ ደቡብም ፡ ይመጣል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኋለኛው ፡ እንደ ፡ ፊተኛው ፡ አይኾንም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 30 ፤ የኪቲም ፡ መርከቦች ፡ ይመጡበታልና ፥ ስለዚህ ፡ ዐዝኖ ፡ ይመለሳል ፥ በቅዱሱም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ላይ ፡ ይቈጣል ፥ ፈቃዱንም ፡ ያደርጋል ፤ ተመልሶም ፡ ቅዱሱን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ የተዉትን ፡ ሰዎች ፡ ይመለከታል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሰራዊቶች ፡ ይቆማሉ ፥ መቅደሱንም ፣ ግንቡንም ፡ ያረክሳሉ ፥ የዘወትሩንም ፡ መሥዋዕት ፡ ያስቀራሉ ፥ የጥፋትንም ፡ ርኵሰት ፡ ያቆማሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 32 ፤ ቃል ፡ ኪዳኑን ፡ የሚበድሉትንም ፡ በማታለል ፡ ያስታል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካቸውን ፡ የሚያውቁ ፡ ሕዝብ ፡ ይበረታሉ ፥ ያደርጋሉም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 33 ፤ በሕዝቡም ፡ መካከል ፡ ያሉ ፡ ጥበበኞች ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያስተምራሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰይፍና ፡

በእሳት ፡ ነበልባል ፡ በምርኮና ፡ በመበዝበዝ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ይወድቃሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 34 ፤ በወደቁም ፡ ጊዜ ፡ በጥቂት ፡ ርዳታ ፡ ይረዳሉ ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በግብዝነት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተባብረው ፡ ይሰበሰባሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 35 ፤ እስከተወሰነውም ፡ ዘመን ፡ ይኾናልና ፥ ከጥበበኞቹ ፡ ዐያሌዎቹ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ይነጥሩና ፡ ይጠሩ ፣ ይነጡም ፡ ዘንድ ፡ ይወድቃሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ንጉሡም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ያደርጋል ፤ ራሱንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፥ በአማልክት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ራሱን ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋል ፥ በአማልክትም ፡ አምላክ ፡ ላይ ፡ በትዕቢት ፡ ይናገራል ፤ ቀሣጣም ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ይከናወንለታል ፥ የተወሰነው ፡ ይደረጋልና ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 37 ፤ የአባቶቹንም ፡ አማልክት ፡ የሴቶችንም ፡ ምኞት ፡ አይመለከትም ፤ ራሱንም ፡ በኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ያደርጋልና ፥ አማልክትን ፡ ኹሉ ፡ አይመለከትም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 38 ፤ በእነዚህ ፡ ፋንታ ፡ ግን ፡ የዐምባዎቹን ፡ አምላክ ፡ ያከብራል ፤ አባቶቹም ፡ ያላወቁትን ፡ አምላክ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ በዕንቊና ፡ በከበረ ፡ ነገር ፡ ያከብረዋል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 39 ፤ በእንግዳም ፡ አምላክ ፡ ርዳታ ፡ በጽኑ ፡ ዐምባ ፡ ላይ ፡ ያደርጋል ፤ ለሚያውቁት ፡ ክብር ፡ ያበዛላቸዋል ፥ በብዙም ፡ ላይ ፡ ያስገዛቸዋል ፥ ምድርንም ፡ በዋጋ ፡ ይከፍላል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 40 ፤ በፍጻሜ ፡ ዘመንም ፡ የደቡብ ፡ ንጉሥ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ፤ የሰሜንም ፡ ንጉሥ ፡ ከሠረገላዎችና ፡ ከፈረሰኞች ፡ ከብዙም ፡ መርከቦች ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣበታል ፤ ወደ ፡ አገሮችም ፡ ይገባል ፥ ይጐርፍማል ፥ ያልፍማል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 41 ፤ ወደ ፡ መልካሚቱም ፡ ምድር ፡ ይገባል ፥ ብዙ ፡ አገሮችም ፡ ይወድቃሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኤዶምያስና ፡ ሞዐብ ፡ ከዐሞንም ፡ ልጆች ፡ የበለጡት ፡ ከእጁ ፡ ይድናሉ ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 42 ፤ እጁን ፡ በአገሮች ፡ ላይ ፡ ይዘረጋል ፥ የግብጽም ፡ ምድር ፡ አታመልጥም ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 43 ፤ በወርቅና ፡ በብርም ፡ መዝገብ ፡ ላይ ፥ በከበረችም ፡ በግብጽ ፡ ዕቃ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ይሠለጥናል ፤ የልብያና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎችም ፡ ይከተሉታል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 44 ፤ ከምሥራቅና ፡ ከሰሜን ፡ ግን ፡ ወሬ ፡ ያውከዋል ፤ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ይገድል ፡ ዘንድና ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ በታላቅ ፡ ቀሣጣ ፡ ይወጣል ።

ዳን. ፡ 11 ፡ 45 ፤ ንጉሣዊ ፡ ድንኳኑንም ፡ በባሕርና ፡ በከበረው ፡ በቅዱስ ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ ይተክላል ፤ ወደ ፡ ፍጻሜው ፡ ግን ፡ ይመጣል ፥ ማንም ፡ አይረዳውም ።

ትንቢተ ፡ ዳንኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ስለሕዝብኽ ፡ ልጆች ፡ የሚቆመው ፡ ታላቁ ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል ፡ ይነሣል ፤ ሕዝብም ፡ ከኾነ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚያ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፡ ያልኾነ ፡ የመከራ ፡ ዘመን ፡ ይኾናል ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ በመጽሐፉ ፡ ተጽፎ ፡ የተገኘው ፡ ሕዝብኽ ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ይድናል ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 2 ፤ በምድርም ፡ ትቢያ ፡ ውስጥ ፡ ካንቀላፉቱ ፡ ብዙዎች ፡ ይነቃሉ ፤ እኩሌታዎቹ ፡ ወደዘለዓለም ፡ ሕይወት ፥ እኩሌታዎቹም ፡ ወደ ፡ ዕፍረትና ፡ ወደዘለዓለም ፡ ጕስቊልና ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ጥበበኞቹም ፡ እንደሰማይ ፡ ጸዳል ፥ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ወደ ፡ ጽድቅ ፡ የሚመልሱ ፡ እንደ ፡

ከዋክብት ፡ ለዘለዓለም ፡ ይደምቃሉ ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ቃሉን ፡ ዝጋ ፥ መጽሐፉንም ፡ ዐትም ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይመረምራሉ ፥ ዕውቀትም ፡ ይበዛል ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 5 ፤ እኔም ፡ ዳንኤል ፡ አየኹ ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ሌላዎች ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥ አንዱ ፡ በዚህ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፥ ሌላውም ፡ በዚያ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 6 ፤ አንዱም ፡ ከወንዙ ፡ ውሃ ፡ በላይ ፡ የነበረውን ፡ በፍታም ፡ የለበሰውን ፦ የዚህ ፡ ድንቅ ፡ ፍጻሜ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ አለው ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ከወንዙም ፡ ውሃ ፡ በላይ ፡ የነበረው ፡ በፍታም ፡ የለበሰው ፡ ሰው ፡ ቀኝና ፡ ግራ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አንሥቶ ፦ ለዘመንና ፡ ለዘመናት ፡ ለዘመንም ፡ እኩሌታ ፡ ነው ፤ የተቀደሰውም ፡ ሕዝብ ፡ ኀይል ፡ መበተን ፡ በተጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸማል ፡ ብሎ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ በሚኖረው ፡ ሲምል ፡ ሰማኹ ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ሰማኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላስተዋልኹም ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ የዚህ ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አልኹ ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳንኤል ፡ ሆይ ፥ ቃሉ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተዘጋና ፡ የታተመ ፡ ነውና ፥ ኺድ ፤

ዳን. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰውነታቸውን ፡ ያጠራሉ ፥ ያነጡማል ፥ ይነጥሩማል ፤ ክፉዎች ፡ ግን ፡ ክፋትን ፡ ያደርጋሉ ፤ ክፉዎችም ፡ ኹሉ ፡ አያስተውሉም ፥ ጥበበኞች ፡ ግን ፡ ያስተውላሉ ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 11 ፤ የዘወትሩም ፡ መሥዋዕት ፡ ከቀረ ፡ ዠምሮ ፥ የጥፋትም ፡ ርኵሰት ፡ ከቆመ ፡ ዠምሮ ፡ ሺሕ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ዘጠና ፡ ቀን ፡ ይኾናል ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 12 ፤ የሚታገሥ ፥ እስከ ፡ ሺሕ ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዐምስት ፡ ቀንም ፡ የሚደርስ ፡ ምስጉን ፡ ነው ።

ዳን. ፡ 12 ፡ 13 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፍጻሜው ፡ ድረስ ፡ ኺድ ፤ አንተም ፡ ታርፋለኽ ፥ በቀኑም ፡ መጨረሻ ፡ በዕጣ ፡ ክፍልኽ ፡ ትቆማለኽ ፞

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ በዖዝያንና ፡ በኢዮአታም ፡ በአካዝና ፡ በሕዝቅያስም ፡ ዘመን ፡ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በዮአስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ዘመን ፡ ወደብኤሪ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሆሴዕ ፡ የመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ መገሥመሪያ ፡ በሆሴዕ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሆሴዕን ፦ ምድሪቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ርቃ ፡ ታላቅ ፡ ግልሙትና ፡ ታደርጋለችና ፡ ኺድ ፤ ጋለሞታን ፡ ሴትና ፡ የግልሙትናን ፡ ልጆች ፡ ለአንተ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ርሱም ፡ ኼዶ ፡ የዴቤላይምን ፡ ልጅ ፡ ጎሜርን ፡ አገባ ፤ ርሷም ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደችለት ።

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ከጥቂት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ የኢይዝራኤልን ፡ ደም ፡ በኢዩ ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እበቀላለኹና ፥ ከእስራኤልም ፡ ቤት ፡ መንግሥትን ፡ እሽራለኹና ፡ ስሙን ፡ ኢይዝራኤል ፡ ብለኽ ፡ ጥራው ፤

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በኢይዝራኤል ፡ ሸለቆ ፡ ውስጥ ፡ የእስራኤልን ፡ ቀስት ፡ እሰብራለኹ ፡ አለው ።

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ደግሞ ፡ ፀነሰች ፡ ሴት ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ። እግዚአብሔርም ፦ ይቅር ፡ እላቸው ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አልምርምና ፡ ስሟን ፡ ሎሩሃማ ፡ ብለኽ ፡ ጥራት ፤

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ እምራለኹ ፤ በአምላካቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አድናቸዋለኹ ፡ እንጂ ፡ በቀስት ፡ ወይም ፡ በሰይፍ ፡ ወይም ፡ በሰልፍ ፡ ወይም ፡ በፈረሶች ፡ ወይም ፡ በፈረሰኞች ፡ አላድናቸውም ፡ አለው ።

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ሎሩሃማም ፡ ጡት ፡ ባስጣለች ፡ ጊዜ ፥ ደግሞ ፡ ፀነሰች ፡ ወንድ ፡ ልጅንም ፡ ወለደች ።

ሆሴ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ሕዝቤ ፡ አይደላችኹምና ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ አልኾናችኹምና ፡ ስሙን ፡ ሎዓሚ ፡ ብለኽ ፡ ጥራው ፡ አለው ።

_____ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ሆሴ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ የእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡ እንደማይሰፈርና ፡ እንደማይቈጠር ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይኾናል ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ እናንተ ፡ ሕዝቤ ፡ አይደላችኹም ፡ ተብሎ ፡ በተነገረበት ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ የሕያው ፡ አምላክ ፡ ልጆች ፡ ይባላሉ ።

ሆሴ. ፥ 2 ፥ 2 ፤ የይሁዳ ፡ ልጆችና ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ በአንድነት ፡ ይሰበሰባሉ ፥ ለእነርሱም ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ ይሾማሉ ፥ ከምድሪቱም ፡ ይወጣሉ ፤ የኢይዝራኤል ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ።

ሆሴ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ ወንድሞቻችኹን ፦ ዓሚ ፥ እኅቶቻችኹንም ፦ ሩሃማ ፡ በሏቸው ።

ሆሴ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ እናታችኹ ፡ ሚስቴ ፡ አይደለችምና ፥ እኔም ፡ ባሏ ፡ አይደለኹምና ፡ ተሟገቱ ፤ ከእናታችኹ ፡ ጋራ ፡ ተሟገቱ ። ግልሙትናዋን ፡ ከፊቷ ፥ ምንዝርናዋንም ፡ ከጡቶቿ ፡ መካከል ፡ ታስወግድ ፤

ሆሴ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ ዕራቍቷን ፡ እንዳልገፋት ፥ እንደተወለደችበትም ፡ ቀን ፡ እንዳላደርጋት ፥ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳና ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ምድር ፡ እንዳላደርጋት ፥ በጥማትም ፡ እንዳልገድላት ፤

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ የግልሙትናዋ ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፥ ልጆቿን ፡ አልምርም ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እናታቸው ፡ አመንዝራለች ፤ የፀነሰቻቸውም ፦ እንጀራዬንና ፡ ውሃዬን ፥ ጥጤንና ፡ የተልባ ፡ እግሬን ፥ ዘይቴንና ፡ መጠጤን ፡ ከሚሰጡኝ ፡ ከውሽማዎቼ ፡ በኋላ ፡ እኼዳለኹ ፡ ብላ ፡ አስነወረቻቸው ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ መንገድሽን ፡ በሾክ ፡ እዘጋለኹ ፥ መንገዷንም ፡ እንዳታገኝ ፡ ቅጥርን ፡ እቀጥርባታለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ውሽማዎቿንም ፡ ትከተላለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትደርስባቸውም ፤ ትፈልጋቸውማለች ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አታገኛቸውም ፤ ርሷም ፦ ከዛሬ ፡ ይልቅ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ይሻለኝ ፡ ነበርና ፥ ተመልሼ ፡ ወደቀደመው ፡ ባሌ ፡ እኼዳለኹ ፡ ትላለች ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ርሷም ፡ እኽልንና ፡ ወይንን ፡ ጠጅ ፡ ዘይትንም ፡ የሰጠኋት ፥ ለበዓልም ፡ የተሠራውን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ያበዛኹላት ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አላወቀችም ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እኽሌን ፡ በጊዜዋ ፥ ወይን ፡ ጠጄንም ፡ በወረቷ ፡ እወስዳለኹ ፥ ዕራቍትነቷንም ፡ እንዳትሸፍን ፡ ጥጤንና ፡ የተልባ ፡ እግሬን ፡ እገፈፍታለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ አኹንም ፡ ውሽማዎቿ ፡ እያዩ ፡ ነውሯን ፡ እገልጣለኹ ፤ ከእጄም ፡ ማንም ፡ አያድናትም ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ደስታዋንም ፡ ሹሉ ፥ በዓላቷንም ፥ መባቻዎቿንም ፥ ሰንበቶቿንም ፥ የተቀደሱትንም ፡ ጉባኤዎችን ፡ ሹሉ ፡ አስቀራለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ርሷም ፦ ውሽማዎቼ ፡ የሰጡኝ ፡ ዋጋዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ያለችውን ፡ ወይኗንና ፡ በለሷን ፡ አጠፋለኹ ፤ ዱርም ፡ አደርገዋለኹ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አራዊት ፡ ይበሉታል ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እኔን ፡ ረስታ ፡ ውሽማዎቿን ፡ እየተከተለች ፥ በጕትቾቿና ፡ በጌጧም ፡ እያጌጠች ፡ ለበዓሊም ፡ ያጠነችበትን ፡ ወራት ፡ እበቀልባታለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ አባብላታለኹ ፥ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ አመጣታለኹ ፥ ለልቧም ፡ እናገራለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ከዚያም ፡ የወይን ፡ ቦታዋን ፥ የተስፋ ፡ በርም ፡ እንዲኾንላት ፡ የዐኮርን ፡ ሸለቆ ፡ እሰጣታለኹ ፤ በዚያም ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ወጣችበት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሕፃንነቷ ፡ ወራት ፡ ትዘምራለች ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ባሌ ፡ ብለሽ ፡ ትጠሪኛለሽ ፡ እንጂ ፡ ዳግመኛ ፡ በኣሌ ፡ ብለሽ ፡ አትጠሪኝም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ የበዓሊምን ፡ ስም ፡ ከአፏ ፡ አስወግደዋለኹና ፥ በስማቸውም ፡ እንግዲህ ፡ አይታሰቡምና ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ከመሬትም ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አደርግላቸዋለኹ ፤ ቀስትንና ፡ ሰይፍን ፡ ሰልፍንም ፡ ከምድሩ ፡ እሰብራለኹ ፥ ተከልለውም ፡ እንዲኖሩ ፡ አስተኛቸዋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ለዘለዓለምም ፡ ለእኔ ፡ እንድትኾኚ ፡ ዐጭሻለኹ ፤ በጽድቅና ፡ በፍርድ ፡ በምሕረትና ፡ በርኅራኄ ፡ ዐጭሻለኹ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ለኔም ፡ እንድትኾኚ ፡ በመታመን ፡ ዐጭሻለኹ ፤ አንቺም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታውቂያለሽ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እመልሳለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ለሰማይ ፡ እመልሳለኹ ፥ ሰማይም ፡ ለምድር ፡ ይመልሳል ፤

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ምድርም ፡ ለእኽልና ፡ ለወይን ፡ ጠጅ ፡ ለዘይትም ፡ ትመልሳለች ፤ እነርሱም ፡ ለኢይዝራኤል ፡ ይመልሳሉ ።

ሆሴ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ለእኔ ፡ እዘራታለኹ ፤ ምሕረትም ፡ የሌላትን ፡ እምራለኹ ፥ ሕዝቤም ፡ ያልኾነውን ፦ አንተ ፡ ሕዝቤ ፡ ነኽ ፡ እለዋለኹ ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ አምላኬ ፡ ነኽ ፡ ይለኛል ።

_____ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ሆሴ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፦ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ ሌላዎች ፡ አማልክት ፡ ቢመለሱና ፡ የዘቢብ ፡ ጥፍጥፍን ፡ ቢወዱ ፡ እንኳ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንደሚወዳቸው ፡ አንተም ፡ ውሽማዋን ፡ የምትወዲውን ፡ አመንዝራዪትን ፡ ሴት ፡ ውደድ ፡ አለኝ ።

ሆሴ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ እኔም ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ብርና ፡ ባንድ ፡ ቆሮስ ፡ መስፈሪያ ፡ ተኩል ፡ ገብስ ፡ ገዛኋት ።

ሆሴ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ተቀመጪ ፥ አታመንዝሪም ፥ ለሌላ ፡ ሰውም ፡ አትኹኚ ፤ እኔም ፡ እንዲሁ ፡ እኾንልሻለኹ ፡ አልኋት ።

ሆሴ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ያለንጉሥና ፡ ያለአለቃ ፥ ያለመሥዋዕትና ፡ ያለዐምድ ፥ ያለኤፉድና ፡ ያለተራፊም ፡ ብዙ ፡ ወራት ፡ ይቀመጣሉና ፤

ሆሴ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ተመልሰው ፡ አምላካቸውን ፡ እግዚአብሔርንና ፡ ንጉሣቸውን ፡ ዳዊትን ፡ ይፈልጋሉ ፤ በኋለኛውም ፡ ዘመን ፡ ፈርተው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ወደ ፡ በረከቱ ፡ ይመጣሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እውነትና ፡ ምሕረት ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ማወቅ ፡ በምድር ፡ ስለሌለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድሩ ፡ ላይ ፡ ከሚኖሩ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ርግማንና ፡ ሐሰት ፡ ግዳይና ፡ ስርቆት ፡ ምንዝርናም ፡ ወጥተዋል ፤ ደምም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ደርሷል ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ምድሪቱ ፡ ታለቅሳለች ፥ በርሷም ፡ የሚቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ ከምድር ፡ አራዊትና ፡ ከሰማይ ፡ ወፎች ፡ ጋራ ፡ ይደክማሉ ፤ የባሕሩም ፡ ዓሣዎች ፡ ያልቃሉ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕዝብኽ ፡ ከካህን ፡ ጋራ ፡ እንደሚከራከሩ ፡ ናቸውና ፥ ማንም ፡ አይከራከር ፥ ማንም ፡ አይገሥፍ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ በቀንም ፡ ትሰናከላለኽ ፥ ነቢዩም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በሌሊት ፡ ይሰናከላል ፤ እናትኽንም ፡ አጠፋታለኹ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ሕዝቤ ፡ ዕውቀት ፡ ከማጣቱ ፡ የተነሣ ፡ ጠፍቷል ፤ አንተም ፡ ዕውቀትን ፡ ጠልተኻልና ፥ እኔ ፡ ካህን ፡ እንዳትኾነኝ ፡ እጠላኻለኹ ፤ የአምላክኽንም ፡ ሕግ ፡ ረስተኻልና ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ልጆችኽን ፡ እረሳለኹ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ ብዛታቸው ፡ መጠን ፡ ኀጢአት ፡ ሠሩብኝ ፤ እኔም ፡ ክብራቸውን ፡ ወደ ፡ ነውር ፡ እለውጣለኹ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ የሕዝቤም ፡ ኀጢአት ፡ መብል ፡ ኾኖላቸዋል ፥ ልባቸውንም ፡ ወደ ፡ በደላቸው ፡ አድርገዋል ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እንደ ፡ ሕዝቡም ፡ እንዲሁ ፡ ካህኑ ፡ ይኾናል ፤ በመንገዳቸውም ፡ እበቀላቸዋለኹ ፥ ሥራቸውንም ፡ እመልስባቸዋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ መጠበቅ ፡ ትተዋልና ፥ ሲበሉ ፡ አይጠግቡም ፥ ሲያመነዝሩም ፡ አይበዙም ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ግልሙትናና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ስካርም ፡ አእምሮን ፡ ያጠፋል ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ የግልሙትና ፡ መንፈስ ፡ ሕዝቤን ፡ አስቷቸዋልና ፥ እነርሱም ፡ ከአምላካቸው ፡ ርቀው ፡ አመንዝረዋልና ፥ በትራቸውን ፡ ይጠይቃሉ ፥ ዘንጋቸውም ፡ ይመልስላቸዋል ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ በተራራዎችም ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ይሠዋሉ ፤ ጥላውም ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ከኮምበልና ፡ ከልብን ፣ ከአሆማም ፡ ዛፍ ፡ በታች ፡ በኰረብታዎች ፡ ላይ ፡ ያጥናሉ ፤ ስለዚህ ፥ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹ ፡ ይገለሙታሉ ፥ ሙሽሮቻችኹም ፡ ያመነዝራሉ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ወንዶችም ፡ ደግሞ ፡ ከጋለሞታዎች ፡ ጋራ ፡ ይጫወታሉና ፥ ከጋለሞታዎችም ፡ ጋራ ፡ ይሠዋሉና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹ ፡ በገለሞቱ ፡ ጊዜ ፥ ሙሽሮቻችኹም ፡ ባመነዘሩ ፡ ጊዜ ፡ አልቀጣቸውም ፤ የማያስተውልም ፡ ሕዝብ ፡ ይገለበጣል ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ብታመነዝር ፡ ይሁዳ ፡ አይበድል ፤ እናንተም ፡ ወደ ፡ ገልገላ ፡ አትግቡ ፥ ወደ ፡ ቤትአዌንም ፡ አትውጡ ፥ ወይም ፦ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን! ፡ ብላችኹ ፡ አትማሉ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ እስራኤል ፡ እንደ ፡ እልከኛ ፡ ጊደር ፡ እንቢ ፡ ብሏል ፤ እግዚአብሔርስ ፡ በሰፊው ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ጠቦት ፡ ያሰማራዋልን ፧

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ኤፍሬም ፡ ከጣዖታት ፡ ጋራ ፡ ተጋጠመ ፤ ተወው ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ስካርን ፡ ፈጽመዋል ፥ ግልሙትናንም ፡ አብዝተዋል ፤ አለቃዎቿም ፡ ነውርን ፡ እጅግ ፡ ወደዱ ።

ሆሴ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ነፋስ ፡ በክንፏ ፡ አስሯታል ፤ ከመሥዋዕታቸውም ፡ የተነሣ ፡ ያፍራሉ ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ አድምጡ ፤ የንጉሥ ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ ልብ ፡ አድርጉ ፤ በምጽጻ ፡ ላይ ፡ ወጥመድ ፥ በታቦርም ፡ ላይ ፡ የተዘረጋ ፡ አሽክላ ፡ ኾናችኋልና ፥ ፍርድ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ዐመፀኞችም ፡ ዕርድ ፡ አብዝተዋል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እነዚያን ፡ ኹሉ ፡ እዘልፋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ኤፍሬምን ፡ ዐውቀዋለኹ ፥ እስራኤልም ፡ ከእኔ ፡ አልተሰወረም ፤ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡ አመንዝረኻል ፥ እስራኤልም ፡ ረክሷል ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሥራቸውን ፡ አላቀኑም ፤ የግልሙትና ፡ መንፈስ ፡ በውስጣቸው ፡ አለና ፤ እግዚአብሔርንም ፡ አላወቁምና ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ የእስራኤልም ፡ ትዕቢት ፡ በፊቱ ፡ ይመሰክራል ፤ ስለዚህ ፥ እስራኤልና ፡ ኤፍሬም ፡ በኀጢአታቸው ፡ ይሰናከላሉ ፤ ይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ይሰናከላል ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ለመሻት ፡ በጎቻቸውንና ፡ ላሞቻቸውን ፡ ነድተው ፡ ይኼዳሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ ከነርሱም ፡ ተመልሷልና ፥ አያገኙትም ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ዲቃላዎችን ፡ ልጆች ፡ ወልደዋልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ ወንጅለዋል ፤ አኹንም ፡ አንድ ፡ ወር ፡ እነርሱንና ፡ ርስታቸውን ፡ ይበላቸዋል ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ በጊብዓ ፡ መለከትን ፥ በራማ ፡ እንቢልታን ፡ ንፉና ፦ ብንያም ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ በኋላ ፥ እያላችኹ ፡ በቤትአዌን ፡ ላይ ፡ እሪ ፡ በሉ ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ኤፍሬም ፡ በዘለፋ ፡ ቀን ፡ የፈረሰ ፡ ይኾናል ። በእስራኤል ፡ ነገዶች ፡ ዘንድ ፡ በርግጥ ፡ የሚኾነውን ፡ ነገር ፡ ገልጣለኹ ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ የይሁዳ ፡ አለቃዎች ፡ ድንበርን ፡ እንደሚነቅሉ ፡ ኾነዋል ፤ እኔም ፡ መዓቴን ፡ እንደ ፡ ውሃ ፡ አፈስባቸዋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ኤፍሬም ፡ ከትእዛዝ ፡ በኋላ ፡ መኼድን ፡ ወዷልና ፥ የተገፋና ፡ በፍርድ ፡ የተጐዳ ፡ ኾኗል ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እኔም ፡ ለኤፍሬም ፡ እንደ ፡ ብል ፥ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ነቀዝ ፡ ኾኖለኹ ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ኤፍሬምም ፡ ደዌውን ፥ ይሁዳም ፡ ቍስሉን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ኤፍሬም ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ኼደ ፡ ወደ ፡ ንጉሡም ፡ ወደ ፡ ኢያሪም ፡ መልእክተኛን ፡ ላከ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይፈውሳችኹ ፡ ዘንድ ፥ ከቍስላችኹም ፡ ያድናችኹ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ እኔም ፡ ለኤፍሬም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፥ ለይሁዳም ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦል ፡ እኾናለኹና ፤ እኔም ፡ ነጥቄ ፡ እኼዳለኹ ፡ እወስድማለኹ ፥ የሚያድንም ፡ አይገኝም ።

ሆሴ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ በደላቸውንም ፡ እስኪያውቁ ፡ ድረስ ፥ ፊቴንም ፡ እስኪሹ ፡ ድረስ ፡ ኼጄ ፡ ወደ ፡ ስፍራዬ ፡ እመለሳለኹ ፤ በመከራቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አድርገው ፡ ፊቴን ፡ ይፈልጋሉ ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ኑ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንመለስ ፤ ርሱ ፡ ሰብሮናልና ፥ ርሱም ፡ ይፈውሰናል ፤ ርሱ ፡ መቶናል ፥ ርሱም ፡ ይጠግነናል ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ከኹለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ያድነናል ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ያስነሣናል ፥ በፊቱም ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እንወቅ ፤ እናውቀውም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንከተል ፤ እንደ ፡ ወገግታም ፡ ተዘጋጅቶ ፡ እናገኘዋለን ፤ እንደ ፡ ዝናብም ፡ ምድርንም ፡ እንደሚያጠጣ ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ ዝናብ ፡ ይመጣል ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ምሕረታችኹ ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ደመና ፥ በማለዳም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ጠል ፡ ነውና ፥ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላድርግልኽ ፧ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላድርግልኽ ፧

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ በነቢያት ፡ እጅ ፡ ቈረጥኋቸው ፥ በአፌም ፡ ቃል ፡ ገደልኋቸው ፤ ፍርዴም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ይወጣል ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ከመሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ ምሕረትን ፥ ከሚቃጠልም ፡ መሥዋዕት ፡ ይልቅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማወቅ ፡ እወዳለኹና ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ ቃል ፡ ኪዳንን ፡ ተላልፈዋል ፤ በዚያም ፡ ላይ ፡ ወንጀለውኛል ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ገለዓድ ፡ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ከተማ ፥ በደምም ፡ የተቀባ ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ለሰውም ፡ እንደሚያደቡ ፡ ወንበዴዎች ፥ እንዲሁ ፡ የካህናት ፡ ወገኖች ፡ በሴኬም ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ይገድላሉ ፤ ሴሰኝነትንም ፡ ያደርጋሉ ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ የሚያስፈራን ፡ ነገር ፡ አይቻለኹ ፤ በዚያ ፡ በኤፍሬም ፡ ውስጥ ፡ ግልሙትና ፡ ተገኘ ፥ እስራኤልም ፡ ረክሷል ።

ሆሴ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ የሕዝቤን ፡ ምርኮ ፡ በምመልስበት ፡ ጊዜ ፡ ለአንተ ፡ ደግሞ ፡ መከር ፡ ተወስኖልኻል ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ በሐሰት ፡ አድርገዋልና ፥ ሌባም ፡ ገብቷልና ፥ በውጭም ፡ ወንበዴዎች ፡ ቀምተዋልና ፥ እስራኤልን ፡ እፈውስ ፡ ዘንድ ፡ በወደድኹ ፡ ጊዜ ፡ የኤፍሬም ፡ ኀጢአትና ፡ የሰማርያ ፡ ክፋት ፡ ተገለጠ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ እኔም ፡ ክፋታቸውን ፡ ኹሉ ፡ እንዳሰብኹ ፡ በልባቸው ፡ አያስቡም ፡ አኹንም ፡ ሥራቸው ፡ ከዋቸዋለች ፥ በፊቴም ፡ አለች ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ንጉሡን ፡ በክፋታቸው ፥ አለቃዎቹንም ፡ በሐሰታቸው ፡ ደስ ፡ አሰኝተዋል ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ኹሉም ፡ አመንዝራዎች ፡ ናቸው ፤ ጋጋሪ ፡ እንደሚያነድ፡ት ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ናቸው ፤ ኹሉ ፡ እስኪቦካ ፡ ድረስ ፡ እሳትን ፡ መቈስቈስና ፡ ርሾን ፡ መለወስ ፡ ይቈያል ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ በንጉሣችን ፡ ቀን ፡ አለቃዎች ፡ ከወይን ፡ ጠጅ ፡ ሙቀት ፡ የተነሣ ፡ ታመሙ ፤ ርሱም ፡ ከዋዘኞች ፡ ጋራ ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ እያደቡ ፡ ልባቸውን ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ አዘጋጅተዋል ፤ አበዛቸውም ፡ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ አንቀላፋ ፤ በጠባም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ይነዳል ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ምድጃ ፡ ግለዋል ፥ ፈራጆቻቸውንም ፡ በሉ ፤ ነገሥታታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ወደቁ ፤ ከነርሱም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚጮኽ ፡ የለም ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ኤፍሬም ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቀ ፤ ኤፍሬም ፡ እንዳልተገላበጠ ፡ ቂጣ ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ እንግዳዎች ፡ ጕልበቱን ፡ በሉት ፥ ርሱም ፡ አላወቀም ፤ ሽበትም ፡ ወጣበት ፥ ርሱም ፡ አላወቀም ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ የእስራኤልም ፡ ትዕቢቱ ፡ በፊቱ ፡ መሰከረ ፤ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አልተመለሱም ፥ በዚህም ፡ ኹሉ ፡ አልፈለጉትም ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ኤፍሬምም ፡ አእምሮ ፡ እንደሌላት ፡ እንደ ፡ ሰነፍ ፡ ርግብ ፡ ነው ፤ ግብጽን ፡ ጠሩ ፥ ወደ ፡ አሶርም ፡ ኼዱ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ሲኼዱ ፡ አሽክላዬን ፡ እዘረጋባቸዋለኹ ፤ እንደሰማይ ፡ ወፎች ፡ አወርዳቸዋለኹ ፤ መከራቸውን ፡ ሰሰሙ ፡ እገሥጻቸዋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ከእኔ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋልና ፥ ወዮላቸው! ፡ በእኔም ፡ ላይ ፡ ዐምፀዋልና ፥ ጥፋት ፡ ይምጣባቸው! ፡ እኔ ፡ ልታደጋቸው ፡ ወደድኹ ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ በሐሰት ፡ ተናገሩብኝ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ በመኝታቸው ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ ያለቅሱ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በልባቸው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልጮኹም ፤ ስለ ፡ እኽልና ፡ ስለ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ነበር ፤ በእኔም ፡ ላይ ፡ ዐመፁ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ እኔም ፡ ክንዳቸውን ፡ አስተማርኹና ፡ አጸናኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ መከሩብኝ ።

ሆሴ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ተመለሱ ፤ እንደ ፡ ተንኰለኛ ፡ ቀስት ፡ ኾኑ ፤ አለቃዎቻቸው ፡ ከምላሳቸው ፡

ቀ-ጣ ፡ የተነሣ ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፤ ይህ ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ ውስጥ ፡ መሳለቂያ ፡ ይኾንባቸዋል ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 1 ፤ መለከትን ፡ ወደ ፡ አፍኽ ፡ አቅርብ ፤ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ ተላልፈዋልና ፥ በሕጌም ፡ ላይ ፡ ዐምፀዋልና ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ ይመጣል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 2 ፤ እነርሱም ፦ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እኛ ፡ እስራኤል ፡ ዐወቅንኽ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይጮኻሉ ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 3 ፤ እስራኤል ፡ ደግነትን ፡ ጥሏል ፤ ጠላትም ፡ ያሳድዱታል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 4 ፤ ለራሳቸው ፡ ነገሥታትን ፡ አነገሡ ፥ ከእኔም ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፤ አለቃዎችንም ፡ አደረጉ ፥ እኔም ፡ አላወቅኹም ፤ ለጥፋታቸውም ፡ ከብራቸውና ፡ ከወርቃቸው ፤ ጣዖታትን ፡ ለራሳቸው ፡ አደረጉ ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 5 ፤ ሰማርያ ፡ ሆይ ፥ እንቦሳኽን ፤ ጥሏል ፤ ቀ-ጣዬ ፡ በላያቸው ፡ ነዷል ፤ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ንጹሕ ፡ ሊኾኑ ፡ አይችሉም ፧

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 6 ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤ ሠራተኛ ፡ ሠራው ፥ ርሱም ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፤ የሰማርያም ፡ እንቦሳ ፡ ይቈራረጣል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 7 ፤ ነፍስን ፡ ዘርተዋል ፥ ዐውሎ ፡ ነፍስንም ፡ ያጭዳሉ ፤ አገዳ ፡ የለውም ፥ ከፍሬውም ፡ ዱቄት ፡ አይገኝም ፤ ቢገኝም ፡ እንግዳዎች ፡ ይበሉታል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 8 ፤ እስራኤል ፡ ተውጧል ፥ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ዛሬ ፡ እንደ ፡ ረከሰ ፡ ዕቃ ፡ ኾኗል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 9 ፤ ለብቻውም ፡ እንደሚቀመጥ ፡ እንደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አህያ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ወጥተዋል ፤ ኤፍሬምም ፡ ወዳጆቹን ፡ በእጅ ፡ መንሻ ፡ ገዛ ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለአሕዛብ ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ቢሰጡ ፡ እኔ ፡ አኹን ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ከንጉሥና ፡ ከአለቃዎችም ፡ ሸክም ፡ የተነሣ ፡ ይደክማሉ ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 11 ፤ ኤፍሬም ፡ ኀጢአትን ፡ ለመሥራት ፡ መሠዊያ ፡ አብዝቷልና ፥ መሠዊያ ፡ ለኀጢአት ፡ ይኾንለታል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ የሕጌን ፡ ብዛት ፡ ጽፌለታለኹ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ቈጥረውታል ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ መሥዋዕቴን ፡ ያቀርባሉ ፥ ሥጋንም ፡ ያርዳሉ ፥ ይበላሉም ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አይቀበላቸውም ፤ በደላቸውንም ፡ ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይቀጣል ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ይመለሳሉ ።

ሆሴ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ እስራኤል ፡ ፈጣሪውን ፡ ረስቷል ፥ መስገጃዎችንም ፡ ሠርቷል ፤ ይሁዳም ፡ የተመሸጉትን ፡ ከተማዎች ፡ አብዝቷል ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በከተማዎች ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለኹ ፥ አዳራሾችንም ፡ ትበላለች ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ከአምላክኽ ፡ ተለይተኽ ፡ አመንዝረኻልና ፥ እንደ ፡ አሕዛብ ፡ ደስ ፡ አይበልኽ ፥ ሐሴትንም ፡ አታድርግ ፤ በእኽሉ ፡ ዐውድማ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ የግልሙትናን ፡ ዋጋ ፡ ወደኻል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 2 ፤ ዐውድማውና ፡ መጥመቂያው ፡ አይመግባቸውም ፥ ጕሽ ፡ ጠጅም ፡ ይጐድልባታል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 3 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አይቀመጡም ፤ ኤፍሬምም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡

ይመለሳል ፥ በአሶርም ፡ ርኩስን ፡ ነገር ፡ ይበላሉ ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 4 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ የወይን ፡ ጠጅን ፡ ቍርባን ፡ አያፈሱም ፥ መሥዋዕታቸውም ፡ ደስ ፡ አያሠኘውም ፤ የሐዘንም ፡ እንጀራ ፡ ይኾንላቸዋል ፥ የሚበላውም ፡ ኹሉ ፡ ይረክሳል ፤ እንጀራቸውም ፡ ለሰውነታቸው ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ አይገባም ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 5 ፤ በዓመት ፡ በዓል ፡ ቀንና ፡ በእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 6 ፤ እንሆ ፥ ከጥፋት ፡ ሸሽተው ፡ ኼዱ ፥ ግብጽም ፡ ትሰበስባቸዋለች ፥ ሜምፎስም ፡ ትቀብራቸዋለች ፤ ሳማም ፡ የብራቸውን ፡ ጌጥ ፡ ይወርሳል ፥ ሾኽም ፡ በድንኳኖቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበቅላል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 7 ፤ የበቀል ፡ ወራት ፡ መጥቷል ፥ የፍዳም ፡ ወራት ፡ ደርሷል ፥ እስራኤልም ፡ ያውቃል ፤ ከኀጢአትኽና ፡ ከጠላትነትኽ ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ነቢዩ ፡ ሰንፏል ፥ መንፈስም ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ አብዷል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 8 ፤ ኤፍሬም ፡ ከአምላኬ ፡ ጋራ ፡ ተመልካች ፡ ነበረ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ነቢዩ ፡ በመንገዱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የወፍ ፡ ወጥመድ ፡ ኾነ ፥ በአምላኩም ፡ ቤት ፡ ጠላትነት ፡ አለ ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 9 ፤ በጊብዓ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ ረከሱ ፤ ርሱም ፡ በደላቸውን ፡ ያስባል ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ይበቀላል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 10 ፤ እስራኤልን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንዳለ ፡ ወይን ፡ ኾኖ ፡ አገኘኹት ፤ አባቶቻችኹንም ፡ ከመዠመሪያዋ ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ በኵራት ፡ ኾነው ፡ አየኋቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ብዔልፌጎር ፡ መጡ ፥ ለነውርም ፡ ተለዩ ፥ እንደ ፡ ወደዱትም ፡ ርኩስ ፡ ኾኑ ፥

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 11 ፤ የኤፍሬምም ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ በሮ ፡ ይጠፋል ፤ መውለድና ፡ መፅነስ ፡ ማርገዝም ፡ አይኾንላቸውም ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 12 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ ቢያሳድጉ ፡ ሰው ፡ እንዳይቀርላቸው ፡ ልጅ ፡ አልባ ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ ከነርሱም ፡ በራቅኹ ፡ ጊዜ ፡ ወዮላቸው! ፡

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ እኔ ፡ እንዳየኹ ፡ የኤፍሬም ፡ ልጆች ፡ ለምርኮ ፡ ተሰጥተዋል ፤ ኤፍሬምም ፡ ልጆቹን ፡ ወደ ፡ ገዳዩች ፡ ያወጣል ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ አቤቱ ፥ ስጣቸው ፤ ምን ፡ ትሰጣቸዋለኽ ፧ የሚጨነግፍን ፡ ማሕፀን ፡ የደረቀውንም ፡ ጡት ፡ ስጣቸው ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ ክፋታቸው ፡ ኹሉ ፡ በገልገላ ፡ አለ ፤ በዚያ ፡ ጠልቻቸዋለኹ ፤ ስለሠሩት ፡ ክፋት ፡ ከቤቴ ፡ አሳድዳቸዋለኹ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አልወዳቸውም ፤ አለቃዎቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ዐመፀኞች ፡ ናቸው ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 16 ፤ ኤፍሬም ፡ ተመታ ፥ ሥሩም ፡ ደረቀ ፥ ፍሬም ፡ አያፈራም ፤ ደግሞም ፡ ቢወልዱ ፡ የማሕፀናቸውን ፡ ፍሬ ፡ እገድላለኹ ።

ሆሴ. ፥ 9 ፥ 17 ፤ አልሰሙትምና ፡ አምላኬ ፡ ይጥላቸዋል ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ተቅበዝባዥች ፡ ይኾናሉ ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 1 ፤ እስራኤል ፡ ፍሬው ፡ የበዛለት ፡ የለመለመ ፡ ወይን ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ፍሬው ፡ ብዛት ፡ መሠዊያውን ፡ አብዝቷል ፤ እንደ ፡ ምድሩም ፡ ማማር ፡ መጠን ፡ ሐውልቶችን ፡ እያሳመሩ ፡ ሠርተዋል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 2 ፤ ልባቸው ፡ ተከፈለ ፤ አኹንም ፡ በደላቸውን ፡ ይሸከማሉ ፤ ርሱ ፡ መሠዊያቸውን ፡

ያፈርሳል ፥ ሐውልቶቻቸውን ፡ ያጠፋል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 3 ፤ አኹንም ፦ ንጉሥ ፡ የለንም ፥ እግዚአብሔርን ፡ አልፈራንምና ፤ ንጉሥስ ፡ ምን ፡ ያደርግልናል ፧ ይላሉ ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 4 ፤ የማይረባውን ፡ ቃል ፡ ይናገራሉ ፤ ቃል ፡ ኪዳን ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ በሐሰት ፡ ይምላሉ ፤ ስለዚህ ፥ መርዛም ፡ ሣር ፡ በዕርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ እንደሚበቅል ፥ መቅሠፍት ፡ ይበቅልባቸዋል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 5 ፤ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ ስለቤትአዌን ፡ እንቦሳ ፡ ይፈራሉ ፤ ክብሩም ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቷልና ፥ ሕዝቡ ፡ ያለቅሱለታል ፥ የጣዖቱ ፡ ካህናትም ፡ በሐዘን ፡ ይንተባተባሉ ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ ለንጉሡ ፡ ለኢያሪም ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አሶር ፡ ይማረካል ፤ ኤፍሬምን ፡ ዕፍረት ፡ ይይዘዋል ፥ እስራኤልም ፡ በምክሩ ፡ ያፍራል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 7 ፤ ሰማርያ ፡ ከንጉሧ ፡ ጋራ ፡ በውሃ ፡ ላይ ፡ እንዳለ ፡ ዐረፋ ፡ ጠፍታለች ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 8 ፤ የእስራኤል ፡ ኀጢአት ፡ የኾኑት ፡ የአዌን ፡ የከሠረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይፈርሳሉ ፤ ሾኽና ፡ አሜከላ ፡ በመሠዊያዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይበቅላል ፤ ተራራዎችንም ፦ ክደኑን ፥ ኰረብታዎችንም ፦ ውደቁብን ፡ ይሏቸዋል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 9 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ከጊብዓ ፡ ዘመን ፡ ገምረኽ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተኻል ፤ በዚያ ፡ ጸንተዋል ፤ በጊብዓ ፡ ላይ ፡ ሰልፍ ፡ አይደርስባቸውምን ፧

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ በፈቀድኹም ፡ ጊዜ ፡ እገሥጻቸዋለኹ ፤ ስለ ፡ ኹለቱም ፡ ኀጢአታቸው ፡ በታሰሩ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ ይሰበሰቡባቸዋል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ ኤፍሬም ፡ ማበራየት ፡ እንደ ፡ ለመደች ፡ ጊደር ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፡ በዐንገቱ ፡ ውበት ፡ እጫንበታለኹ ፤ በኤፍሬም ፡ ላይ ፡ እጠምድበታለኹ ፥ ይሁዳም ፡ ያርሳል ፥ ያዕቆብም ፡ ዐፈሩን ፡ ያለሰልሳል ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ መጥቶ ፡ ጽድቅን ፡ እስኪያዘንብላችኹ ፡ ድረስ ፡ ርሱን ፡ የምትሹበት ፡ ዘመን ፡ ነውና ፥ ለእናንተ ፡ በጽድቅ ፡ ዝሩ ፥ እንደ ፡ ምሕረቱም ፡ መጠን ፡ ዕጨዱ ፥ ጥጋታችኹንም ፡ ዕረሱ ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 13 ፤ ክፋትን ፡ ዐርሳችኋል ፥ ኀጢአትንም ፡ ዐጭዳችኋል ፥ የሐሰትንም ፡ ፍሬ ፡ በልታችኋል ፤ በኀያላንኽ ፡ ብዛት ፥ በመንገድኽም ፡ ላይ ፡ ታምነኻልና ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 14 ፤ በሕዝብኽም ፡ መካከል ፡ ሽብር ፡ ይነሣል ፤ እናትም ፡ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ በተፈጠፈጠች ፡ ጊዜ ፡ ሰልማን ፡ ቤትአርብኤልን ፡ በሰልፍ ፡ ቀን ፡ እንዳፈረሰ ፥ ዐምባዎችኽ ፡ ኹሉ ፡ ይፈርሳሉ ።

ሆሴ. ፥ 10 ፥ 15 ፤ ከኀጢአታችኹም ፡ ክፋት ፡ የተነሣ ፡ ቤቴል ፡ እንዲሁ ፡ ያደርግባችኋል ፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ፈጽሞ ፡ ይጠፋል ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ሆሴ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ እስራኤል ፡ ሕፃን ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ወደድኩት ፥ ልጄንም ፡ ከግብጽ ፡ ጠራኹት ።

ሆሴ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ አብዝቼ ፡ ብጠራቸው ፡ አጥብቀው ፡ ከፊቴ ፡ ራቁ ፤ ለበዓሊምም ፡ ይሠዉ ፡ ነበር ፥ ለተቀረጹ ፡ ምስሎችም ፡ ያጥኑ ፡ ነበር ።

ሆሴ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ እኔም ፡ ኤፍሬምን ፡ ክንዱን ፡ ይገፍ ፡ በእግሩ ፡ እንዲኼድ ፡ መራኹት ፤ እኔም ፡ እፈውሳቸው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ አላወቁም ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ በሰው ፡ ገመድ ፡ በፍቅርም ፡ እስራት ፡ ሳብኋቸው ፤ ለእነርሱም ፡ ቀምበርን ፡ ከጫንቃቸው ፡ ላይ ፡ እንደሚያነሣ ፡ ኾንኹ ፥ ድርቆሽም ፡ ጣልኩላቸው ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ አልወደዱምና ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ምድር ፡ ይመለሳሉ ፥ አሶርም ፡ ንጉሣቸው ፡ ይኾናል ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ከመከሩትም ፡ ምክር ፡ የተነሣ ፡ ሰይፍ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ፥ ከበርቴዎችንም ፡ ያጠፋል ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ሕዝቤም ፡ ከእኔ ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፤ ወደ ፡ ላይም ፡ ቢጠሯቸው ፡ ማንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ኤፍሬም ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ እጥልኻለኹ ፧ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እንዴትስ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጥኻለኹ ፧ እንዴትስ ፡ እንደ ፡ አዳማ ፡ እጥልኻለኹ ፧ እንዴትስ ፡ እንደ ፡ ሲባዮ ፡ አደርግኻለኹ ፧ ልቤ ፡ በውስጤ ፡ ተናውጣለች ፥ ምሕረቴም ፡ ተነሣሥታለች ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ አይደለኹምና ፥ በመካከልኽም ፡ ቅዱሱ ፡ ነኝና ፡ የቍጣዬን ፡ መቅሠፍት ፡ አላደርግም ፥ ኤፍሬምንም ፡ አጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልመለስም ፤ በመዓትም ፡ አልመጣም ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ይከተላሉ ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ያገሣል ፤ ባገሣም ፡ ጊዜ ፡ ልጆች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ።

ሆሴ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ እንደ ፡ ወፍም ፡ ከግብጽ ፥ እንደ ፡ ርግብም ፡ ከአሶር ፡ ምድር ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ይመጣሉ ፤ በቤታቸውም ፡ አኖራቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

_____ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ኤፍሬም ፡ በሐሰት ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ በተንኰል ፡ ከበበኝ ፤ ይሁዳም ፡ ከታመነው ፡ ቅዱሱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አይጸናም ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ኤፍሬም ፡ ነፋስን ፡ ይበላል ፥ የምሥራቅንም ፡ ነፋስ ፡ ይከተላል ፤ ኹልጊዜም ፡ ሐሰትንና ፡ ተንኰልን ፡ ያበዛል ፤ ከአሶር ፡ ጋራ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ያደርጋሉ ፥ ወደ ፡ ግብጽም ፡ ዘይት ፡ ይወስዳሉ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ከይሁዳ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለው ፥ ያዕቆብንም ፡ እንደ ፡ መንገዱ ፡ ይቀጣል ፤ እንደ ፡ ሥራውም ፡ ይመልስለታል ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ በማሕፀን ፡ ውስጥ ፡ ወንድሙን ፡ በተረከዙ ፡ ያዘው ፥ በጕልማሳነቱም ፡ ጊዜ ፡ ከአምላክ ፡ ጋራ ፡ ታገለ ፤

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ከመልአኩም ፡ ጋራ ፡ ታግሎ ፡ አሸነፈ ፤ አልቅሶም ፡ ለመነው ። በቤቴልም ፡ አገኘው ፥ በዚያም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፤ የመታሰቢያው ፡ ስም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ተመለስ ፤ ምሕረትንና ፡ ፍርድን ፡ ጠብቅ ፥ ዘወትርም ፡ በአምላክኽ ፡ ታመን ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ከከነዓን ፡ ወገን ፡ ነው ፤ በእጁ ፡ የተንኰል ፡ ሚዛን ፡ አለ ፥ ሸንገላንም ፡ ይወዳል ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ኤፍሬምም ፦ ባለጠጋ ፡ ኾኛለኹ ፥ ሀብትንም ፡ አግኝቻለኹ ፥ በድካሜም ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአት ፡ የሚኾን ፡ በደል ፡ አይገኝብኝም ፡ አለ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ እኔም ፡ ከግብጽ ፡ ዠምሬ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ እንደ ፡ ዓመት ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በድንኳን ፡ እንድትኖር ፡ አደርግኻለኹ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ለነቢያትም ፡ ተናግሬያለኹ ፥ ራእይንም ፡ አብዝቻለኹ ፤ በነቢያትም ፡ እጅ ፡ ምሳሌዎችን ፡ አውጥቻለኹ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ኀጢአት ፡ በገለዓድ ፡ አለ ፤ ፈጽመው ፡ ከንቱ ፡ ናቸው ፤ ወይፈኖች ፡ በገልገላ ፡ ይሠዋሉ ፥ መሠዊያዎቻቸውም ፡ በዕርሻ ፡ ትልም ፡ ላይ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ይኾናሉ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ያዕቆብ ፡ ወደሶርያ ፡ አገር ፡ ሸሸ ፥ እስራኤልም ፡ ስለ ፡ ሚስት ፡ አገለገለ ፥ ስለ ፡ ሚስትም ፡ ጠባቂ ፡ ነበረ ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በነቢይ ፡ እጅ ፡ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ አወጣ ፥ በነቢይም ፡ እጅ ፡ ጠበቀው ።

ሆሴ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ኤፍሬም ፡ አስመርሮ ፡ አስቈጣው ፤ ስለዚህ ፥ ደሙ ፡ በላዩ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ጌታውም ፡ ስድቡን ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ይመልሳል ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ኤፍሬም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ፍርሀት ፡ ነበረ ፥ በእስራኤልም ፡ ዘንድ ፡ ታበየ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዓልን ፡ በማምለክ ፡ በበደለ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ አኹንም ፡ ኀጢአትን ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ጨመሩ ፤ በብራቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምስልን ፥ እንደ ፡ ጥበባቸውም ፡ ጣዖታትን ፡ ሠርተዋል ፤ ኹሉም ፡ የሠራተኛ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ። ስለ ፡ እነርሱም ፦ የሚሠዉ ፡ ሰዎች ፡ እንቦሳውን ፡ ይሳሙ ፡ ይላሉ ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ስለዚህም ፡ እንደ ፡ ማለዳ ፡ ደመና ፥ በጧትም ፡ እንደሚያልፍ ፡ ጠል ፥ በዐውሎ ፡ ነፍስም ፡ ከዐውድማ ፡ እንደሚበተን ፡ እብቅ ፥ ከመስኮትም ፡ እንደሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ይኾናሉ ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ዠምሬ ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፤ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አታውቅም ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ መድኀኒት ፡ የለም ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ በምድረ ፡ በዳ ፥ እጅግ ፡ በደረቀ ፡ ምድር ፡ ዐውቄኽ ፡ ነበር ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ከተሰማሩ ፡ በኋላ ፡ ጠገቡ ፥ በጠገቡም ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ታበየ ፤ ስለዚህ ፥ ረሱኝ ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ስለዚህም ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ኾንኹባቸው ፥ እንደ ፡ ነብርም ፡ በመንገድ ፡ አጠገብ ፡ አደባባቸዋለኹ ፤

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ልጇ ፡ እንደ ፡ ተነጠቀባት ፡ ድብ ፡ እገጥማቸዋለኹ ፥ የልባቸውንም ፡ ስብ ፡ እቀዳለኹ ፤ በዚያም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ እበላቸዋለኹ ፥ የምድረ ፡ በዳም ፡ አውሬ ፡ ይነጣጠቃቸዋል ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ በረዳትኽ ፡ ላይ ፡ በመነሣትኽ ፡ ጥፋትኽ ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በየከተማኽ ፡ ኹሉ ፡ ያድንኽ ፡ ዘንድ ፡ ንጉሥኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ስለ ፡ እነርሱም ፦ ንጉሥንና ፡ አለቃዎችን ፡ ስጠኝ ፡ ብለኽ ፡ የተናገርኸው ፡ መሳፍንቶችኽ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ በቀ፡ጣዬ ፡ ንጉሥን ፡ ሰጠኹኽ ፥ በመዓቴም ፡ ሻርኹት ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ የኤፍሬም ፡ በደል ፡ ታስሯል ፥ ኀጢአቱም ፡ ተከማችቷል ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ምጥ ፡ እንደ ፡ ያዛት ፡ ሴት ፡ ጭንቅ ፡ ይመጣበታል ፤ በሚወለድበት ፡ ጊዜ ፡ በማሕፀን ፡ አፍ ፡ ቀጥ ፡ ብሎ ፡ አይወጣምና ፡ አእምሮ ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ከሲኦል ፡ እጅ ፡ እታደጋቸዋለኹ ፥ ከሞትም ፡ እቤዣቸዋለኹ ፤ ሞት ፡ ሆይ ፥ ቸነፈርኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ሲኦል ፡ ሆይ ፥ ማጥፋትኽ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ርኅራኄ ፡ ከዐይኔ ፡ ተሰወረች ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ፍሬያማ ፡ ቢኾን ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ይመጣል ፥ የእግዚአብሔር ፡ ነፋስ ፡ ከምድረ ፡ በዳ ፡ ይመጣል ፤ ምንጩንም ፡ ያደርቃል ፥ ፈሳሹንም ፡ ያጠፋል ፥ የተከበሩ ፡ ዕቃዎች ፡ ኹሉ ፡ ያሉበትን ፡ መዝገብ ፡ ይበዘብዛል ።

ሆሴ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ሰማርያ ፡ በአምላኳ ፡ ላይ ፡ ዐምፃለችና ፡ በደሏን ፡ ትሸከማለች ፤ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ ሕፃኖቻቸውም ፡ ይፈጠፈጣሉ ፥ እርጉዞቻቸውም ፡ ይቀደዳሉ ።

ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ በኀጢአትኽ ፡ ወድቀኻልና ፥ ወደ ፡ አምላክኽ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለስ ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ቃልን ፡ ውሰዱ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተመልሳችኹ ፦ ኀጢአትን ፡ ኹሉ ፡ አስወግድ ፥ በቸርነትም ፡ ተቀበለን ፥ በወይፈንም ፡ ፋንታ ፡ የከንፈራችንን ፡ ፍሬ ፡ እንሰጣለን ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ አሶር ፡ አያድነንም ፤ በፈረስ ፡ ላይ ፡ አንቀመጥም ፤ ድኻ ፡ አደጉም ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ምሕረትን ፡ ያገኛልና ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለእጆቻችን ፡ ሥራ ። አምላኮቻችን ፡ ናችኹ ፡ አንላቸውም ፡ በሉት ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ቀ፡ጣዬ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመልሷልና ፥ ዐመፃቸውን ፡ እፈውሳለኹ ፥ በገዛ ፡ ፈቃዴ ፡ እወዳቸዋለኹ ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ለእስራኤልም ፡ እንደ ፡ ጠል ፡ እኾነዋለኹ ፤ እንደ ፡ አበባም ፡ ያብባል ፥ እንደ ፡ ሊባኖስም ፡ ሥሩን ፡ ይሰዳል ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ቅርንጫፎቹም ፡ ይዘረጋሉ ፥ ውበቱም ፡ እንደ ፡ ወይራ ፥ ሽታውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ይኾናል ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ከጥላውም ፡ በታች ፡ የሚቀመጡ ፡ ይመለሳሉ ፤ ከእኽሉም ፡ የተነሣ ፡ ይጠግባሉ ፤ እንደ ፡ ወይንም ፡ ዐረግ ፡ ያብባሉ ፤ መታሰቢያውም ፡ እንደ ፡ ሊባኖስ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይኾናል ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ጣዖት ፡ ለኤፍሬም ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እኔ ፡ ሰምቼዋለኹ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ እመለከታለኹ ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ለመለመ ፡ ጥድ ፡ ነኝ ፤ ፍሬኽ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ይገኛል ።

ሆሴ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ የሚያስተውል ፡ ጠቢብ ፥ የሚያውቃትም ፡ አስተዋይ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ቅን ፡ ነው ፥ ጻድቃንም ፡ ይኼዱበታል ፤ ተላላፊዎች ፡ ግን ፡ ይወድቁበታል ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በቴቁሔ ፡ ከላም ፡ ጠባቂዎች ፡ መካከል ፡ የነበረ ፡ ዓሞጽ ፡ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ ዘመን ፥ በእስራኤልም ፡ ንጉሥ ፡ በዮአስ ፡ ልጅ ፡ በኢዮርብዓም ፡ ዘመን ፥ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ከ"ኾነበቱ ፡ ከ"ኹለት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ያየው ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ "ኾኖ ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይጮኻል ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ "ኾኖ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል ፤ የእረኞችም ፡ ማሰማሪያዎች ፡ ያለቅሳሉ ፥ የቀርሜሎስም ፡ ራስ ፡ ይደርቃል ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ገለዓድን ፡ በብረት ፡ መንኰራኵር ፡ አ"ዲቋልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የደማስቆ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ በአዛሄል ፡ ቤት ፡ እሳትን ፡ እሰዳለ"ኹ ፥ የወልደ ፡ አዴርንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ የደማስቆንም ፡ መወርወሪያ ፡ እሰብራለ"ኹ ፥ ተቀማጮችንም ፡ ከአዌን ፡ ሸለቆ ፡ አጠፋለ"ኹ ፥ በትር ፡ የያዘውንም ፡ ከዔዴን ፡ ቤት ፡ አጠፋለ"ኹ ፤ የሶርያም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ቂር ፡ ይማረካል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ለኤዶምያስ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧቸው ፡ ዘንድ ፡ ምርኮኞችን ፡ "ኹሉ ፡ ማርከዋልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የጋዛ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ በጋዛ ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለ"ኹ ፥ አዳራሾቿንም ፡ ትበላለች ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ተቀማጮችን ፡ ከአዛጦን ፡ አጠፋለ"ኹ ፥ በትር ፡ የያዘውንም ፡ ከአስቀሎና ፡ አጠፋለ"ኹ ፤ እጄንም ፡ በዐቃሮን ፡ ላይ ፡ እመልሳለ"ኹ ፥ ከፍልስጥኤማውያንም ፡ የቀሩት ፡ ይጠፋሉ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ምርኮኞችን ፡ "ኹሉ ፡ ለኤዶምያስ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጥተዋልና ፥ የወንድሞችንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አላሰቡምና ፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የጢሮስ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በጢሮስ ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለ"ኹ ፥ አዳራሾቿንም ፡ ትበላለች ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወንድሙን ፡ በሰይፍ ፡ አሳዶታልና ፥ ርኅራኄንም ፡ "ኹሉ ፡ ጥሏልና ፥ ቀጣውም ፡ "ኹልጊዜ ፡ ቀዷልና ፥ መዓቱንም ፡ ለዘለዓለም ፡ ጠብቋልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የኤዶምያስ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በቴማን ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለ"ኹ ፥ የባሶራንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዳርቻቸውን ፡ ያሰፉ ፡ ዘንድ ፡ የገለዓድን ፡ እርጉዞች ፡ ቀደዋልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የዐሞን ፡ ልጆች ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ በረባት ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ አነዳለ"ኹ ፤ በሰልፍም ፡ ቀን ፡ በጨኸት ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ቀን ፡ በሠከት ፡ አዳራሾቿን ፡ ትበላለች ፤

ዓሞ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ንጉሣቸውም ፡ ከአለቃዎቹ ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ይማረካል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

_____ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የኤዶምያስን ፡ ንጉሥ ፡ ዐጥንት ፡ ዐመድ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ አቃጥሎታልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የሞዐብ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በሞዐብ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለኹ ፥ የቂርዮትንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ፤ ሞዐብም ፡ በውካታና ፡ በጩኸት ፡ በመለከትም ፡ ድምፅ ፡ ይሞታል ፤

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ፈራጅንም ፡ ከመካከሏ ፡ አጠፋለኹ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አለቃዎቿን ፡ ኹሉ ፡ እገድላለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ጥለዋልና ፥ ትእዛዙንም ፡ አልጠበቁምና ፥ አባቶቻቸውም ፡ የተከተሉት ፡ ሐሰታቸው ፡ አስቷቸዋልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የይሁዳ ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ እሰዳለኹ ፥ የኢየሩሳሌምንም ፡ አዳራሾች ፡ ትበላለች ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ጻድቁን ፡ ስለ ፡ ብር ፥ ችጋረኛውንም ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ጥንድ ፡ ጫማ ፡ ሸጠውታልና ፥ ስለ ፡ ሦስት ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አራት ፡ የእስራኤል ፡ ኀጢአት ፡ መቅሠፍቴን ፡ ከማድረግ ፡ አልመለስም ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ የድኻዎችን ፡ ራስ ፡ በምድር ፡ ትቢያ ፡ ላይ ፡ ይረግጣሉ ፥ የትሑታንንም ፡ መንገድ ፡ ያጣምማሉ ፤ ቅዱሱንም ፡ ስሜን ፡ ያረክሱ ፡ ዘንድ ፡ አባትና ፡ ልጁ ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ይገባሉ ፤

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በመሠዊያውም ፡ ኹሉ ፡ አጠገብ ፡ ለመያዣነት ፡ በተወሰደው ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ ይተኛሉ ፤ በአምላካቸውም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በካሣ ፡ የተወሰደውን ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣሉ ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ቁመቱ ፡ እንደ ፡ ዝግባ ፡ ቁመት ፥ ብርታቱም ፡ እንደ ፡ ኮምበል ፡ ዛፍ ፡ የነበረውን ፡ አሞራዊውን ፡ ከፊታቸው ፡ አጠፋኹ ፤ ፍሬውንም ፡ ከላዩ ፥ ሥሩንም ፡ ከታቹ ፡ አጠፋኹ ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ የአሞራዊውንም ፡ ምድር ፡ ትወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አወጣኋችኹ ፥ በምድረ ፡ በዳም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ መራኋችኹ ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ከወንድ ፡ ልጆቻችኹም ፡ ነቢያትን ፥ ከጕበዛዝታችኹም ፡ ናዝራውያንን ፡ አስነሣኹ ፤ እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ናዝራውያኑን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አጠጣችኋቸው ፤ ነቢያቱንም ፦ ትንቢትን ፡ አትናገሩ ፡ ብላችኹ ፡ አዘዛችኋቸው ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ ነዶ ፡ የተሞላች ፡ ሠረገላ ፡ እንደምትደቀድቅ ፡ እንዲሁ ፡ እደቀድቃችኋለኹ ።

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ከሯጪም ፡ ሽሽት ፡ ይጠፋል ፥ ብርቱውም ፡ በብርታቱ ፡ አይበረታም ፥ ኀያሉም ፡ ነፍሱን ፡ አያድንም ፤

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ቀስተኛውም ፡ አይቆምም ፥ ፈጣኑም ፡ አይድንም ፥ ፈረሰኛውም ፡ ነፍሱን ፡ አያድንም ፤

ዓሞ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ በኀያላኑም ፡ መካከል ፡ ልበ ፡ ሙሉው ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ዕራቍቱን ፡ ኾኖ ፡ ይሸሻል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፥ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ባወጣኹት ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 2 ፤ እንዲህም ፡ ብሏል ፦ እኔ ፡ ከምድር ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ እናንተን ፡ ብቻችኹን ፡ ዐውቄያችኋለኹ ፤ ስለዚህ ፥ ስለ ፡ ኀጢአታችኹ ፡ ኹሉ ፡ እበቀላችኋለኹ ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 3 ፤ በእውኑ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ሳይስማሙ ፡ በአንድነት ፡ ይኼዳሉን ፧

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 4 ፤ ወይስ ፡ አንበሳ ፡ የሚነጥቀው ፡ ነገር ፡ ሳያገኝ ፡ በጫካ ፡ ውስጥ ፡ ያገሣልን ፧ ወይስ ፡ የአንበሳ ፡ ደቦል ፡ አንዳች ፡ ሳይዝ ፡ በመደቡ ፡ ኾኖ ፡ ይጮኻልን ፧

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 5 ፤ ወይስ ፡ ወፍ ፥ አጥማጅ ፡ ከሌለው ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ በወጥመድ ፡ ይያዛልን ፧ ወይስ ፡ ወስፈንጠር ፡ አንዳች ፡ ሳይዝ ፡ ከምድር ፡ ይፈነጠራልን ፧

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 6 ፤ ወይስ ፡ በከተማ ፡ ውስጥ ፡ መለከት ፡ ሲነፋ ፡ ሕዝቡ ፡ አይፈራምን ፧ ወይስ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በከተማ ፡ ላይ ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያደረገው ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለምን ፧

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 7 ፤ በእውነት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጢሩን ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ለነቢያት ፡ ካልነገረ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አያደርግም ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 8 ፤ አንበሳው ፡ አገሣ ፤ የማይፈራ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረ ፤ ትንቢት ፡ የማይናገር ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 9 ፤ በአዛጦን ፡ አዳራሾችና ፡ በግብጽ ፡ ምድር ፡ አዳራሾች ፡ አውሩና ፦ በሰማርያ ፡ ተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተሰብሰቡ ፥ በውስጧም ፡ የኾነውን ፡ ታላቁን ፡ ውካታ ፥ በመካከሏም ፡ ያለውን ፡ ግፍ ፡ ተመልከቱ ፡ በሉ ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 10 ፤ ግፍንና ፡ ቅሚያን ፡ በአዳራሾቻቸው ፡ የሚያከማቹት ፡ ቅን ፡ ነገርን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አያውቁም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 11 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በምድሪቱ ፡ ዙሪያ ፡ ጠላት ፡ ይመጣል ፤ ብርታትሽንም ፡ ከአንቺ ፡ ያወርዳል ፥ አዳራሾችሽም ፡ ይበዘበዛሉ ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እረኛ ፡ ከአንበሳ ፡ አፍ ፡ ኹለት ፡ እግርን ፡ ወይም ፡ የገሮን ፡ ጫፍ ፡ እንደሚያድን ፥ እንዲሁ ፡ በሰማርያ ፡ በዐልጋ ፡ ማእዘን ፥ በደማስቆም ፡ በምንጣፍ ፡ ላይ ፡ የተቀመጡት ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይድናሉ ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 13 ፤ ስሙ ፥ በያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ መስክሩ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 14 ፤ እስራኤልን ፡ ስለ ፡ ኀጢአቱ ፡ በምበቀልበት ፡ ቀን ፡ የቤቴልን ፡ መሠዊያዎች ፡ ደግሞ ፡ እበቀላለኹ ፤ የመሠዊያው ፡ ቀንዶች ፡ ይሰበራሉ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ ይወድቃሉ ።

ዓሞ. ፥ 3 ፥ 15 ፤ የክረምቱንና ፡ የበጋውን ፡ ቤት ፡ እመታለኹ ፤ በዝኆንም ፡ ጥርስ ፡ የተለበጡት ፡ ቤቶች ፡ ይጠፋሉ ፥ ታላላቆችም ፡ ቤቶች ፡ ይፈርሳሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዓሞ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ በሰማርያ ፡ ተራራ ፡ የምትኖሩ ፥ ድኻዎችንም ፡ የምትበድሉ ፥ ችጋረኞችንም ፡ የምታሰጨንቁ ፥ ጌታዎቻቸውንም ፦ አምጡ ፡ እንጠጣ ፡ የምትሉ ፡ እናንተ ፡ የባሳን ፡ ላሞች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ እናንተን ፡ በሰልፍ ፡ ዕቃ ፡ ቅሬታችኹንም ፡ በመቃጥን ፡ የሚወስዱበት ፡ ቀን ፡ እንሆ ፡ በላያችኹ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡ በቅዱስነቱ ፡ ምሏል ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እያንዳንዳችኹ ፡ በየፊታችኹ ፡ በተነደለ ፡ ስፍራ ፡ ትወጣላችኹ ፤ በሬማንም ፡ ትጣላላችኹ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡ ወዳጆችኺልና ፡ ወደ ፡ ቤቴል ፡ ኑና ፡ ኀጢአትን ፡ ሥሩ ፤ ወደ ፡ ገልገላ ፡ ኑና ፡ ኀጢአትን ፡ አብዙ ፤ በየማለዳውም ፡ መሥዋዕታችኹን ፡ በየሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ዐሥራታችኹን ፡ አቅርቡ ፤

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ርሾ ፡ ካለበትም ፡ የምስጋናውን ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርቡ ፡ በፈቃዳችኹም ፡ የምታቀርቡትን ፡ ዐውጁና ፡ አውሩ ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በከተማችኹ ፡ ኹሉ ፡ ጥርስን ፡ ማጥራት ፡ በስፍራችኹም ፡ ኹሉ ፡ እንጀራን ፡ ማጣት ፡ ሰጠኺችኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ መከር ፡ ሳይደርስ ፡ ገና ፡ ከሦስት ፡ ወር ፡ በፊት ፡ ዝናብ ፡ ከለከልኺችኹ ፤ በአንድም ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ አዘነብኹ ፡ በሌላውም ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ እንዳይዘንብ ፡ አደረግኹ ፤ ባንድ ፡ ወገን ፡ ዘነበ ፡ ያልዘነበበትም ፡ ወገን ፡ ደረቀ ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ የኹለት ፡ ወይም ፡ የሦስት ፡ ከተማዎች ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ከተማ ፡ ውሃ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ፡ ኼዱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልረኩም ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ በዋግና ፡ በዐረማሞ ፡ መታኺችኹ ፤ የአታክልታችኹንም ፡ ብዛት ፡ ወይኖቻችኹንም ፡ በለሶቻችኹንም ፡ ወይራዎቻችኹንም ፡ ተምች ፡ በልቷል ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ በግብጽ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ ቸነፈርን ፡ ሰደድኹባችኹ ፤ ጐበዛዝታችኹን ፡ በሰይፍ ፡ ገደልኹ ፡ ፈረሶቻችኹንም ፡ አስማረክኹ ፤ የሰፈራችኹንም ፡ ግማት ፡ ወደ ፡ አፍንጫችኹ ፡ አወጣኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ገለበጣቸው ፡ እንዲሁ ፡ ገለበጥኺችኹ ፡ እናንተም ፡ ከእሳት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ተነጠቀ ፡ ትንታግ ፡ ኾናችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፡ እስራኤል ፡ ሆይ ፡ እንደዚህ ፡ አደርግብኻለኹ ፤ እስራኤልም ፡ ሆይ ፡ እንደዚህ ፡ ስለማደርግብኽ ፡ አምላክኽን ፡ ለመገናኘት ፡ ተዘጋጅ ።

ዓሞ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ እንሆ ፡ ተራራዎችን ፡ የሠራ ፡ ነፋስንም ፡ የፈጠረ ፡ የልቡንም ፡ ዐሳብ ፡ ለሰው ፡ የሚነግር ፡ ንጋትን ፡ ጨለማ ፡ የሚያደርግ ፡ በምድርም ፡ ከፍታዎች ፡ ላይ ፡ የሚረግጥ ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ለሙሾ ፡ የማነሣውን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ስሙ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ የእስራኤል ፡ ድንግል ፡ ወደቀች ፡ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አትነሣም ፤ በምድሯ ፡ ላይ ፡ ተጣለች ፡ የሚያስነሣትም ፡ የለም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ሺሕ ፡ ከሚወጣባት ፡ ከተማ ፡ መቶ ፡ ይቀርላታል ፥ መቶም ፡ ከሚወጣባት ፡ ከተማ ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ዐሥር ፡ ይቀርላታል ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለእስራኤል ፡ ቤት ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ እኔን ፡ ፈልጉ ፥ በሕይወትም ፡ ትኖራላችኹ ፤

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ገልገላ ፡ ፈጽሞ ፡ ትማረካለችና ፥ ቤቴልም ፡ ከንቱ ፡ ትኾናለችና ፡ ቤቴልን ፡ አትፈልጉ ፥ ወደ ፡ ገልገላም ፡ አትግቡ ፥ ወደ ፡ ቤርሳቤሕም ፡ አትለፉ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ በዮሴፍ ፡ ቤት ፡ እሳት ፡ እንዳትቃጠል ፥ በቤቴል ፡ የሚያጠፋትም ፡ ሳይኖር ፡ እንዳትበላ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ፈልጉ ፥ በሕይወትም ፡ ትኖራላችኹ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ፍርድን ፡ ወደ ፡ ሬት ፡ የምትለውጡ ፥ ጽድቅንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የምትጥሉ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ሰባቱን ፡ ከዋክብትና ፡ ኦሪዮን ፡ የተባለውን ፡ ኮከብ ፡ የፈጠረውን ፥ የሞትን ፡ ጥላ ፡ ወደ ፡ ንጋት ፡ የሚለውጠውን ፥ ቀኑንም ፡ በሌሊት ፡ የሚያጨልመውን ፥ የባሕሩንም ፡ ውሃዎች ፡ ጠርቶ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የሚያፈሳቸውን ፥

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ዐምባውም ፡ እንዲፈርስ ፡ በብርቱ ፡ ላይ ፡ የድንገት ፡ ጥፋት ፡ የሚያመጣውን ፡ ፈልጉ ፤ ስሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ በበሩ ፡ አደባባይ ፡ የሚገሥጸውን ፡ ጠሉ ፥ እውነትም ፡ የሚናገረውን ፡ ተጸየፉ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ድኻውንም ፡ ደብድባችኋልና ፥ የስንዴውንም ፡ ቀረጥ ፡ ከርሱ ፡ ወስዳችኋልና ፥ ከተጠረበ ፡ ድንጋይ ፡ ቤቶችን ፡ ሠርታችኋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትቀመጡባቸውም ፤ ያማሩ ፡ የወይን ፡ ቦታዎች ፡ ተክላችኋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከወይን ፡ ጠጃቸው ፡ አትጠጡም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ጻድቁን ፡ የምታስጨንቁ ፥ ጕቦንም ፡ የምትቀበሉ ፥ በበሩም ፡ አደባባይ ፡ የችጋረኛውን ፡ ፍርድ ፡ የምታጣምሙ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ በደላችኹ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ በዛ ፥ ኀጢአታችኹም ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ክፉ ፡ ዘመን ፡ ነውና ፥ በዚያ ፡ ዘመን ፡ አስተዋይ ፡ የሚኾን ፡ ዝም ፡ ይላል ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ በሕይወት ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ እንጂ ፡ ክፉውን ፡ አትፈልጉ ፤ እንዲህም ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ተናገራችኹ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ክፉውን ፡ ጥሉ ፥ መልካሙንም ፡ ውደዱ ፥ በበሩም ፡ አደባባይ ፡ ፍርድን ፡ አጽኑ ፤ ምናልባት ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዮሴፍ ፡ ቅሬታ ፡ ይራራ ፡ ይኾናል ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በያደባባዩ ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ዋይታ ፡ ይኾናል ፤ በየመንገዱም ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ወዮ ፡ ወዮ ፡ ይባላል ፤ ገበሬዎቹም ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፥ አልቃሾቹም ፡ ወደ ፡ ዋይታ ፡ ይጠራሉ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ በመካከልኽ ፡ ዐልፋለኹና ፡ በወይኑ ፡ ቦታ ፡ ዥሉ ፡ ልቅሶ ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቀን ፡ ለምትፈልጉ ፡ ወዮላችኹ! ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቀን ፡ ለምን ፡ ትፈልጋላችኹ ፧ ጨለማ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ አይደለም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ከአንበሳ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡ ድብም ፡ እንዳገኘው ፡ ሰው ፥ ወይም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡

እጁን ፡ በግድግዳ ፡ ላይ ፡ እንዳስደገፈና ፡ እባብ ፡ እንደ ፡ ነደፈው ፡ ሰው ፡ ነው ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ብርሃን ፡ ሳይኾን ፡ ጨለማ ፡ አይደለምን ፧ ጸዳል ፡ የሌለውም ፡ ድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ አይደለምን ፧

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ዓመት ፡ በዓላችኹን ፡ ጠልቼዋለኹ ፡ ተጸይፌውማለኹ ፤ የተቀደሰውም ፡ ጉባኤያችኹ ፡ ደስ ፡ አያሠኘኝም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕታችኹና ፡ የእኽሉን ፡ ቍርባናችኹን ፡ ብታቀርቡልኝም ፡ እንኳ ፡ አልቀበለውም ፤ ለምስጋና ፡ መሥዋዕት ፡ የምታቀርቡልኝን ፡ የሰቡትን ፡ እንስሳዎች ፡ አልመለከትም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ የዝማሬኽንም ፡ ጩኸት ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ አርቅ ፤ የመሰንቆኽንም ፡ ዜማ ፡ አላደምጥም ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ፍርድ ፡ እንደ ፡ ውሃ ፥ ጽድቅም ፡ እንደማይደርቅ ፡ ፈሳሽ ፡ ይፍሰስ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በእውኑ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ መሥዋዕትንና ፡ ቍርባንን ፡ አቅርባችኹልኛልን ፧

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ለራሳችኹም ፡ የሠራችኋቸውን ፡ ምስሎች ፥ የሞሎክን ፡ ድንኳንና ፡ የአምላካችኹን ፡ የሬፋን ፡ ኮከብ ፡ አነሣችኹ ።

ዓሞ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ ከደማስቆ ፡ ወደዚያ ፡ አስማርካችኋለኹ ፥ ይላል ፡ ስሙ ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ የተባለ ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ በጽዮን ፡ ላሉ ፡ ዓለመኞች ፥ በሰማርያም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ተዘልለው ፡ ለተቀመጡ ፥ የእስራኤልም ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ለመጡባቸው ፡ ለአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ ወዮላቸው! ፡

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ ካልኔ ፡ ዐልፋችኹ ፡ ተመልከቱ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ሐማት ፡ ኺዱ ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፍልስጥኤም ፡ ጌት ፡ ውረዱ ፤ እነርሱ ፡ ከነዚህ ፡ መንግሥታት ፡ ይሻላሉን ፧ ወይስ ፡ ድንበራቸው ፡ ከድንበራችኹ ፡ ይሰፋልን ፧

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ክፉውን ፡ ቀን ፡ ከእናንተ ፡ ለምታርቁ ፥ የግፍንም ፡ ወንበር ፡ ለምታቀርቡ ፥

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ከዝኖን ፡ ጥርስ ፡ በተሠራ ፡ ዐልጋ ፡ ላይ ፡ ለምትተኙ ፥ በምንጣፋችኹም ፡ ላይ ፡ ተደላድላችኹ ፡ ለምትቀመጡ ፥ ከበጎችም ፡ መንጋ ፡ ጠቦትን ፡ ከጋጥም ፡ ውስጥ ፡ ጥጃን ፡ ለምትበሉ ፥

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ በመሰንቆም ፡ ድምፅ ፡ ለምትንጫጨ ፥ እንደ ፡ ዳዊትም ፡ የዜማን ፡ ዕቃ ፡ ለምታዘጋጁ ፥

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በፋጋ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ለምትጠጡ ፥ እጅግ ፡ ባማረ ፡ ሽቱም ፡ ለምትቀቡ ፥ ስለዮሴፍ ፡ መከራ ፡ ግን ፡ ለማታዝኑ ፡ ለእናንተ ፡ ወዮላችኹ! ፡

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ በምርኮ ፡ መገ፮ሪያ ፡ ይማረካሉ ፥ ተደላድለው ፡ ከተቀመጡትም ፡ ዘንድ ፡ ዘፈን ፡ ይርቃል ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ የያዕቆብን ፡ ትዕቢት ፡ ተጸይፌያለኹ ፥ አዳራሾቹንም ፡ ጠልቻለኹ ፤ ስለዚህ ፥ ከተማዪቱንና ፡ የሚኖሩባትን ፡ ኹሉ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፡ ብሎ ፡ በራሱ ፡ ምሏል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እንዲሀም ፡ ይኾናል ፤ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ቢቀሩ ፡ እነርሱ ፡ ይሞታሉ ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ዐጥንቱንም ፡ ከቤቱ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ዘመድና ፡ አቃጣዩ ፡ ባነሡት ፡ ጊዜ ፥ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፦ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ገና ፡ ሰው ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አለን ፧ ባለው ፡ ጊዜ ፥ ርሱም ፦ ማንም ፡ የለም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እንጠራ ፡ ዘንድ ፡ አይገ፡ባንምና ፥ ዝም ፡ በል ፡ ይለዋል ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ ያዛል ፤ ታላቁንም ፡ ቤት ፡ በማፍረስ ፥ ታናሹንም ፡ ቤት ፡ በመሰባበር ፡ ይመታል ።

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ 13 ፤ ፍርድን ፡ ወደ ፡ ሐሞት ፥ የጽድቅንም ፡ ፍሬ ፡ ወደ ፡ ሬት ፡ የለወጣችኹ ፥ በከንቱም ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚላችኹ ፦ በ፡ነይላችን ፡ ቀንድ ፡ የወሰድን ፡ አይደለምን ፧ የምትሉ ፥ እናንተ ፡ ሆይ ፥ በእውኑ ፡ ፈረሶች ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ ይጋልባሉን ፧ ወይስ ፡ በሬዎች ፡ በዚ.ያ ፡ ላይ ፡ ያርሳሉን ፧

ዓሞ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ ሕዝብን ፡ አስነሣባችኋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፤ እነርሱም ፡ ከሐማት ፡ መግቢ.ያ ፡ ዠምረው ፡ እስከዐረባ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ ያስጨንቋችኋል ።

_____ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ፤ እንሆም ፥ የኋለኛው ፡ ሣር ፡ በሚበቅልበት ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ አንበጣን ፡ ፈጠረ ፤ እንሆም ፥ ከንጉሡ ፡ ዐጨዳ ፡ በኋላ ፡ የበቀለ ፡ የገቦ ፡ ነበረ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የምድሩንም ፡ ሣር ፡ በልተው ፡ ከጨረሱ ፡ በኋላ ፥ እኔ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ይቅር ፡ እንድትል ፡ እለምንኻለኹ ፤ ያዕቆብ ፡ ታናሽ ፡ ነውና ፥ እንዴት ፡ ይቆማል ፧ አልኹ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተጸጸተ ፤ ይህ ፡ አይኾንም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ፤ እንሆም ፥ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእሳት ፡ ለመፍረድ ፡ ጠራ ፤ ርሷም ፡ ታላቁን ፡ ቀላይና ፡ ምድርን ፡ በላች ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እንድትተው ፡ እለምንኻለኹ ፤ ያዕቆብ ፡ ታናሽ ፡ ነውና ፥ እንዴት ፡ ይቆማል ፧ አልኹ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተጸጸተ ፤ ይህ ፡ ደግሞ ፡ አይኾንም ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ እንዲህም ፡ አሳየኝ ፤ እንሆም ፥ ጌታ ፡ ቱንቢውን ፡ ይዞ ፡ በቱንቢ ፡ በተሠራ ፡ ቅጥር ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔርም ፦ ዓሞጽ ፡ ሆይ ፥ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለኝ ። እኔም ፦ ቱንቢ ፡ ነው ፡ አልኹ ። ጌታም ፦ እንሆ ፥ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ቱንቢ ፡ አደርጋለኹ ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ አላልፋቸውም ፤

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ የይሥሐቅም ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃዎች ፡ ይፈርሳሉ ፥ የእስራኤልም ፡ መቅደሶች ፡ ባድማ ፡ ይኾናሉ ፤ በኢ.ዮርብዓምም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ በሰይፍ ፡ እነሣለኹ ፡ አለ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ 11 ፤ የቤቴልም ፡ ካህን ፡ አሜስያስ ፡ ወደእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኢ.ዮርብዓም ፡ ልኮ ፦ ዓሞጽ ፦ ኢ.ዮርብዓም ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታል ፥ እስራኤልም ፡ ከአገሩ ፡ ተማርኮ ፡ ይኼዳል ፡ ብሏልና ፥ ዓሞጽ ፡ በእስራኤል ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ዐምፆብኻል ፤ ምድሪቱም ፡ ቃሉን ፡ ኹሉ ፡ ልትሸከም ፡ አትችልም ፡ አለ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ አሜስያስም ፡ ዓሞጽን ፦ ባለራእዩ ፡ ሆይ ፥ ኺድ ፡ ወደይሁዳም ፡ ምድር ፡ ሽሽ ፥ በዚያም ፡ እንጀራን ፡ ብላ ፥

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በዚያም ፡ ትንቢትን ፡ ተናገር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቤቴል ፡ የንጉሥ ፡ መቅደስና ፡ የመንግሥት ፡ ቤት ፡ ናትና ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በዚህ ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ አትናገር ፡ አለው ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ዓሞጽም ፡ መልሶ ፡ አሜስያስን ፡ አለው ፦ እኔ ፡ ላም ፡ ጠባቂና ፡ ወርካ ፡ ለቃሚ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ የነቢይ ፡ ልጅ ፡ አይደለኹም ፤

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጎቹን ፡ ከመከተል ፡ ወሰደኝ ፥ እግዚአብሔርም ፦ ኺድ ፥ ለሕዝቤም ፡ ለእስራኤል ፡ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ አለኝ ።

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ አኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ስማ ፤ አንተ ፦ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ አትናገር ፥ በይሥሐቅም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ አትስበክ ፡ ብለኻል ፤

ዓሞ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሚስትኽ ፡ በከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ጋለሞታ ፡ ትኾናለች ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆችኽም ፡ በሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ፥ ምድርኽም ፡ በገመድ ፡ ትከፈላለች ፤ አንተም ፡ በረከሰች ፡ ምድር ፡ ትሞታለኽ ፥ እስራኤልም ፡ ከምድሩ ፡ ተማርኮ ፡ ይኼዳል ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አሳየኝ ፡ እንሆም ፥ የቃርሚያ ፡ ፍሬ ፡ የሞላበት ፡ እንቅብ ፡ ነበረ ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ርሱም ፦ ዓሞጽ ፡ ሆይ ፥ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለኝ ። እኔም ፦ የቃርሚያ ፡ ፍሬ ፡ የሞላበት ፡ እንቅብ ፡ ነው ፡ አልኹት ። እግዚአብሔርም ፡ አለኝ ፦ ፍጻሜ ፡ በሕዝቤ ፡ በእስራኤል ፡ ላይ ፡ መጥቷል ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ አላልፋቸውም ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ የመቅደሱ ፡ ዝማሬ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ዋይታ ፡ ይኾናል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ የሰዎችም ፡ ሬሳ ፡ ይበዛል ፥ በስፍራውም ፡ ኹሉ ፡ በዝምታ ፡ ይጣላል ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ችጋረኛውን ፡ የምትውጡ ፥ የአገሩንም ፡ ድኻ ፡ የምታጠፉ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፦

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እኽልን ፡ እንሸጥ ፡ ዘንድ ፡ መባቻው ፡ መቼ ፡ ያልፋል ፧ የኢፍ ፡ መስፈሪያውንም ፡ እያሳነስን ፥ ሰቅሉንም ፡ እያበዛን ፥ በሐሰተኛም ፡ ሚዛን ፡ እያታለልን ፥

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ድኻውን ፡ በብር ፡ ችጋረኛውንም ፡ ባንድ ፡ ጥንድ ፡ ጫማ ፡ እንገዛ ፡ ዘንድ ፥ የስንዴውን ፡ ግርድ ፡ እንሸጥ ፡ ዘንድ ፡ ስንዴውን ፡ እንድንሸምት ፡ ሰንበት ፡ መቼ ፡ ያልፋል ፧ የምትሉ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ስሙ ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በያዕቆብ ፡ ክብር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ምሏል ። ሥራቸውን ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ ምንም ፡ አልረሳም ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በእውኑ ፡ ምድሪቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አትናወጥምን ፧ በርሷም ፡ የሚኖር ፡ ኹሉ ፡ አያለቅስምን ፧ መላዋም ፡ እንደ ፡ ወንዙ ፡ ትነሣለች ፤ እንደ ፡ ግብጽም ፡ ወንዝ ፡ ትነሣለች ፡ ደግሞም ፡ ትወርዳለች ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ፀሓይ ፡ በቀትር ፡ እንድትገባ ፡ አደርጋለኹ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በብርሃንም ፡ ቀን ፡ ምድሩን ፡ አጨልማለኹ ።

ዓሞ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ዓመት ፡ በዓላችኹንም ፡ ወደ ፡ ልቅሶ ፥ ዝማሬያችኹንም ፡ ወደ ፡ ዋይታ ፡

እለውጣለኹ ፤ ማቅንም ፡ በወገብ ፡ ኹሉ ፥ ራስ ፡ መንጨትንም ፡ በኹሉ ፡ ላይ ፡ አመጣለኹ ፤ እንደ ፡ አንድያ ፡ ልጅም ፡ ልቅሶ ፥ ፍጻሜውንም ፡ እንደ ፡ መራራ ፡ ቀን ፡ አደርገዋለኹ ።

ዓሞ. ፥ 8 ፥ 11 ፤ እንሆ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ራብን ፡ የምሰድበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከመስማት ፡ እንጂ ፡ እንጀራን ፡ ከመራብና ፡ ውሃን ፡ ከመጠማት ፡ አይደለም ።

ዓሞ. ፥ 8 ፥ 12 ፤ ከባሕርም ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፥ ከሰሜንም ፡ እስከ ፡ ምሥራቅ ፡ ድረስ ፡ ይቅበዘበዛሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመሻት ፡ ይሯሯጣሉ ፥ አያገኙትምም ።

ዓሞ. ፥ 8 ፥ 13 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ መልካካሞች ፡ ደናግል ፡ ጕበዛዝትም ፡ በጥም ፡ ይዝላሉ ።

ዓሞ. ፥ 8 ፥ 14 ፤ በሰማርያ ፡ ኀጢአት ፡ የሚምሉና ፦ ዳን ፡ ሆይ ፥ ሕያው ፡ አምላክኽን! ፡ ደግሞ ፦ ሕያው ፡ የቤርሳቤሕን ፡ መንገድ! ፡ ብለው ፡ የሚሉ ፥ እነርሱ ፡ ይወድቃሉ ፥ ደግሞም ፡ አይነሡም ።

ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 1 ፤ ጌታን ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ አየኹት ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ መድረኮቹ ፡ ይናወጡ ፡ ዘንድ ፡ ጕልላቶቹን ፡ ምታ ፥ በራሳቸውም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሰባብራቸው ፤ እኔም ፡ ከነርሱ ፡ የቀሩትን ፡ በሰይፍ ፡ እገድላለኹ ፤ የሚሸሽ ፡ አያመልጥም ፥ የሚያመልጥም ፡ አይድንም ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 2 ፤ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ቢወርዱ ፡ እጄ ፡ ከዚያ ፡ ታወጣቸዋለች ፤ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ቢወጡ ፡ ከዚያ ፡ አወርዳቸዋለኹ ፤

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 3 ፤ በቀርሜሎስም ፡ ራስ ፡ ውስጥ ፡ ቢሸሸጉ ፡ ፈልጌ ፡ ከዚያ ፡ አወጣቸዋለኹ ፤ በጥልቅ ፡ ባሕርም ፡ ውስጥ ፡ ከዐይኔ ፡ ቢደበቁ ፡ ከዚያ ፡ እባቡን ፡ አዛለኹ ፥ ርሱም ፡ ይነድፋቸዋል ፤

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 4 ፤ በጠላቶቻቸውም ፡ ፊት ፡ ተማርከው ፡ ቢኼዱ ፡ ከዚያ ፡ ሰይፍን ፡ አዛለኹ ፥ ርሱም ፡ ይገድላቸዋል ፤ ዐይኔንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ለክፋት ፡ እንጂ ፡ ለመልካም ፡ አላደርግም ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 5 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምድርን ፡ ይዳስሳል ፡ ርሷም ፡ ትቀልጣለች ፥ የሚኖሩባትም ፡ ኹሉ ፡ ያለቅሳሉ ፤ መላዋም ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ትነሣለች ፥ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ግብጽ ፡ ወንዝ ፡ ትወርዳለች ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 6 ፤ አዳራሹን ፡ በሰማይ ፡ የሠራ ፥ ጠፈሩንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የመሠረተ ፥ የባሕርንም ፡ ውሃ ፡ ጠርቶ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ላይ ፡ የሚያፈሰው ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ስሙም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 7 ፤ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ለእኔ ፡ እንደኢትዮጵያ ፡ ልጆች ፡ አይደላችኹምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፦ እስራኤልን ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፥ ፍልስጥኤማውያንንም ፡ ከከፍቶር ፥ ሶርያውያንንም ፡ ከቂር ፡ አላወጣኹምን ፧

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 8 ፤ እንሆ ፥ የጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ በኀጢአተኛ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ናቸው ፥ ከምድርም ፡ ፊት ፡ አጠፋታለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የያዕቆብን ፡ ቤት ፡ ፈጽሜ ፡ አላጠፋም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 9 ፤ እንሆ ፥ አዛለኹ ፥ እኽልም ፡ በወንፊት ፡ እንዲነፋ ፡ የእስራኤልን ፡ ቤት ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ እነፋለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንዲት ፡ ቅንጣት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ።

ዓሞ. ፥ 9 ፥ 10 ፤ ክፉው ፡ ነገር ፡ አይደርስብንም ፥ አያገኘንምም ፡ የሚሉ ፡ የሕዝቤ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይሞታሉ ።

ዓሞ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ የወደቀችውን ፡ የዳዊትን ፡ ድንኳን ፡ አነሣለኹ ፥ የተናደውንም ፡ ቅጥሯን ፡ እጠግናለኹ ፤ የፈረሰውንም ፡ ዐድሳለኹ ፥ እንደ ፡ ቀደመውም ፡ ዘመን ፡ እሠራታለኹ ፤

ዓሞ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ይኸውም ፡ የኤዶምያስን ፡ ቅሬታ ፥ ስሜም ፡ የተጠራባቸውን ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአብሔር ።

ዓሞ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ አራሹ ፡ ዐጫጁን ፥ ወይን ፡ ጠማቂውም ፡ ዘሪውን ፡ የሚያገኝበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ተራራዎችም ፡ በተሐውን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ያንጠባጥባሉ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ኹሉ ፡ ይቀልጣሉ ።

ዓሞ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ የሕዝቤን ፡ የእስራኤልን ፡ ምርኮ ፡ እመልሳለኹ ፥ የፈረሱትንም ፡ ከተማዎች ፡ ሠርተው ፡ ይቀመጡባቸዋል ፤ ወይንንም ፡ ይተክላሉ ፥ የወይን ፡ ጠጁንም ፡ ይጠጣሉ ፤ አታክልትንም ፡ ያበጃሉ ፥ ፍሬውንም ፡ ይበላሉ ።

ዓሞ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ በምድራቸውም ፡ እተክላቸዋለኹ ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ከሰጠኋቸው ፡ ከምድራቸው ፡ አይነቀሉም ፥ ይላል ፡ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ❖

ትንቢተ ፡ ሚክያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሚክ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ነገሥታት ፡ በኢዮአታምና ፡ በአካዝ ፡ በሕዝቅያስም ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ሞሬታዊው ፡ ወደ ፡ ሚክያስ ፡ የመጣው ፥ ስለ ፡ ሰማርያና ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያየው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦—

ሚክ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፥ ስሙ ፤ ምድርም ፡ መላዋም ፡ ታድምጥ ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፥ ርሱም ፡ በቅዱስ ፡ መቅደሱ ፡ የኾነ ፡ ጌታ ፥ ይመስክርባችኹ ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ እንሆ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከስፍራው ፡ ይወጣል ፥ ወርዶም ፡ በምድር ፡ ከፍታዎች ፡ ላይ ፡ ይረግጣል ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ተራራዎችም ፡ በእሳት ፡ ፊት ፡ እንዳለ ፡ ሠም ፥ በገደልም ፡ ወርዶ ፡ እንደሚፈስ ፡ ውሃ ፥ በበታቹ ፡ ይቀልጣሉ ፥ ሸለቆዎችም ፡ ይሰነጠቃሉ ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ስለያዕቆብ ፡ በደልና ፡ ስለእስራኤል ፡ ቤት ፡ ኀጢአት ፡ ነው ። የያዕቆብም ፡ በደል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ሰማርያ ፡ አይደለችምን ፧ የይሁዳስ ፡ የኰረብታው ፡ መስገጃ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ኢየሩሳሌም ፡ አይደለችምን ፧

ሚክ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ሰማርያን ፡ በሜዳ ፡ እንደሚገኝ ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፥ ወይን ፡ እንደሚተከልበትም ፡ ስፍራ ፡ አደርጋታለኹ ፤ ድንጋዮቹንም ፡ ወደ ፡ ሸለቆ ፡ እወረውራለኹ ፥ መሠረቶቹንም ፡ እገልጣለኹ ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የተቀረጹትም ፡ ምስሎቹ ፡ ይደቃሉ ፥ በግልሙትና ፡ ያገኘችው ፡ ዋጋ ፡ ኹሉ ፡ በእሳት ፡ ይቃጠላል ፥ ጣዖታቷንም ፡ ኹሉ ፡ አጠፋለኹ ፤ በግልሙትና ፡ ዋጋ ፡ ሰበሰበቻቸው ፥ ወደ ፡ ግልሙትናም ፡ ዋጋ ፡ ይመለሳሉና ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ዋይ ፡ ብላ ፡ ታለቅሳለች ፥ ባዶ ፡ እግሯንና ፡ ዕራቍቷን ፡ ኾና ፡ ትኼዳለች ፤ እንደ ፡ ቀበሮ ፡ ታለቅሳለች ፥ እንደ ፡ ሰጐንም ፡ ዋይ ፡ ትላለች ፤

ሚክ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ቍስሏ ፡ የማይፈወስ ፡ ነውና ፤ እስከ ፡ ይሁዳም ፡ ደርሷልና ፥ ወደሕዝቤም ፡ በር ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ቀርቧልና ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በጌት ፡ ላይ ፡ አታውሩ ፤ በአኮ ፡ ላይ ፡ እንባን ፡ አታድርጉ ፤ በቤትዓፍራ ፡ በትቢያ ፡ ላይ ፡ ተንከባለሉ ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በሻፊር ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ በዕራቍትነትሽና ፡ በዕፍረት ፡ ዕለፊ ፤ በጸዓናን ፡ የምትቀመጠው ፡ አልወጣችም ፤ የቤትኤጼል ፡ ልቅሶ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ መኖሪያውን ፡ ይወስዳል ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እስከኢየሩሳሌም ፡ በር ፡ ድረስ ፡ ወርዷልና ፥ በማሮት ፡ የምትቀመጠው ፡ በጎነትን ፡ ትጠባበቃለች ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በለኪሶ ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ ሠረገላውን ፡ ለፈረስ ፡ እሰሪ ፤ ርሷ ፡ ለጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ የኀጢአት ፡ መገኮሪያ ፡ ነበረች ፤ የእስራኤል ፡ በደል ፡ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ተገኝቷልና ።

ሚክ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ትሎት ፡ ለሞሬሼትጌት ፡ ትሰጪያለሽ ፤ የአክዚብ ፡ ቤቶች ፡ ለእስራኤል ፡ ነገሥታት ፡ አታላይ ፡ ይኾናሉ ።

ሚክ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ በመሪሳ ፡ የምትቀመጪ ፡ ሆይ ፥ ወራሽ ፡ አመጣብሻለኹ ፤ የእስራኤል ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ ዓዶላም ፡ ይመጣል ።

ሚክ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ተማርከው ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ወጥተዋልና ፥ ስለተድላሽ ፡ ልጆች ፡ ራስሽን ፡ ንጪ ፥ ጠጕርሽንም ፡ ተቈረጪ ፤ ቡሓነትሽንም ፡ እንደ ፡ ንስር ፡ አስፊ ።

ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በመኝታቸው ፡ ላይ ፡ በደልን ፡ ለሚያስቡ ፡ ክፋትንም ፡ ለሚያደርጉ ፡ ወዮላቸው! ፡ ኀይል ፡ በእጃቸው ፡ ነውና ፥ ሲነጋ ፡ ይፈጽሙታል ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በዕርሻው ፡ ላይ ፡ ይመኛሉ ፥ በግዴታም ፡ ይይዙታል ፤ በቤቶችም ፡ ላይ ፡ ይመኛሉ ፥ ይወስዷቸውማል ፤ ሰውንና ፡ ቤቱን ፥ ሰውንና ፡ ርስቱንም ፡ ይነጥቃሉ ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ ዐስባለኹ ፥ ከዚያም ፡ ዐንገታችኹን ፡ አታነሡም ፤ ዘመኑም ፡ ክፉ ፡ ነውና ፥ ቀጥ ፡ ብላችኹ ፡ አትኼዱም ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በምሳሌ ፡ ይመስሉባችኋል ፥ በጽኑ ፡ ልቅሶም ፡ ያለቅሱላችኋል ፤ እነርሱም ፦ ፈጽመን ፡ ጠፍተናል ፤ የሕዝቤን ፡ ዕድል ፡ ፈንታ ፡ ይሰፍራል ፥ ርሱንም ፡ የሚከለክል ፡ የለም ፤ ዕርሻችንን ፡ ለዐመፀኞች ፡ ይከፍላል ፡ ይላሉ ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡ መካከል ፡ በዕጣ ፡ ገመድ ፡ የሚጥል ፡ አይኖርኽም ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ትንቢት ፡ አትናገሩ ፡ ብለው ፡ ይናገራሉ ፤ በእነዚህ ፡ ላይ ፡ ትንቢት ፡ አይናገሩም ፥ ስድብም ፡ አይርቅም ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ የተባልኽ ፡ ሆይ ፥ በእውኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ የማይታገሥ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ሥራው ፡ እንደዚች ፡ ናትን ፧ ቃሌስ ፡ በቅን ፡ ለሚኼድ ፡ በጎነት ፡ አያደርግምን ፧

ሚክ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሕዝቤ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ ኾኖ ፡ ተነሥቷል ፤ ቀሚስንና ፡ መጐናጸፊያን ፡ ገፈፋችኹ ፤ ሳይፈሩም ፤ የሚያልፉትን ፡ ከሰልፍ ፡ እንደሚመለሱ ፡ አደረጋችኋቸው ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ የሕዝቤንም ፡ ሴቶች ፡ ከተሸለሙ ፡ ቤቶቻቸው ፡ አሳደዳችኋቸው ፤ ከሕፃናታቸውም ፡ ክብሬን ፡ ለዘለዓለም ፡ ወሰዳችኹ ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ በዚህ ፡ ዕረፍት ፡ የላችኹምና ፡ ተነሥታችኹ ፡ ኺዱ ፤ በርኵሰት ፡ ምክንያት ፡ ክፉ ፡ ጥፋት ፡ ታጠፋችኋለች ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ነፋስንም ፡ ተከትሎ ፦ ስለወይን ፡ ጠጅና ፡ ስለ ፡ ስካር ፡ ትንቢት ፡ እናገርልኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ሐሰትን ፡ የሚናገር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ርሱ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ነቢይ ፡ ይኾናል ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ያዕቆብ ፡ ሆይ ፥ ኹሉንተናኽን ፡ ፈጽሞ ፡ እሰበስባለኹ ፥ የእስራኤልንም ፡ ቅሬታ ፡ ፈጽሞ ፡ አከማቻለኹ ፤ እንደ ፡ ባሶራ ፡ በጎችና ፡ እንደ ፡ መንጋ ፡ በማሰማሪያቸው ፡ ውስጥ ፡ በአንድነት ፡ አኖራቸዋለኹ ፤ ከሰው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ድምፃቸውን ፡ ያሰማሉ ።

ሚክ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ሰባሪው ፡ በፊታቸው ፡ ወጥቷል ፤ እነርሱም ፡ ሰብረው ፡ ወደ ፡ በሩ ፡ አልፈዋል ፥ በርሱም ፡ በኩል ፡ ወጥተዋል ፤ ንጉሣቸውም ፡ በፊታቸው ፡ ዐልፏል ፥ እግዚአብሔርም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ነው ።

ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንዲህም ፡ አልኹ ፦ የያዕቆብ ፡ አለቃዎችና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ገዢዎች ፡ ሆይ ፥ እባካችኹ ፡ ስሙኝ ፤ ፍርድን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አይገባችኹምን ፧

ሚክ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ መልካሙን ፡ ጠልታችኋል ፥ ክፉውንም ፡ ወዳችኋል ፤ ቍርበታቸውን ፡ ገፈችኋቸዋል ፥ ሥጋቸውንም ፡ ከዐጥንታቸው ፡ ለያይታችኋል ፤

ሚክ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ የሕዝቤን ፡ ሥጋ ፡ በልታችኋል ፥ ቍርበታቸውንም ፡ ገፈችኋቸዋል ፥ ዐጥንታቸውንም ፡ ሰብራችኋል ፤ ለአፍላል ፡ እንደሚኾን ፡ ሥጋ ፡ ለድስትም ፡ እንደሚኾን ፡ ሙዳ ፡ ቈራረጣችኋቸው ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጮኻሉ ፥ ርሱም ፡ አይሰማቸውም ፤ ሥራቸውንም ፡ ክፉ ፡ አድርገዋልና ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ፊቱን ፡ ከነርሱ ፡ ይሰውራል ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቤን ፡ ስለሚያስቱ ፡ ነቢያት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፤ በጥርሳቸው ፡ ሲነክሱ ፡ በሰላም ፡ ይሰብካሉ ፤ በአፋቸው ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ በማይሰጥ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ሰልፍን ፡ ያስቡበታል ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ሌሊት ፡ ይኾንባችኋል ፡ እንጂ ፡ ራእይ ፡ አይኾንላችኹም ፤ ጨለማም ፡ ይኾንባችኋል ፡ እንጂ ፡ አታሟርቱም ፤ ፀሓይም ፡ በነቢያት ፡ ላይ ፡ ትገባለች ፥ ቀኑም ፡ ይጠቍርባቸዋል ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ መልስ ፡ የለምና ፡ ባለራእዩቹ ፡ ያፍራሉ ፥ ሟርተኞችም ፡ ይዋረዳሉ ፤ ኹሉም ፡ ከንፈራቸውን ፡ ይሸፍናሉ ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በደሉን ፡ ለያዕቆብ ፥ ኀጢአቱንም ፡ ለእስራኤል ፡ እነግር ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ኀይልንና ፡ ፍርድን ፡ ብርታትንም ፡ ተሞልቻለኹ ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ፍርድን ፡ የምትጠሉ ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ ኹሉ ፡ የምታጣምሙ ፡ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ አለቃዎችና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ገዢዎች ፡ ሆይ ፥ እባካችኹ ፡ ይህን ፡ ስሙ ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ጽዮንን ፡ በደም ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ በኀጢአት ፡ ይሠራሉ ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ አለቃዋቿ ፡ በጕቦ ፡ ይፈርዳሉ ፥ ካህናቷም ፡ በዋጋ ፡ ያስተምራሉ ፥ ነቢያቷም ፡ በገንዘብ ፡ ያሟርታሉ ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ። እግዚአብሔር ፡ በመካከላችን ፡ አይደለምን ፧ ክፉ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ አይመጣብንም ፡ እያሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይታመናሉ ።

ሚክ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ጽዮን ፡ እንደ ፡ ዕርሻ ፡ ትታረሳለች ፥ ኢየሩሳሌምም ፡ የድንጋይ ፡ ክምር ፡ ትኾናለች ፥ የቤቱም ፡ ተራራ ፡ እንደ ፡ ዱር ፡ ከፍታ ፡ ይኾናል ።

ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ በመጨረሻውም ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተራራ ፡ በተራራዎች ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ጸንቶ ፡ ይቆማል ፥ ከኰረብታዎችም ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፤ አሕዛብም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይጐርፋሉ ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ከጽዮን ፡ ሕግ ፥ ከኢየሩሳሌምም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይወጣልና ፥ ብዙዎች ፡ አሕዛብ ፡ ኼደው ፦ ኑ ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፥ ወደያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ቤት ፡ እንውጣ ፤ ርሱም ፡ መንገዱን ፡ ያስተምረናል ፥ በፍለጋውም ፡ እንኼዳለን ፡ ይላሉ ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ በብዙዎችም ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይፈርዳል ፥ በሩቅም ፡ ባሉ ፡ በብርቱዎች ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ ይበይናል ፤ ሰይፋቸውንም ፡ ማረሻ ፥ ጦራቸውንም ፡ ማጭድ ፡ ለማድረግ ፡ ይቀጠቅጣሉ ፤ ሕዝብም ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ ሰይፍ ፡ አያነሣም ፡ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ሰልፍ ፡ አይማሩም ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አፍም ፡ ተናግሯልና ፥ ሰው ፡ እያንዳንዱ ፡ ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ይቀመጣል ፥ የሚያስፈራውም ፡ የለም ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ሕዝብም ፡ ሹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ በያምላኩ ፡ ስም ፡ ይኼዳል ፥ እኛም ፡ በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ለዘለዓለም ፡ እንኼዳለን ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ዐንካሳዉቱን ፡ እሰበስባለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ የባከነችውንና ፡ ያስጨነቅኋትንም ፡ አከማቻለኹ ፤

ሚክ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ዐንካሳዉቱንም ፡ ለቅሬታ ፥ ወደ ፡ ሩቅም ፡ የተጣለችውን ፡ ለብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ አደርጋታለኹ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይነግሣል ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ አንተም ፡ የመንጋ ፡ ግንብ ፡ ሆይ ፥ የጽዮን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ዐምባ ፥ ወዳንተ ፡ ትመጣለች ፤ የቀደመችው ፡ ግዛት ፥ የኢየሩሳሌም ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ መንግሥት ፡ ትደርሳለች ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ አኹንስ ፡ ለምን ፡ ትጮኺያለሽ ፧ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ ምጥ ፡ የደረሰብሽ ፥ ንጉሥ ፡ ስለሌለሽ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ መካሪ ፡ ስለ ፡ ጠፋብሽ ፡ ነውን ፧

ሚክ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንደምትወልድ ፡ ሴት ፡ አምጠሽ ፡ ውለጂ ፤ አኹን ፡ ከከተማ ፡ ትወጣለሽና ፥ በሜዳም ፡ ትቀመጣለሽ ፥ ወደ ፡ ባቢሎንም ፡ ትደርሻለሽ ፤ በዚያም ፡ ያድንሻል ፥ በዚያም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጠላቶችሽ ፡ እጅ ፡ ይቤዥሻል ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ አኹንም ፦ ርኩስ ፡ ትኹን ፥ ዐይናችንም ፡ በጽዮን ፡ ላይ ፡ ይይ ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ተሰብስበዋል ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ዐሳብ ፡ አያውቁም ፥ ምክሩንም ፡ አያስተውሉም ፤ እንደ ፡ ነዶ ፡ ወደ ፡ ዐውድማ ፡ አከማችቷቸዋልና ።

ሚክ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ቀንድሽን ፡ ብረት ፥ ጥፍርሽንም ፡ ናስ ፡ አደርጋለኹና ፡ ተነሺ ፥ አኺጂ ፤ ብዙ ፡ አሕዛብንም ፡ ታደቂያለሽ ፤ ትርፋቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፥ ሀብታቸውንም ፡ ለምድር ፡ ሹሉ ፡ ጌታ ፡ ትቀድሻለሽ ።

_____ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ሚክ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ የጭፍራዎች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ጭፍራዎችሽን ፡ አኹን ፡ ሰብስቢ ፤ ከዖ ፡ አስጨንቆናል ፤ የእስራኤልን ፡ ፈራጅ ፡ ጕንጭን ፡ በበትር ፡ ይመታሉ ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ አንቺም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ኤፍራታ ፡ ሆይ ፥ አንቺ ፡ በይሁዳ ፡ አእላፋት ፡ መካከል ፡ ትኾኚ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ ነሽ ፤ ከአንቺ ፡ ግን ፡ አወጣጡ ፡ ከቀድሞ ፡ ዠምሮ ፡ ከዘለዓለም ፡ የኾነ ፥ በእስራኤልም ፡ ላይ ፡ ገዢ ፡ የሚኾን ፡ ይወጣልኛል ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ወላጂቱ ፡ እስከምትወልድበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣቸዋል ፤ የቀሩትም ፡ ወንድሞቹ ፡ ወደ ፡ እስራኤል ፡ ልጆች ፡ ይመለሳሉ ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ ይቆማል ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ኀይል ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ግርማ ፡ መንጋውን ፡ ይጠብቃል ፤ እነርሱም ፡ ይኖራሉ ፤ ርሱ ፡ አኹን ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ይህም ፡ ለሰላም ፡ ይኾናል ፤ አሶራዊውም ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፥ ምድራችንንም ፡

በረገጠ ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ እረኞችና ፡ ስምንት ፡ አለቃዎች ፡ እናስነሣበታለን ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ የአሶርንም ፡ አገር ፡ በሰይፍ ፥ የናምሩድንም ፡ አገር ፡ በመግቢያው ፡ ውስጥ ፡ ያፈርሳሉ ፤ አሶራዊውም ፡ ወደ ፡ አገራችን ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፥ ዳርቻዎቻችንንም ፡ በረገጠ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ይታደገናል ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ የያዕቆብም ፡ ቅሬታ ፡ በብዙ ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንደሚወርድ ፡ ጠል ፥ በሣር ፡ ላይ ፡ እንደሚወርድ ፡ ካፊያ ፤ ሰውንም ፡ እንደማይጠብቅ ፥ የሰውንም ፡ ልጆች ፡ ተስፋ ፡ እንደማያደርግ ፡ ይኾናል ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ በዱር ፡ አራዊትም ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ አንበሳ ፥ በበጎች ፡ መንጋም ፡ መካከል ፡ ዐልፎ ፡ እንደሚረግጥ ፥ የሚታደግም ፡ ሳይኖር ፡ እንደሚነጥቅ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ደቦል ፥ እንዲሁ ፡ የያዕቆብ ፡ ቅሬታ ፡ በአሕዛብና ፡ በብዙ ፡ ወገኖች ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ እጅኽ ፡ በጠላቶችኽ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትበል ፥ ጠላቶችኽም ፡ ሹሉ ፡ ይጥፉ ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ፈረሶችኽን ፡ ከመካከልኽ ፡ አጠፋለኹ ፥ ሠረገላዎችኽንም ፡ እሰብራለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤

ሚክ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ የምድርኽንም ፡ ከተማዎች ፡ አጠፋለኹ ፥ ምሽጎችኽንም ፡ ሹሉ ፡ አፈርሳለኹ ፤

ሚክ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ መተትንም ፡ ከእጅኽ ፡ አጠፋለኹ ፥ ሟርተኞችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኾኑልኽም ፤

ሚክ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ የተቀረጹትን ፡ ምስሎችኽንና ፡ ሐውልቶችኽን ፡ ከመካከልኽ ፡ አጠፋለኹ ፥ ለእጅኽም ፡ ሥራ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አትሰግድም ፤

ሚክ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ የማምለኪያ ፡ ዐጸዶችኽንም ፡ ከመካከልኽ ፡ እነቅላለኹ ፥ ከተማዎችኽንም ፡ አፈርሳለኹ ።

ሚክ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ባልሰሙም ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ በቍጣና ፡ በመዓት ፡ እበቀላለኹ ።

_____ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ሚክ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ አኹን ፦ ተነሣ ፥ በተራራዎችም ፡ ፊት ፡ ተፋረድ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ቃልኽን ፡ ይስሙ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚለውን ፡ ስሙ ።

ሚክ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ተራራዎች ፡ ሆይ ፥ ጠንካራዎች ፡ የምድር ፡ መሠረቶችም ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ክርክር ፡ አለውና ፥ ከእስራኤልም ፡ ጋራ ፡ ይፋረዳልና ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ክርክር ፡ ስሙ ።

ሚክ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ አድርጌካለኹ ፧ በምንስ ፡ አድክሜካለኹ ፧ መስክርብኝ ።

ሚክ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ አውጥቼካለኹ ፥ ከባርነት ፡ ቤትም ፡ ተቤዥቼካለኹ ፤ በፊትኽም ፡ ሙሴንና ፡ አሮንን ፡ ማርያምንም ፡ ልኬልኽ ፡ ነበር ።

ሚክ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ የሞዐብ ፡ ንጉሥ ፡ ባላቅ ፡ የመከረውን ፥ የቢዖርም ፡ ልጅ ፡ በለዓም ፡ የመለሰለትን ፡ አኹን ፡ ዐስብ ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ የጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከሰጢም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ገልገላ ፡ ድረስ ፡ ዐስብ ።

ሚክ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ምን ፡ ይገቼ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ልምጣና ፡ በልዑል ፡ አምላክ ፡ ፊት ፡ ልስገድ ፧ የሚቃጠለውን ፡ መሥዋዕትና ፡ የአንዱን ፡ ዓመት ፡ ጥጃ ፡ ይገቼ ፡ በፊቱ ፡ ልምጣን ፧

ሚክ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔርስ ፡ በሺሕ ፡ አውራ ፡ በጎች ፡ ወይስ ፡ በእልፍ ፡ የዘይት ፡ ፈሳሾች ፡ ደስ ፡

ይለዋልን ፧ ወይስ ፡ የበኵር ፡ ልጄን ፡ ስለ ፡ በደሌ ፥ የሆዴንም ፡ ፍሬ ፡ ስለነፍሴ ፡ ኀጢአት ፡ እሰጣለኹን ፧

ሚክ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ ሰው ፡ ሆይ ፥ መልካሙን ፡ ነግሮኻል ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚሻው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ፍርድን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፥ ምሕረትንም ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፥ ከአምላክኽም ፡ ጋራ ፡ በትሕትና ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ አይደለምን ፧

ሚክ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ከተማዩቱን ፡ ይጠራታል ፤ ስምኽን ፡ መፍራት ፡ ጥበብ ፡ ነው ፤ የመቅሠፍትን ፡ በትር ፥ ርሱንም ፡ ያዘጋጀ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስሙ ።

ሚክ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ በእውኑ ፡ በኀጢአተኛ ፡ ቤት ፡ የኀጢአት ፡ መዝገብ ፥ የተጸየፈም ፡ ውሸተኛ ፡ መስፈሪያ ፡ ገና ፡ አለ ፡ ይኾን ፧

ሚክ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ በአባይ ፡ ሚዛንና ፡ በከረጢት ፡ ባለ ፡ በተንኰል ፡ መመዘኛ ፡ ንጹሕ ፡ እኾናለኹን ፧

ሚክ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ ባለጠጋዎቿን ፡ ግፍ ፡ ሞልቶባቸዋል ፤ በርሷም ፡ የሚኖሩ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋል ፥ ምላሳቸውም ፡ በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ተንኰለኛ ፡ ነው ።

ሚክ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በክፉ ፡ ቍስል ፡ መታኹኽ ፤ ስለ ፡ ኀጢአትኽም ፡ አፈረስኹኽ ።

ሚክ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ ትበላለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትጠግብም ፤ ችጋርኽም ፡ በመካከልኽ ፡ ይኾናል ፤ ትወስዳለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አታድንም ፤ የምታድነውንም ፡ ለሰይፍ ፡ እሰጣለኹ ።

ሚክ. ፥ 6 ፥ 15 ፤ ትዘራለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አታጭድም ፤ ወይራውንም ፡ ትጨምቃለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዘይቱን ፡ አትቀባም ፤ ወይኑንም ፡ ትጨምቃለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የወይን ፡ ጠጁን ፡ አትጠጣም ።

ሚክ. ፥ 6 ፥ 16 ፤ አንተን ፡ ለጥፋት ፥ በርሷም ፡ የሚኖሩትን ፡ ለማፏጫ ፡ እሰጥ ፡ ዘንድ ፡ የዘንበሪን ፡ ሥርዐትና ፡ የአክአብን ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ኾሉ ፡ ጠብቃችኋል ፥ በምክራቸውም ፡ ኼዳችኋል ፤ የሕዝቤንም ፡ ስድብ ፡ ትሸከማላችኹ ።

ትንቢተ ፡ ሚክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 1 ፤ የዛፍ ፡ ፍሬና ፡ የወይን ፡ ፍሬ ፡ ከተለቀሙ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ቀረው ፡ ቃርሚያ ፡ ኾኖለኹና ፡ ወዮልኝ! ፡ መብል ፡ የሚኾን ፡ ዘለላ ፥ ነፍሴም ፡ የተመኘችው ፡ በመገኘመሪያ ፡ የበሰለው ፡ በለስ ፡ የለም ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 2 ፤ ደግ ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ ጠፍቷል ፥ በሰውም ፡ መካከል ፡ ቅን ፡ የለም ፤ ኹሉ ፡ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ ያደባሉ ፥ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ወንድሙን ፡ በመረብ ፡ ለመያዝ ፡ ይከታተለዋል ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 3 ፤ እጆቻቸውን ፡ ለክፋት ፡ ያነሣሉ ፤ አለቃውና ፡ ፈራጁ ፡ ጉቦን ፡ ይፈልጋሉ ፥ ትልቁም ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ምኞት ፡ ይናገራል ፤ እንዲሁም ፡ ክፋትን ፡ ይጐነጉናሉ ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ኹሉ ፡ የተሻለው ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ አሜከላ ፡ ነው ፥ ከኹሉም ፡ ቅን ፡ የኾነው ፡ እንደ ፡ ኵርንችት ፡ ነው ፤ ጠባቂዎችኽ ፡ የሚጐበኙበት ፡ ቀን ፡ መጥቷል ፤ አኹን ፡ ይሸበራሉ ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 5 ፤ ባልንጀራን ፡ አትመኑ ፥ በወዳጅም ፡ አትታመኑ ፤ የአፍኽን ፡ ደጅ ፡ በብብትኽ ፡ ከምትተኛው ፡ ጠብቅ ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ ይንቃልና ፥ ሴት ፡ ልጅ ፡ በእናቷ ፡ ላይ ፥ ምራቲቱም ፡ በአማቷ ፡ ላይ ፡ ትነሣለችና ፥ የሰው ፡ ጠላቶች ፡ የቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ናቸውና ።

ሚክ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እመለከታለኹ ፥ የመድኀኒቴንም ፡ አምላክ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ፤ አምላኬም ፡ ይሰማኛል ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ጠላቴ ፡ ሆይ ፥ ብወድቅ ፡ እነሣለኹና ፥ በጨለማም ፡ ብቀመጥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ይኾንልኛልና ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አይበልሽ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርቻለኹና ፡ እስኪ.ሟገትልኝ ፡ ድረስ ፥ ፍርድን ፡ ለእኔ ፡ እስኪ.ያደርግ ፡ ድረስ ፡ ቍጣውን ፡ እታገሣለኹ ። ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣኛል ፥ ጽድቅንም ፡ አያለኹ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ጠላቴም ፡ ታያለች ፥ እኔንም ፦ አምላክኽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ያለች ፡ በዕፍረት ፡ ትከደናለች ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ ዐይኖቼ ፡ ይመለከቷታል ፤ አኹን ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ ጭቃ ፡ ትረገጣለች ። ቅጥርሽ ፡ በሚሠራበት ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ድንበርሽ ፡ ትስፋፋለች ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከአሶርና ፡ ከግብጽ ፡ ከተማዎች ፥ ከግብጽ ፡ እስከ ፡ ወንዙ ፥ ከባሕርም ፡ እስከ ፡ ባሕር ፥ ከተራራም ፡ እስከ ፡ ተራራ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣሉ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ምድሪቱ ፡ ግን ፡ በሚኖሩባት ፡ በሥራቸው ፡ ፍሬ ፡ ምክንያት ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ በቀርሜሎስ ፡ መካከል ፡ ባለው ፡ ዱር ፡ ብቻቸውን ፡ የተቀመጡት ፡ ሰዎችኽ ፥ የርስትኽን ፡ በጎች ፥ በበትርኽ ፡ አግድ ፤ እንደ ፡ ቀደመውም ፡ ዘመን ፡ በበሳንና ፡ በገለዓድ ፡ ይሰማሩ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ወጣኽበት ፡ ዘመን ፡ ተአምራትን ፡ አሳያቸዋለኹ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ አሕዛብ ፡ አይተው ፡ በጕልበታቸው ፡ ኹሉ ፡ ያፍራሉ ፤ እጃቸውን ፡ በአፋቸው ፡ ላይ ፡ ያኖራሉ ፥ ጐሯቸውም ፡ ትደነቍራለች ፤

ሚክ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እንደ ፡ እባብም ፡ መሬት ፡ ይልሳሉ ፥ እንደምድርም ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ እየተንቀጠቀጡ ፡ ከግንባቸው ፡ ይመጣሉ ፤ ፈርተውም ፡ ወደ ፡ አምላካችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመጣሉ ፥ ስለ ፡ አንተም ፡ ይፈራሉ ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ በደልን ፡ ይቅር ፡ የሚል ፥ የርስቱንም ፡ ቅሬታ ፡ ዐመፅ ፡ የሚያሳልፍ ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ያለ ፡ አምላክ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ምሕረትን ፡ ይወዳ.ልና ፥ ቍጣውን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጠብቅም ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ተመልሶ ፡ ይምረናል ፤ ክፋታችንንም ፡ ይጠቀጥቃል ፥ ኀጢአታችንንም ፡ በባሕሩ ፡ ጥልቅ ፡ ይጥለዋል ።

ሚክ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ከቀድሞ ፡ ዘመን ፡ ዠምረኽ ፡ ለአባቶቻችን ፡ የማልኽላቸውን ፡ እውነት ፡ ለያዕቆብ ፥ ምሕረትንም ፡ ለአብርሃም ፡ ታደርጋለኽ ❖

ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ወደባቱኤል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢዮኤል ፡ የመጣው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እናንተ ፡ ሽማግሌዎች ፥ ይህን ፡ ስሙ ፤ በምድርም ፡ የምትኖሩ ፡ ኹሉ ፥ አድምጡ ። ይህ ፡ በዘመናችኹ ፡ ወይስ ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ዘመን ፡ ኾኖ ፡ ነበርን ፧

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ይህን ፡ ለልጆቻችኹ ፡ ንገሩ ፤ ልጆቻችኹም ፡ ለልጆቻቸው ፥ ልጆቻቸውም ፡ ለኺለኛው ፡ ትውልድ ፡ ይንገሩ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከተምች ፡ የቀረውን ፡ አንበጣ ፡ በላው ፤ ከአንበጣም ፡ የቀረውን ፡ ደጐብያ ፡ በላው ፤ ከደጐብያም ፡ የቀረውን ፡ ኵብኵባ ፡ በላው ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በተሓ ፡ ወይን ፡ ጠጪችኹ ፡ ከአፋችኹ ፡ ተወግዷልና ፥ እናንተ ፡ ሰካራሞች ፥ ነቅታችኹ ፡ አልቅሱ ፤ እናንተም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የምትጠጡ ፡ ኹሉ ፥ ዋይ ፡ በሉ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ቍጥርም ፡ የሌለው ፡ ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ በምድሬ ፡ ላይ ፡ ወጥቷልና ፤ ጥርሳቸው ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጥርስ ፥ መንጋጋቸውም ፡ እንደ ፡ እንስቲቱ ፡ አንበሳ ፡ መንጋጋ ፡ ነው ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ወይኔን ፡ ባዶ ፡ ምድር ፡ አደረገው ፥ በለሴንም ፡ ሰበረው ፤ ባዶም ፡ አደረገው ፥ ጣለውም ፤ ቅርንጫፎቹም ፡ ነጡ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ለቀኑንሥርናዋ ፡ ባል ፡ ማቅ ፡ ለብሳ ፡ እንደምታለቅስ ፡ ድንግል ፡ አልቅሺ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ የእኽሉ ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተወግዷል ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አገልጋዮች ፡ ካህናቱ ፡ አለቀሱ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እኽሉ ፡ ጠፍቷልና ፥ ወይኑም ፡ ደርቋልና ፥ ዘይቱም ፡ ጐድሏልና ፥ ዕርሻው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾኗል ፥ ምድሪቱም ፡ አልቅሳለች ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ መከሩ ፡ ከዕርሻቸው ፡ ጠፍቷልና ፥ ገበሬዎች ፡ ስለ ፡ ስንዴውና ፡ ስለ ፡ ገብሱ ፡ ዐፈሩ ፤ የወይን ፡ አትክልተኞችም ፡ አለቀሱ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ወይኑ ፡ ደርቋል ፥ በለሱም ፡ ጠውልጓል ፤ ሮማኑና ፡ ተምሩ ፡ እንኰዩም ፡ የምድርም ፡ ዛፎች ፡ ኹሉ ፡ ደርቀዋል ፤ ደስታም ፡ ከሰው ፡ ልጆች ፡ ዘንድ ፡ ርቋል ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ የእኽሉ ፡ ቍርባንና ፡ የመጠጡ ፡ ቍርባን ፡ ከአምላካችኹ ፡ ቤት ፡ ቀርቷልና ፥ እናንተ ፡ ካህናት ፥ ማቅ ፡ ታጥቃችኹ ፡ አልቅሱ ፤ እናንተም ፡ የመሠዊያ ፡ አገልጋዮች ፥ ዋይ ፡ በሉ ፤ እናንተ ፡ የአምላኬ ፡ አገልጋዮች ፥ ኑ ፥ ሌሊቱን ፡ ኹሉ ፡ በማቅ ፡ ላይ ፡ ተኙ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ጾምን ፡ ቀድሱ ፥ ጉባኤውንም ፡ ዐውጁ ፤ ሽማግሌዎችንና ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ሰብስቡ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጩኹ ።

ኢዮኤ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቧልና ፥ ለቀኑ ፡ ወዮ! ፡ ርሱም ፡ ኹሉን ፡ ከሚችል ፡ ከአምላክ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጥፋት ፡ ይመጣል ።

ኢዮኤ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ከዐይናችን ፡ ፊት ፡ ምግብ ፡ ከአምላካችንም ፡ ቤት ፡ ደስታና ፡ እልልታ ፡ የጠፋ ፡ አይደለምን ፧

ኢዮኤ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ዘሩ ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ በሰበሰ ፤ እኽሉ ፡ ደርቋልና ፥ ጐተራዎቹ ፡ ባዶ ፡ ናቸው ፥ ጐታዎቹም ፡ ፈርሰዋል ።

ኢዮኤ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እንስሳዎች ፡ እጅግ ፡ ጮኹ ፤ የላምም ፡ መንጋዎች ፡ ማሰማሪያ ፡ የላቸውምና ፡ ተጠራጠሩ ፤ የበግም ፡ መንጋዎች ፡ ጠፍተዋል ።

ኢዮኤ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ አቤቱ ፥ እሳት ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ማሰማሪያ ፡ በልቷልና ፥ ነበልባሉም ፡ የዱሩን ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ አቃጥሏልና ፥ ወዳንተ ፡ እጮኻለኹ ።

ኢዮኤ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ፈሳሹ ፡ ውሃ ፡ ደርቋልና ፥ እሳቱም ፡ የምድረ ፡ በዳውን ፡ ማሰማሪያ ፡ በልቷልና ፥ የምድር ፡ አራዊት ፡ ወዳንተ ፡ አለከለኩ ።

ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ መጥቷልና ፥ ርሱም ፡ ቀርቧልና ፥ በጽዮን ፡ መለከትን ፡ ንፉ ፥ በቅዱሱም ፡ ተራራዬ ፡ ላይ ፡ እሪ ፡ በሉ ፤ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ይንቀጥቀጡ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ መጥቷልና ፤

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ የጨለማና ፡ የጭጋግ ፡ ቀን ፥ የደመናና ፡ የድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ቀን ፡ ነው ፤ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ወገግታ ፡ ተዘርግቷል ፤ ከዘለዓለምም ፡ ዠምሮ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ያለ ፡ አልነበረም ፥ ከነርሱም ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ብዙ ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ያለ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኾንም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እሳት ፡ በፊታቸው ፡ ትባላለች ፥ በኋላቸውም ፡ ነበልባል ፡ ታቃጥላለች ፤ ምድሪቱ ፡ በፊታቸው ፡ እንደ ፡ ዔዴን ፡ ገነት ፥ በኋላቸውም ፡ የምድረ ፡ በዳ ፡ በረሓ ፡ ናት ፤ ከነርሱም ፡ የሚያመልጥ ፡ የለም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ፈረስ ፡ መልክ ፡ ነው ፥ እንደ ፡ ፈረሶችም ፡ ይሮጣሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በተራራ ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ሠረገላዎች ፡ ድምፅ ፥ ገለባውንም ፡ እንደሚበላ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ድምፅ ፥ ለሰልፍም ፡ እንደ ፡ ተዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ብርቱ ፡ ሕዝብ ፡ ያከሥበኵባሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ከፊታቸው ፡ አሕዛብ ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፤ የሰውም ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ይጠቀሩራል ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ ኀያላን ፡ ይሮጣሉ ፥ እንደ ፡ ሰልፈኞችም ፡ በቅጥሩ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፤ እያንዳንዱም ፡ በመንገዱ ፡ ላይ ፡ ይራመዳል ፥ ከርምጃቸውም ፡ አያፈገፍጉም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ አንዱ ፡ ካንዱ ፡ ጋራ ፡ አይጋፉም ፥ እያንዳንዱም ፡ መንገዱን ፡ ይጠበጥባል ፤ በሰልፍ ፡ መካከል ፡ ያልፋሉ ፥ እነርሱም ፡ አይቈስሉም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በከተማም ፡ ያከሥበኵባሉ ፥ በቅጥሩም ፡ ላይ ፡ ይሮጣሉ ፤ ወደ ፡ ቤቶችም ፡ ይወጣሉ ፥ እንደ ፡ ሌባም ፡ በመስኮቶች ፡ ይገባሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ምድሪቱም ፡ ከፊታቸው ፡ ትናወጣለች ፥ ሰማያትም ፡ ይንቀጠቀጣሉ ፤ ፀሓይና ፡ ጨረቃም ፡ ይጨልማሉ ፥ ከዋክብትም ፡ ብርሃናቸውን ፡ ይሰውራሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በሰራዊቱ ፡ ፊት ፡ ድምፁን ፡ ይሰጣል ፤ ሰፈሩ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፥ ቃሉንም ፡ የሚያደርግ ፡ ርሱ ፡ ኀያል ፡ ነውና ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቀን ፡ ታላቅና ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነውና ፥ ማንስ ፡ ይችለዋል ፧

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ አኹንስ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ በፍጹም ፡ ልባችኹ ፥ በጾምም ፥ በልቅሶና ፡ በዋይታ ፡ ወደ ፡

እኔ ፡ ተመለሱ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ልባችኹን ፡ እንጂ ፡ ልብሳችኹን ፡ አትቅደዱ ፤ አምላካችኹም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቸርና ፡ መሐሪ ፥ ቍጣው ፡ የዘገየ ፥ ምሕረቱም ፡ የበዛ ፥ ለክፋትም ፡ የተጸጸተ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመለሱ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ የሚመለስና ፡ የሚጸጸት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ለአምላካችኹም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የእኽልና ፡ የመጠጥ ፡ ቍርባን ፡ የሚኾነውን ፡ በረከት ፡ የሚያተርፍ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፧

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ በጽዮን ፡ መለከትን ፡ ንፉ ፥ ጾምንም ፡ ቀድሱ ፥ ጉባኤውንም ፡ ዐውጁ ፥

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ሕዝቡንም ፡ አከማቹ ፥ ማኅበሩንም ፡ ቀድሱ ፥ ሽማግሌዎቹንም ፡ ሰብስቡ ፥ ሕፃናቱንና ፡ ጡት ፡ የሚጠቡትን ፡ አከማቹ ፤ ሙሽራው ፡ ከዕልፍኙ ፥ ሙሽራዪቱም ፡ ከጫጉላዋ ፡ ይውጡ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ አገልጋዮች ፡ ካህናት ፡ ከወለሉና ፡ ከመሠዊያው ፡ መካከል ፡ እያለቀሱ ፦ አቤቱ ፥ ለሕዝብኽ ፡ ራራ ፥ አሕዛብም ፡ እንዳይነቅፏቸው ፡ ርስትኽን ፡ ለማላገጫ ፡ አሳልፈኽ ፡ አትስጥ ፤ ከአሕዛብ ፡ መካከል ፦ አምላካቸው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ስለ ፡ ምን ፡ ይላሉ ፧ ይበሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ምድሩ ፡ ቀና ፥ ለሕዝቡም ፡ ራራለት ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፡ ሕዝቡን ፦ እንሆ ፥ እኽልንና ፡ ወይንን ፡ ዘይትንም ፡ እሰድላችኋለኹ ፥ እናንተም ፡ በርሱ ፡ ትጠግባላችኹ ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲያ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ መሰደቢያ ፡ አላደርጋችኹም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ የሰሜንንም ፡ ሰራዊት ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አርቃለኹ ፥ ወደ ፡ በረሓና ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፥ ፊቱን ፡ ወደምሥራቁ ፡ ባሕር ፡ ገፍርባውንም ፡ ወደምዕራቡ ፡ ባሕር ፡ አድርጌ ፡ አሳድደዋለኹ ፤ ርሱም ፡ ትዕቢትን ፡ አድርጓልና ፥ ግማቱ ፡ ይወጣል ፥ ክርፋቱም ፡ ይነሣል ፡ አለ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ምድር ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አድርጓልና ፥ አትፍሪ ፥ ደስም ፡ ይበልሽ ፥ እልልም ፡ በዪ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እናንተ ፡ የምድር ፡ እንስሳዎች ፡ ሆይ ፥ የምድረ ፡ በዳው ፡ ማሰማሪያ ፡ ለምልሟልና ፥ ዛፉም ፡ ፍሬውን ፡ አፍርቷልና ፥ በለሱና ፡ ወይኑም ፡ ኀይላቸውን ፡ ሰጥተዋልና ፥ አትፍሩ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ እናንተ ፡ የጽዮን ፡ ልጆች ፥ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፊተኛውን ፡ ዝናብ ፡ በጽድቅ ፡ ሰጥቷችኋልና ፥ እንደ ፡ ቀድሞውም ፡ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ዝናብ ፡ አዝንቦላችኋልና ፥ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ለርሱም ፡ እልል ፡ በሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ዐውድማዎችም ፡ እኽልን ፡ ይሞላሉ ፥ መጥመቂያዎችም ፡ የወይን ፡ ጠጅንና ፡ ዘይትን ፡ አትረፍርፈው ፡ ያፈሳሉ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ የሰደድኹባችኹ ፡ ታላቁ ፡ ሰራዊቴ ፡ አንበጣና ፡ ደጐብያ ፡ ኵብኵባና ፡ ተምች ፡ የበላቸውን ፡ ዓመታት ፡ እመልስላችኋለኹ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ብዙ ፡ መብል ፡ ትበላላችኹ ፥ ትጠግቡማላችኹ ፤ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ተአምራትን ፡ የሠራውን ፡ የአምላካችኹን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ታመሰግናላችኹ ፤ ሕዝቤም ፡ ለዘለዓለም ፡ አያፍርም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ እኔም ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ እንዳለኹ ፥ እኔም ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ ታውቃላችኹ ፤ ሕዝቤም ፡ ለዘለዓለም ፡ አያፍርም ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ መንፈሴን ፡ በሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አፈሳለኹ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፥ ሽማግሌዎቻችኹም ፡ ሕልምን ፡ ያልማሉ ፥ ጐበዞቻችኹም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፤

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ ደግሞም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ ባሪያዎች ፡ ላይ ፡ መንፈሴን ፡ አፈሳለኹ ፤

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ድንቆችን ፡ አሳያለኹ ፥ በታች ፡ በምድርም ፡ ደምና ፣ እሳት ፣ የጢስም ፡ ጭጋግ ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 31 ፤ ታላቁና ፡ የሚያስፈራው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ፀሓይ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፥ ጨረቃም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ይለወጣል ።

ኢዮኤ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ እንዲህም ፡ ይኾናል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፡ ይድናል ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ በጽዮን ፡ ተራራና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ መድኀኒት ፡ ይገኛል ። ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ የጠራቸው ፥ የምሥራች ፡ የሚሰበከላቸው ፡ ይገኛሉ ።

ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንሆም ፥ በዚያ ፡ ወራትና ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፥ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ምርኮ ፡ በምመልስበት ፡ ጊዜ ፥

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቤ ፡ ወደኢዮሳፍጥ ፡ ሸለቆ ፡ አወርዳቸዋለኹ ፤ በዚያም ፡ ስለ ፡ ሕዝቤና ፡ ስለ ፡ ርስቴ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ የበተኗቸውን ፡ ምድሬንም ፡ የተካፈሏትን ፡ እፋረድባቸዋለኹ ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በሕዝቤም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ፤ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ለጋለሞታ ፡ ዋጋ ፡ ሰጡ ፥ ሴት ፡ ልጅን ፡ ለወይን ፡ ጠጅ ፡ ሸጡ ፥ ጠጡም ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ጢሮስና ፡ ሲዶና ፡ የፍልስጥኤምም ፡ ግዛት ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ለእኔ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ በእውኑ ፡ ብድራትን ፡ ትመልሱልኛላችኹን ፧ ብድራትን ፡ ብትመልሱልኝ ፡ ፈጥኜ ፡ በችኮላ ፡ ብድራታችኹን ፡ በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ብሬንና ፡ ወርቄን ፡ ወስዳችኋልና ፥ የተወደደውንም ፡ መልካሙን ፡ ዕቃዬን ፡ ወደ ፡ መቅደሳችኹ ፡ አግብታችኋልና ፥

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ከዳርቻቸውም ፡ ታርቋቸው ፡ ዘንድ ፡ የይሁዳንና ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ ልጆች ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ሸጣችኋልና ፥

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንሆ ፥ እነርሱን ፡ ከሸጣችኹበት ፡ ስፍራ ፡ አስነሣቸዋለኹ ፥ ብድራታችኹንም ፡ በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ተናግሯልና ፥ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ እጅ ፡ እሸጣለኹ ፥ እነርሱም ፡ ለሩቆቹ ፡ ሕዝብ ፡ ለሳባ ፡ ሰዎች ፡ ይሸጧችኋል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ይህን ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ዐውጁ ፡ ለሰልፍ ፡ ተዘጋጁ ፡ ኀያላንን ፡ አስነሡ ፡ ሰልፈኞች ፡ ኹሉ ፡ ይቅረቡ ፡ ይውጡም ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ማረሻችኹን ፡ ሰይፍ ፥ ማጭዳችኹንም ፡ ጦር ፡ ለማድረግ ፡ ቀጥቅጡ ፤ ደካማውም ፦ እኔ ፡ ብርቱ ፡ ነኛ ፡ ይበል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ በዙሪያ ፡ ያላችኹ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፥ ተኰላችኹ ፡ ኑ ፥ ተሰብሰቡ ፤ አቤቱ ፥ ኀያላንኽን ፡ ወደዚያ ፡ አውርድ ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ አሕዛብ ፡ ይነሡ ፥ ወደኢዮሳፍጥ ፡ ሸለቆም ፡ ይውጡ ፤ በዙሪያ ፡ ባሉ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እፈርድ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ እቀመጣለኹና ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ መከሩ ፡ ደርሷልና ፥ ማጭድ ፡ ስደዱ ፤ መጥመቂያውም ፡ ሞልቷልና ፥ ኑ ፡ ርገጡ ፤ ክፋታቸውም ፡ በዝቷልና ፥ መጥመቂያ ፡ ኹሉ ፡ ፈርሷል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በፍርድ ፡ ሸለቆ ፡ ቀርቧልና ፥ የብዙ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ውካታ ፡ በፍርድ ፡ ሸለቆ ፡ አለ ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡ ጨልመዋል ፥ ከዋክብትም ፡ ብርሃናቸውን ፡ ሰውረዋል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ኾኖ ፡ ድምፁን ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ ይጮኻል ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ኾኖ ፡ ቃሉን ፡ ይሰጣል ፤ ሰማይና ፡ ምድርም ፡ ይናወጣሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለሕዝቡ ፡ መሸሸጊያ ፥ ለእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ መጠጊያ ፡ ይኾናል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ እኔም ፡ በተቀደሰው ፡ ተራራዬ ፡ በጽዮን ፡ የምቀመጥ ፡ አምላካችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የተቀደሰች ፡ ትኾናለች ፥ እንግዳዎችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አያልፉባትም ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ተራራዎች ፡ በተሓ ፡ ጠጅ ፡ ያንጠባጥባሉ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ወተትን ፡ ያፈሳሉ ፥ በይሁዳም ፡ ያሉት ፡ ፈፋዎች ፡ ኹሉ ፡ ውሃን ፡ ያጐርፋሉ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ምንጭ ፡ ትፈልቃለች ፥ የሰጢምንም ፡ ሸለቆ ፡ ታጠጣለች ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ በአገራቸው ፡ ንጹሑን ፡ ደም ፡ አፍሰዋልና ፥ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ስላደረጉት ፡ ግፍ ፡ ግብጽ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፥ ኤዶምያስም ፡ በረሓ ፡ ይኾናል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይሁዳ ፡ ለዘለዓለም ፥ ኢየሩሳሌምም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ መኖሪያ ፡ ይኾናል ።

ኢዮኤ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ እኔም ፡ ንጹሕ ፡ ያላደረግኹትን ፡ ደማቸውን ፡ ንጹሕ ፡ አደርገዋለኹ ፥ እግዚአብሔርም ፡ በጽዮን ፡ ያድራል ❖

ትንቢተ ፡ ዐብድዩ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዐብድዩ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ዐብ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የዐብድዩ ፡ ራእይ ፦ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኤዶምያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወሬ ፡ ሰምተናል ፤ መልእክተኛ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ተልኮ ፦ ተነሡ ፥ በላይዋም ፡ በሰልፍ ፡ እንነሣ ፡ ብሏል ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እንሆ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታናሽ ፡ አድርጌሃለኹ ፤ አንተ ፡ እጅግ ፡ ተንቀሃል ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በተሠነጠቀ ፡ አለት ፡ ውስጥ ፡ የምትኖር ፥ ማደሪያኽንም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረግኽ ፥ በልብኽም ፦ ወደ ፡ ምድር ፡ የሚያወርደኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የምትል ፡ አንተ ፡ ሆይ ፥ የልብኽ ፡ ትዕቢት ፡ አታሎኃል ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እንደ ፡ ንስር ፡ መጥቀኽ ፡ ብትወጣ ፥ ቤትኽም ፡ በከዋክብት ፡ መካከል ፡ ቢኾን ፥ ከዚያ ፡ አወርድሃለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ሌባዎች ፡ ቢመጡብኽ ፡ ወይም ፡ ወንበዴዎች ፡ በሌሊት ፡ ቢመጡ ፥ የሚበቃቸውን ፡ የሚሰርቁ ፡ አይደሉምን ፧ ወይንንም ፡ የሚቈርጡ ፡ ወዳንተ ፡ ቢመጡ ፡ ቃርሚያ ፡ አያስቀሩምን ፧

ዐብ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ምንኛ ፡ ጠፋኽ! ፡ ዔሳው ፡ ምንኛ ፡ ተመረመረ! ፡ የተሸሸገበት ፡ ነገር ፡ ምንኛ ፡ ተፈለገ! ፡

ዐብ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የተማማልኻቸው ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ዳርቻኽ ፡ ሰደዱኽ ፤ የታመንኻቸው ፡ ሰዎች ፡ አታለሉኽ ፥ አሸነፉኽም ፤ በበታችኽም ፡ አሽክላ ፡ ዘረጉብኽ ፥ እነርሱም ፡ ማስተዋል ፡ የላቸውም ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከኤዶምያስ ፡ ጥበበኞችን ፥ ከዔሳውም ፡ ተራራ ፡ ማስተዋልን ፡ አላጠፋምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ቴማን ፡ ሆይ ፥ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ከዔሳው ፡ ተራራ ፡ በመገደል ፡ ይጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ኀያላንኽ ፡ ይደነግጣሉ ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በወንድምኽ ፡ በያዕቆብ ፡ ላይ ፡ ስለተደረገ ፡ ግፍ ፡ ዕፍረት ፡ ይከድንኻል ፥ ለዘለዓለምም ፡ ትጠፋለኽ ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በፊቱ ፡ አንጻር ፡ በቆምኽ ፡ ቀን ፥ አሕዛብ ፡ ጭፍራውን ፡ በማረኩበት ፥ እንግዳዎችም ፡ በበሩ ፡ በገቡበት ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ዕጣ ፡ በተጣጣሉበት ፡ ቀን ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ነበርኽ ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመከራው ፡ ቀን ፡ ወንድምኽን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በይሁዳ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይልኽ ፡ ዘንድ ፥ በጭንቀትም ፡ ቀን ፡ በትዕቢት ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሕዝቤ ፡ በር ፡ ትገባ ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ መከራቸውን ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፥ በጥፋታቸውም ፡ ቀን ፡ በሀብታቸው ፡ ላይ ፡ እጅኽን ፡ ትዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

ዐብ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ የሸሹትንም ፡ ለመግደል ፡ በመንታ ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ትቆም ፡ ዘንድ ፥ በጭንቀትም ፡ ቀን ፡ ከርሱ ፡ የቀሩትን ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አይገባኽም ፡ ነበር ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ቀርቧልና ፤ አንተ ፡ እንዳደረግኸው ፡ እንዲሁ ፡
ይደረግብኻል ፥ ፍዳኽም ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ይመለሳል ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ በቅዱስ ፡ ተራራዬ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ጠጣችኹ ፡ እንዲሁ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ዘወትር ፡
ይጠጣሉ ፤ አዎን ፡ ይጠጣሉ ፥ ይጨልጡማል ፥ እንዳልኾኑም ፡ ይኾናሉ ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ የሚያመልጡ ፡ ይኾናሉ ፥ ርሱም ፡ ቅዱስ ፡
ይኾናል ፤ የያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ሰዎች ፡ ርስታቸውን ፡ ይወርሳሉ ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ተናግሯልና ፥ የያዕቆብ ፡ ቤት ፡ እሳት ፥ የዮሴፍ ፡ ቤት ፡ ነበልባልም ፥ የዔሳው ፡
ቤት ፡ ገለባ ፡ ይኾናሉ ፤ እነርሱንም ፡ ያቃጥሏቸዋል ፡ ይበሏቸውማል ፤ ከዔሳውም ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ የለውም ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ የደቡብም ፡ ሰዎች ፡ የዔሳውን ፡ ተራራ ፥ የቈላውም ፡ ሰዎች ፡ ፍልስጥኤማውያንን ፡
ይወርሳሉ ፤ የኤፍሬምንም ፡ አገር ፡ የሰማርያንም ፡ አገር ፡ ይወርሳሉ ፤ ብንያምም ፡ ገለዓድን ፡ ይወርሳል ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ይህም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ የጭፍራቸው ፡ ምርኮ ፡ የከነዓንን ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ሰራጵታ ፡
ድረስ ፡ ይወርሳል ፤ በስፋራድም ፡ የሚኖሩ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ምርኮኞች ፡ የደቡብን ፡ ከተማዎች ፡ ይወርሳሉ ።

ዐብ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ በዔሳውም ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ይፈርዱ ፡ ዘንድ ፡ አዳኞች ፡ ወደጽዮን ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡
ይወጣሉ ፤ መንግሥቱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይኾናል ❖

ትንቢተ ፡ ዮናስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዮና. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደዐማቴ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዮና. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ተነሥተኽ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኺድ ፥ ክፋታቸውም ፡ ወደ ፡ ፊቴ ፡ ወጥቷልና ፥ በርሷ ፡ ላይ ፡ ስበክ ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ዮናስ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይኰበልል ፡ ዘንድ ፡ ተነሣ ፤ ወደ ፡ ኢዮጴም ፡ ወረደ ፥ ወደ ፡ ተርሴስም ፡ የምታልፍ ፡ መርከብ ፡ አገኘ ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ኰብሎ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ሰጥቶ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገባ ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በባሕሩ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ነፋስን ፡ አመጣ ፥ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ ኾነ ፥ መርከቢቱም ፡ ልትሰበር ፡ ቀረበች ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 5 ፤ መርከበኞቹም ፡ ፈሩ ፥ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ጮኸ ፤ መርከቢቱም ፡ እንድትቀልላቸው ፡ በውስጧ ፡ የነበረውን ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉት ፤ ዮናስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ መርከቡ ፡ ውስጠኛው ፡ ክፍል ፡ ወርዶ ፡ ነበር ፥ በከባድ ፡ እንቅልፍም ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 6 ፤ የመርከቡም ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርቦ ፦ ምነው ፡ ተኝተኻል ፧ እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስበን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተነሥተኽ ፡ አምላክኽን ፡ ጥራ ፡ አለው ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፥ ዕጣ ፡ እንጣጣል ፡ ተባባሉ ። ዕጣም ፡ ተጣጣሉ ፥ ዕጣውም ፡ በዮናስ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 8 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፦ ይህ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ በማን ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኘን ፡ እባክኽ ፡ ንገረን ፤ ሥራኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ከወዴትስ ፡ መጣኽ ፧ አገርኽስ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ከማን ፡ ወገን ፡ ነኽ ፧ አሉት ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ርሱም ፦ እኔ ፡ ዕብራዊ ፡ ነኝ ፤ ባሕሩንና ፡ የብሱን ፡ የፈጠረውን ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመልካለኹ ፡ አላቸው ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እነዚያም ፡ ሰዎች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ኰበለለ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ነገራቸው ፡ ዐውቀዋልና ፥ እጅግ ፡ ፈርተው ፦ ይህ ፡ ያደረግኸው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉት ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ባሕሩንም ፡ ሞገዱ ፡ አጥብቆ ፡ ያናውጠው ፡ ነበርና ፦ ባሕሩ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ጸጥ ፡ እንዲል ፡ ምን ፡ እናድርግብኽ ፧ አሉት ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ርሱም ፦ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ማዕበል ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ እንዳገኛችኹ ፡ ዐውቃለኹና ፡ አንሥታችኹ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ጣሉኝ ፥ ባሕሩም ፡ ጸጥ ፡ ይልላችኋል ፡ አላቸው ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ሰዎቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድሩ ፡ ሊመለሱ ፡ አጥብቀው ፡ ቀዘፉ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ባሕሩ ፡ እጅግ ፡ አብዝቶ ፡ ይናወጥባቸው ፡ ነበርና ፥ አልቻሉም ።

ዮና. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኹው ፦ አቤቱ ፥ እንደ ፡ ወደድኽ ፡ አድርገኻልና ፥ እንለምንኻለን ፤ አቤቱ ፥ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ እንዳንጠፋ ፡ ንጹሕም ፡ ደም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ እንዳታደርግ ፡ እንለምንኻለን ፡ አሉ ።

ዮና. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ዮናስንም ፡ ወስደው ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ጣሉት ፤ ባሕሩም ፡ ከመናወጡ ፡ ጸጥ ፡ አለ ።

ዮና. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ሰዎችም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረቡ ፥ ስእለትንም ፡ ተሳሉ ።

_____ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዮና. ፡ 2 ፡ 1 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፡ የሚውጥ ፡ ታላቅ ፡ ዓሣ ፡ አሰናዳ ፤ ዮናስም ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ በዓሣው ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ነበረ ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ዮናስም ፡ በዓሣው ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ወደ ፡ አምላኩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸለየ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦

ዮና. ፡ 2 ፡ 3 ፤ በመከራዬ ፡ ሳለኹ ፡ ወደ ፡ አምላኬ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጮኽኹ ፥ ርሱም ፡ ሰማኝ ፤ በሲኦልም ፡ ሆድ ፡ ውስጥ ፡ ኾኜ ፡ ጮኽኹ ፥ ቃሌንም ፡ አዳመጥኽ ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ወደ ፡ ባሕሩ ፡ ውስጥ ፡ ጣልኸኝ ፥ ፈሳሾችም ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበሩ ፤ ማዕበልኽና ፡ ሞገድኽ ፡ ኹሉ ፡ በላዬ ፡ ዐለፉ ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እኔም ፦ ከዐይንኽ ፡ ፊት ፡ ተጣልኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስኽ ፡ ደግሞ ፡ እመለከታለኹ ፡ አልኹ ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ውሃዎችም ፡ እስከ ፡ ነፍሴ ፡ ድረስ ፡ ከበቡኝ ፤ ጥልቁ ፡ ባሕር ፡ በዙሪያዬ ፡ ነበረ ፤ የባሕሩ ፡ ሣር ፡ በራሴ ፡ ተጠምጥሞ ፡ ነበር ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ወደተራራዎች ፡ መሠረት ፡ ወረድኹ ፤ በምድርና ፡ በመወርወሪያዎቿ ፡ ለዘለዓለም ፡ ተዘጋኹ ፤ አንተ ፡ ግን ፥ አቤቱ ፡ አምላኬ ፥ ሕይወቴን ፡ ከጕድጓዱ ፡ አወጣኽ ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ነፍሴ ፡ በዛለችብኝ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዐሰብኹት ፤ ጸሎቴም ፡ ወዳንተ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ መቅደስኽ ፡ ገባች ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ከንቱነትንና ፡ ሐሰትን ፡ የሚጠብቁ ፡ ምሕረታቸውን ፡ ትተዋል ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 10 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በምስጋና ፡ ቃል ፡ እሠዋልኻለኹ ፤ የተሳልኹትንም ፡ እከፍላለኹ ። ደኅንነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮና. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዓሣውን ፡ አዘዘው ፥ ርሱም ፡ ዮናስን ፡ በየብስ ፡ ላይ ፡ ተፋው ።

_____ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዮና. ፡ 3 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ወደ ፡ ዮናስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዮና. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ተነሥተኽ ፡ ወደዚያች ፡ ወደ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኺድ ፥ የምነግርኽንም ፡ ስብከት ፡ ስበክላት ፡ አለው ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ዮናስም ፡ ተነሥቶ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ ኼደ ፤ ነነዌም ፡ የሦስት ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ዮናስም ፡ የአንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱ ፡ ውስጥ ፡ ሊገባ ፡ ገሥመረ ፤ ጮኾም ፦ በሦስት ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነነዌ ፡ ትገለበጣለች ፡ አለ ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 5 ፤ የነነዌም ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመኑ ፤ ለጾም ፡ ዐዋጅ ፡ ነገሩ ፥ ከታላቁም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታናሹ ፡ ድረስ ፡ ማቅ ፡ ለበሱ ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ወሬውም ፡ ወደነነዌ ፡ ንጉሥ ፡ ደረሰ ፤ ርሱም ፡ ከዙፋኑ ፡ ተነሥቶ ፡ መጐናጸፊያውን ፡ አወለቀ ፡ ማቅም ፡ ለበሰ ፥ በዐመድም ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ዐዋጅም ፡ አስነገረ ፥ በነነዌም ፡ ውስጥ ፡ የንጉሡንና ፡ የመኳንንቱን ፡ ትእዛዝ ፡ አሳወጀ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ሰዎችና ፡ እንስሳዎች ፡ ላሞችና ፡ በጎች ፡ አንዳችን ፡ አይቅመሱ ፤ አይሰማሩም ፡ ውሃንም ፡ አይጠጡ ፤

ዮና. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ሰዎችና ፡ እንስሳዎችም ፡ በማቅ ፡ ይከደኑ ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በብርቱ ፡ ይጮኹ ፤ ሰዎችም ፡ ዅሉ ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸውና ፡ በእጃቸው ፡ ካለው ፡ ግፍ ፡ ይመለሱ ።

ዮና. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እኛ ፡ እንዳንጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፡ ይጸጸት ፡ እንደ ፡ ዅነ ፥ ከጽኑ ፡ ቍጣውም ፡ ይመለስ ፡ እንደ ፡ ዅነ ፡ ማን ፡ ያውቃል ፧

ዮና. ፡ 3 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከክፉ ፡ መንገዳቸው ፡ እንደተመለሱ ፡ ሥራቸውን ፡ አየ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ያደርግባቸው ፡ ዘንድ ፡ በተናገረው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ተጸጽቶ ፡ አላደረገውም ።

ትንቢተ ፡ ዮናስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ይህም ፡ ዮናስን ፡ ከቶ ፡ ደስ ፡ አላሠኘውም ፥ ርሱም ፡ ተቈጣ ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ጸለየና ፦ አቤቱ ፥ እለምንኻለኹ ፤ በአገሬ ፡ ሳለኹ ፡ የተናገርኹት ፡ ይህ ፡ አልነበረምን ፧ አንተ ፡ ቸርና ፡ ይቅር ፡ ባይ ፥ ታጋሽም ፥ ምሕረትኽም ፡ የበዛ ፥ ከክፉው ፡ ነገርም ፡ የተነሣ ፡ የምትጸጸት ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ዅንኽ ፡ ዐውቄ ፡ ነበርና ፥ ስለዚህ ፡ ወደ ፡ ተርሴስ ፡ ለመኰብለል ፡ ፈጥኜ ፡ ነበር ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 3 ፤ አኹንም ፥ አቤቱ ፥ ከሕይወት ፡ ሞት ፡ ይሻለኛልና ፥ እባክኽ ፥ ነፍሴን ፡ ከእኔ ፡ ውሰድ ፡ አለው ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፦ በእውኑ ፡ ትቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻልን ፧ አለ ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ዮናስም ፡ ከከተማዪቱ ፡ ወጣ ፥ ከከተማዪቱም ፡ በስተምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ተቀመጠ ፤ ከተማዪቱንም ፡ የሚያገኛትን ፡ እስኪያይ ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ለራሱ ፡ ዳስ ፡ ሠርቶ ፡ ከጥላው ፡ በታች ፡ ተቀመጠ ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔር ፡ አምላክም ፡ ቅል ፡ አዘጋጀ ፥ ከፍንቀቱም ፡ ታድነው ፡ ዘንድ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ጥላ ፡ እንድትኾን ፡ በዮናስ ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋት ፤ ዮናስም ፡ ስለ ፡ ቅሊቱ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 7 ፤ በነጋው ፡ ግን ፡ ወገግ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትልን ፡ አዘጋጀ ፥ ርሷም ፡ ቅሊቱን ፡ እስክትደርቅ ፡ ድረስ ፡ መታቻት ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኵስ ፡ የምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ አዘጋጀ ፡ ዮናስ ፡ እስኪዝል ፡ ድረስም ፡ ፀሓይ ፡ ራሱን ፡ መታው ፤ ለራሱም ፡ ሞትን ፡ ፈለገና ፦ ከሕይወት ፡ ሞት ፡ ይሻለኛል ፡ አለ ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዮናስን ፦ በእውኑ ፡ ስለዚች ፡ ቅል ፡ ትቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻልን ፧ አለው ። ርሱም ፦ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እቈጣ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ አለ ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔርም ፦ አንተ ፡ ትበቅል ፡ ዘንድ ፡ ላልደከምኽባት ፡ ላላሳደግኻትም ፥ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ለበቀለች ፥ ባንድ ፡ ሌሊትም ፡ ለደረቀችው ፡ ቅል ፡ አዝነኻል ።

ዮና. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እኔስ ፡ ቀኛቸውንና ፡ ግራቸውን ፡ የማይለዩ ፡ ከመቶ ፡ ኻያ ፡ ሺሕ ፡ የሚበልጡ ፡ ሰዎችና ፡ ብዙ ፡ እንስሳዎች ፡ ላሉባት ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ለነነዌ ፡ አላዝንምን ፧ አለው ፞

ትንቢተ ፡ ናሖም ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ናሖ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ ነነዌ ፡ የተነገረ ፡ ሸክም ፤ የኤልቆሻዊው ፡ የናሖም ፡ የራእዩ ፡ መጽሐፍ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ ቀናተኛና ፡ ተበቃይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተበቃይና ፡ መዓትን ፡ የተሞላ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ተቃዋሚዎቹን ፡ ይበቀላል ፥ ለጠላቶቹም ፡ ቍጣውን ፡ ይጠብቃል ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ትዕግሥተኛ ፥ ኀይሉም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ በደለኛውንም ፦ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ አይልም ፤ እግዚአብሔር ፡ በወጀብና ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ውስጥ ፡ መንገድ ፡ አለው ፥ ደመናም ፡ የእግሩ ፡ ትቢያ ፡ ነው ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ባሕሩንም ፡ ይገሥጻታል ፥ ያደርቃትማል ፥ ወንዞችንም ፡ ኹሉ ፡ ያደርቃል ፤ ባሳንና ፡ ቀርሜሎስም ፡ ላልተዋል ፥ የሊባኖስም ፡ አበባ ፡ ጠውልጓል ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ተራራዎችም ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ታወኩ ፥ ኰረብታዎችም ፡ ቀለጡ ፤ ምድርና ፡ ዓለም ፡ የሚኖሩበትም ፡ ኹሉ ፡ ከፊቱ ፡ ተናወጡ ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በቍጣው ፡ ፊት ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፧ የቍጣውንም ፡ ትኵሳት ፡ ማን ፡ ይታገሣል ፧ መዓቱ ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይፈሳል ፥ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ አለቶች ፡ ተሰነጠቁ ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ መልካም ፡ ነው ፥ በመከራ ፡ ቀንም ፡ መሸሸጊያ ፡ ነው ፤ በርሱ ፡ የሚታመኑትንም ፡ ያውቃል ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ስፍራዋን ፡ ግን ፡ በሚያጥለቀልቅ ፡ ጐርፍ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋታል ፥ ጠላቶቹንም ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ያሳድዳቸዋል ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የምታስቡት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠፋል ፥ መከራም ፡ ኹለተኛ ፡ አይነሣም ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንደ ፡ ተመሰቃቀለ ፡ ሾኽ ፡ ቢኾኑ ፥ በመጠጣቸውም ፡ ቢሰክሩ ፡ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ገለባ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠፋሉ ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ የሚያስብ ፥ ክፋትን ፡ የሚመክር ፥ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ወጥቷል ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ኀይለኞችና ፡ ብዙዎች ፡ ቢኾኑ ፡ እንዲሁ ፡ ይቈረጣሉ ፥ ርሱም ፡ ያልቃል ። እኔም ፡ አስጨንቄኻለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አላስጨንቅኽም ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ አኹንም ፡ ቀንበሩን ፡ ከአንተ ፡ እሰብራለኹ ፥ እስራትኽንም ፡ እበጥሳለኹ ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከስምኽ ፡ ማንም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳይዘራ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ አዟል ፤ ከአምላኮችኽ ፡ ቤት ፡ የተቀረጸውንና ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራውን ፡ ምስል ፡ አጠፋለኹ ፤ አንተም ፡ የተጠቃኽ ፡ ነኽና ፥ መቃብርኽን ፡ እምሳለኹ ።

ናሖ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ እንሆ ፥ የምሥራችን ፡ የሚያመጣ ፡ ሰላምንም ፡ የሚያወራ ፡ ሰው ፡ እግር ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ነው! ፡ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ አጥፊው ፡ ፈጽሞ ፡ ጠፍቷልና ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ አያልፍምና ፡ ዓመት ፡ በዓሎችኽን ፡ አድርግ ፥ ስእለቶችኽን ፡ ክፈል ።

ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ የሚቀጠቅጥ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ወጥቷል ፤ ምሽግን ፡ ጠብቅ ፥ መንገድንም ፡ ሰልል ፤ ወገብኽን ፡ አጽና ፥ ኀይልኽንም ፡ እጅግ ፡ አበርታ ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 2 ፤ ዘራፊዎች ፡ ዘርፈዋቸዋልና ፥ የወይናቸውንም ፡ ዐረግ ፡ አጥፍተዋልና ፥ እግዚአብሔር ፡ የያዕቆብን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ክብር ፡ ይመልሳል ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ የኀያላኑ ፡ ጋሻ ፡ ቀልቷል ፥ ጽኑዓንም ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ ለብሰዋል ። ርሱም ፡ በሚያዘጋጅበት ፡ ቀን ፡ ሠረገላዎች ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይንቦገቦጋሉ ፤ የጦሩም ፡ ሰማያ ፡ ይወዛወዛል ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ ሠረገላዎች ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ይነጉዳሉ ፥ አደባባይም ፡ ይጋጫሉ ፤ መልካቸው ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነው ፥ እንደ ፡ መብረቅም ፡ ይከንፋሉ ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ መሳፍንቱን ፡ ያስባል ፤ በአረማመዳቸው ፡ ይሰናከላሉ ፤ ፈጥነው ፡ በቅጥሯ ፡ ላይ ፡ ይወጣሉ ፥ መጠጊያም ፡ ተዘጋጀለት ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 6 ፤ የወንዞቹም ፡ መዝጊያዎች ፡ ተከፈቱ ፥ የንጉሡ ፡ ቤትም ፡ ቀለጠች ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 7 ፤ ንግሥት ፡ ተገለጠች ፥ ተማረከችም ፥ ሴቶች ፡ ባሪያዎቿም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ እየጮኹና ፡ ደረታቸውን ፡ እየመቱ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 8 ፤ ነነዌ ፡ ግን ፡ ከዱሮ ፡ ዘመን ፡ ዝምራ ፡ እንደ ፡ ተከማች ፡ ውሃ ፡ ነበረች ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ይሸሻሉ ፤ እነርሱም ፦ ቁሙ ፥ ቁሙ ፡ ይላሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የሚመለስ ፡ የለም ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 9 ፤ መዝገቧ ፡ መጨረሻ ፡ የለውምና ፥ የከበረውም ፡ የዕቃዋ ፡ ዥሉ ፡ ብዛት ፡ አይቈጠርምና ፡ ብሩን ፡ በዝብዙ ፥ ወርቁንም ፡ በዝብዙ ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 10 ፤ ባዶና ፡ ባድማ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ኾናለች ፤ ልብ ፡ ቀልጧል ፥ ጕልበቶችም ፡ ተብረክርከዋል ፤ በወገብም ፡ ዥሉ ፡ ሕማም ፡ አለ ፥ የሰዎችም ፡ ዥሉ ፡ ፊት ፡ ጠቍሯል ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 11 ፤ የአንበሳዎችም ፡ መደብ ፥ የአንበሳዎችም ፡ ደቦል ፡ የሚሰማራበት ፥ አንበሳውና ፡ አንበሳዩቱ ፡ ግልገሉም ፡ ሳይፈሩ ፡ የሚኼዱት ፡ ስፍራ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧

ናሖ. ፥ 2 ፥ 12 ፤ አንበሳው ፡ ለልጆቹ ፡ የሚበቃውን ፡ ነጠቀ ፥ ለእንስቶቹም ፡ ሰበረላቸው ፡ ዋሻውን ፡ በንጥቂያ ፥ መደቡንም ፡ በቅሚያ ፡ ሞልቶታል ።

ናሖ. ፥ 2 ፥ 13 ፤ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሠረገላዎቿንም ፡ አቃጥዬ ፡ አጤሳለኹ ፥ ሰይፍም ፡ የአንበሳ ፡ ደቦሎችሽን ፡ ይበላቸዋል ፤ ንጥቂያሽንም ፡ ከምድር ፡ አጠፋለኹ ፥ የመልክተኞችሽን ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይሰማም ።

ትንቢተ ፡ ናሖም ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ናሖ. ፥ 3 ፥ 1 ፤ ለደም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! ፡ በሹለንተናዋ ፡ ሐሰትና ፡ ቅሚያ ፡ ሞልቶባታል ፤ ንጥቂያ ፡ ከርሷ ፡ አያልቅም ።

ናሖ. ፥ 3 ፥ 2 ፤ የዐለንጋ ፡ ድምፅ ፥ የመንኰራኵርም ፡ ድምፅ ፥ የፈረሶችም ፡ ኰቴ ፥ የፈጣን ፡ ሠረገላም ፡ ጭኸት ፡ ተሰምቷል ፤

ናሖ. ፥ 3 ፥ 3 ፤ ፈረሰኛው ፡ ይጋልባል ፥ ሰይፍም ፡ ይንቦገቦጋል ፥ ጦርም ፡ ይብለጨለጫል ፤ የተገደሉትም ፡

ይበዛሉ ፥ በድኖችም ፡ በክምር ፡ ይከመራሉ ፥ ሬሳቸውም ፡ አይቈጠርም ፤ በሬሳቸውም ፡ ይሰናከላሉ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ስለተዋበችው ፡ ጋለሞታ ፡ ግልሙትና ፡ ብዛት ፡ ይህ ፡ ኾኗል ፤ ርኳም ፡ በመተታ ፡ እጅግ ፡ በለጠች ፥ አሕዛብንም ፡ በግልሙትናዋ ፥ ወገኖችንም ፡ በመተታ ፡ ሸጠች ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እንሆ ፥ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ልብስሽን ፡ በፊትሽ ፡ እገልጣለኹ ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋሽንም ፡ ለአሕዛብ ፥ ነውርሽንም ፡ ለመንግሥታት ፡ አሳያለኹ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ርኵሰትንም ፡ በላይሽ ፡ እጥላለኹ ፥ እንቅሽማለኹ ፥ ማላገጫም ፡ አደርግሻለኹ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የሚያይሽም ፡ ኹሉ ፡ ከአንቺ ፡ ሸሽቶ ፦ ነነዌ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፤ የሚያለቅስላትስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ የሚያጽናናትንስ ፡ ከወዴት ፡ እፈልጋለኹ ፧ ይላል ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ አንቺ ፡ በመስኖች ፡ መካከል ፡ ከተቀመጠችው ፥ ውሃም ፡ በዙሪያዋ ፡ ከነበራት ፥ ምሽጓም ፡ ባሕር ፡ ከነበረ ፥ ቅጥሯም ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ከነበረ ፡ ከኖእ ፡ ዐሞን ፡ ትበልጣለሽን ፧

ናሖ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ኢትዮጵያና ፡ ግብጽ ፡ የማይቈጠር ፡ ኀይሏ ፡ ነበሩ ፤ ፉጥና ፡ ልብያ ፡ ረዳቶቿ ፡ ነበሩ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ርኳ ፡ ግን ፡ ተማርካ ፡ ፈለሰች ፤ ሕፃናቷ ፡ በመንገድ ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ተፈጠፈጡ ፤ በከበርቴዎቿም ፡ ላይ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉ ፥ ታላላቆቿም ፡ ኹሉ ፡ በሰንሰለት ፡ ታሰሩ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ አንቺም ፡ ትሰክሪያለሽ ፡ ወራዳም ፡ ትኾኛለሽ ፤ አንቺ ፡ ደግሞ ፡ ከጠላት ፡ የተነሣ ፡ መጠጊያን ፡ ትፈልጊያለሽ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ዐምባሽ ፡ ኹሉ ፡ የመዠመሪያውን ፡ የበሰለ ፡ ፍሬ ፡ እንደ ፡ ያዙ ፡ እንደ ፡ በለስ ፡ ዛፎች ፡ ነው ፤ ቢወዛወዝ ፡ በሚበላው ፡ አፍ ፡ ውስጥ ፡ ይወድቃል ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ እንሆ ፥ በመካከልሽ ፡ ያሉ ፡ ሕዝብሽ ፡ ሴቶች ፡ ናቸው ፤ የአገርሽ ፡ በሮች ፡ ለጠላቶችሽ ፡ ፈጽሞ ፡ ተከፍተዋል ፥ እሳትም ፡ መወርወሪያዎችኽን ፡ በልቷል ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ከዕው ፡ ያስጨንቁሻልና ፥ ውሃን ፡ ቅዂ ፤ ዐምባሽን ፡ አጠንክሪ ፤ ወደ ፡ ጭቃ ፡ ገብተሽ ፡ ርገጪ ፤ የጡብን ፡ መሠሪያ ፡ ያዢ ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ በዚያ ፡ እሳት ፡ ይበላሻል ፥ ሰይፍ ፡ ያጠፋሻል ፥ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ይበላሻል ፤ እንደ ፡ ደጐብያ ፡ ብዛር ፥ እንደ ፡ አንበጣም ፡ ተባዛር ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ነጋዴዎችሽን ፡ ከሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ይልቅ ፡ አበዛሽ ፤ ደጐብያ ፡ ተዘረጋ ፥ በረረም ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ባንቺ ፡ ዘንድ ፡ ዘውድ ፡ የጫኑት ፡ እንደ ፡ አንበጣ ፥ አለቃዎችሽም ፡ እንደሚንቀሳቀሱ ፡ ኵብኵባዎች ፡ ናቸው ፤ በብርድ ፡ ቀን ፡ በቅጥር ፡ ውስጥ ፡ ይቀመጣሉ ፥ ፀሓይም ፡ በወጣች ፡ ጊዜ ፡ ያኰበኵባሉ ፤ ስፍራቸው ፡ በየት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይታወቅም ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ የአሶር ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ እረኞችኽ ፡ አንቀላፍተዋል ፤ መኳንንቶችኽም ፡ ዐርፈዋል ፤ ሕዝብኽም ፡ በተራራዎች ፡ ላይ ፡ ተበትኗል ፥ የሚሰበስበውም ፡ የለም ።

ናሖ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ስብራትኽ ፡ አይፈወስም ፥ ቀኑስልኽም ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ወሬኽንም ፡ የሚሰሙ ፡ ኹሉ ፡ እጃቸውን ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ያጨበጭባሉ ፤ ክፋትኽ ፡ ኹልጊዜ ፡ ያላለፈችበት ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነውና ❖

ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዕን. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ነቢዩ ፡ ዕንባቆም ፡ ያየው ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 2 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ስጮኽ ፡ የማትሰማው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ ስለ ፡ ግፍ ፡ ወዳንተ ፡ እጮኻለኹ ፥ አንተም ፡ አታድንም ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በደልንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሳየኸኝ ፧ ጠማምነትንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትመለከታለኽ ፧ ጥፋትና ፡ ግፍ ፡ በፊቴ ፡ ነው ፤ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ይነሣሉ ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ስለዚህ ፥ ሕግ ፡ ላልታል ፥ ፍርድም ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አይወጣም ፤ ኀጢአተኛ ፡ ጻድቅን ፡ ይከባ፡ልና ፤ ስለዚህ ፥ ፍርድ ፡ ጠማማ ፡ ኾኖ ፡ ይወጣል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 5 ፤ እናንተ ፡ የምትንቁ ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ቢተርክላችኹ ፡ ስንኳ ፡ የማታምኑትን ፡ ሥራ ፡ በዘመናችኹ ፡ እሠራለኹና ፡ እዩ ፥ ተመልከቱ ፥ ተደነቁ ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እንሆ ፥ የእነርሱ ፡ ያልኾነውን ፡ መኖሪያ ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ስፋት ፡ ላይ ፡ የሚኼዱትን ፡ መራሮችንና ፡ ፈጣኖችን ፡ ሕዝብ ፡ ከለዳውያንን ፡ አስነሣለኹ ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እነርሱ ፡ የሚያስፈሩና ፡ የሚያስደነግጡ ፡ ናቸው ፤ ፍርዳቸውና ፡ ክብራቸው ፡ ከራሳቸው ፡ ይወጣል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ፈረሶቻቸውም ፡ ከነብር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ፥ ከማታም ፡ ተኵላ ፡ ይልቅ ፡ ጨካኞች ፡ ናቸው ፤ ፈረሰኞቻቸውም ፡ ይንሳፈፋሉ ፥ ከሩቅም ፡ ይመጣሉ ፥ ለመብልም ፡ እንደሚቸኵል ፡ ንስር ፡ ይበ፡ራሉ ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ኹሉም ፡ ለግፍ ፡ ሥራ ፡ ይመጣሉ ፥ ፊታቸውንም ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ያቀናሉ ፤ ምርኮኞችንም ፡ እንደ ፡ አሸዋ ፡ ይሰበስባሉ ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በነገሥታት ፡ ላይ ፡ ያላግጣሉ ፥ መሳፍንትም ፡ ዋዛ ፡ ኾነውላቸዋል ፤ በምሽጉ ፡ ኹሉ ፡ ይሥቃሉ ፥ ዐፈሩንም ፡ ከምረው ፡ ይወስዱታል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ዐልፎ ፡ ይኼዳል ፥ ይበድልማል ፤ ኀይሉንም ፡ አምላክ ፡ ያደርገዋል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 12 ፤ አቤቱ ፥ የተቀደስኽ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ከዘለዓለም ፡ ዠምሮ ፡ አልነበርኽምን ፧ እኛ ፡ አንሞትም ፤ አቤቱ ፥ ለፍርድ ፡ ሠርተኸዋል ፥ ለተግሣጽም ፡ አድርገኸዋል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ክፉ ፡ እንዳያዩ ፡ ንጹሓን ፡ ናቸው ፥ ጠማምነትንም ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ፤ አታላዮችንስ ፡ ለምን ፡ ትመለከታለኽ ፧ ኀጢአተኛውስ ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ጻድቅ ፡ የኾነውን ፡ ሲውጠው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ትላለኽ ፧

ዕን. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ሰዎችንም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ዓሣዎች ፥ አለቃም ፡ እንደሌላቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ለምን ፡ ታደርጋቸዋለኽ ፧

ዕን. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ኹሉን ፡ በመቃጥን ፡ ያወጣል ፥ በመረቡም ፡ ይይዛቸዋል ፥ በአሽክላውም ፡ ውስጥ ፡

ያከማቻቸዋል ፤ ስለዚህ ፥ ደስ ፡ እያለው ፡ እልል ፡ ይላል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ በእነርሱ ፡ ሰብታለችና ፥ መብሉም ፡ በዝቷልና ፥ ስለዚህ ፡ ለመረቡ ፡ ይሠዋል ፥ ለአሽክላውም ፡ ያጥናል ።

ዕን. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ስለዚህ ፥ መረቡን ፡ ይጥላልን ፧ አሕዛብንም ፡ ዘወትር ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ አይራራምን ፧

_____ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዕን. ፥ 2 ፥ 1 ፤ በመጠበቂያዬ ፡ ላይ ፡ እቆማለኹ ፥ በዐምባ ፡ ላይም ፡ እወጣለኹ ፤ የሚናገረኝንም ፥ ስለ ፡ ክርክሬም ፡ የምመልሰውን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ እመለከታለኹ ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ አንባቢው ፡ ይፈጥን ፡ ዘንድ ፡ ራእዩን ፡ ጻፍ ፥ በጽላትም ፡ ላይ ፡ ግለጠው ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 3 ፤ ራእዩ ፡ ገና ፡ እስከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ፍጻሜውም ፡ ይቸኵላል ፥ ርሱም ፡ አይዋሽም ፤ ቢዘገይም ፡ በርግጥ ፡ ይመጣልና ፥ ታገሠው ፤ ርሱ ፡ አይዘገይም ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 4 ፤ እንሆ ፥ ነፍሱ ፡ ኰርታለች ፥ በውስጡም ፡ ቅን ፡ አይደለችም ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ በእምነቱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 5 ፤ ርሱ ፡ አታላይና ፡ ኵሩ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ በስፍራው ፡ ዐርፎ ፡ አይቀመጥም ፤ ሥሥቱን ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ያሰፋል ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ሞት ፡ አይጠግብም ፤ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይሰበስባል ፥ ወገኖቹንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያከማቻል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 6 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፦ ለርሱ ፡ ያልኾነውን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለሚሰበስብ ፡ መያዣውንም ፡ ለራሱ ፡ የሚያበዛ ፡ ወዮለት! ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ እያሉ ፡ ምሳሌ ፡ አይመስሉበትምን ፧

ዕን. ፥ 2 ፥ 7 ፤ ተረትም ፡ አይተርቱበትምን ፧ የሚነክሱኽ ፡ ድንገት ፡ አይነሡብኽምን ፧ የሚያስጨንቁኽም ፡ ይነቃሉ ፤ ለእነርሱም ፡ ብዝበዛ ፡ ትኾናለኽ ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 8 ፤ የሰውን ፡ ደም ፡ ስላፈሰስኽ ፥ በምድሪቱና ፡ በከተማዪቱም ፡ በርሷም ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡ ግፍ ፥ አንተ ፡ ብዙዎችን ፡ አሕዛብን ፡ በዝብዘኻልና ፥ ከአሕዛብ ፡ የቀሩት ፡ ኹሉ ፡ ይበዘብዙኻል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 9 ፤ ከክፉ ፡ እንዲድን ፡ ጐጆውን ፡ በከፍታ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱ ፡ ክፉ ፡ ትርፍን ፡ ለሚሰበስብ ፡ ወዮለት! ፡

ዕን. ፥ 2 ፥ 10 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍተኻልና ፥ ለቤትኽ ፡ ዕፍረትን ፡ መክረኻል ፥ በነፍስኽም ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ አድርገኻል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 11 ፤ ድንጋይም ፡ ከግንብ ፡ ውስጥ ፡ ይጮኻል ፥ ዕንጨትም ፡ ከውቅር ፡ ውስጥ ፡ ይመልስለታል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 12 ፤ ከተማን ፡ በደም ፡ ለሚሠራ ፥ ከተማንም ፡ በኀጢአት ፡ ለሚመሠርት ፡ ወዮለት! ፡

ዕን. ፥ 2 ፥ 13 ፤ እንሆ ፥ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ እሳት ፡ እንዲሠሩ ፥ ወገኖችም ፡ ስለ ፡ ከንቱነት ፡ እንዲደክሙ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ አይደለምን ፧

ዕን. ፥ 2 ፥ 14 ፤ ውሃ ፡ ባሕርን ፡ እንደሚከድን ፥ ምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ በማወቅ ፡ ትሞላለችና ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 15 ፤ ጎፍረተ ፡ ሥጋውን ፡ ለማየት ፡ ባልንጀራውን ፡ ለሚያጠጣ ፥ ክፉንም ፡

ለሚጨምርበት ፥ ለሚያሰክረውም ፡ ወዮለት! ፡

ዕን. ፥ 2 ፥ 16 ፤ በክብር ፡ ፋንታ ፡ ዕፍረት ፡ ሞልቶብኻል ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ጠጥተኽ ፡ ተንገድገድ ፤ የእግዚአብሔር ፡ የቀኙ ፡ ጽዋ ፡ ይመለስብኻል ፥ ዕፍረትም ፡ በክብርኽ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 17 ፤ የሰውንም ፡ ደም ፡ ስላፈሰስኽ ፥ በምድሪቱና ፡ በከተማዪቱም ፡ በርሷም ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡ ግፍ ፥ በሊባኖስ ፡ ላይ ፡ የሠራኸው ፡ ግፍ ፡ ይከድንኻል ፤ የአራዊትም ፡ አደጋ ፡ ያስፈራራኻል ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 18 ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ሠሪው ፡ የቀረጸው ፡ ለምን ፡ ጥቅም ፡ ነው ፧ ዲዳንም ፡ ጣዖት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሠሪው ፡ የታመነበቱ ፥ ሐሰትን ፡ የሚያስተምር ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፧

ዕን. ፥ 2 ፥ 19 ፤ ዕንጨቱን ፦ ንቃ ፥ ዲዳውንም ፡ ድንጋይ ፦ ተነሣ ፡ ለሚለው ፡ ወዮለት! ፡ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ያስተምራልን ፧ እንሆ ፥ በወርቅና ፡ በብር ፡ ተለብጧል ፥ ምንም ፡ እስትንፋስ ፡ የለበትም ።

ዕን. ፥ 2 ፥ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በተቀደሰ ፡ መቅደሱ ፡ አለ ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ዝም ፡ ትበል ።

ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 1 ፤ የነቢዩ ፡ የዕንባቆም ፡ ጸሎት ፡ በመዝሙር ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 2 ፤ አቤቱ ፥ ዝናኽን ፡ ሰምቼ ፡ ፈራኹ ፤ አቤቱ ፥ በዓመታት ፡ መካከል ፡ ሥራኽን ፡ ፈጽም ፤ በዓመታት ፡ መካከል ፡ ትታወቅ ፤ በመዓት ፡ ጊዜ ፡ ምሕረትን ፡ ዐስብ ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከቴማን ፥ ቅዱሱም ፡ ከፋራን ፡ ተራራ ፡ ይመጣል ። ክብሩ ፡ ሰማያትን ፡ ከድኗል ፥ ምስጋናውም ፡ ምድርን ፡ ሞልቷል ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 4 ፤ ጸዳሉም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ ጨረር ፡ ከእጁ ፡ ወጥቷል ፤ ኀይሉም ፡ በዚያ ፡ ተሰውሯል ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 5 ፤ ቸነፈር ፡ በፊቱ ፡ ይኼዳል ፥ የእሳትም ፡ ነበልባል ፡ ከእግሩ ፡ ይወጣል ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 6 ፤ ቆመ ፥ ምድርንም ፡ አወካት ፤ ተመለከተ ፥ አሕዛብንም ፡ አናወጠ ፤ የዘለዓለምም ፡ ተራራዎች ፡ ተቀጠቀጡ ፥ የዘለዓለምም ፡ ኰረብታዎች ፡ ቀለጡ ፤ መንገዱ ፡ ከዘለዓለም ፡ ነው ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 7 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ድንኳኖች ፡ ሲጨነቁ ፡ አየኹ ፤ የምድያም ፡ አገር ፡ መጋረጃዎች ፡ ተንቀጠቀጡ ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 8 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፡ ተቈጥቷልን ፧ ቍጣኽ ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፥ መዓትኽም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ነውን ፧ በፈረሶችኽና ፡ በማዳንኽ ፡ ሠረገላዎች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠኻልና ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 9 ፤ በቃልኽ ፡ እንደ ፡ ማልኽ ፡ መቅሠፍትኽን ፡ አወጣኽ ፤ ቀስትኽንም ፡ ገተርኽ ፤ ምድርን ፡ ሰንጥቀኽ ፡ ፈሳሾችን ፡ አወጣኽ ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 10 ፤ ተራራዎች ፡ አንተን ፡ አይተው ፡ ተጨነቁ ፤ የውሃ ፡ ሞገድ ፡ ዐልፏል ፤ ቀላዩም ፡ ድምፁን ፡ ሰጥቷል ፥ እጁንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥቷል ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 11 ፤ ፍላጻዎችኽ ፡ ከወጡበት ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፥ ከሚንቦገቦገውም ፡ ከጦርኽ ፡ ጸዳል ፡ የተነሣ ፥ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡ በመኖሪያቸው ፡ ቆሙ ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 12 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በመዓት ፡ ተራመድኽ ፤ አሕዛብን ፡ በቍጣ ፡ አኼድኻቸው ።

ዕን. ፥ 3 ፥ 13 ፤ ሕዝብኽን ፡ ለመታደግ ፥ የቀባኽውንም ፡ ለማዳን ፡ ወጣኽ ፤ የኀጢአተኛውን ፡ ቤት ፡ ራስ ፡

ቀጠቀጥኽ ፤ መሠረቱን ፡ እስከ ፡ ዐንገቱ ፡ ድረስ ፡ ገለጥኽ ።

ዕን. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የአለቃዎችን ፡ ራስ ፡ በገዛ ፡ በትራቸው ፡ ወጋኽ ፤ እኔን ፡ ይበትኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ መጡ ፤ ችግረኛውን ፡ በስውር ፡ ለመዋጥ ፡ ደስታቸው ፡ ነው ።

ዕን. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ፈረሶችኽን ፡ በባሕር ፥ በብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ ላይ ፡ አስረገጥኽ ።

ዕን. ፡ 3 ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ልቤም ፡ ደነገጠብኝ ፤ ከድምፁ ፡ የተነሣ ፡ ከንፈሮቼ ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ መንቀጥቀጥ ፡ ወደ ፡ ዐጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ በስፍራዬ ፡ ኾኜ ፡ ተናወጥኹ ፤ በሚያስጨንቁን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የመከራን ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ እጠብቃለኹ ።

ዕን. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በለስም ፡ ባታፈራ ፥ በወይንም ፡ ሐረግ ፡ ፍሬ ፡ ባይገኝ ፥ የወይራ ፡ ሥራ ፡ ቢጐድል ፥ ዕርሾችም ፡ መብልን ፡ ባይሰጡ ፥ በጎች ፡ ከበረቱ ፡ ቢጠፉ ፥ ላሞችም ፡ በጋጡ ፡ ውስጥ ፡ ባይገኙ ፥

ዕን. ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ በመድኀኒቴ ፡ አምላክ ፡ ሐሤት ፡ አደርጋለኹ ።

ዕን. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይሌ ፡ ነው ፤ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ዋላ ፡ እግሮች ፡ ያደርጋል ፤ በከፍታዎችም ፡ ላይ ፡ ያስኼደኛል ❖

ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በዓሞጽ ፡ ልጅ ፡ በኢዮስያስ ፡ ዘመን ፡ ወደሕዝቅያስ ፡ ልጅ ፡ ወደአማርያ ፡ ልጅ ፡ ወደጎዶልያስ ፡ ልጅ ፡ ወደኩሲ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ሶፎንያስ [278] ፡ የመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦—

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ነገርን ፡ ሹሉ ፡ ከምድር ፡ ፊት ፡ ፈጽሜ ፡ አጠፋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ሰውንና ፡ እንስሳን ፡ አጠፋለኹ ፤ የሰማይን ፡ ወፎችና ፡ የባሕርን ፡ ዓሣዎች ፡ ማሰናከያንም ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ አጠፋለኹ ፤ ሰውንም ፡ ከምድር ፡ ፊት ፡ እቈርጣለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ እጄንም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚኖሩት ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ እዘረጋለኹ ፤ ከዚህም ፡ ስፍራ ፡ የበዓልን ፡ ቅሬታና ፡ የጣዖታቱን ፡ ካህናት ፡ ስም ፡ አጠፋለኹ ፤

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በሰገነትም ፡ ላይ ፡ ለሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ የሚሰግዱትን ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በንጉሣቸው ፡ በሚልኮም ፡ ምለው ፡ የሚሰግዱትን ፥

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ከመከተል ፡ የተመለሱትን ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ያልፈለጉትንና ፡ ያልጠየቁትን ፡ አጠፋለኹ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቧልና ፥ እግዚአብሔር ፡ መሥዋዕትን ፡ አዘጋጅቷልና ፥ የጠራቸውንም ፡ ቀድሷልና ፥ በጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ በሉ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ መሥዋዕት ፡ ቀን ፡ አለቃዎችንና ፡ የንጉሥን ፡ ልጆች ፡ እንግዳ ፡ ልብስ ፡ የሚለብሱትንም ፡ ሹሉ ፡ እቀጣለኹ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በመድረኩ ፡ ላይ ፡ የሚዘሉትን ፥ የጌታቸውን ፡ ቤት ፡ ዐመፃንና ፡ ሽንገላን ፡ የሚሞሉትን ፡ እቀጣለኹ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ከዓሣው ፡ በር ፡ የጩኸት ፡ ድምፅ ፥ ከከተማውም ፡ በኹለተኛው ፡ ክፍል ፡ ውካታ ፥ ከኰረብታዎቹም ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ ይኾናል ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እናንተ ፡ በመክቴሽ ፡ የምትኖሩ ፡ ሆይ ፥ የከነዓን ፡ ሕዝብ ፡ ሹሉ ፡ ጠፍተዋልና ፥ ብርም ፡ የተሸከሙ ፡ ሹሉ ፡ ተቈርጠዋልና ፥ አልቅሱ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ በመብራት ፡ እመረምራለኹ ፤ በአተላቸውም ፡ ላይ ፡ የሚቀመጡትን ፥ በልባቸውም ፦— እግዚአብሔር ፡ መልካምን ፡ አያደርግም ፥ ክፉም ፡ አያደርግም ፡ የሚሉትን ፡ ሰዎች ፡ እቀጣለኹ ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ብልጥግናቸውም ፡ ለምርኮ ፡ ይኾናል ፥ ቤቶቻቸውም ፡ ይፈርሳሉ ፤ ቤቶችንም ፡ ይሠራሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አይቀመጡባቸውም ፤ ወይንንም ፡ ይተክላሉ ፥ የወይን ፡ ጠጁን ፡ ግን ፡ አይጠጡም ።

ሶፎ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ታላቁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ቀርቧል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ድምፅ ፡ ቀርቧል ፡ እጅግም ፡ ፈጥኗል ፤ ኀያሉም ፡ በዚያ ፡ በመራራ ፡ ልቅሶ ፡ ይጮኻል ።

---

278 ዕብ. ፥ ጸፋንያህ ፡ (ጸፈነ ፡ እግዚእ • ጌታ ፡ ሰወረ ፥ ጨፈነ) ።

ሶፎ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ያ ፡ ቀን ፡ የመዓት ፡ ቀን ፡ የመከራና ፡ የጭንቀት ፡ ቀን ፥ የመፍረስና ፡ የመጥፋት ፡ ቀን ፥ የጨለማና ፡ የጭጋግ ፡ ቀን ፥ የደመናና ፡ የድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ቀን ፥

ሶፎ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ በተመሸጉ ፡ ከተማዎችና ፡ በረዘሙ ፡ ግንቦች ፡ ላይ ፡ የመለከትና ፡ የሰልፍ ፡ ጩኸት ፡ ቀን ፡ ነው ።

ሶፎ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሠርተዋልና ፥ እንደ ፡ ዕውር ፡ እስኪ ኼዱ ፡ ድረስ ፡ ሰዎችን ፡ አስጨንቃለኹ ፤ ደማቸውም ፡ እንደ ፡ ትቢያ ፥ ሥጋቸውም ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ ይፈሳል ።

ሶፎ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ቀን ፡ ብራቸውና ፡ ወርቃቸው ፡ ሊያድናቸው ፡ አይችልም ፤ ርሱም ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ኹሉ ፡ ፈጥኖ ፡ ይጨርሳቸዋልና ፥ ምድር ፡ ኹሉ ፡ በቅንአቱ ፡ እሳት ፡ ትበላለች ።

_____ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 1-2 ፤ እናንተ ፡ ዕፍረት ፡ የሌላችኹ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ ትእዛዝ ፡ ሳይወጣ ፥ ቀኑም ፡ እንደ ፡ ገለባ ፡ ሳያልፍ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ትኵሳት ፡ ሳይመጣባችኹ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ቀን ፡ ሳይደርስባችኹ ፡ ተሰብሰቡ ፥ ተከማቹም ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እናንተ ፡ ፍርዱን ፡ የጠበቃችኹ ፡ የምድር ፡ ትሑታን ፡ ኹሉ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ፈልጉ ፤ ጽድቅንም ፡ ፈልጉ ፥ ትሕትናንም ፡ ፈልጉ ፤ ምናልባት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ቀን ፡ ትሰወሩ ፡ ይኾናል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ጋዛ ፡ ትበረበራለች ፥ አስቀሎናም ፡ ባድማ ፡ ትኾናለች ፤ አዞጦንንም ፡ በቀትር ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ያሳድዷታል ፥ ዐቃሮንም ፡ ትነቀላለች ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በባሕር ፡ ዳር ፡ ለሚኖሩ ፡ ለከሊታውያን ፡ ሕዝብ ፡ ወዮላቸው! ፡ የፍልስጥኤማውያን ፡ ምድር ፡ ከነዓን ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነው ፥ የሚቀመጥብኽም ፡ ሰው ፡ እንዳይኖር ፡ አጠፋኻለኹ ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ቀርጤስም ፡ የእረኞች ፡ መኖሪያና ፡ የመንጋዎች ፡ በረት ፡ ይኾናል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ የባሕሩም ፡ ዳር ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ቅሬታ ፡ ይኾናል ፥ በዚያም ፡ ይሰማራሉ ፤ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጐበኛቸዋልና ፥ ምርኳቸውንም ፡ ይመልሳልና ፥ በአስቀሎና ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ ማታ ፡ ይተኛሉ ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በሕዝቤም ፡ ላይ ፡ ያላገጡባትን ፥ በድንበራቸውም ፡ ላይ ፡ እየታበዩ ፡ የተናገሩባትን ፡ የሞዐብን ፡ ማላገጥና ፡ የዐሞንን ፡ ልጆች ፡ ስድብ ፡ ሰምቻለኹ ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ የእስራኤል ፡ አምላክ ፣ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ በርግጥ ፡ ሞዐብ ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፥ የዐሞንም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ገሞራ ፥ የሳማ ፡ ስፍራና ፡ የጨው ፡ ጕድጓድ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኾነው ፡ ይኖራሉ ፤ የሕዝቤም ፡ ቅሬታ ፡ ይበዘብዛቸዋል ፥ ከወገኔም ፡ የተረፉት ፡ ይወርሷቸዋል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ አላግጠዋልና ፥ እየታበዩም ፡ ተናግረዋልና ፥ ይህ ፡ ስለ ፡ ትዕቢታቸው ፡ ያገኛቸዋል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የተፈራ ፡ ይኾናል ፥ የምድርንም ፡ አማልክት ፡ ኹሉ ፡ ያከሳቸዋል ፤ በአሕዛብም ፡ ደሴቶች ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በስፍራቸው ፡ ኾነው ፡ ለርሱ ፡ ይሰግዳሉ ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ እናንተም ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ደግሞ ፥ በሰይፌ ፡ ትገደላላችኹ ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ በሰሜን ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ይዘረጋል ፥ አሶርንም ፡ ያጠፋል ፤ ነነዌንም ፡ ባድማ ፥ እንደ ፡

በረሓም ፡ ደረቅ ፡ ያደርጋታል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ መንጋዎችም ፡ የምድርም ፡ አራዊት ፡ ኹሉ ፡ በውስጧ ፡ ይመሰጋሉ ፤ ይብራና ፡ ጕርት ፡ በዐምዶቿ ፡ መካከል ፡ ያድራሉ ፤ ድምፃቸው ፡ በመስኮቶቿ ፡ ይጮኻል ፤ የዝግባም ፡ ዕንጨት ፡ ሥራ ፡ ይገለጣልና ፥ በመድረኮቿ ፡ ላይ ፡ ጥፋት ፡ ይኾናል ።

ሶፎ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ተዘልላ ፡ የተቀመጠች ፥ በልቧም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ያለች ፡ ደስተኛዪቱ ፡ ከተማ ፡ ይህች ፡ ናት ፤ አራዊት ፡ የሚመሰጉባት ፡ ባድማ ፡ እንዴት ፡ ኾነች! ፡ በርሷ ፡ በኩል ፡ የሚያልፈው ፡ ኹሉ ፡ እጁን ፡ እያወዛወዘ ፡ ያፏጫል ።

ትንቢተ ፡ ሶፎንያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ለዐመፀኛዪቱና ፡ ለረከሰች ፡ ለአስጨናቂዪቱም ፡ ከተማ ፡ ወዮላት! ፡

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ድምፅን ፡ አልሰማችም ፥ ተግሣጽንም ፡ አልተቀበለችም ፤ በእግዚአብሔርም ፡ አልታመነችም ፥ ወደ ፡ አምላኳም ፡ አልቀረበችም ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በውስጧ ፡ ያሉ ፡ አለቃዎቿ ፡ እንደሚያገሡ ፡ አንበሳዎች ፡ ናቸው ፤ ፈራጆቿም ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንደማያስቀሩ ፡ እንደ ፡ ማታ ፡ ተኵላዎች ፡ ናቸው ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ነቢያቷ ፡ ቅሌታሞችና ፡ ተንኰለኞች ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፤ ካህናቷም ፡ መቅደሱን ፡ አርክሰዋል ፥ በሕግም ፡ ላይ ፡ ግፍ ፡ ሠርተዋል ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ በውስጧ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ፤ ክፋትን ፡ አያደርግም ፤ ፍርዱን ፡ በየማለዳው ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ያወጣል ፥ ሳያወጣውም ፡ አይቀርም ፤ ዐመፀኛው ፡ ግን ፡ ዕፍረትን ፡ አያውቅም ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ አሕዛብን ፡ አጥፍቻለኹ ፤ ግንቦቻቸው ፡ ኹሉ ፡ ፈርሰዋል ፤ መንገዳቸውን ፡ ማንም ፡ እንዳያልፍባት ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አድርጌያለኹ ፥ ከተማዎቻቸውም ፡ ማንም ፡ እንዳይኖርባቸው ፥ አንድስ ፡ እንኳ ፡ እንዳይቀመጥባቸው ፡ ፈርሰዋል ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እኔም ፦ ይፈሩኛል ፥ ተግሣጽንም ፡ ይቀበላሉ ፤ ካዘዝኋትም ፡ ኹሉ ፡ ከዐይኗ ፡ ምንም ፡ አይጠፋም ፡ ብዬ ፡ ነበር ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ በማለዳ ፡ ተነሥተው ፡ ድርጊታቸውን ፡ ኹሉ ፡ አረከሱ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ መዓቴንና ፡ የቀኑጣዬን ፡ ትኵሳት ፡ ኹሉ ፡ አፈስባቸው ፡ ዘንድ ፡ ፍርዴ ፡ አሕዛብን ፡ ለመሰብሰብ ፥ መንግሥታትንም ፡ ለማከማቸት ፡ ነውና ፥ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ በቅንአቴ ፡ እሳት ፡ ትበላለችና ፡ ስለዚህ ፡ ለመበዝበዝ ፡ እስከምነሣበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ጠብቂኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ኾነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያገለግሉት ፡ ዘንድ ፡ ስሙን ፡ እንዲጠሩ ፡ ንጹሓን ፡ ልሳን ፡ እመልስላቸዋለኹ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ወንዞች ፡ ማዶ ፡ የሚማልዱኝ ፥ የተበተኑት ፡ ሴቶች ፡ ልጆቼ ፥ ቍርባኔን ፡ ያመጡልኛል ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እየታበዩ ፡ የሚፎክሩትን ፡ ከመካከልሽ ፡ አወጣለኹና ፥ አንቺም ፡ በቅዱስ ፡ ተራራዬ ፡ ዳግመኛ ፡ አትኰሪምና ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተላልፈሽ ፡ በሠራሽው ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አትፍሪም ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ በመካከልሽም ፡ የዋህና ፡ ትሑት ፡ ሕዝብን ፡ አስቀራለኹ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ ይታመናሉ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ የእስራኤል ፡ ቅሬታ ፡ ኀጢአትን ፡ አይሠሩም ፥ ሐሰትንም ፡ አይናገሩም ፥ በአፋቸውም ፡ ውስጥ ፡ ተንኰለኛ ፡ ምላስ ፡ አይገኝም ፤ እነርሱም ፡ ይሰማራሉ ፥ ይመሰጉማል ፥ የሚያስፈራቸውም ፡ የለም ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ዘምሪ ፤ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በል ፤ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ በፍጹም ፡ ልብሽ ፡ ሐሤት ፡ አድርጊ ፡ ደስም ፡ ይበልሽ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔር ፡ ፍርድሽን ፡ አስወግዷል ፥ ጠላትሽንም ፡ ጥሏል ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከልሽ ፡ አለ ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ አታዩም ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለኢየሩሳሌም ፦ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ አትፍሪ ፥ እጆችሽም ፡ አይዛሉ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ አምላክሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከልሽ ፡ ታዳጊ ፡ ኀያል ፡ ነው ፤ በደስታ ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ በፍቅሩም ፡ ያርፋል ፥ በእልልታም ፡ ባንቺ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ ይባላል ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ከጉባኤው ፡ ርቀው ፡ የሚያዝኑትን ፥ ከአንቺም ፡ የኾኑትን ፡ እሰበስባለኹ ፤ ስድብ ፡ እንደ ፡ ሸክም ፡ ከብዶባቸው ፡ ነበር ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፥ እንሆ ፥ ባስጨነቁሽ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ አደርግባቸዋለኹ ፤ ዐንካሳዩቱንም ፡ አድናለኹ ፥ የተጣለችውንም ፡ እሰበስባለኹ ፤ ባፈሩባትም ፡ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ለምስጋናና ፡ ለከበረ ፡ ስም ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ሶፎ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ አስገባችኋለኹ ፥ በዚያም ፡ ዘመን ፡ እሰበስባችኋለኹ ፤ ምርኳችኹንም ፡ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ በመለስኹ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ለከበረ ፡ ስምና ፡ ለምስጋና ፡ አደርጋችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ❖

ትንቢተ ፡ ሐጌ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሐጌ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሐጌ ፥ 1 ፥ 1 ፤ በንጉሡ ፡ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ ወደይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ወደሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዘሩባቤል ፥ ወደ ፡ ታላቁም ፡ ካህን ፡ ወደኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሐጌ ፥ 1 ፥ 2 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፦ ዘመኑ ፡ አልደረሰም ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ የሚሠራበት ፡ ዘመን ፡ አልደረሰም ፡ ይላል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 3 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሐጌ ፥ 1 ፥ 4 ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ሳለ ፡ እናንተ ፡ ራሳችኹ ፡ በተሸለሙ ፡ ቤቶቻችኹ ፡ ለመኖር ፡ ጊዜው ፡ ነውን ፧

ሐጌ ፥ 1 ፥ 5 ፤ አኹንም ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችኹን ፡ በመንገዳችኹ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 6 ፤ ብዙ ፡ ዘራችኹ ፥ ጥቂትም ፡ አገባችኹ ፤ በላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልጠገባችኹም ፤ ጠጣችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልረካችኹም ፤ ለበሳችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልሞቃችኹም ፤ ደመ ፡ ወዙን ፡ የተቀበለ ፡ ሰው ፡ በቀዳዳ ፡ ከረጢት ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ ተቀበለ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ልባችኹን ፡ በመንገዳችኹ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 8 ፤ ወደ ፡ ተራራው ፡ ውጡ ፥ ዕንጨትንም ፡ አምጡ ፥ ቤቱንም ፡ ሥሩ ፤ እኔም ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ እኔም ፡ እመሰገናለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 9 ፤ እናንተ ፡ ብዙ ፡ ነገርን ፡ ተስፋ ፡ አደረጋችኹ ፥ እንሆም ፥ ጥቂት ፡ ኾነ ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ባገባችኹት ፡ ጊዜ ፡ እፍ ፡ አልኹበት ፦ ይህ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፦ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እየቤታችኹ ፡ እየሮጣችኹ ፡ የእኔ ፡ ቤት ፡ ፈርሶ ፡ ስለ ፡ ተቀመጠ ፡ ነው ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ሰማያት ፡ በላያችኹ ፡ ጠልን ፡ ከልክለዋል ፥ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ ከልክላለች ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 11 ፤ እኔም ፡ በምድርና ፡ በተራራዎች ፥ በእኽልና ፡ በወይንም ፥ በዘይትና ፡ ምድርም ፡ በምታበቅለው ፡ ላይ ፥ በሰዎችና ፡ በእንስሳዎችም ፡ ላይ ፥ እጅም ፡ በሚደክምበት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ድርቅን ፡ ጠርቻለኹ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 12 ፤ የሰላትያልም ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፥ ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፥ የቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የአምላካቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ድምፅ ፡ የነቢዩንም ፡ የሐጌን ፡ ቃል ፥ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ ኹሉ ፡ ሰሙ ፤ ሕዝቡም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ፈሩ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 13 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልእክተኛ ፡ ሐጌ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልእክት ፡ ሕዝቡን ፦ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ሐጌ ፥ 1 ፥ 14 ፤ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የይሁዳን ፡ አለቃ ፡ የሰላትያልን ፡ ልጅ ፡ የዘሩባቤልን ፡ መንፈስ ፥ የታላቁንም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅን ፡ ልጅ ፡ የኢያሱን ፡ መንፈስ ፥ የቀሩትንም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡

አስነሣ ፤ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስድስተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ መጡ ፥ የአምላካቸውንም ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤት ፡ ሠሩ ።

ትንቢተ ፡ ሐጌ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 1 ፤ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ ከወሩም ፡ በኻያ ፡ አንደኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሐጌ ፥ 2 ፥ 2 ፤ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ለዘሩባቤል ፥ ለታላቁም ፡ ካህን ፡ ለኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ለኢያሱ ፥ ለቀሩትም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ተናገር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 3 ፤ በቀድሞ ፡ ክብሩ ፡ ሳለ ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ ያየ ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ የቀረ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ዛሬስ ፡ እንዴት ፡ ኾኖ ፡ አያችኹት ፧ በዐይናችኹ ፡ እንደ ፡ ምናምን ፡ አይደለምን ፧

ሐጌ ፥ 2 ፥ 4 ፤ አኹን ፡ ግን ፥ ዘሩባቤል ፡ ሆይ ፥ በርታ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ታላቁም ፡ ካህን ፡ የኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሆይ ፥ በርታ ፥ እናንተም ፡ የአገሩ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፥ በርቱና ፡ ሥሩ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እኔ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 5 ፤ መንፈሴም ፡ በመካከላችኹ ፡ ይኖራልና ፥ አትፍሩ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ገና ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቅርብ ፡ ዘመን ፡ እኔ ፡ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንና ፡ የብስንም ፡ አናውጣለኹ ፤

ሐጌ ፥ 2 ፥ 7 ፤ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ አናውጣለኹ ፥ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የተመረጠውም ፡ ዕቃ ፡ ይመጣል ፤ ይህንም ፡ ቤት ፡ በክብር ፡ እምላዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 8 ፤ ብሩ ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ወርቁም ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 9 ፤ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የዚህ ፡ የኹለተኛው ፡ ቤት ፡ ክብር ፡ ይበልጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ሰላምን ፡ እሰጣለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 10 ፤ በዳርዮስም ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በነቢዩ ፡ በሐጌ ፡ እጅ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሐጌ ፥ 2 ፥ 11 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ካህናቱን ፡ ስለ ፡ ሕጉ ፡ ጠይቅ ፤

ሐጌ ፥ 2 ፥ 12 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ የተቀደሰ ፡ ሥጋ ፡ በልብሱ ፡ ዘርፍ ፡ ቢይዝ ፥ በዘርፉም ፡ እንጀራ ፡ ወይም ፡ ወጥ ፥ ወይም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፥ ወይም ፡ ዘይት ፥ ወይም ፡ ማናቸውም ፡ መብል ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በእውኑ ፡ ይቀደሳልን ፧ ብለኽ ፡ ካህናቱን ፡ ጠይቃቸው ፤ ካህናቱም ፦ አይኾንም ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 13 ፤ ሐጌም ፦ በሬሳ ፡ የረከሰ ፡ ሰው ፡ ከነዚህ ፡ አንዱን ፡ ቢነካ ፡ ያ ፡ የተነካው ፡ በእውኑ ፡ ይረክሳልን ፧ አለ ። ካህናቱም ፦ አዎን ፡ ይረክሳል ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 14 ፤ ሐጌም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ሕዝብና ፡ ይህ ፡ ወገን ፡ በፊቴ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ የእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤ በዚያም ፡ ያቀረቡት ፡ ነገር ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 15 ፤ አኹንም ፡ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ሳይነባበር ፥ ከዛሬ ፡ ገምራችኹ ፡ ወዳለፈው ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 16 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሰው ፡ ኻያ ፡ መስፈሪያ ፡ ወዳለበት ፡ ምርት ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የተገኘው ፡

ዐሥር ፡ መስፈሪያ ፡ ብቻ ፡ ነው ፤ ዐምሳ ፡ ማድጋም ፡ ይቀዳ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ መጥመቂያው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የተገኘው ፡ ኻያ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 17 ፤ በእጃችኹ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በዋግና ፡ በዐረማሞ ፡ በበረዶም ፡ መታኋችኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አልተመለሳችኹም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 18 ፤ ከዛሬው ፡ ከዘጠነኛው ፡ ወር ፡ ከኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ ዠምራችኹ ፡ የሚመጣውን ፡ ዘመን ፡ ልብ ፡ አድርጉ ፤ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ መሠረት ፡ ከተተከለበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ልብ ፡ አድርጉ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 19 ፤ ዘር ፡ በጐተራ ፡ ገና ፡ ይኖራልን ፧ ወይንና ፡ በለስ ፡ ሮማንና ፡ ወይራ ፡ አላፈሩም ፤ ከዚች ፡ ቀን ፡ ዠምሬ ፡ እባርካችኋለኹ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 20 ፤ በወሩ ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹለተኛ ፡ ወደ ፡ ሐጌ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ሐጌ ፥ 2 ፥ 21 ፤ ለይሁዳ ፡ አለቃ ፡ ለዘሩባቤል ፡ ተናገር ፡ እንዲህም ፡ በል ፦ ሰማያትንና ፡ ምድርን ፡ አናውጣለኹ ፤

ሐጌ ፥ 2 ፥ 22 ፤ የመንግሥታትንም ፡ ዙፋን ፡ እገለብጣለኹ ፥ የአሕዛብንም ፡ መንግሥታት ፡ ኀይል ፡ አጠፋለኹ ፤ ሠረገላዎችንና ፡ የሚቀመጡባቸውንም ፡ እገለብጣለኹ ፤ ፈረሶችና ፡ ፈረሰኞቻቸውም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በወንድማቸው ፡ ሰይፍ ፡ ይወድቃሉ ።

ሐጌ ፥ 2 ፥ 23 ፤ ባሪያዬ ፡ የሰላትያል ፡ ልጅ ፡ ዘሩባቤል ፡ ሆይ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ እወስድኻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ እኔ ፡ መርጬኻለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ እንደ ፡ ቀለበት ፡ ማተሚያ ፡ አደርግኻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ❖

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዘካ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ በስምንተኛው ፡ ወር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደአዶ ፡ ልጅ ፡ ወደበራክዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ ነበር ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ስለዚህ ፥ እንዲህ ፡ በላቸው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ የቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሰብከዋል ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከክፉ ፡ መንገዳችኹና ፡ ከክፉ ፡ ሥራችኹ ፡ ተመለሱ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ፥ እኔንም ፡ አላደመጡም ፤ እንደ ፡ እነርሱ ፡ አትኹኑ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ አባቶቻችኹ ፡ ወዴት ፡ ናቸው ፧ ነቢያትስ ፡ ለዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉን ፧

ዘካ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ለባሪያዎቼስ ፡ ለነቢያት ፡ ያዘዝኋቸው ፡ ቃሎቼና ፡ ሥርዐቴ ፡ በአባቶቻችኹ ፡ ላይ ፡ አልደረሱምን ፧ እነርሱም ፡ ተመልሰው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንገዳችንና ፡ በሥራችን ፡ መጠን ፡ ያደርግብን ፡ ዘንድ ፡ እንዳሰበ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጎብናል ፡ አሉ ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ በዳርዮስ ፡ በኹለተኛው ፡ ዓመት ፡ ሳባጥ ፡ በሚባል ፡ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ወር ፡ በኻያ ፡ አራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደአዶ ፡ ልጅ ፡ ወደበራክዩ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ነቢዩ ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ በመጋላ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጦ ፡ በሌሊት ፡ አየኹ ፥ ርሱም ፡ በሸለቆው ፡ ውስጥ ፡ ባሉ ፡ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ በስተኋላውም ፡ መጋላና ፡ ሐመር ፡ ዐምባላይም ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹ ። ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አሳይኻለኹ ፡ አለኝ ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ሰው ፦ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የላካቸው ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ በባርሰነት ፡ ዛፎች ፡ መካከልም ፡ ቆሞ ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፦ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለስን ፥ እንሆም ፥ ምድር ፡ ኹሉ ፡ ዝም ፡ ብላ ፡ ዐርፋ ፡ ተቀምጣለች ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፦ አቤቱ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ሰባ ፡ ዓመት ፡ የተቈጣኻቸውን ፡ ኢየሩሳሌምንና ፡ የይሁዳን ፡ ከተማዎች ፡ የማትምራቸው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ አለ ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መልሶ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረው ፡ መልአክ ፡ በመልካምና ፡ በሚያጽናና ፡ ቃል ፡ ተናገረው ።

ዘካ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ስለዚህም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ስበክ ፡ እንዲህም ፡

በል ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እኔ ፡ በታላቅ ፡ ቅንአት ፡ በኢየሩሳሌምና ፡ በጽዮን ፡ ቀንቻለኹ ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ጥቂት ፡ ብቻ ፡ ተቈጥቼ ፡ ሳለኹ ፡ እነርሱ ፡ ክፋትን ፡ ስላገዙት ፥ ባልተቸገሩት ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቻለኹ ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በምሕረት ፡ ተመልሻለኹ ፤ ቤቴ ፡ ይሠራባታል ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ላይ ፡ ገመድ ፡ ይዘረጋበታል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ደግሞም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ ስበክ ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ከተማዎቼ ፡ ደግሞ ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ይረካሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ ጽዮንን ፡ ያጽናናል ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ደግሞ ፡ ይመርጣል ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፥ እንሆ ፥ አራት ፡ ቀንዶች ፡ አየኹ ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውን ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ። ርሱም ፦ እነዚህ ፡ ይሁዳንና ፡ እስራኤልን ፡ ኢየሩሳሌምንም ፡ የበተኑ ፡ ቀንዶች ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔርም ፡ አራት ፡ ጠራቢዎች ፡ አሳየኝ ።

ዘካ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እኔም ፦ እነዚህ ፡ የመጡት ፡ ምን ፡ ሊሠሩ ፡ ነው ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ራሱን ፡ እስከማያነሣ ፡ ድረስ ፡ እነዚህ ፡ ቀንዶች ፡ ይሁዳን ፡ የበተኑ ፡ ናቸው ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ ሊያስፈራሯቸው ፥ የይሁዳንም ፡ አገር ፡ ይበትኑ ፡ ዘንድ ፡ ቀንዳቸውን ፡ ያነሡትን ፡ የአሕዛብን ፡ ቀንዶች ፡ ሊጥሉ ፡ መጥተዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አነሣኹ ፤ እንሆም ፥ በእጁ ፡ የመለኪያ ፡ ገመድ ፡ የያዘ ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ አየኹ ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እኔም ፦ አንተ ፡ ወዴት ፡ ትኼዳለኽ ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ የኢየሩሳሌምን ፡ ወርድና ፡ ርዝመት ፡ ስንት ፡ መኾኑን ፡ ሰፍሬ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ እኼዳለኹ ፡ አለኝ ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እንሆም ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ወጣ ፥ ሌላም ፡ መልአክ ፡ ሊገናኘው ፡ ወጣ ፥

ዘካ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እንዲህም ፡ አለው ፦ ሩጥ ፥ ይህንም ፡ ጕልማሳ ፡ እንዲህ ፡ በለው ፦ ኢየሩሳሌም ፡ በውስጧ ፡ ካሉት ፡ ሰዎችና ፡ እንስሳዎች ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ቅጥር ፡ እንደሌላቸው ፡ መንደሮች ፡ ኾና ፡ ትኖራለች ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እኔ ፡ በዙሪያዋ ፡ የእሳት ፡ ቅጥር ፡ እኾንላታለኹ ፥ በውስጧም ፡ ክብርን ፡ እኾናለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እናንተ ፡ ሆይ ፥ ከሰሜን ፡ ምድር ፡ ሽሹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንደ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፍሳት ፡ በትኖችኋለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ አንቺ ፡ ከባቢሎን ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ የምትኖሪ ፡ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ኰብልዪ ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ከክብሩ ፡ በኋላ ፡ ወደበዘበዟችኹ ፡ አሕዛብ ፡ ልኮኛል ፤ የሚነካችኹ ፡ የዐይኑን ፡ ብሌን ፡ የሚነካ ፡ ነውና ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ እንሆ ፥ እጄን ፡ በላያቸው ፡ አወዛውዛለኹ ፥ ተገዝተው ፡ ለነበሩት ፡ ብዝበዛ ፡ ይኾናሉ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ መጥቼ ፡ በመካከልሽ ፡ እኖራለኹና ፡ ዘምሪ ፥ ደስም ፡ ይበልሽ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠጋሉ ፥ ሕዝብም ፡ ይኾኑኛል ፤ በመካከልሽም ፡ እኖራለኹ ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቂያለሽ ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይሁዳን ፡ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ አድርጎ ፡ በተቀደሰችው ፡ ምድር ፡ ይወርሰዋል ፥ ኢየሩሳሌምንም ፡ ዳግመኛ ፡ ይመርጣል ።

ዘካ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከተቀደሰ ፡ ማደሪያው ፡ ነቅቷልና ፥ ሥጋ ፡ ለባሽ ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ በፊቱ ፡ ዝም ፡ በል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ርሱም ፡ ታላቁን ፡ ካህን ፡ ኢያሱን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ አሳየኝ ፥ ሰይጣንም ፡ ይከሰው ፡ ዘንድ ፡ በስተቀኙ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ሰይጣንን ፦ ሰይጣን ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይገሥጽኽ ፤ ኢየሩሳሌምን ፡ የመረጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይገሥጽኽ ፤ በእውኑ ፡ ይህ ፡ ከእሳት ፡ የተነጠቀ ፡ ትንታግ ፡ አይደለምን ፧ አለው ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ኢያሱም ፡ እድፋም ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ በመልአኩ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። ርሱም ፡ መልሶ ፡ በፊቱ ፡ የቆሙትን ፦ እድፋሙን ፡ ልብስ ፡ ከርሱ ፡ ላይ ፡ አውልቁ ፡ አላቸው ። ርሱንም ፦ እንሆ ፥ አበሳኽን ፡ ከአንተ ፡ አርቄያለኹ ፥ ጥሩ ፡ ልብስም ፡ አለብስኻለኹ ፡ አለው ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ደግሞ ፦ ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አድርጉ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ንጹሕ ፡ ጥምጥም ፡ አደረጉ ፥ ልብስንም ፡ አለበሱት ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ መልአክ ፡ በኢያሱ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ አዳኘበት ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በመንገዴ ፡ ብትኼድ ፡ ትእዛዜንም ፡ ብትጠብቅ ፥ በቤቴ ፡ ላይ ፡ ትፈርዳለኽ ፥ አደባባዮቼንም ፡ ትጠብቃለኽ ፥ በዚህም ፡ ከቆሙት ፡ ከነዚህ ፡ ጋራ ፡ መግባትን ፡ እሰጣለኹ ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ታላቁ ፡ ካህን ፡ ኢያሱ ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ በፊትኽም ፡ የሚቀመጡት ፡ ባልንጀራዎችኽ ፡ ለምልክት ፡ የሚኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ናቸውና ፥ ይስሙ ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ባሪያዬን ፡ ቀጥቃጥ ፡ አወጣለኹ ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በኢያሱ ፡ ፊት ፡ ያኖርኹት ፡ ድንጋይ ፥ እንሆ ፥ አለ ፤ በአንዱ ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዐይኖች ፡ አሉ ፤ እንሆ ፥ ቅርጹን ፡ እቀርጻለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የዚያችንም ፡ ምድር ፡ በደል ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ አስወግዳለኹ ።

ዘካ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ እያንዳንዱ ፡ ከወይኑና ፡ ከበለሱ ፡ በታች ፡ ኾኖ ፡ ባልንጀራውን ፡ ይጠራል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ተመልሶ ፡ ከእንቅልፉ ፡ እንደሚነቃ ፡ ሰው ፡

አነቃኝ ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ርሱም ፦ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለኝ ። እኔም ፦ እንሆ ፥ ኹለንተናው ፡ ወርቅ ፡ የኾነውን ፡ መቅረዝ ፡ አየኹ ፤ የዘይትም ፡ ማሰሮ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፥ ሰባትም ፡ መብራቶች ፡ ነበሩበት ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ ለነበሩት ፡ መብራቶች ፡ ሰባት ፡ ቧንቧዎች ፡ ነበሯቸው ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ዛፎች ፥ አንዱ ፡ በማሰሮው ፡ በስተቀኝ ፡ አንዱም ፡ በስተግራው ፡ ኾነው ፥ በአጠገቡ ፡ ነበሩ ፡ አልኹ ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልሼ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አታውቅምን ፧ አለኝ ። እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አላውቅም ፡ አልኹ ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ መልሶም ፦ ለዘሩባቤል ፡ የተባለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ፦ በመንፈሴ ፡ እንጂ ፡ በኀይልና ፡ በብርታት ፡ አይደለም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ታላቅ ፡ ተራራ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ምንድር ፡ ነኽ ፧ በዘሩባቤል ፡ ፊት ፡ ደልዳላ ፡ ሜዳ ፡ ትኾናለኽ ፤ ሰዎችም ፦ ሞገስ ፥ ሞገስ ፡ ይኹንለት ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ርሱ ፡ መደምደሚያውን ፡ ድንጋይ ፡ ያወጣል ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ የዘሩባቤል ፡ እጆች ፡ ይህን ፡ ቤት ፡ መሠረቱ ፥ የርሱም ፡ እጆች ፡ ይፈጽሙታል ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ የጥቂቱን ፡ ነገር ፡ ቀን ፡ የናቀ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እነዚህ ፡ ሰባቱ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በዘሩባቤል ፡ እጅ ፡ ቱንቢውን ፡ ያያሉ ፤ እነዚህም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ የሚዘዋወሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐይኖች ፡ ናቸው ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እኔም ፡ መልሼ ፦ በመቅረዙ ፡ በስተቀኝና ፡ በስተግራ ፡ ያሉ ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ዛፎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ኹለተኛም ፡ መልሼ ፦ በኹለቱ ፡ የወርቅ ፡ ቧንቧዎች ፡ አጠገብ ፡ ኾነው ፡ የወርቁን ፡ ዘይት ፡ የሚያፈሱ ፡ እነዚህ ፡ ኹለት ፡ የወይራ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አታውቅምን ፧ አለኝ ። እኔም ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ አላውቅም ፡ አልኹት ።

ዘካ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ርሱም ፦ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ አጠገብ ፡ የቆሙት ፡ ኹለቱ ፡ የተቀቡት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ አለኝ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዘካ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ተመልሼም ፡ ዐይኖቼን ፡ አነሣኹ ፥ እንሆም ፥ አንድ ፡ በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አየኹ ።

ዘካ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ርሱም ፦ የምታየው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለኝ ። እኔም ፦ በራሪ ፡ የመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ አያለኹ ፤ ርዝመቱ ፡ ኻያ ፡ ክንድ ፡ ወርዱም ፡ ዐሥር ፡ ክንድ ፡ ነው ፡ አልኹ ።

ዘካ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ ይህ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የሚወጣው ፡ ርግማን ፡

ነው ፤ የሚሰርቅ ፡ ዥሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በዚህ ፡ በኩል ፡ እንደተጻፈው ፡ ዥሉ ፡ ይጠፋል ፥ በሐሰት ፡ የሚምልም ፡ ዥሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በዚያ ፡ በኩል ፡ እንደተጻፈው ፡ ዥሉ ፡ ይጠፋል ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ እኔ ፡ አስወጣዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ወደሚሰርቀውም ፡ ቤት ፥ በሐሰትም ፡ በስሜ ፡ ወደሚምለው ፡ ቤት ፡ ይገባል ፤ በቤቱም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራል ፥ ርሱንም ፥ ዕንጨቱንና ፡ ድንጋዩን ፥ ይበላል ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረው ፡ መልአክ ፡ ወጥቶ ፦ ዐይኖችኽን ፡ አንሣ ፥ ይህችም ፡ የምትወጣው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እይ ፡ አለኝ ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ እኔም ፦ ምንድር ፡ ናት ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ ይህች ፡ የምትወጣው ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያ ፡ ናት ፡ አለኝ ። ደግሞም ፦ በምድር ፡ ዥሉ ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ በደላቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ እንሆም ፥ የርሳሱን ፡ መክሊት ፡ አነሡት ፤ እንሆም ፥ በኢፍ ፡ መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ ርሱም ፦ ይህች ፡ ክፋት ፡ ናት ፡ አለኝ ፤ በኢፍ ፡ መስፈሪያው ፡ ውስጥ ፡ ጣላት ፥ የርሳሱንም ፡ ጠገራ ፡ በመስፈሪያ ፡ አፍ ፡ ላይ ፡ ጣለ ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ ዐይኖቼንም ፡ አንሥቼ ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ወጡ ፥ ነፋስም ፡ በክንፎቻቸው ፡ ነበረ ፤ ክንፎቻቸውም ፡ እንደ ፡ ሽመላ ፡ ክንፎች ፡ ነበሩ ፤ የኢፍ ፡ መስፈሪያውንም ፡ በምድርና ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ አነሡት ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 10 ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ የነበረውን ፡ መልአክ ፦ እነዚህ ፡ የኢፍ ፡ መስፈሪያውን ፡ ወዴት ፡ ይወስዱታል ፧ አልኹት ።

ዘካ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ ርሱም ፦ በሰናዖር ፡ ምድር ፡ ቤት ፡ ይሠሩለት ፡ ዘንድ ፡ ይወስዱታል ፤ በተዘጋጀም ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ በስፍራው ፡ ይኖራል ፡ አለኝ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 1 ፤ ተመልሼም ፡ ዐይኖቼን ፡ አነሣኹ ፥ እንሆም ፥ አራት ፡ ሠረገላዎች ፡ ከኹለት ፡ ተራራ ፡ መካከል ፡ ሲወጡ ፡ አየኹ ፤ ተራራዎቹም ፡ የናስ ፡ ተራራዎች ፡ ነበሩ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 2 ፤ በፊተኛው ፡ ሠረገላ ፡ መጋላ ፡ ፈረሶች ፥ በኹለተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ፥

ዘካ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ በሦስተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ዐምባላይ ፡ ፈረሶች ፥ በአራተኛውም ፡ ሠረገላ ፡ ቅጥልጣል ፡ ፈረሶች ፡ ነበሩ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ለነበረውም ፡ መልአክ ፡ መልሼ ፦ ጌታዬ ፡ ሆይ ፥ እነዚህ ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አልኹት ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ መልአኩም ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ዥሉ ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ ከቆሙበት ፡ ስፍራ ፡ የሚወጡ ፡ አራቱ ፡ የሰማይ ፡ ነፋሳት ፡ ናቸው ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ ዱሪ ፡ ፈረሶች ፡ ያሉበት ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፡ ይወጣል ፤ ዐምባላዮቹም ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ይወጣሉ ፥ ቅጥልጣሎችም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይወጣሉ ፡ አለኝ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ መጋላዎቹም ፡ ደግሞ ፡ ወጡ ፡ በምድርም ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ ለመኼድ ፡ ይፈልጉ ፡

ነበር ፤ ርሱም ፦ ኺዱ ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተመላለሱ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ ጮኾም ፦ እንሆ ፥ ወደሰሜን ፡ ምድር ፡ የሚወጡት ፡ እነርሱ ፡ መንፈሴን ፡ በሰሜን ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ አሳርፈዋል ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ ከባቢሎን ፡ ከመጡት ፡ ምርኮኞች ፡ ከሔልዳይና ፡ ከጦብያ ፡ ከዮዳዔም ፡ ውሰድ ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ መጥተኽ ፡ ወደሶፎንያስ ፡ ልጅ ፡ ወደኢዮስያስ ፡ ቤት ፡ ግባ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ ብርንና ፡ ወርቅን ፡ ከነርሱ ፡ ውሰድ ፥ አክሊሎችንም ፡ ሥራ ፤ በታላቁም ፡ ካህን ፡ በኢዮሴዴቅ ፡ ልጅ ፡ በኢያሱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ድፋቸው ፥

ዘካ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ እንዲህም ፡ በለው ፦ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ስሙ ፡ ቍጥቋጥ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ በስፍራው ፡ ይበቅላል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ ርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራል ፥ ክብርንም ፡ ይሸከማል ፥ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ይነግሣል ፤ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ካህን ፡ ይኾናል ፥ የሰላምም ፡ ምክር ፡ በኹለቱ ፡ መካከል ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ አክሊሎችም ፡ ለሔሌምና ፡ ለጦብያ ፡ ለዮዳዔም ፡ ለሶፎንያስም ፡ ልጅ ፡ ለሔን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ውስጥ ፡ ለመታሰቢያ ፡ ይኾናሉ ።

ዘካ. ፥ 6 ፥ 15 ፤ በሩቅም ፡ ያሉት ፡ መጥተው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ይሠራሉ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ታውቃላችኹ ። የአምላካችኹንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ አጥብቃችኹ ፡ ብትሰሙ ፡ ይህ ፡ ይኾናል ።

_____ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ዘካ. ፥ 7 ፥ 1 ፤ በንጉሡም ፡ በዳርዮስ ፡ በአራተኛው ፡ ዓመት ፡ ካሴሉ ፡ በሚባል ፡ በዘጠነኛው ፡ ወር ፡ በአራተኛው ፡ ቀን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ መጣ ።

ዘካ. ፥ 7 ፥ 2 ፤ የቤቴልም ፡ ሰዎች ፡ ሳራሳርንና ፡ ሬጌሜሌክን ፡ ሰዎቻቸውንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፥

ዘካ. ፥ 7 ፥ 3 ፤ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ካህናት ፡ ለነቢያትም ፦ ባለፉት ፡ ዓመታት ፡ እንዳደረግኹት ፡ በዐምስተኛው ፡ ወር ፡ መለየትና ፡ ማልቀስ ፡ ይገባኛልን ፧ ብለው ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ ልኳቸው ፡ ነበር ።

ዘካ. ፥ 7 ፥ 4 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፥ 7 ፥ 5 ፤ ለምድሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ለካህናትም ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ተናገራቸው ፦ በዚህ ፡ በሰባው ፡ ዓመት ፡ በዐምስተኛውና ፡ በሰባተኛው ፡ ወር ፡ በጾማችኹና ፡ ባለቀሳችኹ ፡ ጊዜ ፥ በእውኑ ፡ ለእኔ ፡ ጾም ፡ ጾማችኹልኝ ፧

ዘካ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ በምትበሉበትና ፡ በምትጠጡበትስ ፡ ጊዜ ፥ ለራሳችኹ ፡ የምትበሉና ፡ የምትጠጡ ፡ አይደላችኹምን ፧

ዘካ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ ኢየሩሳሌምና ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉ ፡ ከተማዎች ፡ ገና ፡ ሰዎች ፡ ባሉባቸው ፡ ጊዜ ፥ በምቾትም ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፥ ደቡቡና ፡ ቈላውም ፡ ሰዎች ፡ ባሉባቸው ፡ ጊዜ ፥ እግዚአብሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ እጅ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ መስማት ፡ አይገባችኹምን ፧

ዘካ. ፥ 7 ፥ 8 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ ዘካርያስ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናግሯል ፦ እውነተኛውን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤ ቸርነትንና ፡ ምሕረትን ፡ ኹላችኹ ፡ ለወንድሞቻችኹ ፡ አድርጉ ፤

ዘካ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ መበለቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፥ መጻተኛውንና ፡ ችግረኛውን ፡ አትበድሉ ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ ክፉውን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ አያስብ ።

ዘካ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ደንደሳቸውን ፡ አዞሩ ፡ እንጂ ፡ መስማትን ፡ እምቢ ፡ አሉ ፤ እንዳይሰሙም ፡ ጐሯቸውን ፡ አደነቈሩ ።

ዘካ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ እጅ ፡ በመንፈሱ ፡ የላከውን ፡ ሕጉንና ፡ ቃሉን ፡ እንዳይሰሙ ፡ ልባቸውን ፡ እንደ ፡ አልማዝ ፡ አጠነከሩ ፤ ስለዚህ ፥ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ቍጣ ፡ መጣ ።

ዘካ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ በጠራኹ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ እንዳልሰሙኝ ፥ እንዲሁ ፡ እነርሱ ፡ በሚጠሩበት ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ አልሰማም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤

ዘካ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ወደማያውቋቸውም ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ በተንኳቸው ። እንዲሁ ፡ ከነርሱ ፡ በኋላ ፡ ምድሪቱ ፡ ባድማ ፡ ኾናለች ፥ የሚተላለፍባትና ፡ የሚመላለስባትም ፡ አልነበረም ፤ ያማረችውንም ፡ ምድር ፡ ባድማ ፡ አደረጓት ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ስለ ፡ ጽዮን ፡ ታላቅ ፡ ቅንአት ፡ ቀንቻለኹ ፥ በታላቅም ፡ ቍጣ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ቀንቻለኹ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ወደ ፡ ጽዮን ፡ ተመልሻለኹ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ መካከል ፡ እኖራለኹ ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ የእውነት ፡ ከተማ ፡ ትባላለች ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ተራራ ፡ የተቀደሰ ፡ ተራራ ፡ ይባላል ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ዳግመኛ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ ባልቴቶች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ይቀመጣሉ ፤ ሰውም ፡ ኹሉ ፡ ከዕድሜው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ምርኩዝ ፡ በእጁ ፡ ይይዛል ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ የከተማዪቱም ፡ አደባባዮች ፡ በእነዚያ ፡ በሚጫወቱ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ይሞላሉ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚህ ፡ ወራት ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ድንቅ ፡ ቢኾን ፥ በእውኑ ፡ በእኔ ፡ ዐይን ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ድንቅ ፡ ይኾናልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እንሆ ፥ ሕዝቤን ፡ ከምሥራቅ ፡ ምድርና ፡ ከምዕራብ ፡ ምድር ፡ አድነዋለኹ ፤

ዘካ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ አመጣቸዋለኹም ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ ውስጥ ፡ ይኖራሉ ፤ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑኛል ፥ እኔም ፡ በእውነትና ፡ በጽድቅ ፡ አምላክ ፡ እኾናቸዋለኹ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ መቅደሱ ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከተመሠረተበት ፡ ቀን ፡ ገምሮ ፡ ከነቢያት ፡ አፍ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሰማችኹ ፡ እናንተ ፡ ሆይ ፥ እጃችኹን ፡ አበርቱ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ከዚያ ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡ ለሰውና ፡ ለእንስሳ ፡ ዋጋ ፡ አልነበረምና ፤ እኔም ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ አስነሥቼ ፡ ነበርና ፥ ካስጨናቂው ፡ የተነሣ ፡ ለሚገባውና ፡ ለሚወጣው ፡ ሰላም ፡ አልነበረም ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ቀደመው ፡ ዘመን ፡ በዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ላይ ፡ አልኾንም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰላምን ፡ እዘራለኹ ፤ ወይኑ ፡ ፍሬውን ፡ ይሰጣል ፥ ምድርም ፡ አዝመራዋን ፡ ታወጣለች ፥ ሰማያትም ፡ ጠላቸውን ፡ ይሰጣሉ ፤ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ቅሬታ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አወርሳለኹ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ የይሁዳ ፡ ቤትና ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ሆይ ፥ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ርግማን ፡ እንደ ፡ ነበራችኹ ፥ እንዲሁ ፡ አድናችኋለኹ ፥ በረከትም ፡ ትኾናላችኹ ፤ አትፍሩ ፥ እጃችኹንም ፡ አበርቱ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ አባቶቻችኹ ፡ እጅግ ፡ ባስቈጡኝ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ለማድረግ ፡ እንዳሰብኹ ፥ እንዳልተጸጸትኹም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥

ዘካ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ እንዲሁ ፡ ዳግመኛ ፡ ለኢየሩሳሌምና ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ በዚህ ፡ ወራት ፡ በጎነትን ፡ ላደርግ ፡ ዘንድ ፡ ዐስቤያለኹ ፤ አትፍሩ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ የምትሠሩት ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እያንዳንዳችኹ ፡ ከባልንጀራችኹ ፡ ጋራ ፡ እውነትን ፡ ተነጋገሩ ፤ በበር ፡ አደባባያችኹም ፡ የእውነትንና ፡ የሰላምን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፤

ዘካ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ኹላችኹም ፡ በባልንጀራችኹ ፡ ላይ ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ በልባችኹ ፡ አታስቡ ፤ የሐሰትንም ፡ መሐላ ፡ አትውደዱ ፤ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እጠላለኹና ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መጣ ፦

ዘካ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ የአራተኛው ፡ ወር ፡ ጾም ፡ የዐምስተኛውም ፡ የሰባተኛውም ፡ የዐሥረኛውም ፡ ወር ፡ ጾም ፡ ለይሁዳ ፡ ቤት ፡ ደስታና ፡ ተድላ ፡ የሐሤትም ፡ በዓላት ፡ ይኾናል ፤ ስለዚህም ፡ እውነትንና ፡ ሰላምን ፡ ውደዱ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በብዙ ፡ ከተማዎች ፡ የሚቀመጡ ፡ አሕዛብ ፡ ገና ፡ ይመጣሉ ፤

ዘካ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ በአንዲትም ፡ ከተማ ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎች ፦ እግዚአብሔርን ፡ እንለምን ፡ ዘንድ ፥ የሰራዊትንም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንፈልግ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ እንኺድ ፤ እኔም ፡ እኼዳለኹ ፡ እያሉ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ከተማ ፡ ይኼዳሉ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ብዙ ፡ ወገኖችና ፡ ኀይለኞች ፡ አሕዛብ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የሰራዊትን ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ይለምኑ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣሉ ።

ዘካ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ የሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከአሕዛብ ፡ ቋንቋ ፡ ኹሉ ፡ ዐሥር ፡ ሰዎች ፡ የአንዱን ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ልብስ ፡ ዘርፍ ፡ ይዘው ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳለ ፡ ሰምተናልና ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንኺድ ፡ ይላሉ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ በሴድራክ ፡ ምድር ፡ ላይ ፡ ነው ፥ በደማስቆም ፡ ላይ ፡ ያርፋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዐይን ፡ ወደ ፡ ሰውና ፡ ወደእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤

ዘካ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ደግሞም ፡ በዳርቻዋ ፡ ባለችው ፡ በሐማት ፡ ላይ ፥ እጅግ ፡ ጠቢበኞች ፡ በኾኑ ፡ በጢሮስና ፡

በሲዶና ፡ ላይ ፡ ነው ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ጢሮስም ፡ ምሽግን ፡ ለራሷ ፡ ሠርታለች ፥ ብሩንም ፡ እንደ ፡ ዐፈር ፥ ጥሩውንም ፡ ወርቅ ፡ እንደ ፡ መንገድ ፡ ጭቃ ፡ አከማችታለች ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ ጌታ ፡ ይገፋታል ፥ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ብርታቷን ፡ ይመታል ፤ ርሷም ፡ በእሳት ፡ ትበላለች ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ አስቀሎና ፡ አይታ ፡ ትፈራለች ፤ ጋዛ ፡ ደግሞ ፡ አይታ ፡ እጅግ ፡ ትታመማለች ፤ ዐቃሮንም ፡ እንዲሁ ፥ ተስፋዋ ፡ ይቈረጣልና ፤ ንጉሡም ፡ ከጋዛ ፡ ይጠፋል ፥ በአስቀሎናም ፡ የሚቀመጥ ፡ አይገኝም ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ የተደባለቀ ፡ ወገን ፡ በአዛጦን ፡ ይቀመጣል ፥ የፍልስጥኤማውያንንም ፡ ትዕቢት ፡ አጠፋለኹ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ደሙንም ፡ ከአፉ ፡ ውስጥ ፡ ርኩሱንም ፡ ነገር ፡ ከጥርሱ ፡ መካከል ፡ አስወግዳለኹ ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ለአምላካችን ፡ ቅሬታ ፡ ይኾናል ፤ በይሁዳም ፡ እንደ ፡ አለቃ ፡ ይኾናል ፥ ዐቃሮንም ፡ እንደ ፡ ኢያቡሳዊ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ እኔም ፡ ማንም ፡ እንዳይኼድና ፡ እንዳይመለስ ፡ እንደ ፡ ጠባቂ ፡ ጦር ፡ ኾኖ ፡ በቤቴ ፡ ዙሪያ ፡ ሰፈር ፡ አደርጋለኹ ፤ አኹንም ፡ በዐይኔ ፡ አይቻለኹና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አስጨናቂ ፡ አያልፍባቸውም ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ አንቺ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፤ አንቺ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ እልል ፡ በዪ ፤ እንሆ ፥ ንጉሥሽ ፡ ጻድቅና ፡ አዳኝ ፡ ነው ፤ ትሑትም ፡ ኾኖ ፡ በአህያም ፥ በአህያዪቱ ፡ ግልገል ፡ በውርንጫዪቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ሠረገላውንም ፡ ከኤፍሬም ፡ ፈረሱንም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ አጠፋለኹ ፤ የሰልፉም ፡ ቀስት ፡ ይሰበራል ፥ ለአሕዛብም ፡ ሰላምን ፡ ይናገራል ፤ ግዛቱም ፡ ከባሕር ፡ እስከ ፡ ባሕር ፥ ከወንዙም ፡ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድርስ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ላንቺም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ቃል ፡ ኪዳንሽ ፡ ደም ፥ እስሮችሽን ፡ ውሃ ፡ ከሌለበት ፡ ጕድጓድ ፡ አውጥቻለኹ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ እናንተ ፡ በተስፋ ፡ የምትኖሩ ፡ እስሮች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ዐምባ ፡ ተመለሱ ፤ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጌ ፡ እንድመልስልሽ ፡ ዛሬ ፡ እነግርሻለኹ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ይሁዳን ፡ ለእኔ ፡ ገትሬያለኹ ፤ ቀስቱን ፡ በኤፍሬም ፡ ሞልቻለኹ ፤ ጽዮን ፡ ሆይ ፥ ልጆችሽን ፡ በግሪክ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አስነሣለኹ ፥ አንቺንም ፡ እንደ ፡ ኀያል ፡ ሰው ፡ ሰይፍ ፡ አደርግሻለኹ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይገለጣል ፥ ፍላጻውም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ይወጣል ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ መለከትን ፡ ይነፋል ፥ በደቡብም ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ይኼዳል ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይጠብቃቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ይበሏቸዋል ፥ የወንጭፉንም ፡ ድንጋዮች ፡ ይረግጣሉ ፤ እንደ ፡ ወይን ፡ ጠጅም ፡ ይጠጧቸዋል ፥ እንደ ፡ ጥዋዎችም ፡ እንደ ፡ መሠዊያም ፡ ማእዘኖች ፡ የተሞሉ ፡ ይኾናሉ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሕዝቡ ፡ መንጋ ፡ ያድናቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ለአክሊል ፡ እንደሚኾኑ ፡ እንደ ፡ ከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ ይኾናሉ ፥ በምድሩም ፡ ላይ ፡ ይብለጨለጫሉ ።

ዘካ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ በጎነቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! ፡ ውበቱስ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ ነው! ፡ እኽል ፡ ጐበዛዝቱን ፥ ጕሽ ፡ ጠጅም ፡ ቈነጕሾቹን ፡ ያለመልማል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ በኋለኛው ፡ ዝናብ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዝናቡን ፡ ለምኑ ፤ እግዚአብሔር ፡ መብረቅ ፡ ያደርጋል ፤ ርሱም ፡ የበልግ ፡ ዝናብን ፡ ለያንዳንዱም ፡ በሜዳ ፡ ውስጥ ፡ ሣርን ፡ ይሰጣል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ ተራፊም ፡ ከንቱነትን ፡ ተናግረዋልና ፥ ሟርተኞችም ፡ ውሸትን ፡ አይተዋልና ፤ ሕልምንም ፡ የሚያዩ ፡ በሐሰት ፡ ተናግረዋል ፥ በከንቱም ፡ ያጽናናሉ ፤ እረኛም ፡ የላቸውምና ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ ተቅበዝብዘዋል ፡ ተጨንቀውማል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ቍጣዬ ፡ በእረኞች ፡ ላይ ፡ ነደ፧ል ፥ አውራ ፡ ፍየሎችንም ፡ እቀጣለኹ ፤ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ መንጋውን ፡ ጐብኝቷል ፥ በሰልፍም ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ፈረስ ፡ ያደርጋቸዋል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ የማእዘኑ ፡ ድንጋይ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ ችንካሩ ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ የሰልፉ ፡ ቀስት ፥ ከርሱም ፡ ዘንድ ፡ አስገባሪው ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ይመጣሉ ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ በሰልፍም ፡ ጊዜ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ በመንገድ ፡ ጭቃ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚረግጡ ፡ ኀያላን ፡ ይኾናሉ ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ ይዋጋሉ ፥ ፈረሰኞችም ፡ ያፍራሉ ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ወድጃቸዋለኹና ፡ የይሁዳን ፡ ቤት ፡ አበረታለኹ ፥ የዮሴፍንም ፡ ቤት ፡ አድናለኹ ፤ አደላድላቸዋለኹም ፤ እመልሳቸዋለኹ ፤ እኔም ፡ አምላካቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝና ፥ እኔም ፡ እሰማቸዋለኹና ፡ እንዳልጣልኋቸው ፡ ይኾናሉ ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ የኤፍሬምም ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኀያላን ፡ ይኾናሉ ፥ ልባቸውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንደ ፡ ጠጣ ፡ ሰው ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ልጆቻቸውም ፡ አይተው ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፥ ልባቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሐሤት ፡ ያደርጋል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ተቤዥቻቸዋለኹና ፡ በፉጨት ፡ ጠርቼ ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ቀድሞም ፡ በዝተው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ይበዛሉ ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ በአሕዛብም ፡ መካከል ፡ ብዘራቸው ፡ እንኳ ፡ በሩቅ ፡ አገር ፡ ሳሉ ፡ ያስቡኛል ፥ ከልጆቻቸውም ፡ ጋራ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ፥ ይመለሱማል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ከግብጽም ፡ ምድር ፡ እመልሳቸዋለኹ ፥ ከአሶርም ፡ እሰበስባቸዋለኹ ፤ ወደ ፡ ገለዓድና ፡ ወደሊባኖስ ፡ ምድር ፡ አመጣቸዋለኹ ፥ የሚበቃም ፡ ቦታ ፡ አይገኝላቸውም ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ በጭንቅ ፡ ባሕር ፡ ያልፋል ፥ የባሕርንም ፡ ሞገድ ፡ ይመታል ፥ የወንዙም ፡ ጥልቅ ፡ ኹሉ ፡ ይደርቃል ፤ የአሶርም ፡ ትዕቢት ፡ ይዋረዳል ፥ የግብጽም ፡ በትረ ፡ መንግሥት ፡ ይርቃል ።

ዘካ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ በአምላካቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አበረታቸዋለኹ ፥ በስሙም ፡ ይመካሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፡ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ዘካ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ሊባኖስ ፡ ሆይ ፥ ደጆችኽን ፡ ክፈት ፥ እሳትም ፡ ዝግባዎችኽን ፡ ትብላ ።

ዘካ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ የጥድ ፡ ዛፍ ፡ ሆይ ፥ ዝግባ ፡ ወድቋልና ፥ ከበርቴዎችም ፡ ጠፍተዋልና ፥ ዋይ ፡ በል ፤ እናንተም ፡ የባሳን ፡ ዛፎች ፡ ሆይ ፥ ጽኑው ፡ ጫካ ፡ ተቈርጧልና ፥ ዋይ ፡ በሉ ።

ዘካ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ የእረኞች ፡ ክብር ፡ ተዋርዷልና ፥ የዋይታቸው ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ፤ የዮርዳኖስ ፡ ትዕቢት ፡

ተዋርዷልና ፥ የአንበሳዎች ፡ ግሣት ፡ ድምፅ ፡ ተሰምቷል ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ፦ ለዕርድ ፡ የሚኾኑትን ፡ በጎች ፡ ጠብቅ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ የገዟቸው ፡ ያርዷቸዋል ፥ ራሳቸውንም ፡ እንደ ፡ በደለኞች ፡ አድርገው ፡ አይቈጥሩም ፤ የሸጧቸውም ፦ ባለጠጋ ፡ ኾነናልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ይላሉ ፤ እረኞቻቸውም ፡ አይራሩላቸውም ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩ ፡ አልራራም ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እንሆም ፥ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በባልንጀራውና ፡ በንጉሡ ፡ እጅ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለኹ ፤ ምድሪቱንም ፡ ይመታሉ ፥ ከእጃቸውም ፡ አላድናቸውም ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ እኔም ፡ ለዕርድ ፡ የሚኾኑትን ፡ በጎች ፥ የመንጋውን ፡ ችግረኞች ፡ ጠበቅኹ ። ኹለት ፡ በትሮችንም ፡ ወሰድኹ ፤ የአንዲቱን ፡ ስም ፡ ውበት ፡ የኹለተኛዪቱንም ፡ ስም ፡ ማሰሪያ ፡ ብዬ ፡ ጠራኹ ፤ መንጋውንም ፡ ጠበቅኹ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ ባንድ ፡ ወርም ፡ ሦስቱን ፡ እረኞች ፡ አጠፋኹ ፤ ነፍሴም ፡ ተሰቀቀቻቸው ፥ ነፍሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ እኔን ፡ ጠላች ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 9 ፤ እኔም ፦ እናንተን ፡ አልጠብቅም ፤ የሚሞተው ፡ ይሙት ፥ የሚጠፋውም ፡ ይጥፋ ፤ የቀረውም ፡ እያንዳንዱ ፡ የባልንጀራውን ፡ ሥጋ ፡ ይብላ ፡ አልኹ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 10 ፤ እኔም ፡ ከሕዝቦች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ የገባኹትን ፡ ቃል ፡ ኪዳኔን ፡ አፈርስ ፡ ዘንድ ፡ ውበት ፡ የተባለችውን ፡ በትሬን ፡ ወስጄ ፡ ቈረጥኹ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 11 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ተሰበረች ፤ እንዲሁም ፡ እኔን ፡ የተመለከቱ ፡ የመንጋው ፡ ችግረኞች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዐወቁ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 12 ፤ እኔም ፦ ደስ ፡ ብሏችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዋጋዬን ፡ ስጡኝ ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ተዉት ፡ አልኹ ። እነርሱም ፡ ለዋጋዬ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ መዘኑ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 13 ፤ እግዚአብሔርም ፦ የተስማሙበትን ፡ የከበረውን ፡ ዋጋዬን ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኑረው ፡ አለኝ ። እኔም ፡ ሠላሳውን ፡ ብር ፡ ወስጄ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ባለው ፡ በግምጃ ፡ ቤቱ ፡ ውስጥ ፡ አኖርኹት ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 14 ፤ በይሁዳና ፡ በእስራኤል ፡ መካከል ፡ ያለውንም ፡ ወንድማማችነት ፡ እሰብር ፡ ዘንድ ፡ ማሰሪያ ፡ የተባለችውን ፡ ኹለተኛዪቱን ፡ በትሬን ፡ ቈረጥኹ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 15 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አለኝ ፦ ዳግመኛም ፡ የሰነፍን ፡ እረኛ ፡ ዕቃ ፡ ውሰድ ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 16 ፤ እንሆ ፥ በአገሩ ፡ ውስጥ ፡ እረኛ ፡ አስነሣለኹ ፤ ርሱም ፡ የጠፋውን ፡ አያስብም ፥ የባዘነውን ፡ አይፈልግም ፥ የተሰበረውን ፡ አይጠግንም ፤ የዳነውንም ፡ አይቀልብም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የሰባውን ፡ ሥጋ ፡ ይበላል ፥ ሰኮናውንም ፡ ይቀለጣጥማል ።

ዘካ. ፥ 11 ፥ 17 ፤ መንጋውን ፡ ለሚተው ፡ ለምናምንቴ ፡ እረኛ ፡ ወዮለት! ፡ ሰይፍ ፡ በክንዱና ፡ በቀኝ ፡ ዐይኑ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ ክንዱም ፡ አጥብቃ ፡ ትደርቃለች ፥ ቀኝ ፡ ዐይኑም ፡ ፈጽሞ ፡ ትጨልማለች ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ የተነገረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ፦ ሰማያትን ፡

የዘረጋ ፥ ምድርንም ፡ የመሠረተ ፥ የሰውንም ፡ መንፈስ ፡ በውስጡ ፡ የሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ዘካ. ፥ 12 ፥ 2 ፤ እንሆ ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ በዙሪያዋ ፡ ላሉት ፡ ለአሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ የመንገድገድ ፡ ዋንጫ ፡ አደርጋታለኹ ፤ ደግሞም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ስትከበብ ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 3 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ለአሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ ከባድ ፡ ድንጋይ ፡ አደርጋታለኹ ፤ የሚሸከሟት ፡ ዥሉ ፡ እጅግ ፡ ይቈስላሉ ፤ የምድርም ፡ አሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ በላይዋ ፡ ላይ ፡ ይከማቻሉ ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 4 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፥ ፈረስን ፡ ዥሉ ፡ በድንጋጤ ፥ ተቀማጭንም ፡ በእብድነት ፡ እመታለኹ ፤ ዐይኖቼንም ፡ በይሁዳ ፡ ላይ ፡ እከፍታለኹ ፥ የአሕዛብንም ፡ ፈረሶች ፡ ዥሉ ፡ በዕውርነት ፡ እመታለኹ ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 5 ፤ የይሁዳም ፡ አለቃዎች ፡ በልባቸው ፦ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ በአምላካቸው ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብርታት ፡ አለ ፡ ይላሉ ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 6 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ የይሁዳን ፡ አለቃዎች ፡ በዕንጨት ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ ትንታግ ፥ በነዶዎችም ፡ መካከል ፡ እንዳለ ፡ እንደ ፡ ፋና ፡ ነበልባል ፡ አደርጋቸዋለኹ ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ በዙሪያ ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ ይበላሉ ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በስፍራዋ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትኖራለች ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ክብርና ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ ክብር ፡ በይሁዳ ፡ ክብር ፡ ላይ ፡ እንዳይታበይ ፡ የይሁዳን ፡ ድንኳኖች ፡ አስቀድሞ ፡ ያድናል ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 8 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩት ፡ ይመክትላቸዋል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከነርሱ ፡ መካከል ፡ ደካማው ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ ይኾናል ፤ የዳዊትም ፡ ቤት ፡ በፊታቸው ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ እንደ ፡ አምላክ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 9 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ የሚመጡትን ፡ አሕዛብ ፡ ዥሉ ፡ ለማጥፋት ፡ እጋደላለኹ ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 10 ፤ በዳዊትም ፡ ቤት ፡ ላይ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፥ የሞገስንና ፡ የልመናን ፡ መንፈስ ፡ አፈሳለኹ ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ ወደወጉት ፡ ይመለከታሉ ፤ ሰውም ፡ ለአንድያ ፡ ልጁ ፡ እንደሚያለቅስ ፡ ያለቅሱለታል ፥ ሰውም ፡ ለበኵር ፡ ልጁ ፡ እንደሚያዝን ፡ በመራራ ፡ ሐዘን ፡ ያዝኑለታል ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 11 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በመጊዶን ፡ ሜዳ ፡ እንደ ፡ ነበረው ፡ እንደ ፡ ሐዳድሪሞን ፡ ልቅሶ ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፥ 12 ፥ 12 ፤ ምድሪቱም ፡ ታለቅሳለች ፤ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ የዳዊት ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የናታን ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤

ዘካ. ፥ 12 ፥ 13 ፤ የሌዊ ፡ ቤት ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤ የሰሜኢ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፤

ዘካ. ፥ 12 ፥ 14 ፤ የቀሩት ፡ ወገኖች ፡ ዥሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወገን ፡ ለብቻው ፥ ሴቶቻቸውም ፡ ለብቻቸው ፡ ያለቅሳሉ ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ለዳዊት ፡ ቤትና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ከኀጢአትና ፡ ከርኵሰት ፡ የሚያነጻ ፡ ምንጭ ፡ ይከፈታል ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 2 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ የጣዖታትን ፡ ስም ፡ ከምድር ፡

አጠፋለኹ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አይታሰቡም ፤ ደግሞም ፡ ሐሰተኞችን ፡ ነቢያትና ፡ ርኩስ ፡ መንፈስን ፡ ከምድር ፡ ላይ ፡ አስወግዳለኹ ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 3 ፤ ማንም ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ቢናገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፦ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ሐሰትን ፡ ተናግረኻልና ፥ በሕይወት ፡ አትኖርም ፡ ይሉታል ፤ ትንቢትንም ፡ ሲናገር ፡ የወለዱት ፡ አባቱና ፡ እናቱ ፡ ይወጉታል ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ነቢያቱ ፡ ኹሉ ፡ ትንቢትን ፡ ሲናገሩ ፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ራእዩ ፡ ያፍራል ፤ ያታልሉም ፡ ዘንድ ፡ የማቅ ፡ ልብስ ፡ አይለብሱም ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 5 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ከታናሽነቴ ፡ ዠምሮ ፡ ባሪያ ፡ ኾኜ ፡ ነበርኩና ፡ ገበሬ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ነቢይ ፡ አይደለኹም ፡ ይላል ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 6 ፤ ሰውም ፦ ይህ ፡ በእጅኽ ፡ መካከል ፡ ያለ ፡ ቍስል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይለዋል ። ርሱም ፦ በወዳጆቼ ፡ ቤት ፡ የቈሰልኹት ፡ ቍስል ፡ ነው ፡ ይላል ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 7 ፤ ሰይፍ ፡ ሆይ ፥ ባልንጀራዬ ፡ በኾነው ፡ ሰው ፡ በእረኛዬ ፡ ላይ ፡ ንቃ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ እረኛውን ፡ ምታ ፥ በጎቹም ፡ ይበተናሉ ፤ እጄንም ፡ በታናናሾች ፡ ላይ ፡ እመልሳለኹ ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 8 ፤ በምድርም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኹለት ፡ ክፍል ፡ ተቈርጠው ፡ ይሞታሉ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ሦስተኛውም ፡ ክፍል ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ይቀራል ።

ዘካ. ፥ 13 ፥ 9 ፤ ሦስተኛውንም ፡ ክፍል ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ አገባለኹ ፥ ብርም ፡ እንደሚነጥር ፡ አነጥራቸዋለኹ ፥ ወርቅም ፡ እንደሚፈተን ፡ እፈትናቸዋለኹ ፤ እነርሱም ፡ ስሜን ፡ ይጠራሉ ፥ እኔም ፡ እሰማቸዋለኹ ፤ እኔም ፦ ይህ ፡ ሕዝቤ ፡ ነው ፡ እላለኹ ፤ ርሱም ፦ እግዚአብሔር ፡ አምላኬ ፡ ነው ፡ ይላል ።

ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 1 ፤ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፥ ብዝበዛሽንም ፡ በውስጥሽ ፡ ይካፈላሉ ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 2 ፤ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ለሰልፍ ፡ እሰበስባለኹ ፤ ከተማዪቱም ፡ ትያዛለች ፥ ቤቶችም ፡ ይበዘበዛሉ ፥ ሴቶችም ፡ ይነወራሉ ፤ የከተማዪቱም ፡ እኩሌታ ፡ ለምርኮ ፡ ይወጣል ፥ የቀረው ፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ከከተማ ፡ አይጠፋም ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ይወጣል ፥ በሰልፍም ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ተዋጋ ፡ ከነዚያ ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ይዋጋል ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 4 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ እግሮቹ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ትይዩ ፡ በምሥራቅ ፡ በኩል ፡ ባለው ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ላይ ፡ ይቆማሉ ፤ ደብረ ፡ ዘይትም ፡ በመካከል ፡ ወደ ፡ ምሥራቅና ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ይሰነጠቃል ፥ እጅግም ፡ ታላቅ ፡ ሸለቆ ፡ ይኾናል ፤ የተራራውም ፡ እኩሌታ ፡ ወደ ፡ ሰሜን ፥ እኩሌታውም ፡ ወደ ፡ ደቡብ ፡ ይርቃል ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 5 ፤ የተራራዎችም ፡ ሸለቆ ፡ እስከ ፡ አጸል ፡ ይደርሳልና ፥ በተራራዎች ፡ ሸለቆ ፡ ትሸሻላችኹ ፤ በይሁዳም ፡ ንጉሥ ፡ በዖዝያን ፡ ዘመን ፡ ከኾነው ፡ ከምድር ፡ መናወጥ ፡ ፊት ፡ እንደ ፡ ሸሻችኹ ፡ ትሸሻላችኹ ፤ አምላኬ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 6 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በረዶና ፡ ውርጭ ፡ እንጂ ፡ ብርሃን ፡ አይኾንም ።

ዘካ. ፥ 14 ፥ 7 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ይኾናል ፥ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኾናል ፤ ቀንም ፡ አይኾንም ፥ ሌሊትም ፡ አይኾንም ፤ ሲመሽም ፡ ብርሃን ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ይወጣል ፤ እኩሌታው ፡ ወደምሥራቁ ፡ ባሕር ፥ እኩሌታውም ፡ ወደምዕራቡ ፡ ባሕር ፡ ይኼዳል ፤ ይህ ፡ በበጋና ፡ በክረምት ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በምድር ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ይነግሣል ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፥ ስሙም ፡ አንድ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ምድር ፡ ሹሉ ፡ ከጌባ ፡ ዠምሮ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ደቡብ ፡ በኩል ፡ እስካለችው ፡ እስከ ፡ ሬሞን ፡ ድረስ ፡ ተለውጣ ፡ እንደ ፡ ዐረባ ፡ ትኾናለች ፤ ርሷም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ትላለች ፥ ከብንያምም ፡ በር ፡ ዠምሮ ፡ እስከፊተኛው ፡ በር ፡ ስፍራ ፡ እስከማእዘኑ ፡ በር ፡ ድረስ ፥ ከሐናንኤልም ፡ ግንብ ፡ ዠምሮ ፡ እስከንጉሡ ፡ መጥመቂያ ፡ ድረስ ፡ በስፍራዋ ፡ ትኖራለች ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ሰዎችም ፡ ይኖሩባታል ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ርግማን ፡ አይኾንም ፤ ኢየሩሳሌምም ፡ ተዘልላ ፡ ትኖራለች ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ጋራ ፡ የተዋጉትን ፡ አሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ የሚቀሥፍበት ፡ ቸነፈር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በእግራቸው ፡ ሲቆሙ ፡ ሥጋቸው ፡ ይበሰብሳል ፥ ዐይኖቻቸውም ፡ በዐይነ ፡ ሥባቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበሰብሳሉ ፥ ምላሳቸውም ፡ በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ ይበሰብሳል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ሽብር ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ፤ እያንዳንዱም ፡ የባልንጀራውን ፡ እጅ ፡ ይይዛል ፥ እጁም ፡ በባልንጀራው ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ይነሣል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ይሁዳም ፡ ደግሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ኾኖ ፡ ይዋጋል ፤ በዙሪያም ፡ ያሉት ፡ የአሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ ሀብት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ልብስም ፡ ይሰበሰባል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ በፈረስና ፡ በበቅሎ ፥ በግመልና ፡ በአህያ ፥ በዚያም ፡ ሰፈር ፡ ባለ ፡ እንስሳ ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡ ቸነፈር ፡ እንደዚያ ፡ ያለ ፡ ቸነፈር ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ ከመጡት ፡ ከአሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ የቀሩት ፡ ሹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፥ የዳስ ፡ በዓልንም ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ በየዓመቱ ፡ ይወጣሉ ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ከምድርም ፡ ወገኖች ፡ ሹሉ ፡ ለንጉሡ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለማይወጡ ፡ ለእነርሱ ፡ ዝናብ ፡ አይዘንብላቸውም ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ የግብጽም ፡ ወገን ፡ ባይወጣ ፡ ወደዚያም ፡ ባይመጣ ፥ እግዚአብሔር ፡ የዳስ ፡ በዓልን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይወጡትን ፡ አሕዛብ ፡ የሚቀሥፍበት ፡ ቸነፈር ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ የግብጽ ፡ ቅጣት ፥ የዳስ ፡ በዓልንም ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ የማይወጡት ፡ የአሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ ቅጣት ፡ እንደዚህ ፡ ይኾናል ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በፈረሶች ፡ ሻኮራ ፡ ላይ ፦ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሰ ፡ ተብሎ ፡ ይጻፋል ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ያሉ ፡ ምንቸቶች ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ እንዳሉ ፡ ዳካዎች ፡ ይኾናሉ ።

ዘካ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ በኢየሩሳሌምና ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ምንቸቶችም ፡ ሹሉ ፡ ለሰራዊት ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተቀደሱ ፡ ይኾናሉ ፤ የሚሠዉትም ፡ ሰዎች ፡ ሹሉ ፡ ይመጣሉ ፡ ከነዚያም ፡ ወስደው ፡ ይቀቅሉባቸዋል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ከነዓናዊው ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ አይገኝም ።

ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሚል. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በሚልክያስ ፡ እጅ ፡ ለእስራኤል ፡ የኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ወድጃችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ በምን ፡ ወደድኸን ፧ ብላችኋል ። ዔሳው ፡ የያዕቆብ ፡ ወንድም ፡ አልነበረምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ያዕቆብንም ፡ ወደድኹ ፥ ዔሳውንም ፡ ጠላኹ ፤

ሚል. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ተራራዎቹንም ፡ በረሓ ፡ አደረግኋቸው ፥ ርስቱንም ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ ቀበሮዎች ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋቸው ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ኤዶምያስ ፦ እኛ ፡ ፈርሰናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የፈረሰውን ፡ መልሰን ፡ እንሠራለን ፡ ቢል ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነርሱ ፡ ይሠራሉ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አፈርሳለኹ ፤ በሰዎችም ፡ ዘንድ ፦ የበደል ፡ ዳርቻና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ የተቈጣው ፡ ሕዝብ ፡ ይባላል ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ዐይኖቻችኹም ፡ ያያሉ ፥ እናንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ ወዲያ ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፡ ትላላችኹ ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እናንተ ፡ ስሜን ፡ የምታቃልሉ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ልጅ ፡ አባቱን ፥ ባሪያም ፡ ጌታውን ፡ ያከብራል ፤ እኔስ ፡ አባት ፡ ከኾንኹ ፡ ክብሬ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ጌታስ ፡ ከኾንኹ ፡ መፈራቴ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እናንተም ፦ ስምኽን ፡ ያቃለልን ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 7 ፤ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ርኩስ ፡ እንጀራ ፡ ታቀርባላችኹ ። እናንተም ፦ ያረከስንኽ ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። የእግዚአብሔር ፡ ገበታ ፡ የተነቀፈ ፡ ነው ፡ በማለታችኹ ፡ ነው ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ዕውር ፡ መሥዋዕትንም ፡ ስታቀርቡ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ አይደለምን ፧ ዐንካሳውንና ፡ የታመመውን ፡ ስታቀርቡ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ አይደለምን ፧ ያን ፡ ለአለቃኽ ፡ አቅርብ ፤ በእውኑ ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለዋልን ፧ ወይስ ፡ ፊትኽን ፡ ይቀበላልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 9 ፤ አኹንም ፡ ጸጋን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኑ ፤ ይህ ፡ ከእጃችኹ ፡ የተሰጠ ፡ ሲኾን ፡ ከቶ ፡ ፊታችኹን ፡ ይቀበላልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ በከንቱ ፡ እንዳታቃጥሉ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ደጅ ፡ የሚዘጋ ፡ ሰው ፡ ምነው ፡ በተገኘ! ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡ አይለኝም ፥ ቍርባንንም ፡ ከእጃችኹ ፡ አልቀበልም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ መግቢያዋ ፡ ድረስ ፡ ስሜ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ፤ በየስፍራውም ፡ ለስሜ ፡ ዕጣን ፡ ያጥናሉ ፥ ንጹሕም ፡ ቍርባን ፡ ያቀርባሉ ፤ ስሜ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ገበታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ፍሬውና ፡ መብሉም ፡ የተናቀ ፡ ነው ፡ በማለታችኹ ፡ አስነቀፋችኹት ።

ሚል. ፥ 1 ፥ 13 ፤ እናንተ ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ድካም ፡ ነው ፡ ብላችኹ ፡ ጢቅ ፡ አላችኹበት ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡

ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በቅሚያ ፡ የያዛችኹትንም ፡ ዐንካሳውንም ፡ የታመመውንም ፡ አቅርባችኋል ፤ እንዲሁ ፡ ቍርባንን ፡ ታመጣላችኹ ፤ በእውኑ ፡ ከእጃችኹ ፡ ይህን ፡ ልቀበለውን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፡ 1 ፡ 14 ፤ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስሜም ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ የተፈራ ፡ ነውና ፥ በመንጋው ፡ ውስጥ ፡ ተባት ፡ እያለው ፡ ለጌታ ፡ ተስሎ ፡ ነውረኛውን ፡ የሚሠዋ ፡ ሸንጋይ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ።

ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 1 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ለእናንተ ፡ ነው ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ለስሜ ፡ ክብር ፡ ትሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ባትሰሙ ፥ በልባችኹም ፡ ባታደርጉት ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ርግማን ፡ እሰድባችኋለኹ ፥ በረከታችኹንም ፡ እረግማታለኹ ፤ አኹንም ፡ በልባችኹ ፡ አላደረጋችኹትምና ፡ እኔ ፡ ረግሜያታለኹ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ ክንዳችኹን ፡ እገሥጻለኹ ፥ የመሥዋዕታችኹንም ፡ ፋንድያ ፡ በፊታችኹ ፡ ላይ ፡ እበትናለኹ ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ትወሰዳላችኹ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ከሌዊ ፡ ጋራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሰደድኹላችኹ ፡ ታውቃላችኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሕይወትና ፡ የሰላም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ነበረ ፤ ይፈራ ፡ ዘንድም ፡ እነርሱን ፡ ሰጠኹት ፤ ርሱም ፡ ፈራኝ ፥ ከስሜም ፡ የተነሣ ፡ ደነገጠ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 6 ፤ የእውነት ፡ ሕግ ፡ በአፉ ፡ ውስጥ ፡ ነበረች ፥ በከንፈሩም ፡ ውስጥ ፡ በደል ፡ አልተገኘበትም ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ በሰላምና ፡ በቅንነት ፡ ኼደ ፥ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ከኀጢአት ፡ መለሰ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ካህኑ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛ ፡ ነውና ፥ ከንፈሮቹ ፡ ዕውቀትን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባቸዋል ፥ ሰዎችም ፡ ሕግን ፡ ከአፉ ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ ይገባቸዋል ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ከመንገዱ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላችኋል ፤ በሕግም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አሰናክላችኋል ፤ የሌዊንም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ አስነውራችኋል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ መንገዴን ፡ እንዳልጠበቃችኹ ፥ በሕግም ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳዳላችኹ ፡ መጠን ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ የተናቃችኹና ፡ የተዋረዳችኹ ፡ አድርጌያችኋለኹ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ለኹላችን ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ያለን ፡ አይደለምን ፧ አንድ ፡ አምላክስ ፡ የፈጠረን ፡ አይደለምን ፧ የአባቶቻችንን ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለማስነቀፍ ፡ እኛ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወንድማችንን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አታለልን ፧

ሚል. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ መቅደስ ፡ ይሁዳ ፡ አርክሷልና ፥ የእንግዳውንም ፡ አምላክ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ አድርጎ ፡ አግብቷልና ፥ ይሁዳ ፡ አታሏል ፥ በእስራኤልና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ርኵሰት ፡ ተሠርቷል ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ይህን ፡ ከሚያደርግ ፡ ሰው ፥ እግዚአብሔር ፡ የሚጠራውንና ፡ የሚመልሰውን ፡ ለሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቍርባን ፡ የሚያቀርበውን ፡ ከያዕቆብ ፡ ድንኳን ፡ ያጠፋል ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ አድርጋችኋል ፤ እግዚአብሔር ፡ ቍርባኑን ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይመለከት ፥ ከእጃችኹም ፡ በደስታ ፡ እንዳይቀበለው ፡ መሠዊያውን ፡ በእንባና ፡ በልቅሶ ፡ በሐዘንም ፡ ትከድናላችኹ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 14 ፤ እናንተም ፦ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። ሚስትኽ ፡ ባልንጀራኽና ፡ የቃል ፡ ኪዳንኽ ፡

ሚስት ፡ ኾና ፡ ሳለች ፡ ርሷን ፡ አታለኻታልና ፥ እግዚአብሔር ፡ በአንተና ፡ በልጅነት ፡ ሚስትኽ ፡ መካከል ፡ ምስክር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሕይወትን ፡ መንፈስ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ጠብቆልን ፡ የለምን ፧ ርሱም ፡ የሚፈልገው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ዘር ፡ አይደለምን ፧ ስለዚህ ፡ መንፈሳችኹን ፡ ጠብቁ ፥ ማንም ፡ የልጅነት ፡ ሚስቱን ፡ አያታል ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 16 ፤ መፋታትን ፡ እጠላለኹ ፥ ይላል ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ልብሱንም ፡ በግፍ ፡ ሥራ ፡ የሚከድነውን ፡ ሰው ፡ እጠላለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ስለዚህ ፥ እንዳታታልሉ ፡ መንፈሳችኹን ፡ ጠብቁ ።

ሚል. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በቃላችኹ ፡ አታክታችኻል ። እናንተም ፦ ያታከትነው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኻል ። ክፉን ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ በእነርሱ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ወይስ ፦ የፍርድ ፡ አምላክ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ በማለታችኹ ፡ ነው ።

_____ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ሚል. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንሆ ፥ መልእክተኛዬን ፡ እልካለኹ ፥ መንገድንም ፡ በፊቴ ፡ ያስተካክላል ፤ እናንተም ፡ የምትፈልጉት ፡ ጌታ ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ይመጣል ፤ የምትወዱትም ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ መልእክተኛ ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ እንደ ፡ አንጥረኛ ፡ እሳትና ፡ እንደ ፡ ዐጣቢ ፡ ሳሙና ፡ ነውና ፥ የሚመጣበትን ፡ ቀን ፡ መታገሥ ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱስ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሚል. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ ብርን ፡ እንደሚያነጥርና ፡ እንደሚያጠራ ፡ ሰው ፡ ይቀመጣል ፥ የሌዊንም ፡ ልጆች ፡ ያጠራል ፥ እንደ ፡ ወርቅና ፡ እንደ ፡ ብርም ፡ ያነጥራቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ቍርባንን ፡ የሚያቀርቡ ፡ ይኾናሉ ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ ዘመንና ፡ እንደ ፡ ቀደሙት ፡ ዓመታት ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቍርባን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ለፍርድ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እቀርባለኹ ፤ በመተተኞችና ፡ በአመንዝራዎች ፥ በሐሰትም ፡ በሚምሉ ፥ የምንደኛውን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በሚከለክሉ ፥ መበለቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ በሚያስጨንቁ ፥ የመጻተኛውንም ፡ ፍርድ ፡ በሚያጣምሙ ፥ እኔንም ፡ በማይፈሩ ፡ ላይ ፡ ፈጣን ፡ ምስክር ፡ እኾንባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልለወጥም ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ የጠፋችኹ ፡ አይደላችኹም ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ከአባቶቻችኹ ፡ ዘመን ፡ ዠምር ፡ ከሥርዐቴ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላችኻል ፥ ርሷንም ፡ አልጠበቃችኹም ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፥ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ግን ፦ የምንመለሰው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኻል ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሰርቃልን ፧ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ሰርቃችኻል ። እናንተም ፦ የሰረቅንኽ ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኻል ። በዓሥራትና ፡ በበኵራት ፡ ነው ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እናንተ ፥ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ እኔን ፡ ሰርቃችኻልና ፥ በርግማን ፡ ርጉሞች ፡ ናችኹ ።

ሚል. ፡ 3 ፡ 10 ፤ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ መብል ፡ እንዲኾን ፡ ዓሥራቱን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጐተራ ፡ አግቡ ፤ የሰማይንም ፡

መስኮት ፡ ባልከፍትላችኹ ፥ በረከትንም ፡ አትረፍርፌ ፡ ባላፈስላችኹ ፡ በዚህ ፡ ፈትኑኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 11 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ ነቀዙን ፡ እገሥጻለኹ ፥ የምድራችኹንም ፡ ፍሬ ፡ አያጠፋም ፤ በዕርሻችኹም ፡ ያለው ፡ ወይን ፡ ፍሬውን ፡ አያረግፍም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 12 ፤ የተድላ ፡ ምድር ፡ ትኾናላችኹና ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ብፁዓን ፡ ብለው ፡ ይጠሯችኋል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 13 ፤ ቃላችኹ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ድፍረት ፡ ኾኗል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ግን ፦ ባንተ ፡ ላይ ፡ ደፍረን ፡ የተናገርነው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 14 ፤ እናንተም ፦ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ ትእዛዙንስ ፡ በመጠበቅ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሐዘንተኞች ፡ ኾነን ፡ በመኼድ ፡ ምን ፡ ይረባናል ፧

ሚል. ፥ 3 ፥ 15 ፤ አኹንም ፡ የሚታበዩትን ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ብለን ፡ እንጠራቸዋለን ፤ ክፉንም ፡ የሚሠሩ ፡ ጸንተዋል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ይፈታተናሉ ፥ ያመልጣሉም ፡ ብላችኋል ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 16 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አደመጠ ፥ ሰማም ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ለሚፈሩ ፡ ስሙንም ፡ ለሚያስቡ ፡ የመታሰቢያ ፡ መጽሐፍ ፡ በፊቱ ፡ ተጻፈ ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 17 ፤ እኔ ፡ በምሠራበት ፡ ቀን ፡ እነርሱ ፡ የእኔ ፡ ገንዘብ ፡ ይኾናሉ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሰውም ፡ የሚያገለግለውን ፡ ልጁን ፡ እንደሚምር ፥ እንዲሁ ፡ እምራቸዋለኹ ።

ሚል. ፥ 3 ፥ 18 ፤ ተመልሳችኹም ፡ በጻድቁና ፡ በኀጢአተኛው ፡ መካከል ፥ ለእግዚአብሔር ፡ በሚገዛውና ፡ በማይገዛው ፡ መካከል ፡ ትለያላችኹ ።

ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 1 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ምድጃ ፡ እሳት ፡ የሚነድ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፤ ትዕቢተኞችና ፡ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ኹሉ ፡ ገለባ ፡ ይኾናሉ ፤ የሚመጣውም ፡ ቀን ፡ ያቃጥላቸዋል ፥ ሥርንና ፡ ቅርንጫፍንም ፡ አይተውላቸውም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስሜን ፡ ለምትፈሩት ፡ ለእናንተ ፡ የጽድቅ ፡ ፀሓይ ፡ ትወጣላችኋለች ፥ ፈውስም ፡ በክንፎቿ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናል ፤ እናንተም ፡ ትወጣላችኹ ፥ እንደ ፡ ሰባም ፡ እንቦሳ ፡ ትፈነጫላችኹ ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 3 ፤ በምሠራበት ፡ ቀን ፡ በደለኞች ፡ ከእግራችኹ ፡ ጫማ ፡ በታች ፡ ዐመድ ፡ ይኾናሉና ፡ እናንተ ፡ ትረግጧቸዋላችኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 4 ፤ ለእስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ሥርዐትንና ፡ ፍርድን ፡ አድርጌ ፡ በኮሬብ ፡ ያዘዝኹትን ፡ የባሪያዬን ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ ዐስቡ ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 5 ፤ እንሆ ፥ ታላቁና ፡ የሚያስፈራው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ነቢዩን ፡ ኤልያስን ፡ እልክላችኋለኹ ።

ሚል. ፥ 4 ፥ 6 ፤ መጥቼም ፡ ምድርን ፡ በርግማን ፡ እንዳልመታ ፡ ርሱ ፡ የአባቶችን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ልጆች ፥ የልጆችንም ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ አባቶች ፡ ይመልሳል ❖

ተጨማሪ ፡ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ።

የቀሮና ፡ መጻሕፍት ።

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ሱቴኤል ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ፡ ካልዕ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ጦቢት ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ዮዲት ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ አስቴር ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ቀዳማዊ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ካልዕ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ መቃብያን ፡ ሣልስ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ሲራክ ። (ይዘጋጃል)

ጸሎተ ፡ ምናሴ ። (ይዘጋጃል)

ተረፈ ፡ ኤርምያስ ። (ይዘጋጃል)

ሶስና ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ባሮክ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ጥበብ ። (ይዘጋጃል)

መዝሙረ ፡ ሠለስቱ ፡ ደቂቅ ። (ይዘጋጃል)

ተረፈ ፡ ዳንኤል ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ኩፋሌ ። (ይዘጋጃል)

መጽሐፈ ፡ ሔኖክ ። (ይዘጋጃል)

የጌታችንና ፡ የመድኀኒታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐዲስ ፡ ኪዳን ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ማቴ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ የ[279]ኢየሱስ ([279]) ፡ [280]ክርስቶስ ([280]) ፡ ትውልድ ፡ መጽሐፍ ።

ማቴ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ አብርሃም ፡ ይሥሐቅን ፡ ወለደ ፤ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤ ያዕቆብም ፡ ይሁዳንና ፡ ወንድሞቹን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ይሁዳም ፡ ከትዕማር ፡ ፋሬስንና ፡ ዛራን ፡ ወለደ ፤ ፋሬስም ፡ ኤስሮምን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ኤስሮምም ፡ አራምን ፡ ወለደ ፤ አራምም ፡ ዐሚናዳብን ፡ ወለደ ፤ ዐሚናዳብም ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ፤ ነአሶንም ፡ ሰልሞንን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ሰልሞንም ፡ ከራኬብ ፡ ቦኤዝን ፡ ወለደ ፤ ቦኤዝም ፡ ከሩት ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ፤ ኢዮቤድም ፡ እሴይን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እሴይም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ።

ማቴ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ሰሎሞንም ፡ ሮብዓምን ፡ ወለደ ፤ ሮብዓምም ፡ አቢያን ፡ ወለደ ፤ አቢያም ፡ አሣፍን ([281]) ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ አሣፍም ፡ ኢዮሳፍጥን ፡ ወለደ ፤ ኢዮሳፍጥም ፡ ኢዮራምን ፡ ወለደ ፤ ኢዮራምም ፡ ዖዝያንን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ዖዝያንም ፡ ኢዮአታምን ፡ ወለደ ፤ ኢዮአታምም ፡ አካዝን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ አካዝም ፡ ሕዝቅያስን ፡ ወለደ ፤ ሕዝቅያስም ፡ ምናሴን ፡ ወለደ ፤ ምናሴም ፡ አሞፅን ([282]) ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ አሞፅም ፡ ኢዮስያስን ፡ ወለደ ፤ ኢዮስያስም ፡ በባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ጊዜ ፡ ኢኮንያንንና ፡ ወንድሞቹን ፡ ወለደ ።

ማቴ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ከባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ በኋላ ፡ ኢኮንያን ፡ ሰላትያልን ፡ ወለደ ፤ ሰላትያልም ፡ ዘሩባቤልን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ዘሩባቤልም ፡ አብዩድን ፡ ወለደ ፤ አብዩድም ፡ ኤልያቄምን ፡ ወለደ ፤ ኤልያቄምም ፡ ዐዛርን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ዐዛርም ፡ ሳዶቅን ፡ ወለደ ፤ ሳዶቅም ፡ አኪምን ፡ ወለደ ፤ አኪምም ፡ ኤልዩድን ፡ ወለደ ፤

---

279 ግ. ፥ የሱስ ፡ (መድኀን) ፥ (ዕብ. ፥ የሆሹዐ) ፤ 'ኢ.' ፡ ከጽርእ ፡ 'የውጣ-ሪ' ፡ የተወረሰ ፡ ትርፍ ፡ ነው ።

280 ግ. ፥ መሲሕ ፡ (ዕብ. ፥ መሺያሕ) ። 'ክርስቶስ' ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በጽርእ ፡ 'ኀሪያ-የተቀባ ፥ ምርጥ' ፡ (χρίω) ፡ ካለው ፡ የወጣ ፡ ነው ፤ ከ'ኀረየ' ፡ የተገኘ ፡ ይመስላል ። ዐይነተኛው ፡ የግእዝ ፡ አጠራሩ ፡ 'መሲሕ' ፡ ነው ። ሐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ከጽርእ ፡ ወደ ፡ ግእዝ ፡ ሲመለስ ፥ ብዙ ፡ የስም ፡ አጠራሮች ፡ ከጽርኡ ፡ በተቀዱበት ፡ አባባል ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ደርሰዋል ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ ቢስተካከሉ ፡ ይበጃል ። [አዘጋጅ]

281 ዕብ. ፥ አሣ ።

282 ዕብ. ፥ አሞን ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ ኤልዩድም ፡ አልዓዛርን ፡ ወለደ ፤ አልዓዛርም ፡ ማታንን ፡ ወለደ ፤ ማታንም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ፤

ማቴ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ያዕቆብም ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየሱስን ፡ የወለደች ፡ የማርያምን ፡ ዕጮኛ ፡ ዮሴፍን ፡ ወለደ ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፡ ከአብርሃም ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፥ ከዳዊትም ፡ እስከባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፥ ከባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ ትውልድ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ልደት ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። እናቱ ፡ ማርያም ፡ ለዮሴፍ ፡ በታጨች ፡ ጊዜ ፥ ሳይገናኙ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፀንሳ ፡ ተገኘች ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ዕጮኛዋ ፡ ዮሴፍም ፡ ጻድቅ ፡ ኾኖ ፡ ሊገልጣት ፡ ስላልወደደ ፥ በስውር ፡ ሊተዋት ፡ ዐሰበ ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሲያስብ ፥ እንሆ ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ታየው ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ዮሴፍ ፡ ሆይ ፥ ከርሷ ፡ የተፀነሰው ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ዕጮኛኽን ፡ ማርያምን ፡ ለመውሰድ ፡ አትፍራ ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ልጅም ፡ ትወልዳለች ፤ ርሱ ፡ ሕዝቡን ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ያድናቸዋልና ፥ ስሙን ፡ ኢየሱስ ፡ ትለዋለኽ ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ በነቢይ ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፦

ማቴ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ እንሆ ፥ ድንግል ፡ ትፀንሳለች ፡ ልጅም ፡ ትወልዳለች ፥ ስሙንም ፡ ዐማኑኤል ፡ ይሉታል ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ ኾኗል ፥ ትርጓሜውም ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ የሚል ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ዮሴፍም ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ እንዳዘዘው ፡ አደረገ ፤ ዕጮኛውንም ፡ ወሰደ ፤

ማቴ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ የበኵር ፡ ልጁንም ፡ እስክትወልድ ፡ ድረስ ፡ አላወቃትም ፤ ስሙንም ፡ ኢየሱስ ፡ አለው ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ማቴ. ፡ 2 ፡ 1-2 ፤ ኢየሱስም ፡ በይሁዳ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ በንጉሡ ፡ በሄሮድስ ፡ ዘመን ፡ በተወለደ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ሰብአ ፡ ሰገል ፦ የተወለደው ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ኮከቡን ፡ በምሥራቅ ፡ አይተን ፡ ልንሰግድለት ፡ መጥተናልና ፥ እያሉ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ንጉሡ ፡ ሄሮድስም ፡ ሰምቶ ፡ ደነገጠ ፥ ኢየሩሳሌምም ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፤

ማቴ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ የካህናትንም ፡ አለቃዎች ፡ የሕዝቡንም ፡ ጸሊዎች ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ክርስቶስ ፡ ወዴት ፡ እንዲወለድ ፡ ጠየቃቸው ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 5-6 ፤ እነርሱም ፦ አንቺ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፥ የይሁዳ ፡ ምድር ፥ ከይሁዳ ፡ ገዢዎች ፡ ከቶ ፡ አታንሺም ፤ ሕዝቤን ፡ እስራኤልን ፡ የሚጠብቅ ፡ መስፍን ፡ ከአንቺ ፡ ይወጣልና ፥ ተብሎ ፡ በነቢይ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፏልና ፥ በይሁዳ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ነው ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልን ፡ በስውር ፡ ጠርቶ ፡ ኮከቡ ፡ የታየበትን ፡ ዘመን ፡ ከነርሱ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተረዳ ፥

ማቴ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ እነርሱን ፡ ሰዶ ፦ ኺዱ ፥ ስለ ፡ ሕፃኑ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሩ ፤ ባገኛችኹትም ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ መጥቼ ፡ እንድሰግድለት ፡ ንገሩኝ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ ንጉሡን ፡ ሰምተው ፡ ኼዱ ፤ እንሆም ፥ በምሥራቅ ፡ ያዩት ፡ ኮከብ ፡ ሕፃኑ ፡ ባለበት ፡ ላይ ፡ መጥቶ ፡ እስኪቆም ፡ ድረስ ፡ ይመራቸው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ኮከቡንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ገብተው ፡ ሕፃኑን ፡ ከእናቱ ፡ ከማርያም ፡ ጋራ ፡ አዩት ፥ ወድቀውም ፡ ሰገዱለት ፥ ሣጥኖቻቸውንም ፡ ከፍተው ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ወርቅና ፡ ዕጣን ፡ ከርቤም ፡ አቀረቡለት ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ሄሮድስም ፡ እንዳይመለሱ ፡ በሕልም ፡ ተረድተው ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ኼዱ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ ከኼዱ ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ለዮሴፍ ፡ ታይቶ ፦ ሄሮድስ ፡ ሕፃኑን ፡ ሊገድለው ፡ ይፈልገዋልና ፥ ተነሣ ፥ ሕፃኑንና ፡ እናቱንም ፡ ይዘኽ ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ሽሽ ፥ እስክነግርኽም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 14-15 ፤ ርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ በሌሊት ፡ ያዘና ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ በነቢይ ፦ ልጄን ፡ ከግብጽ ፡ ጠራኹት ፡ የተባለው ፡ እንዲፈጸም ፥ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ኼደ ፥ ሄሮድስም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ኖረ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰብአ ፡ ሰገል ፡ እንደ ፡ ተሣለቁበት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ተቈጣና ፡ ልኮ ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፡ እንደ ፡ ተረዳው ፡ ዘመን ፡ በቤተ ፡ ልሔምና ፡ በአውራጃዋ ፡ የነበሩትን ፥ ኹለት ፡ ዓመት ፡ የኾናቸውን ፡ ከዚያም ፡ የሚያንሱትን ፡ ሕፃናት ፡ ኾሉ ፡ አስገደለ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 17-18 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፥ ድምፅ ፡ በራማ ፡ ተሰማ ፥ ልቅሶና ፡ ብዙ ፡ ዋይታ ፤ ራሔል ፡ ስለ ፡ ልጆቿ ፡ አለቀሰች ፥ መጽናናትም ፥ አልወደደችም ፥ የሉምና ፡ የተባለው ፡ ተፈጸመ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ሄሮድስም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፥ እንሆ ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ በግብጽ ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ ታይቶ ፦

ማቴ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ የሕፃኑን ፡ ነፍስ ፡ የፈለጉት ፡ ሞተዋልና ፥ ተነሣ ፥ ሕፃኑን ፡ እናቱንም ፡ ይዘኽ ፡ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ ኺድ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ ያዘና ፡ ወደእስራኤል ፡ አገር ፡ ገባ ።

ማቴ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ በአባቱም ፡ በሄሮድስ ፡ ፈንታ ፡ አርኬላዎስ ፡ በይሁዳ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚያ ፡ መኼድን ፡ ፈራ ፤ በሕልምም ፡ ተረድቶ ፡ ወደገሊላ ፡ አገር ፡ ኼደ ፤

ማቴ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ በነቢያት ፦ ናዝራዊ ፡ ይባላል ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፥ ናዝሬት ፡ ወደምትባል ፡ ከተማ ፡ መጥቶ ፡ ኖረ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 1-2 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ ብሎ ፡ በይሁዳ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ እየሰበከ ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፦ የጌታን ፡ መንገድ ፡ አዘጋጁ ፡ ጥርጊያውንም ፡ አቅኑ ፡ እያለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚጮኽ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ የተባለለት ፡ ይህ ፡ ነውና ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ራሱም ፡ ዮሐንስ ፡ የግመል ፡ ጠጕር ፡ ልብስ ፡ ነበረው ፥ በወገቡም ፡ ጠፍር ፡ ይታጠቅ ፡ ነበር ፤ ምግቡም ፡ አንበጣና ፡ የበረሓ ፡ ማር ፡ ነበረ ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይሁዳም ፡ ኾሉ ፡ በዮርዳኖስም ፡ ዙሪያ ፡ ያለ ፡ አገር ፡ ኾሉ ፡ ወደ ፡

ርሱ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፤

ማቴ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ኀጢአታቸውንም ፡ እየተናዘዙ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ከርሱ ፡ ይጠመቁ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ብዙዎች ፡ ወደ ፡ ጥምቀቱ ፡ ሲመጡ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ የእፍኝት ፡ ልጆች ፥ ከሚመጣው ፡ ቍጣ ፡ እንድትሸሹ ፡ ማን ፡ አመለከታችኹ ፧

ማቴ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እንግዲህ ፡ ለንስሓ ፡ የሚገባ ፡ ፍሬ ፡ አድርጉ ፤

ማቴ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በልባችኹም ፦ አብርሃም ፡ አባት ፡ አለን ፡ እንደምትሉ ፡ አይምሰላችኹ ፤ እላችኋለኹና ፦ ከነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ለአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ሊያስነሣለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይችላል ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ አኹንስ ፡ ምሣር ፡ በዛፎች ፡ ሥር ፡ ተቀምጧል ፤ እንግዲህ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ የማያደርግ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይቈረጣል ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ይጣላል ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እኔስ ፡ ለንስሓ ፡ በውሃ ፡ አጠምቃችኋለኹ ፤ ጫማውን ፡ እሸከም ፡ ዘንድ ፡ የማይገባኝ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ ይበረታል ፤ ርሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእሳትም ፡ ያጠምቃችኋል ፤

ማቴ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ መንሹም ፡ በእጁ ፡ ነው ፥ ዐውድማውንም ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠራል ፥ ስንዴውንም ፡ በጐተራው ፡ ይከታል ፥ ገለባውን ፡ ግን ፡ በማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ያቃጥለዋል ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በዮሐንስ ፡ ሊጠመቅ ፡ ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ዮርዳኖስ ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ዮሐንስ ፡ ግን ፦ እኔ ፡ ባንተ ፡ ልጠመቅ ፡ ያስፈልገኛል ፡ አንተም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጣለኽን ፧ ብሎ ፡ ይከለክለው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ አኹንስ ፡ ፍቀድልኝ ፤ እንዲህ ፡ ጽድቅን ፡ ኹሉ ፡ መፈጸም ፡ ይገባናልና ፥ አለው ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ፈቀደለት ።

ማቴ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ኢየሱስም ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ከውሃ ፡ ወጣ ፤ እንሆም ፥ ሰማያት ፡ ተከፈቱ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ሲወርድ ፡ በርሱ ፡ ላይም ፡ ሲመጣ ፡ አየ ፤

ማቴ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ እንሆም ፥ ድምፅ ፡ ከሰማያት ፡ መጥቶ ፦ በርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አለ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ኢየሱስ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ይፈተን ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወሰደው ፥

ማቴ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ አርባ ፡ ቀንና ፡ አርባ ፡ ሌሊትም ፡ ከጦመ ፡ በኋላ ፡ ተራበ ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ፈታኝም ፡ ቀርቦ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከኾንኽ ፥ እነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ እንጀራ ፡ እንዲኾኑ ፡ በል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አፍ ፡ በሚወጣ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ አይኖርም ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ዲያብሎስ ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ከተማ ፡ ወሰደውና ፡ ርሱን ፡ በመቅደስ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፦

ማቴ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ መላእክቱን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ያዝልኻል ፡ እግርኽንም ፡ በድንጋይ ፡ ከቶ ፡ እንዳትሰናከል ፡ በእጃቸው ፡ ያነሡኻል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ ከኾንኽ ፥ ወደ ፡ ታች ፡ ራስኽን ፡ ወርውር ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፦ ጌታን ፡ አምላክኽን ፡ አትፈታተነው ፡ ተብሎ ፡ ደግሞ ፡ ተጽፏል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ደግሞ ፡ ዲያብሎስ ፡ እጅግ ፡ ረዥም ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ተራራ ፡ ወሰደው ፥ የዓለምንም ፡ መንግሥታት ፡ ሹሉ ፡ ክብራቸውንም ፡ አሳይቶ ፦

ማቴ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ወድቀኽ ፡ ብትሰግድልኝ ፡ ይህን ፡ ሹሉ ፡ እሰጥኻለኹ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፦ ኺድ ፥ አንተ ፡ ሰይጣን ፡ ለጌታኽ ፡ ለአምላክኽ ፡ ስገድ ፡ ርሱንም ፡ ብቻ ፡ አምልክ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፥ አለው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ዲያብሎስ ፡ ተወው ፥ እንሆም ፥ መላእክት ፡ ቀርበው ፡ ያገለግሉት ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ኢየሱስም ፡ ዮሐንስ ፡ ዐልፎ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ናዝሬትንም ፡ ትቶ ፡ በዛብሎንና ፡ በንፍታሌም ፡ አገር ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወዳለችው ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ መጥቶ ፡ ኖረ ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 14-16 ፤ በነቢዩም ፡ በኢሳይያስ ፦ የዛብሎን ፡ ምድርና ፡ የንፍታሌም ፡ ምድር ፥ የባሕር ፡ መንገድ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፥ የአሕዛብ ፡ ገሊላ ፤ በጨለማ ፡ የተቀመጠው ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ብርሃን ፡ አየ ፥ በሞት ፡ አገርና ፡ ጥላ ፡ ለተቀመጡትም ፡ ብርሃን ፡ ወጣላቸው ፡

ማቴ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ኾነ ። ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ዠምሮ ፡ ኢየሱስ ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለችና ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ እያለ ፡ ይሰብክ ፡ ዠመር ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ በገሊላ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ሲመላለስም ፡ ኹለት ፡ ወንድማማች ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚሉትን ፡ ስምዖንን ፡ ወንድሙንም ፡ እንድርያስን ፡ መረባቸውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሲጥሉ ፡ አየ ፥ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ነበሩና ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ርሱም ፦ በኋላዬ ፡ ኑና ፡ ሰዎችን ፡ አጥማጆች ፡ እንድትኾኑ ፡ አደርጋችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ወዲያውም ፡ መረባቸውን ፡ ትተው ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ከዚያም ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ሌላዎችን ፡ ኹለት ፡ ወንድማማች ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡ ከአባታቸው ፡ ከዘብዴዎስ ፡ ጋራ ፡ በታንኳ ፡ መረባቸውን ፡ ሲያበጁ ፡ አየ ፤ ጠራቸውም ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ እነርሱም ፡ ወዲያው ፡ ታንኳዩ ፡ ትንና ፡ አባታቸውን ፡ ትተው ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ በምኩራቦቻቸው ፡ እያስተማረ ፡ የመንግሥትንም ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከ ፡ በሕዝብም ፡ ያለውን ፡ ደዌና ፡ ሕማም ፡ ሹሉ ፡ እየፈወሰ ፡ በገሊላ ፡ ሹሉ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ዝናውም ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ሹሉ ፡ ወጣ ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌና ፡ ሥቃይም ፡ ተይዘው ፡ የታመሙትን ፡ ሹሉ ፡ አጋንንትም ፡ ያደሩባቸውን ፡ በጨረቃም ፡ የሚነሣባቸውን ፡ ሽባዎችንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፥ ፈወሳቸውም ።

ማቴ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ከገሊላም ፡ ከዐሥሩ ፡ ከተማም ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ከይሁዳም ፡ ከዮርዳኖስም ፡ ማዶ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉት ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 1 ፤ ሕዝቡንም ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፤ በተቀመጠም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ፤

ማቴ. ፥ 5 ፥ 2 ፤ አፉንም ፡ ከፍቶ ፡ አስተማራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 3 ፤ በመንፈስ ፡ ድኻዎች ፡ የኾኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ የሚያዝኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ መጽናናትን ፡ ያገኛሉና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ የዋሆች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ ምድርን ፡ ይወርሳሉና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ ጽድቅን ፡ የሚራቡና ፡ የሚጠሙ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ ይጠግባሉና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ የሚምሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ ይማራሉና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ ልበ ፡ ንጹሐች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታልና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 9 ፤ የሚያስተራርቁ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 10 ፤ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ የሚሰደዱ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፥ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የእነርሱ ፡ ናትና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ ሲነቅፏችኹና ፡ ሲያሳድዷችኹ ፡ በእኔም ፡ ምክንያት ፡ ክፉውን ፡ ኹሉ ፡ በውሸት ፡ ሲናገሩባችኹ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 12 ፤ ዋጋችኹ ፡ በሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ሐሴትም ፡ አድርጉ ፤ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ የነበሩትን ፡ ነቢያትን ፡ እንዲሁ ፡ አሳደዋቸዋልና ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 13 ፤ እናንተ ፡ የምድር ፡ ጨው ፡ ናችኹ ፤ ጨው ፡ ዐልጫ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ በምን ፡ ይጣፍጣል ፧ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጥሎ ፡ በሰው ፡ ከመረገጥ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለምንም ፡ አይጠቅምም ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 14 ፤ እናንተ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ናችኹ ። በተራራ ፡ ላይ ፡ ያለች ፡ ከተማ ፡ ልትሰወር ፡ አይቻላትም ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 15 ፤ መብራትንም ፡ አብርተው ፡ ከእንቅብ ፡ በታች ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፡ በመቅረዙ ፡ ላይ ፡ ያኖሩታል ፡ በቤት ፡ ላሉት ፡ ኹሉም ፡ ያበራል ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 16 ፤ መልካሙን ፡ ሥራችኹን ፡ አይተው ፡ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ አባታችኹን ፡ እንዲያከብሩ ፡ ብርሃናችኹ ፡ እንዲሁ ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ይብራ ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 17 ፤ እኔ ፡ ሕግንና ፡ ነቢያትን ፡ ለመሻር ፡ የመጣኹ ፡ አይምሰላችኹ ፤ ልፈጽም ፡ እንጂ ፡ ለመሻር ፡ አልመጣኹም ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 18 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ሰማይና ፡ ምድር ፡ እስኪያልፍ ፡ ድረስ ፥ ከሕግ ፡ አንዲት ፡ የውጣ ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ነጥብ ፡ ከቶ ፡ አታልፍም ፥ ኹሉ ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ።

ማቴ. ፥ 5 ፥ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ከነዚህ ፡ ከኹሉ ፡ ካነሱት ፡ ትእዛዛት ፡ አንዲቱን ፡ የሚሽር ፡ ለሰውም ፡ እንዲሁ ፡ የሚያስተምር ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከኹሉ ፡ ታናሽ ፡ ይባላል ፤ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ የሚያስተምርም ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡ ርሱ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ታላቅ ፡ ይባላል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ እላችኋለኹና ፦ ጽድቃችኹ ፡ ከጻፊዎችና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ጽድቅ ፡ ካልበለጠ ፥ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከቶ ፡ አትገቡም ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ለቀደሙት ፦ አትግደል ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ፤ የገደለም ፡ ኹሉ ፡ ፍርድ ፡ ይጎሳዋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ በወንድሙ ፡ ላይ ፡ የሚቈጣ ፡ ኹሉ ፡ ፍርድ ፡ ይጎሳዋል ፤ ወንድሙንም ፡ ጨርቃም ፡ የሚለው ፡ ኹሉ ፡ የሸንጎ ፡ ፍርድ ፡ ይጎሳዋል ፤ ደንቈሮ ፡ የሚለውም ፡ ኹሉ ፡ የገሃነመ ፡ እሳት ፡ ፍርድ ፡ ይጎሳዋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ እንግዲህ ፡ መባኽን ፡ በመሠዊያው ፡ ላይ ፡ ብታቀርብ ፥ በዚያም ፡ ወንድምኽ ፡ አንዳች ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እንዳለው ፡ ብታስብ ፥

ማቴ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ በዚያ ፡ በመሠዊያው ፡ ፊት ፡ መባኽን ፡ ትተኽ ፡ ኺድ ፥ አስቀድመኽም ፡ ከወንድምኽ ፡ ጋራ ፡ ታረቅ ፥ በኋላም ፡ መጥተኽ ፡ መባኽን ፡ አቅርብ ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ዐብረኸው ፡ በመንገድ ፡ ሳለኽ ፡ ከባላጋራኽ ፡ ጋራ ፡ ፈጥነኽ ፡ ተስማማ ፤ ባላጋራ ፡ ለዳኛ ፡ እንዳይሰጥኽ ፡ ዳኛም ፡ ለሎሌው ፥ ወደ ፡ ወህኒም ፡ ትጣላለኽ ፤

ማቴ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ የመጨረሻዋን ፡ ሳንቲም ፡ እስክትከፍል ፡ ድረስ ፡ ከቶ ፡ ከዚያ ፡ አትወጣም ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ አታመንዝር ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ ወደ ፡ ሴት ፡ ያየ ፡ ኹሉ ፡ የተመኛትም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ አመንዝሯል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ቀኝ ፡ ዐይንኽም ፡ ብታሰናክልኽ ፡ አውጥተኽ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፤ ሙሉ ፡ ሰውነትኽ ፡ በገሃነም ፡ ከሚጣል ፡ ይልቅ ፡ ከአካላትኽ ፡ አንድ ፡ ቢጠፋ ፡ ይሻልኻልና ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ ቀኝ ፡ እጅኽም ፡ ብታሰናክልኽ ፡ ቈርጠኽ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፤ ሙሉ ፡ ሰውነትኽ ፡ በገሃነም ፡ ከሚጣል ፡ ይልቅ ፡ ከአካላትኽ ፡ አንድ ፡ ቢጠፋ ፡ ይሻላልና ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ሚስቱን ፡ የሚፈታት ፡ ኹሉ ፡ የፍቺን ፡ ጽሕፈት ፡ ይስጣት ፡ ተባለ ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ ያለዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ኹሉ ፡ አመንዝራ ፡ ያደርጋታል ፥ የተፈታችውንም ፡ የሚያገባ ፡ ኹሉ ፡ ያመነዝራል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ ደግሞ ፡ ለቀደሙት ፦ በውሸት ፡ አትማል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መሐላዎችኽን ፡ ለጌታ ፡ ስጥ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 34 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፦ ከቶ ፡ አትማሉ ፤ በሰማይ ፡ አይኾንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ነውና ፤

ማቴ. ፡ 5 ፡ 35 ፤ በምድርም ፡ አይኾንም ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ ናትና ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ አይኾንም ፡ የታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ ከተማ ፡ ናትና ፤

ማቴ. ፡ 5 ፡ 36 ፤ በራስኽም ፡ አትማል ፥ አንዲቱን ፡ ጠጕር ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቊር ፡ ልታደርግ ፡ አትችልምና ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 37 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃላችኹ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ አይደለም ፡ ይኹን ፤ ከነዚህም ፡ የወጣ ፡ ከክፉው ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 38 ፤ ዐይን ፡ ስለ ፡ ዐይን ፡ ጥርስም ፡ ስለ ፡ ጥርስ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 39 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ ክፉውን ፡ አትቃወሙ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ቀኝ ፡ ጕንጭኽን ፡ በጥፊ ፡ ለሚመታኽ ፡ ኹሉ ፡ ኹለተኛውን ፡ ደግሞ ፡ አዙርለት ፤

ማቴ. ፡ 5 ፡ 40 ፤ እንዲከስኽም ፡ እጀ ፡ ጠባብኽንም ፡ እንዲወስድ ፡ ለሚወድ ፡ መጐናጸፊያኽን ፡ ደግሞ ፡ ተውለት ፤

ማቴ. ፡ 5 ፡ 41 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ምዕራፍ ፡ ትኼድ ፡ ዘንድ ፡ ቢያስገድድኽ ፡ ኹለተኛውን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኺድ ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 42 ፤ ለሚለምንኽ ፡ ስጥ ፥ ከአንተም ፡ ይበደር ፡ ዘንድ ፡ ከሚወደው ፡ ፈቀቅ ፡ አትበል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 43 ፤ ባልንጀራኽን ፡ ውደድ ፡ ጠላትኽንም ፡ ጥላ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡ ሰምታችኋል ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 44-45 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ በሰማያት ፡ ላለ ፡ አባታችኹ ፡ ልጆች ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ጠላቶቻችኹን ፡ ውደዱ ፥ የሚረግሟችኹንም ፡ መርቁ ፥ ለሚጠሏችኹም ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፥ ስለሚያሳድዷችኹም ፡ ጸልዩ ፤ ርሱ ፡ በክፉዎችና ፡ በበጎዎች ፡ ላይ ፡ ፀሓይን ፡ ያወጣልና ፥ በጻድቃንና ፡ በኀጢአተኞችም ፡ ላይ ፡ ዝናቡን ፡ ያዘንባልና ።

ማቴ. ፡ 5 ፡ 46 ፤ የሚወዷችኹን ፡ ብትወዱ ፡ ምን ፡ ዋጋ ፡ አላችኹ ፧ ቀራጮችስ ፡ ያንኑ ፡ ያደርጉ ፡ የለምን ፧

ማቴ. ፡ 5 ፡ 47 ፤ ወንድሞቻችኹንም ፡ ብቻ ፡ እጅ ፡ ብትነሡ ፡ ምን ፡ ብልጫ ፡ ታደርጋላችኹ ፧ አሕዛብስ ፡ ያንኑ ፡ ያደርጉ ፡ የለምን ፧

ማቴ. ፡ 5 ፡ 48 ፤ እንግዲህ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችኹ ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናንተ ፡ ፍጹማን ፡ ኹኑ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ለሰዎች ፡ ትታዩ ፡ ዘንድ ፡ ምጽዋታችኹን ፡ በፊታቸው ፡ እንዳታደርጉ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ያለዚያ ፡ በሰማያት ፡ ባለው ፡ አባታችኹ ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ የላችኹም ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ እንግዲህ ፡ ምጽዋት ፡ ስታደርግ ፥ ግብዞች ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሊከበሩ ፡ በምኵራብ ፡ በመንገድም ፡ እንደሚያደርጉ ፡ በፊትኽ ፡ መለከት ፡ አታስነፋ ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለዋል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 3-4 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ምጽዋት ፡ ስታደርግ ፡ ምጽዋትኽ ፡ በስውር ፡ እንዲኾን ፡ ቀኝኽ ፡ የምትሠራውን ፡ ግራኽ ፡ አትወቅ ፤ በስውር ፡ የሚያይ ፡ አባትኽም ፡ በግልጥ ፡ ይከፍልኻል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ስትጸልዩም ፡ እንደ ፡ ግብዞች ፡ አትኹኑ ፤ ለሰው ፡ ይታዩ ፡ ዘንድ ፡ በምኵራብና ፡ በመንገድ ፡ ማእዘን ፡ ቆመው ፡ መጸለይን ፡ ይወዳሉና ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለዋል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ስትጸልይ ፥ ወደ ፡ ዕልፍኝኽ ፡ ግባ ፥ መዝጊያኽንም ፡ ዘግተኽ ፡ በስውር ፡ ላለው ፡ አባትኽ ፡ ጸልይ ፤ በስውር ፡ የሚያይ ፡ አባትኽም ፡ በግልጥ ፡ ይከፍልኻል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ አሕዛብም ፡ በመናገራቸው ፡ ብዛት ፡ እንዲሰሙ ፡ ይመስላቸዋልና ፥ ስትጸልዩ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ በከንቱ ፡ አትድገሙ ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ አትምሰሏቸው ፤ ሳትለምኑት ፡ አባታችኹ ፡ የሚያስፈልጋችኹን ፡ ያውቃልና ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እንግዲህ ፡ እናንተስ ፡ እንዲህ ፡ ጸልዩ ፦ በሰማያት ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፥

ማቴ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ስምኽ ፡ ይቀደስ ፤ መንግሥትኽ ፡ ትምጣ ፤ ፈቃድኽ ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዲሁ ፡ በምድር ፡ ትኹን ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ የዕለት ፡ እንጀራችንን ፡ ዛሬ ፡ ስጠን ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ የበደሉንን ፡ ይቅር ፡ እንደምንል ፡ በደላችንን ፡ ይቅር ፡ በለን ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ከክፉም ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ፤ መንግሥት ፡ ያንተ ፡ ናትና ፥ ኀይልም ፡ ክብርም ፡ ለዘለዓለሙ ፤ አሜን ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ለሰዎች ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ብትሉ ፥ የሰማዩ ፡ አባታችኹ ፡ እናንተን ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ ይላችኋልና ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ለሰዎች ፡ ግን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ባትሉ ፥ አባታችኹም ፡ ኀጢአታችኹን ፡ ይቅር ፡ አይላችኹም ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ስትጦሙም ፥ እንደ ፡ ግብዞች ፡ አትጠውልጉ ፤ ለሰዎች ፡ እንደ ፡ ጦመኛ ፡ ሊታዩ ፡ ፊታቸውን ፡ ያጠፋሉና ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ዋጋቸውን ፡ ተቀብለዋል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 17-18 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ስትጦም ፥ በስውር ፡ ላለው ፡ አባትኽ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጦመኛ ፡ ለሰዎች ፡ እንዳትታይ ፡ ራስኽን ፡ ተቀባ ፡ ፊትኽንም ፡ ታጠብ ፤ በስውር ፡ የሚያይ ፡ አባትኽም ፡ በግልጥ ፡ ይከፍልኻል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ብልና ፡ ዝገት ፡ በሚያጠፉት ፡ ሌባዎችም ፡ ቄፍረው ፡ በሚሠርቁት ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ መዝገብ ፡ አትሰብስቡ ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብልም ፡ ዝገትም ፡ በማያጠፉት ፡ ሌባዎችም ፡ ቄፍረው ፡ በማይሠርቁት ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ በሰማይ ፡ መዝገብ ፡ ሰብስቡ ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ መዝገብኽ ፡ ባለበት ፡ ልብኽ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ይኾናልና ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ የሰውነት ፡ መብራት ፡ ዐይን ፡ ናት ። ዐይንኽ ፡ እንግዲህ ፡ ጤናማ ፡ ብትኾን ፥ ሰውነትኽ ፡ ኹሉ ፡ ብሩህ ፡ ይኾናል ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ዐይንኽ ፡ ግን ፡ ታማሚ ፡ ብትኾን ፥ ሰውነትኽ ፡ ኹሉ ፡ የጨለመ ፡ ይኾናል ። እንግዲህ ፡ ባንተ ፡ ያለው ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ ከኾነ ፥ ጨለማውስ ፡ እንዴት ፡ ይበረታ! ፡

ማቴ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ለኹለት ፡ ጌታዎች ፡ መገዛት ፡ የሚቻለው ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ወይም ፡ አንዱን ፡ ይጠላል ፡ ኹለተኛውንም ፡ ይወዳል ፤ ወይም ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ይጠጋል ፡ ኹለተኛውንም ፡ ይንቃል ፤ ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብ ፡ መገዛት ፡ አትችሉም ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ እላችኋለኹ ፥ ስለ ፡ ነፍሳችኹ ፡ በምትበሉትና ፡ በምትጠጡት ፥ ወይም ፡ ስለ ፡ ሰውነታችኹ ፡ በምትለብሱት ፡ አትጨነቁ ፤ ነፍስ ፡ ከመብል ፣ ሰውነትም ፡ ከልብስ ፡ አይበልጥምን ፧

ማቴ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወፎች ፡ ተመልከቱ ፤ አይዘሩም ፡ አያጭዱምም ፡ በጐተራም ፡ አይከቱም ፥ የሰማዩ ፡ አባታችኹም ፡ ይመግባቸዋል ፤ እናንተ ፡ ከነርሱ ፡ እጅግ ፡ አትበልጡምን ፧

ማቴ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ከእናንተ ፡ ተጨንቆ ፡ በቁመቱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ መጨመር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ ስለ ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትጨነቃላችኹ ፧ የሜዳ ፡ አበባዎች ፡ እንዴት ፡ እንዲያድጉ ፡ ልብ ፡ አድርጋችኹ ፡ ተመልከቱ ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ አይደክሙም ፡ አይፈትሉምም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ሰሎሞንስ ፡ እንኳ ፡ በክብሩ ፡ ኹሉ ፡ ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ አልለበሰም ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ያለውን ፡ ነገም ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ የሚጣለውን ፡ የሜዳን ፡ ሣር ፡ እንዲህ ፡ የሚያለብሰው ፡ ከኾነ ፥ እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችኹ ፥ እናንተንማ ፡ ይልቁን ፡ እንዴት ፧

ማቴ. ፡ 6 ፡ 31 ፤ እንግዲህ ፦ ምን ፡ እንበላለን ፧ ምንስ ፡ እንጠጣለን ፧ ምንስ ፡ እንለብሳለን ፧ ብላችኹ ፡ አትጨነቁ ፤

ማቴ. ፡ 6 ፡ 32 ፤ ይህንስ ፡ ኹሉ ፡ አሕዛብ ፡ ይፈልጋሉ ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ እንዲያስፈልጋችኹ ፡ የሰማዩ ፡ አባታችኹ ፡ ያውቃልና ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 33 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድማችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ጽድቁንም ፡ ፈልጉ ፥ ይህም ፡ ኹሉ ፡ ይጨመርላችኋል ።

ማቴ. ፡ 6 ፡ 34 ፤ ነገ ፡ ለራሱ ፡ ይጨነቃልና ፥ ለነገ ፡ አትጨነቁ ፤ ለቀኑ ፡ ክፋቱ ፡ ይበቃዋል ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 1-2 ፤ እንዳይፈረድባችኹ ፡ አትፍረዱ ፤ በምትፈርዱበት ፡ ፍርድ ፡ ይፈረድባችኋልና ፥ በምትሰፍሩበትም ፡ መስፈሪያ ፡ ይሰፈርባችኋል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ በወንድምኽም ፡ ዐይን ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታያለኽ ፥ በዐይንኽ ፡ ግን ፡ ያለውን ፡ ምሰሶ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትመለከትም ፧

ማቴ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ወይም ፡ ወንድምኽን ፦ ከዐይንኽ ፡ ጕድፍ ፡ ላውጣ ፡ ፍቀድልኝ ፡ እንዴትስ ፡ ትለዋለኽ ፧ እንሆም ፥ በዐይንኽ ፡ ምሰሶ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ አንተ ፡ ግብዝ ፥ አስቀድመኽ ፡ ከዐይንኽ ፡ ምሰሶውን ፡ አውጣ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከወንድምኽ ፡ ዐይን ፡ ጕድፉን ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡ አጥርተኽ ፡ ታያለኽ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ በእግራቸው ፡ እንዳይረግጡት ፡ ተመልሰውም ፡ እንዳይነክሷችኹ ፥ የተቀደሰውን ፡ ለውሻዎች ፡ አትስጡ ፥ ዕንቊዎቻችኹንም ፡ በዕሪያዎች ፡ ፊት ፡ አትጣሉ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ለምኑ ፥ ይሰጣችኹማል ፤ ፈልጉ ፥ ታገኙማላችኹ ፤ መዝጊያን ፡ አንኳኩ ፥ ይከፈትላችኹማል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የሚለምነው ፡ ኹሉ ፡ ይቀበላልና ፥ የሚፈልገውም ፡ ያገኛል ፥ መዝጊያንም ፡ ለሚያንኳኳ ፡ ይከፈትለታል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ወይስ ፡ ከእናንተ ፥ ልጁ ፡ እንጀራ ፡ ቢለምነው ፥ ድንጋይን ፡ የሚሰጠው ፡ ከእናንተ ፡ ማን ፡ ሰው ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ዓሣስ ፡ ቢለምነው ፡ እባብን ፡ ይሰጠዋልን ፧

ማቴ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እንኪያስ ፡ እናንተ ፡ ክፉዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ለልጆቻችኹ ፡ መልካም ፡ ስጦታ ፡ መስጠትን ፡ ካወቃችኹ ፥ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችኹ ፡ ለሚለምኑት ፡ እንዴት ፡ አብልጦ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ይሰጣቸው ፧

ማቴ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ ሰዎች ፡ ሊያደርጉላችኹ ፡ የምትወዱትን ፡ ኹሉ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፤ ሕግም ፡ ነቢያትም ፡ ይህ ፡ ነውና ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በጠበበው ፡ ደጅ ፡ ግቡ ፤ ወደ ፡ ጥፋት ፡ የሚወስደው ፡ ደጅ ፡ ሰፊ ፥ መንገዱም ፡ ትልቅ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚገቡ ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤

ማቴ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሕይወት ፡ የሚወስደው ፡ ደጅ ፡ የጠበበ ፥ መንገዱም ፡ የቀጠነ ፡ ነውና ፥ የሚያገኙትም ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ የበግ ፡ ለምድ ፡ ለብሰው ፡ ከሚመጡባችኹ ፡ በውስጣቸው ፡ ግን ፡ ነጣቂዎች ፡ ተኵላዎች ፡ ከኾኑ ፡ ከሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ተጠንቀቁ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ከፍሬያቸው ፡ ታውቋቸዋላችኹ ። ከሾኽ ፡ ወይን ፡ ከኵርንችትስ ፡ በለስ ፡ ይለቀማልን ፧

ማቴ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ እንዲሁ ፡ መልካም ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ያደርጋል ፥ ክፉም ፡ ዛፍ ፡ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ ያደርጋል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ መልካም ፡ ዛፍ ፡ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ ማፍራት ፥ ወይም ፡ ክፉ ፡ ዛፍ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ማፍራት ፡ አይቻለውም ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ መልካም ፡ ፍሬ ፡ የማያደርግ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይቈረጣል ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ይጣላል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ስለዚህም ፡ ከፍሬያቸው ፡ ታውቋቸዋላችኹ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ እንጂ ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የሚለኝ ፡ ኹሉ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ብዙዎች ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በስምኽ ፡ ትንቢት ፡ አልተናገርንምን ፥ በስምኽስ ፡ አጋንንትን ፡ አላወጣንምን ፥ በስምኽስ ፡ ብዙ ፡ ተኣምራትን ፡ አላደረግንምን ፧ ይሉኛል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፦ ከቶ ፡ አላወቅኋችኹም ፤ እናንተ ፡ ዐመፀኞች ፥ ከእኔ ፡ ራቁ ፡ ብዬ ፡ እመሰክርባቸዋለኹ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ይህን ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የሚያደርገው ፡ ኹሉ ፡ ቤቱን ፡ በአለት ፡ ላይ ፡ የሠራ ፡ ልባም ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ዝናብም ፡ ወረደ ፥ ጐርፍም ፡ መጣ ፥ ነፋስም ፡ ነፈሰ ፥ ያንም ፡ ቤት ፡ ገፋው ፤ በአለት ፡ ላይም ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ አልወደቀም ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ይህንም ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የማያደርገው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ቤቱን ፡ በአሸዋ ፡ ላይ ፡ የሠራ ፡ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ዝናብም ፡ ወረደ ፥ ጐርፍም ፡ መጣ ፥ ነፋስም ፡ ነፈሰ ፥ ያንም ፡ ቤት ፡ መታው ፥ ወደቀም ፤ አወዳደቁም ፡ ታላቅ ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ፤ እንደ ፡ ጻፊዎቻቸው ፡ ሳይኾን ፡

ማቴ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ እንደ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበርና ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ከተራራም ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ ለምጻም ፡ ቀርቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ብትወድስ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለኽ ፡ እያለ ፡ ሰገደለት ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፦ እወዳለኹ ፥ ንጻ ፡ አለው ። ወዲያውም ፡ ለምጹ ፡ ነጻ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፦ ለማንም ፡ እንዳትናገር ፡ ተጠንቀቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኼደኽ ፡ ራስኽን ፡ ለካህን ፡ አሳይ ፥ ለእነርሱም ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ መባ ፡ አቅርብ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ ቅፍርናሖምም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥

ማቴ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ብላቴናዬ ፡ ሽባ ፡ ኾኖ ፡ እጅግ ፡ እየተሣቀየ ፡ በቤት ፡ ተኝቷል ፡ ብሎ ፡ ለመነው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ መጥቼ ፡ እፈውሰዋለኹ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በቤቴ ፡ ጣራ ፡ ከታች ፡ ልትገባ ፡ አይገባኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተናገር ፥ ብላቴናዬም ፡ ይፈወሳል ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ለሌላዎች ፡ ተገዢ ፡ ነኝና ፥ ከእኔም ፡ በታች ፡ ጭፍራ ፡ አለኝ ፤ አንዱንም ፦ ኺድ ፡ ብለው ፡ ይኼዳል ፥ ሌላውንም ፦ ና ፡ ብለው ፡ ይመጣል ፥ ባሪያዬንም ፦ ይህን ፡ አድርግ ፡ ብለው ፡ ያደርጋል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፡ ተደነቀና ፡ ለተከተሉት ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በእስራኤል ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ እምነት ፡ አላገኘኹም ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ እላችኋለኹም ፥ ብዙዎች ፡ ከምሥራቅና ፡ ከምዕራብ ፡ ይመጣሉ ፡ ከአብርሃምና ፡ ከይሥሐቅ ፡ ከያዕቆብም ፡ ጋራ ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ይቀመጣሉ ፤

ማቴ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ ወዳለው ፡ ጨለማ ፡ ይጣላሉ ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ ለመቶ ፡ አለቃ ፦ ኺድና ፡ እንዳመንኽ ፡ ይኹንልኽ ፡ አለው ። ብላቴናውም ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ተፈወሰ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዐማቱን ፡ በንዳድ ፡ ታማ ፡ ተኝታ ፡ አያት ፤

ማቴ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ እጇንም ፡ ዳሰሰ ፥ ንዳዱም ፡ ለቀቃት ፤ ተነሥታም ፡ አገለገለቻቸው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 16-17 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ያደረባቸውን ፡ ብዙዎችን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፦ ርሱ ፡ ድካማችንን ፡ ተቀበለ ፡ ደዌያችንንም ፡ ተሸከመ ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፥ መናፍስትን ፡ በቃሉ ፡ አወጣ ፥ የታመሙትንም ፡ ኹሉ ፡ ፈወሰ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ኢየሱስም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሲከቡት ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ እንዲሻገሩ ፡ አዘዘ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ አንድ ፡ ጸሊም ፡ ቀርቦ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ወደምትኼድበት ፡ ኹሉ ፡ እከተልኻለኹ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ኢየሱስም ፦ ለቀበሮዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ለሰማይም ፡ ወፎች ፡ መሳፈሪያ ፡ አላቸው ፥ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ የለውም ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሌላው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አስቀድሜ ፡ እንድኼድ ፡ አባቴን ፡ እንድቀብር ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ኢ.የሱስም ፦ ተከተለኝ ፥ ሙታናቸውንም ፡ እንዲቀብሩ ፡ ሙታንን ፡ ተዋቸው ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ ታንኳም ፡ ሲገባ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ እንሆም ፥ ማዕበሉ ፡ ታንኳዩቱን ፡ እስኪደፍናት ፡ ድረስ ፡ በባሕር ፡ ታላቅ ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አድነን ፥ ጠፋን ፡ እያሉ ፡ አስነሡት ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ርሱም ፦ እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችኹ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈራላችኹ ፧ አላቸው ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ነፋሱንና ፡ ባሕሩን ፡ ገሠጸ ፥ ታላቅ ፡ ጸጥታም ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ሰዎቹም ፦ ነፋሳትና ፡ ባሕርስ ፡ ስንኳ ፡ የሚታዘዙለት ፥ ይህ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ነው ፧ እያሉ ፡ ተደነቁ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ወደ ፡ ማዶም ፡ ወደ ፡ ጌርጋሴኖን ፡ አገር ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ አጋንንት ፡ ያደሩባቸው ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ከመቃብር ፡ ወጥተው ፡ ተገናኙት ፤ እነርሱም ፡ ሰው ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ማለፍ ፡ እስኪሳነው ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ክፉዎች ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ እንሆም ፦ ኢ.የሱስ ፡ ሆይ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለን ፧ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ ልትሣቅየን ፡ ወደዚህ ፡ መጣኽን ፧ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ከነርሱም ፡ ርቆ ፡ የብዙ ፡ ዕሪያ ፡ መንጋ ፡ ይሰማራ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ አጋንንቱም ፦ ታወጣንስ ፡ እንደኾንኽ ፥ ወደዕሪያው ፡ መንጋ ፡ ስደደን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ፦ ኺዱ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ እነርሱም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ዕሪያዎቹ ፡ ኼዱና ፡ ገቡ ፤ እንሆም ፥ የዕሪያዎቹ ፡ መንጋ ፡ ኹሉ ፡ ከአፋፉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እየተጣደፉ ፡ ሮጡ ፡ በውሃም ፡ ውስጥ ፡ ሞቱ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ እረኞችም ፡ ሸሹ ፥ ወደ ፡ ከተማዩቱም ፡ ኼደው ፡ ነገሩን ፡ ኹሉ ፡ አጋንንትም ፡ ባደሩባቸው ፡ የኾነውን ፡ አወሩ ።

ማቴ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ እንሆም ፥ ከተማው ፡ ኹሉ ፡ ኢ.የሱስን ፡ ሊገናኝ ፡ ወጣ ፥ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡ ከአገራቸው ፡ እንዲኼድላቸው ፡ ለመኑት ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ በታንኳም ፡ ገብቶ ፡ ተሻገረና ፡ ወደገዛ ፡ ከተማው ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ በዐልጋ ፡ የተኛ ፡ ሽባ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ። ኢ.የሱስም ፡ እምነታቸውን ፡ አይቶ ፡ ሽባውን ፦ አንተ ፡ ልጅ ፥ አይዞኽ ፥ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ እንሆም ፥ ከጻፊዎቹ ፡ አንዳንዱ ፡ በልባቸው ፦ ይህስ ፡ ይሳደባል ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ኢ.የሱስም ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ በልባችኹ ፡ ክፉ ፡ ታስባላችኹ ፧

ማቴ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ ከማለት ፡ ወይስ ። ተነሣና ፡ ኺድ ፡ ከማለት ፡ ማናቸው ፡ ይቀላል ፧

ማቴ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ያስተሰርይ ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣን ፡

እንዳለው ፡ እንድታውቁ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሽባውን ፦ ተነሣ ፤ ዐልጋኽን ፡ ተሸከምና ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 7 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 8 ፤ ሕዝቡም ፡ አይተው ፡ ተደነቁ ፥ ለሰውም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 9 ፤ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ዐልፎ ፡ በመቅረጫው ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረ ፡ ማቴዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አየና ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ተከተለው ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 10 ፤ በቤቱም ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ እንሆ ፥ ብዙ ፡ ቀራጮችና ፡ ኀጢአተኞች ፡ መጥተው ፡ ከኢየሱስና ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ተቀመጡ ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 11 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ አይተው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦ መምህራችኹ ፡ ከቀራጮችና ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይበላል ፧ አሏቸው ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 12 ፤ ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፦ ሕመምተኞች ፡ እንጂ ፡ ባለጤናዎች ፡ ባለመድኀኒት ፡ አያስፈልጋቸውም ፤

ማቴ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኼዳችኹ ፦ ምሕረትን ፡ እወዳለኹ ፡ መሥዋዕትንም ፡ አይደለም ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተማሩ ፤ ኀጢአተኞችን ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣኹምና ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ እኛና ፡ ፈሪሳውያን ፥ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የምንጦመው ፥ ደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ ግን ፡ የማይጦሙት ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉት ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ሚዜዎች ፡ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ ሊያዝኑ ፡ ይችላሉን ፧ ነገር ፡ ግን ፡ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ የሚወሰድበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፥ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ይጦማሉ ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 16 ፤ በአረጀ ፡ ልብስ ፡ ዐዲስ ፡ ዕራፊ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ መጣፊያው ፡ ልብሱን ፡ ይቦጭቀዋልና ፥ መቀደዱም ፡ የባሰ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 17 ፤ በአረጀ ፡ አቀኑማዳ ፡ ዐዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፥ አቀኑማዳው ፡ ይፈነዳል ፥ የወይን ፡ ጠጁም ፡ ይፈሳል ፡ አቀኑማዳውም ፡ ይጠፋል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐዲሱን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በዐዲስ ፡ አቀኑማዳ ፡ ያኖረዋል ፥ ኹለቱም ፡ ይጠባበቃሉ ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 18 ፤ ይህንም ፡ ሲነግራቸው ፥ አንድ ፡ መኰንን ፡ መጥቶ ፦ ልጄ ፡ አኹን ፡ ሞተች ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መጥተኽ ፡ እጅኽን ፡ ጫንባት ፥ በሕይወትም ፡ ትኖራለች ፡ እያለ ፡ ሰገደለት ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 19 ፤ ኢየሱስም ፡ ተነሥቶ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ተከተለው ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 20 ፤ እንሆም ፥ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ዝምሮ ፡ ደም ፡ የሚፈሳት ፡ ሴት ፡ በኋላው ፡ ቀርባ ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ዳሰሰች ፤

ማቴ. ፥ 9 ፥ 21 ፤ በልቧ ፦ ልብሱን ፡ ብቻ ፡ የዳሰስኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እድናለኹ ፡ ትል ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 22 ፤ ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አያትና ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አይዞሽ ፤ እምነትሽ ፡ አድኖሻል ፡ አላት ። ሴቲቱም ፡ ከዚያች ፡ ሰዓት ፡ ዝምራ ፡ ዳነች ።

ማቴ. ፥ 9 ፥ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደመኰንኑ ፡ ቤት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ እንቢልተኞችንና ፡ የሚንጫጫውን ፡ ሕዝብ ፡ አይቶ ፦

ማቴ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ብላቴናዩቱ ፡ ተኝታለች ፡ እንጂ ፡ አልሞተችምና ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፡ አላቸው ። በጣምም ፡ ሣቁበት ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ሕዝቡን ፡ ግን ፡ ከአስወጡ ፡ በኋላ ፡ ገብቶ ፡ እጇን ፡ ያዛት ፥ ብላቴናዩቱም ፡ ተነሣች ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ያም ፡ ዝና ፡ ወደዚያ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ወጣ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ሲያልፍ ፡ ኹለት ፡ ዕውሮች ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ማረን ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ዕውሮቹ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ፥ ኢየሱስም ፦ ይህን ፡ ማድረግ ፡ እንድችል ፡ ታምናላችኹን ፧ አላቸው ፦ አዎን ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፦ እንደ ፡ እምነታችኹ ፡ ይኹንላችኹ ፡ ብሎ ፡ ዐይኖቻቸውን ፡ ዳሰሰ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ዐይኖቻቸውም ፡ ተከፈቱ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ ኢየሱስም ፦ ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ብሎ ፡ በብርቱ ፡ አዘዛቸው ። እነርሱ ፡ ግን ፡ ወጥተው ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሹሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አወሩ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ እነርሱም ፡ ሲወጡ ፥ እንሆ ፥ ጋኔን ፡ ያደረበትን ፡ ዲዳ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ጋኔኑንም ፡ ካወጣው ፡ በኋላ ፡ ዲዳው ፡ ተናገረ ። ሕዝቡም ፦ እንዲህ ፡ ያለ ፡ በእስራኤል ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አልታየም ፡ እያሉ ፡ ተደነቁ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፦ በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ አጋንንትን ፡ ያወጣል ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፡ በምኩራቦቻቸው ፡ እያስተማረ ፥ የመንግሥትንም ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከ ፥ በሕዝብም ፡ ያለውን ፡ ደዌና ፡ ሕማም ፡ ሹሉ ፡ እየፈወሰ ፥ በከተማዎችና ፡ በመንደሮች ፡ ሹሉ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 36 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ እረኛ ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ በጎች ፡ ተጨንቀው ፡ ተጥለውም ፡ ነበርና ፥ ዐዘነላቸው ።

ማቴ. ፡ 9 ፡ 37 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦ መከሩስ ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ ሠራተኞች ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፤

ማቴ. ፡ 9 ፡ 38 ፤ እንግዲህ ፡ የመከሩን ፡ ጌታ ፡ ወደመከሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንዲልክ ፡ ለምኑት ፡ አላቸው ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ማቴ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፥ እንዲያወጧቸው ፡ በርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ ላይ ፡ ደዌንና ፡ ሕማምንም ፡ ሹሉ ፡ እንዲፈውሱ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ የዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ሐዋርያት ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፤ መገሥመሪያው ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ ስምዖን ፡ ወንድሙ ፡ እንድርያስም ፥ የዘብዴዎስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፡ ወንድሙ ፡ ዮሐንስም ፥

ማቴ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ፊልጶስም ፡ በርተሎሜዎስም ፥ ቶማስም ፡ ቀራጩ ፡ ማቴዎስም ፥ የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፡ ታዴዎስም ፡ የተባለው ፡ ልብድዮስ ፥

ማቴ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ቀነናዊውም ፡ ስምዖን ፡ ደግሞም ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ እነዚህን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ኢየሱስ ፡ ላካቸው ፥ አዘዛቸውም ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ በአሕዛብ ፡ መንገድ ፡ አትኺዱ ፥ ወደሳምራውያንም ፡ ከተማ ፡ አትግቡ ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ይልቅስ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፡ ወደሚኾኑ ፡ ወደጠፉት ፡ በጎች ፡ ኺዱ ፡ እንጂ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ኼዳችኹም ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ቀርባለች ፡ ብላችኹ ፡ ስበኩ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ድውዮችን ፡ ፈውሱ ፤ ሙታንን ፡ አስነሡ ፤ ለምጻሞችን ፡ አንጹ ፤ አጋንንትን ፡ አውጡ ፤ በከንቱ ፡ ተቀበላችኹ ፥ በከንቱ ፡ ስጡ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ናስ ፡ በመቀነታችኹ ፥

ማቴ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ወይም ፡ ለመንገድ ፡ ከረጢት ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ ወይም ፡ ጫማ ፡ ወይም ፡ በትር ፡ አታግኙ ፤ ለሠራተኛ ፡ ምግቡ ፡ ይገባዋልና ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ በምትገቡባትም ፡ በማናቸዉቱም ፡ ከተማ ፡ ወይም ፡ መንደር ፥ በዚያ ፡ የሚገባው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በጥንቃቄ ፡ መርምሩ ፤ እስክትወጡም ፡ ድረስ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ስትገቡ ፡ ሰላምታ ፡ ስጡ ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ቤቱም ፡ የሚገባው ፡ ቢኾን ፡ ሰላማችኹ ፡ ይድረስለት ፤ ባይገባው ፡ ግን ፡ ሰላማችኹ ፡ ይመለስላችኹ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ከማይቀበላችኹም ፡ ቃላችኹንም ፡ ከማይሰሙ ፡ ኹሉ ፥ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ወይም ፡ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ስትወጡ ፡ የእግራችኹን ፡ ትቢያ ፡ አራግፉ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶምና ፡ ለገሞራ ፡ አገር ፡ ይቀልላቸዋል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ እንደ ፡ በጎች ፡ በተኵላዎች ፡ መካከል ፡ እልካችኋለኹ ፤ ስለዚህ ፥ እንደ ፡ እባብ ፡ ልባሞች ፡ እንደ ፡ ርግብም ፡ የዋሆች ፡ ኹኑ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፥ በምኩራቦቻቸውም ፡ ይገርፏችኋልና ፥ ከሰዎች ፡ ተጠበቁ ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ለእነርሱና ፡ ለአሕዛብም ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ገዢዎች ፡ ወደ ፡ ነገሥታትም ፡ ትወሰዳላችኹ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ አሳልፈውም ፡ ሲሰጧችኹ ፥ የምትናገሩት ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ይሰጣችኋልና ፥ እንዴት ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ እንድትናገሩ ፡ አትጨነቁ ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ በእናንተ ፡ የሚናገር ፡ የአባታችኹ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ የምትናገሩ ፡ እናንተ ፡ አይደላችኹምና ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ወንድምም ፡ ወንድሙን ፥ አባትም ፡ ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፥ ልጆችም ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፡ ይገድሏቸውማል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ በኹሉም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተጠላችኹ ፡ ትኾናላችኹ ፤ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የሚጸና ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይድናል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ በአንዲቱ ፡ ከተማም ፡ መከራ ፡ ቢያሳይዋችኹ ፡ ወደ ፡ ሌላዪቱ ፡ ሽሹ ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹና ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የእስራኤልን ፡ ከተማዎች ፡ አትዘልቁም ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከመምህሩ ፥ ባሪያም ፡ ከጌታው ፡ አይበልጥም ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡ መምህሩ ፥ ባሪያም ፡ እንደ ፡ ጌታው ፡ መኾኑ ፡ ይበቃዋል ። ባለቤቱን ፡ ብዔል ፡ ዜቡል ፡ ካሉት ፥ ቤተ ፡ ሰዎቹንማ ፡ እንዴት ፡ አብዝተው ፡ አይሏቸው! ፡

ማቴ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፡ አትፍሯቸው ፤ የማይገለጥ ፡ የተከደነ ፥ የማይታወቅም ፡ የተሰወረ ፡ ምንም ፡ የለምና ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ በጨለማ ፡ የምነግራችኹን ፡ በብርሃን ፡ ተናገሩ ፤ በጉሮም ፡ የምትሰሙትን ፡ በሰገነት ፡ ላይ ፡ ስበኩ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ሥጋንም ፡ የሚገድሉትን ፡ ነፍስን ፡ ግን ፡ መግደል ፡ የማይቻላቸውን ፡ አትፍሩ ፤ ይልቅስ ፡ ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ በገሃነም ፡ ሊያጠፋ ፡ የሚቻለውን ፡ ፍሩ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ኹለት ፡ ድንቢጦች ፡ በዐምስት ፡ ሳንቲም ፡ ይሸጡ ፡ የለምን ፧ ከነርሱም ፡ አንዲቱ ፡ ያለአባታችኹ ፡ ፈቃድ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አትወድቅም ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ የእናንተስ ፡ የራሳችኹ ፡ ጠጕር ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ ተቈጥሯል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ እንግዲህ ፡ አትፍሩ ፡ ከብዙ ፡ ድንቢጦች ፡ እናንተ ፡ ትበልጣላችኹ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ ስለዚህ ፥ በሰው ፡ ፊት ፡ ለሚመሰክርልኝ ፡ ኹሉ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሰማያት ፡ ባለው ፡ በአባቴ ፡ ፊት ፡ እመሰክርለታለኹ ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ በሰው ፡ ፊትም ፡ የሚክደኝን ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሰማያት ፡ ባለው ፡ በአባቴ ፡ ፊት ፡ እክደዋለኹ ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰላምን ፡ ለማምጣት ፡ የመጣኹ ፡ አይምሰላችኹ ፤ ሰይፍን ፡ እንጂ ፡ ሰላምን ፡ ለማምጣት ፡ አልመጣኹም ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ ሰውን ፡ ከአባቱ ፥ ሴት ፡ ልጅንም ፡ ከእናቷ ፥ ምራትንም ፡ ከአማቷ ፡ እለያይ ፡ ዘንድ ፡ መጥቻለኹና ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ ለሰውም ፡ ቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ጠላቶች ፡ ይኾኑበታል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሚወድ ፡ ለእኔ ፡ ሊኾን ፡ አይገባውም ፤ ከእኔ ፡ ይልቅም ፡ ወንድ ፡ ልጁን ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ልጁን ፡ የሚወድ ፡ ለእኔ ፡ ሊኾን ፡ አይገባውም ፤

ማቴ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ መስቀሉንም ፡ የማይዝ ፡ በኋላዬም ፡ የማይከተለኝ ፡ ለእኔ ፡ ሊኾን ፡ አይገባውም ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 39 ፤ ነፍሱን ፡ የሚያገኝ ፡ ያጠፋታል ፥ ነፍሱንም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚያጠፋ ፡ ያገኛታል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 40 ፤ እናንተን ፡ የሚቀበል ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፥ እኔንም ፡ የሚቀበል ፡ የላከኝን ፡ ይቀበላል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 41 ፤ ነቢይን ፡ በነቢይ ፡ ስም ፡ የሚቀበል ፡ የነቢይን ፡ ዋጋ ፡ ይወስዳል ፥ ጻድቅንም ፡ በጻድቅ ፡ ስም ፡ የሚቀበል ፡ የጻድቁን ፡ ዋጋ ፡ ይወስዳል ።

ማቴ. ፡ 10 ፡ 42 ፤ ማንም ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ ለአንዱ ፡ ቀዝቃዛ ፡ ጽዋ ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ በደቀ ፡ መዝሙር ፡ ስም ፡

የሚያጠጣ ፥ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ዋጋው ፡ አይጠፋበትም ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ማቴ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ማዘዝ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ በከተማዎቻቸው ፡ ሊያስተምርና ፡ ሊሰብክ ፡ ከዚያ ፡ ዐለፈ ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ ዮሐንስም ፡ በወህኒ ፡ ሳለ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥራ ፡ ሰምቶ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹለት ፡ ላከና ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ የሚመጣው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ ወይስ ፡ ሌላ ፡ እንጠብቅ ፧ አለው ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ኼዳችኹ ፡ ያያችኹትን ፡ የሰማችኹትንም ፡ ለዮሐንስ ፡ አውሩለት ፤

ማቴ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ ዕውሮች ፡ ያያሉ ፡ ዐንካሳዎችም ፡ ይኼዳሉ ፥ ለምጻሞችም ፡ ይነጻሉ ፡ ደንቈሮዎችም ፡ ይሰማሉ ፥ ሙታንም ፡ ይነሣሉ ፡

ማቴ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ ለድኻዎችም ፡ ወንጌል ፡ ይሰበካል ፤ በእኔም ፡ የማይሰናከለው ፡ ኹሉ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ እነዚያም ፡ ሲኼዱ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ሊናገር ፡ ገምረ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጣችኹ ፧

ማቴ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ ነፋስ ፡ የሚወዘወዘውን ፡ ሸምበቆን ፧ ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችኹ ፧ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰውን ፧ እንሆ ፥ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ በነገሥታት ፡ ቤት ፡ አሉ ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 9 ፤ ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችኹ ፧ ነቢይን ፧ አዎን ፡ እላችኋለኹ ፥ ከነቢይም ፡ የሚበልጠውን ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 10 ፤ እንሆ ፥ መንገድኽን ፡ በፊትኽ ፡ የሚጠርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊትኽ ፡ እልካለኹ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈለት ፡ ይህ ፡ ነውና ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 11 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከሴቶች ፡ ከተወለዱት ፡ መካከል ፡ ከመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚበልጥ ፡ አልተነሣም ፤ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ግን ፡ ከኹሉ ፡ የሚያንሰው ፡ ይበልጠዋል ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 12 ፤ ከመጥምቁም ፡ ከዮሐንስ ፡ ዘመን ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ትገፋለች ፥ ግፈኞችም ፡ ይናጠቋታል ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 13 ፤ ነቢያት ፡ ኹሉና ፡ ሕጉ ፡ እስከ ፡ ዮሐንስ ፡ ድረስ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፤

ማቴ. ፥ 11 ፥ 14 ፤ ልትቀበሉትስ ፡ ብትወዱ ፥ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ኤልያስ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 15 ፤ የሚሰማ ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ትውልድ ፡ በምን ፡ እመስለዋለኹ ፧ በገበያ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ልጆች ፡ ይመስላሉ ፥ እነርሱም ፡ ባልንጀራዎቻቸውን ፡ እየጠሩ ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 17 ፤ እንቢልታ ፡ ነፋንላችኹ ፥ ዘፈንም ፡ አልዘፈናችኹም ፤ ሙሾ ፡ አወጣንላችኹ ፥ ዋይ ፡ ዋይም ፡ አላላችኹም ፡ ይሏቸዋል ።

ማቴ. ፥ 11 ፥ 18 ፤ ዮሐንስ ፡ ሳይበላና ፡ ሳይጠጣ ፡ መጣ ፥ እነርሱም ፦ ጋኔን ፡ አለበት ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ እየበላና ፡ እየጠጣ ፡ መጣ ፥ እነርሱም ፦ እንሆ ፥ በላተኛና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጪ ፥ የቀራጮችና ፡ የኀጢአተኞች ፡ ወዳጅ ፡ ይሉታል ። ጥበብም ፡ በልጆቿ ፡ ጸደቀች ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሚበዙ ፡ ተአምራት ፡ የተደረገባቸውን ፡ ከተማዎች ፡ ንስሓ ፡ ስላልገቡ ፡ ሊነቅፋቸው ፡ ዠመረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ማቴ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ወዮልሽ ፡ ኮራዚ ፤ ወዮልሽ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፤ በእናንተ ፡ የተደረገው ፡ ተአምራት ፡ በጢሮስና ፡ በሲዶና ፡ ተደርጎ ፡ ቢኾን ፥ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ዐመድም ፡ ነስንሰው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ንስሓ ፡ በገቡ ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ ለጢሮስና ፡ ለሲዶና ፡ ይቀልላቸዋል ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ አንቺም ፡ ቅፍርናሖም ፥ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ከፍ ፡ አልሽን ፧ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ትወርጃለሽ ፤ ባንቺ ፡ የተደረገው ፡ ተአምራት ፡ በሰዶም ፡ ተደርጎ ፡ ቢኾን ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በኖረች ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከአንቺ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶም ፡ አገር ፡ ይቀልላታል ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፥ ይህን ፡ ከጥበበኞችና ፡ ከአስተዋዮች ፡ ሰውረኽ ፡ ለሕፃናት ፡ ስለ ፡ ገለጥኽላቸው ፡ አመሰግንኻለኹ ፤

ማቴ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ አዎን ፥ አባት ፡ ሆይ ፥ ፈቃድኽ ፡ በፊትኽ ፡ እንዲህ ፡ ኾኗልና ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ ኹሉ ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ተሰጥቶኛል ፤ ከአብ ፡ በቀር ፡ ወልድን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፥ ከወልድም ፡ በቀር ፡ ወልድም ፡ ሊገለጥለት ፡ ከሚፈቅድ ፡ በቀር ፡ አብን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ እናንተ ፡ ደካማዎች ፡ ሸክማችኹ ፡ የከበደ ፡ ኹሉ ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ኑ ፥ እኔም ፡ አሳርፋችኋለኹ ።

ማቴ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ቀንበሬን ፡ በላያችኹ ፡ ተሸከሙ ፡ ከእኔም ፡ ተማሩ ፥ እኔ ፡ የዋህ ፡ በልቤም ፡ ትሑት ፡ ነኝና ፥ ለነፍሳችኹም ፡ ዕረፍት ፡ ታገኛላችኹ ፤

ማቴ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ቀንበሬ ፡ ልዝብ ፡ ሸክሜም ፡ ቀሊል ፡ ነውና ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ማቴ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ በዕርሻ ፡ መካከል ፡ ዐለፈ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተራቡና ፡ እሸት ፡ ይቀጥፉ ፡ ይበሉም ፡ ዠመር ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ አይተው ፦ እንሆ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ በሰንበት ፡ ማድረግ ፡ ያልተፈቀደውን ፡ ያደርጋሉ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 3-4 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ዳዊትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ በተራቡ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ ያደረገውን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ካህናትም ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ርሱና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሊበሉት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ የመሥዋዕቱን ፡ ኅብስት ፡ እንደ ፡ በላ ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ካህናትም ፡ በሰንበት ፡ በመቅደስ ፡ ሰንበትን ፡ እንዲያረክሱ ፡ ኀጢአትም ፡ እንዳይኾንባቸው ፡ በሕጉ ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ከመቅደስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ምሕረትን ፡ እወዳለኹ ፡ መሥዋዕትንም ፡ አይደለም ፡ ያለው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብታውቁስ ፡

ኀጢአት ፡ የሌለባቸውን ፡ ባልኰነናችኹም ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰንበት ፡ ጌታ ፡ ነውና ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ከዚያም ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ ምኵራባቸው ፡ ገባ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ እንሆም ፥ እጁ ፡ የሰለለች ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ይከሱትም ፡ ዘንድ ። በሰንበት ፡ መፈወስ ፡ ተፈቅዷልን ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ከእናንተ ፡ አንድ ፡ በግ ፡ ያለው ፡ በሰንበት ፡ በጕድጓድ ፡ ቢወድቅበት ፥ ይዞ ፡ የማያወጣው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ ከበግ ፡ ይልቅ ፡ እንደምን ፡ አይበልጥም! ፡ ስለዚህ ፡ በሰንበት ፡ መልካም ፡ መሥራት ፡ ተፈቅዷል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ሰውየውን ፦ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ። ዘረጋትም ፥ እንደ ፡ ኹለተኛዉ ፡ ደኅና ፡ ኾነች ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ወጥተው ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዲያጠፉት ፡ ተማከሩበት ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐውቆ ፡ ከዚያ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ተከተሉት ፥ ኹሉንም ፡ ፈወሳቸው ፥ እንዳይገልጡትም ፡ አዘዛቸው ፤

ማቴ. ፡ 12 ፡ 16-17 ፤ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ማቴ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ የመረጥኩት ፡ ብላቴናዬ ፥ ነፍሴ ፡ ደስ ፡ የተሠኘችበት ፡ ወዳጄ ፤ መንፈሴን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ አኖራለኹ ፥ ፍርድንም ፡ ለአሕዛብ ፡ ያወራል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ አይከራከርም ፡ አይጮኽምም ፥ ድምፁንም ፡ በአደባባይ ፡ የሚሰማ ፡ የለም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ፍርድን ፡ ድል ፡ ለመንሣት ፡ እስኪያወጣ ፥ የተቀጠቀጠን ፡ ሸምበቆ ፡ አይሰብርም ፡ የሚጤስን ፡ የጧፍ ፡ ክርም ፡ አያጠፋም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ አሕዛብም ፡ በስሙ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጋኔን ፡ ያደረበትን ፡ ዕውር ፡ ዲዳም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤ ዕውሩም ፡ ዲዳውም ፡ እስኪያይና ፡ እስኪናገር ፡ ድረስ ፡ ፈወሰው ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ተገረሙና ፦ እንኳ ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ይኾንን ፧ አሉ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ሰምተው ፦ ይህ ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፡ አጋንንትን ፡ አያወጣም ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ርስ ፡ በርሷ ፡ የምትለያይ ፡ መንግሥት ፡ ኹላ ፡ ትጠፋለች ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ የሚለያይ ፡ ከተማም ፡ ኹሉ ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ አይቆምም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ ሰይጣንም ፡ ሰይጣንን ፡ የሚያወጣ ፡ ከኾነ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ ተለያየ ፥ እንግዲህ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዴት ፡ ትቆማለች ፧

ማቴ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ እኔስ ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከኾንኩ ፥ ልጆቻችኹ ፡ በማን ፡

ያወጧቸዋል ፤ ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ፈራጆች ፡ ይኾኑባችኋል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከኾንኹ ፥ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ደርሳለች ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ ወይስ ፡ ሰው ፡ አስቀድሞ ፡ ኀይለኛውን ፡ ሳያስር ፡ ወደ ፡ ኀይለኛው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዕቃውን ፡ ሊነጥቀው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቤቱን ፡ ይበዘብዛል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 30 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያልኾነ ፡ ይቃወመኛል ፥ ከእኔ ፡ ጋራም ፡ የማያከማች ፡ ይበትናል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ እላችኋለኹ ፥ ኀጢአትና ፡ ስድብ ፡ ኹሉ ፡ ለሰዎች ፡ ይሰረይላቸዋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለሰደበ ፡ አይሰረይለትም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 32 ፤ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ ኹሉ ፡ ይሰረይለታል ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ የሚናገር ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በሚመጣው ፡ አይሰረይለትም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 33 ፤ ዛፍ ፡ ከፍሬዋ ፡ ትታወቃለችና ፡ ዛፉን ፡ መልካም ፥ ፍሬዋንም ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፥ ወይም ፡ ዛፉን ፡ ክፉ ፡ ፍሬዋንም ፡ ክፉ ፡ አድርጉ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 34 ፤ እናንተ ፡ የእፍኝት ፡ ልጆች ፥ ክፉዎች ፡ ስትኾኑ ፡ መልካም ፡ ለመናገር ፡ እንዴት ፡ ትችላላችኹ ፤ በልብ ፡ ሞልቶ ፡ ከተረፈው ፡ አፍ ፡ ይናገራልና ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 35 ፤ መልካም ፡ ሰው ፡ ከልቡ ፡ መልካም ፡ መዝገብ ፡ መልካም ፡ ነገርን ፡ ያወጣል ፥ ክፉ ፡ ሰውም ፡ ከክፉ ፡ መዝገብ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ያወጣል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 36 ፤ እኔ ፡ እላችኋለኹ ፥ ሰዎች ፡ ስለሚናገሩት ፡ ስለ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ መልስ ፡ ይሰጡበታል ፤

ማቴ. ፡ 12 ፡ 37 ፤ ከቃልኽ ፡ የተነሣ ፡ ትጸድቃለኽና ፡ ከቃልኽም ፡ የተነሣ ፡ ትኰነናለኽ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 38 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከጻፊዎችና ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አንዳንዶቹ ፡ መለሱና ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ምልክት ፡ እንድናይ ፡ እንወዳለን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 39 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ክፉና ፡ አመንዝራ ፡ ትውልድ ፡ ምልክትን ፡ ይሻል ፥ ከነቢዩም ፡ ከዮናስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 40 ፤ ዮናስ ፡ በዓሣ ፡ ዐንበሪ ፡ ሆድ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ልብ ፡ ሦስት ፡ ቀንና ፡ ሦስት ፡ ሌሊት ፡ ይኖራል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 41 ፤ የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋራ ፡ ተነሥተው ፡ ይፈርዱበታል ፤ በዮናስ ፡ ስብከት ፡ ንስሓ ፡ ገብተዋልና ፥ እንሆም ፥ ከዮናስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 42 ፤ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋራ ፡ ተነሥታ ፡ ትፈርድበታለች ፤ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ መጥታለችና ፥ እንሆም ፥ ከሰሎሞን ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 43 ፤ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ ዕረፍት ፡ እየፈለገ ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ያልፋል ፥ አያገኝምም ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 44 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፦ ወደወጣኹበት ፡ ቤቴ ፡ እመለሳለኹ ፡ ይላል ፤ ቢመጣም ፡ ባዶ ፡ ኾኖ ፡

ተጠርጎና ፡ አጊጦ ፡ ያገኘዋል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 45 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይኼድና ፡ ከርሱ ፡ የከፉትን ፡ ሰባት ፡ ሌላዎችን ፡ አጋንንት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይወስዳል ፥ ገብተውም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፤ ለዚያም ፡ ሰው ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ ይብስበታል ። ለዚህ ፡ ክፉ ፡ ትውልድ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾንበታል ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 46 ፤ ገናም ፡ ለሕዝቡ ፡ ሲናገር ፥ እንሆ ፥ እናቱና ፡ ወንድሞቹ ፡ ሊነጋገሩት ፡ ፈልገው ፡ በውጭ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 47 ፤ አንዱም ፦ እንሆ ፥ እናትኽና ፡ ወንድሞችኽ ፡ ሊነጋገሩኽ ፡ ፈልገው ፡ በውጭ ፡ ቆመዋል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 48 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ለነገረው ፡ መልሶ ፦ እናቴ ፡ ማን ፡ ናት ፧ ወንድሞቼስ ፡ እነማን ፡ ናቸው ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 12 ፡ 49 ፤ እጁንም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ዘርግቶ ፦ እንሆ ፥ እናቴና ፡ ወንድሞቼ ፤

ማቴ. ፡ 12 ፡ 50 ፤ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፥ ርሱ ፡ ወንድሜ ፡ እኅቴም ፡ እናቴም ፡ ነውና ፥ አለ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ኢየሱስ ፡ ከቤት ፡ ወጥቶ ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ተቀመጠ ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ርሱም ፡ በታንኳ ፡ ገብቶ ፡ እስኪቀመጥ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በወደቡ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ በምሳሌም ፡ ብዙ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ ዘሪ ፡ ሊዘራ ፡ ወጣ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ ሲዘራ ፡ አንዳንዱ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ወደቀ ፥ ወፎችም ፡ መጥተው ፡ በሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ሌላውም ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡ በሌለበት ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ ጥልቅ ፡ መሬትም ፡ ስላልነበረው ፡ ወዲያው ፡ በቀለ ፥

ማቴ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ፀሓይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ጠወለገ ፥ ሥርም ፡ ስላልነበረው ፡ ደረቀ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ሌላውም ፡ በሾኽ ፡ መካከል ፡ ወደቀ ፥ ሾኽም ፡ ወጣና ፡ ዐነቀው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ሌላውም ፡ በመልካም ፡ መሬት ፡ ወደቀ ፤ አንዱም ፡ መቶ ፥ አንዱም ፡ ስድሳ ፥ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ ፍሬ ፡ ሰጠ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ የሚሰማ ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፦ ስለ ፡ ምን ፡ በምሳሌ ፡ ትነግራቸዋለኽ ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ለእናንተ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ ተሰጥቷችኋል ፥ ለእነርሱ ፡ ግን ፡ አልተሰጣቸውም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ላለው ፡ ይሰጠዋልና ፥ ይበዛለትማል ፤ ከሌለው ፡ ግን ፡ ያው ፡ ያለው ፡ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ እያዩ ፡ ስለማያዩ ፥ እየሰሙም ፡ ስለማይሰሙ ፥ ስለማያስተውሉም ፡ በምሳሌ ፡

እነግራቸዋለኹ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ መስማት ፡ ትሰማላችኹና ፡ አታስተውሉም ፥ ማየትም ፡ ታያላችኹና ፡ አትመለከቱም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ በዐይናቸው ፡ እንዳያዩ ፥ በጐሯቸውም ፡ እንዳይሰሙ ፥ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፥ ተመልሰውም ፡ እንዳልፈውሳቸው ፥ የዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ደንድኗልና ፥ ጐሯቸውም ፡ ደንቍሯል ፥ ዐይናቸውንም ፡ ጨፍነዋል ፡ የሚል ፡ የኢሳይያስ ፡ ትንቢት ፡ በእነርሱ ፡ ይፈጸማል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ የእናንተ ፡ ግን ፡ ዐይኖቻችኹ ፡ ስለሚያዩ ፡ ጐሮዎቻችኹም ፡ ስለሚሰሙ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ብዙዎች ፡ ነቢያትና ፡ ጻድቃን ፡ የምታዩትን ፡ ሊያዩ ፡ ተመኝተው ፡ አላዩም ፥ የምትሰሙትንም ፡ ሊሰሙ ፡ ተመኝተው ፡ አልሰሙም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ እናንተ ፡ የዘሪውን ፡ ምሳሌ ፡ ስሙ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ የመንግሥትን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ በማያስተውል ፡ ኹሉ ፥ ክፉው ፡ ይመጣል ፥ በልቡ ፡ የተዘራውንም ፡ ይነጥቃል ፤ በመንገድ ፡ ዳር ፡ የተዘራው ፡ ይህ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ የተዘራውም ፡ ይህ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ ወዲያው ፡ በደስታ ፡ የሚቀበለው ፡ ነው ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለጊዜው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ሥር ፡ የለውም ፥ በቃሉ ፡ ምክንያትም ፡ መከራ ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ይሰናከላል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ በሾኽ ፡ መካከል ፡ የተዘራውም ፡ ይህ ፡ ቃሉን ፡ የሚሰማ ፡ ነው ፥ የዚህም ፡ ዓለም ፡ ዐሳብና ፡ የባለጠግነት ፡ መታለል ፡ ቃሉን ፡ ያንቃል ፥ የማያፈራም ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ በመልካም ፡ መሬት ፡ የተዘራውም ፡ ይህ ፡ ቃሉን ፡ ሰምቶ ፡ የሚያስተውል ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ፍሬ ፡ ያፈራል ፡ አንዱም ፡ መቶ ፡ አንዱም ፡ ስድሳ ፡ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ ያደርጋል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ አቀረበላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በዕርሻው ፡ መልካም ፡ ዘርን ፡ የዘራን ፡ ሰው ፡ ትመስላለች ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ሰዎቹ ፡ ሲተኙ ፡ ግን ፡ ጠላቱ ፡ መጣና ፡ በስንዴው ፡ መካከል ፡ እንክርዳድን ፡ ዘርቶ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ ስንዴውም ፡ በበቀለና ፡ ባፈራ ፡ ጊዜ ፥ እንክርዳዱ ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ታየ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ የባለቤቱም ፡ ባሪያዎች ፡ ቀርበው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ መልካምን ፡ ዘር ፡ በዕርሻኽ ፡ ዘርተኽ ፡ አልነበርኽምን ፧ እንክርዳዱንስ ፡ ከወዴት ፡ አገኘ ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ርሱም ፦ ጠላት ፡ ይህን ፡ አደረገ ፡ አላቸው ። ባሮቹም ፦ እንግዲህ ፡ ኼደን ፡ ብንለቅመው ፡ ትወዳለኽን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ እንክርዳዱን ፡ ስትለቅሙ ፡ ስንዴውን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳትነቅሉት ፡ አይኾንም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ ተዉአቸው ፤ እስከ ፡ መከር ፡ ጊዜ ፡ ዐብረው ፡ ይደጉ ፤ በመከር ፡ ጊዜም ፡ ዐጫጆችን ፦ እንክርዳዱን ፡ አስቀድማችኹ ፡ ልቀሙ ፡ በእሳትም ፡ ለማቃጠል ፡ በየነዶው ፡ እሰሩ ፥ ስንዴውን ፡ ግን ፡ በጐተራዬ ፡ ክተቱ ፡ እላለኹ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ አቀረበላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሰው ፡ ወስዶ ፡ በዕርሻው ፡ የዘራትን ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ትመስላለች ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ ርሷም ፡ ከዘር ፡ ሹሉ ፡ ታንሳለች ፥ ባደገች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፥ ከአታክልቶች ፡ ትበልጣለች ፡ የሰማይም ፡ ወፎች ፡ መጥተው ፡ በቅርንጫፎቿ ፡ እስኪሰፍሩ ፡ ድረስ ፡ ዛፍ ፡ ትኾናለች ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ሹሉ ፡ እስኪቦካ ፡ ድረስ ፡ ሴት ፡ ወስዳ ፡ በሦስት ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፡ የሸሸገችውን ፡ ርሾ ፡ ትመስላለች ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 34-35 ፤ ኢየሱስም ፡ ለሕዝቡ ፡ ይህን ፡ ሹሉ ፡ በምሳሌ ፡ ተናገረ ፤ በነቢዩም ፦ በምሳሌ ፡ አፌን ፡ እከፍታለኹ ፥ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ የተሰወረውንም ፡ እናገራለኹ ፡ የተባለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ያለምሳሌ ፡ አልተናገራቸውም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 36 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገባ ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ የዕርሻውን ፡ እንክርዳድ ፡ ምሳሌ ፡ ተርጉምልን ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 37 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ መልካምን ፡ ዘር ፡ የዘራው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነው ፤ ዕርሻውም ፡ ዓለም ፡ ነው ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 38 ፤ መልካሙም ፡ ዘር ፡ የመንግሥት ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 39 ፤ እንክርዳዱም ፡ የክፉው ፡ ልጆች ፡ ናቸው ፥ የዘራውም ፡ ጠላት ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፤ መከሩም ፡ የዓለም ፡ መጨረሻ ፡ ነው ፥ ዐጫጆችም ፡ መላእክት ፡ ናቸው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 40 ፤ እንግዲህ ፡ እንክርዳድ ፡ ተለቅሞ ፡ በእሳት ፡ እንደሚቃጠል ፥ በዓለም ፡ መጨረሻ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 41 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ መላእክቱን ፡ ይልካል ፥ ከመንግሥቱም ፡ እንቅፋትን ፡ ሹሉ ፡ ዐመፃንም ፡ የሚያደርጉትን ፡ ይለቅማሉ ፥

ማቴ. ፡ 13 ፡ 42 ፤ ወደ ፡ እቶነ ፡ እሳትም ፡ ይጥሏቸዋል ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 43 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጻድቃን ፡ በአባታቸው ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ይበራሉ ። የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 44 ፤ ደግሞ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በዕርሻ ፡ ውስጥ ፡ የተሰወረውን ፡ መዝገብ ፡ ትመስላለች ፤ ሰውም ፡ አግኝቶ ፡ ሰወረው ፥ ከደስታውም ፡ የተነሣ ፡ ኼዶ ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ ሸጠና ፡ ያን ፡ ዕርሻ ፡ ገዛ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 45 ፤ ደግሞ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መልካምን ፡ ዕንቁ ፡ የሚሻ ፡ ነጋዴን ፡ ትመስላለች ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 46 ፤ ዋጋዋም ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ አንዲት ፡ ዕንቁ ፡ በአገኘ ፡ ጊዜ ፡ ኼዶ ፡ ያለውን ፡ ሹሉ ፡ ሸጠና ፡ ገዛት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 47 ፤ ደግሞ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ የተጣለች ፡ ከሹሉም ፡ ዐይነት ፡ የሰበሰበች ፡ መረብን ፡ ትመስላለች ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 48 ፤ በሞላችም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወደቡ ፡ አወጧት ፥ ተቀምጠውም ፡ መልካሙን ፡ ለቅመው ፡ በዕቃዎች ፡ ውስጥ ፡ አከማቹ ፡ ክፉውን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 49 ፤ በዓለም ፡ መጨረሻ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ፤ መላእክት ፡ መጥተው ፡ ኀጢአተኞችን ፡ ከጻድቃን ፡ መካከል ፡ ይለይዋቸዋል ፥ ወደ ፡ እቶነ ፡ እሳትም ፡ ይጥሏቸዋል ፤

ማቴ. ፡ 13 ፡ 50 ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 51 ፤ ኢ.የሱስም ፦ ይህን ፡ ኹሉ ፡ አስተዋላችኹን ፧ አላቸው ፦ አዎን ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 52 ፤ ርሱም ፦ ስለዚህ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የኾነ ፡ ጻፊ ፡ ኹሉ ፡ ከመዝገቡ ፡ ዐዲሱንና ፡ አሮጌውን ፡ የሚያወጣ ፡ ባለቤትን ፡ ይመስላል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 53 ፤ ኢ.የሱስም ፡ እነዚህም ፡ ምሳሌዎች ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 54 ፤ ወደገዛ ፡ አገሩም ፡ መጥቶ ፡ እስኪገረሙ ፡ ድረስ ፡ በምኩራባቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፤ እንዲህም ፡ አሉ ፦ ይህን ፡ ጥበብና ፡ ተአምራት ፡ ይህ ፡ ከወዴት ፡ አገኘው ፧

ማቴ. ፡ 13 ፡ 55 ፤ ይህ ፡ የጸራቢ ፡ ልጅ ፡ አይደለምን ፧ እናቱስ ፡ ማርያም ፡ ትባል ፡ የለምን ፧ ወንድሞቹስ ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሳ ፡ ስምዖንም ፡ ይሁዳም ፡ አይደሉምን ፧

ማቴ. ፡ 13 ፡ 56 ፤ እኅቶቹስ ፡ ኹሉ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያሉ ፡ አይደሉምን ፧ እንኪያስ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ከወዴት ፡ አገኘው ፧ ተሰናከሉበትም ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 57 ፤ ኢ.የሱስ ፡ ግን ፦ ነቢይ ፡ ከገዛ ፡ አገሩና ፡ ከገዛ ፡ ቤቱ ፡ በቀር ፡ ሳይከበር ፡ አይቀርም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 13 ፡ 58 ፤ ባለማመናቸውም ፡ ምክንያት ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ አላደረገም ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡ ሄሮድስ ፡ የኢ.የሱስን ፡ ዝና ፡ ሰማ ፥

ማቴ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ ለሎሌዎቹም ፦ ይህ ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቷል ፥ ስለዚህም ፡ ኀይል ፡ በርሱ ፡ ይደረጋል ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ሄሮድስ ፡ በወንድሙ ፡ በፊልጶስ ፡ ሚስት ፡ በሄሮድያዳ ፡ ምክንያት ፡ ዮሐንስን ፡ አስይዞ ፡ አሳስሮት ፡ በወህኒ ፡ አኑሮት ፡ ነበርና ፤

ማቴ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ዮሐንስ ፦ ርሷ ፡ ለአንተ ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ አልተፈቀደም ፡ ይለው ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ሊገድለውም ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፥ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ስላዩት ፡ ፈራቸው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሄሮድስ ፡ የተወለደበት ፡ ቀን ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ የሄሮድያዳ ፡ ልጅ ፡ በመካከላቸው ፡ ዘፈነች ፡ ሄሮድስንም ፡ ደስ ፡ አሠኘችው ፤

ማቴ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ስለዚህም ፡ የምትለምነውን ፡ ኹሉ ፡ እንዲሰጣት ፡ በመሐላ ፡ ተስፋ ፡ አደረገላት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ርሷም ፡ በእናቷ ፡ ተመክራ ፦ የመጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ በዚህ ፡ በወጭት ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ንጉሡም ፡ ዐዘነ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ መሐላው ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠው ፡ ስላሉት ፡ ሰዎች ፡ እንዲሰጧት ፡ አዘዘ ፤

ማቴ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ልኮም ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ በወህኒ ፡ አስቈረጠው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ራሱንም ፡ በወጭት ፡ አምጥተው ፡ ለብላቴናዪቱ ፡ ሰጧት ፥ ወደ ፡ እናቷም ፡ ወሰደችው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፡ በድኑን ፡ ወሰዱና ፡ ቀበሩት ፥ መጥተውም ፡ ለኢ.የሱስ ፡

አወሩለት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ከዚያ ፡ ብቻውን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በታንኳ ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፤ ሕዝቡም ፡ ሰምተው ፡ ከከተማዎቹ ፡ በእግር ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ወጥቶም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አየና ፡ ዐዘነላቸው ፡ ድውዮቻቸውንም ፡ ፈወሰ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ ቦታው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነው ፥ አኹንም ፡ ሰዓቱ ፡ ዐልፏል ፤ ወደ ፡ መንደሮች ፡ ኼደው ፡ ለራሳቸው ፡ ምግብ ፡ እንዲገዙ ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናብት ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ኢየሱስም ፦ እናንተ ፡ የሚበሉትን ፡ ስጧቸው ፡ እንጂ ፡ ሊኼዱ ፡ አያስፈልግም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ እነርሱም ፦ ከዐምስት ፡ እንጀራና ፡ ከኹለት ፡ ዓሣ ፡ በቀር ፡ በዚህ ፡ የለንም ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ እነዚያን ፡ ወደዚህ ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ሕዝቡም ፡ በሣር ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዘዘ ፥ ዐምስቱንም ፡ እንጀራና ፡ ኹለቱን ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሻቅቦ ፡ አየና ፡ ባረከ ፥ እንጀራውንም ፡ ቈርሶ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለሕዝቡ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ኾሉም ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፥ የተረፈውንም ፡ ቀ፡ርስራሽ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መሶብ ፡ ሙሉ ፡ አነሡ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ከሴቶችና ፡ ከልጆችም ፡ በቀር ፡ የበሉት ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ወንዶች ፡ ያኽሉ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ወዲያውም ፡ ሕዝቡን ፡ ሲያሰናብት ፡ ኅሊ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በታንኳዩቱ ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ እንዲቀድሙት ፡ ግድ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ሕዝቡንም ፡ አሰናብቶ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ብቻውን ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ። በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ብቻውን ፡ በዚያ ፡ ነበረ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ ታንኳዩቱም ፡ አኹን ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ኅሊች ፥ ነፋስ ፡ ከወደ ፡ ፊት ፡ ነበርና ፥ በማዕበል ፡ ትጨነቅ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ ከሌሊቱም ፡ በአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ኢየሱስ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እየኼደ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲኼድ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፦ ምትሀት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ታወኩ ፡ በፍርሀትም ፡ ጮኹ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ ተናገራቸውና ፦ አይዟችኹ ፥ እኔ ፡ ነኝ ፤ አትፍሩ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተስ ፡ ከኾንኽ ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ ወዳንተ ፡ እንድመጣ ፡ እዘዘኝ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ርሱም ፦ ና ፡ አለው ። ጴጥሮስም ፡ ከታንኳዩቱ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ሊደርስ ፡ በውሃው ፡ ላይ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የነፋሱን ፡ ኀይል ፡ አይቶ ፡ ፈራ ፥ ሊሰጥምም ፡ በዠመረ ፡ ጊዜ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አድነኝ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ያዘውና ፦ አንተ ፡ እምነት ፡ የጐደለኽ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ተጠራጠርኽ ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ወደ ፡ ታንኳዩቱም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ነፋሱ ፡ ተወ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 33 ፤ በታንኳዩቱም ፡ የነበሩት ፦ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፡ ብለው ፡ ሰገዱለት ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 34 ፤ ተሻግረውም ፡ ወደ ፡ ጌንሴሬጥ ፡ ምድር ፡ መጡ ።

ማቴ. ፡ 14 ፡ 35 ፤ የዚያ ፡ ቦታ ፡ ሰዎችም ፡ ባወቁት ፡ ጊዜ ፡ በዙሪያው ፡ ወዳለ ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ላኩ ፥ ሕመምተኞችንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤

ማቴ. ፡ 14 ፡ 36 ፤ የልብሱንም ፡ ጫፍ ፡ ብቻ ፡ ሊዳስሱ ፡ ይለምኑት ፡ ነበር ፤ የዳሰሱትም ፡ ኹሉ ፡ ዳኑ ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ማቴ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረቡና ፦

ማቴ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ የሽማግሌዎችን ፡ ወግ ፡ ይተላለፋሉ ፧ እንጀራ ፡ ሲበሉ ፡ እጃቸውን ፡ አይታጠቡምና ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እናንተስ ፡ ስለ ፡ ወጋችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትተላለፋላችኹ ፧

ማቴ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፦ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤ ደግሞ ፦ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሰደበ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሙት ፡ ብሏልና ፤

ማቴ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፦ ከእኔ ፡ የምትጠቀምበት ፡ መባ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ኹሉ ፥

ማቴ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ አያክብርም ፡ ትላላችኹ ፤ ስለ ፡ ወጋችኹም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሻራችኹ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፥ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፦

ማቴ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በከንፈሩ ፡ ያከብረኛል ፥ ልቡ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው ፤

ማቴ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ የሰውም ፡ ሥርዐት ፡ የኾነ ፡ ትምህርት ፡ እያስተማሩ ፡ በከንቱ ፡ ያመልኩኛል ፡ ብሎ ፡ በእውነት ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ሕዝቡንም ፡ ጠርቶ ፦ ስሙ ፡ አስተውሉም ፤

ማቴ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ሰውን ፡ የሚያረክሰው ፡ ወደ ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፥ ከአፍ ፡ የሚወጣው ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ የሚያረክሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ቀርበው ፦ ፈሪሳውያን ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ እንደ ፡ ተሰናከሉ ፡ ዐወቅኽን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ የሰማዩ ፡ አባቴ ፡ ያልተከለው ፡ ተክል ፡ ኹሉ ፡ ይነቀላል ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ተዉአቸው ፤ ዕውሮችን ፡ የሚመሩ ፡ ዕውሮች ፡ ናቸው ፤ ዕውርም ፡ ዕውርን ፡ ቢመራው ፡ ኹለቱም ፡ ወደ ፡ ጕድጓድ ፡ ይወድቃሉ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ ምሳሌውን ፡ ተርጕምልን ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እስካኹን ፡ የማታስተውሉ ፡ ናችኹን ፧

ማቴ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሆድ ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ እዳሪ ፡ እንዲጣል ፡ አትመለከቱምን ፧

ማቴ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ከአፍ ፡ የሚወጣ ፡ ግን ፡ ከልብ ፡ ይወጣል ፥ ሰውንም ፡ የሚያረክሰው ፡ ያ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ከልብ ፡ ክፉ ፡ ዐሳብ ፥ መግደል ፥ ምንዝርነት ፥ ዝሙት ፥ መስረቅ ፥ በውሸት ፡ መመስከር ፥ ስድብ ፡ ይወጣልና ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ሰውን ፡ የሚያረክሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ባልታጠበ ፡ እጅ ፡ መብላትስ ፡ ሰውን ፡ አያረክሰውም ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ጢሮስና ፡ ወደ ፡ ሲዶና ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ እንሆም ፥ ከነናዊት ([283]) ፡ ሴት ፡ ከዚያ ፡ አገር ፡ ወጥታ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የዳዊት ፡ ልጅ ፥ ማረኝ ፤ ልጄን ፡ ጋኔን ፡ ክፉኛ ፡ ይዟታል ፡ ብላ ፡ ጮኸች ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ አልመለሰላትም ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ቀርበው ፦ በኋላችን ፡ ትጮኻለችና ፡ አሰናብታት ፡ እያሉ ፡ ለመኑት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ለጠፉት ፡ በጎች ፡ በቀር ፡ አልተላክኹም ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ መጥታ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ርዳኝ ፡ እያለች ፡ ሰገደችለት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ የልጆችን ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ ለቡችሎች ፡ መጣል ፡ አይገባም ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ርሷም ፦ አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ ቡችሎችም ፡ እኮ ፡ ከጌታዎቻቸው ፡ ማእድ ፡ የወደቀውን ፡ ፍርፋሪ ፡ ይበላሉ ፡ አለች ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ እምነትሽ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ወደድሽ ፡ ይኹንልሽ ፡ አላት ። ልጂም ፡ ከዚያች ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ ዳነች ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ ዐልፎ ፡ ወደገሊላ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ መጣ ፥ ወደ ፡ ተራራም ፡ ወጥቶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ዐንካሳዎችን ፥ ዕውሮችንም ፥ ዲዳዎችንም ፥ ጕንድሾችንም ፥ ሌላዎችንም ፡ ብዙ ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ፥ በኢየሱስም ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ጣሏቸው ፤ ፈወሳቸውም ፤

ማቴ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ ስለዚህም ፡ ሕዝቡ ፡ ዲዳዎች ፡ ሲናገሩ ፥ ጕንድሾችም ፡ ሲድኑ ፥ ዐንካሳዎችም ፡ ሲኼዱ ፥ ዕውሮችም ፡ ሲያዩ ፡ አይተው ፡ ተደነቁ ፤ የእስራኤልንም ፡ አምላክ ፡ አከበሩ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠርቶ ፦ ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እስካኹን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ውለዋልና ፥ የሚበሉት ፡ ስለሌላቸው ፡ አዝንላቸዋለኹ ፤ በመንገድም ፡ እንዳይዝሉ ፡ ጦማቸውን ፡ ላሰናብታቸው ፡ አልወድም ፡ አላቸው ።

---

283 ከነዓናዊት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ ይህን ፡ ያኽል ፡ ሕዝብ ፡ የሚያጠግብ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ እንጀራ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ከወዴት ፡ እናገኛለን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፦ ስንት ፡ እንጀራ ፡ አላችኹ ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ ሰባት ፥ ጥቂትም ፡ ትንሽ ፡ ዓሣ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 35 ፤ ሕዝቡም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዘዘ ፤

ማቴ. ፡ 15 ፡ 36 ፤ ሰባቱንም ፡ እንጀራ ፡ ዓሣውንም ፡ ይዞ ፡ አመሰገነ ፡ ቈርሶም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለሕዝቡ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 37 ፤ ኹሉም ፡ በሉና ፡ ጠገቡ ፥ የተረፈውንም ፡ ቍርስራሽ ፡ ሰባት ፡ ቅርጫት ፡ ሙሉ ፡ አነሡ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 38 ፤ የበሉትም ፡ ከሴቶችና ፡ ከልጆች ፡ በቀር ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ወንዶች ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 15 ፡ 39 ፤ ሕዝቡንም ፡ ካሰናበተ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ታንኳዱቱ ፡ ገብቶ ፡ ወደመጌዶል ፡ አገር ፡ መጣ ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

ማቴ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ ሰዱቃውያንም ፡ ቀርበው ፡ ሲፈትኑት ፡ ከሰማይ ፡ ምልክት ፡ እንዲያሳያቸው ፡ ለመኑት ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በመሸ ፡ ጊዜ ፦ ሰማዩ ፡ ቀልቷልና ፥ ብራ ፡ ይኾናል ፡ ትላላችኹ ፤

ማቴ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ማለዳም ፦ ሰማዩ ፡ ደምኖ ፡ ቀልቷልና ፥ ዛሬ ፡ ይዘንባል ፡ ትላላችኹ ። የሰማዩን ፡ ፊትማ ፡ መለየት ፡ ታውቃላችኹ ፥ የዘመኑንስ ፡ ምልክት ፡ መለየት ፡ አትችሉምን ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ክፉና ፡ አመንዝራ ፡ ትውልድ ፡ ምልክትን ፡ ይሻል ፥ ከነቢዩም ፡ ከዮናስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ። ትቷቸውም ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እንጀራ ፡ መያዝን ፡ ረሱ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ኢየሱስም ፦ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ርሾ ፡ ተጠንቀቁና ፡ ተጠበቁ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፦ እንጀራ ፡ ባንይዝ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችኹ ፥ እንጀራ ፡ ስለሌላችኹ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትነጋገራላችኹ ፧ ገና ፡ አታስተውሉምን ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ለዐምስቱ ፡ ሺሕ ፡ ዐምስቱ ፡ እንጀራ ፥ ስንት ፡ መሶብም ፡ እንዳነሣችኹ ፡ ትዝ ፡ አይላችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ ወይስ ፡ ለአራቱ ፡ ሺሕ ፡ ሰባቱ ፡ እንጀራ ፥ ስንት ፡ ቅርጫትም ፡ እንዳነሣችኹ ፡ ትዝ ፡ አይላችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ርሾ ፡ እንድትጠበቁ ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ እንጀራ ፡ እንዳልተናገርኋችኹ ፡ እንዴት ፡ አታስተውሉምን ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ትምህርት ፡ እንጂ ፡ ከእንጀራ ፡ ርሾ ፡ እንዲጠበቁ ፡ እንዳላላቸው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አስተዋሉ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደፊልጶስ ፡ ቂሳርያ ፡ አገር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦ ሰዎች ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይሉታል ፧ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ እነርሱም ፦ አንዳንዱ ፡ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፥ ሌላዎችም ፡ ኤልያስ ፥ ሌላዎችም ፡ ኤርምያስ ፡ ወይም ፡ ከነቢያት ፡ አንዱ ፡ ነው ፡ ይላሉ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ እናንተስ ፡ እኔን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ትላላችኹ ፧ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባቴ ፡ እንጂ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ይህን ፡ አልገለጠልኽምና ፡ ብፁዕ ፡ ነኽ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ እኔም ፡ እልኻለኹ ፥ አንተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነኽ ፥ በዚችም ፡ አለት ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ እሠራለኹ ፥ የገሃነም ፡ ደጆችም ፡ አይችሏትም ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ የመንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ መክፈቻዎች ፡ እሰጥኻለኹ ፤ በምድር ፡ የምታስረው ፡ ኹሉ ፡ በሰማያት ፡ የታሰረ ፡ ይኾናል ፥ በምድርም ፡ የምትፈታው ፡ ኹሉ ፡ በሰማያት ፡ የተፈታ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለማንም ፡ እንዳይነግሩ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አዘዛቸው ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ከሽማግሌዎችና ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ከጻፊዎችም ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ይቀበልና ፡ ይገደል ፡ ዘንድ ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ይገልጥላቸው ፡ ዠመር ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወስዶ ፦ አይኹንብኽ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ ይህ ፡ ከቶ ፡ አይደርስብኽም ፡ ብሎ ፡ ሊገሥጸው ፡ ዠመረ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ጴጥሮስን ፦ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ኺድ ፥ አንተ ፡ ሰይጣን ፤ የሰውን ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ አታስብምና ፡ ዕንቅፋት ፡ ኾነኽብኛል ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እኔን ፡ መከተል ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፥ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋታል ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ነፍሱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ኹሉ ፡ ያገኛታል ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ሰው ፡ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ ቢያተርፍ ፡ ነፍሱንም ፡ ቢያጐድል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፧ ወይስ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ ይሰጣል ፧

ማቴ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከመላእክቱ ፡ ጋራ ፡ በአባቱ ፡ ክብር ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አለውና ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ለኹሉ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ያስረክበዋል ።

ማቴ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በመንግሥቱ ፡ ሲመጣ ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፡ እዚህ ፡ ከሚቆሙት ፡ ሞትን ፡ የማይቀምሱ ፡ አንዳንድ ፡ አሉ ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ማቴ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ ከስድስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡ ይዞ ፡

ወደ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፡ ብቻቸውን ፡ አወጣቸው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ በፊታቸውም ፡ ተለወጠ ፥ ፊቱም ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ በራ ፥ ልብሱም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነጭ ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ እንሆም ፥ ሙሴና ፡ ኤልያስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ታዩዋቸው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ ኢየሱስን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ መኾን ፡ ለእኛ ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ብትወድስ ፥ በዚህ ፡ ሦስት ፡ ዳስ ፡ አንዱን ፡ ለአንተ ፡ አንዱንም ፡ ለሙሴ ፡ አንዱንም ፡ ለኤልያስ ፡ እንሥራ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፥ እንሆ ፥ ብሩህ ፡ ደመና ፡ ጋረዳቸው ፥ እንሆም ፥ ከደመናው ፦ በርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ርሱን ፡ ስሙት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሰምተው ፡ በፊታቸው ፡ ወደቁ ፡ እጅግም ፡ ፈርተው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፡ ቀርቦ ፡ ዳሰሳቸውና ፦ ተነሡ ፡ አትፍሩም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ዐይናቸውንም ፡ አቅንተው ፡ ሲያዩ ፡ ከኢየሱስ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ አላዩም ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ከተራራውም ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፥ ኢየሱስ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከሙታን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ ያያችኹትን ፡ ለማንም ፡ አትንገሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ እንግዲህ ፡ ጻፊዎች ፦ ኤልያስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊመጣ ፡ ይገባዋል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይላሉ ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ኤልያስማ ፡ አስቀድሞ ፡ ይመጣል ፡ ኹሉንም ፡ ያቀናል ፤

ማቴ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ኤልያስ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ መጣ ፤ የወደዱትንም ፡ ኹሉ ፡ አደረጉበት ፡ እንጂ ፡ አላወቁትም ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከነርሱ ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ አለው ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለ ፡ መጥምቁ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡ አስተዋሉ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሕዝቡም ፡ ሲደርሱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበና ፡ ተንበርክኮ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ልጄን ፡ ማርልኝ ፥ በጨረቃ ፡ እየተነሣበት ፡ ክፉኛ ፡ ይሣቀያልና ፤

ማቴ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእሳት ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በውሃ ፡ ይወድቃልና ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትኽም ፡ አመጣኹት ፡ ሊፈውሱትም ፡ አቃታቸው ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ የማታምን ፡ ጠማማ ፡ ትውልድ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለኹ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ እታገሣችኋለኹ ፧ ወደዚህ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ኢየሱስም ፡ ገሠጸው ፡ ጋኔኑም ፡ ከርሱ ፡ ወጣ ፥ ብላቴናውም ፡ ከዚያች ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ ተፈወሰ ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረቡና ፦ እኛ ፡ ልናወጣው ፡ ያልቻልን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 17 ፡ 20 ፤ ኢየሱስም ፦ ስለእምነታችኹ ፡ ማነስ ፡ ነው ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡

የሚያኽል ፡ እምነት ፡ ቢኖራችኹ ፥ ይህን ፡ ተራራ ፦ ከዚህ ፡ ወደዚያ ፡ ዕለፍ ፡ ብትሉት ፡ ያልፋል ፤ የሚሳናችኹም ፡ ነገር ፡ የለም ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 21 ፤ ይህ ፡ ዐይነት ፡ ግን ፡ ከጸሎትና ፡ ከጦም ፡ በቀር ፡ አይወጣም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 22 ፤ በገሊላም ፡ ሲመላለሱ ፥ ኢየሱስ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሰዎች ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፥ ይገድሉትማል ፥

ማቴ. ፥ 17 ፥ 23 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላቸው ። እጅግም ፡ ዐዘኑ ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 24 ፤ ወደ ፡ ቅፍርናሖምም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ግብር ፡ የሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቀረቡና ፦ መምህራችኹ ፡ ኹለቱን ፡ ዲናር ፡ [*] ፡ አይገብርምን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 25 ፤ አዎን ፡ ይገብራል ፡ አለ ። ወደ ፡ ቤትም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ አስቀድሞ ፦ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ይመስልኻል ፧ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ቀረጥና ፡ ግብር ፡ ከማን ፡ ይቀበላሉ ፧ ከልጆቻቸውን ፡ ወይስ ፡ ከእንግዳዎች ፧ አለው ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 26 ፤ ጴጥሮስም ፦ ከእንግዳዎች ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፦ እንኪያስ ፡ ልጆቻቸው ፡ ነጻ ፡ ናቸው ።

ማቴ. ፥ 17 ፥ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳናሰናክላቸው ፥ ወደ ፡ ባሕር ፡ ኺድና ፡ መቃጥን ፡ ጣል ፥ መጥመሪያም ፡ የሚወጣውን ፡ ዓሣ ፡ ውሰድና ፡ አፉን ፡ ስትከፍት ፡ ስታቴር ፡ [**] ፡ ታገኛለኽ ፤ ያን ፡ ወስደኽ ፡ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ።

* ፤ አንድ ፡ ዲናር ፡ ዐምሳ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ ሳንቲም ፡ ያኽል ፡ ነው ።

** ፤ ስታቴር ፡ ኹለት ፡ ብር ፡ ያኽል ፡ ነው ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ። _____

ማቴ. ፥ 18 ፥ 1 ፤ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀርበው ፦ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከኾሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ማን ፡ ይኾን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፥ 18 ፥ 2 ፤ ሕፃንም ፡ ጠርቶ ፡ በመካከላቸው ፡ አቆመ ፡

ማቴ. ፥ 18 ፥ 3 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ካልተመለሳችኹ ፡ እንደ ፡ ሕፃናትም ፡ ካልኾናችኹ ፥ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከቶ ፡ አትገቡም ።

ማቴ. ፥ 18 ፥ 4 ፤ እንግዲህ ፡ እንደዚህ ፡ ሕፃን ፡ ራሱን ፡ የሚያዋርድ ፡ ኾሉ ፥ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚበልጥ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ማቴ. ፥ 18 ፥ 5 ፤ እንደዚህም ፡ ያለውን ፡ አንድ ፡ ሕፃን ፡ በስሜ ፡ የሚቀበል ፡ ኾሉ ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፤

ማቴ. ፥ 18 ፥ 6 ፤ በእኔም ፡ ከሚያምኑ ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ የሚያሰናክል ፡ ኾሉ ፥ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በዐንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ጥልቅ ፡ ባሕር ፡ መስጠም ፡ ይሻለው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፥ 18 ፥ 7 ፤ ወዮ ፡ ለዓለም ፡ ስለ ፡ ማሰናከያ ፤ ማሰናከያ ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርሱ ፡ ጠንቅ ፡ ማሰናከያ ፡ ለሚመጣበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ።

ማቴ. ፥ 18 ፥ 8 ፤ እጅኽ ፡ ወይም ፡ እግርኽ ፡ ብታሰናክልኽ ፥ ቈርጠኽ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፤ ኹለት ፡ እጅ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ እግር ፡ ኖሮኽ ፡ ወደዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ከምትጣል ፡ ይልቅ ፡ ዐንካሳ ፡ ወይም ፡ ጕንድሽ ፡ ኾነኽ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡

መግባት ፡ ይሻልኻል ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ዐይንኽ ፡ ብታሰናክልኽ ፡ አውጥተኽ ፡ ከአንተ ፡ ጣላት ፤ ኹለት ፡ ዐይን ፡ ኖሮኽ ፡ ወደ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ከምትጣል ፡ ይልቅ ፡ አንዲት ፡ ዐይን ፡ ኖራኽ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻልኻል ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ እንዳትንቁ ፡ ተጠንቀቁ ፤ መላእክታቸው ፡ በሰማያት ፡ ዘወትር ፡ በሰማያት ፡ ያለውን ፡ የአባቴን ፡ ፊት ፡ ያያሉ ፡ እላችኋለኹና ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የጠፋውን ፡ ለማዳን ፡ መጥቷልና ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ ላንድ ፡ ሰው ፡ መቶ ፡ በጎች ፡ ቢኖሩት ፡ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ቢባዝን ፥ ዘጠና ፡ ዘጠኙን ፡ በተራራ ፡ ትቶ ፡ ኼዶም ፡ የባዘነውን ፡ አይፈልግምን ፧

ማቴ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ቢያገኘውም ፥ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ካልባዘኑቱ ፡ ከዘጠና ፡ ዘጠኙ ፡ ይልቅ ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ እንደዚሁ ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱ ፡ እንዲጠፋ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችኹ ፡ ፈቃድ ፡ አይደለም ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ወንድምኽም ፡ ቢበድልኽ ፥ ኼደኽ ፡ አንተና ፡ ርሱ ፡ ብቻችኹን ፡ ኾናችኹ ፡ ውቀሠው ። ቢሰማኽ ፥ ወንድምኽን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግኸው ፤

ማቴ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ባይሰማኽ ፡ ግን ፥ በኹለት ፡ ወይም ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ አፍ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እንዲጸና ፥ ዳግመኛ ፡ አንድ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ውሰድ ፤

ማቴ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ እነርሱንም ፡ ባይሰማ ፥ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንገራት ፤ ደግሞም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ባይሰማት ፥ እንደ ፡ አረመኔና ፡ እንደ ፡ ቀራጭ ፡ ይኹንልኽ ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በምድር ፡ የምታስሩት ፡ ኹሉ ፡ በሰማይ ፡ የታሰረ ፡ ይኾናል ፥ በምድርም ፡ የምትፈቱት ፡ ኹሉ ፡ በሰማይ ፡ የተፈታ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ደግሞ ፡ እላችኋለኹ ፥ ከእናንተ ፡ ኹለቱ ፡ በምድር ፡ በማናቸውም ፡ በሚለምኑት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ቢስማሙ ፡ በሰማያት ፡ ካለው ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ይደረግላቸዋል ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ በስሜ ፡ በሚሰበሰቡበት ፡ በዚያ ፡ በመካከላቸው ፡ እኾናለኹና ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወንድሜ ፡ ቢበድለኝ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ልተውለት ፧ እስከ ፡ ሰባት ፡ ጊዜን ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ እስከ ፡ ሰባ ፡ ጊዜ ፡ ሰባት ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ አልልኽም ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ስለዚህ ፥ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ባሮቹን ፡ ሊቈጣጠር ፡ የወደደን ፡ ንጉሥ ፡ ትመስላለች ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ መቈጣጠርም ፡ በገፐመረ ፡ ጊዜ ፥ እልፍ ፡ መክሊት ፡ ዕዳ ፡ ያለበትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ የሚከፍለውም ፡ ቢያጣ ፥ ርሱና ፡ ሚስቱ ፡ ልጆቹም ፡ ያለውም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሸጥና ፡ ዕዳው ፡ እንዲከፈል ፡ ጌታው ፡ አዘዘ ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ ባሪያው ፡ ወድቆ ፡ ሰገደለትና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ታገሠኝ ፥ ኹሉንም ፡ እከፍልኻለኹ ፡

አለው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ የዚያም ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ ዐዘነለትና ፡ ለቀቀው ፥ ዕዳውንም ፡ ተወለት ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ያ ፡ ባሪያ ፡ ወጥቶ ፡ ከባልንጀራዎቹ ፡ ከባሮቹ ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ ዕዳ ፡ ያለበትን ፡ አንዱን ፡ አገኘና ፦ ዕዳኽን ፡ ክፈለኝ ፡ ብሎ ፡ ያዘና ፡ ዐነቀው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ስለዚህ ፥ ባልንጀራው ፡ ባሪያ ፡ ወድቆ ፦ ታገሠኝ ፥ ኹሉንም ፡ እከፍልኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ ርሱም ፡ አልወደደም ፥ ግን ፡ ኼዶ ፡ ዕዳውን ፡ እስኪከፍል ፡ ድረስ ፡ በወህኒ ፡ አኖረው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ ባልንጀራዎቹ ፡ የኾኑ ፡ ባሪያዎችም ፡ ያደረገውን ፡ አይተው ፡ እጅግ ፡ ዐዘኑ ፥ መጥተውም ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ለጌታቸው ፡ ገለጡ ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ጌታው ፡ ጠርቶ ፦ አንተ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፥ ስለ ፡ ለመንኸኝ ፡ ያን ፡ ዕዳ ፡ ኹሉ ፡ ተውኹልኽ ፤

ማቴ. ፡ 18 ፡ 33 ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ማርኹኽ ፡ ባልንጀራኽ ፡ የኾነውን ፡ ያን ፡ ባሪያ ፡ ልትምረው ፡ ለአንተስ ፡ አይገባኽምን ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 34 ፤ ጌታውም ፡ ተቈጣና ፡ ዕዳውን ፡ ኹሉ ፡ እስኪከፍለው ፡ ድረስ ፡ ለሚሣቅዩት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ።

ማቴ. ፡ 18 ፡ 35 ፤ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ ወንድሙን ፡ ከልቡ ፡ ይቅር ፡ ካላለ ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ የሰማዩ ፡ አባቴ ፡ ያደርግባችኋል ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ከፈጸመ ፡ በኋላ ፥ ከገሊላ ፡ ኼዶ ፡ ወደይሁዳ ፡ አውራጃ ፡ ወደዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ መጣ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ተከተሉት ፥ በዚያም ፡ ፈወሳቸው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡና ፡ ሊፈትኑት ፦ ሰው ፡ በኾነው ፡ ምክንያት ፡ ኹሉ ፡ ሚስቱን ፡ ሊፈታ ፡ ተፈቅዶለታልን ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ፈጣሪ ፡ በመዠመሪያ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አደረጋቸው ፥

ማቴ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ አለም ፦ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፥ ከሚስቱም ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፥ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ኹለት ፡ አይደሉም ። እግዚአብሔር ፡ ያጣመረውን ፡ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ አይለየው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፦ እንኪያስ ፡ ሙሴ ፡ የፍቺን ፡ ጽሕፈት ፡ ሰጥተው ፡ እንዲፈቷት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አዘዘ ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ርሱም ፦ ሙሴስ ፡ ስለልባችኹ ፡ ጥንካሬ ፡ ሚስቶቻችኹን ፡ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደላችኹ ፤ ከጥንት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አልነበረም ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ ያለዝሙት ፡ ምክንያት ፡ ሚስቱን ፡ ፈቶ ፡ ሌላዪቱን ፡ የሚያገባ ፡ ኹሉ ፡ ያመነዝራል ፥ የተፈታችውንም ፡ የሚያገባ ፡ ያመነዝራል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ የባልና ፡ የሚስት ፡ ሥርዐት ፡ እንዲህ ፡ ከኾነ ፡ መጋባት ፡ አይጠቅምም ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ ለተሰጣቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለኹሉ ፡ አይደለም ፤

ማቴ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ በእናት ፡ ማሕፀን ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ ኾነው ፡ የተወለዱ ፡ አሉ ፥ ሰውም ፡ የሰለባቸው ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ አሉ ፥ ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ራሳቸውን ፡ የሰለቡ ፡ ጃን ፡ ደረባዎች ፡ አሉ ፦ ሊቀበለው ፡ የሚችል ፡ ይቀበለው ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እጁን ፡ እንዲጭንባቸውና ፡ እንዲጸልይ ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ገሠጿቸው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስ ፦ ሕፃናትን ፡ ተዉአቸው ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ አትከልክሏቸው ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉ ፡ ናትና ፥ አለ ፤

ማቴ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ እጁንም ፡ ጫነባቸውና ፡ ከዚያ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ ቀርቦ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ እንዳገኝ ፡ ምን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ላድርግ ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ ስለ ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ትጠይቀኛለኽ ፧ መልካም ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ብትወድ ፡ ግን ፡ ትእዛዛትን ፡ ጠብቅ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ የትኞችን ፧ አለው ። ኢየሱስም ፦ አትግደል ፥ አታመንዝር ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት ፡ አትመስክር ፥

ማቴ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፥ ባልንጀራኽንም ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ጐበዙም ፦ ይህንማ ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ዠምሬ ፡ ጠብቄያለኹ ፥ ደግሞስ ፡ የሚጐድለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፦ ፍጹም ፡ ልትኾን ፡ ብትወድ ፥ ኺድና ፡ ያለኽን ፡ ሸጠኽ ፡ ለድኻዎች ፡ ስጥ ፥ መዝገብም ፡ በሰማያት ፡ ታገኛለኽ ፥ መጥተኽም ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ጐበዙም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ንብረት ፡ ነበረውና ፡ እያዘነ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ለባለጠጋ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ ጭንቅ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ዳግመኛም ፡ እላችኋለኹ ፥ ባለጠጋ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከሚገባ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቢገባ ፡ ይቀላል ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሰምተው ፡ እጅግ ፡ ተገረሙና ፦ እንኪያስ ፡ ማን ፡ ሊድን ፡ ይችላል ፧ አሉ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ኢየሱስም ፡ እነርሱን ፡ ተመልክቶ ፦ ይህ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ኹሉ ፡ ይቻላል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልሶ ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ ኹሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንኽ ፤ እንኪያስ ፡ ምን ፡ እናገኝ ፡ ይኾን ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ እናንተስ ፡ የተከተላችኹኝ ፥ በዳግመኛ ፡ ልደት ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በክብሩ ፡ ዙፋን ፡ በሚቀመጥበት ፡ ጊዜ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ስትፈርዱ ፡ በዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዙፋን ፡ ትቀመጣላችኹ ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ስለ ፡ ስሜም ፡ ቤቶችን ፡ ወይም ፡ ወንድሞችን ፡ ወይም ፡ እኅቶችን ፡ ወይም ፡ አባትን ፡ ወይም ፡ እናትን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ ወይም ፡ ዕርሻን ፡ የተወ ፡ ኹሉ ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ ይቀበላል ፡ የዘለዓለምንም ፡ ሕይወት ፡ ይወርሳል ።

ማቴ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ብዙዎቹ ፡ ፊተኞች ፡ ኋለኞች ፥ ኋለኞችም ፡ ፊተኞች ፡ ይኾናሉ ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ማቴ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለወይኑ ፡ አትክልት ፡ ሠራተኞችን ፡ ሊቀጥር ፡ ማልዶ ፡ የወጣ ፡ ባለቤት ፡ ሰውን ፡ ትመስላለችና ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ ሠራተኞችንም ፡ በቀን ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተስማምቶ ፡ ወደወይኑ ፡ አትክልት ፡ ሰደዳቸው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ በሦስት ፡ ሰዓትም ፡ ወጥቶ ፡ ሥራ ፡ የፈቱ ፡ ሌላዎችን ፡ በአደባባይ ፡ ቆመው ፡ አየ ፥

ማቴ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ እነዚያንም ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ወደወይኔ ፡ አትክልት ፡ ኺዱ ፥ የሚገባውንም ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ኼዱ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ በስድስትና ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወጥቶ ፡ እንዲሁ ፡ አደረገ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛውም ፡ ሰዓት ፡ ወጥቶ ፡ ሌላዎችን ፡ ቆመው ፡ አገኘና ፦ ሥራ ፡ ፈታችኹ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትቆማላችኹ ፧ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ የሚቀጥረን ፡ ስላጣን ፡ ነው ፡ አሉት ። ርሱም ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ወደወይኔ ፡ አትክልት ፡ ኺዱ ፥ የሚገባውንም ፡ ትቀበላላችኹ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ አዛዡን ፦ ሠራተኞችን ፡ ጥራና ፡ ከኋለኞች ፡ ዠምረኽ ፡ እስከ ፡ ፊተኞች ፡ ድረስ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ስጣቸው ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ በዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ሰዓትም ፡ የገቡ ፡ መጥተው ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተቀበሉ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ፊተኞችም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አብዝተው ፡ የሚቀበሉ ፡ መስሏቸው ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ ተቀበሉ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 11-12 ፤ ተቀብለውም ፦ እነዚህ ፡ ኋለኞች ፡ አንድ ፡ ሰዓት ፡ ሠሩ ፥ የቀኑንም ፡ ድካምና ፡ ትኵሳት ፡ ከተሸከምን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አስተካከልኻቸው ፡ ብለው ፡ በባለቤቱ ፡ ላይ ፡ አንጐራጐሩ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ ከነርሱ ፡ ለአንዱ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ አልበደልኹኽም ፡ ባንድ ፡ ዲናር ፡ አልተስማማኽኝምን ፧

ማቴ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ድርሻኽን ፡ ውሰድና ፡ ኺድ ፤ እኔ ፡ ለዚህ ፡ ለኋለኛው ፡ እንደ ፡ አንተ ፡ ልሰጠው ፡ እወዳለኹ ፤ በገንዘቤ ፡ የወደድኹትን ፡ ላደርግ ፡ ዘንድ ፡ መብት ፡ የለኝምን ፧

ማቴ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ወይስ ፡ እኔ ፡ መልካም ፡ ስለ ፡ ኾንኹ ፡ ዐይንኽ ፡ ምቀኛ ፡ ናትን ፧

ማቴ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ እንዲሁ ፡ ኋለኞች ፡ ፊተኞች ፥ ፊተኞችም ፡ ኋለኞች ፡ ይኾናሉ ፤ የተጠሩ ፡ ብዙዎች ፥ የተመረጡ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሊወጣ ፡ ሳለ ፥ በመንገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አቅርቦ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ለጻፊዎች ፡ ይሰጣል ፤ የሞት ፡ ፍርድም ፡ ይፈርዱበታል ፥

ማቴ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ሊዘባበቱበትም ፡ ሊገርፉትም ፡ ሊሰቅሉትም ፡ ለአሕዛብ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የዘብዴዎስ ፡ ልጆች ፡ እናት ፡ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ እየሰገደችና ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እየለመነች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበች ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ ምን ፡ ትፈልጊያለሽ ፧ አላት ። ርሷም ፦ እነዚህ ፡ ኹለቱ ፡ ልጆቼ ፡ አንዱ ፡ በቀኝኽ ፡ አንዱም ፡ በግራኽ ፡ በመንግሥትኽ ፡ እንዲቀመጡ ፡ እዘዝ ፡ አለችው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ የምትለምኑትን ፡ አታውቁም ፦ እኔ ፡ ልጠጣው ፡ ያለውን ፡ ጽዋ ፡ ልትጠጡ ፡ እኔም ፡ የምጠመቀውን ፡ ጥምቀት ፡ ልትጠመቁ ፡ ትችላላችኹን ፧ አለ ። እንችላለን ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ ጽዋዬንስ ፡ ትጠጣላችኹ ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ መቀመጥ ፡ ግን ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ለተዘጋጀላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ የምሰጥ ፡ አይደለኹም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ ዐሥሩም ፡ ሰምተው ፡ በኹለቱ ፡ ወንድማማች ፡ ተቈጡ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ እንዲገዟቸው ፡ ታላላቆቹም ፡ በላያቸው ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ታውቃላችኹ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ በእናንተስ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ ከእናንተ ፡ ታላቅ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ የእናንተ ፡ አገልጋይ ፡ ይኹን ፥

ማቴ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ ፊተኛ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ የእናንተ ፡ ባሪያ ፡ ይኹን ፤

ማቴ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ እንዲሁም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሊያገለግል ፡ ነፍሱንም ፡ ለብዙዎች ፡ ቤዛ ፡ ሊሰጥ ፡ እንጂ ፡ እንዲያገለግሉት ፡ አልመጣም ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ ከኢያሪኮም ፡ ሲወጡ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉት ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 30 ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ዕውሮች ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጠው ፥ ኢየሱስ ፡ እንዲያልፍ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የዳዊት ፡ ልጅ ፥ ማረን ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 31 ፤ ሕዝቡም ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ ገሠጿቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የዳዊት ፡ ልጅ ፥ ማረን ፡ እያሉ ፡ አብዝተው ፡ ጮኹ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 32 ፤ ኢየሱስም ፡ ቆሞ ፡ ጠራቸውና ፦ ምን ፡ ላደርግላችኹ ፡ ትወዳላችኹ ፧ አለ ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 33 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዐይኖቻችን ፡ ይከፈቱ ፡ ዘንድ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 20 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐዘነላቸውና ፡ ዐይኖቻቸውን ፡ ዳሰሰ ፥ ወዲያውም ፡ አዩና ፡ ተከተሉት ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ማቴ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ቀርበው ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፋጌ ፡ ሲደርሱ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹለት ፡ ላከ ፥

ማቴ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ በፊታችኹ ፡ ወዳለችው ፡ መንደር ፡ ኺዱ ፥ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የታሰረችን ፡ አህያ ፡ ውርንጫም ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ታገኛላችኹ ፤ ፈቷ፡ችኹ ፡ አምጡልኝ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ማንም ፡ አንዳች ፡ ቢላችኹ ፦ ለጌታ ፡ ያስፈልጉታል ፡ በሉ ፤ ወዲያውም ፡ ይሰዳቸዋል ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 4-5 ፤ ለጽዮን ፡ ልጅ ፦ እንሆ ፥ ንጉሥሽ ፡ የዋህ ፡ ኾኖ ፡ በአህያ ፡ ላይና ፡ በአህያዪቱ ፡ ግልገል ፡ በውርንጫዪቱ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ አንቺ ፡ ይመጣል ፡ በሏት ፡ ተብሎ ፡ በነቢይ ፡ የተነገረው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ኼደው ፡ ኢየሱስ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ፥

ማቴ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ አህያዪቱንና ፡ ውርንጫዋንም ፡ አመጡለት ፥ ልብሳቸውንም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፥ ተቀመጠባቸውም ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ከሕዝቡም ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ልብሳቸውን ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አነጠፉ ፥ ሌላዎችም ፡ ከዛፍ ፡ ጫፍ ፡ ጫፉን ፡ እየቈረጡ ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ ያነጥፉ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ የሚቀድሙትም ፡ ሕዝብ ፡ የሚከተሉትም ፦ ሆሣዕና ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ መላው ፡ ከተማ ፦ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ተናወጠ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ሕዝቡም ፦ ይህ ፡ ከገሊላ ፡ ናዝሬት ፡ የመጣ ፡ ነቢዩ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባና ፡ በመቅደስ ፡ የሚሸጡትንና ፡ የሚገዙትን ፡ ኹሉ ፡ አወጣ ፥ የገንዘብ ፡ ለዋጮችንም ፡ ገበታዎች ፡ የርግብ ፡ ሻጪዎችንም ፡ ወንበሮች ፡ ገለበጠና ፦

ማቴ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ቤቴ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ትባላለች ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ የወንበዴዎች ፡ ዋሻ ፡ አደረጋችኋት ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ በመቅደስም ፡ ዕውሮችና ፡ ዐንካሳዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡና ፡ ፈወሳቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጻፊዎች ፡ ያደረገውን ፡ ድንቃድንቅ ፡ በመቅደስም ፦ ሆሣዕና ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡ እያሉ ፡ የሚጮኹትን ፡ ልጆች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ተቈጥተው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ እነዚህ ፡ የሚሉትን ፡ አትሰማምን ፧ አሉት ። ኢየሱስም ፦ እሰማለኹ ፤ ከሕፃናትና ፡ ከሚጠቡት ፡ አፍ ፡ ምስጋናን ፡ ለራስኽ ፡ አዘጋጀኽ ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ ከቶ ፡ አላነበባችኹምን ፧ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ትቷቸውም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ወጣ ፡ በዚያም ፡ ዐደረ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ በማለዳም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ሲመለስ ፡ ተራበ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ በመንገድም ፡ አጠገብ ፡ በለስ ፡ አይቶ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ መጣ ፤ ከቅጠልም ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ምንም ፡

አላገኘባትምና ፦ ለዘለዓለሙ ፡ ፍሬ ፡ አይገኝብሽ ፡ አላት ። በለሲቱም ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ደረቀች ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ይህን ፡ አይተው ፦ በለሲቱ ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ እንዴት ፡ ደረቀች ፧ ብለው ፡ ተደነቁ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ እምነት ፡ ቢኖራችኹ ፡ ባትጠራጠሩም ፥ በበለሲቱ ፡ እንደ ፡ ኾነባት ፡ ብቻ ፡ አታደርጉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ተራራ ፡ እንኳ ፦ ተነቅለኽ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወርወር ፡ ብትሉት ፡ ይኾናል ፤

ማቴ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ አምናችኹም ፡ በጸሎት ፡ የምትለምኑትን ፡ ኹሉ ፡ ትቀበላላችኹ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ ሲያስተምር ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ የሕዝብ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡና ፦ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ ታደርጋለኽ ፧ ይህንስ ፡ ሥልጣን ፡ ማን ፡ ሰጠኽ ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቃችኋለኹ ፤ እናንተም ፡ ያችን ፡ ብትነግሩኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እነዚህን ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እንዳደርግ ፡ እነግራችኋለኹ ፤

ማቴ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ የዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ከወዴት ፡ ነበረች ፧ ከሰማይን ፡ ወይስ ፡ ከሰው ፧ አላቸው ። እነርሱም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲነጋገሩ ፦ ከሰማይ ፡ ብንል ፦ እንኪያስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አላመናችኹበትም ፧ ይለናል ፤

ማቴ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ከሰው ፡ ግን ፡ ብንል ፥ ዮሐንስን ፡ ኹሉም ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ያዩታልና ፥ ሕዝቡን ፡ እንፈራለን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ ለኢየሱስም ፡ መልሰው ፦ አናውቅም ፡ አሉት ። ርሱም ፡ ደግሞ ፦ እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ አልነግራችኹም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ አንድ ፡ ሰው ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፤ ወደ ፡ አንደኛው ፡ ቀርቦ ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡ ኺድና ፡ በወይኔ ፡ አትክልት ፡ ሥራ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ አልወድም ፡ አለ ፤ ኋላ ፡ ግን ፡ ተጸጸተና ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ወደ ፡ ኹለተኛውም ፡ ቀርቦ ፡ እንዲሁ ፡ አለው ፡ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ዕሺ ፡ ጌታዬ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አልኼደም ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ከኹለቱ ፡ የአባቱን ፡ ፈቃድ ፡ ያደረገ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ፊተኛው ፡ አሉት ። ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ቀራጮችና ፡ ጋለሞታዎች ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመግባት ፡ ይቀድሟችኋል ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ ዮሐንስ ፡ በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ መጥቶላችኹ ፡ ነበርና ፥ አላመናችኹበትም ፤ ቀራጮችና ፡ ጋለሞታዎች ፡ ግን ፡ አመኑበት ፤ እናንተም ፡ ይህን ፡ አይታችኹ ፡ ታምኑበት ፡ ዘንድ ፡ በኋላ ፡ ንስሓ ፡ አልገባችኹም ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ ሌላ ፡ ምሳሌ ፡ ስሙ ። የወይን ፡ አትክልት ፡ የተከለ ፡ ባለቤት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ቅጥርም ፡ ቀጠረለት ፥ መጥመቂያም ፡ ማሰለት ፥ ግንብም ፡ ሠራና ፡ ለገበሬዎች ፡ አከራይቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ የሚያፈራበትም ፡ ጊዜ ፡ ሲቀርብ ፥ ፍሬውን ፡ ሊቀበሉ ፡ ባሮቹን ፡ ወደ ፡ ገበሬዎች ፡ ላከ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 35 ፤ ገበሬዎቹም ፡ ባሮቹን ፡ ይዘው ፡ አንዱን ፡ ደበደቡት ፡ አንዱንም ፡ ገደሉት ፡ ሌላውንም ፡ ወገሩት ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 36 ፤ ደግሞ ፡ ከፊተኞች ፡ የሚበዙ ፡ ሌላዎች ፡ ባሪያዎችን ፡ ላከ ፥ እንዲሁም ፡ አደረጉባቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 37 ፤ በኋላ ፡ ግን ፦ ልጄንስ ፡ ያፍሩታል ፡ ብሎ ፡ ልጁን ፡ ላከባቸው ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 38 ፤ ገበሬዎቹ ፡ ግን ፡ ልጁን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ኑ ፥ እንግደለውና ፡ ርስቱን ፡ እናግኝ ፡ ተባባሉ ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 39 ፤ ይዘውም ፡ ከወይኑ ፡ አትክልት ፡ አወጡና ፡ ገደሉት ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 40 ፤ እንግዲህ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ በሚመጣ ፡ ጊዜ ፡ በእነዚህ ፡ ገበሬዎች ፡ ምን ፡ ያደርግባቸዋል ፧

ማቴ. ፡ 21 ፡ 41 ፤ እነርሱም ፦ ክፉዎችን ፡ በክፉ ፡ ያጠፋቸዋል ፥ የወይኑንም ፡ አትክልት ፡ ፍሬውን ፡ በየጊዜው ፡ ለሚያስረክቡ ፡ ለሌላዎች ፡ ገበሬዎች ፡ ይሰጠዋል ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 42 ፤ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ግንበኞች ፡ የናቁት ፡ ድንጋይ ፡ ርሱ ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ ኾነ ፤ ይህም ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ኾነ ፥ ለዐይኖቻችንም ፡ ድንቅ ፡ ነው ፡ የሚለውን ፡ ከቶ ፡ በመጽሐፍ ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 21 ፡ 43 ፤ ስለዚህ ፥ እላችኋለኹ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከእናንተ ፡ ትወሰዳለች ፥ ፍሬዋንም ፡ ለሚያደርግ ፡ ሕዝብ ፡ ትሰጣለች ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 44 ፤ በዚህም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ ይቀጠቀጣል ፤ ድንጋዩ ፡ ግን ፡ የሚወድቅበትን ፡ ኹሉ ፡ ይፈጨዋል ።

ማቴ. ፡ 21 ፡ 45 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ምሳሌዎቹን ፡ ሰምተው ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አስተዋሉ ፤

ማቴ. ፡ 21 ፡ 46 ፤ ሊይዙትም ፡ ሲፈልጉት ፡ ሳሉ ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ስላዩት ፡ ፈሯቸው ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፡ ደግሞም ፡ በምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ማቴ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለልጁ ፡ ሰርግ ፡ ያደረገ ፡ ንጉሥን ፡ ትመስላለች ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ የታደሙትንም ፡ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ይጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ባሮቹን ፡ ላከ ፡ ሊመጡም ፡ አልወደዱም ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ደግሞ ፡ ሌላዎችን ፡ ባሪያዎች ፡ ልኮ ፦ የታደሙትን ፦ እንሆ ፥ ድግሴን ፡ አዘጋጀኹ ፥ ኰርማዎቼና ፡ የሰቡት ፡ ከብቶቼ ፡ ታርደዋል ፥ ኹሉም ፡ ተዘጋጅቷል ፤ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ኑ ፡ በሏቸው ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ችል ፡ ብለው ፡ አንዱ ፡ ወደ ፡ ዕርሻው ፥ ሌላውም ፡ ወደ ፡ ንግዱ ፡ ኼደ ፤

ማቴ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ የቀሩትም ፡ ባሮቹን ፡ ይዘው ፡ አንገላቷቸው ፡ ገደሏቸውም ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ንጉሡም ፡ ተቈጣ ፥ ጭፍራዎቹንም ፡ ልኮ ፡ እነዚያን ፡ ገዳዮች ፡ አጠፋ ፤ ከተማቸውንም ፡ አቃጠለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባሮቹን ፦ ሰርጉስ ፡ ተዘጋጅቷል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የታደሙት ፡ የማይገ፡ባቸው ፡ ኾኑ ፤

ማቴ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ እንግዲህ ፡ ወደመንገድ ፡ መተላለፊያ ፡ ኼዳችኹ ፡ ያገኛችኹትን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ጥሩ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ እነዚያም ፡ ባሪያዎች ፡ ወደ ፡ መንገድ ፡ ወጥተው ፡ ያገኙትን ፡ ኹሉ ፡ ክፉዎችንም ፡ በጎዎችንም ፡ ሰበሰቡ ፤ የሰርጉንም ፡ ቤት ፡ ተቀማጮች ፡ ሞሉት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ንጉሡም ፡ የተቀመጡትን ፡ ለማየት ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ የሰርግ ፡ ልብስ ፡ ያለበሰ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አየና ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥

ማቴ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ የሰርግ ፡ ልብስ ፡ ሳትለብስ ፡ እንዴት ፡ ወደዚህ ፡ ገባኽ ፧ አለው ፡ ርሱም ፡ ዝም ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሡ ፡ አገልጋዮቹን ፦ እጁንና ፡ እግሩን ፡ አስራችኹ ፡ በውጭ ፡ ወዳለው ፡ ጨለማ ፡ አውጡት ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ የተጠሩ ፡ ብዙዎች ፥ የተመረጡ ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውና ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ ፈሪሳውያን ፡ ኼዱና ፥ እንዴት ፡ አድርገው ፡ በነገር ፡ እንዲያጠምዱት ፡ ተማከሩ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርታቸውንም ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ላኩበት ፥ እነርሱም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ በእውነትም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ እንድታስተምር ፡ እናውቃለን ፥ ለማንምም ፡ አታደላም ፥ የሰውን ፡ ፊት ፡ አትመለከትምና ፤

ማቴ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይመስልኻል ፧ ንገረን ፡ ለቄሳር ፡ ግብር ፡ መስጠት ፡ ተፈቅዷልን ፡ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ ኢየሱስም ፡ ክፋታቸውን ፡ ዐውቆ ፦ እናንተ ፡ ግብዞች ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈትኑኛላችኹ ፧

ማቴ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ የግብሩን ፡ ብር ፡ አሳዩኝ ፡ አለ ። እነርሱም ፡ ዲናር ፡ አመጡለት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ ይህች ፡ መልክ ፡ ጽሕፈቷስ ፡ የማን ፡ ናት ፧ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ የቄሳር ፡ ነው ፡ አሉት ። በዚያ ፡ ጊዜ ፦ እንኪያስ ፡ የቄሳርን ፡ ለቄሳር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስረክቡ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ ይህንም ፡ ሰምተው ፡ ተደነቁ ፥ ትተውትም ፡ ኼዱ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፦ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡ ፥

ማቴ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ሙሴ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ ሳይወልድ ፡ ሲሞት ፡ ወንድሙ ፡ ሚስቱን ፡ አግብቶ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ ይተካ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ ሰባት ፡ ወንድማማች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ፤ ፊተኛውም ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ሞተ ፥ ዘርም ፡ ስለሌለው ፡ ሚስቱን ፡ ለወንድሙ ፡ ተወለት ፤

ማቴ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ኹለተኛው ፡ ሦስተኛውም ፥ እስከ ፡ ሰባተኛው ፡ ድረስ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ ከኹሉም ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ሞተች ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ኹሉ ፡ አግብተዋታልና ፥ በትንሣኤ ፡ ቀንስ ፥ ከሰባቱ ፡ ለማናቸው ፡ ሚስት ፡ ትኾናለች ፧

ማቴ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ መጻሕፍትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኀይል ፡ አታውቁምና ፡ ትስታላችኹ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ በትንሣኤስ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ በሰማይ ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፡ አያገቡም ፡ አይጋቡምም ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 31-32 ፤ ስለ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ ግን ፦ እኔ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፥ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ የሚል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የተባለውን ፡ አላነበባችኹምን ፧ የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡ አይደለም ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 33 ፤ ሕዝቡም ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 34 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ሰዱቃውያንን ፡ ዝም ፡ እንዳሠኛቸው ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ዐብረው ፡ ተሰበሰቡ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 35 ፤ ከነርሱም ፡ አንድ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂ ፡ ሊፈትነው ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 36 ፤ መምህር ፡ ሆይ ፥ ከሕግ ፡ ማናቸዉቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 37 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ጌታ ፡ አምላክኽን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹም ፡ ነፍስኽም ፡ በፍጹም ፡ ዐሳብኽም ፡ ውደድ ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 38 ፤ ታላቂቱና ፡ ፊተኛዉቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 39 ፤ ኹለተኛዉቱም ፡ ይህችን ፡ ትመስላለች ፥ ርሷም ፦ ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ነፍስኽ ፡ ውደድ ፡ የምትለው ፡ ናት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 40 ፤ በእነዚህ ፡ በኹለቱ ፡ ትእዛዛት ፡ ሕጉም ፡ ኹሉ ፡ ነቢያትም ፡ ተሰቅለዋል ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 41-42 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፥ ኢየሱስ ፦ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ የማንስ ፡ ልጅ ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 43-44 ፤ ርሱም ፦ እንኪያስ ፡ ዳዊት ፦ ጌታ ፡ ጌታዬን ፦ ጠላቶችኽን ፡ የእግርኽ ፡ መረገጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡ ሲል ፡ እንዴት ፡ በመንፈስ ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ ይጠራዋል ፧

ማቴ. ፡ 22 ፡ 45 ፤ ዳዊትስ ፡ ጌታ ፡ ብሎ ፡ ከጠራው ፥ እንዴት ፡ ልጁ ፡ ይኾናል ፧ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 22 ፡ 46 ፤ አንድም ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ ይመልስለት ፡ ዘንድ ፡ የተቻለው ፡ የለም ፥ ከዚያ ፡ ቀንም ፡ ዠምሮ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ማንም ፡ ሊጠይቀው ፡ አልደፈረም ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሕዝቡና ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነገራቸው ፦

ማቴ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ በሙሴ ፡ ወንበር ፡ ተቀምጠዋል ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ያዘዟችኹን ፡ ኹሉ ፡ አድርጉ ፥ ጠብቁትም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እየተናገሩ ፡ አያደርጉትምና ፥ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ አታድርጉ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ ከባድና ፡ አስቸጋሪ ፡ ሸክም ፡ ተብትበው ፡ በሰው ፡ ትከሻ ፡ ይጭናሉ ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ በጣታቸው ፡ ስንኳ ፡ ሊነኩት ፡ አይወዱም ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ ለሰውም ፡ እንዲታዩ ፡ ሥራቸውን ፡ ኹሉ ፡ ያደርጋሉ ፤ ስለዚህ ፥ ዐሽን ፡ ክታባቸውን ፡ ያሰፋሉ ፥ ዘርፉንም ፡ ያስረዝማሉ ፥

ማቴ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ በምሳም ፡ የከበሬታ ፡ ስፍራ ፥ በምኵራብም ፡ የከበሬታ ፡ ወንበር ፥

ማቴ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ በገበያም ፡ ሰላምታና ፦ መምህር ፡ ሆይ ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ ተብለው ፡ እንዲጠሩ ፡ ይወዳሉ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ መምህር ፡ ተብላችኹ ፡ አትጠሩ ፤ መምህራችኹ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እናንተም ፡ ኵላችኹ ፡ ወንድማማች ፡ ናችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ አባታችኹ ፡ አንዱ ፡ ርሱም ፡ የሰማዩ ፡ ነውና ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ማንንም ፦ አባት ፡ ብላችኹ ፡ አትጥሩ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ሊቃችኹ ፡ አንድ ፡ ርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ፦ ሊቃውንት ፡ ተብላችኹ ፡ አትጠሩ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ከእናንተም ፡ የሚበልጠው ፡ አገልጋያችኹ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ራሱን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ዝሑሉ ፡ ይዋረዳል ፥ ራሱንም ፡ የሚያዋርድ ፡ ዝሑሉ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ስለምትዘጉ ፥ ወዮላችኹ ፡ እናንተ ፡ አትገቡም ፡ የሚገቡትንም ፡ እንዳይገቡ ፡ ትከለክላላችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ በጸሎት ፡ ርዝመት ፡ እያመካኛችኹ ፡ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ ስለምትበሉ ፥ ወዮላችኹ ፤ ስለዚህ ፥ የባሰ ፡ ፍርድ ፡ ትቀበላላችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ ልታሳምኑ ፡ በባሕርና ፡ በደረቅ ፡ ስለምትዞሩ ፥ በኾነም ፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ የባሰ ፡ የገሃነም ፡ ልጅ ፡ ስለምታደርጉት ፥ ወዮላችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ እናንተ ፦ ማንም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የሚምል ፡ ምንም ፡ የለበትም ፤ ማንም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወርቅ ፡ የሚምል ፡ ግን ፡ በመሐላው ፡ ይያዛል ፡ የምትሉ ፥ ዕውሮች ፡ መሪዎች ፥ ወዮላችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ እናንተ ፡ ደንቈሮዎችና ፡ ዕውሮች ፥ ማናቸው ፡ ይበልጣል ፧ ወርቁ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ወርቁን ፡ የቀደሰው ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፧

ማቴ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ደግሞ ፦ ማንም ፡ በመሠዊያው ፡ የሚምል ፡ ምንም ፡ የለበትም ፤ ማንም ፡ በላዩ ፡ ባለው ፡ መባ ፡ የሚምል ፡ ግን ፡ በመሐላው ፡ ይያዛል ፡ ትላላችኹ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ እናንተ ፡ ደንቈሮዎችና ፡ ዕውሮች ፥ ማናቸው ፡ ይበልጣል ፧ መባው ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ መባውን ፡ የሚቀድሰው ፡ መሠዊያው ፧

ማቴ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ እንግዲህ ፡ በመሠዊያው ፡ የሚምለው ፡ በርሱና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ዝሑሉ ፡ ይምላል ፤

ማቴ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ የሚምለው ፡ በርሱና ፡ በርሱ ፡ በሚኖረው ፡ ይምላል ፤

ማቴ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ በሰማይም ፡ የሚምለው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዙፋንና ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ በተቀመጠው ፡ ይምላል ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ ከአዝሙድና ፡ ከእንስላል ፡ ከከሙንም ፡ ዓሥራት ፡ ስለምታወጡ ፥ ፍርድንና ፡ ምሕረትን ፡ ታማኝነትንም ፥ በሕግ ፡ ያለውን ፡ ዋና ፡ ነገር ፡ ስለምትተዉ ፥ ወዮላችኹ ፤ ሌላውን ፡ ሳትተዉ ፡ ይህን ፡ ልታደርጉ ፡ ይገባችኹ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ እናንተ ፡ ዕውሮች ፡ መሪዎች ፥ ትንኝን ፡ የምታጠሩ ፡ ግመልንም ፡ የምትውጡ ።

ማቴ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ በውስጡ ፡ ቅሚያና ፡ ሥሥት ፡ ሞልቶ ፡ ሳለ ፡

የጽዋውንና ፡ የወጭቱን ፡ ውጭ ፡ ስለምታጠሩ ፥ ወዮላችኹ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 26 ፤ አንተ ፡ ዕውር ፡ ፈሪሳዊ ፥ ውጭው ፡ ደግሞ ፡ ጥሩ ፡ እንዲኾን ፡ አስቀድመኽ ፡ የጽዋውንና ፡ የወጭቱን ፡ ውስጡን ፡ አጥራ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 27 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ በውጭ ፡ አምረው ፡ የሚታዩ ፡ በውስጡ ፡ ግን ፡ የሙታን ፡ ዐጥንት ፡ ርኵሰትም ፡ ሞሉ ፡ የተሞሉ ፡ በኖራ ፡ የተለሰኑ ፡ መቃብሮችን ፡ ስለምትመስሉ ፥ ወዮላችኹ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 28 ፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በውጭ ፡ ለሰው ፡ እንደ ፡ ጻድቃን ፡ ትታያላችኹ ፥ በውስጣችኹ ፡ ግን ፡ ግብዝነትና ፡ ዐመፀኝነት ፡ ሞልቶባችኋል ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 29 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ የነቢያትን ፡ መቃብር ፡ ስለምትሠሩ ፡ የጻድቃንንም ፡ መቃብር ፡ ስለምታስጌጡና ፦

ማቴ. ፥ 23 ፥ 30 ፤ በአባቶቻችን ፡ ዘመን ፡ ኖረን ፡ በኾነስ ፥ በነቢያት ፡ ደም ፡ ባልተባበርናቸውም ፡ ነበር ፡ ስለምትሉ ፥ ወዮላችኹ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 31 ፤ እንግዲያስ ፡ የነቢያት ፡ ገዳዮች ፡ ልጆች ፡ እንደኾናችኹ ፡ በራሳችኹ ፡ ላይ ፡ ትመሰክራላችኹ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 32 ፤ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ የአባቶቻችኹን ፡ መስፈሪያ ፡ ሙሉ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 33 ፤ እናንተ ፡ እባቦች ፥ የእፍኝት ፡ ልጆች ፥ ከገሃነም ፡ ፍርድ ፡ እንዴት ፡ ታመልጣላችኹ ፧

ማቴ. ፥ 23 ፥ 34 ፤ ስለዚህ ፥ እንሆ ፥ ነቢያትንና ፡ ጥበበኞችን ፡ ጻፊዎችንም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እልካለኹ ፤ ከነርሱም ፡ ትገድላላችኹ ፡ ትሰቅሉማላችኹ ፥ ከነርሱም ፡ በምኵራባችኹ ፡ ትገርፋላችኹ ፡ ከከተማም ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ታሳድዳላችኹ ፤

ማቴ. ፥ 23 ፥ 35 ፤ ከጻድቁ ፡ ከአቤል ፡ ደም ፡ ዠምሮ ፡ በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በመሠዊያው ፡ መካከል ፡ እስከገደላችኹት ፡ እስከበራክዩ ፡ ልጅ ፡ እስከዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ የፈሰሰው ፡ የጻድቅ ፡ ደም ፡ ሞሉ ፡ ይደርስባችኹ ፡ ዘንድ ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 36 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ሞሉ ፡ በዚህ ፡ ትውልድ ፡ ላይ ፡ ይደርሳል ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 37 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሆይ ፥ ነቢያትን ፡ የምትገድል ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ የተላኩትንም ፡ የምትወግር ፥ ዶሮ ፡ ጫጨቶቿን ፡ ከክንፎቿ ፡ በታች ፡ እንደምትሰበስብ ፡ ልጆችሽን ፡ እሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ወደድኹ! ፡ አልወደዳችኹምም ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 38 ፤ እንሆ ፥ ቤታችኹ ፡ የተፈታ ፡ ኾኖ ፡ ይቀርላችኋል ።

ማቴ. ፥ 23 ፥ 39 ፤ እላችኋለኹና ፥ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ እስክትሉ ፡ ድረስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታዩኝም ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 24 ። _____

ማቴ. ፥ 24 ፥ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ ከመቅደስ ፡ ወጥቶ ፡ ኼደ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ የመቅደሱን ፡ ግንቦች ፡ ሊያሳዩት ፡ ቀረቡ ።

ማቴ. ፥ 24 ፥ 2 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ ይህን ፡ ሞሉ ፡ ታያላችኹን ፧ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ በዚህ ፡ አይቀርም ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለብቻቸው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ ንገረን ፥ ይህ ፡ መቼ ፡ ይኾናል ፧ የመምጣትኽና ፡ የዓለም ፡ መጨረሻ ፡ ምልክቱስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉት ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ማንም ፡ እንዳያስታችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ብዙዎች ፦ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ይመጣሉና ፤ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ ጦርንም ፡ የጦርንም ፡ ወሬ ፡ ትሰሙ ፡ ዘንድ ፡ አላችኹ ፤ ይህ ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነውና ፥ ተጠበቁ ፥ አትደንግጡ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መጨረሻው ፡ ገና ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ሕዝብ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መንግሥትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ይነሣልና ፥ ራብም ፡ ቸነፈርም ፡ የምድርም ፡ መናወጥ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ይኾናል ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ የምጥ ፡ ጣር ፡ መዠመሪያ ፡ ናቸው ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ለመከራ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፡ ይገድሏችኹማል ፥ ስለ ፡ ስሜም ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የተጠላችኹ ፡ ትኾናላችኹ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ብዙዎች ፡ ይሰናከላሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጣጣሉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ይጣላሉ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያትም ፡ ይነሣሉ ፡ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ከዐመፃም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ፍቅር ፡ ትቀዘቅዛለች ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የሚጸና ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይድናል ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ለአሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፡ ይህ ፡ የመንግሥት ፡ ወንጌል ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ይሰበካል ፥ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ መጨረሻው ፡ ይመጣል ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ በነቢዩ ፡ በዳንኤል ፡ የተባለውን ፡ የጥፋትን ፡ ርኵሰት ፡ በተቀደሰችው ፡ ስፍራ ፡ ቆሞ ፡ ስታዩ ፥ አንባቢው ፡ ያስተውል ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ ያሉት ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ይሸሹ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ በሰገነትም ፡ ያለ ፡ በቤቱ ፡ ያለውን ፡ ሊወስድ ፡ አይውረድ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ በዕርሻም ፡ ያለ ፡ ልብሱን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመለስ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ በዚያችም ፡ ወራት ፡ ለእርጉዞችና ፡ ለሚያጠቡ ፡ ወዮላቸው ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሸሽታችኹ ፡ በክረምት ፡ ወይም ፡ በሰንበት ፡ እንዳይኾን ፡ ጸልዩ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከዓለም ፡ መዠመሪያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ያልኾነ ፡ እንግዲህም ፡ ከቶ ፡ የማይኾን ፡ ታላቅ ፡ መከራ ፡ ይኾናልና ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ እነዚያ ፡ ቀኖች ፡ ባያጥሩ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ ባልዳነም ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነዚያ ፡ ቀኖች ፡ ስለተመረጡት ፡ ሰዎች ፡ ያጥራሉ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ማንም ፦ እንሆ ፥ ክርስቶስ ፡ ከዚህ ፡ አለ ፡ ወይም ፦ ከዚያ ፡ አለ ፡ ቢላችኹ ፡

አትመኑ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ሐሰተኞች ፡ ክርስቶሶችና ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ይነሣሉና ፥ ቢቻላቸውስ ፡ የተመረጡትን ፡ እንኳ ፡ እስኪያስቱ ፡ ድረስ ፡ ታላላቅ ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ያሳያሉ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ እንሆ ፥ አስቀድሜ ፡ ነገርኋችኹ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፦ እንሆ ፥ በበረሓ ፡ ነው ፡ ቢሏችኹ ፥ አትውጡ ፤ እንሆ ፥ በዕልፍኝ ፡ ነው ፡ ቢሏችኹ ፥ አትመኑ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ መብረቅ ፡ ከምሥራቅ ፡ ወጥቶ ፡ እስከ ፡ ምዕራብ ፡ እንደሚታይ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መምጣት ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናልና ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 28 ፤ በድን ፡ ወዳለበት ፡ በዚያ ፡ አሞራዎች ፡ ይሰበሰባሉ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 29 ፤ ከዚያች ፡ ወራትም ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ፀሓይ ፡ ይጨልማል ፥ ጨረቃም ፡ ብርሃኗን ፡ አትሰጥም ፥ ከዋክብትም ፡ ከሰማይ ፡ ይወድቃሉ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 30 ፤ የሰማያትም ፡ ኀይላት ፡ ይናወጣሉ ። በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ ይታያል ፥ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የምድር ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ፥ የሰው ፡ ልጅንም ፡ በኀይልና ፡ በብዙ ፡ ክብር ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡ ሲመጣ ፡ ያዩታል ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 31 ፤ መላእክቱንም ፡ ከታላቅ ፡ መለከት ፡ ድምፅ ፡ ጋራ ፡ ይልካቸዋል ፥ ከሰማያትም ፡ ዳርቻ ፡ እስከ ፡ ዳርቻው ፡ ከአራቱ ፡ ነፋሳት ፡ ለርሱ ፡ የተመረጡትን ፡ ይሰበስባሉ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 32 ፤ ምሳሌውንም ፡ ከበለስ ፡ ተማሩ ፤ ጫፏ ፡ ሲለሰልስ ፡ ቅጠሏም ፡ ሲያቈጠቍጥ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጋ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ታውቃላችኹ ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 33 ፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ስታዩ ፡ በደጅ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ዕወቁ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 34 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ትውልድ ፡ አያልፍም ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 35 ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፥ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 36 ፤ ስለዚያች ፡ ቀንና ፡ ስለዚያች ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ ከአባት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፡ ልጅም ፡ ቢኾን ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 37 ፤ የኖኅ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ መምጣት ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናልና ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 38 ፤ በዚያች ፡ ወራት ፡ ከጥፋት ፡ ውሃ ፡ በፊት ፥ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ እስከገባበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ሲበሉና ፡ ሲጠጡ ፡ ሲያገቡና ፡ ሲጋቡም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 39 ፤ የጥፋት ፡ ውሃም ፡ መጥቶ ፡ ኹሉን ፡ እስከወሰደ ፡ ድረስ ፡ እንዳላወቁ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ መምጣት ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 40 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ በዕርሻ ፡ ይኾናሉ ፤ አንዱ ፡ ይወሰዳል ፡ አንዱም ፡ ይቀራል ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 41 ፤ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ በወፍጮ ፡ ይፈጫሉ ፤ አንዲቱ ፡ ትወሰዳለች ፡ አንዲቱም ፡ ትቀራለች ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 42 ፤ ጌታችኹ ፡ በምን ፡ ሰዓት ፡ እንዲመጣ ፡ አታውቁምና ፡ እንግዲህ ፡ ንቁ ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 43 ፤ ያን ፡ ግን ፡ ዕወቁ ፤ ባለቤት ፡ ከሌሊቱ ፡ በየትኛው ፡ ክፍል ፡ ሌባ ፡ እንዲመጣ ፡ ቢያውቅ ፡ ኖሮ ፥ በነቃ ፡ ቤቱም ፡ ሊቈፈር ፡ ባልተወም ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 44 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ተዘጋጅታችኹ ፡ ኑሩ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በማታስቡበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣልና ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 45 ፤ እንኪያስ ፡ ምግባቸውን ፡ በጊዜው ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ በቤተ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ የሾመው ፡ ታማኝና ፡ ልባም ፡ ባሪያ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 24 ፡ 46 ፤ ጌታው ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲያደርግ ፡ የሚያገኘው ፡ ያ ፡ ባሪያ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፤

ማቴ. ፡ 24 ፡ 47 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ባለው ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመዋል ።

ማቴ. ፡ 24 ፡ 48 ፤ ያ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፡ ግን ፦ ጌታዬ ፡ እስኪመጣ ፡ ይዘገያል ፡ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ቢያስብ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 49 ፤ ባልንጀራዎቹን ፡ ባሪያዎች ፡ ሊመታ ፡ ቢገሥር ፥ ከሰካሮችም ፡ ጋራ ፡ ቢበላና ፡ ቢጠጣ ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 50 ፤ የዚያ ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ ባልጠበቃት ፡ ቀን ፡ ባላወቃትም ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፥

ማቴ. ፡ 24 ፡ 51 ፤ ከኹለትም ፡ ይሰነጥቀዋል ፥ ዕድሉንም ፡ ከግብዞች ፡ ጋራ ፡ ያደርግበታል ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መብራታቸውን ፡ ይዘው ፡ ሙሽራውን ፡ ሊቀበሉ ፡ የወጡ ፡ ዐሥር ፡ ቈነጕሾችን ፡ ትመስላለች ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ ከነርሱም ፡ ዐምስቱ ፡ ሰነፎች ፡ ዐምስቱም ፡ ልባሞች ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ሰነፎቹ ፡ መብራታቸውን ፡ ይዘው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ዘይት ፡ አልያዙምና ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ልባሞቹ ፡ ግን ፡ ከመብራታቸው ፡ ጋራ ፡ በማሰሯቸው ፡ ዘይት ፡ ያዙ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ ሙሽራውም ፡ በዘገየ ፡ ጊዜ ፡ ሹሉ ፡ እንቅልፍ ፡ እንቅልፍ ፡ አላቸውና ፡ ተኙ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ እኩል ፡ ሌሊትም ፡ ሲኾን ፦ እንሆ ፥ ሙሽራው ፡ ይመጣል ፥ ትቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ ውጡ ፡ የሚል ፡ ውካታ ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያ ፡ ቈነጕሾች ፡ ሹሉ ፡ ተነሡና ፡ መብራታቸውን ፡ አዘጋጁ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ሰነፎቹም ፡ ልባሞቹን ፦ መብራታችን ፡ ሊጠፋብን ፡ ነው ፤ ከዘይታችኹ ፡ ስጡን ፡ አሏቸው ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ልባሞቹ ፡ ግን ፡ መልሰው ፦ ምናልባት ፡ ለእኛና ፡ ለእናንተ ፡ ባይበቃስ ፤ ይልቅስ ፡ ወደሚሸጡት ፡ ኼዳችኹ ፡ ለራሳችኹ ፡ ግዙ ፡ አሏቸው ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ሊገዙም ፡ በኼዱ ፡ ጊዜ ፡ ሙሽራው ፡ መጣ ፥ ተዘጋጅተው ፡ የነበሩትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰርግ ፡ ገቡ ፥ ደጁም ፡ ተዘጋ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ በኋላም ፡ ደግሞ ፡ የቀሩቱ ፡ ቈነጕሾች ፡ መጡና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክፈትልን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ አላውቃችኹም ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ ቀኒቱንና ፡ ሰዓቲቱን ፡ አታውቁምና ፥ እንግዲህ ፡ ንቁ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ የሚኼድ ፡ ሰው ፡ ባሮቹን ፡ ጠርቶ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናልና ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ዐቅሙ ፥ ለአንዱ ፡ ዐምስት ፡ መክሊት ፡ ለአንዱ ፡ ኹለት ፡ ለአንዱም ፡ አንድ ፡ ሰጠና ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ወዲያው ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ ዐምስት ፡ መክሊትም ፡ የተቀበለው ፡ ኼዶ ፡ ነገደበት ፡ ሌላም ፡ ዐምስት ፡ አተረፈ ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ እንዲሁም ፡ ኹለት ፡ የተቀበለው ፡ ሌላ ፡ ኹለት ፡ አተረፈ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ አንድ ፡ የተቀበለው ፡ ግን ፡ ኼዶ ፡ ምድርን ፡ ቈፈረና ፡ የጌታውን ፡ ገንዘብ ፡ ቀበረ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ የእነዚያ ፡ ባሪያዎች ፡ ጌታ ፡ መጣና ፡ ተቈጣጠራቸው ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ ዐምስት ፡ መክሊት ፡ የተቀበለውም ፡ ቀረበና ፡ ሌላ ፡ ዐምስት ፡ መክሊት ፡ አስረክቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዐምስት ፡ መክሊት ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ነበር ፤ እንሆ ፥ ሌላ ፡ ዐምስት ፡ መክሊት ፡ አተረፍኩበት ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ ጌታውም ፦ መልካም ፥ አንተ ፡ በጎ ፡ ታማኝም ፡ ባሪያ ፤ በጥቂቱ ፡ ታምነኻል ፥ በብዙ ፡ እሾምኻለኹ ፤ ወደ ፡ ጌታኽ ፡ ደስታ ፡ ግባ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ ኹለት ፡ መክሊትም ፡ የተቀበለው ፡ ደግሞ ፡ ቀርቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ኹለት ፡ መክሊት ፡ ሰጥተኸኝ ፡ ነበር ፤ እንሆ ፥ ሌላ ፡ ኹለት ፡ መክሊት ፡ አተረፍኩበት ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ ጌታውም ፦ መልካም ፥ አንተ ፡ በጎ ፥ ታማኝም ፡ ባሪያ ፤ በጥቂቱ ፡ ታምነኻል ፥ በብዙ ፡ እሾምኻለኹ ፥ ወደ ፡ ጌታኽ ፡ ደስታ ፡ ግባ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ አንድ ፡ መክሊትም ፡ የተቀበለው ፡ ደግሞ ፡ ቀርቦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ካልዘራኽባት ፡ የምታጭድ ፡ ካልበተንኽባትም ፡ የምትሰበስብ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ መኾንኽን ፡ ዐውቃለኹ ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ ፈራኹም ፡ ኼጄም ፡ መክሊትኽን ፡ በምድር ፡ ቀበርኹት ፤ እንሆ ፥ መክሊትኽ ፡ አለኽ ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ ጌታውም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ክፉና ፡ ሀኬተኛ ፡ ባሪያ ፥ ካልዘራኹባት ፡ እንዳጭድ ፡ ካልበተንኹባትም ፡ እንድሰበስብ ፡ ታውቃለኽን ፧

ማቴ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ ገንዘቤን ፡ ለለዋጮች ፡ ዐደራ ፡ ልትሰጠው ፡ በተገባኽ ፡ ነበር ፥ እኔም ፡ መጥቼ ፡ ያለኝን ፡ ከትርፉ ፡ ጋራ ፡ እወስደው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 28 ፤ ስለዚህ ፥ መክሊቱን ፡ ውሰዱበት ፥ ዐሥር ፡ መክሊትም ፡ ላለው ፡ ስጡት ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 29 ፤ ላለው ፡ ሹሉ ፡ ይሰጠዋልና ፥ ይበዛለትማል ፤ ከሌለው ፡ ግን ፡ ያው ፡ ያለው ፡ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 30 ፤ የማይጠቅመውንም ፡ ባሪያ ፡ በውጭ ፡ ወዳለው ፡ ጨለማ ፡ አውጡት ፤ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 31 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በክብሩ ፡ በሚመጣበት ፡ ጊዜ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ቅዱሳን ፡ መላእክቱ ፡ ሹሉ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በክብሩ ፡ ዙፋን ፡ ይቀመጣል ፤

ማቴ. ፡ 25 ፡ 32 ፤ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ይሰበሰባሉ ፤ እረኛም ፡ በጎቹን ፡ ከፍየሎች ፡ እንደሚለይ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይለያቸዋል ፥

ማቴ. ፡ 25 ፡ 33 ፤ በጎችን ፡ በቀኙ ፡ ፍየሎችንም ፡ በግራው ፡ ያቆማቸዋል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 34 ፤ ንጉሡም ፡ በቀኙ ፡ ያሉትን ፡ እንዲህ ፡ ይላቸዋል ፦ እናንተ ፡ የአባቴ ፡ ቡሩካን ፥ ኑ ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረበት ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ የተዘጋጀላችኹን ፡ መንግሥት ፡ ውረሱ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 35 ፤ ተርቤ ፡ አብልታችኹኛልና ፥ ተጠምቼ ፡ አጠጥታችኹኛልና ፥ እንግዳ ፡ ኾኜ ፡ ተቀብላችኹኛልና ፥ ታርዤ ፡ አልብሳችኹኛልና ፥

ማቴ. ፡ 25 ፡ 36 ፤ ታምሜ ፡ ጠይቃችኹኛልና ፥ ታስሬ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥታችኋልና ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 37 ፤ ጻድቃንም ፡ መልሰው ፡ ይሉታል ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተርበኽ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ አበላንኽስ ፧ ወይስ ፡ ተጠምተኽ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ አጠጣንኽ ፧

ማቴ. ፡ 25 ፡ 38 ፤ እንግዳ ፡ ኾነኽስ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ ተቀበልንኽ ፧ ወይስ ፡ ታርዘኽ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ አለበስንኽ ፧

ማቴ. ፡ 25 ፡ 39 ፤ ወይስ ፡ ታመኽ ፡ ወይስ ፡ ታስረኽ ፡ አይተን ፡ መቼ ፡ ወዳንተ ፡ መጣን ፧

ማቴ. ፡ 25 ፡ 40 ፤ ንጉሡም ፡ መልሶ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከኹሉ ፡ ከሚያንሱ ፡ ከነዚህ ፡ ወንድሞቼ ፡ ለአንዱ ፡ እንኳ ፡ ስላደረጋችኹት ፡ ለእኔ ፡ አደረጋችኹት ፡ ይላቸዋል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 41 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በግራው ፡ ያሉትን ፡ ደግሞ ፡ ይላቸዋል ፦ እናንተ ፡ ርጉማን ፥ ለሰይጣንና ፡ ለመላእክቱ ፡ ወደተዘጋጀ ፡ ወደዘለዓለም ፡ እሳት ፡ ከእኔ ፡ ኺዱ ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 42 ፤ ተርቤ ፡ አላበላችኹኝምና ፥ ተጠምቼ ፡ አላጠጣችኹኝምና ፥ እንግዳ ፡ ኾኜ ፡ አልተቀበላችኹኝምና ፥

ማቴ. ፡ 25 ፡ 43 ፤ ታርዤ ፡ አላለበሳችኹኝምና ፥ ታምሜ ፡ ታስሬም ፡ አልጠየቃችኹኝምና ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 44 ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይመልሱና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተርበኽ ፡ ወይስ ፡ ተጠምተኽ ፡ ወይስ ፡ እንግዳ ፡ ኾነኽ ፡ ወይስ ፡ ታርዘኽ ፡ ወይስ ፡ ታመኽ ፡ ወይስ ፡ ታስረኽ ፡ መቼ ፡ አይተን ፡ አላገለገልንኽም ፧ ይሉታል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 45 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከኹሉ ፡ ከሚያንሱ ፡ ከነዚህ ፡ ለአንዱ ፡ ስላላደረጋችኹት ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ አላደረጋችኹትም ፡ ብሎ ፡ ይመልስላቸዋል ።

ማቴ. ፡ 25 ፡ 46 ፤ እነዚያም ፡ ወደዘለዓለም ፡ ቅጣት ፥ ጻድቃን ፡ ግን ፡ ወደዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ይኼዳሉ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ ኹሉ ፡ በፈጸመ ፡ ጊዜ ፥

ማቴ. ፡ 26 ፡ 2 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ ከኹለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፋሲካ ፡ እንዲኾን ፡ ታውቃላችኹ ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡ ሊሰቀል ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ የሕዝብም ፡ ሽማግሌዎች ፡ ቀያፋ ፡ በሚባለው ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግቢ ፡ ተሰበሰቡ ፥

ማቴ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ኢየሱስንም ፡ በተንኰል ፡ ሊያስይዙት ፡ ሊገድሉትም ፡ ተማከሩ ፤

ማቴ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ሁከት ፡ እንዳይነሣ ፡ በበዓል ፡ አይኹን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ ኢየሱስም ፡ በቢታንያ ፡ በለምጻሙ ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ ሳለ ፥

ማቴ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ አንዲት ፡ ሴት ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ሽቱ ፡ የሞላው ፡ የአልባስጥሮስ ፡ ብልቃጥ ፡ ይዛ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበች ፡ በማእዱም ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰችው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ይህን ፡ አይተው ፡ ተቈጡና ፦ ይህ ፡ ጥፋት ፡ ለምንድር ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ ይህ ፡ በብዙ ፡ ዋጋ ፡ ተሸጦ ፡ ለድኻዎች ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻል ፡ ነበርና ፥ አሉ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠርታልኛለችና ፡ ሴቲቱንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታደክሚታላችኹ ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ ድኻዎች ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉና ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አልኖርም ፤

ማቴ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ርሷ ፡ ይህን ፡ ሽቱ ፡ በሰውነቴ ፡ ላይ ፡ አፍሳ ፡ ለመቃብሬ ፡ አደረገች ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ወንጌል ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ በሚሰበክበት ፡ ርሷ ፡ ያደረገችው ፡ ደግሞ ፡ ለርሷ ፡ መታሰቢያ ፡ እንዲኾን ፡ ይነገራል ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ፡ የሚባለው ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ ወደካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ኼዶ ፦

ማቴ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ ምን ፡ ልትሰጡኝ ፡ ትወዳላችኹ ፡ እኔም ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣችኋለኹ ፧ እነርሱም ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ መዘኑለት ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ ከዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ይሻ ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 17 ፤ በቂጣው ፡ በዓል ፡ በመዠመሪያ ፡ ቀን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀርበው ፦ ፋሲካን ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ወዴት ፡ ልናሰናዳልኽ ፡ ትወዳለኽ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ ወደ ፡ ከተማ ፡ ከአገሌ ፡ ዘንድ ፡ ኼዳችኹ ፦ መምህር ፦ ጊዜዬ ፡ ቀርቧል ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ጋራ ፡ ከአንተ ፡ ዘንድ ፡ ፋሲካን ፡ አደርጋለኹ ፡ ይላል ፡ በሉት ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ኢየሱስ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉ ፡ ፋሲካንም ፡ አሰናዱ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ በማእዱ ፡ ተቀመጠ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ሲበሉም ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ እኔን ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 22 ፤ እጅግም ፡ አዝነው ፡ እያንዳንዱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ እኾንን ፧ ይሉት ፡ ዠመር ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እጁን ፡ በወጭቱ ፡ ያጠለቀ ፥ እኔን ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጥ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ የሰው ፡ ልጅስ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይኼዳል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዐልፎ ፡ ለሚሰጥበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ባልተወለደ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ አሳልፎ ፡ የሚሰጠው ፡ ይሁዳም ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ እኾንን ፧ አለ ፤ አንተ ፡ አልኽ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ ሲበሉም ፡ ኢየሱስ ፡ እንጀራን ፡ አንሥቶ ፡ ባረከ ፡ ቈርሶም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠና ፦ እንካችኹ ፥ ብሉ ፡ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ ጽዋንም ፡ አንሥቶ ፡ አመስግኖም ፡ ሰጣቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ኹላችኹ ፡ ከርሱ ፡ ጠጡ ፤

ማቴ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ ለኀጢአት ፡ ይቅርታ ፡ የሚፈስ ፡ የዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ደሜ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 29 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ በአባቴ ፡ መንግሥት ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ከዚህ ፡ ከወይን ፡ ፍሬ ፡ ዐዲሱን ፡ እስከምጠጣበት ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሬ ፡ አልጠጣውም ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ መዝሙርም ፡ ከዘመሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወጡ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፦ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ኹላችኹ ፡ በእኔ ፡ ትሰናከላላችኹ ፤ እረኛውን ፡ እመታለኹ ፡ የመንጋውም ፡ በጎች ፡ ይበተናሉ ፡ የሚል ፡ ተጽፏልና ፤

ማቴ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ ከተነሣኹ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 33 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ ኹሉም ፡ ባንተ ፡ ቢሰናከሉ ፡ እኔ ፡ ከቶ ፡ አልሰናከልም ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 34 ፤ ኢየሱስ ፦ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ዶሮ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለኽ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 35 ፤ ጴጥሮስ ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ መሞት ፡ እንኳ ፡ የሚያስፈልገኝ ፡ ቢኾን ፥ ከቶ ፡ አልክድኽም ፡ አለው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 36 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ጌቴሴማኒ ፡ ወደምትባል ፡ ስፍራ ፡ መጣ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፦ ወዲያ ፡ ኼጄ ፡ ስጸልይ ፡ ሳለ ፡ በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 37 ፤ ጴጥሮስንም ፡ ኹለቱንም ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጆች ፡ ወስዶ ፡ ሊያዝን ፡ ሊተክዝም ፡ ዠመር ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 38 ፤ ነፍሴ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ዐዘነች ፤ በዚህ ፡ ቈዩ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ትጉ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 39 ፤ ጥቂትም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በፊቱ ፡ ወደቀና ፡ ሲጸልይ ፦ አባቴ ፥ ቢቻልስ ፥ ይህች ፡ ጽዋ ፡ ከእኔ ፡ ትለፍ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ እንደምትወድ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ እንደምወድ ፡ አይኹን ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 40 ፤ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ መጣ ፤ ተኝተውም ፡ አገኛቸውና ፡ ጴጥሮስን ፦ እንዲሁም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ እንኳ ፡ ልትተጉ ፡ አልቻላችኹምን ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 41 ፤ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ትጉና ፡ ጸልዩ ፤ መንፈስስ ፡ ተዘጋጅታለች ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 42 ፤ ደግሞ ፡ ኹለተኛ ፡ ኼዶ ፡ ጸለየና ፦ አባቴ ፥ ይህች ፡ ጽዋ ፡ ሳልጠጣት ፡ ታልፍ ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ፈቃድኽ ፡ ትኹን ፡ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 43 ፤ ደግሞም ፡ መጥቶ ፡ ዐይኖቻቸው ፡ በእንቅልፍ ፡ ከብደው ፡ ነበርና ፥ ተኝተው ፡ አገኛቸው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 44 ፤ ደግሞም ፡ ትቷቸው ፡ ኼደ ፥ ሦስተኛም ፡ ያንኑ ፡ ቃል ፡ ደግሞ ፡ ጸለየ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 45 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጥቶ ፦ እንግዲህስ ፡ ተኙ ፡ ዕረፉም ፤ እንሆ ፥ ሰዓቲቱ ፡ ቀርባለች ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ በኀጢአተኞች ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 46 ፤ ተነሡ ፥ እንኺድ ፤ እንሆ ፥ አሳልፎ ፡ የሚሰጠኝ ፡ ቀርቧል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 47 ፤ ይህንም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፥ እንሆ ፥ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ ይሁዳ ፡ መጣ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሰይፍና ፡ ጐመድ ፡ ይዘው ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ከሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ዘንድ ፡ መጡ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 48 ፤ አሳልፎ ፡ የሚሰጠውም ፦ የምስመው ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ያዙት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 49 ፤ ወዲያውም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረበና ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ ብሎ ፡ ሳመው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 50 ፤ ኢየሱስም ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ ነገር ፡ መጣኽ ፧ አለው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቀረቡ ፡ እጃቸውንም ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ ጭነው ፡ ያዙት ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 51 ፤ እንሆም ፥ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ከነበሩት ፡ አንዱ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘና ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ባሪያ ፡ መቶ ፡ ጉሮሮውን ፡ ቈረጠው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 52 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ሰይፍ ፡ የሚያነሡ ፡ ኹሉ ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፋሉና ፡ ሰይፍኽን ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ መልስ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 53 ፤ ወይስ ፡ አባቴን ፡ እንድለምን ፡ ርሱም ፡ አኹን ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ጭፍራዎች ፡ የሚበዙ ፡ መላእክት ፡ እንዲሰድልኝ ፡ የማይቻል ፡ ይመስልኻልን ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 54 ፤ እንዲህ ፡ ከኾነስ ፦ እንደዚህ ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ፡ የሚሉ ፡ መጻሕፍት ፡ እንዴት ፡ ይፈጸማሉ ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 55 ፤ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ኢየሱስ ፡ ለሕዝቡ ፦ ወንበዴን ፡ እንደምትይዙ ፡ ሰይፍና ፡ ጐመድ ፡ ይዛችኹ ፡ ልትይዙኝ ፡ ወጣችኹን ፧ በመቅደስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያስተማርኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ስቀመጥ ፡ ሳለኹ ፡ አልያዛችኹኝም ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 56 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ የኾነ ፡ የነቢያት ፡ መጻሕፍት ፡ ይፈጸሙ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለ ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹሉ ፡ ትተውት ፡ ሸሹ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 57 ፤ ኢየሱስን ፡ የያዙትም ፡ ጻፊዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደተከማቹበት ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወደ ፡ ቀያፋ ፡ ወሰዱት ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 58 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ እስከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግቢ ፡ ድረስ ፡ ሩቅ ፡ ኾኖ ፡ ተከተለው ፥ የነገሩንም ፡ ፍጻሜ ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ከሎሌዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 59 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ሸንጎውም ፡ ኹሉ ፡ እንዲገድሉት ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ የሐሰት ፡ ምስክር ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፥ አላገኙም ፤

ማቴ. ፡ 26 ፡ 60 ፤ ብዙም ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮች ፡ ምንም ፡ ቢቀርቡ ፡ አላገኙም ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 61 ፤ በኋላም ፡ ኹለት ፡ ቀርበው ፦ ይህ ፡ ሰው ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፍርሼ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ልሠራው ፡ እችላለኹ ፡ ብሏል ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 62 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ተነሥቶ ፦ እነዚህ ፡ ለሚመሰክሩብኽ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡

አትመልስምን ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 63 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለ ። ሊቀ ፡ ካህናቱም ፦ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ የኾንኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንድትነግረን ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ አምልኻለኹ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 64 ፤ ኢየሱስም ፦ አንተ ፡ አልኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀይል ፡ ቀኝ ፡ ሲቀመጥ ፥ በሰማይም ፡ ደመና ፡ ሲመጣ ፡ ታያላችኹ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 65 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ልብሱን ፡ ቀዶ ፦ ተሳድቧል ፡ እንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ምስክሮች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያስፈልገናል ፧ እንሆ ፥ ስድቡን ፡ አኹን ፡ ሰምታችኋል ፤ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ አለ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 66 ፤ እነርሱም ፦ ሞት ፡ ይገ፡ባዋል ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 67 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ተፉበት ፤ ጐሰሙትም ፥ ሌላዎችም ፡ በጥፊ ፡ መትተው ፦ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፥ በጥፊ ፡ የመታኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ማቴ. ፡ 26 ፡ 68 ፤ ትንቢት ፡ ተናገርልን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 69 ፤ ጴጥሮስም ፡ ከቤት ፡ ውጭ ፡ በዐጥሩ ፡ ግቢ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ አንዲት ፡ ገረድም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርባ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከገሊላው ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ነበርኽ ፡ አለችው ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 70 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የምትዩውን ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ በኹሉ ፡ ፊት ፡ ካደ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 71 ፤ ወደ ፡ በሩም ፡ ሲወጣ ፡ ሌላዪቱ ፡ አየችውና ፡ በዚያ ፡ ላሉት ፦ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከናዝሬቱ ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ አለች ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 72 ፤ ዳግመኛም ፡ ሲምል ፦ ሰውየውን ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ካደ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 73 ፤ ጥቂትም ፡ ቈይተው ፡ በዚያ ፡ ቆመው ፡ የነበሩ ፡ ቀርበው ፡ ጴጥሮስን ፦ አነጋገርኽ ፡ ይገልጥኻልና ፥ በእውነት ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ ነኽ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 74 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፦ ሰውየውን ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ሊራገምና ፡ ሊምል ፡ ዠመረ ። ወዲያውም ፡ ዶሮ ፡ ጮኸ ።

ማቴ. ፡ 26 ፡ 75 ፤ ጴጥሮስም ፦ ዶሮ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለኽ ፡ ያለው ፡ የኢየሱስ ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለው ፤ ወደ ፡ ውጭም ፡ ወጥቶ ፡ መራራ ፡ ልቅሶ ፡ አለቀሰ ።

የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ሲነጋም ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ የሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ ሊገድሉት ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ ተማከሩ ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ አስረውም ፡ ወሰዱት ፥ ለገዢው ፡ ለጳንጤናዊው ፡ ጲላጦስም ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ ይሁዳ ፡ እንደ ፡ ተፈረደበት ፡ አይቶ ፡ ተጸጸተ ፥ ሠላሳውንም ፡ ብር ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ለሽማግሌዎች ፡ መልሶ ፦

ማቴ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ንጹሕ ፡ ደም ፡ አሳልፌ ፡ በመስጠቴ ፡ በድያለኹ ፡ አለ ። እነርሱ ፡ ግን ፦ እኛስ ፡ ምን ፡ አግዶን ፧ አንተው ፡ ተጠንቀቅ ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ ብሩንም ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ጥሎ ፡ ኼደና ፡ ታንቆ ፡ ሞተ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ብሩን ፡ አንሥተው ፦ የደም ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፥ ወደ ፡ መባ ፡ ልንጨምረው ፡ አልተፈቀደም ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ተማክረውም ፡ የሸክላ ፡ ሠሪውን ፡ መሬት ፡ ለእንግዳዎች ፡ መቃብር ፡ ገዙበት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ያ ፡ መሬት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የደም ፡ መሬት ፡ ተባለ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በነቢዩ ፡ በኤርምያስ ፡ የተባለው ፦ ከእስራኤል ፡ ልጆችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ የገመቱትን ፥ የተገመተውን ፡ ዋጋ ፡ ሠላሳ ፡ ብር ፡ ያዙ ፥

ማቴ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ ጌታም ፡ እንዳዘዘኝ ፡ ስለሸክላ ፡ ሠሪ ፡ መሬት ፡ ሰጡት ። የሚል ፡ ተፈጸመ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ በገዢው ፡ ፊት ፡ ቆመ ፤ ገዢውም ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤ ኢየሱስም ፦ አንተ ፡ አልኽ ፡ አለው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ሲከሱት ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጲላጦስ ፦ ስንት ፡ ያኽል ፡ እንዲመሰክሩብኽ ፡ አትሰማምን ፧ አለው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ገዢውም ፡ እጅግ ፡ እስኪደነቅ ፡ ድረስ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ስንኳ ፡ አልመለሰለትም ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ በዚያም ፡ በዓል ፡ ሕዝቡ ፡ የወደዱትን ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ ሊፈታላቸው ፡ ለገዢው ፡ ልማድ ፡ ነበረው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በርባን ፡ የሚባል ፡ በጣም ፡ የታወቀ ፡ እስረኛ ፡ ነበራቸው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ እነርሱ ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፡ ጲላጦስ ፦ በርባንን ፡ ወይስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየሱስን ፡ ማንኛውን ፡ ልፈታላችኹ ፡ ትወዳላችኹ ፧ አላቸው ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ በቅንአት ፡ አሳልፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ ሚስቱ ፦ ስለ ፡ ርሱ ፡ ዛሬ ፡ በሕልም ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ ተቀብያለኹና ፥ በዚያ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ አታድርግ ፡ ብላ ፡ ላከችበት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ግን ፡ በርባንን ፡ እንዲለምኑ ፡ ኢየሱስን ፡ ግን ፡ እንዲያጠፉ ፡ ሕዝቡን ፡ አባበሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ገዢውም ፡ መልሶ ፦ ከኹለቱ ፡ ማንኛውን ፡ ልፈታላችኹ ፡ ትወዳላችኹ ፧ አላቸው ፤ እነርሱም ፦ በርባንን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ ጲላጦስ ፦ ክርስቶስ ፡ የተባለውን ፡ ኢየሱስን ፡ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ላድርገው ፧ አላቸው ፤ ኹሉም ፦ ይሰቀል ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ ገዢውም ፦ ምን ፡ ነው ፧ ያደረገው ፡ ክፋት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ ይሰቀል ፡ እያሉ ፡ ጨኸት ፡ አበዙ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ ጲላጦስም ፡ ሁከት ፡ እንዲገርመር ፡ እንጂ ፡ አንዳች ፡ እንዳይረባ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ውሃ ፡ አንሥቶ ፦ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፤ እናንተ ፡ ተጠንቀቁ ፡ ሲል ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ እጁን ፡

ታጠበ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ መልሰው ፦ ደሙ ፡ በእኛና ፡ በልጆቻችን ፡ ላይ ፡ ይኹን ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በርባንን ፡ ፈታላቸው ፥ ኢየሱስን ፡ ግን ፡ ገርፎ ፡ ሊሰቀል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የገዢው ፡ ወታደሮች ፡ ኢየሱስን ፡ ወደገዢው ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ወሰዱት ፡ ጭፍራውንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አከማቹ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 28 ፤ ልብሱንም ፡ ገፈው ፡ ቀይ ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ፥

ማቴ. ፡ 27 ፡ 29 ፤ ከሾኽም ፡ አክሊል ፡ ጐንጉነው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፥ በቀኝ ፡ እጁም ፡ መቃ ፡ አኖሩ ፥ በፊቱም ፡ ተንበርክከው ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ እያሉ ፡ ዘበቱበት ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 30 ፤ ተፉበትም ፡ መቃውንም ፡ ይዘው ፡ ራሱን ፡ መቱት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 31 ፤ ከዘበቱበትም ፡ በኋላ ፡ ቀዩን ፡ ልብስ ፡ ገፈፉት ፥ ልብሱንም ፡ አለበሱት ፡ ሊሰቅሉትም ፡ ወሰዱት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 32 ፤ ሲወጡም ፡ ስምዖን ፡ የተባለው ፡ የቀሬናን ፡ ሰው ፡ አገኙ ፤ ርሱንም ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ አስገደዱት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 33 ፤ ትርጓሜው ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ስፍራ ፡ ወደሚኾን ፥ ጎልጎታ ፡ ወደሚባለው ፡ ስፍራ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜም ፥

ማቴ. ፡ 27 ፡ 34 ፤ በሐሞት ፡ የተደባለቀ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ሊጠጣ ፡ አቀረቡለት ፤ ቀምሶም ፡ ሊጠጣው ፡ አልወደደም ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 35 ፤ ከሰቀሉትም ፡ በኋላ ፡ ልብሱን ፡ ዕጣ ፡ ጥለው ፡ ተካፈሉ ፥

ማቴ. ፡ 27 ፡ 36 ፤ በዚያም ፡ ተቀምጠው ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 37 ፤ ይህ ፡ ኢየሱስ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ የክሱን ፡ ጽሕፈት ፡ ከራሱ ፡ በላይ ፡ አኖሩ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 38 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ወንበዴዎች ፡ አንዱ ፡ በቀኝ ፡ አንዱም ፡ በግራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተሰቀሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 39 ፤ የሚያልፉትም ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ይሰድቡት ፡ ነበርና ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 40 ፤ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የምታፈርስ ፡ በሦስት ፡ ቀንም ፡ የምትሠራው ፥ ራስኽን ፡ አድን ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ ከኾንኽ ፡ ከመስቀል ፡ ውረድ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 41 ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ከጻፊዎችና ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ እየዘበቱበት ፡ እንዲህ ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 42 ፤ ሌላዎችን ፡ አዳነ ፥ ራሱን ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፤ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ከኾነ ፥ አኹን ፡ ከመስቀል ፡ ይውረድ ፡ እኛም ፡ እናምንበታለን ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 43 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ታምኗል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሏልና ፥ ከወደደውስ ፡ አኹን ፡ ያድነው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 44 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የተሰቀሉት ፡ ወንበዴዎች ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ እያሉ ፡ ይነቅፉት ፡ ነበር ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 45 ፤ ከስድስት ፡ ሰዓትም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ጨለማ ፡ ኾነ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 46 ፤ በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ኢየሱስ ፦ ኤሎሄ ፥ ኤሎሄ ፥ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፧ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። ይህም ፦ አምላኬ ፡ አምላኬ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ተውኸኝ ፧ ማለት ፡ ነው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 47 ፤ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ሰምተው ፦ ይህስ ፡ ኤልያስን ፡ ይጠራል ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 48 ፤ ወዲያውም ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ ሮጠ ፤ ሰፍነግም ፡ ይዞ ፡ ሐምጣጤ ፡ ሞላበት ፥ በመቃም ፡ አድርጎ ፡ አጠጣው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 49 ፤ ሌላዎቹ ፡ ግን ፦ ተው ፥ ኤልያስ ፡ መጥቶ ፡ ያድነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንይ ፡ አሉ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 50 ፤ ኢየሱስም ፡ ኹለተኛ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ነፍሱን ፡ ተወ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 51 ፤ እንሆም ፥ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ከኹለት ፡ ተቀደደ ፥ ምድርም ፡ ተናወጠች ፥ አለቶችም ፡ ተሰነጠቁ ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 52 ፤ መቃብሮችም ፡ ተከፈቱ ፥ ተኝተው ፡ ከነበሩትም ፡ ከቅዱሳን ፡ ብዙ ፡ ሥጋዎች ፡ ተነሡ ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 53 ፤ ከትንሣኤውም ፡ በኋላ ፡ ከመቃብሮች ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ ከተማ ፡ ገቡና ፡ ለብዙዎች ፡ ታዩ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 54 ፤ የመቶ ፡ አለቃም ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኢየሱስን ፡ የሚጠብቁ ፡ መናወጡንና ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ አይተው ፦ ይህ ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡ ብለው ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 55 ፤ ኢየሱስን ፡ እያገለገሉ ፡ ከገሊላ ፡ የተከተሉት ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ በሩቅ ፡ ኾነው ፡ ሲመለከቱ ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 56 ፤ ከነርሱም ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምና ፡ የያዕቆብና ፡ የዮሳ ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ የዘብዴዎስም ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 57 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ዮሴፍ ፡ የተባለው ፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ከአርማትያስ ([284]) ፡ መጣ ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ የኢየሱስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፤

ማቴ. ፡ 27 ፡ 58 ፤ ይኸውም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ቀርቦ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ለመነው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 59 ፤ ጲላጦስም ፡ እንዲሰጡት ፡ አዘዘ ። ዮሴፍም ፡ ሥጋውን ፡ ይዞ ፡ በንጹሕ ፡ በፍታ ፡ ከፈነው ፥

ማቴ. ፡ 27 ፡ 60 ፤ ከአለት ፡ በወቀረው ፡ በዐዲሱ ፡ መቃብርም ፡ አኖረው ፥ በመቃብሩም ፡ ደጃፍ ፡ ታላቅ ፡ ድንጋይ ፡ አንከባሎ ፡ ኼደ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 61 ፤ መግደላዊት ፡ ማርያምም ፡ ኹለተኛዪቱም ፡ ማርያም ፡ በመቃብሩ ፡ አንጻር ፡ ተቀምጠው ፡ በዚያ ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 62 ፤ በማግስቱም ፡ ከመዘጋጀት ፡ በኋላ ፡ በሚኾነው ፡ ቀን ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ተሰበሰቡና ፦

ማቴ. ፡ 27 ፡ 63 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ያ ፡ አሳች ፡ በሕይወቱ ፡ ገና ፡ ሳለ ፦ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እነሣለኹ ፡ እንዳለ ፡

284 ዕብ. ፡ ራማህ ።

ትዝ ፡ አለን ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 64 ፤ እንግዲህ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጥተው ፡ በሌሊት ፡ እንዳይሰርቁት ፡ ለሕዝቡም ፦ ከሙታን ፡ ተነሣ ፡ እንዳይሉ ፥ የኋለኛዉቱ ፡ ስሕተት ፡ ከፊተኛዉቱ ፡ ይልቅ ፡ የከፋች ፡ ትኾናለችና ፡ መቃብሩ ፡ እስከ ፡ ሦስተኛ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንዲጠበቅ ፡ እዘዝ ፡ አሉት ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 65 ፤ ጲላጦስም ፦ ጠባቂዎች ፡ አሏችኹ ፤ ኼዳችኹ ፡ እንዳወቃችኹ ፡ አስጠብቁ ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 27 ፡ 66 ፤ እነርሱም ፡ ኼደው ፡ ከጠባቂዎች ፡ ጋራ ፡ ድንጋዩን ፡ ዐትመው ፡ መቃብሩን ፡ አስጠበቁ ።

_____የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ። _____

ማቴ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ በሰንበትም ፡ መጨረሻ ፡ መዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ሲነጋ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምና ፡ ኹለተኛዉቱ ፡ ማርያም ፡ መቃብሩን ፡ ሊያዩ ፡ መጡ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ስለ ፡ ወረደ ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፤ ቀርቦም ፡ ድንጋዩን ፡ አንከባሎ ፡ በላዩ ፡ ተቀመጠ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ መልኩም ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ልብሱም ፡ እንደ ፡ በረዶ ፡ ነጭ ፡ ነበረ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ ጠባቂዎቹም ፡ ርሱን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ ተናወጡ ፡ እንደ ፡ ሞቱም ፡ ኾኑ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ መልአኩም ፡ መልሶ ፡ ሴቶቹን ፡ አላቸው ፦ እናንተስ ፡ አትፍሩ ፥ የተሰቀለውን ፡ ኢየሱስን ፡ እንድትሹ ፡ ዐውቃለኹና ፤

ማቴ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ተነሥቷልና ፥ በዚህ ፡ የለም ፤ የተኛበትን ፡ ስፍራ ፡ ኑና ፡ እዩ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ ፈጥናችኹም ፡ ኺዱና ፦ ከሙታን ፡ ተነሣ ፥ እንሆም ፥ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ይቀድማችኋል ፡ በዚያም ፡ ታዩታላችኹ ፡ ብላችኹ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ንገሯቸው ። እንሆም ፥ ነገርኋችኹ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ በፍርሀትና ፡ በታላቅ ፡ ደስታም ፡ ፈጥነው ፡ ከመቃብር ፡ ኼዱ ፥ ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሊያወሩ ፡ ሮጡ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ እንሆም ፥ ኢየሱስ ፡ አገኛቸውና ፦ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፡ ቀርበው ፡ እግሩን ፡ ይዘው ፡ ሰገዱለት ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፦ አትፍሩ ፤ ኼዳችኹ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እንዲኼዱ ፡ ለወንድሞቼ ፡ ተናገሩ ፥ በዚያም ፡ ያዩኛል ፡ አላቸው ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ሲኼዱም ፡ ኅሉ ፥ እንሆ ፥ ከጠባቂዎቹ ፡ አንዳንድ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መጥተው ፡ የኾነውን ፡ ኹሉ ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎች ፡ አወሩ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ከሽማግሌዎች ፡ ጋራም ፡ ተሰብስበው ፡ ተማከሩና ፡ ለጭፍራዎች ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥተዋቸው ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ እኛ ፡ ተኝተን ፡ ኅለን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በሌሊት ፡ መጥተው ፡ ሰረቁት ፡ በሉ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ ይህም ፡ በገዢው ፡ ዘንድ ፡ የተሰማ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እኛ ፡ እናስረዳዋለን ፡ እናንተም ፡ ያለሥጋት ፡ እንድትኾኑ ፡ እናደርጋለን ፡ አሏቸው ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፡ ገንዘቡን ፡ ተቀብለው ፡ እንዳስተማሯቸው ፡ አደረጉ ። ይህም ፡ ነገር ፡ በአይሁድ ፡

ዘንድ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሲወራ ፡ ይኖራል ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ዐሥራ ፡ አንዱ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ ወዳዘዛቸው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ኼዱ ፥

ማቴ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡ ሰገዱለት ፤ የተጠራጠሩ ፡ ግን ፡ ነበሩ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ ኢየሱስም ፡ ቀረበና ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ፦ ሥልጣን ፡ ኹሉ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ተሰጠኝ ።

ማቴ. ፡ 28 ፡ 19-20 ፤ እንግዲህ ፡ ኺዱና ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ በአብ ፡ በወልድና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ እያጠመቃችኋቸው ፥ ያዘዝኋችኹንም ፡ ኹሉ ፡ እንዲጠብቁ ፡ እያስተማራችኋቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አድርጓቸው ፤ እንሆም ፡ እኔ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ኹልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ማር. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ መዠመሪያ ።

ማር. ፥ 1 ፥ 2-3 ፤ እንሆ ፥ መንገድኽን ፡ የሚጠርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊትኽ ፡ እልካለኹ ፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ አዘጋጁ ፡ ጥርጊያውንም ፡ አቅኑ ፡ እያለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚጮኽ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ ተብሎ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥

ማር. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ዮሐንስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እያጠመቀ ፡ የንስሐንም ፡ ጥምቀት ፡ ለኀጢአት ፡ ስርየት ፡ እየሰበከ ፡ መጣ ።

ማር. ፥ 1 ፥ 5 ፤ የይሁዳም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ የኢየሩሳሌምም ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ እየተናዘዙ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ከርሱ ፡ ይጠመቁ ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ዮሐንስም ፡ የግመል ፡ ጠጕር ፡ ለብሶ ፡ በወገቡ ፡ ጠፍር ፡ ይታጠቅ ፡ አንበጣና ፡ የበረሓ ፡ ማርም ፡ ይበላ ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ተጐንብሼ ፡ የጫማውን ፡ ጠፍር ፡ መፍታት ፡ የማይገባኝ ፡ ከእኔ ፡ የሚበረታ ፡ በኋላዬ ፡ ይመጣል ።

ማር. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እኔ ፡ በውሃ ፡ አጠመቅኋችኹ ፡ ርሱ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያጠምቃችኋል ፡ እያለ ፡ ይሰብክ ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ኢየሱስ ፡ ከገሊላ ፡ ናዝሬት ፡ መጥቶ ፡ ከዮሐንስ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ፡ ተጠመቀ ።

ማር. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ወዲያውም ፡ ከውሃው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ሰማያት ፡ ሲቀደዱ ፡ መንፈስም ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ሲወርድበት ፡ አየና ፦ የምወድኽ ፡ ልጄ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፥

ማር. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማያት ፡ መጣ ።

ማር. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ወዲያውም ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ አወጣው ።

ማር. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በምድረ ፡ በዳም ፡ ከሰይጣን ፡ እየተፈተነ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ ሰነበተ ፡ ከአራዊትም ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥ መላእክቱም ፡ አገለገሉት ።

ማር. ፥ 1 ፥ 14-15 ፤ ዮሐንስም ፡ ዐልፎ ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ወንጌል ፡ እየሰበከና ፦ ዘመኑ ፡ ተፈጸመ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ ቀርባለች ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ በወንጌልም ፡ እመኑ ፡ እያለ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ መጣ ።

ማር. ፥ 1 ፥ 16 ፤ በገሊላ ፡ ባሕርም ፡ አጠገብ ፡ ሲያልፍ ፡ ስምዖንን ፡ ወንድሙንም ፡ እንድርያስን ፡ መረባቸውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሲጥሉ ፡ አየ ፥ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ነበሩና ።

ማር. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፦ በኋላዬ ፡ ኑና ፡ ሰዎችን ፡ አጥማጆች ፡ እንድትኾኑ ፡ አደርጋችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ወዲያውም ፡ መረባቸውን ፡ ትተው ፡ ተከተሉት ።

ማር. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ከዚያም ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ የዘብዴዎስን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ ወንድሙንም ፡ ዮሐንስን ፡ ደግሞ ፡ በታንኳ ፡ ላይ ፡ መረባቸውን ፡ ሲያበጁ ፡ አየ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ወዲያውም ፡ ጠራቸው ፡ አባታቸውንም ፡ ዘብዴዎስን ፡ ከሞያተኞቹ ፡ ጋራ ፡ በታንኳ ፡ ላይ ፡ ትተው ፡ ተከትለውት ፡ ኼዱ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ወደ ፡ ቅፍርናሖምም ፡ ገቡ ፤ ወዲያውም ፡ በሰንበት ፡ ወደ ፡ ምኩራብ ፡ ገብቶ ፡ አስተማረ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 22 ፤ እንደ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጻፊዎች ፡ አይደለምና ፡ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በምኩራባቸው ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ማር. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ርሱም ፦ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለን ፧ ልታጠፋን ፡ መጣኽን ፧ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ዐውቄያለኹ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱሱ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ኢየሱስም ፦ ዝም ፡ በል ፡ ከርሱም ፡ ውጣ ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ርኩሱም ፡ መንፈስ ፡ አንፈራገጠውና ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፡ ከርሱ ፡ ወጣ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ኹሉም ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በሥልጣን ፡ ርኩሳን ፡ መናፍስትን ፡ ያዛል ፤ እነርሱም ፡ ይታዘዙለታልና ፥ ይህ ፡ ዐዲስ ፡ ትምህርት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ እስኪጠያየቁ ፡ ድረስ ፡ አደነቁ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 28 ፤ ዝናውም ፡ ወዲያው ፡ በየስፍራው ፡ ወደገሊላ ፡ ዙሪያ ፡ ኹሉ ፡ ወጣ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ወዲያውም ፡ ከምኩራብ ፡ ወጥቶ ፡ ከያዕቆብና ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ወደስምዖንና ፡ ወደእንድርያስ ፡ ቤት ፡ ገባ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 30 ፤ የስምዖንም ፡ ዐማት ፡ በንዳድ ፡ ታማ ፡ ተኝታ ፡ ነበር ፥ ስለ ፡ ርሷም ፡ ወዲያው ፡ ነገሩት ።

ማር. ፡ 1 ፡ 31 ፤ ቀርቦም ፡ እጇን ፡ ይዞ ፡ አስነሣት ፡ ንዳዱም ፡ ወዲያው ፡ ለቀቃትና ፡ አገለገለቻቸው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 32 ፤ ፀሓይም ፡ ገብቶ ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፥ የታመሙትንና ፡ አጋንንት ፡ ያደረባቸውን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤

ማር. ፡ 1 ፡ 33 ፤ ከተማዩቱም ፡ ኹላ ፡ በደጅ ፡ ተሰብስባ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 1 ፡ 34 ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌም ፡ የታመሙትን ፡ ብዙዎችን ፡ ፈወሰ ፥ ብዙዎችንም ፡ አጋንንት ፡ አወጣ ፥ አጋንንትም ፡ ክርስቶስ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀው ፡ ነበርና ፥ ሊናገሩ ፡ አልፈቀደላቸውም ።

ማር. ፡ 1 ፡ 35 ፤ ማለዳም ፡ ተነሥቶ ፡ ገና ፡ ሌሊት ፡ ሳለ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ ኼዶ ፡ በዚያ ፡ ጸለየ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 36 ፤ ስምዖንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትም ፡ ገሥግሠው ፡ ተከተሉት ፥

ማር. ፡ 1 ፡ 37 ፤ ባገኙትም ፡ ጊዜ ፦ ኹሉ ፡ ይፈልጉኻል ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 1 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ በዚያ ፡ ደግሞ ፡ ልሰብክ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ በቅርብ ፡ ወዳሉ ፡ መንደሮች ፡

እንኪድ ፡ ስለዚህ ፡ ወጥቻለኹና ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 39 ፤ በምኵራባቸውም ፡ እየሰበከ ፡ አጋንንትንም ፡ እያወጣ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ኹሉ ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 40 ፤ ለምጻምም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፡ ተንበረከከና ፦ ብትወድስ ፡ ልታነጻኝ ፡ ትችላለኽ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 41 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐዘነለት ፡ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፦ እወዳለኹ ፤ ንጻ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 42 ፤ በተናገረም ፡ ጊዜ ፡ ለምጹ ፡ ወዲያው ፡ ለቀቀውና ፡ ነጻ ።

ማር. ፡ 1 ፡ 43 ፤ በብርቱም ፡ ተናግሮ ፡ ወዲያው ፡ አወጣው ፤

ማር. ፡ 1 ፡ 44 ፤ ለማንም ፡ አንዳች ፡ እንዳትናገር ፡ ተጠንቀቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኼደኽ ፡ ራስኽን ፡ ለካህን ፡ አሳይ ፡ ለእነርሱም ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፡ ስለ ፡ መንጻትኽ ፡ ሙሴ ፡ ያዘዘውን ፡ አቅርብ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 1 ፡ 45 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሲወጣ ፡ ብዙ ፡ ሊሰብክና ፡ ነገሩን ፡ ሊያወራ ፡ ዠመረ ፥ ስለዚህም ፡ ኢየሱስ ፡ ተገልጦ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ መግባት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተሳነው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በውጭ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ ከየስፍራውም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ማር. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ ደግሞ ፡ ገብቶ ፡ በቤት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተሰማ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በደጅ ፡ ያለው ፡ ስፍራም ፡ እስኪጠባቸው ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ፤ ቃሉንም ፡ ይነግራቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 2 ፡ 3 ፤ አራት ፡ ሰዎችም ፡ የተሸከሙትን ፡ ሽባ ፡ አመጡለት ።

ማር. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ስለሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ማቅረብ ፡ ቢያቅታቸው ፡ ርሱ ፡ ያለበትን ፡ የቤቱን ፡ ጣራ ፡ አነሡ ፥ ነድለውም ፡ ሽባው ፡ የተኛበትን ፡ ዐልጋ ፡ አወረዱ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ እምነታቸውን ፡ አይቶ ፡ ሽባውን ፦ አንተ ፡ ልጅ ፥ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ከጻፊዎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ በልባቸውም ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ስድብ ፡ ይናገራል ፧

ማር. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ኀጢአት ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧ ብለው ፡ ዐሰቡ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ በልባቸው ፡ እንዲህ ፡ እንዳሰቡ ፡ በመንፈስ ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በልባችኹ ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታስባላችኹ ፧

ማር. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ሽባውን ፦ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ ከማለት ፡ ወይስ ፦ ተነሣ ፡ ዐልጋኽንም ፡ ተሸከምና ፡ ኺድ ፡ ከማለት ፡ ማናቸው ፡ ይቀላል ፧

ማር. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለሰው ፡ ልጅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንድታውቁ ፤

ማር. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሽባውን ፦ አንተን ፡ እልኻለኹ ፥ ተነሣ ፥ ዐልጋኽን ፡ ተሸከምና ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ተነሥቶም ፡ ወዲያው ፡ ዐልጋውን ፡ ተሸክሞ ፡ በዥሉ ፡ ፊት ፡ ወጣ ፥ ስለዚህም ፡ ሰዎች ፡ ዥሉ ፡ ተገረሙና ፦ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ከቶ ፡ አላየንም ፡ ብለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ደግሞም ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ወጣ ፤ ሕዝቡም ፡ ዥሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡና ፡ አስተማራቸው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ሲያልፍም ፡ በመቅረጫው ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረውን ፡ የእልፍዮስን ፡ ልጅ ፡ ሌዊን ፡ አየና ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ። ተነሥቶም ፡ ተከተለው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 15 ፤ በቤቱም ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ ብዙ ፡ ቀራጮችና ፡ ኀጢአተኞች ፡ ከኢየሱስና ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጡ ፤ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ይከተሉትም ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያንም ፥ ከቀራጮችና ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ ሲበላ ፡ አይተው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ ከቀራጮችና ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፦ ሕመምተኞች ፡ እንጂ ፡ ብርቱዎች ፡ ባለመድኀኒት ፡ አያስፈልጋቸውም ፤ ኀጢአተኞችን ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣኹም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 18 ፤ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ይጦሙ ፡ ነበር ። መጥተውም ፦ የዮሐንስና ፡ የፈሪሳውያን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ የሚጦሙት ፡ የአንተ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ የማይጦሙት ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ኢየሱስም ፡ አላቸው ፦ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ ሚዜዎች ፡ ሊጦሙ ፡ ይችላሉን ፧ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ ሊጦሙ ፡ አይችሉም ።

ማር. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ የሚወሰድበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፥ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ይጦማሉ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 21 ፤ በአረጀ ፡ ልብስ ፡ ዐዲስ ፡ ዕራፊ ፡ የሚጥፍ ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፥ ዐዲሱ ፡ መጣፊያ ፡ አሮጌውን ፡ ይቦጭቀዋል ፥ መቀደዱም ፡ የባሰ ፡ ይኾናል ።

ማር. ፡ 2 ፡ 22 ፤ በአረጀ ፡ አቀኑማዳም ፡ ዐዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፥ የወይን ፡ ጠጁ ፡ አቀኑማዳውን ፡ ያፈነዳል ፡ የወይኑም ፡ ጠጅ ፡ ይፈሳል ፡ አቀኑማዳውም ፡ ይጠፋል ፡ ዐዲሱን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ግን ፡ በዐዲስ ፡ አቀኑማዳ ፡ ያኖራሉ ።

ማር. ፡ 2 ፡ 23 ፤ በሰንበትም ፡ በዕርሻ ፡ መካከል ፡ ሲያልፍ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እየኼዱ ፡ እሸት ፡ ይቀጥፉ ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ፈሪሳውያንም ፦ እንሆ ፥ በሰንበት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ ዳዊት ፡ ባስፈለገውና ፡ በተራበ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ ዐብረውት ፡ ከነበሩት ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፥

ማር. ፡ 2 ፡ 26 ፤ አብያተር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፥ ከካህናት ፡ በቀር ፡ መብላት ፡ ያልተፈቀደውን ፡ የመሥዋዕትን ፡ እንጀራ ፡ እንደ ፡ በላ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ከቶ ፡ አላነበባችኹምን ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 2 ፡ 27 ፤ ደግሞ ፦ ሰንበት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ተፈጥሯል ፡ እንጂ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሰንበት ፡ አልተፈጠረም ፤

ማር. ፡ 2 ፡ 28 ፤ እንዲሁም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ለሰንበት ፡ እንኳ ፡ ጌታዋ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ማር. ፥ 3 ፥ 1 ፤ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ምኩራብ ፡ ገባ ፥ በዚያም ፡ እጁ ፡ የሰለለች ፡ ሰው ፡ ነበር ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 2 ፤ ሊከሱትም ፥ በሰንበት ፡ ይፈውሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይጠባበቁት ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 3 ፥ 3 ፤ እጁ ፡ የሰለለችውንም ፡ ሰው ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ መካከል ፡ ና ፡ አለው ።

ማር. ፥ 3 ፥ 4 ፤ በሰንበት ፡ በጎ ፡ ማድረግ ፡ ተፈቅዷልን ፧ ወይስ ፡ ክፉ ፧ ነፍስ ፡ ማዳን ፡ ወይስ ፡ መግደል ፧ አላቸው ፤ እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ።

ማር. ፥ 3 ፥ 5 ፤ ስለልባቸውም ፡ ድንዛዜ ፡ ዐዝኖ ፡ ዙሪያውን ፡ እየተመለከተ ፡ በቍጣ ፡ አያቸው ፥ ሰውየውንም ፦ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ።

ማር. ፥ 3 ፥ 6 ፤ ዘረጋትም ፥ እጁም ፡ ዳነች ። ፈሪሳውያንም ፡ ወጥተው ፡ ወዲያው ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዲያጠፉት ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ተማከሩበት ።

ማር. ፥ 3 ፥ 7 ፤ ኢየሱስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፤ ከገሊላ ፡ የመጡም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 8 ፤ እንዴት ፡ ትልቅ ፡ ነገርም ፡ እንዳደረገው ፡ ሰምተው ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከይሁዳ ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ከኤዶምያስም ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ማዶም ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ምድርም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ።

ማር. ፥ 3 ፥ 9 ፤ ሰዎቹም ፡ እንዳያጋፉት ፡ ታንኳን ፡ ያቈዩለት ፡ ዘንድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አዘዛቸው ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 10 ፤ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አድኖ ፡ ነበርና ፥ ስለዚህም ፡ ሥቃይ ፡ ያለባቸው ፡ ኹሉ ፡ እንዲዳስሱት ፡ ይወድቁበት ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 3 ፥ 11 ፤ ርኩሳን ፡ መናፍስትም ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ በፊቱ ፡ ተደፍተው ፦ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ማር. ፥ 3 ፥ 12 ፤ እንዳይገልጡትም ፡ በጣም ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፥ 3 ፥ 13 ፤ ወደ ፡ ተራራም ፡ ወጣ ፥ ራሱም ፡ የወደዳቸውን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠራ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ኼዱ ።

ማር. ፥ 3 ፥ 14 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እንዲኖሩና ፡ ለመስበክ ፡ እንዲልካቸው ፥

ማር. ፥ 3 ፥ 15 ፤ ድውዮችንም ፡ ሊፈውሱ ፡ አጋንንትንም ፡ ሊያወጡ ፡ ሥልጣን ፡ ይኾንላቸው ፡ ዘንድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አደረገ ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 16 ፤ ስምዖንንም ፡ ጴጥሮስ ፡ ብሎ ፡ ሰየመው ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 17 ፤ የዘብዴዎስንም ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብን ፡ የያዕቆብንም ፡ ወንድም ፡ ዮሐንስን ፡ ቦአኔርጌስ ፡ ብሎ ፡ ሰየማቸው ፥ የነጐድጓድ ፡ ልጆች ፡ ማለት ፡ ነው ፤

ማር. ፥ 3 ፥ 18 ፤ እንድርያስንም ፡ ፊልጶስንም ፡ በርተሎሜዉስንም ፡ ማቴዎስንም ፡ ቶማስንም ፡ የእልፍዮስን ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብንም ፡ ታዴዎስንም ፡ ቀነናዊውንም ፡ ስምዖንን ፥

ማር. ፥ 3 ፥ 19 ፤ አሳልፎ ፡ የሰጠውንም ፡ የአስቆሮቱን ፡ ይሁዳን ።

ማር. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ መጡ ፤ እንጀራም ፡ መብላት ፡ ስንኳ ፡ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ።

ማር. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ዘመዶቹም ፡ ሰምተው ፦ አበደ ፡ ብለዋልና ፥ ሊይዙት ፡ ወጡ ።

ማር. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ከኢየሩሳሌም ፡ የወረዱ ፡ ጻፊዎችም ፦ ብዔል ፡ ዜቡል ፡ አለበት ፤ ደግሞ ፦ በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ አጋንንትን ፡ ያወጣል ፡ ብለው ፡ ተናገሩ ።

ማር. ፡ 3 ፡ 23 ፤ እነርሱንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፡ በምሳሌ ፡ አላቸው ፦ ሰይጣን ፡ ሰይጣንን ፡ ሊያወጣው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

ማር. ፡ 3 ፡ 24 ፤ መንግሥትም ፡ ርስ ፡ በርሷ ፡ ከተለያየች ፡ ያች ፡ መንግሥት ፡ ልትቆም ፡ አትችልም ፤

ማር. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ቤትም ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከተለያየ ፡ ያ ፡ ቤት ፡ ሊቆም ፡ አይችልም ።

ማር. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ሰይጣንም ፡ ራሱን ፡ ተቃውሞ ፡ ከተለያየ ፥ መጨረሻ ፡ ይኾንበታል ፡ እንጂ ፡ ሊቆም ፡ አይችልም ።

ማር. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድሞ ፡ ኀይለኛውን ፡ ሳያስር ፡ ወደኀይለኛው ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ዕቃውን ፡ ሊበዘብዝ ፡ የሚችል ፡ የለም ፥ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቤቱን ፡ ይበዘብዛል ።

ማር. ፡ 3 ፡ 28 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ለሰው ፡ ልጆች ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ የሚሳደቡትም ፡ ስድብ ፡ ኹሉ ፡ ይሰረይላቸዋል ፤

ማር. ፡ 3 ፡ 29 ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ የሚሳደብ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ የዘለዓለም ፡ ኀጢአት ፡ ዕዳ ፡ ይኾንበታል ፡ እንጂ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይሰረይለትም ።

ማር. ፡ 3 ፡ 30 ፤ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ አለበት ፡ ይሉ ፡ ነበርና ።

ማር. ፡ 3 ፡ 31 ፤ እናቱና ፡ ወንድሞቹም ፡ መጡ ፥ በውጭም ፡ ቆመው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ልከው ፡ አስጠሩት ።

ማር. ፡ 3 ፡ 32 ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በዙሪያው ፡ ተቀምጠው ፡ ነበሩና ፦ እንሆ ፥ እናትኽ ፡ ወንድሞችኽም ፡ በውጭ ፡ ቆመው ፡ ይፈልጉኻል ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 3 ፡ 33 ፤ መልሶም ፦ እናቴ ፡ ማን ፡ ናት ፧ ወንድሞቼስ ፡ እነ ፡ ማን ፡ ናቸው ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 3 ፡ 34 ፤ በዙሪያው ፡ ተቀምጠው ፡ ወደነበሩትም ፡ ተመለከተና ፦ እንሆ ፥ እናቴ ፡ ወንድሞቼም ።

ማር. ፡ 3 ፡ 35 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፥ ርሱ ፡ ወንድሜ ፡ ነው ፡ እኅቴም ፡ እናቴም ፡ አለ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ማር. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ደግሞም ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ሊያስተምር ፡ ዠመረ ። እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ርሱ ፡ በታንኳ ፡ ገብቶ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ተቀመጠ ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነበሩ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 2 ፤ በምሳሌም ፡ ብዙ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፥ በትምህርቱም ፡ አላቸው ፦ ስሙ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 3-4 ፤ እንሆ ፥ ዘሪ ፡ ሊዘራ ፡ ወጣ ። ሲዘራም ፡ አንዳንዱ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ወደቀና ፡ ወፎች ፡ መጥተው ፡ በሉት ።

ማር. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ሌላውም ፡ ብዙ ፡ መሬት ፡ በሌለበት ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ ጥልቅ ፡ መሬት ፡ ስላልነበረው ፡ ወዲያው ፡ በቀለ ፤

ማር. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ፀሓይም ፡ ሲወጣ ፡ ጠወለገ ፥ ሥርም ፡ ስላልነበረው ፡ ደረቀ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ሌላውም ፡ በሾኽ ፡ መካከል ፡ ወደቀ ፥ ሾኽም ፡ ወጣና ፡ ዐነቀው ፥ ፍሬም ፡ አልሰጠም ።

ማር. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ሌላውም ፡ በመልካም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፡ ወጥቶ ፡ አድጎ ፡ ፍሬ ፡ ሰጠ ፥ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ አንዱም ፡ ስድሳ ፡ አንዱም ፡ መቶ ፡ አፈራ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 9 ፤ የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ብቻውንም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ በዙሪያው ፡ የነበሩት ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ምሳሌው ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 4 ፡ 11-12 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ለእናንተ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ ተሰጥቷችኋል ፤ በውጭ ፡ ላሉት ፡ ግን ፥ አይተው ፡ እንዲያዩ ፡ እንዳይመለከቱም ፥ ሰምተውም ፡ እንዲሰሙ ፡ እንዳያስተውሉም ፥ እንዳይመለሱ ፡ ኀጢአታቸውም ፡ እንዳይሰረይላቸው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በምሳሌ ፡ ይኾንባቸዋል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 13 ፤ አላቸውም ፦ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ አታውቁምን ፧ እንዴትስ ፡ ምሳሌዎቹን ፡ ኹሉ ፡ ታውቃላችኹ ፧

ማር. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ዘሪው ፡ ቃሉን ፡ ይዘራል ። ቃልም ፡ በተዘራበት ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ የኾኑት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 15 ፤ በሰሙት ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ ወዲያው ፡ መጥቶ ፡ በልባቸው ፡ የተዘራውን ፡ ቃል ፡ ይወስዳል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 16 ፤ እንዲሁም ፡ በጭንጫ ፡ ላይ ፡ የተዘሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥ ቃሉንም ፡ ሰምተው ፡ ወዲያው ፡ በደስታ ፡ ይቀበሉታል ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ለጊዜውም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእነርሱ ፡ ሥር ፡ የላቸውም ፥ ኋላም ፡ በቃሉ ፡ ምክንያት ፡ መከራ ፡ ወይም ፡ ስደት ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ወዲያው ፡ ይሰናከላሉ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 18 ፤ በሾኽም ፡ የተዘሩት ፡ ሌላዎች ፡ ናቸው ፥ ቃሉን ፡ የሰሙት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 19 ፤ የዚህም ፡ ዓለም ፡ ዐሳብና ፡ የባለጠግነት ፡ ማታለል ፡ የሌላውም ፡ ነገር ፡ ምኞት ፡ ገብተው ፡ ቃሉን ፡ ያንቃሉ ፥ የማያፈራም ፡ ይኾናል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 20 ፤ በመልካምም ፡ መሬት ፡ የተዘሩት ፡ ቃሉን ፡ ሰምተው ፡ የሚቀበሉት ፡ አንዱም ፡ ሠላሳ ፡ አንዱም ፡ ስድሳ ፡ አንዱም ፡ መቶ ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈሩት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ማር. ፡ 4 ፡ 21 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ መብራትን ፡ ከእንቅብ ፡ ወይስ ፡ ከዐልጋ ፡ በታች ፡ ሊያኖሩት ፡ ያመጡታልን ፧ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ ሊያኖሩት ፡ አይደለምን ፧

ማር. ፡ 4 ፡ 22 ፤ እንዲገለጥ ፡ ባይኾን ፡ የተሰወረ ፡ የለምና ፤ ወደ ፡ ግልጥ ፡ እንዲመጣ ፡ እንጂ ፡ የተሸሸገ ፡ የለም ።

ማር. ፡ 4 ፡ 23 ፤ የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ይስማ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 24 ፤ አላቸውም ፦ ምን ፡ እንድትሰሙ ፡ ተጠበቁ ። በምትሰፍሩበት ፡ መስፈሪያ ፡ ይሰፈርላችኋል ፡ ለእናንተም ፡ ይጨመርላችኋል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ላለው ፡ ይሰጠዋልና ፤ ከሌለውም ፡ ያው ፡ ያለው ፡ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ በምድር ፡ ዘርን ፡ እንደሚዘራ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደዚህ ፡ ናት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ይተኛልም ፡ ይነሣልም ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ እንዴት ፡ እንደሚኾን ፡ ሳያውቅ ፡ ዘሩ ፡ ይበቅላል ፡ ያድግማል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 28 ፤ ምድሪቱም ፡ ዐውቃ ፡ በመዠመሪያ ፡ ቡቃያ ፡ ኋላም ፡ ዛላ ፡ ኋላም ፡ በዛላው ፡ ፍጹም ፡ ሰብል ፡ ታፈራለች ።

ማር. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ፍሬ ፡ ግን ፡ ሲበስል ፡ መከር ፡ ደርሷልና ፥ ወዲያው ፡ ማጭድ ፡ ይልካል ።

ማር. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በምን ፡ እናስመስላታለን ፧ ወይስ ፡ በምን ፡ ምሳሌ ፡ እንመስላታለን ፧

ማር. ፡ 4 ፡ 31 ፤ እንደ ፡ ሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ናት ፥ ርሷም ፡ በምድር ፡ በተዘራች ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ካለ ፡ ዘር ፡ ሹሉ ፡ ታንሳለች ፤ በተዘራችም ፡ ጊዜ ፡ ትወጣለች ፡ ከአትክልትም ፡ ሹሉ ፡ የምትበልጥ ፡ ትኾናለች ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 32 ፤ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ በጥላዋ ፡ ሊሰፍሩ ፡ እስኪችሉ ፡ ታላላቅ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ታደርጋለች ።

ማር. ፡ 4 ፡ 33 ፤ መስማትም ፡ በሚችሉበት ፡ መጠን ፡ እነዚህን ፡ በሚመስል ፡ በብዙ ፡ ምሳሌ ፡ ቃሉን ፡ ይነግራቸው ፡ ነበር ፤ ያለምሳሌ ፡ ግን ፡ አልነገራቸውም ፥

ማር. ፡ 4 ፡ 34 ፤ ለብቻቸውም ፡ ሲኾኑ ፡ ነገሩን ፡ ሹሉ ፡ ለገዛ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ይፈታላቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 4 ፡ 35 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፦ ወደ ፡ ማዶ ፡ እንሻገር ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 4 ፡ 36 ፤ ሕዝቡንም ፡ ትተው ፡ በታንኳ ፡ እንዲያው ፡ ወሰዱት ፥ ሌላዎች ፡ ታንኳዎችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 37 ፤ ብርቱ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ተነሣና ፡ ውሃ ፡ በታንኳዩቱ ፡ እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ ማዕበሉ ፡ በታንኳዩቱ ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 4 ፡ 38 ፤ ርሱም ፡ በስተኋላዋ ፡ ትራስ ፡ ተንተርሶ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፤ አንቅተውም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ስንጠፋ ፡ አይገድኽምን ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 4 ፡ 39 ፤ ነቅቶም ፡ ነፋሱን ፡ ገሠጸው ፡ ባሕሩንም ፦ ዝም ፡ በል ፥ ጸጥ ፡ በል ፡ አለው ። ነፋሱም ፡ ተወ ፥ ታላቅ ፡ ጸጥታም ፡ ኾነ ።

ማር. ፡ 4 ፡ 40 ፤ እንዲህ ፡ የምትፈሩ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧ እንዴትስ ፡ እምነት ፡ የላችኹም ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 4 ፡ 41 ፤ እጅግም ፡ ፈሩና ፦ እንግዲህ ፡ ነፋስም ፡ ባሕርም ፡ የሚታዘዙለት ፡ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ተባባሉ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ማር. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ወደባሕር ፡ ማዶም ፡ ወደጌርጌሴኖን ፡ አገር ፡ መጡ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ከታንኳዩቱም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፥ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ የያዘው ፡ ሰው ፡ ከመቃብር ፡ ወጥቶ ፡ ወዲያው ፡ ተገናኘው ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በመቃብር ፡ ይኖር ፡ ነበር ፥ በሰንሰለትም ፡ ስንኳ ፡ ማንም ፡ ሊያስረው ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አይችልም ፡ ነበር ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በእግር ፡ ብረትና ፡ በሰንሰለት ፡ ይታሰር ፡ ነበርና ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሰንሰለቱን ፡ ይበጣጥስ ፡ እግር ፡ ብረቱንም ፡ ይሰባብር ፡ ነበር ፥ ሊያሸንፈውም ፡ የሚችል ፡ አልነበረም ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ዥልጊዜም ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በመቃብርና ፡ በተራራ ፡ ኾኖ ፡ ይጮኽ ፡ ነበር ፡ ሰውነቱንም ፡ በድንጋይ ፡ ይቧጭር ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ኢየሱስንም ፡ ከሩቅ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሮጦ ፡ ሰገደለት ፥

ማር. ፡ 5 ፡ 7 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየጮኸ ፦ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ እንዳታሠቃየኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምልኻለኹ ፡ አለ ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 8 ፤ አንተ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፥ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ውጣ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፦

ማር. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ስምኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ፦ ብዙዎች ፡ ነንና ፡ ስሜ ፡ ሌጌዎን ([285]) ፡ ነው ፡ አለው ፥

ማር. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ከአገርም ፡ ውጭ ፡ እንዳይሰዳቸው ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ በተራራ ፡ ጥግ ፡ ብዙ ፡ የዕሪያ ፡ መንጋ ፡ ይሰማራ ፡ ነበርና ፦

ማር. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ዕሪያዎቹ ፡ እንድንገባ ፡ ስደደን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ።

ማር. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ ፈቀደላቸው ። ርኩሳን ፡ መናፍስቱም ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ዕሪያዎቹ ፡ ገቡ ፥ ኹለት ፡ ሺሕም ፡ የሚያኽል ፡ መንጋ ፡ ከአፋፉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተጣደፉና ፡ በባሕር ፡ ሰጠሙ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 14 ፤ እረኞቹም ፡ ሸሽተው ፡ በከተማውና ፡ በአገሩ ፡ አወሩ ፤ ነገሩም ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለማየት ፡ መጡ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ወደ ፡ ኢየሱስም ፡ መጡ ፥ አጋንንትም ፡ ያደሩበትን ፡ ሌጌዎንም ፡ የነበረበትን ፡ ሰው ፡ ተቀምጦ ፡ ለብሶም ፡ ልቡም ፡ ተመልሶ ፡ አዩና ፡ ፈሩ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ያዩት ፡ ሰዎችም ፡ አጋንንት ፡ ላደሩበት ፡ ሰው ፡ የኾነውንና ፡ ስለ ፡ ዕሪያዎቹ ፡ ተረኩላቸው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ከአገራቸውም ፡ እንዲኼድላቸው ፡ ይለምኑት ፡ ገመር ።

ማር. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ ታንኳዩቱም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ዐድረውበት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዲኖር ፡ ለመነው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ኢየሱስም ፡ አልፈቀደለትም ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ በቤተ ፡ ሰዎችኽ ፡ ዘንድ ፡ ኼደኽ ፡ ጌታ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገልኽ ፡ እንዴትስ ፡ እንደ ፡ ማረኽ ፡ አውራላቸው ፡ አለው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ኼዶም ፡ ኢየሱስ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገለት ፡ ዐሥር ፡ ከተማ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ ይሰብክ ፡ ገመር ፤ ኹሉም ፡ ተደነቁ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ በታንኳዩቱ ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ ከተሻገረ ፡ በኋላ ፥ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፥ በባሕርም ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

---

285 ሮማ. ፡ ሌጌዎን ፡ (ሰራዊት ፥ ጭፍራ ፤ 6000 ፡ ጭፍራ ፡ ከናለቃው ፡ አንድ ፡ ሌጌዎን ፡ ይባላል ። ኪ.ወ.ክ. ፥ ገ.558) ።

ማር. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ኢያኢሮስ ፡ የተባለ ፡ ከምኩራብ ፡ አለቃዎች ፡ አንዱ ፡ መጣ ፤ ባየውም ፡ ጊዜ ፡ በእግሩ ፡ ላይ ፡ ወደቀና ፦

ማር. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ታናሺቱ ፡ ልጄ ፡ ልትሞት ፡ ቀርባለችና ፡ እንድትድንና ፡ በሕይወት ፡ እንድትኖር ፡ መጥተኽ ፡ እጅኽን ፡ ጫንባት ፡ ብሎ ፡ አጥብቆ ፡ ለመነው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኼደ ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ተከተሉት ፡ አጋፉትም ።

ማር. ፡ 5 ፡ 25 ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመትም ፡ ገምሮ ፡ ደም ፡ የሚፈሳት ፡ ሴት ፡ ነበረች ፥

ማር. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ከብዙ ፡ ባለመድኀኒቶችም ፡ ብዙ ፡ ተሠቃየች ፤ ገንዘቧንም ፡ ኹሉ ፡ ከስራ ፡ ባሰባት ፡ እንጂ ፡ ምንም ፡ አልተጠቀመችም ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 27 ፤ የኢየሱስንም ፡ ወሬ ፡ ሰምታ ፡ በስተኋላው ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ መጥታ ፡ ልብሱን ፡ ዳሰሰች ።

ማር. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ልብሱን ፡ ብቻ ፡ የዳሰስኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እድናለኹ ፡ ብላለችና ።

ማር. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ወዲያውም ፡ የደሟ ፡ ምንጭ ፡ ደረቀ ፡ ከሥቃይዋም ፡ እንደ ፡ ዳነች ፡ በሰውነቷ ፡ ዐወቀች ።

ማር. ፡ 5 ፡ 30 ፤ ወዲያውም ፡ ኢየሱስ ፡ ከርሱ ፡ ኀይል ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ዐውቆ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፦ ልብሴን ፡ የዳሰሰ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ ሕዝቡ ፡ ሲያጋፉኽ ፡ እያየኽ ፦ ማን ፡ ዳሰሰኝ ፡ ትላለኽን ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 5 ፡ 32 ፤ ይህንም ፡ ያደረገችውን ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ይመለከት ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 5 ፡ 33 ፤ ሴቲቱ ፡ ግን ፡ የተደረገላትን ፡ ስላወቀች ፥ እየፈራች ፡ እየተንቀጠቀጠችም ፥ መጥታ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋች ፡ እውነቱንም ፡ ኹሉ ፡ ነገረችው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 34 ፤ ርሱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እምነትሽ ፡ አድኖሻል ፤ በሰላም ፡ ኺጂ ፡ ከሥቃይሽም ፡ ተፈወሽ ፡ አላት ።

ማር. ፡ 5 ፡ 35 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ከምኩራብ ፡ አለቃው ፡ ቤት ፡ ዘንድ ፡ የመጡት ፦ ልጅኽ ፡ ሞታለች ፤ ስለ ፡ ምን ፡ መምህሩን ፡ አኹን ፡ ታደክመዋለኽ ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 5 ፡ 36 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ አድምጦ ፡ ለምኩራቡ ፡ አለቃ ፦ እመን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ አትፍራ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 37 ፤ ከጴጥሮስም ፡ ከያዕቆብም ፡ ከያዕቆብም ፡ ወንድም ፡ ከዮሐንስ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ እንዲከተለው ፡ አልፈቀደም ።

ማር. ፡ 5 ፡ 38 ፤ ወደምኩራቡ ፡ አለቃ ፡ ቤትም ፡ መጥቶ ፡ ሰዎች ፡ ሲንጫጫሉና ፡ ሲያለቅሱ ፡ ዋይታም ፡ ሲያበዙ ፡ አየ ፤

ማር. ፡ 5 ፡ 39 ፤ ገብቶም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ትንጫጫላችኹ ፥ ታለቅሳላችኹም ፧ ብላቴናዪቱ ፡ ተኝታለች ፡ እንጂ ፡ አልሞተችም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 40 ፤ በጣምም ፡ ሣቁበት ። ርሱ ፡ ግን ፡ ኹሉን ፡ አስወጥቶ ፡ የብላቴናዪቱን ፡ አባትና ፡ እናትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትንም ፡ ይዞ ፡ ብላቴናዪቱ ፡ ወዳለችበት ፡ ገባ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 41 ፤ የብላቴናዩቱንም ፡ እጅ ፡ ይዞ ፦ ጣሊታ ([286]) ፡ ቁሚ ፡ አላት ፤ ፍችውም ፡ አንቺ ፡ ብላቴና ፡ ተነሽ ፡ እልሻለኹ ፡ ነው ።

ማር. ፡ 5 ፡ 42 ፤ ብላቴናዩቱም ፡ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ ነበረችና ፡ ወዲያው ፡ ቆማ ፡ ተመላለሰች ። ወዲያውም ፡ ታላቅ ፡ መገረም ፡ ተገረሙ ።

ማር. ፡ 5 ፡ 43 ፤ ይህንም ፡ ማንም ፡ እንዳያውቅ ፡ አጥብቆ ፡ አዟቸው ። የምትበላውን ፡ ስጧት ፡ አላቸው ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ማር. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ወደገዛ ፡ አገሩ ፡ መጣ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ተከተሉት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ሰንበትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ በምኩራብ ፡ ያስተምር ፡ ገሥመር ፤ ብዙዎችም ፡ ሰምተው ፡ ተገረሙና ፦ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ይህ ፡ ከወዴት ፡ አገኛቸው ፧ ለዚህ ፡ የተሰጠችው ፡ ጥበብ ፡ ምንድር ፡ ናት ፧ በእጁም ፡ የሚደረጉ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ተኣምራት ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧

ማር. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ይህስ ፡ ጸራቢው ፡ የማርያም ፡ ልጅ ፡ የያዕቆብም ፡ የዮሳም ፡ የይሁዳም ፡ የስምዖንም ፡ ወንድም ፡ አይደለምን ፧ እኅቶቹስ ፡ በዚህ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ አይደሉምን ፧ አሉ ፤ ይሰናከሉበትም ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፦ ነቢይ ፡ ከገዛ ፡ አገሩና ፡ ከገዛ ፡ ዘመዶቹ ፡ ከገዛ ፡ ቤቱም ፡ በቀር ፡ ሳይከበር ፡ አይቀርም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 5 ፤ በዚያም ፡ በጥቂቶች ፡ ድውዮች ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጭኖ ፡ ከመፈወስ ፡ በቀር ፥ ተኣምር ፡ ሊያደርግ ፡ ምንም ፡ አልቻለም ።

ማር. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ስላለማመናቸውም ፡ ተደነቀ ። በመንደሮችም ፡ እያስተማረ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 7 ፤ አስራ ፡ ኹለቱንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠራ ፥ ኹለት ፡ ኹለቱንም ፡ ይልካቸው ፡ ገሥመር ፥ በርኩሳን ፡ መናፍስትም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ፥

ማር. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ለመንገድም ፡ ከበትር ፡ በቀር ፡ እንጀራም ፡ ቢኾን ፡ ከረጢትም ፡ ቢኾን ፡ መሐለቅም ፡ በመቀነታቸው ፡ ቢኾን ፡ እንዳይዙ ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 9 ፤ በእግራችኹ ፡ ጫማ ፡ አድርጉ ፡ እንጂ ፡ ኹለት ፡ እጀ ፡ ጠባብ ፡ አትልበሱ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 10 ፤ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ብትገቡ ፡ ከዚያ ፡ እስክትወጡ ፡ ድረስ ፡ በዚያው ፡ ተቀመጡ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ከማይቀበሏችኹና ፡ ከማይሰሟችኹ ፡ ስፍራ ፡ ሹሉ ፥ ከዚያ ፡ ወጥታችኹ ፡ ምስክር ፡ ይኾንባቸው ፡ ዘንድ ፡ ከእግራችኹ ፡ በታች ፡ ያለውን ፡ ትቢያ ፡ አራግፉ ። እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶምና ፡ ለገሞራ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ይቀልላቸዋል ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ወጥተውም ፡ ንስሓ ፡ እንዲገቡ ፡ ሰበኩ ፥ ብዙ ፡ አጋንንትንም ፡ አወጡ ፥

ማር. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ብዙ ፡ ድውዮችንም ፡ ዘይት ፡ እየቀቡ ፡ ፈወሷቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ስሙም ፡ ተገልጧልና ፥ ንጉሡ ፡ ሄሮድስ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቷል ፡ ስለዚህም ፡ ኀይል ፡ በርሱ ፡ ይደረጋል ፡ አለ ።

---

286 ሱር. ፥ ጣልያታ ፡ (ጣሊታ • ሴት ፡ ልጅ ፥ ቄንጦ ፥ ገና ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያልሞላች) ።

ማር. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ሌላዎችም ፦ ኤልያስ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ሌላዎችም ፦ ከነቢያት ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ ነቢይ ፡ ነው ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ሄሮድስ ፡ ግን ፡ ሰምቶ ፦ እኔ ፡ ራሱን ፡ ያስቈረጥኹት ፡ ዮሐንስ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ርሱ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቷል ፡ አለ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ሄሮድስ ፡ የወንድሙን ፡ የፊልጶስን ፡ ሚስት ፡ ሄሮድያዳን ፡ አግብቶ ፡ ነበርና ፥ በርሷ ፡ ምክንያት ፡ ራሱ ፡ ልኮ ፡ ዮሐንስን ፡ አስይዞ ፡ በወህኒ ፡ አሳስሮት ፡ ነበር ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ዮሐንስ ፡ ሄሮድስን ፦ የወንድምኽ ፡ ሚስት ፡ ለአንተ ፡ ልትኾን ፡ አልተፈቀደም ፡ ይለው ፡ ነበርና ።

ማር. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ሄሮድያዳ ፡ ግን ፡ ተቃውማው ፡ ልትገድለው ፡ ትፈልግ ፡ ነበር ፡ አልቻለችም ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ሄሮድስ ፡ ዮሐንስ ፡ ጻድቅና ፡ ቅዱስ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቆ ፡ ይፈራውና ፡ ይጠባበቀው ፡ ነበር ፤ ርሱንም ፡ ሰምቶ ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ ያመነታ ፡ ነበር ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 21 ፤ በደስታም ፡ ይሰማው ፡ ነበር ። ሄሮድስም ፡ በተወለደበት ፡ ቀን ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለሻለቃዎቹ ፡ ለገሊላም ፡ ሹማምንት ፡ ግብር ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ምቹ ፡ ቀን ፡ ኾነላትና ፡

ማር. ፡ 6 ፡ 22 ፤ የሄሮድያዳ ፡ ልጅ ፡ ገብታ ፡ ስትዘፍን ፡ ሄሮድስንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የተቀመጡትን ፡ ደስ ፡ አሠኘቻቸው ። ንጉሡም ፡ ብላቴናዪቱን ፦ የምትወጂውን ፡ ኹሉ ፡ ለምኚኝ ፡ እሰጥሽማለኹ ፡ አላት ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 23 ፤ የመንግሥቴ ፡ እኩሌታ ፡ ስንኳ ፡ ቢኾን ፡ የምትለምኚውን ፡ ኹሉ ፡ እሰጥሻለኹ ፡ ብሎ ፡ ማለላት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ወጥታም ፡ ለእናቷ ፦ ምን ፡ ልለምነው ፧ አለች ። ርሷም ፦ የመጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ አለች ።

ማር. ፡ 6 ፡ 25 ፤ ወዲያውም ፡ ፈጥና ፡ ወደ ፡ ንጉሡ ፡ ገብታ ፦ የመጥምቁን ፡ የዮሐንስን ፡ ራስ ፡ በወጭት ፡ አኹን ፡ ልትሰጠኝ ፡ እወዳለኹ ፡ ብላ ፡ ለመነችው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 26 ፤ ንጉሡም ፡ እጅግ ፡ ዐዝኖ ፡ ስለ ፡ መሐላው ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ስለተቀመጡት ፡ ሊነሣት ፡ አልወደደም ።

ማር. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ወዲያውም ፡ ንጉሡ ፡ ባለወግ ፡ ልኮ ፡ ራሱን ፡ እንዲያመጣ ፡ አዘዘው ። ኼዶም ፡ በወህኒ ፡ ራሱን ፡ ቈረጠ ፥

ማር. ፡ 6 ፡ 28 ፤ ራሱንም ፡ በወጭት ፡ አምጥቶ ፡ ለብላቴናዪቱ ፡ ሰጣት ፥ ብላቴናዪቱም ፡ ለእናቷ ፡ ሰጠች ።

ማር. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሰምተው ፡ መጡ ፡ በድኑንም ፡ ወስደው ፡ ቀበሩት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 30 ፤ ሐዋርያትም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ተሰብስበው ፡ ያደረጉትንና ፡ ያስተማሩትን ፡ ኹሉ ፡ ነገሩት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 31 ፤ እናንት ፡ ራሳችኹ ፡ ብቻችኹን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኑና ፡ ጥቂት ፡ ዕረፉ ፡ አላቸው ፤ የሚመጡና ፡ የሚኼዱ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩና ፥ ለመብላት ፡ እንኳ ፡ ጊዜ ፡ ዐጡ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 32 ፤ በታንኳውም ፡ ብቻቸውን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኼዱ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 33 ፤ ሰዎችም ፡ ሲኼዱ ፡ አይዋቸው ፡ ብዙዎችም ፡ ዐወቋቸውና ፡ ከከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ በእግር ፡ እየሮጡ ፡ ወዲያ ፡ ቀደሟቸው ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ ተሰበሰቡ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 34 ፤ ኢ.የሱስም ፡ ወጥቶ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አየና ፡ እረኛ ፡ እንደሌላቸው ፡ በጎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ዐዘነላቸው ፥ ብዙም ፡ ነገር ፡ ያስተምራቸው ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 35 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ ሰዓት ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ ቦታው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ነው ፡ አኹንም ፡ መሸቷል ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 36 ፤ የሚበሉት ፡ የላቸውምና ፡ በዙሪያ ፡ ወዳሉ ፡ ገጠሮችና ፡ መንደሮች ፡ ኼደው ፡ እንጀራ ፡ ለራሳቸው ፡ እንዲገዙ ፡ አሰናብታቸው ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 37 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ እናንተ ፡ የሚበሉትን ፡ ስጧቸው ፡ አላቸው ፦ ኼደን ፡ እንጀራ ፡ በኹለት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ እንግዛላቸውን ፧ እንዲበሉም ፡ እንስጣቸውን ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ ስንት ፡ እንጀራ ፡ አላችኹ ፧ ኺዱና ፡ እዩ ፡ አላቸው ። ባወቁም ፡ ጊዜ ፦ ዐምስት ፥ ኹለትም ፡ ዓሣ ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 6 ፡ 39 ፤ ኾሉንም ፡ በየክፍሉ ፡ በለመለመ ፡ ሣር ፡ ላይ ፡ እንዲያስቀምጧቸው ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 40 ፤ መቶ ፡ መቶውና ፡ ዐምሳ ፡ ዐምሳው ፡ እየኾኑ ፡ በተራ ፡ በተራ ፡ ተቀመጡ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 41 ፤ ዐምስቱንም ፡ እንጀራ ፡ ኹለቱንም ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሻቅቦ ፡ አየና ፡ ባረከ ፥ እንጀራውንም ፡ ቈርሶ ፡ እንዲያቀርቡላቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፥

ማር. ፡ 6 ፡ 42 ፤ ኹለቱን ፡ ዓሣ ፡ ደግሞ ፡ ለኾሉ ፡ ከፈለ ። ኾሉም ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 43 ፤ ከቀሩርስራሹም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መሶብ ፡ የሞላ ፡ አነሡ ፥ ከዓሣውም ፡ ደግሞ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 44 ፤ እንጀራውንም ፡ የበሉት ፡ ወንዶቹ ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 45 ፤ ወዲያውም ፡ ሕዝቡን ፡ ሲያሰናብት ፡ ሳለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በታንኳ ፡ ገብተው ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ እንዲቀድሙት ፡ ግድ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 46 ፤ ካሰናበታቸውም ፡ በኋላ ፡ ሊጸልይ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 47 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ታንኳዩቱ ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ሳለች ፡ ርሱ ፡ ብቻውን ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 48 ፤ ነፋስ ፡ ወደ ፡ ፊታቸው ፡ ነበረና ፡ እየቀዘፉ ፡ ሲጨነቁ ፡ አይቶ ፥ ከሌሊቱ ፡ በአራተኛው ፡ ክፍል ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እየኼደ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ መጣ ፤ ሊያልፋቸውም ፡ ይወድ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 49 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሲኼድ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ምትሀት ፡ መሰላቸውና ፡ ጮኹ ፥

ማር. ፡ 6 ፡ 50 ፤ ኾሉ ፡ አይተውታልና ፥ ታወኩም ። ወዲያውም ፡ ተናገራቸውና ፦ አይዟችኹ ፤ እኔ ፡ ነኝ ፥ አትፍሩ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 6 ፡ 51 ፤ ወደ ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ታንኳዩቱ ፡ ገባ ፥ ነፋሱም ፡ ተወ ፤ በራሳቸውም ፡ ያለመጠን ፡ እጅግ ፡ ተገረሙ ፤

ማር. ፡ 6 ፡ 52 ፤ ስለ ፡ እንጀራው ፡ አላስተዋሉምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልባቸው ፡ ደንዝዞ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 53 ፤ ተሻግረውም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ጌንሴሬጥ ፡ ደረሱ ፡ ታንኳዩቱንም ፡ አስጠጉ ።

ማር. ፡ 6 ፡ 54 ፤ ከታንኳዉቱም ፡ ሲወጡ ፡ ወዲያው ፡ ዐውቀውት ፡

ማር. ፡ 6 ፡ 55 ፤ በዚያች ፡ አገር ፡ ዙሉ ፡ ዙሪያ ፡ ሮጡና ፡ ርሱ ፡ እንዳለ ፡ ወደሰሙበት ፡ ስፍራ ፡ ሕመምተኞችን ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ያመጡ ፡ ዝመር ።

ማር. ፡ 6 ፡ 56 ፤ በገባበትም ፡ ስፍራ ፡ ዙሉ ፥ መንደርም ፡ ከተማም ፡ ገጠርም ፡ ቢኾን ፥ በገበያ ፡ ድውዮችን ፡ ያኖሩ ፡ ነበር ፤ የልብሱንም ፡ ጫፍ ፡ እንኳ ፡ ሊዳስሱ ፡ ይለምኑት ፡ ነበር ፡ የዳሰሱትም ፡ ዙሉ ፡ ዳኑ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ማር. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ ከጻፊዎች ፡ ወገን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የመጡትም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ አንዳንድ ፡ በርኩስ ፡ ማለት ፡ ባልታጠበ ፡ እጅ ፡ እንጀራ ፡ ሲበሉ ፡ አዩ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ አይሁድም ፡ ዙሉ ፡ የሽማግሌዎችን ፡ ወግ ፡ ሲጠብቁ ፡ እጃቸውን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ሳይታጠቡ ፡ አይበሉምና ፥

ማር. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ከገበያም ፡ ተመልሰው ፡ ካልታጠቡ ፡ አይበሉም ፥ ጽዋንም ፡ ማድጋንም ፡ የናስ ፡ ዕቃንም ፡ ዐልጋንም ፡ እንደ ፡ ማጠብ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ሊጠብቁት ፡ የተቀበሉት ፡ ብዙ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ጻፊዎችም ፦ ደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ እንደ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወግ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አይኼዱም ፧ ነገር ፡ ግን ፡ እጃቸውን ፡ ሳይታጠቡ ፡ እንጀራ ፡ ይበላሉ ፡ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ኢሳይያስ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ስለ ፡ ግብዞች ፦ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ በከንፈሩ ፡ ያከብረኛል ፡ ልቡ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ በጣም ፡ የራቀ ፡ ነው ፤

ማር. ፡ 7 ፡ 7 ፤ የሰውም ፡ ሥርዐት ፡ የኾነ ፡ ትምህርት ፡ እያስተማሩ ፡ በከንቱ ፡ ያመልኩኛል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በእውነት ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ትታችኹ ፡ ጽዋን ፡ ማድጋንም ፡ እንደ ፡ ማጠብ ፡ የሰውን ፡ ወግ ፡ ትጠብቃላችኹ ፥ ይህንም ፡ የመሰለ ፡ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ታደርጋላችኹ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 9 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ወጋችኹን ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ እጅግ ፡ ንቃችኋል ።

ማር. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ሙሴ ፦ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤ ደግሞ ፦ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፡ የሰደበ ፡ ፈጽሞ ፡ ይሙት ፡ ብሏልና ።

ማር. ፡ 7 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ትላላችኹ ፦ ሰው ፡ አባቱን ፡ ወይም ፡ እናቱን ፦ ከእኔ ፡ የምትጠቀምበት ፡ ነገር ፡ ዙሉ ፡ ቍርባን ፡ ማለት ፡ መባ ፡ ነው ፡ ቢል ፥

ማር. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ለአባቱና ፡ ለእናቱ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሊያደርግ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አትፈቅዱለትም ፤

ማር. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ባስተላለፋችኹትም ፡ ወግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ትሽራላችኹ ፤ እንደዚሁም ፡ ይህን ፡ የሚመስል ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ታደርጋላችኹ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ደግሞም ፡ ሕዝቡን ፡ ጠርቶ ፦ ዙላችኹ ፡ እኔን ፡ ስሙ ፥ አስተውሉም ።

ማር. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ከሰው ፡ የሚወጡት ፡ ሰውን ፡ የሚያረክሱ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፥ ከሰው ፡ ውጭ ፡ የሚገባውስ ፡ ሊያረክሰው ፡ የሚችል ፡ ምንም ፡ የለም ።

ማር. ፡ 7 ፡ 16 ፤ የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ይስማ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ከሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ምሳሌውን ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ የማታስተውሉ ፡ ናችኹን ፧ ከውጭ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ የሚገባ ፡ ሊያረክሰው ፡ ምንም ፡ እንዳይችል ፡ አትመለከቱምን ፧

ማር. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ሆድ ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡ እዳሪ ፡ ይወጣል ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ልብ ፡ አይገባምና ፤ መብልን ፡ ኹሉ ፡ እያጠራ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ርሱም ፡ አለ ፦ ከሰው ፡ የሚወጣው ፡ ሰውን ፡ የሚያረክስ ፡ ያ ፡ ነው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ከውስጥ ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ የሚወጣ ፡ ክፉ ፡ ዐሳብ ፥

ማር. ፡ 7 ፡ 22 ፤

ዝሙት ፥ መስረቅ ፥ መግደል ፥ ምንዝርነት ፥ መጐምጐጥ ፥ ክፋት ፥ ተንኰል ፥ መዳራት ፥ ምቀኝነት ፥ ስድብ ፥ ትዕቢት ፥ ስንፍና ፡ ናቸውና ፤

ማር. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ይህ ፡ ክፉው ፡ ኹሉ ፡ ከውስጥ ፡ ይወጣል ፡ ሰውን ፡ ያረክሰዋል ።

ማር. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ጢሮስና ፡ ወደሲዶና ፡ አገር ፡ ኼደ ። ወደ ፡ ቤትም ፡ ገብቶ ፡ ማንም ፡ እንዳያውቅበት ፡ ወደደ ፡ ሊሰወርም ፡ አልተቻለውም ፤

ማር. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ወዲያው ፡ ግን ፡ ታናሺቱ ፡ ልጇ ፡ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ያደረባት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ሰምታ ፡ መጣችና ፡ በእግሩ ፡ ላይ ፡ ተደፋች ፡

ማር. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ሴቲቱም ፡ ግሪክ ፥ ትውልዷም ፡ ሲሮፊኒቃዊት ፡ ነበረች ፤ ከልጇ ፡ ጋኔን ፡ ያወጣላት ፡ ዘንድ ፡ ለመነችው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ ልጆቹ ፡ በፊት ፡ ይጠግቡ ፡ ዘንድ ፡ ተዉ ፡ የልጆቹን ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ ለቡችሎች ፡ መጣል ፡ አይገባምና ፥ አላት ።

ማር. ፡ 7 ፡ 28 ፤ ርሷም ፡ መልሳ ፦ አዎን ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ቡችሎች ፡ እንኳ ፡ ከማእዱ ፡ በታች ፡ ኾነው ፡ የልጆችን ፡ ፍርፋሪ ፡ ይበላሉ ፡ አለችው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 29 ፤ ርሱም ፦ ስለዚህ ፡ ቃልሽ ፡ ኺጂ ፡ ጋኔኑ ፡ ከልጅሽ ፡ ወጥቷል ፡ አላት ።

ማር. ፡ 7 ፡ 30 ፤ ወደ ፡ ቤቷም ፡ ኼዳ ፡ ጋኔኑ ፡ ወጥቶ ፡ ልጇም ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝታ ፡ አገኘች ።

ማር. ፡ 7 ፡ 31 ፤ ደግሞም ፡ ከጢሮስ ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ በሲዶና ፡ ዐልፎ ፡ ዐሥር ፡ ከተማ ፡ በሚባል ፡ አገር ፡ መካከል ፡ ወደገሊላ ፡ ባሕር ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 32 ፤ ደንቈሮና ፡ ኰልታፋም ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፥

ማር. ፡ 7 ፡ 33 ፤ እጁንም ፡ ይጭንበት ፡ ዘንድ ፡ ለመኑት ። ከሕዝቡም ፡ ለይቶ ፡ ለብቻው ፡ ወሰደው ፥ ጣቶቹንም ፡ በጐሮዎቹ ፡ አገባ ፡ እንትፍም ፡ ብሎ ፡ ምላሱን ፡ ዳሰሰ ፤

ማር. ፡ 7 ፡ 34 ፤ ወደ ፡ ሰማይም ፡ አሻቅቦ ፡ አይቶ ፡ ቃተተና ፦ ኤፍታሕ ፡ አለው ፥ ርሱም ፡ ተከፈት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ማር. ፡ 7 ፡ 35 ፤ ወዲያውም ፡ ጐሮዎቹ ፡ ተከፈቱ ፡ የምላሱም ፡ እስራት ፡ ተፈታ ፡ አጥርቶም ፡ ተናገረ ።

ማር. ፡ 7 ፡ 36 ፤ ለማንም ፡ አትንገሩ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ፡ እነርሱ ፡ ግን ፡ ባዘዛቸውም ፡ መጠን ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ አወሩት ።

ማር. ፡ 7 ፡ 37 ፤ ያለመጠንም ፡ ተገረሙና ፦ ኹሉን ፡ ደኅና ፡ አድርጓል ፤ ደንቈሮዎችም ፡ እንዲሰሙ ፡ ዲዳዎችም ፡ እንዲናገሩ ፡ ያደርጋል ፡ አሉ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ማር. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበረ ፡ የሚበሉትም ፡ ስለሌላቸው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠርቶ ፦

ማር. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ሕዝቡ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እስካኹን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ውለዋልና ፥ የሚበሉት ፡ ስለሌላቸው ፡ አዝንላቸዋለኹ ፤

ማር. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከሩቅ ፡ መጥተዋልና ፥ ጦማቸውን ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ባሰናብታቸው ፡ በመንገድ ፡ ይዝላሉ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ በዚህ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እንጀራ ፡ ከየት ፡ አግኝቶ ፡ ሰው ፡ እነዚህን ፡ ማጥገብ ፡ ይችላል ፧ ብለው ፡ መለሱለት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ርሱም ፦ ስንት ፡ እንጀራ ፡ አላችኹ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ፥ እነርሱም ፦ ሰባት ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ሕዝቡም ፡ በምድር ፡ እንዲቀመጡ ፡ አዘዘ ። ሰባቱንም ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ አመሰገነ ፥ ቈርሶም ፡ እንዲያቀርቡላቸው ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፥ ለሕዝቡም ፡ አቀረቡ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ጥቂትም ፡ ትንሽ ፡ ዓሣ ፡ ነበራቸው ፤ ባረከውም ፡ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ እንዲያቀርቡላቸው ፡ አዘዘ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በሉም ፡ ጠገቡም ፥ የተረፈውንም ፡ ቍርስራሽ ፡ ሰባት ፡ ቅርጫት ፡ አነሡ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 9 ፤ የበሉትም ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ነበሩ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 10 ፤ አሰናበታቸውም ። ወዲያውም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታንኳዱቱ ፡ ገብቶ ፡ ወደዳልማኑታ ፡ አገር ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ወጡና ፡ ሊፈትኑት ፡ ከሰማይ ፡ ምልክት ፡ ከርሱ ፡ ፈልገው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይከራከሩ ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 8 ፡ 12 ፤ በመንፈሱም ፡ እጅግ ፡ ቃተተና ፦ ይህ ፡ ትውልድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ ይፈልጋል ፧ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ለዚህ ፡ ትውልድ ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ፡ አለ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ትቷቸውም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ታንኳዱቱ ፡ ገብቶ ፡ ወደ ፡ ማዶ ፡ ኼደ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 14 ፤ እንጀራ ፡ መያዝም ፡ ረሱ ፥ ለእነርሱም ፡ ካንድ ፡ እንጀራ ፡ በቀር ፡ በታንኳዱቱ ፡ አልነበራቸውም ።

ማር. ፡ 8 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ ተጠንቀቁ ፤ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሄሮድስ ፡ ርሾ ፡ ተጠበቁ ፡ ብሎ ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 16 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ እንጀራ ፡ ስለሌለን ፡ ይኾናል ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እንጀራ ፡ ስለሌላችኹ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትነጋገራላችኹ ፧ ገና ፡ አልተመለከታችኹምን ፧ አላስተዋላችኹምን ፧

ማር. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ልባችኹስ ፡ ደንዝዟልን ፧ ዐይን ፡ ሳላችኹ ፡ አታዩምን ፧ ጐሮስ ፡ ሳላችኹ ፡ አትሰሙምን ፧ ትዝስ ፡ አይላችኹምን ፧

ማር. ፡ 8 ፡ 19 ፤ ዐምስቱን ፡ እንጀራ ፡ ለዐምስት ፡ ሺሕ ፡ በቈረስኹ ፡ ጊዜ ፥ ቀሪስራሹ ፡ የሞላ ፡ ስንት ፡ መሶብ ፡ አነሣችኹ ፧ እነርሱም ፦ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ሰባቱን ፡ እንጀራስ ፡ ለአራት ፡ ሺሕ ፡ በቈረስኹ ፡ ጊዜ ፥ ቀሪስራሹ ፡ የሞላ ፡ ስንት ፡ ቅርጫት ፡ አነሣችኹ ፧ እነርሱም ፦ ሰባት ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ገና ፡ አላስተዋላችኹምን ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳም ፡ መጡ ። ዕውርም ፡ አመጡለት ፥ እንዲዳስሰውም ፡ ለመኑት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ዕውሩንም ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ከመንደር ፡ ውጭ ፡ አወጣው ፥ በዐይኑም ፡ ተፍቶበት ፡ እጁንም ፡ ጭኖበት ። አንዳች ፡ ታያለኽን ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 24 ፤ አሻቅቦም ፦ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ዛፍ ፡ ሲመላለሱ ፡ አያለኹ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ እጁን ፡ በዐይኑ ፡ ላይ ፡ ጫነበት ፡ አጥርቶም ፡ አየና ፡ ዳነም ፡ ከሩቅም ፡ ሳይቀር ፡ ኹሉን ፡ ተመለከተ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ ሰደደውና ፦ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አትግባ ፡ በመንደሩም ፡ ለማንም ፡ አንዳች ፡ አትናገር ፡ አለው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ኢየሱስና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በፊልጶስ ፡ ቂሳርያ ፡ ወዳሉ ፡ መንደሮች ፡ ወጡ ፡ በመንገድም ፦ ሰዎች ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ይላሉ ፧ ብሎ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠየቃቸው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 28 ፤ እነርሱም ፦ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፥ ሌላዎችም ፡ ኤልያስ ፥ ሌላዎችም ፡ ከነቢያት ፡ አንዱ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 29 ፤ እናንተስ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ትላላችኹ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። ጴጥሮስም ፦ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነኽ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ማር. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገሩ ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 31 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፥ ከሽማግሌዎችም ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ከጻፊዎችም ፡ ሊጣል ፥ ሊገደልም ፡ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ሊነሣ ፡ እንዲገባው ፡ ያስተምራቸው ፡ ዝመር ፤ ቃሉንም ፡ ገልጦ ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወስዶ ፡ ይገሥጸው ፡ ዝመር ።

ማር. ፡ 8 ፡ 33 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ አለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ አይቶ ፡ ጴጥሮስን ፡ ገሠጸውና ፦ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ኺድ ፥ አንተ ፡ ሰይጣን ፤ የሰውን ፡ እንጂ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አታስብምና ፡ አለው ።

ማር. ፡ 8 ፡ 34 ፤ ሕዝቡንም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በኋላዬ ፡ ሊመጣ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፥ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ።

ማር. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋታልና ፥ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ነፍሱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ያድናታል ።

ማር. ፡ 8 ፡ 36 ፤ ሰው ፡ ዓለምን ፡ ኹሉ ፡ ቢያተርፍ ፡ ነፍሱንም ፡ ቢያጐድል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፧

ማር. ፡ 8 ፡ 37 ፤ ሰውስ ፡ ስለነፍሱ ፡ ቤዛ ፡ ምን ፡ ይሰጣል ፧

ማር. ፡ 8 ፡ 38 ፤ በዚህም ፡ በዘማዊና ፡ በኀጢአተኛ ፡ ትውልድ ፡ መካከል ፡ በእኔና ፡ በቃሌ ፡ የሚያፍር ፡ ኹሉ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ በአባቱ ፡ ክብር ፡ ከቅዱሳን ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በርሱ ፡ ያፍርበታል ።

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ማር. ፡ 9 ፡ 1 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በዚህ ፡ ከቆሙት ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በኀይል ፡ ስትመጣ ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፥ ሞትን ፡ የማይቀምሱ ፡ አንዳንዶች ፡ አሉ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ከስድስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ዮሐንስንም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፡ ብቻቸውን ፡ አወጣቸው ። በፊታቸውም ፡ ተለወጠ ፥ ልብሱም ፡ አንጸባረቀ ፤

ማር. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ዐጣቢም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደዚያ ፡ ሊያነጣው ፡ እስከማይችል ፡ በጣም ፡ ነጭ ፡ ኾነ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ኤልያስና ፡ ሙሴም ፡ ታዩዋቸው ፥ ከኢየሱስም ፡ ጋራ ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፡ ኢየሱስን ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ መኾን ፡ ለእኛ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ አንድ ፡ ለአንተ ፡ አንድም ፡ ለሙሴ ፡ አንድም ፡ ለኤልያስ ፡ ሦስት ፡ ዳሶች ፡ እንሥራ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 6 ፤ እጅግ ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ የሚለውን ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ደመናም ፡ መጥቶ ፡ ጋረዳቸው ፥ ከደመናውም ፦ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ርሱን ፡ ስሙት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ድንገትም ፡ ዞረው ፡ ሲመለከቱ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ከኢየሱስ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ አላዩም ።

ማር. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ከተራራውም ፡ ሲወርዱ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከሙታን ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡ ያዩትን ፡ ለማንም ፡ እንዳይነግሩ ፡ አዘዛቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ቃሉንም ፡ ይዘው ፦ ከሙታን ፡ መነሣት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እያሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተጠያየቁ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 11 ፤ እነርሱም ፦ ኤልያስ ፡ አስቀድሞ ፡ ሊመጣ ፡ እንዲገባው ፡ ጻፊዎች ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይላሉ ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ኤልያስማ ፡ አስቀድሞ ፡ ይመጣል ፥ ኹሉንም ፡ ያቀናናል ፤ ስለ ፡ ሰው ፡ ልጅም ፡ እንዴት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፧ ብዙ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ እንዲናቅም ።

ማር. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ኤልያስ ፡ ደግሞ ፡ መጥቷል ፥ ስለ ፡ ርሱም ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የወደዱትን ፡ ኹሉ ፡ አደረጉበት ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ሲከቧቸው ፥ ጻፊዎችም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ አየ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ወዲያውም ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ባዩት ፡ ጊዜ ፡ ደነገጡ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ ሮጠው ፡ እጅ ፡ ነሡት ።

ማር. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ጻፊዎችንም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ትከራከራላችኹ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ከሕዝቡ ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ዲዳ ፡ መንፈስ ፡ ያደረበትን ፡ ልጄን ፡ ወዳንተ ፡ አምጥቻለኹ ፤

ማር. ፡ 9 ፡ 18 ፤ በያዘውም ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ ይጥለዋል ፤ ዐረፋም ፡ ይደፍቃል ፥ ጥርሱንም ፡ ያፋጫል ፡ ይደርቃልም ፤ እንዲያወጡለትም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ ነገርኋቸው ፥ አልቻሉምም ፡ አለው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ የማታምን ፡ ትውልድ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለኹ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ እታገሣችኋለኹ ፧ ወደ ፡ እኔ ፡ አምጡት ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ አመጡት ። ርሱንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ መንፈስ ፡ ወዲያው ፡ አንፈራገጠው ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ ወድቆ ፡ ዐረፋ ፡ እየደፈቀ ፡ ተንፈራፈረ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 21 ፤ አባቱንም ፦ ይህ ፡ ከያዘው ፡ ስንት ፡ ዘመን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ርሱም ፦ ከሕፃንነቱ ፡ ገምሮ ፡ ነው ፤

ማር. ፡ 9 ፡ 22 ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ሊያጠፋው ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ወደ ፡ ውሃም ፡ ጣለው ፤ ቢቻልኽ ፡ ግን ፡ ዕዘንልን ፥ ርዳንም ፡ አለው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፦ ቢቻልኽ ፡ ትላለኽ ፤ ለሚያምን ፡ ኹሉ ፡ ይቻላል ፡ አለው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ወዲያውም ፡ የብላቴናው ፡ አባት ፡ ጮኾ ፦ አምናለኹ ፤ አለማመኔን ፡ ርዳው ፡ አለ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ኢየሱስም ፡ ሕዝቡ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሲራወጥ ፡ አይቶ ፡ ርኩሱን ፡ መንፈስ ፡ ገሠጸና ፦ አንተ ፡ ዲዳ ፡ ደንቈሮም ፡ መንፈስ ፥ እኔ ፡ አዝኻለኹ ፥ ከርሱ ፡ ውጣ ፡ እንግዲህም ፡ አትግባበት ፡ አለው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ጮኾም ፡ እጅግም ፡ አንፈራግጦት ፡ ወጣ ፤ ብዙዎችም ፦ ሞተ ፡ እስኪሉ ፡ ድረስ ፡ እንደ ፡ ሙት ፡ ኾነ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ አስነሣው ፡ ቆመም ።

ማር. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ እኛ ፡ ልናወጣው ፡ ያልቻልን ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ብቻውን ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ይህ ፡ ወገን ፡ በጸሎትና ፡ በጦም ፡ ካልኾነ ፡ በምንም ፡ ሊወጣ ፡ አይችልም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 30-31 ፤ ከዚያም ፡ ወጥተው ፡ በገሊላ ፡ በኩል ፡ ዐለፉ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ያስተምር ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ማንም ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፤ ለእነርሱም ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሰዎች ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ፥ ይገድሉትማል ፥ ተገድሎም ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ ይላቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 9 ፡ 32 ፤ እነርሱም ፡ ነገሩን ፡ አላስተዋሉም ፥ እንዳይጠይቁትም ፡ ፈሩ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ወደ ፡ ቅፍርናሖምም ፡ መጣ ። በቤትም ፡ ኾኖ ፦ በመንገድ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ምን ፡ ተነጋገራችኹ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 34 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ በመንገድ ፦ ከኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ማን ፡ ይኾን ፧ ተባብለው ፡ ነበርና ፥ ዝም ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 35 ፤ ተቀምጦም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ጠርቶ ፦ ሰው ፡ ፊተኛ ፡ ሊኾን ፡ ቢወድ ፡ ከኹሉ ፡ በኋላ ፡

የ"ሹሉም ፡ አገልጋይ ፡ ይኹን ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 36 ፤ ሕፃንም ፡ ይዞ ፡ በመካከላቸው ፡ አቆመው ፡ ዐቅፎም ።

ማር. ፡ 9 ፡ 37 ፤ እንደዚህ ፡ ካሉ ፡ ሕፃናት ፡ አንዱን ፡ በስሜ ፡ የሚቀበል ፡ ሹሉ ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፤ የሚቀበለኝም ፡ ሹሉ ፡ የላከኝን ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ አይቀበልም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 9 ፡ 38 ፤ ዮሐንስ ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ በስምኽ ፡ አጋንንትን ፡ ሲያወጣ ፡ አየነው ፥

ማር. ፡ 9 ፡ 39 ፤ ስለማይከተለንም ፡ ከለከልነው ፡ አለው ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አለ ፦ በስሜ ፡ ተአምር ፡ ሠርቶ ፡ በቶሎ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ መናገር ፡ የሚችል ፡ ማንም ፡ የለምና ፡ አትከልክሉት ፤

ማር. ፡ 9 ፡ 40 ፤ የማይቃወመን ፡ ርሱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነውና ።

ማር. ፡ 9 ፡ 41 ፤ የክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፡ በስሜ ፡ ጽዋ ፡ ውሃ ፡ የሚያጠጣችኹ ፡ ሹሉ ፥ ዋጋው ፡ እንዳይጠፋበት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ።

ማር. ፡ 9 ፡ 42 ፤ በእኔም ፡ ከሚያምኑት ፡ ከነዚህ ፡ ከታናናሾቹ ፡ አንዱን ፡ የሚያሰናክል ፡ ሹሉ ፡ ትልቅ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በዐንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ቢጣል ፡ ይሻለው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 9 ፡ 43-44 ፤ እጅኽ ፡ ብታሰናክልኽ ፡ ቀ"ረጣት ፤ ኹለት ፡ እጅ ፡ ኖሮኽ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወደማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ከመኼድ ፡ ጕንድሽ ፡ ኾነኽ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻላል ።

ማር. ፡ 9 ፡ 45-46 ፤ እግርኽ ፡ ብታሰናክልኽ ፡ ቀ"ረጣት ፤ ኹለት ፡ እግር ፡ ኖሮኽ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ወደማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ከመጣል ፡ ዐንካሳ ፡ ኾነኽ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ መግባት ፡ ይሻልኻል ።

ማር. ፡ 9 ፡ 47-48 ፤ ዐይንኽ ፡ ብታሰናክልኽ ፡ አውጣት ፤ ኹለት ፡ ዐይን ፡ ኖሮኽ ፡ ትላቸው ፡ ወደማይሞትበት ፡ እሳቱም ፡ ወደማይጠፋበት ፡ ወደ ፡ ገሃነመ ፡ እሳት ፡ ከመጣል ፡ አንዲት ፡ ዐይን ፡ ኖራኽ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ ይሻልኻል ።

ማር. ፡ 9 ፡ 49 ፤ ሰው ፡ ሹሉ ፡ በእሳት ፡ ይቀመማልና ፥ መሥዋዕትም ፡ ሹሉ ፡ በጨው ፡ ይቀመማል ።

ማር. ፡ 9 ፡ 50 ፤ ጨው ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ጨው ፡ ግን ፡ ዐልጫ ፡ ቢኾን ፡ በምን ፡ ታጣፍጡታላችኹ ። በነፍሳችኹ ፡ ጨው ፡ ይኑርባችኹ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹም ፡ ተስማሙ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ማር. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ከዚያም ፡ ተነሥቶ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ወደይሁዳ ፡ አገር ፡ መጣ ፥ ደግሞም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተሰበሰቡ ፡ እንደ ፡ ልማዱም ፡ ደግሞ ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 2 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ቀርበው ፦ ሰው ፡ ሚስቱን ፡ ሊፈታ ፡ ተፈቅዶለታልን ። ብለው ፡ ሊፈትኑት ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ ሙሴ ፡ ምን ፡ አዘዛችኹ ። አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፦ ሙሴስ ፡ የፍቺን ፡ ጽሕፈት ፡ ጽፎ ፡ እንዲፈታት ፡ ፈቀደ ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ስለልባችኹ ፡ ጥንካሬ ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡

ጻፈላችኹ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ከፍጥረት ፡ መዠመሪያ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ አደረጋቸው ፤

ማር. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፥ ከሚስቱም ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፥

ማር. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ፤ ስለዚህ ፥ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ኹለት ፡ አይደሉም ።

ማር. ፡ 10 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ያጣመረውን ፡ እንግዲህ ፡ ሰው ፡ አይለየው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 10 ፤ በቤትም ፡ ደግሞ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ርሱም ፦ ሚስቱን ፡ ፈቶ ፡ ሌላ ፡ የሚያገባ ፡ ዥሉ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ ያመነዝራል ፤

ማር. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ርሷም ፡ ባሏን ፡ ፈት ፡ ሌላ ፡ ብታገባ ፡ ታመነዝራለች ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 13 ፤ እንዲዳስሳቸውም ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ያመጧቸውን ፡ ገሠጿቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አይቶ ፡ ተቈጣና ፦ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ተዉ ፥ አትከልክሏቸው ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ ናትና ።

ማር. ፡ 10 ፡ 15 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ የማይቀበላት ፡ ዥሉ ፡ ከቶ ፡ አይገባባትም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ዐቀፋቸውም ፡ እጁንም ፡ ጭኖ ፡ ባረካቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ በመንገድ ፡ ሲወጣ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሮጦ ፡ ተንበረከከለትና ፦ ቸር ፡ መምህር ፡ ሆይ ፥ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እወርስ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ኢየሱስም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ቸር ፡ ትለኛለኽ ፧ ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ቸር ፡ ማንም ፡ የለም ።

ማር. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ትእዛዛትን ፡ ታውቃለኽ ፤ አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት ፡ አትመስክር ፥ አታታል ፥ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፡ አለው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ዥሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ዠምሬ ፡ ጠብቄያለኹ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመልክቶ ፡ ወደደውና ፦ አንድ ፡ ነገር ፡ ጐደለኽ ፤ ኺድ ፥ ያለኽን ፡ ዥሉ ፡ ሽጠኽ ፡ ለድኻዎች ፡ ስጥ ፥ በሰማይም ፡ መዝገብ ፡ ታገኛለኽ ፥ መስቀሉንም ፡ ተሸክመኽ ፡ ና ፥ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ፊቱ ፡ ጠቈረ ፥ ብዙ ፡ ንብረት ፡ ነበረውና ፡ እያዘነም ፡ ኼደ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ አይቶ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦ ገንዘብ ፡ ላላቸው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ ይኾናል ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እነዚህን ፡ ቃሎች ፡ አደነቁ ። ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ መልሶ ፦ ልጆች ፡ ሆይ ፥ በገንዘብ ፡ ለሚታመኑ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ ነው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ባለጠጋ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከሚገባ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ቢያልፍ ፡ ይቀላል ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 26 ፤ እነርሱም ፡ ያለመጠን ፡ ተገረሙና ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ እንግዲያ ፡ ማን ፡ ሊድን ፡ ይችላል ፧ ተባባሉ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ኢየሱስም ፡ ተመለከታቸውና ፦ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፤ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ሹሉ ፡ ይቻላልና ፥ አለ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ጴጥሮስም ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ ሹሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንኽ ፡ ይለው ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ስለ ፡ እኔና ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ቤትን ፡ ወይም ፡ ወንድሞችን ፡ ወይም ፡ እኅቶችን ፡ ወይም ፡ አባትን ፡ ወይም ፡ እናትን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ ወይም ፡ ዕርሻን ፡ የተወ ፥

ማር. ፡ 10 ፡ 30 ፤ አኹን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከስደት ፡ ጋራ ፡ ቤቶችን ፡ ወንድሞችንና ፡ እኅቶችንም ፡ እናቶችንም ፡ ልጆችንም ፡ ዕርሻንም ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፥ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የማይቀበል ፡ ማንም ፡ የለም ።

ማር. ፡ 10 ፡ 31 ፤ ግን ፡ ብዙ ፡ ፊተኞች ፡ ኋለኞች ፡ ኋለኞችም ፡ ፊተኞች ፡ ይኾናሉ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 32 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሊወጡ ፡ በመንገድ ፡ ነበሩ ፥ ኢየሱስም ፡ ይቀድማቸው ፡ ነበርና ፥ ተደነቁ ፤ የተከተሉትም ፡ ይፈሩ ፡ ነበር ። ደግሞም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አቅርቦ ፡ ይደርስበት ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ይነግራቸው ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 33 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፥ የሰው ፡ ልጅም ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ለጻፊዎች ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ፥ የሞት ፡ ፍርድም ፡ ይፈርዱበታል ፥ ለአሕዛብም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፥

ማር. ፡ 10 ፡ 34 ፤ ይዘብቱበትማል ፡ ይተፉበትማል ፡ ይገርፉትማል ፡ ይገድሉትማል ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 35 ፤ የዘብዴዎስ ፡ ልጆች ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ የምንለምንኽን ፡ ሹሉ ፡ እንድታደርግልን ፡ እንወዳለን ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 10 ፡ 36 ፤ ርሱም ፦ ምን ፡ ላደርግላችኹ ፡ ትወዳላችኹ ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 37 ፤ እነርሱም ፦ በክብርኽ ፡ ጊዜ ፡ አንዳችን ፡ በቀኝ ፡ አንዳችንም ፡ በግራኽ ፡ መቀመጥን ፡ ስጠን ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 10 ፡ 38 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ የምትለምኑትን ፡ አታውቁም ። እኔ ፡ የምጠጣውን ፡ ጽዋ ፡ ልትጠጡ ፥ እኔ ፡ የምጠመቀውንስ ፡ ጥምቀት ፡ ልትጠመቁ ፡ ትችላላችኹን ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 39 ፤ እነርሱም ፦ እንችላለን ፡ አሉት ። ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ የምጠጣውን ፡ ጽዋ ፡ ትጠጣላችኹ ፥ እኔ ፡ የምጠመቀውንም ፡ ጥምቀት ፡ ትጠመቃላችኹ ፤

ማር. ፡ 10 ፡ 40 ፤ በቀኝና ፡ በግራ ፡ መቀመጥ ፡ ግን ፡ ለተዘጋጀላቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምሰጥ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 41 ፤ ዐሥሩም ፡ ሰምተው ፡ በያዕቆብና ፡ በዮሐንስ ፡ ይቈጡ ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 42 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የአሕዛብ ፡ አለቃዎች ፡ ተብሎ ፡

የምታስቡት ፡ እንዲገዟቸው ፡ ታላላቆቻቸውም ፡ በላያቸው ፡ እንዲሠለጥኑ ፡ ታውቃላችኹ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 43 ፤ በእናንተስ ፡ እንዲህ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ ከእናንተ ፡ ታላቅ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ የእናንተ ፡ አገልጋይ ፡ ይኹን ፥

ማር. ፡ 10 ፡ 44 ፤ ከእናንተም ፡ ማንም ፡ ፊተኛ ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ የኹሉ ፡ ባሪያ ፡ ይኹን ፤

ማር. ፡ 10 ፡ 45 ፤ እንዲሁ ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ ሊያገለግልና ፡ ነፍሱን ፡ ለብዙዎች ፡ ቤዛ ፡ ሊሰጥ ፡ እንጂ ፡ እንዲያገለግሉት ፡ አልመጣም ።

ማር. ፡ 10 ፡ 46 ፤ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ መጡ ። ከደቀ ፡ መዛሙርቱና ፡ ከብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ከኢያሪኮ ፡ ሲወጣ ፡ የጤሜዎስ ፡ ልጅ ፡ ዕውሩ ፡ በርጤሜዎስ ፡ እየለመነ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 47 ፤ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ማረኝ ፡ እያለ ፡ ይጮኽ ፡ ገሥመር ።

ማር. ፡ 10 ፡ 48 ፤ ብዙዎችም ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ ገሠጹት ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ማረኝ ፡ እያለ ፡ አብዝቶ ፡ ጮኸ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 49 ፤ ኢየሱስም ፡ ቆመና ፦ ጥሩት ፡ አለ ። ዕውሩንም ፦ አይዞኽ ፥ ተነሣ ፥ ይጠራኻል ፡ ብለው ፡ ጠሩት ።

ማር. ፡ 10 ፡ 50 ፤ ርሱም ፡ እየዘለለ ፡ ተነሣና ፡ ልብሱን ፡ ጥሎ ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 10 ፡ 51 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ምን ፡ ላደርግልኽ ፡ ትወዳለኽ ፧ አለው ። ዕውሩም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ አይ ፡ ዘንድ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 10 ፡ 52 ፤ ኢየሱስም ፦ ኺድ ፤ እምነትኽ ፡ አድኖኻል ፡ አለው ። ወዲያውም ፡ አየ ፡ በመንገድም ፡ ተከተለው ።

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ማር. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ከደብረ ፡ ዘይት ፡ አጠገብ ፡ ወዳሉቱ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፋጌና ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፥ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹለቱን ፡ ልኮ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 2 ፤ በፊታችኹ ፡ ወዳለችው ፡ መንደር ፡ ኺዱ ፥ ወዲያውም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገብታችኹ ፡ ከሰው ፡ ማንም ፡ ገና ፡ ያልተቀመጠበት ፡ ውርንጫ ፡ ታስሮ ፡ ታገኛላችኹ ፤ ፈቷ፡ችኹ ፡ አምጡልኝ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ማንም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ ታደርጋላችኹ ፧ ቢላችኹ ። ለጌታ ፡ ያስፈልገዋል ፡ በሉት ፥ ወዲያውም ፡ ደግሞ ፡ ወደዚህ ፡ ይሰደዋል ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ኼዱም ፡ ውርንጫውንም ፡ በመንገድ ፡ መተላለፊያ ፡ በደጅ ፡ ውጭ ፡ ታስሮ ፡ አገኙት ፥ ፈቱትም ፦

ማር. ፡ 11 ፡ 5 ፤ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ አንዳንዶቹ ፦ ውርንጫውን ፡ የምትፈቱት ፡ ምን ፡ ልታደርጉት ፡ ነው ፡ አሏቸው ።

ማር. ፡ 11 ፡ 6 ፤ እነርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ እንዳዘዘ ፡ አሏቸው ፤ ተዉአቸውም ፦

ማር. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ውርንጫውንም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ አመጡት ፥ ልብሳቸውንም ፡ በላዩ ፡ ጣሉ ፥ ተቀመጠበትም ።

ማር. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ልብሳቸውን ፡ በመንገድ ፡ ላይ ፡ አነጠፉ ፥ ሌላዎችም ፡ ከዛፍ ፡ ቅጠሎችን ፡ እየቈረጡ ፡ ያነጥፉ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 11 ፡ 9 ፤ የሚቀድሙትም ፡ የሚከተሉትም ፦ ሆሣዕና ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤

ማር. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የምትመጣ ፡ የአባታችን ፡ የዳዊት ፡ መንግሥት ፡ የተባረከች ፡ ናት ፤ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ፤ ዘወር ፡ ብሎም ፡ ዙሉን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፥ ጊዜው ፡ መሽቶ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ወጣ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 12 ፤ በማግስቱም ፡ ከቢታንያ ፡ ሲወጡ ፡ ተራበ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ቅጠልም ፡ ያላት ፡ በለስ ፡ ከሩቅ ፡ አይቶ ፡ ምናልባት ፡ አንዳች ፡ ይገኝባት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብሎ ፡ መጣ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የበለስ ፡ ወራት ፡ አልነበረምና ፡ መጥቶ ፡ ከቅጠል ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ አላገኘባትም ።

ማር. ፡ 11 ፡ 14 ፤ መልሶም ፦ ካኹን ፡ ዠምሮ ፡ ለዘለዓለም ፡ ማንም ፡ ከአንቺ ፡ ፍሬ ፡ አይብላ ፡ አላት ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሰሙ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ መጡ ። ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ በመቅደስ ፡ የሚሸጡትንና ፡ የሚገዙትን ፡ ያወጣ ፡ ዠመር ፥ የገንዘብ ፡ ለዋጮችንም ፡ ገበታዎች ፡ የርግብ ፡ ሻጪዎችንም ፡ ወንበሮች ፡ ገለበጠ ፤

ማር. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ዕቃም ፡ ተሸክሞ ፡ ማንም ፡ በመቅደስ ፡ ሊያልፍ ፡ አልፈቀደም ።

ማር. ፡ 11 ፡ 17 ፤ አስተማራቸውም ፦ ቤቴ ፡ ለአሕዛብ ፡ ዙሉ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ትባላለች ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧ እናንተ ፡ ግን ፡ የወንበዴዎች ፡ ዋሻ ፡ አደረጋችኋት ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 11 ፡ 18 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ጻፊዎችም ፡ ሰምተው ፥ ሕዝቡ ፡ ዙሉ ፡ በትምህርቱ ፡ ይገረሙ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ ይፈሩት ፡ ነበርና ፥ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዲያጠፉት ፡ ፈለጉ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ማታ ፡ ማታም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጣ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ማለዳም ፡ ሲያልፉ ፡ በለሲቱን ፡ ከሥሯ ፡ ደርቃ ፡ አይዋት ።

ማር. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ጴጥሮስም ፡ ትዝ ፡ ብሎት ። መምህር ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ የረገምኻት ፡ በለስ ፡ ደርቃለች ፡ አለው ።

ማር. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 23 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ማንም ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ እንዲደረግለት ፡ ቢያምን ፡ በልቡ ፡ ሳይጠራጠር ፥ ይህን ፡ ተራራ ፦ ተነቅለኽ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተወርወር ፡ ቢል ፡ ይኾንለታል ።

ማር. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ እላችኋለኹ ፥ የጸለያችኹትን ፡ የለመናችኹትንም ፡ ዙሉ ፡ እንዳገኛችኹት ፡ እመኑ ፥ ይኾንላችኹማል ።

ማር. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ለጸሎትም ፡ በቆማችኹ ፡ ጊዜ ፥ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችኹ ፡ ደግሞ ፡ ኀጢአታችኹን ፡ ይቅር ፡ እንዲላችኹ ፥ በማንም ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢኖርባችኹ ፡ ይቅር ፡ በሉት ።

ማር. ፡ 11 ፡ 26 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ ባትሉ ፡ በሰማያት ፡ ያለው ፡ አባታችኹም ፡ ኀጢአታችኹን ፡ ይቅር ፡ አይላችኹም ።

ማር. ፡ 11 ፡ 27 ፤ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጡ ። ርሱም ፡ በመቅደስ ፡ ሲመላለስ ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጻፊዎች ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፦

ማር. ፡ 11 ፡ 28 ፤ እነዚህን ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ ታደርጋለኽ ፧ ወይስ ፡ እነዚህን ፡ ለማድረግ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ማን ፡ ሰጠኽ ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔም ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቃችኋለኹ ፥ እናንተም ፡ መልሱልኝ ፥ እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ እነግራችኋለኹ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 30 ፤ የዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ከሰማይ ፡ ነበረችን ፡ ወይስ ፡ ከሰው ፧ መልሱልኝ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ሲነጋገሩ ፦ ከሰማይ ፡ ነው ፡ ብንል ፦ እንግዲያውስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አላመናችኹበትም ፧ ይለናል ፤

ማር. ፡ 11 ፡ 32 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ከሰው ፡ ነው ፡ እንበልን ፧ አሉ ፤ ኾሉ ፡ ዮሐንስን ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ነቢይ ፡ ያዩት ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡን ፡ ፈሩ ።

ማር. ፡ 11 ፡ 33 ፤ ለኢየሱስም ፡ መልሰው ፦ አናውቅም ፡ አሉት ፡ ኢየሱስም ፦ እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ አልነግራችኹም ፡ አላቸው ።

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ማር. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በምሳሌም ፡ ይነግራቸው ፡ ገመር ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ የወይን ፡ አትክልት ፡ ተከለ ፥ ቅጥርም ፡ ቀጠረለት ፥ መጥመቂያም ፡ ማሰለት ፥ ግንብም ፡ ሠራና ፡ ለገበሬዎች ፡ አከራይቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 2 ፤ በጊዜውም ፡ ከወይን ፡ አትክልት ፡ ፍሬ ፡ ከገበሬዎቹ ፡ እንዲቀበል ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ወደ ፡ ገበሬዎቹ ፡ ላከ ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ይዘውም ፡ ደበደቡት ፡ ባዶውንም ፡ ሰደዱት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ዳግመኛም ፡ ሌላውን ፡ ባሪያ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ላከ ፡ ርሱንም ፡ ወግረው ፡ ራሱን ፡ አቈሰሉት ፡ አዋርደውም ፡ ሰደዱት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ሌላውንም ፡ ላከ ፤ ርሱንም ፡ ገደሉት ፥ ከሌላዎችም ፡ ከብዙዎች ፡ አንዳንዱን ፡ ደበደቡ ፡ አንዳንዱንም ፡ ገደሉ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 6 ፤ የሚወደው ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ገና ፡ ነበረው ፤ ልጄንስ ፡ ያፍሩታል ፡ ብሎ ፡ ርሱን ፡ ከኾሉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ላከ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 7 ፤ እነዚያ ፡ ገበሬዎች ፡ ግን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ኑ ፥ እንግደለው ፥ ርስቱም ፡ ለኛ ፡ ይኾናል ፡ ተባባሉ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ይዘውም ፡ ገደሉት ፥ ከወይኑም ፡ አትክልት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጣሉት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 9 ፤ እንግዲህ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፧ ይመጣል ፥ ገበሬዎቹንም ፡ ያጠፋል ፥ የወይኑንም ፡ አትክልት ፡ ለሌላዎች ፡ ይሰጣል ።

ማር. ፡ 12 ፡ 10-11 ፤ «ግንበኞች ፡ የናቁት ፡ ድንጋይ ፡ ርሱ ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ ኾነ ፤ ይህም ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ ኾነ ፥ ለዐይኖቻችንም ፡ ድንቅ ፡ ነው» ፡ የሚለውን ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማር. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ምሳሌውንም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ዐውቀዋልና ፥ ሊይዙት ፡ ፈለጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሕዝቡን ፡ ፈሩ ። ትተውትም ፡ ኼዱ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 13 ፤ በንግግርም ፡ ሊያጠምዱት ፡ ከፈሪሳውያንና ፡ ከሄሮድስ ፡ ወገን ፡ የኾኑትን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ላኩ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 14 ፤ መጥተውም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ የሰውን ፡ ፊት ፡ ሳትመለከት ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንገድ ፡ ታስተምራለኽና ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ለማንምም ፡ እንዳታደላ ፡ እናውቃለን ፤ ለቄሳር ፡ ግብር ፡ መስጠት ፡ ተፈቅዷልን ፡ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ፧ እንስጥን ፡ ወይስ ፡ አንስጥ ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ግብዝነታቸውን ፡ ዐውቆ ፦ ለምን ፡ ትፈትኑኛላችኹ ፧ አየው ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ዲናር ፡ አምጡልኝ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 12 ፡ 16 ፤ እነርሱም ፡ አመጡለት ፦ ይህች ፡ መልክ ፡ ጽሕፈቷስ ፡ የማን ፡ ናት ፧ አላቸው ፤ እነርሱም ፦ የቄሳር ፡ ናት ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ የቄሳርን ፡ ለቄሳር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስረክቡ ፡ አላቸው ። በርሱም ፡ ተደነቁ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፡ ጠየቁት ፡ እንዲህም ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 19 ፤ መምህር ፡ ሆይ ፥ ሙሴ ፦ የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንድም ፡ ሚስቱን ፡ ትቶ ፡ ልጅ ፡ ሳያስቀር ፡ ቢሞት ፥ ወንድሙ ፡ ሚስቱን ፡ አግብቶ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ ይተካ ፡ ብሎ ፡ ጻፈልን ።

ማር. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ሰባት ፡ ወንድማማቾች ፡ ነበሩ ፤ ፊተኛውም ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ዘር ፡ ሳያስቀር ፡ ሞተ ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ኹለተኛውም ፡ አገባት ፥ ዘርም ፡ ሳይተው ፡ ሞተ ፤ ሦስተኛውም ፡ እንዲሁ ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ሰባቱም ፡ አገቧት ፥ ዘርም ፡ አላስቀሩም ። ከኹሉም ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ደግሞ ፡ ሞተች ።

ማር. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ሰባቱ ፡ አግብተዋታልና ፥ በትንሣኤ ፡ ቀን ፡ ሲነሡ ፡ ከነርሱ ፡ ለማናቸው ፡ ሚስት ፡ ትኾናለች ፧

ማር. ፡ 12 ፡ 24 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ መጻሕፍትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ኀይል ፡ አታውቁምና ፡ ስለዚህ ፡ የምትስቱ ፡ አይደለምን ፧

ማር. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ከሙታንስ ፡ ሲነሡ ፡ በሰማያት ፡ እንዳሉ ፡ መላእክት ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፡ አያገቡም ፥ አይጋቡምም ።

ማር. ፡ 12 ፡ 26 ፤ ስለ ፡ ሙታን ፡ ግን ፡ እንዲነሡ ፡ እግዚአብሔር ፦ እኔ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ እንዳለው ፡ በሙሴ ፡ መጽሐፍ ፡ በቀጥቋጦው ፡ ዘንድ ፡ የተጻፈውን ፡ አላነበባችኹምን ፧

ማር. ፡ 12 ፡ 27 ፤ የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡ አይደለም ። እንግዲህ ፡ እጅግ ፡ ትስታላችኹ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 28 ፤ ከጻፊዎችም ፡ አንዱ ፡ ቀርቦ ፡ ሲከራከሩ ፡ ሰማና ፡ መልካም ፡ አድርጎ ፡ እንደ ፡ መለሰላቸው ፡ አስተውሎ ፦ ከኹሉ ፡ ፊተኛዉቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ማናቸዉቱ ፡ ናት ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ማር. ፡ 12 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ከትእዛዛቱ ፡ ኹሉ ፡ ፊተኛዉቱ ፦ እስራኤል ፡ ሆይ ፥ ስማ ፤ ጌታ ፡ አምላካችን ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ ነው ፥

ማር. ፡ 12 ፡ 30 ፤ አንተም ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ነፍስኽ ፡ በፍጹምም ፡ ዐሳብኽ ፡ በፍጹምም ፡ ኀይልኽ ፡ ጌታ ፡ አምላክኽን ፡ ውደድ ፡ የምትል ፡ ናት ። ፊተኛዉ ፡ ትእዛዝ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ማር. ፡ 12 ፡ 31 ፤ ኹለተኛዉ ፡ ግን ፡ ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፡ የምትል ፡ ርሷን ፡ የምትመስል ፡ ይህች ፡ ናት ። ከነዚህ ፡ የምትበልጥ ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ የለችም ።

ማር. ፡ 12 ፡ 32 ፤ ጸሐፊውም ፦ መልካም ፡ ነው ፥ መምህር ፡ ሆይ ፤ አንድ ፡ ነው ፥ ከርሱም ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ ብለኽ ፡ በእውነት ፡ ተናገርኽ ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 33 ፤ በፍጹም ፡ ልብ ፡ በፍጹም ፡ አእምሮም ፡ በፍጹም ፡ ነፍስም ፡ በፍጹም ፡ ኀይልም ፡ ርሱን ፡ መውደድ ፥ ባልንጀራንም ፡ እንደ ፡ ራስ ፡ መውደድ ፡ በሙሉ ፡ ከሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ከሌላው ፡ መሥዋዕት ፡ ኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነው ፡ አለው ።

ማር. ፡ 12 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ በአእምሮ ፡ እንደ ፡ መለሰ ፡ አይቶ ፦ አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የራቅኽ ፡ አይደለኽም ፡ አለው ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ማንም ፡ ሊጠይቀው ፡ አልደፈረም ።

ማር. ፡ 12 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፡ በመቅደስ ፡ ሲያስተምር ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ጸሐፊዎች ፡ ክርስቶስ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ ይላሉ ፧

ማር. ፡ 12 ፡ 36 ፤ ዳዊት ፡ ራሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፦ ጌታ ፡ ጌታዬን ፦ ጠላቶችኽን ፡ የእግርኽ ፡ መረገጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡ አለ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 37 ፤ ዳዊትም ፡ ራሱ ፡ ጌታ ፡ አለው ፤ እንዴትስ ፡ ልጁ ፡ ይኾናል ፧ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ በደስታ ፡ ይሰሙት ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 12 ፡ 38-39 ፤ ሲያስተምርም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ረዣዥም ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ መዞርን ፥ በገበያም ፡ ሰላምታን ፥ በምኩራብም ፡ የከበሬታን ፡ ወንበር ፥ በግብርም ፡ የከበሬታን ፡ ስፍራ ፡ ከሚወዱ ፡ ከጸሐፊዎች ፡ ተጠበቁ ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 40 ፤ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ የሚበሉ ፡ ጸሎታቸውንም ፡ በማስረዘም ፡ የሚያመካኙ ፡ እነዚህ ፡ የባሰ ፡ ፍርድ ፡ ይቀበላሉ ።

ማር. ፡ 12 ፡ 41 ፤ ኢየሱስም ፡ በመዝገብ ፡ አንጻር ፡ ተቀምጦ ፡ ሕዝቡ ፡ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ እንዴት ፡ እንዲጥሉ ፡ ያይ ፡ ነበር ፤ ብዙ ፡ ባለጠጋዎችም ፡ ብዙ ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 42 ፤ አንዲትም ፡ ድኻ ፡ መበለት ፡ መጥታ ፡ አንድ ፡ ሳንቲም ፡ የሚያኽሉ ፡ ኹለት ፡ ናስ ፡ ጣለች ።

ማር. ፡ 12 ፡ 43 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ ጠርቶ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በመዝገብ ፡ ውስጥ ፡ ከሚጥሉት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ይህች ፡ ድኻ ፡ መበለት ፡ አብልጣ ፡ ጣለች ፤

ማር. ፡ 12 ፡ 44 ፤ ኹሉ ፡ ከትርፋቸው ፡ ጥለዋልና ፥ ይህች ፡ ግን ፡ ከጕድለቷ ፡ የነበራትን ፡ ኹሉ ፡ ትዳሯን ፡ ኹሉ ፡ ጣለች ፡ አላቸው ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ማር. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ርሱም ፡ ከመቅደስ ፡ ሲወጣ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ድንጋይዎችና ፡ እንዴት ፡ ያሉ ፡ ሕንጻዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እይ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እነዚህን ፡ ታላላቅ ፡ ሕንጻዎች ፡ ታያለኽን ፧ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ በዚህ ፡ አይቀርም ፡ አለው ።

ማር. ፡ 13 ፡ 3 ፤ በመቅደስም ፡ ትይዩ ፡ በደብረ ፡ ዘይት ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ ጴጥሮስና ፡ ያዕቆብ ፡ ዮሐንስም ፡ እንድርያስም ።

ማር. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ንገረን ፥ ይህ ፡ መቼ ፡ ይኾናል ፧ ይህስ ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ለብቻቸው ፡ ጠየቁት ።

ማር. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ ይላቸው ፡ ዠመር ፦ ማንም ፡ እንዳያስታችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ብዙዎች ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ይመጣሉና ፥ ብዙዎችንም ፡ ያስታሉ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ጦርንም ፡ የጦርንም ፡ ወሬ ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፡ አትደንግጡ ፤ ይህ ፡ ሊኾን ፡ ግድ ፡ ነውና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መጨረሻው ፡ ገና ፡ ነው ።

ማር. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ሕዝብ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፡ መንግሥትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ይነሣልና ፤ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ይኾናል ፤ ራብ ፡ ይኾናል ፤ እነዚህ ፡ የምጥ ፡ ጣር ፡ መዠመሪያ ፡ ናቸው ።

ማር. ፡ 13 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፡ በምኩራብም ፡ ትገረፋላችኹ ፡ ምስክርም ፡ ይኾንባቸው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ በገዢዎችና ፡ በነገሥታት ፡ ፊት ፡ ትቆማላችኹ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 10 ፤ አስቀድሞም ፡ ወንጌል ፡ ለአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይሰበክ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

ማር. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ሲጐትቷችኹና ፡ አሳልፈው ፡ ሲሰጧችኹም ፡ ምን ፡ እንድትናገሩ ፡ አስቀድማችኹ ፡ አትጨነቁ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ የሚሰጣችኹን ፡ ተናገሩ ፤ የሚነግረው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ አይደላችኹምና ።

ማር. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ወንድምም ፡ ወንድሙን ፡ አባትም ፡ ልጁን ፡ ለሞት ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፥ ልጆችም ፡ በወላጆቻቸው ፡ ላይ ፡ ይነሣሉ ፤ ይገድሏቸውማል ።

ማር. ፡ 13 ፡ 13 ፤ በኹሉም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተጠላችኹ ፡ ትኾናላችኹ ፤ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ የሚጸና ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ይድናል ።

ማር. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በነቢዩ ፡ በዳንኤል ፡ የተባለውን ፡ የጥፋት ፡ ርኵሰት ፡ በማይገባው ፡ ስፍራ ፡ ቆሞ ፡ ብታዩ ፥ አንባቢው ፡ ያስተውል ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ይሸሹ ፥

ማር. ፡ 13 ፡ 15 ፤ በሰገነትም ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አይውረድ ፡ ከቤቱም ፡ አንዳች ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ አይግባ ፥

ማር. ፡ 13 ፡ 16 ፤ በዕርሻም ፡ ያለ ፡ ልብሱን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመለስ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 17 ፤ በዚያ ፡ ወራትም ፡ ለእርጉዞችና ፡ ለሚያጠቡ ፡ ወዮላቸው ።

ማር. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሸሽታችኹ ፡ በክረምት ፡ እንዳይኾን ፡ ጸልዩ ፤

ማር. ፡ 13 ፡ 19 ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ ከፍጥረት ፡ መዠመሪያ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ያልኾነ ፡ ደግሞም ፡ የማይኾን ፡ የመከራ ፡ ዐይነት ፡ ይኾናልና ።

ማር. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ጌታስ ፡ ወራቶቹን ፡ ባያሳጥር ፥ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ ባልዳነም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለመረጣቸው ፡ ምርጦች ፡ ወራቶቹን ፡ አሳጠረ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ማንም ፦ እንሆ ፥ ክርስቶስ ፡ ከዚህ ፡ አለ ፥ ወይም ፦ እንሆ ፥ ከዚያ ፡ አለ ፡ ቢላችኹ ፡ አትመኑ ፤

ማር. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ሐሰተኞች ፡ ክርስቶሶችና ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ይነሣሉና ፥ ቢቻላቸውስ ፡ የተመረጡትን ፡ እንኳ ፡ ያስቱ ፡ ዘንድ ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ያደርጋሉ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 23 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ተጠንቀቁ ፤ እንሆ ፥ አስቀድሜ ፡ ኹሉን ፡ ነገርኋችኹ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 24 ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ መከራ ፡ በኋላ ፡ ፀሓይ ፡ ይጨልማል ፡ ጨረቃም ፡ ብርሃኗን ፡ አትሰጥም ፥

ማር. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ከዋክብትም ፡ ከሰማይ ፡ ይወድቃሉ ፥ የሰማያትም ፡ ኀይላት ፡ ይናወጣሉ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በብዙ ፡ ኀይልና ፡ ክብር ፡ በደመና ፡ ሲመጣ ፡ ያዩታል ።

ማር. ፡ 13 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ መላእክትን ፡ ይልካል ፡ ከአራቱ ፡ ነፋሳትም ፡ ከምድር ፡ ዳርቻ ፡ እስከሰማይ ፡ ዳርቻ ፡ የተመረጡትን ፡ ይሰበስባቸዋል ።

ማር. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ምሳሌውንም ፡ ከበለስ ፡ ተማሩ ፤ ጫፏ ፡ ሲለሰልስ ፡ ቅጠሏም ፡ ሲያቈጠቍጥ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጋ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ታውቃላችኹ ፤

ማር. ፡ 13 ፡ 29 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ መኾኑን ፡ ስታዩ ፡ ቀርቦ ፡ በደጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕወቁ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 30 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ትውልድ ፡ አያልፍም ።

ማር. ፡ 13 ፡ 31 ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ።

ማር. ፡ 13 ፡ 32 ፤ ስለዚያች ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ ስለዚያች ፡ ሰዓት ፡ ግን ፡ የሰማይ ፡ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፡ ልጅም ፡ ቢኾን ፡ ከአባት ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ።

ማር. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ጊዜው ፡ መቼ ፡ እንዲኾን ፡ አታውቁምና ፡ ተጠንቀቁ ፤ ትጉ ፤ ጸልዩም ።

ማር. ፡ 13 ፡ 34 ፤ ቤቱን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እንደ ፡ ኼደ ፡ ሰው ፡ ነው ፥ ለባሮቹም ፡ ሥልጣን ፡ ለያንዳንዱም ፡ ሥራውን ፡ ሰጥቶ ፡ በረኛውን ፡ እንዲተጋ ፡ አዘዘ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 35 ፤ እንግዲህ ፡ በማታ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ወይም ፡ ዶሮ ፡ ሲጮኽ ፡ ወይም ፡ በማለዳ ፡ ቢኾን ፡ ባለቤቱ ፡ መቼ ፡ እንዲመጣ ፡ አታውቁምና ፡

ማር. ፡ 13 ፡ 36 ፤ ድንገት ፡ መጥቶ ፡ ተኝታችኹ ፡ እንዳያገኛችኹ ፡ ስለዚህ ፡ ትጉ ።

ማር. ፡ 13 ፡ 37 ፤ ለእናንተም ፡ የምነግራችኹ ፡ ለኹሉ ፡ እላለኹ ፤ ትጉ ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ማር. ፡ 14 ፡ 1 ፤ ከኹለት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ፋሲካና ፡ የቂጣ ፡ በዓል ፡ ነበረ ። የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ጻፊዎችም ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ በተንኰል ፡ እንደሚይዙትና ፡ እንደሚገድሉት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 14 ፡ 2 ፤ የሕዝብ ፡ ሁከት ፡ እንዳይኾን ፡ በበዓል ፡ አይኹን ፡ ይሉ ፡ ነበርና ።

ማር. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ በቢታንያ ፡ በለምጻሙ ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ በማእዱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፥ አንዲት ፡ ሴት ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ ጥሩ ፡ ናርዶስ ፡ ሽቱ ፡ የመላበት ፡ የአልባስጥሮስ ፡ ቢልቃጥ ፡ ይዛ ፡ መጣች ፤ ቢልቃጡንም ፡ ሰብራ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰችው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 4 ፤ አንዳንዶችም ፦ ይህ ፡ የሽቱ ፡ ጥፋት ፡ ለምንድር ፡ ነው ፧

ማር. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ይህ ፡ ሽቱ ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ በሚበልጥ ፡ ዋጋ ፡ ተሸጦ ፡ ለድኻዎች ፡ ሊሰጥ ፡ ይቻል ፡ ነበርና ፥ ብለው ፡ በራሳቸው ፡ ይቈጡ ፡ ነበር ፤ ርሷንም ፡ ነቀፏት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ተዋ፧ት ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ታደክሚታላችኹ ፧ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሠርታልኛለች ።

ማር. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ድኻዎች ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉና ፥ በማናቸውም ፡ በወደዳችኹት ፡ ጊዜ ፡ መልካም ፡ ልታደርጉላቸው ፡ ትችላላችኹ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አልኖርም ።

ማር. ፡ 14 ፡ 8 ፤ የተቻላትን ፡ አደረገች ፤ አስቀድማ ፡ ለመቃብሬ ፡ ሥጋዬን ፡ ቀባችው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 9 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ወንጌል ፡ በዓለሙ ፡ ዅሉ ፡ በሚሰበክበት ፡ በማናቸውም ፡ ስፍራ ፥ ርሷ ፡ ያደረገችው ፡ ደግሞ ፡ ለርሷ ፡ መታሰቢያ ፡ ሊኾን ፡ ይነገራል ።

ማር. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ አንዱ ፡ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ኼደ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ሲሰሙም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ ብርም ፡ ይሰጡት ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ሰጡት ። በሚመች ፡ ጊዜም ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጠው ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 14 ፡ 12 ፤ ፋሲካን ፡ በሚያርዱበት ፡ በቂጣ ፡ በዓል ፡ መዠመሪያ ፡ ቀን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ። ፋሲካን ፡ ትበላ ፡ ዘንድ ፡ ወዴት ፡ ኼደን ፡ ልናሰናዳ ፡ ትወዳለኽ ፧ አሉት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ኹለት ፡ ላከ ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ወደ ፡ ከተማ ፡ ኺዱ ፥ ማድጋ ፡ ውሃ ፡ የተሸከመ ፡ ሰውም ፡ ይገናኛችኋል ፤

ማር. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ተከተሉት ፥ የሚገባበትንም ፡ የቤቱን ፡ ጌታ ፦ መምህሩ ፦ ከደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ጋራ ፡ ፋሲካን ፡ የምበላበት ፡ የእንግዳ ፡ ቤት ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ይላል ፡ በሉት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ርሱም ፡ በደርብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የተሰናዳና ፡ የተነጠፈ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ያሳያችኋል ፤

ማር. ፡ 14 ፡ 16 ፤ በዚያም ፡ አሰናዱልን ፦ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወጡ ፡ ወደ ፡ ከተማም ፡ ኼደው ፡ እንዳላቸው ፡ አገኙ ፥ ፋሲካንም ፡ አሰናዱ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 17 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ጋራ ፡ መጣ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ተቀምጠውም ፡ ሲበሉ ፡ ኢየሱስ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከእናንተ ፡ አንዱ ፥ ርሱም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የሚበላው ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኛል ፡ አለ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፡ ያዝኑ ፥ እያንዳንዳቸውም ፦ እኔ ፡ እኾንን ፧ ይሉት ፡ ዠመር ።

ማር. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ወጭቱ ፡ እጁን ፡ የሚያጠልቀው ፡ ነው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 21 ፤ የሰው ፡ ልጅስ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ይኼዳል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ዐልፎ ፡ ለሚሰጥበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ባልተወለደ ፡ ይሻለው ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ሲበሉም ፡ ኢየሱስ ፡ እንጀራን ፡ አንሥቶ ፡ ባረከ ፡ ቈርሶም ፡ ሰጣቸውና ፦ እንካችኹ ፤ ይህ ፡

ሥጋዬ ፡ ነው ፡ አለ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ጽዋንም ፡ አንሥቶ ፡ አመስግኖም ፡ ሰጣቸው ፥ ኹሉም ፡ ከርሱ ፡ ጠጡ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 24 ፤ ርሱም ፦ ይህ ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ የሚፈስ ፡ የዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ደሜ ፡ ነው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 25 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከወይኑ ፡ ፍሬ ፡ ዐዲሱን ፡ እስከምጠጣበት ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ደግሞ ፡ አልጠጣውም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 26 ፤ መዝሙርም ፡ ከዘመሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወጡ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ኢየሱስም ፦ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ኹላችኹ ፡ በእኔ ፡ ትሰናከላላችኹ ፤ እረኛውን ፡ እመታለኹ ፥ በጎችም ፡ ይበተናሉ ፡ የሚል ፡ ተጽፏልና ።

ማር. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከተነሣኹ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እቀድማችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ጴጥሮስም ፦ ኹሉም ፡ ቢሰናከሉ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ አልሰናከልም ፡ አለው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፦ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ዶሮ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለኽ ፡ አለው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 31 ፤ ርሱም ፡ ቃሉን ፡ አበርትቶ ፦ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የምሞት ፡ እንኳ ፡ ቢኾን ፡ ከቶ ፡ አልክድኽም ፡ አለ ። ኹሉም ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ጌቴሴማኒ ፡ ወደምትባልም ፡ ስፍራ ፡ መጡ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፦ ስጸልይ ፡ ሳለኹ ፥ በዚህ ፡ ተቀመጡ ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 33 ፤ ጴጥሮስንና ፡ ያዕቆብን ፡ ዮሐንስንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፤ ሊደነግጥም ፡ ሊተክዝም ፡ ገሥመረና ፦

ማር. ፡ 14 ፡ 34 ፤ ነፍሴ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ዐዘነች ፤ በዚህ ፡ ቈዩ ፡ ትጉም ፡ አላቸው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 35 ፤ ጥቂትም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ በምድርም ፡ ወድቆ ፥ ይቻልስ ፡ ቢኾን ፡ ሰዓቲቱ ፡ ከርሱ ፡ እንድታልፍ ፡ ጸለየና ፦

ማር. ፡ 14 ፡ 36 ፤ አባ ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ኹሉ ፡ ይቻልኻል ፤ ይህችን ፡ ጽዋ ፡ ከእኔ ፡ ውሰድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ የምትወደው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ የምወደው ፡ አይኹን ፡ አለ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 37 ፤ መጣም ፡ ተኝተውም ፡ አገኛቸው ፥ ጴጥሮስንም ፦ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ ተኝተኻልን ፧ አንዲት ፡ ሰዓት ፡ ስንኳ ፡ ልትተጋ ፡ አልቻልኽምን ፧

ማር. ፡ 14 ፡ 38 ፤ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ትጉ ፡ ጸልዩም ፤ መንፈስስ ፡ ተዘጋጅታለች ፥ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ አለው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 39 ፤ ደግሞም ፡ ኼዶ ፡ ያንኑ ፡ ቃል ፡ ጸለየ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 40 ፤ ደግሞም ፡ መጥቶ ፡ ዐይኖቻቸው ፡ በእንቅልፍ ፡ ከብደው ፡ ነበርና ፥ ተኝተው ፡ አገኛቸው ፥ የሚመልሱለትንም ፡ አላወቁም ።

ማር. ፡ 14 ፡ 41 ፤ ሦስተኛም ፡ መጥቶ ፦ እንግዲህስ ፡ ተኙ ፡ ዕረፉም ፤ ይበቃል ፤ ሰዓቲቱ ፡

ደረሰች ፤ እንሆ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀጢአተኞች ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ይሰጣል ።

ማር. ፥ 14 ፥ 42 ፤ ተነሡ ፥ እንኺድ ፤ እንሆ ፥ አሳልፎ ፡ የሚሰጠኝ ፡ ቀርቧል ፡ አላቸው ።

ማር. ፥ 14 ፥ 43 ፤ ወዲያውም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ ይሁዳ ፡ መጣ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰይፍና ፡ ጐመድ ፡ ይዘው ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ከጻፊዎች ፡ ከሽማግሌዎችም ፡ ዘንድ ፡ መጡ ።

ማር. ፥ 14 ፥ 44 ፤ አሳልፎ ፡ የሚሰጠውም ፦ የምስመው ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ ያዙት ፡ ተጠንቅቃችኹም ፡ ውሰዱት ፡ ብሎ ፡ ምልክት ፡ ሰጥቷቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 14 ፥ 45 ፤ መጥቶም ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረበና ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ መምህር ፡ ሆይ ፥ ብሎ ፡ ሳመው ፤

ማር. ፥ 14 ፥ 46 ፤ እነርሱም ፡ እጃቸውን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጭነው ፡ ያዙት ።

ማር. ፥ 14 ፥ 47 ፤ በአጠገብ ፡ ከቆሙት ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ሰይፉን ፡ መዞ ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ባሪያ ፡ መታ ፡ ጆሮውንም ፡ ቈረጠ ።

ማር. ፥ 14 ፥ 48 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ወንበዴ ፡ እንደምትይዙ ፡ ሰይፍና ፡ ጐመድ ፡ ይዛችኹ ፡ ልትይዙኝ ፡ መጣችኹን ፧

ማር. ፥ 14 ፥ 49 ፤ በመቅደስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያስተማርኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ስኖር ፡ አልያዛችኹኝም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መጻሕፍት ፡ ይፈጸሙ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ኾነ ፡ አላቸው ።

ማር. ፥ 14 ፥ 50 ፤ ኹሉም ፡ ትተውት ፡ ሸሹ ።

ማር. ፥ 14 ፥ 51 ፤ ዕርቃኑን ፡ በነጠላ ፡ የሸፈነ ፡ አንድ ፡ ጐበዝ ፡ ይከተለው ፡ ነበር ፥

ማር. ፥ 14 ፥ 52 ፤ ጐበዛዝቱም ፡ ያዙት ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ነጠላውን ፡ ትቶ ፡ ዕራቍቱን ፡ ሸሸ ።

ማር. ፥ 14 ፥ 53 ፤ ኢየሱስንም ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ወሰዱት ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ኹሉ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ጻፊዎችም ፡ ተሰበሰቡ ።

ማር. ፥ 14 ፥ 54 ፤ ጴጥሮስም ፡ እስከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ በሩቁ ፡ ተከተለው ፥ ከሎሌዎችም ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፡ እሳት ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ።

ማር. ፥ 14 ፥ 55 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ሸንጎውም ፡ ኹሉ ፡ እንዲገድሉት ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ ምስክር ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፥ አላገኙምም ፤

ማር. ፥ 14 ፥ 56 ፤ ብዙዎች ፡ በሐሰት ፡ ይመሰክሩበት ፡ ነበርና ፥ ምስክርነታቸው ፡ ግን ፡ አልተሰማማም ።

ማር. ፥ 14 ፥ 57-58 ፤ ሰዎችም ፡ ተነሥተው ፦ እኔ ፡ ይህን ፡ በእጅ ፡ የተሠራውን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፈርሰዋለኹ ፡ በሦስት ፡ ቀንም ፡ ሌላውን ፡ በእጅ ፡ ያልተሠራውን ፡ እሠራለኹ ፡ ሲል ፡ ሰማነው ፡ ብለው ፡ በሐሰት ፡ መሰከሩበት ።

ማር. ፥ 14 ፥ 59 ፤ ምስክርነታቸውም ፡ እንዲሁ ፡ እንኳ ፡ አልተሰማማም ።

ማር. ፥ 14 ፥ 60 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ በመካከላቸው ፡ ተነሥቶ ፦ አንዳች ፡ አትመልስምን ፧ እነዚህስ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ የሚመሰክሩብኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ኢየሱስን ፡ ጠየቀው ።

ማር. ፥ 14 ፥ 61 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አለ ፥ አንዳችም ፡ አልመለሰም ። ደግሞ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡

ጠየቀውና ፦ የቡሩክ ፡ ልጅ ፡ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 62 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ ነኝ ፤ የሰው ፡ ልጅም ፡ በኀይል ፡ ቀኝ ፡ ሲቀመጥ ፡ በሰማይም ፡ ደመና ፡ ሲመጣ ፡ ታያላችኹ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 63 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደና ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ምስክሮችን ፡ ምን ፡ ያስፈልገናል ፧

ማር. ፡ 14 ፡ 64 ፤ ስድቡን ፡ ሰማችኹ ፤ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ አለ ። እነርሱም ፡ ኹሉ ፦ ሞት ፡ ይገባዋል ፡ ብለው ፡ ፈረዱበት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 65 ፤ አንዳንዶችም ፡ ይተፉበት ፡ ፊቱንም ፡ ሸፍነው ፡ ይጐሰሙትና ፦ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ ይሉት ፡ ገቦመር ፤ ሎሌዎችም ፡ በጥፊ ፡ እየመቱ ፡ ወሰዱት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 66 ፤ ጴጥሮስም ፡ በግቢ ፡ ውስጥ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ሳለ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ገረዶች ፡ አንዲቱ ፡ መጣች ፥

ማር. ፡ 14 ፡ 67 ፤ ጴጥሮስም ፡ እሳት ፡ ሲሞቅ ፡ አይታ ፡ ተመለከተችውና ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከናዝሬቱ ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ነበርኽ ፡ አለችው ።

ማር. ፡ 14 ፡ 68 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የምትዩውን ፡ አላውቅም ፡ አላስተውልምም ፡ ብሎ ፡ ካደ ። ወደ ፡ ውጭም ፡ ወደ ፡ ደጅ ፡ ወጣ ፤ ዶሮም ፡ ጮኸ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 69 ፤ ገረዲቱም ፡ አይታው ፡ በዚያ ፡ ለቆሙት ፦ ይህም ፡ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ስትል ፡ ኹለተኛ ፡ ትነግራቸው ፡ ገቦመር ።

ማር. ፡ 14 ፡ 70 ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ካደ ። ጥቂት ፡ ቈይተውም ፡ በዚያ ፡ የቆሙት ፡ ዳግመኛ ፡ ጴጥሮስን ፦ የገሊላ ፡ ሰው ፡ ነኽና ፥ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ በእውነት ፡ ነኽ ፡ አሉት ።

ማር. ፡ 14 ፡ 71 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ይህን ፡ የምትሉትን ፡ ሰው ፡ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ይረገምና ፡ ይምል ፡ ገቦመር ። ወዲያውም ፡ ዶሮ ፡ ኹለተኛ ፡ ጮኸ ።

ማር. ፡ 14 ፡ 72 ፤ ጴጥሮስንም ፡ ኢየሱስ ፦ ዶሮ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለኽ ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለው ፤ ነገሩንም ፡ ዐስቦ ፡ አለቀሰ ።

_____የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ማር. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ወዲያውም ፡ ማለዳ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ከሽማግሌዎችና ፡ ከጻፊዎች ፡ ከሸንጎውም ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከተማከሩ ፡ በኋላ ፥ ኢየሱስን ፡ አሳስረው ፡ ወሰዱትና ፡ ለጲላጦስ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ጲላጦስም ፦ አንተ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነኽን ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ርሱም ፦ አንተ ፡ አልኽ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 3 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ብዙ ፡ ያሳጡት ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ።

ማር. ፡ 15 ፡ 4 ፤ ጲላጦስም ፡ ደግሞ ፦ አንዳች ፡ አትመልስምን ፧ እንሆ ፥ በስንት ፡ ነገር ፡ ያሳጡኻል ፡ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ እስኪደነቅ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ አልመለሰም ።

ማር. ፡ 15 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ በዓል ፡ የለመኑትን ፡ አንድ ፡ እስረኛ ፡ ይፈታላቸው ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 15 ፡ 7 ፤ በዐመፅም ፡ ነፍስ ፡ ከገደሉት ፡ ከዐመፀኞች ፡ ጋራ ፡ የታሰረ ፡ በርባን ፡ የተባለ ፡ ነበረ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ሕዝቡም ፡ ወጥተው ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ያደርግላቸው ፡ ዘንድ ፡ እየጮኹ ፡ ይለምኑት ፡ ገሮመር ።

ማር. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ጲላጦስም ፦ የአይሁድን ፡ ንጉሥ ፡ እፈታላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳላችኹን ፧ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፤

ማር. ፡ 15 ፡ 10 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ በቅንአት ፡ አሳልፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ።

ማር. ፡ 15 ፡ 11 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ግን ፡ በርባንን ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ይፈታላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሕዝቡን ፡ አወኳቸው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ጲላጦስም ፡ ዳግመኛ ፡ መልሶ ፦ እንግዲህ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ የምትሉትን ፡ ምን ፡ ላደርገው ፡ ትወዳላችኹ ፧ አላቸው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ ዳግመኛ ፦ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ጲላጦስም ፦ ምን ፡ ነው ፧ ያደረገው ፡ ክፋት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ። እነርሱ ፡ ግን ፦ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጩኹት ፡ አበዙ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ጲላጦስም ፡ የሕዝቡን ፡ ፈቃድ ፡ ሊያደርግ ፡ ወዶ ፡ በርባንን ፡ ፈታላቸው ፥ ኢየሱስንም ፡ ገርፎ ፡ እንዲሰቀል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ወታደሮችም ፡ ፕራይቶሪዮን[287] ፡ ወደሚባል ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ወሰዱት ፥ ጭፍራውንም ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ጠሩ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ቀይ ፡ ልብስም ፡ አለበሱት ፥ የሾኽ ፡ አክሊልም ፡ ጐንጉነው ፡ ደፉበት ፤

ማር. ፡ 15 ፡ 18 ፤ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ እያሉ ፡ እጅ ፡ ይነሡት ፡ ገሮመር ፤

ማር. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ራሱንም ፡ በመቃ ፡ መቱት ፡ ተፉበትም ፥ ተንበርክከውም ፡ ሰገዱለት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ከተዘባበቱበትም ፡ በኋላ ፡ ቀዩን ፡ ልብስ ፡ ገፈፉት ፥ ልብሱንም ፡ አለበሱት ፥ ሊሰቅሉትም ፡ ወሰዱት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 21 ፤ አንድ ፡ መንገድ ፡ ዐላፊም ፡ የአሌክስንድሮስና ፡ የሩፎስ ፡ አባት ፡ ስምዖን ፡ የተባለ ፡ የቀሬና ፡ ሰው ፡ ከገጠር ፡ ሲመጣ ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ አስገደዱት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ትርጓሜውም ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ስፍራ ፡ ወደሚኾን ፡ ጎልጎታ ፡ ወደተባለ ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 23 ፤ ከርቤም ፡ የተቀላቀለበትን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እንዲጠጣ ፡ ሰጡት ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አልተቀበለም ።

ማር. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ሰቀሉትም ፥ ልብሱንም ፡ ማን ፡ ማን ፡ እንዲወስድ ፡ ዕጣ ፡ ተጣጥለው ፡ ተካፈሉ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 25 ፤ በሰቀሉትም ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ነበረ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 26 ፤ የክሱ ፡ ጽሕፈትም ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ የሚል ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ኹለት ፡ ወንበዴዎች ፡ አንዱን ፡ በቀኙ ፡ አንዱንም ፡ በግራው ፡ ሰቀሉ ።

---

287 ፕራይቶሪዮን ፤ ምኵናን ፥ ችሎት ።

ማር. ፡ 15 ፡ 28 ፤ መጽሐፍም ፦ ከዐመፀኞች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠረ ፡ ያለው ፡ ተፈጸመ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 29 ፤ የሚያልፉትም ፡ ራሳቸውን ፡ እየነቀነቁ ፡ ይሰድቡት ፡ ነበርና ፦ ዋ ፥ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ የምታፈርስ ፡ በሦስት ፡ ቀንም ፡ የምትሠራ ፥

ማር. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ከመስቀል ፡ ወርደኽ ፡ ራስኽን ፡ አድን ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 31 ፤ እንዲሁም ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ደግሞ ፡ ከጻፊዎች ፡ ጋራ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እየተዘባበቱ ፦ ሌላዎችን ፡ አዳነ ፤ ራሱን ፡ ሊያድን ፡ አይችልም ፤

ማር. ፡ 15 ፡ 32 ፤ አይተን ፡ እናምን ፡ ዘንድ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ክርስቶስ ፡ አኹን ፡ ከመስቀል ፡ ይውረድ ፡ አሉ ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰቀሉት ፡ ይነቅፉት ፡ ነበር ።

ማር. ፡ 15 ፡ 33 ፤ ስድስት ፡ ሰዓትም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ጨለማ ፡ ኾነ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 34 ፤ በዘጠኝ ፡ ሰዓትም ፡ ኢየሱስ ፦ ኤሎሄ ፥ ኤሎሄ ፥ ላማ ፡ ሰበቅታኒ ፧ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ፤ ትርጓሜውም ፡ አምላኬ ፥ አምላኬ ፥ ለምን ፡ ተውኸኝ ፧ ማለት ፡ ነው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 35 ፤ በዚያም ፡ ከቆሙት ፡ ሰዎች ፡ ሰምተው ፦ እንሆ ፥ ኤልያስን ፡ ይጠራል ፡ አሉ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 36 ፤ አንዱም ፡ ሮጦ ፡ ሐምጣጤ ፡ በሰፍነግ ፡ ሞላ ፡ በመቃም ፡ አድርጎ ። ተዉ ፤ ኤልያስ ፡ ሊያወርደው ፡ ይመጣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንይ ፡ እያለ ፡ አጠጣው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 37 ፤ ኢየሱስም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ፡ ነፍሱንም ፡ ሰጠ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 38 ፤ የቤተ ፡ መቅደስም ፡ መጋረጃ ፡ ከላይ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ከኹለት ፡ ተቀደደ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 39 ፤ በዚያም ፡ በአንጻሩ ፡ የቆመ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ እንደዚህ ፡ ጮኾ ፡ ነፍሱን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡ አለ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 40-41 ፤ ሴቶችም ፡ ደግሞ ፡ በሩቅ ፡ ኾነው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ፤ ከነርሱም ፡ በገሊላ ፡ ሳለ ፡ ይከተሉትና ፡ ያገለግሉት ፡ የነበሩ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያም ፡ የታናሹ ፡ ያዕቆብና ፡ የዮሳም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ሰሎሜም ፡ ነበሩ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ የወጡ ፡ ሌላዎች ፡ ብዙዎች ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 42 ፤ አኹንም ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ የሰንበት ፡ ዋዜማ ፡ የኾነ ፡ የማዘጋጀት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፥ የከበረ ፡ አማካሪ ፡ የኾነ ፡ የአርማትያስ ፡ ዮሴፍ ፡ መጣ ፥

ማር. ፡ 15 ፡ 43 ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ደፍሮም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ገባና ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ለመነው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 44 ፤ ጲላጦስም ፡ አኹኑን ፡ እንዴት ፡ ሞተ ፡ ብሎ ፡ ተደነቀ ፥ የመቶ ፡ አለቃውንም ፡ ጠርቶ ፡ ከሞተ ፡ ቈይቷልን ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ፤

ማር. ፡ 15 ፡ 45 ፤ ከመቶ ፡ አለቃውም ፡ ተረድቶ ፡ በድኑን ፡ ለዮሴፍ ፡ ሰጠው ።

ማር. ፡ 15 ፡ 46 ፤ በፍታም ፡ ገዝቶ ፡ አውርዶም ፡ በበፍታ ፡ ከፈነው ፡ ከአለትም ፡ በተወቀረ ፡ መቃብር ፡ አኖረው ፥ በመቃብሩ ፡ ደጃፍም ፡ ድንጋይ ፡ አንከባለለ ።

ማር. ፡ 15 ፡ 47 ፤ መግደላዊትም ፡ ማርያም ፡ የዮሳም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ወዴት ፡ እንዳኖሩት ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ።

የማርቆስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ማር. ፥ 16 ፥ 1 ፤ ሰንበትም ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ መግደላዊት ፡ ማርያም ፡ የያዕቆብም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ሰሎሜም ፡ መጥተው ፡ ሊቀቡት ፡ ሽቱ ፡ ገዙ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 2 ፤ ከሳምንቱም ፡ በፊተኛው ፡ ቀን ፡ እጅግ ፡ በማለዳ ፡ ፀሐይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ መጡ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 3 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ድንጋዩን ፡ ከመቃብር ፡ ደጃፍ ፡ ማን ፡ ያንከባልልልናል ፧ ይባባሉ ፡ ነበር ፤

ማር. ፥ 16 ፥ 4 ፤ ድንጋዩ ፡ እጅግ ፡ ትልቅ ፡ ነበርና ፤ አሻቅበውም ፡ አይተው ፡ ድንጋዩ ፡ ተንከባሎ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ተመለከቱ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 5 ፤ ወደ ፡ መቃብሩም ፡ ገብተው ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ የተጐናጸፈ ፡ ጕልማሳ ፡ በቀኝ ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ አዩና ፡ ደነገጡ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 6 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ አትደንግጡ ፤ የተሰቀለውን ፡ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ ትፈልጋላችኹ ፤ ተነሥቷል ፥ በዚህ ፡ የለም ፤ እንሆ ፥ ርሱን ፡ ያኖሩበት ፡ ስፍራ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኼዳችኹ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለጴጥሮስም ፦ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ይቀድማችኋል ፤ እንደ ፡ ነገራችኹ ፡ በዚያ ፡ ታዩታላችኹ ፡ ብላችኹ ፡ ንገሯቸው ፡ አላቸው ።

ማር. ፥ 16 ፥ 8 ፤ መንቀጥቀጥና ፡ መደንገጥ ፡ ይዟቸው ፡ ነበርና ፥ ወጥተው ፡ ከመቃብር ፡ ሸሹ ፤ ይፈሩ ፡ ነበርና ፥ ለማንም ፡ አንዳች ፡ አልነገሩም ። እነርሱም ፡ ያዘዛቸውን ፡ ኹሉ ፡ ለጴጥሮስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ላሉት ፡ በዐጪሩ ፡ ተናገሩ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ድኅነት ፡ የኾነውን ፡ የማይለወጠውን ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ከፀሐይ ፡ መውጫ ፡ እስከ ፡ መጥለቂያው ፡ ድረስ ፡ በእጃቸው ፡ ላከው ።

ማር. ፥ 16 ፥ 9 ፤ ከሳምንቱም ፡ በመዠመሪያው ፡ ቀን ፡ ማልዶ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፥ አስቀድሞ ፡ ሰባት ፡ አጋንንት ፡ ላወጣላት ፡ ለመግደላዊት ፡ ማርያም ፡ ታየ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 10 ፤ ርሷ ፡ ኼዳ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፡ ለነበሩት ፡ ሲያዝኑና ፡ ሲያለቅሱ ፡ ሳሉ ፡ አወራችላቸው ፤

ማር. ፥ 16 ፥ 11 ፤ እነርሱም ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለርሷም ፡ እንደ ፡ ታያት ፡ ሲሰሙ ፡ አላመኑም ።

ማር. ፥ 16 ፥ 12 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከነርሱ ፡ ለኹለቱ ፡ ወደ ፡ ባላገር ፡ ሲኼዱ ፡ በመንገድ ፡ በሌላ ፡ መልክ ፡ ተገለጠ ፤

ማር. ፥ 16 ፥ 13 ፤ እነርሱም ፡ ኼደው ፡ ለሌላዎቹ ፡ አወሩ ፤ እነዚያንም ፡ ደግሞ ፡ አላመኗቸውም ።

ማር. ፥ 16 ፥ 14 ፤ ኋላም ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ለዐሥራ ፡ አንዱ ፡ ተገለጠ ፥ ተነሥቶም ፡ ያዩትን ፡ ስላላመኗቸው ፡ አለማመናቸውንና ፡ የልባቸውን ፡ ጥንካሬ ፡ ነቀፈ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 15 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ወደ ፡ ዓለም ፡ ኹሉ ፡ ኺዱ ፥ ወንጌልንም ፡ ለፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ስበኩ ።

ማር. ፥ 16 ፥ 16 ፤ ያመነ ፡ የተጠመቀም ፡ ይድናል ፥ ያላመነ ፡ ግን ፡ ይፈረድበታል ።

ማር. ፥ 16 ፥ 17 ፤ ያመኑትንም ፡ እነዚህ ፡ ምልክቶች ፡ ይከተሏቸዋል ፤ በስሜ ፡ አጋንንትን ፡ ያወጣሉ ፤ በዐዲስ ፡ ቋንቋ ፡ ይናገራሉ ፤ እባቦችን ፡ ይይዛሉ ፥

ማር. ፥ 16 ፥ 18 ፤ የሚገድልም ፡ ነገር ፡ ቢጠጡ ፡ አይጐዳቸውም ፤ እጃቸውን ፡ በድውዮች ፡ ላይ ፡ ይጭናሉ ፡

እነርሱም ፡ ይድናሉ ።

ማር. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ።

ማር. ፡ 16 ፡ 20 ፤ እነርሱም ፡ ወጥተው ፡ በየስፍራው ፡ ኹሉ ፡ ሰበኩ ፥ ጌታም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፥ በሚከተሉትም ፡ ምልክቶች ፡ ቃሉን ፡ ያጸና ፡ ነበር ❖

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ሉቃስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 1-4 ፤ የከበርኽ ፡ ቴዎፍሎስ ፡ ሆይ ፥ ከመዠመሪያው ፡ በዐይን ፡ ያዩትና ፡ የቃሉ ፡ አገልጋዮች ፡ የኾኑት ፡ እንዳስተላለፉልን ፥ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ስለተፈጸመው ፡ ነገር ፡ ብዙዎች ፡ ታሪክን ፡ በየተራው ፡ ለማዘጋጀት ፡ ስለ ፡ ሞከሩ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ስለተማርኸው ፡ ቃል ፡ ርግጡን ፡ እንድታውቅ ፡ በጥንቃቄ ፡ ኹሉን ፡ ከመዠመሪያው ፡ ተከትዬ ፡ በየተራው ፡ ልጽፍልኽ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፡ ታየኝ ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በይሁዳ ፡ ንጉሥ ፡ በሄሮድስ ፡ ዘመን ፡ ከአብያ ፡ ክፍል ፡ የኾነ ፡ ዘካርያስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ካህን ፡ ነበረ ፤ ሚስቱም ፡ ከአሮን ፡ ልጆች ፡ ነበረች ፥ ስሟም ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ኹለቱም ፡ በጌታ ፡ ትእዛዝና ፡ ሕግጋት ፡ ኹሉ ፡ ያለነቀፋ ፡ እየኼዱ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቃን ፡ ነበሩ ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ኤልሳቤጥም ፡ መካን ፡ ነበረችና ፡ ልጅ ፡ አልነበራቸውም ፤ ኹለቱም ፡ በዕድሜያቸው ፡ አርጅተው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ርሱም ፡ በክፍሉ ፡ ተራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሲያገለግል ፥

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እንደ ፡ ካህናት ፡ ሥርዐት ፡ ወደጌታ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ለማጠን ፡ ዕጣ ፡ ደረሰበት ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በዕጣንም ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ በውጭ ፡ ቆመው ፡ ይጸልዩ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የጌታም ፡ መልአክ ፡ በዕጣኑ ፡ መሠዊያ ፡ ቀኝ ፡ ቆሞ ፡ ታየው ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ዘካርያስም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ ደነገጠ ፥ ፍርሀትም ፡ ወደቀበት ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ መልአኩም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ዘካርያስ ፡ ሆይ ፥ ጸሎትኽ ፡ ተሰምቶልኻልና ፥ አትፍራ ፤ ሚስትኽ ፡ ኤልሳቤጥም ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልድልኻለች ፥ ስሙንም ፡ ዮሐንስ ፡ ትለዋለኽ ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ደስታና ፡ ተድላም ፡ ይኾንልኻል ፥ በመወለዱም ፡ ብዙዎች ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ በጌታ ፡ ፊት ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ፥ የወይን ፡ ጠጅና ፡ የሚያሰክር ፡ መጠጥ ፡ አይጠጣም ፤ ገናም ፡ በእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ሳለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሞላበታል ፤

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ከእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ብዙዎችን ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ አምላካቸው ፡ ይመልሳል ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ርሱም ፡ የተዘጋጁትን ፡ ሕዝብ ፡ ለጌታ ፡ እንዲያሰናዳ ፥ የአባቶችን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ልጆች ፡ የማይታዘዙትንም ፡ ወደጻድቃን ፡ ጥበብ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ በኤልያስ ፡ መንፈስና ፡ ኀይል ፡ በፊቱ ፡ ይኼዳል ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ ዘካርያስም ፡ መልአኩን ፦ እኔ ፡ ሽማግሌ ፡ ነኝ ፥ ሚስቴም ፡ በዕድሜዋ ፡ አርጅታለችና ፥ ይህን ፡ በምን ፡ ዐውቃለኹ ፧ አለው ።

ሉቃ. ፥ 1 ፥ 19 ፤ መልአኩም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የምቆመው ፡ ገብርኤል ፡

ነኝ ፥ እንድናገርኽም ፡ ይህችንም ፡ የምሥራች ፡ እንድሰብክልኽ ፡ ተልኬ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እንሆም ፥ በጊዜው ፡ የሚፈጸመውን ፡ ቃሌን ፡ ስላላመንኽ ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ እስከሚኾን ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ዲዳ ፡ ትኾናለኽ ፡ መናገርም ፡ አትችልም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ሕዝቡም ፡ ዘካርያስን ፡ ይጠብቁት ፡ ነበር ፤ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ዘገየ ፡ ይደነቁ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ በወጣም ፡ ጊዜ ፡ ሊነግራቸው ፡ አልቻለም ፥ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ራእይ ፡ እንዳየ ፡ አስተዋሉ ፤ ርሱም ፡ ይጠቅሳቸው ፡ ነበር ፤ ድዳም ፡ ኾኖ ፡ ኖረ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ የማገልገሉም ፡ ወራት ፡ ሲፈጸም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 24-25 ፤ ከዚህም ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ሚስቱ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ፀነሰችና ፦ ነቀፌታዬን ፡ ከሰው ፡ መካከል ፡ ያስወግድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ በተመለከተበት ፡ ወራት ፡ እንዲህ ፡ አድርጎልኛል ፡ ስትል ፡ ራሷን ፡ ዐምስት ፡ ወር ፡ ሰወረች ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ በስድስተኛውም ፡ ወር ፡ መልአኩ ፡ ገብርኤል ፡ ናዝሬት ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ከተማ ፥

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ከዳዊት ፡ ወገን ፡ ለኾነው ፡ ዮሴፍ ፡ ለሚባል ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ታጨች ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ድንግል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተላከ ፥ የድንግሊቱም ፡ ስም ፡ ማርያም ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ መልአኩም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ገብቶ ፦ ደስ ፡ ይበልሽ ፥ ጸጋ ፡ የሞላብሽ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ አንቺ ፡ ከሴቶች ፡ መካከል ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽ ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ርሷም ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ከንግግሩ ፡ በጣም ፡ ደነገጠችና ፦ ይህ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ሰላምታ ፡ ነው ፧ ብላ ፡ ዐሰበች ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ መልአኩም ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ ማርያም ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጸጋ ፡ አግኝተሻልና ፥ አትፍሪ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ እንሆም ፥ ትፀንሻለሽ ፡ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ትወልጃለሽ ፥ ስሙንም ፡ ኢየሱስ ፡ ትዩዋለሽ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ ርሱ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናል ፡ የልዑል ፡ ልጅም ፡ ይባላል ፥ ጌታ ፡ አምላክም ፡ የአባቱን ፡ የዳዊትን ፡ ዙፋን ፡ ይሰጠዋል ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 33 ፤ በያዕቆብ ፡ ቤትም ፡ ላይ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይነግሣል ፥ ለመንግሥቱም ፡ መጨረሻ ፡ የለውም ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 34 ፤ ማርያምም ፡ መልአኩን ፦ ወንድ ፡ ስለማላውቅ ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ፧ አለችው ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 35 ፤ መልአኩም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባንቺ ፡ ላይ ፡ ይመጣል ፥ የልዑልም ፡ ኀይል ፡ ይጸልልሻል ፡ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ከአንቺ ፡ የሚወለደው ፡ ቅዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባላል ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 36 ፤ እንሆም ፡ ዘመድሽ ፡ ኤልሳቤጥ ፥ ርሷ ፡ ደግሞ ፡ በእርጅናዋ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ፀንሳለች ፥ ለርሷም ፡ መካን ፡ ትባል ፡ ለነበረችው ፡ ይህ ፡ ስድስተኛ ፡ ወር ፡ ነው ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 37 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሳነው ፡ ነገር ፡ የለምና ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 38 ፤ ማርያምም ፦ እንሆኝ ፡ የጌታ ፡ ባሪያ ፡ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ይኹንልኝ ፡ አለች ። መልአኩም ፡ ከርሷ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 39 ፤ ማርያምም ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ፡ ተራራማው ፡ አገር ፡ ወደይሁዳ ፡ ከተማ ፡ ፈጥና ፡ ወጣች ፥

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 40 ፤ ወደዘካርያስም ፡ ቤት ፡ ገብታ ፡ ኤልሳቤጥን ፡ ተሳለመቻት ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 41 ፤ ኤልሳቤጥም ፡ የማርያምን ፡ ሰላምታ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ፅንሱ ፡ በማሕፀኗ ፡ ውስጥ ፡ ዘለለ ፤ በኤልሳቤጥም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባት ፥

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 42 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ ጮኻ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦ አንቺ ፡ ከሴቶች ፡ መካከል ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽ ፥ የማሕፀንሽም ፡ ፍሬ ፡ የተባረከ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 43 ፤ የጌታዬ ፡ እናት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይኾንልኛል ፧

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 44 ፤ እንሆ ፥ የሰላምታሽ ፡ ድምፅ ፡ በጐሮዬ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ፅንሱ ፡ በማሕፀኔ ፡ በደስታ ፡ ዘሏልና ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 45 ፤ ከጌታ ፡ የተነገረላት ፡ ቃል ፡ ይፈጸማልና ፥ ያመነች ፡ ብፅዕት ፡ ናት ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 46 ፤ ማርያምም ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 47 ፤ ነፍሴ ፡ ጌታን ፡ ታከብረዋለች ፥ መንፈሴም ፡ በአምላኬ ፡ በመድኀኒቴ ፡ ሐሴት ፡ ታደርጋለች ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 48 ፤ የባሪያዩቱን ፡ ውርደት ፡ ተመልክቷልና ። እንሆም ፥ ከዛሬ ፡ ገምሮ ፡ ትውልድ ፡ ኹሉ ፦ ብፅዕት ፡ ይሉኛል ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 49 ፤ ብርቱ ፡ የኾነ ፡ ርሱ ፡ በእኔ ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ አድርጓልና ፤ ስሙም ፡ ቅዱስ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 50 ፤ ምሕረቱም ፡ ለሚፈሩት ፡ እስከ ፡ ትውልድና ፡ ትውልድ ፡ ይኖራል ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 51 ፤ በክንዱ ፡ ኀይል ፡ አድርጓል ፤ ትዕቢተኞችን ፡ በልባቸው ፡ ዐሳብ ፡ በትኗል ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 52 ፤ ገዥዎችን ፡ ከዙፋናቸው ፡ አዋርዷል ፤ ትሑታንንም ፡ ከፍ ፡ አድርጓል ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 53 ፤ የተራቡትን ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ አጥግቧል ፤ ባለጠጋዎችንም ፡ ባዷቸውን ፡ ሰዷቸዋል ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 54-55 ፤ ለአባቶቻችን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ ለአብርሃምና ፡ ለዘሩ ፡ ለዘለዓለም ፡ ምሕረቱ ፡ ትዝ ፡ እያለው ፡ እስራኤልን ፡ ብላቴናውን ፡ ረድቷል ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 56 ፤ ማርያምም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ የሚያኽል ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጠች ፡ ወደ ፡ ቤቷም ፡ ተመለሰች ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 57 ፤ የኤልሳቤጥም ፡ የመውለጃዋ ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ፥ ወንድ ፡ ልጅም ፡ ወለደች ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 58 ፤ ጎረቤቶቿም ፡ ዘመዶቿም ፡ ጌታ ፡ ምሕረቱን ፡ እንዳገነነላት ፡ ሰምተው ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 59 ፤ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ሕፃኑን ፡ ሊገርዙት ፡ መጡ ፥ በአባቱም ፡ ስም ፡ ዘካርያስ ፡ ሊሉት ፡ ወደዱ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 60 ፤ እናቱ ፡ ግን ፡ መልሳ ፦ አይኾንም ፥ ዮሐንስ ፡ ይባል ፡ እንጂ ፡ አለች ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 61 ፤ እነርሱም ፦ ከወገንሽ ፡ ማንም ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ የተጠራ ፡ የለም ፡ አሏት ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 62 ፤ አባቱንም ፡ ማን ፡ ሊባል ፡ እንዲወድ ፡ ጠቀሱት ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 63 ፤ ብራናም ፡ ለምኖ ፦ ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ጻፈ ። ኹሉም ፡ አደነቁ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 64 ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ አፉ ፡ ተከፈተ ፥ ምላሱም ፡ ተፈታ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ እየባረከ ፡ ተናገረ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 65 ፤ ለጎረቤቶቻቸውም ፡ ኹሉ ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ፤ ይህም ፡ ኹሉ ፡ ነገር ፡ በይሁዳ ፡ በተራራማው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ተወራ ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 66 ፤ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፦ እንኪያ ፡ ይህ ፡ ሕፃን ፡ ምን ፡ ይኾን ፧ እያሉ ፡ በልባቸው ፡ አኖሩት ፤ የጌታ ፡ እጅ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረችና ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 67 ፤ አባቱ ፡ ዘካርያስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላበትና ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ እንዲህም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 68 ፤ የእስራኤል ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ ይባረክ ፥ ጐብኝቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ ቤዛ ፡ አድርጓልና ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 69-70 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ በነበሩት ፡ በቅዱሳን ፡ ነቢያት ፡ አፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፥ በብላቴናው ፡ በዳዊት ፡ ቤት ፡ የመዳን ፡ ቀንድን ፡ አስነሥቶልናል ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 71 ፤ ማዳኑም ፡ ከወደረኞቻችንና ፡ ከሚጠሉን ፡ ኹሉ ፡ እጅ ፡ ነው ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 72-73 ፤ እንደዚህ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ምሕረት ፡ አደረገ ፤ ለአባታችን ፡ ለአብርሃምም ፡ የማለውን ፡ መሐላውን ፡ ቅዱሱን ፡ ኪዳን ፡ ዐሰበ ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 74-75 ፤ በርሱም ፡ ከጠላቶቻችን ፡ እጅ ፡ ድነን ፡ በዘመናችን ፡ ኹሉ ፡ ያለፍርሀት ፡ በቅድስናና ፡ በጽድቅ ፡ በፊቱ ፡ እንድናገለግለው ፡ ሰጠን ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 76 ፤ ደግሞም ፡ አንተ ፡ ሕፃን ፡ ሆይ ፥ የልዑል ፡ ነቢይ ፡ ትባላለኽ ፥ መንገዱን ፡ ልትጠርግ ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ ትኼዳለኽና ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 77 ፤ እንደዚህም ፡ የኀጢአታቸው ፡ ስርየት ፡ የኾነውን ፡ የመዳን ፡ ዕውቀት ፡ ለሕዝቡ ፡ ትሰጣለኽ ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 78 ፤ ይህም ፡ ከላይ ፡ የመጣ ፡ ብርሃን ፡ በጐበኘበት ፡ በአምላካችን ፡ ምሕረትና ፡ ርኀራኄ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፤

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 79 ፤ ብርሃኑም ፡ በጨለማና ፡ በሞት ፡ ጥላ ፡ ተቀምጠው ፡ ላሉት ፡ ያበራል ፡ እግሮቻችንንም ፡ በሰላም ፡ መንገድ ፡ ያቀናል ።

ሉቃ. ፡ 1 ፡ 80 ፤ ሕፃኑም ፡ አደገ ፥ በመንፈስም ፡ ጠነከረ ፥ ለእስራኤልም ፡ እስከታየበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ኖረ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ እንዲጻፍ ፡ ከአውግስጦስ ፡ ቄሳር ፡ ትእዛዝ ፡ ወጣች ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ቄሬኔዎስ ፡ በሶርያ ፡ አገር ፡ ገዢ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ የመዝመሪያ ፡ ጽሕፈት ፡ ኾነ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ኹሉም ፡ እያንዳንዱ ፡ ይጻፍ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 4-5 ፤ ዮሴፍም ፡ ደግሞ ፡ ከዳዊት ፡ ቤትና ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከገሊላ ፡ ከናዝሬት ፡ ከተማ ፡ ተነሥቶ ፡

ቤተ ፡ ልሔም ፡ ወደምትባል ፡ ወደዳዊት ፡ ከተማ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፥ ፀንሳ ፡ ከነበረች ፡ ከዕጮኛው ፡ ከማርያም ፡ ጋራ ፡ ይጻፍ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 6 ፤ በዚያም ፡ ሳሉ ፡ የመውለጃዋ ፡ ወራት ፡ ደረሰ ፥

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 7 ፤ የበኵር ፡ ልጇንም ፡ ወለደች ፥ በመጠቅለያም ፡ ጠቀለለችው ፤ በእንግዳዎችም ፡ ማደሪያ ፡ ስፍራ ፡ ስላልነበራቸው ፡ በግርግም ፡ አስተኛችው ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 8 ፤ በዚያም ፡ ምድር ፡ መንጋቸውን ፡ በሌሊት ፡ ሲጠብቁ ፡ በሜዳ ፡ ያደሩ ፡ እረኞች ፡ ነበሩ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 9 ፤ እንሆም ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረበ ፡ የጌታ ፡ ክብርም ፡ በዙሪያቸው ፡ አበራ ፥ ታላቅ ፡ ፍርሀትም ፡ ፈሩ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 10 ፤ መልአኩም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ የሚኾን ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ የምሥራች ፡ እነግራችኋለኹና ፡ አትፍሩ ፤

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 11 ፤ ዛሬ ፡ በዳዊት ፡ ከተማ ፡ መድኀኒት ፡ ርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታ ፡ የኾነ ፡ ተወልዶላችኋልና ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 12 ፤ ይህም ፡ ምልክት ፡ ይኾንላችኋል ፤ ሕፃን ፡ ተጠቅሎ ፡ በግርግምም ፡ ተኝቶ ፡ ታገኛላችኹ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 13 ፤ ድንገትም ፡ ብዙ ፡ የሰማይ ፡ ሰራዊት ፡ ከመልአኩ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ። እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገኑ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 14 ፤ ክብር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በአርያም ፡ ይኹን ፡ ሰላምም ፡ በምድር ፡ ለሰውም ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 15 ፤ መላእክትም ፡ ከነርሱ ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፥ እረኞቹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ። እንግዲህ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ድረስ ፡ እንኺድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የገለጠልንን ፡ ይህን ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ እንይ ፡ ተባባሉ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 16 ፤ ፈጥነውም ፡ መጡ ፡ ማርያምንና ፡ ዮሴፍን ፡ ሕፃኑንም ፡ በግርግም ፡ ተኝቶ ፡ አገኙ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 17 ፤ አይተውም ፡ ስለዚህ ፡ ሕፃን ፡ የተነገረላቸውን ፡ ነገር ፡ ገለጡ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 18 ፤ የሰሙትን ፡ ኹሉ ፡ እረኞቹ ፡ በነገሯቸው ፡ ነገር ፡ አደነቁ ፤

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 19 ፤ ማርያም ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በልቧ ፡ እያሰበች ፡ ትጠብቀው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 20 ፤ እረኞችም ፡ እንደ ፡ ተባለላቸው ፡ ስለ ፡ ሰሙትና ፡ ስላዩት ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑና ፡ እያከበሩ ፡ ተመለሱ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 21 ፤ ሊገርዙት ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ በሞላ ፡ ጊዜ ፥ በማሕፀን ፡ ሳይረገዝ ፡ በመልአኩ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ ስሙ ፡ ኢየሱስ ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 22-24 ፤ እንደ ፡ ሙሴም ፡ ሕግ ፡ የመንጻታቸው ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፥ በጌታ ፡ ሕግ ፦ የእናቱን ፡ ማሕፀን ፡ የሚከፍት ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ለጌታ ፡ የተቀደሰ ፡ ይባላል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ ሊያቆሙት ፥ በጌታም ፡ ሕግ ። ኹለት ፡ ዋሊያ ፡ ወይም ፡ ኹለት ፡ የርግብ ፡ ጫጨቶች ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ መሥዋዕት ፡ ሊያቀርቡ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወሰዱት ።

ሉቃ. ፥ 2 ፥ 25 ፤ እንሆም ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ስምዖን ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ ይህም ፡ ሰው ፡ የእስራኤልን ፡ መጽናናት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ፤ ጻድቅና ፡ ትጉህም ፡ ነበረ ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ በጌታም ፡ የተቀባውን ፡ ሳያይ ፡ ሞትን ፡ እንዳያይ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተረድቶ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ በመንፈስም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ወጣ ፤ ወላጆቹም ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ልማድ ፡ ያደርጉለት ፡ ዘንድ ፡ ሕፃኑን ፡ ኢየሱስን ፡ በአስገቡት ፡ ጊዜ ፥

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ተቀብሎ ፡ ዐቀፈው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እየባረከ ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ እንደ ፡ ቃልኽ ፡ ባሪያኽን ፡ በሰላም ፡ ታሰናብተዋለኽ ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 30-31 ፤ ዐይኖቼ ፡ በሰዎች ፡ ዅሉ ፡ ፊት ፡ ያዘጋጀኸውን ፡ ማዳንኽን ፡ አይተዋልና ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ ይህም ፡ ለአሕዛብ ፡ ዅሉን ፡ የሚገልጥ ፡ ብርሃን ፡ ለሕዝብኽም ፡ ለእስራኤል ፡ ክብር ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 33 ፤ የሴፍና ፡ እናቱም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በተባለው ፡ ነገር ፡ ይደነቁ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 34-35 ፤ ስምዖንም ፡ ባረካቸው ፡ እናቱን ፡ ማርያምንም ፦ እንሆ ፥ የብዙዎች ፡ ልብ ፡ ዐሳብ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፥ ይህ ፡ በእስራኤል ፡ ላሉት ፡ ለብዙዎቹ ፡ ለመውደቃቸውና ፡ ለመነሣታቸው ፡ ለሚቃወሙትም ፡ ምልክት ፡ ተሾሟል ፥ ባንቺም ፡ ደግሞ ፡ በነፍስሽ ፡ ሰይፍ ፡ ያልፋል ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 36 ፤ ከአሴር ፡ ወገንም ፡ የምትኾን ፡ የፋኑኤል ፡ ልጅ ፡ ሐና ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ ነቢዪት ፡ ነበረች ፤ ርሷም ፡ ከድንግልናዋ ፡ ዠምራ ፡ ከባሏ ፡ ጋራ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ ኖረች ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 37 ፤ ርሷም ፡ ሰማንያ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ መበለት ፡ ኾና ፡ በጣም ፡ አርጅታ ፡ ነበር ፤ በጾምና ፡ በጸሎትም ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ እያገለገለች ፡ ከመቅደስ ፡ አትለይም ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 38 ፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ቀርባ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነች ፤ የኢየሩሳሌምንም ፡ ቤዛ ፡ ለሚጠባበቁ ፡ ዅሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ትናገር ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 39 ፤ ዅሉንም ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ሕግ ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፥ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ወደ ፡ ከተማቸው ፡ ወደ ፡ ናዝሬት ፡ ተመለሱ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 40 ፤ ሕፃኑም ፡ አደገ ፥ ጥበብም ፡ ሞልቶበት ፡ በመንፈስ ፡ ጠነከረ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ጸጋ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 41 ፤ ወላጆቹም ፡ በያመቱ ፡ በፋሲካ ፡ በዓል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 42 ፤ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ እንደ ፡ በዓሉ ፡ ሥርዐት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 43 ፤ ቀኖቹንም ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፥ ሲመለሱ ፡ ብላቴናው ፡ ኢየሱስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቀርቶ ፡ ነበር ፥ የሴፍም ፡ እናቱም ፡ አላወቁም ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 44 ፤ ከመንገደኞች ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ያንድ ፡ ቀን ፡ መንገድ ፡ ኼዱ ፥ ከዘመዶቻቸውም ፡ ከሚያውቋቸውም ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉት ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 45 ፤ ባጡትም ፡ ጊዜ ፡ እየፈለጉት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 46 ፤ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በመምህራን ፡ መካከል ፡ ተቀምጦ ፡ ሲሰማቸውም ፡ ሲጠይቃቸውም ፡ በመቅደስ ፡ አገኙት ፤

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 47 ፤ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ በማስተዋሉና ፡ በመልሱ ፡ ተገረሙ ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 48 ፤ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡ ተገረሙ ፥ እናቱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ ለምን ፡ እንዲህ ፡ አደረግኽብን ፧ እንሆ ፥ አባትኽና ፡ እኔ ፡ እየተጨነቅን ፡ ስንፈልግኽ ፡ ነበርን ፡ አለችው ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 49 ፤ ርሱም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ፈለጋችኹኝ ፧ በአባቴ ፡ ቤት ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባኝ ፡ አላወቃችኹምን ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 50 ፤ እነርሱም ፡ የተናገራቸውን ፡ ነገር ፡ አላስተዋሉም ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 51 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ወርዶ ፡ ወደ ፡ ናዝሬት ፡ መጣ ፥ ይታዘዝላቸውም ፡ ነበር ። እናቱም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በልቧ ፡ ትጠብቀው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 2 ፡ 52 ፤ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ በጥበብና ፡ በቁመት ፡ በሞገስም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ያድግ ፡ ነበር ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ጢባርዮስ ፡ ቄሳርም ፡ በነገሠ ፡ በዐሥራ ፡ ዐምስተኛዉ ፡ ዓመት ፥ ጳንጤናዊው ፡ ጲላጦስም ፡ በይሁዳ ፡ ሲገዛ ፥ ሄሮድስም ፡ በገሊላ ፡ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፥ ወንድሙ ፡ ፊልጶስም ፡ በኢጡርያስ ፡ በጥራኮኒዶስም ፡ አገር ፡ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፥ ሊሳኒዮስም ፡ በሳቢላኒስ ፡ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡ ኾነው ፡ ሳሉ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሐናና ፡ ቀያፋም ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ሳሉ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ወደዘካርያስ ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መጣ ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 3-6 ፤ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ ቃል ፡ መጽሐፍ ፦ የጌታን ፡ መንገድ ፡ አዘጋጁ ፡ ጥርጊያውንም ፡ አቅኑ ፡ እያለ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚጮኽ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፤ ዐዘቅቱ ፡ ኹሉ ፡ ይሙላ ፡ ተራራውና ፡ ኮረብታውም ፡ ኹሉ ፡ ዝቅ ፡ ይበል ፥ ጠማማውም ፡ የቀና ፡ መንገድ ፡ ይኹን ፥ ሻካራውም ፡ መንገድ ፡ ትክክል ፡ ይኹን ፤ ሥጋም ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማዳን ፡ ይይ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ለኀጢአት ፡ ስርየት ፡ የንስሓን ፡ ጥምቀት ፡ እየሰበከ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ዙሪያ ፡ ወዳለችው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ መጣ ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ከርሱ ፡ ሊጠመቁ ፡ ለወጡት ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ ይላቸው ፡ ነበር ፦ እናንተ ፡ የእፍኝት ፡ ልጆች ፥ ከሚመጣው ፡ ቍጣ ፡ እንድትሸሹ ፡ ማን ፡ አመለከታችኹ ፧

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ እንግዲህ ፡ ለንስሓ ፡ የሚገባ ፡ ፍሬ ፡ አድርጉ ፤ በልባችኹም ፦ አብርሃም ፡ አባት ፡ አለን ፡ ማለትን ፡ አትገምሩ ፤ ከነዚህ ፡ ድንጋዮች ፡ ለአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ሊያስነሣለት ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲችል ፡ እላችኋለኹና ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ አኹንስ ፡ ምሣር ፡ ደግሞ ፡ በዛፎች ፡ ሥር ፡ ተቀምጧል ፤ እንግዲህ ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ የማያደርግ ፡ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ይቈረጣል ፡ ወደ ፡ እሳትም ፡ ይጣላል ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ሕዝቡም ፦ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ ብለው ፡ ይጠይቁት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ መልሶም ፦ ኹለት ፡ ልብስ ፡ ያለው ፡ ለሌለው ፡ ያካፍል ፥ ምግብም ፡ ያለው ፡ እንዲሁ ፡ ያድርግ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ቀራጮችም ፡ ደግሞ ፡ ሊጠመቁ ፡ መጥተው ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ እናድርግ ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ከታዘዘላችኹ ፡ አብልጣችኹ ፡ አትውሰዱ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ጭፍራዎችም ፡ ደግሞ ፦ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ ብለው ፡ ይጠይቁት ፡
ነበር ። ርሱም ፦ በማንም ፡ ግፍ ፡ አትሥሩ ፡ ማንንም ፡ በሐሰት ፡ አትክሰሱ ፥ ደመ ፡ ወዛችኹም ፡ ይብቃችኹ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ሕዝቡም ፡ ሲጠብቁ ፡ ኅሉ ፡ ኹሉም ፡ በልባቸው ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፦ ይህ ፡ ክርስቶስ ፡
ይኾንን ፧ ብለው ፡ ሲያስቡ ፡ ነበር ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ዮሐንስ ፡ መልሶ ፦ እኔስ ፡ በውሃ ፡ አጠምቃችኋለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የጫማውን ፡ ጠፍር ፡
መፍታት ፡ ከማይገባኝ ፡ ከእኔ ፡ የሚበረታ ፡ ይመጣል ፤ ርሱ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በእሳት ፡ ያጠምቃችኋል ፤

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ መንሹም ፡ በእጁ ፡ ነው ፥ ዐውድማውንም ፡ ፈጽሞ ፡ ያጠራል ፥ ስንዴውንም ፡ በጐተራው ፡
ይከታል ፥ ገለባውን ፡ ግን ፡ በማይጠፋ ፡ እሳት ፡ ያቃጥለዋል ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ ሕዝቡን ፡ በብዙ ፡ ሌላ ፡ ምክር ፡ እየመከራቸው ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብክላቸው ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡ ሄሮድስ ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ሄሮድያዳ ፡ ስለ ፡ ወንድሙ ፡ ስለ ፡ ፊልጶስ ፡
ሚስትና ፡ ሄሮድስ ፡ ስላደረገው ፡ ሌላ ፡ ክፋት ፡ ኹሉ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ገሠጸው ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ይህን ፡ ደግሞ ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ጨምሮ ፡ ዮሐንስን ፡ በወህኒ ፡ አገባው ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ደግሞ ፡ ተጠመቀ ። ሲጸልይም ፡ ሰማይ ፡
ተከፈተ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በአካል ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ወረደ ፤ የምወድኽ ፡ ልጄ ፡
አንተ ፡ ነኽ ፥ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፡ የሚል ፡ ድምፅም ፡ ከሰማይ ፡ መጣ ።

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ ሊያስተምር ፡ ሲገምር ፡ ዕድሜው ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ ኾኖት ፡
ነበር ፤ እንደመሰላቸው ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ኾኖ ፥ የኤሊ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ የማቲ ፡ ልጅ ፥ የሌዊ ፡ ልጅ ፥ የሚልኪ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ የዮና ፡ ልጅ ፥ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፥ የማታትዩ ፡ ልጅ ፥ የዓሞጽ ፡ ልጅ ፥ የናሖም ፡ ልጅ ፥ የኤሲሊም ፡
ልጅ ፡

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ የናጌ ፡ ልጅ ፥ የማአት ፡ ልጅ ፥ የማታትዩ ፡ ልጅ ፡ የሴሜይ ፡ ልጅ ፥ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ የዮዳ ፡ ልጅ ፥ የዮናን ፡ ልጅ ፥ የሬስ ፡ ልጅ ፥ የዘሩባቤል ፡ ልጅ ፥ የሰላትያል ፡ ልጅ ፥ የኔሪ ፡
ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ የሚልኪ ፡ ልጅ ፥ የሐዲ ፡ ልጅ ፥ የዮሳስ ፡ ልጅ ፥ የቆሳም ፡ ልጅ ፥ የኤልሞዳም ፡ ልጅ ፥ የኤር ፡
ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ የዮሴዕ ፡ ልጅ ፥ የኤልዓዘር ፡ ልጅ ፡ የዮራም ፡ ልጅ ፥ የማጣት ፡ ልጅ ፥ የሌዊ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ የስምዖን ፡ ልጅ ፥ የይሁዳ ፡ ልጅ ፥ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ የዮናን ፡ ልጅ ፥ የኤልያቄም ፡ ልጅ ፥ የሜልያ ፡ ልጅ ፥ የማይናን ፡ ልጅ ፥ የማጣት ፡
ልጅ ፥ የናታን ፡ ልጅ ፡

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ የዳዊት ፡ ልጅ ፥ የእሴይ ፡ ልጅ ፥ የኢዮቤድ ፡ ልጅ ፥ የቦዔዝ ፡ ልጅ ፥ የሰልሞን ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 33 ፤ የነአሶን ፡ ልጅ ፥ የዐሚናዳብ ፡ ልጅ ፥ የአራም ፡ ልጅ ፥ የአሮኒ ፡ ልጅ ፥ የኤስሮም ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 34 ፤ የፋሬስ ፡ ልጅ ፥ የይሁዳ ፡ ልጅ ፥ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፥ የይሥሐቅ ፡ ልጅ ፥ የአብርሃም ፡ ልጅ ፥ የታራ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 35 ፤ የናኮር ፡ ልጅ ፥ የሴሮህ ፡ ልጅ ፥ የራጋው ፡ ልጅ ፥ የፋሌቅ ፡ ልጅ ፥ የአቤር ፡ ልጅ ፥ የሳላ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 36 ፤ የቃይንም ፡ ልጅ ፥ የአርፋክስድ ([288]) ፡ ልጅ ፥ የሴም ፡ ልጅ ፥ የኖኅ ፡ ልጅ ፥ የላሜህ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 37 ፤ የማቱሳላ ፡ ልጅ ፥ የሔኖክ ፡ ልጅ ፥ የያሬድ ፡ ልጅ ፥

ሉቃ. ፡ 3 ፡ 38 ፤ የመላልኤል ፡ ልጅ ፥ የቃይናን ፡ ልጅ ፥ የሄኖስ ፡ ልጅ ፥ የሴት ፡ ልጅ ፥ የአዳም ፡ ልጅ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መልቶበት ፡ ከዮርዳኖስ ፡ ተመለሰ ፥ በመንፈስም ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ተመርቶ ፥

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ አርባ ፡ ቀን ፡ ከዲያብሎስ ፡ ተፈተነ ። በነዚያም ፡ ቀኖች ፡ ምንም ፡ አልበላም ፥ ከተጨረሱም ፡ በኋላ ፡ ተራበ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ዲያብሎስም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከኾንኽ ፥ ይህን ፡ ድንጋይ ፦ እንጀራ ፡ ኹን ፡ ብለኽ ፡ እዘዝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፦ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ እንጂ ፡ በእንጀራ ፡ ብቻ ፡ አይኖርም ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ዲያብሎስም ፡ ረዥም ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ተራራ ፡ አውጥቶ ፡ የዓለምን ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ በቅጽበት ፡ አሳየው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ዲያብሎስም ፦ ይህ ፡ ሥልጣን ፡ ኹሉ ፡ ክብራቸውም ፡ ለእኔ ፡ ተሰጥቷል ፡ ለምወደውም ፡ ለማንም ፡ እሰጠዋለኹና ፡ ለአንተ ፡ እሰጥኻለኹ ፤

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፡ በእኔ ፡ ፊት ፡ ብትሰግድ ፥ ኹሉ ፡ ለአንተ ፡ ይኾናል ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ለጌታ ፡ ለአምላክኽ ፡ ስገድ ፡ ርሱንም ፡ ብቻ ፡ አምልክ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 9-11 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ደግሞ ፡ ወሰደው ፤ በመቅደስም ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አቁሞ ፦ ይጠብቁኽ ፡ ዘንድ ፡ መላእክቱን ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ያዝልኻል ፥ እግርኽንም ፡ በድንጋይ ፡ ከቶ ፡ እንዳትሰናከል ፡ በእጃቸው ፡ ያነሡኻል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፥ የእግዚአብሔር ፡ ልጅስ ፡ ከኾንኽ ፥ ከዚህ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ራስኽን ፡ ወርውር ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ጌታን ፡ አምላክኽን ፡ አትፈታተነው ፡ ተብሏል ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ዲያብሎስም ፡ ፈተናውን ፡ ኹሉ ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ከርሱ ፡ ተለየ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ኢየሱስም ፡ በመንፈስ ፡ ኀይል ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ተመለሰ ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ በዙሪያው ፡ ባለችው ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ዝና ፡ ወጣ ።

---

288 ዕብ. ፡ አርፓክሻድ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ርሱም ፡ በምኵራባቸው ፡ ያስተምር ፥ ኹሉም ፡ ያመሰግኑት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ወዳደገበትም ፡ ወደ ፡ ናዝሬት ፡ መጣ ፤ እንደ ፡ ልማዱም ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ገባ ፥ ሊያነብም ፡ ተነሣ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 17-19 ፤ የነቢዩንም ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ሰጡት ፥ መጽሐፉንም ፡ በተረተረ ፡ ጊዜ ፦ የጌታ ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነው ፥ ለድኻዎች ፡ ወንጌልን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ቀብቶኛልና ፤ ለታሰሩትም ፡ መፈታትን ፡ ለዕውሮችም ፡ ማየትን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፥ የተጠቁትንም ፡ ነጻ ፡ አወጣ ፡ ዘንድ ፡ የተወደደችውንም ፡ የጌታን ፡ ዓመት ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ልኮኛል ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈበትን ፡ ስፍራ ፡ አገኘ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ መጽሐፉንም ፡ ጠቅሎ ፡ ለአገልጋዩ ፡ ሰጠውና ፡ ተቀመጠ ፤ በምኵራብም ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡ ይመለከቱት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ ዛሬ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በጕሯችኹ ፡ ተፈጸመ ፡ ይላቸው ፡ ዠመር ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ኹሉም ፡ ይመሰክሩለት ፡ ነበር ፡ ከአፉም ፡ ከሚወጣው ፡ ከጸጋው ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ እየተደነቁ ፦ ይህ ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ አይደለምን ፧ ይሉ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ ያለጥርጥር ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፦ ባለመድኀኒት ፡ ሆይ ፥ ራስኽን ፡ ፈውስ ፤ በቅፍርናሖም ፡ እንዳደረግኸው ፡ የሰማነውን ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ በገዛ ፡ አገርኽ ፡ ደግሞ ፡ አድርግ ፡ ትሉኛላችኹ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ነቢይ ፡ በገዛ ፡ አገሩ ፡ ከቶ ፡ አይወደድም ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በኤልያስ ፡ ዘመን ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ሰማይ ፡ ተዘግቶ ፡ ሳለ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ብርቱ ፡ ራብ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ በእስራኤል ፡ ብዙ ፡ መበለቶች ፡ ነበሩ ፤

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ኤልያስም ፡ በሲዶና ፡ አገር ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡ ሰራጵታ ፣ ወደ ፡ አንዲት ፡ መበለት ፡ እንጂ ፥ ከነርሱ ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ አልተላከም ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ በነቢዩ ፡ በኤልሳዕ ፡ ዘመንም ፡ በእስራኤል ፡ ብዙ ፡ ለምጻሞች ፡ ነበሩ ፥ ከሶርያዊው ፡ ከንዕማን ፡ በቀር ፡ ከነርሱ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልነጻም ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ በምኵራብም ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፡ ቍጣ ፡ ሞላባቸው ፥ ተነሥተውም ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጡት ፥

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ይጥሉትም ፡ ዘንድ ፡ ከተማቸው ፡ ተሠርታባት ፡ ወደነበረች ፡ ወደተራራው ፡ አፋፍ ፡ ወሰዱት ፤

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ በመካከላቸው ፡ ዐልፎ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ወደገሊላ ፡ ከተማም ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ ወረደ ። በሰንበትም ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 32 ፤ ቃሉ ፡ በሥልጣን ፡ ነበርና ፥ በትምህርቱ ፡ ተገረሙ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 33 ፤ በምኵራብም ፡ የርኩስ ፡ ጋኔን ፡ መንፈስ ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ ጮኸ ፦

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 34 ፤ ተው ፥ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለን ፧ ልታጠፋን ፡ መጣኽን ፧ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ዐውቄኻለኹ ፥ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅዱሱ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፦ ዝም ፡ በል ፡ ከርሱም ፡ ውጣ ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ። ጋኔኑም ፡ በመካከላቸው ፡ ጥሎት ፡ ሳይጐዳው ፡ ከርሱ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 36 ፤ ዅሉንም ፡ መደነቅ ፡ ያዛቸው ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ ይህ ፡ ቃል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በሥልጣንና ፡ በኀይል ፡ ርኩሳን ፡ መናፍስትን ፡ ያዛልና ፥ ይወጡማል ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 37 ፤ ዝናም ፡ በዙሪያው ፡ ባለች ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ዅሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 38 ፤ በምኵራብም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደስምዖን ፡ ቤት ፡ ገባ ። የስምዖንም ፡ ዐማት ፡ በብርቱ ፡ ንዳድ ፡ ታማ ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ ርሷም ፡ ለመኑት ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 39 ፤ በአጠገቧም ፡ ቆሞ ፡ ንዳዱን ፡ ገሠጸውና ፡ ለቀቃት ፤ ያን ፡ ጊዜውንም ፡ ተነሥታ ፡ አገለገለቻቸው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 40 ፤ ፀሓይም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ደዌ ፡ የተያዙ ፡ በሽተኞችን ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጧቸው ፤ ርሱም ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጭኖ ፡ ፈወሳቸው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 41 ፤ አጋንንትም ፡ ደግሞ ፦ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፡ እያሉ ፡ እየጮኹም ፡ ከብዙዎች ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፤ ገሠጻቸውም ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቀውት ፡ ነበርና ፥ እንዲናገሩ ፡ አልፈቀደላቸውም ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 42 ፤ በጸባም ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ኼደ ፤ ሕዝቡም ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ መጡ ፥ ከነርሱም ፡ ተለይቶ ፡ እንዳይኼድ ፡ ሊከለክሉት ፡ ወደዱ ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 43 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ስለዚህ ፡ ተልኬያለኹና ፡ ለሌላዎቹ ፡ ከተማዎች ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ወንጌል ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 4 ፡ 44 ፤ በገሊላም ፡ ምኵራቦች ፡ ይሰብክ ፡ ነበር ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ሕዝቡም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እየሰሙ ፡ ሲያስጠብቡት ፡ ሳሉ ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ በጌንሳሬጥ ፡ ባሕር ፡ ዳር ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በባሕር ፡ ዳርም ፡ ቆመው ፡ የነበሩትን ፡ ኹለት ፡ ታንኳዎች ፡ አየ ፤ ዓሣ ፡ አጥማጆች ፡ ግን ፡ ከነርሱ ፡ ውስጥ ፡ ወጥተው ፡ መረቦቻቸውን ፡ ያጥቡ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ከታንኳዎቹም ፡ የስምዖን ፡ ወደነበረች ፡ ወደ ፡ አንዲቱ ፡ ገብቶ ፡ ከምድር ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ እንዲያደርጋት ፡ ለመነው ፤ በታንኳዪቱም ፡ ተቀምጦ ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ነገሩንም ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፥ ስምዖንን ፦ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ፈቀቅ ፡ በል ፡ መረቦቻችኹንም ፡ ለማጥመድ ፡ ጣሉ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ስምዖንም ፡ መልሶ ፦ አቤቱ ፥ ሌሊቱን ፡ ዅሉ ፡ ዐድረን ፡ ስንደክም ፡ ምንም ፡ አልያዝንም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቃልኽ ፡ መረቦቹን ፡ እጥላለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ይህንም ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ዓሣ ፡ ያዙ ፤ መረቦቻቸውም ፡ ተቀደዱ ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ በሌላ ፡ ታንኳም ፡ የነበሩትን ፡ ጓደኞቻቸውን ፡ መጥተው ፡ እንዲያግዟቸው ፡ ጠቀሱ ፤ መጥተውም ፡ ኹለቱ ፡ ታንኳዎች ፡ እስኪሰጥሙ ፡ ድረስ ፡ ሞሏቸው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሱስ ፡ ጕልበት ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ነኝና ፡ ከእኔ ፡ ተለይ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ስላጠመዱት ፡ ዓሣ ፡ ርሱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራም ፡ የነበሩ ፡ ኹሉ ፡ ተደንቀዋልና ፥

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ የስምዖን ፡ ባልንጀራዎች ፡ የነበሩ ፡ የዘብዴዎስ ፡ ልጆች ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስም ፡ ተደነቁ ። ኢየሱስም ፡ ስምዖንን ፦ አትፍራ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሰውን ፡ የምታጠምድ ፡ ትኾናለኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ታንኳዎችንም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አድርሰው ፡ ኹሉን ፡ ትተው ፡ ተከተሉት ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ከከተማዎችም ፡ በአንዲቱ ፡ ሳለ ፥ እንሆ ፥ ለምጽ ፡ የሞላበት ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ኢየሱስንም ፡ አይቶ ፡ በፊቱ ፡ ወደቀና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ብትወድስ ፥ ልታነጻኝ ፡ ትችላለኽ ፡ ብሎ ፡ ለመነው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ እጁንም ፡ ዘርግቶ ፡ ዳሰሰውና ፦ እወዳለኹ ፥ ንጻ ፡ አለው ፤ ወዲያውም ፡ ለምጹ ፡ ለቀቀው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ርሱም ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገር ፡ አዘዘው ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ኼደኽ ፡ ራስኽን ፡ ለካህን ፡ አሳይ ፥ ለእነርሱም ፡ ምስክር ፡ እንዲኾን ፡ ስለ ፡ መንጻትኽ ፡ ሙሴ ፡ እንዳዘዘ ፡ መሥዋዕት ፡ አቅርብ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ወሬው ፡ ግን ፡ አብዝቶ ፡ ወጣ ፥ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ሊሰሙትና ፡ ከደዌያቸው ፡ ሊፈወሱ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፤ ከገሊላና ፡ ከይሁዳ ፡ መንደሮችም ፡ ኹሉ ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ መጥተው ፡ የነበሩ ፡ ፈሪሳውያንና ፡ የሕግ ፡ መምህራን ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ እንዲፈውስ ፡ የጌታ ፡ ኀይል ፡ ኾነለት ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሽባ ፡ በዐልጋ ፡ ተሸክመው ፡ አመጡ ፤ አግብተውም ፡ በፊቱ ፡ ሊያኖሩት ፡ ይሹ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ እንዲያገቡት ፡ ሲያቅታቸው ፥ ወደ ፡ ሰገነቱ ፡ ወጡ ፡ የጣራውንም ፡ ጡብ ፡ አሳልፈው ፡ በመካከል ፡ በኢየሱስ ፡ ፊት ፡ ከነዐልጋው ፡ አወረዱት ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ እምነታቸውንም ፡ አይቶ ፦ አንተ ፡ ሰው ፥ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያንም ፦ ይህ ፡ የሚሳደብ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ኀጢአት ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ማን ፡ ይችላል ፧ ብለው ፡ ያስቡ ፡ ገቦመር ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐሳባቸውን ፡ እያወቀ ፡ መልሶ ፦ በልባችኹ ፡ ምን ፡ ታስባላችኹ ፧

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ኀጢአትኽ ፡ ተሰረየችልኽ ፡ ከማለት ፡ ወይስ ፦ ተነሣና ፡ ኺድ ፡ ከማለት ፡ ማናቸው ፡ ይቀላል ፧

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምድር ፡ ላይ ፡ ኀጢአት ፡ ሊያስተሰርይ ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንድታውቁ ፡ ብሎ ፥ ሽባውን ፦ አንተን ፡ እልኻለኹ ፥ ተነሣ ፥ ዐልጋኽን ፡ ተሸክመኽ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ በፊታቸው ፡ ተነሣ ፥ ተኝቶበትም ፡ የነበረውን ፡ ተሸክሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ኹሉንም ፡ መገረም ፡ ያዛቸው ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አመስግነው ፦ ዛሬስ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ አየን ፡ እያሉ ፡ ፍርሀት ፡ ሞላባቸው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ወጥቶ ፡ ሌዊ ፡ የሚባል ፡ ቀራጭ ፡ በመቅረጫው ፡ ተቀምጦ ፡ ተመለከተና ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ዥሉንም ፡ ተወ ፤ ተነሥቶም ፡ ተከተለው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ሌዊም ፡ በቤቱ ፡ ታላቅ ፡ ግብዣ ፡ አደረገለት ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩ ፡ ከቀራጮችና ፡ ከሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበሩ ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ ጻፊዎቻቸውም ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ላይ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ከቀራጮችና ፡ ከኀጢአተኞች ፡ ጋራ ፡ ትበላላችኹ ፡ ትጠጡማላችኹ ፧ ብለው ፡ አንጐራጐሩ ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ሕመምተኞች ፡ እንጂ ፡ ባለጤናዎች ፡ ባለመድኀኒት ፡ አያስፈልጋቸውም ፤

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ ኀጢአተኞችን ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንጂ ፡ ጻድቃንን ፡ ልጠራ ፡ አልመጣኹም ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ እነርሱም ፦ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ብዙ ፡ ይጦማሉ ፡ ጸሎትስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፥ ደግሞም ፡ የፈሪሳውያን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደዚሁ ፡ ያደርጋሉ ፤ የአንተ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ይበላሉ ፡ ይጠጣሉም ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፦ ሙሽራው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ ሚዜዎችን ፡ ልታስጦሙ ፡ ትችላላችኹን ፧

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 35 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወራት ፡ ይመጣል ፥ ሙሽራውም ፡ ከነርሱ ፡ ሲወሰድ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ ወራት ፡ ይጦማሉ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 36 ፤ ደግሞም ፡ ምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ነገራቸው ፦ የዐዲስ ፡ ልብስ ፡ ዕራፊ ፡ ባረጀ ፡ ልብስ ፡ ላይ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፡ ዐዲሱን ፡ ይቀደዋል ፡ ደግሞም ፡ ዐዲስ ፡ ዕራፊ ፡ ለአሮጌው ፡ አይስማማውም ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 37 ፤ ባረጀ ፡ አቍማዳም ፡ ዐዲስ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የሚያኖር ፡ የለም ፤ ቢደረግ ፡ ግን ፡ ዐዲሱ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ አቍማዳውን ፡ ያፈነዳል ፥ ርሱም ፡ ይፈሳል ፡ አቍማዳውም ፡ ይጠፋል ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 38 ፤ ዐዲሱን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ግን ፡ በዐዲስ ፡ አቍማዳ ፡ ማኖር ፡ ይገባል ፥ ኹለቱም ፡ ይጠባበቃሉ ።

ሉቃ. ፡ 5 ፡ 39 ፤ አሮጌ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ሲጠጣ ፡ ዐዲሱን ፡ የሚሻ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ አሮጌው ፡ ይጣፍጣል ፡ ይላልና ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ በሰንበትም ፡ በዕርሻ ፡ መካከል ፡ ያልፍ ፡ ነበር ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እሸት ፡ ይቀጥፉ ፡ በእጃቸውም ፡ እያሹ ፡ ይበሉ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ከፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ አንዳንዶቹ ፦ በሰንበት ፡ ሊያደርግ ፡ ያልተፈቀደውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧ አሏቸው ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 3-4 ፤ ኢየሱስም ፡ ለእነርሱ ፡ መልሶ ፦ ዳዊት ፡ በተራበ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ዐብረውት ፡ ከነበሩ ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፥ ወደእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ከካህናት ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ መብላቱ ፡ ያልተፈቀደውን ፡ የመሥዋዕትን ፡ እንጀራ ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ በላ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ለነበሩት ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ይህን ፡ አላነበባችኹምን ፧ አለ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰንበት ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ አላቸውም ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በሌላው ፡ ሰንበትም ፡ ወደ ፡ ምኩራብ ፡ ገብቶ ፡ አስተማረ ፤ በዚያም ፡ ቀኝ ፡ እጁ ፡ የሰለለች ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ መክሰሻ ፡ ሊያገኙበት ፡ በሰንበት ፡ ይፈውስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይጠባበቁት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቆ ፡ እጁ ፡ የሰለለችውን ፡ ሰው ፦ ተነሣና ፡ በመካከል ፡ ቁም ፡ አለው ፤ ተነሥቶም ፡ ቆመ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ኢየሱስም ፦ እጠይቃችኋለኹ ፤ በሰንበት ፡ በጎ ፡ ማድረግ ፡ ተፈቅዷልን ፡ ወይስ ፡ ክፉ ፡ ፡ ነፍስ ፡ ማዳንን ፡ ወይስ ፡ መግደል ፡ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ኹላቸውንም ፡ ዙሪያውን ፡ አየና ፡ ሰውዬውን ፦ እጅኽን ፡ ዘርጋ ፡ አለው ። ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አደረገ ፥ እጁም ፡ እንደ ፡ ኹለተኛዉቱ ፡ ዳነች ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እነርሱም ፡ ቍጣ ፡ ሞላባቸው ፥ በኢየሱስም ፡ ምን ፡ እንዲያደርጉበት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተባባሉ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ በነዚህም ፡ ወራት ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ፥ ሌሊቱንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲጸልይ ፡ ዐደረ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ጠራ ፥ ከነርሱም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መረጠ ፡ ደግሞም ፡ ሐዋርያት ፡ ብሎ ፡ ሰየማቸው ፤

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ እነርሱም ፥ ጴጥሮስ ፡ ብሎ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የሰየመው ፡ ስምዖን ፥ ወንድሙም ፡ እንድርያስ ፥ ያዕቆብም ፡ ዮሐንስም ፥ ፊልጶስም ፡ በርተሎሜዎስም ፥

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ ማቴዎስም ፡ ቶማስም ፥ የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፡ ቀናተኛ ፡ የሚባለው ፡ ስምዖንም ፥

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ የያዕቆብ ፡ ይሁዳም ፥ አሳልፎ ፡ የሰጠውም ፡ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ወርዶ ፡ በተካከለ ፡ ስፍራ ፡ ቆመ ፥ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወገን ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ነበረ ፥ ደግሞም ፡ ሊሰሙትና ፡ ከደዌያቸው ፡ ሊፈወሱ ፡ ከይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ባሕር ፡ ዳርም ፡ የመጡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ከርኩሳንም ፡ መናፍስት ፡ ይሠቃዩ ፡ የነበሩት ፡ ተፈወሱ ፤

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ከርሱም ፡ ኀይል ፡ ወጥቶ ፡ ኹሉን ፡ ይፈውስ ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሊዳስሱት ፡ ይሹ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ዐይኑን ፡ አነሣ ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ ድኻዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የእናንተ ፡ ነውና ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ እናንተ ፡ አኹን ፡ የምትራቡ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ፥ ትጠግባላችኹና ። እናንተ ፡ አኹን ፡ የምታለቅሱ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ፥ ትሥቃላችኹና ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ሰዎች ፡ ስለሰው ፡ ልጅ ፡ ሲጠሏችኹ ፡ ሲለይዋችኹም ፡ ሲነቅፏችኹም ፡ ስማችኹንም ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ ሲያወጡ ፥ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ እንሆ ፥ ዋጋችኹ ፡ በሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ዝለሉም ፤ አባቶቻቸው ፡ ነቢያትን ፡ እንዲህ ፡ ያደርጉባቸው ፡ ነበርና ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ ባለጠጋዎች ፡ ወዮላችኹ ፥ መጽናናታችኹን ፡ ተቀብላችኋልና ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ እናንተ ፡ አኹን ፡ የጠገባችኹ ፡ ወዮላችኹ ፥ ትራባላችኹና ። እናንተ ፡ አኹን ፡ የምትሥቁ ፡

ወዮላችኹ ፥ ታዝናላችኹና ፡ ታለቅሱማላችኹ ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 26 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ መልካም ፡ ሲናገሩላችኹ ፥ ወዮላችኹ ፤ አባቶቻቸው ፡ ለሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጉላቸው ፡ ነበርና ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእናንተ ፡ ለምትሰሙ ፡ እላችኋለኹ ፥ ጠላቶቻችኹን ፡ ውደዱ ፥ ለሚጠሏችኹ ፡ መልካም ፡ አድርጉ ፥

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 28 ፤ የሚረግሟችኹንም ፡ መርቁ ፥ ስለሚበድሏችኹም ፡ ጸልዩ ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 29 ፤ ጕንጭኽን ፡ ለሚመታኽ ፡ ደግሞ ፡ ኹለተኛውን ፡ ስጠው ፥ መጐናጸፊያኽንም ፡ ለሚወስድ ፡ እጀ ፡ ጠባብኽን ፡ ደግሞ ፡ አትከልክለው ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 30 ፤ ለሚለምንኽ ፡ ኹሉ ፡ ስጥ ፥ ገንዘብኽንም ፡ የሚወስድ ፡ እንዲመልስ ፡ አትጠይቀው ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 31 ፤ ሰዎችም ፡ ሊያደርጉላችኹ ፡ እንደምትወዱ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 32 ፤ የሚወዷችኹንማ ፡ ብትወዱ ፥ ምን ፡ ምስጋና ፡ አላችኹ ፧ ኀጢአተኞች ፡ ደግሞ ፡ የሚወዷቸውን ፡ ይወዳሉና ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 33 ፤ መልካምም ፡ ለሚያደርጉላችኹ ፡ መልካም ፡ ብታደርጉ ፥ ምን ፡ ምስጋና ፡ አላችኹ ፧ ኀጢአተኞች ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ ያደርጋሉና ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 34 ፤ እንድትወስዱባቸው ፡ ተስፋ ፡ ለምታደርጓቸው ፡ ብታበድሩ ፥ ምን ፡ ምስጋና ፡ አላችኹ ፧ ኀጢአተኞች ፡ ደግሞ ፡ በትክክል ፡ እንዲቀበሉ ፡ ለኀጢአተኞች ፡ ያበድራሉ ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 35 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጠላቶቻችኹን ፡ ውደዱ ፤ መልካም ፡ አድርጉ ፤ ምንም ፡ ተስፋ ፡ ሳታደርጉም ፡ አበድሩ ፥ ዋጋችኹም ፡ ታላቅ ፡ ይኾናል ፥ የልዑልም ፡ ልጆች ፡ ትኾናላችኹ ፥ ርሱ ፡ ለማያመሰግኑ ፡ ለክፉዎችም ፡ ቸር ፡ ነውና ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 36 ፤ አባታችኹ ፡ ርኅሩኅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርኅሩኆች ፡ ኹኑ ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 37 ፤ አትፍረዱ ፡ አይፈረድባችኹምም ፤ አትኰንኑ ፡ አትኰነኑምም ። ይቅር ፡ በሉ ፡ ይቅርም ፡ ትባላላችኹ ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 38 ፤ ስጡ ፡ ይሰጣችኹማል ፤ በምትሰፍሩበት ፡ መስፈሪያ ፡ ተመልሶ ፡ ይሰፈርላችኋልና ፥ የተጨቈነና ፡ የተነቀነቀ ፡ የተትረፈረፈም ፡ መልካም ፡ መስፈሪያ ፡ በዕቅፋችኹ ፡ ይሰጣችኋል ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 39 ፤ ምሳሌም ፡ አላቸው ፦ ዕውር ፡ ዕውርን ፡ ሊመራ ፡ ይችላልን ፧ ኹለቱ ፡ በጕድጓድ ፡ አይወድቁምን ፧

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 40 ፤ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከመምህሩ ፡ አይበልጥም ፤ ፈጽሞ ፡ የተማረ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ መምህሩ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 41 ፤ በወንድምኽም ፡ ዐይን ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታያለኽ ፥ በራስኽ ፡ ዐይን ፡ ግን ፡ ያለውን ፡ ምሰሶ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አትመለከትም ፧

ሉቃ. ፥ 6 ፥ 42 ፤ በዐይንኽ ፡ ያለውን ፡ ምሰሶ ፡ ራስኽ ፡ ሳታይ ፥ እንዴት ፡ ወንድምኽን ፦ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ በዐይንኽ ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ላውጣ ፡ ፍቀድልኝ ፡ ልትል ፡ ትችላለኽ ፧ አንተ ፡ ግብዝ ፥ አስቀድመኽ ፡ ከዐይንኽ ፡ ምሰሶውን ፡ አውጣ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በወንድምኽ ፡ ዐይን ፡ ያለውን ፡ ጕድፍ ፡ ታወጣ ፡ ዘንድ ፡ አጥርተኽ ፡

ታያለኽ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 43 ፤ ክፉ ፡ ፍሬ ፡ የሚያደርግ ፡ መልካም ፡ ዛፍ ፡ የለምና ፥ እንዲሁም ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ የሚያደርግ ፡ ክፉ ፡ ዛፍ ፡ የለም ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 44 ፤ ዛፍ ፡ ኹሉ ፡ ከፍሬው ፡ ይታወቃልና ፤ ከሾኽ ፡ በለስ ፡ አይለቅሙም ፥ ከዐጣጥ ፡ ቍጥቋጦም ፡ ወይን ፡ አይቈርጡም ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 45 ፤ በልብ ፡ ሞልቶ ፡ ከተረፈው ፡ አፉ ፡ ይናገራልና ፥ መልካም ፡ ሰው ፡ ከልብ ፡ መልካም ፡ መዝገብ ፡ መልካሙን ፡ ያወጣል ፥ ክፉ ፡ ሰውም ፡ ከልብ ፡ ክፉ ፡ መዝገብ ፡ ክፉውን ፡ ያወጣል ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 46 ፤ ስለ ፡ ምን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ትሉኛላችኹ ፥ የምለውንም ፡ አታደርጉም ፧

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 47 ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚመጣ ፡ ኹሉ ፡ ቃሌንም ፡ ሰምቶ ፡ የሚያደርገው ፥ ማንን ፡ እንዲመስል ፡ አሳያችኋለኹ ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 48 ፤ ቤት ፡ ሲሠራ ፡ አጥልቆ ፡ የቈፈረ ፡ በአለት ፡ ላይም ፡ የመሠረተ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ፤ ጐርፍም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወንዙ ፡ ያን ፡ ቤት ፡ ገፋው ፥ በአለት ፡ ላይም ፡ ስለ ፡ ተመሠረተ ፡ ሊያናውጠው ፡ አልቻለም ።

ሉቃ. ፡ 6 ፡ 49 ፤ ሰምቶ ፡ የማያደርገው ፡ ግን ፡ ያለመሠረት ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ቤቱን ፡ የሠራ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ፤ ወንዙም ፡ ገፋው ፡ ወዲያውም ፡ ወደቀ ፡ የዚያ ፡ ቤት ፡ አወዳደቅም ፡ ታላቅ ፡ ኾነ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ቃሉን ፡ ኹሉ ፡ በሕዝብ ፡ ጐሮዎች ፡ በጨረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ ገባ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ አንድ ፡ የመቶ ፡ አለቃም ፡ ነበረ ፤ የሚወደውም ፡ ባሪያው ፡ ታሞ ፡ ሊሞት ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ስለ ፡ ኢየሱስም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የአይሁድን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ላከና ፡ መጥቶ ፡ ባሪያውን ፡ እንዲያድን ፡ ለመነው ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ መጥተው ፦ ይህን ፡ ልታደርግለት ፡ ይገባዋል ፤

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ሕዝባችንን ፡ ይወዳልና ፥ ምኩራብም ፡ ራሱ ፡ ሠርቶልናል ፡ ብለው ፡ አጽንተው ፡ ለመኑት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ኢየሱስም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ኼደ ። አኹንም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የመቶው ፡ አለቃ ፡ ወዳጆቹን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ላከ ፤ አለውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፡ በቤቴ ፡ ጣራ ፡ በታች ፡ ልትገባ ፡ አይገባኝምና ፥ አትድከም ፤

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ስለዚህም ፡ ወዳንተ ፡ ልመጣ ፡ እንዲገባኝ ፡ ሰውነቴን ፡ አልቈጠርኹትም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃል ፡ ተናገር ፥ ብላቴናዬም ፡ ይፈወሳል ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከሌላዎች ፡ በታች ፡ የምገዛ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፥ ከእኔም ፡ በታች ፡ ወታደሮች ፡ አሉኝ ፥ አንዱንም ፦ ኺድ ፡ ብለው ፡ ይኼዳል ፥ ሌላውንም ፦ ና ፡ ብለው ፡ ይመጣል ፥ ባሪያዬንም ፦ ይህን ፡ አድርግ ፡ ብለው ፡ ያደርጋል ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ በርሱ ፡ ተደነቀ ፥ ዘወርም ፡ ብሎ ፡ ለተከተሉት ፡ ሕዝብ ፦ እላችኋለኹ ፥ በእስራኤልስ ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ እምነት ፡ አላገኘኹም ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ የተላኩትም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ተመልሰው ፡ ባሪያውን ፡ ባለጤና ፡ ኾኖ ፡ አገኙት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ በነገውም ፡ ናይን ፡ ወደምትባል ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ ከተማ ፡ ኼደ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ኼዱ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ከተማዪቱም ፡ በር ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ የሞተ ፡ ሰው ፡ ተሸክመው ፡ አወጡ ፤ ርሱም ፡ ለእናቱ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፥ ርሷም ፡ መበለት ፡ ነበረች ፥ ብዙም ፡ የከተማ ፡ ሕዝብ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ነበሩ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ጌታም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ዐዘነላትና ፦ አታልቅሺ ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ቀርቦም ፡ ቃሬዛውን ፡ ነካ ፥ የተሸከሙትም ፡ ቆሙ ፤ አለውም ፦ አንተ ፡ ጐበዝ ፥ እልኻለኹ ፥ ተነሣ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ የሞተውም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ተቀመጠ ፡ ሊናገርም ፡ ዠመረ ፥ ለእናቱም ፡ ሰጣት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ኹሉንም ፡ ፍርሀት ፡ ያዛቸውና ፦ ታላቅ ፡ ነቢይ ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ ተነሥቷል ፥ ደግሞ ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ጐበኘ ፡ እያሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ይህም ፡ ዝና ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ በዙሪያውም ፡ ባለች ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለዮሐንስ ፡ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ አወሩ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ዮሐንስም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹለት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፦ የሚመጣው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፡ ወይስ ፡ ሌላውን ፡ እንጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ላከ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሰዎቹም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፦ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፦ የሚመጣው ፡ አንተ ፡ ነኽን ፡ ወይስ ፡ ሌላውን ፡ እንጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ወዳንተ ፡ ላከን ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ከደዌና ፡ ከሥቃይ ፡ ከክፉዎች ፡ መናፍስትም ፡ ብዙዎችን ፡ ፈወሰ ፥ ለብዙ ፡ ዕውሮችም ፡ ማየትን ፡ ሰጠ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ኼዳችኹ ፡ ያያችኹትን ፡ የሰማችኹትንም ፡ ለዮሐንስ ፡ አውሩለት ፤ ዕውሮች ፡ ያያሉ ፥ ዐንካሳዎችም ፡ ይኼዳሉ ፥ ለምጻሞችም ፡ ይነጻሉ ፥ ደንቈሮዎችም ፡ ይሰማሉ ፥ ሙታንም ፡ ይነሣሉ ፥ ለድኻዎችም ፡ ወንጌል ፡ ይሰበካል ፤

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ በእኔም ፡ የማይሰናከለው ፡ ኹሉ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ የዮሐንስ ፡ መልክተኞችም ፡ ከኼዱ ፡ በኋላ ፥ ለሕዝቡ ፡ ስለ ፡ ዮሐንስ ፡ ይናገር ፡ ዠመር ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወጣችኹ ፡ ነፋስ ፡ የሚወዘውዘውን ፡ ሸምበቆን ፡ ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችኹ ፡

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ቀጭን ፡ ልብስ ፡ የለበሰውን ፡ ሰውን ፡ እንሆ ፥ ጌጠኛ ፡ ልብስ ፡ የሚለብሱና ፡ በቅምጥልነት ፡ የሚኖሩ ፡ በነገሥታት ፡ ቤት ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ ወይስ ፡ ምን ፡ ልታዩ ፡ ወጣችኹ ፡ ነቢይን ፡ አዎን ፡ እላችኋለኹ ፥ ከነቢይም ፡ የሚበልጠውን ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ እንሆ ፥ መንገድኽን ፡ በፊትኽ ፡ የሚጠርግ ፡ መልክተኛዬን ፡ በፊትኽ ፡ እልካለኹ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈለት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ እላችኋለኹ ፥ ከሴቶች ፡ ከተወለዱት ፡ መካከል ፡ ከመጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚበልጥ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ከኹሉ ፡ የሚያንሰው ፡ ይበልጠዋል ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ የሰሙትም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ቀራጮች ፡ እንኳ ፡ ሳይቀሩ ፡ በዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ተጠምቀው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አጸደቁ ፤

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ስላልተጠመቁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምክር ፡ ከራሳቸው ፡ ጣሉ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 31 ፤ እንግዲህ ፡ የዚችን ፡ ትውልድ ፡ ሰዎች ፡ በምን ፡ አስመስላቸዋለኹ ፧ ማንንስ ፡ ይመስላሉ ፧

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 32 ፤ በገበያ ፡ የሚቀመጡትን ፡ ልጆች ፡ ይመስላሉ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ እየተጠራሩ ። እንቢልታ ፡ ነፋንላችኹ ፡ አልዘፈናችኹምም ፤ ሙሾ ፡ አወጣንላችኹ ፡ አላለቀሳችኹምም ፡ ይላል ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፡ እንጀራ ፡ ሳይበላ ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ ሳይጠጣ ፡ መጥቶ ፡ ነበርና ፥— ጋኔን ፡ አለበት ፡ አላችኹት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ እየበላና ፡ እየጠጣ ፡ መጥቷልና ፥— እንሆ ፥ በላተኛና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጪ ፥ የቀራጮችና ፡ የኀጢአተኞች ፡ ወዳጅ ፡ አላችኹት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ ጥበብም ፡ ለልጆቿ ፡ ኹሉ ፡ ጸደቀች ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ ከፈሪሳውያንም ፡ አንድ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፤ በፈሪሳዊው ፡ ቤትም ፡ ገብቶ ፡ በማእዱ ፡ ተቀመጠ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ እንሆም ፡ በዚያች ፡ ከተማ ፡ ኀጢአተኛ ፡ የነበረች ፡ አንዲት ፡ ሴት ፤ በፈሪሳዊው ፡ ቤት ፡ በማእዱ ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፥ ሽቱ ፡ የሞላበት ፡ የአልባስጥሮስ ፡ ቢልቃጥ ፡ አመጣች ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ በስተኋላውም ፡ በእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ቆማ ፡ እያለቀሰች ፡ በእንባዋ ፡ እግሩን ፡ ታርስ ፡ ዠመር ፥ በራስ ፡ ጠጕሯም ፡ ታብሰው ፡ እግሩንም ፡ ትስመው ፡ ሽቱም ፡ ትቀባው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 39 ፤ የጠራው ፡ ፈሪሳዊም ፡ አይቶ ፥— ይህስ ፡ ነቢይ ፡ ቢኾን ፥ ይህች ፡ የምትዳስሰው ፡ ሴት ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዴትስ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ ባወቀ ፡ ነበር ፥ ኀጢአተኛ ፡ ናትና ፥ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 40 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፥— ስምዖን ፡ ሆይ ፥ የምነግርኽ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ አለው ። ርሱም ፥— መምህር ፡ ሆይ ፥ ተናገር ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 41 ፤ ላንድ ፡ አበዳሪ ፡ ኹለት ፡ ተበዳሪዎች ፡ ነበሩት ፡ በአንዱ ፡ ዐምስት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ ነበረበት ፡ በኹለተኛውም ፡ ዐምሳ ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 42 ፤ የሚከፍሉትም ፡ ቢያጡ ፡ ለኹለቱም ፡ ተወላቸው ። እንግዲህ ፡ ከነርሱ ፡ አብልጦ ፡ የሚወደው ፡ ማንኛው ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 43 ፤ ስምዖንም ፡ መልሶ ፥— ብዙ ፡ የተወለቱ ፡ ይመስለኛል ፡ አለ ። ርሱም ፥— በእውነት ፡ ፈረድኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 44 ፤ ወደ ፡ ሴቲቱም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ስምዖንን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፥— ይህችን ፡ ሴት ፡ ታያለኽን ፧ እኔ ፡ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ገባኹ ፥ ውሃ ፡ ስንኳ ፡ ለእግሬ ፡ አላቀረብኽልኝም ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ በእንባዋ ፡ እግሬን ፡ አራሰች ፡ በጠጕሯም ፡ አበሰች ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 45 ፤ አንተ ፡ አልሳምኸኝም ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ ከገባኹ ፡ ዠምራ ፡ እግሬን ፡ ከመሳም ፡ አላቋረጠችም ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 46 ፤ አንተ ፡ ራሴን ፡ ዘይት ፡ አልቀባኸኝም ፤ ርሷ ፡ ግን ፡ እግሬን ፡ ሽቱ ፡ ቀባች ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 47 ፤ ስለዚህ ፥ እልኻለኹ ፥ እጅግ ፡ ወዳለችና ፥ ብዙ ፡ ያለው ፡ ኀጢአቷ ፡ ተሰርዮላታል ፤ ጥቂት ፡ ግን ፡ የሚሰረይለት ፡ ጥቂት ፡ ይወዳል ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 48 ፤ ርሷንም ፦ ኀጢአትሽ ፡ ተሰርዮልሻል ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 49 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩት ፡ በልባቸው ፦ ኀጢአትን ፡ እንኳ ፡ የሚያስተሰርይ ፡ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ይሉ ፡ ዠመር ።

ሉቃ. ፡ 7 ፡ 50 ፤ ሴቲቱንም ፦ እምነትሽ ፡ አድኖሻል ፤ በሰላም ፡ ኺጂ ፡ አላት ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ እየሰበከና ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የምሥራች ፡ እየተናገረ ፡ በየከተማዉቱ ፡ በየመንደሩም ፡ ያልፍ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፥ ከክፉዎች ፡ መናፍስትና ፡ ከደዌም ፡ ተፈውሰው ፡ የነበሩ ፡ አንዳንድ ፡ ሴቶች ፤ እነርሱም ፡ ሰባት ፡ አጋንንት ፡ የወጡላት ፡ መግደላዊት ፡ የምትባል ፡ ማርያም ፥

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ የሄሮድስ ፡ አዛዥ ፡ የኩዛ ፡ ሚስት ፡ ዮሐናም ፡ ሶስናም ፡ ብዙዎች ፡ ሌላዎችም ፡ ኾነው ፡ በገንዘባቸው ፡ ያገለግሉት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ከከተማዎችም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በምሳሌ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገራቸው ፦

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ዘሪ ፡ ዘሩን ፡ ሊዘራ ፡ ወጣ ። ሲዘራም ፡ አንዳንዱ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ወደቀ ፡ ተረገጠም ፥ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ በሉት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ሌላውም ፡ በአለት ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፥ በበቀለም ፡ ጊዜ ፡ ርጥበት ፡ ስላልነበረው ፡ ደረቀ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ሌላውም ፡ በሾኽ ፡ መካከል ፡ ወደቀ ፥ ሾኹም ፡ ዐብሮ ፡ በቀለና ፡ ዐነቀው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ሌላውም ፡ በመልካም ፡ መሬት ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፤ በበቀለም ፡ ጊዜ ፡ መቶ ፡ ዕጥፍ ፡ አፈራ ። ይህን ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፦ የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ለእናንተ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ምስጢር ፡ ማወቅ ፡ ተሰጥቷችኋል ፤ ለሌላዎች ፡ ግን ፡ እያዩ ፡ እንዳያዩ ፡ እየሰሙም ፡ እንዳያስተውሉ ፡ በምሳሌ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ምሳሌው ፡ ይህ ፡ ነው ። ዘሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ በመንገድ ፡ ዳርም ፡ ያሉት ፡ የሚሰሙ ፡ ናቸው ፤ ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ዲያብሎስ ፡ ይመጣል ፡ አምነውም ፡ እንዳይድኑ ፡ ቃሉን ፡ ከልባቸው ፡ ይወስዳል ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ በአለት ፡ ላይም ፡ ያሉት ፡ ሲሰሙ ፡ ቃሉን ፡ በደስታ ፡ የሚቀበሉ ፡ ናቸው ፤ እነርሱም ፡ ለጊዜው ፡ ብቻ ፡ ያምናሉ ፡ እንጂ ፡ በፈተና ፡ ጊዜ ፡ የሚክዱ ፡ ሥር ፡ የሌላቸው ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ በሾኽ ፡ መካከልም ፡ የወደቀ ፡ እነዚህ ፡ የሚሰሙት ፡ ናቸው ፤ መንገዳቸውንም ፡ ኼደው ፡ በሕይወት ፡ ዘመን ፡ በዐሳብና ፡ በባለጠግነት ፡ ምኞት ፡ ይታነቃሉ ፥ ሙሉ ፡ ፍሬም ፡ አያፈሩም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ በመልካም ፡ መሬት ፡ ላይም ፡ የወደቀ ፡ እነርሱ ፡ በመልካምና ፡ በበጎ ፡ ልብ ፡ ቃሉን ፡ ሰምተው ፡ የሚጠብቁት ፡ በመጽናትም ፡ ፍሬ ፡ የሚያፈሩ ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ መብራትንም ፡ አብርቶ ፡ በዕቃ ፡ የሚከድነው ፡ ወይም ፡ ከዐልጋ ፡ በታች ፡ የሚያኖረው ፡ የለም ፥ የሚገቡት ፡ ሰዎች ፡ ብርሃኑን ፡ እንዲያዩ ፡ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ ያኖረዋል ፡ እንጂ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ የማይገለጥ ፡ የተሰወረ ፡ የለምና ፥ የማይታወቅም ፡ ወደ ፡ ግልጥም ፡ የማይመጣ ፡ የተሸሸገ ፡ የለም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ እንድትሰሙ ፡ ተጠበቁ ፤ ላለው ፡ ሹሉ ፡ ይሰጠዋልና ፥ ከሌለውም ፡ ሹሉ ፥ ያው ፡ ያለው ፡ የሚመስለው ፡ እንኳ ፡ ይወሰድበታል ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እናቱና ፡ ወንድሞቹም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ፥ ከሕዝቡም ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሊያገኙት ፡ አልተቻላቸውም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ እናትኽና ፡ ወንድሞችኽ ፡ ሊያዩኽ ፡ ወደው ፡ በውጭ ፡ ቆመዋል ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ እናቴና ፡ ወንድሞቼስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ የሚያደርጉት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ከዕለታቱም ፡ በአንዱ ፡ ርሱ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታንኳ ፡ ገብቶ ፦ ወደባሕር ፡ ማዶ ፡ እንሻገር ፡ አላቸው ፤ ተነሡም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ሲኼዱም ፡ አንቀላፋ ። ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ወረደ ፥ ውሃውም ፡ ታንኳዩቱን ፡ ይሞላ ፡ ነበርና ፥ ይጨነቁ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ ቀርበውም ፦ አቤቱ ፥ አቤቱ ፡ ጠፋን ፡ እያሉ ፡ አስነሡት ። ርሱም ፡ ነቅቶ ፡ ነፋሱንና ፡ የውሃውን ፡ ማዕበል ፡ ገሠጻቸው ፤ ተዉም ፥ ጽጥታም ፡ ኾነ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ እምነታችኹ ፡ የት ፡ ነው ፧ አላቸው ። ፈርተውም ፡ ተደነቁ ፥ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ እንዲህ ፡ ነፋሳትንና ፡ ውሃን ፡ እንኳ ፡ የሚያዝ ፡ ለርሱም ፡ የሚታዘዙለት ፡ ይህ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ በገሊላም ፡ አንጻር ፡ ወዳለችው ፡ ወደጌርጌሴኖን ፡ አገር ፡ በታንኳ ፡ ደረሱ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ አጋንንት ፡ ያደሩበት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከከተማ ፡ ወጥቶ ፡ ተገናኘው ፥ ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ ዝምንም ፡ ልብስ ፡ ሳይለብስ ፡ በመቃብር ፡ እንጂ ፡ በቤት ፡ አይኖርም ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ኢየሱስንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ጮኾ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅም ፦ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ እንዳትሣቀየኝ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ ርኩሱን ፡ መንፈስ ፡ ከሰውዬው ፡ እንዲወጣ ፡ ያዘው ፡ ነበርና ። ብዙ ፡ ዘመንም ፡ ይዞት ፡ ነበርና ፥ በሰንሰለትና ፡ በእግር ፡ ብረትም ፡ ታስሮ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበር ፤ እስራቱንም ፡ ሰብሮ ፡ በጋኔኑ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ይነዳ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፦ ስምኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ርሱም ፡ ብዙዎች ፡ አጋንንት ፡ ገብተውበት ፡ ነበርና ፦ ሌጌዎን ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ ወደ ፡ ጥልቁም ፡ ሊኼዱ ፡ እንዳያዛቸው ፡ ለመኑት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ በዚያም ፡ በተራራው ፡ የብዙ ፡ ዕሪያ ፡ መንጋ ፡ ይሰማሩ ፡ ነበር ፤ ወደ ፡ እነርሱም ፡ ሊገቡ ፡

እንዲፈቅድላቸው ፡ ለመኑት ፤ ፈቀደላቸውም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ አጋንንትም ፡ ከሰውዬው ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ዕሪያዎች ፡ ገቡ ፥ መንጋውም ፡ ከአፋፉ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተጣደፉና ፡ ሰጠሙ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ እረኞችም ፡ የኾነውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ሸሽተው ፡ በከተማውና ፡ በአገሩ ፡ አወሩት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ሊያዩ ፡ ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ መጡ ፥ አጋንንትም ፡ የወጡለትን ፡ ሰው ፡ ለብሶ ፡ ልቡም ፡ ተመልሶ ፡ በኢየሱስ ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጦ ፡ አገኙትና ፡ ፈሩ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ ያዩትም ፡ ደግሞ ፡ አጋንንት ፡ ያደሩበት ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ አወሩላቸው ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 37 ፤ በዙሪያውም ፡ በጌርጌሴኖን ፡ አገር ፡ ያሉት ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ ይዟቸዋልና ፥ ከነርሱ ፡ እንዲኼድ ፡ ለመኑት ፡ በታንኳም ፡ ገብቶ ፡ ተመለሰ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 38 ፤ አጋንንት ፡ የወጡለት ፡ ሰውም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፤

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 39 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ወደ ፡ ቤትኽ ፡ ተመለስ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገልኽ ፡ ንገር ፡ ብሎ ፡ አሰናበተው ። ኢየሱስም ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ እንዳደረገለት ፡ በከተማው ፡ ኹሉ ፡ እየሰበከ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 40 ፤ ኢየሱስም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁት ፡ ነበርና ፥ ሕዝቡ ፡ ተቀበሉት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 41 ፤ እንሆም ፥ ኢያኢሮስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ መጣ ፥ ርሱም ፡ የምኩራብ ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፡ በኢየሱስም ፡ እግር ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ እንዲገባ ፡ ለመነው ፤

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 42 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ የኾናት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነበረችውና ፤ ርሷም ፡ ለሞት ፡ ቀርባ ፡ ነበር ። ሲኼድም ፡ ሕዝቡ ፡ ያጨናንቁት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 43 ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዓመትም ፡ ገምሮ ፡ ደም ፡ የሚፈሳት ፡ ሴት ፡ ነበረች ፥ ትዳሯንም ፡ ኹሉ ፡ ለባለመድኀኒቶች ፡ ከስራ ፥ ማንም ፡ ሊፈውሳት ፡ አልተቻለውም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 44 ፤ በኋላውም ፡ ቀርባ ፡ የልብሱን ፡ ጫፍ ፡ ዳሰሰች ፥ የደሟም ፡ ፈሳሽ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ቆመ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 45 ፤ ኢየሱስም ፦ የዳሰሰኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ። ኹሉም ፡ በካዱ ፡ ጊዜ ፥ ጴጥሮስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፦ አቤቱ ፥ ሕዝቡ ፡ ያጭንቁኻልና ፥ ያጋፉኽማል ፤ የዳሰሰኝ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ትላለኽን ፧ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 46 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ዳሶኛል ፥ ኀይል ፡ ከእኔ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹና ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 47 ፤ ሴቲቱም ፡ እንዳልተሰወረች ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ እየተንቀጠቀጠች ፡ መጥታ ፡ በፊቱ ፡ ተደፋች ፥ በምን ፡ ምክንያትም ፡ እንደ ፡ ዳሰሰችው ፡ ፈጥናም ፡ እንደ ፡ ተፈወሰች ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ አወራች ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 48 ፤ ርሱም ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ እምነትሽ ፡ አድኖሻል ፤ በሰላም ፡ ኺጂ ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 49 ፤ ርሱም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከምኩራብ ፡ አለቃው ፡ ቤት ፡ መጥቶ ፦ ልጅኽ ፡ ሞታለች ፤ እንግዲህ ፡ መምህሩን ፡ አታድክም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 50 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ሰምቶ ፦ አትፍራ ፤ እመን ፡ ብቻ ፡ ትድንማለች ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 51 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ ሲገባ ፡ ከጴጥሮስና ፡ ከያዕቆብ ፡ ከዮሐንስም ፡ ከብላቴናዪቱም ፡ አባትና ፡ እናት ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አልፈቀደም ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 52 ፤ ኹሉም ፡ እያለቀሱላት ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይሉ ፡ ነበር ። ርሱ ፡ ግን ፦ አታልቅሱ ፤ ተኝታለች ፡ እንጂ ፡ አልሞተችም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 53 ፤ እንደ ፡ ሞተችም ፡ ዐውቀው ፡ በጣም ፡ ሣቁበት ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 54 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እጇን ፡ ይዞ ፦ አንቺ ፡ ብላቴና ፥ ተነሺ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 55 ፤ ነፍሷም ፡ ተመለሰች ፥ ፈጥናም ፡ ቆመች ፥ የምትበላውንም ፡ እንዲሰጧት ፡ አዘዘ ።

ሉቃ. ፡ 8 ፡ 56 ፤ ወላጆቿም ፡ ተገረሙ ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ የኾነውን ፡ ለማንም ፡ እንዳይነግሩ ፡ አዘዛቸው ።

_____የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱንም ፡ ሐዋርያት ፡ በአንድነት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፡ በአጋንንት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ደዌንም ፡ ይፈውሱ ፡ ዘንድ ፡ ኀይልና ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ፤

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርንም ፡ መንግሥት ፡ እንዲሰብኩና ፡ ድውዮችን ፡ እንዲፈውሱ ፡ ላካቸው ፥

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ በትርም ፡ ቢኾን ፥ ከረጢትም ፡ ቢኾን ፥ እንጀራም ፡ ቢኾን ፥ ብርም ፡ ቢኾን ፡ ለመንገድ ፡ ምንም ፡ አትያዙ ፥ ኹለት ፡ እጀ ፡ ጠባብም ፡ አይኹንላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ በማናቸውም ፡ በምትገቡበት ፡ ቤት ፡ በዚያ ፡ ተቀመጡ ፡ ከዚያም ፡ ውጡ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ማናቸውም ፡ የማይቀበሏችኹ ፡ ቢኾኑ ፥ ከዚያ ፡ ከተማ ፡ ወጥታችኹ ፡ ምስክር ፡ እንዲኾንባቸው ፡ ከእግራችኹ ፡ ትቢያ ፡ አራግፉ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ወጥተውም ፡ ወንጌልን ፡ እየሰበኩና ፡ በስፍራው ፡ ኹሉ ፡ እየፈወሱ ፡ በየመንደሩ ፡ ያልፉ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡ ሄሮድስም ፡ የተደረገውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሰምቶ ፥ አንዳንድ ፡ ሰዎች ፦

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ዮሐንስ ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ፥ ሌላዎችም ፦ ኤልያስ ፡ ተገለጠ ፥ ሌላዎችም ፦ ከቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፡ ተነሥቷል ፡ ይሉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ አመነታ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ሄሮድስም ፦ ዮሐንስን ፡ እኔ ፡ ራሱን ፡ አስቈረጥኩት ፤ ይህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ የምሰማበት ፡ ማን ፡ ነው ∴ አለ ። ሊያየውም ፡ ይሻ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ሐዋርያትም ፡ ተመልሰው ፡ ያደረጉትን ፡ ኹሉ ፡ ነገሩት ። ከርሱ ፡ ጋራም ፡ ወስዷቸው ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ከምትባል ፡ ከተማ ፡ አጠገብ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ለብቻው ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ሕዝቡም ፡ ዐውቀው ፡ ተከተሉት ፤ ተቀብሏቸውም ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ይነግራቸው ፡ ነበር ፥ መፈወስ ፡ ያስፈለጋቸውንም ፡ ፈወሳቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ቀኑም ፡ ይመሽ ፡ ዝመር ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ቀርበው ፦ በዚህ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ነንና ፡ በዙሪያችን ፡ ወዳሉ ፡ መንደሮችና ፡ ገጠሮች ፡ ኼደው ፡ እንዲያድሩና ፡ ምግብ ፡ እንዲያገኙ ፡ ሕዝቡን ፡ አሰናብት ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ እናንተ ፡ የሚበሉትን ፡ ስጧቸው ፡ አላቸው ። እነርሱም ፦ ኼደን ፡ ለዚህ ፡ ኹሉ ፡ ሕዝብ ፡ ምግብ ፡ ካልገዛን ፥ ከዐምስት ፡ እንጀራና ፡ ከኹለት ፡ ዓሣ ፡ የሚበልጥ ፡ የለንም ፡ አሉት ፤ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ያኽሉ ፡ ነበርና ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ በየክፍሉ ፡ ዐምሳ ፡ ዐምሳውን ፡ አስቀምጧቸው ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ እንዲህም ፡ አደረጉ ፡ ኹሉንም ፡ አስቀመጧቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ዐምስቱንም ፡ እንጀራና ፡ ኹለቱን ፡ ዓሣ ፡ ይዞ ፥ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሻቅቦ ፡ አየና ፡ ባረካቸው ፡ ቈርሶም ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ኹሉም ፡ በልተው ፡ ጠገቡ ፥ ከነርሱም ፡ የተረፈውን ፡ ቀ፡ርስራሽ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መሶብ ፡ ወሰዱ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ለብቻውም ፡ ሲጸልይ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩና ፦ ሕዝቡ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ይላሉ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፡ መልሰው ፦ መጥምቁ ፡ ዮሐንስ ፥ ሌላዎችም ፦ ኤልያስ ፥ ሌላዎችም ፦ ከቀደሙት ፡ ነቢያት ፡ አንዱ ፡ ተነሥቷል ፡ ይላሉ ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ እናንተስ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ትላላችኹ ፧ አላቸው ። ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ ከእግዚአብሔር ፡ የተቀባኽ ፡ ነኽ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 21-22 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፡ በሽማግሌዎችም ፡ በካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ በጻፊዎችም ፡ ሊጣል ፡ ሊገደልም ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ሊነሣ ፡ ይገ፡ባዋል ፡ ብሎ ፡ ለማንም ፡ ይህን ፡ እንዳይናገሩ ፡ አስጠንቅቆ ፡ አዘዘ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ለ፡ኹሉም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ በኋላዬ ፡ ሊመጣ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፥ ራሱን ፡ ይካድ ፡ መስቀሉንም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ተሸክሞ ፡ ይከተለኝ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚወድ ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋታልና ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ ነፍሱን ፡ የሚያጠፋ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ያድናታል ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ሰው ፡ ዓለሙን ፡ ኹሉ ፡ አትርፎ ፡ ራሱን ፡ ቢያጠፋ ፡ ወይም ፡ ቢያጐድል ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፧

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ በእኔና ፡ በቃሌ ፡ የሚያፍር ፡ ኹሉ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በክብሩ ፡ በአባቱና ፡ በቅዱሳን ፡ መላእክቱ ፡ ክብርም ፡ ሲመጣ ፡ በርሱ ፡ ያፍርበታል ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በዚህ ፡ ከሚቆሙት ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እስኪያዩ ፡ ድረስ ፡ ሞትን ፡ የማይቀምሱ ፡ አንዳንድ ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ከዚህም ፡ ቃል ፡ በኋላ ፡ ስምንት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ቈይቶ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ያዕቆብንም ፡ ይዞ ፡ ሊጸልይ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ሲጸልይም ፡ የፊቱ ፡ መልክ ፡ ተለወጠ ፤ ልብሱም ፡ ተብለጭልጭ ፡ ነጭ ፡ ኾነ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ እንሆም ፥ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ እነርሱም ፡ ሙሴና ፡ ኤልያስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ በክብርም ፡ ታይተው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሊፈጽም ፡ ስላለው ፡ ስለ ፡ መውጣቱ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጴጥሮስንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ እንቅልፍ ፡ ከበደባቸው ፤ ነቅተው ፡ ግን ፡ ክብሩንና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ቆመው ፡ የነበሩትን ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ አዩ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ከርሱም ፡ ሲለዩ ፥ ጴጥሮስ ፡ ኢየሱስን ፦ አቤቱ ፥ በዚህ ፡ መኾን ፡ ለእኛ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ አንድ ፡ ለአንተ ፡ አንድም ፡ ለሙሴ ፡ አንድም ፡ ለኤልያስ ፡ ሦስት ፡ ዳሶች ፡ እንሥራ ፡ አለው ፤ የሚለውንም ፡ አያውቅም ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ ይህንም ፡ ሲናገር ፡ ደመና ፡ መጣና ፡ ጋረዳቸው ፤ ወደ ፡ ደመናውም ፡ ሲገቡ ፡ ሳሉ ፡ ፈሩ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ ከደመናውም ፦ የመረጥኹት ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ርሱን ፡ ስሙት ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ መጣ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 36 ፤ ድምፁም ፡ ከመጣ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ብቻውን ፡ ኾኖ ፡ ተገኘ ። እነርሱም ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ ካዩትም ፡ ነገር ፡ በዚያ ፡ ወራት ፡ ምንም ፡ ለማንም ፡ አላወሩም ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 37 ፤ በነገውም ፡ ከተራራ ፡ ሲወርዱ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተገናኙት ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 38 ፤ እንሆም ፥ ከሕዝቡ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ለእኔ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ነውና ፥ ልጄን ፡ እንድታይልኝ ፡ እለምንኻለኹ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 39 ፤ እንሆም ፥ ጋኔን ፡ ይይዘዋል ፥ ድንገትም ፡ ይጮኻል ፡ ዐረፋም ፡ እያስደፈቀው ፡ ያንፈራግጠዋል ፥ እየቀጠቀጠም ፡ በጭንቅ ፡ ይለቀዋል ፤

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 40 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትኽንም ፡ እንዲያወጡት ፡ ለመንኹ ፥ አልቻሉምም ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 41 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እናንተ ፡ የማታምን ፡ ጠማማ ፡ ትውልድ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እኖራለኹ ፧ እስከ ፡ መቼስ ፡ እታገሣችኋለኹ ፧ ልጅኽን ፡ ወደዚህ ፡ አምጣው ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 42 ፤ ሲቀርብም ፡ ጋኔኑ ፡ ጣለውና ፡ አንፈራገጠው ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ርኩሱን ፡ መንፈስ ፡ ገሥጾ ፡ ብላቴናውን ፡ ፈወሰው ፡ ለአባቱም ፡ መለሰው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 43 ፤ ኾሉም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ታላቅነት ፡ የተነሣ ፡ ተገረሙ ። ኾሉም ፡ ኢየሱስ ፡ ባደረገው ፡ ኾሉ ፡ ሲደነቁ ፥

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 44 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ አለውና ፥ እናንተ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ በገሮሯችኹ ፡ አኑሩ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 45 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ አላስተዋሉም ፥ እንዳይገባቸውም ፡ ተሰውሮባቸው ፡ ነበር ፤ ስለዚህ ፡ ነገርም ፡ እንዳይጠይቁት ፡ ፈሩ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 46 ፤ ከነርሱም ፡ ማን ፡ እንዲበልጥ ፡ ክርክር ፡ ተነሣባቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 47 ፤ ኢየሱስም ፡ የልባቸውን ፡ ዐሳብ ፡ ዐውቆ ፡ ሕፃንን ፡ ያዘ ፤ በአጠገቡም ፡ አቁሞ ፦

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 48 ፤ ማንም ፡ ይህን ፡ ሕፃን ፡ በስሜ ፡ የሚቀበል ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፤ የሚቀበለኝም ፡ ኾሉ ፡ የላከኝን ፡ ይቀበላል ፤ ከኹላችኹ ፡ የሚያንስ ፡ ርሱ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 49 ፤ ዮሐንስም ፡ መልሶ ፦ አቤቱ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ በስምኽ ፡ አጋንንትን ፡ ሲያወጣ ፡ አየነው ፥ ከእኛ ፡ ጋራም ፡ ስለማይከተል ፡ ከለከልነው ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 50 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ የማይቃወማችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነውና ፥ አትከልክሉት ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 51 ፤ የሚወጣበትም ፡ ወራት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለመኼድ ፡ ፊቱን ፡ አቀና ፥

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 52 ፤ በፊቱም ፡ መልክተኞችን ፡ ሰደደ ። ኼደውም ፡ ሊያሰናዱለት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ወደሳምራውያን ፡ መንደር ፡ ገቡ ፤

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 53 ፤ ፊቱም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደሚኼድ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ አልተቀበሉትም ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 54 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ያዕቆብና ፡ ዮሐንስ ፡ አይተው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ኤልያስ ፡ ደግሞ ፡ እንዳደረገ ፡ እሳት ፡ ከሰማይ ፡ ወርዶ ፡ ያጥፋቸው ፡ እንል ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለኽን ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 55 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ገሠጻቸውና ፦ ምን ፡ ዐይነት ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ኾነላችኹ ፡ አታውቁም ፤

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 56 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ ሊያድን ፡ እንጂ ፡ ሊያጠፋ ፡ አልመጣም ፡ አለ ። ወደ ፡ ሌላ ፡ መንደርም ፡ ኼዱ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 57 ፤ እነርሱም ፡ በመንገድ ፡ ሲኼዱ ፡ አንድ ፡ ሰው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወደምትኼድበት ፡ ኹሉ ፡ እከተልኻለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 58 ፤ ኢየሱስም ፦ ለቀበሮዎች ፡ ጕድጓድ ፡ ለሰማይም ፡ ወፎች ፡ መሳፈሪያ ፡ አላቸው ፥ ለሰው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ የሚያስጠጋበት ፡ የለውም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 59 ፤ ሌላውንም ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ። ርሱ ፡ ግን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አስቀድሜ ፡ ልኺድና ፡ አባቴን ፡ እቀብር ፡ ዘንድ ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 60 ፤ ኢየሱስም ፦ ሙታናቸውን ፡ እንዲቀብሩ ፡ ሙታንን ፡ ተዋቸው ፤ አንተስ ፡ ኼደኽ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ስበክ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 61 ፤ ደግሞ ፡ ሌላው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እከተልኻለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድሜ ፡ ከቤቴ ፡ ሰዎች ፡ እንድሰናበት ፡ ፍቀድልኝ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 9 ፡ 62 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ ማንም ፡ ዕርፍ ፡ በእጁ ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ የሚመለከት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የተገባ ፡ አይደለም ፡ አለው ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጌታ ፡ ሌላዎቹን ፡ ሰብዓ ፡ ሾመ ፥ ኹለት ፡ ኹለትም ፡ አድርጎ ፡ ርሱ ፡ ሊኼድበት ፡ ወዳለው ፡ ከተማና ፡ ስፍራ ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ላካቸው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ አላቸውም ፦ መከሩስ ፡ ብዙ ፡ ነው ፥ ሠራተኞች ፡ ግን ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸው ፤ እንግዴህ ፡ የመከሩን ፡ ጌታ ፡ ለመከሩ ፡ ሠራተኞች ፡ እንዲልክ ፡ ለምኑት ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ኺዱ ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ በጎች ፡ በተኵላዎች ፡ መካከል ፡ እልካችኋለኹ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ኰረጆም ፡ ከረጢትም ፡ ጫማም ፡ አትያዙ ፤ በመንገድም ፡ ለማንም ፡ እጅ ፡ አትንሡ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ወደምትገቡበት ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ አስቀድማችኹ ፦ ሰላም ፡ ለዚህ ፡ ቤት ፡ ይኹን ፡ በሉ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ የሰላም ፡ ልጅ ፡ ቢኖር ፥ ሰላማችኹ ፡ ያድርበታል ፤ አለዚያም ፡ ይመለስላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ቤት ፡ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ እየበላችኹና ፡ እየጠጣችኹ ፡ ተቀመጡ ፤ ለሠራተኛ ፡ ደመ ፡ ወዙ ፡ ይገባዋልና ። ከቤት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ አትተላለፉ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ወደምትገቡባትም ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ቢቀበሏችኹ ፥ ያቀረቡላችኹን ፡ ብሉ ፤

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ በርሷም ፡ ያሉትን ፡ ድውዮችን ፡ ፈውሱና ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቀረበች ፡ በሏቸው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደምትገቡባት ፡ ከተማ ፡ ኹሉ ፡ ባይቀበሏችኹ ፥ ወደ ፡ አደባባይዋ ፡ ወጥታችኹ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ከከተማችኹ ፡ የተጣበቀብንን ፡ ትቢያ ፡ እንኳን ፡ እናራግፍላችኋለን ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደ ፡ ቀረበች ፡ ይህን ፡ ዕወቁ ፡ በሉ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ እላችኋለኹ ፥ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ ይልቅ ፡ ለሰዶም ፡ ይቀልላታል ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ወዮልሽ ፡ ኮራዚን ፥ ወዮልሽ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፤ በእናንተ ፡ የተደረገው ፡ ተኣምራት ፡ በጢሮስና ፡ በሲዶና ፡ ተደርጎ ፡ ቢኾን ፥ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ በዐመድም ፡ ተቀምጠው ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ንስሓ ፡ በገቡ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፍርድ ፡ ከእናንተ ፡ ይልቅ ፡ ለጢሮስና ፡ ለሲዶና ፡ ይቀልላቸዋል ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ አንቺም ፡ ቅፍርናሖም ፥ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ከፍ ፡ አልሽን ፧ ወደ ፡ ሲኦል ፡ ትወርጃለሽ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ የሚሰማችኹ ፡ እኔን ፡ ይሰማል ፥ እናንተንም ፡ የጣለ ፡ እኔን ፡ ይጥላል ፤ እኔንም ፡ የጣለ ፡ የላከኝን ፡ ይጥላል ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ሰብዓውም ፡ በደስታ ፡ ተመልሰው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አጋንንት ፡ ስንኳ ፡ በስምኽ ፡ ተገዝተውልናል ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፡ ሰይጣንን ፡ እንደ ፡ መብረቅ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወድቅ ፡ አየኹ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እንሆ ፥ እባቡንና ፡ ጊንጡን ፡ ትረግጡ ፡ ዘንድ ፥ በጠላትም ፡ ኀይል ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጥቻችኋለኹ ፥ የሚጐዳችኹም ፡ ምንም ፡ የለም ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መናፍስት ፡ ስለ ፡ ተገዙላችኹ ፡ በዚህ ፡ ደስ ፡ አይበላችኹ ፥ ስማችኹ ፡ ግን ፡ በሰማያት ፡ ሰለ ፡ ተጻፈ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ኢየሱስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሐሤት ፡ አደረገና ፦ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ከጥበበኞችና ፡ ከአስተዋዮች ፡ ሰውረኽ ፡ ለሕፃናት ፡ ስለ ፡ ገለጥኽላቸው ፥ አመሰግናለኹ ፤ አዎን ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ፈቃድኽ ፡ በፊትኽ ፡ እንዲህ ፡ ኾኗልና ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ኹሉ ፡ ከአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ተሰጥቶኛል ፥ ወልድንም ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከአብ ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፥ አብንም ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከወልድ ፡ በቀር ፡ ወልድም ፡ ሊገልጥለት ፡ ከሚፈቅድ ፡ በቀር ፡ የሚያውቅ ፡ የለም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ለብቻቸው ፦ የምታዩትን ፡ የሚያዩ ፡ ዐይኖች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ እላችኋለኹና ፥ እናንተ ፡ የምታዩትን ፡ ብዙዎች ፡ ነቢያትና ፡ ነገሥታት ፡ ሊያዩ ፡ ወደዱ ፡ አላዩምም ፥ የምትሰሙትንም ፡ ሊሰሙ ፡ ወደው ፡ አልሰሙም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ እንሆም ፥ አንድ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂ ፡ ሊፈትነው ፡ ተነሥቶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ እንድወርስ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ በሕግ ፡ የተጻፈው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እንዴትስ ፡ ታነባለኽ ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ አምላክኽን ፡ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ በፍጹም ፡ ነፍስኽም ፡ በፍጹም ፡ ኀይልኽም ፡ በፍጹም ፡ ዐሳብኽም ፡ ውደድ ፥ ባልንጀራኽንም ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ ኢየሱስም ፦ እውነት ፡ መለስኽ ፤ ይህን ፡ አድርግ ፡ በሕይወትም ፡ ትኖራለኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ሊያጸድቅ ፡ ወዶ ፡ ኢየሱስን ፦ ባልንጀራዬስ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ኢያሪኮ ፡ ወረደ ፡ በወንበዴዎችም ፡ እጅ ፡ ወደቀ ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ገፈፉት ፡ ደበደቡትም ፡ በሕይወትና ፡ በሞት ፡ መካከልም ፡ ትተውት ፡ ኼዱ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ ድንገትም ፡ አንድ ፡ ካህን ፡ በዚያ ፡ መንገድ ፡ ወረደ ፥ አይቶትም ፡ ገለል ፡ ብሎ ፡ ዐለፈ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ ሌዋዊ ፡ ወደዚያ ፡ ስፍራ ፡ መጣና ፡ አይቶት ፥ ገለል ፡ ብሎ ፡ ዐለፈ ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ አንድ ፡ ሳምራዊ ፡ ግን ፡ ሲኼድ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ፥ አይቶትም ፡ ዐዘነለት ፤

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ ቀርቦም ፡ ዘይትና ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ በቀኑስሎቹ ፡ ላይ ፡ አፍሶ ፡ አሰራቸው ፤ በራሱ ፡ አህያም ፡ ላይ ፡ አስቀምጦት ፡ ወደእንግዳዎች ፡ ማደሪያ ፡ ወሰደው ፥ ጠበቀውም ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ በማግስቱም ፡ ኹለት ፡ ዲናር ፡ አውጥቶ ፡ ለባለቤቱ ፡ ሰጠና ፦ ጠብቀው ፥ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የምትከስረውን ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ ስመለስ ፡ እከፍልኻለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ እንግዲህ ፡ ከነዚህ ፡ ከሦስቱ ፡ በወንበዴዎች ፡ እጅ ፡ ለወደቀው ፡ ባልንጀራ ፡ የኾነው ፡ ማንኛው ፡ ይመስልኻል ፧

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ ርሱም ፦ ምሕረት ፡ ያደረገለት ፡ አለ ። ኢየሱስም ፦ ኺድ ፥ አንተም ፡ እንዲሁ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ ሲኼዱም ፡ ርሱ ፡ ወደ ፡ አንዲት ፡ መንደር ፡ ገባ ፤ ማርታ ፡ የተባለች ፡ አንዲት ፡ ሴትም ፡ በቤቷ ፡ ተቀበለችው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 39 ፤ ለርሷም ፡ ማርያም ፡ የምትባል ፡ እኅት ፡ ነበረቻት ፥ ርሷም ፡ ደግሞ ፡ ቃሉን ፡ ልትሰማ ፡ በኢየሱስ ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 40 ፤ ማርታ ፡ ግን ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ በዛባት ፡ ባከነች ፤ ቀርባም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ እንድሠራ ፡ እኅቴ ፡ ብቻዬን ፡ ስትተወኝ ፡ አይገድኽምን ፧ እንኪያስ ፡ እንድታግዘኝ ፡ ንገራት ፡ አለችው ።

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 41 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ማርታ ፥ ማርታ ፥ በብዙ ፡ ነገር ፡ ትጨነቂያለሽ ፡ ትታወኪማለሽ ፥

ሉቃ. ፡ 10 ፡ 42 ፤ የሚያስፈልገው ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነው ፤ ማርያምም ፡ መልካም ፡ ዕድልን ፡ መርጣለች ፡ ከርሷም ፡ አይወሰድባትም ፡ አላት ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ርሱም ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፥ በጨረሰም ፡ ጊዜ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ እንዳስተማረ ፡ እንጸልይ ፡ ዘንድ ፡ አስተምረን ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ አላቸውም ፦ ስትጸልዩ ፡ እንዲህ ፡ በሉ ፦ በሰማያት ፡ የምትኖር ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፤ ስምኽ ፡ ይቀደስ ፤ መንግሥትኽ ፡ ትምጣ ፤ ፈቃድኽ ፡ በሰማይ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዲሁ ፡ በምድር ፡ ትኹን ፤

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ የዕለት ፡ እንጀራችንን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ስጠን ፤

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ኀጢአታችንንም ፡ ይቅር ፡ በለን ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ የበደሉንን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ ብለናልና ፤ ከክፉ ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ አታግባን ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ እንዲሀም ፡ አላቸው ፦ ከእናንተ ፡ ማናቸውም ፡ ወዳጅ ፡ ያለው ፥ በእኩል ፡ ሌሊትስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ኼዶ ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ሦስት ፡ እንጀራ ፡ አበድረኝ ፥

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ አንድ ፡ ወዳጄ ፡ ከመንገድ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥቶ ፡ የማቀርብለት ፡ የለኝምና ፡ ይላልን ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ያም ፡ ከውስጥ ፡ መልሶ ፦ አታድክመኝ ፤ አኹን ፡ ደጁ ፡ ተቈልፏል ፡ ልጆቼም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ አሉ ፤ ተነሥቼ ፡ ልሰጥኽ ፡ አልችልም ፡ ይላልን ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ እላችኋለኹ ፥ ወዳጅ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ተነሥቶ ፡ ባይሰጠው ፡ እንኳ ፥ ስለ ፡ ንዝነዛው ፡ ተነሥቶ ፡ የሚፈልገውን ፡ ኹሉ ፡ ይሰጠዋል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ እኔም ፡ እላችኋለኹ ፦ ለምኑ ፥ ይሰጣችኹማል ፤ ፈልጉ ፥ ታገኙማላችኹ ፤ መዝጊያን ፡ አንኳኩ ፥ ይከፍትላችኹማል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ የሚለምን ፡ ኹሉ ፡ ይቀበላልና ፥ የሚፈልግም ፡ ያገኛል ፥ መዝጊያውንም ፡ ለሚያንኳኳው ፡ ይከፈትለታል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ አባት ፡ ከኾናችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ከማንኛችኹም ፡ ልጁ ፡ እንጀራ ፡ ቢለምነው ፥ ርሱም ፡ ድንጋይ ፡ ይሰጠዋልን ። ዓሣ ፡ ደግሞ ፡ ቢለምነው ፡ በዓሣ ፡ ፋንታ ፡ እባብ ፡ ይሰጠዋልን ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ወይስ ፡ ዕንቁላል ፡ ቢለምነው ፡ ጊንጥ ፡ ይሰጠዋልን ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ እንኪያስ ፡ እናንተ ፡ ክፉዎች ፡ ስትኾኑ ፡ ለልጆቻችኹ ፡ መልካም ፡ ስጦታ ፡ መስጠት ፡ ካወቃችኹ ፥ በሰማይ ፡ ያለው ፡ አባት ፡ ለሚለምኑት ፡ እንዴት ፡ አብልጦ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ይሰጣቸው ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ዲዳውንም ፡ ጋኔን ፡ ያወጣ ፡ ነበር ፤ ጋኔኑም ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ ዲዳው ፡ ተናገረ ፡ ሕዝቡም ፡ ተደነቁ ፤

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነርሱ ፡ አንዳንዱ ፦ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ በአጋንንት ፡ አለቃ ፡ አጋንንትን ፡ ያወጣል ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ሌላዎችም ፡ ሲፈትኑት ፡ ከሰማይ ፡ ምልክት ፡ ከርሱ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ርስ ፡ በርሷ ፡ የምትለያይ ፡ መንግሥት ፡ ኹሉ ፡ ትጠፋለች ፤ ቤትም ፡ በቤት ፡ ላይ ፡ ይወድቃል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ አጋንንትን ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ እንዳወጣ ፡ ትላላችኹና ፡ ሰይጣን ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከተለያየ ፡ መንግሥቱ ፡ እንዴት ፡ ትቆማለች ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ እኔስ ፡ በብዔል ፡ ዜቡል ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከኾንኹ ፥ ልጆቻችኹ ፡ በማን ፡ ያወጧቸዋል ። ስለዚህ ፡ እነርሱ ፡ ፈራጆች ፡ ይኾኑባችኋል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጣት ፡ አጋንንትን ፡ የማወጣ ፡ ከኾንኹ ፥ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ደርሳለች ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ኀይለኛ ፡ ሰው ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ይዞ ፡ የራሱን ፡ ግቢ ፡ ቢጠብቅ ፥ ያለው ፡ ገንዘቡ ፡ በሰላም ፡ ይኾናል ፤

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ የሚበረታ ፡ መጥቶ ፡ ሲያሸንፈው ፡ ግን ፥ ታምኖበት ፡ የነበረውን ፡ ጋሻና ፡ ጦር ፡ ይወስድበታል ፡ ምርኮውንም ፡ ያካፍላል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያልኾነ ፡ ይቃወመኛል ፥ ከእኔ ፡ ጋራም ፡ የማያከማች ፡ ይበትናል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ርኩስ ፡ መንፈስ ፡ ከሰው ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ዕረፍትን ፡ እየፈለገ ፡ ውሃ ፡ በሌለበት ፡ ቦታ ፡ ያልፋል ፤ ባያገኝም ፦ ወደወጣኹበት ፡ ቤቴ ፡ እመለሳለኹ ፡ ይላል ፤

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ሲመጣም ፡ ተጠርጎ ፡ አጊጦም ፡ ያገኘዋል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይኼድና ፡ ከርሱ ፡ የከፉትን ፡ ሌላዎችን ፡ ሰባት ፡ አጋንንት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይይዛል ፥ ገብተውም ፡ በዚያ ፡ ይኖራሉ ፤ ለዚያም ፡ ሰው ፡ ከፊተኛው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ ይብስበታል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ ይህንም ፡ ሲናገር ፥ ከሕዝቡ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ድምፂን ፡ ከፍ ፡ አድርጋ ፦ የተሸከመችኽ ፡ ማሕፀንና ፡ የጠባኻቸው ፡ ጡቶች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ አለችው ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ አዎን ፥ ብፁዓንስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ የሚጠብቁት ፡ ናቸው ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ገመር ፦ ይህ ፡ ትውልድ ፡ ክፉ ፡ ነው ፤ ምልክት ፡ ይፈልጋል ፥ ከነቢዩም ፡ ከዮናስ ፡ ምልክት ፡ በቀር ፡ ምልክት ፡ አይሰጠውም ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ዮናስ ፡ ለነነዌ ፡ ሰዎች ፡ ምልክት ፡ እንደ ፡ ኾናቸው ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ለዚህ ፡ ትውልድ ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ንግሥተ ፡ አዜብ ፡ በፍርድ ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተነሥታ ፡ ትፈርድባቸዋለች ፤ የሰሎሞንን ፡ ጥበብ ፡ ለመስማት ፡ ከምድር ፡ ዳር ፡ መጥታለችና ፥ እንሆም ፥ ከሰሎሞን ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ የነነዌ ፡ ሰዎች ፡ በፍርድ ፡ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ጋራ ፡ ተነሥተው ፡ ይፈርዱበታል ፤ በዮናስ ፡ ስብከት ፡ ንስሓ ፡ ገብተዋልና ፥ እንሆም ፥ ከዮናስ ፡ የሚበልጥ ፡ ከዚህ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ መብራትንም ፡ አብርቶ ፡ በስውር ፡ ወይም ፡ በእንቅብ ፡ በታች ፡ የሚያኖረው ፡ የለም ፥ የሚገቡ ፡ ሰዎች ፡ ብርሃኑን ፡ እንዲያዩ ፡ በመቅረዝ ፡ ላይ ፡ ያኖረዋል ፡ እንጂ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ የሰውነትኽ ፡ መብራት ፡ ዐይንኽ ፡ ናት ። ዐይንኽ ፡ ጤናማ ፡ በኾነች ፡ ጊዜ ፡ ሰውነትኽ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ብሩህ ፡ ይኾናል ። ዐይንኽ ፡ ታማሚ ፡ በኾነች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሰውነትኽ ፡ ደግሞ ፡ የጨለመ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ እንግዲህ ፡ ባንተ ፡ ያለው ፡ ብርሃን ፡ ጨለማ ፡ እንዳይኾን ፡ ተመልከት ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ እንግዲህ ፡ ሰውነትኽ ፡ ኹሉ ፡ የጨለማ ፡ ቍራጭ ፡ የሌለበት ፡ ብሩህ ፡ ቢኾን ፥ መብራት ፡

በደመቀ ፡ ብርሃን ፡ እንደሚያበራልኽ ፡ በጭራሽ ፡ ብሩህ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 37 ፤ ይህንም ፡ ሲናገር ፡ አንድ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ምሳ ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ፡ ገብቶም ፡ ተቀመጠ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 38 ፤ ከምሳም ፡ በፊት ፡ አስቀድሞ ፡ እንዳልታጠበ ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፥ ፈሪሳዊው ፡ ተደነቀ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 39 ፤ ጌታም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አኹን ፡ እናንተ ፡ ፈሪሳውያን ፡ የጽዋውንና ፡ የወጭቱን ፡ ውጭ ፡ ታጠራላችኹ ፥ ውስጣችኹ ፡ ግን ፡ ቅሚያና ፡ ክፋት ፡ ሞልቶበታል ፡

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 40 ፤ እናንት ፡ ደንቈሮዎች ፥ የውጩን ፡ የፈጠረ ፡ የውስጡን ፡ ደግሞ ፡ አልፈጠረምን ፧

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 41 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በውስጥ ፡ ያለውን ፡ ምጽዋት ፡ አድርጋችኹ ፡ ስጡ ፥ እንሆም ፥ ኹሉ ፡ ንጹሕ ፡ ይኾንላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 42 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ ፈሪሳውያን ፥ ከአዝሙድና ፡ ከጤና ፡ አዳም ፡ ከአትክልትም ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ ስለምታወጡ ፥ ፍርድንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደድ ፡ ስለምትተላለፉ ፥ ወዮላችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሌላውን ፡ ሳትተዉ ፡ ይህን ፡ ልታደርጉት ፡ ይገባችኹ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 43 ፤ እናንተ ፡ ፈሪሳውያን ፥ በምኩራብ ፡ የከበሬታ ፡ ወንበር ፡ በገበያም ፡ ሰላምታ ፡ ስለምትወዱ ፥ ወዮላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 44 ፤ እናንተ ፡ ግብዞች ፡ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፥ ሰዎች ፡ ሳያውቁ ፡ በላዩ ፡ የሚኼዱበት ፡ የተሰወረ ፡ መቃብር ፡ ስለምትመስሉ ፥ ወዮላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 45 ፤ ከሕግ ፡ ዐዋቂዎችም ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ማለትኽ ፡ እኛን ፡ ደግሞ ፡ መስደብኽ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 46 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፥ አስቸጋሪ ፡ ሸክም ፡ ለሰዎች ፡ ስለምታሸክሙ ፥ ራሳችኹም ፡ በአንዲት ፡ ጣታችኹ ፡ ስንኳ ፡ ሸክሙን ፡ ስለማትነኩት ፥ ወዮላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 47 ፤ አባቶቻችኹ ፡ የገደሏቸውን ፡ የነቢያትን ፡ መቃብር ፡ ስለምትሠሩ ፥ ወዮላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 48 ፤ እንግዲህ ፡ ለአባቶቻችኹ ፡ ሥራ ፡ ትመሰክራላችኹ ፡ ትስማማላችኹም ፤ እነርሱ ፡ ገድለዋቸዋልና ፥ እናንተም ፡ መቃብራቸውን ፡ ትሠራላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 49 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ እንዲህ ፡ አለች ፦ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ነቢያትንና ፡ ሐዋርያትን ፡ እልካለኹ ፥ ከነርሱም ፡ ይገድላሉ ፥ ያሳድዱማል ፥

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 50 ፤ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ የፈሰሰው ፡ የነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ደም ፥

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 51 ፤ ከአቤል ፡ ደም ፡ ዠምሮ ፡ በመሠዊያውና ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ጠፋው ፥ እስከ ፡ ዘካርያስ ፡ ደም ፡ ድረስ ፥ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ እንዲፈለግ ፡ አዎን ፡ እላችኋለኹ ፥ ከዚህ ፡ ትውልድ ፡ ይፈለጋል ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 52 ፤ እናንተ ፡ ሕግ ፡ ዐዋቂዎች ፥ የዕውቀትን ፡ መክፈቻ ፡ ስለ ፡ ወሰዳችኹ ፥ ወዮላችኹ ፡ ራሳችኹ ፡ አልገባችኹም ፡ የሚገቡትንም ፡ ከለከላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 11 ፡ 53-54 ፤ ይህንም ፡ ሲናገራቸው ፥ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ በአፉ ፡ የተናገረውን ፡ ሊነጥቁ ፡ ሲያደቡ ፥ እጅግ ፡ ይቃወሙና ፡ ስለ ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እንዲናገር ፡ ያነሣሡ ፡ ዠመር ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የሕዝብ ፡ አእላፍ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እስኪረጋገጡ ፡ ድረስ ፡ ተሰብስበው ፡ ሳሉ ፥ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንዲህ ፡ ይል ፡ ዠመር ። አስቀድማችኹ ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ርሾ ፡ ተጠበቁ ፥ ርሱም ፡ ግብዝነት ፡ ነው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የማይገለጥ ፡ የተከደነ ፥ የማይታወቅም ፡ የተሰወረ ፡ ምንም ፡ የለም ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 3 ፤ ስለዚህ ፥ በጨለማ ፡ የምትናገሩት ፡ ኹሉ ፡ በብርሃን ፡ ይሰማል ፥ በዕልፍኝም ፡ ውስጥ ፡ በጉሮሮ ፡ የምትናገሩት ፡ በሰገነት ፡ ላይ ፡ ይሰበካል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 4 ፤ ለእናንተም ፡ ለወዳጆቼ ፡ እላችኋለኹ ፥ ሥጋን ፡ የሚገድሉትን ፡ በኋላም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚበልጥ ፡ ሊያደርጉ ፡ የማይችሉትን ፡ አትፍሩ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 5 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የምትፈሩትን ፡ አሳያችኋለኹ ፤ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ለመጣል ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ ፍሩ ። አዎን ፡ እላችኋለኹ ፥ ርሱን ፡ ፍሩ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 6 ፤ ዐምስት ፡ ድንቢጦች ፡ በዐሥር ፡ ሳንቲም ፡ ይሸጡ ፡ የለምን ፧ ከነርሱም ፡ አንዲቱ ፡ ስንኳ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ አትረሳም ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእናንተ ፡ የራሳችኹ ፡ ጠጕር ፡ ኹሉ ፡ እንኳ ፡ የተቈጠረ ፡ ነው ፤ እንግዲያስ ፡ አትፍሩ ፡ ከብዙ ፡ ድንቢጦች ፡ ትበልጣላችኹ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 8 ፤ እላችኹማለኹ ፥ በሰው ፡ ፊት ፡ የሚመሰክርልኝ ፡ ኹሉ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ደግሞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ይመሰክርለታል ፤

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 9 ፤ በሰውም ፡ ፊት ፡ የሚክደኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ይካዳል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 10 ፤ በሰው ፡ ልጅም ፡ ላይ ፡ ቃል ፡ የሚናገር ፡ ኹሉ ፡ ይሰረይለታል ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የሚሰድብ ፡ ግን ፡ አይሰረይለትም ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 11 ፤ ወደ ፡ ምኩራቦችና ፡ ወደ ፡ መኳንንቶችም ፡ ወደ ፡ ገዥዎችም ፡ ሲጐትቷችኹ ፥ እንዴት ፡ ወይም ፡ ምን ፡ እንድትመልሱ ፡ ወይም ፡ እንድትናገሩ ፡ አትጨነቁ ፤

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 12 ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ልትናገሩ ፡ የሚገባችኹን ፡ ያስተምራችኋልና ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 13 ፤ ከሕዝቡም ፡ አንድ ፡ ሰው ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ርስቱን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እንዲካፈል ፡ ለወንድሜ ፡ ንገረው ፡ አለው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 14 ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ ሰው ፥ ፈራጅና ፡ አካፋይ ፡ በላያችኹ ፡ እንድኾን ፡ ማን ፡ ሾመኝ ፧ አለው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 15 ፤ የሰው ፡ ሕይወት ፡ በገንዘቡ ፡ ብዛት ፡ አይደለምና ፡ ተጠንቀቁ ፥ ከመጐምጐጥም ፡ ኹሉ ፡ ተጠበቁ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 16 ፤ ምሳሌም ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ አንድ ፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ዕርሻ ፡ እጅግ ፡ ፍሬያም ፡ ኾነችለት ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 17 ፤ ርሱም ፦ ፍሬዬን ፡ የማከማችበት ፡ ስፍራ ፡ ዐጥቻለኹና ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 18 ፤ እንዲህ ፡ አደርጋለኹ ፤ ጐተራዬን ፡ አፍርሼ ፡ ሌላ ፡ የሚበልጥ ፡ እሠራለኹ ፥ በዚያም ፡

ፍሬዬንና ፡ በረከቴን ፡ ኹሉ ፡ አከማቻለኹ ፤

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ነፍሴንም ፦ አንቺ ፡ ነፍሴ ፥ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የሚቀር ፡ ብዙ ፡ በረከት ፡ አለሽ ፤ ዕረፊ ፥ ብዪ ፥ ጠጪ ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ እላታለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፦ አንተ ፡ ሰነፍ ፥ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ነፍስኽን ፡ ከአንተ ፡ ሊወስዷት ፡ ይፈልጓታል ፤ ይህስ ፡ የሰበሰብኸው ፡ ለማን ፡ ይኾናል ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ለራሱ ፡ ገንዘብ ፡ የሚያከማች ፥ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድም ፡ ባለጠጋ ፡ ያልኾነ ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ስለዚህ ፡ እላችኋለኹ ፥ ለነፍሳችኹ ፡ በምትበሉት ፡ ወይም ፡ ለሰውነታችኹ ፡ በምትለብሱት ፡ አትጨነቁ ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ነፍስ ፡ ከመብል ፡ ሰውነትም ፡ ከልብስ ፡ ይበልጣልና ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ ቀሩራዎችን ፡ ተመልከቱ ፤ አይዘሩም ፡ አያጭዱምም ፥ ዕቃ ፡ ቤትም ፡ ወይም ፡ ጐተራ ፡ የላቸውም ፥ እግዚአብሔርም ፡ ይመግባቸዋል ፤ እናንተስ ፡ ከወፎች ፡ እንዴት ፡ ትበልጣላችኹ ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ከእናንተ ፡ ተጨንቆ ፡ በቁመቱ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ክንድ ፡ መጨመር ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፡ ትንሹን ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡ የማትችሉ ፡ ከኾናችኹ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ በሌላ ፡ ትጨነቃላችኹ ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ አበባዎችን ፡ እንዴት ፡ እንዲያድጉ ፡ ተመልከቱ ፤ አይደክሙም ፡ አይፈትሉምም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላችኋለኹ ፥ ሰሎሞንስ ፡ እንኳ ፡ በክብሩ ፡ ኹሉ ፡ ከነዚህ ፡ እንደ ፡ አንዱቱ ፡ አለበሰም ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ያለውን ፡ ነገም ፡ ወደ ፡ እቶን ፡ የሚጣለውን ፡ በሜዳ ፡ የኾነውን ፡ ሣር ፡ እንዲህ ፡ የሚያለብሰው ፡ ከኾነ ፥ እናንተ ፡ እምነት ፡ የጐደላችኹ ፥ እናንተንማ ፡ ይልቁን ፡ እንዴት ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ እናንተም ፡ የምትበሉትን ፡ የምትጠጡትንም ፡ አትፈልጉ ፥ አታወላውሉም ፤

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 30 ፤ ይህንስ ፡ ኹሉ ፡ በዓለም ፡ ያሉ ፡ አሕዛብ ፡ ይፈልጉታልና ፤ የእናንተም ፡ አባት ፡ ይህ ፡ እንዲያስፈልጋችኹ ፡ ያውቃል ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 31 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መንግሥቱን ፡ ፈልጉ ፡ ይህም ፡ ኹሉ ፡ ይጨመርላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 32 ፤ አንተ ፡ ታናሽ ፡ መንጋ ፥ መንግሥትን ፡ ሊሰጣችኹ ፡ የአባታችኹ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፥ አትፍሩ ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 33 ፤ ያላችኹን ፡ ሽጡ ፡ ምጽዋትም ፡ ስጡ ፤ ሌባ ፡ በማይቀርብበት ፡ ብልም ፡ በማያጠፋበት ፡ በሰማያት ፡ የማያልቅ ፡ መዝገብ ፡ የሚኾኑትን ፡ የማያረጁትንም ፡ ኰረጆዎች ፡ ለራሳችኹ ፡ አድርጉ ፤

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 34 ፤ መዝገባችኹ ፡ ባለበት ፡ ልባችኹ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ይኾናልና ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 35 ፤ ወገባችኹ ፡ የታጠቀ ፡ መብራታችኹም ፡ የበራ ፡ ይኹን ፤

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 36 ፤ እናንተም ፡ ጌታቸው ፡ መጥቶ ፡ ደጁን ፡ ሲያንኳኳ ፡ ወዲያው ፡ እንዲከፍቱለት ፡ ከሰርግ ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎችን ፡ ምሰሉ ፡

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 37 ፤ ጌታቸው ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ሲተጉ ፡ የሚያገኛቸው ፡ እነዚያ ፡ ባሪያዎች ፡ ብፁዓን ፡

ናቸው ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ታጥቆ ፡ በማእዱ ፡ ያስቀምጣቸዋል ፡ ቀርቦም ፡ ያገለግላቸዋል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 38 ፤ ከሌሊቱም ፡ በኹለተኛው ፡ ወይም ፡ በሦስተኛው ፡ ክፍል ፡ መጥቶ ፡ እንዲሁ ፡ ቢያገኛቸው ፥ እነዚያ ፡ ባሪያዎች ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 39 ፤ ይህን ፡ ግን ፡ ዕወቁ ፡ ባለቤት ፡ በምን ፡ ሰዓት ፡ ሌባ ፡ እንዲመጣ ፡ ቢያውቅ ፡ ኖሮ ፥ በነቃ ፥ ቤቱም ፡ እንዲቈፈር ፡ ባልፈቀደም ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 40 ፤ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ተዘጋጅታችኹ ፡ ኑሩ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በማታስቡበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣልና ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 41 ፤ ጴጥሮስም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ ለእኛ ፡ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ለሹሉ ፡ ትናገራለኽን ፧ አለው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 42 ፤ ጌታም ፡ አለ ፦ እንኪያስ ፡ ምግባቸውን ፡ በጊዜው ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ጌታው ፡ በቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ላይ ፡ የሚሾመው ፡ ታማኝና ፡ ልባም ፡ መጋቢ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 43 ፤ ጌታው ፡ መጥቶ ፡ እንዲህ ፡ ሲያደርግ ፡ የሚያገኘው ፡ ያ ፡ ባሪያ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 44 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ባለው ፡ ሹሉ ፡ ላይ ፡ ይሾመዋል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 45 ፤ ያ ፡ ባሪያ ፡ ግን ፦ ጌታዬ ፡ እስኪመጣ ፡ ይዘገያል ፡ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ቢያስብ ፡ ሎሌዎችንና ፡ ገረዶችንም ፡ ይመታ ፡ ይበላም ፡ ይጠጣም ፡ ይሰክርም ፡ ዘንድ ፡ ቢገዥምር ፥

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 46 ፤ የዚያ ፡ ባሪያ ፡ ጌታ ፡ ባልጠበቃት ፡ ቀን ፡ ባላወቃትም ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፥ ከኹለትም ፡ ይሰነጥቀዋል ፡ ዕድሉንም ፡ ከማይታመኑ ፡ ጋራ ፡ ያደርጋል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 47 ፤ የጌታውንም ፡ ፈቃድ ፡ ዐውቆ ፡ ያልተዘጋጀ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱም ፡ ያላደረገ ፡ ያ ፡ ባሪያ ፡ እጅግ ፡ ይገረፋል ፤

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 48 ፤ ያላወቀ ፡ ግን ፥ መገረፍ ፡ የሚገባውንም ፡ ያደረገ ፡ ጥቂት ፡ ይገረፋል ። ብዙም ፡ ከተሰጠው ፡ ሰው ፡ ሹሉ ፡ ከርሱ ፡ ብዙ ፡ ይፈለግበታል ፥ ብዙ ፡ ዐደራም ፡ ከተሰጠው ፡ ከርሱ ፡ አብዝተው ፡ ይሹበታል ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 49 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ እሳት ፡ ልጥል ፡ መጣኹ ፥ አኹንም ፡ የነደደ ፡ ከኾነ ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ እፈልጋለኹ ፧

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 50 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የምጠመቃት ፡ ጥምቀት ፡ አለችኝ ፥ እስክትፈጸምም ፡ ድረስ ፡ እንዴት ፡ እጨነቃለኹ ፧

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 51 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ሰላምንም ፡ ለመስጠት ፡ የመጣኹ ፡ ይመስላችኋልን ፧ እላችኋለኹ ፥ አይደለም ፥ መለያየትን ፡ እንጂ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 52 ፤ ካኹን ፡ ገዥምሮ ፡ በአንዲት ፡ ቤት ፡ ዐምስት ፡ ሰዎች ፡ ይኖራሉና ፤ ሦስቱም ፡ በኹለቱ ፡ ላይ ፡ ኹለቱም ፡ በሦስቱ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ይለያያሉ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 53 ፤ አባት ፡ በልጁ ፡ ላይ ፡ ልጅም ፡ በአባቱ ፡ ላይ ፥ እናት ፡ በልጇ ፡ ላይ ፡ ልጇም ፡ በእናቷ ፡ ላይ ፥ ዐማት ፡ በምራቷ ፡ ላይ ፡ ምራትም ፡ በአማቷ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ይለያያሉ ።

ሉቃ. ፥ 12 ፥ 54 ፤ ደግሞም ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ደመና ፡ ከምዕራብ ፡ ሲወጣ ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፥ ወዲያው ። ዝናብ ፡ ይመጣል ፡ ትላላችኹ ፥ እንዲሁም ፡ ይኾናል ፤

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 55 ፤ በአዜብም ፡ ነፋስ ፡ ሲነፍስ ፦ ትኵሳት ፡ ይኾናል ፡ ትላላችኹ ፥ ይኾንማል ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 56 ፤ እናንት ፡ ግብዞች ፥ የምድሩንና ፡ የሰማዩን ፡ ፊት ፡ ልትመረምሩ ፡ ታውቃላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ዘመን ፡ የማትመረምሩ ፡ እንዴት ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 57 ፤ ራሳችኹ ፡ ደግሞ ፡ ጽድቅን ፡ የማትፈርዱ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 58 ፤ ከባላጋራኽ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሹም ፡ ብትኼድ ፥ ወደ ፡ ዳኛ ፡ እንዳይጐትትኽ ፡ ዳኛውም ፡ ለሎሌው ፡ አሳልፎ ፡ እንዳይሰጥኽ ፡ ሎሌውም ፡ በወህኒ ፡ እንዳይጥልኽ ፥ ገና ፡ በመንገድ ፡ ሳለኽ ፡ ከባላጋራኽ ፡ እንድትታረቅ ፡ ትጋ ።

ሉቃ. ፡ 12 ፡ 59 ፤ እልኻለኹ ፥ የመጨረሻዋን ፡ ግማሽ ፡ ሳንቲም ፡ እስክትከፍል ፡ ድረስ ፡ ከዚያ ፡ ከቶ ፡ አትወጣም ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ ጲላጦስ ፡ ደማቸውን ፡ ከመሥዋዕታቸው ፡ ጋራ ፡ ስላደባለቀው ፡ ስለገሊላ ፡ ሰዎች ፡ አወሩለት ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እነዚህ ፡ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ደረሰባቸው ፥ ከገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ኀጢአተኞች ፡ የኾኑ ፡ ይመስሏችኋልን ፧

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ እላችኋለኹ ፥ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንስሓ ፡ ባትገቡ ፡ ኹላችኹ ፡ እንዲሁ ፡ ትጠፋላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ወይስ ፡ በሰሌሆም ፡ ግንቡ ፡ የወደቀባቸውና ፡ የገደላቸው ፡ እነዚያ ፡ ዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ሰዎች ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ በደለኞች ፡ ይመስሏችኋልን ፧ አይደለም ፥ እላችኋለኹ ፤

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ንስሓ ፡ ባትገቡ ፡ ኹላችኹ ፡ እንደዚሁ ፡ ትጠፋላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ አለ ፦ ላንድ ፡ ሰው ፡ በወይኑ ፡ አትክልት ፡ የተተከለች ፡ በለስ ፡ ነበረችው ፥ ፍሬም ፡ ሊፈልግባት ፡ መጥቶ ፡ ምንም ፡ አላገኘም ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ የወይን ፡ አትክልት ፡ ሠራተኛውንም ፦ እንሆ ፥ ከዚች ፡ በለስ ፡ ፍሬ ፡ ልፈልግ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ እየመጣኹ ፡ ምንም ፡ አላገኘኹም ፤ ቍረጣት ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ደግሞ ፡ መሬቱን ፡ ታጐሳቀላለች ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዙሪያዋን ፡ እስክኰተኵትላትና ፡ ፋንድያ ፡ እስካፈስላት ፡ ድረስ ፡ በዚች ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፡ ተዋት ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ ብታፈራ ፥ ደኅና ፡ ነው ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ ትቈርጣታለኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ በሰንበትም ፡ ባንድ ፡ ምኵራብ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ እንሆም ፥ ከዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ የድካም ፡ መንፈስ ፡ ያደረባት ፡ ሴት ፡ ነበረች ፥ ርሷም ፡ ጐባጣ ፡ ነበረች ፥ ቀንታም ፡ ልትቆም ፡ ከቶ ፡ አልተቻላትም ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ኢየሱስም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ ጠራትና ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ ከድካምሽ ፡ ተፈትሻል ፡ አላት ፥ እጁንም ፡ ጫነባት ፤

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ቀጥ ፡ አለች ፥ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነች ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ የምኵራብ ፡ አለቃ ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ በሰንበት ፡ ስለ ፡ ፈወሰ ፡ ተቈጥቶ ፡ መለሰና ፡ ሕዝቡን ፦ ሊሠራባቸው ፡ የሚገባ ፡ ስድስት ፡ ቀኖች ፡ አሉ ፤ እንግዲህ ፡ በእነርሱ ፡ መጥታችኹ ፡ ተፈወሱ ፡ እንጂ ፡ በሰንበት ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ ጌታም ፡ መልሶ ፦ እናንተ ፡ ግብዞች ፥ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ በሰንበት ፡ በሬውን ፡ ወይስ ፡ አህያውን ፡ ከግርግሙ ፡ ፈቶ ፡ ውሃ ፡ ሊያጠጣው ፡ ይወስደው ፡ የለምን ፧

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ይህችም ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ኾና ፡ ከዐሥራ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ ሰይጣን ፡ ያሰራት ፡ በሰንበት ፡ ቀን ፡ ከዚህ ፡ እስራት ፡ ልትፈታ ፡ አይገባምን ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ይህንም ፡ ሲናገር ፡ ሳለ ፡ የተቃወሙት ፡ ኹሉ ፡ ዐፈሩ ፤ ከርሱም ፡ በተደረገው ፡ ድንቅ ፡ ኹሉ ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ምን ፡ ትመስላለች ፥ በምንስ ፡ አስመስላታለኹ ፧

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ ሰው ፡ ወስዶ ፡ በአትክልቱ ፡ የጣላትን ፡ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ ትመስላለች ፤ አደገችም ፡ ታላቅ ፡ ዛፍም ፡ ኾነች ፥ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ በቅርንጫፎቿ ፡ ሰፈሩ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ደግሞም ፥ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ በምን ፡ አስመስላታለኹ ፧

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ሴት ፡ ወስዳ ፡ ኹሉ ፡ እስኪቦካ ፡ ድረስ ፡ በሦስት ፡ መስፈሪያ ፡ ዱቄት ፡ የሸሸገችውን ፡ ርሾ ፡ ትመስላለች ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲኼድ ፡ ከተማዎችንና ፡ መንደሮችን ፡ እያስተማረ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የሚድኑ ፡ ጥቂቶች ፡ ናቸውን ፧ አለው ። ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ በጠበበው ፡ በር ፡ ለመግባት ፡ ተጋደሉ ፤ እላችኋለኹና ፥ ብዙዎች ፡ ሊገቡ ፡ ይፈልጋሉ ፡ አይችሉምም ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ባለቤቱ ፡ ተነሥቶ ፡ በሩን ፡ ከቈለፈ ፡ በኋላ ፥ እናንተ ፡ በውጭ ፡ ቆማችኹ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ክፈትልን ፡ እያላችኹ ፡ በሩን ፡ ልታንኳኩ ፡ ትዠምራላችኹ ፡ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ አላውቃችኹም ፡ ይላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፦ በፊትኽ ፡ በላን ፡ ጠጣንም ፡ በአደባባያችንም ፡ አስተማርኽ ፡ ልትሉ ፡ ትዠምራላችኹ ፤

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ ርሱም ፦ እላችኋለኹ ፥ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ አላውቃችኹም ፤ ኹላችኹ ፡ ዐመፀኞች ፥ ከእኔ ፡ ራቁ ፡ ይላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ አብርሃምንና ፡ ይሥሐቅን ፡ ያዕቆብንም ፡ ነቢያትንም ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ባያችኹ ፡ ጊዜ ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ተጥላችኹ ፡ ስትቀሩ ፥ በዚያ ፡ ልቅሶና ፡ ጥርስ ፡ ማፋጨት ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ ከምሥራቅና ፡ ከምዕራብም ፡ ከሰሜንና ፡ ከደቡብም ፡ ይመጣሉ ፥ በእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ በማእዱ ፡ ይቀመጣሉ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ እንሆም ፥ ከኋለኞች ፡ ፊተኞች ፡ የሚኾኑ ፡ አሉ ፥ ከፊተኞችም ፡ ኋለኞች ፡ የሚኾኑ ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አንዳንዱ ፡ ቀርበው ፦ ሄሮድስ ፡ ሊገድልኽ ፡ ይወዳልና ፥ ከዚህ ፡

ውጣና ፡ ኺድ ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ኼዳችኹ ፡ ለዚያች ፡ ቀበሮ ፦ እንሆ ፥ ዛሬና ፡ ነገ ፡ አጋንንትን ፡ አወጣለኹ ፡ በሽተኞችንም ፡ እፈውሳለኹ ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ እፈጸማለኹ ፡ በሏት ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ነቢይ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ውጭ ፡ ይጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አይገባውምና ፥ ዛሬና ፡ ነገ ፣ ከነገ ፡ በስቲያም ፡ ልኼድ ፡ ያስፈልገኛል ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 34 ፤ ኢየሩሳሌም ፥ ኢየሩሳሌም ፥ ነቢያትን ፡ የምትገድል ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ የተላኩትንም ፡ የምትወግር ፥ ዶሮ ፡ ጫጩቶቿን ፡ በክንፎቿ ፡ በታች ፡ እንደምትሰበስብ ፡ ልጆችሽን ፡ እሰበስብ ፡ ዘንድ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ወደድኩ ፥ እናንተም ፡ አልወደዳችኹም ።

ሉቃ. ፡ 13 ፡ 35 ፤ እንሆ ፥ ቤታችኹ ፡ የተፈታ ፡ ኾኖ ፡ ይቀርላችኋል ። እላችኋለኹም ፦ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ እስክትሉ ፡ ድረስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አታዩኝም ።

_____የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ በሰንበትም ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አለቃዎች ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ቤት ፡ እንጀራ ፡ ሊበላ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እነርሱ ፡ ይጠባበቁት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ እንሆም ፥ ሆዱ ፡ የተነፋ ፡ ሰው ፡ በፊቱ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ በሰንበት ፡ መፈወስ ፡ ተፈቅዷልን ፡ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ፧ ብሎ ፡ ለሕግ ፡ ዐዋቂዎችና ፡ ለፈሪሳውያን ፡ ተናገረ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ዝም ፡ አሉ ። ይዞም ፡ ፈወሰውና ፡ አሰናበተው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ከእናንተ ፡ አህያው ፡ ወይስ ፡ በሬው ፡ በጕድጓድ ፡ ቢወድቅ ፡ በሰንበት ፡ ወዲያው ፡ የማያወጣው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፡ ነገርም ፡ ሊመልሱለት ፡ አልተቻላቸውም ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ የታደሙትንም ፡ የከበሬታ ፡ ስፍራ ፡ እንደ ፡ መረጡ ፡ ተመልክቶ ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ማንም ፡ ለሰርግ ፡ ቢጠራኽ ፡ በከበሬታ ፡ ስፍራ ፡ አትቀመጥ ፤ ምናልባት ፡ ከአንተ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ተጠርቶ ፡ ይኾናልና ፥ አንተን ፡ ርሱንም ፡ የጠራ ፡ መጥቶ ፦

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ለዚህ ፡ ስፍራ ፡ ተውለት ፡ ይልኻል ፥ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ እያፈርኽ ፡ በዝቅተኛው ፡ ስፍራ ፡ ልትኾን ፡ ትገሥምራለኽ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተጠራኽ ፡ ጊዜ ፥ የጠራኽ ፡ መጥቶ ፦ ወዳጄ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ላይ ፡ ውጣ ፡ እንዲልኽ ፥ ኼደኽ ፡ በዝቅተኛው ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጥ ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ በተቀመጡት ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ክብር ፡ ይኾንልኻል ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ራሱን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ይዋረዳልና ፥ ራሱንም ፡ የሚያዋርድ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ የጠራውንም ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ ምሳ ፡ ወይም ፡ እራት ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፥ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በተራቸው ፡ ምናልባት ፡ እንዳይጠሩኽ ፡ ብድራትም ፡ እንዳይመልሱልኽ ፥ ወዳጆችኽንና ፡ ወንድሞችኽን ፡ ዘመዶችኽንም ፡ ባለጠጋዎች ፡ ጎረቤቶችኽንም ፡ አትጥራ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ግብዣ ፡ ባደረግኽ ፡ ጊዜ ፡ ድኻዎችንና ፡ ጕንድሾችን ፡ ዐንካሳዎችንም ፡ ዕውሮችንም ፡ ጥራ ፤

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ የሚመልሱት ፡ ብድራት ፡ የላቸውምና ፡ ብፁዕ ፡ ትኾናለኽ ፤ በጻድቃን ፡ ትንሣኤ ፡ ይመለስልኻልና ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ከተቀመጡትም ፡ አንዱ ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፦ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንጀራ ፡ የሚበላ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ታላቅ ፡ እራት ፡ አድርጎ ፡ ብዙዎችን ፡ ጠራ ፤

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ በእራትም ፡ ሰዓት ፡ የታደሙትን ፦ አኹን ፡ ተዘጋጅቷልና ፥ ኑ ፡ እንዲላቸው ፡ ባሪያውን ፡ ላከ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ኹላቸውም ፡ በአንድነት ፡ ያመካኙ ፡ ዠመር ። የፊተኛው ፦ መሬት ፡ ገዝቻለኹ ፡ ወጥቼም ፡ ላየው ፡ በግድ ፡ ያስፈልገኛል ፤ ይቅር ፡ እንድትለኝ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ሌላውም ፦ ዐምስት ፡ ጥምድ ፡ በሬዎች ፡ ገዝቻለኹ ፡ ልፈትናቸውም ፡ እኼዳለኹ ፤ ይቅር ፡ እንድትለኝ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ሌላውም ፦ ሚስት ፡ አግብቻለኹ ፡ ስለዚህም ፡ ልመጣ ፡ አልችልም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ባሪያውም ፡ ደርሶ ፡ ይህን ፡ ለጌታው ፡ ነገረው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ባለቤቱ ፡ ተቈጥቶ ፡ ባሪያውን ፦ ወደከተማ ፡ ጐዳናና ፡ ወደ ፡ ስላች ፡ ፈጥነኽ ፡ ውጣ ፡ ድኻዎችንና ፡ ጕንድሾችን ፡ ዐንካሳዎችንና ፡ ዕውሮችንም ፡ ወደዚህ ፡ አግባ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ባሪያውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንዳዘዝኸኝ ፡ ተደርጓል ፥ ገናም ፡ ስፍራ ፡ አለ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ጌታውም ፡ ባሪያውን ፦ ቤቴ ፡ እንዲሞላ ፡ ወደ ፡ መንገድና ፡ ወደ ፡ ቅጥር ፡ ውጣና ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ በላቸው ፤

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ እላችኋለኹና ፥ ከታደሙት ፡ ከነዚያ ፡ ሰዎች ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ እራቴን ፡ አይቀምስም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ ብዙም ፡ ሕዝብ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፥ ዘወር ፡ ብሎም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ ማንም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚመጣ ፡ ቢኖር ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ሚስቱንም ፡ ልጆቹንም ፡ ወንድሞቹንም ፡ እኅቶቹንም ፡ የራሱን ፡ ሕይወት ፡ ስንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ባይጠላ ፥ ደቀ ፡ መዝሙሬ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ማንም ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፡ በኋላዬ ፡ የማይመጣ ፥ ደቀ ፡ መዝሙሬ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ ከእናንተ ፡ ግንብ ፡ ሊሠራ ፡ የሚወድ ፡ ለመደምደሚያ ፡ የሚበቃ ፡ ያለው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስቀድሞ ፡ ተቀምጦ ፡ ከሳራውን ፡ የማይቈጥር ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ያለዚያ ፡ መሠረቱን ፡ ቢመሠርት ፥ ሊደመድመውም ፡ ቢያቅተው ፥ ያዩት ፡ ኹሉ ፦

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ሊሠራ ፡ ዠምሮ ፡ ሊደመድመው ፡ አቃተው ፡ ብለው ፡ ሊዘብቱበት ፡ ይዠምራሉ ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ ወይም ፡ ሌላውን ፡ ንጉሥ ፡ በጦርነት ፡ ሊጋጠም ፡ የሚኼድ ፥ ከኹለት ፡ እልፍ ፡ ጋራ ፡ የሚመጣበትን ፡ ባንድ ፡ እልፍ ፡ ሊገናኝ ፡ የሚችል ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስቀድሞ ፡ ተቀምጦ ፡ የማያስብ ፡ ንጉሥ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 32 ፤ ባይኾንስ ፡ ሌላው ፡ ገና ፡ ሩቅ ፡ ሳለ ፡ መልክተኞች ፡ ልኮ ፡ ዕርቅ ፡ ይለምናል ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 33 ፤ እንግዲህ ፡ እንደዚሁ ፡ ማንም ፡ ከእናንተ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ የማይተው ፡ ደቀ ፡ መዝሙሬ ፡ ሊኾን ፡ አይችልም ።

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 34 ፤ ጨው ፡ መልካም ፡ ነው ፤ ጨው ፡ ዐልጫ ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ በምን ፡ ይጣፈጣል ፧

ሉቃ. ፡ 14 ፡ 35 ፤ ለምድር ፡ ቢኾን ፡ ለፍግ ፡ መቈለያም ፡ ቢኾን ፡ አይረባም ፤ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይጥሉታል ። የሚሰማ ፡ ጐሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

_____የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ቀራጮችና ፡ ኀጢአተኞችም ፡ ኹሉ ፡ ሊሰሙት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይቀርቡ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ፈሪሳውያንና ፡ ጻፊዎችም ፦ ይህስ ፡ ኀጢአተኞችን ፡ ይቀበላል ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ይበላል ፡ ብለው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ አንጐራጐሩ ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ መቶ ፡ በግ ፡ ያለው ፡ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ ቢጠፋ ፥ ዘጠና ፡ ዘጠኙን ፡ በበረሓ ፡ ትቶ ፡ የጠፋውን ፡ እስኪያገኘው ፡ ድረስ ፡ ሊፈልገው ፡ የማይኼድ ፡ ከእናንተ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ባገኘውም ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ በጫንቃው ፡ ይሸከመዋል ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ቤትም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወዳጆቹንና ፡ ጎረቤቶቹን ፡ በአንድነት ፡ ጠርቶ ፦ የጠፋውን ፡ በጌን ፡ አግኝቼዋለኹና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ይላቸዋል ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ እላችኋለኹ ፥ እንዲሁ ፡ ንስሓ ፡ ከማያስፈልጋቸው ፡ ከዘጠና ፡ ዘጠኝ ፡ ጻድቃን ፡ ይልቅ ፡ ንስሓ ፡ በሚገባ ፡ ባንድ ፡ ኀጢአተኛ ፡ በሰማይ ፡ ደስታ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ወይም ፡ ዐሥር ፡ ድሪም ([289]) ፡ ያላት ፡ አንድ ፡ ድሪም ፡ ቢጠፋባት ፥ መብራት ፡ አብርታ ፡ ቤቷንም ፡ ጠርጋ ፡ እስክታገኘው ፡ ድረስ ፡ አጥብቃ ፡ የማትፈልግ ፡ ሴት ፡ ማን ፡ ናት ፧

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ ባገኘችውም ፡ ጊዜ ፡ ወዳጆቿንና ፡ ጎረቤቶቿን ፡ በአንድነት ፡ ጠርታ ፦ የጠፋውን ፡ ድሪሜን ፡ አግኝቼዋለኹና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ትላቸዋለች ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ እላችኋለኹ ፥ እንዲሁ ፡ ንስሓ ፡ በሚገባ ፡ ባንድ ፡ ኀጢአተኛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ ደስታ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ከነርሱም ፡ ታናሹ ፡ አባቱን ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ ከገንዘብኽ ፡ የሚደርሰኝን ፡ ክፍል ፡ ስጠኝ ፡ አለው ። ገንዘቡንም ፡ አካፈላቸው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ታናሹ ፡ ልጅ ፡ ገንዘቡን ፡ ኹሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ኼደ ፥ ከዚያም ፡ እያባከነ ፡ ገንዘቡን ፡ በተነ ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ ኹሉንም ፡ ከከሰረ ፡ በኋላ ፡ በዚያች ፡ አገር ፡ ጽኑ ፡ ራብ ፡ ኾነ ፥ ርሱም ፡ ይጨነቅ ፡ ገመር ።

---

289 ጽር. ፥ ድራኽሚ ፡ (የፋርስ ፡ ገንዘብ ፡ ስም ፥ የወቄት ፡ ወርቅ ፡ 1/16 ኛ ፤ 2 ፡ ቀመት ፡ 1 ፡ ድሪም ፡ ይኾናል) ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ኼዶም ፡ ከዚያች ፡ አገር ፡ ሰዎች ፡ ከአንዱ ፡ ጋራ ፡ ተዳበለ ፥ ርሱም ፡ ዕሪያ ፡ ሊያሰማራ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሰደደው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ ዕሪያዎችም ፡ ከሚበሉት ፡ ዐሠር ፡ ሊጠግብ ፡ ይመኝ ፡ ነበር ፥ የሚሰጠውም ፡ አልነበረም ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ልቡም ፡ ተመልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እንጀራ ፡ የሚተርፋቸው ፡ የአባቴ ፡ ሞያተኞች ፡ ስንት ፡ ናቸው ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ በራብ ፡ እጠፋለኹ ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ተነሥቼም ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ እኼዳለኹና ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ በሰማይና ፡ በፊትኽ ፡ በደልኹ ፥

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ ልጅኽ ፡ ልባል ፡ አይገባኝም ፤ ከሞያተኞችኽ ፡ እንደ ፡ አንዱ ፡ አድርገኝ ፡ እለዋለኹ ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ መጣ ። ርሱም ፡ ገና ፡ ሩቅ ፡ ሳለ ፡ አባቱ ፡ አየውና ፡ ዐዘነለት ፥ ሮጦም ፡ ዐንገቱን ፡ ዐቀፈውና ፡ ሳመው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ልጁም ፦ አባቴ ፡ ሆይ ፥ በሰማይና ፡ በፊትኽ ፡ በደልኹ ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ልጅኽ ፡ ልባል ፡ አይገባኝም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ ባሪያዎቹን ፡ አለ ፦ ፈጥናችኹ ፡ ከኹሉ ፡ የተሻለ ፡ ልብስ ፡ አምጡና ፡ አልብሱት ፥ ለእጁ ፡ ቀለበት ፡ ለእግሩም ፡ ጫማ ፡ ስጡ ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ የሰባውን ፡ ፊሪዳ ፡ አምጥታችኹ ፡ ዕረዱት ፥ እንብላም ፡ ደስም ፡ ይበለን ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ይህ ፡ ልጄ ፡ ሞቶ ፡ ነበርና ፥ ደግሞም ፡ ሕያው ፡ ኾኗል ፤ ጠፍቶም ፡ ነበር ፡ ተገኝቷልም ። ደስም ፡ ይላቸው ፡ ገሮመር ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ ታላቁ ፡ ልጁ ፡ በዕርሻ ፡ ነበረ ፤ መጥቶም ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የመሰንቆና ፡ የዘፈን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ ከብላቴናዎችም ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፤ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ርሱም ፦ ወንድምኽ ፡ መጥቷልና ፥ በደኅና ፡ ስላገኘው ፥ አባትኽ ፡ የሰባውን ፡ ፊሪዳ ፡ ዐረደለት ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ ተቈጣም ፡ ሊገባም ፡ አልወደደም ፤ አባቱም ፡ ወጥቶ ፡ ለመነው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ መልሶ ፡ አባቱን ፦ እንሆ ፥ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ተገዝቼልኻለኹ ፡ ከትእዛዝኽም ፡ ኩቶ ፡ አልተላለፍኹም ፤ ለኔም ፡ ከወዳጆቼ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ አንድ ፡ ጥቦት ፡ ስንኳ ፡ አልሰጠኸኝም ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ገንዘብኽን ፡ ከጋለሞታዎች ፡ ጋራ ፡ በልቶ ፡ ይህ ፡ ልጅኽ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የሰባውን ፡ ፊሪዳ ፡ ዐረድኽለት ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነኽ ፥ ለኔም ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ የአንተ ፡ ነው ፤

ሉቃ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ወንድምኽ ፡ ሞቶ ፡ ነበረ ፡ ሕያው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ጠፍቶም ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ ደስ ፡ እንዲለን ፡ ፍሥሐም ፡ እንድናደርግ ፡ ይገባናል ፡ አለው ።

_____የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 1 ፤ ደግሞም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ መጋቢ ፡ የነበረው ፡ አንድ ፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ በርሱ ፡ ዘንድ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ያለኽን ፡ ይበትናል ፡ ብለው ፡ ከሰሱት ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 2 ፤ ጠርቶም ፦ ይህ ፡ የምሰማብኽ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወደ ፡ ፊት ፡ ለእኔ ፡ መጋቢ ፡ ልትኾን ፡ አትችልምና ፡ የመጋቢነትኽን ፡ ሒሳብ ፡ አስረክበኝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 3 ፤ መጋቢውም ፡ በልቡ ፦ ጌታዬ ፡ መጋቢነቱን ፡ ከእኔ ፡ ይወስዳልና ፥ ምን ፡ ላድርግ ፧ ለመቈፈር ፡ ኀይል ፡ የለኝም ፥ መለመንም ፡ ዐፍራለኹ ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 4 ፤ ከመጋቢነቱ ፡ ብሻር ፡ በቤታቸው ፡ እንዲቀበሉኝ ፡ የማደርገውን ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 5 ፤ የጌታውንም ፡ ባለዕዳዎች ፡ እያንዳንዳቸውን ፡ ጠርቶ ፡ የፊተኛውን ፦ ለጌታዬ ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ዕዳ ፡ አለብኽ ፧ አለው ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 6 ፤ ርሱም ፦ መቶ ፡ ማድጋ ፡ ዘይት ፡ አለ ። ደብዳቤኽን ፡ እንካ ፡ ፈጥነኽም ፡ ተቀምጠኽ ፡ ዐምሳ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 7 ፤ በኋላም ፡ ሌላውን ፦ አንተስ ፡ ስንት ፡ ዕዳ ፡ አለብኽ ፧ አለው ። ርሱም ፦ መቶ ፡ ጫን ፡ ስንዴ ፡ አለ ። ደብዳቤኽን ፡ እንካ ፡ ሰማንያ ፡ ብለኽም ፡ ጻፍ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 8 ፤ ጌታውም ፡ ዐመፀኛውን ፡ መጋቢ ፡ በልባምነት ፡ ስላደረገ ፡ አመሰገነው ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ልጆች ፡ ለትውልዳቸው ፡ ከብርሃን ፡ ልጆች ፡ ይልቅ ፡ ልባሞች ፡ ናቸውና ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 9 ፤ እኔም ፡ እላችኋለኹ ፥ የዐመፃ ፡ ገንዘብ ፡ ሲያልቅ ፡ በዘለዓለም ፡ ቤቶች ፡ እንዲቀበሏችኹ ፥ በርሱ ፡ ወዳጆችን ፡ ለራሳችኹ ፡ አድርጉ ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 10 ፤ ከኹሉ ፡ በሚያንስ ፡ የታመነ ፡ በብዙ ፡ ደግሞ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥ ከኹሉ ፡ በሚያንስም ፡ የሚያምፅ ፡ በብዙ ፡ ደግሞ ፡ ዐመፀኛ ፡ ነው ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 11 ፤ እንግዲያስ ፡ በዐመፃ ፡ ገንዘብ ፡ ካልታመናችኹ ፥ እውነተኛውን ፡ ገንዘብ ፡ ማን ፡ ዐደራ ፡ ይሰጣችኋል ፧

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 12 ፤ በሌላ ፡ ሰው ፡ ገንዘብ ፡ ካልታመናችኹ ፥ የእናንተን ፡ ማን ፡ ይሰጣችኋል ፧

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 13 ፤ ለኹለት ፡ ጌታዎች ፡ መገዛት ፡ የሚቻለው ፡ ባሪያ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ወይም ፡ አንዱን ፡ ይጠላልና ፥ ኹለተኛውንም ፡ ይወዳል ፥ ወይም ፡ ወደ ፡ አንዱ ፡ ይጠጋል ፡ ኹለተኛውንም ፡ ይንቃል ። ለእግዚአብሔርና ፡ ለገንዘብ ፡ መገዛት ፡ አትችሉም ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 14 ፤ ገንዘብንም ፡ የሚወዱ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ሰምተው ፡ ያፌዙበት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 15 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ራሳችኹን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ የምታጸድቁ ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ልባችኹን ፡ ያውቃል ፤ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ርኵሰት ፡ ነውና ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 16 ፤ ሕግና ፡ ነቢያት ፡ እስከ ፡ ዮሐንስ ፡ ነበሩ ፤ ከዚያ ፡ ዠምሮ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ይሰበካል ፤ ኹሉም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ በኀይል ፡ ይገቡባታል ።

ሉቃ. ፥ 16 ፥ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሕግ ፡ አንዲት ፡ ነጥብ ፡ ከምትወድቅ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ሊያልፍ ፡ ይቀላል ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ሚስቱንም ፡ የሚፈታ ፡ ዥሉ ፡ ሌላዪቱንም ፡ የሚያገባ ፡ ያመነዝራል ፥ ከባሏም ፡ የተፈታችውን ፡ የሚያገባ ፡ ያመነዝራል ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ቀይ ፡ ልብስና ፡ ቀጭን ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ የለበሰ ፡ አንድ ፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ እየተመቸው ፡ በደስታ ፡ ይኖር ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ አልዓዛርም ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ድኻ ፡ በቍስል ፡ ተወርሶ ፡ በደጁ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፥

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ከባለጠጋውም ፡ ማእድ ፡ ከሚወድቀው ፡ ፍርፋሪ ፡ ሊጠግብ ፡ ይመኝ ፡ ነበር ፤ ውሻዎች ፡ እንኳ ፡ መጥተው ፡ ቍስሎቹን ፡ ይልሱ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ድኻውም ፡ ሞተ ፥ መላእክትም ፡ ወደአብርሃም ፡ ዕቅፍ ፡ ወሰዱት ፤ ባለጠጋው ፡ ደግሞ ፡ ሞተና ፡ ተቀበረ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ በሲኦልም ፡ በሥቃይ ፡ ሳለ ፡ አሻቅቦ ፡ አብርሃምን ፡ በሩቅ ፡ አየ ፡ አልዓዛርንም ፡ በዕቅፉ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ርሱም ፡ እየጮኸ ፦ አብርሃም ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ማረኝ ፥ በዚህ ፡ ነበልባል ፡ እሣቀያለኹና ፡ የጣቱን ፡ ጫፍ ፡ በውሃ ፡ ነክሮ ፡ ምላሴን ፡ እንዲያበርድልኝ ፡ አልዓዛርን ፡ ስደድልኝ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ አብርሃም ፡ ግን ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በሕይወትኽ ፡ ሳለኽ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ተቀበልኽ ፡ ዐስብ ፡ አልዓዛርም ፡ እንዲሁ ፡ ክፉ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ በዚህ ፡ ይጽናናል ፡ አንተም ፡ ትሣቀያለኽ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ከዚህም ፡ ዥሉ ፡ ጋራ ፡ ከዚህ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ሊያልፉ ፡ የሚፈልጉ ፡ እንዳይችሉ ፥ ወዲያ ፡ ያሉ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ እንዳይሻገሩ ፡ በእኛና ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ ገደል ፡ ተደርጓል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ርሱም ፦ እንኪያስ ፥ አባት ፡ ሆይ ፥ ወዳባቴ ፡ ቤት ፡ እንድትሰደው ፡ እለምንኻለኹ ፤ ዐምስት ፡ ወንድሞች ፡ አሉኝና ፤

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ወደዚህ ፡ ሥቃይ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይመጡ ፡ ይመስክርላቸው ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ አብርሃም ፡ ግን ፦ ሙሴና ፡ ነቢያት ፡ አሏቸው ፤ እነርሱን ፡ ይስሙ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ርሱም ፦ አይደለም ፥ አብርሃም ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከሙታን ፡ አንዱ ፡ ቢኼድላቸው ፡ ንስሓ ፡ ይገባሉ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ ሙሴንና ፡ ነቢያትንም ፡ የማይሰሙ ፡ ከኾነ ፥ ከሙታንም ፡ እንኳ ፡ አንድ ፡ ቢነሣ ፡ አያምኑም ፡ አለው ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ መሰናክል ፡ ግድ ፡ ሳይመጣ ፡ አይቀርም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መሰናክሉን ፡ ለሚያመጣው ፡ ወዮለት ፤

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ከነዚህ ፡ ከታናናሾች ፡ አንዱን ፡ ከማሰናከል ፡ ይልቅ ፡ የወፍጮ ፡ ድንጋይ ፡ በዐንገቱ ፡ ታስሮ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ቢጣል ፡ ይጠቅመው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ። ወንድምኽ ፡ ቢበድልኽ ፡ ገሥጸው ፥ ቢጸጸትም ፡ ይቅር ፡ በለው ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ በቀንም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፡ እንኳ ፡ ቢበድልኽ ፡ በቀንም ፡ ሰባት ፡ ጊዜ ፦ ተጸጸትኹ ፡ እያለ ፡ ወዳንተ ፡ ቢመለስ ፥ ይቅር ፡ በለው ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ ሐዋርያትም ፡ ጌታን ፦ እምነት ፡ ጨምርልን ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ጌታም ፡ አለ ፦ የሰናፍጭ ፡ ቅንጣት ፡ የሚያኽል ፡ እምነት ፡ ቢኖራችኹ ፥ ይህን ፡ ሾላ ፦ ተነቅለኽ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ተተከል ፡ ብትሉት ፥ ይታዘዝላችኹ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ከእናንተም ፡ የሚያርስ ፡ ወይም ፡ ከብትን ፡ የሚጠብቅ ፡ ባሪያ ፡ ያለው ፥ ከዕርሻ ፡ ሲመለስ ፦ ወዲያው ፡ ቅረብና ፡ በማእዱ ፡ ተቀመጥ ፡ የሚለው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ የምበላውን ፡ እራቴን ፡ አሰናዳልኝ ፥ እስክበላና ፡ እስክጠጣ ፡ ድረስ ፡ ታጥቀኽ ፡ አገልግለኝ ፥ በኋላም ፡ አንተ ፡ ብላና ፡ ጠጣ ፡ የሚለው ፡ አይደለምን ፧

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ያን ፡ ባሪያ ፡ ያዘዘውን ፡ ስላደረገ ፡ ያመሰግነዋልን ፧

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ የታዘዛችኹትን ፡ ኹሉ ፡ ባደረጋችኹ ፡ ጊዜ ፦ የማንጠቅም ፡ ባሪያዎች ፡ ነን ፥ ልናደርገው ፡ የሚገባንን ፡ አድርገናል ፡ በሉ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ሲኼድ ፡ በገሊላና ፡ በሰማርያ ፡ መካከል ፡ ዐለፈ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ አንዲት ፡ መንደርም ፡ ሲገባ ፡ በሩቅ ፡ የቆሙት ፡ ዐሥር ፡ ለምጻሞች ፡ ተገናኙት ፤

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ እየጮኹ ፦ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ አቤቱ ፥ ማረን ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ አይቶም ፦ ኺዱ ፥ ራሳችኹን ፡ ለካህናት ፡ አሳዩ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ እንሆም ፥ ሲኼዱ ፡ ነጹ ። ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ እንደ ፡ ተፈወሰ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያከበረ ፡ ተመለሰ ፥

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ እያመሰገነውም ፡ በእግሩ ፡ ፊት ፡ በግንባሩ ፡ ወደቀ ፤ ርሱም ፡ ሳምራዊ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ዐሥሩ ፡ አልነጹምን ፧ ዘጠኙስ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ከዚህ ፡ ከልዩ ፡ ወገን ፡ በቀር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊያከብሩ ፡ የተመለሱ ፡ አልተገኙም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ ርሱንም ፦ ተነሣና ፡ ኺድ ፤ እምነትኽ ፡ አድኖኻል ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 20 ፤ ፈሪሳውያንም ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መቼ ፡ ትመጣለች ፡ ብለው ፡ ቢጠይቁት ፥ መልሶ ፦ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመጠባበቅ ፡ አትመጣም ፤

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 21 ፤ ደግሞም ፦ እንኋት ፡ በዚህ ፡ ወይም ፦ እንኋት ፡ በዚያ ፡ አይሏትም ። እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመካከላችኹ ፡ ናትና ፥ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 22 ፤ ለደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ቀኖች ፡ አንዱን ፡ ልታዩ ፡ የምትመኙበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፡ አታዩትምም ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 23 ፤ እነርሱም ፦ እንሆ ፥ በዚህ ፥ ወይም ፦ እንሆ ፥ በዚያ ፡ ይሏችኋል ፤ አትኺዱ ፡ አትከተሏቸውም ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ መብረቅ ፡ በርቆ ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ካለ ፡ ካንድ ፡ አገር ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ እንደሚያበራ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በቀኑ ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 25 ፤ አስቀድሞ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፥ ከዚህም ፡ ትውልድ ፡ እንዲጣል ፡ ይገ፡ባዋል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 26 ፤ በኖኅ ፡ ዘመንም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በሰው ፡ ልጅ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 27 ፤ ኖኅ ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ እስከገባበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ይበሉና ፡ ይጠጡ ፡ ያገቡና ፡ ይጋቡም ፡ ነበር ፥ የጥፋት ፡ ውሃም ፡ መጣ ፡ ኹሉንም ፡ አጠፋ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 28 ፤ እንዲሁ ፡ በሎጥ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፤ ይበሉ ፡ ይጠጡም ፡ ይገዙም ፡ ይሸጡም ፡ ይተክሉም ፡ ቤትም ፡ ይሠሩ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 29 ፤ ሎጥ ፡ ከሰዶም ፡ በወጣበት ፡ ቀን ፡ ግን ፡ ከሰማይ ፡ እሳትና ፡ ዲን ፡ ዘነበ ፡ ኹሉንም ፡ አጠፋ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 30 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በሚገለጥበት ፡ ቀን ፡ እንዲሁ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 31 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በሰገነት ፡ ያለ ፡ በቤቱ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ ሊወስድ ፡ አይውረድ ፥ እንዲሁም ፡ በዕርሻ ፡ ያለ ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ አይመለስ ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 32 ፤ የሎጥን ፡ ሚስት ፡ ዐስቢት ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 33 ፤ ነፍሱን ፡ ሊያድን ፡ የሚፈልግ ፡ ኹሉ ፡ ያጠፋታል ፥ ነፍሱንም ፡ የሚያጠፋ ፡ ኹሉ ፡ በሕይወት ፡ ይጠብቃታል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 34 ፤ እላችኋለኹ ፥ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ባንድ ፡ ዐልጋ ፡ ይኾናሉ ፤ አንዱ ፡ ይወሰዳል ፡ ኹለተኛውም ፡ ይቀራል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 35 ፤ ኹለት ፡ ሴቶች ፡ ባንድ ፡ ወፍጮ ፡ ይፈጫሉ ፤ አንዲቱ ፡ ትወሰዳለች ፡ ኹለተኛዪቱም ፡ ትቀራለች ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 36 ፤ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ በዕርሻ ፡ ይኾናሉ ፤ አንዱ ፡ ይወሰዳል ፡ ኹለተኛውም ፡ ይቀራል ።

ሉቃ. ፡ 17 ፡ 37 ፤ መልሰውም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወዴት ፡ ነው ፧ አሉት ። ርሱም ፦ ሥጋ ፡ ወዳለበት ፡ በዚያ ፡ አሞራዎች ፡ ይሰበሰባሉ ፡ አላቸው ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ ሳይታክቱም ፡ ዘወትር ፡ ሊጸልዩ ፡ እንዲገባቸው ፡ የሚል ፡ ምሳሌን ፡ ነገራቸው ፥

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፦ በአንዲት ፡ ከተማ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማይፈራ ፡ ሰውንም ፡ የማያፍር ፡ አንድ ፡ ዳኛ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ በዚያችም ፡ ከተማ ፡ አንዲት ፡ መበለት ፡ ነበረች ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ እየመጣች ፦ ከባላጋራዬ ፡ ፍረድልኝ ፡ ትለው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ዐያሌ ፡ ቀንም ፡ አልወደደም ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በልቡ ፦ ምንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ባልፈራ ፡ ሰውንም ፡ ባላፍር ፥

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ ይህች ፡ መበለት ፡ ስለምታደክመኝ ፡ ኹልጊዜም ፡ እየመጣች ፡ እንዳታውከኝ ፡ እፈርድላታለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ጌታም ፡ አለ ፦ ዐመፀኛው ፡ ዳኛ ፡ ያለውን ፡ ስሙ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንኪያስ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለሚጮኹ ፡ ለሚታገሣቸውም ፡ ምርጦቹ ፡ አይፈርድላቸውምን ፧

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ እላችኋለኹ ፥ ፈጥኖ ፡ ይፈርድላቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ እምነትን ፡ ያገኝ ፡ ይኾንን ፧

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ጻድቃን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ በራሳቸው ፡ ለሚታመኑና ፡ ሌላዎቹን ፡ ኹሉ ፡ በጣም ፡ ለሚንቁ ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፥

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ሊጸልዩ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ወጡ ፥ አንዱ ፡ ፈሪሳዊ ፡ ኹለተኛውም ፡ ቀራጭ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ፈሪሳዊም ፡ ቆሞ ፡ በልቡ ፡ ይህን ፡ ሲጸልይ ፦ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፥ ቀማኞችና ፡ ዐመፀኞች ፡ አመንዝራዎችም ፥ ወይም ፡ እንደዚህ ፡ ቀራጭ ፡ ስላልኾንኹ ፡ አመሰግንኻለኹ ፤

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ በየሳምንቱ ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ እጦማለኹ ፥ ከማገኘውም ፡ ኹሉ ፡ ዓሥራት ፡ አወጣለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ቀራጩ ፡ ግን ፡ በሩቅ ፡ ቆሞ ፡ ዐይኖቹን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሊያነሣ ፡ እንኳ ፡ አልወደደም ፥ ነገር ፡ ግን ፦ አምላክ ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ ኀጢአተኛውን ፡ ማረኝ ፡ እያለ ፡ ደረቱን ፡ ይደቃ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ እላችኋለኹ ፥ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡ ይህ ፡ ጻድቅ ፡ ኾኖ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተመለሰ ፤ ራሱን ፡ ከፍ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ይዋረዳልና ፥ ራሱን ፡ ግን ፡ የሚያዋርድ ፡ ከፍ ፡ ይላል ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ እንዲዳስሳቸውም ፡ ሕፃናትን ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ አይተው ፡ ገሠጿቸው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፦ ሕፃናት ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ተዉአቸው ፡ አትከልክሏቸውም ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ላሉት ፡ ናትና ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሕፃን ፡ የማይቀበላት ፡ ኹሉ ፡ ከቶ ፡ አይገባባትም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ከአለቃዎችም ፡ አንዱ ፦ ቸር ፡ መምህር ፥ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ እንድወርስ ፡ ምን ፡ ላድርግ ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ኢየሱስም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ቸር ፡ ትለኛለኽ ፧ ከአንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ቸር ፡ ማንም ፡ የለም ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ትእዛዛቱን ፡ ታውቃለኽ ፥ አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ በሐሰት ፡ አትመስክር ፥ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ዠምሬ ፡ ጠብቄያለኹ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፦ አንዲት ፡ ገና ፡ ቀርታኻለች ፤ ያለኽን ፡ ኹሉ ፡ ሽጠኽ ፡ ለድኻዎች ፡ ስጥ ፥ በሰማይም ፡ መዝገብ ፡ ታገኛለኽ ፥ መጥተኽም ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ባለጠጋ ፡ ነበርና ፥ ብዙ ፡ ዐዘነ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ኢየሱስም ፡ ብዙ ፡ እንዳዘነ ፡ አይቶ ፦ ገንዘብ ፡ ላላቸው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ እንዴት ፡ ጭንቅ ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ባለጠጋ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከሚገባ ፡ ይልቅ ፡ ግመል ፡ በመርፌ ፡ ቀዳዳ ፡ ሊገባ ፡ ይቀላል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ የሰሙትም ፦ እንግዲህ ፡ ማን ፡ ሊድን ፡ ይችላል ፧ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የማይቻል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቻላል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ጴጥሮስም ፦ እንሆ ፥ እኛ ፡ ኹሉን ፡ ትተን ፡ ተከተልንኽ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ርሱም ፦ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ቤትን ፡ ወይም ፡ ወላጆችን ፡ ወይም ፡ ወንድሞችን ፡ ወይም ፡ ሚስትን ፡ ወይም ፡ ልጆችን ፡ የተወ ፥

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ዕጥፍ ፡ በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ የማይቀበል ፡ ማንም ፡ የለም ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አቅርቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንወጣለን ፥ ስለሰው ፡ ልጅም ፡ በነቢያት ፡ የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸማል ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ ለአሕዛብ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታልና ፥ ይዘብቱበትማል ፡ ያንገላቱትማል ፡ ይተፉበትማል ፤

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 33 ፤ ከገረፉትም ፡ በኋላ ፡ ይገድሉታል ፥ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ይነሣል ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 34 ፤ እነርሱም ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ አላስተዋሉም ፥ ይህም ፡ ቃል ፡ ተሰውሮባቸው ፡ ነበር ፥ የተናገረውንም ፡ አላወቁም ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 35 ፤ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ዕውር ፡ እየለመነ ፡ በመንገድ ፡ ዳር ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 36 ፤ ሕዝብም ፡ ሲያልፍ ፡ ሰምቶ ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 37 ፤ እነርሱም ፦ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ያልፋል ፡ ብለው ፡ አወሩለት ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፥ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ማረኝ ፡ እያለ ፡ ጮኸ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 39 ፤ በስተፊት ፡ ይኼዱ ፡ የነበሩትም ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ ገሠጹት ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፥ ማረኝ ፡ እያለ ፡ አብዝቶ ፡ ጮኸ ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 40 ፤ ኢየሱስም ፡ ቆሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እንዲያመጡት ፡ አዘዘ ። በቀረበም ፡ ጊዜ ፦ ምን ፡ ላደርግልኽ ፡ ትወዳለኽ ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 41 ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አይ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 42 ፤ ኢየሱስም ፦ እይ ፤ እምነትኽ ፡ አድኖኻል ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 18 ፡ 43 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ አየ ፥ እግዚአብሔርም ፡ እያከበረ ፡ ተከተለው ። ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አይተው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 1-2 ፤ ወደ ፡ ኢያሪኮም ፡ ገብቶ ፡ ያልፍ ፡ ነበር ። እንሆም ፡ ዘኬዎስ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፥ ርሱም ፡ የቀራጮች ፡ አለቃ ፡ ነበረ ፥ ባለጠጋም ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ኢየሱስንም ፡ የትኛው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሊያይ ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ፤ ቁመቱም ፡ ዐጪር ፡ ነበረና ፡ ስለሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ አቃተው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ በዚያችም ፡ መንገድ ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡ አለውና ፡ ያየው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሮጦ ፡ ባንድ ፡ ሾላ ፡ ላይ ፡ ወጣ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደዚያ ፡ ስፍራ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ አሻቅቦ ፡ አየና ፦ ዘኬዎስ ፡ ሆይ ፥ ዛሬ ፡ በቤትኽ ፡ እውል ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛልና ፥ ፈጥነኽ ፡ ውረድ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ፈጥኖም ፡ ወረደ ፡ በደስታም ፡ ተቀበለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ኹሉም ፡ አይተው ፦ ከኀጢአተኛ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ሊውል ፡ ገባ ፡ ብለው ፡ አንጐራጐሩ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ዘኬዎስ ፡ ግን ፡ ቆሞ ፡ ጌታን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ካለኝ ፡ ኹሉ ፡ እኩሌታውን ፡ ለድኻዎች ፡ እሰጣለኹ ፤ ማንንም ፡ በሐሰት ፡ ከስሼ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አራት ፡ ዕጥፍ ፡ እመልሳለኹ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ ኢየሱስም ፦ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ነውና ፥ ዛሬ ፡ ለዚህ ፡ ቤት ፡ መዳን ፡ ኾኖለታል ፤

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ የጠፋውን ፡ ሊፈልግና ፡ ሊያድን ፡ መጥቷልና ፥ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ እነርሱም ፡ ይህን ፡ ሲሰሙ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መቅረቡ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ ፈጥኖ ፡ ሊገለጥ ፡ እንዳለው ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፡ ምሳሌ ፡ ጭምር ፡ ተናገረ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ስለዚህም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ አንድ ፡ መኰንን ፡ ለራሱ ፡ መንግሥትን ፡ ይዞ ፡ ሊመለስ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ ዐሥር ፡ ባሪያዎችንም ፡ ጠርቶ ፡ ዐሥር ፡ ምናን ፡ ሰጣቸውና ፦ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ነግዱ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ የአገሩ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ይጠሉት ፡ ነበርና ፦ ይህ ፡ በላያችን ፡ ሊነግሥ ፡ አንወድም ፡ ብለው ፡ በኋላው ፡ መልክተኞችን ፡ ላኩ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ መንግሥትንም ፡ ይዞ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፥ ገንዘብ ፡ የሰጣቸውን ፡ እነዚህን ፡ ባሪያዎች ፡ ነግደው ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ እንዳተረፉ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንዲጠሩለት ፡ አዘዘ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ የፊተኛውም ፡ ደርሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምናንኽ ፡ ዐሥር ፡ ምናን ፡ አተረፈ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ መልካም ፥ አንተ ፡ በጎ ፡ ባሪያ ፥ በጥቂት ፡ የታመንኽ ፡ ስለ ፡ ኾንኽ ፡ በዐሥር ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ይኹንልኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ ኹለተኛውም ፡ መጥቶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምናንኽ ፡ ዐምስት ፡ ምናን ፡ አተረፈ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ይህንም ፡ ደግሞ ፦ አንተም ፡ በዐምስት ፡ ከተማዎች ፡ ላይ ፡ ኹን ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ሌላውም ፡ መጥቶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በጨርቅ ፡ ጠቅልዬ ፡ የጠበቅኺት ፡ ምናንኽ ፡ እንሆ ፤

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ፈርቼኻለኹና ፥ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ኾንኽ ፤ ያላኖርኸውን ፡ ትወስዳለኽ ፡ ያልዘራኸውንም ፡ ታጭዳለኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ርሱም ፦ አንተ ፡ ክፉ ፡ ባሪያ ፥ አፍኽ ፡ በተናገረው ፡ እፈርድብኻለኹ ። እኔ ፡ ያላኖርኹትን ፡

የምወስድና ፡ ያልዘራኹትን ፡ የማጭድ ፡ ጨካኝ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ዐወቅኽ ፤ ምን ፡ ነው ፡ ገንዘቤን ፡ ለለዋጮች ፡ ዐደራ ፡ ያልሰጠኸው ፡፡

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ እኔም ፡ መጥቼ ፡ ከትርፉ ፡ ጋራ ፡ እወስደው ፡ ነበር ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ በዚያም ፡ ቆመው ፡ የነበሩትን ፦ ምናኑን ፡ ውሰዱበት ፡ ዐሥሩ ፡ ምናን ፡ ላለውም ፡ ስጡት ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ እነርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ዐሥር ፡ ምናን ፡ አለው ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ እላችኋለኹ ፥ ላለው ፡ ኹሉ ፡ ይሰጠዋል ፥ ከሌለው ፡ ግን ፡ ያው ፡ ያለው ፡ ስንኳ ፡ ይወሰድበታል ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነዚያን ፡ በላያቸው ፡ ልነግሥ ፡ ያልወደዱትን ፡ ጠላቶቼን ፡ ወደዚህ ፡ አምጧቸው ፡ በፊቴም ፡ ዕረዷቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ይህንም ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሲወጣ ፡ ይቀድማቸው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ደብረ ፡ ዘይትም ፡ በሚባል ፡ ተራራ ፡ አጠገብ ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ፋጌና ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፥ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹለቱን ፡ ላከና ፦

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ በፊታችኹ ፡ ወዳለችው ፡ መንደር ፡ ኺዱ ፥ ወደ ፡ ርሷም ፡ ገብታችኹ ፡ ከሰው ፡ ማንም ፡ ገና ፡ ያልተቀመጠበት ፡ ውርንጫ ፡ ታስሮ ፡ ታገኛላችኹ ፥ ፈቷ ፡ ችኹም ፡ አምጡት ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ ማንም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈቱታላችኹ ፡፡ ብሎ ፡ ቢጠይቃችኹ ፥ እንዲህ ፦ ለጌታ ፡ ያስፈልገዋል ፡ በሉ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ የተላኩትም ፡ ኼደው ፡ እንዳላቸው ፡ አገኙ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ እነርሱም ፡ ውርንጫውን ፡ ሲፈቱ ፡ ጌታዎቹ ፦ ውርንጫውን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈቱታላችኹ ፡፡ አሏቸውም ፡

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ እነርሱም ፦ ለጌታ ፡ ያስፈልገዋል ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 35 ፤ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ አመጡት ፥ በውርንጫውም ፡ ላይ ፡ ልብሳቸውን ፡ ጭነው ፡ ኢየሱስ ፡ አስቀመጡት ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 36 ፤ ሲኼድም ፡ ልብሳቸውን ፡ በመንገድ ፡ ያነጥፉ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 37 ፤ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ቀ ፡ ልቀ ፡ ለትም ፡ አኹን ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ኹላቸው ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ተአምራትን ፡ ኹሉ ፡ ስላዩ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያመሰግኑ ፡ ገምረው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 38 ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ ንጉሥ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ በሰማይ ፡ ሰላም ፡ በአርያምም ፡ ክብር ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 39 ፤ ከሕዝብም ፡ መካከል ፡ ከፈሪሳውያን ፡ አንዳንዱ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርትኽን ፡ ገሥጻቸው ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 40 ፤ መልሶም ፦ እላችኋለኹ ፥ እነዚህ ፡ ዝም ፡ ቢሉ ፡ ድንጋዮች ፡ ይጮኻሉ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 41 ፤ ሲቀርብም ፡ ከተማዪቱን ፡ አይቶ ፡ አለቀሰላት ፥

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 42 ፤ እንዲህ ፡ እያለ ፦ ለሰላምሽ ፡ የሚኾነውን ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ አንቺስ ፡ ስንኳ ፡ ብታውቂ ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ከዐይንሽ ፡ ተሰውሯል ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 43 ፤ ወራት ፡ ይመጣብሻልና ፥ ጠላቶችሽም ፡ ቅጥር ፡ ይቀጥሩብሻል ፡ ይከቡሻልም ፡ በየበኵሉም ፡ ያስጨንቁሻል ፤

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 44 ፤ አንቺንም ፡ ባንቺም ፡ ውስጥ ፡ የሚኖሩትን ፡ ልጆችሽን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ይጥላሉ ፥ ባንቺ ፡ ውስጥም ፡ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ አይተዉም ፥ የመጐብኘትሽን ፡ ዘመን ፡ አላወቅሺምና ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 45 ፤ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገብቶ ፡ በርሱ ፡ የሚሸጡትን ፡ የሚገዙትንም ፡ ያወጣ ፡ ዠመር ፤

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 46 ፤ ርሱም ፦ ቤቴ ፡ የጸሎት ፡ ቤት ፡ ይኾናል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ የወንበዴዎች ፡ ዋሻ ፡ አደረጋችኹት ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 47 ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ በመቅደስ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ የሕዝቡ ፡ ታላላቆችም ፡ ሊገድሉት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፥

ሉቃ. ፡ 19 ፡ 48 ፤ የሚያደርጉበትንም ፡ ዐጡ ፤ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ሲሰሙት ፡ ተንጠልጥለውበት ፡ ነበርና ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሕዝቡን ፡ በመቅደስ ፡ ሲያስተምር ፡ ወንጌልንም ፡ ሲሰብክላቸው ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጸሐፊዎች ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀረቡና ፦

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ እስኪ ፡ ንገረን ፤ እነዚህን ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ ታደርጋለኽ ፡ ወይስ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ተናገሩት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ መልሶም ፦ እኔ ፡ ደግሞ ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ እጠይቃችኋለኹ ፥ እናንተም ፡ ንገሩኝ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ የዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ከሰማይ ፡ ነበረችን ፡ ወይስ ፡ ከሰው ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ሲነጋገሩ ፦ ከሰማይ ፡ ብንል ፦ ስለ ፡ ምን ፡ አላመናችኹበትም ፧ ይለናል ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ከሰው ፡ ብንል ፡ ግን ፡ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ይወግሩናል ፤ የዮሐንስ ፡ ነቢይ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ኹሉ ፡ ያምኑ ፡ ነበርና ፥ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ መልሰውም ፦ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አናውቅም ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔም ፡ በምን ፡ ሥልጣን ፡ እነዚህን ፡ እንዳደርግ ፡ አልነግራችኹም ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ይህንም ፡ ምሳሌ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይላቸው ፡ ዠመር ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ የወይን ፡ አትክልት ፡ ተከለ ፡ ለገበሬዎችም ፡ አከራይቶ ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ በጊዜውም ፡ ከወይኑ ፡ አትክልት ፡ ፍሬ ፡ እንዲሰጡት ፡ አንድ ፡ ባሪያ ፡ ወደ ፡ ገበሬዎች ፡ ላከ ፤ ገበሬዎቹ ፡ ግን ፡ ደበደቡት ፡ ባዶውንም ፡ ሰደዱት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ጨምሮም ፡ ሌላውን ፡ ባሪያ ፡ ላከ ፤ እነርሱም ፡ ያን ፡ ደግሞ ፡ ደበደቡት ፡ አዋርደውም ፡ ባዶውን ፡ ሰደዱት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ ጨምሮም ፡ ሦስተኛውን ፡ ላከ ፤ እነርሱም ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ አቍስለው ፡ አወጡት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ የወይኑም ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፦ ምን ፡ ላድርግ ፧ የምወደውን ፡ ልጄን ፡ እልካለኹ ፤ ምናልባት ፡ ርሱን ፡ አይተው ፡ ያፍሩታል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ገበሬዎቹ ፡ ግን ፡ አይተውት ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲነጋገሩ ፦ ወራሹ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ርስቱ ፡ ለእኛ ፡ እንዲኾን ፡ ኑ ፡ እንግደለው ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ከወይኑም ፡ አትክልት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጥተው ፡ ገደሉት ። እንግዲህ ፡ የወይኑ ፡ አትክልት ፡ ጌታ ፡ ምን ፡ ያደርጋቸዋል ፧

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ይመጣል ፡ እነዚህንም ፡ ገበሬዎች ፡ ያጠፋል ፥ የወይኑንም ፡ አትክልት ፡ ለሌላዎች ፡ ይሰጣል ። ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ ይህስ ፡ አይኹን ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተመልክቶ ፦ እንግዲህ ፦ ግንበኞች ፡ የናቁት ፡ ድንጋይ ፡ ርሱ ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ ኾነ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈው ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ በዚያም ፡ ድንጋይ ፡ ላይ ፡ የሚወድቅ ፡ ኹሉ ፡ ይቀጠቀጣል ፤ የሚወድቅበትን ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ይፈጨዋል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጻፊዎችም ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ዐውቀው ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ እጃቸውን ፡ ሊጭኑበት ፡ ፈለጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሕዝቡን ፡ ፈሩ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ሲጠባበቁም ፡ ወደገዢ ፡ ግዛትና ፡ ሥልጣን ፡ አሳልፈው ፡ እንዲሰጡት ፡ ጻድቃን ፡ መስለው ፡ በቃሉ ፡ የሚያጠምዱትን ፡ ሸማቂዎች ፡ ሰደዱበት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ጠይቀውም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ እውነትን ፡ እንድትናገርና ፡ እንድታስተምር ፡ ለሰው ፡ ፊትም ፡ እንዳታደላ ፡ እናውቃለን ፥ በእውነት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ታስተምራለኽ ፡ እንጂ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ለቄሳር ፡ ግብር ፡ ልንሰጥ ፡ ተፈቅዷልን ፧ ወይስ ፡ አልተፈቀደም ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ተንኰላቸውንም ፡ ተመልክቶ ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈትኑኛላችኹ ፧ አንድ ፡ ዲናር ፡ አሳዩኝ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ መልኩ ፡ ጽሕፈቱስ ፡ የማን ፡ ነው ፧ አላቸው ። መልሰውም ፦ የቄሳር ፡ ነው ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ እንኪያስ ፡ የቄሳርን ፡ ለቄሳር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስረክቡ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ በሕዝቡም ፡ ፊት ፡ በቃሉ ፡ ሊያጠምዱት ፡ አልቻሉም ፡ በመልሱም ፡ እየተደነቁ ፡ ዝም ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ትንሣኤ ፡ ሙታንንም ፡ የሚክዱ ፡ ከሰዱቃውያን ፡ አንዳንዶቹ ፡ ቀርበው ፡ ጠየቁት ፥

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ እንዲህ ፡ ሲሉ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ሙሴ ፦ ሚስት ፡ ያለችው ፡ የአንድ ፡ ሰው ፡ ወንድም ፡ ልጅ ፡ ሳይወልድ ፡ ቢሞት ፥ ወንድሙ ፡ ሚስቱን ፡ አግብቶ ፡ ለወንድሙ ፡ ዘር ፡ ይተካ ፡ ብሎ ፡ ጻፈልን ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ እንግዲያስ ፡ ሰባት ፡ ወንድማማች ፡ ነበሩ ፤ የፊተኛውም ፡ ሚስት ፡ አግብቶ ፡ ልጅ ፡ ሳይወልድ ፡ ሞተ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 30-31 ፤ ኹለተኛውም ፡ አገባት ፥ ሦስተኛውም ፥ እንዲሁም ፡ ሰባቱ ፡ ደግሞ ፡ ልጅ ፡ ሳይተዉ ፡ ሞቱ ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 32 ፤ ከኹሉም ፡ በኋላ ፡ ሴቲቱ ፡ ደግሞ ፡ ሞተች ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 33 ፤ እንግዲህ ፡ ሰባቱ ፡ አግብተዋታልና ፥ ሴቲቱ ፡ በትንሣኤ ፡ ከነርሱ ፡ ለማንኛቸው ፡ ሚስት ፡ ትኾናለች ፧

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ልጆች ፡ ያገባሉ ፡ ይጋባሉም ፥

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 35 ፤ ያን ፡ ዓለምና ፡ ከሙታን ፡ ትንሣኤ ፡ ሊያገኙ ፡ የሚገባቸው ፡ እነዚያ ፡ ግን ፡ አያገቡም ፡ አይጋቡምም ፥ እንደ ፡ መላእክት ፡ ናቸውና ፥

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 36 ፤ ሊሞቱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አይቻላቸውም ፥ የትንሣኤም ፡ ልጆች ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ናቸው ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 37 ፤ ሙታን ፡ እንዲነሡ ፡ ግን ፡ ሙሴ ፡ ደግሞ ፡ በቍጥቋጦው ፡ ዘንድ ፡ ጌታን ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፡ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ በማለቱ ፡ አስታወቀ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 38 ፤ ኹሉ ፡ ለርሱ ፡ ሕያዋን ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ የሕያዋን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሙታን ፡ አይደለም ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 39 ፤ ከጻፊዎችም ፡ አንዳንዶቹ ፡ መልሰው ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ መልካም ፡ ተናገርኽ ፡ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 40 ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡ ሊጠይቁት ፡ አልደፈሩም ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 41 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ክርስቶስ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንዴት ፡ ይላሉ ፧

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 42-43 ፤ ዳዊትም ፡ ራሱ ፡ በመዝሙራት ፡ መጽሐፍ ፦ ጌታ ፡ ጌታዬን ፦ ጠላቶችኽን ፡ ለእግርኽ ፡ መርገጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡ ይላል ።

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 44 ፤ እንግዲህ ፡ ዳዊት ፦ ጌታ ፡ ብሎ ፡ ይጠራዋል ፥ እንዴትስ ፡ ልጁ ፡ ይኾናል ፧

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 45 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ሲሰሙ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 46 ፤ ረዣዥም ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ መዞር ፡ ከሚፈልጉ ፥ በገበያም ፡ ሰላምታ ፥ በምኩራብም ፡ የከበሬታ ፡ ወንበር ፥ በምሳም ፡ የከበሬታ ፡ ስፍራ ፡ ከሚወዱ ፡ ከጻፊዎች ፡ ተጠበቁ ፤

ሉቃ. ፡ 20 ፡ 47 ፤ የመበለቶችን ፡ ቤት ፡ የሚበሉ ፡ ጸሎታቸውንም ፡ በማስረዘም ፡ የሚያመካኙ ፥ እነዚህ ፡ የባሰ ፡ ፍርድ ፡ ይቀበላሉ ፡ አለ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ ዐይኑንም ፡ አንሥቶ ፡ መባቸውን ፡ በመዝገብ ፡ የሚጥሉ ፡ ባለጠጋዎችን ፡ አየ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ አንዲትም ፡ ድኻ ፡ መበለት ፡ ኹለት ፡ ሳንቲም ፡ በዚያ ፡ ስትጥል ፡ አየና ፦

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህች ፡ ድኻ ፡ መበለት ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ አብልጣ ፡ ጣለች ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ ከትርፋቸው ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መዝገብ ፡ ጥለዋልና ፤ ይህች ፡ ግን ፡ ከጕድለቷ ፡ የነበራትን ፡ ትዳሯን ፡ ኹሉ ፡ ጣለች ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ አንዳንዶቹም ፡ ስለ ፡ መቅደስ ፡ በመልካም ፡ ድንጋይና ፡ በተሰጠው ፡ ሽልማት ፡ እንዳጌጠ ፡ ሲነጋገሩ ፦ ይህማ ፡ የምታዩት ፡ ኹሉ ፥

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ድንጋይ ፡ በድንጋይ ፡ ላይ ፡ ሳይፈርስ ፡ በዚህ ፡ የማይቀርበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣል ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ እነርሱም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ መቼ ፡ ይኾናል ፧ ይህስ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ምልክቱ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ እንዳትስቱ ፡ ተጠንቀቁ ፤ ብዙዎች ፦ እኔ ፡ ነኝ ፥ ዘመኑም ፡ ቀርቧል ፡ እያሉ ፡ በስሜ ፡ ይመጣሉና ፤ እነርሱን ፡ ተከትላችኹ ፡ አትኺዱ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ጦርንና ፡ ሁከትንም ፡ በሰማችኹ ፡ ጊዜ ፡ አትደንግጡ ፤ ይህ ፡ አስቀድሞ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ነውና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መጨረሻው ፡ ወዲያው ፡ አይኾንም ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ሕዝብ ፡ በሕዝብ ፡ ላይ ፥ መንግሥትም ፡ በመንግሥት ፡ ላይ ፡ ይነሣል ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ታላቅም ፡ የምድር ፡ መናወጥና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራ ፡ ቸነፈር ፡ ራብም ፡ ይኾናል ፤ የሚያስፈራም ፡ ነገር ፡ ከሰማይም ፡ ታላቅ ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ በፊት ፡ እጃቸውን ፡ በላያችኹ ፡ ይጭናሉ ፡ ያሳድዷችኹማል ፤ ስለ ፡ ስሜም ፡ ወደ ፡ ምኩራብና ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፥ ወደ ፡ ነገሥታትና ፡ ወደ ፡ ገዢዎችም ፡ ይወስዷችኋል ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ይህም ፡ ለምስክርነት ፡ ይኾንላችኋል ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፡ እንዴት ፡ እንድትመልሱ ፡ አስቀድማችኹ ፡ እንዳታስቡ ፡ በልባችኹ ፡ አኑሩት ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ወደረኞቻችኹ ፡ ኹሉ ፡ ሊቃወሙና ፡ ሊከራከሩ ፡ የማይችሉትን ፡ አፍና ፡ ጥበብ ፡ እሰጣችኋለኹና ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ወላጆችም ፡ ስንኳ ፡ ወንድሞችም ፡ ዘመዶችም ፡ ወዳጆችም ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጧችኋል ፥ ከእናንተም ፡ አንዳንዱን ፡ ይገድላሉ ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ በኹሉም ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ የተጠላችኹ ፡ ትኾናላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ከራሳችኹም ፡ አንዲት ፡ ጠጕር ፡ ስንኳ ፡ አትጠፋም ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ በመታገሣችኹም ፡ ነፍሳችኹን ፡ ታገኛላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ በጭፍራ ፡ ተከባ ፡ ስታዩ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጥፋቷ ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ዕወቁ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በይሁዳ ፡ ያሉ ፡ ወደ ፡ ተራራዎች ፡ ይሸሹ ፥ በመካከሏም ፡ ያሉ ፡ ከርሷ ፡ ፈቀቅ ፡ ይበሉ ፥ በገጠር ፡ ያሉም ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ አይግቡ ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ እንዲፈጸም ፡ ይህ ፡ የበቀል ፡ ጊዜ ፡ ነውና ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ወራት ፡ ለእርጉዞችና ፡ ለሚያጠቡ ፡ ወዮላቸው ፤ ታላቅ ፡ ችግር ፡ በምድር ፡ ላይ ፥ በዚህም ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ ቍጣ ፡ ይኾናልና ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ በሰይፍ ፡ ስለትም ፡ ይወድቃሉ ፤ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉም ፡ ይማረካሉ ፤ የአሕዛብም ፡ ዘመን ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በአሕዛብ ፡ የተረገጠች ፡ ትኾናለች ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ በፀሓይና ፡ በጨረቃም ፡ በከዋክብትም ፡ ምልክት ፡ ይኾናል ፤ በምድር ፡ ላይም ፡ አሕዛብ ፡ ከባሕሩና ፡ ከሞገዱም ፡ ድምፅ ፡ የተነሣ ፡ እያመነቱ ፡ ይጨነቃሉ ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ ሰዎችም ፡ ከፍርሀትና ፡ በዓለም ፡ የሚመጣበትን ፡ ከመጠበቅ ፡ የተነሣ ፡ ይደክማሉ ፤ የሰማያት ፡ ኀይላት ፡ ይናወጣሉና ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 27 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀይልና ፡ በብዙ ፡ ክብር ፡ በደመና ፡ ሲመጣ ፡ ያዩታል ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 28 ፤ ይህም ፡ ሊኾን ፡ ሲጐምር ፡ ቤዛችኹ ፡ ቀርቧልና ፥ አሻቅባችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ አንሡ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ ምሳሌንም ፡ ነገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ በለስንና ፡ ዛፎችን ፡ ኹሉ ፡ እዩ ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ሲያቈጠቍጡ ፡ ተመልክታችኹ ፡ በጋ ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ቀረበ ፡ ራሳችኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ ይህ ፡ ኹሉ ፡ መኾኑን ፡ ስታዩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ቀረበች ፡ ዕወቁ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ይህ ፡ ኹሉ ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡ ይህ ፡ ትውልድ ፡ አያልፍም ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋሉ ፡ ቃሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልባችኹ ፡ በመጠጥ ፡ ብዛትና ፡ በስካር ፡ ስለ ፡ ትዳርም ፡ በማሰብ ፡ እንዳይከብድ ፥ ያ ፡ ቀንም ፡ በድንገት ፡ እንዳይመጣባችኹ ፡ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፤

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 35 ፤ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በሚቀመጡ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ወጥመድ ፡ ይደርስባቸዋልና ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 36 ፤ እንግዲህ ፡ ሊመጣ ፡ ካለው ፡ ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ ለማምለጥ ፥ በሰው ፡ ልጅም ፡ ፊት ፡ ለመቆም ፡ እንድትችሉ ፡ ስትጸልዩ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ትጉ ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 37 ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ በመቅደስ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ፥ ሌሊት ፡ ግን ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ወደምትባል ፡ ተራራ ፡ ወጥቶ ፡ ያድር ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 21 ፡ 38 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ይሰሙት ፡ ዘንድ ፡ ማልደው ፡ በመቅደስ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ ፋሲካም ፡ የሚባለው ፡ የቂጣ ፡ በዓል ፡ ቀረበ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጻፊዎችም ፡ እንዴት ፡ እንዲያጠፉት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ ሕዝቡን ፡ ይፈሩ ፡ ነበርና ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ ሰይጣንም ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ቍጥር ፡ አንዱ ፡ በነበረው ፡ የአስቆሮቱ ፡ በሚባለው ፡ በይሁዳ ፡ ገባ ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ኼዶም ፡ እንዴት ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ከመቅደስ ፡ አዛዦች ፡ ጋራ ፡ ተነጋገረ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፥ ገንዘብም ፡ ሊሰጡት ፡ ተዋዋሉ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ ዕሺም ፡ አለ ፥ ሕዝብም ፡ በሌለበት ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ይፈልግ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ ፋሲካንም ፡ ሊያርዱበት ፡ የሚገባው ፡ የቂጣ ፡ በዓል ፡ ደረሰ ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስንም ፦ ፋሲካን ፡ እንድንበላ ፡ ኼዳችኹ ፡ አዘጋጁልን ፡ ብሎ ፡ ላካቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፦ ወዴት ፡ እናዘጋጅ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለኽ ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ርሱም ፡ አላቸው ፦ እንሆ ፥ ወደ ፡ ከተማ ፡ ስትገቡ ፡ ማድጋ ፡ ውሃ ፡ የተሸከመ ፡ ሰው ፡ ይገናኛችኋል ፤ ወደሚገባበት ፡ ቤት ፡ ተከተሉት ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ለባለቤቱም ፦ መምህሩ ፦ ከደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ጋራ ፡ ፋሲካን ፡ የምበላበት ፡ የእንግዳ ፡ ቤት ፡ ክፍል ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ይልኻል ፡ በሉት ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ ያም ፡ በደርብ ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ የተነጠፈ ፡ ታላቅ ፡ አዳራሽ ፡ ያሳያችኋል ፤ በዚያም ፡ አሰናዱልን ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ኼደውም ፡ እንዳላቸው ፡ አገኙና ፡ ፋሲካን ፡ አሰናዱ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ሰዓቱም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ በማእዱ ፡ ተቀመጠ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ርሱም ፦ ከመከራዬ ፡ በፊት ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ ፋሲካ ፡ ልበላ ፡ እጅግ ፡ እመኝ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ እላችኋለኹና ፥ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ ከዚህ ፡ አልበላም ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ ጽዋንም ፡ ተቀበለ ፡ አመስግኖም ፦ ይህን ፡ እንካችኹ ፥ በመካከላችኹም ፡ ተካፈሉት ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ እላችኋለኹና ፥ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እስክትመጣ ፡ ድረስ ፡ ካኹን ፡ ዠምሮ ፡ ከወይኑ ፡ ፍሬ ፡ አልጠጣም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ እንጀራንም ፡ አንሥቶ ፡ አመሰገነ ፡ ቈርሶም ፡ ሰጣቸውና ፦ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚሰጠው ፡ ሥጋዬ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ለመታሰቢያዬ ፡ አድርጉት ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ እንዲሁም ፡ ከእራት ፡ በኋላ ፡ ጽዋውን ፡ አንሥቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ይህ ፡ ጽዋ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በሚፈሰው ፡ በደሜ ፡ የሚኾን ፡ ዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አሳልፎ ፡ የሚሰጠኝ ፡ እጅ ፥ እንሆ ፥ በማእዱ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ናት ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ የሰው ፡ ልጅስ ፡ እንደተወሰነው ፡ ይኼዳል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዐልፎ ፡ ለሚሰጥበት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ወዮለት ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ ከነርሱም ፡ ይህን ፡ ሊያደርግ ፡ ያለው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይጠያየቁ ፡ ዠመር ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ ደግሞም ፡ ማናቸውም ፡ ታላቅ ፡ ኾኖ ፡ እንዲቈጠር ፡ በመካከላቸው ፡ ክርክር ፡ ኾነ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ የአሕዛብ ፡ ነገሥታት ፡ ይገዟቸዋል ፥ በላያቸውም ፡ የሚሠለጥኑት ፡ ቸርነት ፡ አድራጊዎች ፡ ይባላሉ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አትኹኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ በመካከላችኹ ፡ እንደ ፡ ታናሽ ፥ የሚገዛም ፡ እንደሚያገለግል ፡ ይኹን ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ በማእዱ ፡ የተቀመጠ ፡ ወይስ ፡ የሚያገለግል ፡ ማናቸው ፡ ታላቅ ፡ ነው ፧ የተቀመጠው ፡ አይደለምን ፧ እኔ ፡ ግን ፡ በመካከላችኹ ፡ እንደሚያገለግል ፡ ነኝ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ በፈተናዎቼ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ጸንታችኹ ፡ የኖራችኹ ፡ ናችኹ ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 29-30 ፤ አባቴ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ሾመኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በመንግሥቴ ፡ ከማእዴ ፡ ትበሉና ፡ ትጠጡ ፡ ዘንድ ፥ በዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ በእስራኤል ፡ ነገድ ፡ ስትፈርዱ ፡ በዙፋኖች ፡ ትቀመጡ ፡ ዘንድ ፡ ለመንግሥት ፡ እሾማችኋለኹ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 31 ፤ ጌታም ፦ ስምዖን ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ ሰይጣን ፡ እንደ ፡ ስንዴ ፡ ሊያበጥራችኹ ፡ ለመነ ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 32 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እምነትኽ ፡ እንዳይጠፋ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ አማለድኹ ፤ አንተም ፡ በተመለስኽ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞችኽን ፡ አጽና ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 33 ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ወህኒም ፡ ወደ ፡ ሞትም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ለመኼድ ፡ የተዘጋጀኹ ፡ ነኝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 34 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፥ እልኻለኹ ፥ እንዳታውቀኝ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እስክትክደኝ ፡ ድረስ ፡ ዛሬ ፡ ዶሮ ፡ አይጮኽም ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 35 ፤ ደግሞም ፦ ያለኰረጆና ፡ ያለከረጢት ፡ ያለጫማም ፡ በላክኋችኹ ፡ ጊዜ ፥ አንዳች ፡ ጐደለባችኹን ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ አንዳች ፡ እንኳ ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 36 ፤ ርሱም ፦ አኹን ፡ ግን ፡ ኰረጆ ፡ ያለው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይውሰድ ፥ ከረጢትም ፡ ያለው ፡ እንዲሁ ፤ የሌለውም ፡ ልብሱን ፡ ሸጦ ፡ ሰይፍ ፡ ይግዛ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 37 ፤ እላችኋለኹና ፥ ይህ ፦ ከዐመፀኞች ፡ ጋራ ፡ ተቈጠረ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈው ፡ በእኔ ፡ ሊፈጸም ፡ ግድ ፡ ነው ፤ አዎን ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚኾነው ፡ አኹን ፡ ይፈጸማልና ፥ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 38 ፤ እነርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ በዚህ ፡ ኹለት ፡ ሰይፎች ፡ አሉ ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ይበቃል ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 39 ፤ ወጥቶም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ኼደ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ደግሞ ፡ ተከተሉት ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 40 ፤ ወደ ፡ ስፍራውም ፡ ደርሶ ፦ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ጸልዩ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 41 ፤ ከነርሱም ፡ የድንጋይ ፡ ውርወራ ፡ የሚያኽል ፡ ራቀ ፥ ተንበርክኮም ፦ አባት ፡ ሆይ ፥

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 42 ፤ ብትፈቅድ ፡ ይህችን ፡ ጽዋ ፡ ከእኔ ፡ ውሰድ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእኔ ፡ ፈቃድ ፡ አይኹን ፡ የአንተ ፡ እንጂ ፡ እያለ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 43 ፤ ከሰማይም ፡ መጥቶ ፡ የሚያበረታ ፡ መልአክ ፡ ታየው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 44 ፤ በፍርሀትም ፡ ሲጣጣር ፡ አጽንቶ ፡ ይጸልይ ፡ ነበር ፤ ወዙም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንደሚወርድ ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ነጠብጣብ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 45 ፤ ከጸሎትም ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጣና ፡ ከሐዘን ፡ የተነሣ ፡ ተኝተው ፡ ሲያገኛቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 46 ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ትተኛላችኹ ፧ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትገቡ ፡ ተነሥታችኹ ፡ ጸልዩ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 47 ፤ ገናም ፡ ሲናገር ፥ እንሆ ፥ ሰዎች ፡ መጡ ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱም ፡ ይሁዳ ፡ የሚባለው ፡

ይቀድማቸው ፡ ነበር ፥ ሊስመውም ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ ቀረበ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 48 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ ይሁዳ ፡ ሆይ ፥ በመሳም ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ አሳልፈኽ ፡ ትሰጣለኽን ፧ አለው ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 49 ፤ በዙሪያውም ፡ የነበሩት ፡ የሚኾነውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በሰይፍ ፡ እንምታቸውን ፧ አሉት ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 50 ፤ ከነርሱም ፡ አንዱ ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱን ፡ ባሪያ ፡ መቶ ፡ ቀኝ ፡ ጉሮሮውን ፡ ቈረጠው ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 51 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ ይህንስ ፡ ፍቀዱ ፡ አለ ፤ ጉሮሮውንም ፡ ዳሶ ፡ ፈወሰው ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 52 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለመጡበት ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ለመቅደስ ፡ አዛጉሮች ፡ ለሽማግሌዎችም ፦ ወንበዴን ፡ እንደምትይዙ ፡ ሰይፍና ፡ ጐመድ ፡ ይዛችኹ ፡ ወጣችኹን ፧

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 53 ፤ በመቅደስ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ስኾን ፡ እጆቻችኹን ፡ አልዘረጋችኹብኝም ፤ ይህ ፡ ግን ፡ ጊዜያችኹና ፡ የጨለማው ፡ ሥልጣን ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 54 ፤ ይዘውም ፡ ወሰዱት ፡ ወደሊቀ ፡ ካህናት ፡ ቤትም ፡ አገቡት ፤ ጴጥሮስም ፡ ርቆ ፡ ይከተለው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 55 ፤ በግቢ ፡ መካከልም ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ በአንድነት ፡ ተቀምጠው ፡ ሳሉ ፡ ጴጥሮስ ፡ በመካከላቸው ፡ ተቀመጠ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 56 ፤ በብርሃኑም ፡ በኩል ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ አንዲት ፡ ገረድ ፡ አየችውና ፡ ትኵር ፡ ብላ ፦ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ አለች ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 57 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ አላውቀውም ፡ ብሎ ፡ ካደ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 58 ፤ ከጥቂት ፡ ጊዜም ፡ በኋላ ፡ ሌላው ፡ አይቶት ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ወገን ፡ ነኽ ፡ አለው ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፦ አንተ ፡ ሰው ፥ እኔ ፡ አይደለኹም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 59 ፤ አንድ ፡ ሰዓትም ፡ የሚያኽል ፡ ቈይቶ ፡ ሌላው ፡ አስረግጦ ፦ ርሱ ፡ የገሊላ ፡ ሰው ፡ ነውና ፥ በእውነት ፡ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ አለ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 60 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፦ አንተ ፡ ሰው ፥ የምትለውን ፡ አላውቅም ፡ አለ ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ዶሮ ፡ ጮኸ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 61 ፤ ጌታም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ጴጥሮስን ፡ ተመለከተው ፤ ጴጥሮስም ፦ ዛሬ ፡ ዶሮ ፡ ሳይጮኽ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ትክደኛለኽ ፡ እንዳለው ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 62 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥቶ ፡ ምርር ፡ ብሎ ፡ አለቀሰ ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 63 ፤ ኢየሱስንም ፡ የያዙት ፡ ሰዎች ፡ ይዘብቱበትና ፡ ይደበድቡት ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 64 ፤ ሸፍነውም ፡ ፊቱን ፡ ይመቱት ፡ ነበርና ፦ በጥፊ ፡ የመታኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ትንቢት ፡ ተናገር ፡ እያሉ ፡ ይጠይቁት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 65 ፤ ሌላም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ እየተሳደቡ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይናገሩ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፥ 22 ፥ 66 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ የሕዝቡ ፡ ሽማግሌዎችና ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ጸሊዎችም ፡ ተሰብስበው ፡ ወደሸንጎቸው ፡ ወሰዱትና ፡

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 67 ፤ ክርስቶስ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ ንገረን ፡ አሉት ። ርሱ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ብነግራችኹ ፡ አታምኑም ፤

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 68 ፤ ብጠይቅም ፡ አትመልሱልኝም ፡ አትፈቱኝምም ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 69 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ካኹን ፡ ዠምሮ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ቀኝ ፡ ይቀመጣል ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 70 ፤ ኹላቸውም ፦ እንግዲያስ ፡ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽን ፧ አሉት ። ርሱም ፦ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እናንተ ፡ ትላላችኹ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 22 ፡ 71 ፤ እነርሱም ፦ ራሳችን ፡ ከአፉ ፡ ሰምተናልና ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ምን ፡ ምስክር ፡ ያስፈልገናል ፧ አሉ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ኹሉም ፡ በሞላው ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ወሰዱትና ፦

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ይህ ፡ ሕዝባችንን ፡ ሲያጣምም ፡ ለቄሳርም ፡ ግብር ፡ እንዳይሰጥ ፡ ሲከለክል ፡ ደግሞም ፦ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ አገኘነው ፡ ብለው ፡ ይከሱት ፡ ዠመር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ ጲላጦስም ፦ አንተ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነኽን ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ። ርሱም ፡ መልሶ ፦ አንተ ፡ አልኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ ጲላጦስም ፡ ለካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ለሕዝቡ ፦ በዚህ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ አላገኘኹበትም ፡ አለ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ አጽንተው ፦ ከገሊላ ፡ ዠምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ እያስተማረ ፡ ሕዝቡን ፡ ያውካል ፡ አሉ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ ጲላጦስ ፡ ግን ፦ ገሊላ ፡ ሲሉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፦ የገሊላ ፡ ሰው ፡ ነውን ፧ ብሎ ፡ ጠየቀ ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ከሄሮድስም ፡ ግዛት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰደደው ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነበረና ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ሄሮድስም ፡ ኢየሱስን ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ ሰማ ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ ዠምሮ ፡ ሊያየው ፡ ይመኝ ፡ ነበርና ፥ ምልክትም ፡ ሲያደርግ ፡ ሊያይ ፡ ተስፋ ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ በብዙ ፡ ቃልም ፡ ጠየቀው ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልመለሰለትም ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ጸሊዎችም ፡ አጽንተው ፡ ሲከሱት ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ ሄሮድስም ፡ ከሰራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ናቀው ፡ ዘበተበትም ፥ የጌጥ ፡ ልብስም ፡ አልብሶ ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ መልሶ ፡ ሰደደው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ ሄሮድስና ፡ ጲላጦስም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ወዳጆች ፡ ኾኑ ፥ ቀድሞ ፡ በመካከላቸው ፡ ጥል ፡ ነበረና ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ጲላጦስም ፥ የካህናትን ፡ አለቃዎችና ፡ መኳንንትን ፡ ሕዝቡንም ፡ በአንድነት ፡ ጠርቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ ሕዝቡን ፡ ያጣምማል ፡ ብላችኹ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ አመጣችኹት ፤ እንሆም ፥ በፊታችኹ ፡ መርምሬ ፡ ከምትከሱበት ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ አላገኘኹበትም ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ ሄሮድስም ፡ ደግሞ ፡ ምንም ፡ አላገኘም ፤ ወደ ፡ እኛ ፡ መልሶታልና ፤ እንሆም ፥ ለሞት ፡ የሚያደርሰው ፡ ምንም ፡ አላደረገም ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 16-17 ፤ እንግዲያስ ፡ ቀጥቼ ፡ እፈታዋለኹ ። በበዓሉ ፡ አንድ ፡ ይፈታላቸው ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ነበረና ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ኹላቸውም ፡ በአንድነት ፦ ይህን ፡ አስወግድ ፥ በርባንንም ፡ ፍታልን ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ ሁከትን ፡ በከተማ ፡ አንሥቶ ፡ ሰውን ፡ ስለ ፡ ገደለ ፡ በወህኒ ፡ ታስሮ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ ጲላጦስም ፡ ኢየሱስን ፡ ሊፈታ ፡ ወዶ ፡ ዳግመኛ ፡ ተናገራቸው ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱ ፦ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ ሦስተኛም ፦ ምን ፡ ነው ፧ ያደረገውስ ፡ ክፋት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ለሞት ፡ የሚያደርሰው ፡ በደል ፡ አላገኘኹበትም ፤ ስለዚህ ፥ ቀጥቼ ፡ እፈታዋለኹ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ እንዲሰቀል ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ አጽንተው ፡ ለመኑት ። የእነርሱ ፡ ጩኸትና ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ቃል ፡ በረታ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ ጲላጦስም ፡ ልመናቸው ፡ እንዲኾንላቸው ፡ ፈረደበት ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ ያን ፡ የለመኑትንም ፥ ስለ ፡ ሁከት ፡ ሰውንም ፡ ስለ ፡ መግደል ፡ በወህኒ ፡ ታስሮ ፡ የነበረውን ፡ አስፈታላቸው ፥ ኢየሱስን ፡ ግን ፡ ለፈቃዳቸው ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ በወሰዱትም ፡ ጊዜ ፡ ስምዖን ፡ የተባለ ፡ የቀሬናን ፡ ሰው ፡ ከገጠር ፡ ሲመጣ ፡ ይዘው ፡ ከኢየሱስ ፡ በኋላ ፡ መስቀሉን ፡ እንዲሸከም ፡ ጫኑበት ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ከሚሉና ፡ ሙሾ ፡ ከሚያወጡ ፡ ሴቶችና ፡ ከሕዝቡ ፡ እጅግ ፡ ብዙዎች ፡ ተከተሉት ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 28-29 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ የኢየሩሳሌም ፡ ልጆች ፥ ለኔስ ፡ አታልቅሱልኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፦ መካኖችና ፡ ያልወለዱ ፡ ማሕፀኖች ፡ ያላጠቡ ፡ ጡቶችም ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ የሚሉበት ፡ ጊዜ ፥ እንሆ ፥ ይመጣልና ፥ ለራሳችኹና ፡ ለልጆቻችኹ ፡ አልቅሱ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ተራራዎችን ፦ በላያችን ፡ ውደቁ ፥ ኰረብታዎችንም ፦ ሰውሩን ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ይጐምራሉ ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ በርጥብ ፡ ዕንጨት ፡ እንዲህ ፡ የሚያደርጉ ፡ ከኾኑ ፥ በደረቀውስ ፡ እንዴት ፡ ይኾን ፧

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ ሌላዎችንም ፡ ኹለት ፡ ክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ወሰዱ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ ቀራንዮም ፡ ወደሚባል ፡ ስፍራ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ ርሱን ፡ ክፉ ፡ አድራጊዎቹንም ፡ አንዱን ፡ በቀኝ ፡ ኹለተኛውንም ፡ በግራ ፡ ሰቀሉ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ የሚያደርጉትን ፡ አያውቁምና ፡ ይቅር ፡ በላቸው ፡ አለ ። ልብሱንም ፡ ተካፍለው ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉበት ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 35 ፤ ሕዝቡም ፡ ቆመው ፡ ይመለከቱ ፡ ነበር ። መኳንንቱም ፡ ደግሞ ፦ ሌላዎችን ፡ አዳነ ፤ ርሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተመረጠው ፡ ክርስቶስ ፡ ከኾነ ፥ ራሱን ፡ ያድን ፡ እያሉ ፡ ያፌዙበት ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 36 ፤ ጭፍራዎችም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ቀርበው ፡ ሐምጣጤም ፡ አምጥተው ፦

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 37 ፤ አንተስ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ከኾንኽ ፥ ራስኽን ፡ አድን ፡ እያሉ ፡ ይዘብቱበት ፡ ነበር ፦

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 38 ፤ ይህ ፡ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በግሪክና ፡ በሮማይስጥ ፡ በዕብራይስጥም ፡ ፊደል ፡ የተጻፈ ፡ ጽሕፈት ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 39 ፤ ከተሰቀሉት ፡ ከክፉ ፡ አድራጊዎቹም ፡ አንዱ ፦ አንተስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለኽምን ፧ ራስኽንም ፡ እኛንም ፡ አድን ፡ ብሎ ፡ ሰደበው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 40 ፤ ኹለተኛው ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ፍርድ ፡ ሳለኽ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከቶ ፡ አትፈራውምን ፧

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 41 ፤ ስላደረግነውም ፡ የሚገባንን ፡ እንቀበላለንና ፡ በእኛስ ፡ እውነተኛ ፡ ፍርድ ፡ ነው ፤ ይህ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ክፋት ፡ አላደረገም ፡ ብሎ ፡ ገሠጸው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 42 ፤ ኢየሱስንም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በመንግሥትኽ ፡ በመጣኽ ፡ ጊዜ ፡ ዐስበኝ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 43 ፤ ኢየሱስም ፦ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ ዛሬ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በገነት ፡ ትኾናለኽ ፡ አለው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 44 ፤ ስድስት ፡ ሰዓትም ፡ ያኽል ፡ ነበረ ፥ ጨለማም ፡ እስከ ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ኾነ ፥ ፀሓይም ፡ ጨለመ ፥

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 45 ፤ የቤተ ፡ መቅደስም ፡ መጋረጃ ፡ ከመካከሉ ፡ ተቀደደ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 46 ፤ ኢየሱስም ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኾ ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ ነፍሴን ፡ በእጅኽ ፡ ዐደራ ፡ እሰጣለኹ ፡ አለ ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ ነፍሱን ፡ ሰጠ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 47 ፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ ጻድቅ ፡ ነበረ ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበረ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 48 ፤ ይህንም ፡ ለማየት ፡ ተከማችተው ፡ የነበሩ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ የኾነውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ደረታቸውን ፡ እየደቁ ፡ ተመለሱ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 49 ፤ የሚያውቁቱ ፡ ግን ፡ ኹሉ ፡ ከገሊላ ፡ የተከተሉት ፡ ሴቶችም ፡ ይህን ፡ እያዩ ፡ በሩቅ ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 50 ፤ እንሆም ፥ በጎና ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ የሸንጎ ፡ አማካሪም ፡ የኾነ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚባል ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 51 ፤ ይህም ፡ በምክራቸውና ፡ በሥራቸው ፡ አልተባበረም ፡ ነበር ፤ አርማትያስም ፡ ከምትባል ፡ ከአይሁድ ፡ ከተማ ፡ ኾኖ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ይጠባበቅ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 52 ፤ ይኸውም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ቀርቦ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ለመነው ፤

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 53 ፤ አውርዶም ፡ በተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡ ከፈነው ፥ ማንም ፡ ገና ፡ ባልተቀበረበት ፡ ከአለትም ፡ በተወቀረ ፡ መቃብር ፡ አኖረው ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 54 ፤ የመዘጋጀት ፡ ቀንም ፡ ነበረ ፤ ሰንበትም ፡ ሊገምር ፡ ነበረ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 55 ፤ ከገሊላም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የመጡት ፡ ሴቶች ፡ ተከትለው ፡ መቃብሩን ፡ ሥጋውንም ፡ እንዴት ፡ እንዳኖሩት ፡ አዩ ።

ሉቃ. ፡ 23 ፡ 56 ፤ ተመልሰውም ፡ ሽቱና ፡ ቅባት ፡ አዘጋጁ ። በሰንበትም ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ዐረፉ ።

የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከሳምንቱ ፡ በመገመሪያው ፡ ቀን ፡ ያዘጋጁትን ፡ ሽቱ ፡ ይዘው ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ እጅግ ፡ ማልደው ፡ መጡ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 2 ፤ ድንጋዩንም ፡ ከመቃብሩ ፡ ተንከባሎ ፡ አገኙት ፥

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 3 ፤ ገብተውም ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ አላገኙም ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፡ በዚህ ፡ ሲያመነቱ ፥ እንሆ ፥ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ የሚያንጸባርቅ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረቡ ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ፈርተውም ፡ ፊታቸውን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ አቀርቅረው ፡ ሳሉ ፥ እንዲህ ፡ አሏቸው ፦ ሕያውን ፡ ከሙታን ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈልጋላችኹ ፧ ተነሥቷል ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ የለም ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 6-7 ፤ የሰው ፡ ልጅ ፡ በኀጢአተኞች ፡ እጅ ፡ ዐልፎ ፡ ሊሰጥና ፡ ሊሰቀል ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ሊነሣ ፡ ግድ ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ገና ፡ በገሊላ ፡ ሳለ ፡ ለእናንተ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ዐስቡ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 8-9 ፤ ቃሎቹንም ፡ ዐሰቡ ፥ ከመቃብሩም ፡ ተመልሰው ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ለዐሥራ ፡ አንዱና ፡ ለሌላዎች ፡ ኹሉ ፡ ነገሯቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ይህንም ፡ ለሐዋርያት ፡ የነገሯቸው ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምና ፡ ዮሐና ፡ የያዕቆብም ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሌላዎች ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ ይህም ፡ ቃል ፡ ቅዠት ፡ መስሎ ፡ ታያቸውና ፡ አላመኗቸውም ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሮጠ ፤ በዚያም ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፡ ሲመለከት ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስን ፡ ብቻ ፡ አየ ፤ በኾነውም ፡ ነገር ፡ እየተደነቀ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ እንሆም ፥ ከነርሱ ፡ ኹለቱ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ስድሳ ፡ ምዕራፍ ፡ ያኽል ፡ ወደሚርቅ ፡ ኤማሁስ ፡ ወደሚባል ፡ መንደር ፡ ይኼዱ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ስለዚህም ፡ ስለ ኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይነጋገሩ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ ሲነጋገሩና ፡ ሲመራመሩም ፥ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ ቀርቦ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኼድ ፡ ነበር ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳያውቁት ፡ ዐይናቸው ፡ ተይዞ ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ ርሱም ፦ እየጠወለጋችኹ ፡ ስትኼዱ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ የምትነጋገሯቸው ፡ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ምንድር ፡ ናቸው ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ ቀለዮጳ ፡ የሚባልም ፡ አንዱ ፡ መልሶ ፦ አንተ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንግዳ ፡ ኾነኽ ፡ ለብቻኽ ፡ ትኖራለኽን ፧ በእነዚህ ፡ ቀኖች ፡ በዚያ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ አታውቅምን ፧ አለው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ርሱም ፦ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ። እነርሱም ፡ እንዲህ ፡ አሉት ፦ በእግዚአብሔርና ፡ በሕዝቡ ፡ ፊት ፡ በሥራና ፡ በቃል ፡ ብርቱ ፡ ነቢይ ፡ ስለነበረው ፡ ስለናዝሬቱ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 20 ፤ ርሱንም ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ መኳንንቶቻችን ፡ ለሞት ፡ ፍርድ ፡ እንዴት ፡ አሳልፈው ፡ እንደ ፡ ሰጡትና ፡ እንደ ፡ ሰቀሉት ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 21 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እስራኤልን ፡ እንዲቤዥ ፡ ያለው ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተስፋ ፡ አድርገን ፡ ነበር ፤ ደግሞም ፡ ከዚህ ፡ ሹሉ ፡ ጋራ ፡ ይህ ፡ ከኾነ ፡ ዛሬ ፡ ሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ነው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ደግሞም ፡ ከእኛ ፡ ውስጥ ፡ ማልደው ፡ ከመቃብሩ ፡ ዘንድ ፡ የነበሩት ፡ አንዳንድ ፡ ሴቶች ፡ አስገረሙን ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ ሥጋውንም ፡ ባጡ ፡ ጊዜ ፦ ሕያው ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡ የመላእክትን ፡ ራእይ ፡ ደግሞ ፡ አየን ፡ ሲሉ ፡ መጥተው ፡ ነበር ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ከነበሩት ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ኼደው ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ ተናገሩት ፡ ኾኖ ፡ አገኙት ፥ ርሱን ፡ ግን ፡ አላዩትም ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ ርሱም ፦ እናንተ ፡ የማታስተውሉ ፥ ነቢያትም ፡ የተናገሩትን ፡ ሹሉ ፡ ልባችኹ ፡ ከማመን ፡ የዘገየ ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ ክርስቶስ ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድና ፡ ወደ ፡ ክብሩ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ ይገ҃ባው ፡ የለምን ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ ከሙሴና ፡ ከነቢያት ፡ ሹሉ ፡ ገምሮ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በመጻሕፍት ፡ ሹሉ ፡ የተጻፈውን ፡ ተረጐመላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 28 ፤ ወደሚኼዱበትም ፡ መንደር ፡ ቀረቡ ፥ ርሱም ፡ ሩቅ ፡ የሚኼድ ፡ መሰላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 29 ፤ እነርሱ ፦ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ዕደር ፥ ማታ ፡ ቀርቧልና ፥ ቀኑም ፡ ሊመሽ ፡ ገምሯል ፡ ብለው ፡ ግድ ፡ አሉት ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ሊያድር ፡ ገባ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 30 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ በማእዱ ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ እንጀራውን ፡ አንሥቶ ፡ ባረከው ፥ ቈርሶም ፡ ሰጣቸው ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 31 ፤ ዐይናቸውም ፡ ተከፈተ ፥ ዐወቁትም ፤ ርሱም ፡ ከነርሱ ፡ ተሰወረ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 32 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፦ በመንገድ ፡ ሲናገረን ፡ መጻሕፍትንም ፡ ሲከፍትልን ፡ ልባችን ፡ ይቃጠልብን ፡ አልነበረምን ፧ ተባባሉ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 33-34 ፤ በዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ተነሥተው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፥ ዐሥራ ፡ አንዱና ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትም ፦ ጌታ ፡ በእውነት ፡ ተነሥቷል ፡ ለስምዖንም ፡ ታይቷል ፡ እያሉ ፡ በአንድነት ፡ ተሰብስበው ፡ አገኟቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 35 ፤ እነርሱም ፡ በመንገድ ፡ የኾነውን ፡ እንጀራውንም ፡ በቈረሰ ፡ ጊዜ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ታወቀላቸው ፡ ተረኩላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 36 ፤ ይህንም ፡ ሲነጋገሩ ፡ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሞ ፦ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 37 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ደነገጡና ፡ ፈሩ ፡ መንፈስም ፡ ያዩ ፡ መሰላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ትደነግጣላችኹ ፧ ስለ ፡ ምንስ ፡ ዐሳብ ፡ በልባችኹ ፡ ይነሣል ፧

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 39 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ እጆቼንና ፡ እግሮቼን ፡ እዩ ፤ በእኔ ፡ እንደምታዩት ፥ መንፈስ ፡ ሥጋና ፡ ዐጥንት ፡ የለውምና ፡ እኔን ፡ ዳስሳችኹ ፡ እዩ ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 40 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እጆቹንና ፡ እግሮቹን ፡ አሳያቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 41 ፤ እነርሱም ፡ ከደስታ ፡ የተነሣ ፡ ገና ፡ ስላላመኑ ፡ ሲደነቁ ፡ ሳሉ ፦ በዚህ ፡ አንዳች ፡ የሚበላ ፡ አላችኹን ፧ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 42 ፤ እነርሱም ፡ ከተጠበሰ ፡ ዓሣ ፡ አንድ ፡ ቍራጭ ፥ ከማር ፡ ወለላም ፡ ሰጡት ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 43 ፤ ተቀብሎም ፡ በፊታቸው ፡ በላ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 44 ፤ ርሱም ፦ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለኹ ፡ በሙሴ ፡ ሕግና ፡ በነቢያት ፡ በመዝሙራትም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የተጻፈው ፡ ኹሉ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ የነገርኋችኹ ፡ ቃሌ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 45 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ መጻሕፍትን ፡ ያስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ አእምሯቸውን ፡ ከፈተላቸው ፤

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 46 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ ይቀበላል ፡ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ ይነሣል ፥

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 47 ፤ በስሙም ፡ ንስሓና ፡ የኀጢአት ፡ ስርየት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ገምሮ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይሰበካል ፡ ተብሎ ፡ እንዲሁ ፡ ተጽፏል ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 48 ፤ እናንተም ፡ ለዚህ ፡ ምስክሮች ፡ ናችኹ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 49 ፤ እንሆም ፥ አባቴ ፡ የሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ እኔ ፡ እልክላችኋለኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ ኀይል ፡ እስክትለብሱ ፡ ድረስ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ ቈዩ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 50 ፤ እስከ ፡ ቢታንያም ፡ አወጣቸው ፡ እጆቹንም ፡ አንሥቶ ፡ ባረካቸው ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 51 ፤ ሲባርካቸውም ፡ ከነርሱ ፡ ተለየ ፡ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ዐረገ ።

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 52 ፤ እነርሱም ፤ ሰገዱለትና ፡ በብዙ ፡ ደስታ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፥

ሉቃ. ፡ 24 ፡ 53 ፤ ዘወትርም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገኑና ፡ እየባረኩ ፡ በመቅደስ ፡ ኖሩ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በመዠመሪያው ፡ ቃል ፡ ነበረ ፥ ቃልም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፥ ቃልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ይህ ፡ በመዠመሪያው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ኾነ ፥ ከኾነውም ፡ አንዳች ፡ ስንኳ ፡ ያለርሱ ፡ አልኾነም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ በርሱ ፡ ሕይወት ፡ ነበረች ፥ ሕይወትም ፡ የሰው ፡ ብርሃን ፡ ነበረች ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ብርሃንም ፡ በጨለማ ፡ ይበራል ፥ ጨለማም ፡ አላሸነፈውም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተላከ ፡ ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ እንዲያምኑ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ብርሃን ፡ ይመሰክር ፡ ዘንድ ፡ ለምስክር ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ስለ ፡ ብርሃን ፡ ሊመሰክር ፡ መጣ ፡ እንጂ ፥ ርሱ ፡ ብርሃን ፡ አልነበረም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ የሚያበራው ፡ እውነተኛው ፡ ብርሃን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ይመጣ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በዓለም ፡ ነበረ ፥ ዓለሙም ፡ በርሱ ፡ ኾነ ፥ ዓለሙም ፡ አላወቀውም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ የርሱ ፡ ወደኾነው ፡ መጣ ፥ የገዛ ፡ ወገኖቹም ፡ አልተቀበሉትም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ለተቀበሉት ፡ ኹሉ ፡ ግን ፥ በስሙ ፡ ለሚያምኑት ፡ ለእነርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጣቸው ፤

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ እነርሱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተወለዱ ፡ እንጂ ፡ ከደም ፡ ወይም ፡ ከሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ወይም ፡ ከወንድ ፡ ፈቃድ ፡ አልተወለዱም ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ቃልም ፡ ሥጋ ፡ ኾነ ፤ ጸጋንና ፡ እውነትንም ፡ ተመልቶ ፡ በእኛ ፡ ዐደረ ፥ አንድ ፡ ልጅም ፡ ከአባቱ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ክብር ፡ የኾነው ፡ ክብሩን ፡ አየን ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ዮሐንስ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ መሰከረ ፡ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ፦ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ርሱ ፡ ከእኔ ፡ በፊት ፡ ነበረና ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ኾኗል ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ ያልኹት ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ከሙላቱ ፡ ተቀብለን ፡ በጸጋ ፡ ላይ ፡ ጸጋ ፡ ተሰጥቶናልና ፥ ሕግ ፡ በሙሴ ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበርና ፤

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ጸጋና ፡ እውነት ፡ ግን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኾነ ።

ዮሐ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ መቼም ፡ ቢኾን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያየው ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ፤ በአባቱ ፡ ዕቅፍ ፡ ያለ ፡

አንድ ፡ ልጁ ፡ ርሱ ፡ ተረከው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ አይሁድም ፦ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ ብለው ፡ ይጠይቁት ፡ ዘንድ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ካህናትንና ፡ ሌዋውያንን ፡ በላኩበት ፡ ጊዜ ፥ የዮሐንስ ፡ ምስክርነት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ መሰከረም ፡ አልካደምም ፤ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለኹም ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ እንኪያስ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ ኤልያስ ፡ ነኽን ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ፦ አይደለኹም ፡ አለ ፦ ነቢዩ ፡ ነኽን ፧ አይደለኹም ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ እንኪያስ ፦ ማን ፡ ነኽ ፧ ለላኩን ፡ መልስ ፡ እንድንሰጥ ፤ ስለ ፡ ራስኽ ፡ ምን ፡ ትላለኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ርሱም ፦ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዳለ ፦ የጌታን ፡ መንገድ ፡ አቅኑ ፡ ብሎ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የሚጮኽ ፡ ሰው ፡ ድምፅ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 24-25 ፤ የተላኩትም ፡ ከፈሪሳውያን ፡ ነበሩና ፦ እንኪያስ ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይም ፡ ኤልያስ ፡ ወይም ፡ ነቢዩ ፡ ካይደለኽ ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታጠምቃለኽ ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ዮሐንስ ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ በውሃ ፡ አጠምቃለኹ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ የማታውቁት ፡ በመካከላችኹ ፡ ቆሟል ፤

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ እኔ ፡ የጫማውን ፡ ጠፍር ፡ ልፈታ ፡ የማይገባኝ ፥ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ የሚመጣው ፡ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ የሚከብር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ ዮሐንስ ፡ ያጠምቅበት ፡ በነበረው ፡ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ በቢታንያ ፡ በቤተ ፡ ራባ ፡ ኾነ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ በነገው ፡ ዮሐንስ ፡ ኢየሱስን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲመጣ ፡ አይቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እንሆ ፥ የዓለምን ፡ ኀጢአት ፡ የሚያስወግድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ በግ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፥ ከእኔም ፡ በፊት ፡ ነበርና ፥ ከእኔ ፡ ይልቅ ፡ የከበረ ፡ ኾኗል ፡ ብዬ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ያልኹት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ እኔም ፡ አላውቀውም ፡ ነበር ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለእስራኤል ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ በውሃ ፡ እያጠመቅኹ ፡ እኔ ፡ መጣኹ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ ዮሐንስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ። መንፈስ ፡ ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ኾኖ ፡ ሲወርድ ፡ አየኹ ፤ በርሱ ፡ ላይም ፡ ኖረ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 33 ፤ እኔም ፡ አላውቀውም ፡ ነበር ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በውሃ ፡ አጠምቅ ፡ ዘንድ ፡ የላከኝ ፡ ርሱ ፦ መንፈስ ፡ ሲወርድበትና ፡ ሲኖርበት ፡ የምታየው ፥ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚያጠምቅ ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ አለኝ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 34 ፤ እኔም ፡ አይቻለኹ ፡ ርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መስክሬያለኹ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 35 ፤ በነገው ፡ ደግሞ ፡ ዮሐንስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ኹለት ፡ ቆመው ፡ ነበር ፥

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 36 ፤ ኢየሱስም ፡ ሲኼድ ፡ ተመልክቶ ፦ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ በግ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 37 ፤ ኹለቱም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ሲናገር ፡ ሰምተው ፡ ኢየሱስን ፡ ተከተሉት ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 38 ፤ ኢየሱስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ሲከተሉትም ፡ አይቶ ፦ ምን ፡ ትፈልጋላችኹ ፧ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 39 ፤ እነርሱም ፦ ረቢ ፥ ወዴት ፡ ትኖራለኽ ፧ አሉት ፤ ትርጓሜው ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 40 ፤ መጥታችኹ ፡ እዩ ፡ አላቸው ። መጥተው ፡ የሚኖርበትን ፡ አዩ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ዋሉ ፤ ዐሥር ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 41 ፤ ከዮሐንስ ፡ ዘንድ ፡ ሰምተው ፡ ከተከተሉት ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱ ፡ የስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንድም ፡ እንድርያስ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 42 ፤ ርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የራሱን ፡ ወንድም ፡ ስምዖንን ፡ አገኘውና ፦ መሲሕን ፡ አግኝተናል ፡ አለው ፤ ትርጓሜውም ፡ ክርስቶስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 43 ፤ ወደ ፡ ኢየሱስም ፡ አመጣው ። ኢየሱስም ፡ ተመልክቶ ፦ አንተ ፡ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ነኽ ፤ አንተ ፡ ኬፋ ፡ ትባላለኽ ፡ አለው ፤ ትርጓሜው ፡ ጴጥሮስ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 44 ፤ በነገው ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ሊወጣ ፡ ወደደ ፥ ፊልጶስንም ፡ አገኘና ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 45 ፤ ፊልጶስም ፡ ከእንድርያስና ፡ ከጴጥሮስ ፡ ከተማ ፡ ከቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 46 ፤ ፊልጶስ ፡ ናትናኤልን ፡ አግኝቶ ፦ ሙሴ ፡ በሕግ ፡ ነቢያትም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የጻፉትን ፡ የዮሴፍን ፡ ልጅ ፡ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ አግኝተነዋል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 47 ፤ ናትናኤልም ፦ ከናዝሬት ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሊወጣ ፡ ይችላልን ፧ አለው ። ፊልጶስ ፦ መጥተኽ ፡ እይ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 48 ፤ ኢየሱስ ፡ ናትናኤልን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲመጣ ፡ አይቶ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፦ ተንኰል ፡ የሌለበት ፡ በእውነት ፡ የእስራኤል ፡ ሰው ፥ እንሆ ፥ አለ ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 49 ፤ ናትናኤልም ፦ ከወዴት ፡ ታውቀኛለኽ ፧ አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ፊልጶስ ፡ ሳይጠራኽ ፥ ከበለስ ፡ በታች ፡ ሳለኽ ፥ አየኹኽ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 50 ፤ ናትናኤልም ፡ መልሶ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፤ አንተ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ነኽ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 51 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ከበለስ ፡ በታች ፡ አየኹኽ ፡ ስላልኹኽ ፡ አመንኽን ፧ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ ታያለኽ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 1 ፡ 52 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ሰማይ ፡ ሲከፈት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መላእክት ፡ በሰው ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ሲወጡና ፡ ሲወርዱ ፡ ታያላችኹ ፡ አለው ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ በገሊላ ፡ ቃና ፡ ሰርግ ፡ ነበረ ፥ የኢየሱስም ፡ እናት ፡ በዚያ ፡ ነበረች ፤

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ ሰርጉ ፡ ታደሙ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ የወይን ፡ ጠጅም ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ የኢየሱስ ፡ እናት ፦ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እኮ ፡ የላቸውም ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ አለኝ ፧ ጊዜዬ ፡ ገና ፡ አልደረሰም ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እናቱም ፡ ለአገልጋዮቹ ፦ የሚላችኹን ፡ ሹሉ ፡ አድርጉ ፡ አለቻቸው ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ አይሁድም ፡ እንደሚያደርጉት ፡ የማንጻት ፡ ልማድ ፡ ስድስት ፡ የድንጋይ ፡ ጋኖች ፡ በዚያ ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፥ እያንዳንዳቸውም ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ እንስራ ፡ ይይዙ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፦ ጋኖቹን ፡ ውሃ ፡ ሙሏቸው ፡ አላቸው ፦ እስከ ፡ አፋቸውም ፡ ሙሏቸው ፡ አላቸው ። እስከ ፡ አፋቸውም ፡ ሞሏቸው ፦

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ ቀድታችኹ ፡ ለአሳዳሪው ፡ ስጡት ፡ አላቸው ፤ ሰጡትም ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ አሳዳሪውም ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ የኾነውን ፡ ውሃ ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ አላወቀም ፤ ውሃውን ፡ የቀዱት ፡ አገልጋዮች ፡ ግን ፡ ያውቁ ፡ ነበር ፤ አሳዳሪው ፡ ሙሽራውን ፡ ጠርቶ ፦

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ሰው ፡ ሹሉ ፡ አስቀድሞ ፡ መልካሙን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ያቀርባል ፥ ከሰከሩም ፡ በኋላ ፡ መናኛውን ፤ አንተስ ፡ መልካሙን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ አቈይተኻል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡ የምልክቶች ፡ መጠመሪያ ፡ በገሊላ ፡ ቃና ፡ አደረገ ፤ ክብሩንም ፡ ገለጠ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በርሱ ፡ አመኑ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ከእናቱና ፡ ከወንድሞቹ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ ወረደ ፥ በዚያም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኖሩ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ የአይሁድ ፡ ፋሲካም ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ፥ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በመቅደስም ፡ በሬዎችንና ፡ በጎችን ፡ ርግቦችንም ፡ የሚሸጡትን ፡ ገንዘብ ፡ ለዋጮችንም ፡ ተቀምጠው ፡ አገኘ ፤

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ የገመድም ፡ ጅራፍ ፡ አበጅቶ ፡ ሹሉን ፡ በጎችንም ፡ በሬዎችንም ፡ ከመቅደስ ፡ አወጣቸው ፥ የለዋጮችንም ፡ ገንዘብ ፡ አፈሰሰ ፡ ገበታዎቻቸውንም ፡ ገለበጠ ፥

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ርግብ ፡ ሻጪዎችንም ፦ ይህን ፡ ከዚህ ፡ ውሰዱ ፤ የአባቴን ፡ ቤት ፡ የንግድ ፡ ቤት ፡ አታድርጉት ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ የቤትኽ ፡ ቅናት ፡ ይበላኛል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ዐሰቡ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ አይሁድ ፡ መልሰው ፦ ይህን ፡ ስለምታደርግ ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ ታሳየናለኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ይህን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አፍርሱት ፥ በሦስት ፡ ቀንም ፡ አነሣዋለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ስለዚህ ፥ አይሁድ ፦ ይህ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ከአርባ ፡ ስድስት ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ ይሠራ ፡ ነበር ፥ አንተስ ፡ በሦስት ፡ ቀን ፡ ታነሣዋለኽን ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ሰውነቱ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ይል ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ ከሙታን ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ዐሰቡና ፥ መጽሐፍንና ፡ ኢየሱስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ አመኑ ።

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ በፋሲካ ፡ በዓልም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሳለ ፥ ያደረገውን ፡ ምልክት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በስሙ ፡ አመኑ ፤

ዮሐ. ፡ 2 ፡ 24-25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስ ፡ ሰዎችን ፡ ሹሉ ፡ ያውቅ ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ ሰውም ፡ ማንም ፡ ሊመሰክር ፡ አያስፈልገውም ፡ ነበርና ፥ አይተማመናቸውም ፡ ነበር ፤ ራሱ ፡ በሰው ፡ ያለውን ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ከፈሪሳውያንም ፡ ወገን ፡ የአይሁድ ፡ አለቃ ፡ የኾነ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤ ርሱም ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ መጥቶ ፦

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ መምህር ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከኾነ ፡ በቀር ፡ አንተ ፡ የምታደርጋቸውን ፡ እነዚህን ፡ ምልክቶች ፡ ሊያደርግ ፡ የሚችል ፡ የለምና ፡ መምህር ፡ ኾነኽ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መጣኽ ፡ እናውቃለን ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ ሰው ፡ ዳግመኛ ፡ ካልተወለደ ፡ በቀር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ሊያይ ፡ አይችልም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ኒቆዲሞስም ፦ ሰው ፡ ከሸመገለ ፡ በኋላ ፡ እንዴት ፡ ሊወለድ ፡ ይችላል ፧ ኹለተኛ ፡ ወደ ፡ እናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ገብቶ ፡ ይወለድ ፡ ዘንድ ፡ ይችላልን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ ሰው ፡ ከውሃና ፡ ከመንፈስ ፡ ካልተወለደ ፡ በቀር ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ሊገባ ፡ አይችልም ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ፥ ከመንፈስም ፡ የተወለደ ፡ መንፈስ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ዳግመኛ ፡ ልትወለዱ ፡ ያስፈልጋችኋል ፡ ስላልኹኽ ፡ አታድንቅ ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ነፋስ ፡ ወደሚወደው ፡ ይነፍሳል ፥ ድምፁንም ፡ ትሰማለኽ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ወዴትም ፡ እንዲኼድ ፡ አታውቅም ፤ ከመንፈስ ፡ የተወለደ ፡ ሹሉ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ኒቆዲሞስ ፡ መልሶ ፦ ይህ ፡ እንዴት ፡ ሊኾን ፡ ይችላል ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ አንተ ፡ የእስራኤል ፡ መምህር ፡ ስትኾን ፡ ይህን ፡ አታውቅምን ፧

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ የምናውቀውን ፡ እንናገራለን ፡ ያየነውንም ፡ እንመሰክራለን ፥ ምስክራችንንም ፡ አትቀበሉትም ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ስለ ፡ ምድራዊ ፡ ነገር ፡ በነገርኋችኹ ፡ ጊዜ ፡ ካላመናችኹ ፥ ስለ ፡ ሰማያዊ ፡ ነገር ፡ ብነግራችኹ ፡ እንዴት ፡ ታምናላችኹ ፧

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ከሰማይም ፡ ከወረደ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣ ፡ ማንም ፡ የለም ፥ ርሱም ፡ በሰማይ ፡ የሚኖረው ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 14-15 ፤ ሙሴም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ እባብን ፡ እንደ ፡ ሰቀለ ፡ እንዲሁ ፡ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሹሉ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዲኖረው ፡ እንጂ ፡ እንዳይጠፋ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ይሰቀል ፡ ይገባዋል ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሹሉ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዲኖረው ፡ እንጂ ፡ እንዳይጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድያ ፡ ልጁን ፡ እስኪሰጥ ፡ ድረስ ፡ ዓለሙን ፡ እንዲሁ ፡ ወዷልና ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ዓለም ፡ በልጁ ፡ እንዲድን ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በዓለም ፡ እንዲፈርድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ አልላከውምና ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ በርሱ ፡ በሚያምን ፡ አይፈረድበትም ፤ በማያምን ፡ ግን ፡ በአንዱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ስላላመነ ፡ አኹን ፡ ተፈርዶበታል ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ብርሃንም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ ሰዎችም ፡ ሥራቸው ፡ ክፉ ፡ ነበርና ፥ ከብርሃን ፡ ይልቅ ፡ ጨለማን ፡ ስለ ፡ ወደዱ ፡ ፍርዱ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ክፉ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ብርሃንን ፡ ይጠላልና ፥ ሥራውም ፡ እንዳይገለጥ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አይመጣም ፤

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ እውነትን ፡ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተደርጎ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ይመጣል ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደይሁዳ ፡ አገር ፡ መጣ ፥ በዚያም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፡ ያጠምቅ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ዮሐንስም ፡ ደግሞ ፡ በሳሌም ፡ አቅራቢያ ፡ በሄኖን ፡ በዚያ ፡ ብዙ ፡ ውሃ ፡ ነበርና ፥ ያጠምቅ ፡ ነበር ፥

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ እየመጡም ፡ ይጠመቁ ፡ ነበር ፤ ዮሐንስ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አልተጨመረም ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ስለዚህም ፡ በዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትና ፡ በአይሁድ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ማንጻት ፡ ክርክር ፡ ኾነ ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ወደ ፡ ዮሐንስም ፡ መጥተው ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ በዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ አንተም ፡ የመሰከርኽለት ፥ እንሆ ፥ ርሱ ፡ ያጠምቃል ፡ ኹሉም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጣሉ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ዮሐንስ ፡ መለሰ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ከሰማይ ፡ ካልተሰጠው ፡ ሰው ፡ አንዳች ፡ ሊቀበል ፡ አይችልም ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ እናንተ ፦ እኔ ፡ ክርስቶስ ፡ አይደለኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ከርሱ ፡ በፊት ፡ ተልኬያለኹ ፡ እንዳልኹ ፡ ራሳችኹ ፡ ትመሰክሩልኛላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ ሙሽራዪቱ ፡ ያለችው ፡ ርሱ ፡ ሙሽራ ፡ ነው ፤ ቆሞ ፡ የሚሰማው ፡ ሚዜው ፡ ግን ፡ በሙሽራው ፡ ድምፅ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ። እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ደስታዬ ፡ ተፈጸመ ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 30 ፤ ርሱ ፡ ሊልቅ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ ላንስ ፡ ያስፈልጋል ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 31 ፤ ከላይ ፡ የሚመጣው ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ነው ፤ ከምድር ፡ የሚኾነው ፡ የምድር ፡ ነው ፥ የምድሩንም ፡ ይናገራል ። ከሰማይ ፡ የሚመጣው ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 32 ፤ ያየውንና ፡ የሰማውንም ፡ ይህን ፡ ይመሰክራል ፥ ምስክሩንም ፡ የሚቀበለው ፡ የለም ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 33 ፤ ምስክሩን ፡ የተቀበለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አተመ ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 34 ፤ እግዚአብሔር ፡ የላከው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይናገራልና ፤ እግዚአብሔር ፡ መንፈሱን ፡ ሰፍሮ ፡ አይሰጥምና ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 35 ፤ አባት ፡ ልጁን ፡ ይወዳል ፡ ኹሉንም ፡ በእጁ ፡ ሰጥቶታል ።

ዮሐ. ፡ 3 ፡ 36 ፤ በልጁ ፡ የሚያምን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፤ በልጁ ፡ የማያምን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ይኖራል ፡ እንጂ ፡ ሕይወትን ፡ አያይም ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፦ ኢየሱስ ፡ ከዮሐንስ ፡ ይልቅ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ያደርጋል ፡ ያጠምቅማል ፡ ማለትን ፡ ፈሪሳውያን ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፡ ጌታ ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፥

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 2-3 ፤ ይሁዳን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ደግሞ ፡ ኼደ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንጂ ፡ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ አላጠመቀም ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ በሰማርያም ፡ ሊያልፍ ፡ ግድ ፡ ኾነበት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ያዕቆብ ፡ ለልጁ ፣ ለዮሴፍ ፡ በሰጠው ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ወደምትኾን ፥ ሲካር ፡ ወደምትባል ፡ የሰማርያ ፡ ከተማ ፡ መጣ ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በዚያም ፡ የያዕቆብ ፡ ጕድጓድ ፡ ነበረ ። ኢየሱስም ፡ መንገድ ፡ ከመኼድ ፡ ደክሞ ፡ በጕድጓድ ፡ አጠገብ ፡ እንዲህ ፡ ተቀመጠ ፤ ጊዜውም ፡ ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ከሰማርያ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ውሃ ፡ ልትቀዳ ፡ መጣች ። ኢየሱስም ፦ ውሃ ፡ አጠጪኝ ፡ አላት ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ምግብ ፡ ሊገዙ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ኼደው ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ ሳምራዊቲቱ ፦ አንተ ፡ የይሁዳ ፡ ሰው ፡ ስትኾን ፡ ሳምራዊት ፡ ሴት ፡ ከምኾን ፡ ከእኔ ፡ መጠጥ ፡ እንዴት ፡ ትለምናለኽ ፧ አለችው ፤ አይሁድ ፡ ከሳምራውያን ፡ ጋራ ፡ አይተባበሩም ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታና ፦ ውሃ ፡ አጠጪኝ ፡ የሚልሽ ፡ ማን ፡ መኾኑንስ ፡ ብታውቂ ፥ አንቺ ፡ ትለምኚው ፡ ነበርሽ ፡ የሕይወትም ፡ ውሃ ፡ ይሰጥሽ ፡ ነበር ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ሴቲቱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ መቅጃ ፡ የለኽም ፡ ጕድጓዱም ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ እንግዲህ ፡ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ከወዴት ፡ ታገኛለኽ ፧

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ በእውኑ ፡ አንተ ፡ ይህን ፡ ጕድጓድ ፡ ከሰጠን ፡ ከአባታችን ፡ ከያዕቆብ ፡ ትበልጣለኽን ፧ ራሱም ፡ ልጆቹም ፡ ከብቶቹም ፡ ከዚህ ፡ ጠጥተዋል ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ከዚህ ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣ ፡ ዅሉ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይጠማል ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ እኔ ፡ ከምሰጠው ፡ ውሃ ፡ የሚጠጣ ፡ ዅሉ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ አይጠማም ፥ እኔ ፡ የምሰጠው ፡ ውሃ ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚፈልቅ ፡ የውሃ ፡ ምንጭ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ሴቲቱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንዳልጠማ ፡ ውሃም ፡ ልቀዳ ፡ ወደዚህ ፡ እንዳልመጣ ፡ ይህን ፡ ውሃ ፡ ስጠኝ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ኢየሱስም ፦ ኺጂና ፡ ባልሽን ፡ ጠርተሽ ፡ ወደዚህ ፡ ነዪ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ሴቲቱ ፡ መልሳ ፦ ባል ፡ የለኝም ፡ አለችው ። ኢየሱስ ፦ ባል ፡ የለኝም ፡ በማለትሽ ፡ መልካም ፡ ተናገርሽ ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ዐምስት ፡ ባሎች ፡ ነበሩሽና ፥ አኹን ፡ ከአንቺ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ ባልሽ ፡ አይደለም ፤ በዚህስ ፡ እውነት ፡ ተናገርሽ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ሴቲቱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ነቢይ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ አያለኹ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ አባቶቻችን ፡ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ሰገዱ ፤ እናንተም ፦ ሰው ፡ ሊሰግድበት ፡ የሚገባው ፡ ስፍራ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ነው ፡ ትላላችኹ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላት ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ እመኚኝ ፥ በዚህ ፡ ተራራ ፡ ወይም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለአብ ፡ የማትሰግዱበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ እናንተስ ፡ ለማታውቁት ፡ ትሰግዳላችኹ ፤ እኛ ፡ መዳን ፡ ከአይሁድ ፡ ነውና ፥ ለምናውቀው ፡ እንሰግዳለን ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእውነት ፡ የሚሰግዱ ፡ ለአብ ፡ በመንፈስና ፡ በእውነት ፡ የሚሰግዱበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ፡ አኹንም ፡ ኾኗል ፤ አብ ፡ ሊሰግዱለት ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ይሻልና ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነው ፥ የሚሰግዱለትም ፡ በመንፈስና ፡ በእውነት ፡ ሊሰግዱለት ፡ ያስፈልጋቸዋል ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ሴቲቱ ፦ ክርስቶስ ፡ የሚባል ፡ መሲሕ ፡ እንዲመጣ ፡ ዐውቃለኹ ፤ ርሱ ፡ ሲመጣ ፡ ኹሉን ፡ ይነግረናል ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ኢየሱስ ፦ የምናገርሽ ፡ እኔ ፡ ርሱ ፡ ነኝ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ መጡና ፡ ከሴት ፡ ጋራ ፡ በመነጋገሩ ፡ ተደነቁ ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ምን ፡ ትፈልጊያለሽ ፧ ወይም ፦ ስለ ፡ ምን ፡ ትናገራታለኽ ፧ ያለ ፡ ማንም ፡ አልነበረም ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ ሴቲቱም ፡ እንስራዋን ፡ ትታ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ኼደች ፡ ለሰዎችም ፦

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ያደረግኹትን ፡ ኹሉ ፡ የነገረኝን ፡ ሰው ፡ ኑና ፡ እዩ ፤ እንጃ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ይኾንን ፧ አለች ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ከከተማ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ይህም ፡ ሲኾን ፡ ሳለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ብላ ፡ ብለው ፡ ለመኑት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 32 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ እናንተ ፡ የማታውቁት ፡ የምበላው ፡ መብል ፡ ለእኔ ፡ አለኝ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 33 ፤ ስለዚህ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ የሚበላው ፡ አንዳች ፡ ሰው ፡ አምጥቶለት ፡ ይኾንን ፧ ተባባሉ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የእኔስ ፡ መብል ፡ የላከኝን ፡ ፈቃድ ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሥራውንም ፡ እፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 35 ፤ እናንተ ፦ ገና ፡ አራት ፡ ወር ፡ ቀርቷል ፡ መከርም ፡ ይመጣል ፡ ትሉ ፡ የለምን ፧ እንሆ ፥ እላችኋለኹ ፥ ዐይናችኹን ፡ አንሡ ፡ አዝመራውም ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ነጣ ፡ ዕርሻውን ፡ ተመልከቱ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 36 ፤ የሚያጭድ ፡ ደመ ፡ ወዝን ፡ ይቀበላል ፥ የሚዘራና ፡ የሚያጭድም ፡ ዐብረው ፡ ደስ ፡ እንዲላቸው ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ፍሬን ፡ ይሰበስባል ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 37 ፤ አንዱ ፡ ይዘራል ፡ አንዱም ፡ ያጭዳል ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ በዚህ ፡ እውነት ፡ ኾኗልና ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 38 ፤ እኔም ፡ እናንተ ፡ ያልደከማችኹበትን ፡ ታጭዱ ፡ ዘንድ ፡ ሰደድኋችኹ ፤ ሌላዎች ፡ ደከሙ ፡ እናንተም ፡ በድካማቸው ፡ ገባችኹ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 39 ፤ ሴቲቱም ፦ ያደረግኹትን ፡ ኹሉ ፡ ነገረኝ ፡ ብላ ፡ ስለመሰከረችው ፡ ቃል ፡ ከዚያች ፡ ከተማ ፡ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ አመኑበት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 40 ፤ የሰማርያ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ እንዲኖር ፡ ለመኑት ፤ በዚያም ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ያኽል ፡ ኖረ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 41 ፤ ስለ ፡ ቃሉ ፡ ከፊተኞች ፡ ይልቅ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ፤

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 42 ፤ ሴቲቱንም ፦ አኹን ፡ የምናምን ፡ ስለ ፡ ቃልሽ ፡ አይደለም ፥ እኛ ፡ ራሳችን ፡ ሰምተነዋልና ፤ ርሱም ፡ በእውነት ፡ ክርስቶስ ፡ የዓለም ፡ መድኀኒት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ፡ ይሏት ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 43 ፤ ከኹለቱ ፡ ቀኖችም ፡ በኋላ ፡ ከዚያ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ኼደ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 44 ፤ ነቢይ ፡ በገዛ ፡ አገሩ ፡ እንዳይከበር ፡ ኢየሱስ ፡ ራሱ ፡ መስክሯልና ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 45 ፤ ወደ ፡ ገሊላም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ራሳቸው ፡ ደግሞ ፡ ለበዓል ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፥ በበዓል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያደረገውን ፡ ኹሉ ፡ ስላዩ ፡ ተቀበሉት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 46 ፤ ኢየሱስም ፡ ውሃውን ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ወዳደረገባት ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ቃና ፡ ዳግመኛ ፡ መጣ ። በቅፍርናሖምም ፡ ልጁ ፡ የታመመበት ፡ ከንጉሥ ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ ሹም ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 47 ፤ ርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ሰምቶ ፡ ልጁ ፡ ሊሞት ፡ ስለ ፡ አለው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ኼደ ፡ ወርዶም ፡ እንዲፈውስለት ፡ ለመነው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 48 ፤ ስለዚህም ፡ ኢየሱስ ፦ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ካላያችኹ ፡ ከቶ ፡ አታምኑም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 49 ፤ ሹሙም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ብላቴናዬ ፡ ሳይሞት ፡ ውረድ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 50 ፤ ኢየሱስም ፦ ኺድ ፤ ልጅኽ ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ አለው ። ሰውዬውም ፡ ኢየሱስ ፡ የነገረውን ፡ ቃል ፡ አምኖ ፡ ኼደ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 51 ፤ ርሱም ፡ ሲወርድ ፡ ሳለ ፡ ባሮቹ ፡ ተገናኙትና ፦ ብላቴናኽ ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ ብለው ፡ ነገሩት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 52 ፤ ርሱም ፡ በጎ ፡ የኾነበትን ፡ ሰዓት ፡ ጠየቃቸው ፤ እነርሱም ፦ ትናንት ፡ በሰባት ፡ ሰዓት ፡ ንዳዱ ፡ ለቀቀው ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 53 ፤ አባቱም ፥ ኢየሱስ ፦ ልጅኽ ፡ በሕይወት ፡ አለ ፡ ባለው ፡ በዚያ ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቀ ፤ ርሱም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ አመነ ።

ዮሐ. ፡ 4 ፡ 54 ፤ ይህም ፡ ደግሞ ፡ ኢየሱስ ፡ ከይሁዳ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ መጥቶ ፡ ያደረገው ፡ ኹለተኛ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የአይሁድ ፡ በዓል ፡ ነበረ ፥ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ በበጎች ፡ በር ፡ አጠገብ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ የምትባል ፡ አንዲት ፡ መጠመቂያ ፡ ነበረች ፤ ዐምስትም ፡ መመላለሻ ፡ ነበረባት ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ በእነዚህ ፡ ውስጥ ፡ የውሃውን ፡ መንቀሳቀስ ፡ እየጠበቁ ፡ በሽተኞችና ፡ ዕውሮች ፡ ዐንካሳዎችም ፡

ሰውነታቸውም ፡ የሰለለ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ይተኙ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ መጠመቂያዩቱ ፡ ወርዶ ፡ ውሃውን ፡ ያናውጥ ፡ ነበርና ፤ እንግዲህ ፡ ከውሃው ፡ መናወጥ ፡ በኋላ ፡ በመገቦመሪያ ፡ የገባ ፡ ከማናቸው ፡ ካለበት ፡ ደዌ ፡ ጤናማ ፡ ይኾን ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ በዚያም ፡ ከሠላሳ ፡ ስምንት ፡ ዓመት ፡ ገምሮ ፡ የታመመ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ተኝቶ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ እስከ ፡ አኹን ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዐውቆ ፦ ልትድን ፡ ትወዳለኽን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ድውዩም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ውሃው ፡ በተናወጠ ፡ ጊዜ ፡ በመጠመቂያዩቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚያኖረኝ ፡ ሰው ፡ የለኝም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ ስመጣ ፡ ሳለኹ ፡ ሌላው ፡ ቀድሞኝ ፡ ይወርዳል ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ኢየሱስ ፦ ተነሣና ፡ ዐልጋኽን ፡ ተሸክመኽ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ወዲያውም ፡ ሰውዬው ፡ ዳነ ፡ ዐልጋውንም ፡ ተሸክሞ ፡ ኼደ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ያም ፡ ቀን ፡ ሰንበት ፡ ነበረ ። ስለዚህ ፡ አይሁድ ፡ የተፈወሰውን ፡ ሰው ፦ ሰንበት ፡ ነው ፥ ዐልጋኽንም ፡ ልትሸከም ፡ አልተፈቀደልኽም ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ያዳነኝ ፡ ያ ፡ ሰው ፦ ዐልጋኽን ፡ ተሸክመኽ ፡ ኺድ ፡ አለኝ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እነርሱም ፦ ዐልጋኽን ፡ ተሸክመኽ ፡ ኺድ ፡ ያለኽ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ሕዝብ ፡ ሰለ ፡ ነበሩ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈቀቅ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፥ የተፈወሰው ፡ ሰው ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላወቀም ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ በመቅደስ ፡ አገኘውና ፦ እንሆ ፥ ድነኻል ፤ ከዚህ ፡ የሚብስ ፡ እንዳይደርስብኽ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ኀጢአት ፡ አትሥራ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ሰውዬው ፡ ኼዶ ፡ ያዳነው ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለአይሁድ ፡ ነገረ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ስለዚህም ፡ በሰንበት ፡ ይህን ፡ ስላደረገ ፡ አይሁድ ፡ ኢየሱስን ፡ ያሳድዱት ፡ ነበር ፡ ሊገድሉትም ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፦ አባቴ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ይሠራል ፡ እኔም ፡ ደግሞ ፡ እሠራለኹ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ ሰንበትን ፡ ስለ ፡ ኻረ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ደግሞ ፡ ራሱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አስተካክሎ ፦ እግዚአብሔር ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ አለ ፥ ስለዚህ ፡ አይሁድ ፡ ሊገድሉት ፡ አብዝተው ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ኢየሱስ ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ አብ ፡ ሊያደርግ ፡ ያየውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ወልድ ፡ ከራሱ ፡ ሊያደርግ ፡ ምንም ፡ አይችልም ፤ ያ ፡ የሚያደርገውን ፡ ኹሉ ፡ ወልድ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ እንዲሁ ፡ ያደርጋልና ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ አብ ፡ ወልድን ፡ ይወዳልና ፥ የሚያደርገውንም ፡ ኹሉ ፡ ያሳየዋል ፤ እናንተም ፡ ትደነቁ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ሥራ ፡ ያሳየዋል ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ አብ ፡ ሙታንን ፡ እንደሚያነሣ ፡ ሕይወትም ፡ እንደሚሰጣቸው ፥ እንዲሁ ፡ ወልድ ፡ ደግሞ ፡ ለሚወዳቸው ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣቸዋል ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 22-23 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ አብን ፡ እንደሚያከብሩት ፡ ወልድን ፡ ያከብሩት ፡ ዘንድ ፥ ፍርድን ፡ ኹሉ ፡ ለወልድ ፡ ሰጠው ፡ እንጂ ፡ አብ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አይፈርድም ። ወልድን ፡ የማያከብር ፡ የላከውን ፡ አብን ፡ አያከብርም ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ቃሌን ፡ የሚሰማ ፡ የላከኝንም ፡ የሚያምን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፥ ከሞትም ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ተሻገረ ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ አይመጣም ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ሙታን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ድምፅ ፡ የሚሰሙበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፡ ርሱም ፡ አኹን ፡ ነው ፤ የሚሰሙትም ፡ በሕይወት ፡ ይኖራሉ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ አብ ፡ በራሱ ፡ ሕይወት ፡ እንዳለው ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ለወልድ ፡ በራሱ ፡ ሕይወት ፡ እንዲኖረው ፡ ሰጥቶታልና ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ የሰው ፡ ልጅም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 28-29 ፤ በመቃብር ፡ ያሉቱ ፡ ኹሉ ፡ ድምፁን ፡ የሚሰሙበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፤ መልካምም ፡ ያደረጉ ፡ ለሕይወት ፡ ትንሣኤ ፡ ክፉም ፡ ያደረጉ ፡ ለፍርድ ፡ ትንሣኤ ፡ ይወጣሉና ፡ በዚህ ፡ አታድንቁ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ እኔ ፡ ከራሴ ፡ አንዳች ፡ ላደርግ ፡ አይቻለኝም ፤ እንደ ፡ ሰማኹ ፡ እፈርዳለኹ ፡ ፍርዴም ፡ ቅን ፡ ነው ፥ የላከኝን ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ ፈቃዴን ፡ አልሻምና ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ እኔ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ስለ ፡ ራሴ ፡ ብመሰክር ፡ ምስክሬ ፡ እውነት ፡ አይደለም ፤

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚመሰክር ፡ ሌላ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚመሰክረው ፡ ምስክር ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቃለኹ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ እናንተ ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ ልካችኋል ፡ ርሱም ፡ ለእውነት ፡ መስክሯል ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 34 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ምስክር ፡ አልቀበልም ፥ እናንተ ፡ እንድትድኑ ፡ ይህን ፡ እላለኹ ፡ እንጂ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 35 ፤ ርሱ ፡ የሚነድና ፡ የሚያበራ ፡ መብራት ፡ ነበረ ፥ እናንተም ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ በብርሃኑ ፡ ደስ ፡ ሊላችኹ ፡ ወደዳችኹ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 36 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከዮሐንስ ፡ ምስክር ፡ የሚበልጥ ፡ ምስክር ፡ አለኝ ፤ አብ ፡ ልፈጽመው ፡ የሰጠኝ ፡ ሥራ ፥ ይህ ፡ የማደርገው ፡ ሥራ ፥ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ይመሰክራልና ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 37 ፤ የላከኝ ፡ አብም ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ መስክሯል ። ድምፁን ፡ ከቶ ፡ አልሰማችኹም ፥ መልኩንም ፡ አላያችኹም ፤

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 38 ፤ ርሱም ፡ የላከውን ፡ እናንተ ፡ አታምኑምና ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የሚኖር ፡ ቃሉ ፡ የላችኹም ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 39 ፤ እናንተ ፡ በመጻሕፍት ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችኹ ፡ ይመስላችኋልና ፥ እነርሱን ፡ ትመረምራላችኹ ፤ እነርሱም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ የሚመሰክሩ ፡ ናቸው ፤

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 40 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕይወት ፡ እንዲኾንላችኹ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ልትመጡ ፡ አትወዱም ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 41-42 ፤ ከሰው ፡ ክብርን ፡ አልቀበልም ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በራሳችኹ ፡ እንደ ፡

ሌላችኹ ፡ ዐውቃችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 43 ፤ እኔ ፡ በአባቴ ፡ ስም ፡ መጥቻለኹ ፡ አልተቀበላችኹኝምም ፤ ሌላው ፡ በራሱ ፡ ስም ፡ ቢመጣ ፡ ርሱን ፡ ትቀበሉታላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 44 ፤ እናንተ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ክብር ፡ የምትቀባበሉ ፡ ከአንዱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ክብር ፡ የማትፈልጉ ፥ እንዴት ፡ ልታምኑ ፡ ትችላላችኹ ፧

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 45 ፤ እኔ ፡ በአብ ፡ ዘንድ ፡ የምከሳችኹ ፡ አይምሰላችኹ ፤ የሚከሳችኹ ፡ አለ ፤ ርሱም ፡ ተስፋ ፡ የምታደርጉት ፡ ሙሴ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 46 ፤ ሙሴንስ ፡ ብታምኑት ፡ እኔን ፡ ባመናችኹ ፡ ነበር ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ጽፏልና ።

ዮሐ. ፡ 5 ፡ 47 ፤ መጻሕፍትን ፡ ካላመናችኹ ፡ ግን ፡ ቃሌን ፡ እንዴት ፡ ታምናላችኹ ፧

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደገሊላ ፡ ባሕር ፡ ማዶ ፡ ተሻገረ ፤ ርሱም ፡ የጥብርያዶስ ፡ ባሕር ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ በበሽተኞችም ፡ ያደረገውን ፡ ምልክቶች ፡ ስላዩ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ተከተሉት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ወጣና ፡ በዚያ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ የአይሁድ ፡ በዓልም ፡ ፋሲካ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ ዐይኖቹን ፡ አንሥቶ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲመጣ ፡ አየና ፡ ፊልጶስን ፦ እነዚህ ፡ እንዲበሉ ፡ እንጀራ ፡ ከወዴት ፡ እንገዛለን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ራሱ ፡ ሊያደርግ ፡ ያለውን ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፥ ሊፈትነው ፡ ይህን ፡ ተናገረ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ፊልጶስ ፦ እያንዳንዳቸው ፡ ትንሽ ፡ ትንሽ ፡ እንኳ ፡ እንዲቀበሉ ፡ የኹለት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ እንጀራ ፡ አይበቃቸውም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፡ የስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ወንድም ፡ እንድርያስ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ዐምስት ፡ የገብስ ፡ እንጀራና ፡ ኹለት ፡ ዓሣ ፡ የያዘ ፡ ብላቴና ፡ በዚህ ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነዚህን ፡ ለሚያኽሉ ፡ ሰዎች ፡ ይህ ፡ ምን ፡ ይኾናል ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፦ ሰዎቹን ፡ እንዲቀመጡ ፡ አድርጉ ፡ አለ ። በዚያም ፡ ስፍራ ፡ ብዙ ፡ ሣር ፡ ነበረበት ። ወንዶችም ፡ ተቀመጡ ፡ ቍጥራቸውም ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽል ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ እንጀራውን ፡ ያዘ ፥ አመስግኖም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሰጠ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለተቀመጡት ፡ ሰዎች ፡ ሰጧቸው ፡ እንዲሁም ፡ ከዓሣው ፡ በፈለጉት ፡ መጠን ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ከጠገቡም ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፦ አንድ ፡ ስንኳ ፡ እንዳይጠፋ ፡ የተረፈውን ፡ ቍርስራሽ ፡ አከማቹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፡ አከማቹ ፥ ከበሉትም ፡ ከዐምስቱ ፡ የገብስ ፡ እንጀራ ፡ የተረፈውን ፡ ቍርስራሽ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መሶብ ፡ ሞሉ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ ሰዎቹ ፡ ኢየሱስ ፡ ያደረገውን ፡ ምልክት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ በእውነት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የሚመጣው ፡ ነቢይ ፡ ነው ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ኢየሱስ ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡ ሊመጡና ፡ ሊነጥቁት ፡ እንዳላቸው ፡ ዐውቆ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ብቻውን ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ወረዱ ፥

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ በታንኳም ፡ ገብተው ፡ በባሕር ፡ ማዶ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ ይመጡ ፡ ነበር ። አኹንም ፡ ጨልሞ ፡ ነበር ፤ ኢየሱስም ፡ ገና ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ አልመጣም ፡ ነበር ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ብርቱ ፡ ነፋስም ፡ ስለ ፡ ነፈሰ ፡ ባሕሩ ፡ ተናወጠ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ኻያ ፡ ዐምስት ፡ ወይም ፡ ሠላሳ ፡ ምዕራፍ ፡ ከቀዘፉ ፡ በኋላም ፥ ኢየሱስ ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ እየኼደ ፡ ወደ ፡ ታንኳዩቱ ፡ ሲቀርብ ፡ አይተው ፡ ፈሩ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ እኔ ፡ ነኝ ፤ አትፍሩ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ በታንኳዩቱ ፡ ሊቀበሉት ፡ ወደዱ ፤ ወዲያውም ፡ ታንኳዩቱ ፡ ወደሚኼዱበት ፡ ምድር ፡ ደረሰች ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ በነገው ፡ በባሕር ፡ ማዶ ፡ ቆመው ፡ የነበሩ ፡ ሕዝቡ ፡ ከአንዲት ፡ ጀልባ ፡ በቀር ፡ በዚያ ፡ ሌላ ፡ ጀልባ ፡ እንዳልነበረች ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ለብቻቸው ፡ እንደ ፡ ኼዱ ፡ እንጂ ፡ ኢየሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ታንኳዩቱ ፡ እንዳልገባ ፡ አዩ ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሌላዎች ፡ ጀልባዎች ፡ ጌታ ፡ የባረከውን ፡ እንጀራ ፡ ወደበሉበት ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ከጥብርያዶስ ፡ መጡ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ሕዝቡም ፡ ኢየሱስ ፡ ወይም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በዚያ ፡ እንዳልነበሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ራሳቸው ፡ በጀልባዎቹ ፡ ገብተው ፡ ኢየሱስን ፡ እየፈለጉ ፡ ወደ ፡ ቅፍርናሖም ፡ መጡ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 25 ፤ በባሕር ፡ ማዶም ፡ ሲያገኙት ። መምህር ፡ ሆይ ፥ ወደዚህ ፡ መቼ ፡ መጣኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 26 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የምትፈልጉኝ ፡ እንጀራን ፡ ስለ ፡ በላችኹና ፡ ስለ ፡ ጠገባችኹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ምልክቶችን ፡ ስላያችኹ ፡ አይደለም ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 27 ፤ ለሚጠፋ ፡ መብል ፡ አትሥሩ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ለሚኖር ፡ መብል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ለሚሰጣችኹ ፡ ሥሩ ፤ ርሱን ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዐትሞታልና ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 28 ፤ እንግዲህ ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ እንድንሠራ ፡ ምን ፡ እናድርግ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 29 ፤ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፦ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ ርሱ ፡ በላከው ፡ እንድታምኑ ፡ ነው ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 30 ፤ እንግዲህ ፦ እንኪያ ፡ አይተን ፡ እንድናምንኽ ፡ አንተ ፡ ምን ፡ ምልክት ፡ ታደርጋለኽ ፧ ምንስ ፡ ትሠራለኽ ፧

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 31 ፤ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ከሰማይ ፡ እንጀራ ፡ ሰጣቸው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ አባቶቻችን ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መና ፡ በሉ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 32 ፤ ኢየሱስም ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ እውነተኛ ፡ እንጀራ ፡ ከሰማይ ፡ የሚሰጣችኹ ፡ አባቴ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰማይ ፡ እንጀራ ፡ የሰጣችኹ ፡ ሙሴ ፡ አይደለም ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 33 ፤ የእግዚአብሔር ፡ እንጀራ ፡ ከሰማይ ፡ የሚወርድ ፡ ለዓለምም ፡ ሕይወትን ፡ የሚሰጥ ፡ ነውና ፥ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 34 ፤ ስለዚህ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ እንጀራ ፡ ዘወትር ፡ ስጠን ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ የሕይወት ፡ እንጀራ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ወደ ፡ እኔ ፡ የሚመጣ ፡ ከቶ ፡ አይራብም ፡ በእኔ ፡ የሚያምንም ፡ ዅልጊዜ ፡ ከቶ ፡ አይጠማም ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 36 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አይታችኹኝ ፡ እንዳላመናችኹ ፡ አልኋችኹ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 37 ፤ አብ ፡ የሚሰጠኝ ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣል ፥ ወደ ፡ እኔም ፡ የሚመጣውን ፡ ከቶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አላወጣውም ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 38 ፤ ፈቃዴን ፡ ለማድረግ ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፡ የላከኝን ፡ ፈቃድ ፡ ለማድረግ ፡ ከሰማይ ፡ ወርጃለኹና ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 39 ፤ ከሰጠኝም ፡ ዅሉ ፡ አንድን ፡ ስንኳ ፡ እንዳላጠፋ ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ እንዳስነሣው ፡ እንጂ ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ፈቃድ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 40 ፤ ልጅንም ፡ አይቶ ፡ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ዅሉ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እንዲያገኝ ፡ የአባቴ ፡ ፈቃድ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ እኔም ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ አስነሣዋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 41 ፤ እንግዲህ ፡ አይሁድ ፦ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ እንጀራ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አንጐራጐሩና ፦

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 42 ፤ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ የምናውቃቸው ፡ ይህ ፡ የዮሴፍ ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ አይደለምን ፧ እንግዲህ ፦ ከሰማይ ፡ ወርጃለኹ ፡ እንዴት ፡ ይላል ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 43 ፤ ኢየሱስ ፡ መለሰ ፡ አላቸውም ፦ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አታንጐራጉሩ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 44 ፤ የላከኝ ፡ አብ ፡ ከሳበው ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ሊመጣ ፡ የሚችል ፡ የለም ፥ እኔም ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ አስነሣዋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 45 ፤ ዅሉም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተማሩ ፡ ይኾናሉ ፡ ተብሎ ፡ በነቢያት ፡ ተጽፏል ፤ እንግዲህ ፡ ከአብ ፡ የሰማ ፡ የተማረም ፡ ዅሉ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣል ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 46 ፤ አብን ፡ ያየ ፡ ማንም ፡ የለም ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከኾነ ፡ በቀር ፥ ርሱ ፡ አብን ፡ አይቷል ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 47 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፡ በእኔ ፡ የሚያምን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 48 ፤ የሕይወት ፡ እንጀራ ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 49 ፤ አባቶቻችኹ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መና ፡ በሉ ፥ ሞቱም ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 50 ፤ ሰው ፡ ከርሱ ፡ በልቶ ፡ እንዳይሞት ፡ ከሰማይ ፡ አኹን ፡ የወረደ ፡ እንጀራ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 51 ፤ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ ሕያው ፡ እንጀራ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ሰው ፡ ከዚህ ፡ እንጀራ ፡ ቢበላ ፡ ለዘለዓለም ፡

ይኖራል ፤ እኔም ፡ ስለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የምሰጠው ፡ እንጀራ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 52 ፤ እንግዲህ ፡ አይሁድ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ሥጋውን ፡ ልንበላ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧ ብለው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከራከሩ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 53 ፤ ስለዚህ ፥ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሥጋ ፡ ካልበላችኹ ፡ ደሙንም ፡ ካልጠጣችኹ ፡ በራሳችኹ ፡ ሕይወት ፡ የላችኹም ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 54 ፤ ሥጋዬን ፡ የሚበላ ፡ ደሜንም ፡ የሚጠጣ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፥ እኔም ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ አስነሣዋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 55 ፤ ሥጋዬ ፡ እውነተኛ ፡ መብል ፡ ደሜም ፡ እውነተኛ ፡ መጠጥ ፡ ነውና ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 56 ፤ ሥጋዬን ፡ የሚበላ ፡ ደሜንም ፡ የሚጠጣ ፡ በእኔ ፡ ይኖራል ፡ እኔም ፡ በርሱ ፡ እኖራለኹ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 57 ፤ ሕያው ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እኔም ፡ ከአብ ፡ የተነሣ ፡ ሕያው ፡ እንደምኾን ፥ እንዲሁ ፡ የሚበላኝ ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ የተነሣ ፡ ሕያው ፡ ይኾናል ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 58 ፤ ከሰማይ ፡ የወረደ ፡ እንጀራ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ አባቶቻችኹ ፡ መና ፡ በልተው ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ አይደለም ፤ ይህን ፡ እንጀራ ፡ የሚበላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 59 ፤ በቅፍርናሖም ፡ ሲያስተምር ፡ ይህን ፡ በምኩራብ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 60 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ብዙዎች ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ ይህ ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ንግግር ፡ ነው ፤ ማን ፡ ሊሰማው ፡ ይችላል ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 61 ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለዚህ ፡ እንዳንጐራጐሩ ፡ በልቡ ፡ ዐውቆ ፡ አላቸው ፦ ይህ ፡ ያሰናክላችኋልን ፧

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 62 ፤ እንግዲህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደነበረበት ፡ ሲወጣ ፡ ብታዩ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ፧

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 63 ፤ ሕይወትን ፡ የሚሰጥ ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ ሥጋ ፡ ምንም ፡ አይጠቅምም ፤ እኔ ፡ የነገርኋችኹ ፡ ቃል ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡ ሕይወትም ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 64 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ የማያምኑ ፡ አሉ ። ኢየሱስ ፡ የማያምኑት ፡ እነማን ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጠውም ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከመገመሪያ ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 65 ፤ ደግሞ ፦ ስለዚህ ፡ አልኋችኹ ፥ ከአብ ፡ የተሰጠው ፡ ካልኾነ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ሊመጣ ፡ የሚችል ፡ የለም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 66 ፤ ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ብዙዎች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመለሱ ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አልኼዱም ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 67 ፤ ኢየሱስም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ልትኼዱ ፡ ትወዳላችኹን ፧ አለ ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 68 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ማን ፡ እንኼዳለን ፧ አንተ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ቃል ፡ አለኽ ፤

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 69 ፤ እኛስ ፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ አምነናል ፡ ዐውቀናልም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 70 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ እናንተን ፡ ዐሥራ ፡ ኹለታችኹን ፡ የመረጥኋችኹ ፡ አይደለምን ፧ ከእናንተም ፡ አንዱ ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ዮሐ. ፡ 6 ፡ 71 ፤ ስለስምዖንም ፡ ልጅ ፡ ስለአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ፡ ተናገረ ፤ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ የኾነ ፡ ርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ አለውና ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ አይሁድ ፡ ሊገድሉት ፡ ይፈልጉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ በይሁዳ ፡ ሊመላለስ ፡ አይወድም ፡ ነበርና ፥ በገሊላ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የአይሁድም ፡ የዳስ ፡ በዓል ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ እንግዲህ ፡ ወንድሞቹ ፦ ደቀ ፡ መዛሙርትኽ ፡ ደግሞ ፡ የምታደርገውን ፡ ሥራ ፡ እንዲያዩ ፡ ከዚህ ፡ ተነሣና ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ኺድ ፤

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ ራሱ ፡ ሊገለጥ ፡ እየፈለገ ፡ በስውር ፡ የሚሠራ ፡ የለምና ። እነዚህን ፡ ብታደርግ ፥ ራስኽን ፡ ለዓለም ፡ ግለጥ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ወንድሞቹ ፡ ስንኳ ፡ አላመኑበትም ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ጊዜዬ ፡ ገና ፡ አልደረሰም ፥ ጊዜያችኹ ፡ ግን ፡ ዘወትር ፡ የተመቸ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ዓለም ፡ እናንተን ፡ ሊጠላ ፡ አይቻለውም ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ክፉ ፡ መኾኑን ፡ እመሰክርበታለኹና ፡ እኔን ፡ ይጠላኛል ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ወደዚህ ፡ በዓል ፡ ውጡ ፤ እኔስ ፡ ጊዜዬ ፡ ገና ፡ ስላልተፈጸመ ፡ ወደዚህ ፡ በዓል ፡ ገና ፡ አልወጣም ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ይህንም ፡ አላቸውና ፡ በገሊላ ፡ ቀረ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ወንድሞቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ በዓሉ ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በግልጥ ፡ ሳይኾን ፡ ተሰውሮ ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ አይሁድም ፦ ርሱ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ እያሉ ፡ በበዓሉ ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ በሕዝብም ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ብዙ ፡ ማንጐራጐር ፡ ነበረ ፤ አንዳንዱም ፦ ደግ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ሌላዎች ፡ ግን ፦ አይደለም ፥ ሕዝቡን ፡ ግን ፡ ያስታል ፡ ይሉ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ማንም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በግልጥ ፡ አይናገርም ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ አኹንም ፡ በበዓሉ ፡ እኩሌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ወጥቶ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ አይሁድም ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ሳይማር ፡ መጻሕፍትን ፡ እንዴት ፡ ያውቃል ፧ ብለው ፡ ይደነቁ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ኢየሱስ ፡ መለሰ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ትምህርቴስ ፡ ከላከኝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከእኔ ፡ አይደለም ፤

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ ፈቃዱን ፡ ሊያደርግ ፡ የሚወድ ፡ ቢኖር ፥ ርሱ ፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ እኔ ፡ ከራሴ ፡ የምናገር ፡ ብኾን ፡ ያውቃል ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 18 ፤ ከራሱ ፡ የሚናገር ፡ የራሱን ፡ ክብር ፡ ይፈልጋል ፤ የላከውን ፡ ክብር ፡ የሚፈልግ ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፥ በርሱም ፡ ዐመፃ ፡ የለበትም ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ሙሴ ፡ ሕግን ፡ አልሰጣችኹምን ፧ ከእናንተ ፡ ግን ፡ ሕግን ፡ የሚያደርግ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ። ልትገድሉኝ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈልጋላችኹ ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ ሕዝቡ ፡ መለሱና ፦ ጋኔን ፡ አለብኽ ፤ ማን ፡ ሊገድልኽ ፡ ይፈልጋል ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ ኢየሱስ ፡ መለሰ ፡ አላቸውም ፦ አንድ ፡ ሥራ ፡ አደረግኹ ፡ ኹላችኹም ፡ ታደንቃላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፥ ሙሴ ፡ መገረዝን ፡ ሰጣችኹ ፤ ከአባቶችም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሙሴ ፡ አይደለም ፤ በሰንበትም ፡ ሰውን ፡ ትገርዛላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ የሙሴ ፡ ሕግ ፡ እንዳይሻር ፡ ሰው ፡ በሰንበት ፡ መገረዝን ፡ የሚቀበል ፡ ከኾነስ ፡ ሰውን ፡ ኹለንተናውን ፡ በሰንበት ፡ ጤናማ ፡ ስላደረግኹ ፡ ትቈጡኛላችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ፍረዱ ፡ እንጂ ፥ በመልክ ፡ አትፍረዱ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ እንግዲህ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ሰዎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ ሊገድሉት ፡ የሚፈልጉት ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ እንሆም ፥ በግልጥ ፡ ይናገራል ፥ አንዳችም ፡ አይሉትም ። አለቃዎቹ ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ በእውነት ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእውነት ፡ ዐወቁን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቀናል ፤ ክርስቶስ ፡ ሲመጣ ፡ ግን ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማንም ፡ አያውቅም ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ እንግዲህ ፡ ኢየሱስ ፡ በመቅደስ ፡ ሲያስተምር ፦ እኔንም ፡ ታውቁኛላችኹ ፡ ከወዴትም ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቃላችኹ ፤ እኔም ፡ በራሴ ፡ አልመጣኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ የማታውቁት ፡ የላከኝ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ነኝ ፡ ርሱም ፡ ልኮኛልና ፥ ዐውቀዋለኹ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ ሊይዙት ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጊዜው ፡ ገና ፡ ስላልደረሰ ፡ ማንም ፡ እጁን ፡ አልጫነበትም ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 31 ፤ ከሕዝቡ ፡ ግን ፡ ብዙዎች ፡ አመኑበትና ፦ ክርስቶስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ካደረጋቸው ፡ ምልክቶች ፡ ይልቅ ፡ ያደርጋልን ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 32 ፤ ፈሪሳውያንም ፡ ሕዝቡ ፡ ሰለ ፡ ርሱ ፡ እንደዚህ ፡ ሲያንሾራጕሩ ፡ ሰሙ ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ፈሪሳውያም ፡ ሊይዙት ፡ ሎሌዎችን ፡ ላኩ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ ኢየሱስም ፦ ገና ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እቈያለኹ ፡ ወደላከኝም ፡ እኼዳለኹ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ ትፈልጉኛላችኹ ፡ አታገኙኝምም ፤ እኔም ፡ ወዳለኹበት ፡ እናንተ ፡ ልትመጡ ፡ አትችሉም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ እንግዲህ ፡ አይሁድ ፦ እኛ ፡ እንዳናገኘው ፡ ይህ ፡ ወዴት ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፧ በግሪክ ፡

ሰዎች ፡ መካከል ፡ ተበትነው ፡ ወደሚኖሩት ፡ ሊኼድና ፡ የግሪክን ፡ ሰዎች ፡ ሊያስተምር ፡ አለውን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ ርሱ ፦ ትፈልጉኛላችኹ ፡ አታገኙኝምም ፡ እኔም ፡ ወዳለኹበት ፡ እናንተ ፡ ልትመጡ ፡ አትችሉም ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ቃል ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብለው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ ከበዓሉም ፡ በታላቁ ፡ በኺለኛው ፡ ቀን ፡ ኢየሱስ ፡ ቆሞ ፦ ማንም ፡ የተጠማ ፡ ቢኖር ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ይምጣና ፡ ይጠጣ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ በእኔ ፡ የሚያምን ፡ መጽሐፍ ፡ እንዳለ ፥ የሕይወት ፡ ውሃ ፡ ወንዝ ፡ ከሆዱ ፡ ይፈልቃል ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 39 ፤ ይህን ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ የሚያምኑ ፡ ሊቀበሉት ፡ ስላላቸው ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ተናገረ ፤ ኢየሱስ ፡ ገና ፡ ስላልከበረ ፥ መንፈስ ፡ ገና ፡ አልወረደም ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 40 ፤ ስለዚህ ፥ ከሕዝቡ ፡ ዐያሌ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሲሰሙ ፦ ይህ ፡ በእውነት ፡ ነቢዩ ፡ ነው ፡ አሉ ፤

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 41 ፤ ሌላዎች ፦ ይህ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ሌላዎች ፡ ግን ፦ ክርስቶስ ፡ በእውኑ ፡ ከገሊላ ፡ ይመጣልን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 42 ፤ ክርስቶስ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ዳዊትም ፡ ከነበረባት ፡ መንደር ፡ ከቤተ ፡ ልሔም ፡ እንዲመጣ ፡ መጽሐፍ ፡ አላለምን ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 43 ፤ እንግዲህ ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ መለያየት ፡ ኾነ ፤

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 44 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሊይዙት ፡ ወደዱ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እጁን ፡ ማንም ፡ አልጫነበትም ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 45 ፤ ሎሌዎቹም ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ወደ ፡ ፈሪሳውያን ፡ መጡ ፤ እነዚያም ፦ ያላመጣችኹት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧ አሏቸው ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 46 ፤ ሎሌዎቹ ፦ እንደዚህ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ እንዲሁ ፡ ከቶ ፡ አልተናገረም ፡ ብለው ፡ መለሱ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 47 ፤ እንግዲህ ፡ ፈሪሳውያን ፦ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ሳታችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 48 ፤ ከአለቃዎች ፡ ወይስ ፡ ከፈሪሳውያን ፡ በርሱ ፡ ያመነ ፡ አለን ፧

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 49 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕግን ፡ የማያውቀው ፡ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ርጉም ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መለሱላቸው ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 50 ፤ ከነርሱ ፡ አንዱ ፡ በሌሊት ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥቶ ፡ የነበረ ፡ ኒቆዲሞስ ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 51 ፤ ሕጋችን ፡ አስቀድሞ ፡ ከርሱ ፡ ሳይሰማ ፡ ምንስ ፡ እንዳደረገ ፡ ሳያውቅ ፡ በሰው ፡ ይፈርዳልን ፧ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 52 ፤ እነርሱም ፡ መለሱና ፦ አንተም ፡ ደግሞ ፡ ከገሊላ ፡ ነኽን ፧ ነቢይ ፡ ከገሊላ ፡ እንዳይነሣ ፡ መርምርና ፡ እይ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 7 ፡ 53 ፤ እያንዳንዱም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ኼደ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ኢ.የሱስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ኼደ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ማለዳም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ደረሰ ፥ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ። ተቀምጦም ፡ ያስተምራቸው ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ጻፊዎችና ፡ ፈሪሳውያንም ፡ በምንዝር ፡ የተያዘችን ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አመጡ ፡ በመካከልም ፡ ርሱዋን ፡ አቁመው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ መምህር ፡ ሆይ ፥ ይህች ፡ ሴት ፡ ስታመነዝር ፡ ተገኝታ ፡ ተያዘች ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ሙሴም ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ እንዲወገሩ ፡ በሕግ ፡ አዘዘን ፤ አንተስ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ምን ፡ ትላለኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ የሚከሱበትንም ፡ እንዲያገኙ ፡ ሊፈትኑት ፡ ይህን ፡ አሉ ። ኢ.የሱስ ፡ ግን ፡ ጐንበስ ፡ ብሎ ፡ በጣቱ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጻፈ ፤

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ መላልሰው ፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ቀና ፡ ብሎ ፦ ከእናንተ ፡ ኀጢአት ፡ የሌለበት ፡ አስቀድሞ ፡ በድንጋይ ፡ ይውገራት ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፡ ጐንበስ ፡ ብሎ ፡ በጣቱ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ጻፈ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ ይህን ፡ ሲሰሙ ፡ ኅሊናቸው ፡ ወቀሣቸውና ፡ ከሽማግሌዎች ፡ ዠምረው ፡ እስከ ፡ ኋለኞች ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እያሉ ፡ ወጡ ፤ ኢ.የሱስም ፡ ብቻውን ፡ ቀረ ፥ ሴቲቱም ፡ በመካከል ፡ ቆማ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ኢ.የሱስም ፡ ቀና ፡ ብሎ ፡ ከሴቲቱ ፡ በቀር ፡ ማንንም ፡ ባላየ ፡ ጊዜ ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ እነዚያ ፡ ከሳሾችሽ ፡ ወዴት ፡ አሉ ፧ የፈረደብሽ ፡ የለምን ፧ አላት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ርሷም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አለች ። ኢ.የሱስም ፦ እኔም ፡ አልፈርድብሽም ፤ ኺጂ ፥ ካኹንም ፡ ዠምሮ ፡ ደግመሽ ፡ ኀጢአት ፡ አትሥሪ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ደግሞም ፡ ኢ.የሱስ ፦ እኔ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ነኝ ፤ የሚከተለኝ ፡ የሕይወት ፡ ብርሃን ፡ ይኾንለታል ፡ እንጂ ፡ በጨለማ ፡ አይመላለስም ፡ ብሎ ፡ ተናገራቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ፈሪሳውያንም ፦ አንተ ፡ ስለ ፡ ራስኽ ፡ ትመሰክራለኽ ፤ ምስክርነትኽ ፡ እውነት ፡ አይደለም ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ ኢ.የሱስ ፡ መለሰ ፥ አላቸውም ፦ እኔ ፡ ስለ ፡ ራሴ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብመሰክር ፡ ከወዴት ፡ እንደመጣኹ ፡ ወዴትም ፡ እንድኼድ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ምስክርነቴ ፡ እውነት ፡ ነው ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ መጣኹ ፡ ወዴትም ፡ እንድኼድ ፡ አታውቁም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ እናንተ ፡ ሥጋዊ ፡ ፍርድን ፡ ትፈርዳላችኹ ፤ እኔ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ስንኳ ፡ አልፈርድም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ የላከኝ ፡ አብ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብቻዬን ፡ አይደለኹምና ፡ እኔ ፡ ብፈርድ ፡ ፍርዴ ፡ እውነት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ የኹለት ፡ ሰዎችም ፡ ምስክርነት ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሕጋችኹ ፡ ተጽፏል ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ራሴ ፡ የምመሰክር ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ የላከኝም ፡ አብ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ይመሰክራል ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፦ አባትኽ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አሉት ። ኢ.የሱስ ፡ መልሶ ፦ እኔንም ፡ ወይም ፡ አባቴንም ፡

አታውቁም ፤ እኔንስ ፡ ብታውቁኝ ፡ አባቴን ፡ ደግሞ ፡ ባወቃችኹ ፡ ነበር ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ኢየሱስ ፡ በመቅደስ ፡ ሲያስተምር ፡ በግምጃ ፡ ቤት ፡ አጠገብ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፤ ጊዜው ፡ ገና ፡ አልደረሰምና ፡ ማንም ፡ አልያዘውም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፦ እኔ ፡ እኼዳለኹ ፡ ትፈልጉኛላችኹም ፡ በኀጢአታችኹም ፡ ትሞታላችኹ ፡ እኔ ፡ ወደምኼድበት ፡ እናንተ ፡ ልትመጡ ፡ አትችሉም ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ አይሁድም ፦ እኔ ፡ ወደምኼድበት ፡ እናንተ ፡ ልትመጡ ፡ አትችሉም ፡ ማለቱ ፡ ራሱን ፡ ይገድላልን ፧ እንጃ ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ እናንተ ፡ ከታች ፡ ናችኹ ፥ እኔ ፡ ከላይ ፡ ነኝ ፤ እናንተ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ናችኹ ፥ እኔ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለኹም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ እንግዲህ ፦ በኀጢአታችኹ ፡ ትሞታላችኹ ፡ አልኋችኹ ፤ እኔ ፡ እንደኾንኹ ፡ ባታምኑ ፡ በኀጢአታችኹ ፡ ትሞታላችኹና ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ እንግዲህ ፦ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ አሉት ። ኢየሱስም ፦ ከመገሥመሪያ ፡ ለእናንተ ፡ የተናገርኹት ፡ ነኝ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ የምናገረው ፡ የምፈርደውም ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የላከኝ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፥ እኔም ፡ ከርሱ ፡ የሰማኹትን ፡ ይህን ፡ ለዓለም ፡ እናገራለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ስለ ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ነገራቸው ፡ አላስተዋሉም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ስለዚህም ፡ ኢየሱስ ፦ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ባደረጋችኹት ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ አባቴም ፡ እንዳስተማረኝ ፡ እነዚህን ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ ከራሴ ፡ አንዳች ፡ እንዳላደርግ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ የላከኝም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ ዘወትር ፡ አደርጋለኹና ፡ አብ ፡ ብቻዬን ፡ አይተወኝም ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ይህን ፡ ሲናገር ፡ ብዙዎች ፡ በርሱ ፡ አመኑ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ ኢየሱስም ፡ ያመኑትን ፡ አይሁድ ፦ እናንተ ፡ በቃሌ ፡ ብትኖሩ ፡ በእውነት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ናችኹ ፤

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ እውነትንም ፡ ታውቃላችኹ ፡ እውነትም ፡ ሐራነት ፡ ያወጣችኋል ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ እነርሱም ፡ መልሰው ፦ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ ነን ፡ ለአንድም ፡ ስንኳ ፡ ከቶ ፡ ባሪያዎች ፡ አልኾንም ፤ አንተ ፦ ሐራነት ፡ ትወጣላችኹ ፡ እንዴት ፡ ትላለኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ ኢየሱስ ፡ መለሰ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ኀጢአት ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ የኀጢአት ፡ ባሪያ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ባሪያም ፡ ለዘለዓለም ፡ በቤት ፡ አይኖርም ፤ ልጁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ እንግዲህ ፡ ልጁ ፡ ሐራነት ፡ ቢያወጣችኹ ፡ በእውነት ፡ ሐራነት ፡ ትወጣላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 37 ፤ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ መኾናችኹንስ ፡ ዐውቃለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ቃሌ ፡ በእናንተ ፡ አይኖርምና ፡

ልትገድሉኝ ፡ ትፈልጋላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 38 ፤ እኔ ፡ በአባቴ ፡ ዘንድ ፡ ያየኹትን ፡ እናገራለኹ ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ በአባታችኹ ፡ ዘንድ ፡ ያያችኹትን ፡ ታደርጋላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 39 ፤ መልሰውም ፦ አባታችንስ ፡ አብርሃም ፡ ነው ፡ አሉት ። ኢየሱስም ፦ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ብትኾኑ ፡ የአብርሃምን ፡ ሥራ ፡ ባደረጋችኹ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 40 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሰማኹትን ፡ እውነት ፡ የነገርኋችኹን ፡ ሰው ፡ ልትገድሉኝ ፡ ትፈልጋላችኹ ፤ አብርሃም ፡ እንዲህ ፡ አላደረገም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 41 ፤ እናንተ ፡ የአባታችኹን ፡ ሥራ ፡ ታደርጋላችኹ ፡ አላቸው ፦ እኛስ ፡ ከዝሙት ፡ አልተወለድንም ፤ አንድ ፡ አባት ፡ አለን ፥ ርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 42 ፤ ኢየሱስም ፡ አላቸው ፦ እግዚአብሔርስ ፡ አባታችኹ ፡ ከኾነ ፡ በወደዳችኹኝ ፡ ነበር ፤ እኔ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወጥቼ ፡ መጥቻለኹና ፤ ርሱ ፡ ላከኝ ፡ እንጂ ፡ ከራሴ ፡ አልመጣኹምና ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 43 ፤ ንግግሬን ፡ የማታስተውሉ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ቃሌን ፡ ልትሰሙ ፡ ስለማትችሉ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 44 ፤ እናንተ ፡ ከአባታችኹ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ናችኹ ፡ የአባታችኹንም ፡ ምኞት ፡ ልታደርጉ ፡ ትወዳላችኹ ። ርሱ ፡ ከመገዖመሪያ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነበረ ፤ እውነትም ፡ በርሱ ፡ ስለሌለ ፡ በእውነት ፡ አልቆመም ። ሐሰትን ፡ ሲናገር ፡ ከራሱ ፡ ይናገራል ፥ ሐሰተኛ ፡ የሐሰትም ፡ አባት ፡ ነውና ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 45 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እውነትን ፡ የምናገር ፡ ስለ ፡ ኾንኹ ፡ አታምኑኝም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 46 ፤ ከእናንተ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ የሚወቅሰኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧ እውነት ፡ የምናገር ፡ ከኾንኹ ፡ እናንተ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አታምኑኝም ፧

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 47 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የኾነ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይሰማል ፤ እናንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደላችኹምና ፡ ስለዚህ ፡ አትሰሙም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 48 ፤ አይሁድ ፡ መልሰው ፦ ሳምራዊ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ጋኔንም ፡ እንዳለብኽ ፡ በማለታችን ፡ እኛ ፡ መልካም ፡ እንል ፡ የለምን ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 49 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ እኔስ ፡ ጋኔን ፡ የለብኝም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አባቴን ፡ አከብራለኹ ፡ እናንተም ፡ ታዋርዱኛላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 50 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ የራሴን ፡ ክብር ፡ አልፈልግም ፤ የሚፈልግ ፡ የሚፈርድም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 51 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ቃሌን ፡ የሚጠብቅ ፡ ቢኖር ፡ ለዘለዓለም ፡ ሞትን ፡ አያይም ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 52 ፤ አይሁድ ፦ ጋኔን ፡ እንዳለብኽ ፡ አኹን ፡ ዐወቅን ። አብርሃም ፡ ስንኳ ፡ ሞተ ፥ ነቢያትም ፤ አንተም ፦ ቃሌን ፡ የሚጠብቅ ፡ ቢኖር ፡ ለዘለዓለም ፡ ሞትን ፡ አይቀምስም ፡ ትላለኽ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 53 ፤ በእውኑ ፡ አንተ ፡ ከሞተው ፡ ከአባታችን ፡ ከአብርሃም ፡ ትበልጣለኽን ፧ ነቢያትም ፡ ሞቱ ፤ ራስኽን ፡ ማንን ፡ ታደርጋለኽ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 54 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፥ አለም ፦ እኔ ፡ ራሴን ፡ ባከብር ፡ ክብሬ ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ የሚያከብረኝ ፡ እናንተ ፡ አምላካችን ፡ የምትሉት ፡ አባቴ ፡ ነው ፤

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 55 ፤ አላወቃችኹትምም ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ዐውቀዋለኹ ። አላውቀውም ፡ ብል ፡ እንደናንተ ፡ ሐሰተኛ ፡ በኾንኹ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐውቀዋለኹ ፡ ቃሉንም ፡ እጠብቃለኹ ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 56 ፤ አባታችኹ ፡ አብርሃም ፡ ቀኔን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ፥ አየም ፡ ደስም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 57 ፤ አይሁድም ፦ ገና ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ያልኾነኽ ፡ አብርሃምን ፡ አይተኻልን ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 58 ፤ ኢየሱስም ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ አብርሃም ፡ ሳይወለድ ፡ እኔ ፡ አለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 8 ፡ 59 ፤ ስለዚህ ፥ ሊወግሩት ፡ ድንጋይ ፡ አነሡ ፤ ኢየሱስ ፡ ግን ፡ ተሰወራቸው ፥ ከመቅደስም ፡ ወጥቶ ፡ በመካከላቸው ፡ ዐልፎ ፡ ኼደ ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ሲያልፍም ፡ ከመወለዱ ፡ ዠምሮ ፡ ዕውር ፡ የኾነውን ፡ ሰው ፡ አየ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ እንዲወለድ ፡ ኀጢአት ፡ የሠራ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ ወይስ ፡ ወላጆቹ ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፦ የእግዚአብሔር ፡ ሥራ ፡ በርሱ ፡ እንዲገለጥ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ርሱ ፡ ወይም ፡ ወላጆቹ ፡ ኀጢአት ፡ አልሠሩም ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ ቀን ፡ ሳለ ፡ የላከኝን ፡ ሥራ ፡ ላደርግ ፡ ይገባኛል ፤ ማንም ፡ ሊሠራ ፡ የማይችልባት ፡ ሌሊት ፡ ትመጣለች ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ በዓለም ፡ ሳለኹ ፡ የዓለም ፡ ብርሃን ፡ ነኝ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ይህን ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ መሬት ፡ እንትፍ ፡ አለ ፡ በምራቁም ፡ ጭቃ ፡ አድርጎ ፡ በጭቃው ፡ የዕውሩን ፡ ዐይኖች ፡ ቀባና ፦

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ኺድና ፡ በሰሊሐም ፡ መጠመቂያ ፡ ታጠብ ፡ አለው ፤ (ትርጓሜው ፡ 'የተላከ' ፡ ነው) ። ስለዚህ ፡ ኼዶ ፡ ታጠበ ፥ እያየም ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ጎረቤቶቹም ፡ ቀድሞም ፡ ሲለምን ፡ አይተውት ፡ የነበሩ ፦ ይህ ፡ ተቀምጦ ፡ ይለምን ፡ የነበረ ፡ አይደለምን ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ሌላዎች ፦ ርሱ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ሌላዎች ፦ አይደለም ፡ ርሱን ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ አሉ ፤ ርሱ ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ታድያ ፦ ዐይኖችኽ ፡ እንዴት ፡ ተከፈቱ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ርሱ ፡ መልሶ ፦ ኢየሱስ ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ጭቃ ፡ አድርጎ ፡ አይኖቼን ፡ ቀባና ፦ ወደሰሊሐም ፡ መጠመቂያ ፡ ኼደኽ ፡ ታጠብ ፡ አለኝ ፤ ኼጄ ፡ ታጥቤም ፡ አየኹ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ያ ፡ ሰው ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አሉት ፦ አላውቅም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ በፊት ፡ ዕውር ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ወሰዱት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ኢየሱስም ፡ ጭቃ ፡ አድርጎ ፡ ዐይኖቹን ፡ የከፈተበት ፡ ቀን ፡ ሰንበት ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ ፈሪሳውያን ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ እንዳየ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ጠየቁት ። ርሱም ፦ ጭቃ ፡ በዐይኖቼ ፡ አኖረ ፥ ታጠብኹም ፥ አያለኹም ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ከፈሪሳውያንም ፡ አንዳንዶቹ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ሰንበትን ፡ አያከብርምና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደለም ፡ አሉ ። ሌላዎች ፡ ግን ፦ ኀጢአትና ፡ ሰው ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ምልክቶች ፡ ሊያደርግ ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ በመካከላቸውም ፡ መለያየት ፡ ኾነ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ዕውሩን ፦ አንተ ፡ ዐይኖችኽን ፡ ስለከፈተ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ምን ፡ ትላለኽ ፧ ደግሞ ፡ አሉት ። ርሱም ፦ ነቢይ ፡ ነው ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ አይሁድ ፡ የዚያን ፡ ያየውን ፡ ወላጆች ፡ እስኪጠሩ ፡ ድረስ ፡ ዕውር ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንዳየም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አላመኑም ፥

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ እነርሱንም ፦ እናንተ ፡ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ ተወለደ ፡ የምትሉት ፡ ልጃችኹ ፡ ይህ ፡ ነውን ፧ ታድያ ፡ አኹን ፡ እንዴት ፡ ያያል ፧ ብለው ፡ ጠየቋቸው ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ወላጆቹም ፡ መልሰው ፦ ይህ ፡ ልጃችን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዕውርም ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ እናውቃለን ፤

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አኹን ፡ እንዴት ፡ እንዳየ ፡ አናውቅም ፥ ወይም ፡ ዐይኖቹን ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ከፈተ ፡ እኛ ፡ አናውቅም ፤ ጠይቁት ፡ ርሱ ፡ ሙሉ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ይናገራል ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ ወላጆቹ ፡ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ይህን ፡ አሉ ፤ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የሚመሰክር ፡ ቢኖር ፡ ከምኩራብ ፡ እንዲያወጡት ፡ አይሁድ ፡ ከዚህ ፡ በፊት ፡ ተስማምተው ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ ስለዚህ ፥ ወላጆቹ ፦ ሙሉ ፡ ሰው ፡ ነው ፥ ጠይቁት ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ዕውር ፡ የነበረውን ፡ ሰው ፡ ኹለተኛ ፡ ጠርተው ፦ እግዚአብሔርን ፡ አክብር ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ኀጢአተኛ ፡ መኾኑን ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ኀጢአተኛ ፡ መኾኑን ፡ አላውቅም ፤ ዕውር ፡ እንደ ፡ ነበርኹ ፡ አኹንም ፡ እንዳይ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ ደግመውም ፦ ምን ፡ አደረገልኽ ፧ እንዴትስ ፡ ዐይኖችኽን ፡ ከፈተ ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ አስቀድሜ ፡ ነገርኋችኹ ፡ አልሰማችኹምም ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ዳግመኛ ፡ ልትሰሙ ፡ ትወዳላችኹ ፧ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ልትኾኑ ፡ ትወዳላችኹን ፧ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ ተሳድበውም ፦ አንተ ፡ የርሱ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነኽ ፥ እኛ ፡ ግን ፡ የሙሴ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ነን ፤

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ፥ ይህ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አናውቅም ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ሰውዬው ፡ መለሰ ፡ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናንተ ፡ አለማወቃችኹ ፡ ይህ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ ነው ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ዐይኖቼን ፡ ከፈተ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ፈቃዱንም ፡ የሚያደርግ ፡ ቢኖር ፡ ያን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይሰማዋል ፡ እንጂ ፡ ኀጢአተኞችን ፡ እንዳይሰማ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ ዕውር ፡ ኾኖ ፡ የተወለደውን ፡ ዐይኖች ፡ ማንም ፡ እንደ ፡ ከፈተ ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ አልተሰማም ፤

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባይኾን ፡ ምንም ፡ ሊያደርግ ፡ ባልቻለም ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ መልሰው ፦ አንተ ፡ ኹለንተናኽ ፡ በኀጢአት ፡ ተወለድኽ ፥ አንተም ፡ እኛን ፡ ታስተምረናለኽን ፧ አሉት ። ወደ ፡ ውጭም ፡ አወጡት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ እንዳወጡት ፡ ሰማ ፤ ሲያገኘውም ፦ አንተ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ታምናለኽን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 36 ፤ ርሱም ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በርሱ ፡ አምን ፡ ዘንድ ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 37 ፤ ኢየሱስም ፦ አይተኸዋልም ፡ ከአንተ ፡ ጋራም ፡ የሚናገረው ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 38 ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አምናለኹ ፡ አለ ፤ ሰገደለትም ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 39 ፤ ኢየሱስም ፦ የማያዩ ፡ እንዲያዩ ፡ የሚያዩም ፡ እንዲታወሩ ፡ እኔ ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ለፍርድ ፡ መጣኹ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 40 ፤ ከፈሪሳውያንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ይህን ፡ ሰምተው ፦ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ዕውሮች ፡ ነንን ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 9 ፡ 41 ፤ ኢየሱስም ፡ አላቸው ፦ ዕውሮችስ ፡ ብትኾኑ ፡ ኀጢአት ፡ ባልኾነባችኹም ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፦ እናያለን ፡ ትላላችኹ ፤ ኀጢአታችኹ ፡ ይኖራል ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ወደበጎች ፡ በረት ፡ በበሩ ፡ የማይገባ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ግን ፡ የሚወጣ ፡ ርሱ ፡ ሌባ ፡ ወንበዴም ፡ ነው ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በበሩ ፡ የሚገባ ፡ ግን ፡ የበጎች ፡ እረኛ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ለርሱ ፡ በረኛው ፡ ይከፍትለታል ፤ በጎቹም ፡ ድምፁን ፡ ይሰሙታል ፥ የራሱንም ፡ በጎች ፡ በየስማቸው ፡ ጠርቶ ፡ ይወስዳቸዋል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የራሱንም ፡ ኹሉ ፡ ካወጣቸው ፡ በኋላ ፡ በፊታቸው ፡ ይኼዳል ፥ በጎቹም ፡ ድምፁን ፡ ያውቃሉና ፡ ይከተሉታል ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ከሌላው ፡ ግን ፡ ይሸሻሉ ፡ እንጂ ፡ አይከተሉትም ፥ የሌላዎችን ፡ ድምፅ ፡ አያውቁምና ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡ ምሳሌ ፡ ነገራቸው ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ የነገራቸው ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላስተዋሉም ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፡ ደግሞ ፡ አላቸው ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ እኔ ፡ የበጎች ፡ በር ፡ ነኝ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ከእኔ ፡ በፊት ፡ የመጡ ፡ ኹሉ ፡ ሌባዎችና ፡ ወንበዴዎች ፡ ናቸው ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በጎቹ ፡ አልሰሟቸውም ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ በሩ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ በእኔ ፡ የሚገባ ፡ ቢኖር ፡ ይድናል ፥ ይገባልም ፡ ይወጣልም ፡ መሰማሪያም ፡

ያገኛል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ሌባው ፡ ሊሰርቅና ፡ ሊያርድ ፡ ሊያጠፋም ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ አይመጣም ፤ እኔ ፡ ሕይወት ፡ እንዲኾንላቸው ፡ እንዲበዛላቸውም ፡ መጣኹ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ መልካም ፡ እረኛ ፡ እኔ ፡ ነኝ ። መልካም ፡ እረኛ ፡ ነፍሱን ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ ያኖራል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ እረኛ ፡ ያልኾነው ፡ በጎቹም ፡ የርሱ ፡ ያልኾኑ ፡ ሞያተኛ ፡ ግን ፥ ተኵላ ፡ ሲመጣ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ በጎቹን ፡ ትቶ ፡ ይሸሻል ፤ ተኵላም ፡ ይነጥቃቸዋል ፡ በጎቹንም ፡ ይበትናቸዋል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ሞያተኛ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ለበጎቹም ፡ ስለማይገደው ፡ ሞያተኛው ፡ ይሸሻል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 14-15 ፤ መልካም ፡ እረኛ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥ አብም ፡ እንደሚያውቀኝ ፡ እኔም ፡ አብን ፡ እንደማውቀው ፡ የራሴን ፡ በጎች ፡ ዐውቃለኹ ፡ የራሴም ፡ በጎች ፡ ያውቁኛል ፤ ነፍሴንም ፡ ስለ ፡ በጎች ፡ አኖራለኹ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ከዚህም ፡ በረት ፡ ያልኾኑ ፡ ሌላዎች ፡ በጎች ፡ አሉኝ ፤ እነርሱን ፡ ደግሞ ፡ ላመጣ ፡ ይገባኛል ፥ ድምፄንም ፡ ይሰማሉ ፥ አንድም ፡ መንጋ ፡ ይኾናሉ ፥ እረኛውም ፡ አንድ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ነፍሴን ፡ ደግሞ ፡ አነሣት ፡ ዘንድ ፡ አኖራለኹና ፡ ስለዚህ ፡ አብ ፡ ይወደኛል ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ እኔ ፡ በፈቃዴ ፡ አኖራታለኹ ፡ እንጂ ፡ ከእኔ ፡ ማንም ፡ አይወስዳትም ። ላኖራት ፡ ሥልጣን ፡ አለኝ ፡ ደግሞም ፡ ላነሣት ፡ ሥልጣን ፡ አለኝ ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ከአባቴ ፡ ተቀበልኹ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ከዚህ ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ በአይሁድ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ መለያየት ፡ ኾነ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ከነርሱም ፡ ብዙዎች ፦ ጋኔን ፡ አለበት ፡ አብዷልም ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ትሰሙታላችኹ ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ሌላዎችም ፦ ይህ ፡ ጋኔን ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ አይደለም ፤ ጋኔን ፡ የዕውሮችን ፡ ዐይኖች ፡ ሊከፍት ፡ ይችላልን ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የመቅደስ ፡ መታደስ ፡ በዓል ፡ ኾነ ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ክረምትም ፡ ነበረ ። ኢየሱስም ፡ በመቅደስ ፡ በሰሎሞን ፡ ደጅ ፡ መመላለሻ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ አይሁድም ፡ ርሱን ፡ ከበው ፦ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ በጥርጣሪ ፡ ታቈየናለኽ ፧ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ገልጠኽ ፡ ንገረን ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰላቸው ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ነገርኋችኹ ፡ አታምኑምም ፡ እኔ ፡ በአባቴ ፡ ስም ፡ የማደርገው ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ይመሰክራል ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ነገርኋችኹ ፡ ከበጎቼ ፡ ስላልኾናችኹ ፡ አታምኑም ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ በጎቼ ፡ ድምፄን ፡ ይሰማሉ ፡ እኔም ፡ ዐውቃቸዋለኹ ፡ ይከተሉኝማል ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ እኔም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወትን ፡ እሰጣቸዋለኹ ፥ ለዘለዓለምም ፡ አይጠፉም ፥ ከእጄም ፡ ማንም ፡ አይነጥቃቸውም ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ የሰጠኝ ፡ አባቴ ፡ ከኹሉ ፡ ይበልጣል ፥ ከአባቴም ፡ እጅ ፡ ሊነጥቃቸው ፡ ማንም ፡ አይችልም ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ እኔና ፡ አብ ፡ አንድ ፡ ነን ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ አይሁድ ፡ ሊወግሩት ፡ ደግመው ፡ ድንጋይ ፡ አነሡ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ ኢየሱስ ፦ ከአባቴ ፡ ብዙ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ አሳየኋችኹ ፤ ከነርሱ ፡ ስለ ፡ ማናቸው ፡ ሥራ ፡ ትወግሩኛላችኹ ፧ ብሎ ፡ መለሰላቸው ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ አይሁድም ፦ ስለ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ አንወግርኽም ፤ ስለ ፡ ስድብ ፤ አንተም ፡ ሰው ፡ ስትኾን ፡ ራስኽን ፡ አምላክ ፡ ስለ ፡ ማድረግኽ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ፦ እኔ ፦ አማልክት ፡ ናችኹ ፡ አልኹ ፡ ተብሎ ፡ በሕጋችኹ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለምን ፧

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ መጽሐፉ ፡ ሊሻር ፡ አይቻልምና ፡ እነዚያን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የመጣላቸውን ፡ አማልክት ፡ ካላቸው ፥

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ስላልኹ ፡ እናንተ ፡ አብ ፡ የቀደሰውን ፡ ወደ ፡ ዓለምም ፡ የላከውን ፦ ትሳደባለኽ ፡ ትሉታላችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ እኔ ፡ የአባቴን ፡ ሥራ ፡ ባላደርግ ፡ አትመኑኝ ፤

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ ባደርገው ፡ ግን ፥ እኔን ፡ ስንኳ ፡ ባታምኑ ፡ አብ ፡ በእኔ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኔም ፡ በአብ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታውቁና ፡ ታስተውሉ ፡ ዘንድ ፡ ሥራውን ፡ እመኑ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 39 ፤ እንግዲህ ፡ ደግመው ፡ ሊይዙት ፡ ፈለጉ ፤ ከእጃቸውም ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 40 ፤ ዮሐንስም ፡ በመዠመሪያ ፡ ያጠምቅበት ፡ ወደነበረው ፡ ስፍራ ፡ ወደዮርዳኖስ ፡ ማዶ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ኼደ ፡ በዚያም ፡ ኖረ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 41 ፤ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጥተው ፦ ዮሐንስ ፡ አንድ ፡ ምልክት ፡ ስንኳ ፡ አላደረገም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ዮሐንስ ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ የተናገረው ፡ ኹሉ ፡ እውነት ፡ ነበረ ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 10 ፡ 42 ፤ በዚያም ፡ ብዙዎች ፡ በርሱ ፡ አመኑ ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ ከማርያምና ፡ ከእኅቷ ፡ ከማርታ ፡ መንደር ፡ ከቢታንያ ፡ የኾነ ፡ አልዓዛር ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ታሞ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ማርያምም ፡ ጌታን ፡ ሽቱ ፡ የቀባችው ፡ እግሩንም ፡ በጠጕሯ ፡ ያበሰችው ፡ ነበረች ፤ ወንድሟም ፡ አልዓዛር ፡ ታሞ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ እኅቶቹ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንሆ ፥ የምትወደው ፡ ታሟል ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ላኩ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፡ ሰምቶ ፦ ይህ ፡ ሕመም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ በርሱ ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሞት ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ ማርታንና ፡ እኅቷን ፡ አልዓዛርንም ፡ ይወድ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ታመመም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ በነበረበት ፡ ስፍራ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ ዋለ ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ ደግሞ ፡ እንኺድ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ መምህር ፡ ሆይ ፥ አይሁድ ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ሊወግሩኽ ፡ ይፈልጉ ፡ ነበር ፥ ደግሞም ፡ ወደዚያ ፡ ትኼዳለኽን ፧ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ቀኑ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሰዓት ፡ አይደለምን ፧ በቀን ፡ የሚመላለስ ፡ ቢኖር ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ብርሃን ፡ ያያልና ፥ አይሰናከልም ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ በሌሊት ፡ የሚመላለስ ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ ብርሃን ፡ በርሱ ፡ ስለሌለ ፡ ይሰናከላል ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ይህን ፡ ተናገረ ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፦ ወዳጃችን ፡ አልዓዛር ፡ ተኝቷል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእንቅልፉ ፡ ላስነሣው ፡ እኼዳለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ተኝቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይድናል ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ኢየሱስስ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ተናግሮ ፡ ነበር ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እንቅልፍ ፡ መተኛት ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ መሰላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በግልጥ ፦ አልዓዛር ፡ ሞተ ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ እንድታምኑም ፡ በዚያ ፡ ባለመኖሬ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ እንኺድ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ ዲዲሞስ ፡ የሚሉት ፡ ቶማስ ፥ ለባልንጀራዎቹ ፣ ለደቀ ፡ መዛሙርት ፦ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንሞት ፡ ዘንድ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንኺድ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በመቃብር ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ኾኖት ፡ አገኘው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ቢታንያም ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ምዕራፍ ፡ ያኽል ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ቅርብ ፡ ነበረች ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ ከአይሁድም ፡ ብዙዎች ፡ ስለ ፡ ወንድማቸው ፡ ሊያጽናኗቸው ፡ ወደ ፡ ማርታና ፡ ወደ ፡ ማርያም ፡ መጥተው ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ማርታም ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ልትቀበለው ፡ ወጣች ፤ ማርያም ፡ ግን ፡ በቤት ፡ ተቀምጣ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ማርታም ፡ ኢየሱስን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በዚህ ፡ ኖረኽ ፡ ብትኾን ፡ ወንድሜ ፡ ባልሞተም ፡ ነበር ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ አኹንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የምትለምነውን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲሰጥኽ ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፦ ወንድምሽ ፡ ይነሣል ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ማርታም ፦ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ በትንሣኤ ፡ እንዲነሣ ፡ ዐውቃለኹ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ኢየሱስም ፦ ትንሣኤና ፡ ሕይወት ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ የሚያምንብኝ ፡ ቢሞት ፡ እንኳ ፡ ሕያው ፡ ይኾናል ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ሕያው ፡ የኾነም ፡ የሚያምንብኝም ፡ ኹሉ ፡ ለዘለዓለም ፡ አይሞትም ፤ ይህን ፡ ታምኚያለሽን ፧ አላት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ ርሷም ፦ አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፤ አንተ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የሚመጣው ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ እኔ ፡ አምናለኹ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ይህንም ፡ ብላ ፡ ኼደች ፥ እኅቷንም ፡ ማርያምን ፡ በስውር ፡ ጠርታ ፦ መምህሩ ፡ መጥቷል ፡ ይጠራሽማል ፡ አለቻት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ርሷም ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ ተነሣች ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ መጣች ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፡ ማርታ ፡ በተቀበለችበት ፡ ስፍራ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ መንደሩ ፡ አልገባም ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ሲያጽናኗት ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ በቤት ፡ የነበሩ ፡ አይሁድም ፡ ማርያም ፡ ፈጥና ፡ እንደ ፡ ተነሣችና ፡ እንደ ፡ ወጣች ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ መቃብር ፡ ኼዳ ፡ በዚያ ፡ ልታለቅስ ፡ መስሏቸው ፡ ተከተሏት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ ማርያምም ፡ ኢየሱስ ፡ ወዳለበት ፡ መጥታ ፡ ባየችው ፡ ጊዜ ፡ በእግሩ ፡ ላይ ፡ ወድቃ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በዚህ ፡ ኖረኽ ፡ ብትኾን ፡ ወንድሜ ፡ ባልሞተም ፡ ነበር ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ ኢየሱስም ፡ ርሷ ፡ ስታለቅስ ፡ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ የመጡት ፡ አይሁድ ፡ ሲያለቅሱ ፡ አይቶ ፡ በመንፈሱ ፡ ዐዘነ ፡ በራሱም ፡ ታወከ ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ ወዴት ፡ አኖራችኹት ፧ አለም ። እነርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ መጥተኽ ፡ እይ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፡ እንባውን ፡ አፈሰሰ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ስለዚህ ፥ አይሁድ ፦ እንዴት ፡ ይወደው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እዩ ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 37 ፤ ከነርሱ ፡ ግን ፡ አንዳንዶቹ ፦ ይህ ፡ የዕውሩን ፡ ዐይኖች ፡ የከፈተ ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ እንዳይሞት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ባልቻለም ፡ ነበርን ፧ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 38 ፤ ኢየሱስም ፡ በራሱ ፡ ዐዝኖ ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ መጣ ፤ ርሱም ፡ ዋሻ ፡ ነበረ ፤ ድንጋይም ፡ ተገጥሞበት ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 39 ፤ ኢየሱስ ፦ ድንጋዩን ፡ አንሡ ፡ አለ ። የሞተውም ፡ እኅት ፡ ማርታ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ከሞተ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ ኾኖታልና ፥ አኹን ፡ ይሸታል ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 40 ፤ ኢየሱስ ፦ ብታምኚስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ እንድታዩ ፡ አልነገርኹሽምን ፧ አላት ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 41 ፤ ድንጋዩንም ፡ አነሡት ። ኢየሱስም ፡ ዐይኖቹን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥቶ ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ሰማኸኝ ፡ አመሰግንኻለኹ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 42 ፤ ዘወትር ፡ እንድትሰማኝ ፡ ዐወቅኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ዙሪያ ፡ ስለቆሙት ፡ ሕዝብ ፡ ተናገርኹ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 43 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ አልዓዛር ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ውጭ ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 44 ፤ የሞተውም ፡ እጆቹና ፡ እግሮቹ ፡ በመግነዝ ፡ እንደ ፡ ተገነዙ ፡ ወጣ ፤ ፊቱም ፡ በጨርቅ ፡ እንደ ፡ ተጠመጠመ ፡ ነበር ። ኢየሱስም ፦ ፍቱትና ፡ ይኺድ ፡ ተዉት ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 45 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ማርያም ፡ ከመጡት ፥ ኢየሱስም ፡ ያደረገውን ፡ ካዩት ፡ ከአይሁድ ፡ ብዙዎች ፡ በርሱ ፡ አመኑ ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 46 ፤ ከነርሱ ፡ አንዳንዶቹ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ኼደው ፡ ኢየሱስ ፡ ያደረገውን ፡ ነገሯቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 47 ፤ እንግዲህ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ፈሪሳውያን ፡ ሸንጎ ፡ ሰብስበው ፦ ምን ፡ እናድርግ ፧ ይህ ፡ ሰው ፡ ብዙ ፡ ምልክቶች ፡ ያደርጋልና ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 48 ፤ እንዲሁ ፡ ብንተወው ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ያምናሉ ፤ የሮሜም ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ አገራችንን ፡ ወገናችንንም ፡ ይወስዳሉ ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 49 ፤ በዚያችም ፡ ዓመት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የነበረ ፡ ቀያፋ ፡ የሚሉት ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፦ እናንተ ፡ ምንም ፡ አታውቁም ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 50 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ከሚጠፋ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ እንዲሻለን ፡ አታስቡም ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 51 ፤ ይህንም ፡ የተናገረ ፡ ከራሱ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያች ፡ ዓመት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ነበረና ፡ ኢየሱስ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ሊሞት ፡ እንዳለው ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፤

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 52 ፤ ስለ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የተበተኑትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጆች ፡ ደግሞ ፡ በአንድነት ፡ እንዲሰበስባቸው ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 53 ፤ እንግዲህ ፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ገዖምረው ፡ ሊገድሉት ፡ ተማከሩ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 54 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ኢየሱስ ፡ በአይሁድ ፡ መካከል ፡ ተገልጦ ፡ አልተመላለሰም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዚያ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ አጠገብ ፡ ወዳለች ፡ ምድር ፥ ኤፍሬም ፡ ወደምትባል ፡ ከተማ ፡ ኼደ ፤ በዚያም ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 55 ፤ የአይሁድም ፡ ፋሲካ ፡ ቀርቦ ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ራሳቸውን ፡ ያነጹ ፡ ዘንድ ፡ ከፋሲካ ፡ በፊት ፡ ከአገሩ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጡ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 56 ፤ ኢየሱስንም ፡ ይፈልጉት ፡ ነበር ፤ በመቅደስም ፡ ቆመው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ምን ፡ ይመስላችኋል ፧ ወደ ፡ በዓሉ ፡ አይመጣም ፡ ይኾንን ፧ ተባባሉ ።

ዮሐ. ፡ 11 ፡ 57 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ይይዙት ፡ ዘንድ ፥ ርሱ ፡ ያለበትን ፡ ስፍራ ፡ የሚያውቀው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ እንዲያመለክታቸው ፡ አዘው ፡ ነበር ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ከፋሲካም ፡ በፊት ፡ በስድስተኛው ፡ ቀን ፡ ኢየሱስ ፡ ከሙታን ፡ ያስነሣው ፡ አልዓዛር ፡ ወደ ፡ ነበረበት ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ በዚያም ፡ እራት ፡ አደረጉለት ፤ ማርታም ፡ ታገለግል ፡ ነበር ፤ አልዓዛር ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተቀመጡት ፡ አንዱ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ማርያምም ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ የጥሩ ፡ ናርዶስ ፡ ሽቱ ፡ ንጥር ፡ ወስዳ ፡ የኢየሱስን ፡ እግር ፡ ቀባች ፤ በጠጉሯም ፡ እግሩን ፡ አበሰች ፤ ቤቱም ፡ ከናርዶስ ፡ ሽቱ ፡ ሞላ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፡ አሳልፎ ፡ ሊሰጠው ፡ ያለው ፡ የስምዖን ፡ ልጅ ፡ የአስቆሮቱ ፡ ይሁዳ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ይህ ፡ ሽቱ ፡ ለሦስት ፡ መቶ ፡ ዲናር ፡ ተሸጦ ፡ ለድኻዎች ፡ ያልተሰጠ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ነው ፧ አለ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ይሁንም ፡ የተናገረ ፡ ሌባ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለድኻዎች ፡ ተገዶላቸው ፡ አይደለም ፤ ከረጢትም ፡ ይዞ ፡ በውስጡ ፡ ከሚገባው ፡ ይወስድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፦ ለምቀበርበት ፡ ቀን ፡ እንድትጠብቀው ፡ ተዋት ፤

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ድኻዎችስ ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኖራሉና ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ዘልጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ አልኖርም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ከአይሁድም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በዚያ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ዐውቀው ፡ መጡ ፥ ከሙታንም ፡ ያስነሣውን ፡ አልዓዛርን ፡ ደግሞ ፡ እንዲያዩ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ አልዓዛርን ፡ ደግሞ ፡ ሊገድሉት ፡ ተማከሩ ፥

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ከአይሁድ ፡ ብዙዎች ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ኼደው ፡ በኢየሱስ ፡ ያምኑ ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በማግስቱ ፡ ወደ ፡ በዓሉ ፡ መጥተው ፡ የነበሩ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲመጣ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ የዘንባባ ፡ ዛፍ ፡ ዝንጣፊ ፡ ይዘው ፡ ሊቀበሉት ፡ ወጡና ፦ ሆሣዕና ፤ በጌታ ፡ ስም ፡ የሚመጣ ፡ የእስራኤል ፡ ንጉሥ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 14-15 ፤ አንቺ ፡ የጽዮን ፡ ልጅ ፡ አትፍሪ ፤ እንሆ ፥ ንጉሥሽ ፡ በአህያ ፡ ውርንጫ ፡ ላይ ፡ ተቀምጦ ፡ ይመጣል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ኢየሱስ ፡ የአህያ ፡ ውርንጫ ፡ አግኝቶ ፡ በርሱ ፡ ተቀመጠ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በመዠመሪያ ፡ አላስተዋሉም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስ ፡ ከከበረ ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ይህ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ይህንም ፡ እንዳደረጉለት ፡ ትዝ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ አልዓዛርንም ፡ ከመቃብር ፡ ጠርቶ ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሕዝብ ፡ ይመሰክሩለት ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ ደግሞ ፡ ሕዝቡ ፡ ይህን ፡ ምልክት ፡ እንዳደረገ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ፥ ሊቀበሉት ፡ ወጡ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ልታደርጉ ፡ እንዳይቻላችኹ ፡ ታያላችኹን ፧ እንሆ ፥ ዓለሙ ፡ በኋላው ፡ ተከትሎት ፡ ኼዷል ፡ ተባባሉ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ በበዓሉም ፡ ሊሰግዱ ፡ ከወጡት ፡ አንዳንዶቹ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ ከገሊላ ፡ ቤተ ፡ ሳይዳ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ መጥተው ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ኢየሱስን ፡ ልናይ ፡ እንወዳለን ፡ ብለው ፡ ለመኑት ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ፊልጶስም ፡ መጥቶ ፡ ለእንድርያስ ፡ ነገረው ፤ እንድርያስና ፡ ፊልጶስ ፡ መጥተው ፡ ለኢየሱስ ፡ ነገሩት ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰላቸው ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ የሰው ፡ ልጅ ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፡ ሰዓቱ ፡ ደርሷል ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ የስንዴ ፡ ቅንጣት ፡ በምድር ፡ ወድቃ ፡ ካልሞተች ፡ ብቻዋን ፡ ትቀራለች ፤ ብትሞት ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ታፈራለች ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ነፍሱን ፡ የሚወድ ፡ ያጠፋታል ፥ ነፍሱንም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚጠላ ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ይጠብቃታል ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ የሚያገለግለኝ ፡ ቢኖር ፡ ይከተለኝ ፥ እኔም ፡ ባለኹበት ፡ አገልጋዬ ፡ ደግሞ ፡ በዚያ ፡ ይኾናል ፤ የሚያገለግለኝም ፡ ቢኖር ፡ አብ ፡ ያከብረዋል ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ አኹን ፡ ነፍሴ ፡ ታውካለች ፡ ምንስ ፡ እላለኹ ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ ከዚህ ፡ ሰዓት ፡ አድነኝ ። ነገር ፡ ግን ፥ ስለዚህ ፡ ወደዚህ ፡ ሰዓት ፡ መጣኹ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ አባት ፡ ሆይ ፥ ስምኽን ፡ አክብረው ። ስለዚህም ፦ አከበርኹት ፥ ደግሞም ፡ አከብረዋለኹ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ በዚያ ፡ ቆመው ፡ የነበሩትም ፡ ሕዝብ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ ነጐድጓድ ፡ ነው ፡ አሉ ፤ ሌላዎች ፦ መልአክ ፡ ተናገረው ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፥ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ይህ ፡ ድምፅ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ መጥቷል ፡ እንጂ ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ አይደለም ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 31 ፤ አኹን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍርድ ፡ ደርሷል ፤ አኹን ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዢ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይጣላል ፤

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 32 ፤ እኔም ፡ ከምድር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያልኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ኹሉን ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እስባለኹ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 33 ፤ በምን ፡ ዐይነትም ፡ ሞት ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ሲያመለክታቸው ፡ ይህን ፡ ተናገረ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 34 ፤ እንግዲህ ፡ ሕዝቡ ፦ እኛስ ፥ ክርስቶስ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንዲኖር ፡ ከሕጉ ፡ ሰምተናል ፤ አንተስ ፥ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡ እንዲያስፈልገው ፡ እንዴት ፡ ትላለኽ ፦ ይህ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ነው ፦ ብለው ፡ መለሱለት ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 35 ፤ ኢየሱስም ፦ ገና ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነው ። ጨለማ ፡ እንዳይደርስባችኹ ፡ ብርሃን ፡ ሳለላችኹ ፡ ተመላለሱ ፤ በጨለማም ፡ የሚመላለስ ፡ ወዴት ፡ እንዲኼድ ፡ አያውቅም ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 36 ፤ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ እንድትኾኑ ፡ ብርሃን ፡ ሳለላችኹ ፡ በብርሃኑ ፡ እመኑ ፡ አላቸው ። ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ኼደና ፡ ተሰወረባቸው ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 37-38 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ያኽል ፡ ምልክት ፡ በፊታቸው ፡ ምንም ፡ ቢያደርግ ፤ ነቢዩ ፡ ኢሳይያስ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ማን ፡ ምስክርነታችንን ፡ አመነ ፦ የእግዚአብሔርስ ፡ ክንድ ፡ ለማን ፡ ተገለጠ ፦ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፥ በርሱ ፡ አላመኑም ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 39-40 ፤ ኢሳይያስ ፡ ደግሞ ፦ በዐይኖቻቸው ፡ እንዳያዩ ፥ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፥ እንዳይመለሱም ፥ እኔም ፡ እንዳልፈውሳቸው ፥ ዐይኖቻቸውን ፡ አሳወረ ፡ ልባቸውንም ፡ አደነደነ ፡ ብሏልና ፥ ስለዚህ ፡ ማመን ፡ አቃታቸው ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 41 ፤ ክብሩን ፡ ስላየ ፡ ኢሳይያስ ፡ ይህን ፡ አለ ፥ ስለ ፡ ርሱም ፡ ተናገረ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 42 ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ከአለቃዎች ፡ ደግሞ ፡ ብዙዎች ፡ በርሱ ፡ አመኑ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከምኩራብ ፡ እንዳያስወጧቸው ፡ በፈሪሳውያን ፡ ምክንያት ፡ አልመሰከሩለትም ፤

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 43 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ይልቅ ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ወደዋልና ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 44 ፤ ኢየሱስም ፡ ጮኸ ፥ እንዲህም ፡ አለ ፦ በእኔ ፡ የሚያምን ፡ በላከኝ ፡ ማመኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በእኔ ፡ አይደለም ፤

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 45 ፤ እኔንም ፡ የሚያይ ፡ የላከኝን ፡ ያያል ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 46 ፤ በእኔ ፡ የሚያምን ፡ ኹሉ ፡ በጨለማ ፡ እንዳይኖር ፡ እኔ ፡ ብርሃን ፡ ኾኜ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጥቻለኹ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 47 ፤ ዓለምን ፡ ላድን ፡ እንጂ ፡ በዓለም ፡ ልፈርድ ፡ አልመጣኹምና ፡ ቃሌን ፡ ሰምቶ ፡ የማይጠብቀው ፡ ቢኖር ፡ የምፈርድበት ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 48 ፤ የሚጥለኝ ፡ ቃሌንም ፡ የማይቀበለው ፡ ርሱ ፡ የሚፈርድበት ፡ አለው ፤ እኔ ፡ የተናገርኹት ፡ ቃል ፡ ርሱ ፡ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ ይፈርድበታል ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 49 ፤ እኔ ፡ ከራሴ ፡ አልተናገርኹምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የላከኝ ፡ አብ ፡ ርሱ ፡ የምለውን ፡ የምናገረውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ሰጠኝ ።

ዮሐ. ፡ 12 ፡ 50 ፤ ትእዛዙም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ዐውቃለኹ ። ስለዚህ ፡ እኔ ፡ የምናገረውን ፡ አብ ፡ እንደ ፡ ነገረኝ ፡ እንዲሁ ፡ እናገራለኹ ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ ከፋሲካ ፡ በዓል ፡ በፊት ፥ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ወደ ፡ አብ ፡ የሚኼድበት ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ዐውቆ ፥ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ያሉትን ፡ ወገኖቹን ፡ የወደዳቸውን ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ወደዳቸው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ እራትም ፡ ሲበሉ ፡ ዲያብሎስ ፡ በስምዖን ፡ ልጅ ፡ በአስቆሮቱ ፡ በይሁዳ ፡ ልብ ፡ አሳልፎ ፡ እንዲሰጠው ፡ ዐሳብ ፡ ካገባ ፡ በኋላ ፥

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ኢየሱስ ፡ አብ ፡ ኹሉን ፡ በልጁ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲኼድ ፡ ዐውቆ ፥

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ከእራት ፡ ተነሣ ፡ ልብሱንም ፡ አኖረ ፥ ማበሻም ፡ ጨርቅ ፡ ወስዶ ፡ ታጠቀ ፤

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ በኋላም ፡ በመታጠቢያው ፡ ውሃ ፡ ጨመረ ፥ የደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ እግር ፡ ሊያጥብና ፡ በታጠቀበትም ፡ ማበሻ ፡ ጨርቅ ፡ ሊያብስ ፡ ዠመረ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ወደ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ መጣ ፤ ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ የእኔን ፡ እግር ፡ ታጥባለኽን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ አንተ ፡ አኹን ፡ አታውቅም ፥ በኋላ ፡ ግን ፡ ታስተውለዋለኽ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ጴጥሮስም ፦ የእኔን ፡ እግር ፡ ለዘለዓለም ፡ አታጥብም ፡ አለው ። ኢየሱስም ፦ ካላጠብኹኽ ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዕድል ፡ የለኽም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እጄንና ፡ ራሴን ፡ ደግሞ ፡ እንጂ ፡ እግሬን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፦ የታጠበ ፡ እግሩን ፡ ከመታጠብ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አያስፈልገውም ፥ ኹለንተናው ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ ንጹሓን ፡ ናችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹላችኹ ፡ አይደላችኹም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ አሳልፎ ፡ የሚሰጠውን ፡ ያውቅ ፡ ነበርና ፤ ስለዚህ ፦ ኹላችኹ ፡ ንጹሓን ፡ አይደላችኹም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ እግራቸውንም ፡ ዐጥቦ ፡ ልብሱንም ፡ አንሥቶ ፡ ዳግመኛ ፡ ተቀመጠ ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ ያደረግኹላችኹን ፡ ታስተውላላችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ መምህርና ፡ ጌታ ፡ ትሉኛላችኹ ፤ እንዲሁ ፡ ነኝና ፡ መልካም ፡ ትላላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፡ ጌታና ፡ መምህር ፡ ስኾን ፡ እግራችኹን ፡ ካጠብኹ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ እግራችኹን ፡ ትተጣጠቡ ፡ ዘንድ ፡ ይገባችኋል ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ለእናንተ ፡ እንዳደረግኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ምሳሌ ፡ ሰጥቻችኋለኹና ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ባሪያ ፡ ከጌታው ፡ አይበልጥም ። መልእክተኛም ፡ ከላከው ፡ አይበልጥም ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ይህን ፡ ብታውቁ ፥ ብታደርጉትም ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ስለ ፡ ኹላችኹ ፡ አልናገርም ፤ እኔ ፡ የመረጥኋቸውን ፡ ዐውቃለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መጽሐፍ ፦ እንጀራዬን ፡ የሚበላ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ተረከዙን ፡ አነሣብኝ ፡ ያለው ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፥ ካኹን ፡ ዠምሬ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይኾን ፡ እነግራችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ማናቸውን ፡ የምልከውን ፡ የሚቀበል ፡ እኔን ፡ ይቀበላል ፥ እኔንም ፡ የሚቀበል ፡ የላከኝን ፡ ይቀበላል ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡ ብሎ ፡ በመንፈሱ ፡ ታወከ ፡ መስክሮም ፦ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኛል ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስለ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ አመንትተው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተያዩ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ ይወደው ፡ የነበረ ፥ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንዱ ፥ በኢየሱስ ፡ ደረት ፡ ላይ ፡ ተጠጋ ፤

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ርሱን ፡ ጠቅሶ ፦ ስለማን ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ንገረን ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ርሱም ፥ በኢየሱስ ፡ ደረት ፡ እንዲህ ፡ ተጠግቶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ማን ፡ ነው ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ ቍራሽ ፡ አጥቅሼ ፡ የምሰጠው ፡ ርሱ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ። ቍራሽም ፡ አጥቅሶ ፡ ለአስቆሮቱ ፣ ለስምዖን ፡ ልጅ ፣ ለይሁዳ ፡ ሰጠው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ ቍራሽም ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ገባበት ። እንግዲህ ፡ ኢየሱስ ፦ የምታደርገውን ፡ ቶሎ ፡ ብለኽ ፡ አድርግ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከተቀመጡት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ይህን ፡ እንዳለው ፡ ማንም ፡ አላወቀም ፤

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ ይሁዳ ፡ ከረጢቱን ፡ የያዘ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኢየሱስ ፦ ለበዓሉ ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ግዛ ፥ ወይም ፡ ለድኻዎች ፡ ምጽዋት ፡ እንዲሰጥ ፡ ያለው ፡ ለአንዳንዱ ፡ መስሏቸው ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ ርሱም ፡ ቍራሹን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ወጣ ፤ ሌሊትም ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ ከወጣም ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አኹን ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ከበረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ከበረ ፤

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የከበረ ፡ ከኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ ርሱን ፡ ራሱን ፡ ያከብረዋል ፡ ወዲያውም ፡ ያከብረዋል ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፡ ገና ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፤ ትፈልጉኛላችኹ ፤ ለአይሁድም ፦ እኔ ፡ ወደምኼድበት ፡ እናንተ ፡ ልትመጡ ፡ አይቻላችኹም ፡ እንዳልኋቸው ፡ አኹን ፡ ለእናንተ ፡ ደግሞ ፡ እላችኋለኹ ፦

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 34 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትዋደዱ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ወደድኋችኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትዋደዱ ፡ ዘንድ ፡ ዐዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ እሰጣችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 35 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ፍቅር ፡ ቢኖራችኹ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ያውቃሉ ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 36 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፡ ወዴት ፡ ትኼዳለኽ ፧ አለው ። ኢየሱስም ፦ ወደምኼድበት ፡ አኹን ፡ ልትከተለኝ ፡ አትችልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ትከተለኛለኽ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 37 ፤ ጴጥሮስም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አኹን ፡ ልከተልኽ ፡ አለመቻሌ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ነፍሴን ፡ ስንኳ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እሰጣለኹ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 13 ፡ 38 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፦ ነፍስኽን ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ትሰጣለኽን ፧ እውነት ፡ እውነት ፡ እልኻለኹ ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እስክትክደኝ ፡ ድረስ ፡ ዶሮ ፡ አይጮኽም ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፤ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ ልባችኹ ፡ አይታወክ ፤ በእግዚአብሔር ፡ እመኑ ፤ በእኔም ፡ ደግሞ ፡ እመኑ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ በአባቴ ፡ ቤት ፡ ብዙ ፡ መኖሪያ ፡ አለ ፤ እንዲህስ ፡ ባይኾን ፡ ባልኋችኹ ፡ ነበር ፤ ስፍራ ፡ አዘጋጅላችኹ ፡ ዘንድ ፡ እኼዳለኹና ፤

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ኼጄም ፡ ስፍራ ፡ ባዘጋጅላችኹ ፤ እኔ ፡ ባለኹበት ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንድትኾኑ ፡ ኹለተኛ ፡ እመጣለኹ ፡ ወደ ፡ እኔም ፡ እወስዳችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ወደምኼድበትም ፡ ታውቃላችኹ ፤ መንገዱንም ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ቶማስም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፤ ወደምትኼድበት ፡ አናውቅም ፤ እንዴትስ ፡ መንገዱን ፡ እናውቃለን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ኢየሱስም ፦ እኔ ፡ መንገድና ፡ እውነት ፡ ሕይወትም ፡ ነኝ ፤ በእኔ ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ አብ ፡ የሚመጣ ፡ የለም ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ እኔንስ ፡ ብታውቁኝ ፡ አባቴን ፡ ደግሞ ፡ ባወቃችኹ ፡ ነበር ። ካኹንም ፡ ገምራችኹ ፡ ታውቁታላችኹ ፡ አይታችኹትማል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ፊልጶስ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፤ አብን ፡ አሳየንና ፡ ይበቃናል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ኢየሱስም ፡ አለው ፦ አንተ ፡ ፊልጶስ ፤ ይህን ፡ ያኽል ፡ ዘመን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ስኖር ፡ አታውቀኝምን ፧ እኔን ፡ ያየ ፡ አብን ፡ አይቷል ፤ እንዴትስ ፡ አንተ ፦ አብን ፡ አሳየን ፡ ትላለኽ ፧

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ እኔ ፡ በአብ ፡ እንዳለኹ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ እንዳለ ፡ አታምንምን ፧ እኔ ፡ የምነግራችኹን ፡ ቃል ፡

ከራሴ ፡ አልናገረውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእኔ ፡ የሚኖረው ፡ አብ ፡ ርሱ ፡ ሥራውን ፡ ይሠራል ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ እኔ ፡ በአብ ፡ እንዳለኹ ፡ አብም ፡ በእኔ ፡ እንዳለ ፡ እመኑኝ ፤ ባይኾንስ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ እመኑኝ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ በእኔ ፡ የሚያምን ፡ እኔ ፡ የማደርገውን ፡ ሥራ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ያደርጋል ፤ ከዚህም ፡ የሚበልጥ ፡ ያደርጋል ፥

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ እኼዳለኹና ፤ አብም ፡ ስለ ፡ ወልድ ፡ እንዲከበር ፡ በስሜ ፡ የምትለምኑትን ፡ ኹሉ ፡ አደርገዋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ማናቸውንም ፡ ነገር ፡ በስሜ ፡ ብትለምኑ ፡ እኔ ፡ አደርገዋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 15-16 ፤ ብትወዱኝ ፡ ትእዛዜን ፡ ጠብቁ ። እኔም ፡ አብን ፡ እለምናለኹ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዲኖር ፡ ሌላ ፡ አጽናኝ ፡ ይሰጣችኋል ፤

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ርሱም ፡ ዓለም ፡ የማያየውና ፡ የማያውቀው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሊቀበለው ፡ የማይቻለው ፡ የእውነት ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚኖር ፡ በውስጣችኹም ፡ ስለሚኾን ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ወላጆች ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ ልጆች ፡ አልተዋችኹም ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመጣለኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ ገና ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ አለ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ዓለም ፡ አያየኝም ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ታዩኛላችኹ ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ሕያዋን ፡ ትኾናላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ እኔ ፡ በአባቴ ፡ እንዳለኹ ፡ እናንተም ፡ በእኔ ፡ እንዳላችኹ ፡ እኔም ፡ በእናንተ ፡ እንዳለኹ ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ትእዛዜ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለችው ፡ የሚጠብቃትም ፡ የሚወደኝ ፡ ርሱ ፡ ነው ፤ የሚወደኝንም ፡ አባቴ ፡ ይወደዋል ፡ እኔም ፡ እወደዋለኹ ፡ ራሴንም ፡ እገልጥለታለኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ የአስቆሮቱ ፡ ያይደለ ፡ ይሁዳ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ለዓለም ፡ ሳይኾን ፡ ራስኽን ፡ ለእኛ ፡ ልትገልጥ ፡ ያለኽ ፡ እንዴት ፡ ነው ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ መለሰ ፥ አለውም ፦ የሚወደኝ ፡ ቢኖር ፡ ቃሌን ፡ ይጠብቃል ፤ አባቴም ፡ ይወደዋል ፡ ወደ ፡ ርሱም ፡ እንመጣለን ፡ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ መኖሪያ ፡ እናደርጋለን ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 24 ፤ የማይወደኝ ፡ ቃሌን ፡ አይጠብቅም ፤ የምትሰሙትም ፡ ቃል ፡ የላከኝ ፡ የአብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የእኔ ፡ አይደለም ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 25 ፤ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስኖር ፡ ይህን ፡ ነግሬያችኋለኹ ፤

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 26 ፤ አብ ፡ በስሜ ፡ የሚልከው ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የኾነው ፡ አጽናኝ ፡ ርሱ ፡ ኹሉን ፡ ያስተምራችኋል ፥ እኔም ፡ የነገርኋችኹን ፡ ኹሉ ፡ ያሳስባችኋል ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 27 ፤ ሰላምን ፡ እተውላችኋለኹ ፥ ሰላሜን ፡ እሰጣችኋለኹ ፤ እኔ ፡ የምሰጣችኹ ፡ ዓለም ፡ እንደሚሰጥ ፡ አይደለም ። ልባችኹ ፡ አይታወክ ፡ አይፍራም ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 28 ፤ እኔ ፡ እኼዳለኹ ፡ ወደ ፡ እናንተም ፡ እመጣለኹ ፡ እንዳልኋችኹ ፡ ሰማችኹ ። የምትወዱኝስ ፡ ብትኾኑ ፡ ከእኔ ፡ አብ ፡ ይበልጣልና ፥ ወደ ፡ አብ ፡ በመኼዴ ፡ ደስ ፡ ባላችኹ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 29 ፤ ከ"ኾነም ፡ በ"ኋላ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ አ"ኩን ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይ"ኮን ፡ ነግሬያች"ኋለ"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 30 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ አልናገርም ፥ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዢ ፡ ይመጣልና ፤ በእኔ ፡ ላይም ፡ አንዳች ፡ የለውም ፤

ዮሐ. ፡ 14 ፡ 31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አብን ፡ እንድወድ ፡ ዓለም ፡ ሊያውቅ ፥ አብም ፡ እንዳዘዘኝ ፥ እንዲሁ ፡ አደርጋለ"ኹ ። ተነሡ ፤ ከዚህ ፡ እን"ኪድ ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ እውነተኛ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ገበሬውም ፡ አባቴ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ ፍሬ ፡ የማያፈራውን ፡ በእኔ ፡ ያለውን ፡ ቅርንጫፍ ፡ "ሹሉ ፡ ያስወግደዋል ፤ ፍሬ ፡ የሚያፈራውንም ፡ "ሹሉ ፡ አብዝቶ ፡ እንዲያፈራ ፡ ያጠራዋል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ እናንተ ፡ ስለነገር"ኋች"ኹ ፡ ቃል ፡ አ"ኩን ፡ ንጹሓን ፡ ናች"ኹ ፤

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ በእኔ ፡ ኑሩ ፡ እኔም ፡ በእናንተ ። ቅርንጫፍ ፡ በወይኑ ፡ ግንድ ፡ ባይኖር ፡ ከራሱ ፡ ፍሬ ፡ ሊያፈራ ፡ እንዳይቻለው ፥ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በእኔ ፡ ባትኖሩ ፡ አትችሉም ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ እኔ ፡ የወይን ፡ ግንድ ፡ ነኝ ፡ እናንተም ፡ ቅርንጫፎች ፡ ናች"ኹ ። ያለእኔ ፡ ምንም ፡ ልታደርጉ ፡ አትችሉምና ፡ በእኔ ፡ የሚኖር ፡ እኔም ፡ በርሱ ፥ ርሱ ፡ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ያፈራል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ በእኔ ፡ የማይኖር ፡ ቢ"ኮን ፡ እንደ ፡ ቅርንጫፍ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይጣላል ፡ ይደርቅማል ፤ እነርሱንም ፡ ሰብስበው ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ይጥሏቸዋል ፥ ያቃጥሏቸውማል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ በእኔ ፡ ብትኖሩ ፡ ቃሎቼም ፡ በእናንተ ፡ ቢኖሩ ፡ የምትወዱትን ፡ "ሹሉ ፡ ለምኑ ፡ ይ"ኮንላች"ኹማል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ብዙ ፡ ፍሬ ፡ ብታፈሩና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ ብት"ኾኑ ፡ በዚህ ፡ አባቴ ፡ ይከበራል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 9 ፤ አብ ፡ እንደ ፡ ወደደኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ወደድ"ኋች"ኹ ፤ በፍቅሬ ፡ ኑሩ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ እኔ ፡ የአባቴን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ጠበቅ"ኩ ፡ በፍቅሩም ፡ እንደምኖር ፥ ትእዛዜን ፡ ብትጠብቁ ፡ በፍቅሬ ፡ ትኖራላች"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ደስታዬም ፡ በእናንተ ፡ እንዲ"ኮን ፡ ደስታች"ኹም ፡ እንዲፈጸም ፡ ይህን ፡ ነግሬያች"ኋለ"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ እኔ ፡ እንደ ፡ ወደድ"ኋች"ኹ ፡ ርስ ፡ በርሳች"ኹ ፡ ትዋደዱ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዜ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ ነፍሱን ፡ ስለ ፡ ወዳጆቹ ፡ ከመስጠት ፡ ይልቅ ፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥ ፡ ፍቅር ፡ ለማንም ፡ የለውም ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ እኔ ፡ ያዘዝ"ኋች"ኹን ፡ "ሹሉ ፡ ብታደርጉ ፡ እናንተ ፡ ወዳጆቼ ፡ ናች"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባሪያዎች ፡ አልላች"ኹም ፤ ባሪያ ፡ ጌታው ፡ የሚያደርገውን ፡ አያውቅምና ፤ ወዳጆች ፡ ግን ፡ ብያች"ኋለ"ኹ ፥ ከአባቴ ፡ የሰማ"ኩትን ፡ "ሹሉ ፡ ለእናንተ ፡ አስታውቄያች"ኋለ"ኹና ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 16 ፤ እኔ ፡ መረጥ"ኋች"ኹ ፡ እንጂ ፡ እናንተ ፡ አልመረጣች"ኹኝም ፤ አብም ፡ በስሜ ፡ የምትለምኑትን ፡ "ሹሉ ፡ እንዲሰጣች"ኹ ፥ ልትኼዱና ፡ ፍሬ ፡ ልታፈሩ ፡ ፍሬያች"ኹም ፡ ሊኖር ፡ ሾምኋች"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ ርስ ፡ በርሳች"ኹ ፡ እንድትዋደዱ ፡ ይህን ፡ አዛች"ኋለ"ኹ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ዓለም ፡ ቢጠላችኹ ፡ ከእናንተ ፡ በፊት ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ጠላኝ ፡ ዕወቁ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ከዓለምስ ፡ ብትኾኑ ፡ ዓለም ፡ የራሱ ፡ የኾነውን ፡ ይወድ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኔ ፡ ከዓለም ፡ መረጥኋችኹ ፡ እንጂ ፡ ከዓለም ፡ ስላይደላችኹ ፡ ስለዚህ ፡ ዓለም ፡ ይጠላችኋል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ባሪያ ፡ ከጌታው ፡ አይበልጥም ፡ ብዬ ፡ የነገርኋችኹን ፡ ቃል ፡ ዐስቡ ። እኔን ፡ አሳደውኝ ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ እናንተን ፡ ደግሞ ፡ ያሳድዷችኋል ፤ ቃሌን ፡ ጠብቀው ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ቃላችኹን ፡ ደግሞ ፡ ይጠብቃሉ ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የላከኝን ፡ አያውቁምና ፡ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡ ያደርጉባችኋል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ እኔ ፡ መጥቼ ፡ ባልነገርኋቸውስ ፡ ኀጢአት ፡ ባልኾነባቸውም ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ለኀጢአታቸው ፡ ምክንያት ፡ የላቸውም ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ እኔን ፡ የሚጠላ ፡ አባቴን ፡ ደግሞ ፡ ይጠላል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ሌላ ፡ ሰው ፡ ያላደረገውን ፡ ሥራ ፡ በመካከላቸው ፡ ባላደረግኹ ፥ ኀጢአት ፡ ባልኾነባቸውም ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እኔንም ፡ አባቴንም ፡ አይተውማል ፡ ጠልተውማል ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕጋቸው ፦ በከንቱ ፡ ጠሉኝ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የምልክላችኹ ፡ አጽናኝ ፡ ርሱም ፡ ከአብ ፡ የሚወጣ ፡ የእውነት ፡ መንፈስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፥ ርሱ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ይመሰክራል ፤

ዮሐ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ከመገ፞ሥመሪያ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ኖራችኋልና ፥ ትመሰክራላችኹ ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ እንዳትሰናከሉ ፡ ይህን ፡ ተናግሬያችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ከምኩራባቸው ፡ ያወጧችኋል ፤ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፡ የሚገድላችኹ ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚያገለግል ፡ የሚመስልበት ፡ ጊዜ ፡ ይመጣል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ይህንም ፡ የሚያደርጉባችኹ ፡ አብንና ፡ እኔን ፡ ስላላወቁ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጊዜው ፡ ሲደርስ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ነገርኋችኹ ፡ ታስቡ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ተናግሬያችኋለኹ ። ከእንናንተም ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ነበርኹ ፡ በመገ፞ሥመሪያ ፡ ይህን ፡ አልነገርኋችኹም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ወደላከኝ ፡ እኼዳለኹ ፡ ከእናንተም ፦ ወዴት ፡ ትኼዳለኽ ፧ ብሎ ፡ የሚጠይቀኝ ፡ የለም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ ስለ ፡ ተናገርኋችኹ ፡ ሐዘን ፡ በልባችኹ ፡ ሞልቷል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ እነግራችኋለኹ ፤ እኔ ፡ እንድኼድ ፡ ይሻላችኋል ። እኔ ፡ ባልኼድ ፡ አጽናኙ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አይመጣምና ፤ እኔ ፡ ብኼድ ፡ ግን ፡ ርሱን ፡ እልክላችኋለኹ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ጽድቅም ፡ ስለ ፡ ፍርድም ፡ ዓለምን ፡ ይወቅሳል ፤

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 9-10 ፤ ስለ ፡ ኀጢአት ፥ በእኔ ፡ ስለማያምኑ ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ጽድቅም ፥ ወደ ፡ አብ ፡ ስለምኼድ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስለማታዩኝ ፡ ነው ፤

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ስለ ፡ ፍርድም ፥ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገዢ ፡ ስለ ፡ ተፈረደበት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ የምነግራችኹ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ አለኝ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ ልትሸከሙት ፡ አትችሉም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ግን ፡ ርሱ ፡ የእውነት ፡ መንፈስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ኹሉ ፡ ይመራችኋል ፤ የሚሰማውን ፡ ኹሉ ፡ ይናገራል ፡ እንጂ ፡ ከራሱ ፡ አይነግርምና ፤ የሚመጣውንም ፡ ይነግራችኋል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ርሱ ፡ ያከብረኛል ፥ ለእኔ ፡ ካለኝ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋልና ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ለአብ ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ ስለዚህ ፦ ለእኔ ፡ ካለኝ ፡ ወስዶ ፡ ይነግራችኋል ፡ አልኹ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ አታዩኝምም ፤ ደግሞም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ ታዩኛላችኹም ፥ እኔ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ እኼዳለኹና ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ አታዩኝምም ፤ ደግሞም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ ታዩኛላችኹም ፤ ደግሞ ፦ ወደ ፡ አብ ፡ እኼዳለኹና ፡ የሚለን ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ተባባሉ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፦ ጥቂት ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ የሚናገረውን ፡ አናውቅም ፡ አሉ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ኢየሱስም ፡ ሊጠይቁት ፡ እንደ ፡ ወደዱ ፡ ዐውቆ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ አታዩኝምም ፤ ደግሞም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ አለ ፥ ታዩኛላችኹ ፡ ስላልኹ ፥ ስለዚህ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትመራመራላችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ እናንተ ፡ ታለቅሳላችኹ ፡ ሙሾም ፡ ታወጣላችኹ ፥ ዓለም ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ እናንተም ፡ ታዝናላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሐዘናችኹ ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ ይለወጣል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ሴት ፡ በምትወልድበት ፡ ጊዜ ፡ ወራቷ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ታዝናለች ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕፃን ፡ ከወለደች ፡ በኋላ ፥ ሰው ፡ በዓለም ፡ ተወልዷልና ፥ ስለ ፡ ደስታዋ ፡ መከራዋን ፡ ኋላ ፡ አታስበውም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ እንግዲህ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ አኹን ፡ ታዝናላችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ገና ፡ አያችኋለኹ ፡ ልባችኹም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፥ ደስታችኹንም ፡ የሚወስድባችኹ ፡ የለም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ በዚያ ፡ ቀንም ፡ ከእኔ ፡ አንዳች ፡ አትለምኑም ። እውነት ፡ እውነት ፡ እላችኋለኹ ፥ አብ ፡ በስሜ ፡ የምትለምኑትን ፡ ኹሉ ፡ ይሰጣችኋል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ እስከ ፡ አኹን ፡ በስሜ ፡ ምንም ፡ አልለመናችኹም ፤ ደስታችኹ ፡ ፍጹም ፡ እንዲኾን ፡ ለምኑ ፡ ትቀበሉማላችኹ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ ይህን ፡ በምሳሌ ፡ ነግሬያችኋለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ አብ ፡ ለእናንተ ፡ በግልጥ ፡ የምናገርበት ፡ እንጂ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ በምሳሌ ፡ የማልናገርበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ በስሜ ፡ ትለምናላችኹ ፤ እኔም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አብን ፡ እንድለምን ፡ የምላችኹ ፡ አይደለኹም ፤

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ እናንተ ፡ ስለ ፡ ወደዳችኹኝ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ወጣኹ ፡ ስላመናችኹ ፡ አብ ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ይወዳችኋልና ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ከአብ ፡ ወጥቼ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጥቻለኹ ፤ ደግሞ ፡ ዓለምን ፡ እተወዋለኹ ፡ ወደ ፡ አብም ፡ እኼዳለኹ ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ እንሆ ፥ አኹን ፡ በግልጥ ፡ ትናገራለኽ ፡ በምሳሌም ፡ ምንም ፡ አትነግርም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ኹሉን ፡ እንድታውቅ ፥ ማንምም ፡ ሊጠይቅኽ ፡ እንዳትፈልግ ፡ አኹን ፡ እናውቃለን ፤ ስለዚህ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ወጣኽ ፡ እናምናለን ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ ኢየሱስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰላቸው ። አኹን ፡ ታምናላችኹን ፧

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ እንሆ ፥ እያንዳንዳችኹ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ የምትበታተኑበት ፡ እኔንም ፡ ለብቻዬ ፡ የምትተዉበት ፡ ሰዓት ፡ ይመጣል ፥ አኹንም ፡ ደርሷል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አብ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ብቻዬን ፡ አይደለኹም ።

ዮሐ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ በእኔ ፡ ሳላችኹ ፡ ሰላም ፡ እንዲኾንላችኹ ፡ ይህን ፡ ተናግሬያችኋለኹ ። በዓለም ፡ ሳላችኹ ፡ መከራ ፡ አለባችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አይዟችኹ ፤ እኔ ፡ ዓለምን ፡ አሸንፌዋለኹ ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ። _____

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 1-2 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐይኖቹን ፡ አነሣና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ አባት ፡ ሆይ ፥ ሰዓቱ ፡ ደርሷል ፤ ልጅኽ ፡ ያከብርኽ ፡ ዘንድ ፥ በሥጋም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሰጠኸው ፥ ለሰጠኸው ፡ ኹሉ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይሰጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ልጅኽን ፡ አክብረው ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ የኾንኽ ፡ አንተን ፡ የላክኸውንም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ይህች ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ናት ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ላደርገው ፡ የሰጠኸኝን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሜ ፡ በምድር ፡ አከበርኹኽ ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ አኹንም ፥ አባት ፡ ሆይ ፥ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበረኝ ፡ ክብር ፡ አንተ ፡ በራስኽ ፡ ዘንድ ፡ አክብረኝ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ከዓለም ፡ ለሰጠኸኝ ፡ ሰዎች ፡ ስምኽን ፡ ገለጥኹላቸው ። የአንተ ፡ ነበሩ ፡ ለኔም ፡ ሰጠኻቸው ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ ቃልኽንም ፡ ጠብቀዋል ። የሰጠኸኝ ፡ ኹሉ ፡ ከአንተ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አኹን ፡ ያውቃሉ ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ የሰጠኸኝን ፡ ቃል ፡ ሰጥቻቸዋለኹና ፤ እነርሱም ፡ ተቀበሉት ፥ ከአንተም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ወጣኹ ፡ በእውነት ፡ ዐወቁ ፥ አንተም ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ አመኑ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ እለምናለኹ ፤ ስለ ፡ ዓለም ፡ አልለምንም ፡ ስለሰጠኸኝ ፡ እንጂ ፤ የአንተ ፡ ናቸውና ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ የእኔም ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ የአንተ ፡ ነው ፡ የአንተውም ፡ የእኔ ፡ ነው ፤ እኔም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ከብሬያለኹ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በዓለም ፡ አይደለኹም ፥ እነርሱም ፡ በዓለም ፡ ናቸው ፥ እኔም ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለኹ ። ቅዱስ ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ እነዚህን ፡ የሰጠኸኝን ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ አንድ ፡ እንዲኾኑ ፡ በስምኽ ፡ ጠብቃቸው ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በዓለም ፡ ሳለኹ ፡ የሰጠኸኝን ፡ በስምኽ ፡ እኔ ፡ እጠብቃቸው ፡ ነበር ፤ ጠበቅኋቸውም ፡ መጽሐፉም ፡ እንዲፈጸም ፡ ከጥፋት ፡ ልጅ ፡ በቀር ፡ ከነርሱ ፡ ማንም ፡ አልጠፋም ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ ወዳንተ ፡ እመጣለኹ ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ደስታዬ ፡ የተፈጸመ ፡ እንዲኾንላቸው ፡ ይህን ፡ በዓለም ፡ እናገራለኹ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ እኔ ፡ ቃልኽን ፡ ሰጥቻቸዋለኹ ፤ እኔም ፡ ከዓለም ፡ እንዳይደለኹ ፡ ከዓለም ፡ አይደሉምና ፡ ዓለም ፡

ጠላቸው ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ከክፉ ፡ እንድትጠብቃቸው ፡ እንጂ ፡ ከዓለም ፡ እንድታወጣቸው ፡ አልለምንም ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ከዓለም ፡ እንዳይደለኹ ፡ ከዓለም ፡ አይደሉም ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ በእውነትኽ ፡ ቀድሳቸው ፤ ቃልኽ ፡ እውነት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ እንዲሁ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ላክኋቸው ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 19 ፤ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ በእውነት ፡ የተቀደሱ ፡ እንዲኾኑ ፡ እኔ ፡ ራሴን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ እቀድሳለኹ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 20-21 ፤ ኹሉም ፡ አንድ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፥ ከቃላቸው ፡ የተነሣ ፡ በእኔ ፡ ስለሚያምኑ ፡ ደግሞ ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ብቻ ፡ አልለምንም ፤ አንተ ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ ዓለም ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፥ አንተ ፥ አባት ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ እንዳለኽ ፡ እኔም ፡ ባንተ ፥ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በእኛ ፡ አንድ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ እለምናለኹ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 22-23 ፤ እኛም ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ አንድ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፤ እኔም ፡ በእነርሱ ፡ አንተም ፡ በእኔ ፡ ስትኾን ፥ ባንድ ፡ ፍጹማን ፡ እንዲኾኑ ፥ የሰጠኸኝን ፡ ክብር ፡ እኔ ፡ ሰጥቻቸዋለኹ ፤ እንዲሁም ፡ ዓለም ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ በወደድኸኝም ፡ መጠን ፡ እነርሱን ፡ እንደ ፡ ወደድኻቸው ፡ ያውቃል ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ አባት ፡ ሆይ ፥ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ስለ ፡ ወደድኸኝ ፡ የሰጠኸኝን ፡ ክብሬን ፡ እንዲያዩ ፡ እኔ ፡ ባለኹበት ፡ የሰጠኸኝ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ።

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 25 ፤ ጻድቅ ፡ አባት ፡ ሆይ ፥ ዓለም ፡ አላወቀኽም ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ዐወቅኹኽ ፡ እነዚህም ፡ አንተ ፡ እንደ ፡ ላክኸኝ ፡ ዐወቁ ፤

ዮሐ. ፡ 17 ፡ 26 ፤ እኔንም ፡ የወደድኽባት ፡ ፍቅር ፡ በእነርሱ ፡ እንድትኾን ፡ እኔም ፡ በእነርሱ ፥ ስምኽን ፡ አስታወቅኋቸው ፡ አስታውቃቸውማለኹ ።

የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ ኢየሱስም ፡ ይህን ፡ ብሎ ፡ አትክልት ፡ ወዳለበት ፡ ስፍራ ፡ ወደቄድሮን ፡ ወንዝ ፡ ማዶ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወጣ ፤ ርሱም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በዚያ ፡ ገቡ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ ኢየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደዚያ ፡ ስለ ፡ ተሰበሰቡ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ ይሁዳ ፡ ደግሞ ፡ ስፍራውን ፡ ያውቅ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ይሁዳ ፡ ጭፍራዎችንና ፥ ከካህናት ፡ አለቃዎች ፣ ከፈሪሳውያንም ፡ ሎሌዎችን ፡ ተቀብሎ ፥ በችቦና ፡ በፋና ፣ በጋሻ ፡ ጦርም ፡ ወደዚያ ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ኢየሱስም ፥ የሚመጣበትን ፡ ኹሉ ፡ ዐውቆ ፡ ወጣና ፦ ማንን ፡ ትፈልጋላችኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ ብለው ፡ መለሱለት ። ኢየሱስ ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላቸው ። አሳልፎ ፡ የሰጠውም ፡ ይሁዳ ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ እንግዲህ ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈግፍገው ፡ በምድር ፡ ወደቁ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ደግሞም ፦ ማንን ፡ ትፈልጋላችኹ ፧ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እነርሱም ፦ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ኢየሱስ ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ ነኝ ፡ አልኋችኹ ፤ እንግዲህ ፡ እኔን ፡ ትፈልጉ ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ እነዚህ ፡ ይኺዱ ፡ ተዉአቸው ፡ አለ ፤

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ይህም ፦ ከነዚህ ፡ ከሰጠኸኝ ፡ አንዱን ፡ ስንኳ ፡ አላጠፋኹም ፡ ያለው ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ሰይፍ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ መዘዘው ፥ የሊቀ ፡ ካህናቱንም ፡ ባሪያ ፡ መቶ ፡ ቀኝ ፡ ጕሮውን ፡ ቈረጠ ፤ የባሪያውም ፡ ስም ፡ ማልኮስ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ ጴጥሮስን ፦ ሰይፍኽን ፡ ወደ ፡ ሰገባው ፡ ክተተው ፤ አብ ፡ የሰጠኝን ፡ ጽዋ ፡ አልጠጣትምን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ የሻለቃውና ፡ ጭፍራዎቹ ፡ የአይሁድም ፡ ሎሌዎች ፡ ኢየሱስን ፡ ይዘው ፡ አሰሩት ፥

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ አስቀድመውም ፡ ወደ ፡ ሐና ፡ ወሰዱት ፤ በዚያች ፡ ዓመት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ለነበረው ፡ ለቀያፋ ፡ ዐማቱ ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ ቀያፋም ፦ አንድ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ይሻላል ፡ ብሎ ፡ ለአይሁድ ፡ የመከራቸው ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 15 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ሌላውም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ኢየሱስን ፡ ተከተሉ ። ያም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነበረ ፥ ወደሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ግቢ ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ ገባ ፤

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 16 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ በውጭ ፡ በበሩ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፡ በሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀው ፡ ሌላው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወጣ ፥ ለበረኛዪቱም ፡ ነግሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ አስገባው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 17 ፤ በረኛ ፡ የነበረችዪቱም ፡ ገረድ ፡ ጴጥሮስን ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ሰው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አንዱ ፡ አይደለኽምን ፧ አለችው ። ርሱ ፦ አይደለኹም ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ ብርድ ፡ ነበረና ፡ ባሪያዎችና ፡ ሎሌዎች ፡ የፍም ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ ቆሙ ፡ ይሞቁም ፡ ነበር ፤ ጴጥሮስም ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቆሞ ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ኢየሱስን ፡ ስለ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱና ፡ ስለ ፡ ትምህርቱ ፡ ጠየቀው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ኢየስስም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ በግልጥ ፡ ለዓለም ፡ ተናገርኹ ፤ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ በሚሰበሰቡበት ፡ በምኩራብና ፡ በመቅደስ ፡ እኔ ፡ ኹልጊዜ ፡ አስተማርኹ ፥ በስውርም ፡ ምንም ፡ አልተናገርኹም ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ስለምን ፡ ትጠይቀኛለኽ ፧ ለእነርሱ ፡ የተናገርኹትን ፡ የሰሙትን ፡ ጠይቅ ፤ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ እኔ ፡ የነገርኹትን ፡ ያውቃሉ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ይህንም ፡ ሲል ፡ በዚያ ፡ ቆሞ ፡ የነበረው ፡ ከሎሌዎች ፡ አንዱ ፦ ለሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ እንዲህ ፡ ትመልሳለኽን ፧ ብሎ ፡ ኢየሱስን ፡ በጥፊ ፡ መታው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ክፉ ፡ ተናግሬ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ መስክር ፤ መልካም ፡ ተናግሬ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ግን ፡ ሰለ ፡ ምን ፡ ትመታኛለኽ ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ሐና ([290]) ፥ እንደ ፡ ታሰረ ፥ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፣ ወደ ፡ ቀያፋ ፡ ሰደደው ።

---

290 ዕብ. ፡ ሐናንያ ። ጽር. ፡ ἀνὰς ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ቆሞ ፡ እሳት ፡ ይሞቅ ፡ ነበር ። እንግዲህ ፦ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አይደለኽምን ፧ አሉት ። ርሱም ፦ አይደለኹም ፡ ብሎ ፡ ካደ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ጴጥሮስ ፡ ጕሮውን ፡ የቈረጠው ፡ ዘመድ ፡ የኾነ ፡ ከሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ባሪያዎች ፡ አንዱ ፦ በአትክልቱ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እኔ ፡ አይቼኽ ፡ አልነበረምን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ጴጥሮስም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ካደ ፥ ወዲያውም ፡ ዶሮ ፡ ጮኸ ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ኢየሱስንም ፡ ከቀያፋ ፡ ወደገዢው ፡ ግቢ ፡ ወሰዱት ፤ ማለዳም ፡ ነበረ ፤ እነርሱም ፡ የፋሲካ ፡ በግ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ እንዳይረክሱ ፡ ወደገዢው ፡ ግቢ ፡ አልገቡም ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 29 ፤ ስለዚህ ፥ ጲላጦስ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፤ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ወጥቶ ፦ ይህን ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትከሱታላችኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 30 ፤ እነርሱም ፡ መልሰው ፦ ይህስ ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ ባይኾን ፡ ወዳንተ ፡ አሳልፈን ፡ ባልሰጠነውም ፡ ነበር ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 31 ፤ ጲላጦስም ፦ እናንተ ፡ ወስዳችኹ ፡ እንደ ፡ ሕጋችኹ ፡ ፍረዱበት ፡ አላቸው ። አይሁድም ፦ ለእኛስ ፡ ማንንም ፡ ልንገድል ፡ አልተፈቀደልንም ፡ አሉት ፤

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 32 ፤ ኢየሱስ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ ሞት ፡ ሊሞት ፡ እንዳለው ፡ ሲያመለክት ፡ የተናገረው ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 33 ፤ ጲላጦስም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደገዢው ፡ ግቢ ፡ ገባና ፡ ኢየሱስን ፡ ጠርቶ ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ አንተ ፡ ነኽን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 34 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ አንተ ፡ ይህን ፡ የምትለው ፡ ከራስኽ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ሌላዎች ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ነገሩኽን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 35 ፤ ጲላጦስ ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነኝን ፧ ወገኖችኽና ፡ የካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ለእኔ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡኽ ፤ ምን ፡ አድርገኻል ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 36 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ መንግሥቴ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ፤ መንግሥቴስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ብትኾን ፥ ወደ ፡ አይሁድ ፡ እንዳልሰጥ ፡ ሎሌዎቼ ፡ ይዋጉልኝ ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፡ መንግሥቴ ፡ ከዚህ ፡ አይደለችም ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 37 ፤ ጲላጦስም ፦ እንግዲያ ፡ ንጉሥ ፡ ነኽን ፧ አለው ። ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አንተ ፡ ትላለኽ ። እኔ ፡ ለእውነት ፡ ልመሰክር ፡ ስለዚህ ፡ ተወልጃለኹ ፡ ስለዚህም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጥቻለኹ ፤ ከእውነት ፡ የኾነ ፡ ኹሉ ፡ ድምፄን ፡ ይሰማል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 38 ፤ ጲላጦስ ፦ እውነት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ ዳግመኛ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ወጥቶ ፦ እኔስ ፡ አንዲት ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ አላገኘኹበትም ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 39 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በፋሲካ ፡ አንድ ፡ ልፈታላችኹ ፡ ልማድ ፡ አላችኹ ፤ እንግዲህ ፡ የአይሁድን ፡ ንጉሥ ፡ ልፈታላችኹ ፡ ትወዳላችኹን ፧ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 18 ፡ 40 ፤ ኹሉም ፡ ደግመው ፦ በርባንን ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ አይደለም ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። በርባን ፡ ግን ፡ ወንበዴ ፡ ነበረ ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። _____

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 1 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ጲላጦስ ፡ ኢየሱስን ፡ ይዞ ፡ ገረፈው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 2 ፤ ወታደሮችም ፡ ከሾኽ ፡ አክሊል ፡ ጐንጉነው ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አኖሩ ፡ ቀይ ፡ ልብስም ፡ አለበሱት ፤

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 3 ፤ እየቀረቡም ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ፡ ይሉት ፡ ነበር ፤

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 4 ፤ በጥፊም ፡ ይመቱት ፡ ነበር ። ጲላጦስም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጥቶ ፦ እንሆ ፥ አንዲት ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ እንዳላገኘኹበት ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ርሱን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጣላችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ የሾኽ ፡ አክሊል ፡ ደፍቶ ፡ ቀይ ፡ ልብስም ፡ ለብሶ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 6 ፤ ጲላጦስም ፦ እንሆ ፥ ሰውዬው ፡ አላቸው ። የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ሎሌዎች ፡ ባዩትም ፡ ጊዜ ፦ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ጲላጦስም ፦ እኔስ ፡ አንዲት ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ አላገኘኹበትምና ፡ እናንተ ፡ ወስዳችኹ ፡ ስቀሉት ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 7 ፤ አይሁድም ፡ መልሰው ፦ እኛ ፡ ሕግ ፡ አለን ፥ እንደ ፡ ሕጋችንም ፡ ሊሞት ፡ ይገባዋል ፥ ራሱን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አድርጓልና ፥ አሉት ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ጲላጦስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ እጅግ ፡ ፈራ ፤

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 9 ፤ ተመልሶም ፡ ወደገዢው ፡ ግቢ ፡ ገባና ፡ ኢየሱስን ፦ አንተ ፡ ከወዴት ፡ ነኽ ፧ አለው ። ኢየሱስ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ አልመለሰለትም ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ጲላጦስ ፦ አትነግረኝምን ፧ ልሰቅልኽ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለኝ ፡ ወይም ፡ ልፈታኽ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለኝ ፡ አታውቅምን ፧ አለው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 11 ፤ ኢየሱስም ፡ መልሶ ፦ ከላይ ፡ ካልተሰጠኽ ፡ በቀር ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ ባልነበረኽም ፤ ስለዚህ ፥ ለአንተ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠኝ ፥ ኀጢአቱ ፡ የባሰ ፡ ነው ፡ አለው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 12 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጲላጦስ ፡ ሊፈታው ፡ ፈለገ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አይሁድ ፦ ይህንስ ፡ ብትፈታው ፡ የቄሳር ፡ ወዳጅ ፡ አይደለኽም ፤ ራሱን ፡ ንጉሥ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ የቄሳር ፡ ተቃዋሚ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 13 ፤ ጲላጦስም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ኢየሱስን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አወጣው ፥ በዕብራይስጥም ፡ ገበታ ፡ በተባለው ፡ ጸፍጸፍ ፡ በሚሉት ፡ ስፍራ ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ተቀመጠ ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 14 ፤ ለፋሲካም ፡ የማዘጋጀት ፡ ቀን ፡ ነበረ ፤ ስድስት ፡ ሰዓትም ፡ የሚያኽል ፡ ነበረ ፤ አይሁድንም ፦ እንሆ ፥ ንጉሣችኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 15 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፦ አስወግደው ፥ አስወግደው ፥ ስቀለው ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ። ጲላጦስም ፦ ንጉሣችኹን ፡ ልስቀለውን ፧ አላቸው ። የካህናት ፡ አለቃዎችም ፦ ከቄሳር ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ የለንም ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 16 ፤ ስለዚህ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንዲሰቀል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 17 ፤ ኢየሱስንም ፡ ይዘው ፡ ወሰዱት ፤ መስቀሉንም ፡ ተሸክሞ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ጎልጎታ ፡ ወደተባለው ፡ የራስ ፡ ቅል ፡ ስፍራ ፡ ወደሚሉት ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፥ 19 ፥ 18 ፤ በዚያም ፡ ሰቀሉት ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ሌላዎች ፡ ኹለት ፥ አንዱን ፡ በዚህ ፡ አንዱን ፡ በዚያ ፡

ኢየሱስንም ፡ በመካከላቸው ፡ ሰቀሉ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ጲላጦስም ፡ ደግሞ ፡ ጽሕፈት ፡ ጽፎ ፡ በመስቀሉ ፡ ላይ ፡ አኖረው ፤ ጽሕፈቱም ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ የሚል ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ ኢየሱስም ፡ የተሰቀለበት ፡ ስፍራ ፡ ለከተማ ፡ ቅርብ ፡ ነበረና ፡ ከአይሁድ ፡ ብዙዎች ፡ ይህን ፡ ጽሕፈት ፡ አነበቡት ፤ በዕብራይስጥና ፡ በሮማይስጥ ፡ በግሪክም ፡ ተጽፎ ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ የአይሁድ ፡ ካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ጲላጦስን ፦ ርሱ ፦ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡ እንዳለ ፡ እንጂ ፥ የአይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ብለኽ ፡ አትጻፍ ፡ አሉት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ጲላጦስም ፦ የጻፍኹትን ፡ ጽፌያለኹ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ ጭፍራዎችም ፡ ኢየሱስን ፡ በሰቀሉት ፡ ጊዜ ፡ ልብሶቹን ፡ ወስደው ፡ ለያንዳንዱ ፡ ጭፍራ ፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ኾኖ ፡ በአራት ፡ ከፋፈሉት ፤ እጀ ፡ ጠባቡን ፡ ደግሞ ፡ ወሰዱ ። እጀ ፡ ጠባቡም ፡ ከላይ ፡ ዠምሮ ፡ ወጥ ፡ ኾኖ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ የተሰፋ ፡ አልነበረም ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ለማን ፡ እንዲኾን ፡ በርሱ ፡ ዕጣ ፡ እንጣጣልበት ፡ እንጂ ፥ አንቅደደው ፡ ተባባሉ ። ይህም ፦ ልብሴን ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተከፋፈሉ ፡ በእጀ ፡ ጠባቤም ፡ ዕጣ ፡ ተጣጣሉበት ፡ የሚለው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ ጭፍራዎችም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ። ነገር ፡ ግን ፥ በኢየሱስ ፡ መስቀል ፡ አጠገብ ፡ እናቱ ፥ የእናቱም ፡ እኅት ፥ የቀለዮጳም ፡ ሚስት ፡ ማርያም ፥ መግደላዊትም ፡ ማርያም ፡ ቆመው ፡ ነበር ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ኢየሱስም ፡ እናቱን ፡ ይወደው ፡ የነበረውንም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እናቱን ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ እንሆ ፥ ልጅሽ ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፦ እናትኽ ፡ እንሂት ፡ አለው ። ከዚህም ፡ ሰዓት ፡ ዠምሮ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰዳት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ አኹን ፡ ሹሉ ፡ እንደተፈጸመ ፡ ዐውቆ ፥ የመጽሐፉ ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፦ ተጠማኹ ፡ አለ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ በዚያም ፡ ሐምጣጤ ፡ የሞላበት ፡ ዕቃ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ፤ እነርሱም ፡ ሐምጣጤውን ፡ በሰፍነግ ፡ ሞልተው ፡ በሁሶፕም ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ አፉ ፡ አቀረቡለት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፡ ሐምጣጤውን ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፦ ተፈጸመ ፡ አለ ፥ ራሱንም ፡ አዘንብሎ ፡ ነፍሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ አይሁድም ፡ የማዘጋጀት ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ያ ፡ ሰንበት ፡ ትልቅ ፡ ነበረና ፡ ሥጋቸው ፡ በሰንበት ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ እንዳይኖር ፥ ጭናቸውን ፡ ሰብረው ፡ እንዲያወርዷቸው ፡ ጲላጦስን ፡ ለመኑት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ ጭፍራዎችም ፡ መጥተው ፡ የፊተኛውን ፡ ጭን ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የተሰቀለውን ፡ የሌላውን ፡ ጭን ፡ ሰበሩ ፤

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ አይተው ፡ ጭኑን ፡ አልሰበሩም ፤

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከጭፍራዎች ፡ አንዱ ፡ ጐኑን ፡ በጦር ፡ ወጋው ፤ ወዲያውም ፡ ደምና ፡ ውሃ ፡ ወጣ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 35 ፤ ያየውም ፡ መስክሯል ፤ ምስክሩም ፡ እውነት ፡ ነው ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ርሱ ፡ እውነት ፡ እንዲናገር ፡ ያውቃል ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 36 ፤ ይህ ፡ የኾነ ፦ ከርሱ ፡ ዐጥንት ፡ አይሰበርም ፡ የሚል ፡ የመጽሐፉ ፡ ቃል ፡ እንዲፈጸም ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 37 ፤ ደግሞም ፡ ሌላው ፡ መጽሐፍ ፦ የወጉትን ፡ ያዩታል ፡ ይላል ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 38 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡ በስውር ፡ የኢየሱስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የነበረ ፡ የአርማትያስ ፡ ዮሴፍ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ሊወስድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመነ ፤ ጲላጦስም ፡ ፈቀደለት ። ስለዚህም ፡ መጥቶ ፡ የኢየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ወሰደ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 39 ፤ ደግሞም ፡ አስቀድሞ ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፡ መጥቶ ፡ የነበረ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ መቶ ፡ ንጥር ፡ የሚያኽል ፡ የከርቤና ፡ የሬት ፡ ቅልቅል ፡ ይዞ ፡ መጣ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 40 ፤ የኢየሱስንም ፡ ሥጋ ፡ ወስደው ፥ እንደ ፡ አይሁድ ፡ አገናነዝ ፡ ልማድ ፥ ከሽቱ ፡ ጋራ ፡ በተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡ ከፈኑት ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 41 ፤ በተሰቀለበትም ፡ ስፍራ ፡ አትክልት ፡ ነበረ ፥ በአትክልቱም ፡ ማንም ፡ ገና ፡ ያልተቀበረበት ፡ ዐዲስ ፡ መቃብር ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 19 ፡ 42 ፤ ስለዚህ ፥ መቃብሩ ፡ ቅርብ ፡ ነበረና ፥ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ማዘጋጀት ፡ ቀን ፡ ኢየሱስን ፡ በዚያ ፡ አኖሩት ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ ከሳምንቱም ፡ በፊተኛው ፡ ቀን ፥ መግደላዊት ፡ ማርያም ፥ ገና ፡ ጨለማ ፡ ሳለ ፡ ማለዳ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ መጣች ፤ ድንጋዩም ፡ ከመቃብሩ ፡ ተፈንቅሎ ፡ አየች ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ እየሮጠችም ፡ ወደ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስና ፥ ኢየሱስ ፡ ይወደው ፡ ወደ ፡ ነበረው ፣ ወደ ፡ ሌላው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ መጥታ ፦ ጌታን ፡ ከመቃብር ፡ ወስደውታል ፥ ወዴትም ፡ እንዳኖሩት ፡ አናውቅም ፡ አለቻቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ጴጥሮስና ፡ ሌላው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ መቃብሩ ፡ ኼዱ ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ኹለቱም ፡ ዐብረው ፡ ሮጡ ፤ ሌላው ፡ ደቀ ፡ መዝሙርም ፡ ከጴጥሮስ ፡ ይልቅ ፡ ፈጥኖ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ሮጠና ፡ አስቀድሞ ፡ ከመቃብሩ ፡ ደረሰ ፤

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ ዝቅም ፡ ብሎ ፡ ቢመለከት ፡ የተልባ ፡ እግሩን ፡ ልብስ ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አልገባም ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ተከትሎት ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ መቃብሩም ፡ ገባ ፤ የተልባ ፡ እግሩን ፡ ልብስ ፡ ተቀምጦ ፡ አየ ፥

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 7 ፤ ደግሞም ፡ በራሱ ፡ የነበረውን ፡ ጨርቅ ፡ ለብቻው ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ተጠምጥሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ከተልባ ፡ እግሩ ፡ ልብስ ፡ ጋራ ፡ ተቀምጦ ፡ እንዳልነበረ ፡ አየ ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ የመጣውም ፡ ሌላው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፡ ገባ ፥ አየም ፥ አመነም ፤

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 9 ፤ ከሙታን ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባው ፡ የሚለውን ፡ የመጽሐፉን ፡ ቃል ፡ ገና ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 10 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ደግሞ ፡ ኼዱ ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 11 ፤ ማርያም ፡ ግን ፡ እያለቀሰች ፡ ከመቃብሩ ፡ በስተውጭ ፡ ቆማ ፡ ነበር ። ስታለቅስም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ዝቅ ፡ ብላ ፡ ተመለከተች ፤

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 12 ፤ ኹለት ፡ መላእክትም ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ የኢየሱስ ፡ ሥጋ ፡ ተኝቶበት ፡ በነበረው ፡ አንዱ ፡ በራስጌ ፡ ሌላውም ፡ በእግርጌ ፡ ተቀምጠው ፡ አየች ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታለቅሻለሽ ፧ አሏት ። ርሷም ፦ ጌታዬን ፡ ወስደውታል ፡ ወዴትም ፡ እንዳኖሩት ፡ አላውቅም ፡ አለቻቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 14 ፤ ይህንም ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ዘወር ፡ ስትል ፡ ኢየሱስን ፡ ቆሞ ፡ አየችው ፤ ኢየሱስም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላወቀችም ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 15 ፤ ኢየሱስም ፦ አንቺ ፡ ሴት ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታለቅሻለሽ ፧ ማንንስ ፡ ትፈልጊያለሽ ፧ አላት ። ርሷም ፡ የአትክልት ፡ ጠባቂ ፡ መስሏት ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ወስደኸው ፡ እንደ ፡ ኾንክ ፡ ወዴት ፡ እንዳኖርኸው ፡ ንገረኝ ፡ እኔም ፡ እወስደዋለኹ ፡ አለችው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 16 ፤ ኢየሱስም ፦ ማርያም ፡ አላት ። ርሷ ፡ ዘወር ፡ ብላ ፡ በዕብራይስጥ ፦ ረቡኒ ፡ አለችው ፤ ትርጓሜውም ፦ መምህር ፡ ሆይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 17 ፤ ኢየሱስም ፦ ገና ፡ ወደ ፡ አባቴ ፡ አላረግኹምና ፡ አትንኪኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ወንድሞቼ ፡ ኼደሽ ፦ እኔ ፡ ወደ ፡ አባቴና ፡ ወደ ፡ አባታችኹ ፡ ወደ ፡ አምላኬና ፡ ወደ ፡ አምላካችኹ ፡ ዐርጋለኹ ፡ ብለሽ ፡ ንገሪያቸው ፡ አላት ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 18 ፤ መግደላዊት ፡ ማርያም ፡ መጥታ ፡ ጌታን ፡ እንዳየች ፡ ይህንም ፡ እንዳላት ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ነገረች ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 19 ፤ ያም ፡ ቀን ፡ ርሱም ፡ ከሳምንቱ ፡ ፊተኛው ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተሰብስበው ፡ በነበሩበት ፥ አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈሩ ፡ ደጆቹ ፡ ተዘግተው ፡ ሳሉ ፥ ኢየሱስ ፡ መጣ ፤ በመካከላቸውም ፡ ቆሞ ፦ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 20 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እጆቹንም ፡ ጐኑንም ፡ አሳያቸው ። ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ጌታን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 21 ፤ ኢየሱስም ፡ ዳግመኛ ፦ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ፤ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እልካችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸውና ፦ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ኀጢአታቸውን ፡ ይቅር ፡ ያላችኋቸው ፡ ኹሉ ፡ ይቀርላቸዋል ፤ የያዛችኹባቸው ፡ ተይዞባቸዋል ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ አንዱ ፡ ዲዲሞስ ፡ የሚሉት ፡ ቶማስ ፡ ኢየሱስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አልነበረም ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ ሌላዎቹም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፦ ጌታን ፡ አይተነዋል ፡ አሉት ። ርሱ ፡ ግን ፦ የችንካሩን ፡ ምልክት ፡ በእጆቹ ፡ ካላየኹ ፡ ጣቴንም ፡ በችንካሩ ፡ ምልክት ፡ ካላገባኹ ፡ እጄንም ፡ በጐኑ ፡ ካላገባኹ ፡ አላምንም ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ደግመው ፡ በውስጥ ፡ ነበሩ ፥ ቶማስም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ። ደጆች ፡ ተዘግተው ፡ ሳሉ ፡ ኢየሱስ ፡ መጣ ፤ በመካከላቸውም ፡ ቆሞ ፦ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ቶማስን ፦ ጣትኽን ፡ ወደዚህ ፡ አምጣና ፡ እጆቼን ፡ እይ ፤ እጅኽንም ፡ አምጣና ፡ በጐኔ ፡ አግባው ፤ ያመንኽ ፡ እንጂ ፡ ያላመንኽ ፡ አትኹን ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ ቶማስም ፦ ጌታዬ ፡ አምላኬም ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 29 ፤ ኢየሱስም ፦ ስላየኸኝ ፡ አምነኻል ፤ ሳያዩ ፡ የሚያምኑ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 30 ፤ ኢየሱስም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፈ ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ምልክት ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ፊት ፡ አደረገ ፤

ዮሐ. ፡ 20 ፡ 31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፥ አምናችኹም ፡ በስሙ ፡ ሕይወት ፡ ይኾንላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ተጽፏል ።

_____የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ኢየሱስ ፡ በጥብርያዶስ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ተገለጠላቸው ፤

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 2 ፤ እንዲህም ፡ ተገለጠ ። ስምዖን ፡ ጴጥሮስና ፡ ዲዲሞስ ፡ የሚባለው ፡ ቶማስ ፡ ከገሊላ ፡ ቃና ፡ የኾነ ፡ ናትናኤልም ፡ የዘብዴዎስም ፡ ልጆች ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ ሌላዎች ፡ ኹለት ፡ በአንድነት ፡ ነበሩ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 3 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፦ ዓሣ ፡ ላጠምድ ፡ እኼዳለኹ ፡ አላቸው ። እነርሱም ፦ እኛም ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ እንመጣለን ፡ አሉት ። ወጥተውም ፡ ወደ ፡ ታንኳዩቱ ፡ ገቡ ፡ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ ምንም ፡ አላጠመዱም ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 4 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ኢየሱስ ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ ቆመ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ግን ፡ ኢየሱስ ፡ መኾኑን ፡ አላወቁም ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፦ ልጆች ፡ ሆይ ፥ አንዳች ፡ የሚበላ ፡ አላችኹን ፧ አላቸው ። የለንም ፡ ብለው ፡ መለሱለት ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 6 ፤ ርሱም ፦ መረቡን ፡ በታንኳዩቱ ፡ በስተቀኝ ፡ ጣሉት ፡ ታገኙማላችኹ ፡ አላቸው ። ስለዚህ ፡ ጣሉት ፤ በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ከዓሣው ፡ ብዛት ፡ የተነሣ ፡ ሊጐትቱት ፡ አቃታቸው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ኢየሱስ ፡ ይወደው ፡ የነበረውም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ጴጥሮስን ፦ ጌታ ፡ እኮ ፡ ነው ፡ አለው ። ስለዚህ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፡ ጌታ ፡ መኾኑን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ዕራቍቱን ፡ ነበረና ፥ ልብሱን ፡ ታጥቆ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ራሱን ፡ ጣለ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ሌላዎቹ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ከምድር ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ክንድ ፡ ያኽል ፡ እንጂ ፡ እጅግ ፡ አልራቁም ፡ ነበርና ፥ ዓሣ ፡ የሞላውን ፡ መረብ ፡ እየሳቡ ፡ በጀልባ ፡ መጡ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ ምድርም ፡ በወጡ ፡ ጊዜ ፡ ፍምና ፡ ዓሣ ፡ በላዩ ፡ ተቀምጦ ፡ እንጀራም ፡ አዩ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 10 ፤ ኢየሱስም ፦ አኹን ፡ ካጠመዳችኹት ፡ ዓሣ ፡ አምጡ ፡ አላቸው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 11 ፤ ስምዖን ፡ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ጀልባዩቱ ፡ ገብቶ ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ሦስት ፡ ታላላቅ ፡ ዓሣዎች ፡ ሞልቶ ፡ የነበረውን ፡ መረብ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጐተተ ፤ ይህንም ፡ ያኽል ፡ ብዙ ፡ ሲኾን ፡ መረቡ ፡ አልተቀደደም ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ኢየሱስም ፦ ኑ ፥ ምሳ ፡ ብሉ ፡ አላቸው ። ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፦ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ ብሎ ፡ ሊመረምረው ፡ የደፈረ ፡ አልነበረም ፤ ጌታ ፡ መኾኑን ፡ ዐውቀው ፡ ነበርና ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ ኢየሱስም ፡ መጣና ፡ እንጀራ ፡ አንሥቶ ፡ ሰጣቸው ፥ እንዲሁም ፡ ዓሣውን ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ኢየሱስ ፡ ከሙታን ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሲገለጥላቸው ፡ ይህ ፡ ሦስተኛው ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ ምሳ ፡ ከበሉ ፡ በኋላም ፡ ኢየሱስ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስን ፦ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ ከነዚህ ፡ ይልቅ ፡ ትወደኛለኽን ፧ አለው ፦ አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንድወድኽ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፡ አለው ፦ ግልገሎቼን ፡ አሰማራ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ደግሞ ፡ ኹለተኛ ፦ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ ትወደኛለኽን ፧ አለው ፦ አዎን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንድወድኽ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፡ አለው ፦ ጠቦቶቼን ፡ ጠብቅ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ሦስተኛ ፡ ጊዜ ፦ የዮና ፡ ልጅ ፡ ስምዖን ፡ ሆይ ፥ ትወደኛለኽን ፧ አለው ። ሦስተኛ ፦ ትወደኛለኽን ፧ ስለ ፡ አለው ፡ ጴጥሮስ ፡ ዐዘነና ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ኹሉን ፡ ታውቃለኽ ፤ እንድወድኽ ፡ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፡ አለው ። ኢየሱስም ፦ በጎቼን ፡ አሰማራ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ እውነት ፡ እውነት ፡ እልኻለኹ ፥ አንተ ፡ ጕልማሳ ፡ ሳለኽ ፡ ወገብኽን ፡ በገዛ ፡ ራስኽ ፡ ታጥቀኽ ፡ ወደምትወደው ፡ ትኼድ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሸመገልኽ ፡ ጊዜ ፡ እጆችኽን ፡ ትዘረጋለኽ ፥ ሌላውም ፡ ያስታጥቅኻል ፡ ወደማትወደውም ፡ ይወስድኻል ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ በምን ፡ ዐይነት ፡ ሞት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብር ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ ሲያመለክት ፡ ይህን ፡ አለ ። ይህንም ፡ ብሎ ፦ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ጴጥሮስም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ ኢየሱስ ፡ ይወደው ፡ የነበረውን ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ሲከተለው ፡ አየ ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ በእራት ፡ ጊዜ ፡ በደረቱ ፡ ተጠግቶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አሳልፎ ፡ የሚሰጥኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ያለው ፡ ነበረ ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ጴጥሮስም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ ኢየሱስን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ይህስ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ፧ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ኢየሱስም ፦ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ብወድስ ፥ ምን ፡ አግዶኽ ፧ አንተ ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ስለዚህ ፦ ያ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ አይሞትም ፡ የሚለው ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ወንድሞች ፡ ወጣ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስ ፦ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ብወድስ ፡ ምን ፡ አግዶኽ ፧ አለው ፡ እንጂ ፡ አይሞትም ፡ አላለውም ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ ስለ ፡ እነዚህም ፡ የመሰከረ ፡ ይህንም ፡ ጽፎ ፡ ያለ ፡ ይህ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነው ፥ ምስክሩም ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ ኢየሱስም ፡ ያደረገው ፡ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ አለ ፤ ኹሉ ፡ በያንዳንዱ ፡ ቢጻፍ ፡ ለተጻፉት ፡ መጻሕፍት ፡ ዓለም ፡ ራሱ ፡ ባልበቃቸውም ፡ ይመስለኛል ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ ቴዎፍሎስ ፡ ሆይ ፥ ኢየሱስ ፡ የመረጣቸውን ፡ ሐዋርያትን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካዘዛቸው ፡ በኋላ ፡ እስከዐረገበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ያደርገውና ፡ ያስተምረው ፡ ዘንድ ፡ ስለገሥመረው ፡ ዅሉ ፡ መገሥመሪያውን ፡ ነገር ፡ ጻፍኹ ፤

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ደግሞ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ እየታያቸው ፡ ስለእግዚአብሔርም ፡ መንግሥት ፡ ነገር ፡ እየነገራቸው ፥ በብዙ ፡ ማስረጃ ፡ ከሕማማቱ ፡ በኋላ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ ለእነርሱ ፡ ራሱን ፡ አሳያቸው ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ሳለ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጡ ፡ አዘዛቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፦ ከእኔ ፡ የሰማችኹትን ፡ አብ ፡ የሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ጠብቁ ፤

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ዮሐንስ ፡ በውሃ ፡ አጥምቆ ፡ ነበርና ፥ እናንተ ፡ ግን ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠመቃላችኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ እነርሱም ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ወራት ፡ ለእስራኤል ፡ መንግሥትን ፡ ትመልሳለኽን ፧ ብለው ፡ ጠየቁት ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ርሱም ፦ አብ ፡ በገዛ ፡ ሥልጣኑ ፡ ያደረገውን ፡ ወራትንና ፡ ዘመናትን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ አልተሰጣችኹም ፤

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ኀይልን ፡ ትቀበላላችኹ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ በይሁዳም ፡ ዅሉ ፡ በሰማርያም ፡ እስከምድር ፡ ዳርም ፡ ድረስ ፡ ምስክሮቼ ፡ ትኾናላችኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ይህንም ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ እነርሱ ፡ እያዩት ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፤ ደመናም ፡ ከዐይናቸው ፡ ሰውራ ፡ ተቀበለችው ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ርሱም ፡ ሲኼድ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱ ፡ ሳሉ ፥ እንሆ ፥ ነጫጭ ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ በአጠገባቸው ፡ ቆሙ ፤

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ደግሞም ፦ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እየተመለከታችኹ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ቆማችኋል ፧ ይህ ፡ ከእናንተ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣው ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲኼድ ፡ እንዳያችኹት ፥ እንዲሁ ፡ ይመጣል ፡ አሏቸው ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡ ከሚባለው ፡ ተራራ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፥ ርሱም ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የሰንበት ፡ መንገድ ፡ ያኽል ፡ የራቀ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በገቡም ፡ ጊዜ ፡ ወደሚኖሩበት ፡ ሰገነት ፡ ወጡ ፥ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፣ ያዕቆብም ፣ እንድርያስም ፣ ፊልጶስም ፣ ቶማስም ፣ በርተሎሜዎስም ፣ ማቴዎስም ፣ የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ያዕቆብም ፣ ቀናተኛ ፡ የሚባለው ፡ ስምዖንም ፣ የያዕቆብ ፡ ልጅ ፡ ይሁዳም ።

ሐዋ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ እነዚህ ፡ ዅሉ ፡ ከሴቶችና ፡ ከኢየሱስ ፡ እናት ፡ ከማርያም ፡ ከወንድሞቹም ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ ለጸሎት ፡ ይተጉ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ በዚህም ፡ ወራት ፡ ጴጥሮስ ፡ መቶ ፡ ኻያ ፡ በሚያኽል ፡ በሰዎች ፡ ማኅበር ፡ ዐብረው ፡ በነበሩ ፡ በወንድሞቹ ፡ መካከል ፡ ተነሥቶ ፡ አለ ፦

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ኢየሱስን ፡ ለያዙት ፡ መሪ ፡ ስለኾናቸው ፡ ስለ ፡ ይሁዳ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አስቀድሞ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ተቈጥሮ ፡ ነበርና ፥ ለዚህም ፡ አገልግሎት ፡ ታድሎ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ በዐመፅ ፡ ዋጋ ፡ መሬት ፡ ገዛ ፥ በግንባሩም ፡ ተደፍቶ ፡ ከመካከሉ ፡ ተሠነጠቀ ፥ አንጐቱም ፡ ኹሉ ፡ ተዘረገፈ ፤

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ለሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ታወቀ ፤ ስለዚህም ፡ ያ ፡ መሬት ፡ በቋንቋቸው ፡ አኬልዳማ ([291]) ፡ ተብሎ ፡ ተጠራ ፥ ርሱም ፡ የደም ፡ መሬት ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ በመዝሙር ፡ መጽሐፍ ፦ መኖሪያው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ትኹን ፥ የሚኖርባትም ፡ አይኑር ፤ ደግሞም ፦ ሹመቱን ፡ ሌላ ፡ ይውሰዳት ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 21-22 ፤ ስለዚህ ፥ ከዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ ዠምሮ ፥ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ እስካረገበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፥ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በእኛ ፡ መካከል ፡ በገባበትና ፡ በወጣበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ከነበሩት ፡ ሰዎች ፥ ከነዚህ ፡ አንዱ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ የትንሣኤው ፡ ምስክር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ኢዮስጦስም ፡ የሚሉትን ፡ በርስያን ፡ የተባለውን ፡ ዮሴፍንና ፡ ማትያስን ፡ ኹለቱን ፡ አቆሙ ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 24-25 ፤ ሲጸልዩም ፦ የኹሉን ፡ ልብ ፡ የምታውቅ ፡ አንተ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ይሁዳ ፡ ወደገዛ ፡ ራሱ ፡ ስፍራ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ በተዋት ፡ በዚች ፡ አገልግሎትና ፡ ሐዋርያነት ፡ ስፍራን ፡ እንዲቀበል ፡ የመረጥኸውን ፡ ከነዚህ ፡ ከኹለቱ ፡ አንዱን ፡ ሹመው ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ዕጣም ፡ ተጣጣሉላቸው ፥ ዕጣውም ፡ ለማትያስ ፡ ወደቀና ፡ ከዐሥራ ፡ አንዱ ፡ ሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ ተቈጠረ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በዓለ ፡ ኀምሳ ፡ የተባለውም ፡ ቀን ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፥ ኹሉም ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ ዐብረው ፡ ሳሉ ፥

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ድንገት ፡ እንደሚነጥቅ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከሰማይ ፡ ድምፅ ፡ መጣ ፥ ተቀምጠው ፡ የነበሩበትንም ፡ ቤት ፡ ኹሉ ፡ ሞላው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ እንደ ፡ እሳትም ፡ የተከፋፈሉ ፡ ልሳኖች ፡ ታይዋቸው ፤ በያንዳንዳቸውም ፡ ላይ ፡ ተቀመጡባቸው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ በኹሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ፥ መንፈስም ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ በሌላ ፡ ልሳኖች ፡ ይናገሩ ፡ ዠመር ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ከሰማይም ፡ በታች ፡ ካሉ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በጸሎት ፡ የተጉ ፡ አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ይህም ፡ ድምፅ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ተሰበሰቡ ፥ እያንዳንዱም ፡ በገዛ ፡ ቋንቋው ፡ ሲናገሩ ፡ ይሰማ ፡ ስለ ፡ ነበር ፡ የሚሉትን ፡ ዐጡ ።

---

291 አኬልዳማ ፦ (ግ.) ፥ 'ሐቅለ ፡ ድማኅ ፥ ገራህተ ፡ ደም ፡ ብሂል' ፡ (ሐቅለ ፡ ደም • የደም ፡ መሬት) ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ተገርመውም ፡ ተደንቀውም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ እንሆ ፥ እነዚህ ፡ የሚናገሩት ፡ ኹሉ ፡ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉምን ፧

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እኛም ፡ እያንዳንዳችን ፡ የተወለድንበትን ፡ የገዛ ፡ ቋንቋችንን ፡ እንዴት ፡ እንሰማለን ፧

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ የጳርቴና ፡ የሜድ ፡ የኢላሜጤም ፡ ሰዎች ፥ በኹለት ፡ ወንዝም ፡ መካከል ፡ በይሁዳም ፡ በቀጳዶቅያም ፡ በጳንጦስም ፡ በእስያም ፥

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ በፍርግያም ፡ በጵንፍልያም ፡ በግብጽም ፡ በቀሬናም ፡ በኩል ፡ ባሉት ፡ በሊብያ ፡ ወረዳዎች ፡ የምንኖር ፥ በሮሜም ፡ የምንቀመጥ ፥ አይሁድም ፡ ወደ ፡ ይሁዲነትም ፡ የገባን ፥

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ የቀርጤስና ፡ የዐረብ ፡ ሰዎች ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅ ፡ ሥራ ፡ በልሳኖቻችን ፡ ሲናገሩ ፡ እንሰማቸዋለን ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ኹሉም ፡ ተገረሙና ፡ አመንትተው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ እንኳ ፥ ይህ ፡ ምን ፡ ይኾን ፧ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ሌላዎች ፡ ግን ፡ እያፌዙባቸው ፦ ጕሽ ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠግበዋል ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጴጥሮስ ፡ ከዐሥራ ፡ አንዱ ፡ ጋራ ፡ ቆመ ፥ ድምፁንም ፡ ከፍ ፡ አድርጎ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገራቸው ፦ አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ የምትኖሩ ፡ ኹላችኹ ፥ ይህ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኹን ፥ ቃሎቼንም ፡ አድምጡ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ለእናንተ ፡ እንደ ፡ መሰላችኹ ፡ እነዚህ ፡ የሰከሩ ፡ አይደሉም ፥ ከቀኑ ፡ ሦስተኛ ፡ ሰዓት ፡ ነውና ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ በነቢዩ ፡ በኢዮኤል ፡ የተባለው ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፦ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ እንዲህ ፡ ይኾናል ፤ ሥጋ ፡ በለበሰ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈሳለኹ ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻችኹም ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፥ ጐበዞቻችኹም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፥ ሽማግሌዎቻችኹም ፡ ሕልም ፡ ያልማሉ ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ደግሞም ፡ በዚያች ፡ ወራት ፡ በወንዶችና ፡ በሴቶች ፡ ባሪያዎቼ ፡ ላይ ፡ ከመንፈሴ ፡ አፈሳለኹ ፡ ትንቢትም ፡ ይናገራሉ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ድንቆችን ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፥ ምልክቶችንም ፡ በታች ፡ በምድር ፡ እሰጣለኹ ፤ ደምም ፡ እሳትም ፡ የጢስ ፡ ጭጋግም ፡ ይኾናል ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ የተሰማም ፡ የጌታ ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ ጨረቃም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ይለወጣሉ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ የጌታን ፡ ስም ፡ የሚጠራም ፡ ኹሉ ፡ ይድናል ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ቃል ፡ ስሙ ፤ ራሳችኹ ፡ እንደምታውቁ ፥ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመካከላችኹ ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ ባደረገው ፡ ተኣምራትና ፡ በድንቆች ፡ በምልክቶችም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለእናንተ ፡ የተገለጠ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ርሱንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ በተወሰነው ፡ ዐሳቡና ፡ በቀደመው ፡ ዕውቀቱ ፡ ተሰጥቶ ፡ በዐመፀኞች ፡ እጅ ፡ ሰቅላችኹ ፡ ገደላችኹት ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የሞትን ፡ ጣር ፡ አጥፍቶ ፡ አስነሣው ፥ ሞት ፡ ይይዘው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለምና ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ዳዊት ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፦ ጌታን ፡ ዘውልጊዜ ፡ በፊቴ ፡ አየኹት ፥ እንዳልታወክ ፡ በቀኜ ፡ ነውና ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ ልቤን ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ልሳኔም ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ፥ ደግሞም ፡ ሥጋዬ ፡ በተስፋ ፡ ያድራል ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ ነፍሴን ፡ በሲኦል ፡ አትተዋትምና ፥ ቅዱስኽንም ፡ መበስበስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትሰጠውም ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ የሕይወትን ፡ መንገድ ፡ አስታወቅኸኝ ፤ ከፊትኽ ፡ ጋራ ፡ ደስታን ፡ ትሞላብኛለኽ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስላባቶች ፡ አለቃ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ሞተም ፡ እንደ ፡ ተቀበረም ፡ ለእናንተ ፡ በግልጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ፍቀዱልኝ ፤ መቃብሩም ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ ነቢይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ከወገቡም ፡ ፍሬ ፡ በዙፋኑ ፡ ያስቀምጥ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ እንደ ፡ ማለለት ፡ ስላወቀ ፥

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 31 ፤ ስለክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ አስቀድሞ ፡ አይቶ ፥ ነፍሱ ፡ በሲኦል ፡ እንዳልቀረች ፡ ሥጋውም ፡ መበስበስን ፡ እንዳላየ ፡ ተናገረ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 32 ፤ ይህን ፡ ኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ አስነሣው ፡ ለዚህም ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 33 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ብሎና ፥ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ከአብ ፡ ተቀብሎ ፥ ይህን ፡ እናንተ ፡ አኹን ፡ የምታዩትንና ፡ የምትሰሙትን ፡ አፈሰሰው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 34-35 ፤ ዳዊት ፡ ወደ ፡ ሰማያት ፡ አልወጣምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፦ ጌታ ፡ ጌታዬን ፦ ጠላቶችኽን ፡ የእግርኽ ፡ መረገጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ አለው ፡

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 36 ፤ አለ ፦ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ እናንተ ፡ የሰቀላችኹትን ፡ ኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታም ፡ ክርስቶስም ፡ እንዳደረገው ፡ የእስራኤል ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ በርግጥ ፡ ይወቅ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 37 ፤ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ተነካ ፥ ጴጥሮስንና ፡ ሌላዎችንም ፡ ሐዋርያት ። ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ እናድርግ ፡ አሏቸው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 38 ፤ ጴጥሮስም ፦ ንስሓ ፡ ግቡ ፥ ኀጢአታችኹም ፡ ይሰረይ ፡ ዘንድ ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ስጦታ ፡ ትቀበላላችኹ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 39 ፤ የተስፋው ፡ ቃል ፡ ለእናንተና ፡ ለልጆቻችኹ ፡ ጌታ ፡ አምላካችንም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለሚጠራቸው ፡ በሩቅ ፡ ላሉ ፡ ኹሉ ፡ ነውና ፥ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 40 ፤ በብዙ ፡ ሌላ ፡ ቃልም ፡ መሰከረና ፦ ከዚህ ፡ ጠማማ ፡ ትውልድ ፡ ዳኑ ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 41 ፤ ቃሉንም ፡ የተቀበሉ ፡ ተጠመቁ ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሦስት ፡ ሺሕ ፡ የሚያኽል ፡ ነፍስ ፡ ተጨመሩ ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 42 ፤ በሐዋርያትም ፡ ትምህርትና ፡ በኅብረት ፡ እንጀራውንም ፡ በመቍረስ ፡ በየጸሎቱም ፡ ይተጉ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 43 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ፤ በሐዋርያትም ፡ እጅ ፡ ብዙ ፡ ድንቅና ፡ ምልክት ፡ ተደረገ ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 44 ፤ ያመኑትም ፡ ኹሉ ፡ ዐብረው ፡ ነበሩ ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 45 ፤ ያላቸውንም ፡ ኹሉ ፡ አንድነት ፡ አደረጉ ። መሬታቸውንና ፡ ጥሪታቸውንም ፡ እየሸጡ ፥ ማንኛውም ፡ እንደሚፈልግ ፡ ለኹሉ ፡ ያካፍሉት ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 46 ፤ በየቀኑም ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ በመቅደስ ፡ እየተጉ ፡ በቤታቸውም ፡ እንጀራ ፡ እየቈረሱ ፥ በደስታና ፡ በጥሩ ፡ ልብ ፡ ምግባቸውን ፡ ይመገቡ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 2 ፡ 47 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገኑ ፡ በሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ ነበራቸው ። ጌታም ፡ የሚድኑትን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ይጨምር ፡ ነበር ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡ በዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ከሚገቡት ፡ ምጽዋት ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፥ ሰዎች ፡ ተሸክመው ፡ መልካም ፡ በሚሏት ፡ በመቅደስ ፡ ደጅ ፡ በየቀኑ ፡ ያስቀምጡት ፡ የነበሩ ፡ ከእናቱ ፡ ማሕፀን ፡ ዠምሮ ፡ ዐንካሳ ፡ የኾነ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ርሱም ፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ሊገቡ ፡ እንዳላቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ምጽዋትን ፡ ለመናቸው ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ጴጥሮስም ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ተመልክቶ ፦ ወደ ፡ እኛ ፡ ተመልከት ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ርሱም ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ከነርሱ ፡ እንዲቀበል ፡ ሲጠብቅ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ተመለከተ ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፦ ብርና ፡ ወርቅ ፡ የለኝም ፤ ይህን ፡ ያለኝን ፡ ግን ፡ እሰጥኻለኹ ፤ በናዝሬቱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ተነሣና ፡ ተመላለስ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በቀኝ ፡ እጁም ፡ ይዞ ፡ አስነሣው ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ እግሩና ፡ ቍርጭምጭሚቱ ፡ ጸና ፥

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ላይ ፡ ዘሎም ፡ ቆመ ፥ ይመላለስም ፡ ዠመር ፤ እየተመላለሰም ፡ እየዘለለም ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እያመሰገነ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገነ ፡ ሲመላለስ ፡ አዩት ፤

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ መልካምም ፡ በሚሏት ፡ በመቅደስ ፡ ደጅ ፡ ስለ ፡ ምጽዋት ፡ ተቀምጦ ፡ የነበረው ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐወቁት ፤ በርሱም ፡ ከኾነው ፡ የተነሣ ፡ መደነቅና ፡ መገረም ፡ ሞላባቸው ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ይዞ ፡ ሳለ ፥ ሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ እየተደነቁ ፡ የሰሎሞን ፡ ደጅ ፡ መመላለሻ ፡ በሚባለው ፡ ዐብረው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ሮጡ ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ጴጥሮስም ፡ አይቶ ፡ ለሕዝቡ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰ ፦ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ በዚህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትደነቃላችኹ ፧ ወይስ ፡ በገዛ ፡ ኀይላችን ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመፍራታችን ፡ ይህ ፡ ይመላለስ ፡ ዘንድ ፡ እንዳደረግነው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትኵር ፡ ብላችኹ ፡ ታዩናላችኹ ፧

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ የአብርሃምና ፡ የይሥሐቅ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፥ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፥ እናንተ ፡ አሳልፋችኹ ፡ የሰጣችኹትንና ፡ ሊፈታው ፡ ቈርጦ ፡ ሳለ ፡ በጲላጦስ ፡ ፊት ፡ የካዳችኹትን ፡ ብላቴናውን ፡ ኢየሱስን ፡ አከበረው ።

ሐዋ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ቅዱሱን ፡ ጻድቁንም ፡ ክዳችኹ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዩን ፡ ሰው ፡ ይሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡

ለመናችኹ ፥

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 15 ፤ የሕይወትንም ፡ ራስ ፡ ገደላችኹት ፤ ርሱን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ አስነሣው ፥ ለዚህም ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 16 ፤ በስሙም ፡ በማመን ፡ ይህን ፡ የምታዩትንና ፡ የምታውቁትን ፡ የርሱ ፡ ስም ፡ አጸናው ፥ በርሱም ፡ በኩል ፡ የኾነው ፡ እምነት ፡ በኹላችኹ ፡ ፊት ፡ ይህን ፡ ፍጹም ፡ ጤና ፡ ሰጠው ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 17 ፤ አኹንም ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ እንደ ፡ አለቃዎቻችኹ ፡ ደግሞ ፡ ባለማወቅ ፡ እንዳደረጋችኹት ፡ ዐውቄያለኹ ፤

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ አስቀድሞ ፡ በነቢያት ፡ ኹሉ ፡ አፍ ፡ የተናገረውን ፡ እንዲሁ ፡ ፈጸመው ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 19-20 ፤ እንግዲህ ፡ ከጌታ ፡ ፊት ፡ የመጽናናት ፡ ዘመን ፡ እንድትመጣላችኹ ፥ አስቀድሞም ፡ ለእናንተ ፡ የመረጠውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲልክላችኹ ፥ ኀጢአታችኹ ፡ ይደመሰስ ፡ ዘንድ ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፥ ተመለሱም ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ በቅዱሳን ፡ ነቢያቱ ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፥ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እስከሚታደስበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ ሰማይ ፡ ይቀበለው ፡ ዘንድ ፡ ይገባልና ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 22 ፤ ሙሴም ፡ ለአባቶች ፦ ጌታ ፡ አምላክ ፡ እኔን ፡ እንዳስነሣኝ ፡ ነቢይን ፡ ከወንድሞቻችኹ ፡ ያስነሣላችኋል ፤ በሚነግራችኹ ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ ስሙት ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 23 ፤ ያንም ፡ ነቢይ ፡ የማትሰማው ፡ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ ከሕዝብ ፡ ተለይታ ፡ ትጠፋለች ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 24 ፤ ኹለተኛም ፡ ከሳሙኤል ፡ ዠምሮ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የተናገሩት ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ስለዚህ ፡ ወራት ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 25 ፤ እናንተ ፡ የነቢያት ፡ ልጆችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፦ በዘርኽ ፡ የምድር ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ይባረካሉ ፡ ብሎ ፥ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ ያደረገው ፡ የኪዳን ፡ ልጆች ፡ ናችኹ ።

ሐዋ. ፥ 3 ፥ 26 ፤ ለእናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላቴናውን ፡ አስነሥቶ ፥ እያንዳንዳችኹን ፡ ከክፋታችኹ ፡ እየመለሰ ፡ ይባርካችኹ ፡ ዘንድ ፥ ሰደደው ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሐዋ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ ለሕዝቡም ፡ ሲናገሩ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ የመቅደስ ፡ አዛዥ ፡ ሰዱቃውያንም ፥

ሐዋ. ፥ 4 ፥ 2 ፤ ሕዝቡን ፡ ስላስተማሩና ፡ በኢየሱስ ፡ የሙታንን ፡ ትንሣኤ ፡ ስለ ፡ ሰበኩ ፡ ተቸግረው ፥ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረቡ ፥

ሐዋ. ፥ 4 ፥ 3 ፤ እጃቸውንም ፡ ጭነውባቸው ፡ አኹን ፡ መሸቶ ፡ ነበርና ፥ እስከ ፡ ማግስቱ ፡ ድረስ ፡ በወህኒ ፡ አኖሯቸው ።

ሐዋ. ፥ 4 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ቃሉን ፡ ከሰሙት ፡ ብዙዎች ፡ አመኑ ፥ የወንዶችም ፡ ቍጥር ፡ ዐምስት ፡ ሺሕ ፡ ያኽል ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፥ 4 ፥ 5-6 ፤ በነገውም ፡ አለቃዎቻቸውና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጻፊዎችም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሐናም ፡ ቀያፋም ፡ ዮሐንስም ፡ እስክንድሮስም ፡ የሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ዘመዶች ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ተሰበሰቡ ፤

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እነርሱንም ፡ በመካከል ፡ አቁመው ። በምን ፡ ኀይል ፡ ወይስ ፡ በማን ፡ ስም ፡ እናንተ ፡ ይህን ፡ አደረጋችኹ ፧ ብለው ፡ ጠየቋቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ተሞልቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ እናንተ ፡ የሕዝብ ፡ አለቃዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፥

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እኛ ፡ ዛሬ ፡ ለድውዩ ፡ ሰው ፡ ስለተደረገው ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ በምን ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ብንመረመር ፥

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ እናንተ ፡ በሰቀላችኹት ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ ባስነሣው ፡ በናዝሬቱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ደኅና ፡ ኾኖ ፡ በፊታችኹ ፡ እንደ ፡ ቆመ ፥ ለእናንተ ፡ ለኹላችኹ ፡ ለእስራኤልም ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የታወቀ ፡ ይኹን ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ ግንበኞች ፡ የናቃችኹት ፥ የማእዘን ፡ ራስ ፡ የኾነው ፡ ይህ ፡ ድንጋይ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ መዳንም ፡ በሌላ ፡ በማንም ፡ የለም ፤ እንድንበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባን ፡ ለሰዎች ፡ የተሰጠ ፡ ስም ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ሌላ ፡ የለምና ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስም ፡ በግልጥ ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ መጽሐፍን ፡ የማያውቁና ፡ ያልተማሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አስተውለው ፡ አደነቁ ፥ ከኢየሱስም ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ዐወቋቸው ፤

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ የተፈወሰውንም ፡ ሰው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ቆሞ ፡ ሲያዩ ፡ የሚመልሱትን ፡ ዐጡ ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ከሸንጎም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘው ፦ በእነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ እንሥራ ፧

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ የታወቀ ፡ ምልክት ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ተገልጧልና ፥ እንሸሸገው ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፤

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ አብዝቶ ፡ እንዳይስፋፋ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ለማንም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ እንዳይናገሩ ፡ እየዛትን ፡ እንዘዛቸው ፡ ብለው ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተማከሩ ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ጠርተውም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ፈጽመው ፡ እንዳይናገሩና ፡ እንዳያስተምሩ ፡ አዘዟቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ መልሰው ፦ እግዚአብሔርን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡ እናንተን ፡ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የሚገባ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቍረጡ ፤

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ እኛስ ፡ ያየነውንና ፡ የሰማነውን ፡ ከመናገር ፡ ዝም ፡ ማለት ፡ አንችልም ፡ አሏቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደሚቀጡ ፡ ምክንያት ፡ ስላላገኙባቸው ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ዝተው ፡ ከሕዝቡ ፡ የተነሣ ፡ ፈቷቸው ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ስለ ኾነው ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ይህ ፡ የመፈወስ ፡ ምልክት ፡ የተደረገለት ፡ ሰው ፡ ከአርባ ፡ ዓመት ፡ ይበልጠው ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ተፈትተውም ፡ ወደ ፡ ወገኖቻቸው ፡ መጡና ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ያሏቸውን ፡ ኹሉ ፡ ነገሯቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ እነርሱም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ሰማዩንና ፡ ምድሩን ፡ ባሕሩንም ፡ በእነርሱም ፡ የሚኖረውን ፡ ኹሉ ፡ የፈጠርኽ ፥

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በብላቴናኽ ፡ በአባታችን ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፦ አሕዛብ ፡ ለምን ፡ አጒረመረሙ ፧ ሕዝቡስ ፡ ከንቱን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ ዐሰቡ ፧

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ተነሡ ፥ አለቃዎችም ፡ በጌታና ፡ በተቀባው ፡ ላይ ፡ ዐብረው ፡ ተከማቹ ፡ ብለኽ ፡ የተናገርኽ ፡ አምላክ ፡ ነኽ ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 27-28 ፤ በቀባኸው ፡ በቅዱሱ ፡ ብላቴናኽ ፡ በኢየሱስ ፡ ላይ ፡ ሄሮድስና ፡ ጳንጤናዊው ፡ ጲላጦስ ፡ ከአሕዛብና ፡ ከእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፥ እጅኽና ፡ ዐሳብኽ ፡ እንዲኾን ፡ አስቀድመው ፡ የወሰኑትን ፡ ኹሉ ፡ ሊፈጽሙ ፥ በዚኽ ፡ ከተማ ፡ በእውነት ፡ ተሰበሰቡ ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 29-30 ፤ አኹንም ፥ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ ዛቻቸው ፡ ተመልከት ፤ ለመፈወስም ፡ እጅኽን ፡ ስትዘረጋ ፡ በቅዱስ ፡ ብላቴናኽም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ሲደረግ ፥ ባሪያዎችኽ ፡ በፍጹም ፡ ግልጥነት ፡ ቃልኽን ፡ እንዲናገሩ ፡ ስጣቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ከጸለዩም ፡ በኋላ ፡ ተሰብስበው ፡ የነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ ተናወጠ ፥ በኹሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ በግልጥ ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 32 ፤ ያመኑትም ፡ ሕዝብ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ አንዲትም ፡ ነፍስ ፡ ነበሯቸው ፥ ገንዘባቸውም ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ካለው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡ የራሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማንም ፡ አልተናገረም ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 33 ፤ ሐዋርያትም ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ትንሣኤ ፡ በታላቅ ፡ ኀይል ፡ ይመሰክሩ ፡ ነበር ፤ በኹሉም ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ነበረባቸው ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 34 ፤ በመካከላቸው ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ችግረኛ ፡ አልነበረምና ፤ መሬት ፡ ወይም ፡ ቤት ፡ ያላቸው ፡ ኹሉ ፡ እየሸጡ ፡ የተሸጠውን ፡ ዋጋ ፡ ያመጡ ፡ ነበርና ፥

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 35 ፤ በሐዋርያትም ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ያኖሩ ፡ ነበር ፤ ማናቸውም ፡ እንደሚፈልግ ፡ መጠን ፡ ለያንዳንዱ ፡ ያካፍሉት ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 36 ፤ ትውልዱም ፡ የቆጵሮስ ፡ ሰው ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሌዋዊ ፡ ዮሴፍ ፡ የሚሉት ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ በሐዋርያት ፡ በርናባስ ፡ ተባለ ፡ ትርጓሜውም ፡ የመጽናናት ፡ ልጅ ፡ ነው ፤

ሐዋ. ፡ 4 ፡ 37 ፤ ዕርሻም ፡ ነበረውና ፡ ሸጦ ፡ ገንዘቡን ፡ አምጥቶ ፡ ከሐዋርያት ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ አኖረው ።

_____የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ሐናንያም ፡ የተባለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሰጲራ ፡ ከተባለች ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ መሬት ፡ ሸጠ ፥

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ሚስቱም ፡ ደግሞ ፡ ስታውቅ ፡ ከሽያጩ ፡ አስቀረና ፡ እኩሌታውን ፡ አምጥቶ ፡ በሐዋርያት ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ አኖረው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ጴጥሮስም ፦ ሐናንያ ፡ ሆይ ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ታታልልና ፥ ከመሬቱ ፡ ሽያጭ ፡ ታስቀር ፡ ዘንድ ፡ ሰይጣን ፡ በልብኽ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ሞላ ፧

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ ሳትሸጠው ፡ የአንተ ፡ አልነበረምን ፧ ከሸጥኸውስ ፡ በኋላ ፡ በሥልጣንኽ ፡ አልነበረምን ፧ ይህን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በልብኽ ፡ ዐሰብኽ ፧ እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ አልዋሸኽም ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ሐናንያም ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ሰምቶ ፡ ወደቀ ፡ ሞተም ፤ በሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ጕበዞችም ፡ ተነሥተው ፡ ከፈኑት ፡ አውጥተውም ፡ ቀበሩት ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ከሦስት ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ በኋላም ፡ ሚስቱ ፡ የኾነውን ፡ ሳታውቅ ፡ ገባች ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ጴጥሮስም ፡ መልሶ ፦ እስቲ ፡ ንገሪኝ ፥ መሬታችኹን ፡ ይህን ፡ ለሚያኽል ፡ ሸጣችኹትን ፧ አላት ። ርሷም ፦ አዎን ፥ ይህን ፡ ለሚያኽል ፡ ነው ፡ አለች ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ጴጥሮስም ፦ የጌታን ፡ መንፈስ ፡ ትፈታተኑ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተስማማችኹ ፧ እንሆ ፥ ባልሽን ፡ የቀበሩት ፡ ሰዎች ፡ እግር ፡ በደጅ ፡ ነው ፥ አንቺንም ፡ ያወጡሻል ፡ አላት ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ በእግሩ ፡ አጠገብ ፡ ወደቀች ፡ ሞተችም ፤ ጕበዞችም ፡ ሲገቡ ፡ ሞታ ፡ አገኟት ፡ አውጥተውም ፡ በባሏ ፡ አጠገብ ፡ ቀበሯት ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉና ፡ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሀት ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ በሐዋርያትም ፡ እጅ ፡ ብዙ ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ በሕዝብ ፡ መካከል ፡ ይደረግ ፡ ነበር ፤ ኹሉም ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ በሰሎሞን ፡ ደጅ ፡ መመላለሻ ፡ ነበሩ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከሌላዎችም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ሊተባበራቸው ፡ የሚደፍር ፡ አልነበረም ፥

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ሕዝቡ ፡ ግን ፡ ያከብሯቸው ፡ ነበር ፤ የሚያምኑትም ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ለጌታ ፡ ይጨመሩለት ፡ ነበር ፤ ወንዶችና ፡ ሴቶችም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ስለዚህም ፡ ጴጥሮስ ፡ ሲያልፍ ፡ ጥላውም ፡ ቢኾን ፡ ከነርሱ ፡ አንዱን ፡ ይጋርድ ፡ ዘንድ ፡ ድውያንን ፡ ወደ ፡ አደባባይ ፡ አውጥተው ፡ በዐልጋና ፡ በወሰካ ፡ ያኖሯቸው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ደግሞም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ዙሪያ ፡ ካለችው ፡ ከተማ ፡ ድውያንንና ፡ በርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ የተሣቀዩትን ፡ እያመጡ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይሰበስቡ ፡ ነበር ፤ ኹሉም ፡ ይፈወሱ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ግን ፡ የሰዱቃውያን ፡ ወገን ፡ ኾነውም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ኹሉ ፡ ተነሡ ፡ ቅንአትም ፡ ሞላባቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ በሐዋርያትም ፡ ላይ ፡ እጃቸውን ፡ ጭነው ፡ በሕዝቡ ፡ ወህኒ ፡ ውስጥ ፡ አኖሯቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡ የወህኒውን ፡ ደጅ ፡ ከፍቶ ፡ አወጣቸውና ፦

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ኺዱና ፡ ቆማችኹ ፡ የዚህን ፡ ሕይወት ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ ለሕዝብ ፡ በመቅደስ ፡ ንገሩ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ በሰሙም ፡ ጊዜ ፡ ማልደው ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገብተው ፡ አስተማሩ ። ግን ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ መጥተው ፡ ሸንጎውንና ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሽማግሌዎች ፡ ኹሉ ፡ በአንድነት ፡ ጠሩ ፥ ያመጧቸውም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ላኩ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 22-23 ፤ ሎሌዎችም ፡ መጥተው ፡ በወህኒው ፡ አላገኟቸውም ፤ ተመልሰውም ፦ ወህኒው ፡ በጣም ፡ በጥንቃቄ ፡ ተዘግቶ ፡ ጠባቂዎችም ፡ በደጁ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ አገኘን ፥ በከፈትን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ በውስጡ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አላገኘንም ፡ አሏቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ የመቅደስ ፡ አዛዥና ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፦ እንጃ ፡ ይህ ፡ ምን ፡ ይኾን ፧ እያሉ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አመነቱ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ መጥቶ ፦ እንሆ ፥ በወህኒ ፡ ያኖራችኋቸው ፡ ሰዎች ፡ እየቆሙ ፡ ሕዝቡንም ፡

እያስተማሩ ፡ በመቅደስ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ አወራላቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አዛዡ ፡ ከሎሌዎች ፡ ጋራ ፡ ኼዶ ፡ አመጣቸው ፥ በኀይል ፡ ግን ፡ አይደለም ፤ ሕዝቡ ፡ እንዳይወግሯቸው ፡ ይፈሩ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ አምጥተውም ፡ በሸንጎ ፡ አቆሟቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፦ በዚህ ፡ ስም ፡ እንዳታስተምሩ ፡ አጥብቀን ፡ አላዘዝናችኹምን ፧ እንሆም ፥ ኢየሩሳሌምን ፡ በትምህርታችኹ ፡ ሞልታችኋል ፤ የዚያንም ፡ ሰው ፡ ደም ፡ በእኛ ፡ ታመጡብን ፡ ዘንድ ፡ ታስባላችኹ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 29 ፤ ጴጥሮስና ፡ ሐዋርያትም ፡ መልሰው ፡ አሉ ፦ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልንታዘዝ ፡ ይገባል ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 30 ፤ እናንተ ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅላችኹ ፡ የገደላችኹትን ፡ ኢየሱስን ፡ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ አስነሣው ፤

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ይህን ፡ እግዚአብሔር ፥ ለእስራኤል ፡ ንስሓን ፡ የኀጢአትንም ፡ ስርየት ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፥ ራስም ፡ መድኀኒትም ፡ አድርጎ ፡ በቀኙ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ እኛም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፥ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚታዘዙት ፡ የሰጠው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክር ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ እነርሱም ፡ ሲሰሙ ፡ በጣም ፡ ተቈጡ ፥ ሊገድሏቸውም ፡ ዐሰቡ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 34 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የከበረ ፡ የሕግ ፡ መምህር ፡ ገማልኤል ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ፈሪሳዊ ፡ በሸንጎ ፡ ተነሥቶ ፡ ሐዋርያትን ፡ ጥቂት ፡ ፈቀቅ ፡ እንዲያደርጓቸው ፡ አዘዘ ፥

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 35 ፤ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ምን ፡ እንደምታደርጉ ፡ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 36 ፤ ከዚህ ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡ ቴዎዳስ ፦ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ነበርና ፥ አራት ፡ መቶ ፡ የሚያኽሉ ፡ ሰዎችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተባበሩ ፤ ርሱም ፡ ጠፋ ፡ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ ተበተኑ ፡ እንደ ፡ ምናምንም ፡ ኾኑ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 37 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሰዎች ፡ በተጻፉበት ፡ ዘመን ፡ የገሊላው ፡ ይሁዳ ፡ ተነሣ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ አሸፍቶ ፡ አስከተለ ፤ ርሱም ፡ ጠፋ ፡ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ ተበታተኑ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 38 ፤ አኹንም ፡ እላችኋለኹ ፦ ከነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ተለዩ ፡ ተዉአቸውም ፤ ይህ ፡ ዐሳብ ፡ ወይም ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ ከሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይጠፋልና ፤

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 39 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ ታጠፏቸው ፡ ዘንድ ፡ አይቻላችኹም ፥ በርግጥ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስትጣሉ ፡ ምናልባት ፡ እንዳትገኙ ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 40 ፤ ሰሙትም ፥ ሐዋርያትንም ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ጠርተው ፡ ገረፏቸው ፥ በኢየሱስም ፡ ስም ፡ እንዳይናገሩ ፡ አዘው ፡ ፈቷቸው ።

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 41 ፤ እነርሱም ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ይናቁ ፡ ዘንድ ፡ የተገባቸው ፡ ኾነው ፡ ስለ ፡ ተቈጠሩ ፡ ከሸንጎው ፡ ፊት ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ወጡ ፤

ሐዋ. ፡ 5 ፡ 42 ፤ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ በመቅደስና ፡ በቤታቸው ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ማስተማርንና ፡ መስበክን ፡ አይተዉም ፡ ነበር ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ በዚህም ፡ ወራት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እየበዙ ፡ ሲኼዱ ፡ ከግሪክ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ የነበሩት ፡ አይሁድ ፡ በይሁዳ ፡ ኖረው ፡ በነበሩት ፡ አይሁድ ፡ አንጐራጐሩባቸው ፥ በየቀኑ ፡ በተሠራው ፡ አገልግሎት ፡ መበለቶቻቸውን ፡ ችላ ፡ ይሉባቸው ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ኾሉን ፡ ጠርተው ፡ እንዲህ ፡ አሏቸው ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ትተን ፡ ማእዱን ፡ እናገለግል ፡ ዘንድ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ አይደለም ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በመልካም ፡ የተመሰከረላቸውን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ ጥበብም ፡ የሞላባቸውን ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ ከእናንተ ፡ ምረጡ ፥ ለዚህም ፡ ጕዳይ ፡ እንሾማቸዋለን ፤

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ለጸሎትና ፡ ቃሉን ፡ ለማገልገል ፡ እንተጋለን ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ይህም ፡ ቃል ፡ ሕዝብን ፡ ኾሉ ፡ ደስ ፡ አሠኛቸው ፤ እምነትና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሞላበትን ፡ ሰው ፡ እስጢፋኖስን ፡ ፊልጶስንም ፡ ጵሮኮሮስንም ፡ ኒቃሮናንም ፡ ጢሞናንም ፡ ጳርሜናንም ፡ ወደ ፡ ይሁዲነት ፡ ገብቶ ፡ የነበረውን ፡ የአንጾኪያውን ፡ ኒቆላዎስንም ፡ መረጡ ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በሐዋርያትም ፡ ፊት ፡ አቆሟቸው ፥ ከጸለዩም ፡ በኋላ ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እየሰፋ ፡ ኼደ ፥ በኢየሩሳሌምም ፡ የደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ እየበዛ ፡ ኼደ ፤ ከካህናትም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ለሃይማኖት ፡ የታዘዙ ፡ ኾኑ ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ እስጢፋኖስም ፡ ጸጋንና ፡ ኀይልን ፡ ተሞልቶ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ድንቅንና ፡ ታላቅ ፡ ምልክትን ፡ ያደርግ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ የነጻ ፡ ወጪዎች ፡ ከተባለችው ፡ ምኩራብም ፡ ከቀሬናና ፡ ከእስክንድርያም ፡ ሰዎች ፡ ከኪልቅያና ፡ ከእስያም ፡ ከነበሩት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ተነሥተው ፡ እስጢፋኖስን ፡ ይከራከሩት ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ ይናገርበት ፡ የነበረውንም ፡ ጥበብና ፡ መንፈስ ፡ ይቃወሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፦ በሙሴ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ ሲናገር ፡ ሰምተነዋል ፡ የሚሉ ፡ ሰዎችን ፡ አስነሡ ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ ሕዝቡንና ፡ ሽማግሌዎችንም ፡ ጻፊዎችንም ፡ አናደዱ ፥ ቀርበውም ፡ ያዙት ፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ አመጡትና ፦

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ በተቀደሰው ፡ ስፍራ ፡ በሕግም ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ አይተውም ፤

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ይህ ፡ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ ይህን ፡ ስፍራ ፡ ያፈርሰዋል ፡ ሙሴም ፡ ያስተላለፈልንን ፡ ሥርዐት ፡ ይለውጣል ፡ ሲል ፡ ሰምተነዋልና ፥ የሚሉ ፡ የሐሰት ፡ ምስክሮችን ፡ አቆሙ ።

ሐዋ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ በሸንጎም ፡ የተቀመጡት ፡ ኾሉ ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡ ሲመለከቱት ፡ እንደ ፡ መልአክ ፡ ፊት ፡ ኾኖ ፡ ፊቱን ፡ አዩት ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነውን ፧ አለው ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ርሱም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ወንድሞችና ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ስሙ ። የክብር ፡ አምላክ ፡ ለአባታችን ፡ ለአብርሃም ፡ በካራን ፡ ሳይቀመጥ ፡ ገና ፡ በኹለት ፡ ወንዝ ፡ መካከል ፡ ሳለ ፡ ታየና ፦

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ከአገርኽና ፡ ከዘመዶችኽም ፡ ወጥተኽ ፡ ወደማሳይኽ ፡ ወደ ፡ ማንኛውም ፡ ምድር ፡ ና ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ከከለዳውያን ፡ አገር ፡ ወጥቶ ፡ በካራን ፡ ተቀመጠ ። ከዚያም ፡ አባቱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እናንተ ፡ ዛሬ ፡ ወደምትኖሩባት ፡ ወደዚች ፡ አገር ፡ አወጣው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ በዚችም ፡ የእግር ፡ ጫማ ፡ ስንኳ ፡ የሚያኽል ፡ ርስት ፡ አልሰጠውም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልጅ ፡ ሳይኖረው ፡ ለርሱ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ለዘሩ ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ሰጠው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ዘሩ ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ መጻተኞች ፡ እንዲኾኑ ፡ አራት ፡ መቶ ፡ ዓመትም ፡ ባሪያዎች ፡ እንዲያደርጓቸው ፡ እንዲያስጨንቋቸውም ፡ እንዲህ ፡ ተናገረ ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ደግሞም ፡ እግዚአብሔር ፦ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ በሚገዟቸው ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ እፈርድባቸዋለኹ ፥ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይወጣሉ ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ያመልኩኛል ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ የመገረዝንም ፡ ኪዳን ፡ ሰጠው ፤ እንዲሁም ፡ ይሥሐቅን ፡ ወለደ ፡ በስምንተኛውም ፡ ቀን ፡ ገረዘው ፡ ይሥሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ያዕቆብም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱን ፡ የአባቶችን ፡ አለቃዎች ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ የአባቶችም ፡ አለቃዎች ፡ በዮሴፍ ፡ ቀንተው ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ሸጡት ፤ እግዚአብሔርም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፥

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ ከመከራውም ፡ ኹሉ ፡ አወጣው ፥ በግብጽ ፡ ንጉሥ ፡ በፈርዖንም ፡ ፊት ፡ ሞገስንና ፡ ጥበብን ፡ ሰጠው ፥ በግብጽና ፡ በቤቱ ፡ ኹሉ ፡ ላይም ፡ ቢትወደድ ፡ አድርጎ ፡ ሾመው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ በግብጽና ፡ በከነዓንም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ራብና ፡ ብዙ ፡ ጭንቅ ፡ መጣ ፥ አባቶቻችንም ፡ ምግብን ፡ አላገኙም ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ ያዕቆብም ፡ በግብጽ ፡ እኽል ፡ መኖሩን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በመዠመሪያ ፡ አባቶቻችንን ፡ ሰደዳቸው ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ በኹለተኛውም ፡ ዮሴፍ ፡ ለወንድሞቹ ፡ ታወቀ ፥ የዮሴፍም ፡ ትውልድ ፡ በፈርዖን ፡ ዘንድ ፡ ተገለጠ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ ዮሴፍም ፡ አባቱን ፡ ያዕቆብንና ፡ ሰባ ፡ ዐምስት ፡ ነፍስ ፡ የነበረውን ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፡ ኹሉ ፡ ልኮ ፡ አስጠራ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ያዕቆብም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ወረደ ፥ ርሱም ፡ ሞተ ፥ አባቶቻችንም ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ሴኬምም ፡ አፍልሰው ፡ አብርሃም ፡ ከሴኬም ፡ አባት ፡ ከኤሞር ፡ ልጆች ፡ በብር ፡ በገዛው ፡ መቃብር ፡ ቀበሯቸው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 17-18 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአብርሃም ፡ የማለለት ፡ የተስፋው ፡ ዘመን ፡ ሲቀርብ ፥ ዮሴፍን ፡ የማያውቀው ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ በግብጽ ፡ ላይ ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፥ ሕዝቡ ፡ እየተጨመሩ ፡ በግብጽ ፡ በዙ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 19 ፤ ርሱም ፡ ወገናችንን ፡ ተተንኰሎ ፡ ሕፃናትን ፡ በሕይወት ፡ እንዳይጠብቁ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ይጥሉ ፡ ዘንድ ፡ አድርጎ ፡ አባቶቻችንን ፡ አስጨነቀ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 20 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ሙሴ ፡ ተወለደ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ያማረ ፡ ነበር ፤ በአባቱ ፡ ቤትም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ አደገ ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ በተጣለም ፡ ጊዜ ፡ የፈርዖን ፡ ልጅ ፡ አነሣችው ፡ ልጅም ፡ ይኾናት ፡ ዘንድ ፡ አሳደገችው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ ሙሴም ፡ የግብጾችን ፡ ጥበብ ፡ ኹሉ ፡ ተማረ ፥ በቃሉና ፡ በሥራውም ፡ የበረታ ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሲሞላው ፡ ወንድሞቹን ፡ የእስራኤልን ፡ ልጆች ፡ ይጐበኝ ፡ ዘንድ ፡ በልቡ ፡ ዐሰበ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ አንዱም ፡ ሲበደል ፡ አይቶ ፡ ረዳው ፥ የግብጽን ፡ ሰውም ፡ መቶ ፡ ለተገፋው ፡ ተበቀለ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ ወንድሞቹም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጁ ፡ መዳንን ፡ እንዲሰጣቸው ፡ የሚያስተውሉ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፥ እነርሱ ፡ ግን ፡ አላስተዋሉም ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 26 ፤ በማግስቱም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጣሉ ፡ አገኛቸው ፥ ሊያስታርቃቸውም ፡ ወዶ ፦ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ እናንተስ ፡ ወንድማማች ፡ ናችኹ ፤ ስለ ፡ ምን ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትበዳደላላችኹ ፧ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ያም ፡ ባልንጀራውን ፡ የሚበድል ፡ ግን ፦ አንተን ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ ሹምና ፡ ፈራጅ ፡ እንድትኾን ፡ የሾመኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ ወይስ ፡ ትናንትና ፡ የግብጹን ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ገደልኸው ፡ ልትገድለኝ ፡ ትወዳለኽን ፧ ብሎ ፡ ገፋው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 29 ፤ ሙሴም ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡ ሸሸቶ ፡ በምድያም ፡ አገር ፡ መጻተኛ ፡ ኾኖ ፡ ኖረ ፤ በዚያም ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 30 ፤ አርባ ፡ ዓመትም ፡ ሲሞላ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ በቀጥቋጦ ፡ መካከል ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ታየው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 31-32 ፤ ሙሴም ፡ አይቶ ፡ ባየው ፡ ተደነቀ ፤ ሊመለከትም ፡ ሲቀርብ ፡ የጌታ ፡ ቃል ፦ እኔ ፡ የአባቶችኽ ፡ አምላክ ፣ ፡ የአብርሃም ፡ አምላክ ፣ የይሥሐቅም ፡ አምላክ ፣ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ። ሙሴም ፡ ተንቀጥቅጦ ፡ ሊመለከት ፡ አልደፈረም ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 33 ፤ ጌታም ፦ የቆምኽባት ፡ ስፍራ ፡ የተቀደሰች ፡ ምድር ፡ ናትና ፥ የእግርኽን ፡ ጫማ ፡ አውልቅ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 34 ፤ በግብጽ ፡ ያሉትን ፡ የሕዝቤን ፡ መከራ ፡ ፈጽሜ ፡ አይቼ ፡ መቃተታቸውንም ፡ ሰምቼ ፡ ላድናቸው ፡ ወረድኹ ፤ አኹንም ፡ ና ፥ ወደ ፡ ግብጽ ፡ እልክኻለኹ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 35 ፤ ሹምና ፡ ፈራጅ ፡ እንድትኾን ፡ የሾመኽ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብለው ፡ የካዱትን ፥ ይህን ፡ ሙሴን ፡ በቀጥቋጦው ፡ በታየው ፡ በመልአኩ ፡ እጅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሹምና ፡ ቤዛ ፡ አድርጎ ፡ ላከው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 36 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በግብጽ ፡ ምድርና ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በምድረ ፡ በዳም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ድንቅና ፡ ምልክት ፡ እያደረገ ፡ አወጣቸው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 37 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ ለእስራኤል ፡ ልጆች ፦ እግዚአብሔር ፡ ከወንድሞቻችኹ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ያለ ፡ ነቢይ ፡ ያስነሣላችኋል ፤ ርሱን ፡ ስሙት ፡ ያላቸው ፡ ሙሴ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 38 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ከተናገረው ፡ መልአክና ፡ ከአባቶቻችን ፡ ጋራ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በማኅበሩ ፡ ውስጥ ፡ የነበረው ፡ ነው ፤ ይሰጠንም ፡ ዘንድ ፡ ሕይወት ፡ ያላቸውን ፡ ቃላት ፡ ተቀበለ ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 39 ፤ ለርሱም ፡ አባቶቻችን ፡ ሊታዘዙት ፡ አልወደዱም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ገፉት ፡ በልባቸውም ፡ ወደ ፡ ግብጽ ፡ ተመለሱ ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 40 ፤ አሮንንም ፦ በፊታችን ፡ የሚኼዱ ፡ አማልክት ፡ ሥራልን ፤ ይህ ፡ ከግብጽ ፡ ምድር ፡ ያወጣን ፡ ሙሴ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አናውቅምና ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 41 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ጥጃ ፡ አደረጉ ፡ ለጣዖቱም ፡ መሥዋዕት ፡ አቀረቡ ፥ በእጃቸውም ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 42 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ አለ ፡ የሰማይንም ፡ ጭፍራ ፡ ያመልኩ ፡ ዘንድ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፥ በነቢያትም ፡ መጽሐፍ ። እናንተ ፡ የእስራኤል ፡ ቤት ፥ አርባ ፡ ዓመት ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የታረደውን ፡ ከብትና ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረባችኹልኝን ፧

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 43 ፤ ትሰግዱላቸውም ፡ ዘንድ ፡ የሠራችኋቸውን ፡ ምስሎች ፡ እነርሱንም ፡ የሞሎክን ፡ ድንኳንና ፡ ሬምፋም ፡ የሚሉትን ፡ የአምላካችኹን ፡ ኮከብ ፡ አነሣችኹ ፤ እኔም ፡ ከባቢሎን ፡ ወዲያ ፡ እሰዳችኋለኹ ፡ ተብሎ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፏል ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 44 ፤ እንዳየው ፡ ምስል ፡ አድርጎ ፡ ይሠራት ፡ ዘንድ ፡ ሙሴን ፡ ተናግሮ ፡ እንዳዘዘው ፥ የምስክር ፡ ድንኳን ፡ ከአባቶቻችን ፡ ዘንድ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ነበረች ፤

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 45 ፤ አባቶቻችንም ፡ ደግሞ ፡ በተራ ፡ ተቀብለው ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊታቸው ፡ ያወጣቸውን ፡ የአሕዛብን ፡ አገር ፡ በያዙት ፡ ጊዜ ፡ ከኢያሱ ፡ ጋራ ፡ አገቧት ፥ እስከዳዊት ፡ ዘመንም ፡ ድረስ ፡ ኖረች ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 46 ፤ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሞገስ ፡ አግኝቶ ፡ ለያዕቆብ ፡ አምላክ ፡ ማደሪያን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ለመነ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 47 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰሎሞን ፡ ቤት ፡ ሠራለት ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 48-50 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነቢዩ ፦ ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነው ፥ ምድርም ፡ የእግሬ ፡ መረገጫ ፡ ናት ፤ ለእኔ ፡ ምን ፡ ዐይነት ፡ ቤት ፡ ትሠራላችኹ ፧ ይላል ፡ ጌታ ፥ ወይስ ፡ የማርፍበት ፡ ስፍራ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ይህንስ ፡ ኹሉ ፡ እጄ ፡ የሠራችው ፡ አይደለምን ፧ እንዳለ ፥ ልዑል ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ በሠራችው ፡ አይኖርም ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 51 ፤ እናንተ ፡ ዐንገተ ፡ ደንዳናዎች ፥ ልባችኹና ፡ ጐሯችኹም ፡ ያልተገረዘ ፥ እናንተ ፡ ኹልጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ትቃወማላችኹ ፤ አባቶቻችኹ ፡ እንደ ፡ ተቃወሙት ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 52-53 ፤ ከነቢያትስ ፡ አባቶቻችኹ ፡ ያላሳደዱት ፡ ማን ፡ ነው ፧ የጻድቁንም ፡ መምጣት ፡ አስቀድሞ ፡ የተናገሩትን ፡ ገደሏቸው ፤ በመላእክት ፡ ሥርዐት ፡ ሕግን ፡ ተቀብላችኹ ፡ ያልጠበቃችኹት ፡ እናንተም ፡ አኹን ፡ ርሱን ፡ አሳልፋችኹ ፡ ሰጣችኹት ፥ ገደላችኹትም ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 54 ፤ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በልባቸው ፡ በጣም ፡ ተቈጡ ፡ ጥርሳቸውንም ፡ አፋጨበት ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 55 ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ተሞልቶ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ ኢየሱስንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ቆሞ ፡ አየና ፦

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 56 ፤ እንሆ ፥ ሰማያት ፡ ተከፍተው ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ቆሞ ፡ አያለኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 57 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየጮኹ ፡ ጐሯቸውን ፡ ደፈኑ ፥ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነውም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሮጡ ፥

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 58 ፤ ከከተማም ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አውጥተው ፡ ወገሩት ። ምስክሮችም ፡ ልብሳቸውን ፡ ሳውል ፡ በሚሉት ፡ ባንድ ፡ ጐበዝ ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ አኖሩ ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 59 ፤ እስጢፋኖስም ፦ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ነፍሴን ፡ ተቀበል ፡ ብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ይወግሩት ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 7 ፡ 60 ፤ ተንበርክኮም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ኀጢአት ፡ አትቍጠርባቸው ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ። ይህንም ፡ ብሎ ፡ አንቀላፋ ። ሳውልም ፡ በርሱ ፡ መገደል ፡ ተስማምቶ ፡ ነበር ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ በዚያ ፡ ቀንም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ታላቅ ፡ ስደት ፡ ኾነ ፤ ኹሉም ፡ ከሐዋርያትም ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ይሁዳና ፡ ወደሰማርያ ፡ አገሮች ፡ ተበተኑ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ በጸሎትም ፡ የተጉ ፡ ሰዎች ፡ እስጢፋኖስን ፡ ቀበሩት ፡ ታላቅ ፡ ልቅሶም ፡ አለቀሱለት ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ሳውል ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያፈርስ ፡ ነበር ፤ ወደኹሉም ፡ ቤት ፡ እየገባ ፡ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ እየጐተተ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጥ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ የተበተኑትም ፡ ቃሉን ፡ እየሰበኩ ፡ ዞሩ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ ፊልጶስም ፡ ወደሰማርያ ፡ ከተማ ፡ ወርዶ ፡ ክርስቶስን ፡ ሰበከላቸው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ሕዝቡም ፡ የፊልጶስን ፡ ቃል ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ያደርጋት ፡ የነበረውንም ፡ ምልክት ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ የተናገረውን ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ አደመጡ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እየጮኹ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይወጡ ፡ ነበርና ፤ ብዙም ፡ ሽባዎችና ፡ ዐንካሳዎች ፡ ተፈወሱ ፤

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በዚያችም ፡ ከተማ ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ሲሞን ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ግን ፦ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፥ እየጠነቈለ ፡ የሰማርያንም ፡ ወገን ፡ እያስገረመ ፡ ቀድሞ ፡ በከተማ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ከታናናሾችም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላላቆቹ ፡ ድረስ ፦ ታላቁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ኹሉ ፡ ያደምጡት ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ከብዙ ፡ ዘመንም ፡ ዠምሮ ፡ በጥንቈላ ፡ ስላስገረማቸው ፡ ያደምጡት ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥትና ፡ ስለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እየሰበከላቸው ፡ ፊልጶስን ፡ ባመኑት ፡ ጊዜ ፥ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ተጠመቁ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ሲሞንም ፡ ደግሞ ፡ ራሱ ፡ አመነ ፤ ተጠምቆም ፡ ከፊልጶስ ፡ ጋራ ፡ ይተባበር ፡ ነበር ፤ የሚደረገውንም ፡ ምልክትና ፡ ታላቅ ፡ ተአምራት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተገረመ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ የነበሩት ፡ ሐዋርያት ፡ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደተቀበሉ ፡ ሰምተው ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ሰደዱላቸው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ ጸለዩላቸው ፤

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ተጠምቀው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ ከነርሱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ ስንኳ ፡ ገና ፡

አልወረደም ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ተቀበሉ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ሲሞንም ፡ በሐዋርያት ፡ እጅ ፡ መጫን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ ገንዘብ ፡ አመጣላቸውና ፦

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ እጄን ፡ የምጭንበት ፡ ኹሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ሥልጣን ፡ ስጡኝ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታ ፡ በገንዘብ ፡ እንድታገኝ ፡ ዐስበኻልና ፥ ብርኽ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይጥፋ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ልብኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ የቀና ፡ አይደለምና ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ ዕድል ፡ ወይም ፡ ፈንታ ፡ የለኽም ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ እንግዲህ ፡ ስለዚህ ፡ ክፋትኽ ፡ ንስሓ ፡ ግባ ፥ ምናልባትም ፡ የልብኽን ፡ ዐሳብ ፡ ይቅር ፡ ይልኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምን ፤

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ በመራራ ፡ መርዝና ፡ በዐመፅ ፡ እስራት ፡ እንዳለኽ ፡ አይኻለኹና ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ ሲሞንም ፡ መልሶ ፦ ካላችኹት ፡ አንዳች ፡ እንዳይደርስብኝ ፡ እናንተው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ለምኑልኝ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ እነርሱም ፡ ከመሰከሩና ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፤ በሳምራውያን ፡ በብዙ ፡ መንደሮችም ፡ ወንጌልን ፡ ሰበኩ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ የጌታም ፡ መልአክ ፡ ፊልጶስን ፦ ተነሥተኽ ፡ በደቡብ ፡ በኩል ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ጋዛ ፡ ወደሚያወርደው ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ መንገድ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ተነሥቶም ፡ ኼደ ። እንሆም ፥ ሀንደኬ ፡ የተባለች ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ አዛኘና ፡ ጃን ፡ ደረባ ፡ የነበረ ፡ በገንዘቧም ፡ ኹሉ ፡ የሠለጠነ ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ሊሰግድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ ሲመለስም ፡ በሠረገላ ፡ ተቀምጦ ፡ የነቢዩን ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ያነብ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ መንፈስም ፡ ፊልጶስን ፦ ወደዚህ ፡ ሠረገላ ፡ ቅረብና ፡ ተገናኝ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ ፊልጶስም ፡ ሮጦ ፡ የነቢዩን ፡ የኢሳይያስን ፡ መጽሐፍ ፡ ሲያነብ ፡ ሰማና ፦ በእውኑ ፡ የምታነበውን ፡ ታስተውለዋለኽን ፧ አለው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ ርሱም ፦ የሚመራኝ ፡ ሳይኖር ፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ፧ አለው ። ወጥቶም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ፊልጶስን ፡ ለመነው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ያነበውም ፡ የነበረ ፡ የመጽሐፉ ፡ ክፍል ፡ ይህ ፡ ነበረ ፤ እንደ ፡ በግ ፡ ወደ ፡ መታረድ ፡ ተነዳ ፥ የበግ ፡ ጠቦትም ፡ በሸላቹ ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ እንደሚል ፥ እንዲሁ ፡ አፉን ፡ አልከፈተም ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ በውርደቱ ፡ ፍርዱ ፡ ተወገደ ፤ ሕይወቱ ፡ ከምድር ፡ ተወግዳለችና ፡ ትውልዱንስ ፡ ማን ፡ ይናገራል ፧

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ ጃን ፡ ደረባውም ፡ ለፊልጶስ ፡ መልሶ ፦ እባክኽ ፥ ነቢዩ ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ማን ፡ ይናገራል ፧ ስለ ፡ ራሱ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፧ አለው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ፊልጶስም ፡ አፉን ፡ ከፈተ ፥ ከዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ዠምሮ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ወንጌልን ፡ ሰበከለት ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ በመንገድም ፡ ሲኼዱ ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ደረሱ ፤ ጃን ፡ ደረባውም ፦ እንሆ ፥ ውሃ ፤ እንዳልጠመቅ ፡ የሚከለክለኝ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አለው ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 37 ፤ ፊልጶስም ፦ በፍጹም ፡ ልብኽ ፡ ብታምን ፥ ተፈቅዷል ፡ አለው ። መልሶም ፦ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አምናለኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 38 ፤ ሠረገላውም ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፥ ፊልጶስና ፡ ጃን ፡ ደረባው ፡ ኹለቱም ፡ ወደ ፡ ውሃ ፡ ወረዱ ፥ አጠመቀውም ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 39 ፤ ከውሃውም ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ የጌታ ፡ መንፈስ ፡ ፊልጶስን ፡ ነጠቀው ፤ ጃን ፡ ደረባውም ፡ ኹለተኛ ፡ አላየውም ፥ ደስ ፡ ብሎት ፡ መንገዱን ፡ ይኼድ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 8 ፡ 40 ፤ ፊልጶስ ፡ ግን ፡ በአዛጦን ፡ ተገኘ ፥ ወደ ፡ ቂሳርያም ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ እየዞረ ፡ በከተማዎች ፡ ኹሉ ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብክ ፡ ነበር ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ሳውል ፡ ግን ፡ የጌታን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እንዲገድላቸው ፡ ገና ፡ እየዛተ ፡ ወደ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኼደ ፥

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ በዚህ ፡ መንገድ ፡ ያሉትንም ፡ ሰዎች ፡ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ቢያገኝ ፥ እያሰረ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡ በደማስቆ ፡ ላሉት ፡ ምኩራቦች ፡ ደብዳቤ ፡ ከርሱ ፡ ለመነ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ሲኼድም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ በርሱ ፡ ዙሪያ ፡ ከሰማይ ፡ ብርሃን ፡ አንጸባረቀ ፤

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ወድቆ ፡ ሳለ ፦ ሳውል ፡ ሳውል ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደኛለኽ ፧ የሚለውን ፡ ድምፅ ፡ ሰማ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ማን ፡ ነኽ ፧ አለው ። ርሱም ፦ አንተ ፡ የምታሳድደኝ ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ፤ የመውጊያውን ፡ ብረት ፡ ብትቃወም ፡ ለአንተ ፡ ይብስብኻል ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ እየተንቀጠቀጠና ፡ እየተደነቀ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላደርግ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለኽ ፧ አለው ። ጌታም ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ግባና ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ የሚያስፈልግኽን ፡ ይነግሩኻል ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ በመንገድ ፡ የኼዱ ፡ ሰዎች ፡ ድምፁን ፡ እየሰሙ ፡ ማንን ፡ ግን ፡ ሳያዩ ፡ እንደ ፡ ዲዳዎች ፡ ቁሙ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ሳውልም ፡ ከምድር ፡ ተነሣ ፥ አይኖቹም ፡ በተከፈቱ ፡ ጊዜ ፡ ምንም ፡ አላየም ፤ እጁንም ፡ ይዘው ፡ እየመሩ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አገቡት ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ሳያይም ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ኖረ ፤ አልበላምም ፡ አልጠጣምም ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ በደማስቆም ፡ ሐናንያ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፥ ጌታም ፡ በራእይ ፦ ሐናንያ ፡

ሆይ ፥ አለው ። ርሱም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እንሆኝ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 11 ፤ ጌታም ፦ ተነሥተኽ ፡ ቅን ፡ ወደሚባለው ፡ መንገድ ፡ ኺድ ፥ በይሁዳ ፡ ቤትም ፡ ሳውል ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡ የጠርሴስ ፡ ሰው ፡ ፈልግ ፤

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 12 ፤ እንሆ ፥ ርሱ ፡ ይጸልያልና ፤ ሐናንያ ፡ የሚሉትም ፡ ሰው ፡ ገብቶ ፡ ደግሞ ፡ እንዲያይ ፡ እጁን ፡ ሲጭንበት ፡ አይቷል ፡ አለው ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ ሐናንያም ፡ መልሶ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ በቅዱሳንኽ ፡ ላይ ፡ ስንት ፡ ክፉ ፡ እንዳደረገ ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ከብዙዎች ፡ ሰምቻለኹ ፤

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ በዚህም ፡ ስምኽን ፡ የሚጠሩትን ፡ ኹሉ ፡ ለማሰር ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ ጌታም ፦ ይህ ፡ በአሕዛብም ፡ በነገሥታትም ፡ በእስራኤልም ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ስሜን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ ለእኔ ፡ የተመረጠ ፡ ዕቃ ፡ ነውና ፥ ኺድ ፤

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 16 ፤ ስለ ፡ ስሜ ፡ ስንት ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፡ እንዲያስፈልገው ፡ እኔ ፡ አመለክተዋለኹና ፡ አለው ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 17 ፤ ሐናንያም ፡ ኼዶ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ገባ ፥ እጁንም ፡ ጭኖበት ፦ ወንድሜ ፡ ሳውል ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፥ ርሱም ፡ በመጣኽበት ፡ መንገድ ፡ የታየኽ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፥ ደግሞ ፡ ታይ ፡ ዘንድና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይሞላብኽ ፡ ዘንድ ፡ ላከኝ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 18 ፤ ወዲያውም ፡ እንደ ፡ ቅርፊት ፡ ያለ ፡ ከዐይኑ ፡ ወደቀ ፥ ያን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ አየ ፤ ተነሥቶም ፡ ተጠመቀ ፥

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 19 ፤ መብልም ፡ በልቶ ፡ በረታ ። በደማስቆም ፡ ካሉት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ኖረ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 20 ፤ ወዲያውም ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በምኩራቦቹ ፡ ሰበከ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 21 ፤ የሰሙትም ፡ ኹሉ ፡ ተገረሙና ፦ ይህ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይህን ፡ ስም ፡ የሚጠሩትን ፡ ያጠፋ ፡ አይደለምን ፧ ስለዚህስ ፡ ታስረው ፡ ወደካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ይወስዳቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደዚህ ፡ አልመጣምን ፧ አሉ ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 22 ፤ ሳውል ፡ ግን ፡ እየበረታ ፡ ኼደ ፥ በደማስቆም ፡ ለተቀመጡት ፡ አይሁድ ፡ ይህ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስረድቶ ፡ መልስ ፡ ያሳጣቸው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 23 ፤ ብዙ ፡ ቀንም ፡ ሲሞላ ፡ አይሁድ ፡ ሊገድሉት ፡ ተማከሩ ፤

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 24 ፤ ሳውል ፡ ግን ፡ ዐሳባቸውን ፡ ዐወቀ ። ይገድሉትም ፡ ዘንድ ፡ በሌሊትና ፡ በቀን ፡ የከተማዪቱን ፡ በር ፡ ኹሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 25 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡ ወስደው ፡ በቅጥር ፡ ላይ ፡ አሳልፈው ፡ በቅርጫት ፡ አወረዱት ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 26 ፤ ሳውልም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡ ይተባበር ፡ ዘንድ ፡ ሞከረ ፤ ኹሉም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስላላመኑ ፡ ፈሩት ።

ሐዋ. ፥ 9 ፥ 27 ፤ በርናባስ ፡ ግን ፡ ወስዶ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ አገባውና ፡ ጌታን ፡ በመንገድ ፡ እንዴት ፡ እንዳየውና ፡ እንደ ፡ ተናገረው ፡ በደማስቆም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ደፍሮ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነገረ ፡ ተረከላቸው ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ በጌታም ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ደፍሮ ፡ እየተናገረ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ሲወጣና ፡ ሲገባ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ከግሪክ ፡ አገርም ፡ መጥተው ፡ ከነበሩት ፡ አይሁድ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገርና ፡ ይከራከር ፡ ነበር ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ሊገድሉት ፡ ፈለጉ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ ወንድሞችም ፡ ይህን ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ወሰዱት ፡ ወደ ፡ ጠርሴስም ፡ ሰደዱት ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ በይሁዳም ፡ ዥሉና ፡ በገሊላ ፡ በሰማርያም ፡ የነበሩት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሰላም ፡ ኖሩ ፡ ታነጹም ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፍርሀትና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መጽናናት ፡ እየኼዱ ፡ ይበዙ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 32 ፤ ጴጥሮስም ፡ በየስፍራው ፡ ዥሉ ፡ ሲዞር ፡ በልዳ ፡ ወደሚኖሩ ፡ ቅዱሳን ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 33 ፤ በዚያም ፡ ከስምንት ፡ ዓመት ፡ ዠምሮ ፡ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ ተኝቶ ፡ የነበረውን ፡ ኤንያ ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኘ ፤ ርሱም ፡ ሽባ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 34 ፤ ጴጥሮስም ፦ ኤንያ ፡ ሆይ ፥ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይፈውስኻል ፤ ተነሣ ፡ ለራስኽም ፡ አንጥፍ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 35 ፤ ወዲያውም ፡ ተነሣ ። በልዳና ፡ በሰሮናም ፡ የሚኖሩ ፡ ዥሉ ፡ ርሱን ፡ አይተው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ዘወር ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 36 ፤ በኢዮጴም ፡ ጣቢታ ፡ የሚሏት ፡ አንዲት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረች ፥ ትርጓሜውም ፡ ዶርቃ ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ርሷም ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ የሞላባት ፡ ምጽዋትም ፡ የምታደርግ ፡ ነበረች ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 37 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ታመመችና ፡ ሞተች ፤ ዐጥበውም ፡ በሰገነት ፡ አኖሯት ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 38 ፤ ልዳም ፡ ለኢዮጴ ፡ ቅርብ ፡ ናትና ፥ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጴጥሮስ ፡ በዚያ ፡ እንዳለ ፡ ሰምተው ፥ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ከመምጣት ፡ እንዳይዘገይ ፡ እየለመኑ ፡ ኹለት ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ላኩ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 39 ፤ ጴጥሮስም ፡ ተነሥቶ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ መጣ ፤ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ በሰገነት ፡ አወጡት ፡ መበለቶችም ፡ ዥሉ ፡ እያለቀሱ ፡ ዶርቃ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለች ፡ ያደረገቻቸውን ፡ ቀሚሶችንና ፡ ልብሶችን ፡ ዥሉ ፡ እያሳዩት ፡ በፊቱ ፡ ቆሙ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 40 ፤ ጴጥሮስም ፡ ዥሉን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አስወጥቶ ፡ ተንበርክኮም ፡ ጸለየ ፥ ወደ ፡ ሬሳውም ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፦ ጣቢታ ፡ ሆይ ፥ ተነሺ ፡ አላት ። ርሷም ፡ ዐይኖቿን ፡ ከፈተች ፡ ጴጥሮስንም ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠች ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 41 ፤ እጁንም ፡ ለርሷ ፡ ሰጥቶ ፡ አስነሣት ፤ ቅዱሳንንና ፡ መበለቶችንም ፡ ጠራ ፡ ሕያውም ፡ ኾና ፡ በፊታቸው ፡ አቆማት ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 42 ፤ ይህም ፡ በኢዮጴ ፡ ዥሉ ፡ የታወቀ ፡ ኾነ ፥ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በጌታ ፡ አመኑ ።

ሐዋ. ፡ 9 ፡ 43 ፤ በኢዮጴም ፡ ስምዖን ፡ ከሚሉት ፡ ካንድ ፡ ቀዐርበት ፡ ፋቂ ፡ ጋራ ፡ ዐያሌ ፡ ቀን ፡ ኖረ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ በቂሳርያም ፡ ኢጣሊቄ ፡ ለሚሉት ፡ ጭፍራ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ የኾነ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ ርሱም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ዥሉ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክና ፡ የሚፈራ ፡ ለሕዝብም ፡

እጅግ ፡ ምጽዋት ፡ የሚያደርግ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ዥልጊዜ ፡ የሚጸልይ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ከቀኑም ፡ ዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፦ ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፡ የሚለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲገባ ፡ በራእይ ፡ በግልጥ ፡ አየው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ርሱም ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከተው ፡ ደንግጦ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምንድር ፡ ነው ፧ አለ ። መልአኩም ፡ አለው ፦ ጸሎትኽና ፡ ምጽዋትኽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለመታሰቢያ ፡ እንዲኾን ፡ ዐረገ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ አኹንም ፡ ወደአዮጴ ፡ ሰዎችን ፡ ልከኽ ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስመጣ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ ቤቱ ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ባለው ፡ በቀ፡ርበት ፡ ፋቂው ፡ በስምዖን ፡ ዘንድ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጧል ፤ ልታደርገው ፡ የሚገባኽን ፡ ርሱ ፡ ይነግርኻል ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ የተናገረውም ፡ መልአክ ፡ በኼደ ፡ ጊዜ ፥ ከሎሌዎቹ ፡ ኹለቱን ፥ ከማይለዩትም ፡ ጭፍራዎቹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክ ፡ አንዱን ፡ ወታደር ፡ ጠርቶ ፥

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ነገሩን ፡ ኹሉ ፡ ተረከላቸው ፥ ወደ ፡ አዮጴም ፡ ላካቸው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ እነርሱም ፡ በነገው ፡ ሲኼዱ ፡ ወደ ፡ ከተማም ፡ ሲቀርቡ ፥ ጴጥሮስ ፡ በስድስት ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጣራው ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ተርቦም ፡ ሊበላ ፡ ወደደ ፤ ሲያዘጋጁለት ፡ ሳሉም ፡ ተመስጦ ፡ መጣበት ፤

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ሰማይም ፡ ተከፍቶ ፡ ባራት ፡ ማእዘን ፡ የተያዘ ፡ ታላቅ ፡ ሸማ ፡ የሚመስል ፡ ዕቃ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ፤

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ በዚያውም ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያላቸው ፡ ኹሉ ፡ አራዊትም ፡ በምድርም ፡ የሚንቀሳቀሱት ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ ነበሩበት ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፥ ተነሣና ፡ ዐርደኽ ፡ ብላ ፡ የሚልም ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አይኾንም ፤ አንዳች ፡ ርኵስ ፡ የሚያስጸይፍም ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅምና ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፡ ኹለተኛ ፦ እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጣ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ይህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ኾነ ፥ ወዲያውም ፡ ዕቃው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተወሰደ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ጴጥሮስም ፡ ስላየው ፡ ራእይ ፦ ምን ፡ ይኾን ፧ ብሎ ፡ በልቡ ፡ ሲያመነታ ፥ እንሆ ፥ ቆርኔሌዎስ ፡ የላካቸው ፡ ሰዎች ፡ ስለስምዖን ፡ ቤት ፡ ጠይቀው ፡ ወደ ፡ ደጁ ፡ ቀረቡ ፤

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፦ ጴጥሮስ ፡ የተባለው ፡ ስምዖን ፡ በዚህ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጧልን ፧ ብለው ፡ ይጠይቁ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ጴጥሮስም ፡ ስለ ፡ ራእዩ ፡ ሲያወጣ ፡ ሲያወርድ ፡ ሳለ ፥ መንፈስ ፦ እንሆ ፥ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ይፈልጉኻል ፤

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ተነሥተኽ ፡ ውረድ ፥ እኔም ፡ ልኬያቸዋለኹና ፡ ሳትጠራጠር ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ኺድ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ ወርዶ ፦ እንሆ ፥ የምትፈልጉኝ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ የመጣችኹበትስ ፡ ምክንያት ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ እነርሱም ፦ ጻድቅ ፡ ሰው ፣ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፥ በአይሁድም ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ የተመሰከረለት ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ያስመጣኽ ፡ ዘንድ ፥ ከአንተም ፡ ቃልን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ፥ ከቅዱስ ፡ መልአክ ፡ ተረዳ ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ጠርቶ ፡ እንግድነት ፡ ተቀበላቸው ። በነገውም ፡ ተነሥቶ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጣ ፥ በኢዮጴም ፡ ከነበሩት ፡ ወንድሞች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ በነገውም ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ገቡ ፤ ቆርኔሌዎስም ፡ ዘመዶቹንና ፡ የቅርብ ፡ ወዳጆቹን ፡ ባንድነት ፡ ጠርቶ ፡ ይጠባበቃቸው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ጴጥሮስም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ተገናኝቶ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወደቀና ፡ ሰገደለት ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፦ ተነሣ ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ አስነሣው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እየተነጋገረ ፡ ገባ ፥ ብዙዎችም ፡ ተከማችተው ፡ አግኝቶ ፦

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ከሌላ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ይተባበር ፡ ወይም ፡ ይቃረብ ፡ ዘንድ ፡ እንዳልተፈቀደ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ፤ ለእኔ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ማንንም ፡ ሰው ፡ ርኩስና ፡ የሚያስጸይፍ ፡ ነው ፡ እንዳልል ፡ አሳየኝ ፤

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ ብትጠሩኝ ፡ ሳልከራከር ፡ መጣኹ ። አኹንም ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ አስመጣችኹኝ ፧ ብዬ ፡ እጠይቃችኋለኹ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ ቆርኔሌዎስም ፡ እንዲህ ፡ አለው ፦ በዚች ፡ ሰዓት ፡ የዛሬ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ የዘጠኝ ፡ ሰዓት ፡ ጸሎት ፡ በቤቴ ፡ እጸልይ ፡ ነበር ፤ እንሆም ፥ የሚያንጸባርቅ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ በፊቴ ፡ ቆመና ፦

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጸሎትኽ ፡ ተሰማ ፥ ምጽዋትኽም ፡ ታሰበ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 32 ፤ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ኢዮጴ ፡ ልከኽ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስጠራ ፤ ርሱ ፡ በቀ፡ርበት ፡ ፋቂው ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ እንግድነት ፡ ተቀምጧል ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 33 ፤ ስለዚህ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወዳንተ ፡ ላክኹ ፥ አንተም ፡ በመምጣትኽ ፡ መልካም ፡ አድርገኻል ። እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታዘዝኸውን ፡ ኹሉ ፡ እንድንሰማ ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ አኹን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በዚህ ፡ አለን ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 34-35 ፤ ጴጥሮስም ፡ አፉን ፡ ከፍቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳያደላ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ርሱን ፡ የሚፈራና ፡ ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡ በርሱ ፡ የተወደደ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእውነት ፡ አስተዋልኹ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ የኹሉ ፡ ጌታ ፡ በሚኾን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምን ፡ እየሰበከ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ወደእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ላከ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ ዮሐንስ ፡ ከሰበከው ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡ ከገሊላ ፡ ገሥምሮ ፡ በይሁዳ ፡ ኹሉ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሐዋ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ እግዚአብሔር ፡ የናዝሬቱን ፡ ኢየሱስን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኀይልም ፡ ቀባው ፥ ርሱም ፡

መልካም ፡ እያደረገ ፡ ለዲያብሎስም ፡ የተገዙትን ፡ ኹሉ ፡ እየፈወሰ ፡ ዞረ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረና ፤

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 39 ፤ እኛም ፡ በአይሁድ ፡ አገርና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባደረገው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፤ ርሱንም ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡ ገደሉት ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 40 ፤ ርሱን ፡ እግዚአብሔር ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ አስነሣው ፡ ይገለጥም ፡ ዘንድ ፡ ሰጠው ፤

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 41 ፤ ይኸውም ፡ ለሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ የተመረጡ ፡ ምስክሮች ፡ ለኾን ፡ ለእኛ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ ከሙታንም ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የበላን ፡ የጠጣንም ፡ እኛ ፡ ነን ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 42 ፤ ለሕዝብም ፡ እንድንሰብክና ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ሊፈርድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተወሰነ ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንመሰክር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘን ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 43 ፤ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ኹሉ ፡ በስሙ ፡ የኀጢአቱን ፡ ስርየት ፡ እንዲቀበል ፡ ነቢያት ፡ ኹሉ ፡ ይመሰክሩለታል ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 44 ፤ ጴጥሮስ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ገና ፡ ሲናገር ፡ ቃሉን ፡ በሰሙት ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደ ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 45 ፤ ከጴጥሮስም ፡ ጋራ ፡ የመጡት ፡ ኹሉ ፡ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ የኾኑ ፡ ምዕመናን ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስጦታ ፡ ስለ ፡ ፈሰሰ ፡ ተገረሙ ፤

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 46 ፤ በልሳኖች ፡ ሲናገሩ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ሲያከብሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 47 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልሶ ፦ እነዚህ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተቀበሉ ፡ እንዳይጠመቁ ፡ ውሃን ፡ ይከለክላቸው ፡ ዘንድ ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧ አለ ።

ሐዋ. ፥ 10 ፥ 48 ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስምም ፡ ይጠመቁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ እንዲቀመጥ ፡ ለመኑት ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ ሐዋርያትና ፡ በይሁዳም ፡ የነበሩት ፡ ወንድሞች ፡ አሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ሰሙ ።

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ የኾኑት ፡ ሰዎች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተከራክረው ።

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ ወዳልተገረዙ ፡ ሰዎች ፡ ገብተኽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በላኽ ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ከመጠመሪያው ፡ ዠምሮ ፡ በተራ ፡ ገለጠላቸው ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ እኔ ፡ በኢዮጴ ፡ ከተማ ፡ ስጸልይ ፡ ሳለኹ ፡ ተመስጬ ፡ ራእይን ፡ አየኹ ፤ ታላቅ ፡ ሸማ ፡ የመሰለ ፡ ዕቃ ፡ ባራት ፡ ማእዘን ፡ ተይዞ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደና ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጣ ፤

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ ይህንም ፡ ትኵር ፡ ብዬ ፡ ስመለከት ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያላቸውን ፡ የምድር ፡ እንስሳዎች ፡ አራዊትንም ፡ ተንቀሳቃሾችንም ፡ የሰማይ ፡ ወፎችንም ፡ አየኹ ።

ሐዋ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፥ ተነሣና ፡ ዐርደኽ ፡ ብላ ፡ የሚለኝንም ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አይኾንም ፤ ርኩስ ፡ ወይም ፡ የሚያስጸይፍ ፡ ከቶ ፡ ወደ ፡ አፌ ፡ ገብቶ ፡ አያውቅምና ፡ አልኹ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ኹለተኛም ፦ እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ መለሰልኝ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ይህም ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተሳበ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ እንሆም ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ሰዎች ፡ ከቂሳርያ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ ተልከው ፡ ወዳለኹበት ፡ ቤት ፡ ቀረቡ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ መንፈስም ፡ ሳልጠራጠር ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እኼድ ፡ ዘንድ ፡ ነገረኝ ። እነዚህም ፡ ስድስቱ ፡ ወንድሞች ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ መጡ ፡ ወደዚያ ፡ ሰውም ፡ ቤት ፡ ገባን ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ መልአክ ፡ በቤቱ ፡ ቆሞ ፡ እንዳየና ፦ ወደኢዮጴ ፡ ሰዎች ፡ ልከኽ ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለውን ፡ ስምዖንን ፡ አስመጣ ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ርሱም ፡ አንተና ፡ የቤትኽ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ የምትድኑበትን ፡ ነገር ፡ ይነግርኻል ፡ እንዳለው ፡ ነገረን ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ለመናገርም ፡ በዠመርኹ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለእኛ ፡ ደግሞ ፡ በመዠመሪያ ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ ለእነርሱ ፡ ወረደላቸው ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ ዮሐንስ ፡ በውሃ ፡ አጠመቀ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠመቃላችኹ ፡ ያለውም ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ ትዝ ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ላመነው ፡ ለእኛ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ያን ፡ ስጦታ ፡ ለእነርሱ ፡ ከሰጠ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ለመከልከል ፡ እችል ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነበርኹ ፧

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜም ፡ ዝም ፡ አሉና ፦ እንኪያስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ ለሕይወት ፡ የሚኾን ፡ ንስሓን ፡ ሰጣቸው ፡ እያሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አከበሩ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ በእስጢፋኖስም ፡ ላይ ፡ በተደረገው ፡ መከራ ፡ የተበተኑት ፡ እስከ ፡ ፊንቄ ፡ እስከ ፡ ቆጵሮስም ፡ እስከ ፡ አንጾኪያም ፡ ድረስ ፡ ዞሩ ፥ ቃሉንም ፡ ለአይሁድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ላንድ ፡ ስንኳ ፡ አይናገሩም ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ከነርሱ ፡ ግን ፡ የቆጵሮስና ፡ የቀሬና ፡ ሰዎች ፡ የነበሩት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ መጥተው ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስን ፡ ወንጌል ፡ እየሰበኩ ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ የጌታም ፡ እጅ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፤ ቍጥራቸውም ፡ እጅግ ፡ የሚኾን ፡ ሰዎች ፡ አምነው ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ዘወር ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ወሬውም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ባለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ተሰማ ፥ በርናባስንም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ላኩት ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ መጥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ አለው ፥ ኹሉንም ፡ በልባቸው ፡ ፈቃድ ፡ በጌታ ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ መከራቸው ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ደግ ፡ ሰውና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እምነትም ፡ የሞላበት ፡ ነበረና ። ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ተጨመሩ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ በርናባስም ፡ ሳውልን ፡ ሊፈልግ ፡ ወደ ፡ ጠርሴስ ፡ መጣ ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ ባገኘውም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ አመጣው ። በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተሰበሰቡ ፥ ብዙ ፡ ሕዝብንም ፡ አስተማሩ ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ መዠመሪያ ፡ በአንጾኪያ ፡ ክርስቲያን ፡ ተባሉ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ነቢያት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረዱ ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ ከነርሱም ፡ አጋቦስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሥቶ ፥ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ታላቅ ፡ ራብ ፡ ሊኾን ፡ እንዳለው ፡ በመንፈስ ፡ አመለከተ ፤ ይህም ፡ በቀላውዴዎስ ፡ ቄሳር ፡ ዘመን ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ እያንዳንዳቸው ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፡ መጠን ፡ አዋጥተው ፡ በይሁዳ ፡ ለሚኖሩት ፡ ወንድሞች ፡ ርዳታን ፡ ይልኩ ፡ ዘንድ ፡ ወሰኑ ፤

ሐዋ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ እንዲህም ፡ ደግሞ ፡ አደረጉ ፥ በበርናባስና ፡ በሳውልም ፡ እጅ ፡ ወደ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ ሰደዱት ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ንጉሡ ፡ ሄሮድስ ፡ መከራ ፡ ያጸናባቸው ፡ ዘንድ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ባንዳንዶቹ ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ጫነባቸው ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ የዮሐንስንም ፡ ወንድም ፡ ያዕቆብን ፡ በሰይፍ ፡ ገደለው ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ አይሁድንም ፡ ደስ ፡ እንዳሠኛቸው ፡ አይቶ ፡ ጨምሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ ደግሞ ፡ ያዘው ። የቂጣ ፡ በዓልም ፡ ወራት ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ በያዘውም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ አገባው ፡ ከፋሲካም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ያወጣው ፡ ዘንድ ፡ ዐስቦ ፡ እያንዳንዱ ፡ አራት ፡ ወታደሮች ፡ ኾነው ፡ እንዲጠብቁት ፡ ለአራት ፡ ጭፍራ ፡ ክፍል ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ ጴጥሮስም ፡ በወህኒ ፡ ይጠበቅ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሎት ፡ አጥብቆ ፡ ይደረግ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ሄሮድስም ፡ ሊያወጣው ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፥ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ ጴጥሮስ ፡ በኹለት ፡ ሰንሰለት ፡ ታስሮ ፡ ከኹለት ፡ ወታደሮች ፡ መካከል ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፤ ጠባቂዎችም ፡ በደጁ ፡ ፊት ፡ ኾነው ፡ ወህኒውን ፡ ይጠብቁ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ እንሆም ፥ የጌታ ፡ መልአክ ፡ ቀረበ ፡ በቤትም ፡ ውስጥ ፡ ብርሃን ፡ በራ ፤ ጴጥሮስንም ፡ ጐድኑን ፡ መቶ ፡ አነቃውና ፦ ፈጥነኽ ፡ ተነሣ ፡ አለው ። ሰንሰለቶቹም ፡ ከእጁ ፡ ወደቁ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ መልአኩም ፦ ታጠቅና ፡ ጫማኽን ፡ አግባ ፡ አለው ፥ እንዲሁም ፡ አደረገ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ልብስኽንም ፡ ልበስና ፡ ተከተለኝ ፡ አለው ። ወጥቶም ፡ ተከተለው ፤ ራእይንም ፡ የሚያይ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፡ እንጂ ፡ በመልአኩ ፡ የሚደረገው ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላወቀም ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ የመዠመሪያውንና ፡ የኹለተኛውንም ፡ ዘብ ፡ ዐልፈው ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ወደሚያወጣው ፡ ወደብረቱ ፡ መዝጊያ ፡ ደረሱ ፤ ርሱም ፡ ዐውቆ ፡ ተከፈተላቸው ፤ ወጥተውም ፡ አንዲት ፡ ስላች ፡ ዐለፉ ፡ ወዲያውም ፡ መልአኩ ፡ ከርሱ ፡ ተለየ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ተመልሶ ፦ ጌታ ፡ መልአኩን ፡ ልኮ ፡ ከሄሮድስ ፡ እጅና ፡ የአይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ ይጠብቁት ፡ ከነበረው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ አዳነኝ ፡ አኹን ፡ በእውነት ፡ ዐወቅኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ባስተዋለም ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ተከማችተው ፡ ይጸልዩበት ፡ ወደነበረው ፡ ማርቆስ ፡

ወደተባለው ፡ ወደዮሐንስ ፡ እናት ፡ ወደማርያም ፡ ቤት ፡ መጣ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ጴጥሮስም ፡ የደጁን ፡ መዝጊያ ፡ ባንኳኳ ፡ ጊዜ ፡ ሮዴ ፡ የሚሏት ፡ አንዲት ፡ ገረድ ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ ቀረበች ፤

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ የጴጥሮስ ፡ ድምፅ ፡ መኾኑንም ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ከደስታዋ ፡ የተነሣ ፡ ደጁን ፡ አልከፈተችም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሮጣ ፡ ጴጥሮስ ፡ በደጅ ፡ ፊት ፡ ቆሞ ፡ እንዳለ ፡ አወራች ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፦ አብደሻል ፡ አሏት ። ርሷ ፡ ግን ፡ እንዲሁ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታስረግጥ ፡ ነበር ። እነርሱም ፦ መልአኩ ፡ ነው ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ማንኳኳቱን ፡ አዘወተረ ፤ ከፍተውም ፡ አዩትና ፡ ተገረሙ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ግን ፡ ዝም ፡ እንዲሉ ፡ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ ጌታ ፡ ከወህኒ ፡ እንዴት ፡ እንዳወጣው ፡ ተረከላቸውና ፦ ይህን ፡ ለያዕቆብና ፡ ለወንድሞች ፡ ንገሩ ፡ አላቸው ። ወጥቶም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ኼደ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፦ ጴጥሮስን ፡ ምን ፡ አግኝቶት ፡ ይኾን ፧ ብለው ፡ በጭፍራዎች ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሁከት ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ሄሮድስም ፡ አስፈልጎ ፡ ባጣው ፡ ጊዜ ፡ ጠባቂዎችን ፡ መረመረ ፡ ይገድሏቸውም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ ከይሁዳም ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ወርዶ ፡ በዚያ ፡ ተቀመጠ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ከጢሮስና ፡ ከሲዶና ፡ ሰዎችም ፡ ጋራ ፡ ተጣልቶ ፡ ነበር ፤ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነውም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ፥ የንጉሥንም ፡ ቢትወደድ ፡ ብላስጦስን ፡ ዕሺ ፡ አሠኝተው ፡ ዕርቅ ፡ ለመኑ ፥ አገራቸው ፡ ከንጉሥ ፡ አገር ፡ ምግብ ፡ ያገኝ ፡ ነበረና ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ በተቀጠረ ፡ ቀንም ፡ ሄሮድስ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥቱን ፡ ለብሶ ፡ በዙፋን ፡ ተቀመጠ ፡ እነርሱንም ፡ ተናገራቸው ፤

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ሕዝቡም ፦ የእግዚአብሔር ፡ ድምፅ ፡ ነው ፥ የሰውም ፡ አይደለም ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ስላልሰጠ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የጌታ ፡ መልአክ ፡ መታው ፡ በትልም ፡ ተበልቶ ፡ ሞተ ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ያድግና ፡ ይበዛ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ በርናባስና ፡ ሳውልም ፡ አገልግሎታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፥ ማርቆስ ፡ የተባለውን ፡ ዮሐንስንም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይዘውት ፡ መጡ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ በአንጾኪያም ፡ ባለችው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነቢያትና ፡ መምህራን ፡ ነበሩ ፤ እነርሱም ፡ በርናባስ ፥ ኔጌር ፡ የተባለው ፡ ስምዖንም ፥ የቀሬናው ፡ ሉክዮስም ፥ የአራተኛው ፡ ክፍል ፡ ገዢ ፡ የሄሮድስም ፡ ባለሟል ፡ ምናሔ ፥ ሳውልም ፡ ነበሩ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ እነዚህም ፡ ጌታን ፡ ሲያመልኩና ፡ ሲጦሙ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። በርናባስንና ፡ ሳውልን ፡ ለጠራኋቸው ፡ ሥራ ፡ ለዩልኝ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ከጦሙ ፡ ከጸለዩም ፡ እጃቸውንም ፡ ከጫኑ ፡ በኋላ ፡ አሰናበቷቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተልከው ፡ ወደ ፡ ሴሌውቅያ ፡ ወረዱ ፤ ከዚያም ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ በስልማናም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በአይሁድ ፡ ምኵራቦች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሰበኩ ፤ አገልጋይም ፡ ዮሐንስ ፡ ነበራቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ደሴቲቱንም ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ጳፋ ፡ በዞሩ ፡ ጊዜ ፡ በርያሱስ ፡ የሚሉትን ፡ ጠንቋይና ፡ ሐሰተኛ ፡ ነቢይ ፡ የኾነውን ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ አገኙ ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ርሱም ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ ከኾነው ፡ ሰርግዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ከሚባለው ፡ አገረ ፡ ገዢ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ። ይህም ፡ በርናባስንና ፡ ሳውልን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠርቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሊሰማ ፡ ፈለገ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ጠንቋዩ ፡ ግን ፡ ኤልማስ ፥ ስሙ ፡ እንዲሁ ፡ ይተረጐማልና ፥ አገረ ፡ ገዢውን ፡ ከማመን ፡ ሊያጣምም ፡ ፈልጎ ፡ ተቃወማቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ጳውሎስ ፡ የተባለው ፡ ሳውል ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተሞልቶ ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ሲመለከተው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ አንተ ፡ ተንኰል ፡ ኹሉ ፡ ክፋትም ፡ ኹሉ ፡ የሞላብኽ ፥ የዲያብሎስ ፡ ልጅ ፥ የጽድቅም ፡ ኹሉ ፡ ጠላት ፥ የቀናውን ፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ ከማጣመም ፡ አታርፍምን ፧

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ የጌታ ፡ እጅ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ናት ፥ ዕውርም ፡ ትኾናለኽ ፡ እስከ ፡ ጊዜውም ፡ ፀሓይን ፡ አታይም ፡ አለው ። ያን ፡ ጊዜም ፡ ጭጋግና ፡ ጨለማ ፡ ወደቀበት ፥ በእጁም ፡ የሚመራውን ፡ እየዞረ ፡ ፈለገ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ የተደረገውን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ከጌታ ፡ ትምህርት ፡ የተነሣ ፡ ተገርሞ ፡ አመነ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ ጳውሎስም ፡ ከጓደኞቹ ፡ ጋራ ፡ ከጳፋ ፡ ተነሥቶ ፥ የጵንፍልያ ፡ ወደምትኾን ፥ ወደ ፡ ጴርጌን ፡ መጣ ፤ ዮሐንስም ፡ ከነርሱ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተመለሰ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ ከጴርጌን ፡ ዐልፈው ፥ የጲስድያ ፡ ወደምትኾን ፥ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ደረሱ ፤ በሰንበትም ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡ ገብተው ፡ ተቀመጡ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ ሕግና ፡ ነቢያትም ፡ ከተነበቡ ፡ በኋላ ፥ የምኵራቡ ፡ አለቃዎች ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ሕዝብን ፡ የሚመክር ፡ ቃል ፡ እንዳላችኹ ፡ ተናገሩ ፡ ብለው ፡ ላኩባቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ጳውሎስም ፡ ተነሣና ፥ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የእስራኤል ፡ ሰዎችና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩት ፡ ሆይ ፥ ስሙ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ የዚህ ፡ የእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ አምላክ ፡ አባቶቻችንን ፡ መርጦ ፥ በግብጽ ፡ አገር ፡ በእንግድነት ፡ ሳሉ ፥ ሕዝቡን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው ፥ ከፍ ፡ ባለችውም ፡ ክንዱ ፡ ከዚያ ፡ አወጣቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ በበረሓም ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ መገባቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ በከነዓንም ፡ አገር ፡ ሰባት ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍቶ ፥ ምድራቸውን ፡ አወረሳቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፥ እስከ ፡ ነቢዩ ፡ እስከ ፡ ሳሙኤል ፡ ድረስ ፥ አራት ፡ መቶ ፡ ዐምሳ ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ መሳፍንትን ፡ ሰጣቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ንጉሥን ፡ ያነግሥላቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኑ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከብንያም ፡

ወገን ፡ የሚኾን ፡ ሰው ፡ የቂስን ፡ ልጅ ፡ ሳኦልን ፡ አርባ ፡ ዓመት ፡ ሰጣቸው ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ርሱንም ፡ ከሻረው ፡ በኋላ ፥ ዳዊትን ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ እንዲነግሥ ፡ አስነሣው ፥ ሲመሰክርለትም ፦ እንደ ፡ ልቤ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፥ ፈቃዴንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያደርግ ፥ የእሴይን ፡ ልጅ ፡ ዳዊትን ፡ አገኘኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ከዚህም ፡ ሰው ፡ ዘር ፡ እግዚአብሔር ፥ እንደ ፡ ተስፋው ፡ ቃል ፥ ለእስራኤል ፡ መድኀኒትን ፥ ርሱም ፡ ኢየሱስን ፡ አመጣ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ከመምጣቱ ፡ በፊት ፥ ዮሐንስ ፡ አስቀድሞ ፡ ለእስራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ የንስሐን ፡ ጥምቀት ፡ ሰብኮ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ዮሐንስም ፡ ሩጫውን ፡ ሲፈጽም ፡ ሳለ ፦ እኔ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ታስባላችኹ ፧ እኔስ ፡ ርሱን ፡ አይደለኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ የእግሩን ፡ ጫማ ፡ እፈታ ፡ ዘንድ ፡ ከማይገ፡ባኝ ፡ ከእኔ ፡ በኋላ ፡ ይመጣል ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 26 ፤ እናንተ ፡ ወንድሞቻችን ፥ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ ልጆች ፡ ከእናንተ ፡ መካከልም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትፈሩ ፡ ሆይ ፥ ለእናንተ ፡ የዚህ ፡ የመዳን ፡ ቃል ፡ ተላከ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 27 ፤ በኢየሩሳሌም ፡ የሚኖሩ ፡ ሰዎችና ፡ አለቃዎቻቸው ፡ ርሱንና ፡ በየሰንበቱ ፡ የሚነበቡትን ፡ የነቢያትን ፡ ድምፆች ፡ ስላላወቁ ፡ በፍርዳቸው ፡ ፈጽመዋልና ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 28 ፤ ለሞትም ፡ የሚያደርስ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ባያገኙበት ፥ ይገድለው ፡ ዘንድ ፡ ጲላጦስን ፡ ለመኑት ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 29 ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ የተጻፈውን ፡ ኹሉ ፡ በፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ ከዕንጨት ፡ አውርደው ፡ በመቃብር ፡ አኖሩት ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 30 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ አስነሣው ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 31 ፤ በሕዝብም ፡ ዘንድ ፡ ምስክሮቹ ፡ ለኾኑት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከገሊላ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ለወጡት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ታያቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 32 ፤ እኛም ፡ ለአባቶች ፡ የተሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ የምሥራቹን ፡ ለእናንተ ፡ እንሰብካለን ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 33 ፤ ይህን ፡ ተስፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኹለተኛው ፡ መዝሙር ፡ ደግሞ ፦ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነኽ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወለድኹኽ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ኢየሱስን ፡ አስነሥቶ ፡ ለእኛ ፡ ለልጆቻቸው ፡ ፈጽሟልና ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 34 ፤ እንደገናም ፡ ወደ ፡ መበስበስ ፡ እንዳይመለስ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ አስነሣው ፥ እንዲህ ፦ የታመነውን ፡ የዳዊትን ፡ ቅዱስ ፡ ተስፋ ፡ እሰጣችኋለኹ ፡ ብሏል ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 35 ፤ ደግሞ ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፦ ቅዱስኽን ፡ መበስበስን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ አትሰጠውም ፡ ይላልና ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 36 ፤ ዳዊትም ፡ በራሱ ፡ ዘመን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዐሳብ ፡ ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ አንቀላፋ ፥ ከአባቶቹም ፡ ጋራ ፡ ተጨምሮ ፡ መበስበስን ፡ አየ ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 37 ፤ ይህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያስነሣው ፡ ግን ፡ መበስበስን ፡ አላየም ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 38-39 ፤ እንግዲህ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በርሱ ፡ በኩል ፡ የኀጢአት ፡ ስርየት ፡ እንዲነገርላችኹ ፥ በሙሴም ፡ ሕግ ፡ ትጸድቁበት ፡ ዘንድ ፡ ከማይቻላችኹ ፡ ኹሉ ፡ ያመነ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ እንዲጸድቅ ፡

በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኹን ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 40 - 41 ፤ እንግዲህ ፦ እናንተ ፡ የምትንቁ ፥ እዩ ፡ ተደነቁም ፡ ጥፉም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ቢተርክላችኹ ፡ የማታምኑትን ፡ ሥራ ፡ በዘመናችኹ ፡ እኔ ፡ እሠራለኹና ፡ ተብሎ ፡ በነቢያት ፡ የተነገረው ፡ እንዳይደርስባችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 42 ፤ በወጡም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሚመጣው ፡ ሰንበት ፡ ይነግሯቸው ፡ ዘንድ ፡ ለመኗቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 43 ፤ ጉባኤውም ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፡ ከአይሁድና ፡ ወደ ፡ ይሁዲነት ፡ ገብተው ፡ ከሚያመልኩ ፡ ብዙዎች ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ተከተሏቸው ፥ እነርሱም ፡ ሲነግሯቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ አስረዷቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 44 ፤ በኹለተኛውም ፡ ሰንበት ፡ ከጥቂቶቹ ፡ በቀር ፡ የከተማው ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ተሰበሰቡ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 45 ፤ አይሁድም ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ቅንአት ፡ ሞላባቸው ፥ እየተሳደቡም ፡ ጳውሎስ ፡ የተናገረውን ፡ ቃል ፡ ተቃወሙ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 46 ፤ ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ገልጠው ፦ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አስቀድሞ ፡ ለእናንተ ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልጋል ፤ ከገፋችኹትና ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳይገባችኹ ፡ በራሳችኹ ፡ ከፈረዳችኹ ፡ ግን ፥ እንሆ ፥ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ዘወር ፡ እንላለን ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 47 ፤ እንዲሁ ፡ ጌታ ፦ እስከምድር ፡ ዳርቻ ፡ ድረስ ፡ ለማዳን ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃን ፡ አድርጌኻለኹ ፡ ብሎ ፡ አዞናልና ፥ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 48 ፤ አሕዛብም ፡ ሰምተው ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ አከበሩ ፥ ለዘለዓለም ፡ ሕይወትም ፡ የተዘጋጁ ፡ ኹሉ ፡ አመኑ ፤

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 49 ፤ የጌታም ፡ ቃል ፡ ባገሩ ፡ ኹሉ ፡ ተስፋፋ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 50 ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ የሚያመልኩትን ፡ የከበሩትንም ፡ ሴቶችና ፡ የከተማውን ፡ መኳንንት ፡ አወኩ ፥ በጳውሎስና ፡ በበርናባስም ፡ ላይ ፡ ስደትን ፡ አስነሥተው ፡ ከአገራቸው ፡ አወጧቸው ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 51 ፤ እነርሱ ፡ ግን ፡ የእግራቸውን ፡ ትቢያ ፡ አራግፈውባቸው ፡ ወደ ፡ ኢቆንዮን ፡ መጡ ።

ሐዋ. ፡ 13 ፡ 52 ፤ በደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ደስታና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሞላባቸው ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ በኢቆንዮንም ፡ እንደ ፡ ቀድሞ ፡ ወደአይሁድ ፡ ምኩራብ ፡ ገብተው ፡ ከአይሁድና ፡ ከግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ እስኪያምኑ ፡ ድረስ ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ ያላመኑት ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ የአሕዛብን ፡ ልብ ፡ በወንድሞች ፡ ላይ ፡ አነሣሡ ፡ አስከፉም ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ በእጃቸው ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ እየሰጠ ፡ ለጸጋው ፡ ቃል ፡ ስለመሰከረው ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ገልጠው ፡ እየተናገሩ ፡ ረዥም ፡ ወራት ፡ ተቀመጡ ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ የከተማውም ፡ ሕዝብ ፡ ተከፍለው ፡ እኩሌታዎቹ ፡ ከአይሁድ ፡ እኩሌታዎቹም ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ ኾኑ ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ አሕዛብና ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከአለቃዎቻቸው ፡ ጋራ ፡ ሊያንገላቷቸውና ፡ ሊወግሯቸው ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፥

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ዐውቀው ፡ ልስጥራንና ፡ ደርቤን ፡ ወደሚባሉት ፡ ወደሊቃኦንያ ፡ ከተማዎች ፡ በእነርሱም ፡ ዙሪያ ፡ ወዳለው ፡ አገር ፡ ሸሹ ፤

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብኩ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ በልስጥራንም ፡ እግሩ ፡ የሰለለ ፥ ከእናቱም ፡ ማሕፀን ፡ ዝምሮ ፡ ዐንካሳ ፡ የኾነ ፥ ከቶም ፡ ኼዶ ፡ የማያውቅ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተቀምጦ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ይህም ፡ ሰው ፡ ጳውሎስ ፡ ሲናገር ፡ ይሰማ ፡ ነበር ፤ ርሱም ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመለከተውና ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ እምነት ፡ እንዳለው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ ቀጥ ፡ ብለኽ ፡ በእግርኽ ፡ ቁም ፡ አለው ። ብድግ ፡ ብሎም ፡ ተነሥቶ ፡ ይመላለስ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ ሕዝቡም ፡ ጳውሎስ ፡ ያደረገውን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ድምፃቸውን ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ በሊቃኦንያ ፡ ቋንቋ ፦ አማልክት ፡ ሰዎችን ፡ መስለው ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ወርደዋል ፡ አሉ ፤

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ በርናባስንም ፡ ድያ ፡ አሉት ፤ ጳውሎስንም ፡ ርሱ ፡ በመናገር ፡ ዋና ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሄርሜን ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ በከተማውም ፡ ፊት ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ያለው ፡ የድያ ፡ ካህን ፡ ኰርማዎችንና ፡ የአበባን ፡ አክሊሎች ፡ ወደ ፡ ደጃፍ ፡ አምጥቶ ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ ሊሠዋላቸው ፡ ወደደ ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ ሐዋርያት ፡ በርናባስና ፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልብሳቸውን ፡ ቀደው ፡ ወደሕዝቡ ፡ መካከል ፡ እየጮኹ ፡ ሮጡ ፥

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ እንዲህም ፡ አሉ ፦ እናንተ ፡ ሰዎች ፥ ይህን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ታደርጋላችኹ ፧ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ የምንሰማ ፡ ሰዎች ፡ ነን ፥ ከዚህም ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፡ በእነርሱም ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ፈጠረ ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ፡ ወንጌልን ፡ እንሰብካለን ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ባለፉት ፡ ትውልዶች ፡ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ በገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ጐዳና ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ተዋቸው ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ እየሠራ ፥ ከሰማይ ፡ ዝናብን ፡ ፍሬ ፡ የሚኾንበትንም ፡ ወራት ፡ ሲሰጠን ፥ ልባችንንም ፡ በመብልና ፡ በደስታ ፡ ሲሞላው ፡ ራሱን ፡ ያለምስክር ፡ አልተወም ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ ይህንም ፡ ብለው ፡ እንዳይሠዉላቸው ፡ ሕዝቡን ፡ በጭንቅ ፡ አስተዉአቸው ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ከአንጾኪያና ፡ ከኢቆንዮን ፡ መጡ ፤ ሕዝቡንም ፡ አባብለው ፡ ጳውሎስን ፡ ወገሩ ፡ የሞተም ፡ መስሏቸው ፡ ከከተማ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ ጐተቱት ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ ከዕውት ፡ ሳሉ ፥ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ገባ ። በነገውም ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ደርቤን ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፡ 14 ፡ 21-22 ፤ በዚያችም ፡ ከተማ ፡ ወንጌልን ፡ ሰብከው ፡ እጅግ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፥ የደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ልብ ፡ እያጸኑ ፥ በሃይማኖትም ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፡ እየመከሩና ፦ ወደእግዚአብሔር ፡

መንግሥት ፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልገናል ፡ እያሉ ፥ ወደ ፡ ልስጥራን ፡ ወደ ፡ ኢቆንዮንም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያም ፡ ተመለሱ ።

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 23 ፤ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሽማግሌዎችን ፡ ከሾሙላቸው ፡ በኋላ ፡ ጦመውም ፡ ከጸለዩ ፡ በኋላ ፥ ላመኑበት ፡ ለጌታ ፡ ዐደራ ፡ ሰጧቸው ።

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 24 ፤ በጲስድያም ፡ ዐልፈው ፡ ወደ ፡ ጵንፍልያ ፡ መጡ ፥

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 25 ፤ በጴርጌንም ፡ ቃሉን ፡ ከተናገሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አጣልያ ፡ ወረዱ ፥

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 26 ፤ ከዚያም ፡ ስለፈጸሙት ፡ ሥራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ዐደራ ፡ ወደተሰጡበት ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ በመርከብ ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 27 ፤ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ሰብስበው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ሹሉ ፡ ለአሕዛብም ፡ የሃይማኖትን ፡ ደጅ ፡ እንደ ፡ ከፈተላቸው ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፥ 14 ፥ 28 ፤ ከደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ጋራ ፡ ዐያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 1 ፤ አንዳንዶችም ፡ ከይሁዳ ፡ ወረዱና ፦ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሥርዐት ፡ ካልተገረዛችኹ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ አትችሉም ፡ ብለው ፡ ወንድሞችን ፡ ያስተምሩ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 2 ፤ በእነርሱና ፡ በጳውሎስ ፡ በበርናባስም ፡ መካከል ፡ ብዙ ፡ ጥልና ፡ ክርክር ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፥ ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ ጳውሎና ፡ በርናባስ ፡ ከነርሱም ፡ አንዳንዶች ፡ ሌላዎች ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ተቈረጠ ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 3 ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ በመንገድ ፡ እየረዳቸው ፡ እነርሱ ፡ የአሕዛብን ፡ መመለስ ፡ እየተረኩ ፡ በፊንቄና ፡ በሰማርያ ፡ ዐለፉ ፥ ወንድሞችንም ፡ ሹሉ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኟቸው ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 4 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ሐዋርያት ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ተቀበሏቸው ፥ እግዚአብሔርም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ያደረገውን ፡ ሹሉ ፡ አወሩ ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 5 ፤ ከፈሪሳውያን ፡ ወገን ፡ ግን ፡ ያመኑት ፡ አንዳንዶቹ ፡ ተነሥተው ፦ ትገርዟቸው ፡ ዘንድና ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ታዟቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 6 ፤ ሐዋርያትና ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ለመማከር ፡ ተሰበሰቡ ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 7 ፤ ከብዙ ፡ ክርክርም ፡ በኋላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ተነሥቶ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ አሕዛብ ፡ ከአፌ ፡ የወንጌልን ፡ ቃል ፡ ሰምተው ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመዐመሪያው ፡ ዘመን ፡ ከእናንተ ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ መረጠኝ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 8 ፤ ልብንም ፡ የሚያውቅ ፡ አምላክ ፡ ለእኛ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በመስጠት ፡ መሰከረላቸው ፤

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 9 ፤ ልባቸውንም ፡ በእምነት ፡ ሲያነጻ ፡ በእኛና ፡ በእነርሱ ፡ መካከል ፡ አንዳች ፡ አልለየም ።

ሐዋ. ፥ 15 ፥ 10 ፤ እንግዲህ ፡ አባቶቻችንና ፡ እኛ ፡ ልንሸከመው ፡ ያልቻልነውን ፡ ቀንበር ፡ በደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጫንቃ ፡ ላይ ፡ በመጫን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አኹን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈታተናላችኹ ፧

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ እንድን ፡ ዘንድ ፡ እናምናለን ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ዝም ፡ አሉ ፥ በርናባስና ፡ ጳውሎስም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእጃቸው ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያደረገውን ፡ ምልክትና ፡ ድንቅ ፡ ኹሉ ፡ ሲተርኩላቸው ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ እነርሱም ፡ ዝም ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ ያዕቆብ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስሙኝ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለስሙ ፡ የሚኾንን ፡ ወገን ፡ ከአሕዛብ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ጐበኘ ፡ ስምዖን ፡ ተርኳል ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 15 ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የነቢያት ፡ ቃል ፡ ይሰማማል ፥ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 16-17 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የቀሩት ፡ ሰዎችና ፡ በስሜ ፡ የተጠሩት ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ጌታን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ እመለሳለኹ ፥ የወደቀችውንም ፡ የዳዊትን ፡ ድንኳን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እሠራታለኹ ፥ ፍራሿንም ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እሠራታለኹ ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ አቆማታለኹ ፡ ይላል ፡ ይህን ፡ የሚያደርግ ፡ ጌታ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 18 ፤ ከጥንት ፡ ዠምሮ ፡ ሥራው ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ከአሕዛብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የዞሩትን ፡ እንዳናስቸግራቸው ፥

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከጣዖት ፡ ርኵሰትና ፡ ከዝሙት ፡ ከታነቀም ፡ ከደምም ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ እንድንጽፍላቸው ፡ እቈርጣለኹ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ሙሴስ ፡ ከቀደሙት ፡ ትውልድ ፡ ዠምሮ ፡ በሰንበት ፡ በሰንበት ፡ በምኵራቦቹ ፡ ሲያነቡ ፡ በየከተማው ፡ ርሱን ፡ የሚሰብኩ ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ሐዋርያትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከነርሱ ፡ የተመረጡትን ፡ ሰዎች ፡ ከጳውሎስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ይልኩ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀዱ ፤ እነርሱም ፡ በወንድሞች ፡ መካከል ፡ ዋናዎች ፡ ኾነው ፡ በርስያን ፡ የተባለው ፡ ይሁዳና ፡ ሲላስ ፡ ነበሩ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ እንዲህም ፡ ጽፈው ፡ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ላኩ ፦ ሐዋርያትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወንድሞችም ፡ በአንጾኪያና ፡ በሶርያ ፡ በኪልቅያም ፡ ለሚኖሩ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ለኾኑ ፡ ወንድሞች ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርባሉ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ያላዘዝናቸው ፡ ሰዎች ፡ ከእኛ ፡ ወጥተው ፦ ትገረዙ ፡ ዘንድና ፡ ሕግን ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገሥጿኋል ፥ ብለው ፡ ልባችኹን ፡ እያወኩ ፡ በቃል ፡ እንዳናወጧችኹ ፡ ስለ ፡ ሰማን ፥

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 25-26 ፤ ስለ ፡ ጌታችን ፡ ስለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ነፍሳቸውን ፡ ከሰጡት ፡ ከምንወዳቸው ፡ ከበርናባስና ፡ ከጳውሎስ ፡ ጋራ ፡ የተመረጡትን ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንልክ ፡ ዘንድ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነን ፡ ፈቀድን ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ራሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ በቃላቸው ፡ ያንኑ ፡ ይነግሯችኹ ፡ ዘንድ ፡ ይሁዳንና ፡ ሲላስን ፡ ልከናል ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 28-29 ፤ ለጣዖት ፡ ከተሠዋ ፥ ከደምም ፥ ከታነቀም ፥ ከዝሙትም ፡ ትርቁ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ከሚያስፈልገው ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ሸክም ፡ እንዳንጭንባችኹ ፡ እኛና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቅደናልና ፤ ከዚህም ፡ ኹሉ ፡ ራሳችኹን ፡ ብትጠብቁ ፡ በመልካም ፡ ትኖራላችኹ ። ጤና ፡ ይስጣችኹ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ እነርሱም ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረዱ ፥ ሕዝቡንም ፡ ሰብስበው ፡ ደብዳቤውን ፡ ሰጧቸው ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 31 ፤ ባነበቡትም ፡ ጊዜ ፡ ከምክሩ ፡ የተነሣ ፡ ደስ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 32 ፤ ይሁዳና ፡ ሲላስም ፡ ደግሞ ፡ ነቢያት ፡ ነበሩና ፥ ወንድሞችን ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡ መክረው ፡ አጸኗቸው ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ ዐያሌ ፡ ቀንም ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ከወንድሞች ፡ በሰላም ፡ ተሰናብተው ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 34 ፤ ሲላስ ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 35 ፤ ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ ከሌላዎች ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ እያስተማሩና ፡ ወንጌልን ፡ እየሰበኩ ፡ በአንጾኪያ ፡ ይቀመጡ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 36 ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ በርናባስን ፦ ተመልሰን ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ በተናገርንበት ፡ በየከተማው ፡ ዅሉ ፡ ወንድሞችን ፡ እንጐብኛቸው ፥ እንዴት ፡ እንዳሉም ፡ እንወቅ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 37 ፤ በርናባስም ፡ ማርቆስ ፡ የተባለውን ፡ ዮሐንስን ፡ ደግሞ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ዐሰበ ፤

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 38 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሊወስድ ፡ አልፈቀደም ፥ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከጵንፍልያ ፡ ተለይቶ ፡ ነበርና ፥ ወደ ፡ ሥራም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ አልመጣም ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 39 ፤ ስለዚህም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እስኪለያዩ ፡ ድረስ ፡ መከፋፋት ፡ ኾነ ፥ በርናባስም ፡ ማርቆስን ፡ ይዞ ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ኼደ ።

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 40 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲላስን ፡ መረጠ ፥ ወንድሞችም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ዐደራ ፡ ከሰጡት ፡ በኋላ ፡ ወጣ ፤

ሐዋ. ፡ 15 ፡ 41 ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ እያጸና ፡ በሶርያና ፡ በኪልቅያ ፡ ይዞር ፡ ነበር ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ደርቤንና ፡ ወደ ፡ ልስጥራንም ፡ ደረሰ ። እንሆም ፥ በዚያ ፡ የአንዲት ፡ ያመነች ፡ አይሁዳዊት ፡ ልጅ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፤ አባቱ ፡ ግን ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ለርሱም ፡ በልስጥራንና ፡ በኢቆንዮን ፡ ያሉ ፡ ወንድሞች ፡ መሰከሩለት ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ጳውሎስ ፡ ይህ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፥ በእነዚያም ፡ ስፍራዎች ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አይሁድ ፡ ይዞ ፡ ገረዘው ፤ አባቱ ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዅሉ ፡ ያውቁ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ በከተማዎችም ፡ ሲዞሩ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የነበሩት ፡ ሐዋርያትና ፡ ሽማግሌዎች ፡ የቈረጡትን ፡ ሥርዐት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ሰጧቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ በሃያማኖት ፡ ይበረቱ ፡ ነበር ፥ በቍጥርም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይበዙ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ በእስያም ፡ ቃሉን ፡ እንዳይናገሩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ ከለከላቸው ፡ በፍርግያና ፡ በገላትያ ፡ አገር ፡ ዐለፉ ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ በሚስያም ፡ አንጻር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቢታንያ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንን ፡ ሞከሩ ፥ የኢየሱስ ፡ መንፈስም ፡ አልፈቀደላቸውም ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ በሚስያም ፡ አጠገብ ፡ ዐልፈው ፡ ወደ ፡ ጢሮዳ ፡ ወረዱ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ራእይም ፡ ለጳውሎስ ፡ በሌሊት ፡ ታየው ፤ አንድ ፡ የመቄዶንያ ፡ ሰው ፦ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ተሻገርና ፡ ርዳን ፡ እያለ ፡ ቆሞ ፡ ሲለምነው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ ራእዩንም ፡ ካየ ፡ በኋላ ፡ ወዲያው ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ልንወጣ ፡ ፈለግን ፥ ወንጌልን ፡ እንሰብክላቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጠራን ፡ መስሎናልና ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ከጢሮዳም ፡ ተነሥተን ፡ በቀጥታ ፡ ወደ ፡ ሳሞትራቄ ፡ በነገውም ፡ ወደ ፡ ናጺሌ ፡ በመርከብ ፡ ኼድን ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ደረስን ፤ ርሷም ፡ የመቄዶንያ ፡ ከተማ ፡ ኾና ፡ የወረዳ ፡ ዋና ፡ ከተማና ፡ ቅኝ ፡ አገር ፡ ናት ፤ በዚችም ፡ ከተማ ፡ አንዳንድ ፡ ቀን ፡ እንቀመጥ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ በሰንበት ፡ ቀንም ፡ ከከተማው ፡ በር ፡ ውጭ ፡ የጸሎት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ መኾኑን ፡ ስላሰብን ፡ ወደወንዝ ፡ አጠገብ ፡ ወጣን ፤ ተቀምጠንም ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሴቶች ፡ ተናገርን ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ከትያጥሮን ፡ ከተማም ፡ የመጣች ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ ሽያጭ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምታመልክ ፡ ልድያ ፡ የሚሏት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ትሰማ ፡ ነበር ፤ ጳውሎስም ፡ የሚናገረውን ፡ ታዳምጥ ፡ ዘንድ ፡ ጌታ ፡ ልቧን ፡ ከፈተላት ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ርሷም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቿ ፡ ጋራ ፡ ከተጠመቀች ፡ በኋላ ፦ በጌታ ፡ የማምን ፡ እንድኾን ፡ ከፈረዳችኹልኝ ፥ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ገብታችኹ ፡ ኑሩ ፡ ብላ ፡ ለመነችን ፤ በግድም ፡ አለችን ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ ወደጸሎት ፡ ስፍራም ፡ ስንኼድ ፥ የሚርተኝነት ፡ መንፈስ ፡ የነበረባት ፡ ለጌታዎቿም ፡ እየጠነቈለች ፡ ብዙ ፡ ትርፍ ፡ ታመጣ ፡ የነበረች ፡ አንዲት ፡ ገረድ ፡ አገኘችን ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ርሷ ፡ ጳውሎስንና ፡ እኛን ፡ እየተከተለች ። የመዳንን ፡ መንገድ ፡ የሚነግሯችኹ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ባሪያዎች ፡ ናቸው ፡ ብላ ፡ ትጮኽ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ ይህንም ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ አደረገች ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ተቸገረና ፡ ዘወር ፡ ብሎ ፡ መንፈሱን ፦ ከርሷ ፡ እንድትወጣ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አዝኻለኹ ፡ አለው ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ጌታዎቿም ፡ የትርፋቸው ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ገበያ ፡ በሹማምት ፡ ፊት ፡ ጐተቷቸው ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ወደ ፡ ገዢዎችም ፡ አቅርበው ፦ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ አይሁድ ፡ ኾነው ፡ ከተማችንን ፡ እጅግ ፡ ያናውጣሉ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ እኛም ፡ የሮሜ ፡ ሰዎች ፡ ኾነን ፡ እንቀበላቸውና ፡ እናደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ያልተፈቀደልንን ፡ ልማዶች ፡ ይናገራሉ ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ሕዝቡም ፡ ዐብረው ፡ ተነሡባቸው ፥ ገዢዎቹም ፡ ልብሳቸውን ፡ ገፈው ፡ በበትር ፡ ይመቷቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዙ ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ በብዙም ፡ ከደበደቧቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ወህኒ ፡ ጣሏቸው ፥ የወህኒውንም ፡ ጠባቂ ፡ ተጠንቅቆ ፡ እንዲጠብቃቸው ፡ አዘዙት ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ ርሱም ፡ የዚህን ፡ ዐይነት ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብሎ ፡ ወደ ፡ ውስጠኛው ፡ ወህኒ ፡ ጣላቸው ፥ እግራቸውንም ፡ በግንድ ፡ አጣብቆ ፡ ጠረቃቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 25 ፤ በመንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ ግን ፡ ጳውሎስና ፡ ሲላስ ፡ እየጸለዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በዜማ ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበር ፥ እስረኞቹም ፡ ያደምጧቸው ፡ ነበር ፡

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 26 ፤ ድንገትም ፡ የወህኒው ፡ መሠረት ፡ እስኪናወጥ ፡ ድረስ ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መንቀጥቀጥ ፡ ኾነ ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ደጆቹ ፡ ኹሉ ፡ ተከፈቱ ፡ የኹሉም ፡ እስራት ፡ ተፈታ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ የወህኒውም ፡ ጠባቂ ፡ ከእንቅልፉ ፡ ነቅቶ ፡ የወህኒው ፡ ደጆች ፡ ተከፍተው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፥ እስረኞቹ ፡ ያመለጡ ፡ መስሎት ፡ ራሱን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ ዐስቦ ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 28 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ ኹላችን ፡ ከዚህ ፡ አለንና ፡ በራስኽ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አታድርግ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 29 ፤ መብራትም ፡ ለምኖ ፡ ወደ ፡ ውስጥ ፡ ሮጠ ፥ እየተንቀጠቀጠም ፡ ከጳውሎስና ፡ ከሲላስ ፡ ፊት ፡ ተደፋ ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 30 ፤ ወደ ፡ ውጭም ፡ አውጥቶ ፦ ጌታዎች ፡ ሆይ ፥ እድን ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ ይገባኛል ፧ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 31 ፤ እነርሱም ፦ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡ አንተና ፡ ቤተ ፡ ሰዎችኽ ፡ ትድናላችኹ ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 32 ፤ ለርሱና ፡ በቤቱም ፡ ላሉት ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ተናገሯቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 33 ፤ በሌሊትም ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ወስዶ ፡ ቍስላቸውን ፡ ዐጠበላቸው ፥ ያን ፡ ጊዜውንም ፡ ርሱ ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ተጠመቀ ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 34 ፤ ወደ ፡ ቤቱም ፡ አውጥቶ ፡ ማእድ ፡ አቀረበላቸው ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ስላመነ ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 35 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ገዢዎቹ ፦ እነዚያን ፡ ሰዎች ፡ ፍታቸው ፡ ብለው ፡ ሎሌዎቻቸውን ፡ ላኩ ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 36 ፤ የወህኒውም ፡ ጠባቂ ፦ ትፈቱ ፡ ዘንድ ፡ ገዢዎቹ ፡ ልከዋል ፤ እንግዲህ ፡ አኹን ፡ ወጥታችኹ ፡ በሰላም ፡ ኺዱ ፡ ብሎ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ ለጳውሎስ ፡ ነገረው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 37 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፦ እኛ ፡ የሮሜ ፡ ሰዎች ፡ ስንኾን ፡ ያለፍርድ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ ደብድበው ፡ በወህኒ ፡ ጣሉን ፤ አኹንም ፡ በስውር ፡ ይጥሉናልን ፧ አይኾንም ፡ ራሳቸው ፡ ግን ፡ መጥተው ፡ ያውጡን ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 38 ፤ ሎሌዎቹም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ለገዢዎች ፡ ነገሩ ። የሮሜ ፡ ሰዎችም ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈሩ ፤

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 39 ፤ መጥተውም ፡ ማለዷቸው ፥ አውጥተውም ፡ ከከተማ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ለመኗቸው ።

ሐዋ. ፡ 16 ፡ 40 ፤ ከወህኒውም ፡ ወጥተው ፡ ወደልድያ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፥ ወንድሞችንም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አጽናኗቸውና ፡ ኼዱ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ በአንፊጶልና ፡ በአጶሎንያም ፡ ካለፉ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ተሰሎንቄ ፡ መጡ ፥ በዚያም ፡ የአይሁድ ፡ ምኩራብ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ ጳውሎስም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ገባ ፥ ሦስት ፡ ሰንበትም ፡ ያኽል ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየጠቀሰ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ ሲተረጉምም ፥ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበልና ፡ ከሙታን ፡ እንዲነሣ ፡ ይገባው ፡ ዘንድ ፡ እያስረዳ ፦ ይህ ፡ እኔ ፡ የምሰብክላችኹ ፡ ኢየሱስ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ይል ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ተረድተው ፡ ከሚያመልኩም ፡ ከግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ከከበሩትም ፡ ሴቶች ፡ ጥቂቶች ፡ ያይደሉ ፥ ከጳውሎስና ፡ ከሲላስ ፡ ጋራ ፡ ተባበሩ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ ቀንተው ፡ ከሥራ ፡ ፈቶች ፡ ክፉ ፡ ሰዎችን ፡ አመጡ ፡ ሕዝብንም ፡ ሰብስበው ፡ ከተማውን ፡ አወኩ ፥ ወደ ፡ ሕዝብም ፡ ያወጧቸው ፡ ዘንድ ፡ ፈልገው ፡ ወደኢያሶን ፡ ቤት ፡ ቀረቡ ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ባላገኟቸውም ፡ ጊዜ ፡ ኢያሶንንና ፡ ከወንድሞች ፡ አንዳንዶችን ፡ ወደ ፡ ከተማው ፡ አለቃዎች ፡ ጐትተው ፦ ዓለምን ፡ ያወኩ ፡ እነዚህ ፡ ወደዚህ ፡ ደግሞ ፡ መጥተዋል ፥ ኢያሶንም ፡ ተቀብሏቸዋል ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፦ ኢየሱስ ፡ የሚሉት ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ እያሉ ፡ የቄሳርን ፡ ትእዛዝ ፡ ይቃወማሉ ፡ ብለው ፡ ጮኹ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ሕዝቡና ፡ የከተማውም ፡ አለቃዎች ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ታወኩ ፥

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ከኢያሶንና ፡ ከሌላዎቹም ፡ ዋስ ፡ ተቀብለው ፡ ለቀቋቸው ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ወዲያውም ፡ ወንድሞች ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ ቤርያ ፡ ሰደዷቸው ፥ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ ምኩራብ ፡ ገቡ ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ እነዚህም ፡ በተሰሎንቄ ፡ ከሚኖሩት ፡ ይልቅ ፡ ልበ ፡ ሰፊዎች ፡ ነበሩና ፦ ነገሩ ፡ እንደዚሁ ፡ ይኾንን ፧ ብለው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ መጻሕፍትን ፡ እየመረመሩ ፡ ቃሉን ፡ በሙሉ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀበሉ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ስለዚህም ፡ ከነርሱ ፡ ብዙ ፥ ከግሪኮችም ፡ የከበሩት ፡ ሴቶችና ፡ ወንዶች ፡ ጥቂት ፡ ያይደሉ ፥ አመኑ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ በተሰሎንቄ ፡ ያሉት ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ በቤርያ ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰበከ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፥ ወደዚያው ፡ ደግሞ ፡ መጡና ፡ ሕዝቡን ፡ አወኩ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ወንድሞቹ ፡ ወዲያው ፡ ጳውሎስን ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ድረስ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ሰደዱት ፤ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስም ፡ በዚያው ፡ ቀሩ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ ጳውሎስን ፡ የሸኙት ፡ ግን ፡ እስከ ፡ አቴና ፡ አደረሱት ፥ እንደሚቻላቸውም ፡ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሲላስና ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብለው ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ጳውሎስም ፡ በአቴና ፡ ሲጠብቃቸው ፡ ሳለ ፥ በከተማው ፡ ጣዖት ፡ መሙላቱን ፡ እየተመለከተ ፡ መንፈሱ ፡ ተበሳጨበት ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ ስለዚህም ፡ በምኩራብ ፡ ከአይሁድና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በየቀኑም ፡ በገበያ ፡ ከሚያገኛቸው ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ከኤፊቆሮስ ፡ ወገንና ፡ ኢስጦኢኮችም ፡ ከተባሉት ፡ ፈላስፎች ፡ አንዳንዶቹ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ። አንዳንዶቹም ፦ ይህ ፡ ለፍላፊ ፡ ምን ፡ ሊናገር ፡ ይወዳል ፧ አሉ ፤ ሌላዎችም ፡ የኢየሱስንና ፡ የትንሣኤውን ፡ ወንጌል ፡ ስለ ፡ ሰበከላቸው ፦ ዐዲሶችን ፡ አማልክት ፡ የሚያወራ ፡ ይመስላል ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 19-20 ፤ ይዘውም ፦ ይህ ፡ የምትናገረው ፡ ዐዲስ ፡ ትምህርት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይቻለናልን ፧ በጐሯችን ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ታሰማናለኽና ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንፈቅዳለን ፡ ብለው ፡ አርዮስፋጎስ ፡ ወደተባለው ፡ ስፍራ ፡ ወሰዱት ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 21 ፤ የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ኹሉና ፡ በዚያ ፡ የኖሩ ፡ እንግዳዎች ፡ ዐዲስ ፡ ነገርን ፡ ከመናገርና ፡ ከመስማት ፡ በቀር ፡ በሌላ ፡ ጕዳይ ፡ አይውሉም ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 22 ፤ ጳውሎስም ፡ በአርዮስፋጎስ ፡ መካከል ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ አማልክትን ፡ እጅግ ፡ እንደምትፈሩ ፡ እመለከታለኹ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 23 ፤ የምታመልኩትን ፡ እየተመለከትኹ ፡ ሳልፍ ። ለማይታወቅ ፡ አምላክ ፡ የሚል ፡ ጽሕፈት ፡ ያለበትን ፡ መሠዊያ ፡ ደግሞ ፡ አግኝቻለኹና ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሳታውቁ ፡ የምታመልኩትን ፡ እኔ ፡ እነግራችኋለኹ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 24 ፤ ዓለሙንና ፡ በርሱ ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ ርሱ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡ ነውና ፥ እጅ ፡ በሠራው ፡ መቅደስ ፡ አይኖርም ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ ሕይወትንና ፡ እስትንፋስን ፡ ኹሉንም ፡ ለኹሉ ፡ ይሰጣልና ፥ አንዳች ፡ እንደሚጐድለው ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ አይገለገልም ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 26-27 ፤ ምናልባትም ፡ እየመረመሩ ፡ ያገኙት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ እንዲኖሩ ፡ የሰውን ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ ፈጠረ ፥ የተወሰኑትንም ፡ ዘመኖችና ፡ ለሚኖሩበት ፡ ስፍራ ፡ ዳርቻ ፡ መደበላቸው ። ቢኾንም ፡ ከያንዳንዳችን ፡ የራቀ ፡ አይደለም ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 28 ፤ ከእናንተ ፡ ከባለቅኔዎች ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፦ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ዘመዶቹ ፡ ነንና ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ተናገሩ ፥ በርሱ ፡ ሕያዋን ፡ ነንና ፡ እንንቀሳቀሳለን ፡ እንኖርማለን ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 29 ፤ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዘመዶች ፡ ከኾን ፥ አምላክ ፡ በሰው ፡ ብልኀትና ፡ ዐሳብ ፡ የተቀረጸውን ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ድንጋይ ፡ እንዲመስል ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ አይገባንም ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 30 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለማወቅን ፡ ወራት ፡ አሳልፎ ፡ አኹን ፡ በየቦታቸው ፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ያዛል ፤

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 31 ፤ ቀን ፡ ቀጥሯልና ፥ በዚያም ፡ ቀን ፡ ባዘጋጀው ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በዓለሙ ፡ ላይ ፡ በጽድቅ ፡ ሊፈርድ ፡ አለው ፤ ስለዚህም ፡ ርሱን ፡ ከሙታን ፡ በማስነሣቱ ፡ ኹሉን ፡ አረጋግጧል ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 32 ፤ የሙታንንም ፡ ትንሣኤ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እኩሌታዎቹ ፡ አፌዙበት ፥ እኩሌታዎቹ ፡ ግን ፦ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ኹለተኛ ፡ እንሰማኻለን ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 33 ፤ እንዲሁም ፡ ጳውሎስ ፡ ከመካከላቸው ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፡ 17 ፡ 34 ፤ አንዳንዶች ፡ ወንዶች ፡ ግን ፡ ተባብረው ፡ አመኑ ፤ ከነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በአርዮስፋጎስ ፡ ያለው ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈራጅ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ደማሪስ ፡ የሚሏትም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ሌላዎችም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ከአቴና ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ መጣ ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ በወገኑም ፡ የጳንጦስ ፡ ሰው ፡ የሚኾን ፡ አቂላ ፡ የሚሉትን ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ አገኘ ፤ ርሱም ፡

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ከሚስቱ ፡ ከጵርስቅላ (292) ፡ ጋራ ፡ ከኢጣልያ ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፥ አይሁድ ፡ ከሮሜ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ቀላውዴዎስ ፡ አዞ ፡ ነበርና ፤ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ቀረበ ፥

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 3 ፤ ሥራቸውም ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ ባንድ ፡ ላይ ፡ ሠሩ ፤ ሥራቸው ፡ ድንኳን ፡ መስፋት ፡ ነበረና ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 4 ፤ በየሰንበቱም ፡ ዥሉ ፡ በምኵራብ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ፥ አይሁድንና ፡ የግሪክንም ፡ ሰዎች ፡ ያስረዳ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 5 ፤ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ከመቄዶንያ ፡ በወረዱ ፡ ጊዜ ፥ ጳውሎስ ፡ ኢየሱስ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ዥነ ፡ ለአይሁድ ፡ እየመሰከረ ፡ ለቃሉ ፡ ይተጋ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተቃወሙትና ፡ በተሳደቡ ፡ ጊዜ ፥ ልብሱን ፡ እያራገፈ ። ደማችኹ ፡ በራሳችኹ ፡ ነው ፤ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እኼዳለኹ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 7 ፤ ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ኢዮስጦስ ፡ ወደሚባል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደሚያመልክ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ገባ ፡ ቤቱም ፡ በምኵራብ ፡ አጠገብ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 8 ፤ የምኵራብ ፡ አለቃ ፡ ቀርስጶስም ፡ ከቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ ዥሉ ፡ ጋራ ፡ በጌታ ፡ አመነ ፥ ከቆሮንቶስ ፡ ሰዎችም ፡ ብዙ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አምነው ፡ ተጠመቁ ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 9-10 ፤ ጌታም ፡ ሌሊት ፡ በራእይ ፡ ጳውሎስን ፦ እኔ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ ማንም ፡ ክፉ ፡ ሊያደርግብኽ ፡ የሚነሣብኽ ፡ የለምና ፡ አትፍራ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ተናገር ፡ ዝምም ፡ አትበል ፤ በዚህ ፡ ከተማ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ አሉኝና ፡ አለው ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 11 ፤ በመካከላቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እያስተማረ ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ ተቀመጠ ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 12 ፤ ጋልዮስም (293) ፡ በአካይያ (294) ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፥ አይሁድ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ዥነው ፡ በጳውሎስ ፡ ላይ ፡ ተነሡ ፥ ወደፍርድ ፡ ወንበርም ፡ አምጥተው ፦

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 13 ፤ ይህ ፡ ሕግን ፡ ተቃውሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመልኩት ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችን ፡ ያባብላል ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 14 ፤ ጳውሎስም ፡ አፉን ፡ ሊከፍት ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፥ ጋልዮስ ፡ አይሁድን ፦ አይሁድ ፡ ሆይ ፥ ዐመፅ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ በደል ፡ በዥነ ፡ እንድታገሣችኹ ፡ በተገባኝ ፤

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 15 ፤ ስለ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ ስሞች ፡ ስለ ፡ ሕጋችኹም ፡ የምትከራከሩ ፡ ከዥነ ፡ ግን ፥ ራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ፡ እኔ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ፈራጅ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ አልፈቅድምና ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 16 ፤ ከፍርድ ፡ ወንበርም ፡ ፊት ፡ አስወጣቸው ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 17 ፤ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ዥሉ ፡ የምኵራብ ፡ አለቃ ፡ ሶስቴንስን ፡ ይዘው ፡ በወንበሩ ፡ ፊት ፡ መቱት ፤ በእነዚህም ፡ ነገሮች ፡ ጋልዮስ ፡ ግድ ፡ የለውም ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 18 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ ተቀምጦ ፡ ወንድሞቹንም ፡ ተሰናብቶ ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ኼደ ፤ ስለትም ፡ ነበረበትና ፡ ራሱን ፡ በክንክራኦስ ፡ ተላጨ ፤ ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ።

ሐዋ. ፥ 18 ፥ 19 ፤ ወደ ፡ ኤፌሶንም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ እነዚያን ፡ ከዚያ ፡ ተዋቸው ፥ ራሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምኵራብ ፡

292 ጵር. ፥ ፕሪሲላ ።
293 ጵር. ፥ ጋሊዮን ።
294 ጵር. ፥ አኻይያ ፡ (የግሪክ ፡ አገር) ።

ገብቶ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ እነርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲቀመጥላቸው ፡ ሲለምኑት ፡ ዕሺ ፡ አላለም ፤

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሲሰናበታቸው ፦ የሚመጣውን ፡ በዓል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢፈቅድ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እመለሳለኹ ፡ አላቸው ። ከኤፌሶንም ፡ በመርከብ ፡ ተነሣ ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ ወደ ፡ ቂሳርያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቶ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰላምታ ፡ ከሰጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ወረደ ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ ጥቂት ፡ ቀንም ፡ ቈይቶ ፡ ወጣ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ ኹሉ ፡ እያጸና ፡ በገላትያ ፡ አገርና ፡ በፍርግያ ፡ በተራ ፡ ዐለፈ ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ በወገኑም ፡ የእስክንድርያ ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ነገር ፡ ዐዋቂ ፡ የነበረ ፡ አጵሎስ ([295]) ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ወረደ ፤ ርሱም ፡ በመጻሕፍት ፡ ዕውቀት ፡ የበረታ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 25 ፤ ርሱ ፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ የተማረ ፡ ነበረ ፥ የዮሐንስንም ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡ ዐውቆ ፡ በመንፈስ ፡ ሲቃጠል ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ይናገርና ፡ በትክክል ፡ ያስተምር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 26 ፤ ርሱም ፡ በምኩራብ ፡ ገልጦ ፡ ይናገር ፡ ዠመር ። ጵርስቅላና ፡ አቂላም ፡ በሰሙት ፡ ጊዜ ፥ ወስደው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ በትክክል ፡ ገለጡለት ።

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ አካይያ ፡ ማለፍ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፥ ወንድሞቹ ፡ አጸናኑት ፥ ይቀበሉትም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጻፉለት ፤ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ አምነው ፡ የነበሩትን ፡ በጸጋ ፡ እጅግ ፡ ይጠቅማቸው ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 18 ፡ 28 ፤ ኢየሱስ ፡ ርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከመጻሕፍት ፡ እየገለጠ ፡ ለአይሁድ ፡ በኹሉ ፡ ፊት ፡ በጽኑ ፡ ያስረዳቸው ፡ ነበርና ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 1 ፤ አጵሎስም ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሳለ ፡ ጳውሎስ ፡ በላይኛው ፡ አገር ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ መጣ ፥

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 2 ፤ አንዳንድ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ አገኘ ። ባመናችኹ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበላችኹን ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ አልተቀበልንም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዳለ ፡ ስንኳ ፡ አልሰማንም ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ እንኪያ ፡ በምን ፡ ተጠመቃችኹ ፧ አላቸው ። እነርሱም ፦ በዮሐንስ ፡ ጥምቀት ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ጳውሎስም ፦ ዮሐንስስ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ በሚመጣው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝብ ፡ እየተናገረ ፡ በንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ አጠመቀ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ተጠመቁ ፤

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ጳውሎስም ፡ እጁን ፡ በጫነባቸው ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደባቸው ፡ በልሳኖችም ፡ ተናገሩ ፥ ትንቢትም ፡ ተናገሩ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ ሰዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ያኽሉ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ ምኩራብም ፡ ገብቶ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እየተነጋገረና ፡ እያስረዳቸው ፡

295 ጽር. ፥ አፖሎስ ።

ሦስት ፡ ወር ፡ ያኽል ፡ በግልጥ ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ አንዳንዶች ፡ ግን ፡ እልከኞች ፡ ኾነው ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ መንገዱን ፡ እየሰደቡ ፡ ባላመኑ ፡ ጊዜ ፥ ከነርሱ ፡ ርቆ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ለየ ፥ ጢራኖስም ፡ በሚሉት ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ በእስያም ፡ የኖሩት ፡ ኹሉ ፡ አይሁድም ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ የጌታን ፡ ቃል ፡ እስኪሰሙ ፡ ድረስ ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንዲህ ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በጳውሎስ ፡ እጅ ፡ የሚያስገርም ፡ ተአምራት ፡ ያደርግ ፡ ነበር ፤ ስለዚህም ፡ ከአካሉ ፡ ጨርቅ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ድውዮች ፡ ይወስዱ ፡ ነበር ፥

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ደዌያቸውም ፡ ይለቃቸው ፡ ነበር ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስትም ፡ ይወጡ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ አጋንንትንም ፡ እያወጡ ፡ ይዞሩ ፡ ከነበሩት ፡ አይሁድ ፡ አንዳንዶች ። ጳውሎስ ፡ በሚሰብከው ፡ በኢየሱስ ፡ እናምላኮኋለን ፡ እያሉ ፡ ክፉዎች ፡ መናፍስት ፡ ባሉባቸው ፡ ላይ ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስን ፡ ስም ፡ ይጠሩባቸው ፡ ዘንድ ፡ ሞከሩ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ለኾነ ፡ አስቄዋ ([296]) ፡ ለሚሉት ፡ ላንድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ይህን ፡ ያደረጉ ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ ክፉው ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ ኢየሱስንስ ፡ ዐውቀዋለኹ ፡ ጳውሎስንም ፡ ዐውቀዋለኹ ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ማን ፡ ናችኹ ፧ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ ክፉው ፡ መንፈስም ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ ዘለለባቸው ፡ ቈስለውም ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ ዕራቍታቸውን ፡ እስኪሸሹ ፡ ድረስ ፡ በረታባቸው ፡ አሸነፋቸውም ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 17 ፤ ይህም ፡ በኤፌሶን ፡ በሚኖሩት ፡ ኹሉ ፡ በአይሁድና ፡ በግሪክ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ኾነ ፥ በኹላቸውም ፡ ላይ ፡ ፍርሀት ፡ ወደቀባቸው ፥ የጌታም ፡ የኢየሱስ ፡ ስም ፡ ተከበረ ፤

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 18 ፤ አምነውም ፡ ከነበሩት ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ያደረጉትን ፡ እየተናዘዙና ፡ እየተናገሩ ፡ ይመጡ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ ከአስማተኞችም ፡ ብዙዎቹ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ሰብስበው ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ አቃጠሉት ፤ ዋጋውም ፡ ቢታሰብ ፡ ዐምሳ ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ ኾኖ ፡ ተገኘ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ እንዲህም ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ በኀይል ፡ ያድግና ፡ ያሸንፍ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ ይህም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፦ ወደዚያ ፡ ደርሼ ፡ ሮሜን ፡ ደግሞ ፡ አይ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ ፡ በመቄዶንያና ፡ በአካይያ ፡ ዐልፎ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲኼድ ፡ በመንፈስ ፡ ዐሰበ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 22 ፤ ከሚያገለግሉትም ፡ ኹለቱን ፡ ጢሞቴዎስንና ፡ ኤርስጦንን ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ልኮ ፡ ራሱ ፡ በእስያ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ቈየ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 23 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ስለዚህ ፡ መንገድ ፡ ብዙ ፡ ሁከት ፡ ኾነ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 24 ፤ ብር ፡ ሠሪ ፡ የኾነ ፡ ድሜጥሮስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ የአርጤምስን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ምስሎች ፡ በብር ፡ እየሠራ ፡ ለአንጥረኞች ፡ እጅግ ፡ ትርፍ ፡ ያገኝ ፡ ነበርና ፤

---

296 ጽር. ፡ ስኬዋስ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 25 ፤ እነዚህንም ፡ ይህንም ፡ የሚመስለውን ፡ ሥራ ፡ የሠሩትን ፡ ሰብስቦ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ትርፋችን ፡ በዚህ ፡ ሥራ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 26 ፤ ይህም ፡ ጳውሎስ ፦ በእጅ ፡ የተሠሩቱ ፡ አማልክት ፡ አይደሉም ፡ ብሎ ፥ በኤፌሶን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ከጥቂት ፡ ክፍል ፡ በቀር ፡ በእስያ ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብን ፡ እንደ ፡ አስረዳና ፡ እንደ ፡ አሳተ ፡ አይታችኋል ፡ ሰምታችኹማል ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 27 ፤ ሥራችንም ፡ እንዲናቅ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ እስያ ፡ ኹሉ ፡ ዓለሙም ፡ የሚያመልካት ፡ የታላቂቱ ፡ አምላክ ፡ የአርጤምስ ፡ መቅደስ ፡ ምናምን ፡ ኾኖ ፡ እንዲቈጠር ፡ እንጂ ፥ ታላቅነቷም ፡ ደግሞ ፡ እንዳይሻር ፡ ያስፈራል ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 28 ፤ ይህንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣ ፡ ሞላባቸው ። የኤፌሶን ፡ አርጤምስ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ እያሉም ፡ ጮኹ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 29 ፤ ከተማውም ፡ በሙሉው ፡ ተደባለቀ ፥ የመቄዶንያም ፡ ሰዎች ፡ የጳውሎስን ፡ ጓደኞች ፡ ጋይዮስንና ፡ አርስጥሮኮስን ([297]) ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ነጥቀው ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኾነው ፡ ወደጨዋታ ፡ ስፍራ ፡ ሮጡ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 30 ፤ ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ከለከሉት ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 31 ፤ ከእስያም ፡ አለቃዎች ፡ ወዳጆቹ ፡ የኾኑት ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ልከው ፡ ወደጨዋታ ፡ ስፍራ ፡ ራሱን ፡ እንዳይሰጥ ፡ ለመኑት ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 32 ፤ ወዲያና ፡ ወዲህም ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፤ በጉባኤው ፡ ድብልቅልቅ ፡ ኾኖ ፥ የሚበልጡት ፡ ስንኳ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እንደተሰበሰቡ ፡ አላወቁም ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 33 ፤ አይሁድም ፡ ሲያቀርቡት ፥ እስክንድሮስን ፡ ከሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ገፉት ፤ እስክንድሮስም ፡ በእጁ ፡ ጠቅሶ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ እንዲሟገትላቸው ፡ ወደደ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 34 ፤ አይሁዳዊ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባወቁ ፡ ጊዜ ፥ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፦ የኤፌሶን ፡ አርጤምስ ፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ እያሉ ፡ ኹለት ፡ ሰዓት ፡ ያኽል ፡ ጮኹ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 35 ፤ የከተማዩቱም ፡ ጸሓፊ ፡ ሕዝቡን ፡ ጸጥ ፡ አሠኝቶ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ የኤፌሶን ፡ ከተማ ፡ ለታላቂቱ ፡ አርጤምስ ፡ ከሰማይም ፡ ለወረደው ፡ ጣዖቷ ፡ የመቅደስ ፡ ጠባቂ ፡ መኾኗን ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 36 ፤ ይህንም ፡ የሚክደው ፡ ከሌለ ፥ ጸጥ ፡ እንድትሉና ፡ አንዳች ፡ በችኮላ ፡ እንዳታደርጉ ፡ ይገባል ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 37 ፤ የመቅደስን ፡ ዕቃ ፡ ያልሰረቁ ፡ አምላካችንንም ፡ ያልሰደቡ ፡ እነዚህን ፡ ሰዎች ፡ አምጥታችኋቸዋልና ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 38 ፤ ድሜጥሮስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ አንጥረኞች ፡ ግን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ እንዳላቸው ፥ የመጋቢያ ፡ ቀንና ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ አሉ ፤ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይሟገቱ ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 39 ፤ ስለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ ብትፈልጉ ፥ በተደነገገው ፡ ጉባኤ ፡ ይፈታል ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 40 ፤ ዛሬ ፡ ስለተደረገው ፦ ሁከት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ እንዳይከሱን ፡ ያስፈራልና ፤ ስለዚህም ፡ ስብሰባ ፡ ምላሽ ፡ መስጠት ፡ አንችልም ፥ ምክንያት ፡ የለምና ።

ሐዋ. ፡ 19 ፡ 41 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ ጉባኤውን ፡ ፈታው ።

---

297 ጽር. ፥ አሪስታርኾስ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 1 ፤ ሁከቱም ፡ ከቀረ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አስመጥቶ ፡ መከራቸው ፥ ተሰናብቷቸውም ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 2 ፤ ያንም ፡ አገር ፡ እያለፈ ፡ በብዙ ፡ ቃል ፡ ከመከራቸው ፡ በኋላ ፡ ወደግሪክ ፡ አገር ፡ መጣ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 3 ፤ በዚያም ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ በመርከብ ፡ ሊኼድ ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፥ አይሁድ ፡ ሤራ ፡ ስላደረጉበት ፡ በመቄዶንያ ፡ ዐልፎ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ቈረጠ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 4 ፤ የሸኙትም ፡ የቤርያው ፡ ሱሲጳጥሮስ ፡ ከተሰሎንቄ ፡ ሰዎችም ፡ አርስጥሮኮስና ፡ ሲኮንዱስ ፡ የደርቤኑም ፡ ጋይዮስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ የእስያ ፡ ሰዎችም ፡ ቲኪቆስ ፡ ጥሮፊሞስም ፡ ነበሩ ፤

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 5 ፤ እነዚህም ፡ ወደ ፡ ፊታችን ፡ ዐልፈው ፡ በጢሮዳ ፡ ቈዩን ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 6 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ከቂጣ ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከፊልጵስዩስ ፡ በመርከብ ፡ ተነሥተን ፡ በዐምስት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ጢሮዳ ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ደረስንና ፡ በዚያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 7 ፤ ከሳምንቱም ፡ በመዠመሪያ ፡ ቀን ፡ እንጀራ ፡ ለመቍረስ ፡ ተሰብስበን ፡ ሳለን ፥ ጳውሎስ ፡ በነገው ፡ ሊኼድ ፡ ስላሰበ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ይነጋገር ፡ ነበር ፥ እስከ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ነገሩን ፡ አስረዘመ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 8 ፤ ተሰብስበንም ፡ በነበርንበት ፡ ሰገነት ፡ እጅግ ፡ መብራት ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 9 ፤ አውጤኪስ ፡ የሚሉትም ፡ አንድ ፡ ጐበዝ ፡ በመስኮት ፡ ተቀምጦ ፡ ታላቅ ፡ እንቅልፍ ፡ አንቀላፍቶ ፡ ነበር ፤ ጳውሎስም ፡ ነገርን ፡ ባስረዘመ ፡ ጊዜ ፡ እንቅልፍ ፡ ከብዶት ፡ ከሦስተኛው ፡ ደርብ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደቀ ፥ ሞቶም ፡ አነሡት ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 10 ፤ ጳውሎስም ፡ ወርዶ ፡ በላዩ ፡ ወደቀ ፥ ዐቅፎም ፦ ነፍሱ ፡ አለችበትና ፡ አትንጫጩ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 11 ፤ ወጥቶም ፡ እንጀራ ፡ ቈርሶም ፡ በላ ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ እስኪነጋ ፡ ድረስ ፡ ተነጋገረ ፡ እንዲህም ፡ ኼደ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 12 ፤ ብላቴናውንም ፡ ደኅና ፡ ኾኖ ፡ ወሰዱት ፡ እጅግም ፡ ተጽናኑ ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 13 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ጳውሎስን ፡ ከዚያ ፡ እንቀበለው ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ አለን ፥ ወደ ፡ መርከብ ፡ ቀድመን ፡ ኼድንና ፥ ወደ ፡ አሶን ፡ ተነሣን ፤ ርሱ ፡ በመሬት ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ስላሰበ ፡ እንደዚህ ፡ አዞ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 14 ፤ በአሶንም ፡ ባገኘን ፡ ጊዜ ፡ ተቀብለነው ፡ ወደ ፡ ሚጢሊኒ ፡ መጣን ፤

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 15 ፤ በማግስቱም ፡ ከዚያ ፡ በባሕር ፡ ተነሥተን ፡ በኪዩ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ደረስን ፥ በነገውም ፡ ወደ ፡ ሳሞን ፡ ተሻገርን ፡ በትሮጊሊዮም ፡ ዐድረን ፡ በማግስቱ ፡ ወደ ፡ ሚሊጢን ፡ መጣን ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 16 ፤ ጳውሎስ ፡ በእስያ ፡ እጅግ ፡ እንዳይቀመጥ ፡ ኤፌሶንን ፡ ይተው ፡ ዘንድ ፡ ቈርጦ ፡ ነበርና ፥ ቢቻለውም ፡ በዓለ ፡ ኀምሳን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ይውል ፡ ዘንድ ፡ ይቸኵል ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 17 ፤ ከሚሊጢንም ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ልኮ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሽማግሌዎች ፡ አስጠራቸው ፤

ሐዋ. ፥ 20 ፥ 18-19 ፤ ወደ ፡ ርሱም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ወደ ፡ እስያ ፡ ከገባኹበት ፡ ከመዠመሪያ ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፥ በትሕትና ፡ ኾሉና ፡ በእንባ ፡ ከአይሁድም ፡ ሤራ ፡ በደረሰብኝ ፡ ፈተና ፡ ለጌታ ፡ እየተገዛኹ ፡ ዘመኑን ፡ ኹሉ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኖርኹ ፡ እናንተው ፡ ታውቃላችኹ ፤

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 20-21 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ንስሓንና ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማመንን ፡ ለአይሁድና ፡ ለግሪክ ፡ ሰዎች ፡ እየመሰከርኹ ፡ በጉባኤም ፡ በየቤታችኹም ፡ አወራኹላችኹና ፡ አስተማርኋችኹ ፡ እንጂ ፥ ከሚጠቅማችኹ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ ስንኳ ፡ አላስቀረኹባችኹም ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 22 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ በመንፈስ ፡ ታስሬ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እኼዳለኹ ፥ በዚያም ፡ የሚያገኘኝ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላውቅም ፤

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። እስራትና ፡ መከራ ፡ ይቈይኻል ፡ ብሎ ፡ በየከተማው ፡ ኹሉ ፡ ይመሰክርልኛል ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሩጫዬንና ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ የተቀበልኹትን ፡ አገልግሎት ፡ ርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ወንጌልን ፡ መመስከር ፡ እፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ነፍሴን ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ እንደማትከብር ፡ እንደ ፡ ከንቱ ፡ ነገር ፡ እቈጥራለኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 25 ፤ አኹንም ፥ እንሆ ፥ እኔ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እየሰበክኹ ፡ በመካከላችኹ ፡ የዞርኹ ፡ ኹላችኹ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፊቴን ፡ እንዳትዩ ፡ ዐውቃለኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ደም ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ እመሰክርላችኋለኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 27 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ምክር ፡ ኹሉ ፡ ነግሬያችኋለኹና ፥ ምንም ፡ አላስቀረኹባችኹም ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 28 ፤ በገዛ ፡ ደሙ ፡ የዋጃትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትጠብቋት ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እናንተን ፡ ጳጳሳት ፡ አድርጎ ፡ ለሾመባት ፡ ለመንጋው ፡ ኹሉና ፡ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 29-30 ፤ ከኼድኹ ፡ በኋላ ፡ ለመንጋው ፡ የማይራሩ ፡ ጨካኞች ፡ ተኩላዎች ፡ እንዲገቡባችኹ ፥ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ይስቡ ፡ ዘንድ ፡ ጠማማ ፡ ነገርን ፡ የሚናገሩ ፡ ሰዎች ፡ በመካከላችኹ ፡ እንዲነሡ ፡ እኔ ፡ ዐውቃለኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በእንባ ፡ እያንዳንዳችኹን ፡ ከመገሠጽ ፡ እንዳላቋረጥኹ ፡ እያሰባችኹ ፡ ትጉ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 32 ፤ አኹንም ፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ያንጻችኹ ፡ ዘንድ ፡ በቅዱሳንም ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡ ይሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ ለሚችል ፡ ለጸጋው ፡ ቃል ፡ ዐደራ ፡ ሰጥቻችኋለኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 33 ፤ ከማንም ፡ ብር ፡ ወይም ፡ ወርቅ ፡ ወይም ፡ ልብስ ፡ አልተመኘኹም ፤

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 34 ፤ እነዚህ ፡ እጆቼ ፡ በሚያስፈልገኝ ፡ ነገር ፡ ለኔና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ላሉት ፡ እንዳገለገሉ ፡ እናንተ ፡ ታውቃላችኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 35 ፤ እንዲሁ ፡ እየደከማችኹ ፡ ድውዮችን ፡ ልትረዱና ፡ ርሱ ፡ ራሱ ። ከሚቀበል ፡ ይልቅ ፡ የሚሰጥ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ እንዳለ ፡ የጌታን ፡ የኢየሱስን ፡ ቃል ፡ ልታስቡ ፡ ይገባችኹ ፡ ዘንድ ፡ በኹሉ ፡ አሳየኋችኹ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 36 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ ተንበርክኮ ፡ ከኹላቸው ፡ ጋራ ፡ ጸለየ ።

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 37 ፤ ኹሉም ፡ እጅግ ፡ አለቀሱ ፥ ጳውሎስንም ፡ ዐንገቱን ፡ ዐቅፈው ፡ ይስሙት ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 20 ፡ 38 ፤ ይልቁንም ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ፊቴን ፡ አታዩም ፡ ስላላቸው ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ዐዘኑ ፤ እስከ ፡ መርከብም ፡ ድረስ ፡ ሸኙት ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ ከነርሱም ፡ ተለይተን ፡ ተነሣን ፤ በቀጥታም ፡ ኼደን ፡ ወደ ፡ ቆስ ፡ በነገውም ፡ ወደ ፡ ሩድ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጳጥራ ፡ መጣን ፤

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ ወደ ፡ ፊንቄም ፡ የሚሻገር ፡ መርከብ ፡ አግኝተን ፡ ገባንና ፡ ተነሣን ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ ቆጵሮስንም ፡ ባየናት ፡ ጊዜ ፡ በስተግራችን ፡ ተውናት ፡ ወደ ፡ ሶርያም ፡ ኼደን ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ደረስን ፥ መርከቡ ፡ ሸክሙን ፡ በዚያ ፡ የሚያራግፍ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ ደቀ ፡ መዛሙርትንም ፡ ባገኘን ፡ ጊዜ ፡ በዚያ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ፤ እነርሱም ፡ ጳውሎስን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጣ ፡ በመንፈስ ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ ጊዜውንም ፡ በፈጸምን ፡ ጊዜ ፡ ወጥተን ፡ ኼድን ፤ ሹላቸውም ፡ ከሚስቶቻቸውና ፡ ከልጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ከተማው ፡ ውጭ ፡ ድረስ ፡ ሸኙን ፥ በባሕሩም ፡ ዳር ፡ ተንበርክከን ፡ ጸለይን ፤

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ ርስ ፡ በርሳችንም ፡ ተሰነባብተን ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ወጣን ፥ እነዚያም ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ ተመለሱ ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 7 ፤ እኛም ፡ የባሕሩን ፡ መንገድ ፡ ጨርሰን ፡ ከጢሮስ ፡ ወደ ፡ አካ ([298]) ፡ ደረስን ፥ ለወንድሞችም ፡ ሰላምታ ፡ ሰጥተን ፡ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 8 ፤ በነገውም ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ መጣን ፥ ከሰባቱም ፡ አንድ ፡ በሚኾን ፡ በወንጌላዊው ፡ ፊልጶስ ፡ ቤት ፡ ገብተን ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተቀመጥን ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 9 ፤ ለርሱም ፡ ትንቢት ፡ የሚናገሩ ፡ አራት ፡ ደናግል ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 10 ፤ ዐያሌ ፡ ቀንም ፡ ተቀምጠን ፡ ሳለን ፡ ነቢይ ፡ የነበረ ፡ አጋቦስ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ከይሁዳ ፡ ወረደ ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 11 ፤ ወደ ፡ እኛም ፡ መጣና ፡ የጳውሎስን ፡ መታጠቂያ ፡ ወስዶ ፡ የገዛ ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ አስሮ ፦ እንዲሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፦ ይህ ፡ መታጠቂያ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እንደዚህ ፡ ያስሩታል ፡ በአሕዛብም ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ይሰጡታል ፡ ይላል ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 12 ፤ ይህንም ፡ በሰማን ፡ ጊዜ ፡ እኛም ፡ በዚያ ፡ የሚኖሩትም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዳይወጣ ፡ ለመንነው ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 13 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ መልሶ ፦ እያለቀሳችኹ ፡ ልቤንም ፡ እየሰበራችኹ ፡ ምን ፡ ማድረጋችኹ ፡ ነው ፧ እኔ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ስለኢየሱስ ፡ ስም ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ለመሞት ፡ እንኳ ፡ ተሰናድቻለኹ ፡ እንጂ ፡ ለእስራት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ አለ ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 14 ፤ ምክርንም ፡ ሊቀበል ፡ እምቢ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፦ የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ይኹን ፡ ብለን ፡ ዝም ፡ አልን ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 15 ፤ ከዚህም ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ተዘጋጅተን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣን ።

ሐዋ. ፥ 21 ፥ 16 ፤ በቂሳርያም ፡ ከነበሩ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አንዳንዶች ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ መጡ ፥ እነርሱም ፡ ወደምናድርበት ፡ ወደቀደመው ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወደቆጵሮሱ ፡ ምናሶን ፡ ወደሚሉት ፡ ቤት ፡ መሩን ።

---

298 ጽር. ፥ ፕቶሌማይስ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞች ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉን ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ በነገውም ፡ ጳውሎስ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ ገባ ፡ ሽማግሌዎችም ፡ ኹሉ ፡ መጡ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ ሰላምታም ፡ ካቀረበላቸው ፡ በኋላ ፡ በርሱ ፡ ማገልገል ፡ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያደረገውን ፡ በያንዳንዱ ፡ ተረከላቸው ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ እነርሱም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፥ አሉትም ፦ ወንድም ፡ ሆይ ፥ በአይሁድ ፡ መካከል ፡ አምነው ፡ የነበሩት ፡ ስንት ፡ አእላፋት ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ታያለኽ ፤ ኹላቸውም ፡ ለሕግ ፡ የሚቀኑ ፡ ናቸው ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ልጆቻቸውንም ፡ እንዳይገርዙ ፡ በሥርዐትም ፡ እንዳይኼዱ ፡ ብለኽ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ያሉት ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ሙሴን ፡ ይክዱ ፡ ዘንድ ፡ እንድታስተምር ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ነግረዋቸዋል ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይኹን ፧ የአንተን ፡ መምጣት ፡ ይሰማሉና ፡ ብዙዎች ፡ የግድ ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ አይቀሩም ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ የምንልኽን ፡ አድርግ ፤ ስለት ፡ ያለባቸው ፡ አራት ፡ ሰዎች ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 24 ፤ እነዚህንም ፡ ይዘኽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ንጹ ፥ ራሳቸውንም ፡ እንዲላጩ ፡ ገንዘብ ፡ ክፈልላቸው ፤ ኹሉም ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ የተማሩት ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነና ፥ አንተ ፡ ራስኽ ፡ ደግሞ ፡ ሕጉን ፡ እየጠበቅኽ ፡ በሥርዐት ፡ እንድትመላለስ ፡ ያውቃሉ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 25 ፤ አምነው ፡ ስለነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ ለጣዖት ፡ ከተሠዋ ፡ ከደምም ፡ ከታነቀም ፡ ከዝሙትም ፡ ነፍሳቸውን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ፈርደን ፡ እኛ ፡ ጽፈንላቸዋል ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 26 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰዎችን ፡ ይዞ ፡ በማግስቱ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እየነጻ ፥ መንጻታቸውን ፡ የሚፈጽሙበትን ፡ ቀን ፡ አስታውቆ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ መሥዋዕትን ፡ አቀረቡ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 27-28 ፤ ሰባቱ ፡ ቀንም ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ሲቀርብ ፡ ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አይሁድ ፡ በመቅደስ ፡ አይተውት ፡ ሕዝብን ፡ ኹሉ ፡ አወኩና ፦ የእስራኤል ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ርዱን ፤ ሕዝብን ፡ ሕግንም ፡ ይህንም ፡ ስፍራ ፡ ሲቃወም ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ በየስፍራው ፡ የሚያስተምረው ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ጨምሮም ፡ የግሪክን ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ አግብቶ ፡ ይህን ፡ የተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ አርክሷል ፡ ብለው ፡ እየጮኹ ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑበት ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 29 ፤ በፊት ፡ የኤፌሶኑን ፡ ጥሮፊሞስን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በከተማ ፡ አይተውት ፡ ነበርና ፥ ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ያገባው ፡ መስሏቸው ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 30 ፤ ከተማውም ፡ ኹሉ ፡ ታወከ ፡ ሕዝቡም ፡ ኹሉ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ጳውሎስንም ፡ ይዘው ፡ ከመቅደስ ፡ ውጭ ፡ ጎተቱት ፥ ወዲያውም ፡ ደጆች ፡ ተዘጉ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 31 ፤ ሊገድሉትም ፡ ሲፈልጉ ፦ ኢየሩሳሌም ፡ ፈጽማ ፡ ታወከች ፡ የሚል ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ ጭፍራው ፡ ሻለቃ ፡ ወጣ ፤

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 32 ፤ ርሱም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮችን ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ ጋራ ፡ ይዞ ፡ እየሮጠ ፡ ወረደባቸው ፤ እነርሱም ፡ የሻለቃውንና ፡ ወታደሮችን ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስን ፡ መምታት ፡ ተዉ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 33 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የሻለቃው ፡ ቀርቦ ፡ ያዘውና ፡ በኹለት ፡ ሰንሰለት ፡ ይታሰር ፡ ዘንድ ፡ አዞ ፥ ማን ፡ እንደ ፡ ኾነና ፡ ምን ፡ እንዳደረገ ፡ ጠየቀ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 34 ፤ ሕዝቡም ፡ እኩሌታዎቹ ፡ እንዲህ ፡ እኩሌታዎቹም ፡ እንዲያ ፡ እያሉ ፡ ይጮኹ ፡ ነበር ፤ ስለ ፡ ጫጫታውም ፡ ርግጡን ፡ ማወቅ ፡ ባልተቻለ ፡ ጊዜ ፥ ወደወታደሮች ፡ ሰፈር ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 35 ፤ ወደ ፡ ደረጃውም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ስለሕዝቡ ፡ ግፊያ ፡ ወታደሮች ፡ እንዲሸከሙት ፡ ኾነ ፤

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 36 ፤ ብዙ ፡ ሕዝብ ፦ አስወግደው ፡ እያሉና ፡ እየጮኹ ፡ ይከተሉ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 37 ፤ ወደ ፡ ሰፈርም ፡ ሊያገቡት ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፥ ጳውሎስ ፡ የሻለቃውን ፦ አንድ ፡ ነገር ፡ ብነግርኽ ፡ ትፈቅዳለኽን ፧ አለው ። ርሱም ፦ የግሪክ ፡ ቋንቋ ፡ ታውቃለኽን ፧

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 38 ፤ አንተ ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ከነፍሰ ፡ ገዳዮቹ ፡ አራቱን ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ አሸፍተኽ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ያወጣኽ ፡ የግብጽ ፡ ሰው ፡ አይደለኽምን ፧ አለ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 39 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፦ እኔስ ፡ አይሁዳዊ ፡ በኪልቅያ ፡ ያለው ፡ የጠርሴስ ፡ ሰው ፡ ኾኜ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ በኾነ ፡ ከተማ ፡ የምኖር ፡ ነኝ ፤ ለሕዝቡ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ እንድትፈቅድልኝ ፡ እለምንኻለኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 21 ፡ 40 ፤ በፈቀደለትም ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በደረጃው ፡ ላይ ፡ ቆሞ ፡ በእጁ ፡ ወደ ፡ ሕዝቡ ፡ ጠቀሰ ፥ እጅግም ፡ ጸጥታ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ እየተናገረ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 1 ፤ እናንተ ፡ ወንድሞች ፡ አባቶችም ፥ አኹን ፡ ለእናንተ ፡ ነገሬን ፡ ስገልጥ ፡ ስሙኝ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 2 ፤ በዕብራይስጥም ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ዝም ፡ አሉ ። ርሱም ፡ አለ ፦

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 3 ፤ እኔ ፡ የኪልቅያ ፡ በምትኾን ፡ በጠርሴስ ፡ የተወለድኹ ፥ በዚችም ፡ ከተማ ፡ በገማልኤል ፡ እግር ፡ አጠገብ ፡ ያደግኹ ፥ የአባቶችንም ፡ ሕግ ፡ ጠንቅቄ ፡ የተማርኹ ፥ ዛሬውንም ፡ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ እንድትኾኑ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀናተኛ ፡ የኾንኹ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ነኝ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 4 ፤ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ እያሰርኹ ፡ ወደ ፡ ወህኒም ፡ አሳልፌ ፡ እየሰጠኹ ፡ ይህን ፡ መንገድ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ አሳደድኹ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 5 ፤ እንዲህም ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ደግሞ ፡ ሽማግሌዎቹም ፡ ኹሉ ፡ ይመሰክሩልኛል ፤ ከነርሱ ፡ ደግሞ ፡ መልእክትን ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ተቀብዬ ፥ በደማስቆ ፡ ያሉትን ፡ ደግሞ ፡ ታስረው ፡ እንዲቀጡ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ላመጣ ፡ ወደዚያ ፡ እኼድ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 6 ፤ ስኼድም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ በቀረብኹ ፡ ጊዜ ፥ ቀትር ፡ ሲኾን ፡ ድንገት ፡ ከሰማይ ፡ ታላቅ ፡ ብርሃን ፡ በዙሪያዬ ፡ አንጸባረቀ ፤

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 7 ፤ በምድርም ፡ ላይ ፡ ወድቄ ። ሳውል ፡ ሳውል ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደኛለኽ ፧ የሚለኝን ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 8 ፤ እኔም ፡ መልሼ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ አልኹ ። ርሱም ፦ አንተ ፡ የምታሳድደኝ ፡ የናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 9 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበሩትም ፡ ብርሃኑን ፡ አይተው ፡ ፈሩ ፥ የሚናገረኝን ፡ የርሱን ፡ ድምፅ ፡ ግን ፡ አልሰሙም ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 10 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምን ፡ ላድርግ ፧ አልኹት ። ጌታም ፦ ተነሥተኽ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ኺድና ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ስለታዘዘው ፡ ኹሉን ፡ በዚያ ፡ ይነግሩኻል ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 11 ፤ ከዚያ ፡ ብርሃንም ፡ ክብር ፡ የተነሣ ፡ ማየት ፡ ባይኾንልኝ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ እጄን ፡ ይዘው ፡ እየመሩኝ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ደረስኹ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 12 ፤ በዚያም ፡ የኖሩት ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ የመሰከሩለት ፡ እንደ ፡ ሕጉም ፡ በጸሎት ፡ የተጋ ፡ ሐናንያ ፡ የሚሉት ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 13 ፤ ርሱም ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ መጥቶ ፡ ባጠገቤም ፡ ቆሞ ፦ ወንድሜ ፡ ሳውል ፡ ሆይ ፥ እይ ፡ አለኝ ። እኔም ፡ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አየኹ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ርሱም ፡ አለኝ ፦ የአባቶቻችን ፡ አምላክ ፡ ፈቃዱን ፡ ታውቅ ፡ ዘንድና ፡ ጻድቁን ፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ ከአፉም ፡ ድምፅን ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ መርጦኻል ፡

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ባየኸውና ፡ በሰማኸው ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ ምስክር ፡ ትኾንለታለኽና ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ አኹንስ ፡ ለምን ፡ ትዘገያለኽ ፧ ተነሣና ፡ ስሙን ፡ እየጠራኽ ፡ ተጠመቅ ፡ ከኀጢአትኽም ፡ ታጠብ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ኢየሩሳሌምም ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ በመቅደስ ፡ ስጸልይ ፡ ተመስጦ ፡ መጣብኝ ፥

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ ርሱም ፦ ፍጠን ፡ ከኢየሩሳሌምም ፡ ቶሎ ፡ ውጣ ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ የምትመሰክረውን ፡ አይቀበሉኽምና ፡ ሲለኝ ፡ አየኹት ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ የሚያምኑትን ፡ በምኩራብ ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ በወህኒ ፡ አገባና ፡ እደበድብ ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ እነርሱ ፡ ያውቃሉ ፤

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ የሰማዕትኽንም ፡ የእስጢፋኖስን ፡ ደም ፡ ባፈሰሱ ፡ ጊዜ ፥ ራሴ ፡ ደግሞ ፡ በአጠገባቸው ፡ ስቆም ፡ ተስማምቼ ፡ የገዳዮችን ፡ ልብስ ፡ እጠብቅ ፡ ነበር ፡ አልኹ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ ርሱም ፦ ኺድ ፥ እኔ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ከዚህ ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ እልክኻለኹና ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 22 ፤ እስከዚህም ፡ ቃል ፡ ድረስ ፡ ይሰሙት ፡ ነበር ፥ ድምፃቸውንም ፡ ከፍ ፡ አድርገው ። እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ከምድር ፡ አስወግደው ፥ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አይገ፡ባውምና ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 23 ፤ ሲጮኹና ፡ ልብሳቸውን ፡ ሲወረውሩ ፡ ትቢያንም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ሲበትኑ ፥

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 24 ፤ የሻለቃው ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ እንዲያገቡት ፡ አዘዘ ፥ እንደዚህም ፡ የጮኹበትን ፡ ምክንያት ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፦ እየገረፋችኹ ፡ መርምሩት ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 25 ፤ በጠፍርም ፡ በገተሩት ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ባጠገቡ ፡ የቆመውን ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፦ የሮሜን ፡ ሰው ፡ ያለፍርድ ፡ ትገርፉ ፡ ዘንድ ፡ ተፈቅዶላችኋልን ፧ አለው ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 26 ፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ቀርቦ ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ ሮማዊ ፡ ነውና ፥ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ ካለኽ ፡ ተጠበቅ ፡ ብሎ ፡ ነገረው ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 27 ፤ የሻለቃውም ፡ ቀርቦ ፦ አንተ ፡ ሮማዊ ፡ ነኽን ፧ ንገረኝ ፡ አለው ፤ ርሱም ፦ አዎን ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 28 ፤ የሻለቃውም ፡ መልሶ ፦ እኔ ፡ ይህን ፡ ዜግነት ፡ በብዙ ፡ ገንዘብ ፡ አገኘኹት ፡

አለ ። ጳውሎስም ፦ እኔ ፡ ግን ፡ በርሷ ፡ ተወለድኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 29 ፤ ስለዚህም ፡ ሊመረምሩት ፡ ያሰቡት ፡ ከርሱ ፡ ወዲያው ፡ ተለዩ ፤ የሻለቃውም ፡ ደግሞ ፡ ሮማዊ ፡ መኾኑን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ፈራ ፥ አሳስሮት ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 22 ፡ 30 ፤ በማግስቱም ፡ አይሁድ ፡ የከሰሱት ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርግጡን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ፀስቦ ፡ ፈታው ፥ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ሸንጎውም ፡ ኹሉ ፡ ይሰበሰቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፥ ጳውሎስንም ፡ አውርዶ ፡ በፊታቸው ፡ አቆመው ።

_____የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 23 ። _____

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 1 ፤ ጳውሎስም ፡ ሸንጎውን ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመልክቶ ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በመልካም ፡ ኅሊና ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኖሬያለኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 2 ፤ ሊቀ ፡ ካህናቱም ፡ ሐናንያ ፡ አፉን ፡ ይመቱት ፡ ዘንድ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆመው ፡ የነበሩትን ፡ አዘዘ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፦ አንተ ፡ በኖራ ፡ የተለሰነ ፡ ግድግዳ ፥ እግዚአብሔር ፡ አንተን ፡ ይመታ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፤ አንተ ፡ በሕግ ፡ ልትፈርድብኝ ፡ ተቀምጠኽ ፡ ሳለኽ ፡ ያለሕግ ፡ እመታ ፡ ዘንድ ፡ ታዛለኽን ፧ አለው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 4 ፤ በአጠገቡ ፡ የቆሙትም ፦ የእግዚአብሔርን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ትሳደባለኽን ፧ አሉት ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 5 ፤ ጳውሎስም ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ መኾኑን ፡ ባላውቅ ፡ ነው ፤ በሕዝብኽ ፡ አለቃ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ አትናገር ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፥ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 6 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ እኩሌታዎቹ ፡ ሰዱቃውያን ፡ እኩሌታዎቹም ፡ ፈሪሳውያን ፡ መኾናቸውን ፡ አይቶ ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ፈሪሳዊ ፡ የፈሪሳዊም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፤ ስለ ፡ ተስፋና ፡ ስለሙታን ፡ መነሣት ፡ ይፈርዱብኛል ፡ ብሎ ፡ በሸንጎው ፡ ጮኸ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 7 ፤ ይህንም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በፈሪሳውያንና ፡ በሰዱቃውያን ፡ መካከል ፡ ጥል ፡ ኾነ ፡ ሸንጎውም ፡ ተለያየ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 8 ፤ ሰዱቃውያን ፦ ትንሣኤም ፡ መልአክም ፡ መንፈስም ፡ የለም ፡ የሚሉ ፡ ናቸውና ፤ ፈሪሳውያን ፡ ግን ፡ ኹለቱን ፡ ያምናሉ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 9 ፤ ታላቅ ፡ ጩኸትም ፡ ኾነ ፥ ከፈሪሳውያንም ፡ ወገን ፡ የኾኑት ፡ ጻፊዎች ፡ ተነሥተው ፦ በዚህ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላገኘንበትም ፤ መንፈስ ፡ ወይስ ፡ መልአክ ፡ ተናግሮት ፡ ይኾን ፧ ብለው ፡ ተከራከሩ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ ጥልም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የሻለቃው ፡ ጳውሎስን ፡ እንዳይገነጣጥሉት ፡ ፈርቶ ፡ ጭፍራዎቹ ፡ ወርደው ፡ ከመካከላቸው ፡ እንዲነጥቁት ፡ ወደ ፡ ሰፈሩም ፡ እንዲያገቡት ፡ አዘዘ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 11 ፤ በኹለተኛውም ፡ ሌሊት ፡ ጌታ ፡ በአጠገቡ ፡ ቆሞ ፦ ጳውሎስ ፡ ሆይ ፥ በኢየሩሳሌም ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ መሰከርኽ ፡ እንዲሁ ፡ በሮሜም ፡ ትመሰክርልኝ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻልና ፥ አይዞኽ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 12 ፤ በጠባም ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ ጳውሎስን ፡ እስኪገድሉት ፡ ድረስ ፡ እንዳይበሉና ፡ እንዳይጠጡ ፡ በመሐላ ፡ ተስማሙ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 13 ፤ ይህንም ፡ ሤራ ፡ ያደረጉት ፡ ሰዎች ፡ ከአርባ ፡ ይበዙ ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 14 ፤ እነርሱም ፡ ወደካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ ወደ ፡ ሽማግሌዎቹ ፡ መጥተው ፦ ጳውሎስን ፡ እስክንገድል ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ እንዳንቀምስ ፡ ተረጋግመን ፡ ተማምለናል ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ አኹን ፡ እናንተ ፡ ከሸንጎው ፡ ጋራ ፡ ኾናችኹ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አጥብቃችኹ ፡ እንደምትመረምሩ ፡ መስላችኹ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንዲያወርደው ፡ ለሻለቃው ፡ አመልክቱት ፤ እኛም ፡ ሳይቀርብ ፡ እንድንገድለው ፡ የተዘጋጀን ፡ ነን ፡ አሏቸው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 16 ፤ የጳውሎስ ፡ የእኅቱ ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ደባቸውን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፥ መጥቶ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ገባና ፡ ለጳውሎስ ፡ ነገረው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 17 ፤ ጳውሎስም ፡ ከመቶ ፡ አለቃዎች ፡ አንዱን ፡ ጠርቶ ፦ ይህን ፡ ብላቴና ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ውሰድ ፥ የሚያወራለት ፡ ነገር ፡ አለውና ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 18 ፤ ርሱም ፡ ይዞት ፡ ወደ ፡ ሻለቃው ፡ ወሰደውና ፦ ይህ ፡ ብላቴና ፡ የሚነግርኽ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ አለው ፡ እስረኛው ፡ ጳውሎስ ፡ ጠርቶ ፡ ወዳንተ ፡ እንድወስደው ፡ ለመነኝ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 19 ፤ የሻለቃውም ፡ እጁን ፡ ይዞ ፡ ፈቀቅ ፡ አለና ፥ ለብቻው ፡ ኾኖ ፦ የምታወራልኝ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ ጠየቀው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 20 ፤ ርሱም ፦ አይሁድ ፡ ስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ አጥብቀኽ ፡ እንደምትመረምር ፡ መስለኽ ፥ ነገ ፡ ወደ ፡ ሸንጎ ፡ ታወርደው ፡ ዘንድ ፡ ሊለምኑኽ ፡ ተስማምተዋል ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 21 ፤ እንግዲህ ፡ አንተ ፦ በጀ ፡ አትበላቸው ፤ እስኪገድሉት ፡ ድረስ ፡ እንዳይበሉና ፡ እንዳይጠጡ ፡ ተማምለው ፡ ከነርሱ ፡ ከአርባ ፡ የሚበዙ ፡ ሰዎች ፡ ያደቡበታልና ፤ አኹንም ፡ የተዘጋጁ ፡ ናቸው ፥ የአንተንም ፡ ምላሽ ፡ ይጠብቃሉ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 22 ፤ የሻለቃውም ፦ ይህን ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ማመልከትኽን ፡ ለማንም ፡ እንዳትገልጥ ፡ ብሎ ፡ ካዘዘ ፡ በኋላ ፡ ብላቴናውን ፡ አሰናበተው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 23 ፤ ከመቶ ፡ አለቃዎቹም ፡ ኹለት ፡ ጠርቶ ፦ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ወታደሮችንና ፡ ሰባ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ኹለት ፡ መቶም ፡ ባለጦር ፡ መሣሪያዎችን ፡ ከሌሊቱ ፡ በሦስተኛው ፡ ሰዓት ፡ አዘጋጁ ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 24 ፤ ጳውሎስንም ፡ ወደ ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ወደ ፡ ፊልክስ ፡ በደኅና ፡ እንዲያደርሱት ፡ የሚያስቀምጡበትን ፡ ከብት ፡ ያዘጋጁ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 25 ፤ ደብዳቤም ፡ ጻፈ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 26 ፤ ከቀላውዴዎስ ፡ ሉስዮስ ፡ ወደ ፡ ክቡር ፡ አገረ ፡ ገዢው ፡ ወደ ፡ ፊልክስ ፤ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 27 ፤ ይህን ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ ይዘው ፡ ሊገድሉት ፡ ባሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ከጭፍራዎቹ ፡ ጋራ ፡ ደርሼ ፡ አዳንኹት ፥ ሮማዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ዐውቄ ፡ ነበርና ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 28 ፤ የሚከሰስበትንም ፡ ምክንያት ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዐስቤ ፥ ወደ ፡ ሸንጓቸው ፡ አወረድኹት ፤

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 29 ፤ በሕጋቸውም ፡ ስለ ፡ መከራከር ፡ እንደ ፡ ከሰሱት ፡ አገኘኹ ፡ እንጂ ፡ ለሞት ፡ ወይም ፡ ለእስራት ፡ የሚያደርስ ፡ ክስ ፡ አይደለም ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 30 ፤ በዚህም ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ ሤራ ፡ እንዲያደርጉበት ፡ ባመለከቱኝ ፡ ጊዜ ፥ ያን ፡ ጊዜውን ፡ ወዳንተ ፡ ሰደድኹት ፥ ከሳሾቹንም ፡ ደግሞ ፡ በፊትኽ ፡ ይከሱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኋቸው ። ደኅና ፡ ኹን ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 31 ፤ ወታደሮቹም ፡ እንደ ፡ ታዘዙት ፡ ጳውሎስን ፡ ይዘው ፡ በሌሊት ፡ ወደ ፡ አንቲጳጥሪስ ፡ አደረሱት ፤

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 32 ፤ በነገውም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ሰፈር ፡ ተመለሱ ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 33 ፤ እነዚያም ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ገብተው ፡ ደብዳቤውን ፡ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ በሰጡ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስን ፡ ደግሞ ፡ በፊቱ ፡ አቆሙት ።

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 34 ፤ ካነበበውም ፡ በኋላ ፡ የወዴት ፡ አውራጃ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጠየቀው ፤ የኪልቅያ ፡ ሰው ፡ መኾኑንም ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፦

ሐዋ. ፡ 23 ፡ 35 ፤ ከሳሾችኽ ፡ ደግሞ ፡ ሲመጡ ፡ እሰማኻለኹ ፡ አለው ፤ በሄሮድስም ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ 24 ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 1 ፤ ከዐምስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ሊቀ ፡ ካህናቱ ፡ ሐናንያ ፡ ከሽማግሌዎችና ፡ ጠርጠሉስ ፡ ከሚሉት ፡ ካንድ ፡ ጠበቃ ፡ ጋራ ፡ ወረደ ፤ እነርሱም ፡ ስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ አመለከቱት ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 2-3 ፤ በተጠራም ፡ ጊዜ ፡ ጠርጠሉስ ፡ ይከሰው ፡ ዘንድ ፡ ገሥመረ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፦ ክቡር ፡ ፊልክስ ፡ ሆይ ፥ ባንተ ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ሰላም ፡ ስለምናገኝ ፡ ለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ በዐሳብኽ ፡ በየነገሩ ፡ በየስፍራውም ፡ መልካም ፡ መሻሻል ፡ ስለሚኾንለት ፥ በፍጹም ፡ ምስጋና ፡ እንቀበለዋለን ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅግ ፡ እንዳላቄይኽ ፡ በቸርነትኽ ፡ በዐጪሩ ፡ ትሰማን ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 5 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ በሽታ ፡ ኾኖ ፡ በዓለም ፡ ባሉት ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ሁከት ፡ ሲያስነሣ ፥ የመናፍቃን ፡ የናዝራውያን ፡ ወገን ፡ መሪ ፡ ኾኖ ፡ አግኝተነዋልና ፤

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 6 ፤ መቅደስንም ፡ ደግሞ ፡ ሊያረክስ ፡ ሲሞክር ፡ ያዝነው ፥ እንደ ፡ ሕጋችንም ፡ እንፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ ወደድን ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሻለቃው ፡ ሉስዮስ ፡ መጥቶ ፡ በብዙ ፡ ኀይል ፡ ከእጃችን ፡ ወሰደው ፥

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 8 ፤ ከሳሾቹንም ፡ ወዳንተ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፤ አንተም ፡ ራስኽ ፡ ርሱን ፡ መርምረኽ ፡ እኛ ፡ ስለምንከስበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ልታውቅ ፡ ትችላለኽ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 9 ፤ አይሁድም ፡ ደግሞ ፦ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ ተስማሙ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 10 ፤ ገዢውም ፡ በጠቀሰው ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ መለሰ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ገሥመረኽ ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ አንተ ፡ ፈራጅ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ዐውቃለኹና ፡ ደስ ፡ እያለኝ ፡ ስለእኔ ፡ ነገር ፡ እመልሳለኹ ፤

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 11 ፤ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ከወጣኹ ፡ ከዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ቀን ፡ እንዳይበልጥ ፡ ልታውቀው ፡ ትችላለኽ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 12 ፤ ከአንድም ፡ ስንኳ ፡ ስነጋገር ፡ ወይም ፡ ሕዝብን ፡ ስሰበስብ ፡ በመቅደስ ፡ ቢኾን ፡ በምኩራብም ፡ ቢኾን ፡ በከተማም ፡ ቢኾን ፡ አላገኙኝም ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 13 ፤ አኹንም ፡ ስለሚከሱኝ ፡ ያስረዱኽ ፡ ዘንድ ፡ አይችሉም ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህን ፡ እመሰክርልኻለኹ ፤ በሕጉ ፡ ያለውን ፡ በነቢያትም ፡ የተጻፉትን ፡ ኹሉ ፡ አምኜ ፡ የአባቶቼን ፡ አምላክ ፡ እነርሱ ፡ ኑፋቄ ፡ ብለው ፡ እንደሚጠሩት ፡ መንገድ ፡ አመልካለኹ ፤

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 15 ፤ እነዚህም ፡ ራሳቸው ፡ ደግሞ ፡ የሚጠብቁት ፥ ጻድቃንም ፡ ዐመፀኞችም ፡ ከሙታን ፡ ይነሡ ፡ ዘንድ ፡ እንዳላቸው ፡ ተስፋ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ዘወትር ፡ ነውር ፡ የሌለባት ፡ ኅሊና ፡ ትኖረኝ ፡ ዘንድ ፡ እተጋለኹ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 17 ፤ ከብዙ ፡ ዓመትም ፡ በኋላ ፡ ለሕዝቤ ፡ ምጽዋትና ፡ መሥዋዕት ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ መጣኹ ፤

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 18 ፤ ይህንም ፡ ሳደርግ ፡ ሳለኹ ፡ ሕዝብ ፡ ሳይሰበሰብ ፡ ሁከትም ፡ ሳይኾን ፡ በመቅደስ ፡ ስነጻ ፡ አገኙኝ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ ያላቸው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በፊትኽ ፡ መጥተው ፡ ይከሱኝ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባቸው ፡ ከእስያ ፡ የመጡ ፡ አንዳንድ ፡ አይሁድ ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 20-21 ፤ ወይም ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሜ ፦ ዛሬ ፡ ስለ ፡ ሙታን ፡ መነሣት ፡ በፊታችኹ ፡ በእኔ ፡ ይፈርዱብኛል ፡ ብዬ ፡ ከጮኽኹት ፡ ከዚህ ፡ ካንድ ፡ ነገር ፡ በቀር ፥ በሸንጎ ፡ ፊት ፡ ቆሜ ፡ ሳለኹ ፡ በእኔ ፡ አንድ ፡ ዐመፃ ፡ ያገኙ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ እነዚህ ፡ ራሳቸው ፡ ይናገሩ ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 22 ፤ ፊልክስ ፡ ግን ፡ የመንገዱን ፡ ነገር ፡ አጥብቆ ፡ ዐውቋልና ፦ የሻለቃው ፡ ሉስዮስ ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ነገራችኹን ፡ እቈርጣለኹ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አዘገያቸው ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 23 ፤ የመቶውንም ፡ አለቃ ፡ ጳውሎስን ፡ ሲጠብቅ ፡ እንዲያደላለት ፥ ከወዳጆቹም ፡ ማንም ፡ ሲያገለግለው ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ሲመጣ ፡ እንዳይከለክልበት ፡ አዘዘው ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 24 ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ፊልክስ ፡ አይሁዳዊት ፡ ከነበረች ፡ ድሩሲላ ፡ ከሚሷት ፡ ከሚስቱ ፡ ጋራ ፡ መጥቶ ፡ ጳውሎስን ፡ አስመጣ ፥ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ስለ ፡ ማመን ፡ የሚናገረውን ፡ ሰማው ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ ስለ ፡ ጽድቅና ፡ ራስን ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ ስለሚመጣውም ፡ ዘንጌ ፡ ሲነጋገር ፡ ሳለ ፥ ፊልክስ ፡ ፈርቶ ፦ አኹንስ ፡ ኺድ ፥ በተመቸኝም ፡ ጊዜ ፡ ልኬ ፡ አስጠራኻለኹ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 26 ፤ ያን ፡ ጊዜም ፡ ደግሞ ፡ እንዲፈታው ፡ ጳውሎስ ፡ ገንዘብ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፥ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያስመጣ ፡ ያነጋግረው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 24 ፡ 27 ፤ ኹለት ፡ ዓመትም ፡ ከሞላ ፡ በኋላ ፡ ጶርቅዮስ ፡ ፊስጦስ ፡ በፊልክስ ፡ ፈንታ ፡ ተተካ ። ፊልክስም ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ያሠኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ጳውሎስን ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ተወው ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 25 ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 1 ፤ ፊስጦስም ፡ ወደ ፡ አውራጃው ፡ ገብቶ ፡ ከሦስት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ከቂሳርያ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጣ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 2 ፤ የካህናቱ ፡ አለቃዎችና ፡ የአይሁድም ፡ ታላላቆች ፡ በጳውሎስ ፡ ላይ ፡ አመለከቱ ፥

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 3 ፤ ጳውሎስንም ፡ ሲቃወም ፡ እንዲያደላላቸው ፡ እየለመኑ ፥ በመንገድ ፡ ሸምቀው ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡ ዐስበው ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንዲያስመጣው ፡ ማለዱት ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 4 ፤ ፊስጦስ ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ በቂሳርያ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ርሱም ፡ ራሱ ፡ ወደዚያ ፡ ፈጥኖ ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለው ፡ መለሰላቸው ፤

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 5 ፤ እንግዲህ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ክፋት ፡ ቢኾን ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ወርደው ፡ ይክሰሱት ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 6 ፤ በእነርሱም ፡ ዘንድ ፡ ከስምንት ፡ ወይም ፡ ከዐሥር ፡ የማይበልጥ ፡ ቀን ፡ ተቀምጦ ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ወረደ ፤ በነገውም ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ተቀምጦ ፡ ጳውሎስን ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 7 ፤ በቀረበም ፡ ጊዜ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ የወረዱት ፡ አይሁድ ፡ ከበ፡ውት ፡ ቆሙ ፥ ይረቱበትም ፡ ዘንድ ፡ የማይችሉትን ፡ ብዙና ፡ ከባድ ፡ ክስ ፡ አነሡበት ፤

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 8 ፤ ጳውሎስም ፡ ሲሟገት ፦ የአይሁድን ፡ ሕግ ፡ ቢኾን ፡ መቅደስንም ፡ ቢኾን ፡ ቄሳርንም ፡ ቢኾን ፡ አንዳች ፡ ስንኳ ፡ አልበደልኹም ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 9 ፤ ፊስጦስ ፡ ግን ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ያሠኝ ፡ ዘንድ ፡ ወዶ ፡ ጳውሎስን ፦ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥተኽ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ከዚያው ፡ በፊቴ ፡ ትፋረድ ፡ ዘንድ ፡ ትወዳለኽን ፧ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 10 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፦ እፋረድበት ፡ ዘንድ ፡ በሚገ፡ባኝ ፡ በቄሳር ፡ ፍርድ ፡ ወንበር ፡ ፊት ፡ ቆሜያለኹ ። አንተው ፡ ደግሞ ፡ ፈጽመኽ ፡ እንደምታውቅ ፡ አይሁድን ፡ ምንም ፡ አልበደልኹም ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ በድዬ ፡ ወይም ፡ ሞት ፡ የሚገ፡ባውን ፡ ነገር ፡ አድርጌ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከሞት ፡ ልዳን ፡ አልልም ፤ እነዚህ ፡ የሚከሱኝ ፡ ክስ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ግን ፡ ለእነርሱ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ አይችልም ፤ ወደ ፡ ቄሳር ፡ ይግባኝ ፡ ብያለኹ ፡ አለ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ፊስጦስ ፡ ከአማካሪዎቹ ፡ ጋራ ፡ ተማክሮ ፦ ወደ ፡ ቄሳር ፡ ይግባኝ ፡ ብለኻል ፤ ወደ ፡ ቄሳር ፡ ትኼዳለኽ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 13 ፤ ከጥቂት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ንጉሡ ፡ አግሪጳ ፡ በርኒቄም ፡ ለፊስጦስ ፡ ሰላምታ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ወደ ፡ ቂሳርያ ፡ ወረዱ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 14 ፤ በዚያውም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ስለተቀመጡ ፡ ፊስጦስ ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ለንጉሡ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ገለጠ ። ፊልክስ ፡ አስሮ ፡ የተወው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ አለ ፤

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 15 ፤ በኢየሩሳሌምም ፡ ሳለኹ ፡ የካህናት ፡ አለቃዎችና ፡ የአይሁድ ፡ ሽማግሌዎች ፡ እፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ እየለመኑ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ አመለከቱኝ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 16 ፤ እኔም ፦ ተከሳሹ ፡ በከሳሾቹ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሳይቆም ፡ ለተከሰሰበትም ፡ መልስ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ፈንታ ፡ ሳያገኝ ፥ ማንንም ፡ ቢኾን ፡ አሳልፎ ፡ መስጠት ፡ የሮማውያን ፡ ሥርዐት ፡ አይደለም ፡ ብዬ ፡ መለስኹላቸው ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 17 ፤ ስለዚህም ፡ በዚህ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፥ ሳልዘገይ ፡ በማግስቱ ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ተቀምጬ ፡ ያን ፡ ሰው ፡ ያመጡት ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኹ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 18 ፤ ከሳሾቹም ፡ በቆሙ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ ያሰብኹትን ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ክስ ፡ ምንም ፡ አላመጡበትም ፤

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለገዛ ፡ ሃይማኖታቸውና ፡ ጳውሎስ ፦ ሕያው ፡ ነው ፡ ስለሚለው ፥ ስለሞተው ፥ ኢየሱስ ፡ ስለተባለው ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይከራከሩ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 20 ፤ እኔም ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ እንድመረምር ፡ አመንትቼ ፦ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኼደኽ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ከዚያ ፡ ልትፋረድ ፡ ትወዳለኽን ፧ አልኹት ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 21 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ አውግስጦስ ፡ ቄሳር ፡ እስኪቈርጥ ፡ ድረስ ፡ እንዲጠበቅ ፡ ይግባኝ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ቄሳር ፡ እስክሰደው ፡ ድረስ ፡ ይጠበቅ ፡ ዘንድ ፡ አዘዝኹ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 22 ፤ አግሪጳም ፡ ፊስጦስን ፦ ያንንስ ፡ ሰው ፡ እኔ ፡ ዳግም ፡ እኮ ፡ እሰማው ፡ ዘንድ ፡ እወድ ፡ ነበር ፡

አለው ። ርሱም ፦ ነገ ፡ ትሰማዋለኽ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 23 ፤ በነገውም ፡ አግሪጳና ፡ በርኒቄ ፡ በብዙ ፡ ግርማ ፡ መጥተው ፡ ከሻለቃዎችና ፡ ከከተማው ፡ ታላላቆች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ገቡ ፤ ፊስጦስም ፡ ባዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስን ፡ አመጡት ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 24 ፤ ፊስጦስም ፡ አለ ፦ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ እናንተም ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ያላችኹ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ እንዳይገባው ፡ እየጮኹ ፡ የአይሁድ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ በዚህም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የለመኑኝን ፡ ይህን ፡ ሰው ፡ ታዩታላችኹ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 25 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ሞት ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ እንዳላደረገ ፡ አስተዋልኹ ፥ ርሱም ፡ ወደ ፡ አውግስጦስ ፡ ይግባኝ ፡ ስለ ፡ አለ ፡ እሰደው ፡ ዘንድ ፡ ቈረጥኹ ።

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 26 ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ ወደ ፡ ጌታዬ ፡ የምጽፈው ፡ ርግጥ ፡ ነገር ፡ የለኝም ፤ ስለዚህ ፥ ከተመረመረ ፡ በኋላ ፡ የምጽፈውን ፡ ነገር ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ በፊታችኹ ፡ ይልቁንም ፡ በፊትኽ ፥ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፥ አመጣኹት ፤

ሐዋ. ፡ 25 ፡ 27 ፤ እስረኛ ፡ ሲላክ ፡ የተከሰሰበትን ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ አለማመልከት ፡ ሞኝነት ፡ መስሎኛልና ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 26 ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 1 ፤ አግሪጳም ፡ ጳውሎስን ፦ ስለ ፡ ራስኽ ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ ተፈቅዶልኻል ፡ አለው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ እጁን ፡ ዘርግቶ ፡ መለሰ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 2-3 ፤ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፥ የአይሁድን ፡ ሥርዐት ፡ ክርክርንም ፡ ኹሉ ፡ አጥብቀኽ ፡ ዐውቀኻልና ፥ በአይሁድ ፡ በተከሰስኹበት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ዛሬ ፡ በፊትኽ ፡ ስለምመልስ ፥ ራሴን ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ ተመረቀ ፡ አድርጌ ፡ እቈጥረዋለኹ ፤ ስለዚህ ፥ በትዕግሥት ፡ ትሰማኝ ፡ ዘንድ ፡ እለምንኻለኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 4 ፤ ከመገርመሪያ ፡ አንሥቶ ፡ በሕዝቤ ፡ መካከል ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የኾነውን ፥ ከታናሽነቴ ፡ ገምሬ ፡ የኖርኹትን ፡ ኑሮዬን ፡ አይሁድ ፡ ኹሉ ፡ ያውቃሉ ፤

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 5 ፤ ሊመሰክሩ ፡ ይወዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ በአምልኳችን ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ሕግን ፡ በመጠንቀቅ ፡ እንደሚተጋ ፡ ወገን ፡ ፈሪሳዊ ፡ ኾኜ ፡ እንደኖርኹ ፡ ከጥንት ፡ ገምረው ፡ ዐውቀውኛልና ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 6 ፤ አኹንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ለአባቶቻችን ፡ ስለተሰጠው ፡ ስለተስፋ ፡ ቃል ፡ አለኝታ ፡ ልፋረድ ፡ ቆሜያለኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 7 ፤ ወደዚህም ፡ ወደ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ወገኖቻችን ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በትጋት ፡ እያመለኩ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ አለኝታ ፡ አላቸው ፤ ስለዚህም ፡ አለኝታ ፥ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፥ ከአይሁድ ፡ እከሰሳለኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 8 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙታንን ፡ የሚያስነሣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የማይታመን ፡ ነገር ፡ ኾኖ ፡ ይቈጠራል ፧

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 9 ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ የናዝሬቱን ፡ የኢየሱስን ፡ ስም ፡ የሚቃወም ፡ እጅግ ፡ ነገር ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባኝ ፡ ይመስለኝ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 10 ፤ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ አደረግኹት ፤ ከካህናት ፡ አለቃዎችም ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብዬ ፡ እኔ ፡ ከቅዱሳን ፡ ብዙዎችን ፡ በወህኒ ፡ አሳሰርኋቸው ፥ ሲገድሏቸውም ፡ ዐብሬ ፡ ተቸኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 11 ፤ በምኩራብም ፡ ኹሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እየቀጣኹ ፡ ይሰድቡት ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ አልኋቸው ፤ ያለልክ ፡

ስቈጣባቸውም ፡ እስከውጭ ፡ አገር ፡ ከተማዎች ፡ ድረስ ፡ እንኳ ፡ አሳድድ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 12 ፤ ስለዚህም ፡ ነገ ፡ ከካህናት ፡ አለቃዎች ፡ ሥልጣንና ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀብዬ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ስኼድ ፥

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 13 ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ በመንገድ ፡ ሳለኹ ፡ እኩል ፡ ቀን ፡ ሲኾን ፡ በዙሪያዬና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በኼዱት ፡ ዙሪያ ፡ ከፀሓይ ፡ ብሩህነት ፡ የበለጠ ፡ ብርሃን ፡ ከሰማይ ፡ ሲበራ ፡ አየኹ ፤

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 14 ፤ ኹላችንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ በወደቅን ፡ ጊዜ ፦ ሳውል ፡ ሳውል ፥ ስለ ፡ ምን ፡ ታሳድደኛለኽ ፧ የመውጊያውን ፡ ብረት ፡ ብትቃወም ፡ ለአንተ ፡ ይብስብኻል ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ ሲናገረኝ ፡ ሰማኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 15 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ማን ፡ ነኽ ፧ አልኹ ። ርሱም ፡ አለኝ ፦ አንተ ፡ የምታሳድደኝ ፡ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ ነኝ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተነሣና ፡ በእግርኽ ፡ ቁም ፤ ስለዚህ ፥ እኔን ፡ ባየኽበት ፡ ነገር ፡ ለአንተም ፡ በምታይበት ፡ ነገር ፡ አገልጋይና ፡ ምስክር ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ልሾምኽ ፡ ታይቼልኻለኹና ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 17-18 ፤ የኀጢአትንም ፡ ስርየት ፡ በእኔም ፡ በማመን ፡ በተቀደሱት ፡ መካከል ፡ ርስትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፥ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከሰይጣንም ፡ ሥልጣን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ እንዲሉ ፡ ዐይናቸውን ፡ ትከፍት ፡ ዘንድ ፥ ከሕዝቡና ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ከምልክኽ ፡ ከአሕዛብ ፡ አድንኻለኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 19 ፤ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ ከሰማይ ፡ የታየኝን ፡ ራእይ ፡ እምቢ ፡ አላልኹም ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድሜ ፡ በደማስቆ ፡ ላሉት ፡ በኢየሩሳሌምም ፡ በይሁዳም ፡ አገር ፡ ኹሉ ፡ ለአሕዛብም ፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድና ፡ ለንስሓ ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ እያደረጉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወር ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ተናገርኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ አይሁድ ፡ በመቅደስ ፡ ያዙኝ ፥ ሊገድሉኝም ፡ ሞከሩ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 22-23 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ረድኤት ፡ ተቀብዬ ፡ ለታናሹም ፡ ለታላቁም ፡ ስመሰክር ፡ እስከዚች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ቆሜያለኹ ፤ ነቢያትና ፡ ሙሴ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፥ ክርስቶስ ፡ መከራን ፡ እንዲቀበል ፡ በሙታንም ፡ ትንሣኤ ፡ ለሕዝብና ፡ ለአሕዛብ ፡ ብርሃንን ፡ በመገሥመሪያ ፡ ሊሰብክ ፡ እንዳለው ፥ ከተናገሩት ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የተናገርኹት ፡ የለም ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 24 ፤ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ሲመልስ ፡ ፊስጦስ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ ጳውሎስ ፡ ሆይ ፥ አብደኻል ፡ እኮ ፤ ብዙ ፡ ትምህርትኽ ፡ ወደ ፡ እብደት ፡ ያዞርኻል ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 25 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ ክቡር ፡ ፊስጦስ ፡ ሆይ ፥ የእውነትንና ፡ የአእምሮን ፡ ነገር ፡ እናገራለኹ ፡ እንጂ ፡ እብደትስ ፡ የለብኝም ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 26 ፤ በርሱ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ በግልጥ ፡ የምናገረው ፡ ንጉሥ ፡ ይህን ፡ ነገር ፡ ያውቃል ፤ ከዚህ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ እንዳይሰወርበት ፡ ተረድቻለኹና ፤ ይህ ፡ በስውር ፡ የተደረገ ፡ አይደለምና ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 27 ፤ ንጉሥ ፡ አግሪጳ ፡ ሆይ ፥ ነቢያትን ፡ ታምናለኽን ፧ እንድታምናቸው ፡ ዐውቃለኹ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 28 ፤ አግሪጳም ፡ ጳውሎስን ፦ በጥቂት ፡ ክርስቲያን ፡ ልታደርገኝ ፡ ትወዳለኽ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 29 ፤ ጳውሎስም ፦ በጥቂት ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በብዙ ፥ አንተ ፡ ብቻ ፡ አይደለኽም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዛሬ ፡ የሚሰሙኝ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ እስራቴ ፡ በቀር ፥ እንደ ፡ እኔ ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡

እለምናለኹ ፡ አለው ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 30 ፤ ንጉሡም ፡ አገረ ፡ ገዢውም ፡ በርኒቄም ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩት ፡ ተነሡ ፥

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 31 ፤ ፈቀቅ ፡ ብለውም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ እንኳንስ ፡ ለሞት ፡ ለእስራትም ፡ የሚገባ ፡ ምንም ፡ አላደረገ ፡ ብለው ፡ ተነጋገሩ ።

ሐዋ. ፡ 26 ፡ 32 ፤ አግሪጳም ፡ ፈስጦስን ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ እኮ ፡ ወደ ፡ ቄሳር ፡ ይግባኝ ፡ ባይል ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይቻል ፡ ነበር ፡ አለው ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 27 ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ ኢጣሊያም ፡ በመርከብ ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ በተቈረጠ ፡ ጊዜ ፥ ጳውሎስንና ፡ ሌላዎችን ፡ እስረኞች ፡ ከአውግስጦስ ፡ ጭፍራ ፡ ለነበረ ፡ ዩልዮስ ፡ ለሚሉት ፡ ለመቶ ፡ አለቃ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጧቸው ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 2 ፤ በእስያም ፡ ዳርቻ ፡ ወዳሉ ፡ ስፍራዎች ፡ ይኼድ ፡ ዘንድ ፡ ባለው ፡ በአድራሚጢስ ፡ መርከብ ፡ ገብተን ፡ ተነሣን ፤ የመቄዶንያም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ የተሰሎንቄው ፡ አርስጥሮኮስ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 3 ፤ በነገውም ፡ ወደ ፡ ሲዶና ፡ ስንደርስ ፡ ዩልዮስ ፡ ለጳውሎስ ፡ ቸርነት ፡ አድርጎ ፡ ርዳታቸውን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ወዳጆቹ ፡ እንዲኼድ ፡ ፈቀደለት ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 4 ፤ ከዚያም ፡ ተነሥተን ፡ ነፋሱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ነበረና ፡ በቆጵሮስ ፡ ተተግነን ፡ ኼድን ፤

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 5 ፤ በኪልቅያና ፡ በጵንፍልያም ፡ አጠገብ ፡ ያለውን ፡ ባሕር ፡ ከተሻገርን ፡ በኧላ ፡ በሉቅያ ፡ ወዳለ ፡ ወደ ፡ ሙራ ፡ ደረስን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 6 ፤ የመቶ ፡ አለቃውም ፡ በዚያ ፡ ወደ ፡ ኢጣሊያ ፡ የሚኼድ ፡ የእስክንድርያውን ፡ መርከብ ፡ አግኝቶ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ አገባን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 7 ፤ ብዙ ፡ ቀንም ፡ እያዘገምን ፡ ኼደን ፡ በጭንቅ ፡ ወደቀኒዶስ ፡ አንጻር ፡ ደረስን ፤ ነፋስም ፡ ስለ ፡ ከለከለን ፡ በቀርጤስ ፡ ተተግነን ፡ በሰልሙና ፡ አንጻር ፡ ኼድን ፤

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 8 ፤ በጭንቅም ፡ ጥግ ፡ ጥጉን ፡ አልፈን ፡ ለላሲያ ፡ ከተማ ፡ ወደቀረበች ፡ መልካም ፡ ወደብ ፡ ወደሚሏት ፡ ስፍራ ፡ መጣን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 9 ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ካለፈ ፡ በኧላ ፥ የጦም ፡ ወራት ፡ አኹን ፡ ዐልፎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በመርከብ ፡ ለመኼድ ፡ አኹን ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበርና ፥ ጳውሎስ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 10 ፤ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ጕዞ ፡ በጥፋትና ፡ በብዙ ፡ ጕዳት ፡ እንዲኾን ፡ አያለኹ ፤ ጥፋቱም ፡ በገዛ ፡ ሕይወታችን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በጭነቱና ፡ በመርከቡ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ መከራቸው ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 11 ፤ የመቶ ፡ አለቃው ፡ ግን ፡ ጳውሎስ ፡ ከተናገረው ፡ ይልቅ ፡ የመርከብ ፡ መሪውንና ፡ የመርከቡን ፡ ባለቤት ፡ ያምን ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 12 ፤ ያም ፡ ወደብ ፡ ይከርሙበት ፡ ዘንድ ፡ የማይመች ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የሚበዙቱ ፡ ቢቻላቸው ፡ በሰሜንና ፡ በደቡብ ፡ ምዕራብ ፡ ትይዩ ፡ ወዳለው ፡ ፍንቄ ፡ ወደሚሉት ፡ ወደቀርጤስ ፡ ወደብ ፡ ደርሰው ፡ ይከርሙ ፡ ዘንድ ፥ ከዚያ ፡ እንዲነሡ ፡ መከሩ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 13 ፤ ልከኛም ፡ የደቡብ ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፥ እንዳሰቡት ፡ የኾነላቸው ፡ መስሏቸው ፡ ተነሡ ፡ በቀርጤስም ፡ አጠገብ ፡ ጥግ ፡ ጥጉን ፡ ዐለፉ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እጅግ ፡ ሳይዘገይ ፡ አውራቂስ ([299]) ፡ የሚሉት ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡ ከዚያ ፡ ወረደባቸው ፤

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 15 ፤ መርከቡም ፡ ተነጥቆ ፡ ነፋሱን ፡ ሲቃወም ፡ መኼድ ፡ ስላልቻለ ፡ ለቀነው ፡ ተነዳን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 16 ፤ ቄዳ ፡ በሚሏትም ፡ ደሴት ፡ በተተገኑ ፡ ጊዜ ፡ ታንኳዩቱን ፡ ለመግዛት ፡ በጭንቅ ፡ ቻልን ፤

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ ላይም ፡ ካወጧት ፡ በኋላ ፡ መርከቡን ፡ በገመድ ፡ አስታጥቀው ፡ አጸኑ ፤ ስርቲስም ፡ ወደሚሉት ፡ ወደ ፡ አሸዋ ፡ እንዳይወድቁ ፡ ፈርተው ፡ ሸራውን ፡ አውርደው ፡ እንዲሁ ፡ ተነዱ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 18 ፤ ነፋሱም ፡ በርትቶ ፡ ሲያስጨንቀን ፡ በማግስቱ ፡ ከጭነቱ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይጥሉ ፡ ነበር ፥

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 19 ፤ በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ የመርከቡን ፡ ዕቃ ፡ በእጃችን ፡ ወረወርን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 20 ፤ ብዙ ፡ ቀንም ፡ ፀሓይን ፡ ከዋክብትንም ፡ ሳናይ ፡ ትልቅ ፡ ነፋስም ፡ ሲበረታብን ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እንድናለን ፡ የማለት ፡ ተስፋ ፡ ኹሉ ፡ ተቈረጠ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 21 ፤ ሳይበሉም ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፥ ያን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በመካከላቸው ፡ ቆሞ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፦ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ሰምታችኹኝ ፡ በኾነ ፡ ኖሮ ፡ ከቀርጤስ ፡ እንዳትነሡ ፡ ይህንም ፡ ጥፋትና ፡ ጕዳት ፡ እንዳታገኙ ፡ ይገባችኹ ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 22 ፤ አኹንም ፦ አይዟችኹ ፡ ብዬ ፡ እመክራችኋለኹ ፤ ይህ ፡ መርከብ ፡ እንጂ ፡ ከእናንተ ፡ አንድ ፡ ነፍስ ፡ እንኳ ፡ አይጠፋምና ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 23 ፤ የርሱ ፡ የምኾንና ፡ ደግሞ ፡ የማመልከው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ በአጠገቤ ፡ ቆሞ ፡ ነበርና ፥ ርሱም ፦

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 24 ፤ ጳውሎስ ፡ ሆይ ፥ አትፍራ ፤ በቄሳር ፡ ፊት ፡ ልትቆም ፡ ይገባኻል ፤ እንሆም ፥ እግዚአብሔር ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የሚኼዱትን ፡ ኹሉ ፡ ሰጥቶኻል ፡ አለኝ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ አይዟችኹ ፤ እንደ ፡ ተናገረኝ ፡ እንዲሁ ፡ እንዲኾን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምናለኹና ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 26 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደ ፡ አንዲት ፡ ደሴት ፡ እንድንወድቅ ፡ ያስፈልገናል ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 27 ፤ በዐሥራ ፡ አራተኛውም ፡ ሌሊት ፡ በአድርያ ፡ ባሕር ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡ ስንነዳ ፥ መርከበኞች ፡ በእኩለ ፡ ሌሊት ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ምድር ፡ የቀረቡ ፡ መሰላቸው ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 28 ፤ መለኪያ ፡ ገመድም ፡ ቢጥሉ ፡ ኻያ ፡ በሰው ፡ ቁመት ፡ አገኙ ፡ ጥቂትም ፡ ቈይተው ፡ ኹለተኛ ፡ ቢጥሉ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ በሰው ፡ ቁመት ፡ አገኙ ፤

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 29 ፤ ድንጋያማም ፡ ወደ ፡ ኾነ ፡ ስፍራ ፡ እንዳይወድቁ ፡ ፈርተው ፥ ከመርከቡ ፡ በስተኋላ ፡ አራት ፡ መልሕቅ ፡ አወረዱ ፥ ቀንም ፡ እንዲኾን ፡ ተመኙ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 30 ፤ መርከበኞቹም ፡ ከመርከቡ ፡ ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡ ፈልገው ፡ ከመርከቡ ፡ በስተፊት ፡ መልሕቅ ፡ መጣል ፡ እንዳላቸው ፡ አመካኝተው ፡ ታንኳዩቱን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ባወረዱ ፡ ጊዜ ፥

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 31 ፤ ጳውሎስ ፡ ለመቶ ፡ አለቃውና ፡ ለወታደሮቹ ፦ እነዚህ ፡ በመርከቡ ፡ ካልቈዩ ፡ እናንተ ፡ ትድኑ ፡

---

299 ጽር. ፥ ሄውሮክሊዶን ፡ (ከ.ወ.ክ. ፥ ገ.208 ፣ ገ.507)

ዘንድ ፡ አትችሉም ፡ አላቸው ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 32 ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ወታደሮቹ ፡ የታንኳዩቱን ፡ ገመድ ፡ ቈርጠው ፡ ትወድቅ ፡ ዘንድ ፡ ተዉአት ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 33 ፤ ቀንም ፡ ሲነጋ ፡ ጳውሎስ ፡ ምግብ ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ ይለምን ፡ ነበር ፥ እንዲህም ፡ አላቸው ፦ እየጠበቃችኹ ፡ ምንም ፡ ሳትቀበሉ ፡ ጦማችኹን ፡ ከሰነበታችኹ ፡ ዛሬ ፡ ዐሥራ ፡ አራተኛ ፡ ቀናችኹ ፡ ነው ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 34 ፤ ስለዚህ ፡ ምግብ ፡ ትበሉ ፡ ዘንድ ፡ እለምናችኋለኹ ፤ ይህ ፡ ለደኅንነታችኹ ፡ ይኾናልና ፤ ከእናንተ ፡ ከአንዱ ፡ የራስ ፡ ጠጕር ፡ እንኳ ፡ አትጠፋምና ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 35 ፤ ይህንም ፡ ብሎ ፡ እንጀራን ፡ ይዞ ፡ በኹሉ ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፥ ቈርሶም ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ ገመረ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 36 ፤ ኹሉም ፡ ተጽናንተው ፡ ራሳቸው ፡ ደግሞ ፡ ምግብ ፡ ተቀበሉ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 37 ፤ በመርከቡም ፡ ያለን ፡ ኹላችን ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ ሰባ ፡ ስድስት ፡ ነፍስ ፡ ነበርን ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 38 ፤ በልተውም ፡ በጠገቡ ፡ ጊዜ ፡ ስንዴውን ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ እየጣሉ ፡ መርከቡን ፡ አቃለሉት ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 39 ፤ በነጋም ፡ ጊዜ ፡ ምድሩን ፡ አላወቁትም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የአሸዋ ፡ ዳር ፡ ያለውን ፡ የባሕር ፡ ስርጥ ፡ ተመለከቱ ፥ ቢቻላቸውም ፡ መርከቡን ፡ ወደዚያ ፡ ይገፉ ፡ ዘንድ ፡ ቈረጡ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 40 ፤ መልሕቆቹንም ፡ ፈትው ፡ በባሕር ፡ ተዉአቸው ፥ ያን ፡ ጊዜም ፡ የመቅዘፊያውን ፡ ማሰሪያ ፡ ፈቱት ፤ ታናሹንም ፡ ሸራ ፡ ለነፋስ ፡ ከፍ ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ዳር ፡ አቅንተው ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ገመሩ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 41 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹለት ፡ ባሕር ፡ በተገናኙበት ፡ ስፍራ ፡ ወድቀው ፡ መርከቡን ፡ በዲብ ፡ ላይ ፡ ነዱ ፤ በስተፊቱም ፡ ተተክሎ ፡ የማይነቃነቅ ፡ ኾነ ፥ በስተኋላው ፡ ግን ፡ ከማዕበሉ ፡ ግፊያ ፡ የተነሣ ፡ ይሰበር ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 42 ፤ ወታደሮቹም ፡ ከእስረኞች ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ዋኝቶ ፡ እንዳያመልጥ ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ተማከሩ ።

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 43 ፤ የመቶ ፡ አለቃው ፡ ግን ፡ ጳውሎስን ፡ ያድነው ፡ ዘንድ ፡ ዐስቦ ፡ ምክራቸውን ፡ ከለከለ ፤ ዋና ፡ የሚያውቁትም ፡ ከመርከብ ፡ ራሳቸውን ፡ እየወረወሩ ፡ አስቀድመው ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፥

ሐዋ. ፡ 27 ፡ 44 ፤ የቀሩትም ፡ እኩሌታዎቹ ፡ በሳንቃዎች ፡ ላይ ፡ እኩሌታዎቹም ፡ በመርከቡ ፡ ስባሪ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። እንዲሁም ፡ ኹሉ ፡ በደኅና ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ደረሱ ።

የሐዋርያት ፡ ሥራ ፥ ምዕራፍ ፡ 28 ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 1 ፤ በደኅና ፡ ከደረስን ፡ በኋላ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ደሴቲቱ ፡ መላጥያ ፡ እንድትባል ፡ ዐወቅን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 2 ፤ አረማውያንም ፡ የሚያስገርም ፡ ቸርነት ፡ አደረጉልን ፤ ዝናብ ፡ ስለ ፡ ኾነም ፡ ስለ ፡ ብርዱም ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ ኹላችንን ፡ ተቀበሉን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 3 ፤ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ጭራሮ ፡ አከማችቶ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ሲጨምር ፥ እፍኝት ፥ ከሙቀት ፡ የተነሣ ፥ ወጥታ ፡ እጁን ፡ ነደፈችው ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 4 ፤ አረማውያንም ፡ እባብ ፡ በእጁ ፡ ተንጠልጥላ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፦ ይህ ፡ ሰው ፡ በርግጥ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፥ ከባሕርም ፡ ስንኳ ፡ በደኅና ፡ ቢወጣ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ በሕይወት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ አልተወውም ፡ አሉ ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 5 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ እባቢቱን ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ አራገፋት ፥ አንዳችም ፡ አልጐዳችውም ፤

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 6 ፤ እነርሱም ፦ ሊያብጥ ፡ ወይም ፡ ወዲያው ፡ ሞቶ ፡ ሊወድቅ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይጠባበቁት ፡ ነበር ። ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሲጠባበቁ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ የሚያስገርም ፡ ነገር ፡ ምንም ፡ ባላዩ ፡ ጊዜ ፦ ይህስ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ ብለው ፥ ዐሳባቸውን ፡ ለወጡ ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 7 ፤ በዚያም ፡ ስፍራ ፡ አጠገብ ፡ ፑፕልዮስ ፡ የሚሉት ፡ የደሴት ፡ አለቃ ፡ መሬት ፡ ነበረ ፥ ርሱም ፡ እንግድነት ፡ ተቀብሎን ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ በፍቅር ፡ አሳደረን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 8 ፤ የፑፕልዮስም ፡ አባት ፡ በንዳድና ፡ በተቅማጥ ፡ ታሞ ፡ ተኝቶ ፡ ነበር ፤ ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ገብቶ ፡ ጸለየለት ፥ እጁንም ፡ በላዩ ፡ ጭኖ ፡ ፈወሰው ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 9 ፤ ይህም ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ የቀሩት ፡ ደግሞ ፡ በደሴቲቱ ፡ ደዌ ፡ የነበረባቸው ፡ እየመጡ ፡ ተፈወሱ ፤

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 10 ፤ በብዙ ፡ ክብርም ፡ ደግሞ ፡ አከበሩን ፥ በተነሣንም ፡ ጊዜ ፡ በመርከብ ፡ ላይ ፡ የሚያስፈልገንን ፡ ነገር ፡ አኖሩልን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 11 ፤ ከሦስት ፡ ወርም ፡ በኋላ ፡ በደሴቲቱ ፡ ከርሞ ፡ በነበረው ፡ በእስክንድርያው ፡ መርከብ ፡ ተነሣን ፥ በርሱም ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ዐላማ ፡ ነበረበት ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 12 ፤ ወደ ፡ ሰራኩስም ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተቀመጥን ፤

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 13 ፤ ከዚያም ፡ እየተዛወርን ፡ ወደ ፡ ሬጊዩም ፡ ደረስን ። ካንድ ፡ ቀን ፡ በኋላም ፡ የደቡብ ፡ ነፋስ ፡ በነፈሰ ፡ ጊዜ ፡ በኹለተኛው ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ ፑቲዮሉስ ፡ መጣን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 14 ፤ በዚያም ፡ ወንድሞችን ፡ አግኝተን ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ እንድንቀመጥ ፡ ለመኑን ፤ እንዲሁም ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ መጣን ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 15 ፤ ከዚያም ፡ ወንድሞች ፡ ስለኛ ፡ ሰምተው ፡ እስከ ፡ አፍዩስ ፡ ፋሩስና ፡ ሦስት ፡ ማደሪያ ፡ እስከሚባለው ፡ ሊቀበሉን ፡ ወጡ ፥ ጳውሎስም ፡ ባያቸው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፡ ልቡም ፡ ተጽናና ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ሮሜም ፡ በገባን ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ከሚጠብቀው ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ ለብቻው ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ተፈቀደለት ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 17 ፤ ከሦስት ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ የአይሁድን ፡ ታላላቆች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ጠራ ፤ በተሰበሰቡም ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፦ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ሕዝቡን ፡ ወይም ፡ የአባቶችን ፡ ሥርዐት ፡ የሚቃወም ፡ አንዳች ፡ ሳላደርግ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ ታሰርኹ ፡ በሮማውያን ፡ እጅ ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡኝ ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 18 ፤ እነርሱም ፡ መርምረው ፡ ለሞት ፡ የሚገባ ፡ ምክንያት ፡ ስላልነበረብኝ ፡ ሊፈቱኝ ፡ ዐሰቡ ፤

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 19 ፤ አይሁድ ፡ ግን ፡ በተቃወሙ ፡ ጊዜ ፥ ወደ ፡ ቄሳር ፡ ይግባኝ ፡ እንድል ፡ ግድ ፡ ኾነብኝ ፡ እንጂ ፡ ሕዝቤን ፡ የምከስበት ፡ ነገር ፡ ኖሮኝ ፡ አይደለም ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 20 ፤ ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ አያችኹና ፡ እነግራችኹ ፡ ዘንድ ፡ ጠራኋችኹ ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ተስፋ ፡ ይህን ፡ ሰንሰለት ፡ ለብሻለኹና ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 21 ፤ እነርሱም ፦ እኛ ፡ ከይሁዳ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ደብዳቤ ፡ አልተቀበልንም ፥ ከወንድሞችም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላወራልንም ፡ ወይም ፡ አልተናገረብኽም ።

ሐዋ. ፡ 28 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለዚህ ፡ ወገን ፡ በየስፍራው ፡ ኹሉ ፡ እንዲቃወሙ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡

ታውቋልና ፥ የምታስበውን ፡ ከአንተ ፡ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡ እንፈቅዳለን ፡ አሉት ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 23 ፤ ቀንም ፡ ቀጥረውለት ፡ ብዙ ፡ ኾነው ፡ ወደ ፡ መኖሪያው ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ መጡ ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ መንግሥትም ፡ እየመሰከረ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስም ፡ ከሙሴ ፡ ሕግና ፡ ከነቢያት ፡ ጠቅሶ ፡ እያስረዳቸው ፥ ከጧት ፡ ገምሮ ፡ እስከ ፡ ማታ ፡ ድረስ ፡ ይገልጥላቸው ፡ ነበር ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 24 ፤ እኩሌታዎቹም ፡ የተናገረውን ፡ አመኑ ፥ እኩሌታዎቹ ፡ ግን ፡ አላመኑም ፤

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 25 ፤ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ባልተስማሙ ፡ ጊዜ ፥ ጳውሎስ ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ኼዱ ፤ እንዲህም ፡ አለ ፦ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በነቢዩ ፡ በኢሳይያስ ፡ ለአባቶቻችን ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 26 ፤ ወደዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ኺድና ፦ መስማትን ፡ ትሰማላችኹና ፡ አታስተውሉም ፥ ማየትንም ፡ ታያላችኹና ፡ አትመለከቱም ፤

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 27 ፤ በዐይናቸው ፡ እንዳያዩ ፡ በጐሯቸው ፡ እንዳይሰሙ ፡ በልባቸውም ፡ እንዳያስተውሉ ፡ ተመልሰውም ፡ እንዳልፈውሳቸው ፥ የዚህ ፡ ሕዝብ ፡ ልብ ፡ ደንድኗል ፡ ጐሯቸውም ፡ ደንቍሯል ፡ ዐይናቸውንም ፡ ጨፍነዋል ፡ በላቸው ፡ ሲል ፡ መልካም ፡ ተናገረ ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 28 ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ደኅንነት ፡ ለአሕዛብ ፡ እንደ ፡ ተላከ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይኹን ፤ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይሰሙታል ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 29 ፤ ይህንም ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እጅግ ፡ እየተከራከሩ ፡ ኼዱ ።

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 30 ፤ ጳውሎስም ፡ በተከራየው ፡ ቤት ፡ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ሙሉ ፡ ተቀመጠ ፥ ወደ ፡ ርሱም ፡ የሚመጡትን ፡ ኹሉ ፡ ይቀበል ፡ ነበር ፤

ሐዋ. ፥ 28 ፥ 31 ፤ ማንም ፡ ሳይከለክለው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እየሰበከ ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እጅግ ፡ ገልጦ ፡ ያስተምር ፡ ነበር ። ❖

የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደሮሜ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ ሐዋርያ ፡ ሊኾን ፡ የተጠራ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ጳውሎስ ፥ በነቢያቱ ፡ አፍ ፣ በቅዱሳን ፡ መጻሕፍት ፡ አስቀድሞ ፡ ተስፋ ፡ ለሰጠው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ ተለየ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 3-4 ፤ ይህም ፡ ወንጌል ፡ በሥጋ ፡ ከዳዊት ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፥ እንደ ፡ ቅድስና ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ ከሙታን ፡ መነሣት ፡ የተነሣ ፡ በኀይል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኾኖ ፡ ስለተገለጠ ፣ ስለ ፡ ልጁ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በርሱም ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ በአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ ከእምነት ፡ የሚነሣ ፡ መታዘዝ ፡ እንዲገኝ ፡ ጸጋንና ፡ ሐዋርያነትን ፡ ተቀበልን ፤

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በእነርሱም ፡ መካከል ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልትኾኑ ፡ የተጠራችኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ናችኹ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ለተወደዳችኹና ፡ ቅዱሳን ፡ ልትኾኑ ፡ ለተጠራችኹ ፡ በሮሜ ፡ ላላችኹት ፡ ኹሉ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እምነታችኹ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ተሰማች ፡ አስቀድሜ ፡ ስለ ፡ ኹላችኹ ፡ አምላኬን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አመሰግናለኹ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 9-10 ፤ በልጁ ፡ ወንጌል ፡ በመንፈሴ ፡ የማገለግለው ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ፡ ነውና ፤ ምናልባት ፡ ብዙ ፡ ቈይቼ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አኹን ፡ እንድመጣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ መንገዴን ፡ እንዲያቀናልኝ ፡ እየለመንኹ ፡ ኹልጊዜ ፡ ስጸልይ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ሳላቋርጥ ፡ አሳስባለኹ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሳዊ ፡ ስጦታ ፡ እንዳካፍላችኹ ፡ ላያችኹ ፡ እናፍቃለኹና ፤

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ይህንም ፡ ማለቴ ፡ በመካከላችን ፡ ባለች ፡ በእናንተና ፡ በእኔ ፡ እምነት ፡ ዐብረን ፡ በእናንተ ፡ እንድንጽናና ፡ ነው ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በሌላዎቹ ፡ አሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእናንተም ፡ ፍሬ ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ እንዳሰብኹ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ተከለከልኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ለግሪክ ፡ ሰዎችና ፡ ላልተማሩም ፥ ለጥበበኞችና ፡ ለማያስተውሉም ፡ ዕዳ ፡ አለብኝ ፤

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ስለዚህም ፡ በሚቻለኝ ፡ መጠን ፡ በሮሜ ፡ ላላችኹ ፡ ለእናንተ ፡ ደግሞ ፡ ወንጌልን ፡ ልሰብክ ፡ ተዘጋጅቻለኹ ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ በወንጌል ፡ አላፍርምና ፤ አስቀድሞ ፡ ለአይሁዳዊ ፡ ደግሞም ፡ ለግሪክ ፡ ሰው ፥ ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ለማዳን ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ጻድቅ ፡ በእምነት ፡ ይኖራል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ከእምነት ፡ ወደ ፡

እምነት ፡ በርሱ ፡ ይገለጣልና ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እውነትን ፡ በዐመፃ ፡ በሚከለክሉ ፡ ሰዎች ፡ በኀጢአተኝነታቸውና ፡ በዐመፃቸው ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ከሰማይ ፡ ይገለጣልና ፤

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ገለጠላቸው ፥ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊታወቅ ፡ የሚቻለው ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ግልጥ ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 20-21 ፤ የማይታየው ፡ ባሕርይ ፥ ርሱም ፡ የዘለዓለም ፡ ኀይሉ ፥ ደግሞም ፡ አምላክነቱ ፥ ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ ዠምሮ ፡ ከተሠሩት ፡ ታውቆ ፥ ግልጥ ፡ ኾኖ ፡ ይታያልና ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያወቁ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርነቱ ፡ መጠን ፡ ስላላከበሩትና ፡ ስላላመሰገኑት ፡ የሚያመካኙት ፡ ዐጡ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዐሳባቸው ፡ ከንቱ ፡ ኾኑ ፥ የማያስተውለውም ፡ ልባቸው ፡ ጨለመ ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ጥበበኞች ፡ ነን ፡ ሲሉ ፡ ደንቈሮ ፡ ኾኑ ፥

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ የማይጠፋውንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ በሚጠፋ ፡ ሰውና ፡ በወፎች ፡ አራት ፡ እግር ፡ ባላቸውም ፡ በሚንቀሳቀሱትም ፡ መልክ ፡ መስለው ፡ ለወጡ ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ስለዚህ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሥጋቸውን ፡ ሊያዋርዱ ፥ እግዚአብሔር ፡ በልባቸው ፡ ፍትወት ፡ ወደ ፡ ርኩስነት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ይህም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እውነት ፡ በውሸት ፡ ስለ ፡ ለወጡ ፥ በፈጣሪም ፡ ፈንታ ፡ የተፈጠረውን ፡ ስላመለኩና ፡ ስላገለገሉ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ለዘለዓለም ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ አሜን ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ ለሚያስነውር ፡ ምኞት ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤ ሴቶቻቸውም ፡ ለባሕርያቸው ፡ የሚጋፉትን ፡ ሥራ ፡ ለባሕርያቸው ፡ በማይጋፉት ፡ ለወጡ ፤

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ እንዲሁም ፡ ወንዶች ፡ ደግሞ ፡ ለባሕርያቸው ፡ የሚጋፉትን ፡ ሴቶችን ፡ መገናኘት ፡ ትተው ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በፍትወታቸው ፡ ተቃጠሉ ፤ ወንዶችም ፡ በወንዶች ፡ ነውር ፡ አድርገው ፥ በስሕተታቸው ፡ የሚገባውን ፡ ብድራት ፡ በራሳቸው ፡ ተቀበሉ ።

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ለማወቅ ፡ ባልወደዱት ፡ መጠን ፥ እግዚአብሔር ፡ የማይገባውን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለማይረባ ፡ አእምሮ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፤

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ዐመፃ ፡ ኹሉ ፥ ግፍ ፥ መመኘት ፥ ክፋት ፡ ሞላባቸው ፤ ቅናትን ፥ ነፍስ ፡ መግደልን ፥ ክርክርን ፥ ተንኰልን ፥ ክፉ ፡ ጠባይን ፡ ተሞሉ ፤ የሚያሾከሹኩ ፥

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ ሐሜተኞች ፥ አምላክን ፡ የሚጠሉ ፥ የሚያንገላቱ ፥ ትዕቢተኞች ፥ ትምክሕተኞች ፥ ክፋትን ፡ የሚፈላለጉ ፥ ለወላጆቻቸው ፡ የማይታዘዙ ፥

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 31 ፤ የማያስተውሉ ፥ ውል ፡ የሚያፈርሱ ፥ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፥ ምሕረት ፡ ያጡ ፡ ናቸው ፤

ሮሜ. ፡ 1 ፡ 32 ፤ እንደነዚህ ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሞት ፡ ይገባቸዋል ፡ የሚለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ እያወቁ ፡ እነዚህን ፡ ከሚያደርጉ ፡ ጋራ ፡ ይስማማሉ ፡ እንጂ ፡ አድራጊዎች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፥ አንተ ፡ የምትፈርድ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሆይ ፥ የምታመካኘው ፡ የለኽም ፤ በሌላው ፡ በምትፈርድበት ፡ ነገር ፡ ራስኽን ፡ ትኰንናለኽና ፤ አንተው ፡ ፈራጁ ፡ እነዚያን ፡ ታደርጋለኽና ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ እንደዚህም ፡ በሚያደርጉት ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ እውነተኛ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ አንተም ፡ እንደዚህ ፡ በሚያደርጉ ፡ የምትፈርድ ፡ ያንም ፡ የምታደርግ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ የምታመልጥ ፡ ይመስልኻልን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ወይስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንዲመራኽ ፡ ሳታውቅ ፡ የቸርነቱንና ፡ የመቻሉን ፡ የትዕግሥቱንም ፡ ባለጠግነት ፡ ትንቃለኽን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ጥንካሬኽና ፡ ንስሓ ፡ እንደማይገባ ፡ ልብኽ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ በሚገለጥበት ፡ በቀ፡ጣ ፡ ቀን ፡ ቀ፡ጣን ፡ በራስኽ ፡ ላይ ፡ ታከማቻለኽ ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ ለያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ያስረክበዋል ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ በበጎ ፡ ሥራ ፡ በመጽናት ፡ ምስጋናንና ፡ ክብርን ፡ የማይጠፋንም ፡ ሕይወት ፡ ለሚፈልጉ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ይሰጣቸዋል ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ለዐመፃ ፡ በሚታዘዙ ፡ እንጂ ፡ ለእውነት ፡ በማይታዘዙትና ፡ በዐድመኞች ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ቀ፡ጣና ፡ መቅሠፍት ፡ ይኾንባቸዋል ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ክፉውን ፡ በሚያደርግ ፡ ሰው ፡ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ መከራና ፡ ጭንቀት ፡ ይኾንበታል ፥ አስቀድሞ ፡ በአይሁዳዊ ፡ ደግሞም ፡ በግሪክ ፡ ሰው ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎ ፡ ሥራ ፡ ለሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ ሰላምም ፡ ይኾንላቸዋል ፥ አስቀድሞ ፡ ለአይሁዳዊ ፡ ደግሞም ፡ ለግሪክ ፡ ሰው ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ አያዳላምና ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ያለሕግ ፡ ኀጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ኹሉ ፡ ያለሕግ ፡ ደግሞ ፡ ይጠፋሉና ፤ ሕግም ፡ ሳላቸው ፡ ኀጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ ይፈረድባቸዋል ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሕግን ፡ የሚያደርጉት ፡ ይጸድቃሉ ፡ እንጂ ፡ ሕግን ፡ የሚሰሙ ፡ ጻድቃን ፡ አይደሉምና ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ሕግ ፡ የሌላቸው ፡ አሕዛብ ፡ ከባሕርያቸው ፡ የሕግን ፡ ትእዛዝ ፡ ሲያደርጉ ፥ እነዚያ ፡ ሕግ ፡ ባይኖራቸው ፡ እንኳ ፡ ለራሳቸው ፡ ሕግ ፡ ናቸውና ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እነርሱም ፡ ኅሊናቸው ፡ ሲመሰክርላቸው ፥ ዐሳባቸውም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ሲካሰስ ፡ ወይም ፡ ሲያመካኝ ፡ በልባቸው ፡ የተጻፈውን ፡ የሕግ ፡ ሥራ ፡ ያሳያሉ ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ይህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እኔ ፡ በወንጌል ፡ እንዳስተማርኹ ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ የተሰወረውን ፡ በሚፈርድበት ፡ ቀን ፡ ይኾናል ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አይሁዳዊ ፡ ብትባል ፡ በሕግም ፡ ብትደገፍ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ብትመካ ፥

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ፈቃዱንም ፡ ብታውቅ ፡ ከሕግም ፡ ተምረኽ ፡ የሚሻለውን ፡ ፈትነኽ ፡ ብትወድ ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 19-20 ፤ በሕግም ፡ የዕውቀትና ፡ የእውነት ፡ መልክ ፡ ስለ ፡ አለኽ ፥ የዕውሮች ፡ መሪ ፥ በጨለማም ፡ ላሉ ፡ ብርሃን ፥ የሰነፎችም ፡ አስተማሪ ፥ የሕፃናትም ፡ መምህር ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ በራስኽ ፡ ብትታመን ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ እንግዲህ ፡ አንተ ፡ ሌላውን ፡ የምታስተምር ፡ ራስኽን ፡ አታስተምርምን ፧ አትስረቅ ፡ ብለኽ ፡ የምትሰብክ ፡ ትሰርቃለኽን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ አታመንዝር ፡ የምትል ፡ ታመነዝራለኽን ፧ ጣዖትን ፡ የምትጸየፍ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ትዘርፋለኽን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ በሕግ ፡ የምትመካ ፡ ሕግን ፡ በመተላለፍ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታሳፍራለኽን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ በእናንተ ፡ ሰበብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ይሰደባልና ፥ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ሕግን ፡ ብታደርግ ፡ መገረዝስ ፡ ይጠቅማል ፤ ሕግን ፡ ተላላፊ ፡ ብትኾን ፡ ግን ፡ መገረዝኽ ፡ አለ ፡ መገረዝ ፡ ኾኗል ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፡ ያልተገረዘ ፡ ሰው ፡ የሕግን ፡ ሥርዐት ፡ ቢጠብቅ ፡ አለመገረዙ ፡ እንደ ፡ መገረዝ ፡ ኾኖ ፡ አይቈጠርለትምን ፧

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ ከፍጥረቱም ፡ ያልተገረዘ ፡ ሕግን ፡ የሚፈጽም ፡ ሰው ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍና ፡ መገረዝ ፡ ሳለኽ ፡ ሕግን ፡ በምትተላለፈው ፡ ባንተ ፡ ይፈርድብኻል ።

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ በግልጥ ፡ አይሁዳዊ ፡ የኾነ ፡ አይሁዳዊ ፡ አይደለምና ፥ በግልጥ ፡ በሥጋ ፡ የሚደረግ ፡ መገረዝም ፡ መገረዝ ፡ አይደለምና ፤

ሮሜ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በስውር ፡ አይሁዳዊ ፡ የኾነ ፡ አይሁዳዊ ፡ ነው ፥ መገረዝም ፡ በመንፈስ ፡ የሚደረግ ፡ የልብ ፡ መገረዝ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመጽሐፍ ፡ አይደለም ፤ የርሱ ፡ ምስጋና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከሰው ፡ አይደለም ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ የአይሁዳዊ ፡ ብልጫው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ የመገረዝ ፡ ጥቅሙ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በዅሉ ፡ ነገር ፡ ብዙ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ አስቀድሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃላት ፡ ዐደራ ፡ ተሰጧቸው ። ታዲያ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ የማያምኑ ፡ ቢኖሩ ፡ አለማመናቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታማኝነት ፡ ያስቀራልን ፧

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እንዲህ ፡ አይኹን ፤ በቃልኽ ፡ ትጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ በገባኽም ፡ ጊዜ ፡ ትረታ ፡ ዘንድ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ሰው ፡ ዅሉ ፡ ውሸተኛ ፡ ከኾነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ይኹን ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐመፃችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ የሚያስረዳ ፡ ከኾነ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ ቀሣጣን ፡ የሚያመጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዐመፀኛ ፡ ነውን ፧ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድ ፡ እላለኹ ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ እንዲህ ፡ አይኹን ፤ እንዲህ ፡ ቢኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓለም ፡ እንዴት ፡ ይፈርዳል ፧

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በእኔ ፡ ውሸት ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ ለክብሩ ፡ ከላቀ ፡ ስለምን ፡ በእኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ገና ፡ ይፈርድብኛል ፧

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ መልካም ፡ እንዲመጣ ፡ ክፉ ፡ አናደርግም ፧ እንዲሁ ፡ ይሰድቡናልና ፥ አንዳንዱም ፡ እንዲሁ ፡ እንድንል ፡ ይናገራሉና ። የእነርሱም ፡ ፍርድ ፡ ቅን ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይኹን ፧ ከነርሱ ፡ እንበልጣለንን ፧ ከቶ ፡ አይደለም ፤ አይሁድም ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ኹሉ ፡ ከኀጢአት ፡ በታች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ አስቀድመን ፡ ከሰናቸዋልና ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፦

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ጻድቅ ፡ የለም ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፤ አስተዋይም ፡ የለም ፤ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈልግ ፡ የለም ፤ ኹሉ ፡ ተሳስተዋል ፥

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ በአንድነትም ፡ የማይጠቅሙ ፡ ኾነዋል ፤ ቸርነት ፡ የሚያደርግ ፡ የለም ፥ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የለም ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ጉረሯቸው ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡ መቃብር ፡ ነው ፥ በምላሳቸውም ፡ ሸንግለዋል ፤ የእባብ ፡ መርዝ ፡ ከከንፈሮቻቸው ፡ በታች ፡ አለ ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ አፋቸውም ፡ ርግማንና ፡ መራርነት ፡ ሞልቶበታል ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እግሮቻቸው ፡ ደምን ፡ ለማፍሰስ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ጥፋትና ፡ ጕስቍልና ፡ በመንገዳቸው ፡ ይገኛል ፥

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 17-18 ፤ የሰላምንም ፡ መንገድ ፡ አያውቁም ። በዐይኖቻቸው ፡ ፊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ መፍራት ፡ የለም ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ አፍም ፡ ኹሉ ፡ ይዘጋ ፡ ዘንድ ፡ ዓለምም ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ በታች ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሕግ ፡ የሚናገረው ፡ ኹሉ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ እንዲናገር ፡ እናውቃለን ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ይህም ፡ የሕግን ፡ ሥራ ፡ በመሥራት ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ስለማይጸድቅ ፡ ነው ፤ ኀጢአት ፡ በሕግ ፡ ይታወቃልና ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በሕግና ፡ በነቢያት ፡ የተመሰከረለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ያለሕግ ፡ ተገልጧል ፥

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ርሱም ፥ ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ የኾነ ፥ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ የሚገኘው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፤ ልዩነት ፡ የለምና ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ኹሉ ፡ ኀጢአትን ፡ ሠርተዋልና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ጐድሏቸዋል ፤

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በኾነው ፡ ቤዛነት ፡ በኩል ፡ እንዲያው ፡ በጸጋው ፡ ይጸድቃሉ ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ ርሱንም ፡ እግዚአብሔር ፡ በእምነት ፡ የሚገኝ ፡ በደሙም ፡ የኾነ ፡ ማስተስረያ ፡ አድርጎ ፡ አቆመው ፤ ይህም ፡ በፊት ፡ የተደረገውን ፡ ኀጢአት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ችሎታ ፡ ስለ ፡ መተው ፡ ጽድቁን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፥

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ ራሱም ፡ ጻድቅ ፡ እንዲኾን ፡ በኢየሱስም ፡ የሚያምነውን ፡ እንዲያጸድቅ ፡ አኹን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጽድቁን ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ትምክሕት ፡ እንግዲህ ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ ርሱ ፡ ቀርቷል ። በየትኛው ፡ ሕግ ፡ ነው ፧ በሥራ ፡ ሕግ ፡ ነውን ፧ አይደለም ፥ በእምነት ፡ ሕግ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ ሰው ፡ ያለሕግ ፡ ሥራ ፡ በእምነት ፡ እንዲጸድቅ ፡ እንቈጥራለንና ።

ሮሜ. ፡ 3 ፡ 29-30 ፤ ወይስ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአይሁድ ፡ ብቻ ፡ አምላክ ፡ ነውን ፧ የአሕዛብስ ፡ ደግሞ ፡ አምላክ ፡

አይደለምን ፧ አዎን ፥ የተገረዘን ፡ ስለ ፡ እምነት ፡ ያልተገረዘንም ፡ በእምነት ፡ የሚያጸድቅ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የአሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ አምላክ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፥ 3 ፥ 31 ፤ እንግዲህ ፡ ሕግን ፡ በእምነት ፡ እንሽራለንን ፧ አይደለም ፤ ሕግን ፡ እናጸናለን ፡ እንጂ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 1 ፤ እንግዲህ ፡ በሥጋ ፡ አባታችን ፡ የኾነ ፡ አብርሃም ፡ ምን ፡ አገኘ ፡ እንላለን ፧

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 2 ፤ አብርሃም ፡ በሥራ ፡ ጸድቆ ፡ ቢኾን ፡ የሚመካበት ፡ አለውና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 3 ፤ መጽሐፍስ ፡ ምን ፡ አለ ፧ አብርሃምም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመነ ፡ ጽድቅም ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 4 ፤ ለሚሠራ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ እንደ ፡ ዕዳ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጸጋ ፡ አይቈጠርለትም ፤

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለማይሠራ ፥ ኀጢአተኛውንም ፡ በሚያጸድቅ ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ እምነቱ ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ይቈጠርለታል ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 6 ፤ እንደዚህ ፡ ዳዊት ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለሥራ ፡ ጽድቅን ፡ ስለሚቈጥርለት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ብፅዕና ፡ ይናገራል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 7 ፤ ዐመፃቸው ፡ የተሰረየላቸው ፡ ኀጢአታቸውም ፡ የተከደነላቸው ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፤

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 8 ፤ ጌታ ፡ ኀጢአቱን ፡ የማይቈጥርበት ፡ ሰው ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 9 ፤ እንግዲህ ፡ ይህ ፡ ብፅዕና ፡ ስለ ፡ መገረዝ ፡ ተነገረ ፧ ወይስ ፡ ደግሞ ፡ ስላለመገረዝ ፧ እምነቱ ፡ ለአብርሃም ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ፡ እንላለንና ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 10 ፤ እንዴት ፡ ተቈጠረለት ፧ ተገርዞ ፡ ሳለ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ሳይገረዝ ፧ ተገርዞስ ፡ አይደለም ፥ ሳይገረዝ ፡ ነበር ፡ እንጂ ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 11 ፤ ሳይገረዝም ፡ በነበረው ፡ እምነት ፡ ያገኘው ፡ የጽድቅ ፡ ማኅተም ፡ የኾነ ፡ የመገረዝን ፡ ምልክት ፡ ተቀበለ ፤ ይህም ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ጻድቃን ፡ ኾነው ፡ ይቈጠሩ ፡ ዘንድ ፡ ሳይገረዙ ፡ ለሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ አባት ፡ እንዲኾን ፡ ነው ፥

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 12 ፤ ለተገረዙትም ፡ አባት ፡ እንዲኾን ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ለተገረዙት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አባታችን ፡ አብርሃም ፡ ሳይገረዝ ፡ የነበረውን ፡ የእምነቱን ፡ ፍለጋ ፡ ደግሞ ፡ ለሚከተሉ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 13 ፤ የዓለምም ፡ ወራሽ ፡ እንዲኾን ፡ ለአብርሃምና ፡ ለዘሩ ፡ የተሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ በእምነት ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በሕግ ፡ አይደለም ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 14 ፤ ከሕግ ፡ የኾኑትስ ፡ ወራሾች ፡ ከኾኑ ፡ እምነት ፡ ከንቱ ፡ ኾኗል ፡ የተስፋውም ፡ ቃል ፡ ተሽሯል ፤

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 15 ፤ ሕጉ ፡ መቅሠፍትን ፡ ያደርጋልና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሕግ ፡ በሌለበት ፡ መተላለፍ ፡ የለም ።

ሮሜ. ፥ 4 ፥ 16-17 ፤ ስለዚህ ፥ ከሕግ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ከአብርሃም ፡ እምነት ፡ ደግሞ ፡ ለኾነ ፣ ለዘሩ ፡ ኹሉ ፥ የተስፋው ፡ ቃል ፡ እንዲጸና ፡ እንደ ፡ ጸጋ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ በእምነት ፡ ነው ፤ ርሱም ፦ ለብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አባት ፡ አደረግኹኽ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ለሙታን ፡ ሕይወት ፡ በሚሰጥ ፡ የሌለውንም ፡ እንዳለ ፡ አድርጎ ፡ በሚጠራ ፡ ባመነበት ፡ በአምላክ ፡ ፊት ፡ የኹላችን ፡ አባት ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ዘርኽ ፡ እንዲሁ ፡ ሊኾን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ ተስፋ ፡ ባልኾነው ፡ ጊዜ ፡ የብዙ ፡ አሕዛብ ፡ አባት ፡ እንዲኾን ፡ ተስፋ ፡ ይዞ ፡ አመነ ።

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ የመቶ ፡ ዓመትም ፡ ሽማግሌ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንደ ፡ ምውት ፡ የኾነውን ፡ የራሱን ፡ ሥጋና ፡ የሳራ ፡ ማሕፀን ፡ ምውት ፡ መኾኑን ፡ በእምነቱ ፡ ሳይደክም ፡ ተመለከተ ፤

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 20-21 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ እየሰጠ ፥ የሰጠውንም ፡ ተስፋ ፡ ደግሞ ፡ ሊፈጽም ፡ እንዲችል ፡ አጥብቆ ፡ እየተረዳ ፥ በእምነት ፡ በረታ ፡ እንጂ ፡ ባለማመን ፡ ምክንያት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ አልተጠራጠረም ።

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፥ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ።

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ተቈጠረለት ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ብቻ ፡ የተጻፈ ፡ አይደለም ፥ ስለ ፡ እኛም ፡ ነው ፡ እንጂ ፤

ሮሜ. ፡ 4 ፡ 24-25 ፤ ስለ ፡ በደላችን ፡ ዐልፎ ፡ የተሰጠውን ፥ እኛን ፡ ስለ ፡ ማጽደቅም ፡ የተነሣውን ፥ ጌታችንን ፣ ኢየሱስን ፡ ከሙታን ፡ ባስነሣው ፡ ለምናምን ፡ ለእኛ ፡ ይቈጠርልን ፡ ዘንድ ፡ አለው ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ በእምነት ፡ ከጸደቅን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምን ፡ እንያዝ ፤

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ በርሱም ፡ ደግሞ ፡ ወደቆምንበት ፡ ወደዚህ ፡ ጸጋ ፡ በእምነት ፡ መግባትን ፡ አግኝተናል ፤ በእግዚአብሔር ፡ ክብርም ፡ ተስፋ ፡ እንመካለን ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 3-4 ፤ ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መከራ ፡ ትዕግሥትን ፡ እንዲያደርግ ፥ ትዕግሥትም ፡ ፈተናን ፡ ፈተናም ፡ ተስፋን ፡ እንዲያደርግ ፡ እያወቅን ፥ በመከራችን ፡ ደግሞ ፡ እንመካለን ፤

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ በተሰጠንም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በልባችን ፡ ስለ ፡ ፈሰሰ ፥ ተስፋ ፡ አያሳፍርም ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ገና ፡ ደካማዎች ፡ ሳለን ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመኑ ፡ ሲደርስ ፡ ስለ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ሞቷልና ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ ጻድቅ ፡ የሚሞት ፡ በጭንቅ ፡ ይገኛልና ፤ ስለ ፡ ቸር ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ሊሞት ፡ እንኳ ፡ የሚደፍር ፡ ምናልባት ፡ ይገኝ ፡ ይኾናል ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ገና ፡ ኀጢአተኞች ፡ ሳለን ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሞቷልና ፥ እግዚአብሔር ፡ ለእኛ ፡ ያለውን ፡ የራሱን ፡ ፍቅር ፡ ያስረዳል ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ይልቁንስ ፡ እንግዲህ ፡ አኹን ፡ በደሙ ፡ ከጸደቅን ፡ በርሱ ፡ ከቍጣው ፡ እንድናለን ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ጠላቶች ፡ ሳለን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ከታረቅን ፥ ይልቁንም ፡ ከታረቅን ፡ በኋላ ፡ በሕይወቱ ፡ እንድናለን ፤

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ መታረቁን ፡ ባገኘንበት ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደግሞ ፡ እንመካለን ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፥ ኀጢአት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገባ ፥ በኀጢአትም ፡ ሞት ፤ እንደዚሁም ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአትን ፡ ስላደረጉ ፡ ሞት ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ደረሰ ፤

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ሕግ ፡ እስከ ፡ መጣ ፡ ድረስ ፡ ኀጢአት ፡ በዓለም ፡ ነበረና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሕግ ፡ በሌለበት ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአት ፡ አይቈጠርም ፤

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በአዳም ፡ መተላለፍ ፡ ምሳሌ ፡ ኀጢአትን ፡ ባልሠሩት ፡ ላይ ፡ እንኳ ፥ ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ሙሴ ፡ ድረስ ፡ ሞት ፡ ነገሠ ፤ አዳም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ላለው ፡ ለርሱ ፡ አምሳሉ ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስጦታው ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ መጠን ፡ እንደዚያው ፡ አይደለም ፤ ባንድ ፡ ሰው ፡ በደል ፡ ብዙዎቹ ፡ ሞተዋልና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋና ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ የኾነው ፡ ስጦታ ፡ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡ ለብዙዎች ፡ በዛ ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ አንድ ፡ ሰውም ፡ ኀጢአትን ፡ በማድረጉ ፡ እንደኾነው ፡ መጠን ፡ እንደዚያው ፡ ስጦታው ፡ አይደለም ፤ ፍርድ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ ለኵነኔ ፡ መጥቷልና ፥ ስጦታው ፡ ግን ፡ በብዙ ፡ በደል ፡ ለማጽደቅ ፡ መጣ ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ በአንዱም ፡ በደል ፡ ሞት ፡ በአንዱ ፡ በኩል ፡ ከነገሠ ፥ ይልቁን ፡ የጸጋን ፡ ብዛትና ፡ የጽድቅን ፡ ስጦታ ፡ ብዛት ፡ የሚቀበሉ ፡ በአንዱ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ በሕይወት ፡ ይነግሣሉ ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ ባንድ ፡ በደል ፡ ምክንያት ፡ ፍርድ ፡ ለኵነኔ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ መጣ ፥ እንዲሁም ፡ ባንድ ፡ ጽድቅ ፡ ምክንያት ፡ ስጦታው ፡ ሕይወትን ፡ ለማጽደቅ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ መጣ ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ በአንዱ ፡ ሰው ፡ አለመታዘዝ ፡ ብዙዎች ፡ ኀጢአተኞች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በአንዱ ፡ መታዘዝ ፡ ብዙዎች ፡ ጻድቃን ፡ ይኾናሉ ።

ሮሜ. ፡ 5 ፡ 20-21 ፤ በደልም ፡ እንዲበዛ ፡ ሕግ ፡ ጭምር ፡ ገባ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ኀጢአት ፡ በበዛበት ፥ ኀጢአት ፡ በሞት ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፥ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ጸጋ ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተነሣ ፡ በጽድቅ ፡ ምክንያት ፡ ለዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ይነግሥ ፡ ዘንድ ፥ ጸጋ ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ በለጠ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ ጸጋ ፡ እንዲበዛ ፡ በኀጢአት ፡ ጸንተን ፡ እንኑርን ፧ አይደለም ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ለኀጢአት ፡ የሞትን ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዴት ፡ አድርገን ፡ በርሱ ፡ እንኖራለን ፧

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ ወይስ ፡ ከክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ የተጠመቅን ፡ ኹላችን ፡ ከሞቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተጠመቅን ፡ አታውቁምን ፧

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ እንግዲህ ፡ ክርስቶስ ፡ በአብ ፡ ክብር ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ እንዲሁ ፡ እኛም ፡ በዐዲስ ፡ ሕይወት ፡ እንድንመላለስ ፥ ከሞቱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ በጥምቀት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀበርን ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ሞቱንም ፡ በሚመስል ፡ ሞት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተባበርን ፡ ትንሣኤውን ፡ በሚመስል ፡ ትንሣኤ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንተባበራለን ፤

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ከእንግዲህስ ፡ ወዲያ ፡ ለኀጢአት ፡ እንዳንገዛ ፡ የኀጢአት ፡ ሥጋ ፡ ይሻር ፡ ዘንድ ፡ አሮጌው ፡ ሰዋችን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ እናውቃለን ፤ የሞተስ ፡ ከኀጢአቱ ፡ ጸድቋልና ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 7-8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከሞትን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ በሕይወት ፡ እንድንኖር ፡ እናምናለን ፤

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳይሞት ፡ ሞትም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳይገዛው ፡ እናውቃለንና ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ መሞትን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ለኀጢአት ፡ ሞቷልና ፤ በሕይወት ፡ መኖርን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይኖራል ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እንዲሁም ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ለኀጢአት ፡ እንደ ፡ ሞታችኹ ፥ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ ኾናችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያዋን ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ ቈጠሩ ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ ለምኞቱ ፡ እንድትታዘዙ ፡ በሚሞት ፡ ሥጋችኹ ፡ ኀጢአት ፡ አይንገሥ ፤

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ብልቶቻችኹንም ፡ የዐመፃ ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ አድርጋችኹ ፡ ለኀጢአት ፡ አታቅርቡ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከሙታን ፡ ተለይታችኹ ፡ በሕይወት ፡ እንደምትኖሩ ፡ ራሳችኹን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ፥ ብልቶቻችኹንም ፡ የጽድቅ ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፡ አድርጋችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አቅርቡ ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ኀጢአት ፡ አይገዛችኹምና ፤ ከጸጋ ፡ በታች ፡ እንጂ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ አይደላችኹምና ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ ይኹን ፧ ከጸጋ ፡ በታች ፡ እንጂ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ስላይደለን ፡ ኀጢአትን ፡ እንሥራን ፧ አይደለም ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ለመታዘዝ ፡ ባሪያዎች ፡ እንድትኾኑ ፡ ራሳችኹን ፡ ለምታቀርቡለት ፥ ለርሱ ፡ ለምትታዘዙለት ፡ ባሪያዎች ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ አታውቁምን ፧ ወይም ፡ ለሞት ፡ የኀጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ወይም ፡ ለጽድቅ ፡ የመታዘዝ ፡ ባሪያዎች ፡ ናችኹ ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 17-18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድማችኹ ፡ የኀጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ከኾናችኹ ፥ ለተሰጣችኹለት ፡ ለትምህርት ፡ ዐይነት ፡ ከልባችኹ ፡ ስለ ፡ ታዘዛችኹ ፥ ከኀጢአትም ፡ ሐራነት ፡ ወጥታችኹ ፡ ለጽድቅ ፡ ስለ ፡ ተገዛችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይኹን ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ስለሥጋችኹ ፡ ድካም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድ ፡ እላለኹ ፦ ብልቶቻችኹ ፡ ዐመፃ ፡ ሊያደርጉ ፡ ለርኩስነትና ፡ ለዐመፃ ፡ ባሪያዎች ፡ አድርጋችኹ ፡ እንዳቀረባችኹ ፥ እንደዚሁ ፡ ብልቶቻችኹ ፡ ሊቀደሱ ፡ ለጽድቅ ፡ ባሪያዎች ፡ አድርጋችኹ ፡ አኹን ፡ አቅርቡ ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ የኀጢአት ፡ ባሪያዎች ፡ ሳላችኹ ፡ ከጽድቅ ፡ ነጻ ፡ ነበራችኹና ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ እንግዲህ ፡ ዛሬ ፡ ከምታፍሩበት ፡ ነገር ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምን ፡ ፍሬ ፡ ነበራችኹ ፧ የዚህ ፡ ነገር ፡ መጨረሻው ፡ ሞት ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ከኀጢአት ፡ ሐራነት ፡ ወጥታችኹ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ተገዝታችኹ ፥ ልትቀደሱ ፡ ፍሬ ፡ አላችኹ ፤ መጨረሻውም ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ የኀጢአት ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ሞት ፡ ነውና ፤ የእግዚአብሔር ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።

_____ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ሕግን ፡ ለሚያውቁ ፡ እናገራለኹና ፡ ሰው ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፡ ሕግ ፡ እንዲገዛው ፡ አታውቁምን ፧

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ያገባች ፡ ሴት ፡ ባሏ ፡ በሕይወት ፡ ሲኖር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በሕግ ፡ ታስራለችና ፤ ባሏ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ባል ፡ ከኾነው ፡ ሕግ ፡ ተፈታለች ።

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ባሏ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ ለሌላ ፡ ወንድ ፡ ብትኾን ፥ አመንዝራ ፡ ትባላለች ፤ ባሏ ፡

በ.ሞት ፡ ግን ፥ ከሕጉ ፡ ሐራነት ፡ ወጥታለችና ፥ ለሌላ ፡ ወንድ ፡ ብትኾን ፡ አመንዝራ ፡ አይደለችም ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 4 ፤ እንዲሁ ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ለሕግ ፡ ተገድላችኋል ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ፍሬ ፡ እንድናፈራ ፥ እናንተ ፡ ለሌላው ፥ ከሙታን ፡ ለተነሣው ፥ ለርሱ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 5 ፤ በሥጋ ፡ ሳለን ፡ በሕግ ፡ የሚኾን ፡ የኀጢአት ፡ መሻት ፡ ለሞት ፡ ፍሬ ፡ ሊያፈራ ፡ በብልቶቻችን ፡ ይሠራ ፡ ነበርና ፤

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ ለታሰርንበት ፡ ስለ ፡ ሞትን ፥ ከሕግ ፡ ተፈቶናል ፥ ስለዚህም ፡ በዐዲሱ ፡ በመንፈስ ፡ ኑሮ ፡ እንገዛለን ፡ እንጂ ፡ በአሮጌው ፡ በፊደል ፡ ኑሮ ፡ አይደለም ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ ሕግ ፡ ኀጢአት ፡ ነውን ፧ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሕግ ፡ ባይኾን ፡ ኀጢአትን ፡ ባላወቅኹም ፡ ነበር ፤ ሕጉ ፦ አትመኝ ፡ ባላለ ፥ ምኞትን ፡ ባላወቅኹም ፡ ነበርና ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 8 ፤ ኀጢአት ፡ ግን ፡ ምክንያት ፡ አግኝቶ ፡ ምኞትን ፡ ኹሉ ፡ በትእዛዝ ፡ ሠራብኝ ፤ ኀጢአት ፡ ያለሕግ ፡ ምውት ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 9 ፤ እኔም ፡ ዱሮ ፡ ያለሕግ ፡ ሕያው ፡ ነበርኹ ፤ ትእዛዝ ፡ በመጣች ፡ ጊዜ ፡ ግን ፥ ኀጢአት ፡ ሕያው ፡ ኾነ ፥ እኔም ፡ ሞትኹ ፤

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 10 ፤ ለሕይወትም ፡ የተሰጠችውን ፡ ትእዛዝ ፥ ርሷን ፡ ለሞት ፡ ኾና ፡ አገኘኋት ፤

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 11 ፤ ኀጢአት ፡ ምክንያት ፡ አግኝቶ ፡ በትእዛዝ ፡ አታሎኛልና ፥ በርሷም ፡ ገድሎኛል ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ሕጉ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፥ ትእዛዙ.ም ፡ ቅድስትና ፡ ጻድቅት ፣ በጎም ፡ ናት ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 13 ፤ እንግዲህ ፡ በጎ ፡ የኾነው ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ሞት ፡ ኾነብኝን ፧ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኀጢአት ፡ ኾነ ፤ ኀጢአትም ፡ በትእዛዝ ፡ ምክንያት ፡ ያለልክ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ ኀጢአትም ፡ እንዲኾን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ በኾነው ፡ ነገር ፡ ለእኔ ፡ ሞትን ፡ ይሠራ ፡ ነበር ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 14 ፤ ሕግ ፡ መንፈሳዊ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለንና ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከኀጢአት ፡ በታች ፡ ልኾን ፡ የተሸጥኩ ፡ የሥጋ ፡ ነኝ ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 15 ፤ የማደርገውን ፡ አላውቅምና ፤ የምጠላውን ፡ ያን ፡ አደርጋለኹና ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የምወደውን ፡ ርሱን ፡ አላደርገውም ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 16 ፤ የማልወደውን ፡ ግን ፡ የማደርግ ፡ ከኾንኩ ፡ ሕግ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እመሰክራለኹ ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 17 ፤ እንደዚህ ፡ ከኾነ ፡ ያን ፡ የማደርገው ፡ አኹን ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ፥ በእኔ ፡ የሚያድር ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 18 ፤ በእኔ ፡ ማለት ፡ በሥጋዬ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ እንዳይኖር ፡ ዐውቃለኹና ፤ ፈቃድ ፡ አለኝና ፥ መልካሙን ፡ ግን ፡ ማድረግ ፡ የለኝም ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 19 ፤ የማልወደውን ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ አደርጋለኹና ፡ ዳሩ ፡ ግን ፡ የምወደውን ፡ በጎውን ፡ ነገር ፡ አላደርገውም ።

ሮሜ. ፥ 7 ፥ 20 ፤ የማልወደውን ፡ የማደርግ ፡ ከኾንኩ ፡ ግን ፡ ያን ፡ የማደርገው ፡ አኹን ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ፥ በእኔ ፡ የሚኖር ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 21 ፤ እንግዲያስ ፡ መልካሙን ፡ ኣደርግ ፡ ዘንድ ፡ ስወድ ፡ በእኔ ፡ ክፉ ፡ እንዲያድርብኝ ፡ ሕግን ፡ ኣገኛለኹ ።

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 22 ፤ በውስጡ ፡ ሰውነቴ ፡ በእግዚኣብሔር ፡ ሕግ ፡ ደስ ፡ ይለኛልና ፥

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በብልቶቼ ፡ ከኣእምሮዬ ፡ ሕግ ፡ ጋራ ፡ የሚዋጋውንና ፡ በብልቶቼ ፡ ባለ ፡ በኀጢኣት ፡ ሕግ ፡ የሚማርከኝን ፡ ሌላ ፡ ሕግ ፡ ኣያለኹ ።

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 24 ፤ እኔ ፡ ምንኛ ፡ ጕስቋላ ፡ ሰው ፡ ነኝ! ፡ ለዚህ ፡ ሞት ፡ ከተሰጠ ፡ ሰውነት ፡ ማን ፡ ያድነኛል ፧

ሮሜ. ፡ 7 ፡ 25 ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጌታችን ፡ ለእግዚኣብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይኹን ። እንግዲያስ ፡ እኔ ፡ በኣእምሮዬ ፡ ለእግዚኣብሔር ፡ ሕግ ፥ በሥጋዬ ፡ ግን ፡ ለኀጢኣት ፡ ሕግ ፡ እገዛለኹ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ላሉት ፡ ኣኹን ፡ ኵነኔ ፡ የለባቸውም ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ያለው ፡ የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ሕግ ፡ ከኀጢኣትና ፡ ከሞት ፡ ሕግ ፡ ሐራነት ፡ ኣውጥቶኛልና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 3-4 ፤ ከሥጋ ፡ የተነሣ ፡ ስለ ፡ ደከመ ፡ ለሕግ ፡ ያልተቻለውን ፥ እግዚኣብሔር ፡ የገዛ ፡ ልጁን ፡ በኀጢኣተኛ ፡ ሥጋ ፡ ምሳሌ ፡ በኀጢኣትም ፡ ምክንያት ፡ ልኮ ፡ ኣድርጓልና ፤ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ በማንመላለስ ፡ በእኛ ፡ የሕግ ፡ ትእዛዝ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ ኀጢኣትን ፡ በሥጋ ፡ ኰነነ ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ የሚኖሩ ፡ የሥጋን ፡ ነገር ፡ ያስባሉና ፥ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡ የሚኖሩ ፡ ግን ፡ የመንፈስን ፡ ነገር ፡ ያስባሉ ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ማሰብ ፡ ሞት ፡ ነውና ፥ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ማሰብ ፡ ግን ፡ ሕይወትና ፡ ሰላም ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ስለ ፡ ሥጋ ፡ ማሰብ ፡ በእግዚኣብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥል ፡ ነውና ፤ ለእግዚኣብሔር ፡ ሕግ ፡ ኣይገዛምና ፥ መገዛትም ፡ ተስኖታል ፤

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ በሥጋ ፡ ያሉትም ፡ እግዚኣብሔርን ፡ ደስ ፡ ሊያሠኙት ፡ ኣይችሉም ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ የእግዚኣብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ፥ በመንፈስ ፡ እንጂ ፡ በሥጋ ፡ ኣይደላችኹም ። የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ የሌለው ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ይኸው ፡ የርሱ ፡ ወገን ፡ ኣይደለም ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ክርስቶስ ፡ በእናንተ ፡ ውስጥ ፡ ቢኾን ፡ ሰውነታችኹ ፡ በኀጢኣት ፡ ምክንያት ፡ የሞተ ፡ ነው ፥ መንፈሳችኹ ፡ ግን ፡ በጽድቅ ፡ ምክንያት ፡ ሕያው ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኢየሱስን ፡ ከሙታን ፡ ያስነሣው ፡ የርሱ ፡ መንፈስ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ቢኖር ፥ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስን ፡ ከሙታን ፡ ያስነሣው ፡ ርሱ ፡ በእናንተ ፡ በሚኖረው ፡ በመንፈሱ ፥ ለሚሞተው ፡ ሰውነታችኹ ፡ ደግሞ ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጠዋል ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ዕዳ ፡ ኣለብን ፥ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ግን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ለሥጋ ፡ ኣይደለም ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ ብትኖሩ ፡ ትሞቱ ፡ ዘንድ ፡ ኣላችኹና ፤ በመንፈስ ፡ ግን ፡ የሰውነትን ፡ ሥራ ፡ ብትገድሉ ፡ በሕይወት ፡ ትኖራላችኹ ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 14 ፤ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ የሚመሩ ፡ ኹሉ ፡ እነዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 15 ፤ አባ ፡ አባት ፡ ብለን ፡ የምንጮኽበትን ፡ የልጅነት ፡ መንፈስ ፡ ተቀበላችኹ ፡ እንጂ ፡ እንደገና ፡ ለፍርሀት ፡ የባርነትን ፡ መንፈስ ፡ አልተቀበላችኹምና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ መኾናችንን ፡ ያ ፡ መንፈስ ፡ ራሱ ፡ ከመንፈሳችን ፡ ጋራ ፡ ይመሰክራል ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 17 ፤ ልጆች ፡ ከኾን ፡ ወራሾች ፡ ደግሞ ፡ ነን ፤ ማለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወራሾች ፡ ነን ፥ ዐብረንም ፡ ደግሞ ፡ እንድንከበር ፡ ዐብረን ፡ መከራ ፡ ብንቀበል ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ዐብረን ፡ ወራሾች ፡ ነን ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 18 ፤ ለእኛም ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ካለው ፡ ክብር ፡ ጋራ ፡ ቢመዛዘን ፡ የአኹኑ ፡ ዘመን ፡ ሥቃይ ፡ ምንም ፡ እንዳይደለ ፡ ዐስባለኹ ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 19 ፤ የፍጥረት ፡ ናፍቆት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጆች ፡ መገለጥ ፡ ይጠባበቃልና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 20 ፤ ፍጥረት ፡ ለከንቱነት ፡ ተገዝቷልና ፥ በተስፋ ፡ ስላስገዛው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በፈቃዱ ፡ አይደለም ፤

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 21 ፤ ተስፋውም ፡ ፍጥረት ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ከጥፋት ፡ ባርነት ፡ ነጻነት ፡ ወጥቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ወደሚኾን ፡ ክብር ፡ ነጻነት ፡ እንዲደርስ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 22 ፤ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ዐብሮ ፡ በመቃተትና ፡ በምጥ ፡ መኖሩን ፡ እናውቃለንና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 23 ፤ ርሱም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የመንፈስ ፡ በኩራት ፡ ያለን ፡ ራሳችን ፡ ደግሞ ፡ የሰውነታችን ፡ ቤዛ ፡ የኾነውን ፡ ልጅነት ፡ እየተጠባበቅን ፡ ራሳችን ፡ በውስጣችን ፡ እንቃትታለን ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 24 ፤ በተስፋ ፡ ድነናልና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ተስፋ ፡ የሚደረግበቱ ፡ ነገር ፡ ቢታይ ፡ ተስፋ ፡ አይደለም ፤ የሚያየውንማ ፡ ማን ፡ ተስፋ ፡ ያደርገዋል ፧

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 25 ፤ የማናየውን ፡ ግን ፡ ተስፋ ፡ ብናደርገው ፡ በትዕግሥት ፡ እንጠባበቃለን ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 26 ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ መንፈስ ፡ ድካማችንን ፡ ያግዛል ፤ እንዴት ፡ እንድንጸልይ ፡ እንደሚገባን ፡ አናውቅምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መንፈስ ፡ ራሱ ፡ በማይነገር ፡ መቃተት ፡ ይማልድልናል ፤

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 27 ፤ ልብንም ፡ የሚመረምረው ፡ የመንፈስ ፡ ዐሳብ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቃል ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ይማልዳልና ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ለሚወዱት ፡ እንደ ፡ ዐሳቡም ፡ ለተጠሩት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ለበጎ ፡ እንዲደረግ ፡ እናውቃለን ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 29 ፤ ልጁ ፡ በብዙ ፡ ወንድሞች ፡ መካከል ፡ በኩር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ አስቀድሞ ፡ ያወቃቸው ፡ የልጁን ፡ መልክ ፡ እንዲመስሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ደግሞ ፡ ወስኗልና ፤

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 30 ፤ አስቀድሞም ፡ የወሰናቸውን ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ ጠራቸው ፤ የጠራቸውንም ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ አጸደቃቸው ፤ ያጸደቃቸውንም ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ አከበራቸው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 31 ፤ እንግዲህ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ እግዚአብሔር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ከኾነ ፡ ማን ፡ ይቃወመናል ፧

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 32 ፤ ለገዛ ፡ ልጁ ፡ ያልራራለት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ኹላችን ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ ያው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ ኹሉን ፡ ነገር ፡ እንዲያው ፡ እንዴት ፡ አይሰጠንም ፧

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔር ፡ የመረጣቸውን ፡ ማን ፡ ይከሳቸዋል ፧ የሚያጸድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ የሚኰንንስ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 34 ፤ የሞተው ፥ ይልቁንም ፡ ከሙታን ፡ የተነሣው ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ያለው ፥ ደግሞ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የሚማልደው ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 35 ፤ ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ማን ፡ ይለየናል ፧ መከራ ፥ ወይስ ፡ ጭንቀት ፥ ወይስ ፡ ስደት ፥ ወይስ ፡ ራብ ፥ ወይስ ፡ ራቍትነት ፥ ወይስ ፡ ፍርሀት ፥ ወይስ ፡ ሰይፍ ፡ ነውን ፧

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 36 ፤ ስለ ፡ አንተ ፡ ቀኑን ፡ ኹሉ ፡ እንገደላለን ፥ እንደሚታረዱ ፡ በጎች ፡ ተቈጠርን ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 37 ፤ በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ በወደደን ፡ በርሱ ፡ ከአሸናፊዎች ፡ እንበልጣለን ።

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 38 ፤ ሞት ፡ ቢኾን ፥ ሕይወትም ፡ ቢኾን ፥ መላእክትም ፡ ቢኾኑ ፥ ግዛትም ፡ ቢኾን ፥ ያለውም ፡ ቢኾን ፥ የሚመጣውም ፡ ቢኾን ፥ ኀይላትም ፡ ቢኾኑ ፥

ሮሜ. ፡ 8 ፡ 39 ፤ ከፍታም ፡ ቢኾን ፥ ዝቅታም ፡ ቢኾን ፥ ልዩ ፡ ፍጥረትም ፡ ቢኾን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ ካለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ሊለየን ፡ እንዳይችል ፡ ተረድቻለኹ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 1-2 ፤ ብዙ ፡ ሐዘን ፡ የማያቋርጥም ፡ ጭንቀት ፡ በልቤ ፡ አለብኝ ፡ ስል ፡ በክርስቶስ ፡ ኾኜ ፡ እውነትን ፡ እናገራለኹ ፤ አልዋሸምም ፤ ኅሊናዬም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰክርልኛል ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ በሥጋ ፡ ዘመዶቼ ፡ ስለኾኑ ፡ ስለ ፡ ወንድሞቼ ፡ ከክርስቶስ ፡ ተለይቼ ፡ እኔ ፡ ራሴ ፡ የተረገምኹ ፡ እንድኾን ፡ እጸልይ ፡ ነበርና ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ እነርሱ ፡ እስራኤላውያን ፡ ናቸውና ፥ ልጅነትና ፡ ክብር ፡ ኪዳንም ፡ የሕግም ፡ መሰጠት ፡ የመቅደስም ፡ ሥርዐት ፡ የተስፋውም ፡ ቃላት ፡ ለእነርሱ ፡ ናቸውና ፤

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ አባቶችም ፡ ለእነርሱ ፡ ናቸውና ፤ ከነርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ መጣ ፥ ርሱም ፡ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ኾኖ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተባረከ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ አሜን ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የተሻረ ፡ አይደለም ። እነዚህ ፡ ከእስራኤል ፡ የሚወለዱ ፡ ኹሉ ፡ እስራኤል ፡ አይደሉምና ፤ የአብርሃምም ፡ ዘር ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ኹላቸው ፡ ልጆች ፡ አይደሉም ፥

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ በይሥሐቅ ፡ ዘር ፡ ይጠራልኻል ፡ ተባለ ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ይህም ፥ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ልጆች ፡ ዘር ፡ ኾነው ፡ ይቈጠራሉ ፡ እንጂ ፡ እነዚህ ፡ የሥጋ ፡ ልጆች ፡ የኾኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ አይደሉም ፡ ማለት ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 9 ፤ ይህ ፦ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ እመጣለኹ ፡ ለሳራም ፡ ልጅ ፡ ይኾንላታል ፡ የሚል ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 10 ፤ ይህ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ርብቃ ፡ ደግሞ ፡ ከአንዱ ፡ ከአባታችን ፡ ከይሥሐቅ ፡ በፀነሰች ፡ ጊዜ ፥

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ልጆቹ ፡ ገና ፡ ሳይወለዱ ፥ በጎ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ ምንም ፡ ሳያደርጉ ፥ ከጠሪው ፡ እንጂ ፡ ከሥራ ፡ ሳይኾን ፡ በምርጫ ፡ የሚኾን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዐሳብ ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፥

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ ለርሷ ፦ ታላቁ ፡ ለታናሹ ፡ ይገዛል ፡ ተባለላት ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ ያዕቆብን ፡ ወደድኹ ፡ ኤሳውን ፡ ግን ፡ ጠላኹ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዐመፃ ፡ አለ ፡ ወይ ፧ አይደለም ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ለሙሴ ፦ የምምረውን ፡ ኹሉ ፡ እምረዋለኹ ፡ ለምራራለትም ፡ ኹሉ ፡ እራራለታለኹ ፡ ይላልና ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ ምሕረት ፡ ለወደደ ፡ ወይም ፡ ለሮጠ ፡ አይደለም ፥ ከሚምር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ መጽሐፍ ፡ ፈርዖንን ፦ ኀይሌን ፡ ባንተ ፡ አሳይ ፡ ዘንድ ፡ ስሜም ፡ በምድር ፡ ኹሉ ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡ ለዚህ ፡ አስነሣኹኽ ፡ ይላልና ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ የሚወደውን ፡ ይምረዋል ፥ የሚወደውንም ፡ እልከኛ ፡ ያደርገዋል ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ይነቅፋል ፧ ፈቃዱንስ ፡ የሚቃወም ፡ ማን ፡ ነው ፧ ትለኝ ፡ ይኾናል ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንተ ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ የምትመልስ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ ሥራ ፡ ሠሪውን ፦ ስለ ፡ ምን ፡ እንዲህ ፡ አድርገኽ ፡ ሠራኸኝ ፡ ይለዋልን ፧

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ወይም ፡ ሸክላ ፡ ሠሪ ፡ ከአንዱ ፡ ጭቃ ፡ ክፍል ፡ አንዱን ፡ ዕቃ ፡ ለክብር ፡ አንዱንም ፡ ለውርደት ፡ ሊሠራ ፡ በጭቃ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውምን ፧

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 22-23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ቍጣውን ፡ ሊያሳይ ፡ ኀይሉንም ፡ ሊገልጥ ፡ ወዶ ፥ አስቀድሞ ፡ ለክብር ፡ ባዘጋጃቸው ፡ በምሕረት ፡ ዕቃዎች ፡ ላይ ፡ የክብሩን ፡ ባለጠግነት ፡ ይገልጥ ፡ ዘንድ ፥ ለጥፋት ፡ የተዘጋጁትን ፡ የቍጣ ፡ ዕቃዎች ፡ በብዙ ፡ ትዕግሥት ፡ ከቻለ ፥ እንዴት ፡ ነው ፧

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ የምሕረቱ ፡ ዕቃዎችም ፡ ከአይሁድ ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከአሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ የጠራን ፡ እኛ ፡ ነን ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በሆሴዕ ፦ ሕዝቤ ፡ ያልኾነውን ፡ ሕዝቤ ፡ ብዬ ፥ ያልተወደደችውንም ፡ የተወደደችው ፡ ብዬ ፡ እጠራለኹ ፤

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ እናንተ ፡ ሕዝቤ ፡ አይደላችኹም ፡ በተባለላቸውም ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ተብለው ፡ ይጠራሉ ፡ ይላል ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 27-28 ፤ ኢሳይያስም ፦ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ቍጥር ፡ ምንም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ቢኾን ፡ ቅሬታው ፡ ይድናል ፤ ጌታ ፡ ነገሩን ፡ ፈጽሞና ፡ ቈርጦ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ያደርገዋልና ፥ ብሎ ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ይጮኻል ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 29 ፤ ኢሳይያስም ፡ እንደዚሁ ፦ ጌታ ፡ ጸባኦት ፡ ዘር ፡ ባላስቀረልን ፡ እንደ ፡ ሰዶም ፡ በኾነ ፡ ገሞራንም ፡ በመሰልን ፡ ነበር ፡ ብሎ ፡ አስቀድሞ ፡ ተናገረ ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 30 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እንላለን ፧ ጽድቅን ፡ ያልተከተሉት ፡ አሕዛብ ፡ ጽድቅን ፡ አገኙ ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ ከእምነት ፡ የኾነ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፤

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 31 ፤ እስራኤል ፡ ግን ፡ የጽድቅን ፡ ሕግ ፡ እየተከተሉ ፡ ወደ ፡ ሕግ ፡ አልደረሱም ።

ሮሜ. ፡ 9 ፡ 32-33 ፤ ይህስ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በሥራ ፡ እንጂ ፡ በእምነት ፡ ጽድቅን ፡ ስላልተከተሉ ፡ ነው ፤ እንሆ ፥ በጽዮን ፡ የእንቅፋት ፡ ድንጋይና ፡ የማሰናከያ ፡ አለት ፡ አኖራለኹ ፡ በርሱም ፡ የሚያምን ፡ አያፍርም ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ በእንቅፋት ፡ ድንጋይ ፡ ተሰናከሉ ።

ሮሜ ፡ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የልቤ ፡ በጎ ፡ ፈቃድና ፡ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልመናዬ ፡ እንዲድኑ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ በዕውቀት ፡ አይቅኑ ፡ እንጂ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዲቀኑ ፡ እመሰክርላቸዋለኹና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ ሳያውቁ ፡ የራሳቸውንም ፡ ጽድቅ ፡ ሊያቆሙ ፡ ሲፈልጉ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ አልተገዙም ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የሚያምኑ ፡ ኹሉ ፡ ይጸድቁ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕግ ፡ ፍጻሜ ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ሙሴ ፡ ከሕግ ፡ የኾነውን ፡ ጽድቅ ፡ የሚያደርገው ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖር ፡ ጽፏልና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ከእምነት ፡ የኾነ ፡ ጽድቅ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ በልብኽ ፦ ማን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይወጣል ፧ አትበል ፤ ይህ ፡ ክርስቶስን ፡ ለማውረድ ፡ ነው ፤

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ወይም ፦ በልብኽ ፦ ወደ ፡ ጥልቁ ፡ ማን ፡ ይወርዳል ፧ አትበል ፤ ይህ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ለማውጣት ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ምን ፡ ይላል ፧ በአፍኽ ፡ በልብኽም ፡ ኾኖ ፡ ቃሉ ፡ ቀርቦልኻል ፤ ይህም ፡ የምንሰብከው ፡ የእምነት ፡ ቃል ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ኢየሱስ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በአፍኽ ፡ ብትመሰክር ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ እንዳስነሣው ፡ በልብኽ ፡ ብታምን ፡ ትድናለኽና ፤

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ ሰው ፡ በልቡ ፡ አምኖ ፡ ይጸድቃልና ፥ በአፉም ፡ መስክሮ ፡ ይድናልና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ መጽሐፍ ፦ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ኹሉ ፡ አያፍርም ፡ ይላልና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ በአይሁዳዊና ፡ በግሪክ ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ የለምና ፤ አንዱ ፡ ጌታ ፡ የኹሉ ፡ ጌታ ፡ ነውና ፥ ለሚጠሩትም ፡ ኹሉ ፡ ባለጠጋ ፡ ነው ፤

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ የጌታን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፡ ይድናልና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ ያላመኑበትን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ይጠሩታል ፧ ባልሰሙትስ ፡ እንዴት ፡ ያምናሉ ፧ ያለሰባኪስ ፡ እንዴት ፡ ይሰማሉ ፧

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 15 ፤ መልካሙን ፡ የምሥራች ፡ የሚያወሩ ፡ እግሮቻቸው ፡ እንዴት ፡ ያማሩ ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ካልተላኩ ፡ እንዴት ፡ ይሰብካሉ ፧

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ ለምሥራቹ ፡ ቃል ፡ አልታዘዙም ። ኢሳይያስ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ምስክርነታችንን ፡ ማን ፡ አመነ ፧ ብሏልና ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ እንግዲያስ ፡ እምነት ፡ ከመስማት ፡ ነው ፥ መስማትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፦ ባይሰሙ ፡ ነው ፡ ወይ ፧ እላለኹ ። በእውነት ፦ ድምፃቸው ፡ በምድር ፡ ዅሉ ፡ ላይ ፡ ቃላቸውም ፡ እስከዓለም ፡ ዳርቻ ፡ ወጣ ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ እስራኤል ፡ ባያውቁ ፡ ነው ፡ ወይ ፧ እላለኹ ። ሙሴ ፡ አስቀድሞ ፦ እኔ ፡ ሕዝብ ፡ በማይኾነው ፡ አስቀናችኋለኹ ፡ በማያስተውልም ፡ ሕዝብ ፡ አስቈጣችኋለኹ ፡ ብሏል ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 20 ፤ ኢሳይያስም ፡ ደፍሮ ፦ ላልፈለጉኝ ፡ ተገኘኹ ፥ ላልጠየቁኝም ፡ ተገለጥኹ ፡ አለ ።

ሮሜ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ ስለ ፡ እስራኤል ፡ ግን ፦ ቀኑን ፡ ዅሉ ፡ ወደማይታዘዝና ፡ ወደሚቃወም ፡ ሕዝብ ፡ እጆቼን ፡ ዘረጋኹ ፡ ይላል ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፦ እግዚአብሔር ፡ ሕዝቡን ፡ ጣላቸውን ፧ እላለኹ ። አይደለም ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እስራኤላዊና ፡ ከአብርሃም ፡ ዘር ፡ ከብንያምም ፡ ወገን ፡ ነኝና ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ያወቃቸውን ፡ ሕዝብ ፡ አልጣላቸውም ። መጽሐፍ ፡ ስለ ፡ ኤልያስ ፡ በተጻፈው ፡ የሚለውን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እስራኤልን ፡ እንዴት ፡ እንደሚከስ ፥ አታውቁምን ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ነቢያትኽን ፡ ገደሉ ፥ መሠዊያዎችኽንም ፡ አፈረሱ ፥ እኔም ፡ ብቻዬን ፡ ቀረኹ ፥ ነፍሴንም ፡ ይሻታል ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አምላካዊ ፡ መልስ ፡ ምን ፡ አለው ፧ ለበዓል ፡ ያልሰገዱትን ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ለእኔ ፡ አስቀርቻለኹ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ እንደዚሁም ፡ በአኹን ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ በጸጋ ፡ የተመረጡ ፡ ቅሬታዎች ፡ አሉ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ በጸጋ ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ከሥራ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቷል ፤ ጸጋ ፡ ያለዚያ ፡ ጸጋ ፡ መኾኑ ፡ ቀርቷል ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ እስራኤል ፡ የሚፈልጉትን ፡ አላገኙትም ፤ የተመረጡት ፡ ግን ፡ አገኙት ፤

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ ሌላዎቹም ፡ ደነዘዙ ፤ እንዲሁም ፦ ዐይኖቻቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ጐሮዎቻቸውም ፡ እንዳይሰሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእንቅልፍ ፡ መንፈስን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ሰጣቸው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ። ዳዊትም ፦

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ማእዳቸው ፡ ወጥመድና ፡ አሽክላ ፡ ማሰናከያም ፡ ፍዳም ፡ ይኹንባቸው ፤

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ ዐይኖቻቸው ፡ እንዳያዩ ፡ ይጨልሙ ፥ ዠርባቸውንም ፡ ዘወትር ፡ አጕብጥ ፡ ብሏል ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፦ የተሰናከሉ ፡ እስኪወድቁ ፡ ድረስ ፡ ነውን ፧ እላለኹ ። አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱን ፡ ያስቀናቸው ፡ ዘንድ ፡ በእነርሱ ፡ በደል ፡ መዳን ፡ ለአሕዛብ ፡ ኾነ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ በደላቸው ፡ ለዓለም ፡ ባለጠግነት ፡ መሸነፋቸውም ፡ ለአሕዛብ ፡ ባለጠግነት ፡ ከኾነ ፥ ይልቁንስ ፡ መመላታቸው ፡ እንዴት ፡ ይኾን ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 13-14 ፤ ለእናንተም ፡ ለአሕዛብ ፡ እናገራለኹ ። እኔ ፡ የአሕዛብ ፡ ሐዋርያ ፡ በኾንኹ ፡ መጠን ፡ ሥጋዬ ፡ የኾኑትን ፡ አስቀንቼ ፡ ምናልባት ፡ ከነርሱ ፡ አንዳንዱን ፡ አድን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አገልግሎቴን ፡ አከብራለኹ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ የእነርሱ ፡ መጣል ፡ ለዓለም ፡ መታረቅ ፡ ከኾነ ፡ ከሙታን ፡ ከሚመጣ ፡ ሕይወት ፡ በቀር ፡ መመለሳቸው ፡ ምን ፡ ይኾን ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ በኩራቱም ፡ ቅዱስ ፡ ከኾነ ፡ ቡሔው ፡ ደግሞ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ ሥሩም ፡ ቅዱስ ፡ ከኾነ ፡ ቅርንጫፎቹ ፡ ደግሞ ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከቅርንጫፎች ፡ አንዳንዱ ፡ ቢሰበሩ ፡ አንተም ፡ የበረሓ ፡ ወይራ ፡ የኾንኽ ፡ በመካከላቸው ፡ ገብተኽ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የወይራ ፡ ዘይት ፡ ከሚወጣው ፡ ሥር ፡ ተካፋይ ፡ ከኾንኽ ፥ በቅርንጫፎች ፡ ላይ ፡ አትመካ ፤

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ ብትመካባቸው ፡ ግን ፡ ሥሩ ፡ አንተን ፡ ይሸከምኻል ፡ እንጂ ፡ ሥሩን ፡ የምትሸከም ፡ አንተ ፡ አይደለኽም ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፦ እኔ ፡ እንድገባ ፡ ቅርንጫፎች ፡ ተሰበሩ ፡ ትል ፡ ይኾናል ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ መልካም ፤ እነርሱ ፡ ካለማመን ፡ የተነሣ ፡ ተሰበሩ ፥ አንተም ፡ ከእምነት ፡ የተነሣ ፡ ቆመኻል ። ፍራ ፡ እንጂ ፡ የትዕቢትን ፡ ነገር ፡ አታስብ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተፈጠሩት ፡ ለነበሩት ፡ ቅርንጫፎች ፡ የራራላቸው ፡ ካልኾነ ፡ ለአንተ ፡ ደግሞ ፡ አይራራልኽምና ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ እንግዲህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቸርነትና ፡ ጭከና ፡ ተመልከት ፤ ጭከናው ፡ በወደቁት ፡ ላይ ፡ ነው ፥ በቸርነቱ ፡ ግን ፡ ጸንተኽ ፡ ብትኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነው ፤ ያለዚያ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ትቈረጣለኽ ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ እነዚያም ፡ ደግሞ ፡ ባለማመናቸው ፡ ጸንተው ፡ ባይኖሩ ፥ በዛፉ ፡ ውስጥ ፡ ይገባሉ ፤ እግዚአብሔር ፡ መልሶ ፡ ሊያገባቸው ፡ ይችላልና ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ አንተ ፡ በፍጥረቱ ፡ የበረሓ ፡ ከነበረ ፡ ወይራ ፡ ተቈርጠኽ ፡ እንደ ፡ ፍጥረትኽ ፡ ሳትኾን ፡ በመልካም ፡ ወይራ ፡ ከገባኽ ፥ ይልቁንስ ፡ እነዚያ ፡ በፍጥረታቸው ፡ ያሉት ፡ ቅርንጫፎች ፡ በራሳቸው ፡ ወይራ ፡ እንዴት ፡ አይገቡም ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 25 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ልባሞች ፡ የኾናችኹ ፡ እንዳይመስላችኹ ፡ ይህን ፡ ምስጢር ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ፤ የአሕዛብ ፡ ሙላት ፡ እስኪገባ ፡ ድረስ ፡ ድንዛዜ ፡ በእስራኤል ፡ በአንዳንድ ፡ በኩል ፡ ኾነባቸው ፤

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 26 ፤ እንደዚሁም ፡ እስራኤል ፡ ኹሉ ፡ ይድናል ፤ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ። መድኀኒት ፡ ከጽዮን ፡ ይወጣል ፡ ከያዕቆብም ፡ ኀጢአተኛነትን ፡ ያስወግዳል ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ ኀጢአታቸውንም ፡ ስወስድላቸው ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የምገባው ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ በወንጌልስ ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ጠላቶች ፡ ናቸው ፥ በምርጫ ፡ በኩል ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አባቶች ፡ ተወዳጆች ፡ ናቸው ፤

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ እግዚአብሔር ፡ በጸጋው ፡ ስጦታና ፡ በመጥራቱ ፡ አይጸጸትምና ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ እናንተም ፡ ቀድሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳልታዘዛችኹ ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ካለመታዘዛቸው ፡ የተነሣ ፡ ምሕረት ፡ እንዳገኛችኹ ፥

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ እንዲሁ ፡ በተማራችኹበት ፡ ምሕረት ፡ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ ምሕረትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ እነዚህ ፡

ደግሞ ፡ አኹን ፡ አልታዘዙም ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኹሉን ፡ ይምር ፡ ዘንድ ፡ ኹሉን ፡ ባለመታዘዝ ፡ ዘግቶታልና ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባለጠግነትና ፡ ጥበብ ፡ ዕውቀቱም ፡ እንዴት ፡ ጥልቅ ፡ ነው ፤ ፍርዱ ፡ እንዴት ፡ የማይመረመር ፡ ነው ፥ ለመንገዱም ፡ ፍለጋ ፡ የለውም ።

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ የጌታን ፡ ልብ ፡ ያወቀው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ወይስ ፡ አማካሪው ፡ ማን ፡ ነበር ፧ ወይስ ፡ ብድራቱን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ የሰጠው ፡ ማን ፡ ነው ፧

ሮሜ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ኹሉ ፡ ከርሱና ፡ በርሱ ፡ ለርሱም ፡ ነውና ፤ ለርሱ ፡ ለዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ሰውነታችኹን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝና ፡ ሕያው ፡ ቅዱስም ፡ መሥዋዕት ፡ አድርጋችኹ ፡ ታቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ርኅራኄ ፡ እለምናችኋለኹ ፥ ርሱም ፡ ለአእምሮ ፡ የሚመች ፡ አገልግሎታችኹ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ርሱም ፡ በጎና ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ ፍጹምም ፡ የኾነው ፡ ነገር ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ፈትናችኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በልባችኹ ፡ መታደስ ፡ ተለወጡ ፡ እንጂ ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ አትምሰሉ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለያንዳንዱ ፡ የእምነትን ፡ መጠን ፡ እንዳካፈለው ፥ እንደ ፡ ባላእምሮ ፡ እንዲያስብ ፡ እንጂ ፡ ማሰብ ፡ ከሚገባው ፡ ዐልፎ ፡ በትዕቢት ፡ እንዳያስብ ፡ በመካከላችኹ ፡ ላለው ፡ ለያንዳንዱ ፡ በተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ እናገራለኹ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ባንድ ፡ አካል ፡ ብዙ ፡ ብልቶች ፡ እንዳሉን ፥ የብልቶቹም ፡ ኹሉ ፡ ሥራ ፡ አንድ ፡ እንዳይደለ ፥

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ እንዲሁ ፡ ብዙዎች ፡ ስንኾን ፡ በክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ነን ፥ ርስ ፡ በርሳችንም ፡ እያንዳንዳችን ፡ የሌላው ፡ ብልቶች ፡ ነን ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ እንደ ፡ ተሰጠንም ፡ ጸጋ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦታ ፡ አለን ፤ ትንቢት ፡ ቢኾን ፡ እንደ ፡ እምነታችን ፡ መጠን ፡ ትንቢት ፡ እንናገር ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ አገልግሎት ፡ ቢኾን ፡ በአገልግሎታችን ፡ እንትጋ ፤ የሚያስተምርም ፡ ቢኾን ፡ በማስተማሩ ፡ ይትጋ ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ የሚመክርም ፡ ቢኾን ፡ በመምከሩ ፡ ይትጋ ፤ የሚሰጥ ፡ በልግስና ፡ ይስጥ ፤ የሚገዛ ፡ በትጋት ፡ ይግዛ ፤ የሚምር ፡ በደስታ ፡ ይማር ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ፍቅራችኹ ፡ ያለግብዝነት ፡ ይኹን ። ክፉውን ፡ ነገር ፡ ተጸየፉት ፤ ከበጎ ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ ተባበሩ ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ በወንድማማች ፡ መዋደድ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተዋደዱ ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተከባበሩ ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ለሥራ ፡ ከመትጋት ፡ አትለግሙ ፤ በመንፈስ ፡ የምትቃጠሉ ፡ ኹኑ ፤ ለጌታ ፡ ተገዙ ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ በተስፋ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ በመከራ ፡ ታገሡ ፤ በጸሎት ፡ ጽኑ ፤

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ቅዱሳንን ፡ በሚያስፈልጋቸው ፡ ርዱ ፤ እንግዳዎችን ፡ ለመቀበል ፡ ትጉ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ የሚያሳድዷችኹን ፡ መርቁ ፥ መርቁ ፡ እንጂ ፡ አትርገሙ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ ደስ ፡ ከሚላቸው ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ከሚያለቅሱም ፡ ጋራ ፡ አልቅሱ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ባንድ ፡ ዐሳብ ፡ ተስማሙ ፤ የትዕቢትን ፡ ነገር ፡ አታስቡ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የትሕትናን ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ ትጉ ። ልባሞች ፡ የኾናችኹ ፡ አይምሰላችኹ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ለማንም ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ፈንታ ፡ ክፉን ፡ አትመልሱ ፤ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ፊት ፡ መልካም ፡ የኾነውን ፡ ዐስቡ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ቢቻላችኹስ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በሰላም ፡ ኑሩ ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ተወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ራሳችኹ ፡ አትበቀሉ ፥ ለቍጣው ፡ ፈንታ ፡ ስጡ ፡ እንጂ ፤ በቀል ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ብድራቱን ፡ እመልሳለኹ ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ ጠላትኽ ፡ ግን ፡ ቢራብ ፡ አብላው ፤ ቢጠማ ፡ አጠጣው ፤ ይህን ፡ በማድረግኽ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የእሳት ፡ ፍም ፡ ትከምራለኽና ።

ሮሜ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ክፉውን ፡ በመልካም ፡ አሸንፍ ፡ እንጂ ፡ በክፉ ፡ አትሸነፍ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 1 ፤ ነፍስ ፡ ኹሉ ፡ በበላይ ፡ ላሉት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ይገዛ ። ከእግዚአብሔር ፡ ካልተገኘ ፡ በቀር ፡ ሥልጣን ፡ የለምና ፤ ያሉትም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተሾሙ ፡ ናቸው ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 2 ፤ ስለዚህ ፥ ባለሥልጣንን ፡ የሚቃወም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥርዐት ፡ ይቃወማል ፤ የሚቃወሙትም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ፍርድን ፡ ይቀበላሉ ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ገዢዎች ፡ ለክፉ ፡ አድራጊዎች ፡ እንጂ ፥ መልካም ፡ ለሚያደርጉ ፡ የሚያስፈሩ ፡ አይደሉምና ። ባለሥልጣንን ፡ እንዳትፈራ ፡ ትወዳለኽን ፧ መልካሙን ፡ አድርግ ፡ ከርሱም ፡ ምስጋና ፡ ይኾንልኻል ፤

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ ለመልካም ፡ ነገር ፡ ለአንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ። በከንቱ ፡ ግን ፡ ሰይፍ ፡ አይታጠቅምና ፡ ክፉ ፡ ብታደርግ ፡ ፍራ ፤ ቍጣውን ፡ ለማሳየት ፡ ክፉ ፡ አድራጊውን ፡ የሚበቀል ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋይ ፡ ነውና ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ስለ ፡ ቍጣው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ኅሊና ፡ ደግሞ ፡ መገዛት ፡ ግድ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፥ ትገብራላችኹና ፤ በዚህ ፡ ነገር ፡ የሚተጉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸውና ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ ለኹሉ ፡ የሚገባውን ፡ አስረክቡ ፤ ግብር ፡ ለሚገባው ፡ ግብርን ፥ ቀረጥ ፡ ለሚገባው ፡ ቀረጥን ፥ መፈራት ፡ ለሚገባው ፡ መፈራትን ፥ ክብር ፡ ለሚገባው ፡ ክብርን ፡ ስጡ ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ከመዋደድ ፡ በቀር ፡ ለማንም ፡ ዕዳ ፡ አይኑርባችኹ ፥ ሌላውን ፡ የሚወድ ፡ ሕግን ፡ ፈጽሞታልና ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ አታመንዝር ፥ አትግደል ፥ አትስረቅ ፥ በውሸት ፡ አትመስክር ፥ አትመኝ ፡ የሚለው ፡ ከሌላዉቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡— ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ነፍስኽ ፡ ውደድ ፡ በሚለው ፡ ቃል ፡ ተጠቅሷል ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ፍቅር ፡ ለባልንጀራው ፡ ክፉ ፡ አያደርግም ፤ ስለዚህ ፥ ፍቅር ፡ የሕግ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ከእንቅልፍ ፡ የምትነሡበት ፡ ሰዓት ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ ዘመኑን ፡ ዕወቁ ፤ ካመንበት ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡ መዳናችን ፡ ዛሬ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ ቀርቧልና ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ሌሊቱ ፡ ዐልፏል ፥ ቀኑም ፡ ቀርቧል ። እንግዲህ ፡ የጨለማውን ፡ ሥራ ፡ አውጥተን ፡ የብርሃንን ፡ ጋሻ ፡ ጦር ፡ እንልበስ ።

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ በቀን ፡ እንደምንኾን ፡ በአገባብ ፡ እንመላለስ ፤ በዘፈንና ፡ በስካር ፡ አይኹን ፥ በዝሙትና ፡ በመዳራት ፡ አይኹን ፥ በክርክርና ፡ በቅናት ፡ አይኹን ፤

ሮሜ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጌታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ልበሱት ፤ ምኞቱንም ፡ እንዲፈጽም ፡ ለሥጋ ፡ አታስቡ ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ በእምነት ፡ የደከመውንም ፡ ተቀበሉት ፥ በዐሳቡም ፡ ላይ ፡ አትፍረዱ ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ ኹሉን ፡ ይበላ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተፈቀደለት ፡ የሚያምን ፡ አለ ፥ ደካማው ፡ ግን ፡ አትክልት ፡ ይበላል ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ የሚበላ ፡ የማይበላውን ፡ አይናቀው ፡ የማይበላውም ፡ በሚበላው ፡ አይፍረድ ፥ እግዚአብሔር ፡ ተቀብሎታልና ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ አንተ ፡ በሌላው ፡ ሎሌ ፡ የምትፈርድ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧ ርሱ ፡ ቢቆም ፡ ወይም ፡ ቢወድቅ ፡ ለገዛ ፡ ጌታው ፡ ነው ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ሊያቆመው ፡ ይችላልና ፥ ይቆማል ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ ይህ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ከሌላ ፡ ቀን ፡ እንዲሻል ፡ ያስባል ፥ ያ ፡ ግን ፡ ቀን ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያስባል ፤ እያንዳንዱ ፡ በገዛ ፡ አእምሮው ፡ አጥብቆ ፡ ይረዳ ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ ቀንን ፡ የሚያከብር ፡ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ ያከብራል ፤ የሚበላም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናልና ፥ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ ይበላል ፤ የማይበላም ፡ ለጌታ ፡ ብሎ ፡ አይበላም ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ያመሰግናል ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ ከእኛ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ ለራሱ ፡ የሚኖር ፡ የለምና ፥ ለራሱም ፡ የሚሞት ፡ የለም ፤

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ በሕይወት ፡ ኾነን ፡ ብንኖር ፡ ለጌታ ፡ እንኖራለንና ፥ ብንሞትም ፡ ለጌታ ፡ እንሞታለን ። እንግዲህ ፡ በሕይወት ፡ ኾነን ፡ ብንኖር ፡ ወይም ፡ ብንሞት ፡ የጌታ ፡ ነን ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፥ ሙታንንም ፡ ሕያዋንንም ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፥ ክርስቶስ ፡ ሞቷልና ፥ ሕያውም ፡ ኾኗልና ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ አንተም ፡ በወንድምኽ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትፈርዳለኽ ፧ ወይስ ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ወንድምኽን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትንቃለኽ ፧ ኹላችን ፡ በክርስቶስ ፡ ፍርድ ፡ ወንበር ፡ ፊት ፡ እንቆማለንና ፦

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፥ ይላል ፡ ጌታ ፥ ጕልበት ፡ ኹሉ ፡ ለእኔ ፡ ይንበረከካል ፡ ምላስም ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግናል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ እንግዲያስ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ስለ ፡ ራሳችን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልስ ፡ እንሰጣለን ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ እንግዲህ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ አንፈራረድ ፤ ይልቁን ፡ ግን ፡ ለወንድም ፡

እንቅፋትን ፡ ወይም ፡ ማሰናከያን ፡ ማንም ፡ እንዳያኖርበት ፡ ይህን ፡ ቀ፡ረጡ ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ በራሱ ፡ ርኩስ ፡ የ"ኾነ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ሌለ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ "ኾኜ ፡ ዐውቄያለ"ኹ ፡ ተረድቻለ"ኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ርኩስ ፡ እንዲ"ኾን ፡ ለሚቈጥር ፡ ለርሱ ፡ ርኩስ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ወንድም"ኽንም ፡ በመብል ፡ ምክንያት ፡ የምታሳዝን ፡ ከ"ኾንኽ ፡ እንግዲህ ፡ በፍቅር ፡ አልተመላለስ"ኽም ። ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሞተለትን ፡ ርሱን ፡ በመብልኽ ፡ አታጥፋው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ ለእናንተ ፡ ያለው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ አይሰደብ ፤

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ጽድቅና ፡ ሰላም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የ"ኾነ ፡ ደስታ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ አይደለችምና ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ እንደዚህ ፡ አድርጎ ፡ ለክርስቶስ ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሠኛልና ፥ በሰውም ፡ ዘንድ ፡ የተመሰገነ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ እንግዲያስ ፡ ሰላም ፡ የሚቆምበትን ፡ ርስ ፡ በርሳችንም ፡ የምንታነጽበትን ፡ እንከተል ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ በመብል ፡ ምክንያት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ አታፍርስ ። "ኹሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፥ በመጠራጠር ፡ የተበላ ፡ እንደ ፡ "ኾነ ፡ ግን ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ክፉ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 21 ፤ ሥጋን ፡ አለመብላት ፡ ወይንንም ፡ አለመጠጣት ፡ ወንድም"ኽም ፡ የሚሰናከልበትን ፡ አለማድረግ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 22 ፤ ለአንተ ፡ ያለ"ኽ ፡ እምነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለራስ"ኽ ፡ ይ"ኹንልኽ ። ፈትኖ ፡ መልካም ፡ እንዲ"ኾን ፡ በሚቈጥረው ፡ ነገር ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ የማይፈርድ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 14 ፡ 23 ፤ የሚጠራጠረው ፡ ግን ፡ ቢበላ ፡ በእምነት ፡ ስላል"ኾነ ፡ ተኰንኗል ፤ በእምነትም ፡ ያል"ኾነ ፡ "ኹሉ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ እኛም ፡ ኀይለኞች ፡ የ"ኾንን ፡ የደካማዎችን ፡ ድካም ፡ እንድንሸከም ፡ ራሳችንንም ፡ ደስ ፡ እንዳናሠኝ ፡ ይገ"ባናል ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ እያንዳንዳችን ፡ እንድናንጸው ፡ ርሱን ፡ ለመጥቀም ፡ ባልንጀራችንን ፡ ደስ ፡ እናሠኝ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 3 ፤ ክርስቶስ ፡ ራሱን ፡ ደስ ፡ አላሠኘምና ፤ ነገር ፡ ግን ፦ አንተን ፡ የነቀፉበት ፡ ነቀፋ ፡ ወደቀብኝ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ "ኾነበት ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 4 ፤ በመጽናትና ፡ መጻሕፍት ፡ በሚሰጡት ፡ መጽናናት ፡ ተስፋ ፡ ይ"ኾንልን ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሞ ፡ የተጻፈው ፡ "ኹሉ ፡ ለትምህርታችን ፡ ተጽፏልና ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 5-6 ፤ ባንድ ፡ ልብ ፡ "ኾናችኹ ፡ ባንድ ፡ አፍ ፡ እግዚአብሔርን ፥ ርሱም ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፥ ታከብሩ ፡ ዘንድ ፥ የትዕግሥትና ፡ የመጽናናት ፡ አምላክ ፡ እንደክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፈቃድ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ባንድ ፡ ዐሳብ ፡ መ"ኾንን ፡ ይስጣችኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ ተቀበላችኹ ፡ እንዲሁ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተቀባበሉ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 8-9 ፤ ለአባቶች ፡ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡ ደግሞም ፦ ስለዚህ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ አመሰግንሻለኹ ፡ ለስምሽም ፡ እዘምራለኹ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ ምሕረቱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፥ ክርስቶስ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ እውነት ፡ የመገረዝ ፡ አገልጋይ ፡ ኾነ ፡ እላለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 10 ፤ ደግሞም ፦ አሕዛብ ፡ ሆይ ፥ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፡ ይላል ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 11 ፤ ደግሞም ፦ እናንተ ፡ አሕዛብ ፡ ኹላችኹ ፥ ጌታን ፡ አመስግኑ ፡ ሕዝቦቹም ፡ ኹሉ ፡ ይወድሱት ፡ ይላል ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 12 ፤ ደግሞም ፡ ኢሳይያስ ፦ የእሴይ ፡ ሥር ፡ አሕዛብንም ፡ ሊገዛ ፡ የሚነሣው ፡ ይኾናል ፤ በርሱ ፡ አሕዛብ ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋሉ ፡ ይላል ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 13 ፤ የተስፋ ፡ አምላክም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኀይል ፡ በተስፋ ፡ እንድትበዙ ፡ በማመናችኹ ፡ ደስታንና ፡ ሰላምን ፡ ኹሉ ፡ ይሙላባችኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 14 ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ ደግሞ ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በበጎነት ፡ ራሳችኹ ፡ እንደ ፡ ተሞላችኹ ፥ ዕውቀትም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሞላባችኹ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹም ፡ ደግሞ ፡ ልትገሠጹ ፡ እንዲቻላችኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተረድቻለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 15-16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አሕዛብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቀድሰው ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ ሊኾኑ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ካህን ፡ እያገለገልኹ ፥ ለአሕዛብ ፡ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አገልጋይ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በተሰጠኝ ፡ ጸጋ ፡ ምክንያት ፡ ተመልሼ ፡ ላሳስባችኹ ፡ ብዬ ፡ በአንዳንድ ፡ ቦታ ፡ በድፍረት ፡ ጻፍኹላችኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሚኾን ፡ ነገር ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ትምክሕት ፡ አለኝ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 18-19 ፤ አሕዛብ ፡ እንዲታዘዙ ፡ ክርስቶስ ፡ በቃልና ፡ በሥራ ፥ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፡ ኀይል ፥ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኀይል ፡ በእኔ ፡ አድርጎ ፡ ከሠራው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ልናገር ፡ አልደፍርም ፤ ስለዚህ ፥ ከኢየሩሳሌም ፡ ዠምሬ ፡ እስከ ፡ እልዋሪቆን ፡ ድረስ ፡ እየዞርኹ ፡ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ ፈጽሜ ፤ ሰብኬያለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 20 ፤ እንዲሁም ፡ በሌላው ፡ ሰው ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ እንዳልሠራ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ በተጠራበት ፡ ስፍራ ፡ ሳይኾን ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ተጣጣርኹ ፤

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ስለ ፡ ርሱ ፡ ያልተወራላቸው ፡ ያያሉ ፥ ያልሰሙም ፡ ያስተውላሉ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ ነው ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 22 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተከለከልኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 23 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ስለሌለኝ ፥ ከብዙ ፡ ዓመትም ፡ ዠምሬ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ ናፍቆት ፡ ስለ ፡ አለኝ ፥

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 24 ፤ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፡ ሳልፍ ፡ እናንተን ፡ እንዳይ ፥ አስቀድሜም ፡ ጥቂት ፡ ብጠግባችኹ ፡ ወደዚያ ፡ በጕዞዬ ፡ እንድትረዱኝ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 25 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ቅዱሳንን ፡ ለማገልገል ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እኼዳለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 26 ፤ መቄዶንያና ፡ አካይያ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቅዱሳን ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ድኻዎች ፡ ይረዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደዋልና ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 27 ፤ ወደዋልና ፥ የእነርሱም ፡ ባለዕዳዎች ፡ ናቸው ፤ አሕዛብ ፡ በእነርሱ ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገርን ፡ ተካፋዮች ፡ ከኾኑ ፡ በሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ ያገለግሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ይገባቸዋልና ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 28 ፤ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ፈጽሜ ፡ ይህን ፡ ፍሬ ፡ ካተምኩላቸው ፡ በኋላ ፡ በእናንተ ፡ በኩል ፡ ዐልፌ ፡ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ እኼዳለኹ ፤

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 29 ፤ ወደ ፡ እናንተም ፡ ስመጣ ፡ በክርስቶስ ፡ በረከት ፡ ሙላት ፡ እንድመጣ ፡ ዐውቃለኹ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 30 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ እኔ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እየጸለያችኹ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ትጋደሉ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ በመንፈስ ፡ ፍቅር ፡ እለምናችኋለኹ ፤

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 31-32 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በደስታ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥቼ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንዳርፍ ፥ በይሁዳ ፡ ካሉት ፡ ከማይታዘዙ ፡ እድን ፡ ዘንድ ፥ ለኢየሩሳሌምም ፡ ያለኝ ፡ አገልግሎቴ ፡ ቅዱሳንን ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩ ።

ሮሜ. ፡ 15 ፡ 33 ፤ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ከኹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ሮሜ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ በክንክራኦስ ፡ ባለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋይ ፡ የምትኾን ፡ እኅታችንን ፡ ፌቤንን ፡ ዐደራ ፡ ብያችኋለኹ ፤

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ለቅዱሳን ፡ እንደሚገባ ፡ በጌታ ፡ ተቀበሏት ፥ ርሷ ፡ ለብዙዎች ፡ ለኔም ፡ ለራሴ ፡ ደጋፊ ፡ ነበረችና ፥ ከእናንተም ፡ በምትፈልገው ፡ በማናቸውም ፡ ነገር ፡ ርዷት ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ዐብረውኝ ፡ ለሚሠሩ ፡ ለጵርስቅላና ፡ ለአቂላ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ፤

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፡ ስለ ፡ ነፍሴ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ለሞት ፡ አቀረቡ ፥ የአሕዛብም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ የሚያመሰግኗቸው ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለኹም ፤

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ በቤታቸውም ፡ ላለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከእስያ ፡ ለክርስቶስ ፡ በኩራት ፡ ለኾነው ፡ ለምወደው ፡ ለአጤኔጦን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ ብዙ ፡ ለደከመች ፡ ለማርያ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ በሐዋርያት ፡ መካከል ፡ ስመ ፡ ጥሩዎች ፡ ለኾኑ ፥ ደግሞም ፡ ክርስቶስን ፡ በማመን ፡ ለቀደሙኝ ፥ ዐብረውኝም ፡ ለታሰሩ ፡ ለዘመዶቼ ፡ ለአንዲራኒቆንና ፡ ለዩልያን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ በጌታ ፡ ለምወደው ፡ ለጵልያጦን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ በክርስቶስ ፡ ዐብሮን ፡ ለሚሠራ ፡ ለኢሩባኖን ፡ ለምወደውም ፡ ለስንጣክን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ በክርስቶስ ፡ መኾኑ ፡ ተፈትኖ ፡ ለተመሰገነው ፡ ለኤጤሌን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከአርስጣባሉ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ላሉት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ለዘመዴ ፡ ለሄሮድዮና ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከንርቀሱ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ በጌታ ፡ ላሉት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ በጌታ ፡ ኾነው ፡ ለሚደክሙ ፡ ለፕሮፊሞናና ፡ ለጢሮፊሞሳ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። በጌታ ፡ እጅግ ፡ ለደከመች ፡ ለተወደደች ፡ ለጠርሲዳ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ በጌታ ፡ ኾኖ ፡ ለታወቀ ፡ ለሩፎን ፡ ለኔና ፡ ለርሱም ፡ እናት ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ለአስቀሪጦንና ፡ ለአፍለሶንጳ ፡ ለሄሮሜንም ፡ ለጳጥሮባም ፡ ለሄርማንም ፡ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ ወንድሞች ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ ለፍሌጎንና ፡ ለዩልያ ፡ ለኔርያና ፡ ለእኅቱም ፡ ለአልንጦንም ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ላሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ በተቀደሰ ፡ አሳሳም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ። የክርስቶስ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ የተማራችኹትን ፡ ትምህርት ፡ የሚቃወሙትን ፡ መለያየትንና ፡ ማሰናከያን ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሰዎች ፡ እንድትመለከቱ ፡ እለምናችኋለኹ ፥ ከነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀቅ ፡ በሉ ፤

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ እንዲህ ፡ ያሉት ፡ ለገዛ ፡ ሆዳቸው ፡ እንጂ ፡ ለጌታችን ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይገዙምና ፥ በመልካምና ፡ በሚያቈላምጥ ፡ ንግግርም ፡ ተንኰል ፡ የሌለባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ያታልላሉ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ መታዘዛችኹ ፡ ለኹሉ ፡ ተወርቷልና ፤ እንግዲህ ፡ በእናንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ጥበበኞች ፡ ለክፉም ፡ የዋሆች ፡ እንድትኾኑ ፡ እወዳለኹ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ሰይጣንን ፡ ከእግራችኹ ፡ በታች ፡ ፈጥኖ ፡ ይቀጠቅጠዋል ። የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ ዐብሮኝ ፡ የሚሠራ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ዘመዶቼም ፡ ሉቂዮስና ፡ ኢያሶን ፡ ሱሲጴጥሮስም ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 22 ፤ ይህን ፡ መልእክት ፡ የጻፍኹ ፡ እኔ ፡ ጤርጥዮስ ፡ በጌታ ፡ ሰላምታ ፡ አቀርብላችኋለኹ ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 23 ፤ የእኔና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኹሉ ፡ አስተናጋጅ ፡ ጋይዮስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርብላችኋል ። የከተማው ፡ መጋቢ ፡ ኤርስጦስ ፡ ወንድማችንም ፡ ቁአስጥሮስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 24 ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከኹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 25-26 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ወንጌሌ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ተሰበከ ፥ ከዘለዓለም ፡ ዘመንም ፡ የተሰወረው ፡ አኹን ፡ ግን ፡ የታየው ፡ በነቢያትም ፡ መጻሕፍት ፡ የዘለዓለም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ አዘዘ ፡ ለእምነት ፡ መታዘዝ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ለአሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ የታወቀው ፡ ምስጢር ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ መጠን ፡ ሊያበረታችኹ ፡ ለሚችለው ፥

ሮሜ. ፡ 16 ፡ 27 ፤ ብቻውን ፡ ጥበብ ፡ ላለው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

መዠመሪያዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ ሊኾን ፡ የተጠራ ፡ ጳውሎስ ፣ ወንድሙም ፡ ሶስቴንስ ፥

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 2 ፤ በቆሮንቶስ ፡ ላለች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ለተቀደሱት ፥ የእነርሱና ፡ የእኛ ፡ ጌታ ፡ የኾነውን ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ በየስፍራው ፡ ከሚጠሩት ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ቅዱሳን ፡ ለመኾን ፡ ለተጠሩት ፤

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ስላመናችኹ ፡ በተሰጣችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ምክንያት ፡ ዘወትር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አምላክን ፡ አመሰግናለኹ ፤

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 5-6 ፤ ለክርስቶስ ፡ መመስከሬ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ጸና ፥ በነገር ፡ ኹሉ ፣ በቃልም ፡ ኹሉ ፣ በዕውቀትም ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ባለጠጋዎች ፡ እንድትኾኑ ፡ ተደርጋችኋልና ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ እንደዚህ ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ መገለጥ ፡ ስትጠባበቁ ፡ አንድ ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ እንኳ ፡ አይጐድልባችኹም ፤

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቀን ፡ ያለነቀፋ ፡ እንድትኾኑ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ያጸናችኋል ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ወደልጁ ፡ ወደጌታችን ፡ ወደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኅብረት ፡ የጠራችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ኹላችኹ ፡ አንድ ፡ ንግግር ፡ እንድትናገሩ ፡ ባንድ ፡ ልብና ፡ ባንድ ፡ ዐሳብም ፡ የተባበራችኹ ፡ እንድትኾኑ ፡ እንጂ ፡ መለያየት ፡ በመካከላችኹ ፡ እንዳይኾን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እለምናችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በመካከላችኹ ፡ ክርክር ፡ እንዳለ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የቀሎዔ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ አስታውቀውኛልና ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ይህንም ፡ እላለኹ ፦ እያንዳንዳችኹ ፦ እኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ነኝ ፥ እኔስ ፡ የአጵሎስ ፡ ነኝ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ የኬፋ ፡ ነኝ ፥ እኔስ ፡ የክርስቶስ ፡ ነኝ ፡ ትላላችኹ ።

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ክርስቶስ ፡ ተከፍሏልን ፧ ጳውሎስስ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተሰቀለን ፧ ወይስ ፡ በጳውሎስ ፡ ስም ፡ ተጠመቃችኹን ፧

ቆሮ.1 ፥ 1 ፥ 14-15 ፤ በስሜ ፡ እንደ ፡ ተጠመቃችኹ ፡ ማንም ፡ እንዳይል ፡ ከቀርስጶስና ፡ ከጋይዮስ ፡ በቀር ፡ ከእናንተ ፡ አንድን ፡ እንኳ ፡ ስላላጠመቅኹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 16 ፤ የእስጢፋኖስንም ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ አጥምቄያለኹ ፤ ጨምሬ ፡ ሌላ ፡ አጥምቄ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላውቅም ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 17 ፤ ለማጥመቅ ፡ ክርስቶስ ፡ አልላከኝምና ፥ ወንጌልን ፡ ልሰብክ ፡ እንጂ ፤ የክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ከንቱ ፡ እንዳይኾን ፡ በቃል ፡ ጥበብ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 18 ፤ የመስቀሉ ፡ ቃል ፡ ለሚጠፉት ፡ ሞኝነት ፥ ለእኛ ፡ ለምንድን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ነውና ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 19 ፤ የጥበበኞችን ፡ ጥበብ ፡ አጠፋለኹ ፥ የአስተዋዮችንም ፡ ማስተዋል ፡ እጥላለኹ ፥ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 20 ፤ ጥበበኛ ፡ የት ፡ አለ ፧ ጸሐፊ ፡ የት ፡ አለ ፧ የዚች ፡ ዓለም ፡ መርማሪ ፡ የት ፡ አለ ፧ እግዚአብሔር ፡ የዚችን ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ ሞኝነት ፡ እንዲኾን ፡ አላደረገምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 21 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ ምክንያት ፡ ዓለም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጥበቧ ፡ ስላላወቀች ፥ በስብከት ፡ ሞኝነት ፡ የሚያምኑትን ፡ ሊያድን ፡ የእግዚአብሔር ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ኾኗልና ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 22 ፤ መቼም ፡ አይሁድ ፡ ምልክትን ፡ ይለምናሉ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ጥበብን ፡ ይሻሉ ፥

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 23 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ የተሰቀለውን ፡ ክርስቶስን ፡ እንሰብካለን ፤ ይህም ፡ ለአይሁድ ፡ ማሰናከያ ፡ ለአሕዛብም ፡ ሞኝነት ፡ ነው ፥

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 24 ፤ ለተጠሩት ፡ ግን ፥ አይሁድ ፡ ቢኾኑ ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ቢኾኑ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ኀይልና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ የኾነው ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 25 ፤ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሞኝነት ፡ ይጠበባልና ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ድካም ፡ ከሰው ፡ ይልቅ ፡ ይበረታልና ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 26 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ መጠራታችኹን ፡ ተመልከቱ ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ ጥበብ ፡ ጥበበኞች ፡ የኾኑ ፡ ብዙዎች ፥ ኀያላን ፡ የኾኑ ፡ ብዙዎች ፥ ባላባቶች ፡ የኾኑ ፡ ብዙዎች ፡ አልተጠሩም ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ጥበበኞችን ፡ እንዲያሳፍር ፡ የዓለምን ፡ ሞኝ ፡ ነገር ፡ መረጠ ፤ ብርቱንም ፡ ነገር ፡ እንዲያሳፍር ፡ እግዚአብሔር ፡ የዓለምን ፡ ደካማ ፡ ነገር ፡ መረጠ ፤

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ እንዲያጠፋ ፡ የዓለምን ፡ ምናምንቴ ፡ ነገር ፡ የተናቀውንም ፡ ነገር ፡ ያልኾነውንም ፡ ነገር ፡ መረጠ ፥

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 29 ፤ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዳይመካ ።

ቆሮ.1 ፡ 1 ፡ 30-31 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ የሚመካ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይመካ ፡ ተብሎ ፡ እንደተጻፈው ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጥበብና ፡ ጽድቅ ፣ ቅድስናም ፣ ቤዛነትም ፡ በተደረገልን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የኾናችኹ ፡ ከርሱ ፡ ነው ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 1 ፤ እኔም ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እናንተ ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፡ በቃልና ፡ በጥበብ ፡ ብልጫ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስክርነቴን ፡ ለእናንተ ፡ እየነገርኹ ፡ አልመጣኹም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 2 ፤ በመካከላችኹ ፡ ሳለኹ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፥ ርሱም ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡

እንዳላውቅ ፡ ቈርጬ ፡ ነበርና ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 3 ፤ እኔም ፡ በድካምና ፡ በፍርሀት ፡ በብዙ ፡ መንቀጥቀጥም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ነበርኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 4-5 ፤ እምነታችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡ ጥበብ ፡ እንዳይኾን ፥ ቃሌም ፡ ስብከቴም ፡ መንፈስንና ፡ ኀይልን ፡ በመግለጥ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፥ በሚያባብል ፡ በጥበብ ፡ ቃል ፡ አልነበረም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ በበሰሉት ፡ መካከል ፡ ግን ፡ ጥበብን ፡ እንናገራለን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የዚችን ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ አይደለም ፡ የሚሻሩትንም ፡ የዚችን ፡ ዓለም ፡ ገዢዎች ፡ ጥበብ ፡ አይደለም ፤

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ከዘመናት ፡ በፊት ፡ ለክብራችን ፡ የወሰነውን ፥ ተሰውሮም ፡ የነበረውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥበብ ፡ በምስጢር ፡ እንናገራለን ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ ከዚችም ፡ ዓለም ፡ ገዢዎች ፡ አንዱ ፡ እንኳ ፡ ይህን ፡ ጥበብ ፡ አላወቀም ፤ ዐውቀውስ ፡ ቢኾኑ ፡ የክብርን ፡ ጌታ ፡ ባልሰቀሉትም ፡ ነበር ፤

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ዐይን ፡ ያላየችው ፡ ጕሮም ፡ ያልሰማው ፡ በሰውም ፡ ልብ ፡ ያልታሰበው ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚወዱት ፡ ያዘጋጀው ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ እንዲህ ፡ እንናገራለን ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ መንፈስም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡ ሳይቀር ፡ ኹሉን ፡ ይመረምራልና ፥ ለእኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንፈሱ ፡ በኩል ፡ ገለጠው ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ካለው ፡ ከሰው ፡ መንፈስ ፡ በቀር ፡ ለሰው ፡ ያለውን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ ማን ፡ ነው ፧ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በቀር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ማንም ፡ አያውቅም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንዲያው ፡ የተሰጠንን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የኾነውን ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ የዓለምን ፡ መንፈስ ፡ አልተቀበልንም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ መንፈሳዊውን ፡ ነገር ፡ ከመንፈሳዊው ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ አስተያይተን ፡ መንፈስ ፡ በሚያስተምረን ፡ ቃል ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ እንናገራለን ፡ እንጂ ፡ የሰው ፡ ጥበብ ፡ በሚያስተምረን ፡ ቃል ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ለፍጥረታዊ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነገር ፡ ሞኝነት ፡ ነውና ፥ አይቀበለውም ፤ በመንፈስም ፡ የሚመረመር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ሊያውቀው ፡ አይችልም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ መንፈሳዊ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ ኹሉን ፡ ይመረምራል ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ በማንም ፡ አይመረመርም ።

ቆሮ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ እንዲያስተምረው ፡ የጌታን ፡ ልብ ፡ ማን ፡ ዐውቆት ፡ ነው ፧ እኛ ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ልብ ፡ አለን ።

1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ እኔም ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የሥጋ ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፥ በክርስቶስም ፡ ሕፃናት ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፡ እንጂ ፡ መንፈሳውያን ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፡ ልናገራችኹ ፡ አልቻልኹም ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ገና ፡ ጽኑ ፡ መብል ፡ ለመብላት ፡ አትችሉም ፡ ነበርና ፥ ወተት ፡ ጋትኳችኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ገና ፡ ሥጋውያን ፡ ናችኹና ፥ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ገና ፡ አትችሉም ። ቅናትና ፡ ክርክር ፡ ስለሚገኝባችኹ ፡ ሥጋውያን ፡ መኾናችኹ ፡ አይደላችኹምን ፧ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድስ ፡ አትመላለሱምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ አንዱ ፦ እኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ነኝ ፥ ኹለተኛውም ፦ እኔ ፡ የአጵሎስ ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡

መኾናችኹ ፡ አይደለምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ አጵሎስ ፡ እንግዲህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ጳውሎስስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በእነርሱ ፡ እጅ ፡ ያመናችኹ ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸው ፤ ለያንዳንዳቸውም ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ያገለግላሉ ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ እኔ ፡ ተከልኹ ፡ አጵሎስም ፡ አጠጣ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ያሳድግ ፡ ነበር ፤

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንግዲያስ ፡ የሚያሳድግ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ የሚተክል ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ የሚያጠጣ ፡ ቢኾን ፡ አንዳች ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ የሚተክልና ፡ የሚያጠጣ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ ድካም ፡ መጠን ፡ የራሱን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ይቀበላል ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ዕርሻ ፡ ናችኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሕንፃ ፡ ናችኹ ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረን ፡ የምንሠራ ፡ ነንና ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንደተሰጠኝ ፡ መጠን ፡ እንደ ፡ ብልኀተኛ ፡ የዐናጺ ፡ አለቃ ፡ መሠረትን ፡ መሠረትኹ ፥ ሌላውም ፡ በላዩ ፡ ያንጻል ። እያንዳንዱ ፡ ግን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንዲያንጽ ፡ ይጠንቀቅ ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ከተመሠረተው ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ሌላ ፡ መሠረት ፡ ሊመሠርት ፡ አይችልምና ፥ ርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ ማንም ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ በወርቅ ፡ ቢኾን ፡ በብርም ፡ በከበረ ፡ ድንጋይም ፡ በዕንጨትም ፡ በሣርም ፡ ወይም ፡ በአገዳ ፡ ቢያንጽ ፥ የያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ ይገለጣል ፤

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ በእሳት ፡ ስለሚገለጥ ፡ ያ ፡ ቀን ፡ ያሳያልና ፥ የያንዳንዱም ፡ ሥራ ፡ እንዴት ፡ መኾኑን ፡ እሳቱ ፡ ይፈትነዋል ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ማንም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ያነጸው ፡ ሥራ ፡ ቢጸናለት ፡ ደመ ፡ ወዙን ፡ ይቀበላል ፤

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ የማንም ፡ ሥራ ፡ የተቃጠለበት ፡ ቢኾን ፡ ይጐዳበታል ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ግን ፡ ይድናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእሳት ፡ እንደሚድን ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ እንዲኖርባችኹ ፡ አታውቁምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ ማንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቢያፈርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ርሱን ፡ ያፈርሰዋል ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፥ ያውም ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ማንም ፡ ራሱን ፡ አያታል ፤ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ በዚች ፡ ዓለም ፡ ጥበበኛ ፡ የኾነ ፡ ቢመስለው ፡ ጥበበኛ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ሞኝ ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 19-20 ፤ የዚች ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሞኝነት ፡ ነውና ፦ ርሱ ፡ ጥበበኞችን ፡ በተንኰላቸው ፡ የሚይዝ ፤ ደግሞም ፦ ጌታ ፡ የጥበበኞችን ፡ ዐሳብ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያውቃል ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ ስለዚህም ፡ ማንም ፡ በሰው ፡ አይመካ ። ነገር ፡ ኹሉ ፡ የእናንተ ፡ ነውና ፤

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 22 ፤ ጳውሎስ ፡ ቢኾን ፡ አጵሎስም ፡ ቢኾን ፡ ኬፋም ፡ ቢኾን ፡ ዓለምም ፡ ቢኾን ፡ ሕይወትም ፡ ቢኾን ፡ ሞትም ፡ ቢኾን ፡ ያለውም ፡ ቢኾን ፡ የሚመጣውም ፡ ቢኾን ፥

ቆሮ.1 ፡ 3 ፡ 23 ፤ ኹሉ ፡ የእናንተ ፡ ነው ፥ እናንተም ፡ የክርስቶስ ፡ ናችኹ ፡ ክርስቶስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 1 ፤ እንዲሁ ፡ ሰው ፡ እኛን ፡ እንደክርስቶስ ፡ ሎሌዎችና ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ምስጢር ፡ መጋቢዎች ፡ ይቍጠረን ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 2 ፤ እንደዚህም ፡ ሲኾን ፥ በመጋቢዎች ፡ ዘንድ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ መገኘት ፡ ይፈለጋል ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ ብፈረድ ፡ ለእኔ ፡ ምንም ፡ አይደለም ፤ እኔም ፡ በራሴ ፡ እንኳ ፡ አልፈርድም ፤

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ በራሴ ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ አላውቅምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በዚህ ፡ አልጸድቅም ፤ እኔን ፡ የሚፈርድ ፡ ግን ፡ ጌታ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ ስለዚህም ፡ በጨለማ ፡ የተሰወረውን ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ የሚያወጣ ፡ የልብንም ፡ ምክር ፡ የሚገልጥ ፡ ጌታ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ አንዳች ፡ አትፍረዱ ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ምስጋናው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ አንዱ ፡ በአንዱ ፡ ላይ ፡ አንዳችኹም ፡ እንዳይ(ት)ታበዩ ፡— ከተጻፈው ፡ አትለፍ ፡ የሚለውን ፡ በእኛ ፡ ትማሩ ፡ ዘንድ ፥ ይህን ፡ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ራሴና ፡ ስለ ፡ አጵሎስ ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ ተናገርኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ አንተ ፡ እንድትበልጥ ፡ ማን ፡ አድርጎኻል ፧ ያልተቀበልኸውስ ፡ ምን ፡ አለኽ ፧ የተቀበልኽ ፡ ከኾንኽ ፡ ግን ፡ እንዳልተቀበልኽ ፡ የምትመካ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ ጠግባችኋል ፤ አኹንስ ፡ ባለጠጋዎች ፡ ኾናችኋል ፤ ያለእኛ ፡ ነግሣችኋል ፤ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ እንድንነግሥ ፡ ብትነግሡ ፡ መልካም ፡ ይኾን ፡ ነበር ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ለዓለም ፡ ለመላእክትም ፡ ለሰዎችም ፡ መጫወቻ ፡ ኾነናልና ፤ እግዚአብሔር ፡ እኛን ፡ ሐዋርያቱን ፡ ሞት ፡ እንደተፈረደባቸው ፡ ሰዎች ፡ ከኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የኋለኞች ፡ እንዳደረገን ፡ ይመስለኛልና ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ እኛ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞኞች ፡ ነን ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ በክርስቶስ ፡ ልባሞች ፡ ናችኹ ፤ እኛ ፡ ደካማዎች ፡ ነን ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ኀይለኞች ፡ ናችኹ ፤ እናንተ ፡ የከበራችኹ ፡ ናችኹ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ የተዋረድን ፡ ነን ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 11 ፤ እስከዚህ ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ እንራባለን ፥ እንጠማለን ፥ እንራቈታለን ፥ እንጐሰማለን ፥ እንንከራተታለን ፥

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 12 ፤ በገዛ ፡ እጃችን ፡ እየሠራን ፡ እንደክማለን ፤ ሲሰድቡን ፡ እንመርቃለን ፥ ሲያሳድዱን ፡ እንታገሣለን ፥ ክፉ ፡ ሲናገሩን ፡ እንማልዳለን ፤

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ የዓለም ፡ ጥራጊ ፡ የኹሉም ፡ ጕድፍ ፡ ኾነናል ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ እንደምወዳችኹ ፡ ልጆቼ ፡ አድርጌ ፡ ልገሥጻችኹ ፡ እንጂ ፡ ላሳፍራችኹ ፡ ይህን ፡ አልጽፍም ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ በክርስቶስ ፡ አእላፍ ፡ ሞግዚቶች ፡ ቢኖሯችኹ ፡ ብዙ ፡ አባቶች ፡ የሏችኹም ፡ እኔ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በወንጌል ፡ ወልጃችኋለኹና ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ እኔን ፡ የምትመስሉ ፡ ኹኑ ፡ ብዬ ፡ እለምናችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ የምወደውንና ፡ የታመነውን ፥ በጌታ ፡ ልጄ ፡ የኾነውን ፥ ጢሞቴዎስን ፡ ልኬላችኋለኹ ፤ እኔም ፡ በየስፍራው ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ እንደማስተምር ፥ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የሚኾነውን ፡ መንገዴን ፡ ርሱ ፡ ያሳስባችኋል ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ አንዳንዱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የማልመጣ ፡ እየመሰላቸው ፡ የታበዩ ፡ አሉ ፤

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጌታ ፡ ቢፈቅድ ፡ ፈጥኜ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመጣለኹ ፥ የትዕቢተኞችንም ፡ ኀይል ፡ ዐውቃለኹ ፡ እንጂ ፡ ቃላቸውን ፡ አይደለም ፤

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በኀይል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ አይደለምና ።

ቆሮ.1 ፡ 4 ፡ 21 ፤ ምን ፡ ትወዳላችኹ ፧ በበትር ፡ ወይስ ፡ በፍቅርና ፡ በየውሀት ፡ መንፈስ ፡ ልምጣባችኹን ፧

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ በዐጨር ፡ ቃል ፡ በእናንተ ፡ መካከል ፡ ዝሙት ፡ እንዳለ ፡ ይወራል ፡ የዚያም ፡ ዐይነት ፡ ዝሙት ፡ በአሕዛብስ ፡ እንኳ ፡ የማይገኝ ፡ ነው ፥ የአባቱን ፡ ሚስት ፡ ያገባ ፡ ሰው ፡ ይኖራልና ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ እናንተም ፡ ታብያችኋል ፤ ይልቅስ ፡ እንድታዝኑ ፡ አይገባችኹምን ፧ ይህን ፡ ሥራ ፡ የሠራው ፡ ከመካከላችኹ ፡ ይወገድ ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 3-4 ፤ እኔ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በሥጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ባልኾን ፥ በመንፈስ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፥ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ እንዳለኹ ፡ ኾኜ ፡ ይህን ፡ እንደዚህ ፡ በሠራው ፡ ላይ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አኹን ፡ ፈርጄበታለኹ ፤ እናንተና ፡ መንፈሴም ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀይል ፡ ጋራ ፡ ተሰብስበን ፥

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ መንፈሱ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ቀን ፡ ትድን ፡ ዘንድ ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ለሥጋው ፡ ጥፋት ፡ ለሰይጣን ፡ እንዲሰጥ ፡ ፍርዴ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ መመካታችኹ ፡ መልካም ፡ አይደለም ። ጥቂት ፡ ርሾ ፡ ሊጡን ፡ ኹሉ ፡ እንዲያቦካ ፡ አታውቁምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ያለርሾ ፡ እንዳላችኹ ፡ ዐዲሱን ፡ ሊጥ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አሮጌውን ፡ ርሾ ፡ አስወግዱ ። ፋሲካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ታርዷልና ፤

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ በቅንነትና ፡ በእውነት ፡ ቂጣ ፡ በዓልን ፡ እናድርግ ፡ እንጂ ፥ በአሮጌ ፡ ርሾ ፣ በክፋትና ፡ በግፍ ፡ ርሾም ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ከሴሰኞች ፡ ጋራ ፡ እንዳትተባበሩ ፡ በመልእክቴ ፡ ጻፍኩላችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ በጠቅላላው ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ሴሰኞችን ፥ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ የሚመኙትን ፡ ነጣቂዎችንም ፥ ወይም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልኩትን ፡ አላልኹም ፤ ይህስ ፡ ቢኾን ፡ ከዓለም ፡ ልትወጡ ፡ ይገባችኹ ፡ ነበር ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ወንድሞች ፡ ከሚባሉት ፡ አንዱ ፡ ሴሰኛ ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ የሚመኝ ፡ ወይም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልክ ፡ ወይም ፡ ተሳዳቢ ፡ ወይም ፡ ሰካር ፡ ወይም ፡ ነጣቂ ፡ ቢኾን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንዳትተባበሩ ፡ እጽፍላችኋለኹ ፤ እንደነዚህ ፡ ካለው ፡ ጋራ ፡ መብል ፡ እንኳን ፡ አትብሉ ።

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ በውጭ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ መፍረድ ፡ ምን ፡ አግዶኝ ፧ በውስጥ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ እናንተ ፡ አትፈርዱምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ በውጭ ፡ ባሉቱ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ። ክፉውን ፡ ከመካከላችኹ ፡ አውጡት ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 1 ፤ ከእናንተ ፡ አንዱ ፡ ከባልንጀራው ፡ ጋራ ፡ ሙግት ፡ ቢኖረው ፡ በቅዱሳን ፡ ፊት ፡ በመፋረድ ፡ ፋንታ ፡ በዐመፀኞች ፡ ፊት ፡ ሊፋረድ ፡ ይደፍራልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 2 ፤ ቅዱሳን ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ እንዲፈርዱ ፡ አታውቁምን ፧ በዓለምስ ፡ ላይ ፡ ብትፈርዱ ፡ ከ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ ትንሽ ፡ ስለሚኾን ፡ ነገር ፡ ልትፈርዱ ፡ አትበቁምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 3 ፤ የትዳር ፡ ጕዳይ ፡ ይቅርና ፡ በመላእክት ፡ እንኳ ፡ እንድንፈርድ ፡ አታውቁምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 4 ፤ እንግዲህ ፡ ስለትዳር ፡ ጕዳይ ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ቢያስፈልጋችኹ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተናቁትን ፡ ሰዎች ፡ ፈራጆች ፡ አድርጋችኹ ፡ ታስቀምጣላችኹን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 5 ፤ አሳፍራችኹ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ እላለኹ ፥— እንደዚህ ፡ ነውን ፧ በወንድሞች ፡ መካከል ፡ ሽማግሌ ፡ ሊኾን ፡ የሚችል ፡ አንድ ፡ አስተዋይ ፡ ሰው ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አይገኝምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ ይከሳል ፥ ይህም ፡ በማያምኑ ፡ ፊት ፡ ይደረጋልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ፈጽሞ ፡ የርስ ፡ በርስ ፡ ሙግት ፡ እንዳለባችኹ ፡ በእናንተ ፡ ጕድለት ፡ ነው ። ብትበደሉ ፡ አይሻልምን ፧ ብትታለሉስ ፡ አይሻልምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ ትበድላላችኹ ፡ ታታልሉማላችኹ ፥ ያውም ፡ ወንድሞቻችኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ወይስ ፡ ዐመፀኞች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንዳይወርሱ ፡ አታውቁምን ፧ አትሳቱ ፤ ሴሰኞች ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልኩ ፡ ወይም ፡ አመንዝራዎች ፡ ወይም ፡ ቀላጮች ፡ ወይም ፡ ከወንድ ፡ ጋራ ፡ ዝሙት ፡ የሚሠሩ ፡

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ወይም ፡ ሌባዎች ፡ ወይም ፡ ገንዘብን ፡ የሚመኙ ፡ ወይም ፡ ሰካሮች ፡ ወይም ፡ ተሳዳቢዎች ፡ ወይም ፡ ነጣቂዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አይወርሱም ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 11 ፤ ከእናንተም ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ነበራችኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ በአምላካችንም ፡ መንፈስ ፡ ታጥባችኋል ፥ ተቀድሳችኋል ፥ ጸድቃችኋል ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 12 ፤ ኹሉ ፡ ተፈቅዶልኛል ፥ ኹሉ ፡ ግን ፡ አይጠቅምም ። ኹሉ ፡ ተፈቅዶልኛል ፥ በእኔ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ አይሠለጥንብኝም ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 13 ፤ መብል ፡ ለሆድ ፡ ነው ፥ ሆድም ፡ ለመብል ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ይህንም ፡ ያንም ፡ ያጠፋቸዋል ። ሥጋ ፡ ግን ፡ ለጌታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዝሙት ፡ አይደለም ፤ ጌታም ፡ ለሥጋ ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ጌታንም ፡ አስነሣ ፡ እኛንም ፡ በኀይሉ ፡ ያስነሣናል ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ሥጋችኹ ፡ የክርስቶስ ፡ ብልቶች ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቁምን ፧ እንግዲህ ፡ የክርስቶስን ፡ ብልቶች ፡ ወስጄ ፡ የጋለሞታ ፡ ብልቶች ፡ ላድርጋቸውን ፧ አይገባም ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 16 ፤ ወይስ ፡ ከጋለሞታ ፡ ጋራ ፡ የሚተባበር ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ እንዲኾን ፡ አታውቁምን ፧ ኹለቱ ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ፡ ተብሏልና ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 17 ፤ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ የሚተባበር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 18 ፤ ከዝሙት ፡ ሽሹ ። ሰው ፡ የሚያደርገው ፡ ኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ከሥጋ ፡ ውጭ ፡ ነው ፤ ዝሙትን ፡ የሚሠራ ፡ ግን ፡ በገዛ ፡ ሥጋው ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ ይሠራል ።

ቆሮ.1 ፡ 6 ፡ 19-20 ፤ ወይስ ፡ ሥጋችኹ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተቀበላችኹት ፡ በእናንተ ፡ የሚኖረው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አታውቁምን ፧ በዋጋ ፡ ተገዝታችኋልና ፥ ለራሳችኹ ፡ አይደላችኹም ፤ ስለዚህ ፥ በሥጋችኹ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አክብሩ ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 1 ፤ ስለጻፋችኹልኝስ ፡ ነገር ፥ ከሴት ፡ ጋራ ፡ አለመገናኘት ፡ ለሰው ፡ መልካም ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለዝሙት ፡ ጠንቅ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለራሱ ፡ ሚስት ፡ ትኑረው ፥ ለያንዳንዲቱ ፡ ደግሞ ፡ ለራሷ ፡ ባል ፡ ይኑራት ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 3 ፤ ባል ፡ ለሚስቱ ፡ የሚገባትን ፡ ያድርግላት ፥ እንደዚሁም ፡ ደግሞ ፡ ሚስቲቱ ፡ ለባሏ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 4 ፤ ሚስት ፡ በገዛ ፡ ሥጋዋ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የላትም ፥ ሥልጣን ፡ ለባሏ ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ባል ፡ በገዛ ፡ ሥጋው ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፥ ሥልጣን ፡ ለሚስቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ለጸሎት ፡ ትተጉ ፡ ዘንድ ፡ ተስማምታችኹ ፡ ለጊዜው ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አትከላከሉ ፤ ራሳችኹን ፡ ስለ ፡ አለመግዛት ፡ ሰይጣን ፡ እንዳይፈታተናችኹ ፡ ደግሞ ፡ ዐብራችኹ ፡ ኹኑ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 6 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ፈቃድ ፡ እላለኹ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 7 ፤ ሰው ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እኔ ፡ ሊኾን ፡ እወዳለኹና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለራሱ ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ አለው ፥ አንዱ ፡ እንደዚህ ፡ ኹለተኛውም ፡ እንደዚያ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 8 ፤ ላላገቡና ፡ ለመበለቶች ፡ ግን ፡ እላለኹ ፦ እንደ ፡ እኔ ፡ ቢኖሩ ፡ ለእነርሱ ፡ መልካም ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምኞት ፡ ከመቃጠል ፡ መጋባት ፡ ይሻላልና ፥ ራሳቸውን ፡ መግዛት ፡ ባይችሉ ፡ ያግቡ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 10-11 ፤ ሚስትም ፡ ከባሏ ፡ አትለያይ ፥ ብትለያይ ፡ ግን ፡ ሳታገባ ፡ ትኑር ፡ ወይም ፡ ከባሏ ፡ ትታረቅ ፥ ባልም ፡ ሚስቱን ፡ አይተዋት ፡ ብዬ ፡ የተጋቡትን ፡ አዛቸዋለኹ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አላዝም ፥ ጌታ ፡ እንጂ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 12 ፤ ሌላዎችንም ፡ እኔ ፡ እላለኹ ፥ ጌታም ፡ አይደለም ፤ ከወንድሞች ፡ ወገን ፡ ያላመነች ፡ ሚስት ፡ ያለችው ፡ ቢኖር ፡ ርሷም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ልትቀመጥ ፡ ብትስማማ ፥ አይተዋት ፤

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 13 ፤ ያላመነ ፡ ባል ፡ ያላት ፡ ሚስትም ፡ ብትኖር ፡ ይህ ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ሊቀመጥ ፡ ቢስማማ ፥ አትተወው ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 14 ፤ ያላመነ ፡ ባል ፡ በሚስቱ ፡ ተቀድሷልና ፥ ያላመነችም ፡ ሚስት ፡ በባሏ ፡ ተቀድሳለች ፤ አለዚያ ፡ ልጆቻችኹ ፡ ርኩሳን ፡ ናቸው ፤ አኹን ፡ ግን ፡ የተቀደሱ ፡ ናቸው ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 15 ፤ የማያምን ፡ ግን ፡ ቢለይ ፡ ይለይ ፤ ወንድም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ እኅት ፡ እንዲህ ፡ በሚመስል ፡ ነገር ፡ አይገዙም ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በሰላም ፡ ጠርቶናል ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 16 ፤ አንቺ ፡ ሴት ፥ ባልሽን ፡ ታድኚ ፡ እንደ ፡ ኾንሽ ፡ ምን ፡ ታውቂያለሽ ፧ ወይስ ፡ አንተ ፡ ሰው ፥ ሚስትኽን ፡ ታድን ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ምን ፡ ታውቃለኽ ፧

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 17 ፤ ብቻ ፡ ለያንዳንዱ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ከፈለለት ፡ እያንዳንዱም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ጠራው ፡ እንዲሁ ፡ ይመላለስ ። እንዲሁም ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሹሉ ፡ እደነግጋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 18 ፤ ማንም ፡ ተገርዞ ፡ ሳለ ፡ ተጠርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወደ ፡ አለመገረዝ ፡ አይመለስ ፤ ማንም ፡ ሳይገረዝ ፡ ተጠርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይገረዝ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 19 ፤ መገረዝ ፡ ቢኾን ፡ አለመገረዝም ፡ ቢኾን ፡ ከንቱ ፡ ነው ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ መጠበቅ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 20 ፤ እያንዳንዱ ፡ በተጠራበት ፡ መጠራት ፡ እንደዚሁ ፡ ይኑር ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 21 ፤ ባሪያ ፡ ኾነኽ ፡ ተጠርተኽ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አይገድኽም ፤ ሐራነት ፡ ልትወጣ ፡ ቢቻልኽ ፡ ግን ፡ ሐራነትን ፡ ተቀበል ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 22 ፤ ባሪያ ፡ ኾኖ ፡ በጌታ ፡ የተጠራ ፡ የጌታ ፡ ነጻ ፡ ነውና ፤ እንዲሁም ፡ ነጻ ፡ ኾኖ ፡ የተጠራ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 23 ፤ በዋጋ ፡ ተገዝታችኋል ፤ የሰው ፡ ባሪያዎች ፡ አትኹኑ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 24 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እያንዳንዱ ፡ በተጠራበት ፡ እንደዚሁ ፡ ኾኖ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይኑር ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 25 ፤ ስለ ፡ ደናግልም ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ የለኝም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የታመንኹ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ከጌታ ፡ ምሕረትን ፡ የተቀበልኹ ፡ እንደ ፡ መኾኔ ፡ ምክር ፡ እመክራለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፡ ስላኹኑ ፡ ችግር ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ ይመስለኛል ፤ ሰው ፡ እንዲህ ፡ ኾኖ ፡ ቢኖር ፡ መልካም ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 27 ፤ በሚስት ፡ ታስረኽ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ መፋታትን ፡ አትሻ ፤ በሚስት ፡ አልታሰርኽ ፡ እንደ ፡ ኾንኽ ፡ ሚስትን ፡ አትሻ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 28 ፤ ብታገባ ፡ ግን ፡ ኀጢአት ፡ አትሠራም ፡ ድንግሊቱም ፡ ብታገባ ፡ ኀጢአት ፡ አትሠራም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንዲህ ፡ በሚያደርጉ ፡ በሥጋቸው ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ ይኾንባቸዋል ፥ እኔም ፡ እራራላችኹ ፡ ነበር ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 29 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ እናገራለኹ ፤ ዘመኑ ፡ ዐጪር ፡ ኾኗል ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ሚስቶች ፡ ያሏቸው ፡ እንደሌላቸው ፡ ይኹኑ ፥

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 30 ፤ የሚያለቅሱም ፡ እንደማያለቅሱ ፥ ደስ ፡ የሚላቸውም ፡ ደስ ፡ እንደማይላቸው ፥

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 31 ፤ የሚገዙም ፡ ምንም ፡ እንደሌላቸው ፥ በዚችም ፡ ዓለም ፡ የሚጠቀሙ ፡ በሙሉ ፡ እንደማይጠቀሙባት ፡ ይኹኑ ፤ የዚች ፡ ዓለም ፡ መልክ ፡ ዐላፊ ፡ ነውና ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 32 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ያለዐሳብ ፡ ልትኖሩ ፡ እወዳለኹ ። ያላገባው ፡ ጌታን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንዲያሠኘው ፡ የጌታን ፡ ነገር ፡ ያስባል ፤

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 33 ፤ ያገባው ፡ ግን ፡ ሚስቱን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንዲያሠኛት ፡ የዓለምን ፡ ነገር ፡ ያስባል ፥ ልቡም ፡ ተከፍሏል ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 34 ፤ ያልተጋባች ፡ ሴትና ፡ ድንግል ፡ በሥጋም ፡ በነፍስም ፡ እንዲቀደሱ ፡ የጌታን ፡ ነገር ፡ ያስባሉ ፤ የተጋባች ፡ ግን ፡ ባሏን ፡ እንዴት ፡ ደስ ፡ እንድታሠኘው ፡ የዓለምን ፡ ነገር ፡ ታስባለች ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 35 ፤ ይህንም ፡ ለራሳችኹ ፡ ጥቅም ፡ እላለኹ ፤ በአገባብ ፡ እንድትኖሩ ፡ ሳትባክኑም ፡ በጌታ ፡ እንድትጸኑ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ላጠምዳችኹ ፡ ብዬ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 36 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ማግባት ፡ ወደሚገባው ፡ ዕድሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ድንግልናው ፡ ያፈረ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፥ የወደደውን ፡ ያድርግ ፤ ኀጢአት ፡ የለበትም ፤ ይጋቡ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 37 ፤ ሳይናወጥ ፡ በልቡ ፡ የጸና ፡ ግን ፡ ግድ ፡ የለበትም ፥ የወደደውን ፡ እንዲያደርግ ፡ ተፈቅዶለታል ፤ ድንግልናውንም ፡ በልቡ ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ቢጸና ፥ መልካም ፡ አደረገ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 38 ፤ እንዲሁም ፡ ድንግልን ፡ ያገባ ፡ መልካም ፡ አደረገ ፡ ያላገባም ፡ የተሻለ ፡ አደረገ ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 39 ፤ ሴት ፡ ባሏ ፡ በሕይወት ፡ ሳለ ፡ የታሰረች ፡ ናት ፤ ባሏ ፡ ቢሞት ፡ ግን ፡ በጌታ ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፡ የወደደችውን ፡ ልታገባ ፡ ነጻነት ፡ አላት ።

ቆሮ.1 ፡ 7 ፡ 40 ፤ እንደ ፡ ምክሬ ፡ ግን ፡ እንዳለች ፡ ብትኖር ፡ ደስተኛ ፡ ናት ፤ እኔም ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእኔ ፡ ያለ ፡ ይመስለኛል ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 1 ፤ ለጣዖት ፡ ስለተሠዋ ፡ ሥጋም ፥ ኹሉችን ፡ ዕውቀት ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ። ዕውቀት ፡ ያስታብያል ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡ ያንጻል ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 2 ፤ ማንም ፡ አንዳች ፡ የሚያውቅ ፡ ቢመስለው ፡ ሊያውቅ ፡ እንደሚገባው ፡ ገና ፡ አላወቀም ፤

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 3 ፤ ማንም ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢወድ ፡ ርሱ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 4 ፤ እንግዲህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ መብላት ፥ ጣዖት ፡ ኹሉ ፡ በዓለም ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከአንዱም ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አምላክ ፡ እንደሌለ ፡ እናውቃለን ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 5 ፤ መቼም ፡ ብዙ ፡ አማልክትና ፡ ብዙ ፡ ጌታዎች ፡ አሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሰማይ ፡ ኾነ ፡ በምድርም ፡ ኾነ ፡ አማልክት ፡ የተባሉ ፡ ምንም ፡ ቢኖሩ ፥

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ለእኛስ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ የኾነ ፡ እኛም ፡ ለርሱ ፡ የኾን ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ አብ ፡ አለን ፥ ነገር ፡ ኹሉም ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ የኾነ ፡ እኛም ፡ በርሱ ፡ በኩል ፡ የኾን ፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አለን ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ ዕውቀት ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ አይገኝም ፤ አንዳንዶች ፡ ግን ፡ ጣዖትን ፡ እስካኹን ፡ ድረስ ፡ ስለ ፡ ለመዱ ፦ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ይበላሉና ፥ ኅሊናቸው ፡ ደካማ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ይረክሳል ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 8 ፤ መብል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያቀርበንም ፤ ባንበላም ፡ ምንም ፡ አይጐድለንም ፡ ብንበላም ፡ ምንም ፡ አይተርፈንም ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 9 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ መብታችኹ ፡ ለደካማዎች ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳይኾንባቸው ፡ ተጠንቀቁ ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 10 ፤ አንተ ፡ ዕውቀት ፡ ያለኽ ፡ በጣዖት ፡ ቤት ፡ በማእዱ ፡ ስትቀመጥ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ቢያይኽ ፥ ደካማ ፡ ሰው ፡ ቢኾን ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ለመብላት ፡ ኅሊናው ፡ አይታነጽበትምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 11 ፤ ባንተ ፡ ዕውቀትም ፡ ይህ ፡ ደካማ ፡ ይጠፋል ፥ ርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ የሞተለት ፡ ወንድም ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 12 ፤ እንዲህም ፡ ወንድሞችን ፡ እየበደላችኹ ፥ ደካማም ፡ የኾነውን ፡ ኅሊናቸውን ፡ እያቈሰላችኹ ፡

ክርስቶስን ፡ ትበድላላችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 8 ፡ 13 ፤ ስለዚህም ፡ መብል ፡ ወንድሜን ፡ የሚያሰናክለው ፡ ከኾነ ፥ ወንድሜን ፡ እንዳላሰናክለው ፡ ለዘለዓለም ፡ ከቶ ፡ ሥጋ ፡ አልበላም ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 1 ፤ እኔ ፡ ነጻ ፡ አይደለኹምን ፧ ሐዋርያስ ፡ አይደለኹምን ፧ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስንስ ፡ አላየኹትምን ፧ እናንተስ ፡ በጌታ ፡ ሥራዬ ፡ አይደላችኹምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 2 ፤ የሐዋርያነቴ ፡ ማኅተም ፡ በጌታ ፡ እናንተ ፡ ናችኹና ፥ ለሌላዎች ፡ ሐዋርያ ፡ ባልኾን ፡ ለእናንተስ ፡ ምንም ፡ ቢኾን ፡ ሐዋርያ ፡ ነኝ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 3-4 ፤ ለሚመረምሩኝ ፡ መልሴ ፡ ይህ ፡ ነው ። ልንበላና ፡ ልንጠጣ ፡ መብት ፡ የለንምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ሌላዎቹ ፡ ሐዋርያትና ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ ወንድሞች ፡ እንደ ፡ ኬፋም ፥ እኅት ፡ ሚስታችንን ፡ ይዘን ፡ ልንዞር ፡ መብት ፡ የለንምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 6 ፤ ወይስ ፡ ሥራን ፡ ለመተው ፡ መብት ፡ የሌለን ፡ እኔና ፡ በርናባስ ፡ ብቻ ፡ ነን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 7 ፤ ከቶ ፡ በገዛ ፡ ገንዘቡ ፡ በወታደርነት ፡ የሚያገለግል ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ወይን ፡ ተክሎ ፡ ፍሬውን ፡ የማይበላ ፡ ማን ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ መንጋ ፡ እየጠበቀ ፡ ከመንጋው ፡ ወተት ፡ የማይጠጣ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 8 ፤ ይህን ፡ በሰው ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ እላለኹን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 9 ፤ ሕግስ ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ አይልምን ፧ የሚያበራየውን ፡ በሬ ፡ አፉን ፡ አትሰር ፡ ተብሎ ፡ በሙሴ ፡ ሕግ ፡ ተጽፏልና ። እግዚአብሔርስ ፡ ስለ ፡ በሬዎች ፡ ይገደዋልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ይህን ፡ የሚለው ፡ ፈጽሞ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አይደለምን ፧ የሚያርስ ፡ በተስፋ ፡ ሊያርስ ፥ የሚያበራይም ፡ እንዲካፈል ፡ በተስፋ ፡ ሊያበራይ ፡ ስለሚገባው ፡ በእውነት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ተጽፏል ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 11 ፤ እኛ ፡ መንፈሳዊን ፡ ነገር ፡ የዘራንላችኹ ፡ ከኾን ፡ የእናንተን ፡ የሥጋዊን ፡ ነገር ፡ እኛ ፡ ብናጭድ ፡ ትልቅ ፡ ነገር ፡ ነውን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 12 ፤ ሌላዎች ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ይህን ፡ መብት ፡ የሚካፈሉ ፡ ከኾኑ ፥ እኛማ ፡ ይልቁን ፡ እንዴታ ፧ ነገር ፡ ግን ፡ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ እንዳንከለክል ፡ በቸሉ ፡ እንታገሣለን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ መብት ፡ አልተጠቀምንም ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 13 ፤ በመቅደስ ፡ ነገር ፡ የሚያገለግሉ ፡ ከመቅደስ ፡ የኾነውን ፡ ነገርን ፡ እንዲመገቡ ፥ በመሠዊያውም ፡ የሚጸኑ ፡ ከመሠዊያው ፡ እንዲካፈሉ ፡ አታውቁምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 14 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ወንጌልን ፡ የሚሰብኩ ፡ ከወንጌል ፡ ቀለብ ፡ እንዲቀበሉ ፡ ጌታ ፡ ደንግጓል ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ከነዚህ ፡ ቸሉ ፡ ምንም ፡ አልተጠቀምኩም ። እንዲህ ፡ እንዲኾንልኝ ፡ ይህን ፡ አልጽፍም ፤ ማንም ፡ ትምክሕቴን ፡ ከንቱ ፡ ከሚያደርግብኝ ፡ ሞት ፡ ይሻለኛልና ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 16 ፤ ወንጌልን ፡ ብሰብክ ፡ እንኳ ፡ የምመካበት ፡ የለኝም ፤ ግድ ፡ ደርሶብኝ ፡ ነውና ፤ ወንጌልንም ፡ ባልሰብክ ፡ ወዮልኝ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 17 ፤ ይህን ፡ በፈቃዴ ፡ ባደርገው ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ አለኝና ፤ ያለፈቃዴ ፡ ግን ፡ ባደርገው ፡ መጋቢነት ፡

በዐደራ ፡ ተሰጥቶኛል ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ ደመ ፡ ወዜ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወንጌልን ፡ እየሰበክኹ ፡ በወንጌል ፡ ካለኝ ፡ መብት ፡ በሙሉ ፡ እንዳልጠቀም ፡ ወንጌልን ፡ ያለዋጋ ፡ ብናገር ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 19 ፤ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ሐራነት ፡ የወጣኹ ፡ ስኾን ፡ የሚበልጡትን ፡ እንድጠቅም ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ ራሴን ፡ ለኹሉ ፡ አስገዛለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 20 ፤ አይሁድንም ፡ እጠቅም ፡ ዘንድ ፡ ከአይሁድ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ አይሁዳዊ ፡ ኾንኹ ፤ ከሕግ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ እጠቅም ፡ ዘንድ ፥ እኔ ፡ ራሴ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ሳልኾን ፥ ከሕግ ፡ በታች ፡ ላሉት ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ እንዳለኹ ፡ ኾንኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 21 ፤ ሕግ ፡ የሌላቸውን ፡ እጠቅም ፡ ዘንድ ፥ ያለእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ሳልኖር ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ በታች ፡ ሳለኹ ፥ ሕግ ፡ ለሌላቸው ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ሌለኝ ፡ ኾንኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 22 ፤ ደካማዎችን ፡ እጠቅም ፡ ዘንድ ፡ ለደካማዎች ፡ እንደ ፡ ደካማ ፡ ኾንኹ ፤ በኹሉ ፡ መንገድ ፡ አንዳንዶችን ፡ አድን ፡ ዘንድ ፥ ከኹሉ ፡ ጋራ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ኾንኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 23 ፤ በወንጌልም ፡ ማኅበረተኛ ፡ እኾን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ኹሉን ፡ አደርጋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 24 ፤ በእሽቅድምድም ፡ ስፍራ ፡ የሚሮጡት ፥ ኹሉ ፡ እንዲሮጡ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አንዱ ፡ ብቻ ፡ ዋጋውን ፡ እንዲቀበል ፡ አታውቁምን ፧ እንዲሁም ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ ሩጡ ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 25 ፤ የሚታገልም ፡ ኹሉ ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ሰውነቱን ፡ ይገዛል ፤ እነዚያም ፡ የሚጠፋውን ፡ አክሊል ፡ ሊያገኙ ፡ ነው ፥ እኛ ፡ ግን ፡ የማይጠፋውን ።

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 26 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ያለዐሳብ ፡ እንደሚሮጥ ፡ ኹሉ ፥ እንዲሁ ፡ አልሮጥም ፤ ነፋስን ፡ እንደሚጐስም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሁ ፡ አልጋደልም ፤

ቆሮ.1 ፡ 9 ፡ 27 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለሌላዎች ፡ ከሰበክኹ ፡ በኋላ ፡ ራሴ ፡ የተጣልኹ ፡ እንዳልኾን ፡ ሥጋዬን ፡ እየጐሰምኹ ፡ አስገዛዋለኹ ።

_____1 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ። አባቶቻችን ፡ ኹሉ ፡ ከደመና ፡ በታች ፡ ነበሩ ፥ ኹሉም ፡ በባሕር ፡ መካከል ፡ ተሻገሩ ፤

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 2 ፤ ኹሉም ፡ ሙሴን ፡ ይተባበሩ ፡ ዘንድ ፥ በደመናና ፡ በባሕር ፡ ተጠመቁ ፤

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 3 ፤ ኹሉም ፡ ያን ፡ መንፈሳዊ ፡ መብል ፡ በሉ ፥ ኹሉም ፡ ያን ፡ መንፈሳዊ ፡ መጠጥ ፡ ጠጡ ፤

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 4 ፤ ይከተላቸው ፡ ከነበረው ፡ ከመንፈሳዊ ፡ አለት ፡ ጠጥተዋልና ፥ ያም ፡ አለት ፡ ክርስቶስ ፡ ነበረ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 5 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከነርሱ ፡ በሚበዙት ፡ ደስ ፡ አላለውም ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወድቀዋልና ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 6 ፤ እነዚህም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተመኙ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንዳንመኝ ፥ ይህ ፡ ምሳሌ ፡ ኾነልን ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 7 ፤ ሕዝብም ፡ ሊበሉ ፡ ሊጠጡም ፡ ተቀመጡ ፥ ሊዘፍኑም ፡ ተነሡ ፥ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ከነርሱ ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንዳደረጉት ፡ ጣዖትን ፡ የምታመልኩ ፡ አትኹኑ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 8 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንደ ፡ ሴሰኑ ፥ ባንድ ፡ ቀንም ፡ ኹለት ፡ እልፍ ፡ ከሦስት ፡ ሺሕ ፡ እንደ ፡ ወደቁ ፡ አንሴስን ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 9 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ጌታን ፡ እንደ ፡ ተፈታተኑት ፥ በእባቦቹም ፡ እንደ ፡ ጠፉ ፥ ጌታን ፡ አንፈታተን ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 10 ፤ ከነርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ እንዳንጐራጐሩ ፥ በሚያጠፋውም ፡ እንደ ፡ ጠፉ ፥ አታንጐራጕሩ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 11 ፤ ይህም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ ኾነባቸው ፥ እኛንም ፡ የዘመናት ፡ መጨረሻ ፡ የደረሰብንን ፡ ሊገሥጸን ፡ ተጻፈ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ እንደ ፡ ቆመ ፡ የሚመስለው ፡ እንዳይወድቅ ፥ ይጠንቀቅ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 13 ፤ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ከሚኾነው ፡ በቀር ፡ ምንም ፡ ፈተና ፡ አልደረሰባችኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከሚቻላችኹ ፡ መጠን ፡ ይልቅ ፡ ትፈተኑ ፡ ዘንድ ፡ የማይፈቅድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የታመነ ፡ ነው ፥ ትታገሡም ፡ ዘንድ ፡ እንድትችሉ ፡ ከፈተናው ፡ ጋራ ፡ መውጫውን ፡ ደግሞ ፡ ያደርግላችኋል ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፥ ጣዖትን ፡ ከማምለክ ፡ ሽሹ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 15 ፤ ልባሞች ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፡ እላለኹ ፤ በምለው ፡ ነገር ፡ እናንተ ፡ ፍረዱ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 16 ፤ የምንባርከው ፡ የበረከት ፡ ጽዋ ፡ ከክርስቶስ ፡ ደም ፡ ጋራ ፡ ኅብረት ፡ ያለው ፡ አይደለምን ፧ የምንቈርሰውስ ፡ እንጀራ ፡ ከክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ጋራ ፡ ኅብረት ፡ ያለው ፡ አይደለምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 17 ፤ አንድ ፡ እንጀራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እኛ ፡ ብዙዎች ፡ ስንኾን ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ነን ፤ ኹላችን ፡ ያን ፡ አንዱን ፡ እንጀራ ፡ እንካፈላለንና ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 18 ፤ በሥጋ ፡ የኾነውን ፡ እስራኤል ፡ ተመልከቱ ፤ መሥዋዕቱን ፡ የሚበሉ ፡ የመሠዊያው ፡ ማኅበረተኞች ፡ አይደሉምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እላለኹ ፧ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ምናምን ፡ ነው ፡ እላለኹን ፧ ወይስ ፡ ጣዖት ፡ ምናምን ፡ እንዲኾን ፡ እላለኹን ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 20 ፤ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አሕዛብ ፡ የሚሠዉት ፡ ለአጋንንት ፡ እንዲኾን ፡ እንጂ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንዳይሠዉ ፡ እላለኹ ፤ ከአጋንንትም ፡ ጋራ ፡ ማኅበረተኞች ፡ እንድትኾኑ ፡ አልወድም ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 21 ፤ የጌታን ፡ ጽዋና ፡ የአጋንንትን ፡ ጽዋ ፡ ልትጠጡ ፡ አትችሉም ፤ ከጌታ ፡ ማእዱና ፡ ከአጋንንት ፡ ማእድ ፡ ልትካፈሉ ፡ አትችሉም ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 22 ፤ ወይስ ፡ ጌታን ፡ እናስቀናውን ፧ እኛስ ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ እንበረታለንን ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 23 ፤ ኹሉ ፡ ተፈቅዶልኛል ፥ ኹሉ ፡ ግን ፡ የሚጠቅም ፡ አይደለም ፤ ኹሉ ፡ ተፈቅዶልኛል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ የሚያንጽ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 24 ፤ እያንዳንዱ ፡ የባልንጀራውን ፡ ጥቅም ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የራሱን ፡ ጥቅም ፡ አይፈልግ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 25 ፤ በሥጋ ፡ ገበያ ፡ የሚሸጠውን ፡ ኹሉ ፡ ከኅሊና ፡ የተነሣ ፡ ሳትመራመሩ ፡ ብሉ ፤

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 26 ፤ ምድርና ፡ በርሷ ፡ የሞላባት ፡ ኹሉ ፡ የጌታ ፡ ነውና ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 27 ፤ ከማያምኑ ፡ ሰዎች ፡ አንዱም ፡ ቢጠራችኹ ፡ ልትኼዱም ፡ ብትወዱ ፡ ከኀሊና ፡ የተነሣ ፡ ሳትመራመሩ ፡ የሚያቀርቡላችኹን ፡ ኹሉ ፡ ብሉ ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 28 ፤ ማንም ፡ ግን ፦ ይህ ፡ ለጣዖት ፡ የተሠዋ ፡ ነው ፡ ቢላችኹ ፡ ከዚያ ፡ ካስታወቃችኹና ፡ ከኀሊና ፡ የተነሣ ፡ አትብሉ ፤

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 29 ፤ ስለ ፡ ባልንጀራኽ ፡ ኀሊና ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ገዛ ፡ ኀሊናኽ ፡ አልናገርም ። ሐራነቴ ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ኀሊና ፡ የሚፈረድ ፡ ኧረ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 30 ፤ እኔም ፡ በጸጋ ፡ ብበላ ፥ በነገሩ ፡ ስለማመሰግንበት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ እሰደባለኹ ፧

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 31 ፤ እንግዲህ ፡ የምትበሉ ፡ ወይም ፡ የምትጠጡ ፡ ብትኾኑ ፡ ወይም ፡ ማናቸውን ፡ ነገር ፡ ብታደርጉ ፡ ኹሉን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ አድርጉት ።

ቆሮ.1 ፡ 10 ፡ 32-33 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ብዙዎቹ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ ለጥቅማቸው ፡ እንጂ ፡ የራሴን ፡ ጥቅም ፡ ሳልፈልግ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ እንደማሠኝ ፥ ለአይሁድም ፡ ለግሪክም ፡ ሰዎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ማሰናከያ ፡ አትኹኑ ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 1 ፤ እኔ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደምመስል ፡ እኔን ፡ ምሰሉ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 2 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በኹሉ ፡ ስለምታስቡኝና ፡ አሳልፌ ፡ እንደ ፡ ሰጠኋችኹ ፡ ወግን ፡ ፈጽማችኹ ፡ ስለ ፡ ያዛችኹ ፡ አመሰግናችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የወንድ ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ ክርስቶስ ፥ የሴትም ፡ ራስ ፡ ወንድ ፥ የክርስቶስም ፡ ራስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 4 ፤ ራሱን ፡ ተከናንቦ ፡ የሚጸልይ ፡ ወይም ፡ ትንቢት ፡ የሚናገር ፡ ወንድ ፡ ኹሉ ፡ ራሱን ፡ ያዋርዳል ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 5 ፤ ራሷን ፡ ሳትሸፍን ፡ ግን ፡ የምትጸልይ ፡ ወይም ፡ ትንቢት ፡ የምትናገር ፡ ሴት ፡ ኹሉ ፡ ራሷን ፡ ታዋርዳለች ፤ እንደ ፡ ተላጨች ፡ ያኽል ፡ አንድ ፡ ነውና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 6 ፤ ሴትም ፡ ራሷን ፡ ባትሸፍን ፡ ጠጕሯን ፡ ደግሞ ፡ ትቈረጥ ፤ ለሴት ፡ ግን ፡ ጠጕሯን ፡ መቈረጥ ፡ ወይም ፡ መላጨት ፡ የሚያሳፍር ፡ ከኾነ ፡ ራሷን ፡ ትሸፍን ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 7 ፤ ወንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሳሌና ፡ ክብር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ራሱን ፡ መከናነብ ፡ አይገባውም ፤ ሴት ፡ ግን ፡ የወንድ ፡ ክብር ፡ ናት ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 8 ፤ ሴት ፡ ከወንድ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ወንድ ፡ ከሴት ፡ አይደለምና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 9 ፤ ሴት ፡ ስለ ፡ ወንድ ፡ ተፈጠረች ፡ እንጂ ፡ ወንድ ፡ ስለ ፡ ሴት ፡ አልተፈጠረምና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ሴት ፥ ከመላእክት ፡ የተነሣ ፥ በራሷ ፡ ሥልጣን ፡ ሊኖራት ፡ ይገባል ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጌታ ፡ ዘንድ ፡ ሴት ፡ ያለወንድ ፡ ወንድም ፡ ያለሴት ፡ አይኾንም ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 12 ፤ ሴት ፡ ከወንድ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ እንዲሁ ፡ ወንድ ፡ ደግሞ ፡ በሴት ፡ ነውና ፤ ኹሉም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 13 ፤ በእናንተ ፡ በራሳችኹ ፡ መካከል ፡ ፍረዱ ፤ ሴት ፡ ራሷን ፡ ሳትሸፍን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልትጸልይ ፡ ይገባታልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 14-15 ፤ ወንድ ፡ ጠጕሩን ፡ ቢያስረዝም ፡ ነውር ፡ እንዲኾንበት ፥ ሴት ፡ ግን ፡ ጠጕሯን ፡ ብታስረዝም ፡ ክብር ፡ እንዲኾንላት ፡ ተፈጥሮ ፡ እንኳ ፡ አያስተምራችኹምን ፧ ጠጕሯ ፡ መጐናጸፊያ ፡ ሊኾን ፡ ተሰጥቷታልና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 16 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ሊከራከር ፡ ቢፈቅድ ፥ እኛ ፡ ወይም ፡ የእግዚአብሔር ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ልማድ ፡ የለንም ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምትሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ ለሚከፋ ፡ እንጂ ፡ ለሚሻል ፡ ስላልኾነ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ ስሰጥ ፡ የማመሰግናችኹ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 18 ፤ በመዠመሪያ ፡ ወደ ፡ ማኅበር ፡ ስትሰበሰቡ ፡ በመካከላችኹ ፡ መለያየት ፡ እንዳለ ፡ እሰማለኹና ፥ ባንድ ፡ በኩልም ፡ አምናለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 19 ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተፈተኑት ፡ እንዲገለጡ ፡ በመካከላችኹ ፡ ወገኖች ፡ ደግሞ ፡ ሊኾኑ ፡ ግድ ፡ ነውና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 20 ፤ እንግዲህ ፡ ዐብራችኹ ፡ ስትሰበሰቡ ፡ የምትበሉት ፡ የጌታ ፡ እራት ፡ አይደለም ፤

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 21 ፤ በመብላት ፡ ጊዜ ፡ እያንዳንዱ ፡ የራሱን ፡ እራት ፡ ይበላልና ፥ አንዱም ፡ ይራባል ፡ አንዱ ፡ ግን ፡ ይሰክራል ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 22 ፤ የምትበሉባቸውና ፡ የምትጠጡባቸው ፡ ቤቶች ፡ የላችኹምን ፧ ወይስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማኅበር ፡ ትንቃላችኹን ፡ አንዳችም ፡ የሌላቸውን ፡ ታሳፍራላችኹን ፧ ምን ፡ ልበላችኹ ፧ በዚህ ፡ ነገር ፡ ላመስግናችኹን ፧ አላመሰግናችኹም ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 23 ፤ ለእናንተ ፡ ደግሞ ፡ አሳልፌ ፡ የሰጠኹትን ፡ እኔ ፡ ከጌታ ፡ ተቀብያለኹና ፤

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 24 ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ዐልፎ ፡ በተሰጠበት ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ እንጀራን ፡ አንሥቶ ፡ አመሰገነ ፥ ቈርሶም ፦ እንካችኹ ፡ ብሉ ፤ ይህ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የሚኾን ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፤ ይህን ፡ ለመታሰቢያዬ ፡ አድርጉት ፡ አለ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 25 ፤ እንደዚሁም ፡ ከእራት ፡ በኋላ ፡ ጽዋውን ፡ ደግሞ ፡ አንሥቶ ፦ ይህ ፡ ጽዋ ፡ በደሜ ፡ የሚኾን ፡ ዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ ነው ፤ በጠጣችኹት ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ለመታሰቢያዬ ፡ አድርጉት ፡ አለ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 26 ፤ ይህን ፡ እንጀራ ፡ በበላችኹ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፥ ይህንም ፡ ጽዋ ፡ በጠጣችኹ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ጌታ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ሞቱን ፡ ትናገራላችኹና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 27 ፤ ስለዚህ ፥ ሳይገባው ፡ ይህን ፡ እንጀራ ፡ የበላ ፡ ወይም ፡ የጌታን ፡ ጽዋ ፡ የጠጣ ፡ ኹሉ ፥ የጌታ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ዕዳ ፡ አለበት ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 28 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ይፈትን ፥ እንዲሁም ፡ ከእንጀራው ፡ ይብላ ፡ ከጽዋውም ፡ ይጠጣ ፤

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 29 ፤ ሳይገባው ፡ የሚበላና ፡ የሚጠጣ ፡ የጌታን ፡ ሥጋ ፡ ስለማይለይ ፡ ለራሱ ፡ ፍርድ ፡ ይበላልና ፥ ይጠጣልምና ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 30 ፤ ስለዚህ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የደከሙና ፡ የታመሙ ፡ ብዙዎች ፡ አሉ ፥ ዐያሌዎችም ፡ አንቀላፍተዋል ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 31 ፤ ራሳችንን ፡ ብንመረምር ፡ ግን ፡ ባልተፈረደብንም ፡ ነበር ፤

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 32 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በተፈረደብን ፡ ጊዜ ፡ ከዓለም ፡ ጋራ ፡ እንዳንኰነን ፡ በጌታ ፡ እንገሠጻለን ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 33 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ለመብላት ፡ በተሰበሰባችኹ ፡ ጊዜ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተጠባበቁ ።

ቆሮ.1 ፡ 11 ፡ 34 ፤ ማንም ፡ የራበው ፡ ቢኖር ፡ ለፍርድ ፡ እንዳትሰበሰቡ ፡ በቤቱ ፡ ይብላ ። የቀረውንም ፡ ነገር ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፡ እደነግጋለኹ ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ነገርም ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 2 ፤ አሕዛብ ፡ ሳላችኹ ፡ በማናቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንደምትመሩ ፡ ድምፅ ፡ ወደሌላቸው ፡ ወደ ፡ ጣዖታት ፡ እንደ ፡ ተወሰዳችኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 3 ፤ ስለዚህ ፥ ማንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ሲናገር ፦ ኢየሱስ ፡ የተረገመ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ እንደሌለ ፥ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፦ ኢየሱስ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ ሊል ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ እንዳይችል ፡ አስታውቃችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 4 ፤ የጸጋም ፡ ስጦታ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፥ መንፈስ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 5 ፤ አገልግሎትም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፥ ጌታም ፡ አንድ ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 6 ፤ አሠራርም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፥ ኹሉን ፡ በኹሉ ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መግለጥ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለጥቅም ፡ ይሰጠዋል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ለአንዱ ፡ ጥበብን ፡ መናገር ፡ በመንፈስ ፡ ይሰጠዋልና ፥ ለአንዱም ፡ በዚያው ፡ መንፈስ ፡ ዕውቀትን ፡ መናገር ፡ ይሰጠዋል ፥

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 9 ፤ ለአንዱም ፡ በዚያው ፡ መንፈስ ፡ እምነት ፥ ለአንዱም ፡ በአንዱ ፡ መንፈስ ፡ የመፈወስ ፡ ስጦታ ፥ ለአንዱም ፡ ተኣምራትን ፡ ማድረግ ፥

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ለአንዱም ፡ ትንቢትን ፡ መናገር ፥ ለአንዱም ፡ መናፍስትን ፡ መለየት ፥ ለአንዱም ፡ በልዩ ፡ ዐይነት ፡ ልሳን ፡ መናገር ፥ ለአንዱም ፡ በልሳኖች ፡ የተነገረውን ፡ መተርጐም ፡ ይሰጠዋል ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 11 ፤ ይህን ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ያ ፡ አንዱ ፡ መንፈስ ፡ እንደሚፈቅድ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ለብቻው ፡ እያካፈለ ፡ ያደርጋል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 12 ፤ አካልም ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ብዙም ፡ ብልቶች ፡ እንዳሉበት ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የአካል ፡ ብልቶች ፡ ኹሉ ፡ ብዙዎች ፡ ሳሉ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፥ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 13 ፤ አይሁድ ፡ ብንኾን ፡ የግሪክ ፡ ሰዎችም ፡ ብንኾን ፡ ባሪያዎችም ፡ ብንኾን ፡ ጨዋዎችም ፡ ብንኾን ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ባንድ ፡ መንፈስ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ እንድንኾን ፡ ተጠምቀናልና ። ኹላችንም ፡ አንዱን ፡ መንፈስ ፡ ጠጥተናል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 14 ፤ አካል ፡ ብዙ ፡ ብልቶች ፡ እንጂ ፡ አንድ ፡ ብልት ፡ አይደለምና ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 15 ፤ እግር ፦ እኔ ፡ እጅ ፡ አይደለኹምና ፡ የአካል ፡ ክፍል ፡ አይደለኹም ፡ ብትል ፥ ይህን ፡ በማለቷ ፡ የአካል ፡ ክፍል ፡ መኾኗ ፡ ይቀራልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ጕሮም ፦ እኔ ፡ ዐይን ፡ አይደለኹምና ፡ የአካል ፡ ክፍል ፡ አይደለኹም ፡ ቢል ፥ ይህን ፡ በማለቱ ፡ የአካል ፡ ክፍል ፡ መኾኑ ፡ ይቀራልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 17 ፤ አካል ፡ ሹሉ ፡ ዐይን ፡ ቢኾን ፡ መስማት ፡ ወዴት ፡ በተገኘ ፧ ሹሉም ፡ መስማት ፡ ቢኾን ፡ ማሽተት ፡ ወዴት ፡ በተገኘ ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 18 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ ብልቶችን ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በአካል ፡ አድርጓል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 19 ፤ ሹሉም ፡ አንድ ፡ ብልት ፡ ቢኾንስ ፡ አካል ፡ ወዴት ፡ በኾነ ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 20 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ አኹን ፡ ብልቶች ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ አካል ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 21 ፤ ዐይን ፡ እጅን ፦ አታስፈልገኝም ፡ ልትለው ፡ አትችልም ፥ ወይም ፡ ራስ ፡ ደግሞ ፡ እግሮችን ፦ አታስፈልጉኝም ፡ ሊላቸው ፡ አይችልም ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ደካማዎች ፡ የሚመስሉ ፡ የአካል ፡ ብልቶች ፡ ይልቁን ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ናቸው ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 23 ፤ ከአካልም ፡ ብልቶች ፡ ያልከበሩ ፡ ኾነው ፡ የሚመስሉን ፡ በሚበዛ ፡ ክብር ፡ እናለብሳቸዋለን ፥ በምናፍርባቸውም ፡ ብልቶቻችን ፡ ክብር ፡ ይጨመርላቸዋል ፤

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 24-25 ፤ ክብር ፡ ያላቸው ፡ ብልቶቻችን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አያስፈልጋቸውም ። ነገር ፡ ግን ፥ ብልቶች ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ በትክክል ፡ ይተሳሰቡ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ በአካል ፡ መለያየት ፡ እንዳይኾን ፥ ለጐደለው ፡ ብልት ፡ የሚበልጥ ፡ ክብር ፡ እየሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ አካልን ፡ አገጣጠመው ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 26 ፤ አንድም ፡ ብልት ፡ ቢሣቀይ ፡ ብልቶች ፡ ሹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይሣቀያሉ ፤ አንድ ፡ ብልትም ፡ ቢከበር ፡ ብልቶች ፡ ሹሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 27 ፤ እናንተም ፡ የክርስቶስ ፡ አካል ፡ ናችኹ ፡ እያንዳንዳችኹም ፡ ብልቶች ፡ ናችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 28 ፤ እግዚአብሔርም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንዳንዶቹን ፡ አስቀድሞ ፡ ሐዋርያትን ፥ ኹለተኛም ፡ ነቢያትን ፥ ሦስተኛም ፡ አስተማሪዎችን ፥ ቀጥሎም ፡ ተኣምራት ፡ ማድረግን ፥ ቀጥሎም ፡ የመፈወስን ፡ ስጦታ ፥ ርዳታንም ፥ አገዛዝንም ፥ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ ልሳኖችንም ፡ አድርጓል ።

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 29 ፤ ሹሉ ፡ ሐዋርያት ፡ ናቸውን ፧ ሹሉስ ፡ ነቢያት ፡ ናቸውን ፧ ሹሉስ ፡ አስተማሪዎች ፡ ናቸውን ፧ ሹሉስ ፡ ተኣምራትን ፡ ይሠራሉን ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 30 ፤ ሹሉስ ፡ የመፈወስ ፡ ስጦታ ፡ አላቸውን ፧ ሹሉስ ፡ በልሳኖች ፡ ይናገራሉን ፧ ሹሉስ ፡ ይተረጕማሉን ፧

ቆሮ.1 ፡ 12 ፡ 31 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚበልጠውን ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ በብርቱ ፡ ፈልጉ ። ደግሞም ፡ ከሹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ መንገድ ፡ አሳያችኋለኹ ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 1 ፤ በሰዎችና ፡ በመላእክት ፡ ልሳን ፡ ብናገር ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡ ከሌለኝ ፡ እንደሚጮኽ ፡ ናስ ፡ ወይም ፡ እንደሚንሿሿ ፡ ጸናጽል ፡ ኾኖለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 2 ፤ ትንቢትም ፡ ቢኖረኝ ፡ ምስጢርንም ፡ ዅሉና ፡ ዕውቀትን ፡ ዅሉ ፡ ባውቅ ፥ ተራራዎችንም ፡ እስካፈልስ ፡ ድረስ ፡ እምነት ፡ ዅሉ ፡ ቢኖረኝ ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡ ከሌለኝ ፡ ከንቱ ፡ ነኝ ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 3 ፤ ድኻዎችንም ፡ ልመግብ ፡ ያለኝን ፡ ዅሉ ፡ ባካፍል ፥ ሥጋዬንም ፡ ለእሳት ፡ መቃጠል ፡ አሳልፌ ፡ ብሰጥ ፥ ፍቅር ፡ ግን ፡ ከሌለኝ ፡ ምንም ፡ አይጠቅመኝም ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 4 ፤ ፍቅር ፡ ይታገሣል ፥ ቸርነትንም ፡ ያደርጋል ፤ ፍቅር ፡ አይቀናም ፤ ፍቅር ፡ አይመካም ፥ አይታበይም ፤

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 5 ፤ የማይገባውን ፡ አያደርግም ፥ የራሱንም ፡ አይፈልግም ፥ አይበሳጭም ፥ በደልን ፡ አይቈጥርም ፤

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 6 ፤ ከእውነት ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ዐመፃ ፡ ደስ ፡ አይለውም ፤

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ዅሉን ፡ ይታገሣል ፥ ዅሉን ፡ ያምናል ፥ ዅሉን ፡ ተስፋ ፡ ያደርጋል ፥ በዅሉ ፡ ይጸናል ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 8 ፤ ፍቅር ፡ ለዘወትር ፡ አይወድቅም ፤ ትንቢት ፡ ቢኾን ፡ ግን ፡ ይሻራል ፤ ልሳኖች ፡ ቢኾኑ ፡ ይቀራሉ ፤ ዕውቀትም ፡ ቢኾን ፡ ይሻራል ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 9 ፤ ከዕውቀት ፡ ከፍለን ፡ እናውቃለንና ፥ ከትንቢትም ፡ ከፍለን ፡ እንናገራለንና ፤

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 10 ፤ ፍጹም ፡ የኾነ ፡ ሲመጣ ፡ ግን ፡ ተከፍሎ ፡ የነበረው ፡ ይሻራል ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 11 ፤ ልጅ ፡ ሳለኹ ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ እናገር ፡ ነበር ፥ እንደ ፡ ልጅም ፡ ዐስብ ፡ ነበር ፥ እንደ ፡ ልጅም ፡ እቈጥር ፡ ነበር ፤ ጕልማሳ ፡ ኾኜ ፡ ግን ፡ የልጅነትን ፡ ጠባይ ፡ ሸሬያለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 12 ፤ ዛሬስ ፡ በመስተዋት ፡ በድንግዝግዝ ፡ እንደምናይ ፡ ነን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ እናያለን ፤ ዛሬስ ፡ ከዕውቀት ፡ ከፍዬ ፡ ዐውቃለኹ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ታወቅኹ ፡ ዐውቃለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 13 ፡ 13 ፤ እንዲህም ፡ ከኾነ ፥ እምነት ፡ ተስፋ ፡ ፍቅር ፡ እነዚህ ፡ ሦስቱ ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉ ፤ ከነዚህም ፡ የሚበልጠው ፡ ፍቅር ፡ ነው ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 1 ፤ ፍቅርን ፡ ተከታተሉ ፥ መንፈሳዊ ፡ ስጦታንም ፡ ይልቁንም ፡ ትንቢት ፡ መናገርን ፡ በብርቱ ፡ ፈልጉ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 2 ፤ በልሳን ፡ የሚናገርስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ አይናገርም ፤ የሚያስተውለው ፡ የለምና ፥ በመንፈስ ፡ ግን ፡ ምስጢርን ፡ ይናገራል ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 3 ፤ ትንቢትን ፡ የሚናገር ፡ ግን ፡ ለማነጽና ፡ ለመምከር ፡ ለማጽናናትም ፡ ለሰው ፡ ይናገራል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 4 ፤ በልሳን ፡ የሚናገር ፡ ራሱን ፡ ያንጻል ፤ ትንቢትን ፡ የሚናገር ፡ ግን ፡ ማኅበሩን ፡ ያንጻል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 5 ፤ ዅላችኹ ፡ በልሳኖች ፡ ልትናገሩ ፡ እወድ ፡ ነበር ፥ ትንቢትን ፡ ልትናገሩ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ይልቅ ፡ እወዳለኹ ፤ ማኅበሩ ፡ ይታነጽ ፡ ዘንድ ፡ ንግግሩን ፡ ባይተረጐም ፡ በልሳኖች ፡ ከሚናገር ፡ ትንቢትን ፡ የሚናገር ፡ ይበልጣል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 6 ፤ አኹን ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥቼ ፡ በልሳኖች ፡ ብናገር ፥ በመግለጥ ፡ ወይም ፡ በዕውቀት ፡ ወይም ፡ በትንቢት ፡ ወይም ፡ በትምህርት ፡ ካልነገርኋችኹ ፡ ምን ፡ እጠቅማችኋለኹ ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 7 ፤ ነፍስ ፡ የሌለበት ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ ዋሽንትም ፡ ክራርም ፡ ቢኾን ፡ ድምፅ ፡ ሲሰጥ ፡ የድምፁን ፡ ልዩነት ፡ ባይገልጥ ፡ በዋሽንት ፡ የሚነፋው ፡ ወይስ ፡ በክራር ፡ የሚመታው ፡ መዝሙር ፡ እንዴት ፡ ይታወቃል ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 8 ፤ ደግሞም ፡ መለከት ፡ የማይገለጥን ፡ ድምፅ ፡ ቢሰጥ ፡ ለጦርነት ፡ ማን ፡ ይዘጋጃል ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 9 ፤ እንዲሁ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ የተገለጠውን ፡ ቃል ፡ በአንደበት ፡ ባትናገሩ ፡ ሰዎች ፡ የምትናገሩትን ፡ እንዴት ፡ አድርገው ፡ ያስተውሉታል ፧ ለነፋስ ፡ የምትናገሩ ፡ ትኾናላችኹና ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 10 ፤ በዓለም ፡ ምናልባት ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ የቋንቋ ፡ ዐይነት ፡ ይኖራል ፡ ቋንቋም ፡ የሌለው ፡ ሕዝብ ፡ የለም ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ የቋንቋውን ፡ ፍች ፡ ባላውቅ ፡ ለሚናገረው ፡ እንግዳ ፡ እኾናለኹ ፥ የሚናገረውም ፡ ለእኔ ፡ እንግዳ ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 12 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ መንፈሳዊ ፡ ስጦታን ፡ በብርቱ ፡ የምትፈልጉ ፡ ከኾናችኹ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማነጽ ፡ እንዲበዛላችኹ ፡ ፈልጉ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ በልሳን ፡ የሚናገር ፡ እንዲተረጉም ፡ ይጸልይ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 14 ፤ በልሳን ፡ ብጸልይ ፡ መንፈሴ ፡ ይጸልያል ፥ አእምሮዬ ፡ ግን ፡ ያለፍሬ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ በመንፈስ ፡ እጸልያለኹ ፡ በአእምሮም ፡ ደግሞ ፡ እጸልያለኹ ፤ በመንፈስ ፡ እዘምራለኹ ፡ በአእምሮም ፡ ደግሞ ፡ እዘምራለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 16 ፤ እንዲያማ ፡ ካልኾነ ፥ አንተ ፡ በመንፈስ ፡ ብትባርክ ፥ ባልተማሩት ፡ ስፍራ ፡ የተቀመጠው ፡ የምትለውን ፡ ካላወቀ ፥ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ ለምስጋናኽ ፡ አሜን ፡ ይላል ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 17 ፤ አንተማ ፡ መልካም ፡ ታመሰግናለኽ ፥ ሌላው ፡ ግን ፡ አይታነጽበትም ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 18 ፤ ከዚኦላችኹ ፡ ይልቅ ፡ በልሳኖች ፡ እናገራለኹና ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሌላዎችን ፡ ደግሞ ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ በማኅበር ፡ እልፍ ፡ ቃላት ፡ በልሳን ፡ ከመናገር ፡ ይልቅ ፡ ዐምስት ፡ ቃላት ፡ በአእምሮዬ ፡ ልናገር ፡ እወዳለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 20 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በአእምሮ ፡ ሕፃናት ፡ አትኹኑ ፤ ለክፋት ፡ ነገር ፡ ሕፃናት ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ በአእምሮ ፡ የበሰሉ ፡ ኹኑ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 21 ፤ ሌላዎችን ፡ ልሳኖች ፡ በሚናገሩ ፡ ሰዎችና ፡ በሌላ ፡ አንደበት ፡ ለዚህ ፡ ሕዝብ ፡ እነግራቸዋለኹ ፥ እንዲህም ፡ ቢኾን ፡ አይሰሙኝም ፡ ይላል ፡ ጌታ ፡ ተብሎ ፡ በሕግ ፡ ተጽፏል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 22 ፤ እንግዲያስ ፡ በልሳኖች ፡ መናገር ፡ ለማያምኑ ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለሚያምኑ ፡ አይደለም ፥ ትንቢት ፡ ግን ፡ ለሚያምኑ ፡ እንጂ ፡ ለማያምኑ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 23 ፤ እንግዲህ ፡ ማኅበር ፡ ዥሉ ፡ ዐብረው ፡ ቢሰበሰቡ ፡ ዥሉም ፡ በልሳኖች ፡ ቢናገሩና ፡ ያልተማሩ ፡ ወይም ፡ የማያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ቢገቡ ፦ አብደዋል ፡ አይሉምን ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 24 ፤ ዥሉ ፡ ትንቢት ፡ ቢናገሩ ፡ ግን ፡ የማያምን ፡ ወይም ፡ ያልተማረ ፡ ሰው ፡ ቢገባ ፡ በዥሉ ፡ ይወቀሣል ፥ በዥሉም ፡ ይመረመራል ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 25 ፤ በልቡም ፡ የተሰወረ ፡ ይገለጣል ፡ እንዲሁም ፦ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ በመካከላቸው ፡ ነው ፡

ብሎ ፡ እየተናገረ ፡ በፊቱ ፡ ወድቆ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሰግዳል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 26 ፤ እንግዲህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ምንድር ፡ ነው ፧ በምትሰበሰቡበት ፡ ጊዜ ፡ ለያንዳንዱ ፡ መዝሙር ፡ አለው ፥ ትምህርት ፡ አለው ፥ መግለጥ ፡ አለው ፥ በልሳን ፡ መናገር ፡ አለው ፥ መተርጐም ፡ አለው ፤ ኹሉ ፡ ለማነጽ ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 27 ፤ በልሳን ፡ የሚናገር ፡ ቢኖር ፥ ኹለት ፡ ወይም ፡ ቢበዛ ፡ ሦስት ፡ ኾነው ፡ በተራቸው ፡ ይናገሩ ፥ አንዱም ፡ ይተርጉም ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 28 ፤ የሚተረጉም ፡ ባይኖር ፡ ግን ፥ በማኅበር ፡ መካከል ፡ ዝም ፡ ይበልና ፡ ለራሱና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይናገር ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 29 ፤ ነቢያትም ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ኾነው ፡ ይናገሩ ፡ ሌላዎችም ፡ ይለይዋቸው ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 30 ፤ በዚያ ፡ ለሚቀመጥ ፡ ለሌላ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ቢገለጥለት ፡ ፊተኛው ፡ ዝም ፡ ይበል ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 31 ፤ ኹሉም ፡ እንዲማሩ ፡ ኹሉም ፡ እንዲመከሩ ፡ ኹላችኹ ፡ በያንዳንዳችኹ ፡ ትንቢት ፡ ልትናገሩ ፡ ትችላላችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 32 ፤ የነቢያትም ፡ መናፍስት ፡ ለነቢያት ፡ ይገዛሉ ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 33 ፤ እግዚአብሔርስ ፡ የሰላም ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የሁከት ፡ አምላክ ፡ አይደለምና ፤ በቅዱሳንም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 34 ፤ ሴቶች ፡ በማኅበር ፡ ዝም ፡ ይበሉ ፤ ሕግ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚል ፡ እንዲገዙ ፡ እንጂ ፡ እንዲናገሩ ፡ አልተፈቀደላቸውምና ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 35 ፤ ለሴት ፡ በማኅበር ፡ መካከል ፡ መናገር ፡ ነውር ፡ ነውና ፥ ምንም ፡ ሊማሩ ፡ ቢወዱ ፡ በቤታቸው ፡ ባሎቻቸውን ፡ ይጠይቁ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 36 ፤ ምን ፡ ነው ፧ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የወጣ ፡ ከእናንተ ፡ ነውን ፧ ወይስ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ብቻ ፡ ደርሷልን ፧

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 37 ፤ ማንም ፡ ነቢይ ፡ ወይም ፡ መንፈሳዊ ፡ የኾነ ፡ ቢመስለው ፡ ይህች ፡ የጻፍኩላችኹ ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ኾነች ፡ ይወቅ ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 38 ፤ ማንም ፡ የማያውቅ ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ አይወቅ ።

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 39 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ትንቢት ፡ ለመናገር ፡ በብርቱ ፡ ፈልጉ ፥ በልሳኖች ፡ ከመናገርም ፡ አትከልክሉ ፤

ቆሮ.1 ፡ 14 ፡ 40 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ በአገባብና ፡ በሥርዐት ፡ ይኹን ።

_____1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ። _____

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የሰበክኹላችኹን ፡ ደግሞም ፡ የተቀበላችኹትን ፡ በርሱም ፡ ደግሞ ፡ የቆማችኹበትን ፡ በርሱም ፡ ደግሞ ፡ የምትድኑበትን ፡ ወንጌል ፡ አሳስባችኋለኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 2 ፤ በከንቱ ፡ ካላመናችኹ ፡ በቀር ፥ ብታስቡት ፥ በምን ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሰበክኹላችኹ ፡ አሳስባችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 3 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የተቀበልኹትን ፡ ከዥሉ ፡ በፊት ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋችኹ ፡ እንዲህ ፡ ብዬ ። መጽሐፍ ፡ እንደሚል ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታችን ፡ ሞተ ፥ ተቀበረም ፥

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 4 ፤ መጽሐፍም ፡ እንደሚል ፡ በሦስተኛው ፡ ቀን ፡ ተነሣ ፥

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 5 ፤ ለኬፋም ፡ ታየ ፡ በኋላም ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 6 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ከዐምስት ፡ መቶ ፡ ለሚበዙ ፡ ወንድሞች ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ታየ ፤ ከነርሱም ፡ የሚበዙቱ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ አሉ ፡ አንዳንዶች ፡ ግን ፡ አንቀላፍተዋል ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 7 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለያዕቆብ ፡ ኋላም ፡ ለሐዋርያት ፡ ዥሉ ፡ ታየ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 8 ፤ ከዥሉም ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ጭንጋፍ ፡ ለምኾን ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ ታየኝ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 9 ፤ እኔ ፡ ከሐዋርያት ፡ ዥሉ ፡ የማንስ ፡ ነኝና ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስላሳደድኹ ፡ ሐዋርያ ፡ ተብዬ ፡ ልጠራ ፡ የማይገባኝ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የኾንኹ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤ ለኔም ፡ የተሰጠኝ ፡ ጸጋው ፡ ከንቱ ፡ አልነበረም ፡ ከዥላቸው ፡ ይልቅ ፡ ግን ፡ ደከምኹ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለኹም ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 11 ፤ እንግዲህስ ፡ እኔ ፡ ብኾን ፡ እነርሱም ፡ ቢኾኑ ፡ እንዲሁ ፡ እንሰብካለን ፡ እንዲሁም ፡ አመናችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 12 ፤ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ የሚሰበክ ፡ ከኾነ ፡ ግን ፡ ከእናንተ ፡ አንዳንዶቹ ፦ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፡ እንዴት ፡ ይላሉ ፧

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 13 ፤ ትንሣኤ ፡ ሙታንስ ፡ ከሌለ ፡ ክርስቶስ ፡ አልተነሣማ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 14 ፤ ክርስቶስም ፡ ካልተነሣ ፡ እንግዲያስ ፡ ስብከታችን ፡ ከንቱ ፡ ነው ፥ እምነታችኹም ፡ ደግሞ ፡ ከንቱ ፡ ናት ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 15 ፤ ደግሞም ፦ ክርስቶስን ፡ አስነሥቶታል ፡ ብለን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ መሰከርን ፡ ሐሰተኞች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክሮች ፡ ኾነን ፡ ተገኝተናል ፤ ሙታን ፡ ግን ፡ የማይነሡ ፡ ከኾነ ፡ ርሱን ፡ አላስነሣውም ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 16 ፤ ሙታን ፡ የማይነሡ ፡ ከኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ አልተነሣማ ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 17 ፤ ክርስቶስም ፡ ካልተነሣ ፡ እምነታችኹ ፡ ከንቱ ፡ ናት ፤ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ በኀጢአታችኹ ፡ አላችኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 18 ፤ እንግዲያስ ፡ በክርስቶስ ፡ ያንቀላፉት ፡ ደግሞ ፡ ጠፍተዋላ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 19 ፤ በዚች ፡ ሕይወት ፡ ብቻ ፡ ክርስቶስን ፡ ተስፋ ፡ ያደረግን ፡ ከኾነ ፥ ከሰው ፡ ዥሉ ፡ ይልቅ ፡ ምስኪኖች ፡ ነን ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 20 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ላንቀላፉት ፡ በኩራት ፡ ኾኖ ፡ ከሙታን ፡ ተነሥቷል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 21 ፤ ሞት ፡ በሰው ፡ በኩል ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ በሰው ፡ በኩል ፡ ኾኗልና ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 22 ፤ ዥሉ ፡ በአዳም ፡ እንደሚሞቱ ፡ እንዲሁ ፡ ዥሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ሕያዋን ፡ ይኾናሉና ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዱ ፡ በራሱ ፡ ተራ ፡ ይኾናል ፤ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ በኵራት ፡ ነው ፥ በኋላም ፡ በመምጣቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ የኾኑት ፡ ናቸው ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 24 ፤ በኋላም ፥ መንግሥቱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለአባቱ ፡ አሳልፎ ፡ በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ አለቅነትንም ፡ ኹሉና ፡ ሥልጣንን ፡ ኹሉ ፡ ኀይልንም ፡ በሻረ ፡ ጊዜ ፥ ፍጻሜ ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 25 ፤ ጠላቶቹን ፡ ኹሉ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ እስኪያደርግ ፡ ድረስ ፡ ሊነግሥ ፡ ይገባዋልና ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 26 ፤ የኋለኛው ፡ ጠላት ፡ የሚሻረው ፡ ሞት ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 27 ፤ ኹሉን ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አስገዝቷልና ። ነገር ፡ ግን ፦ ኹሉ ፡ ተገዝቷል ፡ ሲል ፥ ኹሉን ፡ ካስገዛለት ፡ በቀር ፡ መኾኑ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 28 ፤ ኹሉ ፡ ከተገዛለት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ኹሉ ፡ በኹሉ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ኹሉን ፡ ላስገዛለት ፡ ይገዛል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 29 ፤ እንዲያማ ፡ ካልኾነ ፥ ስለ ፡ ሙታን ፡ የሚጠመቁ ፡ ምን ፡ ያደርጋሉ ፧ ሙታንስ ፡ ከቶ ፡ የማይነሡ ፡ ከኾነ ፥ ስለ ፡ እነርሱ ፡ የሚጠመቁ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 30 ፤ እኛስ ፡ ዘወትር ፡ በሚያስፈራ ፡ ኑሮ ፡ የምንኖር ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 31 ፤ በጌታችን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ባለኝ ፡ በእናንተ ፡ ትምክሕት ፡ እየማልኹ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እሞታለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 32 ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ በኤፌሶን ፡ ከአውሬ ፡ ጋራ ፡ ከታገልኹ ፥ ሙታንስ ፡ የማይነሡ ፡ ከኾነ ፥ ምን ፡ ይጠቅመኛል ፧ ነገ ፡ እንሞታለንና ፡ እንብላና ፡ እንጠጣ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 33 ፤ አትሳቱ ፤ ክፉ ፡ ባልንጀርነት ፡ መልካሙን ፡ ዐመል ፡ ያጠፋል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 34 ፤ በጽድቅ ፡ ንቁ ፡ ኀጢአትንም ፡ አትሥሩ ፤ እግዚአብሔርን ፡ የማያውቁ ፡ አሉና ፤ አሳፍራችኹ ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ እላለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 35 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፦ ሙታን ፡ እንዴት ፡ ይነሣሉ ፧ በምንስ ፡ ዐይነት ፡ አካል ፡ ይመጣሉ ፧ የሚል ፡ ይኖር ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 36 ፤ አንተ ፡ ሞኝ ፥ አንተ ፡ የምትዘራው ፡ ካልሞተ ፡ ሕያው ፡ አይኾንም ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 37 ፤ የምትዘራውም ፥ ስንዴ ፡ ቢኾን ፡ ከሌላም ፡ ዐይነት ፡ የአንዱ ፡ ቢኾን ፥ ቅንጣት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ የምትዘራው ፡ የሚኾነውን ፡ አካል ፡ አይደለም ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 38 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ አካልን ፡ ይሰጠዋል ፥ ከዘሮችም ፡ ለያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ አካሉን ፡ ይሰጠዋል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 39 ፤ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ አይደለም ፥ የሰው ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ፥ የእንስሳም ፡ ሥጋ ፡ ሌላ ፡ ነው ፥ የወፎችም ፡ ሥጋ ፡ ሌላ ፡ ነው ፥ የዓሣም ፡ ሥጋ ፡ ሌላ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 40 ፤ ደግሞ ፡ ሰማያዊ ፡ አካል ፡ አለ ፥ ምድራዊም ፡ አካል ፡ አለ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሰማያዊ ፡ አካል ፡ ክብር ፡ ልዩ ፡ ነው ፥ የምድራዊም ፡ አካል ፡ ክብር ፡ ልዩ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 41 ፤ የፀሓይ ፡ ክብር ፡ አንድ ፡ ነው ፥ የጨረቃም ፡ ክብር ፡ ሌላ ፡ ነው ፥ የከዋክብትም ፡ ክብር ፡ ሌላ ፡

ነው ፤ በክብር ፡ አንዱ ፡ ኮከብ ፡ ከሌላው ፡ ኮከብ ፡ ይለያልና ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 42 ፤ የሙታን ፡ ትንሣኤ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ነው ። በመበስበስ ፡ ይዘራል ፥ ባለመበስበስ ፡ ይነሣል ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 43 ፤ በውርደት ፡ ይዘራል ፥ በክብር ፡ ይነሣል ፤ በድካም ፡ ይዘራል ፥ በኀይል ፡ ይነሣል ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 44 ፤ ፍጥረታዊ ፡ አካል ፡ ይዘራል ፥ መንፈሳዊ ፡ አካል ፡ ይነሣል ። ፍጥረታዊ ፡ አካል ፡ ካለ ፡ መንፈሳዊ ፡ አካል ፡ ደግሞ ፡ አለ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 45 ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፦ ፊተኛው ፡ ሰው ፡ አዳም ፡ ሕያው ፡ ነፍስ ፡ ኾነ ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏል ፤ ኋለኛው ፡ አዳም ፡ ሕይወትን ፡ የሚሰጥ ፡ መንፈስ ፡ ኾነ ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 46 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አስቀድሞ ፡ ፍጥረታዊው ፡ ቀጥሎም ፡ መንፈሳዊው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መንፈሳዊው ፡ መገኮመሪያ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 47 ፤ የፊተኛው ፡ ሰው ፡ ከመሬት ፡ መሬታዊ ፡ ነው ፤ ኹለተኛው ፡ ሰው ፡ ከሰማይ ፡ ነው ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 48 ፤ መሬታዊው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መሬታውያን ፡ የኾኑት ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ፥ ሰማያዊው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሰማያውያን ፡ የኾኑት ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ናቸው ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 49 ፤ የዚያንም ፡ የመሬታዊውን ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ለበስን ፡ የሰማያዊውን ፡ መልክ ፡ ደግሞ ፡ እንለብሳለን ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 50 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ እላለኹ ፦ ሥጋና ፡ ደም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ሊወርሱ ፡ አይችሉም ፥ የሚበሰብሰውም ፡ የማይበሰብሰውን ፡ አይወርስም ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 51-52 ፤ እንሆ ፥ አንድ ፡ ምስጢር ፡ እነግራችኋለኹ ፤ ኹላችን ፡ አናንቀላፋም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የኋለኛው ፡ መለከት ፡ ሲነፋ ፡ ኹላችን ፡ በድንገት ፡ በቅጽበተ ፡ ዐይን ፡ እንለወጣለን ፤ መለከት ፡ ይነፋልና ፥ ሙታንም ፡ የማይበሰብሱ ፡ ኾነው ፡ ይነሣሉ ፥ እኛም ፡ እንለወጣለን ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 53 ፤ ይህ ፡ የሚበሰብሰው ፡ የማይበሰብሰውን ፡ ሊለብስ ፥ ይህም ፡ የሚሞተው ፡ የማይሞተውን ፡ ሊለብስ ፡ ይገባዋልና ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 54 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ የሚበሰብሰው ፡ የማይበሰብሰውን ፡ ሲለብስ ፡ ይህም ፡ የሚሞተው ፡ የማይሞተውን ፡ ሲለብስ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፦ ሞት ፡ ድል ፡ በመነሣት ፡ ተዋጠ ፡ ተብሎ ፡ የተጻፈው ፡ ቃል ፡ ይፈጸማል ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 55 ፤ ሞት ፡ ሆይ ፥ መውጊያኽ ፡ የት ፡ አለ ፧ ሲኦል ፡ ሆይ ፥ ድል ፡ መንሣትኽ ፡ የት ፡ አለ ፧

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 56 ፤ የሞት ፡ መውጊያ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፥ የኀጢአትም ፡ ኀይል ፡ ሕግ ፡ ነው ፤

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 57 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ ድል ፡ መንሣትን ፡ ለሚሰጠን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 15 ፡ 58 ፤ ስለዚህ ፥ የተወደዳችኹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ድካማችኹ ፡ በጌታ ፡ ከንቱ ፡ እንዳይኾን ፡ ዐውቃችኋልና ፥ የምትደላደሉ ፥ የማትነቃነቁም ፥ የጌታም ፡ ሥራ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ የሚበዛላችኹ ፡ ኹኑ ።

1ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 1 ፤ ለቅዱሳንም ፡ ገንዘብን ፡ ስለ ፡ ማዋጣት ፥ ለገላትያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንደ ፡ ደነገግኹት ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 2 ፤ እኔ ፡ ስመጣ ፡ ይህ ፡ የገንዘብ ፡ ማዋጣት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ እንዳይኾን ፥ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ በየሳምንቱ ፡ በፊተኛው ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ቀናው ፡ መጠን ፡ እያስቀረ ፡ በቤቱ ፡ ያስቀምጥ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 3 ፤ ስመጣም ፡ ማናቸውም ፡ ቢኾኑ ፡ የታመኑ ፡ የሚመስሏችኹ ፡ ሰዎች ፡ ቸርነታችኹን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ያደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ደብዳቤ ፡ ሰጥቼ ፡ እልካቸዋለኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ልኼድ ፡ የሚገባኝ ፡ ብኾን ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ይኼዳሉ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 5 ፤ በመቄዶንያም ፡ ሳልፍ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመጣለኹ ፤ በመቄዶንያ ፡ አድርጌ ፡ ዐልፋለኹና ፤

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 6 ፤ እናንተም ፡ ወደምኼድበት ፡ ወደ ፡ ማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ በጕዞዬ ፡ እንድትረዱኝ ፡ ምናልባት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እቈይ ፡ ወይም ፡ እከርም ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 7 ፤ አኹን ፡ እግረ ፡ መንገዴን ፡ ሳልፍ ፡ ልጐበኛችኹ ፡ አልወድምና ፤ ጌታ ፡ ቢፈቅደው ፡ የኾነውን ፡ ዘመን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ልሰነብት ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹና ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 8 ፤ በኤፌሶን ፡ ግን ፡ እስከ ፡ በዓለ ፡ ኀምሳ ፡ ድረስ ፡ እሰነብታለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 9 ፤ ሥራ ፡ የሞላበት ፡ ትልቅ ፡ በር ፡ ተከፍቶልኛልና ፥ ተቃዋሚዎችም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 10 ፤ ጢሞቴዎስም ፡ የመጣ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለፍርሀት ፡ እንዲኖር ፡ ተጠንቀቁ ፤ እንደ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የጌታን ፡ ሥራ ፡ ይሠራልና ፤ እንግዲህ ፡ ማንም ፡ አይናቀው ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ እጠብቀዋለኹና ፥ ወደ ፡ እኔ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ በሰላም ፡ በጕዞው ፡ ርዱት ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 12 ፤ ስለ ፡ ወንድማችን ፡ ስለ ፡ አጵሎስ ፡ ግን ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ሊኼድ ፡ እጅግ ፡ አድርጌ ፡ ለምኜው ፡ ነበር ፤ ዛሬም ፡ ለመምጣት ፡ ከቶ ፡ ፈቃድ ፡ አልነበረውም ፥ ሲመቸው ፡ ግን ፡ ይመጣል ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 13 ፤ ንቁ ፥ በሃይማኖት ፡ ቁሙ ፥ ጐልምሱ ፥ ጠንክሩ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 14 ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ኹሉ ፡ በፍቅር ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 15 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የእስጢፋኖስ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ የአካይያ ፡ በኩራት ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ቅዱሳንንም ፡ ለማገልገል ፡ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ታውቃላችኹ ፤

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 16 ፤ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ላሉትና ፡ ዐብሮ ፡ ለሚሠራ ፡ ለሚደክምም ፡ ኹሉ ፡ እናንተም ፡ እንድትገዙ ፡ እለምናችኋለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 17 ፤ በእስጢፋኖስና ፡ በፈርዶናጥስ ፡ በአካይቆስም ፡ መምጣት ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ እናንተ ፡ ስለሌላችኹ ፡ የጐደለኝን ፡ ፈጽመዋልና ፤ መንፈሴንና ፡ መንፈሳችኹን ፡ አሳርፈዋልና ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 18 ፤ እንግዲህ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉትን ፡ ዕወቋቸው ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 19 ፤ የእስያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ። አቂላና ፡ ጵርስቅላ ፡ በቤታቸው ፡ ካለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ በጌታ ፡ እጅግ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 20 ፤ ወንድሞች ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ። በተቀደሰ ፡ አሳሳም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ይሀን ፡ ሰላምታ ፡ በገዛ ፡ እጄ ፡ ጽፌያለኹ ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 22 ፤ ጌታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ የማይወድ ፡ ቢኖር ፡ የተረገመ ፡ ይኹን ። ጌታችን ፡ ሆይ ፥ ና ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 23 ፤ የጌታ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ቆሮ.1 ፡ 16 ፡ 24 ፤ ፍቅሬ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ከሹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ነው ። አሜን ❖

ኹለተኛዉ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፡ ወንድሙም ፡ ጢሞቴዎስ ፥ በአካይያ ፡ አገር ፡ �withሉ ፡ ከሚኖሩ ፡ ቅዱሳን ፡ withሉ ፡ ጋራ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ላለች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይwithን ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ የርኅራኄ ፡ አባት ፡ የመጽናናትም ፡ withሉ ፡ አምላክ ፡ የኾነ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ ይባረክ ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ርሱ ፡ በመከራችን ፡ withሉ ፡ ያጽናናናል ፥ ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ራሳችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በምንጽናናበት ፡ መጽናናት ፡ በመከራ ፡ withሉ ፡ ያሉትን ፡ ማጽናናት ፡ እንችላለን ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ የክርስቶስ ፡ ሥቃይ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ በዛ ፥ እንዲሁ ፡ መጽናናታችን ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ በኩል ፡ ይበዛልናልና ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ ብንቀበል ፥ ስለ ፡ መጽናናታችwithና ፡ ስለ ፡ መዳናችwithሉ ፡ ነው ፤ ብንጽናናም ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ የምንሣቀይበት ፡ በዚያ ፡ ሥቃይ ፡ በመጽናት ፡ ስለሚደረግ ፡ ስለ ፡ መጽናናታችwithሉ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ተስፋችንም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ጽኑ ፡ ነው ፤ ሥቃያችንን ፡ እንደ ፡ ተካፈላችwithሉ ፡ እንዲሁም ፡ መጽናናታችንን ፡ ደግሞ ፡ እንድትካፈሉ ፡ እናውቃለንና ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ በእስያ ፡ ስለደረሰብን ፡ መከራችን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንወዳለንና ፤ ስለ ፡ ሕይወታችን ፡ እንኳ ፡ ተስፋ ፡ እስከንቈርጥ ፡ ድረስ ፡ ከዐቅማችን ፡ በላይ ፡ ያለልክ ፡ ከብዶብን ፡ ነበር ፤

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ አዎን ፥ ሙታንን ፡ በሚያነሣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ በራሳችን ፡ እንዳንታመን ፥ እኛ ፡ ራሳችን ፡ የሞትን ፡ ፍርድ ፡ በውስጣችን ፡ ሰምተን ፡ ነበር ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 10-11 ፤ ርሱም ፡ ይህን ፡ ከሚያክል ፡ ሞት ፡ አዳነን ፥ ያድነንማል ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እየጸለያችwithሉ ፡ ዐብራችwithሉ ፡ ስትረዱን ፥ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ በኩል ፡ ስለተሰጠን ፡ ስለጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ብዙዎች ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ያመሰግኑ ፡ ዘንድ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ እንዲያድን ፡ በርሱ ፡ ተስፋ ፡ አድርገናል ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ትምክሕታችን ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንጂ ፡ በሥጋዊ ፡ ጥበብ ፡ ሳይwithን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ቅድስናና ፡ ቅንነት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ይልቁንም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደኖርን ፡ የኅሊናችን ፡ ምስክርነት ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፥ 1 ፥ 13-14 ፤ ከምታነቡትና ፡ ከምታስተውሉት ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አንጽፍላችwithምና ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ቀን ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ትምክሕታችን ፡ እንደምትwithሉ ፡ እንዲሁ ፡ ትምክሕታችwithሉ ፡ እንድንwithን ፥ በከፊል ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ እንዳስተዋላችwithሉ ፡ ፈጽማችwithሉ ፡ ታስተውሉት ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለሁ ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 15 ፤ በዚህም ፡ ታምኜ ፥ ኹለተኛ ፡ ጸጋ ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድሜ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንድመጣ ፥

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 16 ፤ በእናንተም ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ እንዳልፍ ፡ ደግሞም ፡ ከመቄዶንያ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥቼ ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ በጕዞዬ ፡ እንድትረዱኝ ፡ ዐሰብኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ሳስብ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ቅሌትን ፡ አሳየኹን ፧ ወይስ ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ አይደለም ፡ አይደለም ፡ ማለት ፡ እንዲኾን ፡ ያን ፡ የማስበው ፡ በዓለማዊ ፡ ልማድ ፡ ነውን ፧

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 18 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የታመነ ፡ ነው ፥ ለእናንተም ፡ የሚነገረው ፡ ቃላችን ፡ አዎንና ፡ አይደለም ፡ አይኾንም ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 19 ፤ በእኛ ፡ ማለት ፡ በእኔና ፡ በስልዋኖስ ፡ በጢሞቴዎስም ፡ በመካከላችኹ ፡ የተሰበከ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አዎንና ፡ አይደለም ፡ አልነበረም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በርሱ ፡ አዎን ፡ ኾኗል ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለሰጠው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ኹሉ ፡ አዎን ፡ ማለት ፡ በርሱ ፡ ነውና ፥ ስለዚህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ክብሩ ፡ በእኛ ፡ የሚነገረው ፡ አሜን ፡ በርሱ ፡ ደግሞ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 21 ፤ በክርስቶስም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የሚያጸናንና ፡ የቀባን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 22 ፤ ደግሞም ፡ ያተመን ፡ የመንፈሱንም ፡ መያዣ ፡ በልባችን ፡ የሰጠን ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 23 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ልራራላችኹ ፡ ስል ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ እንዳልመጣኹ ፡ በነፍሴ ፡ ላይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምስክር ፡ እጠራለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 1 ፡ 24 ፤ ለደስታችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ የምንሠራ ፡ ነን ፡ እንጂ ፥ በእምነታችኹ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የምንገዛ ፡ አይደለንም ። በእምነታችኹ ፡ ቆማችኋልና ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዳግመኛ ፡ በሐዘን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ቈረጥኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 2 ፤ እኔስ ፡ ባሳዝናችኹ ፥ እንግዲያስ ፡ በእኔ ፡ ምክንያት ፡ ከሚያዝን ፡ በቀር ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘኝ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 3 ፤ ደስ ፡ ሊያሠኙኝ ፡ ከሚገባቸውም ፡ በመምጣቴ ፡ ሐዘን ፡ እንዳይኾንብኝ ፡ ይህንኑ ፡ ጻፍኩላችኹ ፥ ደስታዬ ፡ የኹላችኹ ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ ብዬ ፡ በኹላችኹ ፡ ታምኛለኹና ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 4 ፤ በብዙ ፡ መከራና ፡ ከልብ ፡ ጭንቀት ፡ በብዙም ፡ እንባ ፡ ጽፌላችኹ ፡ ነበርና ፤ ይህም ፡ እናንተን ፡ አብዝቼ ፡ የምወድበትን ፡ ፍቅር ፡ እንድታውቁ ፡ እንጂ ፡ እንዳሳዝናችኹ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ አሳዝኖ ፡ ቢኾን ፥ እንዳልከብድባችኹ ፥ በክፍል ፡ ኹላችኹን ፡ እንጂ ፡ እኔን ፡ ያሳዘነ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 6 ፤ እንደዚህ ፡ ላለ ፡ ሰው ፡ ይህ ፡ ከእናንተ ፡ የምትበዙት ፡ የቀጣችኹት ፡ ቅጣት ፡ ይበቃዋልና ፥ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ከልክ ፡ በሚበዛ ፡ ሐዘን ፡ እንዳይዋጥ ፥

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ይልቅ ፡ ተመልሳችኹ ፡ ይቅር ፡ ማለትና ፡ ማጽናናት ፡ ይገባችኋል ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ፍቅርን ፡ እንድታጸኑ ፡ እለምናችኋለኹ ፤

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ጽፌ ፡ ነበርና ፤ በ"ሹሉ ፡ የምትታዘዙ ፡ እንደ ፡ "ኮናችኹ ፡ የእናንተን ፡ መፈተን ፡ ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዐሳቤ ፡ ነበር ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 10 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ይቅር ፡ የምትሉትን ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ይቅር ፡ እለዋለኹ ፤ እኔም ፡ ይቅር ፡ ካልኹ ፥ ይቅር ፡ ያልኹትን ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በክርስቶስ ፡ ፊት ፡ ይቅር ፡ ብያለኹ ፥

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ በሰይጣን ፡ እንዳንታለል ፤ የርሱን ፡ ዐሳብ ፡ አንስተውምና ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ስለክርስቶስም ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ ጢሮዳ ፡ በመጣኹ ፡ ጊዜ ፥ ለጌታ ፡ ሥራ ፡ በር ፡ ምንም ፡ ቢከፈትልኝ ፥ ቲቶን ፡ ወንድሜን ፡ ስላላገኘኹት ፡ መንፈሴ ፡ ዕረፍት ፡ አልነበረውም ፥

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከነርሱ ፡ ተሰናብቼ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ ወጣኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በክርስቶስ ፡ "ሹል ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ በመንሣቱ ፡ ለሚያዞረን ፡ በእኛም ፡ በየስፍራው ፡ "ሹሉ ፡ የዕውቀቱን ፡ "ሽታ ፡ ለሚገልጥ ፡ ለአምላክ ፡ ምስጋና ፡ ይኹን ፤

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ በሚድኑቱና ፡ በሚጠፉቱ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የክርስቶስ ፡ መዐዛ ፡ ነንና ፤

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ለእነዚህ ፡ ለሞት ፡ የሚ"ኮን ፡ የሞት ፡ "ሽታ ፡ ለእነዚያም ፡ ለሕይወት ፡ የሚ"ኮን ፡ የሕይወት ፡ "ሽታ ፡ ነን ። ለዚህም ፡ ነገር ፡ የሚበቃ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ቆሮ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ቀላቅለው ፡ እንደሚሸቃቅጡት ፥ እንደ ፡ ብዙዎቹ ፡ አይደለንምና ፤ በቅንነት ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተላከን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በክርስቶስ ፡ "ኮነን ፡ እንናገራለን ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ራሳችንን ፡ ልናመሰግን ፡ እንገ"ምራለንን ፧ ወይስ ፡ እንደ ፡ ሌላዎች ፡ የማመስገኛ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ወይስ ፡ ከእናንተ ፡ ያስፈልገን ፡ ይ"ኮንን ፧

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሰዎች ፡ "ሹሉ ፡ የሚያውቁትና ፡ የሚያነቡት ፡ በልባችን ፡ የተጻፈ ፡ መልእክታችን ፡ እናንተ ፡ ናችኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ እናንተም ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ በቀለም ፡ አይደለም ፥ ሥጋ ፡ በ"ኮነ ፡ በልብ ፡ ጽላት ፡ እንጂ ፡ በድንጋይ ፡ ጽላት ፡ ያልተጻፈ ፥ በእኛም ፡ የተገለገለ ፡ የክርስቶስ ፡ መልእክት ፡ እንደ ፡ "ኮናችኹ ፡ የተገለጠ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ በክርስቶስም ፡ በኩል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ እምነት ፡ አለን ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ብቃታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በገዛ ፡ እጃችን ፡ እንደሚ"ኮን ፡ አንዳችን ፡ እንኳ ፡ ልናስብ ፡ ራሳችን ፡ የበቃን ፡ አይደለንም ፤

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 6 ፤ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ በመንፈስ ፡ እንጂ ፡ በፊደል ፡ ለማይ"ኮን ፡ ለዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ አገልጋዮች ፡ እን"ኮን ፡ ዘንድ ፡ አበቃን ፤ ፊደል ፡ ይገድላልና ፥ መንፈስ ፡ ግን ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣል ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ስለዚያ ፡ ስለ ፡ ተሻረው ፡ ስለ ፡ ፊቱ ፡ ክብር ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ትኵር ፡ ብለው ፡ መመልከት ፡ እስኪሳናቸው ፡ ድረስ ፥ ያ ፡ በፊደላት ፡ በድንጋዮች ፡ ላይ ፡ የተቀረጸ ፡ የሞት ፡ አገልግሎት ፡ በክብር ፡ ከ"ኮነ ፥

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ የመንፈስ ፡ አገልግሎት ፡ እንዴት ፡ ይልቅ ፡ በክብር ፡ አይ"ኮንም ፧

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ የኵነኔ ፡ አገልግሎት ፡ ክብር ፡ ከኾነ ፥ ይልቅ ፡ የጽድቅ ፡ አገልግሎት ፡ በክብር ፡ አብዝቶ ፡ ይበልጣልና ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 10 ፤ ያ ፡ የከበረ ፡ እንኳ ፡ እጅግ ፡ በሚበልጠው ፡ ክብር ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ክብሩን ፡ ዐጥቷልና ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ያ ፡ ይሻር ፡ የነበረው ፡ በክብር ፡ ከኾነ ፥ ጸንቶ ፡ የሚኖረውማ ፡ እጅግ ፡ ይልቅ ፡ በክብር ፡ ኾኗልና ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ ካለን ፡ እጅግ ፡ ገልጠን ፡ እንናገራለን ፥

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ የዚያንም ፡ ይሻር ፡ የነበረውን ፡ መጨረሻ ፡ ትዙር ፡ ብለው ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ እንዳይመለከቱ ፥ በፊቱ ፡ መጋረጃ ፡ እንዳደረገ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ አይደለንም ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዐሳባቸው ፡ ደነዘዘ ። ብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ሲነበብ ፡ ያ ፡ መጋረጃ ፡ ሳይወሰድ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ይኖራልና ፤ በክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ የተሻረ ፡ ነውና ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ የሙሴ ፡ መጻሕፍት ፡ በተነበቡ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ ያ ፡ መጋረጃ ፡ በልባቸው ፡ ይኖራል ፤

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ ወደ ፡ ጌታ ፡ ግን ፡ ዘወር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ መጋረጃው ፡ ይወሰዳል ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ ጌታ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ የጌታም ፡ መንፈስ ፡ ባለበት ፡ በዚያ ፡ ሐራነት ፡ አለ ።

ቆሮ.2 ፡ 3 ፡ 18 ፤ እኛም ፡ ኹላችን ፡ በመጋረጃ ፡ በማይከደን ፡ ፊት ፡ የጌታን ፡ ክብር ፡ እንደ ፡ መስተዋት ፡ እያብለጨለጭን ፡ መንፈስ ፡ ከሚኾን ፡ ጌታ ፡ እንደሚደረግ ፡ ያን ፡ መልክ ፡ እንመስል ፡ ዘንድ ፡ ከክብር ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ እንለወጣለን ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ምሕረት ፡ እንደተሰጠን ፡ መጠን ፡ ይህ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ አለን ፡ አንታክትም ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚያሳፍረውን ፡ ስውር ፡ ነገር ፡ ጥለናልና ፥ በተንኰል ፡ አንመላለስም ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ በውሸት ፡ አንቀላቅልም ፤ እውነትን ፡ በመግለጥ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ለሰው ፡ ኅሊና ፡ ኹሉ ፡ ራሳችንን ፡ እናመሰግናለን ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ወንጌላችን ፡ የተከደነ ፡ ቢኾን ፡ እንኳ ፡ የተከደነባቸው ፡ ለሚጠፉ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 4 ፤ ለእነርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የኾነ ፡ የክርስቶስ ፡ የክብሩ ፡ ወንጌል ፡ ብርሃን ፡ እንዳያበራላቸው ፥ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አምላክ ፡ የማያምኑትን ፡ ዐሳብ ፡ አሳወረ ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 5 ፤ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስን ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ ራሳችንን ፡ አንሰብክምና ፥ ስለ ፡ ኢየሱስም ፡ ራሳችንን ፡ ለእናንተ ፡ ባሪያዎች ፡ እናደርጋለን ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 6 ፤ በክርስቶስ ፡ ፊት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የክብሩን ፡ ዕውቀት ፡ ብርሃን ፡ እንዲሰጥ ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ የበራ ፦ በጨለማ ፡ ብርሃን ፡ ይብራ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የኀይሉ ፡ ታላቅነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ ከእኛ ፡ እንዳይኾን ፡ ይህ ፡ መዝገብ ፡ በሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ውስጥ ፡ አለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 8 ፤ በ"ሹሉ ፡ እ"ገፋለን ፡ እንጂ ፡ አንጨነቅም ፤ እናመነታለን ፡ እንጂ ፡ ተስፋ ፡ አንቈርጥም ፤

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 9 ፤ እንሰደዳለን ፡ እንጂ ፡ አንጣልም ፤ እንወድቃለን ፡ እንጂ ፡ አንጠፋም ፤

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 10 ፤ የኢየሱስ ፡ ሕይወት ፡ ደግሞ ፡ በሥጋችን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ "ሹል ፡ ጊዜ ፡ የኢየሱስን ፡ መሞት ፡ በሥጋችን ፡ ተሸክመን ፡ እንዞራለን ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 11 ፤ የኢየሱስ ፡ ሕይወት ፡ ደግሞ ፡ በሚሞት ፡ ሥጋችን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ የ"ኾ"ን ፡ ከኢየሱስ ፡ የተነሣ ፡ ዘወትር ፡ ለሞት ፡ አልፈን ፡ እንሰጣለንና ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ሞቱ ፡ በእኛ ፥ ሕይወቱም ፡ በእናንተ ፡ ይሠራል ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ አመንኹ ፥ ስለዚህም ፡ ተናገርኹ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ ያው ፡ አንዱ ፡ የእምነት ፡ መንፈስ ፡ ስለ ፡ አለን ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እናምናለን ፡ ስለዚህም ፡ እንናገራለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 14 ፤ ጌታን ፡ ኢየሱስን ፡ ያስነሣው ፡ እኛን ፡ ደግሞ ፡ ከኢየሱስ ፡ ጋራ ፡ እንዲያስነሣን ፡ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ እንዲያቀርበን ፡ እናውቃለንና ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 15 ፤ በብዙዎች ፡ በኩል ፡ የተትረፈረፈው ፡ ጸጋ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋናን ፡ ያበዛ ፡ ዘንድ ፥ "ሹሉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ነውና ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ስለዚህም ፡ አንታክትም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የውጭው ፡ ሰውነታችን ፡ ቢጠፋ ፡ እንኳ ፡ የውስጡ ፡ ሰውነታችን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይታደሳል ።

ቆሮ.2 ፡ 4 ፡ 17-18 ፤ የማይታየውን ፡ እንጂ ፡ የሚታየውን ፡ ባንመለከት ፥ ቀላል ፡ የ"ኾነ ፡ የጊዜው ፡ መከራችን ፡ የክብርን ፡ የዘለዓለም ፡ ብዛት ፡ ከ"ሹሉ ፡ መጠን ፡ ይልቅ ፡ ያደርግልናልና ፤ የሚታየው ፡ የጊዜው ፡ ነውና ፥ የማይታየው ፡ ግን ፡ የዘለዓለም ፡ ነው ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 1 ፤ ድንኳን ፡ የሚ"ኾነው ፡ ምድራዊ ፡ መኖሪያችን ፡ ቢፈርስ ፥ በሰማይ ፡ ያለ ፡ በእጅ ፡ ያልተሠራ ፡ የዘለዓለም ፡ ቤት ፡ የሚ"ኾን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሠራ ፡ ሕንጻ ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለንና ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 2 ፤ በዚህ ፡ ውስጥ ፡ በእውነት ፡ እንቃትታለንና ፥

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 3 ፤ ከሰማይም ፡ የሚ"ኾነውን ፡ መኖሪያችንን ፡ እንድንለብስ ፡ እንናፍቃለንና ፡ ለብሰን ፡ ዕራቍታችንን ፡ አንገኝም ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 4 ፤ በእውነትም ፡ የሚሞተው ፡ በሕይወት ፡ ይዋጥ ፡ ዘንድ ፡ ልንለብስ ፡ እንጂ ፡ ልንገፈፍ ፡ የማንወድ ፡ ስለ ፡ "ኾነ ፥ በድንኳኑ ፡ ያለን ፡ እኛ ፡ ከብዶን ፡ እንቃትታለን ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለዚሁ ፡ የሠራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ የመንፈሱን ፡ መያዣ ፡ ሰጠን ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 6-7 ፤ እንግዲህ ፡ "ሹል ፡ ጊዜ ፡ ታምነን ፥ በእምነት ፡ እንጂ ፡ በማየት ፡ አንመላለስምና ፡ በሥጋ ፡ ስናድር ፡ ከጌታ ፡ ተለይተን ፡ በስደት ፡ እንዳለን ፡ የምናውቅ ፡ ከ"ኾ"ን ፥

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ታምነናል ፡ ይልቁንም ፡ ከሥጋ ፡ ተለይተን ፡ በስደት ፡ መኖር ፡ በጌታም ፡ ዘንድ ፡ ማደር ፡ ደስ ፡ ይለናል ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ብናድር ፡ ወይም ፡ ተለይተን ፡ ብንኾን ፡ ርሱን ፡ ደስ ፡ የምናሠኝ ፡ ልንኾን ፡

እንቀናለን ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 10 ፤ መልካም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ እንዳደረገ ፥ እያንዳንዱ ፡ በሥጋው ፡ የተሠራውን ፡ በብድራት ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ኹላችን ፡ በክርስቶስ ፡ በፍርድ ፡ ወንበር ፡ ፊት ፡ ልንገለጥ ፡ ይገባናልና ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ የጌታን ፡ ፍርሀት ፡ ዐውቀን ፡ ሰዎችን ፡ እናስረዳለን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የተገለጥን ፡ ነን ፤ በኅሊናችኹም ፡ ደግሞ ፡ የተገለጥን ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 12 ፤ በመልክ ፡ እንጂ ፡ በልብ ፡ ለማይመኩ ፡ የምትመልሱላቸው ፡ መልስ ፡ እንዲኖራችኹ ፥ በእኛ ፡ ልትመኩ ፡ ምክንያት ፡ እንሰጣችኋለን ፡ እንጂ ፡ ራሳችንን ፡ ደግሞ ፡ ለእናንተ ፡ የምናመሰግን ፡ አይደለንም ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 13 ፤ እብዶች ፡ ብንኾን ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ባላእምሮዎች ፡ ብንኾን ፥ ለእናንተ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 14 ፤ ይህን ፡ ስለቄረጥን ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ግድ ፡ ይለናልና ፤ አንዱ ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፡ ሞተ ፤ እንግዲያስ ፡ ኹሉ ፡ ሞቱ ፤

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 15 ፤ በሕይወትም ፡ ያሉት ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ ለሞተውና ፡ ለተነሣው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ለራሳቸው ፡ እንዳይኖሩ ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፡ ሞተ ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ስለዚህ ፥ እኛ ፡ ካኹን ፡ ዠምሮ ፡ ማንንም ፡ በሥጋ ፡ እንደሚኾን ፡ አናውቅም ፤ ክርስቶስንም ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያወቅነው ፡ ብንኾን ፡ እንኳ ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንደዚህ ፡ አናውቀውም ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ ማንም ፡ በክርስቶስ ፡ ቢኾን ፡ ዐዲስ ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፤ አሮጌው ፡ ነገር ፡ ዐልፏል ፤ እንሆ ፥ ኹሉም ፡ ዐዲስ ፡ ኾኗል ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የኾነው ፡ ኹሉ ፥ በክርስቶስ ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ ካስታረቀን ፡ የማስታረቅም ፡ አገልግሎት ፡ ከሰጠን ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፤

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ኾኖ ፡ ዓለሙን ፡ ከራሱ ፡ ጋራ ፡ ያስታርቅ ፡ ነበርና ፥ በደላቸውን ፡ አይቈጥርባቸውም ፡ ነበር ፤ በእኛም ፡ የማስታረቅ ፡ ቃል ፡ አኖረ ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 20 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ እንደሚማልድ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መልክተኞች ፡ ነን ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡ ብለን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እንለምናለን ።

ቆሮ.2 ፡ 5 ፡ 21 ፤ እኛ ፡ በርሱ ፡ ኾነን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ ኀጢአት ፡ ያላወቀውን ፡ ርሱን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ኀጢአት ፡ አደረገው ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 1 ፤ ዐብረንም ፡ እየሠራን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ በከንቱ ፡ እንዳትቀበሉ ፡ ደግሞ ፡ እንለምናለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 2 ፤ በተወደደ ፡ ሰዓት ፡ ሰማኹኽ ፡ በመዳንም ፡ ቀን ፡ ረዳኹኽ ፡ ይላልና ፤ እንሆ ፥ የተወደደው ፡ ሰዓት ፡ አኹን ፡ ነው ፤ እንሆ ፥ የመዳን ፡ ቀን ፡ አኹን ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 3 ፤ አገልግሎታችንም ፡ እንዳይነቀፍ ፡ በአንዳች ፡ ነገር ፡ ማሰናከያ ፡ ከቶ ፡ አንሰጥም ።

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኹሉ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ራሳችንን ፡ እናማጥናለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 5 ፤ በብዙ ፡ መጽናት ፥ በመከራ ፥ በችግር ፥ በጭንቀት ፥ በመገረፍ ፥ በወህኒ ፥ በሁከት ፥ በድካም ፥ እንቅልፍ ፡ በማጣት ፥

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 6 ፤ በመጦም ፥ በንጽሕና ፥ በዕውቀት ፥ በትዕግሥት ፥ በቸርነት ፥ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፥ ግብዝነት ፡ በሌለው ፡ ፍቅር ፥ በእውነት ፡ ቃል ፥

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 7 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፥ ለቀኝና ፡ ለግራ ፡ በሚኾን ፡ በጽድቅ ፡ የጦር ፡ ዕቃ ፥ በክብርና ፡ በውርደት ፥

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 8 ፤ በክፉ ፡ ወሬና ፡ በመልካም ፡ ወሬ ፡ ራሳችንን ፡ እናማጥናለን ፤ አሳቾች ፡ ስንባል ፡ እውነተኞች ፡ ነን ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ያልታወቁ ፡ ስንባል ፡ የታወቅን ፡ ነን ፤ የምንሞት ፡ ስንመስል ፥ እንሆ ፥ ሕያዋን ፡ ነን ፤ የተቀጣን ፡ ስንኾን ፡ አንገደልም ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ሐዘንተኞች ፡ ስንኾን ፡ ዘወትር ፡ ደስ ፡ ይለናል ፤ ድኻዎች ፡ ስንኾን ፡ ብዙዎችን ፡ ባለጠጋዎች ፡ እናደርጋለን ፤ አንዳች ፡ የሌለን ፡ ስንኾን ፡ ኹሉ ፡ የእኛ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 11 ፤ እናንተ ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ አፋችን ፡ ለእናንተ ፡ ተከፍቷል ፡ ልባችንም ፡ ሰፍቶላችኋል ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 12 ፤ በእኛ ፡ አልጠበባችኹም ፡ በሆዳችኹ ፡ ግን ፡ ጠቦባችኋል ፤

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 13 ፤ ልጆቼ ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፡ ግን ፡ እላችኋለኹ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ብድራት ፡ መልሳችኹልን ፡ ተስፋፉ ።

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ከማያምኑ ፡ ጋራ ፡ በማይመች ፡ አካኼድ ፡ አትጠመዱ ፤ ጽድቅ ፡ ከዐመፅ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ ተካፋይነት ፡ አለውና ፧ ብርሃንም ፡ ከጨለማ ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ ኅብረት ፡ አለው ፧

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ክርስቶስ ፡ ከቤልሖር ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ መስማማት ፡ አለው ፧ ወይስ ፡ የሚያምን ፡ ከማያምን ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ ክፍል ፡ አለው ፧

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 16 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ከጣዖት ፡ ጋራ ፡ ምን ፡ መጋጠም ፡ አለው ፧ እኛ ፡ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ነንና ፡ እንዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ተናገረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ በእነርሱ ፡ እኖራለኹ ፡ በመካከላቸውም ፡ እመላለሳለኹ ፥ አምላካቸውም ፡ እኾናለኹ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝቤ ፡ ይኾናሉ ።

ቆሮ.2 ፡ 6 ፡ 17-18 ፤ ስለዚህም ፡ ጌታ ፦ ከመካከላቸው ፡ ውጡና ፡ የተለያችኹ ፡ ኹኑ ፥ ርኵስንም ፡ አትንኩ ፡ ይላል ፤ ኹሉንም ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፦ እኔም ፡ እቀበላችኋለኹ ፥ ለእናንተም ፡ አባት ፡ እኾናለኹ ፡ እናንተም ፡ ለእኔ ፡ ወንድ ፡ ልጆችና ፡ ሴት ፡ ልጆች ፡ ትኾናላችኹ ፡ ይላል ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ የዚህ ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ ካለን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፍርሀት ፡ ቅድስናን ፡ ፍጹም ፡ እያደረግን ፡ ሥጋንና ፡ መንፈስን ፡ ከሚያረክስ ፡ ኹሉ ፡ ራሳችንን ፡ እናንጻ ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 2 ፤ በልባችኹ ፡ ስፍራ ፡ አስፉልን ፤ ማንንም ፡ አልበደልንም ፥ ማንንም ፡ አላጠፋንም ፥ ማንንም ፡ አላታለልንም ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 3 ፤ ለኵነኔ ፡ አልልም ፤ በአንድነት ፡ ለመሞትና ፡ በአንድነት ፡ ለመኖር ፡ በልባችን ፡ እንዳላችኹ ፡ አስቀድሜ ፡ ብያለኹና ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 4 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ እምነቴ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ትምክሕቴ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ መጽናናት ፡ ሞልቶብኛል ፤ በመከራችን ፡ ኹሉ ፡ ደስታዬ ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ ይበዛል ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 5 ፤ ወደ ፡ መቄዶንያም ፡ በመጣን ፡ ጊዜ ፥ በሹሉ ፡ ነገር ፡ መከራን ፡ ተቀበልን ፡ እንጂ ፡ ሥጋችን ፡ ዕረፍት ፡ አልነበረውም ፤ በውጭ ፡ ጠብ ፡ ነበረ ፥ በውስጥ ፡ ፍርሀት ፡ ነበረ ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሐዘንተኞችን ፡ የሚያጽናና ፡ አምላክ ፡ በቲቶ ፡ መምጣት ፡ አጽናናን ፤

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 7 ፤ በመምጣቱም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ናፍቆታችኹንና ፡ ልቅሷችኹን ፡ ስለ ፡ እኔም ፡ ቅንአታችኹን ፡ ሲናገረን ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ በተጽናናበት ፡ መጽናናት ፡ ደግሞ ፡ ነው ፤ ስለዚህም ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ደስ ፡ አለን ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 8 ፤ በመልእክቴ ፡ ያሳዘንኋችኹ ፡ ብኾን ፡ እንኳ ፡ አልጸጸትም ፤ የተጸጸትኹ ፡ ብኾን ፡ እንኳ ፥ ያ ፡ መልእክት ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ እንዳሳዘናችኹ ፡ አያለኹና ፡ አኹን ፡ ለንስሓ ፡ ስላዘናችኹ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፡ እንጂ ፡ ስላዘናችኹ ፡ አይደለም ፤

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 9 ፤ በምንም ፡ ከእኛ ፡ የተነሣ ፡ እንዳትጐዱ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ዐዝናችኋልና ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 10 ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኾነ ፡ ሐዘን ፡ ጸጸት ፡ የሌለበትን ፥ ወደ ፡ መዳንም ፡ የሚያደርሰውን ፡ ንስሓ ፡ ያደርጋልና ፤ የዓለም ፡ ሐዘን ፡ ግን ፡ ሞትን ፡ ያመጣል ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ ይህ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኾነ ፡ ሐዘን ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትጋት ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ መልስ ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ ቍጣ ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍርሀት ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ ናፍቆት ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ ቅንአት ፥ እንዴት ፡ ያለ ፡ በቀል ፡ በመካከላችኹ ፡ አደረገ ። በዚህ ፡ ነገር ፡ ንጹሓን ፡ እንደ ፡ ኾናችኹ ፡ በሹሉ ፡ አስረድታችኋል ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 12 ፤ እንግዲያስ ፡ የጻፍኹላችኹ ፡ ብኾን ፡ እንኳ ፥ ስለ ፡ እኛ ፡ ያላችኹ ፡ ትጋታችኹ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንዲገለጥ ፡ እንጂ ፥ ስለ ፡ በዳዩ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ተበዳዩ ፡ አልጻፍኹም ። ስለዚህ ፡ ተጽናንተናል ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 13 ፤ በመጽናናታችንም ፡ ስለቲቶ ፡ ደስታ ፡ አብልጦ ፡ ደስ ፡ አለን ፥ መንፈሱ ፡ በሹላችኹ ፡ ዐርፏልና ፤

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 14 ፤ ለርሱ ፡ በምንም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የተመካኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላፈርኹምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሹሉን ፡ ለእናንተ ፡ በእውነት ፡ እንደ ፡ ተናገርን ፥ እንደዚህ ፡ ደግሞ ፡ ትምክሕታችን ፡ በቲቶ ፡ ፊት ፡ እውነት ፡ ኾነ ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 15 ፤ ስለዚህም ፡ በፍርሀትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ እንዴት ፡ እንደተቀበላችኹት ፥ የሹላችኹን ፡ መታዘዝ ፡ እያሰበ ፡ ፍቅሩ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ በዝቷል ።

ቆሮ.2 ፡ 7 ፡ 16 ፤ በነገር ፡ ሹሉ ፡ ተማምኜባችኋለኹና ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ለመቄዶንያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የተሰጠውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ እናስታውቃችኋለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 2 ፤ በብዙ ፡ መከራ ፡ ተፈትነው ፡ ሳሉ ፥ የደስታቸው ፡ ብዛትና ፡ የድኽነታቸው ፡ ጥልቅነት ፡ የልግስናቸውን ፡ ባለጠግነት ፡ አብዝቷል ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 3 ፤ እንደ ፡ ዐቅማቸው ፡ መጠን ፡ ከዐቅማቸውም ፡ የሚያልፍ ፡ እንኳ ፡ ወደው ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ እመሰክርላቸዋለኹና ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 4 ፤ ለቅዱሳን ፡ በኾነው ፡ አገልግሎት ፡ እንዲተባበሩ ፡ ይህን ፡ ቸርነት ፡ በብዙ ፡ ልመና ፡ ከእኛ ፡

ይለምኑ ፡ ነበር ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 5 ፤ አስቀድመውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ራሳቸውን ፡ ለጌታ ፡ ለእኛም ፡ ሰጡ ፡ እንጂ ፥ እንዳሰብን ፡ አይደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 6 ፤ ስለዚህም ፡ ቲቶ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ገሥመረ ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ቸር ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈጽም ፡ ለመንን ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በነገር ፡ ሹሉ ፥ በእምነትና ፡ በቃል ፡ በዕውቀትም ፡ በትጋትም ፡ ሹሉ ፡ ለእኛም ፡ በፍቅራችኹ ፡ እንደ ፡ ተረፋችኹ ፥ በዚህ ፡ ቸር ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ ትረፉ ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 8 ፤ ትእዛዝ ፡ እንደምሰጥ ፡ አልልም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በሌላዎች ፡ ትጋት ፡ በኩል ፡ የፍቅራችኹን ፡ እውነተኛነት ፡ ደግሞ ፡ ልመረምር ፡ እላለኹ ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 9 ፤ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ቸር ፡ ስጦታ ፡ ዐውቃችኋልና ፤ ሀብታም ፡ ሲኾን ፥ እናንተ ፡ በርሱ ፡ ድኽነት ፡ ባለጠጋዎች ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ድኻ ፡ ኾነ ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 10 ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ምክር ፡ እሰጣለኹ ፤ ከዓምና ፡ ገሥራችኹ ፡ ለማድረግ ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለማሰብ ፡ ደግሞ ፡ አስቀድማችኹ ፡ የገሥመራችኹት ፡ ይህ ፡ ይጠቅማችኋልና ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 11 ፤ አኹንም ፡ ለማሰብ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ እንዲሁ ፡ እንዳላችኹ ፡ መጠን ፡ መፈጸም ፡ ደግሞ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ ማድረጉን ፡ ደግሞ ፡ ፈጽሙ ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 12 ፤ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ቢኖር ፥ እንዳለው ፡ መጠን ፡ የተወደደ ፡ ይኾናል ፡ እንጂ ፡ እንደሌለው ፡ መጠን ፡ አይደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 13 ፤ ለሌላዎች ፡ ዕረፍት ፡ ለእናንተም ፡ መከራ ፡ እንዲኾን ፡ አይደለም ፥ ትክክል ፡ እንዲኾን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 14 ፤ የእነርሱ ፡ ትርፍ ፡ ደግሞ ፡ የእናንተን ፡ ጕድለት ፡ እንዲሞላ ፡ በአኹኑ ፡ ጊዜ ፡ የእናንተ ፡ ትርፍ ፡ የእነርሱን ፡ ጕድለት ፡ ይሙላ ፤ በትክክል ፡ እንዲኾን ፥ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 15 ፤ ብዙ ፡ ያከማቸ ፡ አላተረፈም ፥ ጥቂትም ፡ ያከማቸ ፡ አላጐደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በቲቶ ፡ ልብ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ያን ፡ ትጋት ፡ የሰጠ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 17 ፤ ምክራችንን ፡ ተቀብሏልና ፥ ትጋት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ በዛበት ፡ ወዶ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይወጣል ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 18 ፤ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ስለወንጌል ፡ ስብከት ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሹሉ ፡ የተመሰገነውን ፡ ወንድም ፡ እንልካለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 19 ፤ ይህም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የጌታን ፡ የራሱን ፡ ክብርና ፡ የእኛን ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ለማሳየት ፡ በምናገለግለው ፡ በዚህ ፡ ቸር ፡ ሥራ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ እንዲጓደድ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ደግሞ ፡ ተመረጠ ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 20 ፤ ስለምናገለግለው ፡ ስለዚህ ፡ ለጋስ ፡ ስጦታ ፡ ማንም ፡ እንዳይነቅፈን ፡ እንጠነቀቃለን ፤

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 21 ፤ በጌታ ፡ ፊት ፡ ብቻ ፡ ያይደለ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በሰው ፡ ፊት ፡ ደግሞ ፡ መልካም ፡ የኾነውን ፡ እናስባለንና ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 22 ፤ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ መርምረን ፡ ትጉህ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያገኘነውን ፥ አኹንም ፡ በእናንተ ፡ እጅግ ፡ ስለሚታመን ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ ትጉህ ፡ የሚኾነውን ፡ ወንድማችንን ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንልካለን ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 23 ፤ ስለ ፡ ቲቶ ፡ የሚጠይቅ ፡ ቢኖር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ዐብሮኝ ፡ የሚሠራ ፡ ባልንጀራዬ ፡ ነው ፤ ስለ ፡ ወንድሞቻችን ፡ የሚጠይቅ ፡ ቢኖርም ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልእክተኞችና ፡ የክርስቶስ ፡ ክብር ፡ ናቸው ።

ቆሮ.2 ፡ 8 ፡ 24 ፤ እንግዲህ ፡ የፍቅራችኹንና ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ያለውን ፡ የትምክሕታችንን ፡ መግለጫ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ፊት ፡ ለእነርሱ ፡ ግለጡ ።

2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 1 ፤ ለቅዱሳን ፡ ስለሚኾነው ፡ አገልግሎት ፡ ልጽፍላችኹ ፡ አያስፈልግምና ፤

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 2 ፤ በጎ ፡ ፈቃዳችኹን ፡ ዐውቄያለኹና ፤ ስለዚህም ፦ አካይያ ፡ ከዓምና ፡ ዠምሮ ፡ ተዘጋጅቷል ፡ ብዬ ፡ ለመቄዶንያ ፡ ሰዎች ፡ በእናንተ ፡ እመካለኹ ፥ ቅንአታችኹም ፡ የሚበዙቱን ፡ አነሣሥቷል ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእነርሱ ፡ እንዳልኹ ፥ የተዘጋጃችኹ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ በዚህም ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ያለው ፡ ትምክሕታችን ፡ ከንቱ ፡ እንዳይኾን ፡ ወንድሞችን ፡ እልካለኹ ፤

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 4 ፤ ምናልባት ፡ የመቄዶንያ ፡ ሰዎች ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ቢመጡ ፥ ያልተዘጋጃችኹም ፡ ኾናችኹ ፡ ቢያገኟችኹ ፥ እናንተ ፡ እንድታፍሩ ፡ አላልንም ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ እምነታችን ፡ እንድናፍር ፡ አይኹን ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 5 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ በረከት ፡ ኾኖ ፡ ከሥሥት ፡ የማይኾን ፡ ይህ ፡ የተዘጋጀ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ አስቀድመው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መጥተው ፥ አስቀድማችኹ ፡ ተስፋ ፡ የሰጣችኹትን ፡ በረከት ፡ አስቀድመው ፡ እንዲፈጽሙ ፡ ወንድሞችን ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ እንዲያስፈልገኝ ፡ ዐሰብኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 6 ፤ ይህንም ፡ እላለኹ ፦ በጥቂት ፡ የሚዘራ ፡ በጥቂት ፡ ደግሞ ፡ ያጭዳል ፥ በበረከትም ፡ የሚዘራ ፡ በበረከት ፡ ደግሞ ፡ ያጭዳል ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ በደስታ ፡ የሚሰጠውን ፡ ይወዳልና ፥ እያንዳንዱ ፡ በልቡ ፡ እንዳሰበ ፡ ይስጥ ፥ በሐዘን ፡ ወይም ፡ በግድ ፡ አይደለም ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 8-9 ፤ በተነ ፥ ለምስኪኖች ፡ ሰጠ ፥ ጽድቁ ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ተብሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ እግዚአብሔር ፥ ኹልጊዜ ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ብቃትን ፡ ኹሉ ፡ አግኝታችኹ ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ትበዙ ፡ ዘንድ ፥ ጸጋን ፡ ኹሉ ፡ ሊያበዛላችኹ ፡ ይችላል ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 10 ፤ ለዘሪ ፡ ዘርን ፡ ለመብላትም ፡ እንጀራን ፡ በብዙ ፡ የሚሰጥ ፡ ርሱም ፡ የምትዘሩትን ፡ ዘር ፡ ይሰጣችኋል ፡ ያበረክትላችኹማል ፥ የጽድቃችኹንም ፡ ፍሬ ፡ ያሳድጋል ፤

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 11 ፤ በእኛ ፡ በኩል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምስጋና ፡ ምክንያት ፡ የሚኾነውን ፡ ልግስና ፡ ኹሉ ፡ እንድታሳዩ ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ ባለጠጋዎች ፡ ትኾናላችኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 12 ፤ የዚህ ፡ ረድኤት ፡ አገልግሎት ፡ ለቅዱሳን ፡ የሚጐድላቸውን ፡ በሙሉ ፡ የሚሰጥ ፡ ብቻ ፡ አይደለምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ደግሞ ፡ በብዙ ፡ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይበዛል ፤

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 13 ፤ በዚህ ፡ አገልግሎት ፡ ስለ ፡ ተፈተናችኹ ፥ በክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ በማመናችኹ ፡ ስለሚኾን ፡ መታዘዝ ፡ እነርሱንና ፡ ኹሉንም ፡ ስለምትረዱበት ፡ ልግስና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብራሉ ፥

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 14 ፤ ራሳቸውም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ሲያማልዱ ፥ በእናንተ ፡ ላይ ፡ ከሚኾነው ፡ ከሚበልጠው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የተነሣ ፡ ይናፍቋችኋል ።

ቆሮ.2 ፡ 9 ፡ 15 ፤ ስለማይነገር ፡ ስጦታው ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ።

_____2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 1 ፤ እኔም ፡ ራሴ ፡ ጳውሎስ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ሳለኹ ፡ ትሑት ፡ የኾንኹ ፥ ከእናንተ ፡ ግን ፡ ብርቅ ፡ የምደፍራችኹ ፥ በክርስቶስ ፡ የዋህነትና ፡ ገርነት ፡ እመክራችኋለኹ ፤

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 2 ፤ በዓለማዊ ፡ ልማድ ፡ እንደምንመላለስ ፡ በሚቈጥሩን ፡ በአንዳንዶች ፡ ላይ ፡ አምኜ ፡ ልደፍር ፡ ዐስባለኹ ፥ በዚያ ፡ እምነት ፡ ግን ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ኾኜ ፡ እንዳልደፍር ፡ እለምናችኋለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 3 ፤ በሰው ፡ ልማድ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ የምንመላለስ ፡ ብንኾን ፥ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድ ፡ አንዋጋም ፤

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 4 ፤ የጦር ፡ ዕቃችን ፡ ሥጋዊ ፡ አይደለምና ፥ ምሽግን ፡ ለመስበር ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ብርቱ ፡ ነው ፤

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 5 ፤ የሰውንም ፡ ዐሳብ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ዕውቀት ፡ ላይ ፡ የሚነሣውን ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ እናፈርሳለን ፡ ለክርስቶስም ፡ ለመታዘዝ ፡ አእምሮን ፡ ኹሉ ፡ እንማርካለን ፥

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 6 ፤ መታዘዛችኹም ፡ በተፈጸመች ፡ ጊዜ ፡ አለመታዘዝን ፡ ኹሉ ፡ ልንበቀል ፡ ተዘጋጅተናል ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 7 ፤ በፊታችኹ ፡ ያለውን ፡ ተመልከቱ ። ማንም ፡ የክርስቶስ ፡ መኾኑን ፡ ተረድቶ ፡ ቢኾን ፥ ይህን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ በራሱ ፡ ይቀኑጠረው ፤ ርሱ ፡ የክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ነን ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 8 ፤ ጌታ ፡ እናንተን ፡ ለማነጽ ፡ እንጂ ፡ እናንተን ፡ ለማፍረስ ፡ ያይደለ ፡ በሰጠው ፡ በሥልጣናችን ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ብመካ ፡ እንኳ ፡ አላፍርም ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 9 ፤ በመልእክቶቼ ፡ የማስደነግጣችኹ ፡ አይምሰላችኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 10 ፤ መልእክቶቹስ ፡ ከባድና ፡ ኀይለኛ ፡ ናቸው ፥ ሰውነቱ ፡ ግን ፡ ሲታይ ፡ ደካማ ፡ ነው ፥ ንግግሩም ፡ የተናቀ ፡ ነው ፡ ይላሉና ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 11 ፤ እንዲሁ ፡ የሚል ፡ ይህን ፡ ይቀኑጠረው ፤ በሩቅ ፡ ሳለን ፡ በመልእክታችን ፡ በኩል ፡ በቃል ፡ እንዳለን ፥ በፊቱ ፡ ደግሞ ፡ ሳለን ፡ በሥራ ፡ እንዲሁ ፡ ነን ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 12 ፤ ራሳቸውን ፡ ከሚያመሰግኑ ፡ ከአንዳንዶች ፡ ጋራ ፡ ራሳችንን ፡ ልንቈጥር ፡ ወይም ፡ ራሳችንን ፡ ልናስተያይ ፡ አንደፍርምና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እነርሱ ፡ ራሳቸውን ፡ ከራሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲያመዛዝኑ ፥ ራሳቸውንም ፡ ከራሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሲያስተያዩ ፥ አያስተውሉም ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 13 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ወሰነልን ፡ እስከ ፡ እናንተ ፡ እንኳ ፡ እንደሚደርስ ፡ እንደ ፡ ክፍላችን ፡ ልክ ፡ እንጂ ፡ ያለልክ ፡ አንመካም ።

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 14 ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ እንደማንደርስ ፡ አድርገን ፡ ከመጠን ፡ አናልፍምና ፥ የክርስቶስን ፡ ወንጌል ፡ በመስበክ ፡ እስከ ፡ እናንተ ፡ እንኳ ፡ ደርሰናልና ፤

ቆሮ.2 ፡ 10 ፡ 15-16 ፤ በሌላዎች ፡ ድካም ፡ ያለልክ ፡ አንመካም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እምነታችኹ ፡ ሲያድግ ፡ ከእናንተ ፡ ወዲያ ፡ ባለው ፡ አገር ፡ እስክንሰብክ ፡ ሥራችንን ፡ እየጨመርን ፥ በክፍላችን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንድንከብር ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፤ በሌላው ፡ ክፍል ፡ ስለተዘጋጀው ፡ ነገር ፡ አንመካም ።

ቆሮ.2 ፥ 10 ፥ 17-18 ፤ የሚመካ ፡ ግን ፡ በጌታ ፡ ይመካ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሚያመሰግነው ፡ እንጂ ፡ ራሱን ፡ የሚያመሰግን ፡ ርሱ ፡ ተፈትኖ ፡ የሚወጣ ፡ አይደለምና ።

2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 1 ፤ በጥቂቱ ፡ ሞኝነቴ ፡ ብትታገሡኝ ፡ መልካም ፡ ይኾን ፡ ነበር ፤ ቢኾንም ፡ በርግጥ ፡ ታገሡኝ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 2 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቅንአት ፡ እቀናላችኋለኹና ፥ እንደ ፡ ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ እናንተን ፡ ለክርስቶስ ፡ ላቀርብ ፡ ላንድ ፡ ወንድ ፡ ዐጭቻችኋለኹና ፤

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እባብ ፡ በተንኰሉ ፡ ሔዋንን ፡ እንዳሳታት ፥ ዐሳባችኹ ፡ ተበላሽቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከሚኾን ፡ ቅንነትና ፡ ንጽሕና ፡ ምናልባት ፡ እንዳይለወጥ ፡ ብዬ ፡ እፈራለኹ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 4 ፤ የሚመጣውም ፡ ያልሰበክነውን ፡ ሌላ ፡ ኢየሱስ ፡ ቢሰብክ ፥ ወይም ፡ ያላገኛችኹትን ፡ ልዩ ፡ መንፈስ ፡ ወይም ፡ ያልተቀበላችኹትን ፡ ልዩ ፡ ወንጌል ፡ ብታገኙ ፥ በመልካም ፡ ትታገሡታላችኹ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 5 ፤ ከነዚህ ፡ ከዋነኞቹ ፡ ሐዋርያት ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ ጐደልኹ ፡ ራሴን ፡ አልቈጥርም ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 6 ፤ በአነጋገሬ ፡ ያልተማርኹ ፡ ብኾን ፡ እንኳ ፥ በዕውቀት ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አይደለኹም ። ነገር ፡ ግን ፥ በሰው ፡ ኹሉ ፡ መካከል ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ተገልጠንላችኋል ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 7 ፤ ወይስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ወንጌል ፡ ያለደመ ፡ ወዝ ፡ ስለ ፡ ሰበክኹላችኹ ፥ እናንተ ፡ ከፍ ፡ እንድትሉ ፡ ራሴን ፡ እያዋረድኹ ፡ ኀጢአት ፡ አድርጌ ፡ ይኾንን ፧

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 8 ፤ እናንተን ፡ ለማገልገል ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ እየተቀበልኹ ፡ ሌላዎችን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘረፍኹ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 9 ፤ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ሳለኹ ፡ በጐደለኝ ፡ ጊዜ ፥ በማንም ፡ አልከበድኹብትም ፤ ከመቄዶንያ ፡ የመጡት ፡ ወንድሞች ፡ የጐደለኝን ፡ በሙሉ ፡ ሰጥተዋልና ፤ በነገርም ፡ ኹሉ ፡ እንዳልከብድባችኹ ፡ ተጠነቀቅኹ ፡ እጠነቀቅማለኹ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 10 ፤ የክርስቶስ ፡ እውነት ፡ በእኔ ፡ እንዳለ ፥ ይህ ፡ ትምክሕት ፡ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ በአካይያ ፡ አገር ፡ አይከለከልም ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 11 ፤ ስለ ፡ ምን ፧ ስለማልወዳችኹ ፡ ነውን ፧ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ በሚመኩበት ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ ኾነው ፡ ሊገኙ ፥ ምክንያትን ፡ ከሚፈልጉቱ ፡ ምክንያትን ፡ እቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ አኹን ፡ የማደርገውን ፡ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ደግሞ ፡ አደርጋለኹ ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 13 ፤ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስን ፡ ሐዋርያት ፡ እንዲመስሉ ፡ ራሳቸውን ፡ እየለወጡ ፥ ውሸተኞች ፡ ሐዋርያትና ፡ ተንኰለኞች ፡ ሠራተኞች ፡ ናቸውና ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 14 ፤ ይህም ፡ ድንቅ ፡ አይደለም ፤ ሰይጣን ፡ ራሱ ፡ የብርሃንን ፡ መልአክ ፡ እንዲመስል ፡ ራሱን ፡ ይለውጣልና ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 15 ፤ እንግዲህ ፡ አገልጋዮቹ ፡ ደግሞ ፡ የጽድቅን ፡ አገልጋዮች ፡ እንዲመስሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ቢለውጡ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አይደለም ፤ ፍጻሜያቸውም ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.2 ፥ 11 ፥ 16 ፤ እንደ ፡ ገና ፡ እላለኹ ፦ ለማንም ፡ ሰው ፡ ሞኝ ፡ የኾንኹ ፡ አይምሰለው ፤ ያለዚያ ፡ ግን ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ እመካ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሞኝ ፡ እንኳ ፡ ኾኜ ፡ ተቀበሉኝ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 17 ፤ እንደዚህ ፡ ታምኜ ፡ ስመካ ፡ የምናገረው ፥ በሞኝነት ፡ እንጂ ፡ ጌታ ፡ እንዳዘዘኝ ፡ አልናገርም ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 18 ፤ ብዙዎች ፡ በዓለማዊ ፡ ነገር ፡ ስለሚመኩ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እመካለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 19 ፤ ልባሞች ፡ ስለምትኾኑ ፡ በደስታ ፡ ሞኞችን ፡ ትታገሣላችኹና ፤

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 20 ፤ ማንም ፡ ባሪያዎች ፡ ቢያደርጋችኹ ፥ ማንም ፡ ቢበላችኹ ፥ ማንም ፡ ቢቀማችኹ ፥ ማንም ፡ ቢከራባችኹ ፥ ማንም ፡ ፊታችኹን ፡ በጥፊ ፡ ቢመታችኹ ፡ ትታገሣላችኹና ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 21 ፤ ደካማዎች ፡ መስለን ፡ እንደ ፡ ነበርን ፡ በውርደት ፡ እላለኹ ። ነገር ፡ ግን ፥ በሞኝነት ፡ እላለኹ ፤ ማንም ፡ በሚደፍርበት ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እደፍርበታለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 22 ፤ ዕብራውያን ፡ ናቸውን ፧ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ነኝ ። የእስራኤል ፡ ወገን ፡ ናቸውን ፧ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ነኝ ። የአብርሃም ፡ ዘር ፡ ናቸውን ፧ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ነኝ ። የክርስቶስ ፡ አገልጋዮች ፡ ናቸውን ፧

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 23 ፤ እንደ ፡ እብድ ፡ ሰው ፡ እላለኹ ፤ እኔ ፡ እበልጣለኹ ፤ በድካም ፡ አብዝቼ ፥ በመገረፍ ፡ አብዝቼ ፥ በመታሰር ፡ አትርፌ ፥ በመሞት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ኾንኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 24 ፤ አይሁድ ፡ አንድ ፡ ሲጐድል ፡ አርባ ፡ ግርፋት ፡ ዐምስት ፡ ጊዜ ፡ ገረፉኝ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 25 ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ በበትር ፡ ተመታኹ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በድንጋይ ፡ ተወገርኹ ፤ መርከቤ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተሰበረ ፤ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ ኖርኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 26 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመንገድ ፡ ኼድኹ ፤ በወንዝ ፡ ፍርሀት ፥ በወንበዴዎች ፡ ፍርሀት ፥ በወገኔ ፡ በኩል ፡ ፍርሀት ፥ በአሕዛብ ፡ በኩል ፡ ፍርሀት ፥ በከተማ ፡ ፍርሀት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፡ ፍርሀት ፥ በባሕር ፡ ፍርሀት ፥ በውሸተኞች ፡ ወንድሞች ፡ በኩል ፡ ፍርሀት ፡ ነበረብኝ ፤

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 27 ፤ በድካምና ፡ በጥረት ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ እንቅልፍ ፡ በማጣት ፥ በራብና ፡ በጥም ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በመጦም ፥ በብርድና ፡ በራቍትነት ፡ ነበርኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 28 ፤ የቀረውንም ፡ ነገር ፡ ሳልቈጥር ፥ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የሚከብድብኝ ፡ የአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ኹሉ ፡ ዐሳብ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 29 ፤ የሚደክም ፡ ማን ፡ ነው ፥ እኔም ፡ አልደክምምን ፧ የሚሰናከል ፡ ማን ፡ ነው ፥ እኔም ፡ አልናደድምን ፧

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 30 ፤ ትምክሕት ፡ የሚያስፈልግ ፡ ከኾነ ፥ ከድካሜ ፡ በሚኾነው ፡ ነገር ፡ እመካለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 31 ፤ ለዘለዓለም ፡ የተባረከ ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ እንዳልዋሽ ፡ ያውቃል ።

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 32 ፤ በደማስቆ ፡ አርስጦስዮስ ([300]) ፡ ከተባለ ፡ ንጉሥ ፡ በታች ፡ የኾነ ፡ የሕዝብ ፡ ገዢ ፡ ሊይዘኝ ፡ እየወደደ ፡ የደማስቆ ፡ ሰዎችን ፡ ከተማ ፡ ያስጠብቅ ፡ ነበር ፥

ቆሮ.2 ፡ 11 ፡ 33 ፤ በቅጥሩም ፡ ባለ ፡ መስኮት ፡ በቅርጫት ፡ አወረዱኝና ፡ ከእጁ ፡ አመለጥኹ ።

2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 1 ፤ ትምክሕት ፡ የማያስፈልግ ፡ ነው ፥ አይጠቅምም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከጌታ ፡ ወዳለው ፡ ራእይና ፡

300 ጽር. ፥ አሬታስ ።

መገለጥ ፡ እመጣለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 2 ፤ ሰውን ፡ በክርስቶስ ፡ ዐውቃለኹ ፥ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላውቅም ፡ ወይም ፡ ከሥጋ ፡ ውጭ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላውቅም ፥ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ከዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ተነጠቀ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 3 ፤ እንዲህ ፡ ያለውንም ፡ ሰው ፡ ዐውቃለኹ ፥ በሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ወይም ፡ ያለሥጋ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አላውቅም ፥ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ፤

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 4 ፤ ወደ ፡ ገነት ፡ ተነጠቀ ፥ ሰውም ፡ ሊናገር ፡ የማይገባውን ፡ የማይነገረውን ፡ ቃል ፡ ሰማ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 5 ፤ እንደዚህ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ እመካለኹ ፥ ስለ ፡ ራሴ ፡ ግን ፡ ከድካሜ ፡ በቀር ፡ አልመካም ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 6 ፤ ልመካ ፡ ብወድስ ፡ ሞኝ ፡ አልኾንም ፥ እውነትን ፡ እላለኹና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ማንም ፡ ከሚያይ ፡ ከእኔም ፡ ከሚሰማ ፡ የምበልጥ ፡ አድርጎ ፡ እንዳይቈጥረኝ ፡ ትቻለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 7 ፤ ስለዚህም ፡ በመገለጥ ፡ ታላቅነት ፡ እንዳልታበይ ፡ የሥጋዬ ፡ መውጊያ ፥ ርሱም ፡ የሚጐስመኝ ፡ የሰይጣን ፡ መልእክተኛ ፡ ተሰጠኝ ፤ ይኸውም ፡ እንዳልታበይ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ከእኔ ፡ እንዲለይ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ጌታን ፡ ለመንኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ ጸጋዬ ፡ ይበቃኻል ፥ ኀይሌ ፡ በድካም ፡ ይፈጸማልና ፥ አለኝ ። እንግዲህ ፡ የክርስቶስ ፡ ኀይል ፡ ያድርብኝ ፡ ዘንድ ፡ በብዙ ፡ ደስታ ፡ በድካሜ ፡ ልመካ ፡ እወዳለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ በድካም ፣ በመንገላታትም ፣ በችግርም ፣ በስደትም ፣ በጭንቀትም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ስደክም ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ኀይለኛ ፡ ነኝና ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 11 ፤ በመመካቴ ፡ ሞኝ ፡ ኾኛለኹ ፤ እናንተ ፡ ግድ ፡ አላችኹኝ ፤ እናንተ ፡ እኔን ፡ ልታመሰግኑ ፡ ይገባ ፡ ነበርና ። እኔ ፡ ምንም ፡ ባልኾን ፡ እንኳ ፥ ከዋነኞቹ ፡ ሐዋርያት ፡ በምንም ፡ አልጐድልምና ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 12 ፤ በርግጥ ፡ የሐዋርያነት ፡ ምልክት ፡ በመካከላችኹ ፡ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፡ በተአምራትም ፡ በኹሉ ፡ ትዕግሥት ፡ ተደረገ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 13 ፤ እኔ ፡ ራሴ ፡ ካልከበድኹባችኹ ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፥ ከሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያነሳችኹበት ፡ በምን ፡ እኮ ፡ ነው ፧ ይህን ፡ በደሌን ፡ ይቅር ፡ በሉልኝ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 14 ፤ እንሆ ፥ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመጣ ፡ ዘንድ ፡ ስዘጋጅ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛዬ ፡ ነው ፤ አልከብድባችኹምም ፥ እናንተን ፡ እንጂ ፡ ያላችኹን ፡ አልፈልግምና ። ወላጆች ፡ ለልጆች ፡ እንጂ ፡ ልጆች ፡ ለወላጆች ፡ ገንዘብ ፡ ሊያከማቹ ፡ አይገባቸውምና ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 15 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ነፍሳችኹ ፡ በብዙ ፡ ደስታ ፡ ገንዘቤን ፡ እከፍላለኹ ፥ ራሴን ፡ እንኳ ፡ እከፍላለኹ ። ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ ብወዳችኹ ፡ በዚህ ፡ ልክ ፡ ፍቅራችኹ ፡ የሚያንስ ፡ ነውን ፧

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 16 ፤ ይኹን ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አልከበድኹባችኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሽንጋይ ፡ ኾኜ ፡ በተንኰል ፡ ያዝኋችኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 17 ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ ከላክኋቸው ፡ በአንዱ ፡ ስንኳ ፡ አታለልኋችኹን ፧

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 18 ፤ ቲቶን ፡ መከርኹት ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ወንድሙን ፡ ላክኹት ፤ ቲቶስ ፡ አታለላችኹን ፧ ባንድ ፡ መንፈስ ፡ አልተመላለስንምን ፧ ባንድ ፡ ፍለጋስ ፡ አልተመላለስንም ፧

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 19 ፤ ለእናንተ ፡ ስለ ፡ ራሳችን ፡ እንድንመልስ ፡ ዅልጊዜ ፡ ይመስላችኋልን ፧ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በክርስቶስ ፡ ኾነን ፡ እንናገራለን ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወዳጆች ፥ እናንተን ፡ ልናንጻችኹ ፡ ዅሉን ፡ እንናገራለን ።

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 20 ፤ ስመጣ ፥ እንደምወደው ፡ ሳትኾኑ ፡ አገኛችኹ ፡ ይኾናል ፥ እኔም ፡ እንደምትወዱት ፡ ሳልኾን ፡ ታገኙኝ ፡ ይኾናል ፡ ብዬ ፡ እፈራለኹና ፤ ምናልባት ፡
ክርክር ፣ ቅንአትም ፣ ቍጣም ፣ ዐድመኛነትም ፣ ሐሜትም ፣ ማሾክሾክም ፣ ኵራትም ፡ ሁከትም ፡ ይኾናሉ ፤

ቆሮ.2 ፡ 12 ፡ 21 ፤ እንደ ፡ ገና ፡ ስመጣ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ አምላኬ ፡ እንዲያዋርደኝ ፥ አስቀድመውም ፡ ኀጢአት ፡ ከሠሩትና ፡ ስላደረጉት ፡ ርኵሰትና ፡ ዝሙት ፡ መዳራትም ፡ ንስሓ ፡ ካልገቡት ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ ብዙዎች ፡ ምናልባት ፡ ዐዝናለኹ ፡ ብዬ ፡ እፈራለኹ ።

2 ኛ ፡ ቆሮንቶስ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 1 ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ ስመጣ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛዬ ፡ ነው ፤ ዅሉ ፡ ነገር ፡ በኹለትና ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ አፍ ፡ ይጸናል ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 2-3 ፤ ኹለተኛ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበርኹ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተናገርኹ ፡ አኹንም ፡ ደግሞ ፡ በሩቅ ፡ ስኾን ፥ ክርስቶስ ፡ በእኔ ፡ ዐድሮ ፡ እንዲናገር ፡ ማስረጃ ፡ ከፈለጋችኹ ፥ እንደ ፡ ገና ፡ ብመጣ ፡ እንዳልራራላቸው ፡ አስቀድመው ፡ ኀጢአት ፡ ላደረጉት ፡ ለሌላዎችም ፡ ዅሉ ፡ አስቀድሜ ፡ ብያለኹ ፥ አስቀድሜም ፡ እላለኹ ፦ ክርስቶስም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አይደክምም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእናንተ ፡ ኀይለኛ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 4 ፤ በድካም ፡ ተሰቅሏልና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ። እኛ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደክማለንና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ እናንተ ፡ በኾነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 5 ፤ በሃይማኖት ፡ ብትኖሩ ፡ ራሳችኹን ፡ መርምሩ ፤ ራሳችኹን ፡ ፈትኑ ፤ ወይስ ፡ ምናልባት ፡ የማትበቁ ፡ ባትኾኑ ፥ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእናንተ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ አታውቁምን ፧

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 6 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ የማንበቃ ፡ እንዳይደለን ፡ ልታውቁ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 7 ፤ ክፉ ፡ ነገርንም ፡ ከቶ ፡ እንዳታደርጉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጸልያለን ፤ እኛ ፡ የምንበቃ ፡ ኾነን ፡ እንገለጥ ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እኛ ፡ ምንም ፡ እንደማንበቃ ፡ ብንኾን ፥ እናንተ ፡ መልካሙን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 8 ፤ ለእውነት ፡ እንጂ ፡ በእውነት ፡ ላይ ፡ ምንም ፡ ለማድረግ ፡ አንችልምና ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 9 ፤ እኛ ፡ ስንደክም ፡ እናንተም ፡ ኀይለኞች ፡ ስትኾኑ ፡ ደስ ፡ ብሎናልና ፤ እናንተ ፡ ፍጹማን ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ለዚህ ፡ ደግሞ ፡ እንጸልያለን ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ጌታ ፡ ለማፍረስ ፡ ያይደለ ፥ ለማነጽ ፡ እንደ ፡ ሰጠኝ ፡ ሥልጣን ፥ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለኹ ፡ በቀኑርጥ ፡ እንዳልሠራ ፥ በሩቅ ፡ ኾኜ ፡ ይህን ፡ እጽፋለኹ ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 11 ፤ በቀረውስ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ደኅና ፡ ኹኑ ። ፍጹማን ፡ ኹኑ ፥ ምክሬን ፡ ስሙ ፥ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኹኑ ፥ በሰላም ፡ ኑሩ ፥ የፍቅርና ፡ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 12 ፤ በተቀደሰ ፡ አሳሳም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 13 ፤ ቅዱሳን ፡ ዅሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ቆሮ.2 ፡ 13 ፡ 14 ፤ የጌታ ፡ የኢ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፍቅር ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ኅብረት ፡ ከሠላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ። አሜን ❖

የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደገላትያ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ገላትያ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ገላ. ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታንም ፡ ባነሣው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ እንጂ ፡ ከሰዎች ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ያልኾነ ፡ ጳውሎስ ፡ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ወንድሞች ፡ ኹሉ ፥ ወደገላትያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታችንም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ክፉ ፡ ከኾነ ፡ ካኹኑ ፡ ዓለም ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አምላካችንና ፡ እንደ ፡ አባታችን ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ኀጢአታችን ፡ ራሱን ፡ ሰጠ ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ለአብ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ እናንተን ፡ ከጠራችኹ ፡ ከርሱ ፡ ወደ ፡ ልዩ ፡ ወንጌል ፡ እንዲህ ፡ ፈጥናችኹ ፡ እንዴት ፡ እንዳለፋችኹ ፡ እደነቃለኹ ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ወንጌል ፡ አይደለም ፤ የሚያናውጧችኹ ፡ የክርስቶስንም ፡ ወንጌል ፡ ሊያጣምሙ ፡ የሚወዱ ፡ አንዳንዶች ፡ አሉ ፡ እንጂ ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እኛ ፡ ብንኾን ፡ ወይም ፡ ከሰማይ ፡ መልአክ ፥ ከሰበክንላችኹ ፡ ወንጌል ፡ የሚለይ ፡ ወንጌልን ፡ ቢሰብክላችኹ ፥ የተረገመ ፡ ይኹን ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ አስቀድመን ፡ እንዳልን ፡ እንዲሁ ፡ አኹን ፡ ኹለተኛ ፡ እላለኹ ፥ ከተቀበላችኹት ፡ የተለየውን ፡ ማንም ፡ ቢሰብክላችኹ ፡ የተረገመ ፡ ይኹን ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ሰውን ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አኹን ፡ ዕሺ ፡ አሠኛለኹን ፧ ወይም ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ላሠኝ ፡ እፈልጋለኹን ፧ አኹን ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ ባሠኝ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ባልኾንኹም ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በእኔ ፡ የተሰበከ ፡ ወንጌል ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ እንዳይደለ ፡ አስታውቃችኋለኹ ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ገልጦልኛል ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ ከሰው ፡ አልተቀበልኹትም ፡ አልተማርኹትምም ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በአይሁድ ፡ ሥርዐት ፡ በፊት ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ኖርኹ ፡ ሰምታችኋልና ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያለልክ ፡ አሳድድና ፡ አጠፋ ፡ ነበር ፥

ገላ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ለአባቶችም ፡ ወግ ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ እየቀናኹ ፡ በወገኔ ፡ ዘንድ ፡ በዘመኔ ፡ ካሉት ፡ ብዙዎችን ፡ በአይሁድ ፡ ሥርዐት ፡ እበልጥ ፡ ነበር ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 15-16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእናቴ ፡ ማሕፀን ፡ ሳለኹ ፡ የለየኝ ፡ በጸጋውም ፡ የጠራኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ወንጌልን ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ልጁን ፡ በእኔ ፡ ኹኔታ ፡ ሊገልጥ ፡ በወደደ ፡

ጊዜ ፥ ወዲያው ፡ ከሥጋና ፡ ከደም ፡ ጋራ ፡ አልተማከርኹም ፥

ገላ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ከእኔም ፡ በፊት ፡ ሐዋርያት ፡ ወደነበሩት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አልወጣኹም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ወደዐረብ ፡ አገር ፡ ኼድኹ ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ተመለስኹ ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ ከሦስት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ኬፋን ፡ ልጠይቅ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወጥቼ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐሥራ ፡ ዐምስት ፡ ቀን ፡ ሰነበትኹ ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከጌታ ፡ ወንድም ፡ ከያዕቆብ ፡ በቀር ፡ ከሐዋርያት ፡ ሌላ ፡ አላየኹም ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 20 ፤ ስለምጽፍላችኹም ፡ ነገር ፥ እንሆ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 21 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ሶርያና ፡ ወደኪልቅያ ፡ አገር ፡ መጣኹ ።

ገላ. ፥ 1 ፥ 22 ፤ በክርስቶስም ፡ ያሉት ፡ የይሁዳ ፡ ማኅበሮች ፡ ፊቴን ፡ አያውቁም ፡ ነበር ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፦ ቀድሞ ፡ እኛን ፡ ያሳድድ ፡ የነበረ ፥ ርሱ ፡ በፊት ፡ ያጠፋው ፡ የነበረውን ፡ ሃይማኖት ፡ አኹን ፡ ይሰብካል ፡ ተብሎ ፡ ሲነገር ፡ ይሰሙ ፡ ነበር ፤

ገላ. ፥ 1 ፥ 24 ፤ ስለ ፡ እኔም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩ ፡ ነበር ።

_____ገላትያ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ገላ. ፥ 2 ፥ 1 ፤ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ከዐሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ቲቶን ፡ ደግሞ ፡ ይዤ ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ኹለተኛ ፡ ወጣኹ ፤

ገላ. ፥ 2 ፥ 2 ፤ እንደ ፡ ተገለጠልኝም ፡ ወጣኹ ፤ ምናልባትም ፡ በከንቱ ፡ እንዳልሮጥ ፡ ወይም ፡ በከንቱ ፡ ሮጬ ፡ እንዳልኾን ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ የምሰብከውን ፡ ወንጌል ፡ አስታወቅኋቸው ፤ ዋናዎች ፡ ግን ፡ መስለው ፡ ለሚታዩ ፡ ለብቻቸው ፡ አስታወቅኋቸው ።

ገላ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ ቲቶ ፡ እንኳ ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ ሲኾን ፡ ይገረዝ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ አላሉትም ፤

ገላ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ባሪያዎች ፡ ሊያደርጉን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ያለንን ፡ ሐራነታችንን ፡ ይሰልሉ ፡ ዘንድ ፡ ሾልከው ፡ በስውር ፡ ስለገቡ ፡ ስለሐሰተኞች ፡ ወንድሞች ፡ ነበረ ።

ገላ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ የወንጌልም ፡ እውነት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ጸንቶ ፡ እንዲኖር ፡ ላንድ ፡ ሰዓት ፡ እንኳ ፡ ለቀን ፡ አልተገዛንላቸውም ።

ገላ. ፥ 2 ፥ 6 ፤ አለቃዎች ፡ የመሰሉት ፡ ግን ፥ በፊት ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ አይገደኝም ፤ እግዚአብሔር ፡ የሰውን ፡ ፊት ፡ አይቶ ፡ አያደላም ፤ አለቃዎች ፡ የመሰሉት ፡ አንዳች ፡ እንኳ ፡ አልጨመሩልኝምና ፥

ገላ. ፥ 2 ፥ 7 ፤ ተመልሰው ፡ ግን ፡ ጴጥሮስ ፡ ለተገረዙት ፡ የኾነው ፡ ወንጌል ፡ ዐደራ ፡ እንደተሰጠው ፡ እንዲሁ ፡ ለእኔ ፡ ላልተገረዙት ፡ የኾነው ፡ ወንጌል ፡ ዐደራ ፡ እንደተሰጠኝ ፡ አዩ ፤

ገላ. ፥ 2 ፥ 8 ፤ ለተገረዙት ፡ ሐዋርያ ፡ እንዲኾን ፡ ለጴጥሮስ ፡ የሠራለት ፥ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ ለአሕዛብ ፡ ሐዋርያ ፡ እንድኾን ፡ ሠርቷልና ።

ገላ. ፥ 2 ፥ 9 ፤ ደግሞ ፡ የተሰጠኝን ፡ ጸጋ ፡ ዐውቀው ፥ አዕማድ ፡ መስለው ፡ የሚታዩ ፡ ያዕቆብና ፡ ኬፋ ፡ ዮሐንስም ፡ እኛ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እነርሱም ፡ ወደተገረዙት ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ለኔና ፡ ለበርናባስ ፡ ቀኝ ፡ እጃቸውን ፡

ሰጡን ፤

ገላ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ድኻዎችን ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ ለመኑን ፥ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ ላደርግ ፡ ተጋኹ ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኬፋ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተቃወምኹት ፥ ይፈረድበት ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ፡ ነበርና ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ አንዳንድ ፡ ከያዕቆብ ፡ ዘንድ ፡ ሳይመጡ ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ይበላ ፡ ነበርና ፤ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ ያሉትን ፡ ፈርቶ ፡ ያፈገፍግ ፡ ነበርና ፥ ከነርሱ ፡ ተለየ ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ የቀሩትም ፡ አይሁድ ፡ ደግሞ ፥ በርናባስ ፡ ስንኳ ፡ በግብዝነታቸው ፡ እስከ ፡ ተሳበ ፡ ድረስ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ግብዞች ፡ ኾኑ ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ወንጌል ፡ እውነት ፡ በቅንነት ፡ እንዳልኼዱ ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፡ በኹሉ ፡ ፊት ፡ ኬፋን ። አንተ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሳለኽ ፡ በአይሁድ ፡ ኑሮ ፡ ያይደለ ፡ በአሕዛብ ፡ ኑሮ ፡ ብትኖር ፥ አሕዛብ ፡ በአይሁድ ፡ ኑሮ ፡ ሊኖሩ ፡ እንዴት ፡ ግድ ፡ አልኻቸው ፧ አልኹት ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እኛ ፡ በፍጥረት ፡ አይሁድ ፡ ነን ፡ ኀጢአተኞችም ፡ የኾኑ ፡ አሕዛብ ፡ አይደለንም ፤

ገላ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በማመን ፡ እንዲጸድቅ ፡ እንጂ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ እንዳይኾን ፡ ዐውቀን ፥ ሥጋን ፡ የለበሰ ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ስለማይጸድቅ ፥ እኛ ፡ ራሳችን ፡ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ሳይኾን ፡ በክርስቶስ ፡ እምነት ፡ እንጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አምነናል ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በክርስቶስ ፡ ልንጸድቅ ፡ የምንፈልግ ፡ ስንኾን ፡ ራሳችን ፡ ደግሞ ፡ ኀጢአተኞች ፡ ኾነን ፡ ከተገኘን ፥ እንግዲያስ ፡ ክርስቶስ ፡ የኀጢአት ፡ አገልጋይ ፡ ነዋ ፧ አይደለም ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ያፈረስኹትን ፡ ይህን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ የማንጽ ፡ ከኾንኹ ፡ ራሴ ፡ ሕግ ፡ ተላላፊ ፡ እንድኾን ፡ አስረዳለኹና ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እኔ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ፡ ኾኜ ፡ እኖር ፡ ዘንድ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ለሕግ ፡ ሞቼ ፡ ነበርና ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ተሰቅያለኹ ፤ እኔም ፡ አኹን ፡ ሕያው ፡ ኾኜ ፡ አልኖርም ፥ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በእኔ ፡ ይኖራል ፤ አኹንም ፡ በሥጋ ፡ የምኖርበት ፡ ኑሮ ፡ በወደደኝና ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ራሱን ፡ በሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ላይ ፡ ባለ ፡ እምነት ፡ የምኖረው ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ አልጥልም ፤ ጽድቅስ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ከኾነ ፡ እንኪያስ ፡ ክርስቶስ ፡ በከንቱ ፡ ሞተ ።

ገላትያ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ የማታስተውሉ ፡ የገላትያ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ በዐይናችኹ ፡ ፊት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተሰቀለ ፡ ኾኖ ፡ ተሥሎ ፡ ነበር ፤ ለእውነት ፡ እንዳትታዘዙ ፡ ዐዚም ፡ ያደረገባችኹ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ገላ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ይህን ፡ ብቻ ፡ ከእናንተ ፡ እንድማር ፡ እወዳለኹ ፤ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ወይም ፡ ከእምነት ፡ ጋራ ፡ በኾነ ፡ መስማት ፡ መንፈስን ፡ ተቀበላችኹን ፧

ገላ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ እንዲህን ፡ የማታስተውሉ ፡ ናችኹ ፧ በመንፈስ ፡ ገምራችኹ ፡ አኹን ፡ በሥጋ ፡ ትፈጽማላችኹን ፧

ገላ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ በእውኑ ፡ ከንቱ ፡ እንደ ፡ ኾነስ ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ በከንቱ ፡ ተቀበላችኹን ፧

ገላ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እንግዲህ ፡ መንፈስን ፡ የሚሰጣችኹ ፡ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ተአምራት ፡ የሚያደርግ ፥ በሕግ ፡ ሥራ ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ ከእምነት ፡ ጋራ ፡ በኾነ ፡ መስማት ፡ ነው ፧

ገላ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ እንዲሁ ፡ አብርሃም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነና ፡ ጽድቅ ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንኪያስ ፡ ከእምነት ፡ የኾኑት ፡ እነዚህ ፡ የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ኾኑ ፡ ዕወቁ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ መጽሐፍም ፡ እግዚአብሔር ፡ አሕዛብን ፡ በእምነት ፡ እንዲያጸድቅ ፡ አስቀድሞ ፡ አይቶ ፦ ባንተ ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ይባረካሉ ፡ ብሎ ፡ ወንጌልን ፡ ለአብርሃም ፡ አስቀድሞ ፡ ሰበከ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እንደዚህ ፡ ከእምነት ፡ የኾኑት ፡ ካመነው ፡ ከአብርሃም ፡ ጋራ ፡ ይባረካሉ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ከሕግ ፡ ሥራ ፡ የኾኑት ፡ ኹሉ ፡ በርግማን ፡ በታች ፡ ናቸውና ፤ በሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ በተጻፉት ፡ ኹሉ ፡ ጸንቶ ፡ የማይኖር ፡ የማያደርግም ፡ ኹሉ ፡ የተረገመ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ጻድቅ ፡ በእምነት ፡ ይኖራል ፡ ተብሏልና ፥ ማንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሕግ ፡ እንዳይጸድቅ ፡ ግልጥ ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ሕግም ፡ ከእምነት ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፦ የሚያደርገው ፡ ይኖርበታል ፡ ተብሏል ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ በዕንጨት ፡ የሚሰቀል ፡ ኹሉ ፡ የተረገመ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ፥ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ርግማን ፡ ኾኖ ፡ ከሕግ ፡ ርግማን ፡ ዋጀን ፤

ገላ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የመንፈስን ፡ ተስፋ ፡ በእምነት ፡ እንድንቀበል ፥ የአብርሃም ፡ በረከት ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይደርስላቸው ፡ ዘንድ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ሰው ፡ ልማድ ፡ እላለኹ ፦ የሰው ፡ ስንኳ ፡ ቢኾን ፡ ርግጠኛውን ፡ ኪዳን ፡ ማንም ፡ አይንቅም ፡ ወይም ፡ አይጨምርበትም ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ለአብርሃምና ፡ ለዘሩም ፡ የተስፋው ፡ ቃል ፡ ተነገረ ። ስለ ፡ ብዙዎች ፡ እንደሚነገር ፦ ለዘሮቹም ፡ አይልም ፤ ስለ ፡ አንድ ፡ እንደሚነገር ፡ ግን ፦ ለዘርኽም ፡ ይላል ፥ ርሱም ፡ ክርስቶስ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ይህንም ፡ እላለኹ ፤ ከአራት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ የተሰጠው ፡ ሕግ ፡ አስቀድሞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የተረጋገጠውን ፡ ኪዳን ፡ የተስፋውን ፡ ቃል ፡ እስኪሽር ፡ ድረስ ፡ አያፈርስም ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ርስቱ ፡ በሕግ ፡ ቢኾንስ ፡ እንግዲያስ ፡ በተስፋ ፡ ቃል ፡ አይኾንም ፤ በተስፋ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለአብርሃም ፡ ሰጥቷል ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ሕግ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ተስፋው ፡ የተሰጠው ፡ ዘር ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ በመካከለኛ ፡ እጅ ፡ በመላእክት ፡ በኩል ፡ ስለሕግ ፡ መተላለፍ ፡ ተጨመረ ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ መካከለኛውም ፡ ላንድ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ እንግዲህ ፡ ሕግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ የሚቃወም ፡ ነውን ፧ አይደለም ። ሕያው ፡ ሊያደርግ ፡ የሚቻለው ፡ ሕግ ፡ ተሰጥቶ ፡ ቢኾንስ ፡ በእውነት ፡ ጽድቅ ፡ ከሕግ ፡ በኾነ ፡ ነበር ፤

ገላ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከማመን ፡ የኾነው ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ለሚያምኑ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፥ መጽሐፍ ፡ ከኀጢአት ፡ በታች ፡ ኹሉን ፡ ዘግቶታል ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ እምነትም ፡ ሳይመጣ ፥ ሊገለጥ ፡ ላለው ፡ እምነት ፡ ተዘግተን ፥ ከሕግ ፡ በታች ፡ እንጠበቅ ፡

ነበር ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ እንደዚህ ፡ በእምነት ፡ እንጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ ሕግ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚያመጣ ፡ ሞግዚታችን ፡ ኾኗል ፤

ገላ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ እምነት ፡ ግን ፡ መጥቷልና ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከሞግዚት ፡ በታች ፡ አይደለንም ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 26 ፤ በእምነት ፡ በኩል ፡ ኹላችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ናችኹና ፤

ገላ. ፡ 3 ፡ 27 ፤ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ የተጠመቃችኹ ፡ ኹሉ ፡ ክርስቶስን ፡ ለብሳችኋልና ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 28 ፤ አይሁዳዊ ፡ ወይም ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ የለም ፥ ባሪያ ፡ ወይም ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፡ የለም ፥ ወንድም ፡ ሴትም ፡ የለም ፤ ኹላችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ናችኹና ።

ገላ. ፡ 3 ፡ 29 ፤ እናንተም ፡ የክርስቶስ ፡ ከኾናችኹ ፡ እንኪያስ ፡ የአብርሃም ፡ ዘር ፡ እንደተስፋውም ፡ ቃል ፡ ወራሾች ፡ ናችኹ ።

ገላትያ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላለኹ ፥ ወራሹ ፡ ሕፃን ፡ ኾኖ ፡ ባለበት ፡ ዘመን ፡ ኹሉ ፥ ምንም ፡ የኹሉ ፡ ጌታ ፡ ቢኾን ፡ ከቶ ፡ ከባሪያ ፡ አይለይም ፥

ገላ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አባቱ ፡ እስከቀጠረለት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ከጠባቂዎችና ፡ ከመጋቢዎች ፡ በታች ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ እንዲሁ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ሕፃናት ፡ ኾነን ፡ ሳለን ፡ ከዓለም ፡ መዠመሪያ ፡ ትምህርት ፡ በታች ፡ ተገዝተን ፡ ባሪያዎች ፡ ነበርን ፤

ገላ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዘመኑ ፡ ፍጻሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሴት ፡ የተወለደውን ፡ ከሕግም ፡ በታች ፡ የተወለደውን ፡ ልጁን ፡ ላከ ፤

ገላ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ እንደ ፡ ልጆች ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፥ ከሕግ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ይዋጅ ፡ ዘንድ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ልጆችም ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ አባ ፡ አባት ፡ ብሎ ፡ የሚጮኽ ፡ የልጁን ፡ መንፈስ ፡ በልባችኹ ፡ ውስጥ ፡ ላከ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ልጅ ፡ ነኽ ፡ እንጂ ፡ ባሪያ ፡ አይደለኽም ፤ ልጅም ፡ ከኾንኽ ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወራሽ ፡ ነኽ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳታውቁ ፡ በባሕርያቸው ፡ አማልክት ፡ ለማይኾኑ ፡ ባሪያዎች ፡ ኾናችኹ ፡ ተገዛችኹ ፤

ገላ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስታውቁ ፡ ይልቅስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስትታወቁ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ወደ ፡ ደካማ ፡ ወደሚናቅም ፡ ወደመዠመሪያ ፡ ትምህርት ፡ እንዴት ፡ ትመለሳላችኹ ፧ እንደ ፡ ገና ፡ ባሪያዎች ፡ ኾናችኹ ፡ ዳግመኛ ፡ ለዚያ ፡ ልትገዙ ፡ ትወዳላችኹን ፧

ገላ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ቀንንና ፡ ወርን ፡ ዘመንንም ፡ ዓመትንም ፡ በጥንቃቄ ፡ ትጠብቃላችኹ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ምናልባት ፡ በከንቱ ፡ ለእናንተ ፡ ደክሜያለኹ ፡ ብዬ ፡ እፈራችኋለኹ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ እንደናንተ ፡ ኾኛለኹና ፦ እንደ ፡ እኔ ፡ ኹኑ ፡ ብዬ ፡

እለምናችኋለኹ ። አንዳችም ፡ አልበደላችኹኝም ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ በመዠመሪያ ፡ ወንጌልን ፡ በሰበክኹላችኹ ፡ ጊዜ ፡ ከሥጋ ፡ ድካም ፡ የተነሣ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ታውቃላችኹ ፥

ገላ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ በሥጋዬም ፡ ፈተና ፡ የኾነባችኹን ፡ ነገር ፡ አልናቃችኹትምና ፡ አልተጸየፋችኹትም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፥ አዎን ፥ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተቀበላችኹኝ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ደስ ፡ ማሠኘታችኹ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ በቻልስ ፡ ዐይኖቻችኹን ፡ አውጥታችኹ ፡ በሰጣችኹኝ ፡ ብዬ ፡ እመሰክርላችኋለኹ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ እንኪያስ ፡ እውነቱን ፡ ስለ ፡ ነገርኋችኹ ፡ ጠላት ፡ ኾንኹባችኹን ፧

ገላ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በብርቱ ፡ ይፈልጓችኋል ፥ ለመልካም ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በብርቱ ፡ ትፈልጓቸው ፡ ዘንድ ፡ በውጭ ፡ ሊያስቀሯችኹ ፡ ይወዳሉ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ በምኖርበት ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ዘወትር ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ተፈላጊ ፡ ብትኾኑ ፡ መልካም ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ክርስቶስ ፡ በእናንተ ፡ እስኪሣል ፡ ድረስ ፡ ዳግመኛ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ምጥ ፡ ይዞኛል ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ አመነታለኹና ፡ አኹን ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ኾኜ ፡ ድምፄን ፡ ልለውጥ ፡ በወደድኹ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ እናንተ ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ ልትኖሩ ፡ የምትወዱ ፥ ሕጉን ፡ አትሰሙምን ፧ እስኪ ፡ ንገሩኝ ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ አንዱ ፡ ከባሪያዪቱ ፡ አንዱም ፡ ከጨዋዪቱ ፡ የኾኑ ፡ ኹለት ፡ ልጆች ፡ ለአብርሃም ፡ እንደ ፡ ነበሩት ፡ ተጽፏልና ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባሪያዪቱ ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ተወልዷል ፥ የጨዋዪቱ ፡ ግን ፡ በተስፋው ፡ ቃል ፡ ተወልዷል ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ይህም ፡ ነገር ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ እነዚህ ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ ኹለቱ ፡ ኪዳኖች ፡ ናቸውና ። ከደብረ ፡ ሲና ፡ የኾነችው ፡ አንዲቱ ፡ ለባርነት ፡ ልጆችን ፡ ትወልዳለች ፥ ርሷም ፡ አጋር ፡ ናት ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ይህችም ፡ አጋር ፡ በዐረብ ፡ ምድር ፡ ያለችው ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ናት ፤ አኹንም ፡ ያለችውን ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ትመስላለች ፥ ከልጆቿ ፡ ጋራ ፡ በባርነት ፡ ናትና ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ላይኛዪቱ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ግን ፡ በነጻነት ፡ የምትኖር ፡ ናት ፡ ርሷም ፡ እናታችን ፡ ናት ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ አንቺ ፡ የማትወልጅ ፡ መካን ፥ ደስ ፡ ይበልሽ ፤ አንቺ ፡ አምጠሽ ፡ የማታውቂ ፥ እልል ፡ በዪና ፡ ጩኺ ፤ ባል ፡ ካላቱ ፡ ይልቅ ፡ የብቸኛዪቱ ፡ ልጆች ፡ በዝተዋልና ፥ ተብሎ ፡ ተጽፏል ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ እኛም ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ይሥሐቅ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ልጆች ፡ ነን ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ሥጋ ፡ የተወለደው ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ የተወለደውን ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እንዳሳደደው ፡ ዛሬም ፡ እንዲሁ ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መጽሐፍ ፡ ምን ፡ ይላል ፧ የባሪያዪቱ ፡ ልጅ ፡ ከጨዋዪቱ ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡

አይወርስምና ፡ ባሪያዩቱን ፡ ከልጇ ፡ ጋራ ፡ አውጣት ።

ገላ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የጨዋዩቱ ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ እንጂ ፡ የባሪያዩቱ ፡ አይደለንም ።

ገላትያ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ በነጻነት ፡ ልንኖር ፡ ክርስቶስ ፡ ነጻነት ፡ አወጣን ፤ እንግዲህ ፡ ጸንታችኹ ፡ ቁሙ ፡ እንደ ፡ ገናም ፡ በባርነት ፡ ቀንበር ፡ አትያዙ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ እንሆ ፥ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ እላችኋለኹ ፦ ብትገረዙ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንም ፡ አይጠቅማችኹም ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ሕግንም ፡ ኹሉ ፡ እንዲፈጽም ፡ ግድ ፡ አለበት ፡ ብዬ ፡ ለሚገረዙት ፡ ኹሉ ፡ ለያንዳንዶች ፡ ደግሜ ፡ እመሰክራለኹ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ በሕግ ፡ ልትጸድቁ ፡ የምትፈልጉ ፡ ከክርስቶስ ፡ ተለይታችኹ ፡ ከጸጋው ፡ ወድቃችኋል ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ እኛ ፡ በመንፈስ ፡ ከእምነት ፡ የጽድቅን ፡ ተስፋ ፡ እንጠባበቃለንና ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ኾኖ ፥ በፍቅር ፡ የሚሠራ ፡ እምነት ፡ እንጂ ፡ መገረዝ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ አለመገረዝ ፡ አይጠቅምምና ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ በመልካም ፡ ትሮጡ ፡ ነበር ፤ ለእውነት ፡ እንዳትታዘዙ ፡ ማን ፡ ከለከላችኹ ፧

ገላ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ይህ ፡ ማባበል ፡ ከሚጠራችኹ ፡ አልወጣም ። ጥቂት ፡ ርሾ ፡ ሊጡን ፡ ኹሉ ፡ ያቦካል ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 9-10 ፤ የተለየ ፡ ነገር ፡ ከቶ ፡ እንዳታስቡ ፡ እኔ ፡ በጌታ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ታምኛለኹ ፤ የሚያናውጣችኹ ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ ፍርዱን ፡ ሊሸከም ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ገና ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ መገረዝን ፡ ብሰብክ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ድረስ ፡ ለምን ፡ ያሳድዱኛል ፧ እንኪያስ ፡ የመስቀል ፡ ዕንቅፋት ፡ ተወግዷል ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ የሚያውኳችኹ ፡ ይቈረጡ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ለሐራነት ፡ ተጠርታችኋልና ፤ ብቻ ፡ ሐራነታችኹ ፡ ለሥጋ ፡ ምክንያትን ፡ አይስጥ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በፍቅር ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ ኹኑ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ሕግ ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይፈጸማልና ፥ ርሱም ፦ ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፡ የሚል ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ብትነካከሱ ፡ ብትበላሉ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ እንዳትጠፋፉ ፡ ተጠንቀቁ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እላለኹ ፥ በመንፈስ ፡ ተመላለሱ ፥ የሥጋንም ፡ ምኞት ፡ ከቶ ፡ አትፈጽሙ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ሥጋ ፡ በመንፈስ ፡ ላይ ፡ መንፈስም ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ ይመኛልና ፥ እነዚህም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ይቀዋወማሉ ፤ ስለዚህም ፡ የምትወዱትን ፡ ልታደርጉ ፡ አትችሉም ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ በመንፈስ ፡ ብትመሩ ፡ ግን ፡ ከሕግ ፡ በታች ፡ አይደላችኹም ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ የሥጋ ፡ ሥራም ፡ የተገለጠ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ዝሙት ፥ ርኵሰት ፥

ገላ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ መዳራት ፡ ጣዖትን ፡ ማምለክ ፡ ሟርት ፡ ጥል ፡ ክርክር ፡ ቅንአት ፡ ቀሥጣ ፡ ዐድመኛነት ፡

ገላ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ መለያየት ፡ መናፍቅነት ፡ ምቀኝነት ፡ መግደል ፡ ስካር ፡ ዘፋኝነት ፡ ይህንም ፡ የሚመስል ፡ ነው ። አስቀድሜም ፡ እንዳልኹ ፡ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ የሚያደርጉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አይወርሱም ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ የመንፈስ ፡ ፍሬ ፡ ግን ፡
ፍቅር ፡ ደስታ ፡ ሰላም ፡ ትዕግሥት ፡ ቸርነት ፡ በጎነት ፡ እምነት ፡ የውሀት ፡ ራስን ፡ መግዛት ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ የሚከለክል ፡ ሕግ ፡ የለም ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ የኾኑቱ ፡ ሥጋን ፡ ከክፉ ፡ መሻቱና ፡ ከምኞቱ ፡ ጋራ ፡ ሰቀሉ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 25 ፤ በመንፈስ ፡ ብንኖር ፡ በመንፈስ ፡ ደግሞ ፡ እንመላለስ ።

ገላ. ፡ 5 ፡ 26 ፤ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እየተነሣሣንና ፡ እየተቀናናን ፡ በከንቱ ፡ አንመካ ።

_____ገላትያ ፡ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ገላ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፡ ሰው ፡ በማናቸውም ፡ በደል ፡ ስንኳ ፡ ቢገኝ ፡ መንፈሳውያን ፡ የኾናችኹ ፡ እናንተ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ በየውሀት ፡ መንፈስ ፡ አቅኑት ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዳትፈተን ፡ ራስኽን ፡ ጠብቅ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 2 ፤ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ የአንዱን ፡ ሸክም ፡ ይሸከም ፡ እንዲሁም ፡ የክርስቶስን ፡ ሕግ ፡ ፈጽሙ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ አንዱ ፡ ምንም ፡ ሳይኾን ፡ ምንም ፡ የኾነ ፡ ቢመስለው ፡ ራሱን ፡ ያታልላልና ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ሥራ ፡ ይፈትን ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ስለሌላው ፡ ሰው ፡ ያልኾነ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ የሚመካበትን ፡ ያገኛል ፤

ገላ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ እያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ ራሱን ፡ ሸክም ፡ ሊሸከም ፡ ነውና ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ የሚማር ፡ ከሚያስተምረው ፡ ጋራ ፡ መልካምን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ይከፋፈል ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ አትሳቱ ፤ እግዚአብሔር ፡ አይዘበትበትም ። ሰው ፡ የሚዘራውን ፡ ኹሉ ፡ ያንኑ ፡ ደግሞ ፡ ያጭዳልና ፤

ገላ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ በገዛ ፡ ሥጋው ፡ የሚዘራ ፡ ከሥጋ ፡ መበስበስን ፡ ያጭዳልና ፥ በመንፈስ ፡ ግን ፡ የሚዘራው ፡ ከመንፈስ ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ያጭዳል ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ባንዝልም ፡ በጊዜው ፡ እናጭዳለንና ፡ መልካም ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ አንታክት ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ እንግዲያስ ፡ ጊዜ ፡ ካገኘን ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ይልቁንም ፡ ለሃይማኖት ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ መልካም ፡ እናድርግ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ እንዴት ፡ ባሉ ፡ ታላላቆች ፡ ፊደላት ፡ በእጄ ፡ እንደ ፡ ጻፍኩላችኹ ፡ እዩ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ በሥጋ ፡ መልካም ፡ ኾነው ፡ ሊታዩ ፡ የሚወዱ ፡ ኹሉ ፡ እንድትገረዙ ፡ ግድ ፡ አሏችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ እንዳይሰደዱ ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ በሥጋችኹ ፡ እንዲመኩ ፡ ልትገረዙ ፡ ይወዳሉ ፡ እንጂ ፡ የተገረዙቱ ፡ ራሳቸው ፡ እንኳ ፡ ሕግን ፡ አይጠብቁም ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ዓለም ፡ ለእኔ ፡ የተሰቀለበት ፡ እኔም ፡ ለዓለም ፡ የተሰቀልኹበት ፡ ከጌታችን ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ትምክሕት ፡ ከእኔ ፡ ይራቅ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ዐዲስ ፡ ፍጥረት ፡ መኾን ፡ ይጠቅማል ፡ እንጂ ፡ መገረዝ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ አለመገረዝ ፡ አይጠቅምምና ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ በዚህም ፡ ሥርዐት ፡ በሚመላለሱ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እስራኤልም ፡ ላይ ፡ ሰላምና ፡ ምሕረት ፡ ይኹን ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ እኔ ፡ የኢየሱስን ፡ ማኅተም ፡ በሥጋዬ ፡ ተሸክሜያለኹና ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አያድክመኝ ።

ገላ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከመንፈሳችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ። አሜን ❖

የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደኤፌሶን ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፥ በኤፌሶን ፡ ላሉት ፡ ቅዱሳን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ ላሉት ፡ ምእመናን ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ በክርስቶስ ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ በመንፈሳዊ ፡ በረከት ፡ ኹሉ ፡ የባረከን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ ይባረክ ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፥ በፊቱ ፡ ቅዱሳንና ፡ ነውር ፡ የሌለን ፡ በፍቅር ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ መረጠን ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ በበጎ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፥ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥራ ፡ ለርሱ ፡ ልጆች ፡ ልንኾን ፡ አስቀድሞ ፡ ወሰነን ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ በውድ ፡ ልጁም ፡ እንዲያው ፡ የሰጠን ፡ የጸጋው ፡ ክብር ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ አደረገ ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ በውድ ፡ ልጁም ፥ እንደ ፡ ጸጋው ፡ ባለጠግነት ፡ መጠን ፥ በደሙ ፡ የተደረገ ፡ ቤዛነታችንን ፡ አገኘን ፡ ርሱም ፡ የበደላችን ፡ ስርየት ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ጸጋውንም ፡ በጥበብና ፡ በአእምሮ ፡ ኹሉ ፡ አበዛልን ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ በክርስቶስ ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ እንደ ፡ ዐሳቡ ፥ የፈቃዱን ፡ ምስጢር ፡ አስታውቆናልና ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ዐሳቡም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ለመጠቅለል ፡ ነው ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ምክር ፡ ኹሉን ፡ የሚሠራ ፡ እንደ ፡ ርሱ ፡ ዐሳብ ፥ አስቀድመን ፡ የተወሰንን ፡ በክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ርስትን ፡ ተቀበልን ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ይኸውም ፥ በክርስቶስ ፡ አስቀድመን ፡ ተስፋ ፡ ያደረግን ፡ እኛ ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ እንኾን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ የእውነትን ፡ ቃል ፥ ይኸውም ፡ የመዳናችኹን ፡ ወንጌል ፥ ሰምታችኹ ፡ ደግሞም ፡ በክርስቶስ ፡ አምናችኹ ፥ በተስፋው ፡ መንፈስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታተማችኹ ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ርሱም ፡ የርስታችን ፡ መያዣ ፡ ነው ፥ ለእግዚአብሔር ፡ ያለውን ፡ ኹሉ ፡ እስኪዋጅ ፡ ድረስ ፥ ይህም ፡ ለክብሩ ፡ ምስጋና ፡ ይኾናል ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚኾን ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ስለ ፡ ማመንና ፡

ለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ስለሚኾን ፡ መውደድ ፡ ሰምቼ ፥

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ እያመሰገንኹ ፡ ስጸልይ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ማሳሰብን ፡ አልተውም ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ የክብር ፡ አባት ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ ርሱን ፡ በማወቅ ፡ የጥበብንና ፡ የመገለጥን ፡ መንፈስ ፡ እንዲሰጣችኹ ፡ እለምናለኹ ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 18-19 ፤ ይህም ፡ የልባችኹ ፡ ዐይኖች ፡ ሲበሩ ፡ የመጥራቱ ፡ ተስፋ ፡ ምን ፡ እንዲኾን ፡ በቅዱሳንም ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የርስት ፡ ክብር ፡ ባለጠግነት ፡ ምን ፡ እንዲኾን ፡ ለምናምን ፡ ከኹሉ ፡ የሚበልጥ ፡ የኀይሉ ፡ ታላቅነት ፡ ምን ፡ እንዲኾን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 20-21 ፤ ክርስቶስንም ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣው ፥ ከአለቅነትና ፡ ከሥልጣንም ፡ ከኀይልም ፡ ከጌትነትም ፡ ኹሉ ፡ በላይና ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሊመጣ ፡ ባለው ፡ ዓለም ፥ ደግሞ ፡ ከሚጠራው ፡ ስም ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፥ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ በቀኙ ፡ ሲያስቀምጠው ፥ በክርስቶስ ፡ ባደረገው ፡ ሥራ ፡ የብርታቱ ፡ ጕልበት ፡ ይታያል ፤

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 22 ፤ ኹሉንም ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ አስገዛለት ፥ ከኹሉ ፡ በላይም ፡ ራስ ፡ እንዲኾን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጠው ።

ኤፌ. ፥ 1 ፥ 23 ፤ ርሷም ፡ አካሉና ፡ ኹሉን ፡ በኹሉ ፡ የሚሞላ ፡ የርሱ ፡ ሙላቱ ፡ ናት ።

ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 1-2 ፤ በበደላችኹና ፡ በኀጢአታችኹ ፡ ሙታን ፡ ነበራችኹ ፤ በእነርሱም ፥ በዚህ ፡ ዓለም ፡ እንዳለው ፡ ኑሮ ፥ በማይታዘዙትም ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ አኹን ፡ ለሚሠራው ፡ መንፈስ ፡ አለቃ ፡ እንደ ኾነው ፡ በአየር ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ አለቃ ፡ ፈቃድ ፥ በፊት ፡ ተመላለሳችኹባቸው ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 3 ፤ በእነዚህም ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ እኛ ፡ ኹላችን ፡ ደግሞ ፥ የሥጋችንንና ፡ የልቡናችንን ፡ ፈቃድ ፡ እያደረግን ፥ በሥጋችን ፡ ምኞት ፡ በፊት ፡ እንኖር ፡ ነበርን ፡ እንደ ፡ ሌላዎቹም ፡ ደግሞ ፡ ከፍጥረታችን ፡ የቀሥጣ ፡ ልጆች ፡ ነበርን ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ በምሕረቱ ፡ ባለጠጋ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 5 ፤ ከወደደን ፡ ከትልቅ ፡ ፍቅሩ ፡ የተነሣ ፡ በበደላችን ፡ ሙታን ፡ እንኳ ፡ በኾነ ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ሕይወት ፡ ሰጠን ፥ በጸጋ ፡ ድናችኋልና ፥

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 6-7 ፤ በሚመጡ ፡ ዘመናትም ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ለእኛ ፡ ባለው ፡ ቸርነት ፡ ከኹሉ ፡ የሚበልጠውን ፡ የጸጋውን ፡ ባለጠግነት ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስነሣን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስቀመጠን ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 8 ፤ ጸጋው ፡ በእምነት ፡ አድኗችኋልና ፤ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጦታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከእናንተ ፡ አይደለም ፤

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 9 ፤ ማንም ፡ እንዳይመካ ፡ ከሥራ ፡ አይደለም ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 10 ፤ እኛ ፡ ፍጥረቱ ፡ ነንና ፤ እንመላለስበት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቀድሞ ፡ ያዘጋጀውን ፡ መልካሙን ፡ ሥራ ፡ ለማድረግ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተፈጠርን ።

ኤፌ. ፥ 2 ፥ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥጋ ፡ አሕዛብ ፡ የነበራችኹ ፥ በሥጋ ፡ በእጅ ፡ የተገረዙ ፡

በተባሉት ፡ ያልተገረዙ ፡ የተባላችኹ ፥ ይህን ፡ ዐስቡ ፤

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከእስራኤል ፡ መንግሥት ፡ ርቃችኹ ፥ ለተስፋውም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንግዳዎች ፡ ኾናችኹ ፥ በዚህም ፡ ዓለም ፡ ተስፋን ፡ ዐጥታችኹ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ ተለይታችኹ ፥ ያለክርስቶስ ፡ ነበራችኹ ።

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ በፊት ፡ ርቃችኹ ፡ የነበራችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ኾናችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡ ቀርባችኋል ።

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 14-15 ፤ ርሱ ፡ ሰላማችን ፡ ነውና ፤ ኹለቱን ፡ ያዋሐደ ፡ በዐዋጅ ፡ የተነገሩትንም ፡ የትእዛዛትን ፡ ሕግ ፡ ሽሮ ፡ በመካከል ፡ ያለውን ፡ የጥል ፡ ግድግዳን ፡ በሥጋው ፡ ያፈረሰ ፤ ይህም ፡ ከኹለታቸው ፡ አንድን ፡ ዐዲስን ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ይፈጥር ፡ ዘንድ ፡ ሰላምንም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፥

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ጥልንም ፡ በመስቀሉ ፡ ገድሎ ፡ በርሱ ፡ ኹለታቸውን ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ያስታርቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ መጥቶም ፡ ርቃችኹ ፡ ለነበራችኹ ፡ ለእናንተ ፡ ሰላምን ፥ ቀርበው ፡ ለነበሩትም ፡ ሰላምን ፡ የምሥራች ፡ ብሎ ፡ ሰበከ ፤

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ በርሱ ፡ ሥራ ፡ ኹላችን ፡ ባንድ ፡ መንፈስ ፡ ወደ ፡ አብ ፡ መግባት ፡ አለንና ።

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እንግዲያስ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከቅዱሳን ፡ ጋራ ፡ ባላገሮችና ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ናችኹ ፡ እንጂ ፡ እንግዳዎችና ፡ መጻተኞች ፡ አይደላችኹም ።

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ በሐዋርያትና ፡ በነቢያት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ታንጻችኋል ፥ የማእዘኑም ፡ ራስ ፡ ድንጋይ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፤

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ በርሱም ፡ ሕንጻ ፡ ኹሉ ፡ እየተጋጠመ ፡ በጌታ ፡ ቅዱስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዲኾን ፡ ያድጋል ፤

ኤፌ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ በርሱም ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መኖሪያ ፡ ለመኾን ፡ በመንፈስ ፡ ዐብራችኹ ፡ ትሠራላችኹ ።

ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ስለዚህም ፡ አሕዛብ ፡ ስለኾናችኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስር ፡ የኾንኹ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንበረከካለኹ ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ለእናንተ ፡ ስለተሰጠኝ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ መጋቢነት ፡ በርግጥ ፡ ሰምታችኋል ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ አስቀድሜ ፡ በዐጪሩ ፡ እንደ ፡ ጻፍኹ ፥ ይህን ፡ ምስጢር ፡ በመግለጥ ፡ አስታወቀኝ ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ይህንም ፡ ስታነቡ ፡ የክርስቶስን ፡ ምስጢር ፡ እንዴት ፡ እንደማስተውል ፡ ልትመለከቱ ፡ ትችላላችኹ ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 5-6 ፤ ይህም ፥ አሕዛብ ፡ ዐብረው ፡ እንዲወርሱ ፥ ባንድ ፡ አካልም ፡ ዐብረው ፡ እንዲኾኑ ፥ በወንጌልም ፡ መስበክ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በኾነ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ዐብረው ፡ እንዲካፈሉ ፥ ለቅዱሳን ፡ ሐዋርያትና ፡ ለነቢያት ፡ በመንፈስ ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ በሌላዎቹ ፡ ትውልዶች ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ልጆች ፡ አልታወቀም ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንደ ፡ ኀይሉ ፡ ሥራ ፡ እንደተሰጠኝም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስጦታ ፡ መጠን ፡ የወንጌል ፡ አገልጋይ ፡ ኾንኹለት ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 8-9 ፤ ፍለጋ ፡ የሌለውን ፡ የክርስቶስን ፡ ባለጠግነት ፡ ለአሕዛብ ፡ እሰብክ ፡ ዘንድ ፥ ዅሉንም ፡ በፈጠረው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከዘለዓለም ፡ የተሰወረው ፡ የምስጢር ፡ ሥርዐት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ለዅሉ ፡ እገልጥ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ጸጋ ፡ ከቅዱሳን ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ለማንስ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጠ ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ አኹን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኩል ፡ በሰማያዊ ፡ ስፍራ ፡ ውስጥ ፡ ላሉት ፡ አለቃዎችና ፡ ሥልጣናት ፡ ትታወቅ ፡ ዘንድ ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ይህም ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ በጌታችን ፡ የፈጸመው ፡ የዘለዓለም ፡ ዐሳብ ፡ ነበረ ፥

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ በርሱም ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ እምነታችን ፡ በኩል ፡ በመታመን ፡ ድፍረትና ፡ መግባት ፡ በርሱ ፡ አለን ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ ስለ ፡ እናንተ ፡ ስላለ ፡ መከራዬ ፡ እንዳትታክቱ ፡ እለምናችኋለኹ ፥ ክብራችኹ ፡ ነውና ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 14-15 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለ ፡ አባትነት ፡ ዅሉ ፡ ከሚሰየምበት ፡ ከአብ ፡ ፊት ፡ እንበረከካለኹ ፤

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 16-17 ፤ በመንፈሱ ፡ በውስጥ ፡ ሰውነታችኹ ፡ በኀይል ፡ እንድትጠነክሩ ፥ ክርስቶስም ፡ በልባችኹ ፡ በእምነት ፡ እንዲኖር ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ባለጠግነት ፡ መጠን ፡ ይስጣችኹ ፤ የእናንተ ፡ ሥርና ፡ መሠረት ፡ በፍቅር ፡ ይጸና ፡ ዘንድ ፥

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 18-19 ፤ ከቅዱሳን ፡ ዅሉ ፡ ጋራ ፡ ስፋቱና ፡ ርዝመቱ ፣ ከፍታውም ፡ ጥልቅነቱም ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ መኾኑን ፡ ለማስተዋል ፥ ከመታወቅም ፡ የሚያልፈውን ፡ የክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ለማወቅ ፡ ትበረቱ ፡ ዘንድ ፥ እስከ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ፍጹም ፡ ሙላት ፡ ደርሳችኹ ፡ ትሞሉ ፡ ዘንድ ።

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ እንግዲህ ፡ በእኛ ፡ እንደሚሠራው ፡ ኀይል ፡ መጠን ፡ ከምንለምነው ፡ ወይም ፡ ከምናስበው ፡ ዅሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ አብልጦ ፡ ሊያደርግ ፡ ለሚቻለው ፥

ኤፌ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ለርሱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስከ ፡ ትውልዶች ፡ ዅሉ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ በጌታ ፡ እስር ፡ የኾንኹ ፡ እኔ ፡ በተጠራችኹበት ፡ መጠራታችኹ ፡ እንደሚገባ ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ እለምናችኋለኹ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ በትሕትና ፡ ዅሉና ፡ በየዋህነት ፡ በትዕግሥትም ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ በፍቅር ፡ ታገሡ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ በሰላም ፡ ማሰሪያ ፡ የመንፈስን ፡ አንድነት ፡ ለመጠበቅ ፡ ትጉ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ በመጠራታችኹ ፡ ባንድ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ተጠራችኹ ፡ አንድ ፡ አካልና ፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ አለ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ አንድ ፡ ጌታ ፡ አንድ ፡ ሃይማኖት ፡ አንዲት ፡ ጥምቀት ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ከዅሉ ፡ በላይ ፡ የሚኾን ፡ በዅሉም ፡ የሚሠራ ፡ በዅሉም ፡ የሚኖር ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ የዅሉም ፡ አባት ፡ አለ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደክርስቶስ ፡ ስጦታ ፡ መጠን ፡ ለያንዳንዳችን ፡ ጸጋ ፡ ተሰጠን ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፦ ወደ ፡ ላይ ፡ በወጣ ፡ ጊዜ ፡ ምርኮን ፡ ማረከ ፡ ለሰዎችም ፡ ስጦታን ፡ ሰጠ ፡ ይላል ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ወደምድር ፡ ታችኛ ፡ ክፍል ፡ ደግሞ ፡ ወረደ ፡ ማለት ፡ ካልኾነ ፥ ይህ ፡ ወጣ ፡ ማለትስ ፡ ምን ፡ ማለት ፡ ነው ፧

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ይህ ፡ የወረደው ፡ ኹሉን ፡ ይሞላ ፡ ዘንድ ፡ ከሰማያት ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ የወጣው ፡ ደግሞ ፡ ያው ፡ ነው ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ርሱም ፡ አንዳንዶቹ ፡ ሐዋርያት ፥ ሌላዎቹም ፡ ነቢያት ፥ ሌላዎቹም ፡ ወንጌልን ፡ ሰባኪዎች ፥ ሌላዎቹም ፡ እረኞችና ፡ አስተማሪዎች ፡ እንዲኾኑ ፡ ሰጠ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 12-13 ፤ ኹላችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ በማመንና ፡ በማወቅ ፡ ወደሚገኝ ፡ አንድነት ፥ ሙሉ ፡ ሰውም ፡ ወደ ፡ መኾን ፥ የክርስቶስም ፡ ሙላቱ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ ሙላቱ ፡ ልክ ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፥ ቅዱሳን ፡ አገልግሎትን ፡ ለመሥራትና ፡ ለክርስቶስ ፡ አካል ፡ ሕንጻ ፡ ፍጹማን ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ እንደ ፡ ስሕተት ፡ ሽንገላ ፡ ባለ ፡ ተንኰል ፡ በሰዎችም ፡ ማታለል ፡ ምክንያት ፡ በትምህርት ፡ ነፋስ ፡ ኹሉ ፡ እየተፍገመገምን ፡ ወዲያና ፡ ወዲህም ፡ እየተንሳፈፍን ፡ ሕፃናት ፡ መኾን ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ አይገባንም ፥

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እውነትን ፡ በፍቅር ፡ እየያዝን ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ወደርሱ ፡ ራስ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደግ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ከርሱም ፡ የተነሣ ፡ አካል ፡ ኹሉ ፡ እያንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ በልክ ፡ እንደሚሠራ ፥ በተሰጠለት ፡ በኀይማት ፡ ኹሉ ፡ እየተጋጠመና ፡ እየተያያዘ ፥ ራሱን ፡ በፍቅር ፡ ለማነጽ ፡ አካሉን ፡ ያሳድጋል ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ አሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ በአእምሯቸው ፡ ከንቱነት ፡ እንደሚመላለሱ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንዳትመላለሱ ፡ እላለኹ ፡ በጌታም ፡ ኾኜ ፡ እመሰክራለኹ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ እነርሱ ፥ ባለማወቃቸው ፡ ጠንቅ ፥ በልባቸውም ፡ ደንዳናነት ፡ ጠንቅ ፡ ልቡናቸው ፡ ጨለመ ፥ ከእግዚአብሔርም ፡ ሕይወት ፡ ራቁ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ ደንዝዘውም ፡ በመመኘት ፡ ርኵሰትን ፡ ኹሉ ፡ ለማድረግ ፡ ራሳቸውን ፡ ወደ ፡ ሴሰኝነት ፡ አሳልፈው ፡ ሰጡ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ክርስቶስን ፡ እንደዚህ ፡ አልተማራችኹም ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ በርግጥ ፡ ሰምታችኹታልና ፥ እውነትም ፡ በኢየሱስ ፡ እንዳለ ፡ በርሱ ፡ ተምራችኋል ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ፊተኛ ፡ ኑሯችኹን ፡ እያሰባችኹ ፡ እንደሚያታልል ፡ ምኞት ፡ የሚጠፋውን ፡ አሮጌውን ፡ ሰው ፡ አስወግዱ ፥

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ በአእምሯችኹም ፡ መንፈስ ፡ ታደሱ ፥

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 24 ፤ ለእውነትም ፡ በሚኾኑ ፡ ጽድቅና ፡ ቅድስና ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠረውን ፡ ዐዲሱን ፡ ሰው ፡ ልበሱ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 25 ፤ ስለዚህ ፥ ውሸትን ፡ አስወግዳችኹ ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ብልቶች ፡ ኾነናልና ፥ እያንዳንዳችኹ ፡ ከባልንጀራዎቻችኹ ፡ ጋራ ፡ እውነትን ፡ ተነጋገሩ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 26 ፤ ተቈጡ ፡ ኀጢአትንም ፡ አታድርጉ ፤

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 27 ፤ በቀኑ ፡ ላይ ፡ ፀሐይ ፡ አይግባ ፥ ለዲያብሎስም ፡ ፈንታ ፡ አትስጡት ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 28 ፤ የሰረቀ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይስረቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ፈንታ ፡ ለጐደለው ፡ የሚያካፍለው ፡ እንዲኖርለት ፡ በገዛ ፡ እጆቹ ፡ መልካምን ፡ እየሠራ ፡ ይድከም ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 29 ፤ ለሚሰሙት ፡ ጸጋን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፥ እንደሚያስፈልግ ፡ ለማነጽ ፡ የሚጠቅም ፡ ማናቸውም ፡ በጎ ፡ ቃል ፡ እንጂ ፡ ክፉ ፡ ቃል ፡ ከአፋችኹ ፡ ከቶ ፡ አይውጣ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 30 ፤ ለቤዛም ፡ ቀን ፡ የታተማችኹበትን ፡ ቅዱሱን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ አታሳዝኑ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 31 ፤ መራርነትና ፡ ንዴት ፡ ቍጣም ፡ ጩኸትም ፡ መሳደብም ፡ ኹሉ ፡ ከክፋት ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ይወገድ ።

ኤፌ. ፡ 4 ፡ 32 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹም ፡ ቸሮችና ፡ ርኅሩኆች ፡ ኹኑ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችኹ ፡ ይቅር ፡ ተባባሉ ።

ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ እንደተወደዱ ፡ ልጆች ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምትከተሉ ፡ ኹኑ ፥

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ክርስቶስም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ወደዳችኹ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ የመዐዛ ፡ ሽታ ፡ የሚኾንን ፡ መባንና ፡ መሥዋዕትን ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በፍቅር ፡ ተመላለሱ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ለቅዱሳን ፡ እንደሚገባ ፡ ግን ፡ ዝሙትና ፡ ርኵሰት ፡ ኹሉ ፡ ወይም ፡ መመኘት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ አይሰማ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ የሚያሳፍር ፡ ነገርም ፡ የስንፍና ፡ ንግግርም ፡ ወይም ፡ ዋዛ ፡ የማይገቡ ፡ ናቸውና ፥ አይኹኑ ፥ ይልቁን ፡ ምስጋና ፡ እንጂ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ ይህን ፡ ዕወቁ ፤ አመንዝራም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ርኩስ ፡ ወይም ፡ የሚመኝ ፡ ርሱም ፡ ጣዖትን ፡ የሚያመልክ ፡ በክርስቶስና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ርስት ፡ የለውም ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ በማይታዘዙት ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ይመጣልና ፥ ማንም ፡ በከንቱ ፡ ንግግር ፡ አያታሏችኹ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ተካፋዮች ፡ አትኹኑ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ቀድሞ ፡ ጨለማ ፡ ነበራችኹና ፥ አኹን ፡ ግን ፡ በጌታ ፡ ብርሃን ፡ ናችኹ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 9-10 ፤ የብርሃኑ ፡ ፍሬ ፡ በበጎነትና ፡ በጽድቅ ፡ በእውነትም ፡ ኹሉ ፡ ነውና ፥ ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ እየመረመራችኹ ፥ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ልጆች ፡ ተመላለሱ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ፍሬም ፡ ከሌለው ፡ ከጨለማ ፡ ሥራ ፡ ጋራ ፡ አትተባበሩ ፥ ይልቁን ፡ ግለጡት ፡ እንጂ ፥

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ እነርሱ ፡ በስውር ፡ ስለሚያደርጉት ፡ መናገር ፡ እንኳ ፡ ነውር ፡ ነውና ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ኹሉ ፡ ግን ፡ በብርሃን ፡ ሲገለጥ ፡ ይታያል ፤ የሚታየው ፡ ኹሉ ፡ ብርሃን ፡ ነውና ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፦ አንተ ፡ የምትተኛ ፡ ንቃ ፡ ከሙታንም ፡ ተነሣ ፡ ክርስቶስም ፡ ያበራልኻል ፡ ይላል ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ጥበበኞች ፡ እንጂ ፡ ጥበብ ፡ እንደሌላቸው ፡ ሳይኾን ፡ እንዴት ፡ እንድትመላለሱ ፡ በጥንቃቄ ፡ ተጠበቁ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ቀኖቹ ፡ ክፉዎች ፡ ናቸውና ፥ ዘመኑን ፡ ዋጁ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፥ የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አስተውሉ ፡ እንጂ ፡ ሞኞች ፡ አትኹኑ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ መንፈስ ፡ ይሙላባችኹ ፡ እንጂ ፡ በወይን ፡ ጠጅ ፡ አትስከሩ ፡ ይህ ፡ ማባከን ፡ ነውና ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ በመዝሙርና ፡ በዝማሬ ፡ በመንፈሳዊም ፡ ቅኔ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተነጋገሩ ፤ ለጌታ ፡ በልባችኹ ፡ ተቀኙና ፡ ዘምሩ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ኹልጊዜ ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ አምላካችንንና ፡ አባታችንን ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፡ አመስግኑ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 21 ፤ ለያንዳንዳችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ፍርሀት ፡ የተገዛችኹ ፡ ኹኑ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 22 ፤ ሚስቶች ፡ ሆይ ፥ ለጌታ ፡ እንደምትገዙ ፡ ለባሎቻችኹ ፡ ተገዙ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 23 ፤ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ርሱም ፡ አካሉን ፡ የሚያድን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ባል ፡ የሚስት ፡ ራስ ፡ ነውና ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 24 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለክርስቶስ ፡ እንደምትገዛ ፡ እንዲሁ ፡ ሚስቶች ፡ ደግሞ ፡ በኹሉ ፡ ለባሎቻቸው ፡ ይገዙ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 25-26 ፤ ባሎች ፡ ሆይ ፥ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንደ ፡ ወደዳት ፡ ሚስቶቻችኹን ፡ ውደዱ ፤ በውሃ ፡ መታጠብና ፡ ከቃሉ ፡ ጋራ ፡ አንጽቶ ፡ እንዲቀድሳት ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 27 ፤ እድፈት ፡ ወይም ፡ የፊት ፡ መጨማደድ ፡ ወይም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሳይኾንባት ፡ ቅድስትና ፡ ያለነውር ፡ ትኾን ፡ ዘንድ ፡ ክብርት ፡ የኾነችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለራሱ ፡ እንዲያቀርብ ፡ ፈለገ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 28 ፤ እንዲሁም ፡ ባሎች ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ሥጋቸው ፡ አድርገው ፡ የገዛ ፡ ሚስቶቻቸውን ፡ ሊወዷቸው ፡ ይገባቸዋል ። የገዛ ፡ ሚስቱን ፡ የሚወድ ፡ ራሱን ፡ ይወዳል ፤

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 29-30 ፤ ማንም ፡ የገዛ ፡ ሥጋውን ፡ የሚጠላ ፡ ከቶ ፡ የለምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የአካሉ ፡ ብልቶች ፡ ስለ ፡ ኾን ፥ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዳደረገላት ፥ ይመግበዋል ፡ ይከባከበውማል ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 31 ፤ ስለዚህ ፥ ሰው ፡ አባቱንና ፡ እናቱን ፡ ይተዋል ፥ ከሚስቱም ፡ ጋራ ፡ ይተባበራል ፤ ኹለቱም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይኾናሉ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 32 ፤ ይህ ፡ ምስጢር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ስለ ፡ ክርስቶስና ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እላለኹ ።

ኤፌ. ፡ 5 ፡ 33 ፤ ኾኖም ፡ ከእናንተ ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዱ ፡ የገዛ ፡ ሚስቱን ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ አድርጎ ፡ ይውደዳት ፥ ሚስቱም ፡ ባሏን ፡ ትፍራ ።

ኤፌሶን ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 1 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ለወላጆቻችኹ ፡ በጌታ ፡ ታዘዙ ፥ ይህ ፡ የሚገባ ፡ ነውና ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 2-3 ፤ መልካም ፡ እንዲኾንልኽ ፡ ዕድሜኽም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እንዲረዝም ፡ አባትኽንና ፡ እናትኽን ፡ አክብር ፤ ርሷም ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ያላት ፡ ፊተኛዪቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ እናንተም ፡ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ልጆቻችኹን ፡ በጌታ ፡ ምክርና ፡ በተግሣጽ ፡ አሳድጓቸው ፡ እንጂ ፡ አታስቈጧቸው ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ ባሪያዎች ፡ ሆይ ፥ ለክርስቶስ ፡ እንደምትታዘዙ ፡ በፍርሀትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ በልባችኹ ፡ ቅንነት ፡ በሥጋ ፡ ጌታዎቻችኹ ፡ ለኾኑ ፡ ታዘዙ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እንደሚያደርጉ ፡ እንደክርስቶስ ፡ ባሪያዎች ፡ እንጂ ፡ ለሰው ፡ ደስ ፡ እንደምታሠኙ ፡ ለታይታ ፡ የምትገዙ ፡ አትኹኑ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ለሰው ፡ ሳይኾን ፡ ለጌታ ፡ እንደምትገዙ ፡ በትጋትና ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ተገዙ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ባሪያ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ጨዋ ፡ ሰው ፥ እያንዳንዱ ፡ የሚያደርገውን ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ከጌታ ፡ በብድራት ፡ እንዲቀበለው ፡ ታውቃላችኹና ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ እናንተም ፡ ጌታዎች ፡ ሆይ ፥ ዛቻውን ፡ ትታችኹ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉላቸው ፥ በእነርሱና ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡ የሚገዛው ፡ ጌታ ፡ በሰማይ ፡ እንዳለ ፡ ለሰው ፡ ፊትም ፡ እንዳያደላ ፡ ታውቃላችኹና ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ በቀረውስ ፡ በጌታና ፡ በኀይሉ ፡ ችሎት ፡ የበረታችኹ ፡ ኹኑ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 11 ፤ የዲያብሎስን ፡ ሽንገላ ፡ ትቃወሙ ፡ ዘንድ ፡ እንዲቻላችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ኹሉ ፡ ልበሱ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 12 ፤ መጋደላችን ፡ ከደምና ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ አይደለምና ፥ ከአለቃዎችና ፡ ከሥልጣናት ፡ ጋራ ፡ ከዚህም ፡ ከጨለማ ፡ ዓለም ፡ ገዢዎች ፡ ጋራ ፡ በሰማያዊም ፡ ስፍራ ፡ ካለ ፡ ከክፋት ፡ መንፈሳውያን ፡ ሰራዊት ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 13 ፤ ስለዚህ ፥ በክፉው ፡ ቀን ፡ ለመቃወም ፥ ኹሉንም ፡ ፈጽማችኹ ፡ ለመቆም ፡ እንድትችሉ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ ኹሉ ፡ አንሡ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 14-15 ፤ እንግዲህ ፡ ወገባችኹን ፡ በእውነት ፡ ታጥቃችኹ ፥ የጽድቅንም ፡ ጥሩር ፡ ለብሳችኹ ፥ በሰላም ፡ ወንጌልም ፡ በመዘጋጀት ፡ እግሮቻችኹ ፡ ተጫምተው ፡ ቁሙ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ በኹሉም ፡ ላይ ፡ ጨምራችኹ ፡ የሚንበለበሉትን ፡ የክፉውን ፡ ፍላጻዎች ፡ ኹሉ ፡ ልታጠፉ ፡ የምትችሉበትን ፡ የእምነትን ፡ ጋሻ ፡ አንሡ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ የመዳንንም ፡ ራስ ፡ ቍር ፡ የመንፈስንም ፡ ሰይፍ ፡ ያዙ ፡ ርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 18 ፤ በጸሎትና ፡ በልመናም ፡ ኹሉ ፡ ዘወትር ፡ በመንፈስ ፡ ጸልዩ ፤ በዚህም ፡ ዐሳብ ፡ ስለ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ እየለመናችኹ ፡ በመጽናት ፡ ኹሉ ፡ ትጉ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ደግሞ ፡ የወንጌልን ፡ ምስጢር ፡ በግልጥ ፡ እንዳስታውቅ ፡ አፌን ፡ በመክፈት ፡ ቃል ፡ ይሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ ለምኑ ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ ስለ ፡ ወንጌልም ፡ በሰንሰለት ፡ መልእክተኛ ፡ የኾንኹ ፥ መናገር ፡ እንደሚገባኝ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ በግልጥ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡ ለምኑ ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 21 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዴት ፡ እንዳለኹ ፡ ኑሮዬን ፡ እንድታውቁ ፡ የተወደደ ፡ ወንድምና ፡ በጌታ ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ ቲኪቆስ ፡ ኹሉን ፡ ያስታውቃችኋል ፤

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 22 ፤ ወሬያችንን ፡ እንድታውቁና ፡ ልባችኹን ፡ እንዲያጽናና ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የምልከው ፡ ስለዚህ ፡

ምክንያት ፡ ነው ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 23 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰላምና ፡ ፍቅር ፡ ከእምነት ፡ ጋራ ፡ ለወንድሞች ፡ ይኹን ።

ኤፌ. ፡ 6 ፡ 24 ፤ ጌታችንን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ባለመጥፋት ፡ ከሚወዱ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ጸጋ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ፊልጵስዩስ ፡ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 1 ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያዎች ፡ የኾኑ ፡ ጳውሎስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ለሚኖሩ ፡ ከኤጲስ ፡ ቆጶሳትና ፡ ከዲያቆናት ፡ ጋራ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ላሉት ፡ ቅዱሳን ፡ ኹሉ ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 3-5 ፤ ኹልጊዜ ፡ በጸሎቴ ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ኹሉ ፡ በደስታ ፡ እየጸለይኹ ፥ ከፊተኛው ፡ ቀን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ወንጌልን ፡ በመስበክ ፡ ዐብራችኹ ፡ ስለ ፡ ሠራችኹ ፥ ባሰብኳችኹ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ አምላኬን ፡ አመሰግናለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 6 ፤ በእናንተ ፡ መልካምን ፡ ሥራ ፡ የገሠመረው ፡ እስከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እንዲፈጽመው ፡ ይህን ፡ ተረድቻለኹና ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 7 ፤ በእስራቴም ፡ ወንጌልንም ፡ መመከቻና ፡ መጽኛ ፡ በማድረግ ፡ ኹላችኹ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በጸጋ ፡ ተካፋዮች ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፥ በልቤ ፡ ትኖራላችኹና ፡ ስለ ፡ ኹላችኹ ፡ ይህን ፡ ላስብ ፡ ይገባኛል ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 8 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፍቅር ፡ ኹላችኹን ፡ እንዴት ፡ እንድናፍቃችኹ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሬ ፡ ነውና ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 9-11 ፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚገኝ ፡ የጽድቅ ፡ ፍሬ ፡ ሞልቶባችኹ ፥ ለክርስቶስ ፡ ቀን ፡ ተዘጋጅታችኹ ፡ ቅኖችና ፡ አለ ፡ ነውር ፡ እንድትኾኑ ፡ የሚሻለውን ፡ ነገር ፡ ፈትናችኹ ፡ ትወዱ ፡ ዘንድ ፥ ፍቅራችኹ ፡ በዕውቀትና ፡ በማስተዋል ፡ ኹሉ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ እያደገ ፡ እንዲበዛ ፡ ይህን ፡ እጸልያለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 12 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ የደረሰብኝ ፡ በእውነት ፡ ወንጌልን ፡ ለማስፋት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እወዳለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 13 ፤ ስለዚህም ፡ እስራቴ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲኾን ፡ በንጉሥ ፡ ዘበኞች ፡ ኹሉና ፡ በሌላዎች ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ተገልጧል ፥

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 14 ፤ በጌታም ፡ ካሉት ፡ ወንድሞች ፡ የሚበዙት ፡ ስለ ፡ እስራቴ ፡ ታምነው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንዲነግሩ ፡ ያለፍርሀት ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ይደፍራሉ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ አንዳንዶች ፡ ከቅንአትና ፡ ከክርክር ፡ እንኳ ፡ ሌላዎች ፡ ግን ፡ ከበጎ ፡ ፈቃድ ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስን ፡ ይሰብኩታል ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ እነዚህ ፡ ወንጌልን ፡ መመከቻ ፡ ለማድረግ ፡ እንደ ፡ ተሾምኹ ፡ ዐውቀው ፡ በፍቅር ፡ ይሰብካሉ ፥

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ እነዚያ ፡ ግን ፡ በእስራቴ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ ሊያመጡብኝ ፡ መስሏቸው ፥ ለወገናቸው ፡ የሚጠቅም ፡ ፈልገው ፡ በቅን ፡ ዐሳብ ፡ ሳይኾኑ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ያወራሉ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ምን ፡ አለ ፧ ቢኾንም ፡ በሹሉ ፡ ጐዳና ፡ በማመካኘት ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በቅንነት ፡ ቢኾን ፡ ክርስቶስ ፡ ይሰበካል ፡ ስለዚህም ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ ወደ ፡ ፊትም ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ይህ ፡ በጸሎታችኹና ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ መሰጠት ፡ ለመዳኔ ፡ እንዲኾንልኝ ፡ ዐውቃለኹና ፥

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ ይህ ፡ ናፍቆቴ ፡ ተስፋዬም ፡ ነውና ፤ ባንድ ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ አላፍርም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በሕይወት ፡ ብኖር ፡ ወይም ፡ ብሞት ፥ ክርስቶስ ፡ በግልጥነት ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ወትሮው ፡ አኹን ፡ ደግሞ ፡ በሥጋዬ ፡ ይከብራል ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ለእኔ ፡ ሕይወት ፡ ክርስቶስ ፥ ሞትም ፡ ጥቅም ፡ ነውና ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሥጋ ፡ መኖር ፡ ለእኔ ፡ የሥራ ፡ ፍሬ ፡ ቢኾን ፥ ምን ፡ እንድመርጥ ፡ አላስታውቅም ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ በእነዚህም ፡ በኹለቱ ፡ እጨነቃለኹ ፤ ልኼድ ፡ ከክርስቶስም ፡ ጋራ ፡ ልኖር ፡ እናፍቃለኹ ፥ ከሹሉ ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ የሚሻል ፡ ነውና ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በሥጋ ፡ መኖሬ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈልግ ፡ ነው ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 25-26 ፤ ይህንም ፡ ተረድቼ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስለ ፡ መኾኔ ፥ በእኔ ፡ መመካታችኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ይበዛ ፡ ዘንድ ፥ በእምነት ፡ ታድጉና ፡ ደስ ፡ ይላችኹ ፡ ዘንድ ፡ እንድኖር ፡ ከሹላችኹም ፡ ጋራ ፡ እንድቈይ ፡ ዐውቃለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ይኹን ፡ እንጂ ፥ መጥቼ ፡ ባያችኹ ፡ ወይም ፡ ብርቅ ፥ ባንድ ፡ ልብ ፡ ስለወንጌል ፡ ሃይማኖት ፡ ዐብራችኹ ፡ እየተጋደላችኹ ፥ ባንድ ፡ መንፈስ ፡ እንድትቆሙ ፡ ስለ ፡ ኑሯችኹ ፡ እሰማ ፡ ዘንድ ፥ ለክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ እንደሚገባ ፡ ኑሩ ።

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ በአንድም ፡ ነገር ፡ እንኳ ፡ በተቃዋሚዎች ፡ አትደንግጡ ፤ ይህም ፡ ለእነርሱ ፡ የጥፋት ፥ ለእናንተ ፡ ግን ፡ የመዳን ፡ ምልክት ፡ ነው ፥ ይህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ይህ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ተሰጥቷችኋልና ፤ ስለርሱ ፡ መከራ ፡ ደግሞ ፡ ልትቀበሉ ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ልታምኑ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፤

ፊልጵ. ፡ 1 ፡ 30 ፤ በእኔ ፡ ያያችኹት ፡ አኹንም ፡ በእኔ ፡ እንዳለ ፡ የምትሰሙት ፥ ያው ፡ መጋደል ፡ ደርሶባችኋልና ።

ፊልጵስዩስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በክርስቶስም ፡ አንዳች ፡ ምክር ፡ ቢኾን ፥ የፍቅር ፡ መጽናናት ፡ ቢኾን ፥ የመንፈስ ፡ ኅብረት ፡ ቢኾን ፥ ምሕረትና ፡ ርኅራኄ ፡ ቢኾኑ ፥ ደስታዬን ፡ ፈጽሙልኝ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ባንድ ፡ ዐሳብ ፡ ተስማሙ ፥ አንድ ፡ ፍቅር ፡ አንድም ፡ ልብ ፡ አንድም ፡ ዐሳብ ፡ ይኹንላችኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ለወገኔ ፡ ይጠቅማል ፡ በማለት ፡ ወይም ፡ በከንቱ ፡ ውዳሴ ፡ ምክንያት ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ አታድርጉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዱ ፡ ባልንጀራው ፡ ከራሱ ፡ ይልቅ ፡ እንዲሻል ፡ በትሕትና ፡ ይቍጠር ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እያንዳንዱ ፡ ለራሱ ፡ የሚጠቅመውን ፡ አይመልከት ፥ ለባልንጀራው ፡ ደግሞ ፡ እንጂ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የነበረ ፡ ይህ ፡ ዐሳብ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ ይኹን ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ርሱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ ሲኖር ፡ ሳለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ መተካከልን ፡ መቀማት ፡

እንደሚገባ ፡ ነገር ፡ አልቈጠረውም ፥

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የባሪያን ፡ መልክ ፡ ይዞ ፡ በሰውም ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፡ ራሱን ፡ ባዶ ፡ አደረገ ፥

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በምስሉም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ተገኝቶ ፡ ራሱን ፡ አዋረደ ፥ ለሞትም ፡ ይኸውም ፡ የመስቀል ፡ ሞት ፡ እንኳ ፡ የታዘዘ ፡ ኾነ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያለልክ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረገው ፥ ከስምም ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ስም ፡ ሰጠው ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ይህም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ከምድርም ፡ በታች ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ ይንበረከኩ ፡ ዘንድ ፥

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ምላስም ፡ ኹሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ክብር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይመሰክር ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ወዳጆቼ ፡ ሆይ ፥ ኹልጊዜ ፡ እንደ ፡ ታዘዛችኹ ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ በመኖሬ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ይልቁን ፡ አኹን ፡ ስርቅ ፥ በፍርሀትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ የራሳችኹን ፡ መዳን ፡ ፈጽሙ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ስለ ፡ በጎ ፡ ፈቃዱ ፡ መፈለግንም ፡ ማድረግንም ፡ በእናንተ ፡ የሚሠራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 14-15 ፤ በመጥፎና ፡ በጠማማ ፡ ትውልድ ፡ መካከል ፡ ያለነቀፋ ፡ የዋሆችም ፡ ነውርም ፡ የሌለባቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ እንድትኾኑ ፡ ሳታንጐራጉሩ ፡ ክፉም ፡ ሳታስቡ ፡ ኹሉን ፡ አድርጉ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ በእነርሱም ፡ መካከል ፡ የሕይወትን ፡ ቃል ፡ እያቀረባችኹ ፡ በዓለም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ትታያላችኹ ፥ ስለዚህም ፡ በከንቱ ፡ እንዳልሮጥኹ ፡ በከንቱም ፡ እንዳልደከምኹ ፡ በክርስቶስ ፡ ቀን ፡ የምመካበት ፡ ይኾንልኛል ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእምነታችኹ ፡ መሥዋዕትና ፡ አገልግሎት ፡ ተጨምሬ ፡ ሕይወቴ ፡ እንኳ ፡ ቢፈስ ፥ ደስ ፡ ብሎኛል ፤ ከኹላችኹም ፡ ጋራ ፡ ዐብሬ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ ዐብራችኹ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኑሯችኹን ፡ ሳውቅ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ ፈጥኜ ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ልልክላችኹ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ እንደ ፡ ርሱ ፡ ያለ ፥ ስለ ፡ ኑሯችኹ ፡ በቅንነት ፡ የሚጨነቅ ፥ ማንም ፡ የለኝምና ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ኹሉ ፡ የራሳቸውን ፡ ይፈልጋሉና ፥ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስን ፡ አይደለም ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልጅ ፡ ለአባቱ ፡ እንደሚያገለግል ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ ለወንጌል ፡ እንደ ፡ አገለገለ ፡ መፈተኑን ፡ ታውቃላችኹ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ እንደምኾን ፡ ባየኹ ፡ ጊዜ ፥ ርሱን ፡ ቶሎ ፡ እንድልክ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ራሴ ፡ ደግሞ ፡ ግን ፡ ፈጥኜ ፡ እንድመጣ ፡ በጌታ ፡ ታምኛለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሜንና ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ሠራተኛ ፡ ወታደርም ፡ የሚኾነውን ፥ የእናንተ ፡ ግን ፡ መልእክተኛ ፡ የኾነውና ፡ የሚያስፈልገኝን ፡ የሚያገለግለውን ፡ አፍሮዲጡን ፡ እንድልክላችኹ ፡ በግድ ፡ ዐስባለኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ዅላችኹን ፡ ይናፍቃልና ፥ እንደ ፡ ታመመም ፡ ስለ ፡ ሰማችኹ ፡ ይተክዛል ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 27 ፤ በእውነት ፡ ታሞ ፡ ለሞት ፡ እንኳ ፡ ቀርቦ ፡ ነበርና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፡ ማረው ፥ ሐዘን ፡ በሐዘን ፡ ላይ ፡ እንዳይጨመርብኝ ፡ ለእኔ ፡ ደግሞ ፡ እንጂ ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ስታዩት ፡ ደስ ፡ እንዲላችኹ ፡ ለኔም ፡ ሐዘኔ ፡ እንዲቃለል ፡ በብዙ ፡ ፍጥነት ፡ እልከዋለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ እንግዲህ ፡ በሙሉ ፡ ደስታ ፡ በጌታ ፡ ተቀበሉት ፥ ርሱን ፡ የሚመስሉትንም ፡ አክብሯቸው ፤

ፊልጵ. ፡ 2 ፡ 30 ፤ በእኔ ፡ ዘንድ ፡ ካላችኹ ፡ አገልግሎት ፡ እናንተ ፡ ስለሌላችኹ ፡ የጐደለኝን ፡ እንዲፈጽም ፥ በነፍሱ ፡ ተወራርዶ ፡ ከጌታ ፡ ሥራ ፡ የተነሣ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ቀርቧልና ።

ፊልጵስዩስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ በቀረውስ ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በጌታ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ። ስለ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ መልሼ ፡ ልጽፍላችኹ ፡ እኔን ፡ አይታክተኝም ፡ ለእናንተ ፡ ግን ፡ ደኅና ፡ ነው ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ከውሻዎች ፡ ተጠበቁ ፥ ከክፉዎችም ፡ ሠራተኞች ፡ ተጠበቁ ፥ ከሐሰተኛም ፡ መገረዝ ፡ ተጠበቁ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ እኛ ፡ በመንፈስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የምናመልክ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስም ፡ የምንመካ ፡ በሥጋም ፡ የማንታመን ፡ እኛ ፡ የተገረዝን ፡ ነንና ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በሥጋ ፡ ደግሞ ፡ የምታመንበት ፡ አለኝ ። ሌላ ፡ ሰው ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፡ በሥጋ ፡ የሚታመንበት ፡ እንዳለው ፡ ቢመስለው ፥ እኔ ፡ እበልጠዋለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ በስምንተኛው ፡ ቀን ፡ የተገረዝኹ ፥ ከእስራኤል ፡ ትውልድ ፥ ከብንያም ፡ ወገን ፥ ከዕብራውያን ፡ ዕብራዊ ፡ ነኝ ፤ ስለ ፡ ሕግ ፡ ብትጠይቁ ፥ ፈሪሳዊ ፡ ነበርኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ ስለ ፡ ቅንአት ፡ ብትጠይቁ ፥ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አሳዳጅ ፡ ነበርኹ ፤ በሕግ ፡ ስለሚገኝ ፡ ጽድቅ ፡ ብትጠይቁ ፥ ያለነቀፋ ፡ ነበርኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለእኔ ፡ ረብ ፡ የነበረውን ፡ ዅሉ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ጕዳት ፡ ቈጥሬዋለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 8-9 ፤ አዎን ፥ በእውነት ፡ ከዅሉ ፡ ይልቅ ፡ ስለሚበልጥ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ስለ ፡ ጌታዬ ፡ ዕውቀት ፡ ነገር ፡ ዅሉ ፡ ጕዳት ፡ እንዲኾን ፡ እቈጥራለኹ ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ ዅሉን ፡ ተጐዳኹ ፥ ክርስቶስንም ፡ አገኝ ፡ ዘንድ ፥ በክርስቶስም ፡ በማመን ፡ ያለው ፡ ጽድቅ ፡ ማለት ፡ በእምነት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ጽድቅ ፡ እንጂ ፡ ከሕግ ፡ ለእኔ ፡ ያለው ፡ ጽድቅ ፡ ሳይኾንልኝ ፥ በርሱ ፡ እገኝ ፡ ዘንድ ፡ ዅሉን ፡ እንደ ፡ ጕድፍ ፡ እቈጥራለኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 10-11 ፤ ርሱንና ፡ የትንሣኤውን ፡ ኀይል ፡ እንዳውቅ ፥ በመከራውም ፡ እንድካፈል ፥ ወደሙታንም ፡ ትንሣኤ ፡ ልደርስ ፡ ቢኾንልኝ ፥ በሞቱ ፡ እንድመስለው ፡ እመኛለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ አኹን ፡ እንዳገኘኹ ፡ ወይም ፡ አኹን ፡ ፍጹም ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ርሱ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የተያዝኹበትን ፡ ያን ፡ ደግሞ ፡ እይዛለኹ ፡ ብዬ ፡ እፈጥናለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔ ፡ ገና ፡ እንዳልያዝኹት ፡ እቈጥራለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ነገር ፡ አደርጋለኹ ፤ በኋላዬ ፡ ያለውን ፡ እየረሳኹ ፡ በፊቴ ፡ ያለውን ፡ ለመያዝ ፡ እዘረጋለኹ ፥

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጥራት ፡ ዋጋ ፡ እንዳገኝ ፡ ምልክትን ፡ እፈጥናለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ፍጹማን ፡ የኾን ፡ ኹላችን ፡ ይህን ፡ እናስብ ፤ በአንዳች ፡ ነገርም ፡ ልዩ ፡ ዐሳብ ፡ ቢኖራችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ ይገልጥላችኋል ፤

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ኾኖም ፡ በደረስንበት ፡ በዚያ ፡ እንመላለስ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እኔን ፡ የምትመስሉ ፡ ኹኑ ፥ እኛም ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ እንደምንኾንላችኹ ፥ እንዲሁ ፡ የሚመላለሱትን ፡ ተመልከቱ ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ብዙዎች ፡ ለክርስቶስ ፡ መስቀል ፡ ጠላቶቹ ፡ ኾነው ፡ ይመላለሳሉና ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አልኋችኹ ፥ አኹንም ፡ እንኳ ፡ እያለቀስኹ ፡ እላለኹ ፦

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ መጨረሻቸው ፡ ጥፋት ፡ ነው ፥ ሆዳቸው ፡ አምላካቸው ፡ ነው ፥ ክብራቸው ፡ በነውራቸው ፡ ነው ፥ ዐሳባቸው ፡ ምድራዊ ፡ ነው ።

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ እኛ ፡ አገራችን ፡ በሰማይ ፡ ነውና ፥ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ የሚመጣ ፡ መድኀኒትን ፡ ርሱንም ፡ ጌታን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ እንጠባበቃለን ፤

ፊልጵ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ ርሱም ፡ ኹሉን ፡ እንኳ ፡ ለራሱ ፡ ሊያስገዛ ፡ እንደሚችልበት ፡ አሠራር ፥ ክቡር ፡ ሥጋውን ፡ እንዲመስል ፡ የተዋረደውን ፡ ሥጋችንን ፡ ይለውጣል ።

ፊልጵስዩስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፥ የምወዳችኹና ፡ የምናፍቃችኹ ፥ ደስታዬና ፡ አክሊሌ ፡ የምትኾኑ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ እንዲሁ ፡ በጌታ ፡ ቁሙ ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፦

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ባንድ ፡ ዐሳብ ፡ በጌታ ፡ እንዲስማሙ ፡ ኤዎድያንን ፡ እመክራለኹ ፡ ሲንጤኪንንም ፡ እመክራለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ በሥራዬ ፡ ዐብረኽ ፡ የተጠመድኽ ፡ እውነተኛ ፡ ሆይ ፥ እንድታግዛቸው ፡ እለምንኻለኹ ፤ ስሞቻቸው ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ከቀሌምንጦስና ፡ ደግሞ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ከሠሩት ፡ ከሌላዎቹ ፡ ጋራ ፡ በወንጌል ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ ተጋድለዋልና ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ዘልጊዜ ፡ በጌታ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ ደግሜ ፡ እላለኹ ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ገርነታችኹ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ይታወቅ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ጌታ ፡ ቅርብ ፡ ነው ። በነገር ፡ ኹሉ ፡ በጸሎትና ፡ በምልጃ ፡ ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ልመናችኹን ፡ አስታውቁ ፡ እንጂ ፡ በአንዳች ፡ አትጨነቁ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ አእምሮንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያልፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡ ልባችኹንና ፡ ዐሳባችኹን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ይጠብቃል ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ በቀረውስ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እውነተኛ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ጭምትነት ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ጽድቅ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ንጹሕ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ ፍቅር ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ መልካም ፡ ወሬ ፡ ያለበትን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፥ በጎነት ፡ ቢኾን ፡ ምስጋናም ፡ ቢኾን ፥ እነዚህን ፡ ዐስቡ ፤

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ከእኔ ፡ የተማራችኹትንና ፡ የተቀበላችኹትን ፡ የሰማችኹትንም ፡ ያያችኹትንም ፡ እነዚህን ፡ አድርጉ ፤ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኾናል ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አኹን ፡ ከጊዜ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ልታስቡ ፡ ስለ ፡

ዝመራችኹ ፥ በጌታ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ ጊዜ ፡ ዐጣችኹ ፡ እንጂ ፥ ማሰብስ ፡ ታስቡ ፡ ነበር ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ይህን ፡ ስል ፡ ስለ ፡ ጕድለት ፡ አልልም ፤ የምኖርበት ፡ ኑሮ ፡ ይበቃኛል ፡ ማለትን ፡ ተምሬያለኹና ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ መዋረድንም ፡ ዐውቃለኹ ፡ መብዛትንም ፡ ዐውቃለኹ ፤ በያንዳንዱ ፡ ነገር ፡ በነገርም ፡ ኹሉ ፡ መጥገብንና ፡ መራብንም ፡ መብዛትንና ፡ መጕደልን ፡ ተምሬያለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ኀይልን ፡ በሚሰጠኝ ፡ በክርስቶስ ፡ ኹሉን ፡ እችላለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ኾኖም ፡ በመከራዬ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተካፈላችኹ ፡ መልካም ፡ አደረጋችኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ የፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡ ሆይ ፥ ወንጌል ፡ በመዠመሪያ ፡ ሲሰበክ ፥ ከመቄዶንያ ፡ በወጣኹ ፡ ጊዜ ፥ ከእናንተ ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመስጠትና ፡ በመቀበል ፡ ስሌት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ እንዳልተካፈለች ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ታውቃላችኹ ፤

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ በተሰሎንቄ ፡ እንኳ ፡ ሳለኹ ፥ አንድ ፡ ጊዜና ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ያስፈለገኝን ፡ ሰዳችኹልኝ ፡ ነበርና ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ በስሌታችኹ ፡ የሚበዛውን ፡ ፍሬ ፡ እንጂ ፡ ስጦታውን ፡ ፈላጊ ፡ አይደለኹም ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ አለኝ ፡ ይበዛልኝማል ፤ የመዐዛ ፡ ሽታና ፡ የተወደደ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚኾነውን ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ ስጦታችኹን ፡ ከአፍሮዲጡ ፡ ተቀብዬ ፡ ተሞልቻለኹ ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 19 ፤ አምላኬም ፡ እንደ ፡ ባለጠግነቱ ፡ መጠን ፡ በክብር ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ የሚያስፈልጋችኹን ፡ ኹሉ ፡ ይሞላባችኋል ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 20 ፤ ለአምላካችንና ፡ ለአባታችንም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 21 ፤ ለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡ ። ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉቱ ፡ ወንድሞች ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 22 ፤ ቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ይልቁንም ፡ ከቄሳር ፡ ቤት ፡ የኾኑቱ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ፊልጵ. ፡ 4 ፡ 23 ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከመንፈሳችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የመዠመሪያዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደቆላስይስ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ቆላስይስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ቆላ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ወንድሙ ፥

ቆላ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ በቆላስይስ ፡ ለሚኖሩ ፡ ቅዱሳንና ፡ በክርስቶስ ፡ ለታመኑ ፡ ወንድሞች ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ይኹን ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 3-5 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ ስንጸልይ ፥ በሰማይ ፡ ከተዘጋጀላችኹ ፡ ተስፋ ፡ የተነሣ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ስለ ፡ እምነታችኹ ፡ ለቅዱሳንም ፡ ኹሉ ፡ ስላላችኹ ፡ ፍቅር ፡ ሰምተን ፥ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ አባት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ዘልጊዜ ፡ እናመሰግናለን ፤ ስለዚህም ፡ ተስፋ ፡ በወንጌል ፡ እውነት ፡ ቃል ፡ አስቀድማችኹ ፡ ሰማችኹ ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ይህም ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ እንዳለ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ደርሷል ፥ የእግዚአብሔርንም ፡ ጸጋ ፡ በእውነት ፡ ከሰማችኹበትና ፡ ካወቃችኹበት ፡ ቀን ፡ ዠምሮ ፥ በእናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዳለ ፡ እንዲህ ፡ በዓለም ፡ ፍሬ ፡ ያፈራል ፥ ያድግማል ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ከተወደደ ፡ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ባሪያ ፡ ከኾነው ፡ ከኤጳፍራ ፡ እንዲህ ፡ ተማራችኹ ፥ ርሱም ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ታማኝ ፡ የክርስቶስ ፡ አገልጋይ ፡ ነው ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ደግሞም ፡ በመንፈስ ፡ ስለሚኾን ፡ ስለ ፡ ፍቅራችኹ ፡ አስታወቀን ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ስለዚሁ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ከሰማንበት ፡ ቀን ፡ ዠምረን ፡ የፈቃዱ ፡ ዕውቀት ፡ መንፈሳዊ ፡ ጥበብንና ፡ አእምሮን ፡ ኹሉ ፡ እንዲሞላባችኹ ፡ እየለመንን ፥ ስለ ፡ እናንተ ፡ ጸሎትን ፡ አልተውንም ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 10-11 ፤ በበጎ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ፍሬ ፡ እያፈራችኹ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ዕውቀት ፡ እያደጋችኹ ፥

ቆላ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ከደስታም ፡ ጋራ ፡ በኹሉ ፡ ለመጽናትና ፡ ለመታገሥ ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ጕልበት ፡ መጠን ፡ በኀይል ፡ ኹሉ ፡ እየበረታችኹ ፥ በቅዱሳንም ፡ ርስት ፡ በብርሃን ፡ እንድንካፈል ፡ ያበቃንን ፡ አብን ፡ እያመሰገናችኹ ፥ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ልታሠኙ ፡ ለጌታ ፡ እንደሚገባ ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ እንለምናለን ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 13-14 ፤ ርሱ ፡ ከጨለማ ፡ ሥልጣን ፡ አዳነን ፥ ቤዛነቱንም ፡ ርሱንም ፡ የኀጢአትን ፡ ስርየት ፡ ወዳገኘንበት ፡ ወደፍቅሩ ፡ ልጅ ፡ መንግሥት ፡ አፈለሰን ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 15-16 ፤ ርሱም ፡ የማይታይ ፡ አምላክ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ። የሚታዩትና ፡ የማይታዩትም ፥ ዙፋናት ፡ ቢኾኑ ፡ ወይም ፡ ጌትነት ፡ ወይም ፡ አለቅነት ፡ ወይም ፡ ሥልጣናት ፥ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ተፈጥረዋልና ፥ ከፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ በፊት ፡ በዙር ፡ ነው ። ኹሉ ፡ በርሱና ፡ ለርሱ ፡ ተፈጥሯል ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ ርሱም ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ ነው ፥ ኹሉም ፡ በርሱ ፡ ተጋጥሟል ።

ቆላ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ ርሱም ፡ የአካሉ ፡ ማለት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስ ፡ ነው ። ርሱም ፡ በኹሉ ፡ ፊተኛ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ መዠመሪያ ፡ ከሙታንም ፡ በዙር ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 19-20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ሙላቱ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ እንዲኖር ፥ በርሱም ፡ በኩል ፡ በመስቀሉ ፡ ደም ፡ ሰላም ፡ አድርጎ ፡ በምድር ፡ ወይም ፡ በሰማያት ፡ ያሉትን ፡ ኹሉ ፡ ለራሱ ፡ እንዲያስታርቅ ፡ ፈቅዷልና ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 21-22 ፤ እናንተንም ፡ ነውርና ፡ ነቀፋ ፡ የሌላችኹና ፡ ቅዱሳን ፡ አድርጎ ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ያቀርባችኹ ፡ ዘንድ ፥ በፊት ፡ የተለያችኹትን ፡ ክፉ ፡ ሥራችኹንም ፡ በማድረግ ፡ በዐሳባችኹ ፡ ጠላቶች ፡ የነበራችኹትን ፡ አኹን ፡ በሥጋው ፡ ሰውነት ፡ በሞቱ ፡ በኩል ፡ አስታረቃችኹ ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ይህም ፥ ተመሥርታችኹና ፡ ተደላድላችኹ ፡ ከሰማችኹትም ፡ ከወንጌል ፡ ተስፋ ፡ ሳትናወጡ ፥ በሃይማኖት ፡ ጸንታችኹ ፡ ብትኖሩ ፡ ይኾናል ። ያም ፡ ወንጌል ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ባለው ፡ ፍጥረት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ የተሰበከ ፡ ነው ፥ እኔም ፡ ጳውሎስ ፡ የርሱ ፡ አገልጋይ ፡ ኾንኹ ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ አኹን ፡ በመከራዬ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፥ ስለ ፡ አካሉም ፡ ማለት ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሥጋዬ ፡ በክርስቶስ ፡ መከራ ፡ የጐደለውን ፡ እፈጽማለኹ ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ እንደተሰጠኝ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ መጋቢነት ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ፈጽሜ ፡ እንድሰብክ ፡ እኔ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋይ ፡ ኾንኹ ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ ይህም ፡ ቃል ፡ ከዘለዓለምና ፡ ከትውልዶች ፡ ዝምሮ ፡ ተሰውሮ ፡ የነበረ ፡ ምስጢር ፡ ነው ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ለቅዱሳኑ ፡ ተገልጧል ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ለእነርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ የዚህ ፡ ምስጢር ፡ ክብር ፡ ባለጠግነት ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ሊያስታውቅ ፡ ወደደ ፥ ምስጢሩም ፡ የክብር ፡ ተስፋ ፡ ያለው ፡ ክርስቶስ ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ መኾኑ ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 28 ፤ እኛም ፡ በክርስቶስ ፡ ፍጹም ፡ የሚኾን ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ እናቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ እየገሠጽን ፡ ሰውንም ፡ ኹሉ ፡ በጥበብ ፡ ኹሉ ፡ እያስተማርን ፡ የምንሰብከው ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 1 ፡ 29 ፤ ለዚህም ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፥ በእኔ ፡ በኀይል ፡ እንደሚሠራ ፡ እንደ ፡ አሠራሩ ፡ እየተጋደልኹ ፥ እደክማለኹ ።

ቆላስይስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ስለ ፡ እናንተና ፡ በሎዶቅያ ፡ ስላሉት ፡ ፊቴንም ፡ በሥጋ ፡ ስላላዩት ፡ ኹሉ ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ መጋደል ፡ እንዳለኝ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለኹና ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ልባቸው ፡ እንዲጸናና ፥ በፍቅርም ፡ ተባብረው ፡ በማስተዋል ፡ ወደሚገኝበት ፡ ወደመረዳት ፡ ባለጠግነት ፡ ኹሉ ፡ እንዲደርሱ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ምስጢር ፡ ርሱንም ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲያውቁ ፡ እጋደላለኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ የተሰወረ ፡ የጥበብና ፡ የዕውቀት ፡ መዝገብ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ነውና ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ማንም ፡ በሚያባብል ፡ ቃል ፡ እንዳያስታችኹ ፡ ይህን ፡ እላለኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ በሥጋ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብርቅ ፥ በመንፈስ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፥ ሥርዐታችኹንም ፡ በክርስቶስም ፡ ያለውን ፡ የእምነታችኹን ፡ ጽናት ፡ እያየኹ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እንግዲህ ፡ ጌታን ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስን ፡ እንደ ፡ ተቀበላችኹት ፡ በርሱ ፡ ተመላለሱ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ሥር ፡ ሰዳችኹ ፡ በርሱ ፡ ታነጹ ፥ እንደ ፡ ተማራችኹም ፡ በሃይማኖት ፡ ጽኑ ፥ ምስጋናም ፡ ይብዛላችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ እንደክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ሳይኾን ፥ እንደ ፡ ሰው ፡ ወግና ፡ እንደ ፡ ዓለማዊ ፡ እንደ ፡ መዐመሪያ ፡ ትምህርት ፡ ባለ ፡ በፍልስፍና ፡ በከንቱም ፡ መታለል ፡ ማንም ፡ እንዳይማርካችኹ ፡ ተጠበቁ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ በርሱ ፡ የመለኮት ፡ ሙላት ፡ ኹሉ ፡ በሰውነት ፡ ተገልጦ ፡ ይኖራልና ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ለአለቅነትና ፡ ለሥልጣንም ፡ ኹሉ ፡ ራስ ፡ በኾነ ፡ በርሱ ፡ ኾናችኹ ፡ ተሞልታችኋል ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ የሥጋንም ፡ ሰውነት ፡ በመገፈፍ ፥ በክርስቶስ ፡ መገረዝ ፥ በእጅ ፡ ባልተደረገ ፡ መገረዝ ፡ በርሱ ፡ ኾናችኹ ፡ ደግሞ ፡ ተገረዛችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በጥምቀትም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀብራችኹ ፥ በጥምቀት ፡ ደግሞ ፥ ከሙታን ፡ ባስነሣው ፡ በእግዚአብሔር ፡ አሠራር ፡ በማመናችኹ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተነሣችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ እናንተም ፡ በበደላችኹና ፡ ሥጋችኹን ፡ ባለመገረዝ ፡ ሙታን ፡ በኾናችኹ ፡ ጊዜ ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሕይወትን ፡ ሰጣችኹ ። በደላችኹን ፡ ኹሉ ፡ ይቅር ፡ አላችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ በእኛ ፡ ላይ ፡ የነበረውን ፡ የሚቃወመንንም ፡ በትእዛዛት ፡ የተጻፈውን ፡ የዕዳ ፡ ጽሕፈት ፡ ደመሰሰው ። ርሱንም ፡ በመስቀል ፡ ጠርቆ ፡ ከመንገድ ፡ አስወግዶታል ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ አለቅነትንና ፡ ሥልጣናትን ፡ ገፎ ፥ ድል ፡ በመንሣት ፡ በርሱ ፡ እያዞራቸው ፡ በግልጥ ፡ አሳያቸው ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ በመብል ፡ ወይም ፡ በመጠጥ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ በዓል ፡ ወይም ፡ ስለወር ፡ መባቻ ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ሰንበት ፡ ማንም ፡ አይፍረድባችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እነዚህ ፡ ሊመጡ ፡ ያሉት ፡ ነገሮች ፡ ጥላ ፡ ናቸውና ፥ አካሉ ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ትሕትናንና ፡ የመላእክትን ፡ አምልኮ ፡ እየወደደ ፥ ባላየውም ፡ ያለፈቃድ ፡ እየገባ ፥ በሥጋዊም ፡ አእምሮ ፡ በከንቱ ፡ እየታበየ ፡ ማንም ፡ አይፍረድባችኹ ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ራስ ፡ ወደሚኾነው ፡ አይጠጋም ፥ ከርሱም ፡ አካል ፡ ኹሉ ፡ በኀርማትና ፡ በማሰሪያ ፡ ምግብን ፡ እየተቀበለ ፡ እየተጋጠመም ፥ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጠው ፡ ማደግ ፡ ያድጋል ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 20-21 ፤ ከዓለማዊ ፡ ከመዐመሪያ ፡ ትምህርት ፡ ርቃችኹ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከሞታችኹ ፥

ቆላ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እንደ ፡ ሰው ፡ ሥርዐትና ፡ ትምህርት ። አትያዝ ፥ አትቅመስ ፥ አትንካ ፡ ለሚሉት ፡ ትእዛዛት ፡ በዓለም ፡ እንደምትኖሩ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትገዛላችኹ ፧ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ በመደረግ ፡ ሊጠፉ ፡ ተወስነዋልና ።

ቆላ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ይህ ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ፈቃድኽ ፡ በማምለክና ፡ በትሕትና ፡ ሥጋንም ፡ በመጨቈን ፡ ጥበብ ፡ ያለው ፡ ይመስላል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ሥጋ ፡ ያለልክ ፡ እንዳይጠግብ ፡ ለመከልከል ፡ ምንም ፡ አይጠቅምም ።

ቆላስይስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከተነሣችኹ ፥ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጦ ፡ ባለበት ፡ በላይ ፡ ያለውን ፡ ሹ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ በላይ ፡ ያለውን ፡ ዐስቡ ፡ እንጂ ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ አይደለም ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ሞታችኋልና ፥ ሕይወታችኹም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ተሰውሯልና ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ሕይወታችኹ ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፥ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡

ጋራ ፡ በክብር ፡ ትገለጣላችኹ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እንግዲህ ፡ በምድር ፡ ያሉቱን ፡ ብልቶቻችኹን ፡ ግደሉ ፥ እነዚህም ፡ ዝሙትና ፡ ርኵሰት ፡ ፍትወትም ፡ ክፉ ፡ ምኞትም ፡ ጣዖትንም ፡ ማምለክ ፡ የኾነ ፡ መጐምጐት ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ በእነዚህም ፡ ጠንቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በማይታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ላይ ፡ ይመጣል ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ እናንተም ፡ ደግሞ ፡ ትኖሩባቸው ፡ በነበራችኹ ፡ ጊዜ ፥ በፊት ፡ በእነዚህ ፡ ተመላለሳችኹ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ቍጣንና ፡ ንዴትን ፡ ክፋትንም ፥ ከአፋችኹም ፡ ስድብን ፡ የሚያሳፍርንም ፡ ንግግር ፡ እነዚህን ፡ ኹሉ ፡ አስወግዱ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ውሸት ፡ አትነጋገሩ ፥ አሮጌውን ፡ ሰው ፡ ከሥራው ፡ ጋራ ፡ ገፈችኹታልና ፥

ቆላ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ የፈጠረውንም ፡ ምሳሌ ፡ እንዲመስል ፡ ዕውቀትን ፡ ለማግኘት ፡ የሚታደሰውን ፡ ዐዲሱን ፡ ሰው ፡ ለብሳችኹታል ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ በዚያም ፡ የግሪክ ፡ ሰው ፡ አይሁዳዊም ፡ የተገረዘም ፡ ያልተገረዘም ፡ አረማዊም ፡ እስኩቴስም ፡ ባሪያም ፡ ጨዋ ፡ ሰውም ፡ መኾን ፡ አልተቻለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ክርስቶስ ፡ ኹሉ ፡ ነው ፥ በኹሉም ፡ ነው ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ እንግዲህ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ምርጦች ፡ ቅዱሳን ፡ ኾናችኹ ፡ የተወደዳችኹም ፡ ኾናችኹ ፥ ምሕረትን ፥ ርኅራኄን ፥ ቸርነትን ፥ ትሕትናን ፥ የዋህነትን ፥ ትዕግሥትን ፡ ልበሱ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ትዕግሥትን ፡ አድርጉ ፥ ማንም ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ የሚነቅፈው ፡ ነገር ፡ ካለው ፥ ይቅር ፡ ተባባሉ ። ክርስቶስ ፡ ይቅር ፡ እንዳላችኹ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ አድርጉ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ በእነዚህም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ የፍጻሜ ፡ ማሰሪያ ፡ የኾነውን ፡ ፍቅርን ፡ ልበሱት ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ባንድ ፡ አካልም ፡ የተጠራችኹለት ፡ ደግሞ ፡ የክርስቶስ ፡ ሰላም ፡ በልባችኹ ፡ ይግዛ ። የምታመሰግኑም ፡ ኹኑ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በሙላት ፡ ይኑርባችኹ ። በጥበብ ፡ ኹሉ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አስተምሩና ፡ ገሥጹ ። በመዝሙርና ፡ በዝማሬ ፡ በመንፈሳዊም ፡ ቅኔ ፡ በጸጋው ፡ በልባችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘምሩ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ አብን ፡ በርሱ ፡ እያመሰገናችኹ ፥ በቃል ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በሥራ ፡ የምታደርጉትን ፡ ኹሉ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ስም ፡ አድርጉት ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ሚስቶች ፡ ሆይ ፥ በጌታ ፡ እንደሚገባ ፡ ለባሎቻችኹ ፡ ተገዙ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ባሎች ፡ ሆይ ፥ ሚስቶቻችኹን ፡ ውደዱ ፡ መራራም ፡ አትኹኑባቸው ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ለጌታ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ ነውና ፥ በኹሉ ፡ ለወላጆቻችኹ ፡ ታዘዙ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ልባቸው ፡ እንዳይዝል ፡ ልጆቻችኹን ፡ አታበሳጫቸው ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ ባሪያዎች ፡ ሆይ ፥ በቅን ፡ ልብ ፡ ጌታን ፡ እየፈራችኹ ፡ እንጂ ፥ ለሰው ፡ ደስ ፡ እንደምታሠኙ ፡ ለታይታ ፡ የምትገዙ ፡ ሳትኾኑ ፥ በሥጋ ፡ ጌታዎቻችኹ ፡ ለኾኑ ፡ በኹሉ ፡ ታዘዙ ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 23 ፤ ለሰው ፡ ሳይኾን ፡ ለጌታ ፡ እንደምታደርጉ ፥ የምታደርጉትን ፡ ኹሉ ፡ በትጋት ፡ አድርጉት ፥

ቆላ. ፡ 3 ፡ 24 ፤ ከጌታ ፡ የርስትን ፡ ብድራት ፡ እንድትቀበሉ ፡ ታውቃላችኹና ። የምታገለግሉት ፡ ጌታ ፡ ክርስቶስ ፡ ነውና ።

ቆላ. ፡ 3 ፡ 25 ፤ የሚበድልም ፡ የበደለውን ፡ በብድራት ፡ ይቀበላል ፥ ለሰው ፡ ፊትም ፡ አድልዎ ፡ የለም ።

ቆላስይስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ጌታዎች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በሰማይ ፡ ጌታ ፡ እንዳላችኹ ፡ ታውቃላችኹና ፡ ለባሪያዎቻችኹ ፡ በጽድቅና ፡ በቅንነት ፡ አድርጉላቸው ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ከማመስገን ፡ ጋራ ፡ በጸሎት ፡ እየነቃችኹ ፡ ለርሱ ፡ ትጉ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ የታሰርኹበትን ፡ የክርስቶስን ፡ ምስጢር ፡ እንድንነግር ፡ እግዚአብሔር ፡ የቃሉን ፡ ደጅ ፡ ይከፍትልን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ጸልዩ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ልናገር ፡ እንደሚገባኝ ፡ ያኽል ፡ እገልጠው ፡ ዘንድ ፡ ጸልዩልኝ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ዘመኑን ፡ እየዋጃችኹ ፥ በውጭ ፡ ባሉቱ ፡ ዘንድ ፡ በጥበብ ፡ ተመላለሱ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ለያንዳንዱ ፡ እንዴት ፡ እንድትመልሱ ፡ እንደሚገባችኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ንግግራችኹ ፡ ሹልጊዜ ፥ በጨው ፡ እንደ ፡ ተቀመመ ፥ በጸጋ ፡ ይኹን ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ የተወደደ ፡ ወንድምና ፡ የታመነ ፡ አገልጋይ ፡ በጌታም ፡ ዐብሮኝ ፡ ባሪያ ፡ የኾነ ፡ ቲኪቆስ ፡ ኑሮዬን ፡ ኹሉ ፡ ያስታውቃችኋል ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 8-9 ፤ ወሬያችንን ፡ እንድታውቁና ፡ ልባችኹን ፡ እንዲያጽናና ፥ ከእናንተ ፡ ከኾነውና ፡ ከታመነው ፡ ከተወደደውም ፡ ወንድም ፡ ከአናሲሞስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ የምልከው ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። የዚህን ፡ ስፍራ ፡ ወሬ ፡ ኹሉ ፡ ያስታውቋችኋል ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 10-11 ፤ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ ያሉት ፥ ዐብሮ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የታሰረ ፡ አርስጥሮኮስ ፡ የበርናባስም ፡ የወንድሙ ፡ ልጅ ፡ ማርቆስ ፡ ኢዮስጦስም ፡ የተባለ ፡ ኢያሱ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ። ስለ ፡ ማርቆስ ፦ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቢመጣ ፥ ተቀበሉት ፡ የሚል ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀበላችኹ ። በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ዐብረው ፡ የሚሠሩት ፡ እነዚህ ፡ ብቻ ፡ ናቸው ፥ እኔንም ፡ አጽናንተውኛል ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ከእናንተ ፡ የኾነ ፡ የክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ኤጳፍራ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርብላችኋል ። በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ኹሉ ፡ ተረድታችኹና ፡ ፍጹማን ፡ ኾናችኹ ፡ እንድትቆሙ ፥ ሹልጊዜ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በጸሎቱ ፡ ይጋደላል ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ በሎዶቅያም ፡ በኢያራ ፡ ከተማም ፡ ስላሉቱ ፡ እጅግ ፡ እንዲቀና ፡ እመሰክርለታለኹና ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ የተወደደው ፡ ባለመድኀኒቱ ፡ ሉቃስ ፡ ዴማስም ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ በሎዶቅያ ፡ ላሉቱ ፡ ወንድሞችና ፡ ለንምፋን ፡ በቤቱም ፡ ላለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልን ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ ይህችም ፡ መልእክት ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ከተነበበች ፡ በኋላ ፥ በሎዶቅያ ፡ ሰዎች ፡ ማኅበር ፡ ደግሞ ፡ እንድትነበብ ፡ አድርጉ ። ከሎዶቅያም ፡ የምትገኘውን ፡ መልእክት ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ አንቡ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ ለአክሪጳም ፦ በጌታ ፡ የተቀበልኸውን ፡ አገልግሎት ፡ እንድትፈጽመው ፡ ተጠንቀቅ ፡ በሉልኝ ።

ቆላ. ፡ 4 ፡ 18 ፤ በገዛ ፡ እጄ ፡ የተጻፈ ፡ የእኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ሰላምታ ፡ ይህ ፡ ነው ። እስራቴን ፡ ዐስቡ ። ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ❖

የመዠመሪያዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____1ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ ጳውሎስና ፡ ስልዋኖስ ፡ ጢሞቴዎስም ፥ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ወደምትኾን ፡ ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋ ፡ ሰላምም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 2-3 ፤ በጸሎታችን ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ስናሳስብ ፥ የእምነታችኹን ፡ ሥራ ፡ የፍቅራችኹንም ፡ ድካም ፡ በጌታችንም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ የተስፋችኹን ፡ መጽናት ፡ በአምላካችንና ፡ በአባታችን ፡ ፊት ፡ ሳናቋርጥ ፡ እያሰብን ፥ እግዚአብሔርን ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በኹላችኹ ፡ ምክንያት ፡ እናመሰግናለን ፤

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ በእግዚአብሔር ፡ የምትወደዱ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እንደ ፡ ተመረጣችኹ ፡ ዐውቀናልና ።

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ወንጌላችን ፡ በኀይልና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በብዙ ፡ መረዳትም ፡ እንጂ ፡ በቃል ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ አልመጣምና ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ነበርን ፡ ታውቃላችኹ ።

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ደግሞ ፡ እናንተ ፡ ቃሉን ፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ደስታ ፡ ጋራ ፡ ተቀብላችኹ ፥ እኛንና ፡ ጌታን ፡ የምትመስሉ ፡ ኾናችኹ ፤

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ስለዚህም ፡ በመቄዶንያና ፡ በአካይያ ፡ ላሉት ፡ ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ ምሳሌ ፡ ኾናችኹላቸው ።

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ከእናንተ ፡ ወጥቶ ፡ የጌታ ፡ ቃል ፡ በመቄዶንያና ፡ በአካይያ ፡ ብቻ ፡ አልተሰማምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ምንም ፡ እንድንናገር ፡ እስከማያስፈልግ ፡ ድረስ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚኾን ፡ እምነታችኹ ፡ በኹሉ ፡ ስፍራ ፡ ተወርቷል ።

ተሰ.1 ፥ 1 ፥ 9-10 ፤ እነርሱ ፡ ራሳቸው ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መግባታችን ፡ እንዴት ፡ እንደነበረ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ይናገራሉና ፤ ለሕያውና ፡ ለእውነተኛ ፡ አምላክም ፡ ታገለግሉ ፡ ዘንድ ፥ ከሙታንም ፡ ያስነሣውን ፡ ልጁን ፡ ርሱንም ፡ ኢየሱስን ፡ ከሚመጣው ፡ ቍጣ ፡ የሚያድነንን ፡ ከሰማይ ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፥ ከጣዖቶች ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ዘወር ፡ እንዳላችኹ ፡ ይናገራሉ ።

_____1ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ተሰ.1 ፥ 2 ፥ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ራሳችኹ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መግባታችን ፡ ከንቱ ፡ እንዳልኾነ ፡ ታውቃላችኹና ።

ተሰ.1 ፥ 2 ፥ 2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደምታውቁት ፡ በፊልጵስዩስ ፡ አስቀድመን ፡ መከራ ፡ ተቀብለን ፡ ተንገላትንም ፥ በብዙ ፡ ገድል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ወንጌል ፡ ለእናንተ ፡ እንናገር ፡ ዘንድ ፡ በአምላካችን ፡ ደፈርን ።

ተሰ.1 ፥ 2 ፥ 3 ፤ ልመናችን ፡ ከስሕተት ፡ ወይም ፡ ከርኵሰት ፡ ወይም ፡ ከተንኰል ፡ አልነበረምና ፤

ተሰ.1 ፥ 2 ፥ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንጌልን ፡ ዐደራ ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የታመን ፡ ኾነን ፡ እንዳገኘን ፡ መጠን ፥ እንዲሁ ፡ እንናገራለን ፥ ልባችንን ፡ የሚመረምር ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንጂ ፡ ሰውን ፡ ደስ ፡ እንደምናሠኝ ፡ አይደለም ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 5 ፤ እንደምታውቁ ፥ እያቈላመጥን ፡ ከቶ ፡ አልተናገርንም ፥ እግዚአብሔርም ፡ እንደሚመሰክር ፡ እያመካኘን ፡ በመጐምጐጥ ፡ አልሠራንም ፤

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ የክርስቶስም ፡ ሐዋርያት ፡ እንደ ፡ መኾናችን ፡ ልንከብድባችኹ ፡ ስንችል ፥ ከእናንተ ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ከሌላዎች ፡ ክብርን ፡ ከሰው ፡ አልፈለግንም ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሞግዚት ፡ የራሷን ፡ ልጆች ፡ እንደምትከባከብ ፥ በመካከላችኹ ፡ የዋሆች ፡ ኾን ፤

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ እንዲሁም ፡ እያፈቀርናችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ወንጌል ፡ ለማካፈል ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ የገዛ ፡ ነፍሳችንን ፡ ደግሞ ፡ እናካፍላችኹ ፡ ዘንድ ፡ በጎ ፡ ፈቃዳችን ፡ ነበረ ፥ ለእኛ ፡ የተወደዳችኹ ፡ ኾናችኹ ፡ ነበርና ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ድካማችንና ፡ ጥረታችን ፡ ትዝ ፡ ይላችኋልና ፤ ከእናንተ ፡ በአንዱ ፡ ስንኳ ፡ እንዳንከብድበት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ እየሠራን ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ወንጌል ፡ ለእናንተ ፡ ሰበክን ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ በእናንተ ፡ በምታምኑ ፡ ዘንድ ፡ በእንዴት ፡ ያለ ፡ ቅድስናና ፡ ጽድቅ ፡ ነቀፋም ፡ በሌለበት ፡ ኑሮ ፡ እንደ ፡ ኼድን ፥ እናንተና ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስክሮች ፡ ናችኹ ፤

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 11-12 ፤ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ወደ ፡ ክብሩም ፡ ለጠራችኹ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደሚገባ ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ እየመከርንና ፡ እያጸናን ፡ እየመሰከርንላችኹም ፥ አባት ፡ ለልጆቹ ፡ እንደሚኾን ፡ ለያንዳንዳችኹ ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ታውቃላችኹና ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ ስለዚህም ፡ የመልእክትን ፡ ቃል ፡ ርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከእኛ ፡ በተቀበላችኹ ፡ ጊዜ ፥ በእውነት ፡ እንዳለ ፡ በእናንተ ፡ በምታምኑ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚሠራ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ቃል ፡ አድርጋችኹ ፡ ስላልተቀበላችኹት ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሳናቋርጥ ፡ እናመሰግናለን ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ እናንተ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በይሁዳ ፡ የሚኖሩትን ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ያሉትን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ማኅበሮች ፡ የምትመስሉ ፡ ኾናችኋልና ፤ እነርሱ ፡ ከአይሁድ ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ መከራ ፡ ከአገራችኹ ፡ ሰዎች ፡ ተቀብላችኋልና ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ እነዚያም ፡ ጌታን ፡ ኢየሱስን ፡ ደግሞ ፡ ገደሉ ፡ ነቢያትንም ፡ እኛንም ፡ አሳደዱ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ደስ ፡ አያሠኙም ፥ ሰዎችንም ፡ ኹሉ ፡ ይቃወማሉ ፥

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ አሕዛብ ፡ እንዲድኑ ፡ እንዳንናገራቸው ፡ ይከለክሉናልና ። ነገር ፡ ግን ፥ ቍጣው ፡ ወደ ፡ እነርሱ ፡ ፈጽሞ ፡ ደርሷል ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ እኛ ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በልብ ፡ ያይደለ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ዐጥተናችኹ ፥ በብዙ ፡ ናፍቆት ፡ ፊታችኹን ፡ ለማየት ፡ እጅግ ፡ ሞከርን ፤

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልንመጣ ፡ ወደን ፡ ነበርና ፥ እኔ ፡ ጳውሎስም ፡ አንድና ፡ ኹለት ፡ ጊዜ ፥ ሰይጣን ፡ ግን ፡ አዘገየን ።

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ተስፋችን ፡ ወይስ ፡ ደስታችን ፡ ወይስ ፡ የትምክሕታችን ፡ አክሊል ፡ ማን ፡ ነው ፧ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ፊት ፡ በመምጣቱ ፡ እናንተ ፡ አይደላችኹምን ፧

ተሰ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ክብራችን ፡ ደስታችንም ፡ ናችኹና ።

_____1ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ እንታገሥ ፡ ዘንድ ፡ ባልተቻለን ፡ ጊዜ ፥ በአቴና ፡ ብቻችንን ፡ ልንቀር ፡

በጎ ፡ ፈቃዳችን ፡ ኾነ ።

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ስለ ፡ እምነታችኹም ፡ እንዲያጸናችኹና ፡ እንዲመክራችኹ ፡ ወንድማችንን ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ አገልጋይ ፡ ከእኛ ፡ ጋራም ፡ ዐብሮ ፡ በክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ የሚሠራውን ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ላክነው ፤

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ በዚህ ፡ መከራ ፡ ማንም ፡ እንዳይናወጥ ፥ ለዚህ ፡ እንደ ፡ ተመረጥን ፡ ራሳችኹ ፡ ታውቃላችኹና ።

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ በእውነት ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለን ፥ መከራ ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ እንዳለን ፡ አስቀድመን ፡ እንነግራችኹ ፡ ነበር ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ኾነ ፥ ይህንም ፡ ታውቃላችኹ ።

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እታገሥ ፡ ዘንድ ፡ ባልተቻለኝ ፡ ጊዜ ፦ ፈታኝ ፡ ምናልባት ፡ ፈትኗቸዋል ፡ ድካማችንም ፡ ከንቱ ፡ ኾኗል ፡ ብዬ ፡ እምነታችኹን ፡ ለማወቅ ፡ ላክኹ ።

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እኛ ፡ መጥቶ ፡ ስለ ፡ እምነታችኹና ፡ ስለ ፡ ፍቅራችኹ ፡ የምሥራች ፡ ብሎ ፡ በነገረን ፡ ጊዜ ፥ እኛም ፡ እናያችኹ ፡ ዘንድ ፡ እንደምንናፍቅ ፡ ታዩን ፡ ዘንድ ፡ እየናፈቃችኹ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በመልካም ፡ እንደምታስቡን ፡ በነገረን ፡ ጊዜ ፥

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በእምነታችኹ ፡ በኩል ፡ በችግራችንና ፡ በመከራችን ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ተጽናናን ፤

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ በጌታ ፡ ጸንታችኹ ፡ ብትቆሙ ፥ አኹን ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለንና ።

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 9-10 ፤ ፈታችኹን ፡ ልናይ ፡ በእምነታችኹም ፡ የጐደለውን ፡ ልንሞላበት ፡ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ እየጸለይን ፡ በአምላካችን ፡ ፊት ፡ ከእናንተ ፡ የተነሣ ፡ ስለምንደሰተው ፡ ደስታ ፡ ኹሉ ፥ ለእግዚአብሔር ፡ በእናንተ ፡ ምክንያት ፡ ምን ፡ ያኽል ፡ ምስጋና ፡ እናስረክብ ፡ ዘንድ ፡ እንችላለን ፧

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ አምላካችንና ፡ አባታችን ፡ ራሱ ፡ ጌታችንም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ መንገዳችንን ፡ ያቅና ፤

ተሰ.1 ፡ 3 ፡ 12-13 ፤ ጌታችንም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከቅዱሳኑ ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ሲመጣ ፥ በአምላካችንና ፡ በአባታችን ፡ ፊት ፡ በቅድስና ፡ ነቀፋ ፡ የሌለበት ፡ አድርጎ ፡ ልባችኹን ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ለእናንተ ፡ እንደምንኾን ፡ ጌታ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ያላችኹን ፡ ለኹሉም ፡ የሚኾን ፡ ፍቅራችኹን ፡ ያብዛ ፡ ይጨምርም ።

_____1ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ በቀረውስ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ልትመላለሱ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ደስ ፡ ልታሠኙ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገባችኹ ፡ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ተቀበላችኹ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደምትመላለሱ ፥ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ትበዙ ፡ ዘንድ ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ እንለምናችኋለን ፡ እንመክራችኹማለን ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 2 ፤ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ የትኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሰጠናችኹ ፡ ታውቃላችኹና ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ርሱም ፡ መቀደሳችኹ ፡ ነውና ፤

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 4-5 ፤ ከዝሙት ፡ እንድትርቁ ፥ እግዚአብሔርን ፡ እንደማያውቁ ፡ አሕዛብ ፡ በፍትወት ፡ ምኞት ፡ አይደለም ፡ እንጂ ፥ ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ፡ የራሱን ፡ ዕቃ ፡ በቅድስናና ፡ በክብር ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ እንዲያውቅ ፤

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ አስቀድመን ፡ ደግሞ ፡ እንዳልናችኹና ፡ እንደ ፡ መሰከርንላችኹ ፥ ጌታ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሚበቀል ፡ ነውና ፥ ማንም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አይተላለፍ ፡ ወንድሙንም ፡ አያታል ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ለርኵሰት ፡ ሳይኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድስና ፡ ጠርቶናልና ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ እንግዲህ ፡ የሚጥል ፡ ሰውን ፡ የጣለ ፡ አይደለም ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በእናንተ ፡ እንዲኖር ፡ የሰጠውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ እናንተ ፡ ራሳችኹ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ልትዋደዱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተምራችኋልና ፥ ስለወንድማማች ፡ መዋደድ ፡ ማንም ፡ ይጽፍላችኹ ፡ ዘንድ ፡ አያስፈልጋችኹም ፤

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 10-12 ፤ እንዲሁ ፡ በመቄዶንያ ፡ ኹሉ ፡ ላሉት ፡ ወንድሞች ፡ ኹሉ ፡ ታደርጋላችኹና ። ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ልትበዙ ፥ በጸጥታም ፡ ትኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ልትቀኑ ፥ የራሳችኹንም ፡ ጕዳይ ፡ ልትጠነቀቁ ፥ እንዳዘዝናችኹም ፥ በውጭ ፡ ባሉት ፡ ዘንድ ፡ በአገባብ ፡ እንድትመላለሱ ፥ አንዳችም ፡ እንዳያስፈልጋችኹ ፡ በእጃችኹ ፡ ልትሠሩ ፡ እንለምናችኋለን ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ተስፋ ፡ እንደሌላቸው ፡ እንደ ፡ ሌላዎች ፡ ደግሞ ፡ እንዳታዝኑ ፥ አንቀላፍተው ፡ ስላሉቱ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ እንወዳለን ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ ሞተና ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ካመ፟ን ፥ እንዲሁም ፡ በኢየሱስ ፡ ያንቀላፉቱን ፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያመጣቸዋልና ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ በጌታ ፡ ቃል ፡ የምንላችኹ ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ ጌታ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ የምንቀር ፡ ያንቀላፉቱን ፡ አንቀድምም ፤

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ ራሱ ፡ በትእዛዝ ፡ በመላእክትም ፡ አለቃ ፡ ድምፅ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ መለከት ፡ ከሰማይ ፡ ይወርዳልና ፥ በክርስቶስም ፡ የሞቱ ፡ አስቀድመው ፡ ይነሣሉ ፤

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ እኛ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን ፡ የምንቀረው ፥ ጌታን ፡ በአየር ፡ ለመቀበል ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ በደመና ፡ እንነጠቃለን ፤ እንዲሁም ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ከጌታ ፡ ጋራ ፡ እንኾናለን ።

ተሰ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ስለዚህ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ተጽናኑ ።

_____1ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ ዘመናትና ፡ ስለ ፡ ወራት ፡ ምንም ፡ እንዲጻፍላችኹ ፡ አያስፈልጋችኹም ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ የጌታ ፡ ቀን ፥ ሌባ ፡ በሌሊት ፡ እንደሚመጣ ፥ እንዲሁ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ራሳችኹ ፡ አጥብቃችኹ ፡ ዐውቃችኋልና ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ ሰላምና ፡ ደኅንነት ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ ምጥ ፡ እርጉዝን ፡ እንደሚይዛት ፡ ጥፋት ፡ በድንገት ፡ ይመጣባቸዋል ፡ ከቶም ፡ አያመልጡም ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ እናንተ ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ቀኑ ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ይደርስባችኹ ፡ ዘንድ ፡ በጨለማ ፡ አይደላችኹም ፥

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ኹላችኹ ፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ የቀንም ፡ ልጆች ፡ ናችኹና ። እኛ ፡ ከሌሊት ፡ ወይም ፡ ከጨለማ ፡ አይደለንም ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ እንግዲያስ ፡ እንንቃ ፡ በመጠንም ፡ እንኑር ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሌላዎች ፡ አናንቀላፋ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ የሚያንቀላፉ ፡ በሌሊት ፡ ያንቀላፋሉና ፥ የሚሰክሩም ፡ በሌሊት ፡ ይሰክራሉና ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ከቀን ፡ ስለ ፡ ኾ፟ን ፥ የእምነትንና ፡ የፍቅርን ፡ ጥሩር ፡ የመዳንንም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡

ራስ ፡ ቍር ፡ እየለበስን ፡ በመጠን ፡ እንኑር ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ እግዚአብሔር ፡ ለቍጣ ፡ አልመረጠንምና ፥ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መዳንን ፡ ለማግኘት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ የምንነቃም ፡ ብንኾን ፥ የምናንቀላፋም ፡ ብንኾን ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ዐብረን ፡ በሕይወት ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ሞተ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ ስለዚህ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደምታደርጉ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተመካከሩ ፡ አንዱም ፡ አንዱም ፡ ሌላውን ፡ ያንጸው ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 12-13 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በመካከላችኹ ፡ የሚደክሙትን ፡ በጌታም ፡ የሚገዟችኹን ፡ የሚገሥጿችኹንም ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፥ ስለ ፡ ሥራቸውም ፡ በፍቅር ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ ታከብሯቸው ፡ ዘንድ ፡ እንለምናችኋለን ። ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ በሰላም ፡ ኹኑ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እንመክራችኋለን ፤ ያለሥርዐት ፡ የሚኼዱትን ፡ ገሥጿቸው ፤ ድፍረት ፡ የሌላቸውን ፡ አጽኗቸው ፤ ለደካማዎች ፡ ትጉላቸው ፤ ሰውን ፡ ኹሉ ፡ ታገሡ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 15 ፤ ማንም ፡ ለሌላው ፡ በክፉ ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡ እንዳይመልስ ፡ ተጠንቀቁ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ለኹሉም ፡ መልካሙን ፡ ለማድረግ ፡ ትጉ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 17-18 ፤ ሳታቋርጡ ፡ ጸልዩ ፤ በኹሉ ፡ አመስግኑ ፤ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ነውና ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 19 ፤ መንፈስን ፡ አታጥፉ ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 20-21 ፤ ትንቢትን ፡ አትናቁ ፤ ኹሉን ፡ ፈትኑ ፡ መልካሙንም ፡ ያዙ ፤

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 22 ፤ ከማናቸውም ፡ ዐይነት ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ራቁ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 23 ፤ የሰላምም ፡ አምላክ ፡ ራሱ ፡ ኹለንተናችኹን ፡ ይቀድስ ፤ መንፈሳችኹም ፡ ነፍሳችኹም ፡ ሥጋችኹም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ያለነቀፋ ፡ ፈጽመው ፡ ይጠበቁ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 24 ፤ የሚጠራችኹ ፡ የታመነ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ያደርገዋል ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 25 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልዩ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 26 ፤ ከወንድሞች ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ በተቀደሰ ፡ አሳሳም ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 27 ፤ ይህ ፡ መልእክት ፡ ለቅዱሳን ፡ ወንድሞች ፡ ኹሉ ፡ እንዲነበብ ፡ በጌታ ፡ አምላችኋለኹ ።

ተሰ.1 ፡ 5 ፡ 28 ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

ኩለተኛዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____2 ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ ጳውሎስና ፡ ስልዋኖስ ፡ ጢሞቴዎስም ፥ በእግዚአብሔር ፡ በአባታችን ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ወደምትኾን ፡ ወደተሰሎንቄ ፡ ሰዎች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጸጋ ፡ ሰላምም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እምነታችኹ ፡ እጅግ ፡ ስለሚያድግ ፡ የኹላችኹም ፡ የያንዳንዳችኹ ፡ ፍቅር ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ስለሚበዛ ፥ ኹል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደሚገባ ፡ ልናመሰግን ፡ ግድ ፡ አለብን ፤

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ስለዚህ ፥ በምትታገሡበት ፡ በስደታችኹና ፡ በመከራችኹ ፡ ኹሉ ፡ ከመጽናታችኹና ፡ ከእምነታችኹ ፡ የተነሣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ራሳችን ፡ እንመካለን ።

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ መከራ ፡ ለምትቀበሉለት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የምትበቁ ፡ ኾናችኹ ፡ ትቈጠሩ ፡ ዘንድ ፥ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቅን ፡ ፍርድ ፡ ምልክት ፡ ነው ።

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 6-7 ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ከሥልጣኑ ፡ መላእክት ፡ ጋራ ፡ ከሰማይ ፡ በእሳት ፡ ነበልባል ፡ ሲገለጥ ፥ መከራን ፡ ለሚያሳይዋችኹ ፡ መከራን ፥ መከራንም ፡ ለምትቀበሉ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ዕረፍትን ፡ ብድራት ፡ አድርጎ ፡ እንዲመልስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በርግጥ ፡ ጽድቅ ፡ ነውና ።

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ እግዚአብሔርን ፡ የማያውቁትን ፥ ለጌታችንም ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ የማይታዘዙትን ፡ ይበቀላል ፤

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 9-10 ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ በቅዱሳኑ ፡ ሊከብር ፥ ምስክርነታችንንም ፡ አምናችኋልና ፥ በሚያምኑት ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ሊገረም ፡ ሲመጣ ፥ ከጌታ ፡ ፊት ፡ ከኀይሉም ፡ ክብር ፡ ርቀው ፡ በዘለዓለም ፡ ጥፋት ፡ ይቀጣሉ ።

ተሰ.2 ፥ 1 ፥ 11-12 ፤ ስለዚህም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ አምላካችን ፡ እንደ ፡ ጌታም ፡ እንደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፥ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ሊከብር ፡ እናንተም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ልትከብሩ ፥ አምላካችን ፡ ለመጥራቱ ፡ የምትበቁ ፡ አድርጎ ፡ ይቈጥራችኹ ፡ ዘንድ ፥ የበጎነትንም ፡ ፈቃድ ፡ ኹሉ ፡ የእምነትንም ፡ ሥራ ፡ በኀይል ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንጸልያለን ።

_____2 ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 1-2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ስለጌታችን ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መምጣትና ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ስለ ፡ መሰብሰባችን ፥ በመንፈስ ፡ ወይም ፡ በቃል ፡ ወይም ፡ ከእኛ ፡ እንደሚመጣ ፡ በመልእክት ፡— የጌታ ፡ ቀን ፡ ደርሷል ፡ ብላችኹ ፥ ከአእምሯችኹ ፡ ቶሎ ፡ እንዳትናወጡ ፡ እንዳትደነግጡም ፡ እንለምናችኋለን ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 3 ፤ ማንም ፡ በማናቸውም ፡ መንገድ ፡ አያስታችኹ ፤ ክህደቱ ፡ አስቀድሞ ፡ ሳይመጣና ፡ የዐመፅ ፡ ሰው ፡ ርሱም ፡ የጥፋት ፡ ልጅ ፡ ሳይገለጥ ፥ አይደርስምና ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 4 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ዐዋጅ ፡ እየነገረ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡

እስኪቀመጥ ፡ ድረስ ፥ አምላክ ፡ ከተባለው ፡ ሹሉ ፥ ሰዎችም ፡ ከሚያመልኩት ፡ ሹሉ ፡ በላይ ፡ ራሱን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ የሚያደርገው ፡ ተቃዋሚ ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 5 ፤ ገና ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለኹ ፥ ይህን ፡ እንዳልኋችኹ ፡ ትዝ ፡ አይላችኹምን ፧

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 6 ፤ በገዛ ፡ ራሱ ፡ ጊዜም ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፥ የሚከለክለውን ፡ አኹን ፡ ታውቃላችኹ ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 7 ፤ የዐመፅ ፡ ምስጢር ፡ አኹን ፡ ይሠራልና ፤ ብቻ ፡ ከመንገድ ፡ እስኪወገድ ፡ ድረስ ፡ አኹን ፡ የሚከለክል ፡ አለ ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 8 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ በአፉ ፡ መንፈስ ፡ የሚያጠፋው ፥ ሲመጣም ፡ በመገለጡ ፡ የሚሽረው ፡ ዐመፀኛ ፡ ይገለጣል ፤

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 9-10 ፤ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡ የእውነትን ፡ ፍቅር ፡ ስላልተቀበሉ ፡ ለሚጠፉ ፥ የርሱ ፡ መምጣት ፡ በተኣምራት ፡ ሹሉና ፡ በምልክቶች ፡ በሐሰተኞች ፡ ድንቆችም ፡ በዐመፅም ፡ መታለል ፡ ሹሉ ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ አሠራር ፡ ነው ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 11-12 ፤ ስለዚህም ፡ ምክንያት ፥ በእውነት ፡ ያላመኑ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በዐመፅ ፡ ደስ ፡ ይላቸው ፡ የነበሩ ፡ ሹሉ ፡ ፍርድን ፡ እንዲቀበሉ ፥ ሐሰትን ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ የስሕተትን ፡ አሠራር ፡ ይልክባቸዋል ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 13 ፤ እኛ ፡ ግን ፥ በጌታ ፡ የተወደዳችኹ ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ሹል ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልናመሰግን ፡ ግድ ፡ አለብን ፥ እግዚአብሔር ፡ በመንፈስ ፡ መቀደስ ፥ እውነትንም ፡ በማመን ፡ ለመዳን ፡ እንደ ፡ በኩራት ፡ መርጧችኋልና ፤

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 14 ፤ ለዚህም ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ክብር ፡ ለማግኘት ፡ በወንጌላችን ፡ ጠራችኹ ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 15 ፤ እንግዲያስ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ጸንታችኹ ፡ ቁሙ ፥ በቃላችንም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በመልእክታችን ፡ የተማራችኹትን ፡ ወግ ፡ ያዙ ።

ተሰ.2 ፥ 2 ፥ 16-17 ፤ ራሱ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስና ፡ የወደደን ፥ በጸጋም ፡ የዘለዓለምን ፡ መጽናናት ፥ በጎንም ፡ ተስፋ ፡ የሰጠን ፥ እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡ ልባችኹን ፡ ያጽናኑት ፥ በበጎም ፡ ሥራና ፡ በቃል ፡ ሹሉ ፡ ያጽኗችኹ ።

_____2 ኛ ፡ ተሰሎንቄ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 1-2 ፤ በቀረውስ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የጌታ ፡ ቃል ፡ እንዲሮጥ ፡ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ደግሞ ፡ እንደሚኾን ፡ እንዲከበር ፥ እምነትም ፡ ለሹሉ ፡ ስለማይኾን ፡ ከዐመፀኞችና ፡ ከክፉዎች ፡ ሰዎች ፡ እንድንድን ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ጸልዩ ።

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የሚያጸናችኹ ፡ ከክፉውም ፡ የሚጠብቃችኹ ፡ ጌታ ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 4 ፤ የምናዛችኹንም ፡ አኹን ፡ እንድታደርጉ ፡ ወደ ፡ ፊትም ፡ ደግሞ ፡ እንድታደርጉ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በጌታ ፡ ታምነናል ።

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 5 ፤ ጌታም ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ወደክርስቶስም ፡ ትዕግሥት ፡ ልባችንን ፡ ያቅናው ።

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 6 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ከእኛ ፡ እንደተቀበለው ፡ ወግ ፡ ሳይኾን ፡ ያለሥርዐት ፡ ከሚኼድ ፡ ወንድም ፡ ሹሉ ፡ ትለዩ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እናዛችኋለን ።

ተሰ.2 ፥ 3 ፥ 7 ፤ እኛን ፡ ልትመስሉ ፡ እንዴት ፡ እንደሚገባችኹ ፡ ራሳችኹ ፡ ታውቃላችኹና ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለሥርዐት ፡ አልኼድንምና ፤

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ በአንዱ ፡ ስንኳ ፡ እንዳንከብድበት ፥ ሌሊትና ፡ ቀን ፡ በድካምና ፡ በጥረት ፡ እየሠራን ፡ እንኖር ፡ ነበር ፡ እንጂ ፥ ከማንም ፡ እንጀራን ፡ እንዲያው ፡ አልበላንም ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ይህም ፡ እኛን ፡ ልትመስሉ ፡ ራሳችንን ፡ እንደ ፡ ምሳሌ ፡ እንሰጣችኹ ፡ ዘንድ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፥ ያለሥልጣን ፡ ስለ ፡ ኾን ፡ አይደለም ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 10 ፤ ደግሞ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለን ፦ ሊሠራ ፡ የማይወድ ፡ አይብላ ፡ ብለን ፡ አዘናችኹ ፡ ነበርና ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ሥራ ፡ ከቶ ፡ ሳይሠሩ ፥ በሰው ፡ ነገር ፡ እየገቡ ፥ ያለሥርዐት ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚኼዱ ፡ ስለ ፡ አንዳንዶች ፡ ሰምተናልና ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 12 ፤ እንደነዚህ ፡ ያሉትንም ፡ በጸጥታ ፡ እየሠሩ ፡ የገዛ ፡ እንጀራቸውን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እናዛቸዋለን ፡ እንመክራቸውማለን ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ እናንተ ፡ ግን ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ መልካም ፡ ሥራን ፡ ለመሥራት ፡ አትታክቱ ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ በዚህ ፡ መልእክት ፡ ለተላከ ፡ ቃላችን ፡ የማይታዘዝ ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፥ ይህን ፡ ተመልከቱት ፥ ያፍርም ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አትተባበሩ ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ወንድም ፡ ገሥጹት ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ጠላት ፡ አትቊጠሩት ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ የሰላምም ፡ ጌታ ፡ ራሱ ፡ በሹሉ ፡ መንገድ ፡ ዘወትር ፡ ሰላምን ፡ ይስጣችኹ ። ጌታ ፡ ከሹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ በገዛ ፡ እጄ ፡ የተጻፈ ፡ የእኔ ፡ የጳውሎስ ፡ ሰላምታ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ የመልእክቴ ፡ ሹሉ ፡ ማስረጃ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንዲህ ፡ እጽፋለኹ ።

ተሰ.2 ፡ 3 ፡ 18 ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከሹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ❖

የመጠመሪያዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ መድኀኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋችንም ፡ አ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳዘዘው ፡ ትእዛዝ ፡ የአ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፥

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 2 ፤ በእምነት ፡ እውነተኛ ፡ ልጄ ፡ ለኾነ ፡ ለጢሞቴዎስ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከክርስቶስ ፡ አ.የሱስም ፡ ከጌታችን ፡ ጸጋና ፡ ምሕረት ፡ ሰላምም ፡ ይኹን ።

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 3-4 ፤ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ በኼድኹ ፡ ጊዜ ፥ አንዳንዶች ፡ ልዩ ፡ ትምህርትን ፡ እንዳያስተምሩና ፡ ወደ ፡ ተረት ፡ መጨረሻም ፡ ወደሌለው ፡ ወደትውልዶች ፡ ታሪክ ፡ እንዳያደምጡ ፡ ልታዛቸው ፡ በኤፌሶን ፡ ትቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ ለመንኹኽ ፤ እንደ ፡ እነዚህ ፡ ያሉ ፡ ነገሮች ፡ ክርክርን ፡ ያመጣሉና ፡ በእምነት ፡ ግን ፡ ላለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መጋቢነት ፡ አይጠቅሙም ።

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ የትእዛዝ ፡ ፍጻሜ ፡ ግን ፡ ከንጹሕ ፡ ልብና ፡ ከበጎ ፡ ኅሊና ፡ ግብዝነትም ፡ ከሌለበት ፡ እምነት ፡ የሚወጣ ፡ ፍቅር ፡ ነው ፤

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 6-7 ፤ ከነዚህም ፡ አንዳንዶች ፡ ስተው ፥ የሚሉትን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ እነርሱ ፡ አስረግጠው ፡ የሚናገሩትን ፡ ሳያስተውሉ ፥ የሕግ ፡ አስተማሪዎች ፡ ሊኾኑ ፡ እየወደዱ ፥ ወደ ፡ ከንቱ ፡ ንግግር ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋል ።

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሰው ፡ እንደሚገባ ፡ ቢሠራበት ፡ ሕግ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ፤

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 9-11 ፤ ይኸውም ፥ ለበደለኞችና ፡ ለማይታዘዙ ፥ ለዐመፀኞችና ፡ ለኀጢአተኞች ፥ ቅድስና ፡ ለሌላቸውና ፡ ለርኩሳን ፥ አባትና ፡ እናትን ፡ ለሚገድሉ ፥ ለነፍሰ ፡ ገዳዮችና ፡ ለሴሰኞች ፥ ከወንድ ፡ ጋራም ፡ ለሚተኙ ፥ በሰዎችም ፡ ለሚነግዱ ፥ ለውሸተኞችም ፡ በውሸትም ፡ ለሚምሉ ፥ የቡሩክ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ክብር ፡ እንደሚገልጥ ፡ ለእኔ ፡ ዐደራ ፡ እንደ ፡ ተሰጠኝ ፡ ወንጌል ፡ የኾነውን ፡ ደኅና ፡ ትምህርት ፡ ለሚቃወም ፡ ለሌላ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ተሠራ ፡ እንጂ ፡ ለጻድቅ ፡ እንዳልተሠራ ፡ ሲያውቅ ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ለአገልግሎቱ ፡ ሾሞኝ ፡ ታማኝ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ቈጠረኝ ፥ ኀይል ፡ የሰጠኝን ፡ ክርስቶስ ፡ አ.የሱስን ፡ ጌታችንን ፡ አመሰግናለኹ ፤

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ አስቀድሞ ፡ ተሳዳቢና ፡ አሳዳጅ ፡ አንገላችም ፡ ምንም ፡ ብኾን ፥ ይህን ፡ አደረገልኝ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሳላውቅ ፡ ባለማመን ፡ ስላደረግኹት ፡ ምሕረትን ፡ አገኘኹ ፥

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 14 ፤ የጌታችንም ፡ ጸጋ ፡ በክርስቶስ ፡ አ.የሱስ ፡ ካሉ ፡ ከእምነትና ፡ ከፍቅር ፡ ጋራ ፡ አብልጦ ፡ በዛ ።

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 15 ፤ ኀጢአተኞችን ፡ ሊያድን ፡ ክርስቶስ ፡ አ.የሱስ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጣ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የታመነና ፡ ኹሉ ፡ እንዲቀበሉት ፡ የተገባ ፡ ነው ፤ ከኀጢአተኞችም ፡ ዋና ፡ እኔ ፡ ነኝ ፤

ጢ.ሞ.1 ፥ 1 ፥ 16 ፤ ስለዚህ ፡ ግን ፥ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ለማግኘት ፡ በርሱ ፡ ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ላላቸው ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌ ፡ እንድኾን ፥ አ.የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዋና ፡ በምኾን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ትዕግሥቱን ፡ ኹሉ ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፥ ምሕረትን ፡ አገኘኹ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 1 ፡ 17 ፤ ብቻውን ፡ አምላክ ፡ ለሚኾን ፡ ለማይጠፋው ፡ ለማይታየውም ፡ ለዘመናት ፡ ንጉሥ ፡ ምስጋናና ፡ ክብር ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 1 ፡ 18 ፤ ጢሞቴዎስ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አስቀድሞ ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እንደተነገረው ፡ ትንቢት ፥ በርሱ ፡ መልካም ፡ ጦርነት ፡ ትዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ ዐደራ ፡ እሰጥኻለኹ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 1 ፡ 19 ፤ እምነትና ፡ በጎ ፡ ኅሊና ፡ ይኑርኽ ፥ አንዳንዶች ፡ ኅሊናን ፡ ጥለው ፥ መርከብ ፡ አለ ፡ መሪ ፡ እንደሚጠፋ ፥ በእምነት ፡ ነገር ፡ ጠፍተዋልና ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 1 ፡ 20 ፤ ከነዚያም ፥ እንዳይሳደቡ ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ ለሰይጣን ፡ አሳልፌ ፡ የሰጠኋቸው ፥ ሄሜኔዎስና ፡ እስክንድሮስ ፡ ናቸው ።

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 1-2 ፤ እንግዲህ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመምሰልና ፡ በጭምትነት ፡ ኹሉ ፡ ጸጥና ፡ ዝግ ፡ ብለን ፡ እንድንኖር ፥ ልመናና ፡ ጸሎት ፡ ምልጃም ፡ ምስጋናም ፡ ስለ ፡ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ነገሥታትና ፡ ስለ ፡ መኳንንትም ፡ ኹሉ ፡ እንዲደረጉ ፡ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ እመክራለኹ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 3-4 ፤ ሰዎች ፡ ኹሉ ፡ ሊድኑና ፡ እውነቱን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ሊደርሱ ፡ በሚወድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በመድኀኒታችን ፡ ፊት ፡ መልካምና ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 5 ፤ አንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለና ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በሰውም ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ መካከለኛው ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ አለ ፥ ርሱም ፡ ሰው ፡ የኾነ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ነው ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ ራሱንም ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ ሰጠ ፥ ይህም ፡ በገዛ ፡ ዘመኑ ፡ ምስክርነቱ ፡ ነበረ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ እኔም ፡ ለዚህ ፡ ነገር ፡ ዐዋጅ ፡ ነጋሪና ፡ ሐዋርያ ፡ በእምነትና ፡ በእውነትም ፡ የአሕዛብ ፡ አስተማሪ ፡ ለመኾን ፡ ተሾምኹ ፤ እውነት ፡ እናገራለኹ ፤ አልዋሽም ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ እንግዲህ ፡ ወንዶች ፡ በስፍራ ፡ ኹሉ ፡ አለ ፡ ቍጣና ፡ አለ ፡ ክፉ ፡ ዐሳብ ፡ የተቀደሱትን ፡ እጆች ፡ እያነሡ ፡ እንዲጸልዩ ፡ እፈቅዳለኹ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 9-10 ፤ እንዲሁም ፡ ደግሞ ፡ ሴቶች ፡ በሚገባ ፡ ልብስ ፡ ከዕፍረትና ፡ ራሳቸውን ፡ ከመግዛት ፡ ጋራ ፡ ሰውነታቸውን ፡ ይሸልሙ ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንፈራለን ፡ ለሚሉት ፡ ሴቶች ፡ እንደሚገባ ፥ መልካም ፡ በማድረግ ፡ እንጂ ፡ በሽሩባና ፡ በወርቅ ፡ ወይም ፡ በዕንቊ ፡ ወይም ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ በከበረ ፡ ልብስ ፡ አይሸለሙ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሴት ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እየተገዛች ፡ በዝግታ ፡ ትማር ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ሴት ፡ ግን ፡ በዝግታ ፡ ትኑር ፡ እንጂ ፡ ልታስተምር ፡ ወይም ፡ በወንድ ፡ ላይ ፡ ልትሠለጥን ፡ አልፈቅድም ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ አዳም ፡ ቀድሞ ፡ ተፈጥሯልና ፥ በኋላም ፡ ሔዋን ፡ ተፈጠረች ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ የተታለለም ፡ አዳም ፡ አይደለም ፥ ሴቲቱ ፡ ግን ፡ ተታላ ፡ በመተላለፍ ፡ ወደቀች ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእምነትና ፡ በፍቅር ፡ በቅድስናም ፡ ራሳቸውን ፡ እየገዙ ፡ ቢኖሩ ፡ በመውለድ ፡ ትድናለች ።

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ማንም ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስነትን ፡ ቢፈልግ ፡ መልካምን ፡ ሥራ ፡ ይመኛል ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ የታመነ ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ እንግዲህ ፡ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፡ እንዲህ ፡ ሊኾን ፡ ይገባዋል ፤ የማይነቀፍ ፥ የአንዲት ፡ ሚስት ፡ ባል ፥ ልከኛ ፥ ራሱን ፡ የሚገዛ ፥ እንደሚገባው ፡ የሚሠራ ፥ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፥ ለማስተማር ፡ የሚበቃ ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ የማይሰክር ፥ የማይጨቃጨቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ገር ፡ የኾነ ፥ የማይከራከር ፥ ገንዘብን ፡ የማይወድ ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ልጆቹን ፡ በጭምትነት ፡ ኹሉ ፡ እየገዛ ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ በመልካም ፡ የሚያስተዳድር ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ሰው ፡ ግን ፡ የራሱን ፡ ቤት ፡ እንዲያስተዳድር ፡ ባያውቅ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዴት ፡ ይጠብቃታል ፧

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ በትዕቢት ፡ ተነፍቶ ፡ በዲያብሎስ ፡ ፍርድ ፡ እንዳይወድቅ ፥ ዐዲስ ፡ ክርስቲያን ፡ አይኹን ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ በዲያብሎስ ፡ ነቀፋና ፡ ወጥመድም ፡ እንዳይወድቅ ፥ በውጭ ፡ ካሉት ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ መልካም ፡ ምስክር ፡ ሊኖረው ፡ ይገባዋል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ እንዲሁም ፡ ዲያቆናት ፡ ጭምቶች ፥ በኹለት ፡ ቃል ፡ የማይናገሩ ፥ ለብዙ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የማይገዙመገቡ ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ነውረኛ ፡ ረብ ፡ የማይወዱ ፥ በንጹሕ ፡ ኅሊና ፡ የሃይማኖትን ፡ ምስጢር ፡ የሚይዙ ፡ ሊኾኑ ፡ ይገባቸዋል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ እነዚህም ፡ ደግሞ ፡ አስቀድሞ ፡ ይፈተኑ ፥ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ያለነቀፋ ፡ ቢኾኑ ፡ በዲቁና ፡ ሥራ ፡ ያገልግሉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ እንዲሁም ፡ ሴቶች ፡ ጭምቶች ፥ የማያሙ ፥ ልከኞች ፥ በነገር ፡ ኹሉ ፡ የታመኑ ፡ ሊኾኑ ፡ ይገባቸዋል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ ዲያቆናት ፡ ልጆቻቸውንና ፡ የራሳቸውን ፡ ቤቶች ፡ በመልካም ፡ እየገዙ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ የአንዲት ፡ ሴት ፡ ባሎች ፡ ይኹኑ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ በዲቁና ፡ ሥራ ፡ በመልካም ፡ ያገለገሉ ፡ ለራሳቸው ፡ ትልቅ ፡ ማዕርግና ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ባለው ፡ እምነት ፡ ብዙ ፡ ድፍረት ፡ ያገኛሉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ፈጥኜ ፡ ወዳንተ ፡ እንድመጣ ፡ ተስፋ ፡ አድርጌ ፡ ይህን ፡ እጽፍልኻለኹ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ብዘገይ ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ቤት ፡ መኖር ፡ እንዴት ፡ እንደሚገባ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ እጽፍልኻለኹ ፤ ቤቱም ፡ የእውነት ፡ ዐምድና ፡ መሠረት ፥ የሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ የመምሰል ፡ ምስጢር ፡ ያለጥርጥር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፤ በሥጋ ፡ የተገለጠ ፥ በመንፈስ ፡ የጸደቀ ፥ ለመላእክት ፡ የታየ ፥ በአሕዛብ ፡ የተሰበከ ፥ በዓለም ፡ የታመነ ፥ በክብር ፡ ያረገ ።

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 1-2 ፤ መንፈስ ፡ ግን ፡ በግልጥ ፦ በኋለኞች ፡ ዘመናት ፡ አንዳንዶች ፡ የሚያስቱ ፡ መናፍስትንና ፡ በውሸተኞች ፡ ግብዝነት ፡ የተሰጠውን ፡ የአጋንንትን ፡ ትምህርት ፡ እያደመጡ ፥ ሃይማኖትን ፡ ይክዳሉ ፡ ይላል ፤ በገዛ ፡ ኅሊናቸው ፡ እንደሚቃጠሉ ፡ ደንዝዘው ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ እነዚህ ፡ ውሸተኞች ፡ መጋባትን ፡ ይከለክላሉ ፥ አምነውም ፡ እውነትን ፡ የሚያውቁ ፡ ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ መብል ፡ እንዲርቁ ፡ ያዛሉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ሹሉ ፡ መልካም ፡ ነውና ፥ ከምስጋናም ፡ ጋራ ፡ ቢቀበሉት ፡ የሚጣል ፡ ምንም ፡ የለም ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ በጸሎት ፡ የተቀደሰ ፡ ነውና ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞችን ፡ ብታሳስብ ፥ በእምነትና ፡ በተከተልኸው ፡ በመልካም ፡ ትምህርት ፡ ቃል ፡ የምትመገብ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መልካም ፡ አገልጋይ ፡ ትኾናለኽ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ከሚመችና ፡ የአሮጊቶችን ፡ ሴቶች ፡ ጨዋታ ፡ ከሚመስለው ፡ ተረት ፡ ራቅ ። እግዚአብሔርን ፡ ለመምሰል ፡ ግን ፡ ራስኽን ፡ አስለምድ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ሰውነትን ፡ ለሥጋዊ ፡ ነገር ፡ ማስለመድ ፡ ለጥቂት ፡ ይጠቅማልና ፤ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ ግን ፡ የአኹንና ፡ የሚመጣው ፡ ሕይወት ፡ ተስፋ ፡ ስላለው ፥ ለነገር ፡ ሹሉ ፡ ይጠቅማል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ የታመነ ፥ ሹሉም ፡ እንዲቀበሉት ፡ የተገባ ፡ ነው ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ይህን ፡ ለማግኘት ፡ እንደክማለንና ፥ ስለዚህም ፡ እንሰደባለን ፤ ይህም ፡ ሰውን ፡ ሹሉ ፡ ይልቁንም ፡ የሚያምኑትን ፡ በሚያድን ፡ በሕያው ፡ አምላክ ፡ ተስፋ ፡ ስለምናደርግ ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 11-12 ፤ ይህን ፡ እዘዝና ፡ አስተምር ። በቃልና ፡ በኑሮ ፡ በፍቅርም ፡ በእምነትም ፡ በንጽሕናም ፡ ለሚያምኑቱ ፡ ምሳሌ ፡ ኹን ፡ እንጂ ፥ ማንም ፡ ታናሽነትኽን ፡ አይናቀው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ለማንበብና ፡ ለመምከር ፡ ለማስተማርም ፡ ተጠንቀቅ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ በትንቢት ፡ ከሽማግሌዎች ፡ እጅ ፡ መጫን ፡ ጋራ ፡ የተሰጠኽን ፥ ባንተ ፡ ያለውን ፡ የጸጋ ፡ ስጦታ ፡ ቸል ፡ አትበል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ ማደግኽ ፡ በነገር ፡ ሹሉ ፡ እንዲገለጥ ፡ ይህን ፡ ዐስብ ፥ ይህንም ፡ አዘውትር ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ ለራስኽና ፡ ለትምህርትኽ ፡ ተጠንቀቅ ፥ በእነዚህም ፡ ጽና ፤ ይህን ፡ ብታደርግ ፥ ራስኽንም ፡ የሚሰሙኽንም ፡ ታድናለኽና ።

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 1-2 ፤ ሽማግሌ ፡ የኾነውን ፡ አትገሥጸው ፥ ርሱን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ አባት ፥ ጐበዞችን ፡ እንደ ፡ ወንድሞች ፥ የሸመገሉትን ፡ ሴቶች ፡ እንደ ፡ እናቶች ፥ ቈነጕዖቱን ፡ እንደ ፡ እኅቶች ፡ በፍጹም ፡ ንጽሕና ፡ ለምናቸው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ በእውነት ፡ ባልቴቶች ፡ የኾኑትን ፡ ባልቴቶች ፡ አክብር ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ ማንም ፡ ባልቴት ፡ ግን ፡ ልጆች ፡ ወይም ፡ የልጅ ፡ ልጆች ፡ ቢኖሯት ፥ እነርሱ ፡ አስቀድመው ፡ ለገዛ ፡ ቤተ ፡ ሰዎቻቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ ያሳዩ ፡ ዘንድ ፥ ለወላጆቻቸውም ፡ ብድራትን ፡ ይመልሱላቸው ፡ ዘንድ ፡ ይማሩ ፤ ይህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መልካምና ፡ የተወደደ ፡ ነውና ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ብቻዋንም ፡ ኖራ ፡ በእውነት ፡ ባልቴት ፡ የምትኾን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ታደርጋለች ፥ ሌትና ፡ ቀንም ፡ በልመና ፡ በጸሎትም ፡ ጸንታ ፡ ትኖራለች ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ ቅምጥሊቱ ፡ ግን ፡ በሕይወቷ ፡ ሳለች ፡ የሞተች ፡ ናት ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ ያለነቀፋ ፡ እንዲኾኑ ፡ ይህን ፡ ደግሞ ፡ እዘዝ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ ስለ ኾኑት ፡ ይልቁንም ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ሰዎቹ ፡ የማያስብ ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፥ ሃይማኖትን ፡ የካደ ፡ ከማያምንም ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ የሚከፋ ፡ ነው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ ባልቴት ፡ በመዝገብ ፡ ብትጻፍ ፡ ዕድሜዋ ፡ ከስድሳ ፡ ዓመት ፡ እንዳያንስ ፥ የአንድም ፡ ባል ፡ ሚስት ፡ የነበረች ፡ እንድትኾን ፡ ያስፈልጋል ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ ልጆችን ፡ በማሳደግ ፡ እንግዳዎችንም ፡ በመቀበል ፥ የቅዱሳንንም ፡ እግሮች ፡ በማጠብ ፥ የተጨነቁትንም ፡ በመርዳት ፡ በጎንም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ በመከተል ፥ ይህን ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ በማድረግ ፡ የተመሰከረላት ፡ ልትኾን ፡ ይገባል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ ባል ፡ የሞተባቸውን ፡ ቄነጥኾት ፡ ግን ፡ አትቀበል ፤ በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ ተነሥተው ፡ ሲቀማጠሉ ፡ ሊያገቡ ፡ ይወዳሉና ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ የፊተኛውንም ፡ እምነታቸውን ፡ ስለ ፡ ናቁ ፡ ይፈረድባቸዋል ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ቤት ፡ ለቤት ፡ እየዞሩ ፡ ሥራን ፡ መፍታት ፡ ደግሞ ፡ ይማራሉ ፥ የማይገባውንም ፡ እየተናገሩ ፡ ለፍላፊዎችና ፡ በነገር ፡ ገቢዎች ፡ ይኾናሉ ፡ እንጂ ፥ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ ቄነጥኾት ፡ ሊያገቡ ፥ ልጆችንም ፡ ሊወልዱ ፥ ቤቶቻቸውንም ፡ ሊያስተዳድሩ ፥ ተቃዋሚውም ፡ የሚሳደብበትን ፡ አንድን ፡ ምክንያት ፡ ስንኳ ፡ እንዳይሰጡ ፡ እፈቅዳለኹ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 15 ፤ ካኹን ፡ በፊት ፡ አንዳንዶች ፡ ሰይጣንን ፡ እንዲከተሉ ፡ ፈቀቅ ፡ ብለዋልና ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ባልቴቶች ፡ ያሉት ፡ የሚያምን ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ የምታምን ፡ ብትኾን ፥ ይርዷቸው ፥ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እውነተኞችን ፡ ባልቴቶች ፡ እንድትረዳ ፡ አይክበዱባት ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 17 ፤ በመልካም ፡ የሚያስተዳድሩ ፡ ሽማግሌዎች ፥ ይልቁንም ፡ በመስበክና ፡ በማስተማር ፡ የሚደክሙት ፥ ዕጥፍ ፡ ክብር ፡ ይገባቸዋል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 18 ፤ መጽሐፍ ፦ የሚያበራየውን ፡ በሬ ፡ አፉን ፡ አትሰር ፥ ደግሞ ፦ ለሠራተኛ ፡ ደመ ፡ ወዙ ፡ ይገባዋል ፡ ይላልና ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 19 ፤ ከኹለት ፡ ወይም ፡ ከሦስት ፡ ምስክር ፡ በቀር ፡ በሽማግሌ ፡ ላይ ፡ ክስ ፡ አትቀበል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 20 ፤ ሌላዎቹ ፡ ደግሞ ፡ እንዲፈሩ ፥ ኀጢአት ፡ የሚሠሩትን ፡ በኹሉ ፡ ፊት ፡ ገሥጻቸው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 21 ፤ አንድን ፡ እንኳ ፡ በአድልዎ ፡ ሳታደርግ ፥ እነዚህን ፡ ያለመዘንበል ፡ እንድትጠብቅ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተመረጡትም ፡ መላእክት ፡ ፊት ፡ እመክርኻለኹ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 22 ፤ በማንም ፡ ላይ ፡ ፈጥነኽ ፡ እጆችኽን ፡ አትጫን ፥ በሌላዎችም ፡ ኀጢአት ፡ አትተባበር ፤ ራስኽን ፡ በንጽሕና ፡ ጠብቅ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 23 ፤ ስለ ፡ ሆድኽና ፡ ስለ ፡ በሽታኽ ፡ ብዛት ፡ ጥቂት ፡ የወይን ፡ ጠጅ ፡ ጠጣ ፡ እንጂ ፥ ወደ ፡ ፊት ፡ ውሃ ፡ ብቻ ፡ አትጠጣ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 24 ፤ የአንዳንዶች ፡ ሰዎች ፡ ኀጢአት ፡ የተገለጠ ፡ ነው ፥ ፍርድንም ፡ ያመለክታል ፥ ሌላዎችን ፡ ግን ፡ ይከተላቸዋል ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 5 ፡ 25 ፤ እንዲሁ ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ደግሞ ፡ የተገለጠ ፡ ነው ፥ ያልተገለጠም ፡ ከ"ኾነ ፡ ሊሰወር ፡ አይችልም ።

_____1ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ስምና ፡ ትምህርቱ ፡ እንዳይሰደብ ፥ ከቀንበር ፡ በታች ፡ ያሉቱ ፡ ባሪያዎች ፡ "ሹሉ ፡ ለገዟቸው ፡ ጌታዎች ፡ ክብር ፡ "ሹሉ ፡ እንደተገባቸው ፡ ይቊጠሯቸው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 2 ፤ የሚያምኑም ፡ ጌታዎች ፡ ያሏቸው ፥ ወንድሞች ፡ ስለ ፡ "ኾኑ ፡ አይናቋቸው ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በመልካም ፡ ሥራቸው ፡ የሚጠቅሙ ፡ የሚያምኑና ፡ የተወደዱ ፡ ስለ ፡ "ኾኑ ፥ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ያገልግሉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 3 ፤ እነዚህን ፡ አስተምርና ፡ ምከር ። ማንም ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ የሚያስተምር ፡ ከጌታችንም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ"ኾነው ፡ ጤናማ ፡ ቃልና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመምሰል ፡ በሚስማማ ፡ ትምህርት ፡ የማይጠጋ ፡ ቢ"ኾን ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 4-5 ፤ በትዕቢት ፡ ተነፍቷል ፡ አንዳችም ፡ አያውቅም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ምርመራን ፡ በቃልም ፡ መዋጋትን ፡ እንደ ፡ በሽተኛ ፡ ይናፍቃል ፤ ከነዚህም ፡ ቅንአትና ፡ ክርክር ፡ ስድብም ፡ ክፉ ፡ ዐሳብም ፡ ርስ ፡ በርስ ፡ መናደድም ፡ ይወጣሉ ፥ አእምሯቸውም ፡ በጠፋባቸው ፡ እውነትንም ፡ በተቀሙ ፥ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ ማትረፊያ ፡ የሚ"ኾን ፡ በመሰላቸው ፡ ሰዎች ፡ ይገኛሉ ። እንደነዚህ ፡ ካሉት ፡ ራቅ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 6 ፤ ኑሮዬ ፡ ይበቃኛል ፡ ለሚለው ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ እጅግ ፡ ማትረፊያ ፡ ነው ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 7 ፤ ወደ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ አላመጣንምና ፥

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 8 ፤ አንዳችንም ፡ ልንወስድ ፡ አይቻለንም ፤ ምግብና ፡ ልብስ ፡ ከኖረን ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ ይበቃናል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 9 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ባለጠጋዎች ፡ ሊ"ኾኑ ፡ የሚፈልጉ ፡ በጥፋትና ፡ በመፍረስ ፡ ሰዎችን ፡ በሚያሰጥምና ፡ በሚያሰንፍ ፡ በሚጐዳም ፡ በብዙ ፡ ምኞትና ፡ በፈተና ፡ በወጥመድም ፡ ይወድቃሉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 10 ፤ ገንዘብን ፡ መውደድ ፡ የክፋት ፡ "ሹሉ ፡ ሥር ፡ ነውና ፥ አንዳንዶች ፡ ይህን ፡ ሲመኙ ፥ ከሃይማኖት ፡ ተሳስተው ፡ በብዙ ፡ ሥቃይ ፡ ራሳቸውን ፡ ወጉ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 11 ፤ አንተ ፡ ግን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ሆይ ፥ ከዚህ ፡ ሽሽ ፤ ጽድቅንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፡ እምነትንም ፡ ፍቅርንም ፡ መጽናትንም ፡ የዋህነትንም ፡ ተከታተል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 12 ፤ መልካሙን ፡ የእምነት ፡ ገድል ፡ ተጋደል ፥ የተጠራኽለትንም ፡ በብዙም ፡ ምስክሮች ፡ ፊት ፡ በመልካም ፡ መታመን ፡ የታመንኽለትን ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ ያዝ ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 13 ፤ "ሹሉን ፡ በሕይወት ፡ በሚጠብቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፥ በጳንጤናዊውም ፡ በጴላጦስ ፡ ዘንድ ፡ መልካሙን ፡ መታመን ፡ በመሰከረ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፊት ፡ አዝ"ኻለ"ኹ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 14 ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስኪገለጥ ፡ ድረስ ፡ ያለእድፍና ፡ ያለነቀፋ ፡ "ኾነኽ ፡ ትእዛዙን ፡ ጠብቅ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 15 ፤ ያንም ፡ መገለጡን ፡ በራሱ ፡ ጊዜ ፡ ብፁዕና ፡ ብቻውን ፡ የ"ኾነ ፡ ገዢ ፥ የነገሥታት ፡ ንጉሥና ፡ የጌታዎች ፡ ጌታ ፥ ያሳያል ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ብቻ ፡ የማይሞት ፡ ነው ፤ ማንም ፡ ሊቀርበው ፡ በማይችል ፡ ብርሃን ፡ ይኖራል ፤ አንድ ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ አላየውም ፡ ሊያይም ፡ አይቻለውም ፤ ለርሱ ፡ ክብርና ፡ የዘለዓለም ፡ ኀይል ፡ ይ"ኩን ፤ አሜን ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 17 ፤ ባኹኑ ፡ ዘመን ፡ ባለጠጋዎች ፡ የኾኑት ፡ የትዕቢትን ፡ ነገር ፡ እንዳያስቡ ፥ ደስም ፡ እንዲለን ፡ ዥሉን ፡ አትርፎ ፡ በሚሰጠን ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ በሚያልፍ ፡ ባለጠግነት ፡ ተስፋ ፡ እንዳያደርጉ ፡ እዘዛቸው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 18-19 ፤ እውነተኛውን ፡ ሕይወት ፡ ይይዙ ፡ ዘንድ ፥ ለሚመጣው ፡ ዘመን ፡ ለራሳቸው ፡ መልካም ፡ መሠረት ፡ የሚኾንላቸውን ፡ መዝገብ ፡ እየሰበሰቡ ፥ መልካምን ፡ እንዲያደርጉ ፡ በበጎም ፡ ሥራ ፡ ባለጠጋዎች ፡ እንዲኾኑ ፥ ለረዱና ፡ ለያካፍሉም ፡ የተዘጋጁ ፡ እንዲኾኑ ፡ ምከራቸው ።

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 20 ፤ ጢሞቴዎስ ፡ ሆይ ፥ በውሸት ፡ ዕውቀት ፡ ከተባለ ፡ ለዓለም ፡ ከሚመች ፡ ከከንቱ ፡ መለፍለፍና ፡ መከራከር ፡ እየራቅኽ ፥ የተሰጠኽን ፡ ዐደራ ፡ ጠብቅ ፤

ጢ.ሞ.1 ፡ 6 ፡ 21 ፤ ይህ ፡ ዕውቀት ፡ አለን ፡ ብለው ፥ አንዳንዶች ፡ ስለ ፡ እምነት ፡ ስተዋልና ። ጸጋ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ።

ኹለተኛዉ፡ የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____2 ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እንደሚኾን ፡ የሕይወት ፡ ተስፋ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፥

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ለተወደደው ፡ ልጄ ፡ ለጢሞቴዎስ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከጌታችንም ፡ ከክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ጸጋና ፡ ምሕረት ፡ ሰላምም ፡ ይኹን ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ሌትና ፡ ቀን ፡ በልመናዬ ፡ ሳላቋርጥ ፡ ስለማስብኽ ፡ እንደ ፡ አባቶቼ ፡ አድርጌ ፡ በንጹሕ ፡ ኅሊና ፡ የማመልከውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰግናለኹ ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ እንባኽን ፡ እያሰብኹ ፡ በደስታ ፡ እሞላ ፡ ዘንድ ፡ ላይኽ ፡ እናፍቃለኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ባንተ ፡ ያለውን ፡ ግብዝነት ፡ የሌለበትን ፡ እምነትኽን ፡ ዐስባለኹ ፤ ይህም ፡ እምነት ፡ ቀድሞ ፡ ባያትኽ ፡ በሎይድ ፡ በእናትኽም ፡ በኤውንቄ ፡ ነበረባቸው ፥ ባንተም ፡ ደግሞ ፡ እንዳለ ፡ ተረድቻለኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፥ እሳት ፡ እንደሚያቀጣጥል ፡ ሰው ፥ እጆቼን ፡ በመጫኔ ፡ ባንተ ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስጦታ ፡ እንድታነሣሣ ፡ አሳስብኻለኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔር ፡ የኀይልና ፡ የፍቅር ፡ ራስንም ፡ የመግዛት ፡ መንፈስ ፡ እንጂ ፡ የፍርሀት ፡ መንፈስ ፡ አልሰጠንምና ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ እንግዲህ ፡ በጌታችን ፡ ምስክርነት ፡ ወይም ፡ በእስረኛው ፡ በእኔ ፡ አትፈር ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ መጠን ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ዐብረኽኝ ፡ መከራን ፡ ተቀበል ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ያዳነን ፡ በቅዱስም ፡ አጠራር ፡ የጠራን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፥ ይህም ፡ እንደ ፡ ራሱ ፡ ዐሳብና ፡ ጸጋ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሥራችን ፡ መጠን ፡ አይደለም ፤ ይህም ፡ ጸጋ ፡ ከዘለዓለም ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ተሰጠን ፥

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 10 - 11 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በመድኀኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መገለጥ ፡ ታይቷል ። ርሱ ፡ ሞትን ፡ ሽሯልና ፥ እኔ ፡ ሰባኪና ፡ ሐዋርያ ፥ አሕዛብንም ፡ አስተማሪ ፡ እንድኾን ፡ በተሾምኹበት ፡ በወንጌል ፡ ሕይወትንና ፡ አለመጥፋትን ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አውጥቷል ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ ይህን ፡ መከራ ፡ ደግሞ ፡ ተቀብያለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አላፍርበትም ፤ ያመንኹትን ፡ ዐውቃለኹና ፥ የሰጠኹትንም ፡ ዐደራ ፡ እስከዚያ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ሊጠብቅ ፡ እንዲችል ፡ ተረድቻለኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ባለ ፡ እምነትና ፡ ፍቅር ፡ አድርገኽ ፥ ከእኔ ፡ የሰማኸውን ፡ ጤናማ ፡ ቃል ፡ ምሳሌ ፡ ያዝ ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 1 ፥ 14 ፤ መልካሙን ፡ ዐደራ ፡ በእኛ ፡ በሚኖረው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጠብቅ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 1 ፡ 15 ፤ በእስያ ፡ ያሉቱ ፡ ኹሉ ፡ ከእኔ ፡ ፈቀቅ ፡ እንዳሉ ፡ ታውቃለኽ ፥ ከነርሱም ፡ ፊሎጎስና ([301]) ፡ ሄርዋጌኔስ ([302]) ፡ ናቸው ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 1 ፡ 16 ፤ ጌታ ፡ ልሄኔሲፎሩ ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ምሕረትን ፡ ይስጥ ፥ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አሳርፎኛልና ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 1 ፡ 17 ፤ በሰንሰለቴም ፡ አላፈረበትም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በሮሜ ፡ ባደረ ፡ ጊዜ ፡ ፈልጎ ፡ ፈልጎ ፡ አገኘኝ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 1 ፡ 18 ፤ በዚያ ፡ ቀን ፡ ከጌታ ፡ ምሕረትን ፡ እንዲያገኝ ፡ ጌታ ፡ ይስጠው ፤ በኤፌሶንም ፡ እንዴት ፡ እንዳገለገለኝ ፡ አንተ ፡ በደኅና ፡ ታውቃለኽ ።

2 ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፥ ልጄ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ባለው ፡ ጸጋ ፡ በርታ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 2 ፤ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የመሰከሩለትን ፥ ከእኔም ፡ የሰማኸውን ፥ ሌላዎችን ፡ ደግሞ ፡ ሊያስተምሩ ፡ ለሚችሉ ፣ ለታመኑ ፡ ሰዎች ፡ ዐደራ ፡ ስጥ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 3 ፤ እንደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጎ ፡ ወታደር ፡ ኾነኽ ፥ ዐብረኸኝ ፡ መከራ ፡ ተቀበል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 4 ፤ የሚዘምተው ፡ ኹሉ ፡ ለጦር ፡ ያስከተተውን ፡ ደስ ፡ ያሠኝ ፡ ዘንድ ፡ ትዳር ፡ በሚገኝበት ፡ ንግድ ፡ ራሱን ፡ አያጠላልፍም ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 5 ፤ ደግሞም ፡ በጨዋታ ፡ የሚታገል ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፥ እንደሚገባ ፡ አድርጎ ፡ ባይታገል ፥ የድሉን ፡ አክሊል ፡ አያገኝም ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 6 ፤ የሚደክመው ፡ ገበሬ ፡ ፍሬውን ፡ ከሚበሉት ፡ መገኮመሪያ ፡ እንዲኾን ፡ ይገባዋል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 7 ፤ የምለውን ፡ ተመልከት ፤ ጌታም ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ማስተዋልን ፡ ይስጥኽ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 8 ፤ በወንጌል ፡ እንደምሰብከው ፥ ከሙታን ፡ የተነሣውን ፥ ከዳዊት ፡ ዘርም ፡ የኾነውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ዐስብ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 9 ፤ ይህንም ፡ በመስበክ ፡ እንደ ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ እስክታሰር ፡ ድረስ ፡ መከራ ፡ እቀበላለኹ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ አይታሰርም ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ያለውን ፡ መዳን ፡ ከዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ጋራ ፡ እንዲያገኙ ፡ ስለተመረጡት ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እጸናለኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ቃሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ የሚለው ፦ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከሞትን ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ በሕይወት ፡ እንኖራለን ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ብንጸና ፥ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ እንነግሣለን ፤ ብንክደው ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይክደናል ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ ባናምነው ፥ ርሱ ፡ የታመነ ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ፤ ራሱን ፡ ሊክድ ፡ አይችልምና ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ይህን ፡ አሳስባቸው ፥ በቃልም ፡ እንዳይጣሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ምከራቸው ፥ ይህ ፡ ምንም ፡ የማይረባ ፡ የሚሰሙትንም ፡ የሚያፈርስ ፡ ነውና ።

---

301 ጽር. ፥ ፉጌሎስ ፡ (ሸሺ ፥ ኩብላይ) ።

302 ጽር. ፥ ሄርሞጌኔስ ፡ (የሄርሜስ ፡ ተወላጅ) ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ የእውነትን ፡ ቃል ፡ በቅንነት ፡ የሚናገር ፡ የማያሳፍርም ፡ ሠራተኛ ፡ ኾነኽ ፥ የተፈተነውን ፡ ራስኽን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልታቀርብ ፡ ትጋ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ለዓለም ፡ ከሚመች ፡ ከከንቱ ፡ መለፍለፍ ፡ ራቅ ፤ ኀጢአተኝነታቸውን ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ይጨምራሉና ፥ ቃላቸውም ፡ እንደ ፡ ጭንቀኵር ፡ ይባላል ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ከነርሱም ፡ ሄሜኔዎስና ፡ ፊሊጦስ ፡ ናቸው ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 18 ፤ እነዚህም ፦ ትንሣኤ ፡ ካኹን ፡ በፊት ፡ ኾኗል ፡ እያሉ ፥ ስለ ፡ እውነት ፡ ስተው ፥ የአንዳንዶችን ፡ እምነት ፡ ይገለብጣሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ኾኖም ፦ ጌታ ፡ ለርሱ ፡ የኾኑትን ፡ ያውቃል ፥ ደግሞም ፦ የጌታን ፡ ስም ፡ የሚጠራ ፡ ኹሉ ፡ ከዐመፅ ፡ ይራቅ ፡ የሚለው ፡ ማኅተም ፡ ያለበት ፡ የተደላደለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መሠረት ፡ ቆሟል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 20 ፤ በትልቅም ፡ ቤት ፡ የዕንጨትና ፡ የሸክላ ፡ ዕቃ ፡ ደግሞ ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ የወርቅና ፡ የብር ፡ ዕቃ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ እኩሌታዎቹም ፡ ለክብር ፥ እኩሌታዎቹም ፡ ለውርደት ፡ ይኾናሉ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 21 ፤ እንግዲህ ፡ ማንም ፡ ራሱን ፡ ከነዚህ ፡ ቢያነጻ ፥ ለክብር ፡ የሚኾን ፡ የተቀደሰም ፡ ለጌታውም ፡ የሚጠቅም ፡ ለበጎም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ዕቃ ፡ ይኾናል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ከክፉ ፡ የጕልማሳነት ፡ ምኞት ፡ ግን ፡ ሽሽ ፥ በንጹሕም ፡ ልብ ፡ ጌታን ፡ ከሚጠሩ ፡ ጋራ ፡ ጽድቅን ፡ እምነትን ፡ ፍቅርን ፡ ሰላምን ፡ አጥብቀኽ ፡ ተከተል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጠብን ፡ እንዲያመጣ ፡ ዐውቀኽ ፡ ከሰነፎችና ፡ ካልተማሩ ፡ ምርመራ ፡ ራቅ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 24 ፤ የጌታም ፡ ባሪያ ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ገር ፡ ለማስተማርም ፡ የሚበቃ ፡ ለትዕግሥትም ፡ የሚጸና ፡ ሊኾን ፡ እንጂ ፡ ሊጣላ ፡ አይገባውም ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 2 ፡ 25-26 ፤ ደግሞም ፦ ምናልባት ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነትን ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ ንስሓን ፡ ይሰጣቸዋልና ፥ ፈቃዱን ፡ ለማድረግ ፡ በዲያብሎስ ፡ ሕያዋን ፡ ኾነው ፡ ከተያዙበት ፡ ወጥመድ ፡ ወጥተው ፥ ወደ ፡ አእምሮ ፡ ይመለሳሉ ፡ ብሎ ፡ የሚቃወሙትን ፡ በየዋህነት ፡ ይቅጣ ።

2 ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በመጨረሻው ፡ ቀን ፡ የሚያስጨንቅ ፡ ዘመን ፡ እንዲመጣ ፡ ይህን ፡ ዕወቅ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሰዎች ፡ ራሳቸውን ፡ የሚወዱ ፡ ይኾናሉና ፥ ገንዘብን ፡ የሚወዱ ፥ ትምክሕተኞች ፥ ትዕቢተኞች ፥ ተሳዳቢዎች ፥ ለወላጆቻቸው ፡ የማይታዘዙ ፥ የማያመሰግኑ ፥

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ቅድስና ፡ የሌላቸው ፥ ፍቅር ፡ የሌላቸው ፥ ዕርቅን ፡ የማይሰሙ ፥ ሐሜተኞች ፥ ራሳቸውን ፡ የማይገዙ ፥ ጨካኞች ፥ መልካም ፡ የኾነውን ፡ የማይወዱ ፥

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ከዳተኞች ፥ ችኩሎች ፥ በትዕቢት ፡ የተነፉ ፥ ከእግዚአብሔር ፡ ይልቅ ፡ ተድላን ፡ የሚወዱ ፡ ይኾናሉ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ የአምልኮት ፡ መልክ ፡ አላቸው ፡ ኀይሉን ፡ ግን ፡ ክደዋል ፤ ከነዚህ ፡ ደግሞ ፡ ራቅ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 3 ፡ 6-7 ፤ ወደ ፡ ቤቶች ፡ ሾልከው ፡ እየገቡ ፥ ኀጢአታቸው ፡ የተከመረባቸውን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ምኞትም ፡ የሚወሰዱትን ፡ ሹልጊዜም ፡ እየተማሩ ፡ እውነትን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ሊደርሱ ፡ ከቶ ፡ የማይችሉትን ፡ ሞኞችን ፡ ሴቶች ፡ የሚማርኩ ፥ ከነዚህ ፡ ዘንድ ፡ ናቸውና ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 8 ፤ ኢያኔስና ፡ ኢያንበሬስም ፡ ሙሴን ፡ እንደ ፡ ተቃወሙት ፥ እንዲሁ ፡ እነዚህ ፡ ደግሞ ፡ አእምሯቸው ፡ የጠፋባቸው ፡ ስለ ፡ እምነትም ፡ የተጣሉ ፡ ሰዎች ፡ ኾነው ፥ እውነትን ፡ ይቃወማሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 9 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእነዚያ ፡ ሞኝነት ፡ ደግሞ ፡ ግልጥ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሞኝነታቸው ፡ ለ ፡ ሁሉ ፡ ይገለጣልና ፥ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ አይቀናላቸውም ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 10 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ትምህርቴንና ፡ አካኼዴን ፡ ዐሳቤንም ፡ እምነቴንም ፡ ትዕግሥቴንም ፡ ፍቅሬንም ፡ መጽናቴንም ፡ ስደቴንም ፡ መከራዬንም ፡ ተከተልኽ ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 11 ፤ በአንጾኪያና ፡ በኢቆንዮን ፡ በልስጥራንም ፡ የኾነብኝን ፡ የታገሥኹትንም ፡ ስደት ፡ ታውቃለኽ ፤ ጌታም ፡ ከ ፡ ሁሉ ፡ አዳነኝ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 12 ፤ በእውነትም ፡ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየመሰሉ ፡ ሊኖሩ ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ይሰደዳሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክፉዎች ፡ ሰዎችና ፡ አታላዮች ፥ እያሳቱና ፡ እየሳቱ ፥ በክፋት ፡ እየባሱ ፡ ይኼዳሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 14 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ በተማርኽበትና ፡ በተረዳኽበት ፡ ነገር ፡ ጸንተኽ ፡ ኑር ፥ ከማን ፡ እንደ ፡ ተማርኸው ፡ ታውቃለኽና ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 15 ፤ ከሕፃንነትኽም ፡ ዠምረኽ ፡ ክርስቶስ ፡ ኢየሱስን ፡ በማመን ፥ መዳን ፡ የሚገኝበትን ፡ ጥበብ ፡ ሊሰጡኽ ፡ የሚችሉትን ፡ ቅዱሳን ፡ መጻሕፍትን ፡ ዐውቀኻል ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 3 ፥ 16-17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ሰው ፡ ፍጹምና ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ የተዘጋጀ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ያለበት ፡ መጽሐፍ ፡ ሁሉ ፡ ለትምህርትና ፡ ለተግሣጽ ፥ ልብንም ፡ ለማቅናት ፥ በጽድቅም ፡ ላለው ፡ ምክር ፡ ደግሞ ፡ ይጠቅማል ።

_____2 ኛ ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 1 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታንም ፡ ሊፈርድ ፡ ባለው ፡ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፊት ፥ በመገለጡና ፡ በመንግሥቱም ፡ እመክርኻለኹ ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 2 ፤ ቃሉን ፡ ስበክ ፥ በጊዜውም ፡ አለጊዜውም ፡ ጽና ፥ ፈጽመኽ ፡ እየታገሥኽና ፡ እያስተማርኽ ፥ ዝለፍና ፡ ገሥጽ ፡ ምከርም ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 3 ፤ ሕይወት ፡ የሚገኝበትን ፡ ትምህርት ፡ የማይታገሡበት ፡ ዘመን ፡ ይመጣልና ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጕሮዎቻቸውን ፡ የሚያሳክክ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ እንደ ፡ ገዛ ፡ ምኞታቸው ፡ ለራሳቸው ፡ አስተማሪዎችን ፡ ያከማቻሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 4 ፤ እውነትንም ፡ ከመስማት ፡ ጕሮዎቻቸውን ፡ ይመልሳሉ ፥ ወደ ፡ ተረትም ፡ ፈቀቅ ፡ ይላሉ ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 5 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ነገርን ፡ ሁሉ ፡ በልክ ፡ አድርግ ፥ መከራን ፡ ተቀበል ፥ የወንጌል ፡ ሰባኪነትን ፡ ሥራ ፡ አድርግ ፥ አገልግሎትኽን ፡ ፈጽም ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 6 ፤ በመሥዋዕት ፡ እንደሚደረግ ፥ የእኔ ፡ ሕይወት ፡ ይሠዋልና ፥ የምኼድበትም ፡ ጊዜ ፡ ደርሷል ።

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 7 ፤ መልካሙን ፡ ገድል ፡ ተጋድያለኹ ፥ ሩጫውን ፡ ጨርሻለኹ ፥ ሃይማኖትን ፡ ጠብቄያለኹ ፤

ጢ.ሞ.2 ፥ 4 ፥ 8 ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ የጽድቅ ፡ አክሊል ፡ ተዘጋጅቶልኛል ፥ ይህንም ፡ ጻድቅ ፡ ፈራጅ ፡ የኾነው ፡ ጌታ ፡ ያን ፡ ቀን ፡ ለእኔ ፡ ያስረክባል ፥ ደግሞም ፡ መገለጡን ፡ ለሚወዱት ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ ለእኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 9 ፤ በቶሎ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንድትመጣ ፡ ትጋ ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ዴማስ ፡ የአኹኑን ፡ ዓለም ፡ ወዶ ፡ ትቶኛልና ፥ ወደ ፡ ተሰሎንቄም ፡ ኼዷል ፤ ቄርቂስም ፡ ወደ ፡ ገላትያ ፡ ቲቶም ፡ ወደ ፡ ድልማጥያ ፡ ኼደዋል ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 11 ፤ ሉቃስ ፡ ብቻ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አለ ። ማርቆስ ፡ ለአገልግሎት ፡ ብዙ ፡ ይጠቅመኛልና ፥ ይዘኸው ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አምጣው ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ቲኪቆስን ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ላክኹት ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 13 ፤ ስትመጣ ፡ በጢሮዳ ፡ ከአክርጳ ፡ ዘንድ ፡ የተውኹትን ፡ በርኖሱንና ፡ መጻሕፍቱን ፡ ይልቁንም ፡ በብራና ፡ የተጻፉትን ፡ አምጣልኝ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 14 ፤ የናስ ፡ አንጥረኛው ፡ እስክንድሮስ ፡ እጅግ ፡ ከፋብኝ ፤ ጌታ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ ይመልስለታል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 15 ፤ አንተም ፡ ደግሞ ፡ ከርሱ ፡ ተጠበቅ ፥ የምንናገረውን ፡ እጅግ ፡ ተቃውሟልና ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 16 ፤ በፊተኛው ፡ ሙግቴ ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ አልደረሰልኝም ፥ ኹሉም ፡ ተዉኝ ፡ እንጂ ፤ ይህንም ፡ አይቊጠርባቸው ፤

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 17 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የስብከቱ ፡ ሥራ ፡ በእኔ ፡ እንዲፈጸም ፡ አሕዛብም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሰሙት ፥ ጌታ ፡ በእኔ ፡ አጠገብ ፡ ቆሞ ፡ አበረታኝ ፥ ከአንበሳ ፡ አፍም ፡ ዳንኹ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ጌታም ፡ ከክፉ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ያድነኛል ፡ ለሰማያዊውም ፡ መንግሥት ፡ ይጠብቀኛል ፤ ለርሱ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 19 ፤ ለጵርስቅላና ፡ ለአቂላ ፡ ለሄኔሲፎሩም ፡ ቤተ ፡ ሰዎች ፡ ሰላምታ ፡ አቅርብልኝ ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 20 ፤ ኤርስጦስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ቀረ ፥ ጥሮፊሞስን ፡ ግን ፡ ታሞ ፡ በሚሊጢን ፡ ተውኹት ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 21 ፤ ከክረምት ፡ በፊት ፡ እንድትመጣ ፡ ትጋ ። ኤውግሎስና ፡ ጴዴስ ፥ ሊኖስም ፡ ቅላውዲያም ፥ ወንድሞችም ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡልኻል ።

ጢ.ሞ.2 ፡ 4 ፡ 22 ፤ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመንፈስኽ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ። ጸጋ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቲቶ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ቲቶ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ቲቶ ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ባሪያና ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ጳውሎስ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ለተመረጡት ፡ እምነት ፡ እንዲኾንላቸው ፡ በዘለዓለምም ፡ ሕይወት ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ አምልኮት ፡ ያለውን ፡ እውነት ፡ እንዲያውቁ ፡ የተላከ ፤ ስለዚህም ፡ ሕይወት ፡ የማይዋሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከዘለዓለም ፡ ዘመናት ፡ በፊት ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ፥

ቲቶ ፥ 1 ፥ 3 ፤ በዘመኑም ፡ ጊዜ ፥ መድኀኒታችን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳዘዘ ፥ ለእኔ ፡ ዐደራ ፡ በተሰጠኝ ፡ ስብከት ፡ ቃሉን ፡ ገለጠ ፤

ቲቶ ፥ 1 ፥ 4 ፤ በሃይማኖት ፡ ኀብረት ፡ እውነተኛ ፡ ልጄ ፡ ለሚኾን ፡ ለቲቶ ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ከመድኀኒታችንም ፡ ከጌታ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ምሕረት ፡ ሰላምም ፡ ይኹን ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 5 ፤ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ የቀረውን ፡ እንድታደራጅ ፡ በየከተማውም ፥ እኔ ፡ አንተን ፡ እንዳዘዝኹ ፥ ሽማግሌዎችን ፡ እንድትሾም ፡ በቀርጤስ ፡ ተውኹኽ ፤

ቲቶ ፥ 1 ፥ 6 ፤ የማይነቀፍና ፡ የአንዲት ፡ ሚስት ፡ ባል ፡ የሚኾን ፥ የሚያምኑም ፡ ልጆች ፡ ያሉት ፥ ስለ ፡ መዳራትም ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አለመታዘዝ ፡ የማይከሰስ ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፥ ሹመው ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 7 ፤ ኤጲስ ፡ ቆጶስ ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ መጋቢ ፥ የማይነቀፍ ፡ ሊኾን ፡ ይገባዋልና ፤ የማይኰራ ፥ የማይቈጣ ፥ የማይሰክር ፥ የማይጨቃጨቅ ፥ ነውረኛ ፡ ረብ ፡ የማይወድ ፥

ቲቶ ፥ 1 ፥ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንግዳ ፡ ተቀባይ ፥ በጎ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ የሚወድ ፥ ጠንቃቃ ፥ ጻድቅ ፥ ቅዱስ ፥ ራሱን ፡ የሚገዛ ፡ ይኹን ፤

ቲቶ ፥ 1 ፥ 9 ፤ ሕይወት ፡ በሚገኝበት ፡ ትምህርት ፡ ደግሞ ፡ ሊመክር ፡ ተቃዋሚዎቹንም ፡ ሊወቅስ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፥ እንደተማረው ፡ በታመነ ፡ ቃል ፡ ይጽና ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 10 ፤ የማይታዘዙና ፡ ከንቱ ፡ የሚናገሩ ፡ የሚያታልሉ ፡ ይልቁንም ፡ ከተገረዙት ፡ ወገን ፡ የሚኾኑ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፤

ቲቶ ፥ 1 ፥ 11 ፤ እነዚህም ፡ ስለ ፡ ነውረኛ ፡ ረብ ፡ የማይገባውን ፡ እያስተማሩ ፡ ቤቶችን ፡ በሞላው ፡ ስለሚገለብጡ ፥ አፋቸውን ፡ መዝጋት ፡ ይገባል ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 12 ፤ የገዛ ፡ ራሳቸው ፡ ነቢይ ፡ የኾነ ፡ ከነርሱ ፡ አንዱ ፦ የቀርጤስ ፡ ሰዎች ፡ ዘወትር ፡ ውሸተኞች ፥ ክፉዎች ፡ አራዊት ፥ በላተኞች ፥ ሥራ ፡ ፈቶች ፡ ናቸው ፡ ብሏል ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 13-14 ፤ ይህ ፡ ምስክር ፡ እውነተኛ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ የአይሁድን ፡ ተረትና ፡ ከእውነት ፡ ፈቀቅ ፡ የሚሉትን ፡ ሰዎች ፡ ትእዛዝ ፡ ሳያዳምጡ ፥ በሃይማኖት ፡ ጤናማዎች ፡ እንዲኾኑ ፡ በብርቱ ፡ ውቀሣቸው ።

ቲቶ ፥ 1 ፥ 15 ፤ ኹሉ ፡ ለንጹሐች ፡ ንጹሕ ፡ ነው ፤ ለርኩሳንና ፡ ለማያምኑ ፡ ግን ፡ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ምንም ፡ የለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አእምሯቸውም ፡ ኅሊናቸውም ፡ ረክሷል ።

ቲቶ ፡ 1 ፡ 16 ፤ እግዚአብሔርን ፡ እንዲያውቁ ፡ በግልጥ ፡ ይናገራሉ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ የሚያስጸይፉና ፡ የማይታዘዙ ፡ ለበጎ ፡ ሥራም ፡ ኹሉ ፡ የማይበቁ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ በሥራቸው ፡ ይክዱታል ።

ቲቶ ፡ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 1 ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ሕይወት ፡ ለሚገኝበት ፡ ትምህርት ፡ የሚገባውን ፡ ተናገር ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሽማግሌዎች ፡ ልከኞች ፥ ጭምቶች ፥ ራሳቸውን ፡ የሚገዙ ፥ በእምነትና ፡ በፍቅር ፡ በመጽናትም ፡ ጤናማዎች ፡ እንዲኾኑ ፡ ምከራቸው ፤

ቲቶ ፡ 2 ፡ 3 ፤ እንዲሁም ፡ አሮጊቶች ፡ ሴቶች ፡ አካኼዳቸው ፡ ለቅዱስ ፡ አገልግሎት ፡ የሚገባ ፥ የማያሙ ፥ ለብዙ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የማይገዙ ፥ በጎ ፡ የኾነውን ፡ ነገር ፡ የሚያስተምሩ ፡ ይኹኑ ፤

ቲቶ ፡ 2 ፡ 4-5 ፤ ቈነጕዥትም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዳይሰደብ ፥ ባሎቻቸውን ፡ የሚወዱ ፥ ልጆቻቸውን ፡ የሚወዱ ፥ ራሳቸውን ፡ የሚገዙ ፥ ንጹሐች ፥ በቤት ፡ የሚሠሩ ፥ በጎዎች ፥ ለባሎቻቸው ፡ የሚታዘዙ ፡ እንዲኾኑ ፡ ይምከሯቸው ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 6 ፤ ጕበዞችም ፡ እንዲሁ ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲገዙ ፡ ምከራቸው ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 7-8 ፤ የሚቃወም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ የሚናገረውን ፡ መጥፎ ፡ ነገር ፡ ሲያጣ ፡ እንዲያፍር ፥ በነገር ፡ ኹሉ ፡ መልካምን ፡ በማድረግ ፡ ምሳሌ ፡ የሚኾን ፡ ራስኽን ፡ አሳይ ፤ በትምህርትኽም ፡ ደኅንነትን ፥ ጭምትነትን ፥ ጤናማና ፡ የማይነቀፍ ፡ ንግግርን ፡ ግለጥ ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 9-10 ፤ ባሪያዎች ፡ ስለ ፡ መድኀኒታችን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚኾነውን ፡ ትምህርት ፡ በኹሉ ፡ ነገር ፡ ያስመሰግኑ ፡ ዘንድ ፥ ለገዛ ፡ ጌታዎቻቸው ፡ እንዲገዙ ፡ በኹሉም ፡ ደስ ፡ እንዲያሠኙ ፥ ሳይቃወሙና ፡ ሳይሰርቁም ፡ በጎ ፡ ታማኝነትን ፡ ኹሉ ፡ እንዲያሳዩ ፡ ምከራቸው ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 11 ፤ ሰዎችን ፡ ኹሉ ፡ የሚያድን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ተገልጧልና ፤

ቲቶ ፡ 2 ፡ 12-13 ፤ ይህም ፡ ጸጋ ፥ ኀጢአተኝነትንና ፡ ዓለማዊን ፡ ምኞት ፡ ክደን ፥ የተባረከውን ፡ ተስፋችንን ፡ ርሱም ፡ የታላቁን ፡ የአምላካችንንና ፡ የመድኀኒታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ክብር ፡ መገለጥ ፡ እየጠበቅን ፥ ራሳችንን ፡ በመግዛትና ፡ በጽድቅ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ በመምሰል ፡ ባኹኑ ፡ ዘመን ፡ እንድንኖር ፡ ያስተምረናል ፤

ቲቶ ፡ 2 ፡ 14 ፤ መድኀኒታችንም ፡ ከዐመፅ ፡ ኹሉ ፡ እንዲቤዣን ፥ መልካሙንም ፡ ለማድረግ ፡ የሚቀናውን ፡ ገንዘቡም ፡ የሚኾነውን ፡ ሕዝብ ፡ ለራሱ ፡ እንዲያነጻ ፥ ስለ ፡ እኛ ፡ ነፍሱን ፡ ሰጥቷል ።

ቲቶ ፡ 2 ፡ 15 ፤ ይህን ፡ በሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ተናገርና ፡ ምከር ፡ ገሥጽም ፤ ማንም ፡ አይናቅኽ ።

ቲቶ ፡ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ቲቶ ፡ 3 ፡ 1-2 ፤ ለገዢዎችና ፡ ለባለ ፡ ሥልጣኖች ፡ የሚገዙና ፡ የሚታዘዙ ፥ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ የተዘጋጁ ፥ ማንንም ፡ የማይሰድቡ ፥ የማይከራከሩ ፥ ገሮች ፥ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ የዋህነትን ፡ ኹሉ ፡ የሚያሳዩ ፡ እንዲኾኑ ፡ አሳስባቸው ።

ቲቶ ፡ 3 ፡ 3 ፤ እኛ ፡ ደግሞ ፡ አስቀድመን ፡ የማናስተውል ፡ ነበርንና ፤ የማንታዘዝ ፥ የምንስት ፥ ለምኞትና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ተድላ ፡ እንደ ፡ ባሪያዎች ፡ የምንገዛ ፥ በክፋትና ፡ በምቀኝነት ፡ የምንኖር ፥ የምንጣላ ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ የምንጠላላ ፡ ነበርን ።

ቲቶ ፡ 3 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የመድኀኒታችን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነትና ፡ ሰውን ፡ መውደዱ ፡ በተገለጠ ፡

ጊዜ ፥

ቲቶ ፥ 3 ፥ 5 ፤ እንደ ፡ ምሕረቱ ፡ መጠን ፡ ለዐዲስ ፡ ልደት ፡ በሚኾነው ፡ መታጠብና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመታደስ ፡ አዳነን ፡ እንጂ ፥ እኛ ፡ ስላደረግነው ፡ በጽድቅ ፡ ስለ ፡ ነበረው ፡ ሥራ ፡ አይደለም ፤

ቲቶ ፥ 3 ፥ 6-7 ፤ ያን ፡ መንፈስም ፥ በጸጋው ፡ ጸድቀን ፡ በዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ተስፋ ፡ ወራሾች ፡ እንድንኾን ፥ በመድኀኒታችን ፡ በ[ኢ]የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ አትርፎ ፡ አፈሰሰው ።

ቲቶ ፥ 3 ፥ 8 ፤ ቃሉ ፡ የታመነ ፡ ነው ። [እ]ግዚአብሔርንም ፡ የሚያምኑት ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲጸኑ ፥ እነዚህን ፡ አስረግጠኽ ፡ እንድትናገር ፡ እፈቅዳለኹ ። ይህ ፡ መልካምና ፡ ለሰዎች ፡ የሚጠቅም ፡ ነው ፤

ቲቶ ፥ 3 ፥ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሞኝነት ፡ ካለው ፡ ምርመራና ፡ ከትውልዶች ፡ ታሪክ ፡ ከክርክርም ፡ ስለ ፡ ሕግም ፡ ከሚኾን ፡ ጠብ ፡ ራቅ ፤ የማይጠቅሙና ፡ ከንቱዎች ፡ ናቸውና ፤

ቲቶ ፥ 3 ፥ 10-11 ፤ መለያየትን ፡ የሚያነሣ ፡ ሰው ፡ ጠማማ ፡ እንዲኾን ፡ በራሱም ፡ ላይ ፡ ፈርዶ ፡ ኀጢአትን ፡ እንዲያደርግ ፡ ዐውቀኽ ፥ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ኹለት ፡ ጊዜም ፡ ከገሠጽኸው ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ከሚመስል ፡ ሰው ፡ ራቅ ።

ቲቶ ፥ 3 ፥ 12 ፤ አርጢሞንን ([303]) ፡ ወይም ፡ ቲኪቆስን ፡ ወዳንተ ፡ ስልክ ፥ ወደ ፡ ኒቆጵልዮን ([304]) ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ እንድትመጣ ፡ ትጋ ፤ በዚያ ፡ ልከርም ፡ ቈርጫለኹና ።

ቲቶ ፥ 3 ፥ 13 ፤ ሕግ ፡ ዐዋቂውን ፡ ዜማስንና ([305]) ፡ አጵሎስን ፡ ምንም ፡ እንዳይጐድልባቸው ፡ በጕዟቸው ፡ ተግተኽ ፡ ርዳ ።

ቲቶ ፥ 3 ፥ 14 ፤ ከወገናችንም ፡ ያሉት ፡ ደግሞ ፡ ፍሬ ፡ ቢሶች ፡ ኾነው ፡ እንዳይቀሩ ፥ የግድ ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ ነገር ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ እንዲጸኑ ፡ ይማሩ ።

ቲቶ ፥ 3 ፥ 15 ፤ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ያሉት ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡልኻል ። በእምነት ፡ ለሚወዱን ፡ ሰላምታ ፡ አቅርብልን ። ጸጋ ፡ ከኹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

---

303 ጽር. ፥ አርቴማስ ።

304 ጽር. ፥ ኒኮፖሊስ ።

305 ጽር. ፥ ዜናስ ።

የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ፊልሞና ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ፊልሞና ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ፊል. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ እስር ፡ ጳውሎስ ፡ ወንድሙም ፡ ጢሞቴዎስ ፥ ለተወደደውና ፡ ዐብሮን ፡ ለሚሠራ ፡ ለፊልሞና ፥

ፊል. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ለእኅታችንም ፡ ለአፍብያ ፥ ከእኛም ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ወታደር ፡ ለኾነ ፡ ለአርክጳ ፥ በቤትኽም ፡ ላለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ከአባታችን ፡ ከጌታም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ፊል. ፥ 1 ፥ 4-5 ፤ በጌታ ፡ በኢየሱስ ፡ ዘንድ ፡ በቅዱሳንም ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ስላለኽ ፡ ስለ ፡ ፍቅርኽና ፡ ስለ ፡ እምነትኽ ፡ ሰምቼ ፥ በጸሎቴ ፡ እያሳሰብኹ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ አምላኬን ፡ አመሰግናለኹ ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 6 ፤ የእምነትኽም ፡ ኅብረት ፥ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ በማወቅ ፥ ለክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ፍሬ ፡ እንዲያፈራ ፡ እለምናለኹ ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 7 ፤ የቅዱሳን ፡ ልብ ፡ ባንተ ፡ ሥራ ፡ ስለ ፡ ዐረፈ ፥ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ በፍቅርኽ ፡ ብዙ ፡ ደስታንና ፡ መጽናናትን ፡ አግኝቻለኹና ።

ፊል. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ስለዚህ ፥ የሚገባውን ፡ አዝኽ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ብዙ ፡ ድፍረት ፡ ቢኖረኝ ፥

ፊል. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ይልቁንም ፡ እንደዚህ ፡ የኾንኹ ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ሽማግሌው ፥ አኹንም ፡ ደግሞ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እስር ፡ የኾንኹ ፥ ስለ ፡ ፍቅር ፡ እለምናለኹ ።

ፊል. ፥ 1 ፥ 10-11 ፤ አስቀድሞ ፡ ስላልጠቀመኽ ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ለኔም ፡ ለአንተም ፡ ስለሚጠቅም ፡ በእስራቴ ፡ ስለወለድኹት ፡ ስለ ፡ ልጄ ፡ ስለ ፡ ኦናሲሞስ ፡ እለምንኻለኹ ።

ፊል. ፥ 1 ፥ 12 ፤ ርሱን ፡ እልከዋለኹ ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 13 ፤ አንተም ፡ ልቤ ፡ እንደሚኾን ፡ ተቀበለው ። እኔስ ፡ በወንጌል ፡ እስራት ፡ ስለ ፡ አንተ ፡ እንዲያገለግለኝ ፡ ለራሴ ፡ ላስቀረው ፡ እፈቅድ ፡ ነበር ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጎነትኽ ፡ በፈቃድኽ ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ እንዳይኾን ፥ ሳልማከርኽ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ላደርግ ፡ አልወደድኹም ።

ፊል. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ተቀብለኽ ፡ ለዘለዓለም ፡ እንድትይዘው ፡ ስለዚህ ፡ ምናልባት ፡ ለጊዜው ፡ ተለይቶኻልና ፤

ፊል. ፥ 1 ፥ 16 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ እንደ ፡ ባሪያ ፡ አይኾንም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለእኔ ፡ በተለየ ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ ከኾነ ፥ ለአንተማ ፡ ይልቅ ፡ በሥጋውም ፡ በጌታም ፡ ዘንድ ፡ ከባሪያ ፡ የሚሻል ፡ የተወደደ ፡ ወንድም ፡ እንዴት ፡

አይኾንም ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ባልንጀራ ፡ ብትቈጥረኝ ፥ እንደ ፡ እኔ ፡ አድርገኽ ፡ ተቀበለው ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ባንዳች ፡ ነገር ፡ የበደለኽ ፡ ቢኖር ፡ ግን ፡ ወይም ፡ ብድር ፡ ያለበት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ይህን ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ቍጠር ፤

ፊል. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እኔ ፡ ጳውሎስ ፦ እኔ ፡ እመልሰዋለኹ ፡ ብዬ ፡ በእጄ ፡ እጽፋለኹ ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ ለእኔ ፡ የራስኽ ፡ ደግሞ ፡ ብድር ፡ እንዳለብኽ ፡ አልልኽም ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 20 ፤ አዎን ፥ ወንድሜ ፡ ሆይ ፥ በጌታ ፡ እኔ ፡ እንድጠቀምብኽ ፡ ይኹን ፤ በክርስቶስ ፡ ልቤን ፡ አሳርፍልኝ ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ከምልኽ ፡ ይልቅ ፡ አብልጠኽ ፡ እንድታደርግ ፡ ዐውቄ ፡ እንድትታዘዝም ፡ ታምኜ ፡ እጽፍልኻለኹ ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ደግሞ ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የማስተናገጃ ፡ ቤት ፡ አዘጋጅልኝ ፤ በጸሎታችኹ ፡ ለእናንተ ፡ እንድሰጥ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹና ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 23 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ የታሰረ ፡ ኤጳፍራ ፡

ፊል. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ዐብረውኝም ፡ የሚሠሩ ፡ ማርቆስና ፡ አርስጥሮኮስ ፡ ዴማስም ፡ ሉቃስም ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡልኻል ።

ፊል. ፡ 1 ፡ 25 ፤ የጌታችን ፡ የኢሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከመንፈሳችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የሐዋርያው ፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዕብ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ከጥንት ፡ ዝምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ በብዙ ፡ ዐይነትና ፡ በብዙ ፡ ጐዳና ፡ ለአባቶቻችን ፡ በነቢያት ፡ ተናግሮ ፥

ዕብ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ዅሉን ፡ ወራሽ ፡ ባደረገው ፡ ደግሞም ፡ ዓለማትን ፡ በፈጠረበት ፡ በልጁ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ መጨረሻ ፡ ለእኛ ፡ ተናገረን ፤

ዕብ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ርሱም ፡ የክብሩ ፡ መንጸባረቅና ፡ የባሕርዩ ፡ ምሳሌ ፡ ኾኖ ፥ ዅሉን ፡ በሥልጣኑ ፡ ቃል ፡ እየደገፈ ፥ ኀጢአታችንን ፡ በራሱ ፡ ካነጻ ፡ በኋላ ፥ በሰማያት ፡ በግርማው ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ፤

ዕብ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከመላእክት ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ የሚበልጥ ፡ ስምን ፡ በወረሰ ፡ መጠን ፥ እንዲሁ ፡ ከነርሱ ፡ አብዝቶ ፡ ይበልጣል ።

ዕብ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከመላእክትስ ፦ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነኽ ፥ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወልጄኻለኹ ፥ ደግሞም ፦ እኔ ፡ አባት ፡ እኾነዋለኹ ፡ ርሱም ፡ ልጅ ፡ ይኾነኛል ፡

ዕብ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ያለው ፡ ከቶ ፡ ለማን ፡ ነው ፧ ደግሞም ፡ በኵርን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሲያገባ ፦ የእግዚአብሔር ፡ መላእክት ፡ ዅሉም ፡ ለርሱ ፡ ይስገዱ ፡ ይላል ።

ዕብ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ ስለ ፡ መላእክትም ፦ መላእክቱን ፡ መናፍስት ፥ አገልጋዮቹንም ፡ የእሳት ፡ ነበልባል ፡ የሚያደርግ ፡ ይላል ፤

ዕብ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ስለ ፡ ልጁ ፡ ግን ፦ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ዙፋንኽ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ይኖራል ፤ የመንግሥትኽ ፡ በትር ፡ የቅንነት ፡ በትር ፡ ነው ።

ዕብ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ ጽድቅን ፡ ወደድኽ ፥ ዐመፅንም ፡ ጠላኽ ፤ ስለዚህ ፥ እግዚአብሔር ፡ አምላክኽ ፡ ከጓደኞችኽ ፡ ይልቅ ፡ በደስታ ፡ ዘይት ፡ ቀባኽ ፡ ይላል ።

ዕብ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ ደግሞ ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ከጥንት ፡ ምድርን ፡ መሠረትኽ ፥ ሰማዮችም ፡ የእጆችኽ ፡ ሥራ ፡ ናቸው ፤

ዕብ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እነርሱም ፡ ይጠፋሉ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ጸንተኽ ፡ ትኖራለኽ ፤ ዅሉም ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ያረጃሉ ፥

ዕብ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እንደ ፡ መጐናጸፊያም ፡ ትጠቀልላቸዋለኽ ፡ ይለወጡማል ፤ አንተ ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ነኽ ፥ ዓመቶችኽም ፡ ከቶ ፡ አያልቁም ፡ ይላል ።

ዕብ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከመላእክት ፦ ጠላቶችኽን ፡ የእግርኽ ፡ መረገጫ ፡ እስካደርግልኽ ፡ ድረስ ፡ በቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡

ዕብ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ከቶ ፡ ለማን ፡ ብሏል ፧ ዅሉ ፡ መዳንን ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስላላቸው ፡ ለማገዝ ፡ የሚላኩ ፡ የሚያገለግሉም ፡ መናፍስት ፡ አይደሉምን ፧

ዕብራውያን ፡ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፡ ከሰማነው ፡ ነገር ፡ ምናልባት ፡ እንዳንወሰድ ፡ ለርሱ ፡ አብልጠን ፡ ልንጠነቀቅ ፡ ያስፈልገናል ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ በመላእክት ፡ የተነገረው ፡ ቃል ፡ ጽኑ ፡ ከኾነ ፡ መተላለፍና ፡ አለመታዘዝም ፡ ኹሉ ፡ የጽድቅን ፡ ብድራት ፡ ከተቀበለ ፡ እኛስ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ታላቅ ፡ መዳን ፡ ቸል ፡ ብንለው ፡ እንዴት ፡ እናመልጣለን ፧

ዕብ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ይህ ፡ በጌታ ፡ በመገለመሪያ ፡ የተነገረ ፡ ነበርና ፡ የሰሙትም ፡ ለእኛ ፡ አጸኑት ፡

ዕብ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡ በምልክትና ፡ በድንቅ ፡ ነገር ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ተኣምራትም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ በማደል ፡ ዐብሮ ፡ መሰከረለት ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ ስለ ፡ ርሱ ፡ የምንናገርበትን ፡ የሚመጣውን ፡ ዓለም ፡ ለመላእክት ፡ ያስገዛው ፡ አይደለምና ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አንዱ ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፦ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ወይስ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧

ዕብ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ ከመላእክት ፡ ይልቅ ፡ በጥቂት ፡ አሳነስኸው ፤ የክብርና ፡ የምስጋና ፡ ዘውድ ፡ ጫንኸለት ፡ በእጆችኽም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ሾምኸው ፤

ዕብ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ኹሉን ፡ ከእግሮቹ ፡ በታች ፡ አስገዛኸለት ፡ ብሎ ፡ መሰከረ ። ኹሉን ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ ባስገዛ ፡ ጊዜ ፡ ያልተገዛለት ፡ ምንም ፡ አልተወምና ። አኹን ፡ ግን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ተገዛለት ፡ ገና ፡ አናይም ፤

ዕብ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሞትን ፡ ይቀምስ ፡ ዘንድ ፡ ከመላእክት ፡ ይልቅ ፡ በጥቂት ፡ አንሶ ፡ የነበረውን ፡ ኢየሱስን ፡ ከሞት ፡ መከራ ፡ የተነሣ ፡ የክብርና ፡ የምስጋናን ፡ ዘውድ ፡ ተጭኖ ፡ እናየዋለን ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ብዙ ፡ ልጆችን ፡ ወደ ፡ ክብር ፡ ሲያመጣ ፡ የመዳናቸውን ፡ ራስ ፡ በመከራ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ የተነሣ ፡ ኹሉ ፡ በርሱም ፡ ኹሉ ፡ ለኾነ ፡ ለርሱ ፡ ተገብቶታልና ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 11-12 ፤ የሚቀድሰውና ፡ የሚቀደሱት ፡ ኹሉ ፡ ካንድ ፡ ናቸውና ፤

ዕብ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ስለዚህም ፡ ምክንያት ፦ ስምኽን ፡ ለወንድሞቼ ፡ እነግራቸዋለኹ ፡ በማኅበርም ፡ መካከል ፡ በዜማ ፡ አመሰግንኻለኹ ፤ ደግሞም ፦ እኔ ፡ በርሱ ፡ እታመናለኹ ፤ ደግሞም ፦ እንሆኝ ፡ እኔን ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰጠኝንም ፡ ልጆች ፡ ሲል ፡ ወንድሞች ፡ ብሎ ፡ ሊጠራቸው ፡ አያፍርም ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 14-15 ፤ እንግዲህ ፡ ልጆቹ ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ ስለሚካፈሉ ፡ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በሞት ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ በሞት ፡ እንዲሽር ፡ ይኸውም ፡ ዲያብሎስ ፡ ነው ፡ በሕይወታቸውም ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ሞት ፡ ፍርሀት ፡ በባርነት ፡ ይታሰሩ ፡ የነበሩትን ፡ ኹሉ ፡ ነጻ ፡ እንዲያወጣ ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ እንዲሁ ፡ ተካፈለ ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ የአብርሃምን ፡ ዘር ፡ ይዟል ፡ እንጂ ፡ የያዘው ፡ የመላእክትን ፡ አይደለም ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ ስለዚህ ፡ የሕዝብን ፡ ኀጢአት ፡ ለማስተስረይ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ የሚምርና ፡ የታመነ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ እንዲኾን ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ወንድሞቹን ፡ ሊመስል ፡ ተገባው ።

ዕብ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ተፈትኖ ፡ መከራን ፡ ስለ ፡ ተቀበለ ፡ የሚፈተኑትን ፡ ሊረዳቸው ፡ ይችላልና ።

ዕብራውያን ፡ ምዕራፍ ፡ 3 ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ስለዚህ ፥ ከሰማያዊው ፡ ጥሪ ፡ ተካፋዮች ፡ የኾናችኹ ፡ ቅዱሳን ፡ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የሃይማኖታችንን ፡ ሐዋርያና ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ተመልከቱ ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሙሴ ፡ ደግሞ ፡ በቤቱ ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ርሱ ፡ ለሾመው ፡ የታመነ ፡ ነበረ ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ ቤትን ፡ የሚያዘጋጀው ፡ ከቤቱ ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ ክብር ፡ እንዳለው ፡ መጠን ፥ እንዲሁ ፡ ርሱ ፡ ከሙሴ ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ ክብር ፡ የተገባው ፡ ኾኖ ፡ ተቈጥሯልና ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እያንዳንዱ ፡ ቤት ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ተዘጋጅቷልና ፥ ኹሉን ፡ ያዘጋጀ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ሙሴስ ፡ በኋላ ፡ ስለሚነገረው ፡ ነገር ፡ ምስክር ፡ ሊኾን ፡ በቤቱ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሎሌ ፡ የታመነ ፡ ነበረ ፥ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ በቤቱ ፡ ላይ ፡ የታመነ ፡ ነው ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ እኛም ፡ የምንደፍርበትን ፡ የምንመካበትንም ፡ ተስፋ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አጽንተን ፡ ብንጠብቅ ፡ ቤቱ ፡ ነን ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ ስለዚህ ፥ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደሚል ፦

ዕብ. ፡ 3 ፡ 8-9 ፤ ዛሬ ፡ ድምፁን ፡ ብትሰሙት ፥ አባቶቻችኹ ፡ እኔን ፡ የፈተኑበት ፣ የመረመሩበትም ፥ አርባ ፡ ዓመትም ፡ ሥራዬን ፡ ያዩበት ፥ በምድረ ፡ በዳ ፣ በፈተና ፡ ቀን ፡ በማስመረር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ልባችኹን ፡ እልከኛ ፡ አታድርጉ ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ያን ፡ ትውልድ ፡ ተቈጥቼ ፦ ዘወትር ፡ በልባቸው ፡ ይስታሉ ፡ መንገዴን ፡ ግን ፡ አላወቁም ፡ አልኹ ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እንዲሁ ፦ ወደ ፡ ዕረፍቴ ፡ አይገቡም ፡ ብዬ ፡ በቍጣዬ ፡ ማልኹ ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ምናልባት ፡ ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያስክዳችኹ ፡ ክፉና ፡ የማያምን ፡ ልብ ፡ ከእናንተ ፡ ባንዳችኹ ፡ እንዳይኖር ፡ ተጠንቀቁ ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ በኀጢአት ፡ መታለል ፡ እልከኛ ፡ እንዳይኾን ፥ ዛሬ ፡ ተብሎ ፡ ሲጠራ ፡ ሳለ ፥ በያንዳንዱ ፡ ቀን ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ተመካከሩ ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ የመገ፞መሪያ ፡ እምነታችንን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ አጽንተን ፡ ብንጠብቅ ፥ የክርስቶስ ፡ ተካፋዮች ፡ ኾነናልና ፤

ዕብ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ እየተባለ ፦ ዛሬ ፡ ድምፁን ፡ ብትሰሙት ፥ በማስመረር ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ልባችኹን ፡ እልከኛ ፡ አታድርጉ ።

ዕብ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ሰምተው ፡ ያስመረሩት ፡ እነማን ፡ ነበሩ ፧ በሙሴ ፡ ተመርተው ፡ ከግብጽ ፡ የወጡ ፡ ኹሉ ፡ አይደሉምን ፧

ዕብ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ አርባ ፡ ዓመትም ፡ የተቈጣባቸው ፡ እነማን ፡ ነበሩ ፧ ሬሳቸው ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ የወደቀ ፥ ኀጢአትን ፡ ያደረጉት ፡ እነርሱ ፡ አይደሉምን ፧

ዕብ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ካልታዘዙትም ፡ በቀር ፡ ወደ ፡ ዕረፍቱ ፡ እንዳይገቡ ፡ የማለባቸው ፡ እነማን ፡ ነበሩ ፧

ዕብ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ ባለማመናቸውም ፡ ጠንቅ ፡ ሊገቡ ፡ እንዳልተቻላቸው ፡ እናያለን ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ እንግዲህ ፡ ወደ ፡ ዕረፍቱ ፡ ለመግባት ፡ ተስፋ ፡ ገና ፡ ቀርቶልን ፡ ከኾነ ፥ ምናልባት ፡ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ የማይበቃ ፡ መስሎ ፡ እንዳይታይ ፡ እንፍራ ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ለእነዚያ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ተነገረ ፡ ለእኛ ፡ የምሥራች ፡ ተሰብኮልናልና ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የሰሙት ፡ ቃል ፡ ከሰሚዎቹ ፡ ጋራ ፡ በእምነት ፡ ስላልተዋሐደ ፡ አልጠቀማቸውም ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ሥራው ፡ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢፈጸም ፦ እንዲህ ፦ ወደ ፡ ዕረፍቴ ፡ አይገቡም ፡ ብዬ ፡ በቍጣዬ ፡ ማልኹ ፡ እንዳለ ፥ እኛስ ፡ ያመን ፡ ወደ ፡ ዕረፍቱ ፡ እንገባለን ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ ስለ ፡ ሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፦ እግዚአብሔርም ፡ በሰባተኛው ፡ ቀን ፡ ከሥራው ፡ ኹሉ ፡ ዐረፈ ፡ ብሏልና ፤

ዕብ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ በዚህ ፡ ስፍራም ፡ ደግሞ ፦ ወደ ፡ ዕረፍቴ ፡ አይገቡም ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ እንግዲህ ፡ አንዳንዶች ፡ በዚያ ፡ እንዲገቡ ፡ ስለ ፡ ቀሩ ፥ ቀድሞም ፡ የምሥራች ፡ የተሰበከላቸው ፡ ባለመታዘዝ ፡ ጠንቅ ፡ ስላልገቡ ፦

ዕብ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ዛሬ ፡ ድምፁን ፡ ብትሰሙት ፡ ልባችኹን ፡ እልከኛ ፡ አታድርጉ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ተባለ ፥ ይህን ፡ ከሚያኽል ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በዳዊት ፡ ሲናገር ፦ ዛሬ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ይቀጥራል ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ኢያሱ ፡ አሳርፏቸው ፡ ኖሮ ፡ ቢኾንስ ፥ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ቀን ፡ ባልተናገረ ፡ ነበር ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ እንግዲያስ ፡ የሰንበት ፡ ዕረፍት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ቀርቶላቸዋል ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ ወደ ፡ ዕረፍቱ ፡ የገባ ፥ እግዚአብሔር ፡ ከሥራው ፡ እንዳረፈ ፥ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከሥራው ፡ ዐርፏልና ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ እንግዲህ ፡ እንደዚያ ፡ እንደ ፡ አለመታዘዝ ፡ ምሳሌ ፡ ማንም ፡ እንዳይወድቅ ፡ ወደዚያ ፡ ዕረፍት ፡ ለመግባት ፡ እንትጋ ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሕያው ፡ ነውና ፥ የሚሠራም ፥ ኹለትም ፡ አፍ ፡ ካለው ፡ ሰይፍ ፡ ኹሉ ፡ ይልቅ ፡ የተሳለ ፡ ነው ፥ ነፍስንና ፡ መንፈስንም ፡ ዥማትንና ፡ ቅልጥምንም ፡ እስኪለይ ፡ ድረስ ፡ ይወጋል ፥ የልብንም ፡ ስሜትና ፡ ዐሳብ ፡ ይመረምራል ፤

ዕብ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ እኛን ፡ በሚቈጣጠር ፡ በርሱ ፡ ዐይኖቹ ፡ ፊት ፡ ኹሉ ፡ ነገር ፡ የተራቈተና ፡ የተገለጠ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በርሱ ፡ ፊት ፡ የተሰወረ ፡ ፍጥረት ፡ የለም ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ እንግዲህ ፡ በሰማያት ፡ ያለፈ ፡ ትልቅ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ኢየሱስ ፡ ስላለን ፥ ጸንተን ፡ ሃይማኖታችንን ፡ እንጠብቅ ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ ከኀጢአት ፡ በቀር ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ የተፈተነ ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ በድካማችን ፡ ሊራራልን ፡ የማይችል ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የለንም ።

ዕብ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ ምሕረትን ፡ እንድንቀበል ፡ በሚያስፈልገንም ፡ ጊዜ ፡ የሚረዳንን ፡ ጸጋ ፡ እንድናገኝ ፡ ወደጸጋው ፡ ዙፋን ፡ በእምነት ፡ እንቅረብ ።

ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መባንና ፡ መሥዋዕትን ፡ ሊያቀርብ ፡ ከሰው ፡ ተመርጦ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በኾነው ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ይሾማልና ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ርሱ ፡ ራሱም ፡ ደግሞ ፡ ድካምን ፡ ስለሚለብስ ፥ ላልተማሩትና ፡ ለሚስቱት ፡ ሊራራላቸው ፡ ይችላል ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ እንደሚያቀርብ ፡ እንዲሁ ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ መሥዋዕትን ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ሊያቀርብ ፡ ይገባዋል ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ እንደ ፡ አሮንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ከተጠራ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ ክብሩን ፡ ለራሱ ፡ የሚወስድ ፡ የለም ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ እንዲሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሊኾን ፡ ራሱን ፡ አላከበረም ፡ ነገር ፡ ግን ፦ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነኽ ፡ እኔ ፡ ዛሬ ፡ ወልጄኻለኹ ፡ ያለው ፡ ርሱ ፡ ነው ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ እንደዚህም ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ደግሞ ፦ አንተ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ለዘለዓለም ፡ ካህን ፡ ነኽ ፡ ይላል ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ ርሱም ፡ በሥጋው ፡ ወራት ፡ ከሞት ፡ ሊያድነው ፡ ወደሚችል ፡ ከብርቱ ፡ ጩኸትና ፡ ከንባ ፡ ጋራ ፡ ጸሎትንና ፡ ምልጃን ፡ አቀረበ ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ስለ ፡ መፍራቱ ፡ ተሰማለት ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ ምንም ፡ ልጅ ፡ ቢኾን ፥ ከተቀበለው ፡ መከራ ፡ መታዘዝን ፡ ተማረ ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 9-10 ፤ ከተፈጸመም ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ተጠራ ፥ ለሚታዘዙለት ፡ ኹሉ ፡ የዘለዓለም ፡ መዳን ፡ ምክንያት ፡ ኾነላቸው ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ ስለ ፡ ርሱም ፡ የምንናገረው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ አለን ፥ ገሮዎቻችኹም ፡ ስለ ፡ ፈዘዙ ፡ በቃል ፡ ልንተረጉመው ፡ ጭንቅ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ከጊዜው ፡ የተነሣ ፡ አስተማሪዎች ፡ ልትኾኑ ፡ ሲገባችኹ ፥ አንድ ፡ ሰው ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃላት ፡ መገመሪያ ፡ ያለውን ፡ የሕፃንነትን ፡ ትምህርት ፡ እንዲያስተምራችኹ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ያስፈልጋችኋልና ፤ የሚያስፈልጋችኹም ፡ ወተት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ጠንካራ ፡ ምግብ ፡ አይደለም ።

ዕብ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ወተት ፡ የሚጋት ፡ ኹሉ ፡ ሕፃን ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የጽድቅን ፡ ቃል ፡ አያውቅምና ፤

ዕብ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ጠንካራ ፡ ምግብ ፡ ግን ፡ መልካሙንና ፡ ክፉውን ፡ ለመለየት ፡ በሥራቸው ፡ የለመደ ፡ ልቡና ፡ ላላቸው ፡ ለፍጹማን ፡ ሰዎች ፡ ነው ።

_____ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ። _____

ዕብ. ፡ 6 ፡ 1-2 ፤ ስለዚህ ፥ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ መገመሪያ ፡ የሚናገረውን ፡ ቃል ፡ ትተን ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ እንኺድ ፤ መሠረትን ፡ ደግመን ፡ አንመሥርት ፥ ርሱም ፡ ከሞተ ፡ ሥራ ፡ ንስሓና ፡ በእግዚአብሔር ፡ እምነት ፥ ስለ ፡ ጥምቀቶችና ፡ እጆችንም ፡ ስለ ፡ መጫን ፡ ስለሙታንም ፡ ትንሣኤ ፡ ስለዘለዓለም ፡ ፍርድም ፡ ትምህርት ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 3 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ቢፈቅድ ፡ ይህን ፡ እናደርጋለን ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 4 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብርሃን ፡ የበራላቸውን ፡ ሰማያዊውንም ፡ ስጦታ ፡ የቀመሱትን ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ተካፋዮች ፡ ኾነው ፡ የነበሩትን ፡

ዕብ. ፡ 6 ፡ 5 ፤ መልካሙንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃልና ፡ ሊመጣ ፡ ያለውን ፡ የዓለም ፡ ኀይል ፡ የቀመሱትን ፡

ዕብ. ፡ 6 ፡ 6 ፤ በኋላም ፡ የካዱትን ፡ እንደገና ፡ ለንስሓ ፡ እነርሱን ፡ ማደስ ፡ የማይቻል ፡ ነው ፤ ለራሳቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ ይሰቅሉታልና ፥ ያዋርዱትማልና ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 7 ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በርሷ ፡ ላይ ፡ የሚወርደውን ፡ ዝናብ ፡ የምትጠጣ ፡ መሬት ፥ ለሚያርሷትም ፡ ደግሞ ፡ የምትጠቅምን ፡ አትክልት ፡ የምታበቅል ፥ ከእግዚአብሔር ፡ በረከትን ፡ ታገኛለችና ፤

ዕብ. ፡ 6 ፡ 8 ፤ ሾኽና ፡ ኵርንችትን ፡ ግን ፡ ብታወጣ ፥ የተጣለች ፡ ናት ፡ ለመረገምም ፡ ትቀርባለች ፥ መጨረሻዋም ፡ መቃጠል ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 9 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ ግን ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ምንም ፡ እንኳ ፡ እንዲሁ ፡ ብንናገር ፥ አብልጦ ፡ የሚሻለውና ፡ ለመዳን ፡ የሚኾነው ፡ እንዲኾንላችኹ ፡ ተረድተናል ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 10 ፤ እግዚአብሔር ፥ ቅዱሳንን ፡ ስላገለገላችኹ ፡ እስከ ፡ አኹንም ፡ ስለምታገለግሏቸው ፥ ያደረጋችኹትን ፡ ሥራ ፡ ለስሙም ፡ ያሳያችኹትን ፡ ፍቅር ፡ ይረሳ ፡ ዘንድ ፡ ዐመፀኛ ፡ አይደለምና ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 11-12 ፤ በእምነትና ፡ በትዕግሥትም ፡ የተስፋውን ፡ ቃል ፡ የሚወርሱትን ፡ እንድትመስሉ ፡ እንጂ ፡ ዳተኞች ፡ እንዳትኾኑ ፥ ተስፋ ፡ እስኪሞላ ፡ ድረስ ፡ እያንዳንዳችኹ ፡ ያን ፡ ትጋት ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ እንድታሳዩ ፡ እንመኛለን ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 13-14 ፤ እግዚአብሔርም ፡ ለአብርሃም ፡ ተስፋ ፡ በሰጠው ፡ ጊዜ ፦ በእውነት ፡ እየባረክኹ ፡ እባርክኻለኹ ፡ እያበዛኹም ፡ አበዛኻለኹ ፡ ብሎ ፥ ከርሱ ፡ በሚበልጥ ፡ በማንም ፡ ሊምል ፡ ስላልቻለ ፥ በራሱ ፡ ማለ ፤

ዕብ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ እንዲሁም ፡ ርሱ ፡ ከታገሰ ፡ በኋላ ፡ ተስፋውን ፡ አገኘ ።

ዕብ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ሰዎች ፡ ከነርሱ ፡ በሚበልጠው ፡ ይምላሉና ፥ ለማስረዳትም ፡ የኾነው ፡ መሐላ ፡ የሙግት ፡ ኹሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ይኾናል ፤

ዕብ. ፡ 6 ፡ 17-18 ፤ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፥ የተስፋውን ፡ ቃል ፡ ለሚወርሱ ፡ ፈቃዱ ፡ እንደማይለወጥ ፡ አብልጦ ፡ ሊያሳያቸው ፡ ስለ ፡ ፈቀደ ፥ እግዚአብሔር ፡ ሊዋሽ ፡ በማይቻል ፡ በኹለት ፡ በማይለወጥ ፡ ነገር ፥ በፊታችን ፡ ያለውን ፡ ተስፋ ፡ ለመያዝ ፡ ለሸሸን ፡ ለእኛ ፡ ብርቱ ፡ መጽናናት ፡ ይኾንልን ፡ ዘንድ ፥ በመሐላ ፡ በመካከል ፡ ገባ ፤

ዕብ. ፡ 6 ፡ 19 ፤ ይህም ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ነፍስ ፡ መልሕቅ ፡ አለን ፡ ርሱም ፡ ርግጥና ፡ ጽኑ ፡ የኾነ ፡ ወደ ፡ መጋረጃውም ፡ ውስጥ ፡ የገባ ፡ ነው ፤

ዕብ. ፡ 6 ፡ 20 ፤ በዚያም ፡ ኢየሱስ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ለዘለዓለም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ የኾነው ፥ ስለ ፡ እኛ ፡ ቀዳሚ ፡ ኾኖ ፡ ገባ ።

ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ።

ዕብ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ የሳሌም ፡ ንጉሥና ፡ የልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ካህን ፡ የኾነ ፡ ይህ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ አብርሃም ፡ ነገሥታትን ፡ ገድሎ ፡ ሲመለስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተገናኝቶ ፡ ባረከው ፤

ዕብ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ ለርሱም ፡ ደግሞ ፡ አብርሃም ፡ ከኹሉ ፡ ዓሥራትን ፡ አካፈለው ። የስሙም ፡ ትርጓሜ ፡ በመገለመሪያ ፡ የጽድቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፥ ኋላም ፡ ደግሞ ፡ የሳሌም ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ አባትና ፡ እናት ፡ የትውልድም ፡ ቍጥር ፡ የሉትም ፥ ለዘመኑም ፡ ጥንት ፡ ለሕይወቱም ፡ ፍጻሜ ፡ የለውም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ተመስሎ ፡ ለዘለዓለም ፡ ካህን ፡ ኾኖ ፡ ይኖራል ።

ዕብ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ የአባቶች ፡ አለቃ ፡ አብርሃም ፡ ከዘረፋው ፡ የሚሻለውን ፡ ዓሥራት ፡ የሰጠው ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ትልቅ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እስኪ ፡ ተመልከቱ ።

ዕብ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ከሌዊ ፡ ልጆችም ፡ ክህነትን ፡ የሚቀበሉት ፡ ከሕዝቡ ፡ ማለት ፡ ከወንድሞቻቸው ፥ እነርሱ ፡

ምንም ፡ ከአብርሃም ፡ ወገብ ፡ ቢወጡ ፥ ከነርሱ ፡ ዓሥራትን ፡ በሕግ ፡ እንዲያስወጡ ፡ ትእዛዝ ፡ አላቸው ፤

ዕብ. ፥ 7 ፥ 6 ፤ ትውልዱ ፡ ከነርሱ ፡ የማይቈጠረው ፡ ግን ፡ ከአብርሃም ፡ ዓሥራትን ፡ አውጥቷል ፥ የተስፋ ፡ ቃል ፡ የነበረውንም ፡ ባርኳል ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 7 ፤ ትንሹም ፡ በታላቁ ፡ እንዲባረክ ፡ ክርክር ፡ የሌለበት ፡ ነገር ፡ ነው ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 8 ፤ በዚህስ ፡ የሚሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ዓሥራትን ፡ ያስወጣሉ ፥ በዚያ ፡ ግን ፡ የሚያስወጣ ፡ በሕይወት ፡ እንዲኖር ፡ የተመሰከረለት ፡ ርሱ ፡ ነው ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 9 ፤ ይህንም ፡ ለማለት ፡ ሲፈቀድ ፥ ዓሥራትን ፡ የሚያስወጣ ፡ ሌዊ ፡ እንኳ ፡ በአብርሃም ፡ እጅ ፡ ዓሥራትን ፡ ሰጥቷል ፤

ዕብ. ፥ 7 ፥ 10 ፤ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ በተገናኘው ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ በአባቱ ፡ ወገብ ፡ ነበረና ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 11 ፤ እንግዲህ ፡ ሕዝቡ ፡ በሌዊ ፡ ክህነት ፡ የተመሠረተን ፡ ሕግ ፡ ተቀብለዋልና ፥ በዚያ ፡ ክህነት ፡ ፍጹምነት ፡ የተገኘ ፡ ቢኾን ፥ እንደ ፡ አሮን ፡ ሹመት ፡ የማይቈጠር ፥ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ግን ፡ የኾነ ፡ ሌላ ፡ ካህን ፡ ሊነሣ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ያስፈልጋል ፧

ዕብ. ፥ 7 ፥ 12 ፤ ክህነቱ ፡ ሲለወጥ ፥ ሕጉ ፡ ደግሞ ፡ ሊለወጥ ፡ የግድ ፡ ነውና ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 13 ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ የተነገረለት ፡ ርሱ ፡ በሌላ ፡ ወገን ፡ ተካፍሏልና ፥ ከዚያም ፡ መሠዊያውን ፡ ያገለገለ ፡ ማንም ፡ የለም ፤

ዕብ. ፥ 7 ፥ 14 ፤ ጌታችን ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ የተገለጠ ፡ ነውና ፥ ስለዚህም ፡ ነገድ ፡ ሙሴ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ስለ ፡ ክህነት ፡ አልተናገረም ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 15-16 ፤ በማያልፍም ፡ ሕይወት ፡ ኀይል ፡ እንጂ ፡ በሥጋ ፡ ትእዛዝ ፡ ሕግ ፡ ሳይኾን ፡ ሌላ ፡ ካህን ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ምሳሌ ፡ ቢነሣ ፥ ይህ ፡ እጅግ ፡ አብልጦ ፡ የሚገለጥ ፡ ነው ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 17 ፤ አንተ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ለዘለዓለም ፡ ካህን ፡ ነኽ ፡ ብሎ ፡ ይመሰክራልና ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 18-19 ፤ ሕጉ ፡ ምንም ፡ ፍጹም ፡ አላደረገምና ፥ ስለዚህም ፡ የምትደክም ፡ የማትጠቅምም ፡ ስለ ፡ ኾነች ፡ የቀደመች ፡ ትእዛዝ ፡ ተሽራለች ፥ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የምንቀርብበት ፡ የሚሻል ፡ ተስፋ ፡ ገብቷል ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 20-21 ፤ እነርሱም ፡ ያለመሐላ ፡ ካህናት ፡ ኾነዋልና ፤ ርሱ ፡ ግን ፦ ጌታ ፦ አንተ ፡ እንደ ፡ መልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሹመት ፡ ለዘለዓለም ፡ ካህን ፡ ነኽ ፡ ብሎ ፡ ማለ ፡ አይጸጸትም ፡ ብሎ ፡ በተናገረለት ፡ ከመሐላ ፡ ጋራ ፡ ካህን ፡ ኾኗልና ፥ ያለመሐላ ፡ ካህን ፡ እንዳልኾነ ፡ መጠን ፥

ዕብ. ፥ 7 ፥ 22 ፤ እንዲሁ ፡ ኢየሱስ ፡ ለሚሻል ፡ ኪዳን ፡ ዋስ ፡ ኾኗል ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 23 ፤ እነርሱም ፡ እንዳይኖሩ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ከለከላቸው ፡ ካህናት ፡ የኾኑት ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤

ዕብ. ፥ 7 ፥ 24 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ የሚኖር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ የማይለወጥ ፡ ክህነት ፡ አለው ፤

ዕብ. ፥ 7 ፥ 25 ፤ ስለ ፡ እነርሱም ፡ ሊያማልድ ፡ ዘወትር ፡ በሕይወት ፡ ይኖራልና ፥ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ በርሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚመጡትን ፡ ፈጽሞ ፡ ሊያድናቸው ፡ ይችላል ።

ዕብ. ፥ 7 ፥ 26 ፤ ቅዱስና ፡ ያለተንኰል ፡ ነውርም ፡ የሌለበት ፡ ከኀጢአተኞችም ፡ የተለየ ፡ ከሰማያትም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፥ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ይገባልና ፤

ዕብ. ፡ 7 ፡ 27 ፤ ርሱም ፡ እንደነዚያ ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ አስቀድሞ ፡ ስለራሱ ፡ ኀጢአት ፡ በኋላም ፡ ስለሕዝቡ ፡ ኀጢአት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ መሥዋዕትን ፡ ሊያቀርብ ፡ አያስፈልገውም ፤ ራሱን ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ አድርጓልና ።

ዕብ. ፡ 7 ፡ 28 ፤ ሕጉ ፡ ድካም ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አድርጎ ፡ ይሾማልና ፤ ከሕግ ፡ በኋላ ፡ የመጣ ፡ የመሐላው ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ፍጹም ፡ የኾነውን ፡ ልጅ ፡ ይሾማል ።

ዕብራውያን ፡ ምዕራፍ ፡ 8 ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ከተናገርነውም ፡ ዋና ፡ ነገሩ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ በሰማያት ፡ በግርማው ፡ ዙፋን ፡ ቀኝ ፡ የተቀመጠ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አለን ፤

ዕብ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ ርሱም ፡ የመቅደስና ፡ የእውነተኛዉቱ ፡ ድንኳን ፡ አገልጋይ ፡ ነው ፥ ርሷም ፡ በሰው ፡ ሳይኾን ፡ በጌታ ፡ የተተከለች ፡ ናት ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኹሉ ፡ መባንና ፡ መሥዋዕትን ፡ ሊያቀርብ ፡ ይሾማልና ፤ ስለዚህም ፡ ለዚህ ፡ ደግሞ ፡ የሚያቀርበው ፡ አንዳች ፡ ሊኖረው ፡ የግድ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ እንግዲህ ፡ በምድር ፡ ቢኖርስ ፥ እንደ ፡ ሕግ ፡ መባን ፡ የሚያቀርቡት ፡ ስለ ፡ አሉ ፥ ካህን ፡ እንኳ ፡ ባልኾነም ፤

ዕብ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ እነርሱም ፡ ሙሴ ፡ ድንኳኑን ፡ ሊሠራ ፡ ሳለ ፡ እንደ ፡ ተረዳ ፥ ለሰማያዊ ፡ ነገር ፡ ምሳሌና ፡ ጥላ ፡ የሚኾነውን ፡ ያገለግላሉ ። በተራራው ፡ እንደተገለጠልኽ ፡ ምሳሌ ፡ ኹሉን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ተጠንቀቅ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በሚሻል ፡ ተስፋ ፡ ቃል ፡ በተመሠረተ ፡ በሚሻል ፡ ኪዳን ፡ ደግሞ ፡ መካከለኛ ፡ እንደሚኾን ፡ በዚያ ፡ ልክ ፡ እጅግ ፡ የሚሻል ፡ አገልግሎት ፡ አግኝቷል ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ፊተኛው ፡ ኪዳን ፡ ነቀፋ ፡ ባይኖረው ፥ ለኹለተኛው ፡ ስፍራ ፡ ባልተፈለገም ፡ ነበር ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ እነርሱን ፡ እየነቀፈ ፡ ይላቸዋልና ፦ እንሆ ፥ ከእስራኤል ፡ ቤትና ፡ ከይሁዳ ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ ዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ የምገባበት ፡ ወራት ፡ ይመጣል ፡ ይላል ፡ ጌታ ፤

ዕብ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ ከግብጽ ፡ አገር ፡ አወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ እጃቸውን ፡ በያዝኹበት ፡ ቀን ፡ ከአባቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ እንደገባኹት ፡ ኪዳን ፡ አይደለም ፤ እነርሱ ፡ በኪዳኔ ፡ አልጸኑምና ፥ እኔም ፡ ቸል ፡ አልኋቸው ፡ ይላል ፡ ጌታ ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ከዚያ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ከእስራኤል ፡ ቤት ፡ ጋራ ፡ የምገባው ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነውና ፥ ይላል ፡ ጌታ ፤ ሕጌን ፡ በልቡናቸው ፡ አኖራለኹ ፡ በልባቸውም ፡ እጽፈዋለኹ ፥ እኔም ፡ አምላክ ፡ እኾንላቸዋለኹ ፡ እነርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይኾኑልኛል ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ እያንዳንዱም ፡ ጎረቤቱን ፡ እያንዳንዱም ፡ ወንድሙን ፦ ጌታን ፡ ዕወቅ ፡ ብሎ ፡ አያስተምርም ፤ ከታናሹ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቁ ፡ ድረስ ፡ ኹሉ ፡ ያውቁኛልና ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ ዐመፃቸውን ፡ እምራቸዋለኹና ፥ ኀጢአታቸውንም ፡ ደግሜ ፡ አላስብም ።

ዕብ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ ዐዲስ ፡ በማለቱ ፡ ፊተኛውን ፡ አስረጅቷል ፤ አሮጌና ፡ ውራጅ ፡ የኾነውስ ፡ ሊጠፋ ፡ ቀርቧል ።

ዕብራውያን ፡ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 1 ፤ ፊተኛዉቱም ፡ ደግሞ ፡ የአገልግሎት ፡ ሥርዐትና ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ የኾነው ፡ መቅደስ ፡ ነበራት ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 2 ፤ የመገሥመሪያዩቱ ፡ ድንኳን ፡ ተዘጋጅታ ፡ ነበርና ፥ በርሷም ፡ ቅድስት ፡ በምትባለው ፡ ውስጥ ፡ መቅረዙና ፡ ጠረጴዛው ፡ የመሥዋዕቱም ፡ ኅብስት ፡ ነበረባት ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 3 ፤ ከኹለተኛውም ፡ መጋረጃ ፡ ወዲያ ፡ ቅድስተ ፡ ቅዱሳን ፡ የምትባለው ፡ ድንኳን ፡ ነበረች ፥

ዕብ. ፡ 9 ፡ 4 ፤ በዚያም ፡ ውስጥ ፡ የወርቅ ፡ ማዕጠንት ፡ ነበረ ፥ ኹለንተናዋም ፡ በወርቅ ፡ የተለበጠች ፡ የኪዳን ፡ ታቦት ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ መና ፡ ያለባት ፡ የወርቅ ፡ መሶብና ፡ የበቀለች ፡ የአሮን ፡ በትር ፥ የኪዳኑም ፡ ጽላት ፡ ነበሩ ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 5 ፤ በላይዋም ፡ ማስተስረያውን ፡ የሚጋርዱ ፡ የክብር ፡ ኪሩቤል ፡ ነበሩ ፤ ስለ ፡ እነዚህም ፡ ስለ ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ልንናገር ፡ አኹን ፡ አንችልም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 6 ፤ ይህም ፡ እንደዚህ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ሳለ ፥ ካህናት ፡ አገልግሎታቸውን ፡ እየፈጸሙ ፡ ዘወትር ፡ በፊተኛዩቱ ፡ ድንኳን ፡ ይገቡባታል ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 7 ፤ በኹለተኛዩቱ ፡ ግን ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ብቻውን ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይገባባታል ፥ ርሱም ፡ ሰለ ፡ ራሱና ፡ ስለሕዝቡ ፡ ስሕተት ፡ የሚያቀርበውን ፡ ደም ፡ ሳይዝ ፡ አይገባም ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 8 ፤ ፊተኛዩቱም ፡ ድንኳን ፡ በዚህ ፡ ገና ፡ ቆማ ፡ ሳለች ፥ ወደ ፡ ቅድስት ፡ የሚወስደው ፡ መንገድ ፡ ገና ፡ እንዳልተገለጠ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያሳያል ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 9-10 ፤ ይህም ፡ ለአኹኑ ፡ ጊዜ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፥ እንደዚህም ፡ መባና ፡ መሥዋዕት ፡ ይቀርባሉ ፤ እነዚህም ፡ እስከመታደስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የተደረጉ ፥ ስለ ፡ ምግብና ፡ ስለ ፡ መጠጥም ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መታጠብም ፡ የሚኾኑ ፡ የሥጋ ፡ ሥርዐቶች ፡ ብቻ ፡ ናቸውና ፥ የሚያመልከውን ፡ በኅሊና ፡ ፍጹም ፡ ሊያደርጉት ፡ አይችሉም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 11 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክርስቶስ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ላለው ፡ መልካም ፡ ነገር ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ኾኖ ፥ በምትበልጠውና ፡ በምትሻለው ፡ በእጆችም ፡ ባልተሠራች ፡ ማለት ፡ ለዚህ ፡ ፍጥረት ፡ ባልኾነች ፡ ድንኳን ፥

ዕብ. ፡ 9 ፡ 12 ፤ የዘለዓለምን ፡ ቤዛነት ፡ አግኝቶ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ በገዛ ፡ ደሙ ፡ ገባ ፡ እንጂ ፡ በፍየሎችና ፡ በጥጃዎች ፡ ደም ፡ አይደለም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 13 ፤ የኰርማዎችና ፡ የፍየሎች ፡ ደም ፡ በረከሱትም ፡ ላይ ፡ የተረጨ ፡ የጊደር ፡ ዐመድ ፡ ሥጋን ፡ ለማንጻት ፡ የሚቀድሱ ፡ ከኾኑ ፥

ዕብ. ፡ 9 ፡ 14 ፤ ነውር ፡ የሌለው ፡ ኾኖ ፡ በዘለዓለም ፡ መንፈስ ፡ ራሱን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያቀረበ ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ እንዴት ፡ ይልቅ ፡ ሕያውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ልታመልኩ ፡ ከሞተ ፡ ሥራ ፡ ኅሊናችኹን ፡ ያነጻ ፡ ይኾን ፧

ዕብ. ፡ 9 ፡ 15 ፤ ስለዚህም ፡ የፊተኛው ፡ ኪዳን ፡ ሲጸና ፡ ሕግን ፡ የተላለፉትን ፡ የሚቤዥ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የተጠሩት ፡ የዘለዓለምን ፡ ርስት ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ እንዲቀበሉ ፡ ርሱ ፡ የዐዲስ ፡ ኪዳን ፡ መካከለኛ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ ኑዛዜ ፡ ያለ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ የተናዛዡን ፡ ሞት ፡ ማርዳት ፡ የግድ ፡ ነውና ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ሰው ፡ ሲሞት ፡ ኑዛዜው ፡ ይጸናልና ፥ ተናዛዡ ፡ በሕይወት ፡ ሲኖር ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ አይጠቅምም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ስለዚህም ፡ ፊተኛው ፡ ኪዳን ፡ እንኳ ፡ ያለደም ፡ አልተመረቀም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 19-20 ፤ ሙሴም ፡ ትእዛዛትን ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሕጉ ፡ ለሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥ የጥጃዎችንና ፡ የፍየሎችን ፡ ደም ፡ ከውሃና ፡ ከቀይ ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ ከሂሶጵም ፡ ጋራ ፡ ይዞ ፦ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘላችኹ ፡ የኪዳን ፡ ደም ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ብሎ ፡ በመጽሐፉና ፡ በሕዝቡ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ረጨው ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ እንዲሁም ፡ በድንኳኑና ፡ በማገልገያው ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፡ ደምን ፡ ረጨ ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 22 ፤ እንደ ፡ ሕጉም ፡ ከጥቂቶች ፡ በቀር ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ በደም ፡ ይነጻል ፥ ደምም ፡ ሳይፈስ ፡ ስርየት ፡ የለም ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 23 ፤ እንግዲህ ፡ በሰማያት ፡ ያሉትን ፡ የሚመስለው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ሊነጻ ፡ እንጂ ፡ በሰማያት ፡ ያሉቱ ፡ ራሳቸው ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ በሚበልጥ ፡ መሥዋዕት ፡ ሊነጹ ፡ የግድ ፡ ነበረ ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 24 ፤ ክርስቶስ ፡ በእጅ ፡ ወደተሠራች ፥ የእውነተኛዪቱ ፡ ምሳሌ ፡ ወደምትኾን ፡ ቅድስት ፡ አልገባምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አኹን ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ገባ ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 25 ፤ ሊቀ ፡ ካህናትም ፡ በየዓመቱ ፡ የሌላውን ፡ ደም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ እንደሚገባ ፥ ራሱን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሊያቀርብ ፡ አልገባም ፤

ዕብ. ፡ 9 ፡ 26 ፤ እንዲህ ፡ ቢኾንስ ፥ ዓለም ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ ሊቀበል ፡ ባስፈለገው ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ራሱን ፡ በመሠዋት ፡ ኀጢአትን ፡ ሊሽር ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተገልጧል ።

ዕብ. ፡ 9 ፡ 27 ፤ ለሰዎችም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ መሞት ፡ ከርሱ ፡ በኋላም ፡ ፍርድ ፡ እንደ ፡ ተመደበባቸው ፥

ዕብ. ፡ 9 ፡ 28 ፤ እንዲሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፥ የብዙዎችን ፡ ኀጢአት ፡ ሊሸከም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተሠዋ ፡ በኋላ ፥ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሚጠባበቁት ፡ ኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ያለኀጢአት ፡ ይታይላቸዋል ።

ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ሕጉ ፡ ሊመጣ ፡ ያለው ፡ የበጎ ፡ ነገር ፡ እውነተኛ ፡ አምሳል ፡ ሳይኾን ፡ የነገር ፡ ጥላ ፡ አለውና ፥ ስለዚህም ፡ በየዓመቱ ፡ ዘወትር ፡ በሚያቀርቡት ፡ በዚያ ፡ መሥዋዕት ፡ የሚቀርቡትን ፡ ሊፈጽም ፡ ከቶ ፡ አይችልም ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ እንደዚህማ ፡ ባይኾን ፥ የሚያመልኩት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ነጽተው ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ በኀሊናቸው ፡ ኀጢአትን ፡ ስላላወቁ ፡ ማቅረብን ፡ በተዉ ፡ አልነበረምን ፧

ዕብ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ መሥዋዕት ፡ በየዓመቱ ፡ የኀጢአት ፡ መታሰቢያ ፡ አለ ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ የኰርማዎችና ፡ የፍየሎች ፡ ደም ፡ ኀጢአትን ፡ እንዲያስወግድ ፡ የማይቻል ፡ ነውና ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ ስለዚህ ፥ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሲገባ ፦ መሥዋዕትንና ፡ መባን ፡ አልወደድኽም ፡ ሥጋን ፡ ግን ፡ አዘጋጀኽልኝ ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ በሙሉ ፡ በሚቃጠል ፡ መሥዋዕትና ፡ ሰለ ፡ ኀጢአት ፡ በሚሠዋ ፡ መሥዋዕት ፡ ደስ ፡ አላለኽም ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ በዚያ ፡ ጊዜ ፦ እንሆ ፥ በመጽሐፍ ፡ ጥቅል ፡ ስለ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፥ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ፈቃድኽን ፡ ላደርግ ፡ መጥቻለኹ ፡ አልኹ ፡ ይላል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ በዚህ ፡ ላይ ፦ መሥዋዕትንና ፡ መባን ፡ በሙሉ ፡ የሚቃጠል ፡ መሥዋዕትንም ፡ ስለ ፡ ኀጢአትም ፡ የሚሠዋ ፡ መሥዋዕትን ፡ አልወደድኽም ፡ በርሱም ፡ ደስ ፡ አላለኽም ፡ ብሎ ፥ እነዚህም ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ የሚቀርቡት ፡ ናቸው ፥

ዕብ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ቀጥሎ ፦ እንሆ ፥ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ ፈቃድኽን ፡ ላደርግ ፡ መጥቻለኹ ፡ ብሏል ። ኹለተኛውንም ፡ ሊያቆም ፡ የፊተኛውን ፡ ይሽራል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 10 ፤ በዚህም ፡ ፈቃድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ በማቅረብ ፡ ተቀድሰናል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 11 ፤ ሊቀ ፡ ካህናትም ፡ ሹሉ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እያገለገለ ፡ ኀጢአትን ፡ ሊያስወግዱ ፡ ከቶ ፡ የማይችሉትን ፡ እነዚያን ፡ መሥዋዕቶች ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እያቀረበ ፡ ቆሟል ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 12 ፤ ርሱ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ አንድን ፡ መሥዋዕት ፡ ለዘለዓለም ፡ አቅርቦ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ተቀመጠ ፥

ዕብ. ፡ 10 ፡ 13 ፤ ጠላቶቹም ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ እስኪደረጉ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይጠብቃል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 14 ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በማቅረብ ፡ የሚቀደሱትን ፡ የዘለዓለም ፡ ፍጹማን ፡ አድርጓቸዋልና ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 15-16 ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ደግሞ ፡ ስለዚህ ፡ ይመሰክርልናል ፤ ከዚያ ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ የምገባው ፡ ኪዳን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ ጌታ ፤ በልባቸው ፡ ሕጌን ፡ አኖራለኹ ፡ በልቡናቸውም ፡ እጽፈዋለኹ ፡

ዕብ. ፡ 10 ፡ 17 ፤ ብሎ ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፥ ኀጢአታቸውንና ፡ ዐመፃቸውንም ፡ ደግሜ ፡ አላስብም ፡ ይላል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 18 ፤ የእነዚህም ፡ ስርየት ፡ ባለበት ፡ ዘንድ ፥ ከዚህ ፡ ወዲህ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ማቅረብ ፡ የለም ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 19-20 ፤ እንግዲህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ በመረቀልን ፡ ባዲስና ፡ በሕያው ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ በኢየሱስ ፡ ደም ፡ በመጋረጃው ፡ ማለት ፡ በሥጋው ፡ በኩል ፡ እንድንገባ ፡ ድፍረት ፡ ስለ ፡ አለን ፥

ዕብ. ፡ 10 ፡ 21 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ቤት ፡ ላይ ፡ የኾነ ፡ ታላቅ ፡ ካህን ፡ ስለ ፡ አለን ፥

ዕብ. ፡ 10 ፡ 22 ፤ ከክፉ ፡ ኅሊና ፡ ለመንጻት ፡ ልባችንን ፡ ተረጭተን ፡ ሰውነታችንንም ፡ በጥሩ ፡ ውሃ ፡ ታጥበን ፡ በተረዳንበት ፡ እምነት ፡ በቅን ፡ ልብ ፡ እንቅረብ ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 23 ፤ የተስፋን ፡ ቃል ፡ የሰጠው ፡ የታመነ ፡ ነውና ፥ እንዳይነቃነቅ ፡ የተስፋችንን ፡ ምስክርነት ፡ እንጠብቅ ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 24 ፤ ለፍቅርና ፡ ለመልካምም ፡ ሥራ ፡ እንድንነቃቃ ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንተያይ ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 25 ፤ ባንዳንዶችም ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ እንደ ኾነው ፥ መሰብሰባችንን ፡ አንተው ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንመካከር ፡ እንጂ ፤ ይልቁንም ፡ ቀኑ ፡ ሲቀርብ ፡ እያያችኹ ፡ አብልጣችኹ ፡ ይህን ፡ አድርጉ ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 26 ፤ የእውነትን ፡ ዕውቀት ፡ ከተቀበልን ፡ በኋላ ፡ ወደን ፡ ኀጢአት ፡ ብናደርግ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕት ፡ አይቀርልንምና ፥

ዕብ. ፡ 10 ፡ 27 ፤ የሚያስፈራ ፡ ግን ፡ የፍርድ ፡ መጠበቅ ፡ ተቃዋሚዎችንም ፡ ሊበላ ፡ ያለው ፡ የእሳት ፡ ብርታት ፡ አለ ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 28 ፤ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ የናቀ ፡ ሰው ፡ ኹለት ፡ ወይም ፡ ሦስት ፡ ቢመሰክሩበት ፡ ያለርኅራኄ ፡ ይሞታል ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 29 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ልጅ ፡ የረገጠ ፡ ያንም ፡ የተቀደሰበትን ፡ የኪዳኑን ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ርኩስ ፡ ነገር ፡ የቈጠረ ፡ የጸጋውንም ፡ መንፈስ ፡ ያክፋፋ ፥ እንዴት ፡ ይልቅ ፡ የሚብስ ፡ ቅጣት ፡ የሚገባው ፡ ይመስላችኋል ፧

ዕብ. ፡ 10 ፡ 30 ፤ በቀል ፡ የእኔ ፡ ነው ፥ እኔ ፡ ብድራትን ፡ እመልሳለኹ ፡ ያለውን ፡ እናውቃለንና ፤ ደግሞም ፦ ጌታ ፡ በሕዝቡ ፡ ይፈርዳል ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 31 ፤ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ መውደቅ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 32-33 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ግማሽ ፡ በነቀፋና ፡ በጭንቅ ፡ እንደ ፡ መጫወቻ ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፡ ግማሽም ፡ እንዲህ ፡ ካሉት ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ ተካፈላችኹ ፥ ብርሃን ፡ ከበራላችኹ ፡ በኋላ ፡ መከራ ፡ በኾነበት ፡ በትልቅ ፡ ተጋድሎ ፡ የጸናችኹበትን ፡ የቀደመውን ፡ ዘመን ፡ ዐስቡ ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 34 ፤ የሚበልጥና ፡ ለዘወትር ፡ የሚኖር ፡ ገንዘብ ፡ በሰማይ ፡ ራሳችኹ ፡ እንዳላችኹ ፡ ዐውቃችኹ ፥ በእስራቴ ፡ ራራችኹልኝ ፡ የገንዘባችኹንም ፡ ንጥቂያ ፡ በደስታ ፡ ተቀበላችኹ ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 35 ፤ እንግዲህ ፡ ታላቅ ፡ ብድራት ፡ ያለውን ፡ ድፍረታችኹን ፡ አትጣሉ ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 36 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ አድርጋችኹ ፡ የተሰጣችኹን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ እንድታገኙ ፡ መጽናት ፡ ያስፈልጋችኋልና ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 37 ፤ ገና ፡ በጣም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ ሊመጣ ፡ ያለውም ፡ ይመጣል ፡ አይዘገይምም ፤

ዕብ. ፡ 10 ፡ 38 ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ በእምነት ፡ ይኖራል ፡ ወደ ፡ ኋላም ፡ ቢያፈገፍግ ፥ ነፍሴ ፡ በርሱ ፡ ደስ ፡ አይላትም ።

ዕብ. ፡ 10 ፡ 39 ፤ እኛ ፡ ግን ፡ ነፍሳቸውን ፡ ሊያድኑ ፡ ከሚያምኑቱ ፡ ነን ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ከሚያፈገፍጉ ፡ አይደለንም ።

ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 1 ፤ እምነትም ፡ ተስፋ ፡ ስለምናደርገው ፡ ነገር ፡ የሚያስረግጥ ፥ የማናየውንም ፡ ነገር ፡ የሚያስረዳ ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 2 ፤ ለሽማግሌዎች ፡ የተመሰከረላቸው ፡ በዚህ ፡ ነውና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 3 ፤ ዓለሞች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተዘጋጁ ፥ ስለዚህም ፡ የሚታየው ፡ ነገር ፡ ከሚታዩት ፡ እንዳልኾነ ፡ በእምነት ፡ እናስተውላለን ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 4 ፤ አቤል ፡ ከቃየል ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥን ፡ መሥዋዕት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእምነት ፡ አቀረበ ፥ በዚህም ፥ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ስጦታው ፡ ሲመሰክር ፥ ርሱ ፡ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ተመሰከረለት ፤ ሞቶም ፡ ሳለ ፡ በመሥዋዕቱ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ ይናገራል ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 5 ፤ ሔኖክ ፡ ሞትን ፡ እንዳያይ ፡ በእምነት ፡ ተወሰደ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ወሰደው ፡ አልተገኘም ። ሳይወሰድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ እንዳሠኘ ፡ ተመስክሮለታልና ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 6 ፤ ያለእምነትም ፡ ደስ ፡ ማሠኘት ፡ አይቻልም ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚደርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ፡ ለሚፈልጉትም ፡ ዋጋ ፡ እንዲሰጥ ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ ያስፈልገዋልና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 7 ፤ ኖኅ ፡ ገና ፡ ስለማይታየው ፡ ነገር ፡ ተረድቶ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እየፈራ ፡ ቤተ ፡ ሰዎቹን ፡ ለማዳን ፡ መርከብን ፡ በእምነት ፡ አዘጋጀ ፥ በዚህም ፡ ዓለምን ፡ ኰነነ ፥ በእምነትም ፡ የሚገኘውን ፡ ጽድቅ ፡ ወራሽ ፡ ኾነ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 8 ፤ አብርሃም ፡ የተባለው ፡ ርስት ፡ አድርጎ ፡ ሊቀበለው ፡ ወዳለው ፡ ስፍራ ፡ ለመውጣት ፡ በእምነት ፡ ታዘዘ ፥ ወዴትም ፡ እንደሚኼድ ፡ ሳያውቅ ፡ ወጣ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 9 ፤ ለእንግዳዎች ፡ እንደሚኾን ፡ በተስፋ ፡ ቃል ፡ በተሰጠው ፡ አገር ፡ በድንኳን ፡ ኖሮ ፥ ያን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ዐብረውት ፡ ከሚወርሱ ፡ ከይሥሐቅና ፡ ከያዕቆብ ፡ ጋራ ፥ እንደ ፡ መጻተኛ ፡ በእምነት ፡ ተቀመጠ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 10 ፤ መሠረት ፡ ያላትን ፥ እግዚአብሔር ፡ የሠራትንና ፡ የፈጠራትን ፡ ከተማ ፡ ይጠብቅ ፡ ነበርና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 11 ፤ ተስፋ ፡ የሰጠው ፡ የታመነ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ስለ ፡ ቈጠረች ፥ ሳራ ፡ ራሷ ፡ ደግሞ ፡ ዕድሜዋ ፡ እንኳ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ ዘርን ፡ ለመፅነስ ፡ ኀይልን ፡ በእምነት ፡ አገኘች ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፡ ደግሞ ፥ በብዛታቸው ፡ እንደሰማይ ፡ ኮከብ ፡ እንደማይቈጠርም ፡ በባሕር ፡ ዳር ፡ እንዳለ ፡ አሸዋ ፡ የነበሩት ፡ የሞተን ፡ ሰው ፡ እንኳ ፡ ከመሰለው ፡ ከአንዱ ፡ ተወለዱ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 13 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፡ አምነው ፡ ሞቱ ፥ የተሰጣቸውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አላገኙምና ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከሩቅ ፡ ኾነው ፡ አዩትና ፡ ተሳለሙት ፥ በምድሪቱም ፡ እንግዳዎችና ፡ መጻተኞች ፡ እንዲኾኑ ፡ ታመኑ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ እንዲህ ፡ የሚሉት ፡ ለእነርሱ ፡ የሚኾነውን ፡ አገር ፡ እንዲፈልጉ ፡ ያመለክታሉና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ያን ፡ የወጡበትን ፡ አገር ፡ ዐስበው ፡ ቢኾኑ ፥ ሊመለሱ ፡ ጊዜ ፡ በኾነላቸው ፡ ነበር ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ የሚበልጠውን ፡ ርሱም ፡ ሰማያዊ ፡ አገር ፡ ይናፍቃሉ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካቸው ፡ ተብሎ ፡ ሊጠራ ፡ በእነርሱ ፡ አያፍርም ፥ ከተማን ፡ አዘጋጅቶላቸዋልና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 17-18 ፤ አብርሃም ፡ በተፈተነበት ፡ ጊዜ ፡ ይሥሐቅን ፡ በእምነት ፡ አቀረበ ፥ የተስፋን ፡ ቃል ፡ የተቀበለው ። በይሥሐቅ ፡ ዘር ፡ ይጠራልኻል ፡ የተባለለት ፡ ርሱም ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ አቀረበ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከሙታን ፡ እንኳ ፡ ሊያስነሣው ፡ እንዲቻለው ፡ ዐስቧልና ፥ ከዚያም ፡ ደግሞ ፡ በምሳሌ ፡ አገኘው ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 20 ፤ ይሥሐቅ ፡ ሊመጣ ፡ ስለ ፡ አለው ፡ ነገር ፡ ያዕቆብንና ፡ ዔሳውን ፡ በእምነት ፡ ባረካቸው ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 21 ፤ ያዕቆብ ፡ ሲሞት ፡ በእምነት ፡ የዮሴፍን ፡ ልጆች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ባረካቸው ፥ በዘንጉም ፡ ጫፍ ፡ ተጠግቶ ፡ ሰገደ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 22 ፤ ዮሴፍ ፡ ወደ ፡ ሞት ፡ ቀርቦ ፡ ሳለ ፡ በእምነት ፡ ስለእስራኤል ፡ ልጆች ፡ መውጣት ፡ አስታወሰ ፥ ስለ ፡ ዐጥንቱም ፡ አዘዛቸው ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 23 ፤ ሙሴ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ ወላጆቹ ፡ ያማረ ፡ ሕፃን ፡ መኾኑን ፡ አይተው ፡ በእምነት ፡ ሦስት ፡ ወር ፡ ሸሸጉት ፡ የንጉሥንም ፡ ዐዋጅ ፡ አልፈሩም ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 24 ፤ ሙሴ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ የፈርዖን ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ እንዳይባል ፡ በእምነት ፡ እምቢ ፡ አለ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 25-26 ፤ ከግብጽም ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መነቀፍ ፡ እጅግ ፡ የሚበልጥ ፡ ባለጠግነት ፡ እንዲኾን ፡ ዐስቧልና ፥ ለጊዜው ፡ በኀጢአት ፡ ከሚገኝ ፡ ደስታ ፡ ይልቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ መከራ ፡ መቀበልን ፡ መረጠ ፤ ብድራቱን ፡ ትኵር ፡ ብሎ ፡ ተመልክቷልና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 27 ፤ የንጉሡን ፡ ቀሣጣ ፡ ሳይፈራ ፡ የግብጽን ፡ አገር ፡ የተወ ፡ በእምነት ፡ ነበር ፤ የማይታየውን ፡ እንደሚያየው ፡ አድርጎ ፡ ጸንቷልና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 28 ፤ አጥፊው ፡ የበኵሮችን ፡ ልጆች ፡ እንዳይነካ ፡ ፋሲካንና ፡ ደምን ፡ መርጨትን ፡ በእምነት ፡ አደረገ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 29 ፤ በደረቅ ፡ ምድር ፡ እንደሚያልፉ ፡ በቀይ ፡ ባሕር ፡ በእምነት ፡ ተሻገሩ ፥ የግብጽ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ሲሞክሩ ፡ ተዋጡ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 30 ፤ የኢያሪኮ ፡ ቅጥር ፡ ሰባት ፡ ቀን ፡ ከዞሩበት ፡ በኋላ ፡ በእምነት ፡ ወደቀ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 31 ፤ ጋለሞታዪቱ ፡ ረዓብ ፡ ሰላዮችን ፡ በሰላም ፡ ስለ ፡ ተቀበለቻቸው ፡ ከማይታዘዙ ፡ ጋራ ፡ በእምነት ፡ አልጠፋችም ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 32 ፤ እንግዲህ ፡ ምን ፡ እላለኹ ፧ ስለ ፡ ጌዴዎንና ፡ ስለ ፡ ባርቅ ፡ ስለ ፡ ሶምሶንም ፡ ስለ ፡ ዮፍታሔም ፡ ስለ ፡ ዳዊትና ፡ ስለ ፡ ሳሙኤልም ፡ ስለ ፡ ነቢያትም ፡ እንዳልተርክ ፡ ጊዜ ፡ ያጥርብኛልና ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 33 ፤ እነርሱ ፡ በእምነት ፡ መንግሥታትን ፡ ድል ፡ ነሡ ፥ ጽድቅን ፡ አደረጉ ፥ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አገኙ ፥

ዕብ. ፡ 11 ፡ 34 ፤ የአንበሳዎችን ፡ አፍ ፡ ዘጉ ፥ የእሳትን ፡ ኀይል ፡ አጠፉ ፥ ከሰይፍ ፡ ስለት ፡ አመለጡ ፥ ከድካማቸው ፡ በረቱ ፥ በጦርነት ፡ ኀይለኞች ፡ ኾኑ ፥ የባዕድ ፡ ጭፍራዎችን ፡ አባረሩ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 35 ፤ ሴቶች ፡ ሙታናቸውን ፡ በትንሣኤ ፡ ተቀበሉ ፤ ሌላዎችም ፡ መዳንን ፡ ሳይቀበሉ ፡ የሚበልጠውን ፡ ትንሣኤ ፡ እንዲያገኙ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ ተደበደቡ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 36 ፤ ሌላዎችም ፡ መዘበቻ ፡ በመኾንና ፡ በመገረፍ ፡ ከዚህም ፡ በላይ ፡ በእስራትና ፡ በወህኒ ፡ ተፈተኑ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 37 ፤ በድንጋይ ፡ ተወግረው ፡ ሞቱ ፥ ተፈተኑ ፥ በመጋዝ ፡ ተሰነጠቁ ፥ በሰይፍ ፡ ተገድለው ፡ ሞቱ ፥ ኹሉን ፡ እያጡ ፡ መከራን ፡ እየተቀበሉ ፡ እየተጨነቁ ፡ የበግና ፡ የፍየል ፡ ሌጦ ፡ ለብሰው ፡ ዞሩ ፤

ዕብ. ፡ 11 ፡ 38 ፤ ዓለም ፡ አልተገባቸውምና ፡ በምድረ ፡ በዳና ፡ በተራራ ፥ በዋሻና ፡ በምድር ፡ ጕድጓድ ፡ ተቅበዘበዙ ።

ዕብ. ፡ 11 ፡ 39-40 ፤ እነዚህም ፡ ኹሉ ፡ በእምነታቸው ፡ ተመስክሮላቸው ፡ ሳሉ ፡ የተሰጠውን ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ አላገኙም ፥ ያለእኛ ፡ ፍጹማን ፡ እንዳይኾኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ አንዳች ፡ የሚበልጥ ፡ ነገርን ፡ አስቀድሞ ፡ አይቶ ፡ ነበርና ።

_____ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ዕብ. ፡ 12 ፡ 1-2 ፤ እንግዲህ ፡ እነዚህን ፡ የሚያኽሉ ፡ ምስክሮች ፡ እንደ ፡ ደመና ፡ በዙሪያችን ፡ ካሉልን ፥ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ሸክምን ፡ ኹሉ ፡ ቶሎም ፡ የሚከበንን ፡ ኀጢአት ፡ አስወግደን ፥ የእምነታችንንም ፡ ራስና ፡ ፈጻሚውን ፡ ኢየሱስን ፡ ተመልክተን ፥ በፊታችን ፡ ያለውን ፡ ሩጫ ፡ በትዕግሥት ፡ እንሩጥ ፤ ርሱ ፡ ነውርን ፡ ንቆ ፡ በፊቱም ፡ ስለ ፡ አለው ፡ ደስታ ፡ በመስቀል ፡ ታግሦ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ቀኝ ፡ ተቀምጧልና ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ በነፍሳችኹ ፡ ዝላችኹ ፡ እንዳትደክሙ ፥ ከኀጢአተኞች ፡ በደረሰበት ፡ እንዲህ ፡ ባለ ፡ መቃወም ፡ የጸናውን ፡ ዐስቡ ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 4 ፤ ከኀጢአት ፡ ጋራ ፡ እየተጋደላችኹ ፡ ገና ፡ ደምን ፡ እስከ ፡ ማፍሰስ ፡ ድረስ ፡ አልተቃወማችኹም ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 5-6 ፤ እንደ ፡ ልጆችም ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፦ ልጄ ፡ ሆይ ፥ የጌታን ፡ ቅጣት ፡ አታቅል ፥ በሚገሥጽኽም ፡ ጊዜ ፡ አትድከም ፤ ጌታ ፡ የሚወደውን ፡ ይቀጣዋልና ፥ የሚቀበለውንም ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ይገርፈዋል ፡ ብሎ ፡ የሚነጋገረውን ፡ ምክር ፡ ረስታችኋል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ ለመቀጣት ፡ ታገሡ ፤ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ልጆች ፡ ያደርግላችኋልና ፤ አባቱ ፡ የማይቀጣው ፡ ልጅ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዕብ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ የቅጣት ፡ ተካፋይ ፡ ኾኗልና ፥ ያለቅጣት ፡ ብትኖሩ ፡ ዲቃላዎች ፡ እንጂ ፡ ልጆች ፡ አይደላችኹም ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ከዚህም ፡ በላይ ፡ የቀጡን ፡ የሥጋችን ፡ አባቶች ፡ ነበሩን ፡ እናፍራቸውም ፡ ነበር ፤ እንዴትስ ፡ ይልቅ ፡ ለመናፍስት ፡ አባት ፡ አብልጠን ፡ ልንገዛና ፡ በሕይወት ፡ ልንኖር ፡ በተገባን ፧

ዕብ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ እነርሱ ፡ መልካም ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ታያቸው ፡ ለጥቂት ፡ ቀን ፡ ይቀጡን ፡ ነበርና ፥ ርሱ ፡ ግን ፡ ከቅድስናው ፡ እንድንካፈል ፡ ለጥቅማችን ፡ ይቀጣናል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ ቅጣት ፡ ኹሉ ፡ ለጊዜው ፡ የሚያሳዝን ፡ እንጂ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ አይመስልም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በኋላ ፡ ለለመዱት ፡ የሰላምን ፡ ፍሬ ፡ ርሱም ፡ ጽድቅን ፡ ያፈራላቸዋል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ የላሉትን ፡ እጆች ፡ የሰለሉትንም ፡ ጕልበቶች ፡ አቅኑ ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 13 ፤ ያነከሰውም ፡ እንዲፈወስ ፡ እንጂ ፡ እንዳይናጋ ፥ ለእግራችኹ ፡ ቅን ፡ መንገድ ፡ አድርጉ ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 14 ፤ ከሰው ፡ ኹሉ ፡ ጋራ ፡ ሰላምን ፡ ተከታተሉ ፡ ትቀደሱም ፡ ዘንድ ፡ ፈልጉ ፥ ያለርሱ ፡ ጌታን ፡ ሊያይ ፡ የሚችል ፡ የለምና ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 15 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ለማንም ፡ እንዳይጐድለው ፥ ብዙዎቹም ፡ የሚረክሱበት ፡ አንድ ፡ መራራ ፡ ሥር ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ በቅሎ ፡ እንዳያስጨንቅ ፥ ሴሰኛም ፡ የሚኾን ፡ እንዳይገኝ ፥

ዕብ. ፡ 12 ፡ 16 ፤ ወይም ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ መብል ፡ በኵርነቱን ፡ እንደ ፡ ሸጠ ፡ እንደ ፡ ዔሳው ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚመች ፡ ሰው ፡ እንዳይኾን ፡ ተጠንቀቁ ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 17 ፤ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንኳ ፡ በረከቱን ፡ ሊወርስ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተጣለ ፡ ታውቃላችኹና ፤ በእንባ ፡ ተግቶ ፡ ምንም ፡ ቢፈልገው ፡ ለንስሓ ፡ ስፍራ ፡ አላገኘምና ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 18 ፤ ሊዳሰስ ፡ ወደሚችል ፡ ወደሚቃጠልም ፡ እሳት ፡ ወደ ፡ ጭጋግም ፡ ወደ ፡ ጨለማም ፡ ወደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ወደመለከት ፡ ድምፅም ፡ ወደቃሎችም ፡ ነገር ፡ አልደረሳችኹምና ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 19 ፤ ያንም ፡ ነገር ፡ የሰሙት ፡ ሌላ ፡ ቃል ፡ እንዳይጨመርባቸው ፡ ለመኑ ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 20 ፤ እንስሳ ፡ እንኳ ፡ ተራራውን ፡ ቢነካ ፡ ተወግሮ ፡ ይሙት ፡ የምትለውን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊታገሡ ፡ አልቻሉምና ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 21 ፤ ሙሴም ፦ እጅግ ፡ እፈራለኹ ፥ እንቀጠቀጥማለኹ ፡ እስኪል ፡ ድረስ ፡ የሚታየው ፡ እጅግ ፡ የሚያስፈራ ፡ ነበር ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 22 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወደጽዮን ፡ ተራራና ፡ ወደሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ ከተማ ፡ ደርሳችኋል ፥ ወደ ፡ ሰማያዊቱም ፡ ኢየሩሳሌም ፥ በደስታም ፡ ወደተሰበሰቡት ፡ ወደ ፡ አእላፋት ፡ መላእክት ፥

ዕብ. ፡ 12 ፡ 23 ፤ በሰማያትም ፡ ወደተጻፉ ፡ ወደበኵራት ፡ ማኅበር ፥ የኹሉም ፡ ዳኛ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፥ ፍጹማንም ፡ ወደኾኑት ፡ ወደጻድቃን ፡ መንፈሶች ፥

ዕብ. ፡ 12 ፡ 24 ፤ የዐዲስም ፡ ኪዳን ፡ መካከለኛ ፡ ወደሚኾን ፡ ወደ ፡ ኢየሱስ ፥ ከአቤልም ፡ ደም ፡ ይልቅ ፡ የሚሻለውን ፡ ወደሚናገር ፡ ወደመርጨት ፡ ደም ፡ ደርሳችኋል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 25 ፤ ለሚናገረው ፡ እምቢ ፡ እንዳትሉ ፡ ተጠንቀቁ ፤ እነዚያ ፡ በምድር ፡ ላስረዳቸው ፡ እምቢ ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ካላመለጡ ፥ ከሰማይ ፡ ከመጣው ፡ ፈቀቅ ፡ የምንል ፡ እኛስ ፡ እንዴት ፡ እናመልጣለን ፧

ዕብ. ፡ 12 ፡ 26 ፤ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ድምፁ ፡ ምድርን ፡ አናወጠ ፥ አኹን ፡ ግን ፦ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሜ ፡ እኔ ፡ ሰማይን ፡ አናውጣለኹ ፡ እንጂ ፡ ምድርን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ተስፋ ፡ ሰጥቷል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 27 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፦ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሜ ፡ የሚል ፡ ቃል ፥ የማይናወጡት ፡ ጸንተው ፡ እንዲኖሩ ፥ የሚናወጡት ፡ የተፈጠሩ ፡ እንደሚኾኑ ፡ ይለወጡ ፡ ዘንድ ፡ ያሳያል ።

ዕብ. ፡ 12 ፡ 28 ፤ ስለዚህ ፥ የማይናወጥን ፡ መንግሥት ፡ ስለምንቀበል ፥ በማክበርና ፡ በፍርሀት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ እያሠኘን ፡ የምናመልክበትን ፡ ጸጋ ፡ እንያዝ ፤

ዕብ. ፡ 12 ፡ 29 ፤ አምላካችን ፡ በእውነት ፡ የሚያጠፋ ፡ እሳት ፡ ነውና ።

ዕብራውያን ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 1-2 ፤ የወንድማማች ፡ መዋደድ ፡ ይኑር ። እንግዳዎችን ፡ መቀበል ፡ አትርሱ ፤ በዚህ ፡ አንዳንዶች ፡ ሳያውቁ ፡ መላእክትን ፡ እንግድነት ፡ ተቀብለዋልና ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 3 ፤ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ታሰረ ፡ ኾናችኹ ፡ እስሮችን ፡ ዐስቡ ፥ የተጨነቁትንም ፡ ራሳችኹ ፡ ደግሞ ፡ በሥጋ ፡ እንዳለ ፡ ኾናችኹ ፡ ዐስቡ ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 4 ፤ መጋባት ፡ በኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ክቡር ፡ መኝታውም ፡ ንጹሕ ፡ ይኹን ፤ ሴሰኞችንና ፡ አመንዝራዎችን ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 5 ፤ አካኼዳችኹ ፡ ገንዘብን ፡ ያለመውደድ ፡ ይኹን ፥ ያላችኹም ፡ ይብቃችኹ ፤ ርሱ ፡ ራሱ ፦ አልለቅኽም ፡ ከቶም ፡ አልተውኽም ፡ ብሏልና ፤

ዕብ. ፡ 13 ፡ 6 ፤ ስለዚህ ፥ በድፍረት ፦ ጌታ ፡ ይረዳኛልና ፥ አልፈራም ፤ ሰው ፡ ምን ፡ ያደርገኛል ፧ እንላለን ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 7 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የተናገሯችኹን ፡ ዋናዎቻችኹን ፡ ዐስቡ ፥ የኑሯቸውንም ፡ ፍሬ ፡ እየተመለከታችኹ ፡ በእምነታቸው ፡ ምሰሏቸው ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 8 ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትናንትና ፡ ዛሬ ፡ እስከ ፡ ለዘለዓለምም ፡ ያው ፡ ነው ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 9 ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ በኾነ ፡ በእንግዳ ፡ ትምህርት ፡ አትወሰዱ ፤ ልባችኹ ፡ በጸጋ ፡ ቢጸና ፡ መልካም ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በመብል ፡ አይደለም ፤ በዚህ ፡ የሚሠሩባት ፡ አልተጠቀሙምና ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ መሠዊያ ፡ አለን ፥ ከርሱም ፡ ሊበሉ ፡ ድንኳኑን ፡ የሚያገለግሉ ፡ መብት ፡ የላቸውም ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ የእንስሳዎችን ፡ ደም ፡ ያቀርባልና ፤ ሥጋቸው ፡ ግን ፡ ከሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ ይቃጠላል ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ኢየሱስ ፡ ደግሞ ፡ በገዛ ፡ ደሙ ፡ ሕዝቡን ፡ እንዲቀድስ ፡ ከበር ፡ ውጭ ፡ መከራን ፡ ተቀበለ ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ እንግዲህ ፡ ነቀፌታውን ፡ እየተሸከምን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ወደሰፈሩ ፡ ውጭ ፡ እንውጣ ፤

ዕብ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ በዚህ ፡ የምትኖር ፡ ከተማ ፡ የለችንምና ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያላትን ፡ እንፈልጋለን ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ እንግዲህ ፡ ዘወትር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምስጋናን ፡ መሥዋዕት ፥ ማለት ፡ ለስሙ ፡ የሚመሰክሩ ፡ የከንፈሮችን ፡ ፍሬ ፥ በርሱ ፡ እናቅርብለት ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መልካም ፡ ማድረግን ፡ ለሌላዎችም ፡ ማካፈልን ፡ አትርሱ ፤ እንዲህ ፡ ያለው ፡ መሥዋዕት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሠኘዋልና ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ ለዋናዎቻችኹ ፡ ታዘዙና ፡ ተገዙ ፤ እነርሱ ፡ ስሌትን ፡ እንደሚሰጡ ፡ አድርገው ፥ ይህንኑ ፡ በደስታ ፡ እንጂ ፡ በሐዘን ፡ እንዳያደርጉት ፥ ይህ ፡ የማይጠቅማችኹ ፡ ነበርና ፥ ስለ ፡ ነፍሳችኹ ፡ ይተጋሉ ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ ጸልዩልን ፤ በነገር ፡ ኹሉ ፡ በመልካም ፡ እንድንኖር ፡ ወደን ፥ መልካም ፡ ኅሊና ፡ እንዳለን ፡ ተረድተናልና ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 19 ፤ ይልቁንም ፡ ፈጥኜ ፡ እንድመለስላችኹ ፡ ይህን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ አጥብቄ ፡ እለምናችኋለኹ ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 20 ፤ በዘለዓለም ፡ ኪዳን ፡ ደም ፡ ለበጎች ፡ ትልቅ ፡ እረኛ ፡ የኾነውን ፡ ጌታችንን ፡ ኢየሱስን ፡ ከሙታን ፡ ያወጣው ፡ የሰላም ፡ አምላክ ፥

ዕብ. ፡ 13 ፡ 21 ፤ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ በፊቱ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ በእናንተ ፡ እያደረገ ፥ ፈቃዱን ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በመልካም ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹማን ፡ ያድርጋችኹ ፤ ለርሱ ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 22 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የምክርን ፡ ቃል ፡ እንድትታገሡ ፡ እመክራችኋለኹ ፥ በጥቂት ፡ ቃል ፡ ጽፌላችኋለኹና ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 23 ፤ ወንድማችን ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እንደ ፡ ተፈታ ፡ ዕወቁ ፥ ቶሎ ፡ ብሎም ፡ ቢመጣ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አያችኋለኹ ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 24 ፤ ለዋናዎቻችኹ ፡ ኹሉና ፡ ለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርቡልኝ ። ከኢጣልያ ፡ የኾኑቱ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ዕብ. ፡ 13 ፡ 25 ፤ ጸጋ ፡ ከኹላችኹ ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የመዝመሪያዩቱ ፡ የሐዋርያው ፡ የጴጥሮስ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____1ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ ጴጥሮስ ፥ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ አስቀድሞ ፡ እንዳወቃቸው ፡ በመንፈስም ፡ እንደሚቀደሱ ፥ ይታዘዙና ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ይረጩ ፡ ዘንድ ፡ ለተመረጡት ፡ በጳንጦስና ፡ በገላትያ ፡ በቀጳዶቅያም ፡ በእስያም ፡ በቢታንያም ፡ ለተበተኑ ፡ መጻተኞች ፤ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 3-5 ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ በመነሣቱ ፡ ለሕያው ፡ ተስፋና ፡ ለማይጠፋ ፥ እድፈትም ፡ ለሌለበት ፥ ለማያልፍም ፡ ርስት ፡ እንደ ፡ ምሕረቱ ፡ ብዛት ፡ ኹለተኛ ፡ የወለደን ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክና ፡ አባት ፡ ይባረክ ፤ ይህም ፡ ርስት ፡ በመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ለተዘጋጀ ፡ መዳን ፡ በእምነት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ለተጠበቃችኹ ፡ ለእናንተ ፡ በሰማይ ፡ ቀርቶላችኋል ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 6-7 ፤ በዚህም ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ይላችኋል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በእሳት ፡ ምንም ፡ ቢፈተን ፡ ከሚጠፋው ፡ ወርቅ ፡ ይልቅ ፡ አብልጦ ፡ የሚከብር ፡ የተፈተነ ፡ እምነታችኹ ፥ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲገለጥ ፥ ለምስጋናና ፡ ለክብር ፡ ለውዳሴም ፡ ይገኝ ፡ ዘንድ ፡ አኹን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ቢያስፈልግ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ዐዝናችኋል ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 8-9 ፤ ርሱንም ፡ ሳታዩት ፡ ትወዱታላችኹ ፤ አኹንም ፡ ምንም ፡ ባታዩት ፡ በርሱ ፡ አምናችኹ ፥ የእምነታችኹን ፡ ፍጻሜ ፡ ርሱም ፡ የነፍሳችኹን ፡ መዳን ፡ እየተቀበላችኹ ፥ በማይነገርና ፡ ክብር ፡ በሞላበት ፡ ሐሤት ፡ ደስ ፡ ይላችኋል ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ለእናንተም ፡ ስለሚሰጠው ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ የተናገሩት ፡ ነቢያት ፡ ስለዚህ ፡ መዳን ፡ ተግተው ፡ እየፈለጉ ፡ መረመሩት ፤

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 11 ፤ በእነርሱም ፡ የነበረ ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፥ ስለክርስቶስ ፡ መከራ ፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ስለሚመጣው ፡ ክብር ፡ አስቀድሞ ፡ እየመሰከረ ፥ በምን ፡ ወይም ፡ እንዴት ፡ ባለ ፡ ዘመን ፡ እንዳመለከተ ፡ ይመረምሩ ፡ ነበር ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ለእነርሱም ፡ ከሰማይ ፡ በተላከ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌልን ፡ የሰበኩላችኹ ፡ ሰዎች ፡ አኹን ፡ ባወሩላችኹ ፡ ነገር ፡ እናንተን ፡ እንጂ ፡ ራሳቸውን ፡ እንዳላገለገሉ ፡ ተገለጠላቸው ፤ ይህንም ፡ ነገር ፡ መላእክቱ ፡ ሊመለከቱ ፡ ይመኛሉ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ስለዚህ ፥ የልቡናችኹን ፡ ወገብ ፡ ታጥቃችኹና ፡ በመጠን ፡ ኖራችኹ ፥ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲገለጥ ፡ የምታገኙትን ፡ ጸጋ ፡ ፈጽማችኹ ፡ ተስፋ ፡ አድርጉ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 14 ፤ እንደሚታዘዙ ፡ ልጆች ፡ ባለማወቃችኹ ፡ አስቀድሞ ፡ የኖራችኹበትን ፡ ምኞት ፡ አትከተሉ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 15-16 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፦ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ፡ ተብሎ ፡ ስለ ፡ ተጻፈ ፡ የጠራችኹ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በኑሯችኹ ፡ ኹሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ኹኑ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 17 ፤ ለሰው ፡ ፊትም ፡ ሳያደላ ፡ በያንዳንዱ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ የሚፈርደውን ፡ አባት ፡ ብላችኹ ፡ ብትጠሩ ፡ በእንግድነታችኹ ፡ ዘመን ፡ በፍርሀት ፡ ኑሩ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 18-19 ፤ ከአባቶቻችኹ ፡ ከወረሳችኹት ፡ ከከንቱ ፡ ኑሯችኹ ፡ በሚያልፍ ፡ ነገር ፡ በብር ፡ ወይም ፡ በወርቅ ፡

ሳይኾን ፥ ነውርና ፡ እድፍ ፡ እንደ ፡ ሌለው ፡ እንደ ፡ በግ ፡ ደም ፡ በክቡር ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ እንደ ፡ ተዋጃችኹ ፡ ታውቃላችኹ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 20-21 ፤ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ እንኳ ፡ አስቀድሞ ፡ ታወቀ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እምነታችኹና ፡ ተስፋችኹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፥ ከሙታን ፡ ባስነሣው ፡ ክብርንም ፡ በሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ ስለምታምኑ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ በዘመኑ ፡ መጨረሻ ፡ ተገለጠ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 22 ፤ ለእውነት ፡ እየታዘዛችኹ ፡ ግብዝነት ፡ ለሌለበት ፡ ለወንድማማች ፡ መዋደድ ፡ ነፍሳችኹን ፡ አንጽታችኹ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ከልባችኹ ፡ አጥብቃችኹ ፡ ተዋደዱ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 23 ፤ ዳግመኛ ፡ የተወለዳችኹት ፡ ከሚጠፋ ፡ ዘር ፡ አይደለም ፥ በሕያውና ፡ ለዘለዓለም ፡ በሚኖር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከማይጠፋ ፡ ዘር ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 24 ፤ ሥጋ ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ ክብሩም ፡ ኹሉ ፡ እንደ ፡ ሣር ፡ አበባ ፡ ነውና ፤ ሣሩ ፡ ይጠወልጋል ፡ አበባውም ፡ ይረግፋል ፤

ጴጥ.1 ፥ 1 ፥ 25 ፤ የጌታ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ። በወንጌልም ፡ የተሰበከላችኹ ፡ ቃል ፡ ይህ ፡ ነው ።

_____1ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 1 ፤ እንግዲህ ፡ ክፋትን ፡ ኹሉ ፡ ተንኰልንም ፡ ኹሉ ፡ ግብዝነትንም ፡ ቅንአትንም ፡ ሐሜትንም ፡ ኹሉ ፡ አስወግዳችኹ ፥

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 2-3 ፤ ጌታ ፡ ቸር ፡ መኾኑን ፡ ቀምሳችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ለመዳን ፡ በርሱ ፡ እንድታድጉ ፡ አኹን ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ተንኰል ፡ የሌለበትን ፡ የቃልን ፡ ወተት ፡ ተመኙ ።

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 4 ፤ በሰውም ፡ ወደተጣለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ ወደተመረጠና ፡ ክቡር ፡ ወደኾነው ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ ድንጋይ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ እየቀረባችኹ ፥

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 5 ፤ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ሕያዋን ፡ ድንጋዮች ፡ ኾናችኹ ፥ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ የሚያሠኝ ፡ መንፈሳዊ ፡ መሥዋዕትን ፡ ታቀርቡ ፡ ዘንድ ፡ ቅዱሳን ፡ ካህናት ፡ እንድትኾኑ ፡ መንፈሳዊ ፡ ቤት ፡ ለመኾን ፡ ተሠሩ ።

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 6 ፤ በመጽሐፍ ፦ እንሆ ፥ የተመረጠና ፡ የከበረን ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ ድንጋይ ፡ በጽዮን ፡ አኖራለኹ ፥ በርሱም ፡ የሚያምን ፡ አያፍርም ፡ ተብሎ ፡ ተጽፏልና ።

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ክብሩ ፡ ለእናንተ ፡ ለምታምኑት ፡ ነው ፤ ለማያምኑ ፡ ግን ፡ ዐናጢዎች ፡ የጣሉት ፡ ድንጋይ ፡ ርሱ ፡ የማእዘን ፡ ራስ ፡ የዕንቅፋትም ፡ ድንጋይ ፡ የማሰናከያም ፡ አለት ፡ ኾነ ፤

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 8 ፤ የማያምኑ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ በቃሉ ፡ ይሰናከሉበታልና ፤ ለዚህ ፡ ደግሞ ፡ የተመደቡ ፡ ናቸው ።

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 9 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ከጨለማ ፡ ወደሚደነቅ ፡ ብርሃኑ ፡ የጠራችኹን ፡ የርሱን ፡ በጎነት ፡ እንድትናገሩ ፡ የተመረጠ ፡ ትውልድ ፥ የንጉሥ ፡ ካህናት ፥ ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፥ ለርስቱ ፡ የተለየ ፡ ወገን ፡ ናችኹ ፤

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 10 ፤ እናንተ ፡ ቀድሞ ፡ ወገን ፡ አልነበራችኹም ፡ አኹን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ናችኹ ፤ እናንተ ፡ ምሕረት ፡ ያገኛችኹ ፡ አልነበራችኹም ፡ አኹን ፡ ግን ፡ ምሕረትን ፡ አግኝታችኋል ።

ጴጥ.1 ፥ 2 ፥ 11 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ነፍስን ፡ ከሚዋጋ ፡ ሥጋዊ ፡ ምኞት ፡ ትርቁ ፡ ዘንድ ፡ እንግዳዎችና ፡ መጻተኞች ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፡ እለምናችኋለኹ ፤

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ስለሚመለከቱት ፡ ስለ ፡ መልካም ፡ ሥራችኹ ፥ ክፉ ፡ እንደምታደርጉ ፡ በዚያ ፡ እናንተን ፡ በሚያሙበት ፡ ነገር ፥ በሚጐበኝበት ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩት ፡ ዘንድ ፡ በአሕዛብ ፡ መካከል ፡ ኑሯችኹ ፡ መልካም ፡ ይኹን ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ ስለ ፡ ጌታ ፡ ብላችኹ ፡ ለሰው ፡ ሥርዐት ፡ ኹሉ ፡ ተገዙ ፤ ለንጉሥም ፡ ቢኾን ፥ ከኹሉ ፡ በላይ ፡ ነውና ፤

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ለመኳንንትም ፡ ቢኾን ፥ ክፉ ፡ የሚያደርጉትን ፡ ለመቅጣት ፡ በጎም ፡ የሚያደርጉትን ፡ ለማመስገን ፡ ከርሱ ፡ ተልከዋልና ፥ ተገዙ ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 15 ፤ በጎ ፡ እያደረጋችኹ ፥ የማያውቁትን ፡ ሞኞች ፡ ዝም ፡ ታሠኙ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነውና ፤

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ሐራነት ፡ ወጥታችኹ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ባሪያዎች ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ ያ ፡ ሐራነት ፡ ለክፋት ፡ መሸፈኛ ፡ እንዲኾን ፡ አታድርጉ ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ኹሉን ፡ አክብሩ ፥ ወንድሞችን ፡ ውደዱ ፥ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፥ ንጉሥን ፡ አክብሩ ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ሎሌዎች ፡ ሆይ ፥ ለበጎዎችና ፡ ለገሮች ፡ ጌታዎቻችኹ ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ ለጠማማዎች ፡ ደግሞ ፡ በፍርሀት ፡ ኹሉ ፡ ተገዙ ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ በግፍ ፡ መከራን ፡ የሚቀበል ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያሰበ ፡ ሐዘንን ፡ ቢታገሥ ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋልና ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ ኀጢአት ፡ አድርጋችኹ ፡ ስትገሰሙ ፡ ብትታገሡ ፥ ምን ፡ ክብር ፡ አለበት ፧ ነገር ፡ ግን ፡ መልካም ፡ አድርጋችኹ ፡ መከራን ፡ ስትቀበሉ ፡ ብትታገሡ ፥ ይህ ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 21 ፤ የተጠራችኹለት ፡ ለዚህ ፡ ነውና ፤ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ፍለጋውን ፡ እንድትከተሉ ፡ ምሳሌ ፡ ትቶላችኹ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ መከራን ፡ ተቀብሏልና ።

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ርሱም ፡ ኀጢአት ፡ አላደረገም ፥ ተንኰልም ፡ በአፉ ፡ አልተገኘበትም ፤

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ሲሰድቡት ፡ መልሶ ፡ አልተሳደበም ፥ መከራንም ፡ ሲቀበል ፡ አልዛተም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጽድቅ ፡ ለሚፈርደው ፡ ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፤

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 24 ፤ ለኀጢአት ፡ ሞተን ፡ ለጽድቅ ፡ እንድንኖር ፥ ርሱ ፡ ራሱ ፡ በሥጋው ፡ ኀጢአታችንን ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ተሸከመ ፤ [*] ፡

ጴጥ.1 ፡ 2 ፡ 25 ፤ በመገረፉ ፡ ቍስል ፡ ተፈወሳችኹ ። እንደ ፡ በጎች ፡ ትቅበዘበዙ ፡ ነበርና ፥ አኹን ፡ ግን ፡ ወደነፍሳችኹ ፡ እረኛና ፡ ጠባቂ ፡ ተመልሳችኋል ።

[*] ፤ በግእዝ ፡ እንዲህ ፡ ተጽፏል ። ወበእንተ ፡ ኃጥኣዊን ፡ ውእቱ ፡ ተሰቅለ ፡ ዲበ ፡ ዕፅ ፡ በሥጋሁ ፡ ከመ ፡ ያውፅአነ ፡ እምኃጥኣዊን ፡ ወበጽድቁ ፡ ያሕይወነ ።

_____1ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 1-2 ፤ እንዲሁም ፥ እናንተ ፡ ሚስቶች ፡ ሆይ ፥ ከባሎቻችኹ ፡ አንዳንዱ ፡ ለትምህርት ፡ የማይታዘዙ ፡ ቢኖሩ ፥ በፍርሀት ፡ ያለውን ፡ ንጹሑን ፡ ኑሯችኹን ፡ እየተመለከቱ ፡ ያለትምህርት ፡ በሚስቶቻቸው ፡ ኑሮ ፡ እንዲገኙ ፡ ተገዙላቸው ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ ለእናንተም ፡ ጠጕርን ፡ በመሸረብና ፡ ወርቅን ፡ በማንጠልጠል ፡ ወይም ፡ ልብስን ፡ በመጐናጸፍ ፡ በውጭ ፡ የኾነ ፡ ሽልማት ፡ አይኹንላችኹ ፥

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ዋጋው ፡ እጅግ ፡ የከበረ ፡ የዋህና ፡ ዝግተኛ ፡ መንፈስ ፡ ያለውን ፡ የማይጠፋውን ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ የተሰወረ ፡ የልብ ፡ ሰው ፡ ይኹንላችኹ ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ እንዲህ ፡ በቀድሞ ፡ ዘመን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተስፋ ፡ ያደረጉት ፡ ቅዱሳት ፡ ሴቶች ፡ ደግሞ ፡ ለባሎቻቸው ፡ ሲገዙ ፡ ተሸልመው ፡ ነበርና ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ እንዲሁም ፡ ሳራ ፡ ለአብርሃም ፦ ጌታ ፡ ብላ ፡ እየጠራችው ፡ ታዘዘችለት ፤ እናንተም ፡ ከሚያስደነግጥ ፡ ነገር ፡ አንዳች ፡ እንኳ ፡ ሳትፈሩ ፡ መልካም ፡ ብታደርጉ ፥ ልጆቿ ፡ ናችኹ ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ እንዲሁም ፥ እናንተ ፡ ባሎች ፡ ሆይ ፥ ደካማ ፡ ፍጥረት ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ከሚስቶቻችኹ ፡ ጋራ ፡ በማስተዋል ፡ ዐብራችኹ ፡ ኑሩ ፤ ጸሎታችኹ ፡ እንዳይከለከል ፥ ዐብረው ፡ ደግሞ ፡ የሕይወትን ፡ ጸጋ ፡ እንደሚወርሱ ፡ አድርጋችኹ ፡ አክብሯቸው ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ በመጨረሻው ፡ ኹላችኹ ፡ ባንድ ፡ ልብ ፡ ኹኑ ፥ የሌላው ፡ መከራ ፡ ለእናንተ ፡ እንደሚኾን ፡ አድርጉ ፥ እንደ ፡ ወንድሞች ፡ ተዋደዱ ፥ ርኅሩኆችና ፡ ትሑታን ፡ ኹኑ ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ክፉን ፡ በክፉ ፡ ፈንታ ፡ ወይም ፡ ስድብን ፡ በስድብ ፡ ፈንታ ፡ አትመልሱ ፥ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ባርኩ ፡ እንጂ ፤ በረከትን ፡ ልትወርሱ ፡ ለዚህ ፡ ተጠርታችኋልና ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ ሕይወትን ፡ ሊወድ ፡ መልካሞችንም ፡ ቀኖች ፡ ሊያይ ፡ የሚፈልግ ፡ ሰው ፥ ምላሱን ፡ ከክፉ ፡ ከንፈሮቹንም ፡ ተንኰልን ፡ ከመናገር ፡ ይከልክል ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ከክፉ ፡ ፈቀቅ ፡ ይበል ፥ መልካምንም ፡ ያድርግ ፥ ሰላምን ፡ ይሻ ፡ ይከተለውም ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ የጌታ ፡ ዐይኖች ፡ ወደ ፡ ጻድቃን ፡ ናቸውና ፥ ጕሮዎቹም ፡ ለጸሎታቸው ፡ ተከፍተዋል ፥ የጌታ ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ በሚያደርጉ ፡ ላይ ፡ ነው ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ በጎንም ፡ ለማድረግ ፡ ብትቀኑ ፡ የሚያስጨንቃችኹ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ እንኳ ፡ መከራን ፡ ብትቀበሉ ፡ ብፁዓን ፡ ናችኹ ። ማስፈራራታቸውንም ፡ አትፍሩ ፡ አትናወጡም ፥

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ጌታን ፡ ርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ በልባችኹ ፡ ቀድሱት ። በእናንተ ፡ ስላለ ፡ ተስፋ ፡ ምክንያትን ፡ ለሚጠይቋችኹ ፡ ኹሉ ፡ መልስ ፡ ለመስጠት ፡ ዘወትር ፡ የተዘጋጃችኹ ፡ ኹኑ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ በየዋህነትና ፡ በፍርሀት ፡ ይኹን ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ በክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ መልካሙን ፡ ኑሯችኹን ፡ የሚሳደቡ ፡ ሰዎች ፡ ክፉን ፡ እንደምታደርጉ ፡ በሚያሙበት ፡ ነገር ፡ እንዲያፍሩ ፡ በጎ ፡ ኅሊና ፡ ይኑራችኹ ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እንዲህ ፡ ቢኾን ፥ ክፉ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ ሳይኾን ፡ በጎ ፡ ስለ ፡ ማድረግ ፡ መከራን ፡ ብትቀበሉ ፡ ይሻላችኋልና ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያቀርበን ፡ ርሱ ፡ ጻድቅ ፡ ኾኖ ፡ ስለ ፡ ዐመፀኞች ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በኀጢአት ፡ ምክንያት ፡ ሞቷልና ፤ በሥጋ ፡ ሞተ ፡ በመንፈስ ፡ ግን ፡ ሕያው ፡ ኾነ ፥

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 19 ፤ በርሱም ፡ ደግሞ ፡ ኼዶ ፡ በወህኒ ፡ ለነበሩ ፡ ነፍሳት ፡ ሰበከላቸው ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 20 ፤ ጥቂቶች ፡ ማለት ፡ ስምንት ፡ ነፍስ ፡ በውሃ ፡ የዳኑበት ፡ መርከብ ፡ ሲዘጋጅ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ትዕግሥት ፡ በኖኅ ፡ ዘመን ፡ በቄየ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ አልታዘዙም ።

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ ይህም ፡ ውሃ ፡ ደግሞ ፡ ማለት ፡ ጥምቅት ፡ ምሳሌው ፡ ኾኖ ፡ አኹን ፡ ያድነናል ፥ የሰውነትን ፡ እድፍ ፡ ማስወገድ ፡ አይደለም ፥ ለእግዚአብሔር ፡ የበጎ ፡ ኅሊና ፡ ልመና ፡ ነው ፡ እንጂ ፥ ይህም ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ነው ፤

ጴጥ.1 ፡ 3 ፡ 22 ፤ ርሱም ፡ መላእክትና ፡ ሥልጣናት ፡ ኀይላትም ፡ ከተገዙለት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ኼዶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ አለ ።

_____1ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 1-2 ፤ ክርስቶስም ፡ በሥጋ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ መከራን ፡ ስለተቀበለ ፥ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በሥጋ ፡ ልትኖሩ ፡ በቀረላችኹ ፡ ዘመን ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ምኞት ፡ እንዳትኖሩ ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ያን ፡ ዐሳብ ፡ እንደ ፡ ዕቃ ፡ ጦር ፡ አድርጋችኹ ፡ ያዙት ፥ በሥጋ ፡ መከራን ፡ የተቀበለ ፡ ኀጢአትን ፡ ትታልና ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ የአሕዛብን ፡ ፈቃድ ፡ ያደረጋችኹበት ፡ በመዳራትና ፡ በሥጋ ፡ ምኞትም ፡ በስካርም ፡ በዘፈንም ፡ ያለልክም ፡ በመጠጣት ፡ ነውርም ፡ ባለበት ፡ በጣዖት ፡ ማምለክ ፡ የተመላለሳችኹበት ፡ ያለፈው ፡ ዘመን ፡ ይበቃልና ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ በዚህም ፡ ነገር ፡ ወደዚያ ፡ መዳራት ፡ ብዛት ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ስለማትሮጡ ፡ እየተሳደቡ ፡ ይደነቃሉ ፤

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ ግን ፡ እነርሱ ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ላይ ፡ ሊፈርድ ፡ ለተዘጋጀው ፡ መልስ ፡ ይሰጣሉ ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ እንደሰዎች ፡ በሥጋ ፡ እንዲፈረድባቸው ፡ በመንፈስ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲኖሩ ፡ ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ወንጌል ፡ ለሙታን ፡ ደግሞ ፡ ተሰብኮላቸው ፡ ነበርና ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የነገር ፡ ኹሉ ፡ መጨረሻ ፡ ቀርቧል ። እንግዲህ ፡ እንደ ፡ ባላእምሮ ፡ ዐስቡ ፥

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ትጸልዩም ፡ ዘንድ ፡ በመጠን ፡ ኑሩ ፤ ፍቅር ፡ የኀጢአትን ፡ ብዛት ፡ ይሸፍናልና ፥ ከኹሉ ፡ በፊት ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አጥብቃችኹ ፡ ተዋደዱ ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ ያለማንጐራጐር ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ እንግድነትን ፡ ተቀባበሉ ፤

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ልዩ ፡ ልዩን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ደጋግ ፡ መጋቢዎች ፡ እንደ ፡ መኾናችኹ ፥ እያንዳንዳችኹ ፡ የጸጋን ፡ ስጦታ ፡ እንደተቀበላችኹ ፡ መጠን ፡ በዚያው ፡ ጸጋ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አገልግሉ ፤

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 11 ፤ ማንም ፡ ሰው ፡ የሚናገር ፡ ቢኾን ፥ እንደእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይናገር ፤ የሚያገለግልም ፡ ቢኾን ፥ እግዚአብሔር ፡ በሚሰጠኝ ፡ ኀይል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያገልግል ፤ ክብርና ፡ ሥልጣን ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ለርሱ ፡ በሚኾነው ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በኩል ፡ እግዚአብሔር ፡ በነገር ፡ ኹሉ ፡ ይከብር ፡ ዘንድ ፤ አሜን ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 12 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ በእናንተ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ሊፈትናችኹ ፡ ስለሚኾነው ፡ መከራ ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ መጣባችኹ ፡ አትደነቁ ፤

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ክብሩ ፡ ሲገለጥ ፡ ደግሞ ፡ ሐሤት ፡ እያደረጋችኹ ፡ ደስ ፡ እንዲላችኹ ፥ በክርስቶስ ፡ መከራ ፡ በምትካፈሉበት ፡ ልክ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ።

ጴጥ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ ስለክርስቶስ ፡ ስም ፡ ብትነቀፉ ፡ የክብር ፡ መንፈስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ በእናንተ ፡ ላይ ፡

ያርፋልና ፥ ብፁዓን ፡ ናችኹ ።

ጴጥ.1 ፥ 4 ፥ 15 ፤ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ወይም ፡ ሌባ ፡ ወይም ፡ ክፉ ፡ አድራጊ ፡ እንደሚኾን ፡ ወይም ፡ በሌላዎች ፡ ጕዳይ ፡ እንደሚገባ ፡ ኾኖ ፡ መከራን ፡ አይቀበል ፤

ጴጥ.1 ፥ 4 ፥ 16 ፤ ክርስቲያን ፡ እንደሚኾን ፡ ግን ፡ መከራን ፡ ቢቀበል ፡ ስለዚህ ፡ ስም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመስግን ፡ እንጂ ፡ አይፈር ።

ጴጥ.1 ፥ 4 ፥ 17 ፤ ፍርድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ተነሥቶ ፡ የሚገሥመርበት ፡ ጊዜ ፡ ደርሷልና ፤ አስቀድሞም ፡ በእኛ ፡ የሚገሥመር ፡ ከኾነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወንጌል ፡ የማይታዘዙ ፡ መጨረሻቸው ፡ ምን ፡ ይኾን ፧

ጴጥ.1 ፥ 4 ፥ 18 ፤ ጻድቅም ፡ በጭንቅ ፡ የሚድን ፡ ከኾነ ፡ ዐመፀኛውና ፡ ኀጢአተኛው ፡ ወዴት ፡ ይታይ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፧

ጴጥ.1 ፥ 4 ፥ 19 ፤ ስለዚህ ፥ ደግሞ ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ መከራን ፡ የሚቀበሉ ፥ መልካምን ፡ እያደረጉ ፡ ነፍሳቸውን ፡ ለታመነ ፡ ፈጣሪ ፡ ዐደራ ፡ ይስጡ ።

_____1 ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 1 ፤ እንግዲህ ፡ እኔ ፥ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ሽማግሌ ፡ የክርስቶስም ፡ መከራ ፡ ምስክር ፡ ደግሞም ፡ ሊገለጥ ፡ ካለው ፡ ክብር ፡ ተካፋይ ፡ የኾንኹ ፥ በመካከላቸው ፡ ያሉትን ፡ ሽማግሌዎች ፡ እመክራቸዋለኹ ፤

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 2 ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንጋ ፡ ጠብቁ ፤ እንደእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በውድ ፡ እንጂ ፡ በግድ ፡ ሳይኾን ፥ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡ መጥፎውን ፡ ረብ ፡ በመመኘት ፡ ሳይኾን ፡ ጕብኙት ፤

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 3 ፤ ለመንጋው ፡ ምሳሌ ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ ማኅበሮቻችኹን ፡ በጎይል ፡ አትግዙ ፤

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 4 ፤ የእረኞችም ፡ አለቃ ፡ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፡ የማያልፈውን ፡ የክብርን ፡ አክሊል ፡ ትቀበላላችኹ ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 5 ፤ እንዲሁም ፥ ጕበዞች ፡ ሆይ ፥ ለሽማግሌዎች ፡ ተገዙ ፤ ኹላችኹም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ እየተዋረዳችኹ ፡ ትሕትናን ፡ እንደ ፡ ልብስ ፡ ታጠቁ ፥ እግዚአብሔር ፡ ትዕቢተኞችን ፡ ይቃወማልና ፥ ለትሑታን ፡ ግን ፡ ጸጋን ፡ ይሰጣል ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 6 ፤ እንግዲህ ፡ በጊዜው ፡ ከፍ ፡ እንዲያደርጋችኹ ፡ ከጎይለኛው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ በታች ፡ ራሳችኹን ፡ አዋርዱ ፤

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 7 ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ያስባልና ፥ የሚያስጨንቃችኹን ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ጣሉት ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 8 ፤ በመጠን ፡ ኑሩ ፡ ንቁም ፥ ባላጋራችኹ ፡ ዲያብሎስ ፡ የሚውጠውን ፡ ፈልጎ ፡ እንደሚያገሣ ፡ አንበሳ ፡ ይዞራልና ፤

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 9 ፤ በዓለም ፡ ያሉት ፡ ወንድሞቻችኹ ፡ ያን ፡ መከራ ፡ በሙሉ ፡ እንዲቀበሉ ፡ እያወቃችኹ ፡ በእምነት ፡ ጸንታችኹ ፡ ተቃወሙት ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 10 ፤ በክርስቶስ ፡ ኢየሱስ ፡ ወደዘለዓለም ፡ ክብሩ ፡ የጠራችኹ ፥ የጸጋ ፡ ኹሉ ፡ አምላክ ፥ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ መከራን ፡ ከተቀበላችኹ ፡ በኋላ ፥ ራሱ ፡ ፍጹማን ፡ ያደርጋችኋል ፥ ያጸናችኹማል ፥ ያበረታችኹማል ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 11 ፤ ለርሱ ፡ ክብርና ፡ ኀይል ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ጴጥ.1 ፥ 5 ፥ 12 ፤ እየመከርኋችኹና ፡ የምትቆሙባት ፡ ጸጋ ፡ እውነተኛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንድትኾን ፡

እየመሰከርኹላችኹ ፥ የታመነ ፡ ወንድም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በቈጠርኹት ፡ በስልዋኖስ ፡ እጅ ፡ በዐጪሩ ፡ ጽፌላችኋለኹ ።

ጴጥ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ተመርጣ ፡ በባቢሎን ፡ ያለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልጄም ፡ ማርቆስ ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡላችኋል ።

ጴጥ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ በፍቅር ፡ አሳሳም ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ ሰላምታ ፡ ተሰጣጡ ። በክርስቶስ ፡ ላላችኹ ፡ ለኹላችኹ ፡ ሰላም ፡ ይኹን ። አሜን ❖

ኹለተኛዉ ፡ የሐዋርያው ፡ የጴጥሮስ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____2 ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 1 ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያና ፡ ሐዋርያ ፡ የኾነ ፡ ስምዖን ፡ ጴጥሮስ ፥ በአምላካችንና ፡ በመድኀኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽድቅ ፡ ካገኘነው ፡ ጋራ ፡ የተካከለ ፡ የክብር ፡ እምነትን ፡ ላገኙ ፤

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 2-3 ፤ የመለኮቱ ፡ ኀይል ፥ በገዛ ፡ ክብሩና ፡ በበጎነቱ ፡ የጠራንን ፡ በማወቅ ፥ ለሕይወትና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመምሰል ፡ የሚኾነውን ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፥ በእግዚአብሔርና ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ዕውቀት ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ይብዛላችኹ ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ስለ ፡ ክፉ ፡ ምኞት ፡ በዓለም ፡ ካለው ፡ ጥፋት ፡ አምልጣችኹ ፡ ከመለኮት ፡ ባሕርይ ፡ ተካፋዮች ፡ በተስፋ ፡ ቃል ፡ እንድትኾኑ ፥ በእነዚያ ፡ ክብርና ፡ በጎነት ፡ የተከበረና ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ የኾነ ፡ ተስፋን ፡ ሰጠን ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ስለዚህም ፡ ምክንያት ፡ ትጋትን ፡ ኹሉ ፡ እያሳያችኹ ፡ በእምነታችኹ ፡ በጎነትን ፡ ጨምሩ ፥

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ በበጎነትም ፡ ዕውቀትን ፥ በዕውቀትም ፡ ራስን ፡ መግዛት ፥ ራስንም ፡ በመግዛት ፡ መጽናትን ፥ በመጽናትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ መምሰል ፥

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ በመምሰል ፡ የወንድማማችን ፡ መዋደድ ፥ በወንድማማችም ፡ መዋደድ ፡ ፍቅርን ፡ ጨምሩ ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ ለእናንተ ፡ ኾነው ፡ ቢበዙ ፥ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕውቀት ፡ ሥራ ፡ ፈቶችና ፡ ፍሬ ፡ ቢሰች ፡ እንዳትኾኑ ፡ ያደርጓችኋልና ፤

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ እነዚህ ፡ ነገሮች ፡ የሌሉት ፡ ዕውር ፡ ነውና ፥ በቅርብም ፡ ያለውን ፡ ብቻ ፡ ያያል ፥ የቀደመውንም ፡ ኀጢአቱን ፡ መንጻት ፡ ረስቷል ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ስለዚህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ መጠራታችኹንና ፡ መመረጣችኹን ፡ ታጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ከፊት ፡ ይልቅ ፡ ትጉ ፤ እነዚህን ፡ ብታደርጉ ፡ ከቶ ፡ አትሰናከሉምና ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 11 ፤ እንዲሁ ፡ ወደዘለዓለሙ ፡ ወደጌታችንና ፡ መድኀኒታችን ፡ ወደኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ መግባት ፡ በሙላት ፡ ይሰጣችኋልና ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ስለዚህ ፥ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ ምንም ፡ ብታውቁ ፥ በእናንተም ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ እውነት ፡ ምንም ፡ ብትጸኑ ፥ ስለ ፡ እነዚህ ፡ ዘወትር ፡ እንዳሳስባችኹ ፡ ቸል ፡ አልልም ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ኾልጊዜም ፡ በዚህ ፡ ማደሪያ ፡ ሳለኹ ፡ በማሳሰቤ ፡ ላነቃችኹ ፡ የሚገባኝ ፡ ይመስለኛል ።

ጴጥ.2 ፥ 1 ፥ 14 ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳመለከተኝ ፡ ከዚህ ፡ ማደሪያዬ ፡ መለየቴ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲኾን ፡ ዐውቃለኹና ።

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 15 ፤ ከመውጣቴም ፡ በኋላ ፡ እነዚህን ፡ ነገሮች ፡ እንድታስቡ ፡ በየጊዜው ፡ ትችሉ ፡ ዘንድ ፡ እተጋለኹ ።

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 16 ፤ የርሱን ፡ ግርማ ፡ አይተን ፡ እንጂ ፡ በብልኀት ፡ የተፈጠረውን ፡ ተረት ፡ ሳንከተል ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ኀይልና ፡ መምጣት ፡ አስታወቅናችኹ ።

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 17 ፤ ከገናናው ፡ ክብር ፦ በርሱ ፡ ደስ ፡ የሚለኝ ፡ የምወደው ፡ ልጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ያ ፡ ድምፅ ፡ በመጣለት ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ክብርንና ፡ ምስጋናን ፡ ተቀብሏልና ፤

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 18 ፤ እኛም ፡ በቅዱሱ ፡ ተራራ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሳለን ፡ ይህን ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ ሰማን ።

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 19 ፤ ከርሱም ፡ ይልቅ ፡ እጅግ ፡ የጸና ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ አለን ፤ ምድርም ፡ እስኪጠባ ፡ ድረስ ፡ የንጋትም ፡ ኮከብ ፡ በልባችኹ ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፥ ሰው ፡ በጨለማ ፡ ስፍራ ፡ የሚበራን ፡ መብራት ፡ እንደሚጠነቀቅ ፡ ይህን ፡ ቃል ፡ እየጠነቀቃችኹ ፡ መልካም ፡ ታደርጋላችኹ ።

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 20 ፤ ይህን ፡ በመገመሪያ ፡ ዕወቁ ፤ በመጽሐፍ ፡ ያለውን ፡ ትንቢት ፡ ኹሉ ፡ ማንም ፡ ለገዛ ፡ ራሱ ፡ ሊተረጕም ፡ አልተፈቀደም ፤

ጴጥ.2 ፡ 1 ፡ 21 ፤ ትንቢት ፡ ከቶ ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ አልመጣምና ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተልከው ፡ ቅዱሳን ፡ ሰዎች ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተነድተው ፡ ተናገሩ ።

2 ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 1 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ደግሞ ፡ በሕዝቡ ፡ መካከል ፡ ነበሩ ፡ እንዲሁም ፡ በመካከላችኹ ፡ ደግሞ ፡ ሐሰተኞች ፡ አስተማሪዎች ፡ ይኾናሉ ፤ እነርሱም ፡ የዋጃቸውን ፡ ጌታ ፡ እንኳ ፡ ክደው ፡ የሚፈጥንን ፡ ጥፋት ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ እየሳቡ ፡ የሚያጠፋ ፡ ኑፋቄን ፡ አሹልከው ፡ ያገባሉ ፤

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 2 ፤ ብዙዎችም ፡ በመዳራታቸው ፡ ይከተሏቸዋል ፡ በእነርሱም ፡ ጠንቅ ፡ የእውነት ፡ መንገድ ፡ ይሰደባል ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 3 ፤ ገንዘብንም ፡ በመመኘት ፡ በተፈጠረ ፡ ነገር ፡ ይረቡባችኋል ፤ ፍርዳቸውም ፡ ከጥንት ፡ ዝምሮ ፡ አይዘገይም ፡ ጥፋታቸውም ፡ አያንቀላፋም ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 4 ፤ እግዚአብሔር ፡ ኀጢአትን ፡ ላደረጉ ፡ መላእክት ፡ ሳይራራላቸው ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ ጥሎ ፡ በጨለማ ፡ ጕድጓድ ፡ ለፍርድ ፡ ሊጠበቁ ፡ አሳልፎ ፡ ከሰጣቸው ፥

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 5 ፤ ለቀደመውም ፡ ዓለም ፡ ሳይራራ ፡ ከሌላዎች ፡ ሰባት ፡ ጋራ ፡ ጽድቅን ፡ የሚሰብከውን ፡ ኖኅን ፡ አድኖ ፡ በኀጢአተኞች ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የጥፋትን ፡ ውሃ ፡ ካወረደ ፥

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 6 ፤ ኀጢአትንም ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ላሉት ፡ ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ከተማዎችን ፡ ሰዶምንና ፡ ገሞራን ፡ ዐመድ ፡ እስኪኾኑ ፡ ድረስ ፡ አቃጥሎና ፡ ገልብጦ ፡ ከፈረደባቸው ፥

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 7-8 ፤ ጻድቅ ፡ ሎጥም ፡ በመካከላቸው ፡ ሲኖር ፡ እያየና ፡ እየሰማ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በዐመፀኛ ፡ ሥራቸው ፡ ጻድቅ ፡ ነፍሱን ፡ አስጨንቆ ፡ ነበርና ፥ በዐመፀኞች ፡ ሴሰኛ ፡ ኑሮ ፡ የተገፋውን ፡ ያን ፡ ጻድቅ ፡ ካዳነ ፥

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 9-10 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልኩትን ፡ ከፈተና ፡ እንዴት ፡ እንዲያድን ፥ በደለኞችንም ፡ ይልቁንም ፡ በርኩስ ፡ ምኞት ፡ የሥጋን ፡ ፍትወት ፡ እየተከተሉ ፡ የሚመላለሱትን ፡ ጌትነትንም ፡ የሚንቁትን ፡ እየቀጣቸው ፡ ለፍርድ ፡ ቀን ፡ እንዴት ፡ እንዲጠብቅ ፡ ያውቃል ። ደፋሮችና ፡ ኵሩዎች ፡ ኾነው ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውን ፡ ሲሳደቡ ፡ አይንቀጠቀጡም ፤

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ መላእክት ፡ በኀይልና ፡ በብርታት ፡ ከነርሱ ፡ ይልቅ ፡ ምንም ፡ ቢበልጡ ፡ በጌታ ፡ ፊት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ የስድብን ፡ ፍርድ ፡ አያመጡም ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 12 ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ ለመጠመድና ፡ ለመጥፋት ፡ በፍጥረታቸው ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ አእምሮ ፡ እንደ ፡ ሌላቸው ፡ እንስሳዎች ፡ ኾነው ፥ በማያውቁት ፡ ነገር ፡ እየተሳደቡ ፡ በጥፋታቸው ፡ ይጠፋሉ ፤

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 13 ፤ የዐመፃቸውን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ይቀበላሉ ። በቀን ፡ ሲዘፍኑ ፡ እንደ ፡ ተድላ ፡ ይቈጥሩታል ፤ ነውረኞችና ፡ ርኩሳን ፡ ኾነው ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሲጋበዙ ፡ በፍቅር ፡ ግብዣ ፡ ይዘፍናሉ ፤

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 14 ፤ ምንዝር ፡ የሞላባቸው ፡ ኀጢአትንም ፡ የማይተዉ ፡ ዐይኖች ፡ አሏቸው ፤ የማይጸኑትን ፡ ነፍሳት ፡ ያታልላሉ ፤ መመኘትን ፡ የለመደ ፡ ልብ ፡ አላቸው ፤ የተረገሙ ፡ ናቸው ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 15 ፤ ቅንን ፡ መንገድ ፡ ትተው ፡ ተሳሳቱ ፤ የባሶርን ፡ ልጅ ፡ የበለዓምን ፡ መንገድ ፡ ተከተሉ ፤ ርሱ ፡ የዐመፃን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ ወደደ ፥

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 16 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስለ ፡ መተላለፉ ፡ ተዘለፈ ፤ ቃል ፡ የሌለው ፡ አህያ ፡ በሰው ፡ ቃል ፡ ተናግሮ ፡ የነቢዩን ፡ እብድነት ፡ አገደ ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተጠበቀላቸው ፡ እነዚህ ፡ ውሃ ፡ የሌለባቸው ፡ ምንጮች ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ የተነዱ ፡ ደመናዎች ፡ ናቸው ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ከንቱና ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ የኾነውን ፡ ቃል ፡ ይናገራሉና ፥ በስሕተትም ፡ ከሚኖሩት ፡ አኹን ፡ የሚያመልጡትን ፡ በሥጋ ፡ ሴሰኛ ፡ ምኞት ፡ ያታልላሉ ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ራሳቸው ፡ የጥፋት ፡ ባሪያዎች ፡ ኾነው ፦ ሐራነት ፡ ትወጣላችኹ ፡ እያሉ ፡ ተስፋ ፡ ይሰጧቸዋል ፤ ሰው ፡ ለተሸነፈበት ፡ ለርሱ ፡ ተገዝቶ ፡ ባሪያ ፡ ነውና ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 20 ፤ በጌታችንና ፡ በመድኀኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዕውቀት ፡ ከዓለም ፡ ርኵሰት ፡ ካመለጡ ፡ በኋላ ፡ ዳግመኛ ፡ በርሷ ፡ ተጠላልፈው ፡ የተሸነፉ ፡ ቢኾኑ ፥ ከፊተኛው ፡ ኑሯቸው ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ የባሰ ፡ ኾኖባቸዋል ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 21 ፤ ዐውቀዋት ፡ ከተሰጣቸው ፡ ከቅድስት ፡ ትእዛዝ ፡ ከሚመለሱ ፡ የጽድቅን ፡ መንገድ ፡ ባላወቋት ፡ በተሻላቸው ፡ ነበርና ።

ጴጥ.2 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ውሻ ፡ ወደ ፡ ትፋቱ ፡ ይመለሳል ፥ ደግሞ ፦ የታጠበች ፡ ዕሪያ ፡ በጭቃ ፡ ለመንከባለል ፡ ትመለሳለች ፡ እንደሚባል ፡ እውነተኞች ፡ ምሳሌዎች ፡ ኾኖባቸዋል ።

_____2 ኛ ፡ ጴጥሮስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 1-2 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ የምጽፍላችኹ ፡ መልእክት ፡ ይህች ፡ ኹለተኛዪቱ ፡ ናት ። በቅዱሳን ፡ ነቢያትም ፡ ቀድሞ ፡ የተባለውን ፡ ቃል ፡ በሐዋርያታችኹም ፡ ያገኛችኋትን ፡ የጌታንና ፡ የመድኀኒትን ፡ ትእዛዝ ፡ እንድታስቡ ፡ በኹለቱ ፡ እያሳሰብኋችኹ ፡ ቅን ፡ ልቡናችኹን ፡ አነቃቃለኹ ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 3 ፤ በመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ራሳቸው ፡ ምኞት ፡ የሚመላለሱ ፡ ዘባኞች ፡ በመዘበት ፡ እንዲመጡ ፡ ይህን ፡ በፊት ፡ ዕወቁ ፤

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 4 ፤ እነርሱም ፦ የመምጣቱ ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ወዴት ፡ ነው ፧ አባቶች ፡ ከሞቱባት ፡ ጊዜ ፥ ከፍጥረት ፡ መገመሪያ ፡ ይዞ ፡ ኹሉ ፡ እንዳለ ፡ ይኖራልና ፥ ይላሉ ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ሰማያት ፡ ከጥንት ፡ ዠምረው ፡ ምድርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከውሃ ፡ ተጋጥማ ፡ በውሃ ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ወደው ፡ አያስተውሉምና ፤

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 6 ፤ በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ዓለም ፡ በውሃ ፡ ሰጥሞ ፡ ጠፋ ፤

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 7 ፤ አኹን ፡ ያሉ ፡ ሰማያትና ፡ ምድር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የማያመልኩት ፡ ሰዎች ፡ እስከሚጠፉበት ፡ እስከፍርድ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ተጠብቀው ፡ በዚያ ፡ ቃል ፡ ለእሳት ፡ ቀርተዋል ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ በጌታ ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፥ ሺሕ ፡ ዓመትም ፡ እንደ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይህን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ አትርሱ ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ለአንዳንዶች ፡ የሚዘገይ ፡ እንደሚመስላቸው ፡ ጌታ ፡ ስለተስፋ ፡ ቃሉ ፡ አይዘገይም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ንስሓ ፡ እንዲደርሱ ፡ እንጂ ፡ ማንም ፡ እንዳይጠፋ ፡ ወዶ ፡ ስለ ፡ እናንተ ፡ ይታገሣል ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 10 ፤ የጌታው ፡ ቀን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ ኾኖ ፡ ይመጣል ፤ በዚያም ፡ ቀን ፡ ሰማያት ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ያልፋሉ ፥ የሰማይም ፡ ፍጥረት ፡ በትልቅ ፡ ትኵሳት ፡ ይቀልጣል ፥ ምድርም ፡ በርሷም ፡ ላይ ፡ የተደረገው ፡ ኹሉ ፡ ይቃጠላል ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 11-12 ፤ ይህ ፡ ኹሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚቀልጥ ፡ ከኾነ ፥ የእግዚአብሔርን ፡ ቀን ፡ መምጣት ፡ እየጠበቃችኹና ፡ እያስቸኰላችኹ ፥ በቅዱስ ፡ ኑሮ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ በመምሰል ፡ እንደ ፡ ምን ፡ ልትኾኑ ፡ ይገባችኋል ፧ ስለዚያ ፡ ቀን ፡ ሰማያት ፡ ተቃጥለው ፡ ይቀልጣሉ ፡ የሰማይም ፡ ፍጥረት ፡ በትልቅ ፡ ትኵሳት ፡ ይፈታል ፤

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጽድቅ ፡ የሚኖርባትን ፡ ዐዲስ ፡ ሰማይና ፡ ዐዲስ ፡ ምድር ፡ እንደተስፋ ፡ ቃሉ ፡ እንጠብቃለን ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 14 ፤ ስለዚህ ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ እየጠበቃችኹ ፡ ያለነውርና ፡ ያለነቀፋ ፡ ኾናችኹ ፡ በሰላም ፡ በርሱ ፡ እንድትገኙ ፡ ትጉ ፥

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 15 ፤ የጌታችንም ፡ ትዕግሥት ፡ መዳናችኹ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ቊጠሩ ። እንዲህም ፡ የተወደደው ፡ ወንድማችን ፡ ጳውሎስ ፡ ደግሞ ፡ እንደተሰጠው ፡ ጥበብ ፡ መጠን ፡ ጻፈላችኹ ፥ በመልእክቱም ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ነገረ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተናገረ ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 16 ፤ በእነዚያ ፡ ዘንድ ፡ ለማስተዋል ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ አለ ፥ ያልተማሩትና ፡ የማይጸኑትም ፡ ሰዎች ፡ ሌላዎችን ፡ መጻሕፍት ፡ እንደሚያጣምሙ ፡ እነዚህን ፡ ደግሞ ፡ ለገዛ ፡ ጥፋታቸው ፡ ያጣምማሉ ።

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ እናንተ ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ይህን ፡ አስቀድማችኹ ፡ ስለምታውቁ ፥ በዐመፀኞቹ ፡ ስሕተት ፡ ተስባችኹ ፡ ከራሳችኹ ፡ ጽናት ፡ እንዳትወድቁ ፡ ተጠንቀቁ ፤

ጴጥ.2 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በጌታችንና ፡ በመድኀኒታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ዕውቀት ፡ እደጉ ። ለርሱ ፡ አኹንም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለምም ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ ክብር ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የመዠመሪያዉ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____1ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 1 ፤ ስለ ፡ ሕይወት ፡ ቃል ፡ ከመዠመሪያው ፡ የነበረውንና ፡ የሰማነውን ፡ በዐይኖቻችንም ፡ ያየነውን ፡ የተመለከትነውንም ፡ እጆቻችንም ፡ የዳሰሱትን ፡ እናወራለን ፤

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ሕይወትም ፡ ተገለጠ ፡ አይተንማል ፡ እንመሰክርማለን ፥ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ የነበረውንም ፡ ለእኛም ፡ የተገለጠውን ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ እናወራላችኋለን ፤

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 3 ፤ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ኅብረት ፡ እንዲኖራችኹ ፡ ያየነውንና ፡ የሰማነውን ፡ ለእናንተ ፡ ደግሞ ፡ እናወራላችኋለን ። ኅብረታችንም ፡ ከአባት ፡ ጋራ ፡ ከልጁም ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ደስታችኹም ፡ እንዲፈጸም ፡ ይህን ፡ እንጽፍላችኋለን ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከርሱም ፡ የሰማናት ፡ ለእናንተም ፡ የምናወራላችኹ ፡ መልእክት ፦ እግዚአብሔር ፡ ብርሃን ፡ ነው ፥ ጨለማም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከቶ ፡ የለም ፡ የምትል ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ኅብረት ፡ አለን ፡ ብንል ፡ በጨለማም ፡ ብንመላለስ ፡ እንዋሻለን ፡ እውነትንም ፡ አናደርግም ፤

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ በብርሃን ፡ እንዳለ ፡ በብርሃን ፡ ብንመላለስ ፡ ለያንዳንዳችን ፡ ኅብረት ፡ አለን ፥ የልጁም ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደም ፡ ከኀጢአት ፡ ኹሉ ፡ ያነጻናል ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ኀጢአት ፡ የለብንም ፡ ብንል ፡ ራሳችንን ፡ እናስታለን ፥ እውነትም ፡ በእኛ ፡ ውስጥ ፡ የለም ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 9 ፤ በኀጢአታችን ፡ ብንናዘዝ ፡ ኀጢአታችንን ፡ ይቅር ፡ ሊለን ፡ ከዐመፃም ፡ ኹሉ ፡ ሊያነጻን ፡ የታመነና ፡ ጻድቅ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ኀጢአትን ፡ አላደረግንም ፡ ብንል ፡ ሐሰተኛ ፡ እናደርገዋለን ፡ ቃሉም ፡ በእኛ ፡ ውስጥ ፡ የለም ።

_____1ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ዮሐ.1 ፥ 2 ፥ 1 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ ኀጢአትን ፡ እንዳታደርጉ ፡ ይህን ፡ እጽፍላችኋለኹ ። ማንም ፡ ኀጢአትን ፡ ቢያደርግ ፡ ከአብ ፡ ዘንድ ፡ ጠበቃ ፡ አለን ፡ ርሱም ፡ ጻድቅ ፡ የኾነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፥ 2 ፥ 2 ፤ ርሱም ፡ የኀጢአታችን ፡ ማስተስረያ ፡ ነው ፥ ለኀጢአታችንም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ለዓለሙ ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአት ፡ እንጂ ።

ዮሐ.1 ፥ 2 ፥ 3 ፤ ትእዛዛቱንም ፡ ብንጠብቅ ፡ በዚህ ፡ እንዳወቅነው ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፥ 2 ፥ 4 ፤ ዐውቄዋለኹ ፡ የሚል ፡ ትእዛዛቱንም ፡ የማይጠብቅ ፡ ውሸተኛ ፡ ነው ፥ እውነትም ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ የለም ።

ዮሐ.1 ፥ 2 ፥ 5 ፤ ቃሉን ፡ ግን ፡ የሚጠብቅ ፡ ኹሉ ፡ በርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በእውነት ፡

ተፈጽሟል ። በርሱ ፡ እንዳለን ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ፤

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 6 ፤ በርሱ ፡ እኖራለኹ ፡ የሚል ፡ ርሱ ፡ እንደ ፡ ተመላለሰ ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ሊመላለስ ፡ ይገባዋል ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 7 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ከመዠመሪያ ፡ የነበረቻችኹ ፡ አሮጌ ፡ ትእዛዝ ፡ እንጂ ፡ የምጽፍላችኹ ፡ ዐዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለችም ፤ አሮጌዪቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የሰማችኋት ፡ ቃል ፡ ናት ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 8 ፤ ዳግመኛ ፡ ዐዲስ ፡ ትእዛዝን ፡ እጽፍላችኋለኹ ፥ ይህም ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ በእናንተም ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤ ጨለማው ፡ ያልፋልና ፥ እውነተኛውም ፡ ብርሃን ፡ አኹን ፡ ይበራል ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 9 ፤ በብርሃን ፡ አለኹ ፡ የሚል ፡ ወንድሙንም ፡ የሚጠላ ፡ እስከ ፡ አኹን ፡ በጨለማ ፡ አለ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 10 ፤ ወንድሙንም ፡ የሚወድ ፡ በብርሃን ፡ ይኖራል ፡ ማሰናከያም ፡ የለበትም ፤

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 11 ፤ ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ግን ፡ በጨለማ ፡ አለ ፥ በጨለማም ፡ ይመላለሳል ፥ የሚኼድበትንም ፡ አያውቅም ፥ ጨለማው ፡ ዐይኖቹን ፡ አሳውሮታልና ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 12 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ኀጢአታችኹ ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ተሰርዮላችኋልና ፥ እጽፍላችኋለኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 13 ፤ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ከመዠመሪያ ፡ የነበረውን ፡ ዐውቃችኋልና ፥ እጽፍላችኋለኹ ። ጐበዞች ፡ ሆይ ፥ ክፉውን ፡ አሸንፋችኋልና ፥ እጽፍላችኋለኹ ። ልጆች ፡ ሆይ ፥ አብን ፡ ዐውቃችኋልና ፥ እጽፍላችኋለኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 14 ፤ አባቶች ፡ ሆይ ፥ ከመዠመሪያ ፡ የነበረውን ፡ ዐውቃችኋልና ፥ እጽፍላችኋለኹ ። ጐበዞች ፡ ሆይ ፥ ብርቱዎች ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ በእናንተ ፡ ስለሚኖር ፡ ክፉውንም ፡ ስለ ፡ አሸነፋችኹ ፡ እጽፍላችኋለኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 15-16 ፤ ዓለምን ፡ ወይም ፡ በዓለም ፡ ያሉትን ፡ አትውደዱ ፤ በዓለም ፡ ያለው ፡ ኹሉ ፡ ርሱም ፡ የሥጋ ፡ ምኞትና ፡ የዐይን ፡ አምሮት ፡ ስለ ፡ ገንዘብም ፡ መመካት ፡ ከዓለም ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፡ ከአባት ፡ ስላልኾነ ፥ ማንም ፡ ዓለምን ፡ ቢወድ ፡ የአባት ፡ ፍቅር ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ የለም ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 17 ፤ ዓለሙም ፡ ምኞቱም ፡ ያልፋሉ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 18 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ መጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ ነው ፥ የክርስቶስም ፡ ተቃዋሚ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሰማችኹ ፡ አኹን ፡ እንኳ ፡ ብዙዎች ፡ የክርስቶስ ፡ ተቃዋሚዎች ፡ ተነሥተዋል ፤ ስለዚህም ፡ መጨረሻው ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 19 ፤ ከእኛ ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከእኛ ፡ ወገን ፡ አልነበሩም ፤ ከእኛ ፡ ወገንስ ፡ ቢኾኑ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ጸንተው ፡ በኖሩ ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ኹሉ ፡ ከእኛ ፡ ወገን ፡ እንዳልኾኑ ፡ ይገለጡ ፡ ዘንድ ፡ ወጡ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 20 ፤ እናንተም ፡ ከቅዱሱ ፡ ቅባት ፡ ተቀብላችኋል ፥ ኹሉንም ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 21 ፤ እውነትን ፡ የምታውቁ ፡ ስለ ፡ ኾናችኹ ፥ ውሸትም ፡ ኹሉ ፡ ከእውነት ፡ እንዳልኾነ ፡ ስለምታውቁ ፡ እንጂ ፡ እውነትን ፡ ስለማታውቁ ፡ አልጽፍላችኹም ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 22 ፤ ክርስቶስ ፡ አይደለም ፡ ብሎ ፡ ኢየሱስን ፡ ከሚክድ ፡ በቀር ፡ ውሸተኛው ፡ ማን ፡ ነው ፧ አብንና ፡ ወልድን ፡ የሚክድ ፡ ይህ ፡ የክርስቶስ ፡ ተቃዋሚ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 23 ፤ ወልድን ፡ የሚክድ ፡ ኹሉ ፡ አብ ፡ እንኳ ፡ የለውም ፤ በወልድ ፡ የሚታመን ፡ አብ ፡ ደግሞ ፡ አለው ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 24 ፤ እናንተስ ፡ ከመዠመሪያ ፡ የሰማችኹት ፡ በእናንተ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ። ከመዠመሪያ ፡ የሰማችኹት ፡ በእናንተ ፡ ቢኖር ፥ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ በወልድና ፡ በአብ ፡ ትኖራላችኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 25 ፤ ርሱም ፡ የሰጠን ፡ ተስፋ ፡ ይህ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 26 ፤ ስለሚያስቷችኹ ፡ ሰዎች ፡ ይህን ፡ ጽፌላችኋለኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 27 ፤ እናንተስ ፡ ከርሱ ፡ የተቀበላችኹት ፡ ቅባት ፡ በእናንተ ፡ ይኖራል ፥ ማንም ፡ ሊያስተምራችኹ ፡ አያስፈልጋችኹም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የርሱ ፡ ቅባት ፡ ስለ ፡ ኹሉ ፡ እንደሚያስተምራችኹ ፥ እውነተኛም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ውሸትም ፡ እንዳልኾነ ፥ እናንተንም ፡ እንዳስተማራችኹ ፥ በርሱ ፡ ኑሩ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 28 ፤ አኹንም ፥ ልጆች ፡ ሆይ ፥ በሚገለጥበት ፡ ጊዜ ፡ እምነት ፡ እንዲኾንልን ፡ በመምጣቱም ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ እንዳናፍር ፡ በርሱ ፡ ኑሩ ።

ዮሐ.1 ፡ 2 ፡ 29 ፤ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ካወቃችኹ ፡ ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ ዕወቁ ።

_____1ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 1 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ተብለን ፡ ልንጠራ ፡ አብ ፡ እንዴት ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ እዩ ፥ እንዲሁም ፡ ነን ። ስለዚህ ፡ ምክንያት ፡ ዓለም ፡ ርሱን ፡ ስላላወቀው ፡ እኛን ፡ አያውቀንም ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 2 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ አኹን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ነን ፥ ምንም ፡ እንደምንኾን ፡ ገና ፡ አልተገለጠም ። ዳሩ ፡ ግን ፡ ቢገለጥ ፡ ርሱ ፡ እንዳለ ፡ እናየዋለንና ፡ ርሱን ፡ እንድንመስል ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 3 ፤ በርሱም ፡ ይህን ፡ ተስፋ ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ርሱ ፡ ንጹሕ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ራሱን ፡ ያነጻል ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 4 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ ዐመፅን ፡ ደግሞ ፡ ያደርጋል ፥ ኀጢአትም ፡ ዐመፅ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 5 ፤ ርሱም ፡ ኀጢአትን ፡ ሊያስወግድ ፡ እንደ ፡ ተገለጠ ፡ ታውቃላችኹ ፥ በርሱም ፡ ኀጢአት ፡ የለም ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 6 ፤ በርሱ ፡ የሚኖር ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአትን ፡ አያደርግም ፤ ኀጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ አላየውም ፡ አላወቀውምም ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 7 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ማንም ፡ አያስታችኹ ፤ ርሱ ፡ ጻድቅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ጽድቅን ፡ የሚያደርግ ፡ ጻድቅ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 8 ፤ ኀጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ነው ፥ ዲያብሎስ ፡ ከመዠመሪያ ፡ ኀጢአትን ፡ ያደርጋልና ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 9 ፤ ስለዚህ ፥ የዲያብሎስን ፡ ሥራ ፡ እንዲያፈርስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ተገለጠ ። ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአትን ፡ አያደርግም ፥ ዘሩ ፡ በርሱ ፡ ይኖራልና ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ተወልዷልና ፥ ኀጢአትን ፡ ሊያደርግ ፡ አይችልም ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 10 ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጆችና ፡ የዲያብሎስ ፡ ልጆች ፡ በዚህ ፡ የተገለጡ ፡ ናቸው ፤ ጽድቅን ፡ የማያደርግና ፡ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደለም ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 11 ፤ ከመዠመሪያ ፡ የሰማችኋት ፡ መልእክት ። ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንዋደድ ፡ የምትል ፡ ይህች ፡ ናትና ፤

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 12 ፤ ከክፉው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ወንድሙንም ፡ እንደ ፡ ገደለ ፡ እንደ ፡ ቃየል ፡ አይደለም ፤ ስለ ፡ ምንስ ፡ ገደለው ፧ የገዛ ፡ ሥራው ፡ ክፉ ፥ የወንድሙም ፡ ሥራ ፡ ጽድቅ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 13 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ዓለም ፡ ቢጠላችኹ ፡ አትደነቁ ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 14 ፤ እኛ ፡ ወንድሞችን ፡ የምንወድ ፡ ስለ ፡ ኾን ፡ ከሞት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ተሻገርን ፡ እናውቃለን ፤ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ በሞት ፡ ይኖራል ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 15 ፤ ወንድሙን ፡ የሚጠላ ፡ ሹሉ ፡ ነፍሰ ፡ ገዳይ ፡ ነው ፥ ነፍሰ ፡ ገዳይም ፡ የኾነ ፡ ሹሉ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ በርሱ ፡ እንዳይኖር ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 16 ፤ ርሱ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ነፍሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጥቷልና ፥ በዚህ ፡ ፍቅርን ፡ ዐውቀናል ፤ እኛም ፡ ስለ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ነፍሳችንን ፡ አሳልፈን ፡ እንድንሰጥ ፡ ይገባናል ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 17 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ያለው ፥ ወንድሙም ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሲያጣ ፡ አይቶ ፡ ያልራራለት ፡ ማንም ፡ ቢኾን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በርሱ ፡ እንዴት ፡ ይኖራል ፧

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 18 ፤ ልጆቼ ፡ ሆይ ፥ በሥራና ፡ በእውነት ፡ እንጂ ፡ በቃልና ፡ በአንደበት ፡ አንዋደድ ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 19-20 ፤ ልባችንም ፡ በእኛ ፡ ላይ ፡ በሚፈርድበት ፡ ሹሉ ፥ ከእውነት ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ፡ በፊቱም ፡ ልባችንን ፡ እናሳርፋለን ፥ እግዚአብሔር ፡ ከልባችን ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፥ ሹሉንም ፡ ያውቃል ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 21 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ልባችንስ ፡ ባይፈርድብን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ድፍረት ፡ አለን ፥

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 22 ፤ ትእዛዙንም ፡ የምንጠብቅና ፡ በፊቱ ፡ ደስ ፡ የሚያሠኘውን ፡ የምናደርግ ፡ ስለ ኾን ፡ የምንለምነውን ፡ ሹሉ ፡ ከርሱ ፡ እናገኛለን ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 23 ፤ ትእዛዚቱም ፡ ይህች ፡ ናት ፥ በልጁ ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እናምን ፡ ዘንድ ፥ ትእዛዝንም ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንዋደድ ፡ ዘንድ ።

ዮሐ.1 ፡ 3 ፡ 24 ፤ ትእዛዙንም ፡ የሚጠብቅ ፡ በርሱ ፡ ይኖራል ፡ ርሱም ፡ ይኖርበታል ፤ በዚህም ፡ በእኛ ፡ እንዲኖር ፡ ከሰጠን ፡ ከመንፈሱ ፡ እናውቃለን ።

_____1 ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 1 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ መንፈስን ፡ ሹሉ ፡ አትመኑ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ መናፍስት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ኾነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ መርምሩ ፤ ብዙዎች ፡ ሐሰተኞች ፡ ነቢያት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ወጥተዋልና ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 2 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ መንፈስ ፡ በዚህ ፡ ታውቃላችኹ ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የሚታመን ፡ መንፈስ ፡ ሹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፥

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 3 ፤ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የማይታመን ፡ መንፈስ ፡ ሹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደለም ፤ ይህም ፡ የክርስቶስ ፡ ተቃዋሚው ፡ መንፈስ ፡ ነው ፤ ይህም ፡ እንዲመጣ ፡ ሰምታችኋል ፥ አኹንም ፡ እንኳ ፡ በዓለም ፡ አለ ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 4 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ እናንተ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ናችኹ ፡ አሸንፋችኋቸውማል ፥ በዓለም ፡ ካለው ፡ ይልቅ ፡ በእናንተ ፡ ያለው ፡ ታላቅ ፡ ነውና ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 5 ፤ እነርሱ ፡ ከዓለም ፡ ናቸው ፤ ስለዚህ ፥ ከዓለም ፡ የኾነውን ፡ ይናገራሉ ፥ ዓለሙም ፡ ይሰማቸዋል ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 6 ፤ እኛ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነን ፤ እግዚአብሔርን ፡ የሚያውቅ ፡ ይሰማናል ፤ ከእግዚአብሔር ፡ ያልኾነ ፡ አይሰማንም ። የእውነትን ፡ መንፈስና ፡ የስሕተትን ፡ መንፈስ ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 7 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ፍቅር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የሚወደውም ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ተወለደ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ስለሚያውቅ ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንዋደድ ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 8 ፤ ፍቅር ፡ የሌለው ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያውቅም ፥ እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነውና ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 9 ፤ በዚህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ተገለጠ ፥ በርሱ ፡ በኩል ፡ በሕይወት ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ልኮታልና ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 10 ፤ ፍቅርም ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፤ እግዚአብሔር ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ እንደ ፡ ወደደን ፥ ስለኀጢአታችንም ፡ ማስተስረያ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ላከ ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ወደድነው ፡ አይደለም ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 11 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ከወደደን ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ልንዋደድ ፡ ይገባናል ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 12 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ማንም ፡ ከቶ ፡ አላየውም ፤ ርስ ፡ በርሳችን ፡ ብንዋደድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእኛ ፡ ይኖራል ፡ ፍቅሩም ፡ በእኛ ፡ ፍጹም ፡ ኾኗል ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 13 ፤ ከመንፈሱ ፡ ስለ ፡ ሰጠን ፥ በርሱ ፡ እንድንኖር ፡ ርሱም ፡ በእኛ ፡ እንዲኖር ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 14 ፤ እኛም ፡ አይተናል ፡ አባትም ፡ ልጁን ፡ የዓለም ፡ መድኀኒት ፡ ሊኾን ፡ እንደ ፡ ላከው ፡ እንመሰክራለን ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 15 ፤ ኢየሱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ በሚታመን ፡ ኹሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ በርሱ ፡ ይኖራል ፡ ርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይኖራል ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 16 ፤ እኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእኛ ፡ ያለውን ፡ ፍቅር ፡ ዐውቀናል ፡ አምነንማል ። እግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ነው ፥ በፍቅርም ፡ የሚኖር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይኖራል ፡ እግዚአብሔርም ፡ በርሱ ፡ ይኖራል ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 17 ፤ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ድፍረት ፡ ይኾንልን ፡ ዘንድ ፡ ፍቅር ፡ በዚህ ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ተፈጽሟል ፤ ርሱ ፡ እንዳለ ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንዲሁ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነንና ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 18 ፤ ፍጹም ፡ ፍቅር ፡ ፍርሀትን ፡ አውጥቶ ፡ ይጥላል ፡ እንጂ ፡ በፍቅር ፡ ፍርሀት ፡ የለም ፥ ፍርሀት ፡ ቅጣት ፡ አለውና ፤ የሚፈራም ፡ ሰው ፡ ፍቅሩ ፡ ፍጹም ፡ አይደለም ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 19 ፤ ርሱ ፡ አስቀድሞ ፡ ወዶናልና ፥ እኛ ፡ እንወደዋለን ።

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 20 ፤ ማንም ፦ እግዚአብሔርን ፡ እወዳለኹ ፡ እያለ ፡ ወንድሙን ፡ ቢጠላ ፡ ሐሰተኛ ፡ ነው ፤ ያየውን ፡ ወንድሙን ፡ የማይወድ ፡ ያላየውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሊወደው ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፧

ዮሐ.1 ፡ 4 ፡ 21 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ የሚወድ ፡ ወንድሙን ፡ ደግሞ ፡ እንዲወድ ፡ ይህች ፡ ትእዛዝ ፡ ከርሱ ፡ አለችን ።

_____1 ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 1 ፤ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በኢየሱስ ፡ የሚያምን ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተወልዷል ፥ ወላጁንም ፡ የሚወድ ፡ ኹሉ ፡ ከርሱ ፡ የተወለደውን ፡ ደግሞ ፡ ይወዳል ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 2 ፤ እግዚአብሔርን ፡ ስንወድ ፡ ትእዛዛቱንም ፡ ስናደርግ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ልጆች ፡ እንድንወድ ፡ በዚህ ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 3 ፤ ትእዛዛቱን ፡ ልንጠብቅ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ይህ ፡ ነውና ፤ ትእዛዛቱም ፡ ከባዶች ፡ አይደሉም ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 4 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ኹሉ ፡ ዓለምን ፡ ያሸንፋልና ፤ ዓለምንም ፡ የሚያሸንፈው ፡ እምነታችን ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 5 ፤ ኢየሱስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ከሚያምን ፡ በቀር ፡ ዓለምን ፡ የሚያሸንፍ ፡ ማን ፡ ነው ፧

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 6 ፤ በውሃና ፡ በደም ፡ የመጣ ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ በውሃውና ፡ በደሙ ፡ እንጂ ፡ በውሃው ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 7 ፤ መንፈስም ፡ እውነት ፡ ነውና ፥ የሚመሰክረው ፡ መንፈስ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 8 ፤ የሚመሰክሩት ፡ መንፈሱና ፡ ውሃው ፡ ደሙም ፡ ሦስት ፡ ናቸውና ፤ ሦስቱም ፡ ባንድ ፡ ይስማማሉ ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 9 ፤ የሰውን ፡ ምስክር ፡ ብንቀበል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ይበልጣል ፤ ስለ ፡ ልጁ ፡ የመሰከረው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስክር ፡ ይህ ፡ ነውና ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 10 ፤ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሚያምን ፡ በነፍሱ ፡ ምስክር ፡ አለው ፤ በእግዚአብሔር ፡ የማያምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡ የመሰከረውን ፡ ምስክር ፡ ስላላመነ ፡ ሐሰተኛ ፡ አድርጎታል ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 11 ፤ እግዚአብሔርም ፡ የዘለዓለምን ፡ ሕይወት ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ ይህም ፡ ሕይወት ፡ በልጁ ፡ እንዳለ ፡ ምስክሩ ፡ ይህ ፡ ነው ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 12 ፤ ልጁ ፡ ያለው ፡ ሕይወት ፡ አለው ፤ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሌለው ፡ ሕይወት ፡ የለውም ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 13 ፤ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ እንዳላችኹ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ለምታምኑ ፡ ይህን ፡ ጽፌላችኋለኹ ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 14 ፤ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያለን ፡ ድፍረት ፡ ይህ ፡ ነው ፤ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ አንዳች ፡ ብንለምን ፡ ይሰማናል ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 15 ፤ የምንለምነውንም ፡ ኹሉ ፡ እንዲሰማልን ፡ ብናውቅ ፡ ከርሱ ፡ የለመነውን ፡ ልመና ፡ እንደ ፡ ተቀበልን ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 16 ፤ ማንም ፡ ወንድሙን ፡ ሞት ፡ የማይገባውን ፡ ኀጢአት ፡ ሲያደርግ ፡ ቢያየው ፡ ይለምን ፥ ሞትም ፡ የማይገባውን ፡ ኀጢአት ፡ ላደረጉት ፡ ሕይወት ፡ ይሰጥለታል ። ሞት ፡ የሚገባው ፡ ኀጢአት ፡ አለ ፤ ስለዚያ ፡ እንዲጠይቅ ፡ አልልም ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 17 ፤ ዐመፃ ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፥ ሞትም ፡ የማይገባው ፡ ኀጢአት ፡ አለ ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 18 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ኹሉ ፡ ኀጢአትን ፡ እንዳያደርግ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደው ፡ ራሱን ፡ እንዲጠብቅ ፡ ክፉውም ፡ እንዳይነካው ፡ እናውቃለን ።

ዮሐ.1 ፡ 5 ፡ 19 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ኾን ፡ ዓለምም ፡ በሞላው ፡ በክፉው ፡ እንደ ፡ ተያዘ ፡ እናውቃለን ።

ዮ፡ሐ.1 ፡ 5 ፡ 20 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ መጣ ፥ እውነተኛም ፡ የኾነውን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡናን ፡ እንደ ፡ ሰጠን ፡ እናውቃለን ፤ እውነተኛም ፡ በኾነው ፡ በርሱ ፡ አለን ፥ ርሱም ፡ ልጁ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ርሱ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክና ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነው ።

ዮ፡ሐ.1 ፡ 5 ፡ 21 ፤ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ከጣዖታት ፡ ራሳችኹን ፡ ጠብቁ ።

ኹለተኛዉ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____2 ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 1-2 ፤ በእኛ ፡ ስለሚኖርና ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ለዘለዓለም ፡ ስለሚኾን ፡ እውነት ፥ እኔ ፡ ሽማግሌው ፡ በእውነት ፡ ለምወዳቸውና ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ ሳልኾን ፡ እውነትን ፡ የሚያውቁ ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ለሚወዷቸው ፡ ለተመረጠች ፡ እመቤትና ፡ ለልጆቿ ፤

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ከእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ ከአብ ፡ ልጅ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ምሕረት ፡ ሰላምም ፡ በእውነትና ፡ በፍቅር ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ ይኾናሉ ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ትእዛዝን ፡ ከአብ ፡ እንደ ፡ ተቀበልን ፡ ከልጆችሽ ፡ በእውነት ፡ የሚኼዱ ፡ አንዳንዶችን ፡ ስለ ፡ አገኘኋቸው ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛል ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 5 ፤ አኹንም ፥ እመቤት ፡ ሆይ ፥ ርስ ፡ በርሳችን ፡ እንድንዋደድ ፡ እለምንሻለኹ ፤ ይህች ፡ ከመዠመሪያ ፡ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ የነበረች ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ዐዲስ ፡ ትእዛዝን ፡ እንደምጽፍልሽ ፡ አይደለም ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 6 ፤ እንደ ፡ ትእዛዛቱም ፡ እንኼድ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ፍቅር ፡ ነው ፤ ከመዠመሪያ ፡ እንደ ፡ ሰማችኹ ፥ በርሷ ፡ ትኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙ ፡ ይህች ፡ ናት ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ብዙ ፡ አሳቾች ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ገብተዋልና ፥ እነርሱም ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የማያምኑ ፡ ናቸው ፤ ይህ ፡ አሳቹና ፡ የክርስቶስ ፡ ተቃዋሚው ፡ ነው ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 8 ፤ ሙሉ ፡ ደመ ፡ ወዝን ፡ እንድትቀበሉ ፡ እንጂ ፡ የሠራችኹትን ፡ እንዳታጠፉ ፡ ለራሳችኹ ፡ ተጠንቀቁ ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ለሚወጣ ፡ ኹሉ ፡ በክርስቶስም ፡ ትምህርት ፡ ለማይኖር ፡ ሰው ፡ አምላክ ፡ የለውም ፤ በክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ለሚኖር ፡ አብና ፡ ወልድ ፡ አሉት ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ማንም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ቢመጣ ፡ ይህንም ፡ ትምህርት ፡ ባያመጣ ፡ በቤታችኹ ፡ አትቀበሉት ፡ ሰላምም ፡ አትበሉት ፤

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ሰላም ፡ የሚለው ፡ ሰው ፡ በክፉ ፡ ሥራው ፡ ይካፈላልና ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 12 ፤ እንድጽፍላችኹ ፡ የምፈልገው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ሳለኝ ፡ በወረቀትና ፡ በቀለም ፡ ልጽፈው ፡ አልወድም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ደስታችኹ ፡ ፍጹም ፡ እንዲኾን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ልመጣ ፡ አፍ ፡ ለአፍም ፡ ልናገራችኹ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ።

ዮሐ.2 ፥ 1 ፥ 13 ፤ የተመረጠችው ፡ የእኅትሽ ፡ ልጆች ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡልሻል ።

ሦስተኛዉ ፡ የሐዋርያው ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____3 ኛ ፡ ዮሐንስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 1 ፤ ሽማግሌው ፡ በእውነት ፡ እኔ ፡ ለምወደው ፡ ለተወደደው ፡ ለጋይዮስ ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 2 ፤ ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ ነፍስኽ ፡ እንደሚከናወን ፥ በነገር ፡ ኹሉ ፡ እንዲከናወንልኽና ፡ ጤና ፡ እንዲኖርኽ ፡ እጸልያለኹ ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 3 ፤ ወንድሞች ፡ መጥተው ፡ አንተ ፡ በእውነት ፡ እንደምትኼድ ፡ ስለ ፡ እውነትኽ ፡ ሲመሰክሩ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎኛልና ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 4 ፤ ልጆቼ ፡ በእውነት ፡ እንዲኼዱ ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡ የሚበልጥ ፡ ደስታ ፡ የለኝም ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 5 ፤ ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ ምንም ፡ እንግዳዎች ፡ ቢኾኑ ፥ ለወንድሞች ፡ በምታደርገው ፡ ኹሉ ፡ የታመነ ፡ ሥራ ፡ ትሠራለኽ ፥ እነርሱም ፡ በማኅበር ፡ ፊት ፡ ስለ ፡ ፍቅርኽ ፡ መስክረዋል ፤

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 6 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ እንደሚገባ ፡ አድርገኽ ፡ በጕዟቸው ፡ ብትረዳ ፡ መልካም ፡ ታደርጋለኽ ፤

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 7 ፤ ከአሕዛብ ፡ አንዳች ፡ ሳይቀበሉ ፡ ስለ ፡ ስሙ ፡ ወጥተዋልና ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 8 ፤ እንግዲህ ፡ ከእውነት ፡ ጋራ ፡ ዐብረን ፡ እንድንሠራ ፥ እኛ ፡ እንዲህ ፡ ያሉትን ፡ በእንግድነት ፡ ልንቀበል ፡ ይገባናል ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 9 ፤ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጻፍኹ ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ዋናቸው ፡ ሊኾን ፡ የሚወድ ፡ ዲዮጥራጢስ ([306]) ፡ አይቀበለንም ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 10 ፤ ስለዚህ ፥ እኔ ፡ ብመጣ ፥ በእኛ ፡ ላይ ፡ በክፉ ፡ ቃል ፡ እየለፈለፈ ፡ የሚያደርገውን ፡ ሥራውን ፡ አሳስባለኹ ፤ ይህም ፡ ሳይበቃው ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ወንድሞችን ፡ አይቀበልም ፥ ሊቀበሏቸውም ፡ የሚወዱትን ፡ ከልክሎ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያወጣቸዋል ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 11 ፤ ወዳጅ ፡ ሆይ ፥ በጎ ፡ የኾነውን ፡ እንጂ ፡ ክፉን ፡ አትምሰል ። በጎ ፡ የሚያደርግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነው ፤ ክፉን ፡ የሚያደርግ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አላየውም ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 12 ፤ ለድሜጥሮስ ፡ ኹሉ ፡ ይመሰክሩለታል ፥ እውነት ፡ ራሷም ፡ ትመሰክርለታለች ፤ እኛም ፡ ደግሞ ፡ እንመሰክርለታለን ፥ ምስክርነታችንም ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ታውቃላችኹ ።

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 13 ፤ ልጽፍልኽ ፡ የምፈልገው ፡ ብዙ ፡ ነገር ፡ ነበረኝ ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ በቀለምና ፡ በብርዕ ፡ ልጽፍልኽ ፡ አልወድም ፤

ዮሐ.3 ፥ 1 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ወዲያው ፡ ላይኽ ፡ ተስፋ ፡ አደርጋለኹ ፥ አፍ ፡ ለአፍም ፡ እንነጋገራለን ።

---

306 ጽር. ፥ ዲዮትሬፌስ ።

ዮ፡ሐ.3 ፡ 1 ፡ 15 ፤ ሰላም ፡ ለአንተ ፡ ይኹን ። ወዳጆች ፡ ሰላምታ ፡ ያቀርቡልኻል ። ወዳጆችን ፡ በየስማቸው ፡ እየጠራኽ ፡ ሰላምታ ፡ አቅርብልኝ ፞

የሐዋርያው ፡ የያዕቆብ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____ያዕቆብ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ያዕ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የእግዚአብሔርና ፡ የጌታ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ ያዕቆብ ፡ ለተበተኑ ፡ ለዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ ወገኖች ፤ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 2-3 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ የእምነታችኹ ፡ መፈተን ፡ ትዕግሥትን ፡ እንዲያደርግላችኹ ፡ ዐውቃችኹ ፥ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ፈተና ፡ ሲደርስባችኹ ፡ እንደ ፡ ሙሉ ፡ ደስታ ፡ ቍጠሩት ፡

ያዕ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ትዕግሥትም ፡ ምንም ፡ የሚጐድላችኹ ፡ ሳይኖር ፡ ፍጹማንና ፡ ምሉኣን ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ሥራውን ፡ ይፈጽም ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ከእናንተ ፡ ግን ፡ ማንም ፡ ጥበብ ፡ ቢጐድለው ፥ ሳይነቅፍ ፡ በልግስና ፡ ለኹሉ ፡ የሚሰጠውን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምን ፥ ለርሱም ፡ ይሰጠዋል ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ በምንም ፡ ሳይጠራጠር ፡ በእምነት ፡ ይለምን ፤ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ በነፋስ ፡ የተገፋና ፡ የተነቃነቀ ፡ የባሕርን ፡ ማዕበል ፡ ይመስላልና ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 7-8 ፤ ኹለት ፡ ዐሳብ ፡ ላለው ፡ በመንገዱም ፡ ኹሉ ፡ ለሚወላውል ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ ከጌታ ፡ ዘንድ ፡ አንዳች ፡ እንዲያገኝ ፡ አይምሰለው ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 9-10 ፤ የተዋረደው ፡ ወንድም ፡ ግን ፡ በከፍታው ፥ ባለጠጋም ፡ በውርደቱ ፡ ይመካ ፤ እንደ ፡ ሣር ፡ አበባ ፡ ያልፋልና ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ፀሓይ ፡ ከትኵሳት ፡ ጋራ ፡ ይወጣልና ፥ ሣርንም ፡ ያጠወልጋልና ፥ አበባውም ፡ ይረግፋልና ፥ የመልኩም ፡ ውበት ፡ ይጠፋልና ፤ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ባለጠጋው ፡ በመንገዱ ፡ ይዝላል ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ በፈተና ፡ የሚጸና ፡ ሰው ፡ የተባረከ ፡ ነው ፤ ከተፈተነ ፡ በኋላ ፡ ለሚወዱት ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሰጣቸውን ፡ የሕይወትን ፡ አክሊል ፡ ይቀበላልና ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ ማንም ፡ ሲፈተን ፦ በእግዚአብሔር ፡ እፈተናለኹ ፡ አይበል ፤ እግዚአብሔር ፡ በክፉ ፡ አይፈተንምና ፤ ርሱ ፡ ራሱስ ፡ ማንንም ፡ አይፈትንም ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እያንዳንዱ ፡ በራሱ ፡ ምኞት ፡ ሲሳብና ፡ ሲታለል ፡ ይፈተናል ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 15 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ምኞት ፡ ፀንሳ ፡ ኀጢአትን ፡ ትወልዳለች ፤ ኀጢአትም ፡ ካደገች ፡ በኋላ ፡ ሞትን ፡ ትወልዳለች ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 16 ፤ የተወደዳችኹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ አትሳቱ ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 17 ፤ በጎ ፡ ስጦታ ፡ ኹሉ ፡ ፍጹምም ፡ በረከት ፡ ኹሉ ፡ ከላይ ፡ ናቸው ፥ መለወጥም ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከሌለ ፡ በመዞርም ፡ የተደረገ ፡ ጥላ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ከሌለ ፡ ከብርሃናት ፡ አባት ፡ ይወርዳሉ ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 18 ፤ ለፍጥረቱ ፡ የበኵራት ፡ ዐይነት ፡ እንድንኾን ፡ በእውነት ፡ ቃል ፡ ዐስቦ ፡ ወለደን ።

ያዕ. ፥ 1 ፥ 19 ፤ ስለዚህ ፥ የተወደዳችኹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ለመስማት ፡ የፈጠነ ፡ ለመናገርም ፡

የዘገየ ፡ ለቀ-ጣም ፡ የዘገየ ፡ ይኹን ፤

ያዕ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ የሰው ፡ ቀ-ጣ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጽድቅ ፡ አይሠራምና ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ስለዚህ ፥ ርኵሰትን ፡ ኹሉ ፥ የክፋትንም ፡ ትርፍ ፡ አስወግዳችኹ ፥ ነፍሳችኹን ፡ ማዳን ፡ የሚችለውን ፡ በውስጣችኹም ፡ የተተከለውን ፡ ቃል ፡ በየዋህነት ፡ ተቀበሉ ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ ቃሉን ፡ የምታደርጉ ፡ ኹኑ ፡ እንጂ ፡ ራሳችኹን ፡ እያሳታችኹ ፡ የምትሰሙ ፡ ብቻ ፡ አትኹኑ ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ ቃሉን ፡ የሚሰማ ፡ የማያደርገውም ፡ ቢኖር ፡ የተፈጥሮ ፡ ፊቱን ፡ በመስተዋት ፡ የሚያይን ፡ ሰው ፡ ይመስላል ፤

ያዕ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ራሱን ፡ አይቶ ፡ ይኼዳልና ፥ ወዲያውም ፡ እንደ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይረሳል ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ነጻ ፡ የሚያወጣውን ፡ ፍጹሙን ፡ ሕግ ፡ ተመልክቶ ፡ የሚጸናበት ፥ ሥራንም ፡ የሚሠራ ፡ እንጂ ፡ ሰምቶ ፡ የሚረሳ ፡ ያልኾነው ፥ በሥራው ፡ የተባረከ ፡ ይኾናል ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 26 ፤ አንደበቱን ፡ ሳይገታ ፡ ልቡን ፡ እያሳተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመልክ ፡ የሚመስለው ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ የርሱ ፡ አምልኮ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 1 ፡ 27 ፤ ንጹሕ ፡ የኾነ ፡ ነውርም ፡ የሌለበት ፡ አምልኮ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ወላጆች ፡ የሌላቸውን ፡ ልጆች ፡ ባልቴቶችንም ፡ በመከራቸው ፡ መጠየቅ ፥ በዓለምም ፡ ከሚገኝ ፡ እድፍ ፡ ሰውነቱን ፡ መጠበቅ ፡ ነው ።

ያዕቆብ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በክብር ፡ ጌታ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያለውን ፡ እምነት ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ በማድላት ፡ አትያዙ ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ የወርቅ ፡ ቀለበት ፡ ያደረገና ፡ የጌጥ ፡ ልብስ ፡ የለበሰ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ጉባኤያችኹ ፡ ቢገባ ፥ እድፍ ፡ ልብስም ፡ የለበሰ ፡ ድኻ ፡ ሰው ፡ ደግሞ ፡ ቢገባ ፥

ያዕ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ የጌጥ ፡ ልብስም ፡ የለበሰውን ፡ ተመልክታችኹ ። አንተስ ፡ በዚህ ፡ በመልካም ፡ ስፍራ ፡ ተቀመጥ ፡ ብትሉት ፥ ድኻውንም ፦ አንተስ ፡ ወደዚያ ፡ ቁም ፡ ወይም ፡ ከእግሬ ፡ መረገጫ ፡ በታች ፡ ተቀመጥ ፡ ብትሉት ፥ ራሳችኹን ፡ መለያየታችኹ ፡ አይደለምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ክፉ ፡ ዐሳብ ፡ ያላቸውም ፡ ዳኞች ፡ መኾናችኹ ፡ አይደለምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ የተወደዳችኹ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ስሙ ፤ እግዚአብሔር ፡ በእምነት ፡ ባለጠጋዎች ፡ እንዲኾኑ ፡ ለሚወዱትም ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ የሰጣቸውን ፡ መንግሥት ፡ እንዲወርሱ ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ ድኻዎች ፡ አልመረጠምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ድኻዎችን ፡ አዋረዳችኹ ። ባለጠጋዎቹ ፡ የሚያስጨንቋችኹ ፡ አይደሉምን ፧ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ የሚጐትቷችኹ ፡ እነርሱ ፡ አይደሉምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ የተጠራችኹበትን ፡ መልካሙን ፡ ስም ፡ የሚሰድቡ ፡ እነርሱ ፡ አይደሉምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መጽሐፍ ፦ ባልንጀራኽን ፡ እንደ ፡ ራስኽ ፡ ውደድ ፡ እንደሚል ፡ የንጉሥን ፡ ሕግ ፡ ብትፈጽሙ ፡ መልካም ፡ ታደርጋላችኹ ፤

ያዕ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ ለሰው ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ብታደሉ ፡ ኀጢአትን ፡ ትሠራላችኹ ፥ ሕግም ፡ እንደ ፡ ተላላፊዎች ፡

ይወቅሳችኋል ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ሕግን ፡ ሹሉ ፡ የሚጠብቅ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ባንዱ ፡ የሚሰናከል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ በሹሉ ፡ በደለኛ ፡ ይኾናል ፤ አታመንዝር ፡ ያለው ፡ ደግሞ ፦ አትግደል ፡ ብሏልና ፤

ያዕ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ ባታመነዝርም ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ብትገድል ፥ ሕግን ፡ ተላላፊ ፡ ኾነኻል ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በነጻነት ፡ ሕግ ፡ ፍርድን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዳላቸው ፡ ሰዎች ፡ እንዲህ ፡ ተናገሩ ፥ እንዲህም ፡ አድርጉ ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ ምሕረትን ፡ ለማያደርግ ፡ ምሕረት ፡ የሌለበት ፡ ፍርድ ፡ ይኾናልና ፤ ምሕረትም ፡ በፍርድ ፡ ላይ ፡ ይመካል ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ እምነት ፡ አለኝ ፡ የሚል ፥ ሥራ ፡ ግን ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ምን ፡ ይጠቅመዋል ፧ እምነቱስ ፡ ሊያድነው ፡ ይችላልን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ ወንድም ፡ ወይም ፡ እኅት ፡ ዕራቍታቸውን ፡ ቢኾኑ ፡ የዕለት ፡ ምግብንም ፡ ቢያጡ ፥

ያዕ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ ከእናንተ ፡ አንዱም ፦ በደኅና ፡ ኺዱ ፥ እሳት ፡ ሙቁ ፥ ጥገቡም ፡ ቢላቸው ፡ ለሰውነት ፡ ግን ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ባትሰጧቸው ፡ ምን ፡ ይጠቅማቸዋል ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ እንደዚሁም ፡ ሥራ ፡ የሌለው ፡ እምነት ፡ ቢኖር ፡ በራሱ ፡ የሞተ ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንድ ፡ ሰው ፦ አንተ ፡ እምነት ፡ አለኽ ፡ እኔም ፡ ሥራ ፡ አለኝ ፤ እምነትኽን ፡ ከሥራኽ ፡ ለይተኽ ፡ አሳየኝ ፥ እኔም ፡ እምነቴን ፡ በሥራዬ ፡ አሳይኻለኹ ፡ ይላል ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ አንተ ፡ ታምናለኽ ፤ መልካም ፡ ታደርጋለኽ ፤ አጋንንት ፡ ደግሞ ፡ ያምናሉ ፡ ይንቀጠቀጡማል ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ አንተ ፡ ከንቱ ፡ ሰው ፥ እምነት ፡ ከሥራ ፡ ተለይቶ ፡ የሞተ ፡ መኾኑን ፡ ልታውቅ ፡ ትወዳለኽን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ አባታችን ፡ አብርሃም ፡ ልጁን ፡ ይሥሐቅን ፡ በመሠዊያው ፡ ባቀረበ ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ የጸደቀ ፡ አልነበረምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እምነት ፡ ከሥራው ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ ያደርግ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፥ በሥራም ፡ እምነት ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ ትመለከታለኽን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ መጽሐፍም ፦ አብርሃምም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመነ ፡ ጽድቅም ፡ ኾኖ ፡ ተቈጠረለት ፡ ያለው ፡ ተፈጸመ ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ወዳጅ ፡ ተባለ ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ሰው ፡ በእምነት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፡ በሥራ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ታያላችኹ ።

ያዕ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ እንደዚሁም ፡ ጋለሞታዪቱ ፡ ረዓብ ፡ ደግሞ ፡ መልእክተኞቹን ፡ ተቀብላ ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ በሰደደቻቸው ፡ ጊዜ ፡ በሥራ ፡ አልጸደቀችምን ፧

ያዕ. ፡ 2 ፡ 26 ፤ ከነፍስ ፡ የተለየ ፡ ሥጋ ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ ከሥራ ፡ የተለየ ፡ እምነት ፡ የሞተ ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ከእናንተ ፡ ብዙዎቹ ፡ አስተማሪዎች ፡ አይኹኑ ፥ የባሰውን ፡ ፍርድ ፡ እንድንቀበል ፡ ታውቃላችኹና ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ኹላችን ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ እንሰናከላለንና ፤ በቃል ፡ የማይሰናከል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ርሱ ፡ ሥጋውን ፡ ኹሉ ፡ ደግሞ ፡ ሊገታ ፡ የሚችል ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ እንሆ ፥ ፈረሶች ፡ ይታዘዙልን ፡ ዘንድ ፡ ልጓም ፡ በአፋቸው ፡ ውስጥ ፡ እናገባለን ፥ ሥጋቸውንም ፡ ኹሉ ፡ እንመራለን ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ መርከቦች ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ያኽል ፡ ታላቅ ፡ ቢኾኑ ፡ በዐውሎ ፡ ነፋስም ፡ ቢነዱ ፥ የመሪ ፡ ፈቃድ ፡ ወደሚወደው ፡ ስፍራ ፡ እጅግ ፡ ታናሽ ፡ በኾነ ፡ መቅዘፊያ ፡ ይመራሉ ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ እንዲሁም ፡ አንደበት ፡ ደግሞ ፡ ትንሽ ፡ ብልት ፡ ኾኖ ፡ በታላላቅ ፡ ነገር ፡ ይመካል ። እንሆ ፥ ትንሽ ፡ እሳት ፡ እንዴት ፡ ያለ ፡ ትልቅ ፡ ጫካ ፡ ያቃጥላል ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ አንደበትም ፡ እሳት ፡ ነው ። አንደበት ፡ በብልቶቻችን ፡ መካከል ፡ ዐመፀኛ ፡ ዓለም ፡ ኾኗል ፤ ሥጋን ፡ ኹሉ ፡ ያሳድፋልና ፥ የፍጥረትንም ፡ ሩጫ ፡ ያቃጥላል ፥ በገሃነምም ፡ ይቃጠላል ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ የአራዊትና ፡ የወፎች ፡ የተንቀሳቃሾችና ፡ በባሕር ፡ ያለ ፡ የፍጥረት ፡ ወገን ፡ ኹሉ ፡ በሰው ፡ ይገራል ፥ ደግሞ ፡ ተገርቷል ፤

ያዕ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ አንደበትን ፡ ሊገራ ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ አይችልም ፤ የሚገድል ፡ መርዝ ፡ የሞላበት ፡ ወላዋይ ፡ ክፋት ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ በርሱ ፡ ጌታንና ፡ አብን ፡ እንባርካለን ፤ በርሱም ፡ እንደእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ የተፈጠሩትን ፡ ሰዎች ፡ እንረግማለን ፤

ያዕ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ ካንድ ፡ አፍ ፡ በረከትና ፡ መርገም ፡ ይወጣሉ ። ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ እንዲህ ፡ ሊኾን ፡ አይገባም ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ ምንጭስ ፡ ካንድ ፡ አፍ ፡ የሚጣፍጥንና ፡ የሚመርን ፡ ውሃ ፡ ያመነጫልን ፧

ያዕ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በለስ ፡ ወይራን ፡ ወይስ ፡ ወይን ፡ በለስን ፡ ልታፈራ ፡ ትችላለችን ፧ ከጨው ፡ ውሃም ፡ ጣፋጭ ፡ ውሃ ፡ አይወጣም ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ ከእናንተ ፡ ጥበበኛና ፡ አስተዋይ ፡ ማን ፡ ነው ፧ በመልካም ፡ አኗኗሩ ፡ ሥራውን ፡ በጥበብ ፡ የዋህነት ፡ ያሳይ ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ መራራ ፡ ቅንአትና ፡ ዐድመኛነት ፡ በልባችኹ ፡ ቢኖርባችኹ ፥ አትመኩ ፡ በእውነትም ፡ ላይ ፡ አትዋሹ ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ ይህ ፡ ጥበብ ፡ ከላይ ፡ የሚወርድ ፡ አይደለም ፤ ነገር ፡ ግን ፥ የምድር ፡ ነው ፥ የሥጋም ፡ ነው ፥ የአጋንንትም ፡ ነው ፤

ያዕ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ ቅንአትና ፡ ዐድመኛነት ፡ ባሉበት ፡ ስፍራ ፡ በዚያ ፡ ሁከትና ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ አሉና ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ላይኛዪቱ ፡ ጥበብ ፡ ግን ፡ በመገሥመሪያ ፡ ንጽሕት ፡ ናት ፥ በኋላም ፡ ታራቂ ፥ ገር ፥ ዕሺ ፡ ባይ ፡ ምሕረትና ፡ በጎ ፡ ፍሬ ፡ የሞላባት ፥ ጥርጥርና ፡ ግብዝነት ፡ የሌለባት ፡ ናት ።

ያዕ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ የጽድቅም ፡ ፍሬ ፡ ሰላምን ፡ ለሚያደርጉት ፡ ሰዎች ፡ በሰላም ፡ ይዘራል ።

ያዕቆብ ፡ ምዕራፍ ፡ 4 ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ጦርና ፡ ጠብ ፡ ከወዴት ፡ ይመጣሉ ፧ በብልቶቻችኹ ፡ ውስጥ ፡ ከሚዋጉ ፡ ከነዚህ ፡ ከምኞቶቻችኹ ፡ አይደሉምን ፧

ያዕ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ትመኛላችኹ ፡ ለእናንተም ፡ አይኾንም ፤ ትገድላላችኹ ፡ በብርቱም ፡ ትፈልጋላችኹ ፥ ልታገኙም ፡ አትችሉም ፤ ትጣላላችኹ ፥ ትዋጉማላችኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ አትለምኑምና ፡ ለእናንተ ፡ አይኾንም ፤

ያዕ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ትለምናላችኹ ፥ በምኞቶቻችኹም ፡ ትከፍሉ ፡ ዘንድ ፡ በክፉ ፡ ትለምናላችኹና ፡ አትቀበሉም ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ አመንዝራዎች ፡ ሆይ ፥ ዓለምን ፡ መውደድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጥል ፡ እንዲኾን ፡ አታውቁምን ፧ እንግዲህ ፡ የዓለም ፡ ወዳጅ ፡ ሊኾን ፡ የሚፈቅድ ፡ ኹሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጠላት ፡ ኾኗል ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ወይስ ፡ መጽሐፍ ፦ በእኛ ፡ ዘንድ ፡ ያሳደረው ፡ መንፈስ ፡ በቅንአት ፡ ይመኛል ፡ ያለው ፡ በከንቱ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ ይመስላችኋልን ፧

ያዕ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ጸጋን ፡ አብልጦ ፡ ይሰጣል ፤ ስለዚህ ፦ እግዚአብሔር ፡ ትዕቢተኞችን ፡ ይቃወማል ፥ ለትሑታን ፡ ግን ፡ ጸጋን ፡ ይሰጣል ፡ ይላል ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተገዙ ፤ ዲያብሎስን ፡ ግን ፡ ተቃወሙ ፡ ከእናንተም ፡ ይሸሻል ፤

ያዕ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቅረቡ ፡ ወደ ፡ እናንተም ፡ ይቀርባል ። እናንተ ፡ ኀጢአተኞች ፥ እጆቻችኹን ፡ አንጹ ፤ ኹለት ፡ ዐሳብም ፡ ያላችኹ ፡ እናንተ ፥ ልባችኹን ፡ አጥሩ ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 9 ፤ ተጨነቁና ፡ ዕዘኑ ፡ አልቅሱም ፤ ሣቃችኹ ፡ ወደ ፡ ሐዘን ፡ ደስታችኹም ፡ ወደ ፡ ትካዜ ፡ ይለወጥ ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 10 ፤ በጌታ ፡ ፊት ፡ ራሳችኹን ፡ አዋርዱ ፡ ከፍ ፡ ከፍም ፡ ያደርጋችኋል ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 11 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አትተማሙ ። ወንድሙን ፡ የሚያማ ፡ በወንድሙም ፡ የሚፈርድ ፡ ሕግን ፡ ያማል ፡ በሕግም ፡ ይፈርዳል ፤ በሕግም ፡ ብትፈርድ ፡ ፈራጅ ፡ ነኽ ፡ እንጂ ፡ ሕግን ፡ አድራጊ ፡ አይደለኽም ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 12 ፤ ሕግን ፡ የሚሰጥና ፡ የሚፈርድ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ ርሱም ፡ ሊያድን ፡ ሊያጠፋም ፡ የሚችል ፡ ነው ፤ በሌላው ፡ ግን ፡ የምትፈርድ ፡ አንተ ፡ ማን ፡ ነኽ ፧

ያዕ. ፡ 4 ፡ 13 ፤ አኹንም ፦ ዛሬ ፡ ወይም ፡ ነገ ፡ ወደዚህ ፡ ከተማ ፡ እንኼዳለን ፡ በዚያም ፡ ዓመት ፡ እንኖራለን ፡ እንነግድማለን ፡ እናተርፍማለን ፡ የምትሉ ፡ እናንተ ፥ ተመልከቱ ፥ ነገ ፡ የሚኾነውን ፡ አታውቁምና ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 14 ፤ ሕይወታችኹ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ታይቶ ፡ ኋላ ፡ እንደሚጠፋ ፡ እንፋሎት ፡ ናችኹና ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 15 ፤ በዚህ ፡ ፈንታ ፦ ጌታ ፡ ቢፈቅድ ፥ ብንኖርም ፡ ይህን ፡ ወይም ፡ ያን ፡ እናደርጋለን ፡ ማለት ፡ ይገባችኋል ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 16 ፤ አኹን ፡ ግን ፡ በትዕቢታችኹ ፡ ትመካላችኹ ፤ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ትምክሕት ፡ ኹሉ ፡ ክፉ ፡ ነው ።

ያዕ. ፡ 4 ፡ 17 ፤ እንግዲህ ፡ በጎ ፡ ለማድረግ ፡ ዐውቆ ፡ ለማይሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ነው ።

ያዕቆብ ፡ ምዕራፍ ፡ 5 ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 1 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ ባለጠጋዎች ፥ ስለሚደርስባችኹ ፡ ጭንቅ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ እያላችኹ ፡ አልቅሱ ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 2 ፤ ሀብታችኹ ፡ ተበላሽቷል ፥ ልብሳችኹም ፡ በብል ፡ ተበልቷል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 3 ፤ ወርቃችኹም ፡ ብራችኹም ፡ ዝጓል ፥ ዝገቱም ፡ ምስክር ፡ ይኾንባችኋል ፡ ሥጋችኹንም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ይበላል ። ለኋለኛው ፡ ቀን ፡ መዝገብን ፡ አከማችታችኋል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 4 ፤ እንሆ ፥ ዕርሻችኹን ፡ ያጨዱት ፡ የሠራተኞች ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በእናንተ ፡ ተቀምቶ ፡ ይጮኻል ፥ የዐጫጆችም ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ጸባኦት ፡ ጐሮ ፡ ገብቷል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 5 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ ተቀማጥላችኋል ፡ በሴሰኝነትም ፡ ኖራችኋል ፤ ለዕርድ ፡ ቀን ፡ እንደሚያወፍር ፡ ልባችኹን ፡ አወፍራችኋል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 6 ፤ ጻድቁን ፡ ኰንናችኹታል ፡ ገድላችኹትማል ፤ እናንተን ፡ አይቃወምም ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 7 ፤ እንግዲህ ፥ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ ጌታ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡ ታገሡ ። እንሆ ፥ ገበሬው ፡ የፊተኛውንና ፡ የኋለኛውን ፡ ዝናብ ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ ርሱን ፡ እየታገሠ ፡ የከበረውን ፡ የመሬት ፡ ፍሬ ፡ ይጠብቃል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 8 ፤ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ታገሡ ፥ ልባችኹንም ፡ አጽኑ ፤ የጌታ ፡ መምጣት ፡ ቀርቧልና ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 9 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ እንዳይፈረድባችኹ ፡ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ አታጕረምርሙ ፤ እንሆ ፥ ፈራጅ ፡ በደጅ ፡ ፊት ፡ ቆሟል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 10 ፤ ወንድሞች ፡ ሆይ ፥ የመከራና ፡ የትዕግሥት ፡ ምሳሌ ፡ የኾኑትን ፡ በጌታ ፡ ስም ፡ የተናገሩትን ፡ ነቢያትን ፡ ተመልከቱ ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 11 ፤ እንሆ ፥ በትዕግሥት ፡ የጸኑትን ፡ ብፁዓን ፡ እንላቸዋለን ፤ ኢዮብ ፡ እንደ ፡ ታገሠ ፡ ሰምታችኋል ፥ ጌታም ፡ እንደ ፡ ፈጸመለት ፡ አይታችኋል ፤ ጌታ ፡ እጅግ ፡ የሚምር ፡ የሚራራም ፡ ነውና ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 12 ፤ ከሾሉም ፡ በፊት ፥ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ በሰማይ ፡ ቢኾን ፡ በምድርም ፡ ቢኾን ፡ በሌላ ፡ መሐላም ፡ ቢኾን ፡ በምንም ፡ አትማሉ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ከፍርድ ፡ በታች ፡ እንዳትወድቁ ፡ ነገራችኹ ፡ አዎን ፡ ቢኾን ፡ አዎን ፡ ይኹን ፥ አይደለምም ፡ ቢኾን ፡ አይደለም ፡ ይኹን ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 13 ፤ ከእናንተ ፡ መከራን ፡ የሚቀበል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ርሱ ፡ ይጸልይ ፤ ደስ ፡ የሚለውም ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ርሱ ፡ ይዘምር ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 14 ፤ ከእናንተ ፡ የታመመ ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሽማግሌዎች ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይጥራ ፤ በጌታም ፡ ስም ፡ ርሱን ፡ ዘይት ፡ ቀብተው ፡ ይጸልዩለት ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 15 ፤ የእምነትም ፡ ጸሎት ፡ ድውዩን ፡ ያድናል ፡ ጌታም ፡ ያስነሣዋል ፤ ኀጢአትንም ፡ ሠርቶ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ይሰረይለታል ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 16 ፤ ርስ ፡ በርሳችኹ ፡ በኀጢአታችኹ ፡ ተናዘዙ ። ትፈወሱም ፡ ዘንድ ፡ እያንዳንዱ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡ ይጸልይ ፤ የጻድቅ ፡ ሰው ፡ ጸሎት ፡ በሥራዋ ፡ እጅግ ፡ ኀይል ፡ ታደርጋለች ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 17 ፤ ኤልያስ ፡ እንደ ፡ እኛ ፡ የኾነ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፥ ዝናብም ፡ እንዳይዘንብ ፡ አጥብቆ ፡ ጸለየ ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ሦስት ፡ ዓመት ፡ ከስድስት ፡ ወር ፡ አልዘነበም ፤ ኹለተኛም ፡ ጸለየ ፥

ያዕ. ፡ 5 ፡ 18 ፤ ሰማዩም ፡ ዝናብን ፡ ሰጠ ፡ ምድሪቱም ፡ ፍሬዋን ፡ አበቀለች ።

ያዕ. ፡ 5 ፡ 19 ፤ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፥ ከእናንተ ፡ ማንም ፡ ከእውነት ፡ ቢስት ፡ አንዱም ፡ ቢመልሰው ፥

ያዕ. ፡ 5 ፡ 20 ፤ ኀጢአተኛን ፡ ከተሳሳተበት ፡ መንገድ ፡ የሚመልሰው ፡ ነፍሱን ፡ ከሞት ፡ እንዲያድን ፥ የኀጢአትንም ፡ ብዛት ፡ እንዲሸፍን ፡ ይወቅ ❖

የያዕቆብ ፡ ወንድም ፡ የይሁዳ ፡ መልእክት ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የይሁዳ ፡ መልእክት ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ምዕራፍ ፡ 1

ይሁ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሪያ ፡ የያዕቆብም ፡ ወንድም ፡ የኾነ ፡ ይሁዳ ፥ በእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ተወደው ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ተጠብቀው ፡ ለተጠሩ ፤

ይሁ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ምሕረትና ፡ ሰላም ፡ ፍቅርም ፡ ይብዛላችኹ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ስለምንካፈለው ፡ ስለ ፡ መዳናችን ፡ ልጽፍላችኹ ፡ እጅግ ፡ ተግቼ ፡ ሳለኹ ፥ ለቅዱሳን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ስለተሰጠ ፡ ሃይማኖት ፡ እንድትጋደሉ ፡ እየመከርኋችኹ ፡ እጽፍላችኹ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ ኾነብኝ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 4 ፤ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ለዚህ ፡ ፍርድ ፡ የተጻፉ ፡ አንዳንዶች ፡ ሰዎች ፡ ሾልከው ፡ ገብተዋልና ፤ ኀጢአተኞች ፡ ኾነው ፡ የአምላካችንን ፡ ጸጋ ፡ በሴሰኝነት ፡ ይለውጣሉ ፡ ንጉሣችንንና ፡ ጌታችንንም ፡ ብቻውን ፡ ያለውን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ይክዳሉ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 5 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ዅሉን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞ ፡ ምንም ፡ የተማራችኹ ፡ ብትኾኑ ፡ ጌታ ፡ ከግብጽ ፡ አገር ፡ ሕዝቡን ፡ አድኖ ፡ የማያምኑትን ፡ በኋላ ፡ እንዳጠፋቸው ፡ ላሳስባችኹ ፡ እወዳለኹ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ መኖሪያቸውንም ፡ የተዉትን ፡ እንጂ ፡ የራሳቸውን ፡ አለቅነት ፡ ያልጠበቁትን ፡ መላእክት ፡ በዘለዓለም ፡ እስራት ፡ ከጨለማ ፡ በታች ፡ እስከታላቁ ፡ ቀን ፡ ፍርድ ፡ ድረስ ፡ ጠብቋቸዋል ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እንዲሁም ፡ እንደ ፡ እነርሱ ፡ ዝሙትን ፡ ያደረጉና ፡ ሌላን ፡ ሥጋ ፡ የተከተሉ ፡ ሰዶምና ፡ ገሞራ ፡ በዙሪያቸውም ፡ የነበሩ ፡ ከተማዎች ፡ በዘለዓለም ፡ እሳት ፡ እየተቀጡ ፡ ምሳሌ ፡ ኾነዋል ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ እንዲሁም ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ እያለሙ ፡ ሥጋቸውን ፡ ያረክሳሉ ፡ ጌትነትንም ፡ ይጥላሉ ፡ ሥልጣን ፡ ያላቸውንም ፡ ይሳደባሉ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ሚካኤል ፡ ግን ፡ ከዲያብሎስ ፡ ጋራ ፡ በተከራከረ ፡ ጊዜ ፡ ስለሙሴ ፡ ሥጋ ፡ ሲነጋገር ፦ ጌታ ፡ ይገሥጽኽ ፡ አለው ፡ እንጂ ፡ የስድብን ፡ ፍርድ ፡ ሊናገረው ፡ አልደፈረም ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ እነዚህ ፡ ግን ፡ የማያውቁትን ፡ ዅሉ ፡ ይሳደባሉ ፥ አእምሮም ፡ እንደሌላቸው ፡ እንስሳዎች ፡ በፍጥረታቸው ፡ በሚያውቁት ፡ ዅሉ ፡ በርሱ ፡ ይጠፋሉ ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ ወዮላቸው ፥ በቃየል ፡ መንገድ ፡ ኼደዋልና ፥ ስለ ፡ ደመ ፡ ወዝም ፡ ለበለዓም ፡ ስሕተት ፡ ራሳቸውን ፡ አሳልፈው ፡ ሰጥተዋል ፥ በቆሬም ፡ መቃወም ፡ ጠፍተዋል ።

ይሁ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ እነዚህ ፡ ከእናንተ ፡ ጋራ ፡ ሲጋበዙ ፡ በፍቅር ፡ ግብዣችኹ ፡ እንደ ፡ እድፍ ፡ ናቸው ፤ እንደ ፡ እረኞች ፡ ያለፍርሀት ፡ ራሳቸውን ፡ ይጠብቃሉ ፤ በነፋስ ፡ የተወሰዱ ፡ ውሃ ፡ የሌለባቸው ፡ ደመናዎች ፥ ፍሬ ፡ የማያፈሩ ፡ ዅለት ፡ ጊዜ ፡ የሞቱ ፡ ከነሥራቸው ፡ የተነቀሉ ፡ በበጋ ፡ የደረቁ ፡ ዛፎች ፥

ይሁ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ የገዛ ፡ ነውራቸውን ፡ ዐረፋ ፡ እየደፈቁ ፡ ጨካኝ ፡ የባሕር ፡ ማዕበል ፥ ድቅድቅ ፡ ጨለማ ፡ ለዘለዓለም ፡ የተጠበቀላቸው ፡ የሚንከራተቱ ፡ ከዋክብት ፡ ናቸው ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 14-15 ፤ ከአዳም ፡ ዠምሮ ፡ ሰባተኛ ፡ የኾነ ፡ ሔኖክ ፦ እንሆ ፥ ጌታ ፡ በቸሉ ፡ ላይ ፡ እንዲፈርድ ፥ በኀጢአተኝነትም ፡ ስላደረጉት ፡ ስለ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ሥራቸው ፡ ቸሉ ፡ ዐመፀኞችም ፡ ኀጢአተኞች ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተናገሩ ፡ ስለጭከና ፡ ነገር ፡ ቸሉ ፡ ኀጢአተኞችን ፡ ቸሉ ፡ እንዲወቅስ ፡ ከአእላፋት ፡ ቅዱሳኑ ፡ ጋራ ፡ መጥቷል ፡ ብሎ ፡ ለእነዚህ ፡ ደግሞ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ እነዚህ ፡ እንደ ፡ ምኞታቸው ፡ እየኼዱ ፡ የሚያንጐራጕሩና ፡ ስለ ፡ ዕድላቸው ፡ የሚያጉረመርሙ ፡ ናቸው ፥ እንዲረባቸውም ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እያደሉ ፥ አፋቸው ፡ ከመጠን ፡ ይልቅ ፡ ታላቅ ፡ ቃል ፡ ይናገራል ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ እናንተ ፡ ግን ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሐዋርያት ፡ ቀድሞ ፡ የተነገረውን ፡ ቃል ፡ ዐስቡ ፤

ይሁ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ እነርሱ ፦ በመጨረሻው ፡ ዘመን ፡ በኀጢአተኝነት ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ምኞታቸው ፡ እየኼዱ ፡ ዘባቸች ፡ ይኾናሉ ፡ ብለዋችኋልና ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እነዚህ ፡ የሚያለያዩ ፡ ሥጋውያንም ፡ የኾኑ ፡ መንፈስም ፡ የሌላቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ እናንተ ፡ ግን ፥ ወዳጆች ፡ ሆይ ፥ ከቸሉ ፡ ይልቅ ፡ በተቀደሰ ፡ ሃይማኖታችኹ ፡ ራሳችኹን ፡ ለማነጽ ፡ እየተጋችኹ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እየጸለያችኹ ፥

ይሁ. ፡ 1 ፡ 21 ፤ ወደዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ የሚወስደውን ፡ የጌታችንን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ምሕረት ፡ ስትጠባበቁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ራሳችኹን ፡ ጠብቁ ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 22 ፤ አንዳንዶች ፡ ተከራካሪዎችንም ፡ ውቀሱ ፥ አንዳንዶችንም ፡ ከእሳት ፡ ነጥቃችኹ ፡ አድኑ ፥

ይሁ. ፡ 1 ፡ 23 ፤ አንዳንዶችንም ፡ በሥጋ ፡ የረከሰውን ፡ ልብስ ፡ እንኳ ፡ እየጠላችኹ ፡ በፍርሀት ፡ ማሩ ።

ይሁ. ፡ 1 ፡ 24 ፤ ሳትሰናከሉም ፡ እንዲጠብቃችኹ ፥ በክብሩም ፡ ፊት ፡ በደስታ ፡ ነውር ፡ የሌላችኹ ፡ አድርጎ ፡ እንዲያቆማችኹ ፡ ለሚችለው ፡

ይሁ. ፡ 1 ፡ 25 ፤ ብቻውን ፡ ለኾነ ፡ አምላክና ፡ መድኀኒታችን ፡ ከዘመን ፡ ቸሉ ፡ በፊት ፡ አኹንም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለምም ፡ ድረስ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክብርና ፡ ግርማ ፡ ኀይልም ፡ ሥልጣንም ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖

የዮሐንስ ፡ ራእይ ።

(ክለሳ ፡ 8_20080726)

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ። _____

ራእ. ፥ 1 ፥ 1 ፤ ቶሎ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ለባሪያዎቹ ፡ ያሳይ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰጠው ፡ በርሱም ፡ የተገለጠው ፡ ይህ ፡ ነው ፥ ኢየሱስም ፡ በመልአኩ ፡ ልኮ ፡ ለባሪያው ፡ ለዮሐንስ ፡ አመለከተ ፥

ራእ. ፥ 1 ፥ 2 ፤ ርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስክር ፡ ላየውም ፡ ኹሉ ፡ መሰከረ ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 3 ፤ ዘመኑ ፡ ቀርቧልና ፥ የሚያነበው ፥ የትንቢቱን ፡ ቃል ፡ የሚሰሙትና ፡ በውስጡ ፡ የተጻፈውን ፡ የሚጠብቁት ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 4-5 ፤ የ፡ሐንስ ፡ በእስያ ፡ ላሉት ፡ ለሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፤ ካለውና ፡ ከነበረው ፡ ከሚመጣውም ፥ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ካሉት ፡ ከሰባቱ ፡ መናፍስት ፥ ከታመነውም ፡ ምስክር ፡ ከሙታንም ፡ በኵር ፡ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ገዢ ፡ ከኾነ ፡ ከኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡ ለእናንተ ፡ ይኹን ። ለወደደን ፡ ከኀጢአታችንም ፡ በደሙ ፡ ላጠበን ፥

ራእ. ፥ 1 ፥ 6 ፤ መንግሥትም ፡ ለአምላኩና ፡ ለአባቱም ፡ ካህናት ፡ እንድንኾን ፡ ላደረገ ፥ ለርሱ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ክብርና ፡ ኀይል ፡ ይኹን ፤ አሜን ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 7 ፤ እንሆ ፥ ከደመና ፡ ጋራ ፡ ይመጣል ፤ ዐይንም ፡ ኹሉ ፡ የወጉትም ፡ ያዩታል ፥ የምድርም ፡ ወገኖች ፡ ኹሉ ፡ ስለ ፡ ርሱ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ ይላሉ ። አዎን ፥ አሜን ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 8 ፤ ያለውና ፡ የነበረው ፡ የሚመጣውም ፡ ኹሉንም ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፦ አልፋና ፡ ዖሜጋ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ ይላል ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 9 ፤ እኔ ፡ ወንድማችኹ ፡ የኾንኹ ፡ ከእናንተም ፡ ጋራ ፡ ዐብሬ ፡ መከራውንና ፡ መንግሥቱን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ትዕግሥት ፡ የምካፈል ፡ የ፡ሐንስ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ስለኢየሱስ ፡ ምስክር ፡ ፍጥሞ ፡ በምትባል ፡ ደሴት ፡ ነበርኹ ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 10 ፤ በጌታ ፡ ቀን ፡ በመንፈስ ፡ ነበርኹ ፥ በኋላዬም ፡ የመለከትን ፡ ድምፅ ፡ የሚመስል ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፥

ራእ. ፥ 1 ፥ 11 ፤ እንዲሁም ፦ የምታየውን ፡ በመጽሐፍ ፡ ጽፈኽ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶንና ፡ ወደ ፡ ሰምርኔስ ፡ ወደ ፡ ጴርጋሞንም ፡ ወደ ፡ ትያጥሮንም ፡ ወደ ፡ ሰርዴስም ፡ ወደ ፡ ፊልድልፍያም ፡ ወደ ፡ ሎዶቅያም ፡ በእስያ ፡ ወዳሉት ፡ ወደ ፡ ሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ላክ ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 12 ፤ የሚናገረኝንም ፡ ድምፅ ፡ ለማየት ፡ ዘወር ፡ አልኹ ፤ ዘወርም ፡ ብዬ ፡ ሰባት ፡ የወርቅ ፡ መቅረዞች ፡ አየኹ ፥

ራእ. ፥ 1 ፥ 13 ፤ በመቅረዞቹም ፡ መካከል ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ የሚመስለውን ፡ አየኹ ፥ ርሱም ፡ እስከ ፡ እግሩ ፡ ድረስ ፡ ልብስ ፡ የለበሰው ፡ ደረቱንም ፡ በወርቅ ፡ መታጠቂያ ፡ የታጠቀ ፡ ነበር ።

ራእ. ፥ 1 ፥ 14 ፤ ራሱና ፡ የራሱ ፡ ጠጕርም ፡ እንደ ፡ ነጭ ፡ የበግ ፡ ጠጕር ፡ እንደ ፡ በረዶም ፡ ነጭ ፡ ነበሩ ፥ ዐይኖቹም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ነበሩ ፤

ራእ. ፡ 1 ፡ 15 ፤ እግሮቹም ፡ በእቶን ፡ የነጠረ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ ይመስሉ ፡ ነበር ፥ ድምፁም ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎች ፡ ድምፅ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፡ 1 ፡ 16 ፤ በቀኝ ፡ እጁም ፡ ሰባት ፡ ከዋክብት ፡ ነበሩት ፥ ከአፉም ፡ በኹለት ፡ ወገን ፡ የተሳለ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ወጣ ፤ ፊቱም ፡ በኀይል ፡ እንደሚበራ ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፡ 1 ፡ 17 ፤ ባየኹትም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ ሰው ፡ ኾኜ ፡ ከእግሩ ፡ በታች ፡ ወደቅኹ ። ቀኝ ፡ እጁንም ፡ ጫነብኝ ፡ እንዲህም ፡ አለኝ ፦ አትፍራ ፤ ፊተኛውና ፡ መጨረሻው ፡ ሕያውም ፡ እኔ ፡ ነኝ ፥

ራእ. ፡ 1 ፡ 18 ፤ ሞቼም ፡ ነበርኹ ፡ እንሆም ፥ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ሕያው ፡ ነኝ ፥ የሞትና ፡ የሲኦልም ፡ መክፈቻ ፡ አለኝ ።

ራእ. ፡ 1 ፡ 19 ፤ እንግዲህ ፡ ያየኸውን ፡ አኹንም ፡ ያለውን ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ጻፍ ።

ራእ. ፡ 1 ፡ 20 ፤ በቀኝ ፡ እጄ ፡ ያየኻቸው ፡ የሰባቱ ፡ ከዋክብትና ፡ የሰባቱ ፡ የወርቅ ፡ መቅረዞች ፡ ምስጢር ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ የሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መላእክት ፡ ናቸው ፥ ሰባቱም ፡ መቅረዞች ፡ ሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ናቸው ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ። _____

ራእ. ፡ 2 ፡ 1 ፤ በኤፌሶን ፡ ወዳለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ሰባቱን ፡ ከዋክብት ፡ የያዘው ፡ በሰባቱም ፡ የወርቅ ፡ መቅረዞች ፡ መካከል ፡ የሚኼደው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ራእ. ፡ 2 ፡ 2 ፤ ሥራኽንና ፡ ድካምኽን ፡ ትዕግሥትኽንም ፡ ዐውቃለኹ ፤ ክፉዎችንም ፡ ልትታገሥ ፡ እንዳትችል ፥ እንዲሁም ፡ ሳይኾኑ ። ሐዋርያት ፡ ነን ፡ የሚሉቱን ፡ መርምረኽ ፡ ሐሰተኞች ፡ ኾነው ፡ እንዳገኘኻቸው ፡ ዐውቃለኹ ፤

ራእ. ፡ 2 ፡ 3 ፤ ታግሠኽማል ፥ ስለ ፡ ስሜም ፡ ብለኽ ፡ ጸንተኽ ፡ አልደከምኽም ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 4 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የምነቅፍብኽ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፡ የቀደመውን ፡ ፍቅርኽን ፡ ትተኻልና ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 5 ፤ እንግዲህ ፡ ከወዴት ፡ እንደ ፡ ወደቅኽ ፡ ዐስብ ፡ ንስሐም ፡ ግባ ፡ የቀደመውንም ፡ ሥራኽን ፡ አድርግ ፤ አለዚያ ፡ እመጣብኻለኹ ፡ ንስሐም ፡ ባትገባ ፡ መቅረዝኽን ፡ ከስፍራው ፡ እወስዳለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 6 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ይህ ፡ አለኽ ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ የምጠላውን ፡ የኒቆላውያንን ፡ ሥራ ፡ ጠልተኻልና ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 7 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ። ድል ፡ ለነሣው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ገነት ፡ ካለው ፡ ከሕይወት ፡ ዛፍ ፡ እንዲበላ ፡ እሰጠዋለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 8 ፤ በሰምርኔስም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ ሞቶ ፡ የነበረው ፡ ሕያውም ፡ የኾነው ፡ ፊተኛውና ፡ መጨረሻው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ራእ. ፡ 2 ፡ 9 ፤ መከራኽንና ፡ ድኽነትኽን ፡ ዐውቃለኹ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ባለጠጋ ፡ ነኽ ፤ የሰይጣንም ፡ ማኅበር ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ አይሁድ ፡ ሳይኾኑ ፦ አይሁድ ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ የሚሳደቡትን ፡ ስድብ ፡ ዐውቃለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 10 ፤ ልትቀበለው ፡ ያለኽን ፡ መከራ ፡ አትፍራ ። እንሆ ፥ እንድትፈተኑ ፡ ዲያብሎስ ፡ ከእናንተ ፡ አንዳንዶቻችኹን ፡ በወህኒ ፡ ሊያገባችኹ ፡ አለው ፥ ዐሥር ፡ ቀንም ፡ መከራን ፡ ትቀበላላችኹ ። እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ የታመንኽ ፡ ኹን ፡ የሕይወትንም ፡ አክሊል ፡ እሰጥኻለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 11 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ። ድል ፡ የነሣው ፡

በኹለተኛው ፡ ሞት ፡ አይጐዳም ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 12 ፤ በጴርጋሞንም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ በኹለት ፡ ወገን ፡ የተሳለ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ያለው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ራእ. ፡ 2 ፡ 13 ፤ የሰይጣን ፡ ዙፋን ፡ ባለበት ፡ የምትኖርበትን ፡ ዐውቃለኹ ፤ ስሜንም ፡ ትጠብቃለኽ ፥ ሰይጣንም ፡ በሚኖርበት ፥ በእናንተ ፡ ዘንድ ፡ የተገደለው ፡ የታመነው ፡ ምስክሬ ፡ አንቲጳስ ፡ በነበረበት ፡ ዘመን ፡ እንኳ ፡ ሃይማኖቴን ፡ አልካድኽም ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 14 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ለጣዖት ፡ የታረደውን ፡ እንዲበሉና ፡ እንዲሴስኑ ፡ በእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ፊት ፡ ማሰናከያን ፡ ሊያኖርባቸው ፡ ባላቅን ፡ ያስተማረ ፡ የበልዓምን ፡ ትምህርት ፡ የሚጠብቁ ፡ በዚያ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ አሉ ፥ የምነቅፍብኽ ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ አለኝ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 15 ፤ እንዲሁ ፡ የኒቆላውያንን ፡ ትምህርት ፡ እንደ ፡ እነዚህ ፡ የሚጠብቁ ፡ ሰዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ አሉ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 16 ፤ እንግዲህ ፡ ንስሓ ፡ ግባ ፤ አለዚያ ፡ ፈጥኜ ፡ እመጣብኻለኹ ፥ በአፌም ፡ ሰይፍ ፡ እዋጋቸዋለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 17 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ጕሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ። ድል ፡ ለነሣው ፡ ከተሰወረ ፡ መና ፡ እሰጠዋለኹ ፥ ነጭ ፡ ድንጋይንም ፡ እሰጠዋለኹ ፥ በድንጋዩም ፡ ላይ ፡ ከተቀበለው ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ስንኳ ፡ የሚያውቀው ፡ የሌለ ፡ ዐዲስ ፡ ስም ፡ ተጽፏል ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 18 ፤ በትያጥሮንም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ የኾኑ ፡ ዐይኖች ፡ ያሉት ፡ በእቶንም ፡ የነጠረ ፡ የጋለ ፡ ናስ ፡ የሚመስሉ ፡ እግሮች ፡ ያሉት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ራእ. ፡ 2 ፡ 19 ፤ ሥራኽንና ፡ ፍቅርኽን ፡ እምነትኽንም ፡ አገልግሎትኽንም ፡ ትዕግሥትኽንም ፡ ከፊተኛውም ፡ ሥራኽ ፡ ይልቅ ፡ የኋለኛው ፡ እንዲበዛ ፡ ዐውቃለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 20 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፦ ነቢይ ፡ ነኝ ፡ የምትለውን ፡ ባሪያዎቼንም ፡ እንዲሴስኑና ፡ ለጣዖት ፡ የታረደውን ፡ እንዲበሉ ፡ የምታስተምረውንና ፡ የምታስተውን ፡ ያችን ፡ ሴት ፡ ኤልዛቤልን ፡ ስለምትተዋት ፡ የምነቅፍብኽ ፡ ነገር ፡ አለኝ ፤

ራእ. ፡ 2 ፡ 21 ፤ ንስሓም ፡ እንድትገባ ፡ ጊዜ ፡ ሰጠኋት ፡ ከዝሙቷም ፡ ንስሓ ፡ እንድትገባ ፡ አልወደደችም ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 22 ፤ እንሆ ፥ በዐልጋ ፡ ላይ ፡ እጥላታለኹ ፥ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ የሚያመነዝሩትን ፡ ከሥራዋ ፡ ንስሓ ፡ ባይገቡ ፡ በታላቅ ፡ መከራ ፡ እጥላቸዋለኹ ፤

ራእ. ፡ 2 ፡ 23 ፤ ልጆቿንም ፡ በሞት ፡ እገድላቸዋለኹ ፤ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ኹሉ ፡ ኵላሊትንና ፡ ልብን ፡ የምመረምር ፡ እኔ ፡ እንደ ፡ ኾንኹ ፡ ያውቃሉ ፥ ለያንዳንዳችኹም ፡ እንደ ፡ ሥራችኹ ፡ እሰጣችኋለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 24 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ትምህርት ፡ ለማትይዙ ፡ ኹሉ ፡ የሰይጣንንም ፡ ጥልቅ ፡ ነገር ፡ እነርሱ ፡ እንደሚሉት ፡ ለማታውቁ ፡ ለእናንተ ፡ በትያጥሮን ፡ ለቀራችኹት ፡ እላለኹ ፤ ሌላ ፡ ሸክም ፡ አልጭንባችኹም ፥

ራእ. ፡ 2 ፡ 25 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እስክመጣ ፡ ድረስ ፡ ያላችኹን ፡ ጠብቁ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 26-27 ፤ ድል ፡ ለነሣውና ፡ እስከ ፡ መጨረሻም ፡ ሥራዬን ፡ ለጠበቀው ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ከአባቴ ፡ እንደ ፡ ተቀበልኹ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡ ሥልጣንን ፡ እሰጠዋለኹ ፥ በብረትም ፡ በትር ፡ ይገዛቸዋል ፥ እንደ ፡ ሸክላ ፡ ዕቃም ፡ ይቀጠቀጣሉ ፤

ራእ. ፡ 2 ፡ 28 ፤ የንጋትንም ፡ ኮከብ ፡ እሰጠዋለኹ ።

ራእ. ፡ 2 ፡ 29 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ ምዕራፍ ፡ 3 ። _____

ራእ. ፡ 3 ፡ 1 ፤ በሰርዴስም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ ሰባቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መናፍስትና ፡ ሰባቱ ፡ ከዋክብት ፡ ያሉት ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ ሥራኽን ፡ ዐውቃለኹ ፡ ሕያው ፡ እንደ ፡ መኾንኽ ፡ ስም ፡ አለኽ ፥ ሞተኽማል ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 2 ፤ ሥራኽን ፡ በአምላኬ ፡ ፊት ፡ ፍጹም ፡ ኾኖ ፡ አላገኘኹትምና ፡ የነቃኽ ፡ ኹን ፥ ሊሞቱም ፡ ያላቸውን ፡ የቀሩትን ፡ ነገሮች ፡ አጽና ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 3 ፤ እንግዲህ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተቀበልኽና ፡ እንደ ፡ ሰማኽ ፡ ዐስብ ፥ ጠብቀውም ፡ ንስሐም ፡ ግባ ። እንግዲያስ ፡ ባትነቃ ፡ እንደ ፡ ሌባ ፡ እመጣብኻለኹ ፡ በማናቸውም ፡ ሰዓት ፡ እንድመጣብኽ ፡ ከቶ ፡ አታውቅም ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 4 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ልብሳቸውን ፡ ያላረከሱ ፡ በሰርዴስ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ አሉ ፥ የተገባቸውም ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይኼዳሉ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 5 ፤ ድል ፡ የነሣው ፡ እንዲሁ ፡ በነጭ ፡ ልብስ ፡ ይጐናጸፋል ፥ ስሙንም ፡ ከሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ አልደመስስም ፥ በአባቴና ፡ በመላእክቱም ፡ ፊት ፡ ለስሙ ፡ እመሰክርለታለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 6 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 7 ፤ በፊልድልፍያም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ የዳዊት ፡ መክፈቻ ፡ ያለው ፤ የሚከፍት ፥ የሚዘጋም ፡ የሌለ ፤ የሚዘጋ ፥ የሚከፍትም ፡ የሌለ ፤ ቅዱስና ፡ እውነተኛ ፡ የኾነው ፡ ርሱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

ራእ. ፡ 3 ፡ 8 ፤ ሥራኽን ፡ ዐውቃለኹ ፤ እነሆ ፥ ባንተ ፡ ፊት ፡ የተከፈተ ፡ በር ፡ ሰጥቻለኹ ፡ ማንምም ፡ ሊዘጋው ፡ አይችልም ፤ ኀይልኽ ፡ ምንም ፡ ትንሽ ፡ ቢኾን ፡ ቃሌን ፡ ጠብቀኻልና ፥ ስሜንም ፡ አልካድኽምና ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 9 ፤ እነሆ ፥ አይሁድ ፡ ሳይኾኑ ፦ አይሁድ ፡ ነን ፡ ከሚሉ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ ከሚዋሹ ፡ ከሰይጣን ፡ ማኅበር ፡ አንዳንዶችን ፡ እሰጥኻለኹ ፤ እነሆ ፥ መጥተው ፡ በእግሮችኽ ፡ ፊት ፡ ይሰግዱ ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ እንደ ፡ ወደድኹኽ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ አደርጋቸዋለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 10 ፤ የትዕግሥቴን ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ ጠበቅኽ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ይፈትናቸው ፡ ዘንድ ፡ በዓለም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሊመጣ ፡ ካለው ፡ ከፈተናው ፡ ሰዓት ፡ እጠብቅኻለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 11 ፤ እነሆ ፥ ቶሎ ፡ ብዬ ፡ እመጣለኹ ፤ ማንም ፡ አክሊልኽን ፡ እንዳይወስድብኽ ፡ ያለኽን ፡ አጽንተኽ ፡ ያዝ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 12 ፤ ድል ፡ የነሣው ፡ በአምላኬ ፡ መቅደስ ፡ ዐምድ ፡ እንዲኾን ፡ አደርገዋለኹ ፥ ወደ ፡ ፊትም ፡ ከዚያ ፡ ከቶ ፡ አይወጣም ፤ የአምላኬን ፡ ስምና ፡ የአምላኬን ፡ ከተማ ፡ ስም ፥ ማለት ፡ ከሰማይ ፡ ከአምላኬ ፡ ዘንድ ፡ የምትወርደውን ፡ ዐዲሲቱን ፡ ኢየሩሳሌምን ፥ ዐዲሱንም ፡ ስሜን ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ እጽፋለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 13 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 14 ፤ በሎዶቅያም ፡ ወዳለው ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፦ አሜን ፡ የኾነው ፥ የታመነውና ፡ እውነተኛው ፡ ምስክር ፥ በእግዚአብሔርም ፡ ፍጥረት ፡ መገመሪያ ፡ የነበረው ፡ እንዲህ ፡

ይላል ፦

ራእ. ፡ 3 ፡ 15 ፤ በራድ ፡ ወይም ፡ ትኵስ ፡ እንዳይደለኽ ፡ ሥራኽን ፡ ዐውቃለኹ ። በራድ ፡ ወይም ፡ ትኵስ ፡ ብትኾንስ ፡ መልካም ፡ በኾነ ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 16 ፤ እንዲሁ ፡ ለብ ፡ ስላልኽ ፡ በራድም ፡ ወይም ፡ ትኵስ ፡ ስላልኾንኽ ፡ ከአፌ ፡ ልተፋኽ ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 17 ፤ ሀብታም ፡ ነኝና ፡ ባለጠጋ ፡ ኾኛለኹ ፡ አንድም ፡ ስንኳ ፡ አያስፈልገኝም ፡ የምትል ፡ ስለ ፡ ኾንኽ ፥ ጕስቋላና ፡ ምስኪንም ፡ ድኻም ፡ ዕውርም ፡ የተራቈትኽም ፡ መኾንኽን ፡ ስለማታውቅ ፥

ራእ. ፡ 3 ፡ 18 ፤ ባለጠጋ ፡ እንድትኾን ፡ በእሳት ፡ የነጠረውን ፡ ወርቅ ፥ ተጐናጽፈኽም ፡ የራቀኑትነትኽ ፡ ኀፍረት ፡ እንዳይገለጥ ፡ ነጭ ፡ ልብስን ፥ እንድታይም ፡ ዐይኖችኽን ፡ የምትኳለውን ፡ ኩል ፡ ከእኔ ፡ ትገዛ ፡ ዘንድ ፡ እመክርኻለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 19 ፤ እኔ ፡ የምወዳቸውን ፡ ኹሉ ፡ እገሥጻቸዋለኹ ፡ እቀጣቸውማለኹ ፤ እንግዲህ ፡ ቅና ፡ ንስሐም ፡ ግባ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 20 ፤ እንሆ ፥ በደጅ ፡ ቆሜ ፡ አንኳኳለኹ ፤ ማንም ፡ ድምፄን ፡ ቢሰማ ፡ ደጁንም ፡ ቢከፍትልኝ ፥ ወደ ፡ ርሱ ፡ እገባለኹ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ እራት ፡ እበላለኹ ፡ ርሱም ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ ይበላል ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 21 ፤ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ድል ፡ እንደ ፡ ነሣኹ ፡ ከአባቴም ፡ ጋራ ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ እንደተቀመጥኹ ፥ ድል ፡ ለነሣው ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ በዙፋኔ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ እሰጠዋለኹ ።

ራእ. ፡ 3 ፡ 22 ፤ መንፈስ ፡ ለአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የሚለውን ፡ ገሮ ፡ ያለው ፡ ይስማ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። _____

ራእ. ፡ 4 ፡ 1 ፤ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፡ በሰማይ ፡ የተከፈተ ፡ ደጅ ፥ እንደ ፡ መለከትም ፡ ኾኖ ፡ ሲናገረኝ ፡ የሰማኹት ፡ ፊተኛው ፡ ድምፅ ፦ ወደዚህ ፡ ውጣና ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሊኾን ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ነገር ፡ አሳይኻለኹ ፡ አለ ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 2 ፤ ወዲያው ፡ በመንፈስ ፡ ነበርኹ ፤ እንሆም ፥ ዙፋን ፡ በሰማይ ፡ ቆሟል ፡ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ ተቀማጭ ፡ ነበረ ፤

ራእ. ፡ 4 ፡ 3 ፤ ተቀምጦም ፡ የነበረው ፡ በመልኩ ፡ የኢያስጲድንና ፡ የሰርዲኖን ፡ ዕንቊ ፡ ይመስል ፡ ነበር ። በመልኩም ፡ መረግድን ፡ የመሰለ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ በዙፋኑ ፡ ዙሪያ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 4 ፤ በዙፋኑ ፡ ዙሪያም ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ዙፋኖች ፡ ነበሩ ፥ በዙፋኖቹም ፡ ላይ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በራሳቸውም ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ ደፍተው ፡ ኻያ ፡ አራት ፡ ሽማግሌዎች ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 5 ፤ ከዙፋኑም ፡ መብረቅና ፡ ድምፅ ፡ ነጐድጓድም ፡ ይወጣል ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ሰባት ፡ የእሳት ፡ መብራቶች ፡ ይበሩ ፡ ነበር ፥ እነርሱም ፡ ሰባቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መናፍስት ፡ ናቸው ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 6 ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ብርሌ ፡ የሚመስል ፡ የብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ ነበረ ። በዙፋኑም ፡ መካከል ፡ በዙፋኑም ፡ ዙሪያ ፥ በፊትና ፡ በኋላ ፡ ዐይኖች ፡ የሞሏቸው ፡ አራት ፡ እንስሳዎች ፡ ነበሩ ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 7 ፤ ፊተኛውም ፡ እንስሳ ፡ አንበሳን ፡ ይመስላል ፥ ኹለተኛውም ፡ እንስሳ ፡ ጥጃን ፡ ይመስላል ፥ ሦስተኛውም ፡ እንስሳ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረው ፥ አራተኛውም ፡ እንስሳ ፡ የሚበረውን ፡ ንስር ፡ ይመስላል ።

ራእ. ፡ 4 ፡ 8 ፤ አራቱም ፡ እንስሳዎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ ስድስት ፡ ክንፎች ፡ አሏቸው ፥ በዙሪያቸውና ፡

በውስጣቸውም ፡ ዐይኖች ፡ ሞልተውባቸዋል ፤ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ ቅዱስ ፥ የነበረውና ፡ ያለ ፡ የሚመጣውም ፡ ዅሉንም ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ እያሉ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ አያርፉም ።

ራእ. ፥ 4 ፥ 9 ፤ እንስሳዎቹም ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ከዘለዓለምም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ለሚኖረው ፡ ለርሱ ፡ ክብርና ፡ ውዳሴ ፡ ምስጋናም ፡ በሰጡት ፡ ጊዜ ፥

ራእ. ፥ 4 ፥ 10-11 ፤ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ በተቀመጠው ፡ ፊት ፡ ወድቀው ፥ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ በሕይወት ፡ ለሚኖረው ፡ እየሰገዱ ፦ ጌታችንና ፡ አምላካችን ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ዅሉን ፡ ፈጥረኻልና ፥ ስለ ፡ ፈቃድኽም ፡ ኾነዋልና ፥ ተፈጥረውማልና ፥ ክብር ፣ ውዳሴ ፣ ኀይልም ፡ ልትቀበል ፡ ይገባኻል ፡ እያሉ ፥ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ አክሊላቸውን ፡ ያኖራሉ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 5 ። _____

ራእ. ፥ 5 ፥ 1 ፤ በዙፋኑ ፡ ላይም ፡ በተቀመጠው ፡ በቀኝ ፡ እጁ ፡ ላይ ፡ በውስጥና ፡ በኋላ ፡ የተጻፈበት ፡ በሰባትም ፡ ማኅተም ፡ የተዘጋ ፡ መጽሐፍን ፡ አየኹ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 2 ፤ ብርቱም ፡ መልአክ ፦ መጽሐፉን ፡ ይዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ ማኅተሞቹንም ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ ማን ፡ ነው ፧ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሲያውጅ ፡ አየኹ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 3 ፤ በሰማይም ፡ ቢኾን ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ቢኾን ፡ ከምድርም ፡ በታች ፡ ቢኾን ፡ መጽሐፉን ፡ ሊዘረጋ ፡ ወይም ፡ ሊመለከተው ፡ ማንም ፡ አልተቻለውም ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 4 ፤ መጽሐፉን ፡ ሊዘረጋ ፡ ወይም ፡ ሊመለከተው ፡ የሚገባው ፡ ማንም ፡ ስላልተገኘ ፡ እጅግ ፡ አለቀስኹ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 5 ፤ ከሽማግሌዎቹም ፡ አንዱ ፦ አታልቅስ ፤ እንሆ ፥ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የኾነው ፡ አንበሳ ፡ ርሱም ፡ የዳዊት ፡ ሥር ፡ መጽሐፉን ፡ ይዘረጋ ፡ ዘንድ ፡ ሰባቱንም ፡ ማኅተም ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ድል ፡ ነሥቷል ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 6 ፤ በዙፋኑና ፡ ባራቱ ፡ እንስሳዎች ፡ መካከልም ፡ በሽማግሌዎችም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ በግ ፡ ቆሞ ፡ አየኹ ፥ ሰባትም ፡ ቀንዶችና ፡ ሰባት ፡ ዐይኖች ፡ ነበሩት ፡ እነርሱም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ዅሉ ፡ የተላኩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መናፍስት ፡ ናቸው ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 7 ፤ መጥቶም ፡ በዙፋን ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠ ፡ ከዚያ ፡ ከቀኝ ፡ እጁ ፡ መጽሐፉን ፡ ወሰደው ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 8 ፤ መጽሐፉንም ፡ በወሰደ ፡ ጊዜ ፡ አራቱ ፡ እንስሳዎችና ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ ወደቁ ፥ እያንዳንዳቸውም ፡ በገናንና ፡ የቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ የኾነ ፡ ዕጣን ፡ የሞላበትን ፡ የወርቅ ፡ ዕቃ ፡ ያዙ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 9-10 ፤ መጽሐፉን ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡ ማኅተሞቹንም ፡ ትፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻል ፥ ታርደኻልና ፥ በደምኽም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከነገድ ፡ ዅሉ ፡ ከቋንቋም ፡ ዅሉ ፡ ከወገንም ፡ ዅሉ ፡ ከሕዝብም ፡ ዅሉ ፡ ሰዎችን ፡ ዋጅተኽ ፡ ለአምላካችን ፡ መንግሥትና ፡ ካህናት ፡ ይኾኑ ፡ ዘንድ ፡ አደረግኻቸው ፥ በምድርም ፡ ላይ ፡ ይነግሣሉ ፡ እያሉ ፡ ዐዲስን ፡ ቅኔ ፡ ይዘምራሉ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 11 ፤ አየኹም ፥ በዙፋኑም ፡ በእንስሳዎቹም ፡ በሽማግሌዎቹም ፡ ዙሪያ ፡ የብዙ ፡ መላእክትን ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፤ ቍጥራቸውም ፡ አእላፋት ፡ ጊዜ ፡ አእላፋትና ፡ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ ሺሕ ፡ ነበር ፥

ራእ. ፥ 5 ፥ 12 ፤ በታላቅም ፡ ድምፅ ፦ የታረደው ፡ በግ ፡ ኀይልና ፡ ባለጠግነት ፡ ጥበብም ፡ ብርታትም ፡ ክብርም ፡ ምስጋናም ፡ በረከትም ፡ ሊቀበል ፡ ይገባዋል ፡ አሉ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 13 ፤ በሰማይና ፡ በምድርም ፡ ከምድርም ፡ በታች ፡ በባሕርም ፡ ላይ ፡ ያለ ፡ ፍጥረት ፡ ዅሉ ፡ በእነርሱም ፡

ውስጥ ፡ ያለ ፡ ኹሉ ፦ በረከትና ፡ ክብር ፡ ምስጋናም ፡ ኀይልም ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፥ ለበጉም ፡ ይኹን ፡ ሲሉ ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 5 ፥ 14 ፤ አራቱም ፡ እንስሳዎች ፦ አሜን ፡ አሉ ፥ ሽማግሌዎቹም ፡ ወድቀው ፡ ሰገዱ ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 6 ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 1 ፤ በጉም ፡ ከሰባቱ ፡ ማኅተም ፡ አንዱን ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፥ አየኹ ፤ ከአራቱም ፡ እንስሳዎች ፡ አንዱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በሚመስል ፡ ድምፅ ፦ መጥተኽ ፡ እይ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 2 ፤ አየኹም ፥ እንሆም ፥ ዐምባላይ ፡ ፈረስ ፡ ወጣ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ ቀስት ፡ ነበረው ፥ አክሊልም ፡ ተሰጠው ፥ ድልም ፡ እየነሣ ፡ ወጣ ፡ ድል ፡ ለመንሣት ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 3 ፤ ኹለተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፥ ኹለተኛው ፡ እንስሳ ፦ መጥተኽ ፡ እይ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 4 ፤ ሌላም ፡ ዳማ ፡ ፈረስ ፡ ወጣ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ሰላምን ፡ ከምድር ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎችም ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲተራረዱ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ፥ ታላቅም ፡ ሰይፍ ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 5 ፤ ሦስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ ሦስተኛው ፡ እንስሳ ፦ መጥተኽ ፡ እይ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ። አየኹም ፥ እንሆም ፥ ጕራቻ ፡ ፈረስ ፡ ወጣ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ በእጁ ፡ ሚዛን ፡ ያዘ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 6 ፤ ባራቱም ፡ እንስሳዎች ፡ መካከል ፡ ድምፅ ፦ አንድ ፡ ርቦ ፡ ስንዴ ፡ በዲናር ፡ ሦስት ፡ ርቦ ፡ ገብስም ፡ በዲናር ፥ ዘይትንና ፡ ወይንንም ፡ አትጕዳ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 7 ፤ አራተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ የአራተኛው ፡ እንስሳ ፡ ድምፅ ፦ መጥተኽ ፡ እይ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 8 ፤ አየኹም ፥ እንሆም ፥ ሐመር ፡ ፈረስ ፡ ወጣ ፥ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ ስሙ ፡ ሞት ፡ ነበረ ። ሲኦልም ፡ ተከተለው ፤ በሰይፍና ፡ በራብም ፡ በሞትም ፡ በምድርም ፡ አራዊት ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ከምድር ፡ ባራተኛዋ ፡ እጅ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጣቸው ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 9 ፤ ዐምስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፥ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ስለጠበቁት ፡ ምስክር ፡ የታረዱትን ፡ የሰዎች ፡ ነፍሳት ፡ ከመሠዊያ ፡ በታች ፡ አየኹ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 10 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፡ እየጮኹ ፦ ቅዱስና ፡ እውነተኛ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ አትፈርድም ፥ ደማችንንስ ፡ በምድር ፡ በሚኖሩት ፡ ላይ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ አትበቀልም ፧ አሉ ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 11 ፤ ለያንዳንዳቸውም ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ተሰጣቸው ፥ እንደ ፡ እነርሱም ፡ ደግሞ ፡ ይገደሉ ፡ ዘንድ ፡ ያላቸው ፡ የባሪያዎች ፡ ባልንጀራዎቻቸውና ፡ የወንድሞቻቸው ፡ ቍጥር ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፥ ገና ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንዲያርፉ ፡ ተባለላቸው ።

ራእ. ፥ 6 ፥ 12 ፤ ስድስተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ አየኹ ፥ ታላቅም ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፥ ፀሓይም ፡ እንደ ፡ ማቅ ፡ ጠጕር ፡ ጥቍር ፡ ኾነ ፥ ጨረቃም ፡ በሞላው ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ኾነ ፥

ራእ. ፥ 6 ፥ 13 ፤ በለስም ፡ በብርቱ ፡ ነፋስ ፡ ተናውጣ ፡ ቃርያዋን ፡ ፍሬ ፡ እንደምትጥል ፥ የሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወደቁ ፥

ራእ. ፥ 6 ፥ 14 ፤ ሰማይም ፡ እንደ ፡ መጽሐፍ ፡ ተጠቅሎ ፡ ዐለፈ ፥ ተራራዎችና ፡ ደሴቶችም ፡ ኹሉ ፡ ከስፍራቸው ፡

ተወሰዱ ።

ራእ. ፡ 6 ፡ 15 ፤ የምድርም ፡ ነገሥታትና ፡ መኳንንት ፥ ሻለቃዎችም ፣ ባለጠጋዎችም ፣ ጎይለኞችም ፣ ባሪያዎችም ፣ ጌታዎችም ፡ ኹሉ ፡ በዋሻዎችና ፡ በተራራዎች ፡ አለቶች ፡ ተሰወሩ ፤

ራእ. ፡ 6 ፡ 16 ፤ ተራራዎችንና ፡ አለቶችንም ፦ በላያችን ፡ ውደቁ ፥ በዙፋንም ፡ ከተቀመጠው ፡ ፊት ፡ ከበጉም ፡ ቍጣ ፡ ሰውሩን ፤

ራእ. ፡ 6 ፡ 17 ፤ ታላቁ ፡ የቍጣው ፡ ቀን ፡ መጥቷልና ፥ ማንስ ፡ ሊቆም ፡ ይችላል ፧ አሏቸው ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 7 ። _____

ራእ. ፡ 7 ፡ 1 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ባራቱ ፡ በምድር ፡ ማእዘን ፡ ቆመው ፡ አራት ፡ መላእክት ፡ አየኹ ፥ እነርሱም ፡ ነፋስ ፡ በምድር ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ በባሕር ፡ ወይም ፡ በማንም ፡ ዛፍ ፡ እንዳይነፍስ ፡ አራቱን ፡ የምድር ፡ ነፋሳት ፡ ያዙ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 2 ፤ የሕያው ፡ አምላክ ፡ ማኅተም ፡ ያለውም ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ሲወጣ ፡ አየኹ ፥ ምድርንና ፡ ባሕርንም ፡ ሊጐዱ ፡ ለተሰጣቸው ፡ ለአራቱ ፡ መላእክት ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እየጮኸ ፦

ራእ. ፡ 7 ፡ 3 ፤ የአምላካችንን ፡ ባሪያዎች ፡ ግንባራቸውን ፡ እስክናትማቸው ፡ ድረስ ፡ ምድርን ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ባሕርን ፡ ወይም ፡ ዛፎችን ፡ አትጐዱ ፡ አላቸው ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 4 ፤ የታተሙትንም ፡ ቍጥር ፡ ሰማኹ ፤ ከእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገድ ፡ ኹሉ ፡ የታተሙት ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 5 ፤ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ታተሙ ፥ ከሮቤል ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከጋድ ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥

ራእ. ፡ 7 ፡ 6 ፤ ከአሴር ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥

ራእ. ፡ 7 ፡ 7 ፤ ከምናሴ ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከስምዖን ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከሌዊ ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከይሳኮር ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥

ራእ. ፡ 7 ፡ 8 ፤ ከዛብሎን ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከዮሴፍ ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፥ ከብንያም ፡ ነገድ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ሺሕ ፡ ታተሙ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 9 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፥ አንድ ፡ እንኳ ፡ ሊቈጥራቸው ፡ የማይችል ፡ ከሕዝብና ፡ ከነገድ ፡ ከወገንም ፡ ከቋንቋም ፡ ኹሉ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፤ ነጭ ፡ ልብስም ፡ ለብሰው ፡ የዘንባባንም ፡ ዝንጣፊዎች ፡ በእጆቻቸው ፡ ይዘው ፡ በዙፋኑና ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፤

ራእ. ፡ 7 ፡ 10 ፤ በታላቅም ፡ ድምፅ ፡ እየጮኹ ፦ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለአምላካችንና ፡ ለበጉ ፡ ማዳን ፡ ነው ፡ አሉ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 11 ፤ መላእክቱም ፡ ኹሉ ፡ በዙፋኑና ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ባራቱም ፡ እንስሳዎቹ ፡ ዙሪያ ፡ ቆመው ፡ ነበር ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፉ ፥ ለእግዚአብሔርም ፡ እየሰገዱ ፦

ራእ. ፡ 7 ፡ 12 ፤ አሜን ፥ በረከትና ፡ ክብር ፡ ጥበብም ፡ ምስጋናም ፡ ውዳሴም ፡ ኀይልም ፡ ብርታትም ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ለአምላካችን ፡ ይኹን ፤ አሜን ፡ አሉ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 13 ፤ ከሽማግሌዎቹም ፡ አንዱ ፡ ተመልሶ ፦ እነዚህ ፡ ነጩን ፡ ልብስ ፡ የለበሱ ፡ እነማን ፡

ናቸው ፡፡ ከወዴትስ ፡ መጡ ፡፡ አለኝ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 14 ፤ እኔም ፦ ጌታ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ታውቃለኽ ፡ አልኹት ። አለኝም ፦ እነዚህ ፡ ከታላቁ ፡ መከራ ፡ የመጡ ፡ ናቸው ፥ ልብሳቸውንም ፡ ዐጥበው ፡ በበጉ ፡ ደም ፡ አነጹ ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 15 ፤ ስለዚህ ፥ በእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ አሉ ፥ ሌሊትና ፡ ቀንም ፡ በመቅደሱ ፡ ያመልኩታል ፥ በዙፋኑም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያድርባቸዋል ።

ራእ. ፡ 7 ፡ 16 ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይራቡም ፥ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ አይጠሙም ፥ ፀሐይም ፡ ትኵሳትም ፡ ኹሉ ፡ ከቶ ፡ አይወርድባቸውም ፤

ራእ. ፡ 7 ፡ 17 ፤ በዙፋኑ ፡ መካከል ፡ ያለው ፡ በጉ ፡ እረኛቸው ፡ ይኾናልና ፥ ወደ ፡ ሕይወትም ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ ይመራቸዋልና ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንባዎችን ፡ ኹሉ ፡ ከዐይናቸው ፡ ያብሳል ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 8 ። _____

ራእ. ፡ 8 ፡ 1 ፤ ሰባተኛውንም ፡ ማኅተም ፡ በፈታ ፡ ጊዜ ፡ እኩል ፡ ሰዓት ፡ የሚያኽል ፡ ዝምታ ፡ በሰማይ ፡ ኾነ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 2 ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ የሚቆሙትን ፡ ሰባቱን ፡ መላእክት ፡ አየኹ ፥ ሰባትም ፡ መለከት ፡ ተሰጣቸው ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 3 ፤ ሌላም ፡ መልአክ ፡ መጣና ፡ የወርቅ ፡ ጥና ፡ ይዞ ፡ በመሠዊያው ፡ አጠገብ ፡ ቆመ ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ባለው ፡ በወርቅ ፡ መሠዊያ ፡ ላይ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኹሉ ፡ ጸሎት ፡ እንዲጨምረው ፡ ብዙ ፡ ዕጣን ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 4 ፤ የዕጣኑም ፡ ጢስ ፡ ከቅዱሳን ፡ ጸሎት ፡ ጋራ ፡ ከመልአኩ ፡ እጅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ወጣ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 5 ፤ መልአኩም ፡ ጥናውን ፡ ይዞ ፡ የመሠዊያውን ፡ እሳት ፡ ሞላበት ፡ ወደ ፡ ምድርም ፡ ጣለው ፤ ነጐድጓድና ፡ ድምፅም ፡ መብረቅም ፡ መናወጥም ፡ ኾነ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 6 ፤ ሰባቱንም ፡ መለከት ፡ የያዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ሊነፉ ፡ ተዘጋጁ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 7 ፤ ፊተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ ደምም ፡ የተቀላቀለበት ፡ በረዶና ፡ እሳት ፡ ኾነ ፥ ወደ ፡ ምድርም ፡ ተጣለ ፤ የምድርም ፡ ሢሶው ፡ ተቃጠለ ፡ የዛፎችም ፡ ሢሶው ፡ ተቃጠለ ፡ የለመለመም ፡ ሣር ፡ ኹሉ ፡ ተቃጠለ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 8 ፤ ኹለተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በእሳት ፡ የሚቃጠል ፡ ታላቅ ፡ ተራራን ፡ የሚመስል ፡ ነገር ፡ በባሕር ፡ ተጣለ ፤ የባሕርም ፡ ሢሶው ፡ ደም ፡ ኾነ ፡

ራእ. ፡ 8 ፡ 9 ፤ በባሕርም ፡ ከሚኖሩ ፡ ሕይወት ፡ ካላቸው ፡ ፍጥረቶች ፡ ሢሶው ፡ ሞተ ፡ የመርከቦችም ፡ ሢሶው ፡ ጠፋ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 10 ፤ ሦስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ እንደ ፡ ችቦም ፡ የሚቃጠል ፡ ታላቅ ፡ ኮከብ ፡ ከሰማይ ፡ ወደቀ ፥ በወንዞችና ፡ በውሃም ፡ ምንጮች ፡ ሢሶ ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። የኮከቡም ፡ ስም ፡ ሬቶ ፡ ይባላል ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 11 ፤ የውሃውም ፡ ሢሶ ፡ መራራ ፡ ኾነ ፥ መራራም ፡ ስለተደረገ ፡ በውሃው ፡ ጠንቅ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 12 ፤ አራተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ የፀሐይ ፡ ሢሶና ፡ የጨረቃ ፡ ሢሶ ፡ የከዋክብትም ፡ ሢሶ ፡ ተመታ ፥ የእነዚህ ፡ ሢሶ ፡ ይጨልም ፡ ዘንድ ፥ የቀንም ፡ ሢሶው ፡ እንዳያበራ ፥ እንዲሁም ፡ የሌሊት ።

ራእ. ፡ 8 ፡ 13 ፤ አየኹም ፥ አንድም ፡ ንስር ፡ በሰማይ ፡ መካከል ፡ እየበረረ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፦ ሊነፉ ፡ ያላቸው ፡

የሦስቱ ፡ መላእክት ፡ መለከት ፡ ስለሚቀረው ፡ ድምፅ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ለሚኖሩት ፡
ወዮላቸው ፥ ወዮላቸው ፥ ወዮላቸው ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 9 ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 1 ፤ ዐምስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ ከሰማይም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወድቆ ፡ የነበረ ፡ ኮከብ ፡
አየኹ ፥ የጥልቁም ፡ ጉድጓድ ፡ መክፈቻ ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 2 ፤ የጥልቁንም ፡ ጉድጓድ ፡ ከፈተው ፤ ጢስም ፡ ከታላቅ ፡ እቶን ፡ እንደሚወጣ ፡ ጢስ ፡ ኾኖ ፡
ከጉድጓዱ ፡ ወጣ ፤ ፀሓይና ፡ አየርም ፡ በጉድጓዱ ፡ ጢስ ፡ ጨለሙ ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 3 ፤ ከጢሱም ፡ አንበጣዎች ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ወጡ ፥ የምድርም ፡ ጊንጦች ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡
ሥልጣን ፡ ተሰጣቸው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 4 ፤ የእግዚአብሔርም ፡ ማኅተም ፡ በግንባራቸው ፡ ከሌለባቸው ፡ ሰዎች ፡ በቀር ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡
ሣር ፡ ቢኾንም ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ የለመለመ ፡ ነገር ፡ ወይም ፡ ማናቸውንም ፡ ዛፍ ፡ እንዳይጐዱ ፡ ተባለላቸው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 5 ፤ ዐምስትም ፡ ወር ፡ ሊሣቅይዋቸው ፡ ተሰጣቸው ፡ እንጂ ፡ ሊገድሏቸው ፡ አይደለም ፤ እነርሱም ፡
የሚሣቅዩት ፡ ሥቃይ ፡ ጊንጥ ፡ ሰውን ፡ ነድፎ ፡ እንደሚሣቅይ ፡ ነው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 6 ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ሰዎች ፡ ሞትን ፡ ይፈልጋሉ ፥ አያገኙትምም ፤ ሊሞቱም ፡ ይመኛሉ ፥ ሞትም ፡
ከነርሱ ፡ ይሸሻል ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 7 ፤ የአንበጣዎቹም ፡ መልክ ፡ ለጦርነት ፡ እንደተዘጋጁ ፡ ፈረሶች ፡ ነው ፥ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ወርቅ ፡
እንደሚመስሉ ፡ አክሊሎች ፡ ነበሯቸው ፥ ፊታቸውም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ፊት ፡ ነበረ ፤

ራእ. ፥ 9 ፥ 8 ፤ የሴቶችን ፡ ጠጕር ፡ የሚመስል ፡ ጠጕር ፡ ነበራቸው ፥ ጥርሳቸውም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ጥርስ ፡
ነበረ ፤

ራእ. ፥ 9 ፥ 9 ፤ የብረት ፡ ጥሩር ፡ የሚመስልም ፡ ጥሩር ፡ ነበራቸው ፤ የክንፋቸውም ፡ ድምፅ ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡
እንደሚጋልቡ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ፈረሶች ፡ ሠረገላዎች ፡ ድምፅ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 10 ፤ እንደ ፡ ጊንጥም ፡ ኻራት ፡ ያለ ፡ ኻራት ፡ አላቸው ፤ በኻራታቸውም ፡ መውጊያ ፡
አለ ፥ ሰዎችንም ፡ ዐምስት ፡ ወር ፡ እንዲጐዱ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 11 ፤ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ንጉሥ ፡ አላቸው ፤ ርሱም ፡ የጥልቅ ፡ መልአክ ፡ ነው ፥ ስሙም ፡
በዕብራይስጥ ፡ አብዶን (307) ፡ በግሪክም ፡ አጶልዮን (308) ፡ ይባላል ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 12 ፤ ፈተኛው ፡ ወዮ ፡ ዐልፏል ፤ እንሆ ፥ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ገና ፡ ኹለት ፡ ወዮ ፡ ይመጣል ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 13 ፤ ስድስተኛውም ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ካለ ፡ በወርቅ ፡ ከተሠራ ፡ መሠዊያ ፡
ቀንዶች ፡ አንድ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፥

ራእ. ፥ 9 ፥ 14 ፤ መለከትም ፡ ያለውን ፡ ስድስተኛውን ፡ መልአክ ፦ በታላቁ ፡ ወንዝ ፡ በኤፍራጥስ ፡ የታሰሩትን ፡
አራቱን ፡ መላእክት ፡ ፍታቸው ፡ አለው ።

ራእ. ፥ 9 ፥ 15 ፤ የሰዎችንም ፡ ሢሶ ፡ እንዲገድሉ ፥ ለሰዓቱና ፡ ለቀኑ ፣ ለወሩም ፣ ለዓመቱም ፡ ተዘጋጅተው ፡

---

307 ዕብ. ፥ አባዶን ፡ (ባዶ ፣ ባድማ ፡ አድራጊ ፥ አጥፊ) ።
308 ጽር. ፥ አፖሉዎን ፡ (ባዶ ፣ ባድማ ፡ አድራጊ ፥ አጥፊ) ።

የነበሩ ፡ አራቱ ፡ መላእክት ፡ ተፈቱ ።

ራእ. ፡ 9 ፡ 16 ፤ የፈረሰኞችም ፡ ጭፍራ ፡ ቍጥር ፡ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፥ እልፍ ፡ ጊዜ ፡ እልፍ ፡ ነበረ ፤ ቍጥራቸውን ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 9 ፡ 17 ፤ ፈረሶቹንና ፡ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጡትን ፡ እንዲሁ ፡ በራእይ ፡ አየኹ ፤ እሳትና ፡ ያክንት ፣ ዲንም ፡ የሚመስል ፡ ጥሩር ፡ ነበራቸው ፤ የፈረሶቹም ፡ ራስ ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ ራስ ፡ ነበረ ፥ ከአፋቸውም ፡ እሳትና ፡ ጢስ ፣ ዲንም ፡ ወጣ ።

ራእ. ፡ 9 ፡ 18 ፤ ከአፋቸውም ፡ በወጡት ፡ በእሳቱና ፡ በጢሱ ፣ በዲኑም ፥ በእነዚህ ፡ ሦስት ፡ መቅሠፍቶች ፡ የሰዎቹ ፡ ሢሶ ፡ ተገደለ ።

ራእ. ፡ 9 ፡ 19 ፤ የፈረሶቹ ፡ ሥልጣን ፡ በአፋቸውና ፡ በኾራታቸው ፡ ነውና ፤ ኾራታቸው ፡ እባብን ፡ ይመስላልና ፥ ራስም ፡ አላቸው ፥ በርሱም ፡ ይጐዳሉ ።

ራእ. ፡ 9 ፡ 20 ፤ በእነዚህም ፡ መቅሠፍቶች ፡ ያልተገደሉት ፡ የቀሩቱ ፡ ሰዎች ፥ ለአጋንንትና ፡ ያዩ ፡ ወይም ፡ ይሰሙ ፡ ወይም ፡ ይኼዱ ፡ ዘንድ ፡ ለማይችሉ ፥ ከወርቅና ፡ ከብር ፣ ከናስም ፣ ከድንጋይም ፣ ከዕንጨትም ፡ ለተሠሩ ፡ ለጣዖቶች ፡ እንዳይሰግዱ ፡ ስለእጃቸው ፡ ሥራ ፡ ንስሓ ፡ አልገቡም ፤

ራእ. ፡ 9 ፡ 21 ፤ ስለ ፡ መግደላቸውም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ አስማታቸው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ዝሙታቸው ፡ ወይም ፡ ስለ ፡ ስርቆታቸው ፡ ንስሓ ፡ አልገቡም ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 10 ። _____

ራእ. ፡ 10 ፡ 1 ፤ ሌላም ፡ ብርቱ ፡ መልአክ ፡ ደመና ፡ ተጐናጽፎ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየኹ ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ ቀስተ ፡ ደመና ፡ ነበረ ፥ ፊቱም ፡ እንደ ፡ ፀሓይ ፡ እግሮቹም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ዐምዶች ፡ ነበሩ ፥

ራእ. ፡ 10 ፡ 2 ፤ የተከፈተችንም ፡ ታናሽ ፡ መጽሐፍ ፡ በእጁ ፡ ያዘ ። ቀኝ ፡ እግሩንም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ግራውንም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ አኖረ ፥ እንደሚያገሣም ፡ አንበሳ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ።

ራእ. ፡ 10 ፡ 3 ፤ በጮኸም ፡ ጊዜ ፥ ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በየድምፃቸው ፡ ተናገሩ ።

ራእ. ፡ 10 ፡ 4 ፤ ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ልጽፍ ፡ ዐሰብኹ ፤ ከሰማይም ፦ ሰባቱ ፡ ነጐድጓድ ፡ የተናገሩትን ፡ ነገር ፡ በማኅተም ፡ ዝጋው ፥ አትጻፈውም ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 10 ፡ 5 ፤ በባሕርና ፡ በምድርም ፡ ላይ ፡ ሲቆም ፡ ያየኹት ፡ መልአክ ፥ ቀኝ ፡ እጁን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አሻቅቦ ፡ ዘረጋ ፥

ራእ. ፡ 10 ፡ 6 ፤ ሰማይንና ፡ በርሱም ፡ ያሉትን ፥ ምድርንና ፡ በርሷም ፡ ያሉትን ፥ ባሕርንና ፡ በርሱም ፡ ያሉትን ፡ በፈጠረው ፥ ከዘለዓለምም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ሕያው ፡ ኾኖ ፡ በሚኖረው ፡ ምሎ ፦

ራእ. ፡ 10 ፡ 7 ፤ ወደ ፡ ፊት ፡ አይዘገይም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ሰባተኛው ፡ መልአክ ፡ ሊነፋ ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፥ ድምፁም ፡ በሚሰማበት ፡ ዘመን ፥ ለባሪያዎቹ ፡ ለነቢያት ፡ የምሥራች ፡ እንደ ፡ ሰበከላቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምስጢር ፡ ይፈጸማል ፡ አለ ።

ራእ. ፡ 10 ፡ 8 ፤ ከሰማይም ፡ የሰማኹት ፡ ድምፅ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሲናገረኝና ፦ ኺድና ፡ በባሕርና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ከሚቆመው ፡ መልአክ ፡ በእጁ ፡ ያለችውን ፡ የተከፈተችውን ፡ መጽሐፍ ፡ ውሰድ ፡ ሲል ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 10 ፡ 9 ፤ ወደ ፡ መልአኩም ፡ ኼጄ ፦ ታናሺቱን ፡ መጽሐፍ ፡ ስጠኝ ፡ አልኹት ። ርሱም ፦ ውሰድና ፡

ብላት ፥ ሆድኽንም ፡ መራራ ፡ ታደርገዋለች ፥ በአፍኽ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ትጣፍጣለች ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 10 ፥ 10 ፤ ከመልአኩም ፡ እጅ ፡ ታናሺቱን ፡ መጽሐፍ ፡ ወስጄ ፡ በላኋት ፥ በአፌም ፡ እንደ ፡ ማር ፡ ጣፋጭ ፡ ኾነች ፤ ከበላኋት ፡ በኋላም ፡ ሆዴ ፡ መራራ ፡ ኾነ ።

ራእ. ፥ 10 ፥ 11 ፤ በብዙ ፡ ወገኖችና ፡ በአሕዛብም ፣ በቋንቋዎችም ፣ በነገሥታትም ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ትንቢት ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ፡ ይገባኻል ፡ ተባለልኝ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 11 ። _____

ራእ. ፥ 11 ፥ 1 ፤ በትር ፡ የሚመስል ፡ መለኪያ ፡ ለእኔ ፡ ተሰጠኝ ፥ እንዲህም ፡ ተባለልኝ ፦ ተነሥተኽ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስና ፡ መሠዊያውን ፡ በዚያም ፡ የሚሰግዱትን ፡ ለካ ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 2 ፤ በመቅደሱም ፡ ውጭ ፡ ያለው ፡ እድሞ ፡ ለአሕዛብ ፡ ተሰጥቷልና ፥ ተወው ፥ አትለካውም ፤ እነርሱም ፡ አርባ ፡ ኹለት ፡ ወር ፡ የተቀደሰችውን ፡ ከተማ ፡ ይረግጧታል ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 3 ፤ ለኹለቱም ፡ ምስክሮቼ ፡ ማቅ ፡ ለብሰው ፡ ሺሕ ፡ ከኹለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ቀን ፡ ትንቢት ፡ ሊናገሩ ፡ እሰጣለኹ ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 4 ፤ እነዚህ ፡ በምድር ፡ ጌታ ፡ ፊት ፡ የሚቆሙ ፡ ኹለቱ ፡ ወይራዎችና ፡ ኹለቱ ፡ መቅረዞች ፡ ናቸው ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 5 ፤ ማንምም ፡ ሊጐዳቸው ፡ ቢወድ ፡ እሳት ፡ ከአፋቸው ፡ ይወጣል ፡ ጠላቶቻቸውንም ፡ ይበላል ፤ ማንም ፡ ሊጐዳቸው ፡ ቢወድም ፡ እንዲሁ ፡ ሊገደል ፡ ይገባዋል ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 6 ፤ እነዚህ ፡ ትንቢት ፡ በሚናገሩበት ፡ ወራት ፡ ዝናብ ፡ እንዳይዘንብ ፡ ሰማይን ፡ ሊዘጉ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ፥ ውሃዎችንም ፡ ወደ ፡ ደም ፡ ሊለውጡ ፡ በሚፈልጉበትም ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፡ በመቅሠፍት ፡ ኹሉ ፡ ምድርን ፡ ሊመቱ ፡ ሥልጣን ፡ አላቸው ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 7 ፤ ምስክራቸውን ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ ከጥልቁ ፡ የሚወጣው ፡ አውሬ ፡ ይዋጋቸዋል ፡ ያሸንፋቸውማል ፡ ይገድላቸውማል ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 8 ፤ በድናቸውም ፡ በታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ አደባባይ ፡ ይተኛል ፡ ርሷም ፡ በመንፈሳዊ ፡ ምሳሌ ፡ ሰዶምና ፡ ግብጽ ፡ የተባለች ፡ ደግሞ ፡ ጌታቸው ፡ የተሰቀለባት ፡ ናት ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 9 ፤ ከወገኖችና ፡ ከነገዶችም ፡ ከቋንቋዎችም ፡ ከአሕዛብም ፡ የኾኑ ፡ ሰዎች ፡ ሦስት ፡ ቀን ፡ ተኩል ፡ በድናቸውን ፡ ይመለከታሉ ፥ በድናቸውም ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ሊገባ ፡ አይፈቅዱም ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 10 ፤ እነዚህም ፡ ኹለት ፡ ነቢያት ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ስለ ፡ ሣቀዩ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩት ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ በደስታም ፡ ይኖራሉ ፡ ርስ ፡ በርሳቸውም ፡ ስጦታ ፡ ይሰጣጣሉ ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 11 ፤ ከሦስቱ ፡ ቀን ፡ ተኩልም ፡ በኋላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የወጣ ፡ የሕይወት ፡ መንፈስ ፡ ገባባቸው ፡ በእግሮቻቸውም ፡ ቆሙ ፥ ታላቅም ፡ ፍርሀት ፡ በሚመለከቱት ፡ ላይ ፡ ወደቀባቸው ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 12 ፤ በሰማይም ፦ ወደዚህ ፡ ውጡ ፡ የሚላቸውን ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ሰሙ ፤ ጠላቶቻቸውም ፡ እየተመለከቷቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ በደመና ፡ ወጡ ።

ራእ. ፥ 11 ፥ 13 ፤ በዚያም ፡ ሰዓት ፡ ታላቅ ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፥ ከከተማዪቱም ፡ ዐሥረኛው ፡ እጅ ፡ ወደቀ ፥ በመናወጥም ፡ ሰባት ፡ ሺሕ ፡ ሰዎች ፡ ተገደሉ ፥ የቀሩትንም ፡ ፍርሀት ፡ ያዛቸው ፥ ለሰማዩም ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ ሰጡ ።

ራእ. ፡ 11 ፡ 14 ፤ ኹለተኛው ፡ ወዮ ፡ ዐልፏል ፤ እንሆ ፥ ሦስተኛው ፡ ወዮ ፡ በቶሎ ፡ ይመጣል ።

ራእ. ፡ 11 ፡ 15 ፤ ሰባተኛው ፡ መልአክ ፡ ነፋ ፤ በሰማይም ፦ የዓለም ፡ መንግሥት ፡ ለጌታችንና ፡ ለርሱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኾነች ፥ ለዘለዓለምም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይነግሣል ፡

ራእ. ፡ 11 ፡ 16 ፤ የሚሉ ፡ ታላላቅ ፡ ድምፆች ፡ ኾኑ ። በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ በዙፋኖቻቸው ፡ የተቀመጡ ፡ ኻያ ፡ አራቱ ፡ ሽማግሌዎች ፡ በግንባራቸው ፡ ተደፍተው ፡

ራእ. ፡ 11 ፡ 17 ፤ ለእግዚአብሔር ፡ እየሰገዱ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፦ ያለኽና ፡ የነበርኽ ፡ ኹሉን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሆይ ፥ ትልቁን ፡ ኀይልኽን ፡ ስለ ፡ ያዝኽ ፡ ስለ ፡ ነገሥኽም ፡ እናመሰግንኻለን ፤

ራእ. ፡ 11 ፡ 18 ፤ አሕዛብም ፡ ተቈጡ ፥ ቍጣኽም ፡ መጣ ፥ በሙታንም ፡ ትፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ዘመን ፡ መጣ ፥ ለባሪያዎችኽም ፡ ለነቢያትና ፡ ለቅዱሳን ፡ ስምኽንም ፡ ለሚፈሩት ፡ ለታናናሾችና ፡ ለታላላቆችም ፡ ዋጋቸውን ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ፥ ምድርንም ፡ የሚያጠፉትን ፡ ታጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ዘመን ፡ መጣ ።

ራእ. ፡ 11 ፡ 19 ፤ በሰማይም ፡ ያለው ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስ ፡ ተከፈተ ፥ የኪዳኑም ፡ ታቦት ፡ በመቅደሱ ፡ ታየ ፥ መብረቅና ፡ ድምፅም ፡ ነጐድጓድም ፡ የምድርም ፡ መናወጥ ፡ ታላቅም ፡ በረዶ ፡ ኾነ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 12 ። _____

ራእ. ፡ 12 ፡ 1 ፤ ታላቅ ፡ ምልክትም ፡ በሰማይ ፡ ታየ ፡ ፀሓይን ፡ ተጐናጽፋ ፡ ጨረቃ ፡ ከእግሮቿ ፡ በታች ፡ ያላት ፡ በራሷም ፡ ላይ ፡ የዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ከዋክብት ፡ አክሊል ፡ የኾነላት ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ነበረች ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 2 ፤ ርሷም ፡ ፀንሳ ፡ ነበር ፥ ምጥም ፡ ተይዛ ፡ ልትወልድ ፡ ተጨንቃ ፡ ጮኸች ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 3 ፤ ሌላም ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ ታየ ፤ እንሆም ፡ ታላቅ ፡ ቀይ ፡ ዘንዶ ፤ ሰባት ፡ ራሶችና ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶችም ፡ ነበሩት ፡ በራሶቹም ፡ ላይ ፡ ሰባት ፡ ዘውዶች ፡ ነበሩ ፥

ጐራቱም ፡ የሰማይን ፡ ከዋክብት ፡ ሦስ ፡ እየሳበ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣላቸው ። ዘንዶውም ፡ ሴቲቱ ፡ በወለደች ፡ ጊዜ ፡ ሕፃኗን ፡ እንዲበላ ፡ ልትወልድ ፡ ባላት ፡ ሴት ፡ ፊት ፡ ቆመ ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 5 ፤ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ በብረት ፡ በትር ፡ ይገዛቸው ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ልጅ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደች ፤ ልጇም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርና ፡ ወደ ፡ ዙፋኑ ፡ ተነጠቀ ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 6 ፤ ሴቲቱም ፡ ሺሕ ፡ ከኹለት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ቀን ፡ በዚያ ፡ እንዲመግቧት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተዘጋጅቶላት ፡ ወደነበረው ፡ ስፍራ ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ሸሸች ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 7 ፤ በሰማይም ፡ ሰልፍ ፡ ኾነ ፤ ሚካኤልና ፡ መላእክቱ ፡ ዘንዶውን ፡ ተዋጉ ። ዘንዶውም ፡ ከመላእክቱ ፡ ጋራ ፡ ተዋጋ ፥ አልቻላቸውምም ፥

ራእ. ፡ 12 ፡ 8 ፤ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ በሰማይ ፡ ስፍራ ፡ አልተገኘላቸውም ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 9 ፤ ዓለሙንም ፡ ኹሉ ፡ የሚያስተው ፥ ዲያብሎስና ፡ ሰይጣን ፡ የሚባለው ፡ ታላቁ ፡ ዘንዶ ፡ ርሱም ፡ የቀደመው ፡ እባብ ፡ ተጣለ ፤ ወደ ፡ ምድር ፡ ተጣለ ፡ መላእክቱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተጣሉ ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 10 ፤ ታላቅም ፡ ድምፅ ፡ በሰማይ ፡ ሰማኹ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ አኹን ፡ የአምላካችን ፡ ማዳንና ፡ ኀይል ፡ መንግሥትም ፡ የክርስቶስም ፡ ሥልጣን ፡ ኾነ ፥ ቀንና ፡ ሌሊትም ፡ በአምላካችን ፡ ፊት ፡ የሚከሳቸው ፡ የወንድሞቻችን ፡ ከሳሽ ፡ ተጥሏልና ።

ራእ. ፡ 12 ፡ 11 ፤ እነርሱም ፡ ከበጉ ፡ ደም ፡ የተነሣ ፡ ከምስክራቸውም ፡ ቃል ፡ የተነሣ ፡ ድል ፡

ነሡት ፥ ነፍሳቸውንም ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ አልወደዱም ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 12 ፤ ስለዚህ ፥ ሰማይና ፡ በውስጡ ፡ የምታድሩ ፡ ሆይ ፥ ደስ ፡ ይበላችኹ ፤ ለምድርና ፡ ለባሕር ፡ ወዮላቸው ፥ ዲያብሎስ ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ እንዳለው ፡ ዐውቆ ፡ በታላቅ ፡ ቍጣ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ወርዷልና ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 13 ፤ ዘንዶውም ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ እንደ ፡ ተጣለ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ የወለደችውን ፡ ሴት ፡ አሳደዳት ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 14 ፤ ከእባቡም ፡ ፊት ፡ ርቃ ፡ አንድ ፡ ዘመን ፥ ዘመናትም ፥ የዘመንም ፡ እኩሌታ ፡ ወደምትመገብበት ፡ ወደ ፡ ስፍራዋ ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ እንድትበር ፡ ለሴቲቱ ፡ ኹለት ፡ የታላቁ ፡ ንስር ፡ ክንፎች ፡ ተሰጣት ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 15 ፤ እባቡም ፡ ሴቲቱ ፡ በወንዝ ፡ እንድትወሰድ ፡ ሊያደርግ ፡ ወንዝ ፡ የሚያኽልን ፡ ውሃ ፡ ከአፉ ፡ በስተኋላዋ ፡ አፈሰሰ ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 16 ፤ ምድሪቱም ፡ ሴቲቱን ፡ ረዳቻት ፥ ምድሪቱም ፡ አፏን ፡ ከፍታ ፡ ዘንዶው ፡ ከአፉ ፡ ያፈሰሰውን ፡ ወንዝ ፡ ዋጠችው ።

ራእ. ፥ 12 ፥ 17 ፤ ዘንዶውም ፡ በሴቲቱ ፡ ላይ ፡ ተቈጥቶ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዛት ፡ የሚጠብቁትን ፡ የኢየሱስም ፡ ምስክር ፡ ያላቸውን ፡ ከዘሯ ፡ የቀሩትን ፡ ሊዋጋ ፡ ኼደ ፤

ራእ. ፥ 12 ፥ 18 ፤ በባሕርም ፡ አሸዋ ፡ ላይ ፡ ቆመ ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 13 ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 1 ፤ አንድም ፡ አውሬ ፡ ከባሕር ፡ ሲወጣ ፡ አየኹ ፤ ዐሥር ፡ ቀንዶችና ፡ ሰባት ፡ ራሶች ፡ ነበሩት ፥ በቀንዶቹም ፡ ላይ ፡ ዐሥር ፡ ዘውዶች ፡ በራሶቹም ፡ ላይ ፡ የስድብ ፡ ስም ፡ ነበረ ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 2 ፤ ያየኹትም ፡ አውሬ ፡ ነብር ፡ ይመስል ፡ ነበር ፥ እግሮቹም ፡ እንደ ፡ ድብ ፡ እግሮች ፥ አፉም ፡ እንደ ፡ አንበሳ ፡ አፍ ፡ ነበሩ ። ዘንዶውም ፡ ኀይሉንና ፡ ዙፋኑን ፡ ትልቅም ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 3 ፤ ከራሶቹም ፡ ለሞት ፡ እንደ ፡ ታረደ ፡ ኾኖ ፡ አንዱን ፡ አየኹ ፥ ለሞቱ ፡ የኾነውም ፡ ቍስል ፡ ተፈወሰ ። ምድርም ፡ ኹሉ ፡ አውሬውን ፡ እየተከተለ ፡ ተደነቀ ፥

ራእ. ፥ 13 ፥ 4 ፤ ለዘንዶውም ፡ ሰገዱለት ፥ ለአውሬው ፡ ሥልጣንን ፡ ሰጥቶታልና ፤ ለአውሬውም ፦ አውሬውን ፡ ማን ፡ ይመስለዋል ፥ ርሱንስ ፡ ሊዋጋ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 5 ፤ ታላቅንም ፡ ነገርና ፡ ስድብን ፡ የሚናገርበት ፡ አፍ ፡ ተሰጠው ፥ ባርባ ፡ ኹለት ፡ ወርም ፡ እንዲሠራ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 6 ፤ እግዚአብሔርንም ፡ ለመሳደብ ፡ ስሙንና ፡ ማደሪያውንም ፡ በሰማይም ፡ የሚያድሩትን ፡ ሊሳደብ ፡ አፉን ፡ ከፈተ ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 7 ፤ ቅዱሳንንም ፡ ይዋጋ ፡ ዘንድ ፡ ድልም ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡ ተሰጠው ፥ በነገድና ፡ በወገንም ፡ በቋንቋም ፡ በሕዝብም ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 8 ፤ ከዓለምም ፡ ፍጥረት ፡ ዠምሮ ፡ በታረደው ፡ በግ ፡ ሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ስሞቻቸው ፡ ያልተጻፉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ይሰግዱለታል ።

ራእ. ፥ 13 ፥ 9 ፤ ዦሮ ፡ ያለው ፡ ቢኖር ፡ ይስማ ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 10 ፤ ይማረክ ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ወደ ፡ ምርኮነት ፡ ይኼዳል ፤ በሰይፍ ፡ የሚገድል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፡ ራሱ ፡ በሰይፍ ፡ እንዲገደል ፡ ይገ፡ባዋል ። የቅዱሳን ፡ ትዕግሥትና ፡ እምነት ፡ በዚህ ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 11 ፤ ሌላም ፡ አውሬ ፡ ከምድር ፡ ሲወጣ ፡ አየኹ ፥ የበግ ፡ ቀንዶችን ፡ የሚመስሉ ፡ ኹለት ፡ ቀንዶችም ፡ ነበሩት ፡ እንደ ፡ ዘንዶም ፡ ይናገር ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 12 ፤ በፊተኛውም ፡ አውሬ ፡ ሥልጣን ፡ በርሱ ፡ ፊት ፡ ኹሉን ፡ ያደርጋል ። ለሞቱ ፡ የኾነውም ፡ ቍስል ፡ ተፈወሰለት ፡ ለፊተኛው ፡ አውሬ ፡ ምድርና ፡ በርሱ ፡ የሚኖሩት ፡ እንዲሰግዱለት ፡ ያደርጋል ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 13 ፤ እሳትንም ፡ እንኳ ፡ ከሰማይ ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ እስከ፡ያወርድ ፡ ድረስ ፡ ታላላቆችን ፡ ምልክቶች ፡ ያደርጋል ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 14 ፤ በአውሬውም ፡ ፊት ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ከተሰጡት ፡ ምልክቶች ፡ የተነሣ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ያስታል ፤ የሰይፍም ፡ ቍስል ፡ ለነበረውና ፡ በሕይወት ፡ ለኖረው ፡ ለአውሬው ፡ ምስልን ፡ እንዲያደርጉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩትን ፡ ይናገራል ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 15 ፤ የአውሬው ፡ ምስል ፡ ሊናገር ፡ እንኳ ፡ ለአውሬውም ፡ ምስል ፡ የማይሰግዱለትን ፡ ኹሉ ፡ ሊያስገድላቸው ፥ ለአውሬው ፡ ምስል ፡ ትንፋሽ ፡ እንዲሰጠው ፡ ተሰጠው ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 16 ፤ ታናናሾችና ፡ ታላላቆችም ፡ ባለጠጋዎችና ፡ ድኻዎችም ፡ ጌታዎችና ፡ ባሪያዎችም ፡ ኹሉ ፡ በቀኝ ፡ እጃቸው ፡ ወይም ፡ በግንባራቸው ፡ ምልክትን ፡ እንዲቀበሉ ፥

ራእ. ፡ 13 ፡ 17 ፤ የአውሬውም ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የስሙ ፡ ቍጥር ፡ ያለው ፡ ምልክት ፡ የሌለበት ፡ ማንም ፡ ሊገዛ ፡ ወይም ፡ ሊሸጥ ፡ እንዳይችል ፡ ያደርጋል ። ጥበብ ፡ በዚህ ፡ አለ ።

ራእ. ፡ 13 ፡ 18 ፤ አእምሮ ፡ ያለው ፡ የአውሬውን ፡ ቍጥር ፡ ይቍጠረው ፤ ቍጥሩ ፡ የሰው ፡ ቍጥር ፡ ነውና ፥ ቍጥሩም ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ስድሳ ፡ ስድስት ፡ ነው ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 14 ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 1 ፤ አየኹም ፥ እንሆም ፥ በጉ ፡ በጽዮን ፡ ተራራ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ስሙና ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ በግንባራቸው ፡ የተጻፈላቸው ፡ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ ነበሩ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 2 ፤ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃም ፡ ድምፅና ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ ያለ ፡ ከሰማይ ፡ ድምፅን ፡ ሰማኹ ፥ ደርዳሪዎችም ፡ በገና ፡ እንደሚደረድሩ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 3 ፤ በዙፋኑም ፡ ፊት ፡ ባራቱም ፡ እንስሳዎችና ፡ በሽማግሌዎቹ ፡ ፊት ፡ ዐዲስ ፡ ቅኔ ፡ ዘመሩ ፤ ከምድርም ፡ ከተዋጁት ፡ ከመቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ በቀር ፡ ያን ፡ ቅኔ ፡ ሊማር ፡ ለማንም ፡ አልተቻለውም ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 4 ፤ ከሴቶች ፡ ጋራ ፡ ያልረከሱ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ፥ ድንግሎች ፡ ናቸውና ። በጉ ፡ ወደሚኼድበት ፡ የሚከተሉት ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ። ለእግዚአብሔርና ፡ ለበጉ ፡ በኩራት ፡ እንዲኾኑ ፡ ከሰዎች ፡ የተዋጁ ፡ እነዚህ ፡ ናቸው ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 5 ፤ በአፋቸውም ፡ ውሸት ፡ አልተገኘም ፤ ነውር ፡ የለባቸውም ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 6 ፤ በምድርም ፡ ለሚኖሩ ፡ ለሕዝብም ፡ ለነገድም ፡ ለቋንቋም ፡ ለወገንም ፡ ኹሉ ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡ የዘለዓለም ፡ ወንጌል ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ መካከል ፡ ሲበር ፡ አየኹ ፤

ራእ. ፡ 14 ፡ 7 ፤ በታላቅ ፡ ድምፅም ፦ የፍርዱ ፡ ሰዓት ፡ ደርሷልና ፥ እግዚአብሔርን ፡ ፍሩ ፥ ክብርንም ፡ ስጡት ፤ ሰማይንና ፡ ምድርንም ፡ ባሕርንም ፡ የውሃንም ፡ ምንጮች ፡ ለሠራው ፡ ስገዱለት ፡ አለ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 8 ፤ ሌላም ፡ ኹለተኛ ፡ መልአክ ፦ አሕዛብን ፡ ኹሉ ፡ የዝሙቷን ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ያጠጣች ፡ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ ወደቀች ፥ ወደቀች ፡ እያለ ፡ ተከተለው ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 9 ፤ ሦስተኛም ፡ መልአክ ፡ ተከተላቸው ፥ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፦ ለአውሬውና ፡ ለምስሉ ፡ የሚሰግድ ፡ በግንባሩም ፡ ወይም ፡ በእጁ ፡ ምልክቱን ፡ የሚቀበል ፡ ማንም ፡ ቢኖር ፥

ራእ. ፡ 14 ፡ 10 ፤ ርሱ ፡ ደግሞ ፡ በቍጣው ፡ ጽዋ ፡ ሳይቀላቅል ፡ ከተዘጋጀው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ይጠጣል ፥ በቅዱሳንም ፡ መላእክትና ፡ በበጉ ፡ ፊት ፡ በእሳትና ፡ በዲን ፡ ይሳቀያል ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 11 ፤ የሥቃያቸውም ፡ ጢስ ፡ ለዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ ይወጣል ፥ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ የሚሰግዱ ፡ የስሙንም ፡ ምልክት ፡ የሚቀበል ፡ ኹሉ ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 12 ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዛት ፡ የሚጠብቁት ፡ ኢየሱስንም ፡ በማመን ፡ የሚጸኑት ፡ ቅዱሳን ፡ ትዕግሥታቸው ፡ በዚህ ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 13 ፤ ከሰማይም ፦ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ በጌታ ፡ የሚሞቱ ፡ ሙታን ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። መንፈስ ፦ አዎን ፥ ከድካማቸው ፡ ያርፉ ፡ ዘንድ ፥ ሥራቸውም ፡ ይከተላቸዋል ፡ ይላል ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፡ የሚል ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 14 ፤ አየኹም ፥ እንሆም ፡ ነጭ ፡ ደመና ፥ በደመናውም ፡ ላይ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ የሚመስል ፡ ተቀምጧል ፥ በራሱም ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ አክሊል ፡ በእጁም ፡ ስለታም ፡ ማጭድ ፡ ነበረው ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 15 ፤ ሌላ ፡ መልአክም ፡ ከመቅደሱ ፡ ወጥቶ ፡ በደመናው ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፦ የማጨድ ፡ ሰዓት ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ማጭድኽን ፡ ስደድና ፡ ዕጨድ ፥ የምድሪቱ ፡ መከር ፡ ጠውልጓልና ፥ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 16 ፤ በደመናውም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠው ፡ ማጭዱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለው ፡ ምድርም ፡ ታጨደች ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 17 ፤ ሌላ ፡ መልአክም ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፡ መቅደስ ፡ ወጣ ፥ ርሱም ፡ ደግሞ ፡ ስለታም ፡ ማጭድ ፡ ነበረው ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 18 ፤ በእሳትም ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከመሠዊያው ፡ ወጥቶ ፡ ስለታም ፡ ማጭድ ፡ ያለውን ፦ ዘለላዎቹ ፡ ፈጽመው ፡ በስለዋልና ፥ ስለታሙን ፡ ማጭድኽን ፡ ስደድና ፡ በምድር ፡ ያለውን ፡ የወይን ፡ ዛፍ ፡ ዘለላዎች ፡ ቍረጥ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጠራ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 19 ፤ መልአኩም ፡ ማጭዱን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለው ፥ በምድርም ፡ ካለው ፡ ከወይን ፡ ዛፍ ፡ ቈርጦ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ መጥመቂያ ፡ ጣለ ።

ራእ. ፡ 14 ፡ 20 ፤ የወይኑም ፡ መጥመቂያ ፡ ከከተማ ፡ ውጭ ፡ ተረገጠ ፥ እስከፈረሶች ፡ ልጓምም ፡ የሚደርስ ፡ ደም ፡ ርቀቱ ፡ ሺሕ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ምዕራፍ ፡ ኾኖ ፡ ከመጥመቂያው ፡ ወጣ ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 15 ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 1 ፤ ሌላም ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ምልክት ፡ በሰማይ ፡ አየኹ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ በእነርሱ ፡ ስለሚፈጸም ፡ ኻለኞቹን ፡ ሰባት ፡ መቅሠፍቶች ፡ የያዙ ፡ ሰባት ፡ መላእክት ፡ ታዩ ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 2 ፤ በእሳትም ፡ የተቀላቀለውን ፡ የብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ የሚመስለውን ፡ አየኹ ፥ በአውሬውና ፡ በምስሉም ፡ በስሙም ፡ ቍጥር ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ የነበሩት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በገና ፡ ይዘው ፡ በብርጭቆ ፡ ባሕር ፡ ላይ ፡ ሲቆሙ ፡ አየኹ ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 3-4 ፤ ፤ ሹሉን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ሥራኽ ፡ ታላቅና ፡ ድንቅ ፡ ነው ፤ የአሕዛብ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፥ መንገድኽ ፡ ጻድቅና ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፤ ጌታ ፡ ሆይ ፥ የማይፈራኽና ፡ ስምኽን ፡ የማያከብር ፡ ማን ፡ ነው ፧ አንተ ፡ ብቻ ፡ ቅዱስ ፡ ነኽና ፥ የጽድቅም ፡ ሥራኽ ፡ ስለ ፡ ተገለጠ ፡ አሕዛብ ፡ ሹሉ ፡ ይመጣሉ ፡ በፊትኽም ፡ ይሰግዳሉ ፡ እያሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ባሪያ ፡ የሙሴን ፡ ቅኔና ፡ የበጉን ፡ ቅኔ ፡ ይዘምራሉ ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 5 ፤ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አየኹ ፥ የምስክርም ፡ ድንኳን ፡ መቅደስ ፡ በሰማይ ፡ ተከፈተ ፥

ራእ. ፡ 15 ፡ 6 ፤ ሰባቱንም ፡ መቅሠፍት ፡ የያዙ ፡ ሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ከመቅደሱ ፡ ወጡ ፤ ከተልባ ፡ እግርም ፡ የተሠራ ፡ ጥሩ ፡ የጌጥ ፡ ልብስ ፡ ለበሱ ፡ ደረታቸውንም ፡ በወርቅ ፡ መታጠቂያ ፡ ታጠቁ ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 7 ፤ ከአራቱም ፡ እንስሳዎች ፡ አንዱ ፡ ከዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ድረስ ፡ የሚኖር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የሞላባቸውን ፡ ሰባት ፡ የወርቅ ፡ ጽዋዎች ፡ ለሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ሰጣቸው ።

ራእ. ፡ 15 ፡ 8 ፤ ከእግዚአብሔርም ፡ ክብርና ፡ ከኀይሉ ፡ ጢስ ፡ በመቅደሱ ፡ ሞላበት ፥ የሰባቱ ፡ መላእክት ፡ ሰባቱ ፡ መቅሠፍት ፡ እስኪፈጸሙ ፡ ድረስ ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ አልቻለም ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 16 ። _____

ራእ. ፡ 16 ፡ 1 ፤ ለሰባቱም ፡ መላእክት ፦ ኼዳችኹ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍጣ ፡ ጽዋዎች ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ አፍሱ ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ከመቅደሱ ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 2 ፤ ፊተኛውም ፡ ኼዶ ፡ ጽዋውን ፡ በምድር ፡ ውስጥ ፡ አፈሰሰ ፤ የአውሬውም ፡ ምልክት ፡ ባለባቸው ፡ ለምስሉም ፡ በሚሰግዱ ፡ ሰዎች ፡ ክፉኛ ፡ የሚነዘንዝ ፡ ቍስል ፡ ኾነባቸው ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 3 ፤ ኹለተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በባሕር ፡ ውስጥ ፡ አፈሰሰ ፤ እንደ ፡ ሞተም ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ኾነ ፥ በባሕርም ፡ ከሚኖሩት ፡ ሕይወት ፡ ያለበት ፡ ነፍስ ፡ ሹሉ ፡ ሞተ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 4 ፤ ሦስተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በወንዞችና ፡ በውሃ ፡ ምንጮች ፡ ውስጥ ፡ አፈሰሰ ፤ እነርሱም ፡ ደም ፡ ኾኑ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 5 ፤ የውሃውም ፡ መልአክ ፦ ያለኽና ፡ የነበርኽ ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፥ ቅዱስ ፡ ሆይ ፥ እንዲህ ፡ ስለፈረድኽ ፡ ጻድቅ ፡ ነኽ ፤

ራእ. ፡ 16 ፡ 6 ፤ የቅዱሳንና ፡ የነቢያትን ፡ ደም ፡ ስላፈሰሱ ፡ ደምን ፡ ደግሞ ፡ አጠጥተኻቸዋል ፥ የሚገባቸው ፡ ነውና ፥ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 7 ፤ ከመሠዊያውም ፦ አዎን ፥ ሹሉን ፡ የምትገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፥ ፍርዶችኽ ፡ እውነትና ፡ ጽድቅ ፡ ናቸው ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 8 ፤ አራተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በፀሓይ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፤ ሰዎችንም ፡ በእሳት ፡ ልታቃጥል ፡ ተሰጣት ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 9 ፤ ሰዎችም ፡ በታላቅ ፡ ትኵሳት ፡ ተቃጠሉ ፥ በነዚህም ፡ መቅሠፍቶች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ተሳደቡ ፥ ክብርንም ፡ እንዲሰጡት ፡ ንስሓ ፡ አልገቡም ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 10 ፤ ዐምስተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በአውሬው ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፤ መንግሥቱም ፡ ጨለማ ፡ ኾነች ፡ ከሥቃይም ፡ የተነሣ ፡ ምላሶቻቸውን ፡ ያኝኩ ፡ ነበር ፥

ራእ. ፡ 16 ፡ 11 ፤ ከሥቃያቸውና ፡ ከቍስላቸውም ፡ የተነሣ ፡ የሰማይን ፡ አምላክ ፡ ተሳደቡ ፥ ከሥራቸውም ፡ ንስሓ ፡ አልገቡም ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 12 ፤ ስድስተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በታላቁ ፡ ወንዝ ፡ በኤፍራጥስ ፡ ላይ ፡ አፈሰሰ ፤ ከፀሓይም ፡ መውጫ ፡ ለሚመጡ ፡ ነገሥታት ፡ መንገድ ፡ እንዲሰናዳላቸው ፡ ውሃው ፡ ደረቀ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 13 ፤ ከዘንዶውም ፡ አፍና ፡ ከአውሬው ፡ አፍ ፥ ከሐሰተኛውም ፡ ነቢይ ፡ አፍ ፡ ጓጕንቸሮች ፡ የሚመስሉ ፡ ሦስት ፡ ርኩሳን ፡ መናፍስት ፡ ሲወጡ ፡ አየኹ ፤

ራእ. ፡ 16 ፡ 14 ፤ ምልክት ፡ እያደረጉ ፡ የአጋንንት ፡ መናፍስት ፡ ናቸውና ፥ በታላቁም ፡ ኹሉን ፡ በሚገዛ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ወደሚኾነው ፡ ጦር ፡ እንዲያስከትቷቸው ፡ ወደዓለም ፡ ኹሉ ፡ ነገሥታት ፡ ይወጣሉ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 15 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ሌባ ፡ ኾኜ ፡ እመጣለኹ ፤ ዕራቍቱን ፡ እንዳይኼድ ፡ ዕፍረቱንም ፡ እንዳያዩ ፡ ነቅቶ ፡ ልብሱን ፡ የሚጠብቅ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 16 ፤ በዕብራይስጥም ፡ አርማጌዶን ፡ ወደሚባል ፡ ስፍራ ፡ አስከተቷቸው ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 17 ፤ ሰባተኛውም ፡ ጽዋውን ፡ በአየር ፡ ውስጥ ፡ አፈሰሰ ፤ ከመቅደሱም ፡ ውስጥ ። ተፈጽሟል ፡ የሚል ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ከዙፋኑ ፡ ወጣ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 18 ፤ መብረቅና ፡ ድምፅም ፡ ነጐድጓድም ፡ ኾኑ ፥ ትልቅም ፡ የምድር ፡ መናወጥ ፡ ኾነ ፤ ሰው ፡ በምድር ፡ ከተፈጠረ ፡ ዠምሮ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ መናወጥ ፡ ከቶ ፡ አልነበረም ፤ ከኹሉ ፡ በለጠ ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 19 ፤ ታላቂቱም ፡ ከተማ ፡ በሦስት ፡ ተከፋፈለች ፥ የአሕዛብም ፡ ከተማዎች ፡ ወደቁ ። ታላቂቱም ፡ ባቢሎን ፡ የብርቱ ፡ ቍጣው ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የሞላበትን ፡ ጽዋ ፡ እንዲሰጣት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ታሰበች ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 20 ፤ ደሴቶችም ፡ ኹሉ ፡ ሸሹ ፡ ተራራዎችም ፡ አልተገኙም ።

ራእ. ፡ 16 ፡ 21 ፤ በሚዛንም ፡ አንድ ፡ ታላንት ፡ [*] ፡ የሚያኽል ፡ ታላቅ ፡ በረዶ ፡ በሰዎች ፡ ላይ ፡ ከሰማይ ፡ ወረደባቸው ፤ ሰዎቹም ፡ ከበረዶው ፡ መቅሠፍት ፡ የተነሣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ተሳደቡ ፥ መቅሠፍቱ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ።

[*] ፤ አንድ ፡ ታላንት ፡ ሦስት ፡ ፈረሱላ ፡ የሚያኽል ፡ ነው ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 17 ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 1 ፤ ሰባቱንም ፡ ጽዋዎች ፡ ከያዙ ፡ ከሰባቱ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፦ ና ፡ በብዙም ፡ ውሃዎች ፡ ላይ ፡ የተቀመጠችውን ፡ የታላቂቱን ፡ ጋለሞታ ፡ ፍርድ ፡ አሳይኻለኹ ፤

ራእ. ፡ 17 ፡ 2 ፤ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ሴሰኑ ፡ በምድርም ፡ የሚኖሩ ፡ ከዝሙቷ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ሰከሩ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 3 ፤ በመንፈስም ፡ ወደ ፡ በረሓ ፡ ወሰደኝ ፤ የስድብም ፡ ስሞች ፡ በሞሉበት ፥ ሰባት ፡ ራሶችና ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶችም ፡ ባሉበት ፡ በቀይ ፡ አውሬ ፡ ላይ ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ተቀምጣ ፡ አየኹ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 4 ፤ ሴቲቱም ፡ በቀይና ፡ በሐምራዊ ፡ ልብስ ፡ ተጐናጽፋ ፡ በወርቅና ፡ በከበሩ ፡ ድንጋዮች ፡ በዕንቊዎችም ፡ ተሸልማ ፡ ነበር ፥ በእጇም ፡ የሚያስጸይፍ ፡ ነገር ፡ የዝሙቷም ፡ ርኵሰት ፡ የሞላባትን ፡ የወርቅ ፡ ጽዋ ፡ ያዘች ፤

ራእ. ፡ 17 ፡ 5 ፤ በግንባሯም ፡ ምስጢር ፡ የኾነ ፡ ስም ፦ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፥ የጋለሞታዎችና ፡ የምድር ፡ ርኵሰት ፡ እናት ፡ ተብሎ ፡ ተጻፈ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 6 ፤ ሴቲቱም ፡ በቅዱሳን ፡ ደምና ፡ በኢየሱስ ፡ ምስክሮች ፡ ደም ፡ ሰክራ ፡ አየኋት ። ባየኋትም ፡ ጊዜ ፡

እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ድንቅ ፡ አደነቅኹ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 7 ፤ መልአኩም ፡ አለኝ ፦ የምትደነቅ ፡ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ የሴቲቱን ፡ ምስጢርና ፡ የሚሸከማትን ፥ ሰባት ፡ ራሶችና ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶች ፡ ያሉትን ፡ የአውሬውን ፡ ምስጢር ፡ እኔ ፡ እነግርኻለኹ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 8 ፤ ያየኸው ፡ አውሬ ፡ አስቀድሞ ፡ ነበረ ፥ አኹንም ፡ የለም ፥ ከጥልቁም ፡ ይወጣ ፡ ዘንድ ፡ አለው ፥ ወደ ፡ ጥፋትም ፡ ይኼዳል ፤ ስሞቻቸውም ፡ ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ ዠምሮ ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ያልተጻፉ ፡ በምድር ፡ የሚኖሩ ፡ አውሬው ፡ አስቀድሞ ፡ እንደነበረ ፡ አኹንም ፡ እንደሌለ ፥ ነገር ፡ ግን ፥ እንዳለ ፡ ሲያዩ ፡ ያደንቃሉ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 9 ፤ ጥበብ ፡ ያለው ፡ አእምሮ ፡ በዚህ ፡ ነው ። ሰባቱ ፡ ራሶች ፡ ሴቲቱ ፡ የተቀመጠችባቸው ፡ ሰባት ፡ ተራራዎች ፡ ናቸው ፥

ራእ. ፡ 17 ፡ 10 ፤ ሰባት ፡ ነገሥታት ፡ ደግሞ ፡ ናቸው ፤ ዐምስቱ ፡ ወድቀዋል ፡ አንዱም ፡ አለ ፥ የቀረውም ፡ ገና ፡ አልመጣም ፤ ሲመጣም ፥ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ሊቈይ ፡ ይገባዋል ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 11 ፤ የነበረውና ፡ የሌለውም ፡ አውሬ ፡ ራሱ ፡ ደግሞ ፡ ስምንተኛው ፡ ነው ፥ ከሰባቱም ፡ አንዱ ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ጥፋትም ፡ ይኼዳል ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 12 ፤ ያየኻቸውም ፡ ዐሥሩ ፡ ቀንዶች ፡ ገና ፡ መንግሥትን ፡ ያልተቀበሉ ፡ ዐሥር ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ ከአውሬው ፡ ጋራ ፡ ላንድ ፡ ሰዓት ፡ እንደ ፡ ነገሥታት ፡ ሥልጣንን ፡ ይቀበላሉ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 13 ፤ እነዚህ ፡ አንድ ፡ ዐሳብ ፡ አላቸው ፥ ኀይላቸውንና ፡ ሥልጣናቸውንም ፡ ለአውሬው ፡ ይሰጣሉ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 14 ፤ እነዚህ ፡ በጉን ፡ ይወጋሉ ፤ በጉም ፡ የጌታዎች ፡ ጌታና ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ እነርሱን ፡ ድል ፡ ይነሣል ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ያሉ ፡ የተጠሩና ፡ የተመረጡ ፡ የታመኑም ፡ ደግሞ ፡ ድል ፡ ይነሣሉ ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 15 ፤ አለኝም ፦ ጋለሞታዪቱ ፡ የተቀመጠችባቸው ፡ ያየኻቸው ፡ ውሃዎች ፥ ወገኖችና ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሕዛብም ፡ ቋንቋዎችም ፡ ናቸው ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 16 ፤ ያየኻቸውም ፡ ዐሥር ፡ ቀንዶችና ፡ አውሬው ፡ ጋለሞታዪቱን ፡ ይጣላሉ ፤ ባዶዋንና ፡ ዕራቍቷንም ፡ ያደርጓታል ፥ ሥጋዋንም ፡ ይበላሉ ፥ በእሳትም ፡ ያቃጥሏታል ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 17 ፤ እግዚአብሔር ፡ ዐሳቡን ፡ እንዲያደርጉ ፡ አንድንም ፡ ዐሳብ ፡ እንዲያደርጉ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ መንግሥታቸውን ፡ ለአውሬው ፡ እንዲሰጡ ፡ በልባቸው ፡ አግብቷልና ።

ራእ. ፡ 17 ፡ 18 ፤ ያየኻትም ፡ ሴት ፡ በምድር ፡ ነገሥታት ፡ ላይ ፡ የምትነግሥ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ናት ።

የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 18 ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 1 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየኹ ፥ ከክብሩም ፡ የተነሣ ፡ ምድር ፡ በራች ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 2 ፤ በብርቱም ፡ ድምፅ ፦ ታላቂቱ ፡ ባቢሎን ፡ ወደቀች ፥ ወደቀች ፥ የአጋንንትም ፡ ማደሪያ ፡ ኾነች ፥ የርኩሳንም ፡ መናፍስት ፡ ኹሉ ፡ መጠጊያ ፥ የርኩሳንና ፡ የተጠሉም ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፡ መጠጊያ ፡ ኾነች ፤

ራእ. ፡ 18 ፡ 3 ፤ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ከዝሙቷ ፡ ቀሣጣ ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ የተነሣ ፡ ወድቀዋልና ፥ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ከርሷ ፡ ጋራ ፡ ሴሰኑ ፡ የምድርም ፡ ነጋዴዎች ፡ ከቅምጥልነቷ ፡ ኀይል ፡ የተነሣ ፡ ባለጠጋዎች ፡ ኾኑ ፡ ብሎ ፡ ጮኸ ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 4 ፤ ከሰማይም ፡ ሌላ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ሕዝቤ ፡ ሆይ ፥ በኀጢአቷ ፡ እንዳትተባበሩ ፡

ከመቅሠፍቷም ፡ እንዳትቀበሉ ፡ ከርሷ ፡ ዘንድ ፡ ውጡ ፤

ራእ. ፡ 18 ፡ 5 ፤ ኀጢአቷ ፡ እስከ ፡ ሰማይ ፡ ድረስ ፡ ደርሷልና ፥ እግዚአብሔርም ፡ ዐመፃዋን ፡ ዐሰበ ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 6 ፤ ርሷ ፡ እንደ ፡ ሰጠች ፡ መጠን ፡ ብድራት ፡ መልሱላት ፥ እንደ ፡ ሥራዋም ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ ደርቡባት ፤ በቀላቀለችው ፡ ጽዋ ፡ ኹለት ፡ ዕጥፍ ፡ አድርጋችኹ ፡ ቀላቅሉባት ፤

ራእ. ፡ 18 ፡ 7 ፤ ራሷን ፡ እንደ ፡ አከበረችና ፡ እንደ ፡ ተቀማጠለች ፡ ልክ ፡ ሥቃይና ፡ ሐዘን ፡ ስጧት ። በልቧ ፦ ንግሥት ፡ ኾኜ ፡ እቀመጣለኹ ፡ ባልቴትም ፡ አልኾንም ፡ ሐዘንም ፡ ከቶ ፡ አላይም ፡ ስለ ፡ አለች ፥

ራእ. ፡ 18 ፡ 8 ፤ ስለዚህ ፥ ባንድ ፡ ቀን ፡ ሞትና ፡ ሐዘን ፣ ራብም ፡ የኾኑ ፡ መቅሠፍቶቿ ፡ ይመጣሉ ፥ በእሳትም ፡ ትቃጠላለች ፤ የሚፈርድባት ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርቱ ፡ ነውና ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 9 ፤ ከርሷም ፡ ጋራ ፡ የሴሰኑና ፡ የተቀማጠሉ ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ የመቃጠሏን ፡ ጢስ ፡ ሲያዩ ፡ ስለ ፡ ርሷ ፡ ዋይ ፡ ዋይ ፡ እያሉ ፡ ያለቅሳሉ ፤

ራእ. ፡ 18 ፡ 10 ፤ ሥቃይዋንም ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ በሩቅ ፡ ቆመው ። አንቺ ፡ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፥ ብርቱዪቱ ፡ ከተማ ፡ ባቢሎን ፥ ወዮልሽ ፥ ወዮልሽ ፥ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ፍርድሽ ፡ ደርሷልና ፥ እያሉ ፡ ይናገራሉ ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 11 ፤ የመርከባቸውንም ፡ ጭነት ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ የሚገዛ ፡ የለምና ፡ የምድር ፡ ነጋዴዎች ፡ ያለቅሱላታል ፥ ያዝኑላትማል ፤

ራእ. ፡ 18 ፡ 12 ፤ ጭነትም ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ የከበረም ፡ ድንጋይ ፡ ዕንቊም ፥ ቀጭንም ፡ ተልባ ፡ እግር ፡ ቀይም ፡ ሐርም ፡ ሐምራዊም ፡ ልብስ ፡ የሚሸትም ፡ ዕንጨት ፡ ሹሉ ፥ ከዝሆን ፡ ጥርስም ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፥ እጅግም ፡ ከከበረ ፡ ዕንጨት ፡ ከናስም ፡ ከብረትም ፡ ከእብነ ፡ በረድም ፡ የተሠራ ፡ ዕቃ ፡ ሹሉ ፥

ራእ. ፡ 18 ፡ 13 ፤ ቀረፋም ፡ ቅመምም ፡ የሚቃጠልም ፡ ሽቱ ፡ ቅባትም ፡ ዕጣንም ፡ የወይን ፡ ጠጅም ፡ ዘይትም ፡ የተሰለቀ ፡ ዱቄትም ፡ ስንዴም ፡ ከብትም ፡ በግም ፡ ፈረስም ፡ ሠረገላም ፡ ባሪያዎችም ፡ የሰዎችም ፡ ነፍሳት ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 14 ፤ ነፍስሽም ፡ የጐመዠችው ፡ ፍሬ ፡ ከአንቺ ፡ ዘንድ ፡ ዐልፏል ፥ የሚቀማጠልና ፡ የሚያጌጥም ፡ ነገር ፡ ሹሉ ፡ ጠፍቶብሻል ፥ ሰዎችም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ከቶ ፡ አያገኟቸውም ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 15-17 ፤ እነዚህን ፡ የነገዱ ፡ በርሷም ፡ ባለጠጋዎች ፡ የኾኑት ፡ እያለቀሱና ፡ እያዘኑ ፦ በቀጭን ፡ ተልባ ፡ እግርና ፡ በቀይ ፡ ሐምራዊም ፡ ልብስ ፡ ለተጐናጸፈች ፡ በወርቅና ፡ በከበረ ፡ ድንጋይም ፡ በዕንቊም ፡ ለተሸለመች ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወዮላት ፥ ወዮላት ፥ ይህን ፡ የሚያኽል ፡ ታላቅ ፡ ባለጠግነት ፡ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ጠፍቷልና ፥ እያሉ ፡ ሥቃይዋን ፡ ከመፍራት ፡ የተነሣ ፡ በሩቅ ፡ ይቆማሉ ። የመርከብም ፡ መሪ ፡ ሹሉ ፡ በመርከብም ፡ ወደ ፡ ማናቸውም ፡ ስፍራ ፡ የሚኼድ ፡ ሹሉ ፡ መርከበኞችም ፡ ከባሕርም ፡ የሚጠቀሙ ፡ ሹሉ ፡ በሩቅ ፡ ቆሙ ፥

ራእ. ፡ 18 ፡ 18 ፤ የመቃጠሏንም ፡ ጢስ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፦ ታላቂቱን ፡ ከተማ ፡ የምትመስላት ፡ ምን ፡ ከተማ ፡ ነበረች ፧ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 19 ፤ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ ትቢያ ፡ ነስንሰው ፡ እያለቀሱና ፡ እያዘኑ ፦ በባሕር ፡ መርከቦች ፡ ያሏቸውን ፡ ሹሉ ፡ ከባለጠግነቷ ፡ የተነሣ ፡ ባለጠጋዎች ፡ ላደረገች ፡ ለታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ወዮላት ፥ ወዮላት ፥ ባንድ ፡ ሰዓት ፡ ጠፍታለችና ፡ እያሉ ፡ ጮኹ ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 20 ፤ ሰማይ ፡ ሆይ ፥ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ፡ ነቢያትም ፡ ሆይ ፥ በርሷ ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ ይበላችኹ ፥ እግዚአብሔር ፡ ፈርዶላችኋልና ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 21 ፤ አንድም ፡ ብርቱ ፡ መልአክ ፡ ትልቅን ፡ ወፍጮ ፡ የሚመስልን ፡ ድንጋይ ፡ አንሥቶ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡

ወረወረው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ታላቂቱ ፡ ከተማ ፡ ባቢሎን ፡ እንዲህ ፡ ተገፍታ ፡ ትወድቃለች ፡ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ከቶ ፡ አትገኝም ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 22 ፤ በገና ፡ የሚመቱና ፡ የሚዘምሩም ፡ ድምፅ ፡ እንቢልታንና ፡ መለከትንም ፡ የሚነፉ ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፥ የእጅ ፡ ጥበብም ፡ ዅሉ ፡ አንድ ፡ ብልኀተኛ ፡ እንኳ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይገኝም ፥ የወፍጮ ፡ ድምፅም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፥

ራእ. ፡ 18 ፡ 23 ፤ የመብራትም ፡ ብርሃን ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይበራም ፥ የሙሽራና ፡ የሙሽራዪቱም ፡ ድምፅ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ ባንቺ ፡ ውስጥ ፡ ከቶ ፡ አይሰማም ፤ ነጋዴዎችሽ ፡ የምድር ፡ መኳንንት ፡ ነበሩና ፥ በአስማትሽም ፡ አሕዛብ ፡ ዅሉ ፡ ስተዋልና ።

ራእ. ፡ 18 ፡ 24 ፤ በርሷም ፡ ውስጥ ፡ የነቢያትና ፡ የቅዱሳን ፡ ደም ፡ በምድርም ፡ የታረዱ ፡ ዅሉ ፡ ደም ፡ ተገኝባት ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 19 ። _____

ራእ. ፡ 19 ፡ 1-2 ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ በሰማይ ፦ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ በዝሙታ ፡ ምድርን ፡ ያጠፋችዪቱን ፡ ታላቂቱን ፡ ጋለሞታ ፡ ስለ ፡ ፈረደባት ፥ የባሪያዎቹንም ፡ ደም ፡ ከእጇ ፡ ስለ ፡ ተበቀለ ፥ ፍርዶቹ ፡ እውነትና ፡ ጽድቅ ፡ ናቸውና ፥ ማዳንና ፡ ክብር ፡ ኀይልም ፡ የአምላካችን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ ታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ያለ ፡ ድምፅን ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 3 ፤ ደግመውም ፦ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ አሉ ፤ ጢሷም ፡ ለዘለዓለም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይወጣል ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 4 ፤ ኻያ ፡ አራቱም ፡ ሽማግሌዎችና ፡ አራቱ ፡ እንስሳዎች ፡ በፊታቸው ፡ ተደፍተው ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ለተቀመጠው ፡ ለእግዚአብሔር ፦ አሜን ፥ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ እያሉ ፡ ሰገዱለት ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 5 ፤ ድምፅም ፦ ባሪያዎቹ ፡ ዅሉ ፡ ርሱንም ፡ የምትፈሩት ፡ ታናናሾችና ፡ ታላላቆች ፡ ሆይ ፥ አምላካችንን ፡ አመስግኑ ፡

ራእ. ፡ 19 ፡ 6 ፤ ሲል ፡ ከዙፋኑ ፡ ወጣ ። እንደ ፡ ብዙ ፡ ሕዝብም ፡ ድምፅ ፥ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ ድምፅ ፥ እንደ ፡ ብርቱም ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምፅ ፡ ያለ ፡ ድምፅ ፡ ሰማኹ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፦ ሃሌ ፡ ሉያ ፤ ዅሉን ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላካችን ፡ ነግሧልና ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 7 ፤ የበጉ ፡ ሰርግ ፡ ስለ ፡ ደረሰ ፡ ሚስቱም ፡ ራሷን ፡ ስላዘጋጀች ፡ ደስ ፡ ይበለን ፡ ሐሤትም ፡ እናድርግ ፡ ክብርንም ፡ ለርሱ ፡ እናቅርብ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 8 ፤ ያጌጠና ፡ የተጣራ ፡ ቀጭን ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡ እንድትጐናጸፍ ፡ ተሰጥቷታል ። ቀጭኑ ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ የቅዱሳን ፡ ጽድቅ ፡ ሥራ ፡ ነውና ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 9 ፤ ርሱም ፦ ወደበጉ ፡ ሰርግ ፡ እራት ፡ የተጠሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ብለኽ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ። ደግሞም ፦ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ አለኝ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 10 ፤ ልሰግድለትም ፡ በእግሩ ፡ ፊት ፡ ተደፋኹ ። ርሱም ፦ እንዳታደርገው ፡ ተጠንቀቅ ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የኢየሱስም ፡ ምስክር ፡ ካላቸው ፡ ከወንድሞችኽ ፡ ጋራ ፡ ዐብሬ ፡ ባሪያ ፡ ነኝ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ስገድ ፤ የኢየሱስ ፡ ምስክር ፡ የትንቢት ፡ መንፈስ ፡ ነውና ፥ አለኝ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 11 ፤ ሰማይም ፡ ተከፍቶ ፡ አየኹ ፥ እንሆም ፡ ዐምባላይ ፡ ፈረስ ፥ የተቀመጠበትም ፡ የታመነና ፡ እውነተኛ ፡ ይባላል ፥ በጽድቅም ፡ ይፈርዳል ፡ ይዋጋልም ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 12 ፤ ዐይኖቹም ፡ እንደ ፡ እሳት ፡ ነበልባል ፡ ናቸው ፥ በራሱ ፡ ላይም ፡ ብዙ ፡ ዘውዶች ፡ አሉ ፥ ከርሱም ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ እንኳ ፡ የማያውቀው ፡ የተጻፈ ፡ ስም ፡ አለው ፤

ራእ. ፡ 19 ፡ 13 ፤ በደምም ፡ የተረጨ ፡ ልብስ ፡ ተጐናጽፏል ፥ ስሙም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተብሏል ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 14 ፤ በሰማይም ፡ ያሉት ፡ ጭፍራዎች ፡ ነጭና ፡ ጥሩ ፡ ቀጭን ፡ የተልባ ፡ እግር ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ በፀምባላዮች ፡ ፈረሶች ፡ ተቀምጠው ፡ ይከተሉት ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 15 ፤ አሕዛብንም ፡ ይመታበት ፡ ዘንድ ፡ ስለታም ፡ ሰይፍ ፡ ከአፉ ፡ ይወጣል ፤ ርሱም ፡ በብረት ፡ በትር ፡ ይገዛቸዋል ፤ ርሱም ፡ ኹሉን ፡ የሚገዛ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የብርቱ ፡ ቍጣውን ፡ ወይን ፡ መጥመቂያ ፡ ይረግጣል ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 16 ፤ በልብሱና ፡ በጭኑም ፡ የተጻፈበት ፦ የነገሥታት ፡ ንጉሥና ፡ የጌታዎች ፡ ጌታ ፡ የሚል ፡ ስም ፡ አለው ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 17-18 ፤ አንድም ፡ መልአክ ፡ በፀሓይ ፡ ውስጥ ፡ ቆሞ ፡ አየኹ ፥ በሰማይም ፡ መካከል ፡ ለሚበሩ ፡ ወፎች ፡ ኹሉ ፦ መጥታችኹ ፡ የነገሥታትን ፡ ሥጋና ፡ የሻለቃዎችን ፡ ሥጋ ፡ የብርቱዎችንም ፡ ሥጋ ፡ የፈረሶችንም ፡ በእነርሱም ፡ የተቀመጡትን ፡ ሥጋ ፡ የጌታዎችንና ፡ የባሪያዎችንም ፡ የታናናሾችንና ፡ የታላላቆችንም ፡ ኹሉ ፡ ሥጋ ፡ እንድትበሉ ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ወደእግዚአብሔር ፡ እራት ፡ ተከማቹ ፡ ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምፅ ፡ ጮኸ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 19 ፤ በፈረሱም ፡ የተቀመጠውን ፡ ጭፍራዎቹንም ፡ ይወጉ ፡ ዘንድ ፡ አውሬውና ፡ የምድር ፡ ነገሥታት ፡ ጭፍራዎቻቸውም ፡ ተከማችተው ፡ አየኹ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 20 ፤ አውሬውም ፡ ተያዘ ፡ በርሱም ፡ ፊት ፡ ተአምራትን ፡ እያደረገ ፡ የአውሬውን ፡ ምልክት ፡ የተቀበሉትን ፡ ለምስሉም ፡ የሰገዱትን ፡ ያሳተ ፡ ሐሰተኛው ፡ ነቢይ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተያዘ ፤ ኹለቱም ፡ በሕይወት ፡ ሳሉ ፡ በዲን ፡ ወደሚቃጠል ፡ ወደእሳት ፡ ባሕር ፡ ተጣሉ ።

ራእ. ፡ 19 ፡ 21 ፤ የቀሩትም ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ከተቀመጠው ፡ ከአፉ ፡ በሚወጣው ፡ ሰይፍ ፡ ተገደሉ ፤ ወፎችም ፡ ኹሉ ፡ ከሥጋቸው ፡ ጠገቡ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 20 ። _____

ራእ. ፡ 20 ፡ 1 ፤ የጥልቁንም ፡ መክፈቻና ፡ ታላቁን ፡ ሰንሰለት ፡ በእጁ ፡ የያዘ ፡ መልአክ ፡ ከሰማይ ፡ ሲወርድ ፡ አየኹ ።

ራእ. ፡ 20 ፡ 2 ፤ የቀደመውንም ፡ እባብ ፡ ዘንዶውን ፡ ርሱም ፡ ዲያብሎስና ፡ ሰይጣን ፡ የተባለውን ፡ ያዘው ፥

ራእ. ፡ 20 ፡ 3 ፤ ሺሕ ፡ ዓመትም ፡ አሰረው ፥ ወደ ፡ ጥልቅም ፡ ጣለው ፡ አሕዛብንም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ እንዳያስት ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ዘግቶ ፡ ማኅተም ፡ አደረገበት ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይገባዋል ።

ራእ. ፡ 20 ፡ 4 ፤ ዙፋኖችንም ፡ አየኹ ፥ በእነርሱም ፡ ላይ ፡ ለተቀመጡት ፡ ዳኝነት ፡ ተሰጣቸው ፤ ስለኢየሱስም ፡ ምስክርና ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ራሶቻቸው ፡ የተቈረጡባቸውን ፡ ሰዎች ፡ ነፍሳት ፥ ለአውሬውና ፡ ለምስሉም ፡ ያልሰገዱትን ፡ ምልክቱንም ፡ በግንባራቸው ፡ በእጆቻቸውም ፡ ላይ ፡ ያልተቀበሉትን ፡ አየኹ ፤ ከክርስቶስም ፡ ጋራ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ኖሩና ፡ ነገሡ ።

ራእ. ፡ 20 ፡ 5 ፤ የቀሩቱ ፡ ሙታን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ እስኪፈጸም ፡ ድረስ ፡ በሕይወት ፡ አልኖሩም ። ይህ ፡ የፊተኛው ፡ ትንሣኤ ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 20 ፡ 6 ፤ በፊተኛው ፡ ትንሣኤ ፡ ዕድል ፡ ያለው ፡ ብፁዕና ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፤ ኹለተኛው ፡ ሞት ፡ በእነርሱ ፡

ላይ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፥ ዳሩ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የክርስቶስ ፡ ካህናት ፡ ይኾናሉ ፥ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ይህን ፡ ሺሕ ፡ ዓመት ፡ ይነግሣሉ ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 7 ፤ ሺሑም ፡ ዓመት ፡ ሲፈጸም ፡ ሰይጣን ፡ ከእስራቱ ፡ ይፈታል ፥

ራእ. ፥ 20 ፥ 8 ፤ በአራቱም ፡ በምድር ፡ ማእዘን ፡ ያሉትን ፡ አሕዛብ ፥ ጎግንና ፡ ማጎግን ፥ እንዲያስታቸው ፡ ለሰልፍም ፡ እንዲያስከትታቸው ፡ ይወጣል ፤ ቍጥራቸውም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ የሚያኽል ፡ ነው ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 9 ፤ ወደምድርም ፡ ስፋት ፡ ወጡ ፡ የቅዱሳንንም ፡ ሰፈርና ፡ የተወደደችውን ፡ ከተማ ፡ ከበቡ ፤ እሳትም ፡ ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ወርዳ ፡ በላቻቸው ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 10 ፤ ያሳታቸውም ፡ ዲያብሎስ ፡ አውሬውና ፡ ሐሰተኛው ፡ ነቢይ ፡ ወዳሉበት ፡ ወደእሳቱና ፡ ወደዲኑ ፡ ባሕር ፡ ተጣለ ፥ ለዘለዓለምም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ቀንና ፡ ሌሊት ፡ ይሣቀያሉ ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 11 ፤ ታላቅና ፡ ነጭ ፡ ዙፋንን ፡ በርሱም ፡ ላይ ፡ የተቀመጠውን ፡ አየኹ ፥ ምድርና ፡ ሰማይም ፡ ከፊቱ ፡ ሸሹ ፡ ስፍራም ፡ አልተገኘላቸውም ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 12 ፤ ሙታንንም ፡ ታናናሾችንና ፡ ታላላቆችን ፡ በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ ቆመው ፡ አየኹ ፥ መጻሕፍትም ፡ ተከፈቱ ፤ ሌላ ፡ መጽሐፍም ፡ ተከፈተ ፡ ርሱም ፡ የሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ፤ ሙታንም ፡ በመጻሕፍት ፡ ተጽፎ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ሥራቸው ፡ መጠን ፡ ተከፈሉ ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 13 ፤ ባሕርም ፡ በርሱ ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ሙታን ፡ ሰጠ ፥ ሞትና ፡ ሲኦልም ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ ሙታን ፡ ሰጡ ፥ እያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ መጠን ፡ ተከፈለ ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 14 ፤ ሞትና ፡ ሲኦልም ፡ በእሳት ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ተጣሉ ። ይህም ፡ የእሳት ፡ ባሕር ፡ ኹለተኛው ፡ ሞት ፡ ነው ።

ራእ. ፥ 20 ፥ 15 ፤ በሕይወትም ፡ መጽሐፍ ፡ ተጽፎ ፡ ያልተገኘው ፡ ማንኛውም ፡ በእሳት ፡ ባሕር ፡ ውስጥ ፡ ተጣለ ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 21 ። _____

ራእ. ፥ 21 ፥ 1 ፤ ዐዲስ ፡ ሰማይንና ፡ ዐዲስ ፡ ምድርንም ፡ አየኹ ፥ ፊተኛው ፡ ሰማይና ፡ ፊተኛዪቱ ፡ ምድር ፡ ዐልፈዋልና ፥ ባሕርም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የለም ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 2 ፤ ቅድስቲቱም ፡ ከተማ ፡ ዐዲሲቱ ፡ ኢየሩሳሌም ፥ ለባሏ ፡ እንደተሸለመች ፡ ሙሽራ ፡ ተዘጋጅታ ፥ ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ስትወርድ ፡ አየኹ ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 3 ፤ ታላቅም ፡ ድምፅ ፡ ከሰማይ ፦ እንሆ ፥ የእግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ በሰዎች ፡ መካከል ፡ ነው ፥ ከነርሱም ፡ ጋራ ፡ ያድራል ፥ እነርሱም ፡ ሕዝቡ ፡ ይኾናሉ ፥ እግዚአብሔርም ፡ ርሱ ፡ ራሱ ፡ ከነርሱ ፡ ጋራ ፡ ኾኖ ፡ አምላካቸው ፡ ይኾናል ፤

ራእ. ፥ 21 ፥ 4 ፤ እንባዎችንም ፡ ዅሉ ፡ ከዐይኖቻቸው ፡ ያብሳል ፥ ሞትም ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኾንም ፥ ሐዘንም ፡ ቢኾን ፡ ወይም ፡ ጩኸት ፡ ወይም ፡ ሥቃይ ፡ ከእንግዲህ ፡ ወዲህ ፡ አይኾንም ፥ የቀደመው ፡ ሥርዐት ፡ ዐልፏልና ፥ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ ሰማኹ ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 5 ፤ በዙፋንም ፡ የተቀመጠው ፦ እንሆ ፥ ዅሉን ፡ ዐዲስ ፡ አደርጋለኹ ፡ አለ ። ለኔም ፦ እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ የታመኑና ፡ እውነተኞች ፡ ናቸውና ፥ ጻፍ ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 6 ፤ አለኝም ፦ ተፈጽሟል ። አልፋና ፡ ዖሜጋ ፥ መጀመሪያውና ፡ መጨረሻው ፡ እኔ ፡

ነኝ ። ለተጠማ ፡ ከሕይወት ፡ ውሃ ፡ ምንጭ ፡ እንዲያው ፡ እኔ ፡ እሰጣለኹ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 7 ፤ ድል ፡ የሚነሣ ፡ ይህን ፡ ይወርሳል ፡ አምላክም ፡ እኾነዋለኹ ፡ ርሱም ፡ ልጅ ፡ ይኾነኛል ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 8 ፤ ዳሩ ፡ ግን ፡ የሚፈሩና ፡ የማያምኑ ፡ የርኩሳንም ፡ የነፍሰ ፡ ገዳዮችም ፡ የሴሰኞችም ፡ የአስማተኞችም ፡ ጣዖትንም ፡ የሚያመልኩ ፡ የሐሰተኞችም ፡ ኹሉ ፡ ዕድላቸው ፡ በዲንና ፡ በእሳት ፡ በሚቃጠል ፡ ባሕር ፡ ነው ፤ ይኸውም ፡ ኹለተኛው ፡ ሞት ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 9 ፤ ሰባቱም ፡ ኺለኞች ፡ መቅሠፍቶች ፡ የሞሉባቸውን ፡ ሰባቱን ፡ ጽዋዎች ፡ ከያዙት ፡ ከሰባቱ ፡ መላእክት ፡ አንዱ ፡ መጥቶ ፦ ወደዚህ ፡ ና ፥ የበጉንም ፡ ሚስት ፡ ሙሽራዪቱን ፡ አሳይኻለኹ ፡ ብሎ ፡ ተናገረኝ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 10 - 11 ፤ በመንፈስም ፡ ወደ ፡ ታላቅና ፡ ወደ ፡ ረዥም ፡ ተራራ ፡ ወሰደኝ ፥ የእግዚአብሔርም ፡ ክብር ፡ ያለባትን ፡ ቅድስቲቱን ፡ ከተማ ፡ ኢየሩሳሌምን ፡ ከሰማይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ስትወርድ ፡ አሳየኝ ፤ ብርሃኗም ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ ከበረ ፡ ድንጋይ ፡ እንደ ፡ ኢያሰጲድ ፡ ድንጋይ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ የጠራ ፡ ነበረ ፤

ራእ. ፡ 21 ፡ 12 ፤ ታላቅና ፡ ረዥም ፡ ቅጥር ፡ ነበራት ፥ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ደጆች ፡ ነበሯት ፡ በደጆቹም ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መላእክት ፡ ቆሙ ፥ የዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ የእስራኤል ፡ ልጆች ፡ ነገዶች ፡ ስሞች ፡ ተጽፈውባቸው ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 13 ፤ በምሥራቅ ፡ ሦስት ፡ ደጆች ፥ በሰሜንም ፡ ሦስት ፡ ደጆች ፥ በደቡብም ፡ ሦስት ፡ ደጆች ፥ በምዕራብም ፡ ሦስት ፡ ደጆች ፡ ነበሩ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 14 ፤ ለከተማዪቱም ፡ ቅጥር ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ መሠረቶች ፡ ነበሯት ፥ በእነርሱም ፡ ውስጥ ፡ የዐሥራ ፡ ኹለቱ ፡ የበጉ ፡ ሐዋርያት ፡ ስሞች ፡ ተጽፈው ፡ ነበር ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 15 ፤ የተናገረኝም ፡ ከተማዪቱንና ፡ ደጆቿን ፡ ቅጥሯንም ፡ ይለካ ፡ ዘንድ ፡ የወርቅ ፡ ዘንግ ፡ ነበረው ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 16 ፤ ከተማዪቱም ፡ አራት ፡ ማእዘን ፡ ነበራት ፥ ርዝመቷም ፡ እንደ ፡ ስፋቷ ፡ ልክ ፡ ነበረ ። ከተማዪቱንም ፡ በዘንግ ፡ ለካት ፡ ዐሥራ ፡ ኹለትም ፡ ሺሕ ፡ ምዕራፍ ፡ ኾነች ፤ ርዝመቷና ፡ ስፋቷ ፡ ከፍታዋም ፡ ትክክል ፡ ነው ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 17 ፤ ቅጥሯንም ፡ ለካ ፥ መቶ ፡ አርባ ፡ አራት ፡ ክንድ ፡ በሰው ፡ ልክ ፥ ርሱም ፡ በመልአክ ፡ ልክ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 18 ፤ ቅጥሯም ፡ ከኢያሰጲድ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ፥ ከተማዪቱም ፡ ጥሩ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚመስል ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበረች ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 19 ፤ የከተማዪቱም ፡ ቅጥር ፡ መሠረት ፡ በከበረ ፡ ድንጋይ ፡ ኹሉ ፡ ተጌጦ ፡ ነበር ፤ ፊተኛው ፡ መሠረት ፡ ኢያሰጲድ ፥ ኹለተኛው ፡ ሰንፔር ፥ ሦስተኛው ፡ ኬልቄዶን ፥ አራተኛው ፡ መረግድ ፥

ራእ. ፡ 21 ፡ 20 ፤ ዐምስተኛው ፡ ሰርዶንክስ ፥ ስድስተኛው ፡ ሰርድዮን ፥ ሰባተኛው ፡ ክርስቲሎቤ ፥ ስምንተኛው ፡ ቢረሌ ፥ ዘጠነኛው ፡ ወራውሬ ፥ ዐሥረኛው ፡ ክርስጵራስስ ፥ ዐሥራ ፡ አንደኛው ፡ ያክንት ፥ ዐሥራ ፡ ኹለተኛው ፡ አሜቴስጢኖስ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 21 ፤ ዐሥራ ፡ ኹለቱም ፡ ደጆች ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ዕንቊዎች ፡ ነበሩ ፤ እያንዳንዱ ፡ ደጅ ፡ ካንድ ፡ ዕንቊ ፡ የተሠራ ፡ ነበረ ። የከተማዪቱም ፡ አደባባይ ፡ ጥሩ ፡ ብርጭቆ ፡ የሚመስል ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ነበረ ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 22 ፤ ኹሉንም ፡ የሚገዛ ፡ ጌታ ፡ አምላክና ፡ በጉ ፡ መቅደሷ ፡ ናቸውና ፥ መቅደስ ፡ በርሷ ፡ ዘንድ ፡ አላየኹም ።

ራእ. ፡ 21 ፡ 23 ፤ ለከተማዪቱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ስለሚያበራላት ፡ መብራቷም ፡ በጉ ፡ ስለ ፡

ኾነ ፥ ፀሓይ ፡ ወይም ፡ ጨረቃ ፡ እንዲያበሩላት ፡ አያስፈልጓትም ፡ ነበር ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 24 ፤ አሕዛብም ፡ በብርሃኗ ፡ ይመላለሳሉ ፥ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ክብራቸውን ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ያመጣሉ ፤

ራእ. ፥ 21 ፥ 25 ፤ በዚያም ፡ ሌሊት ፡ ስለሌለ ፡ ደጆቿ ፡ በቀን ፡ ከቶ ፡ አይዘጉም ፥

ራእ. ፥ 21 ፥ 26 ፤ የአሕዛብንም ፡ ግርማና ፡ ክብር ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ያመጣሉ ።

ራእ. ፥ 21 ፥ 27 ፤ ለበጉም ፡ በኾነው ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ በቀር ፥ ጸያፍ ፡ ነገር ፡ ኾሉ ፡ ርኵሰትና ፡ ውሸትም ፡ የሚያደርግ ፡ ወደ ፡ ርሷ ፡ ከቶ ፡ አይገባም ።

_____የዮሐንስ ፡ ራእይ ፥ ምዕራፍ ፡ 22 ። _____

ራእ. ፥ 22 ፥ 1 ፤ በአደባባይዋም ፡ መካከል ፡ ከእግዚአብሔርና ፡ ከበጉ ፡ ዙፋን ፡ የሚወጣውን ፡ እንደ ፡ ብርሌ ፡ የሚያንጸባርቀውን ፡ የሕይወትን ፡ ውሃ ፡ ወንዝ ፡ አሳየኝ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 2 ፤ በወንዙም ፡ ወዲያና ፡ ወዲህ ፡ በየወሩ ፡ እያፈራ ፡ ዐሥራ ፡ ኹለት ፡ ፍሬ ፡ የሚሰጥ ፡ የሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ነበረ ፥ የዛፉም ፡ ቅጠሎች ፡ ለሕዝብ ፡ መፈወሻ ፡ ነበሩ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 3 ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ መርገም ፡ ከቶ ፡ አይኾንም ። የእግዚአብሔርና ፡ የበጉም ፡ ዙፋን ፡ በርሷ ፡ ውስጥ ፡ ይኾናል ፥ ባሪያዎቹም ፡ ያመልኩታል ፥ ፊቱንም ፡ ያያሉ ፥

ራእ. ፥ 22 ፥ 4 ፤ ስሙም ፡ በግንባሮቻቸው ፡ ይኾናል ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 5 ፤ ከእንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ሌሊት ፡ አይኾንም ፥ ጌታ ፡ አምላክም ፡ በእነርሱ ፡ ላይ ፡ ያበራላቸዋልና ፥ የመብራት ፡ ብርሃንና ፡ የፀሓይ ፡ ብርሃን ፡ አያስፈልጋቸውም ፤ ለዘለዓለምም ፡ እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይነግሣሉ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 6 ፤ ርሱም ፦ እነዚህ ፡ ቃሎች ፡ የታመኑና ፡ እውነተኞች ፡ ናቸው ፥ የነቢያትም ፡ መናፍስት ፡ ጌታ ፡ አምላክ ፡ በቶሎ ፡ ሊኾን ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ለባሪያዎቹ ፡ እንዲያሳይ ፡ መልአኩን ፡ ሰደደ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 7 ፤ እንሆም ፥ በቶሎ ፡ እመጣለኹ ። የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ቃል ፡ የሚጠብቅ ፡ ብፁዕ ፡ ነው ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 8 ፤ ይህንም ፡ ያየኹትና ፡ የሰማኹት ፡ እኔ ፡ ዮሐንስ ፡ ነኝ ። በሰማኹትና ፡ ባየኹትም ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ ባሳየኝ ፡ በመልአኩ ፡ እግር ፡ ፊት ፡ እሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ተደፋኹ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 9 ፤ ርሱም ፦ እንዳታደርገው ፡ ተጠንቀቅ ፤ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ከወንድሞችኽም ፡ ከነቢያት ፡ ጋራ ፡ የዚህንም ፡ መጽሐፍ ፡ ቃል ፡ ከሚጠብቁ ፡ ጋራ ፡ ዐብሬ ፡ ባሪያ ፡ ነኝ ፤ ለእግዚአብሔር ፡ ስገድ ፡ አለኝ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 10 ፤ ለኔም ፦ ዘመኑ ፡ ቀርቧልና ፥ የዚህን ፡ መጽሐፍ ፡ ትንቢት ፡ ቃል ፡ በማኅተም ፡ አትዝጋው ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 11 ፤ ዐመፀኛው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ያምፅ ፥ ርኩሱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይርከስ ፥ ጻድቁም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ጽድቅ ፡ ያድርግ ፥ ቅዱሱም ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ይቀደስ ፡ አለ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 12 ፤ እንሆ ፥ በቶሎ ፡ እመጣለኹ ፥ ለያንዳንዱም ፡ እንደ ፡ ሥራው ፡ መጠን ፡ እከፍል ፡ ዘንድ ፡ ዋጋዬ ፡ ከእኔ ፡ ጋራ ፡ አለ ።

ራእ. ፥ 22 ፥ 13 ፤ አልፋና ፡ ዖሜጋ ፥ ፊተኛውና ፡ ኋለኛው ፥ መዠመሪያውና ፡ መጨረሻው ፡ እኔ ፡ ነኝ ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 14 ፤ ወደሕይወት ፡ ዛፍ ፡ ለመድረስ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖራቸው ፡ በደጆቿም ፡ ወደ ፡ ከተማዪቱም ፡ እንዲገቡ ፡ ልብሳቸውን ፡ የሚያጥቡ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 15 ፤ ውሻዎችና ፡ አስማተኞች ፡ ሴሰኞችም ፡ ነፍሰ ፡ ገዳዮችም ፡ ጣዖትንም ፡ የሚያመልኩት ፡ ውሸትንም ፡ የሚወዱና ፡ የሚያደርጉ ፡ ኹሉ ፡ በውጭ ፡ አሉ ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 16 ፤ እኔ ፡ ኢየሱስ ፡ በአብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ እንዲመሰክርላችኹ ፡ መልአኬን ፡ ላክኹ ። እኔ ፡ የዳዊት ፡ ሥርና ፡ ዘር ፡ ነኝ ፥ የሚያበራም ፡ የንጋት ፡ ኮከብ ፡ ነኝ ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 17 ፤ መንፈሱና ፡ ሙሽራዪቱም ፦ ና ፡ ይላሉ ። የሚሰማም ፦ ና ፡ ይበል ። የተጠማም ፡ ይምጣ ፥ የወደደም ፡ የሕይወትን ፡ ውሃ ፡ እንዲያው ፡ ይውሰድ ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 18 ፤ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈውን ፡ የትንቢት ፡ ቃል ፡ ለሚሰማ ፡ ኹሉ ፡ እኔ ፡ እመሰክራለኹ ፤ ማንም ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ አንዳች ፡ ቢጨምር ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፉትን ፡ መቅሠፍቶች ፡ ይጨምርበታል ፤

ራእ. ፡ 22 ፡ 19 ፤ ማንምም ፡ በዚህ ፡ በትንቢት ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ቃሎች ፡ አንዳች ፡ ቢያጐድል ፥ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከተጻፉት ፡ ከሕይወት ፡ ዛፍና ፡ ከቅድስቲቱ ፡ ከተማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕድሉን ፡ ያጐድልበታል ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 20 ፤ ይህን ፡ የሚመሰክር ፦ አዎን ፥ በቶሎ ፡ እመጣለኹ ፡ ይላል ። አሜን ፥ ጌታ ፡ ኢየሱስ ፡ ሆይ ፥ ና ።

ራእ. ፡ 22 ፡ 21 ፤ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ከኹላችን ፡ ጋራ ፡ ይኹን ፤ አሜን ❖